ኪዳን ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ።

# መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡
# ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ ።

ኪዳነ፡ ወልድ፡ ክፍሌ።

# መጽሐፈ፡ ሰዋስው፡ ወግስ፡ ወመዝገበ፡ ቃላት፡ ሐዲስ።


ትልቁ ፡ ሊቅ ፡ አለቃ ፡ ኪዳን ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ቤተ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በተወለዱ ፡ በ፳ ፡ ዓመት ፡ በ፲፰፻፹፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወጥተው ፡ በኢየ ሩሳሌም ፡ ሲኖሩ ፡ በ፲፱፻፲፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወዳገራቸው ፡ ተመልሰው ፡ መጡ ። የመ ጡበትም ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ዐልጋ ፡ ወራሽ ፡ (ቀዳማዊ ፡ ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ) ፡ ትችል ፡ እንደ ፡ ኸነ ፡ መጥተኽ ፡ ሕዝቅኤልን ፡ ተርጉም ልኝ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ስለ ፡ ጻፉላቸው ፡ ነው ።

ሕዝቅኤልንም ፡ ንባቡን ፡ ከምሉ ፡ ትርጓሜው ፡ ጋራ ፡ አሳትመው ፡ ካስረ ከቡ ፡ በኋላ ፡ በቅድስት ፡ አገር ፡ የወጠኑትን ፡ ይህን ፡ ብርሃናዊ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ገና ፡ በድሬ ፡ ዳዋ ፡ ማዘጋጀት ፡ ዠመሩ ። በሥራ ፡ ውለው ፡ ማታ ፡ ነፋስ ፡ በመ ቀበል ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሐሳብ ፡ ቢያገኙ ፡ በማስታወሻ ፡ ለመጻፍ ፡ ከውጭ ፡ ወደ ቤት ፡ ይመለሳሉ ። በምሳ ፡ ወይም ፡ በራት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ትርጓሜ ፡ ቢታሰባ ቸው ፡ ምግቡን ፡ ትተው ፡ ብድግ ፡ ይላሉ ። ሌሊትም ፡ ተኝተው ፡ ሳሉ ፡ አንድ ፡ ምስጢር ፡ ቢገጥማቸው ፡ ከመኝታቸው ፡ ተነሥተው ፡ መብራት ፡ አብርተው ፡ ይጽፋሉ ።

ያን ፡ ጊዜም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ያዘዙላቸውን ፡ ቀለብና ፡ ድርጎ ፡ እያደረጁ ፡ በዕለት ፡ መፍቅድ ፡ ይረዷቸው ፡ የነበሩ ፡ የክቡር ፡ ብላታ ፡ አሸኔ ፡ ኪዳነ ፡ ማርያም ፡ ባለቤት ፡ ክብርት ፡ ወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ ገብና ፡ ናቸው ።

ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ ትጋትና ፡ ድካም ፡ በኋላ ፡ ባ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ተመልሶ ፡ መምጣትና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ዠምሮ ፡ የመላ ፡ አፍሪቃን ፡ ነጻነት ፡ ጥቂት ፡ እንኳ ፡ ሳያፍሩ ፡ ሳይፈሩ ፡ በመናገራቸው ፡ ፋሺስቶች ፡ በፊ ለማ ፡ ውስጥ ፡ ስላሰሯቸው ፡ ምንም ፡ ዐይናቸው ፡ ቢጠፋ ፡ በ፰፻፳፰ ፡ ገጽ ፡ እ ንደ ፡ ገለጹት ፡ የሀገርና ፡ የስም ፡ ተራ ፡ መሰብሰብና ፡ መተርጐም ፡ ሲያስቡ ፡ ባ፲ ፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሠኔ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ዐርፈው ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተቀበሩ ።

ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ።



ቀዳማዊ ፡ ሐዪ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
ኢይፈቅድ ፡ ይንግርዎ ፡
ግዕዘ ፡ ለሰብእ ፡ ግእዝ፤
እስመ ፡ ለሊሁ ፡ የአምሮ ።

፤ ንቅዐም ፡ ገንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እም ፡ ጽወሩ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡
ለቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

# መክሥተ ፡ አርእስት ።


ገጽ ፡

ምእማር ፡ ወምስትእማር ። ማመልከቻና ፡ ማስታወቂያ ፡ ፫

የታሪክ ፡ መግቢያ ፡ ፱

ታሪክና ፡ መቅድም ፡ ፲፩

፩ኛ ፡ ክፍል ።

ስለ ፡ ነገድና ፡ ስለ ፡ ቋንቋ ፡ ስለ ፡ ሀገርም ፡ ስም ፡ መፋለስ ፡ ፲፩

፪ኛ ፡ ክፍል ።

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ስለ ፡ ሐዲስ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ መመለስ ፡ ፲፮

፫ኛ ፡ ክፍል ።

ስለ ፡ ፊደል ፡ ተረክቦና ፡ ጥንት ፡ ስለ ፡ ትምርቷም ፡ ለማያዊነት ፡ ፳፪

፬ኛ ፡ ክፍል ።

መቅድመ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ።

ጸዋትወ ፡ ፊደል ፡ ፳፯

ግእዝ ፡ ስለ ፡ ማለትና ፡ ስለ ፡ መባል ፡ ፳፰

ስለ ፡ ፊደላት ፡ ፯ ፡ ፯ነት ፡ ፳፱

አዕጹቅ ፡ ያልናቸው ፡ የ፮ቱ ፡ ፊደላት ፡ ጠባይ ፡ ፴

ፍናወ ፡ ፊደል ፡ ወሑረታቲሁ ፡ ፴፩

ፍልሰተ ፡ ፊደላት ፡ ወአኀዛቲሆን ፡ ፴፪

ማዕርግ ፡ ፊደላት ፡ ፴፫

፩ኛ ፡ ማዕርግ ።

ፊደል ። ስመ ፡ ፊደል ። ኍልቈ ፡ ፊደል ፡ ፴፫

፪ኛ ፡ ማዕርግ ።

መላው ፡ የግእዝ ፡ ፊደል ፡ ከናበጋዙና ፡ ከነዓዙ ፡ ከነአኀዙ ፡ ፴፬

፫ኛ ፡ ማዕርግ ፡ አቡጊዳ ። ፴፭

ያቡጊዳ ፡ ተረፍ ፡ ፴፮

ሐተታ ፤ ስለ ፡ ፊደል ፡ ቍጥር ፡ 〃

፬ኛ ፡ ማዕርግ ።

ከግእዝ ፡ ፊደላት ፡ የተጼቀለ ፡ ያማርኛ ፡ ፊደል ፡ ፴፯

# መክሥተ ፡ አርእስት ።

ገጽ ፡

ምእማር ፡ ወምስትእማር ።   ማመልከቻና ፡ ማስታወቂያ ፡ ፫
የታሪክ ፡ መግቢያ ፡ ፱
ታሪክና ፡ መቅድም ፡ ፲፩

፩ኛ ፡ ክፍል ።

ስለ ፡ ነገድና ፡ ስለ ፡ ቋንቋ ፡ ስለ ፡ ሀገርም ፡ ስም ፡ መፋለስ ፡ ፲፩

፪ኛ ፡ ክፍል ።

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ስለ ፡ ሐዲስ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ መመለስ ፡ ፲፮

፫ኛ ፡ ክፍል ።

ስለ ፡ ፊደል ፡ ተረክበና ፡ ጥንት ፡ ስለ ፡ ትምርቷም ፡ ለማያዊነት ፡ ፳፬

፬ኛ ፡ ክፍል ።

መቅድመ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ።

ጸዋትወ ፡ ፊደል ፡ ፳፯
ግእዝ ፡ ስለ ፡ ማለትና ፡ ስለ ፡ መባል ፡ ፳፰
ስለ ፡ ፊደላት ፡ ፯ ፡ ፯ነት ፡ ፳፱
አዕጹቅ ፡ ያልናቸው ፡ የ፮ቱ ፡ ፊደላት ፡ ጠባይ ፡ ፴
ፍናወ ፡ ፊደል ፡ ወሐረግታቲሁ ፡ ፴፩
ፍልሰተ ፡ ፊደላት ፡ ወአኃዛቲሆን ፡ ፴፪
ማዕርገ ፡ ፊደላት ፡ ፴፫

፩ኛ ፡ ማዕርግ ።

ፊደል ። ስመ ፡ ፊደል ። ኍልቄ ፡ ፊደል ፡ ፴፫

፪ኛ ፡ ማዕርግ ።

መላው ፡ የግእዝ ፡ ፊደል ፡ ከናበጋዙና ፡ ከነጓዙ ፡ ከነአኃዙ ፡ ፴፬
፫ኛ ፡ ማዕርግ ፡ አቡጊዳ ። ፴፭
ያቡጊዳ ፡ ተረፍ ፡ ፴፮
ሐተታ ፤ ስለ ፡ ፊደል ፡ ቍጥር ፡ 〃

፬ኛ ፡ ማዕርግ ።

ከግእዝ ፡ ፊደላት ፡ የተጼቀለ ፡ ያማርኛ ፡ ፊደል ፡ ፴፯

## መክሥት፡ አርእስት።


### ፫ኛ፡ ማዕርግ።
ገጽ፡

ጉባኤ፡ ዝርዋን፡ ፊደላት፥ ፴፱
ቍጥር፡ በፊደልና፡ በአኃዝ፡ ፵፩

### ፬ኛ፡ ማዕርግ።

ስለ፡ እጅ፡ መኪና፡ ፊደል። ዐዋጅና፡ አገባብ፡ ፵፩
ፊደልና፡ ቀየል፡ ከነአኃዙና፡ ከነጓዙ፡ »
የጥፈትና፡ የመጻሕፍት፡ መልክ፡ ፵፫
የታሪክ፡ መርገፍ፡ የመቅድም፡ አጫዋች፡ ፵፬

ዐዌርና፡ ቍርዌኝ፡ ሰዋስው። ፵፰

መገምሪያ፡ ምዕራፍ፡ ባላ፬፡ ክፍል፡.... ።

### ፩ኛ፡ ክፍል።

የሰዋስው፡ ዐዋጅ፡ ርባ፡ ቅምር። ፵፱

መገምሪያ፡ ዕርከን፡ ወይም፡ ቀዳማይ።

የዘርና፡ የነባር፡ ጠባይ።

ዘር፡ ፶
ነባር፡ ፶፪

### ፪ኛ፡ ዕርከን።

የግስ፡ ዐመሎች፡ ፶፬
ከመላላት፡ በቀር፡ መጥበቅ፡ የሌላቸው፡ አ—ዐ፡ ሀ—ሐ—ኀ፡ »
ወና፡ የ፡ ፶፮
ሐተታ፡ ስለ፡ ብህለና፡ ስላ፡ ቤለ፡ ፶፯
ደጊመ፡ ቃል፡ ፶፰

### ፫ኛ፡ ዕርከን።

የግስ፡ ልማድ፡ ባላምስት፡ አዕማድ፡ ፶፱
የትንቢት፡ ሥሮች፡ ወይም፡ ልማዶች፡ ፷

### ፬ኛ፡ ዕርከን።

የግስ፡ አርእስት፡ ባለ፫ና፡ ባላ፬፡ ፊደላት፡ ፷፩

### ፭ኛ፡ ዕርከን።

የጊቱ፡ አርእስት፡ ሰራዊትና፡ ድርቦች፡ ፷፫

### ፮ኛ፡ ዕርከን።

የግስ፡ ዐይነትና፡ ክፍል፡ ፷፭

# መክሥተ ፡ አርእስት ።


## ፩ኛ ፡ ክፍል ። ገጽ ፡

### ጸዋትወ ፡ ቅጽል ፡ ወአኅዝ ፡ የሰዋስው ፡ ባለቤትና ፡ ጓዝ ።

#### ፲፩ኛ ፡ ዕርከን ።

ቅጽል ፡ . . . . ፹፱
ደቂቅ ፡ ቅጽል ፡ ፺፩
ጭብጥ ፡ ቅጽል ፡ ወይም ፡ እማሬ ፡ ፺፪

#### ፲፪ኛ ፡ ዕርከን ።

አኅዝ ፡ ቅጽል ፡ ፺፫
የወንዶች ፡ ድምላና ፡ የሴቶች ፡ ድምላ ፡ ቍጥር ፡ . . . ፺፬
ሐተታ ፡ ስላንድ ፡ ቤት ፡ ቍጥር ፡ ፺፭
ተራ ፡ ቍጥር ፡ በፊደል ፡ ብቻ ፡ »
የወንዶችና ፡ የሴቶች ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ፺፮
የክፍል ፡ ቍጥር ፡ ፺፯
(በጥሬነታቸው ፡ የክፍልን ፡ ኹነታ ፡ የሚያሳዩ ፡ ጥሬዎች) ፡
የዕለታት ፡ አኅዝ ፡ ፺፰
የጊዜያት ፡ አኅዝ ፡ ፻
የዕጽፍ ፡ ቍጥር ፡ »
ሳድስ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ »
የመስፈሪያና ፡ የሚዛን ፡ ዕጽፍ ፡ ፻፩
ደምላይና ፡ ጠቅላይ ፡ መድበላዊ ፡ ቍጥር ፡ »

## ፪ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ባለ፫ ፡ ክፍል ፡ . . . ።

### ፩ኛ ፡ ክፍል ።

ጸዋትወ ፡ ንባብ ፡ . . . ፻፪

#### ፲፫ኛ ፡ ዕርከን ።

ሳቢና ፡ ተሳቢ ፡ . . . . ፻፫

#### ፲፬ኛ ፡ ዕርከን ።

ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ ተናባቢና ፡ ተያያዥ ፡ ፻፲

#### ፲፭ኛ ፡ ዕርከን ።

ቅጽልና ፡ ባለቤት ፡ ፻፲፫
ዘመድ ፡ ቅጽል ፡ ፻፲፬
አኅዝ ፡ ቅጽል ፡ ፻፲፪
ብዕድ ፡ ቅጽል ፡ ፻፲፭
ዝርዝር ፡ ፻፳፫

፯ኛ ፡ ዕርከን ። ገጽ ፡

የርባታ ፡ መደብ ፡ ወይም ፡ ሰራዊት ፡ ፳፯

፪ኛ ፡ ክፍል ።

ጸዋትወ ፡ ርባ ።

የርባታና ፡ ያንቀጽ ፡ ስምና ፡ ረድፍ ፡ ፴፫

፰ኛ ፡ ዕርከን ።

ዐቢይ ፡ ርባታ ፡ ከንኣዙ ፡ ከናበጋዙ ፡ ፴፬
ዐሥሩ ፡ ሰራዊትና ፡ ሰማኒያው ፡ መደብ ፡ ፵

፱ኛ ፡ ዕርከን ።

ንኡሳን ፡ አናቅጽ ፡ ፵፩
ውስጠ ፡ ዘና ፡ መስም ፡ ፵፫
ሳቢ ፡ ዘሮች ፡ ፵፬

፲ኛ ፡ ዕርከን ።

ንኡስ ፡ ርባታ ፡ የዐቢይ ፡ ተረፍ ፡ የደቂቅ ፡ ጺታ ፡ ፵፭

፲፩ኛ ፡ ዕርከን ።

ደቂቅ ፡ ርባታና ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ ባለብዙ ፡ ሕጸጽ ፡ ፵፯

፫ኛ ፡ ክፍል ።

ጸዋትወ ፡ ስም ፡ ወመስም ፡ . . . . . . . . . . ።

፲፪ኛ ፡ ዕርከን ።

የዘርና ፡ የነባር ፡ ጥሬ ፡ ወይም ፡ ዘርና ፡ ነባር ፡ ስም ፡ ፶፩

፲፫ኛ ፡ ዕርከን ።

አገባብ ።

ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ፶፮
ንኡስ ፡ አገባብ ፡ ፶፯
የጊዜ ፡ ጥሬዎች ፡ »
የብዙ ፡ ብዙና ፡ ጭራሽ ፡ የሚያሳዩ ፡ »
ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ፶፰
መድረሻቸውን ፡ የሚለውጡና ፡ የማይለውጡ ፡ የቦታና ፡ የጊዜ ፡ ጥሬዎች ።
የቦታ ፡ ጥሬ ፡ ፶፱
የጊዜያት ፡ ጥሬ ፡ »

## ፬ኛ ፡ ክፍል ።                                        ገጽ ፡

### ፲፱ኛ ፡ ዕርከን ።

| | |
|---|---|
| ዐበይት ፡ አገባቦች ፡ | ፻፹፪ |

### ፳ኛ ፡ ዕርከን ።

| | |
|---|---|
| ንኡሳን ፡ አገባቦች ፡ | ፻፺ |
| አሉታ ፡ የጽድቅ ፡ መከታ ፡ | ፻፺፪ |
| የጊዜያት ፡ ጥሬ ፡ | ፻፺፭ |

### ፳፩ኛ ፡ ዕርከን ።

| | |
|---|---|
| ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ | ፻፺፰ |
| እየተናበቡ ፡ የማነገሩ ፡ የቦታ ፡ ጥሬዎች ፡ | ፻፺፪ |
| የጊዜ ፡ ጥሬዎች ፡ | ፻፺፫ |
| ያባልና ፡ የባሕርይ ፡ ጥሬዎች ፡ | ፻፺፱ |

## ፭ኛ ፡ ክፍል ።

## ጸዋትወ ፡ ቅኔ ፤ የሠምና ፡ የወርቅ ፡ ትርጓሜ ።

### ፳፪ኛ ፡ ዕርከን ።

| | |
|---|---|
| ሠምና ፡ ወርቅ ፡ ....... | ፻፺፱ |

### ፳፫ኛ ፡ ዕርከን ።

| | |
|---|---|
| ብትን ፡ ሰዋስው ፡ | ፻፹፱ |

### ፳፬ኛ ፡ ዕርከን ።

| | |
|---|---|
| ሙሻዝር ፡ | ፻፹፬ |

### ፳፭ኛ ፡ ዕርከን ።

| | |
|---|---|
| ሠረዝ ፡ | ፻፹፪ |

### ፳፮ኛ ፡ ዕርከን ።

| | |
|---|---|
| አንጻር ፡ | ፻፸ |

### ፳፯ኛ ፡ ዕርከን ።

| | |
|---|---|
| የርባ ፡ ቅምርና ፡ የጸዋትወ ፡ ርባ ፡ ተረፍ ፡ በላይ ፡ ረድፍ ። | ፻፸፭ |
| ንኡስ ፡ ርባታ ፡ | ፻፸፱ |

## ፮ኛ ፡ ረድፍ ።

## ዐቢይና ፡ መደብ ፡ የቀዞ ፡ ርባታ ።

| | |
|---|---|
| መደበኛ ፡ አንቀጽ ፡ | ፻፸፰ |
| ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ | 〃 |
| ሣልስ ፡ ቅጽል ፡ | 〃 |
| መድበል ፡ ቅጽል ፡ | 〃 |

## ፩ኛ ፡ ረድፍ ።


| | ገጽ ፡ |
|---|---|
| ያሥሩ ፡ መደብ ፡ ዝርዝር ፥ መሠረ ፡ ርቢታ ፡ | ፻፵፫ |
| የበዝ ፡ አንቀጽ ፡ ዝርዝር ፡ እስከ ፡ ፺ ፡ | ፻፵፯ |
| ፩ኛ ፡ ዐምድ ፡ አስደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ | » |
| ፪ኛ ፡ ዐምድ ፡ ተደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ | » |
| ፫ኛ ፡ ዐምድ ፡ ተደራራጊ ፡ አንቀጽ ፡ | ፻፶፰ |
| ፬ኛ ፡ ዐምድ ፡ አደራራጊ ፡ አንቀጽ ፡ | » |


## ፪ኛ ፡ ረድፍ ።


| | |
|---|---|
| ጽንዕ ፡ አንቀጽ ፡ | ፻፷፰ |
| የዋህ ፡ ጽንዕ ፡ | » |
| መሠረ ፡ ጽንዕ ፡ | ፻፸፱ |


## ፫ኛ ፡ ረድፍ ።


| | |
|---|---|
| አሉታ ፡ አንቀጽ ፡ | ፻፹፱ |
| ጅምላ ፡ ቍጥር ፡ | ፻፺ |
| መፀዛ ፡ ሰዋስው ፡ ፈጣን ፡ . . . . | |
| የግጥም ፡ ስብከት ፡ . . . . | ፻፺፩ |
| ስለ ፡ ቋንቋ ፡ ትምርት ፡ መንገድና ፡ አካኼድ ፤ ስለ ፡ ተማሮችም ፡ አረማመድ ፡ | ፻፺፫ |
| አሠረ ፡ ንጉሥ ፡ ጠቢብ ፡ | ፻፺፮ |
| ዓዲ ፡ ቃለ ፡ ዐዋዲ ፡ | ፻፺፯ |


## ፫ኛ ፡ ምዕራፍ ።

ጸዋትወ ፡ ግስ ፡ . . . .

ከአ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ድረስ ።


| | |
|---|---|
| የቍራኛና ፡ የጥቅስ ፡ ምልክት ፡ | ፻፺፱ |

# መጽሐፈ፡ ሰዋስው፡ ወግስ፡ ወመዝገበ፡ ቃላት፡ ሐዲስ ።

ንባቡ፡ በግእዝ፡ ፍችው፡ ባማርኛ ።


እምኀበ፡ መምህር፡ ዐቢይ፡ ክፍለ፡ ጊዮርጊስ፡ ወእምኀበ፡

ረድኡ፡ ንኡስ፡ ኪዳን፡ ወልድ፡ ክፍሌ፡ ወልደ፡ አበ፡ ተክሌ ።



በአርቲስቲክ፡ ማተሚያ፡ ቤት፡

ደስታ፡ ተክለ፡ ወልድ፡ አሳተመው ።

6288

፲፱፻፵፰፡ ዓመተ፡ ምሕረት ።

ያስፈቀደ ፡ መልሶ ፡ ማሳተምና ፡ ወደ ፡
ሌላ ፡ ቋንቋ ፡ መተርጐም ፡ ክልክል ፡ ነው ።

---

ካለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ተጥፈው ፡ ገና ፡ ያልታተሙ ፡ መጻሕፍት ።

፩ኛ ፡ የዕብራይስጥ ፡ ግስ ፡ በግእዝ ፡ ፊደል ፡ ተጽፎ ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ የተተረጐመ ።
፪ኛ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ባማርኛ ፡ ንባብና ፡ በኹለት ፡ ዐይነት ፡ ግጥም ፡ የተዘጋጀ ።

## ኦርቶዶክሳውያን ፡ ሊቃውንት ፡



መምህር ፡ ክፍለ ፡ ጊዮርጊስ ።



አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ።

አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ባ፲፱፻፴፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በተወለዱ ፡ በ፹፪ ፡ ዓመት ፡ ሠኔ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ቅዳሜ ፡ ዐርፈው ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተቀበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ የማይሞት ፡ ሥራቸው ፡ (ይህ ፡ መጽሐፋቸው) ፡ የኢትዮጵያን ፡ ልጆች ፡ ዘላለም ፡ ሲያስተምር ፡ ይኖራል ።

ደ ፡ ተ ፡

## ምእማር ፡ ወምስትእማር ።

## ማመልከቻና ፡ ማስታወቂያ ።

ናቀድም ፡ ወንኤምር ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ መዝገበ ፡ ቃል ፡ ወመጽሔተ ፡ ፊደል ፥ ግቡር ፡ ሐዲሰ ፡ ወጽሑፍ ፡ ሥልሰ ፡ መጠነ ፡ ሰብዐቱ ፡ አዝማን ፡ ወከመ ፡ ለሊሁ ፡ ውፁእ ፡ ወእስትጉቡእ ፡ በኵሉ ፡ እመጽሐፊ ፡ ጠቢብ ፡ ዲልማን ፡ ወእመጻሕፍት ፡ ካልኣን ፡ እለ ፡ ያረትዑ ፡ ቃለ ፡ ፍኖተ ፡ ግእዝ ፡ ዘበአማን ። እስመ ፡ ርቱዓት ፡ ፍናዊሁ ፡ ለእግዚአ ፡ ልሳን ፡ ግእዝ ፥ ፍናወ ፡ ቃለ ፡ ሕግ ፡ ወትእዛዝ ፡ ጻድቃን ፡ የሐውርዎን ፡ ወኃጥኣን ፡ ይስእንዎን ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ (ሆሴ ፲፬ ፡ ፱) ።

ዲልማንሰ ፡ ሉተራዊ ፡ እምነገደ ፡ ጌርመን ፡ ማእምረ ፡ ልሳናት ፡ ሴማውያን ፡ ወመተርጉመ ፡ ግእዝ ፡ ኀበ ፡ ላቲን ። ጽሩየ ፡ ዐይን ፡ ወበሊኅ ፡ ልሳን ፥ ዘርቱዐ ፡ ይመትር ፡ ቃለ ፡ መጻሕፍት ፡ ወነገረ ፡ ኵሎን ፡ በሓውርት ፡ ወቦ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ በእንቲአሁ ፡ እምደቂቀ ፡ ያፌት ፡ አርዳኢሁ ፡ በለብዎ ፡ ወበአንክሮ ፥ ዘከመ ፡ ወረደ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈሰ ፡ ጥበብ ፡ ወአእምሮ ፥ ወአስተራትዖሙ ፡ በተምህሮ ።

ወንሕነኒ ፡ ዓዲ ፡ ኢሰማዕነ ፡ ወኢርኢነ ፡ ግሙራ ፥ ወኢነገሩነ ፡ አበዊነ ፡ በቃለ ፡ ነከራ ፥ ከመ ፡ ቦ ፡ ባዕድ ፡ እምጸዓድው ፡ ማእምረ ፡ ግእዝ ፡ ከማሁ ፥ ኢእምቅድሜሁ ፡ ወኢእምድኅሬሁ ። ዲልማንኬ ፡ ድልወ ፡ ብፅዓን ፡ ወቡራኬ ፡ ምስለ ፡ አበዊነ ፡ በውሳኬ ፥ እስመ ፡ ሎቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘከመ ፡ ዝኬ ፡ ኀጽዋ ፡ ወመጋቢሃ ፡ ለልሳነ ፡ ግእዝ ፡ ሀንደኬ ፥ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ወኖባ ፡ ወኢትዮጵያ ፡ ወግብሩሂ ፡ ክሡት ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያ ፥ ዘያሜንን ፡ ግብጻ ፡ ወእስክንድርያ ። ማእረሩሰ ፡ ለግእዝ ፡ ብዙኅ ፡ ወፍድፉድ ፥ ወገባሩ ፡ ኅዳጥ ፡ ወውኁድ ፡ ሰአልዎ ፡ እንከ ፡ አ ፡ አርዳእ ፥ ለበዓለ ፡ ማእረር ፡ እግዚእ ፥ ከመ ፡ ይወስክ ፡ ካዕበ ፡ እምድሩ ፥ ገባረ ፡ ለማእረሩ ።

ካኹን ፡ ቀደም ፡ ንጉሥና ፡ ጳጳስ ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ በየወረዳው ፡ ያቆሙት ፡ ታላላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ሰፋፊ ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ ከሌለ ፡ ዘንድ ፥ ካባትና ፡ ከናት ፡ ቤት ፡ ከሥብልሎ ፡ አገር ፡ ላገር ፡ ዙሮ ፡ በልመና ፡ እንጀራ ፡ የሚማሩት ፡ ትምርት ፡ እንደ ፡ ቅምሻና ፡ እንደ ፡ ጕርሻ ፡ የማያጠግብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በሽመታና ፡ በቢገታ ፡ በራቻና ፡ በሽት ፡ ይመሰላል ። ከዚህ ፡ ምሳሌም ፡ የተነሣ ፥ ጥፈትና ፡ ትምርት ፡ እየቅል ፡ ኹኖ ፡ ጥፈት ፡ ዐዋቆች ፡ ከሰዋስው ፡ ትምርት ፡ የራቁ ፥ መጽሐፍ ፡ ዐዋቆችም ፡ ጥፈት ፡ የማያውቁ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ የትምርቱ ፡ አበጋዝ ፡ ጳጳሱም ፡ አክቶ ፡ ፈጽሞ ፡ የግእዝን ፡ መልክአ ፡ ፊደል ፡ የማያውቅ ፡ በዕድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሊቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የግእዝ ፡ አዝመራ ፡ የትምርቱ ፡ ሰብል ፡ በመምህራን ፡ ማጭድ ፡ በበሊኅ ፡ አእምሮ ፥ ተለቅሞ ፡ ታጭዶ ፡ ነዶው ፡ ታስሮ ፥ ተሰብስቦና ፡ ተከምሮ ፥ በታላቁና ፡ በሰፊው ፡ በትምርት ፡ ዐውድማ ፡ ተጥሎ ፥ ምርቱና ፡ ግርዱ ፡ ተንጣሎ ፥ ገና ፡ አልታፈሠም ፡ አልተዛቀም ፡ ስፍሩና ፡ ቍጥሩ ፡ ውጤቱ ፡ አልታወቀም ፡ አዝመራው ፡ በዝቶ ፡ ሠራተኛው ፡ አንሷል ። ከብዙ ፡

በጥቂቱም ፡ የተሠራ ፡ ቢኖር ፡ ተፈጭቶ ፡ ያልተነፋ ፡ ዱቄት ፡ ተበራይቶ ፡ ያልተመረተ ፡ ምርት ፡ ይመስላል ፡ የግሱና ፡ የፊደሉ ፡ እብቅ ፡ ቂንዱና ፡ ግርዱ ፥ የጥፈቱ ፡ ፍሬና ፡ ገለባ ፡ በትምርት ፡ ነፋስ ፡ አልተለየም ። ይልቁንም ፡ የ፪ቱ ፡ አፀና ፡ የ፫ቱ ፡ ሀሐኀ ፡ ግእዞቸው ፡ ከራብዓቸው ፡ በመልክ ፡ ብቻ ፡ ተለይቶ ፡ በድምፅ ፡ ስላልተለየና ፡ ልዩነቱ ፡ ስላልታወቀ ፥ በግእዙ ፡ በታ ፡ ራብዕ ፡ (ጐሥዓ ፡ ሞዓ (ኦ) ፡ በልዓ ፡ በዝኃ ፡ በርሃ) ፡ በራብሁ ፡ ፈንታ ፡ ግእዝ ፡ (ጸሐፈ ፡ ከሀሊ ፡ ወሀቢ) ፡ ተጥፎ ፡ ይገኛል ። የራብዕ ፡ ጠባዩ ፡ አፉ ፡ ማስከፈትና ፡ ቃል ፡ ማገንቃት ፥ ዝርዝር ፡ ማሳየት ፡ ነው ፡ ለግእዝ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ የለውም ፡ በ ፡ ባ ፡ ገ ፡ ጋ ፡ ደ ፡ ዳ ፡ በድምጥና ፡ በመልክ ፡ ልዩ ፡ ልዩዎች ፡ እንደ ፡ ኹኑ ፥ አፀና ፡ ሀሐኀም ፡ ከራብዖቻቸው ፡ ከአዓ ፡ ከሃሓኃ ፡ ልዩዎች ፡ ናቸው ። የራብዖች ፡ ጠባይ ፡ ከግእዞች ፡ ጠባይ ፡ እንደ ፡ መልካቸው ፡ ፍጹም ፡ ልዩ ፡ ሲኾን ፥ የመልክና ፡ የድምጥ ፡ የጠባይ ፡ አንድነት ፡ ወይም ፡ ተወራራሽነት ፡ ሳይኖራቸው ፥ በግእዝ ፡ በታና ፡ በግእዝ ፡ ፈንታ ፡ ራብዕን ፡ መጣፍ ፡ የስሕተት ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ ስሕተትም ፡ የሠለጠነበት ፡ ምክንያት ፡ ጥፈትና ፡ ትምርት ፡ ተብብረው ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ስላልተገኙ ፡ ነው ። ጥፈት ፡ የማያውቁ ፡ መምህራን ፡ የተጣፈውን ፡ ከመተርጐም ፡ በቀር ፡ የጸሐፍትን ፡ ስሕተትና ፡ ግድፈት ፡ ማረምና ፡ ማቅናት ፡ እንዳይችሉ ፥ ሰዋስው ፡ የማያውቅ ፡ ጸሓፊም ፡ መልክእ ፡ ፊደሉን ፡ ሐረጉን ፡ ቅጠሉን ፡ አጣጣሉን ፡ ብቻ ፡ ከማሳመር ፡ በቀር ፡ ንባቡንና ፡ አገባቡን ፡ አጥርቶ ፡ ማወቅ ፡ ፊደሉን ፡ መጠንቀቅ ፡ አይችልም ።

ስሕተት ፡ ፊደል ፡ መለወጥ ፡ ነው ፥ ግድፈት ፡ ግን ፡ ፊደልን ፡ መጣል ፡ ነው ፡ ሚካኤል ፡ ገብርኤል ፡ ያለውን ፡ ሚኤል ፡ ገብርል ፡ እንደ ፡ ማለት ። አፈ ፡ ወርቅም ፡ ትምርትን ፡ ከጥፈት ፡ አስተባብሮ ፡ አለመማር ፡ የጥፈት ፡ ዕንቅፋት ፡ መኾኑን ፡ ሲያጠይቅ ፡ በታስዕ ፡ ድርሳኑ ፥ ስለ ፡ ተማሪና ፡ ስለ ፡ ትምርት ፡ ወበከመ ፡ ዘይመጽእ ፡ ኅበ ፡ ትምህርት ፡ መጽሐፍ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይስማዕ ፡ ቅድመ ፡ ፍካሬ ፡ ሆህያት ፡ ከለ ፡ በኋላ ፥ ስለ ፡ ጥፈትና ፡ ስለ ፡ ጣፊም ፡ ወለጸሓፊኒ ፡ ኢይትከሀሎ ፡ ጠንቅቆተ ፡ ጽሒፍ ፡ ለእመ ፡ ኢያእመረ ፡ ሥርዐተ ፡ ሆህያት ፡ ወባሕቱ ፡ ለእመ ፡ አዝለፈ ፡ አስተሐይጾ ፡ ውስቴታ ፥ ወአብዝኀ ፡ ተመላልሰ ፡ ውስተ ፡ አእምሮ ፡ ፍካሬሃ ፡ ኢይረክበ ፡ ዕቅፍት ፡ ብዓል ። ጥሩ ፡ መስታዮት ፡ ከሌለ ፡ ፊትን ፡ ባይን ፡ ማየት ፥ እድፉን ፡ ጒድፉን ፡ መክላት ፡ እንዳይቻል ፡ የትምርትና ፡ የጥፈትም ፡ ሥራ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ጥሩ ፡ መምህርና ፡ ጥሩ ፡ መጽሐፈ ፡ ግስ ፡ ካልተገኘ ፡ ጥሩነት ፡ የለውም ። መምህርና ፡ መጽሐፍ ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ በጥሩ ፡ ምንጭና ፡ በፈሳሽ ፡ በወራጅ ፥ ተማሪና ፡ ጣፊም ፡ በውሃ ፡ ቀጅ ፡ ይመስላሉ ፡ በጥፈትና ፡ በነገር ፡ የፊደል ፡ ጥንቃቄ ፡ ከሌለ ፡ ግን ፡ ምንባቡ ፡ ደፈረሰ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሀገራችንና ፡ ቋንቋችን ፡ ያረገዙትን ፡ ለመውለድ ፡ ወልዶም ፡ ለማሳደግ ፡ ሐኪምና ፡ ጊዜ ፡ አላገኙም ፤ የተወለደውም ፡ ትምርታችን ፡ ወላጆቹና ፡ ሞግዚቶቹ ፡ ታርደው ፡ ተሰደው ፡ ስላለቁ ፥ እንደ ፡ ሙት ፡ ልጅ ፡ ኹኖ ፡ ከመማኅፀኒትና ፡ ከመመሥፀኒት ፡ በቀር ፡ እያደገና ፡ እየሰፋ ፡ እየፋፋ ፡ መኼድ ፡ አልቻለም ። የግሱም ፡ አካኼድ ፡ እንደ ፡ ፊደሉ ፡ እንደ ፡ ሀለሐመ ፡ ተፋልሰ ፡ በግጥም ፡ አካኼድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ተራውና ፡ ሥራው ፡ ተበላሽቷል ።

ፊደልን ፡ በሀ ፡ መጀመር ፡ ስሕተት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ማስንም ፡ መነሻውን ፡ ትቶ ፡ በመድረሻው ፡ ፊደል ፡ መሰደር ፡ መደርደር ፡ ፍጹም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ የቅኔና ፡ የበለ ቅኔ ፡ እንጂ ፡ የመዝገበ ፡ ቃል ፡ ሕግ ፡ አይዶለም ፤ ሐረግ ፡ በጫፉ ፡ ተይዞ ፡ እንዳይሳብ ፥ ዘርና ፡ ነባርም ፡ ሥሩና ፡ መነሻው ፡ እያለ ፡ በመድረሻው ፡ ተራ ፡ አይጣፍም ። በዚሁ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የአዐ ፥ የሀሐኅ ፥ የሠሰ ፥ የጸፀ ፡ ግሳቸውና ፡ ነባራቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሲኾን ፡ ዐብረው ፡ ባንድነት ፡ መጣፋቸውና ፡ ባንድነት ፡ መገሰሳቸው ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ግፍ ፡ ነው ፤ ግእዝ ፡ ተምሮ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ለጨመረ ፡ ይልቁንም ፡ ዕብራይስጥና ፡ ዐረብ ፡ ለተማረ ፡ በጣም ፡ ያሳዝናል ። ባላንድ ፡ ቋንቋ ፡ እንዳንድ ፡ ዐይና ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ባለኹለት ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ፩ ፡ ዐይና ፡ ነውና ፥ በግራና ፡ በቀኝ ፡ እብዝቶና ፡ አጥርቶ ፡ መዝኖ ፡ አስተካክሎ ፡ አስረግጦ ፡ ማየት ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ በሮማውያን ፡ ዘንድ ፡ የከበሩ ፡ ትምርት ፡ ክጥፈት ፡ ያስተባበሩ ፥ በትምርታቸውም ፡ የተደነቁና ፡ የታወቁ ፥ በሀገራቸው ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ነቢያት ፡ የተናቁ ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ የተጠቁ ፥ እንደ ፡ ዮሴፍም ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ጠልተው ፡ ተመቅኝተው ፡ ለማይረባ ፡ ዋጋ ፡ የሼጧቸው ፥ ያንከበሩ ፡ ሊቀ ፡ መምህር ፡ ክፍሌ ፡ ወልደ ፡ አባ ፡ ተክሌ ፡ ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ባህል ፥ ቋንና ፡ ፊደል ፡ ስለ ፡ ሰሙና ፡ ስላዩ ፡ ስላነበቡ ፥ ይልቁንም ፡ ታላቁን ፡ የዲልማንን ፡ ግስ ፡ ስላገኙ ፥ ሥራን ፡ መንቀፍ ፡ በሥራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ መንቀፍ ፡ አይበቃም ፡ ብለው ፥ ያን ፡ የቀድሞውን ፡ ግስ ፡ በሥራ ፡ ነቅፈው ፡ ይህን ፡ ሐዲስ ፡ ግስ ፡ አውጥተዋል ። ፫ቱ ፡ ሀሐኅና ፡ ፪ቱ ፡ አዐ ፤ ፪ቱ ፡ ሠሰና ፡ ፪ቱ ፡ ጸፀ ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ የድምፅ ፡ ልዩነት ፡ ባይኖራቸው ፡ የመልክ ፡ ልዩነት ፡ አላቸውና ፥ ምስጢራቸውና ፡ ስማቸውም ፡ እንደ ፡ መልካቸው ፡ እየቅል ፡ ነውና ፡ ስንኳን ፡ በጥፈት ፡ በትምርትም ፡ በገሰሰስም ፡ ሊለዩ ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ እየብቻቸው ፡ ለያይተውልናል ። ይህነንም ፡ ግስ ፡ ያወጡት ፥ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተሰደው ፡ ምጽዋዕ ፡ በሚባለው ፡ ደሴት ፡ ካቡነ ፡ ዮሴፍ ፡ ቤት ፡ ሳሉ ፡ ነው ።

ግሱንም ፡ ጨርሰው ፡ ከምጽዋዕ ፡ ወደ ፡ ከረን ፡ ማኅበር ፡ ሲልኩ ፡ የጣፉት ፡ መልእክት ፡ እንሆ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

የዚህ ፡ ግስ ፡ ሥራው ፡ ገና ፡ አልተጨረሰም ፤ ስምና ፡ ግብር ፡ ግዕዝ ፡ ብሔር ፡ ቀርቶቷል ፤ ጊዜ ፡ ቢገኝ ፡ ኋላ ፡ ሲታተም ፡ ይጨረሳል ።

ተራም ፡ ቤቱን ፡ ሳይለቅ ፡ አንዳንድ ፡ የፊደል ፡ ተራ ፡ ተዛውሮ ፡ ይገኛል ፡ ኋላ ፡ ይቀናል ። ዐማርኛው ፡ ለሰው ፡ እንዲሰማ ፡ የሀገረ ፡ ሰብ ፡ ዐማርኛ ፡ አለበት ፤ ሥርና ፡ ሥራ ፡ በብዙ ፡ አንድ ፡ ዐማርኛ ፡ ይኾናሉ ፤ ሥራ ፡ ሲበዛ ፡ ሥሮች ፥ ሥርም ፡ ሲበዛ ፡ ሥሮች ፡ ይባላል ፤ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሲገኝ ፡ ያለመምህር ፡ ለኹሉ ፡ አይሰማም ። ስለዚህ ፡ ሥራ ፡ ብሎ ፡ በብዙ ፡ ሥራዎች ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያለ ፡ ይጥፋል ፤ ለሰው ፡ እንዲረዳ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ ዐማርኛ ፡ አይዶለም ።

ሦስቱ ፡ ሀሐኅ ፥ ኹለቱ ፡ ሠሰ ፥ ኹለቱ ፡ አዐ ፥ ኹለቱ ፡ ጸፀ ፡ እንዳይሳሳቱ ፡ በጣም ፡ መጠንቀቅ ፡ ያስፈልጋል ፤ አለዚያ ፡ ተራ ፡ ይበላሻል ። የፊደልም ፡ ተራ ፡ ሀላዊ ፡

ሳይል ፡ (ኅ) ሀለደ ፡ አይልም ፡ ክላ ፡ ለ ፡ ይቀድማል ፡ ብሎ ፡ ሀለደ ፡ ቢል ፡ ክዊ ፡ ደ ፡ አይቀድምም ፡ ይላሉ ። ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ቤቱን ፡ ካለቀቀ ፡ ግእዝ ፡ ኃምስ ፡ ቢቀዳደሙ ፡ ግድ ፡ የላቸውም ፤ ፫ኛው ፡ ፊደል ፡ ያለተራው ፡ እንዳይገባባቸው ፡ ይጠብቃሉ ። ፍችውም ፥ አእማሪ ፡ ያወቀ ፥ አእማሪት ፡ የወደደች ፥ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሩኅ ፡ አለው ፤ ያንዱ ፡ ፍች ፡ ለኹሉ ፡ ይኾናል ። የፊደል ፡ ግድፈት ፡ ተጠንቀቃችኹ ፡ ተመልከቱ ፤ ዕለቱን ፡ ተጨርሶ ፡ ሳይታረም ፡ መጥቶላችኋል ። ሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሀሉ ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ፡ አሜን ።


ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለማረምና ፡ ለማሳተም ፡ ዕረፍትና ፡ ጊዜ ፡ አላገኙም ፤ ተከረን ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ከሮማ ፡ ወደየሩሳሌም ፡ ሲሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዐለፈ ፡ ይልቁንም ፡ የፊደሉን ፡ ተራ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለማፍረስ ፡ ለመናድ ፥ በዚያው ፡ በጥንቱ ፡ ሕግ ፡ በአሌፋት ፡ መንገድ ፡ በአበገደ ፡ ለማስኬድ ፡ ፍጹም ፡ ሐሳብ ፡ ነበራቸውና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሳይታተም ፡ ቈየ ። ኋላም ፡ በጊዜ ፡ ሞት ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ምሉ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ለነበረው ፡ ለሀገራቸው ፡ ልጅ ፡ ለተማሪያቸው ፡ እንዲህ ፡ ብለውታል ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ይህነን ፡ ግስ ፡ ማሳተም ፡ ብትፈልግ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጥቂት ፡ ዕብራይስጥ ፡ ተምረኽ ፡ ማፍረስና ፡ ማደስ ፡ አለብኽ ፤ በመዠመሪያው ፡ አበገደን ፡ ጥፈኽ ፡ የፊደሉን ፡ ተራ ፡ በዚያው ፡ አስኪደው ። እንባቦችም ፡ እንዳይቸገሩ ፡ ከፊደል ፡ ቀጥለኽ ፡ ዐጅር ፡ ሰዋስው ፡ አግባብት ፤ የጐደለውና ፡ የጠበበው ፡ ኹሉ ፡ መልቶ ፡ ሰፍቶ ፡ ሊጣፍ ፡ ፈቃዴ ፡ ነው ፤ ከሌላው ፡ ንግድ ፡ ይልቅ ፡ ይህን ፡ ፩ ፡ መክሊት ፡ ለማብዛትና ፡ ለማበርከት ፡ ትጋ ፤ ዘር ፡ ኹን ፥ ዘር ፡ ያድርግኽ ፤ ካላጣው ፡ ዕድሜ ፡ አይንፈግኽ ፡ ለሀገርኽ ፡ ያብቃኽ ፡ ብለው ፡ ተሰናበቱት ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሩብ ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፡ ቈይተው ፡ እግዚእየ ፡ ተመጠዋ ፡ ለነፍስየ ፡ ብለው ፡ ከሥጋ ፡ ርስት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሕይወት ፡ ተለዩ ። ገና ፡ አስቀድመው ፡ በግንቦት ፥ ዠንድሮ ፡ ነሐሴን ፡ ብጨርስ ፡ ጳጕሜን ፡ አላልፋትም ፡ እንዳሉ ፡ በ፲፱፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጳጕሜ ፡ በ፫ ፡ የሩፋኤል ፡ ለት ፡ ዐርፈው ፡ በደብረ ፡ ጽዮን ፡ ተቀበሩ ። ዕድሜያቸውም ፡ ፹፫ ፡ ዓመት ፡ ከ፬ ፡ ወር ፡ ከ፳ ፡ ቀን ፡ ነው ። እስከዚህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ነው ።

# የታሪክ ፡ መግቢያ ።

## ፊት ፡ በር ፡ ወይም ፡ ጥንተ ፡ ነገር ።

በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፥ ዋሕድ ፡ መለኮት ፡ ውነዩል ፡ ወሥሉስ ፡ አካል ። ወሥላሴሁኒ ፡ ፍጹምት ፡ በፍና ፡ አካላት ፡ ወበአስማት ፡ ሥላሴ ፡ ዕሩት ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ እንተ ፡ ኢትትኌለቍ ፡ በመለኮት ። ፈጣሬ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፥ ወጸጋዊ ፡ ኵሎን ፡ ሀብታት ፡ ፈጣሪ ፡ በኢጻምዎ ፥ ወጸጋዊ ፡ በኢደንጽዎ ፡ ፈጢሮሰ ፡ ወጸግዎ ፡ አምጽአተ ፡ ኵሉ ፡ በቃሉ ፡ እምኢሀልዎ ፡ ኀበ ፡ ሀልዎ ፡ ንዌቅን ፡



(ዘይክል ፡ ኵሎ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይስእኖ) ።

ጸሐፈ ፡ በለብዎ ፥ ወነገረ ፡ በአሰርግዎ ፥ አርእስተ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ምሉእ ፡ ጥበብ ። ከመ ፡ ናስምዕ ፡ ሰብአ ፡ በቃል ፡ ሐዋዝ ፡ ወበነገር ፡ ምዑዝ ፡ ጥንተ ፡ ነገሩ ፡ ለግእዝ ፥ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ልደቱ ፡ ወዘከመ ፡ እፎ ፡ ርደቱ ፡ እምአይ ፡ ነገድ ፡ ወእምአይ ፡ ትውልድ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ዐርገ ፡ እምነቤነ ፡ ብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ብልየቱ ፥ እንዘ ፡ ከመ ፡ ንስር ፡ ይትሐደስ ፡ ውርዙቱ ። ወከመ ፡ ተዐለዋ ፡ ዓዲ ፡ ኀቤሁ ፡ መጻሕፍት ፡ እምላከውያት ፡ ወአዋልዲሆን ፥ እምአይ ፡ ክናፍር ፡ ወእምአይ ፡ ልሳን ፥ በአይ ፡ መዋዕል ፡ ወበአይ ፡ አዝ

ማን ፡ እስመ ፡ ዛቲ ፡ ጥበብ ፡ ጥበበ ፡ መጽሐፍ ፥ ተረስዐት ፡ እምኀሊሉ ፡ ሰብእ ፥ ወተነብአት ፡ እምእሰዋፍ ፡ እሰዋፍሰ ፡ ክህናት ፡ ወሊቃነ ፡ ክህናት ።

ወጽሒፎትነሂ ፡ አኮ ፡ በአንኖ ፡ በቃለ ፡ ዝንጓዔ ፡ አላ ፡ በአኀጽሮ ፡ ወበጥእማኤ ። ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ወእስከ ፡ ዳግም ፡ ጉባኤ ፥ ዘበቱ ፡ ይትከፈል ፡ ማኅበረ ፡ ምእመናን ፡ ለክልኤ ፡ በመልክአ ፡ ቊርባን ፡ ጽዋዔ ።

ሙብአ ፡ ታሪክ ፡ ወዜና ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ግእዝ ፡ ቅድምና ፡ እምአሪት ፡ ሙሴ ፡ ወእምአብረክሲስ ፥ ጥንተ ፡ ብሉይ ፡ ወጥንተ ፡ ሐዲስ ፡ (ዘፍ ፲፩ ፡ ፩-፱ ። ግብ፪ ፡ ፩-፲፫) ። ያለም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ በየነገዱ ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፥ ግእዝ ፡ ብቻ ፡ በማንም ፡ ነገድ ፡ ስም ፡ አልተጠራም ፡ በራሱ ፡ በገንዘቡ ፡ እንጂ ። ግእዝ ፡ ማለት ፡ ፩ ፡ ፩ኛ ፡ መዠመሪያ ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ የብሉይ ፡ መምህራን ፡ ይልቁንም ፡ የጀርመን ፡ ሊቃውንት ፡ ወከነ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ አሐተ ፡ ከንፈረ ፡ ወአሐደ ፡ ነገረ ፡ ያለውን ፡ ይዘው ፡ ተመርኵዘው ፥ ግእዝ ፡ የአዳም ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ይህችንም ፡ ባህል ፡ ያነቃትና ፡ ያፈለቃት ፥ ከብሉይ ፡ መምህራን ፡ ያጣበቃት ፡ ሲዳ ፡ ጳውሎስ ፡ ነው ፡ ይባላል ፡ መፀልም ፡ ዮሐንስ ፡ የሚሉም ፡ አሉ ፡ ፪ቱም ፡ ጀርመኖች ፡ ናቸው ። ዳግመኛም ፡ የሐዲስ ፡ መምህራን ፥ እሊህም ፡ ፪ቱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ሳይቀሩ ፥ ወአኀዙ ፡ ይንብቡ ፡ በልሳናት ፡ ካልአት ፡ ያለውን ፥ ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ካለው ፡ አያይዘው ፥ ልሳናት ፡ ካልአት ፡ ከተባሉት ፡ ፩ኛው ፡ ግእዝ ፡ ነውና ፥ ከኢትዮጵያም ፡ ለፋሲካ ፡ በዓል ፡ የኼዱት ፡ ፈላሾችና ፡ አይሁድ ፡ የጰራቅሊጦስ ፡ ለት ፡ የጴጥሮስን ፡ ስብከት ፡ (፲፬-፹፩) ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋቸው ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፡ አምነው ፡ ተጠምቀው ፡ ከ፫ቱ ፡ ሺሕ ፡ አርድእት ፡ ተቈጥረዋል ። «አሰማማቸውም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ በራሱ ፡ ቋንቋ ፡ በዕብራይስጥ ፡ እየተናገረ ፡ ሲሰብክ ፥ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ኹሉ ፡ በያገሩ ፡ ፊደል ፡ በቋንቋ ፡ በቋንቋው ፡ ያሰማል ፡ ለሙቶ ፡ ኻያው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ግን ፡ ይልቁንም ፡ ለሐዋርያት ፥ ያለምን ፡ ኹሉ ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ ፡ ከመ ፡ ቅጽበት ፡ ገልጦላቸዋል» ። ከነዚሁ ፡ ደግሞ ፡ እስከ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ሞት ፡ የቈዩና ፡ ወዲያው ፡ በቶሎ ፡ የመጡ ፡ አሉ ፤ በፊትም ፡ በኋላም ፡ የመጡት ፡ ከምሴተ ፡ ኀሙስ ፡ እስከ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ባይናቸው ፡ ያዩትን ፡ ከሐዋርያትም ፡ የሰሙትን ፡ የክርስቶስን ፡ ሥራና ፡ መከራ ፡ መሲሕነቱን ፡ ተረድተው ፥ እንደ ፡ ኖብ ፡ ንግሥት ፡ ጃን ፡ ደረብ ፡ እየዞሩ ፡ በያሀገሩ ፡ ሰብከዋል ፥ ርሱ ፡ ለሱዳኖች ፡ እንደ ፡ ሰበከ ። መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ለጌታችን ፡ ስብከት ፡ መሪ ፡ ፈታውራሪ ፡ ፀዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መጠን ፥ በጴጥሮስም ፡ ስብከት ፡ ያመኑት ፡ ፈላሾችና ፡ አይሁድ ፥ ለሐዋርያት ፡ መንገድና ፡ አካኼድ ፡ መሪዎችና ፡ ፈታውራሮች ፡ ፀዋጆች ፡ ነጋሮች ፡ ኹነዋል ፡ ብለው ፥ አምልተው ፡ አስፍተው ፥ ሥር ፡ መሠረት ፡ ሰጥተው ፡ ቀዋሚ ፡ አፈታት ፡ ይፈቱታል ። ሐተታውንም ፥ ኢትዮጵያ ፡ እንዲህ ፡ አስቀድማ ፡ በልጆቿ ፡ ሐዋርያነት ፡ የወንጌልን ፡ እስኩታ ፡ ገፈታ ፡ ተቀብላ ፡ ቀምሳ ፥ ሕገ ፡ ኦሪትንም ፡ ሳትረሳ ፥ ኹለቱንም ፡ እያጣጣመች ፥ በክርስቶስና ፡ በሐዋርያት ፡ ደም ፡ የበቀለው ፡ ትምርት ፡ በሰማዕታት ፡ ደም ፡ ዘርዝሮ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእትን ፡

እስኪያፈራ ፡ ድረስ ፡ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ ከቈየች ፡ በኋላ ፥ ስለ ፡ ጥምቀትና ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡ ርሷ ፡ ራሷ ፡ ወዳ ፡ ለምዳ ፡ እጅ ፡ መንሻዋን ፡ ሰዳ ፡ ጳጳስ ፡ ላኩልኝ ፡ አለች ፡ እንጂ ፡ ከቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ፳ኛ ፡ ከትናቴዎስ ፡ በፊት ፥ ሀስበና ፡ ሹሞ ፡ የላከላት ፥ ወይም ፡ ተከራክሮ ፡ ያሳመናት ፡ በሰይ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የለም ። በብሉይም ፡ ኸን ፡ በሐዲስ ፡ እጇና ፡ ልቧ ፡ ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ ደም ፥ ከጻድቃን ፡ በቀል ፡ ከሰማዕታት ፡ ቂም ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ብለው ፥ እንዲህ ፡ ያትታሉ ። እስከዚህ ፡ የታሪክ ፡ መግቢያ ፡ ነው ።

## ታሪክና ፡ መቅድም ፡
## የስዋስውና ፡ የግስ ፡ ወንድም ።

ይህም ፡ ታሪክ ፡ በ፬ ፡ አርእስት ፡ ይከፈላል ።
፩ኛው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ነገድና ፡ ስለ ፡ ቋንቋ ፡ ስለ ፡ ሀገርም ፡ ስም ፡ መፋለስ ።
፪ኛው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ብሉይና ፡ ስለ ፡ ሐዲስ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ መመለስ ።
፫ኛው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ፊደል ፡ ተረክቦና ፡ ጥንት ፡ ስለ ፡ ትምርቷም ፡ ሰማያዊነት ።
፬ኛው ፡ ክፍል ፡ መቅድም ፡ ነው ።

## ፩ኛ ፡ ክፍል ።

### ስለ ፡ ነገድና ፡ ስለ ፡ ቋንቋ ፡ ስለ ፡ ሀገርም ፡ ስም ፡ መፋለስ ።

ከማየ ፡ አይኅ ፡ በኋላ ፡ ሳባንና ፡ አቢስን ፡ የወረሱ ፥ በሳባ ፡ በአቢስ ፡ የነገሡ ፡ የሳባ ፡ የአቢስ ፡ ባላባቶችና ፡ መደበኞች ፡ ነገደ ፡ ካም ፡ ናቸው ። ካም ፡ ኵሽን ፥ ኵሽ ፡ ሳባንና ፡ አቢስን ፡ ይወልዳል ፡ ከነዚህም ፡ ሌላ ፡ ፳፯ ፡ ነገድ ፡ ወልዷል ። ከ፳፱ቱ ፡ ነገድ ፡ ሸበእና ፡ ድዳን ፡ የሚባሉት ፡ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ ነገድ ፡ እንደ ፡ ምናሴና ፡ እንደ ፡ ኤፍሬም ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፯) ። አቢስ ፡ የበኵሩ ፡ የሳባ ፡ ሳብዓይ ፡ የናምሩድ ፡ ተከታይ ፡ ፯ኛ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ከሳባ ፡ እስከ ፡ ናምሩድ ፡ ፯ቱ ፡ ሸበእና ፡ ድዳን ፡ ሳይቀሩ ፡ ፰ቱ ፡ ነገድ ፡ በኦሪትና ፡ በዜና ፡ መዋዕል ፡ ተጥፈዋል ፡ የቀሩት ፡ ኻያው ፡ ግን ፡ በታሪክ ፡ እንጂ ፡ በቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ አይገኙም ። አንዳንዱ ፡ ታሪክ ፡ በአቢስ ፡ ፈንታ ፡ ከለው ፥ በከለው ፡ ፈንታ ፡ አቢስ ፡ ይላል ፡ ከለው ፡ የአቢስ ፡ ፪ኛ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ኢትዮጲስ ፡ የኵሽ ፡ ፪ኛ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

የወንድሞቻቸው ፡ የበለው ፡ የኖበ ፡ የሐዊላ ፡ ምድር ፡ በየስማቸው ፡ እንደ ፡ ተጠራ ፥ የሳባና ፡ የአቢስም ፡ ክፍል ፡ በየስማቸው ፡ ተጠርቷል ። ሳባ ፡ የትግሮች ፥ አቢስ ፡ ያማሮች ፡ አገር ፡ ነው ። ከባቢሎንም ፡ ግንብ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ የነበረው ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ ፡ ሲለያይ ፥ ቋንቋቸውም ፡ እንደ ፡ ሀገራቸው ፡ በየስማቸው ፡ ተሰይሟል ። ከሳባም ፡ ቋንቋ ፡ በኋላ ፡ ሳባን ፡ የመሰለ ፡ በየዘመኑ ፡ የታከለ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ ፡ እንዳላቸው ፡ ታውቋል ፡ ይኸውም ፡ በየዋሻውና ፡ በየደንጊያው ፡ በየሐውልቱ ፡ ላይ ፡ ተጥፎ ፡ ይገኛል ።

ማእዝ ፡ ግን ፡ በ፫ ፡ ሺ ፡ ሕ ፡ ከ፳፻ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ፳ኛው ፡ መቶ ፡ ሳይፈጸም ፡ በያዕቆብ ፡ ዘመን ፡ ከእስያ ፡ ክፍል ፡ ከየመን ፡ ፈልሰው ፡ እንዳንበጣ ፡ በገዙተው ፡ ምድር ፡ አላብሰው ÷ አተርትረው ፡ በባብ ፡ እልመንደብ ፡ ተሻግረው ፡ ሳባንና ፡ አቢስን ፡ ለመውረስ ÷ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ ወዳፍሪቃ ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ክም ፡ የገቡ ፡ የነገደ ፡ ሴም ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡፡

ባብ ፡ እልመንደብ ፡ ማለት ፡ የመከራና ፡ የጭንቅ ፡ በር ÷ ወይም ፡ የታረደ ፡ የተቈረጠ ፡ ምድር ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ በኤርትራና ፡ በህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ጫፍ ፡ በ፪ቱ ፡ ባሕሮች ፡ መካከል ፡ ወሰን ፡ ደንበር ፡ ኾኖ ፡ የቆመ ÷ እስያና ፡ አፍሪቃ ፡ የብስ ፡ ለየብስ ፡ ገጥመው ፡ ተያይዘው ፡ የነበሩበት ÷ ከእስያ ፡ ወዳፍሪቃ ፡ ከአፍሪቃ ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ የሚያሳልፍ ፡ ጠባብ ፡ መተላለፊያ ፡ በር ፡ ነበረ ፡፡ ኋላ ፡ ግን ፡ እስክንድር ፡ መቄዶናዊ ፡ በስዊስና ፡ በሳይድ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ በር ÷ የብሱን ፡ ቈርጦ ፡ መሬቱን ፡ ቈፍሮ ፡ ኹለቱን ፡ ባሕሮች ፡ ገጥሞና ፡ አገናኝቶ ፡ እስያና ፡ አፍሪቃን ፡ በባሕር ፡ ስለ ፡ ለያያቸው ÷ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የብስነቱ ፡ ቀርቶ ፡ ባሕር ፡ ኹኗል ፡፡

የመጡበትንም ፡ ምክንያት ፡ ትግሬው ፡ አቶ ፡ ፍሥሓዬ ፡ በታሪኩ ፡ ውስጥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡ ከርሕቀቱ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ በማይባል ፡ ዘመን ፡ በሳሊማና ፡ በበረ ፡ በረሓ ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገባ ፡፡ ክፍላቸውና ፡ ነገዳቸው ፡ በሺ ፡ ሐ ፡ ቋንቋ ፡ ፩ ፡ ዓዳ ፡ ፪ ፡ ጊም ፡ ዓዳ ፡ ፫ ፡ አሰላ ፡ ዓዳ ፡ ፬ ፡ ነካልስ ፡ ዓዳ ፡ ይባላል ፡ «ዓዳ ፡ በዕብራይስጥ ÷ ማኅበረ ፡ ሕዝብ ÷ ጉባኤ ፡ ሕዝብ ÷ የታከበ ፡ የተሰበሰበ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሲያበዛ ፡ ዓዳት ፡ ይላል» ፡፡ ፩ኞች ፡ ሐመደ ፡ ፪ኞች ፡ ደብዓ ፡ ይባላሉ ፡ ሐመድ ፡ ማለት ፡ ዐፈር ፡ መሬት ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ ብዛታቸውን ፡ ያስታውቃል ፡፡ በኋላ ፡ የመጡ ፡ እነዚህ ፡ ኹለቱ ፡ ሐመደና ፡ ደብዓ ፡ ትግረኛ ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፡ በደብዓ ፡ ዘመን ፡ ከጠርነት ፡ ላይ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ምሉ ፡ ዝናም ፡ ሳይዘንም ፡ ድርቅ ፡ ኹኖ ፡ ነበር ፡ ይባላል ፡፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ቶባስ ፡ የሚባል ፡ ኀያል ፡ ንጉሥ ፡ የዐረብን ፡ አገር ፡ ጠቅልሎ ፡ ይገዛ ፡ ነበረና ÷ ኢትዮጵያንም ፡ አጥቅቷታል ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ወርቃቸውን ፡ እየቀበሩ ፡ በያህጉሩ ፡ ተሰደዱ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ሰው ፡ ስላነሳት ፡ ውድማ ፡ ኹና ፡ ነበር ፡ ይላሉ ፡፡ በደብዓ ፡ ዘመን ፡ የኾነው ፡ መከራና ፡ መቅሠፍት ፡ ዘመኑ ፡ አይታወቅም ፡ እንዳልጠይቅም ፡ ለጥያቄው ፡ ምላሽ ፡ የሚሰጥ ፡ ታሪክ ፡ በጥቂ ፡ ሰው ፡ ባገር ፡ ታጣ ፡ ብሎ ፡ ይተርከል ፡፡

የሮማውያን ፡ ታሪክ ፡ ግን ፡ ስደታቸውን ፡ ከእስራኤል ፡ ስደት ፡ አነጻጽሮ ÷ ነገደ ፡ ሴም ፡ ወዳፍሪቃ ፡ ክፍል ፡ መግባታቸው ÷ በኢትዮጵያ ፡ መስፈራቸው ፡ እስራኤል ፡ በግብጽ ፡ ሳሉ ፡ ነው ፡ ይላልና ፡ ይኸ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ዮሴፍ ፡ ለፈርዖን ፡ የተረጐመለት ፡ ፯ቱ ፡ ዓመት ፡ ዘመነ ፡ ረኃብ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በግልጥ ፡ ይታወቃል ፡ (ዘፍ፡፵፩ ፡ ፲፯–፶፯) ፡፡

እሊህንም ፡ ነገደ ፡ ሴም ፡ ያልናቸውን ፡ ሕዝብ ፡ የነጮችና ፡ የዐረቦች ፡ ታሪክ ፡ ሕምያር ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ሐበሻት ፡ ይላቸዋል ፡፡ ዮቅጣን ፡ የተባለም ÷ ፲፫ ፡ ነገድ ፡ የወለደው ፡ ቃናሽ ፡ የዔቦር ፡ ልጅ ፡ የፋሌግ ፡ ወንድም ፡ ነው ፡ (ዘፍ፡፲ ፡ ፳፮–፳፱) ፡፡

እስክንድርም ፡ በዠርማንነታቸው ፡ ተማሮች ፡ ብሏቸዋል ፡ ኑብሮች ፡ ማለት ፡ ነው ። ሕምያር ፡ ማለት ፥ ቀያዮች ፡ የቀይ ፡ ዳሞች ፡ ደበብ ፡ ያሉ ፥ ጠብና ፡ ሸክላ ፡ የሚመሰስሉ ፥ ማእከላዊ ፡ ሕብር ፡ ያላቸው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አዳሎችም ፡ ቀይ ፡ ሰው ፡ ሲሉ ፡ አሳሐመራ ፡ የሚሉት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ስም ፡ ይመስላል ። ሐበሻት ፡ ደማሞ ፡ የጌቱ ፡ ዒዳ ፡ ጠቅላይ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ስምነቱም ፡ ቀዳማዊ ፡ እንጂ ፡ ደኃራዊ ፡ አይዶለም ፡ ግና ፡ ወዳፍሪቃ ፡ ሳይመጡ ፡ በዚያው ፡ በገራቸው ፡ በየመን ፡ ሳሉ ፡ ሐበሻት ፡ ሲባሉ ፡ ኑረዋል ። ትርጓሜውም ፥ ነጻነትና ፡ ልዩነት ፡ አንድነት ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ አንድነቱ ፡ እንደ ፡ ችብና ፡ እንደ ፡ ንዶ ፡ ብንድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የታሰረ ፥ ለብቻው ፡ የቆመ ፡ ከነገደ ፡ ከም ፡ የተለየ ፡ ሴማዊ ፡ ማኅበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዐረቦች ፡ ግን ፡ ቅልቅል ፡ ድብልቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ ምክንያቱም ፡ የዮቅጣን ፡ ልጆች ፡ ፲፫ ፡ ነገድ ፡ ሲኾኑ ፡ ወዳፍሪቃ ፡ የመጡትና ፡ ያልመጡት ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ፳ቱ ፡ ነገድ ፡ ብንግሥት ፡ አዚብ ፡ አባቶች ፡ በሽበእ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ፩ ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ አቁመው ፡ ነገደ ፡ ሴም ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ተብለዋል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ በየነገዳቸው ፡ ተለይተው ፡ አልተጠሩምና ፥ ስለዚህ ፡ ነው ። እውነተኛው ፡ ታሪክ ፡ ይህ ፡ ከኾነ ፡ አቢስ ፡ አቢሲኒያ ፡ ማለትና ፡ ሐበሽ ፡ ሐበሻ ፡ ማለት ፡ በነገድ ፥ በትውልድ ፥ በፊደል ፥ በዘመን ፡ ልዩ ፡ ልዩዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ማስተዋል ፡ ይገባል ።

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

ኢትዮጵያም ፡ ማለት ፡ ከኵሽ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ በ፩ ፡ ሺሕ ፡ ከ፬፻፶ ፡ ዓመት ፡ በበጥሊሞስ ፡ ዘመን ፡ የወጣ ፥ ሐዲስ ፡ እንግዳ ፡ ጽርኣዊና ፡ ደኃራዊ ፡ ስም ፡ ነው ። ፸ ፡ ሊቃናት ፡ ብሉያትን ፡ ከዕብራኒ ፡ ወደ ፡ ዮናኒ ፡ ሲመልሱ ፡ ዕብራይስጡ ፡ ኵሽ ፡ የሚለውን ፡ የኵሽን ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ ኢትዮፕስ ፡ ስላሉት ፥ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከግብጽ ፡ ወዲህ ፡ ያለው ፡ የኵሽ ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተብሏል ። የግእዝም ፡ ብሉይ ፡ ከጽርእ ፡ ስለ ፡ ተቀዳ ፡ እንደ ፡ ጽርኡ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ ዕብራይስጡ ፡ ኵሽ ፡ አይልም ፡ ትርጓሜውም ፡ ጥቍር ፡ ጠቋራ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፲፫ ። ኤር፲፫ ፡ ፳፫) ። ፪ኛም ፡ የሀገር ፡ ስም ፡ ሲኾን ፥ ቋላ ፡ በረሓ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በረሓነት ፡ ላለው ፡ ለእስያም ፡ ክፍል ፡ ለቃደስ ፡ በርኔና ፡ ለሐቅለ ፡ ሲና ፡ ይነገራል ፡ (መዝ ፸፩ ፡ ፱ ። ፸፫ ፡ ፲፬) ። ባ፲፫ኛው ፡ ሴክል ፡ በላስቶች ፡ ዘመን ፡ ኑብረድ ፡ ይሥሐቅ ፡ እልመለክን ፡ ምኒልክ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ሐሳቡ ፡ ከረብ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ የመለሰው ፡ ክብረ ፡ ነገሥት ፡ ግን ፡ ኵሽን ፡ ኵማ ፡ ኵሳ ፡ አክሱናስ ፡ ብሎ ፡ ኢትዮጲስን ፡ የአክሱናስ ፡ ልጅ ፡ ይለዋል ፡ የመላ ፡ የግምት ፡ የነሲብ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ የኑብረድ ፡ ይሥሐቅ ፡ ጕሽ ፡ ክብረ ፡ ነገሥት ፥ ከጠራውና ፡ ከበሰለው ፡ ከቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ይቀድማልን ፥ ወይስ ፡ ይሻላልን ። አሪት ፡ ነቢያትን ፡ ሳላዩ ፡ ሳልሰሙ ፡ ወይም ፡ አይተው ፡ ሰምተው ፡ ለማያስተውሉ ፡ እውነት ፡ ይመስላቸው ፡ ይኾናል ። ወይመስሉሙ ፡ ወልደ ፡ ዮሴፍ ፡ (ሉቃ ፫ ፡ ፳፫) ። እለሰ ፡ አልበሙ ፡ ትምህርት ፡ ወእለ ፡ ኢለበዉ ፡ ይመይጥዎ ፡ ለቃለ ፡ መጽሐፍ ፡ (፪ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፮) ።

የአፍሪቃ ፡ ሰዎች ፡ መጥቈራቸው ፡ ኢትዮጵያም ፡ መባላቸው ፤ ያልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚሉት ፡ የካም ፡ ዘር ፡ በመኾን ፡ አይደለም ። ወምድረ ፡ ከምሰ ፡ መርቄ ፡ ይእቲ ፡ እንጂ ፡ ይላል ፡ (ኩፋሌ) ። ሔኖክ ፡ ያያቸው ፡ ፲፱ቱ ፡ መሳክወ ፡ ፀሓይ ፡ ከመንፈቀ ፡ ሰማይ ፡ ወዲህ ፡ ወደ ፡ ደቡብና ፡ ወደ ፡ አዜብ ፡ በአፍሪቃ ፡ እንጻር ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ የአፍሪቃ ፡ ሰዎች ፡ ለፀሓይ ፡ ይቀርበሉና ፤ ፈላስፎችም ፡ ምድርን ፡ በሉሚ ፡ በንቍላል ፡ መስለው ፡ ወገቧ ፡ ክበቧ ፡ አፍሪክ ፡ አመሪክ ፡ ነው ፡ ይላሉና ፡ የአፍሪቆች ፡ ጥቍረት ፡ አየራቸውና ፡ መሬታቸው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የምድር ፡ ደረት ፡ የፀሓይ ፡ ጎረቤት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከሙቀት ፡ ብዛት ፡ ከሐሩር ፡ ከዋዕይ ፡ ከመሬት ፡ ርስን ፡ ከነፋስ ፡ ከፀሓይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አባታቸው ፡ ኩሽ ፡ ጥቍር ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ ቍራ ፡ ጸልሞ ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ከነዓን ፡ ተረግሞ ፡ በመርገም ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ፡ (ማሕ፩ ፡ ፭ ፡ ፮) ። ያልተረገመው ፡ ካም ፡ ተረግሞ ፡ ጥቍረት ፡ በመርገምስ ፡ ቢኾን ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ በእስያ ፡ ክፍል ፡ በአፍሪቃ ፡ ድንበር ፡ ያሉት ፡ የካም ፡ ነገድ ፡ የከነዓን ፡ ትውልድ ፡ የሚጽራይም ፡ ልጆች ፡ እነሉድ ፡ የኩሽም ፡ ልጆች ፡ እነናምሩድ ፡ እንደ ፡ ያፌትና ፡ እንደ ፡ ሴም ፡ ዘር ፡ ቀያዮች ፡ ነጫጮች ፡ ብጫች ፡ በልኾኑም ፡ ነበር ። የራስ ፡ ቅማልና ፡ የልብስ ፡ ቅማል ፡ ከንድ ፡ ሰው ፡ ተገኝተው ፡ ነጭና ፡ ጥቍር ፡ መኾናቸው ፡ በበታ ፡ ምክንያት ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ በፈጣሪው ፡ ትእዛዝ ፡ ያለበትን ፡ ዓለም ፡ የበቀለበትን ፡ መሬት ፡ ርስቱን ፡ መከኑ ፡ ፍጥረቱን ፡ ይመስል ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ እንዳለበት ፡ የታወቀ ፡ የተረዳ ፡ ነው ። እንሆ ፡ በ፭ቱ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ በእስያና ፡ በአፍሪቃ ፡ በኤውሮፓና ፡ በመሪቃ ፡ በውስትራልያ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፤ ሰማያዊ ፡ ንጉሥ ፡ ያዘጋጀው ፡ የሕያው ፡ የመንግሥቱ ፡ ፀላማ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ቀይ ፡ ጥቍር ፡ ነጭ ፡ ብጫ ፡ ተብሎ ፡ ባራት ፡ ዐይነት ፡ ስሞች ፡ ይጠራል ። ቀለሙና ፡ ሕብሩ ፡ እንደ ፡ መሬቱና ፡ እንዳየሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ቈርበቱና ፡ ገላው ፡ ቀርበ ፡ ሲያዩት ፡ የስንዴ ፡ ሊጥ ፡ የዘጰ ፡ ሰንሬቤት ፡ ፍልጥ ፡ መዳብና ፡ ንሓስ ፤ ወይም ፡ ወርቀ ፡ ዘበ ፡ ደማስ ፡ ይመስላል ። ለዚህም ፡ ላራቱ ፡ ዐይነት ፡ ሕብር ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ሰርከን ፡ አለውና ፤ ክፍሉ ፡ እስከ ፡ ፲፪ ፡ ይደርሳል ። በካምና ፡ በሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ ሳይኾን ፡ ባራተኛው ፡ ብቻ ፡ በከነዓን ፡ ላይ ፡ የተነገረው ፡ የኖኅም ፡ ርግማን ፡ እምላከዊ ፡ ትንቢት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከከነዓን ፡ ስም ፡ ይስማማል ፡ ከነዓን ፡ ማለት ፡ ታዛዥና ፡ ተገዥ ፡ ፈቃደኛ ፡ ትሑት ፡ ማለት ፡ ነውና ። ትርጓሜውም ፡ ነጋዴ ፡ ተብሎ ፡ ለወንድሞቹና ፡ ላጎቶቹ ፡ ቀረጥና ፡ ግብር ፡ መክፈሉን ፤ ነጋዴ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ስም ፡ ከነዓን ፡ መባሉን ፤ ኋላም ፡ በሴም ፡ ሰፃ ፡ ክቀናው ፡ ርስት ፡ ተነቅሎ ፡ የባሮች ፡ ባሪያ ፡ የእስራኤል ፡ ተገዥ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፡ እንጂ ፡ የመልክን ፡ ጥቍረት ፡ አያሳይም ፡ (ዘፍ፡፱ ፡ ፳፭ ። ሕዝ፲፯ ፡ ፬) ።

በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የከነዓን ፡ ዘር ፡ ወደአፍሪቃ ፡ ክፍል ፡ አልመጣም ። ከንድ ፡ አባት ፡ ከንድ ፡ እናት ፡ ቀይና ፡ ጥቍር ፡ መወለዱም ፡ ከንድ ፡ ወይን ፡ ዘለላ ፡ ከንድ ፡ ራስ ፡ ማሽላ ፡ ነጭ ፡ ዐይነትና ፡ ጥቍር ፡ ዐይነት ፡ ፍሬ ፡ እንዲገኝ ፡ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ፡ የናት ፡ ሆድ ፡ ዝንጕርጕር ፡ እንዲሉ ። የሴቶች ፡ ጠባይ ፡ እንደ ፡ ጎሥሥት ፡ ጠባይ ፡ ተለዋጭ ፡ ተገልባጭ ፡ ተታላይ ፡ ያየውን ፡ መሳይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ የሌላ ፡ ወንድ ፡

መልክ ፡ በማየትና ፡ በመመልከት ፡ በመውደድና ፡ በመመኘት ፡ ሳሉ ፡ ከባሎቻቸው ፡ የሚቀበሉት ፡ ዘር ፡ ሌላውን ፡ እንጂ ፡ አባቱን ፡ አይመስልም ። ሴትና ፡ መሬት ፡ ዘር ፡ መለወጣቸው ፡ ከጥንት ፡ ከፍጥረት ፡ ከሰብአ ፡ ትካት ፡ ዠምሮ ፡ ነው ፤ ይህነንም ፡ ገበሬና ፡ ወላድ ፡ አለጥርጥር ፡ ያውቁታል ። ሴቶችም ፡ ዐይናቸው ፡ የወደቀበትን ፡ ልባቸው ፡ የጐመዠበትን ፡ በፎቶግራፍ ፡ ሰንስ ፡ እንዲያነሡትና ፡ ያን ፡ አስመስለው ፡ እንዲወልዱ ፤ እንሆ ፡ በላባንና ፡ በያዕቆብ ፡ በጎች ፡ ይታወቃል ፡ (ዘፍ፡፴ ፡ ፴፯–፵፪) ። ሌላም ፡ የሚያዩትና ፡ የሚወዱት ፡ ባይኖር ፡ ባሎቻቸውን ፡ በፍጹም ፡ ልቡና ፡ ከሎደዱና ፡ የባሎቻቸው ፡ መልክ ፡ በልቡናቸው ፡ ካልተሣለ ፤ በሥም ፡ ላይ ፡ የሚፈስ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አፍሳሹን ፡ ትቶ ፡ ሥሙን ፡ እንዲመስል ፤ ልጆችም ፡ አባቶቻቸውን ፡ መምሰል ፡ ትተው ፡ ፈጽመው ፡ እናቶቻቸውን ፡ ይመስላሉ ፡ ወይም ፡ ከባት ፡ ከናታቸው ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ነሥተው ፡ እንደ ፡ በቅሎ ፡ መከከለኞች ፡ ይኾናሉ ።

ከናምሩድ ፡ አገር ፡ ከባቢሎን ፡ እስከ ፡ ግብጽና ፡ እስከ ፡ የመን ፡ እስከ ፡ ፊንቂ ፡ እስከ ፡ ከነዓን ፡ በእስያ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ዐረብ ፡ ሦስቱ ፡ እጅ ፡ የካም ፡ የኵሽ ፡ ዘር ፡ ነው ፤ ተከፍሎም ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ የተሻገረና ፡ ወደ ፡ ኤውሮፓ ፡ የኼደ ፡ አለ ። ኋላም ፡ በየጊዜው ፡ የሴም ፡ የያፌት ፡ ዘር ፡ ተደምሮበታል ፤ ሰናክሬምም ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ደበላልቆታል ፤ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ያልነቀለውና ፡ ያልተከለው ፡ ያላፈለሰው ፡ ሕዝብ ፡ የለም ። ዛሬም ፡ ባ፫ቱ ፡ ክፍል ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ የሕዝብና ፡ የአሕዛብ ፡ ትውልድ ፡ እንዳረብ ፡ ዘር ፡ ውጥንቅጥ ፡ ኾኗል ። ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በየሐረጉና ፡ በየጕንዱ ፡ በየቦታውና ፡ በያጸዱ ፤ በየዕፃውና ፡ በየክፍሉ ፡ በየፈንታውና ፡ በየዕድሉ ፡ በየነገዱና ፡ በያባቱ ፡ በየመንግሥቱና ፡ በየርስቱ ፡ ተወስኖ ፡ መኖር ፡ ስላልቻለና ፡ ፍጹም ፡ ዐርነት ፡ ስላገኘ ፤ በየኼደበት ፡ በየደረሰበት ፡ አለጕሣውና ፡ አለሕዝቡ ፡ ከማኅም ፡ ሕዝብ ፡ እየተጋባ ፡ ዘሩና ፡ ደሙ ፡ እንዳለሌና ፡ እንደ ፡ ባዝራ ፡ እንደ ፡ ዘይትና ፡ እንደ ፡ ወይራ ፤ እንደ ፡ ጌሾና ፡ እንደ ፡ ብቅል ፡ እንደ ፡ ንፍሮ ፡ እኽል ፡ ተቀላቅሏል ። ይልቁንም ፡ የሮማውያን ፡ ዘር ፡ (ዳን፪ ፡ ፵፫) ። በዘር ፡ በሩካቤ ፡ ያልተዳቀለ ፡ ያልተቀላቀለ ፤ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ያልተመሳሰለና ፡ ያልተጋባ ፡ ያልተዋለደ ፡ ያልተራባ ፡ ሕዝብና ፡ ነገድ ፡ አይገኝም ፡ ቋንቋውም ፡ እንደ ፡ ዘሩ ፡ ኾኗል ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ምድራዊ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ከምን ፡ ከዶ ፡ የሴም ፡ ዘር ፡ ብቻ ፡ ነኝ ፤ ሲምን ፡ ከዶ ፡ የካም ፡ ዘር ፡ ብቻ ፡ ነኝ ፤ ወይም ፡ የያፌት ፡ ብቻ ፡ ነኝ ፡ ቢል ፤ በበዛው ፡ በጸናው ፡ ከሦስት ፡ አንዱን ፡ ብቻ ፡ ሚሰውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ነገሩ ፡ ጥሩ ፡ እውነት ፡ አይኾንም ። በለብዙ ፡ አባትስ ፡ ይቅርና ፡ ያላንድ ፡ አባት ፡ ያላንድ ፡ ምክንያት ፡ ከሴት ፡ ብቻ ፡ የተወለደው ፤ የናቱ ፡ ትውልድ ፡ ከሴም ፡ ከአብርሃም ፡ እስከ ፡ ኢያቄም ፡ እየተንኳለለ ፡ የወረደው ፡ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ወልደ ፡ አብርሃም ፡ የተባለው ፡ ጌታችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ፡ ቢኾን ፡ የሴም ፡ ዘር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ አይባልም ፤ ከካምም ፡ ተወልዷልና ፡ ከያፌትም ፡ ዩኖረው ፡ ይኾናል ፡ እንደ ፡ ካም ፡ ባይጠፋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ (ማቴ ፩ ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ፮) ።

እንደዚህም ፡ ኹሉ ፡ በኋላ ፡ የመጡት ፡ ነገደ ፡ ሴም ፡ ከበላበቶቹ ፡ ከነገደ ፡ ካም ፡ ተዋልደው ፥ በጥበብ ፡ በኀይል ፈድፍደው ፡ የነሱን ፡ ዘር ፡ የሳባንና ፡ የአቢስን ፡ ማኅበር ፡ እያበዙት ፡ እየተበራቱት ፡ ኸደዋል ፡ ኋላ ፡ የመጣ ፡ ዐይን ፡ አወጣ ፡ እንዲሉ ። ነገደ ፡ እስራኤል ፡ በከነዓን ፥ ነገደ ፡ ይስማኤል ፡ በሚጽራይም ፡ ኋላ ፡ ገብተው ፡ እንደ ፡ ሰፈኑ ፥ ነገደ ፡ ዮቅጣንም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ሰፍነዋል ። ኋላም ፡ እንዲህ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እያሉ ፡ ነገሥት ፡ ሳባን ፡ ወግተው ፡ የነሱን ፡ መንግሥት ፡ ቀምተው ፡ ፍራሽ ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋቸው ፡ ዐብሮ ፡ ነግሧል ፡ ቋንቋን ፡ የሚያሰፋው ፡ መንግሥት ፡ እንጂ ፡ ነው ። ጥንታዊውም ፡ ያንድነት ፡ ስማቸው ፡ ሐበሻት ፡ መባል ፡ ወደ ፡ አግዓዝያን ፡ ተለውጧል ። አግዓዝያን ፡ ማለት ፡ ራሳቸውን ፡ ለነሱ ፡ ከመገዛት ፡ ነጻ ፡ ያወጡ ፥ ነጻነት ፡ ያሏቸው ፡ ጌቶች ፡ በለማዕዘኖች ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ኸን ፡ ብሔረ ፡ ሳባን ፡ አግዓዚት ፡ አግዓዝያ ፡ ብሔረ ፡ አግዓዚ ፡ አሰኝተው ፥ የአቢስንም ፡ ክፍል ፡ ዐምሐራ ፡ አሰኝተዋል ፡ ቃሉ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፥ ሐረዋ ፡ የሐረዋ ፡ ልጅ ፡ ማለት ፡ ነው ። ፪ኛም ፡ ግዕዝ ፡ አግዐዘ ፡ ብሎ ፡ ተግዝ ፡ አንዝ ፡ ይላልና ፡ አግዓዝያን ፡ ማለት ፥ የሚያገኙዙና ፡ የሚገዙ ፥ ተሰደው ፡ ተገዘው ፡ የመጡ ፥ ስደተኞች ፡ ባሉባቸው ፡ ጓዞች ፡ ማለትን ፡ ያሳያል ። ከቃናሽ ፡ ነገድ ፡ ከዮቅጣንም ፡ ልጆች ፡ በኋላ ፡ የቃላቀ ፡ ነገድ ፡ የፋሌግ ፡ ልጆች ፡ ነገደ ፡ አብርሃም ፡ በየጊዜው ፡ እየተጓዙ ፡ ከነአረቦቻቸው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብተዋል ። ከዳዊትና ፡ ከሰሎሞን ፡ በፊት ፡ ከነሱ ፡ ዠምሮ ፡ የነበረው ፡ ጥንታዊው ፡ የሳባ ፡ መንግሥት ፡ ከነድልነዓድ ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ ከነሱም ፡ ወደ ፡ ላስታ ፡ ወደ ፡ ዛጌ ፡ ጻታ ፡ እስኪያልፍ ፥ ዐማርኛም ፡ በላስቶች ፡ ዘመን ፡ ከብዙ ፡ ዐይነት ፡ ቋንቋ ፡ ተመርጦ ፡ የመንግሥት ፡ ቋንቋ ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፥ ሴቱም ፡ ወንዱም ፡ ልጁም ፡ ዐዋቂውም ፡ የሚናገርበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥሩ ፡ ቋንቋ ፥ ግእዝ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ይመሰክራል ። ለብሉይ ፡ ለሐዲስ ፡ መብቃቱና ፡ ጥሩ ፡ ቋንቋነቱም ፡ ከሰላማ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሰላማ ፡ በፊት ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ካዕብና ፡ ሣልስ ፥ ራብዕ ፡ ኃምስ ፥ ሳድስ ፡ ሳብዕ ፡ አልነበረውም ። ከብልየት ፡ ደዌ ፡ መታደሱንና ፡ መፈወሱን ፥ የፈደሉንና ፡ የግሱን ፡ ዐመል ፡ ኋላ ፡ በመቅድም ፡ እናመጣዋለን ። ፩ኛው ፡ ክፍል ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ከምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ይኸ ፡ ነው ።

## ፪ኛ ፡ ክፍል ።

## ስለ ፡ ብሉይና ፡ ስለ ፡ ሐዲስ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ መመለስ ።

ኢትዮጵያ ፡ ኢትዮጲስ ፡ ማለት ፡ በሴም ፡ በካም ፡ ቋንቋ ፡ በግእዝ ፡ በሳባ ፡ ያይደለ ፥ በያፌት ፡ ቋንቋ ፡ በዮናን ፡ በጽርእ ፡ ልሳን ፡ ነው ፡ ብለናልና ፡ ብሉያትን ፡ የተቀዳበት ፡ ምንጭ ፥ ነቁና ፡ ዐዘቅቱ ፡ ሥር ፡ መሠረቱ ፡ ከሰብዓ ፡ ሊቃናት ፡ ትርጓሜ ፡ ከጥንታዊ ፡ ጽርእ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ቃሉ ፡ ባለቤቱ ፡ ይመሰክራል ፡ ቍጥር ፡ ከሌላቸው ፡ ከአዋልድ ፡ ወገን ፡ ሌላ ፡ ምስክር ፡ አያሻውም ፡ በውስጡ ፡ ያለው ፡ ጥሬ ፡ ንባብ ፡ የአህጉርና ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ የጽርእ ፡ የዮናን ፡ ቃል ፡ ነውና ። የአህጉር ፡ ስም ፡ ነሱን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሚጽራይምን ፡ ግብጽ ፥ ያም ፡ ሱፍን ፡ ባሕር ፡ ቀይሕ ፡ ወይም ፡

ባሕረ ፡ ቈሐት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ማለት ፡ ፍሌሺትን ፡ ኢሎፍሊ ፥ ፀዛን ፡ ጋዛ ፥ ዐሞራን ፡ ገሞራ ፥ ጾርን ፡ ጢሮስ ፡ ማለት ። ልባኖንን ፡ ሊባኖስ ፥ ያፎን ፡ ኢዮጴ ፥ አራምን ፡ ሶርያ ፥ ባቤልን ፡ ባቢሎን ፥ ሔደቄልን ፡ ጤግሮስ ፥ አራም ፡ ናሃራይም ፡ ያለውን ፡ ማኅከለ ፡ አፍላግ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መስጴጦምያ ፡ ማለት ፥ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡ ነው ። የሰው ፡ ስም ፡ ያልነውም ፡ በመፅሪሻው ፡ ያስ ፡ ያስ ፡ የሚሰው ፡ ኹሉ ፡ የጽርእ ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ ዕብራይስጡ ፡ ሒዝቅያሁ ፡ ዮሺያሁ ፡ ወይም ፡ ይሻዕያሁ ፡ ይርምያሁ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ያስ ፡ አይልም ። ይልቁንም ፡ መጽሐፈ ፡ ዳንኤል ፡ ዕብራይስጡ ፡ (ውሊብኖት ፡ ይሩሻላይም ፡ ዐድ ፡ ማሺያሕ ፡ ናጊድ) ፡ ያለውን ፡ ወትትሐነጽ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ በማለቱ ፡ አለጥርጥር ፡ ያስረዳል ፡ ክርስቶስ ፡ ማለት ፡ በጽርእ ፡ ነውና ። ያጣጣፉም ፡ ሥርዐት ፡ ኢያሱንና ፡ መሳፍንትን ፡ ሩትን ፡ ፩ዐምሮ ፡ ፰ ፡ ብሔረ ፡ አሬት ፡ ማለት ፥ በራተኛውም ፡ ነገሥት ፡ ከዩአቂም ፡ በኋላ ፡ ኢኮንያንን ፡ ባባቱ ፡ ስም ፡ መልሶ ፡ ዩአቂም ፡ ማለት ፥ ይህ ፡ ኹሉ ፡ የሰብዓ ፡ ሊቃናት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የዕብራይስጥ ፡ ባህል ፡ አይደለም ።

ዳግመኛም ፡ በዚህ ፡ በኛ ፡ ብሉይ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ያልተመለሰ ፡ ብዙ ፡ የጽርእ ፡ ቃል ፡ እንዳለበት ፡ በጽርእም ፡ ብሉይ ፡ ወደ ፡ ጽርእ ፡ ያልተመለሰ ፡ የዕብራይስጥ ፡ ቃል ፡ አለና ፡ እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ በኛም ፡ ብሉይ ፡ ውስጥ ፡ ከዚያው ፡ ከጽርኡ ፡ የተቀዳ ፥ አዶናይ ፡ ኤሎሄ ፡ ጸባኦት ፥ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አንዳንድ ፡ የዕብራይስጥ ፡ ቃል ፡ ይገኛል ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ያልተመለሰው ፡ ቃል ፡ ጽርኡም ፡ ዕብራይስጡም ፡ ጥሬ ፡ ይባላል ። ጥሬነቱንም ፡ የቀውስጦስን ፡ ገድል ፡ የጣፉ ፡ ሰዎች ፥ ይልቁንም ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በመጽሐፈ ፡ ምስጢር ፡ ሰፌዳቸው ፡ ሳያበጥሩ ፡ ሳያንጠረጥሩ ፡ ወከመሰ ፡ ተዐለዋ ፡ መጻሕፍት ፡ ነቢያት ፡ እምዕብራይስጢ ፡ ኀበ ፡ ግእዝ ፥ ትረክብ ፡ ትእምርተ ፡ በመጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፥ አዶናይ ፡ ኤሎሄ ፡ ጸባኦት ፡ ብለው ፡ ዕብራይስጡን ፡ ብቻ ፡ ዐፍነው ፡ ሸፍነው ፡ ጠቅሰውታል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጥቅስ ፥ ቈርበት ፡ ነክ ፡ ምስጢረ ፡ በክ ፥ ወይም ፡ ማታለያ ፡ ሽፍጥ ፡ ገበሬ ፡ አስደንግጥ ፡ ይባላል ። ከዕብራይስጥ ፡ ከተመለሰ ፡ የጽርኡን ፡ ጥሬ ፡ ማን ፡ አገባው ፡ ጽርእ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ይቀድማልን ፥ ወይስ ፡ ፪ኛ ፡ ብጽርእ ፡ ታረመን ፡ ብሎ ፡ ለሚጠይቅ ፥ እውነተኛ ፡ ምላሽ ፡ አይገኝም ።

የቀውስጦስም ፡ ገድል ፡ አሬት ፡ ነቢያት ፡ በሰሎሞን ፡ ጊዜ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ ተናግሮ ፡ ፪ኛ ፡ ደግሞ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ በፂዋዌ ፡ ጠፍተው ፡ ከሚጠት ፡ በኋላ ፡ ዘሩባቤል ፡ አይዙር ፡ ከሚባለው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ለምኖ ፡ አሰስዶ ፡ ከግእዝ ፡ ወደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ እንዳስተረጐመ ፡ ይናገራል ። አይዙርስ ፡ ዘነግሠ ፡ መንፈቀ ፡ መዓልት ፡ በሰብዐቱ ፡ ምእት ፡ ሰብዓ ፡ ወክልኤቱ ፡ (በ፯፻፸፪) ፡ ዓ ፡ ም ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ። ይህነንስ ፡ ወዲያ ፡ እንተወውና ፡ ብሉያችን ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ተመልሷል ፡ ማለት ፥ በነብረድ ፡ ይሥሐቅ ፡ እጅ ፡ ሳይከካና ፡ ሳይበክ ፡ ሳይጋገር ፡ ምጣድ ፡ ሳይነካ ፡ እምኀበ ፡ አልቦ ፡ የተገኘ ፡ የሐሳብ ፡ የምኞት ፡ የሕልም ፡ እንጀራ ፡ ነው ።

በማሕልይም ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ዚቅና ፡ እንደ ፡ ስሯጽ ፡ ከያሬድ ፡ በኋላ ፡ የገባ ፡ መዝሙራን ፡ የማያዜሙት ፡ መዝሙራን ፡ የሚተረጕሙት ፡ ጥሬነት ፡ የሌለው ፡ ትርፍ ፡

ንበበ ፡ ሌላ ፡ ስሙንም ፡ ከጽርኡ ፡ ምላሽ ፡ ለይተው ፡ ዕብራይስጥ ፡ ይሉታል ። ርሱ ፡ ግን ፡ ከግእዝ ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ጥሬ ፡ በዕብራይስጥ ፡ አይገኝምና ፡ ግእዝ ፡ እንጂ ፥ ዕብራይስጥ ፡ ሊሉት ፡ አይገባም ፡ ዕብራይስጥ ፡ ብሎ ፡ ስም ፡ የሰጠው ፡ ከማኽል ፡ አግብቶ ፡ ያስቀመጠው ፡ ከቶ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አልታወቀም ። ብጽርእ ፡ በዮናን ፡ የሌለውን ፡ ከዕብራይስጥ ፡ የማይገኘውን ፡ ዕብራይስጥ ፡ ብሎ ፡ ፀፍሖ ፡ ማግበት ፡ የድፍረት ፡ ድፍረት ፡ ነው ፡ ከብሮቹ ፡ ከነቢያት ፡ ይልቅ ፡ ጌታን ፡ ማሳበል ፡ ይኾናል ፡ አስጣፊውና ፡ አስተርጓሚው ፡ ርሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ነውና ፤ (ዘዳ፴ ፡ ፪ ። ፲፪ ፡ ፴፪ ። ራእ፳፪ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱) ።

ብሉያትም ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ የተመለሱ ፡ ከሐዲስ ፡ ጋራ ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ ከዚያውም ፡ በ፬ኛው ፡ መቶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሉቱኤል ፡ ዕገዛን ፡ ያላየ ፡ ያልሰማ ፡ ስለ ፡ ጣፈው ፡ ፀሞፎ ፡ ደርቦ ፡ እየዋሸ ፡ ታሪክ ፡ ያበላሸ ፡ የቀውስጦስ ፡ መጽሐፈ ፡ ገድልና ፡ መጽሐፈ ፡ ምስጢር ፡ እንደሚሉት ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ አይዶለም ። የመለሳቸውም ፡ ዕብራዊ ፡ ሌዋዊ ፡ ወይም ፡ ግብጻዊ ፡ ያይዶለ ፡ ጽርአዊውና ፡ ጢሮሳዊው ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ስላልነ ፡ ግን ፡ የሜፍራውን ፡ ሥራ ፡ ላለቃው ፡ ሰጥቶ ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኹነው ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ዐብረው ፡ የመለሱ ፥ ግእዝና ፡ ጽርእ ፡ ዐረብና ፡ ሱርስት ፡ የሚያውቁ ፡ ብዙ ፡ ያገር ፡ ልጆች ፥ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ ፳፮) ። ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ከተባለው ፡ ከንደኛው ፡ ሰላማ ፡ ከፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ የቀረውም ፡ ብሉይ ፥ ከላስቶች ፡ መንግሥት ፡ በኋላ ፡ ብርሃን ፡ አዜብ ፡ በተባለው ፡ በከልኢ ፡ ሰላማ ፥ ከዐረብ ፡ ቋንቋ ፡ ተመልሷል ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ የብሉይ ፡ መምህራን ፡ ስለ ፡ ጥበብና ፡ ስለ ፡ መክብብ ፡ እንዲህ ፡ ያትታሉ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ወደ ፡ ጽርእ ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ዐረብ ፡ ከዐረብ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ የተመለሰው ፡ ጥበብን ፡ አስቀድሞ ፡ መክብብን ፡ ያስከትላል ። ከዕብራይስጥ ፡ ወደ ፡ ጽርእ ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ የተመለሰው ፡ ግን ፡ መክብብን ፡ አስቀድሞ ፡ ጥበብን ፡ ያስከትላል ፡ ብለው ፡ ይተርካሉ ። ይህም ፡ ታሪክ ፡ ፭ቱ ፡ መጽሐፈ ፡ ሰሎሞን ፥ ወይም ፡ መላው ፡ የግእዝ ፡ ብሉይ ፡ ከጽርእ ፡ ብቻ ፡ እንዳልተመለሰ ፥ ፪ኛ ፡ ደግሞ ፡ ከዐረብ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ ያሳያል ፡ አስተያየቱ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ብልዝ ፡ ዐይን ፡ ነው ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ ፪ ፡ አድርጎታል ። የዐረብም ፡ ቋንቋ ፡ በግብጽ ፡ የሠለጠነ ፡ ከፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ በኋላ ፡ ፬፻ ፡ ዓመት ፡ ቈይቶ ፡ በተንባላት ፡ ዘመን ፡ ነው ።

ስለ ፡ ከልኤ ፡ ዕገዛም ፡ እንዲህ ፡ ያትታሉ ፡ ከዐረብ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ የተመለሰው ፡ በቀዳሚት ፡ ዓመት ፡ መንግሥቱን ፡ ያስቀድማል ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ የተመለሰው ፡ ግን ፥ ወአምጽአ ፡ ኢዮስያስን ፡ ያስቀድማል ፡ ብለው ፡ ይተርካሉ ። ይህም ፡ ታሪክ ፡ ምንም ፡ መላው ፡ ብሉይ ፡ ከዐረብ ፡ ቋንቋ ፡ ባይመለስ ፡ የጽርኡ ፡ ቅሬታ ፡ ከዐረብ ፡ ተመልሷልና ፥ ከጽርእም ፡ የተመለሰው ፡ በዐረብ ፡ ታርሟልና ፡ ታሪክነቱ ፡ ለውነት ፡ የቀረበ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ ጥሩ ፡ እውነት ፡ አይዶለም ። ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ግን ፡ ብሉያችን ፡ ከሐዲስ ፡ ጋራ ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ መመለሱን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፥ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ አለመመለሱን ፡ ያስረዳል ።

የሰው ፡ ኹሉ ፡ ብሉይ ፡ ኋላ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ይታረም ፡ እንጂ ÷ መዠመሪያ ፡ ከጽርእ ፡ ተቀድቷል ፡ የኛ ፡ ብሉይ ፡ ግን ፡ በዕብራይስጥ ፡ ስላልታረመና ፡ የቅጂ ፡ ቅጂ ፡ ስለ ፡ ኾነ ÷ ከናቱ ፡ ከምንጩ ፡ ከጽርእ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ካያቱና ፡ ከቅድሙ ፡ አያቱ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ አይስማማም ፡ ፀልፎ ፡ ፀልፎ ፡ መሥመር ፡ ይጥላል ÷ ቃል ፡ ይለውጣል ። ይህነንም ፡ ዕብራይስጥና ፡ ጽርእ ፡ የሚያውቁ ፡ ግእዝ ፡ የተማሩ ÷ እንደነመፀልም ፡ የሐንስ ÷ እንደነዲልማን ፡ እንደነጕይዲ ፡ ያሉ ፡ ብዙ ፡ ፀዋቆች ፡ ይመሰክራሉ ። ጀርመናዊው ፡ ሊቅ ፡ ሲዲ ፡ ጳውሎስም ፡ ለጐንደር ፡ ሊቃውንት ÷ ትፈቅዱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ብሉያችኹን ፡ ከዕብራይስጥ ÷ ሐዲሳችኹን ፡ ከጽርእ ፡ እያስማማኹ ፡ ፀርሚ ፡ ንበዉን ፡ ከንትርጓሜው ፡ አሳትሚ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ላምጣላችኹ ፡ ቢላቸው ፡ አንፈልግም ፡ ብለው ፡ በምቀኝነት ፡ እንዳስቀሩት ÷ ቅንነት ፡ ያላቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይተርኩታል ፡ ርሱም ፡ በታሪኩ ፡ ጽፎታል ፡ ይባላል ።

የአዋልድም ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ኩፋሌና ፡ ሔኖክ ፡ ሳይቀሩ ፡ የብሉይ ፡ አዋልድ ፡ ኹሉ ፡ መዠመሪያ ፡ እንደናቶቻቸው ፡ ከጽርእ ፡ ከዮናን ፡ ተመልሰዋል ፡ ከዐረብም ፡ የተመለሱና ፡ በዐረብ ፡ የታረሙ ፡ አሉ ። በበጥሊሞስ ፡ ጊዜ ፡ ታሪኩና ፡ ሥራው ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚጨመር ፡ ኅምሮና ፡ ውጥን ፡ ስለ ፡ ኾነ ÷ ፸ ፡ ሊቃናት ፡ እንደ ፡ መቃቢስ ፡ ዘብንያምና ፡ እንደ ፡ መቃቢስ ፡ ዘሞአብ ፡ ከዕብራኒ ፡ ወደ ፡ ዮናኒ ፡ ያልመለሱት ፡ ደገኛው ፡ ታሪክ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ መቃብያን ፡ ብቻ ፡ በሰላማና ፡ በሰላማ ፡ ከጽርእ ፡ ከዐረብ ፡ ሳይመለስ ፡ ቀርቶ ÷ ከግራኝ ፡ በኋላ ፡ በሱስንዮስ ፡ ዘመን ፡ ኢየሱሳውያን ፡ ከሮማይስጥ ፡ መልሰውታል ። የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ያ ፡ የ፺ቱ ፡ ዓመት ፡ ደሞና ፡ ቂም ፡ እየታሰባቸው ፡ ሮማውያንን ፡ ስለ ፡ ጠሉና ፡ ከሮማይስጥ ፡ ስለ ፡ ተመለሰ ፡ መጽሐፉን ፡ አልተቀበሉትም ። ኋላም ፡ በቴዎድሮስ ፡ ከጐንደር ፡ ተዘርፎ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ስለ ፡ ወጣ ፡ እንግሊዞች ፡ ማርከው ፡ ወስደውታል ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ በሮማውያን ፡ እጅ ፡ ከብሉያት ፡ ጋራ ፡ ታትሞ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እየገዛ ፡ ያነበዋል ።

በቴዎድሮስ ፡ ጊዜ ፡ የተቃጠሉት ፡ የተቈነጸሉት ÷ ይልቁንም ፡ ተዘርፈውና ፡ ተማርከው ፡ የኼዱት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ በግራኝ ፡ ጊዜ ፡ ከጠፉት ፡ ቢበልጡ ፡ እንጂ ÷ አያንሱም ፡ እንግሊዞች ፡ ብቻ ፡ በያይነቱ ፡ ፲፰፻፷፰ ፡ መጽሐፍ ፡ ወስደዋል ፡ ይባላል ። ከዚያም ፡ በፊት ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ወደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ተሻግረዋል ÷ ዛሬም ፡ ይሻገራሉ ፡ የግእዝ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ዘር ፡ ያልኼዱበትና ፡ የሌሉበት ፡ ሀገርና ፡ መንግሥት ፡ አይገኝም ፡ ትምርታቸውንም ፡ ከኛ ፡ ይልቅ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ጠግበውታል ። ይኸውም ፡ ዲልማን ፡ በጣፈው ፡ ግስ ፡ ይታወቃል ፡ የመጽሐፉ ፡ አርእስት ፡ መቅድሙ ፡ በትጋትና ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ የሰበሰበውን ፡ መዝገበ ፡ ቃል ፡ ፺፫ ፡ መጽሐፍ ፡ አንብቦ ፡ ከዚያ ፡ እንደ ፡ ለቀመው ፡ ይተርካል ። የብራና ፡ መጽሐፍ ፡ ጥራቱና ፡ ሥራው ፡ እጅግ ፡ የሚያደንቅም ፡ ሲፈልግም ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የማይገኝ ፡ ሩቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ÷ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ መኼዱ ፡ ምንም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ቢያሳዝን ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የግእዝን ፡ ቋንቋ ፡ በኤውሮፓ ፡ ዘርቶ ፡ የዲልማንን ፡ መጽሐፍ ፡ በማብቀሉና ፡ በማፍራቱ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ (መዝ ፡ ፻፳፰ ፡ ፳ ፡ ፯) ።

ሐዲሳችን ፡ ግን ፡ ፪ኛ ፡ በክልእ ፡ ሰላማ ፡ ከዐረብ ፡ ቋንቋ ፡ ተመልሷል ። ይኸውም ፡ ሳዊሮስ ፡ ዘእስሙናይን ፡ በእንተ ፡ ብዝኅ ፡ ተደምሮቶሙ ፡ ምስለ ፡ ተንባላት ፡ እስመ ፡ ጠፍአ ፡ ልሳኖሙ ፡ ቅብጥ ፡ ዘእምኔሁ ፡ የአምሩ ፡ ጽድቀ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ ይላልና ፡ ተንባላት ፡ ግብጽ ፡ ከገቡና ፡ የቅብጥን ፡ ቋንቋ ፡ ካጠፉት ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ቈይቶ ፡ ነው ። ክልእ ፡ ሰላማም ፡ የመጣው ፡ ከዪ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ በኋላ ፡ በአግብአ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሮማው ፡ ታውቋል ፤ ካንደኛው ፡ ሰላማ ፡ እስከ ፡ ኹለተኛው ፡ ቢቈጥሩ ፡ ትርፉን ፡ ትቶ ፡ ፱፻ ፡ ዓመት ፡ ይገኛል ። የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፡ ሐዲስ ፡ አብነቱ ፡ በጥፈት ፡ ተዛንቆ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ በመኾን ፡ ከጽርእ ፡ ከዐረብ ፡ ተጣልቷና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መታረቅና ፡ መስማማት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ መኾን ፡ ያሻዋል ። ሊቃውንትና ፡ የሐዲስ ፡ አዋልድ ፡ እኩሉ ፡ ከጽርእ ፡ እኩሉ ፡ ከዐረብ ፡ ተመልሰዋል ፤ ከሌላም ፡ ቋንቋ ፡ የተተረጐመ ፡ ይኖራል ። ከጽርእ ፡ በተመለሱት ፡ የጽርእ ፡ ጥሬ ፡ እንዲገኝብቸው ፡ ከዐረብም ፡ በተመለሱት ፡ የዐረብ ፡ ጥሬ ፡ ይገኝባቸዋል ፡ የመላሾቹና ፡ የተርጓሞቹም ፡ ስም ፡ ካንዳንድ ፡ በቀር ፡ የኹሉ ፡ አልተጻፈም ።

## ፫ኛ ፡ ሐተታ ።

አሪት ፡ ነቢያት ፡ ጭራሽ ፡ በዚዋዌ ፡ ጠፍተው ፡ ከዕብራውያን ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ታጡ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ዕዝራ ፡ አስጦፏቸዋል ፡ የሚሉት ፡ ግን ፡ ፈራሽ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ንባቡ ፡ እንጂ ፡ ትርጓሜው ፡ እውነት ፡ አይዶለም ። ይህን ፡ ታሪክ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አይሉትም ፥ አይቀበሉትም ፡ መጽሐፉን ፡ ቅሉ ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ነቅፈው ፡ ከቍጥር ፡ አውጥተውታል ። ይህን ፡ መጽሐፈ ፡ ግስ ፡ ያወጡ ፡ መምህር ፡ ክፍለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ግን ፡ የሕዝቅኤል ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡ ጐን ፡ መተኛት ፡ እልፍ ፡ አእላፍ ፡ ሙታን ፡ ማስነሣት ፡ በራእይ ፡ በሕልም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ የሱቱኤል ፡ ዕዝራም ፡ መጻሕፍትን ፡ ማስጣፍ ፡ የተጣፉትን ፡ ፺፬ ፡ ብሎ ፡ መቍጠር ፡ በራእይ ፡ በሕልም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በብርዕ ፡ በቀለም ፡ አይዶለም ፡ ብለዋል ። ስለ ፡ ምን ፡ ቢሉ ፥ እስራኤል ፡ የተማረኩ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ መጀመሪያውና ፡ ኹለተኛው ፡ ምርክ ፡ አልጐዳቸውም ። ሕዝቡ ፡ ከንጉሣቸው ፡ ከሀናቱ ፡ ከነመጻሕፍቻቸው ፡ ሳይቀሙ ፡ ሳይንገላቱ ፡ ሳይሳቡ ፡ ሳይጐትቱ ፡ በክብረት ፡ ወርደዋል ፡ ኑሰራቸውና ፡ መከራቸው ፡ በሦስተኛው ፡ ነው ፡ (ኤር፶፪ ፡ ፳፰—፴) ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ መጻሕፍት ፡ ከብዛት ፡ አንሰዋል ፡ እንጂ ፥ አባቶቻችን ፡ እንደሚሉት ፡ ተፈርሰው ፡ ዕልም ፡ ድርግም ፡ ብለው ፡ አልጠፉም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ከለዳውያንን ፡ በሚመስሉ ፡ በጕዲትና ፡ በፈላሾች ፡ በነግራኝ ፡ ዘመን ፡ ጭራሽ ፡ እንዳልጠፉ ፡ ዘራቸው ፡ እንዳልተመተረ ። ዕዝራ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ማነሳቸው ፡ ያዝን ፡ ይቈረቈር ፡ ነበረና ፡ ከሚጠት ፡ በኋላ ፡ በዝተው ፡ እንዲጣፉ ፡ ቍጥራቸውንም ፡ የኋለኞች ፡ አይሁድ ፡ እንዲህ ፡ በ፳፬ ፡ እንዲወስኑት ፡ ጌታ ፡ በራእይ ፡ ገልጾለታል ። የአይሁድን ፡ ቍጥር ፡ ለማየትና ፡ ለመረዳት ፡ ፳፬ ፡ መኾኑን ፡ ለማግኘት ፡ ብ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከትርጓሜው ፡ ጋራ ፡ የታተመ ፡ ሐዲሱን ፡ መጽሐፈ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ከ፳፫፲፭ ፡ ገጽ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ተመልከት ። ሕዝቅኤልም ፡ ከዕዝራ ፡ አስቀድሞ ፡ በባቢ

ሎን ፡ መጽሐፈ ፡ አሪትን ፡ እንደ ፡ ጻፈ ፡ ከዚያው ፡ ታገኛለኽ ፡ (ገጽ ፡ ፳፱፮) ። ዕዝራም ፡ ከሕዝቅኤል ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ባ፸፫ኛ ፡ ዓመት ፡ መነሣቱን ፡ አመ ፡ ፴ ፡ ክረምት ፡ እምዘወድቀት ፡ ሀገሪትን ፡ ብሎ ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ዕዝራ ፡ በጥንቱ ፡ መጽሐፉ ፡ ይነግርኻል ። ይልቁንም ፡ ወተጽሕፉ ፡ በእማንቱ ፡ ፵ ፡ መዋዕል ፡ ፺ወ፬ ፡ መጻሕፍት ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ወይቤለኒ ፡ ልዑል ፡ ዝክነ ፡ ዘቀደምክሙ ፡ ጽሒፈ ፡ ገሃደ ፡ ረሲ ፡ ወያንብቡ ፡ ኵሉ ፡ ዘይደልዎ ፡ ወዘኢይደልዎ ፡ ይላልና ። ከቍጥርም ፡ ስላልገቡት ፡ መጻሕፍት ፡ ስለ ፡ ብሉይ ፡ አዋልድ ፡ ጌታ ፡ ወለዝንቱሰ ፡ ዕቀብ ፡ ከመ ፡ ተሀብሙ ፡ ለጠቢባን ፡ ሕዝብ ፡ እስመ ፡ ቦሙ ፡ ማኅቶተ ፡ ብርሃን ፡ ወነቅዐ ፡ ጥበብ ፡ ወአእምሮ ፡ ከመ ፡ ውሒዝ ፡ ብሎታል ።

ኹለተኛም ፡ ከእሊህ ፡ ከ፳፬ቱ ፡ የከፈሏቸውንና ፡ ከ፸ ፡ ሊቃናት ፡ ቍጥር ፡ ያወጧቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ለብቻቸው ፡ ፲፬ ፡ ይሏቸዋል ። ደረቅ ፡ ትንቢት ፡ ያላቸውን ፡ ግን ፡ ከዕብራይስጥ ፡ አጥፍተዋቸዋል ። ወያንብቦ ፡ ኵሉ ፡ ያለው ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ወደ ፡ ጽርእ ፡ ቋንቋ ፡ ተመልሰው ፡ ለአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ እንዲሰጡና ፡ እንዲኖሩ ፡ የትምርታቸው ፡ ጕርፍ ፡ ሕዝቅኤል ፡ እንዳየው ፡ ፈሳሽ ፡ ወንዝ ፡ ኹኖ ፡ ከኹሉ ፡ እንዲደርስ ፡ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ እንዲመላ ፡ ያጠይቃል ፡ (ሕዝ፵፯ ፡ ፩—፲፪) ። ዘይደልዎ ፡ የተባለ ፡ አይሁዳዊ ፡ ወዘኢይደልዎ ፡ አረማዊ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ኅጽዋ ፡ ለህንደኬ ፡ እንደነቆርኔሌዎስ ፡ ያሉ ፡ ብዙ ፡ አንባብያን ፡ ብዙ ፡ አማንያን ፡ አሉና ፡ (ግብ፰ ፡ ፳፯—፴፰ ። ዮሐ፲፪ ፡ ፳ ። ዘካ፲፬ ፡ ፲፯—፲፱) ። ዕዝራ ፡ የበጥሊሞስ ፡ ጸሐፍቱ ፡ የ፸ ፡ ሊቃናት ፡ አምሳል ፡ ናቸው ። ፵ ፡ መዋዕል ፡ ያለውም ፡ ዘመነ ፡ በጥሊሞስን ፡ ወይም ፡ ከዕርገት ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ጥጦስ ፡ ያለ ፡ ዘመን ፡ አይሁድን ፡ ያሳያል ። የብሉይን ፡ ቍጥር ፡ ፺፬ ፡ ብለው ፡ የወሰኑ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፡ ዓመቱን ፡ በዕለት ፡ መቍጠር ፡ የብሉይ ፡ ልማድ ፡ ነው ። አሐተ ፡ ዕለት ፡ ትኩንክሙ ፡ ከመ ፡ ዓመት ፡ ወአነ ፡ ወሀብኩክ ፡ ዓመታተ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ በኍልቈ ፡ መዋዕል ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ወተስዓ ፡ ዕለት ፡ ወረሰይኩ ፡ ለከ ፡ ዕለተ ፡ ከመ ፡ ዓመት ፡ እንዳለ ፡ (ዘኍ፲፬ ፡ ፴፬ ። ሕዝ፬ ፡ ፫—፮) ።   የሱቱኤል ፡ መጽሐፍ ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ መጨ ፡ ራእይና ፡ ሕልም ፡ ነው ፡ የነቢያት ፡ ቃል ፡ ስንኳን ፡ ራእዩ ፡ ትንቢቱ ፡ ቢኾን ፡ ወትሮ ፡ በቁሙ ፡ አይፈታም ፡ ማስተዋል ፡ ያሻል ። ከእልፍ ፡ አሪት ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ቢቃጠል ፡ አነሰ ፡ ጐደለ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፥ ጭራሽ ፡ ጠፋ ፡ ተደመሰሰ ፡ አይባልም ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ከግዜር ፡ የተገኙ ፡ የግዜር ፡ ምስክሮች ፡ ናቸውና ፡ ተፈርሰው ፡ ሊጠፉ ፡ አይችሉም ። ከለዳውያንም ፡ የተላኩ ፡ እስራኤልን ፡ ለመቅጣት ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ መጻሕፍትን ፡ ለማጥፋት ፡ አይደለም ፡ ቤተ ፡ መቅደስም ፡ መቃጠሉ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ስላደረጉት ፡ ነው ። መጻሕፍትሳ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ይጠፋሉ ፡ አምላካቸውን ፡ እንኳ ፡ የከዱት ፡ ሕዝቡና ፡ ካህናቱ ፡ ጭራሽ ፡ እንዲጠፉ ፡ አላደረገም ። መጻሕፍቱንና ፡ ንዋያቱን ፡ ርሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ጠብቋቸዋል ።

ያልጠራ ፡ ያልበራ ፡ እንቶ ፡ ፈንቶ ፡ ታሪክ ፡ ብዋቆችና ፡ በመርማሮች ፡ ዘንድ ፡ ያሳፍራል ፡ እንጂ ፥ አያኰራም ፡ ኢትዮጵያንም ፡ እንደ ፡ ርሷ ፡ የሚያረክሱና ፡ የሚያስመኩት ፥ ጃንሆይና ፡ እቴጌም ፡ የሚያሰኛት ፡ ምንሽ ፡ ሲማስና ፡ ዱሪ ፡ ሲማስ ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ የነበረው ፡ የነገደ ፡ ኵሽ ፡ ልብስ ፡ መንግሥት ፡ አርድ ፡ አንቀጥቀጥ ፡ የዘውዳ

ቸውም ፡ ፈርጥ ፥ የነጻነቷ ፡ ሽልማትና ፡ ጌጥ ፡ መንግሥት ፡ ሳበዋ ፥ አርጌው ፡ ክበዋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በኋላ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ አጅ ፡ መንሽ ፡ ኹኖ ፡ የመጣላት ፡ የሰሎሞን ፡ ድርብ ፡ ምኒልክ ፡ የዘውዱ ፡ ቀጺላ ፥ የንግሥት ፡ አዜብ ፡ ወርቅ ፡ ድብብ ፡ የየመን ፡ ጃን ፡ ጥላ ፡ አይዶለም ። የሰሎሞንና ፡ የየመኑስ ፥ በሰንበት ፡ ላይ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ እንዲሉ ፥ ሰለተ ፡ በዓል ፡ የገጠመው ፡ የስንክሳር ፡ ታሪክ ፡ ወበዛቲ ፡ ነው ። ፪ኛው ፡ ክፍል ፡ ባሉብዙ ፡ ፍሬ ፡ የታመነ ፡ የመጻሕፍት ፡ ወሬ ፡ እስከዚህ ፡ ነው ።

## ፫ኛ ፡ ክፍል ።

## ስለ ፡ ፊደል ፡ ተረክቦና ፡ ጥንት ፥ ስለ ፡ ትምርቷም ፡ ሰማያዊነት ።

ፊደልና ፡ ጥሬት ፡ ለአዳም ፡ ልጆች ፡ የተገለጡና ፡ የተሰጡ ፡ በአዳም ፡ ዕድሜ ፡ ነው ፡ ከዚያውም ፡ በሳብዓይ ፡ ምእት ፡ በማልሳይ ፡ ትውልድ ፡ በሄኖስ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታውቋል ። የተሰጡበትም ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ በግዚር ፡ ምሳሌ ፡ መፈጠሩ ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ሕያው ፡ ኹኖ ፡ በሕግ ፡ ልቡና ፡ ሊኖር ፡ እንጂ ፥ በተፈጥሮ ፡ የተሰጠውን ፡ ሕግ ፡ ረስቶ ፡ ዘንግቶ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መጽሐፋዊ ፡ ሕግ ፡ ሊጥፍና ፡ ሊያስጥፍ ፡ ልቡናውን ፡ በመጽሐፍ ፡ ሊደግፍ ፥ ሕይወቱንም ፡ ፀጥቶ ፡ ሊቀበር ፡ ከመሬት ፡ ሊወ ተፍ ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ሊረግፍ ፡ አልነበረም ። መጽሐፈ ፡ ኩፋሌ ፡ ሺሑን ፡ ዓመት ፡ ፩ ፡ ዕለት ፡ ብሎ ፥ አዳም ፡ ዕለቱን ፡ ተፈጥሮ ፡ ወዲያው ፡ በድሎ ፡ አንዲቱን ፡ ቀን ፡ እንኳ ፡ ሳይፈጽም ፡ ሞተ ፡ ይላል ፡ ይኸውም ፡ ለሺሕ ፡ ፸ ፡ ዓመት ፡ ሲቀረው ፡ በ፱፻፴ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሺሑ ፡ ዓመት ፡ በግዚር ፡ ዘንድ ፡ ፩ ፡ ዕለት ፡ ሲባል ፡ አንዱ ፡ ሰዓት ፡ ደግሞ ፡ ፵፩ ፡ ዓመት ፡ ከ፰ ፡ ወር ፡ ከ፫ ፡ ቀን ፡ ከ፮ ፡ ሰዓት ፡ ከ፲ ፡ ደቂቃ ፡ ከ፴ ፡ (ሴኮንድ) ፡ ቅጽበት ፡ ይኾናል ። አዳምም ፡ የበሕርዩ ፡ ጠላት ፡ የሌለበት ፡ መስሎ ፡ ፀርፎ ፡ ተዘልሎ ፡ በተ ድላ ፡ ሳለ ፥ የኅሊና ፡ ጽንት ፡ ኀጢአትና ፡ ሞት ፡ እነዚህ ፡ ፫ቱ ፡ የበሕርዩ ፡ ሳይኾኑ ፡ ከበሕርዩ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ፈትልና ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ እንደ ፡ ፀምርና ፡ እንደ ፡ ቀለም ፡ ተሰ ማሚነት ፡ ስላላቸው ፥ ከእፍኢ ፡ መጥቀው ፡ በሕርዩን ፡ እንደ ፡ ፈትል ፡ እንደ ፡ ፀምር ፡ ቀልመው ፡ አሳድፈው ፡ ንጣቱን ፡ ጥሬቱን ፡ አጠፉበት ። ርሱም ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ነጻነትና ፡ ልጅነት ፡ የልጅነት ፡ ሥልጣን ፡ ስላለው ፡ ተሰማሚነትን ፡ በርትዐት ፡ ጨቁኖ ፡ ከጽንትና ፡ ከኀጢአት ፡ ጋራ ፡ መዋጋት ፡ መታገል ፥ ተቃማቶና ፡ ታግሎም ፡ ማሸነፍ ፡ መጣል ፥ ምክረ ፡ ከይሲንም ፡ አለመስማት ፡ አለመቀበል ፡ ሲቻለው ፡ እግዚር ፡ በልቡ ናው ፡ ያዳፈነለትን ፡ እሳተ ፡ ሕግ ፡ ገላልጦና ፡ አንድዶ ፡ በመሞቅ ፡ ፈንታ ፡ አጥፍቶ ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ፥ እንደ ፡ ዲያብሎስ ፡ ጽድቅን ፡ ጠልቶ ፡ ፀመፃን ፡ ቢወድ ፥ ሙዳና ፡ ፈቃዱ ፡ ጽንትን ፥ ጽንት ፡ ኀጢአትን ፥ ኀጢአት ፡ ሞትን ፡ ከርግማን ፡ ጋራ ፡ ስበው ፡ ተሰ ስበው ፡ ተበብረው ፡ ተመፍረው ፡ መጡበት ። የበሕርዩም ፡ አለመኾናቸው ፡ ሊታወቅ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ምሉ ፡ በገነት ፡ ሲኖር ፡ የኀልዮና ፡ የነቢብ ፡ የገቢር ፡ ኀጢአት ፡ አልተገኘ በትም ። እስከ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ግን ፡ እንደዚያ ፡ በጽድቅና ፡ በርትዕ ፡ በንጽሕ ፡ ጠባ ይዕ ፡ ጸንቶ ፡ ቢኾን ፡ ብልየትና ፡ ሞት ፡ ሳያገኙት ፡ ረቆ ፡ ታድሶ ፡ በግዘሩ ፡ ፈንታ ፡ ርቀ ትን ፡ ለብሶ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ያልመሉ ፡ ልጆቹ ፡ እያዩት ፡ ከዓለመ ፡ ሥጋ ፡ ወደ ፡ ዓለመ ፡

ነፍስ ፡ ሊያርግ ፡ ነበር ፡ ዳግማይ ፡ አዳም ፡ የተባለው ፡ ልጁ ፡ በትንሣኤ ፡ ረቆ ፡ ታድሶ ፡ ወንድሞቹ ፡ እያዩት ፡ እንዳረገ ።

እንዲህ ፡ በተፈጥሮው ፡ ንጹሕና ፡ ጽሩይ ፡ ምሉዕ ፡ ጥዑም ፡ የነበረ ፡ የሰው ፡ ምንጭ ፡ አዳም ፡ ከ፯ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ፍትወታት ፡ እኩያት ፡ ኀጣውእ ፡ ተሰብስበው ፡ ገብተው ፡ ሲዋኙበት ፡ ምድራዊነቱ ፡ ተናውጦ ፡ ሰማያዊነቱም ፡ ተበጥብጦ ፡ ንጽሐ ፡ ጠባይዑ ፡ ስላደፈና ፡ ስለ ፡ ደፈረሰ ፡ በዘር ፡ በሩካቤ ፡ ከርሱ ፡ እየተቀዳ ፡ ሞትና ፡ መቃብር ፡ ሳያቋርጡ ፡ የሚጠጡት ፡ ምድራዊ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በፈሳሽነቱ ፡ እየተለና ፡ እየጐሸ ፡ እየሸገተና ፡ እየገማ ፡ እየተበላሸ ፡ ከፈጣሪውም ፡ እየሸሸ ፡ ኼደ ። ምድር ፡ አፏ ፡ አውጥታ ፡ እስክትከሰውና ፡ እስክትፋረደው ፤ ሰማይም ፡ ስለ ፡ ምድር ፡ በንፍር ፡ ውሃ ፡ እስኪጠብሰውና ፡ እስኪያነደው ፡ ዳኛውም ፡ እግዜር ፡ ሰውን ፡ በመፍጠሩ ፡ ዐዝኖ ፡ ተጠጥቶ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ ብቻ ፡ አስቀርቶ ፡ ኹሉን ፡ በማየ ፡ አይኅ ፡ እስኪያጠፋው ፡ ድረስ ፡ ከመበስ ፡ በቀር ፡ መመለስ ፡ አልቻለም ።

በሄኖስም ፡ ዘመን ፡ ከነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ ከናባታቸው ፡ ሲቀሩ ፡ የቃየልና ፡ የወንድሞቹ ፡ ዘር ፡ ልጆቹም ፡ ዐዋቂውም ፡ ተፈልጠውና ፡ ተገርኝተው ፡ ወዳምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ስለ ፡ ኼዱ ፡ ክፉታቸውም ፡ በብዛታቸው ፡ ልክ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የማየ ፡ አይኅን ፡ እስኩታ ፡ ገፈታ ፡ ቀምሰዋል ፡ ማየ ፡ ማዩን ፡ እንደ ፡ ሰፍሬ ፡ ታዘ ፡ ከሰውም ፡ ከከብትም ፡ ሚሶ ፡ ሚሶውን ፡ አጥፍቷል ፡ ምድርም ፡ ቀድሞ ፡ በአዳም ፡ እንደ ፡ ተረገመች ፡ የዘሩባትን ፡ ዘር ፡ ቁርጥማ ፡ ያልዘሩባትን ፡ ሦክና ፡ አሜከላ ፡ ደንደር ፡ ኰሸሽላ ፡ ዶቢና ፡ ሳማ ፡ ኮሬንችት ፡ ዐቃቅማ ፡ አበቀለች ፡ ይህም ፡ ኹኖ ፡ ባሱ ፡ እንጂ ፤ አልተመለሱም ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በሊመዱት ፡ ግብር ፡ ስቦ ፡ ለመመለስ ፡ የአዳም ፡ እረኛ ፡ ያቅርታው ፡ እየሮጠ ፡ ተከተላቸው ፡ መከተሉም ፡ ይህ ፡ ነው ። ዕንጨት ፡ ደንጊያውን ፡ ጠርበው ፡ አለዝበው ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ቀለም ፡ እየቀቡ ፡ ሸልመው ፡ አስጊጠው ፡ በሚያመልኩት ፡ በሥዕሉና ፡ በምስሉ ፡ ፈንታ ፡ በደንጊያና ፡ በንጨት ፡ ሰሌዳ ፡ በእንስሳትም ፡ አንዳ ፡ ተቀርጾ ፡ ተጥሮ ፡ ተደጕሶ ፡ ታፍሮ ፡ ኹለንተናው ፡ ግዝፎ ፡ የሚታይና ፡ የሚዳሰስ ፡ መጽሐፋዊ ፡ ሕግ ፡ ያቆምላቸው ፡ ዘንድ ፡ ስላሰበ ፤ ሄኖስን ፡ በራእይ ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ስቦ ፡ በባለሟልነት ፡ አቅርቦ ፡ ረቂቁን ፡ ሕግና ፡ ትእዛዝ ፡ አግዝፈው ፡ አጕልተው ፡ የሚያሳዩ ፡ የዐይነ ፡ ልቡና ፡ መነጽሮች ፡ ፊደላትን ፡ ሰጠው ። ፳፪ቱን ፡ አሌፋት ፡ በ፳፪ቱ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ አምሳል ፡ በጻፍጻፈ ፡ ሰማይ ፡ ጥፎ ፡ አሳይቶ ፡ ወዲያው ፡ በልቡ ፡ እየሣለ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረትን ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላትን ፡ በቃል ፡ በፊደል ፡ ያስተምራቸው ፡ ዘንድ ፤ ያለፈውንም ፡ ታሪክና ፡ ዜና ፡ ተረስቶና ፡ ተዘንግቶ ፡ እንዳይቀር ፡ ለቅጥ ፡ ሰብስቦ ፡ ይጥፍላቸው ፡ ዘንድ ፡ ሥራውንና ፡ አሠራሩን ፡ ኹሉ ፡ ነድፎ ፡ አሳይቶ ፤ ፊደላትም ፡ በስማቸውና ፡ በቍጥራቸው ፡ የፈጣሪና ፡ የፍጥረት ፡ ምሳሌ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ምስጢራቸውን ፡ አስረድቶ ፡ የጥፈትና ፡ የትምርት ፡ አበጋዝ ፤ የዕውራን ፡ ዐይን ፡ የሐንካሳን ፡ ምርኵዝ ፡ የሰው ፡ ኹሉ ፡ መገሥጽ ፡ መናዘዝ ፡ አደርጎታል ። መናዘዝነቱም ፡ የአዳምን ፡ ተስፋ ፡ ዳግማይ ፡ አዳምን ፡ በአርአያ ፡ ፊደል ፡ ሥሎ ፡ መስሎ ፤ ስሙንም ፡ አሌፍ ፡ ወታው ፡ ብሎ ፡ በማሳየትና ፡ በመስበክ ፡ ነው ፡ የኋላ ፡ ልጆች ፡ ነቢያት ፡ ይልቁንም ፡

ዳዊት ፡ ኤርምያስ ፡ አቡቀለምሲስ ፡ ርሱን ፡ መስለውና ፡ ተከትለው ፥ ከባለቤቱም ፡ አፍ ፡ ተቀብለው ፡ ፊደላዊ ፡ ስሙን ፡ በፊደል ፡ እንደ ፡ ሰበኩ ። የጽርእ ፡ ፊደል ፡ በአልፋ ፡ ዠምሮ ፡ በዖሜጋ ፡ ስለ ፡ ጨረሰ ፥ ቀድሞ ፡ ለሄኖስ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ አሌፍ ፡ ወታው ፡ ያለውን ፡ ኋላ ፡ ለዮሐንስ ፡ አልፋ ፡ ወዖ ፡ ብሎ ፡ መድገሙ ፡ የራእያቸውን ፡ አንድነት ፡ ያሳያል ። ተቀባዩና ፡ ሠራተኛው ፡ ሄኖስ ፡ ብቻ ፡ ሲኾን ፥ የፊደላት ፡ መሰጠትና ፡ መገለጥ ፡ በጊዜያቸው ፡ በዘመናቸው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ይህን ፡ የሄኖስን ፡ ሥራ ፡ ገድለ ፡ አዳም ፡ ለአዳም ፡ ብቻ ፥ ፈላስፋው ፡ ቀረጦን ፡ ለሴት ፡ ብቻ ፡ ሰጥቶ ፡ ይተርካል ፡ በለቤትነት ፡ ግን ፡ ከሄኖስ ፡ አይወጣም ።

ሄኖስ ፡ ማለት ፥ ፍጹም ፡ ሰው ፥ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ያለው ፥ ነባቢ ፡ ለባዊ ፡ ሕያው ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ ስሙ ፡ ከግብሩ ፡ የተስማማ ፡ የደብር ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ሄኖስም ፡ እንዲህ ፡ ከፈጣሪው ፡ ተሹሞና ፡ ቀሶ ፡ የሚያገዝ ፡ የሚናዝዝ ፥ የቃቦተ ፡ ሕጉ ፡ ዐቃቢና ፡ ገበዝ ፥ የመሲሑም ፡ ጸሓፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ አውቃሪ ፡ ልቡናው ፡ በድሕንጻ ፡ መንፈስ ፡ ተቃኝቶለት ፡ ፊደሉን ፡ ከቋንቋ ፡ ቋንቋውን ፡ ከፊደል ፡ አሰማምቶ ፥ ቀኝ ፡ እጁን ፡ በነፍስ ፡ ግራ ፡ እጁን ፡ በሥጋ ፥ ዐሥር ፡ ጣቶቹን ፡ ባሥሩ ፡ ቃላት ፡ መስሎ ፡ አነጻጽሮ ፥ በንደበቱና ፡ በጣቱ ፡ እያነበበና ፡ እየጣፈ ፡ የፊደልን ፡ ሥራ ፡ ከሕግና ፡ ከትእዛዝ ፡ ጋራ ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ አስተምሯል ። ሕግ ፡ አታድርግ ፡ አታድርግ ፡ ትእዛዝ ፡ ግን ፡ አድርግ ፡ አድርግ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ፡ የ፪ቱም ፡ ራስና ፡ ቀንድ ፡ በፍጹም ፡ ልቡና ፡ እግዜርንና ፡ ባልንጀራን ፡ መውደድ ፡ ናቸው ። በመሐላም ፡ ጊዜ ፡ የግዜርን ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ እንዲጠሩ ፥ እጠራሩንም ፡ እንዲፈሩና ፡ እንዲያከብሩ ፡ እንደ ፡ ቀድሞቻቸው ፡ ግን ፡ ደመ ፡ አቤል ፡ ያጥፋን ፡ እያሉ ፡ በሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ደም ፡ ወይም ፡ በጣዖት ፡ ስም ፡ እንዳይምሉ ፡ አስጠንቅቋቸዋል ። ወውእቱ ፡ ዘአንዘ ፡ ይጼውዕ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳለ ፡ (ኩፋሌ) ። ልጁም ፡ ቃይናን ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ ንጉሥና ፡ ነቢይ ፡ ወዲህም ፡ ፈላስፋ ፡ ነበረና ፡ ሕዝቡን ፡ እንዳባቱ ፡ በቀና ፡ መንገድ ፡ መርቷቸዋል ። ከርሱም ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ላሜኽና ፡ እስከ ፡ ኖኅ ፡ ተያይዘና ፡ ተከታትሎ ፡ የሚመጣው ፡ ኹሉ ፡ ተገልጦለት ፡ ለነመላልኤል ፡ ለልጆቹና ፡ ለሕዝቡ ፡ በሰላድወ ፡ እብን ፡ እየጣፈ ፡ ከቤተ ፡ መዛግብት ፡ እንዳኖረው ፡ የአይሁድ ፡ ኩፋሌ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቃል ፡ ይተርካል ።

በዚህም ፡ በሄኖስና ፡ በቃይናን ፡ ሥራ ፡ ግራዝማች ፡ ዲያብሎስ ፡ ቀንቶ ፡ ተመቀኝቶ ፡ ጥሩውን ፡ ትምርት ፡ ለማደፍረስ ፡ በስንዴውም ፡ ፊደል ፡ መካከል ፡ ክርዳድ ፡ ለመዝራት ፡ ለመነስነስ ፡ ፔንሙ ፡ የሚባል ፡ ፱ኛውን ፡ ያጋንንት ፡ አለቃ ፡ ጸሓፌ ፡ ትእዛዝ ፡ አድርጎ ፡ በጠላትነት ፡ አስነሥቷል ፡ በሙሴ ፡ በአሮን ፡ እነኢያኔስን ፡ እንዳስነሣ ። ፔንሙም ፡ ከግዜር ፡ በተገኘው ፡ በቅዱሱ ፡ ፊደል ፡ ሌላ ፡ ርኩስ ፡ ትምርት ፡ ጥንቊላና ፡ ሟርት ፡ ስመ ፡ አጋንንት ፡ እንዲጥፉና ፡ እንዲያነቡ ፡ ያስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ ለሄኖስ ፡ እንዳሳየው ፡ ኹሉ ፥ ርሱም ፡ በምትሀቱ ፡ ቀለምና ፡ ክርታስ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ርኩስ ፡ ትምርቱን ፡ እየጣፈና ፡ እየጠለሰመ ፡ መጽሐፍ ፡ አድርጎ ፡ አሳይቷቸዋል ። በቃሉም ፡ ጨኾ ፡ እየሰበከ ፥ ሳይሬኽም ፡ ቀርቦ ፡ እንደ ፡ ባለቅኔ ፡ እያሾከሾከ ፡ ምስጢሩን ፡ ኹሉ ፡ በጉሮሯቸውና ፡ በዐይናቸው ፡ አጥግቧቸዋል ። ይልቁንም ፡ ጽልሙታን ፡

ከዋክብት ፡ የተባሉ ፡ የደቂቀ ፡ ሴትን ፡ አለቆች ፡ እንስማግዟቸን ፡ ማናን ፡ አምርሮ ፡ ወተቱን ፡ እጥቀኍር ፡ በመንገርና ፡ በማሳየት ፡ እንደናታቸው ፡ እንደ ፡ ሔዋን ፡ እያስጐመዠ ፡ ማርኳቸዋል ፡ ሕዝቡንም ፡ ባለቆቹ ፡ ዐድሮ ፡ እየሳበ ፡ ቊፍራ ፡ አድርጓቸዋል ። ዛሬም ፡ የርሱን ፡ አሠር ፡ ተከትለው ፡ በቅዱሱ ፡ መጽሐፍ ፡ በዳዊት ፡ በወንጌል ፡ በኍልቈ ፡ ፊደል ፡ የሚያሻርቱ ፥ ርሱንም ፡ እንዳረግ ፡ በገዛ ፡ አስማቱ ፡ የሚስቡ ፡ የሚጐትቱ ፥ ምስጢሩንም ፡ በገሮሬቸው ፡ ሰምተው ፡ እያዜሙ ፡ ለጠየቋቸው ፡ የሚያሰሙ ፥ ለዲያብሎስም ፡ መልክ ፡ ደርሰው ፡ ጠላታቸውን ፡ ለመጕዳት ፡ በዳዊት ፡ ፈንታ ፡ መልኩን ፡ የሚደግሙ ፥ የሰብአ ፡ ትካት ፡ ቀኍራፎች ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ጌታም ፡ በወንጌል ፡ ወሰበ ፡ ያነውሙ ፡ ሰብኢ ፡ መጽአ ፡ ጺላኢ ፡ ወዘርዐ ፡ ክርዳደ ፡ ማእከለ ፡ ሥርናይ ፡ ወኀለፈ ፡ ያለው ፥ ከአዳም ፡ ከሄኖስ ፡ እስከ ፡ ርሱ ፡ ድረስ ፡ ለነበረው ፡ መጽሐፍና ፡ ትምርት ፡ ላለፈው ፡ ኹሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለሚመጣው ፡ ብቻ ፡ አይዶለም ፡ (ማቴ ፲፩ ፡ ፲፫—፲፬) ።

ከዚህም ፡ ቀጥለን ፡ ላለፈውና ፡ ለሚመጣው ፡ ከመጽሐፈ ፡ ሔኖክ ፡ እንጠቅሳለን ። (ሔኖ ፷፱ ፡ ፰—፲) ፡ ወራብዕ ፡ ስሙ ፡ ፔንሙ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ዘአርአየ ፡ ለውሉደ ፡ ሰብእ ፡ መሪረ ፡ ወመዐርዒረ ፡ ወአርአዮሙ ፡ ኵሎ ፡ ኅቡአተ ፡ ጥበቢሙ ፡ (ለአጋንንት) ፡ ወአለበዎሙ ፡ ውእቱ ፡ ለሰብእ ፡ መጽሐፈ ፡ በማየ ፡ ሕመት ፡ ወበክርታስ ። ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ብዙኃን ፡ ይስሕቱ ፡ እምዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡ ወእስከ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ እስመ ፡ ኢተወልደ ፡ ሰብእ ፡ ለዘከመ ፡ ዝ ፡ ግብር ፥ ከመ ፡ ያጽንዑ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ በቀለም ፡ ወበረቅ ፡ እስመ ፡ ኢተፈጥረ ፡ ሰብእ ፡ ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ መላእክት ፥ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ጻድቃነ ፡ ወንጹሓነ ። ወሞት ፡ ዘኵሉ ፡ ያማስን ፡ እምኢገሰሶሙ ፡ አላ ፡ በዝ ፡ አእምሮቶሙ ፡ ይትሀጐሉ ፡ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ይበልዐኒ ፡ ኀይል ፡ እንዳለ ።

ኀጢአት ፡ የባሕርያችን ፡ ናት ፡ ለሚሉም ፡ አለመኾኗን ፡ ሲያጠይቅ ፥ መሐልኩ ፡ ለክሙ ፡ ኃጥኣን ፡ ከመ ፡ ኢኮነ ፡ ደብር ፡ ገብረ ፡ ወኢይከውን ፡ ወኢወግር ፡ አመተ ፡ ለብእሲት ፡ ከማሁ ፡ ኀጢአትኒ ፡ ኢተፈነወት ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ አላ ፡ ሰብእ ፡ እምርእሰሙ ፡ ፈጠርዋ ፡ ወለመርገም ፡ ዐቢይ ፡ ይከውኑ ፡ እለ ፡ ገብርዋ ፡ ብሎባቸዋል ።

## ሐተታ ።

የአዳም ፡ ኀጢአት ፡ ከባት ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ መውረዱ ፡ አዳምን ፡ መስለው ፡ ተከትለው ፡ በሚሠሩት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በማይሠሩትና ፡ በሚነቅፉት ፡ እንደ ፡ ሔኖክ ፡ በሚጸየፉት ፡ በልጆቹ ፡ ኹሉ ፡ አይዶለም ፡ ይኸውም ፡ በርኩት ፡ እንቲ ፡ እምእንስት ፡ ወቡሩክ ፡ ፍሬ ፡ ከርሥኪ ፡ በተባሉት ፡ በናትና ፡ ልጁ ፡ ይታወቃል ። ጽድቁም ፡ እንደ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፡ ከባሕርይ ፡ ተከፍሎ ፡ በመወለድ ፡ አይወረስም ፡ አባትን ፡ መስሎ ፡ በመሥራት ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ (ሕዝ ፲፰ ፡ ፬ና ፡ ፳) ። በዘርም ፡ እንዳይወርድ ፡ የአዳም ፡ ኀጢአት ፡ የነፍስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ የሥጋ ፡ አይዶለም ፡ ነፍስም ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ ነፍስ ፡ ከፈጣሪ ፡ እፍታ ፡ በንጽሐ ፡ ጠባይዕ ፡ ተገኝታ ፡ ከባት ፡ ከናት ፡ በተከፈለው ፡ በዘርና ፡ በደም ፡ ታድራለች ፡ እንጂ ፥ ርሷ ፡ አትከፈልም ፡ (ኢሳ ፶፫ ፡ ፭ ። ዘካ ፲፫ ፡ ፩) ። ወእንዘ ፡ ማይ ፡

ሙእቱ ፡ ታረግዎ ፡ በጥበብከ ፡ ወትነፍኅ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈሰ ፡ ሕይወት ። ወእምአሐቲ ፡ መዝገብ ፡ ዘእምእስትንፋሰ ፡ አፉሁ ፡ ይሠርጻ ፡ ወያሕመለምላ ፡ ነፍሳት ፡ እለ ፡ ይትወለዱ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ እንዳለ ፡ (ቅዳ ፡ ኢት ፡ ግሩ) ። ሱቱኤል ፡ ዕዝራም ፡ ወዘሰ ፡ ነገረ ፡ ሞት ፡ እምከመ ፡ ወፅአ ፡ ቃለ ፡ ትእዛዝ ፡ እምኀበ ፡ ልዑል ፡ ወይቤ ፡ እገሌአ ፡ ይሙት ፡ ወትወፅእ ፡ እምላዕሌሁ ፡ መንፈሱ ፡ እምነ ፡ ሥጋሁ ፡ ከመ ፡ ትግብእ ፡ ኀበ ፡ ዘወሀባ ፡ (ዘፈነዋ) ፡ ወታቀድም ፡ ሰጊደ ፡ ለስብሐተ ፡ ልዑል ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ይሰማማል ። የእክል ፡ የተክል ፡ ዘር ፡ ዝናም ፡ ካላገኘ ፡ እንዳይበቅል ፡ የሰውም ፡ ዘር ፡ ሥጋ ፡ አለነፍስ ፡ አይበቅልም ። ነፍስም ፡ ስትፈጠር ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ነጻነትና ፡ ዕውቀት ፡ ሥልጣን ፡ ያላት ፡ የወደደችውን ፡ ማድረግ ፡ የምትችል ፥ ነባቢት ፡ ለባዊት ፡ ሕያውት ፡ ፍጽምተ ፡ አካል ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ካባት ፡ ከናት ፡ ስላልተከፈለች ፡ በየጥቂቱ ፡ ማደግ ፡ የለባትም ። (መቅ ፡ ወን) ፡ ወገብረ ፡ ላቲ ፡ ሥልጣነ ፡ በውስቴታ ፡ ትግበር ፡ ዘከመ ፡ ኀርየት ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘይኴንና ፡ ወዘይኄይላ ፥ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሠናያቲሃ ፡ ወእከያቲሃ ፡ በሥምረተ ፡ ኀሊናሃ ፡ በአምሳለ ፡ መላእክት ። ተፈጥሮዋም ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከተፈጠረች ፡ ዠምሮ ፡ አለሥራ ፡ መኖር ፡ አትችልም ፡ ግዙፉ ፡ መሣሪያ ፡ ሥጋዋ ፡ እስኪያድግና ፡ እስኪጸና ፡ ድረስ ፡ በራሷ ፡ በገንዘቧ ፡ መሥራት ፡ ትችላለች ፡ በርቀቷ ፡ የምትሠራውን ፡ ግን ፡ ከፈጣሪ ፡ በቀር ፡ የሚያውቃትና ፡ የሚያውቅበት ፡ የለም ። ቀደስኩከ ፡ እምከርሡ ፡ እምከ ፡ (ኤር ፩ ፡ ፭) ። እምከርሡ ፡ እምየ ፡ አንተ ፡ አምላኪየ ። ተንክሩ ፡ ኃጥኣን ፡ እማሕፀን ፡ እምከርሥ ፡ ስሕቱ ፡ ወነበቡ ፡ ሐሰተ ፡ (መዝ ፶፯ ፡ ፫) ። ኀጢአትና ፡ ሞት ፡ ድንቍርና ፡ እንዲህ ፡ በስተኋላ ፡ የመጡ ፡ ባዕዶችና ፡ እንግዶች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ከሥጋና ፡ ከነፍስ ፡ የሚሠርጹ ፡ የባሕርይ ፡ ዘመዶች ፡ አይደሉም ። የባሕርይም ፡ ካለመኾናቸው ፡ የተነሣ ፥ እንሆ ፡ በአዳም ፡ ኀጢአት ፡ ያልተወገዱና ፡ ያልቈሰሉ ፡ ሔኖክ ፡ ኤልያስን ፡ የመሰሉ ፡ ሳያረጁና ፡ ሳይሞቱ ፡ በተሐድሶ ፡ የሚኖሩ ፥ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ በተሰሎንቄ ፡ ከታቡ ፡ ኋላ ፡ ተለውጠው ፡ እንዲገቡ ፡ የተናገራቸው ፡ ብዙ ፡ ጻድቃን ፡ ያዳም ፡ ልጆች ፡ አሉ ፡ (ማቴ ፲፱ ፡ ፲፪) ። ቦታቸውም ፡ ብሔረ ፡ ሕያዋን ፡ ይባላል ። ወእምድኅረ ፡ ዓመተ ፡ ኵነኔ ፡ በኀምሳ ፡ ምእት ፡ ኣመ ፡ ዐሡሩ ፡ ለጽልመተ ፡ ሣልስ ፡ ወርኅ ፥ ወመዕሊሁ ፡ ተስዓ ፡ ወክልኤቱ ፡ ይእተ ፡ እሚረ ፡ ነሥእዎ ፡ ለዕዝራ ፡ ወወሰድዎ ፡ ብሔረ ፡ እለ ፡ ከማሁ ፡ እንዳለ ፡ (ዕዝ ፲፬ ፡ ፵፰) ። ያዳምና ፡ የሔዋን ፡ ምንኵነት ፡ ከላይ ፡ አቀዳዱ ፡ ወደታችም ፡ አወራረዱ ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ከመጻሕፍት ፡ የተገኘውና ፡ የሚገኘው ፡ እውነተኛው ፡ ታሪክ ፡ ይህ ፡ ሲኾን ፥ በ፲፱፻፵፰ ፡ ስለ ፡ ዕርሻና ፡ ስለ ፡ ተግባረ ፡ እድ ፥ ስለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ክርክር ፥ ከለቃ ፡ አፈወርቅ ፡ በውጥንቅጥንት ፡ ተጥፎ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ የታተመው ፡ መጽሔተ ፡ ጥበብ ፡ ግን ፡ በ፻፺፱ ፡ ገጽ ፡ ስለ ፡ ፈደልና ፡ ስለ ፡ ጥፈት ፡ ሔኖክን ፡ ጠቅሶ ፡ ሲተርክ ፡ መልኩን ፡ እንደ ፡ ሰይጣን ፡ ሥዕል ፡ አጥፍቶና ፡ አከፍቶ ፡ ገበሬ ፡ አስደንግጥ ፡ አድርጎታል ። መዠመሪያ ፡ ምክንያቱንና ፡ ጊዜውን ፡ ሳይለይ ፥ ተቀባዩንም ፡ ሳያሳይ ፥ የሄኖስንና ፡ የሔኖክን ፡ ነገር ፡ በለማስተዋል ፡ ዐፍኖ ፡ ሸፍኖ ፡ ያልሆነውን ፡ የኾነ ፡ አስመስሎ ፡ ፈደልና ፡ ጥፈት ፡ ጥን

ቱን ፡ ከሰይጣን ፡ ትምርት ፡ የተገኙ ፡ የሰይጣን ፡ ግንዘቦች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ የግዜር ፡ እን ዳይዶሉ ፥ በኋላ ፡ ግን ፡ እግዜር ፡ ከሰይጣን ፡ ተውሶ ፡ በሰይጣን ፡ መሣሪያ ፡ ስሙንና ፡ ቃሉን ፡ እንዳስጣፈ ፡ ለውጦ ፡ ገልብጦ ፡ ይተርካል ። ስለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ስሙን ፡ ኦርቶዶክስ ፡ አሰኝቶ ፡ እንደ ፡ ፔንሙ ፡ ጨለማውን ፡ ብርሃን ፡ ብርሃኑን ፡ ጨለማ ፡ እያለ ፡ መጻሕፍትንም ፡ እያስተባበለ ፡ ብዙ ፡ ስሕተት ፡ ጥፏል ፡ (መክ፲ ፡ ፩ ። ኢሳ፰ ፡ ፳) ። ይትኄፈሩኬ ፡ ኵሎሙ ፡ አርድእተ ፡ ፔንሙ ፡ እለ ፡ ልሳኖሙ ፡ ፀፈራ ፡ ለሕብል ፥ ወእለ ፡ ረሰያ ፡ ጽዕልተ ፡ እምንእሳ ፡ ለእመ ፡ መጻሕፍት ፡ ፊደል ፥ እንዘ ፡ ይብል ፡ ወለተ ፡ ሳጥ ናኤል ። በከመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ ፀጻዊ ፡ ኖኀቶሙ ፡ እፍ ! ዝሉፍ ፡ ለይትገሠጽ ፡ በቀ ስታመ ፡ ቃል ፡ ንቁጽ ፥ ሐበሊ ፡ ለይትነፃኅ ፡ ከመ ፡ ቈጽለ ፡ አርዝ ፡ ወይዘርዝር ፡ ነሶሉ ፡ ዘፍጥረታተ ፡ ሕምዝ ። ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ኢታትሕት ፡ ሎቱ ፡ ርእሰከ ፥ ወኢታርምም ፡ ሎቱ ፡ አፉከ ፡ ለብእሲ ፡ አብድ ፡ ወመስተአብድ ፡ አላ ፡ ገሥጾ ፡ ወአመጽሉ ፡ ገጾ ፥ እስመ ፡ ነሣኤ ፡ ገጽ ፡ በፀምዖ ።

## ፩ኛ ፡ ክፍል ።

## የሰዋስው ፡ ቡቃያና ፡ ተክል ።

## መቅድመ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡

ጸያሔ ፡ ንባብ ፡ መብእስ ፡ ወመርትዔ ፡ ነገር ፡ ሐንካስ ፡
ለዘውስተ ፡ ኀይል ፡ እምነይል ፡ የሐውር ፡ ወይገይሥ ።

## ጸዋትወ ፡ ፊደል ፡

## በበ ፡ ማዕርግ ፡ ወበበ ፡ ክፍል ።

እስመ ፡ ለሊሃ ፡ ፊደል ፡ እመ ፡ መቅድመ ፡ ቃል ፡ ከዊና ፡
ሰዋስው ፡ ዘትክል ፡ ለዘእምታሕቱ ፡ የዐርግ ፡ ኀበ ፡ ላዕል ።

፩ ፡ ፊደል ፡ ማለት ፡ የቋንቋና ፡ የቃል ፡ ያነጋገር ፡ ኹሉ ፡ ምልክት ፡ አምሳል ፥ ወይም ፡ መግለጫ ፡ ማስታወቂያ ፡ ማለት ፡ ነው ። የሰው ፡ ኹሉ ፡ መልክ ፡ በጥና ፡ ሥዕ ልና ፡ በመስታዮት ፡ ታይቶ ፡ ተለይቶ ፡ እንዲታወቅ ፥ የማይታየውም ፡ ኅቡእ ፡ ንባብ ፡ ረቂቅ ፡ ሐሳብ ፡ በቀለም ፡ ገዝፎ ፥ በክርታስ ፡ ተጥፎ ፥ በፊደሉ ፡ መልክ ፡ ታይቶ ፡ ተለ ይቶ ፡ ይታወቃልና ፡ ስለዚህ ፡ ምልክት ፡ አምሳል ፡ መግለጫ ፡ ማስታወቂያ ፡ አሉት ። በግእዝም ፡ ፈደለ ፡ ብሎ ፡ ጣፈ ፡ ቈጠረ ፡ ለየ ፡ መረጠ ፡ ይላልና ፡ ፊደል ፡ ከዚህ ፡ ይወ ጣል ፡ ልዩ ፡ ምርጥ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቅንጣቱን ፡ ቅንጣትነቱን ፡ የቃል ፡ ዘር ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ። ዐረቦች ፡ ሐርፍ ፥ ዕብራውያን ፡ ኦት ፡ ይሉታል ፡ በተገናኝ ፡ ምልክት ፡ ማለት ፡ ነው ።

፪ ፡ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ሥር ፡ መሠረት ፡ የትግሬና ፡ ያማርኛም ፡ ጥንት ፡ እሊህ ፡ ናቸው ። አ ፡ በ ፡ ገ—ጐ ፡ ደ ፡ ሀ ፡ ወ ፡ ዘ ፡ ሐ ፡ ኀ—ኈ ፡ ጠ ፡ የ ፡ ከ—ኰ ፡ ለ ፡ መ ፡ ነ ፡ ሠ ፡ ዐ ፡ ፈ ፡ ጸ—ፀ ፡ ቀ—ቈ ፡ ረ ፡ ሰ ፡ ተ ፡ «ጰ—ፐ» ።

የፊደል ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ አርእስቱና ፡ መዠመሪያው ፥ ማንሻው ፡ መነሻው ፡ አልፉ ፡ አ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ፊደል ፡ ኹሉ ፡ በአ ፡ ዠምሮ ፡ በማናቸውም ፡ ይፈጸርሳል ፡ ምንም ፡ መዠመሪያው ፡ ፩ ፡ ቢኾን ፥ መፈጸሚያው ፡ ከሱርስትና ፡ ከዕብራይስጥ ፡ አይተባበርም ። ዐረብና ፡ ጽርእ ፡ ሮማይስጥ ፡ በየ ፡ በዖ ፡ በዘ ፡ ይፈጸርሳሉ ፡ ሌላውም ፡ ኹሉ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ መፈጸሚያውን ፡ ይለውጣል ። ከጥንት ፡ ከአበው ፡ ከሄኖስ ፡ ከቃይናን ፥ ኋላም ፡ ከዔበር ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ የወረደ ፥ ከከላውዴዎን ፡ ከብሔረ ፡ የመን ፡ የመጣ ፡ ጥንታዊው ፡ የግእዝ ፡ ፊደል ፡ ግን ፥ ኀን ፡ ከሐ ፡ ፀን ፡ ከጸ ፡ ደርበ ፡ ዘሩ ፡ ፳፪ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ተራውና ፡ ስሙ ፡ ሳይፋለስ ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ በአልፍ ፡ ዠምሮ ፡ በታው ፡ ይፈጸርሳል ።

፫ ፡ ፬ቱ ፡ ፊደላት ፡ ጷና ፡ ፐ ፡ ግን ፡ የተፈጸመሩ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ መፈጸመራቸውም ፡ መጻሕፍት ፡ ከተቀዱበት ፡ ምንጭ ፡ ከጽርእ ፡ ከዮናን ፡ ለማሰማማት ፡ እንጂ ፥ በግእዝ ፡ ፊደላት ፡ ሕጸጽ ፡ ኑሮ ፡ አይዶለም ። ከ፬ቱ ፡ ደግሞ ፡ መደበኛው ፡ ፐ ፡ ነው ፡ ምንም ፡ በመልክና ፡ በቅርጽ ፡ በመጥበቅና ፡ በመላላት ፡ ፪ ፡ መስለው ፡ ታይተው ፡ ፪ ፡ ቢባሉ ፥ ፊደልነታቸው ፡ ፩ ፡ ነው ፡ ሲላላ ፡ ፐ ፡ የሚባለው ፡ ሲጠብቅ ፡ ጰ ፡ ይባላል ። የጰ ፡ መልክና ፡ ቅርጽ ፡ ከጸ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነቍጣ ፡ ፈጸምረው ፡ ጸን ፡ ጰ ፡ ብለውታል ፤ ድምጡ ፡ ግን ፡ የሳባ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡ ይባላል ፤ ከጋልኛም ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ። ፐም ፡ ከፊ ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ መልኩ ፡ ግን ፡ የጽርእ ፡ ተ ፡ ነው ፤ ፐ ፡ መባሉ ፡ በግእዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በጽርእ ፡ በላቲን ፡ ተ ፡ ይባላል ። እኛ ፡ አኀዝ ፡ አድርገን ፡ ፻ ፡ የምንለውን ፡ ጽርአውያንና ፡ ቅብጣውያን ፡ ፐ ፡ ይሉታል ፡ ፊ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዕብራውያንም ፡ ነቍጣ ፡ ፈጸምረው ፡ ፊን ፡ ፐ ፡ ይሉታል ፤ ቍጥሩም ፡ በጽርእና ፡ በቅብጥ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ሰማንያ ፡ ነው ፡ አኀዛችን ፡ ኹሉ ፡ የጽርእና ፡ የቅብጥ ፡ ፊደል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኋላ ፡ በቦታው ፡ እናመጣዋለን ። ጰ ፡ ከጋልኛ ፡ እንዲስማማ ፡ ፐ ፡ ደግሞ ፡ ከወላምኛ ፡ ይስማማል ።

፬ ፡ ጷና ፡ ፐ ፡ ለግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ በውድ ፡ እንጂ ፥ በግድ ፡ አያስፈልጉም ፤ እንሆ ፡ ዐረቦች ፡ ጴጥሮስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጲላጦስ ፥ ወይም ፡ ፔትሮስ ፡ ፓውሎስ ፡ ፒላጦስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፥ ቡጥሩስ ፡ ቡሉስ ፡ ቢላጦስ ፡ ይላሉና ፤ ዕብራውያንም ፡ ፌጥሮስ ፡ ፌሎስ ፡ ፊላጦስ ፡ ይላሉና ፤ ለግእዝም ፡ በጷና ፡ በፐ ፡ ፈንታ ፡ በ ፡ ወይም ፡ ፊ ፡ ይበቃው ፡ ነበር ። ከጽርእና ፡ ከቅብጥ ፡ ወይም ፡ ከሮማይስጥ ፡ የመጣ ፡ ጥሬና ፡ ነባር ፡ ስም ፡ ከል ፡ ኾነ ፡ በቀር ፡ በግእዝና ፡ ባማርኛ ፡ በትግሬኛም ፡ ሳይቀር ፡ ጷንና ፡ ፐን ፡ የሚያስፈልግ ፡ ቃል ፡ የለንም ። ከጥንት ፡ የነበረ ፡ የግእዝ ፡ ፊደል ፡ አለመኾኑ ፥ ቅድምና ፡ ዝምድና ፡ የሌለው ፡ በዕድና ፡ ደባል ፡ የኋላ ፡ ቅጥል ፡ መኾኑ ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ። ጥንታዊነትና ፡ ዘመድነት ፡ ያለው ፡ የግእዝ ፡ ፊደልስ ፡ ቢኾን ፡ ስንኳን ፡ ከግእዝ ፡ ካማርኛና ፡ ከትግሬ ፡ ከትግረኛ ፡ በልታጣም ፡ ነበር ፥ አባታቸው ፡ ግእዝ ፡ ነውና ፡ በግስም ፡ ውስጥ ፡ ጸንገለ ፡ ሄጸ ፡ ደፔ ፡ ኀንጸለ ፡ ጸንጸወ ፡ እያለ ፡ ቢገኝ ፡ ኹሉም ፡ በበና ፡ በፊ ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፡ ነው ።

## ግእዝ ፡ ስለ ፡ ማለትና ፡ ስለ ፡ መባል ።

፩ ፡ ግእዝ ፡ ማለት ፡ ዋሕድ ፡ ማለት ፡ ነው ፥ ጕንድ ፡ እንደ ፡ ማለት ፤ ጕንድነቱም ፡ ፮ ፡ ፀጽቅ ፡ ባለው ፡ በተቋመ ፡ ወርቅ ፡ ይመሰላል ። ግእዝ ፡ የቋንቋና ፡ የፊደል ፡ ስም ፡

ሲኸን ፡ በአልፋ ፡ አ ፡ እንጂ ፡ በዐይን ፡ አይጣፍም ፡ በዐይኑ ፡ ዐ ፡ ሲጣፍ ፡ ትርጓሜው ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ ገአዘንና ፡ ግዕዘን ፡ ተመልከት ። ከጌታችን ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ ኋላም ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ እስከ ፡ አብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ካዕብ ፡ ሣልስ ፡ ራብዕ ፡ ኃምስ ፡ ሳድስ ፡ ሳብዕ ፡ ሳይኖር ፡ በግእዙ ፡ ብቻ ፡ ይጥፉበትና ፡ ያነቡበት ፡ ይናገሩበት ፡ ነበረና ፡ ግእዝ ፡ የተባለ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

፮ ፡ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ በጥንታዊ ፡ ፊደል ፡ ተጥፎ ፡ ከአኩስም ፡ ሐውልት ፡ የተገኘ ፡ ጥንታዊው ፡ የግእዝ ፡ ንባብ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

«ዘ ፤ ሐወለተ ፤ ዘአገበረ ፤ አገዘ ፤ ለአበወሀ ፤ ወሰሐበ ፤ መሐዘተ ፤ አወየ ፤ ለነ ፤ ፀበለነ ፤ ወሐለፈነ ፤ ወመጸ ፤ ነገሠ ፤ ወፈተወ ፤ የነገሠነ ፤ አነዘ ፤ ሀለከ ፤ በአከሰመ ፤ ዘከመ ፤ ገአዘ ፤ አበወሀ ፤ በነደየ ፤ ፀወወነ ፤ ፀወ ፤ መፀ ፤ አከሰመ ፤ ወፀአየ ፤ ዘአደወየ ፤ ወወከሐ ፤ ዘመጸአ ፤ አመ ፤ ቀደመ ፤ የተከበወ ፤ ደመ ፤ ቀነየከ ፤ ነገሠ ፤ አከሰመ ፤ ወፈነወከወ ፤ የነጸረ ፤ አከሰመ ፤ በሐረ ፤ መነገሠተየ» ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ንባብ ፡ አለ ፡ መልክአ ፡ ፊደሉም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ መልክ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በየዘመኑ ፡ ተለዋውጧል ። ከፊተኞች ፡ ይልቅ ፡ የኋለኞች ፡ አሻሽለውታል ፡ አሠራሩንም ፡ ከሰማርያና ፡ ከፊንቂ ፡ አመሳስለውታል ፡ ካህኑ ፡ ዕዝራ ፡ ዕብራይስጥን ፡ ከአሶር ፡ ፊደል ፡ እንዳመሳሰለ ።

## ስለ ፡ ፊደላት ፡ ፯ ፡ ፯ነት ።

፯ ፡ ቋንቋነቱና ፡ ፊደሉም ፡ ያረጀ ፡ ያፈጀ ፡ ግእዝ ፡ ብቻ ፡ ኹኖ ፡ ለሐዲሱ ፡ ዘመን ፡ እነጋገር ፡ ንባብ ፡ የሚያከፋ ፡ ምስጢር ፡ የሚያጠፋ ፡ አፍ ፡ የሚያስከፍት ፡ ነገር ፡ የሚያስገኘትት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ መጻሕፍትን ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ሲመልስና ፡ ሲያስመልስ ፡ በግእዝ ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ለመተርጐም ፡ አልመችኽ ፡ ቢለው ፡ ያይሁዶችንና ፡ ያረቦችን ፡ የጽርኦችን ፡ ፊደል ፡ እንደ ፡ ቋንቋው ፡ ሥርዐት ፡ ድምጥ ፡ እየለወጠ ፡ በሚያስኬድ ፡ በነቍጣና ፡ በዋየል ፡ ፈንታ ፡ ከካዕብ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ ስድስቱን ፡ አዕጹቅ ፡ አግብቶ ፡ በጽርእ ፡ ቋንቋ ፡ ሸ ፡ የሚሉ ፡ ፊደል ፡ ስለ ፡ ሌለ ፡ ሸን ፡ ሥ ፡ ብሎ ፡ ከሸነቱ ፡ አውጥቶ ፡ በንባቡና ፡ ባገባቡ ፡ ከጽርእ ፡ ፊደል ፡ አስማምቶ ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ ዐድሶታል ፡ ለብሉይና ፡ ለሐዲስ ፡ የበቃና ፡ የተቀደሰ ፡ ብርሃን ፡ የለበሰ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ነው ።

፰ ፡ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ከጥንት ፡ ከአበው ፡ የተገኘ ፡ ከውሉድም ፡ የተሰናኘ ፡ ትርጓሜ ፡ ፊደል ፡ ያበ ፡ ሰላማን ፡ ትጋትና ፡ ሥራ ፡ ሲተርክ ፡ ወአምጽአ ፡ ለነ ፡ ሰላማ ፡ ጳጳስ ፡ ፊደለ ፡ እምሕርክትያኑስ ፤ ወሚጠሙ ፡ በአዱ ፡ ልሳን ፡ ወእሙንቱ ፡ ሰብዐቱ ፡ ፊደላት ፡ ብሎ ፡ ይመሰክራል ። ሰባት ፡ ማለቱ ፡ ከግእዝ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ከሰባቱ ፡ ደግሞ ፡ ስድስቱ ፡ ከነዚያውም ፡ ፪ ፡ ፪ቱ ፡ ግእዝና ፡ ሳድስ ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ሣልስና ፡ ኃምስ ፡ ሱቱፋን ፡ ናቸው ፡ ይጠራረሳሉ ። ይኸውም ፡ በገቢር ፡ እንቀጽ ፡ ሞአ ፡ ፀረ ፡ ወጸላኤ ፡ ሐነጸ ፡ ቤቶ ፡ ወጽርሐ ፡ ያለውን ፡ በተገብሮ ፡ ተሞአ ፡ ፀር ፡ ወጸላኢ ፡ ተሐንጸ ፡ ቤቱ ፡

ወጽርሑ ፡ እያለ ፡ መኾዱን ፡ መናገር ፡ ነው ። ራብዕ ፡ ግን ፡ ኃምስና ፡ ሳብዕ ፡ ሳይቀሩ ፡ ከኹሉም ፡ ተፈቃቃሪ ፡ ነው ፥ መልኩንና ፡ ድምፁን ፡ ሳይለውጥ ፡ ኹሉን ፡ ይከታል ፡ ይህም ፡ በልዐ ፡ ሥጋ ፡ ወመና ፥ ተበልዐ ፡ ሥጋ ፡ ወመና ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ኃምስ ፡ ሳብዕ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ራብዕ ፡ ናቸው ፡ ቀሠመ ፡ ጽጌ ፡ ወፍሬ ፥ ተቀሥመ ፡ ጽጌ ፡ ወፍሬ ፡ አኀዘ ፡ ዶርሆ ፡ ወእንቆቅሖ ፥ ተአኀዘ ፡ ዶርሆ ፡ ወእንቆቅሖ ፡ እያሰኙ ፡ ግቢር ፡ ተገብሮ ፡ ይከታሉ ። ፮ ፡ ያልናቸው ፡ ፫ቱ ፡ መዋርስቶች ፡ ባይንና ፡ በገሮ ፡ ባፍንጫ ፡ ይመስላሉ ፡ ራብዕ ፡ በአፍ ፡ ይመስላል ። በለቅዳሴዎች ፡ ግን ፡ ሰባቱን ፡ ኹሉ ፡ በሰባቱ ፡ ዕለታትና ፡ በሰባቱ ፡ ሀብታት ፥ በሰባቱ ፡ ምስጢራት ፡ ይመስሏቸዋል ።

፱ ፡ ሕርክትያኑስ ፡ የዐረብ ፡ ቃል ፡ ነው ፥ ሓፉ ፡ የጽርእ ፡ ይመስላል ፡ ዐረብ ፡ ግን ፡ ሐረከ ፡ ብሎ ፡ አማሰለ ፡ ይላልና ፥ ሕርክት ፡ ከዚህ ፡ ይወጣል ፡ የፊደልን ፡ ድምጥ ፡ የሚለዋውጡ ፡ ነቍጣትንም ፡ መወልጣን ፡ ሲል ፡ እልሐረካት ፡ ይላል ። ትርጓሜውም ፥ የተማሰለ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ እንዲኾን ፡ እንዲቀላቀል ፡ ነቍጣው ፡ ወይም ፡ ዋየሉ ፡ ከፊደሉ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ የኾነ ፡ የተቀላቀለ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዋየል ፡ ነቍጣ ፡ የሚባል ፡ ቅጥሉ ፡ ነው ፡ ቅጥልም ፡ ባይኖረው ፡ ሰባሩና ፡ ዐንከሳ ፡ መኾኑ ፡ ራሱን ፡ ማጽነኑ ፡ እንደ ፡ ቅጥል ፡ ኹኖ ፡ ዋየል ፡ ይባላል ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነቍጣ ፡ ይታሰባል ። ዋየል ፡ የላቲን ፡ ቃል ፡ ነው ፡ መላው ፡ የአ ፡ ቤት ፡ ፊደል ፡ ፮ቱ ፡ ዐይነት ፡ ኹሉ ፡ በሮማይስጥ ፡ ዋየል ፡ ይባላል ፡ ድምፅ ፡ ወይም ፡ ጕህና ፡ ማለት ፡ ነው ፥ መወልጠ ፡ ድምፅም ፡ ይሉታል ፡ ድምፅ ፡ ለራሱ ፡ መወልጥ ፡ ለሌላው ። እኛ ፡ በሰዋስው ፡ ግእዝ ፡ ፀመል ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ የምንላቸውን ፡ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ ኤውሮፓች ፡ ከንሰን ፡ ዋየል ፡ ዱብል ፡ ይሏቸዋል ። እሊሁም ፡ ከነሰ ፡ ወየለ ፡ ደበለ ፡ ከማለት ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ናቸው ፥ በንባብ ፡ በምስጢር ፡ ይገጥማሉ ፡ እንዲያውም ፡ በጭራሽ ፡ ከነዚህ ፡ የወጡ ፡ ይመስላሉ ። በግእዝና ፡ በማርኛም ፡ በሌላውም ፡ በሴም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ በዐረብ ፡ በሱርስት ፡ በዕብራይስጥ ፥ አና ፡ ሀ ፡ ወና ፡ የ ፡ እሊህ ፡ ፬ቱ ፡ እንደ ፡ ዋየል ፡ ናቸው ፡ ለራሳቸው ፡ ድምፅ ፡ እየኾኑ ፡ የሌሎቹን ፡ ድምፅ ፡ ይለዋውጣሉ ። አለዋወጣቸው ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ድምጣቸውንና ፡ ድምጥነታቸውን ፡ በግስ ፡ ዐመል ፡ ፋች ፡ ተመልከት ።

## አዕጼቅ ፡ ያልናቸው ፡ የ፮ቱ ፡ ፊደላት ፡ ጠባይ ።

፲ ፡ በካዕብ ፡ በሳብዕ ፡ ወ ፥ በሣልስ ፡ በኃምስ ፡ የ ፥ በራብዕ ፡ በሳድስ ፡ አና ፡ ሀ ፡ አሉ ። የወ ፡ ጠባይ ፡ ራሱን ፡ ጐርዶ ፡ ሌላውን ፡ ፊደል ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ማድረግ ፡ ነውና ፡ የካዕብ ፡ የሳብዕ ፡ ቅጥይ ፡ ዐንካስነት ፡ ህየንተ ፡ ወ ፡ ኹኖ ፡ በወ ፡ ፈንታ ፡ ገብቷል ። የየ ፡ ጠባይ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ወ ፡ ራሱን ፡ ጐርዶ ፡ ሌላውን ፡ ፊደል ፡ ሣልስና ፡ ኃምስ ፡ ማድረግ ፡ ነውና ፡ የሣልስ ፡ የኃምስ ፡ ቅጥይ ፡ ኹሉ ፡ ህየንተ ፡ የ ፡ ኹኖ ፡ በየ ፡ ፈንታ ፡ ገብቷል ። የአና ፡ የሀም ፡ ጠባይ ፡ እንደ ፡ ወና ፡ እንደ ፡ የ ፡ ራስን ፡ ጐርዶ ፡ ወይም ፡ ሳይጐርዱ ፡ ሌላውን ፡ ፊደል ፡ ራብዕ ፡ ሳድስ ፡ ማድረግ ፡ ነውና ፡ የራብዕና ፡ የሳድስ ፡ ቅጥይ ፡ ሰባርነትና ፡ ዐንካስነት ፡ ስለ ፡ አ ፡ ስለ ፡ ሀ ፡ የገባ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ አና ፡ እንደ ፡ ሀ ፡ ይታሰባል ፡ አና ፡ ሀ ፡ ጠባያቸው ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ፪ቱ ፡ ስላንድ ፡ ይቈጠራሉ ።

ለዜማ ፡ ምልክት ፡ ሥረይ ፡ እንዳለው ፥ ለፊደልም ፡ ድምፅ ፡ ለጠበዩና ፡ ለቅጥዩ ፡ ሥረ
ዮቹ ፡ ዉ ፡ ዩዩ ፥ አ—ሀ ፡ ናቸው ፡ ቅጥይ ፡ ኹሉ ፡ በለቤት ፡ አክል ፡ ነውና ፡ ጕንደ ፡
ፊደሉን ፡ ነዉ ፡ ነዎ ፡ ነዪ ፡ ነዩ ፡ ነአ ፡ ነሀ ፡ በማለት ፡ ፈንቃ ፥ ኑ ፡ ኖ ፡ ኒ ፡ ኔ ፡ ና ፡ ን ፡ እያ
ሰኘ ፡ በ፮ ፡ ስልት ፡ ማስኬዱ ፡ የነዚህ ፡ ምልክት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡፡ የርሳቸውም ፡ ቅጥይ ፡
ምልክትነቱ ፡ ሥረይ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የድምጣቸውን ፡ ስልት ፡ ልዩ ፡ ልዩነቱን ፡
እያጕላ ፡ እያጋነነ ፡ ያሳያል ፡፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ችም ፡ ብዙውን ፡ ፊደል ፡ ጠቅልሎ ፡ አሳ
ንሶ ፡ በእጅ ፡ መኪና ፡ ለመጣፍ ፡ ግእዞችን ፡ ብቻ ፡ በኡ—ቡ ፥ በኢ—ቢ ፥ በአ—ባ ፥
በኤ—ቤ ፥ በእ—ብ ፥ በኦ—ቦ ፡ እያሉ ፡ በአ ፡ ብቻ ፡ ማስኬድ ፡ ይቻላል ፡ ይህነንም ፡ ኋላ ፡
በ፮ኛው ፡ ማዕርገ ፡ ፊደል ፡ እናመጣዋለን ፡፡

፲፩ ፡ ዳግመኛም ፡ ያራቱ ፡ ዲቃሎች ፡ የነጐኈኰኵቈ ፡ ቅጥይ ፡ ከግእዛቸው ፡ በቀር ፡
ኹሉም ፡ መንታ ፡ መንታ ፡ ዐይነት ፡ መኾኑ ፥ ዋየለቻቸው ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡
የግእዛቸው ፡ ቅጥል ፡ ግን ፡ እንደነሆሎፎ ፡ እንደነሮቆቶ ፡ መኾኑ ፥ ፩ ፡ ዋየል ፡ ብቻ ፡
ወን ፡ ያሳያል ፡ ቀለበቱ ፡ ሀየንተ ፡ ወ ፡ ነው ፡፡ ይህም ፡ ገወ—ጐ ፥ ገወዪ—ጒ ፥ ገውዋ—ጓ ፥
ገወዩ—ጔ ፥ ገወሀ—ጕ ፥ እያለ ፡ ኹሉን ፡ ያሳያል ፡፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ መተዋቸው ፡ የካዕ
ቡን ፡ ድምጥ ፡ ማልሳቸውና ፡ ሳድሳቸው ፡ ጉ ፡ ጕ ፥ የሳብዑን ፡ ድምጥ ፡ ግእዛቸው ፡
ጐ ፡ ደርበ ፡ ስለ ፡ ወረሰው ፡ ነው ፡፡ ሳድሳቸው ፡ የካዕብ ፡ ድምጥ ፡ ስለ ፡ ደረበ ፡ ካኹን ፡
ቀደም ፡ ጐ ፡ ጕ ፥ ኈ ፡ ኍ ፥ ኰ ፡ ኵ ፥ ቈ ፡ ቍ ፡ እያለ ፡ ቦታውን ፡ ትቶ ፡ አለቦታው ፡ ገብቶ ፡
በካዕብ ፡ ቦታ ፡ ይጣፍ ፡ ነበር ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ከቦታው ፡ ገብቶ ፡ መፀረሻ ፡ ኹኗል ፡፡ ሳድስ
ነቱም ፡ ጕሕቍ ፡ ኵሕሰ ፡ በለው ፡ ይታወቃል ፡ ግስ ፡ በካዕብ ፡ በማልስ ፡ አይነጣምና ፡፡
ግእዛቸው ፡ በቅኔና ፡ በመልክ ፡ ከግእዝ ፡ ጋራ ፡ እንዲገባ ፡ ሳድሳቸውም ፥ ሰርጕ ፡ እኍ ፡
ጽኵ ፡ ጽጕ ፡ ጕልቍ ፡ እያለ ፡ ከሳድስ ፡ ጋራ ፡ ይገባል ፡ ከካዕብ ፡ ግን ፡ አይተባበርም ፡
ቤት ፡ ያፈርሳል ፡፡

፲፪ ፡ ከናባ ፡ ሰላማግም ፡ በኋላ ፡ እስከናዒ ፡ ካሌብ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡
ዘመን ፡ ሕዝቡ ፡ ሰራዊቱ ፡ ይህን ፡ ሐዲስ ፡ ግእዝ ፡ አንለምድኽ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ከሀ
ናቱ ፡ ታዜና ፡ ወልደ ፡ አልዐሚዳ ፡ ካሌብ ፡ በማለት ፡ ፈንቃ ፥ ተዘነ ፡ ወለደ ፡ አለፀመደ ፡
ከለበ ፡ እያሉ ፡ በዚያው ፡ ባሮጌው ፡ ግእዝ ፡ ሲጥፉ ፡ እንደ ፡ ኖሩ ፥ ባኵስምና ፡ በሽሚ
ዛና ፡ በደንጊያ ፡ ተጥፎ ፡ የሚገኝ ፡ ጥንተ ፡ ጥፈታቸው ፡ ይመሰክራል ፡፡

ፍናወ ፡ ፊደል ፡ ወሑረታቲሁ ፡፡

፲፫ ፡ የጥንቱ ፡ ግእዝ ፡ ፍጹም ፡ የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አካኼዱና ፡ መንገዱ ፡
እንደ ፡ ወንድሞቹ ፡ እንዳረብና ፡ እንደ ፡ ሱርስጥ ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡
ግራ ፡ ነበረ ፡ ይህነንም ፡ በየመን ፡ ያሉ ፡ ሕምያር ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፥ ዕብራውያንም ፡
ሳይቀሩ ፡ በቃል ፡ በታሪክ ፡ ይመሰክራሉ ፡፡ ፪ኛም ፡ ፊደሉና ፡ ቋንቋው ፡ ቅን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡
እንደርሻ ፡ አካኼድ ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ በ፪ ፡ ወገን ፡ ይጣፍና ፡
ይነበብ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ፡፡ ይህነንም ፡ እኤ ፡ ከቃላቸው ፡ እንደ ፡ ሰማኹ ፥ በትግሬ ፡
መሬት ፡ ከዚያውም ፡ ባጋሜ ፡ ወረዳ ፡ ከዋሻ ፡ ውስጥ ፡ በደንጊያ ፡ ተጥሮ ፡ ያዩትና ፡

ያገኙት ፡ አሉ ። ኋላ ፡ ግን ፡ በሰላማ ፡ ጊዜ ፡ በአብርሀና ፡ በአጽብሐ ፡ ዘመን ፥ የያሬድት ፡ ልጆች ፡ ጽርአውያን ፥ የከምም ፡ ልጆች ፡ ግብጻውያን ፡ ከያሬድት ፡ ቋንቋ ፡ ሊያሰማሙ ፡ በዳዊራሽ ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ አዙረውት ፡ ከሴም ፡ ቋንቋ ፡ መንገድ ፡ ወጥቷል ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በጕረሮ ፡ የሚነገረው ፡ ቃል ፡ የሐውት ፡ ሐና ፡ የዐይኑ ፡ ዐ ፡ ድምጥ ፡ እየደከመና ፡ እያነሰ ፡ እየጠፋ ፡ ኺዷል ። ትግሮች ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከቋንቋቸው ፡ አላጠፉትም ፡ እንዳይሁድና ፡ እንዳረቦች ፡ ለዩተው ፡ ጠንቅቀው ፡ ይናገሩታል ።

፲፬ ፡ ፊደሉ ፡ ግእዝ ፡ ብቻ ፡ ኹኖ ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ መኼዱም ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ፡ በጥንታዊ ፡ ፊደል ፡ ተጥፎ ፡ ከነስም ፡ የተገኘው ፡ እንቷከ ፡ እንሆ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

| የማናይ ። | ፀጋማይ ። |
|---|---|
| መሐጸበወ | ወበጸሐሙ ፡ |
| መረሐበ | ብሐሮሙ ፡ |
| መሰለፊአ | አፍለሶሙ ፡ |
| መሀሰሰነአ | እንስሳሆሙ ፡ |
| ረበከየ | ይክበር ፥ ማለት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቃል ፡ |

በቃል ፡ ተርጕመውታል ። አነስሞች ፡ ግን ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ስለ ፡ ተጣፈ ፡ ዕብራይስጥ ፡ ይሉታል ። (ተረት) አባቱን ፡ አያውቅ ፡ አያቱን ፡ ናፈቀ ፡ እንዲሉ ። ወዲያ ፡ ማዶም ፡ በየመንና ፡ በናግራን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አንቷከ ፡ ጥፈት ፡ በየዋሻውና ፡ በየደንጊያው ፡ በየመቃብሩ ፡ ይገኛል ፡ የብራናም ፡ መጽሐፍ ፡ አይታጣ ፡ ሕምያሮች ፡ ግን ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋቸውን ፡ አጥፍተው ፡ እንደ ፡ ግብጦች ፡ ዐረቦች ፡ ኹነዋል ።

ፍልሰተ ፡ ፊደላት ፡ ወኢነዛቲሆን ።

፲፭ ፡ የፊደል ፡ ተራ ፡ የተፋለሰና ፡ አልፍ ፡ አ ፡ ከርስቱ ፡ ከቀዳማዊነት ፡ ተነቅሎ ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ሆይ ፡ ሀ ፡ መዠመሪያ ፡ ፊደል ፡ የኾነ ፡ ከፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ አበገደሀ ፡ የነበረውን ፡ ሀለሐመሁ ፡ ብለው ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ያፋለሱትም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ የነበሩ ፡ ጽርአውያንና ፡ ቅብጣውያን ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ያፋለሱበትም ፡ ምክንያት ፡ የግእዝን ፡ ፊደል ፡ ከኢነግዞነት ፡ አውጥቶ ፡ የርሳቸውን ፡ ፊደል ፡ አልፋ ፡ ቤታ ፡ ጋማ ፡ የነበረውን ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ እያሉ ፡ በግእዝ ፡ ፊደል ፡ ላይ ፡ አኃዝ ፡ አድርጎ ፡ ለማግባት ፡ እንዲመቻቸው ፡ ነው ፡ አኃዞችን ፡ ኹሉ ፡ የጽርእና ፡ የቅብጥ ፡ ፊደል ፡ መኾኑን ፡ ኋላ ፡ በቦታው ፡ እናመጣዋለን ። ይህም ፡ ሥራ ፡ የግእዝን ፡ ፊደል ፡ ከሴም ፡ ቋንቋ ፡ ዐዋጅ ፡ አውጥቶ ፡ ጥርጊያ ፡ መንገዱን ፡ አጥፍቶ ፡ ቊጥሩን ፡ አሳስቶ ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ የቀረ ፡ አይደለም ፡ በሄኖስ ፡ ራእይ ፡ ተመሥርቶ ፡ የታነጸውን ፡ ያልፋ ፡ ወዖን ፡ ምስጢር ፡ አፍርሷል ።

፲፮ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አበገደ ፡ እየተረሳና ፡ እየጠፋ ፥ ሀለሐመ ፡ እየሰፋ ፡ ኺዷል ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ በኹሉ ፡ አገር ፡ ጠፍቶ ፡ በሸዋ ፡ በስሜን ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ እኩሉ ፡ የሸዎች ፡ ፊደል ፥ እኩሉ ፡ የስሜኖች ፡ ፊደል ፡ ይሉታል ፡ ርሱ ፡ ግን ፡ ከጥ

ንት ፡ ከሰላማ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ አንቲካ ፡ ፊደል ፡ ነው ። አንቲካነቱንም ፡ ዐረቦች ፡ ሳይቀሩ ፡ ሴማውያንም ፡ ያፌታውያንም ፡ በፊደል ፡ ታሪክ ፡ ይመሰክራሉ ፤ በሀገራችንም ፡ ባኵስም ፡ ሐውልት ፡ በስሜን ፡ መጻሕፍት ፥ በሺዋም ፡ በያድባራቱ ፡ በየገዳማቱ ፥ ይልቁንም ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አለ ፤ ያስተምሩበታል ። ስሙንም ፡ ከሀለሐመ ፡ ለይተው ፡ በዚያው ፡ በጥንቱ ፡ አጠራር ፡ አበገደ ፡ ወይም ፡ አቡጊዳ ፡ ይሉታል ፤ አቡጊዳም ፡ ማለት ፡ የግእዙ ፡ ተራ ፡ ሳይፋለስ ፡ ከካዕብ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ያሉት ፡ ፮ቱ ፡ አዕጹቅ ፡ በመፋለስና ፡ በመዋረስ ፡ እየተዛነቁ ፡ ይጣፋሉና ፥ ስለዚህ ፡ ነው ፤ መዛነቃቸውም ፡ ውጥንቅጥ ፡ ኹኖ ፡ የሕዝቅኤልን ፡ ምግብ ፡ ይመስላል ፡ (ሕዝ፬ ፡ ፱) ።

## ማዕርገ ፡ ፊደላት ።

፲፯ ፤ የፊደላት ፡ ማዕርግ ፡ ባጣጣፍና ፡ በትምርት ፡ ከ፫ ፡ ይከፈላል ፤ ፫ቱ ፡ ክፍል ፡ የግእዝ ፡ ብቻ ፤ ፪ኛው ፡ ያማርኛ ፡ ብቻ ፤ ፫ኛው ፡ የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ መድበል ፥ ጉባኤ ፡ ፊደል ፡ ነው ። የግእዙ ፡ ማዕርግ ፡ ከ፫ ፡ መከፈሉ ፥ የወጣኒና ፡ የማእከላዊ ፡ የፍጹም ፡ ትምርት ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፤ ያማርኛውና ፡ መድበሉም ፡ ከ፫ቱ ፡ የሚበልጥ ፡ የፍጹም ፡ ፍጹም ፡ ነው ።

## ፩ኛ ፡ ማዕርግ ።

| ፲፰ ፤ ፊደል ። | ስመ ፡ ፊደል ። | ኍልቈ ፡ ፊደል ። |
|---|---|---|
| አ | አልፍ ፡ | አሐድ ፡ |
| በ (ጰ) | ቤት ፡ | ክልኤት ፡ |
| ገ (ጐ) | ገምል ፡ | ሠለስት ፡ |
| ደ | ድልት ፡ | አርባዕት ፡ |
| ሀ | ሆይ ፡ | ኀምስት ፡ |
| ወ | ዋዌ ፡ | ሰድስት ፡ |
| ዘ | ዛይ ፡ | ሰብዐት ፡ |
| ሐ (ኀ—ኈ) | ሐውት ፡ | ሰምንት ፡ |
| ጠ | ጠይት ፡ | ተስዐት ፡ |
| የ | የማን ፡ | ዐሥርት ፡ |
| ከ (ኰ) | ካፍ ፡ | ዕሥራ ፡ |
| ለ | ላዊ ፡ | ሠላሳ ፡ |
| መ | ማይ ፡ | አርብዓ ፡ |
| ነ | ነሐስ ፡ | ኀምሳ ፡ |
| ሠ | ሠውት ፡ | ስሳ ፡ |
| ዐ | ዐይን ፡ | ሰብዓ ፡ |
| ፈ (ፐ) | ፈፍ ፡ | ሰማንያ ፡ |
| ጸ (ፀ) | ጻደይ ፡ | ተስዓ ፡ |

| | | |
|---|---|---|
| ቀ (ቈ) | ቆፍ ፡ | ምእት ፡ |
| ረ | ርእስ ፡ | በ ፡ ምእት ፡ |
| ሰ | ሳት ፡ (ሰዓት) ፡ | ገ ፡ ምእት ፡ |
| ተ | ታው ፡ | ደ ፡ ምእት ። |

## ሐተታ ።

፲፱ ፡ እሊህም ፡ ፳፮ቱ ፡ ፊደላት ፡ የመልክ ፡ ልዩነት ፡ ያላቸው ፡ ፬ቱ ፡ ድርቦች ፡ (ኀፀጸፐ) ፡ ሳይቀሩ ፡ በ፭ ፡ ጸታ ፡ ተከፍለው ፡ በ፭ቱ ፡ ሕዋሳት ፡ አፍ ፡ በጕረሮና ፡ በትናጋ ፡ በምላስና ፡ በከንፈር ፡ በጥርስ ፡ ይነገራሉ ፤ ጸታቸውና ፡ ክፍላቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ።

፩ኛ ፤ — በጕረሮ ፡ የሚነገሩ ፡ ፭ ፤ — አ ፡ ሀ ፡ ሐ ፡ ኀ ፡ ዐ ።
(እነዚህ ፡ ፭ቱ ፡ ከመላላት ፡ በቀር ፡ መጥበቅ ፡ የላቸውም) ።

፪ኛ ፤ — በትናጋ ፡ የሚነገሩ ፡ ፬ ፤ — ገ ፡ የ ፡ ከ ፡ ቀ ።

፫ኛ ፤ — በምላስ ፡ የሚነገሩ ፡ ፭ ፤ — ደ ፡ ጠ ፡ ለ ፡ ነ ፡ ተ ።

፬ኛ ፤ — በከንፈር ፡ የሚነገሩ ፡ ፮ ፤ — በ ፡ ወ ፡ መ ፡ ፈ ፡ ጰ ፡ ፐ ።

፭ኛ ፤ — በጥርስ ፡ የሚነገሩ ፡ ፮ ፤ — ዘ ፡ ሠ ፡ ጸ ፡ ፀ ፡ ረ ፡ ሰ ።

## ፪ኛ ፡ ማዕርግ ።

፳፮ ፤ መላው ፡ የግእዝ ፡ ፊደል ፡ ከናበጋዙና ፡ ከነኀዙ ፡ ከነአኃዙ ።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ | ፩ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ | ፪ |
| ገ ጐ | ጉ | ጊ ጒ | ጋ ጓ | ጌ ጔ | ግ ጕ | ጎ | ፫ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ | ፬ |
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ | ፭ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ | ፮ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ | ፯ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ | ፰ |
| ኀ ኈ | ኁ | ኂ ኊ | ኃ ኋ | ኄ ኌ | ኅ ኍ | ኆ | ፱ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ | ፲ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ | ፳ |
| ከ ኰ | ኩ | ኪ ኲ | ካ ኳ | ኬ ኴ | ክ ኵ | ኮ | ፴ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ | ፵ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ | ፶ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ | ፷ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ | ፸ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ | ፹ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ | ፺ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ | ፻ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ | ፪፻ |
| ቀ ቈ | ቁ | ቂ ቊ | ቃ | ቄ ቋ | ቅ ቍ | ቆ | ፫፻ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ | ፬፻ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ | ፭፻ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ | ፮፻ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ | ፯፻ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ | ፰፻ |

## ፫ኛ ፡ ማዕርግ ፡ አቡጊዳ ፡፡

፳፩ ፡ አቡጊዳሰ ፡ ውእቱ ፡ ኅዉሠ ፡ ዘርዕ ፡ ወሠርጽ ፡ ወቱሱሐ ፡ መልክእ ፡ ሐንፈጽ ፡፡ ሑረቱ ፡ አምሳለ ፡ ፍርዝ ፡ እንዘ ፡ በየማኑ ፡ ወበፀጋሙ ፡ አኃዝ ፡ ወፍናዊሁኒ ፡ መብእስ ፡ ወደጋን ፡ አዕቃጼ ፡ ረዋጺ ፡ ሕፃን ፡፡ የፊደሉና ፡ የአኃዙ ፡ ተራ ፡ ከታው ፡ በታች ፡ ፬ቱን ፡ ድርበች ፡ ኀፀጸፐንና ፡ ፪ቱን ፡ ዲቃሎች ፡ ኈቈን ፡ ጨምሮ ፡ እስከ፲፻ ፡ ይወርድና ፡ ፻ ፡ ለማለት ፡ የአልፍ ፡ አን ፡ ሳድስ ፡ እን ፡ ይጥፋል ፡ አጣጣፉም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | አ | ቡ | ጊ | ዳ | ሄ | ው | ዘ | ፯ |
| ፪ | በ | ጉ | ዲ | ሃ | ዌ | ዝ | ሐ | ፰ |
| ፫ | ገ | ዱ | ሂ | ዋ | ዜ | ሕ | ጠ | ፱ |
| ፬ | ደ | ሁ | ዊ | ዛ | ሔ | ጥ | ዮ | ፲ |
| ፭ | ሀ | ዉ | ዚ | ሓ | ጤ | ይ | ከ | ፳ |
| ፮ | ወ | ዙ | ሒ | ጣ | ዬ | ክ | ሎ | ፴ |
| ፯ | ዘ | ሑ | ጢ | ያ | ኬ | ል | ሞ | ፵ |
| ፰ | ሐ | ጡ | ዪ | ካ | ሌ | ም | ኖ | ፶ |
| ፱ | ጠ | ዩ | ኪ | ላ | ሜ | ን | ሦ | ፷ |
| ፲ | የ | ኩ | ሊ | ማ | ኔ | ሥ | ዖ | ፸ |
| ፳ | ከ | ሉ | ሚ | ና | ሤ | ዕ | ፎ | ፹ |
| ፴ | ለ | ሙ | ኒ | ሣ | ዔ | ፍ | ጾ | ፺ |
| ፵ | መ | ኑ | ሢ | ዓ | ፌ | ጽ | ቆ | ፻ |
| ፶ | ነ | ሡ | ዒ | ፋ | ጼ | ቅ | ሮ | ፪፻ |
| ፷ | ሠ | ዑ | ፊ | ጻ | ቄ | ር | ሶ | ፫፻ |
| ፸ | ዐ | ፉ | ጺ | ቃ | ሬ | ስ | ቶ | ፬፻ |
| ፹ | ፈ | ጹ | ቂ | ራ | ሴ | ት | ኆ | ፭፻ |
| ፺ | ጸ | ቁ | ሪ | ሳ | ቴ | ኅ | ፆ | ፮፻ |
| ፻ | ቀ | ሩ | ሲ | ታ | ኄ | ዕ | ጵ | ፯፻ |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፪፻ | ሯ | ሡ | ቷ | ኃ | ዔ | ጵ | ፖ | ፳፻ |
| ፫፻ | ሰ | ቱ | ኂ | ፃ | ጼ | ፕ | ኦ | ፩ |
| ፬፻ | ተ | ኍ | ዒ | ጳ | ፔ | እ | ቦ | ፪ |
| ፭፻ | ኅ | ፁ | ጺ | ፓ | ኤ | ብ | ሖ | ፫ |
| ፮፻ | ፀ | ጱ | ፒ | አ | ቤ | ግ | ዶ | ፬ |
| ፯፻ | ጸ | ፑ | ኢ | ባ | ጌ | ድ | ሆ | ፭ |
| ፰፻ | ፐ | ኡ | ቢ | ጋ | ዴ | ህ | ዎ | ፮ |
| ፱፻ | ኈ | | | | | | | |
| ፲፻ | ቈ | | | | | | | |
| ፻ | አ | | | | | | | |

ያቡጊዳ ፡ ተረፍ ።

፳፱ ፤ መልካቸውንና ፡ ድምጣቸውን ፡ አካኼዳቸውን ፡ ለውጠው ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ትተው ፡ ፭ ፡ ፭ ፡ ብቻ ፡ እየኾኑ ፡ በሕጹጽነት ፡ የሚጣፉ ፡ ፬ቱ ፡ ሕጹጻን ፡ ዲቃሎች ፡ ከናባቶቻቸው ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ገ | — | ጐ | ጕ | ጓ | ጔ | ጒ |
| ኀ | — | ኈ | ኍ | ኋ | ኌ | ኊ |
| ከ | — | ኰ | ኵ | ኳ | ኴ | ኲ (ኾ) |
| ቀ | — | ቈ | ቍ | ቋ | ቌ | ቊ |

የኀና ፡ የከ ፡ ዲቃሎች ፡ ኋና ፡ ኯ ፡ ቅጥላቸውና ፡ ድምጣቸው ፡ ፩ ፡ ፀይነት ፡ ፩ ፡ ስልት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ባማርኛ ፡ ይዋረሳሉ ፤ እናንተ ፡ በሚል ፡ ባ፬ኛው ፡ መደብ ፡ አይታችኋል＝አይታችኯል ፥ ሰምታችኋል＝ሰምታችኯል ፥ ኋላ＝በኯላ ፡ እያሰኙ ፡ ይዋረሳሉና ፤ ከ፪ቱ ፡ ባንዱ ፡ በወደዱት ፡ መጣፍ ፡ ይቻላል ።

ሐተታ ፤ ስለ ፡ ፊደል ፡ ቍጥር ።

፴፫ ፤ ፊደላችንና ፡ የፊደል ፡ ቍጥራችን ፡ በሀለሐ ፡ አካኼድ ፡ ተፋልሶ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ስለ ፡ ተሳሳተ ፥ ቍጥሩም ፡ በዚያው ፡ በስሕተቱ ፥ ዛሬም ፡ በውነቱ ፡ ፳፻ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ የዘጠኝ ፡ መቶና ፡ ያሥር ፡ መቶ ፡ የእልፍ ፡ ምልክት ፡ ፊደል ፡ አልነበረውም ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ባቡጊዳ ፡ ቍጥር ፡ ምእት ፡ ብሎ ፡ አምኣት ፡ ሳይሉ ፡ እልፍ ፡ ማለት ፡ ስሕተትና ፡ ግድፈት ፡ እንዳይኾን ፥ ከፐ ፡ በታች ፡ ፫ ፡ ፊደላት ፡ ኈ ፡ ቈ ፡ እ ፡ ተጨምረውለት ፡ እስከ ፡ እልፍ ፡ መልቷል ። እስከ ፡ እልፍም ፡ በፊደል ፡ መቍጠር ፡ የጥንት ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ያኹን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ አይደለም ። የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፤ በየፊደሉ ፡ እስከ ፡ እልፍ ፡ ይቈጥራል ።

፴፬ ፤ ኈ ፡ ስለ ፡ ቀለበቱ ፡ የ፱፻ ፡ አኃዝ ፡ መኾኑ ፥ አባቱ ፡ ኅርም ፡ ኀ ፡ የሐ ፡ ተወራጅ ፡ ነውና ፥ በተራ ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ጠ ፡ ዘጠነኛነት ፡ ስላለው ፡ ነው ። ቈም ፡ ስለ ፡ ቀለበቱ ፡ ያ፲፻ ፡ ወይም ፡ የሺሕ ፡ አኃዝ ፡ መኾኑ ፥ ቆፍ ፡ ፲ ፡ ነውና ፤ የርሱን ፡ አሥር ፡

ተከትሎ ፡ ነው ። እ ፡ ደግሞ ፡ እልፍ ፡ መባሉና ፡ ያ፲ ፡ ሺሕ ፡ አኃዝ ፡ መኾኑ ፥ በራሱ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተቀዳጃት ፡ ስላንዲቱ ፡ ቅንጣት ፡ ነቍጣ ፡ ነው ። የእልፍ ፡ እ ፡ ጠባይ ፡ በዕብራይስጥም ፡ እንዲዚህ ፡ ነው ፤ ብቻውን ፡ አሐዱ ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነቍጣ ፡ ሲኾንበት ፡ ፩ ፡ እልፍ ፡ ይባላል ። ዕብራውያን ፡ ግን ፡ እልፍ ፡ የሚሉት ፡ እንዳረቦች ፡ ዐሥሩን ፡ መቶ ፡ ነው ። የግእዝም ፡ እልፍ ፡ ጥንታዊው ፡ እንደዚህ ፡ ነበረ ፤ ይኸውም ፡ በአኃዙ ፡ አካኼድ ፡ ይታወቃል ፡ ምእት ፡ ብሎ ፡ እልፍ ፡ በማለቱ ። ዐሥሩን ፡ መቶ ፡ ወይም ፡ አንዱን ፡ ሺሕ ፡ አምኣት ፡ ብሎ ፡ ፲ሩን ፡ ሺሕ ፡ ፩ ፡ እልፍ ፡ ማለት ፡ ከጽርእና ፡ ከቅብጥ ፡ የመጣ ፡ የሐዲስ ፡ ግእዝ ፡ ልማድ ፡ ነው ።

፳፰ ፤ ካኹን ፡ ቀደም ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ የቃጣነው ፡ የአኃዙም ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ጥንታዊው ፡ የግእዝ ፡ አኃዝ ፡ እንደ ፡ ሱርስት ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ እንደ ፡ ጽርእ ፡ እንደ ፡ ቅብጥ ፡ ያው ፡ ራሱ ፡ ፊደሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ እንዳረብና ፡ እንደ ፡ ላቲን ፡ ሌላ ፡ ቍጥር ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ አኃዝ ፡ አልነበረውም ፤ ይህነንም ፡ ባንደኛው ፡ ማዕርግ ፡ አሳይተናል ። በኋላ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ከሰላማ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ቅብጣውያንና ፡ ጽርኣውያን ፡ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርነ ፤ የግእዝን ፡ ፊደል ፡ ተራውን ፡ አፋልሰው ፡ ከአኃዝነት ፡ አውጥተው ፡ የጽርእን ፡ ፊደል ፡ ለግእዝ ፡ ፊደል ፡ አኃዝ ፡ አድርገው ፡ አላኳያውና ፡ አላምሳያው ፡ አለፈርጁ ፡ አላጣማጁ ፡ እያቈራኙ ፡ ስለ ፡ ጣፉት ፤ እንሆ ፡ ይህ ፡ ከአሐዱ ፡ እስከ ፡ እልፍ ፡ (፩—፼) ፡ ያለ ፡ አኃዝ ፡ ከሰብዓ ፡ (፸) ፡ በቀር ፡ ኹሉም ፡ የጽርእና ፡ የቅብጥ ፡ ፊደል ፡ ነው ።

፳፱ ፤ የፊደል ፡ ትውልድ ፡ አወራረዱና ፡ አቀዳዱ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ብትል ፤ የፊንቅያ ፡ ፊደል ፡ ከዕብራይስጥ ፥ የጽርእ ፡ ፊደል ፡ ከፊንቅያ ፥ የላቲን ፡ ፊደል ፡ ከጽርእ ፡ ተቀድቷል ። የጽርእ ፡ ፊደላት ፡ መላው ፡ ፳፬ ፡ ናቸው ፤ የቅብጥ ፡ ደግሞ ፡ በነዚህ ፡ ላይ ፡ ፯ ፡ ጨምሮ ፡ ፴፩ ፡ ነው ። ለኛ ፡ ግን ፡ አኃዝ ፡ የኾኑልን ፡ ፲፯ ፡ ናቸው ፤ ከነዚሁም ፡ ፮ቱና ፡ ፺ ፡ አኃዝ ፡ እንጂ ፡ ፊደል ፡ አይባሉም ፤ ፊደልነት ፡ ስለሌላቸው ፡ በፊደላት ፡ ተራ ፡ አይጣፉም ። ፬ቱ ፡ ደ ፡ ነው ፤ መልኩ ፡ ተለውጦ ፡ ዐይኑ ፡ ዐን ፡ ይመስላል ፤ በወዲያ ፡ ግን ፡ ዴልታ ፡ ፫ ፡ ማእዝን ፡ ነው ። ፭ቱም ፡ ኄ ፡ ነው ፤ ኤ ፡ ይሉታል ። ፯ቱም ፡ ዛይ ፡ ነው ፤ በጽርእ ፡ ፊደል ፡ ዋው ፡ ስለሌለ ፡ ዛይን ፡ ፪ ፡ ጊዜ ፡ ጥፈው ፡ እግሮቹን ፡ ዘርግተው ፡ ቈልፈው ፡ የገን ፡ ሣልስና ፡ ኃምስ ፡ አስመስለው ፡ ፯ና ፡ ፮ ፡ አድርገውታል ፤ ቈላፋው ፡ ዛይ ፡ ነው ፤ ዝርጉ ፡ ስም ፡ የለውም ። አንዱን ፡ እልፉ ፡ ጐዳና ፡ ቀንዳም ፡ አድርገው ፡ ጕዳውን ፡ አሐዱ ፡ ፩ ፥ ቀንዳሙን ፡ ዕሥራ ፡ ፳ ፡ እንዳሉት ፡ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። ፰ቱም ፡ ሔት ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ሬሳ ፡ ተጋድሞ ፡ ተጥፏል ፤ በጽርእ ፡ ኤታ ፡ በሮማይስጥ ፡ ሐሽ ፡ ይባላል ። ፱ቱና ፡ ፲ቱም ፡ ጤትና ፡ ዮድ ፡ ናቸው ፤ ቴታ ፡ ዮታ ፡ ይሏቸዋል ። ባለቀንዱም ፡ ፳ ፡ ፩ ፡ ነው ፤ ፩ዱም ፡ እልፉ ፡ ነው ። ፴ና ፡ ፵ም ፡ ተዛውረውና ፡ ተዘቅዝቀው ፡ አለመልካቸው ፡ ተጥፈዋል ፤ ፴ ፡ እንደ ፡ ሥዕለ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቍልቍሊት ፡ ተጥፎ ፡ ራብዑን ፡ ሃ ፡ ይመስላል ፤ አቅንቶ ፡ ሲያዩት ፡ ላምዳ ፡ ነውና ፥ በጽርእ ፡ ሡላሳ ፡ ይባላል ። ፶ም ፡ ኑን ፡ ነውና ፥ በጽርእ ፡ ኀምሳ ፡ ይባላል ። ፵ም ፡ ሚም ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ላምዳ ፡ ቍልቍሊት ፡ ተጥፎ ፡ ራብዑን ፡ ሣ ፡ ይመስላል ።

፳፯፤ ፎ፡ ግን፡ የግእዝ፡ ሮ፡ ነው፤ ፆሚክሮን፡ የሚሉት፡ ቃናሹ፡ ፆ፥ በዴልታ፡ ምትክ፡ አድርገው፡ ፬ቱ፡ ካሉት፡ ከዐይኑ፡ ዐ፡ ጋራ፡ በስምና፡ በመልክ፡ ተባብሮ፡ ፩፡ ዐይነት፡ ስለ፡ ኾነባቸው፥ በፆ፡ ፈንታ፡ ሮን፡ አግብተው፡ አለስሙና፡ አለቍጥሩ፡ ሰብዐ፡ ብለውታል። ፹ም፡ ፈ፡ ነው፤ በጽርእ፡ ፐ፡ ይባላል፤ መልኩ፡ አልተለወጠም። ፺፡ ግን፡ አኀዝ፡ ብቻ፡ እንጂ፡ ፊደል፡ ስላልኾነ፡ ከቍጥር፡ ስም፡ በቀር፡ የፊደልነት፡ ስም፡ የለውም፤ መልኩ፡ ተለውጦ፡ እንደ፡ ን፡ ኹኗል፤ ጥንተ፡ መልኩ፡ ግን፡ ራሱ፡ ገጥሞ፡ እግሩ፡ ቀጥ፡ ያለ፡ ነው። በጽርእ፡ ፊደል፡ ዋውና፡ ጻዴ፡ ቆፍ፡ እነዚህ፡ ፫ቱ፡ ስለሌሉ፡ ቦታቸውን፡ በአኀዝነት፡ ሌሎች፡ ወርሰውታል። ፻፡ የተባለም፡ ሬስ፡ ነው፤ መልኩ፡ የግእዝን፡ የ፡ ይመስላል፤ በጽርእና፡ በቅብጥ፡ ሮ፥ በሮማይስጥ፡ ፐ፡ ይባላል፤ ሬስ፡ መቶ፡ መባሉ፡ ቦታውን፡ ትቶ፡ በቆፍ፡ ቦታ፡ ገብቶ፡ ነው፡ እንጂ፥ በግእዝና፡ በዕብራይስጥ፡ ኹለት፡ መቶ፡ ነው። ፼ም፡ ኹለት፡ ሮ፡ ነው፤ በጽርእ፡ ሚርያ፡ ይባላል፤ ፪ቱን፡ ሮ፡ አቈራኝቶና፡ አስተሳስሮ፡ እልፍ፡ ማለት፥ እንደ፡ ጽርአውያን፡ መቶ፡ ጊዜ፡ መቶ፡ ማለት፡ ነው፡ እንጂ፥ እንደ፡ ሴማውያን፡ ፲፡ ጊዜ፡ መቶ፡ ወይም፡ ሺሕ፡ ማለት፡ አይደለም።

## ፬ኛ፡ ማዕርግ።

## ከግእዝ፡ ፊደላት፡ የተዴቀለ፡ ያማርኛ፡ ፊደል።

፳፰፤ ምሉ፡ ዐማርኛ፡ ያላቸው፡ ፊደላት፡ ፯፡ ብቻ፡ ናቸው፤ ለቀሩት፡ ግን፡ ከራብዖቻቸው፡ በቀር፡ ያማርኛ፡ ቅጥል፡ የላቸውም፤ ከነራብዑም፡ በጭራሽ፡ የሌላቸው፡ አሉ፤ (አ—ዐ፡ ሀ—ሐ፡ ወ—የ፡ ጸ—ፐ)። ፯፡ ያልናቸውም፡ ምሉአንና፡ ፍጹማን፡ ፊደላት፡ እነዚህ፡ ናቸው።

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ደ | — | ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ዘ | — | ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| ጠ | ጸፀ | ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ከ | — | ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ነ | — | ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| ሰ | — | ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ተ | — | ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |

## ሐተታ።

፳፱፤ ጨ፡ የወጣ፡ ከጠና፡ ከጸፀ፡ ነው፡ እንጂ፥ ከጠ፡ ብቻ፡ አይደለም፤ በግእዝ፡ ጸ—ፀ፡ የሚባለው፡ በማርኛ፡ ጠና፡ ጨ፡ ይኾናል። ማስረጃ፡ ጸመ፡ ጦመ፡ ጻልአ፡ ጠላ፤ ጸጕር፡ ጠጕር፡ ጭገር፤ ጸልመ፡ ጨለመ፤ ጼው፡ ጨው፤ ጻጹት፡ ጫጩት፤ ጸርቅ፡ ጨርቅ። ፀመደ፡ ጠመደ፤ ፀመረ፡ ጨመረ፤ ፀበጠ፡ ጨበ።

ዐማርኛና ፡ ትግሬ ፡ ትግሪኛ ፡ ከባቶቻቸው ፡ ከግእዝ ፡ ጕያ ፡ ሳይወጡ ፡ ጀሸኸ ፡ በማለት ፡ ከዐረብ ፡ ከሱርስት ፡ ከዕብራይስጥ ፥ ዠኘቸ ፡ በማለት ፡ ከሮማይስጥና ፡ ከልጆቹ ፡ ይሰማማሉ ፤ ጨ ፡ በማለት ፡ ግን ፡ ከማንም ፡ ከማን ፡ የማይገጥሙ ፡ ብቶኞች ፡ ናቸው ። ሸን ፡ ከጥንታዊ ፡ ግእዝ ፡ ወርሰውታል ፤ ጀ ፡ የዐረቦች ፡ ገ ፡ ነው ፥ ዐረብ ፡ ገ ፡ ሲል ፡ ጂም ፡ ጀመል ፡ ይላል ። ከን ፡ ኸ ፡ ማለት ፡ የዕብራይስጥና ፡ ያማርኛ ፡ የትግሬኛም ፡ ነው ፤ ባረብና ፡ ባሮጌው ፡ ግእዝ ፡ ግን ፡ ኸ ፡ የሚባለው ፡ ኀርም ፡ ኀ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ ከፍ ፡ አልነበረም ። ሸ ፡ የሚባለውም ፡ ንጉሡ ፡ ሠ ፡ እንጂ ፥ ሳቱ ፡ ሰ ፡ አልነበረም ፤ ሠውት ፡ ሠና ፡ ሳት ፡ ሰ ፡ ተዛውረውና ፡ ተፋልሰው ፡ አለቦታቸው ፡ ተጥፈዋል ፤ መፋለሳቸውም ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ፤ ነጋሢ ፡ ነጋሽ ፥ ሢመት ፡ ሹመት ፥ ሦክ ፡ ሾኽ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

በጓኋኳቋ ፡ አንጻር ፡ ከግእዙም ፡ ከማርኛውም ፡
የሚገኙ ፡ የራብዕ ፡ ዲቃሎች ፡ ራብዖች ፡ ብቻ ።

(ከግእዙ) ።

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፴፤ | ባ | ዳ | ዛ | ጣ | ላ | ማ | ና | ሣ | ፋ | ጻ | ፃ | ራ | ሳ | ታ | ። |
| | ቧ | ዷ | ዟ | ጧ | ሏ | ሗ | ኗ | ሧ | ፏ | ጿ | | ሯ | ሷ | ቷ | ። |

(ከማርኛው) ።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጃ | ዠ | ጫ | ኻ | ኛ | ሻ | ቻ | ። |
| ጇ | ዧ | ጯ | ዃ | ኟ | ሿ | ቿ | ። |

ለነዚህ ፡ ፊደሎች ፡ ለኹሉም ፡ ዋየላቸው ፡ ዋ ፡ ነው ፤ ቅጥላቸው ፡ ኹሉ ፡ ሀየንተ ፡ ዋ ፡ ኹኖ ፡ በዋ ፡ ፈንታ ፡ ገብቷል ። ቅጥላቸው ፡ ቀርቶ ፡ በዝርዝር ፡ ፊደል ፡ ሲጣፉ ፡ ግን ፡ ቡአ ፡ ዱአ ፡ ጁአ ፡ ጩአ ፡ ያሰኛሉ ፤ በዚህም ፡ ዉአ ፡ ይገኛል ፤ ይኸውም ፡ ዋ ፡ ማለት ፡ ነው ። ኹሉንም ፡ ዘርዝሮ ፡ ሲጥፉት ፥ በዉአ ፡ ደዉአ ፡ ጀዉአ ፡ እያሰኘ ፡ የቅጥላቸው ፡ መንታነት ፡ ስለ ፡ ፪ቱ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ። ሗኗሧጿሯቷ ፡ እነዚህ ፡ ፯ቱ ፡ እንደ ፡ ጓኋኳቋ ፡ ናቸውና ፥ ለግእዝም ፡ ይሰማሙታል ። ተሗቅሐ ፡ ይትመዋቃሕ ፡ ይትሗቃሕ ። ተኗለወ ፡ ይትነዋሉ ፡ ይትኗሉ ፤ ምሧዕ ፡ መሧዕት ። መጿት ፡ መጿቲ ፡ ምጿት ። ምሯጽ ፡ ስሯጽ ። ተቷስሐ ፡ ይተዋሳሕ ፡ ይቷሳሕ ፤ ተቷሳሒ ። አስተቷስሐ ፡ ያስተተዋስሕ ፡ ያስተቷስሕ ፤ አስተቷሳሒ ፡ መስተቷስሕ ። ዋ ፡ ካዕብና ፡ ራብዕ ፡ ማዛመዱ ፡ ቅጥሉ ፡ የአ ፡ ምስለኔ ፡ ስለ ፡ ኾነለት ፡ ነው ፡ (ቍ፲) ።

፪ኛ ፡ ማዕርግ ።

፴፩ ፤ ጉባኤ ፡ ዝርዋን ፡ ፊደላት ፥ ፊደላተ ፡ ግእዝ ፡ ወዐምሐራ ፡ እለ ፡ ምስለ ፡ ሱርስት ፡ ወዐረብ ፡ ወምስለ ፡ ዕብራይስጥ ፡ የኅብሩ ።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | — | ኤ | እ | ኦ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቧ | ቤ | ብ | ቦ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | — | ጌ | ግ | ጎ |
| ጐ | » | ጒ | ጓ | — | ጔ | ጕ | » |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዷ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጇ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | — | ሄ | ህ | ሆ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | — | ዌ | ው | ዎ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዟ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዧ | ዤ | ዥ | ዦ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | — | ሔ | ሕ | ሖ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | — | ኄ | ኅ | ኆ |
| ኈ | » | ኊ | ኋ | — | ኌ | ኍ | » |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጧ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጯ | ጬ | ጭ | ጮ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | — | ዬ | ይ | ዮ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | — | ኬ | ክ | ኮ |
| ኰ | » | ኲ | ኳ | — | ኴ | ኵ | » |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ዃ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሏ | ሌ | ል | ሎ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሟ | ሜ | ም | ሞ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኗ | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኟ | ኜ | ኝ | ኞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሧ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | — | ዔ | ዕ | ዖ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፏ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጿ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | — | ፄ | ፅ | ፆ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | — | ቄ | ቅ | ቆ |
| ቈ | » | ቊ | ቋ | — | ቌ | ቍ | » |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሯ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሷ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሿ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቷ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቿ | ቼ | ች | ቾ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | — | ጴ | ጵ | ጶ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | — | ፔ | ፕ | ፖ |

## ቍጥር ፡ በፊደልና ፡ በአኃዝ ።

አ በ ገ ደ ሀ ወ ዘ ሐ ጠ የ ከ ለ መ ነ ሠ ዐ ፈ ጸ ቀ ቈ እ
፩ ፪ ፫ ፬ ፭ ፮ ፯ ፰ ፱ ፲ ፳ ፴ ፵ ፶ ፷ ፸ ፹ ፺ ፻ ፲፻ ፼

## ፫ኛ ፡ ማዕርግ ።

### ስለ ፡ እጅ ፡ መኪና ፡ ፊደል ።

፴፪ ፡ ኤውሮፖች ፡ ፊደላቸውን ፡ ሳያሳንሱና ፡ ሳይከፍሉ ፡ እናሳንስም ፡ ሳይሉ ፡ መላውን ፡ ፊደል ፡ ፳፮ቱን ፡ ዘር ፡ ከነአኃዙና ፡ ከነንጓዙ ፡ አሳክተውና ፡ አስማምተው ፡ በእጅ ፡ መኪና ፡ እንዲጥፉ ፥ የኛም ፡ ፊደል ፡ በኤውሮፖች ፡ ልክ ፡ ፳፮ ፡ ዘር ፡ ነውና ፡ እንደ ፡ መገርመሪያው ፡ ማዕርግ ፡ ሞፍራውን ፡ ትቶ ፡ አበጋዙን ፡ ብቻ ፡ ግእዝ ፡ ግእዙን ፡ ባንድ ፡ አይቅር ፡ ሰብስቦ ፡ በ፯ ፡ ዋየል ፡ ቢያስኬዱት ፡ ከእጅ ፡ መኪና ፡ ተስማምቶ ፡ እንደ ነሱ ፡ ፊደል ፡ ይኼዳል ። አኃዙንም ፡ ፲ኛውን ፡ ዘሮ ፡ አድርጎ ፡ የላይ ፡ የታች ፡ ሠረዝ ፡ ቀርቶበት ፡ ከ፩ ፡ እስከ ፡ ፱ ፡ ያለውን ፡ ባ፲ቱ ፡ ዘሮነት ፡ ቢያስኬዱት ፡ ከአኃዛቸው ፡ ይስ ማማል ። ዘሮ ፡ ማለት ፡ የአኃዝ ፡ ዋየል ፡ ወይም ፡ ምእላድ ፥ ወላጤ ፡ ፍቅድ ፡ ወመፈ ድፍድ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ብቻውን ፡ ሲኼን ፡ ባዶ ፡ ጠፍ ፥ አኃዝ ፡ ሲከተለው ፡ አብዢ ፡ ይባላል ፤ ጥሬንቱም ፡ ዘረወንና ፡ ዘርዘረን ፡ ይመስላል ።

### ፊደልና ፡ ዋየል ፡ ከነአኃዙና ፡ ከነንጓዙ ።

አ በ ገ ደ ሀ ወ ዘ ሐ ኀ ጠ የ ከ ለ
መ ነ ሠ ዐ ፈ ጸ ፀ ቀ ረ ሰ ተ ጰ ፐ ።

### ዲቃሎች ።

ጐ ጀ ዠ ኈ ጨ ኰ ኸ ኘ ቈ ሸ ቸ ።

### ዋየሎች ።

ኡ ኢ ኣ—ዋ ኤ እ ኦ ።

### አኃዞች ።

፩ ፪ ፫ ፬ ፭ ፮ ፯ ፰ ፱ ፲ ።

### ምልክቶች ።

. ፡ ፣ ፤ ፥ ። . , . ? ! ( ) - « » — \ —

### ፀዋጅና ፡ አገባብ ።

፴፫ ፡ ግእዝ ፡ ፊደል ፡ በግእዝነት ፡ ዋየልም ፡ በፊደልነት ፡ ሲነገር ፡ ኹሉም ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ በየጠባዩ ፡ ይነገራል ። ግእዝ ፡ ኹሉ ፡ ዋየል ፡ መፈለጉ ፡ ከካዕብ ፡ እስከ ፡

ሳብዕ ፡ ነው ፡ ዋየልም ፡ ድምፁን ፡ የሚያወርስ ፡ ለግእዝ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ ራሱን ፡
ችሎ ፡ ገደለ ፡ ተገደለ ፡ ቀበረ ፡ ተቀበረ ፡ እያለ ፡ በዋየልም ፡ ቃዝሎ ፡ በኡ—ቡ ፡ በኢ—ቢ ፡
በአ—ባ ፡ በዋ—ቧ ፡ በኤ—ቤ ፡ በእ—ብ ፡ በኦ—ቦ ፡ እያሰኘ ፡ ከገ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ያሉትን ፡
የኹሉን ፡ አካኼድ ፡ ያሳያል ። ዋየልም ፡ በፊደልነቱ ፡ መነሻ ፡ መድረሻ ፡ መከከልም ፡
ቢኾን ፡ እንደ ፡ ግእዝ ፡ ራሱን ፡ ይችላል ፡ ይህም ፡ ኡረኡኤለእ—ኡሩኤል ፡ ኢየአ
በእ—ኢዮብ ፡ አፈእአ ፡ አፍአ ፡ ኤለእየአሰእ—ኤልያስ ፡ እነኤ—እኔ ፡ እኘአ—እኛ ፡
ኦረኢተእ—ኦሪት ፡ እያሰኘና ፡ በቁም ፡ ቀሪነቱን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ዋየልነቱንም ፡
ያሳያል ።   ዋ ፡ ደግሞ ፡ በመነሻና ፡ በመድረሻ ፡ ፊደል ፡ በአንቀጽ ፡ ሲገባ ÷ በጥሬ ፡
መነሻም ፡ ሲገባ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። ምሳሌ ፡ ጐዋጐረ—ጓጐረ ፡ ጐዋጐዋረአ—ጓጓራ ፡
ተነእፈዋፈዋ—ተንፏፏ ፡ ፈዋፈዋተኤ—ፏፏቴ ። በጥሬ ፡ መድረሻ ፡ ሲገባ ፡ ግን ፡
የሩቅ ፡ ሴት ፡ ዝርዝር ፡ ይኾናል ። ምሳሌ ፡ በኣለዋ—ባሏ ፡ ለእጅዋ—ልጇ ፡ ዐመእ
ቾዋ—ዐማቿ ። የጥሬው ፡ መድረሻ ፡ ግልስና ፡ ራብዕ ፡ ኃምስና ፡ ሳብዕ ፡ ሲኾንበት ፡ ርሱ ፡
ራሱ ፡ ብቻ ፡ ይበቃል ፡ ይህም ፡ ሰነእጠኢ—ሰንጢ ፡ ሰንጢዋ ፡ ከኣረእዋ—ካራዋ ፡
ጐፈረኤዋ—ጐፈሬዋ ፡ መኢደኦዋ—ሚዶዋ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ማእከል ፡ ኹኖ ፡
ግእዝ ፡ ሲቀድመውና ፡ ሲከተል ፡ ግን ÷ ድምፁን ፡ ለግእዝ ፡ እንዳያወርስና ፡ በቁም ፡
ቀሪ ፡ ኹኖ ፡ እንዲነገር ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ፪ ፡ ነቍጥ ፡ ይደረግበታል ፡ ይህም ፡ እስተዋለ ፡
ተዋዋለ ፡ ከኡረ ÷ ለኢየ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። የኤውሮፓን ፡ ቋንቋ ፡
ተምረው ፡ ለሚጥፉና ፡ ለሚያነቡ ፡ ከላገር ፡ ቋንቋና ፡ ስለ ፡ አጅ ፡ መኪናም ፡ ለሚያ
ስቡ ፡ ማመልከቻ ፡ ይኸው ፡ ይበቃል ። የእንዚህም ፡ ነገር ፡ ዐሥርቱ ፡ ዘሮ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡
ዐረቦች ፡ ከህንዶች ፡ ኤውሮፖች ፡ ከረቦች ፡ እንደ ፡ ወሰዱት ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡
ህንዶች ፡ አኃዝ ፡ ይኼዳል ፡ ከመልክ ፡ በቀር ፡ ያካኼድ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። አኃዝነ
ቱና ፡ ፊደልነቱም ፡ የጽርእና ፡ የቅብጥ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በ፫ኛው ፡ ማዕርግ ፡ ተነግሯል ፡
(ቍ፳፫ና ፡ ፳፬) ። የምልክቶችም ፡ አገባብ ፡ ከነስማቸው ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይነገራል ።

ያልተነገረውም ፡ ያራቱ ፡ ዐይነት ፡ ቍጥር ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡ ነው ።

+ የመደመር ፡

— የመቀነስ ፡

\ የማብዛት ፡

÷ የማካፈል ።

## የንባብ ፡ ማሳያ ።

መአአ ፡ አነእበሰአ ፡ ዘእመእነገደ ፡ የእሀኡደአ ፡ ቀደኣመአወኢ ፡ ኀየእለ ፡ ሠእ
ለኣሰኤ ፡ ሠእየኡመ ፡ እገእዘኢአበእሐኤረእ ፡ ነእገኡሠ ፡ ነገሠእተእ ፡ ዘኢተእየአጰእ
የአ ።   ሞአ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥዩመ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።   ፲፱፻፴፬ ፡ ወይም ፡ 1942 ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## የጥፈትና ፡ የመጻሕፍት ፡ መልክ ።

፵፬ ፤ ከንገት ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ በፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ መልክ ፡ በየራሱና ፡ በየገጹ ፡ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ ያላቸው ፡ ብዙ ፡ ሕዋሳት ፡ እንዳሉ ፥ በመጻሕፍትም ፡ መልክ ፡ በያንዳንዱ ፡ ገጽ ፡ ብዙ ፡ ስም ፡ ያለው ፡ ክፍል ፡ አለበት ። ያልተቀጻው ፡ ብራና ፡ ወረቀት ፡ አንዳንዱ ፡ ጥቅል ፡ ሰሌዳ ፥ ወይም ፡ ሉሕ ፡ ይባላል ፤ ዝርግ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዚያ ፡ የሚቀጻው ፡ አንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ ሳይታጠፍ ፡ ቅጽ ፥ ሲታጠፍ ፡ ቅጠል ፡ ይባላል ። ፪ኛ ፡ ቅጠል ፡ የሌለው ፡ እኩሌታ ፡ ቅጽ ፡ ሲኾን ፡ ጎላፍ ፡ ይባላል ። ፬ቱ ፡ ወይም ፡ ፰ቱ ፡ ቅጽ ፡ እየታጠፈ ፡ ባንድነት ፡ ሲታሰር ፡ ጥራዝ ፡ ይባላል ። አንዱ ፡ ቅጽ ፡ ተሠምሮ ፡ ሲታጠፍ ፡ ባላ፬ ፡ ገጽ ፡ ከኾነ ፡ ዘንድ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ የ፪ቱ ፡ ገጽ ፡ ስምና ፡ መልክ ፡ በየክፍሉ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ውግ ፡ ያለበት ፡ ክፍል ፡ ግራና ፡ ቀኙ ፡ ጠርዝ ፥ መግለጫውና ፡ መግለጫው ፡ ግልየት ፥ ላይኛው ፡ አርእስት ፥ ታችኛው ፡ ኅዳግ ፥ መካከለኛው ፡ ዐምድ ፤ ዕጥፋቱን ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፡ አማክሎ ፡ ወደ ፡ ጥራዝ ፡ ያለው ፡ ማዶና ፡ ማዶው ፡ ምስማክ ፡ ይባላል ፡ መከዳ ፡ ማለት ፡ ነው ። በመካከልም ፡ በያንዳንዱ ፡ ውግ ፡ ፊት ፡ ወስፌውና ፡ ርሳሱ ፡ ያለፈበት ፡ ሰንበር ፡ ሰንበሩ ፡ ሚራክ ፥ ቀለም ፡ የሚወድቅበት ፡ ቃዳው ፡ ተለላው ፡ መሥመር ፥ በፊደልና ፡ በፊደል ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ክፍት ፡ ክፍቱ ፡ ሞኅት ፥ በየፊደሉ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፥ ከርሥ ፡ ይባላል ፤ የነፊሁ ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ። የመሥመርም ፡ ሥራ ፡ አብነቱ ፡ የተገኘና ፡ የተቀዳ ፡ ከሙገዝ ፡ ቅጠልና ፡ ከጕናጕና ፡ ነው ፡ ይባላል ። የጥቍሩ ፡ ደግሞ ፡ አንዳንዱ ፡ ፊደል ፥ ቀለም ፡ ወይም ፡ ኅር(ወ)መት ፡ ይባላል ፤ ቅርጽ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከነቍጥ ፡ እስከ ፡ ነቍጥ ፡ የሚሰደረው ፡ አንዳንዱ ፡ ስክ ፡ ንባብ ፡ ይባላል ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ ነው ። ቃልንም ፡ ከቃል ፡ በየንባቡና ፡ በየስልቱ ፡ በየብልቱ ፡ ለይተው ፡ ነጥለው ፡ ዘርዝረው ፡ ደምረው ፡ ፩ ፡ ፈርጅ ፡ አድርገው ፡ የሚያሳዩ ፡ የቃል ፡ ምልክቶች ፡ ፩ ፡ ናቸው ፤ መልካቸውና ፡ ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ።

| መልካቸው ። | ስማቸው ። |
| --- | --- |
| . | ነጥብ ፥ አው ፡ (ወይም) ፡ ነቍጥ ፥ ማጥበቂያ ። |
| ፡ | ንኡስ ፡ ነጥብ ፥ አው ፡ ንጻል ፡ (ነጠላ) ። |
| ፥　፣ | ንኡስ ፡ ሠረዝ ፥ አው ፡ ንጻል ። |
| ፤ | ዐቢይ ፡ ሠረዝ ፥ አው ፡ ክፁብ ፡ (ድርብ) ። |
| ። | ዐቢይ ፡ ነጥብ ፥ አው ፡ ክፁብ ። |

## ሐተታ ።

፵፭ ፤ ነጥብና ፡ ነቍጥ ፡ ፩ ፡ ስም ፡ ናቸው ፤ ነጥብ ፡ የግእዝ ፡ ብቻ ፡ ነቍጥ ፡ የዐረብና ፡ የዕብራይስጥ ፡ ነው ፤ ያውም ፡ አንዳንዱ ፡ ጠብታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ ፪ቱና ፡ ፬ቱ ፡ አይዶለም ፤ ሲበዛ ፡ ነቍጣት ፡ ነጥባት ፡ ወይም ፡ ነጠብጣብ ፡ ያሰኛል ። የጥንቱ ፡ ነጥብ ፡ እንደ ፡ ዜማ ፡ ይዘት ፡ ፩ ፡ ቅንጣት ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ፤ ፪ኛም ፡ ባንዱ ፡ ነጥብ ፡ ፈንታ ፡ እንዳ፲ቱ ፡ ያለ ፡ ዘንግ ፡ ነበረ ፤ ፫ኛ ፡ ግን ፡ አንዱ ፡ ነጥብ ፡ የመጥበቅ ፡ ምልክት ፡ ስለ ፡

ኽን ፡ እንዳይሞክሽ ፡ በዘንጉ ፡ ፈንታ ፡ ፪ ፡ ነጥብ ፡ ኹኗል ። ፪ቱን ፡ ፬ቱን ፡ ነቍጥ ፡ ነጥብ ፡ ብሎ ፡ ባንድነት ፡ ስም ፡ መጥራት ፡ በዚያው ፡ በጥንቱ ፡ በንዱ ፡ ቅንጣት ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሰዋስው ፡ መንገድ ፡ አይዶለም ። ባማርኛ ፡ ፪ ፡ ነጥብ ፡ ፬ ፡ ነጥብ ፡ ተብሎ ፡ ከቅጽል ፡ ጋራ ፡ ይነገራል ፤ ጣፎችና ፡ በለመጣፎች ፡ ግን ፡ ነቍጥን ፡ ለ፪ቱ ፡ ብቻ ፡ ነጥብን ፡ ላ፬ቱ ፡ ብቻ ፡ ሰጥተው ፡ አለቅጽል ፡ ፪ቱን ፡ ነቍጥ ፡ ፬ቱን ፡ ነጥብ ፡ ብለው ፡ በተለየ ፡ ስም ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ አድርገው ፡ ይጠሩታል ። ባለቅኔዎችም ፥ ቃልከ ፡ ነቍጥ ፡ እንዘ ፡ ክልኤቲ ፡ ልሳንከ ፡ አሐቲ ፡ ይእቲ ። ፍቅደ ፡ ነጥብ ፡ በዓላተ ፡ ወልድ ፡ ተስዐቱ ፡ ውእቱ ፡ እያሉ ፡ በውስጠ ፡ ብዙነት ፡ ያገቡታል ። ነጥብን ፡ ተስዐቱ ፡ ማለት ፡ ፬ ፡ ቀይ ፡ ሲጨመርበት ፡ ነው ።

## አገባባቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ።

፴፯ ፡ ነቍጥ ፡ የንኡሳን ፡ ቃላት ፡ መለያ ፡ ነው ፤ በንባብ ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ በያንዳንዱ ፡ ስክ ፡ ይገባል ። ነጠላ ፡ ወይም ፡ ንኡስ ፡ ሠረዝ ፡ ጠበዩ ፡ ፩ ፡ ሲኾን ፡ መልኩ ፡ ፪ ፡ ነው ፤ ልዩነት ፡ ስላላቸው ፡ እየራሳቸው ፡ በሚታሰሩና ፡ በማይመፈሩ ፡ ባመሮር ፡ ቃሎች ፡ ይገባል ። ምሳሌ ፤ አነ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወአነ ፡ ደኀራዊ ፥ ርእስ ፡ ወማኅለቅት ፡ ጥንት ፡ ወተፍጻሜት ። አንተ ፡ ዘአሚሃ ፡ ወአንተ ፡ ዘይእዜ ፥ አንተ ፡ ዘእሙንቱ ፡ ወአንተ ፡ ዘለን ። ተፈለጥ ፡ የማነ ፡ አው ፡ ፀጋመ ፥ ወእመ ፡ አኮ ፡ ግባእ ፡ ድኅረ ፤ ወኢትሖር ፡ ቅድመ ። ድርብ ፡ ወይም ፡ ዐቢይ ፡ ሠረዝ ፥ በፍጹም ፡ ቃል ፡ ማኽል ፡ በንዳንዱ ፡ ፈርጅ ፡ (ፍራዝ) ፡ ውስጥ ፡ እየራሱ ፡ በሚታሰርና ፡ በሚነገር ፡ በስረጅና ፡ በፍራሽ ፡ ይገባል ። ምሳሌ ፤ ወምድርሰ ፡ ኢታስተርኢ ፤ ወኢኮነት ፡ ድሉተ ፤ ወጽልመት ፡ መልዕልተ ፡ ቀላይ ፤ ወመንፈስ ፡ እግዚ ፡ ይጹልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ። ወይቤ ፡ እግዚ ፤ ለይኩን ፡ ብርሃን ፤ ወኮነ ፡ ብርሃን ። ነዐ ፡ ንበር ፡ ማእከሌነ ፡ ወንግረነ ፤ እስመ ፡ ኪያከ ፡ አልሀቀ ፡ እግዚ ። ፈርሀ ፡ ወደንገፀ ፤ ባሕቱ ፡ ኢጐየ ፡ ወኢገገጸ ። ነጥብ ፡ (።) ንኡስ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ፤ አንባቢን ፡ እንደ ፡ ልጓም ፡ ኹኖ ፡ ይገታል ። አንዱ ፡ ፍጹም ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ ፈርጅ ፡ ዐዊርም ፡ ረዥምም ፡ ቢኾን ፡ ተሳቢው ፡ ተከቶ ፡ ነገሩ ፡ ሲጨረስ ፡ እንደ ፡ ጕልላት ፡ በመፉ ፡ በጥንፊጣው ፡ ይገባል ። ረዥም ፡ ቃል ፥ ወምድርስ ፡ እንዳል ነው ፡ ያለ ፡ ነው ። ዐዊር ፡ ቃል ፥ በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ። ያማርኛውም ፡ እንደ ፡ ግእዙ ፡ ነው ፤ ለብቻው ፡ የተለየ ፡ ዐዋጅ ፡ የለውም ።

፴፰ ፡ በነዚህ ፡ በራቱ ፡ ላይ ፡ ደማሞ ፡ . . . . . ነጠብጣብና ፡ ( ) ቀርን ፡ ‹‹ ›› አቅርንት ፡ ሲጨመሩ ፡ ቍጥራቸው ፡ ፯ ፡ ይኾናል ፡ የነዚህም ፡ የ፫ቱ ፡ አገባብ ፡ እንዲህ ፡ ነው ። ነጠብጣብ ፡ ከያንዳንዱ ፡ ምዕራፍና ፡ አንቀጽ ፡ ፍሬ ፡ ፍሬው ፡ ጥቅስ ፡ በጥፈት ፡ ሲለቀም ፡ በቀረው ፡ ቃል ፡ ፈንታ ፡ ይገባል ። ምሳሌ ፤ መጽሐፈ ፡ ልደቱ ፡ ለኢ ፡ ክር ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ወልደ ፡ አብርሃም ። አብርሃም ፡ ወለዶ ፡ ለይሥሐቅ ፡ . . . . ወእሴይ ፡ ወለደ ፡ ዳዊትሃ ፡ ንጉሠ ፡ . . . . ወኵሉንኬ ፡ ትውልድ ፡ እምአብርሃም ፡ እስከ ፡ ዳዊት ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአርባዕቱ ። ቀዳሚሁ ፡ ቃል ፡ . . . . ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ። ዳግመኛም ፡ በቋንቋ ፡ መጣፍ ፡ ውስጥ ፡ የተጣፈውን ፡ ቃል ፡ አንዱን ፡ ስም ፡ መላ

ልሶ ፡ በመጣፍ ፡ ፊንቃ ፡ በቀረው ፡ ፊደል ፡ ልክ ፡ ይገባል ። ምሳሌ ፤ ጎግ ፥ ማ . . ። ዳዊት ፥ መዝሙረ ፡ . . . ። አምላክ ፥ ወልደ ፡ . . . . ። ቀርን ፡ እንደ ፡ ዋዌና ፡ እንደ ፡ አው ፡ ነው ፤ ሞክሼና ፡ ባዕድ ፡ አስረጅ ፡ ወይም ፡ ተወላጅ ፡ ስለ ፡ ኹነ ፡ ተጥፎ ፡ በማይነበብ ፥ በ ፡ ዘይቤ ፡ በሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ በትርፍ ፡ ንባብ ፡ ይገባል ። ምሳሌ ፤ ወንጌል ፡ ብሂል ፡ በልሳነ ፡ ጽርእ ፤ ወትርጓሜሃ ፡ ስብከት ፡ (ብሥራት) ። እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ብሂል ፡ ቅቡዕ ፡ (መሲሕ) ። ፲፱፻፴፱ ፡ (፵፪) ፡ ዓ ፡ ም ፡ በግስም ፡ ሲገባ ፡ ጽሒፍ ፤ (ጸሐፈ ፡ ይጽሕፍ ፡ ይጽሐፍ) ፡ መጣፍ ፡ አጣጣፍ ። ጸሓፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ጸሐፍት) ፡ ያሰኛል ። አቅርንት ፡ ያንዱን ፡ ደራሲ ፡ ቃል ፡ ከሌላው ፡ ድርሰት ፡ ለመለየት ፡ ባለድርሳኑ ፡ ሌሎች ፡ ከደረሱት ፡ ከድርሳን ፡ ከተግሣጽ ፡ አብዝቶ ፡ አሳንሶ ፡ በሚጠቅሰው ፡ ቃል ፡ በጥቅስና ፡ በስሬጽ ፡ ይገባል ፤ ጥቅስና ፡ ስሬጽ ፡ የንባብ ፡ የምስጢር ፡ የድርሰት ፡ ማቅኛ ፡ ስለ ፡ ኹኑ ፥ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ምሳሌ ፤ ከመ ፡ ዝ ፡ ነአምን ፡ ወከመ ፡ ዝ ፡ ንትአመን ፤ ወንበል ፡ ጸሎተ ፡ ሃይማኖት ። «ነአምን ፡ በአሐዱ ፡ አምላክ ፡ . . . . ። ወንሴፎ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፤ ወሕይወተ ፡ ዘይመጽእ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም» ። ንግባእኬ ፡ ኀበ ፡ ጥንተ ፡ ነገር ።

፴፰ ፤ ጣፎችና ፡ ፀሓፊዎች ፡ የፊደላትን ፡ ዘር ፡ በብራና ፡ ማሕፀናቸው ፡ በወረቀት ፡ ሰፋድላቸው ፡ ከመምህራን ፡ እየተቀበሉ ፡ ፀንሰውና ፡ አምጠው ፡ በቀለም ፡ በብርዕ ፡ የሚወልዱት ፡ የጥፈትና ፡ የመጻሕፍት ፡ መልክ ፡ ድርሰቱ ፡ መድበሉ ፡ ከምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ይህ ፡ ነው ። ይህ ፡ የጣፍነው ፡ ኹሉ ፡ ስምና ፡ መልክ ፡ ቃትም ፡ ተጥፎ ፡ ተጠርዞና ፡ ታፍፎ ፥ ድጕሱና ፡ ማኅደሩ ፡ ተከናውኖ ፥ ግዙፉና ፡ ምእዙን ፡ ኹኖ ፡ ሥራው ፡ ከለቀለት ፡ በኋላ ፤ መጽሐፉ ፡ በጽላት ፥ ማኅደሩ ፡ በታቦት ፥ ዙሪያው ፡ በ፬ቱ ፡ ማእዝን ፡ ይመሰላል ። ከዚያውም ፡ ዘንድ ፥ ቀኙ ፡ የምሥራቅ ፡ ግራው ፡ የምዕራብ ፥ ራሱ ፡ የሰሜን ፡ እግሩ ፡ የደቡብ ፡ ፬ቱ ፡ ቀርን ፡ በነዚህ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የንኡስ ፡ ማእዝን ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

፴፱ ፤ ለንባቡም ፡ ትምርት ፥ ለስልቱና ፡ ለማዕርጉ ፡ እንዳሮቱ ፡ ጸዋትወ ፡ ዜማ ፡ ፫ ፡ ክፍል ፡ አለው ፡ ፩ኛው ፡ ቍጥር ፥ ፪ኛው ፡ ግእዝ ፥ ፫ኛው ፡ ወርድ ፥ ፬ኛው ፡ ዐቢይ ፥ ፫ኛው ፡ ድጋም ፡ ወይም ፡ ማንብንብ ፡ ይባላል ። እነዚህም ፡ ፫ቱ ፡ ክፍሎች ፡ ጸዋትወ ፡ ንባብ ፡ ተብለው ፡ ኹሉም ፡ በሕፃን ፡ አካኼድ ፡ ይመሰላሉ ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ መንኾቀቅ ፥ ግእዝ ፡ እንደ ፡ መዳኽ ፡ ነው ፡ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ በግር ፡ በሥንጥር ፡ ይነገራሉ ። ቍጥር ፡ በኖኅትና ፡ በኖኅት ፡ መከከል ፡ ያለውን ፡ የያንዳንዱን ፡ ፊደል ፡ ራስ ፡ ራሱን ፡ በግር ፡ እየነኩ ፥ ፩ ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹሉ ፡ ስም ፡ ስሙን ፡ ለይቶ ፡ መጥራት ፡ ነው ። ግእዝ ፥ ከነቍጥ ፡ እስከ ፡ ነቍጥ ፡ በያንዳንዱ ፡ ስኝ ፡ ያሉትን ፡ ፊደሎች ፡ እንደ ፡ መሠረዝ ፡ ግሩን ፡ በላያቸው ፡ እያሳለፉ ፡ በቅርብ ፡ በቅርቡ ፡ ማጋጠም ፡ ነው ። ወርድ ፥ ዘርፍና ፡ በለቤት ፡ ሳቢና ፡ ተሳቢ ፡ በማዘረፍና ፡ በማናበብ ፡ የሚወድቅና ፡ የሚነሣ ፡ የሚጠብቅና ፡ የሚላላ ፡ ቀለም ፡ ለይቶ ፡ በሐዘንዚን ፡ ቃል ፡ እየመኹና ፡ እያሊፉ ፡ እየተደገፉ ፡ ማንበብ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እጅን ፡ ተይዞ ፡ እቱ ፡ ሥግሬ ፡ ቃቱ ፡ ሥግሬ ፥ ወይም ፡ ዳዴ ፡ ዳዴ ፥ እንድ ፡ ኹሉት ፡ እየተባሉ ፡ በመኼድና ፡ በመራመድ ፥ በማንገር

ገር ፡ በመወናከር ፡ ይመስላል ። አቡጊዳና ፡ ወርድ ፡ ንባብ ፡ ለተማሪ ፡ በጣም ፡ ይጠቅማሉ ፡ እሊነዚህ ፡ እሊኹለቱ ፡ በፊደል ፡ በንባብ ፡ ቶሎ ፡ መሠልጠን ፡ አይቻልም ። ዐቢይ ፡ ንባብ ÷ ራስን ፡ ችሎ ፡ እየተቀናጡ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እንደ ፡ መኼድ ፡ ኹሉ ፤ በነቍጥ ፡ በሠረዝ ፡ የተለየውን ፡ ቃል ፡ ከነጥብ ፡ እስከ ፡ ነጥብ ፡ እንደሚገባው ፡ እያሰሙ ፡ እያሰ ማጡ ፡ ማንበብ ፡ ነው ። ድጋም ፡ ከደጋሚው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የማይሰማው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በሩጫ ፡ አከኼድ ፡ ይመስላል ። የሚጠብቅና ፡ የሚላላ ፡ ቀለም ፡ ያልነውም ፡ ልዩ ፡ ልዩነቱ ፡ በንባብ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ÷ በምስጢርም ፡ እንጂ ፡ መላላት ፡ የሥራ ውን ፡ ቀሊልነትና ፡ ገርነት ÷ መጥበቅ ፡ ግን ፡ ከባድነቱን ÷ ቡነይልና ፡ በግድ ፡ መኾ ኑን ፡ ያሳያል ። ከግእዝም ፡ ይልቅ ፡ ዐማርኛ ÷ ገደለ ፡ ሰበረ ÷ ዐረሰ ፡ ቈፈረ ÷ ዐጨደ ፡ ነቀለ ፡ እያሰኘ ፡ አጥብቆ ፡ ያሳያል ፤ ዕብራይስጥም ፡ እንዳማርኛ ፡ ነው ። ጸዋትወ ፡ ፊደል ፡ የተባለው ፡ የሰዋስውና ፡ የግስ ፡ መቅድም ፡ እስከዚህ ፡ ነው ።

## የታሪክ ፡ መርገፍ ፡ የመቅድም ፡ አጫዋች ።

### ውዳሴ ፡ ዕበዩ ፡ ወክብሩ ፡ ለብእሲተ ፡ ሰማይ ፡ ፊደል ፡ አርአያ ፡ ድንግል ።

፩ ፡ ንግባእኬ ፡ ኀበ ፡ ጥንተ ፡ ነገር ፡ ወባህል ፤ ወንሕትታ ፡ ከዕበ ፡ ለቅድስት ፡ ፊደል ÷ በዘዘ ፡ ዚአሁ ፡ አርአያ ፡ ወዘዘ ፡ ዚአሁ ፡ አምሳል ፡ እንዘ ፡ ኪያሃ ፡ ንሚስል ፡ ወናስተማስል ። በመኑ ፡ በአምሳለ ፡ መኑ ፡ ትትሚሰል ፡ ፊደል ፤ በምድረ ፡ ሎዛኑ ፡ ወዳቤር ፡ ሀገረ ፡ ሰዋስው ፡ ወመጽሐፍ ÷ ወሚመ ፡ በሲና ፡ ጉባኤ ፡ መላእክት ፡ አእ ላፍ ፤ አው ፡ በጽዮን ፡ ሀገረ ፡ ዳዊት ÷ ወእመ ፡ አኮ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቅድስት ፤ ጽዮ ንሰ ፡ ወሳሌም ÷ መካነ ፡ ርእሱ ፡ ለአዳም ÷ ወመክፈልተ ፡ ርስቱ ፡ ለሴም ፤ እስመ ፡ እም ጽዮን ፡ ይወፅእ ፡ ሕግ ፡ ወቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ። ፊደልሰ ፡ አሚን ፡ መሠረተ ፡ ነገር ፡ ወጥንት ፤ ወከልአኒሃ ፡ መጻሕፍት ፡ ሕንጻ ፡ ወንድቅ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ምግባር ፡ ወትሩፋት ። ሥረዊሃ ፡ ሥርወ ፡ ቀለማት ÷ ዐቃቂረ ፡ ፊውስ ፡ ወመድኀኒት ፡ ዘመሀሮ ፡ ለኖኅ ፡ አሐዱ ፡ እመላእክት ፡ ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ታቦት ፤ ወሥ ርወ ፡ ነገሩ ፡ ይቀውም ፡ በስምዐ ፡ ሠለስቱ ፡ ገጻት ፡ ከመ ፡ ሥርወ ፡ እሴይ ፡ ወዳዊት ። ሠናይትኬ ፡ ሠናይት ፡ እምኵሎን ፡ ሠናያት ÷ ላሕየ ፡ ፈጣሪ ፡ ሕያው ፡ ወሥን ፡ ኵሉ ፡ ፍጥ ረት ፡ እስመ ፡ ኍላቄሃ ፡ ዕሥራ ፡ ወክልኤቱ ፤ ወሱባዔሃኒ ፡ ፍጹም ፡ ሱባዔ ፡ ዕለት ፡ እም ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ማእገ ፡ እስከነ ፡ ሳብዕት ። አርአያሃኒ ፡ አዳም ፡ አርአያ ፡ ሥላሴ ፡ ቅድስት ፡ ወአምሳሊሃኒ ፡ ነዮሙ ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላት ÷ ወሰሌዳቲሃ ፡ ጽላት ። ጽሕፈታሂ ፡ መንክር ፡ ዘእ ግዚአብሔር ፡ ጽሕፈት ፡ በጸፍጸፈ ፡ ሰማይ ፡ ሳብዕ ፡ ሰሌዳ ፡ እሳት ፡ ወግብረታሂ ፡ ዕጹብ ፡ ግብረ ፡ መለኮት ፡ እምኀበ ፡ አልቦ ፡ ማየ ፡ ሕመት ። ታቦታ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ወደብተራሃ ፡ ሰብአ ፡ ትካት ። አዕማዲሃሰ ፡ ኖኅ ፡ ወሴም ፡ ካም ፡ ወያፌት ፡ ወምዕማዲሃ ፡ ነቢያት ፡ ወካ ህናት ። አርእስቲሃ ፡ አብርሃም ፡ ይሥሐቅ ፡ ወያዕቆብ ፡ አርእስተ ፡ አበው ፡ ቀደምት ፡ ወደመና ፡ ርእሳ ፡ ብሩህ ፡ መንፈሰ ፡ ትንቢት ። አረፋቲሃ ፡ ዘዕንቍ ፡ እአባነ ፡ ልብሰ ፡ አሮን ፡ ሕስት ፡ ወመሠረታ ፡ ዘጽድቅ ፡ ኩኑነ ፡ ሃይማኖት ፡ ወኩነኑ ፡ ክርስቶስ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ እብነ ፡ ርእስ ፡ ኵሉ ፡ ማእዘንት ፡ ዘመነንም ፡ ነደቅት ። ቅድስተ ፡

ቅዱሳን፡ አበው፡ ነቅዐ፡ ምስጢራት፡ ወመንበረ፡ ስብሐት፡ ድልው፡ እምአፈ፡ ደቂቅ፡ ወሕፃናት ። ዝልንቃሃ፡ ወርቅ፡ ተቀሥጦ፡ ማኅቶት፡ ወመድሎተ፡ ወርቃ፡ ጽሩይ፡ መጠን፡ መክሊት፡ አስጸፌቂሃኒ፡ አዕጹቀ፡ ዘይት፡ አምሳለ፡ ሰብዐቱ፡ ሀብታት፡ ወመሰውሪሃ፡ አእላፍ፡ ብሩሃን፡ አልባብ፡ ጳሕፍት ። ጸዳለ፡ ብርሃና፡ ወሥና፡ ብዝኀ፡ ትምሀርት፡ ወብርሃናስ፡ ውእቱ፡ ገባሬ፡ ብርሃናት፡ ዐበይት፡ ዘበጸዳሉ፡ ብርሃኑ፡ ሰሰለ፡ ጽልመት ።

፺፩፡ ጥብልልተ፡ ራእዩ፡ ወኑእሙ፡ ለበላዔ፡ መጽሐፍ፡ ሕዝቅኤል፡ ወስቴ፡ ጽዋዑ፡ ለዕዝራ፡ ደመ፡ ሕብረ፡ እሳት፡ አስከለ፡ ዘያወዒ፡ ልበ፡ ወያንበለብል ። ይእቲኬ፡ ድንግል፡ ወላዲት፡ ቃል፡ በብሥራተ፡ መልአክ፡ ገብርኤል፡ መዋበቢተ፡ አብዳን፡ ሞሎት፡ ወሰብአ፡ ሰገል፡ እለ፡ ውስተ፡ ዓለም፡ ጎል፡ እስመ፡ ሀላዌሁ፡ ሊቃል፡ ሀላዌ፡ ፊደል፡ በከመ፡ ተነበየ፡ ዳንኤል፡ ወፈከረ፡ ላቲ፡ በብዙኅ፡ አምሳል ። ወኮከባኒ፡ ቃው፡ ጽዱል፡ ኮከበ፡ ወንጌል፡ ዘቦቱ፡ ትእምርተ፡ መስቀል ። አበዊነሂ፡ ይብልዋ፡ በዘአበዊሆሙ፡ ባህል፡ ወሰቱ፡ ለሄኖስ፡ ንእስተ፡ አካል፡ ወእኅተ፡ አበሁ፡ ለመላልኤል ። ፍኅርቱ፡ ለያሬድ፡ ልሂቅ፡ ብሉየ፡ መዋዕል፡ ወመፅመርተ፡ ብርዑ፡ ለሔኖክ፡ ጸሓፊ፡ ጥበቡ፡ ለልዑል ። ሱታፌ፡ ንበቡ፡ ወቃሉ፡ ለማቱሳላ፡ በዕል፡ ወፍቅርተ፡ ላሜሕ፡ ወኖኅ፡ ወራዙተ፡ ኀይል ።

፺፪፡ ልህቅት፡ ይእቲ፡ እምሰብዓ፡ ሊቃናት፡ ወብሊት፡ ዘእምቅድመ፡ ብሉይ፡ ኦሪት ። ሐፃኒተ፡ሙሴ፡ ሕፃን፡ ዘአኮ፡ ይብስተ፡ አጥባት፡ ወጥልልተ፡ ርሥአን፡ ዕቤርት፡ እሞን፡ ለዕቤራተ፡ ሕግ፡ መጻሕፍት፡ ወለአዋልድ፡ ንኡሳት፡ በከመ፡ ትብሀለ፡ ስሳ፡ እማንቱ፡ ንግሥታት፡ ወሰማንያ፡ ዕቁባት፡ አዋልድስ፡ እለ፡ አልቦን፡ ኍልቍ፡ ወመስፈርት ። ወላዲቱ፡ ለጥበብ፡ ሕያው፡ ወላዴ፡ ሕይወት፡ ወእምሔውቱ፡ ለነገረ፡ ዝሉን፡ በሓውርት ። ጽዕዳዌ፡ ሥዕርታ፡ ክርስቶስ፡ ቅቡዐ፡ መንፈስ፡ ከመ፡ ፀምረ፡ በግዕ፡ ጌዴዎን፡ ወከመ፡ ሚላት፡ ፍሑስ፡ ወቂሐት፡ ገጻ፡ ልሁብ፡ መንፈስ፡ ጸጋሁ፡ ለአብ፡ መስተፍሥሔ፡ ልብ ። ድምድማሃ፡ ድሉል፡ በመሥዕርተ፡ ብርዕ፡ ወሕብረ፡ ቀለማ፡ ጸሊም፡ ከመ፡ ሕብረ፡ ቋዕ፡ ወቀይሕ፡ ከመ፡ ደመ፡ በግዕ ። በእንተ፡ ዝ፡ ትልሒ፡ እምዐሓይ፡ ወእምኵሉ፡ ንብረተ፡ ከዋክብት ። እንዘ፡ ምስለ፡ ብርሃን፡ ትትቃወም፡ ትትረከብ፡ ከመ፡ ቀዳማዊት፡ ወእንዘ፡ በርሥእ፡ ሀለወት፡ ኵሎ፡ ትሔድስ፡ ወለትውልደ፡ ትውልድ፡ ውስተ፡ ነፍሰ፡ ጻድቃን፡ ትትፋለስ ።

፺፫፡ ይእቲ፡ ትኑዩስ፡ እምዕንቍ፡ ክቡር፡ ወኵሉ፡ ክብር፡ ኢመጠና ። ላቲ፡ ምክር፡ ወዕዘዝ፡ ወላቲ፡ ጽንዕ፡ ወአእምሮ ። ብቲ፡ ነገሥት፡ ይነግሡ፡ ወብቲ፡ ኀያላን፡ ይጽሕፉ፡ ጽድቀ ። ብቲ፡ ዐቢያን፡ ይከብሩ፡ ወብቲ፡ መኳንንት፡ ይእኅዙ፡ ምድረ ። እለ፡ ያፈቅርዋ፡ ታፈቅር፡ ወእለ፡ የዐቅብዋ፡ ተዐቅብ፡ ወእለ፡ የኀሥሥዋ፡ ላቲ፡ ይረክቡ፡ ሞገሰ ። ውስተ፡ ፍናወ፡ ጽድቅ፡ ታንሶሱ፡ ወውስተ፡ አሠረ፡ ጽድቅ፡ ትትመየጥ፡ ከመ፡ ተሀበሙ፡ ለእለ፡ የአምርዋ፡ ጥሪተ፡ ወመዛግብቲሆሙ፡ ከመ፡ ትምላእ፡ ተድላ ። ዘኵሎ፡ የአምር፡ ውእቱ፡ የአምራ፡ ወዘኵሎ፡ ይመልክ፡ ውእቱ፡ አሠነየ፡

ፍኖታ ። ውእቱ ፡ ወሀበ ፡ ለሄኖስ ፡ ቀኖልዔሁ ፡ ወለቃይናን ፡ ቅዱሱ ። ወእምዝ ፡ አስተርአየት ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤ ወአንሶሰወት ፡ ውስተ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ። ናሁ ፡ ሐነጸት ፡ ላቲ ፡ ቤተ ፤ ወአቀመት ፡ ሰብዐተ ፡ አዕማደ ። ዘብሐት ፡ ዘዚአሃ ፡ ጥብሐ ፥ ወቶስሐት ፡ ውስተ ፡ ስያሓ ፡ ዘዚአሃ ፡ ወይነ ፤ ወአስተዳለወት ፡ ዘዚአሃ ፡ ማእደ ። ወፈነወት ፡ ዘዚአሃ ፡ አግብርተ ፡ በነዋኅ ፡ ስብከት ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ዘአብድ ፡ ውእቱ ፡ ይትገሐሥ ፡ ኀቤየ ፤ ወለእለሂ ፡ የሐጽሙ ፡ አእምሮ ፡ ትጼውዕ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፥ ንዑ ፡ ብልዑ ፡ ኅብዝትየ ፡ ወስተዩ ፡ ወይንየ ፤ ወኅድግዋ ፡ ለእበድ ፡ ወሕየዉ ። ፊደልሰ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘለክአ ፡ ወእደ ፡ መንፈሱ ፡ ቅዱስ ፡ ዘአስተናበሮ ፡ ወሡርያ ፥ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ይኩን ፡ ስፉሐ ፡ ሰሌዳ ፡ ተሰብአ ፥ ወምስለ ፡ ኃጥኣን ፡ ይትኌለቍ ፡ በሱባዔ ፡ ኅሉት ፡ ተኰርያ ፥ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አልፋ ፡ ወዖ ፤ በበ ፡ ስብዕ ፡ ስብዐ ፡ እንበለ ፡ አጽርያ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ትውልድ ፡ ያስተበፅዖ ፥ በአሐዱ ፡ ቃለ ፡ አውሥኦ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እግዚኦ ፡ እግዚኦ ። ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአኰቴት ፡ ዕበይ ፡ ወበርከት ፥ ውዳሴ ፡ ወማሕሌት ፤ ክብር ፡ ወብዕል ፡ ዕዘዝ ፡ ወኀይል ፡ ለልዑል ፡ ወሃቤ ፡ ፊደል ፤ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ። ወለእለሂ ፡ ነሥእዋ ፡ እምኔሁ ፡ በአሚን ፡ ከመ ፡ ጽላተ ፡ ሕግ ፡ ወኪዳን ፡ ወከመ ፡ ቅዱስ ፡ ቍርባን ፥ ለርእሰ ፡ ነቢያት ፡ ሄኖስ ፡ ወለበኵረ ፡ ነገሥት ፡ ቃይናን ፤ እስመ ፡ ከመ ፡ ሙሴ ፡ ወአሮን ፡ ክቡዳን ፡ ክልኤ ፡ አቅርንት ፡ ወአምርሕተ ፡ ሠናይ ፡ ፍኖት ፡ ለዕዉራን ፡ ልብ ፡ ሰብአ ፡ ትካት ። ፍኖትሰ ፡ ፊደል ፡ ዕንስተ ፡ ወንጌል ፥ ወስፍሕተ ፡ ማሕፀን ፡ ትንቢት ፡ ለወሊደ ፡ ተስፉ ፡ ሥግው ፡ እምኑልቄ ፡ ዕሥራ ፡ ወክልኤቱ ፡ ዘመደ ፡ ፍጥረት ፡ አበው ፥ ወእምዝርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ሰዋስው ።

## ዐዋርና ፡ ቍርጫኝ ፡ ሰዋስው ፡

የመምህራን ፡ ዐይን ፡ ያዕቆብ ፡ እንደ ፡ ረኸርሙ ፡ አጥርቶና ፡ ቀምሎ ፡
ያላየው ፥ ቀርበም ፡ እንደ ፡ ሐኪም ፡ ያልዳሰሰውና ፡ ያልፈወሰው ።

ሰዋስው ፡ ማለት ፡ ዘይቤው ፡ መሰላል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እሙን ፡ ትርጓሜው ፡ ግን ፡ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ዐዋጅ ፥ ያሰክኩና ፡ ያጣጣፉ ፡ ያነጋገሩ ፡ ፈርጅ ፥ የንበቡ ፡ ኹሉ ፡ እጅና ፡ ፍንጅ ፥ አስተሳሰሩና ፡ አፈታቱ ፡ ተለይቶ ፡ የሚታወቅበት ፡ የትምርት ፡ ደንብ ፡ ፍርድና ፡ አገባብ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹሉ ።

አገዘመሩ ፡ ታኳደዱ ፡ ሲሰበሰብ ፡ ብዙው ፡ አገዳ ፡ ፩ ፡ እስር ፡ ነዶ ፥ ብዙው ፡ ነዶ ፡ ፩ ፡ ሙሉ ፡ ዕቅፍ ፥ ብዙው ፡ ዕቅፍ ፡ ፩ ፡ ጕቾ ፥ ብዙው ፡ ጕቾ ፡ ፩ ፡ ታላቅ ፡ ክምር ፡ እንዲኾን ፡ የሰዋስውም ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ምዕራፍ ፡ በታላቅ ፡ ክምር ፡ ይመሰላል ። ብዙው ፡ ብትን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ በየወገኑና ፡ በያይነቱ ፡ ሲሰበሰብና ፡ ሲለቀም ፡ ነዶውና ፡ ዕቅፉ ፡ ጕቾው ፡ በ፫ ፡ ዐይነት ፡ ቍጥር ፡ ተቈጥሯል ፡ ብትኑ ፡ ቃል ፡ በነዶው ፡ ቍጥር ፥ ነዶው ፡ ቃል ፡ በዕርከን ፥ ዕርከንም ፡ በዐቢይ ፡ ክፍል ፡ ተጠቅልሎ ፡ ፯ ፡ ብቻ ፡ ኹኗል ። በየንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ አርእስተ ፡ ቃል ፡ ንኡስ ፡

ክፍል ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ዕርከን ፡ ተብሏል ፤ ፩ ፡ ክፍል ፡ ትምርት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ፩ ፡ ሙሉ ፡ ዕቅፍ ፡ እንደ ፡ ማለት ። ከ፯ቱ ፡ ደግሞ ፡ ፬ቱና ፡ ፫ቱ ፡ አንዳንድ ፡ ወገን ፡ ኹነው ፡ በ፪ ፡ ምዕራፍ ፡ ይከፈላሉ ፤ ክፍላቸውና ፡ ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ።

## የሰዋስው ፡ ክፍሎች ፡ ስምና ፡ ተራ ።

### መግመሪያ ፡ ምዕራፍ ፡ ባላ፬ ፡ ክፍል ።

፩ኛ ፡ ክፍል ፡ ጸዋትወ ፡ ቅምር ፡ ባለብዙ ፡ ሕብር ።
፪ኛ ፡ ክፍል ፡ ጸዋትወ ፡ ርባ ፡ የሰዋስው ፡ ሆድና ፡ ገርባ ።
፫ኛ ፡ ክፍል ፡ ጸዋትወ ፡ ጥሬ ፡ የርባታ ፡ ቅንጣትና ፡ ፍሬ ።
፬ኛ ፡ ክፍል ፡ ጸዋትወ ፡ ቅጽል ፡ ባለቤት ፡ አከል ።

### ፪ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ባለ፫ ፡ ክፍል ።

፭ኛ ፡ ክፍል ፡ ጸዋትወ ፡ ንባብ ፡ ሳቢና ፡ ተሳቢ ፡ ተናባቢ ።
፮ኛ ፡ ክፍል ፡ ጸዋትወ ፡ አገባብ ፡ የዘርና ፡ የነባር ፡ ሕንባብ ።
፯ኛ ፡ ክፍል ፡ ጸዋትወ ፡ ቅኔ ፡ የሠምና ፡ የወርቅ ፡ ኵርጓኔ ።

### ፫ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ጸዋትወ ፡ ግስ ፡
### ባለ፳፮ ፡ ክፍልና ፡ ራስ ፡ ከአ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ድረስ ።

ጸዋትውም ፡ ማለት ፡ ኅዝና ፡ ወገን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ጸዋትወ ፡ ቅዳሴ ፡ እንዲሉ ።　ያጭሩ ፡ ሰዋስው ፡ ልክና ፡ መልክ ፥ ወርዱና ፡ ቁመቱ ፡ አርእስቱ ፡ ይህ ፡ ነው ። የቀረውን ፡ በየነዶውና ፡ በየቅፉ ፡ በየጕቾው ፡ ቃል ፡ ተመልከት ፤ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ላንዱ ፡ መቅድምና ፡ አርእስት ፡ እየኾነ ፡ ሰዋስውነቱን ፡ ሰንሰለት ፡ አድርጎ ፡ ያሳይ ኻል ።　ከዚህም ፡ ሰዋስው ፡ የቀረውን ፡ ረኃርም ፡ ትምርት ፡ ኅሊናችን ፡ ዐጥሮ ፡ ስላልደረሰበት ፡ ለኋላ ፡ ልጆች ፡ ትተነዋል ፡ (ማቴ፯ ፡ ፯ና ፡ ፰) ።

### መግመሪያ ፡ ምዕራፍ ፡ ባለ፬ ፡ ክፍል ፡ ጎረ ፡ ቤተ ፡ ወንጌል ።

### ፩ኛ ፡ ክፍል ።

### የሰዋስው ፡ ዐዋጅ ፡ ርባ ፡ ቅምር ።

የፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ዐይነት ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያውም ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ተባትና ፡ እንስት ፡ እንዲባል ፡ ሰዋስው ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ የቋንቋም ፡ ዐይነት ፡ ፪ ፡ ነው ፡ ዘርና ፡ ነባር ፥ ወይም ፡ ስምና ፡ ግብር ። ወንድና ፡ ተባት ፡ ሴትና ፡ እንስት ፡ አንዳ ንድ ፡ ወገን ፡ ኹነው ፡ በ፪ነት ፡ እንዲታዩ ፥ እነዚህም ፡ ፬ቱ ፡ ስሞች ፡ ዘርና ፡ ግብር ፡ ነባ ርና ፡ ስም ፡ አንዳንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ፪ኛም ፡ የመሰላል ፡ ዕርከን ፡ ብዙ ፡ ሲኾን ፡ በ፪ ፡ አዕማድ ፡ እንዲወሰን ፡ የቋንቋም ፡ ትምርት ፡ ስሙና ፡ ክፍሉ ፥ ስልቱና ፡ ባህሉ ፡ ብዙ ፡ ሲኾን ፡ ዐይነቱና ፡ ሕብሩ ፡ አርእስተ ፡ ነገሩ ፡ በነዚህ ፡ በ፪ቱ ፡ ብቻ ፡ ተወስኗል ፡ ከስ ምና ፡ ከግብር ፡ አይወጣም ። ሲዘረዘሩ ፡ ግን ፡ እንቀጽና ፡ ርባታ ፡ ዝርዝር ፥ ቅጽልና ፡

ጥሬ ፥ አገባብ ፥ ሠምና ፡ ወርቅ ፥ ሙሻዘር ፥ ሠረዝ ፥ እንጻር ፡ ተብለው ፡ ፲ ፡ ይኾናሉ ፡ ዝርዝር ፡ ከርባታ ፥ አገባብ ፡ ከጥሬ ፡ ሲደረቡ ፡ ግን ፡ ፰ ፡ ብቻ ፡ ኹነው ፡ ይቀራሉ ። የሰዋስውን ፡ ክፍል ፡ ዝቅ ፡ ብለው ፡ ፫ና ፡ ፬ ፡ ፯ ፥ ከፍ ፡ ብለው ፡ ፲፪ና ፡ ፲፫ ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

## መዠመሪያ ፡ ዕርከን ፡ ወይም ፡ ቀዳማይ ።

## የዘርና ፡ የነባር ፡ ጠባይ ።

### ዘር ።

፩ ፡ ነጠላ ፡ ግስን ፡ ከነርባው ፡ የሚያስገኝ ፥ ጥሬ ፡ ዘርን ፡ ኹሉ ፡ የሚወልድ ፡ በሊሰ ፡ ሰተየ ፡ ጸጊብ ፡ ሰከረ ፡ መዊት ፡ ሐዩው ፡ እያለ ፡ በሦስት ፡ ፊደል ፡ በቅሉ ፡ የሚኼድ ፥ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኀጠተ ፡ ቃል ፥ አባት ፡ ዘር ፡ ይባላል ፤ አባትነቱም ፡ አዳምን ፡ ይመስላል ። አባት ፡ ዘር ፥ ርሱ ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ሥር ፡ ኹኖ ፡ ሌላውን ፡ ፍሬ ፡ ቃል ፡ ቢያስገኝ ፡ እንጂ ፡ ለርሱ ፡ አስገኝና ፡ አባት ፡ የለውም ። ፪ኛም ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ መሠረተ ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ አርእስት ፡ ይባላል ። ፫ኛም ፡ ዐጕል ፡ አንቀጽ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ንኡስ ፡ ይባላል ። ስሞቹ ፡ እንደ ፡ ፊደሎቹ ፡ ፫ ፡ ናቸው ፤ አባት ፡ ዘር ፥ አርእስት ፥ ንኡስ ፡ አንቀጽ ።

፪ ፡ ዘር ፡ በቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ የግስ ፡ ጥንት ፡ የርባ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ከአናቅጽ ፡ በፊት ፡ ይጣፋል ፤ ከርባታ ፡ በፊት ፡ ይነገራል ። ጣፊም ፡ አንባቢም ፡ ወንጌል ፡ ዘዮሐንስ ፡ ሳይል ፡ ቀዳሚሁ ፡ ቃል ፡ እንዳይል ፡ አርእስትን ፡ በጥፈትም ፡ በመነገርም ፡ ንባብ ፡ እንዳይቀድመው ፥ ዘርንም ፡ አንቀጽና ፡ ጥሬ ፡ አይቀድሙትም ። የዚህ ፡ መጽሐፈ ፡ ግስ ፡ ቀዋሚ ፡ ግብሩ ፡ ደገኛ ፡ ነገሩ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እናት ፡ ዘር ፡ ሳትቀበል ፡ እንዳትፀንስ ፡ ርሱም ፡ ዘር ፡ ሳያስቀድም ፡ አንቀጽ ፡ አይጥፍም ። ምንጩን ፡ አሳይቶ ፡ ውሃውን ፥ ዛፉን ፡ አሳይቶ ፡ ፍሬውን ፡ እንደ ፡ መስጠት ፡ ኹሉ ፥ ዘሩን ፡ በፊት ፡ አንቀጹን ፡ በኋላ ፡ ያመጣዋል ፤ ባፈ ፡ ታሪክም ፡ የቀድሞ ፡ መምህራን ፡ ዘር ፡ ሳያስቀድሙ ፡ አይገሱም ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

፫ ፡ ዘር ፡ መባሉም ፡ በምሳሌ ፡ ነው ፡ ዘር ፡ በዘሩት ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ቅንጣት ፡ ብዙ ፡ ቅንጣቶች ፡ እንዲያፈራ ፥ ንኡስ ፡ አንቀጽም ፡ በረቡትና ፡ በገሰሱት ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ቃላት ፡ ያፈራልና ፤ ስለዚህ ፡ ዘር ፡ ተባለ ፡ (ዮሐ ፲፪ ፡ ፳፬) ። በዕብራይስጥም ፡ ሾሬሽ ፡ ምቆር ፡ ይባላል ፤ ሥርው ፡ ነቅዕ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዘር ፡ ከማለት ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ። አማናዊው ፡ የባሕርዩ ፡ ስሙ ፡ ግን ፡ ግብር ፡ ይባላል ፤ ግብርነቱም ፡ ሠራተኛው ፡ ያልታወቀለት ፥ ለሠራተኛ ፡ ያልተሰጠ ፥ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚሰጥ ፥ በኋላፊና ፡ በትንቢት ፡ መካከል ፡ የቆመ ፡ ዐጕል ፡ ማእከላዊ ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ ከባት ፡ ዘር ፡ የሚገኝ ፡ ጥሬ ፡ ዘር ፥ ስምና ፡ መስም ፥ ርሱም ፡ እንዳባቱ ፡ ሲገሰስ ፥ ዘርነቱ ፡ ወዳንቀጽነት ፡ ተለውጦ ፡ ጥሬ ፡ ግስ ፡ ይኾናል ። ከባቱ ፥ አባት ፡ የመሰለ ፡ የ፫ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ እንዲገኝ ፥ ከጥሬውም ፡ ጥሬ ፡ የመሰለ ፡ ይገኛል ፤ አገኛኘቱንም ፡ በግስ ፡ አርእስት ፡ ውስጥ ፡ ባ፵፬ ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት ።

፬ ፡ በ፫ ፡ ፊደል ፡ እግር ፡ የቆሙ ፡ ዘርና ፡ ግስ ፡ የሚነሡባቸው ፡ ፊደላት ፡ ወይም ፡ ቀለማት ፡ ፭ ፡ ናቸው ፡ በላገባቦች ፡ መራኁት ፡ ይኋቸዋል ፡ መክፈቾች ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ እሊሁም ፡ ግእዝ ፡ ራብዕ ፡ ኃምስ ፡ ሳድስ ፡ ሳብዕ ፡ ናቸው ፡ ዘርና ፡ ግስ ፡ በነዚህ ፡ ብቻ ፡ ቢነሡ ፡ እንጂ ፡ በካዕብ ፡ በሣልስ ፡ አይነሡም ፡፡ የዘርና ፡ የግስ ፡ አነሣሥ ፥ አከኻኼድና ፡ አጕዛገዝ ፡ እንደ፡ት ፡ እንደ ፡ ኹነ ፡ በግስ ፡ አርእስት ፡ ተመልከት ፡፡ የዘር ፡ መድረሻ ፡ ወይም ፡ መጨረሻ ፡ ፪ ፡ ናቸው ፡ ሳድስና ፡ ሳብዕ ፥ ይህም ፡ ነዌም ፡ ነቂህ ፥ ሰብሐ ፡ ዘምሮ ፡ እያለ ፡ በነዚህ ፡ ብቻ ፡ መድረሱን ፡ ያሳያል ፡፡ ግስ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ዘር ፡ ቢሳ፭ ፡ መነሻ ፡ ቢኾን ፥ በላንድ ፡ መድረሻ ፡ ነውና ፡ ቀደሰ ፡ ባረከ ፡ ሤመ ፡ ጦሕረ ፡ ሖረ ፡ እያለ ፡ በግእዝ ፡ ብቻ ፡ ይጨርሳል ፡ ይኸውም ፡ የሩቅ ፡ ወንድ ፡ አንቀጽ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡ ግእዝ ፡ የሩቅ ፡ ዝርዝር ፡ ነውና ፡፡ ሲረባና ፡ ሲዘረዘር ፡ ግን ፡ ከኃምስ ፡ በቀር ፡ በሌሎቹ ፡ ኹሉ ፡ ይጨርሳል ፡፡

፭ ፡ አባት ፡ ዘር ፡ ከ፫ቱ ፡ ልጆቹ ፡ (ቀዳማይ ፡ ካልኣይ ፡ ሣልሳይ) ፡ ከዐበይት ፡ አና ቅጽ ፡ በኋላ ፡ ፬ና ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ኹኖ ፥ ቀቲል ፡ ቀቲሎት ፥ ቀድሶ ፡ ቀድሶት ፥ ባርኮ ፡ ባርኮት ፥ ብሂል ፡ ብሂሎት ፡ እያለ ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ መነገሩና ፡ ምእላድ ፡ ፊ ደል ፡ ትን ፡ እየጨመረ ፡ መኼዱ ፥ ለመዘርዘርና ፡ ለማዛረፍ ፡ ለማብዛትና ፡ ለማብለጥ ፡ ንባብ ፡ ለማስጌጥ ፡ ነው ፡፡ በዝርዝር ፡ ጊዜ ፥ ቀቲልሁ ፡ ቀቲሎቱ ፥ ቀድሶሁ ፡ ቱ ፥ ባር ከሁ ፡ ቱ ፥ ብሂልሁ ፡ ብሂሎቱ ፡ ቢል ፡ እንጂ ፥ ቀቲሉ ፡ ቀድሱ ፡ ባርኩ ፡ ብሂሉ ፡ ብሎ ፡ በዘመድ ፡ አይዘረዝርም ፤ ይህ ፡ በሊ ፡ ሲያዝርፍ ፡ ነው ፡፡ በዘና ፡ በግእዝ ፡ ሲያዛርፍ ፡ ግን ፡ እንዳለ ፡ ይገባል ፤ ይህም ፡ ቀቲል ፡ ዘዳዊት ፥ ዘዳዊት ፡ ቀቲሎት ፥ ቀቲለ ፡ ዳዊት ፡ ቀቲሎተ ፡ ዳዊት ፡ ጎልያድህ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ፡፡ ባላገባቦችም ፡ ለብ ሂል ፡ ለ ፡ የለው ፥ ለብሂሎት ፡ ዘ ፡ የለው ፡ ብለው ፡ ያውጃሉ ፤ ይህም ፡ ብሂሉ ፡ ለዳ ዊት ፥ ብሂሎት ፡ ዘዳዊት ፡ አለማለቱን ፡ ያሳያል ፡ በብሂል ፡ ኹሉን ፡ መናገር ፡ ነው ፡፡ ሲያበዛና ፡ ሲዘረዝርም ፥ ህልዎታት ፡ ህልዎታቱ ፡ ቲሁ ፡ ያሰኛል ፡፡

፮ ፡ ዘር ፡ ጥንቱን ፡ ሲፈጠር ፡ ሲቃኝጽ ፡ ሲቀረጽ ፡ ከ፫ ፡ ፊደል ፡ ባሕርይ ፡ መገኘ ቱና ፡ በ፫ ፡ ፊደል ፡ ብቻ ፡ መመሥረቱ ፥ ወደ ፡ ፪ና ፡ ወዳ፬ ፡ አለመውረድ ፡ አለመው ጣቱ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ብትል ፡ እግዚር ፡ በ፮ና ፡ ቀን ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርኣያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ ብሎ ፡ አዳምን ፡ ሲፈጥር ፡ ቋንቋውንም ፡ አርኣያና ፡ አምሳል ፡ አድርጎታ ልና ፥ ስለዚህ ፡ ነው ፡፡ ይኸውም ፡ እኑ ፡ ውእቱ ፡ አልፋ ፡ ወዖ ፡ ወይም ፡ አሌፍ ፡ ወታው ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ፡ (ራእሽ፪ ፡ ፲፫) ፡፡ ኋላም ፡ በባቢሎን ፡ ንዑ ፡ ንረድ ፡ ወንክዐው ፡ ህየ ፡ ነገሮሙ ፡ ከመ ፡ ኢይስማዕ ፡ ብእሲ ፡ ከንፈረ ፡ ቢጹ ፡ ብሎ ፡ የልጆቹን ፡ ቋንቋ ፡ ሲለያይ ፡ ይህ ፡ የአዳም ፡ ቋንቋ ፡ በሴም ፡ ብቻ ፡ ቀርቷል ፡ (ዘፍ፲፩ ፡ ሸ፯ ፡፡ ፲፩ ፡ ፯) ፡፡ በሴም ፡ ዘር ፡ የቀረ ፡ ቋንቋው ፡ ብቻ ፡ አይዶለም ፡ ተስፋውና ፡ ሃይማኖቱም ፡ እንጂ ፡፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ ዘሩ ፡ ሥረ ፡ ነገሩ ፥ ዋሕደ ፡ ቃል ፡ ሥሉስ ፡ ፊደል ፡ እየ ኾነ ፡ በ፫ ፡ ፊደላት ፡ ተወስኗል ፡ ከ፫ ፡ ቅንጣት ፡ ፊደል ፡ አይወጣም ፡ ወደ ፡ ፪ ፡ ፊደል ፡ አይወርድም ፡፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ፊደሉ ፡ አርኣያ ፡ አካላት ፥ ቃሉ ፡ አምሳለ ፡ መለኮት ፡ ተብሏል ፡፡

፺፯ ፡ ግእዝም ፡ ከላይ ፡ ከአዳም ፡ የነቃ ፡ ከቃችም ፡ ከኖኅ ፡ የፈለቀ ፡ ሴማዊና ፡ አዳማዊ ፡ ቋንቋ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ዘሩን ፡ በኖኅ ፡ ልጆች ፡ አምሳል ፡ ሲሰፍርና ፡ ሲቈጥር ፡ ከ፳ ፡ ፊደላት ፡ አያበልጥም ፤ አያሳንስም ። ቀቲል ፡ ገቢር ፥ ቀዊም ፡ ሐዊር ፥ ማርር ፡ ሐድሶ ፥ ሐውጾ ፡ ገሥጾ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ወንድሞቹ ፡ እንዳረብና ፡ እንደ ፡ ሱርስት ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ በ፳ ፡ ፊደላት ፡ ይኼዳል ።

«ዋዜማ ፡ ዘሰሚቱ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ።

አካልከ ፡ ነጋዴ ፡ ሕግ ፡  
ለአጥርዮ ፡ ሕማም ፡ ሲሳዩ ፡ ውስተ ፡ ቀራንዮ ፡ ወረደ ፤  
ጊዮርጊስ ፡ መብረቀ ፡ ስባሔ ፡ ዘትጸውር ፡ ነደ ።  
ወበውስተ ፡ ዓለም ፡ ይዝራዕ ፡ ገቢረ ፡ ተአምር ፡ ዘመደ ፡  
ክሣድከ ፡ ኖኅ ፡ ሠለስተ ፡ ወለደ ፤  
ወበእሉ ፡ አ.ወሰከ ፡ ባዕደ» ።

፺፰ ፡ መጻሕፍት ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ሲመለሱ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የገባ ፡ የሳባ ፡ የኖባ ፥ የጽርእ ፡ የቅብጥ ፡ ቃል ፡ የኋላ ፡ ቅጥል ፡ ከልኾነ ፡ በቀር ፥ ከለዳዊና ፡ ዮቅጣናዊ ፡ ሕምያራዊ ፡ ለሚባለው ፡ ለጥንታዊው ፡ ግእዝ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። ኋላ ፡ ግን ፡ በታደሰ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ባዕድ ፡ ቋንቋ ፡ ገብቶበታል ፤ ባዕድ ፡ የተባለም ፡ የከምና ፡ የያፌት ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ከ፳ ፡ ከ፴ ፡ ቢከፈል ፡ ነቁ ፡ ሥር ፡ መሠረቱ ፡ እንደ ፡ ምንጭ ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ እንደ ፡ ሕንጻ ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ርስ ፡ በርሱ ፡ ይስማማልና ፤ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ዘመድ ፡ እንጂ ፥ ባዕድ ፡ አይባልም ። የጐደለውንም ፡ አንዱ ፡ ከንዱ ፡ ቢወስድ ፡ ብድር ፡ አይኾንም ፥ ገንዘቡ ፡ ነውና ፤ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ ወንድም ፡ እኅት ፡ ወዳጅ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ እያለ ፡ ከባዕድ ፡ መበደር ፡ አይገባም ፥ ቃላቅ ፡ ስንፍና ፡ ነው ፡ ሳይቸገሩም ፡ መበደር ፡ ዝሙት ፡ ይባላል ።

ነባር ።

፺፱ ፡ ዘርነት ፡ የሌለው ፥ ከዘር ፡ ከአንቀጽ ፡ የማይገኝ ፡ የቋንቋ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ እየ ኾነ ፡ በውጥንቅጥንት ፡ የሚገኝ ፡ ጥሬ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ነባር ፡ ይባላል ፤ ትርጓሜውም ፡ የማይፈልስ ፡ የማይናወጥ ፡ የማይጠፋ ፡ የማይለወጥ ፡ ስም ፡ ማለት ፡ ነው ። ከነባር ፡ የሚገኝ ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ አይዶለም ፥ አንቀጽና ፡ አገባብም ፡ እንጂ ፡ ከዘሩ ፡ ዘር ፡ የመሰለ ፡ አንቀጽ ፡ እንዲገኝ ፥ ከነባሩም ፡ ነባር ፡ የመሰለ ፡ ይገኛል ። ካባት ፡ ዘር ፡ የሚገኝ ፡ ጥሬ ፡ ዘር ፥ አንቀጽ ፡ እየኾነ ፡ እንዲገሰስ ፡ ግስነቱም ፡ ዲቃላ ፡ እንዲባል ፥ ከነባርም ፡ ጥሬ ፥ አንቀጽ ፡ እየኾነ ፡ የሚገሰስ ፡ ብዙ ፡ ስም ፡ አለ ፤ ነባር ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ዘር ፡ ኹሞ ፡ ሊረባ ፡ ሊገሰስ ፡ አንቀጽ ፡ ሊወጣለት ፡ ይቻላል ። ይህም ፡ ሰብእ ፡ ብሶ ፡ ተሰብአ ፥ ወይን ፡ ወየነ ፡ አውየነ ፥ እብን ፡ አበነ ፡ አእበነ ፥ ክርስቲያን ፡ ክረስተነ ፥ ደብተራ ፡ ደብተረ ፡ ተደብተረ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ከተጸውዖ ፡ ስም ፡ በቀር ፡ የማይበዛና ፡ የማይረባ ፡ የማይገሰስ ፡ ስም ፡ የለም ፡ ከነባር ፡ ስም ፡ የሚወጣ ፡ አንቀጽ ፡ ነባር ፡ ግስ ፡ ይባላል ።

፲ ፤ ነባር ፡ መባሉም ፡ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ስላልታወቀ ፡ እንጂ ፥ ዘር ፡ የሌለው ፡ ኹኖ ፡ አይዶለም ፤ ልጅ ፡ አላባት ፡ አለናት ፡ እንዳይገኝ ፥ ነባርም ፡ አለዘር ፡ በቅሉ ፡ አይገኝም ። ጥሬ ፡ ዘር ፡ እንደ ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ ነባር ፡ ግን ፡ ከባት ፡ ከናቱ ፡ እንደ ፡ ሚጣልና ፡ ሌሎች ፡ አንሥተው ፡ እንደሚያሳድጉት ፥ ወይም ፡ እናቱ ፡ ታውቃ ፡ አባቱ ፡ እንደማይታወቅ ፡ዲቃላ ፡ ነው ። ከዘር ፡ አንቀጽም ፡ እየተዱቀለ ፡ ስሙና ፡ ጠባዩ ፡ ተለውጦ ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ የሚባል ፡ አለ ፤ ሐሰወ ፡ ሐሰ ፥ ነዐወ ፡ ነዐ ፥ አበየ ፡ እንቢ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፤ የቀረውን ፡ በደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ተመልከት ።

፲፩ ፤ ለጥሬ ፡ ለነባር ፡ እንደ ፡ ዘር ፡ እንደ ፡ ግስ ፡ የፊደል ፡ ውሳኔ ፡ የለውም ፡ ከግእዝ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ብሉት ፡ በጎቱ ፡ ኹሉ ፡ ተንሥቶ ፡ ከግእዝ ፡ በቀር ፡ በጎቱ ፡ ኹሉ ፡ ይፈጸርሳል ። ያገባብም ፡ ቃል ፡ እመ ፡ ሰበ ፡ ከመ ፡ ሌላውም ፡ ኹሉ ፡ መድረሻው ፡ ግእዝ ፡ መኾኑ ፡ ሲናበብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ ሲያርፍና ፡ ሲወድቅ ፡ ሳድስ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ አክኼድ ፡ የተነሣ ፡ ነባር ፡ ከዘርና ፡ ከግስ ፡ ተዛንቆ ፥ የፊደሉን ፡ ተራ ፡ ጠብቆ ፥ ተባብሮ ፡ ተጫፍሮ ፡ ባንድነት ፡ ይጣፋል ፡ እንጂ ፡ ለብቻው ፡ የተለየ ፡ ቦታ ፡ የለውም ። ያለም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ ሲጣፍ ፡ ሲነገር ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ነባርን ፡ ከዘር ፡ አይለየውም ። የፊደሉም ፡ ተራ ፡ ሥሩን ፡ መነሻውን ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ መልክና ፡ እንደ ፡ ቅኔ ፡ እንደ ፡ሙሾና ፡ እንደ ፡ ዘፈን ፡ ግጥም ፡ ጫፉን ፡ መድረሻውን ፡ አይሸም ። በለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ከቅኔያቸው ፡ እንዲስማማላቸው ፡ መነሻውን ፡ ትተው ፡ መድረሻውን ፡ ብቻ ፡ ይሸሉ ፡ ግሡንም ፡ ሎሐ ፡ ለብሐ ፡ ለስሐ ፡ እያሉ ፡ በቅኔያቸው ፡ መንገድ ፡ ስላስኬዱት ፤ የርባታው ፡ መንገድ ፡ የዘሩና ፡ የነባሩ ፡ አክኼድ ፡ የጥፈቱ ፡ ረገድ ፡ ተበላሽቶ ፡ ከለም ፡ ቋንቋ ፡ መንገድ ፡ ወጥቷል ። የሐ ፡ ግስ ፡ የሚባል ፡ በሐ ፡ የሚነሣ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በሌላ ፡ ተነሥቶ ፡ በሐ ፡ የሚፈጽርስ ፡ አይዶለም ፤ የሌላውም ፡ ፊደል ፡ እንዲሁ ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ ፊደልና ፡ ግስ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ነውና ፤ ፪ቱንም ፡ ያፋለሷቸው ፡ ሰባክያን ፡ ናቸው ፡ ይባላል ፥ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ (መቅ ፡ ፲፫) ።

፲፪ ፤ የርባታውም ፡ መበላሸትና ፡ መሳሳት ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ፡ አመረ ፡ በመላላቱ ፡ የቀተለ ፡ ቤት ፡ ሲኾን ፤ አመረ ፡ (የአምር ፡ ይእምር ፡ አሚር ፡ አሚሮት) ፡ ዐወቀ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አስደራጊውን ፡ አእመረን ፡ መደበኛ ፡ ያ፬ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ አድርገ ፡ አእመረ ፡ (የአምር ፡ ያእምር ፤ አእምሮ ፡ ሮት) ፡ አሳወቀ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹሉ ፡ ዐወቀ ፡ እያሉ ፡ በደንገፀ ፡ ቤት ፡ መግሰስና ፡ ማርባት ፡ የስሕተት ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አስደራጊውን ፡ መደበኛ ፡ ትንቢቱን ፡ ኀላፊ ፡ ስላሉት ፡ የአእመረና ፡ የይቤ ፡ ርባታ ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ ጫፍ ፡ ተበላሽቷልና ፤ ሌላውንም ፡ እንደነዚህ ፡ እየው ። አእኰተ ፡ አግመረ ፡ አድምዐ ፡ አጥብዐ ፡ አጥመቀ ፡ አልጸቀ ፡ አይድዐ ፡ አርመመ ፡ አዕረፈ ፡ አፍቀረ ፤ ተገብረ ፡ ተወከለ ፡ ተለበለ ፡ ተሰፈወ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ዐመል ፡ ያለበት ፡ ግስ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ይቤና ፡ እንደ ፡ አእመረ ፡ ያልታረመ ፡ ያልተጠነቀቀ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ነው ።

፲፫ ፡ አንቀጽ ፡ የሌላቸው ፡ አገባቦችና ፡ የመጠሪያ ፡ ስሞች ፡ ፊደልና ፡ አኀዝም ፡ አንዳንድ ፡ ቅንጣት ፡ ዘሮች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ቊጥራቸውና ፡ ክፍላቸው ፡ ከነባሮች ፡ ነው ። ዘርና ፡ ነባርን ፡ በጥፈት ፡ በትምርት ፡ ለመለየት ፡ በግእዝ ፡ ንባብ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ቊጥ

ርን ፡ አሐድ ፡ ዱ ፡ ክልኤት ፡ ቱ ፡ ዐሥርት ፡ ቱ ፡ እያሉ ፡ ኹሉን ፡ በፊደል ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ በአኀዝ ፡ ብቻ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ብለው ፡ ወይም ፡ አኀዝና ፡ ፊደል ፡ አቈራኝቶ ፡ ፩ዱ ፡ ፪ቱ ፡ ፲ቱ ፡ ያልቁንም ፡ ፳ኤል ፡ እያሉ ፡ መጣፍ ፡ አይገባም ፡ የንባቡና ፡ የትርጓሜው ፡ የምስጢሩ ፡ ጣዕም ፡ ይበላሻል ። በአኀዝ ፡ ሊጣፍ ፡ የሚገባው ፡ ምዕራፍና ፡ ክፍል ፡ በውስጡ ፡ ያለው ፡ ነዶ ፡ ቃል ፡ ያማርኛ ፡ ንባብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ አይስማማውም ።

## ፪ኛ ፡ ዕርከን ።

## የግስ ፡ ዐመሎች ።

፲፬ ፡ ግስ ፡ ማለት ፡ የቋንቋ ፡ ጓዝ ፡ የዘርና ፡ የነባር ፡ እክት ፡ ወይም ፡ ዕቃ ፡ ግሴት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሰማይ ፡ ከነግሱ ፡ ምድር ፡ ከነልብሱ ፡ እንዲሉ ፥ ከነጓዙ ፡ ሲሉ ። የሚያጠግበውና ፡ የሚያረካው ፡ እሙን ፡ ትርጓሜው ፡ ግን ፡ ተወራራሽና ፡ ተመላላሽ ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ ነው ። ፩ዱ ፡ አንቀጽ ፡ እስከ ፡ ፺ ፡ ጥሬው ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ መደብ ፡ መረባቱና ፡ መዘርዝሩ ፡ ያንዱ ፡ ለብዙ ፡ የወንዱ ፡ ለሴት ፡ የሩቁ ፡ ለቅርብ ፡ እየተሰጠ ፡ በመፋለስና ፡ በመዋረስ ፡ በመመሳሰል ፡ ነውና ። በገሲስ ፡ ዘይቤም ፡ ሲፈቱት ፡ መደቦችና ፡ መደበኞች ፡ ኹነው ፡ የሚዳሰሱና ፡ የሚያዙ ፡ ዐሥሩን ፡ ሰራዊት ፡ ያሳያል ፡ (ቍ፵፯) ። ለግስ ፡ አከፋፈል ፡ ብዙ ፡ ስም ፡ አለው ። መዠመሪያ ፡ ትርጓሜና ፡ አፈታት ፡ እንደ ፡ ገጠመው ፡ ሲነገር ፡ ከተማ ፡ ግስ ፡ ፪ኛ ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡ ሲነገር ፡ መንደር ፡ ግስ ፡ ፫ኛ ፡ እንደ ፡ ፊደሉ ፡ ተራ ፡ በየወገኑና ፡ በየቤቱ ፡ በየሰራዊቱ ፡ ሲነገር ፡ ተራ ፡ ግስ ፡ ይባላል ። የቀረውም ፡ ኋላ ፡ በ፯ኛ ፡ ዕርከን ፡ ይመጣል ።

፲፭ ፡ ነጠላ ፡ ግስ ፡ ከ፪ ፡ ፊደል ፡ አይወርድም ፡ ከ፬ ፡ ፊደል ፡ አይወጣም ፡ ልማድና ፡ በዕድ ፡ ሲጨመር ፡ ግን ፡ ፭ም ፡ ፮ም ፡ ፯ም ፡ ይኾናል ፤ ከ፯ ፡ በላይ ፡ ግን ፡ አይወጣም ፡ ይህን ፡ ኋላ ፡ በበታው ፡ እናመጣዋለን ። በግስ ፡ ያሉ ፡ ዐመሎች ፡ ፫ ፡ ናቸው ፤ አና ፡ ሀ ፥ ወና ፡ የ ፥ ደጊመ ፡ ቃል ። አና ፡ ሀ ፡ ስላንድ ፥ ወና ፡ የ ፡ ስላንድ ፡ ይቈጠራሉ ፤ ደጊመ ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ለብቻው ፡ ፩ ፡ ነው ፤ አሊህ ፡ ፫ቱ ፡ ዐመሎች ፡ ያሉበት ፡ ግስ ፡ ቤቱን ፡ ሳይለቅ ፡ ድምጥና ፡ መንገድ ፡ ይለውጣል ። ዐመሎችን ፡ ሕርመት ፡ ወይም ፡ ጸዋትው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

### ከመላላት ፡ በቀር ፡ መጥበቅ ፡ የሌላቸው ፡ አ—ዐ ፡ ሀ—ሐ—ኀ ።

አና ፡ ሀ ፡ በመካከሉ ፡ ያሉበት ፡ ግስ ፡ የቀተለ ፡ ሰርዌ ፡ አርእስቱ ፡ በግእዝ ፡ ይነሣ ፡ የነበረውን ፡ ለውጦ ፡ ሳድስ ፡ ያደርጋል ፤ ይህም ፡ ልኢክ ፡ ለአከ ፥ ልሒኰ ፡ ለሐኰ ፡ ጽዒል ፡ ጸዐለ ፥ ምሒር ፡ መሀረ ፥ ግሒሥ ፡ ገሐሠ ፥ ዝኂር ፡ ዘኀረ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ አንቀጹ ፡ ሳይቀር ፡ ፪ቱንም ፡ በሳድስ ፡ ያስነሣል ፤ ይህም ፡ ንኢድ ፡ ንእደ ፥ ጥዒም ፡ ጥዕመ ፥ ብሂል ፡ ብህለ ፥ ጥሒር ፡ ጥሕረ ፥ ጕሒቍ ፡ ጕሕቈ ፥ ድኂን ፡ ድኅነ ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ። አና ፡ ሀ ፡ ማእከል ፡ ኹነው ፡ እንዲህ ፡ ከለወጡት ፡ በቀር ፡ ዘርና ፡ አንቀጽ ፡ በሳድስ ፡ ፊደል ፡ አይነሣም ። ዳግመኛም ፡ በመካከሉ ፡ ዐመል ፡ ያለበት ፡ ግስ ፡ እንደ ፡ ጓሥሥት ፡ የሚለዋወጥ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡

ተዠኀረ ፡ ተዠነረ ፥ ተልዕለ ፡ ተለሀለ ፥ ተውዕረ ፡ ተወፀረ ፥ ተዎሀረ ፡ ተመሀረ ፥ ተክዕወ ፡ ተከፀወ ፡ እያለ ፡ ይገኛል ። በክህለም ፡ ያለ ፡ ሀ ፡ እስከ ፡ ቿ ፡ ሰራዊት ፡ በካልኣይ ፡ ኹሉ ፡ ይታጣል ፡ ይህም ፡ ክህለ ፡ ይክል ፥ ክህልክ ፡ ትክል ፥ ክህልኩ ፡ እክል ፡ እያለ ፡ ጭራሽ ፡ መታጣቱን ፡ ያሳያል ። የብህለም ፡ አካኼድ ፡ እንደ ፡ ክህለ ፡ ነው ፡ ሀን ፡ በካልኣይ ፡ ኹሉ ፡ ያወጣል ። ይህም ፡ ብህለ ፡ ይብል ፥ ብህልኩ ፡ እብል ፥ ብህልነ ፡ ንብል ፡ ማለቱን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ይብህል ፡ እብህል ፡ ንብህል ፡ አለማለቱን ፡ ያሳያል ። በቤለ ፡ አካኼድ ፡ ግን ፡ መሪና ፡ ተከታይ ፡ የሌለው ፡ ባሕታዊ ፡ ፍኖት ፡ ነው ፡ ቤሰን ፡ ተመልከት ።

፲፮ ፡ ፫ኛም ፡ ከቀተለ ፡ እስከ ፡ ማህረከ ፡ ባሉት ፡ በ፯ቱ ፡ አርእስት ፡ አና ፡ ሀ ፡ መድረሻ ፡ ሲኾኑ ፡ ፪ኛው ፡ ፊደል ፡ ወይም ፡ ፫ኛው ፡ ግእዝ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ለውጠው ፡ ሳድስ ፡ ያደርጉታል ። ይህም ፡ ገብአ ፡ ፈርሀ ፥ ጸውዐ ፡ ሰብሐ ፥ ሰርሐ ፡ ሣርኀ ፡ ባልሐ ፥ ቁቅሐ ፡ ቶስሐ ፡ ሞቅሐ ፥ ገፍትዐ ፡ ቀሕቅሐ ፥ ላዕልዐ ፡ ላሕልሐ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ፯ቱ ፡ አርእስቶች ፡ ማን ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ባመል ፡ መፈጸሪያ ፡ ተመልከት ። ፬ኛም ፡ በ፫ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፥ ከዚያውም ፡ በቀተለ ፡ ቤት ፡ በሣልሳይ ፡ አንቀጽ ፡ ሳድስ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፥ ይግብአ ፡ ይፍራሀ ፥ ይብላዕ ፡ ይክላሕ ፡ ይበአ ፡ ይፃእ ፡ ይብዛኅ ፡ እያሰኙ ፡ ወደ ፡ ራብዕ ፡ ይለውጡታል ። ፪ኑታቸው ፡ ስላንድ ፡ የሚቈጠር ፡ የአና ፡ የሀ ፡ ግብር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ወና ፡ የ ።

፲፯ ፡ የወና ፡ የየ ፡ ፀመል ፡ መጕረድና ፡ ድምጥ ፡ መለወጥ ፡ ነው ፡ ራሳቸውን ፡ እየጐረዱና ፡ እየዋጡ ፥ ወይም ፡ በጥፈት ፡ እየታጡ ፡ እየተዋጡ ፡ ለሌሎቹ ፡ መወልጣን ፡ ድምፅ ፡ ይኾናሉ ። የድምጣቸውም ፡ ስልት ፡ በፊደላት ፡ ጠባይ ፡ በ፲ኛው ፡ ቍጥር ፡ በመቅድም ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ነው ፡ የወ ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ማድረግ ፥ የየ ፡ ሣልስና ፡ ኃምስ ፡ ማድረግ ።

ወ ።

፲፰ ፡ ወ ፡ መድረሻ ፡ ወይም ፡ መፈጸሪያ ፡ ሲኾን ፥ ካልኣዩ ፡ ሳድስ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ጕርዶ ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ያደርጋል ፡ ይህም ፥ በግቢር ፡ ዘረወ ፡ ይዘሩ ፥ ሠረወ ፡ ይሤሩ ፥ ፈነወ ፡ ይፌኑ ፡ ማለቱን ፡ በተግብሮም ፡ ተዘርወ ፡ ይዘሮ ፥ ተሠረወ ፡ ይሤሮ ፥ ተፈነወ ፡ ይትፌኖ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ደግሞ ፡ ሲኾን ፡ በጭራሽ ፡ አይጐርድም ፡ ይህም ፥ ከወወ ፡ ይከውው ፥ ለወወ ፡ ይለውው ፥ ጼወወ ፡ ይጼውው ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ። ሳድስ ፡ ቅጽሉንም ፡ መከከሉ ፡ ካዕብ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ሳድስ ፡ ያደርጋል ፡ ይህም ፡ ዝርው ፡ ሥርው ፡ ፍንው ፡ ሀልው ፡ ቅንው ፡ ጺውው ፡ ምጥው ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ።

፲፱ ፡ ኹለተኛም ፡ ወ ፡ በቀተለ ፡ ሰርዌ ፡ ማእከል ፡ ሲኾን ፡ ያንቀጹ ፡ መነሻ ፡ ግእዝ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ጕርዶ ፡ ሳብዕ ፡ ያደርጋል ፡ ይህም ፡ ሀዊብ ፡ ሆበ ፡ የሀውብ ፡ ይሁብ ፥ ሐዊር ፡ ሖረ ፥ ጸዊር ፡ ጾረ ፥ ነዊም ፡ ኖመ ፥ ቀዊም ፡ ቆመ ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፤

እንዳርእስቱ ፡ ሀወበ ፡ ሐወረ ፡ ጸወረ ፡ ነወመ ፡ ቀወመ ፡ አለማለቱን ፡ ያሳያል ። ባ፩ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ ማእከል ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ ያርእስቱንም ፡ ጫፍ ፡ እንደ ፡ ሥሩ ፡ ሳብዕ ፡ ያደርጋል ። ይህም ፡ ኖልዎ ፡ ኖለወ ፥ ሶስዎ ፡ ሶሰወ ፥ ቶስሐ ፡ ቶስሐ ፥ ቆጽሮ ፡ ቆጸረ ፡ እያለ ፡ በ፫ ፡ ፊደል ፡ ብቻ ፡ መኼዱን ፤ ነውልዎ ፡ ነውለወ ፥ ሰውስዎ ፡ ሰውሰወ ፥ ተውስሐ ፡ ተውስሐ ፥ ቀውጽሮ ፡ ቀውጸረ ፡ አለማለቱን ፡ ያሳያል ።

፺ ፤ ሦስተኛም ፡ ወ ፡ ለሦስት ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ መነሻ ፡ ሲኾን ፥ ጥሬ ፡ ዘሩ ፡ ፬ ፡ ፊደል ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ጕርዶ ፡ ፫ ፡ ፊደል ፡ ብቻ ፡ ያደርጋል ። ይህም ፡ ወጊስ ፡ ወገሰ ፡ ብሎ ፡ ሞገስ ፤ ወጥሖ ፡ ወጥሐ ፡ ብሎ ፡ ሞጥሕ ፤ ወቂሕ ፡ ወቅሐ ፡ ብሎ ፡ ሞቅሕ ፤ ወጊድ ፡ ወገደ ፡ ብሎ ፡ ሞገድ ፤ ወገረ ፡ ሙጋር ፥ ወደየ ፡ ሙዳይ ፥ ወድቀ ፡ ሙዳቅ ፥ ውሕዘ ፡ ሙሓዝ ፥ ወለደ ፡ ሙላድ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ሳቢ ፡ ዘሩ ፡ ግን ፥ ልደት ፡ ፀአት ፡ ድቀት ፡ ርደት ፡ እያለ ፡ ወይም ፡ ሳይጐርድ ፡ ውግረት ፡ ውኅደት ፡ ውኅጠት ፡ ውጥነት ፡ ውዕፈት ፡ እያለ ፡ ይኼዳል ። ሣልሳዩንም ፡ ከቀደሰና ፡ ከባረከ ፡ ቤት ፡ ብቀር ፡ ኹሉን ፡ ይጐርዳል ፤ ይህም ፡ ወሀበ ፡ ይውህብ ፡ ብሎ ፡ የሀብ ፡ ይገስ ፡ ይቃሕ ፡ ይገድ ፡ ይገር ፡ ይደቅ ፡ የሐዝ ፡ ይለድ ፡ ይፈጥ ፥ ይፀፍ ፡ ይረድ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ።

፺፩ ፤ አራተኛም ፡ ከ፪ቱ ፡ ፀመሎች ፡ ሲገናኝ ፡ አርእስቱ ፡ ሳድስ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ወደ ፡ ራብዕ ፡ ይለውጠዋል ፤ ይህም ፡ ዋሕይ ፡ ዋሕዮት ፥ ዋሐየ ፡ ይዋሒ ፡ ይዋሒ ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ። ዳግመኛም ፡ ውዕይ ፡ ውዕዮት ፡ ውዕየ ፡ ወይም ፡ ወፀየ ፡ ይውዒ ፡ የፀይ ፡ ይላልና ፥ ዋሐየም ፡ እንደ ፡ ውዕየ ፡ ሊኼድ ፡ ይችላል ፤ ይህም ፡ አከኼድ ፡ በቀተለ ፡ ቤት ፡ ነው ። በቀደሰና ፡ በባረከ ፡ ቤት ፡ ግን ፤ ወደሰ ፡ ይዌድስ ፡ ይወድስ ፥ ወጥሐ ፡ ይዌጥሕ ፡ ይወጥሕ ፥ ወሠረ ፡ ይዌሥር ፡ ይወሥር ፥ ዋሐደ ፡ ይዋሕድ ፡ ይዋሕድ ፥ ዋከየ ፡ ይዋኪ ፡ ይዋኪ ፥ ዋነየ ፡ ይዋኒ ፡ ይዋኒ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ቀተለ ፡ ቤት ፡ አይጐርድም ። ወ ፡ መነሻም ፡ መድረሻም ፡ ማእከልም ፡ ኹኖ ፡ ካልጐረደው ፡ በቀር ፥ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ግስ ፡ በሳብዕ ፡ ቀለም ፡ አይነሣም ፤ በካዕብ ፡ በሳብዕ ፡ አይጨርስም ፤ ጥሬ ፡ ዘሩም ፡ በካዕብ ፡ በሳብዕ ፡ አይነሣም ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ የወን ፡ ጠባይና ፡ ፀመል ፡ እኹል ፡ ገብ ፡ ፊደል ፡ መኾኑን ፡ በቦታው ፡ ተመልከት ።

## የ ።

፺፪ ፤ የ ፡ መድረሻ ፡ ወይም ፡ መጨረሻ ፡ ሲኾን ፥ ክልኤቱ ፡ ሳድስ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ጕርዶ ፡ ሣልስ ፡ ያደርጋል ፤ ያርእስቱንም ፡ ማእከል ፡ ሣልስ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ለውጦ ፡ ሳድስ ፡ ያደርጋል ። ይህም ፥ ሐቅይ ፡ ሐቀየ ፡ የሐቂ ፤ ሰቅይ ፡ ሰቀየ ፡ ይሰቂ ፤ ፈድይ ፡ ፈደየ ፡ ይፈዲ ፤ ግንይ ፡ ገነየ ፡ ይገኒ ፤ ኀርይ ፡ ኀረየ ፡ የኀሪ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። በበዝ ፡ አንቀጽም ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤ ሣልስ ፡ ይሆን ፡ የነበረውን ፡ ሳድስ ፡ ያደርጋል ። ወርእያ ፡ ደንገፀት ፤ በሊዖ ፡ ወሰትዮ ፤ አዕሚቆ ፡ ወንልዮ ፡ እንዲል ።

፺፫ ፤ ፪ኛም ፡ የ ፡ በቀተለ ፡ ሰርዌ ፡ በ፫ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ ማእከል ፡ ሲኾን ፡ መነሻው ፡ ግእዝ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ለውጦና ፡ ጕርዶ ፡ ኃምስ ፡ ያደርጋል ። ይህም ፡ ገዪሥ ፡

ጌሠ፥ ጠዩስ፡ ጤሰ፥ መዩጥ፡ ሜጠ፥ ሠዩም፡ ሜመ፥ ዐዩል፡ ዔለ፥ በዩል፡ ቤለ፡እ
ያለ፡ መኼዱን፡መደብ፡ አድርጎ፤ እንዳርእስቱ፥ ገየሠ፡ ጠየሰ፥ መየጠ፡ ሠየመ፤ ዐ
የለ፡ በየለ፡ አለማለቱን፡ ያሳያል ። በ፩፡ ፊደል፡ ግስ፡ ማእከል፡ ሲኾን፡ ግን፡ አርእስ
ቱንም፡ እንዳንቀጹ፡ በኃምስ፡ ያስነሣል፤ ይህም፡ ዴግኖ፡ ዴገነ፥ ጌግዮ፡ ጌገየ፥ ሴልዮ፡
ሴለየ፥ ቄቅዮ፡ ቄቀየ፥ ሴስዮ፡ ሴሰየ፡ ማለቱን፡ መደብ፡ አድርጎ፤ ደይግኖ፡ ደይገነ፥
ገይግዮ፡ ገይገየ፥ ለይልዮ፡ ለይለየ፥ ቀይቅዮ፡ ቀይቀየ፥ ሰይስዮ፡ ሰይሰየ፥ አለማለ
ቱን፡ ያሳያል ። የ፡ ማእከልና፡ መድረሻ፡እየኾነ፡ካልጐረደው፡በቀር፥ ግስ፡በኃምስ፡
ፊደል፡ አይነሣም፤ በሣልስ፡ ፊደል፡ አይጨርስም፤ ጥሬና፡ ነባርም፡ እንደዚህ፡ ነው ።

ሐተታ፡ ስለ፡ ብህለና፡ ስለ፡ ቤለ ።

፷፬፤ ሀሎ፡ የሀለወ፡ ክፉይ፡ ወይም፡ ካዕቡ፥ መንቲያው፡ ድርቡ፡ እንደ፡ ኾነ፤
ቤለም፡ የብህለ፡ ካዕብ፡ መንቲያና፡ ድርብ፡ ይባላል፤ ያንዱ፡ ቅንጣት፡ ዘር፡ ግስ፡
ባለ፪፡ ዐመል፡ ስለ፡ ኾነ፡ በሀና፡ በየ፡ ስልት፡ በ፪ቱ፡ አካኼድ፡ ይኼዳል ። የሀውን፡
አካኼድ፡ በሀ፡ ተናግረናል፤ የየውም፡ አካኼድ፡ እንዲህ፡ ነው ። በሀ፡ ማእከልነት፡
ብሂል፡ ብሂሎት፡ ብህለ፡ የተባለው፤ ፪ኛ፡ ደግሞ፡ በየ፡ ማእከልነት፥ በዩል፡ በዩ
ሎት፡ ቤለ፡ ተብሎ፥ አስደራጊውንም፥ አበለ፡ ያብል፡ እያሰኘ፡ ልውጥና፡ ግልብጥ፡
ሕግ፡ ወጥ፡ አካኼድ፡ ይኼዳል፤ ብህለም፡ ቤለ፡ መባሉ፡ በወዲያኛው፡ ትግሬ፡ በሐ
ባቦች፡ ቋንቋ፡ ይታወቃል፤ በወዲህኛውም፡ ትግሪኛ፥ ሐማሴኖች፡ የለ፥ አኵስሞ
ችና፡ ዐዶች፡ በለ፡ ይሉታል ። ያካኼዱም፡ ሕግ፡ ወጥነት፡ ይህ፡ ነው፤ ቤለ፡ ይበይል፡
ይቢል፡ ብሎ፥ እንደ፡ ዔለና፡ እንደ፡ ሜመ፡ ፊት፡ ለፊት፡ በመኼድ፡ ፊንታ፥ ቤለ፡
ይቤ፡ ይበል፡ ይበል፤ ቤልከ፡ ትቤ፡ ትበል፡ በል፤ ቤለት፡ ትቤ፡ ትበል፡ ትበል፤
ቤልኩ፡ እቤ፡ እበል፡ እበል፤ ቤልነ፡ ንቤ፡ ንበል፡ ንበል፡ እያለ፡ በነዚህ፡ በ፳ቱ፡
ሰራዊት፡ ለን፡ እያሶገደ፥ የን፡ እየጐረደ፡ በዔለና፡ በሜመ፡ አካኼድ፡ ግእዝ፡ ይኾን፡
የነበረውን፡ በ፥ በካልአይ፡ ኹሉ፡ ኃምስ፡ ያደርጋል ። በቀሩት፡ ደግሞ፡ በ፳ቱ፡
ኹሉ፥ ቤሉ፡ ይቤሉ፡ ይበሉ፡ ይበሉ፤ ቤልክሙ፡ ትቤሉ፡ ትበሉ፡ በሉ፤ ቤላ፡ ይቤላ፡
ይበላ፡ ይበላ፤ ቤልክን፡ ትቤላ፡ ትበላ፡ በላ፤ ቤልኪ፡ ትቤሊ፡ ትበሊ፡ በሊ፡ እያሰኘ፡
የን፡ በመጕረዱ፡ ላይ፡ ለን፡ እየጨመረ፡ ይኼዳል ። ትንቢትነቱንም፥ ይቤ፡ ትቤ፡
እቤ፡ ንቤ፡ ብሎ፡ በሥርወ፡ ቀለሙ፡ ያስረዳል፤ ይህነንም፡ በአሥራውና፡ በብሂል፡
አፈታት፡ ተመልከት ። ባላገባቦች፡ ግን፡ ባለመጽሐፎችም፡ ሳይቀሩ፥ የይቤ፡ ቀዳ
ማይ፡ ቤለ፡ መኾኑን፡ ስላላስተዋሉ፤ ፪ኛም፡ ቀዳማይ፡ አንቀጽ፤ ሥርወ፡ ፊደል፡ አለ
መለወጡን፥ በሣልስ፡ በኃምስ፡ አለመጕረዱን፥ አጥብቀው፡ አጥልቀው፡ ስላልመረ
መሩ፥ ይቤን፡ በቤለ፡ ፈንታ፡ ቀዳማይ፡ አንቀጽ፡ አድርገው፥ እኩሉ፡ ዘርና፡ አርእ
ስት፡ የሌለው፡ ለብቻው፡ የቆመ፡ ነባር፡ ቀዳማይ፡ ነው፤ እኩሉም፡ የቀዳማይ፡ አን
ቀጽ፡ የብህለ፡ ድርብ፡ ነው፡ እያሉ፡ በቀዳማይነት፡ ስላቆሙት፥ ርባታውና፡ አፈታቱ፡
ከሥር፡ እስከ፡ ጫፍ፡ ተበላሽቷል፡ (ቍ፲፪) ።

፷፭፤ የአንና፡ የሀን፥ የወንና፡ የየን፡ የነዚህን፡ የኹለቱን፡ ስልት፥ የመንገዳ
ቸውን፡ ልዩነት፥ ያካኼዳቸውን፡ መጥፎነት፥ ነውጠኞችና፡ ዐመለኞች፡ ኹነው፡ የማ

ስን፡ ቤት፡ ኹሉ፡ ማናወጣቸውን፥ ጠባይና፡ ዘር፡ ማስለወጣቸውን፡ ለማስተዋልና፡ ለመመርመር፡ ይህ፡ የጣፍነው፡ ብቻ፡ ይበቃል ፤ ከዚህ፡ የቀረውን፡ የየን፡ ጠባይና፡ ዐመል፡ በበታው፡ ተመልከት ። በመካከሉ፡ እነዚህ፡ ዐመሎች፡ የሌሉበት፡ ግስ፡ በግእዝ፡ በራብዕ፡ ቢነማ፡ እንጂ፥ በኃምስ፡ በሳድስ፡ በሳብዕ፡ ፈደል፡ አይነማም ። በግእዝ፡ መነማት፡ የዐረብ፥ በራብዕ፡ መነማት፡ የሱርስትና፡ የዕብራይስጥ፡ ነው ፤ ግእዝም፡ የዐረብ፡ የሱርስት፡ የዕብራይስጥ፡ ወንድም፡ ስለ፡ ኾነ፥ በነዚህ፡ አካኼድ፡ ይኼዳል ። የነዚህም፡ ያራቱ፡ ልሳናት፡ ዘራቸውና፡ ነባራቸው፥ ንባባቸውና፡ ምስጢራቸው፡ እንደ፡ ወንጌላት፡ ቃል፡ ይገጥማል ፤ ልዩነቱ፡ ጥቂት፡ ጥቂት፡ ነው ።

## ደጊመ፡ ቃል ።

፹፯፡ ደጊመ፡ ቃል፡ ያለው፡ የ፫፡ ፈደል፡ ግስ፡ ከዚያውም፡ የቀተለ፡ ሰርዌ፡ እንደ፡ ወና፡ እንደ፡ የ፡ ይገመርዳል ፤ አገመራረዱ፡ ግን፡ እየቅል፡ ነው ። ፪ኛው፡ ፈደል፡ ፫ኛውን፡ ውጦ፡ ካዕብና፡ ሳብዕ፡ ወይም፡ ኃልስና፡ ኃምስ፡ ሳይኾን፡ እየጠበቀ፡ የ፪፡ ፈደል፡ ግስ፡ ይኾናል ። ይህም፡ ጠቢብ፡ ጠበ፥ ነቢብ፡ ነበ፥ ነዲድ፡ ነደ፥ ጸኒን፡ ጸነ፥ ቀሊል፡ ቀለ፥ ቁረር፡ ቁረ፥ ተኒን፡ ተነ፡ እያለ፡ መኼዱን፡ ያሳያል ። ወና፡ የ፡ ደጊመ፡ ቃል፡ እሊህ፡ ፫ቱ፡ ዐመሎች፡ ካልገመረዱት፡ በቀር፡ የ፫፡ እንጂ፡ የ፪፡ ፈደል፡ ግስ፡ አይገኝም ።

፹፰፡ ዕጥፍ፡ ደጊመ፡ ቃል፡ ያለውም፡ ቡነቡነ፥ ገመድገመደ፥ ደግደገ፥ ጠብጠበ፥ ከብከበ፥ በልበለ፥ ቀልቀለ፥ ፈልፈለ፥ ጸንጸነ፥ ተንተነ፥ እንደዚህ፡ ያለ፡ ይህን፡ የመሰለ፡ ኹሉ፡ ፈተኛውና፡ ፫ኛው፡ ስላንድ፡ ተቈጥሮ፡ የ፫፡ ፈደል፡ ግስ፡ ይበላል ፤ ምንም፡ ቅንጣቱ፡ ፬፡ ቢኾን፡ ፈደሉ፡ ፪፡ ነውና፥ ግስነቱም፡ ደጊመ፡ ቃል፡ ካለው፡ ከ፪፡ ፈደል፡ ግስ፡ የወጣ፡ ተቀጥላ፡ ግስ፡ ነውና፥ በ፭፡ ግስ፡ ፭፡ ብቻ፡ እንጂ፡ ፪፡ ደጊመ፡ ቃል፡ አይኾንም ።

፹፱፡ ደጊመ፡ ቃል፥ ገሰሰ፡ ኀሠሠ፥ አረረ፡ ሣረረ፥ ኰነነ፡ መነነ፥ ሐተተ፡ ፈተተ፡ እያለ፡ ፫ኛ፡ ሲኾን፡ ለብቻው፡ በራሱ፡ ይቈጠራል ፤ ገብሰሰ፡ ደምሰሰ፥ ደንገገ፡ ፈርገገ፥ ጠንቀቀ፡ ሐንቀቀ፡ እያለ፡ ፬ኛ፡ ፈደል፡ ሲኾን፡ ግን፡ ፬ኛው፡ ዲቃላ፡ ነውና፥ ከ፫ኛው፡ ጋራ፡ ስላ፭፡ ተቈጥሮ፡ የ፫፡ ፈደል፡ ግስ፡ ይበላል ፤ አርእስቱ፡ ግን፡ ደንገፀ፡ ነጠ ።

፺፡ ያ፬፡ ፈደል፡ ግስ፡ ያልናቸውም፡ ኖለወ፥ ሎለወ፥ ሶሰወ፥ ጌገየ፥ ሴለየ፥ ቈቀየ፥ ሴሰየ፡ እሊህን፡ የመሰሉ፡ ኹሉ፡ በምስጢር፡ በውሳጣይ፡ ቍጥር፡ ያ፬፡ ፈደል፡ ግስ፡ ሲኾኑ፡ የተገመረደው፡ ፪ኛውና፡ ያልተገመረደው፡ ፬ኛው፡ ፈደል፡ ስላንድ፡ ተቈጥሮ፡ የ፫፡ ፈደል፡ ግስ፡ ይበላሉ ። ይኸውም፡ ከ፬፡ አንዱ፡ ፈደል፡ ተገመርዶ፡ ፫፡ ብቻ፡ ስለ፡ ቀረ፡ ነው ። ደጊመ፡ ቃልም፡ ባይኖር፡ ወና፡ የ፡ ያሉበት፡ ቶስሐን፡ ዴገነን፡ የመሰለ፡ ያ፬፡ ፈደል፡ ግስ፡ ወና፡ የ፡ በንባብ፡ በጥፈት፡ ተውጠው፡ ተገመርደው፡ ስለ፡ ቀሩ፡ ፪ኛው፡ ፈደል፡ ከፈተኛው፡ ጋራ፡ ስላንድ፡ ተቈጥሮ፡ የ፫፡ ፈደል፡ ግስ፡ ይበላል ።

፻፬ ፡ በትናጋ ፡ የሚነገሩም ፡ ፫ቱ ፡ ፊደላት ፡ ገ ፡ ከ ፡ ቀ ፡ በምላስ ፡ ከሚነገሩትም ፡ ነ ፡ እነዚህ ፡ ፬ቱ ፡ የግስ ፡ መድረሻ ፡ ሲኾኑ ፡ ከና ፡ ነ ፡ ደግሞ ፡ መድረሻና ፡ ትራስ ፡ እየ ኾኑ ፡ በምእላድነት ፡ ሲጨመሩ ፡ ገና ፡ ቀ ፡ ተወራራሾች ፡ ናቸውና ፡ ከ ፡ ባለቤቸው ፡ ባ፫ቱ ፡ ቅርቦች ፡ ላይ ፡ አቅራቢውን ፡ ከ ፡ ደጊመ ፡ ቃልነት ፡ ስላለው ፡ ውጠውና ፡ ጐር ደው ፡ በንባብ ፡ በጥፈት ፡ ያስቀሩታል ። ይህም ፡ (ዐረግከ ፡ ሰበክከ ፡ ጠየቅከ) ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፥ ዐረገ ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ሰበከ ፡ ለነ ፡ ልደተ ፡ እግዚእ ፡ ጠየቀኑ ፡ አ ፡ ፍቁር ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ነ ፡ ደግሞ ፡ የንሕነ ፡ ዝርዝር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ (ከንነ ፡ ድ ኅንነ ፡ አመንነ) ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፥ ከነ ፡ ድኅነ ፡ አመነ ፡ እያለ ፡ በመጥበቅ ፡ ደጊሙን ፡ ይጐርዳል ። በተና ፡ በደ ፡ በጠ ፡ የሚጨርስ ፡ ግስ ፡ በንዲቱ ፡ ሴት ፡ ሳድስ ፡ ቅጽልና ፡ በመድበል ፡ ቅጽል ፡ ሳይጐርድም ፡ እየጐረደም ፡ እንዲሁ ፡ ይጠብቃል ። ይህም ፡ ት ሑት ፡ ብሎ ፡ ትሕት ፡ ሐታት ፡ ሐተት ። ብፁድ ፡ ፍሉጥ ፡ ብሎ ፡ ብዕድ ፡ ፍልጥ ። ፀ ጸዲ ፡ መሣጢ ፡ ብሎ ፡ ዐጸድ ፡ መሡጥ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ።

## ፫ኛ ፡ ዕርከን ።

## የግስ ፡ ልማድ ፡ ባላ፫ ፡ አዕማድ ።

፻፭ ፡ በኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ ተውሳክ ፡ እየኾኑ ፡ የግስን ፡ ጸታ ፡ ያንቀጽን ፡ ርባታ ፡ በየቤቱና ፡ በየሰራዊቱ ፡ ለይተው ፡ የሚመሩና ፡ የሚያስኬዱ ፡ የግስ ፡ ልማዶች ፡ እንዳ፫ቱ ፡ አዕማድ ፡ ፫ ፡ ናቸው ፡ አ ፡ ተ ፡ አስተ ፡ አን ፡ አስ ። ካ፫ቱ ፡ ደግሞ ፡ መደበኞቹ ፡ አና ፡ ተ ፡ ፪ቱ ፡ ናቸው ። ስና ፡ ን ፡ ስሬጽ ፡ ይባላሉ ፡ ፫ ፡ አዕማድ ፡ የተባሉም ፡ አድራጊ ፡ አስደራጊ ፡ ተደራጊ ፡ ተደራራጊ ፡ አደራራጊ ፡ ናቸው ። አ ፡ እነፈለሰን ፡ በሚመስሉ ፡ ባ፺ትል ፡ ግሶች ፡ ላይ ፡ ሲገባ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የማድረግና ፡ የማስደረግ ፡ ልማድ ፡ ይኾ ናል ፡ ይህም ፡ አምጽአ ፡ ብሎ ፡ አመጣ ፡ አስመጣ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ፡ እነቀተለን ፡ በሚ መስል ፡ በገቢር ፡ ግስ ፡ ግን ፡ የማስደረግ ፡ ብቻ ፡ ይኾናል ።

፻፮ ፡ ተ ፡ የመደረግና ፡ የመደራረግ ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ በጥርስ ፡ በምላስ ፡ ከሚነገሩ ፡ ከሥራንዱ ፡ ፊደላት ፡ በ፯ቱ ፡ ብቻ ፡ (ደ ፡ ዘ ፡ ጠ ፡ ሠሰ ፡ ጸፀ ፡ ተ) ፡ ለሚነሡ ፡ ግሶች ፡ ልማድ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፥ በሩቆችና ፡ አነ ፡ ንሕነ ፡ በሚል ፡ በትንቢት ፡ በዘንድ ፡ በትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ተውጦ ፡ ተጐርዶ ፡ ይቀርና ፡ ባ፬ቱ ፡ ቅርቦች ፡ በትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ ይገኛል ። ይ ህም ፥ ተድኅረ ፡ ይዴኀር ፡ ይደኅር ፡ ተዘብጠ ፡ ይዘበጥ ፡ ተጠውመ ፡ ይጠወም ፡ ተሠ ይመ ፡ ይሠየም ፡ ተፀምደ ፡ ይፀመድ ፡ ተፀመድኩ ፡ ነ ፡ እፀመድ ፡ ንፀመድ ፡ ከለ ፡ በኋላ ፡ ያራቱን ፡ ቅርቦች ፡ ተፀመድ ፡ ዲ ፡ ዱ ፡ ዳ ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ፡ በንዱ ፡ የኹሉ ፡ ይታወቃል ።

፻፯ ፡ አስተ ፡ መደቡ ፡ የማደራረግ ፥ ድርቡ ፡ የማድረግና ፡ የማስደረግ ፡ የመደ ረግም ፡ ነው ፡ አስተ ፡ የማደራረግ ፡ ልማድና ፡ መደብ ፡ መኾኑ ፡ ባስደራጊው ፡ ልማድ ፡ በአና ፡ በተ ፡ መካከል ፡ ስ ፡ ስሬጽ ፡ ኹኖ ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ ሥርወ ፡ ቀለ ሙን ፡ አስተቃተለ ፡ ብሎ ፡ ራብዕ ፡ በማድረግ ፡ ይታወቃል ፡ የማያሳስት ፡ መለዮውና ፡ ምልክቱ ፡ ይህ ፡ ነው ። የማድረግና ፡ የማስደረግ ፡ የመደረግ ፡ ልማድ ፡ መኾኑም ፥

አስ ፡ በአነቱ ፡ ማድረግንና ፡ ማስደረግን ፡ ብቻ ፡ እንዲሻ ፤ ተም ፡ በተነቱ ፡ መደረግን ፡ ብቻ ፡ ይሻልና ፤ ስለ ፡ አና ፡ ስለ ፡ ተ ፡ ጠባይ ፡ ነው ፤ በነዚህ ፡ በ፫ቱ ፡ ድርቦች ፡ ሥርወ ፡ ቀለሙን ፡ ግእዝና ፡ ሳድስ ፡ ቢያደርግ ፡ እንጂ ፤ ራብዕ ፡ ማድረግ ፡ አይችልም ፤ መለዮው ፡ ይህ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሐመመ ፡ አስተሐመመ ፤ ረሰየ ፡ አስተረሰየ ፤ በዕዐ ፡ አስተብዕዐ ፤ ረከበ ፡ አስተርከበ ፤ ርእየ ፡ አርአየ ፡ አስተርአየ ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ።

፴፩ ፤ አን ፡ ደግሞ ፡ የማድረግና ፡ የመደረግ ፡ ልማድ ፡ ይኾናል ፤ ነ ፡ በዕብራይስጥ ፡ እንደ ፡ ተ ፡ የመደረግ ፡ ልማድ ፡ ነውና ፤ አና ፡ ነ ፡ በየራሳቸው ፡ ፪ ፡ ልማዶች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ገጥመው ፡ ፩ዱን ፡ ግስ ፡ በማድረግና ፡ በመደረግ ፡ በ፪ ፡ ጾታ ፡ ያስፈታሉ ። ሲገቡም ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ ባለው ፡ ከደጊመ ፡ ቃልም ፡ በሚደቅል ፡ ገለገን ፡ ጌገየን ፡ በልበለን ፡ ጐድጐደን ፡ በሚመስል ፡ በ፫ና ፡ ባ፬ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ ይገባሉ ፤ ይህም ፡ ነገወ ፡ ብሎ ፡ አንነገወ ፤ ቀልቀለ ፡ ብሎ ፡ አንቀልቀለ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ።

፴፪ ፤ አስና ፡ አል ፡ ከግእዝ ፡ ይልቅ ፡ በማርኛ ፡ ውስጥ ፡ ይበዛል ፤ አስ ፡ በስደራጊ ፡ ጾታ ፤ አል ፡ በአልቦ ፡ ባሉታ ። አስ ፡ እንደ ፡ አን ፡ ኹኖ ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ ግስ ፡ ሲገባ ፡ ስ ፡ እንደ ፡ ን ፡ ግእዝ ፡ እየኾነ ፡ ለጥሬ ፡ ዘሩ ፡ መነሻ ፡ ይኾናል ። ይኸውም ፡ አንጐድጐደ ፡ ብሎ ፡ ነጐድጓድ ፡ እንዲል ፤ ዐዘዘ ፡ ዕዘዝ ፡ ባለው ፡ አስዖዘዘ ፡ ብሎ ፡ ሰዖዝዝ ፤ ቈቀወ ፡ ባለው ፡ አስቈቀወ ፡ ብሎ ፡ ሰቈቃው ፤ ቈሪር ፡ ቈረ ፡ አቍረረ ፡ ባለው ፡ አስቈረረ ፡ ብሎ ፡ ሰቈራር ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ የልማድ ፡ ፍች ፡ በበታው ፡ በለመደ ፡ ተራ ፡ ተመልከት ።

## የትንቢት ፡ ሥሮች ፡ ወይም ፡ ልማዶች ።

፴፫ ፤ የትንቢትም ፡ ልማድ ፡ ሥርወ ፡ ቃሉና ፡ ተውሳከ ፡ ፊደሉ ፡ እንደ ፡ ነቢያት ፡ ፬ ፡ ነው ፤ የ ፡ ተ ፡ አ ፡ ነ ። እነዚህ ፡ ፬ቱ ፡ ግእዞች ፡ ሳድስና ፡ ራብዕ ፡ መኾን ፡ ሳይቀር ፡ ለትንቢት ፡ አንቀጽ ፡ መነሻ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ አሥራወ ፡ ትንቢት ፡ ይባላሉ ። የ ፡ ለሩቅ ፡ ለሩቆች ፡ ለ፫ ፡ መደብ ፡ ብቻ ፤ ተ ፡ ላንዲቱ ፡ ሩቅና ፡ ላ፬ቱ ፡ ቅርቦች ፤ አ ፡ ለእነ ፡ ብቻ ፤ ነ ፡ ለንሕነ ፡ ብቻ ፤ የሥርወ ፡ ቀለም ፡ ሥር ፡ እየኾኑ ፡ ትንቢትን ፡ ኹሉ ፡ ከነላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ይለያሉ ፤ ይህም ፡ ቀተለ ፡ ልከ ፡ ልኩ ፡ ልነ ፡ ብሎ ፤ ይቀትል ፡ ትቀትል ፡ እቀትል ፡ ንቀትል ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ።

፴፬ ፤ መሠረታቸው ፡ ሳድስነት ፡ ሲኾን ፡ ግእዝና ፡ ራብዕ ፡ መኾናቸው ፡ ባመል ፡ ምክንያት ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ሖረ ፡ ባለው ፡ ግእዝ ፡ ብቻ ፤ አሖረ ፡ አስተሓወረ ፡ ባለው ፡ ራብዕ ፡ ብቻ ፤ ውሕዘ ፡ ባለው ፡ ሳድስና ፡ ግእዝ ፡ እየኾኑ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያሉ ፤ አንቀጹም ፡ አሉታ ፡ ሲኾን ፤ ኢቀተልኩ ፡ ብሎ ፡ ኢይቀትል ፡ ሲል ፡ አን ፡ የ ፡ ይወርሰዋል ፤ ከእነ ፡ በቀር ፡ የዘጠኙ ፡ አይለወጥም ። በኋምስ ፡ የሚጐርድ ፡ ይቤም ፡ የቤለ ፡ ካልኢይ ፡ ስለ ፡ ኸነ ፡ ፍጹም ፡ ትንቢት ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ በኒህ ፡ ባራቱ ፡ አሥራው ፡ ይኼዳል ፤ ትንቢትነቱን ፡ ግን ፡ ካኹን ፡ ቀደም ፡ ያየለትና ፡ የሰማለት ፡ ያወቀለት ፡ የለም ፡ (ቍ፳፬) ። አንዳንድ ፡ ዐይናሞች ፡ ግን ፡ በሚቀኙት ፡ ቅኔ ፡ ትንቢት ፡ አንቀጽ ፡ ኹኖ ፡

ይገኛል ። ወሠናይት ፡ ላሕይ ፡ መርዓት ፡ ደብረ ፡ ክርቤ ፥ ሰዐሙኒ ፡ ሰዐሙኒ ፡ ትቤ ። በኀበ ፡ ዐናብርት ፡ ዮናስ ፡ ሚ ፡ ይሜኒ ፤ እስመ ፡ ይቤ ፡ ኀጡኒ ፡ ኀጡኒ ። ስድስቱ ፡ አክናፍ ፡ አዝማዲሁ ፡ ይቤልዎ ፡ ገበሁ ፡ ገበሁ ። በእ ፡ የሚነሣ ፡ የ፫ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ ሥርወ ፡ ትንቢቱ ፡ እንደ ፡ ሖረ ፡ ነው ። አመረ ፡ የአምር ፡ ይአምር ። ተደራጊውና ፡ ተደራራጊው ፡ ግን ፡ ኹሉን ፡ ሳድስ ፡ ያደርጋል ። ተአምረ ፡ ይትአመር ፡ ይትአመር ። ተኣመረ ፡ ይትኣመር ፡ ይትኣመር ። አስደራጊውና ፡ አደራራጊውም ፡ እንደ ፡ አሖረ ፡ ነው ፤ ኹሉን ፡ ራብዕ ፡ ያደርጋል ። ይህም ፡ አእመረ ፡ ያአምር ፡ ያእምር ፤ አስተአመረ ፡ ያስተአምር ፡ ያስተአምር ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ጠብቆም ፡ በቀደሰ ፡ ቤት ፡ ሲነገር ፥ እመረ ፡ ይኤምር ፡ የእምር ። ሐወጸ ፡ ይሔውጽ ፡ የሐውጽ ፡ እያሰኘ ፡ ሳድስና ፡ ግእዝ ፡ ያደርጋል ። የአሥራው ፡ አካኼድ ፡ ይህ ፡ ነው ። ትንቢት ፡ አንቀጽ ፡ በግስ ፡ ኹሉ ፡ ከመጥበቅ ፡ በቀር ፡ መላላት ፡ የለውም ፤ ከትንቢት ፡ አንቀጽም ፡ የሚወጡ ፡ መድበል ፡ ቅጽልና ፡ ሳድስ ፡ ቅጽል ፡ ኹሉም ፡ ይጠብቃሉ ። ይህም ፡ ቀደመ ፡ ይቀድም ፡ ብሎ ፡ ቀደምት ፤ ዐጺወት ፥ ዐቀበት ። ተሰምየ ፡ ይሰመይ ፡ ብሎ ፡ ስሙይ ፤ ቅኑይ ፥ እኩት ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ላልቶ ፡ ሲነገር ፡ ግን ፡ ቀተለ ፡ ብሎ ፡ ቀተልት ፥ ተቀትለ ፡ ብሎ ፡ ቅቱል ፡ እያሰኘ ፡ ከኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ይወጣል ። ከትንቢት ፡ መውጣቱን ፡ የማያውቁ ፡ ግን ፡ በመጥበቁ ፡ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ መስሏቸው ፡ ይነቅፉታል ፤ ይልቁንም ፡ መድበል ፡ ቅጽልን ፡ ዐጉል ፡ ሰባሪ ፡ ይሉታል ።

## ፬ኛ ፡ ዕርከን ።

### የግስ ፡ አርእስት ፡ ባለ፫ና ፡ ባላ፬ ፡ ፊደላት ።

፻፳ ፤ ከኹለት ፡ ፊደል ፡ እስካ፬ ፡ ፊደል ፡ ያሉ ፡ ግሶች ፡ እንዲህ ፡ ናቸው ። ከአልፍ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ላለ ፡ ግስ ፡ ኹሉ ፡ ጠቅላዮችና ፡ መደበኞች ፡ ኹነው ፡ ነጠላ ፡ ግስን ፡ የሚመሩ ፡ የግስ ፡ አርእስቶች ፥ ከግእዝ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ባሉት ፡ በ፯ቱ ፡ ፊደላት ፡ አምሳል ፡ ፯ ፡ ናቸው ፤ ከ፯ቱ ፡ ደግሞ ፡ ፫ቱ ፡ የ፫ ፡ የ፫ ፡ ፊደል ፡ ፬ቱ ፡ ያ፬ ፡ ያ፬ ፡ ፊደል ፡ ናቸው ። ስማቸውና ፡ ተራቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ዘራቸውና ፡ አንቀጻቸው ፡ እንደ ፡ ማዕርጉ ፡ ተጥኗል ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፩ ፤ | ቀቲል ፤ | ቀተለ ፤ | ይቀትል ፡ | ይቅትል ። |
| ፪ ፤ | ቀድሶ ፤ | ቀደሰ ፤ | ይቄድስ ፡ | ይቀድስ ። |
| ፫ ፤ | ባርኮ ፤ | ባረከ ፤ | ይባርክ ፡ | ይባርክ ። |
| ፬ ፤ | ደᎀግኖ ፤ | ደᎀገነ ፤ | ይደᎀግን ፡ | ይደᎀግን ። |
| ፭ ፤ | ኖልዎ ፤ | ኖለወ ፤ | ይኖሉ ፡ | ይኖሉ ። |
| ፮ ፤ | ደንግፆ ፤ | ደንገፀ ፤ | ይደነግፅ ፡ | ይደንግፅ ። |
| ፯ ፤ | ማህርኮ ፤ | ማህረከ ፤ | ይማህርክ ፡ | ይማህርክ ። |

፻፳፩ ፤ ከነዚሁ ፡ ከ፯ቱ ፡ ደግሞ ፡ እንደሽት ፡ ተመርጠው ፡ ተለይተው ፡ ሕጸጽና ፡ ተውሳክ ፡ የሌላቸው ፡ ምሉአን ፡ ፍጹማን ፡ የኾኑ ፡ ሥረ ፡ ወጦች ፡ የ፫ ፡ ፊደል ፡ ግሶች ፡

ቀተለ ፡ ቀደሰ ፡ ባረከ፡ናቸው ፤ እሊህ ፡ ፫ቱ ፡ በየራሳቸው ፡ የቆሙ ፡ ጕንዶችና ፡ ነገዶች ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ቅጥዮችና ፡ ዲቃሎች ፡ አይደሉም ። ጠባያቸውም ፡ የ፪ቱ ፡ መሳላት ፡ መጥበቅ ፥ የ፫ኛው ፡ በራብዕ ፡ ተነሥቶ ፡ ኹሉን ፡ በራብዕ ፡ መጨረስ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ስላልን ፡ ግን ፡ የቀደሰ ፡ ጠባይ ፡ መጥበቅ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ መሳላትም ፡ አለው ፤ በ፫ቱ ፡ ጾታ ፡ ይጠብቅና ፡ በቀረው ፡ እንደ ፡ ቀተለ ፡ ይኼዳል ፤ ይህም ፡ ቀደሰ ፡ ተቀደሰ ፡ አቀደሰ ፥ ወይም ፡ አስተቀደሰ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፥ ተቃደሰ ፡ አስተቃደሰ ፡ እያለ ፡ መላላቱንና ፡ ከቀተለ ፡ መንገድ ፡ መግባቱን ፡ ያሳያል ። ባረከም ፡ በራብዕ ፡ ስለ ፡ ተነሣ ፡ ተደራጊው ፡ መደራረግን ፥ አስደራጊው ፡ ማደራረግን ፡ ደርቦ ፡ በ፪ ፡ በ፪ ፡ ይፈታል ፤ ይህም ፡ ተባረከ ፡ ብሎ ፡ በቁሙ ፡ ተባረከ ፥ ተበራረከ ፤ አስተባረከ ፡ ብሎ ፡ አስባረከ ፥ አበራረከ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ፤ አባረከ ፡ ሲል ፡ ግን ፡ ማስደረግ ፡ ብቻ ፡ ይኾናል ፤ አስተ ፡ ካለለ ፡ ማደራረግን ፡ አይደርብም ፤ መንገድና ፡ አካኼድ ፡ የማይለውጥ ፡ ቀተለ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የዴገንና ፡ የኖለወም ፡ ጠባይ ፡ በ፫ቱ ፡ ጾታ ፡ ሳይለወጥ ፡ ባ፬ኛውና ፡ ባ፰ኛው ፡ ጾታ ፡ መነሻውን ፡ ሳድስ ፡ አድርጎ ፡ የጐረዳቸውን ፡ ፊደላት ፡ የንና ፡ ወን ፡ ራብዕ ፡ በማድረግ ፡ ይለወጣል ። አካኼዱንም ፡ ባ፯ኛው ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት ። የደንገፀና ፡ የማህረከም ፡ ጠባይ ፡ መነሻውን ፡ አለመለወጥ ፡ ነው ።

፵ ፤ ዴገነ ፡ ኖለወ ፡ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ እንደነቀተለ ፡ የ፫ ፡ ፊደል ፡ ግሶች ፡ ሲኾኑ ፡ በኀምስ ፡ በሳብዕ ፡ መነሣታቸው ፥ አስቀድመን ፡ ባመል ፡ ትርጓሜ ፡ (ቍ፲፱ና ፡ ፳፫) ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ በ፫ንታቸው ፡ ርባዔ ፡ አለና ፤ ፪ቱን ፡ ዐመሎች ፡ የንና ፡ ወን ፡ ስለ ፡ ጐረዱ ፡ ነው ። ዐመላቸውን ፡ ባይጐርዱና ፡ ጐራጅ ፡ ባይኾኑ ፡ ግን ፡ ደይገነ ፡ ነውለወ ፡ ማለት ፡ የባላራት ፡ ፊደል ፡ የደንገፀ ፡ መንገድ ፡ የደንገፀ ፡ አካኼድ ፡ ነውና ፤ የ፫ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ ተብለው ፡ ለየብቻቸው ፡ ፪ ፡ አርእስት ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ከአርእስትነት ፡ ባልገቡም ፡ ነበር ፤ ዘራቸውና ፡ ምንጫቸው ፡ ግን ፡ ሥር ፡ መሠረታቸው ፡ ፫ ፡ ቅንጣት ፡ ፊደል ፡ ነው ፤ ደዩግ ፡ ዴገ ፥ ወይም ፡ ዳገነ ። ነዊል ፡ ኖለ ፥ ነወለ ።

፵፩ ፤ ደንገፀ ፡ ማህረከ ፡ እነዚህ ፡ ደግሞ ፡ ከሴም ፡ ቋንቋ ፡ ዐዋጅ ፡ ወጥተው ፡ ኹለቱ ፡ ብቻ ፡ አላመል ፡ አለደጊመ ፡ ቃል ፡ ያራት ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ መኾናቸው ፥ እንደነዴገነ ፡ ከ፫ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ የወጡ ፥ እንዳጽቅ ፡ ኹነው ፡ የበቀሉ ፡ የተቀጠሉ ፥ ቅጥዮችና ፡ ዲቃሎች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነው ፤ ፫ቱ ፡ ፊደላት ፡ እንዳንድ ፡ አባት ፥ ፬ኛው ፡ ፊደል ፡ እንደናት ፡ ኹነው ፡ ዴቅለዋቸዋል ። ደንገፀ ፡ ከደጐጸና ፡ ከተደጕጸ ፡ ወጥቷል ፤ ደጐጸ ፡ በሕሰኑ ፡ ፪ኛ ፡ ፊደል ፡ ንን ፡ ስሯጽ ፡ አግብቶ ፡ ደንገፀን ፡ ይወልዳል ። ማህረከም ፡ የመሀረ ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ ከምሂር ፡ ወጥቷል ፤ መሀረ ፡ በራሱ ፡ ፬ኛ ፡ ፊደል ፡ ከን ፡ ምእላድ ፡ ጨምሮ ፡ ማህረከን ፡ ይወልዳል ፤ ምስጢሩም ፡ የምርከ ፡ ሥራ ፡ በሥጋዊና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ኀይል ፡ በትምርትና ፡ በታምራት ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፤ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ግስ ፡ ዲቃላ ፡ ወይም ፡ ተቀጥላ ፡ ይባላል ።

፵፪ ፤ የግስ ፡ ጠባይ ፡ እንደ ፡ ተክል ፡ እንጂ ፡ ነው ፤ ተክል ፡ ከማይመስለው ፡ ዕንጨት ፡ ሲጋባ ፡ ወይም ፡ ሲራከብ ፡ ሲከተብ ፡ ጣዕሙና ፡ መልኩ ፡ ተለውጦ ፡ ሌላ ፡ ፀይነት ፡ እንዲኾን ፥ አባት ፡ ግስ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፤ የሌላ ፡ ፊደል ፡ ዘር ፡ ባዕድና ፡

ምእላድ ፡ ስሯጽ ፡ እየ ኾነ ፡ በሥር ፡ በጫፉ ፡ በመካከሉ ፡ ሲገባበት ፡ ሦስትነቱ ፡ ይቀራ ልና ፤ ንባቡም ፡ ምስጢሩም ፡ መንገዱና ፡ አካኼዱ ፡ ኹሉ ፡ ተለውጦ ፡ እንደ ፡ በቅሉ ፡ ዲቃላ ፡ ይኾናል ። ግስ ፡ የሚደቀል ፡ ወይም ፡ ዲቃላ ፡ የሚባል ፡ ባራት ፡ ወገን ፡ ነው ፤ በባዕድና ፡ በምእላድ ፡ ፈደል ፥ በስሯጽ ፡ በደጊመ ፡ ቃል ።

፻፫ ፤ በባዕድ ፥ ረተመ ፡ ብሎ ፡ ሐርተመ ፤ ጸለወ ፡ መጽለወ ፤ ነሰወ ፡ መንሰወ ፤ ነደበ ፡ መንደበ ፤ ነቀወ ፡ ሰንቀወ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። በምእላድ ፡ እንደ ፡ ማህረከ ፤ ኀሐለ ፡ ኀሕለወ ፤ ደነጸ ፡ ደንጸወ ፤ ጸዐደ ፡ ጸዕደወ ፤ በስሯጽ ፡ እንደ ፡ ደንገፀ ፤ ጠቀለ ፡ ጠንቈለ ፤ ሰአለ ፡ ሰንአለ ፤ ፀግዐ ፡ ፀንግዐ ፤ ገፍዐ ፡ ገፍትዐ ፤ ደከመ ፤ ደክተመ ፤ የመሰ ለው ፡ ኹሉ ። በደጊመ ፡ ቃልም ፡ እንደ ፡ ደምሰሰ ፤ በረደ ፡ ብርደደ ፤ ብሕረ ፡ ባሕረረ ፤ ገሥደደ ፡ ገሥድገሥደ ፤ ጠበ ፡ ጠብጠበ ፤ በረ ፡ በርበረ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። የቀረውን ፡ በደ ጊመ ፡ ቃል ፡ ፍች ፡ እይ ።

፻፬ ፤ ጥሬ ፡ ዘር ፡ ደግሞ ፥ ይልቁንም ፡ ስምና ፡ መስም ፥ በባዕድ ፡ ፈደል ፡ ላይ ፡ የማድረግና ፡ የመደረግ ፡ ልማድ ፡ ጨምሮ ፡ አንቀጽ ፡ እየ ኾነ ፡ በዲቃልነት ፡ ሲገሰስ ፡ በደንገፀና ፡ በማህረከ ፡ በ፪ቱ ፡ አካኼድ ፡ ይኼዳል ፤ ይህም ፡ ደበለ ፡ መድበል ፥ መድ በለ ፡ አመድበለ ። ዘበረ ፡ መዝበር ፥ መዝበረ ፡ አመዝበረ ፤ ተመዝበረ ። ረዐወ ፡ መር ዕው ፥ መርዐወ ፡ አመርዐወ ፤ ተመርዐወ ። ኀብረ ፡ ማኅበር ፥ አማኅበረ ። አከለ ፡ ማእ ከል ፥ አማእከለ ፤ ተማእከለ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። አንዳንዱም ፡ ጥሬ ፡ ዘር ፡ ፈደሎቹ ፡ በወ ፡ ምክንያት ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በኖለወ ፡ አካኼድ ፡ ይኼዳል ፤ ይህም ፡ ወገደ ፡ ብሎ ፡ ሞገድ ፥ ሞገደ ፡ አሞገደ ። ወገሰ ፡ ሞገስ ፥ ሞገሰ ፡ አሞገሰ ፤ ተሞ ገሰ ። ወጥሐ ፡ ሞጥሕ ፥ አሞጥሐ ፤ ተሞጥሐ ። ወቅሐ ፡ ሞቅሕ ፥ ሞቅሐ ፥ ተሞቅሐ ፡ አሞቅሐ ፡ እያለ ፡ ጥሬ ፡ ዘርነቱን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ዲቃልነቱን ፡ ያሳያል ።

## ፫ኛ ፡ ዕርከን ።

## የ፯ቱ ፡ አርእስት ፡ ሰራዊትና ፡ ድርበች ።

፻፭ ፤ ቀተለ ፡ የግስ ፡ ኹሉ ፡ አባት ፥ መሪ ፡ ፊታውራሪ ፥ የአርእስት ፡ በኵር ፥ ታላቅ ፡ ወንድምና ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፥ ጠቅላይ ፡ መስፍን ፡ ርእስ ፡ ርኡሳን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ለብቻው ፡ ፯ ፡ ሰራዊት ፡ አሉት ፤ ለቀሩት ፡ ግን ፡ ለ፮ቱ ፡ አርእስት ፡ ባመል ፡ ምክንያት ፡ የሚለወጥ ፡ ድርብ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፥ ከጭፍራ ፡ በቀር ፡ ሰርዌ ፡ የላቸውም ። ባላገባቦች ፡ ግን ፡ የግስን ፡ ጠባይ ፡ ፈጽመው ፡ ስላልመረመሩ ፥ ልማድ ፡ ያለበትን ፡ ጨምረው ፡ አር እስትን ፡ ፰ ፥ ሰራዊትን ፡ ፴ ፡ ወይም ፡ ፴፪ ፡ ይላሉ ፤ ፶ ፡ ብለው ፡ የሚቈጥሩም ፡ አሉ ። ሰራዊትም ፡ ማለት ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ አለቆች ፡ ባለብዙ ፡ ጭፍሮች ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሰረ ወንና ፡ ሠረወን ፡ ተመልከት ። ቀተለ ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፥ የቀሩት ፡ ፮ቱ ፡ እንደ ፡ ራስ ፥ ሰራዊት ፡ እንደ ፡ ደጃዝማች ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በታች ፡ እንዳሉት ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀኛዝ ማች ፡ ግራዝማች ፡ የሻንበል ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ እንደሚባሉት ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ጭፍራ ፡ እንደ ፡ ወታደር ፡ አይደሉም ።

፺፮ ፧ ቀተለን ፡ የሚከተሉ ፡ የሰራዊት ፡ ስምና ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡ ነው ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩ ፧ | ነቢብ ፧ | ነበ ፧ | ይነብብ ፡ | ይንብብ ፡ | ነባቢ ። |
| ፪ ፧ | ሠዩም ፧ | ሤመ ፧ | ይሠይም ፡ | ይሢም ፡ | ሠያሚ ። |
| ፫ ፧ | ቀዊም ፧ | ቆመ ፧ | ይቀውም ፡ | ይቁም ፡ | ቀዋሚ ። |
| ፬ ፧ | ገቢር ፧ | ገብረ ፧ | ይገብር ፡ | ይግበር ፡ | ገባሪ ። |
| ፭ ፧ | ገሪም ፧ | ገረመ ፧ | ይጌርም ፡ | ይግርም ፡ | ገራሚ ። |
| ፮ ፧ | ጠፊር ፧ | ጠፈረ ፧ | ይጠፍር ፡ | ይጠፍር ፡ | ጠፋሪ ። |
| ፯ ፧ | ጥሒር ፧ | ጥሕረ ፧ | ይጥሕር ፡ | ይጥሐር ፡ | ጠሓሪ ። |

እነዚህም ፡ ፯ቱ ፡ ሰራዊት ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ቀተለን ፡ ሲመስሉ ፥ ከርሱ ፡ የሚለዩበት ፡ ጠባይና ፡ አካኼድ ፡ ይህ ፡ ነው ። ያ፩ኛው ፡ ሰርዌ ፡ ፫ኛውን ፡ ፊደል ፡ ደጊመ ፡ ቃሉን ፡ ውጦ ፡ መጥበቅና ፡ ፪ ፡ ፊደል ፡ መኾን ። የ፪ኛና ፡ የ፫ኛ ፡ ሰርዌ ፡ ማእከሉን ፡ ጕርዶ ፡ በኃምስ ፡ በሳብዕ ፡ መነሣትና ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ፪ ፡ ፊደል ፡ መኾን ። ያ፬ኛው ፡ ሰርዌ ፡ ማእከሉን ፡ ሳድስ ፡ ሣልሳዩን ፡ ግእዝ ፡ ማድረግ ። ያ፭ኛው ፡ ሰርዌ ፡ ላልቶ ፡ ካልኣዩን ፡ እንደ ፡ ቀደስ ፡ ኃምስ ፡ ማድረግ ። የ፮ኛው ፡ ሰርዌ ፡ ጠብቆ ፡ ኹሉን ፡ በግእዝ ፡ መጨረስ ። የ፯ኛው ፡ ሰርዌ ፡ በሳድስ ፡ ተነሥቶ ፡ ኹሉን ፡ በሳድስ ፡ መጨረስ ፡ ነው ።

፺፯ ፧ ከነዚሁ ፡ ደግሞ ፡ ቀተለን ፡ መደብ ፡ አድርገው ፥ ቀደሰንም ፡ እየደረቡ ፡ ላልተውና ፡ ጠብቀው ፡ በቀተለና ፡ በቀደሰ ፡ በ፪ቱ ፡ አካኼድ ፡ የሚኼዱ ፡ አሉ ፧ ስማቸ ውም ፡ ቱሱሕ ፡ ይባላል ፧ ቅልቅል ፡ ድብልቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፧ ኰሳኵስ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹሉ ። ይኸውም ፡ በቀተለ ፡ አካኼድ ፡ ገቢር ፡ ገብረ ፥ አሚር ፡ አመረ ፥ ጸኒዕ ፡ ጸንዐ ፡ ያሉ ትን ፧ ፪ኛ ፡ በቀደሰ ፡ አካኼድ ፥ ገብሮ ፡ ገበረ ፡ ይጌብር ፥ ተገበረ ፡ ይትጌበር ፥ አገበረ ፡ ያጌብር ። አምሮ ፡ አመረ ፡ ይኤምር ፥ ተአመረ ፡ ይትኤመር ፥ ጸንዖ ፡ ጸንዐ ፡ ይጼንዕ ፡ ይጸንዕ ፡ እያሰኙ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያሉ ። መጥበቃቸውም ፡ በ፫ ፡ በ፫ ፡ አዕማድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፧ ባ፬ኛና ፡ ባ፭ኛ ፡ ዐምድ ፡ ከመላላት ፡ በቀር ፡ መጥበቅ ፡ ስለሌለ ፥ ተመ ልሰው ፡ ከዚያው ፡ ከወጡበት ፡ ከቀተለ ፡ መንገድ ፡ ይገባሉ ፧ ቀደሰም ፡ እንዲሁ ፡ ነውና ፡ (ቍ፡፴፱) ።

፺፰ ፧ ዐመል ፡ ያለባቸው ፡ የ፮ቱ ፡ አርእስት ፡ ድርቦች ፡ ደግሞ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ ፧ | ሰብሖ ፧ | ሰብሐ ፧ | ነስሐ ፧ | ሠርሐ ፧ | ጸውዐ ፧ | የቀደሰ ። |
| ፪ ፧ | ባልሖ ፧ | ባልሐ ፧ | ሣርኀ ፧ | | ዘውዐ ፧ | የባረከ ። |
| ፫ ፧ | ቈቅሖ ፧ | ቈቅሐ ፧ | ቈቀየ ፧ | ሴሰየ ፧ | ሴለየ ፧ | የዴገነ ። |
| ፬ ፧ | ዶስሖ ፧ | ዶስሐ ፧ | ሞቅሐ ፧ | ሞገደ ፧ | ሞገሰ ፧ | የኖለወ ። |
| ፭ ፧ | ገፍትዖ ፧ | ገፍትዐ ፧ | ፀንግዐ ፧ | ቀሕቅሐ ፧ | | የደንገፀ ። |
| ፮ ፧ | ጣእጥኦ ፧ | ጣእጥአ ፧ | ላዕልዐ ፧ | ላሕልሐ ፧ | ናሕንሐ ፧ | የማህረከ ። |

የድርቦች ፡ ጠባይ ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በእና ፡ በሀ ፥ በወና ፡ በየ ፡ ፍች ፡ በ፪ቱ ፡ ዐመ ሎች ፡ ተነግሯል ፡ (ቍ፲፯—፹፫) ።

፵፱ ፡ ዳግመኛም ፡ ከ፯ቱ ፡ አርእስት ፡ ለቀተለ ፡ ብቻ ፡ ከ፫ ፡ ፊደል ፡ ግሶች ፡ ብልጫ ፡ እንዳለው ÷ ለደንገፀም ፡ ከ፬ ፡ ፊደል ፡ ግሶች ፡ ብልጫ ፡ አለው ፤ ብልጫውም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ ባዕድና ፡ ልማድ ፡ ያለባቸው ፡ ዲቃሎችና ፡ አዕማዶች ፡ ኹሉ ፡ ያርእስታቸውን ፡ መድረሻ ፡ ሳብዕ ፡ በማድረግ ፡ ደንገፀን ፡ መስለው ፡ ተከትለው ÷ በርሱ ፡ መሪነት ፡ ይኼዳሉ ፡፡ ይህም ÷ ገንጽሎ ፡ ተንብሎ ÷ ገመድጕዶ ፡ አንገመድጕዶ ÷ አቅትሎ ፡ ተቀትሎ ፡ ተቃትሎ ፡ አስተቃትሎ ÷ አእምሮ ፡ ተአምሮ ÷ ተኣምሮ ፡ አስተኣምሮ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ፡፡ ማህረከም ፡ እንደ ፡ ባረከ ÷ ጻዕደወንና ፡ ሣእሥአን ፡ መስለው ፡ በራብዕ ፡ ብቻ ፡ ለሚነሡ ፡ ላ፬ ፡ ፊደል ፡ ግሶች ፡ መሪ ፡ ነው ፤ የዲቃላ ፡ ግስ ፡ ጠባዩ ፡ ካባቱ ፡ ጠባይ ፡ ልዩ ፡ ስለ ፡ ኾነ ÷ ዲቃላን ፡ ከዲቃላ ፡ በቀር ፡ የ፫ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ ሊመራው ፡ አይችልም ፡፡

፶ ፡ በ፲፫ኛ ፡ ቊጥር ÷ ግስ ፡ ከ፯ ፡ ፊደል ፡ አይወጣም ፡ ያልነውም ÷ አስተ ፡ ባ፬ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ ሲገባ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ አስተድያገነ ÷ ያስተደያግን ÷ ያስተድያግን ፤ አስተ ንዋለወ ፡ (ወይም ፡ አስተኗለወ ፡ ያስተንዋሉ ÷ ያስተንዋ(ኗ)ሉ) ፤ አስተደናገፀ ÷ አስተ ማህረከ ÷ አስተጣእጥአ ፡ እያለ ፡ ሰባትነቱን ፡ ያሳያል ፤ መስሙም ፡ በአ ፡ ፈንታ ፡ መ ፡ ስለ ፡ ገባበት ÷ መስተድያግን ÷ መስተንዋልው ÷ መስተደናግፅ ÷ መስተማህርክ ፡ መስ ተጣእጥእ ፡ እያለ ፡ ፯ ፡ ፯ ፡ ፊደል ፡ ይኾናል ፡፡

## ፯ኛ ፡ ዕርከን ፡፡

## የግስ ፡ ዐይነትና ፡ ክፍል ፡፡

፶፩ ፡ ግስ ፡ ኹሉ ፡ ገቢርና ፡ ዐጕል ፡ ተብሎ ፡ በ፪ ፡ ስምና ፡ በ፪ ፡ ዐይነት ፡ ይከፈ ላል ፡ የቋንቋ ፡ ዐይነት ፡ ከስምና ፡ ከግብር ፡ እንዳይወጣ ፡ የግስም ፡ ዐይነት ፡ ከነዚህ ፡ ከ፪ቱ ፡ አይወጣም ፡፡ ገቢር ፡ ግስ ፡ ተሳቢና ፡ ተቀባይ ፡ ያለው ÷ ሥራው ፡ ከድራጊ ፡ ወደ ፡ ተደራጊ ፡ የሚያልፍ ÷ በተደራጊ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸም ፡ ነው ፡፡ ምሳሌ ፤ ቀተለ ፡ ደምሰሰ ÷ ሰብሐ ፡ ወደሰ ÷ ባረከ ፡ ቀደሰ ÷ አኀዘ ፡ ገሰሰ ÷ ፈተወ ፡ ኀሠሠ ÷ ዘገነ ፡ ሐፈሠ ÷ ሠለሰ ፡ ሰደሰ ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ ገቢር ፡ ይባላል ፡፡

፶፪ ፡ ዐጕል ፡ ግስ ፡ ግን ፡ ተሳቢ ፡ የሌለው ÷ ሥራው ፡ ከዚያው ፡ ከድራጊው ፡ የማይወጣ ፡ በድራጊው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የሚፈጸም ፡ ነው ፡፡ ምሳሌ ፤ ሠነየ ፡ ቀደወ ÷ ም ዕዘ ፡ ጼነወ ÷ ልህቀ ፡ ወርዘወ ÷ ጥሕረ ፡ ነቀወ ÷ ሞተ ፡ ሐይወ ÷ ቆመ ፡ ሖረ ÷ ሮጸ ፡ በረ ÷ ደክመ ፡ ነበረ ÷ ኖመ ፡ ንኅረ ÷ ነደ ፡ ቈረ ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ ዐጕል ፡ ይባላል ፤ ፈናፍንት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ ተገብሮ ፡ እንዳይባል ፡ ሌላ ፡ ገባሪ ፡ የለውም ፡ ገቢር ፡ እንዳይባል ፡ ሌላ ፡ ተሳቢ ፡ የለውም ፤ አድራጊውም ፡ ተደራጊውም ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ÷ ዐጓጕል ፡ ይባላል ፡፡ ፈናፍንታም ፡ ሰው ፡ ከወንድነት ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ሴት ነት ፡ እንዲያደላ ÷ ይህም ፡ ከገቢር ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ተገብሮ ፡ ያደላል ፡ ቊጥሩም ፡ ከተገ ብሮ ፡ ነው ፡፡

፶፫ ፡ ጠባዩ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ የወል ፡ እንደ ፡ ምሰሶ ፡ የመካከል ፡ ኹኖ ፡ በገቢ ርና ፡ በተገብሮ ፡ ማኽል ፡ የቆመ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተገብሮን ፡ ብቻ ፡ ለይቶና ፡ አጥርቶ ፡

## ፫ኛ ፡ ዕርከን ።

## የርባታ ፡ መደብ ፡ ወይም ፡ ሰራዊት ።

፻፷ ፡ በባሕርይ ፡ ስም ፡ ፈንታ ፡ የአካል ፡ ስምና ፡ የስም ፡ ዐጸፋ ፡ እየ ኾኑ ፡ ስምነታቸው ፡ ሳይጠራ ፡ በዝርዝር ፡ ብቻ ፡ ፰ቱን ፡ አዕማድ ፡ በ ኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ በወንድና ፡ በሴት ፡ በሩቅና ፡ በቅርብ ፡ ባንድና ፡ በብዙ ፡ ለይተው ፡ ዘርዝረው ፡ የሚያሳዩና ፡ የሚመሩ ፡ የርባታ ፡ መደቦች ፡ እንዳሥርቱ ፡ ቃላት ፡ ፲ ፡ ናቸው ። እነዚሁም ፥ ውእቱ ፡ እሙንቱ ፥ ይእቲ ፡ እማንቱ ፥ አንተ ፡ አንትሙ ፥ አንቲ ፡ አንትን ፥ አነ ፡ ንሕነ ፡ ይባላሉ ። ከሥሩ ፡ ደግሞ ፡ ፭ቱ ፡ ያንዳንድ ፡ ፭ቱ ፡ የብዙ ፡ ፬ቱ ፡ የወንዶች ፡ ብቻ ፡ ፬ቱ ፡ የሴቶች ፡ ብቻ ፡ ፪ቱ ፡ ግን ፡ አነና ፡ ንሕነ ፡ የወንድም ፡ የሴትም ፡ እየ ኾኑ ፥ ፬ቱ ፡ በሩቅ ፡ በሩቆች ፥ ፮ቱ ፡ በቅርብ ፡ በቅርቦች ፡ ይነገራሉ ። ዳግመኛም ፡ ዐይነታቸውና ፡ ቍጥራቸው ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ሲኾን ፡ ክፍላቸው ፡ ፫ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ዐይነት ፡ ወንድና ፡ ሴት ፥ ቍጥር ፡ አንድና ፡ ብዙ ፥ ክፍል ፡ ግን ፡ ቅርብና ፡ ሩቅ ፡ አነ ፡ ንሕነ ፡ ናቸው ። አነና ፡ ንሕነ ፡ ምንም ፡ ከቅርቦች ፡ ቢቈጠሩ ፡ ስማቸውንና ፡ ግብራቸውን ፡ እኔ ፡ እኛ ፡ እያሉ ፡ ራሳቸው ፡ የሚናገሩ ፥ ወንድና ፡ ሴት ፡ የሚያስተባብሩ ፡ ነባቢ ፡ ወነባብያን ፥ ነባቢት ፡ ወነባብያት ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ በጠባያቸው ፡ ከ፰ቱ ፡ መደብ ፡ ይለያሉ ። የዘጠኙ ፡ ጥንትና ፡ መሠረት ፡ አባት ፡ እናታቸው ፡ ውእቱ ፡ ነው ፤ ዘጠኙ ፡ ኹሉ ፡ በደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ከንድ ፡ ከውእቱ ፡ የወጡ ፡ ነባር ፡ ስሞችና ፡ ነባር ፡ አንቀጾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ የርባታ ፡ መሠረት ፡ ኹነው ፡ ስማቸውን ፡ በዘመድ ፡ በባዕድ ፡ እየዘረዘሩ ፡ አንዱን ፡ አንቀጽ ፡ እስከ ፡ ፺ ፡ ያስረባሉ ።

፻፷፩ ፡ የስሞቻቸውም ፡ ዐጸፋ ፡ ወይም ፡ ዝርዝር ፡ ፫ቱ ፡ በዘመድ ፡ ፯ቱ ፡ በባዕድ ፡ ይነገራል ፤ ዘመድ ፡ ዝርዝር ፡ የ፫ቱ ፡ ብቻ ፡ የውእቱና ፡ የእሙንቱ ፡ የእማንቱ ፡ ፊደል ፡ ግእዝና ፡ ካዕብ ፡ ራብዕ ፡ መኾን ፡ ነው ፤ (ቀተለ ፡ ሉ ፡ ላ) ። ባዕድ ፡ ዝርዝር ፡ ግን ፡ ት ፡ (ቀተለት) ፡ በሩቂቱ ፡ ሴት ፡ በይእቲ ፡ ፈንታ ፡ የቀሩት ፡ ፮ቱ ፡ (ቀተል) ከ ፡ ኪ ፡ ኩ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ነ ፥ በ፮ቱ ፡ ቅርቦች ፡ ተጨምረው ፡ አንተ ፡ አንቲ ፡ አነ ፡ አንትሙ ፡ አንትን ፡ ንሕነ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይነገራሉ ። ዐይነታቸው ፡ በወንድና ፡ በሴት ፥ ቍጥራቸው ፡ ባንድና ፡ በብዙ ፥ ክፍላቸው ፡ በሩቅና ፡ በቅርብ ፡ ተለይቶ ፡ በ፪ነት ፡ እንዲነገር ፡ ዝርዝራቸውም ፡ ዘመድና ፡ ባዕድ ፡ ተብሎ ፡ በ፪ ፡ ስሞች ፡ ይጠራል ። ባዕድ ፡ ያሰኘውም ፡ በየመድረሻቸው ፡ የሚጨመር ፡ ምእላድ ፡ ፊደል ፡ ነው ፡ ዝርዝርነትን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ በዐጸፋና ፡ ቅጽል ፡ ይኾናል ።

| ዘመድ ፡ ዝርዝር ። | | ባዕድ ፡ ዝርዝር ። |
|---|---|---|
| የሩቅ ፡ ወንድ ፡ | ግእዝ ፡ ሳብዕ ፡ ካዕብ ። | ሁ ፡ ዎ ፡ ዩ ። |
| የሩቂቱ ፡ ሴት ፡ | ት ፡ ራብዕ ። | ሃ ፡ ዋ ፡ ያ ። |
| የሩቅ ፡ ወንዶች ፡ | ካዕብ ፡ ሳብዕና ፡ ሙ ። | ሆሙ ፡ ዎሙ ፡ ዮሙ ። |
| የሩቅ ፡ ሴቶች ፡ | ራብዕ ፡ ሳብዕና ፡ ን ። | ሆን ፡ ዎን ፡ ዮን ። |

«ሙና ፡ ን ፡ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ አብገሮች ፡ ናቸው» ።

የቅርብ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ያንድና ፡ የብዙ ፡ ከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ።
አነ ፡ የሚሉ ፡ የወንድና ፡ የሴት ፥ ነባቢ ፡ ወነባቢት ፡ ኢ ፡ የ ፡ ተ ።
ንሕነ ፡ የሚሉ ፡ የወንዶች ፡ የሴቶች ፥ ነባብያን ፡ ወነባብያት ፡ ነ ።
ከ ፡ ኢ ፡ የ ፡ ተ ፡ ነ ፥ እነዚህ ፡ ፊደሎች ፡ ኹሉም ፡ ሳቦችና ፡ አቀራቦች ፡ ይባላሉ ።

የርባታን ፡ መንገድ ፡ ያንቀጽን ፡ አካኼድ ፡ የሚለዩና ፡ የሚያስለዩ ፥ ጸዋትወ ፡ ርባን ፡ በየስልቱ ፡ ለይተው ፡ አጥርተው ፡ የሚያሳዩ ፡ ያውራው ፡ ትምርት ፡ በግ ፡ የርባ ፡ ቅምር ፡ ዐይኖችና ፡ ቀንዶች ፡ ፲ ፡ ናቸው ፡ (ራእ፳ ፡ ፯) ። እነዚሁም ፡ አርእስት ፥ ሰራዊት ፥ ዐመል ፥ ልማድ ፥ አዕማድ ፥ አሥራው ፥ ምእላድ ፡ (ወይም ፡ ዝርዝር) ፡ ይባላሉ ፤ እስከዚህ ፡ ርባ ፡ ቅምር ፡ ነው ።

## ፪ኛ ፡ ክፍል ።

## ጸዋትወ ፡ ርባ ፡

የሰዋስው ፡ ሆድና ፡ ዠርባ ፤ ወርዱና ፡ ቁመቱ ፡ ስፋቱ ፡ እንደ ፡ ጽዮን ፡ አንባ ፥ በየዋሁ ፡ በዳዊት ፡ ግንብና ፡ በመሠረው ፡ በሰሎሞን ፡ ቤት ፡ ልክ ፡ ተመሥርቶ ፡ ስለ ፡ ተገነባ ፥ ፲ ፡ መደብ ፡ ቁጥር ፡ የሚከት ፡ ፹ውንም ፡ የሚያገባ ።

## «ጃን ፡ ደረባ ፡ ዐዋጅ» ።

## የርባታና ፡ ያንቀጽ ፡ ስምና ፡ ረድፍ ።

፻፲ ፤ የርባታ ፡ ስሞች ፡ እንዳገባብ ፡ ስሞች ፡ ፫ ፡ ናቸው ፤ ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ ደቂቅ ፡ ይባላሉ ፤ ዐቢይ ፡ ርባታ ፡ እስከ ፡ ፹ ፡ አካል ፡ የሚዘመት ፡ የ፫ቱ ፡ ዐበይት ፡ አናቅጽ ፡ የኀላፊና ፡ የትንቢት ፡ የትእዛዝ ። ንኡስ ፡ ርባታ ፡ ያ፳ቱ ፡ ንኡሳን ፡ አናቅጽ ፤ እሊሁም ፡ ዘንድና ፡ አርእስት ፥ በዝና ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፥ ሳቢ ፡ ዘር ፡ ናቸው ። ደቂቅ ፡ ርባታ ፡ የጥሬ ፡ ዘርና ፡ የነባር ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ በስገኙነቱ ፡ አባት ፡ ዘር ፡ እንዲባል ፡ ኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ደግሞ ፡ የከልአይና ፡ የኅልሳይ ፡ በኵር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ቀዳማይ ፡ ይባላል ፡ የቀረውም ፡ ጥሬ ፡ ባ፲ ፡ መደብ ፡ የሚረባ ፡ ኹሉ ፥ ንኡስና ፡ ደቂቅ ፡ ይባላል ፤ ታናናሽ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፻፱ ፤ ባቢይ ፡ ርባታ ፡ ውስጥ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ አለ ፤ ያለፈና ፡ ያኹን ፡ የሚመጣ ፤ የዐቢይ ፡ ርባታም ፡ መንገድና ፡ አካኼድ ፡ ፬ ፡ ረድፍ ፡ ነው ። ፩ኛው ፡ ረድፍ ፥ ቀተለ ፡ (ኀላፊ) ፡ ገደለ ። ይቀትል ፡ (ያኹንና ፡ ትንቢት) ፡ ይገድል ። ይቅትል ፡ (ዘንድና ፡ ትእዛዝ) ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፥ እንዲገድል ፡ ሊገድል ፤ (ይቅትል) ፡ ይግደል ፡ እያለ ፡ በመደበኛነት ። ፪ኛው ፡ ረድፍ ፡ ቀተሎ ፡ ገደለው ፤ ይቀትሎ ፡ ይገድለው ፥ ይቅትሎ ፡ ይገድለው ፡ ዘንድ ፡ ይግደለው ፡ እያሰኘ ፡ በዝርዝርነት ። ፫ኛው ፡ ረድፍ ፥ ቀተሎ ፡ ሀለወ ፥ ገድሏል ፡ ገድሎ ፡

ነበር ፡ ይቀትል ፡ ሀሎ ፥ ይገድላል ፡ ይገድል ፡ ነበር ፡ ቀቲሎ ፡ የሀሉ ፡ ገድሎ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፥ ገድሎ ፡ ይኑር ፡ እያሰኘ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ይዘምታል ። የነዚህም ፡ የ፫ቱ ፡ ረድፎች ፡ ስም ፡ የዋህ ፥ መሠሪ ፥ ጽንዕ ፡ ይባላል ።

፳፭ ፡ ኸነ ፡ አለ ፡ ኖረ ፡ ነበረ ፡ የሚያሰኙ ፡ የጽንዕ ፡ አንቀጾች ፡ ፬ ፡ ናቸው ፡ ፬ቱ ፡ ዘማቾች ፥ ፬ቱ ፡ ነባሮች ፡ ዘማቾች ፡ ሀሎና ፡ ኮነ ፥ ነባሮች ፡ ውእቱና ፡ ቦ ፡ ሎ ፡ ቦና ፡ ሎ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ኮነ ፡ በትንቢት ፡ ብቻ ፡ ትርጓሜ ፡ እየኸነ ፡ በቀዳማይነት ፡ ይገባል ። ይህም ፡ ኮነ ፡ ይፈርህ ፥ ኮነ ፡ ይጐይይ ፥ ኮነ ፡ ይትነበእ ፡ እያሰኘ ፡ ይፈራ ፡ ነበር ፡ ይሸሽ ፡ ይደበቅ ፡ ነበር ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ፡ ሀሎም ፡ ኮነ ፡ በገባበት ፡ ይገባል ። ትርአስ ፡ እየኸ ነም ፡ በካልኣይነት ፡ ሲገባ ፡ ቀቲሎ ፡ ይከውን ፥ ይቀትል ፡ ይከውን ፡ እያሰኘ ፡ ጥያቄና ፡ ምኞት ፡ ይኸናል ። አለና ፡ ነበረ ፥ ወይም ፡ አልና ፡ ነበር ፡ ተብለው ፡ የሚፈቱ ፡ አና ቅጽ ፡ ኹሉም ፡ ጽንዕ ፡ ይባላሉ ፡ አልና ፡ ነበር ፡ ቦነላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ሲገቡ ፥ አል ፡ ጥቂት ፡ የቈየ ፡ የዘገየ ፡ ማእከላይ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ያለፈና ፡ የራቀ ፡ ረዥም ጊዜ ፡ ያሳያል ፡ በትንቢት ፡ አንቀጽም ፡ ሲገቡ ፥ ነገሩ ፡ የማይቀር ፡ የማይጠረጠር ፥ ርግጥና ፡ ቍርጥ ፡ መኾኑን ፥ ጥናቱን ፡ ብርታቱን ፡ ያሳያሉ ። ፩ኛው ፡ ረድፍ ፡ አ ሉታ ፡ ነው ፡ አሉታም ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ። ኢቀቲል ፡ ሎት ፡ አለመግደል ። ኢቀተለ ፡ አልገደለ ፥ አልገደለም ፡ ኢይቀትል ፥ አይገድል ፡ አይገድልም ። ኢይቅትል ፡ እንዳይ ገድል ፥ ላይገድል ፥ ሳይገድል ። ኢይቅትል ፡ አይግደል ፡ እያሰኘ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ይዘም ታል ። እስከዚህ ፡ ዐዋጅ ፡ ነው ።

፳፮ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የ፲ውን ፡ አርእስት ፡ ፲ሩን ፡ መደብ ፡ ፲ውም ፡ ሳይ ቀር ፥ ነገር ፡ ለማሳጠር ፡ ካልኣይና ፡ ሣልሳይ ፡ ሳንጨምር ፡ በቀዳማይ ፡ ብቻ ፡ ከነሰራ ዊቱ ፡ እያቈራኘን ፡ እንጥፋለን ፡ በርባታ ፡ ጊዜ ፡ ዝርዝራቸው ፡ በቂ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ም ንም ፡ ስማቸው ፡ ባይፈለግ ፡ የርባታን ፡ መደብ ፡ ስሙን ፡ ጠርቶ ፡ ራሱን ፡ ቈርቶ ፡ ለመ ንገርና ፡ ለማሳየት ፡ ማቈራኘት ፡ ይገባልና ። የብዙ ፡ ወንድና ፡ የብዙ ፡ ሴት ፡ አንቀጽ ፡ (ፆቁ ፡ ፆቃ) ፡ በግእዝ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሲኾን ፥ በማርኛ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ፡ የሴቶቹም ፡ በወንዶቹ ፡ ስልት ፡ ዐወቁ ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ።

## ፳ኛ ፡ ዕርከን ።

## ዐቢይ ፡ ርባታ ፡ ከነጓዙ ፡ ከናበጋዙ ።

፳፯ ፡ (አንዳንድ ፡ሩቅና ፡ ቅርብ ፡ ወንድና ፡ ሴት) ፡ (ብዙዎች ፡ ሩቆችና ፡ ቅርቦች ፡ ወንድና ፡ ሴት) ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቱ ፡ | ቀተለ ። | እሙንቱ ፡ | ቀተሉ ። |
| ይእቲ ፡ | ቀተለት ። | እማንቱ ፡ | ቀተላ ። |
| አንተ ፡ | ቀተልከ ። | አንትሙ ፡ | ቀተልክሙ ። |
| አንቲ ፡ | ቀተልኪ ። | አንትን ፡ | ቀተልክን ። |
| (ነባቢ ፡ ት) ፡ | (ወንድና ፡ ሴት) ፡ | (ነባብያን ፡ ት) ፡ | (ወንድና ፡ ሴት) ፡ |
| አነ ፡ | ቀተልኩ ። | ንሕነ ፡ | ቀተልነ ። |

ይህ፡ ፲ሩ፡ መደብ፡ በሥሩ፡ አንቀጽ፡ ኹሉ ፥ ወይም፡ በ፩ሰው ፥ ገዳዩን፡ ብቻ፡ እንጂ ፥ የሟቹን፡ አንድና፡ ብዙነት ፥ ወንድና፡ ሴትነት ፥ ቅርብና፡ ሩቅነት፡ የማይለይ፡ ዕፍንና፡ ጭፍን፡ ድፍን፡ ስለ፡ ኾነ፡ የዋህ፡ ይባላል፡ ሞኝ፡ ማለት፡ ነው ። ከዚህ፡ ቀጥሎ፡ የሚመጣው፡ ፲፫ው፡ አንቀጽ፡ ግን፡ ኹሉን፡ ዘርዝሮ፡ የሚያሳይ፡ ጠቃሽ፡ ስለ፡ ኾነ፡ ስሙ፡ መሠሪ፡ ይባላል፤ ባላገቦች፡ ግን፡ የዋሁን፡ መሠሪ ፥ መሠሪውን፡ የዋህ፡ ይሉታል ። መሠሪም፡ ያሰኘው ፥ ቀተሎ፡ ብሎ፡ ባንዲት፡ ቃል ፥ ገደለው፡ ገደለበት፡ ገደለለት፡ እያሰኘ፡ እንዳዝማሪ፡ ግጥም፡ ክፉና፡ መልካም፡ ማሳየት፡ ነው ። ምሳሌ፡ ትሰሙ፡ እንደ ኾነ፡ የወንጌል፡ ቃል ፥ አለ-መስጠት፡ ያጸድቃል ።

፳፫ ፡ ሲዘረዝርም፡ ፬ቱን፡ ሩቆች፡ ባ፲፡ ባ፲፡ ይዘረዝርና፡ ከ፰ቱ፡ ቅርቦች፡ ፬ቱን፡ በ፰፡ በ፰ ፥ ፪ቱን፡ በ፳፡ በ፳፡ ይዘረዝራል፤ ፻፡ መባሉ፡ ስለዚህ፡ ነው ። ለመሠሪ፡ ርባታ፡ ፫፡ አዝማችና፡ ፫፡ መዝመቻ፡ አለው፤ አዝማች፡ ፩ና፡ ብዙ ፥ መዝመቻ፡ ሩቅና፡ ቅርብ፡ ናቸው ። በ፩ኛው፡ አዝማች፡ አንዱ፡ ፲ሩን፡ በሩቅ፡ በሩቅ ፥ ፰ቱን፡ በቅርብ፡ በቅርብ፡ ይገድላል፤ ሟቾች፡ ፲፰፡ ገዳያቸው፡ ፩ ። በ፪ኛው፡ አዝማች፡ ፲ሩ፡ አንዱን፡ በሩቅ፡ በሩቅ ፥ ፰ቱ፡ በቅርብ፡ በቅርብ፡ ይገድሉታል፤ ሟች፡ ፩ ፥ ገዳዮች፡ ፲፰ ። በ፫ኛው፡ አዝማች፡ የሩቅና፡ የቅርብ፡ ጠቅላዮች፡ እኔ፡ ንሕነ፡ ባዮች፡ እነዚህ፡ ፪ቱ ፥ ከ፳ቱ፡ መደብ፡ ፬ቱን፡ ሩቆች፡ በሩቅ፡ በሩቅ ፥ ፬ቱን፡ ቅርቦች፡ በቅርብ፡ በቅርብ፡ ይገድላሉ ። ፪፡ ጊዜ፡ ፳፡ ፲፰፡ ነው፡ ፷፬ቱ፡ ፲፰፡ ፻፡ ይባላል ። ግስ፡ ኹሉ፡ እንዲህ፡ በ፫፡ አዝማች፡ ባ፲፡ ሰራዊት፡ በ፻፡ መደብ፡ ሲረባ፡ ፻፲፯፡ አንቀጽ፡ ይኾናል፤ ከዚሁ፡ ደግሞ፡ ፻ው፡ ኀላፊ ፥ ፻ው፡ ትንቢት ፥ ፻ው፡ ትእዛዝ፡ ይባላል፤ ፫ቱ፡ ፻፡ ፻፲፯፡ ነው ።

## ዐሥሩ፡ ሰራዊትና፡ ሰማኒያው፡ መደብ ።

| | |
|---|---|
| ውእቱ)፡ | ቀተሎ፡ ላ፡ ሎሙ፡ ሎን ። ቀተለከ፡ ኪ፡ ክሙ፡ ክን፡ ኒ፡ ነ፡ (፲) ። |
| አንተ)፡ | ቀተልከ፡ ካ፡ ከሙ፡ ክን፡ ከኒ፡ ነ፡ (፰) ። |
| እሙንቱ)፡ | ቀተልዎ፡ ዋ፡ ዎሙ፡ ዎን ። ሉከ፡ ኪ፡ ክሙ፡ ክን፡ ኒ፡ ነ፡ (፲) ። |
| አንትሙ)፡ | ቀተልክምዎ፡ ዋ፡ ዎሙ፡ ዎን፡ ሙኒ፡ ነ፡ (፰) ። |
| ይእቲ)፡ | ቀተለቶ፡ ታ፡ ቶሙ፡ ቶን ። ተከ፡ ኪ፡ ክሙ፡ ክን፡ ተኒ፡ ነ፡ (፲) ። |
| አንቲ)፡ | ቀተልኪዮ፡ ያ፡ ዮሙ፡ ዮን፡ ክኒ፡ ክነ፡ (፰) ። |
| እማንቱ)፡ | ቀተላሁ፡ ሃ፡ ሆሙ፡ ሆን ። ላከ፡ ኪ፡ ክሙ፡ ክን፡ ኒ፡ ነ፡ (፲) ። |
| አንትን)፡ | ቀተልክናሁ፡ ሃ፡ ሆሙ፡ ሆን፡ ናኒ፡ ናነ፡ (፰) ። |
| አነ)፡ | ቀተልክዎ፡ ዋ፡ ዎሙ፡ ዎን ። ኩከ፡ ኪ፡ ክሙ፡ ክን፡ (፰) ። |
| ንሕነ)፡ | ቀተልናሁ፡ ሃ፡ ሆሙ፡ ሆን ። ናከ፡ ኪ፡ ክሙ፡ ክን፡ (፰) ። |

የሩቅ፡ ወንድና፡ ሴት፡ ባዕዱ፡ ዝርዝራቸው፡ ወይም፡ ዐጸፋቸው፡ ሁ፡ ሃ፡ ስለ፡ ኾነ ፥ ቀተልከ፡ ካ፡ ከሙ፡ ክን፡ ባለው ፥ ቀተልክሁ፡ ሃ፡ ሆሙ፡ ሆን፡ ይላል፤ ፍችው፡ ፩፡ ነው ። ፈጠርካሆሙ፡ ለመላእክት ። ወልደከ፡ ዘቀባዕካሁ፡ (ድጓ ። ግብ) ።

፳፬ ፡ ዳግመኛም፡ በትናጋ፡ የሚነገሩና፡ ተወራራሽነት፡ ያላቸው፡ ፫ቱ፡ ወንድማማች፡ ፊደላት፡ ገከቀ ፥ የግስ፡ መድረሻ፡ ሲኾኑ፡ በ፰ቱ፡ ቅርቦች፡ ያለውን፡ ከ፡

ደጊመ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ መኾኑ ÷ ውጠውና ፡ ጎርደው ፡ እያጠበቁ ፡ ከመጣፉና ፡ ከመና ገር ፡ በግድ ፡ ያስቀሩታል ፡፡ ይህም ÷ አንተ ፡ ነደግ ፡ ሆነ ፡ ዖቀ ፡ አንቺ ፡ ነደጊ ፡ ሆኪ ፡ ዖቂ ፡ አንትሙ ፡ ነደግሙ ፡ ሆክሙ ፡ ዖቅሙ ፡ አንትን ፡ ነደግን ፡ ሆክን ፡ ዖቅን ፡ አነ ፡ ነደጉ ፡ ሆኩ ፡ ዖቁ ፡ እያሰኘ ፡ መዋጡንና ፡ መጥበቁን ፡ ያሳያል ፡፡ የቅርቡ ፡ ወንድና ፡ የሩቁ ፡ ወንድ ÷ ነደገ ፡ ሆነ ፡ ዖቀ ፡ የእነና ፡ የሩቆቹም ፡ ወንዶች ÷ ነደጉ ፡ ሆኑ ፡ ዖቁ ፡ ከመጥበቅና ፡ ከመላላት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መለዮ ፡ የለውም ፡፡ የርባታን ፡ ዐዋጅ ፡ ያላየ ፡ ያልሰማ ፡ ጣፊና ፡ አንባቢ ፡ ግን ÷ የሚጠብቀውን ፡ የቅርቡን ፡ ነደግ ፡ ሆነ ፡ ዖቀ ፡ ከማ ይጠብቀው ፡ ከሩቁ ፡ ነደገ ፡ ሆነ ፡ ዖቀ ፡ አጥብቆ ፡ ሊለየው ፡ አይችልም ፡፡ ወየጡ ፡ ለሰ ዋስው ፡ ትምርት ÷ የንባብና ፡ የትርጓሜ ፡ መብራት ፡ (ቍ፴) ፡፡

፫፻፫ ፡ የሀለወና ፡ የሀሎም ፡ ርባታ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ፪ቱም ፡ እስከ ፡ ሣልሳይ ፡ ይረ ባሉ ፡፡ ሀሎ ፡ በ፲፯ ፡ ሰራዊት ÷ ውእቱ ፡ አንተ ፡ አንትሙ ፡ አንቺ ፡ አንትን ÷ አነ ፡ ንሕነ ፡ ባለው ÷ በነዚህ ፡ ሲረባ ፡ በቀዳማይ ፡ ብቻ ፡ ይገኛል ፡ ይህም ፡ ሀሎ ፡ ሀሎከ ፡ ሀሎ ክሙ ፡ ሀሎኪ ፡ ሀሎክን ፡ ሀሎኩ ፡ ሀሎን ፡ እያለ ፡ በጎራጅነት ፡ መገኘቱን ÷ አለመቃ ጣቱን ፡ ያሳያል ፡፡ ሀሎና ፡ ሀለወ ፡ ባ፲ ፡ ሰራዊት ፡ ሲረቡ ፡ በየፊታቸው ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ፡ አን ቀጽ ፡ ይኾኑና ÷ ሲደመሩ ፡ ፴፬ ፡ አንቀጽ ፡ ይኾናሉ ፡ ከሀሎ ፡ በቀር ፡ ፴ ፡ እንጂ ፡ ፴፬ ፡ የሚኾን ፡ የለም ፡ አረባቡና ፡ አኳኋኑም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

| (ጎራጅ) ፡፡ | | (ሥርው) ፡፡ | |
|---|---|---|---|
| ፫ ፡ | ሀሎ ፡ ይሄሉ ፡ የሀሉ ፡ | ፩ ፡ | ሀለወ ፡ |
| ፫ ፡ | ሀሎከ ፡ ትሄሉ ፡ ሀሉ ፡ | ፫ ፡ | ሀለዉ ፡ ይሄልዉ ፡ የሀልዉ ፡ |
| ፩ ፡ | ሀሎክሙ ፡ | ፫ ፡ | ሀለውክሙ ፡ ትሄልዉ ፡ ሀልዉ ፡ |
| ፪ ፡ | ትሄሉ ፡ ተሀሉ ፡ | ፩ ፡ | ሀለወት ፡ |
| ፩ ፡ | ሀሎኪ ፡ | ፪ ፡ | ትሄልዊ ፡ ሀልዊ ፡ |
| ፩ ፡ | ሀሎክን ፡ | ፫ ፡ | ሀለዋ ፡ ይሄልዋ ፡ የሀልዋ ፡ |
| ፫ ፡ | ሀሎኩ ፡ እሄሉ ፡ አሀሉ ፡ | ፫ ፡ | ሀለውክን ፡ ትሄልዋ ፡ ሀልዋ ፡ |
| ፫ ፡ | ሀሎን ፡ ንሄሉ ፡ ነሀሉ ፡ | ፩ ፡ | ሀለውን ፡ |
| | ድምር ፡ ፲፯ ፡ አንቀጽ ፡፡ | | ድምር ፡ ፲፯ ፡፡ ፲፯ና ፡ ፲፯ ፡ ፴፬ ፡፡ |

በዝርዝር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ኹሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ፡፡

፫፻፬ ፡ ሆበና ፡ ወሀበም ፡ ሲረቡ ÷ የሆበ ፡ አካኼድ ፡ እንደ ፡ ሆከና ፡ እንደ ፡ ሖረ ፡ በቶመ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የወሀበም ፡ እንደ ፡ ወሐከና ፡ እንደ ፡ ወዐለ ፡ በቀተለ ፡ ቤት ፡ ነው ፡፡ ይህም ÷ ሀዊብ ፡ ሆበ ፡ የሀውብ ፡ ይሁብ ፡፡ ውሂብ ፡ ወሀበ ፡ ይውህብ ፡ የሀብ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ፡፡ መምህራን ፡ ግን ፡ ሆበን ፡ ከወሀበ ፡ አዝንቀው ÷ የሆበን ፡ ሣልሳይ ፡ ይሁብን ፡ ለወሀበ ፡ ካልአይ ፡ አድርገው ፡ በይውህብ ፡ ፈንታ ÷ ወሀበ ፡ ይሁብ ÷ ወሀብከ ፡ ትሁብ ÷ ወሀብኩ ፡ እሁብ ፡ እያሉ ፡ አለመንገዱ ፡ ያረቡታል ፡፡ የቤለን ፡ ካልአይ ፡ ይቤን ፡ ከብ ሀለ ፡ ደርበው ፡ ቀዳማይ ፡ አንቀጽ ፡ እንዳሉት ፡ የብሀለንም ፡ ትንቢት ፡ ይብልን ፡ ለይቤ ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡ ቀሐመንም ፡ ከቀምሐ ፡ ደርበው ፡ አለስሙና ፡ አለመልኩ ፡ አለዘይ

ቤው ፡ እንዲፈቱት ፥ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። የቃላቁ ፡ ዳብ ፡ የአእመረና ፡ የብህለ ፡ የይቤም ፡ ሊጥንት ፥ በትምርት ፡ አለመብሰሉ ፥ ያውም ፡ ያልተነፋ ፡ ዶቄት ፡ መኾኑ ፡ በ፲፪ና ፡ በ፲፫ ፡ በ፳፬ ፡ ቍጥር ፡ ተነግሯል ። የዐበይት ፡ አናቅጽ ፡ አካኼድና ፡ አረማመድ ፡ የርባታቸውም ፡ ጥርጊያ ፡ መንገድ ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። የቀረውን ፡ በቃላቁ ፡ ግስ ፡ ውስጥ ፡ በየፊደሉ ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ይልቅ ፡ በዚያ ፡ የተጣፈው ፡ ያጠግብኻል ።

## ፱ኛ ፡ ዕርከን ።

## ንኡሳን ፡ አናቅጽ ።

፻፺፯ ፤ ከዐበይት ፡ አናቅጽ ፡ በኋላ ፡ ንኡሳን ፡ አናቅጽ ፡ ተብለው ፡ በንኡስ ፡ ርባታ ፡ የሚረቡ ፥ አስቀድመን ፡ ባ፶፯ ፡ ቍጥር ፡ የጣፍናቸው ፡ ዘንድና ፡ አርእስት ፥ በግዝና ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፥ ሳቢ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ ፫ቱ ፡ ከመሳብ ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ፫ቱ ፡ ዐበይት ፡ አናቅጽ ፡ ነገር ፡ ሰብስበው ፡ የማያስሩ ፡ የማይጠቀልሉ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ንኡሳን ፡ አናቅጽ ፡ ይባላሉ ። ዘንድ ፡ አንቀጽ ፡ በአነ ፡ በንሕነ ፡ ባራቱ ፡ ሩቆች ፥ በነዚህ ፡ በ፮ቱ ፡ ኹሉ ፡ ከትእዛዝ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ዐይነት ፡ ነው ፤ ካፈታት ፡ በቀር ፡ የንባብ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ፤ ልዩነቱ ፡ በ፬ቱ ፡ ቅርቦች ፡ ነው ፤ ባካኼዱ ፡ ኹሉ ፡ አሥራውን ፡ አይተውም ፤ ጠባዩም ፡ ሳቢና ፡ ተሳቢ ፡ እየኾነ ፡ የአንቀጽን ፡ ሥራ ፡ መግለጥ ፡ ነው ። ትእዛዝ ፡ ግን ፡ ከአነና ፡ ከንሕነ ፡ በቀር ፡ ባራቱ ፡ ቅርቦች ፥ ቅትል ፡ ሉ ፡ ሊ ፡ ላ ፡ እያለ ፡ አሥራውን ፡ ይተዋል ። ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ትእዛዝ ፡ መኾኑ ፡ ወይም ፡ መባሉ ፡ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ሲነገር ፡ ነው ፤ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲነገር ፡ ግን ፡ ልመናና ፡ ጸሎት ፡ ይባላል ። የዘንድና ፡ የትእዛዝ ፡ ምስጢር ፡ ምንም ፡ ከትንቢት ፡ ባይወጣ ፥ ትእዛዝ ፡ የሚባል ፡ በቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ ያ፬ቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ አንተ ፡ አንቲ ፡ አንትሙ ፡ አንትን ፡ ከሚባሉት ፡ ከነዚህ ፡ ከ፬ቱ ፡ በቀር ፡ በአነና ፡ በንሕነ ፡ ፊት ፡ ቁሞ ፡ የሚታዘዝ ፡ የለም ። ምክንያቱም ፡ ያራቱ ፡ ትእዛዝ ፡ አሥራውን ፡ ትቶ ፡ ብቻውን ፡ የሚኼድ ፥ የ፮ቱ ፡ ግን ፡ አላሥራው ፡ የማይኼድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፤ ስማቸውም ፡ ሣልሳይና ፡ ትእዛዝ ፡ ተብሎ ፡ ይለያል ፤ ሣልሳይ ፡ ላሥሩ ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ፤ ትእዛዝ ፡ ግን ፡ ላ፬ቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፻፺፰ ፤ አባት ፡ ዘር ፡ ያልነው ፡ የቃላቁም ፡ የንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ጠባይ ፥ ሙያውና ፡ ዐመሉ ፥ ስሙም ፡ ዘርና ፡ አርእስት ፡ መባሉ ፥ አዘራዘሩና ፡ አረባቡ ፡ ሳይቀር ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በመገርመሪያው ፡ ክፍል ፡ ባ፫ኛ ፡ ቍጥር ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በ፪ኛው ፡ ክፍል ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ተነግሯል ፤ አኹንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በንኡስ ፡ ርባታ ፡ ይመጣል ። የዘንድና ፡ የሣልሳይ ፡ ዐመል ፡ ከርእስት ፡ በፊት ፡ መነገሩ ፥ ስላናቅጽ ፡ ተራ ፡ ነው ፤ እንጂ ፤ ስለ ፡ ማዕርግ ፡ አይዶለም ፤ በስምና ፡ በማዕርግስ ፡ አርእስት ፡ ይቀድማል ።

፻፺፱ ፤ ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ እንደ ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ከያዕማዱ ፡ ሲወጣ ፡ ቀቲሎ ፡ አቅቲሎ ፡ ተቀቲሎ ፥ ተቃቲሎ ፡ አስተቃቲሎ ፡ እያለ ፡ መድረሻውን ፡ ሳብዕ ፡ ያደርግና ፡ አንቀጽነቱ ፡ በዘንተኛ ፡ ሰነፍ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ መዋቆ ፡ ሐይወ ፡ ቀዲሐ ፡ ከዐወ ፡ እያለ ፥ ሌላ ፡ አንቀጽ ፡ በመሳብ ፡ ቸልታ ፡ ኹኖ ፡ ይቀራል ። ሀለወንና ፡ ውእቱን ፡ ሲስብ ፡ ግን ፡ ባ፷፱ ፡

ቀኖር ፡ እንደ ፡ ተባለ ፥ በዝነቱ ፡ ጽንዕ ፡ እየኾነለት ፡ በቀዳማይነት ፡ ይዘምታል ፤ ይህም ፡ ቀተሎ ፡ ሀለወ ፡ ወይም ፡ ቀተሎ ፡ ውእቱ ፤ ቀተላ ፡ ይእቲ ፡ ቀተልየ ፡ አነ ፥ ቀተለነ ፡ ንሕነ ፡ እያሰኘ ፥ ገድሎናል ፡ ገድለን ፡ ነበር ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ።

፹ ፡ ፫ኛም ፡ ዐበይት ፡ አገባቦች ፡ አመ ፡ ሰበ ፡ ድኅረ ፡ እንዘ ፡ በሚገቡባቸው ፡ በዐበይት ፡ አናቅጽ ፡ ፈንታ ፡ ወተወሊዶ ፡ ወተጠሚቆ ፡ ወጸቢሖ ፡ ወቀቲሮ ፡ ወመስዮ ፡ ወምሴተ ፡ ከዊኖ ፥ ወከዊኖ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ እያለ ፡ በወ ፡ ከፋይነት ፡ ይገባና ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ከመሸ ፡ በኋላ ፥ ሲመሽ ፡ መሽቶ ፡ ሳለ ፡ እያሰኘ ፡ እንዳበይት ፡ አናቅጽ ፡ ይፈታል ። ሲረባም ፡ እንዳበይት ፡ አናቅጽ ፡ በሥሩ ፡ መደብ ፥ ቀቲሎ ፡ ላ ፡ ለከ ፡ ለኪ ፡ ልየ ። ቀቲሎሙ ፡ ሎን ፡ ለክሙ ፡ ክን ፡ ለነ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፥ ቀቲሎሁ ፡ ሃ ፡ ሎከ ፡ ኪ ፡ ሎየ ። ቀቲሎሆሙ ፡ ሆን ፡ ሎክሙ ፡ ክን ፡ ሎነ ፡ ብሎ ፤ ቅርቡንም ፡ ቀቲለከሁ ፡ ሃ ፡ ከሆሙ ፡ ሆን ፡ ከኒ ፡ ከነ ፡ እያሰኘ ፡ እስከ ፡ ፺ ፡ ይዘምታል ፤ ካ፳ቱ ፡ ንኡሳን ፡ አናቅጽ ፡ ከዘንድና ፡ ከቦዝ ፡ ከ፪ቱ ፡ በቀር ፡ እስካሥር ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ እስከ ፡ ፺ ፡ የሚወጣ ፡ የለም ።

## ውስጠ ፡ ዘና ፡ መስም ።

፹፩ ፡ ሠራተኛ ፡ አካል ፡ በሥራው ፡ የሚጠራባቸው ፡ ስሞች ፡ ኹሉ ፡ በውስጣቸው ፡ ዘ ፡ እንተ ፡ እለ ፡ ስላሉባቸው ፡ ኹሉም ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ተብለው ፡ ለተጸውዖና ፡ ለተቀብዖ ፡ ለባሕርይ ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ በቅጽልነት ፡ ወይም ፡ በበቂነት ፡ ይነገራሉ ፡ ቅጽል ፡ ባለቤት ፡ አካል ፡ ነውና ። የውስጠ ፡ ዘም ፡ ዐይነት ፡ ፫ ፡ ነው ፤ ሣልስና ፡ ሳድስ ፡ ማእከል ። ሣልስ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ካ፳ቱ ፡ አዕማድ ፡ ይወጣል ። መስም ፡ ደግሞ ፡ የሣልስ ፡ ድርብ ፡ እየኾነ ፡ ከተገብሮ ፡ በቀር ፡ ካራቱ ፡ አዕማድ ፡ ይወጣል ፤ ይህም ፡ ቀታሊ ፡ መቅትል ፥ አቅታሊ ፡ መቅተሊ ፥ ተቃታሊ ፡ አስተቃታሊ ፡ መስተቃትል ፡ ብሎ ፥ በሌላውም ፡ አንቀጽ ፡ ሐዋሪ ፡ ሐዋርያ ፥ ከያኒ ፡ ኬንያ ፥ ገሣጺ ፡ መገሥጽ ፥ ኰናኒ ፡ መኰንን ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ቀተል ፡ ሥራ ፥ ቀታሊ ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ የሠራተኛ ፡ ስም ፡ ቀትል ፡ የሥራው ፡ ስም ፡ ምቅታል ፡ ምስትቅታል ፡ የቦታና ፡ የመሣሪያ ፡ ስም ፡ ይኾናል ።

፹፪ ፡ ሳድስ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ከተገብሮና ፡ ከሐውልት ፡ ይወጣል ፤ ገቢርና ፡ አግብሮ ፡ በሣልስ ፡ ቅጽል ፡ ላይ ፡ መስም ፡ እንዲደርቡ ፡ ተገብሮና ፡ ሐውልት ፡ ፪ቱ ፡ ደግሞ ፡ ተቀታሊ ፡ ቅቱል ፥ ተቀዳሲ ፡ ቅዱስ ፥ መዋቲ ፡ ምዉት ፥ ፈላሲ ፡ ፍሉስ ፡ እያሰኙ ፡ ፪ቱንም ፡ ዐይነት ፡ በሣልስ ፡ በሳድስ ፡ ያስኬዳሉ ፤ ሣልስና ፡ ሳድስ ፡ ያሰኛቸው ፡ መጨረሻቸው ፡ ነው ። ምእላዳቸው ፡ ትና ፡ ን ፡ አንድና ፡ ብዙ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ የሚለዩ ፥ ሩቅና ፡ ቅርብ ፡ የማይለዩ ፡ ብልዞች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፤ ፰ቱ ፡ በአነ ፡ በንሕነ ፡ እየቀኑ ፡ ፫ ፡ ፫ቱ ፡ ባንዳንድ ፡ ንባብ ፡ ተጠቅልለው ፡ በ፮ ፡ በ፮ ፡ ይፈታሉ ። ይህም ፡ ውእቱ ፡ አንተ ፡ አነ ፥ ቀታሊ ፤ አው ፡ ቅቱል ። እሙንቱ ፡ አንትሙ ፡ ንሕነ ፥ ቀታልያን ፤ አው ፡ ቅቱላን ። ይእቲ ፡ አንቲ ፡ አነ ፥ ቀታሊት ፤ አው ፡ ቅትልት ። እማንቱ ፡ አንትን ፡ ንሕነ ፥ ቀታልያት ፡ አው ፡ ቅቱላት ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ።

፻፫ ፤ ማእከል ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ሣልስና ፡ ሳድስ ፡ ቀላቅሎ ፡ ሣልሱን ፡ አማክሎ ፡ በሊኅ ፡ ኃን ፡ ኃት ፥ በላኅ ። ሐዲስ ፡ ሳን ፡ ሳት ፥ ሐዳስ ። ዐቢይ ፡ ያን ፡ ያት ፥ ዐባይ ። ጸሊም ፡ ማን ፡ ማት ፥ ጸላም ። ጠቢብ ፡ ባን ፤ ጠባብ ፡ ባት ። ነዊኅ ፡ ኃን ፥ ነዋኅ ፡ ኃት ፡ እያለ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሣልሱን ፡ በራብዕ ፡ ለውጦ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ እያስተባበረ ፡ ነቋር ፡ ጸጓር ፡ ፀዋግ ። ሳያስተባብርም ፡ ዋሕድ ፡ ሕያው ፡ ክዋው ፥ ጻድቅ ፡ ኃጥእ ፥ ራትዕ ፡ ባዕድ ፡ ላእክ ፡ ኄር ፡ ዴጋን ፡ እያለ ፡ ይኼዳል ። ከሣልስና ። ከማእከል ፡ ከ፪ቱ ፡ የሚወጣ ፡ መድበል ፥ ቀተልት ፥ ነደቅት ፥ ጸወርት ፥ ገበርት ፥ ዐበይት ፥ ጠበብት ፥ ቀደምት ፥ ደኀርት ፥ ዐቀብት ፥ ኖሎት ፥ ነዋልው ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ስም ፥ ብዙዎቹን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ያስተባብራል ፤ መድበል ፡ መባሉ ፡ ስለ ዚህ ፡ ነውና ።

## ሳቢ ፡ ዘሮች ።

፻፬ ፤ የሳቢ ፡ ዘር ፡ ዐይነትና ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ ነው ፤ ለ፪ቱም ፡ አንቀጽነትና ፡ ጥሬነት ፡ አላቸው ፤ ስማቸውም ፡ ሳድስና ፡ ኃምስ ፡ ይባላል ። ፩ኛው ፡ ዐይነት ፡ እንደ ፡ ፪ኛው ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ትን ፡ ምእላድ ፡ አድርጎ ፡ ከቀተለና ፡ ከሰራዊቱ ፡ ቤት ፡ ቅትለት ፥ ሕንጸት ፥ ግብረት ፡ እያለ ፡ አርእስቶቹን ፡ ቀቲሎትንና ፡ ሐኒጸትን ፡ ገቢሮትን ፡ መስሎ ፡ ይወጣል ፤ ከንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ የሚለየው ፡ መካከሉን ፡ ግእዝ ፡ ማድረግና ፡ በሳድስ ፡ ብቻ ፡ መነሣት ፡ ነው ፤ ወና ፡ የ ፡ ባሉበት ፡ ግስ ፡ ግን ፡ ቁመት ፡ ሢመት ፡ እያለ ፡ በካዕብ ፡ በሣልስ ፡ ይነሣል ። ሳቢነቱም ፡ መደበኛ ፡ አንቀጹ ፡ እንደ ፡ ቀተለ ፡ ገቢር ፡ ይኾንና ፡ ካድራጊና ፡ ከተደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ሲወጣ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ቅትለት ፡ ብሎ ፡ መግደል ፥ መገደል ፥ አገዳደል ፥ ገዳይነት ፥ ተገዳይነት ፥ ግድያ ፡ ትግል ፡ እያሰኘ ፡ ሳቢነቱን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ጥሬነቱንም ፡ ያሳያል ።

፻፭ ፤ የወጣበት ፡ አንቀጽ ፡ እንደ ፡ ቆመና ፡ እንደ ፡ ጥሕረ ፡ ዐኰልና ፡ ሐውልት ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ ሳቢነት ፡ የለውም ፤ ይህም ፡ ጥሕረት ፡ ብሎ ፥ መጮኽ ፡ አጯጯኽ ፥ ጯኺነት ፥ ጩኸት ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፤ ማስጮኽ ፡ አሰኝቶ ፡ ሌላ ፡ ጯኺ ፡ አይስብም ። ጥሕረትን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ ብህለት ፡ ብዕለት ፡ ክህለት ፡ ንኅለት ፡ እያለ ፡ እንደዚህ ፡ ይፈታል ። ባላገባቦች ፡ ግን ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፡ ፩ ፡ ዐይነት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ያውም ፡ ካ፫ቱ ፡ ሰራዊት ፡ ከቀተለና ፡ ከገብረ ፥ ከነበ ፡ ከሤመ ፥ ከቆመ ፡ ቤት ፡ በቀር ፡ ከሌሎች ፡ አናቅጽ ፡ እንዳይወጣ ፡ ወስነው ፡ ይናገራሉ ፤ ውሳኔያቸውም ፡ የመላ ፡ የግምት ፡ የነሲብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ ድርስና ፡ ቍርጥ ፡ ቃል ፡ አይደለም ፤ ድርሱና ፡ ቍርጡስ ፡ ይህ ፡ ያለፈውና ፡ የሚመጣው ፡ ነው ።

፻፮ ፤ ፪ኛው ፡ ዐይነት ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ መዠመሪያው ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ምእላድ ፡ ሳይጨምር ፡ መድረሻውን ፡ ኃምስ ፡ አድርጎ ፡ ከቀተለ ፡ በታች ፡ ካሉት ፡ ከ፮ቱ ፡ አርእስት ፥ ቅዳሴ ፡ ቡራኬ ፡ ዲጋኔ ፡ ኑላዌ ፡ ድንጋጼ ፡ ምህራኬ ፡ እያለ ፡ ሳቢነቱን ፡ ሳይለቅ ፡ ዘመድ ፡ ዘር ፡ ኹኖ ፡ ይወጣል ። አፈታቱም ፡ እንደ ፡ ቅትለትና ፡ እንደ ፡ ጥሕረት ፡ ነው ፤ ድንጋጼ ፡ ጥሕረትን ፥ የቀሩት ፡ ቅትለትን ፡ ይመስላሉ ። ሰብሐ ፡ ተሰብሐ ፡

ብሎ ፡ ሰባሔ ፡ ከ፮ቱ ፡ አንቀጽ ፡ ይወጣል ፤ ፍችውም ፡ ሳቢና ፡ ተሳቢ ፥ ጥሬ ፡ ዘርነት ፡ ነው ። ሳቢ ፥ ማመስገን ፡ አመሰጋገን ፡ አመስጋኝነት ። ተሳቢ ፥ መመስገን ፡ ምስጉንነት ፡ ተመስጋኝነት ። ጥሬ ፥ ምስጋና ፡ ክብር ፤ የክብር ፡ ብርሃን ፡ ያሰኛል ፤ አንዱ ፡ ቃል ፡ ሰባሔ ፡ ባፈታቱ ፡ ከሰብሖና ፡ ከተሰብሐ ፡ ከስብሐት ፡ እንዲገጥም ፡ አስተውል ።

፸፯ ፤ ከዊን ፡ ከነ ፡ ካለውም ፡ ክዋኔ ፡ ኩነት ፡ ይልና ፥ መኾን ፡ አኳኋን ፡ ኋኝነት ፡ ኹነታ ፡ ባሕርይ ። ሀልዎ ፡ ሀለወ ፡ ካለውም ፡ ሀላዌ ፡ ይልና ፥ መኖር ፡ መገኘት ፥ አና ምር ፡ ኑሮ ፡ እያሰኘ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ሡግዎ ፡ ሠገወ ፡ ተሠገወ ፡ ካለውም ፡ ሥጋዌ ፡ ይልና ፥ ሥጋ ፡ መኾን ፥ ሥጋ ፡ መልበስ ፡ መግዘፍ ፥ ሥጋነት ፡ ሥግውነት ፡ ግዘፍ ፡ ዕበይ ፥ የሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ ያሰኛል ፤ እንትና ፡ መኾን ፡ ፯ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ሳቢና ፡ ተሳቢ ፡ መኾኑ ፡ ከገቢርና ፡ ከተገብሮ ፡ አንቀጽ ፡ ሲወጣ ፡ ነው ፤ ከሐውልት ፡ አንቀጽ ፡ ሲወጣ ፡ ግን ፥ ንኡስነትና ፡ ጥሬነት ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ሳቢ ፡ ዘርነት ፡ የለውም ። ያ፰ቱ ፡ ንኡሳን ፡ አናቅጽ ፡ ጠባይና ፡ ስም ፤ የንኡስ ፡ ርባታ ፡ መቅድም ፡ እስከዚህ ፡ ነው ።

## ፲ኛ ፡ ዕርከን ።

### ንኡስ ፡ ርባታ ፡ የዐቢይ ፡ ተረፍ ፡ የደቂቅ ፡ ጾታ ።

፸፰ ፤ ከ፰ቱ ፡ ንኡሳን ፡ አናቅጽ ፥ ዘንድ ፡ አንቀጽና ፡ ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ እስከ ፡ ፹ ፡ አካል ፡ እንዲረቡ ፥ ከንኡስ ፡ ርባታ ፡ እንዳይገቡ ፡ በ፸ኛው ፡ ቍ ፡ ተነግሯል ፤ ባ፲ ፡ መደብ ፡ ብቻ ፡ ተወስነው ፡ በንኡስ ፡ ርባታ ፡ የሚረቡ ፡ ፫ ፡ አናቅጽ ፡ ናቸው ፤ አርእስት ፥ ውስጠ ፡ ዘ ፥ ሳቢ ፡ ዘር ። ያርእስት ፡ ዐይነቶች ፡ (ቀቲል ፡ ቀቲሎት) ፡ እንደ ፡ ሳቢ ፡ ዘሮች ፡ (ኩነት ፡ ክዋኔ) ፡ መንታ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በመንታ ፡ መንገድ ፡ ይኼ ዳሉ ፤ አኪኼዳቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ (ቀቲል) ፡ ቀቲልሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ። ቀቲልከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፤ ቀቲልየ ፡ ልነ ፡ መግደላችን ። ከ፲ሩ ፡ መደብ ፡ አነ ፡ ባለው ፡ ብቻ ፡ አር እስትና ፡ ቦዝ ፡ ይገጥማሉ ፤ ካፈታት ፡ በቀር ፡ የንባብ ፡ ልዩነት ፡ የላቸውም ፤ ይህም ፡ ቀቲልየ ፥ መግደሌ ፤ ቀቲልየ ፥ ገድዬ ፤ ገቢርየ ፡ ነቢብ(ር)የ ፡ ጥሒርየ ፡ እያለ ፡ ከቀደሰና ፡ ከባረከ ፡ በቀር ፡ በቀተለና ፡ በሰራዊቱ ፡ ቤት ፡ መግጠሙን ፡ ያሳያል ።

፸፱ ፤ (ቀቲሎት) ፡ ቀቲሎቱ ፡ ታ ፡ ቶሙ ፡ ቶን ። ቀቲሎትከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፤ ትየ ፡ ትነ ። የገቢር ፡ ተሳቢም ፡ ሲኾን ፥ ቀቲለ ፡ ቀቲሎተ ፥ ቀቲሎቶ ፡ ተከ ፡ ተኪ ፡ ተ ክሙ ፡ ተክን ፡ ተነ ፡ እያሰኘ ፡ እነዚህን ፡ ፬ቱን ፡ ብቻ ፡ ይለውጣል ። የቀሩትም ፡ ያሉቱ ፡ አዕማድ ፡ አርእስት ፤ አቅትሎሁ ፡ ቱ ፤ ተቀትሎሁ ፡ ቱ ፤ ተቃትሎሁ ፡ ቱ ፤ አስተቃት ሎሁ ፡ ቱ ፡ እያሰኘ ፡ ባ፲ ፡ ባ፲ ፡ መደብ ፡ ይረባል ። ፩ኛውን ፡ መንገድ ፡ ከጥቂት ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ ኹሉ ፡ አያውቀውም ። የቦዝም ፡ ርባታ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤ መዠመሪያ ፡ ከሥር ፡ መደብ ፡ ዐልፎ ፡ በራሱ ፡ ብቻ ፡ እስከ ፡ ፹ ፡ መዝመቱን ፥ ፪ኛም ፡ ሀሎን ፡ በመሳብ ፡ ጽንዕ ፡ እየኾነ ፡ በቀዳማይና ፡ በዘንድ ፡ በሣልሳይ ፡ ኹሉ ፡ መግባቱን ፡ የሚያውቅ ለት ፡ የለም ፡ (ቍ፷፱ና ፡ ፸) ።

፹ ፤ ሣልስ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ (ቀቃሊ ፡ ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ።

ቀቃሊሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፤ ሊከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፤ ሊየ ፡ ሊነ ።

ቀታልያኒሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፤ ኒከ ፡ ንኪ ፡ ኒክሙ ፡ ክን ፤ ንየ ፡ ኒነ ።
ቀታሊቱ ፡ ታ ፡ ቶሙ ፡ ቶን ፤ ትከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፤ ትየ ፡ ትነ ።
ቀታልያቲሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፤ ቲከ ፡ ትኪ ፡ ቲክሙ ፡ ክን ፤ ትየ ፡ ቲነ ። ዳግመኛም ፡ ከአዕማድና ፡ ከመስም ፥ እንጻሒ ፡ መንጽሒ ፤ አጽናዒ ፡ መጽንዒ ፤ አቅታሊ ፡ መቅተሊ ፤ አስተፍጣሒ ፡ መስተፍሥሒ ፡ እያለ ፡ የሚገኝ ፡ ጣልስ ፥ ኹሉም ፡ እንደዚህ ፡ ይረባል ።

፻፲፩ ፤ ሳድስ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፤ (ቅቱል ፡ ላን ፡ ላት ፡ ትልት) ።

ቅቱሉ ፡ ላ ፡ ሎሙ ፡ ሎን ፤ ልከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፤ ልየ ፡ ልነ ።
ቅቱላኑ ፡ ና ፡ ኖሙ ፡ ኖን ፤ ንከ ፡ ኪ ፡ ኒክሙ ፡ ክን ፤ ንየ ፡ ንነ ። አው ፡
ቅቱላኒሁ ፡ ኒሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፤ ኒከ ፡ ንኪ ፡ ኒክሙ ፡ ክን ፤ ንየ ፡ ኒነ ።
ቅትልቱ ፡ ታ ፡ ቶሙ ፡ ቶን ፤ ትከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፤ ትየ ፡ ትነ ።
ቅቱላቱ ፡ ታ ፡ ቶሙ ፡ ቶን ፤ ትከ ፡ ኪ ፡ ትክሙ ፡ ክን ፤ ትየ ፡ ትነ ። አው ፡
ቅቱላቲሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፤ ቲከ ፡ ትኪ ፡ ቲክሙ ፡ ክን ፤ ትየ ፡ ቲነ ። መስም ፡ ያል ነውም ፡ በጣልስ ፡ ሲጨርስ ፡ እንደ ፡ ጣልሱ ፥ በሳድስ ፡ ሲጨርስ ፡ እንደ ፡ ሳድሱ ፡ ይኼዳል ፤ ሌላውም ፡ የውስጠ ፡ ዘ ፡ ድርብ ፥ ብዑድ ፡ ባዕድ ፤ ልኡክ ፡ ላእክ ፥ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡ በዘመድ ፡ በባዕድ ፡ ይረባል ።

፻፲፪ ፤ ሳድስና ፡ ኃምስ ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፡ (ኩነት ፡ ክዋኔ) ፤ ቅትለት ።

ቅትለቱ ፡ ታ ፡ ቶሙ ፡ ቶን ፤ ትከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፤ ትየ ፡ ትነ ። በዝቶም ፡ ሲዘረዝር ፡ ቅትለታቲሁ ፡ ይልና ፡ በምእላድ ፡ ላይ ፡ ምእላድ ፡ ጨምሮ ፡ ስያፍና ፡ በዕድ ፡ እየኾነ ፡ ገቢር ፡ ተገብሮ ፡ ይከታል ። የቀረውም ፡ ጥሬና ፡ ነባር ፥ ፊደሉ ፡ ፊደላቲሁ ፥ መጽሐፉ ፡ መጻሕፍቲሁ ፡ እያለ ፡ በዘመድ ፡ በባዕድ ። በባዕድም ፡ ብቻ ፡ አቡሁ ፡ አበዊሁ ፥ እፉሁ ፡ አፈዊሁ ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ፤ ነገርን ፡ ነገር ፡ እየሳበው ፡ ከዚህ ፡ ደረስን ፡ እንጂ ፥ የጥሬና ፡ የነባር ፡ ነገር ፡ ኋላ ፡ በየክፍሉ ፡ ይመጣል ። ኃምስ ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፤ ቅዳሴሁ ፡ ቡራኬሁ ፡ ዲጋኔሁ ፡ እያሰኘ ፡ በዝቶም ፡ ሲዘረዝር ፤ ቅዳስያቲሁ ፤ ቡራክያቲሁ ፡ ዲጋን ያቲሁ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ቀታሊና ፡ እንደ ፡ መቅተሊ ፡ ይኼዳል ።

## ፲፩ኛ ፡ ዕርከን ።

## ደቂቅ ፡ ርባታና ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ ባለብዙ ፡ ሕጸጽ ።

፻፲፫ ፤ ንኡስ ፡ ርባታ ፡ የዐቢይ ፡ ተረፍ ፡ እንዲባል ፥ ደቂቅ ፡ ርባታም ፡ የንኡስ ፡ ቅሬታ ፡ ይባላል ፤ አካኼዱም ፡ በጥሬ ፡ ዘር ፡ ዐመል ፡ እየረባ ፥ በአንቀጽ ፡ ዐመል ፡ ሩቅና ፡ ቅርብ ፡ አንድና ፡ ብዙ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ የሚለይ ፡ ነው ። ነባር ፡ አንቀጽም ፡ የጥሬ ፡ ዘር ፡ ዐይነት ፡ ነውና ፤ ከቀዳማይ ፡ በቀር ፡ ከልአይ ፡ ጣልሳይ ፡ ስለሌለው ፡ ደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ይባላል ። የነባር ፡ አንቀጽም ፡ ዐይነትና ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ዘማች ፡ አንቀጽ ፡ ፬ ፡ ነው ፤ ጽድቅና ፡ አሉታ ፤ ጽድቅ ፡ አንቀጽ ፥ ውእቱ ፡ ብ ፡ ሎ ፤ አሉታ ፡ አንቀጽ ፥ አከ ፡ ሐሰ ፡ ኢ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ፮ቱ ፡ አናቅጽ ፡ ሲረቡና ፡ ሲዘረዘሩ ፥ ፫ቱ ፡ ጽድቆች ፡ በየራሳቸው ፥ ፫ቱ ፡ አሉቶች ፡ በለ ፡ ተዘርዝረው ፡ ኹሉም ፡ እንደ ፡ ጥሬ ፡ ባ፲ ፡ ባ፲ ፡ መደብ ፡ ይረባሉ ።

፻፬ ፡ ውእቱ ፡ ሁ ፡ ከተባለው ፡ ከሩቁ ፡ ዝርዝር ፡ ስለ ፡ ወጣ ፥ መደበኛ ፡ የሩቅ ፡ አንቀጽ ፡ ኹኖ ፡ ሲገሰስና ፡ ሲረባ ፡ ፲ ፡ መደብ ፡ ሲኾን ፥ አረባቡና ፡ አፈታቱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

፩ ፡ ውእቱ ፡ ነው ፡ ኾነ ፡ አለ ፡ ኖረ ፡ ነበረ ።
፪ ፡ ይእቲ ፡ ነች ፡ ናት ፡ ኾነች ፡ አለች ፡ ኖረች ፡ ነበረች ።
፫ ፡ ውእቶሙ ፡ አው ፡ እሙንቱ ፡ ናቸው ፡ ኾኑ ፡ አሉ ፡ ኖሩ ፡ ነበሩ ።
፬ ፡ ውእቶን ፡ አው ፡ እማንቱ ፡ ግዚ ፡ ከማሁ ።
፭ ፡ አንተ ፡ ነኽ ፡ ኾንክ(ኽ) ፡ አለኽ ፡ ኖርኽ ፡ ነበርኽ ።
፮ ፡ አንቲ ፡ ነሽ ፡ ኾንሽ ፡ አለሽ ፡ ኖርሽ ፡ ነበርሽ ።
፯ ፡ አንትሙ ፡ ናችኹ ፡ ኾናችኹ ፡ አላችሁ ፡ ኖራችኹ ፡ ነበራችኹ ።
፰ ፡ አንትን ፡ ግዚ ፡ ከማሁ ።
፱ ፡ አነ ፡ ነኝ ፡ ኾንኹ ፡ አለኹ ፡ ኖርኩ ፡ ነበርኩ ፡ ኹ ።
፲ ፡ ንሕነ ፡ ነን ፡ ነነ ፡ ኾነ ፡ አለነ ፡ ኖርን ፡ ነበርን ፡ ን ።

ውእቶሙና ፡ እሙንቱ ፥ ውእቶንና ፡ እማንቱ ፡ አንዳንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ ዘማቾቹም ፡ ነውና ፡ ኾነ ፡ አለና ፡ ኖረ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ ነበረም ፡ የኖረ ፡ ጽንዕ ፡ ነው ።

፻፭ ፡ ብላጎበኞች ፡ ግን ፡ በነዚህ ፡ ባሥሩ ፡ አናቅጽ ፡ ላይ ፡ ይኖራል ፡ ይኑር ፡ እያሉ ፡ ፲ ፡ ከልአይ ፡ ፲ ፡ ሣልሳይ ፡ ፀምረው ፥ ፴ ፡ አናቅጽ ፡ ይሉና ፤ ፴ውን ፡ ደግሞ ፡ ከብትን ፡ ጋራ ፡ በየዋህ ፡ በ፪ ፡ ጾታ ፥ በመሠሪ ፡ በ፬ ፡ ጾታ ፡ እያረቡ ፡ ፪፻፵ ፡ አንቀጽ ፡ ያደርጉታል ። የየዋህ ፡ ርባታም ፡ አከኼድ ፡ ባንደኛው ፡ ጾታ ።

ዘመዱ ፡ ውእቱ ፡ ዘመዱ ፡ አንተ ፡ ዘመዱ ፡ አነ ።
ዘመዱ ፡ ይእቲ ፡ ዘመዱ ፡ አንቲ ፡ » »
አዝማዱ ፡ ውእቶሙ ፡ አዝማዱ ፡ አንትሙ ፡ አዝማዱ ፡ ንሕነ ።
አዝማዱ ፡ ውእቶን ፡ አዝማዱ ፡ አንትን ፡ እያሰኘ ፡ በ፪ኛውም ፡

አከኼድ ፡ ዘመዱ ፡ ውእቱ ፡ ዘመድኪ ፡ ውእቱ ፡
ዘመዳ ፡ ውእቱ ፡ ዘመድክሙ ፡ ውእቱ ፡
ዘመዶሙ ፡ ውእቱ ፡ ዘመድክን ፡ ውእቱ ፡
ዘመዶን ፡ ውእቱ ፡ ዘመድየ ፡ ውእቱ ፡
ዘመድከ ፡ ውእቱ ፡ ዘመድነ ፡ ውእቱ ፡ እያሰኘ ፡ ሩቅ ፡ ሩቆቹን ፡ ባ፲ ፡ ባ፲ ፥ ቅርብ ፡ ቅርቦቹን ፡ በ፮ ፡ በ፮ ፡ አነና ፡ ንሕነን ፡ በ፰ ፡ በ፰ ፡ ዘርዝሮ ፡ ከንደኛው ፡ ጾታ ፡ ፪፻፵ ፡ አንቀጽ ፤ ከ፪ኛውም ፡ ፪፻፵ ፡ አንቀጽ ፡ ያስገኛል ።

፻፮ ፡ የመሠሪ ፡ ርባታም ፡ አከኼድ ፡ ባንድ ፡ ጾታ ፡ ብቻ ፡ እየረባ ፡ ባራት ፡ ማዕርጋት ፡ ይከፈላል ፤ አከፋፈሉም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሩቅና ፡ ቅርብ ፡ ወንድ ፥ ፩ ፡ ክፍል ። ቅርቦችና ፡ ሩቆች ፡ ወንዶች ፥ ፩ ፡ ክፍል ። ሩቂቱና ፡ ቅርቢቱ ፡ ሴት ፥ ፩ ፡ ክፍል ። ቅርቦችና ፡ ሩቆች ፡ ሴቶች ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ናቸው ፤ መንገዳቸውም ፡ ሩቅና ፡ ቅርብ ፡ መዘመድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። አራቱ ፡ ክፍሎች ፡ እንዲህ ፡ ባንድ ፡ አዝማች ፡ (ጾታ) ፡ ባራት ፡ ማዕርጋት ፥ በመሠሪ ፡ ርባ ፡ እየረቡ ፡ ፪፻፵ ፡ አንቀጽ ፡ ይኾናሉ ። ከንደኛው ፡ ማዕ

ርግ ፡ ፹፯ ። ከኹለተኛው ፡ ፷፱ ። ከሦስተኛው ፡ ማዕርግ ፡ ፶፩ ። ከ፬ኛው ፡ ፴፫ ፡ አንቀጽ ፤ ድምር ፡ ፪፻፵ ። በነዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የእነና ፡ የንሕነ ፡ ፳፬ ፡ አንቀጽ ፡ ሲጨመር ፡ መላው ፡ ፪፻፷፬ ፡ አናቅጽ ፡ ይኾናሉ ።

፹፯ ፤ ውእቱ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዘማች ፡ አንቀጽ ፡ ከልአይ ፡ ሣልሳይ ፡ የሌለው ፡ እውነተኛ ፡ ነባር ፡ ነውና ፥ አንቀጽነቱ ፡ ቀዳማይ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከ፲ ፡ መደብ ፡ ዐልፎ ፡ እስከ ፡ ፹ ፡ ለመዝመት ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ትብትብ ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፥ የዘማች ፡ አንቀጽ ፡ ኀይል ፡ የለውም ፤ ተማሮችም ፡ የትብትቡ ፡ አፈታት ፥ ንባብ ፡ አልባ ፥ ቢከፍቱ ፡ ተልባ ፡ ስለ ፡ ኾነባቸው ፡ ስሙን ፡ የፈታና ፡ ደንጊያ ፡ ይሉታል ። በንና ፡ ሎን ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ውእቱ ፡ ከልአይ ፡ ሣልሳይ ፡ ጨምረው ፡ በየዋህና ፡ በመሠሪ ፡ ርባታ ፡ እያረቡ ፡ ፪፻፵ ፡ አንቀጽ ፡ ያደርጓቸዋል ፤ ማስረጃ ፡ ምስክር ፡ የላቸውም ። ውእቱና ፡ ሀሎ ፡ ሳይገቡበት ፡ ነጠላውን ፡ አንቀጽ ፥ ቀተለ ፡ ይቀትል ፡ ያለውን ፡ ገድሏል ፡ ገድሎ ፡ ነበር ፤ ይገድላል ፡ ይገድል ፡ ነበር ፡ እያሉ ፡ ያልተነበበውን ፡ በጽንዕ ፡ አፈታት ፡ እንዲፈቱ ፥ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

፹፰ ፤ ነ ፡ ደግሞ ፡ በነባርነቱ ፡ ሲረባ ፡ አገባብና ፡ አንቀጽ ፡ ይኾናል ፤ አገባብ ፥ ናሁ ፡ ነዋ ፥ እንሆ ። አንቀጽ ፥ ነዮ ፡ (ያ ፡ ዮሙ ፡ ዮን ፤ ነየከ ፡ ኪ ፡ ከሙ ፡ ክን ፡ ነየ ፡ ነየን) ፥ እንሆት ፡ ይኸው ፡ ከዚህ ፡ አለ ። ፪ኛም ፡ እንሆለት ፥ ይኸውለት ፥ ከዚህ ፡ አለለት ፡ ያሰኛል ።

፹፱ ፤ የዘ ፡ እንተ ፡ እለም ፡ ደቂቆች ፡ እነዝኩ ፡ ዝስኩ ፡ በ፰ ፡ መደብ ፡ ሲረቡ ፡ ቈብጦ ፡ አንቀጽና ፡ ቈብጦ ፡ ቅጽል ፡ ናቸው ፤ ምስጢራቸውም ፡ ማሳየትና ፡ ማመልከት ፡ ነው ፤ እማሬ ፡ እንደ ፡ ማለት ። ከ፰ቱ ፡ ደግሞ ፡ ፬ቱ ፡ የቅርብ ፡ ሩቆች ፥ ፬ቱ ፡ የቅርብ ፡ ቅርቦች ፡ ናቸው ። እነና ፡ ንሕነ ፡ የሏቸውም ፤ እኹን ፡ በዚህ ፡ ዕርከን ፡ የሚነገር ፡ አንቀጽነታቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(የቅርብ ፡ ሩቆች) ።

| | |
|---|---|
| ዝኩ ፡ ዝስኩ ፡ ዝክቱ ፤ | ያው ፡ ያውና ፤ ያ ፡ ነው ። |
| እንትኩ ፡ እንታክቲ ፤ | ያቻት ፡ ያችው ፥ ያችውና ፤ ያች ፡ ናት ። |
| እልኩ ፡ እልክቱ ፤ | እኒያው ፡ እኒያውና ፤ እኒያ ፡ እነዚያ ፡ ናቸው ። |
| እልከን ፡ እልክቶን ፤ | ዝኒ ፡ ከማሁ ። |

(የቅርብ ፡ ቅርቦች) ።

| | |
|---|---|
| ዝ ፡ ዝንቱ ፤ | ይኸው ፡ ይኸውና ፤ ይህ ፡ ነው ። |
| ዛ ፡ ዛቲ ፤ | ይችው ፡ ይችውና ፤ ይህች ፡ ይች ፡ ይቺ ፡ ናት ። |
| እሉ ፡ እሎንቱ ፤ | እኒሁ ፡ እኒሁና ፤ እኒህ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። |
| እላ ፡ እሎን ፡ እላንቱ ፤ | ዝኒ ፡ ከማሁ ። |

ቅጽልነታቸው ፡ ኋላ ፡ በ፲፫ኛ ፡ ዕርከን ፡ ይነገራል ፡ (ቍ፻፲፰) ። ዝኩ ፡ እንትኩ ፡ እልኩ ፡ ማለት ፡ ዘከሃ ፡ እንተ ፡ ከሃ ፡ እለ ፡ ከሃ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ።

፺፤ቦ፡አልቦ፡ሎ። በና፡ለ፡ባንድ፡ጊዜ፡አንቀጽና፡አገባብ፡እየኾኑ፡ከው
እቱ፡እስከ፡ንሕነ፡ባሉት፡ባሥሩ፡ሰራዊት፡ሲዘረዘሩና፡ሲረቡ፥አንቀጽነታቸው፡
አገባብነቱን፡አይለቅም፤የበና፡የሎ፡ፍች፡መለዮው፡ይህ፡ነው፤በ፡በበነቱ፡ቂሞ፡
ለም፡በለነቱ፡ቂሞ፡መፈታት። አልቦም፡የቦ፡አሉታ፡ነው፤አል፡ደግሞ፡በኢ፡
ፈንታ፡ገብቶ፡የተጣፈ፡የኢ፡ተውላጥ፡ነው፤አሉታነቱም፡ያማርኛና፡የዕብራይ
ስጥ፡እንጂ፥የግእዝ፡አይዶለም፤ይኸውም፡ሊታወቅ፡ከቦ፡በቀር፡በሌላ፡አንቀጽ፡
ገብቶ፡አይገኝም። ቀተለ፡ብሎ፡ኢቀተለ፡ማለት፡ጽድቅና፡አሉታ፡እንደ፡ኾነ፥
ቦ፡ብሎም፡ኢቦ፡በማለት፡ፈንታ፡አልቦ፡ማለት፡ጽድቅና፡አሉታ፡ነው፤ርባታ
ውም፡ከሎ፡ተለይቶ፡በየዋህና፡በመሠሪ፡በጽድቅ፡ባሉታ፡ይረባል፡(ቍ፷፱)።

| (የዋህና፡ጽድቅ)። | (ኀላፊና፡ጽንዕ)። |
| --- | --- |
| ፺፩፤በ፡ውእቱ፤ | ርሱ፡አለ፤ኖረ፤ኑሯል፤ነበረ። |
| በ፡ይእቲ፤ | ርሷ፡አለች፤ኖረች፤ኑራለች፤ነበረች። |
| በ፡ውእቶሙ፤ | ርሳቸው፡አሉ፤ኖሩ፤ኑረዋል፤ነበሩ። |
| በ፡ውእቶን፤ | ዝኒ፡ከማሁ። |
| በ፡አንተ፤ | በቊሙ፡አለኽ፤ኖርኽ፤ኑረኻል፤ነበርኽ። |
| በ፡አንቲ፤ | አንቺ፡አለሽ፤ኖርሽ፤ኑረሻል፤ነበርሽ። |
| በ፡አንትሙ፤ | እናንት፡አላችኹ፤ኖራችኹ፤ኑራችኋል፤ነበራችኹ። |
| በ፡አንትን፤ | ዝኒ፡ከማሁ። |
| በ፡አነ፤ | እኔ፡አለኹ፤ኖርኹ፤ኑሬያለኹ፤ነበርኹ። |
| በ፡ንሕነ፤ | እኛ፡አለን፤ኖርን፤ኑረናል፤ነበርን፡ን። |

አሉታውንም፤አልቦ፡ብለኽ፥የለም፤አልኖረም፤አልነበረም። የለችም፤አልኖረ
ችም፤አልነበረችም፡እያልኽ፡ኹሉን፡እንዲህ፡ፍታ።

| (ዝርዝር)። | (አፈታት)። |
| --- | --- |
| ፺፪፤ቦ፡ቦቱ፤ | አለው፤አለበት፤ኖረው፤ኖረበት፤ኑሮታል፤ኑሮበታል፤ነበረበት፤በርሱ። |
| ባ፡ባቲ፤ | አላት፤አለባት፤ኖራት፤ኖረባት፤ኑሯታል፤ኑሮባታል፤ነበረባት፤በርሷ። |
| ቦሙ፡(ቦቶሙ)፤ | አላቸው፤አለባቸው፤ኖራቸው፤ኖረባቸው፤ኑሯቸዋል፤ኑሮባቸዋል፤ነበረባቸው፤በርሳቸው። |
| ቦን፡(ቦቶን)፤ | ዝኒ፡ከማሁ። |
| ብከ፤ | አለኽ፤አለብኽ፤ኖረኽ፤ኖረብኽ፤ኑሮኻል፤ኑሮብኻል፤ነበረብኽ፤ባንተ። |
| ብኪ፤ | አለሽ፤አለብሽ፤ኖረሽ፤ኖረብሽ፤ኑሮሻል፤ኑሮብሻል፤ነበረብሽ፤ባንቺ። |

| | |
|---|---|
| ብክሙ ፤ | አላችኹ ፤ አለባችኹ ፤ ኖራችኹ ፤ ኖረባችኹ ፤ ኑሯችኋል ፤ ኑሮባችኋል ፤ ነበረባችኹ ፤ በናንተ ። |
| ብክን ፤ | ዝኒ ፡ ከማሁ ። |
| ብየ ፤ | አለኝ ፤ አለብኝ ፤ ኖረኝ ፤ ኖረብኝ ፤ ኑሮኛል ፤ ኑሮብኛል ፤ ነበረብኝ ፤ በኔ ። |
| ብነ ፤ | አለን ፤ አለብን ፤ ኖረን ፤ ኖረብን ፤ ኑሮናል ፤ ኑሮብናል ፤ ነበረብን ፤ በኛ ። |

አሉታውንም ፤ አልቦ ፡ አልቦቱ ፡ ብለኽ ፥ የለውም ፤ የለበትም ፤ አልኖረውም ፤ አልኖረበትም ፤ አልነበረበትም ፡ እያልኽ ፡ ኹሉን ፡ እንዲህ ፡ ፍታ ። አልቦ ፡ አልቦቱ ፤ አልቦሙ ፤ አልቦን ። አልብከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ ።

| | |
|---|---|
| ፺፫ ፤ ሎ ፡ ሎቱ ፤ | ለርሱ ፥ አለው ፤ አለለት ፤ ኖረለት ፤ ነበረለት ፤ ይገባል ፤ ይገባዋል ። |
| ላ ፡ ላቲ ፤ | ለርሷ ፥ አላት ፤ አለላት ፤ ኖረላት ፤ ነበረላት ፤ ይገባል ፤ ይገባታል ። |
| ሎሙ ፡ ሎቶሙ ፤ | ለርሳቸው ፥ አላቸው ፤ አለላቸው ፤ ኖረላቸው ፤ ነበረላቸው ፤ ይገባ(ቸዋ)ል ። |
| ሎን ፡ ሎቶን ፤ | ዝኒ ፡ ከማሁ ። |
| ለከ ፤ | ላንተ ፥ አለኽ ፤ አለልኽ ፤ ኖረልኽ ፤ ነበረልኽ ፤ ይገባል ፤ ይገባኻል ። |
| ለኪ ፤ | ላንቺ ፥ አለሽ ፤ አለልሽ ፤ ኖረልሽ ፤ ነበረልሽ ፤ ይገባል ፤ ይገባሻል ። |
| ለክሙ ፤ | ለናንተ ፥ አላችኹ ፤ አለላችኹ ፤ ኖረላችኹ ፤ ነበረላችኹ ፤ ይገባል ፤ ይገባችኋል ። |
| ለክን ፤ | ዝኒ ፡ ከማሁ ። |
| ልየ ፡ ሊተ ፤ | ለኔ ፥ አለኝ ፤ አለልኝ ፤ ኖረልኝ ፤ ነበረልኝ ፤ ይገባል ፤ ይገባኛል ። |
| ለነ ፤ | ለኛ ፥ አለን ፤ አለልን ፤ ኖረልን ፤ ነበረልን ፤ ይገባል ፤ ይገባናል ። |

፺፬ ፤ ጽድቅ ፡ አንቀጽ ፡ የሚሰማባቸው ፡ የነባር ፡ ዲቃሎች ፡ ወይም ፡ በዞች ፡ እወና ፡ አሆም ፡ ውስጠ ፡ ውእቱዎች ፡ ናቸውና ፥ በጥያቄና ፡ በትእዛዝ ፡ ጊዜ ፡ የጽድቅ ፡ ተሰጦ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ቊጥራቸውና ፡ ክፍላቸው ፡ ከውእቱ ፡ ነው ፤ ንኡስ ፡ አገባብም ፡ ይኾናሉ ። እወ ፤ አዎን ፥ እውነት ፡ ነው ፤ ወይም ፡ እውነት ፥ በውነት ፡ እያሰኘ ፡ ምስክርነትን ፡ ያሳያል ፤ የያዙቱን ፡ ነገር ፡ ለማጽደቅ ፡ እንደ ፡ መሐላ ፡ ነው ። እወ ፡ ውእቱ ፥ እወ ፡ ይእቲ ፡ እያለ ፡ እስከ፲ ፡ ይዘምታል ፤ እወ ፡ እግዚአ ፥ እወ ፡ አብ ፥ እወ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ እያለ ፡ በገባበት ፡ ኹሉ ፡ ውእቱን ፡ ያሰማል ። በጥያቄም ፡ ጊዜ ፡ ተሰጦ ፡ ሲኾን ፡ በሉታና ፡ በጽድቅ ፡ ይገባል ፤ ይህም ፡ ኢመጽአኑ ፡ ምትኪ ፥ እወ ፡ ኢመጽአ ፤ ዳግንኑ ፡ አቡኪ ፥ እወ ፡ ዳግን ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። አሆ ፡ ማለትም ፡ አንቀጽ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በብ

ሂል ፡ ተስቦ ፡ ዕሺ ፡ በጎ ፡ ይኹን ፡ እያሰኘ ፡ በይቤ ፡ ዝርዝር ፡ ይረባል ፤ ይህም ፡ አሆ ፡ ይቤ ፥ አሆ ፡ ትቤ ፥ አሆ ፡ በልም ፡ እያለ ፡ በብሂል ፡ መዝመቱን ፡ ያሳያል ። በጥሬነቱም ፡ የጥሬ ፡ ተሰጦ ፡ እየኾነ ፡ አቤቶ ፡ ሆይ ፥ እሜቶ ፡ ሆይ ፤ ወይም ፡ ባጭር ፡ ቃል ፥ አቤት ፡ እመት ፡ ያሰኛል ፤ ሁ ፡ የተባለው ፡ የሩቁ ፡ ዝርዝር ፡ ከአ ፡ ጋራ ፡ ገጥሞ ፡ አሆ ፡ ስለ ፡ ተባለ ፥ እንዲህ ፡ በ፱ ፡ ስልት ፡ ይፈታል ።

፺፭ ፤ ሦስቱ ፡ አሉቶች ፡ ደግሞ ፡ አከና ፡ ሐሰ ፡ ኢ ፡ ፬ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ አከ ፡ ባ፲ ፡ ሰራዊት ፡ እየገባ ፡ እንደ ፡ በ ፡ በኹሉ ፡ ይፈታል ። ይህም ፡ አከ ፡ ውእቱ ፤ አከ ፡ ይእቲ ፤ አከ ፡ አንትሙ ፤ አከ ፡ ንሕነ ፡ እያሰኘ ፡ በወንድና ፡ በሴት ፡ ባንድና ፡ በብዙ ፡ በሩቅና ፡ በቅርብ ፡ መዝመቱን ፡ ያሳያል ። አፈታቱም ፥ ነው ፡ ኾነ ፡ አለ ፡ ኖረ ፡ ነበረ ፡ ያለውን ፡ ያነኑ ፡ የውእቱን ፡ ጽድቅ ፥ አይዶለም ፡ አልኾነም ፥ የለም ፡ አልኖረም ፡ አልነበረም ፡ እያሉ ፡ መለወጥና ፡ መገልበጥ ፡ ማስተባበል ፡ ነው ። ፪ኛም ፡ አከ ፡ በቱ ፡ አከ ፡ ሎቱ ፡ እያለ ፡ በበና ፡ በለ ፡ ሲዘምት ፥ በርሱ ፡ ለርሱ ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ። ፫ኛም ፡ አከ ፡ አከ ፡ ብሎ ፡ በደጊም ፡ ሲነገር ፡ እንኳን ፡ እንኳን ፥ ወይም ፡ አልኾነም ፡ አይኾንም ፡ እያሰኘ ፡ አካቶ ፡ ፈጽሞ ፡ ጨራሽ ፡ ማለትን ፡ ያሳያል ።

፺፮ ፤ ሐሰ ፡ ከሐሰወ ፡ የተከፈለ ፡ ነው ፤ ሀሎ ፡ ከሀለወ ፥ ነዐ ፡ ከነዐወ ፡ እንደ ፡ ተከፈሉ ፤ ሐሰንና ፡ ነዐን ፡ ነባር ፡ ያሰኛቸው ፡ ወን ፡ መጕረድና ፡ ሕገ ፡ ወጥነት ፡ ነው ። ሐሰ ፡ ዘርነት ፡ ስላለው ፡ በፈታቱ ፡ ኹሉ ፥ ሐሰት ፡ ውሸት ፥ አይዶለም ፤ አልኾነም ፤ አይኾንም ፤ አይኹን ፡ እያሰኘ ፡ ትንቢትና ፡ ትእዛዝ ፡ ያናግራል ። ሲዘረዝርም ፡ ሐሰ ፡ በቱ ፤ ሐሰ ፡ ሎቱ ፤ አይኹንበት ፤ አይድረስበት ፤ ሐሰት ፡ ይኹንለት ፤ ሕልም ፡ ያድርግለት ፡ እያሰኘ ፤ ሐሰ ፡ ብቲ ፡ ሐሰ ፡ ላቲ ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ ንሕነ ፡ ይዘረዝራል ።

ኢ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ አከና ፡ እንደ ፡ አልቦ ፡ አይዶለም ፡ የለም ፡ አልነበረም ፡ እያሰኘ ፥ ኢ ውእቱ ፡ ኢ ይእቲ ፡ በማለት ፡ እስከ፲ ፡ ይረባል ። ሲዘረዝርም ፡ እንደ ፡ አከና ፡ እንደ ፡ ሐሰ ፤ ኢ ቦቱ ፡ ኢ ሎቱ ፥ ኢ ባቲ ፡ ኢ ላቲ ፥ ኢ ብከ ፡ ኢ ለከ ፥ ኢ ብየ ፡ ኢ ሊተ ፡ እያሰኘ ፡ እስከ፲ ፡ ይረባል ።

፺፯ ፤ ባላገባቦች ፡ አንቀጽ ፡ በገባብ ፡ ይዘምታል ፡ የሚሉት ፡ ይህን ፡ አካኼድ ፡ ነው ፤ ይዘምታልም ፡ ማለት ፡ አንቀጽ ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ሳይፈልስ ፡ አገባብ ፡ እየተከተለ ፡ ባገባብ ፡ ዝርዝር ፥ ሩቅና ፡ ቅርብ ፥ አንድና ፡ ብዙ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ለይቶ ፡ ይኼዳል ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አገባቦቹም ፡ በና ፡ ለ ፡ ናቸው ። የእወ ፡ የአሆም ፡ አሉታና ፡ አፍራሽ ፡ ፪ ፡ ናቸው ፤ እንዳዒና ፡ እንቢ ፤ እንዳዒ ፡ በለ ፥ እንቢ ፡ በራሱ ፡ ይዘረዝራል ፤ ይህም ፡ እንዳዒ ፡ ሎቱ ፡ ላቲ ፡ ሎሙ ፡ ሎን ፡ ለከ ፤ እንቢሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፥ እንቢከ ፡ ኪ ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ። እንጋም ፡ እንደ ፡ እንዳዒ ፡ ውስጠ ፡ ኢ ፡ ነውና ፥ ያሉታና ፡ የጥርጥር ፡ አንቀጽ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በለ ፡ ይዘምታል ፤ አል ፡ ስለ ፡ ኢ ፡ እንደ ፡ ገባ ፥ እንዳዒም ፡ በእንጋ ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፡ ዕብራይስጣዊ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጃ ፤ ግእዝ ፡ አይዶለም ፤ እንቢ ፡ ግን ፡ የአበየ ፡ ዘር ፡ ነው ።

## ፫ኛ ፡ ክፍል ።

## ጸዋትወ ፡ ስም ፡ ወመስም ፥ ስሙም ፡ ጥሬ ፡ የሰዋስው ፡ ፍሬ ።

### ፲፪ኛ ፡ ዕርከን ።

### የዘርና ፡ የነባር ፡ ጥሬ ፤ ወይም ፡ ዘርና ፡ ነባር ፡ ስም ።

፺፰ ፤ የጥሬ ፡ ዘር ፡ ዐይነትና ፡ ስም ፡ ፬ ፡ ነው ፤ ፩ኛው ፡ ዘመድ ፥ ፪ኛው ፡ ባዕድ ፥ ፫ኛው ፡ ምእላድ ፥ ፬ኛው ፡ ባዕድ ፡ ከምእላድ ፡ ይባላል ። ዘመድ ፡ ዘር ፡ አንቀጹንና ፡ አርእስቱን ፡ መስሎ ፡ የሚወጣ ፡ ስም ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ነደ ፡ ነድ ፥ ቆመ ፡ ቆም ፥ ሤጠ ፡ ሤጥ ፥ ቀተለ ፡ ቀትል ፥ ገብረ ፡ ገብር ፥ ግብር ፤ ጠቢብ ፡ (ጠበ) ፡ ጥበብ ፤ ነቢብ ፡ (ነበ) ፡ ንባብ ፤ ሐጺጽ ፡ (ሐጸ) ፡ ሕጸጽ ፤ ዐብየ ፡ ዕበይ ፡ እያለ ፡ ዘመድን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ።

፺፱ ፤ ባዕድ ፡ ዘር ፡ የግሱን ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በባዕድ ፡ ፊደል ፡ የሚነሣ ፡ ስም ፡ ነው ፤ ፊደሎቹም ፡ ፰ ፡ ናቸው ፥ አመተሰነ ፤ ግእዛቸው ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተነገረ ፡ ካዕብና ፡ ራብዕ ፥ ሳድስና ፡ ሳብዕ ፡ አይቀሩም ፤ እነዚሁም ፡ አ ፡ ተ ፡ አስተ ፡ አን ፡ አስ ፡ ከተባሎት ፡ ከ፰ቱ ፡ ልማዶች ፡ የወጡ ፡ ናቸው ፡ (ቍ፴፩) ። አ ፡ የማድረግና ፡ የማስደረግ ፡ ልማድ ፡ እየኾነ ፡ በቀዳማይ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባና ፡ ወዲያው ፡ ለጥሬው ፡ ባዕድ ፡ ይኾናል ። ምሳሌ ፤ ርእየ ፡ አርአየ ፥ አርአያ ። መሰለ ፡ አምሰለ ፥ አምሳል ። ሰትዐ ፡ አስትዐ ፥ አስትዓ ። በረየ ፡ አብረየ ፥ እብሬት ። ገዝአ ፡ አግዝአ ፥ እግዚእ ። ለትሐ ፡ አልትሐ ፥ እልታሕ ፥ የመሰለው ፡ ኹሉ ። መ ፡ ደግሞ ፡ ከተ ፡ በቀር ፡ ፫ቱ ፡ ልማዶች ፡ ከገቡበት ፡ አንቀጽ ፡ በሚወጣ ፡ ጥሬ ፡ አን ፡ እየጐረደ ፡ በአ ፡ ፈንታ ፡ ገብቶ ፡ ይነገራል ፤ ይህም ፡ አፍርሀ ፡ መፍርህ ፥ አደንገፀ ፡ መደንግፅ ፤ አስተብቍዐ ፡ መስተብቍዕ ፤ አንቀልቀለ ፡ መንቀልቅል ፤ አስቈረረ ፡ መስቈርር ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ልማድ ፡ ከሌለበት ፡ ከመደበኛ ፡ አንቀጽ ፡ በሚወጣ ፡ ስም ፡ ግን ፥ ሰቀለ ፡ መስቀል ፥ ሐበ ፡ ማሕየብ ፤ ቀድሐ ፡ ምቅዳሕ ፤ ወረደ ፡ ሙራድ ፤ ወፀፈ ፡ ሞፀፍ ፡ እያለ ፡ በራሱ ፡ ባዕድነት ፡ ይነገራል ። ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ራብዕ ፡ መኾኑ ፡ በ፪ቱ ፡ ዐመሎች ፡ በወና ፡ በሀአ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፤ ሳድስ ፡ መኾኑም ፡ ጥሬነቱ ፡ የቦታና ፡ የመሣሪያ ፡ ስም ፡ ሲኾን ፡ ነው ፡ (ቍ፴) ። ተ ፡ ባዕድ ፡ ሲኾን ፡ የመደረግ ፡ ልማድ ፡ ነውና ፥ ከተደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ይወጣል ፤ ይህም ፡ ተገሥጸ ፡ ተግሣጽ ፤ ተኀመሰ ፡ ታኅማስ ፤ ተሠገወ ፡ ትሥጉት ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ሰ ፡ ባዕድ ፡ ሲኾን ፡ ከአስ ፡ ልማድነት ፡ ይወጣል ፤ ይህም ፡ አስያዘዘ ፡ ሰያዝዝ ፤ አስቈቀወ ፡ ሰቈቃው ፤ አስቈረረ ፡ ሰቈራር ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ፡ (ቍ፴፫) ። አስተና ፡ አስ ፡ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ ልማዶች ፡ እንደ ፡ ሀለወና ፡ እንደ ፡ ሀሎ ፡ ናቸው ፤ ተን ፡ ከመጕረድ ፡ በቀር ፡ ልዩነት ፡ የለም ። ነ ፡ ባዕድ ፡ ሲኾን ፡ ከአን ፡ ልማድነት ፡ ይወጣል ፤ ይህም ፥ በልበለ ፡ አንበልበለ ፥ ነበልባል ፤ በስበሰ ፡ አንበስበሰ ፥ ነበስባስ ፤ ጐድጐደ ፡ አንጐድጐደ ፥ ነጐድጓድ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ።

አንና ፡ አስተም ፡ ከአና ፡ ከተ ፡ ሳይለዩ ፡ እንዳሉ ፡ ባዕድ ፡ ይኾናሉ ፤ አን ፡ እን ፡ እየኾነ ፡ ሲገባ ፥ ገለገ ፡ አንገለገ ፡ እንግልጋ ። ሰሰወ ፡ አንሰሰወ ፡ (ነሰሳው) ፡ እንስሳ ። አስ

ተም ፡ እስት ፡ እየኾነ ፡ ሲገባ ፥ ነፍሰ ፡ አንፈሰ ፡ አስተንፈሰ ፥ እስትንፋስ ። ጋብአ ፡ አስተጋብአ ፡ እስትጉቡእ ፥ (መስተጋብእ) ። ረከበ ፡ አርከበ ፡ አስተርከበ ፥ እስትርኩብ ፤ ተራከበ ፡ አስተራከበ ፡ ብሎ ፡ ምስትርካብ ፡ መስተራክብ ፡ እያለ ፡ ጥሬ ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ ከሚመስለው ፡ እንጂ ፡ ከማይመስለው ፡ አንቀጽ ፡ እንዳይወጣ ፡ በግልጥ ፡ ያስረዳል ።

፻ ፤ ምእላድ ፡ ዘር ፡ ደግሞ ፡ በዘመድ ፡ ተነሥቶ ፡ በባዕድ ፡ የሚጨርስ ፡ ወሳኬ ፡ ባዕድ ፡ ነው ፤ ምእላዶቹም ፡ ፮ ፡ ናቸው ፥ ዊው ፡ ዩያይ ፡ ል ፡ ም ፡ ናን ፡ ት ። ይህም ፥ አብ ፡ አበዊ ፥ አበው ። ሐዳስ ፡ ሐዳስዩ ፥ ኢቶጵ ፡ ኢትዎ(ዮ)ጵያ ፤ አንስት ፡ አንስትያ ፤ ባሕር ፡ ባሕር(ራ)ይ ። ኪሩብ ፡ ኪሩቤል ፡ ም ፡ ን ፤ ሱራፊ ፡ ሱራፌል ፡ ም ፡ ን ። በዕፀ ፡ ብፁዕና ፡ ብፁዓን ፤ ቀደመ ፡ ቅድምና ፤ ፈለጠ ፡ ፍልጣን ፤ በርሀ ፡ ብርሃን ። ሐመየ ፡ ሐሜት ፤ ቀነወ ፡ ቀኖት ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ልምን ፡ እነዚህ ፡ ፫ቱ ፡ ምእላዶች ፡ እንደ ፡ ውና ፡ ት ፡ አብገርዎች ፡ ናቸው ፤ ል ፡ በምና ፡ በን ፡ ፈንታ ፡ በጸሐፊ ፡ ስሕተት ፡ የገባ ፡ ነው ፤ ም ፡ የዕብራይስጥና ፡ የሐባብ ፥ ን ፡ የግእዝና ፡ የዐረብ ፡ አብገር ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ በወንድ ፡ አንቀጽ ፡ ለሚነገር ፡ ብቻ ፤ በዝርዝር ፡ ግን ፡ ምእላድነቱ ፡ የሴቶች ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ (አንትሙ ፡ አንትን) ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ሐባቦችና ፡ ዕብራውያን ፥ ኪሩቤም ፡ ሱራፌም ፥ ጻድቃም ፡ ኃጥአም ፥ እስመ ፡ ብዙኃም ፡ ጽዉዓም ፡ ወኅዳጣም ፡ ኅሩያም ፡ እያሉ ፡ በም ፡ ያበዛሉ ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ግእዝና ፡ እንዳረብ ፡ በን ፡ አያበዙም ። አል ፡ ከቦ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ገብቶ ፡ እንዳይገኝ ፥ ልና ፡ ም ፡ ደግሞ ፡ ከሱራፊና ፡ ከኪሩብ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ጥሬ ፡ ገብተው ፡ አይገኙም ።

፻፩ ፤ ባዕድ ፡ ከምእላድ ፡ የተባለውም ፡ ፪ኛው ፡ ዐይነት ፥ በባዕድ ፡ ተነሥቶ ፡ በባዕድ ፡ ይጨርሳል ፤ ይህም ፡ ከፈለ ፡ መክፈልት ፥ ሰፈረ ፡ መስፈርት ፥ ሣረረ ፡ መሠረት ፥ ተደመረ ፡ ትድምርት ፥ ተሠለሰ ፡ ትሥልስት ፥ ተምሀረ ፡ ትምህርት ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። የስም ፡ ዘርፎች ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ጥሬው ፡ ዐይነት ፡ ፪ ፡ ናቸው ፤ ባሕርይና ፡ ግብር ፡ ተጸውዖና ፡ ተቀብዖ ። ሕዋሳተ ፡ አፍአ ፡ በሚባሉት ፡ ባይንና ፡ በጆሮ ፡ ባፍንጫና ፡ ባፍ ፡ በጅ ፡ በነዚህ ፡ ባ፭ቱ ፡ መሣሪያነት ፡ የሚሠራ ፡ ኹሉ ፥ ማየትና ፡ መስማት ፡ ማሽተትና ፡ መቅመስ ፡ መዳሰስ ፥ የባሕርይ ፡ ሥራ ፡ ይባላል ፤ ሌሎች ፡ ግን ፡ ባሕርይ ፡ ይሉታል ። ሥራነቱን ፡ ደግሞ ፡ የሚያጐላና ፡ የሚገልጥ ፡ የሚያረጋግጥ ፥ ዕፅ ፡ (በማየትና ፡ በመታየት) ፤ ድምፅ ፡ (በመስማትና ፡ በመሰማት) ፤ ዕጣን ፡ (በማሽተትና ፡ በመሸተት) ፤ ጥፍጥ ፡ መራራ ፡ (በመቅመስና ፡ በመቀመስ) ፤ ልዝብ ፡ ሸካራ ፥ (በገሲስና ፡ በተገሰ) ፡ ማለትና ፡ መባል ፥ የባሕርይ ፡ ስም ፡ ነው ።

፻፪ ፤ የባሕርይ ፡ ስምና ፡ የባሕርይ ፡ ግብር ፥ ሕይወት ፡ ላለውና ፡ ለሌለው ፥ ለሚታይና ፡ ለማይታይ ፥ ለፈጣሪም ፡ ሳይቀር ፡ ለፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ አለው ። የማይታየውን ፡ ስምና ፡ ግብር ፥ በማይታዩት ፡ በሕዋሳተ ፡ ውስጥ ፡ እስተያየት ፥ በጥልቅ ፡ ልብ ፥ በረቂቅ ፡ ሐሳብ ፡ ማሰብ ፡ ነው ፤ አኮ ፡ ከመ ፡ ይትረአይ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ይትኀለይ ፡ እንዳለ ፡ (ኪዳ) ። የሚታየው ፡ ስም ፡ ግን ፥ ወንድና ፡ ሴት ፡ እያስተባበረ ፡ ባንድነትና ፡ በውስጠ ፡ ብዙነት ፥ ወይም ፡ በጠቅላይነት ፥ ባስተጋባኢነት ፡ ይነገራል ። ምሳሌ ፤ ሰብእ ፡ እንስሳ ፥ አርዌ ፡ ዖፍ ፤ መርዔት ፡ ፍጥረት ፡ ዘመድ ፤ ልብስ ፡ መጽሐፍ ፡ ንዋይ ፥ የመሰለው ፡

ኹሉ ፤ ዘመድና ፡ ፍጥረት ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ነው ። ወገብረ ፡ ዕሥራ ፡ ወክልኤተ ፡ ዘመደ ፡
(ኩፋሌ) ። ያካልና ፡ የግብር ፡ የስም ፡ መሠረት ፡ ባሕርይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ አካልን ፡ እክሴ ፡
የሚያሰኝ ፡ እውነተኛ ፡ ስም ፡ የሚወጣ ፡ ከባሕርይና ፡ ከግብር ፡ ነው ። ግብርም ፡ አካል ፡
በባሕርይ ፡ የሚሠራው ፡ ወይም ፡ የሚያፈራው ፡ የባሕርይ ፡ ፍሬ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ።
የግብር ፡ ስም ፡ በውስጡ ፡ ዘና ፡ በመስም ፡ ተነግሯል ፡ (ቍ፻፫) ። የተጸውዖና ፡ የተቀ
ብዖም ፡ አኹን ፡ በተራው ፡ ይመጣል ።

፻፫ ፤ የነዚህም ፡ ያራቱ ፡ ዐይነት ፡ ስሞች ፡ አበዛዝ ፥ እንዳወጣጣቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
ነው ፤ እኩሉ ፡ በባዕድ ፡ ፊደል ፡ በአ ፡ ብቻ ፥ ልብ ፡ አልባብ ፤ ዘመድ ፡ አዝማድ ፤ ነገድ ፡
አንጋድ ፤ ቤት ፡ አብያት ፡ እያሰኙ ፤ እኩሉም ፡ ጥብ ፡ አጥባት ፤ ነቅዕ ፡ አንቅዕት ፤ ባሕር ፡
አብሕርት ፤ ግብር ፡ አግብርት ፡ እያሰኙ ፡ በአና ፡ በት ፡ ይበዛሉ ። እኩሉ ፡ ደግሞ ፡ በም
እላድ ፡ ብቻ ፥ በዕድ ፡ በዕዳን ፤ ኃጥእ ፡ ኃጥአን ፤ ጻድቅ ፡ ጻድቃን ፤ ጽድቅ ፡ ጽድቃት ፡
አብ ፡ አበው ፥ አበ ፡ አባት ፤ ቃል ፡ ቃላት ፤ ጠል ፡ ጠላት ፤ ዝናም ፡ ዝናማት ፤ ነድ ፡ ነዳት ፤
ቆም ፡ ቆማት ፤ ሰግላ ፡ ሰጋልው ፤ ሰሌዳ ፡ ሰላድው ፥ ወይም ፡ ሰሌዳት ፡ እያሰኙ ፡ በንና ፡
በት ፡ በው ፡ ይበዛሉ ። በዕድና ፡ መስም ፡ የተባለው ፤ መኰንን ፡ መኳንንት ፥ መስፍን ፡
መሳፍንት ፤ መምህር ፡ መምህራን ፥ ማእምር ፡ ማእምራን ፡ እያሰኙ ፤ ባዕድ ፡
ከምእላድ ፡ ያልነውም ፥ መክፈልት ፡ መክፈልታት ፤ ትምህርት ፡ ትምህርታት ፡ እያ
ሰኙ ፡ በምእላድ ፡ ላይ ፡ ምእላድ ፡ ጨምሮ ፡ ይበዛል ። እኩሉ ፡ ግን ፡ በዕድና ፡ ምእ
ላድ ፡ አንና ፡ ትን ፡ ተውሳክ ፡ ሳይጨምሩ ፥ ፊደሎቻቸውን ፡ ለዋውጠው ፡ ሳድስና ፡
ራብዕ ፡ በማድረግ ፤ ኀጢአት ፡ ኀጣይእ ፤ መቅደስ ፡ መቃድስ ፤ መድሎት ፡ መዳልው ፤
መክሊት ፡ መካልይ ፤ ደብተራ ፡ ደባትር ፡ እያሰኙ ፡ በራሳቸው ፡ ብቻ ፡ ይበዛሉ ።

፻፬ ፤ ፫ኛም ፡ በካዕብ ፡ በሳብዕ ፡ ወ ፥ በሣልስ ፡ በኃምስ ፡ የ ፡ ስላሉበት ፥ ተገኖር
ደው ፡ የነበር ፡ ወና ፡ የ ፡ ገበ ፡ ገበዋት ፤ ግልፎ ፡ ግልፍዋት ፤ ቀዳሲ ፡ ቀዳስያን ፥ ቀዳሴ ፡
ቀዳስያት ፤ ደዌ ፡ ደውያት ፤ ዴዴ ፡ ዴድያት ፡ እያሰኙ ፡ ከት ፡ ጋራ ፡ በራብዕነት ፡ ያበ
ዛሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፥ ዳዕሮ ፡ ዳዕርው ፤ ከበሮ ፡ ከባርው ፤ ቀቀኖ ፡ ቀቃንው ፤
ሰገኖ ፡ ሰጋንው ፤ ፍኖት ፡ ፍናው ። ግምዔ ፡ ገማዕይ ፤ ቍልዔ ፡ ቈላዕይ ፡ እያሰኙ ፡ ብቻ
ቸውን ፡ በሳድስነት ፡ ያበዛሉ ። ይህነንም ፡ ዐዋጅ ፡ አፍርሰው ፥ ውጽቦ ፡ አውጻብ ፤ ጸ
ልቦ ፡ አጽላብ ፤ ዶርሆ ፡ ደዋርህ ፤ መርኆ ፡ መራኁት ፤ ሐለስትዮ ፡ ሐለስትዮታት ።
ጠሊ ፡ አጣሊ ፤ ከይሲ ፡ አክይስት ፤ ሰርዌ ፡ ሰራዊት ፡ እያሰኙ ፡ በአና ፡ በት ፡ የሚበዙ ፡
አሉ ። ከዚህ ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፥ ግብ ፡ ግበብ ፡ ግበባት ፤ ዕፅ ፡ ዕፀው ፡ ዕፀዋት ፤ እብን ፡
እበን ፡ አእባን ፤ እግር ፡ እገር ፡ አእጋር ። ቀሡት ፡ ቀሡታት ፡ ቀሣውት ፤ ቀሲስ ፡ ቀሲ
ሳን ፡ ቀሳውስት ። ከልብ ፡ ከለባት ፡ አክላብ ፤ ንህብ ፡ አንህብት ፡ አንሃብ ፤ ውሒዝ ፡ ው
ሒዛት ፡ ወሓይዝት ። ድርህም ፡ ድርህማት ፡ ደራህም ፤ ኅብዝ ፡ ኅብዛት ፡ ኅባውዝ ፡ እያ
ሰኙ ፡ በ፪ ፡ ዐይነት ፡ ብኻ ፡ የሚበዙ ፡ ብዙ ፡ ስሞች ፡ አሉ ።

፻፭ ፤ በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ በአ ፡ ብቻ ፡ ለሚበዙና ፡ በአና ፡ በት ፡ በየራሳቸውም ፡
ለሚበዙ ፥ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ለመኾን ፡ ፬ኛ ፡ አበዛዝ ፡ አላቸው ። ይህም ፡ ክሊል ፡ አክሊል ፡
አክሊላት ፤ መለክ ፡ አምላክ ፡ አማልክት ፤ ጠሊ ፡ አጣሊ ፡ አጣልያት ፤ ከይሲ ፡ አክይ

ስት ፡ አክይስታት ፡ መቅደስ ፡ መቃድስ ፡ መቃድሳት ፡ መቅበርት ፡ መቃብር ፡ መቃብራት ፡ እያሰኘ ፡ በብዛት ፡ ላይ ፡ ብዛት ፡ ጨምሮ ፡ የብዙ ፡ ብዙነት ፡ ያሳያል ፡፡ ዳግመኛም ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ኹኖ ፡ ባንድና ፡ በብዙ ፡ የሚነገር ፡ ጠቅላይና ፡ አስተጋባኢ ፡ ስም ፤ ሕዝብ ፡ ሰራዊት ፡ ሐራ ፡ ሰብእ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡፡ ባንድነትም ፡ ብቻ ፡ የሚነገር ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ባሕርያዊ ፡ ስም ፤ ወርቅ ፡ ብሩር ፡ ጼው ፡ ኖጻ ፥ ጸበል ፡ መሬት ፡ ሐሪጽ ፥ ሐሊብ ፡ ቅብዕ ፥ መዓር ፡ ሰከር ፤ ብእሲ ፡ ብእሲት ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፥ ግልጠ ፡ ብዙነት ፡ የለውም ፡፡

፻፮ ፤ ውስጠ ፡ ብዙነት ፡ የሌለው ፡ ስመ ፡ ተጸውዖም ፥ የሰውና ፡ ያገር ፡ የባሕርና ፡ የወንዝ ፡ የተራራ ፡ ስም ፤ ሙሴ ፡ አሮን ፥ ግብጽ ፡ ከነዓን ፥ ኤርትራ ፡ ዮርዳን ፥ ሲናይ ፡ ሔርሞን ፥ ይህን ፡ የመሰለ ፡ መጠሪያ ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ ይሞካሻል ፡ እንጂ ፤ አይበዛም ፡፡ ቢበዛም ፡ ቅሉ ፡ ከሞክሼነት ፡ በቀር ፡ ውስጠ ፡ ብዙነት ፡ የለውም ፤ ይኸውም ፡ ወአበዊነ ፡ ሠለስቱ ፡ መቃርሳት ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ፤ ዐረቡም ፡ ተላታ ፡ መጋራት ፡ ይላል ፡ (ቅዳ) ፡፡ ስመ ፡ ተቀብዖም ፡ የሚባለው ፡ የሹመትና ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፥ ጳጳስ ፡ ቀሲስ ፡ ንጉሥ ፡ ርእስ ፥ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ክቡር ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ በሹመት ፡ ጊዜ ፡ ከመሰጠት ፡ በቀር ፡ ከግብርና ፡ ከተጸውዖ ፡ ስም ፡ ልዩነት ፡ የለውም ፡፡ የከበሬታ ፡ ስም ፤ እግዚእ ፡ እግዓዚ ፡ አጋዕዝት ፥ ሊቅ ፡ ሊቃውንት ፥ ረብ ፡ አርባብ ፡ ረበዋት ፥ ረባን ፡ ረባናን ፥ ረብ(በ)ናት ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፥ ማር ፡ ማሪ ፡ ማራን ፡ ማለት ፡ ከተቀብዖ ፡ ስም ፡ ይገባል ፡፡

፻፯ ፤ የስምና ፡ የባለስም ፡ ዐይነት ፡ ፪ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የወንድ ፡ ዐይነትና ፡ የሴት ፡ ዐይነት ፡፡ በተፈጥሯቸው ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ የኾኑ ፡ ኹሉ ፡ በመልካቸውና ፡ በስማቸው ፡ ታይተው ፡ ተለይተው ፡ ይታወቃሉ ፡፡ ምሳሌ ፤ ብእሲ ፡ ብእሲት ፥ አብ ፡ እም ፥ ወልድ ፡ ወለት ፥ እኁ ፡ እኅት ፡፡ ዕጓል ፡ ዕጐልት ፥ በግዕ ፡ በግዕት ፥ እድግ ፡ እድግት ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡፡ በተፈጥሮው ፡ ተባትና ፡ እንስት ፡ ያልኾነ ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ የሌለው ፡ ማንኛውም ፡ ፍጥረት ፡ የስም ፡ ባለቤት ፥ ቦታና ፡ መሣሪያ ፥ ግብርና ፡ ነገር ፤ ሌላውም ፡ ቊሳቊስ ፥ ስም ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፤ በወንድና ፡ በሴት ፡ ሲነገር ፡ መለየው ፡ ፪ ፡ ዐይነት ፡ ነው ፤ ዐብሮት ፡ የሚነገር ፡ አንቀጽና ፡ ቅጽል ፡፡ በአንቀጽ ፡ ሲለይ ፥ ይትፌሣሕ ፡ ሰማይ ፥ ወትትሐሠይ ፡ ምድር ፤ አድባር ፡ አንፈርዐጹ ፡ ሣህል ፡ ወርትዕ ፡ ተራከባ ፤ ጽድቅ ፡ ወሰላም ፡ ተሳዐማ ፡ ርትዕሰ ፡ እምድር ፡ ሠረጸት ፤ ወጽድቅኒ ፡ እምሰማይ ፡ ሐወጸ ፡፡ በወንድ ፡ አንቀጽ ፡ የጠራውን ፡ ሰማይና ፡ ጽድቅ ፡ መልሶ ፡ ደግሞ ፡ ሰማይ ፡ ትጠወም ፥ ወሰማይኒ ፡ ተጠውመት ፡ ከመ ፡ ክርታስ ፤ ወጽድቅኒ ፡ ታግዕዘክሙ ፡ ይላል ፡፡ በቅጽልም ፡ ሲለይ ፥ ወርኢኩ ፡ ሰማየ ፡ ሐዲሰ ፡ ወምድረ ፡ ሐዳሰ ፡ እስመ ፡ ሰሰለ ፡ ሰማይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወምድርኒ ፡ ቀዳሚት ፤ ዛቲ ፡ ባሕር ፡ ዐባይ ፡ ወረሐብ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ፡፡ አንድና ፡ ብዙነት ፡ የሌለው ፥ ወንድና ፡ ሴት ፡ የማይለይ ፡ ጥሬ ፥ አገባብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ አለመለየቱም ፡ ስምነትና ፡ ግብርነት ፡ የሌለው ፡ ዝራፊ ፥ የዘርና ፡ የነባር ፡ ጫላፊ ፥ የንባብ ፡ እንቃሪ ፡ የርባታ ፡ ዝቃጭ ፥ ወይም ፡ አተላ ፡ ሙጣጭ ፥ ድፍርስ ፡ ተራዋጭ ፥ ልቃሚ ፡ ብጣሪ ፡ እንቅጥቃጭ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡፡

## ፲፫ኛ ፡ ዕርከን ።

### አገባብ ።

፻፳ ፤ አገባብ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ መፍትው ፡ ርትዕ ፡ ድሎት ፡ ካለው ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ ዘይቤውም ፡ የተገባ ፡ ግቡ ፥ የሚገባ ፡ ሥርዐት ፥ የነገር ፡ አጣጣል ፥ የንባብ ፡ አሰ ካክ ፥ ወይም ፡ በይግባኝ ፡ መምህር ፡ የሚፈርደው ፡ ፍትሐ ፡ ሰዋስው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የሰዋስውን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። ፪ኛም ፡ አገባብ ፡ ማለትን ፡ ጨው ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ እኈል ፡ ገብ ፡ ቃል ፡ ይሉና ፥ ትርጓሜውን ፡ የብትን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ መሰብሰቢያና ፡ ማሰ ማሚያ ፥ የቋንቋ ፡ ቅመም ፥ የንባብ ፡ መቃስም ፥ ወይም ፡ ማጣፈጫ ፥ የምስጢር ፡ መግ ለጫ ፡ ይሉታል ። ያገባብም ፡ ዐይነት ፡ ስሙና ፡ ክፍሉ ፡ ፫ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ ደቂቅ ፡ ይባላል ፤ ፫ቱም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደሚጣፈው ፡ ነው ።

### ዐቢይ ፡ አገባብ ።

፻፳፩ ፤ በነባር ፡ በዘማች ፡ በዐበይት ፡ አናቅጽ ፡ እየገባ ፡ ማሰሪያነትን ፡ የሚያስለ ቅቅ ፡ ኹሉ ፡ ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ይባላል ፤ በስማቸውና ፡ በግብራቸው ፡ ከንኡስ ፡ ከደቂቅ ፡ ተለይተው ፡ ዐበይት ፡ አገባቦች ፡ የሚባሉም ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።

| | | |
|---|---|---|
| እስመ ፡ | መጠነ ፡ ዐቅመ ፡ | መዋዕለ ፡ |
| አኮኑ ፡ | አምጣነ ፡ | ዕለተ ፡ |
| በእንተ ፡ | ከመ ፡ | ሰዓ ፡ ሰዓተ ፡ |
| በይነ ፡ | በዘ ፡ | እስከ ፡ |
| እንበይነ ፡ | እምዘ ፡ | ድኅረ ፡ |
| ህየንተ ፡ | አርአያ ፡ | ዘ ፡ እንተ ፡ እለ ፡ |
| ተውላጠ ፡ | አምሳለ ፡ ሕገ ፡ | አላ ፡ |
| ፍዳ ፡ በቀለ ፡ | እመ ፡ | ዳእሙ ፡ |
| ኅበ ፡ | ሶበ ፡ | ባሕቱ ፡ |
| መንገለ ፡ | አመ ፡ | እንበለ ፡ |
| ወ(ው)እደ ፡ | ጊዜ ፡ | ዓዲ ፡ |
| እንዘ ፡ | ዓመተ ፡ | ብሂል ። |

ከነዚሁ ፡ ደግሞ ፡ ዐቢይነትን ፡ መደብ ፡ አድርገው ፥ ንኡስነትና ፡ ደቂቅነት ፡ የሚ ደርቡ ፡ አሉ ። ንኡስነት ፡ የሚደርቡ ፥ እስመ ፡ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ባሕቱ ፡ እንበለ ፡ ናቸው ። ደቂቅነት ፡ የሚደርቡ ፥ በእንተ ፡ ህየንተ ፡ ተውላጠ ፡ ፍዳ ፥ ኅበ ፡ መንገለ ፡ ወእደ ፡ መጠነ ፡ አምጣነ ፥ ከመ ፡ አርአያ ፡ አምሳለ ፥ አመ ፡ ሶበ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ድኅረ ፥ እንተ ፡ እንበለ ፡ ዓዲ ፡ ናቸው ፤ እንበለ ፡ ከኹሉ ፡ ይገባል ። ከንዳንዶቹና ፡ ከጥቂቶቹ ፡ በቀር ፡ ብዙዎቹ ፡ ጥሬና ፡ ነባር ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፡ ባ፲ ፡ ባ፲ ፡ ይዘረዘራሉ ። ሊዘረዘሩ ፡ ግን ፡ የማይችሉ ፤ እስመ ፡ አኮኑ ፡ እመ ፡ አላ ፡ ዳእሙ ፥ ወእደ ፡ እንዘ ፡ ባሕቱ ፡ ናቸው ።

## ንኡስ ፡ አገባብ ።

፻፲ ፤ በነባር ፡ በዘማች ፥ በዐቢይ ፡ በንኡስ ፥ በአናቅጽ ፡ ኹሉ ፡ እየገባ ፡ ማሰሪያ ነትን ፡ የማያስለቅቅ ፤ ጥያቄና ፡ አንክሮ ፥ ደስታና ፡ ሐዘን ፥ ልመናና ፡ ምኞት ፥ አሉታና ፡ አፍራሽ ፡ ዕሽታና ፡ እንቢታ ፥ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፥ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ የሚያሳይ ፡ ፊደልና ፡ ቃል ፥ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ ይባላል ፤ ከዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ተለይተው ፡ ንኡስ ፡ አገ ባቦች ፡ የሚባሉም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰ ፡ | አ ፡ | ሐዊሳ ፡ | እንቋዕ ፡ |
| እም ፡ | አሌ ፡ | እስኩ ፡ | ጥቀ ፡ |
| መ ፡ ሚ ፡ | ወይ ፡ ዋይ ፡ | ዮጊ ፡ | እንከ ፡ |
| እፎ ፡ በእፎ ፡ | ወይሌ ፡ | እንጋ ፡ | አ ፡ |
| አይ ፡ ምንት ፡ ተ ፡ | አህ ፡ አሀህ ፡ | ክመ ፡ ጽመ ፡ | ሰ ፡ |
| ሁ ፡ ኑ ፡ በኑ ፡ | ሰይ ፡ ዬ ፡ | ኄ ፡ | ኬ ፡ |
| አይ ፡ መኑ ፡ | አይ ፡ አይቴ ፡ | አይ ፡ ማእዜ ፡ | ስፍን ፡ |
| አሉታ ፤ ......... | አል ፡ | ኢ ፡ | አከ ፡ |
| አማራጭ ፤ ........ | አው ፡ ዮጊ ፡ ሚመ ፡ እመ ፡ አከ ፡ ሰበ ፡ አከ ፡ | | |
| አማፋሪ ፤ ........ | ወ ፡ ሂ ፡ ኒ ፡ ዓዲ ፡ | | |
| ከፋይ ፤ ......... | ወ ፡ ሂ ፡ ኒ ፡ ሰ ፡ ባሕቱ ፡ | | |
| አጋናኝ ፤ ........ | ወ ፡ ሂ ፡ ኒ ፡ ጥቀ ፡ | | |
| ጉድና ፡ ድንቅ ፤ | ዕጹብ ፡ ግሩም ፡ ተአምር ፡ ግናይ ። | | |

## የጊዜ ፡ ጥሬዎች ።

| | | |
|---|---|---|
| ቅድመ ፡ ቅድም ፡ | ትማልም ፡ | ጌሠም ፡ ሳኒታ ፡ |
| ትካት ፡ ዓለም ፡ | አሚር ፡ ዮም ፡ | ወትረ ፡ ዘልፈ ፡ |
| እስፌር ፡ | ጎሪፍ ፡ | ለዝሉ(ላ)ፉ ፡ |
| ናሁ ፡ | ይእዜ ፡ | ግሙራ ፡ ለግሙራ ፡ |
| ማእዜ ፡ | ወትር ፡ ዘልፍ ፡ | ለፍጻሜ ። |

## የብዙ ፡ ብዙና ፡ ጭራሽ ፡ የሚያሳዩ ።

፻፲፩ ፤ ጥቀ ፡ ፈድፋደ ፡ ብዙኅ ፡ ይሙኑ ፤ በሕቁ ፡ በፍድፋዴ ። ለዓለም ፡ ለዝሉፉ ፤ ለፍጻሜ ፥ ግሙራ ፡ ለግሙራ ። ምንተ ፡ ጽመ ፡ ክመ ፥ እምድሩ ፡ በምልኡ ፡ ስብዐ ። ዳግመኛም ፡ መድረሻቸው ፡ ግእዝ ፡ እየሆነ ፥ ወይም ፡ በ ፡ ወድቆባቸው ፡ በሳድስነት ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ የሚኾኑ ፡ ሳድስ ፡ ቅጽሎች ፡ ከምሉ ፡ በክፍሉ ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፍጹመ ፡ | በፍጹም ፡ | ጥዩቀ ፡ | በጥዩቅ ፡ |
| ጥንቁቀ ፡ | በጥንቁቅ ፡ | ሕቀ ፡ | በሕቅ ፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ህልወ ፡ | በህልው ፡ | ኅዳጠ ፡ | በኅዳጥ ፡ |
| ድቡተ ፡ | በድቡት ፡ | ውኁደ ፡ | በውኁድ ፡ |
| ህዱአ ፡ | በህዱእ ፡ | ንስቲተ ፡ | በንስቲት ፡ |
| ክቡተ ፡ | በክቡት ፡ | ፍድፉደ ፡ | በፍድፉድ ፡ |
| ኅቡአ ፡ | በኅቡእ ፡ | ንሕኑሐ ፡ | በንሕኑሕ ፡ |
| ክሡተ ፡ | በክሡት ፡ | ብዙኅ ፡ | በብዙኅ ፡ |
| ግሁደ ፡ | በግሁድ ፡ | ርቱዐ ፡ | በርቱዕ ፡ |
| መፍትወ ፡ | በመፍትው ፡ | ድልወ ፡ | በድልው ። |

በነዚህ ፡ አምሳል ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ እየኾነ ፡ ለሚነገር ፡ ቅጽል ፡ ውሳኔ ፡ የለውም ። ፫ኛም ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ የሚሰማባቸው ፡ ጥሬዎችና ፡ ቅጽሎች ፥ ወይም ፡ ውስጠ ፡ ውእቱዎች ። ድልወት ፡ መፍትው ፤ ብፁሕ ፡ ርትዕ ። መፍቅድ ፡ ፈቃድ ፡ ፍትወት ፡ ጻሕቅ ፡ ሥምረት ፡ ማኅሠሥ ። ግብር ፡ ኵርህ ፡ ግድ ፡ ግዱድ ። ፬ኛም ፡ ጽድቅና ፡ አሉታ ፡ አንቀጽ ፡ የሚሰማባቸው ፡ የጥሬና ፡ ያንቀጽ ፡ ልቃሞች ፥ ወይም ፡ እንጥብጣቦች ። ናሁ ፡ ዮጊ ፡ ነዋ ፡ የኔ ፤ እንሆ ። ነዮ ፡ (ያ ፡ ዮሙ ፡ ዮን ፤ ነየከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፤ ነየ ፡ ነየነ) ፤ እንሆት ፤ እንሆለት ። እወ ፡ አሜን ፡ አማን ፤ አዎን ፡ እውነት ። እንዳዒ ፡ እንጋ ፤ እንጃ ። አሆ ፡ እንቢ ፡ (ቍ፺፬) ። አሀ ፡ አሀሀ ፥ አሀ ፡ አሀ ፤ ወዲያ ፡ ወዲያ ። ብሥራት ፤ ብሥራትከ ፡ (ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን) ፤ የምሥራች ፥ ደስ ፡ ይበልኽ ፤ ተፈሣሕ ፡ ወተሐሠይ ። ፭ኛም ፡ ከትእዛዝ ፡ እየተጨመሩ ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ የሚኾኑ ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጾች ። ሀብ ፤ ሀቡ ፤ ሀቢ ፤ ሀባ ፡ (ወሀበ) ። ሀብኬ ፡ ንትኃሠሥ ። ነዐ ፤ ነዑ ፤ ንዒ ፤ ንዓ ፡ (ነዐወ) ። ንዑ ፡ ንረድ ፡ ንሁ ፡ ንምሳሕ ። ሕንክ ፡ ክሙ ፡ ሕንኪ ፡ ካ ፡ (ሐነከ) ። ሕንክሙ ፡ ብልዑ ።

## ደቂቅ ፡ አገባብ ።

፲፲፪ ፤ በብትን ፡ ሰዋስው ፡ ባራት ፡ ሰራዊት ፡ በሩቅ ፡ በሩቆች ፡ እየገባ ፡ በሥር ፡ መደብ ፡ የሚዘረዘር ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ይባላል ፤ በተገናኝ ፡ የባለቤትን ፡ ኹኔታና ፡ ሥራ ፡ ለመግለጥ ፡ በብትን ፡ ላይ ፡ የሚጨመር ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ተረፈ ፡ ንኡስ ፡ እንደ ፡ ማለት ። ለዚህም ፡ ፪ ፡ ዐይነት ፡ አለው ፤ መድረሻውን ፡ የሚለውጥና ፡ የማይለውጥ ። መድረሻቸውን ፡ የማይለውጡ ፡ ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባ፬ ፡ ረድፍ ፡ የተጣፉት ፡ ናቸው ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቤዛ ፡ | ፍና ፡ | ውስተ ፡ ጠ ፡ | ለ ፡ ለለ ፡ |
| በስበ ፡ | ዲበ ፡ | ውሳጤ ፡ | በ ፡ በበ ፡ |
| ዕሴተ ፡ | ላዕለ ፡ | ቅድመ ፡ | ዘ ፡ ዘዘ ፡ |
| ተክለ ፡ | መልዕልተ ፡ | ማእከለ ፡ | ምስለ ፡ ከመ ፡ |
| በይነ ፡ | ታሕተ ፡ | አፍአ ፡ | አርአያ ፡ |
| አፈ ፡ | መትሕተ ፡ | ዝየ ፡ ለፌ ፡ | ህየ ፡ ከሃ ። |

## መድረሻቸውን ፡ የሚለውጡና ፡ የማይለውጡ ፡ የቦታና ፡ የጊዜ ፡ ጥሬዎች ።

### የቦታ ፡ ጥሬ ።

ላዕል ፡ መልዕልት ፡ ላዕሊት ። ታሕት ፡ መትሕት ፡ ታሕቲት ። ትርአስ ፡ ትርጋፅ ፡ አፍአ ፤ ውስጥ ፡ ውሳጢ ፡ ውሳጢት ። ቅድም ፡ ፍጽም ፡ ገጽ ፤ አንጻር ፡ ምንጻር ። ድኅሪት ፡ ከዋላ ፤ ማንጽሊት ፡ ግፍትዒት ፡ ቀኀልቀኅሊት ። የማን ፡ ይምን ፤ ፀጋም ፡ ዕግም ። ጽንፍ ፡ ክንፍ ፡ ከንፈር ፡ ሐይቅ ፤ ድንጋግ ፡ ወሰን ። አድያም ፡ ደወል ፡ ብሔር ። ዝየ ፡ ህየ ፡ ለፌ ፡ ከሃ ። ጥቃ ፡ ጎር ፡ ሕፅን ፡ ገቦ ፡ ጕንድ ፡ ጽጕ ፡ ጽጕጕ ፡ ዐውድ ፡ ዘውር ፡ ማድም ፡ ኑኀ ፡ ኑለሄ ።

### የጊዜያት ፡ ጥሬ ።

ቅድም ፡ ቀዲሙ ፡ አቅዲሙ ፡ ቀዳሚ ፡ መቅድም ። ድኅር ፡ ደኅሪ ፡ ከዋላ ። ምዕር ፡ ወትር ፡ ዘልፍ ። ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ ኵሎ ፡ ሰዓ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፥ ኵሎ ፡ አሚረ ፥ ኵሎ ፡ ዘመነ ። ንእስ ፡ ናእስ ፤ ውርዙት ፡ ውርዛዌ ። ርሥእ ፡ ርሥእና ፡ ርሥአን ። ትከት ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፤ ፍጻሜ ፡ ተፍጻም ፡ ተፍጻሜት ።      ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ ደቂቅ ፡ የተባሉት ፡ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ያገባብ ፡ ጥሬዎች ፡ እንዲህ ፡ እንደሽት ፡ ተመርጠው ፥ ታሽተው ፡ ተፈልፍለው ፡ በ፫ ፡ ማእሰረ ፡ ክፍል ፡ የታሰሩ ፡ ኋላ ፡ እንዲፈቱ ፡ ነውና ፤ ግቢያቸውንና ፡ ባህላቸውን ፡ አፈታታቸውን ፡ በየተራቸው ፡ በ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ ተመልከት ።

### ፩ኛ ፡ ክፍል ።

### ጸዋትወ ፡ ቅጽል ፡ ወአኀዝ ፡ የሰዋስው ፡ ባለቤትና ፡ ኀዝ ።

### ፲፩ኛ ፡ ዕርከን ።

፻፲፫ ፡ ቅጽል ፡ ማለት ፡ ተጨማሪ ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ ነው ፤ መለዮ ፡ ምልክት ፡ እንደ ፡ ማለት ፤ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ የባለቤትን ፡ ስምና ፡ ግብር ፥ ጠባይና ፡ አኳኋን ፥ መልኩን ፡ ዐይነቱን ፥ ወርዱን ፡ ቁመቱን ፡ ስፍሩን ፡ ቍጥሩን ፤ ሌላውንም ፡ ኹሉ ፡ የሚያሳይ ፡ የስምና ፡ የግብር ፡ ፍካሬ ፥ ወይም ፡ ጽጌና ፡ ፍሬ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ (እስመ ፡ እምፍሬሁ ፡ ይትዐወቅ ፡ ዕፅ) ። የቅጽልም ፡ ዐይነት ፡ እንደ ፡ ሰዋስው ፡ ክፍል ፡ ፱ ፡ ነው ፤ ፭ኛው ፡ ዘር ፥ ፱ኛው ፡ ነባር ፡ ይባላል ፤ ዘር ፡ ቅጽል ፡ አንቀጽ ፡ ያለው ፥ ነባር ፡ ግን ፡ አንቀጽ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

፻፲፬ ፡ ዘር ፡ ቅጽሎች ፡ ፬ ፡ ናቸው ፤ ውስጠ ፡ ዘና ፡ መስም ፥ ጥሬ ፡ ዘርና ፡ ወገን ፡ ቅጽል ፥ አኀዝ ። ለዘር ፡ ቅጽል ፡ ኹሉ ፡ ውስጠ ፡ ዘንት ፡ አለው ፤ የውስጠ ፡ ዘም ፡ ነገር ፡ በ፸፫ ፡ ቍጥር ፡ ከመስም ፡ ጋራ ፡ ተነግሯል ። የጥሬ ፡ ዘርም ፡ ውስጠ ፡ ዘንት ፥ ዘርፍ ፡ እየያዘ ፡ ሲቀጸል ፡ ነው ፤ ዘርፍ ፡ የሌለው ፡ ጥሬ ፥ ነጠላ ፡ ስም ፡ እንጂ ፡ ቅጽል ፡ አይባልም ። በአንቀጽ ፡ በብትን ፡ እየገቡ ፡ የልክ ፡ ቅጽልና ፡ አገባብ ፡ የሚኾኑ ፡ መጠንና ፡ አምጣን ፡ ዐቅም ፥ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ዘር ፡ ቅጽሎች ፡ ናቸው ። ወገን ፡ ቅጽሎች ፡ የተባሉም ፡ አስቀድመን ፡ በ፬ ፡ ቍጥር ፡ እንዳርእስት ፡ የተናገርናቸው ፡ ዊና ፡ ይ ፡ ናቸው ፡

(ቀዳማዊ ፡ ይ ፥ ወደኃራዊ ፡ ይ) ፡ እነዚህ ፡ ፬ቱ ፡ ምእላዶች ፥ ዘርፍ ፡ አያያዥነት ፡ ባላ
ቸው ፡ ብ፬ቱ ፡ ፊደላትና ፡ (ግእዝ ፡ ራብዕ ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕ) ፡ በ፬ቱ ፡ አገባብ ፡ በለ ፡ በዘ ፡
ፈንታ ፡ እየገቡ ፥ የዘርፍና ፡ የቅጽል ፡ አፈታት ፡ ስላገኙ ፥ ከቅጽሎች ፡ ጋራ ፡ ተቈጥረ
ዋል ፡ ስማቸውም ፡ የሙሻዘር ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ይባላል ። ወገንነታቸው ፡ በወገን ፡ ጥሬ ፡
ሲገቡ ፡ ነው ። ምድር ፡ ምድራዊ ፥ ሰማይ ፡ ሰማያዊ ፥ ኢትዮጵያዊ ። አኃዝ ፡ ቅጽልም ፡
ካንድ ፡ እስከ ፡ ምእልፊት ፡ ያለ ፡ ቍጥር ፡ ነው ፡ ኋላ ፡ በቦታው ፡ ይነገራል ።

፻፲፰ ፡ ነባር ፡ ቅጽሎችም ፥ እንደ ፡ ዘር ፡ ቅጽሎች ፡ ፰ ፡ ናቸው ፤ ነባር ፡ ጥሬና ፡
ግልጸ ፡ ዘ ፥ የቦታና ፡ የጊዜ ፡ ቅጽሎች ፥ ንኡስና ፡ ደቂቅ ። ነባር ፡ ጥሬ ፥ የሚበዛና ፡ የማ
ይበዛ ፡ ስም ፡ ነው ፤ የሚበዛ ፡ ስም ፥ እብን ፡ አእባን ፤ ይህን ፡ የመሰለ ። የማይበዛ ፡ የመ
ጠሪያ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ዳዊት ፡ ሰሎሞን ፥ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ግልጸ ፡ ዘ ፡ የሚባል ፡ ዐበ
ይት ፡ አገባቦች ፡ ዘ ፡ አንተ ፡ እለ ፡ የገቡበት ፡ ዘማች ፡ አንቀጽና ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፤
የዘ ፡ አንተ ፡ እለም ፡ ዝርዝር ፡ ምስጢሩ ፡ ዘርፍ ፡ አያያዥነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ግልጸ ፡ ዘ ፡ ይባ
ላል ፤ ዘ ፡ ያንድ ፥ እንተ ፡ ያንዲት ፥ እለ ፡ የብዙ ፡ ቅጽል ፡ ነው ። የቦታና ፡ የጊዜ ፡ ቅጽ
ሎች ፡ የተባሉም ፡ የዘንና ፡ የበን ፡ ፀማርኛ ፡ ይዘው ፡ የሚፈቱ ፡ ዐበይት ፡ አገባቦች ፡
ናቸው ፤ የዘን ፡ ፀማርኛ ፡ መያዛቸው ፡ በባለቤቱ ፡ ላይ ፡ አገባብ ፡ ሳይኖር ፡ ነው ፡ አገ
ባብ ፡ ሲኖር ፡ ግን ፡ የዘ ፡ ፀማርኛ ፡ የ ፡ ተበዝብዞ ፡ ይቀራል ፡ እንጂ ፡ አይነገርም ።

፻፲፱ ፡ የቦታ ፡ ቅጽሎች ፡ ኀበና ፡ መንገለ ፡ ውእደ ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ ፫ቱ ፡ አገ
ባብ ፡ በሌለው ፡ ሲቀጸሉ ፤ መከን ፡ ኀበ ፡ ይትገበር ፡ መንገለ ፡ ይትገበር ፡ ውእደ ፡ ይት
ገበር ፡ መሥዕተ ፡ ቅዳሴ ፡ ቅዱስ ፡ ውእቱ ፤ የሚደረግበት ፡ ቦታ ። አገባብ ፡ ባለውም ፡
ሲቀጸሉ ፤ ውስተ ፡ መከን ፡ ኀበ ፡ ቆመ ፡ መንገለ ፡ ቆመ ፡ ውእደ ፡ ቆመ ፡ እግረ ፡ እግዚእን ፡
የጌታችን ፡ እግር ፡ ከቆመበት ፡ በቆመበት ፡ ቦታ ፡ ያሰኛሉ ። በነባር ፡ አንቀጽም ፡ ሲገቡ ፡
በምድረ ፡ በድው ፡ ኀበ ፡ አልቦ ፡ መንገለ ፡ አልቦ ፡ ውእደ ፡ አልቦ ፡ ዕፅ ፡ ወማይ ፤ ዕንጨ
ትና ፡ ውሃ ፡ በሌለበት ፡ እያሰኙ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያሉ ። የጊዜም ፡ ቅጽሎች ፡
የሚባሉ ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ በነባር ፡ አንቀጽ ፡ እየገቡ ፡ የዘን ፡ ፀማርኛ ፡ የበን ፡ ዝር
ዝር ፡ ይዘው ፡ የሚፈቱ ፡ ዐበይት ፡ አገባቦች ፡ አመ ፡ ሶበ ፡ ጊዜ ፡ ሰዓ ፡ ሰዓተ ፡ ዕለተ ፡
መዋዕለ ፡ ዓመተ ፡ ናቸው ። ሲገቡም ፡ በኀላፊ ፡ አመ ፡ ተእኅዘ ፡ ሶበ ፡ ተእኅዘ ፡ እግዚ
እን ፤ ጌታችን ፡ የተያዘበት ። በትንቢት ፡ አመ ፡ ይብሉ ፡ ሶበ ፡ ይብሉ ፡ ጊዜ ፡ ይብሉ ፡
ብፁዓት ፡ መከናት ፤ መካኖች ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ፡ የሚሉበት ። በነባርም ፡ አመ ፡ ቦ ፡
ወአመ ፡ አልቦ ፡ እያለ ፡ ይገባል ። የቀሩትም ፡ ሰዓ ፡ ሰዓተ ፡ ዕለተ ፡ መዋዕለ ፡ ዓመተ ፡ ምስጢ
ራቸውን ፡ ይዘው ፡ እየገቡ ፡ ሰዓት ፡ ቀን ፡ ቀኖች ፡ ዘመኖች ፡ ወራት ፡ ዓመት ፡ ተብለው ፡
በያማርኛቸው ፡ ይፈታሉ ። ይህም ፡ በመዋዕለ ፡ ትኤብስ ፡ በምትበድልበት ፡ ወራት ።
በዓመተ ፡ ሞተ ፡ ዖዝያን ፡ ንጉሥ ፤ ንጉሡ ፡ ዖዝያን ፡ በሞተበት ፡ ዓመት ፡ ማለቱን ፡ ያሳ
ያል ። የልክ ፡ ቅጽሎች ፡ የሚባሉም ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ በነባር ፡ አንቀጽ ፡ እየገቡ ፡
ያኽል ፡ ተብለው ፡ የሚፈቱ ፡ ዐበይት ፡ አገባቦች ፡ መጠነ ፡ አምጣነ ፡ ዐቅመ ፡ ናቸው ።
ሲገቡም ፡ በኀላፊ ፡ ከብረ ፡ ዮሴፍ ፡ መጠነ ፡ አምጣነ ፡ ዐቅመ ፡ ተዋረደ ፡ ወከነ ፡ ገብረ ፡
ዮሴፍ ፡ የተዋረደና ፡ ባሪያ ፡ የኾነውን ፡ ያኽል ፡ ከበረ ። በትንቢት ፥ መጠነ ፡ ይክል ፡

አፉየ ፡ አስተብዕዕ ፡ ዕበየኪ ፡፡ በነባርም ፥ መጠን ፡ ብየ ፡ እሁብ ፡ ያለኝን ፡ ያለብኝን ፡ ያኽል ፡ እሰጣለኹ ፡ ያሰኛል ፡፡ የቀረውን ፡ ፍች ፡ በአኃዝ ፡ ቅጽል ፡ መጨረሻና ፡ በቢይ ፡ አገባብ ፡ ውስጥ ፡ ተመልከት ፡፡

፻፲፯ ፡ ንኡስ ፡ ቅጽልም ፡ የሚባሉ ፡ በንኡስ ፡ አገባብ ፡ የሚገኙ ፡ የጥያቄና ፡ ያን ክሮ ፡ ጥሬዎች ፡ አይ ፡ ምንት ፥ አይ ፡ መኑ ፥ አይ ፡ ማእዜ ፥ አይ ፡ አይቴ ፥ አይ ፡ አያት ፥ ስፍን ፡ እስፍንት ፡ ናቸው ፡፡ አይ ፡ ምንት ፡ ምን ፡ ምንድር ፡ አያት ፡ ምንታት ፥ ምኖች ፡ ምንድሮች ፡ የነገር ፡ ቅጽሎች ፡ ናቸው ፡ አይ ፡ አያት ፡ ላካልም ፡ ይኾናል ፡፡ አይ ፡ መኑ ፥ ማን ፡ አያት ፡ እለ ፡ መኑ ፥ እነማን ፡ ያካል ፡ ቅጽሎች ፡ ናቸው ፡፡ አይ ፡ ማእዜ ፥ መች ፡ መቼ ፡ የጊዜ ፡ ቅጽሎች ፡፡ አይ ፡ አይቴ ፥ ሔት ፡ ወዴት ፡ የቦታ ፡ ቅጽሎች ፡፡ አይ ፡ አ ያት ፥ ማንኛው ፡ ማናቸው ፡ ማንኛቸው ፡ ማናቻቸው ፡ ከፋዮች ፡፡ ስፍን ፡ እስፍንት ፥ ስንት ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ቍጥር ፡ ጠያቆች ፡፡ የጥያቄያቸውም ፡ ቀሰጠና ፡ ምስጢር ፡ አኃዝ ፡ ቅጽል ፡ ነው ፡ አንክሮም ፡ ይኾናል ፡፡ አይ ፡ አይቴ ፡ ከአየየ ፥ ስፍን ፡ እስፍንት ፡ ከሰፈነ ፡ የወጡ ፡ ናቸው ፡ ነባርነታቸው ፡ በጠባይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በትውልድ ፡ አይደለም ፡ (ቍ ፲) ፡፡ ከማእዜ ፡ በቀር ፡ ኹሉም ፡ በ፲ ፡ መደብ ፡ ይረባሉ ፡ አኃዝ ፡ ቅጽልም ፡ ከደቂቅ ፡ በኋላ ፡ ይመጣል ፡፡

## ደቂቅ ፡ ቅጽል ፡፡

፻፲፰ ፡ በ፹፱ ፡ ቍጥር ፡ በደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ቃጥተን ፡ የተውናቸው ፡ ደቂቅ ፡ ቅጽ ሎች ፡ ከነርባታቸው ፡ ከናፈታታቸው ፡ እሊሀ ፡ ናቸው ፡፡

(ሩቅና ፡ ድብቅ) ፡፡

| | |
|---|---|
| ውእቱ ፡ | ርሱ ፡ |
| ይእቲ ፡ | ርሷ ፡ |
| ውእቶሙ ፡ እሙንቱ ፡ | ርሳቸው ፡ እነርሱ ፡ |
| ውእቶን ፡ እማንቱ ፡ | ግዝኒ ፡ ከማሁ ፡፡ |

(ቅርብ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለ) ፡፡

| | |
|---|---|
| አንተ ፡ | በቁሙ ፡ አንተ ፡ |
| አንቲ ፡ | አንቺ ፡ ች ፡ |
| አንትሙ ፡ | እላንተ ፡ ት ፡ |
| አንትን ፡ | ግዝኒ ፡ ከማሁ ፡፡ |

(ነባቢ ፡ ወነባቢት) ፡፡

| | |
|---|---|
| አነ ፡ | እኔ ፡ (ወንድና ፡ ሴት) ፡ |

(ነባብያን ፡ ወነባብያት) ፡፡

| | |
|---|---|
| ንሕነ ፡ | እኛ ፡ (ወንዶችና ፡ ሴቶች) ፡ |

ምብጥ ፡ ቅጽል ፡ ወይም ፡ አማሬ ።

(የቅርብ ፡ ሩቅ ፡ የሚታይ) ።

| | |
|---|---|
| ዝኩ ፡ ዝስኩ ፡ ዝክቱ ፡ | ያ ፡ ያኛው ፡ |
| እንትኩ ፡ እንታክቲ ፡ | ያች ፡ ያችኛዋ ፡ ይቱ ፡ |
| እልኩ ፡ እልክቱ ፡ | እሊያ ፡ እሊያኞች ፡ ቹ ፡ |
| እልኩን ፡ እልክቶን ፡ | ዝኒ ፡ ከማሁ ። |

(የቅርብ ፡ ቅርብ ፡ የሚዳሰስ) ።

| | |
|---|---|
| ዝ ፡ ዝንቱ ፡ | ይህ ፡ |
| ዛ ፡ ዛቲ ፡ | ይህች ፡ |
| እሉ ፡ እሎንቱ ፡ | እሊህ ፡ |
| እላ ፡ እሎን ፡ እላንቱ ። | ዝኒ ፡ ከማሁ ። |

ዝኩ ፡ ዝስኩ ፡ በዮች ፡ አነና ፡ ንሕነ ፡ ስለ ፡ ኹኑ ፥ ርባታው ፡ በ፳ ፡ መደብ ፡ ተወስኗል ፡ ሲዘረዘር ፡ ግን ፡ ከውእቱ ፡ እስከ ፡ ንሕነ ፡ ላሉት ፡ ዘርፍ ፡ እያያኘ ፡ ኹኖ ፡ ይቀጸላል ።

ዚአሁ ፡ እንቲአሁ ፡ እሊአሁ ፡ (ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን) ፡ የርሱ ፡ የርሱን ፥ የርሱ ፡ ነው ።

ዚአከ ፡ እንቲአከ ፡ እሊአከ ፡ (ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን) ፡ ያንተ ፡ ያንተን ፥ ያንተ ፡ ነው ።

ዚአየ ፡ (ነ) ፡ የኔ ፡ የኔን ፥ የኔ ፡ ነው ። ኹሉን ፡ እንዲህ ፡ ፍታ ።

፻፲፱ ፡ የገቢር ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ። ኪያ ፡ (ዐረብ ፡ ኢያ) ፡ ርስን ፡ ራስን ።

ኪያሁ ፡ (ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን) ፡ ርሱን ፡ ራሱን ።

ኪያከ ፡ (ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ) ፡ አንተን ፡ ራስኽን ።

የተገብሮ ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ። ለል ፡ (ለለ) ፡ ርስ ፥ ቅል ፡ ራስ ።

ለሊሁ ፡ (ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን) ፡ ርሱ ፡ ቅሉ ፥ ራሱ ፡ በለቤቱ ።

ለሊከ ፡ (ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ልየ ፡ ሊነ) ፡ አንተ ፡ ቅልኽ ፡ ራስኽ ።

ደምላይና ፡ ጠቅላይ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ። ኵል ፡ (ክሉል) ፡ ድምር ፡ ጥቅል ።

ኵሉ ፡ (ላ ፡ ሎሙ ፡ ሎን) ፡ ኵ—ኹሉ ፥ መላው ፡ ጠቅላላው ፥ ፩ ፡ ሳይቀር ።

ኵልከ ፡ (ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ልየ ፡ ልነ) ፡ ኹልኽ ፡ መላኽ ።

ኵለንታ ፡ (የሕዋሳት ፡ ቅጽል) ፡ ኹለንተና ፡ ኹለመና ፡ ከራስ ፡ እስከ ፡ እግር ።

ኵለንታሁ ፡ (ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ። ከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ) ፡ ኹለንተ(መ)ናው ።

ባሕቲት ፡ (ብሕተ ፡ ባሕተወ) ፡ ብቻ ፡ ብቻነት ፡ ነጠላነት ።

ባሕቲቱ ፡ (ታ ፡ ቶሙ ፡ ቶን ። ትከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ) ፡ ብቻው ፡ ራሱ ።

ዕራቅ ፡ ዕራቍትነት ፡ ባዶ ፡ ብቻ ፡ ነጠላ ፡ መለመላ ፥ አንዳች ፡ የሌለበት ።

ዕራቁ ፡ (ቃ ፡ ቆሙ ፡ ቆን ። ቅከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ) ፡ ዕራቍቱ ፡ ባዶው ፡ ብቻው ።

በይን ፡ በይናት ፡ ብቻ ፥ ርስ ፡ ራስ ። በበይናት ፡ ርስ ፡ በርስ ።

በበይናቲሆሙ ፡ (ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ። ከ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ትኪ ፡ ትየ ፡ ቲነ) ፡ ርስ ፡ በርሱ ።

ከንቱ ፡ በቁሙ ፥ ብላሽ ፡ የገዝም ፡ ብሎ ፥ ዋጋ ፡ የሌለው ፡፡

በክ ፡ ገዚ ፡ ከማሁ ፡ ከንቱ ፡ ብላሽ ፡ ጠፍ ፡፡ በክት ፡ ሙቶ ፡ ያደረ ፥ ቢያክ ፡ ቢያክ ፡ የሚባል ፡ የሚያስጠይፍ ፡፡ የዝርዝሮችም ፡ ጠባይ ፥ ስማቸውና ፡ መልካቸው ፥ ዘመድና ፡ ባዕድ ፡ መባላቸው ፡ ዐጸፋና ፡ ቅጽል ፡ መኾናቸው ፡ በ፶፯ ፡ ቍጥር ፡ ተነግሯል ፡ ከነባር ፡ ቅጽልም ፡ መቈጠራቸው ፥ በስም ፡ ዐጸፋነት ፡ እየገቡ ፡ ሩቅና ፡ ቅርብ ፡ ፩ና ፡ ብዙ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ የሚለያዩና ፡ የሚያሳዩ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነው ፡፡

## ፲፫ኛ ፡ ዕርከን ፡፡

## አኃዝ ፡ ቅጽል ፡፡

፻፳ ፡ አኃዝ ፡ ዘርና ፡ ነባር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በዘርነቱ ፡ ከዘር ፡ ቅጽሎች ፡ እንዲስማማ ፥ በነባርነቱም ፡ ከነባር ፡ ቅጽሎች ፡ ከንኡስ ፡ ከደቂቅ ፡ ይሰማማልና ፡ ቍጥሩ ፡ ከ፪ቱም ፡ ነው ፡፡ ነባርነቱ ፡ በ፲፫ኛ ፡ ቍጥር ፡ ተነግሯል ፡ ዘርነቱም ፡ በዝርዝር ፡ ፈደል ፡ ሲጣፍ ፡ ነው ፡፡ አኃዝ ፡ ከንድ ፡ እስከ ፡ ምእልፌት ፡ ያለ ፡ የቍጥር ፡ ኹሉ ፡ ጠቅላይ ፡ ስም ፡ ነው ፡ አኃዝ ፡ ማለት ፥ መያዣ ፡ ዐረቡን ፥ ወይም ፡ ኻ፻ምርና ፡ ውጥን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ መያዣው ፡ አንዳንድ ፡ ቅንጣት ፡ ፊደል ፡ (፩ ፡ ፪ ፡ ፫—አ ፡ በ ፡ ገ) ፡ ውጥኑም ፡ ቃል ፡ ነው ፡ አንድ ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ማለት ፡፡ ከ፺ ፡ እስከ ፻፻ ፡ ምንም ፡ በየክፍሉ ፡ ፍጹም ፡ ቢሆን ፡ ያንዱ ፡ ቤት ፡ ላሥር ፥ ያሥሩ ፡ ለመቶ ፥ የመቶው ፡ ለሺሕ ፥ የሺሑ ፡ ለእልፍ ፥ የእልፉ ፡ ለምእልፌት ፡ ውጥን ፡ ይባላል ፤ ፲ሩ ፡ የርባታ ፡ መደብ ፡ ለ፻ው ፡ መደብ ፡ ውጥን ፡ እንዲባል ፡፡ አኃዝ ፡ ሲባል ፡ ኹሉም ፡ ውስጠ ፡ ዘና ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ስም ፡ ነው ፤ ስፍን ፡ ስፍናዊ ፡ ብሎ ፡ ለሚጠይቅ ፥ ወይም ፡ ለሚያስብ ፥ የብትኖችን ፡ ማነስና ፡ መብዛት ፥ ስንትነትና ፡ ስንተኛነት ፡ ዘርዝሮ ፡ ደምሮ ፡ ለማሳየት ፡ ከባለቤት ፡ በፊት ፡ እየገባ ፡ ዐብሮ ፡ የሚነገር ፥ ባለቤትም ፡ ባይኖር ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ በቍ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ቅጽል ፡ ይባላል ፡፡ ርስ ፡ በርሱም ፡ ይቀጻጸላል ፡፡ ካንድ ፡ እስከ ፡ ምእልፌት ፡ ያለ ፡ አኃዛዊ ፡ ቍጥር ፡ ባንድ ፡ ረኻ፻ም ፡ ገመድ ፡ ሲመሰል ፡ ቤቱና ፡ ክፍሉ ፡ ፰ ፡ ፰ ፡ ይኾኑለታል ፤ ቤት ፥ ፩ ፡ ፲ ፡ ፻ ፡ ፲፻ ፡ ፻፻ ፡፡ ክፍል ፥ መዘርጋት ፡ መተርተር ፡ መክፈል ፡ ማጠፍ ፡ መጠቅለል ፡ ናቸው ፡፡ መዘርጋት ፥ ብዛትንና ፡ ስንትነትን ፡ እንደ ፡ ነዶና ፡ እንደ ፡ ችቦ ፡ አስሮ ፡ ሰብስቦ ፡ የሚያሳይ ፡ የጅምላ ፡ ቍጥር ፡ ነው ፡፡ ምሳሌ ፤ ፩ ፡ ፪ ፡ ፲ ፥ እንዲሁ ፡፡ መተርተር ፥ ስንትነታቸው ፡ ከታወቀ ፡ ከብዙዎች ፡ ማኸል ፡ ስንተኛነትን ፡ ለይቶ ፡ የሚያሳይ ፡ የተራ ፡ ቍጥር ፡ ነው ፡፡ ምሳሌ ፡ ፩ኛ ፡ ፪ኛ ፡ ፲ኛ ፥ እንዲሁ ፡፡ መክፈል ፥ የክፍሎችን ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ እየለየ ፡ በየማዕርጉ ፡ የሚያሳይ ፡ ክፍላዊ ፡ ቍጥር ፡ ነው ፡፡ ምሳሌ ፤ መንፈቅ ፡ ሣልሲት ፡ ራብዒት ፥ ወከማሁ ፡፡ ማጠፍ ፡ ጅምላውን ፡ ቍጥር ፡ ዐጥፎ ፡ ደርቦ ፡ እያሳየ ፡ በመንታ ፡ መንገድ ፡ የሚወስድ ፡ ያጸፉ ፡ ቍጥር ፡ ነው ፡፡ ምሳሌ ፡ አሐዳት ፥ አው ፡ ካዕበተ ፡ አሐዱ ፥ ፩ ፡ ዕጽፍ ፡፡ ክልኤታት ፥ አው ፡ ካዕበተ ፡ ክልኤቱ ፥ ፪ ፡ ዕጽፍ ፥ ፬ ፡ ነጠላ ፤ ወከማሁ ፡፡ መጠቅለል ፥ እንዳራቱ ፡ ክፍሎች ፡ አኃዝ ፡ ሳይኖረው ፥ በቅጽልነቱ ፡ ማነስና ፡ መብዛት ፡ ሕጸጽና ፡ ምልአት ፡ የሚያሳይ ፥ የአኃዝ ፡ ቅጽ

ሎች ፡ ሰብሳቢና ፡ ከታች ፡ የሚኾን ፡ መድበል ፡ ቍጥር ፡ ነው ፤ ያውም ፡ ኀዳጥ ፡ ብዙኅ ፡ ኵሉ ÷ ይህን ፡ የመሰለ ።

፻፹፩ ፡ ሥራቸውንና ፡ ጣሩቸውን ፡ በገመድ ፡ ዘይቤ ፡ ሰበን ፡ ጕትተን ፡ መዘርጋት ፡ መተርተር ፡ ያልናቸው ፡ ጅምላና ፡ ተራ ÷ አካኼዳቸው ፡ እንደ ፡ የዋህና ፡ እንደ ፡ መሠሪ ፡ ርባ ፡ ስለ ፡ ኾነ ÷ ስማቸው ፡ የዋህ ፡ ቍጥርና ፡ መሠሪ ፡ ቍጥር ፡ ይባላል ፤ የዋሁ ፡ ጅምላ ÷ መሠሪው ፡ ተራ ፡ ነው ፡ የቀሩትም ፡ ሦስቱ ፡ መክፈልና ፡ ማጠፍ ፡ መጠቅለል ፡ ያልናቸው ፡ ክፋይና ፡ ዐጣፊ ፡ ጠቅላይ ፡ ይባላሉ ። ጅምላና ፡ ተራ ፡ ካንድ ፡ እስከ ፡ ኻያ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ እየለዩ ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ግን ፡ ሳይለዩ ፡ ዐሥራ ፡ ሠላሳ ፡ በማለት ፡ እያስተባበሩ ፡ ይኼዳሉ ፡ ይኸውም ፡ ምእላድ ፡ ሳይኖር ፡ ነው ፤ ምእላድ ፡ ሲኖር ፡ ግን ፡ ዐሥራ ፡ ሠላሳ ፡ ያለውን ፡ ዐሥራዊ ፡ ዊት ፡ ሠላሳዊ ፡ ዊት ፡ ያሰኘልና ፤ ከመለየት ፡ በቀር ፡ ማስተባበር ፡ የለም ። የጅምላ ፡ ቍጥር ፡ አጣጣፍና ፡ አፈታት ፡ ፪ ፡ ዐይነት ፡ ነው ፡ አጣጣፍ ፡ በአኃዝ ፡ በፊደል ፡ አፈታት ፡ እንደ ፡ ንባቡ ፡ አንድ ፡ አንዱ ÷ ኹለት ፡ ኹለቱ ፡ እያሉ ፡ በሳድስ ፡ በካዕብ ፡ መጨረስ ፡ ነው ። የሴቶችም ፡ ቍጥር ፡ ካንድ ፡ እስከ ፡ ኻያ ፡ ከፊደል ፡ እንጂ ፡ ከአኃዝ ፡ ጋራ ፡ አይስማማም ፤ ዱብና ፡ ቅል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አሐት ፡ አሐቲ ፡ ክልኤ ፡ ክልኤቲ ፡ ሠላስ ፡ አርባዕ ፡ ኀምስ ፡ እያለ ፡ በፊደል ፡ ብቻ ፡ ይጣፋል ። አኃዝ ፡ ቅጽል ፡ ዘርና ፡ ነባር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ርባታውና ፡ ዝርዝሩ ፡ እስከ፲ ፡ መደብ ፡ ነው ።

፻፹፪ ፡ የወንዶች ፡ ጅምላና ፡ የሴቶች ፡ ጅምላ ፡ ቍጥር ።

| | የወንዶች ። | | የሴቶች ። |
|---|---|---|---|
| ፩ ፡ | አሐድ ፡ ዱ ፡ | አንድ ፡ ዱ ፡ | አሐ(ድ)ቲ ፡ ቲ ፡ |
| ፪ ፡ | ክልኤ ፡ ት ፡ ቱ ፡ | ኹለት ፡ ቱ ፡ | ክልኤ ፡ ቲ ፡ |
| ፫ ፡ | ሠለስት ፡ ቱ ፡ | | ሠላስ ፡ |
| ፬ ፡ | አርባዕት ፡ ቱ ፡ | | አርባዕ ፡ |
| ፭ ፡ | ኀምስት ፡ ቱ ፡ | ዐምስት ፡ ቱ ፡ | ኀምስ ፡ |
| ፮ ፡ | ሰድስት ፡ ቱ ፡ | | ስሱ ፡ |
| ፯ ፡ | ሰብዐት ፡ ቱ ፡ | | ሰብዑ ፡ |
| ፰ ፡ | ሰምንት ፡ ቱ ፡ | | ሰማኒ ፡ ኒቱ ፡ |
| ፱ ፡ | ተስዐት ፡ ቱ ፡ | ዘጠኝ ፡ ኙ ፡ | ተስዑ ፡ |
| ፲ ፡ | ዐሥርት ፡ ቱ ፡ | ዐሥር ፡ ሩ ፡ | ዐሥሩ ፡ |
| ፲ወ፩ ፡ | ዐሥርት ፡ ወአሐድ ፡ ዱ ፡ | | ዐሥር ፡ ወአሐቲ ፡ ቲ ፡ |
| ፲ወ፪ ፡ | ዐሥርት ፡ ወክልኤት ፡ ቱ ፡ | | ዐሥር ፡ ወክልኤ ፡ ቲ ፡ |
| ፲ወ፫ ፡ | ዐሥርት ፡ ወሠለስት ፡ ቱ ፡ | | ዐሥር ፡ ወሠላስ ፡ |
| ፲ወ፬ ፡ | ዐሥርት ፡ ወአርባዕት ፡ ቱ ፡ | | ዐሥር ፡ ወአርባዕ ፡ |
| ፲ወ፭ ፡ | ዐሥርት ፡ ወኀምስት ፡ ቱ ፡ | | ዐሥር ፡ ወኀምስ ፡ |
| ፲ወ፮ ፡ | ዐሥርት ፡ ወሰድስት ፡ ቱ ፡ | | ዐሥር ፡ ወስሱ ፡ |
| ፲ወ፯ ፡ | ዐሥርት ፡ ወሰብዐት ፡ ቱ ፡ | | ዐሥር ፡ ወሰብዑ ፡ |
| ፲ወ፰ ፡ | ዐሥርት ፡ ወሰምንት ፡ ቱ ፡ | | ዐሥር ፡ ወሰማኒ ፡ ኒቱ ፡ |

፲ወ፱ ፡ ዐሥርት ፡ ወተስዐት ፡ ቱ ፡    ዐሥር ፡ ወተስዑ ፡
፳ ፡ ዕሥራ ፡ ኻያ ፡ ካያ ÷ ካዕበተ ፡ ዮድ ።    ዕሥራ ፡ ፪ ፡ ጊዜ ፡ ፲ ።
በወንዶች ፡ ዕሥራ ፡ ወአሐዱ ፡ ዱ ፡ በሴቶች ፡ ወአሐቲ ፡ ቲ ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ ፳፱ ፡ እንዲሁ ፡ ተመፍሮ ፡ ይኼዳል ።

፴ ፡ ሠላሳ ፡    በቁሙ ፡    ሦስት ፡ ዐሥር ፡
፵ ፡ አርብዓ ፡    አርባ ፡    አራት ፡ ዐሥር ፡
፶ ፡ ኀምሳ ፡    ዐምሳ ፡    ዐምስት ፡ ዐሥር ፡
፷ ፡ ስ(ድ)ሳ ፡    በቁሙ ፡    ስድስት ፡ ዐሥር ፡
፸ ፡ ሰብዓ ፡    ሰባ ፡    ሰባት ፡ ዐሥር ፡
፹ ፡ ሰማንያ ፡    ሰማኒያ ፡    ስምንት ፡ ዐሥር ፡
፺ ፡ ተስዓ ፡    ዘጠና ፡    ዘጠኝ ፡ ዐሥር ፡
፻ ፡ ምእት ፡    መቶ ፡    ዐሥር ፡ ዐሥር ፡
፲፻ ፡ አምእት ÷ አው ፡ ዐሥርቱ ፡ ምእት ፡    ዐሥር ፡ መቶ ÷ ፩ ፡ ሺሕ ፡
፳፻ ፡ ዕሥራ ፡ ምእት ፡    ኹለት ፡ ሺሕ ፡
፴፻ ፡ ሠላሳ ፡ ምእት ፡    ሦስት ፡ ሺሕ ፡
፵፻ ፡ አርብዓ ፡ ምእት ፡    አራት ፡ ሺሕ ፡
፶፻ ፡ ኀምሳ ፡ ምእት ፡    ዐምስት ፡ ሺሕ ፡
፷፻ ፡ ስሳ ፡ ምእት ፡    ስድስት ፡ ሺሕ ፡
፸፻ ፡ ሰብዓ ፡ ምእት ፡    ሰባት ፡ ሺሕ ፡
፹፻ ፡ ሰማንያ ፡ ምእት ፡    ስምንት ፡ ሺሕ ፡
፺፻ ፡ ተስዓ ፡ ምእት ፡    ዘጠኝ ፡ ሺሕ ፡
፼ ፡ እልፍ ፡    (መቶ ፡ ጊዜ ፡ መቶ) ፡    ዐሥር ፡ ሺሕ ፡
፲፼ ፡ ዐሥርቱ ፡ እልፍ ÷ አው ፡ እእላፍ ፡    መቶ ፡ ሺሕ ፡
፳፼ ፡ ዕሥራ ፡ እልፍ ÷ ሠላሳ ፡ እልፍ ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ ፺፱፼ ፡ ይኼዳል ።
፻፼ ፡ አእላፋት ፡    መቶ ፡ እልፍ ÷ ወይም ፡ ፲፻ ፡ ሺሕ ፡ (ሚልዮን) ፡
፲፻፼ ፡ ትእልፊት ፡    ሺሕ ፡ እልፍ ÷ ወይም ፡ እልፍ ፡ ሺሕ ፡ (፲ ፡ ሚልዮን) ፡
፳፻፼ ፡ ዕሥራ ፡ ምእት ፡ እልፍ ፡    እንዲህ ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ ፺፻ ፡ ይኼዳል ።
፼፼ ፡ ምእልፊት ፡    እልፍ ፡ ጊዜ ፡ እልፍ ፡ (፻ ፡ ሚልዮን) ።

ሐዲስ ፡ ሐሳብ ፡ እንግዳ ፡ ቍጥር ÷ በምእልፊት ፡ ላይ ፡ የሚፈፀመር ÷ የቢልዮንና ፡ የትሪልዮን ፡ አንጻር ።

ምእልፊትን ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ እልፍ ፡ ፲ ፡ ፻ ፡ ፲፻ ፡ ፼ ፡ እያሉ ፡ ባዕቱ ፡ ቅጽሎች ፡ ሲያበዙት ፡ አንድ ፡ የነበረው ፡ ፼ ፡ ምእልፊት ፡ ይኾናል ። ኹለተኛም ፡ በሚልዮንና ፡ በቢልዮን ፡ ተራ ፡ ሲያወርዱት ÷ ትሪልዮን ፡ ከሚባለው ፡ ቍጥር ፡ ይሰማማል ። ከእልፍና ፡ ከአእላፍ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ቍጥር ፡ በውሳኔም ፡ አለውሳኔም ፡ ይነገራልና ፡ ውሳኔው ፡ ይህ ፡ ነው ። ያለውሳኔ ፡ ግን ፡ ሲነገር ÷ አእላፈ ፡ አእላፋት ፡ ወትእልፊተ ፡ አእላፋት ፡ ምእልፊት ፡ ይላል ፡ ብዛቱ ፡ እንዳሸዋና ፡ እንደ ፡ ከከብ ፡ ሰፍሮ ፡ ቈጥሮ ፡ ሊያው

ቁጥ ፡ የማይቻል ፥ ከፈጣሪ ፡ በቀር ፡ ሰፋሪ ፡ ቈጣሪ ፥ ልክና ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አብይን ፡ በሚልፋ ፡ እንዲሉ ፡ (ዘፍ ፲፫ ፡ ፲፮ ። ፲፰ ፡ ፫) ።

## ሐተታ ፡ ስላንድ ፡ ቤት ፡ ቍጥር ።

፻፹፫ ፡ ሠለስት ፡ የተባለው ፡ ሦስት ፡ መኾኑ ፡ ለ ፡ ስለ ፡ ላላ ፡ ነው ፤ ሲጠብቅ ፡ ግን ፡ (ሠላሲ ፡ ሲት ፡ ስያን ፡ ያት) ፡ ሠለስት ፡ መድበል ፡ ቅጽል ፡ ኹኖ ፡ ፫ ፡ የሚያደርጉ ፡ ፫ ፡ አድራጎች ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፥ ፫ነትን ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ መኾንን ፡ አያሳይምና ፤ ከማጥበቅ ፡ ተጠንቀቅ ። ሰድስት ፡ ያልነውም ፡ ስድስት ፡ ተብሎ ፡ እንዳማርኛው ፡ በሳድስ ፡ ሲነማ ፡ ያንዲት ፡ ሴት ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ነውና ፥ ውስጠ ፡ ብዙነቱ ፡ ምንም ፡ ርግጥ ፡ ቢኾን ፥ በሰዋ ስው ፡ ሕግ ፡ ለውስጠ ፡ ብዙ ፡ ወንድ ፡ ሊነገርና ፡ ጅምላ ፡ ቍጥር ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ። አጥብቀን ፡ ሰምንትና ፡ ዐሥርት ፡ ያልናቸውም ፡ (ሰማኒ ፡ ኒት ፡ ንያን ፡ ያት) ፡ ዐሣሪ ፡ ራት ፡ ርያን ፡ ያት) ፡ ሰመንትና ፡ ዐሠርት ፡ ሲባሉ ፥ አድራጊነትን ፡ ቢያሳዩ ፡ እንጂ ፥ ኗኝነትን ፡ አያሳዩምና ፤ በሰምንትና ፡ በዐሥርት ፡ ፈንታ ፡ ሰመንትና ፡ ዐሠርት ፡ ከማ ለት ፡ ተጠንቀቅ ፤ ካንድ ፡ እስከሥር ፡ ያሉ ፡ አኃዞች ፡ ኹሉም ፡ በውስጠ ፡ ብዙነት ፡ ከተ ደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ አፈታታቸው ፡ ያስረዳኻል ።

፻፹፬ ፡ ዳግመኛም ፡ ከክልኤት ፡ እስከ ፡ ዐሥርት ፡ ያለው ፡ ት ፡ ምእላድ ፡ መኾ ኑን ፡ የአኃዞችም ፡ ሥር ፡ ከሦስት ፡ ቅንጣት ፡ ፊደል ፡ ወዳራት ፡ አለመውጣቱን ፡ አስ ተውል ፤ ይኸውም ፡ ምእላድ ፡ በሌለው ፡ በአሐድና ፡ በጊዜያት ፡ አኃዝ ፡ ይታወቃል ። ት ፡ ምእላድ ፡ ኹኖ ፡ በሳድስነት ፡ መጨመሩ ፡ የወንዱን ፡ ከሴት ፡ ለመለየትና ፡ ለማብ ዛት ፥ ለመዘርዘርም ፡ እንዲመች ፡ ነው ። የዝርዝሩ ፡ ከዕብነት ፡ ቱ ፡ ብእሲሁ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹኖ ፡ ዐጸፋን ፡ ብቻ ፡ ያሳያል ፤ ዝርዝሩ ፡ ዐጸፋ ፡ ባይኾን ፡ ግን ፡ በገቢር ፡ ጊዜ ፡ የሳድስ ፡ ወራሽ ፡ ግእዝ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ የካዕብም ፡ ወራሽ ፡ ሳብዕ ፡ ነውና ፤ አሐዱ ፡ ክልኤቱ ፡ ያለውን ፡ አሐደ ፡ ክልኤተ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አሐዶ ፡ ክልኤቶ ፡ ያሰኝ ፡ ነበር ። አርባዕት ፡ ባዕድ ፡ ከምእላድ ፥ አርብዓም ፡ ባዕድ ፡ ዘር ፡ ይባላል ፤ ባዕድ ፡ ኹኖ ፡ ባዕድ ፡ ያሰኘውም ፡ አ ፡ ነው ።

## ተራ ፡ ቍጥር ፡ በፊደል ፡ ብቻ ።

፻፹፭ ፡ የተራ ፡ ቍጥር ፡ መነሻ ፡ ኹሉም ፡ ራብዕ ፡ ፊደል ፡ ነው ፤ በራብዕ ፡ ተነ ሥቶ ፡ ምእላድ ፡ ሳይጨምር ፡ በ፫ ፡ በ፫ ፡ ፊደል ፥ እየጨመረም ፡ በ፬ ፡ በ፬ ፡ ፊደል ፡ ይኼ ዳል ፤ የምእላዶቹም ፡ (ዊ ፡ ይ ፡ ት) ፡ ሓያ ፡ መዘርዘርና ፡ ዐጻፋ ፡ መኾን ፡ ነው ፤ አንደኛ ፡ አንደኛው ፥ አንደኛት ፡ አንደኛይቱ ፡ እያልኽ ፡ ኹሉን ፡ እንዲህ ፡ ፍታ ፤ ንባቡ ፡ መንታ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ፍችውም ፡ መንታ ፡ ነው ። በጅምላና ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ ከአሐዱና ፡ ከክ ልኤቱ ፡ የሚተባበሩ ፥ ስለነርሱም ፡ የሚነገሩ ፡ ቅጽሎች ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፤ ዋሕድ ፡ ግእዝ ፡ አኃዝ ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ ቀዳም ፡ ቀዳሚ ፡ በኵር ፥ የአሐዱ ። ዳግም ፡ ካዕብ ፡ ሠንታ ፡ ዘውግ ፡ ዕምድ ፥ የክልኤቱ ፡ ናቸው ።

፻፳፮ ፡ የወንዶችና ፡ የሴቶች ፡ ተራ ፡ ቍጥር ።

| የወንዶች ። | የሴቶች ። |
|---|---|
| አሐድ ፡ አሐዳይ ፡ ዊ ፡ | አሐ(ድ)ት ፡ አሐቲ ፡ |
| (ግእዝ ፡ ጥንት ፡ ቀዳማዊ ፡ በኵር) ፡ | (ቀዳሚት ፡ ማዩት) ፡ |
| ክልእ ፡ ክልኣይ ፡ ዊ ፡ | ክልእት ፡ ክልኣዩ(ዊ)ት ፡ |
| (ካዕብ ፡ ዳግም ፡ ዳግማይ ፡ ዊ) ፡ | (ዳግምት ፡ ሚት ፡ ማዩት) ፡ |
| ሣልስ ፡ ሣልሳይ ፡ ዊ ፡ | ሣልስት ፡ ሣልሳዊ(ዩ)ት ፡ |
| ራብዕ ፡ ራብዓይ ፡ ዊ ፡ | ራብዕት ፡ ራብዓዊ(ዩ)ት ፡ |
| ኃምስ ፡ ኃምሳይ ፡ ዊ ፡ | ኃምስት ፡ ኃምሳዊ(ዩ)ት ፡ |
| ሳድስ ፡ ሳድሳይ ፡ ዊ ፡ | ሳድስት ፡ ሳድሳዊ(ዩ)ት ፡ |
| ሳብዕ ፡ ሳብዓይ ፡ ዊ ፡ | ሳብዕት ፡ ሳብዓዊ(ዩ)ት ፡ |
| ሳምን ፡ ሳምናይ ፡ ዊ ፡ | ሳምንት ፡ ሳምናዊ(ዩ)ት ፡ |
| ታስዕ ፡ ታስዓይ ፡ ዊ ፡ | ታስዕት ፡ ታስዓዊ(ዩ)ት ፡ |
| ዓሥር ፡ ዓሥራይ ፡ ዊ ፡ | ዓሥርት ፡ ዓሥራዊ(ዩ)ት ፡ |

በወንዶች ፡ ዓሥር ፡ ወአሐድ ፡ ወክልእ ፡ ወሣልስ ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ ታስዕ ፥ በሴቶችም ፡ እንደዚሁ ፡ ዕሥራዊ ፡ ት ፡ ሠላሳዊ ፡ ምእታዊ ፡ እልፋዊ ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ ምእልፊት ፡ ይኼዳል ። ሲበዛም ፡ አበዛዙ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ቀደምት ፡ ቀዳም(ማው)ያን ፡ ያት ፡     የወንዶችና ፡ የሴቶች ።
ደኀርት ፡ ክልኣን ፡ ኣት ፥ ክልኣው(ይ)ያን ፡ ያት ፡
(ዳግማን ፡ ት ፥ ዳግማው(ይ)ያን ፡ ያት) ፡
ሣልሳን ፡ ት ፥ ሣልሳው(ይ)ያን ፡ ያት ፡
ራብዓን ፡ ት ፥ ራብዓይ(ው)ያን ፡ ያት ፡
ኃምሳን ፡ ት ፥ ኃምሳው(ይ)ያን ፡ ያት ፡
ሳድሳን ፡ ት ፥ ሳድሳው(ይ)ያን ፡ ያት ፡
ሳብዓን ፡ ት ፥ ሳብዓይ(ው)ያን ፡ ያት ፡
ሳምናን ፡ ት ፥ ሳምናው(ይ)ያን ፡ ያት ፡
ታስዓን ፡ ት ፥ ታስዓይ(ው)ያን ፡ ያት ፡
ዓሥራን ፡ ት ፥ ዓሥራው(ይ)ያን ፡ ያት ።

፻፳፯ ፡ የብዙዎች ፡ አኃዝ ፡ በብዙዎቹ ፡ ብቻ ፡ በሦስት ፡ ሰራዊት ፡ በእሙንቱና ፡ በአንትሙ ፡ በንሕነ ፡ ይዘረዘራል ፡ እነሣሡም ፡ አሐዱን ፡ አይሻም ፡ ካንድ ፡ የወጣ ፡ ብዙ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከ፪ ፡ ይነሣል ። ክልኤሆሙ ፡ ን ፥ ክልኤቶሙ ፡ ን ፥ ክልኤቲሆሙ ፡ ን ። ክልኤክሙ ፡ ን ፥ ክልኤት ፡ ቲ ፡ ክሙ ፡ ን ፥ ክልኤነ ፡ ክልኤትነ ። ሠለስቶሙ ፡ ቲሆሙ ፡ ን ። ሠለስቲክሙ ፡ ክን ፥ ሠለስትነ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ እስካሥር ፥ ፍችውም ፡ ሦስታችን ፡ ሦስትነታችን ፡ ያሰኛል ። ወደ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ሲለወጥ ፡ ግን ፡ አሐዱን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ አሐዶሙ ፡ ክልኣሙ ፡ ሣልሶሙ ፡ እያለ ፡ በራብዕ ፡ ይነሣል ። ከግእዝ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ያሉ ፡ የ፯ቱ ፡ ፊደላት ፡ ስምና ፡ ቍጥር ፡ ከወንዶች ፡ ተራ ፡ ስለ ፡ ወጣ ፡ ኹሉም ፡ በወንድነት ፡ ይጠራሉ ።

## የክፍል ፡ ቍጥር ።

፻፰ ፡ የብዙዎች ፡ ቍጥር ፡ አሐድን ፡ ትቶ ፡ ከክልኤት ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፥ የክፍልም ፡ ቍጥር ፡ ከመንፈቅ ፡ ይነሣል ፡ ተክፋዩ ፡ አሐዱ ፡ ነውና ። ምንም ፡ አኀኼዱ ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ቢኾን ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ ለብቻና ፡ ለጊዜም ፡ ሲነገር ፡ እንደ ፡ ጅምላ ፡ ነው ።

| | |
|---|---|
| መንፈቅ ፡ ንፍቅ ፡ ክልኢት ፡ | እኩል ፡ እኩሌታ ፡ ፪ኛ ፡ እጅ ፡ |
| ሣልሲት ፡ | ሦስተኚት ፡ ሦስቲያ ፡ ሢሶ ፡ |
| ራብዒት ፡ | ርቢት ፡ አራቲያ ፡ ርበ ፡ ሩብ ፡ |
| ኃምሲት ፡ | ዐምስተኚት ፡ ዐምስቲያ ፡ ዐምሾ ፡ |
| ሳድሲት ፡ | ስድስተኚት ፡ ስድስቲያ ፡ |
| ሳብዒት ፡ | ሰባተኚት ፡ ሰባቲያ ፡ |
| ሳምኒት ፡ | ስምንተኚት ፡ ስምንቲያ ፡ |
| ታስዒት ፡ | ዘጠነኚት ፡ ዘጠኒያ ፡ |
| ዓሥሪት ፡ | ዐሥረኚት ፡ ዐሥሪያ ፡ ካሥር ፡ አንድ ። |

ሲበዛም ፡ ክልኢታት ፡ ሣልሲታት ፡ ዓሥራታት ፡ ያሰኛል ። ከ፲ ፡ በላይ ፡ ግን ፡ ክፍልነቱን ፡ ገልጦ ፡ ዐሥሩቱ ፡ ወአሐዱ ፡ ክፍል ፡ ዕሥራ ፡ ወክልኤቱ ፡ ክፍል ፡ እያለ ፡ በጅምላና ፡ በየዋህ ፡ ቍጥር ፡ ይኼዳል ። ከክልኢት ፡ እስከ ፡ ዓሥሪት ፡ ያሉ ፡ ስሞች ፡ ኹሉም ፡ በ፲ ፡ በ፲ ፡ መደብ ፡ ይረባሉ ፡ ይህም ፡ መንፈቁ ፡ ቃ ፡ ቆሙ ፡ ቆን ፤ ክልኢቱ ፡ ታ ፡ ቶሙ ፡ ቶን ፥ ትከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ትነ ፡ ማስኘታቸውን ፡ ያሳያል ። በጅምላም ፡ አኀኼድ ፡ ሲነገሩ ፡ ስማቸው ፡ እጅ ፡ ክፍል ፡ እየተባለ ፡ ስንትነታቸውን ፡ ይገልጣል ።

| | |
|---|---|
| ምእሕዳት ፡ | ፩ ፡ እጅ ፡ ፩ ፡ ክፍል ፤ እጅና ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። |
| ምክልኢት ፡ ምክዕቢት ፡ | ፪ ፡ እጅ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ |
| ምሥልሲት ፡ | ፫ ፡ እጅ ፡ ፫ ፡ ክፍል ፡ |
| ምርብዒት ፡ | አራት ፡ እጅ ፡ |
| ምኃምሲት ፡ | ዐምስት ፡ እጅ ፡ |
| ምስድሲት ፡ | ስድስት ፡ እጅ ፡ |
| ምስብዒት ፡ | ሰባት ፡ እጅ ፡ |
| ምስምኒት ፡ | ስምንት ፡ እጅ ፡ |
| ምትስዒት ፡ | ዘጠኝ ፡ እጅ ፡ |
| ምዕሥሪት ፡ | ዐሥር ፡ እጅ ፡ |

ሲበዙም ፡ እጅነታቸው ፡ ዕጽፍ ፡ ኹኖ ፥ ምእሕዳታት ፡ ፩ ፡ ዕጽፍ ፡ ፪ ፡ ቀንጃ ። ምክልኢታት ፡ ፪ ፡ ዕጽፍ ፡ ፬ ፡ ቀንጃ ፡ ፬ ፡ ነጠላ ። ምዕሥራታት ፡ ፲ ፡ ዕጽፍ ፡ ፲ ፡ ጥንድ ፡ ፳ ፡ ነጠላ ፡ ፳ ፡ ቀንጃ ፡ እየተባሉ ፡ እንዲህ ፡ በዕጽፍነት ፡ ይፈታሉ ። እጅ ፡ ማለትና ፡ ዕጽፍ ፡ ማለት ፡ ልዩ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ። ለብቻም ፡ ሲቀጸል ፥ ምእሕዳት ፡ ብሎ ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ አውራጃ ፡ ፩ ፡ ጋሻ ፡ ወይም ፡ ቀላድ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ፩ ፡ ፈት ፡ ፩ ፡ እመሥ ፡ ፩ ፡

ግዝም ፡ ፩ ፡ አፍታ ፡ ፩ ፡ ወረራ ፡ ፩ ፡ ፈፋ ፡ ፩ ፡ ቃዳ ፡ ፩ ፡ ተለላ ፡ ያሰኛል ። ከምክልኢት ፡ እስከ ፡ ምዕሥራት ፡ ኹሉን ፡ እንዲህ ፡ ፍታ ።

፻፳፱ ፡ (በጥሬነታቸው ፡ የክፍልን ፡ ኹነታ ፡ የሚያሳዩ ፡ ጥሬዎች) ።

| | | |
|---|---|---|
| ትእሕ(ድ)ዲት ፡ እሕድና ፡ | አንድነት ፡ | ፩ኛነት ፡ |
| ትክልእት ፡ ክላኤ ፡ | ኹለትነት ፡ | ፪ኛነት ፡ |
| ትሥልስት ፡ ሥላሴ ፡ | ሦስትነት ፡ | ፫ኛነት ፡ |
| ትርብዕት ፡ ርባዔ ፡ | አራትነት ፡ | ፬ኛነት ፡ |
| ትኅምስት ፡ ኅማሴ ፡ | ዐምስትነት ፡ | ፭ኛነት ፡ |
| ትስድስት ፡ ስዳሴ ፡ | ስድስትነት ፡ | ፮ኛነት ፡ |
| ትስብዕት ፡ ስባዔ ፡ | ሰባትነት ፡ | ፯ኛነት ፡ |
| ትስምንት ፡ ስማኔ ፡ | ስምንትነት ፡ | ፰ኛነት ፡ |
| ትስዒት ፡ ትሳዔ ፡ | ዘጠኝነት ፡ | ፱ኛነት ፡ |
| ትዕሥርት ፡ ዕሣሬ ፡ | ዐሥርነት ፡ | ፲ኛነት ፡ |

## የዕለታት ፡ አኃዝ ።

፻፴ ፡ አሚር ፡ በጽርእና ፡ በቅብጥ ፡ (ኢሚራ) ፡ ዕለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አኃዝ ፡ አይዶለም ፡ ስለዚህ ፡ ቅጽል ፡ አይኾንም ። ሰኑይም ፡ በዕብራይስጥ ፡ (ሼኒ) ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ነው ፡ ፪ኛ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፤ ፪ ፡ አያሰኝም ፡ አሚርና ፡ ሰኑይ ፡ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ በእሑድና ፡ በክልእ ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ገቡ ፡ በነዚያ ፡ ዘይቤ ፡ ይፈታሉ ። የእሑድና ፡ የቀዳሚም ፡ ስማቸው ፡ ተፋልሷል ፡ እሑድን ፡ እሑድ ፡ ቀዳም ፡ ቀዳሚት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ በውስጡ ፡ ዘ ፡ ንባብ ፡ እሑድ ፡ ብሎ ፡ አንደኛ ፡ ማለት ፡ ቀዳሚንም ፡ ሰቡዕ ፡ ሳብዕት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ቀዳም ፡ ቀዳሚት ፡ ብሎ ፡ በእሑድ ፡ ስም ፡ መጥራት ፡ የመሳሳት ፤ ቋንቋ ፡ ያለማስተዋል ፡ ኀጢ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የታረመ ፡ ግእዝ ፡ አይዶለም ። አይሁድም ፡ ሰኑዩን ፡ ሼኒ ፡ (፪ኛ) ፡ ማለታቸው ፡ እሑድን ፡ ሪሾን ፡ (ቀዳም ፡ ቀዳሚ) ፡ ብለው ፡ ነው ። ፯ኛውም ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ሸማኔ ፡ ዕቃ ፡ ዐርብ ፡ መባሉ ፡ የፊት ፡ ግንዱን ፡ እሑድ ፡ ተጠግቶ ፡ ከሰኞ ፡ እስከሙስ ፡ ያሉትን ፡ ልብ ፡ ባለማድረግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዐሥርነት ፡ በለው ፡ በመዘራዝሩ ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ ሕግ ፡ አይዶለም ። የዐርብ ፡ ዘይቤ ፡ በግእዝም ፡ በዕብራይስጥም ፡ ሡርክ ፡ ነውና ፡ አኃዝ ፡ ኹኖ ፡ ዕለት ፡ ከመባል ፤ ወይም ፡ የዕለት ፡ ስምና ፡ ቀጽል ፡ ከመኾን ፡ አይገባም ። ከሰኑይ ፡ እስከ ፡ ዐሡር ፡ ያሉ ፡ የዕለታት ፡ ስሞች ፡ ከማልስና ፡ ከሳድስ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ስለ ፡ ተደቀሉ ፡ ብግእዝ ፡ ተነሥተው ፡ ከዕብ ፡ እያስከተሉ ፡ በሳድስ ፡ ይጨርሳሉ ፡ አፈታታቸውም ፡ ፪ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ጀምላና ፡ እንደ ፡ ተራ ። እሑድ ፡ እሑድ ፡ አሚር ፡ አንድ ፡ አንደኛ ፡ መበቻ ፡ መዠመሪያ ። ሰኑይ ፡ ሡሉስ ፡ ረቡዕ ፡ ኀሙስ ፡ ሰዱስ ፡ ሰቡዕ ፡ ሰሙን ፡ ተሱዕ ፡ ዐሡር ፡ ዐሥር ፡ ዐሥረኛ ፤ ኹሉን ፡ እንዲህ ፡ ፍታ ። አመና ፡ በ ፡ ሲጨመሩባቸው ፡ መድረሻቸውን ፡ እየዘረዘሩ ፡ ከወርኅ ፡ ተስማምተው ፡ በሳድሱ ፡ ለጽልመት ፡ ወርኅ ። አመ ፡ ዐሡሩ ፡ ወአሚሩ ፤ አመ ፡ ዕሥራ ፡ ወሰኑዩ ፡

እያሰኙ ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ ይኼዳሉ ፤ ጥሬታቸውም ፡ ከፊደል ፡ እንጂ ፡ ከአኃዝ ፡ ጋራ ፡ አይተ
ባበርም ፤ የጊዜያትም ፡ ክፍል ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

፻፴፩ ፤ የጊዜያት ፡ አኃዝ ።

| | | |
|---|---|---|
| እሐድ ፡ ምዕር ፡ | እሐደ ፡ ምዕረ ፡ | ፩ ፡ ጊዜ ÷ በ፩ ፡ ጊዜ ፡ |
| ክልእ ፡ | ክልአ ፡ | |
| ሥልስ ፡ | ሥልሰ ፡ | |
| ርብዕ ፡ | ርብዐ ፡ | |
| ኅምስ ፡ | ኅምሰ ፡ | |
| ስድስ ፡ | ስድሰ ፡ | |
| ስብዕ ፡ | ስብዐ ፡ | |
| ስምን ፡ | ስምነ ፡ | |
| ትስዕ ፡ | ትስዐ ፡ | |
| ዕሥር ፡ | ዕሥረ ፡ | ዐሥር ፡ ጊዜ ÷ በሥር ፡ ጊዜ ። |

ዳግመኛም ፡ አሐደ ፡ ጊዜ ፡ ክልኤተ ፡ ጊዜ ÷ ሰብዐተ ፡ ጊዜያተ ፡ እያሰኘ ፡ በጅምላ ፡
ቍጥር ፡ ይነገራል ፤ ከሥራንድም ፡ በላይ ፡ እንደዚሁ ።

፻፴፪ ፡ የዕጽፍ ፡ ቍጥር ።

| | |
|---|---|
| አሐዳት ÷ አው ፡ ካዕበተ ፡ አሐዱ ፡ | ፩ ፡ ዕጽፍ ፡ |
| ክልኤታት ÷ አው ፡ ካዕበተ ፡ ክልኤቱ ፡ | ፪ ፡ ዕጽፍ ፡ |
| ሠለስታት ÷ ካዕበተ ፡ ሠለስቱ ፡ | ፫ ፡ ዕጽፍ ፡ |
| አርባዕታት ÷ ካዕበተ ፡ አርባዕቱ ፡ | ፬ ፡ ዕጽፍ ፡ |
| ኀምስታት ÷ ካዕበተ ፡ ኀምስቱ ፡ | ፭ ፡ ዕጽፍ ፡ |
| ሰድስታት ÷ ካዕበተ ፡ ሰድስቱ ፡ | ፮ ፡ ጥንድ ፡ |
| ሰብዐታት ÷ ካዕበተ ፡ ሰብዐቱ ፡ | ፯ ፡ ጥንድ ፡ |
| ሰምንታት ÷ ካዕበተ ፡ ሰምንቱ ፡ | ፰ ፡ ጥንድ ፡ |
| ተስዐታት ÷ ካዕበተ ፡ ተስዐቱ ፡ | ፱ ፡ ጥንድ ፡ |
| ዐሥርታት ÷ ካዕበተ ፡ ዐሥርቱ ፡ | ፲ ፡ ዕጽፍ ። |

ዐሥርታት ፡ ወአሐዳት ÷ ወይም ፡ ካዕበተ ፡ ዐሥርቱ ፡ ወአሐዱ ፤ ፲፩ ፡ ዕጽፍ ። ዕሥራት ÷
ካዕበተ ፡ ዕሥራ ፤ ሠላሳት ፡ ካዕበተ ፡ ሠላሳ ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ ምእልፊት ፡ ይኼዳል ። የጊ
ዜም ፡ አኃዞች ፡ እሕዳት ፡ ምዕራት ፡ ሲባሉ ፡ እንደ ፡ ምእሕዲታት ፡ ዕጽፍ ፡ ያሰኛሉ ፤
ክልኣት ፡ ሥልሳት ፡ ርብዓት ፡ ኅምሳት ፡ ስድሳት ፡ ስብዓት ፡ ስምናት ፡ ትስዓት ፡ ዕሥ
ራት ፡ እያሰኙ ፡ ኹሉም ፡ ዕጽፍ ፡ ይኾናሉ ።

## ሳድስ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ።

| | |
|---|---|
| እሑድ ፤ ዋሕድ ፡ (ዳን ፡ ት ፡ ሕድ) ፡ | የቃነደ ፡ አንድ ÷ አንድ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ አን ዲዮ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፤ ኹሉን ፡ እንዲህ ፡ ፍቃ ። |
| ክሉእ ፡ (ኣን ፡ አት ፡ ልእት) ፡ | የተኸለተ ፡ ኹልት ÷ ኹለቶ ፡ ኹለቲዮ ፡ |

| | |
|---|---|
| ምንትው፡ (ዋን፡ ዋት፡ ቱት)፡ | የመነታ ÷ መንቶ፡ መንቲዮ፡ |
| ሥሉስ፡ (ሳን፡ ሳት፡ ልስት)፡ | የተሠለሰ፡ ሥልስ ÷ ሦስቶ፡ ሦስቲዮ፡ |
| ርቡዕ፡ (ዓን፡ ዓት፡ ብዕት)፡ | የታረተ፡ እርት ÷ አራቶ፡ አራቲዮ፡ |
| ኀሙስ፡ (ሳን፡ ሳት፡ ምስት)፡ | የታመሰ፡ ዕምስ ÷ ዐምስቶ፡ አምስቲዮ፡ |
| ስዱስ፡ (ሳን፡ ሳት፡ ድስት)፡ | የተሰደሰ፡ ስድስ ÷ ስድስቶ፡ |
| ስቡዕ፡ (ዓን፡ ዓት፡ ብዕት)፡ | የተሰበተ፡ ስብት ÷ ሰባቶ፡ ቲዮ፡ |
| ስሙን፡ (ናን፡ ናት፡ ምንት)፡ | የተሰመነ፡ ስምን ÷ ስምንቶ፡ |
| ትሱዕ፡ (ዓን፡ ዓት፡ ስዕት)፡ | የተዘጠነ፡ ዝጥን ÷ ዘጠኞ፡ ኚዮ፡ |
| ዐሡር፡ (ራን፡ ራት፡ ሥርት)፡ | የታሠረ፡ ዕሥር ÷ ዐሥሮ፡ ዐሥሪዮ፡ ብሎ፡ |

በዚሁ፡ ይቆማል፡ ከሥር፡ አይወጣም።

## የመስፈሪያና፡ የሚዛን፡ ዕጽፍ።

| | |
|---|---|
| መእሕድ፡ | ፪ቱን፡ ፩፡ የሚያደርግ፡ |
| መክልእ፡ | ፬ቱን፡ ፪፡ የሚያደርግ፡ |
| መሥልስ፡ | ፮ቱን፡ ፫፡ የሚያደርግ፡ |
| መርብዕ፡ | ፰ቱን፡ ፬፡ የሚያደርግ፡ |
| መኅምስ፡ | ፲ሩን፡ ፭፡ የሚያደርግ፡ |
| መስድስ፡ | ፲፪ቱን፡ ፮፡ የሚያደርግ፡ |
| መስብዕ፡ | ፲፬ቱን፡ ፯፡ የሚያደርግ፡ |
| መስምን፡ | ፲፮ቱን፡ ፰፡ የሚያደርግ፡ |
| መትስዕ፡ | ፲፰ቱን፡ ፱፡ የሚያደርግ፡ |
| መዐሥር፡ | ፳ውን፡ ፲፡ የሚያደርግ። |

፪ና፡ መንገድ ÷ መእሕድ፡ ብዙውን፡ ፩፡ የሚያደርግ። መክልእ፡ አንዱን፡ ፪። መሥልስ፡ አንዱን፡ ፫። መዐሥር፡ አንዱን፡ ፲፡ የሚያደርግ፡ እያሉ፡ አንድን፡ ተከፋይ፡ አድርጎ፡ ሲፈቱት፡ ዕጽፍነቱ፡ ቀርቶ፡ ዝርዝርና፡ ብትን፡ ይኾናል። ሲበዛም፡ መእሕድ፡ መክልእ፡ መሣልስ፡ እያለ፡ እስከ፡ መዓሥር፡ ይኼዳል፡ መ፡ ባይኖር፡ ግን፡ ከእሕድ፡ እስከ፡ ዐሥር፡ ኹሉም፡ የጊዜ፡ አኃዝ፡ ናቸው።　　የአኃዝ፡ ነገር፡ እስከ ዚህ፡ ነው።

## ደምላይና፡ ጠቅላይ፡ መድበላዊ፡ ቍጥር።

፻፹፫፡ ኵል፡ ኵሉ፡ ኹሉ፡ መላው፡ ጠቅላላው ÷ ከንድ፡ እስከ፡ ምእልፊት፡ ያለው፡ ወይም፡ በየክፍሉ፡ ፍጹምነት፡ ያለው፡ ያ፳ቱ፡ ቤት፡ ቍጥር፡ አንዱም፡ አንዱም፡ ኹሉ። ስፍርና፡ ቍጥር፡ ለሌለውም፡ ከታች፡ ይበላል፡ ርበታው፡ በደቂቅ፡ ቅጽል፡ ተነግሯል፡ (ቍ፻፲፱)። ኵል፡ ኵሉ፡ ማለት፡ አሐድ፡ አሐዱ፡ እንደ፡ ማለት፡ ነው፡ አሐዱና፡ ኵሉ፡ ይዋረሳሉ፡ ኵሉ፡ አሐዱ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ አሐዱ፡ አሐዱ፡ ወይም፡ ብእሲ፡ ብእሲ፡ ይላል፡ ኵሉ፡ ብእሲ፡ ማለት፡ ነው። ኵሉን፡ የመሰሉ፡ ቅጽሎች፡ ምሉእ፡ ፍጹም፡ ብዙኀ፡ ንሕኑሕ፡ ዝሕዙሕ፡ ፍድፉድ፡ ከፋዮቻቸውም፡

ንኡስ ፡ ሕጹጽ ፡ ኅዳጥ ፡ ውኁድ ፥ ንስቲት ፡ ሕቅ ፡ መጠን ፡ አምጣን ፡ ዐቅም ፡ ናቸው ። ኵል ፡ የክሉል ፡ ክፋይ ፡ ነው ፡ ሲዘረዘርም ፥ ኵሉ ፡ ኵላ ፡ ኵሎሙ ፡ ኵሎን ፡ ኵልከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፥ ኵልየ ፡ ኵልነ ፡ እያሰኘ ፡ ጠብቆ ፡ ይነገራል ። ዕብራውያንም ፡ እንደዚሁ ፡ ባ፲ ፡ ሰራዊት ፡ ይዘረዝሩታል ፤ አንዳንድ ፡ ባላገቦች ፡ ግን ፡ ከ፺ቱ ፡ በቀር ፥ አንተ ፡ አንቲ ፡ አነ ፡ ባለው ፡ በነዚህ ፡ በ፫ቱ ፡ የለውም ፡ ብለው ፡ ያውጃሉ ።

፻፴፬ ፤ መጠንና ፡ አምጣን ፡ ዐቅም ፡ የልክ ፡ ቅጽልና ፡ አገባብ ፡ ተብለው ፡ ከባዕድ ፡ ቅጽሎችና ፡ ከበይት ፡ አገባቦች ፡ ተቈጥረዋል ። ምስጢራቸው ፡ የእኅኅዝ ፡ ግምት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በስፍር ፡ በቍጥር ፡ በእኅዝ ፡ ፈንታ ፡ እየገቡ ፡ ያኽል ፡ ተብለው ፡ ሲፈቱ ፡ ግምታቸው ፡ ምሉእና ፡ ሕጹጽ ፡ ያሳያል ። ምሉእ ፥ መጠኑ ፡ ለረድእ ፡ ከመ ፡ ሊቁ ፥ በአምጣነ ፡ ብሒሩ ፡ ዘርዐ ፡ ዐቅመ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ። ሕጹጽ ፥ መጠነ ፡ ትክል ፡ ጸር ፡ መጠነ ፡ ፀ ፡ ውስተ ፡ እደ፡ከ ፡ ወነበረት ፡ ማርያም ፡ ኀቤሃ ፡ መጠነ ፡ ሠለስቱ ፡ አውራኅ ። ዳግመኛም ፡ ቅጽል ፡ ሲኾኑቸው ፡ አገባቦች ፥ አገባብ ፡ ሲኾናቸው ፡ ቅጽሎች ፡ ኹነው ፡ ይገኛሉ ፤ ይህም ፥ ተዋረደ ፡ ፈርዖን ፡ አምጣነ ፡ (መጠነ ፡ ዐቅመ) ፡ አስተዋረዶሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ። ሲፈታም ፡ በገባብነቱ ፥ እስራኤልን ፡ አዋርዷቸዋልና ፥ እንዳዋረዳቸው ፡ መጠን ፥ ባዋረዳቸው ፡ ልክ ፡ ስላዋረዳቸው ፡ አሰኝቶ ፥ በቅጽልነቱም ፡ ያዋረዳቸውን ፡ ያኽል ፡ ያሰኛልና ፥ መታወቂ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የቀረውን ፡ በገባብ ፡ ተመልከት ። ፬ቱን ፡ ክፍል ፡ እንዳ፬ ፡ ጣት ፡ ፲፰ቱን ፡ ዕርከን ፡ እንደ ፡ ቀለበት ፡ አድርጎ ፥ የሰዋስውን ፡ ሕዋሳትና ፡ ጌጥ ፡ ንዋያተ ፡ ውስጥ ፡ ሰፍሮና ፡ ቈጥሮ ፡ ዘርዝሮ ፡ ደምሮ ፡ ለ፷ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ የሚያስረክብና ፡ የሚሰጥ ፡ የሚያስተላልፍ ፡ ፭ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ተፈጸመ ። ያለፈው ፡ ንባብ ፡ የሚመጣው ፡ መተርጐም ።

## ፷ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ባለ፫ ፡ ክፍል ፡ ኅረ ፡ ቤተ ፡ ሥሉስ ፡ አካል ።

ጸዋትወ ፡ ክፍሉም ፡ ጸዋትወ ፡ ንባብ ፤ ጸዋትወ ፡ አገባብ ፤ ጸዋትወ ፡ ቅኔ ፤ የሠምና ፡ የወርቅ ፡ አንጥረኞች ፡ እነተዋኔ ፥ እንደነኤልያብ ፡ ስለ ፡ ደብተራ ፡ ሕግ ፡ ሥልጣኔ ፥ በመንፈስ ፡ ጥበብ ፡ የሠሩት ፡ የንባብ ፡ ሽልማት ፡ ውሳኔ ፤ የጸያፎችም ፡ መታጠቢያ ፡ ጥሩ ፡ ፈሳሽ ፡ ትምርት ፡ ማየ ፡ ቤተ ፡ ግእዝ ፡ ብለኽ ። ወይም ፡ የሰዋስው ፡ ሥዕርተ ፡ ርእስ ፥ ከ፺ ፡ ቀለም ፡ ቀንድ ፡ በተሠራው ፡ በፊደላት ፡ ማዶ ፡ በጥሩ ፡ ግስ ፥ የሚበጠርና ፡ የሚነቀስ ፡ ክሎታ ፡ ንበቡ ፡ የዕንቍ ፥ ወለባ ፡ ምስጢሩ ፡ የወርቅ ፥ የሚያንጸባርቅ ። መምህራንም ፡ የግእዝን ፡ ቋንቋ ፡ አልብከ ፡ ነውር ፡ ወኢምንትኒ ፡ ላዕሌከ ፡ እያሉ ፡ እንደ ፡ መርዓዊና ፡ እንደ ፡ መርዓት ፡ ሽልመው ፡ አስጊጠው ፡ እንቈጥቍጠው ፡ ለተማሮች ፡ የሚድሩበት ።

## ፳፰ኛ ፡ ክፍል ።

ጸዋትወ ፡ ንባብ ፥ የሰዋስው ፡ ግቢ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፥ ርስ ፡ በርሱ ፡ የሚዛረፍና ፡ የሚናቡብ ፥ ተናቦና ፡ ወድቆም ፡ የሚሳሳብ ፡ ሳቢ ፡ ከተሳቢ ፡ ዘርፍ ፡ ከባለቤት ፥ ቅጽል ፡ ከባ

ለቤት ። እነዚህም ፣ ፫ቱ ፡ አርእስቶች ፡ በ፫ኛውና ፡ በ፬ኛው ፡ ክፍል ፡ ነጠላና ፡ ቀንጃ ፡ እየኾኑ ፡ ኹሉም ፡ ብቻ ፡ ብቻቸውን ፡ ተነግረዋል ። የሳቢና ፡ የተሳቢ ፡ ዐዋጅ ፤ ለመምህርና ፡ ለተማሪ ፡ ለቅኔ ፡ ፈጣሪ ፡ መንገድ ፡ የሚጠርግ ፡ የሚያዘጋጅ ፤ ለባለመጽሐፍም ፡ ለተርጓሚ ፡ ላንባቢ ፡ ለሰሚ ፡ የሚበጅ ። ዝርዋን ፡ ቃላት ፡ እንደ ፡ ድብና ፡ እንደ ፡ ማርዳ ፡ እንደ ፡ ድሪ ፡ እንደ ፡ ሰንሰለት ፥ ወይም ፡ እንደ ፡ ዋንጫ ፡ እንደ ፡ ሕዋሳት ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚያያዙና ፡ የሚሳቡ ፡ የሚሳመኩ ፡ በ፰ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ በዝርፍ ፥ በቅጽል ፥ በባለቤት ፡ በዝርዝር ፥ በሳቢና ፡ በተሳቢ ፥ በገባብ ፥ በሠምና ፡ በወርቅ ። የነዚህንም ፡ ሕግ ፡ ለውጠው ፡ በልዩነት ፡ የሚነገሩ ፡ ፬ቱ ፡ ባህሎች ፥ ብትን ፥ ሙሻዘር ፡ ሡረዝና ፡ እንጻር ፡ እንደኊሁ ፡ ናቸው ፤ ኋላ ፡ በበታቸው ፡ ይነገራሉ ። አንቀጽን ፡ ቅጽልን ፡ ዝርዝርን ፡ ከባለቤት ፡ ጋራ ፡ በሩቅና ፡ በቅርብ ፥ ባንድና ፡ በብዙ ፥ በወንድና ፡ በሴት ፡ አስማምቶ ፡ ለመናገርና ፡ ለመጣፍ ፥ የተጣፈውንም ፡ ድርሰትና ፡ ቅኔ ፡ ለማመስገንና ፡ ለመንቀፍ ፡ ፍጹም ፡ ጥንቃቄ ፡ ያስፈልጋል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመላሾችና ፡ በጣፎች ፡ ስሕተት ፡ የሰዋስውን ፡ ሕግ ፡ ሳይጠብቅ ፡ ሩቁን ፡ በቅርብ ፡ ቅርቡን ፡ በሩቅ ፥ አንዱን ፡ በብዙ ፡ ብዙውን ፡ ባንድ ፥ ወንዱን ፡ በሴት ፡ ሴቱን ፡ በወንድ ፡ እያደባለቀ ፡ ይናገራል ፡ አነጋገሩም ፡ ይህ ፡ ነው ። ተበዕተ ፡ ወእንስተ ፡ ፈጠሮሙ ፤ ሜጡ ፡ ለተብዕት ፡ ኀምሳ ፥ ወለአንስትስ ፡ ሜጣ ፡ ሠላሳ ፤ ፀር ፡ እኩይ ፥ ቢጽ ፡ ሀካይ ፡ ብሎ ፡ ስላንድ ፡ የተናገረውን ፡ መልሶ ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ብዙ ፥ እእንስት ፡ ወይም ፡ አንስትያት ፥ አፅራር ፥ አብያጽ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፥ ጠባባት ፡ እንስት ፡ ሐነጸ ፡ አብያተ ፤ ተጋብኡ ፡ ፀር ፡ እኩያን ፥ ወቢጽ ፡ ሐሳውያን ፤ ይቤሎሙ ፡ ለቢጹ ፡ አርዳእ ፡ ይላል ። አንባቢ ፡ ሆይ ፡ በመጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ጸያፍ ፡ አለና ፤ አሕዛብ ፡ ስሑል ፥ ዘእንበለ ፡ ይቁም ፡ አድባር ፥ ተቈጣዕክምዎሙ ፡ ለይእቲ ፡ ትውልድ ፡ እያለ ፡ አላገባቡ ፡ ገብቶና ፡ ተጥፎ ፡ ብታገኝ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጸያፍ ፡ ንባብ ፡ ኹሉ ፡ የመላሽና ፡ የጸሓፊ ፡ ስሕተት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ የግእዝ ፡ ሕግና ፡ የሰዋስው ፡ ሥርዐት ፡ እንዳይዶለ ፡ አስተውል ። መተርጕማን ፡ ግን ፡ የተቀዳበትን ፡ ጽርኡንና ፡ ዐረቡን ፡ ዕብራይስጡንም ፡ ስላላዩት ፥ መጽሐፍ ፡ ምስጢር ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ሕግ ፡ ሰዋስው ፡ አይጠብቅም ፥ አንድና ፡ ብዙ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ቅርብና ፡ ሩቅ ፡ አይጠንቀቅም ፡ ብለው ፡ ያውጁና ፥ ጸያፍን ፡ ኹሉ ፡ ልማደ ፡ መጻሕፍት ፡ ይሉታል ። በገድል ፡ በታምር ፡ በቅኔ ፡ በመልክና ፡ በሰላምታ ፡ ድርሰት ፡ ብዙ ፡ ጸያፍ ፡ አለመገኘቱ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ብትል ፥ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ግእዝ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነለት ፥ አበባውም ፡ ድርሰት ፡ ከግእዝ ፡ መምህራን ፡ ስለ ፡ ፈነዳና ፡ ከሌላ ፡ ቋንቋ ፡ ስላልተቀዳ ፡ ነው ። የዝ ፡ እንተ ፡ እለም ፡ ጥንቃቄ ፡ ኋላ ፡ በዘርፍ ፡ በቅጽል ፡ ይነገራል ።

## ፲፯ኛ ፡ ዕርከን ።

### ሳቢና ፡ ተሳቢ ፡ የሰዋስው ፡ ክተንቢ ።

፩ ፡ ሳቢና ፡ ተሳቢ ፡ ማለት ፡ ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ ወይም ፡ ቅጽልና ፡ ባለቤት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሳቢው ፡ አንቀጽ ፡ ተሳቢው ፡ ባለቤት ፡ ነውና ። የባለቤትም ፡ ጓዝ ፡ ዘርፍና ፡ ቅጽሉ ፡ ሌላውም ፡ ኹሉ ፡ በተሳቢነት ፡ ይከተታል ። በገቢር ፡ አንቀጽ ፡ አደረገ ፡

አላደረገም ፥ በተገብሮ ፡ ተደረገ ፡ አልተደረገም ፥ ባጕል ፡ አንቀጽ ፡ ኾነ ፡ አልኾነም ፥ በነባር ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ አይዶለም ፡ ተብሎ ፡ የሚነገርለ(በ)ት ፡ አካል ፥ ወይም ፡ ፩ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፥ ባንቀጽ ፡ የሚሳብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ተሳቢ ፥ ማሰሪያ ፡ ተቀባዩ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ባለቤት ፡ ይባላል ። በተሳቢነቱ ፡ አንቀጽ ፡ ቀድሞት ፡ ወይም ፡ ተከትሎት ፡ ሲነገር ፡ አገባብ ፡ አይወድቅበትም ፤ ስሙም ፡ ነባር ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፥ ሳድስ ፡ ግእዝ ፡ ካዕብ ፡ ኹኖ ፡ በቁሙ ፡ ይነገራል ፡ እንጂ ፤ ተለውጦ ፡ ግእዝና ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕ ፡ አይኾንም ። ምሳሌ ፡ ሐዋርያት ፡ ሰበኩ ፥ ወይም ፡ ሰበኩ ፡ ሐዋርያት ፡ ወንጌለ ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ እስከ ፡ በሓውርተ ፡ አሕዛብ ፡ ሲል ፡ ኹሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰበኩ ፡ ባለው ፡ ይሳባል ። ዐቢይ ፡ አንቀጽም ፡ ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ሳይወድቅበት ፡ ከሚስበው ፡ ባለቤትና ፡ ቃል ፡ ቀድሞ ፡ ተከትሎ ፡ ሲነገር ፥ ስሙ ፡ ማሰሪያ ፡ ይባላል ። አገባብ ፡ ወድቆበት ፡ ተሳቢ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ አንቀጽ ፡ እንጂ ፡ ማሰሪያ ፡ አይባልም ። ባለቤትን ፡ ማሰሪያ ፡ ተቀባዩ ፡ ማለት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ባንድነት ፡ ታስረው ፡ የሚነገሩ ፡ ፍጹማን ፡ ቃላት ፡ ከ፪ ፡ አያንሱም ፡ ማነሳቸውና ፡ መብዛታቸውም ፡ ካንቀጽ ፡ ቍጥርና ፡ ከተሳቦቹ ፡ ማጠር ፡ ነው ።

፲፱ ፤ የሳቢና ፡ የተሳቢ ፡ አርእስት ፡ ፪ ፡ ናቸው ፤ መኾን ፥ ወይም ፡ ኗኝነት ፤ መደረግ ፥ ማድረግ ፥ ማስደረግ ፥ መደራረግ ፡ ማደራረግ ። መኾን ፡ ኗኙን ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ የሚስብ ፡ ያጕል ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ ፈለሰ ፡ ነገደ ፡ ዐርገ ፡ ወረደ ፡ ጕሕቈ ፡ ረትዐ ፡ ደከመ ፡ ጸንዐ ፥ ይህን ፡ የመሰለ ። ኗኝ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ አኗኝና ፡ ኗኝ ፡ ፍሉጠ ፡ ርእስ ፡ የሦስት ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ምንም ፡ የመደረግ ፡ ልማድ ፡ ተ ፡ ፬ኛ ፡ ኹኖ ፡ ባይገባበት ፡ አሳሳቡና ፡ አገባቡ ፡ እንደ ፡ መደረግ ፡ ነው ። በነዚህም ፡ በ፯ቱ ፡ አርእስት ፡ የሚገቡ ፡ ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ በ ፡ እም ፡ ለ ፡ ኀበ ፡ መንገለ ፡ ውእደ ፡ እንተ ፡ ውስተ ፡ እስከ ፡ እንዳንቀጹ ፡ ስልት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ አላቸው ፤ ይህም ፡ በ ፡ እንደሚስበው ፡ አንቀጽ ፡ መኾኛ ፡ መደረጊያ ፥ ማድረጊያ ፡ ማስደረጊያ ፥ መደራረጊያ ፡ ማደራረጊያ ፥ እም ፡ ሰጭ ፥ ለ ፡ ተቀባዩ ፡ ይባላሉ ። ሖረ ፡ ተመይጠ ፡ ወፅአ ፡ ወረደ ፡ በሚያሰኙ ፡ አናቅጽ ፡ ሲሳቡ ፡ ግን ፥ እም ፡ መነሻ ፡ ለ ፡ ኀበ ፡ መንገለ ፡ ውእደ ፡ ውስተ ፡ መገሥገሻ ፥ እስከ ፡ መድረሻ ፡ ይባላሉ ።

፳ ፤ መኾን ፡ ኗኝን ፡ መኾኛን ፥ መደረግ ፡ ተደራጊን ፡ መደረጊያን ፥ መነሻን ፥ መገሥገሻን ፥ ወይም ፡ መድረሻን ፥ መነሻና ፡ መድረሻም ፡ ቢቀሩ ፡ ሰጭን ፥ ተቀባዩን ፡ ማሰሪያ ፡ የሚያስለቅቅ ፡ ዐቢይ ፡ አገባብን ፥ ዘንድን ፥ ንኡስ ፡ አንቀጽን ፡ ይስባል ። ማሰሪያ ፡ የማያስለቅቅ ፡ አገባብ ፡ ግን ፡ መደረጊያ ፥ መነሻ ፥ መገሥገሻ ፡ ተቀባዩ ፡ ከተባሉት ፡ ጋራ ፡ ዐቢይ ፡ አገባብም ፡ ቢኾን ፡ ዐብሮ ፡ ይቈጠራል ። መኾን ፡ ኗኝና ፡ መኾኛን ፡ መደረግም ፡ ተደራጊንና ፡ መደረጊያን ፡ ከቢይ ፡ አገባብ ፡ ጋራ ፡ ሲስብ ፥ (ረትዐት) ፡ ተወሰነት ፡ ሃይማኖት ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ በጉባኤ ፡ ኒቅያ ፡ በእፈ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ አመ ፡ ነግሠ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ይላል ። መነሻ ፡ መገሥገሻ ፥ ወይም ፡ መድረሻ ፡ ተደራጊ ፡ አገባብ ፡ ሲስብ ፥ (ፈለሱ ፡ እው ፡ ወፅኡ) ፡ ተፈነዉ ፡ ሐዋርያት ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ብሔረ ፡ አሕዛብ ፡ ሰበ ፡ ፈቀዱ ፡ ፈጽሞተ ፡ ቃሉ ፡ ለእግዚእነ ፡ ይላል ። ተደራጊን ፡ ሰጭን ፡ ተቀባዩን ፡ አገባብን ፡ ሲስብ ፥ (በርሀ) ፡ ተሰብከ ፡ ሃይማኖት ፡ እምቃለ ፡

ሐዋርያት ፡ ለሕዝብ ፡ ድኅረ ፡ ዐርገ ፡ እግዚእን ፡ ይላል ። ፮ቱን ፡ ኹሉ ፡ ሲስብ ፥ (ተመ ሥጦ) ፡ ዐርገ ፡ ኤልያስ ፡ እምድር ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ በሠረገላ ፡ እሳት ፡ እምድኅረ ፡ ተአ ምረ ፡ ዐቂበቱ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይንበር ፡ ህየ ፡ ይላል ። በዚህ ፡ ላይ ፡ በማድረግ ፡ ጊዜ ፡ አድራጊን ፥ በማስደረግ ፡ ጊዜ ፡ አስደራጊን ፡ ፈፅምር ። (መሥጦ) ፡ አዕረገ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ለኤልያስ ፡ አዕርጎተ ፡ ፍቅር ።

፬ ፡ መደራረግ ፡ ተደራራጊን ፡ መደራረጊያን ፡ ተደራጊን ፡ መነሻን ፡ መገሥገሻን ፡ ወይም ፡ መድረሻን ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽን ፡ አገባብን ፡ ይስባል ። ሲገባም ፥ ተራወጹ ፡ ተቃ ሓውያን ፡ ሩጸተ ፡ እመከን ፡ እስከ ፡ መከን ፡ ዘወሰኑ ፡ ሎሙ ፡ በዕዳን ፡ በመርሕብ ፡ በዕ ለተ ፡ አዕረፉ ፡ እምተግባረ ፡ ሥጋ ፡ ይክሥቱ ፡ ፍጥነተ ፡ እግሮሙ ። ፪ኛም ፡ መደራረግ ፡ ተደራራጊን ፡ መደራረጊያን ፡ አገባብን ፡ ሲስብ ፥ ተቃተለ ፡ ዳዊት ፡ ምስለ ፡ ጎልያድ ፡ በመከነ ፡ ዒላ ፡ ሰበ ፡ ዐርጉ ፡ ኢሎፍላውያን ፡ ኀበ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ይላል ። ተደራ ጊንም ፡ ሲፈፅምር ፥ ተራወጹ ፡ አብያጽ ፡ ተቃሓውያን ፡ ሩጸተ ፡ በመርሕብ ፡ በዕለተ ፡ አዕረፉ ፡ እምተግባረ ፡ ሥጋ ፡ ይላል ። መነሻንና ፡ መገሥገሻንም ፡ ሲፈፅምር ፥ ይትራ ወጹ ፡ ሩጸተ ፡ መንፈሳዌ ፡ ሐዋርያት ፡ ወአርድእት ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ ኀበ ፡ እስከ ፡ ብሔረ ፡ አሕዛብ ፡ ወእምህየ ፡ ኀበ ፡ ሳሌም ፡ እንዘ ፡ ይሰብኩ ፡ ወንጌለ ፡ ይላል ። በማደ ራረግም ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ አደራራጊን ፡ ፈፅምር ፡ አስተራወጸ ፡ እግዚእን ፡ ሐዋር ያተ ፡ ወአርድእተ ።

፭ ፡ ዳግመኛም ፡ መደረግ ፡ ተደራጊን ፥ መደራረግ ፡ ተደራራጊን ፥ ግእዝ ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕ ፡ አድርገው ፡ ይስባሉ ። ራብዕ ፡ ግን ፡ ለገቢርና ፡ ለተገብሮ ፡ ስለ ፡ ተመቸ ፡ ኹሉ ፡ ይስቡታል ፡ ይህም ፡ በልዐ ፡ ሥጋ ፡ ወመና ፥ ተበልዐ ፡ ሥጋ ፡ ወመና ፡ ማለቱን ፡ ያሳ ያል ። ስመ ፡ ተጸውዖም ፡ በገቢር ፡ አንቀጽ ፡ ተደራጊ ፡ ተሳቢ ፡ ኹኖ ፡ ሲነገር ፡ የግእዝ ፡ ወራሽ ፡ ሀ ፡ ይፈፅመርበታል ፡ ይህም ፡ ጸውዐ ፡ ሊተ ፡ ናታንሀ ፡ ነቢየ ፡ ወሳዶቅሀ ፡ ካህነ ፡ ውብንያስሀ ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ። መደረግ ፡ ሳድስን ፡ ካዕብን ፡ ግልስን ፡ ሲስብ ፡ ተቀ ትለ ፡ ዐር ፡ ኢወ ፡ ፀሩ ፡ ወሚመ ፡ ጺላኢ ፡ ይላል ። ማድረግ ፡ ግእዝን ፡ ሳብዕን ፡ ኃምስን ፡ ሲስብ ፥ ቀተለ ፡ ፀረ ፡ ኢወ ፡ ፀሮ ፡ ወሚመ ፡ ጺላኤ ፡ ይላል ። በማስደረግ ፡ ጊዜ ፡ አቅተለ ፡ በማደራረግ ፡ ጊዜ ፡ አስተቃተለ ፡ በል ። መደረግ ፡ በነባርነት ፡ ያሉ ፡ የማድረግን ፡ ተሳ ቢች ፡ ይወርሳል ፡ ይህም ፡ ተቀሥመ ፡ ጽጌ ፡ ወፍሬ ፥ ተዘብጠ ፡ ከበሮ ፡ ወመሰንቆ ፡ ማ ለቱን ፡ ያሳያል ። ማድረግም ፡ በጉልትነት ፡ ያሉ ፡ የመደረግን ፡ ተሳቢች ፡ ይወርሳል ። ይህም ፡ አክበረ ፡ አበሁ ፥ ከሠተ ፡ አፉሁ ፥ አፍቀረ ፡ ፈጣሪሁ ፥ አፈቅር ፡ መድኅንየ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ።

፮ ፡ ማናቸውም ፡ አንቀጽ ፡ በንኡስ ፡ አገባብ ፡ ፈንታ ፡ ጥሬዎቹን ፡ ግእዝ ፡ አድ ርጎ ፡ ሲስብ ፡ ማሰሪያ ፡ አንጕላማሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ተሳቢ ፡ አይደለም ። ይ ህም ፡ ፈቲወ ፡ ፈተውኩም ፥ ወፈተወ ፡ ፍትወተ ፥ ልህበ ፡ ልህበተ ፥ ተዐጽበ ፡ ዕጽበተ ፡ ሲል ፥ አከዶ ፡ ፈጽሞ ፡ ጭራሽ ፡ እያሰኘ ፡ ሲላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ፪ኛም ፡ በደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ፈንታ ፡ ዐርገ ፡ ሰማየ ፡ ወረደ ፡ ቀላየ ፥ ተሰቅለ ፡ ቀትረ ፥ ተዘቢጠ ፡ በትረ ፡ እያለ ፡ ባዕድ ፡ ጥሬ ፡ ሲስብ ፡ ግእዝነቱ ፡ የብትን ፡ ስዋስው ፡ ነውና ፡ ኋላ ፡ በቦታው ፡ ይነገራል ።

መደረግ ፡ በጕልትነት ፡ ካሉ ፡ ከነባሮችና ፡ ግእዝ ፡ አድርጎ ፡ ከሚስባቸው ፡ ከራሱ ፡ ጥ ሬዎች ፡ በቀር ፡ ማድረግ ፡ የሚስባቸውን ፡ ግእዝና ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕ ፡ አይስብም ፡ ግንዘበ ቹን ፡ ብቻ ፡ ካዕብና ፡ ሣልስ ፡ ሳድስ ፡ ቢስብ ፡ እንጂ ። ይህም ፡ ተላጸየ ፡ ርእስ ፡ ሱ ፡ ተመ ትረ ፡ ክሣድ ፡ ዱ ፡ ተሀይደ ፡ ንዋይ ፡ ዩ ፡ ተእኅዘ ፡ ሰራቂ ፡ ማለቱን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ርእሰ ፡ ሰ ፡ ክሣደ ፡ ዶ ፡ ንዋየ ፡ ዮ ፡ ሰራቂ ፡ አለማለቱን ፡ ያሳያል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ የገቢ ሩን ፡ ለተገብሮ ፡ ሰጥቶ ፡ ተላጸየ ፡ ርእሰ ፡ ተመትረ ፡ ክሣዶ ፡ ተሀይደ ፡ ንዋዮ ፡ ወብእሲቶ ፡ ይላል ፡ የመላሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ባላገባቦችም ፡ የሚያሰኝ ፡ መስዓቸው ፡ አብ ነት ፡ አድርገው ፡ ይጠቅሱታል ። ፀዋቆችና ፡ ጠንቃቆች ፡ ግን ፡ ስንኳን ፡ ግእዙን ፡ ፀማ ርኛውንም ፡ ይነቅፉሉ ፡ ተላፊ ፡ ተቈረጠ ፡ ተቀማ ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ ዐንገቱን ፡ ገንዘቡን ፡ ሚስቱን ፡ ማለት ፡ ልውጥና ፡ ግልብጥ ፡ ነውና ። ተገብሮ ፡ ግእዝ ፡ የሚስብ ፡ ገቢሩ ፡ እ ንደነመሀረ ፡ ፪ ፡ ግእዝ ፡ ሲስብለት ፡ ነው ፡ (ተምሀረ ፡ መጽሐፈ) ። ይህንንም ፡ ኋላ ፡ በተ ራው ፡ እናመጣዋለን ።

፺ ፡ ሳቦች ፡ አናቅጽ ፡ ፰ ፡ ናቸው ፡ ፫ቱ ፡ ዐበይት ፡ ፭ቱ ፡ ንኡሳት ፡ (ቍ ፶፰) ። በጠበ ይና ፡ በሳሳብ ፡ ግን ፡ ገቢር ፡ ተገብሮ ፡ ተብለው ፡ በ፪ ፡ ይከፈላሉ ፡ (ቍ ፶፭) ። ዐበይት ፡ አና ቅጽ ፡ የሚባሉት ፡ ኀላፊና ፡ ትንቢት ፡ ትእዛዝ ፡ ከንኡሳትም ፡ ዘንድና ፡ ቦዝ ፡ እነዚህ ፡ ፭ቱ ፡ በፊት ፡ ኹነው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ በኋላም ፡ ኹነው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲስቡ ፡ ዐርፈው ፡ እንጂ ፡ ተናበው ፡ አይስቡም ። ይህም ፡ በፊት ፡ ሲኾኑ ፡ በልዐ ፡ ኅብስተ ፡ ይበልዕ ፡ ኅብ ስተ ፡ ይብላዕ ፡ ኅብስተ ፡ ሖረ ፡ ይብላዕ ፡ ኅብስተ ፡ በሊዖ ፡ ኅብስተ ። በኋላም ፡ ሲኾኑ ፡ ኅብ ስተ ፡ በልዐ ፡ ይበልዕ ፡ ይብላዕ ፡ ኅብስተ ፡ ይብላዕ ፡ ሖረ ፡ ኅብስተ ፡ በሊዖ ፡ ማለቱን ፡ ያሳ ያል ፡ በቀሩትም ፡ ባራቱ ፡ አዕማድ ፡ አሳሳባቸው ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፡ አይለወጥም ። አርእ ስትና ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ዐርፈው ፡ ተናበው ፡ በለ ፡ ተያይዘው ፡ በፊትም ፡ በኋላም ፡ ኹነው ፡ ይስባሉ ። ዐርፈው ፡ በፊት ፡ ኹነው ፡ ሲስቡ ፡ በሊዕ ፡ በሊ ዖት ፡ በሊዖት ፡ ኅብስተ ፡ በላዒ ፡ ኅብዝተ ። በኋላም ፡ ኹነው ፡ ሲስቡ ፡ ኅብዝተ ፡ በሊዕ ፡ ዖት ፡ ብልዐት ፡ በላዒ ፡ ያሰኛሉ ። ተናበው ፡ ሲስቡ ፡ በሊዐ ፡ ኅብስት ፡ በሊዖተ ፡ ኅ ፡ ብልዐተ ፡ ኅ ፡ በላዔ ፡ ኅብዝት ። በለ ፡ ተያይዘው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲስቡ ፡ በሊዕሁ ፡ በሊዖቱ ፡ ብልዐቱ ፡ በላዒሁ ፡ ለኅብዝት ። ወደ ፡ ኋላም ፡ ሲስቡ ፡ ለኅብዝት ፡ በሊዕሁ ፡ በሊዖቱ ፡ ብልዐቱ ፡ በላዒሁ ፡ ያሰኛሉ ። የቀረ ፡ ተሳቢ ፡ ሲፈጸምሩና ፡ አገባብ ፡ ሲገናኙቸው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አይስቡም ። ይህም ፡ በሊዐ ፡ ኅብዝት ፡ በማእድ ፡ ቢል ፡ እንጂ ፡ በማእድ ፡ በሊዐ ፡ ኅ ፡ በላዔ ፡ ኅ ፡ አይልም ። ሲያያዝም ። በሊዖቱ ፡ ለኅ ብዝት ፡ በማእድ ፡ ቢል ፡ እንጂ ፡ በማእድ ፡ በሊዖቱ ፡ ለኅብዝት ፡ አይልም ፡ አገባብም ፡ ሲገኝነው ፡ ለበሊዕ ፡ ኅብዝተ ፡ ለበላዒ ፡ ኅብዝት ፡ ቢል ፡ እንጂ ፡ ኅብዝተ ፡ ለበሊዕ ፡ ወይም ፡ ለበላዒ ፡ አይልም ፡ በቀሩትም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

፺፩ ፡ ኹለት ፡ ግእዝ ፡ የሚስቡ ፡ አናቅጽ ፡ ረሰየ ፡ መሀረ ፡ ጸውዐ ፡ ሰመየ ፡ ብህለ ፡ መልአ ፡ ቀብዐ ፡ ከደነ ፡ ዐጸፈ ፡ ናቸው ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ኹሉ ፡ ፪ ፡ ግእዝ ፡ ስበው ፡ ሲገኙ ፡ ፩ኛው ፡ ተሳቢ ፡ ኹኖ ፡ በራሱ ፡ ፪ኛው ፡ ባገባብ ፡ ፈንታ ፡ ይነገራል ፡ ረሰዮ ፡ ለ ማይ ፡ ወይነ ፡ ረሰየ ፡ ማየ ፡ ወይነ ፡ ቢል ፡ ከመ ፡ ወይን ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ የረሰየ ፡ ምስ

ቢሮ ፡ እንዲህ ፡ እንዳኹኑ ፡ ውላጤ ፡ ሲኾን ፡ ተገብሮውንም ፡ ነኑ ፡ ይወርሰዋል ፡ ዋዲሞ ፡ አንክረ ፡ ውእተ ፡ ማየ ፡ ዘከነ ፡ ወይነ ፡ እንዲል ። መሀረም ፡ ትምርቱንና ፡ ተማሪውን ፡ ኹለቱንም ፡ በግእዝ ፡ ሲስብ ፥ መሀረ ፡ ፊደለ ፡ ሕፃናተ ፡ ቢል ፡ የተቀባዩን ፡ ን ፡ አገባብ ፡ ሉን ፡ ግእዝ ፡ ሲወርሰው ፡ ነው ፡ ስትፈታም ፡ ለሕፃናት ፡ ብል ፡ እንጂ ፡ ሕፃናትን ፡ አት ብል ። ፪ኛም ፡ መሀሮሙ ፡ ፊደለ ፡ ለሕፃናት ፡ ወትፈቅዱ ፡ ይምሀሩክሙ ፡ ቀዳሚ ፡ መጽ ሐፈ ፡ እያሰኘ ፡ ተቀባዩን ፡ ባገባብና ፡ በዝርዝር ፥ ተሰባኩን ፡ በግእዝ ፡ ሲስብ ፥ ፩ ፡ አን ቀጽ ፡ ካ፩ ፡ ግቢር ፡ በቀር ፡ ፪ኛ ፡ ግቢር ፡ እንዳይስብ ፡ በግልጥ ፡ ያስረዳል ። ተገብሮውና ፡ ሳድስ ፡ ቅጽሉም ፥ ተምህረ ፡ መጽሐፈ ፥ ብእሲ ፡ ምሁር ፡ መጽሐፈ ፡ እያሰኘ ፡ ግቢር ፡ የሳበውን ፡ መልሶ ፡ በግእዝ ፡ ይስባል ።

፱ ፡ ጸውዐና ፡ ሰመየም ፡ ባለስምን ፡ በዝርዝርና ፡ በጠቃሽ ፥ ስምን ፡ በግእዝ ፡ ሲ ስቡ ፥ ወጸውዑ ፡ ስሞ ፡ ኢየሱስሀ ፡ ወሰመዮ ፡ ለብርሃን ፡ መዓልተ ፡ ወለጽልመት ፡ ሌ ሊተ ፡ ያሰኛሉ ። ተገብሯቸውም ፥ ተጸውዐ ፡ ተጠሩ ፡ ሲኾን ፡ ሳድስ ፡ እንጂ ፡ ግእዝ ፡ አይስብም ፡ ተሰምየ ፡ ግን ፡ ተባለ ፡ ሲኾን ፡ ግእዝና ፡ ነባር ፡ ይስባል ። ተሰመይኪ ፡ እመ ፡ ወአመተ ፡ ተሰምየ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ተባለ ። ተሰምየ ፡ ብሎ ፡ ስሙ ፡ ካላለ ፡ ግእዝ ፡ እንጂ ፡ ሳድስ ፡ አይስብም ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ተሰምየ ፡ ዐማ ኑኤል ፡ ወዳዲ ፡ ይሰመይ ፡ ኢየሱስሀ ፡ ይላል ። ሰመየም ፡ በግእዝ ፡ ፈንታ ፡ ሳድስ ፡ እየ ሳበ ፡ ይገኛል ። ሰመዮ ፡ ለስምዖን ፡ ጴጥሮስ ። ብሀሉና ፡ ይቤም ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ኹሉ ፡ ጥሬ ዎችን ፡ እንደነሰመየ ፡ ሲስብ ፥ መነ ፡ ትብል ፡ ርእሰከ ፡ መነ ፡ ይብለኒ ፡ ሰብእ ፡ ይላል ። በውእቱም ፡ ፈንታ ፥ ቢ ፡ እለ ፡ ይብሉከ ፡ ኤልያስሀ ፡ አው ፡ ኤርምያስሀ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ርእሰሙ ፡ ሐዋርያተ ፡ እያለ ፡ ግእዝ ፡ ይስባል ። በተለየም ፡ አንቀጽና ፡ አገባብ ፡ ሲስብ ፡ ይቤሉ ፡ እግዚእ ፡ ለእግዚእየ ፡ ንበር ፡ በየማንየ ፡ ኢትበል ፡ ለየማን ፡ ወኢለፀጋም ፡ ይላል ። መልእና ፡ ቀብዐ ፡ ከደነና ፡ ዐጸፈም ፡ ፪ ፡ ግእዝ ፡ ስበው ፡ ሲገኙ ፡ ፪ኛው ፡ ባገ ባብ ፡ ፈንታ ፡ ነው ፡ ተገብሯቸውም ፡ ተመልአ ፡ ጥበበ ፥ ተቀብዐ ፡ ዘይተ ፥ ተከድነ ፡ ሠቀ ፥ ተዐጽፈ ፡ ርትዐ ፡ እያሰኘ ፡ እንደነመሀረ ፡ ግእዝ ፡ ይስባል ።

፲ ፡ የነባር ፡ አንቀጽም ፡ አሳሳብ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ውእቱ ፡ በአንቀጽነቱ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሲፈታ ፡ የነባርና ፡ የጥሬ ፡ ዘር ፡ የሣልስና ፡ የሳድስ ፡ ቅጽል ፡ ያርእስትና ፡ የሳቢ ፡ ዘር ፡ ማሰሪያ ፡ ይኾናል ። መሓሪ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ሕግ ፡ መንፈስ ፡ ይእቲ ፡ ነፍስ ፡ መሬት ፡ ውእቱ ፡ ሥጋ ፡ እያለ ፡ በሚስበውና ፡ በሚያስረው ፡ ኹሉ ፡ የባለቤትን ፡ ባሕርይና ፡ግብር ፡ ሌላውንም ፡ ይተረጕማል ። ተገልጠም ፡ ባልተ ነገረበት ፥ ሕይወቱ ፡ ለነዳይ ፡ ስኢለ ፡ ምጽዋት ፡ ወተሰፍዎ ፡ ጸጊብ ፡ ኅብስት ፡ ፈጠር ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ወተፈጥሮ ፡ ዘሰማይ ፡ ወምድር ፡ እያሰኘ ፡ በየደጁ ፡ ይመረመራል ። አከና ፡ ኢ ፡ ደግሞ ፡ አይዶለም ፡ ተብለው ፡ ሲፈቱ ፡ አክኹዳቸው ፡ እንደ ፡ ውእቱ ፡ ነው ፡ ርሱ ፡ የሚስባቸውን ፡ ይስባሉ ። ይህም ፡ አከ ፡ ወይም ፡ ኢመፍትው ፡ አድልዎ ፡ በፍትሕ ፡ አከ ፡ ወይም ፡ ኢሕዝብየ ፡ እሉ ። ተንስሐቱ ፡ ለይሁዳ ፡ አከ ፡ ወይም ፡ ኢከመ ፡ ተንስሐቱ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ።

፲፩ ፡ ቅጽል ፡ ከባለቤት ፡ ሲርቅ ፡ ወይም ፡ በውእቱ ፡ ሲፈረቀቅ ፡ ስሙ ፡ ተለዋጭ ፡ ይበላል ፤ ተለዋጭም ፡ ባሕርይና ፡ ግብር ፡ ስምና ፡ ነገር ፡ ይተረጐማል ፡ አካልም ፡ ያመጣል ፡፡ አካልም ፡ ኹኖ ፡ ቅጽልም ፡ ኹኖ ፡ ማሰሪያ ፡ ከወደቀበት ፡ በግድ ፡ ተለዋጭ ፡ ይኾናል ፤ አካል ፡ ሲያመጣ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ዘለብሰ ፡ ሥጋ ፡ ብሎ ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ አካል ፡ ያሰኛል ፤ ግብርም ፡ ሲተረጐም ፡ ማርያም ፡ ይእቲ ፡ ኪሩቤል ፡ ይላል ፡፡ ከሥሩ ፡ መደብ ፡ ፬ቱ ፡ ሩቆች ፡ በቂና ፡ አንቀጽ ፡ እየኾኑ ፡ ራሳቸውን ፡ ይችላሉ ፡፡ ምሳሌ ፡ ውእቱ ፡ ዘፈጸመ ፡ ሕገ ፡፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ ወለደት ፡ አምላከ ፡፡ ውእቶሙ ፡ አው ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ሰበኩ ፡ ወንጌለ ፤ ውእቶን ፡ አው ፡ እማንቱ ፡ እለ ፡ ብዙኀ ፡ ተጋደላ ፡፡ ዘ ፡ እንተ ፡ እለም ፡ ባልገቡበት ፡ ቅጽልና ፡ ጥሬ ፡ ማሰሪያ ፡ ሲኾኑ ፡ ውእቱ ፡ ሕያው ፥ ወአከ ፡ ምውት ፤ ውእቱ ፡ አብርሃም ፥ ወይእቲ ፡ ሳራ ፤ እሙንቱ ፡ ደቂቅ ፥ ወእማንቱ ፡ አዋልድ ፡ እያሰኙ ፡ ሴላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያሉ ፡፡

፲፪ ፡ ፮ቱ ፡ ቅርቦች ፡ ግን ፡ የሩቁን ፡ አንቀጽ ፡ ውእቱን ፡ ይደርበሉ ፡፡ ውእቱም ፡ ለዋጭ ፡ ተለዋጭ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ በወንድና ፡ በሴት ፡ ባንድና ፡ በብዙ ፡ የቅርብ ፡ አፈቃት ፡ ይፈቃል ፡፡ ምሳሌ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘትገብር ፡ መንክረ ፡፡ አንቲ ፡ ውእቱ ፡ እንተ ፡ ወለድኪ ፡ አምላከ ፡፡ አንትሙ ፡ ውእቱ ፡ እለ ፡ ፆድክሙ ፡ አህጉረ ፡፡ አንትን ፡ ውእቱ ፡ እለ ፡ አፍቀርክን ፡ ንጽሐ ፡፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘአአምን ፡ በክርስቶስ ፡፡ ንሕነ ፡ ውእቱ ፡ እለ ፡ ንትፋቀር ፡ በበይናቲነ ፡፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ አንትሙ ፡ እሙንቱ ፥ አንትን ፡ እማንቱ ፥ ንሕነ ፡ እሙንቱ ፤ ባንዲቱም ፡ አንቲ ፡ ይእቲ ፡ እያሰኝ ፡ ሩቆቹን ፡ ኹሉ ፡ ይደርበል ፡፡ በግልጠ ፡ ዘ ፡ ብቻ ፡ ያይዶለ ፡ በሌላውም ፡ ቅጽልና ፡ ጥሬ ፡ እንዲሁ ፡ ናቸው ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡፡ አንቲ ፡ ውእቱ ፡ ምሥራቅ ፡፡ አንትሙ ፡ ውእቱ ፡ ዘርዕ ፡ ክቡር ፡፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡፡ ፪ኛም ፡ ሩቁን ፡ ትተው ፡ ቅርቡን ፡ ብቻ ፡ ይደርበሉ ፡፡ ምሳሌ ፤ አንተ ፡ መኑ ፡ አንተ ፡፡ አንቲሰ ፡ እብድ ፡ አንቲ ፡፡ አንትሙ ፡ ኢሌበውያን ፡ አንትሙ ፡፡ አንትንሰ ፡ ጠባባት ፡ አንትን ፡፡ እስመ ፡ አነ ፡ ኄር ፡ አነ ፡፡ ንሕነሰ ፡ አግብርቲከ ፡ ንሕነ ፡፡ ፫ኛም ፡ ሩቅና ፡ ቅርብ ፡ ሳይደርቡ ፡ ብቻ ፡ ብቻቸውን ፡ ራሳቸውን ፡ ይችላሉ ፡፡ ምሳሌ ፡ አንተ ፡ ዘትፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ ፡ አንተ ፡ ካህኑ ፡ ለዓለም ፡፡ አንቲ ፡ በአማን ፡ ምክሐ ፡ ዘመድነ ፡፡ አንትሙ ፡ ጼው ፡ ለምድር ፡፡ አንትን ፡ አዋልደ ፡ መኑ ፡፡ አንሰ ፡ ቃለ ፡ ዐዋዲ ፡፡ ወንሕነ ፡ ሰማዕቱ ፡፡

፲፫ ፡ ውእቱ ፡ በግብር ፡ ለውጥ ፡ ሩቁን ፡ በቅርብ ፥ ቅርቡን ፡ በሩቅ ፥ አንዱን ፡ በብዙ ፥ ብዙውን ፡ ባንድ ፥ ወንዱን ፡ በሴት ፥ ሴቱን ፡ በወንድ ፡ ያናግራል ፡፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘያገብር ፡ ኵሎ ፡፡ ማርያም ፡ ኪሩቤል ፡ ይእቲ ፤ ወኪሩቤል ፡ እሙንቱ ፡ ማርያም ፡ በ ፡ ለ ፡ እም ፡ በእንተ ፡ ጸዊረ ፡ አምላክ ፡፡ በአካልም ፡ ለውጥ ፡ ሲገባ ፡ በየራሱ ፡ ያናግራል ፡ ወይም ፡ ተለዋጭ ፡ ይኾናል ፡፡ እመ ፡ አምላክ ፡ ይእቲ ፡ ማርያም ፡ ማርያም ፡ ይእቲ ፡ እመ ፡ አምላክ ፡፡ በባሕርይም ፡ ለውጥ ፥ እብን ፡ ዘአርአዮ ፡ ሰይጣን ፡ ለእግዚእነ ፡ ኅብዝት ፡ ውእቱ ፡ ኅብዝት ፡ ዘአርአዮ ፡ ሰይጣን ፡ ለእግዚእነ ፡ እብን ፡ ውእቱ ፡ ያሰኛል ፡፡ እኪና ፡ ኢ ፡ ደግሞ ፡ የውእቱ ፡ አሉታ ፡ እየኾኑ ፡ እስካኹን ፡ በገባው ፡ ይገባሉ ፡፡

፲፬ ፡ በ ፡ በነባርነቱ ፡ አለ ፡ ኖረ ፡ ነበረ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ውእቱ ፡ ሲፈታ ፡ በ ፡ አዳም ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ እምቅድመ ፡ ዕልወት ፡ መጠነ ፡ ሰብዐቱ ፡ ዓመት ፡ እያሰኝ ፡ ባለ

ቤት ፡ ከገበብ ፡ ይስባል ፡፡ በዝርዝርንቱም ፡ ቦ ፡ ቦቱ ፡ አለው ፡ ኖረው ፡ ነበረው ፡ ተብሎ ፡ ሲፈታ ፥ ወቦ ፡ እኀት ፡ ሠናይት ፡ ለአቤሴሎም ፡፡ ወባቲ ፡ ለርብቃ ፡ እኍ ፡ እያሰኘ ፡ ገን ዘብና ፡ ባለገንዘብን ፡ ከናገባቡ ፡ ይስባል ፡፡ ዝርዝሩ ፡ በቂና ፡ ፀጸፋ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ ዘቦ ፡ ክልኤ ፡ ክፃናት ፡፡ ወቦቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘኢይጠፍእ ፡ እያለ ፡ ገንዘብን ፡ ብቻ ፡ ይስባል ፡፡ ሉሎታውም ፡ አልቦ ፡ አልቦቱ ፡ እንደ ፡ ጽድቁ ፡ ነው ፡፡ ቦ ፡ ነባር ፡ ከዝርዝር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ቦቱ ፡ ግን ፡ ዝርዝር ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ፡፡ ሎ ፡ ሎቱ ፡ ደግሞ ፡ አለው ፡ አለለት ፡ ተብሎ ፡ ሲፈታ ፡ እንደ ፡ ቦቱ ፡ አድርጎ ፡ ይስባል ፤ ማይሰ ፡ ሎሙ ፡ አረፍት ፡ በይምን ፡ ወእረፍት ፡ በፅማም ፡፡ ሎሙ ፡ ሕግ ፡ ወሎሙ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲል ፡፡ ሐሰ ፡ በለ ፡ ሲዘረዘር ፡ ዘንድና ፡ አርእስት ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፡ ይስባል ፡፡ እግዚኦ ፡ ታጥፍአነ ፡ ሐሰ ፡ ለከ ፡፡ ሐሰ ፡ ሊተ ፡ እግበር ፡ እኩየ ፡ አው ፡ ገቢረ ፡ እኩይ ፡ ግብረተ ፡ እኩይ ፡፡ ሳይዘረ ዝርም ፡ እንደነአከ ፡ ብቻውን ፡ ይገባል ፡፡ ኀደፎሙኑ ፡ እግዚ ፡ ለሕዝቡ ፤ ሐሰ ፡፡

፲፮ ፡ የከነም ፡ አከኼድ ፡ እንደ ፡ ውእቱ ፡ ነው ፤ ያርእስትና ፡ የሳቢ ፡ ዘር ፡ የቅ ጽልና ፡ የጥሬ ፡ ማሰሪያ ፡ ይኾናል ፡፡ አንቀጽንቱ ፡ ዐጕል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የረሰዩና ፡ የግብረ ፡ መደረግ ፡ ይባላል ፤ የረሰየ ፡ ሲኾን ፡ በሚለወጥና ፡ በማይለወጥ ፡ ነገር ፡ ግእዝና ፡ ራብዕ ፡ ኃምስና ፡ ሳብዕ ፡ ይስባል ፡፡ ምሳሌ ፡ ሌሊቱ ፡ ከነ ፡ ቀትር ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከነ ፤ ይስማኤል ፡ ከነ ፡ ነዳፌ ፡ ከንቢ ፡ ታቦቶ ፡ ለፈጣሪ ፡፡ የግብረ ፡ መደረግ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ ሳድስ ፡ እንጂ ፡ ግእዝ ፡ አይስብም ፡ ይህም ፡ ከብካብ ፡ ከነ ፡ በቃና ፡ ዮም ፡ ከነ ፡ ሕይወት ፡ ለዝንቱ ፡ ቤት ፡፡ ኢዐቀብነ ፡ ወኢገበርነ ፡ በከመ ፡ አዘዝከነ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሠናይ ፡ ላዕሌነ ፡ ማለ ቱን ፡ ያሳያል ፡፡ በሚለወጥ ፡ ነገር ፡ መደረግ ፡ ሲኾን ፡ በማይለወጠው ፡ ማድረግ ፡ ይኾ ናል ፡ በሚለወጥ ፡ ማለት ፥ ለዋጩ ፡ ሌላ ፡ ተለዋጩ ፡ ሌላ ፡ ሲኾን ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ማየ ፡ ግብጽ ፡ እንደ ፡ ማየ ፡ ቃና ፡፡ በማይለወጥ ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ዐጕል ፡ አንቀጽ ፡ ከኺ፡ኙ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አይስብምና ፤ የራሱ ፡ አድራጊ ፡ ኺ፡ኙም ፡ አኺ፡ኙም ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ ሲኾን ፡ ነው ፤ ይህም ፥ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከነ ፡ ብሎ ፡ ውነደረ ፡ ውስቴትነ ፡ በለው ፡ ይታ ወቃል ፡፡

፲፯ ፡ ዳግመኛም ፡ በወ ፡ ከፋይነትና ፡ አያያዥነት ፡ የነገር ፡ የታሪክ ፡ ማንሻና ፡ መነሻ ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ ብሀለና ፡ እንደ ፡ ይቤ ፡ አንቀጽ ፡ ይስባል ፡፡ ይህም ፥ ወከነ ፡ እም ድኅረ ፡ ሞተ ፡ ሙሴ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚ ፡ ለኢያሱ ፡፡ ወከነ ፡ በመዋዕለ ፡ ሄሮድስ ፡ ንጉሥ ፡ ሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ካህን ፡፡ ወከነ ፡ በውእቱ ፡ መዋዕል ፤ ወፅአ ፡ ትእዛዝ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ፡፡ ጽንዕም ፡ ሲኾን ፥ አከኼዱ ፡ እንደ ፡ ሀለወ ፡ ነው ፤ ከትንቢት ፡ አን ቀጽ ፡ እየተደረበ ፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ፡፡ አገባቡንም ፡ በ፰ኛ ፡ ፅርከን ፡ ተመልከት ፡ (ቍ፰) ፡፡ ሀለወ ፡ ደግሞ ፥ ሀሎ ፡ ይጽሕፍ ፡ አው ፡ ይጽሕፍ ፡ ሀሎ ፡ እያሰኘ ፡ የትን ቢት ፡ ትርአስና ፡ ትርጋፅ ፡ ሲኾን ፡ ይጥፋል ፡ ብሎ ፡ ያኹኑን ፥ ይጥፍ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ያለፈና ፡ የሚመጣ ፡ ጊዜ ፡ ያሳያል ፡፡ ተዘርዝሮም ፥ ሀለዎሙ ፡ ይእመኑ ፡ በቱ ፥ ዘሀለዎ ፡ ይኩን ፡ ፍጡነ ፥ እስመ ፡ ሀለዎ ፡ ይሙት ፡ እያሰኘ ፡ ዘንድ ፡ አንቀጽ ፡ ሲስብ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚመጣ ፡ እንጂ ፡ ያለፈ ፡ አያሳይም ፡፡ የሳቢና ፡ የተሳቢ ፡ ነገር ፡ በጭሩ ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

## መፈጸሚያ ፡ ዐዋጅ ።

፲፯ ፡ ግእዝ ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕ ፡ የሚኾነውን ፥ ሳድስ ፡ ሣልስ ፡ ከዕብ ፡ ከማድረግ ፥ ሳድስ ፡ ሣልስ ፡ ከዕብ ፡ የሚኾነውን ፥ ግእዝ ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕ ፡ ከማድረግ ፡ ተጠንቀቅ ። በባለቤትና ፡ በዘርፍ ፡ በቅጽል ፡ መክከል ፡ ሌላ ፡ እንዳይገባ ፥ በሳቢና ፡ በተሳቢም ፡ ማኽል ፡ ባዕድ ፡ አይገባም ። ይህም ፡ በማእድ ፡ ነዳይ ፡ በሊዐ ፡ ኅብዝት ፡ አለማለቱን ፡ ያሳያል ። ሳቢና ፡ ተሳቢ ፡ ማስተሳለፍ ፡ ብርቱ ፡ ጸያፍ ፡ ነው ። እምአርዑተ ፡ ኀጢአት ፡ ኢየሱስ ፡ ዘአግዐዘ ፡ ትግዝምደ ፡ ሰብእ ፡ ወይም ፡ ለተቀንዎ ፡ አምላክ ፡ ዘኢያኅጸርከ ፡ እእጋረ ፡ እያሰኝም ። የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ጸያፍ ፡ ስሙ ፡ ግሥማሥ ፡ ይባላል ፡ ኅብስተ ፡ ለበሊዐ ፡ አይልም ፡ ያልነውም ፡ መከታ ፡ ይባላል ፡ መከታውም ፡ ለ ፡ ነው ።

## ፲፯ኛ ፡ ዕርከን ።

## ዘርፍና ፡ ባለቤት ፥ ተናባቢና ፡ ተያያዥ ።

፲፰ ፡ ዘርፍ ፡ ማለት ፥ ዘይቤው ፡ ዘፈረ ፡ ቃል ፥ ትርጓሜው ፡ ዐመር ፡ ቅጽል ፥ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ ባለወገንና ፡ ባለገንዘብ ፥ የስም ፡ ተውሳክ ፡ የባለቤት ፡ ምስማክ ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለቤትም ፡ ማለት ፥ ባለዘርፍ ፡ የዘርፍና ፡ የቅጽል ፡ ጌታ ፥ ዘርፉን ፡ ተቈራኝቶ ፡ እንደ ፡ ኩታ ፡ ዐብሮ ፡ የሚታሰር ፡ የሚፈታ ፡ ማለት ፡ ነው ። እገናኝቶም ፡ ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ ሲሉት ፥ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ወይም ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹኖ ፡ ዕሙርነቱን ፡ ያሳያል ። ዘርፍ ፡ ኹሉ ፡ የርሱን ፡ ስምና ፡ ባለገንዘብነት ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ የባለቤቱን ፡ ገንዘብነት ፡ ስሙና ፡ ግብሩን ፡ ወገኑን ፡ ዐይነቱን ፡ ገልጦ ፡ የሚያሳይ ፡ ዐመር ፡ ቅጽል ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፥ በስተሳሰሩና ፡ በፈታቱ ፡ የዘ ፡ እንተ ፡ እለን ፡ ዐማርኛ ፡ የን ፡ አይለቅም ።

፲፱ ፡ ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ የሚባሉ ፡ በ፪ ፡ አገባብ ፡ በለና ፡ በዘእንተእለ ፡ ተያይዘው ፥ ወይም ፡ በ፬ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ በራብዕ ፥ በኃምስ ፡ በሳብዕ ፡ ተናበው ፡ የሚጣፉና ፡ የሚጠሩ ፥ ተከታትለው ፡ የሚነገሩ ፡ ፪ ፡ ስሞች ፡ ናቸው ፡ አምላክ ፥ ሰማይ ፥ እነዚህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ። ፪ቱ ፡ ቀንጃ ፡ ስም ፡ በገባብ ፡ በፊደል ፡ ሲያያዝና ፡ ሲናበብ ፥ አምላኩ ፡ ለሰማይ ፥ አምላክ ፡ ዘሰማይ ፥ አምላከ ፡ ሰማይ ፥ ደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ፍሬ ፡ በለስ ፡ ገቦ ፡ ኢየሱስ ፡ እሰኝቶ ፡ ፍችውንም ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ የኦሪት ፡ ድንኳን ፡ የበለስ ፡ ፍሬ ፡ የኢየሱስ ፡ ጐን ፡ እያሰኘ ፡ ኹሉን ፡ ያሳያል ። መንታ ፡ ዘርፍም ፡ ሲኾን ፡ አምላከ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፥ እግዚእ ፡ መላእክት ፡ ወሰብእ ፥ ነቢያተ ፡ ይሁዳ ፡ ወሰማርያ ፡ ወበቢሎን ፡ እያሰኘ ፡ በወ ፡ ያመፍራል ። ባለቤትም ፡ መንታ ፡ እየኾነ ፡ በዋዊ ፡ ተመፍሮ ፡ በንዳንዱ ፡ ዘርፍ ፡ ላይ ፡ ይናበባል ። ጎኑያን ፡ ወሁናያን ፡ ሊባኖስ ። ተምያጠ ፡ ወተውላጠ ፡ ህላውያት ፡ ጽጌያት ፡ ወፍሬያት ፡ ትሩፋት ። ሦስት ፡ እየኾነም ፡ ሲመፈር ፡ ጥንተ ፡ ወተፍጻመ ፡ ወማእከለ ፡ መዋዕል ። ድምፀ ፡ ወግሕረ ፡ ወግርማ ፡ አራዊት ፡ ይላል ። ይህም ፡ አክኺድ ፡ በመጽሐፍ ፡ እንጂ ፡ በቅኔ ፡ አልተለመደም ።

፳ ፡ ያ፩ኛው ፡ አገባብ ፡ የለ ፡ ፊደሉ ፡ ፩ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐዋጁም ፡ ፩ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ ላንድና ፡ ለብዙ ፡ ለወንድና ፡ ለሴት ፡ እያያዥ ፡ መኾን ፡ ነው ። ዘ ፡ እንተ ፡ እለ ፡

ግን ፡ ምንም ፡ በማያገዝ ፡ እንዘ ፡ ሠለስቱ ፡ አሐዱ ፡ ቢባሉ ፡ የንባብና ፡ የምስጢር ፡ ልዩነት ፡ ስላላቸው ፥ ዐዋጃቸውም ፡ እንደ ፡ ንባባቸው ፡ ፫ ፡ ነው ፡ ዘ ፡ ላንድ ፡ ወንድ ፡ ብቻ ፥ እንተ ፡ ላንዲት ፡ ሴት ፡ ብቻ ፥ እለ ፡ ለ፪ቱም ፡ ወገን ፡ ብዙዎች ፡ ለወንዶች ፡ ለሴቶች ፡ ተብለው ፡ ይነገራሉ ፡ በቅጽልነትም ፡ እንዲሁ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ ዐዋጅ ፡ ያዋቆችና ፡ የጠንቃቆች ፥ ያይናሞችና ፡ የልባሞች ፡ እንጂ ፡ የኹሉ ፡ አይደለም ፤ የሌሎቹስ ፡ ዐዋጅ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ሳይለይ ፥ እንተ ፡ ላንድ ፡ ዘ ፡ ላንድና ፡ ለብዙ ፡ እለ ፡ ለብዙ ፡ ተብሎ ፡ በሽፍንነት ፡ ይነገራል ።

፫፻፩ ፡ ለ ፡ ላንድና ፡ ለብዙ ፥ ለወንድና ፡ ለሴት ፡ እያገኘ ፡ ሲኾን ፥ ጥበቡ ፡ ጥበባቲሁ ፡ ለሰሎሞን ፡ ምክሮሙ ፡ ምክራቲሆሙ ፡ ለጠቢባን ፡ ዕበያ ፡ ዕበያቲሃ ፡ ለድንግል ፡ ክብሮን ፡ ክብራቲሆን ፡ ለአንስት ፡ ያሰኛል ። የዘርፉንም ፡ ዘርፍ ፡ ቀስተ ፡ መሐላሁ ፡ ለኖኅ ፡ ደቂቀ ፡ ጽርሑ ፡ ለዳዊት ፡ ወመንግብተ ፡ ቤቱ ፡ ያሰኛል ። ደፍቶም ፡ ሲያያይዝ ፥ ለኖኅ ፡ ሐመሩ ፥ ለአሮን ፡ በትሩ ፥ ለጌዴዎን ፡ ፀምሩ ፡ ያሰኛል ። የዘርፉንም ፡ ሲደፋ ፥ ለዳዊት ፡ መሰንቆ ፡ መዝሙሩ ፥ ለሰሎሞን ፡ መንበረ ፡ ክብሩ ፥ ለፍሬ ፡ ስብሐት ፡ መጽሐፉ ፡ ያሰኛል ፡ አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ ለ ፡ ለዘርፍ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፥ ለዘርፍ ፡ ዘርፍ ፡ ደፊነት ፡ የለውም ፡ ይላሉ ። ዘ ፡ እንተ ፡ እለም ፡ ሲያያይዙ ፥ መዝሙር ፡ ዘዳዊት ፥ መዝምራን ፡ እለ ፡ ዳዊት ፥ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ዳዊት ፥ ዕቁባት ፡ እለ ፡ ሰሎሞን ፤ ወይም ፡ ደፍተው ፡ ዘዳዊት ፡ መዝሙር ፡ እለ ፡ ዳዊት ፡ መዘምራን ፡ እንተ ፡ ዳዊት ፡ ብእሲት ፥ እለ ፡ ሰሎሞን ፡ ዕቁባት ፡ ያሰኛሉ ።

፫፻፪ ፡ ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ ተሳቢ ፡ ኹኖ ፡ በ፪ ፡ አገባብ ፡ ሲያያዝ ፥ የባለቤቱ ፡ መድረሻ ፡ ነበር ፡ ፊደል ፡ ከልኾነ ፡ በቀር ፡ እንዳንቀጹ ፡ ጠባይ ፡ በመወራረስ ፡ ይነገራል ። ይህም ፡ ቀተለ ፡ ኢዮአብ ፡ ብሎ ፥ ፀረ ፡ ዳዊት ፥ አዕራረ ፡ እለ ፡ ዳዊት ፥ ዕቤረ ፡ እንተ ፡ ዳዊት ፡ ፀሮ ፡ አዕራሮ ፡ ዕቤሮ ፡ ለዳዊት ፡ ወይም ፡ ደፍቶ ፡ ዘዳዊት ፡ ፀረ ፥ እለ ፡ ዳዊት ፡ አዕራረ ፥ እንተ ፡ ዳዊት ፡ ዕቤረ ፡ ለዳዊት ፡ ፀሮ ፡ አዕራሮ ፡ ዕቤሮ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ፀር ፡ አዕራር ፡ ዕቤር ፥ ፀሩ ፡ አዕራሩ ፡ ዕቤሩ ፡ አይልም ፡ ጸላኢ ፡ በለውም ፡ እንዲሁ ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ ተቀትለ ፡ ብሎ ፡ ፀር ፡ ፀሩ ፥ ተቀትሉ ፡ ብሎ ፡ አዕራር ፡ አዕራሩ ፥ ተቀትለት ፡ ብሎ ፡ ዕቤር ፡ ዕቤሩ ፡ ቢል ፡ እንጂ ፥ ፀረ ፡ ፀሮ ፥ አዕራረ ፡ አዕራሮ ፡ ዕቤረ ፡ ዕቤሮ ፡ አይልም ። ከዕብና ፡ ሳብዕ ፡ መዋረሳቸው ፡ ዝርዝሩ ፡ እንዲህ ፡ እንዳኹኑ ፡ ዘመድ ፡ ሲኾን ፡ ነው ፡ ባዕድ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፥ ጕልትነትና ፡ ስያፍነት ፡ ያስቀርባቸዋል ፡ ይህም ፡ ጸላኢሁ ፡ ብሎ ፡ ቀተለ ፡ ተቀትለ ፥ አዕራሪሁ ፡ ብሎ ፡ ቀተሉ ፡ ተቀትሉ ፡ እያሰኘ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ።

፫፻፫ ፡ ዘርፍ ፡ ከባለቤት ፡ በ፪ ፡ አገባብ ፡ ሲያያዝ ፡ የባለቤትን ፡ ፍጻሜ ፡ በግቢርና ፡ በተገብሮ ፡ ለይተው ፡ የማያስታውቁ ፡ ፊደላት ፡ ግእዝና ፡ ሳድስ ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ሣልስና ፡ ኃምስ ፡ እነዚህ ፡ ፮ቱ ፡ ተቃራኒያን ፡ ይባላሉ ፡ ተወራራሾች ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (መቅ ፡ ቀ፦፰) ። መድረሻው ፡ ፊደል ፡ ግን ፡ ነበር ፡ ሲኾን ፥ ዓሣ ፡ ባሕር ፡ ብሎ ፡ አሥገረ ፥ ወይም ፡ ተሠግረ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ብሎ ፥ ቀተለ ፥ ወይም ፡ ተቀትለ ፡ ስብከ ፡ ዕፅ ፡ ብሎ ፡ ሰበረ ፡ ወይም ፡ ተሰብረ ፡ እያሰኘ ፥ ግቢር ፡ ተገብሮ ፡ ያስማማል ፡ እነዚህም ፡ ፫ቱ ፡ ፊደ

ላት ፡ (ማ ፡ ዊ ፡ ክ) ፡ ተፋቃርያን ፡ ይባላሉ ። በ፬ ፡ ፊደልም ፡ ሲናበብ ፡ ፪ቱ ፡ በዝርዝርነት ፡ ፪ቱ ፡ በነባርነት ፡ ገቢር ፡ ተገብሮ ፡ ያስማሙለታል ፡ ዝርዝርነቱም ፡ ሳድሱን ፡ ግእዝ ፥ ማልሱን ፡ ኃምስ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። ግእዝና ፡ ኃምስ ፡ በዝርዝርነት ፡ እየተና በቡ ፡ ሲያስማሙ ፡ ሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ ብሎ ፡ ሰበከ ፡ ወይም ፡ ተሰብከ ፡ ጸሎቱ ፡ ዳዊት ፡ ብሎ ፡ ሞአ ፡ ወይም ፡ ተሞአ ፡ ያሰኛሉ ። ለራብዕና ፡ ለሳብዕ ፡ ግን ፡ ነባርነት ፡ እንጂ ፡ ዝርዝርነት ፡ የላቸውም ፡ የነባርም ፡ ምስጢር ፡ ጕልትነት ፡ ነው ።

፳፱ ፡ ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ በ፪ ፡ አገባብ ፡ ሲያያዙና ፡ በ፬ ፡ ፊደላት ፡ ሲናበቡ ፡ የሚያሳዩትና ፡ የሚያሰሙት ፡ ምስጢር ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ፩ኛው ፡ ገንዘብነትና ፡ ባለገንዘብነት ። ይህም ፡ መዝሙር ፡ ዘዳዊት ፥ መዝሙሩ ፡ ለዳዊት ፥ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ብሎ ፥ የዳዊት ፡ መዝሙር ፡ እያሰኘ ፡ መዝሙር ፡ ገንዘብ ፥ ዳዊት ፡ ባለገንዘብ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ። ማሳየቱም ፡ ዘርፍ ፡ እንዲህ ፡ እንዳኾኑ ፡ ነባቢ ፥ አካል ፡ ኹኖ ፥ ባለቤት ፡ ሲነበቢ ፡ ስም ፡ ሲኾን ፡ ነው ። ፪ኛም ፥ ባለቤት ፡ ነባቢ ፡ ዘርፍ ፡ ኢነባቢ ፡ ኹኖ ፥ መልአክ ፡ ሰማይ ፡ ብእሲ ፡ ምድር ፡ ሲል ፥ ወገንና ፡ ባለወገንን ፡ ያሳያል ፡ መልአክና ፡ ብእሲ ፡ ወገን ፥ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ባለወገን ። መናበብና ፡ መያያዝም ፡ ሲቀር ፡ መልአክ ፡ ሰማያዊ ፡ ብእሲ ፡ ምድራዊ ፡ እያሰኘ ፡ ወገን ፡ ቅጽል ፡ ኹኖ ፡ ይነገራል ። ዘርፎችን ፡ በዘርፍነታቸው ፡ አቁሞ ፡ ባለገንዘብና ፡ ባለወገን ፡ የሚያደርጋቸው ፡ በለ ፡ መያያዝ ፡ ነው ፡ ዘ ፡ እንተ ፡ እለና ፡ መናበብ ፡ ግን ፡ ግልጠ ፡ ዘና ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ኹነው ፡ እንቀጽ ፡ እየሰጡ ፡ ዘርፍን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ቅጽልነት ፡ ይስባሉ ።

፴ ፡ ፫ኛም ፡ ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ ፪ቱም ፡ ኢነባብያን ፡ ሲኾኑ ፡ ዝርዝርና ፡ ለን ፡ አያስገቡምና ፥ በንድ ፡ አገባብ ፡ ብቻ ፡ በዘ ፡ እንተ ፡ እለ ፡ ተያይዘው ፥ በ፬ ፡ ፊደላት ፡ ተናበው ፡ ሲዘረፉና ፡ ሲነገሩ ፡ ቅጽልና ፡ ባለቤት ፡ ኹነው ፡ ሥራንና ፡ መሥሪያን ፡ ያሳያሉ ። ይህም ፡ ተቋም ፡ ዘወርቅ ፥ ልብሰ ፡ ወርቅ ፥ ወልታ ፡ ወርቅ ፥ እርዌ ፡ ብርት ፥ ስብከ ፡ ሰሰ ፡ ብሎ ፡ ተቋሙ ፡ ልብሱ ፡ ወልታሁ ፡ ለወርቅ ፥ እርዌሁ ፡ ለብርት ፡ ስብከሁ ፡ ለዕፅ ፡ አለማሰኘቱን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ተቋምና ፡ ልብስ ፡ ወልታና ፡ እርዌ ፡ ስብከ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ወርቅና ፡ ብርት ፡ ዕፅ ፡ መሥሪያ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ያሳያል ። ሲፈታም ፡ ዘሚበር ፡ እምወርቅ ፡ ዘልቡጥ ፡ በወርቅ ፥ ግቡረ ፡ ብርት ፡ ዘተገብረ ፡ እምዕፅ ፡ እያሰኘ ፡ ቅጽል ፡ ይኾናል ፡ ስሙም ፡ ሥረ ፡ ወጥ ፥ ወይም ፡ ዘመድ ፡ ዘርፍ ፡ ይባላል ።

፴፩ ፡ ፬ኛም ፡ የባሕርይ ፡ ስም ፡ ከሀላዊ ፡ ስም ፡ ተናበ ፡ ሲዘረፍ ፡ የሀላዊ ፡ ስም ፡ ለባሕርይ ፡ ስም ፡ መፍቻና ፡ ቅጽል ፡ እየኾነ ፡ ባሕርይና ፡ መልክን ፡ ያሳያል ። ይህም ፡ ዕፀ ፡ አውልዕ ፡ ብሎ ፡ ወይራ ፡ የሚባል ፡ ዕንጨት ፥ የወይራ ፡ ዕንጨትነት ፥ ወይም ፡ ወይራው ፡ ዕንጨት ፡ እያሰኘ ፡ የዕፅን ፡ ባሕርይነትና ፡ የርሱን ፡ ሀላዊነት ፡ ያስረዳል ። ዕፅ ፡ ባሕርዩና ፡ የባሕርይ ፡ ስሙ ፡ ነው ፡ አውልዕም ፡ ከዕፀዋት ፡ ኹሉ ፡ ተለይቶ ፡ የሚታወቅበት ፡ ሀላዌውና ፡ የሀላዌው ፡ ስም ፡ ነው ። ሀላዌም ፡ ማለት ፡ አናዎር ፡ ጠባይ ፡ ግዘፍ ፡ ባሕርይ ፥ የተፈጥሮ ፡ ልክ ፡ ዐይነትና ፡ መልክ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አካል ፡ እንደ ፡ ማለት ። ሀላዊ ፡ አስተጋባኢ ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለፈጣሪም ፡ ሳይቀር ፡ ለፍጡራን ፡ ኹሉ ፡

ይነገራል ፡ አካል ፡ ግን ፡ እኔ ፡ እገሌ ፡ ብሎ ፡ ስሙንና ፡ ግብሩን ፡ ለሚናገር ፡ ለነባቢ ፡ ባሕርዩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለኢነባብያን ፡ አይኾንም ።

፳፮ ፡ ፪ኛም ፡ የግብር ፡ ስም ፡ ከተጸውዖ ፡ ስም ፡ ሲናበብ ፡ ዘርፉ ፡ ለባለቤት ፡ ቅጽል ፡ እየኾነ ፡ እንዲሁ ፡ ይፈታል ፡ ይህም ፡ ነቢየ ፡ ሙሴ ፡ ብሎ ፡ ሙሴ ፡ የሚባል ፡ ነቢይ ፥ ወይም ፡ ነቢዩ ፡ ሙሴ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። የተቀብዖም ፡ ስም ፡ ካህን ፡ አሮን ፡ ብሎ ፡ እንዲሁ ፡ ይፈታል ፡ በዘርፍም ፡ አፈታት ፡ ሲቃኙት ፡ የሙሴ ፡ ነቢይነት ፡ የአሮን ፡ ካህንነት ፥ ካህን ፡ መኾኑ ፡ ካህን ፡ መባሉ ፡ እያሰኘ ፡ ባሕርይና ፡ ግብርን ፡ ያሳያል ። የተጸውዖ ፡ ስም ፡ ማናቸውም ፡ ስም ፡ ተናበበት ፡ ዘርፍ ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፥ ርሱ ፡ በሌላ ፡ ስም ፡ ተናቦ ፡ የዘርፍ ፡ ባለቤት ፡ አይኾንም ፡ ይህም ፡ ዳዊት ፡ መንግሥት ፡ አሮን ፡ ክህነት ፡ አለማሰኘቱን ፡ ያሳያል ። ያገርም ፡ ስም ፡ ቢኾን ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፡ ናዝሬት ፡ ኢየሱስ ፥ ወይም ፡ ኢየሱሰ ፡ ናዝሬት ፡ አያሰኝም ፡ ናዝሬት ፡ እንተ ፡ ኢየሱስ ፥ ኢየሱስ ፡ ናዝሬዊ ፡ ቢያሰኝ ፡ እንጂ ። በዘ ፡ እንተ ፡ እለም ፡ ሲያያዝ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘልዳ ፥ ማርያም ፡ እንተ ፡ ዕፍረት ፡ ቢል ፥ ዘርፉ ፡ ልዳዊ ፡ ብእሲ ፡ ልዳ ፥ ዕፍረታዊት ፡ በዓልተ ፡ ዕፍረት ፡ እያሰኘ ፡ ወገን ፡ ቅጽል ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ ባለወገን ፡ ዘርፍ ፡ አይኾንም ።

፳፯ ፡ የባሕርይም ፡ ስም ፡ ብእሲ ፡ ዘለምጽ ፥ ዕደው ፡ እለ ፡ ለምጽ ፡ ወይም ፡ ብእሲ ፡ ለምጽ ፥ ዕደወ ፡ ለምጽ ፡ ብሎ ፡ ሲያያዝና ፡ ሲናበብ ፡ ለምጻዊ ፡ ልሙጽ ፡ ዘቦቱ ፡ ለምጽ ፡ ልሙጻን ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ለምጽ ፡ እያሰኘ ፡ በቅጽልነት ፡ ይፈታል ፡ ሲደፋም ፡ ዘብእሲ ፡ ማቴዎስ ፡ ቢል ፡ ፍችው ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ዘርፍን ፡ ከቅጽል ፡ ለይቶ ፡ ዘርፍ ፡ የሚያሰኘው ፡ መያያዝና ፡ መናበብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በፈታትና ፡ በምስጢር ፡ ግን ፡ ከታላቅ ፡ ወንድሙ ፡ ከቅጽል ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። እስካኹን ፡ ድረስ ፡ በነጠላነት ፡ የተነገረው ፡ ዘርፍ ፡ ፪ ፡ ዐይነት ፡ ነው ፡ ፩ኛው ፡ ባለገንዘብና ፡ ባለወገን ፥ ፪ኛው ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ ምሥረ ፡ ወጥ ፡ አካኼዱም ፡ የመጽሐፍ ፡ ንባብ ፡ ነው ፡ ለቅኔም ፡ ይኾናል ። የዘርፍና ፡ የባለቤት ፡ ጠባይ ፡ በሠምና ፡ በወርቅ ፡ አካኼድ ፡ ስሙና ፡ ጓዙ ፡ ስለ ፡ በዛ ፡ ጸዋትወ ፡ ቅኔ ፡ ተብሎ ፡ ለብቻው ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ተጠቅሎ ፡ በልዩነት ፡ ተጽፏልና ፡ ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ በ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ ተመልከት ። አርእስትና ፡ ሳቢ ፡ ዘርም ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ሳይቀር ፡ ሳቢና ፡ ተሳቢ ፡ በመኾን ፡ ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ ኹነው ፡ እየተናበቡ ፡ ግቢር ፡ ተገብሮ ፡ ያሳያሉና ፡ ይህም ፡ በሳቢና ፡ በተሳቢ ፡ ቦታ ፡ ተነግሯል ። የዘርፍ ፡ ነገር ፡ ከሙሉ ፡ በክፍሉ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ፲፫ኛ ፡ ዐርከን ።

## ቅጽልና ፡ ባለቤት ።

፳፰ ፡ ቅጽል ፡ ማለት ፡ ከባለቤት ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ዘርፍ ፡ ሳይያያዝና ፡ ሳይናበብ ፡ የባለቤትን ፡ ጠባዩና ፡ አኗኗር ፡ ለመግለጥ ፡ ዐብሮት ፡ የሚነገር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ባለሟል ፡ ወይም ፡ አስተርጓሚ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ (ቍ፻፲፫) ። ቅጽልም ፡ እንደ ፡ ዘርፍ ፡ ፪ ፡ ዐይነት ፡ ነው ፡ ዘመድ ፡ ቅጽልና ፡ ባዕድ ፡ ቅጽል ። ሲዘረዘር ፡ ግን ፡ ስሙ ፡ ፰ ፡ ነው ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡

ግልጠ : ዘ ÷ ወገን : ቅጽል ÷ መስም ÷ ጥሬ ÷ ንኡስ ÷ ደቂቅ ÷ አኃዝ : ይባላል ። ዘመድና : ባዕድ : ያሰኘውም : ጌታውንና : ባለቤቱን : መምሰልና : አለመምሰል : ነው ።

## ዘመድ : ቅጽል ።

፻፯ : ውስጠ : ዘ : መንፈስ : (ሰ) : ናዛዚ : (ዚ) : መልአክ : (ከ) : ፍንው : (ወ) : አምላክ : (ከ) : ፀቢይ : (የ) : ብእሲ : (ሲ) : መክሕ : (ሐ) : (ቍ፻፬—፻፯) ። ግልጠ : ዘ : ጳውሎስ : ዘተጸውዐ ÷ ፌቤን : እንተ : ትትለአክ ÷ አርድእት : እለ : ተኀርዩ ። ወገን : አብርሃም : (፱) : ክለዳዊ : (ዊ) ። መስም : ዳዊት : መዘምር : ዳዊትሀ : መዘምረ : ሰሎሞን : (ሀ) : ማእምር : (ረ) ። ጥሬ : ወንጌል : ጽንዐ : ሃይማኖት : ክርስቶስ : አክሊለ : ሰማዕት ። ንኡስ : ኢዩ : አፍ : ወኢዩ : ከናፍር ÷ ኢዩ : አክሎቱት ። ደቂቅ : ውእቱ : ሚካኤል : ይእቲ : ማርያም : ዝከ : ብእሲ : እንታክቲ : ብእሲት ። አኃዝ : አሐዱ : እግዚአብሔር ÷ ወአሐቲ : ሃይማኖት ።

፻፰ : ቅጽል : ከባለቤት : ቀድሞ : ወይም : ተከትሎ : ይነገራል : ይህም : ክቡር : አምላክ ÷ አምላክ : ክቡር : እንደ : ማለት : ነው ። ቅጽል ÷ ባለቤት : ሲቀር : በቂ : ይኸናል : ይህም : ድንግል : ወለደት : አምላከ : ዘተወልደ : እምድንግል : አድኅነ : ዓለመ : እንደ : ማለት : ነው ። ቅጽል : ከባለቤቱ : አይርቅም : ቢርቅ : ግን : ማሰሪያ : አስፈላጊ : ወይም : መመርመሪያ : ይኸናል : ይህም : እግዚአብሔር : ክቡር : በነበ : እስራኤል : ሲል : ቅጽልነቱን : እግዚ : በነበ : እስራኤል : ክቡር ÷ ወይም : ዘከብረ : ሲል ÷ ማሰሪያ : ማስፈለጉንና : ተለዋጭነቱን : ያሳያል ። ከባለቤትም : በይርቅ : ተሳቢ : ካለው : ማሰሪያ : ማስፈለግ : አይቀርም : ኔር : እግዚ : ለእለ : ይትዌክፍዎ : እንዲል ። ውስጠ : ዘና : መስም : ሲስቡ : ባለቤታቸውን : መምሰል : አይቀሩም : ይህም : አምላክ : ክቡር : በሀላዊሁ ÷ አምላክ : ክቡረ : በሀላዊሁ ። ማርያም : መስተምሕርት : ኀበ : ወልዳ ÷ ማርያምሃ : መስተምሕርተ : ኀበ : ወልዳ : ማለቱን : ያሳያል ።

፻፱ : ላንድ : ባለቤት : ፬ : ውስጠ : ዘ ÷ ወይም : ፬ : ግልጠ : ዘ : ባንድ : ወገን : ሲቀጸል : መንታ : ይባላል : ይህም : ማርያም : ኅሪተ : አምላክ : ወፍቅርተ : መላእክት : ዐርገተ : ሰማየ ። ተሰብሐ : እግዚአብሔር : ክቡረ : ስም : ወልዑለ : ምክሩናን ። (፬ : ግልጠ : ዘ) : ተፀውቀ : እግዚ : ዘገብረ : ሰማየ : ወምድረ : ወዘለብሰ : ሥጋ : በይዑዳ : እንደ : ማለት : ነው ። ፬ኛም : ላንድ : ባለቤት : ውስጠ : ዘ : ግልጠ : ዘ : እንዲሁ : እንዳኹኑ : ተመጣፍረው : ባንድ : ወገን : አይቀጸሉም : በግራና : በቀኝ : ሲቀጸሉ : ግን : ስማቸው : መከዳ : ይባላል : ይህም : አስተርአየ : ልዑል : አምላክ : ዘኢያስተርኢ : በሥጋ : እንደ : ማለት : ነው ። በመከዳነት : ግን : መንታ : እየኾኑ : ቢቀጸሉ : ጸያፍ : አይባሉም : ይህም : ብዙኃን : መልእክት : ወንዊኅ : ስብከት : ጳውሎስ : ዘተጸውዐ : ወተፈልጠ : እምአርድእት : ተሰብሐ : ጥቀ : እምነተለመሙ : ሐዋርያት : እንደ : ማለት : ነው ።

፻፲ : ፲ኛም : የቅጽል : ባለቤት : ከእንቀጽ : ባለቤት : ቀድሞ : የባለቤት : አንቀጽ : ሲወድቅበት : ኢታላዩ : ቅጽል : ይባላል ። ይህም : ተመትረ : ሥላሴ : ዘፈጠሩ :

ጊዮርጊስ ፡ በሰይፈ ፡ ኀጺን ፡፡ ተሰቅለ ፡ ማርያም ፡ ዘወለደት ፡ አምላክ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ ም ኑን ፡፡ ተንሥኢ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ወሰዱቃን ፡ ዘሰቀሉ ፡ ክርስቶስ ፡ እሙንቱን ፡፡ በዋሬ ፡ ቅጽልም ፥ እሞሙ ፡ ለሰማዕት ፡ ብዙኃን ፡ ማርያም ፡ እያለ ፡ ኢታላይነቱን ፡ ያሳያል ፡፡ በ ባለቤት ፡ ላይ ፡ የሚወድቅ ፡ ነገር ፡ በዘርፍና ፡ በቅጽል ፡ በሳቢም ፡ የሚወድቅ ፡ በተሳቢ ፡ ይጠበቃል ፡፡ በዘርፍ ፡ ሲጠበቅ ፥ አክበርዎ ፡ መላእክት ፡ ለዘሰማይ ፡ አምላክ ፡ ይላል ፡፡ በቅጽልም ፡ ሲጠበቅ ፥ አዕበይዎ ፡ እስራኤል ፡ ለዘንግሥ ፡ ዳዊት ፡ ይላል ፡፡ በባለቤትም ፡ ሲጠበቅ ፥ ወተንፍሩ ፥ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አኀሰሮሙ ፡ ይላል ፡፡ በቅጽል ፡ ተሳ ቢም ፡ ሲጠበቅ ፥ ረስዕዎ ፡ እስራኤል ፡ ለእግዚ ፡ ዘየዐቢ ፡ ኀይለ ፡ ወብዙኀ ፡ መንክረ ፡ ገብረ ፡ ሎሙ ፡ ይላል ፡፡

፴፱ ፡ ፲ኛም ፡ መልክአ ፡ ፊደሉ ፡ ሳይለወጥ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ እያስተባበረ ፡ ለዩ ቱም ፡ ወገን ፡ የሚቀጸል ፥ ፀዋግ ፡ ጸጓር ፡ አዳም ፡ ድንግል ፥ ሐለይት ፡ ሰንቀውት ፡ ቀን ይት ፡ ዐበይት ፥ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ፈናፍንት ፡ ቅጽል ፡ ስሙ ፡ መድበል ፡ ይባላል ፡፡ ሐዋሪ ፡ ከያኒ ፡ ከማለት ፡ የወጡ ፡ ሐዋርያና ፡ ኬንያም ፡ መሳይ ፡ ተከታይ ፡ የሌላቸው ፡ በሕታ ውያን ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ የሣልስ ፡ ዲቃሎች ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ አፍራሾች ፡ ይባላሉ ፡፡ ሐዋር ያትና ፡ ነቢያትም ፡ የሴቶች ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ የወንዶች ፡ አይዶሉም ፡ ሐወርት ፡ ነበይት ፡ ከላለ ፡ መድበል ፡ ኹኖ ፡ አያስተባብርም ፡፡ ይኸውም ፡ በከኹዳቸው ፡ ይታወቃል ፡ ሐ ዋሬ ፡ ሬት ፡ ሐዋርያን ፡ ያት ፡ ሐወርት ፡፡ ነቢይ ፡ ይት ፡ ነቢያን ፡ ያት ፡ ነበይት ፡፡ ነበየ ፡ ተነበየ ፡ ማለት ፥ ነቢብ ፡ ነበ ፡ ተነበ ፡ ከለው ፡ የወጣ ፡ ዲቃላና ፡ ተቀጥላ ፡ ነው ፡፡ የብዙ ውንም ፡ ሳንድ ፡ ሲቀጽል ፥ ሰማዕት ፡ መዓምርት ፡ ይላል ፡ ኹሉም ፡ የስሕተት ፡ ልማድ ፡ ነው ፡፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ይገኛል ፡፡

## ሐተታ ፡፡

፵ ፡ የቅጽሎች ፡ ጠባይ ፡ ውስጠ ፡ ዘና ፡ ግልጠ ፡ ዘ ፡ በማለት ፡ ተወስኗል ፡ ከነ ዚህ ፡ ከ፪ቱ ፡ አይወጣም ፡፡ ሀይነታቸው ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ከግልጠ ፡ ዘም ፡ ይልቅ ፡ የውስጠ ፡ ዘ ፡ ዐይነት ፡ ይበዛል ፡፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ደግሞ ፡ ከመድረሻው ፡ ፊደል ፡ ስም ፡ ነሥቶ ፡ ሣልስና ፡ ሳድስ ፡ ይባላል ፡ የንባቡም ፡ ዐይነት ፡ ስድስት ፡ ነው ፡፡ ፩ኛው ፡ መከ ከሉን ፡ ራብዕ ፡ አድርጎ ፡ ቀታሊ ፡ ተቀታሊ ፡ አቅታሊ ፡ ተቃታሊ ፡ አስተቃታሊ ፡ እያ ሰኘ ፡ ከ፭ቱ ፡ አዕማድ ፡ ከኅላፊና ፡ ከትንቢት ፡ ወጥቶ ፡ በ፱ ፡ ይፈታል ፡፡ ፪ኛው ፡ መከከ ሉን ፡ ሣልስ ፡ አድርጎ ፡ ዐቢይ ፡ ነቢይ ፡ ዐዚዝ ፡ ገዚፍ ፡ ቀጢን ፡ ጸሊም ፡ ቄሪር ፡ እያለ ፡ በሳድስ ፡ ፊደል ፡ ይጨርሳል ፡፡ ፫ኛው ፡ መከከሉን ፡ በሣልስ ፡ ፊንታ ፡ ራብዕ ፡ ያደርጋል ፡ ነዳይ ፡ ሠናይ ፡ ጠዋይ ፡ ቀላይ ፡ መከሕ ፡ ከዋው ፡ ለዋው ፡ ጸያፍ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡፡ ፬ኛው ፡ መነሻውን ፡ ራብዕ ፡ አድርጎ ፡ ኹሉን ፡ በሳድስ ፡ ይጨርሳል ፡ ጻድቅ ፡ ኃጥእ ፡ ራትዕ ፡ ባዕል ፡ ባዕድ ፡ ቃውም ፡ ላእክ ፡ ከሀን ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡፡ ፭ኛው ፡ ፀመል ፡ ስላለበት ፡ (ኄረ ፡ ኄየረ ፡ ኄረወ) ፡ ኄር ፡ ኄራዊ ፡ ደጓገን ፡ ደጓጊ ፡ ሤራዊ ፡ እያለ ፡ በኃ ምስ ፡ ይነሣል ፡ እስከ ኹን ፡ የተነገሩቱ ፡ ሳድሶች ፡ ኹሉም ፡ ከንደኛው ፡ ዐምድ ፡ የወጡ ፡ ናቸው ፡፡

፴፮ ፡ ኺኛው ፡ ግን ፡ ከተገብሮና ፡ ከሐውልት ፡ ይወጣል ፡ አካኼዱም ፡ ከነዚህ ፡ ልዩ ፡ ነው ። በሳድስ ፡ ተነሥቶ ፡ መኻከሉን ፡ ካዕብ ፡ ያደርጋል ። ይህም ፡ ተቀትለ ፡ ቅቱል ፡ ተቀደሰ ፡ ቅዱስ ፡ ተሰብሐ ፡ ስቡሕ ፡ ነበረ ፡ ንቡር ፡ ደከመ ፡ ድኩም ፡ ጸንዐ ፡ ጽኑዕ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። በባረከ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ መነሻውንም ፡ ቡሩክ ፡ ሱቱፍ ፡ ጉቡእ ፡ ሡሩር ፡ እያለ ፡ ካዕብ ፡ ያደርጋል ። በደንገፀ ፡ ቤት ፡ ዲጉን ፡ ሚሩይ ፡ ሊሉይ ፡ ቂቁይ ፡ ጊጉይ ፡ እያለ ፡ በሣልስ ፡ ይነሣል ። መድረሻው ፡ ወ ፡ ሲኾን ፡ ህልው ፡ ሕስው ፡ እያለ ፡ ኹሉን ፡ ሳድስ ፡ ያደርጋል ፡ ያፈታቱም ፡ ምስጢር ፡ ሥራው ፡ ያለቀለት ፡ ያለፈና ፡ ያኹን ፡ ቢያሳይ ፡ እንጂ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚመጣ ፡ ትንቢት ፡ አያሳይም ። በዕብራይስጥም ፡ ሆዌ ፡ ይባላል ፡ ኽጡን ፡ የኾነ ፡ የተደረገ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፴፯ ፡ የማልጠ ፡ ዘም ፡ ጠባይ ፡ ፬ ፡ ነው ፡ በእንቀጽ ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ ቅጽል ፡ በጥሬ ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ ዘርፍ ፡ አያያዥ ፡ ይባላል ። ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ኂሩት ፡ ዘወልድ ፡ ሱታፌ ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ ከቅጽልነት ፡ አይወጣም ። ወገን ፡ ቅጽልም ፡ ከዘርፍ ፡ አያያዥ ፡ ዘ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ አወጣጡም ፡ በዘርፍ ፡ አካኼድ ፡ ተን ግሯል ። መስም ፡ ቅጽልም ፡ የሣልስና ፡ የሳድስ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ድርብ ፡ ነው ፡ ከተገብሮ ፡ በቀር ፡ ከሬቱ ፡ አዕማድ ፡ ከ፱ ፡ ከ፱ቱ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ መስም ፡ ይወጣል ። ይህም ፡ ቀታሊ ፡ አቀ ታሊ ፡ ብሎ ፡ መቅተሊ ፡ መቅትል ፡ ተቃታሊ ፡ አስተቃታሊ ፡ ብሎ ፡ መስተቃትል ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። አፈታቱም ፡ እንዳወጣጡ ፡ ስጥፍ ፡ ድርብ ፡ ነው ፡ በቀታሊ ፡ እንደ ፡ ቀታሊ ፡ በአቅታሊም ፡ እንደ ፡ አቅታሊ ፡ በቀሩትም ፡ እንዲሁ ፡ ይፈታል ፡ በኹሉም ፡ ኀላፊና ፡ ትንቢት ፡ አለበት ።

፴፰ ፡ የዘርና ፡ የንባር ፡ ጥሬም ፡ ዘርፍ ፡ ሳይገዛ ፡ አለመቀጸሉ ፡ ውስጠ ፡ ዘነት ፡ ስለሌለው ፡ ነው ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ሀገረ ፡ ዳዊት ፡ ማርያም ፡ እመ ፡ አምላክ ፡ መላእክት ፡ ሐራ ፡ ሰማይ ፡ ያዕቆብ ፡ እኅወ ፡ እግዚእን ፡ እያለ ፡ ዘርፍ ፡ ሲገዛ ፡ ግን ፡ ውስጠ ፡ ዘነ ትና ፡ የውስጠ ፡ ዘ ፡ አፈታት ፡ ያገኛል ። የግብርና ፡ የተቀብዖም ፡ ስም ፡ ዘርፍ ፡ ሳይገዛ ፡ ለተጸውዖ ፡ ስም ፡ መቀጸሉ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡ ይህም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ቅቡዕ) ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ (ኰኵሓዊ) ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ፡ ግእዙማ ፡ ምን ፡ ተጠ ርጥሮ ። በስልኤል ፡ ነሃቢ ፡ ዮሴፍ ፡ ጸራቢ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክ ፡ ዘካርያስ ፡ ካህን ፡ ወነቢይ ፡ ወሰማዕት ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

፴፱ ፡ ንኡስ ፡ ቅጽል ፡ በጥያቄ ፡ ቃል ፡ የሚነገር ፡ የተጠያቂና ፡ የተመርማሪ ፡ ቅጽል ፡ ነው ፡ አንድና ፡ ብዙ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ያስተባብራል ፡ (ቀ፩፲፯) ። ይህም ፡ አየ ፡ ገቦ ፡ ረገዙ ፡ አያተ ፡ ሥሕጸታተ ፡ ነበቡ ፡ በአይኒ ፡ ታሕጻጽ ፡ አያሰኝ ። ሲበቃም ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ ፡ መኑ ፡ ዝንቱ ፡ መኑ ፡ ይእቲ ፡ ዛቲ ። መኑ ፡ አንተ ፡ ወምንት ፡ ንሕነ ፡ ምንት ፡ እማንቱ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ለጊዜም ፡ ሲቀጸል ፡ በአይ ፡ መዋዕል ፡ ወበ አይ ፡ አዝማን ፡ ለአይ ፡ ዓመታት ፡ ወለማእዜ ፡ መዋዕል ፡ አየ ፡ ጊዜ ፡ ሐይወ ። ለቦ ታም ፡ ሲቀጸል ፡ እምአይ ፡ ብሔር ፡ አንተ ፡ ያሰኛል ። አይቴ ፡ ሲል ፡ ግን ፡ በቁ ፡ እየ ኾነ ፡ ባለቤት ፡ አልቦ ፡ አይቴኑ ፡ እሐውር ፡ አይቴ ፡ ብሔሩ ፡ ወአይቴ ፡ ማኅደሩ ፡ ያሰ ኛል ። ለሴላውም ፡ ጥሬ ፡ ሲቀጸል ፡ በአይ ፡ ሥልጣን ፡ ታሕተ ፡ አይ ፡ ዕፅ ። በከፈልም ፡

አይ፡ ሰዕ፡ ይኁይስ፡ እምዕፀው፡ ያሰኛል ። ስፍን፡ እስፍንቱም፡ እንዲሁ፡ ናቸው፡ ስፍን፡ ኅፍረት፡ ዘይረክበኒ፡ በይእቲ፡ ዕለት፡ እስፍንቱ፡ መዋዕሊከ ። እንክሮም፡ ሲኾኑ፡ እስፍንተ፡ ተአምራተ፡ ረብሐ፡ እስፍንተ፡ እዜኑ፡ እከያቲሃ፡ ለልሳን፡ ያሰኛሉ ።

፺፡ ደቂቅ፡ ቅጽል፡ ከውእቱ፡ እስከ፡ ንሕነ፡ ያሉ፡ ፲ሩ፡ የኪያሁ፡ ተወራራሾች፡ ወይም፡ ተቃዋሚዎቹ፡ ስለ፡ ኾኑ፡ በማድረግ፡ አድራጊ፡ በማስደረግ፡ አስደራጊ፡ በማደራረግ፡ አደራራጊ፡ እየኾኑ፡ ይነገራሉ፡ እንጂ፡ እንደ፡ ኪያሁ፡ በማድረግ፡ ተደራጊ፡ በማስደረግ፡ አድራጊ፡ ተደራጊ፡ በማደራረግ፡ ተደራራጊ፡ ኹነው፡ አይነገሩም፡ (ቍ፻፲፫) ። ኪያም፡ በግቢር፡ ጊዜ፡ ወራሾቸውና፡ ተውላጣቸው፡ ዐጸፋቸውና፡ በቂያቸው፡ ኹኖ፡ ሲዘረዘርና፡ ሲቀጸል፡ ኪያሁ፡ መንፈሰ፡ ኪያሃ፡ ፍኖተ፡ ኪያከ፡ አውልዐ፡ ገዳም፡ ያሰኛል፡ በበቂነትም፡ ሲነገር፡ ዘኪያክሙ፡ ሰምዐ፡ ኪያየ፡ ሰምዐ፡ ይላል ። እነዚህም፡ ጥቅሶች፡ ውእቱ፡ ይእቲ፡ አንተ፡ አንትሙ፡ አነ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ የገቡ፡ ናቸው ። ከሥሩ፡ ሰራዊት፡ ፪ቱ፡ ውእቱና፡ ይእቲ፡ ብቻ፡ ውእተ፡ ይእተ፡ እያሰኙ፡ ራሳቸውን፡ ይችላሉ ። ስምንቱ፡ ግን፡ እግረ፡ ቀለማቸው፡ የማይፈልስ፡ ጉልት፡ ስለ፡ ኾነ፡ አለኪያሁ፡ በራሳቸው፡ ቁመው፡ አይነገሩም ። ኪያሁ፡ በተደራጊነት፡ የውእቱ፡ ወራሽ፡ ስለ፡ ኾነ፡ አገባብ፡ ተጭኖት፡ በይእቲና፡ በውእቶን፡ ፈንታ፡ ለኪያሃ፡ ሰዓት፡ በኪያሆን፡ መዋዕል፡ እያለ፡ አለርስቱ፡ ገብቶ፡ ይገኛል፡ ኹሉም፡ የመላሽ፡ ስሕተት፡ ነው ።

፺፩፡ ለሊሁም፡ እንደ፡ ውእቱ፡ በለቤት፡ ይኾናል፡ እንጂ፡ እንደ፡ ኪያሁ፡ ተደራጊ፡ ተሳቢ፡ አይኾንም ። ሲቀጸልም፡ ለሊሁ፡ እግዚ፡ ጸብአ፡ ሎሙ፡ ለሊሁ፡ አምላክ፡ ይመጽእ፡ ወያድኅነነ፡ ዘለሊሁ፡ ዳዊት፡ እግዚእየ፡ ይቤሎ፡ ያሰኛል ። ለነ ውእቱም፡ ውእቱ፡ ለሊሁ፡ ይእቲ፡ ለሊሃ፡ አንተ፡ ለሊከ፡ እየተባለ፡ ይቀጸላል፡ በዐጸፋነትም፡ በቂ፡ ይኾናል፡ አከኼዱ፡ ኹሉ፡ እንደ፡ ውእቱ፡ ነው ። ኵሉ፡ ከተጸውዖ፡ ስም፡ በቀር፡ ኵሉ፡ ብእሲ፡ ኵላ፡ እከይ፡ እያሰኘ፡ ለብትኖች፡ ኹሉ፡ ይቀጸላል ። ፳ና፡ ደግሞ፡ ባሕቲቱና፡ ዕራቁ፡ እግዚአብሔር፡ ባሕቲቱ፡ ቅዱስ፡ ማርያም፡ ባሕቲታ፡ ልዕልተ፡ ኵሉ፡ ፍጥረት፡ ወመልአ፡ ለነፍስ፡ ዕራቃ፡ በረከተ፡ እያሰኙ፡ ይቀጸላሉ፡ የቀረውም፡ ኋላ፡ በጸፉ፡ ይነገራል ። በይን፡ ደግሞ፡ በይናት፡ በበይናቲሁ፡ እያሰኘ፡ በዝቶና፡ አገባብ፡ ወድቆበት፡ ሲነገር፡ ዐጸፋ፡ እንጂ፡ ቅጽል፡ አይኾንም፡ ማሰሪያውም፡ ፪፡ ብቻ፡ ነው፡ ተደራራጊና፡ አደራራጊ፡ አንቀጽ ።

እኍዝ፡ ቅጽል ።

፺፪፡ የጅምላ፡ እኍዝ፡ ለጥሬ፡ ኹሉ፡ ሲቀጸል፡ ከ፩፡ እስከ፡ ፲፡ በግቢርና፡ በተገብሮ፡ ከ፳፡ እስከ፡ ምእልፊት፡ በወንድና፡ በሴት፡ ይተባበራል ። ሲቀጸልም፡ በክት፡ በከፊል፡ በደጊመ፡ ቃል፡ ይነገራል፡ በክት፡ ሲነገር፡ መጽኡ፡ ዐሥርቱ፡ ዕደው፡ ወነሥረየ፡ ክልኤነ፡ ሰብዓ ። በከፊል፡ አሐዱ፡ እክል፡ እምነ፡ ሠለስቱ፡ እክላት፡ ክነ፡ ሰብአ ። በደጊመ፡ ቃል፡ ንዑ፡ ንረድ፡ ወንንግአ፡ ለነ፡ አሐተ፡ አሐተ፡ ብእሲተ፡ ወንለድ፡

እምኔሆን ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ ውሉደ ፡ ይላል ። ርስ ፡ በርሱም ፡ ተጋብኡ ፡ አሐዱ ፡ ዐሠ ርቱ ፡ ሰብእ ፥ ወይም ፡ አሐዱ ፡ ምእት ፥ ክልኤቱ ፡ ምእት ፥ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ እያለ ፡ ይቀ ጻጻላል ። በብትን ፡ ስዋስው ፡ የሚገቡ ፡ ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ ለአሐዱ ፡ በአሐዱ ፡ ምስለ ፡ አሐዱ ፡ እያሰኙ ፡ ይስማሙታል ፡ ደጊም ፡ እየኾኑም ፡ ሲገቡበት ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ ይፈታል ። ይህም ፥ ለለ ፡ አሐዱ ፡ ላንዱም ፡ ላንዱም ፡ ለያንዳንዱ ። በበ ፡ አሐዱ ፡ በያ ንዳንዱ ፥ እያንዳንዱ ፥ አንዱንም ፡ አንዱንም ። ወእርፍቅዎሙ ፡ በበ ፡ ኀምሳ ፡ ወበበ ፡ ምእት ፥ ፫ ፡ ፫ውን ፡ ፪ ፡ ፪ውን ፡ እያሰኘ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ።

፹፫ ፡ አኀዝ ፡ ጥንትና ፡ መሠረት ፡ እየኾነ ፡ በቃሪክ ፡ ልማድ ፡ ይነገራል ፡ ታሪ ኩም ፡ የዘመን ፡ ቍጥር ፡ ነው ፡ በዐሠርቱ ፡ ወተስዐቱ ፡ ምእት ፡ ወአርብዓ ፡ ዓመት ፡ ሥጋዌ ፡ ተንሥአ ፡ ጎግ ፡ ወማጎግ ፡ ፍሉጣን ፡ ሕግ ፡ ከመ ፡ ይትቃተሉ ፡ በዘይፋቲሆሙ ፡ እንደ ፡ ማለት ። የተርታም ፡ አኀዝ ፡ ከቀዳምና ፡ ከኢሐድ ፡ እስከ ፡ ዓሥር ፡ ወቃስዕ ፡ በወ ንድና ፡ በሴት ፡ እየተለየ ፥ ከዕሥራ ፡ እስከ ፡ ምእልፌት ፡ እየተባበረ ፡ ለጥሬ ፡ ኹሉ ፡ ይቀጸላል ። የዕለትም ፡ አኀዝ ፡ ፀሡር ፡ ወሰኑይ ፥ ፀሡር ፡ ወረቡዕ ፡ መዋዕል ፡ እያለ ፡ ሲቀጸል ፡ አፈታቱ ፡ እንደ ፡ ጅምላ ፡ ነው ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ያሰኛል ፡ የቀረውን ፡ በ፲፩ ፡ ቀኑ ፡ ተመልከት ። የጊዜም ፡ አኀዝ ፡ ምዕር ፡ ሲቀር ፡ ለጊዜያት ፡ ኹሉ ፡ ይቀጸላል ፡ አፈ ታቱም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፡ ሥልሰ ፡ ጊዜያተ ፡ ብሎ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ያሰኛል ። ርብዕ ፡ በእ መት ፡ ዕሥራ ፡ ወከዕበ ፡ በመስፈርት ፡ እያለም ፡ ከልክና ፡ ከመስፈሪያ ፡ ጋራ ፡ ሲነገር ፡ እንዲሁ ፡ ይፈታል ።

፹፬ ፡ ምዕር ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ምዕራት ፡ ፪ ፡ ጊዜ ፥ ወይም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይኾናሉ ፡ ከጅ ምላና ፡ ከተራ ፡ አኀዝ ፡ ጋራ ፡ አሐተ ፡ ምዕረ ፡ ወምዕረ ፡ ካዕበ ፥ ምዕራተ ፡ ብዙኃተ ፡ እያለ ፡ ሲነገር ፥ ምዕር ፡ ባለቤት ፡ አኀዙ ፡ ቅጽል ፡ ይኾናል ። ደቂቅ ፡ ቅጽልም ፥ ዛተ ፡ ምዕረ ፥ ይእተ ፡ ምዕረ ፡ እያለ ፡ ይስማማዋል ፡ ሲዘረዘርም ፡ ምዕሬሁ ፡ ሃ ፡ ምዕሬሃ ፡ ለይ እቲ ፡ መስፈርት ፡ ያሰኛል ። ጎድጊ ፡ ምዕረ ፡ ይጽገቡ ፡ ውሉድ ። ብላዕ ፡ ወስተይ ፡ ም ዕረ ፡ ወተፈሣሕ ፡ ሲል ፥ ጥቂት ፡ አኹን ፡ ፊት ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ። የዕጽፍም ፡ አኀዝ ፡ አፈድዮሙ ፡ ከዕበተ ፡ ሀመዓሆሙ ። ምክዕቢተ ፡ ክብር ፡ ይደልዎሙ ፡ እያሰኘ ፡ ከጥሬው ፡ ተናበ ፡ ይነገራል ። የክፍልም ፡ አኀዝ ፡ ተስዐቱ ፡ እደ ፥ ዐሠርቱ ፡ እደ ፥ ሰብዐቱ ፡ እደ ፡ እያሰኘ ፥ የእደ ፡ ቅጽል ፡ ኹኖ ፡ በጅምላ ፡ ቍጥር ፡ ይነገራል ፡ እደ ፡ የተባለም ፡ ክፍል ፡ ነው ። በተራ ፡ ቍጥር ፡ ግን ፡ ሲነገር ፡ ከእደ ፡ ተናበ ፡ የቅጽል ፡ አፈታት ፡ ይፈታል ፡ ይህም ፡ ኃልስተ ፡ እዴሁ ፡ ለሀገር ፡ ራብዕተ ፡ እዴሁ ፡ ለምድር ፡ ሳድስተ ፡ እዴሁ ፡ ለአን ዝኩ ፡ ሳብዕተ ፡ እደ ፥ ሰብዐቱኛ ፡ እጅ ፡ እያሰኘ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። የዘመድ ፡ ቅጽል ፡ ጓዝ ፡ እስከዚህ ፡ ነው ።

## ባዕድ ፡ ቅጽል ።

፹፭ ፡ ቅጽልን ፡ ባዕድ ፡ የሚያሰኘው ፥ አገባቡ ፡ የባለቤት ፥ አንቀጹ ፡ የተሳቢ ፡ ኹኖ ፡ ሲነገር ፡ ነው ። ባዕድ ፡ ቅጽል ፡ ባፈታት ፡ ሲለይ ፡ ተሳቢውን ፥ ሲነበብ ፡ ባለቤ ቱን ፡ መስሎ ፡ ይነገራል ፡ ዘመድ ፡ ቅጽል ፡ ግን ፡ ሲነበብም ፡ ሲለይም ፡ ባለቤቱን ፡ ብቻ ፡

ይመስላል ፡፡ ደግሞ ፡ ዳዊት ፡ ዘንግሥ ፡ ለእስራኤል ፡ ሲል ፥ ለእስራኤል ፡ የነገሠ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ፡፡ ዳግመኛም ፡ ባዕድ ፡ ቅጽል ፡ አንድና ፡ ብዙ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ቅርብና ፡ ሩቅ ፡ ሳያናግር ፡ ያናገረ ፡ ይመስላል ፡፡ ባዕድ ፡ ቅጽልም ፡ የሚኾኑ ፡ ፳ ፡ ናቸው ፡ ግልጠ ፡ ዘ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፥ የቦታ ፡ የጊዜ ፡ የልክ ፡ ቅጽሎች ፡፡ ባዕድ ፡ ግልጠ ፡ ዘ ፡ በ፳ቱ ፡ አዕማድ ፡ ሲገባ ፡ አንቀጹን ፡ ቢዘረዝርም ፡ ባይዘረዝርም ፡ በዝርዝርነት ፡ ይፈታል ፡፡

፻፺፮ ፡ በድራጊ ፡ ሲገባ ፥ ወይን ፡ እንተ ፡ ተከ(ሉ)ልዋ ፡ ገባእት ፡ ፈረየት ፡ አስካለ ፡፡ በተደራጊ ፥ መስቀል ፡ ዘተሰቀ(ለ)ሉ ፡ ክርስቶስ ፡ ዕፀ ፡ ሎጥ ፡ ውእቱ ፡፡ በአስደራጊ ፥ መቅደስ ፡ እንተ ፡ አሕነ(ጸ)ጸ ፡ ሰሎሞን ፡ ኪሩቤል ፡ መንክርት ፡ ጥቀ ፡፡ በተደራራጊ ፥ ዳዊት ፡ ዘተጻብ (አ ፡ ምስለ)አ ፡ አቤሴሎም ፡ መፍቀሬ ፡ ወልድ ፡ ጥቀ ፡፡ በደራራጊ ፥ ሰሎሞን ፡ ዘአስተጻብ (አ)አ ፡ ዳዊት ፡ ምስለ ፡ ኢዮአብ ፡ ኢፈርሀ ፡ እምኔሁ ፡፡ ተሳቢውንም ፡ ሲዘረዝር ፥ በሐ ውልት ፡ ግስ ፡ ዑብየ ፡ ሰሎሞን ፡ ዘጸንዐት ፡ መንግሥቱ ፡፡ በተገብሮ ፥ ጸድቀ ፡ ኢዮብ ፡ ዘይትነከር ፡ ትዕግሥቱ ፡፡ በማድረግ ፥ ተሞቅሐ ፡ ጳውሎስ ፡ ዘሰበኩ ፡ አርዳኢሁ ፡ ወን ጌለ ፡፡ በአስደራጊ ፥ ጽሙእ ፡ ጥቀ ፡ ዳዊት ፡ ዘአምጽ(እዎ)እ ፡ ሥዩማኒሁ ፡ ማየ ፡ ቤተ ፡ ል ሔም ፡ ሐራ ፡፡ በተደራራጊ ፥ ሞተ ፡ ዓሊ ፡ ዘተቃተሉ ፡ ደቂቁ ፡ ምስለ ፡ ኢሎፍላውያን ፡፡ በደራራጊ ፥ ሞአ ፡ ለዓለም ፡ ክርስቶስ ፡ ዘአስተቃተለት ፡ ወንጌሉ ፡ ሰማዕት ፡ ምስለ ፡ ዐ ላውያን ፡ ይላል ፡፡ የተሳቢውን ፡ ዘርፍና ፡ የዘርፉንም ፡ ዘርፍ ፡ ሲዘረዝር ፥ ዳዊት ፡ ዘየዐ ቀብዎ ፡ ደቂ ፡ ጽርሑ ፡ ብእሲ ፡ ዘንጉልቄ ፡ ስሙ ፡ ፈደሉ ፡ ሠላስ ፡ ይላል ፡፡

፻፺፯ ፡ በባዕድ ፡ ግልጠ ፡ ዘ ፡ የሚዘረዘሩ ፡ ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ ፱ ፡ ናቸው ፡፡ ለ ፡ በቂ ም ፡ ቀሪ ፡ በእንተ ፡ በይነ ፡ እንበይነ ፡ ስለ ፡ ምስለ ፡ ከ—ጋራ ፡ ኀበ ፡ መንገለ ፡ እንተ ፡ ው ስተ ፡ ለ ፡ ወደ ፡ እስከ ፡ በቁሙ ፡ ድረስ ፡ እም ፡ ከ ፡ ከመ ፡ እንደ ፡ መጠን ፡ ያኽል ፡፡ እንበ ለም ፡ ለኒህ ፡ ለዘጠኙ ፡ አሉታና ፡ አፍራሽ ፡ እየኾነ ፡ ከኢ ፡ ተደርቦ ፡ ይገባል ፡፡ ያገባቦ ችም ፡ ዝርዝር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሔዋን ፡ ዘንግሠ ፡ ላቲ ፡ እምላክ ፡፡ አዳም ፡ ዘሞተ ፡ በእን ቲኣሁ ፡ እግዚእ ፡፡ መስቀል ፡ ዘተሰቅለ ፡ ቦቱ ፡ አምላክ ፡፡ ክርስቶስ ፡ ዘሞቱ ፡ ምስሌሁ ፡ ፈያት ፡፡ ማርያም ፡ እንተ ፡ ተፈነወ ፡ ኀቤሃ ፥ አው ፡ እስከኔሃ ፡ ገብርኤል ፡፡ ምጡቅ ፡ ው እቱ ፡ ሰማይ ፡ ዘመጽአ ፡ እምኔሁ ፡ ገብርኤል ፡፡ አርብዓ ፡ ዓመተ ፡ ነግሠ ፡ ዳዊት ፡ ዘነግሠ ፡ ከማሁ ፥ አው ፡ መጠኖ ፡ ሰሎሞን ፡፡ በቀሩትም ፡ አዕማድ ፡ እንዲህ ፡ ተዘርዝረው ፡ ይገ ባሉ ፡፡ ዳግመኛም ፡ ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ ሳይገቡና ፡ ሳይዘረዘሩ ፥ አናቅጽ ፡ ብቻ ፡ ተዘርዝ ረው ፥ ድኅነ ፡ አዳም ፡ ዘሞቶ ፡ እግዚእ ፡ ክብረ ፡ መስቀል ፡ ዘተሰቅሎ ፡ አምላክ ፡ እያሉ ፡ አገባቦችን ፡ ያሰማሉ ፡፡ እንበለም ፡ አሉታና ፡ አፍራሽ ፡ ሲኾን ፥ አዳም ፡ ዘኢተሰቅለ ፡ አምላክ ፡ እንበሌሁ ፥ አበ ፡ ሥጋነ ፡ አምላክ ፡ አ(ያ)ለርሱ ፡ ያልተሰቀለ ፡ አዳም ፡ የሥጋ ፡ አባታችን ፡ ነው ፡ ያሰኛል ፡፡ ይህ ፡ የበእንተ ፡ አፍራሽ ፡ ነው ፡ የቀሩትንም ፡ እንደዚሁ ፡ እያሰማማኽ ፡ አግባ ፡፡ የግልጠ ፡ ዘ ፡ ዐዋጅ ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

፻፺፰ ፡ ባዕድ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ግልጠ ፡ ዘ ፡ ነው ፡ በንባብ ፡ ባለቤቱን ፡ በፍታት ፡ ተሳቢውን ፡ መስሎ ፡ ሲነገር ፥ ተሳቢና ፡ አንቀጽ ፡ አገባብ ፡ ይዘረዝራል ፡ አ ንቀጹን ፡ ዘርዝሮ ፡ ከተሳቢው ፡ እየተናበበ ፡ ሲነገር ፥ ዐይነቱ ፡ ወይም ፡ አርእስቱ ፡ ፫ ፡ ነው ፡፡ ፩ኛው ፡ ተገብሮና ፡ ሐውልት ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ከድራጊ ፡ ተሳቢ ፡ ተናቦ ፡ በገቢር ፡

አንቀጽ ፡ ከስደራጊ ፡ ተሳቢ ፡ ተናበ ፡ ባስደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ይፈታል ። ፪ኛው ፡ ገቢር ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ከድራጊ ፡ ተሳቢ ፡ ተናበ ፡ በድራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ከስደራጊ ፡ ተሳቢ ፡ ተናበ ፡ ባስደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ይፈታል ። ፫ኛው ፡ ተደራራጊ ፡ ሣልስ ፡ ቅጽል ፡ ከተደራራጊ ፡ ተሳቢ ፡ ተናበ ፡ በተደራራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ከደራራጊ ፡ ተሳቢ ፡ ተናበ ፡ በደራራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ይፈታል ።

፹፱ ፡ (፩ኛ) ፡ ወይን ፡ ትክልተ ፡ ገባእት ፡ ፈረየት ፡ አስካለ ፡ ገበራርት ፡ የተከሏት ፡ ወይን ፡ ዘለላን ፡ አፈራች ። ትክልት ፡ በንባቡ ፡ ወይንን ፡ ይመስላል ፡ ሲፈታ ፡ ግን ፡ አገባቡና ፡ ዝርዝሩ ፡ የርሷ ፡ አንቀጹ ፡ የገባእት ፡ ነው ። ገባእት ፡ አድራጊ ፡ ወይን ፡ ተደ ራጊ ፡ ተሳቢ ፡ ናቸውና ፡ የተገብሮ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ከድራጊ ፡ ተሳቢ ፡ ተናበ ፡ በገቢር ፡ አ ንቀጽ ፡ ይፈታል ፡ ያልነው ፡ ይህ ፡ ነው ። ሐውልት ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ከድራጊ ፡ ተናበ ፡ በገ ቢር ፡ አንቀጽ ፡ ሲፈታ ፡ ዳዊት ፡ ንጉሥ ፡ (አው) ፡ ነጋዊ ፡ እግዚአብሔር ፡ እግዜር ፡ ያነገ ሠው ፡ ዳዊት ። ተገብሮ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ከስደራጊ ፡ ተናበ ፡ ባስደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ሲፈታ ፡ መቅደስ ፡ ሕንጽተ ፡ ሰሎሞን ፡ ኪራምህ ፡ ሰሎሞን ፡ ኪራምን ፡ ያሠራት ፡ መቅደስ ፡ ያሰኛል ። (፪ኛ) ፡ ገቢር ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ከድራጊ ፡ ተናበ ፡ በድራጊው ፡ አንቀጽ ፡ ሲፈታ ፡ ኅብስት ፡ በላዔ ፡ ነዳይ ፡ ድኻ ፡ የሚበላው ፡ እንጀራ ። ከስደራጊውም ፡ ተናበ ፡ ባስደ ራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ሲፈታ ፡ ኪራም ፡ ሐናጺ ፡ ሰሎሞን ፡ መቅደሰ ፡ ሰሎሞን ፡ መቅደስን ፡ ያሠራው ፡ ኪራም ፡ ያሰኛል ። (፫ኛ) ፡ የተደራራጊ ፡ ሣልስ ፡ ቅጽል ፡ ከተደራራጊ ፡ ተናበ ፡ በተደራራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ሲፈታ ፡ ዳዊት ፡ ተጻባኢ ፡ አቤሴሎም ፡ ወልዱ ፡ ልጁ ፡ አቤሴሎም ፡ የተጣላው ፡ ዳዊት ። ከደራራጊም ፡ ተናበ ፡ በደራራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ሲፈታ ፡ ሰሎሞን ፡ ተጻባኢ ፡ ዳዊት ፡ ምስለ ፡ ኢዮአብ ፡ ዳዊት ፡ ከኢዮአብ ፡ ጋራ ፡ ያጣላው ፡ ሰሎሞን ፡ ያሰኛል ።

፺ ፡ ተሳቢውንም ፡ ሲዘረዝር ፡ ያ፳ቱ ፡ አዕማድ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ከተሳቢው ፡ ጋራ ፡ ተናበ ፡ እንዳንቀጹ ፡ ስልት ፡ ይፈታል ። የተገብሮ ፡ ሣልስ ፡ አብ ፡ ተሰባሔ ፡ ወልድ ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ ልጁ ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ የተገለጠ ፡ አብ ። የሐውልት ፡ ሳድስ ፡ ሰሎ ሞን ፡ ጽኑዐ ፡ መንግሥት ፡ መንግሥቱ ፡ የጠና ፡ ሰሎሞን ። የገቢር ፡ ሣልስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሰባኬ ፡ አርድእት ፡ ወንጌለ ፡ አርድእቱ ፡ ወንጌልን ፡ ያስተማሩ(ለት) ፡ ጳውሎስ ። ያስ ደራጊ ፡ ሣልስ ፡ ዳዊት ፡ አምጻኤ ፡ ሥዩማን ፡ ማየ ፡ ሐራ ፡ ኢ ሰትየ ፡ እምኔሁ ፡ ሹማምቱ ፡ ወታደሮችን ፡ ውሃ ፡ ያስመጡለት ፡ ዳዊት ፡ ከርሱ ፡ አልጠጣም ። የተደራራጊ ፡ ሣልስ ፡ ዔሊ ፡ ተቃታሌ ፡ ደቂቅ ፡ ምስለ ፡ ኢሎፍላውያን ፡ ልጆቹ ፡ ከኢሎፍላውያን ፡ ጋራ ፡ የተዋጉ ፡ ዔሊ ። ያደራራጊ ፡ ሣልስ ፡ ክርስቶስ ፡ አስተቃታሌ ፡ ወንጌል ፡ ሰማዕተ ፡ ምስለ ፡ ዐላውያን ፡ ወንጌሉ ፡ ሰማዕታትን ፡ ከዐላውያን ፡ ጋራ ፡ ያጋደለች(ለት) ፡ ክርስ ቶስ ። የተጸውዖ ፡ ስም ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሚካኤል ፡ እያሰኘ ፡ የማይዘረዘር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ስም ፡ በተሳቢነት ፡ አይገባም ።

፺፩ ፡ አገባቦቹንም ፡ ሲዘረዝር ፡ ከተሳቢው ፡ ጋራ ፡ ተናበ ፡ ነው ፡ ለን ፡ ሲዘረዝር ፡ ሔዋን ፡ ንግሥተ ፡ አምላክ ፡ አምላክ ፡ ለርሷ ፡ የነገሠ ፡ ወይም ፡ የነገሠላት ፡ ሔዋን ። በእንተን ፡ ሲዘረዝር ፡ አዳም ፡ ምውተ ፡ እግዚእ ፡ ጌታ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የሞተ ፡ አዳም ። በን ፡

ሲዘረዝር ፥ መስቀል ፡ ስቁለ ፡ አምላክ ፡ አምላክ ፡ በርሱ ፡ የተሰቀለ ፥ ወይም ፡ የተሰቀለ በት ። ምስለን ፡ ሲዘረዝር ፥ አምላክ ፡ ምዉት ፥ አው ፡ መዋቱ ፡ ፈያት ፤ ወንበዶች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፥ ወይም ፡ ዐብረውት ፡ የሞቱ ፡ አምላክ ። ኀበን ፡ እስከን ፡ ሲዘረዝር ፥ ማርያም ፡ ፍኖተ ፡ ገብርኤል ፡ እምሰማይ ፤ ገብርኤል ፡ ከሰማይ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፥ እስከ ፡ ርሷ ፡ የተላከ ፡ ማርያም ። እምን ፡ ሲዘረዝር ፥ ሰማይ ፡ ምጹእ ፥ አው ፡ መጻኢ ፡ ገብርኤል ፡ ኀበ ፡ ማርያም ፡ ገብርኤል ፡ ወደ ፡ ማርያም ፡ ከርሱ ፡ የመጣ ፡ ሰማይ ። ከመን ፡ ሲዘረዝር ፡ አልቦ ፡ ሰራቂ ፡ ቅሡፈ ፡ ክርስቶስ ፤ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ የተገረፈ ፡ ሌባ ፡ የለም ። መጠነን ፡ ሲዘረዝር ፥ ብዙኃት ፡ ዓመታተ ፡ ዳዊት ፡ ነጋሥያተ ፥ አው ፡ ንጉሣተ ፡ ሰሎሞን ፡ ሰሎሞን ፡ ርሳቸውን ፡ ያኽል ፡ የነገሡ ፡ የዳዊት ፡ ዘመኖች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፡ በል ። እንበለን ፡ ለኒህ ፡ ለዘጠኙ ፡ አፍራሽና ፡ አሉታ ፡ ስታደርግ ፡ እስከኹን ፡ በተነገሩቱ ፡ ቅጽሎች ፡ ኢን ፡ ጨምር ። ይህም ፡ አበ ፡ ሥጋን ፡ አዳም ፡ ኢስቁለ ፡ አምላክ ፤ አምላክ ፡ ያለርሱ ፡ ያልተሰቀለ ፡ አዳም ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ፡ በቀሩትም ፡ ኢን ፡ እየጨመርኽ ፡ እንዲህ ፡ አግባ ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ የውስጠ ፡ ዘ ፡ ጠባይ ፡ በሳቢና ፡ በተሳቢ ፡ በሙሻዘር ፡ ክፍል ፡ ተመልከት ።

፶፱ ፡ የቦታ ፡ የጊዜ ፡ የልክ ፡ አገባቦች ፥ የነዚህ ፡ የሦስቱ ፡ በዕድ ፡ ቅጽልነት ፡ አገባቦች ፡ እንደ ፡ ግልጠ ፡ ዘ ፡ ባለቤትን ፥ እናቅጽ ፡ ተሳቢን ፡ ያሳያሉና ፤ ስለዚህ ፡ ነው ። የቦታ ፡ አገባቦች ፡ ወንሰግድ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ቆመ ፡ እግረ ፡ እግዚእነ ። መካን ፡ ኀበ ፡ ይትገበር ፡ መንገለ ፡ ይትገበር ፡ ውእደ ፡ ይትገበር ፡ መሢዕተ ፡ ቅዳሴ ፡ ቅዱስ ፡ ውእቱ ። በምድረ ፡ በድው ፡ ኀበ ፡ አልቦ ፡ ዕፀ ፡ ወማይ ። የጊዜ ፡ አገባቦች ፡ ተዘርዉ ፡ ሐዋርያት ፡ በዕለተ ፡ አመ ፡ ተእኀዘ ፡ እግዚእነ ። ይመጽእ ፡ መዋዕል ፡ አመ ፡ ይብሉ ፡ ብፁዓት ፡ መካናት ። የልክ ፡ አገባቦች ፡ ሲቀጸሉ ፡ ከኢንዝ ፡ ጥሬ ፡ ተቈጥረው ፡ እንደ ፡ ተነገሩት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አነጋገር ፡ የላቸውም ። የቦታና ፡ የጊዜ ፡ አገባቦች ፡ ባለቤታቸውን ፡ የሚመስሉ ፡ በዝርዝር ፡ (በቱ ፡ ባቲ) ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ፡ ይህም ፡ እስካኹን ፡ በተነገሩቱ ፡ ይታወቃል ። በባለቤትና ፡ በቅጽል ፡ መከከል ፡ ከባለቤቱ ፡ ዘርፍና ፡ ከዘርፉ ፡ ቅጽል ፡ በቀር ፡ በዕድ ፡ ቃል ፡ አይገባም ፤ ይህም ፡ አምላክ ፡ ሰማይ ፡ ምጡቅ ፡ ሕያው ፡ ማለቱን ፡ አምላክ ፡ ሕያው ፡ ዘሰማይ ፡ ወይም ፡ ተወሰነት ፡ ሃይማኖት ፡ በጉባኤ ፡ ርትዕት ፡ አለማለቱን ፡ ያሳያል ። ከንቀጽ ፡ ወዲያም ፡ ቅጽል ፡ እንደዚሁ ፡ ይፈረቅቃል ፤ ይኸውም ፡ ዮሐንስ ፡ ሰበከ ፡ ወንጌላዊ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፷ ፡ የበቂና ፡ ያጻፋም ፡ ነገር ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ቅጽል ፡ ኹሉ ፡ ባለቤት ፡ ሲቀር ፡ በባለቤት ፡ ፈንታ ፡ በቂ ፡ ተጠያቂ ፥ ወይም ፡ ወኪል ፡ ባለቤት ፡ አከል ፡ መኾኑ ፡ ካኹን ፡ ቀደም ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ተነግሯል ፡ (ቍ፴፩) ። በበቂነቱም ፡ ተሳቢና ፡ ዘርፍ ፡ ይኾናል ፤ ቅጽልም ፡ ይቀጸልለታል ። ተሳቢ ፥ ምንተ ፡ ይመስል ፡ ዘአጥመቀ ፡ በማይ ፤ ዜነውዎ ፡ ለዮሐንስ ፡ ዘትሬእዩ ፡ ወዘትሰምዑ ። ዘርፍ ፥ ወአንተኒ ፡ ሕፃን ፡ ነቢየ ፡ ልዑል ፡ ትሰመይ ፡ ተጠምቀ ፡ ሰማያዊ ፡ በእደ ፡ ምድራዊ ። ቅጽል ፥ ቅዱስ ፡ ኀያል ፡ ናዝራዊ ፡ ቅዱስ ። ዐጸፋ ፡ የሚኾኑ ፡ ግን ፡ ፬ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ ደቂቅ ፡ ቅጽልና ፡ ዝርዝር ።

፺፬ ፡ ከ፲፫ ፡ መደብ ፡ ፬ቱ ፡ ሩቆች ፡ እነውእቱ ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፡ መኾናቸው ፡ በልታየ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ሲቀጸሉና ፡ ሲታጸፉም ፡ በማድረግ ፡ ተደራጊ ፣ በማስደረግ ፡ አስደራጊ ፣ ተደራጊ ፣ በማደራረግ ፡ ተደራራጊ ፡ እየኾኑ ፡ ይነገራሉ ። ይህም ፡ ተፈነወ ፡ ኢዮአብ ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ኤዶምያስ ፣ ወውእቱ ፡ ቀተሎሙ ፡ አቅተሎሙ ፡ አስተቃተሎሙ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። አንቀጽና ፡ ዘርፍም ፡ ሲታጠፍ ፣ ሰበከ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ ብሎ ፣ አንቀጹን ፡ ወበውእቱ ፡ (ስብከት) ፡ ወይም ፡ ወቦቱ ፡ ተሰብሐ ፡ ዘርፉንም ፡ ውእቱኒ ፡ (ክርስቶስ) ፡ ገብረ ፡ ሎቱ ፡ መንክራተ ፡ ይላል ። ተሳቢም ፡ ኹኖ ፡ በተደራጊነት ፡ ሲነገር ፣ ውእተ ፡ ይእተ ፣ ወይም ፡ በወራሹ ፡ ኪያሁ ፡ ኪያሃ ፡ ያሰኛል ። ቅጽልም ፡ ቢኾን ፡ ዐጸፋነት ፡ አይቀርበትም ፤ ወትቤሎ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ሀበኒ ፡ እምውእቱ ፡ ማይ ። ብቻውን ፡ ሲነገር ፡ በቅጽልነቱ ፡ በቂ ፣ በደቂቅነቱ ፡ ዐጸፋ ፤ ከባለቤት ፡ ጋራም ፡ ሲነገር ፡ ጭብጥ ፡ ወይም ፡ ፍሉጥ ፡ ቅጽል ፡ ይባላል ። አንተኑ ፡ ስምዖን ፡ ወልደ ፡ ዮና ፤ አንተኬ ፡ ትሰመይ ፡ ኬፋ ። አንቲኒ ፡ ዓዲ ፡ እምሰአልኪዮ ። አንትሙ ፡ ዕደው ፡ አክብሩ ፡ አንስቲያክሙ ፡ እስመ ፡ እማንቱሂ ፡ ይወርሳ ፡ ክብረ ። ወከማሁ ፡ አንትንሂ ፡ አንስት ። አነ ፡ ዮሐንስ ፡ እኁክሙ ። ንሕነ ፡ አግብርቲከ ፡ ንሴብሐከ ።

፺፭ ፡ የዘ ፡ እንተ ፡ እለም ፡ ደቂቆች ፡ እነዝኩ ፡ ዝክቱ ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፡ መኾናቸው ፡ እንዳራቱ ፡ ቅርቦች ፡ በታየ ፡ ነገር ፡ ሲገቡ ፡ ነው ፤ ምስጢራቸው ፡ እማሬ ፡ ነውና ። ሞተኑ ፡ ዝኩ ፡ ሕፃን ፤ ዳኅንኑ ፡ ዝስኩ ፡ አቡክሙ ፤ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ዝክቱ ፤ ወዝክቲ ፡ ዝንቲ ። ዝ ፡ ዝንቱ ፡ የቅርብ ፡ ቅርብ ፡ ዝኩ ፡ ዝክቱ ፡ የቅርብ ፡ ሩቅ ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ዝኩ ፡ ዝንቱ ፡ ዝኩ ፡ ዘንተ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፣ ውእቱ ፡ ደብር ፡ ርኢ ፡ ውእተ ፡ ደብረ ፡ ይላል ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ውእቱ ፡ የሚቀጸለው ፡ ወይም ፡ የሚያጽፈው ፡ ባለቤት ፡ ባይን ፡ የማይታይ ፡ የሩቅ ፡ ሩቅ ፡ ስውርና ፡ ድብቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባይን ፡ ቀምሎ ፡ በጣት ፡ ጠንቍሎ ፡ የሚያዩትና ፡ የሚያሳዩት ፡ ነገር ፡ አይዶለም ።

፺፮ ፡ ውእቱ ፡ ኪያሁ ፡ ለሊሁ ፡ እነዚህ ፫ቱ ፡ ሲቀጸሉ ፡ ነገር ፡ ለማጽናት ፡ ይደጋግማሉ ፡ ውእቱ ፡ ሰማያዊ ፡ ወውእቱ ፡ ምድራዊ ፤ አንተ ፡ ሐማሚ ፡ ወመዋቲ ፡ ዘከመ ፡ ዕሬናከ ፡ ምስሌነ ፡ ወአንተ ፡ ኢሐማሚ ፡ ወኢመዋቲ ፡ ዘከመ ፡ ዕሬናከ ፡ ምስለ ፡ አብ ። ኪያከ ፡ አበ ፡ ኪያከ ፡ መጋቤ ፡ ወኪያከ ፡ ረዳኤ ። ለሊሁ ፡ ካህን ፡ ወለሊሁ ፡ በግዕ ፡ ወለሊሁ ፡ ምሥዋዕ ። ሲያጸፉም ፡ መልኑ ፡ ጴጥሮስ ፡ መጥባሕተ ፡ ኀጺን ፤ ወይእቲ ፡ ከነፎ ፡ ለእዝን ። ዘእንተ ፡ ርእሱ ፡ በግዕት ፡ ዕድሜ ፡ አኀጸረ ፤ ወኪያሃ ፡ በገነት ፡ ሰወረ ። ሰበኬ ፡ ብርሃን ፡ ዮሐንስ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ ወለሊሁ ፡ ኢኮነ ፡ ብርሃን ። መሀረ ፡ ክርስቶስ ፡ መጥምቀ ፡ ርእስ ፡ እንዘ ፡ ለሊሁ ፡ ይሜጡ ፡ ርእሶ ፡ ያሰኛሉ ። ለሊሁ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ውእቱ ፡ በባለቤት ፡ በዘርፍ ፡ በተሳቢ ፡ ዐጸፋ ፡ ይነገራል ፤ በባለቤት ፣ አብ ፡ ፈነወ ፡ ወልዶ ፡ ለከዊነ ፡ ሰብእ ፡ ወለሊሁ ፡ ኢተፈነወ ። ተፈነወ ፡ ወልዱ ፡ ለአብ ፡ ለከዊነ ፡ ሰብእ ፡ እንዘ ፡ ኢሐዱ ፡ ምስሌሁ ፤ ወለሊሁሰ ፡ ኢኮነ ፡ ሰብአ ። በተሳቢ ፣ አብ ፡ ፈነዎ ፡ ለወልዱ ፡ ወለሊሁ ፡ ሰምዐ ፡ ወተአዘዘ ።

፺፯ ፡ ነቲሉ ፡ ደምላይና ፡ ጠቅላይ ፡ የአኃዝ ፡ ጥሬ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለብዙም ፡ ለጥቂትም ፡ በጠቅላይነት ፡ ይቀጸላል ፡ ካንድ ፡ የወጣ ፡ ፪ም ፡ ፫ም ፡ ነቲሉ ፡ ይባላል ። ነቲሉ ፡

ፍጥረት ፥ ኵሉ ፡ ዓለም ፥ ኵሉ ፡ ትውልድ ፡ ወተሀውከት ፡ ኵላ ፡ ሀገር ፤ አንተ ፡ ወኵሉ ፡ ቤትከ ። ሲበቃም ፡ ኵሉ ፡ ዐረየ ፤ ኵሉ ፡ ይኄሊ ፡ ትከዘ ፡ ርእሱ ፤ ወኵሉ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ ይበሊ ። ሲያጥፍም ፡ በሩቅ ፥ እመኒ ፡ ኵሎሙ ፡ ዐለዉከ ። በቅርብም ፡ ተሰብሕክሙ ፡ አ ፡ ሐዋርያት ፡ በስቢከ ፡ ወንጌል ፡ ወኵልክሙ ፡ ሰማዕት ፡ ክንክሙ ፡ ይላል ። በሕቲቱና ፡ ዕሩቁ ፡ ለባለቤት ፡ ሲቀርቡ ፡ ቅጽል ፥ ከባለቤት ፡ ሲርቁ ፡ ተሳቢ ፡ ይኾናሉ ፤ ዐጸፋነት ፡ ግን ፡ የላቸውም ፤ ከባለቤትም ፡ ባይርቁ ፡ አፈታታቸው ፡ ከተለየ ፡ ተሳቢ ፡ እንጂ ፡ ቅጽል ፡ አይኾኑም ። ቅጽል ፥ አከ ፡ በእንተ ፡ እሉ ፡ በሕቲቶሙ ፡ ዘእስእል ፤ ኢይከውን ፡ ሥጋ ፡ በሕቲቱ ፡ መድኀኒተ ። ተጠምቀ ፡ በማይ ፡ ዕሩቁ ፡ ኢትስተይ ፡ ማየ ፡ ዕሩቆ ። ተሳቢ ፥ ኢይከውን ፡ ሥጋ ፡ መድኀኒተ ፡ በሕቲቶ ፤ ወአሦጡ ፡ ቀዛውተ፡ሀሙ ፡ ዕሩቆ ፡ ኢትቁም ፡ ዕሩቀከ ።

፺፰ ፡ ክንቱ ፡ ቅጽልና ፡ በቂ ፡ ይኾናል ፤ ቅጽል ፥ ክንቱ ፡ ንዋይ ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡ ኢምንት ፡ ለአጽድቆ ፡ ሕልም ፡ ነገሮሙ ፡ ክንቱ ። በቂ ፥ እመ ፡ ኢጻመውከ ፡ በርትዕ ፡ ትረክብ ፡ ክንቶ ፤ እመ ፡ ኢኀደጉ ፡ ክንቶሆሙ ፡ (ጣዖታቸውን) ። ተሳቢም ፡ ሲኾን ፥ ትንብር ፡ ምድር ፡ ክንቱታ ፡ ክንቱ ፡ ኹና ፡ ያሰኛል ። ርእስ ፡ (ርእሱ ፡ ሳ ፡ ሰሙ ፡ ሶን ፡ ስከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ) ፡ ርስ ፡ ራስ ፡ ባለቤት ፥ መክብበ ፡ ሕዋሳት ። ሲዘረዘርም ፡ ፍችው ፡ እንደ ፡ ውእቱና ፡ እንደ ፡ ለሊሁ ፡ ነው ፤ ለሊሁ ፡ ለነውእቱ ፡ እንዲቀጸል ፥ ይህም ፥ ውእቱ ፡ ርእሱ ፡ ይእቲ ፡ ርእሳ ፡ አንተ ፡ ርእስከ ፤ ሲፈታም ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ባለቤቱ ፥ አንተ ፡ ራስኽ ፡ ባለቤትኽ ፡ እያሰኘ ፡ እስከ ፡ ንሕነ ፡ ላሉት ፡ ይቀጸላል ። ለሌላ ፡ ስም ፡ ግን ፡ ዘርፍ ፡ ሳይገዛ ፡ አይቀጸልም ፡ ይህም ፥ እብን ፡ ርእስ ፡ ማእዘንት ፤ ኢጲስቆጶስ ፡ ርእሰ ፡ ክህናት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ የተደራጊ ፡ ተሳቢና ፡ ዐጸፋ ፡ ዘርፍ ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፥ ባለቤት ፡ አይኾንም ። ለሊከኑ ፡ ትንእድ ፡ ርእሰከ ፤ ክርስቶስኒ ፡ አኮ ፡ ርእሰ ፡ ዘንእደ ። ዘርፍ ፡ ሲኾን ፥ ትከዘ ፡ ርእሱ ፤ ምስማከ ፡ ርእሱ ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲጨምር ፥ እድለወ ፡ ለርእሱ ፤ ዘመከረ ፡ ብኪ ፡ መከረ ፡ በርእሱ ፤ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ፡ ይላል ።

## ዝርዝር ።

፺፱ ፡ የዝርዝር ፡ ጠባይ ፡ ከአናቅጽ ፡ ጋራ ፡ ባ፩ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፯ኛና ፡ በ፱ኛ ፡ ዕርከን ፡ ተነግሯል ። ጥሬ ፡ ኹኖ ፡ ነበር ፡ ኹኖ ፡ አገባብም ፡ ኹኖ ፡ ባ፲ ፡ ባ፲ ፡ መደብ ፡ በዘመድ ፡ በባዕድ ፡ የሚዘረዝር ፡ ቃል ፡ ኹሉም ፡ ደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ተብሏል ። ስለ ፡ ንኡሳንም ፡ አናቅጽ ፡ ንኡስ ፡ ርባታ ፡ ይባላል ። ዘመድና ፡ ባዕድ ፡ ዝርዝሮች ፡ ብእሲታ ፡ ብእሲሁ ፥ ዛቲ ፡ ብእሲት ፡ ዝኩ ፡ ብእሲ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እየገቡ ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፡ ይኾናሉ ፡ ሲፈቱም ፡ ይቺ ፡ ሴት ፡ ያ ፡ ሰው ፥ ወይም ፡ ሴትዮዋ ፡ ሰውዮው ፡ ያሰኛሉ ። ጥሬ ፡ ከማእዝ ፡ በቀር ፡ በ፯ቱ ፡ ኹሉ ፡ ይጨርሳል ፤ በካዕብ ፡ የሚጨርስ ፡ ጥሬ ፡ ዝርዝሩ ፡ እንደ ፡ ክንቱ ፡ ነው ፡ (ክንቶሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ን ፡ ክንቱከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ን ፡ የ ፡ ነ) ። በሣልስ ፡ በራብዕ ፡ በኃምስ ፡ በሳብዕ ፡ የሚጨርስም ፡ እንደዚሁ ፡ በባዕድ ፡ ይዘረዝራል ፡ ብእሲ ፡ ብእሲሁ ፥ ደብተራ ፡ ደብተራሁ ፥ ቅዳሴ ፡ ቅዳሴሁ ፥ መሰንቆ ፡ መሰንቆሁ ። በሳ

ድስ፡ የሚፈጸርስ፡ ግን፡ በዘመድ፡ በባዕድ፡ ይዘረዝራል፤ ብእሲት፡ ቱ፥እም፡ ሙ፥ ውሉድ፡ ዱ፥ደቅ፡ ቂ፥አዕይንት፡ ቱ፡ ቲሁ፥እርድእት፡ ቱ፡ ቲሁ፥እርዳእ፡ኢ፡ኢሁ። አብ፡ አቡ፡ አቡሁ። እድ፡ እዱ፡ እዴሁ። ምግባር፡ ሩ፡ሪሁ። አገባቦችም፡ዘርና፡ነባር፡ ስለ፡ ኾኑ፡ በዘመድ፡ በባዕድ፡ ይዘረዘራሉ፤ ተውላጥ፡ ጡ፡ ጣ፤ ኀበ፡ኀቤሁ፡ ሃ። በጭራሽም፡ ዝርዝር፡ የማያስገቡ፡ አሉ፡ (ዕር፲፫፡ ቍ፡፻፱)።

፺፫፡ ዝርዝር፡ ዐጥፎና፡ጠቅሶ፡ የሚያሳየው፡ ፬፡ ነገር፡ ነው፤ ባለቤትና፡ ተሳቢ፡ ዘርፍና፡ ደቂቅ፡ አገባብ። ያንቀጽና፡ የደቂቅ፡ አገባብ፡ ዝርዝር፡ ባለቤትን፡ ሲያሳይ፡ ቀተለ፡ ቀቲለከ፡ በእንቲአሃ፡ ምስሌሆሙ፡ ብሎ፥ ውእቱ፡ አንተ፡ ይእቲ፡ እሙንቱ፡ ማለትን፡ ያሰማል። የዐበይትና፡ የንኡሳት፡ አናቅጽ፡ ዝርዝር፡ በተደራጊና፡ባድራጊ፡ በተደራጊ፡ ተሳቢ፡ ፈንታ፡ ይነገራል። ፈጠሮ፡ እግዚአብሔር፡ ለአዳም፡ ወረሰዮ፡ እግዚእ፡ ፍጥረት። አምጽአ፡ ሰሎሞን፡ ለኪራም፡ ወአሕነጸ፡ መቅደሶ። እመ፡ ብዝኀ፡ ስቱ፡ ከነ፡ መስሐቱ፡ ኢንጎሥሥ፡ አብዝኀኖቶ። እምከመ፡ ከነ፡ እክል፡ ዘያጸንዕ፡ሰብእ፡ ርቱዕ፡ ብልዐቱ። የቀረውም፡ የግቢር፡ አንቀጽ፡ ዝርዝር፡ እንዲሁ፡ እየኾነ፡ በተሳቢ፡ ፈንታ፡ ይነገራል። የሐውልትና፡ የተግብሮ፡ የተጋብሮ፡ አንቀጽ፡ ዝርዝር፡ ባገባቦች፡ ፈንታ፡ ይነገራል፤ ይህም፡ ለእመ፡ መጽአ፡ ዘይከብረከ፡ ሲል፥ እምኔከ፤ ተአምኑ፡ ከመ፡ መጽሐፈ፡ ክርስቶስ፡ ትትለአከክሙ፡ ሲል፥ ለክሙ፡ በኀቤክሙ፤ ወተፈኒዎ፡ ኢየሱስ፡ ኀበ፡ ሄሮድስ፡ ተቃጸበ፡ ሲል፥ ቦቱ፡ በላዕሌሁ፡ እያሰኘ፡ ሌላውን፡ ኹሉ፡ ያሳያል። ያርእስትና፡ የውስጠ፡ ዘ፡ የሳቢ፡ ዘርም፡ ዝርዝር፡ እንዲሁ፡ ባገባብ፡ ፈንታ፡ ይነገራል።

፺፬፡ የተደራጊም፡ ዝርዝር፡ በምስለ፡ ፈንታ፡ ሲነገር፥ መኑ፡ የአምር፡ ኅሊናሁ፡ ለእግዚ፡ ወመኑ፡ ተማከሮ። በአርእስትም፥ ዐርከ፡ ዘእንበይነ፡ ከርሡ፥ ለእመ፡ አልብከ፡ ውእቱ፡ ይቀድም፡ ተቃትሎተከ፤ በውስጠ፡ ዘም፡ ይከውን፡ ተቃታሊከ፡ ያሰኛል። ዳግመኛም፡ ሣልስና፡ ሳድስ፡ ቅጽሎች፡ ሲዘረዘሩ፡ ተሳቢ፡ እየኾኑ፡ በቦዝና፡ በእንዘ፡ ዐማርኛ፡ ይፈታሉ። ይህም፥ ማእዜ፡ ርኢናከ፡ ርኁበከ፡ ወጽሙአከ፡ ወዕሩቀከ፡ ሲል፡ ተርበኽ፡ ተጠምተኽ፡ ታርዘኽ። ነቋረከ፡ ትባእ፡ ውስተ፡ ሕይወት፡ ሲል፥ ፩፡ ዐይና፡ ኹነኽ። ኀደግዋ፡ ለሀገር፡ ርኅታ፡ ከፍተው፥ ወይም፡ ክፍቷን። ኢትነዝም፡ ሕያም፡ በሕይወቱ፡ሳለ፥ደኅንኛውን፥ ወይም፡ ሳይሞት፡ ያሰኛል። ዝርዝሩ፡ ከዕብ፡ ሲኾን፡ ግን፡ ተሳቢና፡ ባለቤት፡ ያሳያል፡ ይህም፥ ሕያወ፡ ተንሥአ፡ ባለው፡ ይታወቃል፡ ሕያው፡ ኹኖ፡ ሲሉት፡ ተሳቢ፥ደኅኛው፡ ሲሉት፡ ባለቤት፡ ይኾናል።

፺፭፡ ያኄቱ፡ አዕማድ፡ አርእስትና፡ የውስጠ፡ ዘ፥የሳቢ፡ ዘርና፡ የጥሬ፡ ዝርዝር፡ በዘርፍ፡ ፈንታ፡ ይነገራል። ተፀቅፉ፡ ፈሪሳውያን፡ በረፈቀ፡ ክርስቶስ፡ ምስለ፡ ኃጥኣን፡ ወበበሊዖቱ፡ ምስሌሆሙ። ስንክሳር፡ ያየድዐነ፡ ዕለተ፡ ሞቶሙ፡ ለሰማዕት፡ ወዘከመ፡ እሮ፡ ተቀትሎቶሙ። እሙን፡ ይኩን፡ ዐርኩ፡ ለንጉሥ፡ ወጸሓፊሁኒ፡ መልእክታተ። ልዑላን፡ ፍጥረታተ፡ እግዚእ፡ እሙንቱ፥ መላእክት፡ ወጥቀ፡ ፍቁራኒሁ። ዕጹብ፡ ውእቱ፡ ንብረተ፡ ባሕታውን፡ ገዳመ፡ ወብልዐቶሙ፡ አቅጽለ። ወልደቱ፡ ተፀውቀ፡ እመንፈስ፡ ቅዱስ። ዕጹብ፡ ጥበበ፡ ሰሎሞን፡ ወመንክር፡ ግብሩ። ባለቤት፡ ለገን

ዘቡ ፡ ኹሉ ፡ ዘርፍ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በዘርፍ ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፡ ዝርዝር ፡ የባለቤትም ፡ ዐጸፋ ፡ ይኾናል ። ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወብዙኅ ፡ አኰቴቱ ፡ ሲል ፥ አኰቴተ ፡ ርእሱ ፡ ወይም ዚአሁ ፡ ይሰማበታል ። አርቆ ፡ ያዕቆብ ፡ ወዮሐንስ ፡ ኅደጉ ፡ አባሆሙ ፡ ወመሣግሪሆሙ ፡ ቢል ፡ አቅርቦም ፡ አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ፡ ቢል ፥ ዘርፉ ፡ ዘመድ ፡ ይኹን ፡ እንጂ ፡ ዐጸፋነቱ ፡ ከዘርፍ ፡ አይወጣም ።

፹፫ ፡ የግቢር ፡ አንቀጽ ፡ አርእስትና ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፡ ከተሳቢ ፡ ጋራ ፡ ሲናበቡ ፡ ዘርፋቸው ፡ በዘ ፡ እንተ ፡ እለ ፡ ይያያዛል ፡ አፍቅሮተ ፡ ሰብእ ፡ ዘእግዚአብሔር ። ከዘርፍም ፡ ጋራ ፡ ሲያያዙና ፡ ሲናበቡ ፡ ተሳቢያቸው ፡ ግእዝና ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕም ፡ ኹኖ ፡ ይነገራል ። ሲያያዝ ፥ በሊዖቱ ፡ ለብእሲ ፡ ኅብስተ ፡ ሲናበብ ፥ በሊዖተ ፡ ብእሲ ፡ ኅብስተ ፡ ይላል ፡ የቀሩትም ፡ እንደዚህ ፡ ናቸው ። በባለቤትና ፡ በተሳቢ ፡ በዘርፍ ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፡ ዝርዝር ፡ በውእቱና ፡ በኪያሁ ፡ ይቀናል ፡ ውእቱንና ፡ ኪያሁን ፡ እስከኹን ፡ በገባው ፡ አስተውል ። በሎ ፡ በሎቱ ፡ የሚቀኑም ፡ ወሀበንና ፡ መጠወን ፡ የመሰሉ ፡ አናቅጽ ፡ አሉ ፡ የግቢር ፡ አናቅጽ ፡ አርእስትና ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፡ ተዘርዝረውና ፡ ዐርፈው ፡ ሲስቡ ፡ በኪያሁ ፥ ሲናበቡ ፡ ግን ፡ በዚአሁ ፡ ይቀናሉ ። የቀሩትም ፡ አዕማድ ፡ ዝርዝሮች ፡ በሚሰማሟቸው ፡ ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ ይቀናሉ ። በዘርፍ ፡ ፈንታም ፡ የሚነገር ፡ ከነዚአሁ ፡ ተናበ ፡ በርሳቸው ፡ ይቀናል ።

፹፬ ፡ ከ፩ኛው ፡ ዐምድ ፡ ከቦዝ ፡ ስለ ፡ ባለቤትም ፡ ዐጸፋ ፡ ከሚነገሩ ፡ ዝርዝሮች ፡ በቀር ፡ የቀሩቱ ፡ በለ ፡ ይገጥማሉ ። የተጋጠሙቱ ፡ አናቅጽና ፡ ተሳቢ ፡ ቢኾኑ ፡ ሳቢና ፡ ተሳቢ ፡ ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ ቢኾኑ ፡ ግን ፡ ጠቃሽ ፡ ተጠቃሽ ፡ ይባላሉ ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ በለ ፡ ሲጋጠም ፡ እንደዚሁ ፡ ጠቃሽ ፡ ተጠቃሽ ፡ ነው ። በአንቀጽ ፡ ዝርዝር ፡ የሚሳብ ፡ ለ ፡ ሳቢው ፡ ገቢር ፡ አንቀጽ ፡ ቢኾን ፡ በልማዳዊ ፡ ዐማርኛ ፡ ይፈታል ፡ ተገብሮ ፡ ቢኾን ፡ ግን ፡ በሚሰማሙቱ ፡ ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ ይፈታል ። ተገሐሣ ፡ ለመዐት ፡ ከቍጣ ፡ ራቅ ። አፍጥን ፡ ተግሕሦታ ፡ ለእከይ ፡ ከክፋት ፡ ፈጥነኽ ፥ ወይም ፡ ቶሎ ፡ ብለኽ ፡ ራቅ ። ዮ ፡ ያ ፡ ዮሙ ፡ ዮን ፡ እኒህ ፡ ዝርዝሮች ፡ በለ ፡ በሎቱ ፡ በሚቀኑ ፡ አናቅጽ ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ እየተጨመሩ ፡ በኪያሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፡ ፈንታ ፡ ይነገራሉ ፤ ስማቸውም ፡ ድርብ ፡ ዝርዝር ፡ ይባላል ። ሀበኒዮ ፥ ሀበሙያ ፥ ጸግወኒያ ፡ ሀበኒዮሙ ፥ ዘወሀበኒዮን ።

፹፭ ፡ የአኀዝ ፡ ዝርዝር ፥ የጅምላው ፡ በበታው ፡ ተነግሯል ፡ (ቍ፻፳፪) ፡ የተራውም ፡ ይህ ፡ ነው ። ቀዳሚሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፡ ቀዳሚከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ ። ቀዳሚቱ ፡ ታ ፡ ቶሙ ፡ ቶን ፡ ቀዳሚትከ ፡ ኪ ። ዳግሙ ፡ ዳግምቱ ፡ ሣልሱ ፡ ሣልስቱ ፡ እያሰኘ ፡ እስከ ፡ ዓሥር ፡ ዓሥርት ፡ ይዘረዘራል ። ዝርዝሩም ፡ ለአካል ፡ ለነገር ፡ ለጊዜ ፡ ለክፍል ፡ ይኾናል ፡ ለአካል ፡ ሲኾን ፥ ወዕአ ፡ ካልኡ ። ለነገር ፥ ሣልስከ ፡ ዝንቱ ። ለጊዜ ፥ ሣልሰሙ ፡ ዮም ። ለክፍል ፥ ሣልስትኪ ፡ በብድብድ ፡ ወበረኀብ ፥ ወሣልስትኪ ፡ በኩናት ። የኹሉም ፡ ዝርዝር ፡ በበታው ፡ ተነግሯል ፡ (ቍ፻፴፫) ።

## ፮ኛ ፡ ክፍል ።

ጸዋትወ ፡ አገባብ ፥ የዘርና ፡ የነባር ፡ ሕንባብ ፥ ወይም ፡ ያገባቦች ፡ አገባብና ፡ ፍች ፥ ፫ኛውን ፡ ክፍል ፡ መልሶ ፡ እየዘረዘረ ፡ የሚተች ። አገባብ ፡ ሲባል ፡ ኹሉም ፡ የገ ርዋን ፡ ቃላት ፡ ሰብሳቢ ፡ ነው ፡ በተለየ ፡ ግን ፡ ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ በአናቅጽ ፡ ብቻ ፥ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ በአናቅጽና ፡ በቅጽል ፥ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ በጥሬ ፡ ወይም ፡ በብትን ፡ ይገባል ፡ ብትንና ፡ ጥሬ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ነው ።

## ፲፱ኛ ፡ ዕርከን ።

### ዐበይት ፡ አገባቦች ።

፷፯ ፡ እስመ ፡ ና ፡ ስለ ፡ እንደ ፡ ይኾናል ። ና ፡ ሲኾን ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ በዘ ንድና ፡ በነባር ፡ አንቀጽ ፡ በጽድቅ ፡ ባሉታ ፡ ይገባል ፡ በኋላ ፡ ኹና ፡ የፊቱን ፥ በፊትም ፡ ኹኖ ፡ የኋላውን ፡ ያስረዳል ። በኀላፊ ፥ ኢያምሥጠ ፡ አዳም ፡ እምነትነኒሁ ፡ ለእግዚአብ ሔር ፥ እስመ ፡ በልዐ ፡ እምዕፅ ፡ ዘኢአዘዘ ፡ ይብልዖ ። ወይም ፥ እስመ ፡ ኢዐቀበ ፡ ትእዛዘ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተወክፈ ፡ አዳም ፡ በድልወት ፡ ፍትሐ ፡ ሞተ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ እም እግዚኡ ። በትንቢት ፡ ሲገባ ፥ ሰማዕት ፡ ኢይፈርሁ ፡ ሞተ ፡ ሥጋ ፤ እስመ ፡ ይሬእይዋ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ በዐይን ፡ ተስፋ ። በዘንድ ፡ ሲገባ ፡ በነባር ፡ ይፈታል ፤ ይህም ፡ ጻድቃን ፡ ይብልዎ ፡ ለክርስቶስ ፡ እንዘ ፡ ያመጽእ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መከራ ፡ ሥጋ ፡ ኑር ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ገዘ ፡ መከራ ፡ ሕይወተ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ሲል ፥ ይህ ፡ መ ከራ ፡ የነፍሳቸው ፡ ሕይወት ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ (እንዲኾን ፡ ሊኾን) ፡ ነውና ፡ ያሰኛል ። በነባር ፡ ሲገባ ፥ ውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ይትዔገሡ ፡ መከራ ፡ እ ስመ ፡ ውእቱ ፡ አርአያሆሙ ። ወይም ፡ እስመ ፡ አከ ፡ ዘቲ ፡ ዓለም ፡ ዘትነብር ፡ ለዓለም ፡ ይሬእይዋ ፡ ጻድቃን ፡ ከመ ፡ እዳው ። እስመ ፡ ና ፡ በተባለበት ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ይሰማማ ዋል ፡ በተለየ ፡ ግን ፡ ስለና ፡ እንደ ፡ ሲኾን ፡ በኀላፊና ፡ በነባር ፡ ይገባል ። ይህም ፡ ተሠ ገወ ፡ ቃል ፥ እስመ ፡ ተዋረደ ፡ አዳም ። አዳም ፡ ስለ ፡ ተዋረደ ። እሙን ፡ ነገር ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ መጽአ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፤ እንደ ፡ መጣ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። አምጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ወርቀ ፡ እስመ ፡ ንጉሥ ፡ ውእቱ ፡ ሲል ፥ ንጉሥ ፡ ነውና ፥ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ተብሎ ፡ በሦስቱም ፡ ይፈታል ። አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ ፬ኛ ፡ ብሎ ፡ ይኾናል ፡ ይላሉ ፡ በስለና ፡ በና ፡ በ፪ቱ ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፡ ትርፍ ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ መደበኛ ፡ አይደለም ። በሦስቱ ፡ ግን ፥ ምእተ ፡ ምክዕቢተ ፡ የዐስዮሙ ፡ ክርስቶስ ፡ ለጻ ድቃኒሁ ፡ እስመ ፡ በእንቲኣሁ ፡ ተወክፉ ፡ መከራ ፡ ተመንደቡሂ ፡ ወሐሙ ፡ ዓዳ ፡ ሰ ቀሉ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ምስለ ፡ ፍትወት ፡ እያሰኘ ፡ በዋዌ ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ አንቀጽ ፡ ይወርዳል ፡ እስከ ፡ ፫ም ፡ ማለት ፡ የሰዋስው ፡ እንጂ ፡ የመጽሐፍ ፡ አይደለም ። እስመ ፡ እንደ ፡ ተ ብሎ ፡ መፈታቱ ፡ በከመ ፡ ቦታ ፡ እየገባ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ነው ። ዳእሙ ፡ በባሕቱ ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ ብቻ ፡ ተብሎ ፡ እንዲፈታ ። ንኡስ ፡ አገባብም ፡ ሲኾን ፡ በኀላፊና ፡ በትን ቢት ፡ በነባር ፡ አንቀጽ ፡ እየገባ ፡ እነ ፡ ቢያ ፡ ይኾናል ፡ ምስጢሩም ፡ ደስታና ፡ ሐዘን ፡

አንክሮ ፡ ነው ። እስመ ፡ ሖረ ፡ ኼደ ፡ እኮ ፥ ኼደ ፡ ቢያ ። እስመ ፡ የሐውር ፡ ዝኒ ፡ ከማሁ ። እስመ ፡ ርኢክኒሁ ፡ አመንክኒ ፡ አይተኸ ፡ እኮ ፥ አይተኸ ፡ ቢያ ። በነባርም ፡ እስመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ አንከ ፡ ሥሪፀ ፡ ዜና ፡ ሲል ፡ እንዲሁ ፡ ይፈታል ።

፺፯ ፡ አኮኑ ፡ ዐቢይ ፡ አገባብ ።　　አኮኑ ፡ በገባብነቱ ፡ አስረጅ ፡ ነውና ፥ እንደ ፡ እስመ ፡ በኀላፊ ፡ በትንቢት ፡ በነባር ፡ አንቀጽ ፡ እየገባ ፡ ና ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ። ፪ኛም ፡ እስመ ፡ ና ፡ በተባለበት ፡ ስለኝ ፡ እንዲደርብ ፥ አኮኑም ፡ በገባብነቱ ፡ ና ፡ ሲባል ፥ በንቀ ጽነቱ ፡ የጥያቄ ፡ አገባብ ፡ ኑ ፡ ሁ ፡ ስላለበት ፡ ነውና ፡ እይዶለምን ፡ ተብሎ ፡ በ፪ ፡ ይፈ ታል ። ይህም ፡ ገደፎሙኑ ፡ እግዚ ፡ ለሕዝቡ ፥ ሐሰ ፡ እኮኑ ፡ አነ ፡ እስራኤላዊ ። አኮኑ ፡ በፋሲካነ ፡ ተሰቅለ ፡ ክርስቶስ ። አኮሁ ፡ ነፍስ ፡ ተዐቢ ፡ እምሲሲት ፡ በለው ፡ ይታወ ቃል ፡ አኮኑ ፡ አገባብ ፡ መባሉ ፥ የኋሊትም ፡ ተሰቅለ ፡ አኮኑ ፡ እያለ ፡ ማሰሪያ ፡ ማስ ጣሉ ፡ በሰዋስው ፡ እንጂ ፥ በመጽሐፍ ፡ አይዶለም ፡ በመጽሐፍስ ፡ ከኑ ፡ በቀር ፡ አኮ ፡ አገባብ ፡ ተብሎ ፡ አይጠራም ። ያንቀጽነቱንም ፡ አሉታና ፡ አፈታት ፡ በደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ተመልከት ፡ (ቍ፺፫) ።　　አምጣነ ፡ ደግሞ ፡ ቅጽል ፡ ሲኾን ፡ ባገባብነቱ ፡ ና ፡ ይኾ ናል ፡ ይኸውም ፡ በሰዋስውና ፡ በቅኔ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በመጽሐፍ ፡ እንደ ፡ አኮኑ ፡ ነው ። እስመ ፡ አኮኑ ፡ አምጣነ ፡ እነዚህ ፡ ፫ቱ ፡ ና ፡ ለመኾን ፡ በኀላፊና ፡ በነባር ፡ ሲገቡ ፡ በጽ ንዕ ፡ ይፈታሉ ፡ ይህም ፡ ቀንአ ፡ ሰይጣን ፡ ላዕለ ፡ አዳም ፡ እስመ ፡ አኮኑ ፡ አምጣነ ፡ እመ ፡ ዐቀበ ፡ ትእዛዘ ፡ ፈጣሪሁ ፡ ኢይመውት ፡ ለዓለም ፡ አይሞትም ፡ ነበርና ። ኢእም ንም ፡ አይሁድ ፡ ለዘዕዉሩ ፡ ተወልደ ፡ ከመ ፡ ተፈወሰ ፡ እስመ ፡ አኮኑ ፡ አምጣነ ፡ ዕዉር ፡ ውእቱ ፡ ዕውር ፡ ነበረና ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ።

፺፰ ፡ በእንተ ፡ በይነ ፡ እንበይነ ።　　እነዚህ ፡ ፫ቱ ፡ ዐበይት ፡ አገባቦች ፡ ሲኾኑ ፡ ዘን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ አድርገው ፡ በኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ እየገቡ ፡ ስለ ፡ ይኾናሉ ። ንወድሳ ፡ ለማ ርያም ፡ በእንተ ፡ ዘተወልደ ፡ እምኔሃ ፡ እግዚእነ ፡ ሞተ ፡ ክርስቶስ ፡ በይነ ፡ ዘሞተ ፡ እን በይነ ፡ ዘሞተ ፡ አዳም ። ምስጢራቸውም ፡ እንደ ፡ ከመ ፡ አንጻርነት ፡ ነው ። ደቂቅ ፡ አገ ባብም ፡ ሲኾኑ ፥ በእንተ ፡ ስለ ፡ በ ፡ ይኾናል ፡ ስለ ፡ የበጎ ፥ በ ፡ የክፉ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ ነገር ፡ በእንተ ፡ ይሁዳ ፡ ወበእንተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በለው ፡ ይታወቃል ፡ ስለ ፡ ይሁዳና ፡ ስለየሩሳሌም ፥ በይሁዳና ፡ በየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ማለት ፡ ነውና ። ን ፡ ሲኾን ፡ ደግሞ ፥ ደስ ፡ ይበለው ፡ ብሎ ፥ ደስ ፡ ይበለው ፡ ሲል ፡ ደስ ፡ አይበለው ፡ ብሎ ፥ ደስ ፡ አይበ ለው ፡ ሲል ፡ ይኾናል ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ በእንተ ፡ አዳም ፡ አዳምን ፡ ደስ ፡ ይበለው ፡ ብሎ ፡ እምአፈ ፡ ደቂቅ ፡ ወሕፃናት ፡ አስተዳሉከ ፡ ስብሐተ ፡ በእንተ ፡ ጸላኢ ፡ ዲያብ ሎስን ፡ ደስ ፡ አይበለው ፡ ብሎ ። ሲዘረዝርም ፥ በእንቲአሁ ፡ ሃ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የር ሱን ፡ ነገር ፥ በርሱ ፡ ላይ ፡ በርሱ ፡ ምክንያት ፡ እያሰኘ ፡ እንዳርእስቱ ፡ ይፈታል ። በይነ ፡ በ ፡ እያጋነነው ፡ ሳያጋንነውም ፥ እንበይነ ፡ ብቻውን ፡ ኹሉ ፡ ፪ቱም ፡ ስለ ፡ ይኾናሉ ። በበይነ ፡ ገነት ፥ በይነ ፡ ምንት ፥ እንበይነ ፡ ምጺት ።

፺፱ ፡ ህየንተ ፡ ተውላጠ ፡ ፍዳ ፡ በቀለ ።　　እነዚህ ፡ ፬ቱ ፡ ዐበይት ፡ አገባቦች ፡ ሲኾኑ ፥ ከበቀለ ፡ በቀር ፡ ፫ቱ ፡ ዘን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ አድርገው ፡ ህየንተና ፡ ፍዳ ፡ በኀላፊ ፥ ተውላጠ ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ እየገቡ ፡ ኹሉም ፡ ስለ ፡ ይኾናሉ ። ህየንት ፡ ዘገብሩ ፡

ግንፋለ ፡፡ ተውላጠ ፡ ዘይሴስይ ፡፡ ተወክፈ ፡ አዳም ፡ ፍትሐ ፡ ሞት ፡ ፍዳ ፡ ዘአበሰ ፡፡ በቀለ ፡ ደግሞ ፡ በቁም ፡ ቀሪነቱን ፡ ሳይለቅ ፡ ስለ ፥ እንደ ፡ ይኾናል ፤ ብፁዕ ፡ ዘይትቤቀለኪ ፡ በቀለ ፡ ተበቀልክነ ፤ ስለ ፡ ተበቀልሽን ፥ እንደ ፡ ተበቀልሽን ፡፡ ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾኑ ፡ ህየንተ ፡ ስለ ፥ ፈንታ ፥ እንደ ፡ ይኾናል ፤ በዋጋ ፡ በለውጥ ፡ በካሳ ፡ ይገባል ፡፡ ስለ ፡ ሲኾን ፥ ይመውት ፡ ህየንተ ፡ ሕዝብ ፡፡ ፈንታ ፥ ፈደዩኒ ፡ እኪተ ፡ ህየንተ ፡ ሠናይት ፡፡ ተቀንየ ፡ ያዕቆብ ፡ ህየንተ ፡ ራሔል ፡፡ እንደ ፡ ሲኾን ፥ አ ፡ እግዚአ ፡ አሕመልምል ፡ ሊተ ፡ ነፍስየ ፡ ህየንተ ፡ ዕፅ ፡ ትክልት ፡ ማእከለ ፡ ገነት ፡፡ ሲዘረዘርም ፡ ህየንቴሁ ፡ ሃ ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ያሰኛል ፡፡ ተውላጠም ፡ ለውጥነት ፡ ባለው ፡ በብትን ፡ እየገባ ፡ ስለ ፡ ይኾናል ፡ ተውላጠ ፡ ዝ ፥ ስለዚህ ፡፡ ሲዘረዘርም ፡ እንደ ፡ ጥሬነቱ ፡ ተውላጡ ፡ ጣ ፡ ብሎ ፡ ለውጡ ፡ ልዋጩ ፡ ያሰኛል ፡፡ ፍዳም ፡ በብትን ፡ ሲገባ ፡ ስለ ፡ ይኾናል ፤ ፍዳ ፡ ወይን ፡ ይስተይ ፡ ማየ ፡ ዝናም ፤ ስለ ፡ ወይን ፥ በወይን ፡ ብድር ፥ ወይም ፡ ፈንታ ፡፡

፫ ፡ ኀበ ፡ መንገለ ፤ ውእደ ፡፡ እነዚህ ፡ ፫ቱ ፡ ዐበይት ፡ አገባቦች ፡ ሲኾኑ ፡ ዘንድ ፡ የ ፡ ይኾናሉ ፡፡ ዘንድ ፡ ሲኾኑ ፡ በዘማች ፡ በነባር ፡ ያስረሉ ፤ ይህም ፡ ተመዊአቱ ፡ ለንጉሥ ፡ ይከውን ፥ ወይም ፡ ውእቱ ፡ ኀበ ፡ መንገለ ፡ ውእደ ፡ ኢፈድፈደ ፡ ሰራዊቱ ፡ ካልበዛ ፡ ዘንድ ፡ ይኾናል ፥ ወይም ፡ ነው ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ፡፡ የ ፡ ሲኾኑ ፡ ግን ፡ የቦታ ፡ ቅጽሎች ፡ ናቸውና ፤ ባ፬ኛ ፡ ክፍል ፡ ተነግረዋል ፡ (ቍ፲፲፪) ፡፡ የቦታም ፡ ቅጽሎች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ፮ ፡ የቦታ ፡ አገባቦች ፡ ይሰማሟቸዋል ፡፡ ፩ኛ ፤ ኀበ ፡ መንገለ ፡ እንተ ፡ ውስተ ፡ ለ ፡ ወደ ፡ ሲኾኑ ፥ ውእደ ፥ ወደ ፡ ለመባል ፡ መደበኛ ፡ አገባብ ፡ ነውና ፡፡ ፪ኛ ፤ እንተ ፡ በ ፡ ሲኾን ፡፡ ፫ኛ ፤ በ ፡ በቁም ፡ ቀሬ ፡ ሲኾን ፡፡ ፬ኛ ፤ እም ፡ መነሻ ፡ ሲኾን ፡፡ ፭ኛ ፤ እስከ ፡ መድረሻ ፡ ሲኾን ፤ የ ፡ ለሚኾን ፡ አገባብ ፡ እነዚህ ፡ ፮ቱ ፡ እየተሰማሙት ፡ ሲነገር ፡ ፍችው ፡ ይበዘበዛል ፡፡ ይህም ፥ የሐውሩ ፡ አግብርት ፡ እምኀበ ፡ ሀለዉ ፡ መንገለ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፥ ውእደ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፥ እንተ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፥ ውስተ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፥ ለኀበ ፡ ሀሎ ፥ እስከ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ እግዚኦሙ ፤ ባሮች ፡ ከሉበት ፡ ጌታቸው ፡ ወዳ ፥ እስከለበት ፡ ይኼዳሉ ፡፡ ይኄልዉ ፡ አግብርት ፡ እንተ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፥ ቡኀበ ፡ ሀሎ ፡ እግዚአሙ ፤ ባሮች ፡ ጌታቸው ፡ ባለበት ፡ ይኖራሉ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ፡፡ ዳግመኛም ፡ በ ፡ እም ፡ እንተ ፡ በየምስጢራቸው ፡ ሲሰማሙት ፥ አልቦ ፡ ቡኀበ ፡ ኢይከብር ፡ ነቢይ ፡ የማይከብርበት ፡፡ በ ፡ ብሔር ፡ እምኀበ ፡ ይወፅእ ፡ ብሩር ፤ የሚወጣበት ፡፡ ኢየአምር ፡ እንተ ፡ ኀበ ፡ ይመጽእ ፡ ኀጢአት ፡ የሚመጣበትን ፡ ያሰኛል ፡፡ የበን ፡ ዝርዝር ፡ በን ፡ ከን ፡ ወደን ፡ ማምጣታቸው ፡ የቦታ ፡ ቅጽሎች ፡ ሲኾኑ ፡ ነው ፤ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ቀደላ ፡፡ ኀበ ፡ ተለይቶ ፡ በትንቢትና ፡ በደገም ፡ ሲገባ ፥ ሲ ፡ ሲ ፡ ሳ ፡ ሳ ፡ ስ ፡ ስ ፡ እየ ፡ እየ ፡ እያሰኘ ፡ በእንዘ ፡ ዐማርኛ ፡ ይፈታል ፡ ሰሎሞን ፡ ኀበ ፡ ኀበ ፡ ይነውም ፡ ይከሥት ፡ ዐይኖ ፡ ሲ ፡ ሲ ፤ ኀበ ፡ ኀበ ፡ ይነቅህሰ ፡ ይከድኖ ፡፡ ማየ ፡ አይኅ ፡ እስከነ ፡ አርብዓ ፡ መዋዕል ፡ ኀበ ፡ ኀበ ፡ ይመልእ ፡ ሖረ ፡ እየ ፡ እየ ፡ ወእምድኅሬሁሰ ፡ ኀበ ፡ ኀበ ፡ ይነትግ ፡፡ ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾኑ ፡ ፫ቱ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፥ አጠገብ ፡ ይኾናሉ ፡፡ አሐውር ፡ ኀበ ፡ አብ ፤ ነበረ ፡ ኀበ ፡ ዐዘቅት ፡፡ ሖሩ ፡ መንገለ ፡ መስዕ ፤ ኢታቅሞ ፡ መንገሌከ ፡፡ እቱ ፡ ውእደ ፡ ሕዝብከ ፤ በውእደ ፡ ማየ ፡ ባሕር ፥ አጠገብ ፡፡ በተለየ ፡ ግን ፡ ኀበ ፡ በአካል ፡ ሲገባ ፡ ዘንድ ፤ መንገለ ፡ ወገን ፡ ይኾናል ፤ እንተ ፡

ሀለወት ፡ ኀበ ፡ አብ ። ኢኮነ ፡ አምላክ ፡ እመንግለ ፡ እሙ ፤ አላ ፡ እመንግለ ፡ አቡሁ ። ሲዘረዘሩም ፡ ኀቤሁ ፡ ሃ ፥ መንገሌሁ ፡ ሃ ፥ ውእዶሁ ፡ ሃ ፥ ወይም ፡ ውእዱ ፡ ዳ ፡ ያሰኛሉ ፤ ከነበና ፡ ከመንገለ ፡ በቀር ፡ የውእደ ፡ ዝርዝር ፡ አልተለመደም ።

፫፻፩ ፤ እንዘ ፤ ዐቢይ ፡ አገባብ ። ሲ ፡ ሳ ፡ ስ ፡ እየ ፡ ቀልታ ፡ ይኾናል ። ሲ ፡ ሳ ፡ ስ ፡ ሲኾን ፡ በነባር ፡ በዘማች ፡ ከዚያውም ፡ በትንቢት ፡ በጽድቅ ፡ ባሉታ ፡ ይገባል ፤ ከሀሉና ፡ ከሀለወ ፡ በቀር ፡ በትንቢት ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ በኀላፊ ፡ አይገባም ። ይህም ፥ እንዘ ፡ ይበልዑ ፡ ኢትበልዑ ፡ ንበልዕ ፤ ሲበሉ ፡ ሳትበሉ ፡ ስንበላ ። እንዘ ፡ ውእቱ ፤ ሲኾን ፡ ሲኖር ፡ ሳለ ። እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በ ፡ አልቦ ፡ አከ ፤ ሳለ ፡ ሳይኖር ፡ ሳይኾን ። ሖደ ፡ አድያመ ፡ ዮርዳኖስ ፡ እንዘ ፡ ይጸርሕ ፤ እየጮኸ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ቀልታም ፡ ሲኾን ፥ ሞተ ፡ እንዘ ፡ የሐምም ፥ ታሞ ፤ ተቀብረ ፡ እንዘ ፡ ይመውት ፥ ሙቶ ፡ ያሰኛል ። ሲ ፡ ስ ፡ እየ ፡ በሚኾንበት ፡ ቀልታነትን ፡ ይደርባል ፤ ይህም ፡ እንዘ ፡ ይበልዕ ፥ ሲበላ ፡ በልቶ ፤ እንዘ ፡ ትበልዕ ፥ ስትበላ ፡ በልተኸ ፤ ጸርሐ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፥ ሲል ፡ እያለ ፡ ብሎ ፡ ማስኘቱን ፡ ያሳያል ።

፫፻፪ ፤ መጠነ ፤ አምጣነ ፤ ዐቅመ ፤ ዐበይት ፡ አገባቦች ። ቅጽልነታቸው ፡ ባንደኛው ፡ ምዕራፍ ፡ መጨረሻ ፡ በ፪፻፩ ፡ ተነግሯል ። አገባብም ፡ ኹነው ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ ሲገቡ ፥ ያኽል ፡ ስለ ፡ እንደ ፡ ይኾናሉ ። ፫ቱ ፡ ኹሉ ፡ ጥሬ ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ፤ አምጣነም ፡ የመጠነ ፡ ብዥ ፡ ነው ፤ ዘይቤያቸው ፡ ልክ ፡ መጠን ፥ ፍቻቸው ፡ ያኽልና ፡ ስለ ፡ እንደ ፤ ምስጢራቸው ፡ ስፍርና ፡ ቍጥር ፡ ግምት ፡ ስለ ፡ ኸነ ፥ ልኩና ፡ መጠኑ ፡ ስፍሩና ፡ ቍጥሩ ፡ በታወቀና ፡ ባልተወቀ ፡ በውስጠ ፡ ብዙነት ፡ ይገባሉ ። በኀላፊ ፥ መጠነ ፡ ጻለይኩ ፡ በሕይወትየ ። በትንቢት ፥ አምጣነ ፡ ትበልዕዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ኅብዝት ፤ ይህን ፡ ኅብዝት ፡ የምትበሉት ፡ ያኽል ፥ ወይም ፡ በምትበሉት ፡ ልክ ፤ ስለምትበሉት ፥ እንደምትበሉት ፡ መጠን ፡ እያሰኘ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ዐቅመ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ኀደረ ፡ ፍቅረ ፡ ቃል ፡ ወሕይወቱ ፤ ያደረበት ፡ ያኽል ፥ በደረበት ፡ ልክ ፤ ስላደረበት ፡ እንዳደረበት ፡ መጠን ። በአንጻራቸውም ፡ ከማሁ ፡ ፈድፋደ ፡ ሲከተሉ ፤ በአምጣነ ፡ ይነፍኅ ፡ ነፋስ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ከማሁ ፡ ይፈደፍድ ፡ ጽንዖሙ ። አምጣነ ፡ ይከልአሙ ፡ ውእቱ ፡ ፈድፋደ ፡ ይነግሩ ፡ ሎቱ ፡ እያለ ፡ እንዲሁ ፡ ይፈታል ። አምጣነ ፡ ተለይቶ ፡ በእንዘ ፡ በታ ፡ እየገባ ፡ ሳ ፡ ይኾናል ፤ ይህም ፥ ወበሕቱ ፡ እብል ፡ አምጣነሰ ፡ ሕፃን ፡ ውእቱ ፥ ሕፃን ፡ ኹኖ ፡ ሳለ ። አምጣነ ፡ ሀሎ ፡ መርዓዊ ፡ ምስሌሆሙ ፥ ሳለ ። ኢይክል ፡ ሰብእ ፡ ሐይወ ፡ አምጣነ ፡ ኢይበልዕ ፡ ወኢይሰቲ ፤ ሳይበላ ፡ ሳይጠጣ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ና ፡ ሲኾን ፡ እስመ ፡ በገባበት ፡ ይገባል ፤ አገባቡም ፡ ከእስመና ፡ ከእኩኑ ፡ ጋራ ፡ ቀድሞ ፡ ተነግሯል ። መጠነ ፡ ደግሞ ፡ ተለይቶ ፡ የሩቁን ፡ በቅርብ ፡ የቅርቡን ፡ በሩቅ ፥ ያንዱን ፡ በብዙ ፡ የብዙውን ፡ ባንድ ፥ ዘርዝሮም ፡ ሳይዘረዝርም ፡ ውጥን ፡ ይጨርሳል ። የሩቁን ፡ በቅርብ ፡ ሲወጥን ፥ አ ፡ ዳዊት ፡ ነግሠ ፡ ሰሎሞን ፡ መጠነ ፡ አንተ ፡ ላዕለ ፡ እስራኤል ፤ አንተ ፡ የነገሥከውን ፡ ያኽል ። የቅርቡን ፡ በሩቅ ፡ ሲወጥን ፥ ሰሎሞን ፡ ነገሥከ ፡ መጠነ ፡ አቡከ ፡ ላዕለ ፡ እስራኤል ። በቀረውም ፡ ሰበከ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወንጌለ ፡ መጠነ ፡ ሙሴ ፡ ኦሪተ ። ኢትሬኢኑ ፡ መጠነ ፡ ይበልዕ ፡ ወይሰቲ ፤ እንዲበላና ፡ እንዲጠጣ ፡ እያሰኘ ፡ ከመ ፡ በገባበት ፡ ይገ

ባል ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾኑ ፡ ከመ ፡ በገባበት ፡ እየገቡ ፡ እንደ ፡ ይኾናሉ ፤ ባፈታ
ታቸውም ፡ ምስጢራቸውን ፡ አይለቁም ።

፲፫ ፤ ከመ ፤ ዐቢይ ፡ አገባብ ። እንደ ፡ ዳ ፡ ዲ ፡ ድ ፡ ይኾናል ። በ ፡ ዘ ፡ እያጋን
ኑት ፡ ሳያጋንኑትም ፥ ከማሁ ፡ አንጻር ፡ እየኾነው ፡ ሳይኾነውም ፡ በኅላፊና ፡ በትን
ቢት ፡ ይገባል ፤ ባንጻር ፡ ባብነት ፡ ይነገራል ። ባንጻር ፥ በከመ ፡ ይምሕር ፡ አብ ፡ ውሉዶ ፡
ከማሁ ፡ ይምሕሮሙ ፤ ወበከመ ፡ ይርሕቅ ፡ ሠርቅ ፡ እምዐረብ ፡ አርሐቀ ፡ እምኔነ ። ባብ
ነት ፥ ተሰቅሉ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወእንድርያስ ፥ በከመ ፡ ተሰቅለ ፡ ክርስቶስ ፡ ይላል ። ውጥን ፡
ጨራሽም ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ መጠን ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ በገባበት ፡ ይገባል ። ፲፬ኛም ፡ ከመ ፡ ዘ ፡
እንተ ፡ እለ ፡ በገቡበት ፡ አንቀጽና ፡ ጥሬ ፡ ሲገባ ፡ መሰለ ፡ ይኾናል ፤ ለምንት ፡ ትኄልዩ ፡
ከመ ፡ ዘኢመጻእኩ ፤ ያልመጣኹ ፡ ይመስል ፥ እንዳልመጣኹ ፡ ኹሉ ፤ ከመ ፡ ዘሰራቂኑ ፥
ሌባ ፡ ይመስል ፥ እንደ ፡ ሌባ ፡ ኹሉ ። በግእዝም ፡ ቦታ ፡ እየገባ ፡ መሰለን ፡ ሲያስከትል ፡
ን ፡ ይኾናል ፤ ይህም ፡ ከመ ፡ ሰዶም ፡ እምከነ ፥ ወከመ ፡ ገሞራ ፡ እመሰልነ ፡ (ገሞራን ፡
በመሰልን) ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ። ሲዘረዘርም ፡ አልቦ ፡ ዘከማሁ ፡ ሃ ፤ ርሱን ፡ የሚመ
ስል ፥ ወይም ፡ የመሰለ ፥ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ ሰኛል ። ፲፭ኛም ፤ ከመ ፥ መሐለ ፡ ነበበ ፡
ዖቀ ፡ ጠየቀ ፡ ርእየ ፡ ሰምዐ ፡ ኀለየ ፡ በሚሉና ፡ ይህን ፡ በመሰሉ ፡ አናቅጽ ፡ ሲሳብ ፡
ነገር ፡ ኹኖ ፡ ማድረግ ፡ መደረግን ፡ ያሳያል ፡ እንጂ ፤ አንጻር ፡ አይኾንም ። ይህም ፥ ኢ
ሰማዕኪኑ ፡ ከመ ፡ ነግሠ ፡ አዶንያስ ። ይትፈጸም ፡ ዘተብህለ ፡ በነቢይ ፡ ከመ ፡ ናዝራዊ ፡
ይሰመይ ፡ ወልድየ ። በነባርም ፡ ወሰምዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ እክል ፡ በብሔረ ፡ ግብጽ ።
ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ከመ ፡ መሬት ፡ ንሕነ ፡ እያሰኘ ፡ ተሳቢነቱን ፡ ያሳያል ። ተሰፈወና ፡
ተነበየ ፡ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ ሲስቡት ፡ ግን ፡ በትንቢት ፡ ብቻ ፡ ይገባል ፤ ተፈሥሐት ፡ ሳራ ፡
በልደተ ፡ ይሥሐቅ ፥ ወተሰፈወት ፡ ከመ ፡ ይልህቅ ። ተነበዩ ፡ ነቢያት ፡ ከመ ፡ ይትወ
ለድ ፡ ክርስቶስ ፥ ወከመ ፡ ይትቀተል ፡ ወይትነሣእ ፤ እንዲወለድ ፥ እንዲሞትና ፡ እንዲ
ነሣ ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ርኢ ፡ ዘከመ ፡ ይጽሕፍ ፥ ወለቡ ፡ ዘከመ ፡ ይነብብ ፥ ወስማዕ ፡
ዘከመ ፡ ያወሥእ ፡ እያለ ፡ ሲገባ ፥ አጣጣፉን ፡ አነጋገሩን ፡ አመላለሱን ፡ ተብሎ ፡ መፈ
ታት ፡ ያምርለታል ። ፲፮ኛም ፤ ሲነባበርና ፡ ሲደረደር ፡ በኅላፊና ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ፤
ሲነባበር ፡ ከመ ፡ ከመ ፡ ቀርበ ፥ ወከመ ፡ ከመ ፡ ይበጽሕ ፡ ጊዜሁ ፡ እያለ ፡ ፈጽሞ ፡ ያሰ
ኛል ። ሲደረደርም ፥ ነአምን ፡ ከመ ፡ ሐመ ፡ ወከመ ፡ ሞተ ፥ ከመሂ ፡ ተንሥአ ፡ ወከመ ፡
ዐርገ ፡ እያሰኘ ፡ በተሳቢነት ፡ ይነገራል ። በቅርብ ፡ ዐጸፋም ፡ ሲገባ ፥ ከመ ፡ ዝ ፡ ወከመ ፡
ዝ ፡ መከርኩ ፡ አነ ፤ እንዲህና ፡ እንዲህ ። ከመ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ግዒሮ ፡ ሞተ ፤ እንዲህ ፡ እን
ዲህ ፡ ብሎ ፥ ወይም ፡ ተናግሮ ፡ እያሰኘ ፡ ተሳቢነቱን ፡ ያሳያል ። ሠረዝም ፡ ሲኾን ፥ ሰሎ
ሞን ፡ ለመንግሥት ፡ ከመ ፡ ዳዊት ፥ ወመንግሥት ፡ ለዳዊት ፡ ከመ ፡ መንበር ፡ እያለ ፡ በነ
ባር ፡ ይገባል ። ከመ ፡ በዘንድ ፡ አንቀጽ ፡ ሲወድቅ ፡ አዳማቂ ፡ ኹኖ ፡ ይቀራል ፤ ከመ ፡
ይብጻሕ ፡ ዘተብህለ ፤ ይህም ፡ ይደርስ ፡ ዘንድ ፥ እንዲደርስ ፡ ሊደርስ ፡ ተብሎ ፡ ሲፈታ ፡
እንዲ ፡ ያሰኘው ፡ ጠባዩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከመ ፡ እንዳይዶለ ፡ አስተውል ። ደቂቅ ፡ አገ
ባብም ፡ ሲኾን ፡ በጥሬ ፡ በቅጽል ፡ በብትን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ እየገባ ፡ እንደ ፡ ይኾናል ፤ ምስ
ጢሩም ፡ አንጻርነት ፡ ነው ። ተቀሥፈ ፡ ከመ ፡ ገብር ፥ ወተስቅለ ፡ ከመ ፡ እቡስ ፤ ከመ ፡

በግዕ ፡ የዋህ ፥ ወከመ ፡ ላሕም ፡ ንጹሕ ፡ እያለ ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ። እንደ ፡ ቀድሞውም ፡ ሲነባበር ፡ አንዱ ፡ በስም ፡ ፪ኛው ፡ በነባር ፡ አንቀጽ ፡ ይወድቃል ፤ ይህም ፥ ሰማዕነ ፡ ኢያሱ ፡ ከመ ፡ ከመ ፡ ሙሴ ፡ በአሪት ፥ ወጳውሎስኒ ፡ ከመ ፡ ከመ ፡ ጴጥሮስ ፡ በወንጌል ፤ ኢያሱ ፡ በአሪት ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ሲደረደርም ፡ ከመ ፡ ዳዊት ፡ ወከመ ፡ ሰሎሞን ፡ ያሰኛል ። ሲዘረዘርም ፡ ከማሁ ፡ ሃ ፥ እንደ ፡ ርሱ ፡ ሏ ፡ እያሰኘ ፡ እስከሥር ፡ ይዘምታል ። ምፅትም ፡ ሲኾን ፡ እምአፍቀርኩ ፡ ይሙት ፥ ወይም ፡ እመ ፡ ይመውት ፡ ጻድቅ ፡ ከመ ፡ ኪሩብ ፡ በሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ይገባል ። መከታም ፡ ሲኾን ፥ እግዚአ ፡ ከመ ፡ ወልታ ፡ ሥሙር ፡ ከለልከነ ፥ ወከመ ፡ ደመና ፡ ሰወርከነ ፡ ያሰኛል ።

፫፻፬ ፤ በዘ ፤ እምዘ ፤ ዐበይት ፡ አገባቦች ።　በዘ ፥ ፍችው ፡ ገንዘብና ፡ ስለ ፥ እንደ ፡ ይኾናል ፤ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ። በት ፡ ተብሎ ፡ ሲፈታ ፡ ዘበቱ ፡ አንተ ፡ ብቱ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሲነገር ፡ ነውና ፤ በየወደቀበት ፡ በቂ ፡ ቅጽል ፡ እንጂ ፡ አገባብ ፡ አይኾንም ፤ በቂነቱም ፡ ለነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ። አገባብ ፡ ኹኖ ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ ሲገባም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ በኀላፊ ፥ ሰለጥኩ ፡ በዘአምጽአ ፡ ሊተ ፡ አፍሮዲጡ ፤ ባመጣልኝ ፡ ገንዘብ ። በዘወድአ ፡ ሞት ፡ ኵሎ ፤ ሞት ፡ ኹሉን ፡ በጨረሰ ፡ ገንዘብ ። በዘቀነዮሙ ፡ ሞት ፤ በገዛቸው ፡ ገንዘብ ። ይትዋረድ ፡ ብእሲ ፡ እኩይ ፡ በዘአስተዋረደ ፡ ሰብአ ፤ ባዋረደ ፡ ገንዘብ ፡ ሰላዋረደ ፡ እያሰኘ ፡ በኀላፊው ፡ ኹሉ ፡ ስለን ፡ ይደርባል ። በትንቢትም ፡ ወትሜህር ፡ በዘታስሕቶሙ ፡ ብሎ ፡ በምታስታቸው ፡ ገንዘብ ፡ ያሰኛል ። በኀላፊ ፡ ገብቶም ፡ እንደ ፡ ሲኾን ፡ ስልቱ ፡ ፪ ፡ ነው ፤ ፩ኛው ፡ የከመ ፥ ፪ኛው ፡ የበገዛ ፤ የከመ ፡ ሲኾን ፡ ወኮነ ፡ በዘአንተ ፡ አዘዝከ ፤ አንተ ፡ እንዳዘዝከው ፡ ኾነ ። የበገዛ ፡ ሲኾን ፥ እመ ፡ ኢረከብከ ፡ በዘበልዐ ፡ ኵሎ ፡ ቤል ፡ ንመውት ፤ ቤል ፡ ኹሉን ፡ እንደ ፡ በላ ፥ ወይም ፡ በልቶ ፡ ባታገኝ ፡ እንሞታለን ።　እምዘ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ በዘ ፡ ሲኾን ፡ አይገኝም ፤ ብቻ ፡ እም ፡ የወደቀበት ፡ ቅጽል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በኀላፊ ፡ ገብቶ ፡ ከ ፡ መኾኑን ፡ ሳይለቅ ፡ ዠምሮ ፡ በኋላ ፡ ይኾናል ፤ ምስጢሩ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። እምዘፀንሰት ፡ ኤልሳቤጥ ፥ ከፀነሰች ፡ ዠምሮ ። እምዘረወዩ ፡ አግማሊሁ ፤ ገመሎቹ ፡ ከጠጡ ፡ በኋላ ። በትንቢት ፡ ሲገባ ፡ ቅጽል ፡ ብቻ ፡ ኹኖ ፡ ይቀራል ። አብልዐኒ ፡ እምዘይበልዑ ፡ ወአስተየኒ ፡ እምዘይሰቲ ፤ ከሚበላው ፡ ከሚጠጣው ።

፫፻፭ ፤ አርአያ ፤ አምሳለ ፤ ሕገ ፤ ዐበይት ፡ አገባቦች ።　ሦስቱ ፡ ኹሉ ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ አንቀጽ ፡ እየገቡ ፡ እንደ ፡ ይኾናሉ ። ምስክሩን ፡ በተራ ፡ ተመልከት ። አርአያ ፡ ጾመ ፡ ሙሴ ፡ ጾመ ፡ ኢየሱስኒ ፤ አርአያ ፡ ይነውም ፡ ዘልፈ ፥ ወትሮ ፡ እንዲተኛ ። አምሳለ ፡ እሙንቱ ፡ ሶጥዎ ፡ ላዕሌነ ፥ ርሳቸው ፡ እንዳሳደዱብን ፤ አምሳለ ፡ ይፈቅድ ፡ ንጉሠ ፥ ማደን ፡ እንዲሻ ። ትፈጽም ፡ ሕገ ፡ ተጽሕፈ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ። ኢተአምሩኑ ፡ አንዊነ ፡ ሕገ ፡ ንነግረክሙ ፤ እንድንነግራችኹ ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾኑ ፥ አርአያ ፡ ከመዝ ፡ ሰረረ ። ይነቁ ፡ አምሳለ ፡ ዖፍ ። ሕገ ፡ ሰብእ ፡ እነብብ ፡ ሕገ ፡ ሰብእ ፡ አናሕሲ ፡ ለነ ፡ እያሰኙ ፡ እንደ ፡ ይኾናሉ ።

፫፻፮ ፤ እመ ፤ ሶበ ፤ ዐበይት ፡ አገባቦች ።　፪ቱም ፡ ውል ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ በነባር ፡ አንቀጽ ፡ እየገቡ ፡ ከ ፡ ካ ፡ ቢ ፡ ብ ፡ ባ ፡ ይኾናሉ ፤ ከ ፡ በኀላፊ ፡ በጽ

ድቅ፣ክ ፡ ባሉታ ፡ ባሥሩ ፡ ሰራዊት ፡ ይገባሉ ፤ እመ ፣ ለ ፡ እያጋነነው ፡ ሳያጋንነውም ፡ ሰበ ፡ ብቻውን ፡ ይነገራል ። ይህም ፣ እመ ፡ ቀተለ ፡ ሰበ ፡ ቀተሉ ፣ ከገደለ ፡ ከገደሉ ፤ ባሉታውም ፡ እመ ፡ ኢቀተለ ፡ ሰበ ፡ ኢቀተልከ ፣ ካልገደለ ፡ ካልገደልኽ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ቢ ፡ በሦስቱ ፡ ሩቆች ፣ ብ ፡ ባንዱ ፡ ቱ ፡ ሩቅና ፡ በ፪ቱ ፡ ቅርቦች ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ። ይህም ፣ እመ ፡ ይቀትል ፡ ሰበ ፡ ትቀትል ፣ ቢገድል ፡ ብትገድል ፤ ባሉታውም ፡ እመ ፡ ሰበ ፡ ኢይቀትል ፣ ባይገድል ፡ እያሰኘ ፡ ኹሉን ፡ ያሳያል ። ከ ፡ ቢ ፡ ብ ፡ የተባሉት ፡ ወደ ፡ ራብዕነት ፡ ተለውጠው ፡ ካ ፡ ባ ፡ መባላቸው ፡ በአ ፡ ምክንያት ፡ ነውና ፤ ካ ፡ ተለይቶ ፡ ዐማርኛው ፡ በአ ፡ በሚነሣ ፡ በጽድቅም ፡ በኀላፊ ፡ ብቻ ፡ ይገባል ። ይህም ፣ እመ ፡ ዖቀ ፡ ወአዖቀ ፣ ካወቀ ፡ ካሳወቀ ፤ ሰበ ፡ አምነ ፡ ወአእመነ ፣ ካመነ ፡ ካሳመነ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ የኀላፊውን ፡ በትንቢት ፡ ወሰበ ፡ እንዘ ፡ ዘበምድር ፡ እነግረክሙ ፡ ኢተአምኑኒ ፤ የትንቢቱንም ፡ በኀላፊ ፡ ለእመ ፡ ኵሉ ፡ ዓለመ ፡ ረብሐ ፡ እያለ ፡ አለመንገዱ ፡ ያገባል ፤ የመላሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። በነባሮችም ፡ ሲገቡ ፣ እመሰ ፡ ሰበሰ ፡ እምላክ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ እፎመ ፡ እምሐመ ፡ ሰበ ፡ ሰቀልዎ ፤ ወእመሂ ፡ ወሰበሂ ፡ ሰብእ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ እፎመ ፡ እምአድኀነ ፡ ፍጡራነ ፤ እምላክ ፡ ብቻ ፡ ቢኾን ፣ ሰውም ፡ ብቻ ፡ ቢኾን ፣ ወይም ፡ ከኾነ ። እመ ፡ አኮ ፡ ሰበ ፡ አኮ ፡ እግዚ ፡ ምስሌነ ፤ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ባይኾን ፣ ካልኾነ ። እመ ፡ ቦ ፡ ሰበ ፡ አልቦ ፤ ቢኖር ፡ ባይኖር ፣ ካለ ፡ ከሌለ ፡ ያሰኛል ። ዳግመኛም ፡ ጥያቄና ፡ አንክሮ ፡ ባለበት ፡ በጥርጥር ፡ ቃል ፡ ሲገቡ ፡ አንቀጻቸው ፡ ቦዝ ፡ እየኾነ ፡ እንደኾን ፡ ተብለው ፡ ይፈታሉ ፤ በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የጥያቄ ፡ አገባብ ፡ ሁ ፡ ትራስ ፡ ሲኾናቸው ፣ ምናልባት ፡ ማለትን ፡ ይጨምራሉ ። እመሰ ፡ ሰበሰ ፡ እኩየ ፡ ነበብኩ ፣ ክፉ ፡ ተናግሬ ፡ እንደኾን ። ይእዜ ፡ ያድኅኖ ፡ እመ ፡ ይፈቅዶ ፤ ይወደው ፡ እንደኾን ፣ ቢወደው ። እመሁ ፡ ሰበሁ ፡ የአምር ፡ በዓለ ፡ ቤት ፣ ምናልባት ፡ ቢያውቅ ፡ ያውቅ ፡ ቢኾን ። ለእመሁ ፡ ትትኤዘዘኒ ፡ በኵሉ ። እመሁ ፡ አንተ ፣ አው ፡ እመ ፡ አንተሁ ፡ ክርስቶስ ፡ ንግረነ ፡ ገሃደ ። ሦስተኛም ፡ እመ ፡ ተለይቶ ፡ የክፍል ፡ አገባቦች ፡ ሂ ፡ ኒ ፡ ትራስ ፡ ሲኾኑት ፣ ዐማርኛውን ፡ ሳይለቅ ፡ ምንም ፡ እያሰኘ ፡ እንደ ፡ እመሁ ፡ ትርፍ ፡ ዐማርኛ ፡ ይጨምራል ፤ ምስጢሩም ፡ አፍራሽነት ፡ ነው ። ይህም ፣ እመኒ ፡ ያበዝኅ ፡ ሰብእ ፡ ጥበበ ፡ ኢይክል ፡ ያእምር ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ። እመኒ ፡ ኰሎሙ ፡ የዐልዉከ ፡ አንሰ ፡ ኢየዐልወከ ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ። በአካል ፡ በነባር ፡ እየገባ ፡ ሲደጋገም ፡ ግን ፣ ዋዌ ፡ ኹኖ ፡ በቁሙ ፡ ይፈታል ፤ እመኒ ፡ አይሁዳዊ ፡ ወእመኒ ፡ አረማዊ ፣ እመሂ ፡ ጳውሎስ ፡ ወእመሂ ፡ አጵሎስ ፤ ቢኾን ። እመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፣ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ፤ እውነት ፡ ቢኾን ፡ እውነት ፣ ሐሰት ፡ ቢኾን ፡ ሐሰት ፤ ወይም ፡ ቢኖር ፡ አለ ፣ ባይኖር ፡ የለም ። በብትን ፡ ሲገባም ፡ እመሂ ፡ በባሕር ፡ ወእመሂ ፡ በአፍላግ ፣ እመሂ ፡ ሠርከ ፡ ወእመሂ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ። በፍጻሜ ፡ ቃልም ፡ እየገባ ፣ እመኒ ፡ ዐረጉ ፡ ወእመኒ ፡ ወረድኩ ፡ ቢል ፡ ፍችው ፡ አይለወጥም ። እመ ፣ በትንቢት ፡ በነባር ፡ ካልኾነ ፡ በኀላፊ ፡ ግብቶ ፡ ቢ ፡ ብ ፡ እንዳይኾን ፡ ካኹን ፡ በፊት ፡ ተነግሯልና ፤ እመኒ ፡ ዐረጉ ፡ ወወረድኩ ፡ ወእመኒ ፡ ነሣእኩ ፡ ክንፈ ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ። እመ ፡ አኮም ፡ እንደ ፡ እመኒ ፡ ሲደጋገምና ፡ ሲማፈር ፡ ፪ቱም ፡ ወይ ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ። እመ ፡ አኮ ፡ አንተ ፡ ኤልያስ ፣ ወእመ ፡ አኮ ፡ አነ ፡ ኤልዛቤል ፤ ወይ ፡ አንተ ፡ ኤልያስ ፡ ተብለኽ ፣ ወይም ፡ እኔ ፡ ኤልዛቤል ፡ ተብዬ ።

ኢይክል ፡ ገብር ፡ ተቀንዮ ፡ ለክልኤ ፡ አጋዕዝት ÷ እመ ፡ አኮ ፡ አሐደ ፡ ይጸልእ ፡ ወካ
ልአ ፡ ያፈቅር ÷ ወእመ ፡ አኮ ፡ ለአሐዱ ፡ ይትኤዘዝ ፡ ወለካልኡ ፡ የአቢ ፡ ያለውም ፡ እን
ዲሁ ፡ ይፈታል ። የእመና ፡ የሰበ ፡ አንድነት ፡ እስከዚህ ፡ ነው ፤ ሰበ ፡ ተለይቶ ፡ ጊዜ ፡
ሲኾን ፡ ግን ፡ ከወንድሞቹ ፡ ከጊዜ ፡ አገባቦች ፡ ጋራ ፡ ተባብሮ ፡ ተማፍሮ ፡ በጊዜነትና ፡
በቅጽልነት ፡ ይነገራል ።

፳፯ ፤ እመ ፤ ሰበ ፤ ጊዜ ፤ ዐበይት ፡ አገባቦች ። ጊዜ ፡ ሲ ፡ ስ ፡ ሳ ፡ የ ፡ ይኾናሉ ፤
በፈታታቸው ፡ ኹሉ ፡ የማድረጊያ ፡ አገባብ ፡ አይለያቸውም ። ቅጽልም ፡ ሲኾኑ ፡
የዘን ፡ ዐማርኛ ፡ የን ፡ የበን ፡ ዝርዝር ፡ ይዘው ፡ ሲፈቱ ፡ ዐዋጃቸው ፡ በቅጽሎች ፡ ተራ ፡
ተነግሯል ፤ ባ፩ኛ ፡ ክፍል ፡ (ቍ፻፲፯) ፡ ተመልከት ፤ ከዚያ ፡ የቀረውም ፡ አኹን ፡ ይነገራል ።
ጊዜ ፡ ሲኾኑ ፡ በኋላፊ ፡ ብቻ ፡ ይገባሉ ፤ ይህም ÷ ወእመ ፡ በጽሐ ፡ ወሰበ ፡ በጽሐ ፡ ወጊዜ ፡
በጽሐ ፡ ዕድሜሁ ፡ ፈነወ ፡ ወልዶ ፤ ቀጠሮው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ልጁን ፡ ላከ ፡ እያለ ፡ መኼ
ዱን ፡ ያሳያል ። በቅጽልነትም ፡ ሲፈታ ፡ ቀጠሮው ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ያሰኛል ። በት
ንቢትም ፡ ገብተው ፡ እንደዚሁ ፡ ሲፈቱ ፡ ቅጽሎች ÷ በእንዘ ፡ ዐማርኛ ፡ ሲ ፡ ስ ፡ ሳ ፡ ተብ
ለው ፡ ሲፈቱ ፡ አገባቦች ፡ ናቸው ፤ ምስጢራቸው ፡ ግን ፡ ከጊዜነቱ ፡ አይወጣም ። ይህም ፡
ወእመ ፡ ይመጽእ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ፤ እመ ፡ ሰበ ፡ ጊዜ ፡ ትመጽእ ፡ በመንግ
ሥትከ ፤ በሚመጣበት ፡ ጊዜ ፤ በምትመጣበት ፡ ጊዜ ÷ ቅጽል ። ሲመጣ ፡ ስትመጣ ÷
አገባብ ። ሳ ፡ ሲኾኑም ፡ በትንቢት ፡ አሉታ ፡ ይገባሉ ፤ እመ ፡ ሰበ ፡ ጊዜ ፡ ኢይትሜ
ሀሩ ፡ ሰዋስወ ፡ ተምህሮ ፡ ትርጓሜ ÷ ከመ ፡ እመ ፡ ሰበ ፡ ጊዜ ፡ ኢይትበጥሑ ፡ ተሐግሞ ፤
ሰዋስውን ፡ ሳይማሩ ፡ ትርጓሜን ፡ መማር ፡ ሳይበጡ ፡ እንደ ፡ መታገም ፡ ነው ። ደቂቅ ፡
አገባብም ፡ ሲኾኑ ፡ ባርእስትና ፡ በሳቢ ፡ ዘር ፡ በጥሬ ፡ በብትን ፡ ይገባሉ ፤ ይህም ÷ እመ ፡
ተሰቅሉቱ ፡ በሥጋ ÷ ሰበ ፡ ሑረቱ ፡ ወሰበ ፡ ግብአቱ ÷ ጊዜ ፡ ፀአተ ፡ ፍትሕ ፤ በፍርድ ፡
መውጣት ፡ ጊዜ ÷ ወይም ፡ ፍርድ ፡ በመውጣቱ ፡ ጊዜ ። እመ ፡ ሰበ ፡ ጊዜ ፡ ወርኅ ፡ ማእ
ረር ፤ በመከር ፡ ወራት ፡ ጊዜ ። በአካልም ፡ ሲገቡ ፡ እመ ፡ ሰበ ፡ ጊዜ ፡ ኤልያስ ፡ ወኤል
ሳዕ ፡ ያሰኛሉ ። እመ ፡ ተለይቶ ፡ በአኃዝና ፡ በጊዜ ፡ ጥሬዎች ፡ ሲገባ ፡ በ ፡ ይኾናል ፤
እመ ፡ አሚሩ ÷ እመ ፡ ሰኑዩ ፤ እመ ፡ ዕለተ ፡ ቀትል ÷ እመ ፡ ሰዓተ ፡ ሞት ። አሚሁ ፡ ሃ ÷
ሶቤሁ ፡ ሃ ÷ ጊዜሁ ፡ ሃ ፡ እያሰኙ ፡ እስከ፲ ፡ ይዘረዘራሉ ። ፫ ፡ አገባቦች ፡ ለ ፡ እም ፡ እስከ ፡
ይሰማሟቸዋል ። ለአሚሃ ፡ እምሶቤሃ ፡ እስከ ፡ ጊዜሃ ፤ ብቻቸውንም ፡ ሲፈቱ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያው ፡ ፈጥኖ ፡ ቶሎ ፡ ያሰኛሉ ፤ ምስጢራቸው ፡ ዐጸፋነት ፡ ነው ፤ ዘይ
ቤያቸውም ፡ ጊዜው ፡ ጊዜዋ ፡ ጊዜኽ ፡ ያሰኛል ። ዝርዝሩም ፡ ቀርቶ ፡ አሚ ፡ ሶቤ ፡ ኹ
ነው ፡ ሲገኙ ፡ ጊዜ ፡ ተብለው ፡ ይፈታሉ ፤ ዘአሚ ፡ ልደቱ ፡ ሰገዱ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ። ይት
ፌሥሑ ፡ ጻድቃን ፡ አሚ ፡ ሞቶሙ ። ወይእተ ፡ ሶቤ ፡ አእመሮሙ ፡ እንዲል ። ዓመተ ፡
መዋዕለ ፡ ዕለተ ፡ ሰዓ ፡ ሰዓተ ፡ ቅጽሎችና ፡ ዐበይት ፡ አገባቦች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ከነ
እመ ፡ ጋራ ፡ ባ፲፩ኛ ፡ ዕርከን ፡ (ቍ፻፲፮) ፡ ተነግሯል ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾኑ ፡ በን ፡
እየያዙ ፡ ሳይዙም ፡ ገብተው ፡ ጊዜ ፡ ይኾናሉ ፤ ባማርኛቸውም ፡ ቢፈቱ ፡ ምስጢራ
ቸው ፡ ከጊዜ ፡ አይወጣም ። ሲገቡም ፤ በመዋዕለ ፡ ሰላም ፤ በሰላም ፡ ወራት ÷ ወይም ፡
ጊዜ ። በዕለተ ፡ ቀትል ፤ በሰልፍ ፡ ቀን ። ሰዓ ፡ ጽባሕ ÷ በሰዓተ ፡ ጽባሕ ፤ ማለዳ ፡ በጧት ።
ዓመተ ፡ ግን ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ኹኖ ፡ አይገኝም ።

፫፰ ፤ እስከ ፤ ዐቢይ ፡ አገባብ ። እስከ ፡ በቁሙ ፣ በትርፍ ፡ ዐማርኛ ፡ ድረስ ፡ ይኾ ናል ፤ አገባብነቱም ፡ የቦታ ፡ የጊዜ ፡ የልክ ፡ ነው ። ፍጻሜ ፡ ባለው ፡ በሌለውም ፡ ነገር ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ፤ ፍጻሜ ፡ ባለው ፡ ሲገባ ፡ ብዛትና ፡ ጽናት ፡ ከልክ ፡ ማለፍን ፡ ያሳያል ። ፍጻሜም ፡ በሌለው ፡ ሲገባ ፡ አካቶ ፡ ፈጽሞ ፡ ጭራሽ ፡ ያሰኛል ። በር ፡ ከፋቾ ቹም ፡ ነ ፡ አመ ፡ ሶበ ፡ ጊዜ ፡ ናቸው ፤ በር ፡ ከፋችም ፡ ሳይዝ ፡ ብቻውን ፡ ይገባል ፤ ሲፈ ታም ፡ በ፲ሩ ፡ ሰራዊት ፡ በኀላፊ ፡ እስከ ፣ በትንቢት ፡ በ፫ቱ ፡ ሰራዊት ፡ እስኪ ፣ በ፯ቱ ፡ እስክ ፡ ያሰኛል ። ባሉታም ፡ ሲገባ ፡ ዐማርኛው ፡ በአ ፡ የሚነሣ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ባሥሩ ፡ ኹሉ ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ እስካ ፡ ይኾናል ። ፍጻሜ ፡ ባለው ፡ ሲገባ ፣ አኢወለደት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ እስከ ፡ ልህቀት ፣ እስከነ ፡ ትልህቅ ፣ እስከ ፡ አመ ፡ ሶበ ፡ ጊዜ ፡ ትልህቅ ። ፍጻሜ ፡ በሌለው ፡ ሲገባ ፣ አኢወለደት ፡ ሜልኮል ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ሞተት ። አኢተመይጠ ፡ ቋዕ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ የብሰ ፡ ማይ ። ብዛትን ፡ ሲያሳይ ፣ ተጋብኡ ፡ ሕዝብ ፡ ኀቤሁ ፡ እስከ ፡ ይመልኢ ፡ መርሕበ ፤ ወይም ፡ እስከ ፡ ኢያገምሮሙ ፡ መካን ። ጥናትንም ፡ ሲያሳይ ፣ ወኢ ይትመየጥ ፡ እስከ ፡ አጠፍኦሙ ። እሌሉ ፡ ምስሌክሙ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕል ፡ እስከ ፡ ኅል ቀተ ፡ ዓለም ። እስከ ፡ ሶበ ፡ ኵሉ ፡ ይትገበር ፡ ወይከውን ፡ ይላል ። ደቂቅ ፡ አገባ ብም ፡ ሲኾን ፡ መድረሻና ፡ ፍጻሜ ፡ እየኾነ ፡ በቦታ ፡ በጊዜ ፡ በልክና ፡ በክፍል ፡ ይገ ባል ። በቦታ ፣ ወምኵናኒከኢ ፡ እስከ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ። በጊዜ ፣ ፀለወኢ ፡ እስከ ፡ ዮም ፡ ወእስከ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ። በልክና ፡ በክፍል ፣ ወበጽሐ ፡ እስከ ፡ ዓሥር ። ከማሁ ፡ ገብረ ፡ እስከ ፡ ሰብዕ ። መሐለ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ እስከ ፡ መንፈቀ ፡ መንግሥቱ ፡ ያሰኛል ። ለ ፡ በገ ባበት ፡ በግብር ፡ በነገር ፡ ሲገባ ፣ በጽሐ ፡ ይበጽሕን ፡ ያመጣል ፤ ይህም ፣ በፍቅር ፡ ተስ ሕበ ፡ እግዚእነ ፡ እስከ ፡ ለሞት ፤ ለሞት ፡ እስኪደርስ ። ተጻብኡ ፡ እስከ ፡ ለበትር ፤ እስ ኪደርሱ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። በቀሩትም ፡ በቦታና ፡ በጊዜ ፡ ጥሬዎች ፡ በኹሉ ፡ ይገ ባል ፤ በማእዚም ፣ ሲገባ ፡ በቁም ፡ ቀሪነቱን ፡ ሳይለቅ ፡ መመኘት ፡ መሰልቸት ፡ ይኾናል ። መመኘት ፣ ተመየጥ ፡ እግዚኦ ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ፤ መሰልቸት ፣ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ እሄሉ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ሥጋ ፡ ዘቱሱሕ ፡ ምስሌየ ። በር ፡ ከፋችም ፡ ይዞ ፡ ሲገባ ፣ እምሥራቀ ፡ ፀሓይ ፡ እስከነ ፡ ዐረብ ፣ ወይም ፡ እስከ ፡ ኀበ ፡ ምዕራቢሃ ፡ ይላል ። ሲዘረዘርም ፣ እስከ ኔሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፤ እስከኔከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፤ ኔየ ፡ ኔነ ፡ እያሰኘ ፣ እስከ ፡ ርሱ ፡ እስ ክንተ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ።

፫፱ ፤ ድኅረ ፤ ዐቢይ ፡ አገባብ ። በኀላፊ ፡ ብቻ ፡ በጊዜ ፡ በቦታ ፡ እየገባ ፡ ኋላ ፡ ይኾናል ፤ እም ፡ እያዳመቀው ፡ ሳያዳምቀውም ፡ ይነገራል ። የጊዜና ፡ የቦታ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በፈታቱ ፡ ኹሉ ፡ ከና ፡ በ ፡ አይለዩትም ፤ ምስጢሩም ፡ ከፋይነት ፡ ነው ። ይህም ፣ ድኅረ ፡ ተንሥአ ፡ እምድኅረ ፡ ተንሥአ ፡ እሙታን ፡ አስተርአዮን ፡ ቀዲሙ ፡ ለአንስት ፤ ከተነሣ ፡ በኋላ ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾን ፡ በቦታ ፡ በጊዜ ፡ ይገባል ፤ በቦታ ፣ ድኅረ ፡ ማዕጾ ፣ እምድኅረ ፡ ማዕጾ ፤ ከመዝጊያ ፡ በኋላ ። አንተም ፡ ሲሰማማው ፡ መጽአት ፡ እንተ ፡ ድኅሬሁ ፡ እያለ ፡ በስተኋላው ፡ በስተዠርባው ፡ ያሰኛል ። በጊ ዜም ፡ ሲገባ ፣ ወድኅረ ፡ ኵሎሙ ፡ አስተርአየኒ ፡ ሊተ ። ሰሎሞን ፡ ነግሠ ፡ እምድኅረ ፡ ዳዊት ፤ ወእምድኅሬሁኒ ፡ ሮብዓም ፡ ይላል ። ድኅረ ፡ ሕቅ ፣ እምድኅረ ፡ ሕቅ ፡ እያለ ፡

ሲገባም ፥ ጥቂት ፡ ቈይቶ ፥ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ያሰኛል ። ሲዘረዘርም ፡ ድኅሬሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፤ ድኅሬከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ሬየ ፡ ነ ፡ እያሰኘ ፥ ኋላው ፡ በኋላው ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ይኾናል ።

፺ ፤ ዘ ፡ እንተ ፡ እለ ፤ ዐበይት ፡ አገባቦች ። ቅጽልነታቸው ፡ በ፴ኛ ፡ ክፍል ፡ በ፲፫ ፡ ቍ ፡ ተነግሯል ፤ አኹንም ፡ በዚህ ፡ ቅጽልነት ፡ ሳይቀር ፡ በየብትኑ ፡ በሚገቡ ፡ በደቂቆች ፡ ላይ ፡ እየገቡ ፡ ኀላፊና ፡ ትንቢት ፡ ነባር ፡ አንቀጽም ፡ ያመጣሉ ። ይህም ፡ ብርሃን ፡ ዘእምብርሃን ፡ ሲል ፥ ተረክበ ፡ ይትረከብ ። እግዚእ ፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ሲል ፥ ደለወ ፡ ይደሉ ። ኵሉ ፡ ዘበሰማይ ፡ ወዘበምድር ፡ ሲል ፥ ሀለወ ፡ ይሄሉ ። ጳውሎስ ፡ ዘእስከ ፡ አድማስ ፡ ሲል ፥ በጽሐ ፡ ይበጽሕ ፡ ማሰኘታቸውን ፡ ያሳያል ። ዘዲበ ፡ ዘላዕለ ፡ ዘላዕሌሆሙ ፥ ዘታሕተ ፡ ዘእምታሕተ ፥ ዘቅድመ ፥ ዘውስተ ፡ እያሉ ፡ በቀሩትም ፡ ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ እየገቡ ፡ ሀለወ ፡ ይሄሉን ፥ ወይም ፡ ውእቱን ፡ ያመጣሉ ። እንተና ፡ እለንም ፡ እንደ ፡ ዘ ፡ አሰማምተኽ ፡ አግባ ። ዚአሁ ፡ ሃ ፥ እንቲአሁ ፡ ሃ ፥ እሊአሁ ፡ ሃ ፡ እያሰኙ ፡ እስካሥር ፡ ሲዘረዘሩ ፡ ግን ፡ የርሱ ፡ የርሷ ፡ ያሰኛሉና ፤ ስማቸው ፡ ዘርፍ ፡ አያያዥ ፡ እንጂ ፡ ቅጽል ፡ አይባልም ። በዚአሁ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ዘዚአሁ ፡ እያለ ፡ ፪ኛ ፡ ዘ ፡ ሲጨመር ፡ ውእቱን ፡ ያመጣልና ፥ ቅጽሎች ፡ ናቸው ፤ ሲፈቱም ፡ የርሱ ፡ የኾነ ፥ ወይም ፡ የሚኾን ፡ ያሰኛሉ ። ኵሉ ፡ ዘዚአየ ፡ ዚአከ ፡ ውእቱ ፤ ወዘዚአከኒ ፡ ዚአየ ፡ ውእቱ ፤ የኔ ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ያንተ ፡ ነው ፤ ያንተም ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ የኔ ፡ ነው ። ዚአከ ፡ ቃለ ፡ ዚአከ ፡ ጥበበ ፡ ያለውም ፡ አንቀጽ ፡ የሚያመጣ ፡ ፪ኛ ፡ ዘ ፡ ስለሌለው ፥ ቃለከ ፡ ጥበበከ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፡ የዘርፍ ፡ ደፌ ፡ እንጂ ፡ ቅጽል ፡ አይባልም ። በዘ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በቀሩትም ፡ እንተ ፡ እንቲአሃ ፡ አመት ፥ እለ ፡ እሊአሁ ፡ አግብርት ፡ እያሰኘ ፥ ይእቲንና ፡ እሙንቱን ፡ ያመጣል ። ዳግመኛም ፡ ዘ ፡ ተለይቶ ፡ ጥያቄን ፡ እየተከተለ ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ ሲገባ ፡ የጥያቄውን ፡ ምክንያት ፡ ይገልጣል ፤ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ዘአፍጠንከ ፡ ረኪበ ፥ ወልድየ ። ምንተ ፡ ከንኪ ፡ ባሕር ፡ ዘጕየይኪ ፡ ወአንተኒ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ዘገባእከ ፡ ድኅሬከ ። እስመም ፡ ዘ ፡ በገባበት ፡ እየገባ ፡ ሊነገር ፡ ይቻላል ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾኑ ፡ ልዩነት ፡ አላቸው ። ዘ ፡ ደቂቅ ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ በበና ፡ እንደ ፡ ለለ ፥ ዘዘ ፡ እያሰኘ ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ በዚአሁ ፡ ዝርዝሮች ፡ ላይ ፡ ሲገባ ፡ እየ ፥ ወይም ፡ እየ ፡ እየ ፡ ይኾናል ፤ ምስጢሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ ነው ፤ ወአኀዙ ፡ ይንብቡ ፡ ዘዘ ፡ ዚአሆሙ ፤ እየራሳቸው ፡ እያንዳንዳቸው ፤ በደጊመ ፡ ቃልም ፡ እየራስ ፡ እየራሳቸው ፡ ያሰኛል ። ይፈልጠሙ ፡ ዘዘ ፡ ዚአሆሙ ፡ አስተራሕቅዎሙ ፡ ዘዘ ፡ ዚአሆሙ ፤ እየብቻቸው ። ወዘዘ ፡ ዚአሁ ፡ ጸጋሁ ፤ ስጦታው ፡ እየቅሉ ፡ ነው ፤ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ እያሰኘ ፡ እንዳመጣጡ ፡ ይፈታል ። በር ፡ ከፋችና ፡ አጋናኝ ፡ መኾኑም ፡ በያገባቡ ፡ ተነግሯል ። እንተ ፥ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ሲኾን ፡ እየ ፡ በ ፡ ወደ ፡ ለ ፡ ን ፡ ይኾናል ፤ እየ ፡ ሲኾን ፡ የሀበነ ፡ ምሕረቶ ፡ ወትረ ፡ እንተ ፡ ጽብሐት ፤ እየጧቱ ፡ እየለቱ ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ዘዘ ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፥ ጧት ፡ ጧት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ያሰኛል ፤ እንተ ፡ ጸብሐ ፡ ሲል ፡ ግን ፡ እየነጋ ፡ ያሰኛልና ፤ ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ነው ። በ ፡ ወደ ፡ ሲኾን ፡ በበታ ፡ ይገባል ፤ እንተ ፡ ክልእ ፡ ገጽ ። ወእንተ ፡ ክልእ ፡ ፍኖት ። ይሔውጺ ፡

እንተ ፡ መሳክው ፡ በ ። ፈነወ ፡ እደ፡ሁ ፡ እንተ ፡ ስቍረት ፡ ወደ ። ለ ፡ ን ፡ ሲኾን ፡ እንተ ፡ ባሕቲቱ ፡ ቃ ፡ ቶሙ ፡ ቶን ፡ እያለ ፡ በአካል ፡ ይገባል ። አገናኝም ፡ ሲኾን ፥ እንተ ፡ ሰበ ፡ ጸዋዕከዎ ፥ እንተ ፡ ጊዜ ፡ ተንሥአ ፡ እያለ ፡ ሰበንና ፡ ጊዜን ፡ ያዳምቃል ። እለም ፡ ደቂቅ ፡ ሲኾን ፡ በጥያቄና ፡ በተጸውዖ ፡ ስም ፡ እየገባ ፡ እነ ፡ ይኾናል ፤ ስሙም ፡ አብገር ፡ ይባላል ። እለ ፡ መኑ ፡ አንትሙ ። ወእምዝ ፡ ኀለፉ ፡ እለ ፡ ጳውሎስ ፡ እምነ ፡ ጳፉ ። ለጸዋዐ ፡ ኤልያስ ፡ ወሔኖክ ፡ እስከ ፡ በእለ ፡ ሔኖክ ፡ ያኀልፉ ፤ እነ ፡ ማን ፡ ናችኹ ፥ እነ ፡ ጳውሎስ ፥ በነሔኖክ ።

፹፩ ፤ አላ ፤ ዳእሙ ፤ ባሕቲ ፤ እንበለ ፤ ዐበይት ፡ አገባቦች ። አራቱ ፡ ኹሉ ፡ እንጂ ፡ ይኾናሉ ፤ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ባሕቱ ፡ በቀዳማይና ፡ በካልኣይ ፡ በሣልሳይ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባሉ ። አሉታውን ፡ በጽድቅ ፡ ይወጥናሉ ፤ ማሰሪያቸውም ፡ አኮ ፡ አልቦ ፡ ኢ ፡ ናቸው ፤ በነባር ፡ በዘማች ፡ በብትን ፡ ሰዋስው ፡ የሚገባ ፡ አገባብ ፡ በማሰሪያቸው ፡ ይገባል ። ይህም ፥ ሥ ቃየ ፡ ገሃነም ፡ አኮ ፡ ዘቦቱ ፡ ፍጻሜ ፤ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ባሕቱ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ፍጻሜ ። አልቦ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ምስጢር ፡ ዓቢእ ፡ እምቅዱሳን ፤ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ክሡት ፡ ሎሙ ፡ ኵሉ ። ኢሰዐረ ፡ እግዚእነ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፤ ባሕቱ ፡ ፈጸሞ ። ኢፈነወ ፡ አብ ፡ ወልዶ ፡ ለኵነኔ ፡ ዓለም ፤ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ባሕቱ ፡ ለሕይወተ ፡ ዓለም ። እንበለም ፡ ዘን ፡ አዳማቂና ፡ በር ፡ ከፋች ፡ አድርጎ ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ፤ በኀላፊ ፡ ኢያን ቀን ፡ አይሁድ ፡ ዕርፈቶሙ ፡ እምድኅረ ፡ ዐርብ ፥ ዘእንበለ ፡ ዘወሰኩ ። በትንቢትም ፡ ኢይመውት ፡ ዘእንበለ ፡ ዘአሐዩ ። መኑ ፡ ውእቱ ፡ ሐሳዊ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይክሕድ ፡ ወይብል ፡ እስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ኢኮነ ፡ መሲሐ ፡ ያሰኛል ። ዳግመኛም ፡ የጽድቁን ፡ ባሉታ ፡ እንዳናገሩ ፥ ያሉታውን ፡ በጽድቅ ፥ ያንዱን ፡ በብዙ ፥ የብዙውን ፡ ባንድ ፡ ያናግራሉ ፤ ውጥንም ፡ ይጨርሳሉ ። ያሉታውን ፡ በጽድቅ ፥ ኢክሕደ ፡ ጴጥሮስ ፡ አሚነ ፡ በክርስቶስ ፤ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ባሕቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘከሡተ ፡ ኪያሁ ፡ በተሰቅሎቱ ፡ ቍልቍሊተ ። በነባር ፡ አንቀጽም ፥ አኮ ፡ ዘሞተት ፡ ሕፃን ፤ አላ ፡ ትነውም ፡ ይላል ። ያንዱን ፡ በብዙ ፥ ጳውሎስ ፡ ሰበከ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፤ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ባሕቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘኢሰበኩ ፡ ሰዱቃውያን ። የብዙውን ፡ ባንድ ፥ ሐዋርያት ፡ ሰበኩ ፡ ወንጌለ ፤ አላ ፡ ይሁዳ ፡ ኢሰበከ ። ውጥንም ፡ ሲጨርሱ ፥ ተንሥአ ፡ እግዚእነ ፡ እምከርሠ ፡ መቃብር ፤ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ባሕቱ ፡ ይሁዳ ፡ እመቃብር ። እንበለም ፥ ወመዝራዕቶሙኒ ፡ ኢያድኅኖሙ ፡ ዘእንበለ ፡ የማንከ ፡ ወመዝራዕትከ ፡ እያሰኘ ፥ አሉታውን ፡ በጽድቅ ፡ ውጥን ፡ ይጨርሳል ። ፪ኛም ፡ ፬ቱ ፡ ኹሉ ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ ይኾናሉ ። አላ ፡ በትንቢትና ፡ በነባር ፥ እንጂ ፡ ግን ፡ ይኾናል ፤ እንጂና ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ ምስጢራቸውም ፡ አፍራሽነት ፡ ነው ። በትንቢት ፡ ዝኒ ፡ ይከውን ፡ ሕዝበ ፡ ዐቢየ ፤ አላ ፡ ዘይንእሰ ፡ የዐብዩ ። በነባርም ፡ አኮ ፡ አነ ፤ አላ ፡ አንተ ፡ ወቤተ ፡ አቡከ ። ዳእሙም ፡ እንጂ ፡ ብቻ ፡ ግን ፡ ይኾናል ፤ ብቻ ፡ ሲኾን ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ። አኮ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ዳእሙ ፡ ከመ ፡ መሬት ፤ እንጂ ። ኢትፍራህ ፥ ተአመን ፡ ዳእሙ ። ወለዘሂ ፡ ቄላፍ ፡ በአሚን ፡ ዳእሙ ፡ ያጸድቆ ። እሉኑ ፡ ዳእሙ ፡ ደቂቅከ ፥ ብቻ ። ግን ፡ ሲኾን ፡ ዳእሙ ፡ ሥርዎ ፡ ወጕንዶ ፡ ኅድጉ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ኵሎ ፡ ዘቦ ፡ መጠውኩከ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፥ ዳእሙ ፡ ኪያሁ ፡ ኢትግስስ ፤ ርሱን ፡ ግን ፡ ወይም ፡

ብቻ ፤ ፪ቱም ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ናቸው ።     ባሕቱም ፡ ግን ፡ ብቻ ፡ ይኾናል ፤ ግን ፡ ሲኾን ፡ ቀድሞ ፡ ተከትሎ ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ። ባሕቱ ፡ ዘንተ ፡ ረከብኩ ። መበለተ ፡ ባሕቱ ፡ ኢታውስብ ። ወን ፡ እየደረበም ፡ ሲገባ ፥ ወባሕቱ ፡ እብለክሙ ። ወእቤለክሙ ፡ ባሕቱ ። ብቻ ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ ዳእሙ ፡ እዥግ ፡ አይገኝም ፡ አላ ፡ ነቅዐ ፡ ማይ ፡ የሀርግ ፡ ባሕቱ ፡ እምነ ፡ ምድር ። በዝንቱ ፡ ባሕቱ ፤ አንተ ፡ ባሕቱ ። በብቻም ፡ ፈንታ ፡ ይልቅ ፡ ሲሉት ፡ ያምራል ። አኮ ፡ ይእዜ ፡ አላ ፡ ባሕቱ ፡ እምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ። እንበለም ፡ ዘ ፡ እያጋነነው ፡ በዘንድ ፡ አንቀጽ ፡ ገብቶ ፡ ሳ ፡ ይኾናል ። ዘእንበለ ፡ ያእምር ፡ ሕፃን ፡ ሰምየ ፡ አቡሁ ፡ ወእሙ ። ዘእንበለ ፡ ይቁሙ ፡ አድባር ።     ፫ኛም ፡ እንበለ ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ሲኾን ፥ በቀር ፡ አለ ፡ ያለ ፡ እንጂ ፡ ይኾናል ። ዘ ፡ እያጋነነው ፡ ሳያጋንነውም ፡ በጥሬ ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ፤ በቀር ፡ ሲኾን ፡ ባሉታና ፡ በክፍል ፡ ይገባል ። ባሉታ ፥ ወኢታገምር ፡ ፍናታ ፡ ዘእንበለ ፡ አሐቲ ፡ ከይደተ ፡ እግረ ፡ ብእሲ ። አልብነ ፡ ዝየ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀምስ ፡ ኅብስት ። በክፍል ፥ ወተዘርዉ ፡ ኵሎሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ሐዋርያት ። አለ ፡ ያለ ፡ ሲኾን ፥ እንበለ ፡ ኀጢአት ፡ ተሰቅለ ፥ ወእንበለ ፡ ድልወት ፡ ተገፍዐ ፡ ያሰኛል ። እንጂ ፡ ሲኾን ፥ አዘዘሙ ፡ ኢይንግሩ ፡ ዘርእዩ ፡ በደብር ፥ ዘእንበለ ፡ አመ ፡ ተንሥአ ፤ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ እንጂ ። አልቦኬ ፡ ዘይበቍዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ለገዲፍ ፡ አፍአ ። ሲዘረዝርም ፥ እንበሌሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፥ እንበሌክ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ ፡ እያሰኘ ፡ አለ ፡ ያለ ፡ በቀር ፡ ይኾናል ።

፺፪ ፡ ዓዲ ፡ ዐቢይ ፡ አገባብ ።   እንጂ ፡ ም ፡ ይኾናል ፤ ቀድሞ ፡ ተከትሎ ፡ ይነገራል ፤ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ባሕቱ ፡ በገቡበት ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ። እንጂ ፡ ሲኾን ፡ ዋዌነቱ ፡ አይቀርም ፤ አሉታውን ፡ በጽድቅ ፡ ሲያናግር ፥ አኮ ፡ በመቄዶንያ ፡ ወአከይደ ፡ ባሕቲቱ ፥ ዓዲ ፡ በኵሉ ፡ በሓውርት ፡ ባገሩም ፡ ኹሉ ፡ እንጂ ። ያሉታውን ፡ ውጥን ፡ በጽድቅ ፡ ሲጨርስ ፤ ምሕሮ ፡ ወአኮ ፡ ለሊቱ ፡ ለባሕቲቱ ፥ ዓዲ ፡ ሊተኒ ፤ እኔንም ፡ ደግሞ ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፡ እንጂ ። ዳእሙ ፡ ዓዲ ፡ እያለ ፡ ሲገባ ፡ እንጂነቱን ፡ ዳእሙ ፡ ወርሶት ፡ ዋዌ ፡ ብቻ ፡ ኹኖ ፡ ይቀራል ። አኮ ፡ ክመ ፡ ሰንበተ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘይስዐር ፡ ዳእሙ ፡ ዓዲ ፡ አቡሁ ፡ ይሬስዮ ፡ ለእግዚ ፤ እግዜርንም ፡ አባቱ ፡ ያደርጋል ፡ እንጂ ።     ንኡስ ፡ አገባብም ፡ ሲኾን ፡ ገና ፥ ደግሞ ፡ ዳግመኛ ፥ አኹን ፡ ም ፡ ይኾናል ። ገና ፡ ሲኾን ፡ ቡኋላፈና ፡ በትንቢት ፡ በትእዛዝና ፡ በነባር ፡ ይገባል ። ይህም ፡ ዓዲ ፡ ሀሎኩ ፡ ምስሌክ ። ይዌስክ ፡ ዓዲሁ ። ተዐገሡ ፡ ዓዲ ፡ ኅዳጠ ። ዓዲ ፡ ብየ ፡ ነገር ። ዘትብሉ ፡ ከመ ፡ ዓዲ ፡ ሕያው ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። እስመ ፡ ዓዲ ፡ እንዘ ፡ ዓዲ ፡ ዘዓዲ ፡ ከመ ፡ ዓዲ ፡ እያሰኘም ፡ በነባር ፡ አንቀጽ ፡ ከሚገቡ ፡ አገባቦች ፡ ጋራ ፡ ይነገራል ። ቡኋላፈ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ባሉታ ፡ ይገባል ። ዓዲ ፡ ኢበጽሐ ፡ ጊዜሁ ። ዓዲሁ ፡ ሃ ፡ እያለም ፡ ሲዘረዝር ፡ ገና ፡ ይኾናል ፤ እንዘ ፡ ዓዲሁ ፡ ጽልመት ። እስመ ፡ ዓዲሃ ፡ ኢተዐውቀት ። ዓዲየ ፡ ኢነሣእኩ ። ደግሞ ፡ ዳግመኛ ፡ ሲኾን ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ፤ ወገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓዲ ፡ አራዊተ ። ወትቤ ፡ ይእዜ ፡ ዓዲ ፡ አእምኖ ። አኹን ፡ ሲኾን ፥ ዓዲ ፡ መጽአ ፡ ዓዲ ፡ ይመጽእ ፡ እያሰኘ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ይገባል ። ዓዲ ፡ ኅዳጠ ፥ አኹን ፡ ጥቂት ፤ ወዓዲ ፡ ኅዳጥ ፥ ጥቂት ፡ ቈይቶ ፥ ከጥቂት ፡ በኋላ ፡ ይኾናል ። ም ፡ ሲኾን ፡ ዋዌ ፡ ነውና ፥ ከወንድሞቹ ፡ ከወሂኒ ፡ ጋራ ፡ ኋላ ፡ በበታው ፡ ይነገራል ።

፺፫ ፡ ብሂል ፡ ዐቢይ ፡ አገባብ ። ዘይቤው ፡ ማለት ፡ ይኾናል ፡ የብህሉና ፡ የይቤ ፡ ራስ ፡ ነው ። ብሂል ፡ ፫ ፡ ነገር ፡ ይኾናል ፡ እነዚህም ፡ ፫ቱ ፡ አንቀጽነትና ፡ አገባብነት ፡ ሰዋስውነት ፡ ናቸው ። በንቀጽነቱ ፡ አንቀጽን ፡ ኹሉ ፡ ይስባል ፡ ሲነገርም ፡ ቀድሞ ፡ ተከትሎ ፥ ዐርፎ ፡ ተናቦ ፡ ይገባል ። ይህም ፥ ብሂል ፡ ሠረቀ ፡ ብሂል ፡ ተወልደ ፡ ወይም ፡ ሠረቀ ፡ ብሂል ፡ ተወልደ ፡ ብሂል ። ብሂለ ፡ ሠረቀ ፡ ብሂለ ፡ ተወልደ ፡ ውእቱ ። በክልአይና ፡ በማልሳይም ፥ ብሂለ ፡ ይሠርቅ ፡ ኮከብ ፡ እምያዕቆብ ። ብሂለ ፡ ንበር ፡ በየማንየ ። በንባርም ፡ አ ይምሰልክሙ ፡ በብሂለ ፡ አብ ፡ ብነ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ፪ኛም ፡ በገቢብነቱ ፡ ዘማች ፡ አንቀጽና ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ ኹሉ ፡ እንዳያስሩ ፡ ይከለክላል ። ይህም ፥ ብሂል ፡ ከፈለ ፡ ሙሴ ፡ ባሕረ ፥ ብሂል ፡ ዐደወ ፡ ብንያም ፡ ብሂል ፡ ሌሊቅ ። በዚ ምህ ፡ አንቀጽነቱ ፡ መሳቡን ፡ ሳይለቅ ፡ በገቢብነቱ ፡ ከፈለና ፡ ዐደወ ፡ እንዳያስሩ ፡ ማሰሪያነትን ፡ አስለቀቀ ፡ ይህ ፡ ሲደረደር ፡ ነው ። ሲነባበር ፡ ደግሞ ፥ ብሂለ ፡ ብሂል ፡ ተወልደ ፡ አምላክ ፡ እማርያም ፡ ሌሊቅ ፡ ይላል ። ግብር ፡ እንዲተረጐም ፡ ስም ፡ ይተረጐማል ፡ ግብር ፡ ያለፈው ፡ ነው ፡ ስም ፡ ሲተረጐም ፥ ሚካኤል ፡ ብሂል ፡ በልሰነ ፡ ዕብራይስጥ ፥ መኑ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ጴጥሮስ ፡ ብሂል ፡ በልሳነ ፡ ጽርእ ፥ ኰኵሐዊ ፥ አው ፡ ብእሴ ፡ ኰኵሕ ። ፫ኛም ፡ በሰዋስውነቱ ፡ ዘርፍና ፡ ምሳሌ ፡ ይኾናል ። ዘርፍና ፡ ምሳሌም ፡ ሲኾን ፡ ለዘርፍነቱ ፡ ብዙ ፡ ስምና ፡ ግብር ፡ አለውና ፡ ኋላ ፡ በቅኔ ፡ ክፍል ፡ በሠምና ፡ በወርቅ ፡ ይነገራል ።

ሐተታ ፡ ያለፈውን ፡ ሰርክን ፡ መልሶ ፡ የሚፈታና ፡ የሚያፍታታ ፡
ያበይት ፡ አገባቦች ፡ ዳግም ፡ ሕግ ፥ ማሰሪያና ፡ አገባብ ፡ የሚያዛውግ ።

፺፬ ፡ ከብሂል ፡ በፊት ፡ ከእስመ ፡ እስከ ፡ ብሂል ፡ ከተነገሩቱ ፡ ተመርጠውና ፡ ተለይተው ፡ ዳግመኛ ፡ መነገር ፡ የሚያሻቸው ፡ ዐበይት ፡ አገባቦች ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡ መደገማቸውም ፡ ስለ ፡ ማሰሪያ ፡ ነው ። ንኡስና ፡ ደቂቅ ፡ መኾናቸው ፡ ሳይቀር ፡ ጠባያቸው ፡ ኹሉ ፡ ተለቅሞ ፡ ተቃርሞ ፡ ተከቶ ፡ ተነግሯል ። የማሰሪያም ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ እስመ ፡ በእንተ ፡ በይነ ፡ እንበይነ ፡ ስለ ፡ ስላ ፡ ሲኾኑ ፡ በራሳቸውና ፡ በባዕድ ፡ ያሳስራሉ ። በራሳቸው ፡ ማለት ፡ በነባር ፡ አንቀጽ ፥ በባዕድ ፡ ማለት ፡ በዘማች ፡ አንቀጽ ፡ ማለት ፡ ነው ። በባዕድ ፡ ሲያሳስሩ ፡ ለነገሩ ፡ ፯ ፡ አገባቦች ፡ ይስማሙታል ። አገባቦቹም ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡ እስመ ፡ አምጣነ ፡ እነኡ ፡ ና ፡ ሲኾኑ ፡ እመ ፡ ሶበ ፡ ብ ፡ ቢ ፡ ሲኾኑ ፡ እመ ፡ እምከመ ፡ ክ ፡ ከ ፡ ሲኾኑ ፡ ኀበ ፡ ዘንድ ፡ ሲኾን ፡ ከመ ፡ እንደ ፡ ሲኾን ፡ እንዘ ፡ እየ ፡ ሲኾን ፡ እንተ ፡ እለ ፡ ዘ ፡ የ ፡ ሲኾኑ ፡ ነው ። በራሳቸው ፡ ሲያሳስሩ ፥ ሞቱ ፡ ለእግዚእ ፡ እስመ ፡ ሞተ ፡ አዳም ፡ በእንተ ፡ በይነ ፡ እንበይነ ፡ ዘሞተ ፡ አዳም ፡ የጌታ ፡ ሞቱ ፡ አዳም ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ነው ። በባዕድ ፡ ሲያሳስሩ ፥ እስመ ፡ ተቀረደ ፡ በእንተ ፡ በይነ ፡ እንበይነ ፡ ዘተቀረደ ፡ አዳም ፡ ሞተ ፡ እግዚእ ፡ ያሰኛል ።

፺፭ ፡ ለነገሩም ፡ ፯ቱ ፡ አገባቦች ፡ ሲሰማሙት ፥ ሞቱ ፡ ለእግዚእ ፡ እስመ ፡ እስመ ፡ ሞተ ፡ አዳም ፡ አምጣነ ፡ በእንተ ፡ ዘሞተ ፡ አዳም ፥ እነኡ ፡ በይነ ፡ እንበይነ ፡ ዘሞተ ፡ አዳም ፥ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ የጌታ ፡ ሞት ፡ አዳም ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ነውና ፥ ምስጋና ፡ ይገባ

ሞቱ ፡ ለሰብእ ፡ ቅድመ ፡ ትንሣኤ ፡ ወድኅረ ፡ ትንሣኤ ፡ ሞተ ፡ ዓለም ። ተፈንዎቱ ፡ ለጰራቅሊጦስ ፡ ኀበ ፡ ሐዋርያት ፡ እምድኅረ ፡ ዐርገ ፡ እግዚእነ ። በበዐድም ፥ መንክር ፡ ኀይሉ ፡ ለጰራቅሊጦስ ፡ እስመ ፡ እምድኅረ ፡ ወረደ ፡ ሎሙ ፡ ጥብዐተ ፡ ሐዋርያት ፡ እለ ፡ እምቅድሜሁ ፡ ኢኮኑ ፡ ጥቡዓነ ። የቀሩትንም ፡ እንዲሁ ፡ አሰማምተኽ ፡ እግባ ።

## ፳ኛ ፡ ዕርከን ።

## ንኡሳን ፡ አገባቦች ።

፻፷፫ ፡ ሰ ፡  ና ፡ ስ ፡ ሳ ፡ ማ ፡ ማን ፡ ትቻ ፡ ይኾናል ፡ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ የኹሉም ፡ አፍራሽ ፡ ነው ። ሲገባም ፡ ትራስ ፡ እየኾነ ፡ በቃል ፡ መጨረሻ ፡ ይገባል ። ሰ ፡ ስ ፡ መኾኑን ፡ ሳይለቅ ፡ ጸንሐ ፡ ተርፈ ፡ ተነድገ ፡ በሚሉ ፡ በነዚህ ፡ በ፫ቱ ፡ በሣልሳይ ፡ ብቻ ፡ እየገባ ፡ ና ፡ ይኾናል ። አገባቡም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ኢፈጸሙ ፡ አይሁድ ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ፡ ይጸናሕሰ ፡ ይትርፍሰ ፡ ይትነደግሰ ፡ ዝንቱ ፤ ሕገ ፡ ኦሪትሂ ፡ ኒ ፡ ጥቀ ፡ ኢፈጸሙ ፡ ሲፈታም ፡ ይህስ ፡ ይቅርና ፡ የኦሪትን ፡ ሕግ ፡ ስንኳ ፡ አልፈጸሙም ። ስ ፡ ብቻ ፡ ሲኾን ፡ በብትን ፡ በቅጽል ፡ ይገባል ፡ ወልድየሰ ፡ መዊቶ ፡ ሀለወ ፥ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ጐንደየ ፤ ልደ፫ስ ፡ ሙቱል ። ውእቱሰ ፡ ሕያው ፡ ርሱስ ፡ ደኅና ፡ ነው ። ሳ ፡ ሲኾን ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ በቅጽል ፡ በብትን ፡ እየገባ ፡ ጥያቄ ፡ ይከተለዋል ። ይቤሎ ፡ ለዘይቤሎ ፡ መጽአ ፡ ላእከኒሁ ፡ ለንጉሥ ፥ ውእቱሰ ፡ ተርፈኑ ፡ ርሱሳ ፡ ቀረን ። አንተሰ ፡ መጻእከ ፥ እኑከሰ ፤ አንተስ ፡ መጣኽ ፥ ወንድምኽሳ ። ማ ፡ ሲኾን ፡ ደግሞ ፡ በቅጽል ፡ በብትን ፡ በገባብ ፡ ገብቶ ፡ በጥያቄ ፡ ምላሽ ፡ ይነገራል ። ይቤሎ ፡ ለዘይቤሎ ፡ ሕያውኑ ፡ እኑከ ፥ ውእቱሰ ፡ ሞተ ፤ ርሱማ ፡ ሞተ ። ግን ፡ ሲኾን ፡ ብቻውን ፡ በብትን ፡ ይገባል ፤ ሰብእሰ ፡ እንዘ ፡ ክቡር ፡ ውእቱ ፡ ኢያእመረ ። መብልዕሰ ፡ ጽኑዕ ፡ ለልሂቅ ። ትቻ ፡ ሲኾን ፡ ወ ፡ ሂ ፡ ኒ ፡ ሰ ፥ ግን ፡ እየኾኑ ፡ ይከተሉታል ። ይህም ፥ ሰብእሰ ፡ ገጸ ፡ ይሬኢ ፡ ወእግዚአብሔርሰ ፡ ልበ ፡ ይሬኢ ። እሙንቱሰ ፡ ተዐቅጹ ፡ ወወድቁ ፡ ወንሕነሰ ፡ ተንሣእነ ፡ ወረታዕነ ። ለአድግሰ ፡ አቅሕሞ ፤ ወለገብርኒ ፡ ገሥጾ ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ። በገባብና ፡ በንቀጽም ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ፤ ሶበሰ ፡ ተአምረ ፥ እመሰ ፡ አማን ፥ እንከሰ ፥ ይረትዕሰ ፥ እፈቱሰ ፡ እፍልስ ።

፻፷፬ ፡ እም ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ።  በ ፡ ባ ፡ ከ ፡ ካ ፡ ኪ ፡ ክ ፡ ይኾናል ፡ ኪ ፡ ክ ፡ ሲኾን ፡ በትርፍ ፡ ዐማርኛ ፡ ይልቅ ፡ ያሰኛል ። እመና ፡ ሰበ ፡ ቀድመውት ፡ ወይም ፡ ተከትለውት ፥ ብቻውንም ፡ ኹኖ ፡ በኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ እየገባ ፡ በጽንዕ ፡ ሲፈታ ፡ በ ፡ ባ ፡ ይኾናል ፡ ምስጢሩም ፡ ባለፈ ፡ ነገር ፡ ጸጸት ፥ በሚመጣ ፡ ነገር ፡ ምኞት ፡ ያሳያል ። እመ ፡ ይኔስሕ ፡ ይሁዳ ፡ እምጸድቀ ፡ በጸደቀ ፡ ነበር ። እምኀየሶ ፡ ሰብ ፡ ኢተወልደ ። እመ ፡ ኢይበልዕ ፡ አዳም ፡ በለሰ ፡ እምኢኀጥአ ፡ ጸጋሁ ፡ ዘተውህበ ፤ ሰበሰ ፡ ትሄሉ ፡ ዝየ ፡ እምኢሞተ ፡ እኁየ ፤ ባልሞተም ፡ ነበር ። የእመና ፡ የሰበ ፡ ጠባይ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ (ዕር፲፱ኛ ፡ ቍ፻፺፮) ፡ ተመልከት ።  ብቻውንም ፥ እምደለወከ ፡ ታግብእ ፡ ወርቅየ ፥ ወመጺእየ ፡ እምአስተገበርክዎ ፡ ለልየ ። መኑ ፡ እምወሀበኒ ፡ ማየ ፡ እያለ ፡ ይገባል ። ከ ፡ ካ ፡ ሲኾን ፡ ከመንና ፡ ዘን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ አድርጎ ፡ እንደዚሁ ፡ በኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባል ፡ እምዘ ፡ እምከመ ፡ የሚባል ፡ አገባብ ፡ የለምና ፡ እምዘ ፡ ከበዘ ፡ ጋራ ፡ በበታው ፡

ተነግሯል ፡ ከመፃ ፡ እምከመ ፡ ለምለመ ፡ ዐጽቁ ፡ ወእምከመ ፡ ወፅአ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፡ እያለ ፡ ይገባል ። ዘእም ፡ እያለም ፡ ሲገባ ፡ እምዘ ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ፡ ይህም ፡ ጸልኢ ፡ ዘእምአፍቀሩ ፡ ከወደዱት ፡ ይልቅ ። አኅሰረከ ፡ ዘእምአክበረከ ፡ ካከበረኽ ፡ ይልቅ ። ሊወዱት ፡ የነበር ፥ ሊያከብሩኽ ፡ የነበር ፡ ብለው ፡ ኀላፊውን ፡ በዘንድ ፡ የሚፈቱ ፡ አሉ ። ሐቀ ፡ ክመ ፡ ዘእምድኅፀ ፡ ሰኰናየ ፡ ዘእምተንተና ፡ እግሬ ፡ ያለውም ፡ እንዲሁ ፡ ይፈታል ። ከ ፡ ክ ፡ ሲኾን ፡ በዘንድ ፡ እየገባ ፡ ይልቅ ፡ ያሰኛል ፡ ማሰሪያውም ፡ ቀለ ፡ ኀየሰ ፡ አፍቀረ ፡ ኀረየ ፥ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነው ። ይቀልል ፡ ኅልፈተ ፡ ሰማይ ፡ እምትደቅ ፡ አሐቲ ፡ ቃል ። ይኄይሰነ ፡ ንቅትል ፡ አሐደ ፡ ብእሴ ፡ እምይትሀጐል ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾን ፥ ከ ፡ ይልቅ ፡ የተነሣ ፡ ዠምሮ ፥ ኋላ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይኾናል ። እም ፡ ከ ፡ ካ ፡ እየኾነ ፡ በሰዋስው ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፥ ተወላጅ ፡ ተከፋዪ ፡ መገኛ ፡ ሰጭ ፡ ይኾናል ። ተወላጅ ፡ ሲኾን ፡ ተወልደ ፡ ቃል ፡ እምአብ ፡ ተከፋዪ ፡ ሲኾን ፡ ተወልደ ፡ ቃል ፡ እምድንግል ፡ ተወላጅና ፡ ተከፋዪ ፡ ሲኾን ፡ ተወልደ ፡ ወልድ ፡ አው ፡ ሕፃን ፡ እምአቡሁ ፡ ወእሙ ። መገኛ ፡ ሲኾን ፡ ወፅአ ፡ ቃል ፡ እምአብ ፡ ተሰብከ ፡ ወንጌል ፡ ለአሕዛብ ፡ እምቃለ ፡ ሐዋርያት ። ሰጭ ፡ ሲኾን ፡ ተውህበ ፡ ወርቅ ፡ እምንጉሥ ፡ ለወዓሊሁ ፡ ያሰኛል ። አለማሱ ፡ የተነበበ ፡ እም ፡ በዝ ፡ እንቀጽ ፡ ይመረመርበታል ፡ ይህም ፡ ዜነዋ ፡ ገብርኤል ፡ ለማርያም ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ቃዘ ፡ ተልከ ። ለዘሐወጻን ፡ እምአርያም ፥ ወርዶ ፡ መጥቶ ። ተንሥአ ፡ እሙታን ፥ ተለይቶ ፡ ቀድሞ ፡ አስቀድሞ ። ስብሕዎ ፡ ለእግዚ ፡ እምሰማያት ፡ ከመላእክት ፡ አብነት ፡ ነሥቻቾኹ ። እምከርሥ ፡ ስሕቱ ፡ ወነበቡ ፡ ሐሰተ ፡ ከማሕፀን ፡ ዠምረው ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። እም ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ሲኾን ፡ ቢተመሳሰይ ፡ ቃል ፡ ይነገራል ፡ ይትበደር ፡ ሰብእ ፡ እምዕንቍ ፡ ሰንፔር ፡ ክቡር ፡ እምወርቅ ፡ ወእምብሩር ፡ ይትበደሩ ፡ ጻድቃን ። አንተ ፡ ተዐብዪ ፡ እምብዙኃት ፡ አንስት ። ውጥንም ፡ ሲፈጽርስ ፡ የፀቢ ፡ ክብሩ ፡ ለማርያም ፡ እምኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ይላል ። የተነሣ ፡ ሲኾን ፡ ነ ፡ መንገለ ፡ በር ፡ ከፋቾች ፡ ኾነው ፡ ሳይኾኑም ፡ ብቻውን ፡ ምክንያት ፡ በለው ፡ ቃል ፡ ይገባል ። ሰቀልዎ ፡ አይሁድ ፡ ለክርስቶስ ፡ እምነ ፡ እመንገለ ፡ ቅንአቶሙ ። የብሰ ፡ እምድንጋጼ ፡ ወጕየ ፡ እምፍርሀት ። ዠምሮ ፡ ሲኾን ፡ በበታ ፡ በጊዜ ፡ ይገባል ፡ በበታ ፥ እምጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ እስከ ፡ ግብጽ ። በጊዜ ፥ እምአዳም ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ እምትንሣኤ ፡ እስከ ፡ ዕርገት ። ኋላ ፡ ሲኾን ፡ በጸሩ ፡ ይገባል ፡ ወእምዝ ፡ ወሰዶ ፡ መንፈስ ፡ ገዳመ ፡ ወእምዝ ፡ መጽአ ፡ እርዳኢሁ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ። ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲኾን ፡ ኢያበርህ ፡ ፀሓይ ፡ እምአድማስ ፡ አላ ፡ እምአድማስ ፡ ይላል ። ሲዘረዘርም ፡ እምኔሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፡ እምኔከ ፡ ኪ ፡ ከሙ ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ ፡ እያሰኘ ፡ እንደሚስማማው ፡ ይፈታል ። እም ፡ ነን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ሳይገዝ ፡ በ ፡ ፈ ፡ ሰ ፡ ጺ ፡ ፐ ፡ ብሎ ፡ በሚነሣ ፡ ቃል ፥ እምበረከት ፡ እምፈቃድ ፡ እምሰማይ ፡ እምጻፉ ፡ እምፓና ፡ እያለ ፡ በቅኔ ፡ ሲገባ ፡ አፈ ፡ ጻያፍ ፡ ነው ። ፱ኛም ፡ ከማእገዝ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ባለው ፡ በመ ፡ ፊደል ፡ በሚነሡ ፡ ቃላት ፡ ሲገባ ፡ ደጊመ ፡ ቃልነት ፡ ስላለው ፡ እየጠበቀና ፡ እየዋጠ ፡ ቀለም ፡ ያስቀራል ። ይህም ፡ እሙብረቅ ፡ እሙላድ ፡ እሚናስ ፡ እማርያም ፡ እሚሉስ ፡ እምሥራቅ ፡ እሞት ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ።

፺፡ አይ፡ ምንት፡ መኑ ። ማእዜ፡ አይቴ፡ ስፍን ። ባለቤት፡ ሲኾን፡ ቅጽል፡ ባለቤት፡ ሲቀር፡ በቁ፡ ይኾናሉ፡ ማእዜ፡ ግን፡ ብቻውን፡ ይበቃል ። ቅጽልነታቸው፡ በ፪ኛና፡ በ፫ኛ፡ ክፍል፡ ተነግሯል ። አኹንም፡ በዚህ፡ የጥያቄ፡ አገባብ፡ ስለ፡ ኹኑ፡ ዐብሮ፡ ይነገራል ። በንባብ፡ ጥያቄ፡ ብቻ፡ ሲመስሉ፡ በምስጢር፡ አሉታ፡ ናቸው፡ ሁ፡ ኑ፡ ያጋንኗቸዋል፡ አላ፡ ዳእሙ፡ ባሕቱ፡ ያጸድቋቸዋል ። አይ፡ ምንት፡ በበቂነትም፡ በቅጽልነትም፡ የግብር፡ የነገድ፡ የተቀብዖ፡ ስም፡ ይፈልጋሉ ። ይህም፡ አይ፡ ምንት፡ ተሰቅለ፡ ወይም፡ አይ፡ ብእሲ፡ ምንት፡ ሰብእ፡ ተሰቅለ፡ በቀራንዮ፡ ነቢይሁ፡ ኑ፡ ወሚመ፡ ሐዋርያ፡ እሙ፡ ረድእ፡ ወእመ፡ አኮ፡ እሙ፡ ጻድቅ፡ አኮ፡ ነቢይ፡ ወአኮ፡ ሐዋርያ፡ ኢረድእ፡ ወኢጻድቅ፡ ዳእሙ፡ እግዚአብሔር፡ ሥግው ። ናሁ፡ ተሰቅለ፡ እሑዱ፡ ብእሲ፡ ምንት፡ ብእሲሁ፡ በለ፡ ጊዜ፡ አይሁዳዊ፡ ወይም፡ ክርስቲያናዊ፡ መኾኑን ። ወናሁ፡ ብእሲ፡ ዲበ፡ መንበር፡ አይ፡ ብእሲ፡ ብሎ፡ ጳጳስ፡ ንጉሥ፡ መኾኑን፡ ይፈልጋል ። ምንት፡ ሲቀር፡ አይ፡ መኑ፡ በክል፡ የተለየ፡ የተጸወዖ፡ ስም፡ ይሻሉ ። ይህም፡ አይ፡ መኑ፡ ተሰቅለ፡ እም ሐዋርያት፡ ቍልቍሊተ፡ በትእይንተ፡ ሮም፡ ጳውሎስኑ፡ ወሚመ፡ ዮሐንስ፡ አልቦ፡ ዘተሰቅለ፡ ዘእንበለ፡ ጴጥሮስ፡ ማለቱን፡ ያሳያል ። ሂ፡ ኒ፡ ትራስ፡ ሲኾኗቸው፡ ማንም፡ ይኾናሉ፡ አይኒ፡ ዘተምህ ። በአይኒ፡ ግብር፡ እም ግብራት ። ዘይዜብጥ፡ መኑሂ፡ ማንኛም፡ ማን ። ኢአይኒ፡ ወኢመኑሂ፡ አንድስ፡ እንኳ፡ ያሰኛሉ ። ኢተገብረ፡ ዘከማሁ፡ ወኢበአይኒ፡ መንግሥት ። አልቦ፡ ዘርእየ፡ ወኢመኑሂ ። በክፉል፡ ሲገቡም፡ እንዲሁ፡ ናቸው ። ምንት፡ ደግሞ፡ ሂ፡ ኒ፡ ትራስ፡ ሲኾኑት፡ ምንምን፡ አንዳች፡ ይኾናል ። አሌሰል፡ እደውየ፡ ኀበ፡ ሰማይ፡ ከመ፡ ኢይኑሥእ፡ ምንተኒ፡ እምንዋይከ ። ዘወሀበ፡ እሑዱ፡ ለከልኡ፡ ምንተኒ ። ኢ፡ ወኢ፡ ሲገቡበት፡ ያልተፈጠረ፡ ከንቱ፡ ስምና፡ ህላዌ፡ የሌለው፡ ተብሎ፡ ይፈታል ። ሰፍሐ፡ ለመድር፡ ዲበ፡ ኢምንት፡ እሙ፡ ዲበ፡ ወኢምንት ።

አይ፡ ማእዜ፡ መቼ፡ ይኾናሉ፡ አየ፡ ዘመነ፡ በአይ፡ ዘመን፡ ማእዜ፡ ተወልደ፡ ክርስቶስ ። አይ፡ ለኹሉ፡ ይኾናል፡ ማእዜ፡ ግን፡ ለጊዜ፡ ብቻ፡ ነው፡ ሂ፡ ኒ፡ ትራስ፡ ሲኾኑት፡ ኢ፡ ሲጠመርበት፡ ማሰሬያው፡ አሉታ፡ ነው ። ኢለከፎን፡ ፀሓይ፡ ማእዜሂ ። ወኢማእዜኒ፡ ኢኮኑ፡ሕያዋነ፡ መቼም፡ መች ። አይቴ፡ ሐቲ፡ ወዴት፡ ይኾናል፡ ሀዋጁ፡ እንደ፡ ማእዜ፡ ነው ። በአይቴ፡ ኀበ፡ አይቴ፡ እንተ፡ አይቴ፡ እምአይቴ፡ እስከ፡ አይቴ፡ እያሰኙ፡ የቦታ፡ አገባቦች፡ ይስማሙታል ። ለ፡ ሲስማማው፡ ኀበን፡ በር፡ ከፋች፡ አድርጎ፡ ለኀበ፡ አይቴ፡ ያሰኛል ። ሂ፡ ኒ፡ ትራስ፡ ኹነውት፡ ሳይኾኑትም፡ ኢ፡ ወኢ፡ ሲጠመርበት፡ ማሰሬያው፡ አሉታ፡ ነው ። ኢትፃእ፡ እምህየ፡ ወኢትሖር፡ አይቴሂ፡ ኢአይቴኒ፡ የትም፡ የት፡ ወደትም፡ ወደት ። ማሙራ፡ ኢያስተርእየ፡ ዘከመ፡ ዝ፡ ወኢበአይቴኒ፡ በየትም፡ በየት፡ በአንድ፡ስንኳ፡ በታ፡ ያሰኛል ። ስፍን፡ እስፍንት፡ ቴ፡ ስንት፡ ምን፡ ያኽል፡ ይኾናሉ፡ ስፍን፡ ያንድ፡ እስፍንት፡ የብዙ፡ ነው፡ ምስጢራቸው፡ አኹንዝ፡ ስለ፡ ኹነ፡ በክፉል፡ ይነገራሉ ። ሲገቡም፡ በበቂነት፡ እስፍንት፡ ኀረየ፡ ወይም፡ በቅጽልነት፡ እስፍንተ፡ ሐዋርያተ፡ ኀረየ፡ ክርስቶስ፡ እምእስራኤል፡ ክልኤተኑ፡ እሙ፡ ሠለስተ፡ ዳእሙ፡ ዐሠርተ፡ ወክልኤተ፡ ያሰኛሉ ። ሂ፡ ኒ፡ ትራስ፡ ይኾኗቸዋል፡ ማለት፡ የለም፡ እንጂ፡ ዐዋጃቸው፡ ኹሉ፡ እንደ፡ ሌሎቹ፡ ነው ።

፺፩ ፡ መ ። ሚ ።   መ ፡ ነገር ፡ ያበረታል ፥ ቃል ፡ ያገናታል ፡ አዳማቂ ፡ ኹኖ ፡ ይቀራል ፡ እንጂ ፥ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ የተለየ ፡ ፍች ፡ የለውም ። እውነተኛ ፡ ፍቹም ፡ ማ ፡ ነበረ ፡ በመምህራን ፡ ልማድ ፡ ከሰ ፡ ተደርቦ ፡ ተነግሯል ። ከአይ ፡ እስከ ፡ እፎ ፡ ባሉት ፡ በንኡሳንና ፡ በደቂቅ ፡ ቅጽሎች ፡ በአንቀጽም ፡ ሳይቀር ፡ ትራስ ፡ እየኾነ ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ። የጥያቄ ፡ አገባብ ፡ ኑ ፡ ሲነተራሰው ፡ ጥርጥር ፡ ያሳያል ። መኑመ ፡ አንተ ፡ ምንተኑመ ፡ ትርእዩ ፡ ወፃእክሙ ። ዝኑመ ። ብቻውንም ፡ አይቴመ ፡ እፎመ ፥ እስኩመ ፡ ውእቱመ ፥ ክልኤመ ። በአንቀጽም ፡ መጽአመ ፡ ዘይመጽእ ፡ እያለ ፡ ይገባል ። ከንኡሳን ፡ በቀር ፡ በሌሎቹ ፡ ማ ፡ ተብሎ ፡ ሲፈታ ፡ ያምርበታል ።   ሚ ፡ ምን ፡ ምንድር ፥ ምንኛ ፡ ስንት ፡ ይኾናል ። ምን ፡ ምንድር ፡ ሲኾን ፡ በአናቅጽ ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ፡ ምስጢሩም ፡ ጥያቄ ፡ ምርመራ ፡ እንክሮ ፡ ነው ። ሚ ፡ የዐቢ ፡ እምረኀብ ፡ ወሚ ፡ ያሐምም ፡ እምቍር ። ሚ ፡ እግብሮ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ። ሚ ፡ ላዕሌን ፡ ምን ፡ አለብን ። ምንኛ ፡ ስንት ፡ ምን ፡ ሲኾን ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ በቅጽል ፡ ይገባል ፡ ሚ ፡ በዝኁ ፡ እለ ፡ ይሣቅዩኒ ። ሚ ፡ ይበዝኁ ፡ ሐዘኑ ፡ እምየ ። ሚ ፡ መጠን ፡ ግርምት ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ። እምነ ፡ ተከትሎ ፡ በ፳፪ት ፡ በምኞት ፡ ሲገባ ፡ ምነው ፡ ይኾናል ። ሚ ፡ እሞትኑ ፡ በግብጽ ፡ ምነው ፡ በሞትኹ ። መጽሐፍ ፡ ማን ፡ እመ ፡ ሞትኩ ፡ ሰበ ፡ ሞትኩ ፡ ይላል ፡ (ዘፀ ፲፮ ፡ ፫) ። ሚመ ፡ ተብሎ ፡ በአንድነት ፡ ሲነገር ፡ አማራጭ ፡ ነውና ፡ ኋላ ፡ ከአው ፡ ጋራ ፡ ይነገራል ።

፺፪ ፡ እፎ ።   እንደምት ፡ ረግ ፥ ምን ፡ ምንኛ ፡ በ ፡ ሲወድቅበት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይኾናል ። አ ፡ ኬ ፡ ኑ ፡ መ ፡ እንጋ ፡ እያገናኙት ፡ ሳያገናኙትም ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ በነባር ፡ በቅጽል ፡ ይገባል ፡ ምስጢሩም ፡ ጥያቄና ፡ እንክሮ ፡ ድንጋጼ ፡ ነው ፡ መዓትም ፡ ያሳያል ። እንደምትና ፡ ረግ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ እፎ ፡ ወድቀ ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ፡ እምሰማይ ። እፎ ፡ አማመርከዮ ፡ ለዘኢይትገመር ። አ ፡ ኬ ፡ ሲያገናኙት ፡ ራብዕ ፡ ያናግራል ፡ አ ፡ ደጋሞ ፡ ኬ ፡ ይኾናል ። እፎአ ፡ እንዘ ፡ አይሁዳዊ ፡ አንተ ፡ ትስእል ፡ በነቤየ ፡ ትስተይ ፡ ማየ ፡ እንዘ ፡ ሳምራዊት ፡ አነ ፡ ኬ ፡ እንደምት ፡ ነዋ ፡ ረግና ። እፎኬ ፡ ሰቀልዎ ፡ እንደምት ፡ ነዋ ፡ ሰቀሉት ። በቀናትም ፡ እፎኑ ፡ ንዜኑ ። እፎመ ፡ ዘኢያምጻእክምዎ ። እፎኑመ ፡ ይኬንን ፡ ዓለመ ። እፎ ፡ እንጋ ፡ ማሕፀነ ፡ ድንግል ፡ ጾሮ ፡ እያለ ፡ ይገባል ። ምን ፡ ምንኛ ፡ ሲኾን ፥ እፎ ፡ ትቤ ። እፎ ፡ ተሰብሐከ ፡ ኢልያስ ፡ ያሰኛል ። በቅጽልም ፡ አ ፡ ሞት ፡ እፎ ፡ ገክርከ ፡ መሪር ፡ እያለ ፡ ምንኛ ፡ ይኾናል ። ስለ ፡ ምን ፡ ሲኾን ፥ በእፎ ፡ ትነውሙ ፡ ዕለት ፡ እምዕለት ፡ ይላል ። በደጊመ ፡ ቃልም ፡ ሲነገር ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ ይፈታል ፡ ይህም ፡ እፎ ፡ እፎ ፥ ወይም ፡ እፎፎ ፡ ምንምን ፥ ምን ፡ ምን ፡ ምንኛ ፡ እንደምት ፡ እንደምት ፥ ረግ ፡ ረግ ። እፎፎ ፡ ትቤ ፡ (ቁር) ። እፎያዊ ፡ እንደምት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ያሰኛል ።

፺፫ ። ሁ ፡ ኑ ።   ጥያቄና ፡ አጋናኝ ፡ ናቸው ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ትራስ ፡ እየኾኑ ፡ ይገባሉ ። ጥያቄ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ ሲገቡ፡ን ፡ ይኾናሉ ፡ ምስጢራቸውም ፡ ጥያቄን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ማድንቅና ፡ መናቅ ፡ መሰልቸት ፡ ያሳያል ። ጥያቄና ፡ ድንቅ ፡ ሲኾኑ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ይነገራሉ ፡ ትሳአሉኒሁ ፡ መጻእክሙ ። ይትከሀልኑ ፡

ይፃእ ፡ ኄር ፡ እምናዝሬት ። ድኩምኑ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ይገብር ። መናቅና ፡ መሰልቸት ፡ ሲኾኑ ፡ ተመላልሰው ፡ ይነገራሉ ፡ መኑ ፡ ያኀድገነ ፡ ፍቅሮ ፡ ለክርስቶስ ፡ ሕማምኑ ፡ ምንዳቤኑ ፡ መጥባሕትኑ ። ይቤ ፡ ነዳይ ፡ ዘጸንዐ ፡ ቦቱ ፡ ምንዳቤ ፥ ምንት ፡ ይኄይሰኒ ፡ ሞትኑ ፡ ስደትኑ ፡ ሰሪቅኑ ፡ ስርቆትን ፡ ያሰኛል ። አጋናኝ ፡ ሲኾኑ ፡ ከአይ ፡ እስከ ፡ እፎ ፡ በሉት ፡ ይገባሉ ። ዳግመኛም ፡ ቦሁ ፡ ቦኑ ፡ እያሉ ፡ ሲገቡ ፡ በውኑ ፡ ተብለው ፡ ይፈታሉ ። ቦኑ ፡ መሚጠተ ፡ ወቍርባነ ፡ አበእክሙ ፡ ሊተ ። ቦኑ ፡ ይብሎ ፡ ጽቡር ፡ ለለብሐዊ ፡ ኢትግበረኒ ፡ ከመ ፡ ዝ ። ቦኑ ፡ ለባሕቲቶሙ ፡ ለአይሁድ ፡ እግዚ ። በቅጽልና ፡ በጥሬ ፡ ግን ፡ አለን ፡ ያሰኛሉ ። ቦሁ ፡ ዘይሴወር ፡ እምኔየ ። ቦኑ ፡ ዘተርፈ ፡ ኀቤከ ። ይቤላሁ ፡ ለዘይቤሎን ፡ ቦኑ ፡ ረአይ ፡ በዛቲ ፡ ሀገር ፥ እወ ፡ ቦ ።

፻፱ ፡ ኦ ። የጥሪ ፡ አገባብ ፡ ነው ፡ ሆይ ፥ ምን ፥ ወዮ ፡ ይብላኝ ፡ ይኾናል ። በተለየም ፡ ላሬቱ ፡ ቅርቦች ፡ የሰሚ ፡ አገባብ ፡ ነው ። ሆይ ፡ ሲኾን ፡ ቃለ ፡ ጽዋዔ ፡ ነው ፡ ምስጢሩም ፡ አክብሮና ፡ አፍቅሮ ፥ አራኅርኆና ፡ ምክር ፥ አፍርሆና ፡ አኅስሮ ፥ ወቀሣም ፡ ያሳያል ። ጽዋዔ ፡ ለሩቅም ፡ ለቅርብም ፡ ሲነገር ፡ የሩቁ ፡ ተጠሪ ፡ የቅርቡ ፡ ሰሚ ፡ ይባላል ፡ ምስጢሩ ፡ አክብሮ ፡ ሲኾን ፡ ኦ ፡ ኢየሱስ ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ተሣሀለነ ። አፍቅሮ ፥ ኦ ፡ ማርያም ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ናፈቅረኪ ። አራኅርኆ ፥ ኦ ፡ መስተምሕርት ፡ እስተምሕሪ ፡ ኀበ ፡ ወልድኪ ። ኦ ፡ ዮሴፍ ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ኢትፍራህ ፡ ነሢአታ ፡ ለማርያም ፡ ፍኅርትከ ። ምክር ፡ ሲኾን ፥ ኦ ፡ ወልድየ ፡ ስምዐኒ ፡ ዘእብለከ ። አፍርሆ ፥ ኦ ፡ ሀገረ ፡ ሰዶም ። አኅስሮ ፥ ኦ ፡ ይሁዳ ፥ ኦ ፡ ሐናንያ ፡ እፎ ፡ መልአ ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ልብከ ። ወቀሣም ፡ ሲኾን ፥ ኦ ፡ አዳም ፡ ምንትኑ ፡ ረሰይናከ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ምን ፡ ሲኾን ፥ ቃለ ፡ አንክሮ ፡ ነው ፡ ለክፉም ፡ ለበጎም ፡ ይነገራል ፡ ለ ፡ እየተከተለው ፡ ሳይከተለውም ፡ በቅጽል ፡ በጥሬ ፡ ይገባል ። ኦ ፡ ግንቱ ፡ ምስጢር ። ኦ ፡ ዕሙቅ ፡ ብዕለ ፡ ጥበቡ ። ኦ ፡ ለዝ ፡ ግንጋሜ ። ኦ ፡ ለዝ ፡ ኀሲና ። ወዮ ፡ ይብላኝ ፡ ሲኾን ፥ ቃለ ፡ ሰቈቃው ፡ ነው ፡ እምና ፡ ለ ፡ ይስማሙታል ። ኦ ፡ ሞት ፡ ኦ ፡ እምግንቱ ፡ ሞት ፡ ዘሥልጥ ፡ ላዕለ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ። ኦ ፡ ለዘሞተ ። ኦ ፡ ለይሁዳ ፡ እስመ ፡ ሤጦ ፡ ለእግዚእ ። ፪ኛም ፡ የሰሚ ፡ አገባብ ፡ ሲኾን ፡ ምስጢሩ ፡ ከጽዋዔነት ፡ አይወጣም ፡ ሰሚዎቹም ፡ ፬ ፡ ናቸው ፡ አንተ ፡ አንቲ ፡ አንትሙ ፡ አንትን ፡ አቅራቢዎቻቸውም ፡ ዝርዝሮች ፡ ፬ ፡ ናቸው ፡ ከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ። ኦ ፡ እየገባባቸው ፡ ሳይገባባቸውም ፡ ብቻቸውን ፡ እየተጠሩ ፡ ይሰማሉ ። ኦ ፡ ቢጽየ ፡ ኦ ፡ እግዚእ ፥ ኦ ፡ ብእሲቶ ፡ ኦ ፡ አንትሙ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፥ ኦ ፡ አዋልድየ ። ኦ ፡ ሲቀር ፥ ስምዐኒ ፡ እግዚኦ ፡ ስምዒ ፡ ወለትየ ፡ አጽምዑ ፡ ሕዝብየ ፡ አዋልደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኢትብክያ ፡ ላዕሌየ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። እነዚህም ፡ ፬ቱ ፡ ቅርቦች ፡ በ፮ ፡ ነገር ፡ ይሰማሉ ፡ በማሰሪያ ፡ አቅራቢ ፡ በንቀጽ ፡ አቅራቢ ፥ በቅጽል ፡ አቅራቢ ፥ በባለቤት ፡ አቅራቢ ፡ በዘርፍ ፡ አቅራቢ ፡ በገባብ ፡ አቅራቢ ፡ ይሰማሉ ። በማሰሪያ ፡ አቅራቢ ፡ ሲሰሙ ፡ ኦ ፡ አብ ፡ ፈኖከ ፡ ወልደ ። በንቀጽ ፡ አቅራቢ ፡ አመ ፡ ፈነውከ ፡ ወልደ ። በቅጽል ፡ አቅራቢ ፡ ፍቁርከ ። በባለቤት ፡ አቅራቢ ፡ ተሰቅለ ፡ ወልድከ ። በዘርፍ ፡ አቅራቢ ፡ ወልደ ፡ ብሕርይከ ። በገባብ ፡ አቅራቢ ፡ አንቃዕደወ ፡ ኀቤከ ። ሰሚ ፡ ከክፍል ፡ ወዲህ ፡ ኹኖ ፡ ከክፍል ፡ ወዲያ ፡ ያለውን ፡ አይሰማም ፡ ይህም ፡ ኦ ፡ አብ ፡ ይነብሩ ፡ እሕዛብ ፡ በአም

ልክ ፡ ጣዖት ፡ ባሕቱ ፡ አሉ ፡ አክ ፡ ሕዝብክ ፡ አለማለቱን ፡ ያሳያል ። እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ ከዋዊ ፡ በታች ፡ ኹና ፡ ከዋዌ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ አይሰማም ፡ ይህም ፥ አ ፡ አብ ፡ አይሁድ ፡ ዐለዉ ፡ ሕገ ፡ ወሰቀሉ ፡ ወልደከ ፡ አለማለቱን ፡ ያሳያል ። ፫ኛም ፡ አአ ፡ ተብሎ ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ ሲነገር ፡ ኡኡ ፡ ይኾናል ፤ የፈታና ፡ የቡታ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ያለኽ ፡ ድረሱልኝ ፡ ማለት ፡ ይሰማበታል ። ሆይ ፡ ሆይ ፡ ተብሎም ፡ ሲፈታ ፡ የከፋ ፡ አንክሮና ፡ ቃለ ፡ አፍርሆ ፡ ነው ፡ የጭንቅና ፡ የመከራ ፡ ብዛት ፡ ያሳያል ። አአ ፡ ጉዩ ፡ እምሰሚን ።

፺፰ ፡ አሌ ፡ ወይ ፡ ወይሌ ፡ ሰይ ። ኹሉም ፡ ቃለ ፡ ብካይ ፡ ናቸው ፡ ወዮ ፡ ወየው ፡ ወዮታ ፡ እዬዬ ፡ ይኾናሉ ። አሌ ፡ ሎ ፡ አሌ ፡ ላ ፡ ወይ ፡ ሊተ ፡ ሰይ ፡ ልየ ፡ ወይሌ ፡ ለቅጥቃጤየ ፡ እያሰኙ ፡ በለ ፡ ሲገቡ ፥ ወዮልኝ ፡ ወዮታ ፡ አለብኝ ፡ ወዮታ ፡ ይገባታል ፡ ወይሌ ፡ ላዕለ ፡ ናባው ፡ ወዮታ ፡ አለባት ፡ ያሰኛሉ ። ብቻቸውንም ፡ ወይ ፡ እኑየ ፡ ወይ ፡ እግዚእየ ፡ እያሉ ፡ በቅርብ ፡ በቅርብ ፡ ይገባሉ ።

አህ ፥ አሀሀ ፡ ዬ ፡ ሐዊሳ ። አህ ፡ አሀሀ ፥ የአንክሮና ፡ የደስታ ፡ የሐዘንና ፡ የነቀፌታ ፡ ነው ፡ የአንክሮና ፡ የደስታ ፡ ሲኾን ፡ እዬ ፡ እዬ ፥ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ይኾናል ። አህ ፡ አህ ፡ አንደደኒ ፡ ፍቅርከ ። አህ ፡ አህ ፡ ለድምፀ ፡ ቅኔሆሙ ። ሐዘንና ፡ ነቀፌታ ፡ ሲኾን ፡ ወዷያ ፡ ወዷያ ፡ ጓድጓ ፡ ይኾናል ፡ አህ ፡ አህ ፡ እምዝተ ፡ ኀፍረት ። አህ ፡ አህ ፡ እምዝተ ፡ ሕሥም ። ዬ ፡ የልቅሶና ፡ የደስታ ፡ ቃል ። የልቅሶ ፡ ሲኾን ፡ በቁሙ ፡ ወዮ ፡ ወየው ፡ እዬዬ ፡ ይኾናል ። ዬ ፡ ዬ ፡ ዬ ፡ አውረድዎ ፡ እምዕፀ ። የደስታ ፡ ሲኾን ፡ እንሆ ፡ ዕሠይ ፡ ይኾናል ። ዬ ፡ መስቀል ፡ ጸገየ ። አንፈርዐጹ ፡ ሰብእ ፡ ሰገል ፡ ረኪቦሙ ፡ ሕፃን ፡ ዘተወልደ ፡ ለነ ፥ ዬ ፡ ዬ ፡ ዬ ። ሐዊሳ ፡ የደስታና ፡ ያንክሮ ፡ ቃል ፡ ዕሠ ፡ ዕሠ ፡ ይኾናል ። ሐዊሳ ፡ ለምጽአትከ ። ሐዊሳ ፡ ሐዊሳ ፡ ለዝንቱ ፡ ሐዋርያ ። ምስጢሩ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ከማየት ፡ ከመስማት ፡ የተነሣ ፡ ራስን ፡ ዐንገትን ፡ በመነቅነቅና ፡ በማድነቅ ፥ ወሰው ፡ ወሰው ፥ መልካም ፡ መልካም ፥ ይበል ፡ ይበል ፡ ማለትን ፡ ያሳያል ። በሓ ፡ በአድንኖተ ፡ ርእስ ፡ የሚነገር ፡ የሰላምታ ፡ ቃል ፥ ሰላም ፡ ለከ ፡ ይኾናል ፡ በሓከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ እያለ ፥ ሳይዘረዘርም ፡ በሓ ፡ ንጉሥነ ፡ ለአይሁድ ፡ እያሰኘ ፡ በራቱ ፡ ቀርቦች ፡ ይነገራል ።

፺፱ ፡ እስኩ ፡ ዮጊ ። እንጋ ፡ እንዳዒ ። እስኩ ፡ እስኪ ፡ ይኾናል ፡ ጥያቄ ፡ በሌለው ፡ ቃል ፡ በሚልሳይ ፡ አንቀጽ ፡ ቀድሞ ፡ ተከትሎ ፡ ይገባል ። እስኩ ፡ ንግረኒ ፡ ምንትኑ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡ ዘትሜህር ። ንግረኒ ፡ እስኩ ፥ ሰብአ ፡ ርሚን ፡ አንተ ። እስኩ ፡ ፍትሑ ፡ ለሊክሙ ። እስኩ ፡ በሎሙ ። ዮጊ ፡ እንሆ ፡ አኹን ፥ ወይ ፡ ምናልባት ፡ ይኾናል ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ። እምትሥዒ ፡ ለአማልክት ፡ ወእምሰጣኑ ፡ ታዕርጊ ፥ ተመትሮት ፡ ከሣድ ፡ አብደርኪ ፡ ወኀረይኪ ፡ ዮጊ ። ኀሥሥ ፡ ለዐርክከ ፡ ዮጊ ፡ ኢገብረ ። ኢትፍቅድ ፡ ከዊነ ፡ መኰንን ፡ ዮጊ ፡ ኢትክል ፡ ተበቅሎቶ ፡ ለዘአበሰ ፥ ወዮጊ ፡ ታደሉ ፡ ለገጸ ፡ ዐቢይ ። እንጋ ፡ እንዳዒ ፡ ንኡስ ፡ ቀጽልና ፡ የጥያቄ ፡ አገባብ ፡ እየተከተሉ ፡ ሲገቡ ፡ እንጃ ፡ ይኾናሉ ፡ ምስጢራቸው ፡ ምኞትና ፡ አንክሮ ፡ ጥርጥር ፡ ያሳያል ። አሐዱኑ ፡ እንጋ ፡ እስከ ፡ እማንቱ ፡ መዋዕል ። መኑ ፡ እንጋ ፡ ይክል ፡ ድኂነ ። እንዳዒ ፡ እመ ፡ ብ ፡ ዘኀለየ ፡ ልብከ ። እንጋ ፡ ተለይዎ ፡ አለጥያቄ ፡ በኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ሲገባ ፡ እንሆ ፡ ይኾናል ። እንጋ ፡ በጽ

ሐት ፡ ኀቤክሙ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ። በነባር ፡ አንቀጽም ፡ እነሁ ፡ እንጋ ፡ እግዚአ ፡ እያለ ፡ ይገባል ።   እንዳዒ ፤ እንጂ ፡ ሲኾን ፡ ርእየ ፡ ሰምዐ ፡ አእመረ ፡ እንዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ግሶች ፡ ይወርሳል ። እንጃ ፡ ማለት ፡ አላየኹም ፡ አልሰማኹም ፡ አላውቅም ፡ ማለት ፡ ነው ። እንዳዒ ፡ አ.ያእመርነ ፡ ከመ ፡ ይመልእ ፡ ነፉሉ ፡ ዝቅ ፡ ወይነ ፡ እንዳዒ ፡ እመ ፡ ብ ፡ ዘትለይከ ። እሉቃውንትም ፡ በጽድቅ ፡ ውጥን ፡ ይጨርሳል ። እልዐ ፡ ዘየዐብየኒ ፡ በዝንቱ ፤ እንዳዒ ፡ ገብርኤል ።

፺፯ ፡ ከመ ። ጽመ ፡ ጽሚተ ። ኳ ። እንቋዕ ። ጥቀ ።   ከመ ፡ ብቻ ፡ መቼም ፡ መች ፤ ድንት ፡ ይኾናል ፡ ኹሉም ፡ የጊዜ ፡ ነው ። ብቻ ፡ ሲኾን ፤ ሐቀ ፡ ከመ ፡ ንሰቲት ፡ ከመ ፤ ተርፎሙ ፡ ይላል ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ማለት ፡ ነው ። መቼም ፡ መች ፡ ሲኾን ፡ ሂ ፡ ኒ ፡ ትራስ ፡ እየኾኑት ፡ ሳይኾኑትም ፡ ብቻውን ፡ ይገባል ። ከመኒ ፡ ኢ.ወረደ ፡ እይኑ ፡ ከመ ፡ እመ ፡ ዋኑ ። ከመ ፡ ኢ.ከነ ፡ ዕረፍት ፡ ለእስራኤል ፡ ከመ ፡ እመ ፡ ንገሥ ፡ ሰሎሞን ። እንተሰ ፡ እንተ ፡ ከመ ። ድንት ፡ ሲኾን ፡ በደዳት ፡ በምዋት ፡ ይገባል ፡ ሰበ ፡ ኢ.ዐሌወ ፡ እው ፡ ሰበ ፡ ኢ.የዐሉ ፡ አዳም ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚኡ ፡ ከመ ፡ እምንበረ ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ በከመ ፡ ይነብሩ ፡ ሔዋክ ፡ ወኤልያስ ። ንበር ፡ ከመ ፡ ያንብርከ ፡ ከመ ፡ እያለም ፡ በማሊሳይ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባል ።   ጽመ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፤ ቀስ ፡ ብሎ ፤ ዝግ ፡ ብሎ ፡ ይኾናል ። መጽአ ፡ ጽመ ፤ ይመጽእ ፡ ጽመ ፤ ነበ ፡ ጽመ ፤ ሐረ ፡ ጽመ ፡ ብላሰ ፡ ጽመ ፡ እያለ ፡ በዘማች ፡ አንቀጽ ፡ ይገባል ።   ጽሚተ ፡ ጽምሚተ ፡ በዝምታ ፡ በቀስታ ፡ በስውር ፡ ይኾናል ፡ ኢ.ፈቀደ ፡ ይክሥታ ፡ አላ ፡ መከረ ፡ ጽሚተ ፡ ይኅድጋ ። እልዐ ፡ ዘተናገርኩ ፡ ጽሚተ ፡ ሰውሬ ፡ በስውር ።   ኳ ፡ እከ ፡ ቢያ ፡ እንኳ ፡ ይኾናል ፡ ትራስ ፡ እየኾነ ፡ በቃል ፡ መጨረሻ ፡ ይገባል ። እከ ፡ ቢያ ፡ ሲኾን ፤ እንግዚህ ፡ እንደ ፡ እስመ ፡ ነው ፡ የእስመን ፡ ርዋውን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። እንኳ ፡ ሲኾን ፤ በብቻን ፡ ይገባል ፡ ሕሡመ ፡ ይሚንዋ ፡ ኳዋእ ፡ ለጻድቅ ፡ ገዘሰ ፡ ይትርፍ ፡ ቀቲሎቶ ፡ ኳ ፤ ይትቀተሉ ፡ ኳ ፡ ይትሜነዩ ።  መግደሉን ፡ እንኳ ፤ ሊገድለው ፡ እንኳ ፡ ይመኛል ።   እንቋዕ ፡ የደስታ ፡ ቃል ፤ እንኳስ ፡ ይኾናል ፡ ዕፁይ ፡ ዕፃ ፡ ወሰው ፡ ውሸን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በነላፊና ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ። እንቋዕ ፡ ተሰብረት ፡ ማዕጾ ፡ አሕዛብ ። እሰ ፡ ይብሉኒ ፡ እንቋዕ ፡ እንቋዕ ።   ጥቀ ፡ ስንኳን ፡ ይኾናል ። ወ ፡ ሂ ፡ ኒ ፡ ስንኳን ፡ ሲኾኑ ፡ ይሰማሙ ቃል ። ይቤሉ ፡ ለዘይቤሉ ፡ ትፈቅድኑ ፡ ይሙት ፡ እጐየ ፤ ጥቀ ፡ ይሙት ፤ ጥቀ ፡ ሞት ፡ ሕማምኒ ፡ ወሕማምሂ ፤ ሕማም ፡ ኳ ፡ ኢ.ይረከበ ። አብርሃም ፡ ጥቀ ፡ ሞተ ፡ ወነቢያትኒ ፡ ሞቱ ። እልዐ ፡ ዘመድ ፡ ጊዜ ፡ ተዋርዶ ፡ ወይከውን ፡ በሰዶ ፡ ጊዜ ፡ ተዋርዶ ፡ ዘመድ ፡ እመሰ ፡ ይትሌዐል ፡ በንብረተ ፡ ሥጋ ፡ ማእደ ፤ ጥቀ ፡ ዘመዱ ፡ ወጥቀ ፡ ነገድ ፤ ባዕድ ፡ ይዘመድ ። እንኳንና ፡ እንኳ ፡ እንኳስና ፡ ስንኳን ፡ ልዩ ፡ ልዩዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ እስተውል ። እንኳን ፡ የእከ ፡ ፍች ፡ ነው ፡ ምስጢሩም ፡ እሉታ ። እንኳ ፡ የኳ ፡ ፍች ፡ ነው ፡ ምስጢሩም ፡ እንክርና ፡ ምዋት ፡ ማበላለጥ ፡ ነው ፡ በማበላለጡ ፡ ከጥቀ ፡ ይጎራበታል ። እንኳስ ፡ የእንቋዕ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ምስጢሩም ፡ ደስታ ። ስንኳን ፡ ግን ፡ የማማረጥና ፡ የማሻሻል ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ከኳ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ አይመሳሰልም ።

፺፰ ፡ እንከ ። እምዮም ፤ እምይእዜ ።  እንከ ፤ እንኪያ ፡ እንግዲህ ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ እንዛ ፡ ይኾናል ፡ የነገር ፡ ዚቅ ፡ ወይም ፡ ዝዬ ፡ ይብላል ። ክኹን ፡

ዝምድ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሚመጣ ፡ ነገር ፡ ቃልን ፡ ተከትሎ ፡ ይገባል ፡ ሰና ፡ ኬ ፡ ትራስ ፡ ሲኾኑት ፡ ግን ፡ በፊትም ፡ በኋላም ፡ ይገባል ። እንኪያ ፡ ሲኾን ፡ ያቤሎ ፡ ለዘያቤሎ ፡ አልብየ ፡ መፍቅድ ፡ ኀቤከ ፡ ለምንት ፡ እንከ ፡ መጻእከ ፡ ኀቤየ ፡ እንኪያ ፡ ወደኔ ፡ ለምን ፡ መጣኽ ። ዘትገብር ፡ እንከ ፡ ፍጡነ ፡ ግበር ። ትሬኢ ፡ እንከ ፡ ዘየዐቢ ፡ ኀጢአተ ፡ እንግዴህ ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲህ ። እንከሰ ፡ አወቅዎ ። ግበሩ ፡ እንከሰ ። እንከሰኬ ፡ ይብልዎ ፡ ፍሬ ፡ ምግባሮሙ ፡ እንግዲህስ ። ኀደገት ፡ እንከ ፡ ብሂሎታ ። ወኢይሰማዕ ፡ እንከ ፡ ዐመፃ ። አልቦ ፡ እንከ ፡ መዋልት ፡ ወኢሌሊት ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ። ሀለዉ ፡ እንከ ፡ ኀቤነ ፡ ክልኤቱ ፡ ኣኅው ፡ እንሆ ። እንከ ፡ እንሆ ፡ መኾኑ ፡ በናሁ ፡ ፈንታ ፡ ሲገባ ፡ ነው ። እምየውም ፡ እምይእዜም ፡ እንከ ፡ በገባበት ፡ እየገቡ ፡ የርሱን ፡ እፈንታት ፡ ይወርሳሉ ።

፺፱ ፡ አ ፡ ሰ ፡ ኬ ። አ ፡ ቃለ ፡ መልእክት ፡ ነው ፡ ትራስ ፡ እየኾነ ፡ በኹሉ ፡ ይገበል ፡ ምስጢሩም ፡ ቊልምማና ፡ ከበረታ ፡ ነው ። በቅርብ ፡ ሲገባ ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ፡ ቃለ ፡ አስተብቍዖ ፡ ቃለ ፡ ተጋንዮ ፡ ይኾናል ። አስተብቍዖ ፡ ሲኾን ፡ ፍችው ፡ እባክኽ ፡ ነው ፡ ያንን ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ ያናግራል ። ተጋንዮ ፡ ሲኾን ፡ መድረሻውን ፡ ፊደል ፡ እንደ ፡ ኬ ፡ ራብዕ ፡ ያደርጋል ፡ በትርጓሜ ፡ በማርኛም ፡ እኮ ፡ ይኾናል ። መልእክት ፡ ሲኾን ፡ ፈነወኩአ ፡ ያዜንወዎሙ ፡ ለእግዚእየ ፡ ዔሳውአ ፡ ከመአ ፡ እርኩብአ ፡ ሞገሰአ ፡ ይላል ። አጋኖ ፡ እንተኑአ ፡ ውእቱ ፡ ግብጻዊ ። እንተኑአ ፡ ዘይመጽእ ፡ ወሚመ ፡ ካልእ ። አስተብቍዖ ፡ አ ፡ እግዚአ ፡ አድኅንአ ፡ አድኅነነአ ፡ እባክኽ ፡ አድነን ፡ ወይም ፡ በደጊም ፡ እባክኽ ፡ እባክኽ ፡ አድነን ፡ አድነን ፡ ያሰኛል ። ተጋንዮ ፡ እግዚእየአ ፡ እኁየአ ፡ እያለ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ሲገባ ፡ ጌታዬዋ ፡ ወንድሜዋ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ፊቱ ፡ ጌታዬ ፡ ጌታዬ ፡ ወንድሜ ፡ ወንድሜ ። ሀበኒአ ፡ ኅድገኒአ ፡ እያለም ፡ ሲገባ ፡ በደጊም ፡ ይፈታል ፡ ወይም ፡ ስጠኝ ፡ ተወኝ ፡ ስጠኝ ፡ እኮ ፡ ተወኝ ፡ እኮ ፡ እያሰኘ ፡ ለክፉም ፡ ለበጎም ፡ ይኾናል ። ሰ ፡ ከአ ፡ የበረታ ፡ የልመና ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ፍርዋ ፡ በለው ፡ ነገር ፡ በሚልሳይ ፡ እንቀጽ ፡ እየገባ ፡ እባክኽ ፡ ይኾናል ። ወይም ፡ እንቀጽ ፡ ይዘረዝራል ። እምላክ ፡ ኅያላን ፡ ተመየጥሰ ፡ ተመየጠነ ፡ ተመየጥ ፡ ለነ ። አድኅንሰ ፡ ሠርሕሰ ፡ አድኅነነ ፡ ሠርሐነ ፡ ሠርሕ ፡ ለነ ። ኬ ፡ እንደ ፡ አ ፡ ትራስ ፡ እየኾነ ፡ በኹሉ ፡ ሲገባ ፡ መድረሻውን ፡ ፊደል ፡ ራብዕ ፡ ያደርጋል ፡ ምስጢሩም ፡ ማጋነንና ፡ ማስደነቅ ፡ ነው ። እንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ራብዕ ፡ ሳያደርግ ፡ አጋኖ ፡ ይቀራል ፡ ወይም ፡ ማ ፡ ይኾናል ፡ ማ ፡ መኾኑም ፡ በመ ፡ ፈንታ ፡ ገብቶ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ፡ ይምጽኡኬ ፡ ያርእዩ ። ውእቱኬ ፡ ዘወረደ ። ገቢኬ ፡ እፎ ፡ ይሁሰ ። ምንተኬ ፡ ሰብአ ። ምንትኬ ፡ ዘአማሰነ ፡ ዐውያት ። ማ ፡ ሲኾን ፡ ጽናሕኬ ፡ ጽንሒኬ ። እንተኬ ፡ ትሰመይ ፡ ኬፋ ፡ እያሰኘ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ይገባል ።

## አሉታ ፡ የጽድቅ ፡ መከታ ።

፻ ፡ አል ፡ ኢ ። አል ፡ የኢ ፡ ፍች ፡ ነው ፡ አሉታንቱም ፡ ያማርኛና ፡ የዕብራይስጥ ፡ እንጂ ፡ የግእዝ ፡ አይደለም ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ከበ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ገብቶ ፡ አይገኝም ፡ በ ፡ አልቦ ። ኢ ፡ በአናቅጽ ፡ ኹሉ ፡ እየገባ ፡ ጽድቁን ፡ አሉታ ፡ ያደርጋል ፡ ሲፈታም ፡ ም ፡ ጽንዕ ፡ እየኾነው ፡ ሳይኾነውም ፡ በኋላፊ ፡ አል ፡ በትንቢትና ፡

በትእዛዝ ፡ አ ÷ በዘንድ ፡ እንዳ ፡ ላ ፡ ሳ ፡ ይኾናል ። ይህም ፡ ኢበልዐ ፡ አልበላ ÷ አልበላም ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ጕዟዥም ፡ አልበልቶም ፡ ኢይበልዕ ፡ አይበላ ÷ አይበላም ። ኢይብላዕ ፡ እንዳይበላ ÷ ላይበላ ፡ ሳይበላ ÷ ኢይብላዕ ፡ አይብላ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። በዐዝም ፡ ሲገባ ፡ ኢነጊሥ ፡ ዳዊት ፡ ኢተዘኪሮ ፡ አበሳነ ፡ ብሎ ÷ ሳይነግሥ ፡ ሳያስብ ፡ ያሰኛል ፡ (፸፫ ፡ ክፍል ፡ ፳፭ ፡ ፲) ። በሣልስ ፡ ቅጽልም ÷ ቃል ፡ ኢሐማሚ ፡ በባሕርዩ ፡ ሥጋ ፡ ዘሐመ ፡ ትውልድ ፡ ኢአማኒት ፡ እያለ ፡ ሲገባ ÷ ያላመነች ፡ የማታምን ፡ ተብሎ ፡ በዝ ፡ ዐማርኛ ፡ ይፈታል ። በሳድስ ፡ ቅጽልም ፡ ኢርቱዕ ÷ ኢመፍትው ፡ ሲል ፡ ያልቀና ፡ ያልተገባ ፡ ያሰኛል ። በዝ ፡ ዐማርኛ ፡ መፈታቱ ፡ ቅጽሉ ፡ በቂ ፡ ሲኾን ፡ ነው ፡ አለዚያ ፡ ግን ፡ ኢ ፡ እንዳንቀጽነቱ ፡ አይዶለም ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ። ማስረያውም ፡ አሉታ ፡ ኹኖ ፡ ወን ፡ እያስከተለ ፡ ሲደረደር ፡ አንቀጽ ፡ እንጂ ፡ አገባብ ፡ አይኾንም ። ፍችው ፡ ግን ፡ ኹኖ ፡ ሲባል ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ ነው ፡ የኹኖም ፡ ምስጢር ፡ እንደ ፡ ወ ፡ ማማፈር ፡ ነውና ፡ አልቦ ፡ በገ፤ ፡ መዋዕል ፡ መልአክ ÷ ኢነቢይ ፡ ወኢንጉሥ ፡ ኢቍርባን ፡ ወኢመሥዋዕት ፡ ነቢይ ፡ የለም ፡ ንጉሥም ፡ የለ ፡ ቍርባን ፡ የለም ፡ መሥዋዕትም ፡ የለ ፡ እያሰኘ ፡ በየደጁ ፡ ያስራል ፡ አገባብ ፡ ሲኾን ፡ ግን ÷ ነቢይ ፡ ኹኖ ፡ ንጉሥም ፡ ኹኖ ÷ ቍርባን ፡ ኹኖ ፡ መሥዋዕትም ፡ ኹኖ ፡ እያለ ፡ በአልቦ ፡ ያስራል ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ እንበለ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ያለ ፡ ይኾናል ፡ በብትን ፡ በርእስት ፡ በጥሬ ፡ ይገባል ። እንበለንም ፡ እየተከተለ ፡ ዘእንበለ ፡ ተምያጥ ፡ ወኢተውላጥ ÷ ኢቡዓደ ፡ ወኢቱስሕት ፡ ብሎ ፡ ሲገባ ÷ አንቀጽና ፡ አገባብ ፡ እየኾነ ፡ በንቀጽነቱ ፡ ሳይኖር ፡ በገባብነቱ ፡ አለ ፡ ያለ ፡ ያሰኛል ። በ ፡ ለ ፡ በጥሬ ፡ በርእስት ፡ ዘ ፡ በቅጽል ፡ ይሰማሙታል ። ግብር ፡ ዘይትገበር ፡ በኢምክር ፡ ወበኢለብዎ ፡ እበድ ፡ ውእቱ ። ማርያምሰ ፡ ፍኅርተ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ዘኢፍኅርት ፡ ምክራብ ÷ ማኅደሩ ፡ ለኢሩካቤ ፡ ወምስራፉ ፡ ለኢሰብሳብ ። እብዳን ፡ ወጕንዱያን ፡ ልብ ፡ ለኢአሚን ። ዘ ፡ ሲሰማማው ፡ በቅጽል ፡ ይገባል ፡ ምንት ፡ ብከ ፡ ዘኢንሣእከ ፡ እምክልእከ ። ኢትንሣእ ፡ ዘኢያንበርከ ። በርእስትም ፡ ብቻውን ፡ ሲገባ ፡ ኢበሊዐ ፡ ሥጋ ፡ ወኢሰትየ ፡ ወይን ፡ ብሎ ፡ አለመብላት ፡ አለመጠጣት ፡ ያሰኛል ። በማርኛም ፡ ኢ ፡ በቍመ ፡ ኢ ፡ ወይም ፡ አይ ፡ አዩ ፡ ተብሎ ፡ ሲነገር ፡ ቃለ ፡ አኅስሮ ፡ ነው ፡ ሐዘንና ፡ አንክሮም ፡ ይኾናል ። ያሉታም ፡ ዐቀጅ ፡ በብሂል ፡ ሲነገር ፡ ብሀሉ ፡ ፪ ÷ ክፍሉ ፡ ፬ ፡ ነው ፡ ፩ኛውና ፡ ፫ኛው ፡ ፪ኛውና ፡ ፬ኛው ፡ አንዳንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ፩ ፡ አሉታ ፡ ፍጹም ፡ አሉታ ፡ ፪ ፡ አሉታ ፡ ፍጹም ፡ ጽድቅ ፡ ፫ ፡ አሉታ ፡ ፍጹም ፡ አሉታ ። ፬ ፡ አሉታ ፡ ፍጹም ፡ ጽድቅ ፡ ይኾናል ። አንድ ፡ አሉታ ÷ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ደዌ ፡ ንስጥሮስ ፡ ባዕል ÷ እንበለ ፡ ኢብሂል ፡ ብሂለ ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ድንግል ። ፪ ፡ አሉታ ÷ ኢደለዎ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሰብእናሁ ፡ ኢብሂል ፡ ከማን ፡ አምላኪየ ፡ ወላዲሁ ። ሦስት ፡ አሉታ ÷ ደለዎ ፡ ለክርስቶስ ፡ በመለኮቱ ፡ ኢብሂል ፡ አከ ፡ አነ ፡ ወአብ ፡ አሐዱ ፡ ንሕነ ÷ በከመ ፡ ደለዎ ፡ ኢብሂል ፡ ዘርእየ ፡ ኪያየ ፡ ርእዮ ፡ ለአቡየ ። አራት ፡ አሉታ ÷ ተውህቦ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ጸጋ ፡ ኢብሂል ፡ ኢሞተ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ÷ በከመ ፡ ተውህበ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሀብተ ፡ ኢብሂል ፡ ኢተማህለነ ፡ አብ ፡ በሞተ ፡ ወልዱ ።

፻፬ ፡ አው ፡ ሚመ ። ወይ ፡ ወይም ፡ ወይስ ፡ ይኾናሉ ፡ ጥያቄ ፡ በለው ፡ ቃል ፡ ተከትለው ፡ ሳይከተሉም ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ይገባሉ ። ምስጢራቸውም ፡ ማሻሻልና ፡ ማማ

ረጥ ፥ ማኔጻጸርና ፡ ማበላለጥ ፡ ነው ፡ ዋዌነትም ፡ አለው ፡፡ ሲገቡም ፡ አው ፡ ቀድሞ ፡ ሚመ ፡ ይከተላል ፡፡ ኢትቁም ፥ አው ፡ ንበር ፥ ወሚመ ፡ ሑር ፡፡ እየብቻቸውም ፥ በሕርኑ ፡ እነ ፥ አው ፡ ቀላይ ፡፡ እምሰማይኑ ፡ ወሚመ ፡ እምሰብእ ፡ ያስኖሉ ፡፡ ተደጋግመውም ፡ ሲነገሩ ፡ አው ፡ ብቻውን ፥ ሚመ ፡ በወ ፡ ይደገማል ፡፡ አው ፡ ሠምዕ ፥ አው ፡ ዘይት ፡፡ ሚመ ፡ ተፈጥሮ ፡ ወሚመ ፡ ኢተፈጥሮ ፡፡ አው ፡ ተለይቶ ፡ ዋዌ ፡ ይኾናል ፡ አው ፡ ሑር ፡ ኅበ ፡ ንህብ ፡፡ አው ፡ ከልእት ፡ ሀገር ፡፡

፻፸፪ ፡ ወ ፡፡ ስሙ ፡ በፊደልነት ፡ ሲጠራ ፡ ዋዌ ፡ ይባላል ፡ ማንጦ ፡ ቍልፍ ፡ ዘለበት ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ በዕብራይስጥም ፡ ዋው ፡ የመስኮት ፡ ስናግ ፡ ቈላፋ ፡ ብረት ፡ ነው ፡ በተግናኝ ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ የወል ፡ እንደ ፡ ምሰሶ ፡ የመካከል ፡ ኹኖ ፡ ግራና ፡ ቀኙን ፡ የሚያያይዝና ፡ የሚያቈራኝ ፡ አያያዥ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ ዘለበትም ፡ ሲባል ፡ በግብሩ ፡ ላይ ፡ መልኩን ፡ ፊውምሮ ፡ ያሳያል ፡፡ ወ ፡ በገባብነቱ ፡ ም ፥ ና ፡ ዘተረስዐ ፥ ቸልታ ፥ ውጥን ፡ ፊሬሽ ፥ ጠቅላይ ፥ ከ ፥ ጊዜ ፥ ስንኳ ፥ እንጂ ፥ ግን ፥ ል ፥ ስ ፥ አዳማቂ ፡ ይኾናል ፡ ምንም ፡ ያማርኛው ፡ ስልት ፡ ቢበዛ ፡ ምስጢሩ ፡ ማያያዝና ፡ ማጫፈር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡፡ ም ፡ ሲኾን ፡ ተሳቢውን ፡ ከቶ ፡ በሚጫፈር ፡ አንቀጽ ፡ ይገባል ፡ ናሁ ፡ ትፀንሲ ፡ ወትወልዲ ፡ ወልደ ፥ ወትሰምዪዮ ፡ ስሞ ፡ ኢየሱስ ፡፡ ተሳቢ ፡ በሌለው ፡ በድርድር ፡ አንቀጽ ፡ ግን ፡ ጠቅላይ ፡ እንጂ ፡ ም ፡ አይኾንም ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ወተቀብረ ፡፡ ወተንሥአ ፡ እሙታን ፡ አመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ ሲል ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተሳቢው ፡ ም ፡ ይኾናል ፡፡ ና ፡ ሲኾን ፡ ዘተረስዐ ፡ ነው ፡ በስምና ፡ በንቀጽ ፡ እየገባ ፡ በሎደቀበት ፡ ላይ ፡ የኋሊት ፡ ይፈታል ፡፡ በስም ፡ ሚካኤል ፡ ወገብርኤል ፡ ጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስ ፡፡ በንቀጽ ፥ ሖረ ፡ ወመጽአ ፥ ቦአ ፡ ወወፅአ ፥ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ኼደና ፡ መጣ ፥ ወይም ፡ ኼዶ ፡ መጣ ፡ እያሰኘ ፡ ዘተረስዐነቱን ፡ ያሳያል ፡፡ ቸልታ ፡ ሲኾን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በወደቀበት ፡ ላይ ፡ ይፈታል ፡ ተንሥአ ፡ ወኀደገ ፡ ልብሶ ፥ ተጠምቀ ፡ ወአድኀነ ፡ ርእሶ ፥ ልብሱን ፡ ጥሎ ፡ ራሱን ፡ አዘንብሎ ፡፡ ውጥንም ፡ ሲፈርስ ፡ በኋላ ፡ ኹኖ ፡ የፊቱን ፥ በፊት ፡ ኹኖ ፡ የኋላውን ፥ የወንዱን ፡ በሴት ፡ ያንዱን ፡ በብዙ ፥ የብዙውን ፡ ባንድ ፡ ያናግራል ፡፡ በኋላ ፡ ኹኖ ፡ የፊቱን ፥ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ የኀልፍ ፡ ሰማይ ፡ ያልፋል ፥ ምድርም ፡ ታልፋለች ፡ ምድር ፡ የፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ እናት ፡ ስለ ፡ ኾነች ፡ በሴት ፡ አንቀጽ ፡ እንጂ ፡ በወንድ ፡ አትጠራም ፡፡ በፊትም ፡ ኹኖ ፡ የኋላውን ፥ መጽአ ፡ ዝኩ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲቱ ፡፡ ባሉቃም ፡ ኢክነ ፡ ደብር ፡ ገብረ ፡ ወኢይክውን ፡ ወኢወግር ፡ አመተ ፡ ለብእሲት ፡፡ ያንዱን ፡ በብዙ ፥ ተውህበ ፡ ጳውሎስ ፡ ሙቁሐ ፡ ወከልአንሂ ፡ ሙቁሓን ፡፡ አገብአ ፡ ለኤልዛቤል ፡ ወለእለ ፡ ዘመሀኒ ፡ ምስሌሃ ፡፡ የብዙውን ፡ ባንድ ፥ ተሰቅሉ ፡ ፈያት ፡ ወክርስቶስኒ ፡ ኅቡረ ፡ ምስሌሆሙ ፡፡ ሩቅና ፡ ቅርብም ፡ ሲወጥን ፡ እንደዚሁ ፡ ያናግራልና ፡ አስማምተኸ ፡ አግባ ፡፡ ጠቅላይ ፡ ሲኾን ፡ ባንቀጽና ፡ በስም ፡ በአኃዝ ፡ ይገባል ፡ ያንቀጹ ፡ ተነግሯል ፡፡ በ፫ ፡ ስሞች ፡ ሲገባ ፡ ፩ኛውና ፡ ፪ኛው ፡ ጠቅላይ ፡ ይኾናል ፡፡ ጳውሎስ ፡ ወስልዋኖስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡፡ በሌላውም ፡ ጥሬ ፥ ክብር ፡ ወስብሐት ፡ ወዕዘዝ ፡ ሲል ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፡፡ በአኃዝ ፡ ሲገባ ፡ ካሥር ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ይጠቀልላል ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ ተስዐቱ ፡ ምእት ፡ ተስዓ ፡ ወተስዐቱ ፡ ከሺሕ ፡ በላይ ፡ ግን ፡ ከ ፡ ይኾናል ፡ ምስጢሩም ፡ ብዙውን ፡

ከዋቂት፡ ማመፈር፡ ነው። ኀምሳ፡ ወኀምስቱ፡ ምእት፡ እልፍ፡ ወሰማራ፡ ምእት። ጊዜ፡ ሲኾን፡ በዐዝ፡ ይገባል፡ አገባቡም፡ በ፱ና፡ ዐርከን፡ በ፰፡ ቍጥር፡ ተነግሯል። ስንኳ፡ እንጂ፡ ግን፡ ሲኾን፡ ነቃፊ፡ ነውና፡ ባሉታና፡ ባፍራሽ፡ ይገባል፡ ኢወሀበ፡ ርስቱ፡ ወኢመጠነ፡ ምምጋረ፡ እግር፡ አንዲት፡ ርምጃ፡ ስንኳ። በልዐ፡ ወኢሰትየ፡ አልጠጣም፡ እንጂ። እግር፡ በሙ፡ ወኢየሐውሩ፡ ያለውም፡ እንጂ፡ ተብሎ፡ ወይም፡ ጠቅላይ፡ ኹና፡ በትች፡ ቃል፡ አስዚያም፡ ዘተረስዐ፡ ኹና፡ በእንዘ፡ ዐማርኛ፡ ይፈቃል። እንኳ፡ ጴጥሮስ፡ ዕድሜሁ፡ ስብከተ፡ ወይሁዳ፡ አኀዘረ፡ ዕለተ፡ ይሁዳ፡ ግን። ል፡ ሲኾን፡ ስምዐኒ፡ ወእንግርከ፡ ቀረበኒ፡ ወእማስስከ፡ እያሰኘ፡ በማልሳይ፡ አንቀጽ፡ ይገባል። ስ፡ ሲኾን፡ በንኡስ፡ ይገባል፡ አይቱኑ፡ አሐውር፡ ወአይቴ፡ እኅድይ፡ ወደትስ። ምንተ፡ በልዐ፡ ወምንተ፡ ሰትየ፡ ምንስ፡ ጠጣ። አዳማቂ፡ ሲኾን፡ በጥንት፡ ነገር፡ ይገባል፡ ወሀሎ፡ አሐዱ፡ ብእሲ። ወከነ፡ በሠላሳ፡ ክረምት። ምስጢሩ፡ ግን፡ ከማቈራኘት፡ አይወጣም፡ የሚቀድመው፡ መጽሐፍ፡ አለና። ወንድና፡ ሴትም፡ ሲያመፍር፡ ተፈጥሩ፡ አዳም፡ ወሔዋን፡ ይላል፡ እንጂ፡ ሔዋን፡ ወአዳም፡ አይልም። ተመፋርሮች፡ ፪፡ ሲኾኑ፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ሴት፡ ያስቀድማል፡ ወረከብዎሙ፡ ለማርያም፡ ወለዮሴፍ፡ ወለሕፃንኒ። በመፋረንቱም፡ ዘርፍና፡ ቀጽል፡ እያተርፍም፡ ዘርፍ፡ አለማትረፉ፡ ባለቤት፡ መንታ፡ ሲኾን፡ ነው፡ ይህም፡ ኅሩያን፡ ወሠናያን፡ ሊባኖስ፡ ያለውን፡ ኅሩያን፡ ሊባኖስ፡ ብሎ፡ ወሠናያን፡ አለማለት፡ ነው። ቀጽል፡ አለማትረፉም፡ ብፁዕ፡ ጴጥሮስ፡ ወጳውሎስ፡ ሲል፡ ነው። በወ፡ የማይወርዱ፡ ፫፡ ናቸው፡ የግእዝ፡ ወራሽ፡ ሀ፡ የሙሻዘር፡ ውስጠ፡ ዘ፡ ዊ፡ ዝርዝር፡ አሉ፡ እም፡ ጸጸትና፡ ተምኔት፡ ሲኾን። ኀረዩ፡ እስጢፋኖስሀ፡ ወፊልጶስሀ። ክርስቶስ፡ ሰማያዊ፡ ወምድራዊ። ነአምን፡ ሕማሞ፡ ወሞቶ። ኢገብረ፡ ኀጢአተ፡ ወኢተረክበ፡ ሐሰት፡ ውስተ፡ አፉሁ። እመ፡ ነስሐ፡ ይሁዳ፡ እምጌድቀ፡ ብሎ፡ ወእምኢተኰነነ፡ ይላል፡ እንጂ፡ ወ፡ እምን፡ ያወርድልኛል፡ ብሎ፡ ወኢተኰነነ፡ አይልም።

፻፫፡ ሂ፡ ኒ፡ ዓዲ። ስማቸው፡ ማስረጃ፡ ከፋዮች፡ ማንጸሪያ፡ ትርጓሜያቸው፡ ም፡ ደግሞ፡ ይኾናል። ሂ፡ ኒ፡ በኋላ፡ ዓዲ፡ በፊትም፡ በኋላም፡ እየገቡ፡ ይነገራሉ። ንትሚ፡ ሰሎ፡ በሕይወቱኒ። የኀድግ፡ ለከሙኒ። ዓዲ፡ ናቄርብ፡ ለከ፡ ፊንወን፡ ምስሌሁ፡ ዓዲ። ሂ፡ ወኒ፡ ኒ፡ ወኒ፡ ም፡ ወይም፡ ደግሞ፡ ተብለው፡ ሲፈቱ፡ ምስጢራቸው፡ ማመፈርን፡ መደብ፡ አድርጎ፡ አንጻርንትና፡ ከፋይነት፡ አማራጭነት፡ ነው። ዘንተሂ፡ ወገከቶሂ። ገዝኒ፡ የኀልፍ፡ ወይሰዐር፡ ገዝኒ። ተደርድረውም፡ ሲያመፍሩ፡ ከሃሊ፡ አንሰ፡ ተጽናስሂ፡ ወተደልዎሂ፡ ርኅበሂ፡ ወጽገብሂ፡ ሐሚመሂ፡ ወተፈሥሖሂ፡ ያሰኛሉ። ፻፬ም፡ ሂ፡ ኒ፡ ሰ፡ ባሕቱ፡ ግን፡ ሲኾኑ፡ ከፋል፡ ናቸውና፡ ወ፡ ግን፡ ሲኾን፡ እንደ፡ ገባው፡ አግባ። ፻፭ም፡ ሂ፡ ኒ፡ ጥቀ፡ ን፡ በብትን፡ ሲገቡ፡ ስንኳ፡ ይኾናሉና፡ ወ፡ ስንኳ፡ ሲኾን፡ እንደ፡ ገባው፡ አግባ። ጥቀ፡ ን፡ በየብቻቸው፡ ተነግረዋል፡ የቀረውም፡ የሂና፡ የኒ፡ አገባብ፡ በኋላ፡ ተነግሯል።

፻፮፡ ቀድመ። ንኡስ፡ አገባብ። እም፡ እያዳመቀው፡ ሳያዳምቀውም፡ ብቻውን፡ በዘንድ፡ አንቀጽ፡ ግብጾ፡ ሳ፡ ይኾናል። እምቅድመ፡ ይትረክብ፡ ሰማያት። በሰ

ማይኒ ፡ ቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ኪሩብ ፡ ሰማዮች ፡ ሳይዘረጉ ፡ ኪሩብ ፡ ሳይፈጠር ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾን ፡ በፊት ፡ ይኾናል ፡ እምና ፡ በ ፡ እየተሰማሙት ፡ በበታ ፡ በጊዜ ፡ ይባል ፡ በበታ ፡ ዘሀሎ ፡ እምቅድመ ፡ ሀገር ። በ [illegible] ፡ ቤት ፡ እግዚአብሔር ። በጊዜም ፡ ሲገባ ፡ እምቅድመ ፡ ዳዊት ፡ በቅድመ ፡ ዳዊት ፡ ቅድመ ፡ ዳዊት ፡ ነግሠ ፡ ሳኦል ፡ ያሰኛል ። ሲዘረዝርም ፡ ቅድሜሁ ፡ ሃ ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ ሥር ፡ ይዘምታል ። የሚገባም ፡ ፊት ፡ በተደረገ ፡ ኋላም ፡ በማይቀር ፡ በቍርጥ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ የበታና ፡ የጊዜ ፡ ጥሬ ፡ ስለ ፡ ኾነ ።

## የጊዜያት ፡ ጥሬ ።

፻፳ ፡ ትካት ፡ ዓለም ። ዱሮ ፡ ጥንት ፡ ቀድሞ ፡ ይኾናሉ ። ትካት ፡ ብቻውን ፥ ሰብእ ፡ ትካት ። ሕዝብ ፡ ዘኢተአምረ ፡ ትካት ፡ እያለ ፥ ከገባብም ፡ ጋራ ፥ እምትካት ፥ ኀበ ፡ ዘትካት ፡ እያለ ፡ ይገባል ። ዓለም ፡ ግን ፡ አገባብ ፡ ሳይገባ ፡ ብቻውን ፡ አይገባም ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ እምዓለም ። ተዘከርኩ ፡ ፍትሐከ ፡ ዘእምዓለም ፡ ከዱሮ ፡ ከጥንት ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ የነበረ ። ለ ፡ ሲወድቅበት ፡ ወትሮ ፡ ዘወትር ፡ ድንት ፡ ይኾናል ። አንተሰ ፡ ትነብር ፡ ለዓለም ። ዘ ፡ ሲጨመርበት ፥ አምላክ ፡ ዘለዓለም ፡ ብሎ ፥ ለድንት ፡ የሚኖር ፡ የማይጠፋ ፡ የማይለወጥ ፥ ጥንትና ፡ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ ያሰኛል ። ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ለዘላለም ፥ በጊዜው ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ያለማቋረጥ ፡ እምዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ከፍጥረት ፡ እስከ ፡ ምጽአት ።

፻፳፩ ፡ ቅድም ፡ ትማልም ። ቅድም ፡ ብቻውን ፡ ሲነገር ፡ ፊት ፡ መጀመሪያ ፡ ይኾናል ፡ ከትማልም ፡ ጋራ ፡ ሲናበብ ፡ ግን ፡ በስቲያ ፡ ወዲያ ፥ ሐች ፡ ይኾናል ። ትማልም ፡ ደግሞ ፡ ትላንት ፡ ዓምና ፡ ይኾናል ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ትማልም ፡ ኀለፈት ። በተገናኝ ፡ ቅድመ ፡ ትማልም ፡ ብሎ ፡ ከትላንት ፡ በስቲያ ፥ ወይም ፡ ወዲያ ፥ ሐች ፡ ዓምና ፥ የወዲያኛው ፡ ዓመት ፡ ያሰኛል ።

ዮም ፡ ይእዜ ። ዛሬ ፡ አኹን ፡ ዘንድሮ ፡ ይኾናሉ ፡ ዘትማልም ፡ ወዮም ። እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ። ቅድምና ፡ ትማልም ፡ ዘመን ፡ ብሉይ ፡ ሲባሉ ፡ ዮምና ፡ ይእዜም ፡ ዘመን ፡ ሐዲስ ፡ ይባላሉ ። ዳግመኛም ፡ በመምህራን ፡ ልማድ ፥ አሜር ፡ አሰፌር ፡ ዓምና ፡ ኀረፍ ፡ ገረፍ ፡ ዘንድሮ ፡ ይባላሉ ፡ በመጻሕፍት ፡ ግን ፡ ከኀረፍ ፡ በቀር ፡ የሦስቱ ፡ ምስክር ፡ አይገኝም ። ኀድጋ ፡ ኀረፈኒ ፡ እመ ፡ ትፈሪ ፡ ለዓሙ ። ምናልባት ፡ ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ብታፈሪ ፡ ዓምና ፡ እንደ ፡ ተውኸት ፡ ዘንድሮም ፡ ተዋት ። ይኸውም ፡ አትክልት ፡ የሚጸገሉበት ፡ የርጥበት ፡ ወራት ፡ ጊዜ ፡ ገሚድ ፡ ነው ።

፻፳፪ ፡ ጌሠም ፡ ሳኒታ ። ነገ ፡ ነገታ ፡ ማግስት ፡ የዮም ፡ ተከታዩ ፥ ፪ኛ ፡ ቀን ። ዮምኬ ፡ ሰብእ ፡ ወጌሠመ ፡ መሬት ። ወበሳኒታ ፡ እምድኅረ ፡ ዐርብ ። በዘመን ፡ ሲገባም ፡ ከርሞ ፡ የዛሬ ፡ ዓመት ፡ ይኾናል ። ኢትበሉኬ ፡ ለጌሠም ፡ እስመ ፡ ጌሠምሰ ፡ ትኄሊ ፡ ለርእሳ ። ዘልፍ ፡ ወትር ፡ ዘልፈ ፡ ወትረ ፡ ወትሮ ፡ ዘወትር ፥ ያለማቋረጥ ፡ ይኾናሉ ። ልማድ ፡ ዘዘልፍ ፥ ዘወትረ ፡ ይሴብሑ ። ለዝሉፉ ፡ ለዝላፉ ፡ ለወትሮ ፡ ለዘወትር ፡ ለዘላለም ፡ ይኾናል ። ግሙራ ፡ ለግሙራ ፥ ለፍጻሜ ፡ ከቶ ፡ አኳቶ ፡ ፈጽሞ ፡ ጨርሶ ፡ ይኾናሉ ። በተገባርም ፡ እንቀጽ ፡ ሲገቡ ፡ ተከቶ ፡ ተኳቶ ፡ ተጨርሶ ፡ ያሰኛሉ ። እምድ

ሩም ፡ እንደ ፡ ግሙራ ፡ ነው ፡ አከቶ ፡ ፈጽሞ ፡ ጭራሽ ፡ ይኾናል ። እመ ፡ እምድሩ ፡ ትከሰ ፡ ልደቶ ። ኑቅዐ ፡ ኀጢአትየ ፡ ለገብረከ ፡ እምድሩ ፡ ይሠሮ ። ብዛትና ፡ ብልጣ ፡ የሚያሳዩ ፥ ጥቀ ፡ ፈድፋደ ፡ በሕቁ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ይኾናሉ ። ጥቀ ፡ ተሰብሐ ። ፈድፋደ ፡ ተለዐለ ። ለእመ ፡ ኢተነሰቡ ፡ በሕቁ ። ቅጽልና ፡ በቂ ፡ እየኾኑ ፡ ሕጸጽ ፡ የሚያሳዩ ፡ ኅዳጥ ፡ ንስቲት ፡ ሕቀ ፡ ጥቂት ፡ ይኾናሉ ፤ ዓዲ ፡ ኅዳጠ ፡ ኢትሬእዩኒ ፤ ወከዐበ ፡ ኅዳጠ ፡ ትሬእዩኒ ። ንስቲት ፡ ሕቅ ፡ ከከመ ፡ ጋራ ፡ ተነግረዋል ።

፻፹ ፡ መድረሻቸው ፡ ግእዝ ፡ እየኾነ ፡ ወይም ፡ በ ፡ ወድቆባቸው ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ የሚኾኑ ፡ ሳድስ ፡ ቅጽሎች ፡ በዐበይትና ፡ በንኡሳት ፡ በአናቅጽ ፡ ኹሉ ፡ እየገቡ ፡ እንደሚስማማቸው ፡ ይፈታሉ ። ይህም ፡ እንግረክሙ ፡ ክሡተ ፥ አው ፡ በክሡት ፡ ብሎ ፡ ገልጬ ፡ ወይም ፡ በግልጥ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። የቀሩትም ፡ ድሎትና ፡ መፍትው ፡ ብዉሕ ፥ በለ ፡ ተዘርዝረው ፡ ሳይዘረዘሩም ፡ በዘንድ ፡ አንቀጽና ፡ ብርእስት ፡ በሳቢ ፡ ዘር ፡ ገብተው ፡ ሲነገሩ ፡ ማሰሪያቸው ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። አከ ፡ ድሎት ፡ ሊተ ፡ አንቃዕዱ ፡ ወእርአይ ። መፍትው ፡ ትግበሩ ፡ ዘንተ ፡ ወዝከተሂ ። አከ ፡ ድሎት ፡ ወአከ ፡ መፍትው ፡ አስተርእዮ ፡ በመንታ ፡ ፍናው ። ብዉሕ ፡ ሊተ ፡ አንብራሂ ፡ ወአሚማሂ ። ጽድቅና ፡ አሉታ ፡ አንቀጽ ፡ የሚያሰሙ ፡ ዮጊ ፡ ዬ ፡ ናሁ ፡ ነዋ ፡ በኹሉ ፡ እየገቡ ፡ እንሆ ፡ ተብለው ፡ ይፈታሉ ፤ ዮጊና ፡ ዬ ፡ በየቦታቸው ፡ ተነግረዋል ። ናሁና ፡ ነዋ ፡ ከነባር ፡ አንቀጽ ፡ ከነ ፡ የወጡ ፡ ናቸው ፡ ርባታቸውም ፡ ነዮ ፡ ያ ፡ በ፲፩ኛ ፡ ዕርከን ፡ ተነግሯል ፤ (ቍ፹፰) ። እነዚህ ፡ ኹለቱ ፡ በቅርብ ፡ አነጋገር ፡ እንሆ ፡ እያሉ ፡ ሩቁን ፡ እንደ ፡ ቅርብ ፡ ሲያደርጉ ፡ ቅርብ ፡ ቅርቡንም ፡ ሲዳርጉ ፥ ደቂቅ ፡ ቅጽል ፡ እንጂ ፡ አገባብ ፡ አይመስሉም ። ናሁ ፡ ለወንድም ፡ ለሴትም ፥ ነዋ ፡ ላንድ ፡ ወንድ ፡ ብቻ ፡ ይነገራል ። ናሁ ፡ ኢመጽአ ፡ ለበዓል ፤ ወናሁ ፡ ኤልሳቤጥኒ ። ነዋ ፡ ወልድኪ ። ናሁ ፡ ተለዩቶ ፡ ቃለ ፡ አንክሮ ፡ ይኾናል ፤ ይኸውም ፡ መጽሐፍ ፡ መላሾች ፥ ዕብራይስጡ ፡ ሚ ፡ ሠናይ ፡ ወሚ ፡ አዳም ፡ ያለውን ፥ ናሁ ፡ ሠናይ ፡ ወናሁ ፡ አዳም ፡ ብለው ፡ ስላገቡት ፡ ነው ። ፪ኛም ፡ በእስመ ፡ ፈንታ ፡ እየገባ ፡ ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ይኾናል ፤ ወሥጋሁኒ ፡ እምድኅረ ፡ ትንሣኤሁ ፡ ከነ ፡ ዘኢይማስን ፡ ወዘኢይመውት ፡ ናሁ ፡ ከነ ፡ ኢሐደ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ። እስመ ፡ ደግሞ ፡ በናሁ ፡ ፈንታ ፡ እየገባ ፡ ንኡስ ፡ ይኾናል ፡ እስመ ፡ ቆሙ ፡ ላዕሌየ ፡ ሰማዕት ፡ ዐመፃ ። እወ ፡ አማን ፡ አሆ ፡ እንቢ ፡ አሀ ፡ ብሥራት ፡ ሀብ ፡ ነዐ ፥ ና ፡ ቶሎ ፡ በል ፤ ሕንክ ፥ ዕንካ ። እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ በ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በ፲፫ኛ ፡ ዕርከን ፡ ከነርባታቸው ፡ ተነግረዋል ፤ (ቍ፻፲፩) ።

አሌ ፡ አሌ ፡ ዐዋይ ፡ ዐዋይ ፥ ስማ ፡ ስማ ፡ ይኾናል ። በጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ዘይትበሀል ፡ አሌ ፡ እንዳል ፤ (ጎድ ፡ ተክ) ። ባላገባቦች ፡ ግን ፡ በአሌ ፡ ፈንታ ፡ ኤር ፡ ኤር ፥ ወይም ፡ ኤል ፡ ኤል ፡ አብሬል ፡ ይላሉ ፡ የአብሬልንም ፡ ፍች ፡ ገብር ፡ ከነ ፡ እግዚእ ፡ ይሉታል ፤ ኹሉም ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ። ኤር ፡ ኤል ፡ በአራት ፡ የለም ፡ አብሬል ፡ ብቻ ፡ አብሬኽ ፡ ተብሎ ፡ ይገኛል ፥ ፍችውም ፡ ብርክ ፡ አስተብርክ ፥ ስግድ ፡ ወአምኅ ፥ ግነይ ፡ ወባርክ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ስለ ፡ ዮሴፍ ፡ ሹመት ፡ የተነገረ ፡ የፈርዖን ፡ ዐዋጅ ፡ ነው ፡ ቃሉም ፡ ዕብራይስጥ ፡ ነው ።

## ፳፩ኛ ፡ ዕርከን ።

## ደቂቅ ፡ አገባቦች ።

፻፱ ፤ ቤዛ ፡ ተክለ ።   በብትን ፡ ገብተው ፡ ስለ ፡ ይኾናሉ ፤ ቤዛ ፡ ለውጥነት ፡ ባለው ፡ ተክለ ፡ ምትክነት ፡ ባለው ፡ ይገባል ። አሜጡ ፡ ነፍስየ ፡ ቤዛ ፡ አባግዕየ ። ተወልደ ፡ ሴት ፡ ተክለ ፡ አቤል ፤ ስለ ፡ በጎቹ ፡ ቤዛ ፥ ስለ ፡ አቤል ፡ ምትክ ። ፪ኛም ፡ በጥሬነታቸው ፡ የበጎቹን ፡ ቤዛ ፡ ነፍሴን ፥ የአቤል ፡ ምትክ ፡ ሴት ፡ ተብለው ፡ ሲፈቱ ፡ ቅጽል ፡ ይኾናሉ ። ዐስበና ፡ ዕሴተም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፤ ዋጋነትን ፡ ሳይለቅ ፡ ይፈታል ። ሲዘረዝርም ፡ ቤዛሁ ፡ ሃ ፥ ተክሉ ፡ ላ ፡ እያለ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፥ ቤዛው ፡ ምትኩ ፡ ያሰኛል ።

የቦታ ፡ አገባቦች ፤ ዲበ ፡ ላዕለ ፡ መልዕልተ ።   ላይ ፡ በላይ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በ ፡ ስለ ፡ ይኾናሉ ። ዘሐነጸ ፡ ቤቶ ፡ ዲበ ፡ ኰኵሕ ። ዐርገ ፡ ዲበ ፡ ሰግላ ። ከልብ ፡ ይገብእ ፡ ዲበ ፡ ቂያኢ ። ዲበ ፡ ሀጕለ ፡ ውሉዶሙ ፡ ይግዕሩ ፤ በልጆቻቸው ፡ ጥፋት ፤ ስለ ፡ ልጆቻቸው ፡ ጥፋት ። ላዕለ ፡ መልዕልተም ፡ እንደዚሁ ፡ ናቸው ። አዕረፈት ፡ በረከት ፡ ላዕለ ፡ ያዕቆብ ። ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ላዕለ ፡ ዮሐንስ ። ዐርጉ ፡ መልዕልተ ፡ ወግር ። ወጽልመት ፡ መልዕልተ ፡ ቀላይ ። ስለ ፡ ሲኾን ፡ ጸልዩ ፡ ላዕሌየ ፡ ወላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ መሢዕት ፡ እያሰኘ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ይገባል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ጥቅም ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ ሲገባ ፡ ለ ፡ ይኾናል ፤ ግበሩ ፡ ምሕረተ ፡ ወምጽዋተ ፡ ላዕለ ፡ አኀዊክሙ ፤ ለወንድሞቻችኹ ። ሲዘረዝሩም ፡ ዲቤሁ ፡ ላዕሉ ፡ ሌሁ ፥ መልዕልቱ ፡ ቴሁ ፡ እያሰኙ ፡ እንዳንቀጹ ፡ ስልት ፡ ይፈታሉ ። ፫ ፡ አገባቦች ፡ በ ፡ እም ፡ እንተ ፡ ይሰማሟቸዋል ። ጸጋ ፡ በዲበ ፡ ጸጋ ። ቀነጸ ፡ እምዲበ ፡ ሐመር ፤ አዝዘኒ ፡ እምጻእ ፡ ኀቤከ ፡ እንተ ፡ ዲበ ፡ ባሕር ። ፪ኛም ፡ በጥሬነታቸው ፡ ዘርፍ ፡ ይዘው ፡ ወይም ፡ ተዘርዝረው ፡ ቅጽል ፡ ይኾናሉ ። ጠፈር ፡ ዲበ ፡ ላዕለ ፡ መልዕልተ ፡ ምድር ፡ ዓለመ ፡ ብርሃናት ፤ ወሰማይኒ ፡ ላዕለ ፡ ጠፈር ፡ ዓለመ ፡ መላእክት ፡ ውእቱ ። ሲፈታም ፡ የምድር ፡ ላይ ፡ ጠፈር ፥ የጠፈር ፡ ላይ ፡ ሰማይ ፥ ወይም ፡ አቅንቶ ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ያለ ፥ ከጠፈር ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ እያሰኘ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ።

፻፲ ፡ ታሕተ ፡ መትሕተ ።   ታች ፡ በታች ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ይኾናሉ ፤ የቦታ ፡ አገባቦች ፡ በ ፡ እም ፡ ኀበ ፡ መንገለ ፡ ውስተ ፡ ወደ ፡ ሲኾኑ ፡ ይሰማሟቸዋል ። በታሕተ ፡ እም ታሕተ ፡ ሰማይ ፥ ኀበ ፡ መትሕት ። ሲዘረዝርም ፡ ታሕቱ ፡ መትሕቱ ፡ ቴሁ ፥ በታቹ ፡ ከርሱ ፡ በታች ፡ ያሰኛል ። በጥሬነቱም ፡ ሲነገር ፡ ተዘርዝሮና ፡ ዘርፍ ፡ ይዞ ፡ ቅጽል ፡ ይኾናል ። በሰማይ ፡ በላዕሉ ፥ ወበምድር ፡ በታሕቱ ። ምድር ፡ ታሕተ ፡ ጠፈር ፡ ወመትሕተ ፡ ደመናት ፡ ዓለመ ፡ ሰብእ ፡ ወእንስሳት ። ስትፈታም ፡ በሰማይ ፡ ላዕሉ ፡ ለምድር ፡ ወበምድር ፡ ታሕቱ ፡ ለሰማይ ፡ ብለኽ ፡ ግጠም ።

፻፲፩ ፤ ውስተ ፥ ውሳጤ ፥ ማእከለ ።   ውስተ ፡ ውስጥ ፤ በውስጥ ፡ በማኸል ፥ በ ፡ ወደ ፡ ይኾናል ። ዓሣ ፡ ዘውስተ ፡ ባሕር ። ሠርዌ ፡ ዘውስተ ፡ ዐይንከ ። ከመ ፡ አንበሳ ፡ ውስተ ፡ እንስሳ ። ኢ.ሀሎ ፡ ውስተ ፡ መካኑ ፥ በቦታው ። ሖርከ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፥ ወደ ። ምስጢሩ ፡ ውስጥን ፡ አይለቅም ፤ የቦታ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በ ፡ እም ፡ እንተ ፡ ይሰማሙታል ። የበ ፡ መሰማማት ፡ ተነግሯል ። ዘይወፅእ ፡ እምውስተ ፡ አፍ ። ወዕአት ፡ ሐጽ ፡

እንተ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፤ በደረቱ ። ሲዘረዘርም ፡ በ ፡ እም ፡ እንተ ፣ ውስቴቱ ፡ ቃ ፡ እያሰኙ ፡ ይሰማሙታል ። ውስጥና ፡ ውሳጤም ፡ ከውስተ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ ውስተ ፡ የተባለው ፡ ውስጥ ፡ ነውና ። ውሳጤም ፡ ውስተ ፡ በገባበት ፡ እየገባ ፣ ውስጥ ፡ በውስጥ ፡ ይኾናል ። ይትኀብኡ ፡ አራዊት ፡ ውሳጤ ፡ ግብ ። በ ፡ እም ፡ ይሰማሙታል ፤ ሲዘረዝርም ፡ ውሳጤሁ ፡ ሃ ፡ እያለ ፡ ውስጡ ፡ ውስጧ ፡ ያሰኛል ። ማእከለም ፡ ማኸል ፡ በማኸል ፡ ወደ ፡ ማኸል ፡ ይኾናል ፤ ምስጢሩ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ላይና ፡ ታች ፡ ክበብ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ ይገባል ። ጽንፍ ፡ ወማእከል ። ቁም ፡ ማእከለ ። ባእ ፡ ማእከለ ፡ ሀገር ። በ ፡ እም ፡ እንተ ፡ ውስተ ፡ ይሰማሙታል ። በማእከለ ፡ ማኅበር ፡ እሴብሐከ ። አወፅኦሙ ፡ እማእከላ ። እንተ ፡ ማእከላ ። ውስተ ፡ ማእከሎሙ ። ሲዘረዝርም ፡ ማእከሉ ፡ ላ ፣ ማእከሌሁ ፡ ሃ ፡ እያሰኘ ፡ በዘመድ ፡ በባዕድ ፡ ይነገራል ።

፻፲፪ ፤ በ ። በቁም ፡ ቀሬ ፤ ም ፡ ን ፡ ለ ፡ ጊዜ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ቸልታ ፡ ይኾናል ። በቁም ፡ ቀሬ ፡ ሲኾን ፡ በማሰሪያ ፡ ኹሉ ፡ እየገባ ፡ ማድረጊያ ፡ ይኾናል ። አድኅነነ ፡ በመለኮቱ ፡ ወቤዘወነ ፡ በትስብእቱ ። ም ፡ ሲኾን ፣ ለእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ በምልአ ። እስመ ፡ ዚአየ ፡ ውእቱ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ በምልኡ ፡ ይላል ። ወምልአ ፡ ወምልኡ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በውስጧም ፡ ያለው ፡ ማለትን ፡ ያሰማል ። ይኸውም ፡ መላሾች ፡ በወፈንታ ፡ ስላገቡት ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ አይገኝም ። ን ፡ ሲኾን ፣ የማእዝ ፡ ወራሽ ፡ ነው ፤ ለምሁራን ፡ ልብ ፡ በጥበብ ። ኢቀባዕከኒ ፡ በዘይት ፤ ጥበበ ፡ ዘይተ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይኄይስ ፡ ተአምኖ ፡ በእግዚ ፡ እምተአምኖ ፡ በዕጓለ ፡ መሕያው ፡ ሲል ፣ በቁም ፡ ቀሬ ፡ ኹኖ ፣ ወይም ፡ ን ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ። ለ ፡ ሲኾን ፡ መንታነትና ፡ ተነጻጻሪነት ፡ ባላቸው ፡ በሕዋሳት ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ፡ አንቀጹም ፡ ተደራራጊና ፡ አደራራጊ ፡ ነው ። ተናጸሩ ፡ ገጸ ፡ በገጽ ፤ ፊት ፡ ለፊት ። ይትጓደዑ ፡ ክንፈ ፡ በክንፍ ። አስተአኀዘሙ ፡ እደ ፡ በእድ ፣ ወእግረ ፡ በእግር ። ወተናገሮ ፡ ቃለ ፡ በቃል ። ጊዜ ፡ ሲኾን ፡ የእመ ፡ ወራሽ ፡ ነው ፤ ኢመፍትው ፡ አድልዎ ፡ በፍትሕ ፤ በፍርድ ፡ ጊዜ ። ጋራ ፡ ሲኾን ፡ የምስለ ፡ ወራሽ ፡ ነው ፤ ተዋሐደ ፡ ቃል ፡ በሥጋ ። እንደ ፡ ሲኾን ፡ የከመ ፡ ወራሽ ፡ ነው ፤ ጽድቅ ፡ በወልታ ፡ የዐውደከ ። ቸልታም ፡ ሲኾን ፡ የእንዘ ፡ ወራሽ ፡ ነው ፤ ጸለየ ፡ ወሰአለ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ፡ በብካይ ፤ አልቅሶ ፡ ወይም ፡ እያለቀሰ ፡ ያሰኛል ። በ ፣ በማይስማማው ፡ ግስ ፡ ገብቶ ፡ ሲገኝ ፡ በሚስማማው ፡ ግስ ፡ ይፈታል ። መጺእክሙ ፡ ተአኀዝክኒ ፡ በአብትር ፤ በበትር ፡ መትታችኹ ፡ ትይዙኝ ፡ ዘንድ ፤ ወይም ፡ መጺእክሙ ፡ በአብትር ፤ በትር ፡ ይዛችኹ ። ከልብኑ ፡ አነ ፡ ከመ ፡ ትምጻእ ፡ ኀቤየ ፡ በአእባን ፡ ወበትር ፤ ደንጊያና ፡ በትር ፡ ይዘኽ ። ነሐውር ፡ በእግረ ፡ ደቂቅ ፣ በልጆች ፡ እግር ፡ ልክ ፣ ወይም ፡ እንደ ፡ ልጆች ፡ እግር ፡ ያሰኛል ። አምላክ ፡ ውእቱ ፡ በሥጋ ፤ በሥጋ ፡ ሳለ ። ወቦቱ ፡ ፍጹም ፡ መለኮት ፡ በአርአያ ፡ ንዴትነ ፤ በነዳይ ፡ ባሕርያችን ፡ ሳለ ፤ ሳይለወጥ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሐመ ፡ ሕማመ ፡ ሥጋ ፡ እሙነ ፡ በመለኮቱ ፤ በምላክነቱ ፡ ሳለ ፣ ሳይታመም ። በቦታ ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ አገባብነቱን ፡ ሳይለቅ ፡ አንቀጽ ፡ ይኾናል ፤ ኤልያስ ፡ በገነት ። አቡነ ፡ ዘበሰማያት ። ሲዘረዘርም ፡ በጥሬነቱ ፣ ቦ ፡ ባ ፡ እያለ ፡ በርሱ ፡ በርሷ ፡ ያሰኛል ። በበ ፣ በየ ፡ ይኾናል ፡ ከተጸውዖ ፡ ስም ፡ በቀር ፡ በብትን ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ፤ በበ ፡ ደመሉ ፣

በያውራጃው ፡፡ ከዕለት ፡ እስከመት ፡ ያሉትን ፡ ጊዜያት ፡ በዝርዝር ፡ ወይም ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ ያናግራል ፡፡ ይህም ፥ በበ ፡ ዕለት ፤ በየለቱ ፥ ዕለት ፡ ዕለት ፡፡ በበ ፡ ወርኅ ፤ በየወሩ ፥ በወር ፡ በወር ፡፡ በበ ፡ ዓመት ፤ በያመቱ ፡ በመት ፡ ባመት ፡፡ ይሠውዑ ፡ በበ ፡ ነግህ ፡ ወበበ ፡ ሠርክ ፤ ጧት ፡ ጧት ፥ ማታ ፡ ማታ ፡፡ በአኀዝም ፡ ገብቶ ፡ እንዲሁ ፡ ይፈታል ፡፡ በበ ፡ አሐዱ ፤ በያንዳንዱ ፥ አንዱም ፡ አንዱም ፥ አንዳንድ ፡፡

፻፲፫ ፤ ለ ፡፡ አቀባይ ፥ ወይም ፡ በቁም ፡ ቀሪ ፤ አቀብሎ ፡ ሽሽ ፥ አዳማቂ ፡፡ የ ፡ ን ፡ ከ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ፡፡ በቁም ፡ ቀሪ ፡ ሲኾን ፡ ሀቡ ፡ ዘቄሳር ፡ ለቄሳር ፥ ወዘእግዚ ፡ ለእግዚ ፡፡ ኢትበሉ ፡ ለጌሠም ፡፡ በባለቤትና ፡ በቅጽልም ፡ እንደ ፡ በ ፡ እየ ተደረበ ፡ ይነገራል ፡፡ ለክህናት ፡ ለደቂቀ ፡ አሮን ፤ ለብእሲት ፡ ለመርዓተ ፡ በግዑ ፤ ለጋ ይዮስ ፡ ለእኁን ፡፡ በና ፡ ለ ፡ በማርኛም ፡ እንደዚሁ ፡ ናቸው ፤ ተደራርበው ፡ ይነገራሉ ፡፡ በሰማይ ፡ በላዕሉን ፡ ተመልከት ፡፡ አቀብሎ ፡ ሽሽ ፡ ሲኾን ፥ ለይኩን ፡ ብርሃን ፤ ለይ ትጋባእ ፡ ማይ ፤ ለትቅረብ ፡ ስእለትየ ፡ ኀቤከ ፡ እያሰኘ ፡ በትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባል ፡፡ አዳማቂም ፡ ሲኾን ፥ ሎኑበ ፡ ሰማያት ፡ ለመንግለ ፡ እግዚ ፤ ለእመ ፡ ርኅበ ፡ ጸላኢከ ፡ እያለ ፡ በገባብ ፡ ይወድቃል ፡፡ የ ፡ ሲኾን ፡ ዘርፍ ፡ አያያዥና ፡ የዘርፍ ፡ ደፊ ፡ ነው ፤ ን ፡ ሲኾን ፡ ተጠቃሽ ፡ ወይም ፡ የግእዝ ፡ ወራሽ ፡ ይባላል ፤ ፪ቱም ፡ በዘርፍና ፡ በባለቤት ፡ ክፍል ፡ ተነግረዋል ፡ (ዕር፲፯ ፡ ቍ፳፪) ፡፡ ከ ፡ ሲኾን ፡ ተሠጠ ፡ ለክልኤ ፤ ተከፍለ ፡ ለአ ርባዕቱ ፡ እያለ ፡ በአኀዝ ፡ ገብቶ ፡ ይነገራል ፡፡ ወደ ፡ ሲኾን ፡ ተመይጠ ፡ ለብሔሩ ፡ ግ ብጽ ፡ ይላል ፡፡ ላይ ፡ ሲኾን ፡ ወአምጽአ ፡ ረኀበ ፡ ለብሔር ፤ በምድር ፡ ላይ ፡፡ ስለ ፡ ሲኾን ፡ ኢትጸሊ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡ ይላል ፡፡ ፪ኛም ፡ ለዝ ፡ ያለው ፡ በቁም ፡ ቀሪ ፡ ሲኾን ፡ ያምርለታል ፡፡ ጋራ ፡ ሲኾን ፡ የምስለ ፡ ወራሽ ፡ ነው ፡፡ ትከውኑ ፡ ሱቱፋነ ፡ ለሐራ ፡ ሰማይ ፡፡ ለ ፥ ላይ ፡ ስለ ፥ መኾኑ ፡ መላሾች ፡ በላዕለና ፡ በበእንተ ፡ ፈንታ ፡ ስላገቡት ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ከዚህ ፡ ቢቀር ፡ በሌላ ፡ አይገኝም ፡፡ በዘ ፡ ፈንታ ፡ ገብቶ ፡ የ ፡ ሲኾን ፡ ውእቱን ፤ በቁም ፡ ቀሪ ፡ ሲኾን ፡ ደለወ ፡ ይደሉን ፡ ያመጣል ፡፡ ለእግዚ ፡ ምድር ፡ በምልአ ፡፡ ለአብ ፡ ስብሐት ፥ ለወልድ ፡ ስግደት ፥ ወለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባር ኮት ፡፡ ሲዘረዘርም ፥ ሎ ፡ ሎቱ ፡ ላ ፡ ላቲ ፡ እያለ ፡ ለርሱ ፡ ለርሷ ፡ ያሰኛል ፤ አንቀጽንቱ ፡ ከበ ፡ ጋራ ፡ በደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ተነግሯል ፡፡ ለለ ፡፡ ለየ ፡ እየ ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ ይኾናል ፡፡ ከተጸውዖ ፡ ስም ፡ በቀር ፡ በብትን ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ፤ ከዕለት ፡ እስከመት ፡ ያሉትን ፡ እንደ ፡ በበ ፡ ይዘረዝራል ፡፡ ለለ ፡ ርእሱ ፥ ለየራሱ ፡ እየራሱ ፡ ራስ ፡ ራሱ ፡፡ ለለ ፡ አሐዱ ፥ ለያንዳንዱ ፡ እያንዳንዱ ፥ አንዳንዱ ፤ አንዱም ፡ አንዱም ፡፡ ለለ ፡ ዕለቱ ፥ ለየለቱ ፡ እየ ለቱ ፥ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እያሰኘ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ፡፡ ፪ኛም ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ ሲገባ ፡ ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ይኾናል ፤ ዐቢይነቱም ፡ አመንና ፡ ሰበን ፡ እንዘን ፡ ይመስላል ፤ ፍችውም ፡ ጊዜና ፡ የ ፡ ሲ ፡ ስ ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ ነው ፡፡ ወለለ ፡ ወለዳ ፤ እው ፡ ወለለ ፡ ይወ ልዳ ፡ ተባዕተ ፡ ቅትላሁ ፤ ወንድ ፡ ወንድ ፡ በወለዱ ፡ ጊዜ ፥ ሲወልዱ ፤ ወይም ፡ የወለ ዱትን ፥ የሚወልዱትን ፥ ወንድ ፡ ወንዱን ፡ ግደሉት ፡፡ ለለ ፡ ተናገርኩ ፡ ተዘከርኩ ፤ በተናገርኹ ፡ በተናገርኹ ፡ ጊዜ ፤ የተናገርኹ ፡ የተናገርኹትን ፡፡ ለለ ፡ እትናገር ፤ ስና ገር ፡ ስናገር ፡፡ በደጊመ ፡ ቃልም ፡ ፈንታ ፡ ቍጥር ፡ ይኾናል ፤ ምስጢሩ ፡ ጊዜን ፡ አይ

ለቅም ። ለለ ፡ ወለዳ ፡ በወለዱ ፡ ቍጥር ፥ ለለ ፡ ተናገርኩ ፡ በተናገርኹ ፡ ቍጥር ። ይኸ ውም ፡ በቀዳማይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፪፻፬ ፤ ምስለ ። ጋራ ፥ ከነ ። እንደ ፥ ከ ፥ ና ፥ ይኾናል ፤ ጋራ ፡ በሚኾንበት ፡ ኅቡረ ፡ ሲጨመር ፡ ዐብሮ ፡ ባንድነት ፡ ያሰኛል ። ንዒ ፡ ኀቤየ ፡ አ ፡ ድንግል ፡ ምስለ ፡ ወል ድኪ ፤ ከልጅሽ ፡ ጋራ ። ወመላእክትኒ ፡ ተጋብኡ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኅቡረ ፤ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ወይም ፡ ባንድነት ። መጽአ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፤ ከነሚስቱ ፥ ወይም ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ። እንደ ፡ ሲኾን ፡ የከመ ፡ ወራሽ ፡ ነው ። አበስነ ፡ ምስለ ፡ አበዊነ ፤ ወኢ ተቀሥፉ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፤ እንደ ፡ ሰው ። ከ ፡ ሲኾን ፡ የእም ፡ ወራሽ ፡ ነው ፤ መለያየ ትን ፡ በሚያሳዩ ፡ ግሶች ፡ ይገባል ፤ ወብእሲትኒ ፡ ኢትትኃደግ ፡ ምስለ ፡ ምታ ፤ ከባሏ ፡ አትፋታ ። ና ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ ወ ፡ አጫፋሪ ፡ ነው ፤ በብዙ ፡ ወንድ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባል ። ከንቶ ፡ ይትናገሩ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፤ አንዱና ፡ ሌላው ፡ ኹለተኛው ። ተማኪ ሮሙ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፤ ባልና ፡ ሚስቱ ። ምስለ ፥ በማይመስለው ፡ ግስ ፡ ሲገባ ፡ ቦዝ ፡ ኹኖ ፡ ይፈታል ። ሰረረ ፡ ንስር ፡ ምስለ ፡ መጽሐፍ ፤ መጽሐፍ ፡ ይዞ ። ሲዘረ ዘርም ፡ ምስሌሁ ፡ ሃ ፡ እያሰኘ ፡ እንደ ፡ ፊተኞቹ ፡ ይፈታል ። አነ ፡ ምስሌክሙ ፥ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌነ ፡ ሲል ፡ በነባር ፡ በዘማች ፡ ያሳስራል ።

፪፻፭ ፤ አያተ ፤ ጽላሎተ ። አያተ ፡ በብትን ፡ ብቻ ፥ ጽላሎተ ፡ በተጸውዖ ፡ ስም ፡ እየገቡ ፡ እንደ ፡ ይኾናሉ ። ተዋሕዶ ፡ ሥጋ ፡ ወቃል ፡ አያተ ፡ ሐመልማል ፡ ወነበልባል ። እስናኒከ ፡ አያተ ፡ አዕናቍ ፡ እለ ፡ ተሰክዓ ። ተሰቅለ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቍልቍሊተ ፡ ጽላሎተ ፡ ዶርሆ ። አርእስትና ፡ ሳቢ ፡ ዘርም ፡ እንደ ፡ ይኾናሉ ፤ ተመትሩ ፡ ያዕቆብ ፡ ወማቴዎስ ፡ ወጳውሎስኒ ፡ ተመትሮተ ፡ መጥምቅ ፡ ምትረተ ፡ መጥምቅ ፡ ዮሐንስ ፤ እንደ ፡ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ።

፪፻፮ ፤ ከደቂቅ ፡ አገባብ ፡ የሚጨመሩ ፡ የቦታና ፡ የጊዜ ፡ ጥሬዎች ። እነዚ ህም ፡ ተናበውና ፡ ተዘርዝረው ፥ ግእዝ ፡ ኃምስ ፡ ኹነው ፡ ይነገራሉ ። ላዕል ፡ ላዕሉ ፡ መልዕልት ፡ ላዕሊት ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ ይኾናሉ ፤ ማሰሪያቸውም ፡ ዐርገ ፡ ርእየ ፡ አንቃዕ ደወ ፡ ነበረ ፡ ሐወጸ ፡ እነዚህን ፡ የመሰለ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። ዐርገ ፡ ወነበረ ፡ ላዕለ ፡ መል ዕልተ ፡ ላዕሊተ ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤ በላይ ፡ ተቀመጠ ። በደጊመ ፡ ቃልም ፡ ይነገ ራሉ ፤ ላዕለ ፡ ላዕለ ፡ እንዘ ፡ ያንቃዐዱ ፥ በነጽሮ ፡ ተሰብረ ፡ ክሣዱ ። ሖረ ፡ ሮጸ ፡ ርእየ ፡ ኖመ ፤ እነዚህን ፡ የመሰለ ፡ አንቀጽ ፡ ሲስባቸው ፡ ሽቅብ ፡ አሻቅቦ ፡ ይኾናሉ ። በቀረው ፡ እንደ ፡ ማንም ፡ ጥሬ ፡ ተደራጊ ፡ ተሳቢ ፥ ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ ኹነው ፡ ይነገራሉ ፤ ፰ቱ ፡ የቦታ ፡ አገባቦች ፡ ይሰማሟቸዋል ፤ ላዕለ ፡ ግን ፡ እየተናበበ ፡ ይነገራል ። የነላዕል ፡ አን ጻር ፥ ታሕት ፡ ታሕቱ ፡ መትሕት ፡ ታሕቲት ፡ ታች ፡ ይኾናሉ ። ሲዘረዘሩም ፡ ላዕል ፡ ታሕት ፡ ያለውን ፡ ላዕሉ ፡ ላዕልከ ፥ ታሕቱ ፡ ታሕትከ ፡ ያሰኛሉ ። ላዕሉና ፡ ታሕቱ ፡ ግን ፡ የማይፈልሱና ፡ የማይበዙ ፡ ጕልት ፡ ቀለም ፡ ናቸው ፤ በቅጽል ፡ ባርእስት ፡ በብትን ፡ በአኃዝ ፡ ይገባሉ ። ክቡር ፡ ውእቱ ፡ ንቡረ ፡ ላዕሉ ፡ ወንጹሬ ፡ ታሕቱ ። ያፈቅር ፡ ባሕ ታዊ ፡ ነጽሮተ ፡ ላዕሉ ፡ እምነጽሮ ፡ ታሕቱ ። አንትሙሰ ፡ እምታሕቱ ፤ ወአንሰ ፡ እምላ ዕሉ ። ዘእምዕሥራ ፡ ዓም ፡ ወዘላዕሉ ፥ አው ፡ ወዘታሕቱ ። የነታሕቱ ፡ አንቀጾች ፡ ወረደ ፡

ሐወጸ ፡ ርእየ ፥ እነዚህንም ፡ የመሰሉ ፡ ኹሉ ። የቀረውም ፡ አገባባቸው ፡ እንደነሳዕል ፡ ነው ። ትርአስ ፡ ትርጋፅ ፤ ውስጥ ፡ ውሳጢ ፡ ውሳጢት ፤ ቅድም ፡ ፍጽም ፡ ገጽ ፤ ድኅር ፡ ከዋላ ፤ የማን ፡ ይምን ፥ ፀጋም ፡ ዕግም ። የነዚህም ፡ ዐዋጅ ፡ እንደነሳዕል ፡ ነው ። ግድም ፥ በደጊም ፡ ብቻ ፡ ይነገራል ፤ አንትሙ ፡ ተሐውሩ ፡ ግድመ ፡ ግድመ ። ድኅሬት ፡ ግንጽሊት ፡ ግፍትዒት ፤ ማሰሪያቸው ፡ ወድቀ ፡ ተአስረ ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ናቸው ። ወድቀ ፡ ዒሊ ፡ ድኅሬተ ፡ ግንጽሊተ ፡ ግፍትዒተ ፤ የኋሊት ። ተአስረ ፥ ወይም ፡ አሰርዎ ፡ ድኅሬተ ፡ ግንጽሊተ ፡ ግፍትዒተ ፤ የኋሊት ፡ የግርንግሬት ።

፻፲፯፤ በዝርዝርነት ፡ ግእዝ ፡ ኃምስ ፡ ኹነው ፡ የሚነገሩ ፡ የቦታ ፡ ጥሬዎች ፡ እሊህ ፡ ናቸው ። አፍአ ፤ ከዋላ ፤ ዝየ ፡ ህየ ፤ ለፌ ፡ ከሃ ፤ ኀለዪ ። አፍአ ፥ ውጭ ፡ በውጭ(ጪ) ፡ ይኾናል ፤ ከንቀጽ ፡ ጋራ ፡ ይነገራል ፤ በቀረው ፡ እንደነሳዕል ፡ ነው ። ይቀውም ፡ አፍአ ፤ አውፅእዎ ፡ አፍአ ። ከዋላ ፥ ኋላ ፡ በኋላ ፡ ይኾናል ፤ ነዐቅብ ፡ ፍጽመ ፡ ወከዋላ ፤ የሐውሩ ፡ ከዋላ ፤ በኋላ ፡ በስተኋላ ። ዝየ ፡ የቅርብ ፡ ቅርብ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ከዚህ ፡ ወደዚህ ፡ ይኾናል ፤ ከዘማች ፡ ከነባር ፡ ዐብሮ ፡ ይነገራል ። ዝየ ፡ አኀድር ። ምንት ፡ ብከ ፡ ዝየ ። አምጽእዎን ፡ ሊተ ፡ ዝየ ። ህየ ፥ የቅርብ ፡ ሩቅ ፡ የዝየ ፡ አንጻር ፡ ነው ፤ በዚያ ፡ ከዚያ ፡ ወደዚያ ፡ ይኾናል ፤ በቦታና ፡ በነገር ፡ ዐጸፋ ፡ ይገባል ። በቦታ ፥ ተከለ ፡ ገነተ ፡ ወሤሞ ፡ ህየ ። በነገር ፥ በህየኒ ፡ ሰመዮ ፡ ወልደ ፤ ወበዝየኒ ፡ ሰመዮ ፡ እኁወ ። ለፌ ፤ ወዲህ ፡ ወደዚህ ፡ ይኾናል ፤ ትመጽእ ፡ ለፌ ፡ ኀበ ፡ አነ ፡ እቀውም ። በጊዜም ፡ ሲገባ ፥ እለ ፡ ይብሉ ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ለፌ ፡ እማርያም ፥ አው ፡ ለፌ ፡ እምጥምቀት ፡ ይላል ። ተደጋግሞና ፡ ተጫፍሮ ፡ ሲነገር ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፥ ቀኝና ፡ ግራ ፡ ይኾናል ። ነጸረ ፡ ለፌ ፡ ወለፌ ። አንጌገየ ፡ ለፌ ፡ ወለፌ ። ሰቀሉ ፡ ምስሌሁ ፡ ክልኤተ ፡ ፈያተ ፡ አሐደ ፡ እምለፌ ፡ ወአሐደ ፡ እምለፌ ። ጽሑፋት ፡ እንተ ፡ (በ ፡ እም) ለፌኒ ፡ ወእንተ ፡ ለፌኒ ።

፻፲፰፤ ከሃ ፥ ወዲያ ፤ ከሃት ፥ ወዲያዎች ፡ ወዲያኞች ፡ ይኾናል ። ዝርዎ ፡ ከሃ ፤ ሑር ፡ ከሃ ። ሲዘረዝርም ፡ ከሃሁ ፡ ከሃቲሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፤ ከሃከ ፡ ከሃቲከ ፡ እያሰኘ ፡ በባዕድ ፡ በራሱ ፡ ያናግራል ። ከዝርዝሩ ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ህየ ፡ ነው ፤ የቦታ ፡ አገባቦች ፡ ይሰማሙታል ። እምለፌሁ ፡ ወእምከሃሁ ። እልክቱ ፡ እምከሃ ፥ ወእሉኒ ፡ እምለፌ ። ሰበከ ፡ ማርቆስ ፡ በግብጽ ፡ ወእምህየ ፡ እስከ ፡ ከሃቲሃ ። ኀለዪ ፤ ቦታ ፡ ኹሉ ፥ መላው ፡ ጠቅላላው ፡ አራቱ ፡ ማእዝን ። ብቻውንም ፡ ከገባብም ፡ ጋራ ፡ ይነገራል ፤ ብቻውን ፥ ሖርኩ ፡ መትሕተ ፡ ሰማይ ፡ ኀለዪ ፤ እስከ ፡ ይሰማዕ ፡ ኀለዪ ። ከገባብም ፡ ጋራ ፥ ምሉእ ፡ በኀለዪ ። ተጋብኡ ፡ ኀቤሁ ፡ እምኀለዪ ፤ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ኀለዪ ። ይነድፍዋ ፡ እንተ ፡ ኀለዪ ፡ እያለ ፡ ይገባል ።

## እየተናበቡ ፡ የሚነገሩ ፡ የቦታ ፡ ጥሬዎች ።

፻፲፱፤ ጽንፍ ፡ ክንፍ ፡ ከንፈር ፡ ሐይቅ ፡ ድንጋግ ፡ ገበዝ ፡ ወሰን ፤ ዳር ፡ ዳርቻ ፥ ጫፍ ፡ ጠርዝ ፡ ይኾናሉ ። ጽንፍ ፥ ለባሕር ፡ ለየብስ ፡ ለኀብስት ፡ ለልብስ ፡ ይኾናል ። ጽንፈ ፡ ባሕር ፡ የብስ ፤ ወጽንፈ ፡ የብስኒ ፡ ባሕር ። ጽንፈ ፡ ኅብስት ፡ ወልብስ ። ክንፍ ፥ ለ

ኹሉ ፡ ይኾናል ፤ ክንፈ ፡ ምድር ፥ ክንፈ ፡ ቤት ። ክንፈር ፡ ሐይቅ ፥ ለባሕር ፡ ይኾናሉ ፤
ድንጋግ ፥ ለወንዝ ፡ ለባሕር ፡ ለዘመን ፡ ይኾናል ። ገበዝ ፥ ለወንዝ ፡ ብቻ ፤ ወሰን ፥ ለኹሉ ፡
ይኾናል ። ወበጽሐ ፡ ዮርዳኖስ ፡ እስከ ፡ ድንጋጊሁ ። ኖኂ ፡ ዘድንጋግ ፡ ባሕር ። ሞት ፡
ድንጋግ ፡ ዕድሜ ፡ ዘኢይበጽሑ ፡ መልአክ ። ተቀበሎ ፡ ዲበ ፡ ገበዝ ፡ ተከዚ ። ኢትትዓ
ደዊ ፡ እምወሰንኪ ። ጽፍሕ ፥ ድልድል ፤ ሰፍሕ ፥ ስፋት ፡ ወልወል ፡ ይኾናል ። ጽፍሐ ፡
መሠረቱ ፤ የመሠረቱ ፡ ድልድል ፥ ወይም ፡ የግንቡ ፡ አርመን ፡ ወርዱ ፡ ሆዱ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፻፷ ፡ አድያም ፡ ደወል ፡ ብሔር ፤ አውራጃ ፡ ቀበሌ ፡ ግዛት ፡ አገር ፡ ይኾናሉ ። አድ
ያመ ፡ ዮርዳኖስ ። ደወለ ፡ ጢሮስ ። ብሔረ ፡ ግብጽ ። ብሔረ ፡ አሕዛብ ። ደወል ፡ ተለ
ይቶ ፡ ወሰን ፡ ደንበር ፡ ይኾናል ፤ ኢታፍልስ ፡ ደወለ ፡ ገራህት ። አፍአና ፡ ማእከል ፡
በየቦታቸው ፡ ተነግረዋል ። ጥቃ ፡ ኀበ ፡ ሕፅን ፡ ገቦ ፡ ጕንድ ፤ አጠገብ ፡ ጎን ፡ ወገብ ፡
ይኾናሉ ፤ የቦታ ፡ አገባቦች ፡ ይሰማሟቸዋል ። ጥቃ ፥ ለቦታ ፡ ብቻ ፤ የቀሩት ፡ ለቦታም ፡
ላካልም ፡ ይኾናሉ ። ይነብር ፡ ጥቃ ፡ ፍኖት ። ወቤቱ ፡ ኀበ ፡ ምኵራብ ። ሕፅነ ፡ ደብር ፡
ገቦ ፡ ደብር ፡ ጕንደ ፡ ደብር ። ኢትጸውዕ ፡ ኀረከ ፤ ይረፍቅ ፡ ውስተ ፡ ሕፅኑ ። ይወድቁ ፡
በገቦከ ። አጻብዒከ ፡ እምጕንደ ፡ ክልኤ ፡ እእጋር ። ጽጕ ፡ ጽጕጕ ፡ ጽጕጓት ፥
ጥግ ፡ ወልወል ፡ ይኾናል ። ጽጐ ፡ ቤት ፤ ጽጐ ፡ ሀገር ፤ ወለእመ ፡ ሀለዉ ፡ ጽጕጓት ፡ ማ
እከለ ፡ አብያት ፥ ወልወል ። ዐውድ ፡ ዘውር ፥ ዙሪያ ፡ ይኾናሉ ፤ ክበብ ፡ ባለው ፡
ኹሉ ፡ ይገባሉ ። ዐውደ ፡ ቤት ፥ ዘውረ ፡ አክሊል ። ዐውድ ፡ ተለይቶ ፡ አደባባይ ፡ ሸንጎ ፡
ዐውድማ ፡ ይኾናል ። ነበሩ ፡ ዐውደ ፡ ለኵንኖቱ ። ዘበቱ ፡ ያነጽሕ ፡ ዐውደ ፡ እክሉ ።
ሲዘረዘሩም ፡ ዐውዱ ፡ ዳ ፥ ዘውሩ ፡ ራ ፡ እያሰኙ ፡ እንዳንቀጹ ፡ ስልት ፡ ይፈታሉ ። ይቀ
ውሙ ፡ ዐውዶ ፤ በዙሪያው ። ንንሥት ፡ ዐውደነ ፤ ሸንጓችንን ፡ እንፍታ ።

## የጊዜ ፡ ጥሬዎች ።

፻፷፩ ፡ ቅድም ፡ መቅድም ፡ ቀዲሙ ፡ አቅዲሙ ፡ ቀዳሚ ፤ ቀድሞ ፡ አስቀድሞ ፡
ፊት ፡ መዠመሪያ ፡ ይኾናሉ ። ቅድምና ፡ መቅድም ፡ ግእዝ ፡ ኹነው ፥ የቀሩት ፡ ጕልት ፡
ኹነው ፡ ሳይፈልሱ ፡ ይነገራሉ ። ቅድም ፡ ተለይቶ ፡ በቦታም ፡ በጊዜም ፡ እንዲገባ ፡
በፊት ፡ ተነግሯል ። ፳፱ቱ ፡ ኹሉ ፥ ላንድና ፡ ለብዙ ፡ ለወንድና ፡ ለሴት ፡ ለሩቅና ፡ ለቅርብ ፡
እየኾኑ ፡ እንዳንቀጻቸው ፡ ስልት ፡ ይፈታሉ ። ቅድመ ፡ አሡኒ ፥ መቅድመ ፡ ኀሡ ። ቀ
ዲሙ ፡ ዜነወነ ፤ ዘነገሩክሙ ፡ ቀዲሙ ፤ አቅዲሙ ፡ ነገረ ፡ በአሪት ። ቀዳሚ ፡ ጸሐፍኩ ፡
ለከ ። መቅድምና ፡ አቅዲሙ ፡ ሲቀሩ ፡ እምና ፡ በ ፡ ይሰማሟቸዋል ። የቅድምና ፡ የቀ
ዳሚ ፡ አንጻሮች ፡ ድኅርና ፡ ደኃሪ ፥ ኋላ ፡ መጨረሻ ፡ ይኾናሉ ፤ አገባባቸውም ፡ እስከ ፡
ነው ። ድኅር ፡ ግእዝ ፡ እየኾነ ፥ ደኃሪ ፡ ከዋላ ፡ በነባርነት ፡ ሲነገሩ ፥ ኋላ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡
ኋላ ፡ ይኾናሉ ። ይነብሩ ፡ ሙታን ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ እስከ ፡ ይትነሥኢ ፡ ድኅረ ፥
አው ፡ ደኃሪ ፡ ከዋላ ። ገብኡ ፡ ድኅረ ። በ ፡ ለ ፡ መንገለ ፡ እም ፡ ይሰማሟቸዋል ፤ ቅድ
መና ፡ ድኅረም ፡ እንደ ፡ ግድም ፡ እንደ ፡ ላዕል ፡ ተደጋግመው ፡ ይነገራሉ ። ቅድመ ፡
ቅድመ ፡ እንዘ ፡ የሐውሩ ፥ ነቢያት ፡ ድኅሬተ ፡ ነጸሩ ። ፈረሱ ፡ ለፈርዖን ፡ ይቤ ፡ ድኅረ ፡
ድኅረ ፤ እስመ ፡ እግሩ ፡ ኢለመደ ፡ ባሕረ ። መቅድም ፡ መስም ፡ ነው ፤ ቀዳሚ ፡ ደኃሪ ፡

ማልስ ፡ ቅጽሎች ፥ ቅድምና ፡ ድኅር ፡ ጥሬዎች ፥ ቀዳሙና ፡ አቅዳሙ ፡ በዝ ፡ አንቀጾች ፡
ናቸው ። ኹሉም ፡ ባ፫ ፡ አርእስት ፡ እየገቡ ፥ ቅድመ ፡ መቅድመ ፥ ቀዳሙ ፡ አቅዳሙ ፡
ቀዳሚ ፥ አው ፡ ድኅረ ፡ ደኅሬ ፡ ጸውዐ ፡ አጸውዐ ፥ ተጸውዐ ፡ ተጻውዐ ፡ አስተጻውዐ ፡
ያሰኛሉ ። ይኸውም ፡ በምልአት ፡ ለሚነገሩ ፡ እንጂ ፡ ለኹሉ ፡ አይዶለም ፤ በሳድስ ፡
ቅጽልም ፡ ሲገቡ ፥ ጽዉዕ ፡ ቅድመ ፡ ቀዳሚ ፡ ወምጹእ ፡ ድኅረ ፡ ደኅሬ ፡ ፊት ፡ የተጠራ ፡
ኋላ ፡ የመጣ ፡ ያሰኛሉ ። ጊዜም ፡ ከነክፍሎቹ ፡ ከቅጽል ፡ ጋራ ፡ ይነገራል ። ቅጽሉም ፡
አኀዝና ፡ የአኀዝ ፡ ጥሬ ፡ ነው ፤ የአኀዙ ፡ በቦታው ፡ ተነግሯል ። ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ ኵሉ ፡ ሰ
ዓተ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ኵሎ ፡ ዘመነ ፤ ኹል ፡ ጊዜ ፥ ኹል ፡ ቀን ፡ ዘወትር ፡
በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ያሰኛሉ ። ተናበው ፡ የሚነገሩ ። ጥንት ፡ መሠረት ፤ መዠመሪያ ።
ፍጻሜ ፡ ተፍጻሜት ፤ መጨረሻ ፡ ይኾናሉ ። ሲገቡም ፡ ጥንተ ፡ ሕይወት ፡ ጥንተ ፡ ዕለት ፥
መሠረተ ፡ ንጽሕ ፡ መሠረተ ፡ ቃል ። ፍጻሜ ፡ ዘመን ፥ ተፍጻሜተ ፡ መዋዕል ፡ ያሰኛሉ ።
መሠረት ፡ ለኹሉ ፡ ይኾናል ። ተዘርዝረው ፡ የሚነገሩ ። ንእስ ፡ ናእስ ፡ ንእስና ፤ ልጅ
ነት ፡ ታናሽነት ። ውርዙት ፡ ውርዛዌ ፡ ውርዝውና ፤ ጕልማስነት ፡ ዐፍላ ፡ ጕብዝና ።
ርሥእ ፡ ርሥኣን ፡ ርሥእና ፤ እርግና ፡ አሮጌነት ። እም ፡ በ ፡ አመ ፡ እስከ ፡ ድኅረ ፡ ይሰ
ማሟቸዋል ። ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ዐቀብኩ ፡ እምንእስየ ። ሰሎሞን ፡ ኮነ ፡ ጠቢበ ፡ እምንእሱ ፡
በንእሱ ፡ አመ ፡ ውርዛዌሁ ፤ ወአመ ፡ ርሥኣኑ ፡ ኮነ ፡ አብደ ። አብርሃም ፡ እምውርዛ
ዌሁ ፡ እስከ ፡ ርሥኣኑ ፡ ኢወለደ ፤ ወበልህቅናሁ ፡ ረከበ ፡ ወልደ ። ወእምድኅረ ፡ ርሥ
ኣን ፡ ጥሉል ።

## ያካልና ፡ የባሕርይ ፡ ጥሬዎች ።

፻፳፱ ፤ ኵለንታ ፤ ኹለንተና ፥ ኹለመና ፡ ይኾናል ። ከራስ ፡ ጠጕር ፡ እስከ ፡
እግር ፡ ጥፍር ፡ እንደ ፡ ማለት ። ጠባይዕ ፤ በቁሙ ፡ ጠባይ ፡ ባሕርይ ፡ ይኾናል ።
አባል ፡ ሕዋስ ፥ መንፈስ ፡ ነፍስ ፥ ነፍስት ፡ መሌሊት ፤ አካል ፡ ብልት ፡ ገላ ፡ ሰውነት ፡
ይኾናሉ ። ቅጽሎቻቸውም ፡ ኵሉ ፡ ኵላ ፡ ናቸው ፤ አኀዝም ፡ ይስማማቸዋል ፤ ለእመ ፡
ሐመ ፡ አሐዱ ፡ አባል ። አካል ፤ በቁሙ ፥ ቁመት ፡ አቋቋም ፥ ለመያዝ ፡ የሚበቃ ፤ መ
ጠን ፡ ግዘፍ ፡ ይኾናል ፤ ዘመጠነ ፡ ገዝ ፡ አካሎን ። ህላዌ ፤ ባሕርይ ፡ አካል ፥ አቋቋም ፡
አናዎር ። ከዋኔ ፤ አኳኋን ፡ ኹነታ ፤ ከዋኒ ፤ ኳኝ ፡ ቀዋሚ ፡ ይኾናሉ ። በት
ምርት ፡ በስሎ ፡ የታጨደው ፡ ያገባበች ፡ ነዶና ፡ ክምር ፥ ክምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ከብዙ ፡ በጥ
ቂቱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ፯ኛ ፡ ክፍል ።

## ጸዋትወ ፡ ቅኔ ፥ የሠምና ፡ የወርቅ ፡ ኵርጓኔ ።

### ፳፱ኛ ፡ ዕርከን ።

ሠምና ፡ ወርቅ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ወንድማማች ፡ በምስጢር ፡ መንታ ፡ ሲኾኑ ፡
በንባብ ፡ ሳይሟፈሩ ፡ በ፩ ፡ ነገር ፡ ተባብረው ፡ ተጣምረው ፡ ፩ ፡ ወጣት ፡ ቃል ፡ መስለው ፡

የሚነገሩ፡ተመሳሳዮች፡ማለት፡ነው ። በተረትም ፥ ሠምና፡ወርቅ፡እንጀራና፡መረቅ፡ ይባላል ።

፻፳፫ ፤ ሠምና፡ወርቅ፡ሲመሰሉ፡ሠም፡ተናበ፡እየቀደመ፡ወርቅ፡ይከተላል ፤ ወርቅም፡ቀድሞ፡ሠም፡ቢከተል፡ካልተናበበ፡ጸያፍ፡አይባልም ፤ ቢናበብ፡ግን፡ ግንባር፡ጸያፍ፡ይባላል ። ፩ኛውን፡ፀዋጅ፡ለማሳየት ፥ ርኁባን፡አሕዛብ፡በልዑ፡ ኅብስተ፡ሃይማኖት ፤ ወይም፡ኅብስተ፡ሃይማኖተ፡በል ። ፪ኛውን፡ለማሳየት ፥ በልዑ፡ ሃይማኖተ፡ኅብስተ፡በል ፤ ይህ፡ጸያፍ፡አይባልም ፤ ሃይማኖተ፡ኅብስት፡ቢል፡ግን፡ ግንባር፡ጸያፍ፡ነው ። ሠም፡ተናበ፡ለወርቅ፡፫፡ፈደላት፡ያተርፍለታል ፤ ፈደላ ቱም፡ግእዝ፡ሳብዕ፡ኃምስ፡ናቸው ። ይህም ፥ ሰሎሞን፡ዐማኑኤል፡ሐነጸ፡መቅደሰ፡ ደሙ፡ማሕየዊ፡ባለ፡ጊዜ፡ሳብዕና፡ኃምስ፡ማስቀረቱን፡ያሳያል ፤ ባይናበበው፡ ግን፡ደሞ፡ማሕየዌ፡ባለ፡ነበረ ። ግእዝ፡ማስቀረቱም ፥ መቅደሰ፡ደም፡ሐነጸ፡በማ ለት፡ይታያል ። ሠም፡ለወርቅ፡የሚያተርፍለት፡ይህ፡ብቻ፡አይዶለም ፤ ከዚህ፡ሌላ፡ ደግሞ፡፯፡ነገር፡ያተርፍለታል ፤ እነዚሁም፡ማሰሪያ ፥ አንቀጽ ፥ ተናባቢ ፥ አፈታት ፥ ቅጽል ፥ ዝርዝር፡ናቸው ። አገባብ፡ያተርፋል፡የሚሉም፡አሉ ፤ አገባብ፡ግን፡በሠም፡ ላይ፡ወድቆ፡ለወርቅ ፥ በወርቅ፡ላይ፡ወድቆ፡ለሠም፡ይኸናልና ፤ ሠም፡ለወርቅ፡ አገባብ፡ያተርፋል፡ማለት፡ለልብ፡አይረዳም ። ፯፡ነገር፡ማትረፉም፡እንዲህ፡ነው ። እመ፡ርኅራኄ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ትወግዕ፡ጥዑመ፡ሥጋዌ፡ሐሊበ፡እግዚእነ፡ለደ ቂቃ፡ምእመናን ፥ በይነ፡ዘአእመረት፡ከመ፡ይከውኖሙ፡ሕይወተ፡ኀይለ፡ሥጋ፡ ብሎ ፥ ትወግዕ፡በማለት፡ማሰሪያ፡ማትረፉን ፥ ጥዑመ፡በማለት፡ቅጽልን ፥ ሐሊበ፡ እግዚእነ፡በማለት፡ተናባቢን ፥ ሥጋዌ፡ወተትን፡በማለት፡አፈታትን ፥ በይነ፡ዘአእ መረት፡በማለት፡አንቀጽን ፥ ለደቂቃ፡በማለት፡ዝርዝር፡ማትረፉን፡ያሳያል ።

፻፳፬ ፤ ባለቤትና፡ዘርፍ፡በሠምና፡በወርቅ፡አካኼድ፡ሲነገሩ፡ብዙ፡ስም፡አላ ቸው፡አስቀድመን፡ባ፲፮ኛ፡ዕርከን፡እንደ፡ተናገርነ፡(ቍ፹፰) ። የሠም፡ባለቤት፡ ከወርቅ፡ዘርፍ፡ተናበ፡የወርቅን፡ባለቤት፡ሲያመጣ፡ውስጠ፡ወይራ፡ያሰኛል ። ይህም፡ነዳያን፡አሕዛብ፡በልዑ፡ኅብስተ፡ጴጥሮስ፡ባዕል፡ባለ፡ጊዜ፡ሃይማኖተ፡ ጴጥሮስ፡ማለቱን፡ያሳያል ። ስሙም፡ክብ፡ውስጠ፡ወይራ፡ይባላል ፤ የሠሙ፡ዘርፍ፡ ባዕል፡ሲቀር፡ግን፡ክብ፡አይባልም ። ፪ኛም፡የወርቅ፡ባለቤት፡እየቀደመ፡የሠም፡ ባለቤት፡ተከትሎ፡ከወርቅ፡ዘርፍ፡ሲናበብ፡ዝምድ፡ያሰኛል ። ይህም፡ተበልዐ፡ ሃይማኖት፡ኅብስተ፡ጴጥሮስ፡ባዕል፡ማለቱን፡ያሳያል ። ስሙም፡ድርብ፡ዝምድ፡ ይባላል ፤ ባዕል፡ሲቀር፡ግን፡ነጠላ፡ዝምድ ፥ ወይም፡ቅጽል፡ከምሳሌ፡ያሰኛል ። ፫ኛም፡የሠም፡ባለቤት፡ከወርቅ፡ዘርፍ፡ተናበ፡እየቀደመ፡የወርቅ፡ባለቤት፡ሲከ ተል፡ፍላጻ፡ይባላል ። ይህም፡ተበልዐ፡ኅብስተ፡ጴጥሮስ፡ባዕል፡ሃይማኖት፡ሲል፡ ድርብ፡ፍላጻ ፤ የሠሙ፡ዘርፍ፡ባዕል፡ሲቀር፡ነጠላ፡ፍላጻ፡ይባላል ። ፬ኛም፡የሠም፡ ባለቤት፡በወርቅ፡ባለቤት፡ላይ፡በሚናበብበት፡ጊዜ፡በወርቅ፡ባለቤት፡ሲጠበቅ፡ ጥምዝ፡ይባላል ። ይህም፡በልዐ፡ኅብስተ፡ዘጴጥሮስ፡ሃይማኖት፡ባለ፡ጊዜ፡ጥምዝ ነቱን፡ያሳያል ። ፭ኛም፡ዘርፍ፡በዘና፡በለ፡ሲደፋ፡ስሙ፡ድፋት፡ይባላል ። ይህም፡

በልዐ ፡ ዘጴጥሮስ ፡ ባዕል ፡ ሃይማኖተ ፡ ኀብስተ ፡ ሲል ፡ የዘ ፡ ድርብ ፡ ድፋት ፤ ባዕል ፡ ሲቀር ፡ ነጠላ ፡ ድፋት ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ። ዳግመኛም ፡ በልዐ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ባዕል ፡ ጥዑመ ፡ ሃይማኖተ ፡ ኀብስቶ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ርኁብ ፡ ሲል ፡ የለ ፡ ድርብ ፡ ድፋት ፤ ባዕል ፡ ሲቀር ፡ ነጠላ ፡ ድፋት ፡ ይባላል ። ፫ኛም ፡ በልዐ ፡ ወይም ፡ ተበልዐ ፡ ሃይማኖተ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኀብስተ ፡ ባዕል ፡ ተብሎ ፡ በየገንዘቡ ፡ ሲነገር ፡ ተቻቻይ ፡ ይባላል ።

፫፻፫ ፡ ብሂልም ፡ በሰዋስውነቱ ፡ ዘርፍና ፡ ምሳሌ ፡ ይኾናል ፤ ከዘርፍም ፡ ሲያገዝ ፡ ለብሂል ፡ ለ ፡ የለው ፡ ለብሂሎት ፡ ዘ ፡ የለው ፡ ይባላል ። ዘርፍ ፡ ሲኾን ፡ ዝምድ ÷ ፍላጻ ÷ ድፋት ÷ ጥምዝ ÷ ክብ ፡ ውስጠ ፡ ወይራ ÷ ምፀት ÷ ሠረዝ ÷ ተራ ፡ ምሳሌ ፡ ይኾናል ። ዝምድ ፡ ሲኾን ÷ ምሕረት ፡ ወርቀ ፡ ብሂል ፡ አድኅን ፡ ነዌ ፡ ለእግዚእ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ንዋዩ ። ፍላጻ ፡ ሲኾን ÷ ወይኑ ፡ ብሂል ፡ ለብሰ ፡ ሥጋ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ መዐዛ ፡ ሃይማኖት ፡ ሰትየ ፡ ቄርሎስ ፡ ንጉሥ ። ድፋት ፡ ሲኾን ÷ ዘብሂል ፡ ተወልደ ፡ እምላክ ፡ ወጴጥሮስ ፡ ተሰቅለ ፡ ቍልቍሊተ ፡ ምስጢረ ፡ ቤተ ፡ ሐንጽኩ ። ጥምዝ ፡ በትረ ፡ ዘብሂል ፡ አጽንዐ ፡ ሕገ ፡ አ ፡ ሰብእ ፡ ለአድኅኖ ፡ ነፍስከ ፡ ወንጌል ፡ ጳውሎስ ፡ ኖላዊ ፡ ነሥአ ፡ በእደ ፡ ጕባኤ ። ያልተከበበ ፡ ውስጠ ፡ ወይራ ፡ ሲኾን ÷ መሰበ ፡ ብሂል ፡ እትወለድ ፡ እምወለተ ፡ ወለትከ ፡ ሰፈየት ፡ ድንግል ፡ መርዓተ ፡ ሙሴ ፡ አ ፡ አዳም ። ክብ ፡ ሲኾን ÷ በግዐ ፡ ብሂል ፡ ተወልደ ፡ አምላክ ፡ እምነ ፡ ማርያም ፡ ባዕል ፡ በልዐ ፡ ዕጕለ ፡ አርዌ ፡ ንስጥሮስ ። ምፀት ÷ ብሂል ፡ እድግት ፡ አውዕአት ፡ ቀርነ ÷ ብሂል ፡ ተናገረት ፡ እብን ፡ ነገረ ። ረሠዝ ÷ ብሂል ፡ ተሰቅለ ፡ እግዚእ ፡ ላዕለ ፡ ጽሒፎተ ፡ ቀይሕ ፡ ቀለም ፡ ወብሂል ፡ ተሰቅለ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቃሕተ ፡ ተርጕሞተ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ይደልምሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ ሊቃውንት ፤ የዋዌ ፡ ሠረዝ ፡ ነው ። ተራ ፡ ምሳሌም ፡ ሲኾን ÷ ወርቀ ፡ ብሂል ፡ ሞተ ፡ እግዚእ ፡ በእንተ ፡ ፍቅረ ፡ ሰብእ ፡ ዘገበ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ባዕል ፡ ይላል ። ከዚህ ፡ የቀረው ፡ የብሂል ፡ ጓዝ ፡ አንቀጽነቱና ፡ አገባብነቱ ፡ በቦታው ፡ ተነግሯል ፡ (ቍ ፹፫) ።

፫፻፬ ፡ የምሳሌ ፡ ዐዋጅ ። ሩቅና ፡ ቅርብ ÷ አንድና ፡ ብዙ ÷ ወንድና ፡ ሴት ፡ አይመስሉም ፤ ይኸውም ፡ በማሰሪያ ፡ በንቀጽ ፡ በቅጽል ፡ ኀብረትና ፡ አንድነት ፡ የላቸውምና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ይህም ÷ ብህለ ፡ ብህልከ ÷ ተብህለ ፡ ተብህሉ ÷ አብሀለ ፡ አብሀለት ÷ በሃሊ ፡ በሃሊት ፡ በማለት ፡ ይታያል ። ፩ኛም ፡ ወ ፡ አንድ ፡ ያደረጋቸው ፡ ኹለት ፡ ስሞች ፡ ሠም ፡ ኹነው ÷ ወርቅም ፡ ኹነው ፡ ከስም ፡ ተዛምደው ፡ አይመሰሉም ። ይህም ፡ ርኁብ ፡ ወነዳይ ፡ አሕዛብ ፡ በልዑ ፡ ኀብስተ ፡ ሃይማኖት ፡ አለማለት ፡ ነው ። ፪ኛም ፡ ነባቢና ፡ ኢነባቢ ÷ የተጸውዖ ፡ ስምና ፡ ስም ÷ ስምና ፡ ግብር ፡ ኀዳሪና ፡ ማኅደር ÷ አንድና ፡ ብዙ ÷ ወንድና ፡ ሴት ÷ እነዚህ ፡ ፫ቱ ፡ ተናበው ፡ አይመስሉም ። ቅርብና ፡ ሩቅ ፡ ግን ፡ ተናበ ፡ ሲመስል ÷ ተበላዕከ ፡ ኀብስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘረትዐ ፡ ሲል ÷ የሠሙ ፡ አቅራቢ ፡ ለወርቁ ፡ ተርፎ ፡ ቅጽሉን ፡ ዘረታዕከ ፡ ያሰኛልና ፤ ጸያፍ ፡ አይባልም ። ይህም ÷ ዘተወልደ ፡ ዘተጠምቀ ፡ ዘተንሥአ ፡ ብሎ ፡ ተሣሀለነ ፡ እግዚኦ ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ፤ የግልጠ ፡ ዘ ፡ ጠባይ ፡ ይህ ፡ ነው ። ውስጠ ፡ ዘም ፡ ቢኾን ፡ ከቅርብና ፡ ከሩቅ ፡ ይስማማል ፤ ባላገባቦች ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ላይኛው ፡ መስዓቸው ፡ በልማድ ፡ ዐዋጅ ፡ ጸያፍ ፡ ነው ፡

ይሉታል ። ነባቢና ፡ ኢነባቢ ፥ ካህን ፡ እብን ፡ ቀዳሲ ። ስምና ፡ ስም ፥ ዳዊት ፡ ሚካኤል ። ስምና ፡ ግብር ፥ ሰሎሞን ፡ ጥበብ ። ኅዳሪና ፡ ማኅደር ፥ ወርቀ ፡ መዝገብ ፥ ወይም ፡ ኅብ ስተ ፡ መሰብ ፡ ብሎ ፡ አለመመሰል ፡ ነው ። ከ፮ቱ ፡ ደግሞ ፡ ፫ቱ ፡ ፊተኞች ፡ ሲቀሩ ፡ ፫ቱ ፡ ኋለኞች ፡ በውስጠ ፡ ወይራነት ፡ ሠም ፡ ለበስ ፡ ኹነው ፡ ሲነገሩ ፡ ከውስጣቸው ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ይወጣል ። ኅዳሪና ፡ ማኅደር ፥ ግሩም ፡ ውእቱ ፡ አንበሳ ፡ ገዳም ፡ በነበ ፡ እራ ዊት ፡ ሰብእ ፡ ብሎ ፥ ባሕታዊ ፡ ገዳም ። እንድና ፡ ብዙ ፥ አዋልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ብሎ ፡ ሐዋሳተ ፡ ጊዮርጊስ ። ወንድና ፡ ሴት ፥ ብእሲተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወለደት ፡ ሠለስተ ፡ ብሎ ፡ ክሣደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አውሐዘት ፡ ደመ ፡ ወማየ ፡ ወሐሊበ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ ዘርፍ ፡ ከዘርፍ ፡ ሳይማሰል ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አንድና ፡ ብዙ ፡ ያናግራል ። ይህም ፥ እደ ፡ ሔዋን ፡ ደሙ ፡ ለዐማኑኤል ፡ መተረ ፡ ፍዳ ፡ ኀጢአታ ፡ ለሔዋን ፡ በለሰ ፡ ገነት ። ትም ህርተ ፡ ሐዋርያት ፡ መቅደሱ ፡ ለሰሎሞን ፡ ተሐንጸት ፡ በወርቅ ፡ አርእዮተ ፡ መንክር ። ምሳሌም ፡ ከንቀጽ ፡ ወዲህ ፡ እንጂ ፡ ከንቀጽ ፡ ወዲያ ፡ የለም ፡ ዝናም ፡ መጽአ ፡ ሀሳዕና ፡ ቢል ፡ ፍርቅ ፡ ይባላል ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ የሠምና ፡ የወርቅ ፡ አከኼድ ፥ የቅኔ ፡ ጕዳና ፥ የንባቡን ፡ አሰካከና ፡ መልክ ፡ ከነስሙ ፡ መጽሔት ፡ በሚባለው ፡ በታላቁ ፡ አገባብ ፡ ተመልከት ፡ (ገጽ ፡ ፫፻፶፯—፫፻፷) ።

## ፳፫ኛ ፡ ዕርከን ።

## ብትን ፡ ሰዋስው ።

### የደቂቅ ፡ አገባብ ፡ እንጻሮች ፥ ወይም ፡ ውስጠ ፡ ወይሮች ።

ብትን ፡ ሰዋስው ፡ ማለት ፥ ፲፡ ቅንጣት ፡ ጥሬ ፥ ወይም ፡ ፲ ፡ ዐይነት ፡ ፍሬ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ውጥንቅጥ ፡ እንደ ፡ ማለት ። እነዚህም ፡ በታና ፡ ጊዜ ፥ በሕርይና ፡ አካል ፥ ስምና ፡ ግብር ፥ ነገር ፡ ናቸው ። ብትን ፡ ሰዋስውም ፡ ያሰኛቸው ፥ አገባብ ፡ ሳይዙ ፡ ብቻ ፡ ብቻ ቸውን ፡ ተነግረው ፡ በፊታቸው ፡ አገባብ ፡ ማምጣት ፡ ነው ።

፻፳፰፡ መድረሻቸው ፡ በዝርዝርነት ፡ በነባርነት ፡ ግእዝ ፡ ራብዕ ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕ ፡ ሲኾን ፡ በልማዳዊ ፡ ዐማርኛው ፥ በ፫ ፡ አናቅጽ ፡ ዐማርኛና ፡ በ፰ ፡ አገባብ ፡ ዐማርኛ ፡ ይ ፈታል ። ልማዳዊ ፡ ዐማርኛው ፡ ን ፡ ነው ፡ ፫ቱም ፡ አናቅጽ ፥ ገብረ ፡ መሰለ ፡ ብህለ ፡ ና ቸው ። ዐማርኛቸውም ፥ ኹኖ ፡ አድርጎ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ መስሎ ፡ አስመስሎ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ብሎ ፡ ተብሎ ፡ አሰኝቶ ፡ ተባብሎ ፡ አባብሎ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ነው ። ኹኖ ፡ መስሎ ፡ ተብሎ ፡ ተባብሎ ፡ ባ፬ ፡ አርእስት ፡ ያሳስራሉ ። አድርጎ ፡ አስመስሎ ፡ ብሎ ፡ አባብሎ ፡ በ፫ ፡ አ ርእስት ፥ አሰኝቶም ፡ በራሱ ፡ ያሳስራሉ ። ያ፰ቱ ፡ አገባብ ፡ ዐማርኛ ፡ በ ፡ ከ ፡ ወደ ፡ ጋራ ፡ ለ ፡ ነው ። ን ፡ ሲኾን ፥ ጼሐ ፡ ፍኖተ ፡ ተከለ ፡ ደብተራ ፡ ቀሠመ ፡ ጽጌ ፡ እንዘ ፡ መርኖ ፡ ይላል ። በ ፡ ሲኾን ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ፡ ወደ ፡ ሲኾን ፡ በበታ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ማሰ ሪያዎቹም ፥ በአ ፡ ወፅአ ፥ ሖረ ፡ መጽአ ፥ ተመይጠ ፡ ገብአ ፥ ዐርገ ፡ ወረደ ፥ ተፈነወ ፡ ነ ገደ ፥ በጽሐ ፡ ተሰደ ፥ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ናቸው ፡ ሲገባም ፥ ዐርገ ፡ ሐመረ ፡ ወረደ ፡ ምድረ ፡ ገየ ፡ ግብጸ ፡ ተመይጠ ፡ ናዝሬተ ፡ ወገሊላ ። ሰፍያ ፡ ንግሥት ፡ ነገደት ፡ ሮሜ ፥

ወበጺሓ ፡ ሮሜ ፡ ሖረት ፡ ተሰሎንቄ ፥ ወእምህየ ፡ ገብአት ፡ ደማስቆ ፡ ያሰኛል ። ባለቦታ ውንም ፡ ፈልጎ ፡ በተጸውዖ ፡ ስም ፡ ሲገባ ፥ ግእዝ ፡ ወራሽ ፡ ቀለም ፡ ይፈልጋል ፡ እነዚ ሁም ፡ ሀ ፡ ሃ ፡ ናቸው ፥ ግእዙ ፡ የወንድ ፡ ራብዑ ፡ የሴት ። ፈነወ ፡ ኪራም ፡ አግብርቲሁ ፡ ሰሎሞንሀ ። ተፈነወ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክ ፡ ማርያምሃ ፡ እያሰኘ ፡ ኀበ ፡ በገባበት ፡ ይ ገባል ።

፻፳፰ ። ግብር ፡ ነገር ፡ በዝርዝርነት ፡ በነባርነት ፡ ግእዝ ፡ ራብዕ ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕ ፡ ሲኾኑ ፡ በ ፡ ይኾናሉ ። በ፪ ፡ ግሶች ፡ ያሳስራሉ ፡ ግሶቹም ፡ ንእሰ ፡ ዐብየ ፡ ዐረየ ፡ ቀደመ ፡ ኀብረ ፡ ሰክረ ፡ ናቸው ። ግብር ፡ በ ፡ ሲኾን ፥ ኢትስክሩ ፡ ወይነ ፡ በወይን ። ንእሰ ፡ ክብረ ፡ ይሁዳ ፡ ዐብየ ፡ ማትያስ ፡ እምይሁዳ ፡ ክብረ ፡ በክብር ። እምከመ ፡ ዐረይነ ፡ ሕማመ ፡ ንዔረ ፡ ክብረ ፡ ምስሌሁ ፡ በመከራ ፡ በክብር ። ቀደመ ፡ አሳሄል ፡ ሩጸተ ፡ እምአብያጺሁ ፡ በሩጫ ። ነገር ፡ በ ፡ ሲኾን ፡ ኀበሩ ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ። ኀብሩ ፡ ምክረ ፡ ወሃይማኖተ ፥ አው ፡ አሚነ ፡ ብሎ ፡ በምክር ፡ በሃይማኖት ፡ ያሰኛል ። ቦታ ፡ ግን ፡ በ ፡ ሲኾን ፡ ሀሎ ፡ ኮነ ፡ ነበረ ፥ እነዚህን ፡ በመሰሉ ፡ ግሶች ፡ ያሳስራል ። ሀሎ ፡ ገዳመ ፡ አው ፡ ቤተ ፡ ነበረ ፡ ላዕለ ፡ አው ፡ ታሕተ ፡ በዱር ፡ በቤት ፥ በላይ ፡ በታች ።

፻፳፱ ፡ ጊዜም ፡ በ ፡ ሲኾን ፡ ለቦታ ፡ በሚስማሙ ፡ አናቅጽ ፡ ያሳስራል ። ይህም ፥ ሌሊተ ፡ ቦአ ፡ ወሌሊተ ፡ ወፅአ ። መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ዕቀበነ ፡ አንተ ። ተሰቅለ ፡ ቀትረ ፥ ወወረደ ፡ ሠርከ ፡ እያሰኘ ፥ በመዓልትና ፡ በሌሊት ፥ በቀትር ፡ በሠርክ ፡ ማለ ቱን ፡ ያሳያል ። አኀዝ ፡ ቅጽል ፡ ሲጨመርበት ፡ ግን ፡ በ ፡ ወይም ፡ ን ፡ ተብሎ ፡ መፈ ታት ፡ የለውም ፡ ዐማርኛው ፡ በአኀዝ ፡ ይበዘበዛል ። ይህም ፡ ነበረ ፡ ሠሉሰ ፡ መዋዕለ ፡ ወሠሉሰ ፡ ለያልየ ። ሰዱሰ ፡ ዕለተ ፡ ተገበር ፡ ግብረከ ። ጾመ ፡ አርብዓ ፡ መዓልተ ፡ ወአ ርብዓ ፡ ሌሊተ ፡ በለው ፡ ይታወቃል ።

፻፴ ፡ ግብር ፡ ነገር ፡ ባሕርይ ፡ አካል ፥ ግእዝና ፡ ራብዕ ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕ ፡ ኾነው ፡ ሲነገሩ ፡ ከ ፡ ይኾናሉ ። የሚስቡቸውም ፡ አናቅጽ ፡ ርኅበ ፡ ጸምአ ፡ ነድየ ፥ ተዐርቀ ፡ ጾመ ፡ ዐብየ ፡ ንእሰ ፥ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ናቸው ። ግብር ፥ ከ ፡ ሲኾን ፥ ተዐርቀ ፡ ልብሰ ፡ ርኅበ ፡ ኅብስተ ፡ ጾመ ፡ መብልዐ ፡ ብሎ ፥ ከልብስ ፡ ከንጀራ ፡ ከመብል ፡ ያሰኛል ። ነገርም ፡ ከ ፡ ሲኾን ፥ ተከልአ ፡ ውዴተ ፡ ወሐሚተ ፥ ከሰብቅ ፡ ከሐሜት ። ባሕርይ ፡ ከ ፡ ሲኾን ፥ ጸምአ ፡ ማየ ፥ ነድየ ፡ ወርቀ ፥ በደረ ፡ ልሂቀ ፡ ከውሃ ፡ ከወርቅ ፡ ከልሂቅ ። አካልም ፡ ከ ፡ ሲኾን ፥ ዐብየ ፡ መልአክ ፡ በኀይል ፡ ሰብአ ፡ ንእሰ ፡ ሰብእ ፡ በኀይል ፡ መልአክ ፡ ያሰኛል ፡ ኹሉንም ፡ ከ ፡ ብለኽ ፡ ፍታ ።

፻፴፩ ፡ ብትን ፡ ሰዋስው ፡ ኹሉ ፡ በዝርዝርነት ፡ በነባርነት ፥ ግእዝ ፡ ራብዕ ፡ ኃምስ ፡ ሳብዕ ፡ ሲኾን ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ይኾናል ። ጋራ ፡ ሲኾን ፡ በመደራረግ ፡ በማደራረግ ፡ ያሳስ ራል ። በመደራረግ ፡ ተማከረ ፡ ሰብአ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ፡ ያሰኛል ። በማ ደራረግም ፡ ጊዜ ፡ አስተማከረ ፡ ሰብአ ፡ በል ። ብትን ፡ ሰዋስው ፡ እንደ ፡ ሲኾን ፡ በዘፈቀደ ፡ ግስ ፡ ያሳስራል ። ተቀሥፈ ፡ እግዚእነ ፡ ሰራቂ ፥ ወተሰቅለ ፡ እቡሰ ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ እንደ ፡ በደለኛ ። ኹናም ፡ ሲኾን ፥ አምላክ ፡ ሞተ ፡ ሰብአ ፡ ሰው ፡ ኹኖ ። አድርጎም ፡ ሲኾን ፥ አስተየ ፡ ማየ ፡ ወይነ ፡ ውሃውን ፡ ወይን ፡ አድርጎ ። መስሎም ፡ ሲኾን ፥ አስተርአየ ፡

ሰይጣን ፡ ሰብአ ። አስመስሎም ፡ ሲኾን ፥ ይውህብ ፡ ሰይጣን ፡ እብነ ፡ ወርቀ ፥ አው ፡ ኅብ ስተ ፡ ይላል ። ተብሎም ፡ ሲኾን ፥ ተሰቅለ ፡ ክርስቶስ ፡ ኃጥአ ። ብሎም ፡ ሲኾን ፥ ሰቀ ልዎ ፡ አይሁድ ፡ ለክርስቶስ ፡ ኃጥአ ። አሰኝቶም ፡ ሲኾን ፥ አስቀለሞሙ ፡ ሰይጣን ፡ ለአ ይሁድ ፡ ክርስቶስሀ ፡ ኃጥአ ። ተባብሎም ፡ ሲኾን ፥ ተቃጸበ ፡ ሄሮድስ ፡ ምስለ ፡ ወዐልቱ ፡ ላዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ ዐላዌ ። አባብሎም ፡ ሲኾን ፥ መስተዋድይ ፡ ያስተፃርፍ ፡ ጻድቃነ ፡ ሐሳዌ ፡ ያሰኛል ።

፪፻፱ ፤ ብትን ፡ ሰዋስው ፡ ለ ፡ ሲኾን ፥ ተቀባይነት ፡ በሚሰማማው ፡ ጥሬ ፡ ይገ ባል ። ይህም ፥ ዘይትቀነይ ፡ ወፍረ ፡ ተኀርየ ፡ ሣሚመተ ፡ ብሎ ፥ ለርሻ ፡ የሚገዛ ፡ ለሹ መት ፡ ተመረጠ ። ወይምህክ ፡ ነዳየ ፡ ወምስኪነ ፡ ብሎ ፥ ለድኻ ፡ ለጦም ፡ ዐዳሪ ፡ ይራ ራል ። ኢያንእስ ፡ እንዘ ፡ ይፌትት ፡ ርእሰ ፡ ብሎ ፥ ለራሱ ፡ ሲቈርስ ፡ አያሳንስ ፡ እያሰኘ ፡ ተቀባይነቱን ፡ ያሳያል ። በተቀብሪ ፡ ስም ፡ ሲገባ ፡ ፍችው ፡ ና ፡ ነት ፡ ይኾናል ። ተሰ ይመ ፡ ጳጳሰ ፥ አው ፡ ቀሲሰ ፡ ወዲያቆነ ፤ ጵጵስና ፡ ቅስና ፡ ዲቁና ፤ ወይም ፡ ጳጳስነት ፡ ቄስ ነት ፡ ዲያቆንነት ። በግእዝም ፡ ቋንቋ ፡ የጥሬው ፡ መድረሻ ፡ ና ፡ ሲኾን ፡ እንዲሁ ፡ ይፈ ታል ፤ ንጽሕና ፡ ቅድስና ፥ ንጹሕነት ፡ ቅዱስነት ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

፪፻፲ ፤ ብትን ፡ ሰዋስው ፡ በዝርዝርነት ፡ በነባርነት ፡ ግእዝ ፡ ራብዕ ፡ ኃምስ ፡ ሳ ብዕ ፡ ኹኖ ፡ በስመ ፡ ነገድ ፡ እየገባ ፡ ኛ ፡ ሲኾን ፡ ቋንቋ ፡ ያሰማል ። ተአምርኑ ፡ ዐረበ ፡ ወዐምሐራ ፥ ዐረብኛና ፡ ዐማርኛ ፤ አው ፡ ጋላ ፡ ወሱማሌ ፥ ጋልኛና ፡ ሱማልኛ ፤ ወዓዲ ፡ ወላሞ ፡ ወላምኛም ፡ ደግሞ ። ይነቁ ፡ እብድ ፡ ዝእበ ፥ አው ፡ አድገ ፤ ኸርብኛ ፡ አህይኛ ። ምስጢሩም ፡ እንጻርነት ፡ ኹኖ ፡ እንደ ፡ ከማለት ፡ ይገባል ። የብትን ፡ ሰዋስው ፡ ዐዋጅ ፡ በጫሩ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ፳፬ኛ ፡ ዕርከን ።

## ሙሻዘር ።

፪፻፲፩ ፡ ሙሻዘር ፡ ማለት ፡ ባማርኛ ፡ መጣብቅ ፡ ይኾናል ፤ በሰዋስው ፡ ግን ፡ ተናበ ፡ የሚስብና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ የሚያመጣ ፥ ተናባቢ ፡ ዘር ፡ ማለት ፡ ነው ። ሙሻዘሮችም ፡ የሚባሉ ፡ ፬ ፡ ናቸው ፤ ሳድስ ፡ ቅጽልና ፡ ሣልስ ፡ ቅጽል ፥ አርእስትና ፡ ሳቢ ፡ ዘር ። የሳ ድስና ፡ የሣልስ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ባዕድ ፡ ቅጽልነት ፥ ተናበውም ፡ ገቢር ፡ ተገብሮ ፡ መሳባ ቸው ፡ ከግልጠ ፡ ዘ ፡ ጋራ ፡ በቦታው ፡ ተነግሯል ፡ (ም፪ ፡ ቍ፺፫) ። አኹን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ካርእስትና ፡ ከሳቢ ፡ ዘር ፡ ጋራ ፡ ሙሻዘር ፡ ያልናቸው ፥ ከብትን ፡ ሰዋስው ፡ ተ ናበው ፡ በባዕድ ፡ ግልጠ ፡ ዘ ፡ የተነገሩትን ፡ ፲ ፡ አገባቦች ፡ የሚያመጡ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነው ፤ ሙሻዘርም ፡ ኹነው ፡ ሲነገሩ ፡ ቅጽልነታቸው ፡ አይቀርም ።

፪፻፲፪ ፤ ሳድስ ፡ ቅጽል ፡ ተናበ ፡ ፲ኙን ፡ አገባብ ፡ ሲያመጣ ። ክርስቶስ ፡ ምዉተ ፡ አዳም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፥ ለአዳም ፡ ስለ ፡ አዳም ፡ የሞተ ። ስቁለ ፡ ፈያት ፡ ሲል ፡ ከወንበዶች ፡ ጋራ ፥ እንደ ፡ ወንበዶች ፡ ማለት ፡ ነው ። ገብርኤል ፡ ፍንወ ፡ ማርያም ፡ ሲል ፥ እስከ ፡ ማ ርያም ፥ ወደ ፡ ማርያም ፡ የተላከ ። ሰሎሞን ፡ ንጉሠ ፡ ዳዊት ፡ ሲል ፥ የዳዊትን ፡ ያኽል ፡

የነገሡ ፡፡ አዳም ፡ ፍጡረ ፡ መሬት ፡ ሲል ፥ ከመሬት ፡ የተፈጠረ ፡፡ ኢየሱስ ፡ ስቁለ ፡ ዕፅ ፡
ወቅንወ ፡ ኀጺን ፤ በንሰት ፡ የተሰቀለ ፥ በብረት ፡ የተቸነከረ ፡፡ ፪ኛም ፡ ያሉታ ፡ አገባብ ፡
ኢ ፡ ወድቆበት ፡ የነዚህን ፡ አፍራሽ ፡ ሲያመጣ ፡ ፍችው ፡ አለ ፡ ያለ ፡ ይኸናል ፡፡ ክርስ
ቶስ ፡ ኢምዉት ፡ አዳም ፥ አላዳም ፡ ያላዳም ፡ ያልሞተ ፡፡ ኢስቁለ ፡ ፈያት ፥ ያለወንበ
ዶች ፡ ያልተሰቀለ ፡፡ ገብርኤል ፡ ኢፍንወ ፡ ማርያም ፥ ያለማርያም ፡ ያልተላከ ፡፡ ሰሎሞን ፡
ኢንጉሠ ፡ ዳዊት ፥ ያለዳዊት ፡ መጠን ፡ ያልነገሠ ፡፡ አዳም ፡ ኢፍጡረ ፡ መሬት ፥ ያለመ
ሬት ፡ ያልተፈጠረ ፡፡ ኢየሱስ ፡ ኢስቁለ ፡ ዕፅ ፡ ወኢቅንወ ፡ ኀጺን ፤ ያለንሰት ፡ ያልተ
ሰቀለ ፡ ያለብረት ፡ ያልተቸነከረ ፡፡ እንበለ ፡ ከኢ ፡ ተሰማምቶ ፡ የ፱ኙ ፡ ኹሉ ፡ አሉታና ፡
አፍራሽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ፡፡ ፱ ፡ ያልናቸውም ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፤ ለ ፡ በእንተ ፡
ከመ ፡ ምስለ ፡ ኀበ ፡ እስከ ፡ መጠነ ፡ እም ፡ በ ፡፡

፪፻፷፮ ፤ ዳግመኛም ፡ የ፮ቱ ፡ አዕማድ ፡ ሣልስ ፡ ቅጽል ፡ ከብትን ፡ ተናበ ፡ እሊህን ፡
፱ኙን ፡ ሲያመጣ ፡ አገባቡ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡፡ የገቢር ፡ ሣልስ ፡ ለንና ፡ በእንተን ፡ ሲያ
መጣ ፥ አብ ፡ መጣዌ ፡ ዓለም ፡ ወልዶ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ቤዛ ፡፡ ከመንና ፡ ምስለን ፡ ሲያ ፥
ጲላጦስ ፡ ቀሣፌ ፡ ሰረቅት ፡ ወሰቃሌ ፡ ፈያት ፡ ክርስቶስሀ ፡፡ ኀበንና ፡ እስከን ፡ ሲያ ፥
አብ ፡ ፈናዌ ፡ ማርያም ፡ ገብርኤልሀ ፡፡ መጠነን ፡ ሲያ ፥ ሳሙኤል ፡ ቀባዔ ፡ ሳኦል ፡ ዳዊ
ትሀ ፡ ወአንጋሢሁ ፤ ዳዊትን ፡ በሳኦል ፡ መጠን ፡ የቀበውና ፡ ያነገሡው ፡፡ እምንና ፡ በን ፡
ሲያ ፥ ወልድ ፡ ፈናዌ ፡ ሰማይ ፡ መንፈሰ ፡ ወከዓዌ ፡ አርድእት ፡ ሞገሰ ፤ ወይም ፡ ፈጣሬ ፡
መሬት ፡ አዳምሀ ፡ ወሠያሜ ፡ ገነት ፡ ኪያሁ ፡ ያሰኛል ፡፡

፪፻፷፯ ፤ የአግብሮ ፡ ሣልስ ፡ ለንና ፡ በእንተን ፡ ሲያመጣ ፥ መሐላ ፡ ውእቱ ፡ አቅ
ታሌ ፡ አዳም ፡ ወሔዋን ፡ ክርስቶስሀ ፡፡ ከመንና ፡ ምስለን ፡ ሲያ ፥ ሕገ ፡ ሮም ፡ አቅሣፌ ፡
ሰረቅት ፡ ወአስቃሌ ፡ ፈያት ፡ ክርስቶስሀ ፡፡ ኀበንና ፡ እስከን ፡ ሲያ ፥ ምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፡
አፈናዌ ፡ ድንግል ፡ መልአኪ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡፡ መጠነን ፡ ሲያ ፥ መዓልት ፡ አምጻኤ ፡
ጽልመት ፡ ብርሃነ ፤ ወሌሊት ፡ አምጻኤ ፡ ብርሃን ፡ ጽልመተ ፡፡ እምንና ፡ በን ፡ ሲያ ፥ ር
ቱዕ ፡ ጥቀ ፡ ፍትሐ ፡ ፈጣሪ ፡ አጺዋዔ ፡ ቤቱ ፡ ለሳኦል ፡ አጋግሀ ፡ ኀበ ፡ ሳሙኤል ፡ ወአቅ
ታሌ ፡ ኵናት ፡ ኪያሁ ፡ በእደ ፡ ነቢይ ፡፡ ለና ፡ በእንተ ፥ ከመና ፡ መጠነ ፡ ምስለ ፡ በምስ
ጢር ፡ አንዳንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡፡

፪፻፷፰ ፤ ያደራራጊ ፡ ሣልስ ፡ ለንና ፡ በእንተን ፡ ሲያመጣ ፥ አብ ፡ አስተጻባኤ ፡ አ
ዳም ፡ ወልዶ ፡ መድኅነ ፡ ምስለ ፡ መልአከ ፡ ሞት ፥ ኄር ፡ ውእቱ ፡፡ ከመንና ፡ መጠነን ፡
ሲያ ፥ በቀለ ፡ ዳዊት ፡ አስተቃታሌ ፡ ኢዮአብ ፡ ሰሎሞንሀ ፡ ምስለ ፡ ሳሚ ፡፡ ምስለንና ፡
በን ፡ ሲያ ፥ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ይእቲ ፡ አስተዋሣኢተ ፡ ንስጥሮስ ፡ ቄርሎስሀ ፡ ወአስ
ተጋባኢተ ፡ ኤፌሶን ፡ ከዕበተ ፡ ምእት ፡ ሊቃውንተ ፡፡ እምንና ፡ ኀበን ፡ እስከን ፡ ሲያ
መጣ ፥ ትንሣኤ ፡ እግዚእነ ፡ አስተራዋጺተ ፡ መቃብር ፡ አንስተ ፡ ኀበ ፡ ሐዋርያት ፤
ወዜና ፡ አንስት ፡ አስተራዋጺተ ፡ መቃብር ፡ ጴጥሮስሀ ፡ ወዮሐንስሀ ፡ ኅቡረ ፡፡ ፊተኛ
ውን ፡ ከ ፥ ኋለኛውን ፡ ወደ ፡ እስከ ፡ ብለኽ ፡ ፍታ ፡፡

፪፻፷፱ ፤ ያጕል ፡ አንቀጽና ፡ የተገብሮ ፡ ያስተጋብሮም ፡ ሣልስ ፡ አገባብ ፡ ሲያመጣ ፡
እንዲሁ ፡ ነው ፡፡ ያጕል ፡ አንቀጽና ፡ የተገብሮ ፡ ሣልስ ፡ ለንና ፡ በእንተን ፡ ምስለንና ፡

ከመን ፡ በን ፡ ሲያ ፥ ክርስቶስ ፡ ተሳታፌ ፡ አዳም ፡ ወሔዋን ፡ ጽዋዐ ፡ ሞት ፡ ምስለ ፡ ውሉዶሙ ፡ ውእቱኬ ፡ ተኰላፊ ፡ ፈያት ፡ ወተከፋሌ ፡ ሐብል ፡ ነዊኅ ፡ ተአስሮተ ፡ ድኅረት ፡ ርስቶሙ ። ነበንና ፡ እስከን ፡ ሲያመጣ ፥ ገብርኤል ፡ ተፈናዊ ፡ ድንግል ። እምን ፡ ሲያ ፥ ዮሴፍ ፡ ገዖያዬ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ግብጸ ፥ ወተመያጤ ፡ ግብጽ ፡ ናዝሬተ ፡ ነሢአ ፡ ሕፃን ፡ ወእሞ ። የተጋብሮ ፡ ሣልስ ፡ ለንና ፡ በእንተን ፡ በን ፡ ሲያመጣ ፥ ዐማኑኤል ፡ ተጻባኤ ፡ አዳም ፡ ወሔዋን ፡ ምስለ ፡ መልአከ ፡ ሞት ፡ በሞቱ ፡ ወተቃሬኔ ፡ ትንሣኤሁ ፡ ምስለ ፡ ስፉሐ ፡ ከርሥ ፡ መቃብር ። ምስለንና ፡ ከመን ፡ መጠነን ፡ ሲያ ፥ ቄርሎስ ፡ ተዋሣኤ ፡ ንስጥሮስ ፡ ወታዖድሪጣ ፥ ወተማላኒ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሰይፈ ፡ ምስሌሆሙ ። እምንና ፡ ነበን ፡ እስከን ፡ ሲያ ፥ ማርያም ፡ መግደላዊት ፡ ተራዋጺተ ፡ መቃብር ፡ ምስለ ፡ አብያጺሃ ፡ ነበ ፡ ሐዋርያት ። ጴጥሮስ ፡ ወዮሐንስ ፡ ተባዳርያነ ፡ መቃብር ፡ ሩጸተ ፡ በጽሑ ፡ በተቃልዎ ።

፻፵ ፡ መስም ፡ ቅጽልም ፡ መድረሻው ፡ ሣልስና ፡ ሳድስ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ቊጥሩ ፡ ከውስጠ ፡ ዘ ፡ ነውና ፥ እንዲሁ ፡ ተናቦ ፡ ፱ኙን ፡ አገባብ ፡ ያመጣል ። ኦ ፡ ዘረሰየከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዶናይ ፡ አምላከ ፡ ለፈርዖን ፡ ሙሴ ፡ ዐጓለ ፡ ማይ ፥ መቅተሌ ፡ ዕብራዊ ፡ ግብጻዊ ፡ ወመድፈኔ ፡ ኆጻ ፡ ከያሁ ፡ ጽሚተ ፡ ክቡደ ፡ መዝራዕት ፡ አንተ ፡ (ለ ፡ በእንተ ፡ በ) ። በትርከሂ ፡ በትረ ፡ ጽድቅ ፡ መገሥጽተ ፡ ውሉድ ፡ ቀላየ ፥ ወመንቅዒተ ፡ ኰኵሕ ፡ ማየ ፡ (ከመ ፡ መጠነ ፡ እም) ። መርሐ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ እምግብጽ ፡ ስሳ ፡ እልፈ ፡ ይቡሳነ ፡ ልብ ፡ ወገጽ ፡ ወመዝለፊተ ፡ አሮን ፡ ሕዝበ ፡ ቅቡጻነ ፡ ተስፋ ፡ በዘዘ ፡ ዚአሁ ፡ ተግሣጽ ፡ ወዘዘ ፡ ዚአሁ ፡ ዘለፋ ፡ (ኀበ ፡ እስከ ፡ ምስለ) ።

፻፵፩ ፡ አርእስትና ፡ ሳቢ ፡ ዘር ። የገቢር ፡ አርእስት ፡ ፱ ፡ አገባብ ፡ ሲያመጣ ፥ ደለዎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ለባሴ ፡ ክህነት ፥ ጸውዖተ ፡ ሐመር ፡ አርድእተ ፡ ወአንኖተ ፡ ዱብር ፡ ስብከተ ፡ መጥዎተ ፡ አዳም ፡ ነፍሶ ፡ ወአኅስሮተ ፡ ገብር ፡ ርእሶ ፡ (እም ፡ በ ፡ ለ ፡ በእንተ ፡ ከመ ፡ መጠነ) ። መዊተ ፡ ፈያት ፡ ስቁለ ፡ ወፈንዎ ፡ ቤቱ ፡ ገነት ፡ የማናየ ፡ ርግበ ፡ በእንተ ፡ መሐላሁ ፡ (ምስለ ፡ ኀበ ፡ እስከ) ። የቀሩትም ፡ ሳቢ ፡ ዘሮችና ፡ አርእስቶች ፡ እንዲህ ፡ ይገባሉ ። ስቅለት ፡ አዳም ፡ ተሰቅሎተ ፡ አዳም ፡ ፈቀደ ፡ እግዚእ ፥ (ለ ፡ በእንተ) ። ልብሰተ ፡ ወይም ፡ ለቢሶተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሥጋ ፡ ማርያም ፡ ለአከለ ፡ ቃል ፡ ባሕቲቱ ፡ (በ) ። ኢዮአብ ፡ ገብረ ፡ ተቃትሎተ ፡ አቤሴሎም ፡ በትእዛዘ ፡ ዳዊት ፡ (ምስለ) ። አፍቀረ ፡ ወልድ ፡ ልደተ ፡ ማርያም ፡ ወይም ፡ ተወልዶተ ፡ ማርያም ፡ (እም) ። ተክህሉ ፡ ለንስር ፡ አብጽሖተ ፡ ኤርምያስ ፡ ጦማረ ፡ (ኀበ ፡ እስከ) ። ተውህበ ፡ ለሰሎሞን ፡ ንብረተ ፡ ዳዊት ፡ ነቢረ ፡ ዳዊት ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ መንግሥት ፡ (መጠነ ፡ ከመ) ። ከንእሱ ፡ ቅጽልም ፡ ተናበው ፡ አገባብ ፡ ሲያመጡ ፥ ስቅለተ ፡ ምንት ፡ ተሰቅሎተ ፡ አይ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚእ ፡ ስቅለተ ፡ ሐብልኑ ፡ ወሚመ ፡ ተሰቅሎተ ፡ ኀጺን ፥ ዳእሙ ፡ ስቅለተ ፡ ዕፅ ። ተሰቃሌ ፡ ምንት ፡ ስቁለ ፡ ምንት ፡ አድኅነ ፡ ዓለመ ። ስቅለተ ፡ አይቴ ፡ ተሰቅሎተ ፡ ማእዜ ፡ ፈቀደ ። ተሰቃሌ ፡ አይ ፡ ሰዓት ፡ ወስቁለ ፡ ምንት ፡ ዕለት ፡ ቤዘወነ ፡ እያሰኙ ፡ በን ፡ ያመጣሉ ። ከደቂቅም ፡ ጥሬ ፡ ተናበው ፡ ነቢረ ፡ ላዕሉ ፥ ነጽሮተ ፡ ላዕሉ ፡ ርደተ ፡ መትሕት ፡ ነጻሬ ፡ ላዕል ፡ ንቡረ ፡ ታሕት ፡ እያሰኙ ፡ በንና ፡ ኀበን ፡ ያመጣሉ ። የቀሩትንም ፡ እንደዚሁ ፡ እያናበብኽ ፡ አግባ ።

፻፵፱ ፡ እንበለ ፡ ለዘጠኙ ፡ አገባብ ፡ አፍራሽና ፡ አሉታ ፡ ሲኾን ፡ በሙሻዘር ፡ ይወጣል ፡ አወጣጡንም ፡ ለማየት ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ኢን ፡ መፈልመር ፡ ነው ። ብቻውንም ፡ ባርእስት ፡ ገብቶ ፡ አሉታ ፡ እየኾነ ፡ ለንና ፡ በአንቀጹን ፡ ሲያፈርስ ፥ ጥቀ ፡ ፍቁር ፡ በኀበ ፡ ወልድ ፡ ተሰቅሎተ ፡ አዳም ፡ ይላል ፡ ስትፈታም ፡ ስላዳም ፡ መሰቀል ፡ ያላዳም ፡ መሰቀል ፡ ብለኽ ፡ በጽድቅ ፡ ባሉታ ፡ በኹለቱም ፡ ፍታ ። ከኢ ፡ ተስማምቶ ፡ የበ ፡ አፍራሽና ፡ አሉታ ፡ ሲኾን ፥ ጻድቃን ፡ ወሰማዕት ፡ ያፈቅሩ ፡ ጥቀ ፡ ኢነሚአ ፡ ሥጋሆሙ ፡ መከራ ። በቅጽልም ፡ የከመ ፡ የምስለ ፡ አፍራሽና ፡ አሉታ ፡ ሲኾን ፥ ክርስቶስ ፡ ኢስቁለ ፡ ፈያት ። ለኀበ ፡ ለእስከ ፡ አሉታ ፡ ሲኾን ፥ ገብርኤል ፡ ኢተፈናዌ ፡ ማርያም ፡ ይላል ። ለእም ፡ አፍራሽ ፡ ሲኾን ፥ ወልድ ፡ ኢተፈናዌ ፡ አብ ፥ ኢፍንወ ፡ አብ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ። ለመጠነም ፡ አፍራሽና ፡ አሉታ ፡ ሲኾን ፥ ጻድቅ ፡ ብእሲ ፡ ይፈቅድ ፡ ኢገቢረ ፡ ዐቅሙ ፡ ኢግብረተ ፡ ዐቅሙ ፡ ትሩፋተ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ ይላል ።

፻፶ ፡ ዳግመኛም ፡ በሙሻዘር ፡ እስከ ኹን ፡ የተነገሩቱ ፡ ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ ፱ኙ ፡ ኹሉ ፡ ባንቀጽ ፡ ዝርዝር ፡ ይዘምታሉ ፡ ዘመቻውና ፡ ዝርዝሩም ፡ ይህ ፡ ነው ። ለና ፡ በእንተ ፡ ባንቀጽ ፡ ሲዘምቱ ፥ አምላክ ፡ ሞታ ፡ ለሔዋን ፡ ይላል ፡ ይህም ፡ ሞተ ፡ ላቲ ፡ ለሔዋን ፥ ወይም ፡ በእንቲአሃ ፡ ለሔዋን ፡ ማለት ፡ ነው ። አምላክ ፡ ተሰቅሎ ፡ ለመስቀል ፡ ሲል ፥ ቦቱ ፡ ለመስቀል ፡ በል ። ተሰቅሎሙ ፡ ለፈያት ፡ ሲል ፡ ምስሌሆሙ ፡ ከማሆሙ ፡ በል ። አብ ፡ ፈነዋ ፡ ለድንግል ፡ ገብርኤልሀ ፡ ሲል ፥ ኀቤሃ ፡ እስከኔሃ ፡ በል ። ሐዋርያት ፡ ተፈነውዋ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ብሔረ ፡ አሕዛብ ፡ ሲል ፥ ተፈነዉ ፡ እምኔሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ በል ። እግዚአብሔር ፡ አንገሦ ፡ ለዳዊት ፡ ሰሎሞንሀ ፡ ሲል ፥ መጠኖ ፡ ለዳዊት ፡ ማለት ፡ ነው ። እንበለን ፡ ለኒህ ፡ ለ፱ኙ ፡ አፍራሽ ፡ ስታደርግ ፡ እኹን ፡ በተናገርናቸው ፡ አናቅጽ ፡ በያንዳንዱ ፡ ኹሉ ፡ ኢን ፡ ፈልምር ። ይህም ፡ ኢሞታ ፡ ለሔዋን ፡ ኢተሰቅሎሙ ፡ ለፈያት ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። የሙሻዘር ፡ መንገድና ፡ አካኼድ ፡ ባጭሩ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ፳፫ኛ ፡ ዕርከን ።

## ሥረዝ ።

፻፶፩ ፡ ሥረዝ ፡ ማለት ፡ ፍጹም ፡ ቃልን ፡ ከቃል ፡ የሚለይ ፡ ማእከላዊ ፡ ነቍጥ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ፬ቱ ፡ ነቍጥ ፡ እንዳንገዘ ፡ ኹኖ ፡ በላይና ፡ በታች ፡ ፪ ፡ መሥመሮች ፡ ሲፈልመሩ ፥ ስሙ ፡ ሥረዝ ፡ ይባላል ። አኹን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ሥረዝ ፡ የምንለው ፡ በሥረዝ ፡ ተከፍሎ ፡ የሚነገር ፡ ፺ ፡ መንታ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ኀዳሪና ፡ ማኅደር ፥ ወላጅና ፡ ተወላጅ ፥ ገንዘብና ፡ ባለገንዘብ ፥ ልዑልና ፡ ትሑት ፥ ሩቅና ፡ ቅርብ ፥ ለሚና ፡ አልሚ ፥ አጥፊና ፡ ጠፊ ። ፪ኛም ፡ ቃጥሮ ፡ ተመላልሶ ፡ እየተዛወረ ፡ የሚነገር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ተዛዋሪ ፡ ይባላል ። ዐበይ ፡ አገባብ ፡ የሌላቸው ፡ የፍጹማን ፡ ቃላት ፡ አነጋገር ፡ በያገባቡ ፡ ሲጠቀለል ፡ ስልቱና ፡ ዐይነቱ ፡ እንደ ፡ ሕዋሳት ፡ ፫ ፡ ነው ። ፩ኛው ፥ በአው ፡ በሚመ ፡ ማሻሻል ፡ ማማረጥ ። ፪ኛው ፥ በዋዌ ፡ መደርደር ፡ ተሠይጠ ፡ ዮሴፍ ፡ ወኮነ ፡ ገብረ ፡ ወሐማ ፡ እንገሪሁ ፡ በመዋቅሕት ፡ እንደ ፡ ማለት ። ፫ኛው ፥ በወሂኒና ፡ በሰ ፡ በባሕቱ ፡ መከፈል ፡ ነው ። ፬ኛው ፥ ነጥሎ ፡ ደርቦ ፡ መሠረዝ ። ፭ኛው ፥ ማነጻጸር ፡ ነው ።

፻፵፫፤ እነዚህም፡የቈጠርናቸው፡ጓቱ፡ጥንድ፡ቃላት፥ነጠላ፡ወይም፡ሠምና፡ወርቅ፡ኹነው፡በክፍል፡በሠረዝ፥በድርድር፡በጥቅል፡እየገቡ፡ይነገራሉ። ኀዳሪ፡ከማኀደር፥ማኀደር፡ከኀዳሪ፡አይዘመዱም። ግብር፡ነገር፡ኀዳሪ፥በታ፡ጊዜ፡ማኀደር፡ይኾናሉ፤ አካል፡ግን፡ገንዘብም፡ባለገንዘብም፡ይኾናል። በክፍልም፡ኹኖ፡በሠረዝም፡ኹኖ፡ሲነገሩ፡ለኹሉም፡የተለየ፡አገባብ፡አላቸው። የኀዳሪ፡ለ፡ነው፤ የማኀደር፡ኀበ፡ዲበ፡ላዕለ፡መልዕልተ፡ታሕተ፡ቅድመ፡ድኅረ፡ውስተ፡ውስጠ፡ማእከለ፤ በ፡እየተስማማቸው፡ኹሉም፡በ፡ናቸው። የወላጅ፡እም፥የተወላጅ፡ለ፡ናቸው። የገንዘብና፡የባለገንዘብ፡ለ፡በ፡ኀበ፡ናቸው። የልዑልና፡የትሑት፡በ፡ኀበ፡ታሕተ፡ቅድም፡እም፡ናቸው። የለሚ፡ለ፡ኀበ፡ቅድመ፥ያልሚ፡በ፡ናቸው። የጠፊና፡ያጥፊ፡በ፡ኀበ፡ቅድመ፡ናቸው። የሩቅ፡እም፥የቅርብ፡ኀበ፡መንገለ፡ለ፡ናቸው። በተገናኝ፡የኹሉም፡ማሰሪያ፡ውእቱ፡ነው።

፻፵፬፤ ኀዳሪና፡ማኀደር፡በነጠላ፡ገብተው፡በክፍል፡ሲነገሩ፥ማርያም፡ለዐማኑኤል፡መዝገብ፡ይእቲ፤ ወዐማኑኤል፡በማርያም፡ወርቅ፡ውእቱ፡ይላል። ስትፈታም፡ማርያም፡ለዐማኑኤል፡ሣጥን፡ናት፤ ዐማኑኤልም፡በማርያም፡ዘንድ፡ወርቅ፡ነው፡በል። በነጠላ፡ገብተው፡በሠረዝ፡ሲነገሩ፥መቃብር፡ወመዋቲ፡ለመዋቲ፥ውታሕተ፡መቃብር፡ገራህተ፡ዘርዕ፡ወዘርዐ፡ገራህት፡ይላል። ስትፈታም፡መቃብር፡ለሟች፡የዘር፡ዕርሻ፡ናት፤ ሟችም፡በመቃብር፡ታች፡የርሻ፡ዘር፡ነው፡በል። ፪ኛም፥በሠምና፡በወርቅ፡ገብተው፡በክፍል፡ሲነገሩ፥ማርያም፡መዝገብ፡ለዐማኑኤል፡ወርቅ፡ሰማይ፡ሙዳይ፡ይእቲ፤ ወዐማኑኤል፡ወርቅ፡በማርያም፡መዝገብ፥ወይም፡በውስተ፡በማእከለ፡በኀበ፡በዲበ፡በታሕተ፡በቅድመ፡ማርያም፡መዝገብ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ብሩር፡ውእቱ፡ይላል። ስትፈታም፥ማርያም፡ሣጥን፡ለዐማኑኤል፡ወርቅ፡ሰማይ፡ሙዳይ፡ናት፤ ዐማኑኤል፡ወርቅም፡በማርያም፡ሣጥን፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ብር፡ነው፡በል። በሠረዝም፡ሲነገሩ፥ማርያም፡መዝገብ፡ወዐማኑኤል፡ወርቅ፥ለዐማኑኤል፡ወርቅ፤ ወበማርያም፡መዝገብ፡ሰማይ፡ሙዳይ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ብሩር፡ይላል፤ እንደ፡ላይኛው፡ፍታ።

፻፵፭፤ ወላጅና፡ተወላጅ፡በነጠላ፡ገብተው፡በሠረዝ፡ሲነገሩ፥ራሔል፡ወዮሴፍ፡ለዮሴፍ፥ወእምራሔል፡ያዕቆብ፡ወብንያም፡ይላል። በሠምና፡በወርቅ፡ገብተው፡በክፍል፡ሲነገሩ፥ገበ፡ኢየሱስ፡ከርሠ፡ዐንበሪ፡ለዮናስ፡ደም፥ክሣደ፡ጊዮርጊስ፡እም፤ ወዮናስ፡ደም፡እምከርሠ፡ዐንበሪ፡ገበ፡ኢየሱስ፡ማየ፡ሕይወት፡ዓሣ፡ውእቱ፡ይላል።

፻፵፮፤ ገንዘብና፡ባለገንዘብም፡በነጠላ፡ገብተው፡በክፍል፡ሲነገሩ፥ዘመነ፡ሊቃውንት፡ለትምህርተ፡ሃይማኖት፡ዘመነ፡ሐዋርያት፡ውእቱ፥ወትምህርተ፡ሃይማኖት፡ለዘመነ፡ሊቃውንት፡መሢዕተ፡ወንጌል፡ውእቱ፡ይላል፤ ይህ፡በታና፡ጊዜ፡ሲገቡ፡ነው። በነጠላ፡ገብተው፡በሠረዝ፡ሲነገሩም፥ተክለ፡በለስ፡ወገነት፡በገነት፡ወለተክለ፡በለስ፡ተክለ፡ወይን፡ወደብር፡ውእቱ፡ይላል፤ ይህም፡በታና፡ግብር፡ሲገቡ፡ነው። በሠምና፡በወርቅ፡ገብተው፡በክፍል፡ሲነገሩ፥አካልም፡ገንዘብና፡

ባለገንዘብ ፡ ሲኾን ፡ ዳዊት ፡ ወልድ ፡ ለሚካኤል ፡ ኢዮአብ ፡ ሰሎሞን ፡ አብ ፡ ውእቱ ፡ ወሚካኤል ፡ ኢዮአብ ፡ ለዳዊት ፡ ወልድ ፡ ገብርኤል ፡ አቢሳ ፡ ውእቱ ፡ ይላል ፡ የኹሉም ፡ አገባብ ፡ ለ ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ አካልና ፡ ነገር ፡ በሠምና ፡ በወርቅ ፡ ሲገቡ ÷ ንስሓ ፡ ወርቅ ፡ ለአዳም ፡ ኪራም ፡ ብሩር ፡ ጌጋይ ፡ ውእቱ ፡ ወአዳም ፡ ኪራም ፡ ለንስሓ ፡ ወርቅ ፡ ዳዊት ፡ ነዌ ፡ ውእቱ ፡ ይላል ። የቀረውም ፡ በኀዳሪና ፡ በማኅደር ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ነው ። ልዑልና ፡ ትሑት ፡ በነጠላ ፡ ገብተው ፡ በክፍል ፡ ሲነገሩ ÷ ወርቅ ፡ እምብሩር ፡ ዕንቊ ፡ ባሕርይ ፡ ውእቱ ፡ ወብሩር ፡ እምወርቅ ፡ ኀጺን ፡ ውእቱ ፡ ይላል ። በሠምና ፡ በወርቅ ፡ ገብተው ፡ በሠረዝ ፡ ሲነገሩ ÷ ጴጥሮስ ፡ ወርቅ ፡ ወይሁዳ ፡ ብሩር ÷ እምይሁዳ ፡ ብሩር ፡ ወእምጴጥሮስ ፡ ወርቅ ፡ ክርስቶስ ፡ ዕንቊ ፡ ባሕርይ ፡ ወመልአከ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኀጺን ፡ ውእቱ ፡ ይላል ።

፻፵፱ ፡ ለሚና ፡ አልሚ ፡ በነጠላ ፡ ገብተው ፡ በሠረዝ ፡ ሲነገሩ ÷ ነፋስ ፡ ወእሳት ፡ ለእሳት ፡ ወበነፋስ ፡ ሕይወት ፡ አርዝ ፡ ውእቱ ፡ ይላል ። በሠምና ፡ በወርቅ ፡ ገብተው ፡ በክፍል ፡ ሲነገሩ ÷ ንጽሕና ፡ ነፋስ ፡ ለሥጋ ፡ ማርያም ፡ እሳት ፡ ክብረ ፡ መላእክት ፡ ሕይወት ፡ ወሥጋ ፡ ማርያም ፡ እሳት ፡ በንጽሕና ፡ ነፋስ ፡ አካለ ፡ ኪሩብ ፡ አርዝ ፡ ውእቱ ፡ ይላል ።   ጠፊና ፡ አጥፊ ፡ ደግሞ ፡ በነጠላ ፡ ገብተው ፡ በሠረዝ ፡ ሲነገሩ ÷ ቤት ፡ ወነፋስ ፡ በነበ ፡ ነፋስ ፡ ወቤት ፡ ደመና ፡ ንስር ፡ ውእቱ ፡ ይላል ። በሠምና ፡ በወርቅ ፡ ገብተው ፡ በክፍል ፡ ሲነገሩ ÷ አበሳ ፡ አዳም ፡ ቤት ፡ በነበ ፡ ደመ ፡ ኢየሱስ ፡ ነፋስ ፡ አበሳ ሔዋን ፡ ደመና ፡ ውእቱ ። ወደመ ፡ ኢየሱስ ፡ ነፋስ ፡ በነበ ፡ አበሳ ፡ አዳም ፡ ቤት ፡ መስቀል ፡ ንስር ፡ ውእቱ ፡ ይላል ። የቀረው ፡ እንደ ፡ ኀዳሪና ፡ እንደ ፡ ማኅደር ፡ ነው ። ሩቅና ፡ ቅርብ ፡ በነጠላ ፡ ሲገቡ ፡ ሩቁ ÷ ፀሓይ ፡ እምነ ፡ ምድር ፡ ሰማይ ። ቅርቡም ÷ ከከብ ፡ ለወርኅ ፡ ፀሓይ ፡ ይላል ። በሠምና ፡ በወርቅ ፡ ሲገቡም ፡ ሩቁ ÷ ሥጋ ፡ ማርያም ፡ ፀሓይ ፡ እምነ ፡ ምድር ፡ አበሳ ፡ አካለ ፡ ሱራፊ ፡ ሰማይ ። ቅርቡም ÷ ሥጋ ፡ ማርያም ፡ ከከብ ፡ ለወርኅ ፡ ንጽሕና ፡ አካለ ፡ ኪሩብ ፡ ፀሓይ ፡ ይላል ። የሠረዝ ፡ አፈታት ፡ ሲገለጥ ፡ ማርያም ፡ ለዐማኑኤል ፡ ከመ ፡ መዝገብ ፡ ይእቲ ፡ ወዐማኑኤል ፡ በማርያም ፡ ከመ ፡ ወርቅ ፡ ውእቱ ፡ ማለት ፡ ነው ። ብ፲፱ኛው ፡ ዕርከን ፡ ቍ፫፫ ፡ ከመ ÷ ሠረዝ ፡ ይኾናል ፡ ያልነው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

፻፶ ፡ በድርድር ፡ በጥቅል ፡ ሲነገሩም ፡ አገባባቸው ፡ እስመ ፡ ነው ፡ ባንድ ፡ አንቀጽ ፡ ታስረው ፡ ባንድ ፡ አገባብ ፡ ይጠቀለላሉ ። ሦስቱም ፡ ድርድር ÷ ወይም ፡ ጕንጕን ፡ ሠረዝ ፡  ሦስተኛ ፡ ደግሞ ፡ በቅኔነቱ ፡ ሥላሴ ፡ የሚባል ።

አስተብዕዑ ፡ ነፍስተ ፡ ዓሣ ፡
ኢየሱስ ፡ ወጴጥሮስ ፡ ወሩፋኤል ፡
በሕረ ፡ ጥብርያዶስ ፡ አኮኑ ፡ እመ ፡ ኢየሱስ ፡ ወፈረ ፡
በኅዳጥ ፡ ዓሣ ፡ አጽገበ ፡ ማኅበረ ።
ወእምከርሠ ፡ ዓሣ ፡ አውፅአ ፡ ጸባሕተ ፡ ቄሳር ፡ ዲናረ ፡
መሠግር ፡ ጴጥሮስ ፡ እመ ፡ አሥገረ ።

ሩፋኤልኒ ፡ ሥራዩ ፡ በዘእአመረ ፡
በዓማሁ ፡ እሕየወ ፡ ዕውረ ።

ይህም ፡ አክኼድ ፡ የተገኘ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ ወመጺአ ፡ ውእቱ ፡ ያዘ ለፎ ፡ ለዓለም ፡ በእንተ ፡ ኀጢአት ፡ ወበእንተ ፡ ጽድቅ ፡ ወበእንተ ፡ ኵነኔ ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ። ነጠላውንም ፡ ቃል ፡ በዘ ፡ ተርጕሞ ፡ ሲሠርዝ፥ዐማኑኤል ፡ ዘበትርጓሚሁ ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ፥እስመ ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፡ በመለኮቱ ፡ ወሰብእ ፡ በትስብእቱ ፡ ይላል ። ዳግመኛም ፡ ፪ ፡ ፍጹማን ፡ ቃላት ፡ እየብቻቸው ፡ እንደ ፡ ነዶ ፡ ታስረው ፡ በወ ፡ ሲደረደሩ ፡ በእስመ ፡ ይጠቀለላሉ ።

እምከዊነ ፡ ካህን ፡ ይኄይስ ፡ ከዊነ ፡ ኖላዊ ፡
ወኀለ ፡ እንስሳ ፡ ትትበደር ፡ እምቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዐባይ ፡
እስመ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ከንቶ ፡ ቤተ ፡ ፈያታይ ፡
ወበላዕለ ፡ ኖሎት ፡ ኢሀለወ ፡
ላዕለ ፡ ካህናት ፡ ዘሀሎ ፡ እከይ ።
ትእምርተ ፡ ዝኒ ፡ ከመ ፡ ንርዩ ፡
በኀለ ፡ እንስሳ ፡ ሠረቀ ፡ ዘኢየዐርብ ፡ ፀሓይ ፡
ወኖሎት ፡ ተዛውዑ ፡ ምስለ ፡ ሐራ ፡ ልዑል ፡ ሰማይ ።
ዓዲ ፡ እምቅድመ ፡ ዝኒ ፡ ብመከነ ፡ ኖሎት ፡ ወመራዕይ ፡
ከመ ፡ ተጸውዑ ፡ ደምፀ ፡ እግረ ፡ ቃለ ፡ ዜና ፡ ሠናይ ፡
ወልደ ፡ እንበረም ፡ ለምስፍና ፡ ወለቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ወልደ ፡ እሴይ ፡ ብሎ ፡ በኀሠመረበት ፡ ይፈጽርሳል ። የሠረዝ ፡ ዐዋጅና ፡ አክኼድ ፡ ባጭሩ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ፳፪ኛ ፡ ዕርከን ።

## አንጻር ።

፻፶፩ ፡ አንጻር ፡ ማለት ፡ ትይዩ ፡ አፋዛኝ ፡ አኳያ ፡ ማለት ፡ ነው ። አኹን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ አንጻር ፡ የምንለው ፥ ፊት ፡ የተነገረው ፡ ፍጹም ፡ ቃል ፡ በደቂቅ ፡ ቅጽል ፡ ሲታጠፍ ፡ ፊተኛውን ፡ ለመግለጥና ፡ ለማስረዳት ፡ ከጸፉ ፡ በኋላ ፡ የሚፈጸመር ፡ ቃል ፡ ነው ። አስተማጠፉም፥ትእምርተ ፡ ዝኒ ፡ ከመ ፡ ንርእዩ ፡ እንዳለው ፡ ነው ።

፻፶፪ ፡ የአንጻር ፡ ጥሬዎች ። ንበብ ፡ ዜና፥ነገር ፡ ጽድቅ ፡ አማን፥እውነት ፡ አምሳል ፡ ምሳሌ ፡ ጽላሎት፥አምሳያ ፡ አርአያ፥አብነት ፡ ተአምር ፡ ትእምርት፥ምልክት ፡ ሲኾኑ ፡ እነዚህንም ፡ የመሰሉ ፡ ተውላጥና ፡ ፍዳ ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ ፍጻሜ ፡ ተፍጻሜት ፡ ተፈጸምረው ፡ ከደቂቅ ፡ ቅጽል ፡ እየተናበቡ ፡ በጥሬንታቸው ፡ ያጸፉ ፡ ባለቤት ፡ ሲኾኑ ፡ ወይም ፡ ከመ ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ በነገር ፡ ገብቶ ፡ ሲገጥሙ ፡ ኋለኛውን ፡ ቃል ፡ ከፊተኛው ፡ ያንጻጽራሉ ። ማሰሪያቸውም ፡ ኮነ ፡ ረሰየ ፡ ጸድቀ ፡ ተሐሰወ ፡ ተከሥተ ፡ ነጸረ ፡ ሰአለ ፡ ለበወ ፡ ዖቀ ፡ ጠየቀ ፡ ጽሕቀ ፡ ተዘከረ ፡ ሐተተ ፡ ተርፈ፥እነዚህን ፡ የመሰለ ፡ ነው ።

፫፻፫ ፡ ሲገቡም ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ከነ ፡ ጻድቃ ፡ ወረሰየ ፡ ርእሶ ፡ ጻድቀ ፡ ወይም ፡ ኵሉ ፡ ሰአለ ፡ ወለበወ ፡ ዖቀ ፡ ወሐተተ ፡ ሃይማኖተ ፥ ወጽሕቀ ፡ ወተዘከረ ፡ ይኩን ፡ ፍጹመ ፡ በዘመነ ፡ ስብከቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወዜና ፡ ዝንቱ ፡ ወጽድቀ ፡ ዝንቱ ፡ ወከመ ፡ አማን ፡ ዝንቱ ፡ ይትዐወቅ ፡ በፍድፋዴ ፡ ምእመናን ። ወምሳሌ ፡ ዝንቱ ፡ ወጽላሎተ ፡ ዝንቱ ፡ ወአርአያ ፡ ዝንቱ ፡ ተከሥተ ፡ በስብከተ ፡ ሐዋርያት ። እስፍንተ ፡ ጥበበ ፡ ዖቀ ፡ ሰሎሞን ፡ ባሕቱ ፡ ተውላጠ ፡ ዝንቱ ፡ ፍዳ ፡ ዝንቱ ፡ ምስብዒተ ፡ አብደ ። ባሕቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ዝንቱ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ዝንቱ ፡ ረሰየ ፡ እበደ ። ጽሕቀ ፡ ኢዮስያስ ፡ ለዐቂበ ፡ ሥርዐት ፡ ወጥንተ ፡ ዝንቱ ፥ ወመሠረተ ፡ ዝንቱ ፡ ይትዐወቅ ፡ በተስእሎቱ ፡ ክህናት ። ኵሉን ፡ ወ ፡ ሂ ፡ ኒ ፡ ጥቀ ፡ ሲከተሉት ፥ እከ ፡ አልቦ ፡ ኢ ፡ የነዚህ ፡ መነሻ ፡ ይኾኑለታል ፡ ሲገቡም ፡ ኵሉ ፡ ዐለወ ፥ አልቦ ፡ ዘይገብራ ፡ ለሠናይት ፡ ወኢአሐዱ ፡ ይትርፍሰ ፡ ንቢሮታ ፡ ኀልዮታሂ ፡ ኀልዮታኒ ፡ ኀልዮታ ፡ ጥቀ ፡ ወኀልዮታ ፡ አልቦ ፡ ኀቤሁ ፡ ይላል ። ዳግመኛም ፡ ኵሉ ፡ ባንድ ፡ ተነሥቶ ፡ በብዙ ፥ በብዙም ፡ ተነሥቶ ፡ ባንድ ፡ ያነጽራል ። ባንድ ፡ ተነሥቶ ፡ በብዙ ፡ ሲያነጽር ፥ ዘማች ፡ አንቀጽ ፡ እንጂ ፡ ነባር ፡ አይመቸውም ። ይህም ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለኖኅ ፡ ነበረ ፡ አሐዱ ፡ ዕልው ፥ ወእከ ፡ አሐዱ ፡ ባሕቲቱ ፥ አላ ፡ ኵሎሙ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። በብዙም ፡ ተነሥቶ ፡ ባንድ ፡ ሲያነጽር ፥ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ እንጂ ፡ ዘማች ፡ አይመቸውም ።        የሠምና ፡ የወርቅ ፡ ጓዝ ፡ ፳፯ኛው ፡ ክፍል ፡ ተፈጸመ ።

## ፳፰ኛ ፡ ዕርከን ።

## የርባ ፡ ቅምርና ፡ የጸዋትወ ፡ ርባ ፡ ተረፍ ፡ ባለ፬ ፡ ረድፍ ።

፫፻፬ ፡ ረድፍ ፡ ማለት ፡ ተከታታይ ፡ ክፍል ፡ ማለት ፡ ነው ፥ ዕርከን ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ እነዚሁም ፡ የዋህ ፡ ርባታና ፡ መሠሪ ፡ ርባታ ፥ ጽንዕ ፡ አንቀጽና ፡ አሉታ ፡ አንቀጽ ፡ ናቸው ። አንዱን ፡ ጽድቅ ፡ አንቀጽ ፡ በየዋህና ፡ በመሠሪ ፡ በጽንዕ ፡ በሉታ ፡ ሲያረቡት ፡ ብዙ ፡ ጠባይ ፡ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ አለውና ፡ ባላ፬ ፡ ረድፍ ፡ ማለት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። የርባታም ፡ ትምርት ፡ የሚገርመር ፡ በብትን ፡ ባርእስትና ፡ በደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዐቢይ ፡ አንቀጽ ፡ አይዶለም ። ከደቂቅ ፡ ርባታም ፡ አስቀድሞ ፡ መራሕያን ፡ የሚባሉትን ፡ ያሥሩን ፡ ሰራዊት ፡ ስምና ፡ ተራ ፥ ውእቱ ፡ አንተ ፥ ውእቶሙ ፡ አንትሙ ፥ ይእቲ ፡ አንቲ ፥ ውእቶን ፡ አንትን ፥ አነ ፡ ንሕነ ፡ እያሉ ፡ ማጥናት ፡ ይገባል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከራስ ፡ ጠጕር ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍር ፡ ያሉትን ፡ ሕዋሳት ፡ በመልክዐስ ፡ ተራ ፡ አንዳንዱን ፡ በየስማቸው ፡ ማርባት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሥዕርት ፡ ብሎ ፡ ሥዕርቱ ፡ ሥዕርትከ ፡ ርእስ ፡ ብሎ ፡ ርእሱ ፡ ርእስከ ፡ አርእስት ፡ ብሎ ፡ አርእስቲሁ ፡ ከ ፡ ሆሙ ፡ ክሙ ፡ እያሰኙ ፡ ከናፈታቱ ፡ ሲነገር ፥ ላቢይ ፡ ርባታ ፡ በር ፡ ከፋች ፡ መቅድም ፥ ለዘማች ፡ አንቀጽ ፡ መሪ ፡ ፈታውራሪ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ። ምሳሌውም ፥ ርካብ ፡ ተረግጦ ፡ ወደ ፡ ኮር ፥ ድንክ ፡ ተረግጦ ፡ ወደ ፡ ዙፋን ፡ እንደ ፡ መውጣት ፡ ነው ።

፫፻፭ ፡ ዐቢይ ፡ ርባታም ፡ የሚገርመር ፡ ገቢርነት ፡ ባለው ፡ በ፫ ፡ ፈደል ፡ ግስ ፡ በቀተለ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ያውም ፡ በምልእት ፡ የሚረባ ፥ በድራጊነቱ ፡ ላይ ፡ አስደራጊና ፡

ተደራጊ ፥ ተደራራጊና ፡ አደራራጊ ፡ የሚደርብ ፥ ላልቶ ፡ የሚነገር ፡ መደበኛ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡፡ ባዋቆችና ፡ በጠንቃቆች ፡ ዐዋጅ ፡ እንደ ፡ አእመረ ፡ የማስደረግ ፡ ልማድ ፡ አ ፡ ያለበት ፡ ያራት ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ አስደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ እንደነተዝጎረም ፡ የመደረግ ፡ ልማድ ፡ ተ ፡ ያለበት ፡ ተደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ የርባታ ፡ መሠረት ፡ አይኾንም ፡፡ ይኸና ልም ፡ ብሎ ፡ ቢያደርጉት ፡ ሲፈተሽና ፡ ሲመረመር ፡ ማሳፈሩና ፡ ማስነወሩ ፡ አይቀርም ፡፡ በእና ፡ በሀ ፡ የሚነሣ ፡ የ፫ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ እንደ ፡ ቀተለ ፡ ላልቶ ፡ ሲነገር ፥ ሥርወ ፡ ትን ቢቱን ፡ በካልአይ ፡ ኹሉ ፡ ግእዝ ፡ ያደርጋል ፤ ዖረ ፡ የዐውር ፤ ሐረ ፡ የሐውር ፡፡ እንደ ፡ ቀደሰም ፡ ጠብቆ ፡ ሲነገር ፡ በካልአዩ ፡ ሳድስ ፥ በቀሩት ፡ ግእዝ ፡ ያደርጋል ፤ አመረ ፡ ይኤምር ፡ የአምር ፡፡ ሐወጸ ፡ ይሔውጽ ፡ የሐውጽ ፡፡

፫፻፯ ፡ ያቢይ ፡ አንቀጽ ፡ ርባ ፡ በዘሩና ፡ በሥረ ፡ ነገሩ ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ኹኖ ፡ በንኡስ ፡ ርባታ ፡ ሲገረመር ፥ ግሱም ፡ የ፫ ፡ ፊደል ፡ ኹኖ ፡ በጥንተ ፡ ፊደሉ ፡ በአልፍ ፡ ሲነሣ ፥ እነሣሡ ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

## አርእስት ፡ ወይም ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡፡

አሚር ፡ አሚሮት ፡ ማወቅ ፥ ዐዋቂነት ፡፡

### ንኡስ ፡ ርባታ ፡፡

አሚርሁ ፡ አሚሮቱ ፡ ማወቁ ፡ የርሱ ፡ ማወቅ ፡፡
አሚርከ ፡ አሚሮትከ ፡ ማወቅኽ ፡፡
አሚርሆሙ ፡ አሚሮቶሙ ፡
አሚርክሙ ፡ አሚሮትክሙ ፡
አሚርሃ ፡ አሚሮታ ፡
አሚርኪ ፡ አሚሮትኪ ፡
አሚርሆን ፡ አሚሮቶን ፡
አሚርክን ፡ አሚሮትክን ፡
አሚርየ ፡ አሚሮትየ ፡
አሚርነ ፡ አሚሮትነ ፡ ማወቃችን ፡፡

የገቢር ፡ ተሳቢም ፡ ሲኾኑ ፡ አሚርሁ ፡ በለው ፡ ይከታሉ ፡ በአሚሮት ፡ ግን ፡ ሙታንየ ፡ ብቻ ፡ (ትሙ ፡ ታ ፡ ቶን ፡ ትየ) ፡ እነዚህ ፡ ፬ቱ ፡ ሲቀሩ ፡ ካዕቡን ፡ ሳብዕ ፥ ሳድሱን ፡ ግእዝ ፡ ይወርሰዋል ፡፡

ይህም ፡ አሚሮቶ ፡ ማወቁን ፡
አሚሮተከ ፡ ተክሙ ፡ ተኪ ፡ ተክን ፡ ተነ ፡ ማወቃችንን ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ፡፡
አርእስትን ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ እያልኽ ፡ አርባ ፡፡

## ፩ኛ ፡ ረድፍ ።

## ዐቢይና ፡ መደብ ፡ የዋህ ፡ ርባታ ።

### መደበኛ ፡ አንቀጽ ።

፻፶፯ ፡ አመረ ፡ ዐወቀ ።
የአምር ፡ ያውቅ ፡
ይእምር ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ እንዲያውቅ ፡ ሊያውቅ ፡
ይእምር ፡ ይወቅ ። ዘንድ ፡ አንቀጽን ፡ ኹሉ ፡ እንደዚህ ፡ ፍቻ ፡ በትንቢቱም ፡ አልን ፡ አትፌጸምር ፡ ዐውቋል ፡ ያውቃል ፡ ማለት ፡ የጽንዕ ፡ አንቀጽ ፡ ፍቺ ፡ ነውና ፤ ኋላ ፡ ይመጣል ።

አመርከ ፡ ተአምር ፡ ትእምር ፡ እምር ።
አመሩ ፡ የአምሩ ፡ ይእምሩ ፡ ይእምሩ ።
አመርክሙ ፡ ተአምሩ ፡ ትእምሩ ፡ እምሩ ።
አመረት ፡ ተአምር ፡ ትእምር ፡ ትእምር ።
አመርኪ ፡ ተአምሪ ፡ ትእምሪ ፡ እምሪ ።
አመራ ፡ የአምራ ፡ ይእምራ ፡ ይእምራ ።
አመርክን ፡ ተአምራ ፡ ትእምራ ፡ እምራ ።
አመርኩ ፡ አአምር ፡ እእምር ፡ እእምር ።
አመርነ ፡ ነአምር ፡ ንእምር ፡ ንእምር ።

### በዝ ፡ አንቀጽ ።

አሚሮ ፡ ዐውቆ ።
አሚረከ ፡ ዐውቀኽ ።
አሚሮሙ ፡ አሚረክሙ ። አሚራ ፡ አሚረኪ ።
አሚሮን ፡ አሚረክን ። አሚርየ ፡ አሚረነ ።

### ሣልስ ፡ ቅጽል ።

አማሪ ፡ አማርያን ፡ አማሪት ፡ አማርያት ።

### መድበል ፡ ቅጽል ።

አመርት ፡ ያወቁ ፡ የሚያውቁ ፡ ዐዋቆች ።

## ፪ኛ ፡ ረድፍ ።

፻፶፰ ፡ ያሥሩ ፡ መደብ ፡ ዝርዝር ፤ መሠረ ፡ ርባታ ።

ካሥሩ ፡ ሰራዊት ፡ ፴ቱ ፡ ሩቆች ፡ ባ፲ ፡ ባ፲ ፤ ፴ቱ ፡ ቅርቦች ፡ በ፯ ፡ በ፯ ፤ አነና ፡ ንሕነ ፡ በ፰ ፡ በ፰ ፡ ሲዘረዘሩ ፡ ድምራቸውና ፡ መደባቸው ፡ ፲፫ ፡ ይኾናል ። እንቀጻቸውም ፡

ያሥሩ ፡ መደብ ፡ ፴ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የ፫ቱ ፡ ውም ፡ ፻፳ ፡ ይኾናል ። መራሕያኑም ፡ እንቀጽ ፡ ተቀባዮች ፡ እየኾኑ ፡ በየመደቡ ፡ ራስ ፡ ተጥፈዋል ። ዝርዝራቸውን ፡ በ፰ኛ ፡ ሰር ከን ፡ ተመልከት ።

(ውእቱ) ፡

አመሮ ፡ ዐወቀው ፡ ዐወቀለት ፡ ዐወቀበት ።
የአምሮ ፡ ያውቀው ፡ ያውቅለት ፡ ያውቅበት ፡
ይእምሮ ፡ ያውቀው ፡ ያውቅለት ፡ ያውቅበት ፡ ዘንድ ፡ እንዲያውቀው ፡ እንዲያውቅለት ፡ በት ፡ ሊያውቀው ፡ ሊያውቅለት ፡ በት ። ኹሉን ፡ እንዳህ ፡ ፍታ ።
ይእምሮ ፡ ይወቀው ፡ ይወቅለት ፡ ይወቅበት ።

አመረከ ፡ የአምረከ ፡ ይእምርከ ፡ ይእምርከ ።
አመሮሙ ፡ የአምሮሙ ፡ ይእምሮሙ ፡ ይእምሮሙ ።
አመረክሙ ፡ የአምረክሙ ፡ ይእምርክሙ ፡ ይእምርክሙ ።
አመራ ፡ የአምራ ፡ ይእምራ ፡ ይእምራ ።
አመረኪ ፡ የአምረኪ ፡ ይእምርኪ ፡ ይእምርኪ ።
አመሮን ፡ የአምሮን ፡ ይእምሮን ፡ ይእምሮን ።
አመረክን ፡ የአምረክን ፡ ይእምርክን ፡ ይእምርክን ።
አመረኒ ፡ የአምረኒ ፡ ይእምረኒ ፡ ይእምረኒ ።
አመረነ ፡ የአምረነ ፡ ይእምረነ ፡ ይእምረነ ።

(አንተ) ፡

አመርኮ ፡ ተአምሮ ፡ ትእምሮ ፡ እምሮ ።
አመርኮሙ ፡ ተአምሮሙ ፡ ትእምሮሙ ፡ እምሮሙ ።
አመርካ ፡ ተአምራ ፡ ትእምራ ፡ እምራ ።
አመርኮን ፡ ተአምሮን ፡ ትእምሮን ፡ እምሮን ።
አመርከኒ ፡ ተአምረኒ ፡ ትእምረኒ ፡ እምረኒ ።
አመርከነ ፡ ተአምረነ ፡ ትእምረነ ፡ እምረነ ።

(ውእቶሙ ፡ አው ፡ እሙንቱ) ፡

፻፵፬ ፡ አመርዎ ፡ የአምርዎ ፡ ይእምርዎ ፡ ይእምርዎ ።
አመሩከ ፡ የአምሩከ ፡ ይእምሩከ ፡ ይእምሩከ ።
አመርዎሙ ፡ የአምርዎሙ ፡ ይእምርዎሙ ፡ ይእምርዎሙ ።
አመሩክሙ ፡ የአምሩክሙ ፡ ይእምሩክሙ ፡ ይእምሩክሙ ።
አመርዋ ፡ የአምርዋ ፡ ይእምርዋ ፡ ይእምርዋ ።
አመሩኪ ፡ የአምሩኪ ፡ ይእምሩኪ ፡ ይእምሩኪ ።

አመርዎን ፡ የአምርዎን ፡ ይእምርዎን ፡ ይእምርዎን ።
አመሩክን ፡ የአምሩክን ፡ ይእምሩክን ፡ ይእምሩክን ።
አመሩኒ ፡ የአምሩኒ ፡ ይእምሩኒ ፡ ይእምሩኒ ።
አመሩነ ፡ የአምሩነ ፡ ይእምሩነ ፡ ይእምሩነ ።

(አንትሙ) ፡

አመርክምዎ ፡ ተአምርዎ ፡ ትእምርዎ ፡ እምርዎ ።
አመርክምዎሙ ፡ ተአምርዎሙ ፡ ትእምርዎሙ ፡ እምርዎሙ ።
አመርክምዋ ፡ ተአምርዋ ፡ ትእምርዋ ፡ እምርዋ ።
አመርክምዎን ፡ ተአምርዎን ፡ ትእምርዎን ፡ እምርዎን ።
አመርክሙኒ ፡ ተአምሩኒ ፡ ትእምሩኒ ፡ እምሩኒ ።
አመርክሙነ ፡ ተአምሩነ ፡ ትእምሩነ ፡ እምሩነ ።

(ይእቲ) ፡

፻፹ ፡ አመረቶ ፡ ተአምሮ ፡ ትእምሮ ፡ ትእምሮ ።
አመረተከ ፡ ተአምረከ ፡ ትእምርከ ፡ ትእምርከ ።
አመረቶሙ ፡ ተአምሮሙ ፡ ትእምሮሙ ፡ ትእምሮሙ ።
አመረተክሙ ፡ ተአምረክሙ ፡ ትእምርክሙ ፡ ትእምርክሙ ።
አመረታ ፡ ተአምራ ፡ ትእምራ ፡ ትእምራ ።
አመረተኪ ፡ ተአምረኪ ፡ ትእምርኪ ፡ ትእምርኪ ።
አመረቶን ፡ ተአምሮን ፡ ትእምሮን ፡ ትእምሮን ።
አመረተክን ፡ ተአምረክን ፡ ትእምርክን ፡ ትእምርክን ።
አመረተኒ ፡ ተአምረኒ ፡ ትእምረኒ ፡ ትእምረኒ ።
አመረተነ ፡ ተአምረነ ፡ ትእምረነ ፡ ትእምረነ ።

(አንቲ) ፡

አመርኪዮ ፡ ተአምሪዮ ፡ ትእምሪዮ ፡ እምሪዮ ።
አመርኪዮሙ ፡ ተአምሪዮሙ ፡ ትእምሪዮሙ ፡ እምሪዮሙ ።
አመርኪያ ፡ ተአምሪያ ፡ ትእምሪያ ፡ እምሪያ ።
አመርኪዮን ፡ ተአምሪዮን ፡ ትእምሪዮን ፡ እምሪዮን ።
አመርክኒ ፡ ተአምርኒ ፡ ትእምርኒ ፡ እምርኒ ።
አመርክነ ፡ ተአምርነ ፡ ትእምርነ ፡ እምርነ ።

(ውእቶን፥አው ፡ እማንቱ) ፡

፻፹፩ ፡ አመራሁ ፡ የአምራሁ ፡ ይእምራሁ ፡ ይእምራሁ ።
አመራከ ፡ የአምራከ ፡ ይእምራከ ፡ ይእምራከ ።
አመራሆሙ ፡ የአምራሆሙ ፡ ይእምራሆሙ ፡ ይእምራሆሙ ።

አመራክሙ ፡ የአምራክሙ ፡ ይእምራክሙ ፡ ይእምራክሙ ።
አመራሃ ፡ የአምራሃ ፡ ይእምራሃ ፡ ይእምራሃ ።
አመራኪ ፡ የአምራኪ ፡ ይእምራኪ ፡ ይእምራኪ ።
አመራሆን ፡ የአምራሆን ፡ ይእምራሆን ፡ ይእምራሆን ።
አመራክን ፡ የአምራክን ፡ ይእምራክን ፡ ይእምራክን ።
አመራኒ ፡ የአምራኒ ፡ ይእምራኒ ፡ ይእምራኒ ።
አመራነ ፡ የአምራነ ፡ ይእምራነ ፡ ይእምራነ ።

(አንትን) ፡

አመርክናሁ ፡ ተአምራሁ ፡ ትእምራሁ ፡ እምራሁ ።
አመርክናሆሙ ፡ ተአምራሆሙ ፡ ትእምራሆሙ ፡ እምራሆሙ ።
አመርክናሃ ፡ ተአምራሃ ፡ ትእምራሃ ፡ እምራሃ ።
አመርክናሆን ፡ ተአምራሆን ፡ ትእምራሆን ፡ እምራሆን ።
አመርክናኒ ፡ ተአምራኒ ፡ ትእምራኒ ፡ እምራኒ ።
አመርክናነ ፡ ተአምራነ ፡ ትእምራነ ፡ እምራነ ።

(አነ) ፡

፻፺፱ ፡ አመርክዎ ፡ አእምሮ ፡ እእምሮ ፡ እእምሮ ።
አመርኩከ ፡ አእምረከ ፡ እእምርከ ፡ እእምርከ ።
አመርክዎሙ ፡ አእምሮሙ ፡ እእምሮሙ ፡ እእምሮሙ ።
አመርኩክሙ ፡ አእምረክሙ ፡ እእምርክሙ ፡ እእምርክሙ ።
አመርክዋ ፡ አእምራ ፡ እእምራ ፡ እእምራ ።
አመርኩኪ ፡ አእምረኪ ፡ እእምርኪ ፡ እእምርኪ ።
አመርክዎን ፡ አእምሮን ፡ እእምሮን ፡ እእምሮን ።
አመርኩክን ፡ አእምረክን ፡ እእምርክን ፡ እእምርክን ።

(ንሕነ) ፡

አመርናሁ ፡ ነአምሮ ፡ ንእምሮ ፡ ንእምሮ ።
አመርናከ ፡ ነአምረከ ፡ ንእምርከ ፡ ንእምርከ ።
አመርናሆሙ ፡ ነአምሮሙ ፡ ንእምሮሙ ፡ ንእምሮሙ ።
አመርናክሙ ፡ ነአምረክሙ ፡ ንእምርክሙ ፡ ንእምርክሙ ።
አመርናሃ ፡ ነአምራ ፡ ንእምራ ፡ ንእምራ ።
አመርናኪ ፡ ነአምረኪ ፡ ንእምርኪ ፡ ንእምርኪ ።
አመርናሆን ፡ ነአምሮን ፡ ንእምሮን ፡ ንእምሮን ።
አመርናክን ፡ ነአምረክን ፡ ንእምርክን ፡ ንእምርክን ።

የበገ ፡ አንቀጽ ፡ ዝርዝር ፡ እስከ ፡ ፲ ።

(ውእቱ) ፡

፻፹፫ ፡ አሚሮሁ ፡ ዐውቆት ፡ ለት ፡ በት ።
አሚሮከ ፡ አሚሮሆሙ ፡ ክሙ ። አሚሮሃ ፡ ኪ ፡ ሆን ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ ።
(አንተ) ፡ አሚረከሁ ፡ ሆሙ ፡ አሚረከሃ ፡ ሆን ፡ ከኒ ፡ ከነ ።
(እሙንቱ) ፡ አሚሮሙሁ ፡ ከ ፡ አሚሮሙሆሙ ፡ ክሙ ።
አሚሮሙሃ ፡ ኪ ፡ አሚሮሙሆን ፡ ክን ፡ ሙኒ ፡ ነ ።
(አንትሙ) ፡ አሚረክሙሁ ፡ ሆሙ ፡ አሚረክሙሃ ፡ ሆን ፡ ኒ ፡ ነ ።
(ይእቲ) አሚራሁ ፡ ከ ፡ አሚራሆሙ ፡ ክሙ ፡ አሚራሃ ፡ ኪ ፡
አሚራሆን ፡ ክን ፡ አሚራኒ ፡ አሚራነ ፡ ዐውቃን ።
(አንቲ) ፡ አሚረኪሁ ፡ ሆሙ ፡ አሚረኪሃ ፡ ሆን ፡ ክኒ ፡ ነ ።
(እማንቱ) ፡ አሚሮንሁ ፡ ከ ፡ ሆሙ ፡ ክሙ ፡ አሚሮንሃ ፡ ኪ ፡
አሚሮንሆን ፡ ክን ፡ አሚሮንኒ ፡ ንነ ፡ ዐውቀውን ።
(አንትን) ፡ አሚረክንሁ ፡ ሆሙ ፡ አሚረክንሃ ፡ ሆን ፡ ናኒ ፡ ናነ ።
(አነ) ፡ አሚርየሁ ፡ ከ ፡ ሆሙ ፡ ክሙ ፡ አሚርየሃ ፡ ኪ ፡ ሆን ፡ ክን ።
(ንሕነ) ፡ አሚረነሁ ፡ ከ ፡ ሆሙ ፡ ክሙ ፡ አሚረነሃ ፡ ኪ ፡ ሆን ፡ ክን ።

፬ኛ ፡ ዐምድ ፡ አስደራጊ ፡ አንቀጽ ።

፻፹፬ ፡ አእመረ ፡ አሳወቀ ።
ያአምር ፡ ያሳውቅ ፡
ያእምር ፡ ያሳውቅ ፡ ዘንድ ፡ ያሳውቅ ፡ እያልኽ ፡ እስከሥር ፡ አርባ ።
ዝርዝሩንም ፡ አእመሮ ፡ አሳወቀው ፡ ለት ፡ በት ።
ያአምሮ ፡ ያሳውቀው ፡ ያሳውቅለት ፡ ብት ፡ እያልኽ ፡ እስከ ፡ ፲፫ ፡
አዝምት ። ከጥንቱ ፡ ልማዱ ፡ የተለወጠበት ፡ ፪ ፡ ነገር ፡ ነው ፥ ሥርወ ፡ ትንቢትና ፡ አፈ
ቃት ፡ ሥረወ ፡ ትንቢት ፥ ማእዝ ፡ የነበረውን ፡ የተአነ ፡ በራብዕ ፡ ያቃኣና ፡ ማለት ፡ አፈ
ቃት ፥ አድራጊ ፡ የነበረውን ፡ ዐወቀን ፡ ትቶ ፡ በስደራጊ ፡ አሳወቀ ፡ ማለት ። ዐወቀ ፡ አሳ
ወቀ ፡ ብለውም ፡ በ፪ ፡ ጾታ ፡ ለሚፈቱት ፡ እወና ፡ አልበ ፡ ይኽንበቻቀል ።

፭ኛ ፡ ዐምድ ፡ ተደራጊ ፡ አንቀጽ ።

፻፹፭ ፡ ተአምረ ፡ ታወቀ ።
ይትአመር ፡ ይታወቅ ፡
ይትአምር ፡ እያልኽ ፡ እስከ፲ ።
ዝርዝሩንም ፡ ተአምሮ ፡ ታወቀው ፡ ለት ፡ በት ።
ይትአመሮ ፡ ይታወቀው ፡
ይትአመሮ ፡ እያልኽ ፡ እስከ ፡ ፲፫ ፡ አርባ ።

## ፩ኛ ፡ ዐምድ ፡ ተደራራጊ ፡ አንቀጽ ።

፻፳፮ ፡ ተአመረ ፡ ተዋወቀ ።
ይትአመር ፡ ይተዋወቅ ፡
ይትአመር ፡ እያልኽ ፡ እስከሥር ።

ዘርዝሩንም ፡ ተአመሮ ፡ ይትአመሮ ፡ ይትአመሮ ፡ እያልኽ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ አርባ ። ሥርወ ፡ ትንቢቱ ፡ እንዳለፈው ፡ ሳድስ ፡ መኾኑን ፥ ሥርወ ፡ ቀለሙ ፡ ግን ፡ ተለይቶ ፡ ራብዕ ፡ መኾኑን ፡ አስተውል ፡ የሚመጣውም ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

## ፪ኛ ፡ ዐምድ ፡ አደራራጊ ፡ አንቀጽ ።

፻፳፯ ፡ አስተአመረ ፥ አስተዋወቀ ፡ ያስተአምር ፡ ያስተአምር ፡ እያልኽ ፥ መሠረውንም ፡ አስተአመሮ ፡ ያስተአምሮ ፡ እያልኽ ፡ አርባ ። ከ፫ቱ ፡ አዕማድ ፡ የሚገኙ ፡ ዐበይት ፡ አናቅጽ ፡ በየዋህ ፡ ርባታ ፡ ፲፬ ። በመሠረ ፡ ርባታ ፡ ሺሕ ፡ ከ፱፻ ፡ ናቸው ። አርእስቶቻቸው ፥ ሣልስና ፡ ሳድስ ፡ ቅጽሎቻቸው ፡ ሳቢ ፡ ዘሮቻቸው ፡ ሳይቀሩ ፡ ንኡሳን ፡ አናቅጽ ፡ ተብለው ፡ በንኡስ ፡ ርባታ ፡ ተነግረዋል ፡ (፲፩ኛ ፡ ዕርከን) ። በምልአት ፡ የሚነገር ፡ ግስ ፡ ልኩና ፡ መልኩ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ፫ኛ ፡ ረድፍ ።

## ጽንዕ ፡ አንቀጽ ።

፻፳፰ ፡ የጽንዕ ፡ አንቀጾች ፡ ከነና ፡ ሀሎ ፡ ውእቱና ፡ ቦ ፡ ሎ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ከናዋጃቸው ፡ ከናገባባቸው ፡ በ፫ኛ ፡ ዕርከን ፡ የመደበኛውም ፡ የሀሎ ፡ ርባታ ፡ በ፱ኛ ፡ ዕርከን ፡ ተነግሯል ። ጽንዕ ፡ የሚባል ፡ ብኅላፊና ፡ በትንቢት ፡ የኾነውን ፡ እንዳልኾነና ፡ እንደማይኾን ፡ ያልኾነውን ፡ እንደ ፡ ኾነና ፡ እንደሚኾን ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳይ ፡ የጸጸት ፡ የምኞት ፡ የፍርድና ፡ የትች ፡ አነጋገር ፡ ነው ። ይህም ፡ በንኡስ ፡ አገባብ ፡ ከእም ፡ ጋራ ፡ ገብቶ ፡ ተነግሯል ። ጽንዕም ፡ ያሰኘው ፡ አንቀጹ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ኹኖ ፡ ሲነገር ፡ የነገሩን ፡ ጥናትና ፡ ብርታት ፡ ማሳየት ፡ ነው ። አንቀጹና ፡ ርባታው ፡ ፍችውም ፡ ይህ ፡ ነው ።

### የዋህ ፡ ጽንዕ ።

አሚሮ ፡ ሀለወ ፡ ዐውቋል ፡ ዐውቆ ፡ ነበር ።
የአምር ፡ ሀሎ ፡ ያውቃል ፡ ያውቅ ፡ ነበር ።
አሚሮ ፡ የሀሉ ፡ ዐውቆ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እንዲኖር ፡ ሊኖር ፡
አሚሮ ፡ የሀሉ ፡ ዐውቆ ፡ ይኑር ። ኹሉን ፡ እንዲህ ፡ ፍታ ።
አሚረከ ፡ ሀሎከ ፡ ተአምር ፡ ሀሎከ ፡ አሚረከ ፡ ተሀሉ ፡ አሚረከ ፡ ሀሉ ።
አሚሮሙ ፡ ሀለዉ ፡ የአምሩ ፡ ሀለዉ ፡ አሚሮሙ ፡ የሀልዉ ።
አሚረክሙ ፡ ሀሎክሙ ፡ ተአምሩ ፡ ሀሎክሙ ።

አሚረክሙ ፡ ተሀልወ ፡ አሚረክሙ ፡ ሀልወ ።
አሚራ ፡ ሀለወት ፡ ተአምር ፡ ሀለወት ፡ አሚራ ፡ ተሀሉ ።
አሚረኪ ፡ ሀሎኪ ፡ ተአምሪ ፡ ሀሎኪ ፡ አሚረኪ ፡ ተሀልዊ ፡ ሀልዊ ።
አሚሮን ፡ ሀለዋ ፡ የአምራ ፡ ሀለዋ ፡ አሚሮን ፡ የሀልዋ ።
አሚረክን ፡ ሀሎክን ፡ ተአምራ ፡ ሀሎክን ፡
አሚረክን ፡ ተሀልዋ ፡ አሚረክን ፡ ሀልዋ ።
አሚርየ ፡ ሀሎኩ ፡ አአምር ፡ ሀሎኩ ፡
አሚርየ ፡ አሀሉ ፡ አሚርየ ፡ አሀሉ ።
አሚረነ ፡ ሀሎነ ፡ ነአምር ፡ ሀሎነ ፡ አሚረነ ፡ ነሀሉ ።

መሠረ ፡ ጽንዕ ።

፻፹፱ ፡ አሚሮሁ ፡ ሀለወ ፡　　ዐውቆታል ፡ ዐውቆለታል ፡ ዐውቆበታል ፡ ዐውቆት ፡ ዐውቆለት ፡ ዐውቆበት ፡ ነበር ።

የአምሮ ፡ ሀሎ ፡　　ያውቀዋል ፡ ያውቅለታል ፡ ያውቅበታል ፡ ያውቀው ፡ ያውቅለት ፡ ያውቅበት ፡ ነበር ።

አሚሮሁ ፡ የሀሉ ፡　　ዐውቆት ፡ ዐውቆለት ፡ ዐውቆበት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እንዲያውቀው ፡ ሊያውቀው ፡ ሊያውቅለት ፡ በት ፡

አሚሮሁ ፡ የሀሉ ፡　　ዐውቆት ፡ ዐውቆለት ፡ በት ፡ ይኑር ።

አሚሮከ ፡ ሀለወ ፡ የአምረከ ፡ ሀሎ ፡ አሚሮከ ፡ የሀሉ ።

አሚሮሆሙ ፡ ሀሎ ፡ የአምሮሙ ፡ ሀሎ ፡ አሚሮሆሙ ፡ የሀሉ ።

አሚሮክሙ ፡ ሀለወ ፡　　ኹሉን ፡ እንዲህ ፡ እያልኽ ፡ እስከ ፡ ፹ ፡ አርባ ። በቀኑትም ፡ ባሉቱ ፡ አዕማድ ፡ በያንዳንዱ ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ፹ ፡ እንዲሁ ፡ ይዘምታል ። ውእቱም ፡ ጽንዕ ፡ እየኾነ ፡ ሀሎ ፡ በገበበት ፡ ሲገባ ፡ በኀላፊና ፡ በትንቢት ፡ ብቻ ፡ ይነገራል ፡ አንቀጽነቱ ፡ ነባር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እንደ ፡ ሀሎ ፡ ዘንድና ፡ ትእዛዝ ፡ የለውም ። ይህም ፡ ዐዊቆ ፡ ውእቱ ፡ የዐውቅ ፡ ውእቱ ። ዐዊቀከ ፡ አንተ ፡ ተዐውቅ ፡ አንተ ፡ እያሰኘ ፡ ዐውቀኻል ፡ ዐውቀኽ ፡ ነበር ፡ ታውቃለኽ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ።

፴ኛ ፡ ረድፍ ።

አሉታ ፡ አንቀጽ ።

፻፺ ፡ ኢአመረ ፡　　አላወቀም ።
ኢየአምር ፡　　አያውቅም ።
ኢይእምር ፡　　እንዳያውቅ ፡ ላያውቅ ፡ ሳያውቅ ፡
ኢይእምር ፡　　አይወቅ ። ኹሉን ፡ እንዲህ ፡ ፍታ ።　በጽድቅ ፡ አንቀጽ ፡ አ ፡ የነበረውን ፡ የአኑን ፡ ሥርወ ፡ ትንቢት ፡ ብቻ ፡ ኢ ፡ ስትወድቅበት ፡ የ ፡ ይወርሰዋል ። ይህም ፡ ኢአመርኩ ፡ ብሎ ፡ ኢየአምር ፡ ኢይእምር ፡ ኢይእምር ፡ እያለ ፡

እንደ፡ሩቁ፡ወንድ፡መ፝ኼዱን፡ያሳያል ። ዳግመኛም፡የ፪ኛና፡ያ፫ኛ፡ዐምድ፡ልማዳቸው፡አ፡በኢ፡ምክንያት፡ያ፡ይ፝ኾናል ። ይህም፡ኢያእመረ፡ኢያአምር፡ኢያእምር፥ኢያእምር ። ኢያስተአመረ፡ኢያስተአምር፡ኢያስተአምር፡እያለ፡ሌላውን፡፝ኹሉ፡ያሳያል ። በግዝ፡አንቀጹንም፡ኢአሚሮ፡ኢአሚረከ፡ብሎ፥ሳያውቅ፡ሳታውቅ፡ያሰኛል ። የቀረውን፡ዐዋጅ፡ተመልሰ፝ኽ፡በርባ፡ቅምርና፡በጸዋትወ፡ርባ፡ተመልከት ።

፻፷፩፡ የአ፝ኀዝም፡ጥሬ፡ካንድ፡እስከሥ፝ር፡ያለው፡፝ኹሉም፡እያንዳንዱ፡ባ፲፡ባ፲፡መደብ፡ሲረባ፡ወይም፡ሲዘረዝር፥ርባታውና፡ዝርዝሩ፡ባጭር፡ቃል፡ይህ፡ነው ።

፫ምላ፡ቍጥር ።

አሐደ፡አሐዱ፡አሐዳ፡አሐዱሙ፡አሐዱን፡አሐድከ፡አሐድኪ፡አሐድክሙ፡ክን፡የ፡ነ ። ክልኤ፡ክልኤሁ፡ሃ፡ሆሙ፡ሆን፡ክልኤከ፡ኪ፡ክሙ፡ክን፡የ፡ነ ። ክልኤቲ፡ክልኤቱ፡ታ፡ቶሙ፡ቶን፡ክልኤትከ፡ኪ፡ክሙ፡ክን፡የ፡ነ ። ፝ኹሉን፡እስከ፡ዐሥርት፡እንዲሁ፡አርባ፡ስትፈታም፡አንዱ፥የርሱ፡አንድ፡፝ኹለቱ፥የርሱ፡፝ኹለት፡እያል፝ኽ፡እስከ፡ንሕነ፡ፍታ ። ዐይነ፡ምስጢሩም፡ሲገለጥ፥ቍጥሩ፡ገንዘብን፥ዝርዝሩ፡ባለገንዘብን፡ያሳያል ። በተራ፡ቍጥር፡ግን፥መነሻውን፡ራብዕ፡አድርጎ፥አሐድ፡ዱ፡ክልእ፡ኡ፡ዓሥር፡ሩ፡እያለ፥አንደኛው፥፝ኹለተኛው፥ዐሥረኛው፡ያሰኛል ። ከዚህ፡የቀረውን፡በአ፝ኀዝ፡ቅጽል፡ተመልከት ።

መፀዛ ፡ ሰዋስው ፡ ሰጣን ፡ ወጺና ፡ ትምህርት ፡ ክርቤ ፡
ለእለ ፡ ያጼንዑ ፡ ምክረ ፡ ወይሰምዑ ፡ ዘይቤ ፡
የግጥም ፡ ስብከት ፥ ወይም ፡ ይባቤ ።

በዶሮ ፡ ሥጋ ፡ አምሳል ፡ ምስጢሩ ፡ እንዲጥም ፡
ዐጭሬ ፡ ረዥሜ ፡ ይባላል ፡ ግጥም ፡
ዐጭሬው ፡ ሰዋስው ፡ ረዥሜው ፡ ግስ ፡
የሦስት ፡ ፊደል ፡ ሥጋ ፡ የርባ ፡ ቅምር ፡ ነፍስ ፡
ለልጆች ፡ እንዲተርፍ ፡ ያዋቆች ፡ መብል ፡
ያቡን ፡ ወጥ ፡ በሚሉት ፡ በተማቲም ፡ ቃል ፡
ሠርቶ ፡ ያቀረበው ፡ የግእዝ ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡
ላስነባቢው ፡ ምሳ ፡ ላንባቢው ፡ እራት ።

ለወጣቶች ፡ ኹሉ ፡ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡
ሰዋስው ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ መኀገደ ፡ ሰማይ ፡
ያዕቆብና ፡ ዕዝራ ፡ የግዜር ፡ ጉበኞች ፡
ቀድሞ ፡ የሰለሉት ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ።

የሰዋስው ፡ ትምርት ፡ ሥጋውና ፡ ዐጥንቱ ፡
ባጭሬው ፡ ተከቷል ፡ ረዥሜነቱ ።
ላንቀጹ ፡ ፍልሰታ ፡ ለርባታው ፡ ሑዳዴ ፡
የተለቀመውን ፡ ጥሩ ፡ ፊደል ፡ ስንዴ ፡
አስተውል ፡ ተመልከት ፡ ጸሓፊና ፡ አንባቢ ፡
ያማርኛ ፡ ገበዝ ፡ የግእዝ ፡ ዐቃቢ ።

የግእዝን ፡ ትምርት ፡ አባይን ፡ በጭልፋ ፡
ቀድቶ ፡ የሚጨርስ ፡ ማነው ፡ ባለተስፋ ፡
ቀድቶም ፡ ባይጨርሰው ፡ ከርሱ ፡ ለሚጠጣ ፡
ለሚሻገረውም ፡ እየተቀናጣ ፡
ከዋቆች ፡ ራስ ፡ ቅል ፡ የተከፈለው ፡
ፉጋውና ፡ ሜዳው ፡ እንሆ ፡ ይኸው ።
ዐዘውም ፡ ስንፍና ፡ ተማሪ ፡ እንዳይነጥቅ ፡
ዋናተኛው ፡ መምህር ፡ ተግቶ ፡ ይጠብቅ ።
በቀለም ፡ ገበያም ፡ ጣፊው ፡ ብር ፡ ሲቀርጥ ፡
ፊደሉ ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ።

ነቢያት ፡ የዘሩት ፡ የፊደላት ፡ ጉበስ ፡
ስሙ ፡ ልጅ ፡ አልቅሶ ፡ ቶሎ ፡ የሚደርስ ፡

ገብሱም ፡ ደረቅ ፡ ትንቢት ፡ ገበሬው ፡ ዘመን ፡
ዐጭዶና ፡ ከምሮ ፡ ያሳየን ፡ እኹን ።

ነዶውም ፡ ክምሩም ፡ የጎግ ፡ ማጎግ ፡ ሥጋ ፡
ለአዕዋፍ ፡ መርዔት ፡ ለአራዊት ፡ መንጋ ፡
እግዜር ፡ የወሰነው ፡ በሕዝቅኤል ፡ አፍ ፡
ሰባት ፡ ዓመት ፡ ብሎ ፡ መንፈቅ ፡ ሳያተርፍ ።

ይህም ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ዘመነ ፡ ማእረር ፡
ከበጉ ፡ ዐይንና ፡ ቀንድ ፡ የሚተባበር ፡
የግእዝም ፡ ፊደል ፡ በሰባትነቱ ፡
ከትንቢት ፡ ከራእይ ፡ ወየው ፡ መስማማቱ ።

ጊዜ ፡ ባስረገጠው ፡ በትምርት ፡ ዐውድማ ፡
ተንጣሎ ፡ ነበረ ፡ የግእዝ ፡ ምርትማ ፡
ፊልግን ፡ ስላጣን ፡ ዐፋሽ ፡ አጐንባሽ ፡
ድካማችን ፡ ኹሉ ፡ እንዳይቀር ፡ ብላሽ ፡
ከምርቱ ፡ ቈንጥረን ፡ ይህን ፡ ሰዋስው ፡
ስሙን ፡ ለኋላ ፡ ልጅ ፡ ዘር ፡ ይኹን ፡ አልነው ።

የዛሬማ ፡ ልጆች ፡ ብስሉን ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡
ባለመማራቸው ፡ አስመሰሉት ፡ ጩርቋ ፡
ጠጅ ፡ ነውም ፡ ብለን ፡ ብንሰጣቸው ፡ ቅሉ ፡
እንደ ፡ ጌታ ፡ ቀምሰው ፡ መጠጣት ፡ እንቢ ፡ አሉ ።
አጥብቆ ፡ ጠያቂም ፡ ሲመረምራቸው ፡
ስለ ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ምላሻቸው ፡

ምንም ፡ ቢንደረከክ ፡ የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ፍሕም ፡
እንደ ፡ ያፌት ፡ ከኛክ ፡ ሆድ ፡ አያሞቅም ፡
ስለ ፡ ሥጋ ፡ ጥበብ ፡ ስለ ፡ ደመወዝ ፡
ከኛኩ ፡ ይሻላል ፡ ከጠጁ ፡ ግእዝ ።

አብዝቶም ፡ ሲጠጡት ፡ በሽልም ፡ ፊደል ፡
ሆድ ፡ ስላላሞቀ ፡ ጠላ ፡ ነው ፡ ብንል ፡
አያስነቅፈንም ፡ በዛሬው ፡ ክረምት ፡
መስከረም ፡ ሲጠባ ፡ እንጃ ፡ ምናልባት ።

የመለኪያውም ፡ ስም ፡ አፈ ፡ ድስቱ ፡ ግብጥ ፡
ማብረጃ ፡ ይባላል ፡ ሙቀት ፡ እንዳይሰጥ ፡
ከማኽልም ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ቢቆም ፡
ዐላፊ ፡ አሳላፊ ፡ መኾን ፡ አልቻለም ።

ዐላፊም ፡ ከሌለው ፡ ለቋንቋ ፡ ትምርት ፡
ራስ ፡ የነበረው ፡ ይኸናል ፡ ኀፍረት ።

ብርሃኑ ፡ ጠፍቶ ፡ ኹኖ ፡ የግብጥ ፡ ፅልረቃ ፡
ስንኳን ፡ ለኛ ፡ ይተርፍ ፡ ለራሱም ፡ አልበቃ ፡
እስላሞች ፡ ሳይቀሩ ፡ የሚሰዩን ፡ ዠግና ፡
ሕዝቡን ፡ እንደ ፡ ምርኮ ፡ ተካፍሎታልና ።

የውጭ ፡ አገር ፡ ጳጳስ ፡ ርብታው ፡ ሕጹጽ ፤
የገንዘብ ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፡ ወይም ፡ ቦዝ ፡ እንቀጽ ፡
ዘርፉና ፡ ቅጽሉም ፡ በዕድ ፡ አታላይ ፡ ስም ፡
የማይስማማ ፡ ከግእዝ ፡ ቀለም ።

## ስለ ፡ ቋንቋ ፡ ትምርት ፡ መንገድና ፡ አኪኼድ ፡ ስለ ፡ ተማሮችም ፡ አረማመድ ።

ዐፄሬ ፡ ግጥም ፡ ቁመተ ፡ ዶሮ ፡ — የሚንጠራራ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ገሮ ፡
ቸብቸበው ፡ ዜማም ፡ ሳይቈረጥ ፡ — በየመሥመሩ ፡ የሚያስረግጥ ፡
ባልተኛ ፡ አዝማሪም ፡ መስሎ ፡ ሲያሥቅ ፡ እንዳቤሴሎም ፡ ልብ ፡ የሚሰርቅ ።

ከቡዱ ፡ መዝራዕት ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ አበት ፡ ኹኗቸው ፡ እንደነሙሴ ፡
ከተረገዙት ፡ በመንግሥት ፡ ሆድ ፡ — ከታዘሉትም ፡ በባንዲራ ፡ ለምድ ፡
ሞግዚታቸውም ፡ ዐዲሳበባ ፡ — ከቀፈታቸው ፡ በክንዱ ፡ ስበ ፡
አንድ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ኹሉን ፡ ሰብስቤ ፡ ዐጥናቸዋለሁ ፡ የምክር ፡ ከርቤ ።

ባንድነት ፡ ደንጊያ ፡ በኅብረት ፡ ዕፅ ፡ መቅደስ ፡ ልባቸው ፡ እንዲታነጽ ፡
ኋላም ፡ እንዳይፈርስ ፡ በጠላት ፡ ቦንብ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የወንጌል ፡ ግንብ ።
እንደ ፡ ፲ ፡ አካል ፡ የተካከሉ ፡ — ስለ ፡ ኅብረትም ፡ አንድ ፡ የሚባሉ ፡
፲ቱን ፡ ጉባኤ ፡ ምሰሶ ፡ አቁሞ ፡ — እግዜር ፡ የሠራው ፡ ከኛ ፡ አስቀድሞ ።

የምክሩም ፡ ከርቤ ፡ ኹለት ፡ ቊቀር ፡ በመቀነት ፡ ልብ ፡ የሚቋጠር ፤
ቍጥሩም ፡ ተገልጦ ፡ ሲታይ ፡ ሲፈታ ፡ ሽታው ፡ የሚነድፍ ፡ ልብ ፡ የሚመታ ፡
ገንዘብነቱም ፡ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ — የሚቀበለው ፡ ገበዝ ፡ ሕፃን ፡
ሰፊውም ፡ ለጋስ ፡ አቶ ፡ መንግሥቱ ፤ ርሱ ፡ ነውና ፡ ባለስለቱ ።

፩ኛ ፡ ቊቀር ፡ ሰጣነ ፡ ሞገር ፤ ልጅ ፡ ዐዋቂውን ፡ ከግእዝ ፡
እንደ ፡ ድጕስና ፡ እንደ ፡ ጥራገ ፡ የሚያጣብቅና ፡ የሚያያይዝ ።
ዘገሰሰ ፡ ፒሳ ፡ ይትአኀዝ ፡ ቦቱ ፡ (ሢራ ፡ ፲፫ ፡ ፩) ።

ስሟ ፡ ጣይቱ ፡ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ — ዐማርኛዋም ፡ ከከብ ፡ ፅልረቃ ፡
ፊደሏ ፡ ብርሃን ፡ ዘእምብርሃን ፡ — ሰባት ፡ ቍልጭልጭ ፡ የግዜር ፡ በግ ፡ ዐይን ።
ግእዝ ፡ ግእዙ ፡ ወርቅ ፡ ቀለም ፡ — በለ፺ ፡ ዕጽቅ ፡ ጉንደ ፡ ተቋም ፡
ሰድስቱም ፡ ዕጽቆች ፡ ግራና ፡ ቀኙ ፡ — ከሱራፌል ፡ ክንፍ ፡ የተሰናኙ ።

ከኪሩቤልም ፡ ክራቱ ፡ ኹሉ ፡ — በራብዕ ፡ ትውልድ ፡ ይዘመዳሉ ፡<br>
በሣልሱማ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ — ኹሉን ፡ ያገባል ፡ ወደ ፡ ቅዳሴ ፡<br>
ከኛ ፡ ቍጥር ፡ አንዱ ፡ ቢጐድል ፡ — ቅዳሴው ፡ እሳት ፡ ይዳፈናል ፡፡

የመላእክትም ፡ ጥንተ ፡ ልሳን ፡ — ያጠራጥራል ፡ ርሷ ፡ እንዳትኾን ፡<br>
የፊደሏ ፡ ምንጭ ፡ ዐይን ፡ ውሃው ፡ — ከላይ ፡ ነውና ፡ የፈለቀው ፡፡

ከሣር ፡ ከቅጠል ፡ በዝቶ ፡ ጊዜዋ ፡ — አሮጊት ፡ ስትኾን ፡ በተፈጥሮዋ ፡<br>
እንደ ፡ ሔኖክ ፡ ንስር ፡ ሕዋሳቶች ፡ — በተሐድሶ ፡ ስለ ፡ ኗረች ፡<br>
ዐይንና ፡ ጥርሷ ፡ ብሉይ ፡ ሐዲስ ፡ — ነጭና ፡ ጥቍር ፡ የሚያጣቅስ ፡፡

ዠርባዋም ፡ ንባብ ፡ እንደ ፡ ሰሎሚ ፡ — ጌታን ፡ ያዘለው ፡ በሰው ፡ ትርጓሚ ፡<br>
ጡቷም ፡ ደረቷም ፡ ባለሳንቃው ፡ — እንደ ፡ ማርያም ፡ የታቀፈው ፡<br>
ለመምህራንም ፡ ላረገዙት ፡ — መወልዲት ፡ ናት ፡ መወልዲት ፡፡

ጌታም ፡ ለሄኖስ ፡ ሲድራት ፡ ብርኩ ፡ — ስላረገዘች ፡ የርሱን ፡ አምልኩ ፡<br>
ከአልፉ ፡ እስከ ፡ ታው ፡ መልኳ ፡ ፊደል ፡ — የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ጠቅላይ ፡ መድበል ፡<br>
የመልኳም ፡ ድርሰት ፡ በማሕልዩ ፡ — ተጥፎለታል ፡ ደግሞ ፡ ለሚያዩ ፡፡<br>
እንደ ፡ ወጌሻ ፡ ገላ ፡ እንደሚያሽ ፡ — እንደ ፡ ሐኪምም ፡ እንደ ፡ ፈታሽ ፡<br>
ኹለንተናዋን ፡ ቀምለን ፡ አይተን ፡ — ስላጣንበት ፡ ነውር ፡ እንከን ፡<br>
መስለናታል ፡ በጥሩ ፡ ዐይናማ ፡ — ከወጣቶች ፡ ልብ ፡ እንድትስማማ ፡<br>
ዐይናማነቷም ፡ ከገጽ ፡ ንስር ፡ — የወረደ ፡ ነው ፡ በፊደል ፡ ዘር ፡፡

ዐይኗን ፡ ስትገልጠው ፡ ከጥርሷ ፡ ጋራ ፡ — አስተያየቷ ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡<br>
ስትናገርም ፡ በፊት ፡ በኋላ ፡ — ከኛ ፡ ይፈሳል ፡ የማር ፡ ወለላ ፡<br>
ልሳኗም ፡ ጥዑም ፡ የወይን ፡ እሸት ፡ — እየተሻሙ ፡ የሚበሉት ፡፡

ከአዳም ፡ ከኖኅ ፡ ካባት ፡ ከናቷ ፡ — ለሴም ፡ የታጨች ፡ ስለ ፡ ውበቷ ፡<br>
ከንጉሡም ፡ ከማዜር ፡ ከባለቤቱ ፡ — ስለ ፡ ተሰጣት ፡ እቴጌነቱ ፡<br>
ምንም ፡ ቢያጅቧት ፡ መኳንንቶች ፡ — ዐይኗና ፡ ልቧ ፡ ከተማሮች ፡፡

እኔም ፡ ልጨፍር ፡ ቃሌን ፡ ላንሣው ፡ — ተማሪን ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ እንዲለው ፡<br>
የተጌ ፡ አሽከሮች ፡ የንጉሡም ፡ ጭፍራ ፡ — ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ትግሬና ፡ ዐማራ ፡<br>
እንዲህ ፡ ብታይዋት ፡ ድኻ ፡ መስላችኹ ፡ — በለጸጋ ፡ ናት ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋችኹ ፡፡

የግምጃ ፡ ቤቷ ፡ ባሕር ፡ መዝገብ ፡ — ዕብራይስጥና ፡ ሱርስት ፡ ዐረብ ፡<br>
በኹርጠንጾቿም ፡ ነገደ ፡ ሴም ፡ — የተሠራጩት ፡ በምድረ ፡ ካም ፡<br>
ታሪኳም ፡ ቈንገር ፡ ስሙ ፡ ብርሃን ፡ — በምሥራቅ ፡ ቋንቋ ፡ የሠለጠነ ፡፡

ማነው ፡ የሚላት ፡ ድኻ ፡ ምስኪን ፡ — ካላዩት ፡ በቀር ፡ ገብተው ፡ ውስጧን ፡<br>
ማእዷም ፡ ትምርት ፡ እንዲህ ፡ መስፋቱ ፡ — ልትበሉለት ፡ ነው ፡ መቼ ፡ ለከንቱ ፡፡

ብዕዶቹ ፡ ነጮች ፡ ሲሻሙባት ፡ — ምነው ፡ እናንተ ፡ የማትደፍሯት ፡<br>
ደፈሩኝ ፡ ብላም ፡ እንዳትከሳችኹ ፡ — እኔ ፡ ስለ ፡ ርሷ ፡ ልማልላችኹ ፡<br>
ከምትገዛቸው ፡ ባስበ ፡ ተፈሪ ፡ — እኔ ፡ ነኝና ፡ አንዱ ፡ አቃጣሪ ፡፡

ደፍሮ፡አለመቅመስ፡እየከጀሉ፡ — የጐደሎ፡ነው፡መቼ፡የሙሉ።
ደፋር፡ወንድ፡እንጂ፡ልቧን፡የሚያግም፡ የከንፈር፡ወዳጅ፡አላጣችም።

በውበት፡በመልክ፡ግእዝ፡ሙሽራ፡ ልዩ፡ስትኾን፡ከጋላ፡ዱብራ፡
ባፉ፡ሊሸኛት፡ከንፈሯን፡ለክፎ፡ — አይገባውም፡ለጦቢያው፡ለፎ።

ባለፈው፡ዘመን፡ከቀን፡ጨለማ፡ — ዐይናማነቷ፡ስላልተስማማ፡
የሌባው፡አካን፡ልሳነ፡ወርቅ፡ — ሰው፡እንዳስፈጀች፡በመደበቅ፡
የደፈሯትን፡ለንጉሡ፡ነግራ፡ — ታስቈርጥ፡ነበር፡ምላስ፡በካራ፤
ያልተቈረጠው፡ካገር፡ተሰዶ፡ — እስኪንከራተት፡ባፍሬቃ፡ማዶ።

እንደ፡ሙሴ፡ፊት፡እንደ፡ምኵራብ፡ እንደ፡ቱርክም፡ሴት፡እንደ፡ዐረብ፡
አብነት፡ነሥታ፡ከባር፡ማሽላ፡ — ባቡን፡በጨጌ፡ድርብ፡ቀጸላ፡
ትወድ፡ነበር፡መሸፋፈን፡ — ልቧ፡ሳይጠላው፡መገለጡን።

እንዳትታይም፡በመሸፈኗ፡ — አልተጠቀመም፡ቀዳዳው፡ዐይኗ፥
ከርሷ፡የታማው፡አንዳንዱ፡ዠግና፡ ታስሮ፡ሲገረፍ፡ታይ፡ነበረና፤
ዳግመኛ፡እንዳያይ፡ዐይኗን፡መጽሐፍ፡ እስኪከልሉት፡በጃቸው፡ሰይፍ፥
ለከተማውም፡ላይነ፡ስውሩ፡ — ብርሃን፡እስኪታይ፡በመቃብሩ።
ብርሃንም፡ታይቶ፡ስላሳፈረ፡ — ከማሰር፡በቀር፡መሰየፍ፡ቀረ፤
በዖዝያንም፡በባለሰይፉ፡ — ለምጽ፡ኾነበት፡ማሰር፡መግረፉ፤
በተራራ፡ላይ፡የሡሩት፡ግፍ፡ — አይሰወርም፡ከታሪክ፡አፍ።

ስለ፡ሃይማኖት፡በመሞት፡ፈንታ፡ መግደል፡መሰየፍ፡የቍርኣን፡ዘንታ፥
ረቂቁማ፡የወንጌል፡ፍርድ፡ — መታረድ፡ነበር፡መቼ፡ማረድ፤
ቀኑ፡ጨልሞ፡ባደባባይ፡ — ያያት፡ሰው፡የለም፡ርሷ፡ስታይ።

ዛሬ፡ግን፡ዐፍራ፡እንደ፡ነጮች፡ የቀድሞ፡ግብሯን፡ስለ፡ተወች፡
መጋረጃዋም፡በታምራት፡ — ከላይ፡እስከ፡ታች፡ተቀዶላት፡
ወደ፡ነጻነት፡ዐይኗን፡አሻግራ፡ — ኹሉን፡ታያለች፡እንደ፡ዲቦራ።

ቅዱስ፡መጽሐፍም፡በርሷ፡ዐማርኛ፡ ከግዜር፡ተልኮ፡መጣ፡ዳግመኛ፥
የትምርቷን፡ወንዝ፡አለወረፉ፡ — ኹሉ፡እንዲቀዳ፡እየተስፋፉ፤
ርሷም፡ጣይቱ፡መሐንድስ፡ኹና፡ — እየቀየሰች፡የሰው፡ልቡና፡
ወጣት፡ወጣቱን፡ለመቀበል፡ — አዘጋጅታለች፡ቤቷን፡ፊደል።

የግእዝን፡ጣዕም፡ብትቀምሱትማ፡ አቲዙም፡ነበር፡ሌላ፡ውሽማ፤
ለንግዴሁ፡ግን፡ውሽማ፡አታብዙ፡ ርሷን፡ዐቅፋችኹ፡ቀድሞ፡ሳቲዙ።

ብትጨምሩ፡ግን፡በርሷ፡ላይ፡ደግሞ፡ ዕዳው፡ገብስ፡ነው፡መች፡ዐረማሞ፡
በዚህስ፡ነገር፡ሐሜት፡ሳትፈሩ፡ — እንደ፡ያዕቆብ፡ብትጨማምሩ፡
ስንኳን፡ነቢያት፡እንዳዊት፡ — አይነቅፏችኹም፡ሐዋርያት።

## አሥረ ፡ ንጉሥ ፡ ጠቢብ ፡

### ኀላፍያትን ፡ የሚያዘክር ፡ መጻእያትን ፡ የሚያሳስብ ።

ዓሣ ፡ ጕርጓሬ ፡ ዘንዶ ፡ ሲያጠጣ ፡ — የሰው ፡ ፈላጊም ፡ የራሱን ፡ ሲያጣ ፡
ከኹለቱ ፡ ዘፍ ፡ ለወደቀው ፡ — አላገር ፡ ቋንቋ ፡ ማነው ፡ አንሺው ።

የሀገር ፡ ቋንቋም ፡ ያላማ ፡ ቀኝ ፡ — ኹሉን ፡ ሰብስቦ ፡ አንድ ፡ የሚያሰኝ ፡
ጋላና ፡ ዐማራ ፡ እስላም ፡ ሳይል ፡ — የፈረስ ፡ ስሙ ፡ አባ ፡ ጠቅል ፡
አባ ፡ ቀስቅስም ፡ የሚሉት ፡ አሉ ፡ — ስላነቃቃቸው ፡ ጠርቶ ፡ ፈደሉ ።

እኛም ፡ ተኝተን ፡ ሕልም ፡ እንዳናልም ፡ አባ ፡ ነጋ ፡ ነው ፡ የጊዜው ፡ ስም ፡
የፀሓይ ፡ መቅድም ፡ አጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ — የሚታይበት ፡ ላፍሪቃ ፡ ሕዝብ ፡
የጠቢያውም ፡ ልጅ ፡ የሴም ፡ ቡችላ ፡ — የሚከፍትበት ፡ ያይኖቹን ፡ ግላ ፡
አፍሪቃን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ባይኑ ፡ ማሚቶ ፡ እየቀመለ ፡ እንደ ፡ ድሪቶ ።
አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እኮ ፡ የትንቢት ፡ ቃል ፡ ሳይታወቅ ፡ ነው ፡ በጥለቅ ፡ የሚል ።

ቋንቆቻችንም ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ — ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚፋቱት ፡
ላይለያዩ ፡ ተለያይተው ፡ — ያሻማቱናል ፡ ኹለት ፡ መስለው ፡
ኩቶ ፡ እኛ ፡ አንችልም ፡ ልንለያቸው ፡ — እግዜር ፡ ነውና ፡ ያጣመራቸው ።
ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ከተለያዩ ፡ — ሕያው ፡ እንዳይኾን ፡ የሰው ፡ ብሕርዩ ፡
ያማርኛም ፡ ቃል ፡ የግእዝ ፡ ሥጋ ፡ — አለግእዝ ፡ ነፍስ ፡ ሬሳ ፡ ባልጋ ፡
ሬሳውን ፡ ቃል ፡ የሚሸከሙ ፡ — በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ሲፈታ ፡ ይስሙ ።

ሥረ ፡ ነገሩ ፡ ግእዝ ፡ ሳይጸድቅ ፡ — ፍሬ ፡ አያፈራም ፡ ዐማርኛ ፡ ዐጽቅ ።
ነገር ፡ ከሥሩ ፡ ውሃ ፡ ከጥሩ ፡ — የተባለውን ፡ እስኪ ፡ መርምሩ ፡
እንማናቸው ፡ ዘሩን ፡ ሳያውቁ ፡ — ፍሬውን ፡ በልተው ፡ የሚፀነቁ ፡
ዘሩንም ፡ ዐውቀው ፡ ሳይገላልጡ ፡ — ሾላ ፡ በድፍን ፡ የሚያላምጡ ፡
አለበትና ፡ ብዙ ፡ ቀኖኖች ፡ — ሆድ ፡ የሚያሳምም ፡ የሚያበሳጭ ፡
ቁስ ፡ ኹኖ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ እጠራው ፡ ነበር ፡ ስማቸውን ።

ዳቦ ፡ የሚልስ ፡ ካልገመጠው ፡ — መላሱ ፡ ብቻ ፡ ምን ፡ ሊያጠግበው ፡
አፍ ፡ አለገሮ ፡ ቢያዜም ፡ ቢያነብ ፡ — አይታነጽም ፡ ሸክላው ፡ ልብ ፡
መርጌታ ፡ ኹኖ ፡ አቡን ፡ ሲቃኝ ፡ — እንዲህ ፡ እንዳለ ፡ አምኛር ፡ ዘፋኝ ፡

የጠቢያው ፡ ሰው ፡ እንዲያው ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ውስጡን ፡ ለምን ፡
ውስጡን ፡ ለቁስ ፡ ለሚናገዝገዝ ፡ ቁሱም ፡ ግእዝ ፡
ስሙ ፡ ፋና ፡ ወይም ፡ መብራት ፡ የነፍስ ፡ አባት ።

እንዶድ ፡ ሳይዙ ፡ ወይም ፡ ሳሙና ፡ — አጥርቶ ፡ ማጠብ ፡ ዘበት ፡ ነውና ፡
አላሰዋስው ፡ አለጥፈት ፡ — ትምርት ፡ አይጠራም ፡ ምንም ፡ ቢያጥቡት ።

የትምርት ፡ ዕንቅርት ፡ አለመጣፍ ፡ — አለመስማትም ፡ ገሮ ፡ ደግፍ ፡
ዐይነት ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ዙሮ ፡ ለሚያይ ፡ ከበድ ፡ ሸክም ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ።

ያኖሩት ፡ ሰንቅርት ፡ ሰሙ ፡ አገልግል ፡ ቢከፍቱ ፡ ተልባ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ቅል ፡
ያለፈው ፡ ዐልኝል ፡ ለወደ ፡ ፊቱ ፡ — በትምርት ፡ ይራቅ ፡ ግብዝነቱ ።

ከፍሬቃ ፡ ወንዞች ፡ ወርቅና ፡ አልማዝ ፡ እንደሚያስገኘው ፡ እንዳባይ ፡ ወንዝ ፡
ተርፎን ፡ እንዲፈስ ፡ ትምርቱ ፡ ንግድ ፡ — በዚህ ፡ ሰዋስው ፡ ጥርጊያ ፡ መንገድ ፡
ይልቅ ፡ ኑ ፡ እንውጣ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፥ — ገበያችንም ፡ ኢትዮጵያ ።

መደብሮቿ ፡ የተዘጉቱ ፡ — ባሩቱ ፡ ማእዘን ፡ እንዲከፈቱ ፡
ልጆቿን ፡ በውቀት ፡ እያሳደገ ፡ — መንገዶቿንም ፡ እያስጠረገ ፡
እግዜር ፡ ያቆማት ፡ ከማኸል ፡ ቦታ ፡ — በውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ እንዳትፈታ ።

ያፍሪቃ ፡ ደንደስ ፡ ሻኛና ፡ ጫንቃ ፡ — ጦቢያው ፡ እንጂ ፡ ናት ፡ ምሥራቅ ፡ አፍሪቃ ፡
የሰማይ ፡ ምድር ፡ የምድር ፡ ሰማይ ፡ — የተከበበች ፡ በነጭ ፡ አባይ ።

ዐይኗም ፡ ሲመስል ፡ በገነት ፡ ዐይን ፡ ነጩ ፡ አባይ ፡ መደብ ፡ ጥቍሩ ፡ ብሌን ፡
ባስተያየትም ፡ ሲመረመሩ ፡ — ማየት ፡ አይችልም ፡ ነጩ ፡ አለጥቍሩ ።
ነጩ ፡ ሲፈትሽ ፡ ውስጠ ፡ ጥቍር ፡ — ጥቍሩም ፡ ሲፈትሽ ፡ ውስጠ ፡ ነጭ ፡ ዘር ፡
ሕብረ ፡ ሰማይ ፡ ነው ፡ ጥቍሩ ፡ አባይማ ፡ በቂጥኛም ፡ አፍ ፡ የማይታማ ።

ነጭና ፡ ጥቍር ፡ የዓለም ፡ ዐይን ፡ — ኹሉም ፡ ተገልጦ ፡ የሚከድን ፡
መከደኛውም ፡ ሞት ፡ ወገዝ ፡ ከንባይ ፡ ነው ፥ ያዳም ፡ ሌባ ፡ ጣት ፡ የሰፋችው ።

ዓዲ ፡ ቃለ ፡ ዐዋዲ ፡

መስቈረ ፡ ጥይዕት ፡ እዝን ፡ ወመክሥተ ፡ ክድንት ፡ ዐይን ።

የማናውቀውን ፡ ፊደል ፡ ሩዝ ፡ — ከሚሰዮን ፡ ቤት ፡ ስንጋበዝ ፡
በትምርት ፡ ወጭት ፡ በጥፈት ፡ ዳክ ፡ — በምላስ ፡ በብርዕ ፡ በቀለም ፡ መንከ ፡
የውጭ ፡ ቋንቋ ፡ ብንፈተፍት ፡ — ከምሳ ፡ በቀር ፡ የለም ፡ እራት ፡
ያጠግባል ፡ እንጂ ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ — ሥንቅ ፡ አይኾነንም ፡ ለሩቅ ፡ ዘመቻ ።

ለዘመቻውስ ፡ ሥንቅ ፡ የሚኾን ፡ — የዳቦ ፡ ቈሎ ፡ ግእዛችን ፡
በኑሮ ፡ ዘመን ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ — የማይነቅዝና ፡ የማይሻግት ፡
ዐማርኛውም ፡ የንብ ፡ እንጀራ ፡ — በላስቶች ፡ ቀፎ ፡ ቀድሞ ፡ ሲሠራ ፡
ካረብ ፡ ከሱርስት ፡ ከዕብራይስጥ ፡ — የተቀመመ ፡ እጅግ ፡ ጥፍጥ ።

ከውጭም ፡ ቋንቋ ፡ የሚገኝ ፡ ጥቅም ፡ ወደኛው ፡ ቋንቋ ፡ በመተርጐም ፥
ሊጥም ፡ እንዳይኾን ፡ ትርጓሜው ፡ ኹሉ ፡ ትምርቱን ፡ ማብሰል ፡ በየፊደሉ ፡
ቋንቋም ፡ ካልጠራ ፡ በሰዋስው ፡ — አነጋገሩ ፡ የለት ፡ ጕሽ ፡ ነው ።

ሰሙ ፡ ፕራቲክ ፡ የድምጫ ፡ ቋንቋ ፡ የከረፈ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ የድቋ ፡
ኀሮ ፡ ሲቀምሰው ፡ ከዋንጫው ፡ አፍ ፡ ያሰኛልና ፡ እንትፍ ፡ እንትፍ ።

በጥሩው ፡ መጠጥ ፡ በሀገር ፡ ፍቅር ፡ ራሴ ፡ ዘሮ ፡ ስቀባጥር ፡
ስላገር ፡ ቋንቋ ፡ ምንም ፡ ብተች ፡ አትፍረዱብኝ ፡ ያገር ፡ ዳኞች ።

ከብቶች ፡ ይልቅ ፡ በሽንኅ ፡ ካሉ ፡ — ወደ ፡ ልጆች ፡ ነው ፡ ነገሬ ፡ ኹሉ ፡
የቋንቋን ፡ ፀዋጅ ፡ ለልጅ ፡ መልፈፍ ፡ በደንጊያ ፡ ጽላት ፡ እንደ ፡ መጣፍ ፤
ገና ፡ የሚያድገው ፡ ጨቅላው ፡ ወጣቱ ፡ ይሻላልና ፡ ከባት ፡ ከናቱ ፤
ዠርሮው ፡ አእምሮው ፡ የላሸውማ ፡ — የነገሩትን ፡ መቼ ፡ ሊሰማ ።

የቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ማርና ፡ ኮሶ ፡ — በዓለም ፡ ቋንቋ ፡ ስሙ ፡ ተፋልሶ ፡
መራራው ፡ ጥዑም ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ — ማር ፡ የማይጥመው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አለ ።
ቢጥመውማ ፡ የማር ፡ ወለላ ፡ — አይጠጣም ፡ ነበር ፡ ኮሶ ፡ በንኩላ ፤
ኮሶውም ፡ አስፈስ ፡ እንዲያ ፡ ሲመር ፡ መላልሶ ፡ አስቀምጦ ፡ የማያሽር ፥
ተስፋውም ፡ ከንቱ ፡ የበጥባጭ ፡ ወሬ ፡ በዶሮ ፡ ፈንታ ፡ ቃሪያ ፡ በርበሬ ።
ትምርትና ፡ ዕውቀት ፡ ቶሎ ፡ እንዲሰፋ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ መንገዱ ፡ የባለተስፋ ።

ምክር ፡ ሠናይት ፡ ለኵሉ ፡ ዘይገብራ ፡ ወለዘያስተጋብእ ፡ ማእረራ ።

እምአርቶዶክሳዊ ፡ ከ ፡ ወ ፡ ክ ፡ ዘልሳነ ፡ ግእዝ ፡ ላእክ ።

## ፫ኛ ፡ ምዕራፍ ።

### ጸዋትወ ፡ ግስ ፥ የዘርና ፡ የነባር ፡ መቅደስ ፡ በለ፹፯ ፡ ክፍልና ፡ ራስ ፡ ከአ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ድረስ ።

### የቍራኛና ፡ የጥቅስ ፡ ምልክት ።

የብሉይ ፡ ጥቅስና ፡ የሐዲስ ፡ ምልክታቸው ፡ በማርኛው ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ መጀመሪያ ፡ ባ፩ኛውና ፡ በ፪ኛው ፡ ገጽ ፡ በክፍለ ፡ ስም ፡ ተወስኖና ፡ ተተርጒሞ ፡ እንደ ፡ ተጣፈው ፡ ነው ።

### የብሉይ ፡ የሐዲስ ፡ አዋልድና ፡ የሊቃውንት ፡ ጥቅስ ፡ ምልክት ።

| | | |
|---|---|---|
| አቡሻ ፡ | ማለት ፡ | አቡሻህር ። |
| አዋል ፡ | » | አዋልድ ። |
| አፈ ፡ | » | አፈ ፡ ወርቅ ። |
| ድ ፡ | » | ድርሳን ። |
| ተ ፡ | » | ተግሣጽ ። |
| አረ ፡ መን ፡ | » | አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ። |
| አር ፡ | » | አርጋኖን ። |
| ገድ ፡ አዳ ፡ | » | ገድለ ፡ አዳም ። |
| ገድ ፡ ዳን ፡ | » | ገድለ ፡ ዳንኤል ። |
| ገድ ፡ ኪሮ ፡ | » | ገድለ ፡ ኪሮስ ። |
| ገድ ፡ ላሊ ፡ | » | ገድለ ፡ ላሊበላ ። |
| ገድ ፡ ፊቅ ፡ | » | ገድለ ፡ ፊቅጦር ። |
| ገድ ፡ ሲኖ ፡ | » | ገድለ ፡ ሲኖዳ ። |
| ገድ ፡ ተክ ፡ | » | ገድለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ። |
| ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ | » | ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ሐሚድ ። |
| ግንዘ ፡ | » | መጽሐፈ ፡ ግንዘት ። |
| ዲድ ፡ | » | ዲድስቅልያ ። |
| ድር ፡ መድ ፡ | » | ድርሳነ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ። |
| ድር ፡ ሚካ ፡ | » | ድርሳነ ፡ ሚካኤል ። |
| ደራሲ ፡ | » | ድርሰት ፡ ደራሽ ። |
| ሃይ ፡ አበ ፡ | » | ሃይማኖተ ፡ አበው ። |
| ሄርማ ፡ | » | ተረፈ ፡ ጳውሎስ ። |
| ውዳ ፡ ማር ፡ | » | ውዳሴ ፡ ማርያም ። |
| ዜና ፡ እስ ፡ | » | ዜና ፡ እስክንድር ። |
| ሔኖ ፡ | » | ሔኖክ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ጥበ ፡ ጠቢ ፡ | ማለት ፡ | ጥበበ ፡ ጠቢባን ። |
| ጠቢ ፡ | 〃 | ጠቢት ። |
| ጥሬ ፡ ሰዋ ፡ | 〃 | ጥሬ ፡ ሰዋስው ። |
| ዮዲ ፡ | 〃 | ዮዲት ። |
| ዮሐ ፡ መደ ፡ | 〃 | ዮሐንስ ፡ መደብር ። |
| ያዕ ፡ ዘእል ፡ | 〃 | ያዕቆብ ፡ ዘእልበረዳኢ ። |
| ዮሴፍ ፡ | 〃 | ዮሴፍ ፡ ወልደ ፡ ኮርዮን ። |
| ኪዳ ፡ | 〃 | መጽሐፈ ፡ ኪዳን ። |
| ኩፋ ፡ | 〃 | ኩፋሌ ። |
| መዋሥ ፡ | 〃 | መዋሥዕት ። |
| መ ፡ ፈ ፡ | 〃 | መጽሐፈ ፡ ፈውስ ። |
| መጽ ፡ ብሕ ፡ | 〃 | መጽሐፈ ፡ ብሕርይ ። |
| መጽ ፡ ባሮ ፡ | 〃 | መጽሐፈ ፡ ባሮክ ። |
| መጽ ፡ ኑዛ ፡ | 〃 | መጽሐፈ ፡ ኑዛዜ ። |
| መጽ ፡ ምስ ፡ | 〃 | መጽሐፈ ፡ ምስጢር ። |
| መጽ ፡ ቄድ ፡ | 〃 | መጽሐፈ ፡ ቄድር ። |
| መቃ ፡ | 〃 | መቃብያን ። |
| መቅ ፡ ወን ፡ | 〃 | መቅድመ ፡ ወንጌል ። |
| ማር ፡ ይሥ ፡ | 〃 | ማር ፡ ይሥሐቅ ። |
| ሥር ፡ ጳኵ ፡ | 〃 | ሥርዐተ ፡ ጳኵሚስ ። |
| ዕር ፡ ኢሳ ፡ | 〃 | ዕርገተ ፡ ኢሳይያስ ። |
| ፈ ፡ መ ፡ | 〃 | ፈውስ ፡ መንፈሳዊ ። |
| ፊልክ ፡ | 〃 | ፊልክስዩስ ። |
| ፈላስ ፡ | 〃 | ፈላስፋ ። |
| ፍ ፡ ነ ፡ | 〃 | ፍትሐ ፡ ነገሥት ። |
| ቅዳ ፡ | 〃 | ቅዳሴ ። |
| ቀሌ ፡ | 〃 | ቀሌምንጦስ ። |
| ቄር ፡ | 〃 | ቄርሎስ ። |
| እስት ፡ | 〃 | እስትጉቡእ ። |
| ጳላ ፡ | 〃 | ጳላድዮስ ። |
| ራእ ፡ ኤል ፡ | 〃 | ራእየ ፡ ኤልያስ ። |
| ሲኖዶ ፡ | 〃 | ሲኖዶስ ። |
| ስንክ ፡ | 〃 | ስንክሳር ። |
| ሱቱ ፡ ዕዝ ፡ | 〃 | ሱቱኤል ፡ ዕዝራ ። |
| ተረ ፡ ኤር ፡ | 〃 | ተረፈ ፡ ኤርምያስ ። |
| ተረ ፡ ቄር ፡ | 〃 | ተረፈ ፡ ቄርሎስ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ቃሬ ፡ አነሡ ፡ | ማለት ፡ | ቃሬከ ፡ አነሡስም ። |
| ቃሬ ፡ ነገ ፡ | | ቃሬከ ፡ ነገሥት ። |
| ትር ፡ ወን ፡ | | ትርጓሜ ፡ ወንጌል ። |

ማእዝን ፡ ከሴምና ፡ ከያፌት ፡ ቋንቋ ፡ ለመግጠምና ፡ ለማመሣፈር ፡
በቀርን ፡ እየተከበበ ፡ የሚጣፍ ፡ ምልክት ።

| | | |
|---|---|---|
| ሶብ ፡ | ማለት ፡ | ሶብሬደስጥ ። |
| ሱር ፡ | | ሱርስት ፡ የአራም ፡ ቋንቋ ። |
| ዐረ ፡ | | ዐረብ ። |
| ጽር ፡ | | ጽርእ ፥ ዮናኒ ። |
| ሮማይ ፡ | | ሮማይስጥ ፥ ላቲን ። |

የሰዋስው ፡ ጥቅስ ፡ ምልክት ።

| | | |
|---|---|---|
| ዕር ፡ | ማለት ፡ | ዕርከን ። |
| ቍ ፡ | | ቍጥር ። |
| እግዚ ፡ | | እግዚአብሔር ። |

የሚጠብቅና ፡ የሚላላ ፡ ምልክቱ ፥ ጥ ፡ ላ ፡ ናቸው ።

(ጥ) አምር ፡ አመረ ። ሰብሐ ፡ ሰብሐ ። ጠፈር ፡ ጠፈረ ፡ ይጠፍር ።
(ላ) አሚር ፡ አመረ ፡ የአምር ፡ ይእምር ። ሠቢሕ ፡ ሠብሐ ፡ ይሠብሕ ፡ ይሥባሕ ።

የብዙ ፡ ምልክት ፡ ብ ፡ ነው ።

ደብር ፡ (ብ ፡ አድባር ፡ ራት) ፡ ተራራ ። ያንዱ ፡ ፍች ፡ ውጥን ፡ ጨረሽ ፡ ኹኖ ፡ የብዙውን ፡ ተራሮች ፡ እንዲያሰኝ ፡ አስተውል ። ፪ኛም ፡ በማስ ፡ አርእስት ፡ ቀቲል ፡ ብሎ ፡ ቀቲሎት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ቀቲን ፡ ጕርዶ ፡ ሎት ፡ ይላልና ፡ በማልስና ፡ በሳድስ ፡ ቅጽልም ፡ ቀታሊ ፡ ብሎ ፡ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፥ ቀተልት) ፡ ቅቱል ፡ ብሎ ፡ (ላን ፡ ላት ፡ ትልት) ፡ እያለ ፡ በንዱ ፡ የኹሉ ፡ የሚታወቅለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ አንዳንዱን ፡ ብቻ ፡ ይፈታል ። ንባቡም ፡ ፍችውም ፡ በክፈል ፡ በውጥን ፡ መጣፉ ፡ ነገር ፡ ለማሳጠር ፡ ነውና ፥ እንዳትሳሳት ፡ ተጠንቀቅ ።

የፊደላትና ፡ የቃላት ፡ ሞክሼ ፡ በያንዳንዱ ፡ መሥመር ፡ ተከታትሎ ፡ መሬና ፡ ተመሬ ፡ እየ ኾነ ፥ መሬው ፡ አለግንዘቡ ፡ ተመሬው ፡ በየግንዘቡ ፡ ቀጥሮ ፡ ልዩ ፡ ልዩነቱን ፡ ያስረዳል ።

# አ

**አ ፡ (ፊደልና ፡ አኃዝ)** ፤ አንደኛ ፡ መጀመሪያ ፡ ፊደል ፡ የፊደል ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ በዠርር ፡ ቀዳማይ ፡ ባለም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ ይልቁንም ፡ በጥንታዊው ፡ ተራ ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ። በሰው ፡ አልፍ ፡ ቍጥሩ ፡ አንድ ፡ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ አ ፡ አሐድ ፡ አሐዱ ፡ ይባላል ። ምስጢሩ ፡ አሐድነትና ፡ የአሐድን ፡ ፍጥረት ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ፈጣሪን ፡ ያሳያል ። (ዘፍ፡፩ ፡ ፩—፳ ። ራእ ፡ ፳፩ ፡ ፮) ። ዳግመኛም ፡ በዕብራይስጥ ፡ ዐዋ፪ ፡ አለንቀጣ ፡ አሐዱ ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ ያው ፡ አንዱ ፡ አሌፍ ፡ አ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነቍጣ ፡ ሲኾንበት ፡ በነቍጣው ፡ ምክንያት ፡ አልፍ ፡ እንዲባል ፡ በግእዝም ፡ ሥርዐት ፡ አ ፡ አልፍ ፡ ይባላል ፡ አልፍ ፡ ያሰኘውም ፡ የራሱ ፡ ነቍጣ ፡ ነው ፡ አሰፈን ፡ ተመልከት ።

**አ** ፤ የማብዛት ፡ ልማድ ፡ አብዢ ፡ ፍችው ፡ ዎች ። **ደብር ፡ አድባር ÷ ወግር ፡ አውግር ÷ ፈለግ ፡ አፍላግ** ፤ ተራሮች ፡ ኰረብቶች ፡ ወንዞች ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ት ፡ ምእላድ ፡ እየኾነለት ፡ ከት ፡ ጋራ ፡ ይበዛል ፡ **ጥብ ፡ አጥባት ÷ ነቅዕ ፡ አንቅዕት ÷ ባሕር ፡ አብሕርት** ። ዳግመኛም ፡ በአ ፡ ብቻ ፡ የሚበዛ ፡ ቃል ፡ ት ፡ ሲጨመርበት ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ይኾናል ፤ **አድባር ፡ ራት ÷ አውግር ፡ ራት ÷ አፍላግ ፡ ጋት** ። በአና ፡ በት ፡ የሚበዛም ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ስለኾነ ፡ ኹለተኛ ፡ ት ፡ ይፈልጋል ፤ **ነቅዕ ፡ ባሕር ፡ ርእስ** ፡ ብሎ ፡ **አንቅዕት ፡ አንቅዕታት ፤ አብሕርት ፡ አብሕርታት ፤ አርእስት ፡ አርእስታት** ። የተን ፡ አፈታት ፡ እይ ።

**አ** ፤ የማስደረግ ፡ ልማድ ፡ አስደራጊ ፡ ፍችው ፡ አስ ። **ቀተለ ፡ አቅተለ ፤ ክህለ ፡ አክህለ ፤ ገብረ ፡ አግበረ** ። ዳግመኛም ፡ **ቆመ ፡ ቦአ ፡ ወፅአ ፡ መጽአ** ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ በሐውልትና ፡ ባንጕል ፡ ግስ ፡ ላይ ፡ ሲጨመር ፡ የማድረግና ፡ የማስደረግ ፡ ልማድ ፡ እየኾነ ፡ እንዱን ፡ አንቀጽ ፡ በ፪ ፡ ጾታ ፡ ያስፈታል ። **አቀመ** ፤ አቆመ ፡ አስቆመ ። **አብአ** ፤ አገባ ፡ አስገባ ። **አውፅአ** ፤ አወጣ ፡ አሶጣ ። **አምጽአ** ፤ አመጣ ፡ አስመጣ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ አ ፡ ከወደቀበት ፡ ማናቸውም ፡ ግስ ፡ በ፪ ፡ ጾታ ፡ ይፈታል ፡ ብለው ፡ ያውጃሉና ፡ አእመረን ፡ ዐወቀ ፡ አሳወቀ ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ አሳወቀ ፡ እንጂ ፡ ዐወቀ ፡ አይሰኝም ፤ አመረን ፡ ተመልከት ። ሦስተኛም ፡ በክልኣይና ፡ በሣልሳይ ፡ ራሱን ፡ እየጐረደ ፡ የትንቢት ፡ መነሻ ፡ እምራውን ፡ ኹሉ ፡ ራብዕ ፡ ያደርጋል ። **አቅተለ ፡ ይቀትል ፡ ይቅትል ። አግበረ ፡ ይገብር ፡ ይግብር ። አእመረ ፡ ይአምር ፡ ይእምር** ። ቀዳማዩን ፡ አመረ ፡ አኰተ ፡ ዐረፈ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አእመረ ፡ አእኰተ ፡ አዕረፈ ፡ ብሎ ፡ ክልኣዩን ፡ ይማም ፡ የአምር ፡ የአኵት ፡ የዐርፍ ፡ ማለት ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ስሕተት ፡ ይባላል ፡ በነዚህ ፡ በሦስቱ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ማየት ፡ ነው ።

**አ** ፤ የትንቢት ፡ መነሻ ፡ የክልኣይ ፡ ሥር ፡ አነ ፡ ለሚል ፡ ብቻ ፡ ባንድ ፡ አካል ። ግእዙ ፡ ብቻ ፡ በሰ ፡ ተነገረ ፡ ሳይሉ ፡ አይቀርም ። **ሖርኩ ፡ አሐውር ÷ ፀረጉ ፡ አፀርግ ÷ ወረድኩ ፡ እወርድ** ። በማስደረግ ፡ ጊዜ ፡ ፪ኛ ፡ አ ፡ ስላለበት ፡ ራብዕ ፡ ይኾናል ። **አሖርኩ ፡ አሐውር ፡ አፀረጉ ፤ ኣፀርግ ፤ አውረድኩ ፡ ኣወርድ ። አእመርኩ ፡ ኣአምር** ።

**አ** ፤ የግስ ፡ ልማድ ፡ ጠባይና ፡ አካኼድ ፡ የሚለውጥ ። በ፫ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ ከዚያውም ፡ በቀተለ ፡ ቤት ፡ መነሻ ፡ መድረሻ ፡ ማእከል ፡ ሲኾን ፡ ሳድስ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ግእዝና ፡ ራብዕ ፡ ግእዝ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ሳድስ ፡ ያደርጋልና ፡ አደራረጉና ፡ አገባቡ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በርባ ፡ ቅምር ፡ ክፍል ፡ ተመልከት ፡ (ዕርዩ ፡ ቍ፲፰) ።

**አ ፡ (ንኡስ ፡ አገባብ)** ፤ እንደ ፡ ዕና ፡ እንደ ፡ ኤ ፡ እንደ ፡ መ ፡ ትራስ ፡ ኹና ፡ በመጨረሻ ፡ ቃል ፡ እየገባ ፡ ቃለ ፡ መልእክት ፡ አጋኖ ፡ አስተብቍዖ ፡ ተጋንዮ ፡ ይኾናል ፡ ምስጢሩም ፡ ቍልምጫና ፡ ክበሬታ ፡ ነው ። አፈታቱንና ፡ ምስክሩን ፡ በንኡስ ፡ አገባብ ፡ ተመልከት ፡ (ዕርኘ ፡ ቍ፺፱) ።

**ኡ** ፤ ኡኡ ፡ (በማርኛ) ፡ ኡኡታ ፡ ኦ ፡ ኦኦ ።

**ኢ** ፤ አሉታ ፡ ነባር ፡ አንቀጽና ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ ሲኾን ፡ ፍችው ፡ እንደ ፡ አኮና ፡ እንደ ፡ ሐሰ ፡ እንደ ፡ አልቦ ፡ ነው ፡ (ዕርፕ፩ ፡ ቍ፺፰) ። ንኡስ ፡ አገባብ ፡ ሲኾን ፡ አል ፡ አ ፡ እንዳ ፡ ላ ፡ ሳ ፡ ይል ፡ የማ ፡ ይኾናል ። ኢጸሐፈ ፡ አል ፡ ኢይጽሕፍ ፡ አ ፡ ኢይጽሕፍ ፡ እንዳ ፡ ላ ፡ ሳ ። ኢጽሒፎ ፡ ሳ ፡ ኢጸሐፈ ፡ ያልጣፈ ፡ የማይጥፍ ። ትራስ ፡ እየኾንም ፡ በኀሩ ፡ ሲገባ ፡ ኤ ፡ ይኾናል ፤ **እፎኢ** ፤ ምስጢሩም ፡ ያሉታ ፡ አንክሮ ፡ ነው ። ደቂቅ ፡ አገባብም ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ እንበለ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ያለ ፡ ይኾናል ። ኢ ፡ ወኢ ፡ እያለ ፡ ሲጣፈርና ፡ ሲደጋገም ፡ ኹና ፡ ሲኾን ፡ ያሰኛል ። ፍችው ፡ አለ ፡ ሲኾን ፡ ከይቤ ፡ በማርኛ ፡ ይስማማል ፡ (ግጥም) ፡ ትሰሙ ፡ እንዲኾን ፡ የወንጌል ፡ ቃል ፡ አለ—መስጠት ፡ ያጸድቃል ። ባማርኛም ፡ ኢ ፡ እዬ ፡ እዬ ፡ ተብሎ ፡ ሲነገር ፡ ቃለ ፡ አኅስሮ ፡ ሐዘንና ፡ አንክሮ ፡ ይኾናል ። ምስጢሩ ፡ አሉታና ፡ አፍራሽ ፡ ሲኾን ፡ ያማርኛው ፡ ስልት ፡ በዝቷልና ፡ ኹሉንም ፡ በንኡስ ፡ አገባብ ፡ ተመልከት ፡ (ዕርኛ ፡ ቍ፶) ።

**አ ፡ (የቀጽል ፡ በር ፡ ከፋች)** ፤ በዝርዝር ፡ ጊዜ ፡ ቅጽሎቹም ፡ ዘ ፡ እንተ ፡ እለ ፡ ናቸው ። **ዚአሁ** ፡

እንቲኣሁ፡ እሊኣሁ፤ ሃ፡ ሆሙ፡ ሆን፤ ዚኣከ፡ እንቲ ኣከ፡ እሊኣከ፡ ኪ፡ ክሙ፡ ክን፡ የ፡ ነ።

**ኤ፤—ስመ፡ ፊደል፤—ዐ፡ ዔ።**

**እ**፤ አልፍ፡ ፲፡ ሺሕ፡ መቶ፡ ጊዜ፡ መቶ።

**አ፤—ስመ፡ አምላክ፤—ዖ፡ አልፋ፡ ወዖ።**

**አ**፤ **(ንኡስ፡ አገባብ)**፤ ሆይ፡ ወዮ፡ ወየው፤ ምን፤ ይብላኝ። በምስጢር፡ ቃለ፡ ጽዋዔ፡ ወአንክሮ፡ ቃለ፡ አክብሮ፡ ወአፍቅሮ፤ ቃለ፡ ብካይ፡ ወሰቈቃው፤ ቃለ፡ አኅስሮ፡ ወአፍርሆ፤ ቃለ፡ አራኅርኆ፡ ይኾናል። ፍችውንና፡ ምስክሩን፡ በቦታው፡ ተመልከት፡ (ዕርጅ፡ ቍ፺፱)።

**አአ**፤ **(ጽር፡ ዖዖ። ዕብ፡ ሆይ፡ ሆይ። ዐረ፡ ያያ)**፤ የጩኸት፡ የቡታ፡ የሬታ፡ ቃል፤ በቁሙ፡ ወይም፡ ኡኡ፡ ዎዎ፡ ወዮ፡ ወዮ፤ ሆይ፡ ሆይ። **አአ፡ ጕዩ፡ እምብሔረ፡ ሰሜን፡** (ዘካ፪፡ ፮)። አንዳንድ፡ መጣፍ፡ ግን፡ ከጣፊ፡ ስሕተት፡ የተነሣ፡ አአ፤ ኦአ፡ ወይም፡ ኹሉን፡ ትቶ፡ ጕዩ፡ ይላል። በኦአ፡ ፈንታ፡ አአ፡ ወይም፡ ኡኡ፡ ማለት፡ ስሕተት፤ ኹሉን፡ መተው፡ ግድ ፈት፡ ይባላል።

**አእይ**፤ **ዮት**፤ **(አአየ፡ የአኢ፡ የአኢ)**፤ ወደ፡ ወጡበት፡ መመለስ፤ መግባት። መስማት፤ እሀ፡ ማለት።

**አኢ**፤ **(አአይከ፡ ተአኢ፡ ተአኢ፡ አኢ)**፤ ትእዛዝ፡ አንቀጽ፤ ግባእ፡ ተመዮጥ። **አኢ፡ ወሑር፡ ብሔረ፡ ግብጽ፡** (ዘፀ፬፡ ፲፱)።

**አኢ**፤ ደዋጅ፡ ቃል፡ ስማ፡ ስማ። **በጽሐ፡ ጊዜ፡ ዘይትበሀል፡ አኢ፡ ዘውእቱ፡ ስማዕ፡ ብሂል፡** (ገድ፡ ተክ)።

**አኤል**፤ **(ዕብ፡ ኤል፡ ኤላው)**፤ የማኅብ፡ ዐምድ፤ ውስጡ፡ ግንብ፡ ኹኖ፡ አፍኣው፡ በሉሕ፡ የተ ጌጠ፡ በልግዘብ፡ ጠርብ፡ የተለበጠ። ኤልንና፡ ኤላውን፡ ተመልከት፤ ከዚህ፡ ጋራ፡ አንድ፡ ነው። **ወአኤል፡ ዘ ኖት፡** (ሕዝ፵፡ ፱)።

**አኤናዖን**፤ **(ጽር። ዕብ፡ ዖላም)**፤ ለዓ ለም፡ ዘለዓለም፡ (ዘዳ፴፫፡ ፲፳፡ ፳፯)።

**አእትሪከን**፤ **(ጽር፡ ቱሎግ)**፤ ገሀርው፡ ቃል፤ ድምፅ፡ ለብኣዊ፤ ፍሬ፡ ነገር፡ የሚሰማበት። **አአ ትሪከን፡ ውእቱ፡ ቃልነ፡ ዘይትከሰው፡ ውስተ፡ አ የር፡ ወእምኔሁ፡ ይትፌኖ፡ ንባብ፡** (ሃይ፡ አበ፡ ጎር፡ ገብ)።

(ጥ) **አብ**፤ **(ዕብራ)**፤ የዕብራውያን፡ ወር፡ ነሐሴ፡ የሚያገባያ፡ ፳፯። በ፱ኛው፡ ቀን፡ ያውም፡ በጨረቃ፡ ቍጥር፡ ፊተኛውና፡ ኋለኛው፡ ፪ቱ፡ መቅደሶች፡ በዘ መን፡ ሩቅ፡ ተከታትለው፡ የፈረሱበት፡ የተቃጠሉበት፡ ስለ፡ ኾነ፡ ዕለቱን፡ ፳፬፡ ሰዓት፡ ይጾሙታል፡ ወርኁ ንም፡ ወርኀ፡ ምግባሬ፡ ይሉታል። መጥበቁም፡ ስለ፡ ደጊመ፡ ቃል፡ ነውና፤ የደገመው፡ ምስጢር፡ ፪ቱን፡ ም ግባሬ፡ ያሳያል። **አብ፡ ዘውእቱ፡ ወርኀ፡ ኀምስ፡** (የሴፍ)።

**እባብ**፤ **(ዐማርኛ። ዐረ፡ ኡባብ፤ ማዕ በል)**፤ በቁሙ፡ ውሀኛ፡ ማዕበልኛ፡ የሚኼድ፡ የሚ ዘል፡ የሚወረወር፡ በልቡ፡ የሚሳብ፡ የሚጐተት፡ መር ዛም፡ ምላስ፡ መንታ፡ የሰይጣን፡ እርኣያ፡ የክፉ፡ ሰው፡ አምሳል፡ እንጂ፡ እባብ፡ ነው፡ እንዲሉ። (ተረት)፡ እ ባብ፡ ግደል፤ ከነበትሩ፡ ገደል።

**አቢብ**፤ **(ዐረብ። ቅብጥ፡ ኤጊፕ)**፤ የግ ብጻውያን፡ ወር፡ ሐምሌ፡ የመስከረም፡ ፲፩ኛ፡ (አቡሻ)።

**አቢብ**፤ **(ዕብራ)**፤ መፀው፤ ዘመነ፡ መፀው፡ ከክረምት፡ ቀጥሎ፡ የሚብት፤ የጽጌ፡ የፍሬ፡ የልም ላሜ፡ ወራት፤ በዓለ፡ ፋሲካ፡ የሚውልበት፡ ወርን፡ ትፍ ሥሕት፡ ወርን፡ ተሐድሶ። ይኸውም፡ ሚያዝያ፡ ነው፡ (ዘፀ፲፫፡ ፲፩)።

**አቢብ**፤ የሰው፡ ስም፤ በትንቢትና፡ በምሳሌ፡ ቡላ፡ ለሚባል፡ መንኰሴ፡ ከግዜር፡ የተሰጠ፤ ብዙኅ፡ ዐጽቅ፡ መፍርየ፡ ጽድቅ። **ተዘኪረከ፡ ክርስቶስ፡ ሥቃ ያተ፡ አቢብ፡ ገብርከ፡** (ነግሥ። ስንክ፡ ጥቅ፳፭)።

**አቢብ፤ ብት፤ (ጥ፡ አበ፡ የአብብ፡ ይእ ብብ)**፤ ማበብ፡ ማፍራት፤ የዕፀዋት። አበባ፡ መልበስ፡ መቀዳጀት፤ የመርዓዊና፡ የመርዓት። አባት፡ መኾን፡ ዘር፡ መስጠት፤ ወልደ፡ ማስለድ፤ የወንድ፡ የተባት።

(ጥላ) **አበ፤ አብ፤ (ብ፡ አበው)**፤ ወላጅ፡ አባት፡ ወንድ፡ ተባት፡ በዘር፡ በሩካቤ፡ የሚወልድና፡ የሚያስ ልድ። **አክብር፡ አባከ፡ ወእመከ፡ እስመ፡ እሙንቱ፡ ምክንያተ፡ ፍጥረትከ፡** (ዲድ)።

**አበ፤ አብ**፤ የግብርና፡ የክብር፡ የማዕርግ፡ ስም። አባት፡ መባል፡ በብዙ፡ ወገን፡ ስለ፡ ኾነ፤ ከግ ዜር፡ ዠምሮ፡ ያባትነት፡ ሥራ፡ ለሚሠሩ፡ ለመንፈሳ ውያን፡ አባቶች፤ ለቄስ፡ ለመንኰሴ፡ ለእኑሩግና፡ ለሊቃ ውንት፡ ለመምህራን፡ ኹሉ፡ ይነገራል። **አቡነ፡ ዘበሰ ማያት፡ ኢታብአነ፡ ውስተ፡ መንሱት፡፡ ትእዛዘ፡ አበ ዊነ፡ ሐዋርያት፡፡ ብፁዕ፡ አባ፡ አቡነ፡ ተክለ፡ ሃይማ ኖት**፤ የመሰለው፡ ኹሉ፡ (ቅዳ፡ ድጓ)።

**አባት**፤ **(ዕብ፡ አበት)**፤ አባቶች። አብ፡ ሲ በዛ፡ አበው፡ እንዳለኝ፡ አባም፡ ሲበዛ፡ በሚድ፡ አባት፡ ያሰኛል፡ በማርኛ፡ ግን፡ ውስጠ፡ ብዙነቱ፡ ሳይታወቅ፡ ፩፡ መስሎ፡ ፩፡ ተብሎ፡ ስላንድ፡ አካል፡ ብቻ፡ ይነገ ራል። አምላክ፡ የመለከ፡ ብዙኅ፡ ሲኾን፡ ስላንድ፡ እን ዲነገር፡ ይህም፡ እንደዚያ፡ ነው፤ መለከን፡ ተመልከት። (ሐተታ)፡ አብ፡ በጥሬነቱ፡ ዘርፍ፡ ይዞ፡ ሲቀጸል፡ ወ ይም፡ በቂ፡ ኹኖ፡ እንደ፡ ዘርፉ፡ ስልት፡ ሲፈታ፡ ምስ ጢሩ፡ ካባትነትና፡ ከጌትነት፡ ከባለቤትነት፡ አይወጣም።

አባም ፡ ባማርኛ ፡ ለሥጋዊ ፡ ሐርበኛ ፡ የፈረስ ፡ ስም ፡ ኹኖ ፡ ሲነገር ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። አባ ፡ ጠቅል ፡ ብሎ ፡ የጠቅል ፡ ጌታ ፡ ወይም ፡ ባለቤት ፡ ያሰኛል ። አብ ፡ የግ እዝ ፡ የዐረብ ፡ የዕብራይስጥ ፡ አባ ፡ የሱርስት ፡ ነው ። አቦ ፡ ገቢር ፡ ተገብሮ ፡ ይከታል ፡ ጉልት ፡ ቀለም ፡ ነው ፡ አብያ ፡ በገቢር ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ይባላል ። **አክብር ፡ አባከ ፡፡**

**አበ ፡ ጉንባሕ ፤ (ትግሪኛ ፡ አባ ፡ ጉን ባሕ)** ፤ ርኩም ፡ ጉንባሳ ፡ የፎጭኸት ፡ ባለቤት ። ጉንባ ሕን ፡ እይ ። **አበ ፡ ጉንባሕ ፡ ወክራ ፡ ሮዮን ፡** (ዘዳ ፲፬ ፡ ፲፰) ።

**አበ ፡ ደም** ፤ ደመኛ ፡ ባለደም ፡ ደም ፡ አፍ ሳሽ ፡ ወይም ፡ የሰፕች ፡ ወገን ፡ ደም ፡ ፈላጊ ። **አ ድኅ ንኒ ፡ እምአበ ፡ ደም ፡** (ደራሲ) ።

**አበ ፡ ላሕም** ፤ አቢ ፡ ላም ፡ ዘላን ፡ ባለብዙ ፡ ላም ፡ የላሞች ፡ ሐዛኒ ፡ መጋቢ ። ወይም ፡ የላም ፡ ጌታ ፡ የከብት ፡ በሽታ ።

**አቤሜሌክ ፤ (ዕብ ፡ አቢሜሌኽ)** ፤ አበ ፡ ንጉሥ ፡ የንጉሥ ፡ አባት ።

**አበ ፡ ምኔት** ፤ የገዳም ፡ አባት ፡ ባለገዳም ።

**አቡ ፡ ፈረጅ ፤ (ዐረብ)** ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ባለጸጋ ፡ ሀብታም ፡ ዕድላም ፡ በትገናኝ ፡ ፱ቱን ፡ ፈርጅ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ኩታ ፡ ገጥሞና ፡ አያይዞ ፡ የሚፈታ ፡ ዘርፉና ፡ ቅጽሉን ፡ የሚቋጭ ፡ ዐይኑ ፡ ምስጢሩን ፡ የሚ ገልጥ ፡ የሚያቀለጨልጭ ፡ ሊቅ ፡ መተርጕም ።

**አቢሳ ፤ (ዕብ ፡ አቢሻይ)** ፤ አበ ፡ ጋዳ ፡ በዓለ ፡ ጋዳ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ የሚሰጥ ፡ ወይም ፡ የሚቀበል ።

**አቡ ፡ ሻህር ፡ (ዐረብ)** ፤ ታላቅ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ የቍጥር ፡ መጽሐፍ ፡ ብዙ ፡ ወግ ፡ ታሪክ ፡ ያለበት ። አበ ፡ ወርኅ ፡ በዓለ ፡ ወርኅ ፡ የፎረቃ ፡ ቍጥር ፡ ባለቤት ። መ ጽሐፉ ፡ የጻሓፊውን ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ያዘ ፡ በጸሓፊው ፡ ስም ፡ ይጠራል ።

**አቤሴሎም ፤ (ዕብ ፡ አብ ፡ ሻሎም)** ፤ አበ ፡ ሰላም ፡ በዓለ ፡ ሰላም ፡ ሰላማዊ ።

**አበወ ፤ (ገቢር)** ፤ ቃለ ፡ መሐላ ፡ ምጥንታም ፡ ይኾናል ። አበውን ፡ አበውና ፡ መሐላ ፡ በአበው ፡ ምጥ ንታ ። ሌላውም ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ በመሐላ ፡ ጊዜ ፡ መድረ ሻው ፡ ማእገዝ ፡ ሲኾንለት ፡ ወይም ፡ የማእገዝ ፡ ወራሽ ፡ ሆ ፡ ሲገባበት ፡ እንደዚህ ፡ ይፈታል ። **ጊዮርጊስሀ ፡ ማር ያምሃ** ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

(ሳ) **አባዊ ፤ አበዋዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ ወገን ፡ ቅጽል ፡ ወይም ፡ መሻዘር ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ዘአበው ፡ እንተ ፡ አበው ። **በጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ተራኅርዎ ፡ ማህል ፡ አባዊት ፡ ላዕለ ፡ ልሕዙት ፡ አዳማዊት ፡** (ያዕ ፡ ዘእል ። ገድ ፡ አዳ) ። **ተዓድዎ ፡ አበዋዊት ፡** (ማር ፡ ይሥሐቅ) ።

(ጥ) **አባዊ** ፤ ስመ ፡ ፈለግ ፡ ነጭ ፡ አባይና ፡ ጥቍር ፡ አባይ ፡ ታላቅ ፡ ፈሳሽ ፡ ጕርፍ ፡ ማዕበል ፡ ማለት ፡ ነው ። ተለይቶ ፡ ግን ፡ ስጥቍሩ ፡ አባይ ፡ ብቻ ፡ ሲነገር ፡ አበ ፡ አፍላግ ፡ በዥረ ፡ አፍላግ ፡ ቀዳማይ ፡ ፈለግ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አብ ፡ ክርሱ ፡ ለሚገቡ ፡ ለታናናሾቹ ፤ በኵር ፡ ቀዳማይ ፡ ለወንድሞቹ ፡ ለሦስቱ ፡ ዐበይት ፡ አፍላጋት ። ኤፌሶንንና ፡ ግዮንን ፡ ተመልከት ። **ፈለገ ፡ አባዊ ፡** (ታሪ ፡ ነገ) ።

**አባዊ** ፤ የመነኮሴ ፡ ወገን ፡ ረድ ፡ አመካሬ ፡ ጥ ቍር ፡ ራስ ፡ ወንጌል ፡ በምናኔ ፡ መቀቅ ፡ ላላደጋት ፡ ለወ ለተ ፡ እንመንስ ፡ ለምንኵስና ፡ የታጨ ።

**አብና** ፤ አብነት ፡ አባትነት ፤ አባት ፡ መኾን ። **እስመ ፡ አብ ፡ ይሰመይ ፡ አበ ፡ በእንተ ፡ አብናሁ ፡፡ በአብ ፡ ቦቱ ፡ ስብሐተ ፡ አብና ፡** (ኢፌ ፡ ድ፪ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**አበውና** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ አባቶችነት ፡ ከዊን ፡ አበው ። **ሲይኩን ፡ ሎሙ ፡ ላዕሌሁ ፡ ማዕርገ ፡ አበ ውና ፡** (ፍ ፡ ን ፡ ፲ ፡ ፮) ።

**አቡን ፤ (ዐማርኛ)** ፤ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ አባት ፡ ጳጳስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ምእመናን ፡ አባታችን ፡ ብለው ፡ የሚጠሩትና ፡ የሚያከብሩት ፡ አበ ፡ አቦ ፡ የሚሉት ። (ተ ረት) ። ያቡን ፡ የፊጌ ፡ ከብት ፡ በየወገኑ ፡ ይከቶት ። **ከመ ፡ ዝ ፡ ይቤሉ ፡ አቡን ፡** (ታሪክ ፡ ጕንደር) ።

**አቡን** ፤ የድጓ ፡ መዝሙር ፡ ስንበት ፡ ነክ ፡ ያይ ደለ ፡ ሌጣ ፡ የዘወትር ። መሬውን ፡ ባምኛር ፡ ተመሪውን ፡ ባቡን ፡ ሲመስሉት ፡ መተባበሩ ፡ እንደ ፡ ጌሾና ፡ እንደ ፡ ብቅል ፡ ኹኖ ፡ ሺሕ ፡ ፷፻ ፡ ዓመት ፡ ሆድ ፡ ያባውን ፡ የግ ብጦችን ፡ ምስጢር ፡ ያወጣዋል ። (ታሪክኛ ፡ ግጥም) ፡ በከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ አንጻር ፡ ብርሃን ፡ አዜብ ፡ ከተ ባለው ፡ ከክልእ ፡ ሰላማ ፡ ዝምሮ ፡ በሰላማና ፡ በስላማ ፡ በ፪ቱ ፡ የቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ኋላ ፡ በማልስ ፡ ሰላማ ፡ በ ቀን ፡ ጨለማ ፡ ትጠፋለች ፡ ትለወጣለች ፡ ተብሎ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ሲነገር ፡ የመጣውን ፡ ነገርና ፡ ትንቢት ፡ ለመፈ ጸም ፡ ፫ኛው ፡ ሰላማ ፡ ደጃች ፡ ውቤንና ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ከዋጋ ፡ በኋላ ፡ ማልሳይነቱን ፡ ቀዳማይ ፡ ትንቢት ፡ እየ መሬው ፡ ከፋሲል ፡ ከተማ ፡ ጕንደር ፡ ገብቶ ፡ በቀንቤ ኖች ፡ ቋንቋ ፡ አፋን ፡ ባልፈታ ፡ አምኛር ፡ ባስተርጓሚ ፡ የመናፍቃንን ፡ ትፋትና ፡ ቅርሻት ፡ ማር ፡ እያስመሰለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ዐሎ ፡ ብሎ ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ ወልድ ፡ ቅብ ፡ በሰውነቱ ፡ አምላክ ፡ እያለ ፡ ለውጦ ፡ ገልብጦ ፡ ስለ ፡ ሰበከ ፡ ወደ ፡ ሺዋም ፡ የማዘት ፡ ወረቀት ፡ ስለ ፡ ላከ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የሺዎች ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ አለቃ ፡ ዐሥራት ፡ ከማህለ ፡ ሥላሴ ፡ ተልከው ፡ ፱፻ ፡ ሰው ፡ አስ ከትለው ፡ እስከ ፡ ጕንደር ፡ ወርደው ፡ በሃይማኖት ፡ ዜማ ፡ በሥግው ፡ ቃል ፡ ትምርት ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ በማለት ፡ ከጕንደር ፡ ሊቃው ንት ፡ ተስማምተው ፡ አቡኑንም ፡ ድርስ ፡ ቍርጥ ፡ ባለው ፡ አነጋገር ፡ በክርክር ፡ ቃኝተው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ መርተው ፡ ሲመለሱ ፡ ያነኮበሩ ፡ ደብተራ ፡ ጕልቱ ፡ የገጠመው ። እን ዳሥራት ፡ ማን ፡ አለ ፡ የሚያውቀው ፡ ድጓውን ፡ ትግሬ ፡ መርቶት ፡ መጣ ፡ ያን ፡ ረኸርም ፡ አቡን ።

(ጥ) **አበ ፤ (ጋልኛ)** ፤ አባቶ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ አንተ ። ትግሮች ፡ አባ ፡ ጋብር ፡ ዐማሮች ፡ አቡየ ፡ የሚሏቸውን ፡

ጻድቅና ፡ ቅዱስ ፡ ጋሎች ፡ አበ ፡ ይሏቸዋል ። (ግጥም ፤ አቦን ፡ የምትዘክር ፡ ያምሳ ፡ ዓመት ፡ ቤት ፡ በመክንንቷ ፡ እንደንኤልሳቤጥ ፡ ስላዘነች) ፤ ልጅ ፡ ታስጠኝ ፡ እንደኹ ፡ ልምጣ ፡ በመጋቢት ፤ የገዘቋላው ፡ አበ ፡ የምድረ ፡ ክብዱ ፡ አባት ። ኋላም ፡ ልጅ ፡ አማኝታ ፡ ደስፈቅ ፡ ስላላት ፤ ያቦን ፡ ገድል ፡ ዐገለሰው ፡ እሽርር ፡ ከሚሉ ፣ ከቶ ፡ እንማናቸው ፡ ወልደው ፡ ያሳዘሉ ።

**አበገደ ፤ (ዐረ ፡ አብጀድ) ፤** የፊደላት ፡ ሴም ፡ የሸፀቱ ፡ አሌፋት ፡ ስምና ፡ አርእስት ፡ የግእዝና ፡ የዕብራይስጥ ፡ የሱርስት ፡ የዐረብ ፡ ሶርና ፡ ምንጭ ፡ ዘሩን ፡ እንደዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ አካኼድ ፡ በአልፍ ፡ ኅምሮ ፡ በታው ፡ የሚጨርስ ። ፪ኛም ፡ የግእዙ ፡ ተራ ፡ ሳይፋለስ ፡ ከካዕብ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ያሉት ፡ ፯ ፡ ፯ቱ ፡ እየተዛነቁ ፡ ሲጣፉ ፡ ስሙ ፡ አቡጊዳ ፡ ይባላል ። (ተረት) ፤ አቡጊዳ ፡ የተማሬ ፡ ዕዳ ።

**አብድ ፤—በሪያ ፤—ዐብድ ።**

**አቢድ ፤ ዶት ፤ (አብደ ፡ የአብድ ፡ ይእበድ ። ዕብ ፡ አባድ) ፤** ማበድ ፤ መቈጣት ፤ አእምሮ ፡ ማጣት ፡ መወግሸት ፡ መንሣሣት ፤ አፈፍ ፡ አፈፍ ፡ ወፈፍ ፡ ወፈፍ ፡ ማለት ፡ መስንፍ ፤ ሞኝ ፡ አላዋቂ ፡ መኾን ፤ መጥፋት ፡ መበላሸት ፤ የልብ ፡ የናላ ። **ተአብደኑ ፡፡ ተአብድኑ ፤ ጳውሎስ ፡፡ ወአብደ ፡ መራዕይ ፡፡ የአብዱ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ነሰክሙ ፡ ኅቡረ ፡ ምስሌሁ ፤** በቁሙ ፡ (ግብ ፲፪ ፡ ፲፭ ። ፳፯ ፡ ፳፱ ። ማርቆ ፡ ፲፫ ። ዲድ ፡ ፵) ። **ወእንዘ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይጥብቡ ፡ አብዱ ፡፡ እስመ ፡ አብዱ ፡ ዋሎት ፡፡ ኢየአብድ ፡ እምኔክሙ ፤** ሰነፈ ፡ (ሮሜ ፩ ፡ ፳፪ ። ኤር ፲ ፡ ፳፩ ። ኢዮ ፲፫ ፡ ፪) ።

**አባዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤** የሚያብድ ፡ የሚሰንፍ ፤ ሰናፊ ፡ ሰንፍ ፤ አላዋቂ ። **ማርያም ፡ መጥብቢተ ፡ ዓለም ፡ አባዲ ፡፡ ልቡ ፡ አባዲ ፡** (ደራሲ ። ስንክ ፡ ታኅ ፯) ።

**አብድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ባድ) ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፡ እብድ ፤ ቍጡ ፤ ሰንፍ ፡ ሞኝ ፡ አላዋቂ ። **እመኒ ፡ በምክንያተ ፡ ጋኔን ፡ ዘያጌብሮ ፡ ዝንቱ ፡ አብድ ፡ ውእቱ ፡፡ አብድ ፡ ከልብ ፡ ዘነሰኮ ፡፡ ከመ ፡ አብድ ፡ ሐራውያ ፡፡ አብዳነ ፡ አጥብብ ፡፡ ኀምስ ፡ አብዳት ፡ ወኀምስ ፡ ጠባባት ፡** (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፪ ። መ ፡ ፈ ። ስንክ ፡ ኅሐ ፳፫ ። ኪዳ ። ማቴ ፳፭ ፡ ፪) ።

**እቡድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ብድ) ፤** ያበደ ፡ የሰከረ ፡ የወገሸ ፤ እብድ ፡ ቍጡ ፡ ብስጩ ፡ ብጢኺ ፤ ደረቅ ። **ከልብ ፡ እቡድ ፡፡ ኮነ ፡ እቡደ ፡ ከመ ፡ ሐራውያ ፤ እቡድ ፡ ወእሱር ፡ በሰናስል ፡፡ ምገዳተ ፡ ባሕር ፡ እቡዳት ፡** (የሚጮኹ ፡ የሚቆሙ) ። **ወለተ ፡ እብድ ፡፡ ብእሲት ፡ እብድ ፡** (ዲድ ፡ ፮ ። ገድ ፡ ተክ ። ይሁ ፡ ፲፫ ። ሚራ ፳፪ ፡ ፫ ። ምሳ ፱ ፡ ፲፫) ። በአብድ ፡ ፈንታ ፡ እቡድ ፡ ይባላል ፡ አያስኝም ። **እምንጉሥ ፡ እቡድ ፡ ይኄይስ ፡ ገብር ፡ ጠቢብ ፡** (አዋል) ። ጠባቢና ፡ ጠቢብ ፡ ፩ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አባዲና ፡ እብድም ፡ ፩ ፡ ናቸው ።

**እበድ ፤ (ዳት) ፤** ማበድ ፡ እብደት ፡ እብድነት ፤ ቍጣ ፤ ስንፍና ፡ ድንቍርና ፤ ሞኝነት ፡ አለመውቀት ፡ አላዋቂነት ፤ ልጅነት ፡ ጅልነት ። **እበድከ ፡ አ.ደንገፀኒ ፡፡ እበድስ ፡ አልብየ ፡፡ ዝንቱ ፡ አሚን ፡ እበድ ፡ ውእቱ ፤ እበደ ፡ ደቂቅ ፡፡ በመዋዕለ ፡ እበድ ፡፡ ፈድፈደት ፡ እበደሙ ፡** (ሚራ ፵፭ ፡ ፲፭ ። ግብ ፳፯ ፡ ፳፱ ። ቄር ፡ እስት ። አቡሻ ፡ ፪ ። ፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፱) ።

**አእበደ ፤** አሳበደ ፡ እብድ ፡ አደረገ ። አሰነፈ ፡ አሞኘ ፡ አታለለ ፡ ሸነገለ ፤ ናቀ ፡ አቃለለ ። **ለምንት ፡ ታእብድ ፡ ሰብእ ፡ እ ፡ ሰይጣን ፡፡ ያአብድዎሙ ፡ አጋንንት ፡** በቁሙ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ኩፋ ፡ ፲) ። **ኢታእብደኒ ፡፡ አኮኑ ፡ አእበዳ ፡ እግዚ ፡ ለጥበበ ፡ ዝ ፡ ዓለም ፡፡ አእብዳ ፡ ለነፍስከ ፡** (መቢ ፲ ፡ ፯ ። ፩ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳ ። ማር ፡ ይሖ ፪ ፡ ፲፩) ። በአእበደ ፡ ፈንታ ፡ አስተእበደ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ አስተአበደ ፡ ይላል ። **ትክልኑ ፡ ታስተአብዶ ፡ ለእግዚ ፡፡ አልቦ ፡ ዘያስተአብዳ ፡ ለውርዙትከ ፡፡ ኢያስተአብዱ ፡ ወኢያስተአክዩ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚ ፡** (ሮሜ ፪ ፡ ፬ ። ፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ። ቀሌ) ።

**አእባዲ ፤ ማእበዲ ፤ መስተአብድ ፤** የሚያሳብድ ፤ የሚያሰንፍ ፤ አስናፊ ፤ አጥፊ ። **ቀታሌ ፡ ሰብእ ፡ ማእበዲ ፡** (ኪዳ ፡ ፩) ።

**አስተአበደ ፤ (አደራራጊ) ፤** አሳነፈ ፡ አሰናነፈ ፤ አቋጣ ፡ አቈጣጣ ፤ አናናቀ ።

**መስተአብድ ፤ (ድት ፡ ዳን ፡ ዳት) ፤** ሰንፎ ፡ የሚያሰንፍ ፤ የሚያሳንፍ ፡ አሳናፊ ፤ ቀዛፍ ፤ ፈዘኛ ፡ ሕጹጸ ፡ አእምሮ ። **መስተአብዳን ፡ ለአስተአብዶ ፡፡ ዕይው ፡ መስተአብዳን ፡** (፪ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፫ ። ዕሮ ፫ ፡ ፬) ።

**አበድቢድ ፤ (ድት ፡ ዳን ፡ ዳት) ፤** እብድ ፡ ሞኝ ፤ ሰንፍ ፡ አላዋቂ ፤ ዕውቀቱ ፡ ትምርቱ ፡ ያጠረ ፡ ወደ ፡ ስንፍና ፡ የሚያደላ ፤ ጥበብና ፡ ምስጢር ፡ የማይገባው ፡ የማይሰማማው ።

—፤ ከሰንፍ ፡ ሰው ፡ አፍ ፡ የሚወጣ ፡ ተርታ ፡ ነገር ፡ ዐልጫ ፡ ቃል ፡ ጣዕምና ፡ ምስጢር ፡ የሌለው ። **ወበአበድቢዳት ፡ ቃላት ፡ ይትቃሐዉ ፡** (ቄር ፡ ጸላ ፩) ። መምህራን ፡ ግን ፡ የበድብደ ፡ ዘር ፡ አድርገው ፡ ፍችውን ፡ የሚያገጣ ፡ ይሉታል ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**አብዶን ፤ (ዕብ ፡ አባዶን) ፤** ፍጹም ፡ ጥፋት ፡ መፍረስ ፡ መደምሰስ ፡ ባዶ ፡ ባድማ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መኾን ፡ ሲኦል ፡ መቃብር ። **ወስሙ ፡ በዕብራይስጥ ፡ አብዶን ፡** (ራእ ፱ ፡ ፲፩) ። ባለብሉዮች ፡ በኤርምያስ ፡ (ም ፳ ፡ ፯) ። ሄሮድያኖስን ፡ ሽመላ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያፈ ፡ ፈንክስ ፡ ብለው ፡ ሲተርኩ ፡ አብዱ ፡ የዲን ፡ ጭቃ ፡ የሚሉት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**አብደረ ፤—አስቀደመ ፤—በዳር ፡ በደረ ።**

**አብደሬናን ፡ ቱቂኢም ፤ (ጽር ፡ አቤዲሬን ፡ አቱኪዩም) ፤** ቃሉ ፡ የዕብራይስጥ ፡ ነው ፡ ዕብ

ፈ.ይሰሙ ፡ ወሀ.ይባሪም ፡ አቲቂም ፡ ያለውን ፡ ጽርኢ ፡ እን ዳለ ፡ በጥሬው ፡ ወስይታል ። ወእሉ ፡ ዜናት ፡ ቀደምት ፤ ነገሬት ፡ ቀደምት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አንቲካ ፡ ወሬ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ (፩ዜና ፡ ፬ ፡ ፳፪) ። ዜናት ፡ ያላቸውም ፡ በኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፡ ይገኛሉ ፡ (ምዕ፳ ፡ ፩--፱) ።

**አበው ፤—የአብ፡ ብዝ፡ ፡ አባቶች ፤—አብ፡ አባ ።**

**አብሐ ፤ —አሠለጠነ ፤ —በዊሕ ፡ በሐ ።**

**አበጠ ፤ —ሳበ ፡ ጐተተ ፤ —ዐበጠ ።**

**አብጥሊስ ፤(ሳት ። ዐረ ፡ እተጥላሳት)** ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ሦስተኛው ፡ የሐዋርያት ፡ ሲኖዶስ ። ፍችው ፡ ቀኖና ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ተጥላስን ፡ እይ ። ግጽው ፤ ወሥርዐት ፤ ወአብጥሊስ ። ረስጠጅ ፤ ዘውእቱ ፤ ቀሌምንጦስ ፤ ሣልስ ። ክመ ፤ ዝ ፤ መሀሩነ ፤ ሐዋርያት ፤ በአብጥሊሰሙ ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ። ቅዳ) ።

**አብይ ፤ዮት ፤(አበየ፡ የአቢ ፡ ይእበይ ። ዐረ ፡ አበይ)** ፤ እንቢ ፡ ማለት ፡ አበያ ፡ እንቢተኛ ፡ መኾን ፡ መጓደድ ፡ የሰጡትንና ፡ ያዘዙትን ፡ የለመኑትን ፡ አለመቀበል ፡ አለመስማት ፤ አለማድረግ ፤ ዕሺ ፡ በጎ ፡ ይኹን ፡ አለማለት ። እንብየን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ፤ ጎ ፡ ስሯጽ ፡ ኹኖ ፡ ስለ ፡ ገባበት ፡ ወደዚያ ፡ ኼዷል ። ተአብዩ ፤ ትእዛዝየ ፤ ሰሚዐ ፤ ወሕግየ ። አበየት ፤ በሚዖቱ ። አበዩ ፤ ጸሎመ ፤ ትእዛዘ ፤ ንጉሥ ። ኢየአቢ ፤ ስእለተከ ። አበየ ፤ ዝናም ፤ ተውህቦ ፤ ሰምድር ። ኢይእበይ ፤ ባዕል ፤ ከመ ፤ ኢይጠመቅ ፤ ምስለ ፤ ነዳይ ። እመ ፤ ጸውዐከ ፤ ኢትእበዮ ፤ (ዘፀ፲፮ ፡ ፳፰ ። አስቴ፩ ፡ ፲፪ ። ዮዲ፩ ፡ ፲፩ ። ክፋ ፡ ፵፭ ። ፶፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፫ ። ሢራ ፡ ፲፫ ፡ ፱) ።

**አባዩ ፤(ዩት ፡ ይያን ፡ ያት)** ፤ እንቢ ፡ ባይ ፡ እንቢተኛ ፤ ተጓዳጅ ፤ አበያ ።

**እበይ ፤(ያት)** ፤ እንቢታ ፡ እንቢተኝነት ።

**አእበየ** ፤ እንቢ ፡ አሰኘ ፡ እንቢታ ፡ አስተማረ ፡ እንቢ ፡ በል ፡ አለ ።

**ተአብየ** ፤ እንቢ ፡ ተባለ ፡ ተጠላ ፡ ተሰለቸ ፡ ተጠገበ ፡ ፍቅሩ ፤ ለእግዚእነ ፤ ኢይትአበይ ፤ (አዋል) ።

**ተአበየ** ፤ እንቢ ፡ ተባባለ ፡ በፈቃድ ፡ በግብር ፡ ተለያየ ፡ ተጣላ ፡ ተፈራቀቀ ፡ አንድነት ፡ ስምምነት ፡ ዐጣ ። እስመ ፡ ሥጋኒ ፡ ይፈቱ ፡ ዘኢይፈቱ ፡ መንፈስ ፡ ወመንፈስኒ ፡ ይፈቱ ፡ ዘኢይፈቱ ፡ ሥጋ ፡ ወይትኣበዩ ፤ በበይናቲሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢትግበሩ ፡ ዘትፈቅዱ ፡ (ገላ፭ ፡ ፲፯) ።

**አብየ ፤—ወፈረ ፡ ላቀ ፤—ዐብየ ።**

**አቢል ፤ሎት ፤(አበለ ፡ የአብል ፡ ይእብል ። ዕብ ፡ አቤር ፤ አጸና)** ፤ መጽናት ፡ መበርታት ፡ ማደግ ፡ እየፈለመሩ ፡ መኼድ ።

**አባል ፤(ላት ። ዕብ ፡ ኤቤር ፤ ኤባር ፤ ብ ፡ ኤብሪም)** ፤ ብልት ፡ የገላ ፡ ክፍል ፤ በየስሙና ፡ በያንጻሩ ፡ እኩያ ፡ አምሳያ ፡ ያለው ፤ ከራስ ፡ ጠጕር ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍር ፡ በየክፍሉና ፡ በያንዳንዱ ፡ በየማውዱ ፡ ያለ ፡ ሥጋ ፤ ሕዋስ ፡ አካል ፡ ገላ ። አከለንና ፡ ሌለየን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ከመ ፤ አባል ፤ ውስተ ፤ መቅፀት ። መተሮ ፤ ለበግዕ ፤ በበ ፤ አባላቲሁ ። እንዘ ፤ ንስቲት ፤ አባል ፤ አንቲ ። ወተዐጽፈ ፤ አባለ ፡ መንፈስ ፤ ረቂቅ ። ለእመ ፤ ሐመ ፤ አሐዱ ፤ አባል ፤ የሐምም ፤ ምስሌሁ ፤ ኵሉ ፤ ነፍስትን ። ዘፈወሰ ፤ አባለ ፤ ሙቱነ ። አባለ ፤ ዘርዕ ። ኢይክሉን ፤ ዕሩቀ ፤ አባል ፤ ቅድመ ፤ መኑሂ ። ብእሲት ፤ አባሉ ፤ ለብእሲ ፤ (ሚክ፫ ፡ ፫ ። ዘሌ፰ ፡ ፳ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ዮሐ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፳፮ ። ዲድ ፡ ፳፭ ። ፌልክ ፡ ፮ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፪ ፡ ፫ ። ዲድ ፡ ፲) ። አባሎ ፡ የሚሉት ፡ ብርቱ ፡ የቈላ ፡ ዕንጨት ፡ ስሙ ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

(ጥ) **አበለ ፤ — አሰኘ ፤—ብሀለ ፡ አብሀለ ።**

**አበለ ፤ — በቍሙ ፡ ዐማርኛ ፤ — ሐቢል ፡ ሐብለ ።**

**አቤል ፤ (ዕብ ፡ ሀቤል)** ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ወልደ ፡ አዳም ፡ (ዘፍ፬ ፡ ፪) ። አቤል ፡ መስክ ፡ ፈረስ ፤ አልቃሽ ። ሀቤል ፡ ከንቱ ፡ ብላሽ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**አቦሊ ፤(ጽር ፡ አቦሎስ)** ፤ የገንዘብ ፡ ስም ፤ ታናሽ ፡ ገንዘብ ፡ ፳ ፡ ሳንቲም ፤ የዲድርክም ፡ ኻያኛ ፤ በዕብራይስጥ ፡ ጌራ ፡ ይባላል ፤ ኻያው ፡ ጌራ ፡ ፩ ፡ ሰቅል ፡ እንዲኾን ፤ ኻያው ፡ አቦሊ ፡ አንድ ፡ ዲድርክም ፡ ነው ። ዕሥራ ፤ አቦሊ ፤ ለአሐቲ ፤ ዲድርክም ፤ (ዘሌ፳፯ ፡ ፳፭ ። ዘኍ፫ ፡ ፵፯ ። ዘፀ፴ ፡ ፲፫ ። ሕዝ ፡ ፬ ፡ ፵፪) ።

**አባል ፤ (ዕብሬ)** ፤ ታናሽ ፡ ወንዝ ፤ ፈፋ ፡ በዱር ፡ በዛፍ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ። የማንብ ፡ ደጃፍ ፡ የድልድይ ፡ በር ። ወሀሎኩ ፡ አነ ፤ በአባል ፤ ኡላይ ፡ (ዳን፰ ፡ ፪) ። ኡላይ ፡ የወንዙ ፡ ስም ፡ ነው ።

**እብላ** ፤ ጨረቃ ፡ የጨረቃ ፡ ስም ። ወቢቱ ፡ ለወርኅ ፤ አርባዕቱ ፤ አስማት ፤ አሶንያ ፡ እብላ ፡ ብናሴ ፡ ኤራስ ፤ (ሔኖ፸፰ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ነሐ፲፯) ።

**እብላሊት ፤— አለብላቢት ፤—በሊል ፡ በለ ።**

**አበሞ ፤ አበሜ ፤ (ጽር ፡ አሞሞን ። ዕብ ፡ ቂዳ)** ፤ ሽቱ ፡ የሽቱ ፡ ስም ፤ ቅመም ፤ ቀረፋ ፡ የጢስ ፡ ዕንጨት ፡ ቅጠላም ፡ ይይይለ ። ቀረፋ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ነው ፤ ቅመምና ፡ ሽቱ ፡ የሚኾን ፡ (ራእ፲፰ ፡ ፲፫ ። ዘፀ፴ ፡ ፳፬ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፲፱) ። ቀንሞስን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**አቡን ፤ —ጳጳስ ፤—አብ ።**

**እብን ፤(ዐረ ፡ ኢብን ። ዕብ ፡ ቤን)** ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተባት ፡ ሲያበዛ ፡ እብናእ ፡ ይላል ። እብን ፤ እልሐኪም ፡ (ነገ ፡ ነገ) ።

**እብን ፡ (ዕብ ፡ ኤቤን ። ሱር ፡ አብናአ) ፡** ደንጊያ ፡ ድንጋይ ፡ በአፍአ ፡ በውስጥ ፡ ከምድር ፡ የሚ ገኝ ፡ የምድር ፡ ዐጥንት ፡ ዕንቍ ። ስዕንፈጿት ፡ ብዙ ፡ ዐይ ነት ፡ እንዳለው ፡ ለደንጊያም ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ አለው ፡ ክቡርና ፡ ኅሱር ፡ ግብዝና ፡ ብርቱ ። **እብን ፡ ዐቢይ ። ጽላት ፡ ዘእብን ። ንሕንጽ ፡ በእብን ፡** (ሕንገ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ። ዘፀ፴፪ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፱ ፡ ፲) ።

**እበን ፡ አእባን ፡ (ናት) ፡** ደንጎች ፡ ደንጊ ያዎች ፡ ድንጋዮች ፡ አዕናቍ ። **እስመ ፡ ሠምሩ ፡ አበ ኒሃ ። አእባን ፡ ዐበይት ። አእባናት ። አእባኒ ፡ ወርቅ ። አእባኒ ፡ ህንደኬ ። አእባን ፡ ክቡራት ፡ በበ ፡ ሕበሪ ሆሙ ፡** (መዝ ፡ ፻፩ ። ኢር፶ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ የካ፱ ፡ ማን ፳ ። መቃ ፡ ፻፳፫ ። ሄኖና ፡ ፳፱ ፡ ፱) ። እበን ፡ ኹለት ፡ ወይም ፡ ጥቂት ፡ አእባን ፡ ብዙ ፤ አእባናት ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ይባላል ፡ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ እበንን ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ይሉ ታል ፡ አያስኘም ፡ አደመንና ፡ እገርን ፡ ተመልከት ።

**አቤኔዜር ፡ (ዕብ ፡ ኤቤን ፡ ሃዓዜር) ፡** እብነ ፡ ረድኤት ፡ የረድኤት ፡ ደንጊያ ። (፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፪) ።

**እብነ ፡ አድማስ ፡** ርባስ ፡ ገንቢዎች ፡ ሕንጻ ፡ የሚሰኩበት ፡ ብረትና ፡ ደንጊያም ፡ ይኾናል ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**እብነ ፡ እዝኅ ፡** ብልጭት ፡ ደንጊያ ፡ በሲታም ፡ (ኢ.ያ፳ ፡ ፱) ።

**እብነ ፡ አስሐትያ ፡** የውርጭ ፡ ደንጊያ ፡ የረ ጋው ፡ ግግሩ ። ወይም ፡ ውርጭ ፡ የሚመስል ፡ ጽሩይ ፡ የብርሌ ፡ ጠብ ፡ ብርሌ ፡ ዐይነት ፡ ደንጊያ ፡ (ሔኖ፸፩ ፡ ፰) ።

**እብነ ፡ በረድ ፡** በቁሙ ፡ የበረድ ፡ ደንጊያ ፡ እንዳረር ፡ እንደ ፡ ጠጠር ፡ ያለ ፡ ከዚያም ፡ የሚበልጥ ፡ ራስ ፡ የሚሰብር ፡ የሚቀጠቅጥ ፡ (ኢያ፲ ፡ ፲፩ ። ሚራ፵፫ ፡ ፲፮ ። ዮሐ፳ ፡ ፰ ። ሕዝ፴፰ ፡ ፳፪ ። ሔኖ፲፬ ፡ ፱) ።

**እብነ ፡ በረድ ፡** ነጭ ፡ ደንጊያ ፡ በረድ ፡ የሚ መስል ፡ የበረዶ ፡ ዐይነት ፡ (ዐማርኛ) ።

**እብን ፡ ክቡር ፡** ዕንቍ ፡ የዕንቍ ፡ ወገን ፡ ሕ ብርና ፡ መልክእ ፡ ያለው ።

**እብነ ፡ ኰኵሕ ፡** ጥኑ ፡ ጠንካራ ፡ ኀይለኛ ፡ ደ ንጊያ ፡ የማይሰበር ፡ የማይፈነክት ፡ አልማስ ፡ አለት ፡ (ዘ ዳ፰ ፡ ፲፩ ። ሮሜ፱ ፡ ፴፫ ። ኢ.ዮ፴፩ ፡ ፲፱ ። ሕዝ፫ ፡ ፰) ።

**እብነ ፡ ማእዘንት ፡** የማእዘን ፡ ደንጊያ ፡ ማ ጠፊያውና ፡ መቀነፊያው ፡ ኹለቱን ፡ ማእዘን ፡ የሚይ ዝና ፡ የሚያያይዝ ፡ ኹለት ፡ ክንፍ ፡ ያለው ፡ (፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፯) ።

**እብነ ፡ መዳልው ፡** የሚዛን ፡ ደንጊያ ፡ ልክ ነት ፡ ያለው ፡ ሌላውን ፡ በርሱ ፡ መመዘኛ ፡ ማስተካከያ ፡ (ሕዝ፳ ፡ ፩) ።

**እብነ ፡ መከራ ፡** የፈተና ፡ ደንጊያ ፡ ታላቅ ፡ ከባድ ፡ ክብ ፡ እንክብል ፡ ድንብልብል ፡ ጕብዝነት ፡ ር ሱን ፡ በማንሣት ፡ በመሸከም ፡ ጕልበታቸውን ፡ የሚፈ ትኑበት ፡ (ሚራ፯ ፡ ፳፱) ።

**እብነ ፡ ሞፀፍ ፡** የወንጭፍ ፡ ደንጊያ ፡ ታና ናሽ ፡ ኵረት ፡ እንደ ፡ ፍሳጻና ፡ እንደ ፡ ጥይት ፡ ርቆ ፡ የሚ ኼድ ፡ የሚወረወር ፡ (ዘካ፱ ፡ ፲) ።

**እብነ ፡ ቀኖናማት ፡** የሚዛን ፡ ደንጊያ ፡ ታላ ቁም ፡ ታናሹም ፡ በየስሙና ፡ በየይነቱ ፡ ተሰብስቦ ፡ በኪስ ፡ በከረጢት ፡ የሚከተት ፡ (ምሳ፲፮ ፡ ፲፩) ።

**እብነ ፡ ሰንፔር ፡** ሰንፔር ፡ የሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ክቡር ፡ ደንጊያ ፡ (ኢ.ዮ፳፰ ፡ ፮ ። ፩ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፪) ።

**አበነ ፡** ደነገየ ፡ ደንጊያ ፡ ኾነ ፤ ወይ ፡ ደንጊያነት ፡ ተለወጠ ፡ ደረቀ ፡ ከረረ ፡ ፈዘዘ ።

**አእበነ ፡** አደነገየ ፡ ደንጊያ ፡ አደረገ ። **እግዚ ፡ አእበና ፡ ወሜጠ ፡ ህላዌሃ ፡ ለከዊነ ፡ ሐውልት ፡** (መጽ ፡ ምስ ። ዘፍ፲፱ ፡ ፳፮) ።

**ኢ.ብን ፡ (ጽር ፡ ይቢስ) ፡** የወንዝ ፡ አሞራ ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ የሚኖር ፡ ነጭ ፡ አፈ ረዥም ፡ ትሎችን ፡ ተሐዋስያንን ፡ የሚለቅም ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ግብጻውያን ፡ ያመልኩት ፡ ነበረ ፡ ይባላል ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፲፯ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፲፯) ። ሰብራብጡ ፡ ግን ፡ ያንሸፍ ፡ ይባል ፡ ጕጕት ፡ ማለት ፡ ነው ።

**አብኖስ ፡ (ዐረ ፡ አብኑስ ። ጽር ፡ ሄቤ ኖስ) ፡** ዛጺ ፡ ጥሩ ፡ ጠንካራ ፡ ዕንፊት ፡ መልኩ ፡ ጥ ቍር ፡ ዋጋው ፡ ክቡር ፡ በህንድና ፡ በሱዳን ፡ አገር ፡ በኢ ትዮጵያ ፡ የሚገኝ ፡ ከክቡርነቱም ፡ የተነሣ ፡ በሚዛን ፡ የሚሸጥ ። **ወገብረ ፡ መጥቅዐ ፡ እምዕፀወ ፡ አብኖስ ፡** (ቀሌ ። ገድ ፡ አዳ) ። ዛጺን ፡ ተመልከት ።

**አብሠረ ፡—አበሠረ ፡—በሠረ ።**

**አበቅ ፡ (ዕብ ፡ አባቅ) ፡** በቁሙ ፡ ጸበል ፡ ት ቢያ ፡ ዐቧራ ፡ ቅንቅን ፡ በነፋስ ፡ የሚበን ፡ ደቃቅ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ።

**አበቅ ፡ (ዕብ ፡ ሻሐፍ ። ጽር ፡ እብሶራን) ፡** ደዌ ፡ ሶሥጋ ፤ ዕከክ ፡ ፈረሳቤት ፡ እንዳበቅ ፡ የሚያሉብስ ፡ አበቅ ፡ የሚመስል ፡ ሰውነት ፡ የሚፋቅ ፡ የሚያሰለስል ። **አበቅ ፡ እኩይ ። ደዌ ፡ ሲሕ ፡ ወአበቅ ። ኢዮብ ፡ አመ ፡ አሣዘ ፡ አበቅ ። አ ፡ ፈታኔ ፡ ኢዮብ ፡ በደዌ ፡ ወአበቅ ።** (ዘዳ፳፰ ፡ ፳፯ ። መቃ ። ስንክ ፡ መስ፩ ። ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**አበቀ ፡** ታመመ ፡ ተደወየ ፡ ዐከከ ፡ ነጣ ፡ ገረጣ ፡ ቈሸሸ ፡ ተበላሸ ። አበቅ ፡ ለበሰ ፡ አበቅ ፡ መሰሉ ፡ ኾነ ።

**እቡቅ ፡ (ቃን ፡ ቃት ፡ ብቅት) ፡** ያከከ ፡ ዕ ከካም ፡ ቈሻሻ ፡ ቋቍሻም ፡ ድውይ ፡ (ዘሌ፳፩ ፡ ፳ ። ፳፪ ፡ ፳፪) ።

**አብቀወ ፡—ከፈተ ፡—በቊው ፡ በቀወ ።**

**አቡቀለምሲስ ፡ (ጽር ፡ አፖካሊፕ ሲስ) ፡** መጽሐፍ ፡ የመጽሐፍ ፡ ስም ። ቃሉ ፡ ኹለት ፡ ነው ፡ ቅጽልና ፡ ባለቤት ። አፖ ፡ ሩቅ ፡ ረቂቅ ፡ ስውር ፡ ድብቅ ፡ ኅቡእ ፡ ክቡት ፤ ካሊፕሲስ ፡ ራእይ ፡ ትንቢት ። **ራእየ ፡ ዮሐንስ ፡ አቡቀለምሲስ ። ዮሐንስ ፡ ጸሐፈ ፡**

ወንጌለ ፡ ወአቡቀለምሲስ ፡ ዘርእየ ፡ ውስተ ፡ ደሴተ ፡ ፍጥሞ ፤ (ስንክ ፡ ታኅሣ ፡ ፴ ። ጥር ፬) ። እንዳረቡ ፡ ቃል ፡ በአብ ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈታ ፡ ግን ፡ ሰባለመጽሐፉ ፡ ስምና ፡ ቅጽል ፡ ይኾናል ።

**አቡቀለምሲስ ፤** አበ ፡ ራእይ ፤ አበ ፡ ቅኔ ፡ ቢት ፡ የሕልም ፡ ጌታ ፡ የራእይ ፡ ባለቤት ፤ ባዓለ ፡ ራእይ ። **ዮሐንስ ፡ ቴዎሎጎስ ፡ ዮሐንስ ፡ አቡቀለምሲስ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘረፈቀ ፡ ውስተ ፡ ሕፅኑ ፡ ለኢየሱስ ። ወንጌለ ፡ መለኮት ፡ ሰበከ ፡ ስምዐ ፡ ጽድቅ ፡ ኮነከ ፡ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ አቡቀለምሲስ ፡ ተሰመይከ ፡** (ድጓ) ።

**አበቅቴ ፤ (ትያት ። ጽር ፡ ሄፓክቴ) ፤** ጭማሪ ፡ ተውሳክ ፤ የቍጥር ፡ ማማያ ፡ ማስተካከያ ። ተረፈ ፡ ዓመት ፤ የቀመር ፡ ትራፊ ፤ ትርፍ ፡ ፍይፋጅ ። **አበቅቴ ፡ ፀሓይ ። አበቅቴ ፡ ወርኅ ። አበቅትያት ። ሥርዐ ፡ ሐሳበ ፡ አበቅቴ ፤** (አቡሻ ፡ ፳፫ ። ፳፭ ። ፴፩ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፲፱) ።

**አብር ፤ (ብ ፡ አባር ። ዐረ ፡ ኢብረት ፤ ብ ፡ ኢባር) ፤** እሾኽ ፡ ቀጭን ፡ ሹል ፤ መርፌ ፡ የሚ መስል ። **ዕፀ ፡ ግረት ፡ እንዘ ፡ ቈጽለ ፡ ዕፀ ፡ ኢይትነገፍ ፡ ወአባሪሆኒ ፡ ኢይጸድፉ ፡** (መጽ ፡ ምስ) ።

**አብር ፡—ድርቅ ፡—ዐቢር ፡ ዐበረ ።**

**እቤር ፡—ባልቴት ፡—ዐቢር ፡ ዐበረ ።**

**አበርባራ ፡—ዶቢ ፡—በሪር ፡ በረ ÷—በርበረ ።**

**አበርጊላ ፤** ገበጣ ፤ የገበጣ ፡ ጨዎት ፡ (ፋ ፡ ን ፡ ማ፫ ፡ ፲፱) ።

**አብሮጥስ ፤ (ጽር ፡ ፔሪዎዴፍቲስ) ፤** ቃላቅ ፡ ቁሞስ ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ ተከታይ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**አብረክሲስ ፤ (ዐረ ፡ አብርክሲስ ። ጽር ፡ ፕራክሲስ) ፤** መጽሐፍ ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ግብረ ፡ ሐዋርያት ፤ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፤ ዜና ፤ ታሪክ ። **መጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ፡** (ፋ ፡ ነ ፡ ፪) ።

**አብሬክ ፤ (ዕብ ፡ አብሬኽ ። ጽር ፡ ኪሪክስ) ፤** ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፤ ብርክ ፡ አስተብርክ ፤ ስግድ ፡ አምኅ ፡ ግነይ ፡ ባርክ ። ዮሴፍ ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ ለሕዝቡ ፡ ግብጽ ፡ የተነገረ ፡ የፈርዖን ፡ ዐዋጅ ፡ ነው ፡ (ዘፍ ፵፩ ፡ ፵፫) ። ዳግመኛም ፡ ረበናት ፡ አብሬኽን ፡ አብ ፡ ራኽ ፡ ብለው ፡ ፪ ፡ ቃል ፡ አድርገው ፡ ይፈቱታል ፤ አብ ፡ በቋሙ ፡ ራኽ ፡ ለጋ ፡ ቀንበጥ ፡ ርጥብና ፡ ወጣት ። አብ ፡ የተባለ ፡ ዮሴፍ ፡ ነው ፡ ራኽ ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ የ፴ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረና ፡ የድሜውን ፡ ማነስ ፤ አብ ፡ የአእምሮውን ፡ መጕልመስ ፡ የሰውነቱን ፡ መሾምና ፡ መንገሥ ፤ ለፈርዖን ፡ እንዳባት ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፤ ለወንድሞቹም ፡ ለኑሮ ፡ ቤል ፡ በመጋቢነቱ ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ አባት ፡ ይባላል ። **ረሰየኒ ፡ አበ ፡ ለፈርዖን ። ለደቂቀ ፡ ያዕቆብ ፡ ወዮሴፍ ፡** (ዘፍ፵፭ ፡ ፰ ። መገ ፡ ፸፯) ። የግእዝ ፡ አሪት ፡ ግን ፡ ወልድ ፡ ይላል ። አብሬኽንም ፡ ኤር ፡ አብሬር ፤ ኤል ፡ አብሬል ፡ ይላል ። ባለብሉዮችም ፡ ፍችውን ፡ ዐዋጅ ፡ ዐዋጅ ፡ ገብር ፡ ኮነ ፡ እግዚእ ፤ ባኀገባቦችም ፡ ይደልዎ ፤ ይበጅ ፡ ያድርግ ፡ ይሉታል ፤ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**አብሪል ፤ (ሮማይ ፡ አፕሪል) ፤** የወር ፡ ስም ፤ ሚያዝያ ።

**አቢስ ፤ (አቢሲን ÷ አቢሲኔ ÷ አቢሲንያ) ፤** ስመ ፡ ነገድ ፤ የኵሽ ፡ ልጅ ፡ የሳባ ፡ ሳብዓይ ፡ የናምሩድ ፡ ተከታይ ። ፪ኛ ፡ ስሙ ፡ ከለው ፡ ይባላል ፤ ፩ቱም ፡ በታሪክ ፡ እንጂ ፡ በቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ አይገኝም ። የሳባ ፡ ክፍል ፡ ሳባ ፡ እንደ ፡ ተባለች ፡ የአቢስም ፡ ክፍል ፡ አቢሲንያ ፡ ተብ ላለች ። አቢሲን ፡ አቢሳውያን ፤ አቢሲኔ ፡ አቢሳዊ ፤ አቢሲ ንያ ፡ ሀገረ ፡ አቢስ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እስክንድርያ ፡ እንደ ፡ ማለት ። ስምንቱም ፡ ከባፍና ፡ ከተክል ፡ የወጣ ፡ ገንታዊ ፡ ስም ፡ ነው ። ቢሲን ፡ ቢሲና ፡ የሚባል ፡ ፍሬው ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ የሚያክክል ፡ ጥሩ ፡ ተክል ፤ አለ ፤ ሕብሩ ፡ እጅግ ፡ ፍጹም ፡ ቀጥር ፡ እጅግም ፡ ፍጹም ፡ ቀይ ፡ ሳይኾን ፡ ደበብ ፡ ያለ ፡ ማእከላዊ ፡ ነው ፤ ጣዕሙና ፡ መልኩ ፡ ደም ፡ ግባቱ ፡ ከመዐዛው ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። አቢሲንም ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ቢሲን ፡ ፍሬ ፡ የሚያምር ፡ የቢሲና ፡ ፍሬ ፡ የሚመስል ፡ ማእከላዊ ፡ ሕብር ፡ ያለው ፡ ጥሩ ፡ ደመ ፡ ግቡ ፡ ማለት ፡ ነው ። ስኒጋል ፡ የሚባለው ፡ ነገድ ፡ የሱዳን ፡ ቍራጭ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ መደገዝካርም ፡ የአቢስ ፡ ቍራጭ ፡ ነው ፡ ይባላል ፤ ይኸውም ፡ በቅርጹና ፡ በመልክአ ፡ ገጹ ፡ ይታወቃል ፡ (ጽርኣዊ ፡ ታሪክ) ።

(ጥ) **አብሰ ፤ ሶት ፤ (አበሰ ፡ ይኤብስ ፡ የአብስ ። ዕብ ፡ አበስ) ፤** ማብላት ፡ ማጥገብ ፡ መቀለብ ፡ መመገብ ፤ ማሥባት ፡ ማወፈር ፤ ከብትን ፡ ሰውነትን ። ወይም ፡ በቂሙ ፡ ማበስ ፡ መጥረግ ፤ አባዝቶ ፡ መብላት ፡ መጋፈፍ ፤ እንደ ፡ እንስሳ ፡ መቀለብ ፤ መሥባት ፡ መወፈር ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ማበስ ፡ መበደል ፤ ኀጢአት ፡ መሥራት ፤ ዐውቆ ፡ ደፍሮ ፡ ኾነ ፡ ብሎ ። **አብሶ ፡ አበስት ። ኢይደግሙ ፡ አብሶ ። ዘይገብር ፡ ኀጢአተ ፡ ይኤብስ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሱ ። ኢተአብስ ፡ በቃልከ ። መላእክት ፡ አበሱ ፡ ምስለ ፡ አዋልደ ፡ ሰብእ ። ዳዊት ፡ አመ ፡ አበሰ ፡ በብእሲተ ፡ ኦርዮ ፡** (ሰቈ፭ ፡ ፳ ። ሔኖ፳ ፡ ፳ ። ሢራ፲፱ ፡ ፬ ። ፴፭ ፡ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፬ ። ዲድ ፡ ፲) ።

**አባሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት) ፤** የሚያብስ ፡ የሚበድል ፡ በዳይ ፡ በደለኛ ፤ ያጥፍ ፡ አጥፊ ፤ ደፋር ፤ ጥጋበኛ ። **ኃጥእ ፡ ወአባሲ ። አባሲ ፡ ዝንቱ ፡ ሕዝብ ፡ አበሳ ፡ ዐቢየ ፡** (አርጋ ። ዘፀ ፴፪ ፡ ፴፩) ።

**መአብስ ፤ (ስት ፡ ሳን ፡ ሳት) ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፡ በደለኛ ። **ዘይስሕት ፡ በአሐቲ ፡ ኮነ ፡ መአብሰ ፡ በኵሉ ። መአብስ ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ እግዚእነ ፡** (ያዕ፪ ፡ ፲ ። ፋ ፡ ነ ፡ ፲፫) ።

**እቡስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ብስት) ፤** ያበሰ ፡ የበደለ ፡ አበሰኛ ፡ ኃጥእ ፡ ወንጀለኛ ። **እቡስ ፡ ትሬስዮሙ ። እቡሳነ ፡ ልብ ። ተሰቅለ ፡ ከመ ፡ እቡስ ፡** (ምሳ፲፫ ፡ ፯ ። መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ መጋ፳፯) ።

**እብሰት ፡** ማበስ ፡ መበደል ፡ አበዳደል ፡ በደላ ፡ በደል ፡ ኀጢአት ፡ ክሕደት ። ወእምገ ፡ በርሕቀት ፡ መዋዕል ፡ ተእኅዘ ፡ ልማደ ፡ እብሰት ፡ ወርስዐት ፡ (ጥበ፲፬ ፡ ፲፮) ።

**አበሳ ፡ (ሳት) ፡** በቁሙ ፡ ዕዳ ፡ በደል ፡ ኀጢአት ፡ ክሕደት ። አልብየ ፡ አበሳ ። አበሳ ፡ ዘኢኮነ ፡ ለሞት ፡ እስመ ፡ ቦ ፡ አበሳ ፡ ዘለሞት ። ኅድግ ፡ ለነ ፡ አበሳነ ። ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ እምአበሳት ። ገባር ያነ ፡ አበሳት ፡ (ኢዮ፴፬ ፡ ፮ ። ፩ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፲፮ ። ፈ ፡ መ ፡ ፮ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ።

**አአበሰ ፡** አሳበሰ ፡ አስበደለ ፡ ኀጢአት ፡ አሠራ ። እንተ ፡ ታሔብስ ፡ ምድረ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫) ።

**አአባሲ ፡ መአብስ ፡** የሚያሳብስ ፡ የሚያስበድል ፡ አገባሪ ፡ ኀጢአት ፡ አሠሪ ።

(ጥ) **አባስ ፡ (ሱርስት) ፡** መምህር ፡ አበ ፡ ማኅበር ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ የገዳም ፡ አባት ፡ (ሥር ፡ ጴኮ) ። አባስ ፡ ካህን ፡ ሮሚ ፡ (ታምረ ፡ ማር) ።

**አቡሻህር ፡—መጽሐፍ ፡—አብ ፡ አቡ ፡ ሻህር ።**

**አብስሊዲስ ፡ (ጽር ፡ እብሳልቲስ) ፡** መዘምር ፡ ዘማሪ ፡ አወዳሽ ፡ ደብተራ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፱) ።

**አብስልዋጥስ ፡ (ሮማይ ፡ እብሶሉቲዮኒስ) ፡** የፍታት ፡ ቃል ፡ የፍታት ፡ ሥርዐት ፡ ናዛዥ ፡ ለተናዛዥ ፡ የሚያሰማው ፡ ቃል ፤ እፌትሐከ ፡ ኩን ፡ ፍቱሐ ፡ ፍትሐት ፡ ዘወልድ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ። የፍታት ፡ ዜማ ፡ ለሙታን ፡ የሚጸለይ ፡ ጸሎት ፡ በማንዘት ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ፍትሐተ ፡ ወንጽሕተ ፡ ረሰያ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። አብስልዋጥስ ፡ ይትበሀል ፡ በዜማ ፡ ግንዘት ፡ (ግንዘ) ።

**አቢሳ ፡—በዓለ ፡ ጋዳ ፡—አቢብ ፡ አብ ።**

**አብሲማዳኮስ ፡ (ጽርእ) ፡** ከኹለት ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ አምሳኩና ፡ ሰው ፡ ፩ ፡ አካል ።

**አብሰረ ፡—አበሠረ ፡—በሠረ ።**

**አቢት ፡ ቶት ፡ (አበተ ፡ የአብት ፡ ይእብት) ፡** ማበት ፡ ሽብ ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡ መሠማገር ፡ አጥብቆ ፡ ማሰር ፡ አብታረግ ፡ እንዲሉ ፡ ኹሉም ፡ ፀማርኛ ፡ ነው ።

**አጊድ ፡ ዶት ፡ (አገደ ፡ የአግድ ፡ ይእግድ ። ዕብ ፡ አጋድ ፡ አሰረ ፡ የነዶ ፡ የችብ) ፡** በቁሙ ፡ ማገድ ፡ መከልከል ፡ መማታት ። መስበር ፡ መቀልጠም ፡ መክፈል ፡ መለየት ፡ የሥጋና ፡ ይጥንት ።

**አገዳ ፡ (ዳት) ፡** እግር ፡ ዛል ፡ ሰዎን ፡ ማኽል ፡ አገዳ ፡ ቅልጥም ፡ የእጅና ፡ የእግር ፡ መይበኛ ፡ ዐጥንት ። ዘቦ ፡ አገዳ ፡ መልዕልተ ፡ እገሪሁ ። አገዳሁ ፡ ዘየማን ። ያነኩዕ ፡ አገዳሆን ። ተሰብረት ፡ አሐቲ ፡ አገዳ ፡ እግሩ ። ሴዊ ፡ እኅው ፡ ይሁዳ ፡ ዘሀብተ ፡ ክህነት ፡ አገዳ ፡ (ዘሌ፳፩ ፡ ፳፩ ። ፯ ፡ ፴፪ ። ዘካ፲፩ ፡ ፲፯ ። ገድ ፡ ተክ ። ደራሲ) ።

—፡ ዐጥቅ ፡ አንጓ ፡ ክፍል ፡ የሸመልና ፡ የቀርከሓ ፡ የመቃ ፡ የሸንበቆ ፡ የሸንኮር ፡ የጥንቅሽ ፡ ያገዳ ፡ እኽል ፡ ኹሉ ። (ቅኔ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ዐጼ ፡ ሳሉ) ፤ ጣሊያንንኒ ፡ የማሽላ ፡ እሸት ፡ እንድታብላው ፡ ጠብሰኽ ፡ ምኒልክ ፡ ያ ፡ ደገኛ ፡ ይመጣልና ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ አምጥተኽ ፡ ቁየው ፡ በፊት ፡ ራስ ፡ ራሱን ፡ ቈርጠኽ ፡ አገዳውንስ ፡ ይመጡታል ፡ እየሰባበሩ ፡ አሽከሮችኽ ።

**አግዋል ፡—ዘለላ ፡—ዐግዋል ።**

**እግዚእ ፡—ጌታ ፡—ገዚእ ፡ ገዝአ ፡ አግዝአ ።**

**አጋዝን ፡ አጋዜን ፡** በቁሙ ፡ የዱር ፡ የበረሓ ፡ ላም ፡ ቀንዳም ፡ ቀንደ ፡ ረዥም ፡ (አዋል) ።



አጋዘን ፡

**አግዮስ ፡ (ጽር ፡ አጊዎስ) ፡** ቅዱስ ፡ ክቡር ፡ ምስጉን ፡ (ቅዳ ፡ ግንዘ) ።

**አግያ ፡ (አጊያ) ፡** ቅድስት ። አግያ ፡ ሶፍያ ። አልመስጦ ፡ አግያ ፡ (አጥል ። ሃይ ፡ አበ) ።

**አግያስማንጦን ፡ (ጽር ፡ አጊዩ ፡ ኘኔፍማቶስ) ፡** ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ (ቅዳ) ።

**አጉል ፡—በቁሙ ፡ ክብ ፡ እንክብል ፡—ዐጉል ።**

**አግል ፡—ዝኒ ፡ ከማሁ ፡—ዐግል ።**

**እጓል ፡—ልጅ ፡—ዕጓል ።**

(ጥ) **አገለ ፡ ተአገለ ፡—ቀማ ፡—ዐግሎ ፡ ዐገለ ።**

**እገሌ ፡—በቁሙ ፡—ገልይ ፡ ገለየ ፡ አግለየ ።**

**አጋም ፡ (ዕብራ ፡ የውሃ ፡ ቦታ ፡ ወንዝ ፡ ኩሬ) ፡** በቁሙ ፡ አጋም ፡ ያጋም ፡ ፍሬ ፡ ጣዕሙና ፡ መልኩ ፡ ከማንጐ ፡ በቀር ፡ የጥቍር ፡ ወይን ፡ እሸት ፡ የሚመስል ፡ ጥፍጥ ፡ ዕንፉሩ ፡ እሾኽም ፡ ዐጥር ፡ የሚኾን ።

**አግመረ ፡** (አስደራጊ) ፡ ገሚር ፡ ገመረ ፡ ማሙራ ።

**አግሙስ ፡** (ብዙ) ፡ ገሚስ ፡ ገመሰ ፡ ገመስ ፡ ገሙስ ።

**አጊን ፡ ኖት ፡** (አገነ ፡ የአግን ፡ ይእግን ። ዐረ ፡ ዐጀነ ፡ አበክ) ፡ መቍረጥ ፡ መክፈል ፡ ማሥመር ፡ የሊጥ ። መገመት ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ማለት ፡ የዋጋ ። አገና ፡ ዋጋ ፡ ገኽና ፡ ሽያጭ ፡ የሚስማሙበት ፡ (ዐማርኛ) ።

**አግን ፡** ቡሖ ፡ ሊጥ ።

**አግን ፡** ጎፍጥ ፡ ያፍንጫ ፡ ኢድፍ ፡ (ሐባብ) ።

**ኤጎንጤ ፡** (ጽር ፡ ጎኒኤ) ፡ ውስጥ ፡ ውሳጤት ፡ (ሕዝ፵፩ ፡ ፲፭) ።

**እጉሥታር ፡—ሬት ፡—ዕጉሥታር ። ዕጉትሣር ÷ ዐገተ ።**

(ጥ) **አግሮ ፡ ሮት ፡** (አገረ ፡ ይኤግር ፡ የአግር ። ትግ ፡ ሐባብ ፡ አግረ ። ዐረ ፡ ጀራህ ። ዕብ ፡ አጋር ፡ ሰበሰበ) ፡ መኽድ ፡ መራመድ ፡ መሮጥ ፡ መፈርጠጥ ፡ እግራም ፡ እግረኛ ፡ መኾን ። በቁሙ ፡ ማገር ፡ መገርገር ፡ ማወክ ፡ መክልከል ፡ ከመንገድ ፡ ከሥራ ፡ ማስተጓጐል ።

**አጋር ፡** (ራን ፡ ራት ። አጋሪ ፡ ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፡ እግረኛ ፡ ፈጭ ፡ ገሥጋሽ ፡ ኻያጅ ፡ ተራማጅ ፡ ዐይማኄው ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ የመላ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ እስከርባ ፡ ዓመት ፡ ያለ ፡ ጕበዝ ፡ ጕልማሳ ፡ ወታደር ፡ ሰልፈኛ ፡ ዘማች ፡ ባዋጅ ፡ በቱልቱላ ፡ የተጠራ ፡ የተሰበሰበ ። ስሳ ፡ እልፍ ፡ አጋር ። አጋሮሙ ። አጋርያን ። ዐሠርቱ ፡ ምእት ፡ አጋር ፡ ብእሲ ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፴፯ ። ዘኁ፲፩ ፡ ፳፩ ። ዮዲ፯ ፡ ፳ ። ፪ ፡ ፲፱ ። ፩ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፯) ።

**መአግር ፡** (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፡ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፡ ለአጋር ፡ ወአጋሪ ።

**አጋር ፡** (ዕብ ፡ ሀጋር) ፡ ስመ ፡ ብእሲት ፡ የፈርዖን ፡ ዲቃላ ፡ ከገረድ ፡ የተወለደች ፡ ኋላም ፡ ለአብርሃም ፡ ሚስት ፡ ለሳራ ፡ ገረድ ፡ ትኹንሽ ፡ ብሎ ፡ የሰጣት ፡ የይስማኤል ፡ እናት ። ፍችው ፡ ማይርት ፡ ፈላሲት ፡ ኩብላይ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የመኸድና ፡ የመራመድ ፡ የፋጣ ፡ የማሥገሣ ፡ ምስጢር ፡ አለበት ፡ (ዘፍ፲፮ ፡ ፳—፲፮) ።

**አጋራዊ ፡** (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፡ ያርበኛ ፡ ወገን ፡ ዐርበኛ ፡ የጦር ፡ ሰው ። የአጋር ፡ ልጅ ፡ የይስማኤል ፡ ዘር ። ወሰብአ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጸሊማን ፡ ወአጋራውያን ፡ ዐርበኛ ። ሞአብ ፡ ወአጋራውያን ፡ ይስማኤላዊ ፡ (ገድ ፡ ፊቅ ። መዝ ፡ ፹፪) ።

(ላ) **እግሬ ፡** በቁሙ ፡ አላባሽ ፡ ጋሻ ፡ (ዐማርኛ) ።

**እግር ፡** (ዕብ ፡ ሬጌል ። ሱር ፡ ሬግላ ። ዐረ ፡ ሪግል) ፡ በቁሙ ፡ መቆሚያ ፡ መርገጫ ፡ መኼጃ ፡ መራመጃ ፡ ከጭን ፡ እስከ ፡ ሰኰና ፡ እንደ ፡ እጅ ፡ ፫ ፡ ክፍል ፡ ያለው ። ኪደት ፡ እግረ ፡ ብእሲ ። ከመ ፡ እግር ፡ ሙቁሕ ። እግር ፡ ቦሙ ፡ ወኢየሐውሩ ። እግረ ፡ ሰብእ ፡ ወእንስሳ ። ክልኤ ፡ እግር ። ዘአርባእቱ ፡ እግሩ ፡ (ሱቱ ፡ ዕዝራ ፡ ፯ ። ሚራጅ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፻፲፫ ። ሕዝ ፡ ፲፭ ። ዓሞጽ ፡ ፲፪ ። ዘፀ፳ ፡ ፱) ።



እግር ፡

**እግር ፡** እግሮች ፡ ለብዙም ፡ ለጥቂትም ፡ ባንድ ፡ ገላ ፡ ባሉ ፡ ባራትም ፡ በኹለትም ፡ ብቻ ፡ ከዚያም ፡ በሚበዙ ፡ ባምሳና ፡ በሺሕ ፡ ይነገራል ። ሺ ፡ እግር ፡ ዐምሳ ፡ እግር ፡ እንዲሉ ። ወይቀውማ ፡ እገሪሁ ። እገሪሆሙ ፡ ይረውጻ ። ወድቀ ፡ ውስተ ፡ እገሪሃ ፡ ለዮዲት ። ርቱዕ ፡ እገሪሆሙ ። ዘብዙኅ ፡ እገሪሁ ፡ (ዘካ፲፬ ፡ ፬ ። ምሳ፩ ፡ ፲፮ ። ዮዲ፲፬ ፡ ፯ ። ሕዝ፩ ፡ ፯ ። ዘሌ፲፩ ፡ ፵፪) ።

**እእጋር ፡** (ራት) ፡ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ እግሮች ። አእጋራት ፡ የብዙ ፡ ብዙ ። አ ፡ አእጋር ፡ እለ ፡ አንሶሰዋ ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ ተቀነዋ ፡ በቅንዋት ። ሰላም ፡ ለአእጋሪከ ፡ እለ ፡ ጠብዓ ፡ ለቀዊም ፡ (ቅዳ ፡ አፈ ። ደራሲ) ።

**እግር ፡** ታች ፡ ታችኛ ፡ ሥር ። ታቦከቦ ፡ ሰግኡዝ ፡ ኅበ ፡ እግረ ፡ ታቦት ፡ (ማንዘ) ።

**እግር ፡** ሓማ ፡ ውስጥ ፡ እግር ፡ የጥላ ፡ መስፈሪያ ፡ ከተረከዝ ፡ እስከውራ ፡ ጣት ፡ ጫፍ ። ጽላሎት ፡ በግንቦት ፡ ዐሥራ ፡ ወአሐዱ ፡ እግር ፡ ወመንፈቀ ፡ እግር ፡ (አዋል ። ቁር) ። ግልያን ፡ ተመልከት ።

**እግር ፡** ሎሬ ፡ ፊደር ፡ ቀርን ፡ ምዕዝር ። እግረ ፡ አሚር ። እገሪሃ ፡ ለፀሓይ ። በረቀ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ከመ ፡ እግረ ፡ ፀሓይ ፡ (ጥበ፲ ፡ ፬ ። ሔኖ፸፩ ፡ ፬ ። መቃ ፡ ገ፲) ።

**እግረ ፡ ደቂቅ ፡** የሕፃናት ፡ መንገድ ፡ የልጆች ፡ አካኼድ ፡ አረማመድ ፡ እቱ ፡ ሥማሬ ፡ ቃቱ ፡ ሥማሬ ። ማለት ፡ ምስጢሩ ፡ ጕዞና ፡ ማዝገግም ፡ ነው ፡ (ዘፍ፴፫ ፡ ፲፬) ።

**እግረ ፡ ማጣ ፡** (ዕብ ፡ ሬጌል ፡ ሚጣ) ፡ የኪሩቤል ፡ ስም ፡ ይራቱ ፡ ኹሉ ። ዘይቤው ፡ ያልጋ ፡ ሽንኮር ፡ የዙፋን ፡ እግር ፡ ምስጢሩ ፡ ጸወርት ፡ መንበር ፡ (ድጓ ። መዋሥ) ። ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ጌታን ፡ በንጉሥ ፡ መንበሩ ፡ መንግሥትን ፡ በኮር ፡ በግላስ ፡ ሰማይ ፡ ውዱድን ፡ ባልጋ ፡ በፈረስ ፡ ኪሩቤልን ፡ ባራት ፡ እግሮቹ ፡ መስሎ ፡ ነው ። (ሕዝ፩ ፡ ፳፮ ። መዝ ፲፯ ፡ ፲፩) ።

**እግረ ፡ መራኁት ፡** የመክፈቻች ፡ እግር ፡ መያገናቸው ፡ መንጠልጠያቸው ፡ ቀስበቱ ፡ ወይም ፡ ሳንቆች ፡

የሚቆሙበት ፡ መድረክ ፡ የመዝጊያ ፡ ቍላ ፡ መንደሜው ፡ (አዋል) ።

**እግሬዊ** ፤ እግሬም ፡ እግረኛ ፡ ዘዋሪ ፡ እግረ ፡ ብዙ ፡ ሺ ፡ እግር ፡ ዐምሳ ፡ እግር ፡ የሚሉት ፡ ጥቍር ፡ ትል ።



እግሬዊ ፡

**አግሪም ፤ (ዕብ ፡ ሀግሪም ፤ ሀግሪኢም)** ፤ አጋሬውያን ፡ የይስማኤል ፡ ልጆች ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ያሉት ። **ፈለገ ፡ አግሬም** ፡ (ዘሌዋ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ። ፱ዜና ፡ ፭፭ ፡ ፲፩) ። ጽርኡና ፡ ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ፈለገ ፡ ጌው ፡ ይላል ፡ የባሕረ ፡ ጌው ፡ ዱሓ ፡ ሸለቆ ፡ ወደ ፡ ባሕረ ፡ ጌው ፡ የሚፈስ ፡ ወንዝ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**አግሪም ፡ (ዕብ ፡ ጊር ፤ ኖራ)** ፤ መገይሬን ፡ ኖራ ፡ እውራዎች ፡ ሸያሪዎች ፡ ቀቦች ፡ ለቅላቆች ። እሊሁም ፡ ሰብእ ፡ ስይም ፡ ናቸው ፡ የጊሮንና ፡ የስይምን ፡ ሩቶች ፡ ተመልከት ።


**አግሪጳስ** ፤ ፬ ፡ እግር ፡ ያለው ፡ አሞራ ። **ወሀሎ ፡ ያፍ ፡ ዘይሰመይ ፡ አግሪጳስ ፡ በሀገረ ፡ ቃራት ፡ ወቦ ፡ አርባዕቱ ፡ አእጋር ፤ ይመሥጥ ፡ ሶረ ፡ ወይሰርር ፡ መልዕልተ ፡ አየር ፡ እንበይነ ፡ ጽንዑ** ፡ (ፊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ፺፰፱) ። ፱ኛም ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ይኾናል ፡ (ግብ፳፭ ፡ ፲፫) ።

**አገተ ፤—ከበበ ፤—ዐጊት ፡ ዐገተ ።**

**እደ ፤—እጅ ፡ እጀታ ፤—አዲው ፡ አደወ ።**

**አዲግ ፤ ጎት ፤ (አደገ ፡ የአድግ ፡ ይእድግ ። ዐረ ፡ ሐደጀ)** ፤ መሸከም ፡ መጫን ፡ ማንገት ፡ ማዘል ፡ መደብለል ፡ ተሸካሚ ፡ መኾን ፡ በዝርርብ ። በቁሙ ፡ ማደግ ፡ መመንደግ ፡ ቁመትና ፡ ጕን ፡ መጨመር ፡ ለሽክም ፡ ለጭነት ፡ መብቃት ፡ የሰው ፡ የከብት ።

**አድግ ፤ (ብ ፡ አእዱግ ፤ ጋት)** ፤ ተሸካሚ ፡ የጭን ፡ የጭነት ፡ የክርቻ ፡ ከብት ፡ አህያ ፡ አጋሰስ ፡ በቅሎ ፡ ፈረስ ፡ ገመል ፡ ዝኆን ። ስምንቱ ፡ የግብር ፡ ነውና ፡ ለኹ




አድግ ፡

ሉም ፡ ይኾናል ፡ ልማዱ ፡ ግን ፡ ላህያ ፡ ብቻ ፡ ነው ። **ኢድግ ፡ ወላሕም ። ኢድገ ፡ ጸላኢከ ። ወቀገ ገድፉ ፡ አእዱጊሁ ፡ ለቂስ ። አእዱግ ፡ ፍኖቶሙ** ፡ (ቅዳ ። ዘፀ ፳፫ ፡ ፭ ። ፩ነገ ፡ ፱ ፡ ፫ ። ቅኔ) ።

**አድግት ፤ እድግት ፤ (ብ ፡ አእድግት ፡ እድግታት)** ፤ እንስት ፡ አህያ ፡ አህዩት ፡ አህዩት ፡ ወላድ ፡ እመሚት ። **ይጼዐን ፡ ዲበ ፤ እድግቱ ። ዲበ ፡ እድግት ፡ ወዲበ ፡ ዕዋል ፡ ዕጓለ ፡ እድግት** ፡ (ዘኍ፳፪ ፡ ፳፱ ። ማቴ፳፩ ፡ ፭) ። እድግታት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አእዱግ ፡ አእኑስ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ፡ (ኢዮ፩ ፡ ፫) ። ፈረስን ፡ ተመልከት ።

**አድገ ፡ ገዳም** ፤ የዱር ፡ የበዳ ፡ አህያ ፡ ሠጋር ፡ ጠጕረ ፡ መልካም ፡ ነብርማ ፡ ሽልምልም ፡ ሽመልመሉ ፡ ዐይነት ። ሐለስትዮን ፡ እይ ። **ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ አድገ ፡ ገዳም ። በበዓቲሆሙ ፡ ለአእዱገ ፡ ገዳም** ፡ (ኢዮ፳፬ ፡ ፭ ። ኢሳ፴፪ ፡ ፲፬ ። ሔኖ፹፱ ፡ ፲፩) ።



አድገ ፡ ገዳም ፡

**አድገ ፡ መረብ ፤ (ዕብ ፡ ቃአት ፡ ሚድበር ። ጽር ፡ ፔሊካን)** ፤ ያፈ ፡ መረብ ፡ የበዳ ፡ ርኩም ፡ ቀቀኖ ፡ ወይም ፡ የርኩም ፡ ዐይነት ፡ መረበ ፡ ጋጋኖ ፡ የባሕር ፡ ደሮ ። እሊህ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ ይመሳሰላሉ ፡ ቀቀኖንና ፡ መረብን ፡ ተመልከት ፡ አድግ ፡ ማለት ፡ ግን ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (መዝ፻፩ ፡ ፯ ። ዘሌ፲፩ ፡ ፲፰) ። ማሕረጸ ፡ አድግ ፡ ቢል ፡ የወፍራም ፡ ግልገል ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አድግ ፡ ታችኛው ፡ እናቱ ፡ ተሸካሚው ፡ ማሕረጽ ፡ ላይኛው ፡ ልጁ ፡ መጁ ። በለሐዲሶች ፡ ግን ፡ አህያ ፡ የሚያዞረው ፡ የመዘውር ፡ ወፍጮ ፡ ይሉታል ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፯) ።

**እድው ፤—ደመኛ ፡ ባለጋራ ፤—ዐደወ ።**

**አዲው ፤ ዎት ፤ (አደወ ፡ የአዱ ፡ ይእዱ ። ዕብ ፡ ያዳህ)** ፤ መጥረግ ፡ መጋፍ ፤ መግፋት ፡ ማስገለል ፡ መኰስተር ፡ መሰብሰብ ፡ ዐፍሥ ፡ መጣል ፡ መወርወር ፡ ማሽቀንጠር ፤ የጕድፍ ። **ወነሥአ ፡ ደናግል ፡ ማእድወ ፡ ወአደዊ ፡ ወአውፅአ ፡ ሎሎ ፡ መሬተ ፡ እምዐውደ ፡ ማኅፈድ** ፡ (ሂርማ) ።

**አዲው** ፤ እጃም ፡ ባለእጅ ፡ መኾን ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ማወቅ ፡ በተግባረ ፡ እድ ፡ መሠልጠን ፡ መራቀቅ ። መያዝ ፡ መጨበጥ ፡ እጅ ፡ ማድረግ ፡ ከእጅ ፡ ማግባት ።

**አዳዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ አደውት)** ፤ የሚጠርግ ፡ ጠራጊ ፡ ባለወግ ፡ የከተማ ፡ የቤት ፡ ክሲያን ።

**ማእድው ፡ (ብ ፡ መእድው ፡ ዋት) ፡** መዋረጊያ ፡ የጉድፍ ፡ መጣሪያ ፡ ማስገለያ ።

**ተእደወ ፡** ተጠረገ ፡ ተኰሰተረ ፡ ተከወነ ፡ ቤቱ ፡ ጉድፉ ።

**እድው ፡ (ዋን ፡ ዋት ፡ ዱት) ፡** የተጠረገ ፡ የተኰሰተረ ፡ ጉድፍ ፡ የሌለበት ። **ይረክቦ ፡ ዕሩቀ ፡ ወእድወ ፡ ወስርግወ ፡** (ማቴ፲፪ ፡ ፵፬ ። ሉቃ፲፩ ፡ ፳፭ ። ሄሮማ) ።

(ጥ) **እዳው ፡ (ዋት) ፡** ጉድፍ ፡ ጥራጊ ፡ ሰመድ ፡ ርኩሽ ፡ ማር ፡ ገለባ ፡ ፍግ ፡ በዘበ ። **ገደፍኩ ፡ ኵሎ ፡ ወረሰይክዎ ፡ ከመ ፡ እዳው ። ይክውን ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ በንቤሁ ፡ ከመ ፡ እዳዋት ፡ ወከመ ፡ ዘብሕ ። ሔደገኑ ፡ እዳዋት ፡** (ፊልጵ፫ ፡ ፰ ። አፈ ፡ ተ፲፰ ። ፍ ፡ ን ፡ ፀ፺ ። ኢሳ፵ ፡ ፳፱) ።

**እድ ፡ (ዕብ ፡ ሱር ፡ ያድ ። ዐረ ፡ የድ) ፡** እጅ ፡ የገላ ፡ ክንፍ ፡ መሥሪያው ፡ መጣሪያው ፡ ከመቅ ከፍት ፡ እስከ ፡ እጽባዕት ፡ እንደ ፡ እግር ፡ ፫ ፡ ክፍል ፡ ያለው ፡ ጠንቻ ፡ ክንድ ፡ መዳፍ ። እደ ፡ ከ ፡ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ ፡ እደ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ጎበ ፡ በጎምስ ፡ ይዘረዝራል ። ምስጢሩ ፡ ሥራን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ኃይልና ፡ ሥልጣንን ፡ ያሳያል ። **አትሕቱ ፡ ርእሰከ ፡ ታሕተ ፡ እዴሁ ። በእድ ፡ ጽንዕት ። እድ ፡ ፀቡስ ። ኵሉ ፡ እድ ፡ ይደክም ። እድ ፡ በሙ ፡ ወሴደገሱ ። ደይ ፡ እዴከ ፡ ላዕለ ፡ እዴየ ። መጥወኒ ፡ እዴከ ፡ ወመጠዎ ፡ እዴሁ ። ከሰባት ፡ ይበልዕዋ ፡ ሰብትረ ፡ እዴሁ ፡ ሔልዛቤል ፡** (ዘፍ፲፮ ፡ ፱ ። ዘፀ፮ ፡ ፩ ። ሚሬ፳፭ ፡ ፳፫ ። ኢሳ፲፫ ፡ ፯ ። መጊ ፡ ፬፲፫ ። ዘፍ፳፱ ፡ ፱ ። ፬ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ። ቅኔ) ።



እድ ፡

**እደው ፡ አእዳው ፡ (ዋት) ፡** እጆች ፡ የገላ ፡ ቅጥዮች ፡ ዐጽቆችና ፡ ክንዶች ። እደው ፡ ኅሉት ፡ አእዳው ፡ ብዙ ፡ አእዳዋት ፡ የብዙ ፡ ብዙ ። እበን ፡ ዕፀው ፡ ቀኖዮች ፡ እግር ፡ ዕፀን ፡ እዘን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ስም ፡ ኅሉስ ፡ መንሻው ፡ መድረሻው ፡ ሳይድብ ፡ ኅሉኖ ፡ መካከሉ ፡ ግእዝ ፡ ዘውግ ፡ ይባላል ። ኅሉስትም ፡ አራትም ፡ ቢኾኑ ፡ ከዚያም ፡ ቢበዙ ፡ ተባብረው ፡ ተመዛኝረው ፡ ተንጻጽረው ፡ ባንድ ፡ በታና ፡ ባንድ ፡ ገላ ፡ ብቻ ፡ ያሉትን ፡ ያሳያል ። **ቀነጢኒ ፡ እደውየ ፡ ወእገርየ ። ሰፍሐ ፡ እደዊሁ ፡ ለሕማም ። ስ ፡ ለእዳው ፡ እለ ፡ ለሐኳሁ ፡ ለሕዳም ፡ ተቀነዋ ፡ በቅንዋት ፡** (መዝ ፡ ፳፩ ። ቅዳ ፡ ዲዮ ። አፈ) ።

**እድ ፡** ቃል ፡ አፍ ፡ እንደበት ። **ወገብረ ፡ እግዚ ፡ ላዕሌከ ፡ በከመ ፡ ነበበ ፡ በእዴየ ። ዘነበበ ፡ በእደ ፡ ሔርምያስ ፡ ነቢይ ። ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚ ፡ በእደ ፡ ሐጌ ፡ ነቢይ ። አምኑ ፡ በእደዊሆ ፡** (፩ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፲፯ ። ኤርም፵፱ ፡ ፪ ። ሐጌ፩ ፡ ፩ ። ፪ነገ ፡ መ፳፯) ። እድ ፡ ቃል ፡ መባሉ ፡ አፍ ፡ ሲናገር ፡ እጅም ፡ እንደ ፡ ምላስ ፡ ይሠራልና ፡ ከቃል ፡ ጋራ ፡ ተባባሪነት ፡ በማለሰው ፡ ነው ። **አንሥአ ፡ እዴሁ ፡ ጳውሎስ ፡** (ግብ፳፯ ፡ ፩) ።

**እድ ፡** ወርች ፡ የፊት ፡ እግር ፡ የእንስሳትና ፡ የአራዊት ። (ተረት) ፡ ወርች ፡ የረገጠው ፡ እግር ፡ አይበተው ። **ዘየሐውር ፡ በእደዊሁ ። ላጽቄት ፡ ዘበእደዊሁ ፡ የሐውር ፡** (ዘሌ፲፩ ፡ ፳፯ ። ምሳ፳፱ ፡ ፳፰) ።

**እደ ፡ አቤሴሎም ፡** ታላቅ ፡ ሐውልት ፡ አቤሴሎም ፡ ለስሙ ፡ ማስጠሪያ ፡ ያቆመው ፡ ኋላም ፡ የተቀበረበት ። ምስጢሩ ፡ በታ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (፪ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰) ።

**እደ ፡ አትሮንስ ፡** ድጋፍ ፡ መከዳ ፡ የመንበረ ፡ መንግሥት ፡ ጌጥ ፡ የንጉሡ ፡ እጆች ፡ የሚረከዙት ፡ የሚመረኰዙት ። ስመጽሐፍ ፡ ቢኾን ፡ ግን ፡ መልሕቅ ፡ ያሰኛል ፡ አትሮንስን ፡ እይ ፡ (፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፱) ።

**እደ ፡ ኀጺን ፡** የብረት ፡ እጅ ። በሰው ፡ እጅ ፡ አምሳል ፡ የተሠራ ፡ ብረት ፡ የሰማዕታት ፡ መማቀያ ። **ገብሩ ፡ አምሳለ ፡ እድ ፡ ወአጻብዕ ፡ ዘኀጺን ። በእደወ ፡ ኀጺን ፡ እንዘ ፡ ይጸፍዕ ፡ ገጾ ፡** (ስንክ ፡ ሐምሌ ። ግንቦት) ።

**እደ ፡ ኀጺን ፡** የሐኪም ፡ መጣሪያ ፡ መመርመሪያ ። የሾርት ፡ የጥንቱዳ ፡ ብረት ፡ መሰማዋ ፡ የሚያሾርቱበት ። **እድ ፡ ዘኀጺን ፡ ዘየሐትት ፡ ዘውስተ ፡ ክርሥ ፡** (ስንክ ፡ ጥር፲፩) ።

**እደ ፡ የማን ፡** የቀኝ ፡ እጅ ፡ የቀኝ ፡ ወርች ፡ በግራ ፡ አንጻር ፡ ያለ ፡ (ሚሬ፳፭ ፡ ፳፭) ።

**እደ ፡ ኩናት ፡** የጦር ፡ እንደበት ፡ ቀጠሱ ፡ ሳንፉ ፡ ሹሉ ፡ ውልብልቢቱ ፡ ወይም ፡ ዘቢያው ፡ ሶማያው ። (ተረት) ፡ በጋሻው ፡ ሰንብርት ፡ በጦሩ ፡ እንደበት ፡ በፈረሱ ፡ ፀንገት ፡ (ኢር፲፰ ፡ ፳፭) ።

**እደ ፡ መንሠማ ፡** የመግዢያ ፡ እጀታ ፡ ወይም ፡ የመወርወሪያው ፡ ለመክፈት ፡ ለመዝጋት ፡ የሚያዘው ፡ (ማሕ፭ ፡ ፭) ።

**እደ ፡ ሰይፍ ፡** አፈ ፡ ሰይፍ ፡ ስለት ፡ እንደበት ፡ ወይም ፡ ውላጋ ፡ እጀታ ፡ መክደ ፡ (መዝ ፡ ፷፪) ።

**እደ ፡ ሰናስል ፡** ፍንጅ ፡ የሰንሰለት ፡ እጅ ፡ እስርና ፡ ቍራኛ ፡ በየክንዳቸው ፡ የሚያገቡት ፡ (መዝ ፡ ፻፵፱) ።

**እድ ፡** ጎን ፡ ሐሰን ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ፡ የበታ ፡ አቀናኝ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ድንበረተኛ ፡ ቀበሌ ፡ አውራጃ ፡ ግድም ፡ ገደማ ። **ኅበ ፡ እደ ፡ ሔማት ። መንገለ ፡ እደ ፡ ማየ ፡ ባሕር ። በእደ ፡ ባሕር ፡** (ሕዝ፵፯ ፡ ፳ ። ኩፋ ፡ ፰ ፡ ፲ ።) ።

**እድ ፡** ክፍል ፡ የክፍል ፡ ስም ። **የኀልቅ ፡ ክልኤ ፡ እድ ፡ ወይትርፍ ፡ ማልስት ፡ እዴሃ ። ራብዕት ፡ እዴሃ ፡**

ሰምድር ፡፡ ትሰቲ ፡ ሳድስተ ፡ እዴሃ ፡ ሰኢን ፡፡ ብር ሃነ ፡ ዚአሁ ፡ ሰብዐተ ፡ እደ ፡ ያበርህ ፡ እምዘወርኀ ፡፡ ሰገዝኩ ፡ ሳብዐተ ፡ እድ ፡ (ዘካ፲፫ ፡ ፰ ፡ ፱ ። ራእ፯ ፡ ፰ ። ሕዝ፱ ፡ ፲፩ ። ሔኖ፸፱ ፡ ፴፯ ። ሱቱ ፡ ዕገዛ፱ ፡ ፶፰) ።

**እድ ፡ ወእድ ፤** ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ። ፍችውን ፡ በወእድ ፡ ተራ ፡ ተመልከት ፤ ሲጣፍ ፡ የሚገ ባው ፡ ከዚህ ፡ ነበረ ፤ ወ ፡ በዋዊነት ፡ ገብቶ ፡ ማርኮ ፡ ስለ ፡ ወሰደው ፡ የወ ፡ ጭፍራ ፡ ኹኗል ።

**አደየ ፤—ከፈለ ፤— ዐድይ ፡ ዐደየ ፤ ዕዳ ።**

**አድያማ ፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ ካምስቱ ፡ አህጉረ ፡ ሰዶም ፡ አንዷቱ ።

**አድያም ፤ (ማት) ፤** ደወል ፡ ዙሪያ ፡ አውራጃ ፤ ሰበካ ፡ ገጠር ፡ ቃናናሽ ፡ አገር ፤ ጕልት ፡ ግዛት ። **እህ ጉር ፡ ወአድያሚሆን ፡፡ በዙሉ ፡ አድያሚነ ፡፡ አድ ያማተ ፡ ትግሬ ፡** (ዘኍ፴፰ ፡ ፪ ። ዳን፪ ፡ ፲፮ ። ገድ ፡ ተክ) ። አድያም ፡ የአዲም ፡ ብዙር ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ። አድያማም ፡ የወጣው ፡ አዲም ፡ አዲሞት ፤ አዳማ ፡ አ ዳሞት ፡ ከማለት ፡ ነው ።

(ላ) **አዲም ፤ ሞት ፤ (አደመ ፡ የአድም ፡ ይ እድም ። ዕብ ፡ አዳም ። ዐረ ፡ አዲመ) ፤** መቅ ባት ፡ ቀይ ፡ መኾን ፤ ደም ፡ መምሰል ፤ ፀለባ ፡ እንሶስባ ፡ መግባት ፡ በቀይ ፡ ሰባቅ ፡ መንከር ፡ መታሰል ፤ የነት ፡ የልብስ ።

**አዲም ፤ (ብ ፡ አድያም) ፤** ቅጽልና ፡ ጥሬ ። ቀይሕ ፡ ቀይሓዊ ፤ ደምማ ፤ ዐረብ ፡ እንቀልባ ፤ ነት ፡ የገባ ፡ ቈርበት ። **ማእሰ ፡ በግዕ ፡ ግቡረ ፡ አዲም ፡፡ ቅናት ፡ ዘአ ዲም ፡፡ ቅናታቲሆሙ ፡ አዲም ፡** (ዘፀ፳፱ ፡ ፭፩ ። ፴ነገ ፡ ፩ ፡ ፰ ። ማቴ፫ ፡ ፬ ። ማር፩ ፡ ፮ ። ሥር ፡ ጳኩ) ።

**ኤዶም ፤ ኤዶምያስ ፤** የዔሳው ፡ ስምና ፡ ሀ ገር ፤ ቀይሕ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፳፭ ፡ ፴ ። ኢሳ፷፫ ፡ ፩ ። መገ ፡ ፶፱) ።

**ኤዶማዊ ፤** የዔሳው ፡ ዘር ፡ የኤዶምያስ ፡ ሰው ። ዔዶኄን ፡ እዩ ።

**አዳማ ፤ (ዕብራ) ፤** ምድር ፡ የብስ ፡ ገራህት ፤ ቀይ ፡ መሬት ፤ መረሬ ፤ ቅጫቱ ፡ ሸክላ ፡ ሕጕሬ ፤ ብስል ፡ በርበሬ ፡ የሚመስል ፤ ያፈር ፡ ወይዘሮ ። አዳማ ፡ በሴት ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፤ ሲያበዛ ፡ አዳሞት ፡ ይላል ። ጋላም ፡ ቀይ ፡ ቢል ፡ ዲማ ፡ ዳማ ፡ ይላል ።

**እድሞ ፤ (ዐማርኛ) ፤** ያፈር ፡ ቤት ፡ ግድግ ዳው ፡ የማንገብ ፤ ጣራው ፡ የንጨት ፡ ኹኖ ፡ ከዳኑ ፡ ዐፈር ፡ መሬት ፤ እንደ ፡ ትግሬና ፡ እንዳደሬ ፡ ሥራ ። የማንገብ ፡ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ መከበቢያ ፤ ወይም ፡ ዐፈር ፡ ቃም ፡ ካብ ።

(ጥዳ) **አዳም ፤** በቁሙ ፤ መዠመሪያ ፡ ሰው ፡ የሰው ፡ ኹሉ ፡ አባት ፤ ጕበዝ ፡ ጕልማሳ ፡ ወንድ ፡ ተባት ። የሥ ጋው ፡ ተፈጥሮ ፡ ከፈር ፡ ከመሬት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አዳም ፡ መባሉን ፡ ከአዳማ ፡ ወሰዱ.ል ። ሥጋው ፡ እምድር ፡ ዘተ ሠገወ ፡ እመሬት ፡ ጽቡር ፡ ልሕኵት ፤ ቀይሕ ፡ ሥን ፡ ብጹሕ ፡ አምጣኑ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱—፳፫) ። ኹለተኛም ፡ እንስሳዊና ፡ መልአካዊ ፡ ፪ ፡ ባሕርያት ፡ ስላሉት ፤ በሥጋው ፡ መዋቲ ፡ ድኩም ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ በነፍሱ ፡ ነባቢ ፡ ለባዊ ፡ ሕያው ፡ ባለእምሮ ፡ ይባላል ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፯) ። አዳም ፡ በ፮ኛ ፡ ቀን ፡ መዠመሪያ ፡ ከ ምድር ፡ የፈለቀ ፡ የሰው ፡ ኹሉ ፡ ምንጭ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በዘር ፡ በሩካቤ ፡ ከርሱ ፡ እየተቀዳ ፡ ሞትና ፡ መቃብር ፡ የሚጠጡት ፡ ምድራዊ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ በምንጩ ፡ ስም ፡ አዳም ፡ ይባላል ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፲፱) ። ግእዝ ፡ ግን ፡ ዕብራይስጥና ፡ ዐረብ ፡ ትግሬና ፡ ዐማርኛም ፡ ሳይቀሩ ፡ አዳም ፡ የሚሉትን ፡ ሰውጠ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ፡ ይላል ፤ ፍችውን ፡ በቦታው ፡ ተመልከት ።

**አዳማዊ ፤** የአዳም ፡ ዘር ፡ ሰው ፤ ወይም ፡ ባሕ ርዩና ፡ ግብሩ ፡ ተፈጥሮው ። **ልሕሸት ፡ አዳማዊት ፡** (ያዕ ፡ ዘእል) ።

(ጥ) **አድሞ ፤ ሞት ፤ (አደመ ፡ ይኤድም ፡ የአ ድም) ፤** ማማር ፡ መዋብ ፤ ደማም ፡ ደመ ፡ ግቡ ፡ መኾን ፡ ማስጕምዠት ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ፤ በባሕርይ ፡ በመልክ ፡ አዳምን ፡ መምሰል ፤ ከርሱ ፡ መተካከል ። **ሥን ፡ ወባ ሕይ ፡ ይኤድማ ፡ ለዐይን ፡፡ እንተ ፡ አደመቶ ፡ እም ኔሆን ፡ ብእሲት ፡፡ ሶበ ፡ ተፈሥሑ ፡ በአድሞ ፡ ሥነ ፡ ላሕዮሙ ፡፡ ቍርባንክሙ ፡ ኢይኤድመኒ ፡፡ አደሞ ፡ ቃላ ፡ በቅድሜሁ ፡፡ በከመ ፡ ይኤድመከ ፡ ግበር ፡ ም ስሌየ ፡፡ ዙሉ ፡ ዘንበየ ፡ ወአደሞ ፡ ለሰሎሞን ፡ በነፍሱ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡** (ሚራ፵ ፡ ፳፱ ። አስቴ፪ ፡ ፱ ። ጥበ፲፫ ፡ ፫ ። ኤር፮ ፡ ፳ ። ዮዲ፲፩ ፡ ፳ ። ጦቢ፫ ፡ ፮ ። ፩ዜና ፡ ፯ ፡ ፲፩) ። በአደመ ፡ ፈንታ ፡ አስተአደመ ፡ ይላል ፤ በሕተት ፡ ነው ። **ኢያስተኤድሞ ፡ ህጕሎሙ ፡ ለሕያዋን ፡** (ጥበ፩ ፡ ፲፫) ።

**አዳም ፤** የሚያምር ፤ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፤ ውብ ፡ ደማ ፡ መልከም ፤ መልካ ፡ መልካም ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፤ ነቋር ፡ ጸጓር ፡ ፀዋማ ፡ ጸያፍ ፤ የዋሀ ፡ መ ካሕ ፤ ሀካይ ፡ ይሆን ፡ የመሰለ ፡ ዐንጕል ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ቅጽልነቱ ፡ ፈናፍንታም ፡ ነው ፤ ለወንድም ፡ ለሴትም ፡ ይኾናል ። **ወራዙት ፡ ዘአዳም ፡ አርአያሆሙ ፡፡ አዳም ፡ አጥባትኪ ፡ እምወይን ፡፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ቈሪር ፡ አዳም ፡ ለነፍስ ፡ ጽምእት ፡፡ አዳም ፡ ወሠናይት ፡፡ አዳመ ፡ ዝክር ፡ ወዜና ፡፡ ወኮነ ፡ አዳመ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ በቅ ድመ ፡ ንጉሥ ፡** (ዮሴፍ ። ማሕ፩ ፡ ፪ ። ምሳ፳፭ ፡ ፳፭ ። ድጓ ። ስንክ ፡ ሐም፲፱ ። ፩ዜና ፡ ፴ ፡ ፬) ።

**መአድም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ የሚያምር ። **እለ ፡ ሠናይ ፡ ራእዮሙ ፡ ወመ አድም ፡ ሥምሙ ፡፡ ብእሲ ፡ ቀይሕ ፡ መአድም ፡ ገጹ ፤ መአድምት ፡ ብእሲት ፡፡ መዐርዒር ፡ ነገር ፡ ወመአ ድም ፡ ንባብ ፡** (አፈ ፡ ተ፲፯ ። ገድ ፡ ተክ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፯) ።


**እዱም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ድምት) ፤** ያማረ ፡ ያጌጠ ፡ የተዋበ ፡ ውብ ፤ መልከም ፡ ደመ ፡ ግቡ ። ሰበ ፡

ሎረ ፡ በፍኖት ፡ ርእየ ፡ እዱመ ፡ ብእሴ ፡ ለቢሶ ፡ አል ባሰ ፡ ጸዐዳ ። እዱመ ፡ ዜና ። እድምት ፡ ሥን ፡ (ዮሴፍ ። አዋል) ።

**አአደመ ፤ (ያኤድም ፡ ያአድም) ፤ አው ፡ አስተአደመ ፤ ያስተኤድም ፡ ያስተአድም ፤** አሳመረ ፤ አስማመረ ፤ አደነቀ ፤ አመሰገነ ፤ አጣጣመ ፤ ደስ ፡ ብሎት ፡ ሠራ ፡ አዘጋጀ ። **ኅፍረት ፡ አስተአድም ፡ ብእሲት ፡ ባዕድ ። አየ ፡ እምክልኤቱ ፡ ግብራት ፡ ትዌድስ ፡ ወታስተኤድም ። ኢያስተአደምኩ ፡ ስቴሁ ፡ ሰንጉሥ ። ወባዕድኒ ፡ ዘአስተአደሙ ፡ በሕይወቶሙ ፤** (ሢራ፡፵፩ ፡ ፲፯ ። አፈ ፡ ድ፳፯ ። አስቴ፱ ። ፪ዕዝ ፡ ፩ ፡ ፯) ።

**አድሜ ፤—ቀጠሮ ፤—ዐደመ ።**

**አድማስ ፤ (ጽር ፡ አዳማስ ። ዕብ ፡ አናኽ ። ዐረ ፡ ዚ፫) ፤** ናእክ ፤ ርሳስ ፤ ወይም ፡ ብረት ፤ የሐዲስ ፡ ሕንጻና ፡ የማእዝን ፡ ልክ ፡ መመዘኛ ፡ ማስተካከያ ፤ ነደቅት ፡ በቀጭን ፡ ገመድ ፡ ማፍ ፡ አስረው ፡ እንደ ፡ መልሕቅ ፡ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚሰዱት ። የድንጊያው ፡ ቀራ ፡ የማእዝኑ ፡ ሥራ ፡ አለአድማስ ፡ አይቃናም ፤ ማእዝኑ ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ስም ፡ ነሥቶ ፡ አድማስ ፡ ይባላል ። **ወናሁ ፡ ብእሲ ፡ ይቀውም ፡ ዲበ ፡ አረፍት ፡ አድማስ ፤ ወውስተ ፡ እዴሁ ፡ አድማስ ። ክመ ፡ ቅጽረ ፡ አድማስ ፤** (ዓሞ፯ ፡ ፯ ፡ ፰ ። ራእ ፡ ባሮ) ። አድማስ ፡ የልክ ፡ የሚዛን ፡ የማእዝን ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ባለቅኔዎች ፡ የምድር ፡ ዳር ፡ ዙሪያዋ ፡ ከበቢ ፡ ቅጥሯ ፡ ዳር ፡ ድንበሯ ፡



አድማስ ፡

ይሉታል ። **ወተሀውከት ፡ ዙላ ፡ ሀገር ፡ ኢየሩሳሌም ፤ ፍኖተ ፡ አድማስ ፡ መከራሃ ፡ አከኑ ፡ ኢይትፌጸም ። ወእንዘ ፡ ዳዊት ፡ ያስቁቁ ፡ በተፈልጦ ፡ አምዖን ፡ ነፍስ ፡ ካዕበ ፡ አደንገፆ ፡ ርሕቀተ ፡ አቤሴሎም ፡ አድማስ ፡** (ቅኔ) ።

**አድማስ ፤ (ዐረ ፡ አልማስ ። ዕብ ፡ ሐላሚሽ) ፤** የድንጊያ ፡ ንጉሥ ፤ አልማዝ ፡ ዕንቍ ፡ ፈርጥ ። ጥኑ ፡ ጠንካራ ፡ ደንጊያ ፤ ኵኵሕ ፡ እሳት ፡ የማይሰበር ፡ የማይፈነከት ። የነጠረ ፡ ብረት ፤ ደንጊያ ፡ የሚጠርብ ፡ ኵኵሕ ፡ የሚነድል ፡ የሚበሳ ፡ የሚሰረስር ። **እብን ፡ አድማስ ፡ ሠራዊ ፡ ወደምሳሴ ፡ ዙሉ ። ጽኑዕ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይትሔየክ ፤ ዘውእቱ ፡ እብን ፡ አድማስ ፡ ኀያል ። መሳዩ ፡ ኀዳውንት ፡ አድማስ ፤** (መቃ ፡ ገ፳፭ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፱) ።

**አደነ ፤—በቁሙ ፤ ሻ ፡ ፈለገ ፤—ዐደነ ።**

**አዶናይ ፤ (ዕብ ፡ አዶን ፤ ጌታ ። አዶኒ ፤ ጌታዬ ። አዶኒም ፡ ጌቶች) ፤** ስመ ፡ አምላክ ፡ ይ ፡ ዘርዝር ፡ ነው ፡ እግዚእየ ፡ አጋዕዝትየ ፡ ወይም ፡ ጌታዬ ፡ ጌቶቼ ። ሳንድም ፡ ለብዙም ፡ ይኾናል ፤ ዐዋጁ ፡ ግን ፡ የብዙ ፡ ወንድኝ ፡ ነው ፡ (ሕዝ፪ ፡ ፬) ። **ክመ ፡ ዝ ፡ ይቤ ፡ አዶናይ ፡ እግዚአብሔር ፡** ተብሎ ፡ ለአምላክ ፡ ሲቀጠልና ፡ የአምላክ ፡ ስም ፡ ሲኾን ፡ ምስጢሩ ፡ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ነውና ፤ አንድነትን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ሦስትነትን ፡ ያሳያል ፤ ዘይቤውም ፡ ጌቶቼ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ያሰኛል ። ይቤ ፡ አንድነቱን ፤ እግዚአብሔር ፡ ባሕርዩን ፡ መለኮቱን ፤ አዶናይ ፡ አካላቱን ፡ ያመለክታል ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ኢሳይያስ ፡ የሱራፌልን ፡ ምስጋና ፡ ፫ ፡ ቅዱስ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፤ **ወሰማዕኩ ፡ ቃሎ ፡ ለአዶናይ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ መኑ ፡ እፌኑ ፡ ወመኑ ፡ የሐውር ፡ ለነ ፡ ኀበ ፡ ዝ፡ሕዝብ ። ወእቤ ፡ ናሁ ፡ አነ ፡ ፈንወኒ ፡ ይ** ላል ። ለነ ፡ ዝርዝሩ ፡ ለአዶናይ ፡ ነው ፤ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርአያነ ፤ ንው ፡ ንረድ ፡ ያለውን ፡ ይመስላል ። አይሁድ ፡ ግን ፡ እንድ ፡ ገጽ ፡ ባዮች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ራሱን ፡ ከሱራፌል ፡ አግብቶ ፡ ይላሉ ። በኦሪትና ፡ በነቢያት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ አለ ፤ ኤሎሂን ፡ ተመልከት ። አዶናይ ፡ በቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ ለአምላክ ፡ ሲቀጸል ፡ እግዚእ ፤ ለሰው ፡ ሲቀጸል ፡ አጋዕዝት ፡ ይባላል ፤ ያውም ፡ ቢኾን ፡ ለብዙዎች ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ሳንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ አይቀጸልም ። ዕብራይስጡ ፡ **አዶናይ ፡ ሱኑና ፡ ኤል ፡ ቤት ፡ ዐብዴኼም ፡** ባለው ፡ ግእዙና ፡ ዐረቡ ፡ ሌላውም ፡ ኹሉ ። **አጋዕዝትየ ፡ ገሐሡ ፡ ቤተ ፡ ገብርክሙ ፡** እንዲል ፡ (ዘፍ፲፱ ፡ ፪) ። እግዚእ ፡ አጋዕዝት ፡ የሚያሰኘው ፡ አንቀጹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ፤ **ይቤ ፡ አዶናይ ፤ ገሐሡ ፡ አዶናይ ።**

**አዶናዊ ፤ አዶናይ ፤ (አዶናውያን ፡ አዶናይያን) ፤** እግዚኣዊ ፤ ወልደ ፡ እግዚእ ፡ ዘበቱ ፡ እግዚእና ። ዓለመኛ ፡ ባላዱኛ ፤ ዘመናይ ። **ንትቀበል ፡ መርዓዌ ፡ አዶናዌ ፤** (ድጓ) ። እዱኛ ፡ እዱኛ ፡ ማለት ፡ ቅሉ ፡ አደን ፡ ከማለት ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**አዱፍ ፤ ፎት ፤ (አደፈ ፡ የአድፍ ፡ ይእድፍ) ፤** ማደፍ ፡ መኾለፍለፍ ፤ እድፋም ፡ ጕድፋም ፡ መኾን ።

**አደፍ ፤ (ብ ፡ አእዳፍ) ፤** በቁሙ ፡ እድፍ ፡ ጕድፍ ፤ ርስሐት ፡ እዳው ። **ግብ፡ዘምሮእ ፡ አደፈ ፡ ወዕዬ ፡** (ስንክ ፡ ሐም፳) ።

**አደፍ ፤** የሴቶች ፡ ግዳጅ ፡ ትክቶ ። ተርታ ፡ መናኛ ፡ እኸል ፡ ጕፋሽ ፡ ገለባ ፡ ሐሠር ፡ ያለው ። ጥሩና ፡ አደፋ ፡ እንዲሉ ፡ (ዐማርኛ) ።

**አደፋዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** እድፋም ፡ ጕድፋም ፡ ጭቅቅታም ።

**አዳር ፤ (ራት ። ዕብራ) ፤** የዕብራውያን ፡ ወር ፡ መጋቢት ፡ የጥቅምት ፡ ፯ኛ ፡ የሚያገባ ፡ ፲፪ኛ ፤ በሠግር ፡ ጊዜ ፡ ፲፫ኛ ፡ (አስቴ፫ ፡ ፯ ። ዕዝ፮ ፡ ፲፭) ። ፍችው ፡ ዕበይ ፡ ርሕብ ፡ ልዕልና ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ኅዳርን ፡ ተመልከት ። (ታሪክ) ፡ በ፫ ፡ በ፫ ፡ ዓመት ፡ አንዳንድ ፡ ወር ፡

ሠግር ፡ እየጨመረ ፡ ዓመታቸው ፡ ፲፫ ፡ ወር ፡ ይኾናል ፡ ስለዚህ ፡ መጋቢት ፡ ከሰቀ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መጋቢት ፡ ይሳሉ ። ይኸውም ፡ በሐይ ፡ ከጨረቃ ፡ የምታተርፈው ፡ ፲ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ አስና ፡ ፱ ፡ ተሰብስቦ ፡ ነው ። **ወሰሰ ፡ ሠለስቱ ፡ ዓመት ፡ ይሠግሩ ፡ አሐደ ፡ ወርኃ ፡ ወይከውኑ ፡ አዳራት ፡ ክልኤቱ** ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ።

**አደር**፤ እሾኽም ፡ ዕንጨት ፡ ጋሬጣ ፡ እሾኹ ፡ እንደ ፡ ችንካር ፡ ያለ ፡ መርዛም ።

**አዴራ**፤ አደርማ ፡ ቀኖት ፡ የቀኖት ፡ ስም ፡ አራተኛ ፡ ቀኖት ፡ የቀኝ ፡ እግሩ ። **ሳዶር ፡ አላዶር ፡ ዳናት ፡ አዴራ ፡ ሮዳስ ፡ ኀምስቱ ፡ ቅንዋተ ፡ መስቀል** ፡ (አዋልድ ፡ የጸሎት ፡ መጽሐፍ) ። ቀኖት ፡ ማለትም ፡ ችንካሩን ፡ ብቻ ፡ አያሳይም ፡ በቀረቱንም ፡ እንጂ ፡ በምስተኛው ፡ ቀኖት ፡ ኵናት ፡ ነው ።

**አዳር ፡ (ብ ፡ አዳሪም ፡ ዕብራ)**፤ ክቡር ፡ ምስጉን ፡ ታላቅ ፡ ገናና ። ጥቀ ፡ ተሰብሐ ፡ ባለው ፡ **ማህ ፡ አዲር ፡ ሽምኽ ፡ እንዲል** ፡ (መዝ ፡ ፺፫) ።

**አድሮሄም ፡ (ዕብ ፡ አዳሬሄም ። ጽር ፡ አዶሪም)**፤ በዐይቶሙ ፡ ጽንዓኒሆሙ ፡ ከቡራኒሆሙ ፡ መሳእክ(ህቅ)ቲሆሙ ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ ገባሮች ፡ ይሉታል ፡ (ነሐ፪ ፡ ፳) ።

**አድርያ ፡ አድርያቲክ**፤ የባሕር ፡ ስም ፡ በኢጣልያና ፡ በግሪክ ፡ መካከል ፡ ያለች ፡ (ግብሐ፳፯ ፡ ፳፯) ።

**አዴሮት ፡ (ዕብ ፡ አዴሬት ፡ ብ ፡ አዳሮት)**፤ የላይ ፡ ልብስ ፡ ታላቅ ፡ ሰፊ ፡ ጀቦ ፡ ካባ ፡ መጐናጠፊያ ፡ ኀይል ፡ ጽንዕ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ሥርጥ ፡ መንገድ ፡ ሰዳሪ ፡ ሽንን ፡ ይሉታል ፡ (ዋሬ ፡ ስዋ) ።

**አደስ ፡ (ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሀዳስ)**፤ በቁሙ ፡ የሽቱ ፡ ዕንጨት ፡ ሽንት ፡ ባርስንት ። ምርስኔን ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**አደሳን ፡ (ሳት ። ሱር ፡ ሀዳሲን ። ዕብ ፡ ሀዳሲም)**፤ አደሶች ፡ የሽንት ፡ የባርስንት ፡ ዛፎች ። **ማእከለ ፡ አዕዋም ፡ ዘአደሳን** ፡ (ዘካ፩ ፡ ፰) ። አንዳንድ ፡ መጠፍ ፡ ዘአደሹም ፡ ይላል ፡ አንዳንዱም ፡ አደሹምን ፡ ትቶ ፡ በአዕዋም ፡ ፈንታ ፡ ማእከለ ፡ ክልኤ ፡ አድባር ፡ ይላል ፡ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**አሀ ፡ (ዕብ ፡ አሀህ)**፤ ንኡስ ፡ አገባብ ። የሐዘን ፡ የጭንቅ ፡ ደሙታ ፡ የንቀፈታ ፡ ቃል ፡ መታመም ፡ መጕሰም ። አይ ፡ አዬ ፡ ዋይ ፡ ወዮ ፡ ወዲያልኝ ፡ ወዲያ ፡ እህ ፡ እህህ ፡ ሐሰ ፡ ኀይማ ፡ ይኾናል ። (ግጥም) ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ገባቶ ፡ አገሩን ፡ ሊሀናኔ ፡ (እኔ) ፡ ቀረን ። **አሀ ፡ አሀ ፡ እምሀቲ ፡ ኅፍረት ። አሀ ፡ እምሀቲ ፡ ሕሠም** ፡ (አፈ ፡ ተ፲፰ ። ፲፰ ። ሕዝ፲፱ ፡ ፲፱) ። ኹለተኛም ፡ አንክሮና ፡ ብዕሉን ፡ የደስታ ፡ ቃል ፡ ይኾናል ፡ ሐሰ ፡ ኀይማ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ዐማርኛው ፡ አይለወጥም ። **አሀ ፡ አሀ ፡ ሰርምፀ ፡ ቅኔሆሙ ። አሀ ፡ አሀ ፡ ሚ ፡ መንክር ፡ ወመድምም ። አሀ ፡ አሀ ፡ እንደደኒ ፡ ፍቅርከ** ፡ (ማንዝ ። አረጋ) ።

**አሆ**፤ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ የትሕትና ፡ የተአዝዞ ፡ ቃል ። ዕሺ ፡ በጎ ፡ በጄ ፡ ይኹን ፡ አደርጋለኹ ፡ ምስጢሩ ፡ እንደ ፡ መሐላ ፡ ነው ። **ወይቤሉ ፡ አሆ ፡ ናገብእ ፡ ሎሙ ፡ በከመ ፡ አዘዝከነ ፡ ከማሁ ፡ ንገብር ። ኢትበልዎ ፡ አሆ ፡ ለፍትወቱ ። አሆ ፡ ብሂልየ ፡ ለመማክርትየ ። አሆ ፡ በሃሊት ። አሆ ፡ በልኒ ። በእንተ ፡ አሆ ፡ ብሂሎቱ ፡ ወትሕትናሁ** ፡ (ነሐ፭ ፡ ፲፪ ። ሮሜ፯ ፡ ፲፪ ። አስቴ ፡ ፫ ። ዳንኤ ፡ ፳ ። ያዕ፫ ፡ ፲፯ ። ፊልክ ፡ ፻፳፱) ።

(ጥያ) **አሀያ ፡ (ቅብጥ ፡ ሂያ ፡ ሂሂያ)**፤ በቁሙ ፡ አድማ ፡ ሲሪሙኹ ፡ ሀሀሀ ፡ የሚል ። (ቱረት) ፡ ዳኛ ፡ ሲያጋድል ፡ በዳኛ ፡ አሀያ ፡ ሲያጋድል ፡ በመሐኛ ። አሀያ ፡ ሠባ ፡ ከልቀበላ ፡ ምን ፡ ረባ ።

(ላ) **አሀያ ፡ ሽራሀያ ፡ (ዕብ ፡ ኤሀዬ ፡ አሼር ፡ ኤሀዬ)**፤ በቁሙ ፡ አምላክ ፡ እሄሉ ፡ ዘእሄሉ ፡ ወይም ፡ እክውን ፡ ዘእክውን ፡ (ዘፀ፫ ፡ ፲፬) ። ሦስተኛም ፡ በዚሁ ፡ ቍጥር ፡ ከዚሁ ፡ አያይዞ ፡ ኤሀዬ ፡ ሽላሐኒ ፡ ይላል ፡ እሄሉ ፡ ፈነወኒ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አንቀጹን ፡ ስም ፡ አድርጎታል ። ዘይቤው ፡ ላባቶቻችኹ ፡ ለሦስቱ ፡ ኹሉ ፡ በሕይወታቸው ፡ ጊዜ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌክ ፡ ያላቸው ፡ አምላክ ፡ ያሰኛል ፡ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አይናይ ፡ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ አስበው ፡ ባ፲፭ ፡ ቍጥር ፡ ያነበበውን ፡ ከዚያው ፡ ባ፲፰ኛው ፡ ተርጕሞታል ፡ ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ ዘይቤውን ፡ ሳይሹ ፡ ዝሀሎ ፡ ወይሄሉ ፡ ብለው ፡ የምስጢር ፡ አፈታት ፡ ይፈቱታል ። ያህና ፡ ይሆዋን ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**አሄል ፡ (ዕብራ)**፤ ድንኳን ፡ የድንኳን ፡ ስም ።

**አሆላ**፤ ድንኳና ፡ ድንኳንነቷ ።

**አሆሊባ**፤ ድንኳኔ ፡ በርሷ ፡ ድንኳኔ ። አን ፡ ትቶ ፡ ሀላ ፡ ወሀሊባ ፡ ይላል ፡ ግድፈት ፡ ነው ። አሆላ ፡ ሰማርያ ፡ አሆሊባ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ (ሕዝ፳፫ ፡ ፳—፬) ።

**አውግሥጦስ**፤ የሮማውያን ፡ ወር ፡ ነሐሴ ፡ አውግሥጦስ ፡ የነገሠበት ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**አዊው ፡ ዎት ፡ (አወ ፡ አወወ ፡ የአውው ፡ ይአ(ው)ወው)**፤ ማወው ፡ ዥብኛ ፡ መሮኸ ፡ አዉ ፡ አዉ ፡ ማለት ። ማያያዝ ፡ ማሜፈር ፡ ማከታተል ፡ ያንን ፡ ደግሞ ፡ ማሻሻል ፡ ማማረጥ ፡ ማበላለጥ ። እውጥ ፡ ዋዌ ፡ ዋው ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ እውጥ ፡ የሕፃናት ፡ ንጥየ ፡ ተውኔት ፡ ዋዌንና ፡ ዋውን ፡ በየታው ፡ ተመልከት ።

(ላ) **አው ፡ (ዕብ ፡ አ ። ሱር ፡ ወዐረ ፡ አው)**፤ ንኡስ ፡ አገባብ ። አማፈሪ ፡ አንጻጻሪ ፡ ቃል ፡ ዋዌ ፡ ወይ ፡ ወይም ፡ በጥያቄ ፡ ጊዜ ፡ ወይስ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከማወ ፡ ጋራ ፡ አው ፡ ውእቱ ፡ ወሚመ ፡ አንተ ፡ ኀው ፡ ሊተ ፡ እያለ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ዋዌ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ብቻውን ፡ በመከታተል ፡ ይገባል ። **ለእመ ፡ አበስኩ ፡ ለከ ፡ በአእምሮ ፡ አው ፡ በኢያእምሮ ፡ አው ፡ በጽልሑት ፡ አው ፡ በእከየ ፡ ልብ ፡ አው ፡ በገቢር ፡ አው ፡ በተናግሮ ፡**

አው ፡ በናእስ ፡ ልብ ። ዕሥራ ፡ ወንምስቱ ፡ አው ፡ ሠላሳ ። አው ፡ ሠምዕ ፡ አው ፡ ዘይት ። ቦኑ ፡ አው ፡ አልቦ ። ንግሩኒ ፡ አው ፡ ትሠውዑ ፡ አው ፡ ኣነሥኢ ፡ ባዕሌክሙ ፡ ጥብጣቤ ፡ ሐብል ፡ (ቅዳ ። ዮሐ፰ ፡ ፲፱ ። ፊል ፡ ፲፮ ፡ ፮ ። መቃ ፡ ገ፱) ። ቀዊንት ፡ በሳስው ፡ አው ፡ ወአው ፡ አይልም ፡ ምስጢሩ ፡ ማማረጥና ፡ ማሻሻል ፡ ነው ።

**እወ ፡** (ዐረ ፡ ኢ.ይ ፡ ነዐም ። ዕብ ፡ ሄን) ፡ ንባር ፡ አንቀጽና ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ። ደምንታ ፡ ቃል ፡ ፍችው ፡ አወን ፡ እውነት ፡ በውነት ። ቦኑ ፡ ቃል ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ወይቤሎ ፡ እወ ፡ ቦ ። እወ ፡ እጐየ ። እወ ፡ እግዚእ ፡ ፍትሖሙ ። እወ ፡ እግዚእ ፡ አምላክ ፡ ሥሉ ፡ እወ ፡ እግዚእ ፡ እጓዜ ፡ ሥሉ ፡ እወ ፡ እግዚእ ፡ ፈጣሬ ፡ ሥሉ ። ወይኩን ፡ ነገርክሙ ፡ እመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ፡ (ኤርሚ፱ ፡ ፲፮ ። ፊልሞ ፡ ፳ ። ማንዘ ። ቅዳ ። ማቴ፭ ፡ ፴፯) ። የቀረውን ፡ በደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ተመልከት ፡ (ዕር፲፭ ፡ ቍ፲፱) ።

**አውያት ፡**—ፊውሽት ፡ ቡታ ፡—ዐወየ ፡ ዐውየወ ።

**አውክክ ፡**— አወከ ፡ አስፈራ ፡— ወከ.ክ ፡ ወከ ፡ ወክክ ።

**አውክሞዲስ ፡** (ጽር ፡ አውክሞዱስ ። ዕብ ፡ ጊብዓት) ፡ ቃናሽ ፡ ተራራ ፡ ገባ ፡ ባማ ፡ የላእል ፡ ክተማ ፡ (ኢሳ፣ ፡ ፲፭ ፡ ፱ ። ፳፯ ፡ ፩) ። ጽኑ ፡ በረሓ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ተራራ ፡ ኩረብታ ፡ ዋሻ ፡ ፍርኰታ ፡ ያለበት ፡ ድኰላ ፡ ሠማ ፡ አጋዘን ፡ ድሩሳ ፡ ሴላውም ፡ ኹሉ ፡ አውሬና ፡ እንስሳ ፡ የሚታደንበት ፡ (ኢሳ፣ ፡ ፳፫ ፡ ፲፱ና ፡ ፲፰ ፡ ፲፱) ።

**አውክዐ ፡**—አደከመ ፡ አሰለቸ ፡—ወከ.ዐ ፡ ወክዐ ።

**አውል ፡** (ዐረ ፡ አል) ፡ ጊሜ ፡ የምድር ፡ ላቦት ፡ እንኰሰት ፡ የጉም ፡ ሽንት ፡ እንደ ፡ ጤፍ ፡ ቅንጣት ፡ ያለ ፡ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ጤዛ ፡ ይሉታል ። ይባርክዎ ፡ ጠል ፡ ወአውል ። ወትተርፍ ፡ ምድር ፡ ባሕቲታ ፡ ዘእንበለ ፡ ጠል ፡ ወአውል ። ክነፊ ፡ አውብ ፡ (ዳን፫ ፡ ፶፰ ። ቀሌ ። አሞል) ።

**አውሎ ፡**—ጥቅል ፡ ነፋስ ፡—ዐዊል ፡ ያለ ፡ ዐውሎ ።

**አውሎግያ ፡** (ጽር ፡ ኤፍሎጊአ) ፡ ቡሩክ ፡ ኅብስት ፡ ተረፈ ፡ መሥዋዕት ፡ ከቍርባን ፡ በኋላ ፡ በቡራኬ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጥ ። እንዘ ፡ ይሜጡ ፡ አውሎግያ ። ኅብስተ ፡ አውሎግያ ፡ (ቅዳ ። ኪዳ) ።

**አውሎማዮስ ፡ ጌርዮስ ፡** (ጽር ፡ ኤፍሎጊቶስ ፡ ኪ.ሪዮስ) ፡ ቡሩክ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ቅዳ) ።

**አውሎግሰን ፡** (ጽር ፡ ኤፍሎጊሰን) ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ባርክ ። መንክሳት ፡ ግን ፡ ቃለ ፡ ጽዋዔ ፡ ይሉታል ፡ ቤቶች ፡ ባለቤቶች ፡ እንጂ ፡ እንተኒ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አውሎግሰን ፡ ብለው ፡ ይጠራሉ ፡ ፍችውንም ፡ ክፈት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፡ አረጋዊ ፡ ዘይደልዎ ፡ ክብር ፡ ይሉታል ፡ (ገድ የ.ሐ) ።

**ኤውላጦን ፡** (ጽር ፡ ሄዊላት ። ዕብ ፡ ሐዊላ) ፡ ስመ ፡ ነገድ ፡ የሰው ፡ ስም ፡ የካም ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የኵሽ ፡ ኹለተኛ ፡ ልጁ ፡ የሳባ ፡ ታናሽ ። ጭጻ ፡ ጭጻዊ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፯) ። ምድረ ፡ ኤውላጦን ፡ (ዕብ ፡ ኤሬጽ ፡ ሐዊላ) ፡ የሐዊላ ፡ መሬት ፡ የወርቅ ፡ አሸዋ ፡ ድቡሽት ፡ ወርቅ ፡ እንዳሸዋ ፡ የሚታፈስበት ፡ ክባይ ፡ በመለስ ፡ ያለ ፡ ቈላ ፡ ዳንግላ ፡ ምድረ ፡ ሽንቅላ ፡ ወዲያ ፡ ማይም ፡ ባባይና ፡ ባባይ ፡ መካከል ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ እስከ ፡ ክርቱም ፡ ያለው ፡ ሽናጣ ፡ ሸጣጣ ፡ ገሞላላ ፡ ሞላላ ፡ ሸንጎ ፡ የሱዳን ፡ ቀበሌ ፡ ሳይቀር ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪) ። ሙሴ ፡ ፵ ፡ ዘመን ፡ በሱዳን ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ኖረ ፡ የሐዊላን ፡ ብዕል ፡ ወርቋን ፡ ወርቃምነቷን ፡ የወርቋን ፡ ጥሩትና ፡ ብዛት ፡ ባየው ፡ ባወቀው ፡ ተናግሯል ፡ (ዮሴፍ) ። ባገራችንም ፡ አሬ ፡ ታሪክ ፡ ሙሴ ፡ በትግሬ ፡ እስከክሮስም ፡ እስከ ፡ ሽሚዛና ፡ በጐንደርም ፡ እስከ ፡ ደንቢያና ፡ እስከ ፡ ጣና ፡ መጥቶ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ። ርሱም ፡ ራቡ ፡ ሱዳናዊት ፡ ሴት ፡ እንዳገባ ፡ በኦሪቱ ፡ ያመለክታል ፡ (ዘኍ፲፪ ፡ ፩) ። ፒዮርፒስ ፡ ጽሩይ ፡ ወርቀ ፡ ኤውላጦን ፡ (ደራ.ቢ) ።

**አውሎኒ ፡ ን ፡ ና ፡** (ጽር ፡ አፍሎኒ) ፡ ዙብጥ ፡ ቈላ ፡ ሜዳ ፡ ረባዳ ፡ (ዮዲ.፯ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ፲ ፡ ፲) ።

**አውልዕ ፡** (ዕብ ፡ ኤሎን ፡ አሎን) ፡ ጥኑ ፡ ጠንካራ ፡ ዕንጨት ፡ ብርቱ ፡ ዛፍ ፡ በሎጥ ፡ (ዘፍ፲፫ ፡ ፩) ።

**አውልዕ ፡** (ዐረ ፡ ወለዐ ፡ አበራ ፡ ለኰሰ) ፡ የበረሓ ፡ ዛይት ፡ ወይራ ፡ መራራ ፡ ጠንካራ ፡ ጥንካሬው ፡ እንደ ፡ በሎጥ ፡ ያለ ። አውልዐ ፡ ገዳም ። ወጽንዑ ፡ ከመ ፡ ጽንዐ ፡ አውልዕ ። ዕፀ ፡ አውልዕ ፡ (ሮሜ፲፩ ፡ ፲፯ ፡ ፳፬ ። ዓሞ፱ ፡ ፱ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**አውናን ፡** (ጽር ፡ አፍናን ። ዕብ ፡ አናን) ። የሰው ፡ ስም ፡ ፪ኛው ፡ የይሁዳ ፡ ልጅ ፡ (ዘፍ፴፰ ፡ ፱) ። አውስበ ፡ አውናን ፡ የአውናን ፡ ዕምረት ፡ ሩካቤ ፡ አውናናዊ ፡ ሥራ ፡ ፈቃድን ፡ ፈጽሞ ፡ ዘር ፡ አስመልበጥ ፡ ከውጭ ፡ ማፍሰስ ፡ (አንቀጸ ፡ ንስሐ ፡ ወይም ፡ መጽሐፈ ፡ ኑዛዜ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፳፱ ፡ ፳)) ።

**አውሥአ ፡**— አስደራገ ፡— ወሚእ ፡ ወሥአ ።

**አፍ ፡**— በቈሙ ፡— ዐዊፍ ፡ ያፈ ።

**አውቃፍ ፡**—አንበሮች ፡—ወቀፈ ።

**አውርዮን ፡** (ጽር ፡ አውሪዮን) ፡ ኋስም ፡ ሳኒታ ፡ (ዘኍ፲፱ ፡ ፳፩) ።


**አርያሬስ ፡** (ዕብ ፡ አር ፡ ሔሬስ) ፡ ዐሐይ ፡ ስመ ፡ ፀሐይ ፡ ምዕሊ ፡ ፀሐይ ፡ አር ፡ ጸዳሉ ፡ ብርሃኑ ፡

ቀርኑ ፡ ምዕዛሩ ፡ ያሬስ ፡ ለሌዳው ፡ ነበቡ ። ቆማስን ፡ ተመልከት ፡ (ሔኖ፻፳፫ ፡ ፳) ። **ኦርያሬስ ፡ ሰማይ ፡ ልብ ስኪ ፡ ወአማእንኪ ፡ እብላ ፡፡ ሰላም ፡ ለእንጣዎስ ፡ ለሃ ይማኖቱ ፡ ዘአጽደላ ፡ እምኦርያሬስ ፡ ወእብላ ፡፡ እ ምታስግዱ ፡ ብርከ ፡ ለኦርያሬስ ፡** (ደራሲ ። ስንክ ፡ ኅ ሐ፲፯ ። ኅዳ፱) ።

**አውራቂስ ፤ (ጽር ፡ ሄውሮክሊዶን) ፤** ብርቱ ፡ ነፋስ ፡ ባሕር ፡ የሚደርጥ ፡ የሚያናውጥ ፡ መርከብ ፡ የሚንጥ ፡ የሚገለብጥ ። ጥፋንቂስን ፡ ኢይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ግብ፳፯ ፡ ፲፬) ።

**አውራስ ፤ (ጽርእ) ፤** ጸዳል ፡ ብርሃን ፡ ነጸብ ራቅ ፡ ውጋጋን ፡ (ሕዝ፰ ፡ ፪) ።

**አውስት ፤ (ጽር ፡ ጊብስ) ፤** ንስር ፡ የጥንብ ፡ አሞራ ፡ አስቀድሞ ፡ ዐይን ፡ የሚያንቁር ፡ ፊት ፡ የሚ ሸፍር ፡ የሚጐፈጭር ፡ ዐይን ፡ ሳያወጣ ፡ የማይበላ ። (ሙሾ) ፤ ዘምቶ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ያዝንለት ፡ አያጣ ፡ አ ሞራ ፡ እንኳ ፡ ወርዶ ፡ ፊቱን ፡ ነጭቶ ፡ ወጣ ። **አውስ ትኒ ፡ ሐቂፎ ፡ ዕጕሊሁ ፡ ይበይት ፡** (ኢዮ፴፱ ፡ ፳፯ ። ሔኖ፹፱ ፡ ፲ ። ፯ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ፡ ፲፯) ።



አውስት ፡

**አዊት ፤ (ዕብ ፡ ኦት) ፤** ምልክት ፡ ፊደል ፡ ታ ምራት ፡ ገቢረ ፡ ኀይል ። የዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ በዓመና ፡ በዓል ፡ ምልክታም ፡ ባለምልክት ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለ ቅኔዎች ፡ ግን ፡ ያገር ፡ ስም ፡ የወይን ፡ እሸት ፡ ጊዜ ፡ ይሉታል ። **በዓል ፡ ዘስሙ ይ ፡ ውእቱ ፡ ዮሐንስ ፡ አዊት ፡፡ ዘአዊት ፡ ዮሐንስ ፡** (አብጥሊ ። አዋል) ።

**አወተ ፤ (ሐባብ) ፤** ተለቃ ፡ ተበደረ ፡ ታደለ ፡ ተቀበለ ።

**አወት ፤** ልቃሕ ፡ ጸጋ ፡ ዕድል ።

**አውታይ ፤ ን ፤ (ዐረ ፡ አውታን) ፤** ታላቅ ፡ ሰፊ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ድንኳን ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ።

**አውቴ ፤ (ጽር ፡ ናዎት ። ዕብ ፡ ናዮት) ፤** የቦታ ፡ ስም ፡ የጸሎት ፡ የትምርት ፡ ቤት ፡ መጋቢያ ፡ መ ሰብሰቢያ ፡ መከን ፡ ጉባኤ ። **አውቴ ፡ ዘራማ ፡** (፩ነገ ፡ ፲ ፱ ፡ ፲፱ ፡ ፳፫) ።

**አውተረ ፤ —አስደራጊ ፤ —ወተር ፡ ወ ተረ ።**

**አዚብ ፤ ቦት ፤ (አዘበ ። ዐረ ፡ ወሱር ፡ ዛብ ። ዕብ ፡ ዘብ) ፤** መፍሰስ ፡ መንዣረር ፡ መንፎክ ፡ ፈር ፡ ፊር ፡ ጭርቅ ፡ ጭርቅ ፡ ጡብ ፡ ጡብ ፡ ማለት ፡ የሽንት ፡ የዘር ፡ የወተት ፡ የደም ፡ የፈሳሽ ፡ ኹሉ ።

**አአዘበ ፤ አስተአዘበ ፤** ሸነ ፡ ሸና ፡ አጨረቀ ፡ ረጨ ፡ ፈንጠቀ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ስለለ ፡ ጕበኘ ፡ ይ ሉታል ። **ዘያስተአዝብ ፡ ኀበ ፡ አረፍት ፡፡** ቅጥር ፡ ተጠ ግቶ ፡ የሚሸን ፡ ውሻ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፳፪ ፡ ፴፬ ። ፫ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፳፳ ። ፬ነገ ፡ ፱ ፡ ፰) ።

**ሚዛብ ፤ (ሐባብ) ፤** ዐይ ፡ መትረብ ፡ አሸንዳ ።

(ጥ) **ዝብ ፤ (ዐረ ። ዕብ ፡ ዘብ) ፤** አባለ ፡ ዘርዕ ፡ እስኪት ፡ ትእምርተ ፡ ተባዕት ።

(ጥዝ) **አዛብ ፤ (ዕብ ፡ ኤዘብ ። ጽር ፡ ሒሶፖስ) ፤** መርጫ ፡ የቀንበጥ ፡ ችቦ ፤ ታናናሽ ፡ ቀጠቅጭን ፡ ቀንበጥ ፡ ሐረግ ፡ መልከም ፡ ሽታ ፡ ያለው ፡ ሳይን ፡ ሳፍንጫ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፤ ናዕናዕ ፡ እደባን ፡ ጕፀ ፡ ሽቱ ፡ ፈላን ፡ በጡ ንባር ፡ የጠጅ ፡ ሣር ፡ ይሆን ፡ የመሰለ ። ቅጥይ ፡ የገበ ፡ በጕን ፡ የሚወጣ ፡ የሚያፈጠፍጥ ፤ በቤት ፡ በግንብ ፡ ላይ ፡ ሳይዘሩት ፡ የሚበቅል ፡ ሣር ፡ ቅጠል ፤ እንዳሸከትና ፡ እ ንደ ፡ ሙጃ ፡ ያለ ። ሁስጴን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ባለመጽሐፎች ፡ ግን ፡ ያንንም ፡ ይኽ ንም ፡ የተጕንጕን ፡ ሐር ፡ እደባን ፡ ስምዛ ፡ እሸክት ፡ ይ ሉታል ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፳፪ ። መዝ ፡ ፶) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ለናዕናዕ ፡ ብቻ ፡ ይነገራል ፤ መደበኛው ፡ ርሱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፳፫ ። ሉቃ፲፩ ፡ ፵፪) ።

**አዜብ ፤ —ደቡብ ፡ በረሓ ፤ —አዝየብ ።**

(ጥ) **አገዘ ፤ ዘት ፤ (አዘዘ ። ዕብ ፡ ጻዌህ) ፤** ማዘዝ ፤ መናዘዝ ፡ (ጥና) መናዘዝ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ወ ይም ፡ በገንዘብ ፡ በርስት ፡ ቍርጥ ፡ ቃል ፡ መስጠት ፡ አድርግ ፡ አታድርግ ፡ ይኹን ፡ አይኹን ፡ ማለት ፡ በቃል ፡ በጥፈት ፡ የሹም ፡ የቄስ ፡ ያባት ፡ የባለቤት ። (ተረት) ፡ ያል ተሾመ ፡ አያገዝ ፤ ያልቀሰሰ ፡ አይናዘዝ ። ሳይሞቱ ፡ መና ዘዝ ፤ ሳይመቱ ፡ መጋበዝ ። **አዝዘ ፡ ይኩን ፡ በጽሒፍ ፡ ወዘእንበለ ፡ ጽሒፍ ፡ ፈታሒ ፡ ያአዝዝ ፡ ሰባእካኒሁ ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚ ፡፡ አዘዘ ፡ ያብእዋ ፡፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘትኤዝዝ ፡ ለበዊእ ፡ ወለወፂእ ፡፡ መኑ ፡ አዘዘክሙ ፡ ትሕንጹ ፡፡ አዘዘ ፡ በእንተ ፡ ቤቱ ፡ ወሞተ ፡፡ ያአዝዝ ፡ እምቅድመ ፡ ምንዛሴናሁ ፡ በእንተ ፡ ንዋዩ ፡ ዘከመ ፡ ፈቀደ ፡** (ፍ ፡ ን ፡ ፵፩ ፡ ፩ ። ፵፫ ፡ ፫ ። ዮዲ፲፪ ፡ ፩ ። ፩ዜና ፡ ፲፩ ፡ ፪ ። ዕዝ፳ ፡ ፫ ። ፬ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳፫ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲) ።

**አዛዚ ፤ (ዚት ፡ ዝያን ፡ ያት) ፤** የሚያዝ ፡ የ ሚናዝዝ ፡ አዛዥ ፡ ናዛዥ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ። **እስ ፡ አልቦሙ ፡ አብ ፡ ወኢእም ፡ ወኢአዛዚ ፡፡ ረበየከ ፡ እ ግዚአብሔር ፡ አዛዜ ፡ ለሰንፋኤየ ፡** (ፍ ፡ ን ፡ ፳፱ ፡ ፫ ። ዮሴፍ) ።

**አአዘዘ ፤ አስተአዘዘ ፤** አሳዘዘ ፡ አዘገ ፡ ናገ ፡ አለ ፡ አዛዥነት ፡ ሾመ ፡ ወከለ ።

**መአዝዝ ፤ መስተአዝዝ ፤ (ዝት ፡ ዛን ፡ ዛት) ፤** የሚያዝ ፡ የሚያሳዝዝ ፡ አዛዥ ፡ አሳዛዥ ።

**ተአዘዘ** ፤ ታዘዘ ፡ ሰማ ፡ ተቀበለ ፡ ዐሺ ፡ በጎ ፡ አለ ፡ ተገዛ ፡ አገለገለ ። ወተአዘዘ ፡ ውእቱ ፡ ፀንበሬ ፡ የ ኄጦ ፡ ለዮናስ ። ኄሊ ፡ ዳእሙ ፡ ዘተአዘዝከ ። አልቦ ፡ ዘይትኤዘዝ ፡ ለቃልከ ። ልህቀ ፡ እንዘ ፡ ይትኤዘዝ ፡ ለአዝማዲሁ ። ተአዘዛ ፡ ለአምታቲክን ፤ (ዮናፀ ፡ ፲፩ ። ማሪቆ ፡ ፳፱ ። ዮዲ ፲፭ ፡ ፲፱ ። ድጓ ። ዲድ ፡ ፱) ።

**ተአዛዚ** ፤ የሚታዘዝ ፡ ታዛዥ ፡ ተለኣኪ ፡ አገል ጋይ ፡ ዐሺ ፡ ባይ ፡ ፈቃደኛ ። ተአዛዚ ፡ ደቦ ፡ ሰብእ ። ተ አዛዚ ፡ ለትፍሥሕት ፡ ወለኑዛዜ ። ረድኡ ፡ ወተአዛ ዚሁ ። ወትከውን ፡ ለከ ፡ ተአዛዚተ ፤ (ሔኖ፳ ፡ ፰ ። ሰ ንክ ፡ የካ፲፪ ። ጥቅ፲፱ ። ፈላስ) ።

**እዙዝ** ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ዝዛት) ፤ በቁሙ ፡ የ ታዘዘ ፡ የተገባ ፡ የተሠራ ፡ የተወሰነ ፡ የተጣፈ ፡ የተነገረ ። እዙዝ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ያጥፍእ ። ሀበ ፡ ክፍሎ ፡ ዘእ ዙዝ ፡ ለከ ። በከመ ፡ እዙዝ ፡ በእንቲኣሆሙ ፡ ወዓዲ ፡ እዙዝ ፡ ውስተ ፡ ሕግ ። ዘኢእዙዝ ፡ በውስተ ፡ ሕግ ፤ (ዮዲ፫ ፡ ፰ ። ሚራኛ ፡ ፴፰ ። ክፋ ፡ ፰ ። ዲድ ፡ ፲ ። ቀሌ) ።

**ትእዛዝ** ፤ (ዛት) ፤ በቁሙ ፡ እግዚኣዊ ፡ አምላ ካዊ ፡ ቃል ፡ ከሥራ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚሰጥ ፡ የሚጣፍ ፡ የሚነገር ፡ ሕግ ፡ ሥርዐት ፡ አድርግ ፡ አድርግ ፡ የሚል ፡ ፈቃድ ፡ ደንብ ፡ ዕድር ፡ የሚገባ ፡ ነገር ። እስመ ፡ በትእ ዛዝ ፡ ውእቱ ፡ ቃሉ ። ወፅአ ፡ ትእዛዝ ፡ እምኀበ ፡ ን ጉሥ ። ይወፅኡ ፡ እምትእዛዝነ ። በእንተ ፡ ትእዛዝ ፡ ወጽሕፈቱ ። ታቦት ፡ እንተ ፡ ትእዛዝ ። ዐቂበ ፡ ትእዛ ዛቲሁ ፡ ለእግዚ ። ትእዛዛት ፡ ሰብእ ። ትእዛዝ ፡ አበ ዊነ ፡ ሐዋርያት ፤ (ሉቃ፱ ፡ ፴፱ ። ዳንኤ ፡ ፲፫ ። ዮሴፍ ። ፍ ፡ ን ፡ ፺፭ ፡ ፰ ። ዘፀ፴፱ ፡ ፲፭ ። ሚራ፳፫ ፡ ፳፯ ። ኢሳ ፳፱ ፡ ፲፫ ። ቅዳ) ። ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ትእዛዝ ፡ መባሉ ፡ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ሲመጣ ፡ ነው ፡ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲመጣ ፡ ግን ፡ ልመና ፡ ጸሎት ፡ ይባላል ።

**ተአዘዘ** ፤ ተዛዘዘ ፡ ተደራረጊ ።

**አስተኣዘዘ** ፤ አስተዛዘዘ ፡ ተዛዘዘ ፡ አለ ፡ አደ ራረገ ።

**መስተአዝዝ** ፤ የሚያስተዛዝዝ ፡ አስተዛዛኝ ።

**እዘዝ** ፤—ጽንዕ ፡ ኀይል ፤—ዕዘዝ ፡ ዐ ዘዘ ።

**እዚኅ** ፤ ኖት ፤ (አዝኅ ፡ የአዝኅ ፡ ይእ ዛኅ ። ዐረ ፡ እዘ ፤ ዐዘ) ፤ መብጣት ፡ መቍረጥ ፤ መ ሰንዘር ፡ መሠንጠቅ ፡ በቅዝዝ ፡ በጠርሙዝ ፡ በሱፋጭ ፡ በምላጭ ። ማገርት ፡ ማፍሰስ ፡ ማንዛት ፡ መወርዛት ። ጸ ወበኝ ፡ ተመልከት ።

**እዝኅ** ፤ (ኀት) ፤ ሻሮ ፡ ብልሐት ፡ ደንጊያ ፡ በረቦጭ ፡ ሲሰብሩት ፡ ስለታም ፡ ሱፋጭ ፡ ራስ ፡ የሚላጭ ። እብነ ፡ እዝኅ ። መጣብሕ ፡ ዘእዝኅ ። አንሥአ ፡ እ ዴሁ ፡ በእዝኅ ። ኰሸሐ ፡ እዝኅ ። ለኰሸሕ ፡ ወለእ ዝኅ ፤ (ኢያ፭ ፡ ፪ ። ፳፭ ፡ ፲፬ ። ኢዮ፳፭ ፡ ፱ ። ጥበ፲፭ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፶፪) ።

**እዝኅ** ፤ (ኀት) ፤ በቁሙ ፡ እሾ ፡ የደም ፡ ውሃ ፡ ቅራሪ ፡ ጥንፋፊ ፡ የመግል ፡ ትራፊ ፡ ከተበጣ ፡ ወይም ፡ እሳት ፡ ከፈጀው ፡ ካበጠ ፡ ከቈሰለ ፡ ገላ ፡ ከሐዲልና ፡ ከፀ ባራ ፡ ሸክላ ፡ የሚፈስ ።

**አዜብ** ፤ **አዝያብ** ፡ (ዐረ ፡ አዝዮብ) ፤ የማ እዝን ፡ ስም ፡ ንኡስ ፡ ማእዝን ፡ የአፍሪቃ ፡ ወገን ፡ በም ዕራብና ፡ በደቡብ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ የደቡብ ፡ ግራ ፡ ምዕ ራብ ፡ የመስዕ ፡ ትይዩና ፡ አንጻር ፡ ፊት ፡ ለፊት ። ባለብሉ ዮች ፡ ቈላ ፡ በረሓ ፡ ይሉታል ። ባርክ ፡ መስዐ ፡ ወአዜብ ። ነፋሰ ፡ አዜብ ። ንግሥተ ፡ አዜብ ። ከመ ፡ ውሒዝ ፡ ውስተ ፡ አዜብ ፤ (ቅዳ ። ሉቃ፲፪ ፡ ፶፭ ። ማቴ፲፪ ፡ ፵፪ ። መዝ ፡ ፻፳፭) ። ጽባሕ ፡ ምሥራቅ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አዜብ ፡ ይላል ፡ የመላሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ነ ፋሰ ፡ አዜብ ። አንሥአ ፡ አዜበ ፤ (ዘፀ፲ ፡ ፲፫ ። ኢዮ፴፯ ፡ ፳፱ ። መዝ ፡ ፸፯ ። ሔኖ፴፯ ፡ ፩) ።

(ጥ) **አዝሎ** ፤ ሎት ፤ (አዘለ ፡ ይኤዝል ፡ የአ ዝል ። ዐረ ፡ አዘረ ። ዕብ ፡ አዛር ፤ ቀነተ) ፤ ማ ደግ ፡ መጐልመስ ፡ ሰጌጥ ፡ ሰመሣሪያ ፡ መድረስ ፤ መጐ ልበት ፡ መግነን ፡ ኀይለኛ ፡ መኾን ።

**እዛል** ፤ ጕበዝ ፡ ጕልማሳ ፡ ብርቱ ፡ ጠንካራ ። በላ ፡ ሎ ፡ እዛል ፡ ዘኢይፈርህ ፡ ሞተ ፡ በቅድመ ፡ ቀታልያን ። አብ ፡ ኖብ ፡ ድንግል ፡ ወእዛል ፡ መስተ ጋድል ፤ (ስንክ ፡ ሐምሌ ። ቅዳ) ።

**እዘለ** ፤ (ዐረ ። ዕብ ፡ እዛል) ፤ ኼደ ፡ ነቀለ ፡ ጓዙን ፡ ዕቃውን ፡ አንሥቶ ፡ ወሰደ ፡ የነጋዴ ፡ የባለክራይ ።

**መእዝል** ፤ (ዕብ ፡ ምእዛል) ፤ የሚኼድ ፡ ነያጅ ፡ ገሥጋሽ ፡ ተመላላሽ ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፲፱) ።

**እዝል** ፤—የዜማ ፡ ስም ፤—ዕዝል ፤

**እዝመር** ፤—ደባበ ፡ ደበሳ ፤—ዘመረ ።

**አዚን** ፤ ኖት ፤ (አዘነ ፡ የአዝን ፡ ይእዝን ። ዕብ ፡ አዜን) ፤ መቀቀር ፡ መቀፈር ፡ ገሮ ፡ መስጠት ፡ ማቅረብ ፡ ለመስማት ።

**እዛኒ** ፤ **መእዝን** ፤ ቀቃሪ ፡ ቀፋሪ ፡ ሽምጣጭ ፡ አድማጭ ።

**እዝን** ፤ (ብ ፡ እዘን ፤ አእዛን ። ዕብ ፡ አ ዜን ። ሱር ፡ አዝና ፤ ኤዝና ። ዐረ ፡ ኡዝን) ፤ ገሮ ፡ መስሚያ ፡ ማድመጫ ፡ መያዣ ፡ መጨበጫ ፡ የመ




እዝን ።

ሣሪያ ። (ተረት) ፡ የነገር ፡ ባዕም ፡ በገሮ ፡ የእኽል ፡

ማዕዘም ፡ በጕረሮ ። እዝን ፡ ይፈልጥ ፡ ነገረ ፡ ወጕርዔ ፡ ይጥዕም ፡ እክለ ። ሰማዕነ ፡ በእዘኒነ ። ሕጽምሙ ፡ አእዛኒክሙ ፡ (ኢዮ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፵፫ ። ኪዳ) ።

**እዝናዊ ፤** ዦሯዊም ፡ ዦሯዊማ ፡ ቈራፋ ፡ ባለዦሮ ፡ ዦሮ ፡ ወዳጅ ።

**ማእዝን ፤ ማእዘን ፡ ት ፤ (ብ ፡ መአዝን ፡ ት ፡ ማእዝናት ፡ ማእዘንታት) ፤** በቁሙ ፡ የቤት ፡ ክፍል ፡ ለብቻው ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የተለየ ፡ እንደ ፡ ዦሮ ፡ ተመሳሳይ ፡ አንጻር ፡ ኹለተኛ ፡ ያለው ። መዠመሪያውን ፡ ምሥራቅ ፡ ቢሉ ፡ አንጻሩ ፡ ምዕራብ ፡ ሰሜን ፡ ቢሉ ፡ አንጻሩ ፡ ደቡብ ፡ መስዕ ፡ ቢሉ ፡ አንጻሩ ፡ አዜብ ፡ ሊባ ፡ ቢሉ ፡ አንጻሩ ፡ ባሕር ። ይቀውሙ ፡ ውስተ ፡ ኣሐቲ ፡ ማእዝን ፡ እመኣዝኒሃ ፡ ለቤት ፡ ክርስቲያን ። በማእዝነ ፡ ቤት ። እማእዘንት ፡ እስከ ፡ ማእዘንት ። ርእሰ ፡ ማእዘንት ። አርባዕቱ ፡ መኣዝነ ፡ ዓለም ። መኣዝኒሃ ፡ ለምድር ። መኣዝኒሆሙ ፡ ለእስራኤል ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፺ ፡ ፲፱ ። ኢሳ ፡ ተ፥፩፰ ። ዮሴ፩ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፻፲፯ ። ዘካ፬ ፡ ፲ ። ራእ፯ ፡ ፩ ። ሄኖ ፡ ፲፱ ፡ ፻፹) ።




ማእዝን ።

**መኣዝነ ፡ ሰብእ ፤** ፊቱ ፡ ኋላው ፡ ቀኙ ፡ ግራው ።

**ምእዙን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ዝንት) ፤** የተማዘነ ፡ አራት ፡ ገጽ ፡ ያለው ፡ ባራት ፡ ማእዝን ።

**አዘረ ፤—በተነ ፤—ዐዚር ፡ ዐዘረ ።**

**አዜራህ ፤—ዕርከን ፤—ዐዘረ ።**

**አገዘረቀ ፤—ኒል ፤—ዘረቀ ።**

**አሓ ፤—ላም ፡ በሬ ፤—አንጐ ፡ እኈ ።**

**አሕ ፤—እዩ ፡ ወዬ ፤—እህ ።**

**እሒድ ፤ ዶት ፤ (አሐደ ፡ ይእሕድ ፡ የ አሐድ ። ዕብ ፡ አሔድ) ፤** አንድ ፡ ማድረግ ፡ ማዋ ደድ ፡ ማስማማት ፡ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ ማዘመድ ፡ ማዋሐድ ፡ ምንታዌን ፡ ማጥፋት ። ወይም ፡ አንድ ፡ መ ኾን ፤ በቶዋሕዶ ፡ አንድ ፡ መባል ፡ ዋሐደን ፡ ተመልከት ።

**አሓዲ ፤ መእሒድ ፤** አንድ ፡ የሚያደርግ ፡ የ ሚያዋሕድ ፡ አዋሓጅ ።

**አሐድ ፤ (ዳት) ፤** ኅብረት ፡ አንድነት ። የተዋ ሐደ ፡ ኅብር ፡ አንድነት ፡ በራስ ፡ ቅሉ ፡ ብቻ ፡ ያሉ ያለ ፡ ብዙነት ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ባሕርይ ፡ የተ ቀመመ ፡ የተጠራቀመ ። ያንድ ፡ ቤት ፡ ኆጥር ፡ ካንድ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ያለ ። አሐዳት ፡ (አቡሻ ፡ ፲፩) ።

(ጥት) **አሐድ ፤ (አሐ(ድ)ት) ፤** አንድ ፡ ብቻ ፡ አን ዳች ። አሐዱ ፡ በየማንከ ፡ ወአሐዱ ፡ በፀጋምከ ፡ (ማር፲ ፡ ፴፯) ።

**አሐዱ ፤ (አሐቲ) ። ዕብ ፡ ኤሐድ ። ሱር ፡ ሐድ ። ዐረ ፡ አሐድ) ፤** የቍጥር ፡ ስም ፡ መዠመሪያ ፡ ቍጥር ፡ ከኹለት ፡ እስከ ፡ ምእልፊት ፡ ላለ ፡ ቍጥር ፡ ኹሉ ፡ ጥንትና ፡ መሠረት ፡ መነሻ ። አንድ ፡ አንዱ ።

**አሐድ ፤ አሐዱ ፤ (አሐ(ድ)ት ፡ አሐቲ) ፤** አንደኛው ፡ መዠመሪያው ፡ መነሻው ። ዝርዝሩ ፡ በቁም ፡ ቀሪ ፡ ኹኖ ፡ ያንን ፡ ባለቤቱን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አካል ፡ አያ ይዝም ፤ ብእሲሁ ፡ ብእሲታ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ስሙም ፡ ዐጸፋ ፡ ይባላል ፡ ዐጸፋም ፡ ቀድሞ ፡ ሲታወቅ ፡ ለተነገረ ፡ ነው ። በሌሎች ፡ ቋንቋ ፡ ግን ፡ አርቲክል ፡ ይባላል ፡ የ ስም ፡ አገባብ ፡ ወይም ፡ ተውሳክ ፡ ስም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የሚገባም ፡ በመነሻ ፡ እንጂ ፡ በመድረሻ ፡ አይደለም ፡ እ ልን ፡ ተመልከት ። የግእዝ ፡ አርቲክል ፡ ዝርዝር ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ካንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በቀር ፡ በስም ፡ ኹሉ ፡ አይገ ባም ፤ ባፈታት ፡ ግን ፡ ሰብእ ፡ ወእንስሳ ፡ ታድኅን ፤ ሰዉን ፡ እንስሳዉን ። ዘገበርከ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፤ ሰማዩን ፡ ምድሩን ፡ ያሰኛል ። አሐዱ ፡ እግዚአብሔር ፤ ወአሐዱ ፡ ሃይማኖት ፤ ወአሐቲ ፡ ጥምቀት ። አዳም ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ እምኔነ ። ኩኑ ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ። አሐቲ ፡ ሕፃን ፡ ለአቡየ ። አሐቲ ፡ እምአሐቲ ። እሠይም ፡ ሎሙ ፡ አሐደ ፡ ኖላዌ ። ዘአሐተ ፡ ብእሲተ ፡ አውሰበ ፡ (ኤፌ፬ ፡ ፭ ። ዘፍ፫ ፡ ፳፪ ። ሚክ፬፥፲ ፡ ፭ ። ሶቢ፫ ፡ ፲ ። መክ፳ ፡ ፳፯ ። ሕዝ፴፬ ፡ ፳፫ ። ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፪) ። በተገ ብሮ ፡ አሐዱ ፡ አሐቲ ፡ ያለውን ፡ በግዕዝ ፡ ጊዜ ፡ አሐደ ፡ አሐተ ፡ ማለቱ ፡ አርቲክል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፤ አርቲክል ፡ ባይኾን ፡ ግን ፡ የካዕብ ፡ ወራሽ ፡ ሳብዕ ፡ የግዕዝ ፡ ወራሽ ፡ ኃምስ ፡ ነውና ፡ አሐዱ ፡ አሐቲ ፡ ባለ ፡ ነበር ። ሌላው ፡ ኹሉ ፡ ያንድ ፡ ቤት ፡ አኃዝ ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አለ ተውል ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ በርባ ፡ ቅምርና ፡ በአኃዝ ፡ ቅጽል ፡ ቀሪ ፡ እይ ፡ (ዕር፩ ፡ ቍ፲፫ ። ዕር፲፩ ፡ ቍ፳፮፫) ።

**አሐድ ፤ (አሐት) ፤** አንደኛ ፡ አንደኛው ፡ (ዕር፲፩ ፡ ቍ፳፮፫) ፡ ተመልከት ።

**አሐዱ ፡ አሐዱ ፤** አንዱም ፡ አንዱም ፡ ራስ ፡ ራሱ ፡ አንዳንዱ ፡ ሰው ፡ (ዘፍ፵ ፡ ፭ ። ዘፀ፴፪ ፡ ፳፯ ። ፴፩ ፡ ፳፩) ።

**በበ ፡ አሐዱ ፤ በበ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፤** በያንዳንዱ ፡ በየብቻው ፡ በየራሱ ፡ በየራስ ፡ በየራሱ ፡ (ሱቱ ፡ ዕገ፲፩ ፡ ፳) ።

**ለለ ፡ አሐዱ ፤ ለለ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፤** ለያንዳንዱ ፡ ላንዱም ፡ ላንዱም ፡ ለኹሉ ፡ (ዘኍ፲፩ ፡ ፬) ።

(ጥት) **አሐት ፤** አንዲት ፡ አንድያ ፡ መዠመሪያ ።

**አሐቲ ፡ (አሐትዩ)** ፡ አንዲቱ ፡ አንደኛይቱ ፡ መዠመሪያይቱ ፡ ወይም ፡ አንዲ ፡ አንደኛዋ ፡ መዠመሪያዋ ።

**አሐተ ፡ (አሐቶዩ)** ፡ አንዲቱን ፡ አንደኛይቱን ፡ አንዲን ፡ አንደኛዋን ። መንሻው ፡ እ ፡ ማእዝ ፡ ሲኾን ፡ የድምፁ ፡ ኣ ፡ ራብዕ ፡ ሲኾን ፡ የቀረ ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ።

**አሐተኔ** ፡ አንድነት ፡ ባንድነት ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አንድነት ። ነበርነ ፡ አሐተኔ ። ተጋቢአነ ፡ አሐተኔ ። ይስተጋብኡ ፡ አሐተኔ ። እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ አሐተኔ ፡ (ቀሌ ። ዲድ ፡ ፩ ። ዮሐ፲፩ ፡ ፶፪ ። ግብ፪ ፡ ፩) ።

**መእሐድት** ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ፊት ፡ ፩ ፡ ኀመሣ ፡ ፩ ፡ ግዝም ፡ ፩ ፡ አፍኣ ፡ ፩ ፡ ወረፋ ፡ ፩ ፡ ፈፋ ፡ ፩ ፡ አውራጃ ፡ ፩ ፡ ቃጻ ፡ ፩ ፡ ተሰላ ፡ ፩ ፡ ትልም ፡ ፩ ፡ መዘረያ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ።

**ምእሕዳት** ፡ አንድ ፡ ስጥፍ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ አንድ ፡ ክፍል ።

**ተእሕደ** ፡ አንድ ፡ ኾነ ፡ አንድ ፡ ተባለ ።

**እሑድ ፡ (ዳን ፡ ዳት ፡ ሕድ)** ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ አንደኛ ፡ መዠመሪያ ፡ የዕለት ፡ ስም ። በዕለተ ፡ እሑድ ። በበ ፡ እሑድ ። ሰጸቢሐ ፡ እሑድ ። ወበእሑድ ፡ ሰንበት ። ናክብር ፡ እሑደ ፡ ሰንበተ ። በበይልዩ ፡ እሑዳት ፡ (ማብሰ ፡ ፯ ። ቆሮ፩ ፡ ፲፮ ፡ ፪ ። ማቴ ፳፰ ፡ ፩ ። ማርቆ፲፮ ፡ ፪ ። ዲድ ፡ ፴፩ ። ፈልክ ፡ ፹፲) ።

**ትእሕድ ፡ ትእሕዳት** ፡ አንድነት ፡ አንድ ፡ መኾን ፡ መዋሐድ ፡ መተባበር ።

**እሕድ** ፡ የጊዜ ፡ ቅጽል ። እሕደ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ። ባላገር ፡ ግን ፡ አንደዜ ፡ አንደዜ ፡ ይላል ።

**ተአሐደ** ፡ ተዋሐደ ፡ ተወሓሐደ ፡ አንድ ፡ ተኳኋነ ፡ ተባበረ ።

**አሐዝ ፡—ቍጥር ፡—እኂዝ ፡ አኀዝ ።**

**አሑር ፡—አውራ ፡—ሐዊር ፡ ሖረ ፡ አሖረ ።**

(ጥ) **አሐቲ፡—እንዲት፡—አሐድ፡እሑድ፡ አሐደ ።**

**እኂው ፡ ዎት ፡ (አኀወ ፡ ይእኁ ፡ ይእኀው)** ፡ መወንድም ፡ ወንድም ፡ ማድረግ ፡ መሳብ ፡ ማቅረብ ፡ ወንድሜ ፡ ወንድሜ ፡ ማለት ፡ (ዮሐ፭ ፡ ፲፯ ። ማቴ፳፫ ፡ ፰) ።

**እኀው ፡ እኁ ፡ እኍ ፡ (ዕብ ፡ አሕ ። ሱር ፡ አሓአ ። ዐረ ፡ አኅ)** ፡ ወንድም ፡ ወልደ ፡ እም ፡ የናት ፡ ያባት ፡ ልጅ ፡ በባትና ፡ በናት ፡ የሚገጥም ፡ በቀዘሩበት ፡ ተዘርቶ ፡ በበቀሉበት ፡ የበቀለ ፡ ወይም ፡ ያባት ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ የናት ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ እኩል ፡ ወንድም ። የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ ወገን ፡ ጎረቤ ፡ ባልንጀራ ፡ ወዳጅ ፡ ዕብሮ ፡ አደግ ፡ ያገር ፡ ልጅ ። መናኒ ፡ ረድእ ፡ ባሕታዊ ፡ መነኰስ ። ወሰበ ፡ ተስእሎ ፡ እኁ ፡ ለአባ ፡ ይስሬን ፡ (ፈልክ ፡ ፩) ። እኅወ ፡ (እኁ) ፡ አቡሁ ። እኁሁ ፡ ለእግዚእ ። እኁሃ ፡ ሰርብቃ ። እኁክ ፡ ኪ ፡ የ ። እኁሆሙ ፡ ሆን ፡ እኁኒሆሙ ፡ ኽን ፡ እኍን ፡ እኍን ፡ እያለ ፡ በሳድስ ፡ በካዕብ ፡ ይኼዳል ፡ ይህም ፡ አሐድ ፡ አሐዱ ፡ ኵልሔት ፡ ኵልኤቱ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ካዕቡ ፡ ገቢር ፡ ይኾናል ። ይቀትል ፡ ብእሲ ፡ እኁሁ ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፪) ።

**እኅዋ ፡ እኁ ፡ (እኅወ ፡ እኍ)** ፡ ወንድምን ። ገይሩ ፡ እኅዋሆሙ ፡ ከመ ፡ በድን ። እኍሁ ፡ ኢያድኅን ፡ እኂሁ ። ወአምጽኡ ፡ እኂክሙ ፡ ዘይንእስ ፡ ኀቤየ ። ሖሩ ፡ ዘያምዕዕ ፡ እኅዋሁ ፡ (መገ ፡ ፴፯ ። ማ፳ ። ዘፍ፵፪ ፡ ፳ ። ማቴ፭ ፡ ፳፪) ።

**አኀው** ፡ ወንድሞች ፡ ወንድማማቾች ፡ ዘመዶች ፡ ዘመዳሞች ፡ ሰዎች ፡ ያዳምና ፡ የሔዋን ፡ ልጆች ፡ መነኰሳት ፡ ማኅበር ፡ ኹነው ፡ በየገዳሙ ፡ የሚኖሩ ። ይሁዳ ፡ ወአኀዊሁ ። ወረከበ ፡ ክልኤተ ፡ አኀወ ። አንትሙሰ ፡ አኀው ፡ አንትሙ ። እነግሮሙ ፡ ስሙከ ፡ ለአኀውየ ። ይቤሉ ፡ አኀው ፡ ማኅበረ ፡ አኀው ፡ (ማቴ፩ ፡ ፪ ። ፬ ፡ ፲፰ ። ፳፫ ፡ ፰ ። ግብ፲ ፡ ፳፪ ። መገ ፡ ፳፩ ። ፈልክ) ።

**እኅት ፡ (ዕብ ፡ አሖት ። ሱር ፡ አሓታ ። ዐረ ፡ ኡኅት)** ፡ በቁሙ ፡ እኅት ፡ የናት ፡ ያባት ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ወንድም ፡ ያለች ፡ የናት ፡ አምሳያ ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ እኩያ ፡ ሚስት ፡ ዕብሮ ፡ አደግ ። መነኵሲት ። ወቦ ፡ እኅት ፡ ሠናይት ፡ ለአቤሴሎም ። እሙ ፡ ወእኅታ ፡ ለእሙ ። በሎሚ ፡ እኅታ ፡ ለማርያም ። እኅትየ ፡ መርዓት ። ኢትትኀሰፊ ፡ እኅትየ ። ተንሥኢ ፡ እኅትየ ፡ ንጸሊ ። እኅየ ፡ ወእኅትየ ። ፈቤን ፡ እኅትነ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፳፭ ። ስንክ ፡ ግንቦ ፳፩ ። ማሕ፬ ፡ ፱ ። ሠዲ ፡ ፳፩ ። ፺ ፡ ፳፱ ። ማቴ፲፪ ፡ ፶ ። ሮሜ፲፮ ፡ ፩) ።

**አኃት ፡ እኅታት** ፡ እኅቶች ፡ እኅቶች ፡ እትማማቾች ። መነኰሳይያት ። እኅተ ፡ አኃትኪ ። ወለንእሳት ፡ ከመ ፡ ዘለአኃቲከ ። አኀዊነ ፡ ወአኃቲነ ። አኃት ፡ ክቡራት ። ይሑር ፡ ኀበ ፡ ምኔት ፡ ወይሥርዖን ፡ ለእኅታት ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፵፮ ። ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፪ ። ቅዳ ። ቄር ። ፈልክ ፡ ፲፩) ።

**እኅዉና ፡ (እኅትና)** ፡ ወንድምነት ፡ ከዊን ፡ እኁ ፡ ዝምድና ፡ ዕሪና ፡ ሱታፌነት ።

**አኀዉና** ፡ ወንድማማችነት ፡ ከዊን ፡ አኀው ። መዓርገ ፡ አኀዉና ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲ ፡ ፯) ።

**ተአኀወ** ፡ ተወዳደመ ፡ ወንድማማች ፡ ኾነ ፡ ተዋደደ ፡ ተዛመደ ፡ ተስማማ ፡ አንድ ፡ ኾነ ። አትርፍቱ ዎስ ፡ ወኢራኢ ፡ ዘተአኀዉ ። ኢፈቀደ ፡ ይትአኀዎሙ ፡ ለኪሩቤል ። ተአኃዎት ፡ መንፈሳዊት ። ልቡ ፡ ገቢር ፡ ምስሌክ ፡ ተአኀዎ ። በከመ ፡ ተአኀውከ ፡ ምስለ ፡ አካዝያስ ። ምስለ ፡ ዘሉ ፡ ሰብእ ፡ ተአኀዉ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳር ። አርጋ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲ ፡ ፯ ። ክሌ ፡ ፴፯ ። ዜዜና ፡ ፳ ፡ ፴፯ ። ሮሜ፲፪ ፡ ፲፰) ።

**ተአኃ** ፤ ወንድምንት ፡ ወዳጅንት ፤ ፍቅር ፡ ዝም ድና ፤ ወንድሜ ፡ ወንድሜ ፡ ማለት ። ሰዐረ ፡ ተአኃሁ ። ተአኃሆሙ ፡ ሰአዐርክት ። ደረትዐ ፡ ተአኃሁ ፡ (ሚራ ፳፱ ፡ ፳ ። ፳፭ ፡ ፩ ። ፳፯ ፡ ፲፰ ። ፮ ፡ ፲፯) ።

**ተአኃ** ፤ ወንድም ፡ የወንድም ፡ ወገን ፡ ዘር ፡ ልጅ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ። ቦኑ ፡ ብከ ፡ ተአኃ ፡ ቢዝየ ። ታ በዝኅ ፡ ተአኃሁ ። ለምስኪኖሙ ፡ ወለተአኃሆሙ ፡ (ዘፍ፲፱ ፡ ፲፱ ። ሚራ፯ ፡ ፳ ። አስቴ፱ ፡ ፳፱) ።

**አስተአኀወ** ፤ አወናደመ ፡ ወንድማማች ፡ አደ ረገ ፤ አቀናጀ ። ለየ ፡ ከፈለ ፡ አመንታ ፤ መንታ ፡ አደረገ ፡ አጣፈረ ። እፎ ፡ ከፈልካሁ ፡ ወእፎ ፡ አመንተውካሁ ፡ ለዋሕድ ፡ ወአስተአኀውካሁ ፡ ለአሐዱ ፡ አካል ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አኃ** ፤ (ሐባብ ። ቀብጥ ፡ ኤሔ) ፤ ላም ፡ በሬ ፤ የቀንድ ፡ ከብት ፤ ባንድ ፡ በረት ፡ የተወለደ ፡ የላም ፡ መንጋ ። ፀምደ ፡ አልሕምት ፡ ባለው ፡ ፀምደ ፡ አኃ ፡ እንዲል ፡ (ሉቃ፲፬ ፡ ፲፱) ።

**እኂዝ** ፤ ዘት ፤ (እኀዘ ፤ ይእኅዝ ፡ የእ ኅዝ ። ዕብ ፡ አሐዝ ። ሱር ፡ ኤሐዝ ። ዐረ ፡ አኀዘ) ፤ መያዝ ፡ መጨበጥ ፡ እጅ ፡ ማድረግ ፤ መቀ በል ፤ ያረቦን ፡ የመያዣ ፡ የዋስ ፡ የመድን ። አኅዝዎ ፡ ለአኃዜ ፡ ኵሉ ። አኀዞ ፡ ለውእቱ ፡ ዓሣ ። በእኂዝ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ (ቅዳ ። ጦቢ፮ ፡ ፱ ። ቀሌ) ።

**እኂዝ** ፤ መማረክ ፡ መውሰድ ፤ ማሰር ፡ መቈራ ኘት ፡ የጠላት ፡ የደዌ ፡ የጋኔን ። አኅዝዎ ፡ ለአጋግ ፡ ሕ ያው ። አልቦ ፡ ዘአኀዝነ ። አኀዞ ፡ ለኢዮብ ፡ ዝልጋሴ ። ዘአኅዞ ፡ ጋኔን ፡ (፩ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፰ ። ሉቃ፰ ፡ ፳ ። ኢዮ፪ ፡ ፯ ። ቀሌ) ።

**እኂዝ** ፤ መግታት ፡ ማቆም ፡ ማገድ ፡ ማገር ፡ መገርገር ፡ መጋበዝ ፡ ቈይ ፡ ዋል ፡ ዕደር ፡ ሰንበት ፡ ማ ለት ። ኢይእኅዙ ፡ ልሳኖሙ ። አኅዝ ፡ እግዚእ ፡ መዋ ግደ ፡ ጸጋከ ። ኢተአኅዘኒ ፤ ፈንዉኒ ፡ እሑር ። ትከ ልኡ ፡ ተእኅዛ ፡ ለትርያ ፡ ከመ ፡ ኢትሑር ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፰ ። አዋል ። ዘፍ፳፬ ፡ ፶፮ ። ኢዮ፴፰ ፡ ፴፮) ።

**እኂዝ** ፤ መግዛት ፡ መውረስ ፤ ገዥ ፡ ወራሽ ፡ መኾን ። እስ ፡ ይእኅዝዋ ፡ ለምድር ። ባቲ ፡ መኳን ንት ፡ ይእኅዙ ፡ ምድረ ። መኑ ፡ አኀዞ ፡ ኵሎ ፡ አጽ ናፈ ፡ ምድር ። እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይእኅዝ ፡ (ሔኖ፴፭ ፡ ፱ ። ምሳ፰ ፡ ፲፮ ። ፳፱ ፡ ፳፯ ። ቅዳ) ።

**እኂዝ** ፤ መደገፍ ፡ መጠበቅ ፡ እንዳይወድቅ ። መዠመር ፡ መወጠን ፡ መሰብሰብ ፡ መቍጠር ፤ የቍጥር ፡ ምልክት ፡ መጣፍ ፡ ማኖር ። አኅዚዮ ፡ ለሕፃን ፡ በእ ደውኢ ። አኅዝኩከ ፡ በእዴየ ። ዘይእኅዝ ፡ ኵሎ ፡ ፍጥረተ ፤ ጠበቀ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፵፪ ፡ ፮ ። ጥበ፯ ፡ ፯) ። ብዝንቱ ፡ ዓመት ፡ አኀዘ ፡ ዐባር ፡ ውስተ ፡ ም ድር ። አኀዙ ፡ ጽብአ ። አኅዝ ፡ ይስብክ ፡ ወይምሀር ። አዘነ ፡ ይሕንጽ ፡ ወስእነ ፡ ፈጽሞ ፤ ዠመረ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱ ። ዮሴፍ ። ማቴ፬ ፡ ፲፯ ። ሉቃ፲፬ ፡ ፴) ። አኅዝ ፡ ኵሎ ፡ ተዓይ ኒሆሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፤ ቈጠረ ፡ (ዘኍ፳፯ ፡ ፱) ።

**እኂዝ** ፤ መጽናት ፡ መበርታት ፡ መጠንከር ፡ ሥር ፡ መስደድ ፡ ካፈር ፡ ከመሬት ፡ መዋሐድ ፤ የማይነ ቀል ፡ የማይፈነቀል ፡ መኾን ፤ የባፍ ፡ የደንጊያ ። ለሰው ፡ ሲኾን ፡ ማገ ፡ ምስጢሩ ፡ መግዛትና ፡ መውረስ ፡ ካለው ፡ ይገባል ። ዘእንበለ ፡ የአኅዝ ፡ ሥርወ ፡ ወኀይለ ። አኅዘ ፡ ሥርወ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፮ ። ሄርማ) ።

**እኂዝ** ፤ (ጥሬ ፡ ዘር) ፤ አያያዝ ፡ አገዛዝ ፤ ኀ ይል ፡ ዕዘዝ ፡ ግዛት ፡ ሥልጣን ፤ የጌትንት ፡ ሥራ ። ስብ ሐት ፡ ወእኂዝ ፤ እስመ ፡ ለከ ፡ እኂዝ ፡ (ቅዳ) ።

**አኃዚ** ፤ (ዚት ፡ ዝያን ፡ ያት ፤ አኀዝት) ፤ የሚይዝ ፡ ያዥ ፤ ዐጋች ፤ ጨባጭ ፡ ቈጣቢ ፡ ንፉግ ፤ የሚ ገዛ ፡ ገዥ ፤ አዛዥ ፤ ጌታ ፡ ጠባቂ ። እደ ፡ ሞት ፡ አኃዚ ። አኃዜ ፡ አኀዝ ። ነጋሢ ፤ አኃዚ ። እኀዘ ፡ ነገሥታት ፡ ወመኳንንት ፡ ወእኀዝ ፡ አኃዝያን ፡ እሙንቱ ፡ በዲበ ፡ ምድር ። አኃዜ ፡ ኵሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ። አኃዜ ፡ ነፍሱ ፡ እምነ ፡ ፍትወታት ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯ ። ጥበ፲፱ ፡ ፲፱ ። መቃ ፡ ገ፱ ። ቅዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፯) ።

**አኀዝ** ፤ ትእዛዝ ፡ እንቀጽ ፤ ያዝ ፡ ጨብጥ ፡ አት ልቀቅ ።

**አኃዝ** ፤ (ዛት) ፤ መዠመሪያ ፤ ዥምር ፡ ው ጥን ፤ አንድ ፡ እንደ ፡ ማለት ። በቁሙ ፡ ቍጥር ፡ ሒሳብ ፡ የቍጥር ፡ ፊደል ፡ ወይም ፡ ምልክት ፡ ከአ ፡ እስከ ፡ እ ፡ ያለ ፤ ይኸውም ፡ እም(፩)አሐዱ ፡ እስከ ፡ (፼) ፡ እልፍ ፡ ማለት ፡ ነው ። የሕዝብ ፡ የገንዘብ ፡ የሰፍር ፡ የሚዛን ፤ የሰዓት ፡ የዕለት ፡ የወርኅ ፡ የዓመት ፡ የሥራ ፡ ኹሉ ፡ ልክ ፤ ማነስ ፡ መብዛቱ ፡ ክፍሉና ፡ ዐይነቱ ፡ በየስሙ ፡ በየነገዱ ፡ ተዘርዝሮና ፡ ተደምሮ ፡ ተሰይቶ ፡ የሚታወቅበት ። አኃዝ ፡ ቢስ ፤ አኃዝ ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ እንዲሉ ። ወሰለ ፤ ኍልቈ ፡ አኃዙ ፡ ቦቱ ፡ አኃዝ ፡ ዘበሚራኩ ። አእሚረክ ፡ አኃዘ ፡ ኍልቈ ። የድ ፡ ዘይቤ ፡ የውጣ ÷ ዝ ፡ ውእቱ ፡ አም ሳለ ፡ ዐሥርቱ ፡ (፲) ፡ አኃዝ ፡ ርቱዕ ፡ ውእቱ ፡ እንበለ ፡ ጸይን ፡ (መቅ ፡ ወን ። ጥሬ ፡ ስዋ) ።

**አኃዝ** ፤ (ዛን ፡ ዛት) ፤ መያዣ ፡ ዕግት ፡ ታቢ ። ተያዥ ፡ ዋስ ፡ መድን ፡ ተጠሪ ፡ ቆፋ ። ሀበኒ ፡ አኃዘ ፤ መ ያዣ ፡ (ዘፍ፴፰ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ። ዘዳ፳፬ ፡ ፲—፲፫ ። ሕዝ፲፰ ፡ ፯) ። አልብየ ፡ አኃዝ ፤ ዋስ ፡ (ኢዮ፴፱ ፡ ፴፯ ። አፈ ፡ ድ ፳፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯) ።

**አእኀዘ** ፤ አስያዘ ፡ አስጨበጠ ፤ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፤ ዐደራ ፡ እለ ፤ አስጠጋ ፡ አስደገፈ ። ወአእኀዝዎ ፡ ኀሊተ ፡ (ማቴ፳፯ ፡ ፳፱) ። በአእኀዞ ፡ ፈንታ ፡ እስተእኅዞ ፡ አስተ አኀዘ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ከስደራጊንት ፡ አ ይወጣም ። ለእመ ፡ አስተአኅዘ ፡ ብእሲ ፡ ንዋየ ፡ ብእ ሲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ምክራ ፡ ኢይደሉ ፡ እኂዝ ። ወአስተ አኀዘ ፡ ኢዮአዳ ፡ ኵሎ ፡ ቤተ ፡ እግዚ ፡ በእደ ፡ ካህናት ። ዕፀ ፡ ሳቤቅ ፡ ዘያስተእኅዝ ፡ በግዐ ፡ ምስለ ፡ አቅርን ቲሁ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፳ ። ፪ዜና ፡ ፳፫ ፡ ፲፰ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ተእኅዘ** ፤ ተያዘ ፡ ተጨበጠ ፤ ታሰረ ፣ ተጣበቀ ፡ ተገታ ፤ ተከለከለ ፣ ተወረሰ ፡ ርስት ፡ ኾነ ። እመ ፡ ተእኅዘ ፡ ተእኅዘ ፡ ሰራቂ ። ተእኅዘ ፡ በመሥገርት ። ዘገሰሰ ፡ ፒሳ ፡ ይትአኀዝ ፡ ቦቱ ። አስራበ ፡ ሰማይ ፡ ተእኅዘ ። ወተእኅዘ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢ ። ተእኅዘ ፡ ልማደ ፡ እብስት ፡ ወርስዐት ፡ (ምሳ፳ ፡ ፴ ። ኤር ፴፩ ፡ ፵፱ ። ሚራ፲፫ ፡ ፩ ። ዘፍ፳ ፡ ፪ ። ሉቃ፳፱ ፡ ፲፮ ፡ ጥበ፲፱ ፡ ፲፮) ።

**ተእኅዘ** ፤ ተያዘ ፡ ተዋሰ ፡ ተዳነ ፤ ተያዥ ፡ ዋስ ፡ መድን ፡ ኾነ ፤ ዋስ ፡ በራሱ ፡ አለ ። ታገተ ፡ ተያዘ ፡ በውስትና ፡ በዕዳ ። አብ ፡ ኢይትአኀዝ ፡ በዕዳ ፡ ልቃሒ ፡ ወልዱ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ዘተለቅሐ ፡ በትእዛዘ ፡ ዚኣሁ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯) ። በአኀዘ ፡ ፈንታ ፡ ተአኀዘ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ኢትትአኀዝ ፡ ማሕረዲ ፡ (ዘዳ፳፱ ፡ ፯ ፡ ፲) ።

**ተአኀዘ** ፤ ተያያዘ ፡ ተባበረ ፤ ተከራከረ ፤ ተካሰሰ ፡ ተሞዋሰ ፡ ተገናመረ ። ይትኣኀዝ ፡ ምስለ ፡ ቤቱ ፡ ረብ ። ተኣኀዝዎ ፡ ለጳውሎስ ። ተኣኀዙ ፡ ይትቃተሉ ፡ (ኢያ ፲፱ ፡ ፲፭ ። ግብ፲፯ ፡ ፲፰ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፰) ።

**እኁዝ** ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ኅዝት) ፤ የያዘ ፡ የጨበጠ ፡ የተያዘ ፡ የታሰረ ፡ የተያያዘ ። ኵሎሙ ፡ እኁዛነ ፡ አስይፍት ። ሱራፌ ፡ እኁዘ ፡ ሰይፍ ። ሲቃናት ፡ እኁዛነ ፡ መዓጥን ፤ የያዘ ፡ (ማሕ፫ ፡ ፰ ። አርጋ ፡ ፭ና ፡ ፫) ። እስመ ፡ ዓለም ፡ ወኵሉ ፡ ዘውስቴቱ ፡ እኁዝ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለእግዚ ። ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ዮሴፍ ፡ እኁዝ ፡ ህየ ። እኁዛነ ፡ አጋንንት ፤ የተያዘ ፡ (ዲድ ፡ ፳፭ ። ቅዳ ። ኩፋ ፡ ፴፱ ። ማር፫ ፡ ፲፭) ። እኁዝ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ለለ ፡ አሐዱ ። ከመ ፡ ይኩኑ ፡ እኁዛነ ። እኁዛን ፡ በበ ይናቲሆሙ ፤ የተያያዘ ፡ (ሕዝ፩ ፡ ፰ ። ማ፩ ፡ ፯ ። አዋል) ።

**እኅዘት** ፤ መያዝ ፡ (ጥያ) መያዝ ፡ አያያዝ ፡ ይዞታ ፡ ያዥነት ፡ ጌትነት ፡ አገዛዝ ። እኅዘትከ ፡ በመጣብሕ ፡ ወበሐብትር ። በእኅዘት ፡ ወሥልጣን ፡ (አዋል ። አፈ ፡ ድ፪) ።

**እኅዘት** ፤ (ዕብ ፡ አሑዛት) ፤ ርስት ፡ ጕልት ፡ ግዛት ፡ ይዞታ ፡ እጅ ፡ ዐደር ፡ ቦታ ። ወእኅዘቶሙ ፡ ይእቲ ፡ በመክፈልት ፡ (ሕዝ፵፮ ፡ ፲፰) ።

**መአኀዝት** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ የከተማ ፡ ቦታ ። መአኀዝተ ፡ ሀገር ፡ ትሁቡ ፡ (ሕዝ፵፰ ፡ ፯) ።

**መእኅዝት** ፤ (ብ ፡ መኣኅዝት) ፤ መያዣ ፡ መጨበጫ ፡ እጀታ ፡ ገሮሮ ፡ ቀለበት ፡ መኣኅዝተ ፡ በዘይ እኅዝዋ ፡ (ዘፀ፴፰ ፡ ፴ ፡ ፲ ፡ ፳፫) ።

**መእኅዝት** ፤ የተቋም ፡ ጽዋ ፡ ቀንዲሉ ፡ ዘይቱና ፡ ፈትሉ ፡ የሚኾንበት ፡ ያገዳው ፡ ሬስ ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፴፩ ፡ ፴፫ ። ፴፯ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ። ፴፯ ፡ ፲፯) ።

**መእኅዝት** ፤ የወርቅ ፡ ኅርወት ፡ መደቡ ፡ ስጕዱ ፡ ጕድጓዱ ፡ ዕንቍ ፡ ፈርጥ ፡ እንዳይነ ፡ ኹሳ ፡ የሚስካበት ፡ የሚያገዝበት ፤ ዐይን ፡ መስሎ ፡ ጕርጦ ፡ ፍጥጥ ፡ ብሎ ፡ የሚታይበት ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፲፮) ።

**መእኅዝት** ፤ የሚይዝ ፡ የሚያያይዝ ፡ ቀለም ፡ መጣብቅ ፤ ከያዘ ፡ የማይለቅ ። ጽቡር ፡ ለመኣኅዝቲ ሆን ፡ (ገድ ፡ ላሊ) ።

**ምእኃዝ** ፤ (ዛት) ፤ መያያዣ ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ፤ ወሰን ፡ ደንበር ፡ አፍዛዥ ፡ አንጻር ። እስከ ፡ ምእኃዝ ፡ ኤዶም ። ምእኃዘ ፡ ገልገል ፡ (ዘኍ፴፬ ፡ ፫ ። ዘዳ፲፭ ፡ ፴) ። ዐይን ፡ ሙሐዝ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ምእኃዝ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (፫ነገ ፡ ፰ ፡ ፱) ።

**አስተአኀዘ** ፤ አያያዘ ፡ አቀጣጠለ ፤ አዣማመረ ። ከመ ፡ ዝ ፡ አስተኣኀዘ ፡ ትምህርተ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እምአሐቲ ፡ ኵሉ ። ለእመ ፡ ዐርጉ ፡ ሮም ፡ መልዕልተ ፡ ማኅፈድ ፡ አስተኣኀዝ ፡ እሳተ ፡ ውስቴቱ ። አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ያስተኣኅዙ ፡ ቤተ ፡ ምስለ ፡ ቤት ። መኑ ፡ ያስተኣኅዝ ፡ ቀትለ ፡ (ገድ ፡ ላሊ ። ዮሴፍ ። ኢሳ፭ ፡ ፰ ። ፫ነገ ፡ ፳ ፡ ፲፱) ።

**እኂል** ፤ እኄላ ፤ (ዕብ ፡ ዒጉል ፡ ድቤላ ፤ ሰክ ፡ በለስ ። ዐረ ፡ ሐለዋት ፤ ጥፍጥ) ፤ ጥዑም ፡ ምቱቅ ፤ የበለስ ፡ ቋንጣ ፡ እንደ ፡ ድባና ፡ እንደ ፡ ማርዳ ፡ እንደ ፡ መቍጠሪያ ፡ ፶ ፡ ፶ው ፡ ፻ ፡ ፻ው ፡ በረዥኙም ፡ ክር ፡ የሚሰካ ። የሰሌን ፡ ፍሬ ፡ እንደ ፡ ሠምና ፡ እንደ ፡ ዳቦ ፡ የሚረጋ ፡ የሚጋገር ፤ ሲበሉት ፡ የሚጥም ፡ የሚጣፍጥ ፡ ማር ፡ ማር ፡ የሚል ። ከልኤተ ፡ ምእተ ፡ እኄላ ፡ በለስ ። ወወሀብዎ ፡ ስባረ ፡ እኄላ ፡ ተመርት ፡ (፩ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፲፰ ። ፴ ፡ ፲፪) ። ደበለን ፡ ተመልከት ።

**እኂር** ፤ ሮት ፤ (አኀረ ፡ ይእኅር ፡ ይእኀር ፤ ዐረ ። ዕብ ፡ ኤሓር ። ሱር ፡ አውሓር) ፤ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማለት ፤ መቈየት ፡ መዘግየት ፤ መትመክመክ ፡ (ጥለ) መለወጥ ፡ ሌላ ፡ መኾን ። ደኀረን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ገር ፡ ነው ።

**እኃሪ** ፤ ደኃሪ ፡ ኋለኛ ፡ የኋላ ፡ የዠርባ ። ለእኃሪ ፡ ዐምድ ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፳፯) ።

**አእኀረ** ፤ አዶኀረ ፡ አቈየ ፡ አዘገየ ፡ ለወጠ ፡ ሌላ ፡ አደረገ ። ከተማ ፡ ዐውድከ ፡ ኢታእኅር ፤ በሥራቱን ፡ ቀዳምያቱን ፡ አታዛግይ ፡ አትለውጥ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፀ ፳፪ ፡ ፳፱) ። ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ ዐውድማኽን ፡ አጥርተኽ ፡ አትጥረግ ፡ ይሉታል ።

**እኅት** ፤—በቁሙ ፤—እኅው ።

**ኢጥያ** ፤ (ጽር ፡ ይቴያ) ፤ ስመ ፡ ዕፀ ፡ ተክላዊ ። ዕፀ ፡ ዘስሙ ፡ ኢጥያ ፡ (ሄርማ ፡ ገ፳፭ና ፡ ፬) ።

**አጠነ** ፤—በቁሙ ፤—ዐጢን ፡ ዐጠነ ።

**አጥናን** ፤—ትጋት ፤—ጠኒን ፡ ጠነ ።

**አጠቀ** ፤—ታጠቀ ፤—ዐጢቅ ፡ ዐጠቀ ።

**አጣቃን** ፤ (ጽር ፡ አታኪን ። ዕብ ፡ ሳልዓም) ፤ የንበጣ ፡ ወገን ፡ ኰብኰባ ፡ ፌንጣ ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፳፪) ።

**አጠረ ፡ (ዕብ ፡ አጣር)** ፡ በቁሙ ፡ ቀጠረ ፡ ጀጐለ ፡ ከበበ ፡ ዙሪያውን ፡ ዘጋ ። ሐጸረን ፡ እይ ። (ተ ረት) ፡ እሾኽ ፡ በጣሪውን ፡ ንገር ፡ ፈጣሪውን ።

**አጣርቆን ፡ (ጽር ፡ አፓርኽን ። ዕብ ፡ ትሩሞት)** ፡ መባእ ፡ መሥዋዕት ፡ መንፈሳዊ ፡ አምኃ ፡ ቁዳምያት ። አጸርጊን ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (፪ነገ ፡ ፭ ፡ ፳፭) ።

**አጥረስክ ፡ (ጽር ፡ ኤንስቶኒስቲኪ)** ፡ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ የሃይማኖት ፡ መጽሐፍ ። ባለሊቃውንቶች ፡ መጽሐፈ ፡ ክፍል ፡ ወተዋሕዶ ፡ ዘትምልዕት ፡ ወዘተዋሕዶ ፡ ከምቱ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ባለቅኔ ዎችም ፡ ተዝካር ፡ ይሉታል ። እምአጥረስክ ፡ ዘዕሥራ ፡ ወሰሐዱ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**አጠሰ ፡—ንጥሻ ፡—ዐጠሰ ።**

**አይ ፡ (ዐረ ፡ አይ ። ዕብ ፡ ኤይ)** ፡ ምን ፡ ምንድር ፡ ማን ፡ ማንኛው ፡ ማናቸው ፡ የቱ ፡ የትኛው ። ለወንድም ፡ ለሴትም ፡ ለሩቅም ፡ ለቅርብም ፡ ይነገራል ፡ ንባቡ ፡ ጥያቄ ፡ ምስጢሩ ፡ አሉታና ፡ አንክሮ ፡ በጥያቄ ነት ፡ ስምን ፡ ቦታን ፡ ጊዜን ፡ ይፈልጋል ፡ ሁ ፡ ኑ ፡ ይጋን ኑታል ፡ መኑንና ፡ ምንትን ፡ አይቴን ፡ ተመልከት ። አይ ፡ ባለቤት ፡ ሲጠራ ፡ ቅጽል ፡ ባለቤት ፡ ሲቀር ፡ በቂ ፡ ይኾ ናል ። አይ ፡ ልቡና ፡ ወአይ ፡ ነቢብ ፡ ወአይ ፡ ሰሚዕ ፡ ዘይክል ፡ ለአምሮ ። አይ ፡ አፍ ፡ ወአይ ፡ ልሳን ፡ ወ አይ ፡ ከርሥ ፡ ዘይገምር ። አይ ፡ ይእቲ ፡ ዛቲ ፡ አይ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ (ውዳ ። ቅዳ ። ድጓ) ። አይኑ ፡ ውእቱ ፡ መዋቲ ፡ ዘይነጽሕ ። አየኑ ፡ ቤት ፡ ተሐንጸ ፡ ሊተ ። በአይ ፡ እምእላንቱ ፡ እሣሀሎሙ ። በታሕተ ፡ አይ ፡ ዕፀ ፡ (ኢዮ ፲፬ ፡ ፲፯ ። ኢሳ ፳፮ ፡ ፩ ። ኤር ፭ ፡ ፯) ። እምዮም ፡ እምይእዜ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ወአይ ፡ ይላል ፡ መቼም ፡ መቼ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፀ፴ ፡ ፲) ። አየዮን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**አያት** ፡ ምኖች ፡ ምንድሮች ፡ ማናቸዎች ፡ የ ትኞች ፡ እነዶች ፡ እነማን ፡ እነዲት ፡ ያሉ ። አያትሙ ፡ ይኄይሱ ። ዕፁብ ፡ ትእዛዛቲሁ ፡ ወይቤሎ ፡ አያት ። አያት ፡ ሥሕጸታት ፡ ዘነበበ ፡ (ፊልክ ፡ ፭ ። ማቴ፲፱ ፡ ፲፰ ። ቄር ፡ ጸሎ) ። (ዕርጅ ፡ ቍ፯) ፡ ተመልከት ።

**ኢዮቤል ፡ (ጽር ፡ ዮቢል ። ዕብ ፡ ዮቤል)** ፡ የበግ ፡ ጠቦት ፡ ወጠጤ ፡ ቀባት ፡ ቀንዳ ፡ መለ ከት ፡ በዓል ፡ ኀምሳ ፡ ከ፯ ፡ ሰባዔ ፡ ወይም ፡ ከ፵፱ ፡ ዓ መት ፡ በኋላ ፡ በምሳኛው ፡ ዓመት ፡ ብዙ ፡ ጠቦት ፡ የሚ ሠዋበት ፡ ቀንዳ ፡ መለከት ፡ የሚነፋበት ፡ (ዘሌ፳፭ ፡ ፰—፲፫) ። ቢያበዛ ፡ ኢዮቤላት ፡ ኢዮቤልዮን ፡ ኢዮቤልዉ ፡ ኢዮቤልምባት ፡ ይላል ፡ (ኩፋ) ።

**ኢያዜር ፡ (ጽር ፡ ያዚር ። ዕብ ፡ ያዕዜር)** ፡ ስሙ ፡ ሀገር ፡ የጋድ ፡ ርስት ፡ ሮቤልና ፡ ጋድ ፡ ሲማረኩ ፡ ሞኦብ ፡ የወረሳት ። ባለብሉዮች ፡ ማን ፡ ሐሊበ ፡ ዮሴ ፡ ይ ሉታል ። ባለቅኔዎችም ፡ ከሊታኽ ፡ ይሉታል ። እስከ ፡ ኢያዜር ፡ ብካየ ፡ ኢያዜር ፡ (ኢሳ፲፮ ፡ ፰፡፱ ። ዘኁ ፴፭ ፡ ፴፪) ።

**ኢያዘር ፡ (ጽር ፡ ወዕብ ፡ ኤዜር)** ፡ ዘውድ ፡ አክሊል ፡ ጋሜ ፡ ጉፌር ፡ አንፋሮ ፡ የብዕበት ፡ ጠጉር ፡ የ ሚይላዊ ። ባለብሉዮች ፡ ማን ፡ ዘውድ ፡ አክሊል ፡ በማ ለት ፡ ፈንታ ፡ ልብስ ፡ መንግሥት ፡ አርድ ፡ እንቀጥቅጥ ፡ ይሉታል ። ወአልበሶ ፡ ልብሰ ፡ ኢያዜር ፡ (፪ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፲፬) ። ያዕዜርና ፡ ኤዜር ፡ ኹለት ፡ ልዩ ፡ ቃሎች ፡ ሲኾኑ ፡ የግእዝ ፡ መላሽ ፡ አንድ ፡ አድርጓቸዋል ።

**አዩኀ ፡ ኖት ፡ (ኤነ ፡ አይነ ፡ የአይኅ ፡ ይኤኅ ፡ ይእዩኅ)** ፡ ማጥፋት ፡ መደምሰስ ፡ መድፈን ፡ መቅበር ፡ ማስጠም ፡ የጐርፍ ፡ የዝናም ፡ የማዕበል ።

**አይኅአ ፡ (አ ፡ ተቀጥላ ፡ ነው)** ፡ ወረደ ፡ ከላይ ፡ ከሰማይ ፡ መጣ ፡ ዘነመ ፡ ፈሰሰ ። አይኅአ ፡ ቃለ ፡ እምሰማይ ። እምሰማያት ፡ እምነብ ፡ አብ ፡ አይ ኅአ ፡ (ድጓ ። ኪዳ) ።

**አይኅ** ፡ ጥፋት ፡ ስጥመት ፡ የዝናም ፡ የጐርፍ ፡ የባሕር ፡ አደጋ ፡ ታላቅ ፡ ብርቱ ፡ ዝናም ፡ ዝናመ ፡ መ ዐት ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ የተረፈ ፡ ዝናመ ፡ ኖኅ ። ማየ ፡ አ ይኅ ። እምነ ፡ ማይ ፡ ዘአመ ፡ አይኅ ። ይመጽእ ፡ ዝናም ፡ ከመ ፡ አይኅ ። አይኅ ፡ ዘነፋስ ። ጸሊየ ፡ ጸ ሎተ ፡ ፒዮርጊስ ፡ ወአውረደ ፡ እምሰማይ ፡ አይኅ ፡ እሳት ፡ ላዕለ ፡ ጽሉማ ፡ ሰብዓ ፡ ነገሥት ፡ (ዘፍ፯ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፳፰ ፡ ፪ ። ሕዝ፲፫ ፡ ፲፩ ። ቀሌ ። መዋሥ) ። ው ሒዝ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አይኅ ፡ ይላል ፡ (ዳን፱ ፡ ፳፮ ። ናሖ፩ ፡ ፰) ።

**ተኤነ ፡ ተአይነ** ፡ ጠፋ ፡ ሰጠመ ፡ ተደፈነ ፡ ውሃ ፡ ለበሰ ። ወከማሁ ፡ ሰበ ፡ ተአይኅ ፡ ምድር ፡ ኢይ ኀነት ፡ ጥበብ ። አመ ፡ ተአይኀ ፡ ዓለም ፡ (ጥበ፲ ፡ ፬ ። ደራሲ) ።

**አዩኅ ፡ (ኀን ፡ ኀት ፡ ይኅት)** ፡ ዝናም ፡ ያ ጠፋው ፡ ያሰጠመው ፡ ውሃ ፡ የበላው ።

**አይጥ ፡—በቁሙ ፡— ዐይጥ ።**

**አየየ ፡—ዘረ ፡ ብክነ ፡ —ዐየየ ።**

**አይያ ፡ ዮት ፡ (አየ ፡ አየየ ፡ የአይያ ፡ ይእየይ ፡ ይእያይ ። አይ)** ። መምሰል ፡ መተከ ከል ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ መኾን ። ኪያን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**አያዩ ፡ (ዩት ፡ ይያን ፡ ያት)** ፡ የሚመስል ፡ መሳይ ፡ አኩያ ፡ አምሳይ ።

**አያይ ፡ (ያት)** ፡ አምሳል ፡ አምሳያ ፡ አንጻር ፡ እኩያ ፡ አብነት ፡ መምህር ፡ መልክ ፡ ጥበር ። ሰላም ፡ ለ ጎርጎርዮስ ፡ ወለአብድራጦስ ፡ አያዩ ። ወበ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘሕብረ ፡ በረድ ፡ አያይ ። ውተወሰጠ ፡ አያዩ ። ክነ ፡ ሐዋርያዊ ፡ በሽብ ፡ አያዩ ፡ (ቡንክ ፡ መቅ፳፱ ። ጥርጅ ።

ሐዋ ፲፯ ፡ ፳፯ ፡ ማቴ ፲፩) ። በኢያይ ፡ ፈንታ ፡ እያይት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹሉ ፡ ጕርድ ፡ ኣሳዋሮ ፡ አያት ፡ ይላል ፡ አምሳል ፡ ማለት ፡ ነው ። ሕዮተ ፡ አዕናቊ ፡ እለ ፡ ተሰክዓ ፡፡ አልቦ ፡ እያተ ፡ ግብራት ፡ ውስቴቱ ፡፡ በዝኬ ፡ አያት ፡ ንሰብ ፡፡ አላ ፡ በካልእ ፡ አየት ፡፡ በአየተ ፡ አላንቱ ፡፡ ወአየቶመውስ ፡ ንነግር ፡ (ደራሲ ፡ ቁር ፡ እስት ፡ ጸላ) ።

**እያተ ፡ መዓር** ፤ የማር ፡ እንጀራ ፡ አምባል ፡ ዕንጕቻ ፡ በማር ፡ በስኳር ፡ የሚሠራ ። የማር ፡ አምሳል ፡ ማር ፡ ማር ፡ የሚል ፡ በሰሰ ፡ ወይን ፡ ተምር ፡ ስኳር ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ወጣዕሙ ፡ ከመ ፡ እያተ ፡ መዓር ፡፡ ይፈደፍድ ፡ ጣዕሙ ፡ እምዝሉ ፡ አያያተ ፡ መዓር ፡ ዘበምድር ፡ (ዘፀ ፲፮ ፡ ፴፩ ። ገድ ፡ ተክ ። ቀሌ) ።

**እያት ፤ (ታት ፡ እያያት)** ፤ በቁሙ ፡ አያት ፡ እሚታ ፡ ያባትና ፡ የናት ፡ ወላጆች ፡ አምሳዮች ።

(ጥዩ) **እዩት** ፤ በቁሙ ፡ የወንድም ፡ ያጎት ፡ ሚስት ፡ የእኅትና ፡ ያክስት ፡ ምሳሌ ፡ ባሏ ፡ አይዋ ፡ አያ ፡ የሚባል ።

**ተአየየ** ፤ ተመሳሰለ ፡ ተነጻጸረ ። ዘመንገለ ፡ ሰብእ ፡ ክቡር ፡ ወልዑል ፡ ወኢይትኣየይ ፡ ምስለ ፡ ካልእ ፡ በልዕልናሁ ፡፡ እምክልኤቱ ፡ እለ ፡ ኢይትኣየያ ፡ ዘውእቱ ፡ መለኮት ፡ ወትስብእት ፡፡ አማንኑ ፡ ከመ ፡ ለብሂል ፡ መርገመ ፡ ኮነ፡ ወኀጢተ፡ ከማሁ ፡ ይትኣየይ ፡ ነገር ፡ ዘይብል ፡ ኮነ፡ ሥጋ ፡ (ቄር ፡ እስት ፡ ጸላ) ።

**እዩይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ይይት)** ፤ የተመሳሰለ ፡ የተካከለ ፡ የተነጻጸረ ፡ ልክና ፡ መልክ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ ብልጫ ፡ ልዩነት ፡ የሌለው ። እዩየ ፡ ግጻዌ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወዕሩየ ፡ መለኮት ፡፡ ዕሩያን ፡ በአካል ፡ ወእዩያን ፡ በሥራኄ ፡ ወበጸዳል ፡ (አርጋ ፡ ፫ ። ቅዳ ። ቄር) ።

**እዩሉል ፡ (ዕብ ፡ ወጽር ፡ ኤሉል)** ፤ ስሙ ፡ ሳድስ ፡ ወርኀ ፡ ዕብራዊ ፡ የዕብራውያን ፡ ስድስተኛ ፡ ወር ፡ ከሚያዝያ ፡ ይኸውም ፡ መስከረም ። አመ ፡ ፭ሁ ፡ ወ፳ሆ ፡ ለጽልመተ ፡ እዩሉል ፡ (ነሐ፮ ፡ ፲፭) ።

**ኤለ ፤—ዞረ ፡ ባከነ ፤—ዐዩል ፡ ዔለ ።**

**ኤላ ፤—ዐዘቅተ ፡ ማይ ፤—ዐዩል ፤—ዔለ ።**

**ኤመ ፤—አፈገ ፡ መሰገ ፤—ዐዩም ፡ ዔመ ።**

**ኢም ፡ (ዕብ ፡ ኢይም)** ፤ ቀበሮት ፡ አንበሳ ፡ የሚፈሩቸው ፡ የቀኮላ ፡ ወገኖች ፡ የበረሓ ፡ ውሾች ። አንዱን ፡ ኢይ ፡ ይለዋል ። ጺም ፡ ምስለ ፡ ኢም ፡ (ኢር ፲፫ ፡ ፳፪) ። ባለቅኔዎች ፡ ቀኝ ፡ ይሉታል ።

**ኢያሚን ፡ (ጽር ፡ ያሚን ። ዕብ ፡ ያዓሀ)** ፤ የመማሪያ ፡ ስም ፡ ክኩም ፡ ክብርት ፡ ክብረት ፡ የሚሠራ ፡ የላይም ፡ መማሪያ ፡ መቀርከሻ ፡ ያመድ ፡ የጕ

ይፋ ፡ መጋፊያ ፡ መዛቂያ ፡ ማፈሻ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ መንክና ፡ እንደ ፡ ሳይዳ ፡ እንዳክፋ ፡ ያለ ፡ (፪ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፲፬) ።

(ጥ) **እይኖ ፤ ኖት ፤ (አየነ ፡ ይኤይን ፡ የአይን)** ፤ መከባከብ ፡ ማደላደል ፡ ማቀማጠል ፡ ማስመቸት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአየነ ፡ ፈንታ ፡ ተአየነ ፡ ይላል ፡ አይራጊውን ፡ በተደራጊ ። ወእመ ፡ ትቤለኒ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ተደላ ፡ እብለከ ፡ ተእይኖ ፡ ሥጋ ፡ ፈድፋደ ፡ ወሴስዮቱ ፡ ሐሲበ ፡ ወመዓረ ፡ ወአዕርፎቱ ፡ እምጻማ ፡ (አፈ ፡ ድ፲፫) ።

**ተአየነ ፤ (ዐረ ፡ አእነ)** ፤ ተከበከበ ፡ ደላው ፡ ተመቸው ፡ ባለጤና ፡ ኾነ ፡ ዕረፍት ፡ አገኘ ።

**አየነ ፤—አየ ፡ ገመተ ፤—ዐይኖ ፡ ዐየነ ።**

**አይቆና ፤ (ጽር ፡ ኢኮን ፤ ኢኮና)** ፤ ሥዕል ፡ መልክእ ፡ ሥዕል ፡ በእጅ ፡ የተሣለ ፡ የተመሰለ ። እምእይቆናሃ ፡ ወዲአ ፡ (ስንክ ፡ ታኅሣሥ) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ የሥዕል ፡ ቤት ፡ ይሉታል ።

**አየር ፤ (ራት ። ጽር ፡ አኤር)** ፤ በቁሙ ፡ ነፋስ ፡ ከፍት ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ከጠፈር ፡ በታች ፡ ባይው ፡ መካከሉ ። ርጉዕ ፡ ነፋስ ፡ በአየር ፡ የመላ ፡ የተመላ ። ሠጢፉ ፡ አየረ ፡፡ በአየረ ፡ ሰማይ ፡፡ አዕዋፍ ፡ ዘውስተ ፡ አየር ፡ ይሰርሩ ፡፡ መልዕልተ ፡ አየር ፡፡ ተመልእት ፡ አየር ፡ እምነ ፡ መላእክት ፡፡ አየር ፡ ጽሕወ ፡ ኮነ ፡፡ ዐርገ ፡ ውስተ ፡ አየራት ፡፡ ይኔጽር ፡ አየራተ ፡ (ሄኖ ፡ አበ ። ዮሴፍ ። ፈላስ ። ምሳ፱ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ ግን፲፱ ። አፈ ፡ ድ፳፫ ። መጽ ፡ ምስ ። ድጓ) ። አይሮፕላን ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ ጠየረን ፡ ተመልከት ።

**አየራዊ** ፤ ላዕላዊ ፡ ነፋሳዊ ። መብረቅ ፡ አየራዊ ፡ (ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**ኢዮር ፤ (ጽር ፡ አኤር ። ዐረ ፡ ኢያር)** ፤ ሰማይ ፡ ከጠፈር ፡ እስከ ፡ መንበር ፡ ያለው ፡ ሰባቱ ፡ ኹሉ ፡ ጠፈርና ፡ ጎቃም ፡ ሳይቀሩ ። ዘዲበ ፡ ኢዮር ፡ መንበሩ ፡፡ ከመ ፡ ክዋክብት ፡ ዘኢዮር ፡ ይበዝኅ ፡ ኀጢአትየ ፡፡ ተራወጸ ፡ በኢዮር ፡ ደመና ፡ (መዋሥ ። መጽ ፡ ኑዛ ። ደራሲ) ።

**ኤዮር** ፤ መካከለኛ ፡ ሰማይ ፡ የጠፈር ፡ አራተኛ ፡ ከበላዩ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት ፡ ሰማይ ፡ ውዱድ ፡ ጽርሐ ፡ አርያም ፡ ያለበት ፡ (ሥን ፡ ፍጥ) ።

(ጥያ) **እያር ፤ (ዕብ ፡ ኢያር)** ፤ የዕብራውያን ፡ ኹለተኛ ፡ ወር ፡ ግንቦት ፡ (ጥሬ ፡ ሰዋ) ።

**አየረ ፤—ሰደበ ፤—ዐይሮ ፡ ዐየረ ።**

**ኤረር** ፤ ብሩህ ፡ ሰማይ ፡ ከጠፈር ፡ በላይ ፡ ከራማ ፡ በታች ፡ ያለ ። ኤረር ፡ ራማ ፡ ኢዮር ፡ እሊህ ፡ ሦስቱ ፡ ዓለመ ፡ መላእክት ፡ ይባላሉ ። የዘመኛ ፡ ነገድ ፡ ከተማ ፡ የሦስት ፡ የሦስቱ ፡ በነዚህ ፡ በሦስቱ ፡ ሰማያት ፡ ተከፍሏል ፡ የሰማዩን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። እሊህም ፡ ከጠፈር ፡ እስከ ፡ ጽርሐ ፡ አርያም ፡ ያሉት ፡ ጕልላት ፡ ስምንት ፡ ላይ ፡ ደርብ ፡ ታች ፡ ደርብ ፡ መካከለኛ ፡ ደርብ ፡ ምድር ፡ ቤት ፡ መመ

ረት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ናቸው ። አየራቸውም ፡ ትክክል ፡ ነው ፤ የርሕቀቱና ፡ የምጥቀቱ ፡ መጠን ፡ ከንዱ ፡ እስክ ንዱ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ያስኬዳል ፡ ይባላል ። ዙሪያ ፡ ቅጥሩ ቸውም ፡ እፍኢው ፡ የማይፈጅ ፡ ውብጡ ፡ የማይፈጅ ፡ የእ ሳት ፡ ቅጥር ፡ ነው ፤ ቀሌምንጦስ ፡ ከጠፈር ፡ በላይ ፡ ያሉ ትን ፡ መንበረ ፡ መንግሥትን ፡ ጨምሮ ፡ ሰብዐቱ ፡ ሰማ ያት ፡ ብርሃን ፡ ይላቸዋል ፡ (ሥን ፡ ፍጥ) ።

**ኢየሩሳሌም ፤ (ዕብ ፡ ይሩሻሌም) ፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ የዳዊት ፡ መዲና ፤ የልጆቹ ፡ ኹሉ ፡ መናገሻ ፤ በም ድረ ፡ ይሁዳ ፡ ያለች ፡ ጥንታዊት ፡ ከተማ ። ኢ ፡ የግእዝ ፡ ተውሳክ ፡ ነው ፤ የሩ ፡ ሀገር ፤ ሳሌም ፡ ሰላም ፤ በተገናኝ ፡ ሀገረ ፡ ሰላም ፡ ማለት ፡ ነው ። ሳሌም ፡ ከመባል ፡ በፊት ፡ ሴዱ ፡ ሰላቀናት ፡ ሳይዳ ፡ ቤተ ፡ ሳይዳ ፡ ትባል ፡ ነበር ፤ ቤተ ፡ ጸጋ ፡ ወማህል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዮሐ፭ ፡ ፪) ። ከ ሴዱ ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ ሳሌም ፡ ስለ ፡ ነገሠባት ፡ ሳሌም ፡ የ ሩሳሌም ፡ ተብባለች ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በሸ፡ ፡ አልተለወ ጠም ፡ (መዝ ፡ ፸፭ ፡ ፪ ። ኢያ፲ ፡ ፩) ። «**እመጽሐፈ ፡ ዮሐንስ ፡ መደብር ፤ ክፍል ፡ ራብዕ ። መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ውእቱ ፡ ዘወፅአ ፡ እምነገደ ፡ ሴዱ ፡ ወልደ ፡ ንጉሠ ፡ ምስር ፡ ወኖባ ፤ ወውእቱ ፡ ሴዱ ፡ ዘነግሠ ፡ በከነዓን ፡ ወውእቱ ፡ እምነገደ ፡ ጽኑዓን ፡ ወውእቱ ፡ ተዳብ ሎሙ ፡ ወተቀንዩ ፡ ሎቱ ፤ ወሶበ ፡ አስተፍሥሕዎ ፡ ነ በረ ፡ ውስቴታ ፡ ወሐነጸ ፡ ሀገረ ፡ ወሰመያ ፡ በስመ ፡ ዚኣሁ ፡ ሳይዳ ፤ ወእስከ ፡ ዮም ፡ ትሰመይ ፡ ሳይዳ ፤ ወአቡሁ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ወፅአ ፡ እምነ ፡ ሳይዳ»** ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ሐሚድ ፡ ግን ፤ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ወ ልደ ፡ ፋሌቅ ፡ ብሎ ፡ የራግውን ፡ ታናሽ ፡ ወንድም ፡ ሴማዊ ፡ ይለዋል ። **ወሐይወ ፡ ፋሌቅ ፡ እምድኅረ ፡ ወለዶ ፡ ለራግው ፡ ክልኤተ ፡ ምእተ ፡ ስሳ ፡ ወተስዐተ ፡** (፪፻፷፱) ፡ **ዓመተ ፡ ወእምዝ ፡ ወለደ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ካህን ፡** (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፳፱) ። **ወሶበ ፡ ቀርበ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ ለ ኖኅ ፡ አማሕፀኖ ፡ ለሴም ፡ ወልዱ ፡ ከመ ፡ ያፍልስ ፡ ሥጋሁ ፡ ለአዳም ፡ ወይቅብሮ ፡ ማእከለ ፡ ምድር ፡ ወይሢም ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ወልደ ፡ ፋሌቅ ፡ ኅበ ፡ መቃብሩ ፡ ከመ ፡ ይትለአክ ፡ እስመ ፡ ካህኑ ፡ ለእግዚ ፡ ውእቱ ፡** (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፲፩) ። **ቀሌምንጦስኒ ፡ ወአቡ ፡ ሻህር ፡ ይቤሉ ፡ ከማሁ ።** ከሳሌም ፡ በኋላ ፡ የነገ ሠም ፡ ንጉሥ ፡ ሳሌም ፡ በመባል ፡ ሳይ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ አዶን ፡ ጼዴቅ ፡ እየተባሉ ፡ በምሳሌ ፡ ስም ፡ ተጠርተዋል ፤ ይኸውም ፡ ንጉሥ ፡ ጻድቅ ፡ እግዚእ ፡ ጻድቅ ፡ ማለት ፡ ነው ። አማናዊው ፡ ንጉሥ ፡ ጻድቅና ፡ እግዚእ ፡ ጻድቅ ፡ ኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ፡ እንደ ፡ በውንቱ ፡ ንጉሥ ፡ አይሁድ ፡ ተብሎ ፡ በመካከሏ ፡ ተሰቅሎ ፤ ደቂቀ ፡ አዳምን ፡ ከአብ ፡ ሕዝብን ፡ ከአሕዛብ ፡ ሰውን ፡ ከመላእክት ፡ ነፍሳትን ፡ ከሥጋት ፡ የሚያስታርቅባት ፡ ስለ ፡ ኾነች ፡ ስሟ ፡ እንደ ፡ ትንቢት ፡ ኹኖ ፡ ከነቢያት ፡ በፊት ፡ በዘመን ፡ አበው ፡ ተነግሯል ፡ (ሉቃ፲፫ ፡ ፴፫ ። ኢሳ፪ ፡ ፲፫—፲፰ ። ቈላ፩ ፡ ፳—፳፪) ። ነቢያት ፡ ግን ፡ በእስራኤል ፡ ከፋት ፡ ሰዶም ፡ ገሞራ ፡ ብለዋታል ፤ ከሰዶምም ፡ ያከፋችና ፡ ያበለጠች ፡ አሉ ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፲ ። ሕዝ፲፮ ፡ ፵፰) ።

**ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት ፤** ሰምስተኛ ፡ ሰማይ ፡ ከጠፈር ፤ ዲያብሎስ ፡ የተፈጠረባት ፤ ርሱ ፡ ከሸ ፈተ ፡ በኋላ ፡ ለአዳም ፡ ልጆች ፡ የተሰጠች ፡ (ዕብ፲፪ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ። ራእ፳፩ ፡ ፪) ።

**አዩስ ፤ ሰት ፤ (ኤስ ፡ የአይስ ፡ ይኢስ ። ዐረ ፡ አዩሰ ። ዕብ ፡ ያኣሽ) ፤** መዛበር ፤ መጨነቅ ፡ መዋለል ፤ መስነፍ ፡ መድከም ፡ መዛል ፤ ተስፋ ፡ መቍረጥ ፤ የበሽተኛ ፡ የሐዘንተኛ ። **አአይስ ፡ በሕማም ፡ ወትረ ። ነፍስየ ፡ ተአነብዝ ፡ ወተአይስ ፡ ልብየ ፡** (ኢዮ፲ ፡ ፲፱ ። ኤር፲፱ ፡ ፲፱) ።

**ኢየሱስ ፤ (ጽር ፤ ይሱስ ። ዐረ ፡ የሱዕ ። ዕብ ፡ የሹዕ) ፤** ስመ ፡ ተጸውዖ ፡ ዐማኑኤልን ፡ የመሰለ ። መድኅን ፡ መድኅኒ ፤ መድኅኒት ፤ ቤዛ ፡ መቤዠው ፡ (ማቴ፩ ፡ ፳፩ ። ዮሐ፬ ፡ ፵፪) ። ኢ ፡ ና ፡ ይ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ና ቸው ፤ የሱስ ፡ ማለት ፡ ይበቃ ፡ ነበር ፤ ኢ ፡ እንዳይው ፡ በከንቱ ፡ ተጨምሯል ፤ ምስጢር ፡ የለውም ፤ ኢያሱ ፡ ኢ ዮስያስ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ ኢን ፡ አኮ ፡ መድኅኒት ፡ ሲሉ ፡ አይሁድ ፡ ጨምረውታል ፡ ብ ለው ፡ ያወራሉ ፤ ውሸት ፡ ነው ። ስምንቱም ፡ ብቻ ፡ የቃል ፡ ብቻ ፡ የሥጋ ፡ ስም ፡ አይደለም ፤ ቃልና ፡ ሥጋ ፡ ተዋሕ ደው ፡ አንድ ፡ የኾኑበት ፡ ያንድ ፡ አካል ፡ የሥግው ፡ ቃል ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ፪ ፡ ባሕርይና ፡ ፪ ፡ ግብር ፤ አምላክ ፡ ወሰብእነት ፡ ያሳያል ፤ እንደማኑኤል ፡ ነው ። **ሶበሰ ፡ አ ምላክ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ እፎመ ፡ እምሐመ ፡ ሶበ ፡ ሰቀልዎ ፤ ወሶበሂ ፡ ሰብእ ፡ ውእቱ ፡ በሕቲቱ ፡ እፎመ ፡ እምአድኅነ ፡ ፍጡራነ ፡** (ሃይ ፡ አበ) ። ቤዛ ፡ ኹኖ ፡ መስቀል ፡ መሞት ፡ ምግብ ፡ ኹኖ ፡ መበላት ፡ መጠጣት ፡ የሰውነት ፡ ማዳን ፡ የአምላክነት ፡ (ዮሐ፮ ፡ ፶፮ ፡ ግብ፬ ፡ ፲፪) ። ከሥጋዊም ፡ በፊት ፡ የርሱ ፡ ምሳሌ ፡ ሊኾኑ ፡ የ ሱስ ፡ የተባሉ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፤ (፩ዜና ፡ ፳፬ ፡ ፲፩ ። ነሐ ፲፪ ፡ ፯) ። ኢያሱና ፡ ሆሴዕም ፡ የዚህ ፡ ቈምር ፡ ናቸው ።

**ኢያሰጲስ ፤ ድ ፤ (ጽር ፡ ያስፒስ ። ዕብ ፡ ያሽፌ) ፤** ዕንቍ ፡ የዕንቍ ፡ ስም ፤ ሕብሩ ፡ ሕብረ ፡ ሰ ማይ ፡ ጽሩይ ፤ ቅዛዝ ፤ መስታዮት ፡ የሚመስል ፡ (ራእ፬ ፡ ፫ ። ፳፩ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ። ሕዝ፳፰ ፡ ፲፫) ።

**አይቴ ፤ (ዐረ ፡ አይነ ። ዕብ ፡ አዩን ፤ አና) ፤** ቃለ ፡ ጥያቄ ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፤ አገባብነቱም ፡ የ በታ ። ፍችው ፡ ሴት ፡ ዬት ፡ ወዴት ፤ ወደዬት ። በታን ፡ የበታን ፡ ስም ፡ ይሻል ፤ ኑ ፡ መ ፡ እያገኑት ፡ ሳያገኑ ትም ፤ ሂ ፡ ኒ ፡ ትራስ ፡ እየኾኑት ፡ ትራስ ፡ ሳይኾኑትም ፡ ይነገራል ። **አይቴኑ ፡ አሐውር ። አይቴመ ፡ ምረግ ፡ ዘ መረግሙ ። አይቴኑመ ፡ ቃለ ፡ እግዚ ። ወኢበአይ ቴኒ ። አይቴ ፡ ሀሎከ ። አይቴ ፡ ቀበርክምዎ ። አይቴ ፡ ብሔሩ ፤ ወአይቴ ፡ ማኅደሩ ፤ አይቴ ፡ ደወላ ፤ ወበአ ይቴ ፡ ተረክበ ፡ አሠረ ፡ ፍኖታ ፡** (መዝ ፡ ፻፴፰ ። ሕዝ ፲፫ ፡ ፲፪ ። ኤር፲፯ ፡ ፲፭ ። ፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ። ኢዮ፴፰ ፡ ፲ ። ዮሐ፲፩ ፡ ፴፬ ። ቅዳ ፡ ኢጲ) ። የበታ ፡ አገባቦች ፡ በ ፡ ኀበ ፡ እንተ ፡ እም ፡ እስከ ፡ ይስማሙታል ። የቀረውን ፡ በበ ታው ፡ ተመልከት ፡ (ዕር፳ ፡ ቍ፯) ።

**አኪው ፡ ዎት ፡(አከወ ፡ የአኩ ፡ ይአኩ)፡** መጀረዋ ፡ ፀሎ ፡ ማለት ፡ ጽድቁን ፡ ባሉታ ፡ መለወጥ ። አከየን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**አከ ፡(ጽር ፡ ኢ'ኽ ። ዕብ ፡ አ'ኽ ፡ ባሕቱ)፡** ነባር ፡ አሉታ ፡ አንቀጽ ፡ እንዳ'ን ፡ አይደለም ፡ አይ'ኸንም ፡ አይ'ኹን ፡ አይደረግ ። ዳግመኛም ፡ ኑ ፡ ሲጨመርበት ፡ ጥያቄና ፡ አበረጅ ፡ እየ'ኾነ ፡ በ'ኹለት ፡ ይፈታል ፡ አበረጅ ፡ ሲ'ኾን ፡ ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ነው ። አከ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ኃጥአ ንሰ ፡ አከ ፡ ከመ ፡ ዝ ። አኮ ፡ አኮ ፡ በቅብዐ ፡ ደነስ ። አከ ፡ ሊተ ፡ ዘሥዐከ ፡ አባግዒከ ። አኮሁ ፡ አነ ፡ ዘእወ ልድ ። አኮኑ ፡ ዛቲ ፡ ባቢሎን ። አኮኑ ፡ ሰማርያ ። አ ኮኑ ፡ ነዳያን ፡ እሙንቱ ፡(መዝ ፡ ፳ ። ደራሲ ። ኢሳ፴፫ ፡ ፴፫ ። ፴፯ ፡ ፱ ። ዳን፬ ፡ ፴፯ ። ሚክ፮ ፡ ፳ ። ኤር፳ ፡ ፱) ።

**አከኑ ፡(ዐቢይ ፡ አገባብ)፡** አበረጅ ፡ ና ፡ እ ንደ ፡ ባሕቱ ፡ በፊትም ፡ በ'ኋላም ፡ ይገባል ። አገባብነቱን ፡ በዐታው ፡ ተመልከት ፡(ዕር፲፱ ፡ ቍ፰፯) ።

**አከደር ፡(ዐረ ፡ አኅደር)፡** የቀጠለ ፡ ዐይ ነት ፡ ቅጠሊይ ፡ አረንጓዴ ። ወንጺፍ ፡ ጸፍጸፉ ፡ በሕ ብረ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ፡ ወያክንት ፡ ወአከደር ፡ ወአስ ፋር ፡(መቃ ፡ ፯፫) ።

**አከ(ቅ)ደር ፡(ጽር ፡ ወዕብ)፡** ጥቍር ፡ ጠ ቈሬ ፡ ክበልማ ። ጽልመት ፡ ጽላሎት ፡ ፊጸለማ ። ቄዳርስ ኀና ፡ ቄድሮስን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ፡ ቀና ፡ ክ ፡ ተወራርሰዋል ።

**አካጥስ ፡(ጽር ፡ አካቲስ ፡ ዕብ ፡ ሺበ)፡** ዕንቍ ፡ የዕንቍ ፡ ስም ፡ ከ፲፪ቱ ፡ አዕናቍ ፡ አንዱ ፡(ዘፀ ፳፰ ፡ ፲፱ ። ፴፱ ፡ ፲፪) ።

**አክዮ ፡ ዮት ፡(አክየ ፡ አከየ ፡ የአኪ ፡ ይእከዮ ፡ ኪ)፡** መክፋት ፡ መባስ ፡ ክፉ ፡ መጥፎ ፡ መ ኾን ፡ የጠባይ ፡ የደዌ ፡ የመልክ ። ፈድፋደ ፡ አክዮ ። አ ልቦ ፡ ዘየአኪ ፡ እምርእስ ፡ አርዌ ፡ ምድር ። እምዘሉ ፡ ቍስል ፡ የአኪ ፡ ቍስለ ፡ ልብ ። እምዘሉ ፡ አዕዋፍ ፡ ተአኪ ፡ ገይብ ፡(ሄርማ ። ሢራ፳፭ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ። ፲፮ ፡ ፲) ።

**አክዮ ፡** መበላት ፡ መግነን ፡ የለምጽ ፡ የቍስል ፡ የክፉ ፡ ነገር ። አክየት ፡ ይእቲ ፡ ሕብር ፡(ዘሌ፲፫ ፡ ፰) ።

**አክዮ ፡** መብዛት ፡ ክፉ ፡ ማለፍ ፡ ከፉ ፡ መ ኾን ፡ መባል ፡ ከ'ኻያ ፡ መክፈል ፡(ዐማርኛ) ።

**እኩይ ፡(ያን ፡ ያት ፡ ኪት)፡** የከፋ ፡ ክፉ ፡ መጥፎ ። ጋኔን ፡ እኩይ ። ዘእኩይ ፡ ምግባሩ ። እኩ ያነ ፡ ልማድ ፡ ወግዐዝ ። እስመ ፡ ክልኤተ ፡ እኩያተ ፡ ገብሩ ፡ ሕዝብየ ። ኢትግበሩ ፡ ለእኪት ፡ ወኢይርከ ብከ ፡ እኩይ ፡(መሳ፱ ፡ ፳፫ ። ዮሐ፫ ፡ ፳ ። ሮሜ፮ ፡ ፳፱ ። ኤር፪ ፡ ፲፫ ። ሢራ፯ ፡ ፩) ።

**እክይ ፡(ያት)፡** ክፋት ፡ ክፉነት ፡ መጥፎነት ፡ ልማም ፡ ተንኰል ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ። እክየ ፡ ልብ ። እ ክዩሃ ፡ የዐልዎ ፡ ለራእይ ። ይኄይስ ፡ እክዩ ፡ ለብእሲ ፡ እምነ ፡ ኂሩታ ፡ ለብእሲት ። ዘኢይትበቀል ፡ በእክዩ ። ሔሮከ ፡ ይጸሕፍ ፡ ዘሎ ፡ እክዮሙ ። ምግባረ ፡ እ ኪይ ፡(መክ፯ ፡ ፱ ። ሢራ፳፭ ፡ ፲፯ ። ፵፪ ፡ ፲፬ ። ኤር፳፬ ፡ ፪ ። ኩፋ ፡ ፬ ። ዕብ፲ ፡ ፳፪) ።

**አእከየ ፡** አከፋ ፡ አባሰ ፡ አስከፋ ፡ አስባሰ ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፡ አስደረገ ፡ አስተንኰለ ። ሰይጣን ፡ አእከየ ፡ ልበ ፡ አይሁድ ፡ ላዕለ ፡ ክርስቶስ ። አእከዩ ፡ ልቦሙ ። አብ ዝኀ ፡ አእክዮ ፡ ምግባሪሁ ። ያእኪ ፡ ዐይኖ ፡ ላዕሌክ ፡(አርጋ ፡ ፪ ። ሢራ፲፯ ፡ ፲ ። ኩፋ ፡ ፴፭) ።

**አስተአከየ ፡(አድራጊ)፡** ገዛ ፡ ከማሁ ፡ አ ከፋ ፡ አከፋፋ ፡ አጥላላ ፡ ናቀ ፡ ንቀፈ ፡ አቃለለ ፡ ቢያክ ፡ ቢ ያክ ፡ አለ ፡ አብዝቶ ፡ መላልሶ ፡ ፈጽሞ ። ኢታስተአክዮ ፡ ለሰብእ ፡ በርሥአቱ ። ኢታስተአክዮ ፡ ለሰብእ ፡ እንበ ይነ ፡ ሕሡሚሁ ። ያስተአኪ ፡ ተግሣጸ ፡ አብ ። ወአስተ አክዮ ፡ ሄሮድስ ፡(ሢራ፰ ፡ ፯ ። ፲፩ ፡ ፪ ። ምሳ፲፭ ፡ ፭ ። ሉቃ፳፫ ፡ ፲፩) ።

**ተአከየ ፡(ተደራራጊ)፡** ተከፋፋ ፡ ተጠላላ ፡ ሆድ ፡ ተባባሰ ፡ ተናናቀ ።

**አስተአከየ ፡(አደራራጊ)፡** አከፋፋ ፡ አጠ ላላ ፡ አናናቀ ፡ መስቀጻልእ ፡ ኾነ ።

**አክዮስ ፡(ጽር ፡ አክሲዮስ)፡** የምስጋና ፡ ቃል ፡ ጳጳስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሲሾም ፡ የሚባል ። ዕሡ ፡ ዕሡ ፡ ይበጅ ፡ ያድርግ ፡ ሹመት ፡ ያዳብር ፡ እንደ ፡ ማለት ። ወ ዓዲ ፡ ይበሉ ፡ አክዮስ ፡ ይደልዎ ፡ ይደልዎ ፡(ኪዳ ። ስንክ ፡ ጥቅ፱ ፡ ፳) ።

**አኪል ፡ ሎት ፡(አከለ ፡ የአክል ፡ ይእ ክል ። ዕብ ፡ አካል ። ሱር ፡ ኤካል ። ዐረ ፡ አ ከለ)፡** መብላት ፡ መመገብ ፡ መጕረሥ ፡ መቃም ፡ ማላ መጥ ፡ መጥጥ ፡ ምግቡን ፡ ወደ ፡ ሆድ ፡ ጕተራ ፡ ማግባት ፡ መክተት ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ በአከለ ፡ ፈንታ ፡ አከለ ፡ ብለው ፡ ይገባሉ ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ።

**እክል ፡(ላት ፡ ዕብ ፡ አኬል ። ዐረ ፡ ኡ ክል ፡ እክል)፡** መብል ፡ ምግም ፡ ሲሳይ ፡ የበሰለ ፡ የተ ዘጋጀ ፡ እንጀራ ፡ ወጥ ። ኅጢአ ፡ እክል ። ጕርዔ ፡ ይጥ ዕም ፡ እክለ ። ብልዒ ፡ እክለኪ ። እክል ፡ ወማይ ። ዘ ይሴሰይ ፡ እክልየ ፡(አርጋ ፡ ፩ ። ኢዮ፲፪ ፡ ፲፩ ። ሩት፪ ፡ ፲፬ ። ሢራ፳፱ ፡ ፳፩ ። መዝ ፡ ፵) ።

**እክል ፡(ዕብ ፡ ዳጋን)፡** በቈሎ ፡ ያገለሙራ ፡ እኽል ፡ በያይነቱ ፡ ያልተፈጨ ፡ ጥሬ ፡ ያገዳ ፡ ያበባ ፡ የሣር ፡ የብር ፡ ፍሬ ፡ ተዘርቶ ፡ የሚበቅል ፡ ታጭዶ ፡ የሚከመር ፡ ተወቅቶ ፡ ተመርቶ ፡ የሚሰፈር ፡ ተፈጭቶ ፡ ተቦክቶ ፡ የሚ ጋገር ፡ ማናቸውም ፡ ኹሉ ። አይቴ ፡ እክል ፡ ወወይን ። ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ዐውደ ፡ እክል ። ወሰምዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ እክል ። ወጸዐኑ ፡ እክሎሙ ። ቀዳሚ ፡ እ ክል ። እክላት ፡(ሰቈ፪ ፡ ፲፪ ። ሆሴዕ ፡ ፳፭ ፡ ፳ ። ማቴ፺ ፡ ፲፪ ። ዘፍ፵፪ ፡ ፳፯ ። ዘፀ፳፫ ፡ ፲፯ ። አቡሻ ፡ ፴፯) ።

**አኪል ፡** ማክል ፡ መተካከል ፡ እኩያ ፡ አምሳያ ፡ መ'ኾን ፡ ለሌላው ። ወመሰከትቦ ፡ ኢይትበሀል ፡ ዘንተ ፡ የአክል ፡ ወዘንተ ፡ ይመስል ፡(ቅዳ ፡ ሕር) ።

**አኪል** ፤ (ጥገ) መንመት ፡ መታሰብ ፡ መቈጠር ፡ ይሆን ፡ ያኽል ፡ መባል ፤ መኾን ። ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገባል ። **እለ ፡ ይውኅዱ ፡ የአክሉ ፡ እልፈ ። ወየአክሉ ፡ ኀነውቱ ፡ ለቤል ፡ ሰብዓ ። ወዠሉ ፡ ሕዝብ ፡ የአክሉ ፡ እልፈ ፡ ብእሴ ። ወነበሩ ፡ ህየ ፡ ዘየአክል ፡ ዐሥርተ ፡ ዓመተ ። ወየአክል ፡ ሠላሳ ፡ ክረምቱ ፡** (ኢሳ፷ ፡ ፳፪ ። ዳን፲፫ ፡ ፫ ። ሺነገ ፡ ፲፱ ፡ ፳፪ ። ሩት፩ ፡ ፬ ። ሉቃ፫ ፡ ፳፫) ።

**አኪል** ፤ ማደግ ፤ መጨመር ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ማድረስ ፤ ምሉእ ፡ ፍጹም ፡ አካላዊ ፡ መኾን ፡ ለራሱ ፡ ቡቃያ ፡ ከዘረዘረና ፡ ከሸተ ፡ በኋላ ፡ ያው ፡ ይበስላል ፡ እንጂ ፡ ቁመት ፡ እንዳይጨምር ፡ እንደዚያ ፡ ማለት ፡ ነው ። **እስከ ፡ ይበጽሕ ፡ ወሬዛ ፡ ለመጠኑ ፡ አካል ። ለእመ ፡ ኢበጽሐ ፡ አካለ ፡ ፍጻሜሃ ፤ ፍጻሜ ፡ መጠኑ ፡ አካል ፡** (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱) ።

**አኪል** ፤ መብቃት ፡ መብቃቃት ፡ በቂ ፡ ልክኛ ፡ መኾን ፡ አለማነስና ፡ አለመትረፍ ። **ኢየአክል ፡ ዠሉ ፡ መሥዋዕት ፡ ለመዐዛ ፡ ሠናይ ። ኢየአክል ፡ ሲባኖስ ፡ ለአንድዶ ። ኢአክሎሙ ፡ ስሕተት ። እመ ፡ ኢየአክል ፡ ለሤጠ ፡ በግዕ ። ዘኅዳጥ ፡ የአክሎ ። አክሎሙ ፡ ወተርፎሙ ፡** (ዮዲ፲፮ ፡ ፲፮ ። ኢሳ፵ ፡ ፲፮ ። ጥበ፲፱ ፡ ፳፪ ። ዘሌ፳ ፡ ፯ ። ሚራ፴፱ ፡ ፲፱ ። ዘፀ፴፮ ፡ ፯) ።

**አኪል** ፤ መወሰን ፡ መደንገግ ፡ የሕግ ። ማግመር ፡ መከተት ፤ መቻል ፤ የበታ ። ምስጢሩ ፡ መብቃት ፡ ነው ። **ዘሰማይ ፡ ኢየአክሎ ። ወኢአክሎሙ ፡ ምድር ፡** (፪ነገ ፡ ፳ ፡ ፳፯ ። ዘፍ፲፫ ፡ ፯) ።

**አካሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት)** ፤ የሚበቃ ፡ በቂ ፡ ልክኛ ። **ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕታቲሁ ፡ ኢአካልያነ ፡ ይትኃሠሠው ፡ ከመ ፡ ይወስኩ ፡ ለአጠይቆ ፡** (ፍ ፡ ነ ፡ ማ፫ ፡ ፯) ።

**እኩል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ክልት)** ፤ ያክለ ፡ የበቃ ፡ ብቁ ። **እንዘ ፡ ጥቀ ፡ እኩል ፡ ዕድሜ ፡ መዋዕል ፡ ሰበ ጹሕ ፡** (ተረ ፡ ቁ፫፻) ። በቁሙ ፡ እኩል ፡ እኩሌታ ፡ ግማሽ ፡ መንፈቅ ፡ (በማርኛ) ።

**አካል ፤ (ላት)** ፤ በቁሙ ፡ ፍጹም ፡ ገጽ ፡ ፍጹም ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ለራሱ ፡ የበቃ ፡ እኔ ፡ የሚል ፡ ህላዌ ፡ ነባቢ ፡ ቁመት ፡ ቁመና ፤ የባሕርይ ፡ የግብር ፡ የስም ፡ ባለቤት ፡ እንግሊ ፡ የሚባል ። እኔ ፡ ማለትም ፡ የሚገባ ፡ ዕውቀት ፡ ቀዋሚነት ፡ ላላቸው ፡ ለማይሞቱና ፡ ለማይጠፉ ፡ ለሦስት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ለእምላክ ፡ ለመልአክ ፡ ለነፍስ ። **በከመ ፡ አብ ፡ ህልው ፡ በአካሉ ፡ ወወልድኒ ፡ ከማሁ ። ዘኢየአምን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አሐዱ ፡ አካል ፡ እምሠለስቱ ፡ አካላት ። እስመ ፡ ህላዌሁ ፡ ለቃል ፡ እው ፡ አካሉ ፡ ኢይትበሀል ፡ ካልእ ፡ ዘእንበለ ፡ አካለ ፡ ርእሱ ፡ ባቲቱ ፡ ዘውእቱ ፡ ቃል ፡** (አፈ ፡ ድ፪ ። ሃይ ፡ አበ) ። አካል ፡ ያለባሕርይ ፡ ብቻውን ፡ አይቆምም ፡ ባሕርይም ፡ ያላካል ፡ አይፈጸምም ። ባሕርይና ፡ አካል ፡ እንደ ፡ ሥርና ፡ እንዳጽቅ ፡ እንደ ፡ ነቅና ፡ እንደ ፡ መትረብ ፡ እንደ ፡ ቅንጣትና ፡ እንዳገዳ ፡ ናቸው ። **በከመ ፡ ሠዋቲ ፡ ይትወለድ ፡ እምነ ፡ ዕሩቅ ፡ ኅጠት ፡** (ማር ፡ ይሥ፪) ። ከዚህ ፡ ምሳሌም ፡ የተነሣ ፡ ሥሩ ፡ የባሕርይ ፡ ፍሬ ፡ ይባላል ። ዳግመኛም ፡ ከራስ ፡ ጠጕር ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍር ፡ ባጥንት ፡ በጅማት ፡ በሥጋ ፡ በቈርበት ፡ ተያይዞና ፡ ተሸፍኖ ፡ ያለው ፡ ባንድነት ፡ አካል ፡ ይባላል ። አካለ ፡ ጕደሎ ፡ እንዲሉ ። **ዠሉ ፡ መሌሊት ፡ ይትበሀል ፡ አካለ ። አካል ፡ በዘየአክል ፡** (አዋል) ። አካል ፡ መባሉም ፡ በነፍስ ፡ ዕውቀትና ፡ በነፍስ ፡ አካልነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በራሱ ፡ በገንዘቡ ፡ አይደለም ፡ በገንዘቡስ ፡ የነፍስ ፡ መጋረጃ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ሥጋ ፡ ገላ ፡ ይባላል ፡ ይኸውም ፡ ገልዓዊ ፡ ገልዕ ፡ ጕልሕ ፡ ግልዋ ፡ ግዙፍ ፡ የሚታይ ፡ የሚያዝ ፡ የሚዳሰስ ፡ አፍኣዊ ፡ መሬታዊ ፡ ሕዋስ ፤ እንስሳዊ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ተረት) ፤ ልብስን ፡ ፀጥቦ ፡ ለገላ ፡ ብርሌን ፡ ፀጥቦ ፡ ለበላ ። የሰው ፡ ገላ ፡ ርጥብ ፡ ሸክላ ፡ ያልተተኰሰ ፡ ያልተኰላ ። (ግጥም) ፡ ከዚያ ፡ ቤት ፡ ያለች ፡ ሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ድኻ ፡ ናት ፡ አሉ ፡ ጠም ፡ ፀዳሪ ፤ ማን ፡ አስተማራት ፡ ጥበቡን ፡ ገል ፡ ፀፈር ፡ መኾኑን ፡ (ገላ) ። መጋረጃነቱም ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ፤ ርሷ ፡ ስትለቀው ፡ በመውደቁ ። **ወአካልየኒ ፡ ወኢከመ ፡ ምንት ፡ በቅድሜከ ። ወኢአካልየ ፡ በመትሕተ ፡ ምድር ፡** (መዝ ፡ ፴፰ ። ፻፴፰) ። የህላዌንና ፡ የጠባይዕን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ዘውግ ፡ ነው ።

**አካል** ፤ ልክ ፡ ዐቅም ፡ መጠን ። **ለእሳትስ ፡ ቦቱ ፡ መጠን ፡ ወቦቱ ፡ አካል ። ዕፀ ፡ ዘይፈሪ ፡ ዕሩየ ፡ ይሁብ ፡ ፍሬሁ ፡ አኮኑ ፡ በበ ፡ አካሉ ፡** (በየቅሙ ፡ በየመጠኑ) ። **ሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ በአካለ ፡ ህላዌነ ፡ በባሕርያችን ፡ መጠን ፡ ማለት ፡ ነው ፡** (ቅዳ ። ኪዳ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**አክል** ፤ ግዘፍ ፡ ወፍር ፡ ድንዳኔ ፡ ታላቅነት ። **አሕማር ፡ ዘመጠኑ ፡ ዝ ፡ አክሎን ፡** (ያዕ፫ ፡ ፬) ።

**አእከለ** ፤ አበላ ፡ አስበላ ፡ አበቃ ፡ አብቃቃ ፡ ጠገበ ፡ በቃኝ ፡ አለ ፡ ፈጸመ ፡ ጨረሰ ፡ አስጨረሰ ። **ወአእከልኩ ። ከመ ፡ አእኪልየ ፡ ኢይኩን ፡ ሐሳዌ ። ወኀበኒ ፡ ኢያእከልኩ ። ወአእክሉ ፡ በርእይ ። አእከለ ፡ ሰቤዝዎቱ ። ሶበ ፡ አእከለ ፡ ተምህሮ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡** (ሢራ፲፰ ፡ ፲፱ ። ምሳ፴፱ ፡ ፴፪ ። ፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፱ ። ጥበ፲፫ ፡ ፯ ። ዘሌ፳፭ ፡ ፳፯ ። ገድ ፡ ኪሮ) ። በአእከለ ፡ ፈንታ ፡ አስተአከለ ፡ ይላል ፡ አብቃቃ ፡ ለማለት ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። **ምድር ፡ እንተ ፡ ኢኮነት ፡ በአስተአክሎ ፡ ዘትበልዖ ፡** (ዘዳ፰ ፡ ፱) ።

**ተእክለ ፤ ተአክለ** ፤ ተበላ ፡ ምግብ ፡ ኾነ ፡ ተወሰነ ፡ ቆመ ፡ ጸና ። **ኀደግን ፡ በብዕለ ፡ ቃላቲሆሙ ፡ ለእበው ፡ ተአኪለነ ። መፍትውስ ፡ ተአኪለነ ፡ በእለ ፡ ቀደሙነ ፡ መምህራን ፡ ትምህርት ፡ ወዘቅዱሳን ፡ ማየ ፡ ተረዊየነ ፡ ናክብር ፡ ለእርምሞ ፡** (ተረ ፡ ቁ፫፻ና ፡ ፯) ።

**ተአከለ** ፤ ተባላ ፡ ተናከሰ ፡ ተካከለ ፡ ተወዳደረ ። **ኢትትአከል ፡ እንዘ ፡ ነዳይ ፡ አንተ ፡ ምስለ ፡ ባዕል ፡** (ምሳ፳፫ ፡ ፬) ።

**አስተአከለ** ፤ አስተካከለ ፡ አወዳደረ ፡ አነጻጸረ ።

**ማእከል** ፤ መካከል ፡ ወገብ ፡ ጕንድ ፡ ሕንብርት ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ማኅደር ፡ ጎዋ ፡ አየር ፡ ወሰን ፡ ደን

በር ፡ እኩሌታ ፡ እኩል ። ኦዐማድ ፡ እለ ፡ ማእከል ። ምትሮሙ ፡ እማእከሎሙ ። ያንቅዐክ ፡ እማእከልከ ። ዝንቱ ፡ መካን ፡ ማእከለ ፡ ምድር ። ፃእ ፡ እማእከላ ። ይሰርር ፡ ማእከለ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ። ማእከለ ፡ ሌሊት ፡ (መሳ፲፰ ፡ ፳፱ ። ዘፍ፲፭ ፡ ፲ ። ዳን፩ ፡ ፵፭ ። ቀሌ ። ኢሳ፶፪ ፡ ፲፩ ። ሉቃ፳ ፡ ፲፫ ። ማቴ፳፭ ፡ ፮) ።

**ማእከለ ፤ (ደቂቅ ፡ አግብብ) ፤** በመካከል ፡ ወደ ፡ መካከል ፡ በውስጥ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ። ቀም ፡ ማእከለ ። ባእ ፡ ማእከለ ። ሖለጽኩ ፡ ማኅፈደ ፡ ማእከሎ ፡ (ሉቃ፮ ፡ ፰ ። ሕዝ፲ ፡ ፪ ። ኢሳ፰ ፡ ፪) ።

**ማእከላዊ ፤ ይ ፤** መካከለኛ ፡ የማናይ ፡ ፀጋማይ ፡ ወይም ፡ ቀዳማይ ፡ ደኃራይ ፡ ላዕላይ ፡ ታሕታይ ፡ ያለው ። ወልዱ ፡ ማእከላዊ ። ፍኖት ፡ ማእከላይ ። ማኅደር ፡ ማእከላይ ። አበው ፡ ማእከላውያን ። ይቤለከ ፡ ከመ ፡ ትፀመድ ፡ ወትትጋደል ፡ በኀይል ፡ ማእከላይ ፡ ከመ ፡ ኢይድክም ፡ ሥጋከ ። እስመ ፡ ማእከላይ ፡ አንተ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፭ ፡ ፱ ። እፈ ፡ ድ፱ ። ቀሌ ። ያዕ ፡ ዘእል ። ስንክ ፡ ማግ፲፰ ፡ ፈእ፱ ፡ ፲፮) ።

**ማእከላዊ ፤** ዳኛ ፡ ጠባቂ ፡ አማላጅ ፡ አስታራቂ ። (ተረት) ፡ ዳኛ ፡ ሃወል ፡ ምስሶ ፡ የመካከል ። ማእከላይሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወሰብእ ፡ (ቄር) ።

**ማእከልና ፤** ማእከላዊነት ። ለእመ ፡ ሞተ ፡ ፍጹም ፡ በእርግናሁ ፡ ወማእከላዊኒ ፡ በማእከልናሁ ፡ ወወጣኒ ፡ በውርዝውናሁ ፡ (ፊልክ ፡ ፱) ።

**አማእከለ ፡ (ዲቃላ ፡ ግስ) ፤** አማከለ ፡ ከበበ ፡ ከማኽል ፡ አገባ ።

**መእክ(ጥ)ል ፤ (ዕብ ፡ (ጥከ) ፡ ማክሌት) ፤** ተሰፍሮ ፡ ለቀለብተኛ ፡ የሚሰጥ ፡ እኽል ። ወሀቦ ፡ ሥርናየ ፡ መእኪጦ ፡ ለቤቱ ፡ (፫ነገ ፡ ፭ ፡ ፲፩) ። ዘይቤው ፡ ቀለብ ፡ ምግብ ።

**አክሊል ፤—በቁሙ ፤—ከልሎ ፡ ከለለ ።**

**አክሊሮስ ፤ (ጽር ፡ ክሊሮስ ፤ ክሊሪክስ) ፤** ቄስ ፡ ገዢ ፡ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ ሹም ፡ አለቃን ፡ ታኝ ። ሰእመ ፡ ሰረቀ ፡ አክሊሮስ ፡ ዘውእቱ ፡ ቀሲስ ፡ ኅበዝ ፡ ንዋይተ ፡ ምሥዋዕ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፯) ።

**አክማም ፤—የክንድ ፡ ልብሶች ፤—ከሚም ፡ ከመ ፡ ከመመ ፤ ክማም ።**

**አክኑ ፤—ና ፤—አክ ፡ ኑ ።**

**አካዕ ፡ (ጽር ፡ አካይዖ) ፤** ስመ ፡ አምላክ ፡ በመሐላ ፡ ጊዜ ፡ ሃማጠሬ ። አ ፡ አልፋ ፡ ከ ፡ ካይ ፡ ዋዊ ፡ ዕ ፡ ዖሜጋ ፡ አካዕ ፡ አወዖ ፡ አልፋ ፡ ወዖ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወደኃራዊ ፡ ርእስ ፡ ወማኅለቅት ፡ ጥንት ፡ ወተፍጻሜት ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለብሉዮቹ ፡ ግን ፡ አምላክ ፡ ከሃሊ ፡ ይሉታል ። ወአንበርዎ ፡ ለዝ ፡ መሐላ ፡ አካዕ ፡ በእዴሁ ፡ ለሚካኤል ። ሰላም ፡ ለእራኃከ ፡ ስመ ፡ መሐላ ፡ ዘፀበጠ ፡ (ሔኖ ። ደራሲ) ።

**አክፌ ፤—አበሰ ፡ ጠረገ ፤—ክፍ ፡ ወኪፍ ፡ ወከፈ ።**

**አክራጦን ፤ (ጽር ፡ አክራቶን) ፤** ጥሩ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ። አክራጦን ፡ ዘአልቦቱ ፡ ቱስሕት ፡ (ተረ ፡ ቄር ። ኢጲ ። አርጋ) ።

**አክሲጦስ ፤ አው ፡ አግሲጦስ ፤** ያልታወቀ ፡ ጥሬ ፡ ትርፍ ፡ ቃል ፡ በጽርኤም ፡ በዕብራይስጡም ፡ የሌለ ። ባለብሉዮች ፡ ጉባኤ ፡ ነቢያት ፡ ጉባኤ ፡ ካህናት ፡ ይሉታል ። ወትቤ ፡ አክሲጦስ ፡ ኢይቴ ፡ ሖረ ፡ ወልድ ፡ እኁኪ ፡ (ማሕ፭ ፡ ፲፯) ። በማሕልይ ፡ ውስጥ ፡ ፀልፎ ፡ ፀልፎ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኀንደ ፡ ዚቅና ፡ እንደ ፡ ስረጽ ፡ ከያሬድ ፡ በኋላ ፡ የገባ ፡ መዘምራን ፡ የማያዜሙት ፡ መምህራን ፡ የሚተረጕሙት ፡ ጥሬነት ፡ የሌለው ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ ንባብ ፡ አለ ፤ ስመሥንም ፡ ከጽርኤ ፡ ምላሽ ፡ ለይተው ፡ ዕብራይስጥ ፡ ይሉታል ። ርሱ ፡ ግን ፡ ከግእዝ ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ጥሬ ፡ በዕብራይስጥ ፡ አይገኝምና ፡ ግእዝ ፡ እንጂ ፡ ዕብራይስጥ ፡ ሊሉት ፡ አይገባም ፡ ዕብራይስጥ ፡ ብሎ ፡ ስም ፡ የሰጠው ፡ ከማኽል ፡ አግብቶ ፡ ያስቀመጠው ፡ ከቶ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አልታወቀም ።

**አኵስም ፤ (ዕብ ፡ አ ፡ ኵሽም) ፤** አ ፡ ጥንት ፡ ቀዳማዊ ፡ ርእስ ፡ ኵሽም ፡ ኵሻውያን ፡ የኵሽ ፡ ልጆች ፡ ሕዝበ ፡ ኵሽ ፡ ነገደ ፡ ኵሽ ። አኵሽም ፡ ጥንታዊት ፡ ቀዳማዊት ፡ የነገደ ፡ ኵሽ ፡ መዲና ፡ የአህጉረ ፡ ኵሽ ፡ ራስ ፡ እምነ ፡ ለአህጉረ ፡ ኵሽ ። ወደበ ፡ ርእሰ ፡ ሀገረ ፡ አቡዊነ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ። ኵሳ ፡ አኵስም ፡ ማለት ፡ በሐዲስ ፡ ግእዝ ፡ ነው ፡ በሳባና ፡ በጥንታዊ ፡ ግእዝ ፡ በዐረብ ፡ በሱርስት ፡ በዕብራይስጥ ፡ በሴም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ ኵሽ ፡ እንጂ ፡ ኵሳ ፡ አይባልም ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፮) ። ዐማሮች ፡ አኵስም ፡ የሚሉትን ፡ ትግሮች ፡ አክሱም ፡ ይሉታል ፡ ይኸውም ፡ ዐብይ ፡ ኮብይ ፡ ጸም ፡ መገስ ፡ ሞገስ ፡ በቱ ፡ ሰቱ ፡ እንደሚሉት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ አጠራር ፡ አይደለም ፡ እውነተኛውስ ፡ አኵስም ፡ ነው ። ፪ኛም ፡ በ ፡ ዘይቤ ፡ ታሪክ ፡ አኵስም ፡ ማለት ፡ ኵሰኵሰ ፡ ኵተኵተ ፡ ከማለት ፡ ካትክልት ፡ ሥራ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ትርጓሜውም ፡ የተክል ፡ ቦታ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላል ፤ በዙሪያዋ ፡ ያሉት ፡ አህጉር ፡ ግን ፡ ጎረ ፡ ቤቶቿና ፡ አቅራቢያ ፡ አክሱም ፡ ዐድ ፡ ሕዙም ፡ ይሏታል ።

**አክሲማሮስ ፤ (ጽር ፡ ሄክሳኢሜሮን) ፤** ስድስት ፡ ቀን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (አቡሻ ፡ ፲፱) ። የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ የኻቱን ፡ ቀን ፡ ሥን ፡ ፍጥረት ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ የሚናገር ፡ ካያ ፡ ኹለት ፡ ብሎ ፡ የሚቈጥር ፡ የኢጲፋንዮስ ፡ መጽሐፍ ።

**አክሳስ ፤ (ጽርእ) ፤** የእንስሳ ፡ ስም ፡ ትንግማኤ ፡ ሙታንን ፡ የሚያበረዳ ። ባለመጽሐፎች ፡ ግን ፡ ሺ ፡ እግር ፡ ቅንቡርስ ፡ የእበት ፡ ትል ፡ ይሉታል ፡ እንጂ ። ወእንስሳሂ ፡ ዘይሰመይ ፡ አክሳስ ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ ኢጲ) ።

**አክሶስያ ፤ (ጽር ፡ ኤክሱሲ.ያ) ፤** ሥልጣን ፡ ክሂል ፡ ጌትነት ። አክሶስያ ፡ ዘይደሉ ፡ ለመለኮት ፡ (ቁር ፡ በምዓት) ።

**አኰት ፤ ቶት ፤ (አኰተ ፡ የአኵት ፡ ይእኵት) ፤** ማመስገን ፡ መባረክ ፡ መመረቅ ፡ መሃበብ ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ፡ ማገልገል ፡ በእጅ ፡ በቃል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአኰተ ፡ ፈንታ ፡ አእኰተ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ሰአኵት ፡ ባረከ ፡ ወፈተተ ። ሰእኵቶትዎ ፡ ጥቀ ። ሰአኰትኩ ፡ እግዚኦ ። ሰእኵቶ ፡ ለዘጸገወከ ። ብእሲት ፡ እንተ ፡ ኢተአኰቶ ፡ ለምታ ፤ (ቅዳ ። ዮሐ.፳ ፡ ፰ ። ኢሳ.፲፪ ፡ ፩ ። ፊልክ ። ሚራ.፳፭ ፡ ፳፪) ።

**አኳቴ ፤ (ቴት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤** የሚያመሰግን ፡ አመስጋኝ ፡ አገልጋይ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ አእኳቴ ፡ ይላል ፡ አያስኝም ። ከነ ፡ ብእሴ ፡ ትሑተ ፡ ወአእኳቴ ፡ እግዚ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፮) ።

**አእኰተ ፤ (ያእኵት ፡ ያእኵት) ፤** አስመስገን ፡ አስመረቀ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ አእመረን ፡ ዐወቀ ፡ አሳወቀ ፡ እንዲሉ ፡ አእኰተንም ፡ በኹለት ፡ ጾታ ፡ ይፈቱታል ፡ ከማስደረግ ፡ በቀር ፡ አይራራንት ፡ አይስማማውም ፡ የአን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ።

**አስተእኰተ ፤ አስተአኰተ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ (አስ.ይራጊ) ።

**አእኳቴ ፤** አስመስጋኝ ። ይህንንም ፡ አመስጋኝ ፡ ይሉታል ።

**ተአኵተ ፤** ተመሰገነ ፡ ተባረከ ፡ ተመረቀ ። እምኅበ ፡ መላእክት ፡ ተአኵተ ። ትትአኰት ፡ በኄቤሁ ። ብእሲ ፡ ኄር ፡ ብዙኅ ፡ ይትአኰት ፤ (ኪዳ ። ዮሐ.፲፪ ፡ ፲፫ ። ምሳ.፳፫ ፡ ፳) ።

**እኩት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ኩት) ፤** የተመሰገነ ፡ ምስጉን ፡ ምሩቅ ። እኩት ፡ አንተ ፡ ወእኩት ፡ ስምከ ። ክቡር ፡ ወእኩት ። እኩት ፡ ወስቡሕ ፡ (ዲን ። ኩፋ ፡ ፴፭ ። ቅዳ) ።

**እኳቴ ፤** ማመስገን ፡ መመስገን ፡ አመሰጋገን ፡ ምስጋና ፡ ብፅዓን ፡ ቡራኬ ። እንተ ፡ ደለዎ ፡ እኳቴ ፡ (ዲ ራሲ.) ።

**አኰቴት ፤** ምስጋና ፡ አገልግሎት ፡ መሥዋ ። ከመ ፡ ተሀቡ ፡ አኰቴተ ፡ ለስምየ ። ወሀበት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አኰቴተ ፡ ወስባሔ ። ያመጽኡ ፡ አኰቴተ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፤ (ሚልክ ፡ ፩ ። ኩፋ ፡ ፳፭ ። ኤር.፲፯ ፡ ፳፯) ። ምስጋናነቱም ፡ ባሰፈ ፡ በትደረገ ፡ ነው ፡ ሐሳብና ፡ ምኞት ፡ ሲፈጸም ፡ ለዚያ ፡ ለፈጸሚው ፡ በደስታ ፡ ቃል ፡ የሚቀርብና ፡ የሚነበብ ፡ የሚዜም ፡ ዜማ ፡ ነው ፡ ንሰብሖ ፡ እንደ ፡ ማለት ።

**አኰቴት ፤** ቍርባን ፡ ኅብስተ ፡ ቍርባን ፡ የቍርባን ፡ ጸሎት ፡ ፍሬ ፡ ቅዳሴ ፡ ንአኵቶ ፡ ንአኵተከ ፡ ብሎ ፡ የሚዠምር ። እምድኅረ ፡ ተመጠዉ ፡ አኰቴተ ። አኰቴተ ፡ ቍርባን ፡ ዘአበዊነ ፡ ሐዋርያት ፤ (ኪዳ ። ቅዳ) ።

**ማእኰት ፤** ጸጋ ፡ ሀብት ፡ ስርየት ፡ በጥምቀት ፡ በቍርባን ፡ በንስሓ ፡ የሚሰጥ ። ሀብ ፡ እግዚኦ ፡ ማእኰተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በዕበየ ፡ ማህልከ ፡ ወምሕረትከ ፡ (ግንዘ) ።

**ማእኰት ፤** ማኵታ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ በረከት ፡ ግብር ፡ ማማለጃ ፡ አመስጋኝና ፡ ተመስጋኝ ፡ የሚሰጡት ፡ የሚቀበሉት ። ነገሥታት ፡ ወመኳንንት ፡ እለ ፡ ይበልዑ ፡ ማእኰተ ። ወመኳንንቲሆሙ ፡ በላዕያነ ፡ ማእኰት ፡ (ቀሌ ። መቃ ፡ ገ፱) ።

**ማእኰት ፤** ምልጃ ፡ ተስፋ ፡ ደጅ ፡ ጥናት ። መሐላ ፡ ኪዳን ፡ ብፅዐት ። ወብየ ፡ ማእኰት ፡ እምኅበ ፡ ዘፈጠረኒ ፡ ከመ ፡ እለ ፡ አስሐትክዎሙ ፡ ይትወደዩ ፡ ምስሌየ ፡ ውስተ ፡ እሳት ። ወወሀቦ ፡ ማእኰተ ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለዘገብረ ፡ ተዝካሮ ፤ (መቃ ፡ ገ፳፱ ። ድር ፡ ሚክ) ።

**ተአኰተ ፤ (ይትአኰት ፡ ይትአኰት) ፤** ተመሰጋገነ ፡ (ተደራራጊ) ።

**ተአኳቴ ፤** ተመሰጋጋኝ ።

**አስተአኰተ ፤ (ያስተአኵት ፡ ያስተአኵት) ፤** አመሰጋገነ ፡ (አደራራጊ) ።

**አስተአኳቴ ፤** አመሰጋጋኝ ።

**መስተእኵት ፤** የሚመሰጋገን ፡ የሚያመሰጋግን ።

**አኩት ፤—ተናካሽ ፤—ዐኪ.ው ፡ ዐከወ ።**

**አል ፤ (ዕብ ፡ አል) ፤** አሉታ ፤ በቁሙ ፡ አል ። ባማርኛ ፡ አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ አልገባም ፡ አልወጣም ፡ አልኼደም ፡ አልመጣም ፡ እያሉ ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ፡ በረ ፡ ግስ ፡ ላይ ፡ ሲገባ ፡ ለና ፡ ረ ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ረ ፡ ልን ፡ እየዋጠ ፡ ይጠብቃል ። ረባ ፡ ረጋ ፡ ረሳ ፡ አረባም ፡ አረጋም ፡ አረሳም ። በጥፈትም ፡ ባንጋገርም ፡ አልረሳም ፡ አያስኝም ፡ አስዚያ ፡ ጥፈትና ፡ ቋንቋ ፡ ይበላሻል ። በግእዝ ፡ ግን ፡ ከባ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ፊደል ፡ አይገባም ፡ ይህም ፡ ቦ ፡ ቦቱ ፡ አልቦ ፡ አልቦቱ ፡ አልባ ፡ አልባቲ ፡ አልብከ ፡ ኪ ፡ አልብየ ፡ ነ ። አልቦሙ ፡ ቦን ፡ አልብከሙ ፡ ክን ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ያውም ፡ ሲቃወሙት ፡ ብሉይ ፡ ተሐዲስ ፡ የሚያስማማሙቱ ፡ ቦና ፡ አልቦ ፡ ቀተለ ፡ ኢቀተለ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያለ ፡ ሲኾን ፡ ጽድቅና ፡ አሉታ ፡ በመኾኑ ፡ ኹለት ፡ ልዩ ፡ አንቀጽ ፡ መስሲቸው ፡ ኹለቱንም ፡ ባንድ ፡ ቅኔ ፡ ውስጥ ፡ ያገቡታል ። (መወድስ ፡ ዘይንቅ ፡ ማርቆስ) ። ለዘጐየ ፡ ሰብእ ፡ እምገጸ ፡ አንበሳ ፡ ከዎ ፡ ዕጹብ ፡ ሶበ ፡ ተሐላ ፡ ገዳም ፡ ረከቦ ፤ ወአመ ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ቦአ ፡ ተረክቦተ ፡ አርዌ ፡ ዐጸቦ ። ንብረተ ፡ ዝንቱስ ፡ ይመስል ፡ ንብረተ ፡ አዳም ፡ በሲኦል ፡ እንዘ ፡ ቦ ፤ እስከ ፡ መንገሌክ ፡ ትቀጽቦ ፤ ሥሉጠ ፡ ልደት ፡ ክርስቶስ ፡ ወመሥዋዕት ፡ አብ ፡ ዘደበ ፡ ጸልቦ ። እምዝኒ ፡ እስምየክ ፡ ምክንያተ ፡ ሖሉ ፡ የብቦ ፤ ዘመድ ፡ ጽሩየ ፡ ፍቅር ፡ እንበሌክ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፤ እመኒ ፡ ትሁቦ ፡ ዐረ

ፍት ፡ ወሀብተ ፡ መከራ ፡ ትሁቦ ፡ እምርእስየ ፡ ለርእ ስየ ፡ አንተ ፡ ትቀርቦ ።

**እል** ፤ (ዐረብ) ፤ የስም ፡ ተውሳክ ፡ ከስም ፡ ጋራ ፡ የሚጨመር ፡ ቃል ። እልሐመል ፤ እልሑት ። እ ልቆሞሳት ፡ (አቡሻ ፡ ፱ ። ገድ ፡ ተክ) ።

(ጥላ) **አላ** ፤ (ዐረ ፡ ኢላ ። ዕብ ፡ ኤላ) ፤ ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ አለለ ፡ ነው ። እንጂ ፡ ግን ፡ ዋዌ ፡ ዳግመኛ ፡ ስ ፡ ይኾናል ፡ እንጂና ፡ ግን ፡ መደ በኞች ፡ የቀሩት ፡ ትርጊኖች ፡ ናቸው ። ባለመጽሐፎች ፡ እን ዳወራረዱ ፡ ሲፈቱ ፡ አላን ፡ ይለዋውጡታል ፡ አላ ፡ ብር ሃነ ፡ ሀበነ ፡ ሲል ፡ (ኪዳ) ፡ ዋዌ ፡ ዓዲ ። አላ ፡ ብሁል ፡ ሲተ ፡ ሲል ፡ (አፈ ፡ ወ) ፡ ነገርስ ። አላ ፡ አትሒቶ ፡ ርእሶ ፡ ነሥአ ፡ አርአያ ፡ ገብር ፡ ቢል ፡ (ቅላ) ፡ የሌለውንስ ፡ ብ ለው ፡ ይፈቱታል ። አኮ ፡ አንትሙ ፡ ዘኀረይክሙኒ ፡ አላ ፡ አነ ፡ ኅረይኩክሙ ፡ እንጂ ። ዝኒ ፡ ይከውን ፡ ሕ ዝበ ፡ ዐቢየ ፡ አላ ፡ እኁሁ ፡ ዘይንእስ ፡ የዐብዮ ፤ ግን ፡ (ዮሐ፲፭ ፡ ፲፮ ። ዘፍ፵፰ ፡ ፲፱) ። (ዕር፲፱ ፡ ቍ፲፭) ።

**እለ** ፤ (ዘ) ፤ ቅጽልና ፡ በቁ ፡ አብገር ፡ የ ፡ እን ። ወቦ ፡ እለ ፡ ወረዱ ። ወእምዝ ፡ ኀለፉ ፡ እለ ፡ ጳው ሎስ ፡ እምነ ፡ ጳፉ ፡ (ግብ፲፭ ፡ ሸ ። ፲፫ ፡ ፲፫) ። እለ ፡ የዘ ፡ ብገር ፡ ነው ፡ ቅጽልነቱ ፡ ለብዙ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ዘ ፡ ሳንድም ፡ ለብዙዎም ፡ አይኾንም ፡ አብገር ፡ ሲኾን ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ይወድቃል ። ሲዘረዘርም ፡ እን ፡ በር ፡ ክፋች ፡ አይርግ ፡ እሊአየ ፡ ከ ፡ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ ፤ እሊአን ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፡ እያለ ፡ ባሥሩ ፡ ስሩ ዊት ፡ ይረባል ። (ዕር፲፱ ፡ ቍ፲) ።

**እሉ** ፤ እሎንቱ ፤ (ዝ ፡ ንቱ ። ዕብ ፡ ኤ ሌሀ) ፤ የብዙ ፡ ወንዶች ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፡ እሊህ ፡ እ ነህ ፡ እነዚህ ፡ እሊሆች ፡ እሊኸኞች ። ባለቤት ፡ ሲኾር ፡ ጭብጥ ፡ ቅጽል ፡ ሲቀር ፡ ዐጸፋና ፡ በቁ ፡ ይኾናል ። እሉ ፡ ሰብእ ። አሐዱ ፡ እምእሉ ። ሠራዔ ፡ ሕገጋት ፡ እሎ ንቱ ። ይኀፅበሙ ፡ ለእሎንቱ ። ወእሎንቱ ፡ ተፈወሱ ፡ ምዕረ ፡ (ሕዝ፲፭ ፡ ፱ ። ቅኔያት) ። እሉና ፡ እሎንቱ ፡ በገ ቢር ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ናቸው ። ወሰሚዕየ ፡ እሎንተ ፡ ቃላተ ።

**እላ** ፤ እላንቱ ፤ እሎን ፤ (ዛ ፡ ዛቲ) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ የብዙ ፡ ሴቶች ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፡ ወንዶቹም ፡ ሴቶቹም ፡ ቅርቦች ፡ ናቸው ። ተዘመርን ፡ እላ ፡ ክልኤ ፡ ቃላተ ። በእላ ፡ ክልኤ ፡ ትእዛዛት ። እላንቱ ፡ አእባን ፡ ይኬልሓ ። እስመ ፡ እሎን ፡ ሠላስ ፡ ይትሜሰላ ፡ (ቁር ። ማቴ፳፪ ፡ ፵ ። ሉቃ፲፱ ፡ ፵ ። ፊልክ ፡ ፺፱) ።

**አሌ** ፡ (ዕብ ፡ አልላይ ፤ አይ) ፤ ቃለ ፡ ብካይ ፡ ወዐውያት ፡ ቃለ ፡ ተግሣጽ ፡ ወመዐት ፡ ወዮ ፡ ዋይታ ፡ ወዮታ ። አሌ ፡ ሊተ ፡ አሌ ፡ ለከ ፡ አሌ ፡ ሎቱ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ወይ ፡ በለ ፡ ይዘምታል ፡ ወዮ ፡ ልኝ ፡ ወዮ ፡ ልኽ ፡ ወዮ ለት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚመጣን ፡ መከ ራና ፡ ሐዘን ፡ ያሳያል ። ወይን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ፡ አሌ ፡ የግእዝ ፡ ወይ ፡ የዐረብኛ ፡ ያማርኛ ። አሌ ፡ ለኪ ፡ ሀገር ፡ እንተ ፡ ንጉሥኪ ፡ ወሬዛ ። አሌ ፡ ላ ፡ ለስ ይፍ ፡ ሊየኑሳሌም ፡ በባዕሌሃ ፡ እስመ ፡ ውሕዘ ፡ ደም ። አሌ ፡ ለክሙ ፡ ጸሐፍት ፡ ወፈሪሳውያን ፡ (መክ፲ ፡ ፲፮ ። ቅኔ ። ማቴ፳፫ ፡ ፲፫) ።

**ኤል** ፤ (ዕብራ) ፤ ናስ ፡ ማኅብ ፡ ዐምድ ፡ (ሕ ዝ፵ ፡ ፳፩ ፡ ፲፮) ። አምላክ ፡ ፈጣሪ ፡ ኤሎሄን ፡ ተመል ከት ።

**አልቦ** ፤ (አል ፡ ቦ) ፤ የቦ ፡ አሉታ ፡ የለም ፡ አ ልኖረም ፡ አልነበረም ፡ የቦን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ። አልቦ ፡ ነገር ፡ ወአልቦ ፡ ነቢብ ፡ (መዝ ፡ ፲፰) ።

**አልቦቱ** ፤ (አል ፡ ቦቱ) ፤ የለውም ፡ የለበ ትም ፡ አልኖረውም ፡ አልነበረውም ፡ አልነበረ(ለ)በትም ። አልቦቱ ፡ ጥንት ፡ ወኢተፍጻሜት ፡ (ቅዳ) ።

**አልቦ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፡ የእግር ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፡ ግርጃ ፡ ድኰት ፡ ጥምዝ ፡ የብር ፡ ድቃ ፡ ከወ ደዛዝር ፡ በቀር ፡ በማንም ፡ ሴት ፡ እግር ፡ የማይገኝ ፡ ሴ ቶች ፡ ኹሉ ፡ የማያደርጉት ። (ግጥም) ፡ እንጥረኛው ፡ ብዙ ፡ በቴዎድሮስ ፡ ቤት ፡ ባላልቦ ፡ አደረጉት ፡ ይኽን ፡ ኹሉ ፡ ሴት ፡ (ባል ፡ አልቦ ፡ አለባል) ።

**እልባልተሪቦን** ፤ (ጽር ፡ ፓቴር ፡ ኢ ሞን) ፤ እል ፡ የዐረብ ፡ ተውሳክ ፡ ፓቴር ፡ አብ ፡ ኢሞን ፡ ን ፡ በተገናኝ ፡ አቡን ፡ ማለት ፡ ነው ። ወጸለየ ፡ በቅድሜ ሆሙ ፡ እልባልተሪቦን ፡ ዘውእቱ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማ ያት ፡ (ስንክ ፡ መጋቢት) ።

**አልባስጥሮስ** ፤ (ጽር ፡ አላባስትሮስ) ፤ የሽቱ ፡ ቢልቃጥ ፡ የብርሌ ፡ የብርጭቆ ፡ ዐይነት ፡ ጥሩ ፡ ሽቱ ፡ ያለበትና ፡ የመላበት ፡ እንዳይተነፍስ ፡ ታትሞ ፡ ተገ ጥሞ ፡ የሚኖር ፡ (ማር፲፬ ፡ ፫ ። ሉቃ፯ ፡ ፴፯) ።

**ኤልግ** ፤ ስመ ፡ ነገድ ፡ ለብቻቸው ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ ፡ ያላቸው ፡ መጣፋቸውን ፡ ለሌላ ፡ ሕዝብ ፡ የማያ ሳዩ ፡ ተደብቀው ፡ የሚጥፉና ፡ የሚማሩ ፡ አምልኳቸው ፡ ከእስላም ፡ ከክርስቲያን ፡ የተለየ ፡ ሌላ ፡ ሸ ፡ ዐይነት ፡ ሕዝብ ። እሊህም ፡ በትግሬ ፡ በሐማሴን ፡ ሠጣፍ ፡ በመረብ ፡ አው ራጃ ፡ በባሬያ ፡ ጸሊም ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ ።

(ጥ) **አለገ** ፤ —ድል ፡ ነጣ ፤ ሰለበ ፤ —ዐልጎ ፡ ዐለገ ፤ ዕልገት ።

(ጥ) **አልዶ** ፤ ዶት ፡ (አለደ ፡ ይ፡ኤልድ ፡ የአ ልድ) ፤ መልቀም ፡ መሰብሰብ ፡ መከመር ፡ መክባብ ፡ መ ደርደር ፡ በላይ ፡ በላዩ ፡ መጨመር ፡ ካንድ ፡ ላይ ፡ መቈ ለል ፡ መጕቸት ፡ ማከማቸት ፡ (ዘኍ፲፭ ፡ ፳ ። ዘዐ፳ ፡ ፲፪ ። ዘፍ፴፩ ፡ ፵፯) ። ላዕለ ፡ እስጢፋኖስ ፡ አይሁድ ፡ አሊዱ ፡ እብነ ፡ ወውእቱ ፡ ወግረ ፡ ስምዕ ፡ ኮነ ። አሊደትን ፡ ው ስተ ፡ ፍኖት ፡ ለብዙኃት ፡ አንስት ፡ ከመ ፡ ይጽዕናሃ ፡ ለማርያም ፡ (ቅኔ ። ዮሴፍ) ።

**አላዲ** ፡ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤ የሚለቅም ፡ የሚሰበስብ ፡ ለቃሚ ፡ ሰብሳቢ ። አላዲሁ ፡ ለዝንቱ ፡ መ ጽሐፍ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭) ።

**ተአለደ** ፤ ተለቀመ ፡ ተሰበሰበ ፡ ተከማቸ ፡ ተወሰነ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ያዘ ። ውስተ ፡ አሐቲኒ ፡ ኅበ ፡ ተአለዱ ። እንዘ ፡ ትትኤለዱ ። ይትአለዱ ፡ ወይትጋብኡ ፡ ዘሎሙ ፡ እስራኤል ። ወአንትሙሰ ፡ ናሁ ፡ ተአለደ ፡ ውስቴትክሙ ፡ ዘሉ ፡ ነውር ። ኢይትአመር ፡ እምኀበ ፡ ይወፅእ ፡ መለከትትከ ፡ ወኀበ ፡ ይትኤለድ ፡ ህላዌከ ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ ። ሚያዝ ። ቈንባ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭ ። የሉና ። ቅዳ ፡ አት) ።

**እሉድ** ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ልድ) ፤ የተሰበሰበ ፡ የተጐቸ ፡ የተከማቸ ፡ ክምር ፡ ቍልል ። ዕፀው ፡ እሉዳን ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**እላዴ** ፤ መሰብሰብ ፡ አሰባሰብ ፡ ስብሰባ ፡ ቍለላ ፡ ክመራ ። እላዴ ፡ ብርዕ ፡ (አዋል) ።

**ምእላድ** ፤ (ዳት) ፤ ማከማቻ ፡ መከማቻ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቦታ ፡ (ዘሉ፡ኆ ፡ ፱) ። ምእላደሆሙ ፡ ለማይት ። ምእላዳት ። ወምእላደ ፡ ገበርክሙ ፡ ማእከለ ፡ ክልኤቱ ፡ አረፍት ፡ (ቄድር ። ቀሌ ። ኢሳ፳፪ ፡ ፲፩) ።

**ምእላድ** ፤ በቁሙ ፡ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ በጭር ፡ ቍሮጭኝ ፡ ቅድ ፡ ቃሉ ፡ ከብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ተለቅሞ ፡ ሉብቻው ፡ የተጣፈ ፡ መጣፍ ፡ እንደ ፡ ፍትሐ ፡ ንገሥት ፡ እንደ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ያለ ፡ ከዚያም ፡ የሚያንስ ፡ ሥን ፡ ፍጥረትን ፡ አዕማደ ፡ ምስጢርን ፡ የመሰለ ፡ በቅርብ ፡ የሚገኝ ፡ የክርስቲያን ፡ ትምርት ።

**ምእላድ** ፤ ተጨማሪ ፡ ፊደል ፡ ትራስ ፡ እየኾነ ፡ በመጨረሻ ፡ ቃል ፡ የሚገባ ፤ ወንድና ፡ ሴት ፡ አንድና ፡ ብዙ ፡ የሚለይበት ። እሊሁም ፡ አራት ፡ ናቸው ፤ ት ፡ ና ፡ ዊው ፡ ዩያይ ፡ አገባቦቻቸውን ፡ በየፊደላቸው ፡ ተመልከት ።

**አላድ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፡ የገንዘብ ፡ ስም ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ ስመ ፡ ንጉሥ ፡ መልክአ ፡ ንጉሥ ፡ ያለበት ፡ ግማሽ ፡ እኩሌታ ፡ ገንዘብ ፡ ምሉ ፡ ይይይል ። አርእዩኒ ፡ ሐላደ ፡ ዲናር ፡ (ማቴ፳፪ ፡ ፲፱) ። የጽርኡ ፡ አብነት ፡ ግን ፡ ወርቀ ፡ ጸባሕት ፡ ንዋየ ፡ ጸባሕት ፡ ይላል ። ባለሐዲሶችም ፡ አላድን ፡ መልክእ ፡ ይሉታል ።

**ኤልዳ** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ የተፈጠሩበት ፡ ማእከለ ፡ ምድር ፡ ጉብኤ ፡ ኵሉ ፡ ምእላደ ፡ ኵሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። ወኀደሩ ፡ ውስተ ፡ ምድረ ፡ ኤልዳ ፡ ምድረ ፡ ፍጥረቶሙ ፡ (ኩፋ ፡ ፫) ።

**አላዶር** ፤ የቀኖት ፡ ስም ፡ ኹለተኛ ፡ ቀኖት ፡ የቀኝ ፡ እጅ ። አዲራን ፡ ተመልከት ።

**አላዳስ ፡ ኤላድ** ፤ (ጽር ፡ ሄላዶስ ፡ ሄላዳ ። ዕብ ፡ ያዋን) ፤ የግሪክ ፡ አገር ፡ ስም ፡ መሳው ። አንድ ፡ ታላቅ ፡ ደሴት ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ (ኢሳ፳፯ ፡ ፲፱ ። ግብ፳ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ግንቦ) ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የግእዝ ፡ መጻሕፍት ፡ ደሴት ፡ ሲሉ ፡ አላዳስ ፡ ይላሉ ። ስሕተት ፡ ነው ። ለአላዳስ ፡ ወለአህጉር ። ለባሕር ፡ ወለአላዳስ ። በባሕር ፡ ወበየብስ ፡ በአሕቁል ፡ ወበአላዳስ ፡ (ክብ ፡ ነገ ። መጽ ፡ ምስ) ፡ ዳግመኛም ፡ ዝብል ፡ ዐፍዕ ፡ ደክዕ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አላዳስ ፡ ይላል ፡ (ሉቃ፲፱ ፡ ፴፭) ።

**ኤሎሃ** ፤ ሱር ። ኢ.ሳህ ፡ ዐረ ። ኤል ፡ ዕብ ። በተገናኝ ፡ አምላክ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ኤሎሄ** ፤ (ዐረ ፡ ኢ.ላሂ ። ዕብ ፡ ኤሊ.) ፡ አምላኬየ ፡ ፈጣሪየ ፡ ለሓኩየ ፡ (ሸንገ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ። ማቴ፳፯ ፡ ፵፮ ። ማር፲፭ ፡ ፴፬) ። ሰላም ፡ ሰዓምጽ ፡ ነባቤ ፡ ቃሉ ፡ ለኤሎሄ ። ኦ ፡ ዘትቤ ፡ ኤሎሄ ፡ ኤሎሄ ፡ ኢየሱስ ፡ አምላክ ፡ ርኅራኄ ፡ (ስንክ ፡ ጳግሜ ። ደራሲ) ።

**ኤሎሂም** ፤ (ዕብ ፡ ወሱር ። ዐረ ፡ ኢ.ላሃት) ፤ አማልክት ፡ አምላኮች ፡ ዳኞች ፡ ፈራጆች ፡ መላእክት ። ለፈጣሪ ፡ ሲቀጠልና ፡ የፈጣሪ ፡ ስም ፡ ሲኾን ፡ በቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ዘይቤው ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ አማልክት ፡ አይባልም ፡ አስመባስም ፡ (በራእ ፡ ኤሎሂም ፡ ፈጠረ ፡ አምላክ) ፡ እያለ ፡ እንቀጹ ፡ ያንድ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡ አምላክም ፡ የመለክ ፡ ብዥ ፡ ነውና ፡ እንደ ፡ ኤሎሂም ፡ ብዙ ፡ ወንድ ፡ ያሳያል ፡ መለክን ፡ እዩ ። ንባርከ ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ እንዘ ፡ አሐዱ ፡ ሠለስቱ ፡ ወእንዘ ፡ ሠለስቱ ፡ አሐዱ ፡ ማለት ፡ ኤሎሂም ፡ አደናይ ፡ ከማለት ፡ ይስማማል ። ስፍጡራን ፡ ግን ፡ ለሰዎችና ፡ ለመላእክት ፡ ለጣዖታትም ፡ ሲነገር ፡ እንቀጹን ፡ መስሎ ፡ ተከትሎ ፡ አማልክት ፡ ይባላል ፡ ከእንቀጽ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መለዮ ፡ የለውም ። አንሰ ፡ እቤ ፡ አማልክት ፡ አንትሙ ። ግበር ፡ ለነ ፡ አማልክተ ፡ ዘየሐውሩ ፡ ቅድሜነ ፡ (መዝ ፡ ፹፩ ። ዘፀ፴፪ ፡ ፩ ፡ ፩) ። መዝገበ ፡ ፊደል ፡ ገጽ ፡ ፺፱—፻፫ ፡ ተመልከት ።

**ኤላው** ፤ (ዕብራ) ፤ አዕማዱ ፡ አረፍቲሁ ፡ ው ፡ ዝርዝር ፡ ነው ። ወኤላው ፡ ካዕበ ፡ እመት ፡ (ሕዝ፵ ፡ ፱) ። ኤልን ፡ ተመልከት ፡ ኤላው ፡ ከኤል ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ኤሴዎን** ፤ (ጽር ፡ ሄሴዎን) ፤ ዘይታም ፡ መክነ ፡ ዘይት ። ደብር ፡ ዘስሙ ፡ ኤሴዎን ፡ (ሉቃ፲፱ ፡ ፳፱ ። ፳፩ ፡ ፴፯) ። ኤልያየንን ፡ እዩ ።

**እልሐዝል** ፤—የጨዎታ ፡ ስም ፤—ኀዝል ።

**እልሐመል** ፤—ከከብ ፤—ሐሚል ፡ ሐመለ ።

**እልሐውት** ፤—ከከብ ፤—ሐውት ፡ ሐውት ።

**እልሐሰሰ** ፤—ሹክ ፡ አለ ፤—ለኈሰ ፡ ለኈሰ ፡ እልኈሰሰ ።

**ኤላጤ** ፤ (ጽር ፡ ኤላቴ ። ዕብ ፡ ዐርሞን) ፤ የተክል ፡ ዛፍ ፡ ስም ፡ ቁመተ ፡ ረዥም ፡ ቅጠሉ ፡ ሰፋፊ ፡ ፍሬው ፡ መድኀኒት ፡ የሚኾን ፡ (ሕዝ፴፩ ፡ ፰) ።

**ኤላጢኑስ** ፤ (ጽር ፡ ኤላቴኖስ ። ዕብ ፡ ቶሬን) ፤ የመርከብ ፡ ዐምድ ፡ ምሰሶ ፡ ወፍራም ፡ ረዥም ፡ የሸራና ፡ ያላማ ፡ መስቀያ ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፭) ።

**ኤልዩ ፡(ጽር ፡ ሄሊ.ውድ)፡** ረዐይታዊ ፡ ረዥም ፡ ወፍራም ፡ ኀይለኛ ፡ ጕልበታም ። ባለብለዮች ፡ ማኅ ፡ የድኩም ፡ ድኩም ፡ ዐዊር ፡ ኵሳሳ ፡ ይሉታል ፡ (ኩፋ ፡ ፮) ።

**አልያጦን ፡(ጽር ፡ አሊ.ዬቶስ)፡** የባሕር ፡ አሞራ ፡ ዓሣ ፡ የሚያድን ፡ የሚለቅም ። ባለብሉዮች ፡ አባብ ፡ ዋዊ ፡ ይሉታል ። በአቦር ፡ ቋንቋ ፡ ጕን ፡ የሚባል ፡ የባብ ፡ ፀይንት ፡ ዓሣ ፡ አስና ፡ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገ ባል ፡ የኖኅን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ፡ (ዘሌ.፲፩ ፡ ፲፫ ። ዘ ዳ.፲፬ ፡ ፲፪) ።



አልያጦን ፡

**ኤልያስ ፡(ጽር ፡ ሄሊ.ያስ)፡** ሰፀ ፡ ዘይት ፡ ፍሬ ፡ ዘይት ፡ ቅብዐ ፡ ዘይት ። ወገደፈቶ ፡ ታሕተ ፡ አ ሐቲ ፡ ኤልያስ ፡፡ ወአሐቲ ፡ መስፈርተ ፡ ኤልያስ ፡ ት ገብር ፡ ዐሠርተ ፡ ምክያደ ፡ ዘይት ፡ (ኩፋ.፲፮ ። ሐ. ፍ.፲ ፡ ፲፱) ።

**ኤልያስ ፡(ጽር ፡ ሔሊ.ያስ ። ዕብ ፡ ኤሊ. ያሁ)፡** ነቢይ ፡ ስመ ፡ ነቢይ ፡ ፍቹው ፡ ኀይሉ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ (፫ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፴፯) ።

**እልኩ ፡ ኵ ፡ እልክቱ ፡(ዝኩ ፡ ዝስኩ ፡ ዝኩ ፡ ዝስኩ)፡** ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፡ ለቅርብ ፡ ሩቆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ። እሊያ ፡ እሊያኞች ፡ እሊያኞቹ ። እልኩ ፡ አብዳት ፡፡ እልክቱ ፡ ደናግል ፡፡ እልክቱ ፡ ይክ ሪን ፡ ገጸሙ ፡ (ማቴ.፳፭ ፡ ፰ ፡ ፲፩) ። ዝኩን ፡ ተመልከት ።

(ጥ) **እልሎ ፡ ሎት ፡(አለለ ፡ ይኤልል ፡ የአ ልል ። ዕብ ፡ አሌል)፡** መሻት ፡ መፈለግ ፡ አይቴ ፡ ቤት ፡ ዘማ ፡ ማለት ፡ ማመንዘር ፡ መቀንዘር ፡ መገስል ፡ መከመር ፡ የተባት ። እልል ፡ ማለት ፡ እንቍራሬትኛ ፡ መ ሬሣኘ ፡ የእንስት ።

**እለሌ ፡** አለሌ ፡ የፈረስ ፡ ያህያ ። **ምልእተ ፡ ክ ርሥ ፡ ዘእንበለ ፡ ዐቅም ፡ ከመ ፡ እለሌ ፡ ፈረስ ፡ ወ ከመ ፡ ሐራውያ ፡ ገዳም ፡** (ሙቃ ፡ ገ፳፱) ። ከአላ ፡ እስከ ፡ አሌ ፡ እልኩም ፡ ሳይቀር ፡ የአለለ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**እለለ ፡—ቀለም ፡ አገባ ፡—ዐልሎ ፡ ዐ ለለ ።**

**ኤሉል ፡—ስመ ፡ ወርኅ ፡—አይሉል ።**

**እለም ፡—በቁሙ ፡—ዓለም ።**

**ኤላም ፡(ጽር ፡ ። ዕብ ፡ ኤላም)፡** በረንዳ ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ በታላቅ ፡ ቤት ፡ ደጃፍ ፡ ወይም ፡ በቅጥሩ ፡ በር ፡ የሚሠራ ፡ (ሕዝ፵ ፡ ፲፮ ። ፵ ፡ ፯ ። ፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፮) ።

**ኤላማው ፡** በረንዳው ፡ ደጀ ፡ ሰላሙ ፡ ው ፡ ዝ ርዝር ፡ ነው ፡ (ሕዝ፵ ፡ ፳፩) ።

**እልሚዛን ፡—በቁሙ ፡ ከከብ ፡—መ ዝኖ ፡ መዘን ፡ ሚዛን ።**

**እልመክኑን ፡—ኅቡእ ፡—ከነ ፡ ከነነ ፡ መክኑን ።**

**እልመቃምር ፡—ቅልሞሽ ፡—ቀምሮ ፡ ቀመረ ።**

**ኤሊ.ማስ ፡(ጽር ፡ ሄሊ.ማስ ። ዐረ ፡ ዐሊ. ሞን)፡** የሠርተኛ ፡ ስም ፡ እንደነኢያኔስ ፡ ያለ ። መሠ ርይ ። ምሁረ ፡ ሥራይ ፡ መሰግል ፡ መዐልመ ፡ ሰገል ፡ ወምትሀት ፡ ጽጉብ ፡ ትምህርት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ስምነቱ ፡ ዐለመ ፡ ከማለት ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ ጽርኡ ፡ ከዐረብ ፡ ወስ ዷታል ፡ ሲ.ጣፍ ፡ የሚገባው ፡ በዐይን ፡ ዐ ፡ እንጂ ፡ በአ ልፍ ፡ አልነበረም ። ወይትዋቀሥሙ ፡ ውእቱ ፡ ዘሥ ራይ ፡ ዘይብልዎ ፡ ኤሊማስ ፡ እስመ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ትር ጓሜ ፡ ስሙ ፡ (ግብ፲፫ ፡ ፰) ።

**ኤልማስ ፡(ጽር ፡ ሔሊ.ሙ ፡ ቴሄሙ)፡** ኤሎሂ ፡ አምላኪየ ። አ ፡ ወልድ ፡ ከባሕ ፡ ከመ ፡ ዘሐመ ፡ ወበል ፡ ሔልማስ ፡ ላማ ፡ ሰበቅታኒ ፡ (ቅዳ ፡ አት) ።

**እልመስጦ ፡–እምነት ፡ ሃይማኖት ፡–መ ስጦ ።**

**እሎን ፡(ጽር ፡ አሎስ)፡** ፊደው ። ባሕረ ፡ አ ሎን ፡ ባሕረ ፡ ጼው ፡ (ኢያ፫ ፡ ፲፮ ። ፲፱ ፡ ፫) ።

**እሎን ፡ (ዕብራ ፡ ብ ፡ አሎኒም)፡** የዛፍ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ባንባ ፡ እንደ ፡ ዋርካ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ የወ ፍራም ፡ ቀሊል ፡ መቅዘፊያ ፡ የሚገኝን ፡ የባሳን ፡ ዛፍ ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፮) ።

**እሎን ፡—እሊ.ሀ ፡ ሴ ፡—እላ ።**

**እሎንቱ ፡—እሊ.ሀ ፡ ወ ፡—እሉ ።**

**እላንቱ ፡—እሊ.ሀ ፡ ሴ ፡—እላ ።**

**አሊ.ፍ ፡ ፎት ፡ (አለፈ ፡ የአልፍ ፡ ይአ ልፍ ። ዕብ ፡ አላፍ)፡** መማር ፡ ፊደል ፡ መቍጠር ፡ አ ፡ አሌፍ ፡ ማለት ። ማብዛት ፡ ማርባት ፡ እልፍ ፡ ማድ ረግ ፡ አ ፡ አንድ ፡ እ ፡ እልፍ ፡ ማለት ፡ የቍጥር ።

**አላፊ ፡(ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፡ አለፍት)፡** አሌፍ ፡ የሚል ፡ ተማሪ ፡ ፊደል ፡ ቈጣሪ ።

**አአለፈ ፡** አስተማረ ፡ ፊደል ፡ አስቈጠረ ፡ አሌፍ ፡ እልፍ ፡ አስኘ ።

**ተአልፈ ፡** ተቈጠረ ፡ በዛ ፡ እልፍ ፡ ኾነ ፡ እልፍ ፡ ተባለ ።

**አሉፍ ፡ (ፋን ፡ ፋት ፡ እልፋት) ፡** የብዙ ፡ የረብ ፡ እልፍ ፡ የኾነ ፡ የተባለ ።

**እልፍ ፡ (ዕብ ፡ ኤሌፍ ። ሱር ፡ አሌፍ ። ዐረ ፡ አልፍ ፡ ሺሕ) ፡** ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ መቶ ፡ (ቀቀ—፺፱ ። ኢ—፻፲ ። ዕብራይስጥና ፡ ሱርስት ፡ ግን ፡ ሺሑን ፡ እልፍ ፡ ብለው ፡ እልፋን ፡ ሬብ ፡ ይላሉ ፡ ዐረብና ፡ ትግሬም ፡ እንዲሁ ፡ ናቸው ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ አራተኛ ፡ ነገሥት ፡ (፲፱ ፡ ፴፭) ፡ **ወቀተለ ፡ እምተዓይኒሆሙ ፡ ለአሶር ፡ ዐሥርተ ፡ ወሰመንተ ፡ እልፈ ፡ ወኃምሳ ፡ ምእተ ፡** ያለውን ፡ ከዐረብ ፡ ቋንቋ ፡ የተቀዳው ፡ መጽሐፈ ፡ ቄርሎስ ፡ በመገምገሪያው ፡ ክፍል ፡ **ምእተ ፡ ወሰማንያ ፡ ወኃምስተ ፡ እልፈ ፡** ይላል ። ፊልክስዩስም ፡ (ተስ፴፯ ፡ መተ) ፡ **ወኃሕተ ፡ ሥልጣኑ ፡ እልፍ ፡ ባሕታውያን ፡ ወክልኤቱ ፡ እልፍ ፡ መነኮሳይያት ፡** ይላል ። ጥንታዊውም ፡ ያሮጌው ፡ ማእዝ ፡ እልፍ ፡ እንደዚሁ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ፡ የሺሕን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ።

**እልፍ ፡** ብዙ ፡ አጅግ ፡ ዐያሌ ። **እስከ ፡ እልፍ ፡ ትውልድ ። አሐዱ ፡ እምእልፍ ። እልፍ ፡ መዘግብተ ፡ ወርቅ ፡ ፀበይት ፡** (ዘዳ፩ ፡ ፲ ። ሚክ፮ ፡ ፯ ። ማሕ፲ ፡ ፲፱ ። የስንደዱና ፡ የግብስ ፡ ዘላም ፡ ክፋሬው ፡ ብዛት ፡ የተነማ ፡ አንዳንዱ ፡ ራስ ፡ እልፍ ፡ ይባላል ። (ተረት) ፡ የስንደው ፡ ዘላ ፡ ስፍኛ ፡ ይመላ ።

**አእላፍ ፡** ብዙ ፡ እልፍና ፡ ሺሕ ፡ ዐሥር ፡ እልፍ ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ (የእ—፲፻፱) ፡ **አእላፍ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ። ባዐለ ፡ አእላፍ ። ይቀትል ፡ ብዙኃ ፡ አእላፈ ፡** (መዝ ፡ ፻፲፰ ። ዘፀ፴፱ ፡ ፯ ። ዳን፲፩ ፡ ፲፱) ።

**አእላፋት ፡** ብዙ ፡ እልፎች ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ዎች ። መቶ ፡ እልፍ ፡ ወይም ፡ ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፡ (ቀእ—፲፻፱) ፡ አንድ ፡ ሚልዮን ። **አእላፈ ፡ አእላፋት ። ርኡሳነ ፡ አእላፋት ፡** (ዳን፯ ፡ ፲ ። ፩ዜና ፡ ፲፫ ፡ ፩) ።

**ትእልፌት ፡** ብዛት ፡ ብዙ ፡ እልፍንት ። ሺሕ ፡ እልፍ ፡ ወይም ፡ እልፍ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ። (ቁእ—፲፻፱፻) ፡ ዐሥር ፡ ሚልዮን ። **ወናሁ ፡ መጽአ ፡ በትእልፌት ፡ ቅዱሳን ። ትእልፌተ ፡ ትእልፌት ። ወትእልፌተ ፡ አእላፋት ፡** (ሔኖ፩ ፡ ፱ ። ፲፱ ፡ ፳፪ ። ዳን፯ ፡ ፲) ።

**ምእልፌት ፡** የእልፍ ፡ እልፍ ፡ እልፍ ፡ ጊዜ ፡ እልፍ ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ እልፍ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፡ (እእ—፻፻፻) ፡ መቶ ፡ ሚልዮን ። **ምእልፌተ ፡ አእላፍ ። ምእልፌት ፡ ትቀሥፍ ፡** (መዝ ፡ ፷፯ ። ጥበ፲፪ ፡ ፳፱) ። ዳግመኛም ፡ በማሽጋሽግ ፡ ትእልፌታት ፡ ብሎ ፡ መቶ ፡ ሚልዮን ፡ ምእልፌት ፡ ብሎ ፡ ሺሕ ፡ ሚሊዮን ፡ ምእልፌታት ፡ ብሎ ፡ እልፍ ፡ ሚልዮን ፡ ያሰኛል ። ከእልፍ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ቍጥር ፡ በውሳኔም ፡ ያለውሳኔም ፡ ይነገራል ፡ ውሳኔው ፡ ይኸ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ። ያለውሳኔ ፡ ግን ፡ ሲነገር ፡ **እልፍ ፡ አእላፍ ፡ አእላፈ ፡ አእላፋት ፡ ወትእልፌት ፡ አእላፋት ፡ ምእልፌት ፡** ይላል ፡ (አዋል) ። ብዛቱ ፡ እንዳሸዋና ፡ እንደ ፡ ኮከብ ፡ ያለ ፡ ስፍሮ ፡ ቁጥሮ ፡ ሊያውቁት ፡ የማይቻል ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ ልክ ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፳፫ ፡ ፲፯ ። ፲፰ ፡ ፳) ። ረበዋትን ፡ እይ ፡ **ረቢብ ፡ ረበ ፡ ረበበ ።**

**አሌፍ ፡ አልፍ ፡ አልፋ ፡** ፊደል ፡ ስመ ፡ ፊደል ፡ አ ። አሌፍ ፡ የዕብራይስጥ ፡ አልፍ ፡ የግእዝና ፡ የዐረብ ፡ አልፋ ፡ የጽርእ ፡ አጠራር ፡ ነው ። አሌፍ ፡ ላም ፡ በሬ ፡ የቀንድ ፡ ከብት ። አልፍ ፡ ፋ ፡ ቀንድ ፡ የበሬ ፡ ራስ ። ምስጢሩ ፡ ቀዳማይ ፡ ርእስ ፡ በኵር ፡ ጥንት ። **አባግዐ ፡ ወአልሕምተ ፡** ባለው ፡ ዕብራይስጡ ፡ **ጸኔ ፡ ወአላፊም ፡** እንዲል ፡ **አልሕምት ፡** ሲል ፡ (መዝ፰ ፡ ፯) ። ቀዳማዊነቱም ፡ በተፈጥሮ ፡ ከሰው ፡ እንስሳ ፡ ከፍጥረት ፡ ፊጠሪ ፡ እንዲቀድም ፡ እንደዚያ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (መዝ፻፲፰ ፡ ፩) ። **ወእምዝ ፡ ትብል ፡ አሌፍ ፡ እስከ ፡ ላሜድ ። እምአሌፍ ፡ እስከ ፡ ታው ። ሆህያተ ፡ አልፋ ። ሆህያተ ፡ ጽርእ ፡ እምአልፋ ፡ ወቤጣ ፡ ወጋማ ፡** (ግንዘ ። ቄድር ፡ አፈ ፡ ድጓ ። ሥር ፡ ጳኵ) ።

**አሌፋት ፡** ፊደላት ፡ ከአሌፍ ፡ እስከ ፡ ታው ፡ ያሉ ። መክብባቸው ፡ አሌፍ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በርሱ ፡ ስም ፡ አሌፋት ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ፡ በሆይ ፡ ሆህያት ፡ ተብለው ፡ እንዲጠሩ ። **አሌፋት ፡ ወግናያት ፡** (አዋል) ። እሊህም ፡ ፳፪ቱ ፡ አሌፋት ፡ እግዚእንና ፡ አዳምን ፡ መደብ ፡ አድርገው ፡ ከሰማይ ፡ እስከ ፡ አዳም ፡ ያሉ ፡ ፳፪ቱን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረትና ፡ ከሴት ፡ እስከ ፡ ያዕቆብ ፡ ያሉ ፡ ፳፪ቱን ፡ አርእስተ ፡ አበው ፡ የሚያሳስቡ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ኤርምያስና ፡ ዳዊት ፡ ፬ ፡ ፬ ፡ ጊዜ ፡ መላልሰው ፡ በመሥመር ፡ በመሥመር ፡ እያገቡ ፡ የቃል ፡ መነሻ ፡ አድርገዋቸዋል ፡ (ሰቈ፩ ፡ ፩—፳፪ ። ፪ ፡ ፩—፳፪ ። ፫ ፡ ፩—፷፮ ። ፬ ፡ ፩—፳፪) ። (መዝ፳፬ ፡ ፩—፳፪ ። ፴፫ ፡ ፩—፳፪ ። ፻፲፩ ፡ ፩—፲ ። ፻፲፪ ፡ ፩—፲) ። በ፻፲፰ኛው ፡ መዝሙር ፡ ግን ፡ ስየብቻቸው ፡ አንዳንድ ፡ መዝሙር ፡ እየኾኑ ፡ በሰፋፊና ፡ በረዣዥሙም ፡ ቃሎች ፡ ስለ ፡ ገቡ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ፰ ፡ ፰ ፡ ቍጥር ፡ አላቸው ፡ የመላው ፡ ፻፸፮ ፡ ይኾናል ።

**አልፋ ፡** ስመ ፡ አምላክ ፡ ቀዳማዊ ፡ (ራእ፩ ፡ ፰ ። ፳፩ ፡ ፮ ። ፳፪ ፡ ፲፫) ። **ክርስቶስ ፡ አልፋ ። በሥምረተ ፡ አልፋ ። በላም ፡ ሰርዶትክ ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ አልፋ ፡** (ስንክ ፡ ጥር፳፱ ። መጋ፲፱ ። ግን፲፰) ።

**አልፋ ፡** ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ አ ፡ አብ ፡ ል ፡ ወልድ ፡ ፋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ምስጢሩ ፡ ግን ፡ ያው ፡ ቅድምና ፡ ነው ፡ አይለወጥም ። **ኢይቀድም ፡ አሐዱ ፡ እምካልኡ ፡ ወካልኡ ፡ እምሣልሱ ። አሐቲ ፡ ቅድምናሆሙ ፡ ለሥላሴ ፡** (ሃይ ፡ አበ) ።

**ኢሎፍሊ ፡ (ጽር ፡ አሎፍሊ) ፡** ስመ ፡ ነገድ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፡ ፍሌስት ፡ ፍልስጥኤም ፡ ፊስስን ፡ ተመልከት ። ይኸውም ፡ ሜዲትራኒ ፡ በሚባለው ፡ በታላቁ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ በዳር ፡ በደንበሩ ፡ በወደቡ ፡ ያሉት ፡ የምድረ ፡ እስራኤል ፡ ገሬ ፡ ቤት ፡ ናት ። **ተጋብኡ ፡ ኢሎፍሊ ፡ ላዕለ ፡ እስራኤል ። ወነሥእዋ ፡ ኢሎፍሊ ፡ ለታቦተ ፡ እግዚ ። ኄምስቱ ፡ አሕዛበ ፡ ኢሎፍሊ ፡** (፩ነገ ፡ ፬ ፡ ፩ ። ፭ ፡ ፩ ። መሳ፫ ፡ ፫) ።

**ኢሎፍላዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ ፍሊ ስጥኤ ፡ የፍሌስጥ ፡ ሰው ፡ ወገን ፡ ዘር ። ናቤብ ፡ ኢሎፍ ላዊ ። አነ ፡ ውእቱ ፡ ኢሎፍላዊ ፡ (ሕነገ ፡ ፲ ፡ ፳ ። ፲፯ ፡ ፵ ፡ ፲) ።

**አሊፍሎሳውያን** ፤ (ጽርእ) ፤ ዐጸውተ ፡ አና ቅጽ ፡ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ በረኞች ።

**አሊቄ** ፤ (ጽር ፡ አሊኪ) ፤ ጨው ፤ ጨዋማ ፡ ባሕረ ፡ ጨው ። ወከነ ፡ ደወሎሙ ፡ እምነ ፡ ሲባ ፡ እስከ ፡ አሐዱ ፡ ጓብር ፡ ዘባሕረ ፡ አሊቄ ፡ (ኢያ፲፭ ፡ ፪) ። አሎ ንን ፡ ተመልከት ፤ አሊቄና ፡ አሎን ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ነው ፡ (ዘፍ፲፱ ፡ ፫) ።

**ኤሎቄ** ፤ (ጽር ፡ ኤሊክስ ፤ ኢሊኪ) ፤ ፀጕሮ ፡ ወይን ፡ ሐረግ ፡ ወይን ። ግእዝ ፡ ግን ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ይላል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (ዘፍ፴፱ ፡ ፲፩) ።

**እለቄጥሩ** ፤ (ጽር ፡ ኤሌክትሮን) ፤ ዘይበ ርቅ ፡ ዘያንጸበርቅ ፤ የብርሃን ፡ ጽርየትና ፡ ብዛት ፡ ዐይን ፡ የሚያፈዝ ፡ የሚበዘብዝ ፤ ኤሌትሪክ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። በሊቃኒዎች ፡ ግን ፡ ያፍ ፡ ዘራብዕ ፡ ርእሱ ፡ ይሉ ታል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ። ከመ ፡ ርእየተ ፡ እለቄጥሩ ፡ (ሕዝ፩ ፡ ፬ ፡ ፳፯ ። ፰ ፡ ፪ ። ድጓ) ።

**እልቅርጥብ** ፤—ነከሸ ፡ ጋጭ ፤—ቅር ጥብ ።

**እልቀታ** ፤—የዱብ ፡ ወገን ፤—ቀታ ።

**አለቅት** ፤—በቁሙ ፤—ዐለቅት ።

**ኤሊሳ** ፤ ስመ ፡ ነገድ ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ መዲና ፡ ብዙ ፡ ደሴት ፡ ያለው ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፬ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፯) ።

**እልሻዳይ** ፤—ስመ ፡ እምላክ ፤—ሰደየ ።

**እልታሕ** ፤—ሥረ ፡ ወጥ ፤—ለቲሕ ፡ ለ ትሐ ።

**አላቲኖን** ፤ (ጽር ፡ አላቲኖስ) ፤ አማን ፡ በ አማን ፡ እውነት ፡ በውነት ፡ (ቅዳ) ።

**አመ** ፤ (ዐቢይ ፡ አገባብ) ፤ በ ፡ ጊዜ ፡ የ ። በና ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ የ ፡ ሲኾን ፡ ደግሞ ፡ ጊዜንቱ ፡ አይቀርም ፡ እንደ ፡ ዘ ፡ ይዘረዘራል ። አመ ፡ አሚሩ ፤ አመ ፡ ዐሡሩ ፡ ይይን ። አመ ፡ ሞትኩ ፡ ቅብ ረኒ ። ይበጽሕ ፡ መዋዕል ፡ አመ ፡ ይብሉ ፡ ብፁዓት ፡ መካናት ፡ እለ ፡ ኢወለዳ ። አልቦ ፡ አመ ፡ ኢሀሎ ፡ ወአ ልቦ ፡ አመ ፡ ተንሥአ ፡ (ማቴ፲፭ ፡ ፳፪ ። ጦቢ፬ ፡ ፫ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እንዚ ፡ ይኾናል ፡ ይላሉ ፤ ምስ ክራቸው ፡ አይጠግብም ። ፲፱ኛ ፡ ዕርክን ፡ ፴፯ ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት ።

**አሜ** ፤ ጊዜ ፡ ሰዓት ፡ ወራት ። ፀሓይ ፡ ዘአሜ ፡ ክረምት ። ወርኅ ፡ ዘአሜ ፡ ገሀሀ ። ይትፌሥሑ ፡ አሜ ፡ ሞቶሙ ። እስከ ፡ አሜ ፡ ሞቱ ፡ ለሄሮድስ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ደራሲ ። ድጓ ። ማቴ፪ ፡ ፲፭) ። አሜሁ ፡ ሃ ፡ አሜከ ፡ ኪ ፡ እያለ ፡ ይዘረዘራል ።

**አሜሃ** ፤ ጊዜዋ ፡ በጊዜዋ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በዚያች ፡ ጊዜ ፤ ወዲያው ፡ ፈጥኖ ፡ ቶሎ ። እምአሜሃ ። እስከ ፡ አሜሃ ። እ ፡ ዘአሜሃ ፡ ትውልድ ፡ (ማቴ፬ ፡ ፲፯ ። ኩፋ ፡ ፴፫ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ። አመና ፡ አመ ፡ እም ፡ እኒህ ፡ ሦስቱ ፡ አገባቦች ፡ የአመመ ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ንባቦች ፡ አይደሉም ።

(ላ) **እም** ፤ (እመ) ፤ ንኡስ ፡ አገባብ ። ከ ፡ ክ ፡ ኪ ፡ ኩ ፡ በ ፡ ባ ፤ ኋላ ፡ ገና ። አገባብነቱ ፡ የመነሻ ፡ የተከፋይ ፡ የ ተወላጅ ፡ ነው ። መደበኛ ፡ ፍችው ፡ ከ ፡ ወይም ፡ ተ ፡ የቀረው ፡ ተውሳክ ። ወረደ ፡ እምሰማይ ፤ ከሰማይ ፡ ተሰ ማይ ። መጽአ ፡ እምላዕሉ ፤ ከላይ ፤ ተላይ ። ከና ፡ ተ ፡ አ ንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ከ ፡ ሲኾን ፡ ከመን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ አድርጎ ፡ አሉታ ፡ ባለበት ፡ በቀዳማይ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባል ። እምከመ ፡ ኢሞትኩ ፡ ዮም ፡ ኢየዐርፍ ፡ እምጻማ ፡ ገዘ ንቱ ፡ ዓለም ፤ ካልሞትኹ ፡ ካ ፡ ያስኘችውም ፡ ኢ ፡ ናት ፤ በዕብራይስጥ ፡ በዘንድ ፡ በእመና ፡ በእም ፡ በዕብ ፡ እየገቡ ፡ ባ ፡ ክ ፡ እንዲ ፡ የሚያሰኙ ፡ ራብዕ ፡ አድራጎች ፡ አኮና ፡ ኢ ፡ አልቦ ፡ ናቸው ። የቀረውን ፡ በንኡስ ፡ አገባብ ፡ ተመል ከት ፡ (ዕርኽ ፡ ቍ፴፱) ።

**እምድ** ፤ በቁሙ ፤—ዐምደ ፡ ዐመደ ፤ ዐምድ ።

**እምድሩ** ፤—አከቶ ፡ ፈጽሞ ፤—መድ ረወ ።

**አማዳሮት** ፤ (ዕብ ፡ ደሀሮት) ፤ ሩጫ ፡ ግል ቢያ ፤ የፈረስ ፡ (መሳ፭ ፡ ፳፪ ።

**እምዳሮት** ፤ እምዳር ፤-ምድሮች ፤-መ ዲር ፡ መደረ ፤ ምድር ።

**እምዘ** ፤ እምዝ ፤—እም ፡ ዘ ፡ ዝ ፤ (ዕር ፲፱ ፡ ቍ፴፱) ።

**እምሔው** ፤ አማሑት ፤—አያት ፤—ሐ ዪው ፡ ሐይወ ።

**እምኖ** ፤ ኖት ፤ (አምኖ ፡ ይኤምኖ ፤ የአ) ፤ እጅ ፡ መንሣት ፤ ባንገት ፡ በወገብ ፡ በጕልበት ፡ መስገድ ፤ ማጐንበስ ፡ ጕልበት ፡ እጅ ፡ መሳም ፡ መሳለም ፤ ሰላምታ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ መስጠት ፡ ማቅረብ ፤ በቃል ፡ በእጅ ። ሰገ ድኩ ፡ ሊተ ፤ ወአማኅኩኒ ። እኤምኅ ፡ አእጋሪከ ። አ ምኁ ፡ ኵሎ ፡ ቅዱሳነ ፤ አምኁክሙ ፡ አኃዊነ ። አዘ ዘሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ዐበይቱ ፡ ከመ ፡ የአምኅዎ ፡ ንዋየ ፡ በከመ ፡ ክሂሎቶሙ ። እለ ፡ ይኤምኁከ ፡ ወርቀ ፡ (ማ ቴ፬ ፡ ፱ ። ደራሲ ። ፊልጵ፬ ፡ ፳፩ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ መጋ ፳፱ ። ሚያዝ) ።

**አማኂ** ፤ (ኂት ፡ ኅያን ፡ ያት) ፤ እጅ ፡ የሚ ነሣ ፤ የሚሳለም ፤ እጅ ፡ መንሻ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጭ ፡ አቅራቢ ።

**አእምኆ** ፤ እጅ ፡ አስነሣ ፡ አሰገደ ፡ እጅ ፡ መ ንሻ ፡ አሰጠ ።

**ተእምኆ** ፤ እጅ ፡ ተነሣ ፤ እጅ ፡ እግሩ ፡ ተሳመ ፤ እጅ ፡ መንሻ ፡ ተሰጠው ፤ ተቀበለ ።

**እሙኁ** ፤ (ኃን ፡ ኃት ፡ እምኆት) ፡ እጅ ፡ የተነሣ ፤ የተሳመ ፤ ሰላም ፡ የተባለ ።

**እማኄ** ፤ (ኄያት) ፤ እጅ ፡ መንሣት ፤ እጅ ፡ ነሣሥ ፤ ሰላምታ ፡ አሰጣጥ ፤ እድንኖ ፤ ሰላምታ ፡ ከበሬታ ። ለዝክረ ፡ ስምኪ ፡ አቅረብኩ ፡ እማኄ ፡ (ደራሲ) ።

**አምኃ** ፡ (ኃት) ፤ ሰላምታ ፤ ስጦታ ፤ የቃል ፡ የእጅ ፡ ያንገት ። እፎኑ ፡ ዘከመ ፡ ዝ ፡ አምኃ ። አምኃ ፡ ዘአምኆ ፡ ባቲ ፡ አብ ፡ ለወልድ ። ጸሎተ ፡ አምኃ ፡ (ሉቃ፩ ፡ ፳፱ ። ቄድር ። ቅዳ) ።

**አምኃ** ፤ በቁሙ ፤ እጅ ፡ መንሻ ፤ በረከት ፡ መቀደያ ፤ እጅ ፡ ነሥኦ ፡ ወዲያው ፡ የሚሰጡት ፡ ስጦታ ፡ ገንዘብ ፤ ማማለጃ ፡ ጉቦ ። ያመጽኡ ፡ አምኃ ፡ ለንጉሥ ፡ ሰማይ ። ወአብኡ ፡ ሎቱ ፡ አምኃ ። ኢትንሣእ ፡ ሕልያነ ፡ ወአምኃ ፡ (ጦቢ፲፫ ፡ ፲፩ ። ማቴ፪ ፡ ፲፩ ። ኩፋ ፡ ፴፩) ።

**ተአምኆ** ፤ እጅ ፡ ተነሣሣ ፤ ተሳሳመ ፤ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያየዘ ፤ ተገናኘ ፡ ወይም ፡ ተሰነባበተ ። ትትአምኁ ፡ በበይናቲክሙ ፡ በአምኃ ፡ ቅድሳት ። ወተአምኆሙ ፡ በአምኃ ፡ መንፈሳዊት ። ዘይፈትዉ ፡ ድንግልና ፡ ይትአማኅ ፡ (ይሰናበቱ) ፡ ኵሎ ፡ ጥሪቶ ፡ ውሂቦ ፡ ለምስኪናን ፡ (ቅዳ ። ገድ ፡ ተክ ። ኪዳ) ።

**አስተአምኆ** ፤ አሳለመ ፤ አሳሳመ ፤ አገናኘ ። አስተአሚኆከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትብል ፡ ጸዋተ ፡ (ግንዘ) ።

**አሜከላ** ፤ (ዕብ ፡ ዳርዳር) ፤ በቁሙ ፤ ኩሸሽላ ፤ የኩሸሽላ ፡ ዐይነት ፤ ኹለንተናው ፡ እሾኽ ፡ የተመላ ፤ እሾኻም ፡ ሬሳም ። ሦክ ፡ ወአሜከላ ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፲፰ ። ኩፋ ፡ ፫ ። ዕብ፮ ፡ ፰) ።



አሜከላ ፡

**አምላክ** ፤—በቁሙ ፤—መሊክ ፡ መለከ ፤ መለክ ።

(ተ) **አምሞ** ፤ ሞት ፤ (አመመ ፡ ይኤምም ፡ የእ ። ዕብ ፡ ሀማም) ፤ ማመም ፤ መረመኽ ፡ መቅመም ። አማሚ ፡ መኾን ፤ ያረም ፡ ያፈዳ ፡ የቀፋሮ ። ማነት ፤ እናት ፡ ማድረግ ፤ እማማ ፡ ማለት ።

**እመም** ፤ (ዐረ ፡ እማም ፤ ቅድም) ፤ በቁሙ ፡ ፊፉ ፡ አፍንታ ፤ ወረራ ፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ እቅንቶ ፡ የሚሠራ ።

(ተ) **እም** ፤ (ዕብ ፡ ኤም ። ሱር ፡ ኤማ ። ዐረ ፡ ኡም) ፤ እናት ፡ ወላጅ ፡ መገኛ ፤ ያባት ፡ ኹለተኛ ፤ ወላድ ፡ ሴት ፤ የጡት ፡ የክርስትና ፡ እናት ፤ አሳዳጊ ፡ ሞግዚት ፤ መነኰሲት ፤ ያገር ፡ ባልቴት ፤ እማሆይ ፡ እመ ፡ እኅዲሉ ። አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ። እሙ ፡ ወእኁሁ ፡ ለእሙ ። እሙ ፡ መንፈሳዊት ፡ እንተ ፡ ተወክፈቶ ፡ በጥምቀት ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፲፪ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፳፭ ። ቀና ፡ ኒቅ) ።

**እም** ፤ ምንጭ ፡ ነቅ ፤ ያባት ፡ የናት ፡ አገር ። ፍትወተ ፡ ሥሥዕት ፡ ዘብዕል ፡ እመ ፡ ኵሎን ፡ ኀጣውእ ፡ እኩያት ። እምነ ፡ ጽዮን ፡ ይብል ፡ ሰብእ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፰ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፹፮) ።

**እመ ፡ አህጉር** ፤ መዲና ፤ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**እመ ፡ ቤት** ፤ በቁሙ ፤ ባልቲ ፡ ቤት ፤ የቤት ፡ ንግሥት ፡ የቤቱ ፡ ሰብ ፡ እናት ፤ መሪ ፡ አሳዳሪ ፤ ራስና ፡ ራስነት ፡ ያላት ። ርእሳ ፡ ለብእሲት ፡ ምታ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፫) ።

**እመ ፡ ሕያው** ፤ ሔዋን ፤ የሰው ፡ ኹሉ ፡ እናት ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፳) ። ዕንለ ፡ መሕያውን ፡ እይ ።

**እመ ፡ ኵሉ** ፤ መቃብር ፤ የኹሉ ፡ ከታች ፡ (ሢራ፵ ፡ ፩) ።

**እመ ፡ ምኔት** ፤ የገዳም ፡ እናት ፤ የመነኮሳይያት ፡ አለቃ ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፯ ፡ ኅዳ፲) ።

**እማት** ፤ እናቶች ። ይቤልዎን ፡ ለእማቲሆሙ ። እማቲነ ፡ ክና ፡ ከመ ፡ መበለታት ፡ (ሰቈ፪ ፡ ፲፪ ። ፭ ፡ ፫) ።

**እመ** ፤ (እም ። ዕብ ፡ ኢም ። ሱር ፡ ኤ ። ዐረ ፡ ኢን) ፤ ዐቢይ ፡ አገባብ ። ቢ ፡ ብ ፡ ብ ፡ ከ ፡ ከ ፤ እንደ ፡ እንደኾነ ፤ ምንም ፤ ምን ፡ አልባት ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘይቤ ። ለእመ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡ ረብሐ ። እመ ፡ አከ ። እመ ፡ ፈቲውከ ። እመሰ ፡ ነቢያት ፡ እሙንቱ ። እመ ፡ እግዚ ፡ ኢሐነጸ ፡ ቤተ ። እመ ፡ አንተሁ ፡ ክርስቶስ ፡ ንግረነ ። እመኒ ፡ ኮሎሙ ፡ ዐለዉከ ። እመ ፡ ትፈሪ ፡ ለዓሙ ። የእመ ፡ አፈታት ፡ ስልቱ ፡ ስለ ፡ በዛ ፡ በየወራረዱ ፡ ማቅኛ ፡ ትርጕ ፡ ዐማርኛ ፡ ይሻልና ፡ ምንም ፤ ምን ፡ አልባት ፡ ማለት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። የቀረውን ፡ በዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ተመልከት ፡ (ዕር፲፱ ፡ ቀኖ፳፪) ።

**አሚን** ፤ ኖት ፤ (አምነ ፡ የአምን ፡ ይእመን ፡ ይእ ። ዕብ ፡ አማን ። ዐረ ፡ አሚነ ። ሱር ፡ ሃይሚን) ፤ ማመን ፡ መቀበል ፤ ተስፋ ፡ ማድረግ ፤ አለመጠራጠር ፤ መናዘዝ ፡ እውነት ፡ መናገር ፡ መመስከር ፤ አወ ፡ አማን ፡ ማለት ። ጻድቅሰ ፡ በአሚን ፡ የሐዩ ። የዋህ ፡ የአምን ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ። ኢትአመንዎሙ ፡ ለእኃዊክሙ ። አምነ ፡ ወኢክሕደ ። አምኑ ፡ ወተኩነኑ ። ዘአምነኒ ፡ በገጸ ፡ ሰብእ ፡ አአምኖ ፡ አነ ፡ በገጸ ፡ አቡየ ፡ (ሮሜ፩ ፡ ፲፯ ። ምሳ፲፬ ፡ ፲፭ ። ኤር፱ ፡ ፬ ። ዮሐ፩ ፡ ፳ ። አስቴ ፡ ፩ ። ዲድ ፡ ፳፭) ። አምኖ ፡ ማመስገን ፡ መውደድ ፡ መፍቀድ ። መነ ፡ የአምነከ ። ዘበአሚን

ክሙ ፡ (መዝ፳ ፡ ፰ ። ፳፱ ፡ ፲፪ ። ዘዳ፲፱ ፡ ፯ ፡ ፲፯) ። በአ ምን ፡ ፈንታ ፡ ተአመነ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ ተ ፡ ይማ ረኛ ፡ እንጂ ፡ የማእገዝ ፡ አይደለም ። መኑ ፡ ተአመነ ፡ በእ ግዚ ፡ ወተኀፍረ ። ኢትትአመኑ ፡ ብዙኀ ። ኢትትአ መኑ ፡ ዘሎ ፡ ቃለ ፡ ዘነገሩከ ። ቴዎዶስዮስ ፡ ተአማኔ ፡ በጽድቅ ። እትአመነክሙ ፡ ከመ ፡ ትፈጽሙ ። ነአ ምን ፡ ወንትአመን ። እንዘ ፡ ይትአመኑ ፡ ኀጣውኢ ሆሙ ፡ (ሚራ፪ ፡ ፲ ። ፯ ፡ ፯ ። ፲፱ ፡ ፲፰ ። ሃይ ፡ አበ ። ሮሜ፲፰ ፡ ፲፱ ። ቅዳ ። ማቴ፫ ፡ ፮) ።

**አማኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፤ የሚያምን ፡ አማኝ ፡ እውነተኛ ፡ ክርስቲያን ። ብእሲ ፡ አማኒ ፡ ዘዘ መወ ፡ በብእሲት ፡ ኢአማኒት ። ትውልድ ፡ ኢአማ ኒት ፡ (ፊ ፡ መ፳ ፡ ፲፰ ። ማቴ፲፯ ፡ ፲፯) ።

**አእመነ ፤** አሳመነ ፡ ወደ ፡ እምነት ፡ ሳበ ፡ አስ ረዳ ፡ ሰበከ ፡ ነገረ ፡ አስተማረ ። ኄሕነ ፡ ናአምዎ ። ዘብ ዙኆ ፡ ሕዝብ ፡ አእመነ ። አእመኖ ፡ በስመ ፡ ኢየሱስ ። አእመኖሙ ፡ በዕደው ፡ እለ ፡ ፈነዎሙ ፡ (ማቴ፳፰ ፡ ፲፱ ። ድጓ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፱ ። ዮሴፍ) ። በአእመነ ፡ ፈንታ ፡ አስተአመነ ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። እንዘ ፡ ያስ ተአምኖ ፡ ዮሐንስ ፡ ይጽሕፍ ። ወበግብሩ ፡ ያስተአ ምን ፡ ዝንቱ ፡ ከመ ፡ አማን ። ወያስተአምን ፡ ዘንተ ፡ እንዘ ፡ ይብል ። ሰይጣን ፡ ያስተአምን ፡ ሎሙ ፡ በግ ብሩ ፡ (ቄር ፡ እስት ። ጳላ ። ቀሌ) ።

**ተአምነ ፤** ታመነ ፡ ታመነበት ፡ የታመነ ፡ ኾነ ፡ በሌሎች ። ተዘለነ ፡ ተዘለለ ፤ ሐሳቡን ፡ ጣለ ፤ ምን ፡ አለ ብኝ ፡ አለ ። ተመከለን ፡ እዩ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። በበ ክዎ ፡ ውስተ ፡ ሕዝብ ፡ ወተአምኖ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ። ወንጌል ፡ ዘአነ ፡ ተአመንኩ ፡ ቦቱ ። በእንተ ፡ ተአምኖ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ላዕለ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ሰላም ፡ ለመቃርዮስ ፡ በእስክንድርያ ፡ ዘተአምኖ ፡ መርጌተ ፡ ክርስቶስ ፡ ይዕቀብ ። ይነብር ፡ ተአሚኖ ። (ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ። ፰ ፡ ፲፰ ። ቀኖና ፡ ፴፰ ። ስንክ ፡ መስ፱ ። ሚራ፮ ፡ ፲፫) ።

**ተአማኒ ፤** የሚታመን ፡ ታማኝ ፡ የማይጠረ ጠር ። ኢይትክሀሎ ፡ ለብእ ፡ ይኩን ፡ ተአማኔ ፡ እመ ፡ ኢያግሐሠ ፡ ርእሶ ፡ እምግዕዘ ፡ ልማዱ ። ተአ ማንያን ፡ (አፈ ፡ ድርሳ፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**እሙን ፡ (ናን ፡ ናት ፡ እምንት)** ፤ በቁሙ ፡ የታመነ ፡ የተረዳ ፡ ርግጥ ፡ እውነት ፡ የተገባ ። ስምዑ ፡ ለእግዚ ፡ እሙን ። እሙን ፡ ከነ ፡ ምክረ ፡ ትካት ። እሙን ፡ ቃል ፡ ዘሰማዕኩ ። እሙን ፡ ሕልሙ ፡ (መዝ ፡ ፲፰ ። ኢሳ፳፭ ፡ ፩ ። ዘዜና ፡ ፱ ፡ ፰ ። ዳን፪ ፡ ፵፭) ።

**እሙነ ፤** በውነት ፤ በሚገባ ። አማን ፡ ተወልደ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ እሙነ ፡ ልህቀ ፥ ወእሙነ ፡ በልዐ ፥ ወእሙነ ፡ ሐመ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ። የሐውር ፡ እሙነ ፡ ታምኖ ፡ ፀርሮ ፡ ተዘልሎ ፡ ምን ፡ አለብኝ ፡ ብሎ ፡ ሳይ ሠጋ ፡ ሳይፈራ ፡ ሳይጠራጠር ፡ (ምሳ፲ ፡ ፱) ።

**እምነት ፡ (ታት)** ፤ በቁሙ ፡ ሃይማኖት ፡ ማ መን ፡ መታመን ፡ እስተማመን ፡ እሙንነት ። ዘወሰጠ ፡ እምነተ ፡ ክርስቲያን ። እምነት ፡ ዘመስቀለ ፡ ክርስ ቶስ ። ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ዘእምነትነ ። እምነታት ፡ (ቀኖ ፡ አንጾ ። ስንክ ፡ መስ፲፯ ። ቄር ፡ ጳላ ። አፈ ፡ ተ፳) ።

**አሚን ፤ (ዐረ ፡ አሚኑ)** ፤ ስም ፡ እሙን ፡ ማለት ፡ ነው ። (ፊእ፫ ፡ ፲፱) ።

**አማን ፤** የታመነ ፡ እውነት ፡ በውነት ። እመ ፡ አማንኑ ፡ ውእቱ ፡ ለሐዊር ፡ ምስሌከ ። እመ ፡ አማነ ፡ ከነ ፡ ወጥዩቀ ፡ ነገሩ ። አማንከሙኑ ፡ ኢታመልኩ ። አማነ ፡ ትቤ ። እስመ ፡ አማን ፡ ከማሁ ፡ ውእቱ ፡ (ጦ ቢ፭ ፡ ፱ ። ዘዳ፲፫ ፡ ፲፬ ። ዳን፫ ፡ ፲፬ ። ቄር ፡ ጳላ ። ዮሐ ፲፩ ፡ ፲) ።

**አማናዊ ፤** ባሕርያዊ ፡ እውነተኛ ፡ ዋንኛ ፡ መደ በኛ ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ ያይደለ ። አምሳክ ፡ አማናዊ ። ድንግልና ፡ አማናዊ ፡ ድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ ይእቲ ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፺ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ተ፳፰) ።

**አማንየ ፤** ቃለ ፡ መሐላ ፡ እውነቱ ። አማንየ ፡ እብለከ ፡ (ስንክ ፡ ሐም፳) ።

**ምእመን ፤ ማእምን ፤ (ንት ፡ ናን ፡ ናት)** ፤ በቁሙ ፡ ያመነ ፡ አማኒ ፡ የታመነ ፡ እሙን ፡ እውነተኛ ፡ ክርስቲያን ፤ ማመኛ ፡ መታመኛ ፡ እግዜር ፤ ዘመድ ፡ ወ ዳጅ ፡ ባልንጀር ፡ የማይጠረጠር ። ይትአመን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ምእመን ፡ በአብ ፡ ወበወልድ ፡ ወበመን ፈስ ፡ ቅዱስ ። ብእሲት ፡ ማእምንት ። ዘምእመን ፡ በስምከ ። ምእመናን ፡ ወምእመናት ። ዕደው ፡ ም እመናን ፡ በኑይሎሙ ። አዋልድ ፡ ምእመናት ። ው እቱ ፡ ምእመኑ ። ወይከውኖ ፡ ምእመነ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፫ ። ሄ፱ ፡ ፳ ። ማንዘ ። ቅዳ ። ዮዲ፪ ፡ ፳ ። ኢሳ፴፪ ፡ ፱ ። ሚ ራ፴፮ ፡ ፲፰ ። ፴፯ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፲፯) ።

**ተአመነ ፤** ተማመነ ፡ ተማማለ ።

**አስተአመነ ፤** አስተማመነ ፡ አማማለ ፡ አገዛ ዘተ ።

**አሜን ፤ (ዕብራ)** ፤ የንባብና ፡ የዜማ ፡ ፍጻሜ ፡ መጨረሻ ፡ ቃል ፡ የጸሎትና ፡ የበረከት ፡ የርግማን ፡ ተ ሰጠ ። እውነት ፡ በውነት ፡ ይኹን ፡ ይደረግ ። ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፥ አሜን ። ወትብል ፡ ይ እቲ ፡ ብእሲት ፡ አሜን ፡ ወአሜን ፡ (ገላ፩ ፡ ፭ ። ዘኍ፭ ፡ ፳፪) ።

**እምን ፤—እም ፡ ን ፤—እም ።**

**አማኑኤል ፤—ስመ ፡ ሥጋዌ ፤—ዐማ ኑኤል ።**

**እም(ብ)ኖዲ ፤ (ቀብጥ ፡ ኘኖቲ)** ፤ አምላክ ።

**አመንክዮስ ፤** የመናፍቅ ፡ ስም ፡ ማኒ ፡ መን ናዊ ፡ ምትሀት ፡ ጽላሎት ፡ የሚል ። እስመ ፡ ሥጋ ፡ ፀረ ፡ አመንክዮስ ፡ (ቄር) ።

**እምንስቲቲ ፡ ሙኪርያ ፤ (ጽር ፡ ምን ስቲቲሙ ፡ ኪሪዮ)** ፤ ተዘከረኒ ፡ እግዚኦ ። አንቲ ፡

ፋሲልዮስ፡(ጽር፡ ኤንቲ፡ (በ)ባሲሊዮስ)፡ በመንግሥትከ፡(ማቴ፡ ሕማ ። ሉቃ፳፫፡ ፵፪) ።

**እሙንቱ፤(ዐረ፡ ሁም ። ዕብ፡ ሄማህ)፤** የውእቱ፡ ርባ፤ ውእቶሙና፡ እሙንቱ፡ እንደ፡ ወንን፡ ናቸው ። እሊያ፤ ርሳቸው፤ እሊያዎች፤ ወይም፡ ናቸው፡ ንን፡ ያሰኛል፤ ቅጽልና፡ በቂ፡ በጸፋና፡ አንቀጽ፡ ይኾናል፤ የውእቱን፡ ፍች፡ ተመልከት ። እሙንቱሰ፡ ኢያእመሩ፤ እሊያ ። እሉ፡ ደናግል፡ እለ፡ መኑ፡ እሙንቱ፤ ናቸው ። ንሕነ፡ እሙንቱ፤ ነን፡ ነን፡ (ሄርማ ። ቅዳ) ።

**እማንቱ፤(ውእቶን)፤** ገዥ፡ ከማሁ፤ የሴቶች ። እማንቱሰ፡ ይትሀጐላ፡(መዝ፡ ፻፩) ።

**አሜሬቅ፤(ጽር፡ አማሬት ። ዕብ፡ ሚፍታን)፤** መድረክ፤ (፩ነገ፡ ፳፡ ፱) ።

(ሞ) **አምሮ፤ሮት፤(አመረ፡ ይኤምር፡ የአምር፡ የአ ። ዕብ፡ አማር፤ብህለ፡ነበበ ። ዐረ፡ አመረ፤አዘዘ)፤** ማመልከት፤ ማሳየት፤ መጠቈም፡ መጠንቈል፤ መንገር፡ ማስተማር፤ በእጅ፡ በቃል ። ታምራት፡ ማድረግ ። ወአመሮ፡ በእዴሁ፡ ከመ፡ ይኑጽር፡ ድኅሬሁ ። አመረኒ፡ በክልኤቱ፡ ትእምርት ። አመረ፡ ባሕረ፡ ለኀበ፡ ሥርዐተ፡ ብሕትውና፤ ወዐውሎታት፡ ለኀበ፡ መከራት፡ (ዮሴፍ ። ዲድ፡ ፳፱ ። ፊልክ፡ ፳፫) ። በአመረ፡ ፈንታ፡ አአመረ፡ ይላል፤ አያሰኝም ። ወናኤምር፡ ከመ፡ እስትጉቡእ ። ያኤምር፡ በዝንቱ፡(ፍ፡ ን ። አፈ፡ ተ፲፱) ።

**አማሪ፤(ሪት፡ርያን፡ያት)፤** የሚያመለክት፤ አመልካች፤ ጠቋሚ፡ ጠንቋይ፤ መክር ።

**አአመረ፤** አስመለከተ፤ አስጠቈመ፤ አስጠንቈለ፤ ምልክት፡ ታምራት፡ አስደረገ ።

**ተአመረ፤** ተመለከተ፤ ታየ፤ ታለመ፤ ምልክት፡ ፀላማ፡ ኾነ፤ ተነፋ፡ መለከቱ ። አንብሮ፡ ኀበ፡ ይትኤመሩ ። ተአመሩ፡ በቃለ፡ ቀርን ። እትኤመሮሙ፡(ዘኍ፳፩፡ ፳ ። ኤር፬፡ ፳ ። ዘካ፲፡ ፳) ። በአመረ፡ ፈንታ፡ ተአመረ፡ ይላል፤ ጠነቈለ፡ ሲል ። ዘይትኤመር፡ በአጻብዕ፡ አው፡ በአሕጻ ። ተአማርያን፡ (ቄድር ። ፍ፡ ን፡ ፵፰) ።

**እሙር፤(ራን፡ ራት፡ ምርት)፤** የተመለከተ፤ ምልክታም፡ ባለምልክት፤ ባለታምራት ።

**እማሬ፤(ርያት)፤** ማመልከት፤ መመልከት፡ አመለካከት፤ ምልክታ፤ ምልክት ። ኢያስተርእዩ፡ ለንዴሬ፡ ወኢይትሌበዉ፡ ለእማሬ ። ዐንባቆም፡ ነቢይ፡ ወልደ፡ ዳኮር፡ ነገደ፡ ኅሬ፤ ሥራዌ፡ ዘሕዝበ፡ አይ

☞

እማሬ፡

ሁድ፡ እንዘ፡ ይኤምር፡ እማሬ ። ይጽሕፍ፡ ውስቴታ፡ እማሬ፡ ዕለታት ። አላ፡ እማሬ፡ ባሕቲቱ፡ ወምሳሌ፡ ዘዝንቱ ። ዜና፡ እማሬ፡ ዘአስተርአየ፡ በእንተ፡ ንሥተተ፡ መቅደስ፡(መጽ፡ ምስ ። ስንክ፡ ኅዳር ። ፍ፡ ን፡ ፵፰፡ ፩ ። ዮሴፍ) ።

**ትእምርት፤(ታት)፤** ምልክት፤ አምሳል፤ አብነት፤ ፀላማ፤ ታምራት፤ ጕድ ። ትእምርተ፡ኪዳንየ ። ትእምርተ፡ተንሥኡ፡ ወትእምርትሰ፡ ኢይትወሀባ፡ ዘእንበለ፡ ትእምርተ፡ ዮናስ፡ ነቢይ ። ወይከውነከሙ፡ ሕዝቅኤል፡ ትእምርተ ። ንሥኡ፡ ትእምርተ ። ወእሁብ፡ ትእምርተ፡ በሰማይ፡ በላዕሉ ። ወይትወለድ፡ትእምርት፡እምእንስት፡(ዘፍ፱፡ ፲፪ ። ማቴ፲፪፡ ፴፱ ። ሕዝ፳፬፡ ፳፬ ። ኤር፳፡ ፩ ። ግብ፪፡ ፲፱ ። ሱቱ፡ ዕዝ፫፡ ፲፪) ። ይትወሰድ፡ ትእምርት፡ ያለው፡ እባብ፡ ዘንዶ፡ አርዌ፡ እንስሳ፡ አሞራ፡ ነው ። የፍጻሜ፡ ዘመን፡ ምልክት ። ሰውም፡ ቢኾን፡ ሽብቶ፡ ጥርስ፡ አውጥቶ፡ ለዘር፡ በቅቶ፡ ማለት፡ ነው፤ እንዲህም፡ ኹሞ፡ ተወልደ፡ ወዲያው፡ ይናገራል ። ወይትወለዱ፡ አክይስት፡ እምሰብእ፤ ወዓዲ፡ አራዊት፡ እኩያን፤ ወይትወለዱ፡ ደቂቅ፡ ዘይትናገሩ፡ ነገረ፡ ጽኑዐ፡ በጊዜሃ፤ ወራእዮሙ፡ ከመ፡ ዘልሂቅ፡ ወልደቶሙ፡ ዘምስለ፡ ሚበት ። ወአንስት፡ ይወልዳ፡ ዘአርባዕቱ፡ እግሩ፤ ወይትናገሩ፡ ደቂቅን፡ በውስተ፡ ማሕፀን፤ ወብዙኅ፡ ተአምር፡ ዘይከውን፡(ኪዳ፳) ። ግናይን፡ ተመልከት ።

**ተአምር፡(ራት)፤** በቁሙ፤ ታምር፡ ታምራት፤ ድንቅ፡ ምልክት፤ እንደ፡ ነቢያት፡ እንደ፡ ሐዋርያት፡ በእግዚአ፡ ኀይል፡ በክርስቶስ፡ ስም፡ ከልኾነ፡ በቀር፡ ማንም፡ ሰው፡ ሊሠራው፡ የማይችል፡ ልዩ፡ ድንቅ፡ ጕድ፡ ብርቅ፡ የኾነ፡ አምላካዊ፡ ሥራ፡ (ዮሐ፲፱፡ ፲፪ ። ዘፀ፬፡ ፳፡ ፱) ።

—፤ ፀሐይ፡ ጨረቃ፡ ኮከብ ። ሰገደ፡ ለጽሉ፡ ተአምረ፡ ሰማይ ። ፀሓይ፡ ወተአምር፡(ዘዜና፡ ፴፫፡ ፫ ። ኤር፲፡ ፪ ። ሔኖ፵፰፡ ፫ ። ኪሩ፡ ፬) ።

**ምእማር፤** ማመልከቻ፤ መመልከቻ፤ ታምራት፡ ምልክት፡ ማድረጊያ፤ ቦታ፡ መማሪያ ።

**አሚር፤ አሜር፤(ጽር፡ ኢሜራ ። ቅብጥ፡ አሜሪ)፤** መዓልት፤ ፀሓይ፡ መጋቤ፡ መዓልት፤ ዕለት፡ ጊዜ፡ ወራት፤ አንድ ። ኵሎ፡ አሚረ፤ ኹል፡ ቀን፤ ኹል፡ ጊዜ፤ ዘወትር፡ ፀሐይ፡ በሠረቀ፡ ቍጥር ። ውእተ፡ አሚረ፤ ያን፡ ቀን፤ ያን፡ ዕለት፤ ያን፡ ጊዜ፤ ወይም፡ በዚያ፡ ቀን፡ በዚያ፡ ወራት ። አመ፡ አሚሩ፡ ለመስከረም፤ በመስከረም፡ ባንድ፡ ቀን፤ የመባቻ፡ ለት ። ስላም፡ ለመልክእኪ፡ ዘተሰርገወ፡ አሚረ፡ ዘያበርህ፡ ወትረ ። እንተ፡ ተሰይ፡ በእግረ፡ አሚር፡(ደራሲ ። ራእ፲፪፡ ፩ ። ጥበ፲፪፡ ፴) ። ባላገባቦች፡ አሜር፡ አስፈር፡ ዓምና፡ ይኾናል፡ ይላሉ፤ ምስክር፡ የለውም ።

(ላ) **አሚር፤ሮት፤(አመረ፡የአምር፡ይእ)፤** ማወቅ፡ መረዳት፡ ይርሱን፡ ርግጡን፡ ማግኘት ። መውደድ፡ወደ፡ ሴት፡ መማባት ። ሠንየ፡ ቀደወ፡ ብሎ፡ አማረ፡

ማለት ፡ ፀማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነውና ፤ አሚር ፡ ማማር ፡ ይኾናል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአመረ ፡ ፈንታ ፡ አእመረ ፡ ይላል ፤ አይበኻም ፤ አይራቢውን ፡ ባስደራቢ ፡ አንቀጽ ፡ ማርባት ፡ ፍጹም ፡ ስሕተት ፡ ነው ። የወዲያኛው ፡ ትግሬ ፡ ሐባብ ፡ እንኳ ፡ ዐወቀ ፡ ሲል ፡ አመረ ፡ እንጂ ፡ አእመረ ፡ አይልም ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አእኵት ፡ አዕረፈ ፡ ሴላም ፡ ብዙ ፡ ስሕተት ፡ አለ ። የፊደልን ፡ ተራ ፡ ያፋለሱና ፡ ያቀወሱ ፡ ሰዎች ፤ አባቶቻቸንንም ፡ ሳይቀሩ ፡ ግዑን ፡ እንደ ፡ ቅኔ ፡ ስላስኬዱት ፡ የቋንቋውን ፡ ሥር ፡ መብቀያውንና ፡ መንሻውን ፡ መንገዱንና ፡ አካኼዱን ፡ ፈጽመው ፡ አሳገፉትም ፤ ብህለንና ፡ ይቤን ፡ ተመልከት ። «የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ግስ ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ አርኣያ ፡ ሥላሴ ፡ ነውና ፤ ዘሩ ፡ ሥረ ፡ ነገሩ ፡ ከሦስት ፡ ቅንጣት ፡ ፊደል ፡ አይወጣም» ፡ አእመረ ፡ ግን ፡ ለግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ የርባ ፡ መዝምሬያ ፡ መኾኑ ፡ ስሕተቱና ፡ ስሕተትነቱ ፡ ስላልታወቀ ፡ ነው ።

**አማሪ**፤(ሪት ፡ ርያን ፡ ያት)፤ የሚያውቅ ፡ ዐዋቂ ፡ የሚወድ ፡ ወዳጅ ።

**አማሪት**፤(ዐማርኛ)፤ በቁሙ ፡ ሴት ፡ ዘፋኝ ፡ ቀንቃኝ ፡ አርኾ ፡ ባለረኸታም ፡ ድምጥ ። የከበሮ ፡ ቁጥ ፤ አታሞ ይቱ ። የበገና ፡ አውታር ፡ ኹለቱ ።

**ማእምር**፤(ርት ፡ ራን ፡ ራት)፤ ባዪ ፡ ከማሁ ። ማእምር ፡ ወፀውቅ ። ማእምረ ፡ ኅቡኣት ። ማእምራን ፡ ለገቢረ ፡ ሠናይ ። ማእምራኒ ፡ ቃል ፤ (መዝ ፡ ፺፬ ። አርጋ ። መክ፱ ፡ ፲፩ ። ሢራ፲፰ ፡ ፳፱) ።

**አእመረ**፤(ያእምር ፡ ያእ)፤ አሳወቀ ፤ አስረዳ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ አድራጊነት ፡ ነው ፤ ዐወቀ ፡ ተረዳ ፤ ወደደ ። በቀተለ ፡ ፈንታ ፡ አቅተለ ፡ ብሎ ፡ ገደለ ፡ ማለት ፡ አሳዋቂና ፡ ዘባራቂ ፡ እንዲያሰኝ ፡ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ፤ ጥሩ ፡ ዕውቀት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ትምርትና ፡ መምር ፡ ያስነቅፋል ። (ምሳሌ) ፤ ሰፈድና ፡ ወንፊት ፡ የላት ፡ ሴት ፡ ያልተነፋ ፡ ዱቄት ፡ አታቦክም ። አእመረ ፡ ዳዊት ፡ ከመ ፡ መጽአ ፡ ሳኦል ። አእምር ፡ ርእሰየ ፡ ከመ ፡ መሬት ፡ ወሐመድ ፡ አነ ። ታእምርኑ ፡ ዘታነብብ ። አእመሩ ፡ ለብእሲቶሙ ። እስመ ፡ እግዚ ፡ ያእምሮሙ ፡ ለመናንያን ፤ (፩ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፫ ። ኢዮ፴፪ ፡ ፯ ። ግብ፰ ፡ ፴ ። ዘፍ፬ ፡ ፩ ። ማር ፡ ይሥ፳ ፡ ፲ ።)

**አእምሮ**፤ሮት፤ ማሳወቅ ፡ ማስረዳት ። ልማዱ ፡ ግን ፡ ማወቅ ፡ መረዳት ። አእምሮ ፡ አእምር ። ኢክህሉ ፡ አእምሮቶ ። ነቢያት ፡ ቀደሙ ፡ አእምሮ ፤ (ምሳ፳፯ ፡ ፳፫ ። ኩፋ ፡ ፴ ። ድጓ) ።

**አእምሮ**፤(እምሮ ። ትግ ፡ አምር)፤ ዕውቀት ፡ ማስተዋል ፤ ከጠባይ ፡ ከትምርት ፡ የሚገኝ ። አእምሮ ፡ ታጌብረከ ፡ ለምህሮ ። ጥበብ ፡ ወአእምሮ ። ወተአተተት ፡ ኵላ ፡ አእምሮቶሙ ። እለ ፡ አልቦሙ ፡ አእምሮ ፤ (ድጓ ። ኪዳ ። ኩፋ ፡ ፳፫ ። ሄይ ፡ አበ) ። ስለ ፡ ተለመደ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አእምሮ ፡ ጥሬ ፡ ዘር ፡ አይኾንም ፡ አርእስት ፡ ነው ።

**ተአምረ**፤ ታወቀ ፡ የታወቀ ፡ የተረዳ ፡ ኾነ ። አራዊት ፡ እለ ፡ ይትአመሩ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ አብድ ፡ ኢትአመር ፡ ጽድቅ ። ልብ ፡ ጠቢብ ፡ ይትአመር ፡ እምአፉሁ ። ኀይላት ፡ ዘኢተአምሩ ፤ (ጥበ፲፭ ፡ ፲፱ ። ምሳ፲፬ ፡ ፴፫ ። ፲፭ ፡ ፳፫ ። ኢር፵ ፡ ፫) ።

**እሙር**፤(ራን ፡ ራት ፡ ምርት)፤ የታወቀ ፤ ዕውቅ ፤ ግልጥ ። እሙረ ፡ ይኩን ፡ ለኵሉ ። መቃብረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስ ፡ ወዮሐንስ ፡ ወቶማስ ፡ እሙራን ፡ ወክሡታን ። በበዓላት ፡ እሙራት ። በእምርት ፡ ዕለት ፡ በዓልኒ ፤ (ሔኖ፵፮ ፡ ፮ ። ኤፌ ፡ ድርሳ ፡ ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ድጓ) ። አምሮና ፡ አሚር ፡ በውስጠ ፡ ዘ ፡ ቱሩሓን ፡ ናቸው ፤ ኹሉም ፡ ይጠብቃሉ ፤ ይኸውም ፡ በመምህራን ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በስዋስው ፡ መንገድ ፡ አይደለም ።

**እምረት**፤ ማወቅ ፡ መታወቅ ፤ አስተዋወቅ ፤ ዕውቂያ ፤ ዕውቀት ፤ ዐዋቂነት ።

**ተእመረ**፤ ተዋወቀ ፤ ተወዳጀ ፤ ተዋደደ ።

**አስተአመረ**፤ አስተዋወቀ ፤ አወዳጀ ።

**አማሲኒት**፤(ጽር ፡ አማሴኒት ። ዕብ ፡ ሀሽማኒት)፤ ኀዋየ ፡ ማሕሌት ፤ በገና ፡ ከራር ፡ ባለ፰ ፡ አውታር ፤ (፩ዜና ፡ ፲፭ ፡ ፳፩) ።

**አምሴር**፤**አምሺር**፤(ቅብጥ ፡ ሜኺር ፤ ማሺር)፤ የግብጦች ፡ ፮ኛ ፡ ወር ፡ የካቲት ፤ (አቡሻ ፡ ፶) ።

(ጥ) **አምቶ**፤ ቶት፤(አመተ ፡ ይኤምት ፡ የአምት ። ዕብ ፡ አሜት)፤ ማመት ፡ መገመት ፤ ማሰብ ፡ መገምገም ፤ የዋጋ ፡ የነገር ። መከንዳት ፤ በእጅ ፡ መስፈር ፡ መለካት ፤ በጣት ፡ ማሳየት ፡ ማመልከት ። መግዛት ፤ መቅጠር ፤ አገልጋይ ፡ ማድረግ ፤ የሴት ፡ ልጅ ።

**ተአመተ**፤ ታመተ ፤ ተገመተ ፤ ተከነዳ ።

**እሙት**፤ የተገመተ ፤ የተከነዳ ።

**እማቴ**፤ መከንዳት ፤ መስፈር ፤ አከንዳድ ፤ ክንዳታ ።

**እመት**፤(ታት ። ዕብ ፡ ወሱ ፡ አማ ። ቅብጥ ፡ ማሂ)፤ ክንድ ፤ ከክርን ፡ እስከ ፡ ታላቅ ፡ ጣት ፡ ጫፍ ፡ ያለው ፡ ኹለቱ ፡ ክፍል ። ዕፀ ፡ ዘትምሳ ፡ በእመት ። እመተ ፡ ሰብእ ፡ ወእመተ ፡ መልአክ ። እደዊሃ ፡ ትሰፍሕ ፡ ደብ ፡ ዘይበቍዐ ፡ ወእመታ ፡ ታጸንዕ ፡ ለፈቲል ። ሰላም ፡ ለእመታቲኪ ፡ እለ ፡ ጸንዓ ፡ ይፍትላ ፤ (አስቴ፭ ፡ ፲፬ ። ራእ፳፩ ፡ ፲፯ ። ምሳ፴፩ ፡ ፲፱ ። ደራሲ) ።

**አመት**፤(ብ ፡ አእማት ። ዕብ ፡ አማህ ። ሱር ፡ አምታ ። ዐረ ፡ አመት)፤ ሴት ፡ ባሪያ ፤ ገረድ ፤ ደንገጥር ። አመት ፡ እንተ ፡ ትነብር ፡ ዲበ ፡ ማሕረጽ ። ለሠዩጠ ፡ ገብር ፡ ወአመት ። አግብርት ፡ ወአእማት ፤ (ዘፀ፲፩ ፡ ፭ ። ኩፋ ፡ ፲፩ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፮) ።

**አመት**፤—በቁሙ ፤—ዓመት ።

**አሜቴስጢኖስ**፤(ጽር ፡ አሜቲስቶስ)፤ ዕንቍ ፤ የዕንቍ ፡ ስም ፤ (ራእ፳፩ ፡ ፳ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፲፱) ።

**አነ ፤ (ዕብ ፡ አኒ ። ሱር ፡ ወፀረ ፡ አና) ፤** ነባቢ ፡ ወንባቢት ፡ ወይም ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፤ ነባቢነት ፡ ከ ሰው ፡ ከፍጡራን ፡ አካል ፡ የሚወጣ ፡ በሰምና ፡ በአካል ፡ ፈንታ ፡ የሚናገር ፡ በቁና ፡ ቅጽል ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ። እኔ ፡ ራሴ ፡ ቅሉ ፤ ባለቤቱ ፤ ነኝ ። ዘሩ ፡ አኒስ ፤ አነሰ ፡ ነው ። አነና ፡ ንሕነ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ያስተባብራሉ ፤ ንሕነ ፡ የ አነ ፡ ብዙ ፡ ነው ። **አነ ፡ ወአብ ፡ በቁ ። አነ ፡ ዮሐንስ ፤ ቅጽል ። ወሰተ ፡ ብቱኤል ፡ አነ ፤** አንቀጽ ፡ ነኝ ። **ወንሕነ ፡ ምንትኑ ፡ ንሕነ ፤** እኛ ፡ ምንድር ፡ ነን ፡ ነን ። **አነ ፡ ኄር ፡ አነ ፤** እኔ ፡ ቸር ፡ ነኝ ፡ በቁና ፡ አንቀጽ ። አንስ ፡ አንተ ፡ ቲ ፡ ትሙ ፡ ትን ፡ ንሕነ ፡ ፯ቱ ፡ ኹሉ ፡ የውእቱ ፡ ርባ ፡ ነው ። አነና ፡ አንስ ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ስ ፡ አፍራሽና ፡ አጋ ፋኝ ፡ አዳማቂ ፡ ነው ፤ ማድነቅም ፡ ይኾናል ፡ የስን ፡ አ ፈታት ፡ ተመልከት ። እኔስ ፡ እኔሳ ፡ እኔማ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ እያሰኘ ፡ እንዳወራረዱ ፡ ይፈታል ፤ ስ ፡ ሲጨመርበት ፡ አ ንስ ፡ ቢል ፡ እንጂ ፡ አነስ ፡ አይልም ። **አንሰ ፡ አረማዊ ፡ እንዘ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ በስም ። ወአንሰ ፡ በጽድቅከ ፡ እሬኢ ፡ ገጸከ ። አንሰ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን ፡ አነ ፤** (ቅኔ ። መዝ ፡ ፲፯ ። ፴፱) ። አንቀጽ ፡ ሲኾን ፡ አፈታቱ ፡ እንደ ፡ ውእቱ ፡ ነው ፡ አነ ፤ ነኝ ፡ ኾንኹ ፡ አለኹ ፡ ነበርኹ ፡ ያሰ ኛል ፡ እንደ ፡ ውእቱም ፡ መረባቱ ፡ የውእቱ ፡ ዝርዝራ ፡ ብለ ፡ ኹን ፡ ነው ፤ የቀሩትም ፡ እስከ ፡ ንሕነ ፡ ያሉት ፡ እ ንደ ፡ አነ ፡ ናቸው ። ውእቱን ፡ እይ ።

**እን ፤** የማድረግና ፡ የመደረግ ፡ ልማድ ። አ ፡ የ ማእገዝ ፤ ን ፡ የዕብራይስጥ ፡ ነው ፤ የአ ፡ ጠባይ ፡ በመዠመ ሪያ ፡ ገጽ ፡ ተነግሯል ። ን ፡ በዕብራይስጥ ፡ እንደ ፡ ተ ፡ ኹና ፡ የመደረግ ፡ ልማድ ፡ ይባላል ። (ማስረጃ) ፡ በተገ ብሮ ፡ አንቀጽ ፡ **ተአስረ ፡ ተቀትለ ፡ ተጸልበ ፡ ሲል ፤ ኒቅ ሻር ፡ ኒቅጣል ፡ ኒጽላብ ፡** እንዲል ። አና ፡ ን ፡ በየራሳ ቸው ፡ ኹለት ፡ ልማዶች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚ ስት ፡ ገጥመው ፡ አንዱን ፡ ግስ ፡ በማድረግና ፡ በመደረግ ፡ በኹለት ፡ ጾታ ፡ ያስፈታሉ ። ግሱም ፡ ከደጊመ ፡ ቃል ፡ ግስ ፡ የሚደቀል ፡ ባላራት ፡ ፊደል ፡ ነው ፡ ይህም ፡ **በ ሊል ፡ በለ ፡ በልበለ ፡** ብሎ ፡ **አንበልበለ ፡** አንበገበገ ፡ ተ ንበገበገ ። (ጐድጐደ) ፡ **አንጐድጐደ ፤** አሰማ ፡ ተሰማ ። (ቀልቀለ ፡ ኵርኵረ) ፡ **አንቀልቀለ ፡ አንኵርኵረ ፤** አን ቀጠቀጠ ፡ አገለባበጠ ፤ ተንቀጠቀጠ ፡ ተገለባበጠ ፡ እያሰኘ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ርባ ፡ ትምር ፡ ፫ኛ ፡ ዕርከን ፡ ፴፱ ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት ።

**እን ፤** የአገባብ ፡ ልማድ ፤ የጥሬ ፡ ዘር ፡ ባዕድ ። ሌላ ፡ ፊደል ፡ አንድም ፡ ኹለትም ፡ ሦስትም ፡ ሲጨመ ርበት ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ አገባብ ፡ ይኾናል ፡ ብቻውን ፡ ግን ፡ ቃልነት ፡ የለውም ፤ አገባብነቱም ፡ በየፊደሉ ፡ ይለወጣል ፡ አገባቡና ፡ መለወጡም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተጣ ፈው ፡ ነው ።

**እንበይነ ፤—ስለ ፤—እን ፡ በይነ ።**

**እንበለ ፤—ያለ ፡ አለ ፤—እን ፡ በለ ።**

**እንጋ ፤—እንጃ ፤—እን ፡ ጋ ።**

**እንዳዒ ፤—እንጃ ፤—እን ፡ ዳዒ ።**

**እንዘ ፤—ሲ ፡ ሳ ፡ ስ ፤—እን ፡ ዘ ።** (ዕር ፲፱ ፡ ቍ፫፮) ።

**እንከ ፤ እንግዲህ ፤—እን ፡ ከ ።**

**እንቋዕ ፤—ዕሦ ፡ ዕሠይ ፤—እን ፡ ቋዕ ።**

**እንተ ፤—የ ፡ በ ፡ ወደ ፤—እን ፡ ተ ።** ባዕድ ፡ ዘር ፡ ሲኾን ፡ አን ፡ በገባበት ፡ ግስ ፤ አንገለገ ፡ እን ግልጋ ፡ ይሏል ። አን ፡ በሌለበትም ፡ ጐድዐ ፡ እንግድዓ ፡ እያለ ፡ ይገኛል ።

**ኢን ፤ (ዕብ ፡ ሂን) ፤** የልክ ፡ ስም ፡ ታናሽ ፡ ገንቦ ፤ የርጥብ ፡ መስፈሪያ ፡ መማሪያ ፡ ፲፪ ፡ ሉግ ፡ የም ቲገዝ ። ያንዱ ፡ ሉግ ፡ መጠን ፡ ፮ ፡ ዕንቍላል ፡ ይኾናል ፡ (ሕዝ፴፩ ፡ ፲፭) ።

**እንበዘ ፤—እስደራጊ ፡ አንቀጽ ፤—ነ ቢዝ ፡ ነበዘ ።**

**አንበሐብሐ ፤—አንቧቧ ፤—ነብሐ ።**

**አንበሕቀወ ፤—አፋሸገ ፤—በቀወ ።**

**አንበ(በ)ጣ ፤—በቁሙ ፤—ነበጠ ።**


**እንብየ ፤ እንቢ ፤ (ዕብ ፡ ኤን ፡ ቢ ፤ አል ብየ) ፤** ነባር ፡ አንቀጽ ፤ እንቢታና ፡ እሉታ ፤ እንቢዮ ፡ እንቢኝ ፤ በቁሙ ፡ እንቢ ፤ እሻፈረኝ ፤ አልሰማም ፡ አል ቀበልም ፤ አይኾንም ፤ አይኹን ። አበየና ፡ እንብየ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ አየና ፡ አከየ ፡ ሐሰና ፡ ሐሰወ ፡ አንድ ፡ እ ንደ ፡ ኾኑ ። **አሆ ፡ በልዎ ፡ ለእግዚ ፤ ወእንብየ ፡ በ ልዎ ፡ ለጋኔን ። እንብየ ፡ ኢይሰምዕ ፤** (ያዕ፬ ፡ ፯ ። ኢር ፳፪ ፡ ፳፭ ። ማቴ፳፭ ፡ ፳፱) ። እንቢክ ፤ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ ፤ እን ቢን ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ። **ይቤሉ ፡ እንቢከ ፤ ኢትበሉ ፡ አሆ ። እንቢክሙ ፡ ደቂ ቅየ ፤** (፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፳ ። ፳ ፡ ፪ ፡ ፳፱) ።

**እንብየ ፤** የሐዘን ፡ የጸጸት ፡ የቍጣ ፡ የብስጭት ፡ ቃል ፡ እንቢልኝ ፡ ወዲያልኝ ፤ ይብሳኝልኝ ። (ግጥም) ፡ እንቢልኝ ፡ ወዲያልኝ ፡ ሰው ፡ መኾን ፡ ሰለቸኝ ፤ ከሳይ ፡ ቤት ፡ አልሠራኹ ፡ በምድር ፡ አልተመቸኝ ።

**እንበይነ ፤—ስለ ፤—በይነ ።**

**እንበለ ፤ (እን ፡ በለ ። ዕብ ፡ ባል ፤ ብሊ) ፤** እን ፡ ተውሳከ ፡ ምልአተ ፡ ንባብ ፤ በለ ፡ አሉታ ። በትግርኛ ፡ ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ ይቂቅ ፡ አገባብ ፡ ነው ። እንጂ ፡ ሳ ፡ አለ ፡ ያለ ፡ ከ— በቀር ፡ ይኾናል ፡ !! ፡ እያደመቀው ፡ ሳያደምቀ ውም ፡ ብቻውን ፡ ይገባል ። አገባብነቱን ፡ ፲፱ኛ ፡ ዕርከን ፡ ፹፭ ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት ።

**እንቢልታ ፤ (ዕብ ፡ ሐሊል) ፤** በቁሙ ፤ ታ ላቅ ፡ ቀጭንት ፡ ውስጠ ፡ ክፍት ፤ ነጋሪታት ፡ መዳኒንት ፡



እንቢልታ ፡

ሲጓዙ ፡ ግብር ፡ ሲያገቡ ፡ ከመለከት ፡ ጋራ ፡ የሚያስንፉት ።

ከደጃዝማች ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሹም ፡ የማይሰንፋው ።

**አንበሳ ፤**—በቁሙ ፤—በሲስ ፡ በሰ ፤ በስ በሰ ፤ አንበስበሰ ።

**እን.ጋ ፤** (እን ፡ .ጋ) ፤ ንኡስ ፡ አገባብ) ፤ የጥያቄና ፡ የጥርጥር ፡ የአንክሮ ፡ ቃል ። እንጃ ፤ ይኸን ፤ እንከ ፡ ናሁ ፡ ይኸናል ፤ እፎ ፡ ሙኑ ፤ ሁ ፡ ኑ ፡ እየቀደሙለት ፡ ሳይቀድሙለትም ፡ ይገባል ። ናሁ ፡ መኸኑ ፡ መሳሶች ፡ በናሁ ፡ ፈንታ ፡ ስላገቡት ፡ እንጂ ፡ ፍችው ፡ ኹና ፡ አይደለም ። አገባቡንና ፡ ምስክሩን ፡ ፳፫ ፡ ዕርከን ፡ ፺፮ ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት ።

**አንገብ ፤** (ትግሬ) ፤ መቀመጫ ፡ ቂጥ ፤ ሙርጥ ፡ ፊንጥጣ ።

**አንጌቤን ፤** ወይዘር ፤ የወይዘሮ ፡ ልጅ ፤ በናቱ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚወለድ ፤ የንገሥታት ፡ ወገን ፤ ተቀማጭ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፤ ድልድል ፡ ቅምጥል ። ቂጣም ፡ ርጥጥ ፤ ዘፍጣጣ ፤ ቅምጥ ።

**አንጌቤናይ ፤** (ዊ ፡ ዪት ፡ ዊት) ፤ ወይዘሮማ ፤ ወይዘር ፤ የወይዛዝር ፡ ወገን ። ሕፃን ፡ ንኡስ ፡ አንጌቤናይ ፡ ወልደ ፡ አንጌቤናዊት ። ሶፍያ ፡ አንጌቤናይት ። አፎምያ ፡ ባዕልት ፡ ወአንጌቤናዊት ፡ (ድን ። ስንክ ፡ መስ፳፫ ። ግን፲፭ ። ሠኔ፲፪) ።

**አንጉግ ፤**—አርጃኖ ፤—ዐንጉግ ።

**አንጎገወ ፤**—ዘረ ፡ ባከነ ፤—ጎግዎ ፡ ጎገወ ።

**አንጌገየ ፤**—ዝኒ ፡ ከማሁ ፤—ጌግይ ፡ ጌገየ ።

**እንግዳ ፤**—በቁሙ ፤—ነገደ ።

**እንግድዓ ፤**—ደረት ፤—ጕዲዕ ፡ ጕድዐ ።

**እንግል.ጋ ፤**—ሽንኅ ፤—ገልኅ ፡ ገለገ ፤ አንገለገ ።

**አናጕንስጢስ ፤** (ሳን ። ጽር ፡ አናግኖስቲስ) ፤ አንባቢ ፤ የንፍቀ ፡ ዲያቆን ፡ ምክትል ።

**አናጕንስጢሳዊ ፤** (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። አናጕንስጢስ ፡ ዘውእቱ ፡ አንባቢ ። አናጕንስጢሳውያን ፡ ወመዘምራን ። አናጕንስጢሳዊት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፭ ፡ ፳ ። ቄስጠ ፡ ፶፫) ።

**አንጕዕ ፤**—አንጓ ፤—ንጕዕ ፡ ንጕዐ ።

**እንጕት ፤**—የሽቱ ፡ ቅጠል ፤— ዕንጕት ።

**አኒድ ፤ ዶት ፤** (አነደ ፡ የአንድ ፡ ይእንድ ። ዕብ ፡ ዐናድ) ፤ ማሰር ፡ ማጥበቅ ፤ አንድ ፡ ማድረግ ፤ ነደ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። መጠፈር ፤ መጕሰብ ፡ ቈርበት ፡ ማልበስ ፤ መደጕስ ፡ መሸለም ፡ ማስጌጥ ፤ የከበሮና ፡ የመጣፍ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። እሒድን ፡ ተመልከት ።

**አነዳ ፤** (ዳት) ፤ ቍርበት ፡ ቈዳ ፡ ዳባ ፤ ጠፍር ፤ ኸሩፍ ። አነዳ ፡ ላሕም ፡ ርጡብ ። አነዳ ፡ ዘመልዕልተ ፡ ሥጋነ ፡ ልብሰ ፡ ሐዘን ፡ ወሕማም ። ይኩን ፡ ልብሱ ፡ እምአነዳ ፡ ማእስ ፡ ዘእንስሳ ። በሐብለ ፡ አነዳ ፡ ተአስሩ ። ዘቀሠፈ ፡ አሐደ ፡ እምአግብርቲሁ ፡ በአነዳ ፡ አው ፡ በበትር ። እንዘ ፡ ይቀሥፍዎ ፡ በይቡስ ፡ አነዳ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፯ ። ስንክ ፡ መጋ፳) ።

**እንድ ፤** በቁሙ ፤ (ዐማርኛ) ፡ አንድ ፡ አይነድ ፡ አንድ ፡ አይፈርድ ፡ እንዲሉ ።

**እንደበራ ፤**—ዲቃላ ፤—ደቢር ፡ ደበረ ፤ ደብረወ ።

**እንዳዒ ፤**—እንጃ ፤—የዲዕ ፡ የድዐ ፤ አይድዐ ።

**እንድቅትዮን ፤** (ሮማይ ፡ ኢንዲክሲዎ) ፤ ተውሳክ ፡ ጭማሪ ፤ የተባለ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፤ ወይም ፡ ያልተባለ ፡ ስውር ። የተወሰነ ፡ ቀመር ፤ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ (አቡሻ) ። ባለመርሐ ፡ ዕውሮች ፡ ግን ፡ የንደቀ ፡ ጥሬ ፡ መስሏቸው ፡ ዕለተ ፡ ንድቀሙ ፡ ለፍጡራን ፤ ዕለተ ፡ ንድቁ ፡ ለአዳም ፡ ይሉታል ።

**እንደር ፤** (ብ ፡ አናዲር ። ትግሬ) ፤ ቀሽንት ፡ የእንቢልታ ፡ ዐይነት ።

**እንዘ ፤** (እን ፡ ዘ) ፤ ዐቢይ ፡ አገባብ ። ሲ ፡ ሳ ፡ ስ ፡ ቸልታ ፡ እየ ፡ ይኸናል ። እንዘ ፡ ይጼዕልዎ ፡ ኢጸዐለ ፤ ሲ ። እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘደይድኅን ፡ እንዘ ፡ ኢየሐጽጽ ፡ በላዕሉ ፡ ሳ ። እመኒ ፡ እንዘ ፡ ትነውም ፡ ወእመኒ ፡ እንዘ ፡ ትነቅህ ፡ ስ ። ረከቦሙ ፡ እንዘ ፡ ይነውሙ ፤ ቸልታ ። አንሶሰወ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ገሊላ ፡ እንዘ ፡ ይሰብክ ፡ በምኵራባቲሆሙ ፤ እየ ። እንዘ ፡ ከሀለወ ፡ በቀር ፡ በቀዳማይ ፡ አንቀጽ ፡ አይገባም ። እንዘ ፡ ሀሰዉ ፡ ኵሎሙ ፡ ኀብረ ፡ (ግብ፪ ፡ ፰) ። ዳግመኛም ፡ ፲፱ኛ ፡ ዕርከን ፡ ፸፰ ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት ።

**እንዝህሉል ፤**—አውታታ ፤—ዛህልሎ ፡ ዛህለለ ።

**እንኈ ፤**—አረዘመ ፤—ነዊኅ ፡ ኖኀ ።

**አንጦርጦስ ፤** (ጽር ። ዕብ ፡ አንጥሪ ፤ ታላቅ ፡ ዋሻ) ፤ የታች ፡ ታች ፡ መጨረሻ ፡ ታች ፤ ሲኦል ፡ ገሃነም ። በርባሮስን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ወቦ ፡ ዘወይቀ ፡ ውስተ ፡ አንጦርጦስ ፡ ዘውእቱ ፡ መትሕተ ፡ ታሕቲት ፡ (አዋል) ።

**እንከ ፤** (እን ፡ ከ) ፤ ንኡስ ፡ አገባብ ። እንኪያ ፡ እንኪያው ፤ እንግዲያው ፤ እንግዲህ ፤ ከዚያ ፡ ወዲያ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ። ስኬ ፡ ትራስ ፡ እየኾኑት ፡ ሳይኾኑትም ፡ በኋላና ፡ በፊት ፡ ይገባል ። አገባቡን ፡ ከነምስክሩ ፡ ፳፫ ፡ ዕርከን ፡ ፺፰ ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት ።

**እንከሐክሐ ፤**—ፈተፈተ ፤—ከሕክሐ ።

**አንጢዲቁ ፡ ማርያጦስ ፤** (ሮማይ ፡ አንቲዲክ ፡ ማሪያኒቴ) ፤ አዕፈረ ፡ ማርያም ፤ በማርያም ፡

ድንግልና ፡ ባይ ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ከፋ ፡ የሚያወሩ ፡ የሚናገሩ ። እሊሁም ፡ ባራተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሥጋዌ ፡ ከኒቅያ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ የተነሡ ፡ ናቸው ፤ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አንክዮን ፤ (ጽር ፡ አኒኪዮን)** ፤ ዕንቍ ፡ የዕንቍ ፡ ስም ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፳ ። ሕዝ፳፰ ፡ ፲፫) ።

**አናኵዕ ፤—ኵብኵብ ፤—ነክይ ፡ ነክየ ፤ ነክዐ ።**

**አንከረ ፤—አደነቀ ፤—ነኪር ፡ ነከረ ።**

**አንክሮጦስ ፤ (ጽር ፡ አግኪሮቶስ)** ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ኢጲፋንዮስ ፡ የጻፈው ። መልሕቅ ፡ መልሕቃዊ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ለሐቀን ፡ እይ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**አንኰርኰረ ፤—ገለበጠ ፤—ኰርኰረ ።**

**አንክሶ ፤ (ጽር ፡ አኒክስ ። ዕብ ፡ ሽሔሌት)** ፤ የሽቱ ፡ ቅጠል ፤ የባሕር ፡ ዛጕል ፡ መልኩም ፡ ሽታ ፡ ያለው ፤ እንደ ፡ ዕጣን ፡ እየደቀቁ ፡ የሚያጤሱት ። ወይም ፡ የሽቱ ፡ ዕቃ ፡ ባሕረ ፡ ወጥ ፡ የደንጊያ ፡ የሰደፍ ፡ የዛጕል ፡ ቢልቃጥ ። ባለብልቃጥ ፡ ግን ፡ ጥሩኝ ፡ ይሉታል ። ማርያም ፡ ድንግል ፡ ምዕዝተ ፡ ምግባር ፡ ዘእምአንክሶ ፡ (ደራሲ ። አርጋ ፡ ፫ ። ሚራ፳፱ ፡ ፲፭) ።

**አኒም ፤ ሞት ፤ (አነመ ፡ የአንም ፡ ይእንም ። ነዊም ፡ ኖመ ፤ አኖመ)** ፤ መዘርጋት ፤ ማጋደም ፤ ድሩን ፡ ዝሐውን ፤ በቁመት ፡ በጐን ፤ ማጕን ፡ ማራወን ፤ በወርድ ። መሥራት ፡ መታታት ፡ ማቈላለፍ ፡ መስፋት ፤ መጥለፍ ፤ የፈትል ፡ የልብስ ። ፈትሎ ፡ ማሬት ፤ ተአንመ ። የአንማ ፡ አንስት ። ይክል ፡ አኒመ ፡ ሜላት ። አኒም ፡ ወሰፍየ ፡ አልባስ ፡ (ኢሳ፶፱ ፡ ፭ ። ፱ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፯ ። ፪ዜና ፡ ፪ ፡ ፲፬ ። ፍን ፡ ፳፫) ።

**አናሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት ፤ አነምት)** ፤ የሚሠራ ፡ ሠሪ ፡ ሸማኔ ፡ ሰፊ ፤ ጠላፊ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ። ፩ዜና ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ። ፳ ፡ ፳) ። ከነ ፡ አናሜ ፡ አልባሳት ፡ ቀጠንት ፡ ወበንዱናት ፡ ክቡራት ። ወአናሚሁኒ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ ፲፱ ። ቅዳ ፡ ሕር) ።

**እንሞ** ፤ የልብስ ፡ የፈትል ፡ ሥራ ፡ ትት ፡ ስፌት ፡ ጥልፍ ፡ ዝምዝማት ፡ ዎንጉትጊ ፡ የእጅጊ ፤ ወይም ፡ በጭራሽ ፡ ሥረ ፡ ወጥ ። ወድማሬሁ ፡ እንሞ ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፴፱) ።


**ማእነም ፤ (ማት)** ፤ መሥሪያ ፡ መማሪያ ፤ የስፌ ፡ የጠላፊ ፡ የሸማኔ ፡ ዕቃ ። ግብረ ፡ ማእነም ። ይትአነም ፡ በማእነም ። ኬነውት ፡ ዘማእነም ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፬ ። ፳፰ ፡ ፲፯ ። ፴፯ ፡ ፳፩) ።

**ምእናም** ፤ መሥሪያ ፡ በታ ፤ የሸማኔ ፡ ጕድጓድ ፡ ዐርብ ። ግብረ ፡ ምእናም ። ማርያም ፡ ምእናም ፡ ግሩም ። ምእናም ፡ አንቲ ፡ ዘእምኔኪ ፡ ሰብሰ ፡ (አፈ ፡ ድ፱ ። ተረ ፡ ቄር፲፰ ። ቅዳ) ።

**አእነመ** ፤ አሠራ ፡ አሰፋ ፡ አስጠለፈ ። አእነመ ፡ ባዕሌሁ ፡ አምሳለ ፡ ኪሩቤል ፡ (፪ዜና ፡ ፫ ፡ ፲፬) ።

**ተአንመ** ፤ ተሠራ ፡ ተሰፋ ፡ ተጠለፈ ። ወሊተ ፡ ልበስ ፡ ልብሰ ፡ ዘተአንመ ፡ በፀምር ፡ ወበዐጌ ። ልብስ ፡ ዘኢተአንመ ፡ ወኲዳን ፡ ዘኢተፈትለ ፡ (ዘዳ፳፱ ፡ ፲፩ ። ዲድ ፡ ፩ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ።

**እኑም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ንምት)** ፤ የተሠራ ፡ ሥር ፤ ሥረ ፡ ወጥ ፤ ጥልፍ ፤ ዝምዝም ። ሜላት ፡ ዘእ



ምእናም ፡


ኑም ፡ በወርቅ ። እኑም ፡ ዘለንታሁ ። መንጦላዕት ፡ ዘሜላት ፡ እኑም ፡ በፈትለ ፡ ወርቅ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፳፫ ። ዮሴፍ ። ዘፀ፳፯ ፡ ፴፩) ።

**እንመት** ፤ መሥራት ፤ መሠራት ፡ አሠራር ፤ የልብስ ፡ ሥራ ። ልብስ ፡ ግሩም ፡ ዘቀጢን ፡ ፍትለቱ ፡ ወሠናይ ፡ እንመቱ ። እንመተ ፡ ማሬት ። ዘእምላዕሉ ፡ እንመቱ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ ። አፈ ፡ ተ፴፱ ። ቅዳ) ።

**አኒን ፤ አባለ ፡ ዘርዕ ፤—ዐኒን ።**

**አኒፍ ፤ ፎት ፤ አነፈ ፡ የአንፍ ፡ ይእንፍ ። ዕብ ፡ አናፍ ፤ ተቈጣ)** ። ማናፈት ፤ ባፍንጫ ፡ መሞከር ፤ እንፍ ፡ ማለት ፡ መናፈጥ ፡ አፍንጫን ፡ መንፋት ፡ መቀባበት ፤ የጠብ ፡ የቍጣ ። መንፈንፍ ፤ ነፍናፈ ፡ መኾን ። ማነፍነፍ ፡ ማሽተት ፤ መማግ ፤ የሽቱ ፡ የትንባኾ ።

**አንፍ ፤ (ዐረ ፡ አንፍ ። ዕብ ፡ አፍ)** ፤ አፍንጫ ፡ የአፍ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ፪ኛ ፤ አፈ ፡ ሕንጻ ፡ የራስ ፡ ቅል ፡ ደጃፍ ፤ ማሽተቻ ፤ ማንፋንፊያ ፡ ከምስቱ ፡ ሕዋሳት ፡ አንዱ ። (ማሕ፯ ፡ ፬ ፡ ፱ ። ኢሳ፴፯ ፡ ፳፱ ። መገ ፡ ፪፲፫) ። ለእመ ፡ ዐጸርከ ፡ አንፈከ ፡ (ምሳ፳፬ ፡ ፴፫) ።



አንፍ ፡

**እእናፍ ፤ (ፋት)** ፤ አፍንጫዎች ። አንፍ ፡ ተረተር ፡ መስሎ ፡ የወረደው ፤ በመካከል ፡ የተሰነደደው ፤ ተረተሩ ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፤ እእናፍ ፡ መከንቱ ፡ ብሱ ። ሰላም ፡ ለእእናፍኪ ፡ መሳክወ ፡ ሠናይ ፡ መፀዛ ። ይትመተሩ ፡ አእናፊሆሙ ። እስከ ፡ ይወፅእ ፡ እምውስተ ፡ እእናፊቲክሙ ፡ (ደራሲ ። ፍ ፡ ነ ፡ ሳ፰ ። ዘኍ፲፩ ፡ ፳) ።

**ማእነፍ ፡ (ብ ፡ መእንፍት)** ፡ የሥልስ ፡ ወሮት ፡ ጸሕስ ፡ ነጺን ፡ ወብርት ፡ ማነተመ ፡ ጎበስት ፡ ጎበስተ ፡ ገጽ ፡ የሚጋገርበት ። ሲጠጉን ፡ ወይም ፡ በሖጡን ፡ በርሱ ፡ እያደረጉ ፡ ከእቶን ፡ አግብተው ፡ ሲያወጡት ፡ ጎበስቱ ፡ ርሱን ፡ መስሎ ፡ የርሱን ፡ መልክ ፡ ንሥቶ ፡ ይወጣልና ፡ ጸሕሉን ፡ ማእነፍ ፡ ያሰኘው ፡ የጎበስቱና ፡ የሥልሱ ፡ ሽታ ፡ ነው ። **ወትግብር ፡ መኣንፍቲሃ** ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፳፱) ። ዳግመኛም ፡ መኣንፍት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መአፍንት ፡ ይላል ፡ መጋገሪያ ፡ ማለት ፡ ነው ። አፈየን ፡ ተመልከት ።

**አንጼዋ ፡—ዐይዋ ፡—ነጽየ ፡ ነጸየ ።**

**አንጻር ፡—በቁሙ ፡—ነጽሮ ፡ ነጸረ ።**

**አኒቅ ፡ ቆት ፡ (አነቀ ፡ የአንቅ ፡ ይእንቅ ። ዕብ ፡ አናቅ ። ሱር ፡ ኤናቅ)** ፡ መራመኽ ፡ ማናቀቅ ፡ መንሰቅሰቅ ፡ የልቅሶ ፡ የሞይንቅ ። መነጠቅ ፡ መመነጠቅ ፡ መቀማት ፡ መመንተፍ ።

**አንቁ ፡ (ብ ፡ እናቅይ)** ፡ ነጠቁ ፡ አሞሬ ፡ ሞይሳት ፡ ሞይልፊት ፡ ሲሳ ፡ ገዲ ፡ የደሮ ፡ ጠላት ። ሾተሌ ፡ አሞራ ፡ ጅብሬ ፡ የሚባል ፡ ምጡቅ ፡ ድምጡ ፡ ትልቅ ፡ ክንፉም ፡ ረዥም ፡ ውዥምዥም ፡ ጥላው ፡ ለሰው ፡ ለእንስሳ ፡ ደዌ ፡ የሚኾን ፡ ርጉዝ ፡ የሚያስወርድ ፡ የሚያስፌንግፍ ፡ ወፍራም ፡ የሚያቀጥን ፡ የሚያመነምን ፡ የሚያሰለስል ። ሾተላይ ፡ ጋኔን ፡ ሕፃናትን ፡ እንደ ፡ ሄሮድስ ፡ ሰይፍ ፡ የሚፈጅ ፡ የሴቶች ፡ በሽታ ። ሾተላይ ፡ መባሉን ፡ ከሾተል ፡ ወስዷል ፡ የግብር ፡ ስሙ ፡ ነው ። **ፍራህ ፡ ዐጋለ ፡ ዶርሆ ፡ ኑፋቄ ፡ እስመ ፡ በርእስከ ፡ ያወ ፡ መልእክ ፡ ሐሰት ፡ አንቁ ። አንቁ ፡ ብሂል ፡ ሽተላይ ፡ መናፍቅ** ፡ (ቅኔ ። ጥሬ ፡ ሰዋ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፱ ። ጥር፴ ። መጋ፳፪ ።

**አኒቆንጦን ፡ (ጽር ፡ አኒክንቶን)** ፡ ስሙ ፡ አህጉር ፡ በተራው ፡ ያሉ ፡ ከዳዊት ፡ በፊት ፡ ተወግተው ፡ ተዘርፈው ፡ የማያውቁ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፯ ፡ ፳ ፡ ፴) ።

**እንቋዕ ፡ (እን ፡ ቋዕ ። ዕብ ፡ ሄእሕ ። ዐረ ፡ ሀይ)** ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ። የደስታ ፡ ቃል ፡ እንኳ ፡ እንኳዕ ፡ ዕሠ ፡ ዕሠይ ፡ ወሰው ፡ ውሽን ፡ ይበል ። **እንቋዕ ፡ ተሰብረት ፡ ማዕጾ ፡ አሕዛብ ። እስ ፡ ይብሉኒ ፡ እንቋዕ ፡ እንቋዕ ፡** (ሕዝ፳፮ ፡ ፪ ። ፴፮ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፴፱ ። ፴፱) ። ስንኳንና ፡ እንኳን ፡ ልዩ ፡ ልዩዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ እንኳስም ፡ ከነዚህ ፡ ልዩ ፡ ነው ። ስንኳን ፡ የማላላቅና ፡ የማበላለጥ ፡ ነው ፡ እንኳን ፡ ግን ፡ የማዋረድና ፡ የማሳነስ ፡ ያሉታና ፡ የነቀፌታ ፡ ነው ። ወ ፡ ሂ ፡ ኒ ፡ ጥቀን ፡ አኮን ፡ ተመልከት ።

**አንቀጽ ፡—በር ፡ ደጅ ፡ አፍ ፡—ነቂጽ ፡ ነቀጸ ፡ አንቀጸ ።**

**አንቆቅሖ ፡—ዕንቍላል ፡—ቆቅሕ ፡ ቆቅሐ ።**

**አንቀር ፡—አንቃር ፡—ነቀኍር ፡ ነቈረ ፡ አንቈረ ።**

**እንቈራ ፡—የንብ ፡ እንጀራ ፡—ነቈረ ።**

**እንቆራ ፡ (ጽር ፡ አንክራ)** ፡ ስሙ ፡ ሀገር ። **ቴዎዶጦስ ፡ ዘእንቆራ** ፡ (ተረ ፡ ቄርሎ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**እንቃስ ፡—ዐዘብ ፡ ሞይቃ ፡—ነቂስ ፡ ነቀሰ ።**

**አኒስ ፡ ሶት ፡ (አነሰ ፡ የአንስ ፡ ይእንስ)** ፡ ሰው ፡ መኾን ፡ እክል ፡ መግዛት ፡ እንደ ፡ አዳምና ፡ እንደ ፡ ሔዋን ፡ ወንድ ፡ ተባት ፡ ሴት ፡ እንስት ፡ ኾኖ ፡ መፈጠር ፡ መገኘት ። መፀነስ ፡ መወለድ ። ዳግመኛም ፡ በቁሙ ፡ ማነስ ፡ ታናሽ ፡ መኾን ፡ (ዐማርኛ) ። ማን ፡ ከማን ፡ አንሶ ፡ እንዲሉ ። ንእሰንና ፡ ሰንአን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ አግዋር ፡ ናቸው ።

**እኑስ ፡ (ሳን ፡ ሳት ፡ ንስት)** ፡ ያነሰ ፡ ንኡስ ፡ ተከታይ ።

**አንስ ፡ (ትግሬ ፡ እናስ ። ዕብ ፡ ኤኖሽ ። ዐረ ፡ ኢንሳን)** ፡ ሰው ፡ ወንድ ፡ ተባት ፡ ጕልማሳ ። አነ ፡ አንስ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡ አነን ፡ ተመልከት ።

**አእኑስ ፡ (ዕብ ፡ እናሽም)** ፡ ሰዎች ፡ ወንዶች ፡ ተባቶች ። የማእገዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ አንስ ፡ አእኑስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተባዕት ፡ ስብእ ፡ ዕደው ፡ ይላል ። ዳግመኛም ፡ አንስት ፡ ብሎ ፡ ብዥውን ፡ አእንስት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መልሶ ፡ አንስት ፡ አንስትያ ፡ አእኑስ ፡ ይላል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ። **ተባዕተ ፡ ወአንስተ ፡ ፈጠሮሙ ። አልቦ ፡ ተባዕት ፡ ወአልቦ ፡ አንስት ። ኢየሐየዉ ፡ ኢተባዕተ ፡ ወኢአንስተ ። ሜጡ ፡ ለተባዕት ፡ ኀምሳ ፡ ወለአንስትሰ ፡ ሜጣ ፡ ሠላሳ ። አፍራስ ፡ አንስት ። ቡርክት ፡ እምአእኑስ ። አፍራስ ፡ አእኑስ ። አእዱግ ፡ አእኑስ ፡** (ዘፍ፳፩ ፡ ፳፯ ። ገላ፫ ፡ ፳፰ ። ፩ነገ ፡ ፳፯ ፡ ፱ ። ዘሌ፳፯ ፡ ፫ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፳፯ ። ዮሐብ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፳፭ ። ኢዮ፳ ፡ ፫ ፡ ፲፱) ። አእኑስ ፡ የአንስ ፡ ብዥ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ።

**አንስት** ፡ ሴት ፡ ሔዋናዊት ፡ ኹለተኛ ፡ ዐይነት ፡ ሰው ፡ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ያላት ፡ ብእሲት ፡ ማለት ፡ ሲሆን ፡ ፈር ፡ አንስ ፡ ወአንስት ፡ አእኑስ ፡ ወአእንስት ፡ ወይም ፡ ዕድ ፡ ወአንስት ፡ ዕደው ፡ ወአእንስት ፡ ያሰኛል ። የማእገዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመጻፎች ፡ ስሕተት ፡ አንስትን ፡ እንደ ፡ ፀርና ፡ እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሳንድም ፡ ሰብዞም ፡ ያደርጋል ፡ በአእኑስ ፡ ፍች ፡ እንደ ፡ ተነገረ ። **ዘይትመሰሎ ፡ እምአንስት ። ኢተንሥአ ፡ እምትውልደ ፡ አንስት ። ብእሲ ፡ ወአንስት ። ዕድ ፡ ወአንስት ። ወእመሰ ፡ አልብከ ፡ ብእሲት ፡ ኢትፍቅድ ፡ አንስተ** ፡ ሴት ፡ (ሚራ፲ ፡ ፲፰ ። ማቴ፲፩ ፡ ፲፩ ። ኪዳ ። ቅዳ ። ፩ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፳፯) ። **ጠባባት ፡ አንስት ፡ ሐነጻ ፡ አብያተ ። አንስት ፡ ምእባውያት ። ይበልዓኑ ፡ አንስት ፡ ፍሬ ፡ ከርሦን ። ወይእኀዛሁ ፡ ሰብዑ ፡ አንስት ። አንትንሂ ፡ አንስት ። ወአንስትኒ ፡ ይበክያሁ** ፡ ሴቶች ፡ (ምሳ፲፬ ፡ ፩ ። ሩት፩ ፡ ፱ ። ሰቈ፪ ፡ ፳ ። ኢሳ፬ ፡ ፩ ። ሕዝ ፡ ፪ ፡ ፩ ። ሉቃ፳፫ ፡ ፳፯) ።

የቀረውን ፡ ፳፫ ፡ ክፍል ፤ በባቢና ፡ በታሳቢ ፡ አርእስት ፡ ተመልከት ።

**እንስቲያ ፤ አንስትያ ፤ (ያት ። ዕብ ፡ ና ሽም ፤ ንሺይ)** ፤ ሴቶች ፤ ሚስቶች ። ያ ፡ መጨመሩ ፡ ለማብዛትና ፡ ለማዘረፍ ፡ ለመዘርዘር ፡ ነው ፤ አንስትያ ፡ ብዙ ፤ ያት ፡ የብዙ ፡ ብዙ ። ደቂቅየ ፡ ወአንስቲያየ ። ሰብዐቱ ፡ ምእት ፡ አንስትያሁ ፡ ለሰሎሞን ። ወአንስቲያሆሙ ፡ ትደጋ ፡ ፍጥረቶን ። ዕደውኒ ፡ ያፍቅሩ ፡ አንስቲያሆሙ ፡ (ዘፍ፴፩ ፡ ፶፰ ። ፩ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፫ ። ሮሜ፩ ፡ ፳፮ ። ኤፌ፭ ፡ ፳፭) ።

**እንስቃይ ፤ ዊ** ፤ ሴታም ፡ ባለሴት ፤ ሴት ፡ ወዳጅ ፤ ሴት ፡ እውል ፤ ጠባቂ ፡ ጕማዳ ፤ ስልብ ፡ ጃን ፡ ደረብ ። ሴትማ ፡ የሴት ፡ ዐይነት ፤ ፈናፍንት ፤ ወንዳገሬድ ። ፈሪ ፡ ወንድ ፤ ጕጋ ፡ እንበልጋ ።

**እንስቲ(ት)ያዊት** ፤ የሴቶች ፡ ወገን ፡ ሴት ፡ እንስት ፡ የተባት ፡ ጓደኛ ፡ ኹለተኛ ፡ (ሔኖ፲፱ ፡ ፰ ። ፰ ፡ ፯ ። ቭ፳፩ ፡ ፫) ።

**እንስት ፤ (ታት)** ፤ ገዝ ፡ ከማሁ ፡ በቁሙ ፤ ሴት ። አንስትና ፡ ብእሲት ፡ ለሰው ፡ ፍጥረት ፡ ብቻ ፤ እንስት ፡ ለሰውም ፡ ለእንስሳም ፡ ለሣር ፡ ለንፌጽ ፡ ሳይቀር ፡ ለፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ፤ መጠኑ ፡ ግን ፡ በእንስት ፡ ፈንታ ፡ ኹሉን ፡ እንስት ፡ ይላል ። ተባዕተ ፡ ወአንስተ ፡ ገብረ ፡ እግዚ ። ወእምነ ፡ ዙሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ታበውእ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ፡ በበ ፡ ክልኤቱ ፡ ተባዕተ ፡ ወአንስተ ፡ (ማር፲ ፡ ፮ ። ዘፍ፯ ፡ ፲፱ ፡ ፰ ። ፯ ፡ ፪ ፡ ፫) ።

**አንሶጠጠ ፤—አሰቀጠጠ ፤—ሠዊጥ ፡ ሦጠ ።**

**እንሰይ ፤ (ዐረ ፡ እንሲ)** ፤ ጻግሜ ፤ የንሐሴ ፡ ማፍ ፡ ተቀጥላ ። እንሰይ ፡ ዘውእቱ ፡ ሰዋሕቅ ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ።

**እንስሳ ፤—በቁሙ ፤—ሰስዎ ፡ ሰሰወ ፤ አንሰሰወ ።**

**አንተ ፤ (ቲ ፡ ትሙ ፡ ትን)** ፤ በቁሙ ፤ የአን ፡ ርባታ ፤ የቅርብ ፡ ወንድ ፤ በቂና ፡ ቅጽል ፤ ነባር ፡ አንቀጽ ፤ ንኽ ። የአንን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ፤ መሬው ፡ ርሱ ፡ ነው ። አንተ ፡ ትቤ ። አንቲኒ ፡ ዓዲ ፡ እምሰአልኪዮ ። አንትሙ ፡ ትሰግዱ ፡ ለዘኢተአምሩ ። ኢትፍርሃ ፡ አንትንሰ ፤ በቂ ፡ (ማቴ፳፰ ፡ ፭፭ ። ፭፮ ፡ ፭ ። ዮሐ፬ ፡ ፲ ፡ ፳፪) ። አንተ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ። ወአንቲኒ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ። አንትሙ ፡ ዕደው ። አንትን ፡ አንስት ፤ ቅጽል ፡ (ሕዝ፪ ፡ ፫ ። ማቴ፪ ፡ ፮ ። ሰኤ ፡ ፫ ። ሰ ፡ ፯) ። ዕራቅከ ፡ አንተ ። አንቲ ፡ መኑ ፡ አንቲ ። አንትሙ ፡ ኢሰባውያን ፡ አንትሙ ። አንትንሰ ፡ ጠባባት ፡ አንትን ፤ አንቀጽ ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፲፩ ። ዮዲ፲ ፡ ፲፪ ። ማቴ፲፭ ፡ ፲፯ ። ዘረፋ) ። ደቂቅ ፡ ርባታ ፡ ፲፭፫ ፡ ዕርከን ፡ ቋ፱ቀ ። ደቂቅ ፡ ቅጽል ፡ ፻፲፰ ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት ።

**እንተ ፤ (እን ፡ ተ ፡ ዘ)** ፤ ዐቢይ ፡ አገባብ ። የሴት ፡ ቅጽል ፤ የ ፡ ቅጽልነቱም ፡ ሳንድ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ዘ ፡ ላንድም ፡ ለብዙም ፡ አይኾንም ። ሀገር ፡ እንተ ፡ ተሐንጸት ፡ መልዕልተ ፡ ደብር ። ደብተራ ፡ እንተ ፡ ኢገብራ ፡ እደ ፡ ሰብእ ። ድንግል ፡ እንተ ፡ ተፍኅረት ፡ ለብእሲ ፡ (ማቴ፭ ፡ ፲፬ ። ዕብ፱ ፡ ፲፩ ። ሉቃ፩ ፡ ፳፯) ። እንቲአየ ፡ ከ ፡ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ ፤ እንቲአን ፡ እያለ ፡ እስከሥር ፡ ይረባል ። እም ፡ ብሎ ፡ እናት ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**እንተ** ፤ ደቂቅ ፡ አገባብ ። ብ ፡ ወደ ፡ ለ ፡ ን ፡ አዳማቂ ፡ እየ ፡ ደጊመ ፡ ቃል ። ኅለፉ ፡ እንተ ፡ የብስ ። ሖሩ ፡ እንተ ፡ እግር ። ይበውኡ ፡ እንተ ፡ መስኮት ፤ በ ፡ (ዘፀ፲፭ ፡ ፲፱ ። ማር፯ ፡ ፴፫ ። ዮኤ፪ ፡ ፱) ። ሖረት ፡ እንተ ፡ አውሎና ፡ ርቱዐ ። ሮጸ ፡ እንተ ፡ መርሕበ ፡ ሀገር ። ንሑር ፡ እንተ ፡ የማን ፡ አው ፡ እንተ ፡ ፀጋም ፤ ወደ ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፲፭ ። አስቴ፭ ፡ ፩ ። ዘረፋ) ። ለና ፡ ን ፡ ሲኾን ፡ በባሕቲት ፡ ይገባል ። እንተ ፡ ባሕቲቱ ፡ ብቻውን ፡ ለብቻው ፡ (ማቴ፲፬ ፡ ፲፫ ። ፳፫ ። ዮሐ፳ ፡ ፯) ። እንተ ፡ ሰበ ፡ ጸዋዕከዎ ፡ ለእግዚ ። እንተ ፡ ጊዜ ፡ ተንሥአ ፡ ሰብእ ። ዘእንበለ ፡ ይቅረብዋ ፡ እንተ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ፤ አዳማቂ ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። ፻፳፫ ። ጦቢ፫ ፡ ፰) ። እየና ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ ሲኾን ፡ በጊዜ ፡ ይገባል ፤ እንተ ፡ ጽባሕ ፤ እንተ ፡ ጽብሐት ፡ ይላል ፤ ጸብሐን ፡ ተመልከት ። ደቂቅንቱንም ፡ ባቢይ ፡ አገባብ ፡ ውስጥ ፡ ፸ቀ ፡ ተመልከት ።

**በእንተ** ፤ ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ። ስለ ፡ በ ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ ቃሰ ፡ ስኢል ፤ ደስ ፡ አይበለው ፡ ብሎ ፤ ደስ ፡ አይበለው ፡ ሲል ፡ ይኾናል ። በንባቡና ፡ በአርእስት ፡ በስም ፡ በግብር ፡ በቦታ ፡ ይገባል ፤ በንባቡ ፡ አንቀጽ ፡ ሲገባ ፡ ዘን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ያደርጋል ። በእንተ ፡ ዘተወልደ ፡ እምኔሃ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ፤ በእንቲአየ ፡ ክ ፡ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ ፡ ን ፡ እያለ ፡ ይዘረዘራል ። አገባብንቱ ፡ ለክፉም ፡ ለበጎም ፡ ይኾናል ፤ ለክፉ ፡ ሲኾን ፡ በ ፡ ላይ ፡ ለበጎ ፡ ሲኾን ፡ ስለ ፡ ይኾውም ፡ ራእይ ፡ ዘርእየ ፡ በእንተ ፡ ይሁዳ ፡ ወበእንተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፩) ። በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ሕፃን ። ወበእንተሰ ፡ ይእቲ ፡ ዕለት ፤ ነገር ፡ (ማቴ፪ ፡ ፰ ። ፳፬ ፡ ፴፮) ። ይፀርፉ ፡ በእንቲአክሙ ። ይቀትሉክሙ ፡ በእንቲአየ ፤ ምክንያት ። በእንተ ፡ ማርያም ፡ ወላዲትከ ፤ ልመና ፡ መሐላና ፡ ምጥንታ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ በ ፡ ይኾናል ። በእንተ ፡ ጸላኢ ፤ ደስ ፡ አይበለው ፡ ብሎ ፤ ሲል ። አርእስት ፡ ሲኾን ፡ በረኽርም ፡ ባጭርም ፡ ቃል ፤ በምዕራፍ ፡ በክፍል ፤ በተለየ ፡ አንቀጽ ፤ በድርሳን ፡ በተግሣጽ ፡ ይገባል ። በእንተ ፡ በብአ ፡ በገል ። በእንተ ፡ እለ ፡ ተቀትሉ ፡ ሕፃናት ። በእንተ ፡ ትምህርተ ፡ ኅቡኣት ። አንቀጽ ፡ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ቤተ ፡ ክር ። ድርሳን ፡ በእንተ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ። ተግሣጽ ፡ በእንተ ፡ ከመ ፡ ኢመፍትው ፡ ይቅበጹ ፡ ቀስፋ ፡ (ማቴ ። ኪዳ ። ፍ ፡ ን ። ቄር ። አፈ ፡ ተ ፡ ፱) ። በድርድር ፡ ሲገባ ፤ በእንተ ፡ ኅጢአት ፤ ወበእንተ ፡ ጽድቅ ፤ ወበእንተ ፡ ኰነኔ ፡ ይላል ፡ (ዮሐ፲፮ ፡ ፰—፲፩) ። ሲዘረዘር ፡ ደግሞ ፡ በበቂንት ፡ በቅጽልነት ፡ ይፈታል ፤ ዘበእንቲአሁ ፡ ቀብዐኒ ፤ በርሱ ፡ ቅብንት ።

ዘበእንቲኣሁ ፡ ተመራሕነ ፤ በርሱ ፡ መሪነት ፡ መምር
ነት ፡ ኢያሰኝ ፡ ሊላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። የቀረ ፡ ቢኖር ፡
አገባብ ፡ ተመልከት ።

**እንትኩ** ፤ (ዝኩ) ፤ እንተ ፡ ከሃ ፡ የሩቅ ፡ ሴት ፡
ፀጸፋና ፡ ቅጽል ፡ ያች ፤ ያችው ፤ ያችኛይቱ ፤ ያችኛዋ ።
እንትኩ ፡ ዕፀ ፡ ዘውስተ ፡ ገነት ። እንትኩ ፡ ጣዕዋ ፡
አንስት ያዊት ፡ (ቅዳ ፡ አት ። ሒኖ ፡ ፳፯) ። ገቢር ፡ ሲኾን ፡
በገዝኩ ፡ አንጻር ፡ እንትኩ ፡ ይላል ።

**እንታክቲ** ፤ (ዝክቱ) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። እን
ታክቲ ፡ ዕጕሊት ፡ ቀደማዊት ። እስመ ፡ ዛቲ ፡ ትትወ
ለድ ፡ እምእንታክቲ ። ለእንታክቲ ፡ ሌሊት ፡ አእመ
ርዋ ፡ (ሔዋ ። ማር ፡ ይሥሸ ። ጥበ፲፰ ፡ ፯) ።

**አንቲክ** ፤ (ዐረብ) ፤ በቁሙ ፤ አንተ ፡ ከሃ ፡
የዱሮ ፡ የቀድሞ ፤ የጥንት ፤ ብዙ ፡ ዓመት ፡ የኖረ ፡ አሮጌ ፤
ብሉይ ።

**አንተለ** ፤ (አቲል ፡ አተለ ። ዕብ ፡ ዓ
ጼል ። ሱር ፡ ዐጤል ። ዐረ ፡ ዐጠለ) ፤ ሰነፈ ፤
ታከተ ፤ በዛን ። አታለ ፡ አታላ ፡ ኾነ ። ጠላ ፤ ሰለቸ ፤ ተሰ
ቀቀ ፤ ናቀ ፡ አቃለለ ፤ ተወ ፡ ቸለ ፡ አለ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡
በአንተለ ፡ ፈንታ ፡ ተአንተለ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ኢተ
እንቲለት ፡ ሎቱ ፡ ነፍሱ ። ከመ ፡ ኢይትአንተሉ ፡ ወኢ
ይሰሉ ፡ ከብደነ ። ጸምአ ፡ ወኢተአንተለ ፤ ኢይኩን ፡
ምዩጠ ፡ ገጽ ፡ እምስእለትየ ፤ እንዘ ፡ ይትአንተል ፡
በእንተ ፡ ኅጣውእየ ። አንጐርጐሩ ፡ ወተአንተሉ ።
ኢትትአንተል ፡ ተግሣጸ ፡ እግዚ ። ያፈጥን ፡ ሰረድኤ
ትየ ፤ ወኢይትአንተሉ ። በእብድ ፡ ወበተአንትሎ ፤
(ኩፉ ፡ ፲፯ ። ቀሌ ። አርጋ ፡ ፬ ። ጥበ፲፪ ፡ ፳፯ ። ምሳ፫ ፡
፲፩ ። ዮሴፍ ። ማር ፡ ፯ ፡ ፱) ።

**እንታሊ** ፤ መእንትል ፤ ታካታ ፡ ሰነፍ ፡ ቸ
ልተኛ ፡ ስልቹ ።

**ተአንተለ** ፤ ተጠላ ፡ ተሰለቸ ፡ ቸለ ፡ ተባለ ።

**እንታሌ** ፤ ቸልታ ፡ ስልቹነት ፡ ስንፍና ፡ በዛን ።

**እንተላም** ፤ (ትግሬኛ) ፤ ታላቅ ፡ መስፈሪያ ፡
፴፪ ፡ ከዕበ ፡ የሚይዝ ። አንዱ ፡ ከዕበ ፡ ፰ ፡ ከፋሎ ፡ ወ
ይም ፡ ፰ ፡ ምኒልክ ፡ (አዋል) ። ይኸውም ፡ የምኒልክ ፡
መልክ ፡ የተማለበት ፡ ዋንጫ ፡ ኰባያ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**እንጳጴ** ፤ እንጳንጴ ፤ (ዕብ ፡ አባዕቡዓ) ፤
የገላ ፡ የቁርበት ፡ በሽታ ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፤ ሰበጥ ፡ ዕከክ ፡ ፈ
ንጣጣ ፡ ቍስል ፡ መግል ፡ የያዘ ፡ ያረገዘ ። ጸውብ ፡ ወእ
ንጳንጴ ፡ (ኢዮ፻ ፡ ፳ ። ኩፉ ፡ ፲፱) ።

**አሠረ** ፤ (ትግሬ) ፤ ተከተለ ፡ ተከትሎ ፡ ኼደ ፡
ሻ ፡ ፈለገ ።

**አሠር** ፤ ራት ፤ (ዐረብ ፡ ኢሸር ፡ አሰር ።
ሱር ፡ አትራ ። ዕብ ፡ አሹር) ፤ ፍለጋ ፡ ዱካ ፡ ርጋጭ ፡
መከየድ ፡ መንገድ ፡ ጥርጊያ ፡ ጐዳና ፤ ርምጃ ፡ አኳኼድ ፡
አብነት ። ደምሰሰ ፡ አሠርየ ፤ አሠረ ፡ ምንት ፡ ዝንቱ ።
እሬኢ ፡ አሠረ ፡ ዕደው ፡ ወአንስት ። እደ ፡ ኬደ ፡
አሠረ ፡ ውሉደ ፡ ሰብእ ። ንሑር ፡ በአሠሩ ። አሠር ፡
ንጹሕ ፡ ዘአልቦ ፡ አሥዋክ ። ወየኀድግ ፡ ውስተ ፡ ፍ
ኖት ፡ አሠሮ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፲፫ ። ዳን፲፫ ፡ ፲፱ ፡ ፰ ። ኩፉ ፡
፴፪ ። ማኅ፬ ፡ ፪ ። ቅዳ ፡ ኢጲ ። መገ ፡ ፹፬) ።

—፤ ምልክት ፡ ጠንከ ፤ ዕትራት ፡ ጠባሳ ፡ ጐዳኒሳ ፡ ፀታ ፡
ስፍራ ። አሠሩ ፡ ለልብ ፡ ፍሡሕ ፡ ገጽ ፡ ብሩህ ። አ
ሠረ ፡ ደም ። አሠረ ፡ ደዊ ። አሠረ ፡ ቅንዋት ፡ ወአ
ሠረ ፡ ርግዘት ። አሠራት ፡ አምላካውያት ፤ መክናት ፡
(ሢራ፲፫ ፡ ፳፯ ። ስንክ ፡ መስ፫ ። ሐምጅ፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱) ።

**አሠረ ፡ ንጉሥ** ፤ የቅኔ ፡ ስም ፡ ለንጉሥ ፡ የሚ
ሰጥ ፡ የዕጣን ፡ ጥገር ፡ ተቀጥላ ።

(ጥ) **አሠረ ፤—ቀጠረ ፤ ከሥር ፡ አንድ ፡ አ
ወጣ ፤—ዐሥሮ ፡ ዐሠረ ።**

(ሳ) **አሠረ ፤—በቁሙ ፤—አሰረ ፡ አሰረ ።
አሥራግ ፤—መስኖች ፤—ሠርግ ፡ ሠ
ረገ ።**

**አፍ ፤ አፍአ ፤—በቁሙ ፤—አፈወ ።**

**ኢፍ ፤ ኤፍ ፤ (ዕብ ፡ ኤፋ)** ፤ የመስፈሪያ ፡
ስም ፤ ታላቅ ፡ ቍና ፡ ቤዶ ፤ ላዳን ፤ የሐሜር ፡ ዐሥረኛ ።
አንዱ ፡ ኢፍ ፡ ፫ ፡ ስአ ፡ ይይዛል ፤ ስአ ፡ እንደ ፡ መሸመቻ ፡
ያለች ፡ ታናሽ ፡ ቍና ፡ ናት ፤ መሥለሰን ፡ እይ ። መስፈ
ርት ፡ ኢፍ ፡ (ዘሌ፭ ፡ ፲፩ ። ዘኍ፭ ፡ ፲፭ ። ሩት፪ ፡ ፲፯ ።
ሕዝ፵፭ ፡ ፲) ።

**አፌድ ፤ (አፈደ ። ዕብ ፡ አፉድ)** ፤ መታ
ጠቅ ፡ መልበስ ፤ ማሸረጥ ፡ ማሸነቀጥ ።

**ኤፉድ ፤ (ጽር ፡ ሄፉድ ። ዕብ ፡ ኤፉድ)** ፤
ልብስ ፡ ተክህኖ ፡ ክህናት ፡ አረት ፡ በተልእኮ ፡ ጊዜ ፡ የሚ
ለብሱት ፡ የሚታጠቁት ፤ ቀሚስ ። ልብሰ ፡ እንግድዓ ፡ ሴ
ደርያ ፡ (ዘፀ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ፡ ፳፰ ፡ ፲፬ ፡ ፫ ። ፴ ፡ ፮ ። ዘፀ
፳፰ ፡ ፬) ። ኤፉደ ፡ ጸሎት ፡ ወዕጣን ፡ (ጥበ፲፰ ፡ ፳፩) ።

— ፤ ፈዶ ፡ ማጠቅ ፡ ዐጭር ፡ ሱሪ ፡ ቍምጣ ፡ ቁረጣ ፤ የ
ሥራ ፡ ልብስ ፤ ማናቸውም ።

**አፈው ፤ ዎት ፤ (አፈወ ፡ የአፉ ፡ ይአፉ ።
አፈየ ። አፈፈ)** ፤ መተንፈስ ፤ እፍ ፡ እፎይ ፡ ማለት ፡
መናገር ፤ አፍን ፡ መልቀቅ ፡ መክፈት ፡ ማፋሸግ ፡ ማዛ
ጋት ። ንፍኀንና ፡ ንፍስን ፡ በቀወን ፡ ተመልከት ።

**አፋዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ የሚተነፍስ ፡
አፈኛ ፡ አፉም ፡ ለፍላፊ ፡ አፈ ፡ ስፌ ። ወንን ፡ ቅጽል ፡ ሲ
ኾን ፡ የአፍ ፡ ያሰኛል ።

**አፍ ፤ (ብ ፡ አፈው ፡ ዋት ። ዕብ ፡ ፌህ ።
ዐረ ፡ ፋህ ፤ ፉህ ፤ ፊህ ፤ ፈም ፤ ፉም ። ሱር ፡ ፉማ)** ፤
በቁሙ ፤ በከንፈርና ፡ በከንፈር ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ክፍት ፡
ጎዋ ፡ መተንፈሻና ፡ መናገሪያ ፡ የቃል ፡ የትንፋሽ ፡ የመ
ብል ፡ የመጠጥ ፡ የነገር ፡ ኹሉ ፡ መውጫ ፡ መግቢያ ፡ ደጅ ፡
የሚከፈትና ፡ የሚዘጋ ፡ የሕዋሳት ፡ በር ። አፍ ፡ አንድ ፡
አፈው ፡ አፎት ፡ ኹለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ አፈዋት ፡ የብዙ ፡

ብዙ ። አፋየ ፡ ክ ፡ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ ፡ አፋን ፡ ከሙ ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ፤ ለታተመ ፡ ለተመረገ ፡ ለጕድጓድ ፡ ለመቃብር ፡ ሳይቀር ፡ አፍ ፡ ሳለው ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። እምተረፈ ፡ ልብ ፡ ይነብብ ፡ አፍ ። ይትናገሮ ፡ አፈ ፡ በአፍ ። ያበቍ ፡ አፉሁ ፡ እስከ ፡ እዝኒሁ ። ይወድስከ ፡ አፈ ፡ ነኪር ፡ ወአኮ ፡ አፈ ፡ ዚአከ ። ተፈፀመ ፡ አፈ ፡ ኵሉ ፡ አራዊት ። አፍ ፡ ቦሙ ፡ ወኢይነቡ ፤ ወአልቦ ፡ መንፈስ ፡ ውስቴቱ ፡ አፉሆሙ ። አፈወ ፡ አንቅዕት ፡ ቀላይ ፡ ዐቢይ ፤ በሰብዑ ፡ አፈው ፤ አፈወ ፡ ማዕምቅት ፡ ምድር ። አፈዋት ፡ አፎች ፡ (ማቴ፳፱ ፡ ፴፬ ። ኤር፴፱ ፡ ፬ ። ሚሬ፳፩ ፡ ፭ ። ፳፯ ፡ ፱ ። ኩፋ ፡ ፫ ። መገ ፡ ፻፴፬ ፡ ኩፋ ፡ ፭ ። ገድ ፡ ተክ) ።

— ፤ ቃል ፤ ነገር ። ትርጁማን ፤ አምሻር ፡ ጠበቃ ፡ ወኪል ፡ የነገር ፡ አባት ። በአፈ ፡ ክልኤቱ ፡ ወሠለስቱ ፡ ሰማዕት ። ኵሉ ፡ ይቀም ፡ በአፈ ፡ ዚአሆሙ ። እምአፈ ፡ ፀሠርቱ ፡ ወንምስቱ ፡ ነቢያት ፤ እምአፈ ፡ ፀሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ሐዋርያት ፤ እምአፈ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ቃል ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፲፮ ። ቀሌ ። ቅዳ) ። ይኩንከ ፡ አፈ ። ትከውን ፡ ከመ ፡ አፉየ ፤ (ባፌ ፡ አፈ ፡ ንጉሥ) ። ወኮነ ፡ አፈ ፡ ጉባኤሆሙ ፡ አበ ፡ ኒቆላዎስ ፡ (ዘፀ፬ ፡ ፲፮ ። ኤር፲፭ ፡ ፲፱ ። ታሪ ፡ ነገ) ።

— ፤ ወደብ ፡ ጠረፍ ፡ ዳፍ ፡ አፋፍ ። መንገለ ፡ አፉሃ ፡ ለባሕር ። አፈ ፡ ምት ፡ (ኩፋ ፡ ፳ ። አዋል) ።

— ፤ ስለት ፤ እንደቤት ። አፈ ፡ ሰይፍ ፡ አፈ ፡ ኲናት ፡ አፈ ፡ ነጺን ። ሰይፍ ፡ ዘክልኤ ፡ አፉሁ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፬ ። ዕብ፲፩ ፡ ፴፬ ። ዮዲ፪ ፡ ፳፯ ። መዝ ፡ ፻፵፱) ።

**አፈ ፡ እቶን ፤** የምድጃ ፡ አፍ ፡ ለንጨቱና ፡ ልጡ ፡ እየተቈረጠ ፡ የሚገባበት ፤ ባጎድ ፡ ወገን ፡ እሳቱ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ጎብስቱ ፡ የሚነድበት ፡ የሚጋገርበት ፤ ወይም ፡ የጢስ ፡ መውጫው ፡ መትኰልኩያው ፤ እንደ ፡ ባቡር ፡ ጋን ፡ ያለው ። ከመ ፡ ጢስ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምአፈ ፡ እቶን ፡ (መቃ ፡ ፻፳፬) ።

**አፈ ፡ ወርቅ ፤** የሰው ፡ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ጽሩየ ፡ ቃል ፡ ነባቤ ፡ ቃል ፡ ጽሩይ ። ቃሉ ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ የጠራ ፡ የከበረ ፤ እድፍ ፡ ጕድፍ ፡ ጸያፍ ፡ የሌለበት ። ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ፲፪) ።

**አፈ ፡ መልበስ ፤** ፊስጌ ፡ ዐንገትጌ ፡ እጅጌ ፡ እግርጌ ፤ የቆብ ፡ የባርኔጣ ፡ የካባ ፡ የጀባ ፡ የቀሚስ ፡ የሱሪ ፡ የሹራብ ፡ የመጫሚያ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፲፰ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፴፪) ።

**አፈ ፡ ጽባሕ ፤** የመግልት ፡ ደጅ ፡ አፍ ፡ መግቢያው ፡ መበቻው ፡ የፀሐይ ፡ ውጋገን ፡ የሚታይበት ፡ መዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ጎሕ ፡ ጎሐ ፡ ጽባሕ ። የጧት ፡ ጧት ፡ ማለዳ ፡ ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ ወፍ ፡ ሲጮኽ ፡ ጎሐን ፡ ተመልክት ። ባልቴቶች ፡ የጧት ፡ ምስጋና ፡ ሲያቀርቡ ፡ ስትዘጋው ፡ አይስማቡኝ ፡ ስትከፍተው ፡ ኩሽ ፡ አይሉብኝ ፡ እንዲሉ ። ዕቅበት ፡ ሌሊት ፡ እንተ ፡ አፈ ፡ ጽባሕ ፡ (ዘፀ፲፬ ፡ ፳፬ ። ዘፍ፲፱ ፡ ፲፭ ። ፪ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፳)

**አፍአ ፤ (ዕብ ፡ ሑጽ) ፤** በቁሙ ፡ ውጭ ፡ ዕዳሪ ፡ ደጅ ፡ ወለወል ፡ ከቤት ፡ ከቅጥር ፡ ከሀገር ፡ ከመንደር ፡ ከወሰን ፡ ከደንበር ፡ በውጭ ፡ ያለ ፡ በውስጥ ፡ ያይደለ ፡ ንኪር ፡ ባዕድ ፡ ልዩ ፡ ቦታ ። አልብነ ፡ ውሳጤ ፡ ወኢአፍአ ። ይቀውም ፡ አፍአ ። ዐጸወ ፡ ደብተራ ፡ እንተ ፡ አፍአ ። ዝንቱሰ ፡ ውስጡ ፡ ጽቡር ፡ ወአፍአሁ ፡ ብርት ። ተሰቅለ ፡ አፍአ ፡ እምትዕይንት ። በአፍኣሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ (ቀሌ ። ሚሬ፳፭ ፡ ፴፫ ። ዮዲ፲፫ ፡ ፲ ። ዳንኤ፲ ፡ ፯ ። ዕብ፲፫ ፡ ፲፪ ። ኤር፲፰ ፡ ፯) ።

**አፍአዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** የአፍኣ ፡ የውጭ ፡ የደጅ ፡ ግልጥ ፡ ገሃድ ። ቅጽር ፡ አፍኣዊ ። ጽልመት ፡ አፍኣዊ ። ኢይሰርገዋ ፡ አንስት ፡ ሰርጐ ፡ አፍኣዊ ። ኢትጽንኑ ፡ መንገለ ፡ ፍኖት ፡ ሕገጋት ፡ አፍኣዊት ፡ (፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፭ ። ፊልክ ፡ ፹፰ ። ፊ ፡ መ ፡ ፴፱ ፡ ፰ ። ፲፰ ፡ ፩) ።

— ፤ ሥጋዊ ፡ ዓለማዊ ፡ መናፍቅ ፡ ኢጥሙቅ ። አፍአውያን ፡ ዓለማውያን ። ምስለ ፡ ሰብእ ፡ አፍኣውያን ። እም ፡ ቦ ፡ ዘኮነ ፡ ውጉዘ ፡ ምስለ ፡ አፍአውያን ፡ (ፊልክ ፡ ፳ ። ፊ ፡ መ ፡ ፴፪ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፫) ።

**አፈው ፤ (ዋት) ፤** ሽታ ፡ መዐዛ ፤ የሽቱ ፡ ትንፋሽ ፤ ሙዳዩ ፡ ቢልቃጡ ፡ ሲከፈት ፡ ካፉ ፡ የሚወጣ ፡ ረቂቅ ፡ እስትንፋስ ። ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ ስም ፤ የሽቱ ፡ ቅመም ። አፈው ፡ እንደ ፡ ሰብእ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ሽታውም ፡ ሽቱውም ፡ ከብዙ ፡ ዕንጨት ፡ ከብዙ ፡ አበባ ፡ እንደ ፡ ተቀመመ ፡ ያሳያል ። አፈወ ፡ ቅብዕ ፡ ጥዑም ። ኵሉ ፡ አፈው ። እሉ ፡ አፈው ። ተማየጣ ፡ አፈወ ፡ (መክ፲ ፡ ፩ ። ሔኖ፴፩ ፡ ፫ ። ፴፪ ፡ ፩ ። ማር፲፮ ፡ ፩) ።

**አፈዋት ፤** ሽታዎች ፡ ሽቱዎች ፤ የሽቱ ፡ ቅመሞች ። ንሣእ ፡ አፈዋተ ። አግማል ፡ እለ ፡ ይጸውሩ ፡ አፈዋተ ። ወአምጽኡ ፡ አፈዋተ ፡ ክርቤ ፡ (ዘፀ፴ ፡ ፴፫ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፪ ። ፳፭ ። ቅዳ) ።

**አሮት ፤ (ዕብ ፡ ፊዮት) ፤** ኹለት ፡ አፍ ፡ ያለው ፡ ሰይፍ ፤ አፉ ፤ ሾተል ፡ ጕራዴ ፡ ጩቤ ። በቁሙ ፡ ሰገባ ፤ ድርቁ ፡ የሰይፍ ፡ ማኅደር ፡ ሸፋፍ ። በስመ ፡ ኅዳሪ ፡ ይጼዋዕ ፡ ማኅደር ።

**እፎ ፤ (ዐረ ፡ ከይፈ ። ዕብ ፡ ኤካ ፤ ኤኽ) ፤** ንኡስ ፡ አገባብ ። እንደት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ምንኛ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ስንት ፡ ለምን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ምነው ፡ ረግ ፡ ይኾናል ፤ የአንክሮና ፡ የጥያቄ ፡ ቃል ፡ ነው ። በ ፡ ኪ ፡ መ ፡ ኑ ፡ እንጋ ፡ እያጋነነት ፤ ሳያጋንንትም ፡ ብቻውን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ ይነገራል ። እፎ ፡ ከነት ፡ ዘማ ፡ ሀገረ ፡ ጽዮን ። እፎ ፡ ኅደጋሁ ፡ ለአቡከ ። አ ፡ ሞት ፡ እፎ ፡ ዝክርከ ፡ መሪር ። እፎ ፡ ተሰባሕከ ፡ ሌሊያስ ። ጽልመትከ ፡ እፎ ። እፎ ፡ ኢተአምኑ ፤ ለምን ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፳፩ ። ጦቢ፲፩ ፡ ፩ ። ሢራ፵፩ ፡ ፩ ። ማቴ ፡ ፮ ። ማቴ፳ ፡ ፳፫ ። ሉቃ፲፪ ፡ ፶፯) ። ምነው ፡ ረግ ፡ ሲኾን ፡ ድንጋጤና ፡ ሐዘን ፡ ያሳያል ። እፎ ፡ ምንተ ፡ ኮንከ ፡ እስመ ፡ ሕዙን ፡ አሬእየከ ፤ ምነው ፡ ምን ፡ ኾንኻል ።

እፎ ፡ ምትኑ ፡ ዝክሩ ፡ ሕፃን ፤ ረግ ፡ ያ ፡ ብላቴና ፡ ሞትን ፡ እያሰኝ ፡ ጥያቄን ፡ ሳይለቅ ፡ ይነገራል ። ከጋኖችና ፡ ከ ዳግቆች ፡ ጋራ ፡ ሲነገር ፤ **በእፎ ፡ ኢይዐቀብከ ፤ እፎኬ ፤ እፎሊ ፤ እፎመ ፤ እፎኑመ ፤ እፎ ፡ እንጋ ፤ እፎ ፡ እንከ ፤** ፈ.ድፋ.ደ ፤ እያለ ፡ ይገባል ።

**እፎ፡እፎ፤እፈፎ፤እፈ፡እፎ፤(ዕብ፡ኤከ ካህ)፤** እንዴት ፡ እንዴት ፡ ምን ፡ ምን ፡ ምንኛ ። **እፎ ፡ ትቤ ፡፡ በል ፡ እፈ ፡ እፎ ፡** (ቁር ፡ ጸላ) ።

**እፎያዊ፤ (ዊት ። ሱር ፡ አይፋናዩታ ። ዕብ፡ኤኩት ። ዐረ ፡ ከይፌየት)፤** ጥሬና ፡ ቅጽል ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፤ ምን ፡ የመሰለ ፤ የሚ ያስፈራ ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ወይም ፡ የሚያስደንቅ ። **ወእ ፎያዊት ፡ ተቃትሎት ፤** (ፊልክ ፡ ፺፰ ። ፻፲) ።

**አፌዝ፤(ዐረ፡እውፋዝ ። ጽር ፡ ዖፋዝ፤ ዑፋዝ ። ዕብ ፡ ፓዝ)፤** የወርቅ ፡ ወርቅ ፤ መዠመሪያ ፡ ወርቅ ፡ የማዕደናት ፡ ራስ ፡ በኵራቸው ፤ ጥሬቱና ፡ ዋጋው ፡ ከወርቅ ፡ የሚበልጥ ፤ ተርታው ፡ ወርቅ ፡ ለ፴ና ፡ ለ፵ ፡ ሲሸጥ ፡ ርሱ ፡ ፷ና ፡ ፹ ፡ የሚያወጣ ። ቃሉ ፡ ፎዝ ፡ ከማ ለት ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ ፋዝን ፡ ተመልከት ። **ወርቀ ፡ አፌዝ ፤** (ዳን፲ ፡ ፭ ። በአፌዝ ፡ ፈንታ ፡ ቁፋዝ ፡ ይላል ፤ አፌዝና ፡ ፋዝ ፡ ቁፋዝ ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ነው ፡ (ማሕ፭ ፡ ፲፩) ። **በላም ፡ ለርእስከ ፡ በወርቀ ፡ አፌዝ ፡ ጽሩይ ፤ ዘአስተማሰለቶ ፡ መርዓት ፡ ሠናይት ፡ ላሕይ ፤** (ደራሲ) ። ባለብሎች ፡ ግን ፡ ኹሉንም ፡ የወርቅ ፡ አገር ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ።

**አፍኅርት ፤—ማጨፉቶች ፤—ፈርኀ ።**

**አፍይ፤ዩት፤(አፈየ፡የአፈ፡ይእፈይ ። ዕብ ፡ አፋህ ። ሱር ፡ ኤፋእ)፤** ነቢብ ፤ መጋገር ፡ ማብሰል ፡ መረመጥ ፤ የሲጥ ፡ የብርኵታ ።

**አፋዪ፤(ዪት ፡ ይያን ፡ ያት)፡** የሚጋግር ፡ ጋጋሪ ፡ ዐበዛ ፡ በዓለ ፡ እቶን ።

**ተአፍየ፤** ተጋገረ ፡ በሰለ ፤ በእቶን ፡ በምጣድ ፡ ወይም ፡ በፍሕም ።

**እፉይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ፈት)፤** የተጋገረ ፤ የበ ሰለ ፡ ትኰስ ። **ኅብስት ፡ እፉይ ፡ ዘእንበለ ፡ ግማኔ ፡** (መጽ ፡ ምስ) ።

**አፍዮማክን ፤ (ጽር ፤ ዖፊዮማኪስ)፤** ሐሱን ፡ ዐሽን ፡ የአንበጣ ፡ ዐይነት ፡ ከምድር ፡ የሚፈላ ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፳፪) ።

**አፍከ ፤ (ዐረ ፡ አፈከ ። ዕብ ፡ ሀፋኽ)፤** ገለበጠ ፡ ተገለበጠ ፡ ዞረ ፡ ተዛወረ ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ከፊት ፡ ወደ ፡ ኋላ ። መልኩን ፡ ሃይማኖቱን ፡ ለወጠ ፡ ተለወጠ ፡ ሌላ ፡ ኾነ ፤ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ተጠጋ ፤ የከፉ ፡ የበጎ ። ሸሸ ፡ አፈገፈገ ፤ ወደ ፡ ኋላ ፡ አለ ።

**አፍክያ ፤ (ጽር ፡ ዲአቲኪያ ። ዕብ ፡ ቴሬስ)፤** ኑዛዜ ፡ ሜንጦ ፡ ዘለበት ፡ ቀለበት ፡ የድንኳን ፡ የመጋረጃ ፡ ቍልፍ ፤ ማያያዣ ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፲፩ ። ኀጸደንና ፡ ኖጻድን ፡ ተመልከት ።

**አፍኒን ፤(ዕብ፡ አፋኒም)፤** መንኰራኵራት ፡ ተሽከርካሪዎች ፤ የሠረገላ ፡ እግሮች ። አንዱ ፡ አፋን ፡ ይ ባላል ፡ (ሕዝ፩ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮) ። ጌልጌልን ፡ ተመልከት ፤ ከ ዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። **ወየዐውድዎ ፡ ለውእቱ ፡ ቤት ፡ ሱራፌን ፡ ወኪሩቤን ፡ ወአፍኒን ፤** (ሔኖ ፡ ፸፩ ፡ ፯) ። በፋኑኤል ፡ ፈንታ ፡ አፍኒን ፡ በአፍኒን ፡ ፈንታ ፡ ፋኑ ኤል ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። **አፍኒን ፡ ሊቀ ፡ መላእ ክት ፡ አሐዱ ፡ እምተስዐቱ ፡ ሊቃናት ፡** (ስንክ ፡ ኅዳ፰) ።

**አፍዖት ፤—እፍኝት ፤—ፈዐወ ።**

**አፈፈ ፤ (ዕብ ፡ አፋፍ ፤ ከበበ ፡ ዐቀፈ)፤** በቁመ ፤ ቈረጠ ፤ ዐረደ ፡ ቀረደደ ፡ አስተካከለ ። አፈፍ ፡ በድረግ ፡ አለ ፤ ፈጥኖ ፡ ተነሣ ፤ ወይም ፡ አንሣ ፡ ያዘ ፤ አ ፈፍ ፡ አደረገ ። አፋ ፡ አፍታ ፡ አፈፋ ፡ አፋፍ ፡ ማለት ፡ አፈ ወና ፡ እፎም ፡ ሳይቀሩ ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ እፈፎን ፡ እይ ።

» **ፈፍ፤** የፊደል ፡ ስም ፡ ፈ ፤ አፍ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ መዠመሪያውን ፡ ፈ ፡ ተመልከት ።

**አፈር ፤—በቁመ ፤—ዐፈር ፡ ዐፈረ ።**

**አፌር ፤ አፌር ፤ (ዕብ ፡ አፌር)፤** ስመ ፡ ነገድ ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ በእስያ ፡ ክፍል ፡ በደቡብ ፡ ዐረብ ፡ በባሕረ ፡ ፋርስ ፡ ወይም ፡ በህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ዳር ፡ ያ ለች ፤ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ወርቅ ፡ እንዳፈር ፡ እንዳሸዋና ፡ እንደ ፡ ጠጠር ፡ ይታፈስባት ፡ የነበረች ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፳፱ ። ፩ነገ ፡ ፱ ፡ ፳፰ ። በአፌር ፡ ፈንታ ፡ ዖፎር ፡ አዝፋር ፡ ይ ላል ፡ (ኢዮ፳፰ ፡ ፲፮ ። መዝ፵፬ ፡ ፲፩) ።

**አፍርኅት ፤—ማጨፉቶች ፤—ፈርኀ ።**

**አፍሬጥልስ ፤** ስንቀ ፤ የስንቀ ፡ ስም ፡ (አረጋ ፡ መል፺፯) ።

**ኤፍራጥስ ፤ (ጽር ፡ ሄፍራቴስ ። ዕብ ፡ ፍራት)፤** ስመ ፡ ፈለግ ፡ ዐቢይ ፤ ራብዓይ ፡ ወንዝ ፡ (ዘ ፍ፪ ፡ ፲፬) ። ምንጩም ፡ ከአርማንያ ፡ ተነሥቶ ፡ በአሶር ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የሚጐርፍ ። ከራቱ ፡ ዐበ ይት ፡ አፍላጋት ፡ ኹለቱ ፡ በአፍሪቃ ፡ ክፍል ፡ ኹለቱ ፡ በእ ስያ ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፤ ግዮን ፡ ከርቱም ፡ ሲደርስ ፡ ከኤ ፈሶን ፡ ገጥሞ ፡ አንድ ፡ ወንዝ ፡ ኹኖ ፡ ሜዲትራኒ ፡ እን ዲገባ ፤ ኤፍራጥስም ፡ ባቢሎን ፡ ሲደርስ ፡ ከጤግሮስ ፡ ጋራ ፡ ይገጥምና ፡ አንድ ፡ ወንዝ ፡ ኹኖ ፡ ወደ ፡ ባሕረ ፡ ፋርስ ፡ ይገባል ። ፍራት ፡ ፈረየ ፡ ከማለት ፡ ወጥቷል ፤ ዘይቤው ፡ ፍሩይ ፡ መፍርይ ፤ ፍሬያማ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ የሚያ ጠጣት ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ባለብዙ ፡ ፍሬ ፡ መኾኗን ፤ የፍሬዋንና ፡ የመንጋዋን ፡ ሙብዛት ፡ መፈይፈይ ፡ መርባት ፡ መዋለድ ፡ ያሳያል ።

**አፍራቅያ ፤—አፍሪቃ ፤—ፈረቀ ፡ ፈ ረቀ ፤ አፍረቀ ።**

**ኤፌሶን፤(ጽር፡ ሄፍሶስ)፤** ስመ፡ ሀገር፡ በታናሽ፡ እስያ፡ ውስጥ፡ ያለች፤ ጳውሎስ፡ ዮሐንስ፡ ያስተማሩባት፡ ሦስተኛው፡ ጉባኤ፡ የቆመባት፤ ንስጥሮስ፡ እንታዎድሪጦስ፡ የተወገዙባት። (፩ቆሮ፡ ፲፭፡ ፴፪። ፩ጢሞ፡ ፩፡ ፫። ኤፌ፡ ፩፡ ፩። ራእ፩፡ ፲፩። ፪፡ ፩)።

**ኤፌሶን፤(ጽር፡ ፌሶን፤ ዕብ፡ ፊሾን)፤** ስመ፡ ፈለግ፤ ከራቱ፡ አፍላጋት፡ አንደኛው፡ መዠመሪያው፡ ወንዝ፤ ጕዛምን፡ የሚከብብ፡ ጥቍር፡ አባይ፡ ጥቍር፡ መባሉም፡ የውሃው፡ መልክ፡ ዐይንቱና፡ ኅብሩ፡ ጥቍር፡ ኒል፡ ስለ፡ መሰለ፡ ነው፡ (ዘፍ፪፡ ፲፩)። ኤ፡ የመ ላሽ፡ ተውሳክ፡ ነው፤ የሱስን፡ ኢየሱስ፡ እንዳለው፤ ፊሶን ንም፡ ኤፌሶን፡ ብሎታል። ዕብራውያን፡ ተልባ፡ የተልባ፡ እግር፡ ሲሉ፡ ፊሽታን፡ ይሉታና፡ ፊሾን፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ወጥቷል፤ ርሱ፡ የሚያጠጣት፡ ምድረ፡ ግብጽ፡ ብዙ፡ ተልባ፡ የሚዘራባት፤ ከዚህ፡ የተነሣ፡ ብዙ፡ ፈትልና፡ ልብስ፡ የምታስገኝ፡ (የከታን) የፊሽታን፡ አገር፡ ስለ፡ ኾነች፤ በማያበቅለውና፡ በማያፋፋው፡ ንጣትና፡ ጥራት፡ በሚሰጠው፡ በፊሽታን፡ ፊሾን፡ ተብሏል። ይኸውም፡ ፈለገ፡ ግብጽ፡ ሀገሪተ፡ ፊሽታን፡ ማለት፡ ነው፤ ምንም፡ ወንዝነቱ፡ የኵሽ፡ ቢኾን፡ ሥራ፡ የሚሠራ፡ በሚጸራይም፡ ክፍል፡ ነውና፤ ስለዚህ፡ የግብጽ፡ ወንዝ፡ ይባላል፡ (ኢሳ፲፱፡ ፱። ሕዝ፳፱፡ ፺። ፳፱፡ ፫፡ ፬)። ባለመጽሐፎች፡ ግን፡ ፈለገ፡ ኒል፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ፈለገ፡ ሐሊብ፡ ይሉታል። ወእንዘ፡ ስሙ፡ ኤፌሶን፡ ፈለገ፡ ጸዐዳ፡ ሐሊብ፡ (ቅኔ። ድጓ)።

**አፍሶት፤—የድውያን፡ ቤት፤—ሐፍሦት፤ ሐፈሠ።**

**ኤፎት፤(ዕብ፡ ንጢፎት)፤** ያንገት፡ ጌጥ፡ እንደ፡ ድሪና፡ እንደ፡ ማርዳ፡ ያለ፡ ጥሩ፡ የወርቅ፡ መጣሪያ። ባዝግናት፡ ዘኤፎት፡ (መሳ፰፡ ፳፯)።

**አጽባዕት፤—ጣት፤—ጸቢዕ፡ ጸብዐ።**

**አጽዕብት፤—ሬሳ፡ አውሬች፤—ጽዕብ።**

**አቃጥን፤—ኵብኵብ፤—አጣቃን።**

**አቀላፍ፤—ያልጋ፡ ጠፍር፤—ቈሊፍ፡ ቈለፈ፤ ቀልፍ።**

**አቅሌስያ፤(ጽር፡ ሄክሊሲያ)፤** ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ጉባኤ፡ ምእመናን፡ (ድጓ)።

**አቅሞንስ፤(ጽር፡ ሄጉሜኖስ)፤** አበ፡ ማኅበር፤ ሊቀ፡ ቀሳውስት። ከሬ፡ ኤጲስቆጶስ፤ ዘውእቱ፡ አቅሞንስ፡ (መጽ፡ ምሥ)።

**አቃኒ፤(ጽር፡ አካን)፤** የደጋ፡ እሾኽ፡ እንቧይ፡ ዝንኪላ፡ ኰሸሽላ። ባለብሉዮች፡ ግን፡ ችፍርግ፡ ቅርሽንባ፡ (እንደኳኩላ) እንዳጉላ፡ ይሉታል፡ (፬ነገ፡ ፲፬፡ ፱)።

**አቃኒም፤—አካላት፤—ቀኑም።**

**አቅራብ፤—ጊንጥ፤—ዐቅራብ።**

**አቃረየ፤—ሠዋ፤—ቀረየ።**

**ኤቍስዮም፤(ጽር፡ ኢኬሲዮን)፤** ቅዳሴ፡ ጥንት፡ (፩ነገ፡ ፲፱፡ ፳፭)። ባለብሉዮች፡ ግን፡ ኀያላን፡ ይሉታል።

**ኤር፤—መልአክ፤—ዔር፤ ዐየረ።**

**አርአያ፤—በቁሙ፤—ርእይ፡ ርእየ፤ አርአየ።**

**አርኤል፤(ዕብ፡ አሪኤል)፤** ምሥዋዕ፡ የምሥዋዕ፡ ስም። አሪ፡ አንበሳ፡ ኤል፡ አምላክ፡ በተገናኘ፡ አንበሳ፡ አምላክ፡ ማለት፡ ነው፤ ሥራውና፡ ቅርጡ፡ አቀማመጡ፡ እንደ፡ አንበሳ፡ ስለ፡ ኾነ፤ ኹለተኛም፡ ለእዕርገ፡ መሥዋዕት፡ የወረደው፡ እሳት፡ በአንበሳ፡ አምሳል፡ ስለ፡ ታየበት፡ አንበሳ፡ ተብሏል፡ (ሕዝ ፵፫፡ ፲፭፡ ፲፮)። ምስጢሩ፡ ግን፡ ሞአ፡ አንበሳ፡ ያለውን፡ ያሳያል፡ (ራእ፭፡ ፭)። በአርኤል፡ ፈንታ፡ አርያል፡ ይባላል፤ የጣፊ፡ ስሕተት፡ ነው፡ (ኢሳ፳፱፡ ፩፡ ፪)። ሀ ሀርኤልን፡ እይ፡ የዚህ፡ ሞክሼ፡ ነው።

**አርባብ፤—ጌቶች፤—ረቢብ፡ ረብ፡ ረብ።**

**አረቦን፤—መያዣ፡ ፈለማ፤—ዐረቦን።**

**አረቦናት፤(ጽር፡ አራቦት። ዕብ፡ ሀሪፎት)፤** የስንዴ፡ ክክ፡ ወይም፡ ፍትግ፡ ደረቄት። ስንዴውን፡ ቀቅለው፡ አድርቀው፡ ይከኩና፡ እንደ፡ እንቀት፡ እንደ፡ ሩዝ፡ በቅቤ፡ አጣፍጠው፡ ይበሉታል። ወሰጥሐት፡ በሙ፡ አረቦናተ፡ (፪ነገ፡ ፲፯፡ ፲፱)።

**አርባዕ፤—አራት፤—ረብዖ፡ ረብዐ።**

**አርበቅ፤—ኵሓ፤ ችባሓ፤—ዐርበት።**

**አራብት—ሜዳ፡ በረሓ፤—ዐራብት።**

**አረግ፤ጎት፤(አረገ፡ የአርግ፡ ይአርግ። ዕብ፡ አራግ፡ አነመ፤ ሰፈየ። አራኽ፤ ኖኀ። ዐረ፡ አርጃእ፤ ጸንሐ)፤** ማርጀት፤ መሸምገል፡ አሮጌ፡ ሽማግሌ፡ መኾን፤ ከዕድሜ፡ ርዝመት፡ ክብዙ፡ መቈየት፡ የተነሣ። ልህቀን፡ ተመልከት። አረገት፡ ሳራ፡ (ሰንክ፡ ንሐ፳፰)።

**አራጊ፤(ጊት፡ ግያን፡ ያት)፤** የሚያረጅ፡ የሚሸመግል፤ ሽምጋይ።

**አረግ፤(ጊት፤(ብ፡ አእሩግ፡ ጋት)፤** አሮጌ፡ ሽማግሌ፡ ታላቅ፡ ልሂቅ፤ ፰፡ ዓመት፡ ያለፈው፡ ዕድሜ፡ የጠገበ፡ ለሞት፡ የቀረበ። ሴት፡ ብትኾን፡ ከ፷፡ ዓመት፡ በላይ፡ ያለች፡ አሮጊት፡ ባልቴት። አረጊት፡ ዘ ድክምት፡ ፈድፋደ። አእሩግ፡ ወሊቃውንት፡ (ፈላስ። ስንክ፡ ታኅ፳፰)።

**አረጋዊ፡ ይ፤(ዊት፡ ዩት፡ ውያን፡ ያት)፤** ያሮጌ፡ ወገን፡ መካከለኛ፡ መዋዕለ፡ ውርዙት፡

ያለፈ ፡ ዕድሜው ፡ ከርባና ፡ ከምሳ ፡ የተረፈ ፡ ጠጕሩ ፡ የጨበረ ፡ የርጅና ፡ መንገድ ፡ የገሠረ ። አረጋዊ ፡ ዘበሥርዐቱ ፡ ይትሉ ፡ ዝሙተ ። ናሁ ፡ አቡነ ፡ አረጋይ ፡ ውእቱ ። አረጋዊት ፡ መበለት ። መነኮሳት ፡ አረጋውያን ፡ (ሚራ ፺፪ ፡ ፰ ። ዘፍ ፲፱ ፡ ፴፩ ። ስንክ ፡ ኅዳ ፳፪ ። ታኅ ፰) ።

— ፤ ባሕታዊ ፡ መነኰሴ ፡ መምህር ፡ አበ ፡ ማኅበር ። አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ። ይቤሎ ፡ እኁ ፡ ለአረጋይ ። ወይቤ ፡ አረጋዊ ፡ (አረጋ ። ፈልክ) ።

**እርግና** ፤ በቁሙ ፡ እርጅና ፡ አሮጌነት ። (ተረት) ፡ እርጅና ፡ ብቻቹን ፡ ና ። ለእመ ፡ ሞተ ፡ በእርግናሁ ፡ (ፈልክ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭) ።

**እእረገ** ፡ አስረጀ ፡ አሸመገለ ፡ አሮጌ ፡ አስኘ ።

**እርጋሄ** ፤ አክርማ ፡ ስንደዶ ፡ ግራምጣ ፡ የስፌት ፡ ማር ። ይሥጥቅሙ ፡ ከመ ፡ እርጋሄ ፡ (ድር ፡ ሚክ) ።

**አርገ** ፤—**ዐረገ ፡ ወጣ** ፤—**ዐርገ** ።


**አሬጋ** ፤ **(ጽር ። ዕብ ፡ አቆ ። ሱር ፡ ያዕላ ። ዐረ ፡ ወዕል)** ፤ ሳላ ፡ የቦኽር ፡ ወገን ፡ ቀንዳም ፡ ቀንደ ፡ ረዥም ፡ ብዕዛን ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሠሥ ፡ ሠሚ ፡ ይሉታል ። ውዕላ ፡ ወአሬጋ ፡ (ዘዳ ፲፬ ፡ ፭) ። ወረጋ ፡ ወሬጋ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ወረጋ ፡ ሌባ ፡ ያልተማነ ፡ ከብት ። ወሬጋ ፡ ቈንገር ፡ መልክ ፡ ቀና ፡ ሴት ።

**ኤረግ** ፤—**ቀሮ ፡ ቅርማት** ፤—**ሐረገ** ፤ **ዐየረ** ፤

**ኤርጋብ** ፤ **(ጽር ፡ ሄርጋብ ። ዕብ ፡ አርጋዝ)** ፤ ማጥን ፡ የማጥን ፡ ስም ፡ (፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ፲፭) ። ግእዙ ፡ ተሜርጋብ ፡ አፍቃዲ ፡ አርጋብ ፡ እያለ ፡ ያልነበረ ፡ ቃል ፡ ይጨምራል ፡ ጽርኤም ፡ በ፰ኛው ፡ ቍጥር ፡ ፌርሴክታን ፡ ያለውን ፡ ባ፲፩ኛው ፡ ሄርጋብ ፡ ይላል ፡ ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ አይለውጥም ። ዳግመኛም ፡ በአርጋዝ ፡ ፈንታ ፡ አሬንዝ ፡ ይላል ፡ ባለብሉዮችም ፡ ድባብ ፡ ኮርቻ ፡ ይሉታል ።

— ፤ ታላቅ ፡ ደንጊያ ፡ ቋጥኝ ፡ ገዎቻ ፡ ቀሸንት ፡ ያለው ፡ መንገደኞች ፡ የሚያርፉበትና ፡ የሚያድሩበት ፡ (፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ፡ ፵፭) ። ኤርጋብ ፡ ያለኘው ፡ ዋሻው ፡ ነው ።

**አርጋኖን** ፤ **(ጽር ፡ አርጋኖን ። ዐረ ፡ አርቀኑን ። ዕብ ፡ ዑጋብ)** ፤ ኪታራ ፡ ሙዚቃ ፡ የዘፈን ፡



አርጋኖን ፡

የማሕሌት ፡ ዕቃ ፡ መዝሙር ፡ በገና ፡ ውዳሴ ፡ ምስጋና ። መልክም ፡ ዜማ ፡ ስገሮ ፡ ለልብ ፡ የሚጣፍጥ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ድምጥ ፡ (፩ዜና ፡ ፯ ፡ ፴፪) ። አድንዐ ፡ አውታረ ፡ አርጋኖን ። አርጋኖን ፡ ውብዕዛ ። አርጋኖነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ (አዋል ። ስንክ ፡ መስ፲፰ ። አረጋ ፡ ፭) ።

**አርደብ** ፤ **(ዐረ ፡ ኢርደብ ። ቅብጥ ፡ ሄርቶብ ። ጽር ፡ አርታቢ)** ፤ የመስፈሪያ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ቆሮስ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ መስፈሪያ ፡ ሚዛን ፡ (አቡሻ ፡ ፶) ።

**አሮድዮን** ፤ **(ጽር ፡ ሄሮዲያዎስ)** ፤ ያሞራ ፡ ስም ፡ ሽመላ ፡ ሄሮድያኖስ ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፲፱ ። ዘዳ ፲፬ ፡ ፲፮) ። አሮድዮን ፡ ሽመላ ፡ መባሉ ፡ በሽመላ ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ ተጣፈ ፡ እንጂ ፡ ፍችው ፡ አይደለም ፡ መሳሽ ፡ አበሳሽቶታል ፡ ሄሮድያኖስን ፡ ተመልከት ።

**አሮድዮን** ፤ ያፈ ፡ ያሬድ ፡ በአምሳለ ፡ ያፍ ፡ ታይቶ ፡ ዜማ ፡ ያስተማረው ፡ ምስጢር ፡ ያናገረው ፡ መልአክ ፡ ወይም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስንክሳር ፡ ግን ፡ ፫ ፡ ወፎች ፡ ይላል ፡ (ግን ፡ ፲፩) ። ስሙ ፡ ቅሉ ፡ ያሬድ ፡ የተባለ ፡ በአሮድዮን ፡ ነው ፡ ይባላል ፡ ድምፁን ፡ እንደ ፡ ነጣ ፡ ስሙንም ፡ ነሥቷል ። **ያፍ ፡ ዘይብልዎ ፡ አሮድዮን ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ጠቢባን ፡ ይትፌሣሕ ፡ ወይትሐሠይ ፡ ሶበ ፡ ይትፌለጥ ፡ እምኅበ ፡ የኀድሩ ፡ ሰብእ ፡ ዓለም ፡ ወየሐውር ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ በድው ፡ ወይነብር ፡ ውስቴቱ ። ወተብህለ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ያፍ ፡ ዘእሙር ፡ በክልኤ ፡ ሑረታት ፡ ከመ ፡ ሆሎ ፡ ዘበምዕ ፡ ቃናሁ ፡ ወንቃወ ፡ ዜማሁ ፡ ይትአሰር ፡ ድኅሬሁ ፡ በሑረቱ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ እስከ ፡ ውእቱኒ ፡ እምጣዕመ ፡ ቃናሁ ፡ ይረስዕ ፡ ሕይወቶ ፡ ወይደክም ፡ ወይመውት** ፡ (ማር ፡ ይሥሐቅ ፡ ፫) ።

**አርዳሚስ** ፤ **አርዴምስ** ፤ አርጤምስ ፡ ስመ ፡ ጣዖት ፡ (ስንክ ፡ ጥር ፳፯ ። ግን ፳፭ ። ሠኔ ፱) ።

**አርዳሚስ** ፤ የሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ የምኒልክ ፡ ታናሽ ፡ የሮብዓም ፡ ታላቅ ፡ በነገሥትና ፡ በዜና ፡ መዋዕል ፡ ያልተጣፈ ፡ ባለሐዲሶች ፡ የሚተርኩት ፡ (ሮሜ ፡ ፭) ። **ሰሎሞን ፡ ወለደ ፡ ለምኒልክ ፡ ወለአርዳሚስ** ፡ (ክብ ፡ ነገ) ።

**አርዌ** ፤ **(ዕብ ፡ አሪ ፡ አርዬ ፤ ብ ፡ አራዮት)** ፤ አንበሳ ፡ ዕጓለ ፡ አንበሳ ፡ ደንበሳ ፡ ወገን ፡ ሥዕሉ ፡ ምስሉ ፡ ቡችላው ፡ ግልገሉ ፡ ደቦሉ ።

**አርዌ** ፤ **(ብ ፡ አራዊት)** ፤ በቁሙ ፡ አውሬ ፡ ነገዱ ፡ ከእንስሳ ፡ ከያፍ ፡ የተለየ ፡ ቍጡ ፡ ጠባየ ፡ ክፉ ፡ ደም ፡ ልሶ ፡ ብርንድ ፡ ጕርሦ ፡ ዐጥንት ፡ ከስክሶ ፡ የሚኖር ፡ የሚያድንና ፡ የሚታደን ፡ በረኸኛ ፡ የሰው ፡ የእንስሳ ፡ ደመኛ ፡ በየስሙና ፡ በየይነቱ ፡ በየነገዱ ። **አርዌ ፡ ፀዋግ ። አርዌ ፡ እኩይ ። አራዊተ ፡ ሐቅል ። አራዊተ ፡ ገዳም** ፡ (ኩፋ ፡ ፴፬ ። ዘፍ ፴፯ ፡ ፴፫ ። ኢዮ ፭ ፡ ፳፪ ። ዳን ፬ ፡ ፳፪) ።

**አርዌ ፡ ባሕር** ፤ የባሕር ፡ አውሬ ፡ ዐሣ ፡ ጉማሬ ፡ ደራጎን ፡ ዐንበሪ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። **እምቅድመ ፡ አራዊተ ፡ ዘባሕር** ፡ (ቅዳ ፡ ዲዮ ። ራእ ፲፩ ፡ ፯) ።

**አርዌ ፡ ብርት** ፤ የእባብ ፡ ምስል ፡ (ዘኍ ፳፩ ፡ ፰ ፡ ፱) ።

**አርዌ ፡ ቤት ፡** ውሻ ፡ ድመት ።

**አርዌ ፡ ሐሪም ፡** አውሬሪም ። ሐርማገዝንና ፡ ሐሪምን ፡ ተመልከት ፡ (ኢዮ፴፱ ፡ ፱ ፡ ፲) ።

**አርዌ ፡ ምድር ፡ (ዐረ ፡ ሐየት ። ሱር ፡ ሒውያ ። ዕብ ፡ ናሐሽ ። ጽር ፡ ዖፊስ) ፡** ከይሲ ፡ እባብ ፡ ዘንዶ ፡ እግር ፡ በስሌለው ፡ ከምድር ፡ ተጣብቆ ፡ ሆዱ ፡ የሚሳብ ፡ መርዛም ፡ ተንኰለኛ ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፩ ። ማቴ፳ ፡ ፲) ።

**አረወ ፡ አው ፡ አርወየ ፡ (የአረዊ ፡ የአርዊ) ፡** አውሬ ፡ ኾነ ፡ አውሬ ፡ ተባለ ፡ በባሕርይ ፡ በግብር ። ተቈጣ ፡ ተነጣጣ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአርወየ ፡ ፈንታ ፡ ተአርወየ ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ።

**አአርወየ ፡** አውሬ ፡ አደረገ ፡ አሰኘ ፡ አስቈጣ ፡ አነጣጣ ። ያአረውዮ ፡ ለየዋህ ፡ ከመ ፡ ድብ ፡ ነራስ ፡ ወይሬስዮ ፡ ከመ ፡ ሐራውያ ፡ ሐቅል ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተአርወየ ፡ (አርወየ) ፡** አውሬ ፡ ኾነ ። ገሠጸ ፡ በተአርውዮ ፡ ወአንበሮ ፡ በተአንስሶ ። ይትአረወዩ ፡ ከመ ፡ አናብስት ። ኖላዊ ፡ ዘይትአረወይ ። እመኒ ፡ ተአርወየ ፡ ላዕሌከ ፡ ከመ ፡ ነምር ፡ አክሞስስ ፡ አንተ ። ለነሳሒ ፡ ኢይደልዎ ፡ ይትመዐዐ ፡ ወኢይትአርወይ ። ቀነየ ፡ ኵሎ ፡ አሕዛበ ፡ እለ ፡ ከኑ ፡ ይትአረወይዎሙ ፡ ለአይሁድ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ኤርሚ፳፫ ፡ ፴፰ ። ሄርማ ። አፈ ፡ ተ፳፱ ፡ ፴፩ ። ዮሴፍ) ።

**አርዊይ ፡ (ዊት ፡ ዊያን ፡ ያት) ፡** አውሬ ፡ የኾነ ፡ ቍጡ ፡ ብስጩ ፡ ክፉ ፡ ጨካኝ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ኤርዌት ፡ (ብ ፡ ኤረው) ፡** ንጉሥት ፡ ገዥምን ፡ (ትግሬ) ።

(ጥ) **እሮት ፡ (ዐማርኛ) ፡** በቁመሙ ፡ የአራዊት ፡ ስ ራዩ ።

**አርወየ ፡—አረከ ፡—ረውይ ፡ ረወየ ።**

**እራዛ ፡—በቁመ ፡—ራዛ ፡ ሩዝ ፡ ረወዘ ።**

**አርዝ ፡ (ዕብ ፡ ኤሬዝ ። ሱር ፡ አርዛ ። ዐረ ፡ አርዝ) ።** ታላቅ ፡ ዛፍ ፡ ጠፍሩም ፡ ደንዳና ፡ ረዥም ፡ ገናና ፡ እንደ ፡ ጥድና ፡ እንደ ፡ ዝግባ ፡ ያለ ። ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አርዝ ፡ ሊባኖስ ፡ ነዋኅ ፡ ወልዑል ። ዐብየ ፡



አርዝ ፡

ወተሰዐሰ ፡ ከመ ፡ አርዝ ። አርዝ ፡ ዐቢይ ፡ (ኢሳ፪ ፡ ፲፫ ። መዝ፺ ፡ ፲፪ ። ሕዝ፴፩ ፡ ፫፰) ።

**አርዛት ፡ አእሩግ ፡** ዘሮች ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአርዛትና ፡ በአእሩግ ፡ ፈንታ ፡ ዕፀወ ፡ አርዝ ፡ ይላል ፡ (፪ነገ ፡ ፩ ፡ ፳፱ ። ፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፳) ። አእሩዝ ፡ ዘገነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ (ሕዝ፴፩ ፡ ፰) ።

**አራዝ ፡ ዛት ፡—ልብስ ፡—ዐርዘ ፡ ዐረዘ ።**

**አርኅ ፡ (የአርኅ ፡ ይእራኅ ። ዕብ ፡ አራኽ ፡ ዮኅ) ፡** ሰፋ ፡ ተዘረጋ ፡ ጠፈጠፈ ፡ ሰፊ ፡ ዝርግ ፡ ጠፍጣፋ ፡ ኾነ ።

**እራኅ ፡ (ኃት) ፡** ጋልማ ፡ ማኽል ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡ እጅ ፡ ከመዳፍ ፡ እስከ ፡ ጣቶች ፡ ጫፍ ፡ ያለው ፡ ዝርጉ ፡ ጠፍጣፋው ፡ ለእግርም ፡ ይኾናል ። እራኅ ፡ ዘይምን ። ትሰፍሕ ፡ እደዊሃ ፡ ወእራኃ ፡ ለውሂብ ። ኵሉ ፡ ውስተ ፡ እራኃት ። አንሥእት ፡ እደዊሆ ፡ እንዘ ፡



እራኅ ፡

ስፉሓት ፡ እራኃቲሆን ። እራኃተ ፡ እደዊሁ ። ኢገብረ ፡ አሚኢ ፡ ለእራኀ ፡ እግሩ ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፬ ። ቀሌ ፡ ገ፳፩ ። ሚ፲፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱ ። ፩ነገ ፡ ፭ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ግን ፡ ፲፱) ።

**አርጣባስ ፡ (ጽር ፡ አርታቢ) ፡** የርጥብ ፡ ሚዛን ፡ የርጥብ ፡ መስፈሪያ ፡ ለእኽልም ፡ ይኾናል ፡ መስፈሪያነቱ ፡ ከአርደብ ፡ ጋራ ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ አርጣባስ ፡ ቃሉ ፡ አርደብ ፡ ከማለት ፡ የወጣ ፡ ስም ፡ ነው ። ወይስ ተዋፅኡ ፡ ሎቱ ፡ ሲሳዮ ፡ ኵሎ ፡ እሚረ ፡ ስንዳሌ ፡ ዕሥረ ፡ ወካዕበ ፡ በመስፈርተ ፡ አርጣባስ ፡ (ዳን፲፬ ፡ ፫) ።

**አርጤምስ ፡ (ጽር ፡ አርቴሚስ) ፡** ስመ ፡ ጣዖት ፡ አርጤምስ ፡ በሚሲት ፡ በመልክም ፡ ሴት ፡ አምሳል ፡ የተሣለ ፡ የሴት ፡ ዐይነት ፡ ጣዖት ። ስሙንና ፡ መል



አርጤምስ ፡

ኩን ፡ ከሴቶቹ ፡ ወርሷል ። ሰንበት ፡ ዐቢያ ፡ ለአርጤምስ ፡ (ግብ፲፱ ፡ ፳፯ ፡ ፴፭) ።

**አርያ ፡ (ጽር ፡ አሬያን) ፡** የሕንጻ ፡ ስም ፡ ሠናይት ፡ ሰርግት ፡ ውብ ፡ መልካም ። የሐዲስ ፡ መዋም

ራን ፡ እ.ድምተ ፡ ሥን ፤ ሥናይት ፡ ሥራሬ ፡ ይሰታል ፡ (ማብ፫ ፡ ፱) ።

**አርይ** ፤ ዮት ፡ (አረየ ፡ የአሪ ፡ ይእሪ ። ዕብ ፡ አራህ) ፤ መልቀም ፡ መቃረም ፡ መሰብሰብ ፡ መምረጥ ፡ ማረም ፡ መንቀል ፤ መለየት ፡ መጣል ፡ (ዘሌ፲፱ ፡ ፱ ። ፳፫ ፡ ፳፪) ። እሑርኑ ፤ ውስተ ፡ ገራህት ፡ እእሪ ፡ እክለ ። ወሖረት ፡ ወአረየት ። ንሑር ፡ ወንእርዮን ። እንዘ ፡ ተአርዩ ፡ ክርዳደ ። ወነቢሮሙ ፡ አረዩ ፡ ሠናዮ ፡ (ሩት፪ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ማቴ፲፫ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ፡ ፵፰) ። አረረንና ፡ ጎረየን ፡ ተመልከት ።

**አራዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ አረይት) ፤ የሚለቅም ፡ የሚቃርም ፡ ቃራሚ ፡ መራጭ ።

**ተአርየ** ፤ ተለቀመ ፡ ተቃረመ ፡ ታረመ ፡ ተመረጠ ።

**እሩይ** ፤ የተለቀመ ፡ ልቅም ፡ ምርጥ ፡ ዕርም ።

**አረየ** ፤—ተካከለ ፤—ዐርይ ፡ ዐረየ ።

**አርዮብ** ፤ (ጽር ፡ አሬዎን ። ዕብ ፡ ክሲል) ። ጉቡኣን ፡ ከዋክብት ፡ ዘወትር ፡ ባንድነት ፡ ኹነው ፡ ችፍግ ፡ ብለው ፡ የሚታዩ ፡ እንደነሥሰቶ ፡ እንደነ ሰድስቶ ፡ ያሉ ፡ (ኢሳ፲፫ ፡ ፲) ። ጸደሰሙ ፡ ለአብያዝ ፡ ወለአርዮብ ፡ (አርጋ ፡ ፯) ።

**አርዮብ** ፤ ታላቅ ፡ ኮከብ ፡ እንደ ፡ ፀሓይ ፡ ያለ ፡ ካራቱ ፡ ፀበይት ፡ ከዋክብት ፡ አንዱ ። ጽዱል ፡ ኮከብ ፡ በጣም ፡ የሚያበራ ፡ የሚያሸበርቅ ። እስመ ፡ ይቤ ፡ አነ ብር ፡ መንበርየ ፡ መልዕልተ ፡ አርዮብ ፡ ወአዐርግ ፡ ውስተ ፡ ምጽንዓት ። ትጸድል ፡ እምሥነ ፡ አርዮብ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ኢሳ፲፬ ፡ ፲፫ ። አርጋ ፡ ፱) ።

**አርያል** ፤—ምሥዋዕ ፤—አሪኤል ።

**አርያም** ፤—ልዕልና ፤—ረይም ፡ ሬመ ፡ ረየመ ።

**አርያሬስ** ፤—ፀሓይ ፤—አወር ፡ አር ።

**አርዮስ** ፤ (ጽር ፡ አሬዉስ) ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ጽርኣዊ ፡ መናፍቅ ፡ ወልድን ፡ ከአብ ፡ የሚለይ ፡ የሚከፍል ፡ በመለኮቱ ፡ ፍጡር ፡ የሚል ፡ የሰውነቱን ፡ ለአምላክነቱ ፡ የሚናገር ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ጉባኤ ፡ ኒቅያ ፡ አምላክ ፡ ጽድቅ ፡ ዘእምአምላክ ፡ ጽድቅ ፡ ዘተወልደ ፡ ወኢኮ ፡ ዘተገብረ ፡ ኅሡረ ፡ ህላዌ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ብላ ፡ ረግማ ፡ አውግዛ ፡ የለየችው ። ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ቃሎ ፡ ርኩሰ ፡ ለአርዮስ ፡ ደንገፁ ፡ ሰራዊተ ፡ ሰማያት ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**አርዮሳዊ** ፤ (ዊት ፤ ውያን ፡ ያት) ፤ የአርዮስ ፡ ወገን ፡ በአርዮስ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያምን ። አርዮሳዊ ፡ እውግዝ ። አርዮሳውያን ፡ (ዝማሬ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ብንያሚ) ።

**አርዮስፋጎስ** ፤ (ጽር ፡ አሪዎስ ፡ ፓጎስ) ፤ የፈላስፎች ፡ ሸንጎ ፡ የጥበበኞች ፡ አደባባይ ፡ የፍርድ ፡ ምላሳቸው ፡ የሕየናት ፡ መራወጫ ፡ መፈንደቂያ ፡ የአእሩግ ፡ ፀሓይ ፡ መሞቂያ ። ቤተ ፡ ምኵናን ፤ ዘስሙ ፡ አርዮስፋጎስ ፡ (ግብ፲፯ ፡ ፲፱) ።

**አሪት** ፤ (ሱር ፡ አራይታ ። ዕብ ፡ ቶራ ። ዐረ ፡ ናሙስ ። ጽር ፡ ኖሞስ) ፤ በቁሙ ፡ ሕግ ፡ ፍትሕ ፡ ትእዛዝ ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላት ። ፍትሕ ፡ የመል ፡ የመክክል ። ሕግ ፡ አታድርግ ፡ አታድርግ ። ትእዛዝ ፡ አድርግ ፡ አድርግ ፡ የሚለው ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዜና ፡ ብርሃን ፡ ስምዕ ፡ ደብር ፡ መደብር ፡ ብለው ፡ ይጠምሩበታል ። እስመ ፡ አሪት ፡ በሙሴ ፡ ተውህበት ፡ ለነ ። አሪትነኑ ፡ ትኴንኖ ፡ ለሰብእ ። ቃቦት ፡ እንተ ፡ ውስቴታ ፡ አሪት ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፲፯ ። ፯ ፡ ፶፩ ። ዕብ ፡ ፱ ፡ ፬) ።

—፤ መጽሐፍ ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ሙሴ ፡ የጻፈው ፡ ዐምስቱ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ዐምስቱ ፡ ብሔር ። አሪት ፡ ወነቢያት ፡ ሰበኩ ፡ በክርስቶስ ። መምህረ ፡ አሪት ። ብሔረ ፡ አሪት ፡ (ሃይ ፡ አበ ። ግብ፭ ፡ ፴፱ ። አብጥ) ። ከኦሪት ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ የሚጣፉ ፡ ኢያሱ ፡ መሳፍንት ፡ ሩት ፡ እሊህ ፡ ሦስቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እንኳ ፡ ኦሪት ፡ አይባሉም ፡ በግእዝ ፡ ልማድ ፡ ግን ፡ እስከማቸው ፡ ኦሪት ፡ ይባላሉ ። ሰመንቱ ፡ በሓውርተ ፡ አሪት ። አሪት ፡ ዘሌዋውያን ። አሪት ፡ ዘመሳፍንት ። አሪት ፡ ዘሩት ።

**አሪታዊ** ፤ የኦሪት ፤ ኦሪታም ፤ ባለኦሪት ፡ ይሁዲ ፡ ፈላሻ ። አሪታዊት ፡ ጠረጴዛ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አርዮጳጌጤስ** ፤ (ጽር ፡ አሬዎፓጊቲስ) ፤ አርዮስፋጎስ ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ግብ፲፯ ፡ ፴፬) ።

**አርክ** ፤—ወዳጅ ፤—ዐረከ ፡ ዐረከ ፤ ዐርክ ።

**አራም** ፤ ስመ ፡ ነገድ ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ ላይኛው ፡ ሶርያ ፡ ደማስቆ ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፳፪ ። ኢሳ፯ ፡ ፩ ፡ ፰) ።

**አረሚ** ፤ (ሚት ፡ ማያን ፡ ያት) ፤ የአራም ፡ ወገን ፡ የአራም ፡ ቋንቋ ፡ ሱርስት ። አራማዊ ፡ ሶርያዊ ፡ ሕዝብ ፡ አሪታውያንን ፡ እንደ ፡ ጋላ ፡ ኹኖ ፡ ይወርና ፡ ይዘርፍ ፡ ይማርክ ፡ የነበረ ፡ የእስራኤል ፡ ጠላት ።

**አረሚ** ፤ አረመኔ ፡ አሕዛብ ፡ በኦሪት ፡ በወንጌል ፡ የማያምን ። አሕዛብ ፡ ሥርዐት ፡ ያለው ፡ አረመኔ ፡ ሥርዐት ፡ የሌለው ። ሰእምንዎ ፡ ለአረሚ ። አረሚ ፡ እለ ፡ ኢየአምርዎ ፡ ለእግዚ ፡ (ቀሌ ። ሸተስ ፡ ፱ ፡ ፳ ። ሮሜ፱ ፡ ፳፬ ፡ ፴) ።

**አረሚ** ፤ ጽርኣዊ ፡ ግሪክ ፡ ዮናን ። ብሔረ ፡ አረሚኑ ፡ የሐውር ፡ ወይሜህሮሙ ፡ ለአረሚ ። እለ ፡ እምአረሚ ፡ (ዮሐ፯ ፡ ፴፭ ። ፲፱ ፡ ፳ ። ሮሜ፩ ፡ ፲፱ ። ፩ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፱—፳፱) ።

**አረማዊ ፡ ዪ** ፤ (ዊት ፡ ዪት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ የአራም ፡ የግሪክ ፡ ወገን ፡ አሕዛብ ፡ አረመኔ ፡ ክፉ ፡ ጨካኝ ፡ እምነት ፡ ርኅራኄ ፡ የሌለው ። ሶአይሁዳዊ ፡ ወለአረማዊ ። ብእሲት ፡ ተንበላታዊት ፡ አው ፡

አረማዊት ። ኢትትመሀሩ ፡ ፍኖተ ፡ አረማውያን ፡ (ሮሜ ፩ ፡ ፲፰ ። ሲኖዶ ። ኤር ፲ ፡ ፪) ።

**አርማጌዶን ፤ (ዕብ ፡ ሀር ፡ ምጊዶን) ፤** የሀገር ፡ የቦታ ፡ ስም ፤ የንፍታሌም ፡ ዕፃ ፤ (ራእ ፲፮ ፡ ፲፮) ።

**አርመመ ፤—አስረመመ ፤—ረሚም ፡ ረመ ፤ ረመመ ።**

**አርሞን ፤ ኤርሞን ፤ (ዕብ ፡ ሔርሞን) ፤** የተራራ ፡ ስም ፤ ጉማም ፡ በረዷም ፤ የዮርዳኖስ ፡ ራስ ። ፍኖቹው ፡ ልዑል ፡ ነዋኅ ፤ ቅዱስ ። የግእዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ከጽርእ ፡ ስለ ፡ ተቀዳና ፡ በጽርእ ፡ ፊደል ፡ ሀ ፡ ሐ ፡ ኤ ፡ ዒ ፡ የሚባሉ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በሔርሞን ፡ ፈንታ ፡ ኤርሞን ፡ አርሞን ፡ ይላል ፡ (ዘዳ ፫ ፡ ፰ ። ማሕ ፬ ፡ ፰ ። ሔኖ ፡ ፮ ። ፲፫) ።

**አርማስ ፤-ታንኮች ፤-ረሚስ ፡ ረምስ ፤ ረምስ ።**

**አርማስቆስ ፤ (ጽር ፡ አርሚስኮስ) ፤** ድሬ ፤ ሰደፍ ፤ ቀሀረማን ፤ እንደ ፡ ፀሌ ፡ እንደ ፡ መቍጠሪያ ፡ ያለ ፡ ያንገት ፡ ጌጥ ። ባለብሉዮች ፡ ማን ፡ ማንብ ፡ መንቀል ፡ የብር ፡ ዘንግ ፡ ዘሪት ፡ ይሉታል ። ኤፎትን ፡ ተመልከት ፡ (ማሕ ፩ ፡ ፲) ። ቀሀረማን ፡ ብጫ ፡ የንቍላል ፡ አስኳል ፡ የሚመስል ፤ ዕጣን ፡ ዕጣን ፡ የሚሸት ፡ ነው ፤ ፱ኛ ፡ በሙ ፡ ቈርበት ፡ ክሬም ።

**አርዑት ፤-ቀንበር ፤-ርዒው ፡ ረዐወ ።**

**አረፈ ፤ (ዐረብ) ፤** ጠረሰ ፡ አበቃ ፡ ፈጸመ ፡ ደመደመ ።

**አረፍት ፤ (ፋት) ፤** ግድግዳ ፤ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ ካብ ፡ ማንብ ፤ ሥራው ፡ ያለቀለት ። **አረፍት ፡ ይሴውሬኒ ። አረፍት ፡ በይምን ፤ ወአረፍት ፡ በፀግም ። አረፋቲሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡** (ሚራ ፳፫ ፡ ፲፰ ። ዘፀ ፲፬ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፶) ።

**እረፍት ፤—በቁሙ ፤—ዐሪፍ ፡ ዐረፈ ፤ አዕረፈ ።**

**አርቆሚን ፤ (ጽር ፡ አርኪኖም ። ዕብ ፡ ባርቃኒም) ፤** እሾሆች ፤ እሾኽም ፡ ዕንጨቶች ፤ እሾኽቻውና ፡ ቅጠላቸው ፡ ንጫጭ ፡ የኾነ ፤ በረቅ ፡ የሚመስል ፡ ኩሸሽሎች ፡ (መሳ ፰ ፡ ፯ ፡ ፲፮) ። ባለብሉዮች ፡ ማን ፡ ማራር ፡ ይሉታል ።

**ኤረር ፤—ሰማይ ፤—አየር ፡ ኢዮር ።**

**አሪር ፤ ሮት ፤ (አረ ፤ አረረ ፡ የአርር ፡ ይእርር ፡ ይእ ። አረየ) ፤** መማረር ፤ ማጨድ ፡ መቍረጥ ፡ መንቀል ፡ መልቀም ፡ መቃረም ፤ መሰብሰብ ፡ ማሰር ፡ መጕቸት ፡ መከመር ፤ ወቅቶ ፡ ማምረት ፤ በጕታ ፡ መከተት ፡ ያገመሬ ። **ዘዘርዐ ፡ ሰብእ ፡ የአርር ። ትዘርዑ ፡ ወተአርሩ ። ካልእ ፡ ዘይዘርዕ ፡ ወካልእ ፡ ዘየአርር ። ወአንስ ፡ ፈነውኩክሙ ፡ ትእርሩ ። አረርኩ ፡ ከርቤ ፡** (ገላ ፮ ፡ ፯ ። ኢሳ ፴፯ ፡ ፴ ። ዮሐ ፬ ፡ ፴፮ ፡ ፴፰ ። ማሕ ፭ ፡ ፩) ።

— ፤ መራኆኽ ፡ እሪ ፡ ማለት ፡ መጥራት ፡ ማቅራራት ፡ ታላቅ ፡ ድምጥ ፡ መስጠት ፡ የሐዘን ፡ የዘፈን ፡ (ዐረብ) ።

**አራሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤** የሚማርር ፡ ማራሪ ፤ ዐጫጅ ፡ ሰብሳቢ ፡ ለቃሚ ፤ ቃራሚ ። (ተረት) ፡ አራሪ ፡ ለማራሪ ፤ ማራሪ ፡ ለበራሪ ፡ ይተው ።

**አእረረ ፤** አሳጨደ ፤ አሰበሰበ ፤ አስከተተ ። **ያእርሮሙ ፡ ማእረሮ ፡** (፩ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፪) ።

**ተአረ ፤** ተማረረ ፤ ታጨደ ፡ ተሰበሰበ ፤ ተለቀመ ፡ ተቈረጠ ፡ (ድጓ) ።

**እሩር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ርርት) ፤** የታጨደ ፤ የተሰበሰበ ፤ ንዶ ፡ ክምር ፡ ቃርሚያ ። ጥንማ ።

**ትእሪር ፤** ማረራ ፤ ዐጨዳ ፡ ቈረጣ ፡ ስብሰባ ፡ ክመራ ፤ ለቀማ ፤ አለቃቀም ። ውጤት ፤ ምርት ።

**ማእረር ፤ (ራት) ፤** መከር ፤ አዝመራ ፤ ፍሬ ፡ ያልታጨደ ፡ ያልተሰበሰበ ። **በልዑ ፡ ማእረረከ ። መዋዕለ ፡ ማእረር ። ማእረሩሰ ፡ ብዙኅ ። ወምድር ፡ ትሁብ ፡ ማእረራ ። ማእረረ ፡ ምግባሮሙ ፤** (ኤር ፭ ፡ ፲፯ ። ሚራ ፳፬ ፡ ፳፯ ። ማቴ ፱ ፡ ፴፯ ። ዘሌ ፳ ፡ ፲፱ ። ኢሳ ፲ ፡ ፲) ።

**አራራይ ፤** እሪታ ፤ ቅርርት ፡ ታላቅ ፡ ጩኸት ። የዜማ ፡ ስም ፤ የዜማ ፡ ስልት ። ሦስተኛ ፡ ዜማ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አምሳል ። **ሠለስቱ ፡ ዜማ ፤ ዘውእቱ ፡ ግእዝ ፡ ወዕዝል ፡ ወአራራይ ፡** (ስንክ ፡ ግን ፲፩) ።

**አኑራን ፤ (ጽር ። ዕብ ፡ ኤሼል) ፤** ታላቅ ፡ ዛፍ ፡ ቅጠሉ ፡ ጽኑዕ ፡ ቁመቱ ፡ ምጡቅ ፡ የኾነ ፤ ስሙ ፡ ያልታወቀ ፤ ባለብሉዮች ፡ ማን ፡ ሮማን ፡ ይሉታል ። **ወቀበርዎ ፡ ታሕተ ፡ አኑራን ፡** (፩ነገ ፡ ፴፩ ፡ ፲፫) ። ታላቅነቱም ፡ ሊታወቅ ፡ በዜና ፡ መዋዕል ፤ ግእዙ ፡ ዘግባ ፡ ዐማርኛው ፡ ስሉን ፡ ይለዋል ፡ (፩ዜና ፡ ፲ ፡ ፲፪) ።

**አራራት ፤** የኖኅ ፡ ተራራ ፡ ስም ። **አራራት ፡ ነበረት ፡ ታቦት ፡** (ድጓ) ።

**አርሺ ፤ (ቅብጥ) ፤** ሊቅ ፤ አለቃ ። አርሲመርተዳስን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። **አርሺ ፤** ዲያቆን ፡ (አቡሻ ፡ ፶) ።

**ኤራስ ፤ (ኀራስ ፤ ለጋ ፡ ጨቅላ) ፤** ጨረቃ ፡ የጨረቃ ፡ ስም ፤ አራተኛ ፡ ስሟ ። እብሳን ፡ ተመልከት ።

**አርስጣላብ ፤ (ጽር ፡ አስትሮላቦስ) ፤** የፀሐይና ፡ የጨረቃ ፡ የኮከብ ፡ መንጽር ፡ መልካቸውን ፡ አቅርቦ ፡ የሚያሳይ ፡ የሚያስመረምር ። ወይም ፡ መንገዳቸውን ፡ የሚናገርና ፡ የሚያስተምር ፡ የፍልስፍና ፡ መጽሐፍ ። **ወነሥአ ፡ አርስጣላበ ፡ ወነጸረ ፡ ውስቴቱ ፡ ዘይብል ፡ እልመክኑን ፡ ቃይናን ፡ ወሊደ ፡ አርፋክስድ ፡ ወጠነ ፡ ጽሒፈ ፡ አርስጣላብ ፡ እምድኅረ ፡ አይኅ ፤ ወእምድኅሬሁ ፡ ጸሐፉ ፡ ህንዳውያን ፡** (ስንክ ፡ ጥቅ ፳ ። ዮሐ ፡ መደ ፡ ክ፴) ።

**አርሳይሮስ ፤ (ጽር ፡ አርኪሄሬፍስ) ፤** የገዳም ፡ አባት ፡ ሹም ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አርሲመርቴዳስ ፤ (ጽር ፡ አርኪማንድሪታስ)** ፤ ገዳኒ ፡ ከማሁ ፤ የካህናት ፡ አለቃ ፤ አበ ፡ ምኔት ፤ አበ ፡ ማኅበር ፤ ርእስ ፡ ባሕታውያን ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

**አርሶን ፤ (ጽር ፡ አርሲን ። ዕብ ፡ ማሣእ ፡ ሰባል)** ፤ ጭነት ፤ ሸክም ፡ የሚከብድ ፡ የሚያስጨንቅ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ጠርብ ፡ ይሉታል ፡ (፪ነገ ፡ ፳ ፡ ን፳ ። ፩ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፱) ።

**አርሲስ ፤ (ሳን ። ጽር ፡ ኤሬሲስ ፤ ኑፋቄ ፤ ዕልወት)** ፤ መናፍቅ ፡ ዐላዊ ፡ ባህሉና ፡ ትርጓሜው ፡ እንደ ፡ ከሓዲ ፡ እንደ ፡ ቅብት ፡ ከሰው ፡ ከመጣፍ ፡ የማይገጥም ፡ ዐልዋን ፡ ዘይሰመዩ ፡ አርሲስ ፡ በነገረ ፡ ጽርእ ። ኢትጸሊ ፡ ምስለ ፡ አርሲሳን ፡ ዘውእቶሙ ፡ ዐላውያን ፡ (አብጥ ፡ ፵፫ ። ሃይ ፡ አበ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፰) ።

**እርሳስ ፤ —በቁሙ ፤ —ርሳስ ።**

**አሬት ፤ —በቁሙ ፤ —አረየ ፤ አራይታ ።**

**አርቶዶክስ ፤ (ጽርእ)** ፤ ስመ ፡ ጉባኤ ፤ የኒቅያ ፡ ማኅበር ፤ አርቶ ፤ ርቱዕ ፡ ደክስ ፡ ባህል ፡ ሐሳብ ፡ ኅሊና ፡ ስብሐት ፡ ምስጋና ፡ ይኾናል ፤ በተገናኝ ፡ ርቱዐ ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ደኩስበተሬን ፡ ተመልከት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአርቶ ፡ ፈንታ ፡ አርቶ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**አርቶዶክሳዊ ፤** ገዳኒ ፡ ከማሁ ፤ የኦርቶ ደክስ ፡ ወገን ፡ ኒቅያዊ ፡ እውነተኛ ፤ ቅን ፡ በሃይማኖቱ ፡ ሐሰትና ፡ ስሕተት ፡ ጽንት ፡ የሌለበት ። ይኩን ፡ ምእመነ ፡ አርቶዶክሳዊ ። ሃይማኖት ፡ አርቶዶክሳዊት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፪ ። ደዐ ፡ ዘእል) ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይልቁንም ፡ ከሓና ፡ ቅባት ፡ ባህላቸውና ፡ ትምርታቸው ፡ ከቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ የሚጣላ ፡ ስሕተት ፡ የተመላ ፡ ከፉ ፡ ጥፉ ፡ ሲኾን ፡ ኦርቶዶክሶች ፡ ነን ፡ ይላሉ ። (ሥላሴ ፡ ዘይንቅ ፡ ማርቆስ ፡ አርቶዶክሳዊ) ። አርዮስ ፡ ወመምህሩ ፡ ላዐለ ፡ ሐዋርያት ፡ አመክንዮ ፡ ብሂለ ፡ ፍጡር ፡ ወልድ ፡ በቀዳማዊ ፡ ልደቱ ፤ ለአጽድቆ ፡ ሕልም ፡ ነገሮሙ ፡ ከንቱ ። ዮምኒ ፡ ይፈጽም ፡ ዐመፃ ፡ በመስፈርተ ፡ እሉ ፡ ክልኤቱ ፡ እንዘ ፡ ፍናዊሃ ፡ በኑልቈ ፡ ቤቱ ፡ ሰብእ ፡ ዘሉ ፡ ለሃይማኖቱ ፡ ይቀብዓ ፡ ስመ ፡ ምእት ፡ ሠለስቱ ። የኦርቶ ደክስ ፡ ባህል ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በተዋሕዶ ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፡ (ዋሕድ ፡ ዋሐደ) ።

**አርቴውቂኖን ፤ (ጽር ፡ አርኬፍቲኖን ። ዕብ ፡ ሽሚን)** ፤ ዘይት ፡ ወይራ ፡ ዕፀ ፡ ቅብዕ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዋንዛ ፡ ዘማዛ ፡ ይሉታል ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፴፩) ።

**አርቲክል ፤ (ሮማይ ፡ አርቲኩሉስ)** ፤ የስም ፡ ተውላጠ ፤ ለ ፡ ላ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ የሚለይበት ። እልኝና ፡ አሐዱን ፡ ተመልከት ።

**ኤርትራ ፤ (ጽር ፡ ኤሬትራ)** ፤ የባሕር ፡ ስም ፡ ከብርቱ ፡ ስይድ ፡ እስከ ፡ ባሕረ ፡ ህንድ ፡ ወይም ፡ ከስዩስ ፡ ወደብ ፡ እስከ ፡ ባብ ፡ እልመንደብ ፡ ያለ ፡ ባሕር ፡ ቀይሕ ፡ ቀይሓዊ ፡ ማለት ፡ ነው ። ባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ (ባሕረ ፡ ሕምያር) ፤ የቀይ ፡ ሕገቡበ ፡ ባሕር ፤ ነሪዎችና ፡ ጥቍሮች ፡ ያይያሉ ፡ ቀያዮች ፡ የመንና ፡ ሳባ ፡ የሚገዙት ፡ ወይም ፡ ለራሱ ፡ ቅላት ፡ ቀይነት ፡ ያለው ፡ ባሕር ። መሬቱ ፡ ቀይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ቀይ ፡ ስልባቦት ፡ ይንሳፈፍበታል ፡ ቀያይ ፡ ዓሣ ፡ ይወለድበታል ፤ በዙሪያውም ፡ ቀያይ ፡ ዓር ፡ ቅጠል ፡ ያበቅላልና ፡ ቀይ ፡ ያሰኘው ፡ ይህ ፡ ነው ። ባሕርነቱም ፡ ከሜዲተራኒ ፡ እስከ ፡ ህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ገጥሞ ፡ ተያይዞ ፡ በስተምሥራቅ ፡ እስያንና ፡ አፍሪቃን ፡ ይለያል ፡ (ዘፀ፲ ፡ ፲፱ ። ፲፫ ፡ ፲፰ ። ፲፭ ፡ ፬) ።

**አስ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ የማስደረግ ፡ ልማድ ፤ **አቅተለ** ፤ አስገደለ ። ተ ፡ ሲጨመርበት ፡ አስተ ፡ እየኾነ ፡ ወደ ፡ ማደራረግ ፡ ይለወጣል ፤ **አስተቃተለ** ፡ አጋደለ ፤ አገዳደለ ። በስ ፡ ማስ ፡ ላይ ፡ ሲነገር ፡ ስን ፡ እየዋጠ ፡ ይጠብቃል ። **አስበረ ፡ አስተሳበረ** ፤ አሰበረ ፡ አሳበረ ፡ አሰባበረ ። **አስገደ ፡ አሥገረ** ፤ አስገደ ፡ አሠገረ ። የአንና ፡ የአስተን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ። ፪ኛም ፡ ስ ፡ በሌለበት ፡ ማስ ፡ እየገባ ፡ ከአ ፡ ቀለይቶ ፡ የጥሬ ፡ መነሻ ፡ ይኾናል ። **ዐዘዘ ፡ አስዐዘዘ ፡ አስያዘዘ ፡ ስያዝዝ ።**

**እስ** ፤ ያገባብ ፡ ልማድ ፡ እንደ ፡ እን ፡ ያለ ፡ እንን ፡ የመሰለ ። ሦስተኛ ፡ ፊደል ፡ ከኩመ ፡ ሲጨመር ፤ **እስከ ፡ እስኩ ፡ እስመ** ፡ እያለ ፡ ርሑ ፡ ራሱ ፡ ፫ ፡ አገባብ ፡ ይኾናል ፤ ልማድነቱም ፡ ከአስተና ፡ ከእስት ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**አስባብ ፤ —ዘበኞች ፤ —ሰቢብ ፡ ሰበ ፤ ሰበበ ።**

**አሰድ ፤ (ዐረ ፡ እልአሰድ)** ፤ አንበሳ ። ኮከብ ፡ የኮከብ ፡ ስም ፤ አንበሳዊ ፤ አንበስ ፡ አንበሶ ፡ ማለት ፡ ነው ። ኮከብነቱም ፡ የሐምሌ ፡ ነው ። ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ ፴፩ ፡ ዕለት ፡ ፲ ፡ ኬክሮስ ፡ ይመግባል ፡ (አቡሻ ፡ ፫) ።

**አስሀርት ፤ —ሠርቀ ፡ ወርኖች ፤ —ሣሀር ።**

**አሲው ፤ ዎት ፤ (አሰወ ፡ የአሱ ፡ ይእሱ ። ዕብ ፡ ሱር ፡ ዐረ ፡ አሳ)** ፤ መፈወስ ፡ ማዳን ፡ መሸም ፡ ማሠልጠን ። (ጥሬ) ፡ መፈወስ ፡ መዳን ፡ ጤና ፡ ማግኘት ፡ ባለጤና ፡ መኾን ፡ በመዳኒት ፡ ወይም ፡ በታምራት ።

—፤ አስት ፡ ማውጣት ፡ ቡላድ ፡ መምታት ፡ ማንደድ ፡ ማቃጠል ፡ ማሞቅ ፡ ማተኮስ ፡ ማጋል ፡ ማጋም ፡ እሳት ፡ ማድረግ ።

**አሳዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ የሚፈውስ ፤ የሚፈወስ ፤ ፈዋሽ ፡ ተፈዋሽ ።

**አሰ** ፤ ወባ ፡ ዓዳይ ፡ ትኵሳት ፡ ሐኪምና ፡ ፈውስ ፡ የሚያስፈልግ ፡ (ትግሬ) ።

**አሶት** ፤ ፈውስ ፤ ህብት ፡ ፈውስ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥልጣን ፡ (ሉቃሮ ፡ ፲፱ ፡ ፱ ፡ ጵጰ ፡ ፴) ። ኅሊይኩ ፡ ቅድስና ፡ ዘነቢያት ፡ ወአሶተ ፡ ዘሐዋርያት ። እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ንሚአ ፡ አሶተ ፡ (አርጋ ፡ ፯ ። ድጓ) ።

**እሳት ፡** (ብ ፡ እሳውት ። ሱር ፡ ኤሽታ ። ዕብ ፡ ኤሽ) ፡ በቁሙ ፡ የሚነድ ፡ የሚበራ ፡ የሚያቃጥል ፡ የሚበላ ፡ የሚፋጅ ፡ የሚልጥ ፡ የሚለመጥጥ ። ይቡስ ፡ ውዑይ ፡ ብሩህ ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያት ፡ አንዱ ፡ በኹሉ ፡ የሚገኝ ፡ በይብሱቱ ፡ ከነፋስ ፡ በውዑየቱ ፡ ከመሬት ፡ በብርሃኑ ፡ ከውሃ ፡ የሚስማማ ። በአምጣኒ ፡ ዕፁ ፡ ለእሳት ፡ የዐቢ ፡ ነዱ ። እሳት ፡ በላዒ ። ድብረ ፡ ሚካኤል ፡ ወለደት ፡ ሊቃውንተ ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ እሳተ ፡ እሳተ ፡ (ሚራ ፡ ፳፰ ፡ ፲ ። ፅ፬ ፡ ፅ፬ ። ቅኔ) ።

**እሳተ ፡ እሳት ፡** የሰማይ ፡ እሳት ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ። ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እሳት ፡ ፯ ፡ እጅ ፡ የሚበልጥ ፡ (ሔኖ ፲፱ ፡ ፳፱) ።

**እሳተ ፡ ገሃነም ፡** ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ እስራኤል ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለሞሎክ ፡ ሠውተው ፡ ያቃጥሉበት ፡ የነበረ ፡ የሰማያዊ ፡ እሳት ፡ ምሳሌ ፡ (ማቴ፭ ፡ ፳፪) ።

**እሳት ፡ ዘለዓለም ፡** የማይጠልስ ፡ የማይጠፋ ፡ የማያልፍ ፡ ሥቃይ ፡ (ማቴ፳፭ ፡ ፵፩) ።

**እሳተ ፡ ሕይወት ፡** መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ማቴ፫ ፡ ፲፩) ።

**እሳተ ፡ መለኮት ፡** ባሕርይ ፡ አካል ፡ ወይም ፡ እሳትነት ፡ (ቅዳ) ።

**እሳታዊ ፡** የእሳት ፡ እሳታም ፡ እሳትማ ፡ ቀይ ፡ ውዑይ ፡ ተፈጥሮው ፡ ከእሳት ፡ የኾነ ፡ እሳትነት ፡ ያለው ። ሳውዳ ፡ ዘውእቱ ፡ ጠባይዕ ፡ እሳታዊ ። እሳታውያን ፡ እለ ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ እሙንቱ ፡ ኪሩቤል ፡ (ፊላስ ። ቅዳ ፡ ሕር) ።

**እስት ፡** በቁሙ ፡ እስቱ ፡ እስታ ፡ እሳታም ፡ ዕንጨት ።

**አስሐወ ፡—አወለቀ ፡—ስሒው ፡ ስሐወ ።**

**አስሐትያ ፡—ውርጭ ፡—ስሒት ፡ ስሕተ ፡ አስሐተ ።**

**አስጣሮት ፡** (ዕብ ፡ ዐሽታሮት ። ጽር ፡ አስታርቲ) ፡ ጣዖታት ፡ የበግ ፡ መንጋ ፡ የሚመስሉ ፡ በበጎች ፡ አምሳል ፡ የተቀረጡና ፡ የተሣሉ ፡ የበግ ፡ ምስሎች ። ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ ከዋክብት ፡ ሾቦቶ ፡ ስድስቶ ፡ ይሏቸዋል ፡ (መሳፍ ፡ ፲፡) ። ፪ኛም ፡ በአስጣሮት ፡ ፈንታ ፡ አስጦራጢ ፡ አስጥርጥዮን ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (፩ነገ ፡ ፴፩ ፡ ፲) ።

**አሰየ ፡—ሰጠ ፡—ዐስይ ፡ ዐሰየ ።**

**እስያ ፡** (ጽር ፡ አሲያ) ፡ ስመ ፡ ክፍለ ፡ ምድር ፡ ስመ ፡ ብሔር ፡ ካምስቱ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ አንዲቱ ፡ ታላቂቱ ፡ ክፍል ፡ የኤውሮፓ ፡ ምሥራቅ ። የቱርክ ፡ አገር ፡ ደግሞ ፡ ስብቻዋ ፡ ታናሽ ፡ እስያ ፡ ትባላለች ፡ (ሐሥ፩ ፡ ፲፩) ።

**እስከ ፡** (እስ ፡ ከ ። ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ) ፡ በቁሙ ፡ በቅርብና ፡ በሩቅ ፡ ሲገባ ፡ እስከ ፡ እስኪ ፡ በትርናፍ ፡ ዐማርኛ ፡ ድረስ ፡ ይኾናል ። አመ ፡ ሶበ ፡ ጊዜ ፡ ኀበ ፡ ለ ፡ ነ ፡ ያዳምቂታል ፡ ቢር ፡ ይከፍቱስታል ፡ ሳይከፍቱስትም ፡ እስከ ፡ እልህቅ ፡ ወአረሥእ ፡ እስከ ፡ ይመሲ ፡ እስከ ፡ ይደብሕ ፡ እያለ ፡ ብቻውን ፡ ይገባል ። ሲዘረዝር ፡ ግን ፡ ነኝ ፡ ብር ፡ ክፋች ፡ አይርን ፡ እስከኔየ ፡ ኔክ ፡ ኔኪ ፡ ኔሁ ፡ ኔሃ ፡ ኔነ ፡ እያለ ፡ በነ ፡ ይዘምታል ። የዐታን ፡ የጊዜን ፡ የስፍርን ፡ የቍጥርን ፡ የሥራን ፡ ኹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ መድረሻውን ፡ መከተቻውን ፡ ያሳያል ። እስከ ፡ ሶበ ፡ እመጽእ ። እስከ ፡ ጊዜ ፡ ይሠርቅ ፡ ፀሓይ ። በጽሐ ፡ እስከ ፡ ኀበ ፡ ልኁመ ፡ ፈረስ ። ተከዘት ፡ ነፍስየ ፡ እስከ ፡ ለሞት ። እስከነ ፡ ዐረብ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ፍጻሜና ፡ ጭራሽ ፡ በሌለው ፡ ኢወለደት ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ሞተት ። ኢያእመራ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ወለደት ፡ እያለ ፡ ይገባል ፡ (ዕር፲፱ ፡ ቍ፴፰) ።

**እስኩ ፡** (እስ ፡ ኩ) ፡ የጥያቄና ፡ የምክር ፡ የልመና ፡ ቃል ፡ እስኪ ፡ እባክኽ ። ንግርኒ ፡ እስኩ ። እስኩ ፡ ፍታሕ ፡ ለሊከ ። እስኩ ፡ ስምዐኒ ። እስኩ ፡ ሀበኒ ፡ እንደ ፡ እንኳም ፡ ክፈትም ፡ ይገባል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ተምኔት ፡ ተግዳሮት ፡ ዘቻ ፡ ግን ፡ ይኾናል ። እስኩ ፡ ንርአይ ፡ እስኩኬ ፡ ንርአይ ። ይዜንዉከ ፡ እስኩ ፡ ወይንግሩከ ። እስኩ ፡ እመ ፡ ኢትገንዩ ፡ ለምስል ፡ ወኢትስግዱ ፡ (ድጓ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፲፱ ። ዳን፫ ፡ ፲፭) ።

**አሰከ ፡** (የአስክ ፡ ይእስክ ፡ አሲክ ፡ ከት) ፡ ዐሽ ፡ እኰሳሽ ፡ ስነጋ ፡ ቀጠቀጠ ፡ ሰበበ ፡ ቈረጠ ። ደረሰ ፡ ነካ ፡ አዋደደ ፡ ስካ ፡ የተባት ፡ ያለሌ ፡ ይውራ ።

**እስኪት ፡** (ብ ፡ እስኪታት ፡ አሰክት ። ዕብ ፡ ኤሼኽ ። ሱር ፡ አሽክ) ፡ ቍላ ፡ የቍላ ፡ ፍሬ ፡ ቈሊጥ ፡ አስካሉ ፡ ዕንቍላሉ ። ቍልሕን ፡ ተመልክት ። ዘአሐቲ ፡ እስኪት ። አልዐለት ፡ እደሃ ፡ ወአኀዘቶ ፡ በካልኤሆን ፡ አስክቲሁ ፡ (ዘሌ፳፩ ፡ ፳ ። ዘዳ፳፭ ፡ ፲፩) ።

**እስኪት ፡** አባለ ፡ ዘርዕ ፡ ሳይኛው ፡ ዘንጉ ፡ መድረሻ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዘሞተ ፡ እስኪቱ ፡ በሥራይ ። ሠጠቀ ፡ መላእክት ፡ እስኪተ ፡ ለማርያ ፡ ሕልያስ ፡ ሊቀ ፡ ምእተ ፡ መንክስይያት ፡ ሶበ ፡ ከነ ፡ ምስሌሁ ፡ በህየ ፡ ፍትወት ። ለእለ ፡ ይዜምዉ ፡ በእንስሳ ፡ ይትመተር ፡ እስኪቶሙ ። ብእሲ ፡ ዘይፈኑ ፡ እስኪቶ ፡ ውስተ ፡ መንደቅ ፡ አው ፡ ውስተ ፡ ስቍረት ፡ አው ፡ ውስተ ፡ እደሁ ፡ ወይወፅእ ፡ እምኔሁ ፡ ፍትወት ፡ (መጽ ፡ ፈ ። ፈ ልክ ፡ ፳፭ ። ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰ ። ሲኖ ይ) ። አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ ስክየ ፡ እስክየ ፡ ብለው ፡ ይገሱና ፡ እስኪትን ፡ ከዚህ ፡ ያወጣሉ ፡ ፍችውንም ፡ እሶቃሽ ፡ አስክሳሽ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ አይሬሽ ፡ ይሉታል ። ዘየዐቅብ ፡ እስኪቶ ፡ የዐቅብ ፡ ሕይወቶ ፡ (ፊላስ) ።

**አስከት ፡** ጭጉጉኝ ፡ የጕያ ፡ ጠጕር ፡ ሸካራ ፡ ቍርንድድ ። አሽክት ፡ ወይም ፡ አሸክት ፡ የገባስና ፡ የበቈላ ፡

ዐረም ፡ ሽካራ ፡ ቅጠል ፡ በወይና ፡ ደጋ ፡ የሚበቅል ። (ተረት) ፤ ያይጥ ፡ ዱሰት ፡ ማበሪያው ፡ አሽክት ።

**ኤስኬዶሬ ፤ (ጽር ፡ ኤክሴድሬ) ፤** የዕቃ ፡ ቤት ፡ ዕልፍኝ ። (ሕዝ፵ ፡ ፵፬) ።

**አስካል ፤—ዘለላ ፡ ፍሬ ፤—ሰኪል ፡ ሰከለ ፤ ሰክል ።**

**አስኬማ ፤ (ጽር ፡ ስኺማ) ፤** ልብስ ፡ መልክ ፡ ቅርጽ ፡ ገጽ ። **ነሥአ ፡ አርአየ ፡ ገብር ፡ ወኮነ ፡ በአምሳለ ፡ ሰብእ ፡ በአስኬማሁ ። ወበአስኬማሁ ፡ አስተርአየ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡** (ቂር ፡ ጳላ) ።

**አስኬማ ፤ (ሱር ፡ ኤስኪማ) ፤** በቂሙ ፡ ልብስ ፡ ምንኵስና ፡ ከቀሚስ ፡ ከቅናት ፡ ከቆብ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ የሚለበስ ፡ የፍጻሜ ፡ ምንኵስና ፡ ምልክት ። ይኸውም ፡ ከንት ፡ ክንቀልባ ፡ እንደ ፡ እንቢያጉሥ ፡ ኹኖ ፡ የሚሠራ ፡ ፲፪ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ያለበት ፡ ነው ። ከስኪማ ፡ በኋላ ፡ ባሕታዊ ፡ መኾን ፡ መዝጋት ፡ እጽንዖ ፡ በኣት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከገዳም ፡ መውጣት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መግባት ፡ ክልክል ፡ ነው ። መልአኩ ፡ ለእንጦንዮስ ፡ ሰለ ፡ ሰጠውና ፡ ምንኵስና ፡ ሕገ ፡ መላእክት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ልብሱም ፡ አስኬማ ፡ መላእክት ፡ ይባላል ። **አልበስዎ ፡ አስኬማ ፡ ዘመላእክት ። ዳንኤል ፡ አስኬማ ፡ መላእክት ፡ ዘለብሰ ። አስኬማክሙ ፡ አልባቲ ፡ ሙስና ፡** (ስንክ ፡ መስ፲፰ ። ኀዳ፲፯ ። ድጓ) ።

**አስከሬን ፤ (ናት ። ሮማይ ፡ ስክሪኒዉም) ፤** የገንዘብ ፡ መያዣ ፤ ታናሽ ፡ ማፋዳ ፡ ኰረጆ ፤ ቀፎ ናማት ፡ ከረጢት ፤ ኪስ ፡ ሙዳይ ፤ ተረንተሬ ። የወርቅ ፡ የብር ፡ የገንዘብ ፡ ማጥን ፤ የልብስ ፡ የጌጥ ፡ የሽልማት ፡ መዝገብ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ (ዮሐ፲፪ ፡ ፮ ። ፲፫ ፡ ፳፱) ። **መባእ ፡ አስከሬን ፡ ይሁዳ ፡ የዐቅብ ። መጋቤ ፡ አስከሬን ። ይሳሕዉ ፡ አስከሬናተ ፡ ሰርጕኪ ፡** (ዲድ ፡ ፳፱ ። ሲኖዶ ። ኢሳ፫ ፡ ፳፯) ።

—፤ መቃብር ፡ የሬሳ ፡ ማጥን ፡ ሮጥብ ፡ ሬሳ ፡ ወይም ፡ ደረቁ ፡ የፈረሰው ፡ የበሰበሰው ። ይህ ፡ ደግሞ ፡ የነፍስ ፡ ማጥን ፡ ማለት ፡ ነው ። ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ አይወጣም ።

**እስኪት ፤—እስክ ፤—አሰከ ።**

**አስል ፤ (ትግሬ ፤ ዐረ) ፤** ዘር ፡ ሥር ፡ ጕንድ ፡ የትውልድ ፡ ምንጭ ።

**እስላም ፤—በቁሙ ፤—ሰሊም ፡ ሰለመ ፡ አስለመ ።**

**እስመ ፤ (እስ ፡ መ) ፤** ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ። ና ፡ ስለ ፡ እንደ ፡ ብሎ ፡ ሲል ፡ እና ፡ ቢያ ፡ ይኸናል ። **አንዘ ፡ ይሔሰን ፡ እስመ ፡ ኢነበሓ ። ምንትኑ ፡ ዝ ፡ ነገር ፤ እስመ ፡ ይኤዝዞሙ ። ንእዶ ፤ እስመ ፡ ከመ ፡ ጠቢብ ፡ ገብረ ፡ ና ፡** (ማቴ፲፭ ፡ ፳ ። ሉቃ፱ ፡ ፴፮ ። ፲፯ ፡ ፰) ። **ሞተ ፡ እስመ ፡ ሐመ ፡ ተርፈ ፡ እስመ ፡ ደከመ ፡ መጽሰወ ፡ እስመ ፡ ጾመ ፡** ስለ ፡ ናና ፡ ስለ ፡ እንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ ና ፡ በገባበት ፡ ስለ ፡ ስለ ፡ በገባበት ፡ ና ፡ ይገባል ። **ዘይክሕድ ፡ ወይብል ፡ እስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ኢኮነ ፡ መሲሐ ። እሙን ፡ ነገር ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ መጽአ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ። ጽሑፍ ፡ እስመ ፡ አሐዱ ፡ እምአኀዊሁ ፡ መጽአ ፤** እንደ ፡ (፩ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፳፪ ። ፩ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። ፊልክ ፡ ፶፱) ። **አምጽኡ ፡ ወርቀ ፡ እስመ ፡ ንጉሥ ፡ ውእቱ ።** ንጉሥ ፡ ነውና ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፤ ንጉሥ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡ ቢሉ ፡ ያሰኛል ። ብለውና ፡ ቢሉ ፡ የውእቱ ፡ ማቅኛ ፡ ትርፍ ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የእስመ ፡ ዘይቤ ፡ አይደለም ። **ጻዐሎ ፡ እስመ ፡ ገብር ፡ አልዐሎ ፡ እስመ ፡ ኄር ፤** ባሪያ ፡ ብሎ ፡ ለጋስ ፡ ብሎ ፡ እያሰኘ ፡ በሚስማማው ፡ ቃል ፡ ይፈታል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ናሁ ፡ ይኸናል ፡ ናሁ ፡ ደግሞ ፡ እስመ ፡ ይኸናል ። እኮና ፡ ቢያ ፡ ሲኾን ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፡ ነው ። **እስመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ አኀዝዙ ፤** ብዙ ፡ ናቸው ፡ እኮ ፤ እኮን ። **እስመ ፡ ርኢክኒሁ ፡ አመንክኒ ፤** አይተኸ ፡ ቢያ ፡ ስለ ፡ ተባለም ፡ ይፈታል ። **እስመ ፡ እንዘ ፡ ትሰምዕ ፡ ተጸመምክኒ ፤** ሰምተኸ ፡ ቢያ ፤ እየሰማኸ ፡ ቢያ ፡ ያሰኛል ። የቀረውን ፡ ባገባብ ፡ ተመልከት ፡ (ዕር፲፱ ፡ ቍ፳፮) ።

**አስማድዮስ ፤ (ጽር ፡ አስሞዴዎስ) ፤** የጋኔን ፡ ስም ፤ ሾተላይ ፡ ጋኔን ፤ በሴት ፡ ዐድሮ ፡ ወንዶችን ፡ በወንዶች ፡ ዐድሮ ፡ ሴቶችን ፡ የሚፈጅ ፡ (ጦቢ፫ ፡ ፰ ፡ ፲፯ ። ዮሐ፱ ፡ ፲፰ ። ማቴ፳፱ ፡ ፳፫—፳፯) ።

**አሶንያ ፤** ጨረቃ ፡ የጨረቃ ፡ ስም ። እብላንና ፡ ኢራብን ፡ ተመልከት ፡ (ሔኖ፸፰ ፡ ፪) ።

**አስፈሊጦስ ፤ (ጽር ፡ አስፋሊቶስ) ፤** የጦብ ፡ የሸክላ ፡ ሙቃ ፡ የሙጫ ፡ ቅጥራን ፡ ለጦብ ፡ ለሸክላ ፡ የሚቀባ ፤ የሚለቀለቅ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሰሊጥ ፡ የባሕር ፡ ዐረፋ ፡ ይሉታል ፡ (ዘፀ፪ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፲ ። ፵፯ ። መቃ ፡ ገ፪ ። ስንክ ፡ ታኅ፪) ።

**አስፌም ፤ (ጽር ፡ ሄሴፊም ። ዕብ ፡ አሱፊም) ፤** የቦታ ፡ ስም ፡ መካን ፡ ጉባኤ ፤ መሰብሰቢያ ፡ መከማቻ ፡ ወይም ፡ ከምቹዎች ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዐጥረ ፡ ገጥ ፡ ይሉታል ፡ ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ መቅረቡን ፡ ያሳያል ፡ (፩ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፲፯) ።

**እስፍንቱ ፤—ስንት ፤ ምን ፡ ያኽል ፤—ሰፈነ ፡ ሰፈነ ፡ ስፍን ፤ እስፍንት ።**

**እስፍንቶፎኔሕ ፤ (ጽር ፤ ቅብጥ ፡ አብስ ንቶምፋኔኽ) ፤** የፍልስፍና ፡ ስም ፡ ፈርዖን ፡ ለዮሴፍ ፡ ያወጣለት ፡ ከግብጹ ፡ ኅቡእ ፡ ማእምረ ፡ ኅቡኣት ። ጸፈነትን ፡ ተመልከት ። (ዘፍ፵፩ ፡ ፵፭) ።

**አስፋር ፤ (ዐረ ፡ አጽፈር) ፤** ያይነት ፡ ስም ፡ ብጫ ፡ ወርቅ ፡ የሚመስል ። **አከደር ፡ ወአስፋር ፡** (መቃ ፡ ገ፫) ።

**አስፋርስ ፤ (አው ፡ መስፈርስ) ፤** የወፍ ፡ በሽታ ፡ ለውነት ፡ ወይበ ፡ የሚያስመስል ፡ ብጫ ፡ የሚያ

ደርግ ። ወየሐምም ፡ ሕማመ ፡ መስፈርስ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

**አስፈር ፤ (ጽር ፡ ሬጎስ ። ዕብ ፡ ዳሌቄት) ፤** ብርቱ ፡ ትኵሳት ፡ ከልክ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ። የሆድ ፡ በሽታ ፤ ብጫ ፡ የሚያደርግ ፤ የሚያጠወልግ ። ይቀሥፈክ ፡ እግዚ ፡ በደዌ ፡ ሲሕ ፡ ወበፈፀንት ፡ ወበአስፈር ፡ (ዘዳ ፳፰ ፡ ፳፪) ።

**አስፌር ፤ —ዓምና ፤ – ሰፈር ፡ ሰፈረ ።**

**ኤስፋር ፤ (ዕብ ፡ ኤሽፋር) ፤** ክፍል ፡ ዕድል ፡ የሥጋ ፡ መቍነን ፡ አንድ ፡ ሙዳ ፡ ጕማ ፡ የልኳንረድ ፡ ሙት ፡ የሚያኽል ። ፋር ፡ የሚዛን ፡ ስም ፡ ልኩ ፡ ፯ ፡ ጕማ ፡ የሚያነማ ፤ ኤስፋር ፡ የፋር ፡ ፯ኛ ፡ እጅ ፡ ክ፯ ፡ አንድ ፡ (፩ዜና ፡ ፲፮ ፡ ፫) ።

**አስፈሬድ ፤ (ዳት ። ጽር ፡ ስፒሪዶስ) ።** ቅርጫት ፡ እንቅብ ፤ ወራንታ ፤ የእንቅብ ፡ የቀፎ ፡ የጐታ ፡ ዐይነት ፡ ከቀጫጭን ፡ ሐረግ ፡ ከለበቅ ፡ ከሸንበቆና ፡ ከቀርከሓ ፡ የሚሠራ ፡ (ማቴ፲፭ ፡ ፴፯ ። ማር፰ ፡ ፰ ። ግብ፱ ፡ ፳፭ ። ገድ ፡ ተክ ። ዳን፲፫ ፡ ፴፫) ።

**አስቀጢን ፤ (ጽር ፡ ስቃክት) ፤** ጥሩ ፡ ሽቱ ፡ ከዕጣን ፡ ከከርቤ ፡ የሚወጣ ፤ ለትኵስ ፡ ሬሳ ፡ የሚቀባ ፡ ሬሳን ፡ እንዳይገማና ፡ እንዳይፈርስ ፡ እንዳይበሰብስ ፡ የሚያደርግ ። ሐንጠንና ፡ ስጡቃጤን ፡ እዩ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (አቡሻ ፡ ፵፰) ።

**አስቄጥስ ፤ (ሮማይ ፡ አስኬታ) ፤** በረሓ ፡ የበረሓ ፡ ስም ፡ በምድረ ፡ ግብጽ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፤ የመቃርዮስ ፡ ክፍል ፡ ገዳም ፡ ሲሃት ። አ ፡ አልቦ ፤ ስኬታ ፡ ጽላሎት ፤ በተገናኝ ፡ አልቦ ፡ ጽላሎት ፡ ማለት ፡ ነው ። ቀድሞ ፡ ብዙ ፡ ገዳማት ፡ ነበሩበት ፤ ዛሬ ፡ ያሉት ፡ ግን ፡ ፬ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ የታላቁ ፡ መቃርዮስና ፡ የመክሲሞስ ፡ የዱማቴዎስ ፡ ያባ ፡ ብሶይና ፡ የዮሐንስ ፡ ከማ ፡ (ስንክ ፡ መጋቢት ፡ ፈልክ) ። በቅብጥ ፡ ቋንቋ ፡ ግን ፡ ሚዛን ፡ የሚዛን ፡ ሳሕን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ መዳልወ ፡ አልባብ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅምት) ።

**አስቀሎብ ፤** አርስጣጣብ ፤ የፍልስፍና ፡ ከታብ ፡ መጽሐፈ ፡ ኮከብ ። አስቀሎብና ፡ አርስጣጣብ ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ናቸው ። ወገብረ ፡ በጥበብ ፡ መጽሐፈ ፡ አስቀሎባ ፡ ወራእየ ፡ ከዋክብት ፡ ወመዳልወ ፡ ፀሓይ ፡ (ክብ ፡ ነገ) ።

**እስቁፍ ፤ (ዐረ ፡ ኡስቁፍ) ፤** ኤጲስቆጶስ ፡ ሲያበዛ ፡ አስቃፍ ፡ ይላል ፡ (ስንክ ፡ ጥቅምት ። ነሐሴ) ።

**አሰር ፤ —ፍለጋ ፤ —አሚር ፡ አሠረ ።**

(ጥ) **አሰረ ፤ —ቀጠረ ፤ ዐሥር ፡ አደረገ ፤ —ዐሥሮ ፤ ዐሠረ ።**

**አሶር ፤ (ዕብ ፡ አሹር) ፤** ስመ ፡ ነገድ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፤ ታናሽው ፡ ሶርያ ፡ ነነዌ ፡ (ዘፍ ፲ ፡ ፲፩ ፡ ፳፪) ።

**አሲር ፤ ሮት ፤ (አሰረ ፡ የአስር ፡ ይእስር ፡ ይእ ። ዕብ ፡ አሳር ። ሱር ፡ ኤሳር ። ዐረ ፡ አሰረ) ፤** ማሰር ፡ ማቈራኘት ፡ ማጣመር ፡ ማዛወግ ፡ ኹለቱን ፡ ሦስቱን ፡ ወይም ፡ ብዙውን ፡ አንድ ፡ ማድረግ ፡ ማከት ፡ መተብተብ ፡ ማጋዝ ፡ ማውገዝ ፡ መገዘት ፡ መለየት ። እስሮ ፡ በእዴሁ ፡ ወእገሪሁ ። ወአሰረ ፡ ኃሊናሁ ፡ ምስለ ፡ እግዚ ። የአስር ፡ በአሥራው ። እስርዎሙ ፡ ከላስስተ ። የአስሩ ፡ ጾረ ፡ ዐቢየ ። አሰሮ ፡ ለሰይጣን ። አውገዝኑ ፡ ወአሰርኑ ፡ (ሔኖ፲ ፡ ፬ ። ሬልክ ፡ ፳፬ ። ቅዳ ፡ ማሩ ። ማቴ ፲፫ ፡ ፴ ። ፳፫ ፡ ፬ ። ድጓ ። መቅ ፡ ታም) ።

**አሳሪ ፤ (ሬት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ አሰርት) ፤** በቊሙ ፡ የሚያስር ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ። እግዕዝነ ፡ ለአልነ ፡ እማእሰረ ፡ ኀጢአት ፡ ዘአሰረነ ፡ አሳሪ ። ወአሳሪሁ ፡ (ግንዘ ። መቅ ፡ ወን) ።

**እእሰረ ፤** አሳሰረ ፡ አስጋዘ ።

**ተአስረ ፤** ታሰረ ፤ ተቈራኘ ፡ አንድ ፡ ኾነ ። ከመ ፡ ከልብ ፡ ዘየሐውር ፡ ለተአስሮ ። ተአስረ ፡ በሲሁ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ። ተአስረት ፡ ነፍስ ፡ በሥጋ ። ነፍሰ ፡ ዮናታን ፡ ተአስረት ፡ በነፍሰ ፡ ዳዊት ፡ (ምሳ፯ ፡ ፳፪ ። ግብ፳፩ ፡ ፲፩ ። ዮሴፍ ። ፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፩) ።

**ተኣሰረ ፤** ተሳሰረ ፤ ተቈራኘ ፤ ተቈላለፈ ።

**እሱር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ስርት) ፤** የታሰረ ፡ የተሳሰረ ፤ የተቈራኘ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፤ እስር ፤ እስርስር ። ንዋይ ፡ ዘኢክነ ፡ እሱረ ፡ ማእሰር ፡ ባዕሌሁ ። እሱራን ፡ ውስተ ፡ ፈለገ ፡ ኤፍራጥስ ። እመ ፡ ክንከ ፡ እሱረ ፡ ምስለ ፡ ብእሲትከ ። ብእሲት ፡ ዘእስርት ፡ በሕግ ። ዘአሰርከ ፡ በምድር ፡ ይኩን ፡ እሱረ ፡ በሰማያት ፡ (ዘኍ፲፱ ፡ ፲፭ ። ራእ፱ ፡ ፲፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፳ ። ፳፭ ። ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱) ።

**እስረት ፤** ማሰር ፡ መታሰር ፡ አስተሳሰር ፡ እስራት ፡ እስርነት ። ውሂብ ፡ እምዲኅረ ፡ ስኢል ፡ እስርተ ፡ እድ ፡ ውእቱ ፤ ወውሂብሰ ፡ ዘእንበለ ፡ ይስአል ፡ ፈቲሐ ፡ እድ ፡ ውእቱ ። በእንተ ፡ እስረቱ ፡ በሐብል ። ለዘይደልዎ ፡ እስረት ። አሰርዎሙ ፡ ክቡደ ፡ እስረተ ፡ (ፈላስ ። አዋል ። ፈ ፡ መ ፡ ፬ ፡ ፲፭ ። መቃ ፡ ገ፪) ።

**ማእሰር ፤ (ራት ፤ መእስር ። ማእሰርት ፤ መእስርት ፤ ታት) ፤** ማሰሪያ ፡ መታሰሪያ ፡ የእስራት ፡ ቦታ ፡ መጣሪያ ። ታወፅእሙ ፡ ለሙቁሓን ፡ እማእሰር ። ማእሰርተ ፡ ኀጺን ። መኣስርቲሆሙ ፡ ሰርጕ ፡ ያክንት ፡ (ኢሳ፵፪ ፡ ፯ ። ሔኖ፶፭ ፡ ፫ ። ሚራ፯ ፡ ፴) ።

— ፤ ልባጥ ፡ ልብጣት ፡ የናስና ፡ የማንብ ። ወማእሰሩ ፡ በዕፀ ፡ ብሔር ፡ (፩ዕገ ፡ ፯ ፡ ፳፱) ።

**ማእሰረ ፡ ግዘት ፤** የግዝት ፡ ቃል ፡ ውጉዝ ፡ ማለት ፡ (አፈ ፡ ተ፱) ።

**ማእሰረ ፡ ልሳን ፤** ድዳነት ፡ ዝምታ ፡ (ማር ፡ ፯ ፡ ፴፭) ።

**ማእሰረ ፡ ዐመፃ ፤** ኀጢአት ፡ ክሕደት ፡ (ቅዳ) ።

**ማእሰረ ፡ ሰላም ፤** ፍቅር ፡ አንድነት ፡ (ኤፌ ፬ ፡ ፫) ።

**ማእሰረ ፡ ቀዋስብ ፤** የግቢ ፡ ሥርዐት ፡ ተክሊል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፱) ። በነገር ፡ ኹሉ ፡ እየተናበበ ፡ እንደ ፡ በልቱና ፡ እንዳወራረዱ ፡ ይፈታል ።

**አስተአሰረ ፤** አስተሳሰረ ፡ አያያዘ ፡ አዋሰበ ፡ አቈረኛኝ ።

**አስራብ ፦ ፈሳሾች ፦ ሰረበ ፡ ሰረበ ፡ ሰርብ ።**

**አሰርዮን ፤ (ጽር ፡ አሳሪዎን ። ዕብ ፡ ኢሳር) ፤** ታናሽ ፡ ገንዘብ ፤ የገንዘብ ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ሶልዲና ፡ እንደ ፡ ቤሳ ፡ ያለች ፡ መዳብ ፤ ንሐስ ፡ (ማቴ ፲ ፡ ፳፱ ። ሉቃ ፲፪ ፡ ፮) ።

**ኤሲሳህ ፤ (ዕብ ፡ አሺሻህ) ፤** የወይን ፡ የበለስ ፡ ቋንጣ ፡ የመጠጥ ፡ ዕቃ ፡ ብርጭቆ ፡ ጠርሙዝ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ፤ በመማሪያው ፡ ጠጅን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ባለብሉዮችም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የዘቢብ ፡ ጕድጓድ ፡ ይሉታል ። ምስጢሩ ፡ ግን ፡ ስሱንና ፡ ስድስን ፡ ያሳያል ፤ የኢን ፡ ፯ኛ ፡ እጅ ፡ ፯ኛ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ከ፯ ፡ ፩ ፡ ማለት ፡ ነው ። የኢንንና ፡ የኤስፋርን ፡ ፍች ፡ እይ ፡ (፩ዜና ፡ ፲፮ ፡ ፫) ።

**እሳት ፦ በቁሙ ፦ አሲው ፡ አሰወ ።**

**አስተ ፤ (አስ ፡ ተ) ፤** አስ ፡ የማስደረግ ፤ ተ ፡ የመደረግና ፡ የመደራረግ ፡ ልማድ ። በተገናኝ ፡ ኹለቱ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፤ አስተ ፡ የማድረግና ፡ የማስደረግ ፡ የማደራረግ ፡ ይኾናል ፤ መደቡ ፡ ግን ፡ የማደራረግ ፡ ነው ። የማድረግና ፡ የማስደረግ ፡ ሲኾን ፡ ሥርወ ፡ ቀለሙን ፡ ግእዝና ፡ ሳድስ ፡ ያደርጋል ፤ ይኸውም ፡ በአ ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ ነው ። ግእዝ ፡ ሲያደርግ ፤ ገበረ ፡ አስተገበረ ፤ ሐመመ ፡ አስተሐመመ ፤ ሐመቀ ፡ አስተሐመቀ ፤ ሐቀረ ፡ አስተሐቀረ ፤ ፀጸበ ፡ አስተፀጸበ ፤ ቀጸለ ፡ አስተቀጸለ ፤ ረሰየ ፡ አስተረሰየ ፡ ይላል ። ሳድስ ፡ ሲያደርግ ፤ በፅዐ ፡ አስተብፅዐ ፤ በቍዐ ፡ አስተብቍዐ ፤ ነፍሰ ፡ አስተንፈሰ ፤ ነተነ ፡ አስተንተነ ፤ ፈሥሐ ፡ አስተፍሥሐ ፤ ርእየ ፡ አስተርእየ ፤ ሰረየ ፡ አስተስረየ ፡ ይላል ። የማደራረግ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ ሥርወ ፡ ቀለሙን ፡ ራብዕ ፡ ያደርጋል ፤ መለዮው ፡ ይህ ፡ ነው ። ይህም ፡ ቢደረ ፡ አስተባደረ ፤ ገብአ ፡ አስተጋብአ ፤ ደለወ ፡ አስተዳለወ ፤ ወደየ ፡ አስተዋደየ ፤ ነበረ ፡ አስተናበረ ፤ ሠነየ ፡ አስተሣነየ ፤ ቀተለ ፡ አስተቃተለ ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ። ልማድን ፡ ተመልከት ።

**ኤስቴኤኪራን ፤ (ጽር ፡ ኢኽሲኢራን) ፤** ዓማት ፡ ዓሦች ፡ ዓሣዎች ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዓሣ ፡ ወጋሮች ፡ ይሉታል ፡ (ኑሐ ፲፪ ፡ ፴፱) ።

**እስትጉቡእ ፦ ክምቹ ፦ ገብአ ፡ አስተጋብአ ።**

**ኤስታዎስ ፤ (ጽር ፡ ኤስ ፡ ቴዎስ) ፤** አሐዱ ፡ አምላክ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ ፲፱ ። ሚያ ፴) ።

**አስትዓ ፦ ግብር ፦ ሰቲዕ ፡ ሰትዐ ።**

**አስቴር ፤ (ትግሬ) ፤** ሰማይ ፡ ጠፈር ፡ አየር ፡ ፈለክ ።

**አስታር ፤ (ዕብራ) ፤** ሰማያዊ ፡ ጠፈራዊ ፡ ኮከብ ፤ ኮከበ ፡ ሠርክ ፡ ፀሓይ ፡ ስትገባ ፡ ወዲያው ፡ ታይቶ ፡ ወዲያው ፡ የሚጠፋ ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ አስታር ፡ በሸኽ ፡ ወይም ፡ አስታርቦ ፡ ሽሽ ፡ የሚባል ። ኮከባዊ ፡ ዕንቍ ፡ አበባ ፤ የባሕር ፡ እንስሳ ፤ መልኩና ፡ ቅርጹ ፡ ኮከብ ፡ የሚመስል ፡ የኮከብ ፡ ዐይነት ። እስመ ፡ ኢይሁብ ፡ እግዚ ፡ አስታረ ፡ ሞገስ ፡ (ሢራ ፴፮ ፡ ፳፩) ። ጽርኡ ፡ ግን ፡ ኢተውህቦ ፡ ጸጋ ፡ እግዚ ፡ ይላል ።

**አስትሮን ፤ (ጽርእ) ፤** ግዘፈ ፡ ብርሃን ፡ ስሌዳ ፡ ከበብ ፤ ወይም ፡ ግዘፋን ፡ ብርሃናት ፡ ፀሓይ ፡ ጨረቃ ፡ ኮከብ ።

**አስታር ፤ (ዐረ ፡ ኢስታር) ፤** ስጢጥራ ። የስጢጥራን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። አስታር ፡ ዘይቤ ፡ ፲፱ ፡ ወቄት ፡ ይላል ፤ የግምት ፡ አፈታት ፡ (ጥሬ ፡ ሰዋ) ።

**አስቴር ፤ (ዕብ ፡ ኤስቴር) ፤** ኅብአት ፡ ስውርት ። ወሰት ፡ ዘስማ ፡ አስቴር ፡ (አስቴ፪ ፡ ፯) ።

**አስጳዳቶስ ፤ (ጽር ፡ አስፓላቶስ) ፤** የሽቱ ፡ ዕንጨት ፤ እሾኽም ፤ ሥሩ ፡ ከሽቱ ፡ ጋራ ፡ የሚቀመም ፡ የሚነጠር ። ባለብሉዮች ፡ ይርዕኒ ፡ ይሉታል ፡ (ሢራ፳፬ ፡ ፲፭ ። አርጋ ፡ ፮) ።

**ኤቴ ፤ (ጽርእ) ፤** ንጥፍ ፡ ደንጊያ ፡ ስፌ ፡ ታላቅ ፡ ልሙጽ ፡ (ፔንጥ ፡ ፩ ፡ ፱) ።

**አቴው ፤ ዎት ፤ (አተወ ፤ አቶ ፡ የአቱ ፡ ይእቱ ። ዕብ ፡ አታህ ። ሱር ፡ አታእ ። ዐረ ፡ አታ) ፤** መግባት ፤ መመለስ ፤ መምጣት ፤ እቶ ፡ መባል ፡ ከሰው ፡ ቍጥር ፡ መግባት ፤ እቻ ፡ መኾን ፡ መተካከል ፡ ከሚስት ፡ ከባልንጀራ ። ተአቱ ፡ መቃብሪከ ። እቱ ፡ ኀበ ፡ ሕዝብከ ። ወአተወ ፡ እምነበ ፡ መዝበር ። ሰእመ ፡ ዳኅነ ፡ አቶክሙ ። ይጐንዲ ፡ አቲወ ፡ (ኢዮ፭ ፡ ፳፮ ። ዘዳ ፴፪ ፡ ፶ ። ኤር፲፱ ፡ ፲፱ ። ጦቢ፰ ፡ ፲፮ ። ማቴ፳፬ ፡ ፵፰) ።

**አታዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ አተውት) ፤** የሚገባ ፡ ገቢ ፡ ተመላሽ ፡ መጪ ፡ እቻ ፡ እኩያ ።

**እትወት ፤** መግባት ፤ መመለስ ፡ ምላሳ ፤ አመጣጥ ። በንግደትከ ፡ ወበእትወትከ ። ቡሩክ ፡ ይኩን ። ውፍረትክሙ ፡ ወእትወትክሙ ፡ (መገ ፡ ፪፰ ። ማን፱) ። እንዘ ፡ የአቱ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እትወቶ ፡ ይላል ፤ የመሳሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ማር፲፭ ፡ ፳፭ ። ሉቃ፳፫ ፡ ፳፮) ።

— ፤ ምርት ፡ ውጤት ፡ የምድር ፡ ዐሳብ ፤ ፍሬ ። በአምጣነ ፡ እትወተ ፡ እክለ ፡ ገራህቱ ። ወይክውን ፡ እትወቱ ፡ በእለ ፡ ይነድቁ ፡ ሀገረ ። በእትወተ ፡ አክማሪሁ ። እንበለ ፡ ዘርዐ ፡ እምድር ፡ እትወተ ፡ (ዘሌ፳፭ ፡ ፲፮ ። ሕዝ፵፰ ፡ ፲፰ ። መቃ ፡ ፯፱ ። ድጓ) ።

**አእተወ**፤ አገባ ፡ አስገባ ፡ መለሰ ፤ አመጣ ። ዅሎ ፡ ጸረ ፡ ያእትዉ ፡ ኢየሩሳሌም ። ያእትዎሙ ፡ ብሔሮሙ ። ያእትዉ ፡ ጸባሕተ ፡ ለንጉሥ ፡ (ነሐ፲፫ ፡ ፲፮ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፪ ። ሺዕዝ ፡ ፱ ፡ ፮) ።

**ምእታው**፤ **(ዋት)**፤ መግቢያ ፡ ማግቢያ ፡ መመለሻ ፡ መምሚያ ፤ ቤት ፡ አገር ። ከመ ፡ ይኩን ፡ ምእታዊክሙ ፡ ኀበ ፡ መላእክት ። ምእታዊሆሙ ፡ ውስተ ፡ ፈለገ ፡ ቢሶል ። ወምእታዊሰ ፡ እርማቴም ። ምእታወ ፡ አፍራሲሁ ፡ እምኔ ፡ ግብጽ ፡ (ሄርማ ። ቀሌ ። ፳ነገ ፡ ፮ ፡ ፲፮ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፳፰) ።

**እቶን**፤ **(ናት ። ሱር ፡ አቱና ። ዐረ ፡ አቱን)**፤ የማድ ፡ ቤት ፡ ፉርን ፡ ማብሰያ ፡ መጋገሪያ ፡ ምድጃ ፡ የእሳት ፡ ጕድጓድ ፡ እቶ ፡ ኖራ ፡ ክሰል ፡ የሚያወጡበት ፡ ጡብ ፡ ሸክላ ፡ የሚተኰሱበት ። ብሱል ፡ በእቶን ። ከመ ፡ እቶን ፡ ዘአንደዱ ፡ ለኀቢዝ ፡ ኅብዝት ። ለእመ ፡ ገብረ ፡ አሐዱ ፡ እቶነ ፡ ዘየዐርግ ፡ እምኔሁ ፡ ጢስ ። በዓለ ፡ እቶን ። እቶነ ፡ ገሃነም ። እቶነ ፡ ኀጺን ፡ (ዘሌ፪ ፡ ፬ ። ሆሴ፯ ፡ ፬ ። ፍ፡ ነ ፡ ፴፮ ። ኛ፫ ። ሱቱ ፡ ዕዝ፮ ፡ ፳ ። ዘዳ፬ ፡ ፳) ።

**እትዌቁህ**፤ **(ዕብ ፡ አቴቌይሃእ)**፤ የግንብ ፡ ፀምድ ፤ ሕንጻውን ፡ ለማጽናት ፡ ዐብሮ ፡ የተሠራ ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ የቆመ ፡ ከላይ ፡ በቀስተ ፡ ደመና ፡ የተያያዘ ፡ (ሕዝ፵፩ ፡ ፳) ።

**ኢትዮጵያ**፤ **(ጽር ፡ ኢቴዮፒአ ። ዐረ ፡ ሱዳን ። ዕብ ፡ ኵሽ ፤ ስመ ፡ ነገድ)**፤ የመልክና ፡ የሕብር ፡ የሀገር ፡ ስም ፤ የሱዳኖች ፡ አገር ፡ መላው ፡ ጠቅላላው ፤ ከማብጽ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ። ጥቍር ፡ ጠቋሬ ፡ ክስልማ ፡ የጥቍሮች ፡ አገር ፡ ማለት ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ። ዅሎሙ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘጸሊም ፡ ሥጋሆሙ ። ወቦ ፡ ዘትከውን ፡ ኀሳረ ፡ በኀበ ፡ ካልኣኒሃ ፡ ከመ ፡ ቀሪጸ ፡ ገጽ ፡ በኀ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወኖባ ። ኖባ ፡ የነገድ ፡ የሀገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመልክ ፡ የሕብር ፡ ስም ፡ (መዝ ፡ ፷፯ ። ቀሌ ። ፍ፡ ነ ፡ ፶፩) ። ዕብራይስጡ ፡ ኵሽ ፡ የሚለውን ፡ የኵሽን ፡ ስም ፡ ዅሉ ፡ ጽርኡ ፡ ኢትዮጵስ ፡ ይለዋል ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ታሪክ ፡ ጣፊዎች ፡ ዅሉ ፡ ኵሽን ፡ የኢትዮጵስ ፡ አባት ፤ ወይም ፡ የአክሱማስ ፡ ልጅ ፡ አንደኛ ፡ ኢቶጲስ ፡ ይሉታል ፡ አክሱማስ ፡ ያሉትም ፡ ኵሽን ፡ ነው ። ዅለተኛም ፡ የኵሽ ፡ አገር ፡ ዅሉ ፡ በልጁ ፡ በኢትዮጲስ ፡ ስም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተብለች ፡ ይላሉ ፡ የመላ ፡ የግምት ፡ አንጋገር ፡ ነው ፡ ዕብራይስጥና ፡ ጽርእ ፡ ሳላዩ ፡ ግን ፡ እውነት ፡ ይመስለዋል ። በጽርእ ፡ ቋንቋ ፡ ኢትዮጲስ ፡ የተባለው ፡ ያው ፡ በዕብራይስጥ ፡ ኵሽ ፡ የተባለው ፡ ዋነኛውና ፡ መደበኛው ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ በኵሩ ፡ ግንባር ፡ ቀደሙ ፡ የካም ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሌላ ፡ ፪ኛ ፡ አካል ፡ የኵሽ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ። ለኵሽ ፡ በኦሪትና ፡ በዜና ፡ መዋዕል ፡ ከተጻፉት ፡ ሳባ ፡ ሐዊላ ፡ ሰብታ ፡ ረዕማ ፡ ሰብተቃ ፡ ናምሩድ ፡ ከሚባሉት ፡ ከ፮ቱ ፡ ሌላ ፡ ፳፪ ፡ ልጆች ፡ እንዳሉት ፡ የናናዊ ፡ ታሪክ ፡ ይናገራል ። ከዚሁ ፡ ከዮናን ፡ የተቀዳው ፡ የሞሪዬም ፡ ታሪክ ፡ የካም ፡ ልጅ ፡ ኵሽ ፡ አርባ ፡ አልቤምን ፡ ኪሬኔ ፡ ከሚባሉ ፡ ከ፫ቱ ፡ እኅቶቹ ፡ ፳፰ ፡ ወልዷል ፤ ዕድሜውም ፡ ፱፻፷፰ ፡ ነው ፡ መዲናውና ፡ መቃብሩ ፡ አኵስም ፡ ናት ፡ ይላል ። ፳፰ ፡ ያላቸውንም ፡ በየስማቸው ፡ ጥፏቸዋል ፡ የ፳፬ቱ ፡ ስም ፡ በኦሪት ፡ እንደ ፡ ተጣፈው ፡ ነው ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፯ ፡ ፰) ። ከቀሩትም ፡ ከ፳፬ቱ ፡ ነገድ ፡ አቢስ ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጲስ ፡ የተባለ ፡ የለም ፡ አቢስን ፡ ግን ፡ የሳባ ፡ ሳባ ፡ ዓይ ፡ የናምሩድ ፡ ተከታይ ፡ ከአልቤምን ፡ የተወለደ ፡ የኵሽ ፡ ፯ኛ ፡ ልጁ ፡ ብሎ ፡ እናቱ ፡ ሳትቀር ፡ ስሙንም ፡ ቍጥሩንም ፡ ጥፎለታል ፡ አቢስን ፡ ተመልከት ። ኢትዮጵስ ፡ ማለት ፡ በጽርእ ፡ ዅለት ፡ ያሳያል ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ሲኾን ፡ ጥቍር ፡ ጠቋሬ ፡ ክስልማ ፤ የሀገር ፡ ስም ፡ ሲኾን ፡ ቈላ ፡ በረሓ ፡ ምድረ ፡ በዳ ። ስያሜውም ፡ ከኵሽ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ በ፪ ፡ ሺሕ ፡ ከ፱፻፲፬ ፡ ዓመት ፡ ፫፻ ፡ ሊቃናት ፡ ያወጡት ፡ ከ፫ ፡ ሊቃናት ፡ የተገኘ ፡ ሐዲስ ፡ እንግዳ ፡ ደኀራዊ ፡ ስም ፡ ነው ። በሱዳን ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትውም ፡ መላይቱ ፡ አፍሪቃ ፤ ይልቁንም ፡ ከነጭ ፡ አባይ ፡ ወዲህ ፡ ያሉቸው ፡ ክፍል ፡ የጥቍሮች ፡ የኵሽ ፡ ልጆች ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ኾነች ፡ በዚህ ፡ ባዲሱ ፡ ስም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ትባላለች ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፲፫) ። በብሉይ ፡ በሐዲስ ፡ የተጣፈው ፡ ዋነኛውና ፡ መደበኛው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ታላቁን ፡ በረሓ ፡ ሰሐራን ፡ ጨምሮ ፡ የኖባ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ (፪ዜና ፡ ፲፬ ፡ ፱ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ፲፮ ፡ ፰ ። ፬ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፱ ። ኢሳ፴፯ ፡ ፱ ። ሕዝ፴ ፡ ፬ ፡ ፭ ፡ ፱ ። ግብሐ ፡ ፰፳) ። ወዲያ ፡ ማዶም ፡ በእስያ ፡ ክፍል ፡ ያለው ፡ ያረቦች ፡ አገር ፡ ቃዴስ ፡ በርኔና ፡ ሐቅለ ፡ ሲና ፡ ሌላውም ፡ ዅሉ ፤ ቈላ ፡ በረሓ ፡ ፍጹም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በዕብራይስጥ ፡ (ጺያ) ፡ ጺይም ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ኵሽ ፡ አይባልም ፤ በጽርእ ፡ ግን ፡ እንዳፍሪቃ ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ኖባ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይባላል ። ይገኙ ፡ ቅድሜሁ ፡ ኢትዮጵያ ። ወወሀብኮሙ ፡ ሲሳዮሙ ፡ ለሕዝበ ፡ ኢትዮጵያ ፡ (መዝ ፡ ፸፩ ። ፸፫) ። የቀረውን ፡ በሰፊው ፡ ታሪክ ፡ ተመልከት ፡ (ክፍል ፡ ፩) ።

**ኢትዮጳዊ**፤ **ኢትዮጵያዊ**፤ የኢትዮጵያ ፡ አፍሪቃዊ ፤ ኖባዊ ፡ ሱዳናዊ ፤ ወይም ፡ አፍሪቄ ፡ ኖቤ ፡ ሱዳኒ ። ምስጢሩ ፡ ጥቍረትና ፡ ቈለኛነት ፡ ነው ። ይዌልጥኑ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ማእሶ ፡ ወነምር ፡ ሕንበርብሬሁ ። ወረከበ ፡ ኢትዮጵያዌ ፡ ንኡሰ ፡ ደበል ፡ ሾንቀላ ፡ (ኤር፲፫ ፡ ፳፫ ። ሬልክ ፡ ፴፱) ።

**እታሚን**፤ **እታኒም**፤ **(ጽር ፡ እታኒን ። ዕብ ፡ ኤታኒም)**፤ ስመ ፡ ወርኅ ፡ የዕብራውያን ፡ ፯ኛ ፡ ወር ፡ ጥቅምት ፤ ፯ኛነቱ ፡ ለሚያገዝያ ፡ (፫ነገ ፡ ፰ ፡ ፪) ። ኤታን ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ ጥንተ ፡ ወርኅ ፡ ጥንተ ፡ ዓመት ፡ ጥንተ ፡ ዓለም ፡ ጥንተ ፡ ፍጥረት ። ኤታኒም ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ፍጥረትን ፡ ያሳያል ፡ ዓለም ፡ የተፈጠረ ፡ በጥቅምት ፡ ነውና ፤ በፀሓይ ፡ ቍጥር ፡ ግን ፡ የመስከረም ፡ ሓማኖ ፡ ይኾናል ። ይኸውም ፡ እመ ፡ ርእሰ ፡ ሳብዕ ፡ ሠርቀ ፡ ወርኅ ፡ ግበሩ ፡ መጥቅዐ ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ፡ (ዘሌ፳፫ ፡ ፳፬) ። የግእዝና ፡ የቅብጥም ፡ ዐውደ ፡

ዓመት ፡ በመስከረም ፡ ራስ ፡ መኾኑ ፡ መጥቅዕን ፡ መሠረት ፡ ይዞ ፡ ነው ። ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ቀዳማይ ፡ ወርኅ ፡ ኢታኒም ፡ ነበረ ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ከግብጽ ፡ የወጡበት ፡ ኒሳን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ የፋሲካው ፡ በዓ ፡ የክርስቶስ ፡ አምሳል ፡ ነውና ፡ ምሳሌውን ፡ ከአማናዊው ፤ ሥጋዊውን ፡ ከመንፈሳዊው ፡ አያይዞ ፡ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ ከግብጽ ፡ እንደ ፡ ወጣችኹ ፡ ኋላም ፡ በዚሁ ፡ ወር ፡ ከገሃነም ፡ ትወጣላችኹ ፡ ሲል ፤ ዓመ ፡ ከመ ፡ ዮም ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ዝንቱ ፡ ወርኅ ፡ ይኩንክሙ ፡ ቀዳማየ ፡ አውራኅ ፡ ብሎ ፡ የጥቅምትን ፡ ቅድምና ፡ ለሚያገዛ ፡ የሚያገዛን ፡ ፪ኛንት ፡ ለጥቅምት ፡ አዋርሶታል ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፪) ። በውዴ ፡ ዓመት ፡ ግን ፡ ምንም ፡ የወር ፡ ቍጥር ፡ ቢፋለስ ፡ ከዚያው ፡ ከጥንቱ ፡ ከጥቅምት ፡ አልወጣም ። ፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ በሚያዝያ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በጥቅምት ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ የሚያፈችል ፡ ቢኖር ፡ ባህሉ ፡ ይኩንክሙ ፡ ቀዳማየ ፡ አውራኅ ፡ ባለው ፡ ቆሎ ፡ ይፈርሳል ፡ ቀዳማዩ ፡ ቀዳማይ ፡ ይኹን ፡ አይባልምና ። አቡ ፡ ሻህርም ፡ ጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ መስከረም ፡ መኾኑን ፡ ለማስታወቅ ፡ የጨረቃን ፡ ቍጥር ፡ ለመጠንቀቅ ፡ ከሚያዝያ ፡ በታች ፡ ፯ ፡ ወሮች ፡ ቀውሳክ ፡ ይፈጸምራል ፡ (አቡሻ ፡ ፴፯) ።

**አቲቅ ፤ (ዕብራ)** ፤ የግንብ ፡ ዐምድ ፡ ፱ ፡ ማእዝን ፡ ያለው ። ኹለተኛም ፡ የዕቃ ፡ ቤት ፡ ዐምድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ፤ እትዊቂህን ፡ እይ ፡ (ሕዝ፵፪ ፡ ፫) ።

**አቱር ፤ (ቅብጥ ፡ አዱር)** ፤ ስመ ፡ ወርኅ ፤ ኅዳር ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ።

**አተርጋዎን ፤ (ጽርእ)** ፤ ቃል ፡ ድምፅ ፤ ቃለ ፡ መሳእክት ፤ ፍሬ ፡ ነገር ፡ የሚሰማበት ፤ አአትሪኮንን ፡ የ መሰለ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**አትራክስ ፤ (ጽር ፡ አንትራክስ)** ፤ የዕንቊ ፡ ስም ፤ ዕንቊ ፡ ፈርጥ ፡ ከደንጊያ ፡ ከሰል ፡ የሚገኝ ፡ (ጠቢ፲፫ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ መስ፲፮) ።

**አትሮንስ ፤ (ጽር ፡ ትሮኖስ)** ፤ የንጉሥ ፡ ዙፋን ፡ የጳጳስ ፡ ወንበር ፡ ታላቅ ፡ ምጡቅ ፤ የስባኪ ፡ የአንባቢ ፡ ስፍራ ፡ በቤተ ፡ ክሲያን ፡ ውስጥ ፡ የሚሠራ ፤ የመጽሐፍ ፡ ወንበር ፡ ታጥፎ ፡ የሚቀመጥበት ፡ ተዘርግቶ ፡ የሚነበብበት ፡ (፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳ ፡ ፴ ። መጋ፲፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳ ፡ ፱) ።

(ጥ) **አቲት ፤ ቶት ፤ (አተተ ፡ የአትት ፡ ይእትት ። ዕብ ፡ አቴት ፤ አመለከተ)** ፤ መራቅ ፡ ማማለል ፤ መለየት ፡ መነጠል ፡ ገለል ፡ ፈቀቅ ፡ ማለት ። ከመ ፡ ይእትት ፡ እምኔክሙ ። የአትት ፡ ዘሉ ፡ ግላ ። የአትቱ ፡ ዘሎሙ ፡ በሞት ፡ (ኛቆሮ ፡ ፰ ፡ ፱ ። ፪ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ። ኩፋ ፡ ፯) ።

—፤ መሻር ፡ መቅረት ፤ መጥፋት ፡ መበላሸት ፡ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገባል ። ወይእትት ፡ ሥልጣኖሙ ፡ እምዘሎ ፡ መካናት ። አእምሮ ፡ ዘኢየአትት ። ተአትት ፡ ዘላ ፡ አእምሮትሙ ፡ (ቀድር ። ቅዳ ። ኩፋ ፡ ፳፫) ። ኹለተኛም ፡ በቀደሰ ፡ ቤት ፡ በአተተ ፡ ፈንታ ፡ ተአተተ ፡ ይባል ፤ አያስኼም ። ኢትትኤተቱ ፡ ወርሐቀ ፡ ኢተሐውሩ ። ተአተተ ፡ ሕቀ ፡ እምህየ ። ኢይትአተቱ ፡ እምኔሁ ። ይትአተት ፡ በትረ ፡ ግብጽ ፡ (ዘፀ፰ ፡ ፳፱ ። ማቴ፳፯ ፡ ፴፱ ። ሔኖ፲፬ ፡ ፳፫ ። ዘካ፲ ፡ ፲፩) ።

**አታቲ ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት)** ፤ የሚርቅ ፡ የሚያገል ፡ አግላይ ፡ ፈቀቅ ፡ ባይ ።

(ባጥ) **እቱት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ትት)** ፤ የራቀ ፡ ያገለለ ፤ የተነቀለ ፡ የተፈነቀለ ፤ ፈቅ ፡ ፈቀቅ ፡ ያለ ፤ ገለልተኛ ። ወእቱት ፡ አረፍተ ፡ ቤቱ ። ረከበት ፡ እብነ ፡ እቱተ ፡ እምአፈ ፡ መቃብር ። ምንባበ ፡ መጻሕፍት ፡ ይኩን ፡ እቱተ ፡ ሕቀ ፡ እምነ ፡ ምሥዋዕ ፡ (ሕዝ፵፩ ፡ ፯ ። ዮሐ፳ ፡ ፩ ። ኪዳ) ።

**እቱተ** ፤ የራቀ ፡ ኾኖ ፤ ርቆ ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ተለይቶ ፡ ብቻውን ። ትነብር ፡ ምስሌየ ፡ እቱተ ። እለ ፡ ይነብሩ ፡ እቱተ ፡ ምስለ ፡ ንጉሥ ። ይቁም ፡ እቱተ ፡ እምነ ፡ ብእሲቱ ፡ (፩ሳሙ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ። አስቴ፩ ፡ ፲፬ ። ፈመ ፡ ፲፬ ፡ ፱) ።

**እታቴ** ፤ መራቅ ፤ አራራቅ ፡ ርቀት ፡ ሩቅነት ።

**አእተተ** ፤ አራቀ ፡ አስራቀ ፡ አስወገደ ፤ አስለደደ ፤ አስጣለ ፡ አሶለቀ ። ናእትቶ ፡ ለልጹቅ ፡ ወናቄርቦ ፡ ለርሑቅ ። አእትቱ ፡ እምፍኖት ፡ እብነ ። ታእትቶ ፡ ለዝሉፉ ። አእትት ፡ አልባሰ ፡ ርሱሐ ፡ እምላዕሌሁ ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ ። ኢሳ፷፪ ፡ ፲ ። ኢዮ፲፬ ፡ ፳ ። ዘካ፫ ፡ ፬) ።

—፤ ገደለ ፤ አጠፋ ፡ በቊጥር ፡ አተተ ፡ ከቍጥር ፡ አወጣ ። ከመ ፡ ያእትቶሙ ። ኢያእተተ ፡ ዘርዖሙ ። ወእም ዘተርፈከ ፡ አሐደ ፡ አእትት ፡ (ኩፋ ፡ ፲፯ ። ሚራ፵፯ ፡ ፳፪ ። መር ፡ ዕው) ።

**ተእተተ** ፤ ተራራቀ ፡ ተለያየ ፡ እየብቻው ፡ ኾነ ። አተተ ፡ የጠፈረና ፡ የፀሰየ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የቀደሰ ፡ ቤት ፡ እንዳይደስ ፡ አስተውል ።

**ኤጳውሉስ ፤ (ጽር ፡ ሄፓፍሌምስ ። ዕብ ፡ ፈሀሒሮት)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ እስራኤል ፡ ስፈርያን ፡ የሠሩበት ፡ ይኸውም ፡ ፈቶም ፡ ነው ፤ መንቆች ፡ ረገሮች ፡ ኹለት ፡ ጣያታት ፡ የቆሙበት ፡ (ዘፀ፲፬ ፡ ፪ ። ፱ ፡ ፲፮) ።

**አጳይዶን ፤ (ጽር ፡ ሄፓይዶን ። ዕብ ፡ ሐርጡሚም)** ፤ መሰማላን ፡ ማርተኞች ፡ ኮከብ ፡ ቈጣሮች ፡ በፊደል ፡ በሥዕል ፡ በግብጻዊ ፡ ስጋል ፡ በሐረግ ፡ በጠልሰም ፡ የሚጠነቍሉ ፡ (ዳንዕ ፡ ፪) ።

**አጴልዮጤን ፤ (ጽር ፡ አፒልዎቲስ)** ፤ የበታ ፡ የማእዝን ፡ ስም ፤ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ መቅሠፍትንት ፡ ያለው ፡ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ (የዳ፯ ፡ ፲፰) ።

**አጵልዮን ፤ (ጽር ፡ አፖልዮን)** ፤ አጥፊ ፡ ጥፋት ፤ ምዝባሬ ፡ ፍርሰት ። አብደንን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ራእ፱ ፡ ፲፩) ።

**አጵሎን ፤ (ጽር ፡ አፖሎ) ፤** ጣዖት ፡ የጣዖት ፡ ስም ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲፰ ። የካ፳፫ ። ነሐ፲) ።

**አጰሊ.ጴ. ፤ (ጽር ፡ አፖሊ.ፐ) ፤** በቤት ፡ ዙሪያ ፡ ያለ ፡ የውስጥ ፡ ወለወል ፡ የተለየ ፡ ክፍል ፡ (ሕዝ ፡ ሳ፰ ፡ ፲፱) ።

**ኤጴሜዳስ ፤ (ጽር ፡ ኤፖሜዴስ) ፤** መትከፊ ፡ አንቀጽ ፤ ደጃፉ.ን ፡ ገብቶ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ያለው ፡ የመዝጊያው ፡ ኋላ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ እብን ፡ በረድ ፡ ይሉታል ፡ (ሕዝ፵ ፡ ፵፰ ። ፵፩ ፡ ፪) ።

**ኤጴሞስ ፤ (ጽር ፡ ኤፖሚዴስ) ፤** ግዝኒ ፡ ከማሁ ፤ መትከፍ ፤ ልብስ ፡ መትከፍ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ቀሚስ ፡ ዘይበጽሕ ፡ እስከ ፡ እግር ፡ እምርእስ ፡ ይሉታል ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፯) ።

**ኤጲፋንያ ፤ (ጽር ፡ ሄፒፋኒያ) ፤** አስተርእዮ ፤ መታየት ፡ መገለጽ ፤ ዕለተ ፡ ጥምቀት ። በዓለ ፡ ኤጲፋንያ ፡ በዘቦቱ ፡ አርአየ ፡ እግዚ. ፡ ስብሐተ ፡ መለኮቱ ፡ በውስተ ፡ ጥምቀት ፡ በቅድመ ፡ ዮሐንስ ፡ በፈለገ ፡ ዮርዳኖስ ። ኤጲፋንያ ፡ ማልሲት ፡ ዘተጠምቀ ፡ ባቲ ፡ ዘኢተጠምቀ ፡ ትካት ፡ (ዲድ ፡ ፳፱ ። ስንክ ፡ ጥር ፲፩ ፡ ፲፪) ።

**ኤጲፋንዮስ ፤ (ጽር ፡ ሄፒፋኒዉስ) ፤** ግዝኒ ፡ ከማሁ ፤ የሰው ፡ ስም ። ይኸውም ፡ ብዙ ፡ ድርሳናት ፡ የጣፈ ፡ የቆጵሮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ ምሁረ ፡ ኦሪት ፡ አይሁዳዊ ፡ ነበር ፤ ጌታ ፡ በታምራት ፡ ማርኮ ፡ መምህረ ፡ ወንጌል ፡ አድርጎታል ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ፲፯ ። ሃይ ፡ አበ ። ቅዳ) ።

**አጵርጌ ፤ (ጽር ፡ አፓርኪ.) ፤** የእሸት ፡ በኵራት ፤ በኵረ ፡ ወይን ፤ በኵረ ፡ በለስ ፤ በኵረ ፡ ኅብስት ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ናቄርብ ፡ ለከ ፡ አጵርጌ ፡ ቀዳምያተ ፡ ፍሬ ፡ ዚኣከ ። አጵርጌ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይበልዕ ፡ (መጽ ፡ ኪዳ ። ራእ ፡ ማር ። ሕዝ፵፬ ፡ ፴) ። ተረፈ ፡ መሥዋዕትም ፡ አጵርጌ ፡ ይባላል ።

**አጵሮግዮን ፤** በኵርነት ፤ ቀዳማዊነት ፤ መዋዕለ ፡ ሠዊት ። እምድኅረ ፡ ዕርገቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ዘበአጵሮግዮን ፡ ለኀበ ፡ ሰማይ ፡ (ማቴ፳፰ ፡ ፳፩) ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ ሥጋ ፡ ይሉታል ።

—፤ ዕንቍ ፡ የዕንቍ ፡ ፈርጥ ፤ ፍሬው ፡ ቅንጣቱ ፡ (ድጓ ፡ መስ፲፩ ። አርጋ ፡ ፯) ።

**ኤጲስቆጶስ ፤ (ሳት ። ጽር ፡ ሄፒስኮፖስ) ፤** ጠባቂ ፤ መምህር ፡ የጳጳስ ፡ ኹለተኛ ፤ የሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ሦስተኛ ። በእንተ ፡ ኤጲስቆጶሳት ። ወይሢም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባሕቲቱ ፤ እስመ ፡ ማልሳይ ፡ ማዕርጊሁ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፭ ። ፯) ። ሲኖዶስ ፡ ትእዛዝ ። ጴጥሮስ ፡ ሊቃናት ፡ ሠለስቱ ፡ ጰታ ፤ ወሠለስቲሆሙ ፡ አሐቲ ፡ ፍና ፡ ይሳቸዋልና ፤ እሊህ ፡ ሦስቱ ፡ በመኾም ፡ በመሻር ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፤ ኹሉም ፡ በኤጲስቆጶስ ፡ ስም ፡ ይጠራሉ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ዘሉ ፡ ፍጥረት ፡ ወልደ ፡ እግዚ. ፡ ዐቢይ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ። አትናቴዎስ ፡ ዘኮነ ፡ ቅድመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባዕለ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ። በከመ ፡ ይቤ ፡ ፊልክስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘሮሜ ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፬ ። ቁር ። ሃይ ፡ አበ) ። ጳጳስን ፡ ተመልከት ።

**ኤጲስቆጶስና ፤** ኤጲስቆጶስነት ፤ ኤጲስቆጶስ ፡ መኾን ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ ሹመት ፡ ማዕርግ ። እምድኅረ ፡ ኤጲስቆጶስናሁ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱ ፡ ፲፭ ። ፳ ። ፊልክ ፡ ፲፰) ።

# በ

**በ ፤** ኹለተኛ ፡ ፊደል ፤ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ። ስሙ ፡ ቤት ፤ ቍጥሩ ፡ ኹለት ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ ፱ ፡ ክልኤት ፡ ቱ ፡ ይባላል ። ዕብራውያን ፡ ግን ፤ ኹለቱን ፡ መደብ ፡ አድርገው ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ነቍጣ ፡ እየጨመሩ ፡ ኹለት ፡ አልፍ ፡ ይሉታል ። ኹለተኛ ፡ ማለት ፤ ምስጢሩ ፡ ለኹለትና ፡ የሰኞን ፡ ፍጥረት ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ኹለተኛውን ፡ አካል ፡ ወልድን ፡ ያሳያል ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፮—፰) ።

**በ ፤ (ደቂቅ ፡ አገባብ) ፤** በቁም ፡ ቀሪ ፡ ማድረጊያ ፡ ን ፡ ጋራ ፤ ቸልታ ፡ ጊዜ ፡ ለ ፡ ወደ ፡ እንደ ፡ ስለ ፡ ይኾናል ። ማድረጊያ ፡ ሲኾን ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ፤ የቀረውን ፡ ባገባብ ፡ ተመልከት ፡ (ዕር፳፭ ። ቍ፻፱) ።

**በ ፤** ነባር ፡ አንቀጽ ። አለ ፤ ኖረ ፤ ነበረ ፤ ኾነ ። ላንድም ፡ ለብዙም ፡ ለወንድም ፡ ለሴትም ፡ ይከታል ። ቦ ፡ ዕርከ ፡ ኀላፌ ። ቦ ፡ ጻድቃን ፡ ውሉደ ፡ ቤትከ ። ቦ ፡ ብእሲት ፡ አንተ ፡ ትሜኒ ፡ እምብእሲት ። ወቦ ፡ አንስትኒ ፡ እለ ፡ ጌሣ ፡ ኀበ ፡ መቃብር ። በ ፡ ቦቱ ፡ ባለው ፡ በዝርዝርነት ፡ ሲፈታ ፡ ግን ፡ ላንድ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ለብዙ ፡ አይኾንም ። ይህም ፡ አለው ፡ አለለት ፡ አለበት ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ። ቦቱ ፡ ክቦ ፡ ተለይቶ ፡ በርሱ ፡ በት ፡ ይኾናል ። ዘቦቱ ፡ ዘሉ ፡ ከነ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ የተፈጠረ ፤ ወይም ፡ የተፈጠረበት ። ዘሉ ፡ ዘየአምን ፡ ቦቱ ፤ የሚያምንበት ፡ ኹሉ ። በርሱ ፡ ቢል ፡ በት ፡ ቢል ፡ ስልቱ ፡ አንድ ፡ ነው ። ለክፋም ፡ ለበጎም ፡ ይኾናል ።

**በእ ፤—ገበ ፤—በዊእ ፡ ቦእ ።**

**በኢ.ናህ ፤ ባውኒ ፤ (ቅብጥ ፡ ፓዎኒ) ፤** የግብጦች ፡ ፲ኛ ፡ ወር ፡ ሠኔ ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ።

**በአኤርጌስ** ፤ (ጽርእ ። ዕብ ፡ ብኔይ ፡ ር ጎሽ) ፤ ደቂቀ ፡ ነጐድጓድ ፡ (ማር፫ ፡ ፲፯) ።

**በእንተ** ፤—ስለ ፤—እንተ ፡ በ ። አገባብ ፡ እይ ፡ (ዕር፲፱ ፡ ቍ፷፯) ።

**ብእ.ስ** ፤ ሶት ፤ (ብእሰ ፡ ይብእስ ፡ ይብእስ ። ዕብ ፡ በአሽ ፤ ገማ ። ዐረ ፡ በኢ.ሰ) ፤ መባስ ፡ መጽናት ፤ መክፋት ፡ ማገርሸት ፡ መቈጣት ፡ እየባሰ ፡ መኼድ ፡ መጉዳት ። መጠላት ፡ ማስጠየፍ ፡ ማስቀየም ፡ የደዌ ፡ የቍስል ፡ የጠባይ ፡ የግብር ፡ የክፉ ፡ ነገር ። በሽታ ፡ ቢስ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ወእመኒ ፡ አርመምኩ ፡ ይብእሰኒ ፡ ሕማምየ ። ዘላዕለ ፡ ኃጥኣን ፡ ይብእስ ፡ ምስብዒተ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ። ይብእሰክ ፡ ረኂፀ ፡ ውስተ ፡ ቀኖት ፡ በሊኅ ። ብእሶ ፡ ለንጉሠ ፡ ፋርስ ። እበድ ፡ ዘይብእሰሙ ፡ (ኢዮ፲፮ ፡ ፮ ። ሚራ፺ ፡ ፰ ። ማብ፱ ፡ ፳ ። ፱ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፱ ። ፩ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፱) ።

—፤ ማደግ ፡ መጕልመስ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ማድረስ ፡ መግነን ፡ ፋጻሚ ፡ ጕብዝ ፡ መኾን ። መድረር ፡ መጨከን ፡ መቀልጠፍ ፡ መፍጠን ፡ ደርበኛ ። ተብዕኖ ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**በእሲ** ፤ (ሲት ፡ ሰያን ፡ ያት) ፤ የሚብስ ፡ የሚከፋ ፡ ጕጂ ፡ አስቀያሚ ።

**ብእ.ስ** ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ እስት) ፤ የባሰ ፡ የከፋ ፡ የተጠላ ፡ ክፉ ፡ መጥፎ ። ብዑድ ፡ ርሑቅ ፡ ማዶፋ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ብኡስ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ፡ (፱ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱) ።

**ብእሰት** ፤ መባስ ፡ መክፋት ፡ አባባስ ፡ አከፋፋ ፡ ብሶት ፡ ችግር ።

**ብእሲ** ፤ (ዕብ ፡ ኢ.ሽ) ፤ ጕልማሳ ፡ ጎይለኛ ፡ መጠት ፡ የ፳ ፡ የ፴ ፡ ዓመት ፡ ጕብዝ ፡ ምሉ ፡ ሰው ፡ ባል ፡ ተባት ፡ ወንድ ፡ ሰውነት ። ተፈሣሕ ፡ ኦ ፡ ብእሲ ፡ በውርዙትከ ። ወአመ ፡ ኮንኩ ፡ ብእሴ ፡ ነሣእኩ ፡ ብእሲተ ። ኮነ ፡ ብእሴ ፡ ወተሰቅለ ። ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ። ትወልድ ፡ ወልደ ፡ ብእሴ ። እስመ ፡ ወለደት ፡ ብእሴ ። እብል ፡ በእንተ ፡ ብሉይ ፡ ብእሲ ፡ (መክ፲፩ ፡ ፱ ። ጦቢ፳ ፡ ፱ ። ጸሎ ፡ ሃይ ። ኤር፳ ፡ ፲፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፯ ። ዮሐ፲፮ ፡ ፳፩ ። ኤፌ፬ ፡ ፳፱) ።

**ብእሲሁ** ፤ ሰውዮው ፡ ሰውነቱ ፡ ይህ ፡ ሰውዬ ፡ ሰው ። ወሳምራዊ ፡ ብእሲሁ ። ብእሲ ፡ ቅሁፍ ። ብሉይ ፡ ብእሲን ፡ (ኢ.ሳ፶፫ ፡ ፫ ። ሮሜ፮ ፡ ፮) ።

**ብእሲ ፡ ብእሲ** ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ በየራሱ ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፳፱ ። ሕዝ፲፬ ፡ ፬ ። ዘሌ፲፭ ፡ ፪) ።

**ብእሴ ፡ እግዚ** ፤ ነቢይ ፡ ሐዋርያ ፡ ጻድቅ ፡ ሰማዕት ፡ ቅዱስ ፡ (፩ነገ ፡ ፱ ፡ ፮ ፡ ፲ ። ፩ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፩) ።

**ብእሴ ፡ ደም** ፤ ደም ፡ አፍሳሽ ፡ ነፍስ ፡ ገዳይ ፡ ዐርበኛ ፡ የጦር ፡ ሰው ፡ (መዝ ፡ ፭) ።

**ብእሴ ፡ ሐቅል** ፤ በረኸኛ ፡ ዐዳኝ ፡ ወንበዴ ፡ ሽፍታ ፡ ወይኔ ፡ (ዘፍ፳፭ ፡ ፳፯) ።

**ብእሴ ፡ ኀይል** ፤ ኀይለኛ ፡ ጕልበታም ፡ ባለእምር ፡ (፫ነገ ፡ ፩ ፡ ፵፪) ።

**ብእሴ ፡ ምድር** ፤ ዐራሽ ፡ ገበሬ ፡ ጀግን ፡ ገበር ፡ የርሻ ፡ ባለቤት ፡ (ዘፍ፵፱ ፡ ፲፭) ።

**ብእሴ ፡ ዐመፃ** ፤ ዐመጠኛ ፡ ዋሾ ፡ ግፈኛ ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ (፪ተሰ ፡ ፪ ፡ ፫) ።

**ብእሴ ፡ ፍትወት** ፤ መውደድ ፡ መወደድ ፡ ያለው ፡ ሥልጡን ፡ ስብቅል ፡ (ዳን፲ ፡ ፲፩) ።

**ብእሴ ፡ ሰላም** ፤ ፍቅረኛ ፡ ፍቅር ፡ ወዳጅ ፡ አስታራቂ ፡ (መዝ ፡ ፴፯) ። ብእሲ ፤ በስም ፡ በግብር ፡ በዘር ፡ በንባር ፡ እየተናበበ ፡ በዚህ ፡ አምሳል ፡ እንደ ፡ ስልቱ ፡ እንዲመጣጡ ፡ ይፈታል ።

**ብእሲት** ፤ (ዕብ ፡ ኢ.ሻ ፤ ኢ.ሽት) ፤ ቈንጆ ፤ ምሉ ፡ ሴት ፡ ሚስት ። ብእሲት ፡ ድንግል ። ብእሲ ፡ ወብእሲት ። ብእሲተ ፡ ብእሲ ፡ (ዘሌ፳፩ ፡ ፲፫ ። ዘፀ፳፩ ፡ ፳፫ ። ዘዳ፳ ፡ ፲፯) ።

**ብእሲታ** ፤ ይች ፡ ሴት ፡ ያች ፡ ሴት ፡ ሴቲቱ ፡ ሴትዮዪቱ ፡ ሴቷ ፡ ሴትነቷ ። ምንት ፡ ብእሲታ ፡ (ሉቃ፯ ፡ ፴፱) ።

**ብእሲቶ** ፤ የቅርብ ፡ ስሚ ፡ ተጠሪ ፡ አንች ፡ ሴት ፤ ሴቶ ፡ እሜቶ ፡ ወይዘሮ ፡ (ዮሐ፪ ፡ ፬ ። ፬ ፡ ፳፩ ። ፳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭) ። ብእሲና ፡ ብእሲት ፡ እንደ ፡ ወርቅና ፡ እንደ ፡ ሐሬ ፡ ውስጠ ፡ ብዙዎች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፤ ግልጠ ፡ ብዙነት ፡ የላቸውም ፡ ብእሲ ፡ ከዕደው ፡ ብእሲት ፡ ከአንስት ፡ ይገባሉ ።

**አብአሰ** ፤ አባሰ ፡ አከፋ ፡ አስከፋ ፤ አስጠላ ።

**መብእስ** ፤ (ስት ፡ ሳን ፡ ሳት) ፤ የሚያብስ ፡ የሚያከፋ ። ክፉ ፡ መንገድ ፡ ወጥ ፡ ጎብ ፡ ሸካራ ፡ ስንክልክላ ፡ ድንጉር ። ይኩን ፡ ኵሉ ፡ መብእስ ፡ መጽያሕተ ፡ ርቱዐ ። ኮነ ፡ ፍናዊሁ ፡ መብእሰ ። የሐውሩ ፡ መብእሰ ። መብእስ ፡ እበይሃ ፡ ለፍኖተ ፡ ኃጥኣን ። ሀበኒ ፡ ርእሶ ፡ ለዮሐንስ ፡ ጸያሔ ፡ መብእስ ፡ (ኢ.ሳ፵ ፡ ፬ ። ሉቃ ፡ ዕገዛ ፡ ፲፭ ። ኤር፳ ፡ ፳፰ ። ሚራ፳፩ ፡ ፲ ። ድጓ) ።

**ተባእሰ** ፤ ተጣላ ፡ ተጠላላ ፡ ታገለ ፡ ተጋደለ ፤ ተሟገተ ፡ ተከራከረ ። ደቂቀ ፡ እምየ ፡ ተባእሱ ፡ በእንቲአየ ። ተባእስ ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ። ወተባእሱ ፡ ይትመየጡ ፡ መንግለ ፡ ምድር ። ተባአሰ ፡ ዮድኣም ፡ (ማሕ፩ ፡ ፮ ። ሚራ፬ ፡ ፳፰ ። ዮናስ ፡ ፲፫ ። ዳን፯ ፡ ፲፱) ። አገበረ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተባእሰ ፡ ይላል ። ተባእሳ ፡ ወአድክማ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱) ።

**ባእስ** ፡ (ሳት) ፤ ብርቱ ፡ ጥል ፤ ጠብ ፡ ሙግት ፡ ክርክር ፡ በድብ ። ቦኑ ፡ ባእስ ፡ ተባአሰ ፡ ምስለ ፡ እስራኤል ። በባእስ ፡ ወበዝንጓጌ ፡ ይፈንዎሙ ። ኃእዝ ፡ ወባእስ ፡ (መሳ፲፩ ፡ ፳፭ ። ኢ.ሳ፳፯ ፡ ፰ ። ምሳ፲፯ ፡ ፲፱) ።

**አስተባእሰ** ፤ አባባሰ ፡ አጣላ ፡ አጠላላ ፡ አሟገተ ፡ አከራከረ ። አባባስ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ መነኰሴ ፡ ይነክል ። አስተባአሶሙ ፡ በጽልእ ። ዘያስተባእስ ፡ ወዘያስተሳልም ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ፡ ኢይደልዎ ፡

ክመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ በውእቱ ፡ ግብር ፡ (ዮሴፋ ፡ ፍ ፡ ኍ ፡ ፻፫ ፡ ፲፪) ።

**መስተባእስ ፤ (ሳን)** ፤ የሚያጣላ ፡ የሚጣላ ፡ ተጣይ ፡ ደመኛ ፡ ተዋጊ ፡ ዐርበኛ ። ኢይኩኑ ፡ መስተባ እሳነ ፡ በእከይ ። መስተባእሳነ ፡ ሃይማኖት ። የዋሃን ፡ ይኩኑ ፡ መስተባእሳነ ፡ (ቀኖ ፡ ኒቅጵ ፡ ቁር ፡ ፲፲፱ ። ዮሴፍ ፡ ፲፭ ። ኩፋ ፡ ፴፫) ።

**ቢስ ፤ (ዐማርኛ ። ሱር ፡ ቢሳእ)** ፤ በቁሙ ፡ ክፉ ፡ ንፉግ ፡ ጩቅ ፤ ቡዳ ፡ ባላይን ፡ ወርቅ ። ቢስ ፡ አይይኽ ፡ ቢሰኛኽን ፡ ያርቅ ፤ ልበ ፡ ቢስ ፡ ቀልበ ፡ ቢስ ፡ እንዲሉ ።

**በአት ፤—መግባት ፤—በዊእ ፡ ቦአ ።**

(ጥ) **በአት ፤—ዋሻ ፤ በዊእ ፡ ቦአ ፤ በአት ።**

(ጥ) **በበ ፤ (ደቂቅ ፡ አገባብ)** ፤ በየ ፡ እየ ፡ ደጊመ ፡ ቃል ። ከተጸውዖ ፡ ስም ፡ በቀር ፡ በብትን ፡ ኹሉ ፡ እየገባ ፡ ይዘረዝራል ፤ ሲዘረዝር ፡ እንዳለ ፡ በቁሙ ፡ ይፈታል ፤ ባይዘረዝርም ፡ ተዘርዝሮ ፡ ወይም ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ ይፈታል ። በበ ፡ ነገዱ ፡ ወበበ ፡ ዘመዱ ፤ በበ ፡ አሐዱ ፤ በየ ፡ እየ ። በበ ፡ ነግህ ፡ በበ ፡ ሠርክ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ ማታ ። በበ ፡ ዕለት ፤ በየለቱ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፤ ዘወትር ። በበ ፡ ወርኅ ፡ በበ ፡ ዓመት ፤ በበ ፡ በዓል ፤ በበ ፡ ሕቅ ፡ በበ ፡ ንስቲት ፡ እያለ ፡ እንደዚህ ፡ ይፈታል ። ነሥኡ ፡ በበ ፡ ዲናር ፤ ድሪም ፡ ድሪም ፤ አንዳንድ ፡ ድሪም ። ፈነዎሙ ፡ በበ ፡ ክልኤቱ ፤ ኹለት ፡ ኹለቱን ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ አርጎ ። ወረፈቀ ፡ በበ ፡ ምእት ፡ ወበበ ፡ ኀምሳ ፤ ፻፻ው ፡ ፶፶ው ፡ ወይም ፡ ፻፻ና ፡ ፶፶ ፡ እየኾኑ ፡ ያሰኛል ። ለሰንና ፡ ለዘን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ናቸው ።

(ጥ) **ቡባ ፤ (ዕብራ)** ፤ አሻንጉሊት ፡ በወንድ ፡ ወይም ፡ በሴት ፡ ልጅ ፡ አምሳል ፡ የሚሠራ ፤ የልጅ ፡ የሕፃን ፡ መጫወቻ ። ልጅን ፡ ና ፡ ልዘልኽ ፡ ሲሉ ፡ እንቡ ፡ እንቡቡ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

(ላ) **ባባ** ፤ አያት ፤ ቅድም ፡ አያት ፡ አበ ፡ አበው ፤ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ፓፓ ፡ (ሐረርና ፡ ዐረብ) ። እንዳማርኛ ፡ ግን ፡ ጠብቆ ፡ ሲነገር ፤ እንቃጭ ፡ ኹኖ ፡ ባባ ፡ አባባ ፡ እዮስ ፡ ፈሪንትንና ፡ ብቡንትን ፡ ያሳያል ።

**ቡብ ፤ (ዐረብ)** ፤ በር ፡ ደጅ ፡ አፍ ፡ መግቢያ ። ኀደበን ፡ እዩ ።

**ባባህ ፤ (ዐረ ። ቅብጥ ፡ ፓዎፒ ፤ ፖፔ ፤ ፋዎፊ)** ፤ ስመ ፡ ወርኅ ፤ የግብጦች ፡ ኹለተኛ ፡ ወር ፡ ጥቅምት ። ቃሉ ፡ የቅብጥ ፡ ፊደሉ ፡ የዐረብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ፐ ፡ ለበ ፡ ተለውጧል ። ግበሩ ፡ በዓለ ፡ በመንፈቀ ፡ ባባህ ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ። በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ብንተ ፡ ዐይን ፡ ያይን ፡ ማማሪቶ ፡ ብሌን ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ባበየ ፤ ቤበየ ፤ (ይቤቢ)** ፤ ሠየ ፡ ጕመዠ ፤ ሮጠ ፡ ናወዘ ፤ ተቅበዘበዘ ፤ የዝሙት ። በበ ፡ ሠርክ ፡ ት ቤቢ ፡ በውስተ ፡ ፍናዊሃ ፡ (ኤርም ፡ ፳፫) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ፈጣን ፡ ቀላል ፤ መንገዷ ፡ ቆታን ፡ የሚመስል ፡ ይላል ።

**ባቢክ** ፤ ፍሬ ፡ ዕፀ ፡ ገነት ፡ አዳም ፡ ይበላው ፡ የነበረ ፡ ወይም ፡ እንዳይበላው ፡ በትእዛዝ ፡ እሾክ ፡ የታጠረ ፡ ቢበሉት ፡ ቢያክ ፡ ቢያክ ፡ የሚያሰኝ ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**ባቢል ፤ (ዐረ ፡ አባቢል)** ፤ ስመ ፡ ዖፍ ፤ የተረቅ ፡ ወፍ ፡ እንደ ፡ ፈንክስ ፡ ያለ ፤ በፍጥረታቱ ፡ ውስጥ ፡ የሌለ ፤ ያልነበረ ፡ ያልተፈጠረ ፤ ሙሐመዳውያን ፡ ሱር ፡ በሚባለው ፡ መጣፋቸው ፡ የሚያወሩት ፡ የሚናገሩት ፤ ወይም ፡ ባቢሎን ፡ ታመልከው ፡ የነበር ። አዕዋፈ ፡ ባቢል ፡ ዘውእቱ ፡ አንርጋናት ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ (አዋል) ።

**ባቤል ፤ (ዕብራ ። ጽር ፡ ባቢሎን)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ ቱሳሔ ፡ ንሡት ፡ ሡጠት ፡ ድብልቅልቅ ፡ ዝብርቅርቅ ፡ ቅይጥ ፡ ውጥንቅጥ ፤ ቅልቅል ፡ ምስቅልቅል ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዝሩት ፡ መካነ ፡ ዝርወት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ተዘርዉ ፡ አበው ፡ ቀደምት ፡ ወተሌለዩ ፡ ልሳናት ፡ ይሉታል ፡ (ዘፍ ፲፩ ፡ ፲ ። ፲፩ ፡ ፱) ። በእንተ ፡ ዝ ፡ ተሰምየት ፡ ዙላ ፡ ምድረ ፡ ሰናዖር ፡ ባቤል ፤ እስመ ፡ በህየ ፡ ሣጠ ፡ ዙሉ ፡ ልሳናቲሆሙ ፡ ለውሉደ ፡ ሰብእ ፡ (ኩፋ ፡ ፲) ። ኹለተኛም ፡ ናቡከደነጾር ፡ የቀድሞ ፡ ስሟን ፡ ለማደስና ፡ ለማወፈር ፡ በቀድሞው ፡ ግንብ ፡ አምሳል ፡ ኹለተኛ ፡ ግንብ ፡ እንደ ፡ መሥራት ፤ ወርዱ ፡ ደረቱ ፡ ፯ ፡ ክንድ ፡ ቁመቱ ፡ ፳ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ወፍራም ፡ ረዥም ፡ ሰማይ ፡ ጠቀስ ፤ ስሙ ፡ ከስሟ ፡ የተስማማ ፡ ቤል ፡ የሚባል ፡ ጣዖት ፡ ስላቆመባት ፤ ባቤልን ፡ ባ ፡ ቤል ፡ ባቲ ፡ ቤል ፤ ቤተ ፡ ቤል ፡ መካነ ፡ ቤል ። (ባብ ፡ ቤል) ፡ አንቀጸ ፡ ቤል ፡ ማዕጾ ፡ ቤል ፡ ብለው ፡ ፪ ፡ ቃል ፡ አድርገው ፡ ይፈቱታል ፡ (ዳንኤ ፡ ፬ ። ኢሳይያ ፡ ፵፮ ፡ ፩) ።

**ባበለ** ፤ ተቀላቀለ ፤ ተዝባረቀ ። ተዘራ ፡ ተበተነ ። በባበለም ፡ ፈንታ ፡ ቢልበለ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ ፩ ፡ ነው ። ወተሰምየ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ ባቢሎን ፡ እስመ ፡ ባቲ ፡ ተበልበሉ ፡ ልሳናት ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፲፫) ።

**ባቢሎሳን** ፤ ቱሱሉን ፡ ኀዉማን ፡ ገርዋን ። አባቢሎሳን ፡ (ዲድ) ።

**አባበለ** ፤ ቀላቀለ ፡ ደባለቀ ፡ ዘባረቀ ። በቁሙ ፡ አባበለ ፡ አሽበለበለ ፡ አቄላመጠ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአ ፡ ፈንታ ፡ ሀ ፡ ይላል ። ሀባባሊ ፡ ለዝሙት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፱ ፡ ፩) ።

**ባቡት** ፤ ዒሊ ፡ ደንጊያ ፡ ልብሱ ፡ ሽልምልም ።

**ባቡቴ** ፤ ክብ ፡ እንክብል ፡ ኅብስት ፡ ሴቶች ፡ በዒቢ ፡ አምሳል ፡ የሚጋግሩት ፤ ይልቁንም ፡ የቡልጋ ፡ ሰዎች ፡ ለሙታን ፡ መክፈልት ፡ የሚያደርጉት ። ዳቦ ፡ ድፎ ፡ ኑብሩቴ ፡ ፀ ፡ ባቡቴ ፡ እንዲሉ ።

**በግኔ ፤ (ዕብ ፡ ናጌን)** ፤ ቃኘ ፡ ነዘረ ፡ መታ ፡ ደረደረ ፡ የንዋየ ፡ ማሕሌት ። ሲጠብቅ ፡ ግን ፡ ነደደ ፡ ተቈጣ ፡ ያሰኛል ።


**በግና** ፤ በቁሙ ፡ መዝሙር ፡ (ዐማርኛ) ።

**በግን ፤ (ትግሬ)** ፤ ጨብጥ ፡ የሽንት ፡ ምጥ ። በበጠን ፡ ተመልከት ።

**በግዖ ፤ ዖት ፤ (በግዐ ፡ ይቤግዕ ፡ ይበግዕ) ፤** በጋ ፡ መንጋ ፡ መኾን ፡ መንጋጋት ፡ ወደ ፡ ወሰዱት ፡ መኼድ ፡ መነዳት ፡፡ በጋ ፡ የጊዜ ፡ የወራት ፤ መንጋ ፡ የሰው ፡ የከብት ፡፡ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ በጎነትና ፡ ቅንነት ፡ መሥዋዕትነት ፤ እንደ ፡ ይሥሐቅ ፡ እንደ ፡ የፍታሔ ፡ ልጅ ፡፡

**በግዕ ፤ (ዕት ፡፡ ዕብ ፡ በግ) ፤** የምግብ ፡ ከፍል ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ድርሻ ፡ መቅነን ፡ ድርጎ ፡፡ በቁሙ ፡ ተባት ፡ በግ ፤ የክርስቶስና ፡ የውንተኛ ፡ ክርስቲያን ፡ ምሳሌ ፡ በጎ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡፡ በግዕ ፡ ዘተኀጥአ ፡፡ ወመጽአ ፡ ይጠባሕ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡፡ አሐቲ ፡ በግዕት ፡ (ኢሳ፶፫ ፡ ፯፬ ፡፡ ሃ፫ ፡ ፮ ፡፡ ሕዝ፵፬ ፡ ፲፭ ፡፡ ፍ ፡ ን ፡ ፴) ፡፡

**አባግዕ ፤ (ዕት ፡ ዓት) ፤** በቁሙ ፡ በጎች ፡ የበግ ፡ መንጎች ፡ ተባቱም ፡ እንስቱም ፡ ወይም ፡ ተባቶች ፡ ብቻ ፡፡ አባግዕ ፡ ወአጣሊ ፡፡ አባግዕ ፡ ወአባግዕት ፡ (አዋል) ፡፡ አባግዓት ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡፡ አባግዕ ፡ አትቡዕ ፡፡ አባግዕ ፡ አንስት ፡፡ በግዕት ፡ አንስት ፡ እያለ ፡ ይጥፋል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (፪ዜና ፡ ፲፯ ፡ ፲፩ ፡፡ ዘኍ፯ ፡ ፲፯ ፡፡ ዘሌ፳ ፡ ፯) ፡፡



አባግዕ ፡

ምእመናንም ፡ በኈራቸውና ፡ ምላዊያቸው ፡ ሳይቀር ፡ በምሳሌ ፡ በጎች ፡ ይባላሉ ፡ (ዮሐ፲ ፡ ፳፱ ፡ ፴፯ ፡፡ ፲ ፡ ፯ ፡ ፳ ፡፡ ፳፭ ፡ ፲፯ ፡፡ ማቴ፲ ፡ ፯ ፡፡ ፲፭ ፡ ፳፱) ፡፡ መሳእክትም ፡ በኈራቸው ፡ ዳግማይ ፡ አዳም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እንደ ፡ ምእመናን ፡ በጎች ፡ ይባላሉ ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፲፪ ፡፡ ሉቃ፲፭ ፡ ፬) ፡፡

**በጊር ፤ ሮት ፤ (በገረ ፡ ይበግር ፡ ይብግር ፡፡ ዕብ ፡ ባጋር) ፤** ማደግ ፡ መጐልመስ ፡ ከልጅነት ፡ ወዳዋቂነት ፡ መውጣት ፤ ከታላላቆች ፡ መጨመር ፤ ዕብሮ ፡ ሙቈጠር ፤ አቶ ፡ እገሌ ፡ መባል ፡፡ በቁሙ ፡ መበገር ፤ መሞከር ፡ መንደፍ ፤ የሥዕል ፡፡ ብግር ፡ ማውጣት ፤ ብግራም ፡ መኾን ፡፡ ብግር ፡ ፪ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ የውርዘዊና ፡ የደዊ ፡፡

**ባጎር ፤** ጕበዝ ፡ ጐልማሳ ፤ ብግራም ፤ ሕፃንነቱን ፡ የጨረሰ ፡ እከለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ ባለአእምሮ ፡ የ፲፱ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የሚበልጥ ፡፡ ጥበበ ፡ ባጎር ፡ ወልደ ፡ ብዙኅ ፡ (ጥበ ፡ ፩) ፡፡ ባጎር ፡ ሰሎሞን ፡ ብዙኅ ፡ ዳዊት ፡፡

**ብዳ ፤ (ዐረ ፡ ቤዳ) ፤** ነጭ ፡ ንጣቱ ፡ ዕንቍላል ፡ ዐመድ ፡ ወይም ፡ ያህያ ፡ ሆድ ፡ የሚመስል ፡፡ ሕብረ ፡ ከብድ ፡ ባለው ፡ ብዳ ፡ ይላል ፡፡ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ብጫ ፡ ይሉታል ፡ (ዘፀ፴፯ ፡ ፱) ፡፡

**በድበደ ፤ (በድወ ፡፡ ዐረ ፡ ባደ) ፤** ታመመ ፡ ሞተ ፡ ጠፋ ፡ ተበላሸ ፡ ዛገ ፡ መረተ ፡፡ ወርቅሙ ፡ ቢድበደ ፡ (ሆሴ፱ ፡ ፮) ፡ አብደን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ፡፡ ትግሬ ፡ ግን ፡ በድበደ ፡ ብሎ ፡ ሰደበ ፡ አዋረደ ፡ ይላል ፡፡

**ብድብድ ፤** ዛሕል ፡ ዝገት ፡፡ ሞተ ፡ ግብት ፡ ቸነፈር ፡ መቅሠፍት ፤ ሰውነትን ፡ ቶሎ ፡ የሚያዝግ ፡ የሚያበወልግ ፤ ፈጥኖ ፡ የሚገድል ፤ እንደ ፡ ነፍጥ ፡ ያለ ፡ በሽታ ፡፡ ባለወግ ፡ መልአክ ፡ ለመዐት ፡ ለመቅሠፍት ፡ የሚላክ ፤ አጥፊ ፡ ቀሣፊ ፡፡ ክፉ ፡ ጨካኝ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ሄሮድስ ፡ እንደ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ያለ ፡ (ዘኍ፲፯ ፡ ፲፪—፲፱ ፡፡ ፪ነገ ፡ ፳፬ ፡ ፲፭—፲፯ ፡፡ ዕብ፲፩ ፡ ፳፰) ፡፡ ወአውሥእዎ ፡ ለውእቱ ፡ ብድብድ ፡ ንጉሥ ፡፡ ጕጉእ ፡ ወመግእዝ ፡ ወነባቢ ፡ ብድብድ ፡ ስሙ ፡ (መቃ ፡ ገ፩ ፡፡ ምሳ፳፩ ፡ ፳፱) ፡፡

**አበድበደ ፤** አዛገ ፡ አባደፈ ፡ ገደለ ፡ ቀሠፈ ፡፡

**አንበድበደ ፤** በቁሙ ፡ አስፈራ ፡ አንቀጠቀጠ ፡፡ ፈራ ፡ ተንበደበደ ፡፡

**እንብድቡድ ፤** ፈሪ ፡ በድባዳ ፡፡

**አበድቢድ ፤—ሞኝ ፡ ሰነፍ ፤—አቢድ ፡ አብደ ፡፡**

**በዲድ ፤ ዶት ፤ (በደ ፤ በደደ ፡ ይበድድ ፡ ይብድድ ፡፡ ዕብ ፡ ባዳድ) ፤** ለየ ፡ ነጠለ ፡ ብቻ ፡ አስቀረ ፤ ብቸኛ ፡ አደረገ ፡፡ በድበደ ፡ በዲድ ፡ በደ ፡ ካለው ፡ የወጣ ፡ ነው ፡፡ (ዲቃላ ፡ ግስ) ፡፡

**በደዶ ፤** ፈንጣጣ ፤ ኩፍኝ ፤ ልዩ ፡ ብቸኛ ፡ በሽታ ፡ የሚገድል ፡ የሚያቈስል ፤ ፊት ፡ የሚነቍር ፡ ዐይን ፡ የሚያሳውር ፡ የዐከከ ፡ ዐይነት ፡፡ ሕማመ ፡ በደዶ ፡ (አዋል) ፡፡

**በዲው ፤ ዎት ፤ (በድወ ፡ ይበዱ ፡ ይብዱ ፡፡ ትግ ፡ በድዐ ፤ በዳ) ፡፡** መውደም ፤ መጥፋት ፡ መፈታት ፤ መፍረስ ፡ መደምሰስ ፤ ውድማ ፡ በረሓ ፡ ባይ ፡ ባድማ ፡ ምድረ ፡ ባዳ ፡ መኾን ፤ ያገር ፡ የመዲና ፡ የድንግልና ፡፡ ምድርክሙኒ ፡ ብድወ ፡፡ ብድወት ፡ ኢየሩሳሌም ፡፡ ንኅሰት ፡ ወብድወት ፡፡ አብደቲሆሙ ፡ ብድዋ ፡ ወተመዝበሩ ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፯ ፡፡ ፷፬ ፡ ፲ ፡፡ ስንክ ፡ የካ፳ ፡፡ አቡሻ ፡ ፶) ፡፡

**ብድው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ዱት) ፤** የጠፋ ፡ የወደመ ፤ ባይ ፡ ባድማ ፡ የኾነ ፤ የተፈታ ፡፡ ምድር ፡ ብዱት ፡፡ ገዳም ፡ ብዱት ፡ (ዮሴፍ ፡፡ ስንክ ፡ መስ፫) ፡፡

**ብድወት ፤** መጥፋት ፡ መፈታት ፤ ውድማነት ፡ ባይነት ፡፡ ኢይርአይ ፡ ብድወታ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፫) ፡፡

**በድው ፤** ምድረ ፡ በዳ ፤ ውድማ ፡ ባድማ ፡ ደረቅ ፡ በረሓ ፤ ባይ ፡፡ በድወ ፡ ፋራን ፡፡ በምድረ ፡ በድው ፡ ኅበ ፡ አልቦ ፡ ዕፀ ፡ ወማይ ፡፡ ባሕር ፡ በድወ ፡ ይመስሎ ፡፡ በድወ ፡ ትከውን ፡ ዘኦላ ፡ ምድር ፡፡ በድው ፡ ውእቱ ፡ እምሰብእ ፡ ወእንስሳ ፡ (ኩፉ ፡ ፲፯ ፡፡ መግ ፡ ፴፪ ፡፡ ኢዮ፡፺፯ ፡ ፳፪ ፡፡ ኤር፱ ፡ ፳፯ ፡፡ ግ ፡ ፲) ፡፡

**በዳ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡፡ ኢትሑር ፡ ፍኖተ ፡ በዳ ፡፡ ትከውን ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ፡ በዳ ፡ ወበድወ ፡ (ሚራ፴፰ ፡ ፳ ፡፡ ሕዝ፳፱ ፡ ፱) ፡፡

(ፐ) ፡ ዳዋ ፡ (ዐማርኛ) ፡ ገዢ ፡ ዓዲ ፡ ከማህ ፡ በ ቂሙ ፡ ዱር ፡ ጥሻ ፡ ጣሻ ፡ (ትረት) ፡ ዐይጥ ፡ በበላ ፡ ዳዋ ፡ ተመታ ።

**አብደወ** ፡ አጠፋ ፡ አስጠፋ ፡ አወደመ ፡ ባዶ ፡ አ ደረገ ። አብደወ ፡ ሀገሮሙ ። ኣበዱ ፡ ፍኖቶሙ ። እሁ ቦን ፡ ለአብድዎ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘይነብሮን ፡ (ዮሴፍ ። ዕርፎ ፡ ፯ ። ኤርሚ ፡ ፳፱) ።

**ተብደወ** ፡ ተለየ ፡ ተበታተነ ፡ ተዘራ ፡ ተረጨ ፡ በየበረሓው ፡ ተሠራጨ ። እምነየሰ ፡ ተባድዎ ፡ እ ምነ ፡ ተጋብኦ ፡ በእንግልጋ ፡ እስመ ፡ ተዘርዎ ፡ ቀጥ ቀጠ ፡ አልባቢነ ፡ ወሶበ ፡ አድኀነ ፡ እግዚ ፡ እምተባ ድዎ ፡ ወአግብአነ ፡ ውስተ ፡ ምድርነ ፡ ዐመፀናሁ ። ይበኪ ፡ ባዕለ ፡ ሙስናሆሙ ፡ ወተባድዎቶሙ ፡ (ዮ ሴፍ) ።

**በደለ** ፡ (ትግሬ ፡ ወዐረ) ፡ ለወጠ ፡ ቀየረ ። (ዐማርኛ) ፡ በቂሙ ፡ በደለኛ ፡ ኾነ ፡ በመልካም ፡ ፈንታ ፡ ክፉ ፡ ሠራ ። ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገባል ።

**በዲን** ፡ ኖት ፡ (በድነ ፡ በደነ ፡ ይበድን ፡ ይብድን) ፡ ሙብደን ፡ መፍዘዝ ፡ መሞት ፡ መገንገን ፡ ሬሳ ፡ መኾን ፡ መማማት ፡ መበስበስ ፡ መፍረስ ። ሥጋ ፡ ትበድን ፡ በንዋም ፡ ከመ ፡ ዘምዉት ፡ ነፍስት ፡ አመ ፡ ፀአተ ፡ ነፍስ ፡ ይበድን ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**በድን** ፡ (ብ ፡ አብድንት) ፡ በቁሙ ፡ ሙት ፡ ሬሳ ፡ ነፍስ ፡ የተለየችው ፡ የማይላወስ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ የፈዘዘ ፡ የተገነዘ ፡ ባዶ ፡ ሥጋ ፡ አስከሬን ። ዘአንሥአ ፡ በድነ ፡ እምነ ፡ ሙታን ። መዊተኒ ፡ ተነበየ ፡ በድኑ ። አልቦ ፡ ቤት ፡ ዘአልቦ ፡ በድን ፡ ውስቴታ ። በዝጐ ፡ አብድንቲሆሙ ። ወቀንሥኡ ፡ ብዙኃን ፡ አብድንቲ ሆሙ ፡ ለጻድቃን ፡ (ሚራ፻፶ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፵፱ ። ኢሳ፳ ፡ ፲፱ ። ማቴ፳፯ ፡ ፶፪) ።

**አብደነ** ፡ አበደነ ፡ አፈዘዘ ፡ ሬሳ ፡ አደረገ ።

**አበደን** ፡ (ዐረብ) ፡ ግሙራ ፡ መቼም ፡ መቼ ፡ ፈጽሞ ፡ ጭራሽ ።

**ቢዶን** ፡ (ዕብ ፡ ኪዶን ። ጽር ፡ ጋይስ) ፡ ጦር ፡ ዘገር ፡ ረምሕ ፡ የሚወረውር ፡ ዐጭር ፡ መጠነኛ ። ባለብሎዎች ፡ ማን ፡ ፱ ፡ ገጽ ፡ ያለው ፡ የብረት ፡ በሎታ ፡ መድፍ ፡ ነፍጥ ፡ በድል ፡ ነጐድ ፡ ይሉታል ፡ (ኤርሚ ፡ ፡ ማ፲) ። በዕብራይስጥ ፡ ቤትና ፡ ካፍ ፡ ተመሳሳዮች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በኪ ፡ ፈንታ ፡ ቢ ፡ ተጽፏል ።

**በዲቅ** ፡ (በደቀ ። ዕብ ፡ ባዳቅ) ፡ ማደስ ፡ መጠገን ። እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ኢትቤድቁ ፡ ቤተ ፡ ለእ ግዚ ፡ (፬ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ፲፪) ።

**ቤደቅ** ፡ (ዕብራ) ፡ የግንብ ፡ ንቃቃት ፡ ነቁ ፡ ሥንጥቁ ፡ ወይም ፡ ሊናድ ፡ የቀረበ ፡ ያረገዘ ፡ የዘበዘበ ፡ የቤት ፡ ግንብ ። ያጥር ፡ የቅጥር ፡ ካብ ። ማናቸውም ፡ የሚታደስና ፡ የሚጠገን ፡ ኹሉ ። ወያጽንዑ ፡ ቤደቀኪ ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፱ ። ፬ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፭) ።

**በዲር** ፡ ሮት ፡ (በደረ ፡ ይበድር ፡ ይብ ድር ። ዐረ ፡ በደረ ፡ ቈረጠ ። ዕብ ፡ በደር ፡ በተነ) ፡ መሮጥ ፡ መፍጠን ፡ መንገዲን ፡ በሩጫ ፡ መቀ ረጥ ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ መቅደም ፡ ዐልፎ ፡ መኼድ ፡ ፊ ተኛ ፡ መኾን ። ይበድሩ ፡ እምተኰላት ፡ ዐረብ ። ይበ ድሩ ፡ እምአንስርት ፡ አፍራሲሆሙ ። ከመ ፡ ይብ ድር ፡ እምረዋጺ ፡ ሮጠ ፡ ፈጠነ ፡ (ሰንባ፰ ፡ ፳ ። ኤ ርሚ ፡ ፲፫ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ። ሖቀ ፡ በደሩክሙ ። ትበድር ፡ ይእቲ ፡ ወትመውእ ፡ ለከ ፡ ጸላኢከ ። ብድሮሙ ፡ ተንሥአ ። ይበድረነ ፡ ኀበ ፡ ገነት ። በደሮ ፡ ለጴጥ ሮስ ፡ በጺሐ ፡ ኀበ ፡ መቃብር ፡ ቀደመ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ። ሚራ፴፱ ፡ ፲፱ ። ፀ፱ ። ዳ፳ ። ፊልክ ፡ ፫ ። ዮሐ፳ ፡ ፬) ።

—፡ ማበደር ፡ ማለቃት ፡ አስቀድሞ ፡ መስጠት ፡ ኋላ ፡ ለመቀበል ፡ (ዐማርኛ) ።

—፡ መውደድ ፡ መምረጥ ፡ ማክበር ፡ ማብለጥ ። ኢክነ ፡ ለዘበደረ ፡ ወለዘረዐ ፡ (ሮሜ፱ ፡ ፲፯) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በበደረ ፡ ፈንታ ፡ አብደረ ፡ ይላል ፡ አያበኝም ። እመ ፡ አብደሩ ፡ ዘአነ ፡ እፈቅድ ። ምጽዋተ ፡ አብድር ፡ እመ ሥዋዕት ። አብደሩ ፡ ሞተ ፡ እምሕይወት ። አብደረ ፡ ይሕምም ፡ ምስለ ፡ ሕዝቡ ። ዘያበድር ፡ ርእሶ ፡ እምነ ፡ እግዚአ ። እስመ ፡ ኅረያ ፡ እግዚ ፡ ወአብደራ ፡ (ኢሳ፶፰ ፡ ፱ ። ሆሴ፮ ፡ ፯ ። ኤር ፡ ፰ ፡ ፫ ። ዕብ፲፩ ፡ ፳፭ ። ዲድ ፡ ፳፭ ። መዝ ፡ ፻፴፩) ።

**በዳሪ** ፡ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፡ በደርት) ፡ የሚሮጥ ፡ የሚቀድም ፡ ፈጭ ፡ መንገድ ፡ ቈራጭ ።

**በድር** ፡ ቅድድም ፡ ፍክክር ፡ ሩጫ ፡ ፍጥነት ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ገድል ፡ ትሩፋት ። በድርየኒ ፡ ፈጸ ምኩ ። ፈጸመ ፡ በድሮ ፡ ሠናየ ፡ (፪ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፩ ። ጥር፲፩ ፡ ፳ ። የካ፱ ። ግን፱) ።

—፡ የጾመ ፡ አይሁድ ፡ ድሮ ፡ ቅበላ ፡ ጾሙው ፡ ከሚው ለብት ፡ ከጾማቸው ፡ ቀን ፡ የሚቀድም ፡ ዋዜማ ፡ ድራር ፡ ማታ ፡ የሚገሠመር ። ይኸውም ፡ የጥቅምት ፡ ጨረቃ ፡ በበቀለች ፡ በ፱ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ (ዘሌዋ፳ ፡ ፳፯—፴፪) ። ወጾመ ፡ በድሮሙ ፡ በእንተ ፡ ላሐ ፡ ያዕቆብ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**በድራ** ፡ (ዐረ ፡ በድረት) ፡ ሚዛን ፡ የሚ ዛን ፡ ስም ። ቍጥሩና ፡ ልኩ ፡ በየሀገሩ ፡ ይለያያል ፡ እ ልፍ ፡ ድሪም ፡ ሺሕ ፡ ድሪም ፡ ፯ ፡ ሺሕ ፡ ይሉታል ፡ ርግጡ ፡ አልተገኘም ። ፯ ፡ ሺሕ ፡ ማለት ፡ ይለያል ፡ እንጂ ፡ ሺሕ ፡ ማለትና ፡ እልፍ ፡ ማለት ፡ ሲቃረብ ፡ ይችላል ፡ እልፍን ፡ ተመልከት ። ኹለተኛም ፡ በድራ ፡ ማለት ፡ ብድር ፡ ክማ ለት ፡ ይሰማማል ። ወወሀቦሙ ፡ ሠለስተ ፡ ምእተ ፡ በ ድራ ፡ ወርቀ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ቡዳር** ፡ (ትግሬ) ፡ ዱሮ ፡ ቀድሞ ፡ ጥንት ፡ ከኹሉ ፡ በፊት ።

**አብደረ** ፡ (አስደራጊ) ፡ አስሮጠ ፡ አስቀ ደመ ። አስተጋድሮ ፡ ፈረስከ ፡ ወአብድር ፡ እምዐ ውሎ ፡ (ደራሲ) ። አሶደደ ፡ አስመረጠ ፡ አስከበረ ፡ አስበ

ሰጠ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ አድራጊነት ፡ ነው ፤ መንገዱ ፡ እንደ ፡ አእመረ ፡ ተሳበቷል ።

**ተብድረ ፤** ተቀደመ ። ተወደደ ፤ ተመረጠ ፡ ከበረ ፡ በለጠ ። **ይትበደር ፡ ቃል ፡ ሠናይ ፡ እምውሂብ ። ኢይትበደር ፡ ብዕል ፡ እምነቢረ ፡ ጥዑይ ። ይትበደር ፡ ሰብእ ፡ እምዕንቍ ፡ ሰንፔር ፡ ክቡር ፤ እምወርቅ ፡ ወእምብሩር ፡ ይትበደሩ ፡ ጻድቃን ። ጥበብ ፡ ትትበደር ፡ እምወርቅ ፡** (ሢራ ፳፰ ፡ ፲፯ ። ፴ ፡ ፲፯ ። ድጓ ። ፈላስ) ።

—፤ በቁሙ ፡ ተበደረ ፡ ተለቃ ። ተበድሎ ፡ ተቀድሞ ፡ እንዲሉ ።

**ብዱር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ድርት) ፤** የተበደረ ፡ የተቀደመ ፤ የተወደደ ፤ ምርጥ ።

**ተባደረ ፤** ተፎካከረ ፤ ተሽቀዳደመ ፡ ተፈካከረ ። **እስመ ፡ ይትባደሩ ፡ ውስተ ፡ ርእሰ ፡ ምርፋቅ ። ተባደሩ ፡ ለሠናይ ። ዘንተ ፡ ስምዑ ፡ ወተባደሩ ፡ ከመ ፡ ትግበሩ ። እለ ፡ ፈጸሙ ፡ ረዊጸ ፡ ወተባድሮ ፡** (ሉቃ ፲፬ ፡ ፯ ። ጀተስ ፡ ፳ ፡ ፲፳ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፱) ።

**አስተባደረ ፤** አቀዳደመ ፡ አሽቀዳደመ ፡ አፈራረቀ ፤ የፈረስ ፡ የእግር ። **አምጣነ ፡ ጊዜ ፡ ሠርክ ፡ ንረውጽ ፡ እንዘ ፡ ናስተባድር ፡ እግረ ፤ እከል ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ወሳሕም ፡ ኀበ ፡ ሖረ ፡** (ቅዳ) ።

**ባዖስ ፤ (ጽር ፡ ባቶስ ። ዕብ ፡ ባት) ፤** የልክ ፡ የመስፈሪያ ፡ ስም ፤ የርጥብ ፡ መስፈሪያ ፤ የዘይት ፡ ግንብ ። **ምእተ ፡ በመስፈርተ ፡ ባዶስ ፡ ቅብዐ ፡** (ሉቃ ፲፮ ፡ ፮) ። መስፈሪያነቱም ፡ የሐሜርን ፡ ፲ኛ ፡ ክፍል ፡ ያነሣል ፤ የባትና ፡ የኢፍ ፡ ልካቸው ፡ አንድ ፡ ነውና ፤ ኢፍን ፡ ተመልከት ፡ (ሕዝቅኤ ፡ ፵፭) ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ባዶስን ፤ ቤይ ፤ ላዳን ፡ የቤት ፡ ሎና ፡ ይሉታል ፤ ቤይ ፡ የወሎ ፡ የትንታ ፡ የደሳንታ ፡ ነው ። **ወእሐቲ ፡ አስፈሬዳ ፡ ታገምር ፡ አርባዕተ ፡ ባዶስ ፡** (ገድ ፡ ተክ) ።

**ብዱት ፤—የተፈታች ፤ ባዶ ፤—በድወ ።**

**ቦሁ ፤ ቦኑ ፤ (ቦ ፡ ሁ ፤ ቦ ፡ ኑ) ፤** ቦ ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፤ ሁ ፡ ኑ ፡ የጥያቄ ፡ ቃል ፤ በተገናኝ ፡ አለን ፤ አለ ፡ ይኾን ፡ ያሰኛል ። **ቦሁ ፡ ኀበ ፡ ይሴወሩ ፡ እምኔየ ። ቦሁ ፡ ዘተርፈ ፡ ኀቤከ ። ቦኑ ፡ ረአይ ፡ ዝየ ፤ እወ ፡ ቦ ፡** (ኤርምያ ፡ ፳፫ ። ዓሞጽ ፡ ፲ ። ሳሙ ፡ ፱ ፡ ፲፩) ። ኹለተኛም ፡ በትርጓ ፡ ዐማርኛ ፡ በውኑ ፡ እውን ፡ እያሰኘ ፡ ጥያቄን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ምርመራን ፡ ወቀማን ፡ ተማሣጽን ፡ ያሳያል ። ትርጓ ፡ ዐማርኛ ፡ ማለት ፡ ቦ ፡ አንቀጽን ፡ ትን ፡ ሳይለቅ ። **ቦሁ ፡ ዘሰአልኩክሙ ፤ ቦኑ ፡ ዘዐመፅኩክሙ ፡** እያለ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ሲገባ ፡ በውኑ ፡ የለመንኋችኹ ፡ የበደልኋችኹ ፡ አለን ፡ ያሰኛልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። አንቀጹ ፡ ሌላ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ ፍችው ፡ በውኑ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ በጥያቄ ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ፡ በውኑ ፡ ማለት ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ጥያቄ ፡ ነውና ። **ቦኑ ፡ በአተ ፡ ፈያት ፡ ውእቱ ፡ ቤትየ ። ቦኑ ፡ ሰባሕቲቶሙ ፡ ለአይሁድ ፡ እግዚ ። ቦኑ ፡ አባእክሙ ፡ ሊተ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወቍርባነ ። ዘአባእክሙ ፡** ቢል ፡ ግን ፡ አለን ፡ ያሰኛል ፤ በውኑ ፡ ሲጨመር ፡ ያምርበታል ፡ (ኤርም ፡ ፲፩ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳፱ ። ግብሩ ፡ ፯ ፡ ፵፪) ።

**ብሂል ፤ ሎት ፤ (ብህለ ፡ ይብል ፡ ይብሀል ። ዐረ ፡ በሀለ ፤ ተረገመ ። ዕብ ፡ ባሄል ፤ ደነገጠ) ፤ አው ፡**

**በዪል ፤ ሎት ፤ (ቤለ ፡ ይበይል ፡ ይቢል ፤ ወይም ፡ ቤለ ፡ ይቤ ፡ ይበል ። ዐረ ፡ ቃል ። ዕብ ፡ ንእም ፤ አማር) ፤** ማለት ፡ መናገር ፡ መናገር ፤ ፍሬ ፡ ቃል ፡ መስጠት ፡ ማሰማት ፤ በአፍ ፡ በመጽሐፍ ፡ መንበብ ፤ ማንበብ ። ብሂል ፡ ፪ ፡ ነገር ፡ ይኾናል ፤ አንቀጽና ፡ አገባብ ። በአንቀጽነቱ ፡ አንቀጽ ፡ ይሰባል ፤ ስም ፡ ይተረጐማል ። ባገባብነቱ ፡ ማስሪያ ፡ ያስቀራል ፡ አገባቡን ፡ ባገባብ ፡ ተመልከት ። **ብሂለ ፡ ይብሉ ። እስመ ፡ ጼዴቅ ፡ ብሂል ፡ ጽድቅ ፡ ብሂል ። ብህለ ፡ ካልእ ፤ በከመ ፡ ብህልከ ። ዘብህልዎ ፡ አበዊነ ። ከዊነ ፡ ውሳጤ ፡ ዘብህሎ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ወግሪስ ። እሳት ፡ አንተ ፡ ብህላ ፡ እግዚእነ ፡** (ኤርምያ ፡ ፳፪ ። አፈ ፡ ድ፲፱ ። አዋል ። አረጋ) ። መሐሉን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። የብህለና ፡ የክህለ ፡ አካኼድ ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሀ ፡ ቢ ክልአያቸው ፡ እየታጣ ፡ በማለሳያቸው ፡ ይገኛል ፤ ባላገ ባቦቹ ፡ ግን ፡ ብህለን ፡ ከክህለ ፡ ለይተው ፡ ይብህል ፡ ይሉታል ፤ እያሰኙም ። ፪ኛም ፡ በበዪል ፡ አካኼድ ፡ እንደ ፡ ሐባብና ፡ እንዳሮጌው ፡ ግእዝ ፤ ቤለ ፡ ይበይል ፡ ይቢል ፤ ወይም ፡ ቤለ ፡ ይቤ ፡ ይበል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ብህለንና ፡ ቤለን ፡ አዘንቀው ፤ ቤለን ፡ አውጥተው ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ይቤን ፡ አግብተው ፤ የብህለን ፡ ክልአይ ፡ ይብልን ፡ ለይቤ ፡ ሰጥተው ፤ ይቤ ፡ ይብል ፡ ይበል ፡ እያሉ ፡ አለመንገዱ ፡ ያረቡታል ። መጻሕፍትም ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ በቤለ ፡ ፈንታ ፡ ይቤ ፡ ይብል ፡ ይበል ፡ ሲሉ ፡ እንጂ ፤ በብሂል ፡ አካኼድ ፡ ብህለ ፡ ብለው ፤ ይብህል ፡ ሲሉ ፡ አይገኙም ። ሀሎ ፡ የሀለወ ፡ ክፋይ ፡ መንቲያው ፡ ወንድሙ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ይቤም ፡ ከበዪል ፡ የወጣ ፤ የቤለ ፡ ክልአይ ፡ የይበይል ፡ ድርብ ፡ ወይም ፡ መንቲያ ፡ ትንቢት ፡ አንቀጽ ፡ ሲኾን ፤ መምህራን ፡ አርእስትና ፡ ዘር ፡ በገዝና ፡ ቅጽል ፡ የለውም ፡ ኀላፊ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ ብለው ፤ እኩሌቶቹም ፡ የብህለ ፡ ድርብ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቀዳማይ ፡ አንቀጽ ፡ ማድረጋቸው ፤ ትንቢትነቱ ፡ ስላልታወቀ ፡ ነው ። በኋላም ፡ መጕረዱም ፡ በመካከሉ ፡ የ ፡ ስላለበት ፡ ነው ። ፪ኛም ፡ ለን ፡ የ ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ የለ ፡ ጸያፎች ፤ ብህለን ፡ ሲያረቡ ፡ ብህየ ፡ ይብይ ፡ ይበይ ፡ ይላሉና ፡ በጸያፍ ፡ እንደበት ፡ የገባ ፡ ነው ፡ ልንል ፡ እንችላለን ። ይብልን ፡ ይብይ ፡ እንደሚሉት ፡ ይብይን ፡ ደግሞ ፡ ይቤ ፡ ብለውት ፡ ይኾናል ፡ አለዚያስ ፡ በኋላምስ ፡ ሲጕርድ ፡ ባልተገኘም ። በጸያፍ ፡ እንደበት ፡ መለወጥም ፡ የማስ ፡ ልማድ ፡ ነው ፤ ረን ፡ ለ ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ የረ ፡ ጸያፎች ፡ በሐረረ ፡ ፈንታ ፡ ሐለለ ፡ ብለው ፡ ኹለተኛ ፡ አንቀጽ ፡ እንዳወጡ ። ባማርኛም ፡ ለን ፡ የ ፡ ይወርሰዋል ፤ ይልቁንም ፡ በሚልበ ፡ ቅጽል ። **ቀታሊ ፡ ከሃሊ ፡ ሐባሊ ፡ ጠን**

ቋሊ ፡ ገዳይ ፡ ቻይ ፡ ዐባይ ፡ ጦንቋይ ፡ የመሰሰው ፡ ኹሉ ። ጕራጅንቱም ፡ ለሩቅ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ለቅርቡ ፡ ወንድና ፡ ለአንት ፡ ለንሕነ ፡ ለነዚህ ፡ ላምስቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፤ ቤለ ፡ ይቤ ፡ ይበል ። ቤለት ፡ ትቤ ፡ ትበል ። ቤልከ ፡ ትቤ ፡ በል ። ቤልኩ ፡ እቤ ፡ እበል ። ቤልነ ፡ ንቤ ፡ ንበል ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ። በቀሩት ፡ ግን ፡ ባምስቱ ፡ ሰራዊት ፤ ቤሉ ፡ ይቤሉ ፡ ይበሉ ። ቤላ ፡ ይቤላ ፡ ይበላ ። ቤልኪ ፡ ትቤሊ ፡ በሊ ። ቤልክሙ ፡ ትቤሉ ፡ በሉ ። ቤልክን ፡ ትቤላ ፡ በላ ፡ እያለ ፡ ዘሩን ፡ በዱልን ፡ መስሎ ፡ ተነክሎ ፡ ይኼዳል ። የበዱል ፡ ዘርና ፡ የቤለ ፡ ክልኤይ ፡ የይበይል ፡ ወንድሞ ፡ ፍጹም ፡ ትንቢት ፡ አንቀጽ ፡ መኾኑ ፤ ንባር ፡ ቀዳማይ ፡ አለመኾኑ ፡ በ፫ ፡ ምስክር ፡ ይረዳል ። መዠመሪያ ፤ በማልሳዩና ፡ ባምስቱ ፡ ሰራዊት ፡ ለን ፡ እየጨመረ ፡ በመኼዱ ፤ ፈጽሞ ፡ ባለመጕረዱ ። ኹለተኛ ፤ የትንቢት ፡ አሥራው ፡ መነሾቹ ፡ ፬ ፡ ፊደሎች ፡ የተአን ፡ ብቻ ፡ ናቸውና ፤ ይቤ ፡ ትቤ ፡ እቤ ፡ ንቤ ፡ እያለ ፡ በነዚህ ፡ ባራቱ ፡ በመኼዱ ። ሦስተኛ ፤ ለንባር ፡ አንቀጽ ፡ ክልኤይ ፡ ማልሳይ ፡ የለውምና ፤ በዘንዱና ፡ በትእዛዙ ፡ ይቃወቃል ። አስተውል ፤ ንባር ፡ ቀዳማይ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ኹኖ ፡ ቢኾን ፡ መንገዱ ፡ እንደ ፡ ሀብና ፡ እንደ ፡ ነሀ ፡ ንበር ፤ ሀብና ፡ ነሀ ፡ ሥርወ ፡ ቀለሙን ፡ ሳይለውጥ ፡ በማፉ ፡ ሌላ ፡ ባዕድ ፡ ፊደል ፡ ሳይጨምር ፤ ሀብ ፡ ቡ ፡ ቢ ፡ ባ ፤ ነሀ ፡ ንዑ ፡ ንዒ ፡ ንዓ ፤ ተብሎ ፡ ባራት ፡ ቅርቦች ፡ ብቻ ፡ እንዲረባ ፤ ይቤም ፡ ሥርወ ፡ ቀለሙን ፡ ሳይለውጥ ፤ ለን ፡ ከቤለ ፡ ከብህለ ፡ ሳይቀላውጥ ፤ ባራት ፡ ሰራዊት ፡ በሩቆች ፡ ብቻ ፡ ይቤ ፡ ይቡ ፡ ይቢ ፡ ይባ ፡ ተብሎ ፡ በተረባ ፡ ነበር ። የብሂል ፡ አፈታት ፡ ሕዝ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ የቀረውን ፡ በርባ ፡ ቅምርና ፡ ባገባብ ፡ በሠምና ፡ ወርቅ ፡ ተመልከት ፡ (፪ኛና ፡ ፲፱ኛ ፡ ፳፪ኛ ፡ ዕር ። ፳፬ ፡ ፵፫ ፡ ፶፳፭ቀ) ።

**ብሂል** ፤ **በዪል** ፤ መምታት ፤ በበትር ፡ ማለት ፡ መደብደብ ፤ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ መስደብ ፤ በነገር ፡ መቀንደብ ፤ ጽዕለትን ፡ ተመልከት ። ብሂላና ፡ ብላዕ ፤ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ፤ ብላ ፡ ብላ ።

**በሃሊ** ፤ (**ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ በሀልት**) ፤ ያለ ፡ የሚል ፡ የሚናገር ፤ ባይ ፡ ተናጋሪ ፤ አልኹ ፡ ባይ ፡ እንዲሉ ። ክመ ፡ ኢይኩን ፡ በሃሌ ፡ አነ ፡ አብዐልኩ ፡ አብራምሀ ። አሆ ፡ በሃሊ ። ወእመሰ ፡ ይቤ ፡ በሃሊ ። በሀልተ ፡ ጽድቅ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፫ ። ያዕ ፡ ፲፯ ። አፈ ፡ ተ ሾ፯ ። አሞል) ።

**ባህል** ፤ (**ላት**) ፤ በቁሙ ፤ ነገር ፡ ክርክር ፤ አባባል ፤ አነጋገር ፤ የነገር ፡ ስልት ፤ ትርጓሜ ፡ ምስጢር ፤ ድርሳን ፤ ልማድ ፡ ሕግ ፡ ሥርዐት ፤ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፤ ቃል ፡ ድምፅ ። ባህለ ፡ ልሳን ። ክሡትከ ፡ ባህለ ፡ መጻሕፍት ፡ ክዱን ። ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ አባ ፡ ቄርሎስ ፡ በውስተ ፡ አሐዱ ፡ እምባህላት ። ይቤ ፡ በእንተ ፡ ትርጓሜ ፡ ባህላት ። ያስተናክሩ ፡ ሥነ ፡ ባህሎሙ ። ባህለ ፡ ብካይ ፡ በማይ ፡ (መገ ፡ ፴ ። ስንክ ፡ ጥር ፲፱ ። ፈ ፡ መ ። ፳፱ ፡ ፬ ። ማር ፡ ይሥሐ ። ቄር ፡ ጸላ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፳) ።

**አብህለ** ፤ (**ያብህል**) ፤ **አው ፡ አበለ ፡ (ያብል)** ፤ አሰኘ ፤ አናገረ ፡ (ማቴ ፳፪ ፡ ፵ ። ግብ ፳ ፡ ፶) ። አሆ ፡ በልኒ ፡ ወአሆ ፡ አብሊዮ ። ለአነ ፡ አሆ ፡ አብሎት ። ንበየ ፡ ክመ ፡ እሙ ፡ አሆ ፡ አበሰቶ ፡ ለተወክፎ ፡ ትእዛዝ ። አንጠይዎ ፡ ክመ ፡ አሆ ፡ ያብልዎ ፡ (አርጋ ። ስንክ ፡ ታኅ ፳ ። ዮሴፍ) ።

**አብሃሊ** ፤ **መብሃሊ** ፤ **መብህል** ፤ የሚያሰኝ ፡ የሚያናግር ፤ አሰኝ ፡ አናጋሪ ።

**ምብሃል** ፤ (**ላት**) ፤ መባያ ፡ መናገሪያ ። ማሰኛ ፤ ማናገሪያ ።

**ተብህለ** ፤ ተባለ ፡ ተተነባ ፤ ተወራ ፡ ተነገረ ፤ ተጠራ ፡ ተሰየመ ። ተብህለ ፡ ለቀደምት ። ዘተብህለ ፡ በዳንኤል ፡ ነቢይ ። ብፅዕንን ፡ እንተ ፡ ተብህለት ፡ ለብዙኃን ። መጽሐፍ ፡ ዘይትበሀል ፡ ፈውስ ፡ መንፈሳዊ ። ዘሀሎ ፡ ይትበሀል ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወልድ ። እስመ ፡ ኅሊና ፡ ፀቡስ ፡ ምንኑ ፡ ይትበሀል ፡ (ማቴ ፳ ፡ ፳፭ ። ፳፱ ፡ ፲፩ ። ፊልክ ፡ ፸፱ ። ፈ ፡ መ ። ዕር ፡ ኢሳ፳ ፡ ፳፭ ። ጥበ፱ ፡ ፲፩) ።

**ብሁል** ፤ (**ላን ፡ ላት ፡ ብህልት**) ፤ የተባለ ፡ የተነገረ ፤ ንግር ። አሳ ፡ ብሁል ፡ ሊተ ፡ (አፈ ፡ ድ፲) ።

**ተባሀለ** ፤ ተባባለ ፡ ተማከረ ፤ ተነጋገረ ፤ ተሟገተ ፡ ተከራከረ ። ተባሀሉ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ። ተባሀሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ክመ ፡ የሀቦ ። እሉ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ተባሀልዎ ፡ ለፈርዖን ። ወአፎ ፡ እክል ፡ ባሕቲትየ ፡ ተባህሎቶሙ ። አመ ፡ ይትባሀሉ ፡ ለሰይጣን ፡ (ዘፍ፲፭ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፳፫ ። ዘፀ፰ ፡ ፳፯ ። ዘዳ፩ ፡ ፲፪ ። ይሁ ፡ ፱) ።

**አስተባሀለ** ፤ አባባለ ፤ አሟገተ ፡ አከራከረ ።

**ብሂም** ፤ **ሞት** ፤ (**ብህመ ፡ ይብህም ፡ ይብህም**) ፤ ድዳ ፡ መኾን ፤ አለመናገር ፤ ልናገርም ፡ ቢሉ ፡ አለመቻል ፤ እንደ ፡ ከብት ፡ መኾን ። ይኄይስ ፡ ብሂም ፡ እምነቢብ ፡ በሐሰት ። ይብህም ፡ ልሳን ። ብህመ ፡ ልሳኑ ። ሜጥኩ ፡ ገጽየ ፡ ወብህምኩ ፡ (ፊላስ ። ማንዘ ። ስንክ ፡ የካ፳ ። ዳን፲ ፡ ፲፭) ።

**በሃም** ፤ (**ምት ፡ ማን ፡ ማት**) ፤ ድዳ ፡ መናገር ፡ የማይችል ፤ ከድምጥ ፡ በቀር ፡ ፍሬ ፡ ቃል ፡ የማይሰጥ ። ክነ ፡ ጽሙመ ፡ ወበሃመ ፡ እምአውሥእትክሙ ። ኢትክውን ፡ እንከ ፡ በሃመ ። ወከመ ፡ በሃም ፡ ዘኢይከሥት ፡ አፉሁ ። ለበሃማን ፡ ከሮሙ ፡ ቃለ ፡ (ማንዘ ። ሕዝ፳፬ ፡ ፳፯ ። መዝ ፡ ፴፯ ። ኪዳ) ።

**ብሁም** ፤ (**ህምት**) ፤ ድዳ ፡ የኾነ ፤ አፋ ፡ እያለው ፡ የማይናገር ። ብእሲት ፡ ብህምት ፡ (ስንክ ፡ ሐም፳) ።

**ብህመት** ፤ ድዳ ፡ መኾን ፤ ድዳነት ። ብህመተ ፡ ልሳን ። ተፈትሐ ፡ ልሳኑ ፡ እምብህመት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ሠኔ፴) ።

**ብሄማ ፧** (ዕብራ ። ዐረ ፡ በሀኢም) ፧ ከብት ፡ እንስሳ ፡ ኢንባቢ ።

**ብሄሞት ፧** (ዕብራ) ፧ ጉማሬ ፡ የወንዝ ፡ አውሬ ፡ የባሕር ፡ ፈረስ ፡ በአፍሪቃ ፡ ወንዞች ፡ በየሐይቆቹ ፡ የሚገኝ ፡ ከውሃ ፡ እየወጣ ፡ ሣርና ፡ ቅጠል ፡ የሚበላ ፧ ታላቅ ፡ ገናና ፡ ቈርበተ ፡ ወፍራም ፡ ዐንገተ ፡ ደንዳና ፧ ቈርበቱ ፡ ኰርባጅ ፡ ፀለንጋ ፡ የሚኾን ፡ መልኩ ፡ ያንድስ ፧ ድምጡ ፡ የፈረስ ፡ ሲያሽካካ ፡ ፈረስ ፡ የሚመስል ። ዱኖ ፡ ጅንጉ ፡ የባሕር ፡ የበረሓ ፡ ጕሽ ፧ ጠባዩ ፡ ያውሬ ፡ መልኩ ፡ የበሬ ። ናሁኬ ፡ ብሄሞት ፡ ዘገበርኩዎ ፡ ምስሌከ ፡ ይበልዕ ፡ ሣዕረ ፡ ከመ ፡ ላሕም ፡ (ኢዮ ፵ ፡ ፲፭) ።

**ብሄሞት ፧** በቁሙ ፡ የየብስ ፡ ዐንበሬ ፡ ከባሕር ፡ ተፈጥሮ ፡ በየብስ ፡ የሚኖር ፡ ግሩማን ፡ አራዊት ፡ የሚፈሩትና ፡ የሚገዙት ፡ ከአራዊት ፡ ኹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ መፈረጃ ፡ ግዙፍ ፧ የእንስሳት ፡ ራስ ፡ የአራዊት ፡ ንጉሥ ፧ በኆራቸው ፡ ቀዳማይቸው ፡ በተፈጥሮ ፡ የሌዋታን ፡ ወንድም ፡ ባሲ ፡ መስሲ ። የሌዋታንን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፧ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዝሆንን ፡ ይሉታል ። ወይትከፈሉ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፧ ክልኤቱ ፡ ዐናብርት ፧ ዐንበሬ ፡ እንስቲያዊት ፡ ዘስማ ፡ ሌዋታን ፡ ከመ ፡ ትኅድር ፡ በልጉተ ፡ ባሕር ፧ ወለተባዕታይ ፡ ስሙ ፡ ብሄሞት ፡ ዘይእኅዝ ፡ በእንግድዓሁ ፡ በድወ ፡ ዘኢያስተርኢ ፧ ወስሙ ፡ ዴንዳ ፡ በምሥራቀ ፡ ገነት ፡ (ሔኖ ፷ ፡ ፰) ።

**አብሀመ ፧** ድዳ ፡ አደረገ ፧ አፍ ፡ አስያዘ ፧ ዝም ፡ አሰኘ ።

**አብሃሚ ፧ መብህም ፧** ድዳ ፡ የሚያደርግ ፧ አፍ ፡ የሚዘጋ ፡ የሚለጉም ።

**በሀነ ፧** (ይብህን ፡ ይብሀን ፡ ብሂን ። ዕብ ፡ ባሐን ፧ ፈተነ) ፧ በነነ ፡ ቡነ ፡ አለ ፡ የድቄት ፡ ያመድ ፡ የትቢያ ።

**ባህነዎ ፧ ኖት ፧** (ባህነነ ፡ ይባህንን ፡ ይባህንን) ፧ መብነን ፡ መባከን ፡ ብን ፡ ብን ፡ ብንን ፡ ብንን ፡ ማለት ፡ ማንስ ፡ መጉደል ፡ መጥፋት ፡ መበላሸት ፡ ከንቱ ፡ መኾን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በባህነን ፡ ፈንታ ፡ ተባህነን ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ይኄይሰኒ ፡ መዊት ፡ እምይት ባህነነኒ ፡ ምዝጋናየ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ መስ፳) ።

—፧ በቁሙ ፡ መባነን ፡ መበርገግ ፡ ደንግጦ ፡ ከንቅልፍ ፡ መንሣት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ብህኑን ፧** (ናን ፡ ኖት ፡ ንንት) ፧ የባነነ ፡ የበነነ ፡ የባከነ ፡ ብኑን ፡ ከንቱ ፡ በኖና ፡ በከና ፡ ፍሉጥ ፡ ብዑድ ። ቃላተ ፡ ሐስወ ፡ ወብህኑነ ፡ ታርኢ ። ይሜህሩ ፡ ብህኑነ ፡ ሥጋዌ ፡ ዘእንበለ ፡ ፀምረተ ፡ መለኮት ። ኢብህኑን ፡ ትስብእቱ ፡ እምድማሬ ፡ መለኮቱ ፡ ወኢብሕትው ፡ መለኮቱ ፡ እምትስብእቱ ፡ (ቄር ፡ ጸላ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ባህን ፧ በህናን ፧** ብናኝ ፡ ትቢያ ፡ ጕድፍ ።

**በዊእ ፧ ኦት ፧** (በእ ፡ ይበውእ ፡ ይባእ ። ዕብ ፡ ቦእ ። ዐረ ፡ ባእ) ፧ መግባት ፡ መከተት ፡ ጥልቅ ፡ ስምጥ ፡ ማለት ፡ ማደር ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ማለፍ ፡ መኼድ ፡ ውሳጣዊ ፡ ማእከላዊ ፡ መኾን ። ቦእ ፡ ቤቶ ። ባእ ፡ ሀገረ ። ባእ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ። ኢትባኢ ፡ ውስተ ፡ ገራህተ ፡ ባዕድ ፡ (ዳን፲፪ ፡ ፲፩ ። ኢር፱ ፡ ፭ ። ዘፍ፰ ፡ ፮ ። ፋትያ ፡ ፳) ። በቦእ ፡ ፈንታ ፡ ተባውአ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ሮሜ፭ ፡ ፲፰ ። ገላ፬ ፡ ፱ ። ፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፮) ። በዊእና ፡ በዉአት ፡ አንድ ፡ ሥር ፡ ናቸው ።

**በዋኢ ፧** (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፧ የሚገባ ፡ ገቢ ፡ መሪዉ ። ጽፉቅ ፡ በዋኤ ፡ ቤታ ። ኅብ ፡ ብዙኅ ፡ በዋኢቱ ። በእንተ ፡ ብዝኆ ፡ በዋእያን ፡ ወወፃእያን ፡ (ምሳ፳፱ ፡ ፲፰ ። ሢራ፲፱ ፡ ፳ ። ፊልክ ፡ ፶ ፡ ፳፪) ።

**ቡአት ፧ በአት ፧** መግባት ፡ አገባብ ፡ መባት ፡ አባባት ። በበአትከ ፡ ወበፀአትከ ። በአተነ ፡ ወፀአተነ ፡ በሰላም ፡ ዕቀብ ። ጥንት ፡ ወበአት ፡ ውስተ ፡ ትምህርት ። በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ በአቱ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ። በአተ ፡ ክረምት ። በአተ ፡ ሰንበት ። በአተ ፡ ሌሊት ። በአተ ፡ ጾም ፡ (ዘዳ፳፰ ፡ ፮ ። ግንዘ ። ቄር ፡ ጸላ ። ስንክ ፡ የካ፳ ። ሠኔ፳፭ ። ማር፲፭ ፡ ፵፪ ። አቡሻ ፡ ፲፪ ። መር ፡ ዕው) ።

**በአት ፧** ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ የብትኑ ፡ ሰዋስው ፡ መግለጫ ፡ እኹል ፡ ገብ ፡ ቃልና ፡ ፊደል ።

(ጥት) **በአት ፧** (ታት) ፧ የመነኰሴ ፡ ቤት ፡ ጕሬ ፡ ዋሻ ፡ ፍርኵታ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ቦታ ፡ ጋጥ ፡ በረት ። ቢደብረ ፡ መቃርዮስ ፡ ኅበ ፡ ተሐንጸ ፡ በአት ። ንበር ፡ በበአትከ ። ወኮነ ፡ ይትፋለስ ፡ እምበአት ፡ ውስተ ፡ በአት ፧ ቤት ፡ (ስንክ ፡ የካ፳ ። ፊልክ ፡ ፳፱ ። ሃ፯) ። በአተ ፡ ፈያት ። በአተ ፡ መዛግብት ። በአታተ ፡ ኵሎሙ ። በአታት ፡ ለመራዕይሁ ፧ ዋሻ ፡ (ኤር፯ ፡ ፲፩ ። ቀሌ ። ኢዮ፴፱ ፡ ፳፫ ። ፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፳፰) ። ቦታ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ፈረንሳዊ ፡ ቢት ፡ የሚለውም ፡ ከዚህ ፡ ይስማማል ፡ ዱብልንና ፡ ቡክልን ፡ ተመልከት ።

**አብአ ፧** አገባ ፡ አስገባ ፡ መለሰ ። አባእናሁ ፡ ውስተ ፡ ገነት ። ኢታብእ ፡ ኵሎ ፡ ሰብአ ፡ ዘረከብከ ፡ ውስተ ፡ ቤትከ ። ዘያወፅአሙ ፡ ወዘያበውአሙ ። አብአሙ ፡ ውስተ ፡ አእምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ኩፋ ፡ ፫ ። ሢራ፲፩ ፡ ፳፱ ። ዘኍ፳፯ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ ግንቦ) ።

—፧ ሰጠ ፡ አቀረበ ። እምከመ ፡ አባእኩ ፡ ለእግዚ ። ካህን ፡ ዘያበውእ ፡ መሥዋዕተ ። አኮ ፡ አባእኩ ፡ ተዝካረ ፡ ስእለትክሙ ፡ ቅድሜሁ ፡ (ሢራ፯ ፡ ፱ ። ዘሌ፯ ፡ ፰ ። ጦቢ፲፪ ፡ ፲፪) ።

**አባኢ ፧ መብእ ፧** (እት ፡ አን ፡ ኣት) ፧ የሚያገባ ፡ አግቢ ፡ መላሽ ። ሰጭ ፡ አቅራቢ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ሙብእ ፧** (ኣት) ፧ መግቢያ ፡ ማግቢያ ፡ ማስገቢያ ፡ በር ፡ ደጃፍ ። ኢየአምር ፡ ሙባእየ ፡ ወሙፃእየ ። እስመ ፡ አንተ ፡ ሀየ ፡ ቦቱ ፡ ሙባአ ፡ ባዕለ ፡ ይሁዳ ። ሙባአ ፡ ግብጽ ። ሙባአ ፡ ባቢሎን ። ሙባአቲሁ ፡ (፫ነገ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ዮዲ፱ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፲ ። ፳ ። ሕዝ፵፫ ፡ ፲፩) ።

**መባእ ፤ (ኣት) ፤** በቁሙ ፡ መባ ፡ እጅ ፡ መኀሻ ፡ በረከት ፡ ቍርባን ፡ መሥዋዕት ። ጸሎተ ፡ መባእ ። ወርቅ ፡ መባእ ፡ ዘሣጺን ። ኢትብል ፡ ቡብዝን ፡ መባእየ ፡ ይብሪ ፡ ሊተ ። አብእ ፡ መባአ ፡ ለእግዚ ፡ (ቅዳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፰ ፡ ፭ ። ሚራ ፡ ፯ ፡ ፱ ። ፲፱ ፡ ፲፭ ። ማቴ፳፰ ፡ ፳፱) ።

**ተባውአ ፤** ተጋባ ፡ ተገባባ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ኾነ ።

**አስተባውአ ፤** አጋባ ፡ አገባባ ፡ አዛወገ ።

**ባእ ፤—ስንዝር ፤—ባዕ ።**

**በዊዝ ፤ ዘት ፤ (በዘ ፡ ይበውዝ ፡ ይቡዝ) ፤** መቡዝ ፡ መፍዘዝ ፡ መበዘን ፡ መበንፍ ።

**ቡዝ ፤** ቸልታ ፡ እንቀጽ ፡ ንባቡ ፡ ስያፍ ፡ ቃሉ ፡ ስንፍ ፡ ነገር ፡ የማያስር ፡ ቀቲሎ ፡ ባሬክ ፡ ቀዲሶ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ። ከሥሩ ፡ አውታረ ፡ ብገና ፡ ያንዱ ፡ ስም ። ቡዝ ፡ ይንጉል ፡ እንዲሉ ። ነሬሙችም ፡ ባውዛ ፡ የሚሉት ፡ የታላቅ ፡ መብሬት ፡ ስም ፡ ከቡዝና ፡ ከቤዝ ፡ ይሰማማል ።

**በዊሕ ፤ ሐት ፤ (በሐ ፡ ይበውሕ ፡ ይብሕ ። ዐረ ፡ ባሐ) ፤** መታየት ፡ መገለጥ ፤ መጕላት ፡ ብሩህ ፡ ጽዱል ፡ ጸዐዳ ፡ መኾን ፤ ሞሬ ፡ በሬቅ ፡ ብሕክ ፡ መምሰል ። ቡሐ ፡ ቡሓ ፡ ብሓ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። መሠልጠን ፡ ሹመት ፡ መብት ፡ ማግኘት ፤ ፈቃድ ፡ ሥልጣን ፡ መቀበል ፡ ከበላዩ ። ብሕተን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**አብሐ ፤ (ያበውሕ ፡ ያብሕ) ፤** አሠለጠነ ፤ ፈቀደ ፡ አሰናበተ ፤ ሾመ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠ ። ኢያብሖ ፡ አቡሁ ። ወዘንተኒ ፡ እምኀበርነ ፡ ሶበ ፡ ያበውሕ ፡ እግዚ ። ንብብ ፡ ሰእመ ፡ አብሐከ ። ወአብሖሙ ፡ ላዕለ ፡ አጋንንት ፡ (ኩፋ ፡ ፴፰ ። ዕብ ፡ ፮ ፡ ፫ ። ሚሬ፴፯ ፡ ፷ ። ማር ፡ ፯ ፡ ፯) ።

**አስተበውሐ ፤** አስፈቀደ ፡ ዕሺ ፡ አሰኘ ፡ አስፈቀደ ፡ አስደፈረ ። አስተበዊሖ ፡ በኀበ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ መጽአ ፡ ከመ ፡ ይሞቅሕ ፡ ኵሎ ። አስተበውሓ ፡ ሰበሊዐ ፡ ዕፀ ፡ ዕልወት ። አስተበውሖቶሙ ፡ ለባሊዐ ፡ ንዋየ ፡ ውስጥ ፡ (ግብ፱ ፡ ፲፬ ። መጽ ፡ ምስ ። ጥበ፲፱ ፡ ፳) ።

**ተበውሐ ፤ (ይትበዋሕ) ፤** ሠለጠነ ፡ ሥልጣን ፡ አገኘ ፡ ተቀበለ ፤ ባለመብት ፡ ኾነ ። ኢይትበውሑ ፡ ላዕለ ፡ ውሉደ ፡ ጻድቃን ። አሚሃ ፡ ተበውሐ ፡ ጤሎስ ፡ በኵሉ ፡ አህጉር ። እስመ ፡ ተበዋሕኩ ፡ እትናገር ። ሥርዐት ፡ ቅድስት ፡ ዘተበዋሕክሙ ፡ የተቀበላችኋት ፡ (ኩፋ ፡ ፲ ። ዮሴፍ ። ዘፍ፲፰ ፡ ፴፰ ። ቀሌ) ።

**ብዉሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ውሕት) ፤** የሠለጠነ ፡ ሥሉጥ ፡ የተገባ ። ብእሲት ፡ ኢኮነት ፡ ብውሕተ ፡ ላዕለ ፡ ርእሳ ፡ ወከማሁ ፡ ብእሲኒ ፡ ኢኮነ ፡ ብዉሐ ። ወአኮሰ ፡ ዘኢኮነ ፡ ብዉሓነ ። ኢኮነት ፡ ብዉሐ ፡ ለብሓዊ ፡ ይግበር ፡ (፩ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፬ ። ፪ተሰ ፡ ፫ ፡ ፱ ። ሮሜ ፱ ፡ ፳፩) ።

**ብዉሕ ፤ (ይደሉ ፤ መፍትው ፤ ርቱዕ) ፤** ይገባል ፡ የተገባ ፡ የሚገባ ፡ ግቡ ፤ አገባብ ። ይደሉ ፡ ሲኾን ፡ በቁሙ ፤ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ሲኾን ፡ ውእቱ ፡ አለበት ። ኢብዉሕ ፡ ይባእ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዘእንበለ ፡ ካህን ። ብዉሕ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ። ብዉሕ ፡ ለከ ፡ ትንብብ ፡ ወትግበር ፡ ዘፈቀድከ ። ኢኮነሁ ፡ ብዉሐ ፡ ለልዑል ፡ ይግበር ፡ ዘፈቀደ ፡ (ዮሴፍ ። ፈ ፡ መ ፡ ፮ ፡ ፪ ። ቀሌ ። ኢዮ፳፪ ፡ ፲፪) ።

**ብውሕና ፤** ጌትነት ፤ ሥልጣንነት ። ኀልዮተ ፡ ብውሕናሁ ፡ (ማር ፡ ይሥ፪ ፡ ፱) ።

**መባሕት ፤** ሥልጣን ፡ መብት ፤ ሹመት ፤ ትእዛዝ ፤ ፈቃድ ። ተውህበ ፡ ሎቱ ፡ መባሕት ። በመባሕተ ፡ መኑ ፡ ትገብር ፡ ዘንተ ። ወሰአለ ፡ መጽሐፈ ፡ መባሕት ። ዲያቆን ፡ ኢይግበር ፡ ምንተኒ ፡ ዘእንበለ ፡ መባሕተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አቡሁ ። እስከ ፡ ይረክብ ፡ መባሕተ ፡ ቃልየ ። ይጽሕፍ ፡ መባሕተ ፡ (ዳንኤ ፡ ፯ ። ማቴ፳፩ ፡ ፳፫ ። ግብ፱ ፡ ፪ ። ዲድ ፡ ፳ ። ቀሌ ። ሲኖዶ) ።

**ቦክ ፤ (ዕብ ፡ ቡኽ) ፤** በዊክ ፤ መባክን ፡ መቅበዝበዝ ፤ እንቡዝ ፡ መኾን ፤ ተለል ፡ ተለል ፡ ማለት ፤ የመንገደኛ ፡ የድውይ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ቍስለ ፡ ሥጋ ፡ ይሉታል ። መጽአከ ፡ ሕማም ፡ ወነሰሰከ ፡ ቦክ ፡ (ኢዮ፱ ፡ ፳) ። ክዳን ፡ ገዚፍ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ክዳን ፡ ቦክ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ማክቤር ፡ ይላል ፤ ልብድ ፡ ለሐፍ ፡ የሌት ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ቡልኮ ፡ ያለ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፫) ።

**በውላ ፤** ስመ ፡ ጫፍሬ ፤ ከቡልዮስ ፡ ቂሳር ፡ የወጣ ፡ (ዮሴፍ) ።

**በውኒ ፤—የወር ፡ ስም ፤—በኢናህ ።**

**ቦዐ ፤ (ዐረ ፡ ባዐ) ፤** ዘረጋ ፤ ጋተ ፤ ስንዘረ ።

**በዕ ፤** ስንዝር ፤ ውስጥ ፡ እጅ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ክንድ ፡ ይሉታል ፡ (ዘዐ፴፯ ፡ ፲፮) ።

**ቦቀ ፤ (ይበውቅ ፡ ይቡቅ ፤ በዊቅ ። ዐረብ ፡ በወቀ) ፤** ነፋ ፡ መታ ፡ አስፈነኸ ፡ ባፍ ፡ በትን ፋሽ ።

**ቡቅ ፤ (ብ ፡ አብዋቅ) ፤** ቀንዳ ፡ መለከት ፡ ሥሥ ፡ ውስጠ ፡ ክፍት ። ወይትነፋኅ ፡ ቀርን ፡ ወብዕዚት ፡ ወአብዋቅ ፡ ፡ (ሥር ፡ አኵ) ። አንቦቀቦቀ ፡ ተንቦቀቦቀ ፡ በቅፅ፡ቃ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ቦቅቡቅ ፤ (ዕብ) ፤** ታናሽ ፡ የውሃ ፡ ዕቃ ፡ ቅል ፡ መንቀል ፡ ጠርሙዝ ፤ አፈ ፡ ጠባብ ፡ ዐንገተ ፡ ረዥም ። ጋላም ፡ ቅሉን ፡ ቡቂ ፡ ይለዋል ።

**በዘ ፤ (ዐቢይ ፡ አገባብ) ፤** ፍችው ፡ ገንዘብ ፡ ምስጢሩ ፡ እንደ ፡ ስለ ፡ ዘንድ ። በንባብና ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ፡ በዘወይእ ፡ ሞተ ፡ ኵሉ ። በዘቀነዮሙ ፡ ሞት ፤ ሞት ፡ ኹሉን ፡ በሬረበ ፡ ገንዘብ ፤ በገዛቸው ፡ ገንዘብ ። ወትሜህር ፡ በዘታስሕቶሙ ፤ በምታስታቸው ፡ ገንዘብ ።

ኀብሩ ፡ በዘይምዕዑኒ ፡ በሚያሳዝኑኝ ፡ ገንዘብ ። በምስጢር ፡ እንጂ ፡ በንባብ ፡ እንደና ፡ በስ ፡ ሲኾን ፡ ምስክር ፡ የለውም ። በርሥእኑ ፤ እንዘ ፡ አልቦ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ በዘረሥአ ፡ ብዘአልቦ ፡ እያለ ፡ ይገኛል ፡ የመሳሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፡፵፱ ፡ ፴፮ ። ፵ ፡ ፲፭) ።

**በዘ** ፤ (በ፡ዘ) ፤ በ ፡ በቁም ፡ ቀሪ ፡ ዘ ፡ ቅጽልና ፡ በቂ ፡ ወይም ፡ የዘርፍ ፡ ደፊ ፡ ይኾናል ። ሰምንት ፡ ትትናገር ፡ በዘይሰምዖ ፡ ሕዝብ ፤ በሚሰሙት ፡ ቋንቋ ። በዘርእየ ፡ ወበዘሰምዐ ፡ ሰማዕተ ፡ ይከውን ፡፡ ባየው ፡ በሰማው ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ፈተኛውም ፡ ባየ ፡ በሰማ ፡ ገንዘብ ፡ ይሰኛል ፡ ምስጢሩ ፡ እንዳየ ፡ እንደ ፡ ሰማ ፡ መጠን ፡ በዓየ ፡ በስ ፡ ስማ ፡ ያየውን ፡ የሰማውን ፤ አይቶ ፡ ሰምቶ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ የበን ፡ አፈታት ፡ ያሳያል ። በዘአይኒራም ፡ ዐፀ ፡ ወበዘአቤሴሎም ፡ እብን ፤ ባይኒራም ፡ ዕንጨት ፡ ባቤሴሎም ፡ ድንጊያ ፡ በቁም ፡ ቀሪና ፡ ደፊ ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ዘ ፡ ቅጽል ፡ ሲኾን ፡ በ ፡ አዳማቂ ፡ ኹኖ ፡ ይቀራል ። ነሥአ ፡ ሰይፈ ፡ በዘይቀትል ፡፡ ልብስ ፡ በዘያስተባሪ ፡ ምክንያት ፡ በዘያስተዋርድ ፡፡ በንና ፡ ዘን ፡ ተመልከት ፡ (ዕር፲፱ ፡ ቍ፻፱) ።

**በዚኅዝ** ፤ ዝት ፤ (በዘ፡ይበዝኅዝ፡ይብዝኅዝ። ዐረ ፡ ዕብ ፡ በዛዝ) ፤ መዛት ፤ ጕራ ፡ መንዛት ።

**በዝበዘ** ፤ (ዕብ ፡ በዝቤዝ) ፤ በቁሙ ፡ በዘበዘ ፡ ዘረፈ ፡ ቀማ ፡ በረበረ ። ዘሬ ፡ በተን ፡ መንዘረ ፡ አባከነ ፡ በክንቱ ። ዐማ ፡ ነቀፈ ፡ ሰደበ ፡ አዋረደ ፤ ናቀ ፡ አቃለለ ።

**በዝግና** ፤—ዝርግፍ ፤—ዘጊን ፡ ዘገነ ።

**ቤዘወ** ፤—ተቤዝ ፤—በዩኅዝ ፡ ቤዘ ።

**በዚኅ** ፤ ኆት ፤ (በዝኀ፡ ይበዝኅ፡ ይብዝኅ) ፤ መብዛት ፡ መርባት ፡ መበርከት ፡ መውለድ ፡ መክበድ ፡ መፈይፈድ ፡ ማየል ፡ መበርታት ፡ (ዘፍ፴፩ ፡ ፵፱ ፡ ፵፯ ። ፵ ፡ ፲፮ ። ዘፀ፩ ፡ ፯) ። ጸንዐ ፡ ማይ ፡ ወበዝኀ ፡፡ በዝኀ ፡ ድምፀ ፡ ሁከት ፡ (ዘፍ፯ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ። ፩ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፲፱) ።

**ብዙኅ** ፤ (ኃን ፡ ኃት ፡ ዝኅት) ፤ የበዛ ፡ ብዙ ፡ እጅግ ፡ ዐያሌ ። ዕንቍ ፡ ዘብዙኅ ፡ ሤጡ ፡፡ ብዙኃን ፡ እምውሉደ ፡ ግብጽ ፡፡ ብዙኃት ፡ አዋልድ ፡፡ ሀገር ፡ ብዝኅት ፡ ሰብእ ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፵፩ ። ክፉ ፡ ፴፪ ። አስቴ፱ ፡ ፲ ። ሕዝ፴፱ ፡ ፲፯) ።

**ብዙኀ** ፤ በዝቶ ፡ ብዙ ፡ ኹኖ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ። መጽአ ፡ ብዙኀ ፡ ወተመይጠ ፡ ኀዳጠ ፡፡ ኢትትአመኖ ፡ ብዙኀ ፡፡ ዘብዙኀ ፡ ተመንደበ ፡ ብዙኀ ፡ ይትሜሰን ፡ (ዘረፋ ። ሢራ፳ ፡ ፳ ። ፴፩ ፡ ፲፩) ።

**ብዝኀት** ፤ መብዛት ፡ አብዛዝ ፡ ብዛት ፡ ብዙነት ። ብዝኀተ ፡ ሰብእ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ብዝኅ** ፤ (ኃት) ፤ ብዛት ፡ ብዙነት ፡ ብዥ ። ብዝኀ ፡ መዋዕል ፡፡ ብዝኀ ፡ ዓማት ፡፡ በብዝኀ ፡ ዓመታት ፡ ወበብዝኀ ፡ ንብረት ፡ (ዘክ፰ ፡ ፲ ። ዮሐ፵፩ ፡ ፳ ። ኢዮ ፲፪ ፡ ፲፱) ።

**አብዝኀ** ፤ አበዛ ፡ አረባ ፡ አበረከተ ። አስበዛ ፡ አስረባ ፡ አስበረከተ ። አብዝኆ ፡ ኣብዝኆ ፡ ለሕማምኪ ፡፡ ዘአብዝኀ ፡ ብዕለ ፡፡ ዘአብዝኀ ፡ ጥበበ ፡ አብዝኀ ፡ ሐዘነ ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፲፮ ። መክ፭ ፡ ፲፩ ። ፩ ፡ ፲፰) ።

**አብዛኂ** ፤ (ኂት ፡ ኃያን ፡ ያት) ፤ የሚያበዛ ፡ የሚያስበዛ ፡ አብዥ ፡ አስበዥ ። ኢይኩን ፡ አብዛኄ ፡ ነገር ፡፡ አብዛኃያነ ፡ ሠሐቅ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳ ፡ ፭ ። ፊ ፡ መ ፡ ፴፱ ፡ ፱) ።

**መብዝኂ** ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ። መብዝኃያነ ፡ ነገር ፡፡ መብዝኂ ፡ ነቢብ ፡፡ ወንሕነ ፡ ብንቤክሙ ፡ ከመ ፡ መብዝኂ ፡ ነገር ፡ (ኪዳ ፡ ገ፱ ። ፊ ፡ መ ፡ ፳፭ ፡ ፫ ። አፈ ፡ ተ፳፫) ።

**መብዝኅት** ፤ የተከፍሎ ፡ ብዛት ፡ ላቂያ ፡ ብልጫ ። ሲነበብና ፡ ሲዘረዘር ፡ የቅጽል ፡ አፈታት ፡ ይፈታል ። መብዝኅት ፡ መዋዕሊሆሙ ፡፡ መብዝኅተ ፡ ሕዝብ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫ ፡ አርጋ) ። የሚበዛው ፡ የሚልቀው ፡ የሚበልጠው ፡ ብዙው ፡ ያሰኛል ። መብዝኅቶሙ ፡ ተነፅኑ ፡ በገዳም ፡፡ ወመብዝኅቶሙ ፡ ሀሰዉ ፡ እስከ ፡ ዮም ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፭ ። ፲፭ ፡ ፮) ።

**መብዝኅቶ** ፤ ብዙውን ፡ ይልቁን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ። መብዝኅቶ ፡ ይወድቅ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡፡ ወአንተሰ ፡ መብዝኅቶ ፡ ትትሜሰል ፡ ከመ ፡ ኃጥእ ፡ (ማቴ፲፯ ፡ ፲፭ ። ሉቃ ፡ ዕገ፳ ፡ ፶፯ ። መቢ፭ ፡ ፯) ።

**ተብዝኀ** ፤ ተባዛ ፡ ተራባ ፡ ተዋለደ ። ወይትባዝኃ ፡ በሙፋሪሆን ፡ (መገ ፡ ፲፻፫ ። ዘፍ፴ ፡ ፵፪) ። በብዝኀ ፡ ፈንታ ፡ ተብዝኀ ፡ ይላል ፤ ፈጽሞ ፡ ሰማለት ። ከመ ፡ ትትባዛኅ ፡ በሕይወትከ ፡፡ ወትትባዛኅ ፡ በረከቱ ፡ ለጻድቅ ፡፡ ተባዝኁ ፡ በእግዚእ ፡ (ሢራ፱ ፡ ፫ ። ፲፭ ፡ ፵፱ ። ፱ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፰) ።

**አስተባዝኀ** ፤ አባዛ ፡ አራባ ፡ አዋለደ ፡ አበራከተ ። አስተባዝኆከ ፡ ጥቀ ፡ (ዘፍ፲፯ ፡ ፮ ፡ ፳) ።

**ባዜቃ** ፤ (ዐረ ፡ ዘይበቅ) ፤ በቁሙ ፡ ፈሳሽ ፡ የማዕደን ፡ ዐይነት ፡ የሚገበቀበቅ ። ጥሩ ፡ ብር ፡ ቅልቅል ፡ የሌለው ። እንዘ ፡ ትሰወጡ ፡ ከመ ፡ ባዜቃ ፡ (ደራሲ) ።

**ባዚቃ** ፤ (ዕብ ፡ በዛቅ) ፤ መብረቅ ፡ ነጸብራቅ ፡ (ሕዝ፩ ፡ ፲፬) ።

**ብዝር** ፤ (ዐረብ) ፤ ፍሬ ፡ ቅንጣት ።

**ብዝር** ፡ **ክታን** ፤ የተልባ ፡ ፍሬ ፡ እንጕጕ ፡ ቅንጣቱ ።

**ባዝራ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፡ እንስት ፡ ፈረስ ፡ ፍሬያማ ፡ ፍሬያም ፡ መፍርዩት ።

**በዝኆ** ፤ ኆት ፤ (በዘተ ፡ ይቤዝት ፡ ይብዝት) ፤ ማቤዘት ፡ መፈልቀቅ ፡ ማፍታታት ፡ መንቀስ ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ማግባት ፡ ለመፍታል ። እንዘ ፡ ትቤዝት ፡ ፀምረ ፡ (ምሳ፴፱ ፡ ፲፭) ።


**በዛቲ** ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤ የሚያቤዝት ፡ አባዣች ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ አግቢ ።

**ተበዘተ** ፡ ተባዘተ ፡ ተፍታታ ፡ ተነቀሰ ።

**ብዙት** ፡ የተባዘተ ፡ ብዝት ፡ ባዘቶ ፡ ፍልቅቅ ። ፀምር ፡ ብዙት ፡ (መሳፍ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ ታኅሣ) ።

**በሓ ፡ ባሕ ፡ (ዐረ ፡ በኀ ፡ አይዞኽ)** ፡ የሰላምታ ፡ የቡራኬ ፡ ቃል ፡ ፍሥሓ ፡ ሰላም ። እንደ ጅት ፡ ዋልኽ ፡ እንደ ጅት ፡ አደርኽ ፡ ጤና ፡ ይስጥኽ ፡ ደስታ ፡ ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይኹን ፡ ጠላትኽን ፡ ያውድቅ ፡ ቢሰኞኽን ፡ ያርቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በሓክ ፡ ኪ ፡ በሓክሙ ፡ ክን ፡ እያለ ፡ በቅርብ ፡ በቅርቦች ፡ ይዘረዝራል ። ኢትበሎ ፡ በሓ ፡ ወእመ ፡ ይቤለከ ፡ በሓ ። በሓ ፡ ብልዋ ፡ ተሳሰምዋ ። ወበሓሂ ፡ ኢትበልዎ ። ባሕ ፡ ሂርማ ። ኢትበልዎሙ ፡ ባሕ ፡ (ፀሐገ ፡ ፱ ፡ ፳፱ ። ድጓ ። ፱ዮሐ ፡ ፲ ፡ ሂርማ ፡ ፪ ። ቀሌ) ። በሓከ ፡ ባሮክ ። ባሕከ ፡ ሂርማ ። በሓኪ ፡ ማርያም ። በሓክሙ ፡ አበው ፡ ቅዱሳን ። ባሕክን ፡ አው ፡ በሓክን ፡ (ፊእ ፡ ባሮ ። ሂርማ ፡ ፲፭ ። ደራሲ ። ማቴ ፳፰ ፡ ፱) ።

**ቢሒ ፡ ብሒ ፡ (ዕብ ፡ ብሄሞት)** ፡ ጉማሬ ፡ የወንዝ ፡ የባሕር ፡ አውሬ ። ብህመን ፡ እይ ። ተጠምቀ ፡ በማይ ፡ ዐራቁ ፡ ከመ ፡ ቈርናናዓት ፡ ወፀንጕኮ ፡ ወብሒ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።



ቢሒ ፡

**ቢሓት ፡ ብሒያት** ፡ ጉማሮች ፡ ጉማሬዎች ። አክይስት ፡ ወዐናብርት ፡ ወሐርገፃት ፡ ወዐናጕግ ፡ ወቢሓት ፡ ወቈርናናዓት ፡ (መቃ ፡ ገ፲፪) ።

**ብሒእ ፡ አት ፡ (ብሒእ ፡ ይብሒእ ፡ ይብሐእ ። ዕብ ፡ ቦሄእ ፡ እጅግ ፡ ፈራ ፡ ተደነቀ)** ፡ መቡካት ፡ መሐምጠጥ ፡ መብሰል ። ሐሊብ ፡ ዘኢብሐአ ። ይፈርሀሙ ፡ ኢይብሒኡ ፡ እስመ ፡ ጸሐብ ፡ ዘቅቡል ፡ ፍጡነ ፡ ይብሒእ ፡ (ግንዘ ። ሂርማ ፡ ገ፶፰) ። በብሒእ ፡ ፈንታ ፡ ተብሕእ ፡ ይላል ፡ አያስኬኝም ። እስከ ፡ ይትበሐእ ፡ (ሆሴዕ ፡ ፱ ። ዘፀ፲፪ ፡ ፴፱) ። በጕብጕን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ብሑእ ፡ (ኣን ፡ ኣት ፡ ሕእት)** ፡ የቦካ ፡ የብሰለ ፡ የሐመጠጠ ። ምስሰ ፡ ኅብስት ፡ ዘብሑእ ። ኢትግበርዎ ፡ ብሑእ ። ኢትዝባሕ ፡ በብሑእ ፡ ደም ፡ ያደረ ፡ (ዘሌዋ ፡ ፳፫ ። ፪ ፡ ፲፭ ። ዘፀ፳፫ ፡ ፲፰) ። በብሑእ ፡ ፈንታ ፡ ብሒእ ፡ ይላል ፡ አያስኬኝም ። ብሒእ ፡ ወይን ። ብሒእ ፡ ሜስ ። ሐምለ ፡ ብሒእ ፡ (ዘኍኅ ፡ ፫ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ። ዘፀ ፲፪ ፡ ፰) ።

**ብሕእት** ፡ መቡካት ፡ አቦካክ ፡ ቡሖነት ፡ ርሾ ፡ (ማቴ፲፮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪) ።

**ብሕእ ፡ (እት)** ፡ ቡሖ ፡ ርሾ ፡ (ሉቃ፲፪ ፡ ፩) ። በብሑእ ፡ ፈንታ ፡ ብሒእ ፡ እንደሚል ፡ በብሕእ ፡ ፈንታ ፡ ብሑእ ፡ ይላል ፡ ጥሬን ፡ በቅጽል ፡ ቅጽልን ፡ በጥሬ ፡ መለዋወጥ ፡ የጣፊና ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ቀዳሚሃ ፡ ቅድስተ ፡ ወብሑእኒ ፡ ቅዱስ ፡ ከማሁ ፡ ቡሖ ፡ ሊጥ ። ኅዳጥ ፡ ብሑእ ፡ ብዙኃ ፡ ሐሪጸ ፡ ደብሐእ ። አንጽሑ ፡ እንከ ፡ ብሑእ ፡ ብሉየ ፡ እምኔክሙ ። ብሑእ ፡ ዘዝሥአት ፡ ብእሲት ፡ ወኀብአቶ ፡ ውስተ ፡ ሐሪጽ ፡ ርሾ ፡ (ሮሜ፲፩ ፡ ፲፮ ። ፩ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ፯ ። ማቴ፲፫ ፡ ፴፫) ።

**ብሒእ** ፡ ርሾ ፡ ሎስን ፡ እይ ። መጣጣ ፡ ዐይብ ፡ ዐዞ ፡ ከል ፡ የተባላሸ ፡ ጠጅ ፡ ሐምጣጤ ። ትጸብኒ ፡ ኅብስተኪ ፡ በብሒእ ። ወአስተዩኒ ፡ ብሒአ ፡ ለጽምእየ ። ከመ ፡ ብሒእ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለቍስል ። ወቦ ፡ ሀየ ፡ ግምዔ ፡ ብሒእ ፡ ዘምሉእ ፡ ወመልኡ ፡ ሰፍነገ ፡ እምብሒእ ፡ (ሩት፪ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፷፰ ። ምሳ፳፭ ፡ ፳ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፳፱) ።

**አብሐእ** ፡ አቦካ ፡ አስቦካ ፡ በረሸ ፡ ለወሰ ፡ አስለወሰ ፡ አሐመጠጠ ፡ ሐምጣጣ ፡ አደረገ ፡ አስደረገ ። አፍጥኒ ፡ ወአብሐኢ ፡ ሠለስተ ፡ መሣልሰ ፡ ወግበሪ ፡ ዳፍንተ ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፮ ። ማቴ፲፫ ፡ ፴፫ ። ሉቃ፲፫ ፡ ፳፩) ።

**ተብሕእ** ፡ ተቦካ ፡ ተለወሰ ፡ ሊጥ ፡ ኾነ ።

**ተባሕአ** ፡ ተቧካ ፡ ተቦካካ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ የዱቄት ፡ የነገር ።

**በሕበሐ ፡ (ዕብ ፡ ቃራጽ ፡ ቀረጸ)** ፡ ማለ ፡ መሰለ ፡ ዐነጠ ፡ ቀረጠ ፡ ሠራ ፡ ፈጠረ ፡ የቡሖ ፡ የጭቃ ፡ የዳቦ ፡ የብስኩት ፡ የሠምዕ ፡ የልሕኵት ።

**ተበሕበሐ ፡ (ይትበሐበሕ ፡ ይትበሕባሕ)** ፡ ተማለ ፡ ተመሰለ ፡ ተፈጠረ ።

**ብሕባሔ** ፡ መፍጠር ፡ መፈጠር ፡ አፈጣጠር ፡ ፈጠራ ፡ ተፈጥሮ ። ዕብራይስጡ ፡ ሚሖሜር ፡ ቀራጽቲ ፡ ያለውን ፡ ግእዙ ፡ ተቀረጽኩ ፡ ተገለፍኩ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እምጽቡር ፡ ብሕባሔኪ ፡ ወእምኔሁ ፡ ቅሳሜነ ፡ ይላል ፡ (ኢዮ፴፫ ፡ ፯) ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ በሕበሐ ፡ ብሎ ፡ ፈጠረ ፡ የሚል ፡ አይገኝም ።

**ብሕውስ ፡ (ዕብ ፡ ባእሻህ)** ፡ አብሾ ፡ አስተናግር ፡ የደሮ ፡ ኸስ ፡ ግማታም ፡ ቅጠል ፡ በባድማና ፡ በድብድብ ፡ የሚበቅል ፡ ቋያ ፡ መጥፎ ፡ ቡቃያ ። ወኮነት ፡ ሀገር ፡ በድው ፡ ወበቈለ ፡ ላዕሌሃ ፡ ሦክ ፡ ወአሜከላ ፡ ወኮነት ፡ ብሕውስ ፡ ወምጕሕያ ፡ (መቃ ፡ ገ፲፪) ።

**በሐኰ ፡ (ብ ፡ አባሕኰ ፡ አብሓኰ)** ፡ የበግ ፡ የፍየል ፡ ተባት ፡ አውራ ፡ ኩርማ ፡ የሚታዘል ፡ የሚንጠለጠል ። በሐኰ ፡ እንዘ ፡ ይሜህል ፡ ላዕለ ፡ መርዔት ። በሐኰ ፡ ወዳቤላ ። ዳቤላት ፡ ወአባሕኰ ። አባሕኩ ፡ አባግዐ ። አባሕኰ ፡ ዘአባግዐ ፡ ወዘአጣሊ ፡ (ምሳ፳፱ ፡ ፳፯ ። ሕዝ፴፱ ፡ ፲፰ ። ዳን ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፷፬ ። ዘፀ፴፩ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ። ፴ ፡ ፴፫) ።

**ብሔሞት** ፤—በቁሙ ፤—ብሂም ፡ ብ ህመ ።

**በሕቁ** ፤—በጆሮ ፤ በጥቂቱ ፤—ሐቂቅ ፡ ሐቀ ፤ ሐቀቀ ፤ ሕቅ ።

**ቢሕቀወ** ፤ አንበሕቀወ ፤—አፋሸገ ፤—በ ቀወ ።

**በሕቀቀ** ፤ ተበሕቀቀ ፤—አወከ ፡ ታ ወከ ፤—ሐብቀቀ ።

**ብሒር** ፤ ሮት ፤ (ብሕረ ፡ ይብሕር ፡ ይብ ሐር ። ፀረ ፡ በሐረ ። ዕብ ፡ ባሐር ፤ መረጠ) ፤ መበፋት ፡ መንጣለል ፤ መዘርጋት ፤ ሰፊ ፡ ዝርግ ፡ ወርዳም ፡ ረዥም ፡ መኾን ፤ የቦታ ፡ የመሬት ፡ የርስት ፡ የማዛት ።

**ብሔር** ፤ (ራት ፤ በሓይርት ፤ በሓው ርት ። ፀረ ፡ ቢሓር ፤ ብ ፡ በሕረት) ፤ ቦታ ፡ ሰፈር ፡ በፍራ ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ታናናሽ ፡ ክፍል ። ይጸብ በነ ፡ ብሔር ፤ ግበሪ ፡ ሰነ ፡ ብሔረ ፡ ኀበ ፡ ንነብር ። ቦ ፡ ብሔር ፡ እምኀበ ፡ ይወፅእ ፡ ብሩር ። አይቴ ፡ ብ ሔሩ ፡ ለጥበብ ። ገዳም ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ። ወበጺ ሖሙ ፡ ብሔረ ፡ ዘስሙ ፡ ጎልጎታ ። ወወፅአ ፡ ስሙ ዓቱ ፡ በኵሉ ፡ በሓውርተ ፡ አይሁድ ፡ (ኢሳ፺፱ ፡ ፳ ። ኢዮ፳፰ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ። ማቴ፲፱ ፡ ፲፭ ። ፳፯ ፡ ፴፫ ። ሉቃ፬ ፡ ፴፯) ። ብሔር ፡ ጥሉል ፤ ወፍራም ፡ ሥቡ ፡ ውሃማ ፡ መ ሬት ፡ ለተክል ፡ የተመቸ ። ብሔር ፡ ሥውር ፤ ሣራም ፤ የ ማር ፡ ቦታ ፡ መስክ ፡ ጨፌ ፡ ክልክል ፡ (ኢሳ፳፰ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፳፱) ።

—፤ ምድር ፡ ሀገር ፡ ከተማ ፤ ገጠር ፤ አውራጃ ፡ ግዛት ፤ ታላላቅ ፡ ክፍል ፡ በስምና ፡ በሹም ፡ በወሰን ፡ በደንበር ፡ የተለየ ። መላይቱ ፡ ምድር ፤ የብስ ፡ ዓለመ ፡ ሰብእ ። አ ይቴ ፡ ብሔርከ ። ብሔረ ፡ ሕያዋን ። ብሔረ ፡ ብን ያም ። ኢመሀከሙ ፡ ለበሓውርት ፡ ኀበ ፡ ነበረ ፡ሎጥ ። በሓውርተ ፡ አሕዛብ ። ውእቱ ፡ ተርፈ ፡ ለብሔር ። ነሥእዎ ፡ እምነ ፡ ብሔር ፡ (ዮናስ ፡ ፰ ። መዝ ፡ ፶፭ ። ኤ ርሽ ፡ ፩ ። ሚራ፲፯ ፡ ፰ ። ኢሳ፲ ፡ ፲፫ ። ሚራ፺፱ ፡ ፲፯ ። ፺፱ ፡ ፲፱) ።

—፤ ሰው ፡ ወገን ፡ ነገድ ፤ ሕዝብ ፡ አሕዛብ ፡ በቋንቋ ፡ በ መንግሥት ፡ በሕግ ፡ በሥርዐት ፡ የተለየ ። ኵሉ ፡ ብሔር ፡ ኢ.መሰሉ ። መፍቅደ ፡ ብሔር ። አንከሩከ ፡ በሓው ርት ። መጽኡ ፡ ኵሉ ፡ በሓውርት ፡ ውስተ ፡ ግብጽ ። ኵሉ ፡ በሓውርት ፡ ዘቤተ ፡ እስራኤል ። በበ ፡ በሓው ርቲከሙ ፡ ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ (ሺነገ ፡ ፲፱ ፡ ፳፱ ። ሚራ፴፰ ፡ ፴፱ ። ፺፯ ፡ ፲፯ ። ዘፍ፵፩ ፡ ፶፯ ። ኤር፪ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፺፰) ።

—፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ሰማይ ፡ ከነግሡ ፡ ምድር ፡ ከነል ብሱ ፡ መላው ፡ ዓለም ። ላዩም ፡ ታቹም ፡ ያንድ ፡ አም ላክ ፡ ግዛት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በምሳሌ ፡ ብሔር ፡ ተብሏል ። ከመ ፡ ዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚእ ፡ ብሔር ፡ (እግዚአብሔር) ፡ ሰማይኒ ፡ መንበርየ ፤ ወምድርኒ ፡ መከየደ ፡ እገርየ ። እስመ ፡ ዚአየ ፡ ውእቱ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ በምልኡ ፡ (ኢ ሳ፷፮ ፡ ፩ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፵፱) ።

—፤ ጊዜ ፤ ሰዓት ፡ ወራት ፡ ባመትና ፡ በወር ፡ በዕለት ፡ ያለ ፡ ክፍል ። ክረምት ፡ ብሔር ። እስመ ፡ ነግህ ፡ ብሔሩ ። ወጸቢሖ ፡ ብሔር ። እስከ ፡ ጸብሐ ፡ ብሔር ። ጽልመት ፡ ብሔር ። መስየ ፡ ብሔር ፡ (፩ዕዝ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ግብ፲ ፡ ፲፩ ። ፳፯ ፡ ፴፫ ። ፩ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፴፯ ። ሚራ፳፫ ፡ ፲፰ ። ገድ ፡ ተክ) ።

—፤ የመጽሐፍ ፡ ክፍል ፤ ታላቅ ፡ ዐቢይ ፡ አንቀጽ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ መጽሐፍ ፤ ሰብቻው ፡ አንድ ፡ ተብሎ ፡ የሚቈጠር ፤ በውስጡ ፡ ብዙ ፡ ምዕራፍ ፡ ያለበት ፤ እንደ ፡ ኦሪትና ፡ እንደ ፡ ነገሥት ፡ እንደ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ሐዲሳት ፡ ያለ ። ይቤ ፡ በኦሪት ፡ ውስተ ፡ ሣልስ ፡ ብሔር ፡ ዘሌዋ ውያን ። በውስተ ፡ ዳግም ፡ ብሔረ ፡ ኦሪት ። ስኦሪት ፡ ባቲ ፡ ኀምስቱ ፡ ብሔር ። አርባዕቱ ፡ ብሔረ ፡ ነገ ሥት ። ክፍል ፡ ኃምስ ፡ እምዳግም ፡ ብሔር ፡ ዘመጽ ሐፈ ፡ ነገሥት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፪ ፡ ፯ ። ፱ ፡ ፩ ። አብጥ ፡ ፵፩ ። አቡሻ ፡ ፲፱) ።

**ባሕር** ፤ (ብ ፡ አብሕርት ። ፀረ ፡ በሕር ። ሱር ፡ ባሕራ) ፤ በቁሙ ፤ መከነ ፡ ማይ ፡ ምቋመ ፡ ማይ ፤ ዓለመ ፡ ማይ ፤ ምእላደ ፡ ማይ ፤ ሰፊ ፡ ጥልቅ ፡ ዕሙቅ ፤ ውሃው ፡ የማያልቅ ፡ የማይደርቅ ፤ ስፋቱ ፡ ከየብስ ፡ የሚ በልጥ ፡ ፫ ፡ እጅ ፡ የሚልቅ ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፱ ፡ ፲) ። ባሕር ፡ ዐቢይ ። ባሕረ ፡ ኤርትራ ። አብሕርት ፡ ወቀላያት ፡ (ዳን ፡ ፯ ፡ ፪ ። ዘፀ፲ ፡ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፪) ። ስፋት ፡ ለሌለው ም ፡ ለታናናሹ ፡ ሐይቅ ፤ ለኵሬ ፡ ሳይቀር ፡ ለወንዝ ፡ ለፈሳሽ ፡ ይነገራል ። ባሕረ ፡ ጺው ፤ ባሕረ ፡ ገሊላ ፤ ባሕረ ፡ ዚይ ፤ ባሕረ ፡ ጣና ፡ እንዲሉ ። ባሕረ ፡ ኒል ። ተከዜ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ባሕር ፡ (አቡሻ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ ሠኔ፱ ። መስ፬) ።

**ባሕረ ፡ እሳት** ፤ በቁሙ ፤ ረቂቅ ፡ ሰማያዊ ፡ እሳት ፤ ወይም ፡ ፍል ፡ ውሃ ፡ (መቃ ፡ ፲፱) ።

**ባሕረ ፡ ብርት** ፤ የብርት ፡ ውሃ ፡ በብርት ፡ ም ዕቃል ፡ የተመላ ፡ መታጠቢያ ፡ ኵሬ ፡ ሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አስፍቶ ፡ የሠራው ፡ (ኤር፶፪ ፡ ፲፯ ። ፱ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯) ።

**ባሕረ ፡ ሐሳብ** ፤ ቍጥር ፡ ያለው ፡ ዘመን ፤ ዓመተ ፡ ዓለም ። ሐሳበ ፡ ባሕር ፤ የዘመን ፡ ቍጥር ። ወበ መስፈርተ ፡ በፈሮ ፡ ለባሕር ፡ (ሱቱ ፡ ዕዝ፪ ፡ ፵፯) ።

**ባሕረ ፡ ጥበባት** ፤ ስሙ ፡ ስርጋዊ ፡ የሉቃስ ፡ ወንጌላዊ ፡ (ድጓ) ።

**ባሕር** ፤ ምዕራብ ፡ ግራ ፡ (ዘፍ፲፪ ፡ ፰ ። ፲፫ ፡ ፲፬ ። ፳፰ ፡ ፲፬ ። ዳን፰ ፡ ፬) ። እመንገለ ፡ ባሕር ፡ ባ ሕረ ፡ ወእመንገለ ፡ ጽባሕ ፡ ጽባሑ ፡ (ሕዝ፵፰ ፡ ፯) ።

—፤ ንኡስ ፡ ማእዝን ፡ በሰሜንና ፡ በምዕራብ ፡ ማኸል ፡ ያለ ፤ የሰሜን ፡ ምዕራብ ፡ የሊባ ፡ አፋዛዥ ፡ ትይዩና ፡ አን ጻር ። ባሕረ ፡ ወሊባ ፡ (ቅዳ) ።

**ባሕራዊ** ፤ የባሕር ፡ የምዕራብ ፤ ምዕራባዊ ።

**ባሕርይ** ፤ (ያት ። ፀረ ፡ በሕሪይ) ፤ ባሕ ራይ ፡ ባሕራዊ ፡ የባሕር ፡ ዕንቍ ፡ ሉል ፡ ከሰደፍ ፡ የሚ ገኝ ፤ ደረቅ ፡ ከሬሬ ፡ ጠንካራ ፡ እብናዊ ፡ የወፍ ፡ ዕንቍ

ባል ፡ የሚመስል ፤ ታናሽ ፡ ክብ ፡ እንክብል ፡ ድብልብል ፡ የሚበርቅ ፡ የሚያንጸበርቅ ። ዕንቍባል ፡ ቅሉ ፡ ዕንቈ ፡ ሉል ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ስሙን ፡ ከሉል ፡ ወስዷል ፤ መመሳሰል ፡ የጋራ ፡ ነውና ፡ (ማቴ፲፫ ፡ ፵ ። ፲፫ ፡ ፴፰ ፡ ፴፮ ። ራእ፳፩ ፡ ፳፩) ። **እስመ ፡ በደፍ ፡ ይወልዶ ፡ ለዕንቍ ። ተናገር ፡ ዕንቈ ፡ ባሕርይ ፡ ወክሥተ ፡ እፎ ፡ ህላዌከ ። ባሕርይ ፡ ዘያንጸበርቅ ። እማንቱ ፡ ዕንቈ ፡ ባሕርያት ፡ ክቡራት ። መጽሐፈ ፡ ባሕርይ ፡** (ማር ፡ ይሖሸዳ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ኢፋ ። እርጋ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ማይ፰ ። ቁድር) ።

—፤ ክቡር ፡ ደንጊያ ፡ የየብስ ፡ ዕንቍ ፡ ሉል ፡ የሚመስል ፡ ባሕርያዊ ። **እብነ ፡ ባሕርይ ፡** (ሔኖ፲፰ ፡ ፯ ። ጥበ፯ ፡ ፱ ። ፲፰ ፡ ፳፱ ። ዮሴፍ) ።

**ባሕርይ ፤ (ዐረ ፡ ጀውሀር ። ዕብ ፡ ዔጹም) ፤** በቁሙ ፡ የነገር ፡ ኹሉ ፡ ሥር ፡ መሠረት ፡ ምንጭ ፡ መውጫ ፡ መፍለቂያ ፡ መገኛ ፡ ጠባይዕ ፡ ህላዌ ፡ ክዋኔ ። ጀውሀር ፡ በዐረብ ፡ ዔጹም ፡ በዕብራይስጥ ፡ ባሕርይም ፡ አካልም ፡ ይኾናል ፡ እንደ ፡ ህላዌና ፡ እንደ ፡ ጠባይዕ ፡ ነው ፡ ባሕርይ ፡ ግን ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ አካላዊ ፡ ፍጹም ፡ አካል ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ አይባልም ፡ አካልም ፡ ባሕርያዊ ፡ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ አይባልም ። በምድር ፡ ያሉ ፡ የፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ሥር ፡ ማይ ፡ መሬት ፡ ነፋስ ፡ እሳት ፡ ናቸው ፡ እሊህ ፡ አራቱ ፡ ባሕርያትም ፡ ጠባይዓትም ፡ ይባላሉ ፡ ባሕርይ ፡ ከብሒረ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ጠባይዕም ፡ ከጠብዐ ፡ ይወጣል ። ባሕር ፡ ስታውዕን ፡ ተብላ ፡ ብዙ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ እንዳስገኘች ፡ ባሕርይም ፡ መገኛ ፡ ማስገኛ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የአካል ፡ የስም ፡ የህላዌ ፡ ጥንት ፡ የሥራ ፡ ምንጭ ፡ የግብር ፡ መሠረት ፡ ይባላል ፡ ይኸውም ፡ አንቀጽና ፡ ቅጽል ፡ ብትን ፡ ጥሬ ፡ ኹሉ ፡ ከዘር ፡ እንዲገኝ ፡ እንደዚሁ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከባሕርይ ፡ ለሚገኝ ፡ ባሕርያዊ ፡ ሥራ ፡ ሠሪው ፡ አካል ፡ መማሪያው ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ አካል ፡ ሠሪ ፡ እንዲባል ፡ ባሕርይ ፡ ደግሞ ፡ ሠሪ ፡ አይባልም ፡ ማዕድ ፡ ማጠንጃ ፡ እንጂ ፡ ዐጣጅ ፡ እንዳይባል ፡ አሠሪም ፡ ቢሉት ፡ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ከመማሪያነት ፡ ይገባል ፡ የሥራ ፡ ባለቤት ፡ ወትሮ ፡ አካል ፡ ነው ። **ወአካላኒ ፡** (ሠሪዋ ፡ ፈጻሚዋ) ፡ **እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡** (አረጋ ፡ ድ፲፰) ። አካልን ፡ ከባሕርይ ፡ ገባሪን ፡ ከግብር ፡ በየስሙና ፡ በየስልቱ ፡ ለይቶ ፡ የማያውቅ ፡ መምህር ፡ ግን ፡ አካል ፡ ሲሉት ፡ ባሕርይ ፡ ባሕርይ ፡ ሲሉት ፡ አካል ፡ ኢያስ ፡ የግእዝን ፡ ቋንቋ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ቃል ፡ የሊቃውንትን ፡ ባህል ፡ ትርጓሜና ፡ ምስጢር ፡ ያበላሻል ። **እስመ ፡ ብሂሎቱ ፡ ኀየሰ ፡ እመላእክት ፡ እኮ ፡ ዘይሔምር ፡ ኀበ ፡ ባሕርዩ ፡ ዘእም ፡ አብ ፡ እስመ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ እኮ ፡ ዘክነ ፡ ሥጋ ፡ አላ ፡ ተወልደ ፡ ወባሕቱ ፡ ይሔምር ፡ ኀበ ፡ ባሕርየ ፡ ሥጋዌሁ ፡** (ኤፌ ፡ ድ፳ ። ዕብ ፡ ፭ ፡ ፱) ። የፈጣሪ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ፍጡር ፡ ባሕርይ ፡ ክባት ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ የማይወርድ ፡ ሊቀዳ ፡ ሊከፈል ፡ ወይም ፡ ሊበረዝ ፡ የማይቻል ፡ አንድ ፡ ሥር ፡ አንድ ፡ ነቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ የኛን ፡ ባሕርይ ፡ ነሥቶ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ የኾነው ፡ አካሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባሕርዩ ፡ ሰው ፡ አልኾነምና ፡ **እኮ ፡ ዘክነ ፡ ሥጋ ፡** አለው ። በተዋሕዶ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ብሎ ፡ በተፀቅቦ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ፫ ፡ መለኮት ፡ የሚሉ ፡ ግን ፡ ጥንቱን ፡ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ተለውጦ ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ባህላቸው ፡ ይፈቱታል ፤ ባህላቸውም ፡ ባሕርዩ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኹኗል ፡ ማለት ፡ ነው ። ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ሊቃውንት ፡ አሐዱ ፡ ያሉትን ፡ የሥላሴን ፡ ባሕርይ ፡ ከፋፍለው ፡ ሠለስቱ ፡ ማለት ፤ በተፀቅቦ ፡ ክልኤቱ ፡ ያሉትን ፡ የወልድን ፡ ባሕርያት ፡ ቀላቅለው ፡ አሐዱ ፡ ማለት ፡ ያሉትና ፡ የሸፍጥ ፡ የምፀት ፡ ቃል ፡ ነው ፤ እውነተኛ ፡ ትርጓሜና ፡ አፈታት ፡ አይደለም ፡ ምንም ፡ ለተርጓሚው ፡ ቀኝ ፡ ቢኾን ፡ ለሰሚው ፡ ግራ ፡ ነው ። ይወልደዋል ፡ ብሎ ፡ አይቀድመውም ፡ አይበልጠውም ፡ ማለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይከፈል ፡ ነውና ፡ ባሕርዩ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ አባቱ ፡ መንፈሱ ፡ ሳይቀሩ ፡ በግድ ፡ ሥላሴ ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ ያሰኛል ፡ እንደ ፡ አካላትም ፡ ሠለስቱ ፡ ቢሉት ፡ በግድ ፡ ሦስት ፡ አማልክት ፡ ያሰኛል ፡ ኹሉም ፡ የተንቀለፈና ፡ የተወገዘ ፡ ነው ። ሰው ፡ መኾንና ፡ ሥጋ ፡ መልበስ ፡ አካቶ ፡ ፈጽሞ ፡ ለአካል ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ለባሕርይ ፡ ሊነገር ፡ አይቻልም ። **ናወግዝ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ አው ፡ ይኄልዩ ፡ ከመ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ሠለስቱ ፡ አካላት ፡ ተሠገዉ ፤ በብሂሎቶሙ ፡ ከመ ፡ መለኮት ፡ ሥለሴንታሁ ፡ ዘንሬኢ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ በአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተሠገወ ። ወናወግዝ ፡ ዓዲ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ሠለስተ ፡ መለኮተ ፡ እንተ ፡ ዘአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወለእመ ፡ ትቤ ፡ መለኮት ፡ ምት ፡ እንተ ፡ ትከውን ፡ ቀታሊሆሙ ፡ ለሥሉስ ፡ ቅዱስ ፤ እስመ ፡ ባሕርየ ፡ ሥላሴ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፤ ዘውእቱ ፡ መለኮት ፡** (ሃይ ፡ አ ፡ ዮሐ ፡ ዘእስ ፡ ወዘአን ። አግና) ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ የባሕርይን ፡ ምስጢርና ፡ አፈታት ፡ በህላዌና ፡ በጠባይዕ ፡ በመለኮት ፡ ተራ ፡ ተመልከት ።

**ባሕርያዊ ፤** የባሕርይ ። ስምን ፡ ግብርን ፡ አካልን ፡ ያሳያል ።

**ባሕረረ ፤ (ዐረ ፡ በሒረ) ፤** ተቀጥላ ፡ ማስ ፡ ባነነ ፡ በረገገ ፡ ደነገጠ ፡ ደነበረ ፡ ከባሕር ፡ ልማ ፡ አለ ።

**አባሕረረ ፤** አባነነ ፡ አስደነበረ ፡ ከባሕር ፡ አገባ ፡ አስጠመ ። **እንበለ ፡ ያደንግፆ ፡ ሞት ፡ ወኢያባሕርሮ ፡** (ስንክ ፡ ኅዳ፪ ። ጥር፳፩ ። ማቴ፰ ፡ ፴፪) ።

**ባሕሩስ ፤** ቀለም ፡ የጉሽ ፡ መቃ ፡ የሸንበቆ ፡ የስንበሌጥ ፡ ዐይነት ፡ ቀጫጭን ፡ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ ዐረቦች ፡ ብርዕ ፡ አድርገው ፡ የሚጥፉበት ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ የሚበቅል ። ቅልጥሙ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ የተከከለ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሳንገትና ፡ ለጣት ፡ ምሳሌ ፡ ኹኖ ፡ ይነገራል ፡ ጣት ፡ መቃ ፡ ዐንገት ፡ መቃ ፡ እንዲሉ ። (መቃ ፡ ጣት ፡ መልክም ፡ እቱ ፡ ስለ ፡ ሞተች ፡ ወንድም) ፡ ትመታኛን ፡

ብዬ ፡ ሴቴቱ ፡ ወንዱን ፤ በመቃጣቷ ፡ ነው ፡ እኳስ ፡ የማዝን ። **ብርዐ ፡ ባሕሩስ ። ብትረ ፡ ባሕሩስ ፤** (ኢሳ፳ ፡ ፱፭ ። ፱ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፭) ። ጽሕድ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ብሮሽ ፡ እንደማለት ፡ ባሕሩስ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። **ለየዐይ ፡ ባሕሩስ ። ኀጺን ፡ ኮነ ፡ ብዙኀ ፡ ከመ ፡ ዕፀ ፡ ባሕሩስ ፡ ወከመ ፡ ብርዐ ፡ ገዳም ፤** (ዘካ፲፭ ፡ ፱ ። ክብ ፡ ነገ) ።

**ብሒት ፤ ቶት ፤ (ብሕተ ፡ ይብሕት ፡ ይብሐት ፤ ብሐ) ፤** መሠልጠን ፡ መሾም ፡ መብት ፡ ችሎት ፡ ምቾት ፡ ማግኘት ። **እንዘ ፡ ትብሕት ፡ አንተ ፡ በዝሰሂ ። ወሶበ ፡ ብሕትኩ ፡ እልእክ ፡ ዘይጼውዐከ ፤** (አርጋ ፡ ፪ ። ማብ፳፱ ፡ ፳፭) ።

**አብሐተ ፤** አባተ ፡ ሾመ ፡ አሠለጠነ ። አሸነፈ ፡ በላይ ፡ ኾነ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ተባሕተ ፤** ተባባተ ፡ ተሳሰፈ ፡ ተዋጋ ፤ ታገለ ፡ ተጋደለ ። **ይትባሐቱ ፡ አጋንንት ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ ወይወድዩ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ፡ ኅሊና ፡ እኩየ ። ዕቀበነ ፡ እግዚኦ ፡ በዛቲ ፡ ሰዓት ፡ እምእለ ፡ ይትባሐቱ ፡ አጋንንት ፤** (ቁስጠ ፡ ፳ ። ደራሲ) ።

**ብሑት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ሕት) ፤** ብዉሕ ፤ የሠለጠነ ፡ የተሾመ ፡ መብት ፡ ያለው ። **ወደቂቀ ፡ አሮንስ ፡ ብሑታን ፡ በቤ ፡ አብሬቶሙ ። ሳቁኤል ፡ ብሑት ፡ ዲበ ፡ መናፍስት ። ኦ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ ብሕት ፡ ከመ ፡ አብ ፡ ህሉት ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ ስፍንት ፡ ከመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤** (፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፭ ። ሄኖክ ፡ ሐም፳ ። ቅዳ ፡ አት) ።

**መባሕት ፤—መብት ፤—ብዊሕ ፤ ቡሐ ፡ ተበውሐ ።**

**በሐተ ፤ (ዋሐደ ። ዐረ ፡ በሑተ ፤ ጥሩ ፡ ኾነ) ፤** ባተ ፡ ገባ ፡ ተሾመ ፤ ተዠመረ ፡ ተቈጠረ ፡ የወር ፡ ያመት ። ብቸኛ ፡ ኾነ ፡ ከሰው ፡ ተለየ ፡ ተንጠለ ፡ እንደ ፡ መባቻ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ተባለ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በበሐተ ፡ ፈንታ ፡ ባሕተወ ፡ ይላል ።

**ብሑት ፤** የባተ ፡ ብቸኛ ፡ የኾነ ፡ ብቸኛ ። **ብሑት ፡ ልደት ። ብሑት ፡ ዘእንበለ ፡ አዝማድ ። መነኮስ ፡ ብሑት ። ገዳማዊ ፡ ብሑት ፤** (ኪዳ ። ቅዳ ፡ ኢጲ ። ፊልክ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ የካ፺) ።

**ባሕቱ ፤ (ባሕት) ፤** ብቻ ፡ እንጂ ፡ ግን ፡ ግና ፡ ነገር ፡ ግን ። እንጂ ፡ ሲኾን ፡ ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ አኮኑ ፡ እንደ ፡ ዳእሙ ፡ በረቂቅም ፡ በጐላኅም ፡ ይገባል ። **በዝንቱ ፡ ባሕቱ ፤** ብቻ ። **ባሕቱ ፡ ዝንቱ ፡ ረከብኩ ። መብለተ ፡ ባሕቱ ፡ ኢታውስብ ፤** ግን ፤ (ዘሌ፳፱ ፡ ፲፭ ። መክ፯ ፡ ፱ ። ዘሌ፳፭ ፡ ፲፱) ። ብቻ ፡ የሚኾን ፡ አገባብ ፡ ባሕቱ ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፡ በመጽሐፍ ፡ ግን ፡ ዳእሙ ፡ አብዝቶት ፡ እጅግ ፡ አይገኝም ። ያባተ ፡ በትም ፡ ምክንያት ፡ መላሽና ፡ ጣፊ ፡ በባሕቱ ፡ ስፍራ ፡ **ኢትፍራህ ፡ ተአመን ፡ ዳእሙ ። ወለዘሂ ፡ ቈሳፍ ፡ በአሚን ፡ ዳእሙ ፡ ያጸድቆ ። እሉኒ ፡ ዳእሙ ፡ ይቀቅክ ፤** እያሉ ፡ በሳንቡት ፡ ነው ። የዳእሙን ፡ ፍቾ ፡ ተመልከት ፤ (ዕር፲፱ ፡ ቀኍ፺፭) ።

**ባሕቲት ፤ (ዕብ ፡ ልበድ) ፤** ብቻ ፡ ብቸታ ፡ ብቻነት ፤ ጥሬት ፡ ጥሩነት ። ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፡ ይኾናል ፤ ባሕቲቱ ፡ ታ ፡ ቶሙ ፡ ቶን ፤ ባሕቲትየ ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ ምር ፡ ይረባል ፤ ሳይዘረዘር ፡ ግን ፡ በሳድስነት ፡ አይገኝም ፤ እንደ ፡ ሰሌና ፡ እንደ ፡ ባሕቱ ፡ ነው ። **ሞተ ፡ ባሕቲቱ ። ኀጢአት ፡ ባሕቲታ ። ለከ ፡ ለባሕቲትከ ። እሉ ፡ ባሕቲቶሙ ። አነ ፡ ባሕቲትየ ። ኪያሁ ፡ ባሕቲቶ ። ባሕቲቶ ፡ ዘበልዐ ፡ እስመ ፡ ይመውት ፡ ባሕቲቶ ።** (ኩፋ ፡ ፳ ። ሙዳ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፶ ። ዮሐ፲፯ ፡ ፳ ። ኢዮ፰ ፡ ፲፰ ። ማቴ፬ ፡ ፲ ። ቅኔ) ። **በፈቃደ ፡ ባሕቲቱ ፤** በራሱ ፡ በብቻው ፡ ፈቃድ ። **በባሕቲቶሙ ፡ ተስእልዎ ፤** ብቻቸውን ፡ በኾኑ ፡ ጊዜ ፡ ኾነው ። **ሠሐቀት ፡ በባሕቲታ ፤** በራሷ ፡ በሰውነቷ ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ብቂርባ ፡ ይላል ። በሆዷ ፡ በልቧ ፡ በሐሳቧ ፡ ብቻ ፡ ጥርስ ፡ ሳይገጥ ፡ ከንፈር ፡ ሳይገለጥ ፡ ማለት ፡ ነው ። **አቀሞን ፡ እንተ ፡ ባሕቲቶን ፤** ለብቻቸው ፤ እየብቻቸው ፡ ብቻቸውን ፤ ለ ፡ እየ ፡ ን ፡ የእንት ፡ ፍቾ ፡ ነው ፤ (ፍ ፡ ን ፡ ፯ ። ማር፬ ፡ ፲ ። ዘፍ፲፰ ፡ ፲፪ ። ፳፭ ፡ ፳፰) ።

**መብሕት ፤** ፍጹም ፡ ጥሩ ፡ አይሮፍ ፡ ጉድፍ ፡ እንከን ፡ የሌለበት ፤ ያልተነካ ፡ ድፍን ። **ምሥዋዐ ፡ ዘእብን ፡ መብሕት ፡ ዘኢተወቅረ ፤** (ኢያ፰ ፡ ፴፫) ።

**ባሕተወ ፤ (በሐተ) ፤** ብቸኛ ፡ ኾነ ፤ ተለየ ፤ ተንጠለ ። **ኢባሕተወ ፡ መለኮቱ ፡ እምትስብእቱ ፡ ወኢትስብእቱ ፡ እመለኮቱ ፤** (መጽ ፡ ምስ) ። ዐዘኑ ፡ አለቀስ ፡ ፈራ ፡ ተጨነቀ ፡ ብቻ ፡ ከመኾን ፡ የተነሣ ። **ምናቤ ፡ ኅሠሠ ፡ ገጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወባሕተወ ፡ በሕቁ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለአምላክ ፡ አበዊሁ ፡ ወጸለየ ፤** (ዲድ ፡ ፯ ። ፪ዜና ፡ ፴፫ ፡ ፲፪) ። በባሕተወ ፡ ፈንታ ፡ ተባሕተወ ፡ ይላል ፤ በዐገለ ፡ ፈንታ ፡ ተዐገለ ፡ እንዲል ። ፍቸው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ አይለወጥም ። **ወእመ ፡ ወሊዶ ፡ ኢተባሕተወ ፡ አቡሁ ፡ ሎቱ ። አመ ፡ ይትባሐቶ ፡ ወይትባአስ ፡ ምስለ ፡ ጎልያድ ። እለ ፡ ይትባሐተዉ ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ወየዐይሉ ፡ ውስተ ፡ ገዳማት ፤** (ቅዳ ፡ ግሩ ። መዝ ፡ ፻፵፩ ። እሌ ፡ ቀ ፡ ፲) ።

**ባሕትዎ ፤ ተባሕትዎ ፤** ብቻ ፡ ብቸኛ ፡ መኾን ፡ ብቸኝነት ። **ወዊአ ፡ እማኅበር ፡ ወተባሕትዎ ፡ ውስተ ፡ በአት ፤** (ፊልክ ፡ ፵፱) ።

**ባሕታዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** ብቻውን ፡ የሚኖር ፡ ባታይ ፡ ባተሌ ፡ ብቸኛ ፡ ለይቶኛ ፡ የበመይ ፡ ድኻ ። **እስመ ፡ ባሕታዊ ፡ ወነዳይ ፡ አነ ። ከመ ፡ ዖፍ ፡ ባሕታዊ ። ርሮአኒ ፡ ሊተ ፡ ለባሕታዊት ። ተማህልኩሙ ፡ ለክልኤ ፡ ባሕታውያን ፤** (መዝ ፡ ፳፬ ። ፻፩ ። አስቴ፬ ፡ ፲፯ ። ጦቢ፫ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፷፯) ።

—፤ በቁሙ ፡ መናኝ ፡ መነኰሴ ፡ ዝጉሕ ፡ ከዓለም ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ከአራዊት ፡ ጋራ ፡ በዱር ፡ በጫካ ፡ በገደል ፡ በጥግ ፡ የሚኖር ፡ ከቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ኤልያስ ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ ከኋላ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ጳውሊና ፡ እንደ ፡

እንጦንስ ፡ ያስ ፡፡ ጳውሊ ፡ ግን ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ሳያይ ፡ በበረሓ ፡ ኑሯል ፤ ስለዚህ ፡ ሊቀ ፡ ባሕታውያን ፡ ይባላል ፡ (ስንክ ፡ የካ፱) ፡፡ ባሕታዊ ፤ ዘምቅሐ ፤ ርእሶ ፡ በጸማ ፅቁ ፡፡ መነኮስ ፡ ባሕታዊ ፡፡ ወነበረ ፡ ሐቅለ ፡ ምስለ ፡ አራዊት ፤ (ፊ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፯ ፡፡ ስንክ ፡ ታኅሣ፳፫ ፡፡ ማርያ ፡ ፲፫) ፡፡

ብሕትው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ቱት) ፤ ብቻ ውን ፡ የኾነ ፡ ብቻውን ፡ የሚኖር ፤ ብቸኛ ፡ ለብቻው ፡ የቆመ ፡ የተለየ ፤ ገላ ፡ አካል ፡ ሰውነት ፡፡ ትኩን ፤ ብሕ ቱተ ፡ በእንተ ፡ ጸሎት ፡፡ ብሕቱትየ ፤ (ኪዳ ፡፡ መካ ፡ ፳፫ ፡፡ ፴፱) ፡፡

ብሕታዌ ፤ ብቻ ፡ መኾን ፤ ብቻ ፡ ብቸታ ፤ ብ ቻነት ፡፡ ትምህርት ፤ መዜንው ፡ በውስተ ፡ ሐዊር ፡ ወ በብሕታዌ ፡፡ ሰላም ፡ ለብሕታዌሁ ፡፡ ብሕታዌ ፡ ንብ ረት ፤ (ፈላስ ፡፡ ስንክ ፡ ጥር፳፱ ፡፡ ግንቦ፳) ፡፡

ብሕትውና ፤ ባሕታዊነት ፤ ብቸኝነት ፤ ፍጹም ፡ ምናኔ ፡፡ በእንተ ፡ ዘከመ ፤ ይኄይስ ፡ ሥርዐተ ፡ ብሕት ውና ፡ እምሥርዐተ ፡ ማኅበር ፡፡ ለመደ ፡ ብሕትውና ፡፡ በኣተ ፡ ብሕትውና ፤ (ፊልክ ፡ ፳ ፡፡ ስንክ ፡ ሐምሌ ፡፡ ፊ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፯) ፡፡

ብሕትውናዊ ፤ የብሕትውና ፤ የባሕታዊነት ፡ ግብር ፡ አኗኗር ፡ ሕግ ፡ ሥርዐት ፡፡ ምንዝስና ፡ ብሕትው ናዊት ፤ (ገድ ፡ ተክ) ፡፡

ተብሕተወ ፤ (ተደራራጊ) ፤ ተለያየ ፤ ተነጣ ጠለ ፤ እየብቻው ፡ ኾነ ፡፡

በኍበኍ ፤ (ብሕአ) ፤ በኸበኸ ፤ በነቸ ፤ በስ በሰ ፡ ተበላሸ ፤ ነቀዘ ፡ ጠነጠነ ፡ ተላ ፤ ገማ ፡ ከረፋ ፡ በሽቀጠ ፤ ምነፍጽት ፡ የማነድ ፡ የገላ ፡ የቍስል ፡፡ በኍበኍ ፡ ሥጋየ ፡ በዕፄያት ፡፡ በቍስለ ፡ ኀጢአት ፡ ሥጋየ ፡ በኍበኍ ፡ ወጼአ ፤ (ኢዮ ፡ ፯ ፡፡ ስንክ ፡ ነሐሴ፳) ፡፡ ይበልዕ ፤ ይት ከዐው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይበኍበኍ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ኢዮ፲፰ ፡ ፲፫ ፡፡ ሕዝ፯ ፡ ፲፯ ፡፡ ኛሐ ፡ ፯) ፡፡

ብኍብኍ ፤ ብኅቡኅ ፤ የበኸበኸ ፤ የበነቸ ፡፡ ከመ ፡ ዕፀ ፡ ብኅቡኅ ፤ (ኢዮ፳፱ ፡ ፳ ፡፡ ሳሳ ፡ ፲፰) ፡፡

ብኍብኌ ፤ ብኅብኄ ፤ ግማት ፡ ክርፋት ፤ ሽ ታው ፡ የማያስቅቅ ፡ የሚጕፈንን ፡፡ እሬኢ ፡ ንስኀተ ፡ ሥጋየ ፡ ከመ ፡ ብኅባኄ ፡ አንበሳ ፤ (ኢዮ ፡ ፯) ፡፡ ባለብ ሉዮች ፡ ግን ፡ ኀይል ፡ ብርታት ፡ ይሉታል ፡፡

ብኅብኄ ፤—መፈጠር ፤—በሕብሐ ፡፡

ቤጣ— ፤ ስመ ፡ ፊደል ፤—በየጣ ፡፡

በጢሕ ፤ ሖት ፤ (በጥሐ ፡ ይበጥሕ ፡ ይብ ጣሕ ፡፡ ዕብ ፡ ባጻዕ ፡፡ ሱር ፡ ብዛዕ ፡፡ ዐረ ፡ በፀዐ) ፤ መብጣት ፡ መፍቃት ፤ መተፋተፍ ፤ መሠንበጥ ፤ ለፈውስ ፡ ወይም ፡ ለጌጥ ፡፡ (ተረት) ፤ ሲያጌጡ ፡ ይመላለጡ ፡፡ ጠቢ ባን ፡ ሶበ ፡ ይበጥሑ ፡ በጽኑዕ ፡ እስከ ፡ ይረክብዎ ፡ ለ ሕማም ፡ ይጠብቡ ፡ ለቤሃ ፤ በዘይዐርፍዎ ፤ ለሕ ሙም ፡ እምተሀውኮ ፡ ወእምድንጋፄ ፤ ነፍስ ፤ ወኢ ይበጥሑ ፡ ዳግመ ፤ አላ ፡ ይወድዩ ፡ ፈውሰ ፡፡ ሚ ፡ መጠኑ ፡ ይጼዕሉ ፡ እለ ፡ ይበጥሑ ፡ እምእለ ፡ ይበ ጥሕዎሙ ፡፡ ኢትብጥሑ ፡ ሥጋክሙ ፤ (አፈ ፡ ተፀ ፡፡ ዘሌዋ፲፱ ፡ ፳) ፡፡

በጥሐ ፤ (ዕብ ፡ ባጣሕ) ፤ አመነ ፤ ተወከለ ፡ ተስፋ ፡ አደረገ ፤ ዐረፈ ፡ ተዘለለ ፡ ገላውን ፡ ሰደደ ፤ ምን ፡ አለብኝ ፡ አለ ፤ የድውይ ፡ የባለጤና ፡፡

በጣሒ ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት) ፤ የሚበጣ ፤ በጭ ፤ በጪ ፡፡ በጣሕያን ፤ (አፈ ፡ ተፀ) ፡፡

ተበጥሐ ፤ ተበጣ ፡ ተፈቃ ፤ ተተፈተፈ ፤ እንደ ፡ ሱዳን ፡፡

ብጡሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ጥሕት) ፤ የተበጣ ፡ ብጥ ፡ ሥንብጥ ፤ ትፍትፍ ፡፡

ብጥሐት ፤ መብጣት ፡ መበጣት ፤ አበጣጥ ፡ ብ ጥነት ፤ ብጥታት ፡፡ ብጥሐተ ፡ ገጽ ፤ (መ ፡ ፈ—፲) ፡፡

(ጥ) በጢሕ ፤ (ሓት ፡፡ ዐረ ፡ በጢኻ) ፤ በቁሙ ፤ የዱባ ፡ ዐይነት ፡ ተክል ፤ ውስጠ ፡ ቀይ ፡ ክብ ፡ እንክብል ፤ ማር ፡ ማር ፡ የሚል ፡ በጥተው ፡ አይተው ፡ የሚገዙት ፡፡ በምጥዋ ፡ ብርቱኳን ፡ ይባላል ፡፡



በጢሕ ፡

በጢጥ ፤ ጦት ፤ (በጠ ፡ ይበጥጥ ፡ ይብ ጥጥ) ፤ መበጠጥ ፡ በጠጥ ፡ ፋንድያ ፡ መጣል ፤ ባጥ ፡ እ ንጣጥ ፡ ማለት ፡ ለመፈንጠጥ ፡ የእንስሳ ፡፡ መግዘል ፡ ፊጤ ፡ መምታት ፡ መፈንጠጥ ፡ የጕበዛዝት ፡፡ በጥ ፡ ለጥ ፡ ሰጥ ፡ ብሎ ፡ በልብ ፡ መተኛት ፡ ዠርባን ፡ ለገፈፋና ፡ ለረጋጭ ፡ አስመችቶ ፡ መስጠት ፡፡ ትማሬ ፡ በጥ ፡ በል ፤ ዐማሪ ፡ ው ደቅ ፡ ወይም ፡ ጣለው ፡ እንዲል ፡፡

በጣጣ ፤ በጣጥስ ፤ (ዐረብ) ፤ ድንች ፡ የድ ንች ፡ ወገን ፡፡

በጥበጠ ፤ በቁሙ ፡ በጠበጠ ፡ ጣለ ፤ የኮሶ ፡ የድ ፍድፍ ፡ የጠጅ ፡፡ ጥሕሉን ፡ ተመልከት ፡፡ ለቤት ፡ ክሲያ ንም ፡ ይኾናል ፡፡ ደብረ ፡ በጥብጥ ፡ እንዲሉ ፡፡

በጢል ፤ ሎት ፤ (በጠለ ፡ ይበጥል ፡ ይ ብጥል ፡፡ ዕብ ፡ ባጣል ፡፡ ሱር ፡ ቤጤል ፡፡ ዐረ ፡ በጠለ) ፤ መበዘን ፡ ማረፍ ፤ መስንፍ ፡ ሥራ ፡ መፍታት ፡፡ መጥፋት ፡ መፍረስ ፤ መሻር ፡ መቅረት ፡ ከንቱ ፡ ብላሽ ፡ መኾን ፡፡ ኢበጠለ ፡ ጸልዕ ፡ አላ ፡ ጸንዐ ፡፡ በጠለት ፡ ት ንቢት ፡ በስብከተ ፡ ሐዋርያት ፡፡ ትበጥል ፡ እንተ ፡ መ

ክርኩ ። በጠለ ፡ ዐቂበ ፡ ትእዛዝ ፡ እምኔየ ። በጠለ ፡ ተአምኖቱ ፡ ሶቱ ። ዘስሕተታት ፡ በጠላ ፡ በትእዛዝከ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ክብ ፡ ፶፫ ። አርጋ ፡ ፭ ። ፍ ፡ ን ፡ ፴፱ ፡ ፪ ። ኪዳ) ። በበጠለ ፡ ፈንታ ፡ ተበጥለ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። እመ ፡ ትትቤጠል ፡ ኦሪት ፡ በሃይማኖት ፡ (ቁር ። ገድ ፡ አዳ) ።

**በጣሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ በጠልት) ፤** የሚጠፋ ፡ ጠፊ ፡ ፈራሽ ፡ ቀሪ ፡ ኀላፊ ። መንግሥት ፡ ምድር ፡ በጣሊ ። መርዓ ፡ በጣሊ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ ። መስከረ) ።

**ብጡል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ጥልት) ፤** የበጠለ ፡ የጠፋ ፡ ጥፉ ፡ መጥፎ ፡ ብልሹ ፡ ከንቱ ። ስብሐት ፡ ብጡል ። ዝንቱ ፡ ብጡል ። ኦሪት ፡ አይሁድ ፡ ብጡል ። ዛቲ ፡ ተደምሮ ፡ ብጥልት ፡ እምሕገ ፡ ሰብሳብ ፡ ወእሰምየ ፡ ኀጢአተ ፡ (ፊልክ ፡ ፳፱ ። ገድ ፡ ተክ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፪ ፡ ፭ ። አቡሻ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፪) ። ድልድል ፡ ቅምጥል ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ አውታታ ፡ ወይም ፡ ዘመናይ ፡ ጌታ ። ብጡል ፡ ወሴ ፡ ብጡል ፡ እንዲል ፡ (የጿዬ) ።

**ብጥለት ፤** መጥፋት ፡ አጠፋፍ ፡ ጥፋት ፡ ከንቱነት ። እስመ ፡ አበው ፡ ዘዝንቱ ፡ ዘመን ፡ ረሰይዎ ፡ ብጥለተ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፫) ።

**አብጠለ ፤** አባጠለ ፡ አብጠለጠለ ፡ አበጠለለ ፡ አባፋለ ፡ ነቀፈ ፡ አጸየፈ ፡ (ዐማርኛ) ። አጠፋ ፡ አበላሸ ፡ ከንቱ ፡ አደረገ ፡ አስቀረ ፡ ከለከለ ፡ አስተጓጐለ ፡ ዐሎ ፡ አለ ። አብጠለ ፡ ተቃትሎቶሙ ። አብጠልከ ፡ ነገረከ ። አብጠለ ፡ ኖሚአ ፡ ሕልያን ፡ በእንተ ፡ ሚመት ፡ ክህነት ። ሶበ ፡ ኮኑ ፡ ሰይጣናት ፡ የሐውሩ ፡ ኀበ ፡ ብሔታን ፡ ከመ ፡ ያስሕትዎሙ ፡ ወያብጥልዎሙ ፡ እምትግባሮሙ ፡ መንፈሳዊ ። እለ ፡ ያበጥሉ ፡ ልደቶ ፡ እምአብ ፡ እምቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ (ዮሴፍ ። አቡሻ ፡ ፶ ። ፊልክ ፡ ፱ ። ዲድ ፡ ፴፪) ። በአብጠለ ፡ ፈንታ ፡ በጠለ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ኦሪት ፡ ንቤጥልኑ ፡ በሃይማኖት ። ይቤጥሎሙ ፡ ጠቢብ ፡ ጳውሎስ ። በጠለ ፡ እግዚ ፡ እምኔሆሙ ፡ መንግሥት ፡ (ቁር) ።

**አብጣሊ ፤ መብጠሊ ፤** የሚያጠፋ ፡ አጥፊ ፡ አስጠፊ ። ከመ ፡ ይኩን ፡ ዝንቱ ፡ መብጠሌ ፡ ሀጕሎሙ ፡ ለግብጽ ፡ (አፈ ፡ ድ፳፯) ።

**ብጥም ፤ ቡጥም ፤ (ዐረ ፡ ቡጥም ። ሱር ፡ ቤጥማ) ፤** በቋሙ ፡ የዛፍ ፡ ስም ፡ ጠርቤንቶስን ፡ ኢይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ይዘብሑ ፡ ታሕተ ፡ ባሉጥ ፡ ወቡጥም ፡ ወገውዝ ፡ ወለውዝ ፡ (ሆሴ ፡ ፬፲፫ ። አቡሻ ፡ ፴፯) ።

**በጢር ፤ ሮት ፤ (በጠረ ፡ ይበጥር ፡ ይብጥር) ፤** መበጠር ፡ ማበጠር ፡ ማንጠርጠር ፡ ማንፈስ ፡ መንቀስ ፡ የእኽል ፡ የጠጕር ፡ የነገር ። ከማእገዝ ፡ ወዳማርኛ ፡ ስለ ፡ ኼደ ፡ ባለቅኔዎች ፡ አይገሉትም ።

**አብጠረ ፤** አስበጠረ ፡ አስነፈሰ ፡ አስነቀሰ ።

**ተበጥረ ፤** ተበጠረ ፡ ተንጠረጠረ ፡ ተነፈሰ ፡ ተነቀሰ ፡ ጥሩ ፡ ኾነ ።

**ምብጣር ፤ (ሩት) ፤** ማበጠሪያ ፡ ማንጠርጠሪያ ፡ ሚዶ ፡ ስፌድ ፡ ፍርድ ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ ነቃሽ ፡ ምስክር ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ።

**በጥሬቃ ፤ (ሮማ ፡ ፓትሪሺያ ። ዐረ ፡ በጥሪቀት) ፤** ታላቅ ፡ ወይዘሮ ፡ ባላባት ፡ የነገሥታት ፡ ወገን ፡ ልዕልት ፡ እግዝእት ። ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ቀዳሚት ፡ በጥሬቃ ፡ ዘሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ (አዋል ። ገድ ፡ ዳን) ።

**በጢስ ፤ ሶት ፤ (በጠሰ ፡ ይበጥስ ፡ ይብጥስ) ፤** መበጠስ ፡ መበጣጠስ ፡ መቍረጥ ፡ መቈጥቈጥ ፡ የቅጠል ፡ የዐጽቅ ።

**በጦስ ፤** እምባ(ቢ)ሶ ፡ የሚቈረጥ ፡ የሚቈጠቈጥ ፡ ለጋውን ፡ ልጆች ፡ እየላጡ ፡ የሚበሉት ። (ዘፈን) ፡ ስለሚያለቅስ ፡ ልጅ ፡ እናትኽ ፡ ውሃ ፡ ወርዳለች ፡ እምባሶውን ፡ ታመጣልኻለች ።

**በጦስ ፤ (ጽር ፡ ባቶስ ። ዕብ ፡ ስኔ) ፤** ጳጦስ ፡ ሳቤቅ ፡ የሾኽ ፡ ቍጥቋጦ ፡ እሾኽም ፡ ዛፍ ፡ ፍሬው ፡ ቀይ ፡ መዐዛው ፡ ሠናይ ። ዕፀ ፡ ባጦስ ፡ (ዘዳ፴፫ ፡ ፲፮ ። ሉቃ፳ ፡ ፴፯) ። ሳቤቅንና ፡ ጳጦስን ፡ እይ ።

**ቤበየ ፤—ሠየ ፡ ጐመዠ ፤—ባበየ ።**

**ቤዝ ፤ (ብ ፡ ቤዛት ፤ አብያዝ) ፤** ጕልሕ ፡ ኮከብ ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ፡ ብርሃን ፡ የሚበራ ፡ የሚያብለጨልጭ ። አንተ ፡ ቤዝ ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ። ለዐይንቲሃ ፡ ይመስል ፡ ሥርቀተ ፡ ቤዝ ። በሰዓት ፡ ሞታ ፡ ደመነ ፡ ቤዝ ። በከመ ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ። ይፈደፍድ ፡ ብርሃኑ ፡ እምዘተርፉ ፡ ቤዛት ። ሰላም ፡ ለአዕይንትኪ ፡ ዘተመሰላ ፡ አብያዘ ፡ (ቁድር ። ገድ ፡ ተክ ። ስንክ ፡ መስ፲፩ ። ፊልክ ፡ ፪፻፸ ። ደራሲ ። አርጋ ፡ ፯ ። ኢዮ፵ ፡ ፲) ።

**ቤዘ ፤ (ይበይዝ ፡ ይቢዝ ፤ በዩዝ ፡ ዘት) ፤** በራ ፡ አበራ ፡ በዘበዘ ።

**ቤዝዎ ፤ ዎት ፤ (ቤዘወ ፡ ይቤዙ ፡ ይቤዙ ። ዐረ ፡ ባዘ ፤ ሸሸ ። ዕብ ፡ ፋዳ) ፤** መቤዠት ፡ ማዳን ፡ መታደግ ፡ ማስጣል ፡ ከጭንቅ ፡ ከባርነት ፡ ማውጣት ፡ ከባለዳ ፡ እጅ ፡ መግዛት ፡ መዋጀት ፡ ለውጥ ፡ መስጠት ፡ ገንዘብን ፡ ወይም ፡ ራስን ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ። አኮ ፡ በወርቅ ፡ ዘአቤዘወክሙ ። በነፍስክሙኑ ፡ ትቤዝውዋ ፡ ለነፍስየ ። መጽአ ፡ ይቤዝወነ ፡ እምኵሉ ፡ አበሳነ ፡ (ኢሳ፶፪ ፡ ፫ ። ኢያ፲፯ ፡ ፱ ። መጥዮ ። ዘዐ፲፫ ፡ ፲፫ ። ፴፬ ፡ ፳) ። በቤዘወ ፡ ፈንታ ፡ ተቤዘወ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ፡ ተ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። ተቤዘውዎሙ ፡ ለፃዉ ዋን ። አልቦ ፡ ዘይክል ፡ ተቤዝዎትየ ። ኢያድኅን ፡ ወርቅ ፡ ወኢይትቤዘው ፡ ብሩር ፡ (ዲድ ፡ ፳፭ ። አርጋ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ። ዘሌዋ ፡ ፴፭ ፡ ፴፪ ። ሲራ ፡ ፭ ፡ ፲፰) ። ቤዘወ ፡ የቤዘ ፡ ቅጥያ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ።

**ቤዛዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ዘውት)** ፤ የሚቤዥ ፡ የሚታደግ ፡ ታዳጊ ። ማርያም ፡ ቤዛዊተ ፡ ዓለም ። እስመ ፡ ቤዛዊሃ ፡ ለነፍስየ ፡ አንተ ፡ (ደራሲ) ።

**መቤዝዊ ፤ ው** ፤ ግዕዝ ፡ ከማሁ ። መድኅኒት ፡ መቤዝዊት ፡ እሞ ፡ ቅድስት ። ወልደከ ፡ መድኅን ፡ ወመቤዝው ። መቤዝወ ፡ ዓለም ፡ (ድጓ ። ስንክ ፡ ታኅሣ ። ቅዳ ፡ ሐዋ ፡ ኢጲ ። ደራሲ) ።

**ቤዛ ፤ (ዛት)** ፤ በቁሙ ፡ ዋጋ ፡ ካሳ ፡ ለውጥ ፡ ምትክ ፡ ፀሓፊ ፡ ዋቢ ፡ ዋስ ፡ መድኅን ፡ ተያዥ ፡ ፋጣማ ፡ ጥላ ፡ ጋሻ ፡ የመስለው ፡ ኹሉ ። ቤዛ ፡ ነፍሱ ፡ ለብእሲ ፡ ጥሪት ፡ ብዕሉ ። አኮ ፡ በቤዛ ። ቤዛ ፡ ኵሉ ፡ ኀጢአትከ ። ማእሰ ፡ ቤዛ ፡ ማእሰ ፡ (ምሳ፲፫ ፡ ፰ ። ኢሳ፵፫ ፡ ፲፫ ። ኢር፲፰ ፡ ፲፫ ። ኢዮ፴ ፡ ፴) ።

**ቤዛ ፤ (ደቂቅ ፡ አገባብ)** ፤ ስለ ፡ ፈንታ ፡ ምክንያት ። እሚጠ ፡ ነፍስየ ፡ ቤዛ ፡ አብግዐየ ፤ ስለ ፡ በጎቼ ። ዐይን ፡ ቤዛ ፡ ዐይን ፡ ወስን ፡ ቤዛ ፡ ስን ፤ በዐይን ፡ ፈንታ ፡ በጥርስ ፡ ፈንታ ። ተሰቅለ ፡ ቤዛነ ፤ ስለኛ ፡ በኛ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ቤዛችን ፡ ተብሎ ፡ በቁ ፡ ይኸ ናል ። ቤዛሁ ፡ ሃ ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ፡ በብትን ፡ እንጂ ፡ በአንቀጽ ፡ አይገባም ።

**አቤዘወ** ፤ አስቤዠ ፡ ቤዛ ፡ አሰጠ ፤ አስለወጠ ፡ አስያዘ ። ታቤዝዉ ፡ ምድረ ፡ (ዘሌ፳፭ ፡ ፳፬) ።

**ተቤዝወ ፤ ተቤዘወ** ፤ ተዋጀ ፡ ተገዛ ፡ ቤዛ ፡ አገኘ ፡ ዳነ ፡ ነጻ ፡ ወጣ ። ቢደሙ ፡ ትትቤዘው ፡ ነፍስ ። እለ ፡ ተቤዘዉ ፡ እምነ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ፤ እለ ፡ ቀደሙ ፡ ተቤዝዎ ። እስመ ፡ እምኢተቤዘውነ ፡ እመ ፡ ኢኮነ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ (ዘሌ፲፯ ፡ ፲፩ ። ሩእ፲፬ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ። ቄር) ።

**ቢዝው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ዙት)** ፤ የዳነ ፡ የተዋጀ ፡ ውጁ ፡ ቤዛ ፡ ያገኘ ።

**ቤጣ ፤ (ጽር ፡ ቤታ)** ፤ ፪ኛ ፡ ፊደል ፡ በ ፡ ቤት ፡ በጽርእና ፡ በቅብጥ ። አልፋ ፡ ወቤጣ ። ምንት ፡ ውእቱ ፡ ቤጣ ፡ (ሥር ፡ ጸሎ ። ኪዳ) ።

**ቤጡልዋ** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ (ዮዲ፬ ፡ ፯) ።

**ቤለ ፤ ይቤ ፤ ይበል ፤—አለ ፤—ብህለ ፡ ይብል ፡ ይብህል ።**

**ቤል ፤ (ዕብ)** ፤ የባቢሎን ፡ ከፊል ፡ ስመ ፡ ጣዖት ፡ ባቢሎናዊ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ያቆመው ፡ ምስል ። ባለ ብሉዮች ፡ ግን ፡ የፈረስ ፡ ምስል ፡ ይሉታል ፡ (ኢሳ፵፮ ፡ ፩ ። ዳን፲ ፡ ፲) ።

(ጥ) **በይኖ ፤ ኖት ፤ (በየነ ፡ ይቤይን ፡ ይብይን ። ዐረ ፡ ባነ ። ዕብ ፡ ባን)** ፤ መበየን ፡ መለየት ፡ መምረጥ ፡ ማስተዋል ፡ መመልከት ፡ ለይቶ ፡ ማወቅ ፡ መረዳት ፤ አስተውሎ ፡ መፍረድ ። ይቤይንዎሙ ፡ ወያነጽሕዎሙ ። ለምንት ፡ ኢትቤይን ፡ እምውስቴቶን ፡ እለ ፡ የዐብያሆን ። ወሠርዌ ፡ ዘውስተ ፡ ዐይንከ ፡ ኢትቤይን ። ይቤይኖ ፡ ለኃጥእ ፡ እንበለ ፡ ይግበር ፡ ኀጢአተ ፡ (ዳን፲፱ ፡ ፲ ። ሄርማ ። ማቴ፯ ፡ ፫ ። ቅዳ ፡ ኤጲ) ።

በበይኖ ፡ ፈንታ ፡ አበይኖ ፡ ይላል ፡ አይሰኝም ። ሕቱ ፡ በአበይኖ ፡ (ቅዳ ፡ አት ። ፩ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯) ።

**በያኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፤ የሚበይን ፡ በያኝ ፡ ዐዋቂ ፡ ፈራጅ ፡ አስተዋይ ፤ ዳኛ ፡ መምር ።

**መበይን ፤ (ንት ፡ ናን ፡ ናት)** ፤ ግዕዝ ፡ ከማሁ ። ኢትማኤ ፡ ገጽ ፡ መበይን ፡ (ዲድ ፡ ፬) ።

**አበየነ** ፤ አስበየነ ፡ አስፈረደ ፤ አስለየ ። አስረዳ ፡ አስታወቀ ። ንፈቅድ ፡ ከመ ፡ ታበይን ፡ ለነ ፡ ስምዓታተ ። ያቤይን ፡ ሎሙ ፡ ክሒደቶ ። ከመ ፡ ታበይን ፡ ዐመፃየ ። አበይኖት ፡ (ፊልክ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳ ። ዮሴፍ ። ገድ ፡ አዳ) ።

**ተበየነ** ፤ ተለየ ፡ ታወቀ ፡ ተረዳ ፤ ታየ ፡ ተገለጠ ። በከመ ፡ ተበየነ ፤ ወበእንተ ፡ ተበይኖ ። ውእቱኬ ፡ ይትቤየን ፡ እምግባረ ፡ ማርታ ፡ ወማርያም ። ናሁ ፡ ተበየነ ፡ ለከ ፡ ጥይቁ ፡ ነገርየ ። ተበየነ ፡ ንዝህላልከ ፡ (ፊልክ ፡ ፫ ። ፺፬ ። ዮሴፍ) ።

**ብዩን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ይንት)** ፤ የተለየ ፤ የታወቀ ፤ የተረዳ ፤ ግልጥ ፡ ጕልሕ ። ዝንቱ ፡ ብዩን ፡ (ዮሴፍ) ።

**ብያኔ ፤ (ያት)** ፤ መለየ ፡ ልዩነት ፤ በቁሙ ፤ ብይን ፡ ፍርድ ፤ አፈራረድ ፤ ፈሊጥ ፡ ዕውቀት ፤ ሥርዐት ። ማእምረ ፡ ብያኔ ። ብያኔ ፡ ልባዊ ። ብያኔ ፡ ሮማዊ ፡ (ታሪ ፡ ነገ ። ፍ ፡ ን ፡ ፴) ።

**በይነ ፤ (በይን ። ሰብ ፡ ቤን ። ሱር ፡ ባይናይ ። ዐረ ፡ በይነ ፤ ማእከል)** ፤ ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ። ስለ ፡ ምክንያት ። ዐቢይ ፡ ሲኾን ፡ ዘን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ አድርጎ ። ተሰብአ ፡ በይነ ፡ ዘአፍቀረ ፡ ሰብአ ፤ ተቀብዐ ፡ በይነ ፡ ዘተሰብአ ፤ ተሰምየ ፡ መሲሕ ፡ በይነ ፡ ዘተቀብዐ ፡ እያለ ፡ ይገባል ። (ሰር፲፱ ፡ ቀ፳፰) ። ደቂቅ ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ ቤዛ ፡ በብትን ፡ ይገባል ፤ በይነ ፡ ምንት ፤ ስለ ፡ ምን ፡ በምን ፡ ምክንያት ። በይኑ ፡ በይና ፡ በይንከ ፡ ኪ ፡ ከሙ ፡ ክን ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ።

**እንበይነ ፤ (እን ፡ በይነ)** ፤ ግዕዝ ፡ ከማሁ ፡ ስለ ። እን ፡ ትርፍና ፡ ተውሳክ ፡ አዳማቂ ፡ ነው ፡ ፍች ፡ የለውም ። እንበይነ ፡ ዘኢበልዐ ። እንበይነ ፡ መኑ ፡ ይብል ። እንበይነ ፡ ምጽዋት ። ሳሕም ፡ ዘእንበይነ ፡ ኀጢአት ። እንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፴ ። ዮሐ፲፫ ፡ ፳፬ ። ሚራ፳፬ ፡ ፴ ። ዘፀ፳፱ ፡ ፴፯ ። ቲቶ፳ ፡ ፳) ።

**በበይነ ፤ (በ ፡ በይን)** ፤ ግዕዝ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፡ ስለ ። በ ፡ እንደ ፡ እን ፡ አዳማቂ ፡ ነው ፤ ሥራ ፡ የለውም ። በበይነ ፡ ነፍሱ ፡ ለዝንቱ ፡ ብእሲ ። በበይነ ፡ ዚአክሙ ። አኮ ፡ በበይነ ፡ ወርቅ ። በበይነ ፡ እግዚ ። በበይነ ፡ መኑ ። በበይነ ፡ ምንት ፡ (ዮና፩ ፡ ፲፬ ። ሚክ፫ ፡ ፲፱ ። ኢሳ፵፰ ፡ ፲ ። ፳፬ ፡ ፲፩ ። ኤንባ ፡ ፲፬ ። ዘ፳፰ ። ሚልኪ ፡ ፪) ።

**በይን** ፤ ብቻ ፡ ርስ ፡ ራስ ፡ ባለቤት ፡ እኔ ፡ የሚል ፡ የተለየ ፡ አካል ። ፩ ፡ ወገን ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ፈርጅ ፡ ነጠላ ፡ ቀንጃ ።

**በይኑ** ፤ ለሊሁ ፡ ብቻው ፡ ርሱ ፤ ራሱ ፡ ባለቤቱ ።

**በበይኑ** ፤ ለብቻው ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ ለብቻው ፡ ብቻውን ። ጻማዊ ፡ ወፈጻሚ ፡ መልእክት ፡ ዘበበይኑ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲) ።

**በበበይኑ** ፤ (በበ ፡ በይኑ) ፤ በየራሱ ፡ በየብቻው ፡ ራስ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ ብቻው ። በበ ፡ ተመልከት ። ሕናብስት ፡ መሠጥ ፡ ወመንኰራኵራት ፡ ዘበበ ፡ በይኑ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲) ።

**በይናት** ፤ ኹለት ፡ ወገን ፡ ኹለት ፡ ክፍል ፡ ጥንድ ፡ ዘወማ ፡ መንታ ፡ እንደ ፡ እጅና ፡ እግር ፡ ያሉ ፡ ተባባሮች ፡ ተንጻጻሮች ፡ ተመሳሳዮች ።

**በበይናት** ፤ በኹለት ፡ ወገን ፡ በኹለት ፡ ክፍል ፡ ኹለት ፡ ወገን ፡ ኹና ።

**በበይናቲሁ** ፤ ርስ ፡ በርሱ ፡ አንዱ ፡ ከንዱ ፡ ጋራ ። በበይናቲሃ ፡ ከ ፡ ቲን ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ። ተባ ህሉ ፡ በበይናቲሆሙ ። ተኣምኑ ፡ በበይናቲክሙ ፡ (ዘፍጥ፵፪ ፡ ፳፩ ። ቅዳ) ።

**በዩጽ** ፤ **ጾት** ፤ (**ቤጺ ፡ ይበይጽ ፡ ይቢጽ ። ዕብ ፡ ባጻዕ ። ዐረ ፡ በፀዐ**) ፤ መለየት ፡ መምረጥ ፡ አለ ተካከሉ ፡ መቍረጥ ። ወቤጻ ፡ ያዕቆብ ፡ አባግዒሁ ። እ በይጽ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ ኃጥኣነ ። ዘይበይጽ ፡ በ ክናፍሪሁ ፡ ሖሎ ፡ እኩየ ፤ ለየ ፡ (ዘፍጥ፴ ፡ ፵ ። ሕዝቅ ፡ ፳፫ ። ምሳ፲፫ ፡ ፴) ።

—፤ መንጣት ፡ መገርጣት ፡ ብጫጫ ፡ ማለት ፡ ሰንቍጣል ፡ ወይም ፡ የበሰለ ፡ ቅጠል ፡ መምሰል ።

**በያጺ** ፤ (**ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት**) ፤ የሚለይ ፡ መራጭ ፡ ቈራጭ ።

**ተበይጸ** ፤ ተለየ ፡ ተመረጠ ፡ ተገለለ ።

**ብዩጽ** ፤ (**ጻን ፡ ጺት ፡ ይጽት**) ፤ የተለየ ፡ ልዩ ፡ ምርጥ ።

**ቢጽ** ፤ (**ዐረ ፡ ጻሕብ ፤ ቀራብ ፤ ሺሪክ ። ዕብ ፡ ሐቤር ፤ ሬዕ**) ፤ ባልንጀራ ፡ እኩያ ፡ አምሳያ ፡ መንድም ፡ መንቲያ ፡ ወዳጅ ፡ ዘመድ ፡ ወገን ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ጎደኛ ፡ ባልደረባ ፡ አቻ ፡ ማለት ፡ ዘማች ፡ ወታደር ፡ ሰራ ዊት ፡ ኅብረት ፡ አንድነት ፡ ትክክልነት ፡ ያለው ፡ ማናቸ ውም ፡ ኹሉ ። ባለመጣፎች ፡ መጣፋቸውን ፡ ተከትለው ፡ ቢጽ ፡ እንደ ፡ ስብእ ፡ ውስጠ ፡ ብዙና ፡ ኢስተጋብኢ ፡ ነው ፡ ሳንድም ፡ ለብዙም ፡ ለወንድም ፡ ለሴትም ፡ ይነገር ፡ ይ ላሉ ፡ ባለትኋያች ፡ ግን ፡ ቢጽና ፡ ዐር ፡ ሳንድ ፡ ብቻ ፡ እ ንጂ ፡ ለብዙ ፡ አይኾኑም ፡ ይላሉና ፡ ዐርን ፡ ተመልከት ። አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ ። ኢከንኩ ፡ አነ ፡ እግ ዚእከ ፡ አሳ ፡ ቢጽከ ። ዘያፈቅር ፡ ቢጾ ፡ ውስተ ፡ ብር ሃን ፡ ይነብር ፡ ወዘሰ ፡ ይጸልእ ፡ ቢጾ ። ብእሲ ፡ እም ቢጺ ። ንግበር ፡ ሎቱ ፡ ቢጸ ። ቢጸ ፡ እስራኤል ፡ ወቢጸ ፡ ይሁዳ ፡ (ዘሌዋ፲፱ ፡ ፲፰ ። ዕር ፡ ኢሳ፷ ፡ ፳ ። ሺዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ። መክ፬ ፡ ፬ ። ዘፍ፪ ፡ ፲፰ ። ሺነገ ፡ ፲፭ ፡ ፬) ።

**አብያጽ** ፤ ባልንጀሮች ፡ (ዳንኤ ፡ ፳ ። ማቴ፲፩ ፡ ፲፯ ። ዘካ፫ ፡ ፰) ። ኢይትፌለጥ ፡ እምአብያጽየ ። አ ጥሪ ፡ አግዋረ ፡ እምቅድመ ፡ ትሕንጽ ፡ አብያተ ፡ ወአ ብያጸ ፡ እምቅድመ ፡ ትሕር ፡ ፍኖተ ። አብያጺከ ፡ እለ ፡ መርቆሬ ፡ (አፈ ፡ ድጓ፳ ። ፈላስ ። ደራሲ) ። በአብ ያጽ ፡ ፈንታ ፡ ይከይድዎ ፡ ቢጹ ፤ ለቢጹ ፡ አርዳእ ፤ ቢጽ ፡ ወራዙት ፤ ቢጽ ፡ እኩያን ፤ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፤ ኀምስቱ ፡ ምእት ፡ ቢጽ ፡ እያለ ፡ ይገኛል ፡ የጣፊና ፡ የ መላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። እሬኢ ፡ በሰሳተ ፡ ቢጸ ፤ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ በለስ ፡ ክፉና ፡ መልካም ፡ (ኤር፳፬ ፡ ፩) ። ቢጽ ፡ የግእዝ ፡ ተውሳክ ፡ ነው ፡ በሌላ ፡ አይገኝም ።

**ተባየጸ** ፤ ባልንጀራ ፡ ኾነ ፡ ተመሳሰለ ፡ ተካከለ ፡ ተዋደደ ፡ ተስማማ ፡ ተሳተፈ ። ውእቱ ፡ መንክስ ፡ ዘተባ የጸከ ። ይትባየጸሙ ፡ ለልዑላን ። ዘይትባየጸ ፡ በማ እድ ። በእንተ ፡ ዘትሠሠ ፡ ተባይጾተ ፡ (ስንክ ፡ ሐም ፳፫ ። አፈ ፡ ድሳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፱) ።

**አስተባየጸ** ፤ አመሳሰለ ፡ አወዳጀ ፡ አቀናጀ ፡ አ ስማማ ። እንዘ ፡ ያስተባይጸሙ ፡ ምስሌሁ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**መስተባይጽ** ፤ (**ጽት ፡ ጻን ፡ ጺት**) ፤ የሚያስ ማማ ፡ የሚስማማ ፡ ስምም ፡ ፍቅረኛ ። ሰሐሱ ፡ በኵ ናሁ ፡ ወከኑ ፡ ሎቱ ፡ መስተባይጻነ ፡ በተጋንዮ ፡ ብዙኃ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፳) ።

**ቤጺ** ፤ **ብጺ** ፤ ብጫ ፡ ብጫቴ ፡ ዐይነቱ ፡ የንቍ ላል ፡ አስኳል ፡ ዐይደ ፡ የሚመስል ፡ አበፈርን ፡ እይ ።

**ቤቃ** ፤ ስመ ፡ አምሳክ ፡ እንደ ፡ እክዕ ፡ ያለ ። ቤ ፡ ኹለተኛ ፡ አካል ፡ ቃ ፡ ቃል ፡ ቀዳማዊ ፡ በሌላው ፡ አን ቀጽ ፡ መቅድመ ፡ ቃል ፡ ብሎ ፡ ይፈታዋል ፡ (ሔኖ) ።

**ቢራ** ፤ **ባሪ** ፤ (**ዕብ ፡ ቢራህ ። ጽር ፡ ባሪ**) ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ መዲና ፡ የንጉሥ ፡ ከተማ ፤ ታላቅ ፡ ሕንጻ ፡ ጸኑ ፡ አንባ ፡ ዕርድ ፡ ምሽግ ፡ (ዳንኤ ፡ ፪ ። ዕዝ ፡ ፯ ፡ ፪) ።

**በይረሙን** ፤ (**ዐረ ፡ በይራም**) ፤ ቅድሳት ፡ ዕለተ ፡ ቅድሳት ፡ አስተርእዮ ፡ ጥምቀት ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲) ።

**ቢስ** ፤—**በቁሙ** ፤ **ንኡግ** ፤ **ፀበጫ** ፤—**ብ እሲ ፡ ብእሲ** ።

**በዩት** ፤ **ቶት** ፤ (**ቤተ ፡ ይበይት ፡ ይቢት ። ሱር ፡ ቡት ፤ ባት ። ዐረ ፡ ባተ**) ፤ ማደር ፡ ባሉበት ፡ ቦታ ፡ ከሠርክ ፡ እስከ ፡ ነግህ ፡ መቈየት ፡ የትም ፡ ውሎ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መመለስ ፡ መግባት ፡ መከተት ፡ ከሰው ፡ መ ጠጋት ። መኖር ፤ ባንድ ፡ አገር ፡ መወሰን ፡ ቦታ ፡ መያዝ ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ አጽንዖ ፡ በኋት ። ቤትኩ ፡ ወወዐልኩ ፡ እንዘ ፡ እጸብት ። ቤቱ ፡ ክልኤሆሙ ፡ በይእቲ ፡ ሌ ሊት ። ትበይት ፡ ሌሊተ ፡ ውስተ ፡ ያም ። አልቦ ፡ ንብ ረት ፡ ዘትበ ፡ መስዮ ፡ ይበይት ። ኀቤየ ፡ ትበይት ፡ ዮም ፤ ዐደረ ፡ ገባ ፡ ተኛ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፯ ። ጦቢ፰ ፡ ፱ ። ኢሳ፳፩ ፡ ፲፫ ። ሚራ፴፯ ፡ ፴፩ ። ዘፍ፲፱ ፡ ፲፫) ። ይበ

ይት ፡ ውስተ ፡ በሐታተ ፡ ኲሎሙ ። በጸጋሁ ፡ ተፈጥረ ፡ ዘሎ ፡ ወበኒፋቱ ፡ ይበይት ፤ ኖረ ፡ (ኢዮ፴፱ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**በያቲ** ፤ (**ቲት ፡ ትያን ፡ ያት**) ፤ የሚያድር ፡ በዳሪ ፡ ነዋሪ ፡ ቤት ፡ ሠሪ ።

**ቤት** ፤ (**ብ ፡ አብያት ። ዕብ ፡ ባይት ። ሱር ፡ ቤታ ። ዐረ ፡ በይት**) ፤ በቁሙ ፡ ማደሪያ ፡ መኖሪያ ፤ ሥራ ፡ መሥሪያ ፤ በደንጊያ ፡ በብረት ፤ በጡብና ፡ በንጨት ፤ በኖራ ፡ በጭቃ ፡ በማር ፡ በልልፈቃ ፡ የሚሠራ ። ውስጡ ፡ ክፍትንት ፡ ያለው ፡ ዕቃ ፡ ቦታ ፤ ዋሻ ፡ ፍርኵታ ፤ ጕሬ ፡ ጕድጓድ ፤ ታላቁም ፡ ታናሹም ፡ ማናቸውም ፡ ኹሉ ። **እቀትሎ ፡ ለቤተ ፡ ምክራም ፡ ወለቤተ ፡ ሐጋይ** ፤ **ይትሀጐሉ ፡ አብያት ፡ ዘቀርን ፤ ንጌ ፡ ወይትከሉ ፡ አብያት ፡ ካልአን ። ይቀሥፎ ፡ ለዐቢይ ፡ ቤት ፡ በድቀት ፡ ወለንኡስ ፡ ቤት ፡ በንፀኝት ። ባእ ፡ ቤተከ ። ቤት ፡ ምሩግ** ፤ (ዓሞ፫ ፡ ፲፭ ። ፮ ፡ ፲፩ ። ኢሳ ፳፯ ፡ ፳ ። ምሳ፳፩ ፡ ፱) ።



ቤት ፡

— ፤ ወገን ፡ ነገድ ፤ ዘር ፡ ትውልድ ፤ ጉባኤ ፡ ማኅበር ፤ ጭፍራ ፡ ወታደር ፡ በያለቃው ። **ርስዒ ፡ ሕዝበኪ ፡ ወቤተ ፡ አቡኪ ። ቤተ ፡ ያዕቆብ ፤ ቤተ ፡ ዳዊት ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ ቤተ ፡ ክህነት ፤ ቤተ ፡ መንግሥት ።**

**ቤት** ፤ ገንዘብ ፤ ዘመድ ፤ ቤተ ፡ ሰብ ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፲፬ ። ዘፀ፩ ፡ ፳፩) ።

**ቤተ ፡ እግር** ፤ መጫሚያ ፡ ሹራብ ፤ ሱሪ ፡ ሃንባሌ ፤ ድርማንቅ ፡ በለሌ ።

**ቤተ ፡ እግዚ** ፤ የሙሴ ፡ ድንኳን ፡ መቅደስ ፡ ሰሎሞን ፤ ቤተ ፡ ክሲያን ፤ ጉባኤ ፡ ምእመናን ፡ (ቀሌ) ።

**ቤተ ፡ እድ** ፤ እጅጌ ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፤ የእጅ ፡ ቤዛ ፡ ሹራብ ። የዕቃ ፡ ገርሮ ፤ ቀለብት ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፳፭) ።

**ቤተ ፡ አማልክት** ፤ የጣዖታት ፡ ቤት ፤ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ጣዖት ፡ ያለበት ፡ መስጊድ ።

**ቤተ ፡ አንስት** ፤ ጥሩ ፡ ዕልፍኝ ፡ የተሸለመ ፤ የተጌጠ ፡ የተንቈጠቈጠ ፡ (አስቴ፪ ፡ ፱ ፡ ፲፫) ።

**ቤተ ፡ አፈው** ፤ የሽቱ ፡ መደብ ፡ የበቀለበት ፡ የተተከለበት ፡ (ማሕ፮ ፡ ፪) ።

**ቤተ ፡ ብለኔ** ፤ የውሽባ ፡ ቤት ፡ መታጠቢያ ፡ ሽቱ ፡ መገዝገቢያ ፡ (ቀሌ) ።

**ቤተ ፡ ማዝእ** ፤ የድግስ ፡ የመሸታ ፡ ቤት ፡ ማቅ ፡ ጨዎት ፡ ስካርና ፡ ዘሙት ፡ ያለበት ፡ (መክ፯ ፡ ፪) ።

**ቤተ ፡ ድውያን** ፤ በሽተኞች ፡ እስኪድኑ ፡ የሚተኙበት ፤ ሕክምና ፡ ፈውስ ፡ ያለበት ፡ ንጹሕ ፡ ቦታ ፡ (ቀኖ ፡ ኒቅ) ።

**ቤተ ፡ ወይን** ፤ የጠጅ ፡ ቤት ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በበርሚል ፡ በጋን ፡ የሚሸምበት ፡ (ማሕ፪ ፡ ፬) ።

**ቤተ ፡ ዝሙት** ፤ የዝሙት ፡ መደብር ፤ ያመንዝሮች ፡ ቤት ፡ ከንፍረት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ንገር ፡ የማይሸጥበት ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፴፱) ።

**ቤተ ፡ ሐኖት** ፤ ቤተ ፡ ዝሙት ፤ የገበያ ፡ ቤት ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ የሚሸጥበት ፡ (ስንክ ፡ ግን፲፪) ።

**ቤተ ፡ ጣዖት** ፤ የሰይጣን ፡ ቤት ፤ ሰይጣን ፡ በጣዖቱ ፡ ዐድሮ ፡ የሚመለክበት ፡ (ኩፋ ፡ ፲፪) ።

**ቤተ ፡ ክሣድ** ፤ ዐንገትጌ ፡ የቀሚስ ፡ አፍ ፤ ራስ ፡ ማግቢያ ።

**ቤተ ፡ ልብስ** ፤ ጋን ፡ ሣጥን ፤ ዕቃ ፡ ቤት ፡ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ ልብስ ፡ የሚከተትበት ፡ (ትእ ፡ ጴጥ) ።

**ቤተ ፡ ላሕ** ፤ የሐዘን ፡ ቤት ፤ ማልቀሻ ፡ እንባ ፡ ማፍሰሻ ፡ (መክ፯ ፡ ፪) ።

**ቤተ ፡ ልሔም** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ ቤተ ፡ ኅብስት ፡ (ዘፍ፴፭ ፡ ፲፱) ።

**ቤተ ፡ መበስላን** ፤ የወጥ ፡ የንፍሮ ፡ ቤት ፤ ማብሰያ ፡ መቀቀያ ።

**ቤተ ፡ መዋጽሕት** ፤ ማረፊያ ፡ መክደኛ ፡ ጉባባ ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፳፱) ።

**ቤተ ፡ ሞቅሕ** ፤ የግዞት ፡ ቤት ፤ ወንጀለኞች ፡ የሚታሰሩበት ፡ (መክ፬ ፡ ፲፬) ።

**ቤተ ፡ ሙታን** ፤ መቃብር ፤ የመቃብር ፡ ቤት ፤ ሲኦል ፡ (ስንክ ፡ የካ፳) ።

**ቤተ ፡ መዛግብት** ፤ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ዕቃና ፡ ልብስ ፡ በሣጥን ፡ መልቶ ፡ የሚቀመጥበት ፡ (ዳንኤ ፡ ፩) ።

**ቤተ ፡ መጥበሕት** ፤ አርድ ፤ ሰገባ ፡ ሽፋፍ ፡ ድርቤ ፡ (ማቴ፳፮ ፡ ፶፪) ።

**ቤተ ፡ ማይ** ፤ ሠገራ ፡ ዐዘቅት ፡ ኰስሕ ፡ (ስንክ ፡ የካ፳፩) ።

**ቤተ ፡ መያሲ** ፤ የመሸታ ፡ ቤት ፤ ከዚያው ፡ እየጠጡ ፡ የሚሰክሩበት ፡ (ኢሳ፭ ፡ ፲፩) ።

**ቤተ ፡ መምህራን** ፤ ታላቅ ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ የፈላስፎች ፡ ትምርት ፡ ያለበት ፡ (ስንክ ፡ ግን፲፬) ።

**ቤተ ፡ ምሥያጥ** ፤ ሱቅ ፡ መደብር ፤ የንግድ ፡ ቤት ፡ (ዮሐ፪ ፡ ፲፮) ።

**ቤተ ፡ መጻሕፍት** ፤ የመጣፍ ፡ ቤት ፡ መጣፍ ፡ ኹሉ ፡ በየይነቱ ፡ የሚገኝበት ፤ (ቢብሊዮቴክ) ፡ ትርጓሜ ፡ የሚነገርበት ፤ የመጣፍ ፡ መክተቻ ፡ ሣጥን ፡ ማኅደር ፤ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ዋሻ ፡ (ጎድ ፡ እዳ) ።

**ቤተ ፡ መቅደስ** ፤ በቁሙ ፤ ቤተ ፡ እግዚ ፡ መቅደስ ፡ አራት ፤ መቅደስ ፡ ወንጌል ፤ ቤተ ፡ ክሲያን ።

**ቤተ ፡ ምርፋቅ** ፤ የምግብ ፡ ቤት ፡ ዳስ ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፤ ቤተ ፡ ልሔም ።

**ቤተ ፡ ምሳሕ** ፤ አዳራሽ ፤ ግብር ፡ ማግቢያ ፤ ምሳ ፡ ማቅረቢያ ፡ (ዳንኤ ፡ ፲) ።

**ቤተ ፡ ነግድ** ፤ እንግዳ ፡ የሚያርፍበት ፤ ሰቀት ፡ ብሎ ፡ የሚገባበት ፡ ልኳንዳ ፡ ሆቴል ፡ (ስንክ ፡ ኅሐ፲፫) ።

**ቤተ ፡ ፍንዱቅ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ቤተ ፡ ነግድ ፡ (ትእ ፡ ጴጥ) ።

**ቤተ ፡ ፍሥሓ** ፤ የሰርግ ፡ የመሸታ ፡ ቤት ፡ (መክ፯ ፡ ፭) ።

**ቤተ ፡ ጸሎት** ፤ ታናሽ ፡ ምኵራብ ፤ የሥዕል ፡ ቤት ፡ ከጸሎት ፡ በቀር ፡ መሥዋዕት ፡ የማይቀርብበት ፤ ወይም ፡ ታላቅ ፡ መቅደስ ፤ ቤተ ፡ ክሲያን ፡ (ኢሳ፶፮ ፡ ፯) ።

**ቤተ ፡ ርእስ** ፤ ቆብ ፡ ባርኔጣ ፤ የክባ ፡ የበርኖስ ፡ ቀንበር ።

**ቤተ ፡ ስምዕ** ፤ ደብተራ ፡ ስምዕ ፤ የሙሴ ፡ ድንኳን ፤ (፩ዜና ፡ ፮ ፡ ፴፪ ። ፪ዜና ፡ ፭ ፡ ፫) ።

**ቤተ ፡ ስታይ** ፤ የድግስ ፡ የመሸታ ፡ ቤት ፤ ያረቁ ፡ መደብር ፡ መጠጥ ፡ ኹሉ ፡ በያይነቱ ፡ የሚገኝበት ፡ (ሚራ፴፫ ፡ ፯) ። ቤት ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ እየተናበበ ፡ በዚህ ፡ አምሳል ፡ እንደ ፡ ዘርፉ ፡ ስልት ፡ ይፈታል ፤ ዘርፍና ፡ ቅጽል ፡ ባለቤትን ፡ ወይም ፡ ስምና ፡ ግብርን ፡ እንዲገልጥ ፡ አስተውል ።

**ቤታዊ ፡ አብያታዊ** ፤ የቤት ፤ ቤታም ፡ ባለ ቤት ፡ ቤት ፡ አባት ፤ አዛዥ ፡ መጋቢ ፤ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ዘመድ ፡ የቤት ፡ ውልድ ። ገብረ ፡ ንጉሥ ፡ ሰብእ ፡ አብያታዊ ፡ (ዮሐ፬ ፡ ፵፮ ፡ ፵፱) ።

**አቤተ** ፤ አሳደረ ፤ እስከ ፡ ነግህ ፡ አቈየ ፤ አኖረ ፤ አስጠጋ ። ወኢያሠንዩ ፡ ማኅተቶሙ ፡ ለአቢቶ ። ወለብዙኃን ፡ ዕሩቃን ፡ አቤትዎሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ልብስ ። ወኢያቤት ፡ ምንተኒ ። ተዘሐላተ ፡ ዕረብ ፡ እለ ፡ ኢያበይቱ ፡ ለነግህ ፡ (፩ነገ ፡ ፫ ፡ ፫ ። ኢዮ፳፬ ፡ ፯ ። ሶፎ፫ ፡ ፫) ።

**ምብያት** ፤ ማደሪያ ፤ ማሳደሪያ ፤ መኖሪያ ፤ ቦታ ፡ ቤት ፡ በረት ። ከመ ፡ መርጌት ፡ ውስተ ፡ ምብያቲሁ ። ምብያቲክ ፡ (ሚክ፪ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፴፯ ፡ ፳፰) ።

**ተበየተ** ፤ ተዳደረ ፤ ተዋገነ ፤ ተጎራበተ ፤ ተከታተመ ።

**አስተበየተ** ፤ አስተዳደረ ፤ አዋገነ ፤ አጎራበተ ።

**መስተባይት** ፤ ተዳዳሪ ፡ አስተዳዳሪ ።

**ቤት** ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ክልኢ ፡ በ ፡ ትርጓሜ ፡ ቤትና ፡ ደጅ ፡ አፍ ፡ የሚመስል ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፱—፲፮ ። ሰቈ፩ ፡ ፪ ። ፪ ፡ ፪ ። ፫ ፡ ፭ ። ፬ ፡ ፪) ። ስሙንና ፡ መልኩን ፡ ከቤት ፡ ወስዷል ።

**ብኵ ፤—ብኩይ ፤—በከየ ።**

**በክ ፤—መበከን ፤—በዊክ ።**

**በኰሐ ፤ ሐት ፤ (በኵሐ ፡ ይበኵሕ ፡ ይብኳሕ ። ዕብ ፡ ፋዋሕ ፤ ያፋሕ ፤ ናፋሕ ፤ ነፍኀ)** ፤ መንፋት ፤ እፍ ፡ ማለት ፤ እሳትን ፡ በአፍ ፡ ወይም ፡ በመናፍ ። ከአፍ ፡ እሳት ፡ ማውጣት ፤ ነበልባል ፡ መትፋት ፤ በምትሀት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በበኵሐ ፡ ፈንታ ፡ አብኵሐ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ፤ አ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። (ሕግዘ፳፪ ፡ ፳ ፡ ፳፭) ። **ዘሎሙ ፡ ያበዙሑ ፡ እሳተ ፡ እምአፉሆሙ** ፡ (ግድ ፡ ተክ) ። መለምለም ፡ መርጠብ ፤ ከነፋስ ፡ ከውሃ ፡ ጠል ፡ መንጣት ።

**አብኵሐ** ፤ አናፋ ፡ አስነፋ ፤ አስተነፈሰ ፤ እፍ ፡ እፍ ፡ አሰኘ ። **ዘያበዙሕ ፡ ምብኳሕ ፡ እሳት** ፡ (ኤር፮ ፡ ፳፱) ።

**መብኵሕ ፤ (ሕት ፡ ሓን ፡ ሓት)** ፤ ቀጽልና ፡ ጥሬ ። የሚያናፋ ፤ አናፊ ። ማናፊያ ፡ ወናፍ ።

**ምብኳሕ ፤ (ሓት)** ፤ አጕደ ፡ ማናፊያ ፤ ወናፍ ። **ምብኳሐ ፡ ነሃቢ ፡ ሥጡቅ ። በብዙኀ ፡ ምብኳሕ** ፡ (ኢዮ ፡ ፴፪ ፡ ፲፱ ። አርጋ ፡ ፫) ።



ምብኳሕ ።

*ክኡሓ ፤ (ሓት)* ፤ እፍታ ፡ እከታ ፤ ትንፋሽ ፡ የሚያነድ ፡ የሚያበርድ ፤ ወይም ፡ ልምሳሜ ፤ ርጥበት ፡ ርጥብነት ። ስመ ፡ ዕፅ ፡ ሓይ ፡ እሓያ ፡ የሚባል ፤ በወንዝ ፡ ዳር ፡ በውሃማ ፡ ቦታ ፡ የሚበቅል ። **ከመ ፡ ኩሓ ፡ ዘኀበ ፡ ሙሓዘ ፡ ማይ ። ውስተ ፡ ኩሓቲሃ** ፡ (ኢሳ፵፬ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፻፴፮) ።

**በክይ ፤ ዮት ፤ (በከየ ፡ ይበኪ ፡ ይብኪ ። ዕብ ፡ ባካ ። ሱር ፡ ብካ ። ዐረ ፡ በካ)** ፤ ማልቀስ ፤ እንባ ፡ ማፍሰስ ፡ ዋይ ፡ ማለት ፡ መራኰስ ፡ መንሰቅሰቅ ። **ኀደገት ፡ በከየ ። ብከዮ ፡ ለዘሞተ ። ኢይበክይዎሙ ። ሰእንተ ፡ ዘሉ ፡ ምንዱብ ፡ እበኪ** ፡ (መቢ፮ ፡ ፭ ። ሚራ ፳፪ ፡ ፲፩ ። ኤርጃ ፡ ፱ ። ኢዮ፴ ፡ ፳፭) ።

**በካዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ በከይት)** ፤ የሚያለቅስ ፡ አልቃሽ ፡ እንባ ፡ አፍሳሽ ፡ ልቅሶኛ ። **ብፁዓን ፡ እንተ ፡ ተብህለት ፡ ለሕዙናን ፡ ወለበካይያን** ፡ (ፊልክ ፡ ፸፱ ። ግድ ፡ አዳ) ።

**መብክይ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ አልቃሽ ፤ ወይም ፡ አስለቃሽ ። **ወበዊእ ፡ ቤተ ፡ ርእየ ፡ መብክያነ** ፡ (ማቴ፱ ፡ ፳፫ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ብኩይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ኪት)** ፤ ያለቀሰ ፡ አልቃሽ ፡ ሐዘንተኛ ።

(ተ) **ብክ ፤ ብኵ ፤ (ዕብ ፡ በኬ)** ፤ ስሙ ፡ ለብእ ፡ ዳዊት ፡ በነዩ ፡ ብኩይ ፡ አልቃሽ ፡ እንባማ ፡ ማለት ፡ ነው ። በገር ፡ ወልደ ፡ ብኵ ፡ (ጥበ፳ ፡ መዝ፹ ፡ ፯—፰) ። የባን ርን ፡ ፋኙ ፡ ተመልከት ።

**ብካይ ፤ (ያት)** ፤ ልቅሶ ፤ ዋይታ ፡ ፋጅጅት ፤ መራራ ፡ ጩኸት ፡ ከእንባ ፡ ጋራ ። በከየ ፡ ብካየ ፡ ዐቢየ ። ብካየ ፡ ሊያዜር ። ብካይ ፡ ወላሕ ። ቃለ ፡ ብካይ ፡ ወ ቃለ ፡ ዐውያት ፡ (ኤር፴፯ ፡ ፫ ። ኢሳ፲፮ ፡ ፱ ። ፳፪ ፡ ፲፪ ። ፳፭ ፡ ፲፱) ።

**አብከየ** ፤ አስለቀሰ ፡ አሳዘነ ፡ አስጮኸ ፡ ዋይ ፡ አሰኘ ፤ እንባ ፡ አስፈሰሰ ። በከየ ፡ ብካየ ፡ መሪረ ፡ እስከ ፡ አብከየ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ህየ ። ለእመ ፡ ኢበከይኩ ፡ በፈ ቃድየ ፡ በዝየ ፡ ያበክዩኒ ፡ በህየ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃድየ ። እለ ፡ አብክዩ ፡ ዕቤረ ፡ ወዕጓለ ፡ ማውታ ። ምንት ፡ ያበክየኪ ፡ (ዮሴፍ ። መቃ ። ማንዘ ። ሺንገ ፡ ፩ ፡ ፰) ።

**ተባከየ** ፤ ተላቀሰ ፡ ተሊቃቀሰ ፤ ተፋጀ ። ሶበ ፡ ተኣምኑ ፡ ወተባከዩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወተሰዐሙ ፡ (ተረ ፡ ባሮ) ።

**አስተባከየ** ፤ አላቀሰ ፡ አሊቃቀሰ ። ስሕልት ፡ ሰይፍከ ፡ ብእሲ ፡ ልዑል ፤ ለሰብአ ፡ ምረት ፡ ወመ ርሐ ፡ ቤቴ ፡ አምኃ ፡ ኢየሱስ ፡ መስተጋድል ። የተሳ ለቹ ፡ ሰይፋችኸ ፡ ታላቅ ፡ ሰው ፡ (ያማርኛ ፡ ግእዝ) ።

**በኪ.ክ ፤ ክት ፤ (በከ ፡ ይበክክ ፡ ይብ ክክ ። ዕብ ፡ ባቃቅ ። ዐረ ፡ በቀ ፤ በካእ)** ፤ ማብ ከክ ፤ ማብከክ ፡ ባይ ፡ ጠፍ ፡ ብላሽ ፡ ከንቱ ፡ ማድረግ ፤ ወይም ፡ መኾን ። እባክኸ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በበክክ ፡ ፈንታ ፡ በከየ ፡ ይላል ፤ የተሳ ሳተ ፡ ነው ። ኢይሬእዩ ፡ ፀሓየ ፡ ዘያበርህ ፡ ወይጠ ፍእ ፡ ወወርኅኒ ፡ ትበኪ ፡ (ኢዮ፴፮ ፡ ፳፮) ።

**በክ** ፤ በከት ፡ ሙቶ ፡ ያደረ ። ባይ ፡ ጠፍ ፡ ብላ ፡ ከንቱ ፡ ብላሽ ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ እንዲያው ፡ የዝም ፡ ብሎ ። ኵሉ ፡ ክበቡ ፡ በክ ። ትንበር ፡ በክ ። ነበሩ ፡ እስራኤል ፡ በበክ ። አብይ ፡ ደፈደፍይ ፡ ነቢብ ፡ በክ ። አኮ ፡ በክ ፡ በከመ ፡ ትሬእዩዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ኅብስት ፡ (ሔኖ፫፬ ፡ ፳ ። ሰቆቃ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ የካቲ፮ ። ሆሴ፫ ፡ ፱ ። መክ፫ ፡ ፲፳ ። ቅዳ ፡ ሕር) ።

**በከ** ፤ በከንቱ ፡ በብላሽ ፡ እንዲያው ፡ ወይም ፡ ለ ፡ ኹኖ ። በከ ፡ ጸመውኩ ። ኢትክዐው ፡ ደመ ፡ በከ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢኔ ። ነሀብከ ፡ በከ ። ኢነሥእ ፡ እምኔ ሆሙ ፡ በከ ። በከ ፡ ለሊነ ፡ ተፈጠርነ ፡ (ኢሳ፶፱ ፡ ፬ ። ኩፋ ፡ ፳፭ ፡ ፲፱ ። ጥበ፪ ፡ ፪) ።

**በኵር ፤ ሮት ፤ (በኰረ ፡ ይበኵር ፡ ይብ ኵር ። ዕብ ፡ ባኬር)** ፤ መብኰር ፡ መበከር ፡ መዥመ ሪያ ፡ መውለድ ፡ ማፍራት ፡ መውለድንና ፡ ማፍራትን ፡ መዠመር ፡ በኵር ፡ መኾን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በበኰረ ፡ ፈንታ ፡ ተበኵረ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ዕጕላት ፡ እለ ፡ ተ በኵራ ። አባግዕ ፡ እለ ፡ ተበኵራ ። መካን ፡ ተበኵረት ፡ ዮሐንስሀ ፡ (ሺንገ ፡ ፯ ፡ ፯ ። ክብ ፡ ንገ፳፫ ። መዋሥ) ።

—፤ በኵር ፡ ማድረግ ፡ ማላቅ ፡ ማብለጥ ፡ የብኵርና ፡ ክ ብር ፡ መስጠት ፤ ወልድየ ፡ ዘበኵርየ ፡ ማለት ፡ (ዘፋ፳፯ ፡ ፳፱ ። ዓ፱ ፡ ፰ ። ዘዐ፱ ፡ ፳፪ ። ዕብ፩ ፡ ፳ ፡ ፯ ። መዝ፹፰ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰) ።

—፤ ማብከር ፡ ማስታጐል ፤ ማቆም ፡ ማቋረጥ ፡ መቅደም ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በበኰረ ፡ ፈንታ ፡ አብኰረ ፡ ይላል ፤ አ ያማርኛ ፡ ነው ። በማይኒ ፡ ለእመ ፡ አብኰረት ፡ ዝ ናመ ፡ (፪ዜና ፡ ፯ ፡ ፳፯) ።

**በኳሬ ፤ (ሬት ፡ ርያን ፡ ያት)** ፤ በካር ፡ ዠ ማሪ ፡ በኵር ፡ አድራጊ ፤ አስታጓይ ።

**አብኰረ** ፤ አስበከረ ፡ በካር ፡ በኵር ፡ አስደረገ ፤ አስተወ ፤ ከለከለ ።

**ተበኵረ** ፤ ተበኰረ ፡ በኵር ፡ ኾነ ፡ በኵር ፡ ተባለ ፤ የበኵርነት ፡ ክብር ፡ ተቀበለ ። ዮሐንስ ፡ እምክርሠ ፡ መካን ፡ ዘተበኵረ ፡ (ድጓ) ።

—፤ ታጐለ ፤ ቀረ ። እምይትበኰር ፡ በዓሉ ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ (ድር ፡ ሚክ) ።

**ብኩር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ኵርት)** ፤ የተበኰረ ፡ በኵር ፡ የኾነ ፡ የተባለ ፡ የቀረ ፡ የታጐለ ።

**በኵር ፤ (ራት ፤ አብኳር ። ዕብ ፡ ብኮር ። ሱር ፡ ቡክራ ። ዐረ ፡ ቢክር)** ፤ በቁሙ ፤ መዥመ ሪያ ፡ ልጅ ፡ ፍሬ ፡ ቀዳማዊ ፤ ታላቅ ፡ አለቃ ፡ ሹም ፤ አን ጋፋ ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፤ ራስ ፡ የተወለደ ፡ የበሰለ ፤ መብ ሰል ፡ የፍሬ ፡ ነው ። ሟፋራ ፡ የሌለው ፡ አለቃ ፡ እንዳይ ባል ፤ ታናሽ ፡ ተከታይ ፡ የሌለውም ፡ ዋሕድ ፡ እንጂ ፡ በ ኵር ፡ አይባልም ። እሮ ፡ አሐደ ፡ ወሊዳ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ዘበኵራ ፤ አላ ፡ እስመ ፡ ኢወለደት ፡ እምድኅ ሬሁ ፡ (ቄር) ። ኵሉ ፡ በኵር ። በኵረ ፡ ወልድከ ። በ ኵሩ ፡ ለላሕም ፤ በኵሩ ፡ ለበግዕ ፡ ወለጠሊዖ ። ደ ቂቀ ፡ ዳዊት ፡ አብኳር ፡ ቀደምት ። አብኳረ ፡ እስራ ኤል ። በኵረ ፡ በለስ ። በኵራት ፡ ይበዐሩ ። ዓሥራት ፡ ወበኵራት ፡ (ዘፀ፲፫ ፡ ፳ ። ፳፪ ፡ ፳፰ ። ፴፬ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። ፩ዜና ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ። ክብ ፡ ንገ ። ሆሴ፱ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ ታኅ፳፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፰) ።

**በኵርና ፤ ብኵርና ፤ (ናት)** ፤ በኵርነት ፡ በኵር ፡ መኾን ፡ በፊት ፡ መወለድ ፡ ልቅና ፡ ቅድምና ። ተሣየጠ ፡ እምኔሁ ፡ ብኵርናሁ ። ብፅዐናት ፡ ወብኵር ናት ፡ (ስንክ ፡ ኅሐ፳፰ ። ቀሌ ። ዕብ፲፪ ፡ ፲፯ ። አፈ ፡ ድ፴፭) ። በብኵርና ፡ ፈንታ ፡ ያንዱን ፡ ቡብዙ ፡ ብኵርናት ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። አውፅአ ፡ ለሮቤል ፡ እምኍልቈ ፡ አኀዊሁ ፡ ወጸገዎ ፡ ብኵርናት ፡ ለዮሴፍ ፡ (ግንዘ) ።

**በኬሴል ፤ (ዕብ ፡ ባሴቤል)** ፤ ባ ፡ በ ፡ ሴ ቤል ፡ ሽክም ፡ በሽክም ፡ በመሸከም ፡ ወይም ፡ ተሸክ መው ፡ (ንሐ፱ ፡ ፲፯) ።

**በል ፤—ትእዛዝ ፤—ብህለ ፤ ቤለ ፡ ይቤ ። ቤልከ ፡ ትቤ ፡ ትበል ፡ በል ።**

**ቤል ፤**—የባቢሎን ፡ ክፋል ፤—በዪል ።

**በልበለ ፤**—አረጀ ፤—በሊል ፡ በለ ። በልየ ።

**በልግ ፤ (ዐማርኛ) ፤** የበጋ ፡ ዝናም ፤ ጸደይ ።

**በለድ ፤ (ትግሬ ፡ ወዐረ) ፤** የተወለዱበት ፡ አገር ።

**በለዝ ፤ (ጽር ፡ ቦሎዝ ። ዕብ ፡ ቦዐዝ) ፤** የዐምድ ፡ ስም ፤ ሰሎሞን ፡ በመቅደሱ ፡ ደጅ ፡ አፍ ፡ በበረንዳው ፡ በደጀ ፡ ሰላሙ ፡ ክቆማቸው ፡ ከኹለቱ ፡ አዕማድ ፡ አንዱ ፡ በስተ ሰሜን ፡ ያለው ፡ የግራው ፡ ዐምድ ። ቦ ፡ ዕዘገዘ፥ሎ ፡ ዕዘዝ፥ ኀይሉ ፡ ወጽንዑ ፡ ዕዘዘ ፡ ለመቅደስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ርትዕ ፡ ይሉታል ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፳፩) ።

**በልሐ ፤**—ተሳለ ፤—በልኅ ።

**በልሐ ፤ ሐት ፤ (ባልሐ ፡ ይበልሕ ፡ ይበልሕ ። ዕብ ፡ በሎሕ ፤ መዝለል ፤ መንገሩ ደድ) ፤** ማዳን ፡ ማውጣት ፤ መታደግ ፡ መቤዠት ፤ ከተያዙ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ። ይባልሖ ፡ ለንጹሕ ። ኢይክልኑ ፡ ባልሖ ፡ አልቦ ፡ ዘያድኅን ፡ ወዘይበልሕ ። ለባልሖትየ ፡ (ኢዮ፳፱ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፶ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፱) ።

**ባላሒ ፤ መባልሒ ፤** የሚያድን ፤ አዳኝ ፡ ታዳጊ ። ባላሒ ፡ ዘልፉ ። ባላሒ ፡ ለዕጓለ ፡ ማውታ ። መባልሒት ፡ (ቅዳ ። ኪዳ ። አርጋ) ።

**ተበልሐ ፤** ዳነ ፤ ወጣ ፡ አመለጠ ። ኢይትባላሕ ፡ ዘተመንደበ ። ዘይትባላሕ ፡ እምኔሃ ። ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ እለ ፡ ተባልሑ ፡ እምእቶን ፡ እሳት ፡ (ኢሳ፰ ፡ ፳፪ ። መክ፯ ፡ ፳፮ ። መዋሥ) ።

**ብሉሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ልሕት) ፤** የዳነ ፡ የወጣ ፡ ያመለጠ ። ብሉሕ ፡ እመቅሠፍት ፡ (አዋል) ።

**አስተባልሐ ፤ (አስደራጊና ፡ አደራራጊ) ፤** አስዳነ ፡ አስቤዠ ፤ አስወጣ ። አዳዳነ ፡ አዋጣ ፡ ዐገዘ ፡ ረዳ ፡ ለማዳን ፡ ለማውጣት ። እስመ ፡ ኢያስተባልሐከ ፡ እግዚ ፡ (መቃ ፡ ገ፳፭) ።

**ቤልሖር ፤ (ጽር ፡ ቤሊአር ። ዕብ ፡ ብሊያዐል) ፤** ሰይጣን ፤ የሰይጣን ፡ ስም ፤ ለሰውም ፡ ይኾናል ። ክፉ ፡ ጥፉ ፤ ልክስክስ ፡ ምናምንቴ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ቀንበር ፡ ሰባር ፡ ዳንደ ፡ ወንበዴ ፡ ቀማኛ ፡ ሽፍታ ፡ ማለት ፡ ነው ። መኑ ፡ ዘያንብሮ ፡ ለክርስቶስ ፡ ምስለ ፡ ቤልሖር ። ወኢይኩንዎሙ ፡ መንፈሰ ፡ ቤልሖር ፡ (፪ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፭ ። ክፋ ፡ ፩) ።

(ሀ) **በሊኅ ፤ ኖት ፤ (በልኀ ፡ ይበልኅ ፡ ይብላኅ) ፤** መብላት ፤ መስላት ፤ መሾል ፡ መፍጠን ፡ ስል ፡ ሹል ፡ ፈጣን ፡ መኾን ። ይበልኅ ፡ እምሰይፍ ። ሚ ፡ ይበልኅ ፡ እምሠርት ። በልኃት ፡ ኩናት ፡ (ዕብ፬ ፡ ፲፪ ። ፈላ፩ ። ሕዝ፳፩ ፡ ፲፩) ። ይበዝኅ ፡ ይጸንዕ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይበልኅ ፡ ይላል ፡ (ዘዐ፲፱ ፡ ፲፱) ።

—፤ መበለኅ ፤ ብልኅ ፡ ዐዋቂ ፡ መኾን ፡ መባል ፡ እንጂ ፡ ምላጭ ፡ ነው ፡ እንዲሉ ፡ (ዐማርኛ) ።

(ጥ) **በሊኅ ፤ (ኃን ፡ ኃት ፡ ላኅ) ፤** የበላ ፡ የሰላ ፡ የሾለ ፡ ስል ፡ ሹል ፡ ትብ ፤ ደፋር ፡ ፊደኛ ፤ ፈጣን ፡ ብልኀተኛ ፤ ጽሩይ ፡ ረቂቅ ። መላጺ ፡ በሊኅ ። ሰይፍ ፡ በሊኅ ። ቀኖት ፡ በሊኅ ። ዘያንኝው ፡ በሊኃን ። ሰባራቱ ፡ ማህው ፡ በሊኃት ። በበሊኅ ፡ ልሳን ። ብእሲ ፡ በሊኅ ፡ በምግባሩ ። በሊኅ ፡ እገሪሆሙ ፡ ለከዒወ ፡ ደም ። በበሊኅ ፡ ዐይን ፡ ልብክን ፡ ትነጽሩ ፡ (መገ ፡ ፶፩ ። ራእ፩ ፡ ፲፮ ። ግብ፱ ፡ ፳ ። አርጋ ። ሚራግ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ መጋ፱ ። ምሳ፳፪ ፡ ፳፱ ። መዝ ፡ ፳ ። ቄር) ። በበላኅ ፡ ፈንታ ፡ ብልኀት ፡ ይላል ፡ አያስኬድም ። ዘሩን ፡ መስሎ ፡ የሚገኝ ፡ ቅጽል ፡ ኀጺር ፡ ንዑኅ ፡ ገዚፍ ፡ ጸሊም ፤ ወቢብ ፡ ሐኪም ፡ ጸቢብ ፡ ርሒብ ፡ ረቂቅ ፡ ቀጢን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ መንገዱ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ከብዙዎች ፡ በቀር ፡ ሳንዲቱ ፡ ሴት ፡ ምእላድ ፡ የላትም ። ቅጽልንቱም ፡ ማልስና ፡ ሳድስ ፡ ያለበት ፡ ቱሱሕ ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ኀጻሬ ፡ ንዋኂ ፡ ገዛፊ ፡ ጸላሚ ፡ ጠባቢ ፡ ረቃቂ ፤ ወይም ፡ ኀጢኣ ፡ ጥቡብ ፡ ርቁቅ ፡ ቅጡን ፡ አያስኬድም ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ማልስ ፡ ትቶ ፡ በሳድስ ፡ ብቻ ፤ ኅጹር ፡ ግዙፍ ፡ ጽሉም ፡ እያለ ፡ ይገኛል ።

**ብልኅ ፤ (ኃት) ፤** ስለት ፡ ሹለት ፡ የሰይፍና ፡ የጦር ፡ አፍ ፡ እንደበት ። ብልኀ ፡ ሰይፍ ፡ ትነድድ ። ቅትሎሙ ፡ በብልኀ ፡ ሰይፍ ። በብልኀ ፡ ሰይፍ ፡ እሙንቱ ፡ ረከቡ ፡ አከሊሰ ። ብልኀ ፡ ኩናት ፡ ዘተረግዘ ፡ ቦቱ ፡ እግዚእነ ። በብልኀ ፡ ኩናት ፡ ገቦሁ ፡ ደጉጸ ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ። አፈ ፡ ተ፲፩ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳ ። ግንቦ፳፫) ።

**ብልኅ ፤ (ዐማርኛ) ፤** በቁሙ ፡ አስተዋይ ፡ ዐዋቂ ።

**ብልኀት ፤** በቁሙ ፡ መስላት ፤ መሾል ፡ መፍጠን ፡ አሰላል ፡ አሿሿል ፡ አፈጣጠን ፤ ስለት ፡ ሹለት ፡ ፍጥነት ፡ ብልኅነት ፡ ፈጣንነት ። ወእምቅድመ ፡ ያስተርኢ ፡ ብልኀተ ፡ መብረቅ ፤ ስለቱ ፡ ፍጥነቱ ፡ ብልጭታው ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**አብልኀ ፤** አበላ ፡ አሰላ ፡ አሾለ ፡ አፈጠነ ፡ አሰፈጠነ ፡ ብልኅ ፡ አደረገ ። ኀጺን ፡ ለኀጺን ፡ ያበልኆ ። አብልኀ ፡ ጸራቢ ፡ ኀጺነ ። ያበልኅ ፡ መዐት ፡ ሰይፈ ፡ መቅሠፍ ። አብልኁ ፡ ልሳኖሙ ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፵፬ ፡ ፲፪ ። ዘክሌ ፡ ፳፩ ። ጥበ፭ ፡ ፳፩ ። መዝ ፡ ፻፴፱) ።

**መብልኂ ፤ ኅ ፤ (ኂት ፡ ኅያን ፡ ያት) ፤** የሚስል ፡ የሚያሾል ፤ ሳይ ፡ አሿይ ።

**መብልኅ ፤ ት ፤ (ብ ፡ መበልኃት) ፤** የብረት ፡ መሣሪያ ፡ ስለትና ፡ ሹለት ፡ ጥርስ ፡ ሴላም ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ያለው ። ካራን ፡ ቢላዎ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ወእምዝ ፡ አዘዞ ፡ ንጉሥ ፡ ለነሃቤ ፡ ኀጺን ፡

ከመ ፡ ይግበር ፡ መባልኅት ፡ ዘንቱ ፡ ግሩም ፤ መሳጺ ያት ፡ ዘእመት ፤ ሙቃኅት ፡ መስብረ ፡ ርእስ ፤ መጥ ወዬ ፡ ክሣድ ፤ መኊሥሥ ፡ ስነ ፡ መውፅኢ ፡ ዐይን ፡ መስረፈ ፡ እንፍ ፡ መቅድሐ ፡ እዝን ፤ ፈታሔ ፡ መለያ ልይ ፡ ምፍሓቅ ፡ ገበዋት ፡ ወመስብረ ፡ ብረክ ፡ ወመ ቀቅየ ፡ እምትንት ፡ ወሥርው ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፭) ።

**ምብላኅ ፤ (ኃት) ፤** መሳያ ፡ ማሽያ ፡ መሳል ፡ ሞረድ ፤ የመስለው ፡ ኹሉ ።

**ባሉጥ ፤ (ዐረ ፡ በሉጥ ። ሱር ፡ ባሉጣ) ፤** የዛፍ ፡ ስም ፡ ጥኑ ፡ ጠንካራ ፡ ዕድሜኛም ፡ ዛፍ ፡ ብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ የሚኖር ፡ ጥንካሬው ፡ ከዕፀዋት ፡ ኹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ስንጨቱም ፡ ከስሉም ፡ በውድ ፡ የሚሸጥ ። ዐብየ ፡ ብሎ ፡ በለጠ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ ድርጅኑና ፡ ባሳኑ ፡ ተመልከት ። ዕድሜያምነቱም ፡ ሊታወቅ ፡ በአብርሃም ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ ሳይደርቅና ፡ ሳይፈልስ ፡ ሳይገረሰስ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አለ ። ዛሬም ፡ ርሱ ፡ ስላረጀ ፡ ከዚያው ፡ ከሥሩ ፡ በርሱው ፡ አምሳል ፡ ፫ ፡ ዐጽቅ ፡ ያለው ፡ ጕንድ ፡ ወጥቶ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እየኼደ ፡ ያየዋል ። የሱፍንም ፡ በታሪክ ፡ ከጥንት ፡ ከፍጥረት ፡ የነበረ ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ፡ ይላል ። **ዐሥርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ዕፀው ፡ ባሉጥ ፤** (ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ሆሴ፬ ፡ ፲፫) ። ዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ዛፉን ፡ አሎን ፡ ብሎ ፡ ፍሬውን ፡ ብጓ ፡ ባሉጥ ፡ ይላል ።



ባሉጥ ፤

**በልይ ፤ የት ፤ (ባልየ ፡ ይበሊ ፡ ይብ ለይ ። ዕብ ፡ ባላህ ። ሱር ፡ ብሊይ ። ዐረ ፡ በ ሊየ) ፤** ማርጀት ፡ ማፍጀት ፡ መለወጥ ፡ መበሳሸት ፡ መ በስበስ ፡ መበጣጠስ ፡ ማለፍ ፡ መቅረት ፡ ማለቅ ፡ መፈ ረስ ፡ መጥፋት ፡ መቃጠት ፡ ዘንዱ ፡ ይብለይ ፡ ነው ፡ በ ለየ ፡ ካላ ፡ ይብሊ ፡ አያስኝም ፡ ኀረየንና ፡ ፈረየን ፡ ጸገ የን ፡ ተመልከት ። ዘሉ ፡ ዘነፍስ ፡ ይበሊ ፡ ከመ ፡ ል ብስ ። ዘሉ ፡ ግብር ፡ ይበሊ ፡ ወየኀልቅ ። በልየ ፡ ሥ ጋየ ፡ ወማእስየ ። ክብርየ ፡ ተወለጠ ፡ ወበልየ ። ወበ ልየ ፡ ነገር ፡ እምኔሆሙ ፡ (ሢራ፲፬ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ። ሰቈ፫ ፡ ፬ ። ዳን፲ ፡ ፰ ። ኢዮ፴፪ ፡ ፲፭) ።

**በላዪ ፤ (ዪት ፡ ዪያን ፡ ያት) ፤** የሚያረጅ ፡ የሚያልፍ ፡ የሚጠፋ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ግብር ፡ በላዪ ፡ ወዘይማስን ። ዓለም ፡ በላዪ ፡ (ጥበ፲፬ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ኅዳ፲፰) ።

**ብሉይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሊት) ፤** በቁሙ ፡ ያ ረጀ ፡ ያፈጀ ፡ አሮጌ ፡ አንቲክ ፡ ጥንታዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ የ ዱሮ ፡ የቀድሞ ፡ የፊት ፡ ሕግ ፡ ኪዳን ፤ መዋዕል ፡ ዘመን ፡ መማሪያ ፡ ልብስ ፡ መጽሐፍ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ብሉይ ፡ መጽሐፍ ። ብሉይ ፡ ብእሲ ። ሕግ ፡ ብሊት ። መጻሕ ፍት ፡ ብሊት ። ጳድቃን ፡ ብሊት ። ብሉያተ ፡ ረበይ ክን ፡ ለመዋዕልየ ፡ (ሮሜ፯ ፡ ፯ ። ኤፌ፬ ፡ ፳፪ ። ፈ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ ሐም፲፩ ። ነሐ፳ ። መዝ ፡ ፻፷) ።

**ብሉየ ፡ መዋዕል ፤** ዘመኑ ፡ ያረጀ ፡ ዘመን ፡ ያስረጀው ፡ የዘመን ፡ አሮጌ ፡ ሽማግሌ ፡ (ዳን፯ ፡ ፱) ።

**ብሉየ ፡ መዋዕልና ፤** ቀዳማዊነት ፡ ቅድምና ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ዘመን ፡ ሳይቈጠር ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ መኖር ። ዕሩያን ፡ በመለኮት ፡ ወበህላዌ ፡ ወበብሉየ ፡ መዋዕልና ፡ በባሕርይ ፡ በአካል ፡ በቅድምና ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**ብልየት ፤** ማርጀት ፡ እርጅና ፡ አሮጌነት ። ሐ ደሰ ፡ ለቤት ፡ እምብልየቱ ። ተሐደሳ ፡ እምብልየት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ። ርቱዕ ፡ ናስሕል ፡ እምላዕ ሌነ ፡ ዘንተ ፡ ብልየተ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ግንቦ ። አፈ ፡ ተ፲፬) ።

**አብለየ ፤** አስረጀ ፡ አሳለፈ ፡ አንቲክ ፡ አደረገ ። አብለይከኒ ፡ ከመ ፡ ዝቅ ። እፎ ፡ ትሬእያ ፡ ለዓለም ፡ ይቤ ፤ እንዘ ፡ ታበሊ ፡ ነፍሳተ ፡ ወትሐድስ ፡ ሥጋተ ፡ ወታኀልፍ ፡ መዋዕላተ ። ሐዳሲ ፡ አብለየታ ፡ ለቀዳ ሚት ፡ (ኢዮ፲፫ ፡ ፳፰ ። ፈላስ ፡ ገ፳፯ ። ዕብ፰ ፡ ፲፫) ።

**አብላዪ ፤ መብለዪ ፤ ልይ ፤** የሚያስረጅ ፡ የሚያደገድግ ፤ አሮጌ ፡ የሚያደርግ ።

**በሊል ፤ ሎት ፤ (በለ ፡ ይበልል ፡ ይብ ልል ፤ ትግ ፡ በለለ ። ዕብ ፡ ባላል) ፤** መብሰል ፡ ማ ብሰል ፤ ማጥፋት ፡ ማበላሸት ፡ መደባለቅ ፡ መዘበረቅ ፤ መ ቀላቀል ፤ ማመሳቀል ፡ መንከር ፡ ማራስ ፡ ማርጠብ ፡ ማ በስበስ ፡ ማማሰል ፤ መለወስ ። በልየና ፡ ብልበለ ፡ የዚህ ፡ ዐጽቆች ፡ ናቸው ።

**አብለለ ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፡ አበለለ ፡ ከንቱ ፡ አደ ረገ ። በለለ ፡ ዐጕልና ፡ ገቢር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በበለለ ፡ ፈንታ ፡ አብለለ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ከፀጠ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፲፩ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፲) ።

**አብላሊት ፤ (ዐማርኛ) ፤** በቁሙ ፡ ወይም ፡ አስብላቢት ፡ ታናሽ ፡ ቅጠል ፡ ሐረጋም ፡ እንደ ፡ ሳማና ፡ እንደ ፡ ደቢ ፡ የምትሰበልብ ፡ የምታንገበግብ ። ሥርወ ፡ አብላሊት ፡ (መጽ ፡ ፈው ። ትእ ፡ ጴጥ) ።

**ብሉል ፤ (ዕብ ፡ በሉል) ፤** ቅይጥ ፡ ውጥን ቅጥ ፡ ንክርት ፡ የራሰ ፡ የለዘዘ ፡ ርጥብ ።

**ብልበለ ፤ (የበልየና ፡ የበለ ፡ ዲቃላ ። ዕብ ፡ ባልቤል) ፤** አረጀ ፡ አፈጀ ፡ ዐለቀ ፡ ተበጣጠሰ ፡ የልብስ ፡ የምንጣፍ ፡ የመማሪያ ። በልይንና ፡ በሊልን ፡ ተመልከት ።

**ብልባሌ ፤** ማርጀት ፡ ማለቅ ፡ እርጅና ፡ እሮጌ ነት ። ብልርቅ ፡ አሮጌ ፡ ማቅ ፡ ዕላቂ ፡ ውዳቂ ፡ ቍርንራፊ ፡

ቅርንጫቡ ፡ የሐዘን ፡ የድኽነት ፡ ልብስ ። ወአፍቀንተክሙ ፡ ብልባሌ ፡ ውስተ ፡ ሐቌክሙ ፡ (ዓሞ፰ ፡ ፲ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፲፱ ። ጥበ ፡ ጠቢ ። አርጋ ፡ ፯) ።

**እንበልበለ** ፧ እንበገበገ ፡ ተንበገበገ ፤ በግ ፡ በግ ፡ ቢል ፡ ቢል ፡ አለ ፡ ነደደ ፡ ተቃጠለ ። እንበልብል ፡ ል ሳኖ ፡ ለገብርከ ። እንተ ፡ ሠረቀ ፡ ዲቤኪ ፡ ወእንበል በለ ፡ ዋዕዩ ። ዘያንበለብል ፡ ነዱ ። እሳት ፡ ዘያንበለ ብል ። እፍኣም ፡ ዘያንበለብል ፡ (ደራሲ ። ሰንክ ፡ ጥቅ ፳፭ ። ሆሴ፯ ፡ ፬ ። ዘፀ፲፱ ፡ ፲፯ ። ዳን፯ ፡ ፱) ። ደገመ ፡ አነበበ ፡ ቢሉ ፡ እንበለበለ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ ቅብትን ፡ ፍጥንትን ፡ ሙቀትን ፡ ያሳያል ።

**እንብልቡል** ፧ (ላን ፡ ላት ፡ ብልት) ፧ የሚንበለበል ፡ የሚቃጠል ፡ በግ ፡ በግ ፡ የሚል ። ክመ ፡ እሳት ፡ እንብልብልት ፡ (ፊልክ ፡ ፻፶፫) ።

**ነበልባል** ፧ (ላት) ፧ በቁሙ ፡ የእሳት ፡ ላንቃ ፡ ነዲዱ ፡ ብርሃኑ ፡ ወላፈኑ ። ነበልባል ፡ ዘእንደ፡ድክሙ ። ነበልባለ ፡ እሳት ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተባየጽክ ፡ ጳጦስ ፡ (ኢ ሳ፵ ፡ ፲፩ ። ዮኤ፩ ፡ ፲፱ ። ደራሲ) ።

**ነበልባላዊ** ፧ እሳታዊ ፡ የእሳት ፡ እሳታም ፡ እ ሳትማ ። ነበልባላዊት ፡ ጽዮን ፡ እመ ፡ ገሥጸቶ ፡ ተዋ ረደ ፡ ወኀደገ ፡ ቤቶ ፡ (ቅኔ) ።

**ብለኔ** ፧ (ጽር ፡ ባላኔዎን ። ዐረ ፡ ሐማም) ፧ መታጠቢያ ፡ መንከሪያ ፡ የውሽባ ፡ ቤት ፡ ፍል ፡ ውሃ ፡ ወ ይም ፡ ዐጣቢው ፡ ባለቤቱ ። ኢይበእ ፡ ቤተ ፡ ብለኔ ። ይ በውእ ፡ ቤተ ፡ ብለኔ ። ዘይትኄፀብ ፡ ምስለ ፡ እንስት ፡ በቤተ ፡ ብለኔ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፳ ። ቀሌ ። ቀኖ ፡ ሎዶ ፡ ፳፱) ።

**በሊን ፡ በሊኖ** ፧ (ዕብ ፡ ባልናር) ፧ ልብስ ፡ ቤቶ ፡ ምጣግብ ፡ ጠጕሬም ፡ ፎጣ ፡ ታላቅ ፡ መንዲል ፡ መክሬ ፡ ሠርመዱ ። በሊን ፡ ዘፀምር ። በሊኖ ፡ (አቡሻ ፡ ፶ ። ቢኖዶ) ።

**ባላን** ፧ (ጽር ፡ ባላኖስ ። ዕብ ፡ አሎን ። ዐረ ፡ በሎጥ) ፧ የዛፍ ፡ ስም ። ድርስንና ፡ ባሎጥን ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ፡ ባሉብሉዮች ፡ ግን ፡ ማ ፉር ፡ ይሉታል ። ታሕተ ፡ ዕፀ ፡ ባላን ፡ (ዘፍ፴፭ ፡ ፰ ። መሳ፱ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፲፫) ።

**ብሌን** ፧ (ዐረ ፡ ሚል ። ጽር ፡ ሚሊ) ፧ የኩል ፡ መኳያ ፡ ማር ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ለዚሁ ፡ ብቻ ፡ የተሠራ ። ያይንን ፡ ማሚቶ ፡ ብረቲቱን ፡ ብሌን ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። እንዳይን ፡ ብሌን ፡ ይጠብቅኝ ፡ እንዲሉ ። አይርባሬት ፡ ዘሕል ፡ የኀልቁ ፡ በብሌን ፡ ወ ከማሁ ፡ ዐይሜሁ ፡ ለብእሲ ፡ በዕለታት ፡ (ትእ ፡ ጴጥ) ።

— ፧ ስሙ ፡ ነገድ ፡ ቋንቋ ፡ በሐማሴን ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ያለ ።

**በሊዕ ፡ ዖት** ፧ (በልዐ ፡ ይበልዕ ፡ ይብ ላዕ ። ዕብ ፡ ባላዕ ። ሱር ፡ ብላዕ ። ዐረ ፡ በሊዐ ፡ ዋጠ) ፧ መብላት ፡ መጕረሥ ፡ መንከስ ፡ መጋጥ ፡ መጣ መጥ ፡ ማላመጥ ፡ መዋጥ ፡ መሰልቀጥ ፡ ምግብን ፡ በገዛ ፡ እጅ ፡ ሰፊኒና ፡ ተቀብሎ ፡ መኾን ፡ መዝገብ ፡ መሰብሰብ ፡ መቀበል ፡ መክተት ፡ የሕያው ፡ ፍጥረት ፤ እከለን ፡ እዶ ። በሊዐ ፡ ወሰትዮ ። ያደዊ ፡ ብዝኃ ፡ በሊዕ ። ብላዕ ፡ በ ዐቅም ፡ (መክ፳ ፡ ፲፯ ። ሚሬ፴፯ ፡ ፴ ። ምሳ፳፭ ፡ ፲፯) ።

—፧ ማቃጠል ፡ ማንደድ ፡ መፍጀት ፡ ማረድ ፡ ማጥፋት ፡ መጕዳት ። በልዐቶሙ ፡ እሳት ። በልዐቶሙ ፡ መጥባ ሕት ። ፈኖከ ፡ መዐተከ ፡ ወበልዖሙ ፡ ከመ ፡ ብርዕ ። ቅንአተ ፡ ቤትከ ፡ በልዐኒ ፡ (ሆሴ፯ ፡ ፯ ። ኢር፪ ፡ ፴ ። ዘፀ ፲፭ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፷፰) ።

—፧ ማማት ፡ መንቀፍ ፡ መቀማት ፡ መዝረፍ ። በሊዐ ፡ ሥጋ ፡ ቢጽ ፡ በሐሜት ። በልዕዎ ፡ ለእስራኤል ። ይበ ልዑ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ (ቀሌ ። ኢር፲ ፡ ፳፭ ። ሚ ክ፫ ፡ ፫) ።

**በላዒ** ፧ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት ፡ ላዕት) ፧ የሚበላ ፡ የሚያቃጥል ፡ በላተኛ ፡ ሆዳም ፡ አጥፊ ፡ ዘራፊ ። ይወድቅ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ በላዒ ። በላዒት ፡ ሰብእ ፡ አ ንቲ ። ነበልባለ ፡ እሳት ፡ በላዒ ። ሥሡዓን ፡ በላዕያን ። በላዕተ ፡ ሰብእ ፡ (ናሆ፫ ፡ ፲፪ ። ሕዝ፴፯ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፮ ። መቃ ፡ ፲፱ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**አብልዐ** ፧ አበላ ፡ አስበላ ፡ አጕረሠ ፡ አዋጠ ፡ አስዋጠ ። ለእመ ፡ ርኅበ ፡ ጸላኢከ ፡ አብልዖ ። አኑ ፡ አብ ልዖሙ ፡ ጻዕረ ። አብልዐኒያ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ። ለእመ ፡ አብልዐ ፡ ገራህተ ፡ ሰብእ ፡ እንስሳሁ ፡ (ምሳ ፳፭ ፡ ፳፩ ። ኤርም ፡ ፲፭ ። ሕዝ፫ ፡ ፪ ። ዘፀ፳፪ ፡ ፬) ።

**መብልዕ** ፧ (ብ ፡ መባልዕት) ፧ በቁሙ ፡ መ ብል ፡ ምግብ ፡ ሲሳይ ፡ አፍን ፡ መንገድ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ሆድ ፡ የሚገባ ፡ ኹሉ ። ለክሙ ፡ ውእቱ ፡ መብልዕ ። ወሀቡ ፡ ፍትወቶሙ ፡ ለመብልዕ ። ግበር ፡ መባል ዕተ ፡ ቅብዕ ። መባልዕት ፡ ጥዑማት ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፳፱ ። ሰ ቈ፭ ፡ ፲፩ ። ኩፋ ፡ ፳፯ ። ቀሌ ። ፪ዜና ፡ ፲ ፡ ፳፱) ። መብ ልዕ ፡ መባልዕት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ብልዕ ፡ ብልዓት ፡ ይ ላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ምብላዕ** ፧ (ዓት) ፧ መብያ ፡ ማብያ ፡ መበያ ፡ ቦታ ፡ ዕቃ ፡ ወጥ ፡ እፍ ።

**ተበልዐ** ፧ ተበላ ፡ ተበላላ ፡ ተዋጠ ፡ ተቃጠለ ። ይትበላዕ ፡ እክል ። ልብስ ፡ ዘተበልዐ ፡ እምቍንቍኔ ። ተበልዑ ፡ እምዓሣት ። በእሳት ፡ ይትበላዕ ፡ (ኢዮ፯ ፡ ፯ ። ፲፫ ፡ ፳፰ ። ሐዋ፲፪ ፡ ፳ ። ሰንክ ፡ ህዳር፳) ።

**ብሉዕ** ፧ (ዓን ፡ ዓት ፡ ልዕት) ፧ የበላ ፡ የበ ገበ ። የተበላ ፡ የተቃጠለ ፡ (ሂሮማ ፡ ገ፳፯—፳፱) ።

(ጥ) **ብላዕ** ፧ (ዓት) ፧ ብላቶ ፡ ቅራሪ ። ብላዐ ፡ አ ርዌ ። ብላዐ ፡ ቍንቍኔ ። ብላዐ ፡ ፀፄ ፡ (ዘሌ፳ ፡ ፲፮ ። ፯ ፡ ፳፱ ። ኢዮ፳፯ ፡ ፲፰ ። ናሆ፩ ፡ ፲) ። በብላዕ ፡ ፈንታ ፡ ብ ልዕ ፡ ይባል ፡ እየሰኘም ።

**ብልዐት** ፧ መብላት ፡ መበላት ፡ አበላል ። ብል ዐተ ፡ እክል ። ለብልዐት ። ብልዐተ ፡ ፀፄ ፡ ረከቦሙ ፡ (መዝ ፡ ፶፱ ። ኩፋ ፡ ፳፫ ። ኢዮ፲ ፡ ፲፱) ።

**ተበልዐ** ፤ ተባላ ፡ ተናከሰ ፡ ተታማ ፡ (ገላ፭ ፡ ፲፭ ። ኩፋ ፡ ፳) ። እንዘ ፡ ይትባልዑ ፡ ሥጋሆሙ ፡ በበ ይናቲሆሙ ፡ (ሔኖ፯ ፡ ፭) ።

**አስተባልዐ** ፤ አባላ ፡ አናከሰ ፡ አፋጀ ፡ አስተላ ለቀ ።

**በሊቅ** ፤ **ቆት** ፤ **(በለቀ ፡ ይበልቅ ፡ ይብ ልቅ ፤ ትግ ፡ በልቀ ። ዕብ ፡ ባላቅ ፤ ለየ ፡ ከፈለ)** ፤ መበለቅ ፡ ለዘር ፡ መብቃት ፡ ማደግ ፡ መጐልመስ ፤ በሕ ልም ፡ ወይም ፡ በውን ፤ ዘር ፡ ማናከስ ፡ ሴት ፡ መዳሰስ ።

**ብሉቅ** ፤ **(ቃን ፡ ቃት ፡ ልቅት)** ፤ የባለቀ ፤ ያደገ ፡ የላቀ ፡ ለዘር ፡ የበቃ ። (ተረት) ፡ የታጠበ ፡ እጅ ፡ ያልባለቀ ፡ ልጅ ።

**ባላቅ** ፤ **(ትግሬ)** ፤ ብዙ ፡ ደንጊያ ፡ ጕር ፤ የደ ንጊያ ፡ ክምር ፤ ገምቻ ፤ ቋጥኝ ፡ ኰኵሕ ፤ አለት ። የሰው ፡ ስም ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጡ ፡ ከፋሊ ፡ ነግቲ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘኍ፳፪ ፡ ፭) ።

**ባላቅ** ፤ **(ብ ፡ አብላቅ ። ጽር ፡ ፕላኬስ)** ፤ የደንጊያ ፡ ሰሌዳ ፡ ገበታ ፡ ጽሌ ። ወአልቦ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ታቦት ፡ ዘእንበለ ፡ ክልኤቱ ፡ አብላቅ ፡ ዘአንበረ ፡ ሙሴ ፡ በደብረ ፡ ኰሬብ ፡ (፪ዜና ፡ ፭ ፡ ፲) ።

**ባላቅ** ፤ **(ዐረ ፡ ሩኃም ። ዕብ ፡ ሽይሽ ። ጽር ፡ ማርማሩ)** ፤ ነጭ ፡ ደንጊያ ፡ እብነ ፡ በረድ ። አ ዕማደ ፡ ባላቅ ። ንጹሕ ፡ ወባላቀ ፡ (ማሕ፭ ፡ ፲፭ ። ራእ ፲፰ ፡ ፲፪) ።

**ባላቅ** ፤ **(ዕብ ፡ ሾሀም ። ጽር ፡ ኦኒኪ)** ፤ ክቡር ፡ ደንጊያ ፡ ዕንቍ ። እንከየማንና ፡ ሰምን ፡ ስርድ ዮንን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ኢበባላቅ ፡ ቅድው ፡ ወኢበሰንፔር ። እምኅበ ፡ አብላቅኑ ፡ አው ፡ እምኅበ ፡ አእባን ፡ (ኢዮ፳፰ ፡ ፲፮ ። ኦሪ ፡ ድ፭) ።

**በልቀም** ፤ **(ዐረ ፡ በልዐም)** ፤ መፈታዊ ፡ ባ ሕርይ ፤ የሚገለ ፡ የሚደክም ፡ የሚተኛ ፡ የሚጋደም ። ላሕስሐን ፡ ተመልከት ፡ (ፈላስ ፡ ገ፲፯) ።

**ብሉር** ፤ **(ዐረ ፡ በሉር ። ሱር ፡ ቤሉራ ። ጽር ፡ ቢረሊ.ምን)** ፤ ብርሌ ፡ ብርጭቆ ። ዕንቍ ፡ ፈ ርጥ ፡ የብርሌ ፡ ዐይነት ፡ (ክብ ፡ ነገ ፡ ፲፯) ። ቢረሌን ፡ ተ መልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**በለስ** ፤ **(ብ ፡ በለሳት ፤ አብላስ ። ዐረ ፡ በ ለስ ። ዕብ ፡ ባላስ)** ፤ በቁሙ ፡ የተክል ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፤ ከወይን ፡ ጋራ ፡ የሚተከል ፡ የሾላ ፡ ወገን ፡ ወተ ታም ። ዕንጨቱም ፡ ፍሬውም ፡ በለስ ፡ ይባላል ። ዘተከለ ፡ በለሰ ፡ ይበልዕ ፡ ፍሬሃ ። እምበለስ ፡ አእምሩ ፡ አም ሳሊሁ ። ቦ ፡ በለስ ፡ እምርት ፡ ውስተ ፡ ዐጸደ ፡ ወይን ። አውያን ፡ ወአብላስ ፤ ዛፍ ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፲፰ ። ማቴ፳፬ ፡ ፴፪ ። ሉቃ፲፫ ፡ ፮ ። መጽ ፡ ምስ) ። ረከቡ ፡ በምሥያጥ ፡ በለሰ ፡ ሐዲሰ ፡ ወተሣየጡ ፡ እምኔሁ ። ረከበ ፡ እ ሉ ፡ በለሳተ ፡ ሐዲሳተ ። ወመልእት ፡ ጽፍንታ ፡ ጥ ሑተ ፡ ወበለሰ ፤ ፍሬ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ፱ ። ራእ ፡ ባሮ ። ዮዳ፲ ፡ ፳) ። በለስ ፡ ፍሬ ፡ በለስ ፡ በኸረ ፡ በለስ ፡ በማ ለት ፡ ፈንታ ፤ ዐጽቀ ፡ በለስ ፤ በለስ ፡ ማእረር ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ኤር፳፬ ፡ ፪) ። ዳግመኛም ፡ በሰግላ ፡ ፈ ንታ ፡ በለስ ፡ ይላል ፤ ሰግላን ፡ ተመልከት ። ዕፀ ፡ በለስ ። ተቃራሚ ፡ በለስ ፡ ሾላ ፡ (፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፳፯ ። ዓሞ፯ ፡ ፲፬) ።

**በለሰን** ፤ ዕፀ ፡ አእምሮ ፤ የገነት ፡ በለስ ፤ አዳ ምና ፡ ሔዋን ፡ ፍሬውን ፡ በልተው ፡ ቅጠሉን ፡ የለበሱት ፤ ኋላም ፡ የልደት ፡ ለት ፡ በታምራት ፡ መልአክ ፡ አምጥቶ ላት ፡ ዳግሚት ፡ ሔዋን ፡ ለልጇ ፡ ለዳግማይ ፡ አዳም ፡ ያለበሰችው ። ከደነቶ ፡ እሙ ፡ ቈጽለ ፡ በለሰን ፡ (ድጓ ። ኵፋ ፡ ፫ ። ዘፍ፫ ፡ ፯) ። *(ሥላሴ ፡ ቅኔ)* ፤ በለሰ ፡ ገነት ፡ ለአዳም ፡ ወሔዋን ፡ መቲሮቶሙ ፡ መንክረ ፡ ልደት ፡ አምላክ ፡ መንግሌሆሙ ፡ ሰሐበ ፤ ወገብርኤልሀ ፡ ዜ ናዊ ፡ ቀጸበ ። አንተ ፡ ከመ ፡ ዝሰ ፡ ግብር ፡ እምከመ ፡ ለአዳም ፡ ተውህበ ፥ ወረከበት ፡ ሔዋን ፡ ዘኢተረ ክበ ፥ ካዕበ ፡ ይስሐብ ፡ ኀቤሆሙ ፡ አበ ፥ ለበለሰ ፡ ይምትርዎ ፡ ካዕበ ።

**በለሳን** ፤ **(ዐረ ፡ በልሳን ። ዕብ ፡ ባሳም ። ጽር ፡ ሚራ ። ሮማይ ፡ ባልሳሙም)** ፤ ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፤ በይሁዳና ፡ በገሊላ ፡ ይልቁንም ፡ በኢ ያሪኮ ፡ የሚበቅል ፤ ከዕፀው ፡ ዕጣን ፡ አንዱ ፡ መዠመሪ ያው ፤ ሽታው ፡ ከሽቱ ፡ ዕንጨት ፡ ኹሉ ፡ የሚበልጥ ፤ ጸ ደሳት ፡ ቅብዐ ፡ ቅዱስ ፡ ሜሮን ፡ የሚያደርጉት ። ዝንቱ ፡ በለሳን ፡ ዘተከልናሁ ፡ ይነብር ፡ ዝየ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ። ቅብዐ ፡ በለሳን ። በእንተ ፡ በለሳን ፡ ወዕጣን ። ተኝ ትመ ፡ ገጸ ፡ በቅብዐ ፡ በለሳን ። በለሳኒ ፡ ከነ ፡ ሀፊ ፡ ሥ ጋሁ ፡ በቍስሉ ፡ (ስንክ ፡ ማግ፳፱ ። ዲድ ፡ ፲፯ ። ቅዳ ። ግ ንዘ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፲፯ ። ደራሲ) ።



በለሳን ፤

(ጥ) **በልቶ** ፤ **ቶት** ፤ **(በለተ ፡ ይቤልት ፡ ይብ ልት ። ዐረ ፡ በለተ ፤ ቈረጠ ። ዕብ ፡ ቢልቲ ፤ ብቻ ፡ ያለ)** ፤ መበለት ፤ መለየት ፡ መነጠል ፤ ሥጋን ፡ በሆብልቱ ፡ ማውጣት ። ማዶኸየት ፤ ድኻ ፡ ብቸኛ ፡ ማድ ረግ ፡ ብቻ ፡ ማስቀረት ።

**በላቲ** ፤ **(ቲት ፡ ትያን ፡ ያት)** ፤ የሚበልት ፡ በላች ፡ በጋማች ፡ ሥጋ ፡ ቤት ፤ ዐራጅ ፡ ባለወግ ።

**ብላታ** ፤ **ብላቴና ፡ ን** ፤ **(ዐማርኛ)** ፤ ሥል ጡን ፡ ለብቅል ፡ አሽከር ። ብላቴን ፡ ጌታ ፤ እግዚእ ፡ ሥ ሉጥ ፡ መልአክ ፡ ምክር ፤ መጋቢ ።

**ተበለተ** ፤ በቁሙ ፡ ተለየ ፡ ተንጠለ ፡ ደኸየ ፡ ብቸኛ ፡ ኾነ ፡ ብቻውን ፡ ቀረ ፡ እንደ ፡ ናሖሚን ፡ (ሩት ፩ ፡ ፭) ።

**ብሉት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ልት)** ፤ የተበለተ ፡ የተለየ ፡ ልዩ ፡ ብቸኛ ።

**መበለት ፤ (ታት)** ፤ ድኻ ፡ ብቸኛ ፡ ሴት ፡ በሉቱ ፡ ባሏ ፡ የሞተባት ፡ በጋማች ፡ ሥጋን ፡ ከሥጋ ፡ እንዲለይ ፡ ሞት ፡ ከባሏ ፡ የለያት ፡ የነጠላት ። መንክር ሲት ፡ (ዘሌዋ ፡ ፳፩ ። ማቴ ፳፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭) ። **ኢይደክሙን ፡ መበለተ ፡ ወኢይሬእዩ ፡ ላሐ ። ለብሰት ፡ አልባሰ ፡ መበለታ ። ወነበረት ፡ መበለተ ። መበለት ፡ ዕቤር ። ወለኂሩሳትስ ፡ መበለታት ፡ ተገሐሥኚ ። መነኮሳት ፡ ወመበለታት** ፡ (ፊልጵ ፡ ፩ ። ዘዳግ ፡ ፲፬ ። ፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፩ ። ፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ መጋ ፳፰) ።

**ብልቴት** ፤ ብልሬት ፡ እዝብት ፡ ሥጋ ፡ የሚቈርጥ ፡ የሚበልት ፡ ብለታም ፡ ደንጊያ ፡ ጎዝጎን ፡ እይ ።

**ብላቴንዓሽ ፤ (ዐረ ፡ በናት ፡ ነዕሺን)** ፤ ብላት ፡ በናት ፡ እዋልድ ፡ ታናናሽ ፡ ከዋክብት ፤ ጎዓሽ ፡ ነዕሺን ፡ ታላቅ ፡ አባት ፡ ኮከብ ፡ ወዐ ፡ የሚባል ፡ ባለብዙ ፡ ጭፍራ ። ባለብለዮች ፡ ጩረታ ፡ ይኸታል ። **ተአምርኑ ፡ ጊዜሃ ፡ ለብላተንዓሽ** ፡ (ኢዮ ፴፰ ፡ ፴፪) ። ስብሬ ይስጡ ፡ ግን ፡ **ታወፅእኑ ፡ ማዛሮተ ፡ በጊዜሁ ፡ ወትመርሖኑ ፡ ለዐይሽ ፡ ምስለ ፡ አዋልዲሁ** ፡ ይላል ፡ ማዛሮት ፡ መገብተ ፡ አውራኅ ፡ ናቸው ።

**ባማ ፤ (ዕብራ)** ፤ የበታ ፡ ስም ፡ ልዑል ፡ አዳጋ ፡ ቍሲልታ ፡ ተራራ ፡ ኰረብታ ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ የተሠራ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ምሥጢ ፡ ጣዖት ፡ የመቃብር ፡ ቤት ። ባማ ፡ ለርኩስ ፡ እንጂ ፡ ለቅዱስ ፡ አይነገርም ፡ ሲያበዛ ፡ ባሞት ፡ ይላል ። **ምንት ፡ ውእቱ ፡ ባማ ፡ ዘተሐውሩ ፡ አንትሙ ፡ ህየ ፡ ወተሰምየ ፡ ስሙ ፡ ባማ** ፡ (ሕዝ ፳ ፡ ፳፱) ።

**በኑ ፤ (በ ፡ ኑ)** ፤ በውኑ ፡ አለን ። በሁን ፡ ተመልከት ፡ ፍችው ፡ ከዚያ ፡ አለልኽ ።

**ብናሴ** ፤ ጩረቃ ፡ የጩረቃ ፡ ስም ። እብላንና ፡ እራብን ፡ ተመልከት ።

(ቀ) **በንቶ ፤ (በነተ ፡ ይቤንት ፡ ይበንት) ፤ አው ፡ በኒት ፤ ቶት ፤ (በነተ ፡ ይበንት ፡ ይብንት ። ዕብ ፡ ማናህ)** ፤ መስጠት ፡ ማደል ፡ መገበር ፡ በፍትርና ፡ በክብር ፡ በፈቃድ ። ዐሥራት ፡ ማውጣት ። ሴት ፡ ልጅ ፡ መውለድ ፡ በሴት ፡ መበከር ። **ወለዘሂ ፡ ጸባሕተ ፡ ጸብሖ ፡ ወለዘሂ ፡ ብንተ ፡ በንቶ** ፡ ዐሥራት ፡ ዐሥራ ፡ (ሮሜ ፲፫ ፡ ፯) ።

**ብንት ፤ (ዕብ ፡ ምናት ። ሱር ፡ ምናታ ፤ ክፍል ፡ ዕድል)** ፤ ዐሥራት ፡ እጅ ፡ መንሽ ፡ በረከት ፡ በፈቃድ ፡ የሚሰጥ ፡ ስጦታ ፡ እንቍጣጣሽ ፡ ግብረ ፡ ስላም ፡ ያክፋይ ፡ የጠም ፡ ቁሎ ፡ የባል ፡ ደሮ ፡ የሽማኄ ፡ የቀጥቃጭ ፡ የመጣፍ ፡ ገላጭ ፡ ይሆን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ (ጥበ ፲፱ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱) ።

**ብንት ፤ (ዕብ ፡ ባት ። ዐረ ፡ ቢንት ። ሱር ፡ ብዲታ)** ፤ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወለት ፡ እንስት ፡ ቈብ ፡ ልጃገረድ ።

**ብንት ፤ (ዕብ ፡ ኢሾን)** ፤ ደይን ፡ ማሚቶ ፡ ጥቍሩ ፡ ብሬቱ ፡ ብሌን ፡ እንደ ፡ መስታዮት ፡ የሰው ፡ መልክ ፡ የሚታይበት ፡ ብርሃን ፡ የሚሣልበት ። **ዕቀበኒ ፡ ከመ ፡ ብንተ ፡ ዐይን ። ብንተ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ይሬኢ ፡ ጽልመተ ። ብንተ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ከመ ፡ ዥሕል ። ኢታረምም ፡ ብንተ ፡ ዐይንኪ** ፡ (መዝ ፲፮ ፡ ፰ ። ምሳ ፳ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ታኅ ፲፩ ። ሰቈ ፡ ፲፰) ።

(ጥ) **በሥሮ ፤ (በሠረ ፡ ይቤሥር ፤ ይበሥር) ፤ አው ፡ በሢር ፤ ሮት ፤ (በሠረ ፡ ይበሥር ፡ ይብሥር ። ዐረ ፡ በሺረ ። ዕብ ፡ ባሤር)** ፤ ማብሠር ፡ የምሥራች ፡ ማለት ፡ ሐዲስ ፡ የደስታ ፡ ወሬ ፡ ማውራት ፡ መንገር ፡ መልካም ፡ ትንቢት ፡ መናገር ። ሥጋ ፡ ማልበስ ፤ ሥጋው ፡ ማድረግ ፡ ምስጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ መስበክ ፡ ማስተማር ፤ በወሬ ፡ በትንቢት ፡ ማስረዳት ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ። መጻሕፍት ፡ ግን ፡ በበሠረ ፡ ፈንታ ፡ አብሰረ ፡ ይላሉ ፡ ባስደራጊና ፡ በሳቢ ፡ ስ ፡ አ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ፡ ሆኑ ፡ አመከ ፡ እንደ ፡ ማለት ። **ገብርኤል ፡ አብሣሬ ፡ ትስብእትከ ። አብሠራ ፡ ለማርያም ። አብሠሮ ፡ ለዘካርያስ ፡ በእንተ ፡ ልደቱ ፡ ለዮሐንስ ። ወንጌለ ፡ መንግሥት ፡ ያበሥር** ፡ (ቁድር ። መዋሥ ። ስንክ ፡ ታኅ ፳፪ ። ፊልስ) ። ብርስንና ፡ ምስር ፡ የሚጣፉ ፡ በሳት ፡ ሰ ፡ ነውና ፡ ሠወም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተሳስቷል ።

**በሣሬ ፤ መበሥር** ፤ የሚያበሥር ፡ አብሣሬ ፡ ወሬ ፡ ነጋሪ ፡ የምሥራች ፡ ባይ ። **ገብርኤል ፡ መበሥር** ፡ (ስንክ ፡ ታኅ ፳፪) ።

**አብሠረ ፤ አስተብሠረ** ፤ አስበሠረ ፡ ደግ ፡ ወሬ ፡ አሰማ ፡ አስነገረ ፡ ወሬኛ ፡ ላከ ።

**አብሣሬ ፤ መስተብሥር** ፤ የሚያስበሥር ፡ አስበሣሪ ፡ ወሬ ፡ አስነጋሪ ።

**ተበሥረ** ፤ በቁሙ ፡ ምሥራች ፡ ሰማ ፤ ሐዲስ ፡ ወሬ ፡ አገኘ ፡ ሰሙዋው ። ተወራ ፡ ተባለ ፡ ተነገረ ፤ ተሰበከ ፡ ወሬው ፡ ትንቢቱ ፡ የምሥራቹ ። **ስምዖን ፡ ዘተበሥረ ፡ ፀንሱ ፡ በአፈ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ። በከመ ፡ ተበሥረ ፡ እምእፈ ፡ ማርቆስ** ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ ፳፱ ። ሚያዝ ፳፱ ። መጋ ፳፰) ።

**ብሥራት ፤ (ታት)** ፤ በቁሙ ፡ ምሥራች ፡ ሐዲስ ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ወሬ ፡ ስብከት ፡ ትንቢት ፡ ወንጌል ፡ ትሥጉት ፡ ቃል ። **ብሥራተ ፡ እግዚ ፡ በልሳነ ፡ ገብርኤል ፡ ዘአብሠራ ፡ ለቅድስት ፡ ድንግል ። ብሥራተ ፡ ማቴዎስ** ፡ (አቡሻ ፡ ፴፰ ። ማቴ ፡ ፩) ። ብሥራትክ ፡ ኪ ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ፡ የምሥራች ፡ ደስ ፡

ይበልኽ ፡ ማለት ፡ ነው ። ብሥራትከ ፡ አ ፡ ንጉሥ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ። ኀኢብ ፡ አገባብ ፡ (ዕር፲ ፡ ቍ፻፲፩) ።



ብሥራት ፤

**ብሥራታዊ** ፤ ባለምሥራች ፡ ወንጌላዊ ፡ መናየ ፡ ዜና ። ሰላም ፡ ለከ ፡ ገብርኤል ፡ ብሥራታዊ ። አባ ፡ ብሥራታዊ ፡ ማርቆስ ፡ (ደራሲ ። አዑሻ ፡ ሂ) ።

**ባሦር** ፤ (ዕብ ፡ ባሣር ። ሱር ፡ ቤስራ) ፤ ሥጋ ፡ የሥጋ ፡ ክፍል ። ወገብረ ፡ ሰርእሱ ፡ ባሦረ ፡ ግሩመ ፡ ወለብሰ ፡ እምኔሃ ፡ ለድንግል ፡ (ቀሌ) ። ዐረቡ ፡ ማን ፡ በሽር ፡ እብን ፡ እልበሽር ፡ ብሎ ፡ ሰብእ ፡ ወልደ ፡ ሰብእ ፡ ይላል ።

**ባዕ ፤—ስንዝር ፤—በዊዕ ፡ ቦዐ ።**

**ብዒድ ፤ ዶት ፤ (በዐደ ፡ ይብዕድ ፡ ይብዐድ ። ዐረ ፡ በዒደ ፡ ራቀ)** ፤ ማባድ ፡ ባዕድ ፡ ማድረግ ፤ መለየት ፡ መንጠል ፡ ማራቅ ፡ ማስገለል ፡ መለወጥ ፡ መቀየር ፤ ሌላውን ፡ በሌላ ፡ ወይም ፡ ያንን ፡ አንዱን ፡ ከ ኀደ ፡ በትረ ፡ ሙሴ ። ዘአመ ፡ በዐደ ፡ ገጸ ፡ እምቅድሜሁ ፡ ለአቤሜሌክ ። አከ ፡ መዩጥ ፡ ርእሶ ፡ ወብዒድ ፡ እምፍጥረቱ ፡ (አርእስተ ፡ መገ ፡ ፴፫ ። መጽ ፡ ምስ) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በበዐደ ፡ ፈንታ ፡ አብዐደ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ሰብእ ፡ ከማነ ፡ ይሬስዮዎ ፡ ወያብዕድዎ ፡ ለምወልድ ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**በዓዲ** ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤ የሚለይ ፡ የሚያርቅ ፡ ባዕድ ፡ የሚያደርግ ።

**አብዐደ** ፤ አስለየ ፡ አስነጠለ ፡ አስራቀ ፡ ባዕድ ፡ አስደረገ ።

**ተብዕደ ፤ ተበዐደ** ፤ ተለየ ፡ ተነጠለ ፡ ራቀ ፡ ወገደ ፡ ባዕድ ፡ ኾነ ፤ ዝምድና ፡ ፀጣ ። ወረደ ፡ እንዘ ፡ ኢይትፈለጥ ፡ እምህላዌሁ ፤ ነገደ ፡ እንዘ ፡ ኢይትበዐድ ፡ እምሥላሴሁ ። ኢተበዐደ ፡ ወኢተፈልጠ ፡ በዘርኡ ፡ ግብሩ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ (ቅዳ ፡ አፈ ። ድጓ ። ኢሳ ፡ ፵) ።

—፤ ተሻረ ፤ ተለወጠ ፡ ተቀየረ ፤ ሌላ ፡ ኾነ ፡ ሌላ ፡ ተባለ ። ኢይትበዐድ ፡ እምሂመቱ ፡ ውስተ ፡ ካልእ ፡ ሂመት ። ኢተበዐደ ፡ እመለኮቱ ፡ ዘእግዚ ፡ ቃል ። እስመ ፡ ኢይትበዐድ ፡ ዘእግዚ ፡ ቃል ፤ አላ ፡ ለዝሉፉ ፡ ውእቱ ፡ ይሄሉ ፡ (ቀሌ ። ድጓ ። ቄር ፡ ጸላ ። እስት) ።

**ብዑድ** ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ዕድ) ፤ የተለየ ፡ ልዩ ፤ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሩቅ ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ። ዘከመ ፡ ተፈልጠ ፡ ማእከለ ፡ አሮን ፡ ወማእከለ ፡ ክርስቶስ ፡ ብዑድ ፡ ፈድፋደ ፤ ከማሁ ። ብዑዳን ፡ ብዙኃን ። ብዑድ ፡ ሥነ ፡ ላሕዩ ። ብዑድ ፡ እምኀሊና ፡ (አፈ ፡ ተ፲፩ ። ቄር ፡ እስት ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ባዕድ** ፤ (ድት ፡ ዳን ፡ ዳት) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፡ ቅጽልና ፡ ጥሬ ። በቁሙ ፤ ልዩ ፡ ሌላ ፤ ነኪር ። ባዕድ ፡ ሰብእ ። አልቦ ፡ ባዕድ ፡ ዘእንበሌሁ ። ይዘግብ ፡ ለባዕድ ። በብሔረ ፡ ባዕድ ። ወቦ ፡ ባዕዳንሂ ። ወባዕዳትኒ ፡ ብዙኃት ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፴፪ ። ዘዳ፲ ፡ ፴፭ ። ሚራ፲፬ ፡ ፬ ። ኤር፭ ፡ ፲፱ ። ግብ፲፯ ፡ ፴፬ ። ማር፲፭ ፡ ፵፩) ።

**ባዕድ ፡ (ጥሬ ፡ ዘር)** ፤ የፊደል ፡ ስም ፡ አገልጋይ ፡ ፊደል ፤ የጥሬ ፡ ዘር ፡ ተውሳክ ፤ ከቅጽል ፡ ከጥሬ ፡ እየተጨመረ ፡ መነሻ ፡ ኹኖ ፡ የሚነገር ። ባዕድ ፡ የሚኾኑ ፡ ፊደላት ፡ ዋነኞቹ ፡ ደ—፬ ፡ ናቸው ፤ አመቱን ፤ ማእዛቸው ፡ ብዙ ፡ ስለ ፡ ተነገረ ፡ ከነ ፡ በቀር ፡ ካዕባቸው ፡ ራብዓቸው ፡ ሳድሳቸውና ፡ ሳብዓቸው ፡ ተለይቶ ፡ አይቀርም ። አ ፡ የማድረግና ፡ የማስደረግ ፡ ልማድ ፡ እየኾነ ፡ በቀዳማይ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባና ፡ ወዲያው ፡ ለጥሬው ፡ ባዕድ ፡ ይኾናል ። (ማስረጃ) ፤ ርእየ ፡ አርአየ ፤ አርኣያ ። ከለለ ፡ አክለለ ፤ አክሊል ። መሰለ ፡ አምሰለ ፤ አምሳል ። ሰትዐ ፡ አስትዐ ፤ አስትዓ ። ገዘአ ፡ አግዝአ ፤ እግዚእ ። ለትሐ ፡ አልትሐ ፤ እልታሕ ። ነገደ ፡ አንገደ ፤ እንግዳ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። መ ፡ ባዕድ ፡ ሲኾን ፤ ቀደሰ ፡ መቅደስ ፤ ነበረ ፡ መንበር ፤ ደበለ ፡ መድበል ። ሙ ፤ ውሕዘ ፡ ሙሓዝ ፤ ወፅአ ፡ ሙፃእ ፤ ወረደ ፡ ሙራድ ። ማ ፤ አመረ ፡ ማእምር ፤ ሐበ ፡ ማሕየብ ፤ ሐረጸ ፡ ማሕረጽ ። ም ፤ ገብረ ፡ ምግባር ፤ ሖረ ፡ ምሕዋር ፤ ቆመ ፡ ምቅዋም ። ሞ ፤ ወሠረ ፡ ሞሠርት ፤ ወፈጠ ፡ ሞፈጥ ፤ ወፀፈ ፡ ሞፀፍ ፡ ይላል ። ሙና ፡ ሞ ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ መኾናቸው ፡ ወን ፡ ስለ ፡ ጕረዱ ፡ ነውና ፤ በወ ፡ ከሚነሣ ፡ ከወ ፡ ግስ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ አይገኙም ። ተ ፡ ደግሞ ፡ የመደረግና ፡ የመደራረግ ፡ ልማድ ፡ እየኾነ ፡ በቀዳማይ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባና ፡ እንደ ፡ አ ፡ ወዲያው ፡ ለጥሬው ፡ ባዕድ ፡ ይኾናል ፤ ይኸውም ፡ ጥሬ ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ ከሚመስለው ፡ እንጂ ፡ ከማይመስለው ፡ አንቀጽ ፡ እንዳይወጣ ፡ በግልጥ ፡ ያስረዳል ። (ማስረጃ) ፤ ገሠጸ ፡ ተገሠጸ ፤ ተግሣጽ ። ወለጠ ፡ ተወለጠ ፤ ተውላጥ ። ሜጠ ፡ ተመይጠ ፤ ተምይጥ ። ፈጸመ ፡ ተፈጸመ ፤ ተፍጻም ። ቀረመ ፡ ቀሠመ ፡ ተቀርመ ፡ ተቀሥመ ፤ ተቅሪም ፡ ተቅሣም ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ታ ፤ ሐጸ ፡ ተሓጸ ፤ ታሕጻጽ ። ኀሠ ፡ ተኀሠ ፤ ታኅሣሥ ። ኀመሰ ፡ ተኀመሰ ፤ ታኅማስ ። ት ፤ መከሐ ፡ ተመክሐ ፤ ትምክሕት ። ሠለሰ ፡ ተሠለሰ ፤ ትሥልስት ። ሠገወ ፡ ተሠገወ ፤ ትሥጉት ። ደመረ ፡ ተደመረ ፤ ትድምርት ። ወፈየ ፡ ተወፈየ ፤ ትውፊት ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ን ፤ ባዕድ ፡ ሲኾን ፡ በን ፡ ከሚነሣ ፡ ከነ ፡ ግስ ፡ በቀር ፡ በዲጊመ ፡ ቃል ፡ ግስ ፡ እየገባ ፡ ከአ ፡ ተለይቶ ፡ ይቀርና ፡ የጥሬ ፡ መነሻ ፡ ይሆናል ።

(ማስረጃ) ፤ በልበለ ፡ አንበልበለ ፤ ነበልባል ። በስበሰ ፡ አንበስበሰ ፤ ነበስባስ ። ጐድጐደ ፡ አንጐድጐደ ፤ ነጐድጓድ ። ገርገረ ፡ ጕርጕረ ፤ አንገርገረ ፤ አንጕርጕረ ፤ ነገርጋር ፤ ነጕርጓር ። ቀጥቀጠ ፡ ቀልቀለ ፤ አንቀጥቀጠ ፡ አንቀልቀለ ፤ ነቀጥቃጥ ፤ ነቀልቃል ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። እንና ፡ አስተም ፡ በአ ፡ ምክንያት ፡ ልማድ ፡ እየኾኑ ፡ ይገቡና ፡ ለጥሬ ፡ ለቅጽል ፡ ባዕድ ፡ ይኾናሉ ፤ እን ፤ እንዳለና ፡ እን ፡ እየኾነ ፡ በደጊመ ፡ ቃል ፡ ግስ ፡ ሲገባ ፤ በስበሰ ፡ አንበስበሰ ፤ አንበሳ ። ገለገ ፡ አንገለገ ፤ እንግልጋ ። ሶሰወ ፡ አንሶሰወ ፤ እንስሳ ። ኆገወ ፡ አንኆገወ ፤ እንጕግው ። ጌገየ ፡ አንጌገየ ፤ እንጌግይ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። የቀረውን ፡ በእንና ፡ በእን ፡ ተመልከት ፡ ክዚያ ፡ ተነግሯል ። አስተ ፡ እስት ፡ እየኾነ ፡ ሲገባ ፡ ነፍሰ ፡ አንፈሰ ፡ አስተንፈሰ ፤ እስትንፋስ ። ገብአ ፡ አግብአ ፡ አስተጋብአ ፤ እስትጉቡእ ። ረከበ ፡ አርከበ ፡ አስተርከበ ፤ እስትርኩብ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። መ ፡ ደግሞ ፡ እን ፡ እየጐረደ ፡ አስተ ፡ በገባበት ፡ ይገባል ፤ ይህም ፡ አስተፍሥሐ ፡ መስተፍሥሕ ፤ አስተመክሐ ፡ መስተመክሕ ፤ አስተሰረየ ፡ መስተስርይ ፤ ምስትስራይ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ።

**ቡዓዴ** ፤ መለየት ፡ አለያየት ፡ ልዩነት ፡ ርሕቀት ። ሥላሴ ፡ ድሙር ፡ በኢቡዓዴ ፡ ወኢቱሳሔ ። አልቦ ፡ አመክንዮ ፡ ወኢቡዓዴ ፡ ለነበ ፡ ዚኣሁ ፡ ህላዌ ። ኀቡራን ፡ በኢቡዓዴ ፡ ወፅሙራን ፡ በኢቱሳሔ ። ኢውላጤ ፡ ዘእንበለ ፡ ቱስሕት ፡ ወኢቡዓዴ ፡ (ሃይ ፡ አበ ። ቅዳ ፡ ግሩ ፡ ቄር ። ሳታት) ።


**ብዕድና** ፤ ባዕድነት ፡ ልዩነት ፡ ውላጤ ። ዘእንበለ ፡ ፉፋቄ ፡ ወብዕድና ፡ (ቄር ፡ እበት) ።

**ተባዕደ** ፤ ተለያየ ፡ ተራራቀ ። ምስጢሩ ፡ ተብዕደ ፡ ተበዐደ ፡ ካለው ፡ ይገባል ፤ መለያየት ፡ የጋራ ፡ ነውና ። ገበርኩ ፡ ክመ ፡ አንቲ ፡ ትኩኒ ፡ እንቲአየ ፡ ወአንቲሰ ፡ ትትባዐዲ ፡ እምኔየ ፤ በከመ ፡ ተባዕዱ ፡ ሰዶም ፡ ወገሞራ ። ዘአልበ ፡ ተባዕዶ ፡ (መቃ ፡ ገ፯ ። ስንክ ፡ ጥር፳) ።

**አስተባዐደ** ፤ አለያየ ፡ አራራቀ ፤ ነጣጠለ ፡ ከፋፈለ ። ያስተባዕድ ፡ ሥላሴ ፤ እፎ ፡ ያስተባዕዶ ፡ ለዘኢይትባዐድ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**መስተባዕድ** ፤ የሚለያይ ፡ የሚያራርቅ ፡ አራራቂ ።

**ብዕዛ** ፤ (ዛት ። ትግሬ ፡ በዕዛ) ፤ ሳላ ፡ የፋየል ፡ ዐይነት ፡ የዱር ፡ የበረሓ ፡ እንስሳ ፡ እንደ ፡ ቦኽር ፡ እንዳጋዘን ፡ ያለ ፡ ቀንዳም ፤ ቀንዱ ፡ ቀጣቀጥን ፡ ረዥምም ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ የተከከለ ፡ በትር ፡ የሚመስል ። ቱልቱላ ፡ የሳላ ፡ ቀንድ ፤ እንደ ፡ እንቢልታ ፡ እንደ ፡ መለከት ፡ በአፍ ፡ የሚነፋ ፡ ወይም ፡ በሳላ ፡ ቀንድ ፡ አምሳል ፡ የተሠራ ፡ መለከት ፡ ንዋየ ፡ ማሕሌት ፤ የሚነፋ ፡ ኹሉ ። ብሉብሉዮች ፡ ግን ፡ ቃሚል ፡ ጸናጽል ፡ ነጋሪት ፡ ይሉታል ። ቀርንና ፡ ብዕዛ ፡ በመጻሕፍት ፡ እንደሚገባቸው ፡ አልተፈቱም ፡ መላሾች ፡ ቀርንን ፡ ከበሮ ፡ ነጋሪት ፡ ብዕዛን ፡ እንቢልታ ፡ መለከት ፡ ብለውታል ፡ በበገናና ፡ በመሰንቆ ፡ በሌላውም ፡ ፈንታ ፡ ብዕዛ ፡ ተጥፎ ፡ ይገኛል ። በአቅርንት ፡ ወበብዕዛ ። አርጋኖን ፡ ወብዕዛ ። ቃለ ፡ ቃርን ፡ ወእንዚራ ፡ ወመሰንቆ ፡ ወብዕዛ ፡ ወማሕሌት ። ወምስሌሁ ፡ መዘምራን ፡ እሴኒ ፡ በጸናጽል ፡ ወእሴኒ ፡ በከበሮ ፡ ወእሴኒ ፡ በብዕዛ ፡ ወበአቅርንት ፡ (፪ዜና ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ። ስንክ ፡ መስ፲፰ ። ዳን፫ ፡ ፭ ። ፪ዜና ፡ ፲፫ ፡ ፰) ።



ብዕዛ ፡

**ብዒል** ፤ ሉት ፤ (ብዕለ ፡ ይብዕል ፤ አው ፡ በዐለ ፡ ይቤዕል ፡ ይብዐል ። ዕብ ፡ ባዐል ። ዐረ ፡ በዐለ ። ሱር ፡ ብዓል) ፤ መክበር ፡ መበልጠግ ፡ መጌትየት ፤ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፤ መላቅ ፡ መብለጥ ፡ በሀብት ፡ ማደግ ። ሚስት ፡ ማግባት ፤ ባል ፡ መኾን ። ነድይኒ ፡ ወብዒልኒ ፡ እምኀበ ፡ እግዚ ። ሠያጢ ፡ ወሰካሪ ፡ ኢይብዕል ። ዘይብዕለከ ። ምንት ፡ ይብዕላ ፡ ለጥበብ ። በከመ ፡ ይብዕል ፡ ወሬዛ ፡ ድንግለ ፡ (ሚራ ፲፩ ፡ ፲፱ ። ፲፱ ፡ ፩ ። ፳ ፡ ፪ ። ጥበ፰ ፡ ፭ ። ኢሳ፷፪ ፡ ፭) ። አክኼዱ ፡ በጥሕረና ፡ በጸዐለ ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በዐለ ፡ ይቤዕል ፤ በከመ ፡ ይቤዕል ፡ ሲል ፡ ይገኛል ። ኹለተኛም ፡ በብዕለ ፡ ፈንታ ፡ ተብዕለ ፡ ይላል ፤ አያስኬድም ። እስ ፡ ይትበዐላ ፡ ደርገ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ፳፯) ።

**ባዕል** ፤ (ልት ፤ ብ ፡ አብዕልት) ፤ ቅጽልና ፡ ጥሬ ። ባለጠጋ ፡ ሀብታም ፤ ክበርቱ ፤ ጌታ ። ባዕል ፡ ደንጻዊ ። ብእሲት ፡ ክብርት ፡ ወባዕልት ። አብዕልትኒ ፡ ወነዳይኒ ። አግብእ ፡ ለአብዕልቲሃ ፡ (ሚራ፳፭ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ ሐም፲፭ ። መገ ፡ ፵፯ ። ጠቢ ፡ ፲፫) ። ባዕል ፡ ቅጽልና ፡ ጥሬ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በጥሬነቱ ፡ በዓልን ፡ ይመስላልና ፡ በበዓል ፡ ፈንታ ፡ ባዕል ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ ጌታ ፡ ባለቤት ፡ ባል ፡ ማለት ፡ ነው ። ባዕለ ፡ ንዋይ ። ባዕለ ፡ ሳሕም ። ባዕለ ፡ ቤት ። ባዕለ ፡ ብሔር ። ባዕለ ፡ ዕዳ ። ባዕለ ፡ ጸጋ ፡ (ዘሌ፳ ፡ ፳፬ ። ዘዐ፳፩ ፡ ፳፰ ። ፳፪ ፡ ፯ ። ዘዳ፲፯ ፡ ፴፫ ። ኢሳ፳፬ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ መስ፳፫) ።

**አብዕልተ ፡ ነውራት** ፤ ነውረኞች ፡ ነውራሞች ፡ ባለብዙ ፡ ነውሮች ፡ (፫ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፳) ።

**አብዕልተ ፡ ኀጣውእ ፡ ንእሳት** ፤ ኀጢአተኞች ፡ ብዙ ፡ ጥቃቅን ፡ ኀጢአት ፡ የሚሠሩ ፡ (፩ ፡ ፳) ።

**አብዕልተ ፡ ጕባኤ ፡ ቅድስት** ፤ የጉባኤ ፡ ጌቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ቅዱሳን ፡ አበው ፡ ሊቃውንት ።

**ባዕላይ፤** ባለብዙ፡ ኀዋይ፤ ባለጠጋ፤ ወይም፡ ባለጠጎች። ሳንድም፥ ለብዙም፡ ይነገራል፡ ማእከላዊ፡ ነው። ክንክ፡ ከመ፡ ነዳይ፡ ሊባዕስ፡ ክቡር፡ ወልደ፡ ባዕላይ። ኢይምሕሮ፡ ለነዳይ፡ ወኢየንፍሮ፡ ለባዕ ላይ። ባዕላይከኒ፡ ኢአምኑ፡ ወነዳያኒከኒ፡ ኢሰምዑ፡ (መዋሥ። ይ፡ን)።

**ብዑል፤(ላን፡ ላት፡ ዕልት)፤** የከበረ፤ የበ ለጠገ፤ የዘመን፤ የጌተየ፡ ብዙ፡ ገንዘብ፤ ያለው። ዕደው፡ ብዑላን። አንስት፡ ብዑላት። ሀገር፡ ብዕልት። አልቦ፡ ብዕል፡ ዘይፈ.ደፍድ፡ እምነፍስ፡ ብዕልተ፡ (ሚራ ፃ፱፡ ፮። ኢሳ፴፪፡ ፱። ፴፫፡ ፳። ፈላስ)። በብዑል፡ ፈ ንታ፡ ባዕል፡ በባዕል፡ ፈንታ፡ ብዑል፡ ይላል፡ ፍችው፡ አንድ፡ ነው፡ (ራእ፪፡ ፱። ፫፡ ፲፯)።

**ብዕል፤(ላት)፤** በቁሙ፤ ብልጥግና፡ ባለጠ ግነት፤ ክብር፡ ድልብ፡ ብዙ፡ ገንዘብ። ብዙኅ፡ ብዕ ልየ። ብዕል፡ ዓለማዊት። ብዕል፡ ዘይትዐቀብ፡ በ ኀበ፡ ዘአጥረየ፡ (ኢዮ፴፩፡ ፳፭። ፈ፡ መ፡ ፲፰፡ ፩። መክ፭፡ ፲፪)።

—፤ ምላት፡ ስፋት፡ ብዛት፡ ብዙኅት። ብዕለ፡ ስብሐ ቲሁ። ብዕለ፡ ጥበቢሁ፡ (ሮሜ፱፡ ፳፫። ፲፩፡ ፴፫)።

**አብዐለ፤** አከበረ፤ አስከበረ፤ አበለጠገ፤ ሰውን፡ ባዕል፡ ዕለትን፡ በዓል፡ አደረገ። ቀሊል፡ በኀበ፡ እግዚ፡ ያብዕሎ፡ ለነዳይ። እድ፡ ጽኑዕ፡ ብእሴ፡ ያብዕል። ቦ፡ እለ፡ ያብዕሉ፡ ርእሶሙ፡ (ሚራ፲፩፡ ፳፩። ምሳ፲፡ ፬። ፲፫፡ ፯)። ተጋብኡ፡ አይሁድ፡ ከመ፡ ያብዕሉ፤ ወአብዐሉ፡ ሰሙነ፡ ዕለተ። ዕለተ፡ ዘያብዕሉ፡ ቦቱ፡ ትንሣኤ፡ ቅድስተ። ባቲ፡ ያብዕሉ፡ ሮም፡ በዓሎ፡ ለእስጢፋኖስ። ተዝካረ፡ ዕረፍቱ፡ ያብዕሉ፡ ሰርዩ፡ (ዮሴፍ። አቡሻ፡ ፵። ስንክ፡ መስ፲፪። ጥር፲፭)። በአብዐለ፡ ፈንታ፡ አስተብዐለ፡ ይላል፤ ፍችው፡ አንድ፡ ነው። እለ፡ ያስተብዕሉ፡ (ይሁ፡ ፲፯)።

**መብዐሊ፤ ዕል፤** የሚያከብር፤ አክባሪ። መ ብዐሊት፡ (አርጋ፡ ፬)።

**መብዐል፤(ብ፡ መባዕላት፡ ልት)፤** ዙሓ፡ ጠገራ፡ ምዝምዝ፡ ጥፍጥፍ፤ የወርቅ፡ የብር፡ የ ንሓስ፡ የብረት፡ የማዕደናት፡ ኹሉ፡ ዝንጀር፡ መንቍር፡ ስንሰለት፡ እግር፡ ብረት። ወያስተዳልዉ፡ ኵሎ፡ መ ባዕላተ፡ ለሰይጣን፡ (ሔኖ፡ ፵)።

**መብዐለ፡ ሜክኖት፤** መክደኛ፡ እንደ፡ ዙሓ፡ ያለ፡ የብረት፡ መግላሊት፡ (፬ነገ፡ ፲፯፡ ፲፯)።

**መብዕል፤ ምብዓል፤(ላት)፤** መክበሪያ፡ ገንዘብ፡ ማግኛ፡ የብረት፡ የዕንፈጨት፡ የደንጊያ፡ መማ ሪያ፡ እንደ፡ ወፍጮ፡ ያለ። ኢትትአኀዝ፡ ማሕረጸ፡ ወኢመድሐ፤ እስመ፡ መብዕለ፡ ነፍስ፡ ውእቱ። አ ዕይንቲሁ፡ ይጤይቅ፡ ኵሎ፡ አምሳለ፡ ምብዓል፡ ወ ትጋሁኒ፡ ከመ፡ ያስተሣኒ፡ ምብዓሎ፡ ወምንዛቦ፡ (ዘዳ፳፬፡ ፮። ሢራ፡ ፴፰፡ ፳፰)።

**ቢያላ፤(ዕብ፡ ብዑላ)፤** ባል፡ ያላት፡ ሴት፡ ባለባል፡ ክብርት፡ ብዕልት። ምድርክሙኒ፡ ቢያላ፡ (ኢሳ፷፪፡ ፬)።

**በዓል፤(ብ፡ አብዕልት። ሴ፡ በዓልት፡ ታት)፤** ምት፡ ባል፡ ሚስት፡ ያለው፡ ወንድ፤ የቤት፡ ገዥ፡ አዛዥ፡ ጌታ፡ ባለቤት፡ (ዘፍ፳፡ ፲፯። ቆሮ፡ ፲፮፡ ፫)። (ግጥም፤ መጥፎ፡ ሚስት)፡ ያውና፡ አዚያ፡ ማይ፡ በግ፡ ይነዳል፡ ሰው፡ ታላየ፡ ታልሰማ፡ ባላህያ፡ ነው። ብእሲት፡ በዓልተ፡ ቤት። ንኡሰት፡ ያውስባ፡ ወይትዋለዳ፡ ወይኩና፡ በዓልታተ፡ ቤት፡ (፫ነገ፡ ፲፯፡ ፲፯። ጢሞ፡ ፭፡ ፲፬)።

**በዓለ፡ እድ፤** እጃም፤ እጀኛ፤ ባለእጅ፡ እጀታ፡ ያለው፡ ዕቃ፡ መማሪያ፡ ሠራተኛ፡ ቀጥቃጭ፡ ሌባ።

**በዓለ፡ እቶን፤** ጋጋሪ፡ የሀገር፡ ዐበዝ፡ ባለ ወግ፡ ጋግሮ፡ የሚሸጥ፡ ወይም፡ የሚጋግር፡ ብቻ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፳፫)።

**በዓለ፡ ቤት፤** ባለቤት፤ የቤት፡ ጌታ፤ ሠራዒ፡ መጋቢ፤ አሳዳሪ፤ (ሉቃ፲፫፡ ፳፭)።

**በዓለ፡ ጊዜ፤** ዘመናይ፤ ሹም፡ ባለጠጋ፡ ን ጉሥ፤ እንደ፡ ወደደ፡ የሚያደርግ። (ተረትና፡ ግጥም፡ ስላጤ፡ ቱ)፤ ዘመናይ፡ ቅል፡ ደንጊያ፡ ይሰብራል። ያን፡ የጕሹን፡ ገዳይ፡ አበጀኹ፡ ቢላችኹ፤ ይህን፡ ባለ ጊዜ፡ ምን፡ ትሉታላችኹ።

**በዓለ፡ ውዶት፤** ነገረ፡ ሠሪ፤ ከሳሽ፡ ባለጋራ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፰)።

**በዓለ፡ ሕብር፤** ባለቀለም፡ ልብስ፡ አቅላሚ፤ ቀለም፡ አግቢ፡ ወይም፡ ሸያጭ፡ ቀማሚ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፳፫)።

**በዓለ፡ ሐመር፤** መርከበኛ፡ ባለመርከብ፤ የ መርከብ፡ አለቃ፤ መሪ፡ ቀዛፊ፡ (ዮሴፍ)።

**በዓልተ፡ የውሀት፡ ወሰላም፤** ገር፡ ፍቅ ረኛ፡ ቂም፡ በቀል፡ የሌላት፡ (ፊልክ፡ ፲፫)።

**በዓልተ፡ ክልኤ፡ ጸራይቅ፤** ባለኹለት፡ ጸሪቅ፡ የጸናጽል፡ ሻሾራ፡ የሚመስል፡ ፪፡ የናስ፡ ቅጠል፡ ያላት፡ ከዚያ፡ በቀር፡ ሌላ፡ ቅርሻ፡ ገንዘብ፡ የሌላት፡ ይህን፡ ብስጥ፡ ምን፡ እውጥ፡ ሳትል፡ ያኝን፡ ፈጸርሳ፡ ከሙዳየ፡ ምጽዋት፡ ያገባች፡ የድኻ፡ ለጋስ፡ ፈጸከኝ፡ ቱፈጥ፡ ባልቴት፡ (ፊልክ፡ ፶፱። ሉቃ፳፩፡ ፪)።

**በዓለ፡ ኪን፤** ተንኰለኛ፡ ብልኀተኛ፡ ተማባረ፡ እድ፡ ያለው።

**በዓለ፡ ምድር፤** ባለርስት፤ ዐራሽ፡ ቱፋሪ፡ ጃን፡ ገበር፡ (ኢዮ፴፩፡ ፴፱)።

**በዓለ፡ መዛግብት፤** የገንዘብ፡ ሹም፡ ዕቃ፡ ቤት፡ ጠባቂ፡ (ዮሴፍ)።

**በዓለ፡ መንበር፤** ባለወንበር፡ መምህር፡ ጳ ጳስ፡ ኤጲስቆጶስ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፬)።

**በዓለ ፡ መጽሐፍ ፤** ባለመጣፍ ፤ ጸሓፊ ፡ ዐ ቃሚ ፡ ሽያጭ ፡ ተርጓሚ ፡ የመጣፍ ፡ መምር ፡ (ዮሴፍ) ።

**በዓለ ፡ ምሳሌ ፤** ባለተረት ፡ ምሳሌ ፡ ዐዋቂ ፡ ኹሉን ፡ በምሳሌ ፡ የሚናገር ፡ (ማቴ ፲፫ ፡ ፴፬) ።

**በዓለ ፡ ዕዳ ፤** አበዳሪ ፡ ወይም ፡ ተበዳሪ ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ (ኢሳ ፳፬ ፡ ፪) ።

**በዓለ ፡ ጸብእ ፤** ወጥ ፡ ቤት ፡ ወጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ቀቃይ ፡ አብሳይ ፡ (ስንክ ፡ የካ ፲፪) ።

**በዓለ ፡ ርዶ ፤** ባላፈጣ ፡ ገንዘቡን ፡ በወለድ ፡ የሚያበድር ፡ (ቄድር) ።

**በዓለ ፡ ሰይፍ ፤** ዐሬጅ ፡ ፈላጭ ፡ ቈራጭ ፡ ባለ መግ ፡ ዳኝ ፡ ወንበዴ ፡ (ስንክ ፡ የካ ፳ ። ፊልክ) ።

**በዓል ፤ (ላት) ፤** በቈመ ፡ የደስታ ፡ የዕረፍት ፡ ቀን ፡ ባመት ፡ በወር ፡ በሳምንት ፡ የሚከበር ፡ ያለፈ ፡ ነ ገር ፡ የሚታሰብበት ፡ ተገዝካር ፡ ሕዝብ ፡ የበዓሉን ፡ ምስ ጢር ፡ እያሰበ ፡ ደስ ፡ ብሎትና ፡ ሰብሶ ፡ አጊጦ ፡ የሚዘፍ ንበት ፡ የሚዘምርበት ፡ እልል ፡ የሚልበት ፡ ሽብሸባ ፡ ጭ ብጨባ ፡ ቀኒጽ ፡ ነፈርዓጽ ፡ የሚያደርግበት ፡ ሲያረግድ ፡ እስክታ ፡ ሲወርድ ፡ ባንገቱ ፡ የሚቀጭበት ፡ እንደ ፡ ጥጃ ፡ የሚፈነጭበት ። ደምፅ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ በዓለ ። ግበሩ ፡ በዓለ ፡ በትፍሥሕት ። በዓሎሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ገደም ። በዓላት ፡ እሙራት ። በዓለ ፡ ልደት ፡ ወበዓለ ፡ ጥም ቀት ። በዓላት ፡ ዘርሑቅ ፡ እምጽድቅ ፡ (መዝ ፡ ፹፩ ። ፻፲፯ ። ኢሳ ፴፬ ፡ ፲፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱ ። ጥ በ፲፪) ።

**በዓለ ፡ አርብዓ ፤** ዕርገት ፡ የትንሣኤ ፡ ፵ኛ ፡ (ሲኖዶ) ።

**በዓለ ፡ ኀምሳ ፤** ጰራቅሊጦስ ፡ የትንሣኤ ፡ ፶ኛ ፡ (ድጓ) ።

**በዓለ ፡ መርዓ ፤** ሰርግ ፡ የሙሽሮች ፡ በዓል ፡ (ራእ ፲፱ ፡ ፱) ።

**በዓላት ፡ ዐዋድያት ፤** የሚዞሩ ፡ የሚወጡና ፡ የሚወርዱ ፡ ወዲ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚሉ ፡ ከነነዌ ፡ እስከ ፡ ምሕላ ፡ ድኅነት ፡ ያሉ ። መዘር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ መሐረም ፡ ነው ፡ (አዋል) ።


**በዓል ፤ (ብ ፡ በዓሊም ፤ ጽርእ ፡ ወዕ ብራ) ፤** ስመ ፡ ጣዖት ፡ ከንዓናውያን ፡ የሚያመልኩት ፡ ጌታ ፡ ማለት ፡ ነው ። ተቀንየ ፡ ለበዓል ፡ ወሰገደ ፡ ሎቱ ። ወገብረ ፡ ምሥዋዐ ፡ ለበዓል ። ተቀንየ ፡ ለበዓሊም ፡ ወሰገደ ፡ ሎሙ ። ወአምለኩ ፡ በዓሊመ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፴፩ ፡ ፴፪ ። ፳፪ ፡ ፶፫ ። መሳ፪ ፡ ፲፩) ።

**ብዔል ፤ (ጽር ፡ ቤኤል ። ዕብ ፡ ባዓል) ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፡ ስመ ፡ ጣዖት ፡ ሞአባውያን ፡ የሚያመል ኩት ። ብዔል ፡ ፌጎር ፤ ብዔል ፡ ጣዖቱ ፡ ፌጎር ፡ ሶምሮ ቱ ። ፌጎርን ፡ ተመልከት ፡ (ዘኍ ፳፭ ፡ ፫ ። ዘዳ፬ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፻፭) ።

**ብዔል ፡ ዜቡል ፤ (ጽርእ ። ዕብ ፡ ወዐረ ፡ በዓል ፡ ዝቡል) ፤** የሰይጣን ፡ ስም ፤ ደጋንንት ፡ አለቃ ፡ ብዔል ፡ በዓል ፡ ዜቡል ፡ መንገድ ፡ ቤት ፡ በተገናኝ ፡ መሪ ፡ አሳዳሪ ፡ ባለቤት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ማቴ ፲፪ ፡ ፳፬ ፡ ፳፯) ። በገዝብል ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ግን ፡ የጕድፍ ፡ ጋኔን ፡ ልክ ስክስ ፡ ጕድፍ ፡ ሰፊዊቱ ፡ ከሰማይ ፡ ቀጠርጎ ፡ የወደቀ ፡ ጕድፉም ፡ ጨምላቃ ፡ የጕድፎች ፡ አለቃ ፡ ያሰኛል ። ምስ ጢሩ ፡ ከሐራውያ ፡ ይስማማል ፡ ዘበስንና ፡ ዜቡልን ፡ ተመልከት ።

**ብዒር ፤ ሮት ፤ (በዐረ ፡ ይብዕር ፡ ይብ ዐር ። ዕብ ፡ ባዐር) ፤** ጨርሶ ፡ መብላት ፡ ማብላት ፡ ማቃጠል ፡ ከብትን ፡ እሳትን ፡ ወደ ፡ ማርና ፡ ወደ ፡ ቋያ ፡ መስደድ ፡ መልቀቅ ። ሞኝ ፡ አላዋቂ ፡ መኾን ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ከብት ፡ እንስሳ ፡ መባል ። ማረስ ፡ መቈፈር ፡ መማስ ፡ መሙንቀር ፡ መደደቅ ፡ መደንጐር ፡ ግብር ፡ ገበሬ ፡ መኾን ።

**ብዕር ፤ ብዕራ ፤ ብዕራይ ፤ (ዕብ ፡ ብዒር ፤ ከብት ። ሱር ፡ ብዒራ ። ዐረ ፡ በዒር ፤ ገመል ፡ አጋሰስ) ፤** በሬ ፤ የቀንድ ፡ ከብት ፤ ተጠምዶ ፡ የሚያ ርስ ፡ የሚያባርስ ። ሞኝ ፡ አላዋቂ ፤ እንገሌ ፡ በሬ ፡ ነው ፡ እንዲሉ ። ብዕር ፡ ላንድ ፡ ብቻ ፤ ብዕራ ፡ ብዕራይ ፡ ላን ድም ፡ ለብዙም ፡ ይኾናል ፤ እንደ ፡ ሐራና ፡ እንደ ፡ ባዕ ላይ ፡ ነው ። አድግ ፡ ወእመሂ ፡ ብዕራ ። ፀምደ ፡ ብዕራ ። አርዑተ ፡ ብዕራ ። ቀየፍን ፡ ወብዕራ ። መጺአ ፡ ዐቢይ ፡ ብዕራይ ፡ በልያሙ ። ብዕራይ ፡ ዘብርት ። ዘይቀ ሥፍ ፡ ብዕራዩሁ ፡ (ዘፀ፳፪ ፡ ፲ ። ኢሳ፭ ፡ ፲ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፭ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ መስ፳፯ ። ሚሬ፴፰ ፡ ፳፭) ።



ብዕር ፡

**ብዕራዊ ፤** የበሬ ፡ በሬማ ፡ በሬያም ፡ ባለበሬ ፡ ዐራሽ ፡ ገበሬ ፡ ባሪያ ፡ ሎሌ ፡ ቅን ፡ አሽከር ፡ ተገዥ ፡ አገ ልጋይ ። ብእሲት ፡ ብዕራዊት ፡ ታስተፌሥሖ ፡ ለምታ ፡ (ሚሬ፳፮ ፡ ፪) ።

**አባዕር ፤** በሮች ፡ እንስሶች ፡ ሞኞች ፡ አላዋ ቆች ። አባዕር ፡ እለ ፡ ይወግኡ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፯) ።

**መብዕር ፤ (ብ ፡ መባዕር) ፤** ዐራሽ ፡ ቈፋሪ ። የበሬ ፡ ዕቃ ፡ ማረሻ ፡ መቈፈሪያ ፡ መደንጐሪያ ።

**ምብዓር ፤ (ራት) ፤** መቈፈሪያ ፡ የርሻ ፡ የቍ ፋሮ ፡ መሣሪያ ።

(ጥ) **በዓት ፤—ዋሻ ፡ ፍርኩታ ፤—በዊእ ፡ በአ ፤ በአት ።**

(፡) **በዓት** ፤ ባት ፡ ክፍንኛ ፡ እስክ ፡ ተረክዝ ።

**በዓታዊ** ፤ ባታም ፡ ባተ ፡ መልክም ፡ ወይም ፡ እግረ ፡ ደንዳና ፤ ደንብ ፡ እግር ።

**በጸወ ፤— እንቀላፋ ፤— በፀወ ።**

**በጺሕ ፤ ሖት ፤ (በጽሐ ፡ ይበጽሕ ፡ ይብጻሕ ። መጽአ ፤ ለጸቀ)** ፤ መድረስ ፡ መምጣት ፡ መቅረብ ፡ መስጠቅ ፡ መንካት ፡ ማግኘት ፤ የእጅና ፡ የእግር ፡ የራስ ፡ የመሌሊት ። ፉት ፡ በጽሐ ፡ ሰማየ ። ዘእንበለ ፡ ይብጽሑ ፡ ምድረ ፡ ግብ ። በጽሐ ፡ ብርሃንኪ ። ዘበጽሐ ፡ እምኤዶም ። በጽሐ ፡ ማኅፈርን ። ይበጽሕ ፡ ደመናተ ፡ ርእሱ ። በጽሐተሙ ፡ አምሳል ፡ ዘመሰሉ ። ዘበጽሐ ፡ እምትድምርት ፡ (ዳን ፬ ፡ ፲፯ ። ፮ ፡ ፳፬ ። ኢሳ ፳ ፡ ፩ ። ፳፫ ፡ ፩ ። ሚራ ፳፬ ፡ ፳፯ ። ሕዝ ፴፩ ፡ ፫ ። ፪ኢ ፯ ፡ ፱ ፡ ፳፱ ። እቡሻ ፡ ፴) ።

—፤ ማደግ ፡ መጉልመስ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ማድረስ ። መኾን ፡ መደረግ ፤ መምላት ፡ መፈጸም ፡ መፀደረስ ፡ የትንቢት ፡ የዘመን ። መርታት ፤ ድል ፡ መንሣት ፡ የውጊያ ፡ የሙግት ። እምከመ ፡ ኢበጽሐ ፡ ቃሉ ፡ ወኢኮነ ፡ በከመ ፡ ይቤ ። በጽሐ ፡ በከመ ፡ ነገረ ። ከመ ፡ ይብጻሕ ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ። ዳዊትስ ፡ ልህቀ ፡ ወበጽሐ ፡ መዋዕሊሁ ፡ መላ ፡ ተፈጸመ ፡ (ዘዳ ፲፰ ፡ ፳፪ ። ኩፉ ፡ ፵ ። ማቴ ፳፮ ፡ ፶፯ ። ፳፯ ። ፩ዜና ፡ ፳፫ ፡ ፩) ። ጌጋይ ፡ በዘኢይክሉ ፡ በጺሖቶ ። አልቦ ፡ እኩይ ፡ ዘበጽሑ ፡ ሎቱ ፡ ረታ ፡ (ግብ ፳፰ ፡ ፯ ፡ ፲፰) ።

—፤ መውጣት ፡ ቀለይቶ ፡ መያዝ ፡ መስጠት ፡ የስዓ ፡ የሹመት ፡ የርስት ፡ የቦታ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ወበጽሐ ፡ ዕፃ ፡ ላዕለ ፡ በትረ ፡ ብንያም ፡ (፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ። ፲፱ ፡ ፵፩ ። ኢያ ፲፰ ፡ ፲፩ ። ፲፱ ፡ ፩) ። ለከ ፡ ይበጽሐከ ፡ ርስታ ። መክፈልት ፡ በርክት ፡ በጽሐት ፡ ለሴም ፡ (ጦቢ ፮ ፡ ፲፪ ። ኩፉ ፡ ፵) ።

**በጻሒ ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት)** ፤ የሚደርስ ፡ ደራሽ ፡ መጪ ። በጻሕያን ፡ ኀበ ፡ ብጽሐተሙ ፡ (ግንዘ) ።

**ብጹሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ጽሕት)** ፤ የደረሰ ፡ ያደገ ፡ የጐለመሰ ፡ የመላ ፡ የተፈጸመ ፡ ፍጹም ። ብጹሕ ፡ አምጣን ። ብጽሕት ፡ አምጣን ። ብጹሓነ ፡ አምጣን ፡ እምዕሥራ ፡ ዓመት ፡ ወከሃ ፡ ብጹሓን ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ (ኦሪ ፩ ፡ ፲፫ ። ሲኖዶ ። ፩ዜና ፡ ፳፫ ፡ ፫ ፡ ፳፬) ።

**በጽሒ ፡ (ትግሬ)** ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፡ ውርዝው ፡ ወሪዛ ፡ ሕፃን ፡ ብጹሐ ፡ አምጣን ።

**ብጹሕ ፡ ውስተ ፡ ትሩፋት** ፤ ከፍጹምነት ፡ የደረሰ ፡ በትሩፋት ፡ የተፈጸመ ፡ ባሕታዊ ።

**ብጹሐ ፡ መዋዕል** ፤ ቀን ፡ የደረሰ ፡ ዕድሜ ፡ የጠገበ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ የቀረበ ፡ አሮጌ ፡ (፩ዜና ፡ ፳፬ ፡ ፳፯) ።

**ብጽሐት ፡ (ታት)** ፤ መድረስ ፡ መምጣት ፡ አደራረስ ። ብጽሐትከ ፡ ኀቤየ ። ሶበ ፡ አእመረ ፡ ብጽሐተሙ ፡ እምቤተ ፡ መቅደስ ። ጊዜ ፡ ብጽሐተ ፡ ሐጋይ ። መጽሐፍ ፡ በጽሐት ፡ ወአስተፍሥሐተኒ ፡ በብጽሐታ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲ ፡ ፮ ። ዮሴፍ) ።

—፤ ምርመራ ፡ ፍተሻ ፡ የተጣራን ፡ ቊጥር ፡ ቀመርን ፡ ንብቶ ፡ ማየት ፡ ድርሱን ፡ ማግኘት ፡ ማወቅ ፡ መረዳት ፡ (አቡሻ ፡ ፴) ።

**ብጽሕ ፡ (ሓት)** ፤ ድርሻ ፡ ፈንታ ፡ ክፍል ፡ ዕድል ።

**አብጽሐ** ፤ አደረሰ ፡ አመጣ ፡ አቀረበ ። ወሰደኒ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወአብጽሐኒ ፡ ኀበ ፡ አንቀጽ ። ያበጽሕዎ ፡ እስከ ፡ ደመና ። አብጻሕክዎ ፡ ኀበ ፡ ዘተመነየ ፡ (ሕዝ ፹ ፡ ፫ ። ሚራ ፲፫ ፡ ፳፬ ። (ዮሴፍ) ።

—፤ አስረዳ ፡ ገለጠ ፡ አስታወቀ ። ለእመ ፡ አብጻሕክሙ ፡ ሊተ ፡ ከመ ፡ ቤል ፡ ይበልዕ ። ወያበጽሕ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ (ዳን ፲፫ ፡ ፱ ። ግብ ፱ ፡ ፳፪ ። ፲፯ ፡ ፫ ። ፲፰ ፡ ፳፰) ። በአብጽሖ ፡ ፈንታ ፡ አስተብጽሖ ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። የኀሥሥኒ ፡ ወያስተብጽሕ ፡ ተስእሎተ ፡ በእንቲአየ ፡ (አፈ ፡ ድርሳ) ። ኹለተኛም ፡ አስተባጽሖ ፡ ይላል ፡ ባደራራጊ ፡ አያስኝም ። ይክልእ ፡ አስተባጽሖ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ። አስተባጽሖሙ ፡ ኀቤሁ ፡ (ፊልክ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ ሚያ ፲፰) ።

**አብጻሒ ፤ መብጽሒ ፤ ሒ** ፤ የሚያደርስ ፡ አድራሽ ፡ ወሳጅ ። ምግባር ፡ ዘመብጽሒት ፡ ኀቤሃ ፡ (ፊልክ ፡ ፳፱) ።

**ምብጻሕ ፤ (ሓት)** ፤ መድረሻ ፤ ማድረሻ ፤ መዳረሻ ፡ መጨረሻ ፤ መግቢያ ፡ ማረፊያ ፡ መጠጊያ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ ። ሔኖ ፸፱ ፡ ፲፩) ።

**ተበጽሐ** ፤ ተዳረሰ ፡ ተጋጠመ ፡ ተገናኘ ፡ አንድ ፡ ኾነ ። እስከ ፡ ይትባጽሖሙ ፡ ወይዴደቅሙ ፡ መዐተ ፡ እግዚ ። ተባጽሖታ ፡ ለልብ ፡ ምስለ ፡ እግዚ ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፱ ። ፊልክ ፡ ፺፫) ።

—፤ ተካሰሰ ፡ ተቈራኘ ፡ ተማላ ፡ ይዞ ፡ ተያይዞ ፡ ኼደ ፡ ከዳኛ ። ወሰደ ፡ አደረሰ ። ተረታታ ፡ ተነጣጠረ ። ወተበጽሕዎ ፡ አይሁድ ፡ ለጳውሎስ ፡ ኀበ ፡ ጋልዮስ ፡ (ግብ ፲፰ ፡ ፲፪ ። ፲፱ ፡ ፴፯ ። ማር ፲፫ ፡ ፱ ። ሉቃ ፲፪ ፡ ፶፰) ።

**አስተበጽሐ** ፤ አዳረሰ ፡ አገናኘ ፡ አጋጠመ ፡ አረታታ ፡ አነጣጠረ ።

**ምስትብጻሕ** ፤ መዳረሻ ፡ መገናኛ ፡ መጋጠሚያ ፡ ጉባኤ ፡ ሸንጎ ።

**በጺል ፤ ሎት ፤ (በጸለ ፡ ይቤጽል ፡ ይብጽል ። ፀረ ፡ በጸለ ። ዕብ ፡ ፋጼል)** ፤ መላጥ ፡ መምለጥ ፡ መቅረፍ ፡ መሸልቀቅ ፡ መግፈፍ ፡ መገሸለጥ ፡ መበፈቅ ፡ መጋጥ ፡ መንፈት ፡ መሳብ ፡ መጐተት ። ክሰባት ፡ ይቤጽልዎሙ ፡ (ኤር ፲፰ ፡ ፫) ።

**ተበጽለ** ፤ ተላጠ ፡ ተመለጠ ፡ ተበፈቀ ፡ ተቈረጠ ። ተቀሥፈ ፡ እስከ ፡ ተበጽለ ፡ አነዳ ፡ ማእሱ ። ይትቤጻል ፡ ማእስየ ፡ ምስለ ፡ ሥጋየ ። በሐብዎ ፡ ደበ ፡

ለእባን ፡ በሲኃት ፡ እስከ ፡ ይትቤጸል ፡ ሥጋሁ ፡ (በ ኀኑ ፡ ሠ፭፳ ። ሐም፳፰ ። ኢዮ፲፱ ፡ ፳ ። መጽ ፡ ምስ) ።

(ጥ) **ብጹል ፤ (ላት) ፤** ልጥ ፡ ቅርፍት ፡ ቅራፊ ፡ ብ ጣቂ ፡ ብጭቅጣቂ ፡ ዕላቂ ፡ ብጣሽ ፡ ቍራጭ ። **ረከብኩ ፡ ብጹላቲሃ ፡ ወአጽርቅቲሃ ፡** (ኤር ፡ ፲፫ ፡ ፯) ።

**በጸል ፤ (ዐረ ፡ በጸል ። ዕብ ፡ ባጸል ። ሱር ፡ ቤጽላ) ፤** ቀይ ፡ ሽንኩርት ፤ የቀይ ፡ ሽንኩርት ፡ ፀይንት ፡ የሚላጥ ፡ የሚመለጥ ፤ ኹለንተናው ፡ ተልጦ ፡ የሚያልቅ ፡ የሚሸለቀቅ ። **ኢይበርኩ ፡ ላዕለ ፡ በጸል ፡** (ፍ ፡ ን ፡ ፲፯) ።

**በጽዐ ፤ — ብጽዐት ፡ ገባ ፤ — በዒዕ ፡ በ ዕዐ ።**

**በጼቃ ፤ (ዐረ ፡ ቡጻቅ ። ዕብ ፡ ባጼቅ ፤ ሊጥ ፡ ቡሖ) ፤** ነጭ ፡ ደንጊያ ፡ በረቅ ፤ ብሓ ፡ ብሕክ ፡ በመኗ ፣ ኖራ ፡ የሚመስል ። **ከመ ፡ ርእየተ ፡ በጼቃ ፡** (አዋል) ። ባዚቃን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ሞክሼ ፡ ነው ።

**በዒው ፤ ዎት ፤ (በፀወ ፡ ይበፀው ፡ ይብፀው ። ዕብ ፡ ባጤእ ፤ ነበበ ። ዐረ ፡ በጡአ ፤ ዋመ) ፤** ማሸለብ ፡ ማንቀላፋት ፤ መተኛት ፡ መጋደም ፡ ጢ ፡ ብሎ ፡ መዘርጋት ። መቃዠት ፡ መቀባጠር ፡ መቀዋዎት ፡ ማቢለት ፡ ያልኾነ ፡ ነገር ፡ መናገር ። **ብላዕ ፡ ማዕረ ፡ ወልበስ ፡ ሣ ዕረ ፡ ወብፁ ፡ ዲበ ፡ ማዕር ፡** (ፊልክ ፡ ፸፯) ። ነፀወን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ብፃው ፤ (ዋት) ፤** እንቅልፍ ፡ እንጕልቻ ፡ ቅ ዠት ፤ ጨዎታ ፡ ቢልት ፡ አለውቀት ። **ክደኖን ፡ ለቀራን ብቲከ ፡ በብፃወ ፡ ኅጣውእ ። ወእመኒ ፡ መጽአኒ ፡ ብ ፃው ፡ ለአፀርያ ፡ ጸሎት ፡** እንቅልፍ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። አ ርጋ ፡ ፪) ። **ወለእመኒ ፡ አእመርዎሙ ፡ እክዮሙ ፡ ይ ብሉ ፡ በብፃው ፡ ገበርኒ ፤** ጨዎታ ፡ (ምሳ፳፮ ፡ ፲፱) ።

**ምብፃው ፤** መኝታ ፡ መተኛ ፡ ማስተኛ ፡ ቦታ ፡ መደብ ፡ ዐልጋ ። **ለእመ ፡ ረከብከ ፡ ብእሴተ ፡ በውስተ ፡ ምብፃውከ ፡** (ፊልክ ፡ ፻፶፫) ።

**በዒዕ ፤ ዖት ፤ (በዕዐ ፡ ይበዕዕ ፡ ይብፃዕ ። ዕብ ፡ ባፃዕ ። ዐረ ፡ በፀዐ ፤ ቤጻ) ፤** መቍረጥ ፡ መወ ሰን ፡ መገምገም ፡ መገመት ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ማለት ፡ የ ዋጋ ፡ የስለት ። በቁሙ ፡ መብፃት ፡ ብፅዐት ፡ መግባት ፡ በገንዘብ ፡ በመሢዕት ፡ ወይም ፡ በራስ ፡ በሰውነት ፡ መ ሳል ፡ ይህን ፡ እሰጣለኹ ፡ እንዲህ ፡ አደርጋለኹ ፡ ማለት ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ራስን ፡ ገንዘብን ፡ መቀ ደስ ፡ መለየት ፡ ለባለቤቱ ፡ ማቅረብ ፡ መስጠት ፡ የተናገሩ ትን ፡ መፈጸም ። **ይበፅዕ ፡ ሤጠ ፡ ካህን ፡ ወበከመ ፡ በ ፅዖ ፡ ከማሁ ፡ ይከውን ። ወእመ ፡ በፅዐ ፡ ብእሲ ፡ ቤተ ፡ ለእግዚ ፡ ወቀደሳ ። ዘበፅዐ ፡ ብፅዐተ ። በፃዕከ ፡ ሊተ ፡ ብፅዐተ ። እንበለ ፡ ትብፃዕ ፡ አስተዳሉ ፡ ብፅዐ ቲከ ። እመ ፡ ኢበፃዕኩ ፡ ለኢየሩሳሌም ። በፃዕኒ ፡ ን ጹም ። በፃዕከ ፡ ትሕንጽ ። ብእሲት ፡ ዘበፅዐት ፡ ከመ ፡ ኢትትወሰብ ። ዘበፅዐት ፡ ርእሳ ፡ ለእግዚአብሔር ፡** (ዘሌ፳፯ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ ። ዘፀ፴፰ ፡ ፳፬ ። ዘኍ፴፩ ፡ ፲፫ ። ሚ ራ፲፫ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፻፴፩ ። ፩ሳገ ፡ ፭ ፡ ማቴ ፡ ፱ ፡ ማሕ ፡ ፊ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፲፯ ። ፯ ፡ ፲፱) ።

**አብፅዐ ፤ (አድራጊ) ፤** አከበረ ፡ አመሰገነ ፡ መረቀ ፡ አደነቀ ፡ ደስ ፡ አሰኘ ፡ በብፅዐት ፡ ሥራ ። **ያበ ፅዖ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። አብፅዖ ፡ በሠናይ ፡ ስርጐ ። በ ዘያበፅዕ ፡ ሰብአ ፡** (መዝ ፡ ፵ ። ሢራ፴፰ ፡ ፯ ። ሮሜ፬ ፡ ፯—፱) ።

**አብፅዐ ፤ (አስደራጊ) ፤** አስከበረ ፡ አስመሰ ገነ ፤ አስመረቀ ፡ አስደነቀ ፡ ብፁዕ ፡ አሰኘ ፡ ራሱን ። **አብ ፃዕኩ ፡ አነኒ ። እመኒ ፡ ብዙኅ ፡ አብፃዕኩ ፡ ርእስየ ፡ በ ኀቤከ ፡ ወዐርገት ፡ ጸሎትየ ፡ ቅድሜከ ፡** (ዘፍ፴ ፡ ፲፫ ። ሉቃ ፡ ዕዝ፲ ፡ ፲፪) ። በአብፅዐ ፡ ፈንታ ፡ አስተብፅዐ ፡ ይ ላል ፡ ፍችው ፡ አድራጊነት ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ላይኛው ። **ተስፀቱ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ አስተብፃዕክዎሙ ። ያስተ በፅዕ ፡ ደኃሪቶሙ ፡ ለጻድቃን ። ያስተበፅዑኒ ፡ ኵሉ ፡ ትውልድ ። ናስተበፅዖሙ ፡ ለእለ ፡ ተዐገሡ ፡** (ሚራ ፳፰ ፡ ፯ ። ጥበ፪ ፡ ፲፮ ። ሉቃ፩ ፡ ፵፰ ። ያዕ፭ ፡ ፲፩) ።

**አስተብፅዐ ፤ (አድራጊ) ፤** አከበረ ፡ አመሰ ገነ ፡ አደነቀ ። ጥቅስ ፡ እንዳለፈው ፡ ነው ። **አስተብፅዑ ፡ ነፍስተ ፡ ዓሣ ፡** (ቅኔ) ።

**ተበፅዐ ፤** ተቈረጠ ፤ ተገመገመ ። ተሰየ ፡ ተቀ ደሰ ፡ ከበረ ፡ ተመሰገነ ፡ ተመረቀ ፡ ብፁዕ ፡ ተባለ ። **ተበ ፅዐ ፡ ኢዮብ ። ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘይትዌደስ ፡ ወይትበ ፃዕ ። እምካልኣኒሁ ፡ ዘተበፅዐ ። ሰላም ፡ ለአእጋሪከ ፡ ዘቱወደሰ ፡ ወተበፅዓ ፡** (አፈ ፡ ተ፳ ። ፈላስ ። ስንክ ፡ ሐ ምሌ፳፰ ። ጥር፳ ። ደራሲ) ። በተበፅዐ ፡ ፈንታ ፡ አብፅዐ ፡ ይ ላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **አይቴኑ ፡ አብፅዖት ከሙ ፡** (ገላ፬ ፡ ፲፭) ።

**ብፁዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ዕዕት) ፤** ብፅዐት ፡ የ ገባ ፡ ባለብፅዐት ፡ የብፅዐት ፡ ልጅ ፡ የብፅዐት ፡ ገንዘብ ። **ኵሉ ፡ ዘብፁዕ ፡ ዘበፅዑ ፡ መሀይምናን ፡** (ሃይ ፡ አበ፫) ። በቁሙ ፡ የታመነ ፡ የተመሰገነ ፡ ሥራውና ፡ ልቡ ፡ የቀና ፡ የተከናወነ ፡ ክቡር ፡ ምስጉን ፡ ምሩቅ ፡ ቡሩክ ፡ ቅዱስ ፡ ጻድቅ ፡ ቸር ፡ ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኢዮብና ፡ እንደ ፡ አብርሃም ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ያለ ። **ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢሖረ ፡ በምክረ ፡ ረሲዓን ። ብፁዕ ፡ ረሰይከኒ ። ኢ ትበሎ ፡ ብፁዐ ፡ ዘእንበለ ፡ ትርአይ ፡ ደኃሪቶ ። ብፅ ዕት ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ ትፈርሆ ፡ ለእግዚ ። ብፁዓን ፡ ነዳ ያን ፡ በመንፈስ ፡** (መዝ ፡ ፩ ። ሉቃ ፡ ዕዝ፲፪ ፡ ፲፱ ። ሚ ራ፲፩ ፡ ፳፰ ። ፴፩ ፡ ፲፯ ። ማቴ፭ ፡ ፫—፲፩) ። ስምንቱ ፡ ማእከላዊ ፡ ነው ፤ ከንጹሕ ፡ በላይ ፡ ከቅዱስ ፡ በታች ፤ ስለዚህ ፡ ለፈጣሪ ፡ ሳይቀር ፡ ለመጣኒና ፡ ለፍጹም ፡ ለ ኹሉ ፡ ይኾናል ። **ለብፁዕ ፡ እግዚአብሔር ፡** (፩ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፩) ።

**ብፁዓዊ ፤** የብፁዕ ፡ ወገን ፡ ንጹሕ ፤ ወጣኒ ፡ መንፈሳዊ ፡ ወይም ፡ ብፁዕ ፡ የተባለ ፡ ብፁዕነት ፡ ያለው ፡ ማእከላዊ ፡ ፍጹም ፡ ቅዱስ ። **ብፁዓዊ ፡ ተካለ ፡ ሃይማ**

ዎት ። አሕዱ ፡ እምብፁዓውያን ፤ (ገድ ፡ ተክ ። ፊልክ ፡ ፳) ።

**ብፅዐት** ፤ (ታት) ፤ መባል ፡ ብፁዕ ፡ መባል ። ስለት ፡ የስለት ፡ ገንዘብ ፡ የብፅዐት ፡ ሥራ ። ኢታጕንዲ ፡ ውሂበ ፡ ብፅዐትከ ። ፍዲ ፡ ብፅዐተከ ። ብፅዐተ ፡ ሕይወትየ ። መሥዋዕት ፡ ዘዘልፍ ፡ ወዘብፅዐት ። ብፅዐት ፡ በሙ ። በእንተ ፡ ብፅዐታት ። እንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘትትዌከፍ ፡ ብፅዐታተ ፡ ወዓሥራተ ፤ (ሚሳ፲፭ ፡ ፳፱ ። ናሖ፪ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፵፭ ። ዮዲ፱ ፡ ፲፱ ። ማብ፲፰ ፡ ፲፩ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲፩ ። ማር ፡ ይሥ) ። ብፅዐትኛ ፡ ብልኅ ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ፤ ስለት ፡ በመባል ። (ሙሾ ፡ ልጆቹ ፡ በሰይፍ ፡ ያለቁበት) ፤ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ ገንዘብ ፡ አትንኩ ፡ በኋችኹ ፡ ምንዋ ፡ ልጆቹ ፡ ስለት ፡ የበላችኹ ።

**ብፅዕና** ፤ ብፁዕነት ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ቅድስና ። ብፁዓን ፡ እሙንቱ ፡ ወዓዲ ፡ ለነሂ ፡ ብፅዕና ፤ (ገድ ፡ ኪሮ) ። በብፅዐት ፡ ፈንታ ፡ ብፅዕና ፡ ብፅዕናት ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ብፅዕናት ፡ ወብጽርናት ፤ (ቀሌ) ።

**ብፅዕ** ፤ (ዓት) ፤ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ብፁዕ ፡ ማለት ፤ መባል ፤ የቡራኬ ፡ ቃል ። ጴጥሮስ ፡ ረከበ ፡ ብፅዐ ፡ እምኀበ ፡ መድኅን ፤ ወይቤሎ ፡ ብፁዕ ፡ አንተ ። ወሀበ ፡ እግዚ ፡ ለእሉኒ ፡ ብፅዐ ፡ በብሂሎቱ ፡ ብፁዓን ፡ መሓርያን ፤ (ቀሌ ። ፊልክ ፡ ፶፩) ።

**ብፅዓን** ፤ (ናት) ፤ ግዜ ፡ ነማዥ ፤ ክብር ፡ ምስጋና ። ብፅዓን ፡ ወፍሥሓ ፡ ለክሙ ። ቃላተ ፡ ብፅዓን ። ብፅዓን ፡ ይደልዎ ፡ ለገብር ፡ ምእመን ። የኀጥእ ፡ ብፅዓኒ ፡ እንተ ፡ ተብህለት ፡ ለሕዙናን ። ቃወሥእሙ ፡ ለኅሩያን ፡ በቃለ ፡ ብፅዓን ፤ (ዮሴፍ ። አፈ ፡ ተ፯ ። ፊመ ፡ ፱ ፡ ፲፩ ። ፊልክ ፡ ፸፱ ። ቅዳ ፡ ያዕ) ።

**በቂው** ፤ ዎት ፤ (በቀወ ፡ ይበቁ ፡ ይብቁ ። ዐረ ፡ በቀ ። ዕብ ፡ ባቃዕ ፤ ከፈተ) ፤ መከፈት ፡ መለቀቅ ፡ ክፍት ፡ መኾን ፡ ዋሻ ፡ መምሰል ፡ ለመጕረሥ ፡ ለመክተት ፡ የአፍ ፡ የጕድጓድ ። በቀወት ፡ ምድር ፡ ወውኅጠቶ ፡ ለዳታን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ አብቀወት ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ፤ (መዝ ፡ ፻፭) ። ለቀወን ፡ እይ ።

**ብቅው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ቁት) ፤ የተከፈተ ፡ የተለቀቀ ፤ ክፍት ፡ ልቅ ፡ ለቃቃ ፤ አፈ ፡ ሰፊ ። ብቅው ፡ ለውኂዋ ። ብቅወ ፡ ጕርዔ ፡ ወአፍ ፤ (አርጋ ፡ ፭ ። ደራሲ) ።

**ብቅወት** ፤ መከፈት ፡ አከፋፈት ፡ ክፍትነት ።

**ብቃው** ፤ አፍ ፡ ክፍት ፡ ዋሻው ፡ የሚጮኸው ፡ የሚናገረው ።

**አብቃው** ፤ አፎች ፡ ላይኛውና ፡ ታችኛው ፡ ክፍል ፡ ብቃውና ፡ አብቃው ፡ ከንፈር ፡ ከናፍር ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ትክሥት ፡ አብቃዊሁ ፡ ወታኬልሖ ፤ (ቅዳ ፡ አት) ።

**አብቀወ** ፤ ከፈተ ፡ ለቀቀ ። አስከፈተ ፡ ክፈት ፡ አለ ። አብቁ ፡ አፉከ ፡ ወብላዕ ። ወመብዝኀቶሙ ፡ ኢክህሉ ፡ ያብቅዉ ፡ አፉሆሙ ፡ ለበሊዕ ። አብቀዉ ፡ አፉሆሙ ፡ ላዕሌየ ። ነዳይ ፡ ሶበ ፡ ይስእል ፡ ያበቁ ፡ አፉሁ ፡ እስከ ፡ እዘኒሁ ። አብቀዉ ፡ ውስተ ፡ ነፋስ ። አብቅዋ ፡ ለገዳም ፤ (ሕዝ፪ ፡ ፰ ። ዮሴፍ ። መዝ ፡ ፴፩ ። ሚራ፳፩ ፡ ፳ ። ኤር፲፬ ፡ ፯ ። ሔኖ፲ ፡ ፬) ።

**አንበሕቀወ** ፤ አበቀወ ፤ በሕቁ ፡ አዛጋ ፡ አፋሸገ ፤ አፉን ፡ አስልክ ፡ ከፈተ ። ወይም ፡ ተከፈተ ፡ ተለቀቀ ፤ በግድ ፡ በቀስመን ፡ በውድና ፡ በፈቃድ ፡ ሳይኾን ። ሕ ፡ ከሕቀ ፡ መጥቶ ፡ ስጸጽ ፡ ኹኗል ፤ ስለዚህ ፡ የበሕቁ ፡ ምስጢር ፡ አለበት ።

**ነበሕቃው** ፤ ፍሽጊያ ፡ የአፍ ፡ አከፋፈት ፤ ክፈታ ፡ ክፍቻ ፡ ለቀቃ ።

(ጥ) **በቅሎ** ፤ ሎት ፤ (በቀለ ፡ ይቤቅል ፡ ይበቅል ። ዐረ ፡ በቀረ ። ዕብ ፡ ባቄር) ፤ መመርመር ፡ መጠየቅ ፡ ማፍን ፡ በደልን ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ ማስብ ፡ መቍጠር ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ መበቀል ፡ መቀየም ፤ መቅጣት ፡ ፍዳውን ፡ መስጠት ፡ ማስበበት ። በለበቅ ፡ በጨንገር ፡ መግረፍ ፤ ማስለፍለፍ ፤ የሕፃንና ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ቅጣት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በበቀለ ፡ ፈንታ ፡ አብቀለ ፡ ተበቀለ ፡ ይላል ፡ ባስደራጊና ፡ በተደራጊ ፡ አንቀጽ ፤ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ አያሰኝም ፤ ተ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። ሳብዕት ፡ በቀለ ፡ ያበቅል ። ዮጊ ፡ ኢትክል ፡ ተበቅሎት ፡ ለዘአበሰ ። ዘይትቤቀሎሙ ፡ ለጸላእቱ ፤ (ዘፍ፬ ፡ ፲፭ ። ሚራ፯ ፡ ፯ ። ፴፬ ፡ ፺) ።

**በቃሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤ የሚበቀል ፡ ተበቃይ ፤ ቂመኛ ፡ ደም ፡ መላሽ ፡ ብድር ፡ ከፋይ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ እንዳማርኛው ፡ ተበቃሊ ፡ ይላል ። እግዚ ፡ ተበቃሊ ፡ ለእለ ፡ ይትገፍዑ ፡ እምእደ ፡ ገፋዕያኒሆሙ ። ይገፍዖ ፡ እግዚ ፡ ለገፋዒ ፡ ወይትቤቀሎ ፡ ለተበቃሊ ፤ (መቃ ፡ ፯ ። ቀሌ) ።

**በቀል** ፤ (ላት) ፤ በቂመ ፡ ቅጣት ፡ የክፉ ፡ ብድራት ፤ ዕዳ ፡ ፍዳ ፡ ቂም ፡ ደም ። እትቤቀሎሙ ፡ አርባዕተ ፡ በቀለ ። እትቤቀል ፡ በቀለ ፡ ህየንተ ፡ አዕይንትየ ። ከመ ፡ ይግብኡ ፡ በቀለ ፡ እምኀበ ፡ እግዚ ፡ ለምድያም ። በቀለ ፡ አኁሁ ፤ (ኤር፲፭ ፡ ፫ ። መሳ፲፮ ፡ ፳፰ ። ዘኍ፴፩ ፡ ፫ ። ፪ነገ ፡ ፫ ፡ ፳፯) ።


**በቀለ** ፤ (ጋቢይ ፡ አገባብ) ፤ ስለ ፡ ፈንታ ። ብፁዕ ፡ ዘይትቤቀለኪ ፡ በቀለ ፡ ተበቀልክነ ፤ (መዝ ፡ ፻፴፮) ። ዕር፲፱ ፡ ቍ፲፱) ።

**አበቀለ** ፤ **አስተበቀለ** ፤ አስበቀለ ፡ በቀል ፡ አስመለሰ ፤ እንዲበቀሉ ፡ አደረገ ።

**መበቅል** ፤ **መስተበቅል** ፤ የሚበቀል ፡ የሚያስበቅል ፤ ተበቃይ ፡ አስበቃይ ። እግዚ ፡ ቀናኢ ፡ ወመስተበቅል ፤ (ናሖ፩ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፸፫ ። ሽተስ ፡ ፱ ፡ ፯ ። ዲድ ፡ ፱) ።

**ተበቀለ** ፤ ተጠየቀ ፡ ተመረመረ ፡ ተሠራ ፡ ተቀጣ ፡ ፍርድ ፡ ለበሰ ።

**በቅል ፤ ልት ፤ (ዐረ ፡ በቅል ። ዕብ ፡ ፌሬድ)** ፤ በቅሎ ፤ አጋሰስ ፡ ከህያ ፡ ከፈረስ ፡ የሚዲቀል ፡ አባቱ ፡ አህያ ፡ እናቱ ፡ ፈረስ ። ተባቱና ፡ እንስቱ ፡ ዘር ፡ ለመስጠትና ፡ ለመቀበል ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የማይገጥሙ ፡ የማይስማሙ ፡ እጅግ ፡ ቅብጥብጦች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ መውለድና ፡ መርባት ፡ የላቸውም ፤ ሲገናኙ ፡ ግን ፡ ይወልዳሉ ፡ አንድ ፡ የሰላሌ ፡ ሰው ፡ በቅሎው ፡ ወልዳ ፡ ላሜ ፡ ምኒልክ ፡ ከንግልገሏ ፡ አምጥቶ ፡ እንዳሳየ ። ፍችው ፡ መስተበቅል ፡ አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ ግን ፡ ሐዲስ ፡ ቡቃያ ፡ ይሉታል ፡ ከጥንቱ ፡ ያልነበረ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ተረትና ፡ ቅኔ) ፡ በቅሎ ፡ ቢወልዳ ፡ እንጂ ፡ አትወልድ ። እኔም ፡ እንዳላማ ፡ ልቱም ፡ ዐዋጅ ፡ ሲነገር ፡ ምን ይልኽ ፡ ሰብእ ፡ ሺዋ ፡ ቅኔ ፡ ተዘርቶ ፡ በቅሎ ፡ ቢቀር ። ኢትኩኑ ፡ ከመ ፡ ፈረስ ፡ ወበቅል ፡ (መዝ ፡ ፴፩) ።



በቅል ።

**አብቅል ፤ (ልት)** ፤ በቅሎች ፡ አባቅልቶች ፡ አጋሰሶች ። ፈነወ ፡ ፀሥርተ ፡ አብቅለ ፡ (ዘፍጥረት ፡ ፵፭) ።

**መስተበቅል** ፤ ባለበቅሎ ፡ በቅሎ ፡ የሚያረባ ፡ የሚሺጥ ፡ የሚያከራይ ፡ ወይም ፡ ለጓሚ ፡ ባልደራስ ፡ በቅሎ ፡ ጠባቂ ። አዘዘ ፡ ያምጽኡ ፡ አልባሰ ፡ ክህነት ፡ ምኩሕ ፡ ወመስተበቅለ ፡ ወበትረ ፡ ክህነት ፡ ወአመ ፡ ሳኒታ ፡ አምጽአ ፡ በቅለ ፡ ወጸሎ ፡ ዘይትፌቀድ ፡ ለፍኖት ፡ ወአጽዐኖ ፡ ለአባ ፡ አትናቴዎስ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ ፲) ።

**በቅል ፤ (ሱማሌ ፡ ሐረር ፡ ጕራጌ)** ፤ የቀ-ጥር ፡ ስም ፡ መቶ ። ሸማግሎችና ፡ ገዞች ፡ አገዛዞች ፡ ወይም ፡ ድር ፡ አይራዎች ፡ መቶውን ፡ ጥንድ ፡ አንድ ፡ በቅል ፡ እንዲሉት ።

**በቀ-ል ፤ ሎት ፤ (በቈለ ፡ ይበቍል ፡ ይብቈል ። ዐረ ፡ በቀለ)** ፤ መብቀል ፡ ማኰንቈል ፡ ከፈር ፡ ከመሬት ፡ መዘመድ ፡ መዋሐድ ፡ መጽደቅ ፡ ሥርን ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ቅጠልን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ መስደድ ፡ መዐነስ ፡ መቋጠር ፡ መወሰድ ፡ መፈጠር ፡ መሥረጽ ፡ መጡጣት ። ይበቍል ፡ ውስቴቱ ፡ ማዕር ፡ ወሦክ ፡፡ ኢበቈለ ፡ ሥርዎሙ ፡፡ ይበቍል ፡ ክነፊሆሙ ፡፡ ይበቍሉ ፡ ከመ ፡ ማዕር ፡፡ ሦክ ፡ ወአሜከላ ፡ ይብቈልክ ፡ (ኢሳ ፡ ፮ ። ፶ ፡ ፳፱ ፡ ፴፭ ። ፶፱ ፡ ፱ ። ኩፋ ፡ ፫ ። ዘፍ፫ ፡ ፲፰) ።

**በቋሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ቈልት)** ፤ የሚበቅል ፡ የሚሠርጽ ፡ በቃይ ፡ ዘር ፡ ቅንጣት ።

**አብቈለ** ፤ አበቀለ ፡ አጸደቀ ፡ ቡቃያ ፡ አወጣ ፡ አቀጠለ ፡ በራሱ ፡ በጐን ። ለታብቍል ፡ ምድር ፡ ሐመልማለ ፡ ሣዕር ፡፡ አብቈልኩ ፡ ሥርውየ ፡፡ አብቍሉ ፡ ጽጌክሙ ፡ ከመ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡፡ ዘኢያብቈለ ፡ ቀርነ ፡ ወጽፍረ ፡ (ዘፍጥ ፡ ፲፩ ። ሲራ-ጽ፱ ፡ ፲፪ ። ፴፱ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፷፰) ።

**አብቈለ ፤ (አስደራጊ)** ፤ አስበቀለ ፡ እንዲያበቅል ፡ እንዲያጸድቅ ፡ አደረገ ፤ ተክለ ፡ ለይኩን ፡ በማለት ፡ ገዛምና ፡ ዘር ፡ በመስጠት ፡ የፈጣሪና ፡ የቈፋሪ ፡ (ዘፍ፡ ፪ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፻፫) ። ዘርዐ ፡ ዘያበቍል ፡ ፈጣሪክ ፡፡ አበቍል ፡ ፆመ ፡፡ ዕፀ ፡ ዘእግዚ ፡ አብቈለ ፡፡ ይበልዕ ፡ ዘሎ ፡ ዕፀ ፡ ዘአብቈልክሙ ፡ (ሢራ-ጿ ፡ ፲፰ ። ኢሳ፵፩ ፡ ፲፰ ። ዳ፱ ፡ ፲፱ ። ዘፀ፲ ፡ ፭) ።


**በቍል ፤ (ላት ፤ አብቋል)** ፤ ቡቃያ ፡ በቈልት ፡ ብቅል ፡ ያታክልት ፡ ፍል ፡ ችግኝ ፡ ግልግል ፡ አኽል ፡ ተክል ፡ ሣር ፡ ቅጠል ፡ ሳይዘሩት ፡ የሚበቅል ፡ ማናቸውም ፡ ኹሉ ። ይሴሰይ ፡ በቍላተ ፡ ምድር ፡፡ አሕማላተ ፡ በቍላት ፡፡ በቍላት ፡ ቀታልያን ፡፡ ሥዕርተ ፡ ርእስክ ፡ ዘስሙር ፡ አብቋሉ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳፰ ። ግን፲ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫ ። ደራሲ) ።

**አብቍልት ፤ (ታት)** ፤ ሐረግ ፡ ዐጽቅ ፡ ስበቅ ፡ የማይሰበር ፡ እንደ ፡ ኸበ ፡ የሚተጣጠፍ ። ፍትሓ ፡ ለመንፈስየ ፡ አቡየ ፡ አብቍልታ ፡ በማእሰረ ፡ ጊጋይ ፡ አብቍልት ፡ ኢትንበር ፡ ሙቅሕታ ፡፡

**አብቍልታ** ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ሐረጉ ፡ ዐጽቁ ። በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ ብፁዕ ፡ አብቍልታ ፡ ወኮነ ፡ እምዘመደ ፡ ክቡራን ፡ ዘሀገረ ፡ እንጽና ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ፳፱ ።

**በቍላዊ** ፤ የቡቃያ ፡ የተክል ፡ ተክላም ፡ ባለተክል ። ኀይል ፡ በቍላዊ ፡ ወእንስሳዊ ፡ (አቀል) ።

**በቀልት ፤ (ታት)** ፤ ሰሌን ፡ ዘንባባ ፡ ፍሬው ፡ ተዘርቶ ፡ የሚበቅል ፡ ቁመታም ። ዘቀምኪ ፡ ይመስል ፡ በቀልተ ፡፡ ወፈረየት ፡ ይእቲ ፡ በቀልት ፡ ዐሥርተ ፡ ወክልኤተ ፡ አስካለ ፡ ሰቤሃ ። በቀልተ ፡ ተመርት ፡፡ በቀ



በቀልት ።

ልታት ፡ ወተምራት ፡፡ በቀልታተ ፡ ወፀበራተ ፡ አሥዐለ ፡ (ማሕልያ ፡ ፯ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ ማያ፳ ። ኢዮ፻፲፱ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ጥር፳፱ ። አርጋ ፡ ፬) ። በቀልት ፡ ግንዱ ፡ ዐመርት ፡

ቅጠሉ ፤ ተምር ፡ ፍሬው ። ዐምርንና ፡ ተምርን ፡ ተመልከት ።

**በቍላ ፤ ቢቈላ ፤ ብቈላ ፤ (ዐረ ፡ ብቊለን ፤ ብቊላእ)** ፤ በቊሙ ፡ ብቈላ ፡ ፋል ፡ ያበባ ፡ እኽል ፤ በቈልት ፡ የሚኾን ። (የውርድ ፡ ንዥ ፡ ስድብና ፡ ምላሽ) ፤ ከሰው ፡ ክፉ ፡ ዲቃላ ፤ ከእኽል ፡ ክፉ ፡ ባቊላ ፤ ከልብስ ፡ ክፉ ፡ ነጠላ ። ጠላት ፡ ይገፋል ፡ ዲቃላ ፡ ወራት ፡ ይገፋል ፡ ባቊላ ፤ ያግደረድራል ፡ ነጠላ ።

**በቍዐ ፤ ዖት ፤ (በቍዐ ፡ ይበቍዕ ፡ ይብቋዕ ። በቀወ)** ፤ መብቃት ፤ መኾን ፡ መገባት ፤ መርባት ፡ መጥቀም ፡ ግዳጅ ፡ መፈጸም ፤ መርዳት ፡ አይዞኽ ፡ ማለት ፤ ልመናን ፡ ምልጃን ፡ መስማት ፡ መቀበል ፤ ዐሺ ፡ በጎ ፡ ማለት ። ምስክሩን ፡ በተራው ፡ ተመልከት ። ይሥሐቅ ፡ ይበቍዕ ፡ ለዘቲ ፡ ሢመት ። ዘይበቍዕ ፡ ለምግበ ፡ ንዋይ ። ምንት ፡ ይበቍዕ ፡ ሥዋዕ ፡ ለአማልክት ። ዐርክ ፡ ወማኅፈር ፡ ይበቍዖ ፡ በመዋዕሊሆሙ ። እግዚ ፡ በቍዐኒ ፡ በሎቱ ። እስእለክሙ ፡ ብቍዑኒ ። ብቍዐኒ ፡ ከመ ፡ ትግበር ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ ፲፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፪ ። ሚራ ፲፱ ፡ ፲፱ ። ዓ ፡ ፳፫ ። ዮሴፍ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ። ፰ዕገ ፡ ፬ ፡ ማ፪) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በተበቍዐ ፡ ፈንታ ፡ በቍዐ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ትሬእዩ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘት በቍዖ ። አልቦ ፡ ዘበቋዕኩ ። አልቦ ፡ ዘይበቍዕ ፡ ዘይረቂ ። ፈቀደ ፡ ይትባረክ ፡ ወይብቋዕ ፡ እምኔክ ፡ (ስንክ ፡ መጋቢ፲ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፫ ። መክ፲ ፡ ፲፩ ። ፊልክ ፡ ፺፮) ።

**በቋዒ ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት)** ፤ የሚበቃ ፡ የሚጠቅም ፡ ጠቃሚ ፤ ግዳጅ ፡ ፈጻሚ ። ክነ ፡ በቋዔ ፡ ለሎሱ ። በቋዒ ፡ ተድላ ። አኮኑ ፡ በምንዳቤ ፡ በቋዕያነ ፡ ይከውኑ ። ኮኑ ፡ በቋዕያነ ፡ ከመ ፡ ይሥርዑ ፡ ንዋዮሙ ፡ (አርጋ ፡ ፭ ። ኪዳ ። ምሳ፲፯ ፡ ፲፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱ ፡ ፫) ። በበቋዒ ፡ ፈንታ ፡ ባቍዕ ፡ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት) ፡ ይላል ፤ ፍቹው ፡ አንድ ፡ ነው ። ባቍዕት ። ባቍዓኒሃ ። ባቍዓን ፡ (አርጋ ፡ ፩ ። ዘክ፭ ፡ ፲ ። ሄርማ) ።

**አብቍዐ** ፤ አበቃ ፡ አብቃቃ ፤ አስበቃ ፡ አስጠቀመ ።

**ተበቍዐ** ፤ ተጠቀመ ፡ ጥቅም ፡ አገኘ ፤ ተረባ ። ተማለደ ፡ ተለመነ ። ዘይትበቋዕ ፡ ቦቱ ፡ ሎቱ ። ትሩፋት ፡ ዘይትበቍዖ ፡ ባቲ ፡ እስ ፡ ይትመርሑ ፡ ቦቱ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፱ ፡ ፪ ። ፊልክ ፡ ፲፭) ።

**ብቍዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ቍዕት)** ፤ የበቃ ፤ የተጠቀመ ፡ ባለጥቅም ፡ (ሄርማ) ። ዳግመኛም ፡ በብቍዕ ፡ ፈንታ ፡ ባቍዕ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ባቍዐ ፡ ረስየኒ ። ባቍዐ ፡ ሎቱ ፡ ጸግዎ ፡ (ሄርማ ። መስተ) ።

**ብቍዐት ፤ በቍዔት ፤ (ታት)** ፤ መብቃት ፡ ብቃት ። መጥቀም ፡ መጠቀም ፤ አጠቃቀም ፤ ጥቅም ፡ ትርፍ ፤ ረብ ፡ ርባታ ፡ ጠቀሜታ ። ኢይከል ፡ በቍዔታ ፡ ለነፍሱ ። ኢይከውነክ ፡ ለበቍዔትከ ። እመ ፡ ኢተፈጸመ ፡ ነሢአ ፡ በቍዔት ፡ ባቲ ። ምስለ ፡ በቍዔታት ። እስመ ፡ ጸም ፡ በቍዔት ፡ ባቲ ። ከመ ፡ ደርኢ ፡ ዐበየ ፡ በቍዔታ ፡ ለሕማማት ፡ (ሚራ፴፯ ፡ ፲፱ ። ፪ነገ ፡ ፲፰ ። ፳፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፰ ። ድጓ ። አፈ ፡ ድ፰) ።

**በቍዔት** ፤ ልመና ፡ ምልጃ ፡ ጸሎት ፤ በጸሎትና ፡ በልመና ፡ የሚገኝ ፡ ጥቅም ። አንተ ፡ ተወከፍ ፡ ዘሎልነ ፡ ሰክዮተ ፡ ወበቍዔተ ፡ (ሊጦን) ።

**በቍዕ ፤ (ዓት)** ፤ በቍዔት ፤ ጥቅም ፡ ትርፍ ፤ የሚበቃ ፡ ዋጋ ። ጻማሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ባቍዕ ። አልባቲ ፡ ባቍዕ ። ይሁብ ፡ አብድ ፡ ዘአልቦ ፡ ባቍዕ ። ለዘአልቦ ፡ ባቍዕ ፡ ወሀብኩ ፡ ኀይልየ ፡ (ጥበ፫ ፡ ፲፩ ። ዕብ፯ ፡ ፲፰ ። ሚራ፳ ፡ ፲፬ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፬) ።

**አስተብቍዐ** ፤ ለመነ ፡ ማለደ ፤ ማላጅ ፡ አማላጅ ፡ ኾነ ፤ ዘበዘበ ፡ ማረኝ ፡ ማርልኝ ፡ አለ ። አሐተ ፡ ስእለተ ፡ አስተበቍዐ ፡ በኀቤከ ። በእንተ ፡ ምንት ፡ ታስተበቍዐኒ ። ወካዕበ ፡ ናስተበቍዖ ፡ ለእምላክ ፡ ምሕረት ። ጊዜ ፡ ጸሎትነ ፡ ወአስተብቍዖትነ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፭ ። አስቴ፭ ፡ ፫ ። ቅዳ) ።

—፤ ናዘዘ ፡ አጽናና ፤ ደስ ፡ አሰኘ ፤ አትዘን ፡ አታልቅስ ፡ አለ ። ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ልመና ፡ ነው ። ኢታብዝኑ ፡ አስተብቍዖትየ ። ያጽንዕክሙ ፡ ወያስተብቍዕክሙ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ (ኢሳ፵፱ ፡ ፬ ። ፩ተሰ ፡ ፫ ፡ ፪ ። ዘፍ፴፯ ፡ ፴፭ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፫) ።

**አስተብቋዒ** ፤ የሚማልድ ፡ የሚያማልድ ፤ ማላጅ ፡ አማላጅ ፤ አስታራቂ ። አስተብቋዕያን ፡ ለክሙ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፩ ። ቅዳ ፡ ሕር) ።

**መስተብቍዕ ፤ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ማልስና ፡ መስም ፡ በፍች ፡ አንድ ፡ ናቸው ። ገሞራውያን ፡ ይነብሩ ፡ በሎሱ ፡ ሕይወቶሙ ፡ ምስለ ፡ መስተብቍዓን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰) ።

**መስተብቍዕ ፤ (ጥሬ ፡ ዘር)** ፤ ምልጃ ፡ ልመና ፡ ዝብዘባ ፤ ጸሎት ፡ ጸዋት ፡ ሐዋርያት ፡ ለቁቦች ፡ የሠሩት ፤ በእንተ ፡ በእንተ ፡ እያሉ ፡ ኹሉን ፡ በየጸታው ፡ የሚጠሩ ። ይኸውም ፡ በቅዳሴ ፡ ትገዛ ፡ ይገኛል ፤ መሠረቱ ፡ ግን ፡ ሲኖዶስ ፡ ነው ። መስተብቍዕ ፡ ዘሐዋርያት ፡ (ቅዳ) ።

**በቍጸ ፤ ጾት ፤ (በቈጸ ፡ ይበቍጽ ፡ ይብቍጽ)** ፤ ማንደድ ፡ ማቃጠል ፤ ማያያዝ ፡ ማጋም ፤ ማፋም ፡ ማምረት ፡ ማብሰል ፡ ማንደርከክ ፤ መቈጣር ፡ መተርከስ ፤ መዝገን ፡ ማፈራ ፤ የከሰል ፡ የፍም ። ነሃቢ ፡ ዘይበቍጽ ፡ አፍሓመ ። ወይበቍጹ ፡ አፍሓመ ፡ (ኢሳ ፶፬ ፡ ፲፮ ። ዮሐ፲፰ ፡ ፲፰) ።

**ተበቍጸ** ፤ ፋመ ፡ መረተ ፤ ተጣራ ፡ ታፈሠ ።

**ብቍጽ ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ቍጽት)** ፤ የተጣራ ፤ የመረተ ፡ የበሰለ ፡ የጋከከ ፤ የተንደረከከ ። ረከቡ ፡ ፍሕመ ፡ ብቍጸ ። አንጻሕከ ፡ ለኢሳይያስ ፡ በፍሕመ ፡ እሳት ፡ ብቍጽ ፡ (ዮሐ፳፩ ፡ ፱ ። ጥበ ፡ ጠቢ ። ስንክ ፡ ታኅሣ፳ ። ሠኔ፲፱ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ምብቋጽ** ፤ (ጺት) ፤ ማንደጃ ፡ ምድጃ ፤ መሶማ ሪያ ፡ መተርከሻ ፡ መዝገኛ ፡ ማረፊያ ፤ ብረት ፡ ገል ።

**በቂቅ** ፤ **ቆት** ፤ (**በቀ ፡ ይበቅቅ ፡ ይብቅቅ**) ፤ መሠንጠቅ ፤ መተርተር ፤ ዕዳሪ ፡ ማውጣት ፡ የርሻ ።

**በቅቤቀ** ፤ በቀበቀ ፤ ኰተኰተ ፤ የማሽላ ።

**አንበቅበቀ** ፤ አንበቀበቀ ፤ ተንበቀበቀ ፤ የፈሳሽ ። ባቅቡቅን ፡ ተመልከት ።

**በር** ፤ (**ሱር ፡ ወዕብ ፡ ባር**) ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፤ ተማሪ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ። **በር ፡ ጤሜዎስ ። በር ፡ ባን ፤** (ማር፲ ፡ ፵፮ ። ማቴ፳፯ ፡ ፲፮) ።

**በሩ** ፤ ስመ ፡ ኪሩብ ፡ ገጸ ፡ ሰብእ ፤ ወልዳዊ ፡ ወልደ ፡ ሰብኣዊ ፡ ማለት ፡ ነው ። ፪ኛም ፡ ባር ፡ ብሎ ፡ ጐሽ ፡ የበረሓ ፡ እንስሳ ፡ ይላልና ፤ ገጸ ፡ ላሕምንም ፡ ያሳ ያል ። ፫ኛም ፡ ባርቡር ፡ ብሎ ፡ በንገተ ፡ ረኸም ፡ ወፍ ፡ ዋንተኛ ፡ የባሕር ፡ አሞራ ፡ ይላልና ፤ ገጸ ፡ ንስርንም ፡ ያሳ ያል ። ፬ኛም ፡ በርና ፡ ዕጓል ፡ አንድ ፡ ናቸውና ፤ ዕጓላዊ ፡ ዕጓለ ፡ አንበሳዊ ፡ አሰኝቶ ፡ ገጸ ፡ አንበሳን ፡ ያሳያል ። **በሩ ፡ መሩ ፡ መሊጦን ፡ ሱርትዮን ፡** (መዋሥ) ።

**ባሪ** ፤ (**ጽርእ**) ፤ መዲና ፤ ግንብ ፡ አዳራሽ ። ቢራን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። **ሱሳ ፡ ዘባሪ ፡** (ዳን፰ ፡ ፪) ።

**ብርእ** ፤ **—መቃ ፡ ሸንበቆ** ፤ **— በሪዕ ፡ በርዐ** ፤ **ብርዕ** ።

**በርብሮ** ፤ **ሮት** ፡ (**በርበረ ፡ ይበረብር ፡ ይበርብር ። በሪር ፡ በረ ፤ በረረ**) ፤ መበርበር ፡ መዝረፍ ፤ መበዝበዝ ፤ የቤትን ፡ ድልብ ፡ በቤት ፡ ያለን ፡ ገንዘብ ፡ ጕርጕሮ ፡ መውሰድ ፤ ባዶ ፡ ማስቀረት ። ጕድጓድ ፡ ቈፋሪ ፡ ዐፈሩን ፡ አውጥቶ ፡ ውስጡን ፡ ባዶ ፡ እንዲያደርግ ፤ እንደዚያ ፡ ማለት ፡ ነው ። **ሰልቦ ፡ ዘይክል ፡ በዊአ ፡ ቤተ ፡ ኀያል ፡ ወበርብሮ ፡ ንዋዮ ፡ እመ ፡ ኢቀደመ ፡ አሲሮቶ ፡ ለኀያል ፤ ወእምዝ ፡ ይበረብር ፡ ቤቶ ። እበረብሮሙ ፡ ኀይሎሙ ። በርበሩኒ ፡ ሾሎ ፡ ንዋይየ ፡** (ማር፫ ፡ ፳፯ ። ኢሳ፲ ፡ ፲፫ ። ጦቢ፩ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፻፰) ።

**በርባሪ** ፡ በቁሙ ፤ የሚበረብር ፤ ወራሪ ፡ ዘራፊ ።

**በርበር** ፤ ዘረፋ ፡ ምርኮ ፤ የብርበራ ፡ የዘረፋ ፡ ገንዘብ ። **እሬስየኪ ፡ በርበረ ፡ ለአሕዛብ ። እለ ፡ ይትካፈሉ ፡ በርበረ ፡** (ሕዝ፳፭ ፡ ፯ ። ኢሳ፱ ፡ ፫ ። ምሳ፩ ፡ ፲፫) ።

**በርበር** ፤ ያልተማረ ፡ ያልሠለጠነ ፡ ሕዝብ ፤ ፈደልና ፡ ጽሕፈት ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ የሌለው ፡ በቅሚያ ፡ የሚኖር ፡ ጭንጫ ፡ አረመኔ ፤ ሽፍታ ፡ ወያኔ ። ስመ ፡ ነገድ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፤ ከግብጽ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኝ ፡ የአፍሪቃ ፡ ክፍል ። የሱማሌም ፡ አገር ፡ በርበራ ፡ አቅኝውና ፡ ዘሩ ፡ የበርበር ፡ ቍራጭ ፡ ነው ፡ ይባላል ፤ በርበርነቱንም ፡ ግብሩ ፡ ይመሰክራል ። **ወመጽኡ ፡ በርበር ፡ አረማውያን ፡ ከመ ፡ ያመዝብሩ ፡ አብያተ ፡ መነኮሳት ። በመጥባሕተ ፡ በርበር ፡ ተቀትሉ ። አዘዘ ፡ እግዚእነ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ሀገረ ፡ በርበር ፡** (ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ጥር፳፯ ። ሠኔ፳፯ ። መስ ፡ ፩) ።

**በርበሪ** ፤ በርበራዊ ፡ የበርበር ፡ ሰው ።

**በርበሬ** ፤ (**ዐረ ፡ ፊልፊል ፡ ባባሪ**) ፤ ቊንዶ ፤ ቊንዶዶ ፡ ጠጕር ፡ ያረረ ፡ የተኰማተረ ። ቊንዶ ፡ በርበሬ ፤ መልኩ ፡ የበርበርን ፡ ጠጕር ፡ የሚመስል ። ቊንዶ ፡ መባልን ፡ ከሻንቅላ ፡ ጠጕር ፡ ወስዶታል ፤ መመሳሰል ፡ የጋራ ፡ ነውና ። **ገብር ፡ ጸሊም ፡ ይቤ ፡ አርኣያየ ፡ ጸሊም ፡ ወጸጕረ ፡ ርእስየ ፡ በርበሬ ፡** (ፈላስ ፡ ገ ፡ ፰) ።

**በርበሬ** ፤ (**ጽር ፡ ፐፐሬ**) ፤ በቁሙ ፤ ቀዮ ፡ በርበሪ ፡ በርበራዊ ፡ ከበርበር ፡ የመጣ ፡ የበርበር ፡ አታክልት ። ስሙ ፡ ፍልፍል ፡ ሲኾን ፡ ከበርበር ፡ አገር ፡ ስለ ፡ መጣ ፡ በርበሪ ፡ ሬ ፡ ይባላል ፤ ይኸውም ፡ ጕንደሬ ፤ በጌምድሬ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዐደስ ፡ ከምስር ፡ አገር ፡ ስለ ፡ መጣ ፡ ምስር ፡ ግብጥ ፡ ምስር ፡ እንዲባል ፡ (መጽ ፡ ፈው) ። በፐፐሬ ፡ አንጻር ፡ ሲፈቱት ፡ ግን ፡ ቀይሕ ፡ እሳታዊ ፡ ነበልባላዊ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በርበራዊነቱ ፡ ሳይቀር ፡ መልኩንም ፡ ግብሩንም ፡ ያሳያል ፤ ፐፐራን ፡ ተመልከት ። (መሾ ፡ በቱም ፡ ጊዜ) ፤ በሺዋ ፡ በትግሬ ፡ በወሎ ፡ በላስታ ፡ በጐዣም ፡ ያሳቸኹ ፤ አንድ ፡ እግር ፡ በርበሬ ፡ መንቀል ፡ ተስፏቸኹ ፤ ተኾሶ ፡ ለብልቦ ፡ አቃጥሎ ፡ ይፍጃችኹ ። ቊንዶውም ፡ ቢኾን ፡ እንደ ፡ ቍራ ፡ ኋላ ፡ ይጥቁር ፡ እንጂ ፡ ጥንቱን ፡ ሲያፈራ ፡ ቀይ ፡ ነው ፡ ይባላል ።



በርበሬ፡

**አበርበረ** ፤ አስበረበረ ፡ አዘረፈ ፡ አሶረረ ።

**አበርበሩ** ፤ ደቢ ፡ የሳማ ፡ ዐይነት ፡ ቅጠል ፤ በድብድባ ፡ ቦታ ፡ የሚበቅል ፤ እንደ ፡ በርበሬ ፡ የሚለበልብ ፡ የሚያንገበግብ ፤ ተኲሳ ፡ ኰስኲሳ ፤ ጭረቱ ፡ እንደ ፡ ናጫና ፡ እንደ ፡ ቃጫ ፡ ገመድ ፡ የሚኾን ፡ (አዋል) ።

**ተበርበረ** ፤ በቁሙ ፤ ተበረበረ ፡ ተበዘበዘ ፡ ተወረረ ፡ ተዘረፈ ። **ይትበረበር ፡ አብያቲሆሙ ። እለ ፡ በርበሩከ ፡ ይትበረበሩ ። ቴዴወዉ ፡ ሕዝብ ፡ ወተበርበሩ ። ረሰይክነ ፡ ለተበርብሮ ። ተበርበረት ፡ ታቦት ፡ ሕግነ ፡** (ሶፎ፩ ፡ ፲፫ ። ኤር፴፯ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፵፪ ፡ ፳፪ ። ጦቢ፫ ፡ ፬ ። ሉቃ ፡ ዕገዘ፱ ፡ ፲ ፡ ፴፱) ።

**ብርቡር** ፤ (**ራን ፡ ራት ፡ ብርት**) ፤ የተበረበረ ፡ የተዘረፈ ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ ባዶ ።

**ብርባሬ** ፤ (**ሳቢና ፡ ጥሬ ፡ ዘር**) ፤ መበርበር ፡ (ጥበ) መበርበር ፤ አበራብር ፡ ብርበራ ፤ ብዝበዛ ፡ ዘረፋ ፡ ወረራ ፡ (አዋል) ።

**በርበር** ፤ የዛፍ ፡ ስም ፡ ብርብራ ፡ ቅጠሉና ፡ ፍሬው ፡ ዓሣ ፡ የሚያሰክር ፡ ባሕር ፡ የሚያሾብር ።

**በርቢር ፤ (ዕብ ፡ ቦር ፤ ብኤር) ፤** ዐዘቅት ፡ የውሃ ፡ ወይም ፡ የእኽል ፡ ጕድጓድ ፡ ቋሻ ፡ ጕሬ ፡ መቃብር ፡ ውስጡ ፡ የተቦረቦረ ፡ (ሕዝ፴፪ ፡ ፳፫ ፡ ፴፬ ፡ ፳፪ ፡ ፳፬) ።

**በርባሮስ ፤ (ጽር ፡ በርበሮስ) ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፡ ታላቅ ፡ ስሬ ፡ ጕድጓድ ፤ ዕመቀ ፡ ምድር ፡ መሠረተ ፡ ምድር ፡ የጥልቅ ፡ ጥልቅ ፡ መጨረሻ ፡ ዕመቅ ፡ (አዋል) ።

**በሪድ ፤ ዶት ፤ (በረደ ፡ ይበርድ ፡ ይብርድ ። ዕብ ፡ ባራድ ። ዐረ ፡ በሩደ) ፤** መብረድ ፡ መቀዝቀዝ ፡ በረዶ ፡ መኾን ፡ መውረድ ፡ መርጋት ፡ የዝናም ፡ የውሃ ። በረደ ፡ መምሰል ፤ በረደ ፡ መልበስ ፡ በውርጭ ፡ በበረድ ፡ መሸፈን ፡ መታፈን ፡ የደጋ ፡ የቆላ ፡ እንደ ፡ የወልና ፡ እንደ ፡ ቢሒት ።

**በራዲ ፤ ብሩድ ፤** የበረደ ፡ በራድ ፡ ብርዳም ፡ በረዳም ፡ በራድ ፡ ቀዝቃዛ ።

**በረድ ፤ (ብ ፡ አብራድ ። ዕብ ፡ ባራድ ። ሱር ፡ ባርዳ ። ዐረ ፡ በረድ) ፤** በቁሙ ፡ በረዶ ፡ የዝናም ፡ ደንጊያ ፡ የውሃ ፡ ጠጠር ፡ በነፋስና ፡ በደመና ፡ ውኆጭ ፡ ከላይ ፡ ከሰማይ ፡ የሚወርድ ፡ የሚወረወር ፡ ዝናመ ፡ መዐት ፡ መጠኑ ፡ የበጠጥ ፡ ከዚያም ፡ የሚበልጥ ፡ የሚዛን ፡ ዐዋቂ ፡ የሚያክል ፡ (ዘፀ፱ ፡ ፳፫ ። ኢሳ፴ ፡ ፴ ። ሕዝ፴፰ ፡ ፳፪ ። ራእ፲፮ ፡ ፳፩) ። ወገሮሙ ፡ እግዚ ፡ እምሰማይ ፡ በእብነ ፡ በረድ ። ሞፀረ ፡ መዐቱ ፡ ይወርድ ፡ አብራደ ፡ (ኢያ፲ ፡ ፲፩ ። ጥበ፲፮ ፡ ፳፫) ።

—፤ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ምድራዊ ፡ በረዶ ፡ በመኪና ፡ ከውሃ ፡ ሲያተው ፡ የሚያወጡት ፡ ግንድ ፡ ግርንቡድ ፡ የጓንቃ ፡ ስባሪ ፡ የሚያክል ።


**በረድ ፤ (ዕብ ፡ ሺሴግ ፡ ቂራሕ) ፤** ብትን ፡ በረዶ ፡ ውርጭ ፡ ዐመዳይ ፡ ተበትኖ ፡ ወርዶ ፡ የሚረጋና ፡ የሚጋገር ፡ ባዘቶ ፡ ኑድፍ ፡ የሚመስል ፡ (መዝ ፡ ፻፵፯ ፡ ኢዮ፴ ፡ ፲፮) ። በረድ ፡ ወእስሐትያ ። ቈረ ፡ ከመ ፡ በረድ ። አጻዐድዎ ፡ ከመ ፡ በረድ ። በረድ ፡ ይዘንም ፡ ባዐሰ ፡ በልሞን ፡ (ጥበ፲፮ ፡ ፳፪ ። ኩፋ ፡ ፳፫ ። ኢሳ፩ ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፷፰) ።

**በረድ ፤** ነጭ ፡ የብርሌ ፡ የብርጭቆ ፡ ዐይነት ፡ ኑጣቱ ፡ የረጋና ፡ የተጋገረ ፡ ውርጭ ፡ የሚመስል ። አርአያ ፡ ዘሕብረ ፡ በረድ ። ባሕር ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ በረድ ፡ (ሕዝ፩ ፡ ፳፪ ። ራእ፬ ፡ ፮) ። የእብነኑን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ።

**አብረደ ፤** አበረደ ፡ አስበረደ ፡ አቀዘቀዘ ፡ በረዶ ፡ አደረገ ፡ አዘነመ ። ዘእንበለ ፡ እሳት ፡ አንደደ ፡ ወዘእንበለ ፡ ማይ ፡ አብረደ ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**በርደደ ፤** በረደደ ፡ ረጋ ፡ ጸና ፡ ደነገየ ፡ በርዳዳ ፡ ኾነ ። መታ ፡ ቀጠቀጠ ፡ ሞረደ ። ወበአእባን ፡ ሥጋሁ ፡ በርደዱ ፡ (ስንክ ፡ ጥን፳) ።

**መብረድ ፤ (ዐረ ፡ መብረድ ፡ ሞረድ) ፤** ማብረጃ ፡ ማቀዝቀዣ ። መሞረጃ ፡ ሞረድ ፡ መጋዝ ። ልሳኖሙ ፡ በሊኅ ፡ ከመ ፡ መብረደ ፡ ኀጺን ፡ ሞረድ ፡ (ዜና ፡ እስ) ።



መብረድ ፡

**በረሀ ፤ ሆት ፤ (በርሀ ፡ ይበርህ ፡ ይብራህ ። ዐረ ፡ በሪሀ ፤ በሀረ ። ዕብ ፡ ባሀር) ፤** መብራት ፡ መበራት ፡ መታየት ፡ መገለጥ ፡ ብርሃን ፡ መኾን ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ፡ ምንት ፡ ይበርህ ፡ እምፀሓይ ። ኢይበርሁ ፡ ከዋክብተ ፡ ሰማይ ። ይበርሁ ፡ ከመ ፡ ብርሃነ ፡ ሰማይ ። ወይበርህ ፡ ሎሙ ፡ ብርሃነ ፡ አምላክ ። ወምድር ፡ በርሀት ፡ እምስብሐቲሁ ። ዘይገብር ፡ ምጽዋተ ፡ እንዘ ፡ ይበርህ ፡ ገጹ ። በርሀ ፡ ልቦሙ ፡ ወኀሊናሆሙ ፡ (ሢራ፲፯ ፡ ፴፩ ። ኢሳ፲፫ ፡ ፲ ። ዳን፲፪ ፡ ፫ ። ሔኖ፳ ፡ ፳ ። ሕዝ፵፫ ፡ ፪ ። ቀሌ) ።

**ብሩህ ፤ (ሃን ፡ ሃት ፡ ርህት) ፤** የበራ ፡ የጠራ ፡ ነጭ ፡ የታየ ፡ ግልጥ ። ደመና ፡ ብሩህ ። ኳህናት ፡ ብሩሃን ፡ ከመ ፡ ፀሓይ ። ከመ ፡ ይኩና ፡ አዕይንቲክ ፡ ብሩሃተ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ቤት ። ጽዕዱት ፡ ወብርህት ፡ (ማቴ፲፯ ፡ ፭ ። መጥሥ ። ፪ዜና ፡ ፮ ፡ ፳ ። ማሕ፰ ፡ ፲) ።

**ብርህርህት ፤** የለምጽ ፡ ቡቃያ ፡ ነጣጭ ፡ ንቍጣ ፡ ነጠብጣብ ፡ (ዘሌ፲፫ ፡ ፴፰) ።

**በርህ ፤ (ሃት) ፤** ብርሃን ፡ ጸዳል ፡ ውጋግ ። እሳት ፡ ፍሕም ፡ ነበልባል ። በርህ ፡ ሠረቀ ፡ ለጻድቃን ። በርህ ፡ ወጽልመት ፡ (መዝ ፡ ፺፯ ። ዳን፺ ፡ ፸፪ ። ድጓ) ። ይስኣን ፡ መንገለ ፡ በርህ ፡ (ማር፲፬ ፡ ፶፬ ። ሉቃ፳፪ ፡ ፶፮) ። በርህ ፡ እሳት ፡ መባሉ ፡ መላሾች ፡ በእሳት ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ጣፉት ፡ እንጂ ፡ ፍችው ፡ ኹሉም ፡ አይደለም ።

**ብርሃን ፤ (ናት) ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፡ በቁሙ ፡ መኻልት ፡ መብራት ፡ ፀሓይ ፡ ጨረቃ ፡ ኮከብ ፡ የእሑድና ፡ የረቡዕ ፡ ፍጥረት ፡ (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ ፲፬—፲፰) ። ወይከውን ፡ ብርሃነ ፡ ወርኅ ፡ ከመ ፡ ብርሃነ ፡ ፀሓይ ። ብርሃነ ፡ ማኅቶት ። ወበእደዊሆሙ ፡ ይጸውሩ ፡ ብርሃናተ ፡ እሳት ፡ (ኢሳ፴ ፡ ፳፮ ። ሉቃ፰ ፡ ፲፮ ። ተረ ፡ ኤር) ።

**ብርሃነ ፡ ገጽ ፤** ደቅርታ ፡ ቸርነት ፡ ባለሟልነት ፡ የደስታና ፡ የፍቅር ፡ ምልክት ፡ (መዝ ፡ ፬) ።

**ብርሃነ ፡ ልብ ፤** ጥሩ ፡ ዕውቀት ፡ ጥበብ ፡ ትምርት ፡ መንፈሳዊ ፡ ሀብት ፡ (ፊልክ) ።

**ብርሃነ ፡ መብረቅ ፤** ነጸብራቅ ፡ ብልጭታ ፡ ብልጭልጭታ ፡ (ዕንቅ ፡ ፲፭) ።

**ብርሃነ ፡ ዐይን ፤** ማሚቶ ፡ ብሌን ፡ ጥራት ፡ ጥሩነት ፡ (መዝ ፡ ፴፯) ።

**ብርሃነ ፡ ስብሐት ፤** የክብር ፡ ብርሃን ፡ ሶምራ ፡ ምዕባር ፡ (ዕብ፩ ፡ ፫) ።

**ብርሃን ፤** ዐይን ፡ ማየት ። **ጸጕከ ፡ ሰዕዉር ፡ ብርሃኒ ፡** (ስንክ ፡ ነሐ፲፰) ።

**ብርሃን ፤ (ዐረ ፡ ቡርሃን) ፤** መምህር ፡ አብ ነት ፡ መፈክር ፡ መተርጕም ፡ ገልጦ ፡ የሚያስረዳ ፡ (ማቴ፰ ፡ ፲፱ ። አቡሻ ፡ ፺፫) ።

**ብርሃናዊ ፤** ብርሃናም ፡ ተፈጥሮው ፡ ከብርሃን ፡ የኾነ ፡ ንጹሕ ፡ ብሩህ ፡ ጽሩይ ፡ ጸዐዳ ። **መልአክ ፡ ብርሃናዊ ። ብርሃናውያን ። ብርሃናዊት ፡** (ቅዳ ፡ ሕር ። ክብ ፡ ነገ ። ገድ ፡ አዳ) ።

**ብርሃና ፤** ብሩሩና ፡ የተፋቀ ፡ የተራመመ ፡ ነጭ ፡ ስሌዳ ፡ ማኅስ ፡ ወይም ፡ ወረቀት ፡ ክርታስ ። ብርሂንና ፡ ብሩሩን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ።

**አብርሀ ፤** አበራ ፡ አስበራ ፡ አሳየ ፡ ገለጠ ፡ አስረዳ ። **አንደዱ ፡ እሳተ ፡ ወአብርሁ ። አብርሀ ፡ አዕይንትየ ። አብርሃ ፡ ለጥበብ ፡ ከመ ፡ ጎሕ ። እግዚ ፡ ያበርህ ፡ ሌተ ፡** (ዮዲ፲፫ ፡ ፲፫ ። ስንክ ፡ ነሐ፲፰ ። ሚሬ፳፱ ፡ ፴፪ ። መገ ፡ ፳፮ ። ዮሐ፳ ፡ ፳) ።

**መብርሂ ፤ (ሂት ፡ ህያን ፡ ያት) ፤** የሚያበራ ፡ አብሪ ፡ ገላጭ ፡ አስረጅ ። ዕንቍ ፡ ፈርጥ ፡ የልብስ ፡ አሮን ፡ ጌጥ ። **ፀሓይ ፡ መብርሂ ። መብርሂ ፡ ሎሱ ። መብርህያት ፡ ወማኅተማት ፡** (ዲራቢ ። አዋል ። ዘፀ ፳፰ ፡ ፳፯) ።

**መብርህ ፤ (ብ ፡ መባርህት) ፤** መብራት ፡ የፋና ፡ የቀንዲል ። **ሶበ ፡ ቦኡ ፡ በመባርህት ፡ ያጠፍኦ ፡ ፋኖስ ፡** (ሥርዐ ፡ አክሶ) ።

**ምብራህ ፤ (ሃት) ፤** መብሪያ ፡ ማብሪያ ፡ በታ ፡ መቅረዝ ።

(ጥ) **በራህ ፤—በራ ፡ መላጣ ፤—በርሐ ።**

**በሬዝ ፤ ዞት ፤ (በረዘ ፡ ይበርዝ ፡ ይብርዝ ። ዐረ ። ዕብ ፡ ባራዝ) ፤** ማግለል ፡ መለየት ፡ ዕዳሪ ፡ መውጣት ፡ ለመናጻት ። መበረዝ ፡ መበጥበጥ ፡ ጠጅ ፡ መጣል ፡ ጠላ ፡ መዘለል ፡ ፈሳሽን ፡ ከፈሳሽ ፡ መቀላቀል ።

**ተበርዘ ፤** ተበረዘ ፡ ተበጠበጠ ፡ ማገ ፡ ድፍድፉ ። ተለየ ፡ ተጣለ ፡ ሐሠሩ ፡ ጕድፉ ።

**ብሩዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ርዝት) ፤** የተበረዘ ፡ የተቀላቀለ ፡ ቅልቅል ፡ ቱሱሕ ።

**ተባረዘ ፤** በቂጠው ፡ ተቀላቀለ ። ተናፈሰ ፡ ተናጻ ፡ ተቃለለ ፡ (ገድ ፡ አዳ ፡ ገ፭፯) ።

**ተብሪዝ ፤** አተላ ፡ አንብላ ፡ ዝቃጭ ፡ ቃራቀጭ ፡ ሐሠር ፡ ሽንት ፡ ቅዘን ፡ ዐይን ፡ ምድር ። **ቀጥቀጥዎሙ ፡ ለመርገማት ፡ ወአረከብዎሙ ፡ ተብሪዝ ፡ ወእልተ** ግቢጥ ፡ (አዋል) ። ገብጥን ፡ እይ ።

**ብርዝ ፤ (ትግ ፡ በቱሐ) ፤** በቂጠው ፡ በተሐ ፡ ለጋ ፡ ጠጅ ፡ ጌሾ ፡ ያልበዛው ፡ ያልበሰለ ።

**በርሐ ፤ ሐት ፤ (በርሐ ፡ ይቤርሕ ፡ ይብርሕ ፡ ዐረ ፡ በሪሐ ። ዕብ ፡ ባራሕ ፡ ሸሸ) ፤** መብራት ፡ መገለጥ ፡ መብሕየት ፡ በራ ፡ መኾን ፡ መመለጥ ፡ መሸሽ ፡ ማምለጥ ፡ መሮጥ ፡ መፈርጠጥ ፡ ከዱር ፡ ከበረሓ ፡ መግባት ። በንሐንና ፡ ቀርሐን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**በራሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት) ፤** በራ ፡ መላጣ ፡ ራሰ ፡ ገላጣ ፡ ወገኑ ፡ የሸሸ ፡ ከዐታው ፡ የታጣ ፡ የራሱ ፡ ቈርበት ፡ መሳልና ፡ ነት ፡ ሳንባና ፡ ጕበት ፡ የሚመስል ። (ዘሌ ፲፫ ፡ ፵ ። ፬ነገ ፡ ፪ ፡ ፳፫) ። **ለሊልሳዕ ፡ ነዊኆ ፡ ቀሰሙ ፡ ወበራሕ ፡ ርእሱ ፡** (ስንክ ፡ ሠኔ፪) ። በረኸኛ ፡ የበረሓ ፡ ሰው ፡ ዐዳኝ ፡ መንኰሴ ።

**ብርሐት ፤** በራ ፡ ቡሓ ፡ መኾን ፡ ቡሕነት ፡ በራነት ፡ መላጥነት ። ሽሽት ፡ በረሓ ፡ መግባት ፡ (ዘሌ፲፫ ፡ ፵፪ ፡ ፵፫) ። **ብርሐት ፡ ትፃእኪ ። ውስተ ፡ ሎሱ ፡ ርእስ ፡ ብርሐት ። ጴጥሮስ ፡ ቦቱ ፡ ብርሐት ፡** (ኢሳ፫ ፡ ፳፬ ። ፲፭ ፡ ፪ ። ቀሌ) ።

**በረሐ ፤** በቂጠው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ (ዐማርኛ) ።

**በርዮ ፤ ዮት ፤ (ባረየ ፡ ይባሪ ፡ ይባሪ ። ዐረ ፡ በረይ) ፤** መለወጥ ፡ መተካት ፡ ማፈራረቅ ፡ ማስተጋገዝ ፡ ማስተራረፍ ። መግዛት ፡ ባሪያ ፡ ማድረግ ። መጸሕፍት ፡ ግን ፡ በባረየ ፡ ፈንታ ፡ አስተባረየ ፡ ይላሉ ። **ያስተብሪ ፡ ክረምተ ፡ በሐጋይ ፡ ወመፀወ ፡ በጸደይ ። ኀምስተ ፡ ዐራዘ ፡ በዘያስተባሪ ። ያስተባሪ ፡ ወርኀ ፡ ምልአተ ፡ ወሕጸተ ፡ ዐውደ ፡ ብርሃኑ ። ይዕጥኑ ፡ በአስተባርዮ ፡ እደው ። ከመ ፡ ዘያስተባሪ ፡ የማኖ ፡ ልዑል ፡** (መጽ ፡ ምስ ። ዘፍ፡ግ፳ ፡ ፳፪ ። አርጋ ፡ ፭ ። ግንዘ ። መገ ፡ ፻፯) ። አባረየ ፡ አስተባረየ ፡ ቢል ፡ አድራጊ ፡ ኹኖ ፡ ከባረየ ፡ ቢደረብ ፡ እንኳ ፡ ለብቻው ፡ አስደራጊ ፡ አይኾንም ።

**ተባረየ ፤** ተለዋወጠ ፡ ተፈራረቀ ፡ ተጋገዘ ፡ ተራረፈ ። **ዘእንበለ ፡ ይኩን ፡ ተባርዮ ፡ ሌሊት ፡ ወመዓልት ። ወእምዝ ፡ ተባረዩ ፡ ፀሓይ ፡ ወወርኅ ፡ ወከዋክብት ። ኀብረ ፡ በተባርዮ ። ዘበጥዎ ፡ በአብትር ፡ እንዘ ፡ ይትባረዩ ፡** (መቃ ፡ ገ፲ ። ፳፫ ። ስንክ ፡ ጥቅ፱ ። ሐም፳) ። ተገዛ ፡ ባሪያ ፡ ኾነ ፡ ባሪያ ፡ ተባለ ፡ ተሸጠ ፡ ተለወጠ ።

**ብሬት ፤ እብሬት ፤** ፈረቃ ፡ ፈንታ ፡ ተራ ፡ ሰሞን ፡ የጊዜ ፡ ክፍል ። **ሰመ ፡ በጽሐ ፡ ዕለተ ፡ እብሬታ ፡ ለአስቴር ፡ ከመ ፡ ትባእ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ። ወፈጺም ፡ መዋዕለ ፡ እብሬቱ ፡ አተወ ፡ ቤቶ ። ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ዘእብሬቱ ፡ ይእቲ ፡ ዓመት ። መዋዕለ ፡ እብሬትከ ፡ እብሬተ ፡ ርትዕ ፡ ወማህል ። እብሬተ ፡ ሰዐታት ፡** (አስቴ፪ ፡ ፲፭ ። ሉቃ፩ ፡ ፳፫ ። ዮሐ፲፩ ፡ ፶፩ ። ስንክ ፡ ጥር፳ ። ሰዓታት ፡ ፳፫ ፡ ፴፬) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በበእንተ ፡ ፈንታ ፡ እየገባ ፡ በስና ፡ ምክንያት ፡ ይኾናል ። **ከመ ፡ ትሕየው ፡ ነፍስየ ፡ በእብሬትኪ ። ይትቀነይ ፡ ሎቱ ፡ በእብሬትከ ፡** (ዘፍ፲፪ ፡ ፲፫ ። ዮዲ፲፩ ፡ ፯) ።

**በረየ ፤** በቂጠው ፡ (ጥየ) በረየ ፡ በረገገ ፡ በሬኛ ፡ ወገሸ ፡ ደነበረ ፡ ፈራ ፡ ደነገጠ ። (ተረት) ፡ እባብ ፡ ያየ ፡ ልጥ ፡ ቢያይ ፡ በረየ ። አበራየ ፡ አረበየ ፡ አኰደ ፡ አስኰደ ፡

አስረገጠ ፡ አስጠቀጠቀ ። ማበራየት ፡ ያውድማ ፡ ማረባየት ፡ የጤፍ ፡ ዕርሻ ፡ ነው ፡ መሬቱ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ከብት ፡ ይንዳበታል ። በሬ ፡ በረት ፡ ባሬያ ፡ ባሬታ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡ በዐረን ፡ እይ ። የወዲያኛው ፡ ትግሬ ፡ ሐባብም ፡ ክሕደ ፡ ቢል ፡ በረየ ፡ ይላል ፡ ምስጢሩ ፡ ፈራ ፡ ደነገጠ ፡ ካለው ፡ ይገባል ።

**በርዮድስ ፤(ጽር ፡ ፔሪዎዶስ)፤** ቀመር ፡ የቀመር ፡ ስም ፤ የጨረቃ ፡ ቢኾን ፡ ፲፱ ፤ የፀሓይ ፡ ቢኾን ፡ ፭፻፴፪ ፡ ዓመት ። ሲያበዛ ፡ በርዮድሳት ፡ ይላል ፡ (አቡሻ ፡ ፭፻፷) ።

**ብርያል ፤(ጽር ፡ ቤሪያል)፤** የሰይጣን ፡ ስም ፤ ቤልሖርን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (፪ቆር ፡ ፮ ፡ ፲፭ ። ፪ ፡ ፲ ። ፪፫ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ። ፴ ፡ ፪ ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ። ፷ ፡ ፳ ፡ ፲፮) ።

**ብርያሚን ፤—ሕጹጻን ፤—ድርያሚን ።**

**በረከ ፤ ከት ፤(በረከ ፡ ይበርክ ፡ ይብርክ ። ዕብ ፡ ባራኽ ። ሱር ፡ ብሬኽ ። ዐረ ፡ በረከ)፤** መብረክ ፡ መብረክረክ ፡ መንበርከክ ፤ ጕልበትን ፡ ማጠፍ ፡ በጕልበት ፡ መቆም ፤ መስገድ ፤ ተንበርክኮ ፡ መኼድ ፤ ተጣጥፎ ፡ መተኛት ፡ (ጥኵ) መኵድኵድ ፡ (ዘኁ፳፬ ፡ ፱፯) ። ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ገመል ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ በረከ ፡ በብረኪሁ ፡ ወኢተንሥአ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፲፱) ።

**ብሩክ ፤(ካን ፡ ካት ፡ ርክት)፤** የበረከ ፡ የተንበረከከ ፡ እንብርክ ።

**ብርክ ፤(ብ ፡ ብረክ ፤ አብራክ)፤** ጕልበት ፡ ጫፍን ፤ ማቀፊያ ፤ መታጠፊያ ፡ መንበርከኪያ ። አዕደወኒ ፡ እስከ ፡ ብርክ ። ወደክመኒ ፡ ብረክየ ፡ በጾም ። አብራኪክ ፡ እለ ፡ አውተራ ፡ ስግደተ ። ሐቂፍ ፡ በአብራክ ። በእንተ ፡ አብራኪሃ ፡ እለ ፡ ሐቀፋከ ፡ (ሕዝ፯፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፻፰ ። ድራሲ ። አርጋ ፡ ፭ ። ሳታት) ። ብራኪ ፡ ብርኮማ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**አብረከ ፤** አበረከ ፡ አብረከረከ ፤ አንበረከከ ፡ አሰገደ ፡ በጕልበት ፡ አቆመ ፤ ራሱን ፡ ሰውነቱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በበረከና ፡ በአብረከ ፡ ቦታ ፤ ይልቁንም ፡ በበረከ ፡ ፈንታ ፡ አስተብረከ ፡ ይላል ፡ እያሰኘም ። አስተብረከ ፡ በብረኪሁ ፡ ከመ ፡ ይስተይ ። አስተብረከ ፡ ወአስተብቍዖ ። ሰገደ ፡ ሎቱ ፡ ወአስተብረከ ። አስተብርኮ ፡ እለ ፡ መነና ፡ (መሳ፯ ፡ ፭ ። ማርቆ ፡ ፲ ። ቀሌ ። ድራሲ) ። ዳግመኛም ፡ በአብረከ ፡ ፈንታ ፡ አቤተ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፵፩ ፡ ፲፭) ።

**ባርከ ፤ ከት ፤(ባረከ ፡ ይባርክ ፡ ይባርክ)፤** ማመስገን ፤ ከመንበርከክ ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ተንበርክኮ ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ። ባርኮና ፡ በሬክ ፡ በሴም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ የዱሮ ፡ ሰዎች ፡ አበው ፡ ቀደምት ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ የፈጣሪን ፡ ስም ፡ ሲጠሩ ፡ ሲጸልዩ ፡ ሲያመሰግኑ ፡ ሰግደው ፡ ተንበርክከው ፡ ነበረና ፤ ባረከ ፡ ማለት ፡ የኹሉንም ፡ ስልት ፡ ያሳያል ። ይባርክዎ ፡ ዅሉ ፡ ግብረ ፡ እግዚ ፡ ለእግዚ ። ወባረኩ ፡ ዘ ፡ ቡራኬ ። ባርኩ ፡ ለስሙ ፡ በዅሉ ፡ ጊዜ ፡ (ዳንኤ ፡ ፫፳—፺፯ ። ዘፀ፲፰ ፡ ፭ ። ሚራ፵፱ ፡ ፵፭) ።

**ባረከ ፤** በቁሙ ፤ አማተበ ፡ ጸሎት ፡ ቡራኬ ፡ ደገመ ። ለእኩት ፡ (ለእኩቱ) ፡ ባረከ ፡ ወፈትቶ ። ኀቡረ ፡ ይባርኩ ፡ ማእደ ፡ በውስተ ፡ ጸሎት ። ኢይባርኩ ፡ ላዕለ ፡ በጸል ፡ (ቅዳ ። ማብ፱ ፡ ፵፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፯) ።

—፤ መረቀ ፡ መልካም ፡ ስጦታን ፡ ሰጠ ፡ ሰው ፡ ተመኘ ፡ ተናገረ ፡ አበዛ ፡ ሰጠ ። አከበረ ፡ ሾመ ፤ አበዛ ፡ አበረከተ ፡ (ዘፀአ ፡ ፳፱ ፡ ፳፫ ። ፲፱ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ፲፯ ፡ ፲፮) ። ወዘእንበለ ፡ ካሕድ ፡ ዘየዐቢ ፡ ይባርኮ ፡ ለዘይንእስ ። ብሔር ፡ ኀበ ፡ ብልዑ ፡ ኅብስተ ፡ ዘባረከ ፡ እግዚእነ ፡ (ዕብ፯ ፡ ፯ ። ዮሐ፮ ፡ ፳፫) ።

—፤ ሰደበ ፡ አዋረደ ፡ ዐማ ፡ ነቀፈ ፡ ረገመ ፡ ካደ ። ውስተ ፡ ገጽከ ፡ ይባርከከ ። ባርኮ ፡ ለእግዚ ፡ ወሙት ። ባረካሁ ፡ ለእግዚ ፡ ወለንጉሥኒ ፡ (ኢዮ፩ ፡ ፲፱ ። ፱ ፡ ፳ ። ፱ ። ፫ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ስንክ ፡ ታኅ፩) ።

**አባረከ ፤** አስባረከ ፡ አስመረቀ ፡ አስመሰገነ ፡ ቡሩክ ፡ አሰኘ ።

**ተባረከ ፤(ተደራጊና ፡ ተደራራጊ)፤** በቁሙ ፡ ተመሰገነ ፡ ተመረቀ ፡ ቡራኬ ፡ ምስጋና ፡ ተቀበለ ፤ በዛ ፡ በረከተ ። ይትባረክ ፡ እግዚ ። ሰገደ ፡ ሎቱ ፡ ወተባረከ ፡ እምኔሁ ፡ (ሩት፩ ፡ ፲፱ ። መዋሥ) ። ተባራረከ ፡ ተመራረቀ ፤ ተመሰጋገነ ፤ ርስ ፡ በርሱ ። ይትባረኩ ፡ ቦቱ ፡ አሕዛበ ፡ ምድር ። ተባረኩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ (መዝ ፡ ፸፩ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ የካ፱) ።

**ቡሩክ ፤(ካን ፡ ካት ፡ ርክት)፤** በቁሙ ፡ የተባረከ ፡ የተመሰገነ ፤ ክቡር ፡ ምስጉን ፡ ምሩቅ ። ሙሴ ፡ ዘቡሩክ ፡ ዝክሩ ። ቡሩክ ፡ አንተ ፡ አምላክነ ። ቡርክት ፡ አንቲ ፡ እምአንስት ፡ ወቡሩክ ፡ ፍሬ ፡ ከርሥኪ ። ቅብዐ ፡ ቡሩክ ፤ ቅዱስ ፡ (ሢራ፵፭ ፡ ፩ ። ዮዲ፲፫ ፡ ፲፯ ። ሉቃ፩ ፡ ፵፪ ። ዘፀ፴፱ ፡ ፳፭) ።

**ቡራኬ ፤(ክያት)፤** ሳቢና ፡ ጥሬ ፡ ዘር ። መባረክ ፡ (ጥባ) መባረክ ፤ አበራረክ ፤ በቁሙ ፡ ቡራኬ ፤ ምስጋና ፡ ምርቃት ። ባርከኒ ፡ አባ ፡ ለወልድከ ፡ ዝኬ ፤ እስመ ፡ ልማዱ ፡ ለመምህር ፡ ቡራኬ ። ጸሎተ ፡ ቡራኬ ። ቡራኬሁ ፡ ለሴም ። ቡራኬ ፡ ወመርገም ። ተጽናስ ፡ ክነ ፡ መርገመ ፡ ወብዐልስ ፡ ክነ ፡ ቡራኬ ፡ (ድራሲ ። ቅዳ ። ያዕቆ ፡ ፲ ። አፈ ፡ ተ፲፰) ።

—፤ የመክፈልት ፡ ወግ ፤ ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ለባለመንቹ ፡ የሚሰጥ ። እሊሁም ፡ መሪጌታና ፡ ቄስ ፡ ዐቃቢ ፡ ናቸው ።

**በረከት ፤(ታት)፤** በቁሙ ፤ ማበርከት ፤ መበርከት ፡ አበረከከት ፤ ብርከታ ፡ ብዛት ። ምስጋና ፡ ምርቃት ፤ ቡሩክ ፡ መባል ፡ ጸጋ ፤ ሀብት ፤ ድልብ ፡ ዐባባ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ። በረከተ ፡ ኅብስት ። በረከቲ ፡ አሮን ፡ ፊት ፡ ባዕለ ፡ ሕዝብከ ። ክብር ፡ ወስብሐት ፡ ወ

በረከት ። ሆሎ ፡ በረከት ፡ እሴ ፡ ባረከኒ ፡ እግዚ ። በረ ከተ ፡ ግብጽ ። ትበልዑ ፡ በረከተ ፡ (ትር ፡ ወን ። ሚራ ፴፮ ፡ ፳፱ ። ራእ ፭ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ኩፋ ፡ ፲፱ ። ዘፍኖ ፴፭ ፡ ፲፰ ። ኢሳ ፶፭ ፡ ፱) ።

**እስተባረከ** ፤ አበራረከ ፡ አመራረቀ ፡ አመሰጋገን ። ዳግመኛም ፡ አባረከ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አስተባረከ ፡ ይላል ፤ ምክንያቱም ፡ የባረከ ፡ ቤት ፡ ተደፋፊ.ው ፡ ከተደራራጊው ፡ እንዲደረብ ፤ አስደራጊውም ፡ ከደራራጊው ፡ ይደረባልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። መደረቡም ፡ ሥርወ ፡ ቀለሙ ፡ ራብዕ ፡ ስለ ፡ ኾነለት ፡ ነው ፤ ተቃተለ ፡ አስተቃተለ ፡ እንደ ፡ ማለት ፤ አስተን ፡ እይ ።

**ብርኮት** ፤ የደንጊያ ፡ ገርንቡድ ፡ ወይም ፡ የብረት ፡ ዙሓ ፡ ከባድ ። ወበኡ ፡ ከልኤቱ ፡ እምእግብርቲሁ ፡ በሌሊት ፡ ወአንበሩ ፡ ዲበ ፡ ገጹ ፡ ለሰምከር ፡ ንጉሥ ፡ ፋርስ ፡ ብርኮተ ፤ ወነበረ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ ወካልኡ ፡ ዲበ ፡ እገሪሁ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ አረጋዊ ፡ ዐቢይ ፡ ወሞተ ፡ ሶቤሃ ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፵፰) ።

**ብርኩታ ፡ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፡ በፍም ፡ የሚበስል ፡ ርሚጦ ፡ ቂጣ ፤ ሲበሉት ፡ የሚያጠግብ ፡ የሚመክት ፡ የሚበረክት ፡ የጭብጦ ፡ ዐይነት ። ከመ ፡ በላዕሌሁ ፡ ያስተርኢ ፡ ግብረ ፡ በሲታ ፤ ዘዕውሩ ፡ ተወልደ ፡ ብርኵታ ፡ (ቅኔ) ።

**ቢረሌ ፤ (ልያት ። ጽር ፡ ቢሪሊዮን)** ፤ ዕንቍ ፡ ፈርጥ ፤ የብርሌ ፡ የብርጭቆ ፡ ደንጊያ ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፳ ። ጦቢ ፲፫ ፡ ፲፯) ። ሳምን ፡ በቢረሌ ፡ ወታስዕ ፡ በወራውሬ ። አናቅጽኪ ፡ ዘቢረሌ ፡ (ራእ፳፩ ፡ ፳ ። ኢሳ፶፬ ፡ ፲፪) ። በቁሙ ፤ ብርሌ ፡ ብርጭቆ ፡ ንጹ ፡ ጥሩ ። ይሰትዩ ፡ ወይነ ፡ በማህው ፡ ወቢረሌ ። ምስኪ ፡ ዘውስተ ፡ ቢረሌ ። ቢረልያት ፡ ብዙኃት ፡ (ዓሞ፮ ፡ ፮ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፱ ። ፊልክ ፡ ፻፴፯) ።

**በርሙዳ ፤ (ቅብጥ)** ፤ የወር ፡ ስም ፡ ሚያዝያ ፡ በጽርእ ፡ ፈርሙ(ቲ)ኒ ፡ ይባላል ፡ (ገድ ፡ አዳ ፡ ኤርጋ ፡ ፪ ፡ ፯) ። በርሙዳ ፡ ይሰመይ ፡ ፈርሙኒ ፡ (አቡሻ ፡ ፳ ። ተረ ፡ ቁር) ።

**በረምሃት ፤ (ቅብጥ)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ስመ ፡ ወርኅ ፡ መጋቢት ። በጽርእ ፡ ፋሚኑት ፡ ይባላል ። በረምሃት ፡ ይሰመይ ፡ ፋሚኑት ፡ (አቡሻ ፡ ፰ ። ተረ ፡ ቁር ፳፭) ።


**በርሞስ** ፤ አስቄጥስ ፡ የንመከሲሞስ ፡ የናርሳንዮስ ፡ ገዳም ፤ ደብረ ፡ ሮም ፡ ገዳመ ፡ ሮም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳፮) ።

**ብርኒ** ፤ ድመት ፡ የጽርኢ ፡ ዐይነት ። ዐይነ ፡ ብር ፡ ዐይናማ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ለድመት ፡ አያበሩላት ፡ እንዲሉ ።

**ብራና ፤ (ዐማርኛ ። ጽር ፡ ሜምብራና)** ፤ በቁሙ ፡ ብርሃና ፤ በርሀን ፡ ተመልክት ። ኅልፍ ፡ አሐደ ፡ ብራና ፡ ወእምዝ ፡ ኅሲፈከ ፡ ሰመንተ ፡ አዕማደ ፡ ወዐሥርተ ፡ ወሠለስተ ፡ መሥመራተ ፡ ትረክብ ፡ መትልወ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ፡ (አዋል) ።

**በረዐ ፤ ዖት ፤ (በርዐ ፡ ይበርዕ ፡ ይብራዕ ። ዐረ ፡ የሪዐ ። ዕብ ፡ ያራዕ)** ፤ መራድ ፡ መንቀጥቀጥ ፤ መታወክ ፡ መናወጥ ፡ መገፋት ፡ መናጥ ፡ መወዛወዝ ፤ ከፍርሀት ፡ ከንፋስ ፡ የተነሣ ፡ (ማቴ፲፭ ፡ ፯) ።

**ብርዕ ፤ (ብ ፡ አብራዕ)** ፤ ሸንበቆ ፡ የጕኽ ፡ መቃ ፡ የሸንበቆ ፡ ዐይነት ፡ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ አገዳ ፡ ቅልጥም ። በቁሙ ፡ የጸሓፊ ፡ ብር ፤ የገብስ ፡ የስንዴ ፡ ብር ፡ ገለባ ፡ ሣር ፡ ቁሻሻ ። በትረ ፡ ብርዕ ። ብርዐ ፡ ባሕሩስ ። አብትር ፡ ፀቡላን ፡ ወአብራዕ ፡ ቅጥቁጣን ። ዐምደ ፡



ብርዕ ፡

ወአብራዲሃ ፡ (ኢሳ፴፯ ፡ ፯ ። ፳ ፡ ፴፩ ። መጽ ፡ ምስ ። ዘዐ፳፭ ፡ ፴፩—፴፯) ። ስብዐቱ ፡ ሰብል ፡ ዘሠዊት ፡ ዘዝሙረጹ ፡ እምአሐዱ ፡ ብርዕ ። ብርዐ ፡ ይመስሎ ፡ መፍጽሕ ። ማዕር ፡ ወብርዕ ፡ ዘይየብስ ። እሳት ፡ እንተ ፡ ትበልዕ ፡ ብርዐ ፡ (ዮሴፍ ። ኢዮ፴፩ ፡ ፳ ፡ ፲፫ ፡ ፳፭ ። ዮኤ፪ ፡ ፭ ። ዓብድ ፡ ፲፰ ። ዘፀ፳ ፡ ፲፪ ። ፲፭ ፡ ፯) ። ብርእ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጡ ፡ በአልፍ ፡ ቢጣፍ ፡ ግን ፤ የማግሰኞ ፡ ፍጥረት ፡ ያሰኛል ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪) ።

**ብርፎሪከን ፤ (ጽር ፡ ፕሮፎሪኮስ)** ፤ የትንቢትና ፡ የስብከት ፡ የተማጻጽ ፡ ቃል ፡ ጩኸ ፡ ገንትቶ ፡ አሰምቶ ፡ የሚናገሩት ። ወብርፎሪከንኒ ፡ ውእቱ ፡ ቃል ፡ ዘሰምዐዎ ፡ ነቢያት ፡ እምእግዚ ፡ ወውእቱ ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ ጎር) ።

**በረጸ ፤ ጾት ፤ (በረጸ ፡ ይበርጽ ፡ ይብርጽ ። ዕብ ፡ ባራጽ ፤ ዐለፈ ፡ ተረፈ ፤ ፈልቶ ፡ ገንፍሎ)** ፤ ማንጸብረቅ ፡ ማሽብረቅ ፤ ማወልወል ፡ ማጽደልደል ፤ የመልክ ፡ የፊት ።

**ተባረጸ** ፤ ተብለጨለጨ ፡ ብልጭልጭ ፡ ቍልጭልጭ ፡ አለ ። እምቅድመ ፡ ይትባረጹ ፡ ከዋክብት ፡ (ቅዳ ፡ አፈ) ።

**በረጽ ፤ (ዐረብ)** ፤ ለምጽ ፡ ንጭ ፡ የሚብለጨለጭ ።

**በረቀ ፤ ቆት ፤ (በረቀ ፡ ይበርቅ ፡ ይብርቅ ። ዕብ ፡ ባራቅ ። ሱር ፡ ብራቅ ። ዐረ ፡ በረቀ)** ፤ መብረቅ ፡ ብልጭ ፡ ማለት ፤ መፍለቅ ፡ ማንጸብረቅ ፤ መወርወር ፡ መመዘዝ ፤ የመብረቅ ፡ የሰይፍ ። ብርቅ ፡ ድንቅ ፡ ታይቶ ፡ የማያውቅ ፡ መኾን ፤ መታየት ፡ መገለጥ ። በረጸና ፡ በረቀ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ በረጽ ፡

ክበረቀ፡ ወጥቷል ። በዕጠሱ፡ ይበርቅ፡ ብርሃን ። ወሳትው፡ ይበርቅ ። በረቀ፡ ሥጋሆሙ ። ግብተ፡ በረቀ፡ መብረቅ፡ ዲቤሁ፡ እምሰማይ፡ (ኢዮ፡፴፯፡ ፬ ። ናሖ፡ ፫ ። መቃ፡ ፲፪ ። ድት ። ግብ፡፱፡ ፫) ። መበርቋት፡ መገርጣት፡ ያገዘመራ ።

**አብረቀ**፤ አበረቀ፡ አባረቀ፤ አብረቀረቀ፡ መብረቅ፡ ጣለ፡ ወረወረ፤ አበራ፡ ገለጠ፤ ብልጭ፡ አደረገ ። እግዚ፡ አብረቀ፡ መብረቀ ። አብርቅ፡ መባርቅቲከ ። ፀሓየ፡ ጽድቅ፡ ዘሞአ፡ ሰሞት፡ ያበርቅ፡ ጸዳሉ፡ ባዕሌ፤ ። አራዊት፡ እለ፡ እምውስተ፡ ዐይኖሙ፡ ፀዋገ፡ ቀለምጺጸ፡ ያበርቁ፡ (፪ነገ፡ ፳፪፡ ፲፭ ። መዝ፡ ፻፲፫ ። አፈ፡ ድ፬ ። ጥበ፡፲፩፡ ፲፱) ።

**መብረቅ**፤ (ብ፡ መበርቅት)፤ በቁሙ፡ የእሳት፡ ሰይፍ፡ የእሳት፡ ፍላጻ፡ በዝናም፡ ጊዜ፡ ከደመና፡ አፎት፡ የሚመዘዝ፡ የሚወረወር ። ብልጭታ፡ መብረቅ ። መብረቅ፡ ወፀዓዕ፡ ወነጐድጓድ ። ይረውጽ፡ መብረቅ፡ ቅድመ፡ ነጐድጓድ ። ገብረ፡ መባርቅተ፡ ለዝናም፡ (ቅዳ፡ ኤጲ ። ራእ፡፬፡ ፭ ። ሚራ፡፴፭፡ ፲ ። ኤር፡፲፡ ፲፫) ።
—፤ የክብር፡ ብርሃን፡ ሙራ፡ ምዕዛር ። ሰላም፡ ለሥንኪ፡ ዘአዋክየ፡ መብረቃ፡ ለብሔረ፡ ጽልመት፡ ወጣቃ ። መብረቅ፡ ሰሥጋሁ፡ ክለላ፡ (ስንክ፡ መጋ፳ ። ሚያ፩) ።

**በረቅ**፤ በቁሙ፤ ነጭ፡ ዐፈር፡ ደንጊያ፡ ብሕክ፡ ጠመኔ፡ የኖራ፡ ዐይነት ።

**ብርቅ**፤ በቁሙ፤ ወትሮ፡ የማይታይ፡ በኹሉ፡ የማይገኝ፡ ድንቅ፡ ሥራ፡ ጉድ፡ ታምራት፡ መንከራት ።

**በራቂኒም**፤ (ዕብ፡ ባርቃኒም)፤ ነጣጭ፡ እሾኾች፡ ኵሽሽሎች፡ ወይም፡ ግራሮች፡ የግራር፡ ዐይነቶች፤ አንዱን፡ ባርቃን፡ ይላል ። አርቆሚንን፡ እይ፤ ከዚህ፡ ጋራ፡ አንድ፡ ነው፡ (መሳ፰፡ ፲፯) ።

**በረር፤ ሮት**፤ (በረ፡ ይበርር፡ ይብርር ። ዕብ፡ ባራር ። ሱር፡ ባር ። ዐረ፡ በረ፤ በሬረ)፤ መምረጥ፡ መለየት፡ መልቀም፡ ማጥራት፤ ጽሩይ፡ ጸዐዳ፡ ማድረግ፤ የማዕደናት ። በርበረን፡ እይ ።

**ተበረ**፤ (ይትበረር)፤ ተለቀመ፤ ጠራ፡ ጥሩ፡ ኾነ ። ብርትና፡ ብሬት፡ የዚህ፡ ዘር፡ ነው ።

**ብሩር**፤ (ራን፡ ራት፡ ርርት)፤ የተመረጠ፡ የተለየ፤ ልቅም፡ ጥሩ፡ ነጭ፡ ማዕደን ።

**ብሩር**፤ (ብ፡ በራውር፤ ብሩራት)፤ ብር፡ ከቡር፡ ገንዘብ፡ የወርቅ፡ ምክትል ። ብሩር፡ ጽሩይ ። ብሩር፡ ኅሩይ ። ሠላሳ፡ ብሩር ። ህየንተ፡ ወርቅ፡ ወብሩር፡ ጸዐዳ፡ (መዝ፡፲፩ ። ምሳ፰፡ ፲፱ ። ማቴ፳፮፡ ፲፭ ። ደራሲ) ።

**በረረ**፤ (ሰረረ)፤ በቁሙ፡ ሮጠ፡ ክንፈ፡ ተጣደፈ ። ዐለፈ፡ ዘለቀ፡ በላ፡ ነደለ ። ወፀአ፡ ኀጺኑ፡ ሰሪሮ ። ረገዘ፡ ለአሕዱ፡ ውስተ፡ ሰንብዑ፡ ወወፀአት፡ ኵናት፡ በሪራ፡ እንተ፡ ዘባኑ፡ ወወግአቶ፡ ለካልኡ ። በረረ፡ ቅትራት፡ ውስተ፡ እገሪሁ ። በረሮ፡ እስከ፡ ዘባኑ ። ኢይበርሮ፡ ቀስተ፡ ብርት፡ (፪ነገ፡ ፪፡ ፳፱ ። ገድ፡ ተክ ። ስንክ፡ ነሐ፲፱ ። መሳ፫፡ ፳፪ ። ኢዮ፳፡ ፳፬) ።

**በራሪ**፤ (ሪት፡ ርያን፡ ያት)፤ በቁሙ፡ የሚያልፍ፡ የሚዘልቅ ።

**በር**፤ በቁሙ፤ ደጅ፡ አፍ፡ መውጫ፡ መግቢያ፡ መዝለቂያ፡ ማለፊያ፡ (ዐማርኛ) ። ነቅጸን፡ ተመልከት ።

**ቤሩሽ**፤ (ዕብ፡ ብሮሽ ። ጽር፡ ኪፓሪሶስ)፤ ጥድ፤ የጥድ፡ ዐይነት፡ ዛፍ፡ ወፍራም፡ ረዥም፡ መለሎ ። ለየዐውዱ፡ ቤሩሽ፡ እስመ፡ ወድቀ፡ ዘግባ፡ (ዘካ፲፩፡ ፪) ።

**ቤሩሲም**፤ በርሲም፤ (ዕብ፡ ብሮሽም)፤ ዝኒ፡ ከማሁ፡ ጥዶች ። ዕፀወ፡ በርሲም፡ (፫ነገ፡ ፭፡ ፰) ።

**ቤርሳቤሕ**፤ (ዕብ፡ ብኤር፡ ሻባዕ)፤ ዐዘቅተ፡ መሐላ፤ የመሐላ፡ ጉድጓድ፡ (ዘፍ፳፩፡ ፴፩) ።

**ቤርሴክታን**፤ (ጽርእ)፤ ማጥን፡ ታቦት፡ የገንዘብ፡ የሬሳ ። ኤርጋብን፡ እይ፡ (፩ነገ፡ ፯፡ ፰) ።

**ብርስኔ፤—ባርሰነት፤—ምርስኔ ።**

**ብርስን**፤ (ዐረ፡ ቡልስን፤ ዐደስ ። ዕብ፡ ዐዳሽ)፤ ምስር፤ ጥሩ፡ ያበባ፡ እኽል፡ ወጥ፡ የሚኾን፤ ቅንጣቱ፡ ታናናሽ፡ ክብ፡ ቀይ ። ምስራዊ፡ ዘእምስር፡ ማለት፡ ነው፤ የግብጥ፡ ብርስን፡ ካገር፡ ኹሉ፡ ብርስን፡ የሚያምር፡ የሚበልጥ፡ በውድ፡ የሚሼጥ፡ ስለ፡ ኾነ፡ የሻም፡ ዐረብ፡ ዐደስ፡ መስሪ፡ እንዲል፡ ምስራዊ፡ ቢል፤ ተርሙስ፡ ግብጠ፡ እንዲባል፡ ብርስንም፡ ምስር፡ ይባላል፤ ጥንተ፡ ስሙ፡ ዐደስ፡ በምርስኔና፡ በብርስኔ፡ ሞክሼ፡ ወደ፡ ባርሰነት፡ ኺዷል ። ፪ኛም፡ ስለ፡ ቅላቱ፡ ግብጥ፡ ይባላል፤ ግብጥ፡ ምስር፡ እንዲሉ ። ልባም፡ ሴት፡ በጥሩ፡ ዐዋዜ፡ ሠርታ፡ ስታቀርበው፡ በቅላት፡ ላይ፡ ቅላት፡ ተጨምሮለት፡ መልኩ፡ ጼሕ፡ ሻዊ፡ እንድኪ፡ ፍሕሶ፤ ዐረብ፡ እንቀልባ፡ የሱፍ፡ አበባ፡ ይመስላልና፤ የምሥራች፡ ለሚል፡ ምስር፡ ብላ፡ ማለት፡ ስለዚህ፡ ነው፤ የምሥራች፡ ቅሉ፡ ከምስር፡ ወጥ፡ መጥቷል ። ሽማግሎችም፡ የምስር፡ ወጥ፡ ብዥርና፡ የሚያሼጥ፡



ብርስን፤

ይሉታል፡ (ዘፍ፳፭፡ ፴፬ ። ኩፋ፡ ፳፬) ። ዐተረ፡ ወብርስኔ ። ገራህተ፡ ዘምሉእ፡ ብርስኔ፡ (፪ነገ፡ ፲፯፡ ፳፰ ። ፳፫፡ ፲፩ ። ሕዝ፬፡ ፱) ። የምስር፡ ዐይነት፡ ፫፡ ነው፡

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ያይጥ ፡ ምስር ፡ የገመል ፡ ምስር ፡ የሚባል ፡ አለ ። ይበልዑ ፡ ሦበስተ ፡ ብርስነ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲፫) ።

**ቡራት ፤ ቡራቴ ፤ (ጽር ፡ ብራቲ ። ዕብ ፡ ብሮት)** ፤ ስመ ፡ ዕፅ ፤ ብርቱ ፡ ጠንካራ ፡ ፅንጨት ፡ የጥድ ፡ የደቅማ ፡ ዐይነት ፡ እንዳዝጋሮ ፡ ያለ ፡ ምፁዝ ፡ ዐዚዝ ። ወይም ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ጥዱ ፡ ደቅማው ፤ ቤሩሽን ፡ እይ ፡ ዕብራይስጡ ፡ ብሮሽን ፡ ሲያበዛ ፡ ብሮት ፡ ይላልና ፤ ቡ ራቴ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ምስጢሩም ፡ ከብሩርና ፡ ከብርት ፡ ይሰማማል ።

**ብርት ፤ (ቃት ። በሬር ፡ በረ ፤ ብሩር)** ፤ በቁሙ ፤ የብረት ፡ ወገን ፡ የብር ፡ ምክትል ፤ ብርቱ ፡ ማዕ ደን ፡ መዳብ ፡ ንሐስ ፤ መዳብ ፡ ቀዩ ፤ ንሐስ ፡ ብጫው ። ግ ብረ ፡ ብርት ፡ ወንጺን ። ብርት ፡ ርሱን ። ብርት ፡ ሲባ ኖስ ። ፍጽምክ ፡ ዘብርት ፡ (ዘፍ፬ ፡ ፳፪ ። ሕዝ፵ ፡ ፫ ። ራእ፩ ፡ ፲፭ ። ኢሳ፷ ፡ ፲፯ ፡ ፬) ።

**ብረት ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፤ ኀጺንን ፡ ተመ ልከት ። ብርቱ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ብርትኳን ፤ (ዐረብ)** ፤ በቁሙ ፤ በሸሬ ፡ ለመጊ ፤ ጥሩ ፡ ጥፍጥ ፡ ተክል ።

**በስብሶ ፤ ሶት ፤ (በስበሰ ፡ ይበሰብስ ፡ ይ በስብስ ። ዐረ ፡ በጸ ፤ በጽበጸ ። ዕብ ፡ ባጻጽ ፡ ባጽቤጽ ፤ ፈለቀ ፡ መነጨ)** ፤ መክፈት ፡ መግለጥ ፡ ማቍለጭለጭ ፤ የዐይን ። መንስንስ ፡ መቍላት ፡ ማወዛ ወዝ ፤ የኸራት ። በቁሙ ፡ መበስበስ ፤ መራስ ፡ መርጠብ ፤ መበላሸት ፡ (ዐማርኛ) ። በጕብጕን ፡ እይ ። ዘሩ ፡ በሲስ ፡ በስ ፡ በሰስ ፡ ነው ።

**አንበስበሰ** ፤ አገለባበጠ ፤ ተገለባበጠ ፤ አርገበ ገበ ፡ ተርገበገበ ፤ የዐይን ፡ የቅንድብ ፤ ለእጅም ፡ ይኾናል ። አንበስብሶ ፡ ዐይን ። አንበስብሶ ፡ ቀራንብቲሆን ፡ (ቀሌ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፱ ፡ ፳) ።


—፤ አራመደ ፡ አሻገረ ፡ ወረወረ ፤ ተራመደ ፡ ተወረወረ ፤ የዐይን ፡ የእግር ፡ የመብረቅ ። ያንበሰብስ ፡ ዲበ ፡ አው ግር ። እምቅድመ ፡ ያንበስብስ ፡ ፀዓዕ ። ያንበሰብሱ ፡ መባርቅት ፡ እምፀአተ ፡ ቃሉ ፡ (ማሕ፱ ፡ ፳ ። ቅዳ ፡ አፈ ። አርጋ) ።

—፤ አመሳለሰ ፡ ተመሳለሰ ፤ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ ከፍት ፡ ዝድግ ፡ አለ ፤ የሰማይ ፡ የዐይን ። ወከመ ፡ ፀሓይ ፡ አን በስበሰት ፤ ተመሳለሰች ፡ (ቅዳ ፡ አት) ።

**ነበስባስ** ፤ የዐይን ፡ የሽፋሽፍት ፡ አገባበጥ ፡ አስ ተያየት ፡ ጥቅሻ ። ዐይንን ፡ ማፍጠጥ ፡ ማጕረጥ ፡ መበል ጠጥ ፤ ከፍ ፡ ዝቅ ፡ ቁለል ፡ ቁለል ፡ ክብለል ፡ ክብለል ፡ ማድረግ ፤ በዐይን ፡ ዐለንጋ ፡ መግረፍ ፡ መሽንቆጥ ፡ መገ ረመም ፡ መግጠጥ ፡ መገላመጥ ። አልቦ ፡ ቀዳመ ፡ ህላዌ ፡ ለአብ ፡ እምወልድ ፡ ኢመጠነ ፡ ቅጽበተ ፡ ዐይን ፡ ወ ኢመጠነ ፡ ነበስባሰ ፡ ቀራንብት ። ሰላም ፡ ለቀራንብ ቲክ ፡ ዘነባስባሶን ፡ ይዋሂ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ደራሲ) ።

—፤ ነፋስ ፡ አስትንፋስ ፤ ሽው ፡ ሽው ፤ እፍ ፡ እፍ ፡ ማለት ፤ ሽውታ ፡ እፍታ ። አንብቦ ፡ መጻሕፍት ፡ ከመ ፡ ነበስ ባስ ፡ ነፋሳት ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ ለአብድ ፤ ይትሜካሕ ፡ በአንብቦታ ፡ ወኢየአምር ፡ ዘውሳጢታ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አንበሳ ፤ (ብ ፡ አናብስት)** ፤ በቁሙ ፤ ግርማ ፡ ያለው ፡ አውሬ ፤ ኀይለኛ ፡ ተፈሪ ፤ ነጣቂ ፡ በባሪ ፤ ዘላይ ፡ ተወርዋሪ ፤ ዐዳኝ ፡ ግሩመ ፡ ዐይን ፡ የድመት ፡ ወገን ። ድ መትን ፡ ብስ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። አንበሳ ፡ ዘጽኑሕ ፡ ለመሂጥ ። ረከቦ ፡ አንበሳ ፡ በፍኖት ፡ ወቀ ተሎ ። ፈነወ ፡ አናብስተ ፡ ወበልዕዎሙ ። ግበ ፡ አናብ ስት ፡ (መዝ ፡ ፲፮ ። ፫ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፳፬ ። ፬ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳፭ ። ዳንኤ ፡ ፯) ።



አንበሳ ።

**አንበሳዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ ያንበሳ ፡ ወገን ፡ ዐይነት ፤ አንበስማ ፤ አንበሳም ፡ ባንበሳ ። ሰባም ፡ እብል ፡ ለአንበሳዊ ፡ አውሎግ ፡ (ስንክ ፡ የካ፲፭) ።

**አንበሳዊት** ፤ አንበሲት ፤ አንበት ፡ አንበሳ ። ጣሕረ ፡ አንበሳ ፡ ወንቃወ ፡ አንበሳዊት ። እምከ ፡ አን በሳዊት ። ከመ ፤ አንበሳዊት ፡ (ኢዮ፬ ፡ ፲ ። ሕዝ፲፱ ፡ ፪ ። ዳንኤ ፡ ፬) ።

**አንበሰ ፤ አው ፡ ተአንበሰ** ፤ አንበሳ ፡ ኾነ ፤ አንበሳ ፡ ተባለ ፡ በጠባይ ፡ በግብር ።

**አንበሳ ፤ ዕጓለ ፡ አንበሳ** ፤ ታላቅ ፡ የታላቅ ፡ ልጅ ፤ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ ንጉሥ ፤ ኀያል ፡ ወልደ ፡ ኀያል ።

**እንቦሳ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፤ ጥጃ ፡ የሚ ዘል ፡ የሚፈነጭ ። (ተረትና ፡ ምርቃት) ፤ ወተት ፡ ለንቦሳ ፤ ሥጋ ፡ ላንበሳ ። ቤት ፡ ለንቦሳ ፤ እሰር ፡ እንቦሳ ።

**በሰከ ፡ (ዐማርኛ)** ፤ በቴክ ፡ በተከ ፤ በጠሰ ። ሰና ፡ ተ ፡ ይዋረሳሉ ፤ ይልቁንም ፡ በዐረብ ፡ በሱርስት ፤ ዕር ፡ ቶር ።

**በሲል ፤ ሎት ፤ (በሰለ ፡ ይበስል ፡ ይብ ስል ። ዕብ ፡ ባሻል ። ሱር ፡ ብሼል)** ፤ መብሰል ፤ መሸከክ ፡ መንደርከክ ፤ በእሳት ፡ በፀሓይ ፡ መለስለስ ፤ ተጋግሮ ፡ ተንፍሮ ፡ ታምሶ ፡ ተጠብሶ ፡ ለመበላት ፡ መድ ረስ ፤ ለጥርስ ፡ መግራት ፤ መሸት ፡ መጕምራት ። ኢብል ዐት ፡ ምንተኒ ፡ በእሳት ፡ ዘበሰለ ። ሥዊት ፡ ዘበሰለ ። ዘእንበለ ፡ ደብስል ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ኢሳ፲፯ ፡ ፳ ። ኤር ፴፩ ፡ ፴፪) ።

**ተበስለ**፤ ተቀቀለ ፡ ተጋገረ ፡ ተቈላ ፡ ተነፈረ ። ሰላም ፡ ለአሮን ፡ ዕጓላተ ፡ ርግብ ፡ ዘአስረረ፤ በእሳት ፡ ወማይ ፡ ይኅሪ ፡ ተበስሉ ፡ ኅቡረ ፡ (ስንክ ፡ ማንጀ፭) ።

**ብሱል**፤ (ላን ፡ ላት ፡ ስልት)፤ የበሰለ ፡ የተቀቀለ፤ ቅቅል ። ረከቦ ፡ ለውእቱ ፡ ጸብኀ ፡ ፍሉሐ ፡ ወብሱለ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲፭) ። ኢብሱል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ብሱል ፡ ይላል ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፴፱) ።

**ብስሎ**፤ ብስል ፡ ቅቅል ፡ አንፊላ ። ብስሉን ፡ ቅቅሉን ። ጥሬዮ ፡ ወኢብስሎ ፡ በማይ ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፴፱) ።

**ተብሲል**፤ ንፍሮ፤ የኽል ፡ ወጥ ። ተብሲለ ፡ ብርስን ፡ (ዘፍ፳፭ ፡ ፳፱ ። ዳን፲፫ ፡ ፴፫) ።

**አብሰለ**፤ አበሰለ፤ አስበሰለ፤ ተኰሰ ፡ ጠበሰ ። ያበስሉክሙ ፡ በጽህርት ። ያበስሉ ፡ ሥጋ ። ንጥፋሕ ፡ ግንፋለ ፡ ወናብስሎ ፡ በእሳት ፡ (ዓሞ፬ ፡ ፪ ። ሕን፫ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ። ዘፍ፲፩ ፡ ፫) ።

**አብሳሊ**፤ **መብሰሊ**፤ **መበስል**፤ (ላን ፡ ላት)፤ የሚያበስል ፡ አብሳይ፤ ጋጋሪ ፡ ቀቃይ ፡ ሊጥ ፡ አፍሳሽ ፡ ወጭት ። ጠባሽ፤ በበዛ ፡ ወጥ ፡ ቤት ። ሊቀ ፡ መበስላን ። ለመበስላት ። ወለኅባዝያት ። ይቤሉ ፡ ለመበስል ፡ (ዘፍ፴፯ ፡ ፴፮ ። ሕን፺ ፡ ፰ ፡ ፲፫ ። ፪ ፡ ፳፫) ።

**መብሰል**፤ (ላት)፤ ማብሰያ ፡ መቀቀያ ። መብሰለ ፡ ብርት ፡ ዘውዑይ ፡ ፍልሐቱ ። በመብሰለ ፡ ብርት ፡ ርሱን ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፳ ። ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**መብስል**፤ የበሰለ ፡ ምግብ ፡ ትኩስ ፡ ለስላሳ ፡ የላመ ፡ የጣመ ። ኢይብልዑ ፡ መብስላተ ፡ አባ ፡ ኀብስተ ፡ ይቡሰ ፡ ወጼወ ፡ ወማየ ፡ (ቄድር) ።

**ባሲላዊ**፤ (ጽር ፡ ባሲሌፍስ)፤ ንጉሣዊ ፡ የንጉሥ ፡ ወገን ። ባሲላውያን ፡ (ቀሌ) ።

**ባሲልያ**፤ መንግሥት፤ ጌትነት ፡ ንጉሥነት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ባሲልያሱ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ፋሲልያሱ ፡ ይላል ፡ ሱ ፡ ዝርዝር ፡ ነው ፡ ከ ። እምንስቲቲን ፡ እይ ።

**ባስልዮስ**፤ የሰው ፡ ስም ፤ ንጉሥ ፡ ንጉሣዊ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ቢሶም**፤ (ዕብ ፡ ቦሼም፤ ባሳም)፤ የሽቱ ፡ ዕንጨት ፡ ዛፍ፤ መልካም ፡ ሽታ ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ኹሉ ፡ በየስሙና ፡ በያይነቱ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሊይቱው ፡ ሾላ ፡ ብሳና ፡ ይሉታል ፡ (ኩፋ ፡ ፳፭) ።

**በሰንስ**፤ **በሸንስ**፤ **ብሸንሶ**፤ (ቅብጥ ፡ ፓሾንስ)፤ የግብጦች ፡ ወር ፡ ግንቦት ። ብሸንሶ ፡ ይሰመይ ፡ በሰንጹስ፤ ወካዕበ ፡ ይሰመይ ፡ ማኹን ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ።

**ብስራት**፤ **ባሶር**፤—**ብሢር** ፡ **በሠረ**፤ **ብሥራት**፤ **ባሦር**፤

**በሲስ**፤ **ሶት**፤ (**በሰ** ፡ **ይበስስ** ፡ **ይብስስ**)፤ መበሰስ ፡ ማደን ፡ በባስ ፡ መኾን ፡ የወሬ ፡ ያውሬ ። በስን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ። ማለዘብ ፡ ማለስለስ ፡ የነገር ፡ የልብስ ።

**ቢሶስ**፤ **ቢሶን**፤ (**ጽር ፡ ቢሱስ** ። **ዕብ ፡ ቡጽ** ። **ሱር ፡ ቡጻ** ። **ዐረ ፡ በዝ**)፤ ክታን ፡ ልብስ ፡ ክታን ፡ ልዝብ ፡ ለስላሳ፤ ወይም ፡ ነዩው ፡ ፈትሉ ። ቢሶስ ፡ ክዑብ ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፬ ። ፳፮ ፡ ፩ ፡ ፴፭ ፡ ፴፮ ። ሉቃ፲፮ ፡ ፲፱) ። ቢያበዛ ፡ ቢሶሳት ፡ ይላል ። **አልባሰ ፡ ቀጠንት ፡ ወቢሶሳት ፡ ወሚራያት** ፡ (መቃ ፡ ገ፳፪) ።

(ጥ) **ባት**፤ (**ዕብራ**)፤ የርጥብ ፡ መስፈሪያ፤ የዘይት ፡ ግንበ ፡ ማድጋ ። **መስፈርተ ፡ ባት ። ባተ ፡ ጽድቅ** ፡ (፫ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፲፮ ። ሕዝ፵፭ ፡ ፲ ፡ ፲፩) ።

**ቤት**፤—**በቁሙ**፤ **ስመ ፡ ፊደል**፤—**በዩት ፡ ቤተ**፤ **በ** ።

**በቲክ**፤ **ኮት**፤ (**በተከ ፡ ይበትክ ፡ ይብትክ** ። **ዐረ ፡ በተከ** ። **ዕብ ፡ ባቴቅ**፤ **ናታቅ**)፤ መበተክ ፡ መበስከ፤ መቍረጥ ፡ መበጠስ፤ አባላ ፡ መምታት፤ መንቀል ፡ መፈንቀል፤ መናድ ፡ ማፍረስ፤ መስበር ፡ መሠንጠር ። **እበትክ ፡ ማኅሜክ ። በተከ ፡ ማእሰረ** ፡ (ነሐ፩ ፡ ፲፫ ። ኤር፭ ፡ ፭) ። በበተክ ፡ ፈንታ ፡ አብተከ ፡ ይላል፤ አያሰኝም ። **ታበትክ ፡ ቃሎሙ ፡ በኀበ ፡ እግዚ** ፡ (ዘፀ፲፰ ፡ ፲፱) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ **ውሂቤእታ** ፡ ይላል፤ **ታበውእ ፡ ታበጽሕ ፡ ታቀርብ** ፡ ማለት ፡ ነው ። መብተክ ፡ መብተክተክ፤ መብሰክሰክ፤ መበላሸት ፡ ከንቱ ፡ መኾን፤ የግብር ፡ የነገር ፡ (ዐማርኛ) ።

**አብተከ**፤ አበተከ ፡ አብተከተከ፤ አስበተከ ፡ አስቈረጠ ፡ አስበጠሰ ።

**ተበትከ**፤ ተበተከ፤ ተቈረጠ፤ ተበጠሰ ፡ ተነቀለ ፡ ተፈንቀለ ። **ይትበተክ ፡ ፈትል ። ኢይትበተክ ፡ ቶታን ፡ አማእኢሆሙ ። ይትበተክ ፡ መሣግሪሆሙ ። ተበትከ ፡ እብን ፡ እምደብር** ፡ (መሳ፲፮ ፡ ፱ ። ኤር፭ ፡ ፳፮ ። ሉቃ፭ ፡ ፮ ። ዳን፪ ፡ ፴፬ ፡ ፵፭) ።

**ብቱክ**፤ (**ካን ፡ ካት ፡ ትክት**)፤ የበተከ፤ የተበተከ ፡ የተቈረጠ ፡ የተበጣጠሰ ፡ ብጥስጥስ ። **መሥገርት ፡ ብቱክ ። አማእን ፡ ብቱክ** ፡ (ኢሳ ፡ ፲፱ ፡ ፱ ። ኢያ፱ ፡ ፫) ።

**ብትክ**፤ አባላ ፡ የተመታ፤ ጥንብ ፡ ውዳቂ፤ ታርዶ ፡ የሰነበተ ፡ (ዘሌ፲፱ ፡ ፯ ። ግብ፳፭ ፡ ፳፭) ።

**ብትክት**፤ መቍረጥ፤ መቈረጥ ፡ መበጠስ፤ አበጣጠስ ፡ ብጠሳ፤ ብጥስነት ። በይብስት ፡ ፈንታ ፡ ብትክት ፡ ይላል፤ ስሕተት ፡ ነው ። **እሰ ፡ አልቦሙ ፡ ብትክት** ፡ (መሳ፲፯ ፡ ፯ ፡ ፳) ።

**ባተለ**፤ (**ዐማርኛ**)፤ በቁሙ፤ ባተሌ ፡ ኾነ፤ ደኸየ ።

**ባቱል**፤ (**ዕብ ፡ ብቱላ**)፤ ድንግል ፡ ወንድ ፡ ያላወቀች ፡ ሴት ፡ ልጅ፤ ልጃገረድ ፡ (አዋል) ።

**ብቱል**፤ (**ላን ፡ ላት ። ዐረብ**)፤ ድንግል ፡ ሴት ፡ ያላወቀ ፡ ወንድ ። ባተሌ ፡ ፈት ፡ መዐስብ ፡ ሚስቱ ፡

መኀታ ፡ ወይም ፡ በነውር ፡ ተፈታ ፡ በቃሎውን ፡ የሚኖር ፤ ይኅግላይ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**በተነ ፤ (ይበትን ፤ ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፡ በተነ ፡ በታተነ ፤ ዘረወ ፡ ዘርዐ ።

**በቲር ፤ ሮት ፤ (በተረ ፡ ይበትር ፡ ይብትር ። ትግ ፡ በትረ ። ዕብ ፡ በታር)** ፤ መቍረጥ ፡ መከርከም ፡ ማረቅ ፡ ማቅናት ፤ ቀጥ ፡ ለጥ ፡ ማድረግ ፤ የንጨት ። መምታት ፡ መውቃት ፤ መነረት ። መተረን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**በትር ፤ (ብ ፡ አብትር)** ፤ በቁሙ ፤ ዘንግ ፡ ሽመል ፡ ምርኵዝ ፡ ዱላ ፡ ጕመድ ፡ ከንተሮ ፡ መንደርቆ ፡ ለበቅ ፡ ፎንገር ። ትወፅእ ፡ በትር ፡ እምሥርወ ፡ እሴይ ። አብትረ ፡ ልብኔ ። ቍስለ ፡ አብትር ። በትርከ ፡ ወቀስታምከ ። ዘይምህከ ፡ በትሮ ፡ (ኢሳ፲፩ ፡ ፩ ። ኤርም ፡ ፲፯ ። ሚራ፳፰ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፳፪ ። ምሳ፲፫ ፡ ፳፬) ።

—፤ ሥልጣን ፡ አገዛዝ ፡ ቀንበር ። በትር ፡ እንተ ፡ ዲበ ፡ ክሣዱ ። በትረ ፡ መንግሥትከ ፡ (ኢሳ፱ ፡ ፬ ። አስቴ፬ ፡ ፲፩ ። መዝ ፡ ፵፬) ።

**በትረ ፡ ብርዕ** ፤ የሸንበቆ ፡ ምርኵዝ ፡ ጎለት ፡ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ (ሕዝ፳፱ ፡ ፮ ። ኢሳ፴፮ ፡ ፮) ።

**በትረ ፡ ወርቅ** ፤ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ በወርቅ ፡ የተጌጠ ፡ የጳጳስና ፡ የንጉሥ ፡ በትር ፡ (አስቴ፭ ፡ ፪ ። ፰ ፡ ፬) ።

**በትረ ፡ ኀጺን** ፤ የብረት ፡ ዘንግ ፤ ባለብረት ፡ ጅንፎ ፤ ጅንፋችም ፡ በትር ፡ (መዝ ፡ ፪ ። ራእ፪ ፡ ፳፯) ።

**በትረ ፡ መሃፒል** ፤ ዐጭር ፡ ወፍራም ፡ መንደ ፤ እንደ ፡ ፎኑንቻ ፡ እንደ ፡ መሮ ፡ መምቻ ፡ ያለ ፤ ሀጣቢ ፡ ቀለም ፡ አግቢ ፡ ልብስ ፡ የሚመታበት ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳፯) ።

**በትረ ፡ መዐት** ፤ መቅሠፍ ፤ ለበቅ ፡ ፎንገር ፡ ረኃብ ፡ ጦር ፤ ዐባር ፡ ቸነፈር ፡ (ኢሳ፲ ፡ ፭) ።

**በትረ ፡ ነገድ** ፤ የነገድ ፡ አለቃ ፡ በኵር ፡ ሹም ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ (፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ግን፲) ።

**በትር** ፤ ወገን ፡ ነገድ ፡ ዘር ፡ ትውልድ ። በበ ፡ በትርክሙ ፡ ወበበ ፡ ሕዝብክሙ ። በትረ ፡ ይሁዳ ፡ ወብንያም ፡ (፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ። ፫ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፳) ።

**በትረ ፡ ያርክ ፤ (ጽር ፡ ፓትሪአርኽ)** ፤ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፤ አብ ፡ ቀዳማዊ ፤ ወይም ፡ መዠመሪያ ፡ ታላቅ ፡ ደገኛ ፡ አባት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲፫ ። ታኅ፩) ።

**በታሮን ፤ (ጽር ፡ ፓቴሮን)** ፤ አበው ፤ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ኖኅ ፡ ያሉ ፡ ዐሥሩ ፡ አባቶች ፤ ወይም ፡ ሌሎች ። ደብረ ፡ በታሮን ፤ ዘውእቱ ፡ ብሂል ፡ ደብረ ፡ አበው ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፰) ።

**በቲት ፤ ቶት ፤ (በተ ፡ ይበትት ፡ ይብትት ። በልዩ)** ፤ መበተት ፤ ብትቱ ፡ መኾን ፡ ማለቅ ፡ ማርጀት ፤ የልብስ ። በልበለን ፡ ተመልከት ።

**በትበተ ፤ (ይበተብት)** ፤ በቁሙ ፤ በተበተ ፡ በጠበጠ ፡ ፈለፈለ ፤ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ በላ ፡ አቃጠለ ፡ የውሻና ፡ የኹርብ ፡ የእሳት ፡ አበላል ። መበጥበጥና ፡ መፈልፈል ፡ የእሸትና ፡ የዳቦ ፡ በሊታ ። (ተረት) ፤ በገዛ ፡ ዳቦዬ ፡ ልብ ፡ ልቡን ፡ ዐጣኹት ። ኹሉም ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ፤ ያማርኛ ፡ ቃል ፤ ከግእዝ ፡ ሲደቀል ፡ ተቀጥላም ፡ ኹኖ ፡ ሲነገር ፤ አበቃቀሉና ፡ አወጣጡ ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ። ሥረ ፡ ነገሩ ፡ ከሦስት ፡ ቅንጣት ፡ ፊደል ፡ አይበልጥም ፤ አያንስም ፤ ቋንቋንቱ ፡ ሱማዊ ፡ ነውና ፤ ፩ኛ ፡ ዕር ፡ ኗኈ ፡ ተመልከት ።

# ገ

**ገ** ፤ ሦስተኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፋ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፤ ስሙ ፡ ገምል ፡ ቍጥሩ ፡ ፫ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ ፫ ፡ ሠለስት ፡ ቱ ፡ ይባላል ። ዕብራውያን ፡ ግን ፡ ሦስትን ፡ መደብ ፡ አድርገው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነቍጣ ፡ እየጨመሩ ፡ ሦስት ፡ አልፋ ፡ ይሉታል ። ምስጢሩ ፡ ሠሉስንና ፡ የሠሉስን ፡ ፍጥረት ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ፫ኛውን ፡ አካል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፤ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሀብትነት ፡ ፍሬ ፡ ጸጋውን ፡ ያሳያል ፡ ገመልን ፡ እይ ፡ (ዘፍ፳፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪) ።

**ጋ** ፤ እን ፡ ሲጨመርበት ፡ (እንጋ ፡ እንጃ) ፡ ይቴቅ ፡ አገባብ ፡ ይኾናል ።

**ኋ ፤ (ንኡስ ፡ አገባብ)** ፤ እኮን ፡ ቢያ ፡ ማ ፡ እንኳ ፡ ስንኳ ። አንተሂኋ ፡ ተሠገርከ ፡ ከማነ ። አንተሰኋ ፡ ሀሎከ ፡ ምስሌየ ። ክለባትኒኋ ፡ (ኢሳ፲፬ ፡ ፲ ። ሉቃ ፲፭ ፡ ፴፩ ። ፊልክ ፡ ፫ ። ማቴ፲፭ ፡ ፳፯) ።

**ጌ ፤ (ጽር ፡ ጊ)** ፤ ምድር ፡ ሀገር ፤ ርስት ። ባለጌ ፡ ሐዬጌ ፡ እትጌ ፡ እንዲሉ ። ሐፀየን ፡ እይ ።

**ግኢዝ ፤ ዞት ፤ (ግእዘ ፤ አው ፡ ገእዘ ፡ ይግእዝ ፡ ይግአዝ ። ሱር ፡ ግዓጽ ፤ ጋየጸ)** ፤ ማዘግ ፡ መቈጣት ፡ መበሳጨት ። መንቀፍ ፡ መጥላት ፡ መጣላት ፡ መውቀሥ ፡ መክሰስ ። ገእዝኩ ፡ ሕይወትየ ። ለምንት ፡ እንከ ፡ ትግእዝ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚ ። ወዳእኑ ፡ ግእዝናሆሙ ። ወግእዘ ፡ ጽንዐ ፡ ልቦሙ ። ምንተ ፡ ረከቡ ፡ በላዕሌየ ፡ በዘይግእዙኒ ። ሶበ ፡ ይግእዘከ ፡ ዐርክከ ። ግእዞ ፡ ሕዝብ ፡ ለሙሴ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፯ ። ሚራ፳፩ ፡

፱ ። ሮሜ ፫ ፡ ፱ ። ማር፲፯ ፡ ፲፱ ። ኤር፪ ፡ ፳ ። ምሳ፳፭ ፡ ፳ ። ዘፀ፲፯ ፡ ፪ ፡ ፯) ።

—፤ ማጋዝ ፡ ከግዞት ፡ ቤት ፡ ማግባት ፡ ግእዝ ፡ መማር ፡ እየቈጠሩ ፡ ማንበብ ።

**ገአዚ** ፤ (**ዚት ፡ ዝያን ፡ ያት ፤ አዝት**) ፤ የሚነቅፍ ፡ ነቃፊ ፤ ወቃሽ ፡ ከሳሽ ፤ ፈራጅ ፡ (ያዕ፬ ፡ ፲፩) ።

**መግእዝ** ፤ (**ዝት ፡ ዛን ፡ ዛት**) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ነዝናዥ ፡ ዘብዛቢ ፤ ኀረኛ ፡ ነገረኛ ። **ጕጕእ ፡ ወመግእዝ ። ዐርክ ፡ መግእዝ ። ብእሲት ፡ መግእዝት** ፡ (ምሳ፳፭ ፡ ፳፬ ። ፳፪ ፡ ፳፬ ። ፱ ፡ ፲፫ ። ዲድ ፡ ፫) ።

**አግአዘ** ፤ አስጠላ ፡ አስነቀፈ ፡ አስጋዘ ፡ አስጕተተ ፤ ከግዞት ፡ አስገባ ፡ ግእዝ ፡ አስተማረ ።

**ተግእዘ** ፤ ተጠላ ፡ ተነቀፈ ፤ ተጋዘ ።

**ግኡዝ** ፤ (**ዛን ፡ ዛት ፡ እዝት**) ፤ የተጋዘ ፡ የተጠላ ፤ የተነቀፈ ፡ ኅቁፍ ።

**ግእዘት** ፤ ማጋዝ ፡ መጋዝ ። መንቀፍ ፡ መነቀፍ ፤ እንቅቅፍ ፤ ነቀፋ ፡ ነቀፌታ ፤ ወቀሣ ፡ ክስሳ ። **በእንተ ፡ ግእዘት ፡ ዘግእዝዎ ። እንበለ ፡ ተካሕዶ ፡ ወግእዘት** ፡ (ዘፀ፲፯ ፡ ፯ ። ደራሲ) ።

**ተጋአዘ** ፤ ተነቃቀፈ ፡ ተጣላ ፤ ተከራከረ ። **አልቦ ፡ ዘትትጋአዙ ፡ በፍኖት ። ደናግለ ፡ ቀተለ ፡ ዮልያኖስ ፡ በተጋእዞ ። አለ ፡ ይትጋአዙ ። ተጋአዝኩ ፡ ምስሌሃ ። ኢይክል ፡ ተጋእዞ ፡ ምስለ ፡ ዘይጸንዕ** ፡ (ዘፍ፵፭ ፡ ፳፬ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲ ። ምሳ፲ ፡ ፲፪ ። መቢ፪ ፡ ፲፬ ። መክ፯ ፡ ፲) ።

**ተጋአዚ** ፤ ተጣይ ፡ ተሃራሪ ፤ ተሟጋች ፡ ተከራካሪ ፤ ባለጋራ ። **ዘይፈትሕ ፡ ማእከለ ፡ ተጋአዝያን ። ኮኑ ፡ ተጋአዝያነ ፡ ምስለ ፡ ሐዋርያት** ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፫ ፡ ፪ ። አቡሻ ፡ ፲፪) ።

**አስተጋአዘ** ፤ አጣላ ፤ አሟገተ ፡ አከራከረ ።

**መስተጋእዝ** ፤ የሚያጣላ ፡ የሚያሟግት ፤ የሚሟገት ፡ ተሟጋች ፡ ተከራካሪ ። **ለእመ ፡ ይቤለከ ፡ አሐዱ ፡ መስተጋእዝ ። መስተጋእዛን ፡ በበይናቲሆሙ** ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፪ ፡ ፲ ። አፈ ፡ ድ፳ ፡ ፳፪) ።

**ጋእዝ** ፤ (**ዛት**) ፤ ጠብ ፡ ክርክር ፡ ሙግት ፤ ንዝንዝ ፡ ስድብ ፡ ውዝግብ ፡ ሞቅሞቅ ። **ለይድም ፡ ደቀ ፡ ድም ፡ ባኳ ፡ ወጋእዝ ። ጋእዘሙ ፡ ስራሕ ፡ ለዘይሰምዖ ። ነገረ ፡ ጋእዝ ። ሰይጣን ፡ አብአ ፡ ፍልጠተ ፡ ወጋእዘ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። መቲረ ፡ ጋእዛት** ፡ (ሢራ ፡ ፳፪ ፡ ፳፬ ። ፳፯ ፡ ፲፭ ። ፩ጢሞ ፡ ፯ ፡ ፱ ። ዲድ ፡ ፴፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፱) ። በቁሙ ፡ ጋዝ ፡ ላንባ ፡ ሽታውና ፡ ጢሱ ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የሚያስቀይም ፤ ነፍጥን ፡ እይ ።

**ግእዝ** ፤ የቋንቋ ፡ ስም ፤ ሴማዊ ፡ አዳማዊ ፡ ቋንቋ ፡ የዕብራይስጥ ፡ ወንድም ፤ ከዐረብ ፡ ከሱርስት ፡ የሚገጥም ። ዘይቤው ፡ አልፍ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ መዠመሪያ ፡ ምስጢሩ ፡ ጥንታዊ ፡ አዳማዊ ፡ ልሳን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፲፩ ፡ ፩) ። ፪ኛም ፡ እንደ ፡ ሴላው ፡ ቋንቋ ፡ ብዙ ፡ ድካም ፡ ስለሌለበት ፡ ቅን ፡ ገር ፡ ብሰው ፡ ይፈቱታል ። **ተተርጕመ ፡ እምልሳነ ፡ ቅብጢ ፡ ለዐረብ ፡ ወእምዐረቢ ፡ ለግእዝ** ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ ፩) ።

**ግእዝ** ፤ የፊደል ፡ ስም ፤ አንድ ፡ ወጣት ፡ አንድ ፡ ቅንጣት ፡ አንድ ፡ በቃል ፤ ዐዝል ፡ ቅጥል ፡ ነጥጣ ፡ ምክትል ፤ ዋየል ፡ አጣማጅ ፡ ኹለተኛ ፡ ፈርጅ ፡ የሌለው ፡ ቀንጃ ፡ ነጠላ ፡ ፊደል ፡ (ኮንሶን) ። ከአ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ያለ ፤ **አ ፡ ብ ፡ ገ ፡ ደ ፡ ሀ ፡ ወ ፡ ዘ** ። ከስላማ ፡ በፊት ፡ ከካዕብ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ድረስ ፡ ሳይኖረው ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ግእዙ ፡ ብቻ ፡ ነበረና ፤ ቋንቋውን ፡ ግእዝ ፡ ያሰኘው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ ከካዕብ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ላሉት ፡ በዥር ፡ ማንባር ፡ ቀደም ፡ ባለኧ ፡ ወንድም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ አንደኛ ፡ ወይም ፡ መዠመሪያ ፡ ይባላል ። **አ ፡ ግእዝ ፤ ቡ ፡ ካዕብ ፤ ጊ ፡ ሣልስ ፤ ዳ ፡ ራብዕ ፤ ሄ ፡ ኃምስ ፤ ው ፡ ሳድስ ፤ ዞ ፡ ሳብዕ** ፡ እንዲሉ ። ግእዝ ፡ አንድ ፡ አንደኛ ፡ መባሉ ፡ በአ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

**ግእዝ** ፤ የንባብ ፡ ስም ፤ መዠመሪያ ፡ ንባብ ፤ ሕፃናት ፡ የፊደልን ፡ ቍጥር ፡ እጅ ፡ እግሩን ፡ ከለዩ ፡ በኋላ ፡ ከነቍጥ ፡ እስከ ፡ ነቍጥ ፡ እየጐተቱ ፡ የሚያማዙት ፡ ማጋዝ ። ለንባብ ፡ ትምርት ፡ በየስልቱ ፡ ፬ ፡ ስም ፡ አለው ፤ ግእዝ ፡ ወርድ ፤ ዐቢይ ፡ ድጋም ።

**ግእዝ** ፤ የዜማ ፡ ስም ፤ አንደኛ ፡ ስልት ፡ መዠመሪያ ፡ ዜማ ፤ ፪ኛው ፡ ዕዝል ፡ ፫ኛው ፡ አራራይ ፡ ይባላል ። **ሠለስቱ ፡ ዜማ ፡ ዘውእቱ ፡ ግእዝ ፡ ወዕዝል ፡ ወአራራይ ። ወእምዝ ፡ ትብል ፡ ጸሎተ ፡ ዘእምዳዊት ፡ በዜማ ፡ ግእዝ ። ህየንተ ፡ ዕዝል ፡ ዘነግህ ፡ ግእዝ** ፡ (ስንክ ፡ ግን፲፩ ። ግንዘ ። ድጓ) ።

**ግእዘ ፤—ተጓዘ ፤ ነጻ ፡ ወጣ ፤—ግዒዝ ፡ ግዕዘ ።**

**ገአረ ፤—ጋረ ፡ ጣረ ፡ ጮኸ ፤—ግዒር ፡ ገዐረ ።**

**ገአት ፤—ገነፎ ፤—ግዒት ፡ ገዐተ ።**

**ገበ ፤—ጐን ፤—ገቢእ ፡ ገብአ ።**

**ግብ ፤—ጕድጓድ ፡ ጕሬ ፤—ገብበ ፡ ገበበ ።**

**ገቢእ** ፤ **አት** ፤ (**ገብአ ፡ ይገብእ ፡ ይግባእ ። በአ ፤ መጽአ ። ገብአ ፡ ትግ ፡ ከነ ፡ ይከውን**) ፤ መግባት ፡ መጥለቅ ፡ መዝለቅ ፤ ወደ ፡ ውስጥ ። መመለስ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መዞር ፡ መታጠፍ ፡ ተመልሶ ፡ መምጣት ። **ገቢአትከ ፡ ውስተ ፡ ሥጋ ። ይትመየጥ ፡ ለገቢእ ። ገብአ ፡ ቤተ ። እገብእ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ገብኡ ፡ እምፍኖት ፡ እኩይ** ፡ (ዕር ፡ ኢሳ፷ ፡ ፳፯ ። መክ፳ ፡ ፲፬ ። መቢ፰ ፡ ፲፩ ። ኢዮ፩ ፡ ፳፩ ። ኤር፴፪ ፡ ፲፰) ።

—፤ መኾን ፤ መያዝ ፡ መስጠት ። **ገብኡ ፡ ታሕተ ፡ እዴ ፡ ትሑት ። ገብኡ ፡ ከመ ፡ ዘኢተወልዱ ። ደኃርት ፡ ይገብኡ ፡ ቀዳሚ ፤ ኮኑ ፡ ይከውኑ ። ገባእነ ፡ ውስተ ፡**

እደ ፡ ጸላእትነ ። ይግባእ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ (ሚራ ፲፭ ፡ ፮ ። ማቴ ፲ ፡ ፲ ። ማርቆ ፲ ፡ ፴፫ ። ሉቃ ፡ ዕብ ፲ ፡ ፴፮ ። ሉቃስ ፲ ፡ ፳) ።

**ገባኢ** ፤ (ኢ ፡ ት ፡ እያን ፡ ያት ፤ ኢት) ፤ ቅጽል ፡ ጥሬ ፤ የሚገባ ፡ ገቢ ፤ ተመላሽ ፤ ተመላላሽ ። ገበሬ ፡ ሀሬሽ ፤ የለት ፡ ምንደኛ ፡ ሙያተኛ ፤ ዐራሚ ፡ ቈፋሪ ፤ አሽከር ፡ ወታደር ፡ አገልጋይ ፡ ሎሌ ። ገባኢ ፡ ዘይጸውር ፡ በተገብሮታ ፡ ለምድር ። ገባኢ ፡ ዘይሴፎ ፡ ዐስቦ ። ይትዓሰብ ፡ ገባእተ ። ገባኢሁ ፡ ለሔፍሬም ፡ (ጥበ ፲፯ ፡ ፲፯ ። ኢዮ ፯ ፡ ፪ ። ማቴ ፳ ፡ ፩ ። ዮዲ ፰ ፡ ፬) ።

**ግቡእ** ፤ (እን ፡ እት ፡ ብእት) ፤ የገባ ፡ የተመለሰ ፡ ምልስ ፡ ቅልስ ።

**ግብአት** ፤ መግባት ፡ መመለስ ፡ አገባብ ፡ አመላለስ ፤ ግቢ ፡ ምላሳ ፡ መያዝ ፡ መሰጠት ። ግብአተ ፡ መንጦላዕት ። ሑረት ፡ ወግብአት ። ግብአትከ ፡ ውስተ ፡ ርስትከ ። ዜና ፡ ግብአቱ ፡ ለአግሪጳስ ፡ ኀበ ፡ ሮሜ ። እፈድየከ ፡ በግብአትየ ። በእንተ ፡ ግብአቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ (ቅዳ ። ዘካ ፮ ፡ ፲፬ ። ቀሌ ። ዮሴፍ ። ሉቃ ፲ ፡ ፴፭ ። ማቴጽ ፯ ፡ ፴፯) ።

**ምግባእ** ፤ (ኣት) ፤ መግቢያ ፡ መመለሻ ፤ ተመልሶ ፡ መምጫ ፡ በታ ። ኀቤየ ፡ ምግባኢሁ ። ውስተ ፡ ምድር ፡ ምግባኢሆሙ ። የሐውር ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ ምግባእ ፡ ለዓለም ፡ (ማሕ ፯ ፡ ፲፭ ። ሚራ ፲፯ ፡ ፴ ። ግንዘ ። ዘፍ ፫ ፡ ፲፯ ። ፱ ፡ ፯) ።

**አግብአ** ፤ አገባ ፡ ከተተ ፡ አስገባ ፤ መለሰ ፡ አስመለሰ ፤ አግባ ፡ መልስ ፡ አለ ። አግብአ ፡ ለመጥባሕትከ ፡ ውስተ ፡ ቤታ ። ያገብኦሙ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ለጠቢባን ። ወያገብኦ ፡ ድኅረ ፡ ዘባኑ ። እመ ፡ አእተተ ፡ መኑ ፡ ያገብኦ ። ወአግብአት ፡ ባሕርኒ ፡ ኵሎ ፡ ሙታነ ፡ (ሜቴጽ ፯ ፡ ፶፪ ። ኢሳ ፵፬ ፡ ፳፭ ። ሚራ ፳፫ ፡ ፲፭ ። ኢዮ ፱ ፡ ፲፪ ። ራእ ፳ ፡ ፲፫) ።

—፤ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፤ ከተቀባይ ፡ እጅ ፡ አገባ ፤ አስያዘ ፡ አስጨበጠ ፤ አመጣ ፡ አቀረበ ፡ አስረከበ ፤ ፈረደ ፡ ፍርድ ፡ አቀና ። ወኢያገብኦ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ጸላኢሁ ። ይሁዳ ፡ ዘአግብኦ ። እለ ፡ አግብኡ ፡ ነፍሶሙ ፡ ለከ ። አግብኡ ፡ ቍርባኖሙ ፡ ለባዕድ ፡ ወክብሮሙኒ ፡ ለካልእ ። እለ ፡ ያገብኡ ፡ ጸባሕተ ። አግብአ ፡ ፍትሐ ፡ ለዘሩባቤል ፡ (መዝ ፵፩ ፡ ፪ ። ማቴ ፲ ፡ ፬ ። ቅዳ ። ዮሐ ። ሚራ ፵፱ ፡ ፭ ። ፪ነገ ፡ ፰ ፡ ፬ ። እርጋ) ።

**ተጋብአ** ፤ ተመላለሰ ፤ መጣ ፡ ገባ ፡ ምልስ ፡ ቅልስ ፡ አለ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በተጋብአ ፡ ፈንታ ፡ ተገባብአ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ወተገባብአ ፡ ኀበ ፡ አረጋዊ ፡ (ፈልክ ፡ ፻፳፫) ።

**አስተጋብአ** ፤ በቁሙ ፡ አስተጋባ ፡ የገደል ፡ የተራራ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ገቦ** ፤ (ብ ፡ ገበዋት ። ሱር ፡ ጋብአ ። ዐረ ፡ ጀንብ ፤ ጃኒብ) ፤ ጐን ፡ ጐድን ፡ ወገብ ፡ ወገን ፡ ማእዘን ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ። ግንቦት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡ ገቦ ፡ ክረምት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ከጳጕሜ ፡ ጋራ ፡ ይሰማማል ። ትሰክብ ፡ በገቦከ ፡ ዘፀጋም ። ለንብር ፡ እኩይ ፡ ሥትሮ ፡ ገበዋቲሁ ። ይትዐጸፍ ፡ ርትዐ ፡ ውስተ ፡ ገቦሁ ። ወልድከ ፡ ዘወፅአ ፡ እምገበዋቲከ ። በገቦ ፡ መስዕ ። ወእምገበዋቲሁ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ። አዝማድ ፡ እለ ፡ ገበዋት ። ገዳም ፡ ዘገቦ ፡ ይታይም ። ዮመት ፡ በገቦሁ ፡ (ሕዝ ፬ ፡ ፬ ። ሚራ ፵፪ ፡ ፭ ። ኢሳ ፲፩ ፡ ፭ ። ፪ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፵፯ ። ራእ ፬ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፬ ። ዮዲ ፲ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ሠኔ ፱) ።

**ዘገቦ** ፤ የገቦ ፡ በጐን ፡ የሚወጣ ፡ የሚያፈጠፍጥ ፡ ቅጥይ ፤ የማሽላ ። ወይም ፡ ሳይዘሩት ፡ የሚበቅል ፡ ወፋፊሽ ። የገቦ ፡ ማለት ፡ ንባቡም ፡ ምስጢሩም ፡ ከሔዋን ፡ ተፈጥሮ ፡ መጥቷል ፡ (ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፳፩) ።

**አግቦ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ ሸውራራ ፡ ስድብ ፤ በራሱ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ አይደለኹ ፡ ብሎ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አስመስሎ ፡ ጠላትን ፡ ለመንካት ፡ የሚነገር ። (ተረት) ፤ ወይኖን ፡ ግረፈው ፡ ፈንዘን ፡ እንዲሰማው ።

**ጋብአ** ፤ አት ፤ (ጋብአ ፡ ይጋብእ ፡ ይጋብእ ። ዐረ ፡ ጀበአ ፤ ተቀበለ ። ሱር ፡ ግባእ) ፤ መሰብሰብ ፡ ማከብ ፤ ማጋበስ ፡ ማግበስበስ ፡ ማከማቸት ፤ መልቀም ፡ ማጠራቀም ፡ መከተት ። ማጠፍ ፡ መኰርተም ፡ የሕዋስ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጋብአ ፡ ፈንታ ፡ አስተጋብአ ፡ ይላል ፤ በሳተፈና ፡ በባረየ ፡ ፈንታ ፡ አስተሳተፈ ፡ አስተባረየ ፡ እንዲል ። መራዕየከ ፡ አስተጋብአ ። አስተጋብአ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ ። ያስተጋብእ ፡ ሥርናየ ፡ ውስተ ፡ መዝገቡ ። ያስተጋብኡ ፡ ክነፊሆሙ ። ታስተጋብእ ፡ እዴከ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፰ ። ስንክ ፡ ሠኔ ፲፫ ። ማቴ ፫ ፡ ፲፪ ። ሕዝ ፳ ፡ ፳፬ ። ምሳ ፳ ፡ ፲) ።

**አጋብአ** ፤ አሰበሰበ ፤ ሰብስቡ ፡ አለ ፡ (አስደራጊ) ።

**አስተጋብአ** ፤ አሰበሰበ ፤ አሰባሰበ ፡ (አስደራጊና ፡ አደራራጊ) ። ልማዱ ፡ ግን ፤ ሰበሰበ ፡ ነው ።

**አስተጋባኢ** ፤ **መስተጋብኢ** ፤ የሚያሰበስብ ፡ አሰብሳቢ ፤ አሰባሳቢ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ ሰብሳቢ ፡ ነው ። ይቤ ፡ አስተጋባኤ ፡ መጽሐፍ ። መስተጋብኤ ፡ ነፍሳት ፡ (ፈላስ ። ሲኖዶ) ።

**መስተጋብእ** ፤ ኢ ፤ ገዚ ፡ ከማሁ ፡ የሚሰበሰብ ፡ ሰብሳቢ ፤ መሰብሰቢያ ፡ ቦታ ። መስተጋብአ ፡ ጸጋ ፡ ተግሣጻት ፡ ውእቱ ። አ ፡ ክርሥ ፡ መስተጋብኢተ ፡ ኵሉ ፡ ርኵሳት ፡ ኀጢአት ፡ (ፈላስ ። ግንዘ) ።

**ተጋብአ** ፤ ተሰበሰበ ፡ ተሰባሰበ ፤ ተከማቸ ፡ ተከመቸ ፤ ተወሰነ ፡ ተጨበጠ ፡ ተኰረኰመ ። ተጋብኡ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ኅቡረ ። ህየ ፡ ይትጋብኡ ፡ አንስርት ። ፀነስኪዮ ፡ እንዘ ፡ ኢይትጋባእ ፡ (ኢሳ ፵፫ ፡ ፱ ። ማቴጽ ፬ ፡ ፳፰ ። ቅዳ) ። በገባእ ፡ ፈንታ ፡ ተጋብአ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ማይ ፡ እምከመ ፡ ተክዕወ ፡ ኢይትጋባእ ። ይትጋባእ ፡ ማይ ፡ ዲበ ፡ ግብጽ ። ትትጋባእኑ ፡ መሥገርት ፡ ዘእንበለ ፡ ተአኀዝ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፲፬ ። ዘፀ ፲፱ ፡ ፳፯ ። ዓሞ ፫ ፡ ፲፭) ።

**ጕቡእ ፤ እስትጉቡእ ፤ (ኣን ፡ ኣት ፡ ብእት)** ፤ የተያዘ ፡ የተሰበሰበ ፤ ስብስብ ፡ ክምቹ ። ቅምጥ ፡ ጥርቅም ። ጉቡእ ፡ በእዴ ። ኵሉ ፡ እስራኤል ፡ ምስሌሁ ፡ ጉቡኣን ። እለ ፡ ጉቡኣን ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ (ምሳ፲፯ ፡ ፱ ። ፩ዜና ፡ ፯ ፡ ፴ ። ፲፪ ፡ ፳) ። እስትጉቡእ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እመጻሕፍት ፡ አምላካውያት ፡ ወቀኖናት ። ወእምዝ ፡ አትሰወ ፡ ብዝንቱ ፡ ከመ ፡ ተግሣጽ ፡ እስትጉቡእ ። ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘእስትጉቡእ ፡ ለኵሉ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ መቅ ። አፈ ፡ ድ፴፫ ። ቀ፴፬) ። በእስትጉቡእ ፡ ፈንታ ፡ ምስትጉቡእ ፡ ይባላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ምስትጉቡኣት ፡ ሕኢባፍ ፡ እም፤ ፡ መላእክት ፡ (አፈ ፡ ድ፴፪) ።

**ጕባኤ ፤ (እያት)** ፤ መሰብሰብ ፤ (ጥስ) መሰብሰብ ፤ አሰባሰብ ፤ ስብሰባ ፡ እክባ ፤ አንድነት ። መሰብሰቢያ ፡ (ጥስ) መሰብሰቢያ ፤ መሰባሰቢያ ፡ መገናኛ ፡ ጊዜ ፡ ቦታ ፤ ገበያ ፡ ሸንጎ ፡ አደባባይ ፡ ገዳም ፡ ቤተ ፡ ክሲያን ፡ የትምርትና ፡ የሰርግ ፡ የልቅሶ ፡ ቤት ፤ የመሰለው ፡ ዅሉ ። ወይም ፡ በቁሙ ፤ የተሰበሰበው ፡ ማኅበር ፡ እንግልጋ ፤ ገበያተኛ ፡ የሰው ፡ መንጋ ። ቢጉባኤክ ። ጉባኤ ፡ ቀኖናት ። በመካነ ፡ ጉባኤያት ፡ ዘከመ ፡ መራሕብት ፡ ወምሥያጣት ፤ ቦታ ፡ (ዘፀ፳፫ ፡ ፲፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፪ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵) ። ተጋብኡ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ እምሮም ፡ ጉባኤ ፡ ብዙኅ ። ጉባኤ ፡ ፀርየ ፡ ዝኑ ። ጉባኤ ፡ ሐራ ። ጉባኤ ፡ ኤጲስቆጶሳት ። ጸሐፈ ፡ መጽሐፈ ፡ ጉባኤ ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ጉባኤ ፡ ዘሐዋርያት ፤ ብዙ ፡ ሰው ፡ (ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ነሐ፲፪ ። አርጋ ። ቀኖ ፡ ኒቅ ። ቅዳ) ።

**ጕባኤ ፡ ቃና** ፤ የቅኔ ፡ ስም ፤ መዝሙረያ ፡ ቅኔ ፡ ባለ፪ ፡ ቤት ። የሰሙ ፡ ንባብና ፡ ምስጢር ፡ ከወንጌል ፡ መጥቷል ፡ (ዮሐ፪ ፡ ፲፩) ።

**ምጕባእ ፤ (ኣት)** ፤ መሰብሰቢያ ፡ መከማቻ ፡ መጠራቀሚያ ፡ ቦታ ። ወበይእቲ ፡ ዕለት ፡ ፈጠረ ፡ ላቲ ፡ ልጕታተ ፡ ዘአብሕርት ፡ በበ ፡ ምጕባኣቲሆሙ ፡ ወኵሎ ፡ አፍላገ ፡ ወምጕባኣቲሆሙ ፡ ለማያት ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ወውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ ወኵሎ ፡ ምዕቃላት ፡ (ኩፋ ፡ ፪) ።

**ምስትጕባእ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ቤተ ፡ ምስትጉባአ ፡ ዚአሁ ። ምስፋሕ ፡ ወምስትጕባእ ፡ (ሔኖ፴፫ ፡ ፳) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ጥሬውን ፡ በቅጽል ፡ ስለወጠ ፤ ምስትጉቡእ ፡ ይላል ፤ እያሰኘም ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ገብበ ፤ በት ፤ (ገበበ ፡ ይጌብብ ፡ ይገብብ ። ዕብ ፡ ጋባብ)** ፤ መሰብሰብ ፤ ማግባት ፡ መክተት ። መቈፈር ፤ መቅበር ። ማጓበብ ፡ መንጓበብ ፤ ጉብ ፡ ጉባባ ፡ መኾን ፤ እንደ ፡ ቀስት ። ጉበ ፡ መስጠት ፡ መቀበል ።

**ግብ ፤ (ብ ፡ ግበብ ፤ ባት ፤ አግባብ ። ዕብ ፡ ጎብ ። ሱር ፡ ጉባ ። ዐረ ፡ ጉብ)** ፤ መከተቻ ፡ መክተቻ ፤ ጉድጓድ ፡ ዐዘቅት ፡ ዋሻ ፡ ጕሬ ፡ መቃብር ፡ የምድር ፡ ቤት ፡ የመሰለው ፡ ዅሉ ። ዘክረየ ፡ ግበ ፡ ለቢጹ ፡ ይወድቅ ፡ ውስቴቱ ። ግበበ ፡ ምድር ። ይደፍኑ ፡ ግበባተ ። እለ ፡ አብያቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ግበበ ፡ ኰኵሕ ። ግበበ ፡ አራዊት ። እለ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ (ሲራ፳፯ ፡ ፳፮ ። ዕብ፲፩ ፡ ፴፰ ። ዮሴፍ ። ኢዮ፴ ፡ ፮ ። ኤር፱ ፡ ፲፩ ። ሕዝ፴፪ ፡ ፲፰) ። ጕብ ፤ ጉበ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ግበ ፡ ዐይን** ፤ ያይን ፡ ጕድጓድ ፡ ዋሻው ፡ ሠርጓዳው ፡ ምዕቃሉ ፤ ብርንደው ፡ እንደ ፡ ፈርጥ ፡ የተሰካበት ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ የመላበት ፡ (ምሳ፳፱ ፡ ፲፯ ። ዘካ፲፬ ፡ ፲፪) ።

**ገብገብ ፤ ገብገቦ** ፤ አዳራሽ ፡ ሰቀላ ፡ በረንዳ ። ሸንጎ ፡ አደባባይ ፤ ዐውደ ፡ ምቅታል ። ወወፅአ ፡ ውስተ ፡ ገብገብ ። አዘዘ ፡ ይሰድዋ ፡ ኀበ ፡ ገብገቦ ፡ ወይምትርዋ ፡ ክሣዳ ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፳፱ ። ስንክ ፡ ታኅ፳) ።

(ጥ) **ጋብ ፤ (ዕብራ)** ፤ ረዥም ፡ ቤት ፤ ሰገነት ፡ የደርብ ፡ ደርብ ፤ ሰንቀሳል ፡ ግንብ ። ወያንኀሉ ፡ ጋቤኪ ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፴፱) ።

**ገቢዝ ፤ ዞት ፤ (ገበዘ ፡ ይገብዝ ፡ ይግብዝ)** ፤ መለካት ፡ መወሰን ፤ ዙሪያውን ፡ መቍረጥ ፡ መክለል ፤ የመሬት ፡ የሕንጻ ። መጕበዝ ፤ መገበዝ ፡ ጕበዝ ፡ ማብዝ ፡ መኾን ። መጋበዝ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ገበዝ** ፤ ዳር ፡ ዳርቻ ፤ ጠረፍ ። ተቀበሉ ፡ ዲበ ፡ ገበዘ ፡ ተከዚ ፡ (ዘፀ፪ ፡ ፲፭) ።

—፤ ብርቱ ፡ ጠባቂ ፡ ዘበኛ ፡ በረኛ ። እምነ ፡ ጽዮን ፡ ገበዘ ፡ አዙስም ። ሰደድዎ ፡ እምሀገር ፡ እለ ፡ ገበዘ ፡ አዙስም ፤ ዕጣና ፡ ለገበዝ ። ቦአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘገበዘ ፡ አዙስም ። ገበዝ ፡ የጽዮን ፡ ቅጥል ፡ ነው ፡ (ሥር ፡ አክ ፡ ገ፹፱ ። መዋሥ ። ስንክ ፡ ግን፲፭) ።

—፤ የሹመት ፡ ስም ፤ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ ሹም ፡ አስተናጋጅ ፡ የሰሞነኞች ፡ አለቃ ። ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ጠባቂነት ፡ ነው ። ቀደሰ ፡ ገበዝ ። ኢይትሰአክ ፡ ከመ ፡ ካህናት ፡ ወኢይኩን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወኢይቀድስ ፡ ከመ ፡ ገበዝ ፡ (ሥር ፡ አክ ። ቄድር ፡ ገ፺፰) ።

—፤ መሐንድስ ፤ ሊቀ ፡ ነደቅት ። ገበዝ ፡ እንባ ፡ እንዲሉ ።

**ገበጣ** ፤ በቁሙ ፤ የጠጠር ፡ ጨዋታ ፤ ልቅምሽ ፡ ቅልምሽ ፤ ማብጠኞ ፡ ወይም ፡ ጠጠር ፡ ጣዮች ፡ ያወጡት ። (ተረት) ፤ ገበጣ ፡ ላዋቂ ፡ ወሬ ፡ ለጠያቂ ። ኢይትላሀዩ ፡ ግብረ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ወገበጣ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፴፪ ፡ ፯) ።

**ግብጠ** ፤ ያበባ ፡ እሽል ፡ መኪ ፡ የሚመስል ፡ ተርመስ ፤ ግብጣዊ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ገብጥ** ፤ የሆድ ፡ በሽታ ፡ ብስና ፡ ጓታ ፡ እህታ ፤ የሚቈርጥ ፡ የሚጕረብጥ ፡ የሚያስቀምጥ ። ቅንጣዌ ፡ ወገብጥ ። ያበዝኆ ፡ ለገብጥ ፡ ሥሥዕት ፡ (ሲራ፴፩ ፡ ፳ ። ፴፯ ፡ ፴) ።

**ተገቢጥ** ፤ ሸታ ፤ ሽንት ፡ ቅዘን ፡ ቀልዋን ፡ ዐይን ፡ ምድር ። በረዘንና ፡ ተብረገግን ፡ አዩ ።

**ገበጥባጥ** ፤ የሆድ ፡ ቅል ፡ ወስፋት ፡ ሹጥ ፡ ሥራይ ። ዘከመ ፡ ዝንቱ ፡ ደዌ ፡ ወገበጥባጥ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫) ።

**ገበይ** ፤ (ትግሬ) ፤ መንገድ ፡ ጐዳና ፡ ገበያ ። ዘሩፍ ፡ ሥሩ ፡ ጉባኤ ፡ ነው ።

**ገበያዊ** ፤ መንገደኛ ፡ ነጋዴ ፡ ገበያተኛ ።

**ገበለ** ፤ (ዕብ ፡ ጋቤል) ፤ ሰወሰ ፡ አበከ ፡ አሳቄጠ ፡ የዱቄት ፡ የሞዩቃ ።

**ግብላ** ፤ (ላት) ፤ ተንዳ ፡ ክማንድ ፡ ክደንጊያ ፡ የሚሠራ ፡ ማቡኪያ ፡ ማላቈጫ ፡ የክብቶች ፡ ውሃ ፡ ማጠጫ ፡ እንደ ፡ ገበታ ፡ የተጠረበ ፡ የተፈለፈለ ። ዘየአምር ፡ ወኢይገብር ፡ ይመስል ፡ ገብላ ፡ ዘምሉእ ፡ ማየ ፡ ዘእምኔሁ ፡ ይሰትዩ ፡ ብዙኃን ፡ ወያነጽሕ ፡ ብዙኃነ ፡ እምርስሐቲሆሙ ። ገብላተ ፡ እብን ፡ ዘይሰትዩ ፡ ባቲ ፡ አፍራስ ፡ (ፊልክ ፡ ፺፱ ። ስንክ ፡ መስ ፳፭ ። ዘፍ ፳፬ ፡ ፳፫ ፡ ፴፰ ። ዘፀ ፪ ፡ ፲፮) ።

**ጌባል** ፤ (ጽርእ ። ዕብ ፡ ጌባል) ፤ የተራራ ፡ ስም ፤ የገሪዛን ፡ ወንድም ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ፤ የርግማን ፡ ቃሎች ፡ የሚነገሩበት ፡ ከገሪዛን ፡ በስተሰሜን ፡ ያለ ፡ ፀጋማይ ፡ ተራራ ። ኹለቱም ፡ በኤፍሬም ፡ ዕፃ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ፡ (ዘዳ ፲፩ ፡ ፳፱ ። ፳፯ ፡ ፲፫) ።

**ገበነ** ፤ (ዕብ ፡ ጋቤን) ፤ አረጋ ፡ ዐየበ ፡ ዐይብ ፡ አደረገ ፡ ወተቱን ።

**ግብን** ፤ ግብነት ፤ (ዕብ ፡ ግቢና ። ሱር ፡ ግቤንታ ። ዐረ ፡ ጁብን) ፤ ጅብና ፡ ርጎ ፡ ዐይብ ፡ ያይብ ፡ ልጥልጥ ፤ በሚሄን ፡ የሚሼጥ ። ከመ ፡ ሐሊብ ፡ ሐለብከኒ ፡ ወአርጋዕከኒ ፡ ከመ ፡ ግብነት ። ዩሐልቦሙ ፡ ለእንስሳ ፡ ወይገብር ፡ ግብነተ ። ግብነት ፡ ዘላሕም ፡ (ኢዮ ፲ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ መስ ፲፰ ። ሥር ፡ ጸሎ) ።

**ግብጽ** ፤ (ጽር ፡ ኤጊብት ። ዕብ ፡ ሚጽራይም ። ዐረ ፡ ሚጽር) ፤ ግብጥ ፡ ስመ ፡ ነገድ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፡ የከም ፡ ዕፃ ። መካን ፡ ጸዐር ፡ ልሳን ፡ ባሕር ፤ የአበያና ፡ ያፍሪቃ ፡ ወሰን ፡ ደንበር ፡ ማለት ፡ ነው ። በግብጽ ፡ ፈንታ ፡ ቅብጥ ፡ ይላል ፤ ፍቹም ፡ አንድ ፡ ነው ። ብሔረ ፡ ግብጽ ። ልሳነ ፡ ቅብጥ ፡ (መገ ፡ ፺፱ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**ገቢር** ፤ ሮት ፤ (ገብረ ፡ ይገብር ፡ ይግበር ። ዕብ ፡ ጋበር ፤ ኀየለ ፡ ጸንዐ) ፤ መሥራት ፡ ማድረግ ፡ መፍጠር ፡ ያልነበረ ፡ ነገር ፡ ማስገኘት ፡ የነበረውን ፡ ማዘጋጀት ፤ ፍጥረትን ፡ ከፍጥረት ፡ ዐውምሮ ፡ ሌላ ፡ ሀላዊ ፡ ማቆም ፡ እንደ ፡ ሥጋና ፡ እንደ ፡ ሽክላ ፡ እንደ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ምንጣፍ ። በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ማየል ፡ መበርታት ፡ መሠልጠን ፡ ከሃሊ ፡ መኾን ። በደሰ ፡ ዕለተ ፡ ትገብር ፡ ግብረ ። ገቢረ ፡ ግበር ፡ በከመ ፡ አዘዝኩ ። ዘገብረ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ። ወገብሮ ፡ እግዚ ፡ ለሰብእ ፡ መሬተ ፡ እምድር ። ገብረ ፡ ወይነ ፡ እምፍሬ ፡ (ዘሌ ፳፫ ፡ ፫ ። ዮዲ ፲፫ ። መዝ ፻፵፭ ። ዘፍ ፪ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፯) ። ገብረ ፡ በሥራ ፡ ኹሉ ፡ አየገባ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ስልት ፡ ይፈታል ። ይግበሩ ፡ ውስተ ፡ ማኅቶት ፡ ቅብዐ ፤ ይደዩ ። ግበር ፡ እዴከ ፡ ዲበ ፡ ዛቲ ፡ ጻሕል ፤ ሚያም ፡ አንብር ፡ ያሰኛል ፡ (ስንክ ፡ ጥቅም ። ቅዳ) ።

**ገባሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ በርት) ፤ የሚሠራ ፡ ሠሪ ፤ አድራጊ ፡ ፈጣሪ ፡ ፈጻሚ ። አሐዱ ፡ ገባሬ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አሐዱ ፡ ግብር ፡ ይላል ፡ የጣፋ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ ጎር ። ብዙ) ። ግብር ፡ ምስለ ፡ ገባሪሁ ። ጥበብ ፡ ገባሪተ ፡ ኵሉ ። ገባርያነ ፡ ብርት ። ገበርት ፡ ዐመፃ ፡ (ጥበ ፳፱ ፡ ፲ ። ፳ ፡ ፳፪ ። ፲፯ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፭) ። ገባሪ ፡ በመላላቱ ፡ የቀተለ ፡ ሰርዌ ፡ ሺኾን ፡ በመጥበቁ ፡ ቀደሰን ፡ ይመስላል ፤ መምሰሉም ፡ ይህ ፡ ነው ።

(ጥ) **ገብሮ** ፤ ሮት ፤ (ገበረ ፡ ይጌብር ፡ ይገብር) ፤ (ጥገ) መገበር ፡ ማረስ ፡ መከፈር ፤ ገበሬ ፡ መኾን ፤ መንገድ ፡ ንግድ ፡ ማድረግ ። (ጥ፩) መገበር ፤ ግብር ፡ መብላት ፡ በግድ ፡ መሥራት ፡ ባሪያ ፡ ገባር ፡ ዜጋ ፡ መኾን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በገበረና ፡ በገበረ ፡ ፈንታ ፡ ተገበረ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ተገበሩ ፡ ጽድቀ ። እለ ፡ ይትጌበሩ ፡ ሚላተ ። ዘይትጌበራ ፡ ለምድር ። ዘይትጌበር ፡ ገራህቶ ። ሐመር ፡ እንተ ፡ ትትጌበር ፡ እምርሑቅ ። ተገበሩ ፡ እንከ ፡ እስከ ፡ አሐቱ ። ንትጌበር ፡ ወንረብሕ ፡ (ዕብ ፲፩ ፡ ፴፫ ። ኢሳ ፲፱ ፡ ፱ ። ምሳ ፲፪ ፡ ፲፩ ። ፳፰ ፡ ፲፱ ። ፳፱ ፡ ፴፩ ። ሉቃ ፲፱ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ። ያዕ ፬ ፡ ፲፫) ።

**ገባር** ፤ (ራት ። ዕብ ፡ ጌቦር ፤ ብርቱ) ፤ በቁሙ ፡ ገበሬ ፡ ሠራተኛ ፤ በግድ ፡ የሚሠራ ፡ ጕልበቱን ፡ ገንዘቡን ፡ ለሹም ፡ የሚያፈስ ፤ ሹማምት ፡ እንደ ፡ ወደዱ ፡ የሚያደርጉት ፡ ባለርስት ፡ ባሪያ ። (ግጥም ፤ ቡልጌ ፡ ያበቡት ፡ ባለጌ ፡ ጤፍ ፡ ሲወቃ) ፤ የየጀርባ ፡ ዝሙን ፡ የከረመ ፡ እንደኾነ ፡ ስንዴን ፡ ገባር ፡ ጢሰኛም ፡ ሰው ፡ አይኾን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በገባሬት ፡ ፈንታ ፡ ገባር ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ወገባሩ ፡ ኀዳጥ ፤ ከመ ፡ ይወስክ ፡ ገባረ ። ናሁ ፡ ዐስቦሙ ፡ ለገባር ። ወሚመ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ሊቃነ ፡ ገባር ፡ ከመ ፡ ይሣቅይዎሙ ፡ በግብር ። ኢዳእተ ፡ ገባር ፡ (ማቴ ፱ ፡ ፴፯ ። ያዕ ፭ ፡ ፬ ። ዘፀ ፩ ፡ ፲፩ ። ፫ ፡ ፯) ። ገባረ ፡ ሪፍ ። ገባራት ። አምጽእ ፡ ገባራተ ፡ ከመ ፡ ያንኅሉ ፡ አረፍተ ፡ ቤት ፡ (ታም ። ማር ። ስንክ ፡ ኅዳ ፳ ። አዋል) ።

**ገባራዊ** ፤ ገዢ ፡ ከማህ ፡ ገበሬ ፡ የነገር ፡ የሥራ ፡ (፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ። ኪብ ፡ ነገ ። ስንክ ፡ ኅዳ ፲) ።

**ገብር** ፤ (ብ ፡ አግብርት) ፤ ባሪያ ፡ ተገዢ ፤ አገልጋይ ፡ ሰው ፤ የተማረከ ፡ ወይም ፡ የተገዛ ፡ ግዝ ፤ ውላጅ ። ገብር ፡ ከመ ፡ እግዚኡ ። ቦኑ ፡ ውእቱ ፡ ገብር ፡ ያዕቆብ ፡ አው ፡ ልደ ፡ ቤት ። ነሥእ ፡ አርአያ ፡ ገብር ። ከመ ፡ ኪያነ ፡ ይቤዙ ፡ እግዚእ ፡ ኮነ ፡ ገብረ ። አግብርትየ ፡ ወአእማትየ ። አግብርተ ፡ ኀጢአት ፡ (ኢሳ ፳፬ ፡ ፪ ። ኤር ፪ ፡ ፲፬ ። ፊልጵ ፪ ፡ ፯ ። ድጓ ። ግብ ፪ ፡ ፲፰ ። ሮሜ ፮ ፡ ፲፯) ።

**ግብርናት** ፤ ብርነት ፡ ገባርነት ፤ ተገዥነት ። ግዕዝክሙ ፡ እምግብርናት ። ገብር ፡ ለእመ ፡ ግዕዘ ፡ እምግብርናቲሁ ። ዲወምሙ ፡ ወወህቦሙ ፡ ለግብርናት ፡ (ዲድ ፡ ፴፫ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ኅዳ ፳፮) ።

**አግበረ**፤ አሠራ፤ አስደረገ። አግበሩነ፡ ዕጹብ፡ ግብረ። እለ፡ ይቀውሙ፡ ወያገብሩ፡ ወያስተፋጥኑ፡ ግብረ፡ እግዚ። ፍቅር፡ ኢታገብር፡ እኩየ፡ ወኢታ ኄሊ፡ ሕሡመ፡ ላዕለ፡ ቢጽ። አግቢሮ፡ ኀዳውንተ። ማሕረሰክሙ፡ አግብሩ፡ ዠያንወ፡ ወማዕጺደክሙ፡ አግብሩ፡ ረምሐ፤ (ዘዳ፳፡ ፲፩፡ ፲፩። ፩ዜና፡ ፳፫፡ ፬። አፈ፡ ተ፲፱። ገድ፡ ላሊ። ዮኤ፬፡ ፲)።

**አግባሪ**፤ አሠሪ፡ አስደራጊ፡ አዛዥ።

**አገበረ**፤ በቁሙ፡ ግድ፡ አለ፡ አስገደደ፡ በግድ፡ አሠራ። መዐቶ፡ ለብእሲ፡ ጻድቅ፡ እግዚ፡ ኢያጌብሮ። ዛቲ፡ መጽሐፍ፡ ኢታጌብረከ፡ ግብረ፡ ዘኢትክል። ሰብእ፡ እኩያን፡ ያጌብሩኒ፡ ዘንተ። ምንትኑ፡ ዘአገበረከ፡ ላዕለ፡ ዝ። አገበሩነ፡ ንግበር። እመኒ፡ አገበሩከ፡ ትብባዕ። ኢያገበርኩከ፡ ከመ፡ ትሡዐ፤ (ያዕ፩፡ ፳፩። ፈላስ። ስንክ፡ ሠኔ፳፫። ዮሴፍ። ዮዲ፫፡ ፱። ሚራ፴፱፡ ፳። ኢሳ፵፫፡ ፳፫)።

**አገባሪ**፤ በቁሙ፤ የሚያስገድድ፡ አስገዳጅ። (ፍ፡ ነ፡ ፴፭)።

**አስተገበረ**፤ (አግበረ፡ አገበረ)፤ አሠራ፡ አስደረገ፤ አሳረሰ፡ አስነገደ። ነፍስነ፡ ትፈቅድ፡ ረድኤተ፡ ጽኑዐ፡ ዘያስተጌብራ፡ ለኀሊናነ። ኢያስተገብረ፡ ኀሊናሁ፡ በምንትኒ፡ ዘይክልእ፡ አብጽሖ፡ ኅበ፡ እግዚ። ወያስተጌብሮሙ፡ ለኬነውት። መጺእየ፡ እምአስተገበርክዎ፤ (አፈ፡ ተ፴፬። ፊልክ፡ ፩። ግብ፲፱። ፳፬። ማቴ፳፭፡ ፳፯። ሉቃ፲፱፡ ፳፫)።

**መስተገብር**፤ (ርት፡ ራን፡ ራት)፤ አግባሪ፡ አገባሪ፡ መገብር፡ የሚያሠራ፡ አሠሪ፡ አስደራጊ። ልማዱ፡ ግን፡ እንደ፡ ተገበረ፡ አድራጊነት፡ ነው፤ አስተገበረን፡ አይመስልም። መስተገብር፡ ውእቱ፡ ዘይትጌበር፡ ዘልፈ። ንህብ፡ መስተገብርት፡ ይእቲ። መስተገብራኒ፡ ማህው። መስተገብራኒ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን። መስተገብራኒ፡ ምድር፤ (ፈ፡ መ፡ ፳፫፡ ፩። ምሳ፲፩፡ ፳። ገድ፡ ላሊ። ዲድ፡ ፲፫)።

**መስተገብራዊ**፤ ግእዝ፡ ከማሁ፡ አሠሪ፡ ባለ ሥራ። ሠሪ፡ ሠራተኛ፤ (ፊልክ፡ ፶፲)። ተግባር፡ ረባሕ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ምስትግባር፡ መስተገብር፡ ይላል፤ ስሕተት፡ ነው፤ (ኢሳ፳፫፡ ፲፰)።

**ተገብረ**፤ (ይትገበር)፤ ተሠራ፡ ተደረገ፤ ተፈጠረ፡ ተበጀ፡ ተዘጋጀ። እንተ፡ ተገብረት፡ በወርቅ፡ ወበዕንቍ። ይትገበር፡ ሎቱ፡ በዓል፡ ዐቢይ። ተገ ቢሮ፡ ሠሐቅዎ፡ መላእክት። ዘበአማን፡ ተወልደ፡ ወኢተገብረ። ተገብረ፡ ዝንቱ፡ ኵሉ፡ በእዴከ፤ (ራእ ፲፰፡ ፲፯። ስንክ፡ ሚያ፳፱። ኢዮ፵፡ ፲፱። ቄር። ዮዲ ፲፭፡ ፲)።

**ተገበረ**፤ (ይትጌበር)፤ ግእዝ፡ ከማሁ፡ በግድ፡ ተሠራ፡ ተደረገ፡ ታረሰ፡ ተነገደ። ልማዱ፡ ግን፡ አድራጊነት፡ ነው፡ በጣም፡ ተሳስቷል፤ መዠመሪያውን፡ እይ። ተገባሬ፡ ምድር፤ (ዘካ፲፫፡ ፭። ፍ፡ ነ፡ ፴፰)።

**ግቡር**፤ (ራን፡ ራት፡ ብርት)፤ የተሠራ፡ የተደረገ፤ ፍጡር። ግቡር፡ በጽድቅ፡ ወበርትዕ። ኅዲን፡ ግቡር። ማእሰ፡ በግዕ፡ ግቡረ፡ መሓን። ለግቡራንሂ፡ ይቤልዎሙ፡ ኢኮኑ፡ ግቡራነ፡ ወኢተፈጥሩሂ፤ አላ፡ ሀለዉ፡ ዘእንበለ፡ ጥንት፤ (መዝ፡ ፻፲። ሕዝ፳፯፡ ፲፱። ዘፀ፴፭፡ ፯። አፈ፡ ድ፳፪)።

**ግብረት**፤ ማድረግ፡ መደረግ፡ መሠራት፡ መፈጠር፤ አሠራር፡ አደራረግ፤ ሥራ። ከመ፡ ግብረቱ፡ ግንፋል። ግብረተ፡ ዕጣን። ግብረተ፡ ፍትሎ። ለኵሉ፡ ግብረቱ፡ ለደብተራ። እምቅድመ፡ ግብረት፡ ሰማያት። ወሠናይ፡ ግብረቱ። ወግብረቶንሂ፡ ግብረተ፡ እግዚእ፤ (ዘፀ፳፱፡ ፲። ፴፡ ፴፭። ፴፮፡ ፳፱። ፴፭፡ ፳፭። ቅዳ፡ ማሩ። ዮሴፍ። አርጋ፡ ፫)።

**ግብር**፤ (ብ፡ ግበር፡ ግብራት)፤ ሥራ፡ ድርጊያ፡ ፍጥረት፤ ነገር፤ የተደረገ፡ ወይም፡ የሚደረግ። ኢትትማከር፡ ምስለ፡ ሀካይ፡ በእንተ፡ ግብር። ንዋየ፡ ግበሪሆሙ። ኵሉ፡ ግብረ፡ እግዚእ። ግብራተ፡ ሰማይ። በእንተ፡ ሠላሰ፡ ግብራት፤ (ሢራ፴፯፡ ፲፩። ዕብ፱፡ ፳፩። ዳን፫፡ ፴፱። ሐዋ፲፭፡ ፲፰። ፊልክ፡ ፲፩)።

**ግብር**፤ ኵርህ፤ ግድ፡ ግዴታ። በግብር፡ ዘእንበለ፡ ፈቃዱ። በግብር፡ ይከውን፡ ዘነበበ፡ ዮናስ። ግብረ፡ ይመጽእ፡ መንቡት፤ (ፈ፡ መ፡ ፭፡ ፲፪። ጦቢ፡ ፲፬፡ ፰። ሉቃ፲፯፡ ፩። ዕብ፱፡ ፲፯)። እወ፡ አማን፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ግብር፡ ይላል፤ አይስማማም፤ (ሉቃ፬፡ ፳፫)።

**ግብር**፤ በቁሙ፤ ጸባሕት፡ አምኃ፡ ድኻ፡ ለመንግሥት፡ የሚሰጠው። ከመ፡ የሀቡ፡ ግብረ። እለ፡ ይቀውሙ፡ ላዕለ፡ ግብር። ርሑብ፡ ግብር። ይሁብዎ፡ ግብረ፡ በበ፡ ዓመት፤ (፪ዜና፡ ፰፡ ፰፡ ፲። ፲፡ ፲፰። ፳፯፡ ፭)።

**ተግባር**፤ በቁሙ፤ ፍጥረት፡ ሥራ፡ ዕርሻ፡ ቀፉሮ፡ ንግድ፤ ጥበበ፡ እድ፡ በየስሙና፡ በያይነቱ። ኵሉ፡ ተግባረ፡ እግዚ፡ ሠናይ፡ ወአልቦ፡ ግዱፍ። ተግባረ፡ ምድር። ወሰምረ፡ ሎቱ፡ ተግባሩ። በንዋየ፡ ብርት፡ ረሰዮ፡ ተግባረኪ። ሜጥ፡ ወተግባር። ተግባረ፡ እደው። ምንተ፡ ተግባርክሙ፤ (፩ጢሞ፡ ፬፡ ፬። ኤር ፲፱፡ ፬። ሉቃ፲፪፡ ፲፯። ሕዝ፳፯፡ ፲፫። ሚራ፳፯፡ ፪። ፯፡ ፲፯። ዘፍ፵፮፡ ፴፫)።

—፤ ጕዳይ፡ ግዳጅ፡ ባሕርያዊ፡ ሥራ። ኀይል፡ ብዕል፡ የንግድ፡ ዕቃ፡ መናገኛ። እምብዝኃ፡ ተግባርኪ። አምጽኡ፡ ዓሣኒ፡ ወባዕደኒ፡ ብዙኃ፡ ተግባሮሙ፤ (ሕዝ ፳፯፡ ፲፰። ነሐ፲፫፡ ፲፮)።

**ትግብርት**፤ ሥራንት፡ አሠራር፡ አደራረግ። ሥራ፡ የሥራ፡ ስልት፡ መልክ። ትግብርቶሙ። ትግብርተ፡ ንህብ፤ (ኩፋ፡ ፲፩። ምሳ፳፡ ፰)። ግርድ፡ ዕንፉፅ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ትግብርት፡ ይላል፤ (ዓሞ፰፡ ፯)።

**መግበር**፤ ት፡ (ብ፡ መጋብርት)፤ መሥሪያ፡ መሣሪያ፤ ዕቃ። ኵሉ፡ ግብሩ፡ ወኵሉ፡ መጋብርቲሁ። ለመጋብርት፤ (ዘፀ፳፯፡ ፲፱። ፴፱፡ ፲፡ ፳፩። ሕዝ፲፭፡ ፫)።

**ምግባር ፤ (ራት) ፤** በቁሙ ፤ ሥራ ፤ የሚገባ ፤ የማይገባ ፤ በሕግ ፤ የታዘዘ ፤ ወይም ፤ ያልታዘዘ ፤ ማናቸውም ፤ ኹሉ ። ለኵሉ ፡ ብእሲ ፡ ይፈድዮ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ። ምግባረ ፡ ወሀብናሁ ። ኵሉ ፡ ምግባሮሙ ፡ ርኩስ ። ንጹሕ ፡ አነ ፡ በምግባርየ ። ሶበሰ ፡ አብርሃም ፡ በምግባሩ ፡ ጸድቀ ። ዘይበቍዕ ፡ ለምግበ ፡ ምግባራቲሁ ፡ ወንዋዩ ። (ሢራ ፴፪ ፡ ፳፱ ። ክፋ ፡ ፫ ። ፳፭ ። ኢዮ ፲፭ ፡ ፲ ። ሮሜ ፬ ፡ ፪ ። ፍ ፡ ን ፡ ፴፪) ።

**ምግባር ፤** መሥሪያ ፤ ማድረጊያ ፤ ቦታ ፤ መሣሪያ ፤ ወይም ፤ ባሕርይ ፤ አካል ፤ ሥራውን ፤ የሚፈጽምበት ። ምግባር ፡ ይመርሕ ፡ ኀበ ፡ ጥያቄ ፡ አስማት ፡ ወምግባርኒ ፡ ይትፈጸም ፡ በህላዌ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**ገቢስ ፤ ሶት ፤ (ገበሰ ፡ ይገብስ ፡ ይግብስ ። ዕብ ፡ ጋበሽ ፤ መላ ። አው ፡ ገብሰሰ ፤ ሶት ፤ ገብሰሰ ፡ ይገበስስ ፡ ይገብስስ) ፤** ማጋበስ ፤ መሰብሰብ ፤ የማር ፤ የንፈጦት ፤ የኵረት ፤ መምላት ፤ ማስተከከል ፤ መምረግ ፤ መለሰን ፤ መቅባት ፤ መለቅለቅ ፤ የግድግዳ ፤ የማንብ ። መምላት ፤ ውስጡን ፤ በኵረት ፤ መለሰን ፤ አፍኣውን ፤ በጭቃ ፤ መለቅለቅ ፤ በኖራ ፤ በበረቅ ። ገሃረን ፡ እይ ።

**ገብሳሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት ፤ ሰስት) ፤** የሚለስን ፤ ለሳኝ ፤ ቀቢ ፤ ለቅላቂ ።

**ተገብሰሰ ፤** ተመረገ ፤ ተለሰነ ፤ ተከከለ ፤ የታባሰ ፤ ነገር ፤ መሰለ ፤ ኖራ ፤ ተቀባ ።

**ግብሱስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ስስት) ፤** የተመረገ ፤ የተለሰነ ፤ ምርግ ፤ ልስን ፤ ቅብ ፤ ልቅልቅ ። አረፍት ፡ ግብስስት ። መቃብር ፡ ግብሱሳን ፡ (ግብ ፳፫ ፡ ፫ ። ማቴ ፳፫ ፡ ፳፯) ።

**ግብስስ ፤ (ጽር ፡ ጊብሶስ ። ዕብ ፡ ሲድ) ፤** ኖራ ፤ በረቅ ፤ የደንጊያ ፤ ዐመድ ፤ ነጭ ፤ ደቃቅ ። አውዐዩ ፡ አዕፅምቲሁ ፡ ለንጉሥ ፡ ለግብስስ ። ዐጥንቱ ፤ ዐመድ ፤ እስኪኾን ፤ ኖራ ፤ እስኪመስል ፤ ማለት ፤ ነው ፤ ባለብሎች ፤ ግን ፤ ግብስስ ፤ ለሚባል ፤ ጣዖት ፤ ይሉታል ፤ (ዓሞ ፪ ፡ ፩) ። አምጽኡ ፡ ግብስሰ ። ከመ ፡ ግብስስ ፡ ድቀቅ ፡ (ሄርማ ፡ ገ፳፫ ። ኢሳ ፳፯ ፡ ፱) ።

— ፤ ልስናት ፤ ልቅልቃት ። የተጣጠ ፤ የተቀረፈ ፤ ምርጊት ፤ የፈረሰ ፤ የተናደ ፤ ቤት ።

**ግብስ ፤** በቁሙ ፤ ሰገም ፤ የብር ፤ እኽል ፤ ነጭ ፤ ነጣንጭ ፤ ማለት ፤ ነው ። ገብስማ ፤ ደሮ ፤ እንዲሉ ።

**ግብት ፤—ድንገት ፤— ወጊብ ፡ ወገበ ።**

**ገበታ ፤ (ብ ፡ ገባትው) ፤** በቁሙ ፤ የንፈጦት ፤ ለገን ፤ ወጭት ፤ ማቡኪያ ፤ ማሻ ፤ መለወሻ ፤ ቆሬ ፤ ወይም ፤ ማማሻ ፤ ገበርማ ፤ ጠፍጣፋ ፤ ሉሕ ፤ ስደቃ ። ዋልታም ፤ ይኸናል ። ወደብ ፡ ገባትው ፡ በዘይገብሩ ፡ ናእተ ፡ (፩ዜና ፳፫ ፡ ፳፱) ።

**ገበታ ፤ (ዕብ ፡ ጋብታ ። ጽር ፡ ጋበታ) ፤** የቦታ ፤ ስም ፤ ከፍታና ፤ ሜዳነት ፤ ያለው ፤ (ዮሐ ፲፱ ፡ ፲፫) ።

**ገበታ ፡ ሐዋርያ ፤ (ዐማርኛ) ፤** የመጽሐፍ ፤ ስም ፤ ገበታዋሪያ ፤ ት ፤ ሰባቱ ፤ የሐዋርያት ፤ መልእክታት ፤ ከያዕቆብ ፤ እስከ ፤ ይሁዳ ፤ ያሉት ። መጽሐፉን ፤ ገበታ ፤ ያሰኘው ፤ ሰንፈጡ ፤ ነው ፤ ፍችውም ፤ ማእድ ፤ ማእደ ፤ ትምህርት ፤ ዘሠርዐዎ ፤ ሐዋርያት ፤ እንደ ፤ ማለት ፤ ነው ።

**ገበታ ፤** የሰው ፤ ስም ። ምስለ ፡ ገቦታ ፡ ወታራ ፡ (አስቴ ፲ ፡ ፲፪) ።

**ጉጋ ፤ ጕጋ ፤** ጉጉት ፤ የጕጕት ፤ ዐይነት ፤ አሞራ ። ባለብሎች ፤ ቍንጫ ፤ ይሉታል ፤ (መዝ ፻፩ ። ዘሌ ፲፩ ፡ ፲፯ ። ዘዳ ፲፬ ፡ ፲፯) ። ቆቃሕ ፤ በማለት ፤ ፈንታ ፤ ጉጋ ፤ ይላል ፤ ስሕተት ፤ ነው ፤ (ጸንገ ፤ ፳፯ ፤ ፳) ።

**ጓጓ ፤** ጋጋኖ ፤ አጎበ ፤ ቀቀኖ ፤ የጥንብ ፡ አሞራ ፤ እንደ ፤ ጋጋኖ ፤ በገዞ ፤ ተንጋግቶ ፤ የሚኼድ ።

**ጋግ ፤ ጋጋ ፤ (ብ ፤ ጋጋት ። ዕብ ፡ ጋግ ፤ ጠፈር ፡ መዋቅር ፡ ባጥ) ፤** መንቴር ፤ ቀንበር ፤ ዘንጅር ፤ የቅጣትና ፤ ያገዛዝ ፤ መሣሪያ ፤ (ዘዳ ፳፰ ፡ ፵፰ ። ፫ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፬ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ሢራ ፳ ፡ ፳፬ ፡ ፳፱ ። ዕን ፪ ፡ ፮) ። ግድፉ ፡ ጋጋ ፡ እምክሣድኪ ። አንትሙ ፡ እሱራን ፡ በሰናስል ፡ ወበጋጋ ፡ ወበመዋቅሕት ። ያከብዱ ፡ ለነ ፡ ጋጋተ ፡ ውስተ ፡ ክሣውዲነ ፡ ዘኢንክል ፡ ጸዊሮቶ ። ወደዩ ፡ አርባዕተ ፡ ጋጋተ ፤ አሐደ ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ፡ ወአሐደ ፡ ውስተ ፡ ገቦሁ ፡ ወአሐደ ፡ ውስተ ፡ ሐቌሁ ፡ ወአሐደ ፡ ውስተ ፡ አብራኪሁ ፡ (ኢሳ ፶፪ ፡ ፪ ። ዮሴፍ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ የካ ፲፫) ።

— ፤ ያንገት ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ ልሻን ፡ ማርዳ ፡ ድሪ ። ጋጋ ፡ ዘወርቅ ፡ (ስንክ ፡ ጥር ፲፯) ።

**ጐጐአ ፤ አ ፤ (ጐጐአ ፡ ይጔጕእ ፡ ይጐጕእ) ፤** መጓጓት ፤ መመኘት ፤ ተስፋ ፤ ማድረግ ፤ መሠየት ፤ መጕምጀት ፤ ከዚህ ፤ የተነሣ ፤ መቸኰል ፤ መጣደፍ ፤ መፍጠን ፤ መቀልጠፍ ፤ መጣር ፤ መፍጨርጨር ፤ መትጋት ። ጐጕአ ፡ ከመ ፡ ይባእ ፡ እምህየ ። ጐጕአ ፡ ከመ ፡ ይዕርግ ። ይጔጕእ ፡ ዘተነድፈ ፡ ይምላኅ ፡ ሐጸ ። እስመ ፡ ቦ ፡ ዘይጔጕእ ፡ ወይሰርሕ ። ይጔጕእ ፡ ይብዐል ፡ (፪ዜና ፡ ፳፯ ፡ ፳ ። ፲ ፡ ፲፰ ። ሢራ ፲፬ ፡ ፲፪ ። ፲፭ ፡ ፲፭ ። ምሳ ፳፰ ፡ ፳፪ ። ፪ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ። ፫ ፡ ፲፬) ።

**ጐጓኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤** የሚቸኵል ፤ ቸኳይ ። አንተ ፡ ብእሲ ፡ ጐጓኢ ፡ (ሄርማ) ።

**ጕጕእ ፤ (እን ፡ እት ፡ ጕእት) ፤** የጓጓ ፤ ጕጕ ፤ የቸኰለ ፤ ችኵል ፤ ፈጣን ፤ ቀልጣፋ ፤ ትጉ ። አፍ ፡ ጕጕእ ። ሰማዕት ፡ ጕጕእ ። ጕጕእ ፡ በክናፍሪሁ ። እመ ፡ ርኢከ ፡ ብእሴ ፡ ጕጕአ ፡ በቃል ፡ (ምሳ ፲ ፡ ፲፬ ። ፲፪ ፡ ፲፱ ። ፲፫ ፡ ፫ ። ፳፱ ፡ ፳) ።

**ጕጓኤ ፤** መጓጓት ፤ ጉጉት ። መቸኰል ፤ አቸኳኰል ፤ ችኰላ ፤ ችኵልነት ፤ (ዮሴፍ) ። በጕጓኤ ፤ ፈንታ ፤ ጕጕኣት ፤ ይላል ፤ አያስኬድም ። እምብዝኀ ፡ ጕጕኣቲ ፡ (ስንክ ፡ ጥር ፲፯) ።

**ጕጕአ** ፤ ተኰሳ ፡ ጥድፊያ ፡ ቅልጠፋ ፡ ትጋት ፡ ጥረት ፡ ድንጋጤ ። ፈነዎሙ ፡ በብዙኅ ፡ ጕጕኣ ። ኅሰፈ ፡ በጕጕኣ ። ጕጕኣ ፡ ኀቢረክሙ ። ቃል ፡ ወሁከት ፡ ወነ ጐድጓድ ፡ ወድልቅልቅ ፡ ወጕጕአ ፡ ባዕለ ፡ ምድር ፡ (ጥበ፲፱ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፻፳ ። ፪ጼ.ጥ ፡ ፩ ፡ ፰ ። አስቴ፩ ፡ ፲፱ ። ሔኖ፩፱ ፡ ፱) ።

**አጕጕአ** ፤ አስቸኰለ ፡ አቻኰለ ፡ አጣደፈ ፡ አስ ደነገጠ ፡ (ዘፍ፲፱ ፡ ፲፭ ። ዘዐ፰ ፡ ፲፫ ። ሔኖ፲፱ ፡ ፰) ። ያጔጕእዎ ፡ ለሐማ ፡ ውስተ ፡ በዓል ። መላእክት ፡ ያ ጔጕኡኒ ። እግዚ ፡ አጕጕአኒ ፡ (አስቴ፮ ፡ ፲፬ ። ሔኖ፶፱ ፡ ፲ ። ኢዮ፳፫ ፡ ፲፮) ።

**አጐጓኢ** ፤ **መጐጕእ** ፤ የሚያጓጓ ፡ የሚያስቸ ኵል ፡ አስቸኳይ ፡ መደንግፅ ።

**ገግጸ ፤ ጸት ፤ (ገገጸ ፡ ይጔግጽ ፡ ይገግጽ)** ፤ መገገጽ ፡ ተግ ፡ ማለት ፡ መቆም ፡ መገታት ፡ ማፈግፈግ ፡ ማሸግሸግ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማለት ፡ በፍርሆ ፡ ፈርቶ ፡ ደንግጦ ። ኢይጔግጽ ፡ እመዋቲ ። ኢይጔግጽ ፡ እምገጸሙ ። ኢ ይጔግጽ ፡ እምጸብእ ፡ ወቀትል ። ገገጹ ፡ እምንጻሬ ፡ ሞት ። እንዘ ፡ ይጔግጹ ። በላም ፡ ለአዕይንቲከ ፡ እለ ፡ ኢገገጻ ፡ እምርእይ ፡ (ኢዮ፴፪ ፡ ፴፩ ። ፴፱ ፡ ፲፱ ። ዮ ሴፍ ። አፈ ፡ ድ፲ ። ኄርማ ። ደራሲ) ። ገጽን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ግጋጼ** ፤ ማፈግፈግ ፡ ኀፍረት ፡ ፍርሀት ፡ ድን ጋጤ ፡ ሽሽት ። ቀርበተ ፡ ለመዊት ፡ እንበለ ፡ ግጋጼ ። በማዕፃተ ፡ ክርስቶስ ፡ እንበለ ፡ ግጋጼ ፡ (ዮሴፍ ። ስ ንክ ፡ ኀሐ፲) ።

**ግግጽና** ፤ ግዘኒ ፡ ከማሁ ፡ አፈግፋጊነት ። ሖረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ እንበለ ፡ ግግጽና ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፱) ።

**አገገጸ** ፤ አስፈገፈገ ፡ አስፈራ ፡ አሳፈረ ፡ ተግ ፡ አ ሰኘ ፡ አስታገሠ ።


**ጋዳ** ፤ **ጋድ** ፤—**በቁሙ** ፤—**ገዲ.ው** ፡ ገ ደወ ።

**ጐድአ** ፤—**መቃ** ፡ **ደሰቀ** ፤—**ጐዲዕ** ፡ ጐ ድዐ ።

**ጐዲብ ፤ በት ፤ (ጐደበ ፡ ይጐድብ ፡ ይ ጕድብ)** ፤ መጕደብ ፡ ማረድ ፡ መቈፈር ፡ ማጐድጐድ ፡ መቆፈጥ ፡ የመሬት ። መመንደብ ፡ መጕረድ ፡ መጕመድ ፡ መፈነፍነፍ ፡ መመንጠር ፡ መስበድ ፡ ከንቻ ፡ መምታት ፡ የንፈነት ። መገደብ ፡ መወደብ ፡ መክተር ፡ ማገድ ፡ የውሃ ። የሦስቱ ፡ ኹሉ ፡ ስልት ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ምስጢሩ ፡ ከመ ቍረጥ ፡ አይወጣም ፡ ገዘመንና ፡ ገመደን ፡ ይመስላል ፡ አንቀጹ ፡ ከማርኛ ፡ በቀር ፡ በግእዝ ፡ ቃላት ፡ አይገኝም ።

**ጕድብ** ፤ በቁሙ ፡ የታረደ ፡ የተቈረጠ ፡ ዕርድ ፡ ምሽግ ። ማንኛቱ ፡ ፈፋ ፡ ውሃ ፡ የበላው ፡ መሬት ።

**ጕድብ ፤ (ባት ። ዕብ ፡ ጋርዜን ፤ ቃር ዱም ። ዐረ ፡ ፋስ)** ፤ ምግዝም ፡ ገዠሞ ፡ የብረት መማሪያ ፡ መጥረቢያ ፡ ምሣር ። ኹለት ፡ አፍ ፡ ብረት ፡ ምማርና ፡ ደማ ፡ የሚቈርጥና ፡ የሚቈፍር ፡ እጀታው ፡ አንድ ፡ ምላሱ ፡ ጥንድ ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ የሚሠራ ፡ (ዘዳ፲፱ ፡ ፭ ። መሳ፱ ፡ ፲፰ ። ፩ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ። ኢሳ፲ ፡ ፲፭ ። መዝ ፡ ፸፫ ። ሉቃ፫ ፡ ፱ ። ሕገዘ ፡ ፪) ። **ከመ ፡ ምሣር ፡ ዘይሤጽር ፡ ወከመ ፡ ጕድብ ፡ ዘይሰብር** ፡ (ዲድ ፡ ፲ ። አዋል) ።



ጕድብ ፡

**ገድገደ ፤ (ገዲድ ፡ ገደ ። ግዘ)** ፤ በቁሙ ፡ ገደ ገደ ፡ አቆመ ፡ አጸና ፡ ተከለ ፡ የይሎ ፡ የድንኳን ።

**ገድገድ** ፤ ግድግዳ ፡ ካብ ፡ ቅጥር ፡ የድንኳን ፡ ከ ስማ ፡ አውታር ፡ የሽማ ፡ ዐጥር ። **በዐውደ ፡ ገድገደ ፡ ቤቱ ። በዐጸደ ፡ ገድገዱኒ ፡ ሲደብተራ** ፡ (መቃ ፡ ገ፳ ። ፲፰) ። አንገደገደ ፡ ተንገደገደ ፡ ገድጋዳ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ገዲድ ፤ ዶት ፤ (ገደ ፤ ገደደ ፡ ይገድድ ፡ ይግድድ ። ዕብ ፡ ጋዳድ ። ዐረ ፡ ጀደ)** ፤ (ጥን) መገደድ ፡ በግድ ፡ መያዝ ፡ ማስገደድ ፡ ግድ ፡ ማለት ፡ የዳኛ ፡ የባለዳ ። መወንበድ ፡ መሸፈት ፡ መፈከን ፡ የሰራ ዊት ። መባስ ፡ መታደስ ፡ ማገርሸት ፡ የደዌ ፡ የክፋት ። መግደድ ፡ ማግደድ ፡ መወላገድ ፡ መጥመም ፡ መጣመም ፡ የመልክ ፡ የጠባይ ፡ ኹሉም ፡ የክፉ ፡ ነው ።

(ጥ) **ግዱድ ፤ (ዕብ ፡ ግዱድ ፤ ወራሪ ፡ ዘራፊ)** ፤ በግድ ፡ የተያዘ ፡ ወይም ፡ የሚይዝ ፡ የሚያስገድድ ፡ ፈፀ ካኝ ፡ ወንበዴ ፡ ሽፍታ ። ወኀይላኒ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ግዱድ ፡ (ሆሴ፮ ፡ ፱) ።

—፤ የባሰ ፡ የጸና ፡ የበረታ ፡ ብርቱ ። **እስመ ፡ ኀጢአቶሙ ፡ ዐቢይ ፡ ወግዱድ ፡ በኀበ ፡ እግዚ** ፡ (ቂድር) ።

**ግድ** ፤ በቁሙ ፡ ውድና ፡ ፈቃድ ፡ የሌለበት መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በግድ ፡ ፈንታ ፡ ግዱድ ፡ ይላል ፡ አያስ ኝም ። **አዘዘ ፡ ይጥዐምዎ ፡ በግዱድ** ፡ (ግንዘ) ።

**ግደት** ፤ መገደድ ፡ ማስገደድ ፡ ግዴታ ፡ ግድ ፡ ግዳጅ ፡ ጥናት ፡ ብርታት ። **እመ ፡ ወድቀ ፡ ብሒት ፡ ውስተ ፡ እከይ ፡ እመ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ድካመ ፡ ሥጋ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ግደተ ፡ ገድል** ፡ (ፈልክ ፡ ፱) ።

**ጐዲድ ፤ ዶት ፤ (ጐደ ፤ ጐደደ ፡ ይጐ ድድ ፡ ይጕድድ)** ፤ መጓደድ ፡ መቈነን ፡ ያካኼድ ፡ ያ ረማመድ ፡ የታቦት ፡ የዑደት ።

**ጐደዳ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ ያዘበ ፡ ጡብ ፡ የኰበት ፡ ጠገራ ፡ ከባድ ፡ ጥፍጥፍ ፡ ሲማገድ ፡ ከእሳት ፡ ሲሞላድ ፡ የሚጓደድ ፡ ብርቱ ፡ ጠንካራ ። (ተረት) ፡ ሆድ ፡ ዕዳ ፡ ያስ በላል ፡ ጐደዳ ።

**ጐድጐደ ፤ (ጐዲዕ ፡ ጐድዐ)** ፤ ደጅ ፡ መቃ ፡ ቀበቀበ ፡ እጅ ፡ ጸፋ ፡ አፈነበፈነበ ፡ ለማስከፈት ። ማስንቂ ፡

ከጐዲ.ስና ፡ ከገዲ.ድ ፡ ከኹ.ለቱ ፡ የተ.ደ.ቀለ ፡ ነው ። ሰበ ፡ ጐ.ድጐ.ደ ፡ ኆኅተ ። ነሥአ ፡ እብነ ፡ ወጐ.ድጐ.ደ ፡ ቦቱ ፡ እንተ.ጸ ። ቦአ ፡ ወጐ.ድጐ.ደ ፡ በኅበ ፡ ዐጸ.ድ ፡ ዘቅድመ ፡ ይብተሩ ። ወለዘ.ኒ ፡ ጐ.ድጐ.ደ ፡ ይትረኀዎ ፡ (ሬልክ ፡ ፺፫ ። ስንክ ፡ የካ፲ ። ዮ.ዲ.፲፬ ፡ ፲፱ ። ማቴ፯ ፡ ፰) ።

**ጕድጕድ** ፡ ክተተ ፡ ክቤት ፡ ክኅዳ ፡ ከጕድኅድ ፡ እንቀ ። ጐ.ደጐ.ደ ፡ ጐ.ድኅድ ፡ ኸን ፡ (ዐማርኛ) ።

**አንጐድጐደ** ፡ አንጐደጐደ ፡ አሰማ ፡ ተንጐ ደጐ.ደ ፡ ተሰማ ፡ (አንገ ፡ ፮ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፲፯) ። ያንጐ ድጐ.ድ ፡ ኀይል ፡ በፀዓዐ ፡ መደንግፅ ። ዘበላዕሉ ፡ አን ጐ.ድጐ.ደ ፡ (ኢ.ዮ ፡ ፴፮ ፡ ፫ ፡ ፬ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ነጐድጓድ** ፡ (ዳት) ፡ በቁሙ ፡ የመብረቅ ፡ ኃታ ፡ ነገሮዳ ፡ ታላቅ ፡ ግሩም ፡ ድምጥ ፡ የሚያስፈራ ፡ የሚ ያስደነግጥ ፡ የሚያርድ ፡ የሚያንቀጠቅጥ ፡ (መዝ ፡ ፸፯ ። ፺፫ ። ኢ.ዮ፡፡፡ ፡ ፬ ። ማር፫ ፡ ፲፯) ። መብረቅ ፡ ወፀዓዐ ፡ ወነጐ.ድጓ.ድ ። ወሰማዕኩ ፡ ቃሎ ፡ ከመ ፡ ነጐ.ድጓ.ድ ። ነጐ.ድጓዳት ፡ ወመባርቅት ፡ (ራእ፬ ፡ ፭ ። ፮ ፡ ፭ ። ክሩ ፡ ፪) ።

**ገዳው** ፡ ዎት ፡ (ገደወ ፡ ይገዱ ፡ ይግዱ) ፡ መስጠት ፡ ማቅረብ ፡ ማስረከብ ። መጋዳት ፡ መክልከል ።

**ጋዳ** ፡ (ዳት) ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ በረከት ፡ መቀ ያያ ፡ በፈቃድ ፡ የሚሰጥ ። ነገሥት ፡ ሳባ ፡ ወዐረብ ፡ ጋዳ ፡ ያመጽኡ ። ጸባሕት ፡ ወጋዳ ። አስትዓ ፡ ወጋዳ ። የሀ በነ ፡ ሰላመ ፡ ጋዳ ፡ (መዝ ፡ ፸፩ ። ማቴ፲፯ ፡ ፳፭ ። ሔኖ ፶፫ ፡ ፩ ። ድጓ) ።

**ጋድ** ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ገድ ፡ ብዕል ፡ በረከት ፡ ማ ለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፴ ፡ ፲፩) ።

**ጎድ** ፡—ጎይል ፡—ገወድ ።

**ገዲል** ፡ ሎት ፡ (ገደለ ፡ ይገድል ፡ ይግ ድል ፡ ቀተለ ። ዕብ ፡ ጋዳል ፡ ዐብየ) ፡ መግደል ፡ ማጥፋት ፡ ማረድ ፡ መቅተል ፡ ማነቅ ፡ ገደል ፡ መጣል ። ፈነወ ፡ ሐጸ ፡ ወነደፎ ፡ ለጊሳው ፡ እኍሁ ፡ ወገደሎ ። ወገደሎ ፡ ዳቤላ ፡ ጣሊ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፰ ። ዳንኤ ፡ ፯) ። በጠ ብሐ ፡ ፈንታ ፡ ገደለ ፡ ይባል ። ወገደለ ፡ ንጉሥ ፡ እም ጥሪተ ፡ ዚአሁ ፡ ወመላእክትኒ ፡ ገደሉ ፡ ለሕዝብ ። እ ገድሳ ፡ ለዛቲ ፡ ደርሆ ፡ ለተዝካረ ፡ አቡየ ፡ (፩ዜና ፡ ፴፭ ፡ ፯ ። ገድ ፡ ተክ ፡ ታም) ።

**ገዳሊ** ፡ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፡ የሚገድል ፡ ገዳይ ፡ ዐራጅ ፡ ገደል ፡ ሰዳጅ ።

**አግደለ** ፡ አስገደለ ፡ ገደል ፡ አስጣለ ።

**ተገድለ** ፡ ተገደለ ፡ ታረደ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ሞተ ፡ ተጣለ ፡ ወደቀ ፡ ገደል ፡ ገባ ።

**ግዱል** ፡ (ላን ፡ ላት ፡ ድልት) ፡ የተገደለ ፡ የ ተጣለ ፡ ገደል ፡ የገባ ።

**ገደላ** ፡ (ላት) ፡ ውዳቂ ፡ ሬሳ ፡ ጥንብ ፡ ገደል ፡ ገባ ፡ (ዘዐ፳፯ ፡ ፴፱—፴፮) ። ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ገደላ ፡ ህየ ፡ ይ ትጋብኡ ፡ አንስርት ፡ (ማቴ፳፬ ፡ ፳፰ ። ሉቃ፲፯ ፡ ፴፯) ።

**ገድል** ፡ (ዕብ ፡ ጋዶል ፡ ዐቢይ) ፡ በቁሙ ፡ ጾድፍ ። (ተረት) ፡ ዘፍኖ ፡ ወፍ ፡ ገደልና ፡ አፋፍ ። በሬ ፡ ሆይ ፡ በሬ ፡ ሆይ ፡ ሣሩን ፡ አየኸና ፡ ገደሉን ፡ ሳታይ ።

**ተጋደለ** ፡ በቁሙ ፡ ታገለ ፡ ተናነቀ ፡ ተማታ ፡ ተቋሰለ ፡ ተጋ ፡ ተዋጋ ፡ ተሳሰፈ ፡ ተቃወመ ፡ ተከራከረ ፡ ተደባደበ ፡ በጕልበት ፡ ባንደበት ፡ በመሰለው ፡ ኹሉ ። ወ ተጋደሎ ፡ ብእሲ ፡ እስከ ፡ ጸብሐ ። ረከበ ፡ ክልኤተ ፡ ዕደወ ፡ እንዘ ፡ ይትጋደሉ ። ንትጋደል ፡ ለጸቢሖትሙ ፡ እስከ ፡ ንመውት ። ይትጋደል ፡ አብ ፡ ምኔት ፡ ለአድ ኅዎቱ ። ተጋድሎታ ፡ ለፍትወት ። ተጋደልዋ ፡ ለኀ ጢአት ። ተጋደለ ፡ በንስሓ ። ተጋደሉ ፡ ሰማዕት ፡ በ ዳማ ፡ ወበምንዳቤ ፡ (ዘፍ፴፪ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ። ዘፀ፪ ፡ ፲፫ ። ዮሴፍ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲ ። ፳፬ ፡ ፳ ። ዕብ፲፪ ፡ ፬ ። መቃ ፡ ገ፲፭ ። መዋሥ) ።

**ተጋዳሊ** ፡ የሚጋደል ፡ ተጋዳይ ። (ተረት) ፡ አል ሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይ ። ገድለኛ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዐርበኛ ። ይቤ ፡ አሐዱ ፡ እምተጋዳልያን ፡ ክቡር ፡ ምቶሙ ፡ ለሰማዕታት ፡ (ፊላስ ፡ ገ፵፱) ።

**ገድል** ፡ (ላት) ፡ በቁሙ ፡ ትግል ፡ ፈተና ፡ ው ጊያ ፡ ሰልፍ ፡ ድልና ፡ አክሊል ፡ አስኪንኝ ፡ ድረስ ፡ የሚ ደክሙት ፡ ድካም ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ የሚቀበሉት ፡ መ ከራ ። ገድለ ፡ መዊእ ። ገድል ፡ ጽኑዕ ። ነበረ ፡ በዝንቱ ፡ ገድል ፡ ሠለስተ ፡ ዓመተ ። እለ ፡ ተጋደሉ ፡ ሠናየ ፡ ገ ድለ ፡ ወሞቱ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ። ዕሴተ ፡ ገድላ ቲሆሙ ፡ ወድካማቲሆሙ ። ለሰማዕታት ፡ ገድላቲ ሆሙ ፡ ተጽሕፈ ፡ ለነ ፡ ንትመሀር ፡ ሃይማኖቶሙ ። ገድላቲሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ (ጥበ፬ ፡ ፪ ። ፲ ፡ ፲፪ ። ገድ ፡ ተክ ። ዲ.ድ ፡ ፳፭ ። ፈ ፡ መ ፡ ፭ ፡ ፪ ። መዋሥ ። አፈ ፡ ድ፳፰) ።

—፡ መንፈሳዊ ፡ ዜና ፡ ወግ ፡ ታሪክ ፡ የቅዱሳንን ፡ መከራና ፡ ጸጋ ፡ ተጋድሏቸውን ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ። ገድለ ፡ አዳም ፡ ገድለ ፡ አብርሃም ፡ ገድለ ፡ ሐዋርያት ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**አስተጋደለ** ፡ አጋደለ ፡ አስታገለ ፡ አስተጋገለ ።

**መስተጋድል** ፡ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፡ የሚ ጋደል ፡ የሚታገል ፡ ተጋዳሊ ። የሚያጋድል ፡ የሚያስታ ግል ፡ አጋዳይ ። ወእመኒ ፡ መስተጋድል ፡ ኢይከውኖ ፡ ምዝጋና ፡ እመ ፡ ዘበሕጉ ፡ ኢተጋደለ ። መስተጋድ ልት ፡ ተሐራሚት ፡ ወንጽሕት ፡ ማርታ ። ሰማዕት ፡ ወጻድቃን ፡ መስተጋድላን ፡ ለሠናይ ፡ (፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ሠኔ፫ ። ቅዳ) ።

**ጐዳል** ፡ ሎት ፡ (ጐደለ ፡ ይጐድል ፡ ይጕድል ፡ ዐማርኛ) ፡ ሐጸጸ ፡ ነቲግ ፡ ንኡስ ፡ መ ጕደል ፡ ማነስ ፡ ሕጹጽ ፡ መኾን ። ለእመ ፡ ክነት ፡ ምግ ባሪቲከ ፡ ሕጹጸተ ፡ እምጸብአ ፡ ለይጣናት ፡ አሳ ፡ ኅሊናከሰ ፡ ርትዕት ፡ ወኢጐ.ደለት ፡ (ፊልክ ፡ ፺፯ ። ፺፱) ።

**ጐደሎ** ፡ በቁሙ ፡ ጐዱል ፡ ያነስ ፡ የጐደለ ፡ ሕጹጽ ። ዘርቱዐ ፡ ግዕዝ ፡ ወሥርዐቱ ፡ ጐደሎ ፡ በእ ንተ ፡ ልኅላኄ ፡ ኅሊናሁ ፡ (ፊልክ ፡ ፬) ።

**ገ*ደላዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ያነሰው ፡ የጐደለው ። ጐደላውያን ፡ እምውስተ ፡ ትምህርት ፡ ዘበእንተ ፡ አእምሮ ፡ ወጽንዐ ፡ ወሙቀት ፡ ፍቅር ። ጐደላውያን ፡ ንሕነ ፡ እምአበው ፡ (ፊልክ ፡ ፵፰ ። ፪፻፲፯) ።

**ጐድለት** ፤ በቁሙ ፡ መጐደል ፡ አጕዳደል ፤ ጐደሎነት ። በጐድለት ፡ ፈንታ ፡ ጐደሎ ፡ ይላል ፡ አያስኝም ። ሕቡን ፡ ምሉእ ፡ ዘሕልዐ ፡ ጐደሎ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ።

**አጕደለ** ፤ በቁሙ ፡ አጐደለ ፤ አሳነሰ ፤ አስጐደለ ፡ አስቀነሰ ።

**ገዲም** ፤ ሞት ፤ (ገደመ ፡ ይገድም ፡ ይግድም ። ዕብ ፡ ጋዳም ፤ ገዘመ) ፤ መጋደም ፤ መተኛት ። (ጥደ) መገደም ፡ መደበር ፡ መክሰል ፤ ዳሩ ፡ እሳት ፡ ማጕኸሉ ፡ ገንት ፡ ይኾን ፡ ማለት ። መንየን ፡ ተመልክት ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ገዳሚ** ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤ የሚጋደም ፡ ተጋዳሚ ፡ ጋድም ። ገዳሚ ፡ ደባሪ ፤ ገዳም ፡ ሠሪ ።

**ግድም** ፤ (ብ ፡ ግደም ፤ ግድማት) ፤ በቁሙ ፡ አግድሞ ፤ ወርድ ፡ ስፋት ። ወእመኒ ፡ ሖርክሙ ፡ ግድመ ፡ ሕነኒ ፡ ሕሐውር ፡ ግድመ ፡ ምስሌክሙ ። ወግድሙ ፡ ስድስቱ ፡ በእመት ። ሕልብነ ፡ ኑዳ ፡ ወግድም ። ኢይትሐመር ፡ ኑኃ ፡ ወግድማ ፡ ወኢቀማ ። እምግደሚሁ ፡ ለደብተራ ፡ (ዘሌ፳፮ ፡ ፳፩—፳፬ ። ዳን፰ ፡ ፭ ። ቀሌ ። ዘፀ፳፮ ፡ ፲፫) ።

**ግዳሜ** ፤ ጋድም ፤ የመስቀል ፡ ክንፍ ። በትረ ፡ ክርካዕ ፡ ውእቱ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ወበትረ ፡ ሰውዝ ፡ ይትሜሰል ፡ በግዳሜሁ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ኤር፭ ፡ ፲፩) ።

**ገዳም** ፤ (ማት ። ዕብ ፡ ሚቅላጥ) ፤ በቁሙ ፤ ምኔት ፡ ደብር ፡ የመነኮሳት ፡ ሰፈር ፤ ታላቅ ፡ ቤት ፡ ክሲያን ፡ ብደለኛ ፡ ሽሽቶ ፡ የሚጠጋበት ፡ ደውሎ ፡ የሚማጠንበት ፡ ደብረ ፡ ምስካይ ፡ (ኢያ፳ ፡ ፩ – ፱) ። ዱር ፡ ጫካ ፡ ጠማ ፡ በረሓ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፤ ከሀገር ፡ ከመንደር ፡ የራቀ ፡ የአራዊት ፡ ክፍል ። ውስተ ፡ ገዳም ፡ ዐቢይ ። አራዊተ ፡ ገዳም ። ገዳም ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ። ገዳማት ፡ ወሕድባራት ። ቦአ ፡ ውስተ ፡ ውሳጤ ፡ ገዳማተ ፡ ቢድው ፡ (ዮዲ፩ ፡ ፳ ። ዘፍ፲፱ ፡ ፳ ። ማቴ፲፱ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ ጥር፳፱ ። የካ፲፳) ።

**ገዳማዊ** ፤ የገዳም ፡ ሰው ፡ በረኸኛ ፤ ዐዳኝ ፡ መነኮሴ ፡ ባሕታዊ ።

**አግደመ** ፤ አጋደመ ፡ አስተኛ ፤ አግድሞ ፡ ወሰደ ። ያጸንንዎሙ ፡ ለፍጹማን ፡ እምዘክሮ ፡ እግዚ ፡ ኀበ ፡ ኀልዮ ፡ ፍጥረቱ ፡ ከመ ፡ ያግድምዎሙ ፡ እመልዕልት ፡ ኀበ ፡ ርኅሰት ፡ (ፊልክ ፡ ፹፰) ።

**አግደምደመ** ፤ አፋተለ ፤ አጣመረ ። ኢታግደምድም ፡ እገሪከ ፡ ሶበ ፡ ትቀውም ፡ ለጸሎት ። ወታግደመድም ፡ እገሪከ ፡ (አዋል ። አረጋ) ።

**መግድም** ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤ የሚያገድም ፡ አግድሞ ፡ የሚያደ ፡ ጠማማ ፡ በጥግ ፡ አግድሞ ፡ አደግ ። ወሶበ ፡ ተናገረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ረከቦሙ ፡ ዓለማውያነ ፡ መግድማነ ፡ (ፊልክ ፡ ፸፱) ።

**አመግደመ** ፤ አግድሞ ፡ አየ ፤ የተንኰል ፡ የክፋት ፡ የንቀት ፡ የስርቆት ፡ አተያይ ።

**ጐዳና** ፤ ጐድን ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፤ አውራ ፡ መንገድ ፤ ገቦ ፡ ዐፅመ ፡ ገቦ ።

**ጐዲዕ** ፤ ዖት ፤ (ጐድዐ ፡ ይጐድዕ ፡ ይጕዳዕ ። ዕብ ፡ ጋዳዕ) ፤ መጕዳት ፡ መንካት ፡ መጕነጥ ፤ መምታት ፡ መደሰቅ ፤ መሰባበር ፡ ማድቀቅ ። መውጋት ፡ መውገጥ ፡ መለጥለጥ ። ጐድዖ ፡ ገቦሁ ። ጐድዐ ፡ እንግድዓሁ ። ጐድዖ ፡ ነፋስ ፡ ለቤት ። ለሊሃ ፡ ትጐድዕ ፡ ወለሊሃ ፡ ትከልሕ ። እንዘ ፡ ይጐድዖሙ ፡ ለእልኩ ፡ አባግዕ ። ኢይጐድዖ ፡ ዐይነ ፡ እኩይ ። ቅብዐ ፡ ንሒጐ ፡ ንጕዳዕ ፤ ወጐድዎ ፡ በተባርዮ ፡ (ግብ፲፪ ፡ ፯ ። ሉቃ፲፰ ፡ ፲፫ ። ጽ፫ ፡ ፴፰ ። ኢዮ፩ ፡ ፲፱ ። ሚራ፲፫ ፡ ፱ ። ሔኖ፹፭ ፡ ፬ ። ደራሲ ። ድር ፡ መድ) ።

**ጐዳዒ** ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት) ፤ የሚጐዳ ፡ የሚነካ ፡ ጕዳት ፡ የሚያመጣ ።

**ተጐድዐ** ፤ ተጐዳ ፡ ተመታ ፤ ተነካ ፡ ተጐነጠ ፡ ተሰበረ ፤ ተፈተነ ። ተጐድዐ ፡ ብረኪሁ ። መጽአ ፡ ድምፀ ፡ ከመ ፡ ዘጽኑዕ ፡ ነፋስ ፡ ወመሰሎሙ ፡ ከመ ፡ ዘተጐድዐ ፡ ገበዋቲሁ ፡ ለቤት ። ይትጐድዑ ፡ አዕማዲክሙ ። ብእሲ ፡ ዘበአሱ ፡ ተጐድዐ ። ወዘሰ ፡ ኢተጐድዐ ፡ ልቡ ፡ ዘየአምር ፡ (ዳን፭ ፡ ፮ ። ሕዝ፯ ፡ ፮ ። መጽ ፡ ምስ ። ሢራ፳፩ ፡ ፳፱ ። ፴፩ ፡ ፲) ።

**ጕዱዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ድዕት) ፤ የተጐዳ ፡ የተነካ ፡ ንክ ፤ ሰባራ ፡ ከሻዋ ፡ ኰሳሳ ።

**ጕድዐት** ፤ መጐዳት ፡ መጕዳት ፡ አጕዳድ ፡ አነካክ ፤ ጕዳት ፡ ንኪት ፡ ስብራት ።

**ተጓድዐ** ፤ ተጓዳ ፤ ተማታ ፡ ተጋጨ ፡ ተጻፋ ፡ (ተዋጋ ፡ ተሳበረ ፡ ተቀራሸመ ፡ የበሬ) ። እንዘ ፡ ይትጓድዑ ፡ ምስለ ፡ ክንፍ ፡ ክንፈ ። ይደነግፁ ፡ ሠረገላት ፡ ወይትጓድዑ ፡ በፍኖት ፡ (ስንክ ፡ ግን፲፱ ። ናሖ፪ ፡ ፭) ።

**ግድዓ** ፤ እንግድዓ ፤ (ዓት) ፤ ደረት ፡ እንቢያ ፤ ፍርእንቢያ ። እን ፡ ምልአት ፡ ንባብ ፡ ነው ፤ ከእንጕድጕደ ፡ መጥቷል ። ግድዓ ፤ ደረት ፡ በሐዘን ፡ ጊዜ ፡ የሚመታ ፡ የሚደሰቅ ። ድጕዓን ፡ እይ ። እንግድዓሁ ፡ ዘብሩር ። ልብሰ ፡ እንግድዓ ። በጐዲዐ ፡ እንግድዓ ፤ ንጐዳዕ ፡ እንግድዓቲነ ። አ ፡ እምኔከ ፡ ሞት ፡ እስመ ፡ ኬድከ ፡ በሰኰናከ ፡ እንግድዓቲሆሙ ፡ ለካህናት ፡ (ዳን፲ ፡ ፬፱ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፱ ። ኢሳ ፡ ተ፳፯ ። ፊልክ ፡ ፻፲ ። ግንዘ) ። ልብ ፡ ሆድ ፡ ትዕግሥት ፡ አእምሮ ። ሖሪ ፡ በእንግድዓኪ ። ለብእሲ ፡ ጸቢብ ፡ እንግድዓ ፡ በግዐዘ ፡ ይጸልእዎ ፡ ሰብእ ። አጥሪ ፡ ትዕግሥተ ፡ ወርሕበተ ፡ እንግድዓ ። ብእሲ ፡ ድኩመ ፡ ኀሊና ፡ ወጸቢበ ፡ እንግድዓ ፡ አብድ ፡ ውእቱ ፡ (ዘፍ፳ ፡ ፲፱ ። ፈላሰ ፡ ገ፵፯ ። ሃ፯ ። አፈ ፡ ተ፲፱) ።

**ገዲፍ** ፤ ፎት ፤ (ገደፈ ፡ ይገድፍ ፡ ይግድፍ ። ዐረ ፡ ጀደፈ ። ዕብ ፡ ጋዴፍ ፤ ሰደበ ፡

**አረከስ)** ፤ መግደፍ ፡ መጣል ፡ መተው ፤ መርሳት ፤ ማጥፋት ፡ የጣፈ ፡ የተማረ ፤ ሰቢ.ማያም ፡ ይኾናል ፤ ገዳፍ ፡ ዘኢ.ያገድፍ ፡ እንዲሉ ። መወርወር ፡ ማሽቀንጠር ፡ ጥሎ ፡ መኼድ ፡ የጐድፍ ፡ የሸክም ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። **ገደፈት ፡ ለሕፃን ፡ ታሕተ ፡ ዕፀ ። ንግድፎ ፡ ውስተ ፡ ግብ ። ይግድፉ ፡ ውሉዶሙ ፡ ውስተ ፡ ፈለግ ። ግድፉ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። አስተዋፀኡ ፡ ወገደፋ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ንዋየሙ** ፡ (ዘፍ፴፯ ፡ ፳፪ ። ፀ፩ ፡ ፳ ። ኩፋ ፡ ፵፯ ። ዘፀ፱ ፡ ፲ ። ዮናስ ፡ ፩) ።

**ገዳፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት)** ፤ በቁሙ ፤ የሚገድፍ ፡ የሚጥል ፡ መናኒ ። **ገዳፍያኒ ፡ ዓለም** ፡ (ፊልክ ፡ ፫) ።

**አግደፈ** ፤ አስገደፈ ፡ አስጣለ ፡ አስተወ ፡ አስረገፈ ። **አገድፈከ ፡ ቀስተከ ። ያገድፎሙ ፡ ዙያንዊሆሙ** ፡ (ሕዝ፴፱ ፡ ፫ ። ኢሳ፵፭ ፡ ፪) ።

**ተገድፈ** ፤ ተገደፈ ፤ ተጣለ ፡ ወደቀ ፡ ተተወ ፡ ተረሳ ፡ ቀረ ፡ ጠፋ ፡ ታጣ ። **ትትገደፍ ፡ ኦሪት ፡ እምካህን ። ይትገደፍ ፡ አብድንቲሆሙ ። ክመ ፡ አባግዐ ፡ ተገደፍነ ። ተገድፈ ፡ ወአልቦ ፡ ዘተረክበ ። በእንተ ፡ ረኪበ ፡ ዘተገድፈ** ፡ (ሕዝ፯ ፡ ፳፯ ። ኢሳ፴፬ ፡ ፫ ። ኣ፫ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፵፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵) ።

**ግዱፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ድፍት)** ፤ የተገደፈ ፡ የተጣለ ፡ የወደቀ ፡ የተኛ ፡ የተጋደመ ፡ የጠፋ ፡ የታጣ ፡ የረከሰ ፡ የተናቀ ። **ክመ ፡ ፀፍዕ ፡ ግዱፍ ፡ ከማሁ ፡ ሀካይ ፡ በንበ ፡ ሰከበ ። ረከበ ፡ ቢድኖ ፡ ግዱፈ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ግዱፍ ፡ ውስቴ ፡ ዴዴሁ ። ግዱፋነ ፡ ይርከብ ። ኵሉ ፡ ተግባረ ፡ እግዚ ፡ ሠናይ ፡ ወአልቦ ፡ ግዱፍ ፡ ወኢ.ምንትኒ** ፡ (ሚራ፳፪ ፡ ፪ ። ዮዲ፲፬ ፡ ፲፭ ። ሉቃ ፲፮ ፡ ፳ ። ኪዳ ። ፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፬) ።

**ግድፈት** ፤ በቁሙ ፡ መግደፍ ፡ መጣል ፡ መገደፍ ፡ አገዳደፍ ፡ ገደፋ ፡ ርሳታ ፡ ዝንጋታ ፡ ገዳፍነት ። **ግድፈተ ፡ ቃል** ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መጨረሻው) ።

**ጐድፍ ፤ (ፋት)** ፤ በቁሙ ፤ ጥፉጊ ፡ ውዳቂ ፡ ግብል ፡ ተጠርጎ ፡ የሚጣል ። **ክመ ፡ ኵሉ ፡ ይከስትር ፡ ቤቶ ፡ አው ፡ መሬተ ፡ አው ፡ ጐድፈ ፡ ይገር ፡ ውስተ ፡ መቃብሪሁ ። ወከነ ፡ ወግረ ፡ ዐቢየ ፡ ውእቱ ፡ ጐድፍ** ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፯ ። መጋ፲) ።

**ጐደፈ** ፤ በቁሙ ፡ አደፈ ፡ ተኰሰፈሰፈ ። እድፋም ፡ ጐድፋም ፡ ኾነ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጌደር ፤ (ዕብ ፡ ጋዴር)** ፤ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ ካብ ፡ ግንብ ፡ መካበቢያ ፡ (ሕዝ፵፪ ፡ ፯) ።

**ጌዶር ፤ (ጽር ፡ ጌዱር ። ዕብ ፡ ግዱድ)** ፤ ወራሬ ፡ ዘራፊ ፡ ፋኖ ፡ ወያኔ ፡ የሽፍታ ፡ ሰራዊት ፡ የወንበዴ ፡ ጭፍራ ። ገዱድን ፡ እዩ ። **እዴግኖሙኑ ፡ ለእሉ ፡ ጌዶር** ፡ (፩ነገ ፡ ፴ ፡ ፰) ።

**ጊደር ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፡ ያልሸረፈችና ፡ ያልተጠቃች ፡ ዕጕልት ።

**ጎህ ፤—ወገግታ ፤—ገዊሕ ፡ ጎሐ ፤ ጎሕ ።**

**ገህግህ ፤ (ዕብ ፡ ጋሃህ ። ሱር ፡ ግሃእ ። ዐረ ፡ ጀህጀህ)** ፤ አራቀ ፡ አስገለለ ፡ ለየ ፡ ከላ ፡ ከለከለ ። **ኀጢአት ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ ዘይገሀግሃ** ፡ (፪ጼጥ ፡ ፪ ፡ ፲፬) ። ዘሩ ፡ ግሂህ ፡ ነው ፤ ገሀሀን ፡ እዩ ።

**ግሂድ ፤ ዶት ፤ (ግሀደ ፡ አው ፡ ገሀደ ፡ ይግሀድ ፡ ይግሀድ ። ዐረ ፡ ጀሀደ ፤ ጀሀረ)** ፤ (ጥጋ) መጋድ ፡ መገለጥ ፡ መታየት ፡ ግልጥ ፡ ገሃድ ፡ መኾን ፡ መታወቅ ፡ መረዳት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በገሀደ ፡ ፈንታ ፡ ተግሀደ ፡ ይላል ፡ አያስኝም ። **ተግሀደ ፡ ሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ። ደትገሀድ ፡ ተአምሪከ ፡ ለሚሃ ። ለእመ ፡ ጸንዐት ፡ ዛቲ ፡ ወተግህደት ። ዘቲግህዱ ፡ በወዊእ ፡ እምትእዛዛት** ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፰) ።

**ገሃድ ፤ ገሃዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት)** ፤ በቁሙ ፡ የሚጋድ ፡ የሚገለጥ ፤ ተገላጭ ፡ ተገላላጭ ፡ ግልጥ ። **ኵሉ ፡ ዘገሃዶ ፡ ብርሃን ፡ ውእቱ ። ኢ.ከነኑ ፡ ገሃደ ፡ ይእዜ ፡ ክመ ፡ ከነ ፡ ሕማነ ። ወብዙኀ ፡ ይጌሥጾሙ ፡ ክመ ፡ ገሃደ ፡ ኢ.ይረስይዎ** ፡ (ኤፌ፭ ፡ ፲፫ ። ቄር ። ማር፫ ፡ ፲፱) ።

**ግሁድ** ፤ ገልጦ ፡ ተገልጦ ፡ ግልጥ ፡ ኹኖ ፤ በግልጥ ፡ በገሃድ ። **ዘገሃደ ፡ ተነበይኩ ። ገሃደ ፡ ይመጽእ ። ዐርገ ፡ ጽሚተ ፡ ወአኮ ፡ ገሃደ** ፡ (ዕር ፡ ኢሳ፵፰ ፡ ፷ ። መግ ፡ ፵፱ ። ዮሐ፯ ፡ ፲) ።

**ግሁድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ሀድ** ፤ የተጋደ ፡ የተገለጠ ፡ ግልጥ ፡ የታየ ፡ የጐላ ፡ የተረዳ ፡ ጕልሕ ። **ኵሉ ፡ ክሡት ፡ ቅድሜከ ፡ ወግሁድ ። ምግባርየ ፡ ዘዐመፃ ፡ ግሁድ ፡ ቅድሜየ ። ለኵሉ ። ዕዉቅ ፡ ወግሁድ ፡ ክመ ፡ . .) ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ግህደ ፡ ኮነት ፡ ክመ ፡ ወሳዴተ ፡ አምላክ ፡ ይእቲ** ፡ (ሔኖ፶ ፡ ፳ ። ግንዘ ። ቄር ። ውዳ ፡ ማር፭) ።

**ግህደት** ፤ መገለጥ ፡ አገላለጥ ፡ ግልጥነት ፡ ገሃድነት ። **አብአ ፡ በግህደት ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ። አሚሃ ፡ ይቀውም ፡ ጻድቅ ፡ በብዙኅ ፡ ግህደት** ፡ (ግንዘ ። ጥበ፭ ፡ ፩) ።

**ግህድና** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ገሃድነት ፤ መገለጥ ። **ረከብነ ፡ ንሕነሂ ፡ ቦቱ ፡ ግህድና ፡ ፍኖት ፡ ኀበ ፡ እግዚ. ። ብነ ፡ ግህድና ፡ ውስተ ፡ በዊአ ፡ ቅዱሳን** ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ገሀድ ፤ ገሃድ** ፤ በቁሙ ፡ የልደት ፡ የጥምቀት ፡ ዋዜማ ፡ እንዳርብና ፡ ረቡ ፡ የሚጦም ። **በላዕ ፡ እብል ፡ ለጾመ ፡ ዕለተ ፡ ዋሕድ ፤ ዘስሙ ፡ ገሀድ** ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲) ።

**አግሀደ** ፤ አጋደ ፡ ገለጠ ፤ አስገለጠ ፤ አሳየ ፡ አስረዳ ፤ ገልጦ ፡ ነገረ ። **አግህድ ፡ ሎቱ ፡ ፍኖቶ ፡ ዘይመጽእ ። እስመ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አግሀደ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየ ፡ ክር ፡ ርእሶ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኢያግሀደ ፡ ርእሶ ፡ ለመኑሂ ፡ መጠነ ፡ ሠላሳ ፡ ዓም ። ጳውሎስ ፡ ያግሀድ ፡ ለነ ፡ ምስጢረ ። ወይእዜሰ ፡ አግሀደ ፡ በብሂሎቱ ፡ ስመ ፡ ክርስቶስ ፡ አግሀዱ** ፡ (ሔኖ፲ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ጥር፲፩ ። ቄር ፡ ጸላ ። አፈ ፡ ድ፫ ። ስንክ ፡ መስ፳፰) ።

**አግሃዲ ፤ መግሀዲ ፡ ህድ ፤** የሚያግድ ፡ የማጋልጥ ፡ ገላጭ ፡ አስረጅ ።

**ምግሃድ ፤** መግለጫ ፡ መገለጫ ፡ ማስረጃ ፡ (በቃ ፡ መግሪያ ፡ ቃል) ።

**ግሂህ ፤ ሆት ፤(ገሀሀ ፡ ይግህሀ ፡ ይግህህ) ፤** መብራት ፡ ማብራት ፡ መጽደል ፤ መምሳት ፡ መተክከል ፡ ምሉእ ፡ ፍጹም ፡ መሆን ፤ መድመቅ ፤ ገሃ ፡ ብሕክ ፡ በረቅ ፡ መምሰል ፤ የወርኅ ።

**ገሃህ ፤ ገሀህ ፤** የጨረቃ ፡ ምላት ፡ ብርሃኗ ፡ በተወለደች ፡ ወይም ፡ በበቀለች ፡ ባ፲፭ኛ ፡ ቀን ፡ መልቶ ፡ ተክክሎ ፡ ሀውድማ ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ። **ከመ ፡ ወርኅ ፡ ምልእት ፡ በዕለተ ፡ ገሃህ ። ወርኅ ፡ ተፈጥረ ፡ ምሉአ ፡ ብርሃን ፡ ከመ ፡ ዕለተ ፡ ገሃሁ ። ሥኑ ፡ ለወርኅ ፡ ገሀህ ። በቀዳሚ ፡ ወርኅ ፡ አመ ፡ ገሃሁ ። ወርኅ ፡ ዘአሚ ፡ ገህህ ፡**(ሚሬ፶ ፡ ፺ ። አቡሻ ፡ ፲፫ ። አርጋ ፡ ፺ ። ሕዝ፴፪ ፡ ፲፯ ። ደራሲ) ።

**ጕሂን ፤ ኖት ፤(ጐህነ ፡ አው ፡ ገሀነ ፡ ይጕህን ፡ ይጕህን) ፤** መሰወር ፡ መደበቅ ። መሬሽ ፡ ማዜም ፡ ማጕረምረም ። ገንሐንና ፡ ገሃየን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ናቸው ። መጓን ፡ ማጓን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ (በማርኛ) ።

**ጐሃኒ ፤(ኒት ፡ ንያን ፡ ያት ፤ ሀንት) ፤** የሚሰውር ፡ ደባቂ ፤ ሬጂሽ ። የሚጕን ፤ የሚያጕን ።

**ጕህን ፤ ጕሃን ፤** ሰዋሬ ፡ ሰውር ፡ ድብቅ ፡ ስውሩ ፡ ድበቃ ፤ ስርቆሽ ። **ወሀብዎ ፡ በዓባተ ፡ በጕሃን ፡ ወመሥዋዕተ ፡ በምስጢር ፡**(ጥበ፲፱ ፡ ፲፰) ።

**ጕህን ፤ (ናት) ፤** ኅቡእ ፡ ነገር ፤ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፤ በትምርትና ፡ በብቃት ፡ የሚገኝ ። **ጳውሎስ ፡ ዘበዙሉ ፡ ጠቢብ ፡ መጋቤ ፡ ጕህናቱ ፡ ለክርስቶስ ፡**(ቁር ፡ ጳላ) ። ኅቡኣቲሁ ፡ ምስጢራቲሁ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ጕህንት ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ።

**ጕህና ፤** በቁመ ፡ ዐቢይ ፡ ዜማ ፡ ስልት ፡ ያለው ፡ ሬጉሽት ፡ ጕማ ፡ ተመማ ፤ ወፍራም ፡ ድምጥ ። **ዝማሬ ፡ ዘበልሳን ፡ ወጣዕመ ፡ ቃል ፡ ዘበጕህና ። ወሕንጻቲሃ ፡ ይእቲ ፡ ዘታቀርበነ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ፡ በአእዝቶ ፡ ማሕሌቱ ፡ ውስቴታ ፡ በዘይደምፅ ፡ ጕህና ፡ ኀቤነ ፡**(አረጋ ፡ ድ፺ ። የሴፍ) ።

**ተጓህነ ፤ ተጓህነወ ፤** ተጓጓነ ፡ ተሬጂሬጂሽ ፡ ተዚያዚያመ ፡ ተኖናረ ።

**አስተጓህነወ ፤** አጓጓነ ፡ አሬጂሬጂሽ ፡ አዚያዚያመ ። **ጸዋዕክዎሙ ፡ ለነቢያት ፡ ከመ ፡ ያስተጓህንዉኒ ፡ በቃለ ፡ ትንቢቶሙ ፡**(መጽ ፡ ምስ) ።

**ገሀነም ፤ ገሃነም ፤(ጽር ፡ ጌሄና ። ዕብ ፡ ጌይሂኖም ። ዐረ ፡ ጀሀነም) ፤** የቦታ ፡ ስም ፤ ከደብረ ፡ ጽዮን ፡ የተያያዘ ፡ የተራራው ፡ እግር ፤ የቄድሮንና ፡ የማየን ፡ ወንዝ ፡ ማየ ፡ ስሊሖም ፡ የሚወርድበት ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ፡ በስተደቡብ ፡ ያለው ፡ ጕድጓዳ ፡ ቈላ ፡ ሸለቆ ፡ ወንዛወንዝ ፡ መቀራቅርት ፡ እስራኤል ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለሞሎኽ ፡ ይሠውበትና ፡ ይጠብሱበት ፡ ያቃጥሉበት ፡ የነበረ ፡ የከተማው ፡ ጕስ ፡ ውስጥ ፡ ስውስጥ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ የሚጕርፍበት ፡ የጥንብና ፡ የጕድፍ ፡ መጣያ ፡ ርኩስ ፡ ቦታ ፤ የውነተኛው ፡ ገሃነም ፡ ምሳሌ ። ሄኖም ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ያቀናው ፡ የወረሰው ፡ የሄኖም ፡ ወንዝ ፤ ወይም ፡ ከሄኖም ፡ ልጆች ፡ ላንዱ ፡ የደረሰ ፡ ያንደኛው ፡ ልጁ ፡ ክፍል ፡ ማለት ፡ ነው ። ጣፈጥን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ኢያ፲፭ ፡ ፰ ። ኤር፯ ፡ ፴፩ ። ፴፪ ። ፱ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ። ፳፫ ፡ ፲) ። በቁሙ ፡ ሲኦል ፡ መቃብር ፡ የእሳት ፡ ጕድጓድ ፡ ዐዘቅት ፤ መከኑ ፡ ኃጥኣን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ የሚኖሩበት ፡ የሥቃይ ፡ ቦታ ፤ እሳቱና ፡ ትሉ ፡ የማይጠፋ ፡ የማያንቀላፋ ፡ (ምሳ፳ ፡ ፲፱ ። ፲፭ ፡ ፲፩ ። መክ፱ ፡ ፲) ። **እቶነ ፡ ገሃነም ። እሳተ ፡ ገሃነም ። ሥቃያት ፡ ዘገሃነም ። ወሞትስ ፡ ዳግም ፡ ገሃነም ፡ ዘእሳት ፡**(ሱቱ ፡ ዕዝ፯ ፡ ፴ ። ማቴ፭ ፡ ፳፪ ። ዕር ፡ ኢሳ፩ ፡ ፫ ። ራእ፳ ፡ ፲፬ ። ማር፱ ፡ ፵፫ ። ኢሳ፳፯ ፡ ፳፱) ።

**ገሃነማዊ ፤** የገሃነም ፡ ሥቃይ ፡ እሳት ፡ ጭፍራ ፡ ሰራዊት ። **ላህብ ፡ ገሃነማዊ ፡**(ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**ጋህረተ ፤—ተጋ ፤—ሀጌር ፡ ሀገረ ፤ ሀግረተ ።**

**ኀግዎ ፤ ዎት ፤(ኅገወ ፡ ይኅጉ ፡ ይኅጉ ፤ ገዊግ) ፤** መሳት ፡ መሳሳት ፤ ከሕግ ፡ ከሥርዐት ፡ ከመንገድ ፡ መውጣት ፤ ከጽድቅ ፡ መራቅ ። ጊገየንና ፡ ሳኰየን ፡ ጠዐወን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

—፤ መንጋጋት ፡ መርባት ፡ መብዛት ፤ መንጋ ፡ መኾን ፤ የሰው ፡ የከብት ። መንጋ ፡ ማለት ፡ ቅሉ ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**አንኀገወ ፤** አባከነ ፡ አባዘነ ፤ አዞረ ፡ አንከረተተ ፤ አናወዘ ፡ አቅበዘበዘ ፤ የዐይን ፡ የእግር ፡ የኅሊና ። **አነ ፡ አንኅግዋ ። አንኅግወከ ፡ ምስለ ፡ ሰራዊትከ ። እንዘ ፡ ታሐምሙ ፡ ልበክሙ ፡ ወታንኅግዉ ። አንኅግዎሙ ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡**(ሆሴ፱ ፡ ፲፯ ። ሕዝ፴፰ ፡ ፬ ። ኤር፭ ፡ ፲፰ ። ፳፯ ፡ ፺) ። ባከኑ ፡ ባዘኑ ፡ ዞረ ፡ ተንከራተተ ። **ያንኅግዉ ፡ በካልእ ፡ ሥርዐት ። አንኅግዎ ፡ ዘስሒት ። የዐቅቡ ፡ አልባቢሆሙ ፡ እምአንኅግዎት ፡ ውስተ ፡ ኅሊናት ፡ እኪት ። ያንኅጉ ፡ አልባቢሆሙ ፡ እምሀገር ፡ ኀበ ፡ ሀገር ፡**(ጥበ፲፬ ፡ ፳፫ ። ሃይ ፡ አበ ። ፈልክ ፡ ፵፭ ። ፲፱) ።

**አንኀጋዊ ፤ መንኅግው ፤(ውት ፡ ጉት ፤ ዋን ፡ ዋት) ፤** የሚያባክን ፡ የሚባክን ፡ በካና ፡ በክንካና ፡ ዘዋሪ ፡ ቀላዋጭ ። **ፍልጠት ፡ ማእከለ ፡ ፈላሲ ፡ ወመንኅግው ፤ እስመ ፡ ፈላሲ ፡ የዐውድ ፡ ውስተ ፡ ምኔታት ፡ ከመ ፡ ይርባሕ ፡ ወያርብሕ ፡ ግብራተ ፡ መንፈሳውያተ ፤ ወመንኅግውሰኬ ፡ ይረብሕ ፡ ግብራተ ፡ ሥጋውያተ ፡**(ፈልክ ፡ ፳፩) ።

**እንጕግው ፤** የባከነ ፡ ብኩን ፤ ዝርው ፡ እንቡዝ ፡ ቅብዝብዝ ። **እስመ ፡ እምርእይ ፡ ወሰሚዐ ፡ ነገር ፡ ብዙኅ ፡ ትከውን ፡ እንጕግወ ፡ ኅሊና ። ኅሊናቲ**

ሆሙ ፡ **እንጕግውት ፡ ይኄሪ ፡ ዘይረክብዎ** ፡ (ፊልክ ፡ ፶፰ ፡፡ ፶፩) ፡፡

**እንጕጋዌ** ፤ መባከን ፡ ብክንት ፤ በክንንት ፡ የ ልቡና ፡ ሁከት ፡፡ **እንጕጋዌ ፡ በእንተ ፡ ቃል ፡ ንእስት** ፡ (ፊልክ ፡ ፶፫) ፡፡

**ነኀጋው** ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፡ ብክንት ፡ ሁከት ፡ ቅብ ዝብዝታ ፡ ቍጣ ፡ ብስጭት ፡ የቅለት ፡ ሥራ ፡፡ **መፍትው ፡ ለነ ፡ ንሑር ፡ በህድአት ፡ ሰሲለነ ፡ እምነኀጋው ፡ ከመ ፡ ኢንደቅ ፡፡ ዘእንበለ ፡ ፍርሀት ፡ ወነኀጋው** ፡ (አፈ ፡ ተ፴፱) ፡፡ **እበድ ፡ ውእቱ ፡ ነኀጋው ፡ አመ ፡ መዐት ፤ ወ ተቀይሞ ፡ እምይኄሪ ፡ ዐርቅ ፡፡ ኄሩት ፡ ለልቡና ፡ ት ዕግሥት ፡ ወሕሠሙሂ ፡ ነኀጋው ፡ ወጕጕአ** ፡ (ፈላስ) ፡፡

**ኅግ** ፤ ስሬዊት ፡ መንጋ ፡ በገዞቶ ፡ የሚኼድ ፡ የ ሚንጋጋ ፡፡

**ማኅግ** ፤ ኅጋዊ ፡ የኅግ ፡ ወገን ፡፡ **ወያስተጋብ ኦሙ ፡ ለኅግ ፡ ወለማኅግ** ፡ (ራእ ፡ ፳) ፡፡

**ኅግ ፡ ማኅግ** ፤ ኅግ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፡ ማኅጋውያን ፡ የወረሱት ፡ (ቃውቃዝ) ፡፡ ማኅግ ፡ ስመ ፡ ንገድ ፡ የያፌት ፡ ልጅ ፡ የመስኮቦች ፡ አባት ፡ (ሕዝ፴፰ ፡ ፪ ፡፡ ራእ ፡ ፳ ፡፡ ዘፍ፲ ፡ ፪) ፡፡ ኹለተኛም ፡ ኅግ ፡ ብዙ ፡ ማኅግ ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ወይም ፡ ኅግ ፡ ጀርመን ፡ ማኅግ ፡ መስኮብ ፡ ይባላል ፤ ም ስጢሩ ፡ ብዛት ፡ ነው ፡፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ከአራት ፡ ዘዳግም ፡ (፴፪ ፡ ፰ ፡ ፱) ፡ አይይዘው ፡ ፸ ፡ ቋንቋ ፡ ፸ ፡ ነገድ ፡ ብለው ፡ በፊደል ፡ ቍጥር ፡ ይፈቱታል ፤ አፈታታቸውም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡፡ ገ ፡ ሳብዕ ፡ መኾኑ ፡ ወን ፡ ጕርደ ፡ ነውና ፡ ሲጥፉ ፡ ገወግ ፡ ማገወግ ፡ ሲያነቡ ፡ ግን ፡ እንደኛ ፡ ኅግ ፡ ማኅግ ፡ ይሉታል ፡፡ ገወግ ፡ ፲፪ ፡ ማገወግ ፡ ፶፪ ፡ ፸፱ ፡፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ገወግ ፡ ማገወግ ፡ ፯ ፡ ብለው ፡ ነጠላ ፡ ቍጥር ፡ ይ ቈጥሩና ፡ ከ፷፱ ፡ ጋራ ፡ ሲግጥሙት ፡ ፸፮ ፡ ይኾናል ፡፡ ፸ው ፡ ወይም ፡ ፸፩ዱ ፡ አሕዛብ ፤ ፸፪ኛው ፡ እስራኤል ፡ ይላሉ ፤ ይህ ፡ ደግሞ ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፳፰) ፡፡ **ብዝኆ ፡ ወተባዝኆ ፡ ወ ምልእዋ ፡ ለምድር** ፡ ያለውን ፡ ያዳምን ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ፡፡

**መግዌ ፤ (ዕብ ፡ ማዊያ ፤ ግላ ፡ በድን ፡ ሬሳ)** ፤ ጥሬገዝ ፡ የመጽሐፍ ፡ ነደ ፡ ገና ፡ ያልተሰፋ ፡ ያል ተጠረዘ ፡፡ **በውኑ ፡ መግዌ** ፡ (አዋል) ፡፡

**ኅድ ፤ (የግዱድ ፡ ክፈል)** ፤ ኅይል ፡ ስሬ ዊት ፡፡ **ይመጽእ ፡ በኅድ** ፡ (መቃ) ፡ በንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡

**ኅሀ ፤—ነጋ ፡ በራ ፤—ገዊሕ ፡ ኅሐ ፡፡**

**ገውዛ ፤ (ዐረ ፡ እልጀውዛ)** ፤ ኮከብ ፡ ስመ ፡ ኮከብ ፡ ከ፲፪ ፡ መናግዝል ፡ አንዱ ፡፡ ሰጥፍ ፡ ጥንድ ፡ መንታ ፡ ኹለት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ መልኩ ፡ በሥዕል ፡ ሲያዩት ፡ ባ ልና ፡ ሚስት ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ይመስላል ፡፡ ኮከብነቱም ፡ የግንቦት ፡ ነው ፤ ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ ፴፩ ፡ ዕለት ፡ ፴ ፡ ኬክ ሮስ ፡ ይመግባል ፡ (አቡሻ ፡ ፱) ፡፡

**ገውዝ ፤ (ዕብ ፡ ኤጎዝ ፡፡ ሱር ፡ ጋውዛ ፡፡ ዐረ ፡ ጀውዝ)** ፤ በቂሙ ፡ የታወቀ ፡ የተክል ፡ ዛፍ ፡ ስም ፤ የፍሬው ፡ ዐጥንት ፡ ደረቅ ፡ ጠንካራ ፤ ውስጡ ፡ የ ሚበላ ፡ መንታንት ፡ ያለው ፡ ዘይት ፡ የሚኾን ፡ ሌላውም ፡ የገውዝ ፡ ዐይነት ፡ ኹሉ ፡፡ **ገውዝ ፡ ወለውዝ ፡፡ እመ ፡ ተከልከ ፡ ገውዘ ፡ ይበቍልኑ ፡ ወይን** ፡ (ሆሴ፬ ፡ ፲፫ ፡፡ መቃ ፡ ገ፰) ፡፡

**ገዊሕ ፤ ሐት ፤ (ኅሐ ፡ ይገውሕ ፡ ይጕሕ ፡፡ ዕብ ፡ ጊያሕ)** ፡፡ መኅሕ ፡ መውገግ ፡ መፍገግ ፡ ወገግ ፡ ፈገግ ፡ ማለት ፡ የንጋት ፡ ምልክት ፡ ማሳየት ፤ ሐመድ ፡ ያ ህያ ፡ ሆድ ፡ መምሰል ፤ የሰማይ ፡፡ **ሶበ ፡ ይገውሕ ፡፡ እ ንዘ ፡ ይገውሕ ፡ ጽባሕ ፡፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ፡ ዘይሠርቅ ፡ ሶበ ፡ ይገውሕ ፡፡ ወይገውሕ ፡ ሶቤሃ ፡ ብርሃንከ** ፡ (ኢ.ያ፷ ፡ ፲፰ ፡፡ ፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳፪ ፡፡ ኢሳ፶፰ ፡ ፶፪ ፡፡ ሃ፳ ፡ ፳) ፡፡

**ኅሕ** ፤ ወገግታ ፡ ውጋጋን ፡ ፈገገን ፡ የንጋት ፡ ብ ርሃን ፡ ከጽባሕ ፡ በፊት ፡ የሚታይ ፡ ያጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ ዘ መን ፡፡ ከንግሀ ፡ ጽባሕ ፡ እንዲቀድም ፡ ከጽባሕ ፡ ደግሞ ፡ ኅሕ ፡ ይቀድማል ፡ ፊርሶ ፡ እስኪታይ ፡ ኅሕ ፡ ይባላል ፡ ከታየ ፡ በኋላ ፡ ፀሓይ ፡ እስክቶጣ ፡ ጽባሕ ፡ ይባላል ፡ ነ ግሀ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡፡ የሦስቱ ፡ ኹሉ ፡ ዘራቸውና ፡ አንቀጻቸው ፡ የተለየ ፡ ነው ፡፡ **ሶበ ፡ ዐርገ ፡ ኅሕ ፡፡ እም ጊዜ ፡ የዐርግ ፡ ኅሕ ፡፡ ከመ ፡ ኅሕ ፡ ይልው ፡ ለወሊደ ፡ ፀሓይ ፡፡ ርእየ ፡ ኅሐ ፡ ወኢርእየ ፡ ጽባሐ** ፡ (መሳ፲፱ ፡ ፳፭ ፡፡ ኅሐ፱ ፡ ፳፯ ፡፡ እርጋ ፡ ፪ ፡፡ ፱) ፡፡

**ተጋውሐ** ፤ ተገለጠ ፡ ተጋለጠ ፤ በራ ፡ አበራ ፡ የብርሃን ፡፡ **እምቅድመ ፡ ይትጋውሑ ፡ ብርሃናት ፡፡ ይሬእ ፡ ይመናተ ፡ ብርሃን ፡ እንዘ ፡ ይትጋውሑ ፡፡ ጸ ዳለ ፡ መብርቅት ፡ እንዘ ፡ ይትጋዋሕ** ፡ (ቅዳ ፡ አፈ ፡፡ አ ረጋ ፡ መልዕ፪ ፡፡ መጽ ፡ ምስ) ፡፡ ሸሸ ፡ ጠፋ ፤ ራቀ ፡ ወ ገደ ፡ ተሰደደ ፤ የጽልመት ፡፡ **ዘይቀድም ፡ ውሂበ ፡ ምጽ ዋት ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በሕይወቱ ፡ ይትጋዋሕ ፡ ሎቱ ፡ ጽ ልመተ ፡ ኀጣውኢሁ ፡ በብርሃነ ፡ ማኅቶት ፡ ዘውሂበ ፡ ምጽዋት** ፡ (መጽ ፡ ምስ) ፡፡

**ገዊል ፤ ሎት ፤ (ገወለ ፡ ይገውል ፡ ይ ጕል ፡፡ ዐረ ፡ ጃል ፡ ጋል)** ፡፡ ማጠር ፡ መቅጠር ፡ ዘ ለሳ ፡ መጣል ፡ መኰብ ፡ መከበብ ፡ ዙሪያውን ፡ መዝጋት ፤ የበረት ፡ ያታክልት ፤ ገዘዘንና ፡ ጸቈንን ፡ ተመልከት ፡፡

**ኅል ፤ (ብ ፡ አግዋል ፡ ላት)** ፤ በረት ፡ የከብ ቶች ፡ ማደሪያ ፡ መታጐሪያ ፡፡ **ወአልሕምትኒ ፡ ኢይት ረከቡ ፡ በውስተ ፡ ኅል ፡፡ አግዋላት ፡ ለእንስሳሁ** ፡ (ዕ ንባ ፡ ፲፯ ፡፡ ፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፳፰) ፡፡

**ኅል ፤ (ዐረ ፡ ማዝወድ ፡፡ ዕብ ፡ ኤቡስ)** ፤ ግርግም ፡ በዚያው ፡ በበረቱ ፡ ውስጥ ፡ ዙሪያውን ፡ ወ ይም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ገንዳ ፡ ኹኖ ፡ የሚሠራ ፡ የእንስሳት ፡ ማእድ ፡ ገለባ ፡ ደረቆ ፡ የሚቀመጡበት ፡፡ **አስ ከበቶ ፡ እሙ ፡ ውስተ ፡ ኅለ ፡ እብን ፡፡ በኅለ ፡ እንስሳ ፡ ተወድየ** ፡ (ዲጓ ፡፡ ቅዳ ፡ ዲዮ) ፡፡ በግርግም ፡ ውስጥ ፡ ማ ለት ፡ ነው ፡፡

**ኅልኅል ፤ (ዕብ ፡ ጊልጋል)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ (ዘዳ፲፩ ፡ ፴) ፡፡

**ጐልጐል ፤(ዕብ ፡ ጉልጎሌት)፤** የራስ ፡ ቅል ፡ የራስ ፡ ሀጥንት ፡ መላው ፡ ከንገት ፡ በላይ ፡ ያለው ። ና ላን ፡ እንጎል ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ጐልጐታ ፤(ዕብ ፡ ጎልጎልታ)፤** መካን ፡ ር እስ ፡ መካን ፡ ድማኅ ። ይኸውም ፡ የአዳም ፡ ራስ ፡ ቅል ፡ የተቀበረበት ፡ ዳግማይ ፡ አዳም ፡ የተሰቀለበት ፡ ቀራንዮ ፡ ናት ፡ (ዮሐ፲፱ ፡ ፲፯) ።

**ጐን ፤(ዕብራ)፤** መልክ ፡ ሕብር ፡ ዐይነት ፤ አን ጻር ፡ አርአያ ፡ አምሳል ። በቁሙ ፡ ጐን ፤ ገቦ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ገውሣን ፤(ዐረ ፡ ገውሽን)፤** የሰልፍ ፡ ል ብስ ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፡ ድርዐ ፡ ጥሩር ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ወከነ ፡ ላዕሌሁ ፡ ገውሣን ፡ ዘወርቅ ፡ ዘንኩር ፡ ግበሪሁ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ጐፍ ፤(ትግ ። ዕብ ፡ ጉፍ)፤** ህላዌ ፡ ጠባይዕ ፡ ገላ ፡ ግዘፍ ፤ ሥጋ ፡ ሬሳ ፡ የሚታይና ፡ የሚዳሰስ ፡ ማና ቸውም ፡ ግዙፍ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ። ገፈፈ ፡ ጐፈፈ ፡ ጕፋያ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ገዋር ፤ሮት ፤(ጎረ ፡ ይገውር ፡ ይጉር ። ዕብ ፡ ጋር)፤** መቅረብ ፡ መጠጋት ፤ ቅርብ ፡ አጠገብ ፡ ጥጎኛ ፡ መኾን ፤ በቤት ፡ በቦታ ። ጉር ፡ ጉሬ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ጎር ፤(ዐረ ፡ ጃር ። ዕብ ፡ ሽኬን)፤** ጎሮ ፡ የ ቤት ፡ ኋላ ። በቁሙ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፤ ቤቱ ፡ የቤት ፡ ቅርብ ፡ ጐን ፡ ሕቡን ፡ አጠገብ ፡ የኾነ ፡ የርስት ፡ የመሬት ፡ የቦታ ፡ አዋሳኝ ፡ ደንበረተኛ ፤ በዙሪያ ፡ ላለ ፡ ለቅርብ ፡ ኹሉ ፡ ይ ነገራል ። ካልእ ፡ ዘጎኑ ። ወቤቱ ፡ ጎረ ፡ ምሥራብ ። ብንበ ፡ ጎርየ ። ጎር ፡ እኩይ ፡ እለ ፡ ይገስሱ ፡ ርስትየ ። ወቦ ፡ ዐጸደ ፡ ሐምል ፡ ጎረ ፡ ቤቱ ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፬ ። ግብ ፲፯ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፴ ። ኤር፲፪ ፡ ፲፬ ። ዳንኤ ፡ ፱) ።

**አግዋር ፤(ራት)፤** ጎረ ፡ ቤቶች ፤ ቅርቦች ፡ አጠ ገቦች ። አክብር ፡ አግዋሪከ ፡ ወአኀዊከ ። ግዕዙ ፡ እም አግዋሪሁ ፡ ለእግዚ ፡ ወመላእክቲሁ ፡ ኀበ ፡ አግዋሪ ሆሙ ፡ ለአጋንንት ። እስመ ፡ ግዕዝነ ፡ እምአግዋሪሁ ፡ ለኀጢት ፡ ወገባእነ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ርግምት ፡ (ፊ ላስ ፡ ገ፳፪ ። ቀሌ ፡ ገ፲፯ ። ፳፫) ።

**ተጋወረ ፤** ተጎራበተ ፤ ተቃረበ ፡ ተቀራረበ ። ኢ ይትጋወርዎን ፡ ለአንስት ። ጳልአ ፡ ተጋውሮ ፡ እንሁ ። ወአርሐቅ ፡ እምተጋውሮ ፡ መላእክት ። በሓውርት ፡ እለ ፡ ይትጋወሩ ፡ ምስለ ፡ ክቲታ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲ ፡ ፳ ። ዮሴፍ ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፱ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ጉር ፤ጎር ፤(ዕብራ)፤** ያንበሳ ፡ ማለገል ፡ የ ኾብ ፡ የተኵላ ፡ የውሻ ፡ ቡኾላ ፡ የናቱን ፡ ጡት ፡ እጥብቆ ፡ የሚመጥ ፡ የሚመጠምጥ ።

**ጎርየመ ፤(ይጎረይም ፡ ይጎሪም)፤** ዐገመ ፡ ዐከመ ፡ ጠባ ፡ ሳበ ፡ መጠመጠ ፤ ደምን ፡ እንደ ፡ ወተት ፡ ለማውጣት ። ሐገመን ፡ እይ ።

**ጎሬም ፤(ብ ፡ ጎራይም)፤** ዐጋሚ ፡ ሐኪም ፡ ባለዋገምት ። ማገሚያ ፡ ዋገምት ፡ የቀንድ ፡ የብርጭቆ ።

**ጕዛ ፤(ዕብ ፡ ጋዝ ፤ ጋስ)፤** ነጣቂ ፡ ወፍ ፡ አ ሞራ ፡ ጭላት ፡ የጭላት ፡ ዐይነት ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፲፮ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፲፯) ። በንስር ፡ ፈንታ ፡ ጕዛ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ከመ ፡ ክንፈ ፡ ጕዛ ፡ (ዘፀ፲፱ ፡ ፬) ።

**ጋዛ ፤ጊዛን ፤(ጽር ፡ ጋዛ ፡ ጋዚስ ። ዕብ ፡ ኦጻር ። ዐረ ፡ ኀዛኢን)፤** የቃ ፡ ቤት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ኰተራ ፡ የብዕል ፡ የገንዘብ ፡ መክተቻ ፡ ማድለቢያ ፡ መሰ ብሰቢያ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ። ቤተ ፡ ዘጋዛ ። እምቤተ ፡ መንግሥትየ ፡ ዘጋዛ ። ለዙሉ ፡ ጋዛ ። ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ጊ ዛን ፡ (ዕዝ፭ ፡ ፲፯ ። ፯ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ። ኢሳ፴፱ ፡ ፪) ።

**ጋዛ ፤(ጽር ፡ ጋዛ ። ዕብ ፡ ዐዛ)፤** ስመ ፡ ሀገር ፡ ያይሁዳ ፡ ክፍል ፡ ከምስቱ ፡ አህጉረ ፡ ኢሎፍሊ ፡ አንዲቱ ፡ የፍልስጥኤም ፡ ደቡብ ፤ እንደ ፡ ዘጌ ፡ እንደ ፡ ቈራጣ ፡ በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ያለች ፡ (ኢያ፲፭ ፡ ፵፯ ። ግብ፰ ፡ ፳፮) ።

**ግዚእ ፤እት ፤(ገዝአ ፡ ይገዝእ ፡ ይግዛእ ። ዐረ ፡ ጀዘአ ፤ ሰጠ ፡ ዐደለ)፤** መግዛት ፡ መዋጀት ፤ መ ጌትየት ፤ ጌታ ፡ መኾን ፤ በገንዘብ ፡ በዜጋ ፡ መሠልጠን ። መቍረስ ፡ መክፈል ፤ መስጠት ፡ ማደል ፡ ማሳለፍ ፡ ማገ ልገል ፤ በጌትነት ፡ ወይም ፡ ባሽከርነት ። ማብላት ፡ መቀ ለብ ፡ መከባከብ ፡ ለማሳደግና ፡ ለማሥባት ፤ የሕፃን ፡ የከ ብት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በገዝአ ፡ ፈንታ ፡ አመግዝአ ፡ ይ ላል ። ይእቲ ፡ አሚረ ፡ ያመገዝእ ፡ ሰብእ ፡ ዕጐልተ ፡ ወክልኤተ ፡ አባግዐ ፡ (ኢሳ፯ ፡ ፳፩) ። ግዕዙን ፡ እይ ፡ የ ዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ግዛእ ፤ግዛኢ ፤(ኢት ፡ እያን ፡ ያት ፤እት)፤** የሚገዛ ፡ ገዥ ፡ ጌታ ፤ ሹም ፡ ባለቤት ። የሚሰጥ ፡ የሚናኝ ፡ ቀጅ ፡ አሳዳጊ ፡ ሰዳይ ፤ የድግስ ፡ አገልጋይ ። ደቂቀ ፡ ግዛ እየ ። በወይኑ ፡ ማሕሌት ፡ እንተ ፡ ይቀድሖ ፡ ግዛኢ ። ደቀ ፡ ጽርሕ ፡ ወግዛእት ። ቦእተ ፡ ይእቲ ፡ ወክልኤ ፡ ግዛእቲሃ ። ወግዛእትሰ ፡ እለ ፡ ቀድሕዎ ፡ (ኢዮ፲፱ ፡ ፲፮ ። ስንክ ፡ ታኅሣ፱ ። ኢሳ፴፱ ፡ ፯ ። ዳንኤ ፡ ፴፮ ። ዮሐ፪ ፡ ፱) ።

**መግዝእ ፤(እት ፡ ኣን ፡ ኣት)፤** ገዢ ፡ ከ ማሁ ፡ ገዥ ፡ ዐዳይ ፡ ቀላቢ ፤ ሐፃኒ ፡ መጋቢ ፡ ሞግዚት ።

**መግዝእ ፤እት ፤(ብ ፡ መጋግዝእ ፡ እት ፤ መጋግዝእት ፡ ታት)፤** ፍሪዳ ፤ ሰንጋ ፡ ድልብ ፡ ቅ ልብ ፤ ኩርማ ፡ ግች ፡ ሙክት ፤ የሥጋ ፡ ከብት ። አም ጽኡ ፡ መግዝአ ፡ ላሕም ፡ ወጥብሑ ። አልሕምት ፡ መጋዝእ ፡ ወመጋዝእ ፡ ደዋርህ ። ጠባሕኩ ፡ መጋዝ እትየ ፡ (ሉቃ፲፭ ፡ ፳፫ ። ፫ነገ ፡ ፬ ፡ ፳፫ ። ማቴ፳፪ ፡ ፬) ።

**አግዝአ ፤** አስገዛ ፡ አጌተየ ፤ ጌታ ፡ አደረገ ፡ ሾመ ፡ አሠለጠነ ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ።

**እግዚእ ፤(እን ፡ እት ፡ ግእት)፤** ቅጽልና ፡ ጥሬ ። የማክበርና ፡ የክብር ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ጌታ ፡ ገዥ ፡ አዛዥ ፡ ሹም ፡ ባለቤት ፡ መምህር ፡ አያት ፤ ታላቅ ፡ ወን ድም ። ጎይታይ ፡ እንዲል ፡ (ትግሬ) ። ገብር ፡ ከመ ፡ እ ግዚእ ። መኑ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእነ ። እግዚእ ፡ አጋዕዝት ፡

(ኢሳ፳፱ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፻፳ ። ፻፴፩) ። እግዚእ ፡ ብሎ ፡ በአልፍ ፡ አጋእዝት ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ። አጋ ስዝት ፡ የአግዓዚ ፡ ብዥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የእግዚእ ፡ ብዥ ፡ እንዳይመስልኽ ፡ ግዕዛንና ፡ አግዐዘን ፡ ተመልከት ። የእ ግዚእስ ፡ ብዥ ፡ ቢኾን ፡ አጋዝእት ፡ ይልልኽ ፡ ነበር ።

**እግዝእት**፤(ታት)፤ እመቤት ፡ ወይዘሮ ፡ ሴት ፡ ኢያት ፡ ታላቅ ፡ እኅት ። እመይቴ ፡ እንዲል ፡ (ትግሬ) ። **አዘዘ ፤ ኢይስምዕዋ ፤ ለረቢብ ፤ እግዝእተ ። አመት ፤ ለእመ ፤ አውፅአት ፤ እግዝእታ ። ለኀሪት ፤ ወለእግዝእት** ፤ (ዮሴፍ ። ምሳ፳፱ ፡ ፶፰ ። ፳ዮሐ ፡ ፩) ።

**እግዝእተ ፡ ኄ**፤ እተጌ ፡ የንጉሥ ፡ ሚስት ፡ ንግሥተ ፡ ምድር ፡ ሐፄጌን ፡ እይ ። (ግጥም ፡ ስለ ፡ ራስ ፡ ሀሊ ፡ እናት) ፤ እኛስ ፡ እንላለን ፡ እተጌ ፡ መነን ፡ ሀሊ ፡ ማን ፡ ይላታል ፡ ቢጠሩ ፡ እናቱን ።

**እግዚአዊ**፤(ዝእታዊ ፡ ይ)፤ የጌታ ፡ የግዜር ፡ ጌትኛ ። **አምሳሊት ፤ እግዚአውያት** ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱) ።

**እግዚእና** ፤ ሥልጣን ፡ ሹመት ፡ መብት ። በቁሙ ፡ ገዥነት ፡ ጌትነት ፡ እግዜርነት ። **መንግሥት ፤ ወእግዚእና ። ወይትአመን ፤ በእግዚእናሁ ። እግዚእናሁ ፤ ላዕሌሃ** ፤ (ቄር ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱ ። ፶፩) ።

**እግዚእ**፤ የጨዋኸትና ፡ ያቤቱታ ፡ የምልጃ ፡ የል መና ፡ ቃል ፡ በቅርብ ፡ ባጠገብ ፡ ፊት ፡ ስፊት ፡ ላለ ፡ ለሚ ያይ ፡ ለሚሰማ ፡ የሚነገር ፤ አቤቱ ፡ ቶ ፡ እግዜር ፡ ሆይ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ ጌቶ ። **እግዚኦ ፤ መሐረነ ፤ ክርስቶስ ።** ሙ ያው ፡ እንደ ፡ እግዚእ ፡ ነው ፤ ቅጽልና ፡ በቁ ፡ ይኾናል ። **እግዚአብሔር ፤ እግዚኦ ። እግዚኦ ፤ ኢየሱስ ፤ ክር** ፤ ቅ ጽል ። **ስምዐኒ ፤ እግዚኦ ፤ ጸሎትየ ፤ እግዚኦ ፤ ጸራሕኩ ፤ ኀቤከ** ፤ በቁ ።

**እግዚአብሔር**፤ **(ዕብ ፡ ይሆዋ ። ሱር ፡ ይያ ። ዐረ ፡ ረብ ። ጽር ፡ ወቅብ ፡ ኪሪዮስ ። ሮማይ ፡ ዶሚኑስ)**፤ ስመ ፡ አምላክ ፤ እግዚእ ፡ ብሔር ፡ እግዚእ ፡ ጌታ ፤ ብሔር ፡ ዓለም ፤ በተገናኝ ፡ የዓለም ፡ ገዥ ፡ የዓለም ፡ ጌታ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የነበረ ፤ ዓለምን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፤ ርሱ ፡ ኹሉን ፡ ቢያስገኝ ፡ ኹሉን ፡ ቢገዛ ፡ እንጂ ፡ ለርሱ ፡ አስገኝና ፡ ጌታ ፡ የሌለው ፤ አበ ፡ ዓለም ፡ ንጉሠ ፡ ዓለም ፤ ወይም ፡ እግዚእ ፡ ኵሉ ፡ ንጉሠ ፡ ኵሉ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ባማርኛ ፡ እግዜር ፡ ተብሎ ፡ በ፫ ፡ ቅንጣት ፡ ፊደል ፡ ይጣፋል ፤ የእልፋ ፡ ምስጢር ፡ አለበት ፡ ብሔርን ፡ እይ ። እግዚእ ፡ እንደ ፡ አዶናይ ፡ ማእከላይ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ለኹሉ ፡ ይኾናል ፤ ብሔር ፡ ሲጨመር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ይሆዋና ፡ እንደ ፡ መለኮት ፡ ነው ፤ ከፈጣሪ ፡ በቀር ፡ ለማ ንም ፡ ፍጡር ፡ አይሰጥም ፤ ፍጡር ፡ ምንም ፡ ቢነግሥ ፡ ምንም ፡ ቢጌትይ ፡ በቃናናኽ ፡ ክፍል ፡ ነውና ፤ ያው ፡ ቅሉ ፡ የፈጣሪ ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፤ የዓለም ፡ ጌታ ፡ ሊኾን ፡ ወይም ፡ እግዜር ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ። ጸባኦት ፡ በሚልበት ፡ ግን ፡ ዕብራይስጡ ፡ **ይሆዋ ፤ ጽባኦት** ፤ እንደሚለው ፡ **እግዚኦ ፤ ጸባኦት** ፤ ቢያሰኝ ፡ እንጂ ፡ **እግዚአብሔር ፤ ጸባኦት** ፤ አያ ሰኝም ፡ ፍጺም ፡ ጺያፍ ፡ ነው ። የጸባኦት ፡ ፍቺ ፡ ኀያላት ፡ ሰራዊት ፡ ነውና ፤ ከዘርፍ ፡ በቀር ፡ ቅጽል ፡ አይኾንም ። ዳግመኛም ፡ ዕብራይስጥና ፡ ዐረብ ፡ ጽርእ ፤ አምላክ ፡ አምላክ ፡ የሚሉትን ፡ ኹሉ ፡ ግእዝ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፩—፲፩ ። ዮሐ፩ ፡ ፩ ፡ ፳ ፡ ፺ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫) ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ አለ ፤ ይህም ፡ ጥንቱን ፡ ሲመለስ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ አለመተርጐሙን ፤ ኋላም ፡ አለመታረሙን ፡ ያስረዳል ።

**እግዚአብሔርና** ፤ እግዜርነት ፡ አምላክነት ፡ እግዜር ፡ መኾን ። **አመ ፤ ጽሕቀ ፤ ለከዊነ ፤ ዐጼለ ፤ መሕየው ፤ ኢኀደገ ፤ እግዚአብሔርናሁ** ፤ (መጽ ፡ ምስ) ።

**እግዚአብሔራዊ** ፤ የግዜር ፡ ግብር ፡ ባሕርይ ፡ ወይም ፡ ወገን ፡ እግዜራም ፡ ባለግዜር ። **ገቢረ ፤ መንክራት ፤ እግዚአብሔራዊ ። ሐውጽዎሙ ፤ በሕዋጼ ፤ እግዚአብሔራዊት ። በዓባት ፤ እግዚአብሔራውያት** ፤ (መጽ ፡ ምስ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፺ ። አቡሻ ፡ ፩) ።

**ተገዝአ** ፤ ተገዛ ፡ ተገዥ ፡ ኾነ ። ታደለ ፡ ተሰጠ ፡ ምግቡ ።

**ግዙእ**፤(ኣን ፡ ኣት ፡ ዝእት)፤ ግዙ ፡ ግዛ ፡ የተገዛ ፡ ተገዥ ፡ ዜጋ ፡ ገብር ፡ ገባር ።

**ግዝእት** ፤ መግዛት ፡ መገዛት ፤ አገዛዝ ፡ ግዙነት ፤ ግዛት ፡ ይዞታ ፡ ርስት ፡ ጕልት ። **አስመ ፤ አሙንቱ ፤ ቅኑያቲ ፤ ወምልክናሁ ፤ ወግዝእት ፤ ሎቱ ። አሐዱ ፤ ግዝእት** ፤ (ቅዳ ፡ ሕር ። አዋል) ።

**ግዝእ**፤(ኣት)፤ ጋሬዳ ፡ ድግስ ፡ መሰናዶ ፤ ፍ ሬዳ ፡ ያለበት ፡ የመብል ፡ የመጠጥ ፡ የምሳ ፡ በዓል ። **ወገብረ ፤ ግዝአ ፤ ዐቢየ ። ቤተ ፤ ግዝእ ። መዋዕለ ፤ ግዝእ** ፤ (ኩፋ ፡ ፲፯ ። መክ፯ ፡ ፪ ። ኢዮ፩ ፡ ፭) ።

**ጊዜ**፤(ብ ፡ **ጊዝያት**)፤ በቁሙ ፡ የተለየ ፡ የተ ወሰነ ፡ ሰዓት ፡ ሰሌት ፡ ወርኅ ፡ ዓመት ፡ ዘመን ፡ ዕድሜ ፡ ሰው ፡ እስኪሞት ፡ እስኪሻር ፡ የሚኖርበት ፤ የሚያርፍበት ፡ የሚሠራበት ፡ ሌትና ፡ መዓልት ፤ ፳፬ ፡ ሰዓት ። (ሙሾ ፡ ያቤ ፡ ቴ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ በዛ) ፤ እስኪ ፡ ቀደም ፡ ብለኽ ፡ ጥቂት ፡ እኽል ፡ ቅመስ ፡ ሰዉ ፡ ያልቅ ፡ የለምይ ፡ ያንተ ፡ ጊዜ ፡ እስኪደርስ ። **በ ፤ ጊዜ ፤ ለዝሉ ። በጊዜ ፤ እምጊዝያት ። ጊዝያቲሆሙ ፤ ለአውራኅ ፤ በዝሉ ፤ ጊዜ** ፤ (መክ፫ ፡ ፩—፱ ። ዮሴፍ ። ኩፋ ፡ ፳፱) ።

**ጊዜ** ፤ ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ቅጽል ፡ ይኾ ናል ፤ አመና ፡ ሰበ ፡ ሰዓትና ፡ ሰሌት ፡ በሚገቡበት ፡ እየ ገባ ፡ ጊዜንቱን ፡ ሳይለቅ ፡ ይፈታል ። ዐቢይ ፡ ሲኾን ፡ በ ኀላፊ ፤ **ጊዜ ፤ ሖረ ።** ቅጽል ፡ ሲኾን ፡ በትንቢት ፤ **ጊዜ ፤ ይመጽእ ።** ደቂቅ ፡ ሲኾን ፡ በጥሬ ፤ **ጊዜ ፤ ቀትል ፤ ጊዜ ፤ ምት** ፤ እያለ ፡ ይገባል ፤ አመንና ፡ ሶበን ፡ ተመልከት ።

**ገዝአ ፤—ገዘገዘ ፤—ገዝዐ ።**

**ጕዝጕዝ ፤(ዐማርኛ ። ገለደ ፡ ነጸፈ)**፤ በቁሙ ፡ ጕዝጕዝ ፡ አንጠፈ ፡ አመቻቸ ።

**ጕዝጕዝ**፤(ብ ፡ ጕዛጕዝ ፤ ዛት)፤ ዐልጋ ፡ በቁሙ ፡ ጕዝጓዝ ፡ ሰርፍ ፡ ስጋጃ ፡ ምንጣፍ ፡ የሌት ፡

ልብስ ፡ ለሐፍ ። አምጽኡ ፡ ዐሥርተ ፡ ዐራታተ ፡ ወጕዘ ጕዘተ ፡ (ዘኍን ፡ ፲፯ ፡ ፳፱) ።

**ገዚዝ ፤ ዞት ፤ (ገዘ ፤ ገዘዘ ፡ ይገዝዝ ፡ ይ ግዝዝ ። ዕብ ፡ ጋዝዝ ፤ ጊዛህ) ፤** መግዘዝ ፡ መሸ ለት ፡ መቍረጥ ፡ መቈጥቈጥ ፡ ማጨድ ፡ መጨርገድ ፡ የ ጠጕር ፡ የፀምር ፡ የማር ፡ የቅጠል ። የተቈረጠውን ፡ መ ጀጐል ፡ ማጠር ፡ መቅጠር ፡ መጋረድ ፡ መከለል ፡ የቡ ቃያ ፡ የተክል ፡ ገድገደን ፡ ተመልከት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በገዘዘ ፡ ፈንታ ፡ አግዘዘ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። አግዘዝኩ ፡ ሎቱ ። በክንፍክሙ ፡ ዐውድየ ፡ አግዘዙ ፡ (ኢሳ፳ ፡ ፪ ። ሰንክ ፡ ኅዳ፳፱) ።

**ግዛዚ ፤ መግዝዝ ፤** የሚቈርጥ ፡ የሚጀጕል ፡ ጀጕል ፡ ሠራ ።

**መግዘዝ ፡ ት ፤ (ብ ፡ መጋዝዝ) ፤** መጋረጃ ፡ ዐጥር ፡ ቅጥር ፤ ክለላ ፡ ጀጕል ፤ ጋሬ ፡ ተራራ ፡ ገመገም ። መገዘዝ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። (ግጥም) ፡ ጣርማ ፡ በር ፡ ኹኜ ፡ ታየኝ ፡ መገዘዝ ፡ ልቤ ፡ ለቡልጋ ፡ ዐደር ፡ ሲ.ጋበዝ ።

**አግዘዘ ፤** አስቈረጠ ፡ አስጀጐለ ፡ ጀጐል ፡ አሠራ ።

**ገዚም ፤ ሞት ፤ (ገዘመ ፡ ይገዝም ፡ ይግ ዝም ። ዕብ ፡ ጋዛም ። ሱር ፡ ግዛም ። ዐረ ፡ ጀ ዘመ) ፤** መግዘም ፡ መቍረጥ ፤ መጕንደብ ፡ መመንደብ ፤ መመልመል ፡ መጨፍጨፍ ፤ ዱል ፡ መንሣት ፡ ማሸንፍ ። ጕደበን ፡ ኢይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ግዝሙ ፡ ዕፀዊሃ ። ይገዝም ፡ በጕድብ ፡ ሖሎ ፡ መሠንየ ፡ አርዝከ ። ገ ዘማ ፡ ከመ ፡ ዕፀ ፡ ለሕይወትየ ፡ (ኤር፮ ፡ ፮ ። ፳፱ ፡ ፮ ። ኢዮ፲፱ ፡ ፲) ።

**ገዛሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት ፤ ዘምት) ፤** የሚገዝም ፡ የሚቈርጥ ፡ ቈራጭ ።

**ግዝም ፤ (ማት) ፤** በቁሙ ፡ ቃዳ ፡ ተለላ ፤ ፈሩ ፡ እሙም ፡ መዝሪያ ፡ ትልም ፡ በዘርና ፡ ባረም ፡ ባጨዳ ፡ ጊዜ ፡ ሠራተኞች ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ የሚያወጡት ፡ ክፍል ።

**አግዘመ ፤** አስገዘመ ፡ አስቈረጠ ። አግዘመ ፡ አ ዕዋመ ። በአፈ ፡ መጥባሕት ፡ ከሣይ ፡ አግዘመ ፡ (ዘሁ፬ ፡ ፱፱ ፡ ፱ ። ዘኍን ፡ ፲፭ ፡ ፲፫ ። ሰንክ ፡ የካ፲፭) ።

**መግዝም ፤** መቍረጫ ፡ ገጀሞ ፡ ጕድባ ። ገዘሚያም ፡ ይኾናል ።

**ተገዝመ ፤** ተቈረጠ ፡ ተቈራረጠ ፡ ተጨፈጨፈ ። ዕፀው ፡ ነዊኃን ፡ ይትገዘሙ ። ዕፀ ፡ እንተ ፡ ተገዝ መት ። ተገዚሞ ፡ ዳግመ ፡ ይፈሪ ፡ (ሐዋ፳፫ ፡ ፱ ። ዳዴ ፡ ፳፭ ። ኢዮ፲፬ ፡ ፯ ። ማቴ፫ ፡ ፲) ።

**ግዙም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ዝምት) ፤** የተቈረጠ ፡ የተጨፈጨፈ ፡ ቍርጥ ፡ ምልምል ። ዕፀው ፡ ግዙማን ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ግዝመት ፤** መግዘም ፡ መገዘም ፡ አገዛዘም ፡ አ ቈራረጥ ፡ ቈረጣ ፡ ምልመላ ፡ ጭፍጨፋ ።

(ጥ) **ግዛም ፤ (ማት) ፤** ጕማጅ ፡ ቍራጭ ፡ ጭፍ ጫሬ ፡ ዝንጣሬ ፡

**ጊዛን ፤—የዕቃ ፡ ቤት ፤—ጋዛ ።**

**ገዚዐ ፤ (ዕብ ፡ ጋዛዕ ። ዐረ ፡ ጀዘዐ) ፤** ከረከረ ፡ ገዘገዘ ፤ ቈረጠ ፡ ገረዘዘ ፤ የመጋዝ ። አዘዘ ፡ መ ኰንን ፡ ይቀንውዎ ፡ ወይሥትሩ ፡ ሥጋሁ ፡ ወይዝሕቁ ፡ አምእስቲሁ ፡ ወይግዝዕዎ ፡ በመጋዝዕ ፡ እደዊሁ ፡ ወ እገሪሁ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳፭) ።

**መግዝዕ ፤ (ብ ፡ መጋዝዕ ፡ ዓት) ፤** መጋዝ ፡ መገዝገዣ ፡ መቍረጫ ፡ መተርተሪያ ። አዘዘ ፡ ይሥት ርዋ ፡ በመጋዝዕ ፡ ወተሰብረ ፡ መጋዝዕ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳) ።

(ጥ) **ግዛዕ ፤ (ዓት ። ዕብ ፡ ጌዛዕ ። ዐረ ፡ ጂዝዕ) ፤** ጕንደ ፡ ዕፅ ፤ ከሥር ፡ በላይና ፡ ከዐጽቅ ፡ በታች ፡ በመካ ከል ፡ ያለው ፤ አስጺቅን ፡ እንደ ፡ ዐምድ ፡ ኹኖ ፡ የሚ ሸከም ። በትግርኛ ፡ ግን ፡ እንዳች ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ገዚፍ ፤ ፎት ፤ (ገዝፈ ፡ ይገዝፍ ፡ ይግ ዝፍ) ፤** መግዘፍ ፡ መወፈር ፡ መድንደን ፤ መዳጐስ ፡ መ ሥባት ፤ ወፍራም ፡ ድንዳም ፡ መኾን ። አጽባዕትየ ፡ ይገዝፍ ፡ ወይጸንዕ ፡ እምሐቌ ፡ አቡየ ። ናሁ ፡ ገዝፋ ፡ አልባቢክሙ ፡ ወክና ፡ ከመ ፡ አእባን ። ከመ ፡ ኢይግ ዝፍ ፡ ልቡ ፡ ወኢይጽልም ፡ አእምሮቱ ፡ (ዘሁ፬ ፡ ፲ ፡ ፲ ። ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

—፤ ማጕራት ፡ መጮኽ ፡ መጩፈር ፤ ሂያ ፡ ሂያ ፡ ማለት ፡ የዘራፍ ።

(ጥ) **ገዚፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ዛፍ) ፤** የገዘፈ ፡ ወፍ ራም ፡ ደንሳ ፡ ድንዳና ፤ ጕልሕ ፡ ሥጋዊ ። ገዚፈ ፡ አባል ። ለምንት ፡ አውሰብከ ፡ ብእሲተ ፡ ንእስተ ፡ ወአንተኒ ፡ ብእሲ ፡ ገዚፍ ፡ ወዐቢይ ። ገዚፍ ፡ ዐምድ ። ልብስ ፡ ገዚፍ ። አምእስተ ፡ ገዚፋን ። አብትር ፡ ዘኅጺን ፡ ገዚፋት ። ምክር ፡ ገዚፍ ፡ (ፊላስ ፡ ገ፶፫ ። ቋ፩ ። ሰንክ ፡ ጳጉ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫ ። ፲ ፡ ፯ ። ገድ ፡ ተክ ። ማር ፡ ይሥ ሐቀ ፡ ፭) ።

**ግዙፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ዝፍት) ፤** በቁሙ ፡ ገዝጊ ፡ ከማሁ ። ይኩን ፡ ልብሶሙ ፡ እምፀምር ፡ ግዙፍ ። ግዙፈ ፡ ከማይ ። ግዙፋን ፡ ልብ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲ ፡ ፮ ። ዘዳ፱ ፡ ፲፫ ። አርጋ ፡ ፮) ።

**ግዝፈት ፤** መግዘፍ ፡ መወፈር ፡ አወፋፈር ፤ ወ ፍራምነት ፤ ውፍረ ፡ ወፍር ፤ ውፋሬ ፡ ድንዳኔ ። በግዝፈ ተ ፡ ልብከ ፤ በግዝፈቱ ፡ ከማይከ ፡ (መቃ ፡ ገ፮ ። ፲፱ ። ስንክ ፡ ታኅ፮) ።

**ግዝፍ ፤ ግዘፍ ፤** በቁሙ ፡ ወፍር ፡ ድንዳኔ ። ግዝፈ ፡ ምድር ። ግዝፈ ፡ ልብ ። ግዝፈ ፡ ደመናት ። ግዝፈ ፡ ዕፀ ። ግዝፈሆን ፡ ለአልባቢክ ፡ (መገ ፡ ጀ፸ ። አርጋ ፡ ፮ ፡ ፭ ። ሕገ፡ ማ፲ ፡ ፳፭ ። ዮሴፍ) ።

**አግዘፈ ፤** አገዘፈ ፡ አወፈረ ፡ አደነደነ ።

**መግዝፈ ፤ ዝፍ ፤** የሚያገዝፍ ፡ አግዛፊ ፡ አ ሥቢ ፡ አወፋሪ ።

**መግዘፍ ፤** መግዘፊያ ፡ ማግዘፊያ ፡ ማወፈሪያ ። ግዘፍ ፡ ወፍር ። ቢናበብ ፡ የቅጽል ፡ አፈታት ፡ ያፈታል ።

በመግዘፈ ፡ ምድር ፡ ከመ ፡ ግዝፈ ፡ ምድር ፡ ግዙፍ ፡ (ዩዲና ፡ ፱ ፡ ፲፯) ።

**ገዚር ፡ ሮት ፡** (ገዝረ ፡ ይገዝር ፡ ይግዝር ። ሱር ፡ ግዝር ። ዕብ ፡ ጋዝር ፡ ናማል ። ዐረ ፡ ጀዘረ ፡ ኀተነ) ፡ መግዘር ፡ መግረዝ ፡ የብልትን ፡ ሸንኰፍ ፡ ቈርጦ ፡ መጣል ፡ ወይም ፡ በሞይራሽ ፡ መስለብ ፡ (ዘፍ ፡ ፲፯ ፡ ፲ ፡ ፲፬ ፡ ፳፫ ። ሉቃ ፡ ፩፥ ። ፪ ፡ ፳፩) ። ዘገዘረ ፡ ወልዶ ፡ በእንተ ፡ ደዌ ። ግዝሩ ፡ እከየ ፡ ልብክሙ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፴፫ ፡ ፳ ። ኤርም ፡ ፬ ። ዘዳ ፡ ፲፮) ።

**ግዝሬ ፡ (ሬት ፡ ርያን ፡ ያት ፡ ዘርት) ፡** በቁሙ ፡ የሚገዝር ፡ ገራዥ ፡ ባለወግ ። ትቤሎ ፡ ማርያም ፡ ለዮሴፍ ፡ አምጽእ ፡ ሊተ ፡ ግዝሬ ፡ ጠቢበ ፡ (ስንክ ፡ ጥር ፮) ።

**አግዘረ ፡** አስገዘረ ፡ አስገረዘ ። **እምድኅረ ፡ ሰቡዕ ፡ መዋዕል ፡ ታግዝር ፡ ወልዳ ፡** (ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፭ ። ዘሌ ፲፪ ፡ ፫) ።

**ተገዝረ ፡** ተገዘረ ፡ ተቈረጠ ፡ ተከረከመ ፡ (ዘፍ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ፡ ፳፬—፳፯) ። ተገዘሩ ፡ ለእግዚአብሔር ። ዘተገዝረ ፡ በምክንያተ ፡ ደዌ ፡ ወእዘዝዎ ፡ ዐቀብተ ፡ ሥራይ ፡ (ኤርም ፡ ፬ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፫ ፡ ፪) ።

**ግዙር ፡ (ራን ፡ ራት ፡ ዝርት) ፡** በቁሙ ፡ የተገዘረ ፡ ግርዝ ፡ ብልተ ፡ ጥሩ ፡ ይሁዲ ፡ ፈላሻ ፡ እስላም ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ወንጌል ፡ እንበለ ፡ ኦሪት ፡ ጥምቀት ፡ እንበለ ፡ ግዝረት ፡ አትረባም ፡ አትጠቅምም ፡ አታጸድቅም ፡ የሚል ። ግዙር ፡ ወቈላፍ ። በእንተ ፡ ኅጽዋን ፡ ወግዙራን ፡ (ሮሜ ፫ ፡ ፴ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፫ ። ግብ ፲፭ ፡ ፩ ፡ ፭ ፡ ፳፬) ።

**ግዝረት ፡** በቁሙ ፡ መግዘር ፡ መገዘር ፡ አገዛዘር ፡ ገዘራ ፡ ግዙርነት ፡ ግዝራት ። ወሀበክሙ ፡ ሙሴ ፡ ግዝረተ ። ወግዝረትሰ ፡ ግዝረተ ፡ ጽላሴ ፡ ልብ ፡ በመንፈስ ። ወምንትኑ ፡ ስባጤሃ ፡ ለግዝረት ። በእንተ ፡ ግዝረት ፡ (ዮሐ ፯ ፡ ፳፪ ። ሮሜ ፪ ፡ ፳፱ ። ፫ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲፭) ።


**ግዝሮ ፡** ግዝረት ፡ ግዝራት ። ዝ ፡ ደመ ፡ ግዝሮሁ ፡ ለወልድየ ። ኢየሐጽጽ ፡ ሕማመ ፡ ግዝሮሁ ፡ ለአረጋይ ፡ እምሕማመ ፡ ሐርደቶሙ ፡ ለንኡሳን ፡ (ዘፀ ፬ ፡ ፳፭ ። መጽ ፡ ምስ) ። ግዝረት ፡ የሚገባ ፡ ለወንድም ፡ ለሴትም ፡ ሲኾን ፡ በወንድ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ይነገራል ። ሴት ፡ ልጅ ፡ ካልተገዘረች ፡ ሙቷ ፡ አይገንም ፡ አይፈፋም ፡ ታባላቅ ፡ አይኾንም ። የፈላሰፎች ፡ መጽሐፍ ፡ ሙት ፡ የሚገባበት ፡ የሚያብጥበት ፡ የሚነፋበት ፡ ምክንያቱ ፡ ግዝረት ፡ ነው ፡ ይላል ። አኔ ፡ ቅድር ፡ ወእጥባትየ ፡ ከመ ፡ ማኅፈድ ፡ ያለውም ፡ ይህንን ፡ ያስረዳል ፡ (ማሕ ፰ ፡ ፲) ።

**ገዚረት ፡ (ዐረ ፡ ጀዚረት) ፡** ደሴት ፡ የየብስ ፡ ቍራጭ ፡ ባሕር ፡ ያጠረው ፡ የከበበው ፡ መሬት ፡ አገር ። አፈ ፡ ወርቅ ፡ ዘሞተ ፡ በስደት ፡ በውስተ ፡ ገዚረት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ግዛት ፡ —በቁሙ ፡ ውግዛት ፡ —ወጊዝ ፡ ወገዘ ።**

**ግሕይ ፡ ዮት ፡ (ገሐየ ፡ ይግሒ ፡ ይግሐይ ። ትግ ፡ ገሐ) ፡** መፍራት ፡ መፍሰስ ። መማስድ ፡ ማስደ ፡ መንማት ። ገሐን ፡ እዩ ፡ የዚህ ፡ ነገር ፡ ነው ።

**ገሓይ ፡ ግሔ ፡ (ሕያት ። ዕብ ፡ ሻፋን ። ዐረ ፡ ወብር ። ጽር ፡ ኪሮግሊዩ) ፡** ሽኮኮ ፡ አሽኮኮ ፡ እንደ ፡ ጥንቸል ፡ ያለ ፡ ሣር ፡ ቅጠል ፡ ቡቃያ ፡ የሚበላ ፡ ማስዳ ፡ ገሕ ፡ ሲቀድ ፡ የሚፈጭኸ ፡ የሚያሸከክ ። ፈሪ ፡



ግሔ ።

ድኩም ፡ ገሓዊ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከርሥከሂ ፡ ጸላዕት ፡ ምጕያየ ፡ ግሔ ፡ ረኅብ ። ወግሕያት ፡ ሕዝብ ፡ ዘኢኮኑ ፡ ጽኑዓነ ። ቈናጽል ፡ ወግሕያት ፡ (ቅኔ ። መዝ ፡ ፻፫ ። ምሳ ፴ ፡ ፴፮ ። ሔኖ ፲፮ ፡ ፪) ።

**ጕሐየ ፡ (ዐረ ፡ ጀሓ) ፡** ዐረመ ፡ ነቀለ ፡ መነገለ ፡ አፈለሰ ።

**ምጕሕያ ፡** ዐረም ፡ እሾኽም ፡ ቅጠል ፡ ኵርንችት ፡ ዐቃቅማ ፡ አሜኬላ ፡ ሙጃ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ሦክ ፡ ወምጕሕያ ፡ (ኢሳ ፯ ፡ ፳፫—፳፭ ። መቃ ፡ ገ፲፪) ።

**ጕሒል ፡ ሎት ፡ (ጕሕለ ፡ አው ፡ ጕሐለ ፡ ይጕሕል ፡ ይጕሐል ። ዐረ ፡ ጀሐለ ። ዕብ ፡ ጋሓል ፡ ጋለ ፡ ጋመ) ፡** ማፍረስ ፡ መጣስ ፡ ማቃጠል ፡ መተኰስ ፡ የሕግ ፡ የቅጥር ፡ የቤት ። መስረቅ ፡ መቀማት ፡ መውረር ፡ መገረፍ ።

**ጕሓሊ ፡ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፡ ሐልት) ፡ ጕሕልያ ፡ (ያት) ፡** ከፋ ፡ አድራጊ ፡ ሌባ ፡ ቀማኛ ፡ ጓንደ ፡ ወንበዴ ፡ ቀማኛ ፡ የቀን ፡ ወራሪ ፡ የሌት ፡ ሰባሪ ፡ ቤት ፡ አቃጣይ ፡ ነፍስ ፡ ገዳይ ። ጕሒላ ፡ እንዲል ፡ (ትግሬ) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በራቂ ፡ ወጕሕልያ ፡ ሰረቅት ፡ ወጕሕልያ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ፀር ፡ እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሳንድም ፡ ሰብዙም ፡ ያደርገዋል ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዩጠጫ ፡ ፱ ፡ ፱ ። ዮሐ ፲ ፡ ፩ ፡ ፰ ። ዐብድ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ኅዳ ፲፪) ።

**ኀሕለወ ፡ (ይኀሐሉ ፡ ይኀሕሉ) ፡** ሸነገለ ፡ አታለለ ፡ ዋሸ ፡ ዐበለ ፡ ከዳ ፡ ተተንኰለ ። ወዘኢኀሕለወ ፡ በልሳኑ ። ወኀሕለዉ ፡ በልሳናቲሆሙ ፡ (መዝ ፲፬ ፡ ፫ ። ሮሜ ፫ ፡ ፲፫) ። ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በኀሕለወ ፡ ፈንታ ፡ ተኀሕለወ ፡ ይላል ፡ (ዘኍ ፳፭ ፡ ፲፰ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳፱ ። ፴፮) ። አሐውርኑ ፡ በተኀሕልዎ ፡ ወበተጠብቦ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ኀሕላዊ ፡ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፡** የሚሸነግል ፡ የሚያታልል ፡ ሸንጋይ ፡ አታላይ ፡ ዋሾ ፡ ዐባይ ፡ ዐላዊ ፡ ከዳተኛ ፡ ተንኰለኛ ፡ (አፈ ፡ ተ ፳፱) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በኀሕላዊ ፡ ፈንታ ፡ ጕሕልያ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ጕሕላዊ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ብእሲ ፡ ደም ፡ ወጕሕላዊ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ጕሕላዊ ። ሰይጣን ፡ ሐሳዊ ፡

ወጐሕሳዊ ፡ ውእቱ ፡፡ እኩያን ፡ ወጐሕሳውያን ፡ ኖሎት ፡ (መዝ ፡ ፳ ፡፡ ዮሴፍ ፡፡ ፈ ፡ መ ፡ ፳፫ ፡ ፳ ፡፡ ዲድ ፡ ፯ ፡፡ ሮሜ፳ ፡ ፳፱) ፡፡ ዩኛም ፡ በጓሕሳዊ ፡ ፈንታ ፡ ጕሕልው ፡ ይባል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡፡ መስተመይናን ፡ ወጕሕልዋን ፡ (አፈ ፡ ድ፴፫) ፡፡

**ተጕሕለ ፤ (ይትጐሐል) ፤** ተደራጊ ፡ የጕሕስ ፡ ተግብሮ ፡፡

**ተጓሕለወ ፤ (ተደራጊና ፡ ተደራራጊ) ፤** ተሸነገለ ፡ ተሞኘ ፡ ተታለለ ፡፡ ቀቀትሰ ፡ በተምይነ ፡ ነገር ፡ ወበተጓሕልዎ ፡፡ ይትጓሐለዉ ፡ በፍቅሮሙ ፡ (ዮሴፍ ፡፡ ፱ጴጥ ፡ ፱ ፡ ፲፫) ፡፡ ተሸናገለ ፡ ተሸነጋገለ ፡ ተተናኰለ ፡ ተተንኳኰለ ፡ ተካዳ ፡ ተከዳዳ ፡፡ ከመ ፡ ኢይትጓሕለውክሙ ፡፡ ተጓሕለወነ ፡ እዩ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፳፱ ፡፡ ፱ነገ ፡ ፱ ፡ ፳፫) ፡፡

**ጕሕልው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሉት) ፤** የተታለለ ፡ የተሸነገለ ፡ ሸንግል ፡ ድልል ፡ ሌሎች ፡ ያታለሉት ፡ የሸነገሉት ፡፡

**ጕሕላዌ ፤ ጕሕሉት ፤** መታለል ፡ ማታለል ፡ አታላይነት ፡፡ ሽንገላ ፡ ልብለባ ፡ ክዳት ፡ ተንኰል ፤ ስይጣናዊ ፡ ባህል ፡፡ ልማደ ፡ አራዊት ፡ ጕሕላዌ ፡፡ ወገብረ ፡ ኢዮአብ ፡ ዘንተ ፡ ጕሕሉተ ፡፡ ክዒወ ፡ ደመ ፡ ሰብእ ፡ በጕሕሉት ፡፡ ወጕሕሉት ፡ ቃለ ፡ አፉሆሙ ፡፡ ጕሕሉት ፡ ወጽልሑት ፡ (ቅኔ ፡፡ ፪ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ፡፡ ቀሌ ፡፡ ኤር፲፱ ፡ ፳ ፡፡ ማሮ፳ ፡ ፳፱) ፡፡

**አስተጓሕለወ ፤** አካዳ ፡ አከዳዳ ፡፡ አስተጓሕለውኪ ፡ (ኢሳ፶፯ ፡ ፱) ፡፡

**ግሒሥ ፤ ሦት ፤ (ግሕሠ ፤ ገሐሠ ፡ ይግሕሥ ፡ ይግሐሥ ፡፡ የጌሠ ፡ ጎር) ፤** መግባት ፡ ማረፍ ፡ ማደር ፡ መጠጋት ፤ መምጣት ፡ መቅረብ ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፳ ፡፡ ፲፱ ፡ ፱ ፡ ፫ ፡፡ መሳ፱ ፡ ፲፰) ፡፡ ወይቤሎ ፡ ገሐሥ ፡ ወንበር ፡ ዝየ ፡ ንትናገር ፤ ወግሕሠ ፡ ወነበረ ፡ (ሩት፬ ፡ ፩) ፡፡

—፤ ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ መፍለስ ፡ ከመንገድ ፡ መውጣት ፡ መጐዳኘት ፡ ማግለል ፡ መራቅ ፤ ገለል ፡ ፈቀቅ ፡ ማለት ፡ ለማደር ፡ ለመስፈር ፡ የመንገደኛ ፡ (መሳ፲፰ ፡ ፲፭ ፡፡ ፲፱ ፡ ፲፭) ፡፡ እስመ ፡ ጕንደየ ፡ ግሒሠ ፡ ህየ ፤ ወግሕሠ ፡ ህየ ፡ ይብላዕ ፡ እክለ ፡ (፩ነገ ፡ ፱ ፡ ፳) ፡፡ ዳግመኛም ፡ በግሕሠ ፡ ፈንታ ፡ ተግሕሠ ፡ ይባል ፡ አያሰኝም ፡ (ሚል፱ ፡ ፳ ፡፡ ዘፍ፴፰ ፡ ፲፱ ፡፡ ዘኍ፲፱ ፡ ፲፭) ፡፡ ተገሐሥ ፡ እምነ ፡ ዐመፃ ፡ ወትትገሐሥ ፡ እምኔክ ፡ ሰሊሃ ፡፡ ተግሕሡ ፡ ማይት ፡ እምደበ ፡ ገጸ ፡ ሰምድር ፡ ውስቴ ፡ አሐዱ ፡ መካን ፡፡ ይትገሐሥ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እምብዙኃን ፡ (ሚራ፯ ፡ ፱ ፡፡ ኩፋ ፡ ፱ ፡፡ ዕር ፡ ኢሳ፫ ፡ ፳፯) ፡፡ እንቀጹን ፡ ተግሕሠ ፡ ካለ ፡ ዘንድ ፡ ጥሬውን ፡ ደግሞ ፡ ትግሕሥት ፡ ይባል ፡፡ ትሜንን ፡ ትግሕሥቶሙ ፡ እምፍኖት ፡ ርቱዕ ፡ (አፈ ፡ ድ፱ና ፡ ፱) ፡፡ አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ተግሕሦቶሙ ፡ ይባል ፡፡

**ገሓሢ ፤ (ሢት ፡ ሥያን ፡ ያት ፤ ሐሥት) ፤** የሚገባ ፡ ገቢ ፡ መሪጪ ፡ የሚርቅ ፡ የሚያገል ፡ አግላይ ፡ ፈቀቅ ፡ ባይ ፡ መናኝ ፡፡

**ግሑሥ ፤ (ሣን ፡ ሣት ፡ ሕሥት) ፤** የገባ ፡ የመጣ ፡፡ የራቀ ፡ ያገለለ ፡ የተለየ ፡ ልዩ ፡ ፍጹም ፡ ባሕታዊ ፡ በረኸኛ ፡፡ ትንሣኤ ፡ ዘግሑሥ ፡ እምሐሰት ፡፡ ልደት ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘግሑሥ ፡ እምአዝማን ፡፡ ዐላውያን ፡ እለ ፡ ርሑቃን ፡ ወግሑሣን ፡ እምኔክ ፡፡ ይኩን ፡ ግሑሠ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ ነበረ ፡ ግሑሠ ፡ በውሳጤ ፡ ገዳም ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፳፱ ፡፡ ማር ፡ ይሥ፲፫ ፡፡ ዳንኤ ፡ ፳ ፡፡ ቀሌ ፡፡ ስንክ ፡ ሠኔ፳፱) ፡፡

**ግሕሠት ፤** መግባት ፡ መራቅ ፡ አራራቅ ፡ ርቀት ፡ ሽሽት ፡ ስደት ፡፡ ምግማቴ ፡ ወግሕሠት ፡ (ምሳ፳ ፡ ፴) ፡፡

**አግሐሠ ፤** አገባ ፡ አስገባ ፡፡ አራቀ ፡ አስራቀ ፡ አስገለለ ፡ አሶገደ ፡ ለየ ፡፡ አግሕሥ ፡ እገሪከ ፡ እምእሠሮሙ ፡፡ ፍናወ ፡ ሕይወት ፡ ይግሕሣ ፡ እምእኩይ ፡፡ አግሐሦሙ ፡ እንተ ፡ ባሕቲቶሙ ፡፡ አስተፋጠኑ ፡ ወአግሐሡ ፡ (ምሳ፩ ፡ ፲፭ ፡፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ፡፡ ጦቢ፲፪ ፡ ፯ ፡፡ ዮዲ ፲፫ ፡ ፩) ፡፡ ዳግመኛም ፡ በአግሐሠ ፡ ፈንታ ፡ አስተግሐሰ ፡ ይባል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ፡፡ መጽብበ ፡ ቦእኩ ፡ ወአልቦ ፡ ዘያስተግሕሥ ፡ ሊተ ፡፡ ፈቀድኩ ፡ አስተግሕሥ ፡ ዝኩ ፡ መጽብበ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፳፫ ፡፡ ሄሮማ) ፡፡ አስተግሐሠ ፡ ቢል ፡ ግን ፡ አደራራጊ ፡ ኹኖ ፡ አራራቀ ፡ አለያየ ፡ ያሰኛል ፡ አስተሉን ፡ ተመልከት ፡፡

**አግሓሢ ፤ መግሕሥ ፤** የሚያገባ ፡ አግቢ ፡ አራቂ ፡ አስገላይ ፡ አጋፋሪ ፡ ከልካይ ፡፡

**ምግሓሥ ፤ (ሣት) ፤** መግቢያ ፡ ማግቢያ ፡ ማግለያ ፡ ማስገለያ ፡ ቦታ ፡ ዐዘቅተ ፡ ኵስሕ ፡፡ ኀበ ፡ አልቦ ፡ ምግሓሥ ፡፡ ምግሓሠ ፡ ጽርሑ ፡ (ዘኍ፳፱ ፡ ፳፯ ፡፡ መሳ፫ ፡ ፳፱) ፡፡

—፤ መሣሪያ ፡ መዘቂያ ፡ ማፈኛ ፡ መውሰጃ ፡ ማንሻ ፡ እንዳክፋና ፡ እንደ ፡ ላይዳ ፡ እንዳስፈፊዳ ፡ ያለ ፡፡ ኢያሚኅና ፡ ኩከም ፡ መስወድ ፡ የዚህ ፡ ዘመንች ፡ ናቸው ፡፡ ምግሓማት ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፫ ፡፡ ፴፰ ፡ ፫) ፡፡

**ግሒፍ ፤ ፎት ፤ (ገሐፈ ፡ ይግሕፍ ፡ ይግሐፍ ፡፡ ዐረ ፡ ጀሐፈ) ፤** መጋፍ ፡ መጥረግ ፡ ማፈሥ ፡ መውሰድ ፡ ማንሣት ፡ ማስገለል ፡፡ መጋፈፍ ፡ ማጋፈፍ ፡ አብዝቶ ፡ መብላት ፡ መጠጣት ፡ አለማትረፍ ፡ ቢተርፍም ፡ በልብስ ፡ መታቀፍ ፡ በኰፊዳ ፡ መከተት ፡ መወቀፍ ፡፡ ከመ ፡ ጸበል ፡ ዘይግሕፎ ፡ ነፋስ ፡ (ጥበ፭ ፡ ፲፭ ፡፡ መዝ ፡ ፩)

**ገሓፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ሐፍት) ፤** የሚግፍ ፡ የሚጠርግ ፡ ጋፊ ፡ ጋፋፊ ፡ ጠራጊ ፡ ሆዳም ፡፡

**አግሐፈ ፤** አስጋፈ ፡ አስጠረገ ፡ አስነሣ ፡፡

**ተግሕፈ ፤** ተጋፈ ፡ ተጠረገ ፡፡

**ግሑፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ሕፍት) ፤** የተጋፈ ፡ የተጠረገ ፡ የታፈሠ ፡፡

**ግሕፈት ፤** መጥረግ ፡ መጠረግ ፡ አጠራረግ ፡ ጠረጋ ፡፡

**ገሓፍት ፤ (ዐረ ፡ ቁፈት ፡፡ ዕብ ፡ ሳል) ፤** ቅርጫት ፡ መሶብ ፡ እንቅብ ፡ አገልግል ፡ ቅንብቻ ፡ ኰፊዳ ፡

ግትዖ ። ወኃነብሮ ፡ ዲበ ፡ ገሓፍት ፡ (ዘፍ ፡ ፳፱ ፡ ፫ ። ፳፫ ፡ ፴፪) ።

**ምግሓፍ ፤ (ፋት) ፤** ግዢ ፡ ከማው ፡ መጋፊያ ፡ ማፊሻ ፡ መጥረጊያ ።

**ጋሕፍ ፤ (ትግ ፡ ጋሕፎ) ፤** የባሕር ፡ ዒሊ ፡ ደንጊያ ፡ ልብሱ ።

**ጕሒ.ቀ ፤ ቆት ፤ (ጕሕቈ ፡ ይጕሕቀ ፡ ይጕሐቀ ። ዐረ ፡ ጀ፦) ፤** መጕበጥ ፡ መጕንበስ ፡ መጸንን ፡ እንደ ፡ ደጋን ፡ መኾን ፡ በደዌ ፡ በርግና ፡ (ሉ ቃ ፲፫ ፡ ፲፩) ። መካን ፡ ዘጕሕቈት ፡ ወሞተ ፡ ማሕፀና ። ዐቤራይት ፡ ዘጕሕቈት ፡ እምአብዝኆ ፡ ውሉድ ፡ (አፈ ፡ ድጓ፳ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ጕሐቀ ፤ (ቋን ፡ ቋት ፡ ሕቀት) ፤** የጕበጠ ፡ ጕብጣ ፡ ቀላሳ ፡ ተርካሳ ።

**ጕሕቈት ፤** መጕበጥ ፡ አጕባበጥ ፡ ጕባጥንት ፡ ጕብጠት ።

**አጕሐቈ ፤** አጕበጠ ፡ አስጕበጠ ፡ ጕባጣ ፡ አደረገ ፡ ዐረቀ ፡ ቀለሰ ፡ አስጕንበሰ ። ፍርግያ ፡ ታጕሕቈ ፡ ዘባና ። ትካዝ ፡ ያጕሕቊ ፡ አባለ ፡ ወያዐውር ፡ አዕይንት ፡ (ኪዳ ። ፈላስ ፡ ገ፹፮) ።

**ጋሕር ፤ (ትግ ፡ ገሕር ። ዕብ ፡ ጊሑር ፤ ፍጹም ፡ ቀይ) ፤** ፍሕም ፡ ፍም ፡ የእሳት ፡ ምርት ፡ የበሰለ ፡ ዕንጨት ፡ ብስል ፡ በርበሬ ፡ የሚመስል ።


**ጎሞ ፤ ጕሞ ፤** በቁመ ፡ ዐባጣ ፡ ሸካራ ፡ የምድር ፡ የመሬት ፡ የበትር ፡ የንጨት ፡ ለእጅም ፡ ይኾናል ። እጂ ፡ ጕጥ ፡ አወጣ ፡ እንዲሉ ።

**ጎጥዮ ፤ ዮት ፤ (ጎጠየ ፡ ይጎጢ ፡ ይጕጢ) ፤** መንጕጥ ፡ መጕጥጕጥ ፡ መሥቅሥቅ ፡ መቈፈር ፡ መሰርሰር ፡ መጕጓት ፡ መትከል ። ማጣበቅ ፡ መቈንጠጥ ፡ አጣብቆ ፡ መያዝ ።

**ጎጣዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤** የሚወጋ ፡ የሚንጕጥ ፡ የሚያጣብቅ ፡ የሚቈነጥጥ ።

**ምጕጣይ ፤ (ያት) ፤** መውጊያ ፡ መንጕጫ ፡ መቈንጠጫ ፡ አሽሙር ፡ ቾንካር ፡ አርቃሽ ። ይብእሲ ፡ ረኀፀ ፡ ውስተ ፡ ቀኖት ፡ ባለው ፡ ጽኑዕ ፡ ለከ ፡ ምጕጣይ ፡ ወተረግፆ ፡ እንዲል ፡ (ግብ፳፮ ፡ ፲፬) ።

**ጕጠት ፤ (ታት) ፤** በቁሙ ፡ መቈንጠጫ ፡ አጥብቆ ፡ አጣብቆ ፡ መያዣ ፡ እንደ ፡ መቀስ ፡ ፪ ፡ ጣት ፡ ያለው ። ፍሕም ፡ ዘነሥአ ፡ በጕጠት ። መጠዋ ፡ በጕጠተ ፡ እሳት ፡ እምሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለክርስቶስ ። ወ



ጕጠት ፤

ደዮ ፡ አፍሓመ ፡ እሳት ፡ ዲበ ፡ እደዊሁ ፡ ወአኀዝዎ ፡ በጕጠት ፡ ብዙኀ ፡ ጊዜ ። ወጕጠታቲሃ ፡ (ኢሳ፮ ፡ ፮ ። ሰንክ ፡ ኀሐ፲፰ ። ታኅሣ፱ ። ዘኍ፬ ፡ ፱) ።

—፤ ሹክ ፡ ሜንጦ ፡ መጕሥሥ ፡ የሥጋ ፡ ማውጫ ፡ የወጣውን ፡ እየወጉ ፡ ማንሻ ፡ እንደ ፡ መንሽ ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ ጣት ፡ ያለው ። ጕጠት ፡ ዘሠላስ ፡ ከተማት ። ጕጠታተ ፡ ሥጋ ፡ (ፊልክ ፡ ፳ ። ፩ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፲፯ ። ፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፲፩) ።

**ጎይ ፤ ዕብ ፡ ጎይ ፤** ሕዝብ ፡ ያንድ ፡ አገርና ፡ ያንድ ፡ መንግሥት ፡ ሰው ፡ ቋንቋውና ፡ ሕጉ ፡ አንድ ፡ የኾነ ። ሲያበዛ ፡ ጎይም ፡ ይላል ፤ አሕዛብ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ጕይይ ፡ ጕየ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ሥር ፡ ወጥቷል ።

**ግይብ ፤ (ዐረ ፡ ጀይብ) ፤** ጀብ ፡ ኪስ ፡ የጀይብን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ።

**ገይብ ፤ (ዕብ ፡ ጋቢያዕ ። ዐረ ፡ ጣስ) ፤** ኮራ ፡ ታላቅ ፡ ጽዋ ፡ ረኸ፦ም ፡ እግሩም ፡ እንደ ፡ ጕሽ ፡ ዋንጫ ፡ በስተላይ ፡ ሰፊ ፡ ለቃቃ ፡ በስተታች ፡ ጠባብ ፡ ሸልቋቋ ፡ ውሃ ፡ አንጥፈው ፡ ያበባ ፡ ችቦ ፡ የሚያኖሩበት ፡ ወይን ፡ ቀድተው ፡ የሚጠጡበት ። ገይበ ፡ ብሩር ፡ ዘቦቱ ፡ ይሰቲ ፡ እግዚእየ ። ሐ ፡ ገይበ ፡ ወርቅ ፡ ምቅዳሐ ፡ ስብሐት ፡ (ዘፍ፵፬ ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ፲ ፡ ፲፮ ። አርጋ) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ አንኮላ ፡ ሽክና ፡ ዐቦሬ ፡ ሽልም ፡ ኰባይ ፡ ክቦ ፡ ይሉታል ።

**ጌግዮ ፤ ዮት ፤ (ጌገየ ፡ ይጌጊ ። ጎገወ) ፤** መሳት ፡ መሳሳት ፡ ከመንገድ ፡ መውጣት ፡ በስሕተት ፡ መበደል ፡ ኀጢአት ፡ መሥራት ። ዮጊ ፡ እጌጊ ፡ እስመ ፡ እንተ ፡ ፍኖተ ፡ ይብር ፡ መጻእኩ ። ይጌግዩ ፡ ዘሎ ፡ ሥርዐተ ፡ ዘዓመታት ። ጌግዩ ፡ በስካር ። አበሱ ፡ ወጌገዩ ፡ (ራእ ፡ ባሮ ። ክፋ ፡ ፯ ። ሚራ፵፰ ፡ ፯) ።

**ጌጋዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤** የሚስት ፡ የሚሳሳት ፡ ተሳሳች ፡ አጥፊ ፡ በዳይ ።

**ጊጉይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ጊት) ፤** የሳተ ፡ ስሑት ፡ አሳጥቂ ፡ በደለኛ ፡ ኃጥእ ። ብእሲ ፡ አብድ ፡ ወጊጉይ ። ጊጉይ ፡ ውእቱ ። ምስለ ፡ ጊጉያን ፡ ተኈለቈ ፡ (ሚራ ፲፯ ፡ ፳፫ ። ፲፱ ፡ ፪ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ።

**ጌጋይ ፤ (ያት) ፤** ስሕተት ፡ በደል ፡ ወንጀል ፡ ኀጢአት ፡ ክፋት ። ዐስበ ፡ ጌጋይ ። ምንት ፡ ጌጋይየ ። ኢይመውቱ ፡ አበው ፡ በጌጋየ ፡ ውሉዶሙ ። መጽሐፈ ፡ ጌጋዩ ። በጌጋየ ፡ ልቦሙ ፡ (ይሁ ፡ ፲፩ ። ኢር፲፭ ፡ ፲ ። ፀሐን ፡ ፲፬ ፡ ፯ ። ማር፲፭ ፡ ፳፯ ። ኢር፳፫ ፡ ፲፮) ።

**አጌገየ ፤** አሳተ ፡ ኀጢአት ፡ አሠራ ። ያስሕት ፡ ወያጌጊ ፡ (ቲቶ፫ ፡ ፲፩) ።

**አንጌገየ ፤ (አንጎገወ) ፤** አዞረ ፡ አባከነ ፡ አቅበዘበዘ ። ዞረ ፡ ባከነ ፡ ተቅበዘበዘ ። ታንጌጊ ፡ በገዳም ። እንዘ ፡ ትንጌጊ ፡ ውስተ ፡ መራዕይ ። እንጌገዩ ፡ ውስተ ፡ ኢድባር ። አንጌገዩ ፡ ፍኖተ ፡ በዳ ። ኢያንጌግዩ ፡ ለፌ ፡ ወለፌ ፡ ከመ ፡ ሐመር ፡ ዘይዘብጥዋ ፡ መዋግድ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፯ ። ማሕ፩ ፡ ፯ ። ዲድ ፡ ፲፪ ። ሰንክ ፡ ጥር፪ ። ቀሌ) ።

**እንጊጉይ ፤** የባከነ ፡ ብኩን ፡ ብኩንኩን ፡ በካና ፡ እንዙገዝ ፡ ቅብዝብዝ ።

**እንጌግይ፤ (ያት)፤** ብክነት ፡ ዙረት ፡ እንባዜ ፡ ቅብዝብዝታ ፡ ቅብዝብዝነት ። ጸሎት ፡ ዘእንበለ ፡ ፀር ፀት ፡ ወኢእንጊግይ ፡ (ፊልክ ፡ ፬ ። ፲፫) ።

**ገዪድ፤ ዶት፤ (ጌደ ፡ ይገይድ ፡ ይጊድ ። ዐረ ፡ ጀይድ፤ ጃደ፤ በረታ)፤** መፍጠን ፡ መሮጥ ፡ መፈርጠጥ ፡ መበርታት ።

(ጥይ) **ገይድ፤ (ዳን)፤** ቅጽል ። ብርቱ ፡ ፈጣኝ ፡ ፈጣን ፡ ሯጭ ፡ ፈርጣጭ ። ፈረስ ፡ ገይድ ፡ ከመ ፡ ዐርክ ፡ ኀር ። ወገይዳን ፡ ከመ ፡ አንተ ፡ ወይጠሉ ፡ (ሚራፅ፳ ፡ ፳ ። ፩ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፳) ።

**አስተጋየደ፤** አፋጠነ ፡ አሯሯጠ ፡ (ሸምጥ ፡ አ ስጋለበ) ። አስተጋይዶ ፡ ፈረሰከ ፡ (ደራሲ) ።

**ጐይይ፤ ዮት፤ (ጐየ፤ ጐየየ ፡ ይጐ ይይ ፡ ይጐየይ ። ዕብ ፡ ጎይ፤ ሕዝብ)፤** መሸሽ ፡ መኰብለል ። መራቅ ፡ መሰደድ ፤ ከሱበት ፡ ከነበሩበት ፡ መጥፋት ፡ መታጣት ፤ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ መኼድ ፡ መ ጠጋት ፤ ሕግን ፡ ባንዲራን ፡ መለወጥ ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ መ ኾን ፡ መባል ። ፈለሰን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ጐየ ፡ እምገጹ ፡ ዔሳው ። ከመ ፡ ዘይጐይይ ፡ እምአርዌ ፡ እኩይ ፡ ከማሁ ፡ ጐየይ ፡ እምኀጢአት ። ጐዩ ፡ እማ እከለ ፡ ባቢሎን ። ወአይቴ ፡ እጐይይ ፡ እምቅድመ ፡ ገጽከ ። ጐየይ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ (ኩፉ ፡ ፴፭ ። ሢራ፳፩ ፡ ፪ ። ኤርም፳፰ ፡ ፮ ። መዝ ፡ ፻፴፰ ። ማቴ፪ ፡ ፲፫ ። ፲ ፡ ፳፫) ።

**ጐያዪ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት፤ የይት)፤** የሚሸሽ ፡ ሸሺታ ፤ ኰብላይ ፤ ፈሪ ፡ ደንባሪ ፤ ሯጭ ፡ ፈር ጣጭ ፤ ዐመለኛ ። ጐያዩ ፡ ከዊኖ ። ብእሲ ፡ ጐያዩ ። እ ንስሳ ፡ ጐያዩ ፡ (ቂር ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፫ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ን ፡ ፴፫ ፡ ፫ ። ፵) ።

**ጐዩይ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ይይት)፤** የሸሸ ፡ የ ራቀ ፡ የኰበለለ ። ተረክቡ ፡ ጐዩያነ ፡ እምሥርዐት ፡ መላእክት ፡ (አዋል) ።

**ጐየት፤** መሸሽ ፡ መኰብለል ፤ ሽሽት ፡ ኰብለላ ፡ ስደት ፡ ሩጫ ፡ ፍርጠጣ ። ይዲዕሉ ፡ ጐየቶ ፡ እለ ፡ ኢየ አምኑ ፡ ትስብእቶ ። ነጽር ፡ ከመ ፡ ጐየተ ፡ ሕፃን ፡ አጐ የዮ ፡ ለዲዮብሎስ ፡ (ተረ ፡ ቄርሎ) ።

**ጐያ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ሽሽት ፡ ስደት ፡ ኰብለላ ፡ (ማቴ፳፬ ፡ ፳ ። ኢሳ፶፪ ፡ ፲፪) ። ይከውን ፡ ዐቢይ ፡ ምን ዳቤ ፡ ወጐየ ፡ ወክዕወተ ፡ ደም ። ዑቁ ፡ በሰንበት ፡ ኢይኩን ፡ ጐያክሙ ። ጐያከ ፡ እምቤተ ፡ ልሔም ፡ ደብረ ፡ ቍስቋም ፡ (ኪዳ ። ድጓ ። አዋል) ።

**ጐያ፤** በቁሙ ፡ የጭንና ፡ የጭን ፡ መካከል ፡ የ ሕፃን ፡ መሸሻ ፡ መደበቂያ ። የናት ፡ ጐያ ፡ እንዲሉ ።

**ጓያ፤** በቁሙ ፡ የታወቀ ፡ ያበባ ፡ እኽል ፡ እግ ሮኝ ፡ ከጕልበት ፡ በታች ፡ የሚሰብር ፡ የሚያወጣምድ ፡ የሚያስነክስ ፡ የሚያሽመደምድ ። (ተረት) ፤ አህያና ፡ ጓያ ፡ ባምሳያ ።

**አጐየየ፤ (ገባሪና ፡ አግባሪ)፤** አሸሸ ፡ አ ራቀ ። (ጥሸ) አሸሸ ፡ አሰደደ ፡ አሳደደ ፡ አባረረ ። አመ ፡ ንእሱ ፡ አጐየየቶ ፡ እሙ ፡ እስከ ፡ ምድረ ፡ ግብፅ ። ኢ ትንሥኡ ፡ ቤዛ ፡ ከመ ፡ ታጐይይዎ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ምስካይ ። እቀም ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአጐይዮሙ ፡ ለሕ ዝብ ፡ እለ ፡ ምስሌሁ ። አጐየዮ ፡ ለንዋም ። ወአጐየ ዮሙ ፡ ከመ ፡ ፋጺተ ፡ ሀየል ፡ (አፈ ፡ ድጓ፰ ። ዘኍ፴፭ ፡ ፴፪ ። ፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ የካ፳፱ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**አጐያዪ፤ መጐይይ፤** የሚያሸሽ ፡ የሚያርቅ ፡ የሚያስርቅ ።

**ምጕያይ፤ (ያት)፤** መሸሻ ፡ መጠጊያ ፤ መማ ጠኛ ፡ የሙጥኝ ፡ መባያ ። ምጕያዩን ፡ ለግሔ ። ኮንከኒ ፡ ምጕያየ ፡ (መዝ ፡ ፻፫ ። ኪዳ) ። ጕያ ፡ ጕየት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ምጕያይ ፡ ይላል ፡ (ናሆ፫ ፡ ፱) ።

**ገዪም፤ ሞት፤ (ጌመ ፡ ይገይም ፡ ይ ጊም ። ዐረ ፡ ዓመ)፤** መጎም ፡ መዳመን ፤ ደመና ፡ መልበስ ፡ በጉም ፡ መታፈን ፡ መሸፈን ፤ መሞኘት ፡ ማስ ገምገም ፤ ማስተጋባት ፤ የስማይና ፡ የቀራሬ ። ገመገም ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ፤ ጕሀንን ፡ እይ ።

**ጊሜ፤ (ዐረ ፡ ዐይም ። ሱር፤ ዓይማ)፤** ጉም ፡ ብዙ ፡ ደመና ፤ ከምድር ፡ ወርዶ ፡ ተራራ ፡ ኰረ ብታ ፡ የሚሸፍን ፤ ወዝ ፡ ለወዝ ፡ የሚጕተት ፡ የቀን ፡ ጨለማ ። ከመ ፡ ጊሜ ፡ ከደንከዋ ፡ ለምድር ። ወረ ሰየ ፡ ላቲ ፡ ደመና ፡ ልብሳ ፡ ወበጊሜ ፡ ጠብለላ ። ወከ ደኑ ፡ ርእሰ ፡ ደብር ፡ በጊሜ ፡ ወጢስ ፡ (ሚራ፵፬ ፡ ፫ ። ኢዮ፴፰ ፡ ፱ ። ውዳ ፡ ማርያ) ።

—፤ ብትን ፡ በረዶ ፤ ውርጭ ፤ ጠል ፡ ካፊያ ። በረድ ፡ ወ ጊሜ ። ይዘርዎ ፡ ለጊሜ ፡ ከመ ፡ ሐመድ ። ከመ ፡ ጊሜ ፡ ውስተ ፡ ፀምር ። ወፈውሰ ፡ ሾሉ ፡ ፍጠሩ ፡ ጊሜ ፡ (ዳን፫ ፡ ፷፱ ። መዝ ፡ ፻፵፯ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፪ ። ሚራ፵፫ ፡ ፳፪) ።

**ጉማ፤** ታላቅ ፡ ጩኸት ፡ ጉህና ፡ ተመማ ፡ የ ብዙ ፡ ሰው ፡ ዚማ ። ገብርኤል ፡ ዘራማ ፡ አዕራጊ ፡ ስብ ሐት ፡ በጉማ ። ጉማ ፡ ቃሎሙ ፡ ሐዋዝ ፡ ወጥዑም ። ይመልእ ፡ ሾሎ ፡ ቤተ ፡ ዕበየ ፡ ጉማ ፡ ቃሎሙ ፡ (ደ ራሲ ። ሚራ፵፮ ፡ ፱ ። ፶ ፡ ፲፰) ። በቁሙ ፤ የንፍስ ፡ ዋጋ ፤ ደውም ፡ የቀነድ ፡ ከብት ፡ የገዳይ ፡ ወገን ፡ ቀንበር ፡ ተ ሸክሞ ፡ እግዚኦ ፡ እያለ ፡ ለሟች ፡ ወገን ፡ የሚሰጠው ፡ ካሳ ። ገመገመ ፡ ማምጋሚ ፡ ማለት ፡ ከጉማ ፡ የወጣ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ሮጎራኝና ፡ ስውጥ ፡ ያሳያል ።

**ጉምጉማ፤ (ትማ ፡ ሐበ)፤** ርኩም ፡ አፈ ፡ ረ ኾርም ፡ ከንፈ ፡ ውኾርምኾርም ፡ ድምቡ ፡ እንደ ፡ ከበሮ ፡ የሚተም ፤ እንደ ፡ ነጋሪት ፡ የሚጕሰም ፤ እንደ ፡ ሰማይ ፡ የሚያስገመግም ።

**ማዮን፤ (ጽር ፡ ጌዖን ። ዕብ ፡ ጊሖን)፤** ስመ ፡ ፈለግ ፤ ከራቱ ፡ ፀበይት ፡ አፍላጋት ፡ ኹለተኛው ፡ ወንዝ ፡ ነጭ ፡ አባይ ፤ ከአፍሪቃ ፡ ደቡብ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ አገር ፡ የሚፈስ ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፲፫) ። ነቂን ፡ ባለጊዎግራፎች ፡ ፯ ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ ይሉታል ፡ ው ሃው ፡ ነጭ ፡ ኒል ፡ ስለ ፡ መሰለ ፡ ነጭ ፡ አባይ ፡ ይባላል ፤ የአባይን ፡ ፋኙ ፡ ተመልከት ። ጊሖን ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ዘየ

ሐውር ፡ በኀይል ፡ ወይርዕም ፡ ወድምፀ ፡ ማዩ ፡ ዐቢይ ፡ ወግሩም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የውሃውን ፡ ብዛት ፡ የመልክውን ፡ ስፋት ፡ ያከኼዱን ፡ ኀይል ፡ የፏፏቴን ፡ ግርማ ፡ ፏፏቴውንና ፡ ተመማውን ፡ ድምጡ ፡ እንደ ፡ ነጐድጓድ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ። ከአፍሪቃ ፡ ወንዞች ፡ ተለይተው ፡ ነጭ ፡ ኒል ፡ ጥቍር ፡ ኒል ፡ የሚመስለው ፡ በአፊትም ፡ ግዮን ፡ ኤፌሶን ፡ የሚባሉ ፡ ነጭ ፡ አባይና ፡ ጥቍር ፡ አባይ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። እሊህም ፡ ኹለቱ ፡ ወንድማማች ፡ ወንዞች ፡ ከየምንጮቻቸው ፡ በኀይል ፡ ተንሥተው ፡ ግርማቸውን ፡ ለብሰው ፡ ተሰልፈው ፡ በየፊታቸው ፡ ያለውን ፡ ሐይቅ ፡ እንደ ፡ መርከብ ፡ ሠንጥቀው ፡ ዐልፈው ፡ ስራዊታቸውን ፡ ከግራና ፡ ከቀኝ ፡ አስከትተው ፡ እንደ ፡ ኹለት ፡ ንጉሥ ፡ ከርቱም ፡ ሲገናኙ ፡ ኹለትንታቸው ፡ ይቀርና ፡ አንድ ፡ ወንዝ ፡ ብቻ ፡ ይኾናሉ ፤ ከከርቱም ፡ ደግሞ ፡ እስከትበራ ፡ ወርደው ፡ ከተከዚ ፡ ጋራ ፡ ይገጥማሉ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የሌላ ፡ ወንዝ ፡ ውሃ ፡ ሳይጨምሩ ፡ ባንድነት ፡ መላ ፡ ምድረ ፡ ግብጽን ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ አጠጥተው ፡ አጥግበው ፡ አርክተው ፤ ዐልፈው ፡ ተርፈው ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ጕርፈው ፡ ሜዲተራኒ ፡ ከሚባለው ፡ ከታላቁ ፡ ባሕር ፡ ይገባሉ ።

**ግዮን** ፤ የየሩሳሌም ፡ ወንዝ ፤ በሲሖም ፡ ስሎሞን ፡ የነገሠበት ፤ ከከተማዪቱ ፡ በስተደቡብ ፡ ያለ ፡ (፫ነገ ፡ ፩ ፡ ፴፫ ። ኢሳ፰ ፡ ፮) ።

**ገዩሥ ፤ ሦት ፤ (ጌሠ ፡ ይገይሥ ፡ ይጊሥ ። ዕብ ፡ ጋየስ ፤ ሰበሰበ)** ። (ጥስ) መሰብሰብ ፡ መከተት ፤ መሰለፍ ፡ ለጦር ፡ ለመንገድ ፡ መዘጋጀት ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መገዘመት ፡ መገሥገሥ ፤ ማልደ ፡ መኼድ ፡ ከነግህ ፡ አስቀድሞ ፡ ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ ወይም ፡ ደሮ ፡ ሲጮኽ ፡ መነሣት ። **ገዩሥክሙ ፡ በጽባሕ ። አሌሊያ ፡ ገዩሥ ። በሌሊት ፡ ትገይሥ ፡ መንፈስየ ፡ ኀቤከ ። ነቂሀ ፡ እምንዋም ፡ ንጊሣ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን** ፡ (ዘፀ ፲፬ ፡ ፳፯ ። ሉቃ፳፬ ፡ ፩ ። ኢሳ፳፮ ፡ ፱ ። ድጓ) ። ገሥገሡን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ድርብ ፡ ነው ።

**ገያሢ ፤ (ሢት ፡ ሥያን ፡ ያት)** ፤ የሚገሠግሥ ፡ ገሥጋሽ ፤ ማላጅ ፡ ማለዳ ፡ ኻያጅ ። (ተረት) ፤ ገበያ ፡ ሳርፋጅ ፡ ቤተ ፡ ክሲያን ፡ ለማላጅ ።

**ጋይሥ ፤ (ብ ፡ አጋይሥ)** ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፤ እንግዳ ፡ መንገደኛ ፤ ዐድሮ ፡ ኻያጅ ፡ ገሥጋሽ ፡ (ትግሬ) ።

**ጊሠት** ፤ መገሥገሥ ፤ አገሣገሥ ፡ ገሥጋሽነት ፡ ግሥገሣ ፡ ማለዳ ።

**አጌሠ** ፤ አገሠገሠ ፤ አስገሠገሠ ፡ አማለደ ፡ አስማለደ ፡ ማለዳ ፡ ወሰደ ። **አመ ፡ ያገይሥዋ ፡ ለታቦት ፡ ካህናት ፡ አግብእዋ ፡ ውስተ ፡ መካና ። እስከ ፡ አመ ፡ ያገይሥዎ ፡ ኀበ ፡ እስራኤል ። ኢርኩስ ፡ ኀሪስኪ ፤ በምንትኪ ፡ አጌሥኪዮ ፡ ለፍሬ ፡ ቅድሳት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ** ፡ (ድጓ ። ሉቃ፩ ፡ ፹ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ጌሠም ፤ (ዕብ ፡ ጌሸም ፤ ብርቱ ፡ ዝናም)** ፤ ነገ ፡ ቢት ፡ ማለዳ ፡ ከርሞ ፡ ሳመት ። **እስከ ፡ ጌሠም ። ጌሠመ ፡ ዘ ፡ ጊዜ ። ጌሠመ ፡ ንመውት ። አኮ ፡ ዮም ፡ ወአንተ ፡ ጌሠም ። ኢትትከዘ ፡ ለጌሠም ፡ እስመ ፡ ጌሠምሰ ፡ ትኄሊ ፡ ለርእሳ** ፡ (፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፲፰ ። ዘፀ፲፫ ፡ ፲፬ ። ሢራ፲ ፡ ፲ ። ፴፰ ፡ ፳፱ ። ማቴ፮ ፡ ፴፬) ። ጌሠም ፡ እንደ ፡ ዮምና ፡ እንደ ፡ ትማልም ፡ ጕልት ፡ ነው ፤ አይፈልስም ፤ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ጌሠመ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ።

**ጋይጸ ፤ ጸት ፤ (ጋየጸ ፡ ይጋይጽ ። ግእዘ)** ፤ መንቀፍ ፡ መስደብ ፡ መገደር ፤ መናቅ ፡ ማጥቃት ፡ ማስጨነቅ ፡ ማስቸገር ። ማጌጥ ፡ መጊጥ ፤ መልበስ ፡ መሸለም ፤ መፀረር ፡ ማማር ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ መኰራት ፡ መታበይ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጋየጸ ፡ ፈንታ ፡ ተጋየጸ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። **እጸልእ ፡ ጸላኢከ ፡ ወእትጋየጽ ፡ ዘይትጋየጸከ ። ይትጋየጽ ፡ ጎረ ፡ ቤቱ** ፡ (ዘፀ፳፫ ፡ ፳፪ ። ኢዮ፳፯ ፡ ፳፫) ። **አይቴ ፡ ሀለዉ ፡ እለ ፡ ይትጋየጹ ፡ በሥን ፡ ወበላሕይ ። ኢርቱዕ ፡ ንትዐበይ ፡ ወንትጋየጽ ፡ በምንትኒ ፡ እምግብር** ፡ (ማንዘ ። አፈ ፡ ተ፪) ።

**ተጋየጸ ፤ (ተደራጊና ፡ ተደራራጊ)** ፤ ተነቀፈ ፤ ተናቀ ። ተነቃቀፈ ፡ ተናናቀ ፡ ተገዳደረ ። ተጊያጊያጠ ፡ ተሸላለመ ። ርስ ፡ በርስ ፡ ወይም ፡ በገዛ ፡ እጅ ።

**ጋይጽ ፤ ጌጽ** ፤ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ ልብስ ፡ መሣሪያ ።

**ጕየጸ ፤ (የጌገየና ፡ የጕየ ፡ ጎር)** ፤ ሳተ ፡ ለቀቀ ፡ የሕፃን ፡ የድውይ ። ሽሽ ፡ አመለጠ ፤ ያይን ፡ ምድር ፡ የፈስ ፤ ፈሳ ፡ ሽሽ ፡ እንዲሉ ። ፈሰወን ፡ ተመልከት ።

**ገይሮ ፤ ሮት ፤ (ገየረ ፡ ይጌይር ፡ ይገይር ። ዕብ ፡ ጋየር)** ፤ በፍቅር ፡ በትምርት ፡ መሳብ ፡ ማቅረብ ፡ ማስጠጋት ፤ አሕዛብን ፡ ከጣዖት ፡ ማፍለስ ፡ በአሪት ፡ ማሳመን ፤ መግዘር ፡ ይሁዲ ፡ ማድረግ ።

—፤ ኖራ ፡ ማውጣት ፤ በኖራ ፡ ሺቃ ፡ መምረግ ፡ መለሰን ፡ መቅባት ፡ መለቅለቅ ። ገብሰሰን ፡ እይ ። **እሰ ፡ ገየርዋ ፡ ለአረፍት ። ከመ ፡ አረፍት ፡ እንተ ፡ ገየሩ** ፡ (ሕዝ፲፫ ፡ ፲፭ ። ኢሳ፲፮ ፡ ፲፩) ።

**ገያሪ ፤ መገይር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት)** ፤ አቅራቢ ፡ አስጠጊ ፤ ይሁዲ ፡ አድራጊ ። ኖራ ፡ አውጪ ፡ ሸያጭ ፡ ለሳኝ ፡ ቀቢ ፡ ለቅላቂ ። **ለመገይራን ፡ ወለወቀርተ ፡ እብን** ፡ (፬ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪) ።

**ጊር ፤ (ዕብራ ። ዐረ ፡ ጀይር)** ፤ ዐዲስ ፡ ትኩስ ፡ ኖራ ፡ ውሃ ፡ ያልነካው ፡ እሳቱ ፡ ያልጠፋ ፡ ያልበረደ ።

**ተገየረ ፤ (ዕብ ፡ ሂትጋየር)** ፤ ወደ ፡ አይሁድ ፡ መጣ ፡ ተጠጋ ፤ ይሁዲ ፡ ኾነ ፡ በአሪት ፡ አመነ ፤ የሀደንና ፡ ተይሀደን ፡ እይ ። ተለሰን ፡ ተቀባ ፤ ተለቀለቀ ።

**ግዩር ፤ (ዕብ ፡ ጌር ። ሱር ፡ ጊዮራ)** ፤ መጤ ፡ መጣተኛ ፡ ስደተኛ ፤ ከገሩ ፡ ከሕጉ ፡ የፈለሰ ፡ ፈላሻ ፡ የአይሁድ ፡ ጥገኛ ፤ በአሪት ፡ ያመነ ፡ ግዙር ። **አሐዱ ፡ ሕግ ፡ ይኩን ፡ ለክሙ ፡ ወለግዩር ፡ ዘማእከሌክሙ ። ግዩራን ፡ ወፈላስያን** ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፵፱ ። ዘሌ፳፭ ፡ ፳፫) ።

—፤ የተለሰን ፡ ልስን ፤ ቅብ ፡ ልቅልቅ ።

**ግያሬ** ፧ ኖራ ፡ አወጣጥ ፡ አሰሳሰን ፤ ልስና ፡ ልቅ ሰቃ ።

**ግይርና** ፧ ስደት ፤ ስደተኛነት ፡ ፈላሽነት ፡ (አ ርጋ) ።

**ጌራ** ፧ **(ብ ፡ ጌራት)** ፧ ቍርዐ ፡ ቍር ፤ ቦርቦ ርቴ ፡ የራስ ፡ ጋሻ ፡ ከወፍራም ፡ ቈርበት ፡ የሚሠራ ፡ ሳዩ ፡ ብረት ፡ ውስጡ ፡ ቈርበት ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የሚለበስ ፡ (፩ተሰ ፡ ፭ ፡ ፰ ። ኤፌ፮ ፡ ፲፯ ። ራእ፱ ፡ ፱ ፡ ፲፯) ። ጌራ ፡



ጌራ ።

መድኀኒት ። ጌራተ ፡ ኀጺን ፡ (ኢሳ፶፱ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ ሐም፲፰) ። የራስ ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፡ ራስ ፡ ወርቅ ፤ ሜትራ ፡ ዘውድ ፡ አክሊል ፡ ኵፌት ፡ ቆብ ፡ ባርኔጣ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ክበበ ፡ ጌራ ፡ ወርቅ ፡ ጽሩይ ። ተቀጸለ ፡ ጌራ ፡ ዐቢየ ፡ ደቢ ፡ ርእሱ ፡ አሕዲጾ ፡ ጌራ ፡ ክህነት ፡ ቅዱስ ። ወገብሩ ፡ ደበ ፡ ርእሱ ፡ ጌራ ፡ ንጉሥ ፡ ወውስተ ፡ እ ዴሁ ፡ በትረ ፡ ወርቅ ። ወያአትቱ ፡ ጌራቲሆሙ ፡ እም ርእሶሙ ፡ (ደራሲ ። ዮሴፍ ። ሕዝ፳፮ ፡ ፲፮) ።

**ጌራ** ፧ **(ዕብ ፡ ጌራህ)** ፧ የገንዘብ ፡ ስም ፤ ታ ናሽ ፡ ግርሽ ፡ የሰቅል ፡ ኻያኛ ፤ የእበሊ ፡ እኩያ ። ወሰቅል ፡ ዕሥራ ፡ ጌራ ፡ (ሕዝ፵፭ ፡ ፲፪) ።

**ጌርዮስ** ፧ **(ጽር ፡ ኪርዮስ)** ፧ እግዚእ ፤ እ ግዚአብሔር ፡ (ቅዳ) ።

**ጌሰ** ፧—**ገሥገሠ** ፧—**ገዪሥ** ፡ **ጌሠ** ።

**ጋይስ** ፧ **(ጽርእ ። ዕብ ፡ ኪዶን)** ፧ ጦር ፡ ዘ ገር ፡ የሚወረወር ፤ ዐጭር ፡ መጠነኛ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሳማርኛ ፡ ስለ ፡ ቀረበ ፡ ጋሻ ፡ ይሉታል ። አልዐል ፡ እዴክ ፡ በጋይሶ ፡ (ኢያ፰ ፡ ፲፰) ። ቢደንን ፡ እይ ።

**ጌተ** ፧ **(ይገይት ፡ ይጊት ፧ ገዪት ። ገዝአ)** ። ጌተየ ፡ ጌታ ፡ ኾነ ፡ ተባለ ።

(ጥ) **ጎት** ፧ **(ትግሬ)** ፧ ብዕል ፡ ሀብት ፤ ጌትነት ።

**ጌት** ፧ ስመ ፡ ሀገር ፤ የኢሎፍሊ ፡ ክፍል ። ፈለ ስት ፡ ታቦተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ጌት ፡ (፩ነገ ፡ ፭ ፡ ፰) ። ሴት ፡ ጌትያዊ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፪) ።

**ጋሌ** ፧ **(ጽር ፡ ጋሊ ። ዕብ ፡ ሖሌድ)** ፧ ፋሮ ፡ ፋደት ፤ መጠማጥ ፡ የዱር ፡ ድመት ፤ ሽላ ፡ ሙጭ ሙጭላ ፤ ደሮ ፡ የሚያድን ፡ የሚበላ ፤ መሬት ፡ የሚፍር ፡ የሚቈፍር ፤ ቃናሽ ፡ ክፉ ፡ አውሬ ። ዐይነቱና ፡ ስሙ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ፪ ፡ አፍ ፡ ያለው ፡ እባብ ፡ ይሉታል ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፴) ።

**ግላ** ፧—**ጨለማ** ፧—**ገሊው** ፡ **ገለወ** ።

**ጎል** ፧—**በረት** ፧—**ገዊል** ፡ **ጎለ** ።

**ገልእ** ፧—**የሸክላ** ፡ **ስባሪ** ፧—**ገሊዕ** ፡ **ገ ልዐ** ።

**ገሊብ** ፧ **ቦት** ፧ **(ገለበ ፡ ይገልብ ፡ ይግ ልብ ። ዐረ ፡ ጀለበ ፧ ሳበ)** ፧ ማጥመድ ፤ መቃጥን ፡ መስደድ ፡ መረብ ፡ መንዛት ፤ መሳብ ፡ መጐተት ፤ መግ ለብ ፡ መሥራት ፤ ያሣ ፡ ወጋሪ ። እንዘ ፡ ንገልብ ፡ (ኪዳ) ። መግለብ ፡ መግለጥ ፤ የንፍረት ፡ የቁጥ ። መሸሽ ፡ መሮጥ ፤ መጋለብ ፡ ማምለጥ ፤ መዘራት ፡ መበተን ፡ መቅለል ፡ መ ንጓለል ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ መኾን ፤ የገለባ ።

**ገለብ** ፧ **መግለብ ፡ ት** ፧ መቃጥን ፡ መንጠቆ ፡ መግለቦ ፡ ዘረ ፡ መትር ፡ ያሣ ፡ ወጥመድ ፡ መያዣ ፡ መጋ ፈሪያ ። ከመ ፡ በመግለብት ፡ ወበመዋቅሕት ፡ ኀጺን ፡ ተሐውር ፡ (ዕር ፡ ኢሳ፫ ፡ ፯) ። ጀልባ ፡ ታንኳ ፡ ፍልካ ፡ ዓሣ ፡ ወጋሮች ፡ የሚቀመጡበት ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በገለብ ፡ ፈንታ ፡ ጌልያ ፡ ብሎ ፡ መርከብ ፡ ይላል ። ገለባ ፡ ኀፋሽ ፡ እንጕላይ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ገለብ** ፧ **(ትግሬ)** ፧ ጋሻ ፡ ዐጋም ፡ በግሬ ፡ የሚ ያገዘ ፡ የሚነገብ ፡ አሳባሽ ፡ አግሬ ።

**ገለባት** ፧ ዠማ ፡ ነጋዴ ፡ ቅፍለት ፤ ማኅበር ፡ ኹሉም ፡ አጋሰሱን ፡ ጭነው ፡ እንደ ፡ ጕርፍ ፡ የሚኼድ ፡ የሚ ያረብድ ።

**አግለበ** ፧ አሸሸ ፤ አባረረ ። ገለባ ፡ አወጣ ፡ አን ለበ ፡ አንጓለለ ። አስገለበ ፡ አስገለጠ ።

**አግላቢ** ፧ **መገልብ** ፧ **(ብት ፡ ባን ፡ ባት)** ፧ የሚያሸሽ ፡ አባራሪ ፤ ዓሣ ፡ ወጋሪ ። መግለቦ ፡ ሠሪ ፤ ገለባ ፡ አውጭ ። መጸብሓዊ ፡ ወመገልብ ፡ (መቅ ፡ ወን) ።

**ገልበበ** ፧ **(ቀቀ ፡ ግ ። ዐረ ፡ ጀልበበ ፧ ገለወ)** ፧ ሸፈነ ፡ ከደነ ፤ አለበሰ ፡ አከናነበ ፤ ጋረደ ፤ ለበጠ ፡ መረገ ፤ ለሰነ ፡ ቀባ ። ገልበቡ ፡ ርእሶሙ ። ይገልብብ ፡ አፉሁ ። ይገለብብዎ ፡ ገጾ ። ሥብሕ ፡ ዘይገለብብ ፡ ከርሦ ። ዘይገለብቦ ፡ ለሰማይ ፡ በደመና ። ወገል በቡ ፡ ኵሎ ፡ ዘውስቴቱ ፡ እምዕፀ ፡ በነፍጥ ፡ ብዙኀ ። ገልበበታ ፡ ለንፍቅ ፡ ፒሳ ፡ (ኢር፲፬ ፡ ፬ ። ዘሌ፫፡ ፡ ፵፭ ። ሉቃ፳፪ ፡ ፷፬ ። ዘፀ፳፱ ፡ ፳፪ ። መዝ ፡ ፻፵፯ ። ዮሴፍ ። ኩፋ ፡ ፵፯) ።

**ገልባቢ** ፧ **መገልብብ** ፧ የሚሸፍን ፤ ከዳኝ ፡ አልባሽ ፡ ጋራጅ ፡ አከናናቢ ።

**ተገልበበ** ፧ ተሸፈነ ፡ ተከናነበ ፤ ተሰወረ ፡ ተደ በቀ ፤ በልብስ ፡ ባለባበስ ። ተገልበበት ፡ ገጻ ። ክዳን ፡ በዘይትገለበቡ ፡ እምጠል ። አንስት ፡ ደናግል ፡ ኢይ ትገልበባ ፡ ርእሶን ፡ በቤተ ፡ ክር ፡ አላ ፡ ሥዐርቶን ፡ ያ ንጎ ። ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ እትገልበብ ፡ ወእባእ ፡ ው ስተ ፡ ቀትል ፡ (ዘፍ፴፰ ፡ ፲፭ ። ኢሳ፬ ፡ ፮ ። ኪዳ ። ፫ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፴) ።

**ግልቡብ** ፧ **(ባን ፡ ባት ፡ ብብት)** ፧ የተሸ ፈነ ፤ የተከናነበ ፡ ሽፉን ፡ ሽፍንፍን ። ግልቡብ ፡ ርእሱ ። እንዘ ፡ ግልቡባን ፡ ገጾሙ ። ብእሲ ፡ ዘግልቡብ ፡

ርእሱ ። ግልቡባት ፤ (፪ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፴ ። ሖሴ፲፫ ፡ ፱ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፶ ። ዲድ ፡ ፫) ።

**ግልባብ ፤ ቤ ፤ (ባብት ፡ ብያት)** ፤ መሸፈኛ ፡ መጋረጃ ፡ ልብስ ፡ ከዳን ፤ ከንብንብ ፡ ሠርመዲ ፡ ሻል ፤ የሐር ፡ የሻሽ ፡ መንዲል ፤ ጥላ ፡ ቀጸላ ። ከሥቲ ፡ ግልባቢኪ ፡፡ ነሥኡ ፡ ግልባብየ ፡፡ ከሠተ ፡ ግልባበ ፡ ገጹ ፡፡ ለብስት ፡ ግልባቤ ፡፡ ቀራንብት ፡ ሥዩማት ፡ እማንቱ ፡ ህየንተ ፡ ምስዋር ፡ ወግልባቤ ፡፡ እምሐሩረ ፡ መርቄ ፡ ወእምቍረ ፡ ሖሉ ፡ ምንዳቤ ፡ አክናፌክሙ ፡ ይኩናኒ ፡ ግልባቤ ፡፡ ግልባቡ ፡ (ኢሳ፶፯ ፡ ፪ ። ማሕ፭ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳ ። ኩፋ ፡ ፵፭ ። ደራሲ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፫ ። መስ፳፭) ።

**ጕልበተ ፤ (ትግ ፡ ግልበተ ፤ ገለበጠ)** ፤ በቁሙ ፤ ጕለበተ ፡ ጕልበታም ፡ ኾነ ፤ ፀየለ ፡ በረታ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጕልበት** ፤ በቁሙ ፤ ብርክ ፡ ኀይል ፡ ብርታት ፡ ጥንካሬ ። (ግጥም ፤ ፱ ፡ ደጃዝማቾች ፡ ሲዋጉ ፡ ትቢተኛው ፡ ድል ፡ ስለ ፡ ኾነ) ፤ አሳዋቂ ፡ ሰፊ ፡ ሱሪ ፡ አሳጥሮበት ፤ የደጃች ፡ እገሌ ፡ ጕልበቱ ፡ ታየበት ።

(ጥ) **ገልጎ ፤ ጎት ፤ (ገለገ ፡ ይጌልግ ፡ ይገልግ ። ዕብ ፡ ጋላግ)** ፤ ማጌጥ ፡ መሸለም ፤ መልበስ ፡ መፀረር ፤ መክናወን ፡ መበጃጀትና ፡ መዘጋጀት ፤ ወደ ፡ ሸንጎ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ወደ ፡ ሰርግ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክሲያን ፡ ለመኼድ ።

**እንገለገ ፤ (ያንጌልግ ፡ ያንገልግ)** ፤ ሰበሰበ ፡ አከማቸ ፡ ጉባኤ ፡ አቆመ ። ተሰበሰበ ፡ ተከማቸ ፤ ሸንጎ ፡ ከተመ ፤ ተጠራቀመ ፤ ዶለተ ፡ መከረ ። እንገለግኒ ፡ ፀቢየ ፡ እንግልጋ ፡፡ አንገለጉ ፡ ሖሉ ፡ ሕዝብ ፡ ባዕሊ ፡ ኤርምያስ ፡፡ ለምንት ፡ አንገለጉ ፡ አሕዛብ ፡ (ነሐ፭ ፡ ፯ ። ኤር፴ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፪ ። ዘኍ፲፮ ፡ ፲፫ ። ግብ፲፭ ፡ ፮ ። ፩ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፱) ።

**እንግልጋ** ፤ መሰብሰብ ፡ መከማቸት ፤ አሰባሰብ ፡ ስብሰባ ፡ ክምችታ ፤ ክምቹነት ። ሸንጎ ፡ ጉባኤ ፡ ማኅበር ፤ ብዙ ፡ ሰው ፤ የሰው ፡ መንጋ ፡ የሚንጋጋ ። ልቅሶኛ ፡ ሰርገኛ ፡ ገበያተኛ ፡ ቤተ ፡ ክሲያን ፡ ሳሚ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። እንግልጋ ፡ አሕዛብ ፡፡ ማእከለ ፡ ማኅበር ፡ ወእንግልጋ ፡፡ ሰላም ፡ ለክሙ ፡ ቅዱሳን ፡ እንግልጋ ፡፡ ምስለ ፡ ብዙኃን ፡ እንግልጋ ፤ ሀገረ ፡ ዳዊት ፡ ማርያም ፡ ዐፀጋ ፡ (ሚራ፳፯ ፡ ፳ ። ምሳ፭ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ መስ፫ ፡ ታኅ፳፰) ።

**ምንግላግ ፤ (ጋት)** ፤ መሰብሰቢያ ፡ መከማቻ ፤ ቦታ ። ምንግላጊሆሙ ፡ ለኢሎፍሊ ፡ (፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፭ ። ዮዲ፯ ፡ ፲፯) ።

**ገልገለ ፤ (ገሊል ፡ ገለ)** ፤ ገለገለ ፡ ገላገለ ፤ ለየ ፡ ነጠለ ፡ አላቀቀ ፤ የሰው ። ዘረገፈ ፡ ቀዳ ፡ ገለበጠ ፤ አጋባ ፡ ባዶ ፡ አደረገ ፤ የዕቃ ። ወገልገልዋ ፡ ለሙዳየ ፡ ምጽዋት ፡ (፪ዜና ፡ ፳፬ ፡ ፲፩) ።

**ገሊጋሊ** ፤ ገልጋይ ፡ ገላጋይ ፤ ዘርጋፊ ፡ ዘራፊ ፡ ወራሪ ፡ በርባሪ ።

**አገልገለ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ። አገልግል ፡ ግልጋሎ ፡ ጕልጓሎ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ተገልገለ ፤ (ዕብ ፡ ጋላህ)** ፤ ተማረከ ፡ ተዘረፈ ፤ ተበረበረ ። እስመ ፡ ገልገላ ፡ ተገልግሎ ፡ ትትገለገል ፡ (ዓሞ፭ ፡ ፭) ። ተዔውዎ ፡ ትዔወው ፤ ፈሊስ ፡ ትፈልስ ፤ ጠፊኦ ፡ ትጠፍኢ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ገልገላ ፤ ዕብ ፡ (ጊልጋል)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ መንኰራኵራት ፡ ማለት ፡ ነው ። እሊሁም ፡ በይሁዳ ፡ ክፍል ፡ ያሉ ፡ ፪ ፡ አህጉር ፡ ናቸው ፤ አንዲቱ ፡ የኢያሪሖ ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ፡ (ኢያ፭ ፡ ፱ ። ፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፯) ። ፪ኛዪቱ ፡ በኬብሮን ፡ ያለች ፡ (ዘዳ፲፩ ፡ ፴ ። ኢያ፲፪ ፡ ፳፫) ።

**ጌልጌል ፤ ጌልጌላ ፤ (ዕብ ፡ ጋልጌል ፡ ጋልጋል)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ መንኰራኵሮች ፡ የሠረገላ ፡ እግሮች ፡ ተሽከርካሪዎች ፡ ተንከባላዮች ፡ (ሕዝ፲ ፡ ፪ ፡ ፲፫) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ሰማይ ፡ ይሉታል ። ደመና ፡ ሰማይ ፡ ብርህት ፡ እንተ ፡ ይብልዋ ፡ ጌልጌላ ፡ (ደራሲ) ።

**ጐልጐታ ፤—ጎልጎታ ፤—ገዊል ፡ ጎለ ፤ ጎል ።**

(ጥ) **ገልዶ ፤ ዶት ፤ (ገለደ ፡ ይጌልድ ፡ ይገልድ ። ዕብ ፡ ጋላድ ፤ ገልድ ፡ ለበሰ)** ፤ መደጕስ ፤ ቈርበት ፡ ማልበስ ። ማንጠፍ ፤ መክፈፍ ፤ ዐልጋን ፡ መኻታን ፡ በገምንዲ ፡ በነት ፡ ወይም ፡ በስርፍ ፡ በሌሐፍ ፡ መሸፈን ፡ ማስጌጥ ። በቀጠንት ፡ ገለድኩ ፡ ምስካብየ ፡ ወዘር ቤታተ ፡ ነጸፍኩ ፡ (ምሳ፯ ፡ ፲፯ ። ዲድ ፡ ፱) ።

**ገላዲ ፤ መገልድ ፤ (ዲት ፡ ዳን ፡ ዳት)** ፤ የሚደጕስ ፡ ደጓሽ ፤ ቈርበት ፡ አልባሽ ፤ አንጣፊ ።

**ገልድ ፤ (ዕብ ፡ ጌሌድ ። ዐረ ፡ ጊልድ ። ሱር ፡ ጌልዳ)** ፤ ቈዳ ፡ ቈርበት ፤ ዠንዲ ፡ ነት ፤ ፀጥፍ ፡ ዳቦ ፤ ሌጦ ፡ እንቀልባ ፤ የባሕር ፡ ዐረብ ፤ ብራና ፡ ቅርፍት ፡ ዕዕ ።

**ገለድ ፤ (ትግሬ)** ፤ ኪዳን ፤ ሰላም ፤ ዕርቅ ፡ ፍቅር ፡ ስምምነት ፤ ቅርበት ፡ ልጽቀት ።

**ተገለደ** ፤ ተቈረበተ ፤ ቈርበት ፡ ለበሰ ፤ ተደጐሰ ።

**ግሉድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ልድ)** ፤ የተገለደ ፤ የለበሰ ፡ የተደጐሰ ። የተነጠፈ ፤ የተጌጠ ፤ ደጓሳ ፡ ወፍራም ።

**ተግሊድ ፤ (ዐረ ፡ ተጅሊድ)** ፤ ድጕሰ ፡ ድጕሰት ፤ አደጓጕስ ፤ አጠራረግ ፤ የድጕስ ፡ ሥራ ።

**መግለድ ፤ (ብ ፡ መጋልድ)** ፤ መድጕስ ፤ መደጐሻ ፤ የድጕሰት ፡ ዕቃ ፡ መጣሪያ ፤ ፲ ፡ ዐይነት ። ርእስ ፡ መድጕስ ፡ ፫ ። መሳቢያ ፡ የድጕሱ ፡ ኹሉ ፡ መከፈፊያ ፡ ፩ ። ዐይነ ፡ ርግብ ፡ ትንሽና ፡ ትልቅ ፡ ፪ ። ቀርን ፡ በግዕ ፡ ፩ ። የውሃ ፡ እናት ፡ ፩ ። ፍዋል ፡ ፈለግ ፡ ፩ ። ድሙር ፡ ፲ ። በነዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ፯ ። ጩምረው ፡ ፲፯ ፤ የሚሉ ፡ አሉ ፤ መደበኞቹ ፡ ግን ፡ ዘጠኝ ፡ ናቸው ፤ የቀረው ፡ ትርፍ ፡ ነው ።

**ገለዶ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ ቃላቅ ፡ ቢላዎ ፡ ካራ ፤ የበጎች ፡ ጠጕር ፡ መሸለቻ ፤ ቈርበት ፡ የሚቀፍ ፡ ቈዳ ፡ የሚቀድ ፤ የሰፌችና ፡ የፋቆች ፡ መጣሪያ ።

**ገሊው ፤ ዎት ፤** (ገለወ ፡ ይገሉ ፡ ይግሉ ። ገለበ ፤ ገለደ ) ፤ መጐልበብ ፡ መለጐም ፤ መሸፈን ፡ መጋረድ ፡ ማልበስ ፡ መለበጥ ፤ መጐስቈ ፡ የሰፌት ፡ መስጐም ፡ የባላፍ ፡ ደታሞ ፡ የክበሮ ፡ መሸፈን ፡ ማልበስ ፡ ሰኰሱ ፡ መለበጥ ፡ ክንጨት ፡ ክደንጊደ ፡ ለተሠሬ ፡ ለቤት ፡ ለማጥን ። ይገልዎሙ ፡ ልቦሙ ። ከመ ፡ ክበሮ ፡ ዘገለውዎ ። ገሞር ፡ ዘገለውዎ ፡ በቈጽለ ፡ ወርቅ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ። ይት ። መጽ ፡ ምስ ። ዘፀ ፲፯ ፡ ፴፫ ። ፫ነገ ፡ ፮ ፡ ፲፭) ።

**ገላዊ ፤ መግልው ፤** የሚጐልብ ፡ የሚሸፍን ፡ ጋራጅ ፡ ለባጭ ።

**ተገልወ ፤** ተሸፈነ ፤ ተጋረደ ። ዘሰሥቀ ፡ ጽልመት ፡ ተገልወ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ግልው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሉት) ፤** የተሸፈነ ፡ ሽፍን ፤ ጉልብ ፡ ልጉም ፡ ልብጥ ።

**ግልወት ፤** መሸፈን ፤ (ዋሽ)መሸፈን ፡ አሸፋፈን ፡ ሽፈና ፡ ልበጣ ። መሸፈኛ ፡ ሽፋን ፡ መጋረጃ ፡ ልባጥ ፡ ስሌዳ ። ግልወታ ፡ በወርቅ ። ለመ ፡ ፊዋዌ ፡ አወፈየ ፡ ሔርምደስ ፡ ዘሎ ፡ ንዋየ ፡ ግብፅሃ ፡ ሰደብተራ ፡ ለሥጠተ ፡ ኵዙሕ ፤ ወተመጢዋ ፡ ክነቶ ፡ ከመ ፡ ግልወተ ፡ ኀጺን ፡ (አዋል ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ግላ ፤** መሸፈኛ ፤ ጥቍር ፡ መጋረጃ ፤ ጨለማ ። ቀላይ ፡ ግላ ። አምሳለ ፡ ግላ ። ጽልመት ፡ ግላ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ግላ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ሕግ ፡ ብሉይ ፡ (ጥበ ፡ ጠቢ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ። አርጋ ፡ ፪ ። ፪ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯) ።

**ጕሎ ፤** ስመ ፡ ዕፅ ፤ ፍሬው ፡ ዘይት ፡ የሚኾን ፡ ቅባታም ፤ ሐኪሞች ፡ ለሆድ ፡ መፈወሻ ፤ ዐበዐቾ ፡ ለምጣድ ፡ ማሟሻ ፡ ፋቆች ፡ ለቈርበት ፡ ማራሻ ፡ ለማለስለሻ ፡ የሚኹት ፤ ዕንጨቱ ፡ ግብግ ፡ ውስጠ ፡ ክፍት ። (ተረት) ፡ የጕሎ ፡ ዘንግ ፡ የባሪያ ፡ ደግ ።

**ግላውቃ ፤ (ጽር ፡ ግላፍክ) ፤** ያሞራብም ፡ ጕጉት ፡ የቀን ፡ ዕውር ፡ የሌት ፡ ዐይን ፡ ብር ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ጣት ፡ አሞራ ፡ ይሉታል ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፲፯ ። ዘዳ ፲፬ ፡ ፲፭) ።

**ጐሊሕ ፤ ሐት ፤ (ጐልሐ ፡ ይጐልሕ ፡ ይጕላሕ ። ዕብ ፡ ጋሌሕ ። ትግ ፡ ገልሐ ፡ ላጨ) ፤** መጕላት ፡ መግዘፍ ፤ መታየት ፡ መገለጥ ፤ እንደ ፡ ልጩ ፡ ራስ ፡ መኾን ። የጥፈት ፡ የሥዕል ፡ የመልክእ ፡ ፊደል ፡ የነገር ፡ የምስጢር ፡ የድምፅ ፡ የቃል ።

**ጕሉሕ ፤ ጕልሕ ፤** በቁሙ ፡ የጕላ ፡ የተገለጠ ፡ ግልጥ ፡ ፈጽጥ ፡ የሚታይ ፡ የሚሰማ ።

**ጕልሓዊ ፤ (ትግ ፡ ጕልሓይ ። ዕብ ፡ ጋሉሕ) ፤** ላጬ ፡ ንፊጭ ፤ ራሱን ፡ ጽሕሙን ፡ ነፍረቱን ፡ የላጨ ፡ የነፈጨ ፡ መላጣ ፡ ቡሓ ፡ ጕዳ ፡ ራብ ፡ በዳ ፡ (ተረት) ፡ የሴት ፡ ላጩ ፡ የወንድ ፡ ነፊጩ ።

**ተጓልሐ ፤** ተጻራ ፡ ተቃበጠ ፡ ተዳለቀ ፡ ተዳሰቀ ፡ በግልጥ ። ወይም ፡ በስውር ፡ ነፍረት ፡ ለንፍረት ፡ ተጋለጠ ፤ ተገላለጠ ። ንፍረት ፡ ተናግሮ ፡ ብእሲተ ፡ ባዕድ ፡ ወኢትትጓልሓ ፡ ላቲ ፤ ወኢትቲጣ ፡ ለወለታ ፤ ወኢትቅረብ ፡ ኀበ ፡ ምስካቢ ፡ (ሚፍታሕ ፡ ፳፱) ።

**ጓልሕ ፤** ድሬ ፡ ቅንጥ ፡ የአፍኣ ። ወይም ፡ የውስጥ ፡ መግላለጥ ።

**አጕልሐ ፤** አጕላ ፤ አገዘፈ ፡ አስገለጠ ፤ አስረዳ ።

**ገልይ ፤ ዮት ፤ (ገለየ ፡ አው ፡ ገልየ ፡ ይገሊ ፡ ይግለይ ። ዕብ ፡ ጋላህ ፤ ገለጠ) ፤** መቀርረጥ ፡ መቈጥቈጥ ፡ መለየት ፤ መግለጥ ፡ መግፈፍ ፡ ማሳየት ፡ ራቍቱን ፡ ግንዱን ፡ መስመሳውን ፡ መቀው ፡ የዛፍ ፡ የሰው ። ይገልይዎ ፡ (ዮሐ፲፫ ፡ ፮) ።

**አግለየ ፤** አስቈረጠ ፡ አስገለጠ ፤ አስለየ ፡ አስታወቀ ፤ አገሌ ፡ አስኘ ፤ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ።

**እገሌ ፤ (ሊት ። ዕብ ፡ ፍሎኒ ። ሱር ፡ ፍላን ። ዐረ ፡ ፉላን) ፤** የስም ፡ ለውጥና ፡ ምትክ ፤ ህየንተ ፡ ስም ፤ በስም ፡ ፈንታ ፡ የሚነገር ፡ ቃል ። እከሌ ፤ እንቶ(ተ)ኔ ፤ እንትን ፡ ያ ፡ ርሱ ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ አንተ ፡ ሰውዬ ፤ ሰዊ ። እከሉ ፡ ታውቆ ፡ ስሙ ፡ ሳሊታውቀ ፡ ለተደበቀ ፡ ሀጸፋና ፡ በቂ ፡ እየኾነ ፡ ለሩቅም ፡ ለቅርብም ፡ ይነገራል ፤ እከለ ፡ በቃ ፡ ይላልና ፤ እከሌ ፡ ቅሉ ፡ እካሉን ፡ አካላዊነቱን ፡ ያሳያል ። ሰውዮውን ፡ ዐውቆ ፡ ስሙን ፡ ባለማወቅ ፡ ወይም ፡ በመደበቅ ፡ ስሙን ፡ ሳይጠሩ ፡ ግብሩን ፡ ለመግለጥ ፤ ሰውዮው ፡ ሴትዮይቱ ፤ አንድ ፡ ሰውዬ ፡ አንዲት ፡ ሴትዮ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሔዱ ፡ ኀበ ፡ እገሌ ። እገሌ ፡ እምቤተ ፡ እገሌ ፡ ውእቱ ። አይቴ ፡ ሀለዉ ፡ እገሌ ፡ ወእገሌት ። ሜጥኩ ፡ በሜጠ ፡ እገሌ ። ረሳዕነ ፡ ግብረ ፡ እገሌ ፡ (ማቴ፳፮ ፡ ፲፰ ። አፈ ፡ ድ፳ ። ግንዘ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፫ ። ገድ ፡ አዳ) ። ሰማዕክኑ ፡ ኦ ፡ እገሌ ። ኢትትአመን ፡ ኦ ፡ እገሌ ፡ ትሕትናሁ ። አንተ ፡ ሆይ ፤ ሰውዬ ፡ ሆይ ፤ እንተቴ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዮሴፍ) ። ጸውዑ ፡ ሊተ ፡ እገሌሀ ፡ ወእገሌተ ፡ ቢል ፡ ያንንም ፡ ያችንም ፤ ርሱንም ፡ ርሷንም ፤ ወንዱንም ፡ ሴቷንም ፡ ሴቲቱንም ፤ ወይም ፡ ባልና ፡ ሚስቱን ፡ ያሰኛል ፡ (ሉቃ ፡ ዕገሪ ፡ ፶፭) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ቅጽል ፡ ይኾናል ። አንተ ፡ እገሌ ። ፈለጥከኒ ፡ እምአመትየ ፡ እገሌት ። ሐር ፡ ኀበ ፡ እገሊት ፡ ሀገር ፡ (ኪዳ ። ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፫) ። ለሥራና ፡ ለመሣሪያ ፡ ሲኾን ፡ እንትን ፡ እንዳች ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ያሰኛል ።

**እገሌያዊ ፤ (ዐረ ፡ ፉላኒ) ፤** የእከሌ ፡ የእንቶ ፡ የርሱ ፡ የዚያ ፤ ያንድ ፡ ሰው ። አዘዘ ፡ ከመ ፡ ኢያንብሩ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ እገሌያዊ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱) ።

**ተገልየ ፤** ተቈረጠ ፤ ተገለጠ ።

**ግሉይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሊት ። ዕብ ፡ ጋሉይ) ፤** የተገለጠ ፡ ግልጥ ፤ ቍርጥ ።

**ግልየት ፤** መግለጥ ፤ መገለጥ ፡ አገላለጥ ፡ ገለጣ ፡ ቈረጣ ። የመጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ሉሕ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተገልጦ ፡ የሚታየው ፡ የሚነበበው ። በተለየ ፡ ግን ፡ ግልየት ፡ የሚባል ፡ ወንዙን ፡ ጥራዙን ፡ ማጠፊያውን ፡ ወሰን ፡ እይ

ርን ፡ በጥፈትና ፡ በዕጥፋት ፡ ማገልል ፡ ወዲያ ፡ ማደና ፡ ወዲህ ፡ ማደ ፡ ያለው ፡ ባደ ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

**ግልያ** ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፡ ገጽ ፡ ግልየት ፡ ሚራክ ፡ በንበረኛ ። **ሐሳበ ፡ እግርስ ፡ ፃዋ ፡ ውስተ ፡ ግልያሁ ፡ ስፍረ ፡ ሰዓት** ፡ (አዋል) ።

**ገሊል ፤ ሎት ፤ (ገለ ፡ አው ፡ ገለለ ፡ ይገልል ፡ ይግልል ። ዕብ ፡ ጋላል)** ፤ መምረጥ ፡ ማንጓለል ፤ መለየት ፡ ማስገለል ። ማንጋለል ፡ በዝርብ ፡ ማስተኛት ። ገልገለ ፡ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ተገለ** ፤ ተለየ ፡ ተገለለ ፡ ተንጓለለ ፡ ተንጋለለ ። (ተረት) ፡ ተንጋለው ፡ ቢተፉ ፡ ተመልሶ ፡ ታፉ ።

**ግሉል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ልልት)** ፤ የተለየ ፡ የተገለለ ፡ የተንጓለለ ፡ የተንጋለለ ።

**ግላል** ፤ እንጕላይ ፡ ንፋሽ ፡ ሐሠር ፡ ምራጭ ፡ እንግሊላ ፡ የኋሊት ።

**ገሊላ ፤ (ዕብ ፡ ግሊላ ፤ ጋሊል)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ የምድረ ፡ እስራኤል ፡ ሰሜን ፡ በዮርዳኖስና ፡ በጥብርያደስ ፡ በዐቢይ ፡ ባሕር ፡ መካከል ፡ ያለ ፤ የይሳኮርና ፡ የዛብሎን ፡ ክፍል ፡ ታችኛው ፤ ላይኛውም ፡ የአሕዛብ ፡ ክፍል ፡ ሳይቀር ። ገለልተኛ ፡ ገጠር ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ ሀገርና ፡ መንደር ፡ ያለበት ፤ ዐውድ ፡ ዘውር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ኢያ፳ ፡ ፯ ። ፫ነገ ፡ ፱ ፡ ፲፩) ። **ናዝሬት ፡ ዘገሊላ ። ቃና ፡ ዘገሊላ ። ወገሊላ ፡ ዘአሕዛብ** ፡ (ሉቃ፩ ፡ ፳፮ ። ዮሐ፪ ፡ ፩ ። ማቴ፬ ፡ ፲፭) ።

(ጥላ) **ጋላ** ፤ በቁሙ ፤ ልዩነት ፡ ያለው ፡ ባለመለዮ ፤ ሕዝብ ፡ ጭፍራ ። ስመ ፡ ነገድ ፡ ጋሎስ ፡ ከሚባል ፡ ሕዝብ ፡ የወጣ ፤ ወይም ፡ ከማኽል ፡ አፍሪቃ ፡ የመጣ ፤ ያማራ ፡ ጠላት ፡ ደመኛ ። (ተረት) ፡ በማና ፡ ተኰላ ፤ በማራና ፡ ጋላ ። ጋላን ፡ ገድሎ ፡ ምንው ፡ ጋሌ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ምንው ፡ ገለሌ ፡ ማለት ፡ ከዚሁ ፡ ከስሙ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ጋላት** ፤ ጋሎች ፡ ጭፍሮች ፡ ወታደሮች ፡ ክልክሎች ፡ አጋፋሮች ። (ግጥም) ፤ ሐዋርያት ፡ ጋሎች ፡ ጥለውት ፡ ቢሸሹ ፡ ታስሮ ፡ ተሰቀለ ፡ ዐማኑኤል ፡ ጕሹ ። **ቦኡ ፡ ጋላተ ፡ ሂመነ ። ዘመጠወ ፡ ርእሶ ፡ ለጋላት ። ተፈነዉ ፡ ጠርባናት ፡ ሜትራይቅይ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ጋላት ፡ በትእዛዘ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ከሓዲ ፡ ከመ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሶ** ፡ (፪ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፡፴፪ ። ድጓ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ጐልሎ ፤ ሎት ፤ (ጐለለ ፡ ይጌልል ፡ ይጐልል)** ፤ መጕለል ፤ በቤት ፡ ራስና ፡ በጕልቻ ፡ ላይ ፡ ማስቀመጥ ፡ ማኖር ፡ መጣድ ፡ ማስረር ።

**ጕላ ፤ አው ፡ ጕሌ ፤ (ብ ፡ ጐላል ። ዐረ ፡ ወዕብ ፡ ጕሎት ። ጽር ፡ ጕላት)** ፤ አፍላል ፡ መጎቀል ፡ የሸክላ ፡ ቅል ፡ ጕልላት ፡ የመንቀል ፡ ዐይነት ። **ወገብረ ፡ ክልኤተ ፡ አዕማደ ፡ ወመልዕልቴሆሙ ፡ ጕላተ** ፡ (፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፲፪) ። እንዳንድ ፡ መጠፍ ፡ ጎላት ፡ ብሎ ፡ በሳብዕ ፡ ይጥፋል ።

**ጕልማ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፡ አበት ፡ ለልጁ ፡ ጌታ ፡ ላሽከሩ ፡ የሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ግዛት ። (ግጥም ፡ ተጠማኝ ፡ ወይም ፡ ተጋኝ) ፤ አይኾንም ፡ እንጂ ፡ ከኹነማ ፤ ከመጋዝ ፡ ይሻላል ፡ ጕልማ ።

**ጐሊም ፤ ሞት ፤ (ጐለመ ፡ ይጐልም ፡ ይጕልም ። ዕብ ፡ ጎሌም)** ፤ መጕለም ፡ ጕልማ ፡ መስጠት ። መጕልመስ ፡ ማደግ ፤ መጐላመም ፡ ጕልማማ ፡ ባለጕልማ ፡ መኾን ። ኰለም ፡ እንዲሉ ፡ ጕልማሜ ፡ ቢሉ ።

**ገላሚዎስ ፤-ጎሥሥት ፤-ከሚሴዎን ።**

**ጋልሙት ፤ (ዕብ ፡ ጋልሙድ)** ፤ ዛዛኝ ፡ ሴሰኛ ፡ አውሬ ፤ የድመት ፡ የመሳይመሳይላ ፡ ዐይነት ። በቁሙ ፤ ጋለሞታ ፡ ባለመሸታ ።

**ገለሠ ፤—ተቀመጠ ፤ ሸነን ፤—ገሊስ ፡ ገለሰ ።**

**ገሊዕ ፤ ዖት ፤ (ገልዐ ፡ ይገልዕ ፡ ይግላዕ ። ዕብ ፡ ጋሎዕ)** ፤ መንቃት ፡ መሠንጠቅ ፡ መሰበር ፡ መድቀቅ ፡ መንከት ፡ መንኮት ፤ መጕዳት ፤ የሸክላ ፡ ያጥንት ።

**ገልዕ ፤ (ዕብ ፡ ሔሬሽ)** ፤ ገል ፡ የሸክላ ፡ ስባሪ ፡ እንክትክች ፡ የሳት ፡ መጫሪያ ። እሳት ፡ በገል ፡ ውሃ ፡ በቅል ፡ እንዲሉ ። **ብሩር ፡ ዘይትወሀብ ፡ ምስለ ፡ ሕብል ፡ ከመ ፡ ገልዕ ፡ ውእቱ ። የብሰ ፡ ሥጋሁ ፡ ከመ ፡ ገልዕ ። ትጽሕፍ ፡ ኅሊናሃ ፡ ውስተ ፡ ገልዕ** ፡ (ምሳ፳፮ ፡ ፳፫ ። ገድ ፡ ተክ ። ስንክ ፡ ጥር፳፯ ። ኢዮ፪ ፡ ፰ ። መዝ፳፩ ፡ ፲፭) ።

**ገልዓት ፤ አግልዕት** ፤ ገሎች ፡ ገላልት ። **አሰሩ ፡ ውስተ ፡ ከሣዱ ፡ ሐብለ ፡ ወዲቤሁ ፡ ሰቀሉ ፡ ገልዓተ ፡ ዘአጽለምዎሙ ፡ በፍሕም ። ከመ ፡ ዘያስተጣግዕ ፡ አግልዕተ** ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳፮ ። ሢራ፳፪ ፡ ፯) ።

**ገለዓድ ፤ (ዕብ ፡ ጊልዓድ)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ ተራራ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ያለ ፡ (ዘኍ፴፪ ፡ ፩) ።

**ገሊፍ ፤ ፎት ፤ (ገለፈ ፡ ይገልፍ ፡ ይግልፍ ። ሱር ፡ ግላፍ ። ዕብ ፡ ጋላፍ)** ፤ መቅረጥ ፡ ማነጥ ፡ ማንጠጥ ፡ ጣዖት ፡ መሥራት ፤ በንፊጽ ፡ በድንጊያ ፡ በልብስ ፡ ላይ ፡ መሣል ፡ መመስል ፡ መፈደል ፡ መጠረብ ፡ መጥለፍ ። **እለ ፡ ይገልፍዎ ፡ ለዕፀ ። ይክል ፡ ገሊፈ ፡ አምሳል ። ገለፈ ፡ ላዕሌሁ ፡ በቀልተ ፡ ወአክሊላተ ። ይግልፍዎ ፡ ውስተ ፡ ኩኵሕ ። እለ ፡ ይገልፉ ፡ ወየኀርዉ ፡ ዐይነ ፡ ማኅተም ። ግልፍ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ አስማተ ። ቀጠንተ ፡ ዘያስረግውዎሙ ፡ በሕብራት ፡ ዘገለፉ ፡ ቦሙ** ፡ (ኢሳ፵፬ ፡ ፲፫ ። ፪ዜና ፡ ፪ ፡ ፲፬ ። ፫ ፡ ፭ ፡ ፯ ። ኢዮ፲፱ ፡ ፳፬ ። ሢራ፴፰ ፡ ፳፯ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫) ።

**ግላፌ ፤ (ፌት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ለፍት)** ፤ የሚቀረጽ ፡ እንጨት ፡ ምስል ፡ አፍላሽ ።

**አግለፈ** ፤ አስቀረጸ ፤ ምስል ፡ አሠራ ፡ አስፈሰሰ ፡ (፪ነገ ፡ ፯ ፡ ፳፱) ።

**ተገልፈ** ፤ ተቀረጸ ፡ ተሣለ ፡ ተመሰለ ። **ይትገለፉ ፡ አናቅጺኪ ። ዘተገልፈ ፡ በሰሌዳ ። ውስተ ፡ ከርሠ ፡ እምየ ፡ ተገለፍኩ ፡ ሥጋ** ፡ (ኢሳ፶ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ መስ፳፮ ። ጥበ፯ ፡ ፩) ።

**ግሉፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ልፍት) ፤** የተቀረጸ ፤ የተጠረ ፤ የተሣለ ። (ግልፍተኛ ፡ ቍጡ) ። እብኑ ፡ ባሕርይ ፡ ግሉፍ ። ግሉፍ ፡ ውስተ ፡ ጽሌ ፡ ልበሙ ። ጽላት ፡ ጽሑፍ ፡ ወግሉፍ ። ወግሉፋን ፡ ኪሩቤል ፡ ወፀበራት ፡ (ጥበ፲፰ ፡ ፳፱ ። ኤር፲፯ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ ነሐ፳ ። ሕዝ፵፩ ፡ ፲፰) ።

**ግልፈት ፤** መቅረጽ ፤ መቀረጽ ፡ አቀራረጽ ። ቅርጽ ፡ ንጥ ፡ ፍልፍል ፤ ያበጠ ፡ የሰመጠ ። ግልፈተ ፡ ዐይኑ ፡ ማኅተም ። ወግልፈት ፡ ላዕሌሃ ። አልባስ ፡ እለ ፡ አልበሙ ፡ ግልፈት ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፳፩ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ተ፳፰) ።

**ግልፎ ፤ (ብ ፡ ግልፍ(ፈ)ዋት) ፤** ቅርጽ ፡ ንጥ ፤ የተቀረጸ ፡ ጣዖት ፤ የሰው ፡ ምስል ። አርእስተ ፡ አዕማድ ፡ ዘግልፎ ። ኵሉ ፡ ግልፎሃ ። ወአቅንእዎ ፡ በግልፎሆሙ ። ግልፍዋት ፡ ኢትግበሩ ። ግልፈዋተ ፡ ጣዖት ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፳፯ ። ሚክ፩ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፸፯ ። ኩፋ ፡ ፳ ። አርጋ ፡ ፬) ። ግንፋልን ፡ እይ ።

**ገልፈፈ ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤** ገፈፈ ፡ ገለፈፈ ፤ የቁርበት ፡ የከንፈር ። (ዐማርኛ) ።

**ገሊጽ ፤ ጾት ፤ (ገለጸ ፡ ይገልጽ ፡ ይግልጽ) ፤** መግለጥ ፡ መግፈፍ ፡ ማሳየት ፤ መንገር ፡ መተርጐም ፡ ማስረዳት ።

**ተገልጸ ፤** ተገለጠ ፡ ግልጥ ፡ ኾነ ፤ ታየ ፡ ተረዳ ። (ሙሴ) ፡ ሶበ ፡ ይትገለበብ ፡ ይትረአይ ፡ ወሶበ ፡ ይትገለጽ ፡ ይሴወር ፡ ወኢይትዐወቅ ፡ (አዋል) ።

**ግሉጽ ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ልጽት) ፤** የተገለጠ ፡ ግልጥ ።

**ገሊስ ፤ ሶት ፤ (ገለሰ ፡ ይገልስ ፡ ይግልስ ። ትግ ፡ ገልሰ ። ዕብ ፡ ጋላስ ። ዐረ ፡ ጀለሰ ፤ ተቀመጠ) ፤** መለበድ ፡ ልብድ ፡ መሰፋት ፤ ቊርበት ፡ ማልበስ ፡ መደጐስ ፤ መደልደል ፡ ማመቻቸት ፤ መሸብለል ፡ መጠቅለል ፤ የኮርቻና ፡ የጫንት ።

**ግላስ ፤** በቊሙ ፤ የኮርቻ ፡ ልብስ ፤ ምንጣፉ ፡ ምቹው ፡ መቀመጫው ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጐልቆ ፤ ቆት ፤ (ጐለተ ፡ ይጔልት ፡ ይጐልት) ፤** መጕለት ፡ መትከል ፤ የጕልቻ ። ማውረስ ፡ መስጠት ፤ የገንዘብ ፡ የርስት ። ይጐልቶሙ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ። በጊዜ ፡ ጐልቶቱ ። ወለእመ ፡ ጐለተ ፡ ላቲ ፡ ኢትሰድ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፰ ። ፳፱ ፡ ፳) ።

**ጐላቲ ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤** የሚጐልት ፡ ጐላች ፤ ሰጭ ፡ አውራሽ ። ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ጐላቲ ፡ ከመ ፡ ይሠየም ፡ ዴበ ፡ ዘጐለተ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፰) ።

**ተጐለተ ፤** በቊሙ ፤ ጕልት ፡ ኾነ ፡ ተሰጠ ፡ ተወረሰ ። ዘተጐለተ ፡ ሎቱ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፰) ።

**ጕልት ፤ (ታት) ፤** ጕልቻ ። በቊሙ ፡ ዐዲስ ፡ ርስት ፤ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ ለዘመዱ ፡ ለባዕድ ፡ ወይም ፡ ለገዳም ፡ የሚያወርሰው ፤ ገንዘብ ፡ ጥሪት ፤ ቦታ ፡ መሬት ። ንሕነ ፡ ጐለትነ ፡ ጕልተ ፡ ለገበዘ ፡ አኵስም ። ብፅዓታት ፡ ወጕልታት ፡ (ክብ ፡ ነገ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፰) ።

—፤ የማይፈልስ ፡ ቀለም ፡ ገቢር ፡ ተገብሮ ፡ የሚከት ፡ የማይለወጥ ። ስሉ ፡ ሰብሉ ፤ የጕም ፡ ትማልም ፡ አፉሁ ፤ እደ፡ሁ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**ጎላት ፤—መንቀሎች ፤—ጐልሎ ፡ ጐለለ ።**

**ጕማ ፤—ድምፅ ፡ ዜማ ፤—የነፍስ ፡ ዋጋ ፤—ገዪም ፡ ጌመ ።**

**ጊሜ ፤—ጕም ፤—ገዪም ፡ ጌመ ።**

(ጥ) **ጋማ ፤ (ጽርእ ፡ ወቅብጥ) ፤** ስመ ፡ ፊደል ፡ ሣልስ ፡ ገ ። አልፋ ፡ ወቤጣ ፡ ወጋማ ፡ (ሥር ፡ ጳኰ) ።

**ጋማ ፤ (ዐማርኛ) ፤** በቊሙ ፤ የፈረስ ፡ የበቅሎ ፡ ያህያ ፡ ጠጕር ፤ ያንገት ፡ የማኽረራት ፡ ጭራ ። የጋማ ፡ ከብት ፡ እንዲሉ ። ያንበሳ ፡ ጐፈር ፡ አንፋሮ ፡ በራስ ፡ የሚታሰር ። ጋሜ ፡ የሰው ፡ ራስ ፡ ጠጕር ፤ ማኽሎ ፡ ተላጭቶ ፡ በዙሪያው ፡ የሚቀር ፤ ዐብሮ ፡ በቀል ፡ ጐፈር ።

**ጋሜ ፤** የደጋን ፡ ዕንጨት ፡ ቀጥታ ፡ ዘለግታ ፡ ያለው ፡ ለብልቦ ፡ ሲያርቁት ፡ እንደ ፡ ቅን ፡ አሽከር ፡ የሚታዘዝ ፤ (ግጥም ፤ ሽበታም ፡ ወይዘሮ ፡ የ፰ ፡ ዓመት ፡ ልጅ) ፤ ራሴ ፡ ጥጥ ፡ ኹኖ ፡ ፈታይ ፡ ስለምን ፡ ልቤ ፡ ተንደፈ ፡ በጋሜ ፡ ደጋን ።

**ጐሜእ ፤ (ዕብራ) ፤** ስመ ፡ ዕፅ ፡ በግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ የሚበቅል ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ የሸንበቆ ፡ የቀርከሐ ፡ ዐይነት ፡ ታንኳ ፡ ፍልኳ ፡ የሚኾን ። ንዋየ ፡ ጐሜእ ፡ (ኢሳ፲፰ ፡ ፪) ።



ጕሜእ፡

**ገሚእ ፤ አት ፤ (ገምአ ፡ ይገምእ ፡ ይግማእ ። ዕብ ፡ ጋሜእ ፡ ማገ ፤ ጠጣ ፤ አሸተተ) ፤** መማማት ፡ መበሽቀጥ ፤ ጽዩእ ፡ መኾን ።

**ግሙእ ፤ (ኣን ፡ ኣት ፡ ምእት) ፤** የገማ ፡ ግም ፡ በሽቃጣ ። (ተረት) ፤ ግም ፡ ለግም ፡ ቢተቃቀፍ ፡ አይነቃቀፍ ።

**ግምእት ፤** መግማት ፡ አገማም ፡ ግማት ፡ ክፉ ፡ ሽታ ።

**ግምኤ ፤—ማሰሮ ፤—ገምዖ ፡ ገምዐ ፤ ግምዒ ።**

**ገመገም ፤** በቁሙ ፤ (ዐማርኛ) ።

**ገሚድ ፤ ዶት ፤ (ገመደ ፡ ይገምድ ፡ ይግምድ ፤ አው ፡ ገምዶ ፡ ዶት ፤ ገመደ ፡ ይጌምድ ፡ ይገምድ ። ዕብ ፡ ጋማድ ፡ ዐረ ፡ ጀመደ) ፤** መጕመድ ፡ መጕማመድ ፤ መቍረጥ ፡ ማጨድ ፡ መጨርገድ ፤ መገዝገዝ ፡ ማረድ ። መቍረስ ፡ መገምደል ። መግመድ ፡ መፍተል ፡ ማክረር ። ጊዜ ፡ ገሚድ ፡ በጽሐ ። ዘእንበለ ፡ ይግምድዎ ። ይገምዱ ፡ አስካለ ። እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ትገምዱ ፡ መጥባሕት ። ገመዱ ፡ መሌሊቶሙ ፡ ከመ ፡ ሥጋ ፡ ውስተ ፡ ጽህርት ። ይጌምድ ፡ ሥጋሁ ፡ በእብን ፡ (ማሕ፩ ፡ ፲፪ ። ኢዮ፳ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፲፰ ፡ ፭ ። ኤር፳፱ ፡ ፮ ። ማር፭ ፡ ፭) ። መላላቱና ፡ መጥበቁ ፡ ቱሱሕ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፤ የቱሱሕን ፡ ፍቾች ፡ ተመልከት ።

**ገማዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤** የሚጕምድ ፡ ቈራጭ ፡ ዐጫጅ ፤ ግማጅ ።

**አግመደ ፤ አገመደ ፤** አስጕመደ ፡ (አስገመደ) ፡ አስቈረጠ ፡ አሳጨደ ።

**ተገምደ ፤ ተገመደ ።** ታረደ ፡ ተጕመደ ፤ ተጕማመደ ፤ ታጨደ ፡ ተቈረጠ ። በሰይፍ ፡ ተገምዱ ፡ ሕፃናት ፡ ንጹሓን ። ዘተገምደ ፡ በመጥባሕት ። ሐረግ ፡ ወይን ፡ እንተ ፡ ትትገመድ ፡ ወትትአረር ። በሐብዎ ፡ ወከኑ ፡ ሥጋሁ ፡ ይትጌመድ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፴ ። መጋ፲፭ ። ድጓ ። አቡሻ ፡ ፶) ።

**ግሙድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ምድ) ፤** የተቈረጠ ፡ ቍርጥ ፡ ጕምድ ፡ ጕማጅ ። ቶማስ ፡ ዘአባላቲሁ ፡ ግሙድ ። ያዕቆብ ፡ ግሙድ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፳፱ ። ኅዳ፳፯) ።

**ግምደት ፤ ግማዴ ፤** መቍረጥ ፡ መቈረጥ ፡ አቈራረጥ ፡ ቈረጣ ፡ ዐጨዳ ፡ ጕማድነት ።


**ግምድ ፤ ግማድ ፤ (ዳት) ፤** ቍራጭ ፤ ጕመድ ፡ ጕማጅ ፤ ጕራጅ ፡ ዕራፊ ፤ ቅናሽ ፡ ሙዳ ፡ ጕማ ። (ግጥም) ፡ ኢየፍሳሴምን ፡ ይመኛል ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፤ ግሽን ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ ግማደ ፡ መስቀሉ ። ግማድ ፡ ዘተርፈ ፡ እምዕፀ ። ግምደ ፡ ደርግሐ ፡ ልብስ ። በግማደ ፡ ልብሱ ። ግማደ ፡ ሥጋ ። ግማዳት ፡ ዘሖሉ ፡ አባል ። ግማዳተ ፡ ሕብድ ፡ (ጥበ፲፫ ፡ ፲፫ ። ማር፪ ፡ ፳፩ ። ፊልክ ፡ ፲ ። ፪፻፶፫ ። ሕዝ፳፬ ፡ ፬ ። ኢዮ፲፮ ፡ ፯ ። ቅኔ) ።

**ትግምድ ፤** መቈረጥ ፡ ቈራጥነት ፡ ቈራጣ ፡ መኾን ። ትግምደ ፡ አልባሲሆሙ ፡ (ግንዘ) ።

**ገመድ ፤** በቁሙ ፡ ሐብል ። ሐቢልን ፡ ተመልከት ።

**ገማዲም ፤** ስሙ ፡ ነገድ ፤ ስሙ ፡ ትውልድ ፡ ያፌታውያን ፡ የገሜር ፡ ቍራጮች ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፲፩) ።

**ገመል ፤ ገምል ፤ (ዕብ ፡ ጋማል ። ሱር ፡ ጋምላ ። ዐረ ፡ ጀመል) ፤** በቁሙ ፤ ግመል ፡ የቤት ፡ እንስሳ ፡ የቈይንት ፡ የኮርቻ ፡ ከብት ፤ በረሓ ፡ ቈላ ፡ የሚደፍር ፡ ውሃ ፡ ጥም ፡ የሚችል ፡ ዐንገተ ፡ ረዥም ፡ ነጭን ፡ ቅልጥም ፡ ከህያ ፡ ከጋስስ ፡ አብልጦ ፡ የሚይገዝ ፡ የሚሸከም ። ቀዩኒ ፡ የበዳ ፡ ግመል ፤ ነብርማ ፡ ዝንጕርጕር ፡ የበዳ ፡ አህያ ፡ የሚመስል ፤ ዐዳኞች ፡ እንዳውሬ ፡ የሚገድሉት ።



ገመል ፡

**ገመላት ፤ አግማል ፤ (ላት) ፤** ገመሎች ፡ ግመሎች ፤ ቀዩኒዎች ። ጸጕረ ፡ ገመል ። ነሥአ ፡ ዐሠርተ ፡ አግማለ ፡ እምአግማለ ፡ እግዚኡ ። አግማላቲሆሙ ፡ (ማቴ፫ ፡ ፬ ። ዘፍ፳፬ ፡ ፲ ። መሳ፯ ፡ ፭) ።

**ገመላዊ ፤** ግመልማ ፤ የግመል ፡ ዐይነት ፤ ግመል ፡ ሳቢ ፡ ጠባቂ ፡ የግመል ፡ እረኛ ፡ ባለግመል ። ቈሪል ፡ ገመላዊ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፳፱) ።

**ገምል ፤** ስሙ ፡ ፊደል ፡ ማለት ፡ ገ ፤ በአበገደ ። ዐረቦች ፡ ጂም ፡ ጀ ፡ ይሉታል ።

**ጋሜል ፤ (ዕብ ፡ ጊሜል) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ስሙ ፡ ፊደል ፡ ገ ። ፍችው ፡ ፍጹም ፡ ዐስብ ፡ ዕሴት ፡ ፍዳ ። ጋሜል ፡ ዕስዮ ፡ ለገብርከ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፲፯) ።

**ገመመ ፤ (ይጌምም ፡ ይገምም ፤ ገምሞ) ፤** ያዘ ፡ ጨበጠ ፤ ላጨ ፡ ቈረጠ ፤ ከረከመ ፤ የለጓሚና ፡ የላጭታ ። ጋማ ፡ ጋሜ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ መጥቷል ። ኹለተኛም ፡ ገሚም ፡ ገመ ፡ ይገምም ፡ ይግምም ፡ ብሎ ፡ ዲቃላውን ፡ ገምገመ ፡ ሲሉት ፡ ገመገም ፡ ከዚህ ፡ ይወጣል ። ጌመኛና ፡ ጕማን ፡ ተመልከት ፤ ፍችው ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ገምኖ ፤ ኖት ፤ (ገመነ ፡ ይጌምን ፡ ይገምን) ፤** ማግመን ፡ ማሳረር ፤ መጥበስ ። ማሳደፍ ፡ ማዥለፍለፍ ፤ ማርከስ ፡ ማስነወር ፤ መለወጥ ፡ መቀየር ፤ የቃል ፡ የነገር ። ንፁብኩ ፡ እገርየ ፡ እፎኑ ፡ እጌምኖን ። እለ ፡ ኢገመኑ ፡ አልባሲሆሙ ። ገመነ ፡ ይሁዳ ፡ መቅደስየ ። እለ ፡ ይጌምኑ ፡ ስመ ፡ ቅዱስ ፤ እስመ ፡ ገመንዋ ፡ ለሲዳና ፡ እጓቶሙ ። ኢይገምን ፡ ቃሎ ፡ (ማሕ፭ ፡ ፫ ። ራእ፫ ፡ ፬ ። ሚል፪ ፡ ፲፩ ። ክቡ ፡ ፴ ። ዘኍ፴ ፡ ፫) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ በገመነ ፡ ፈንታ ፡ አግመነ ፡ አገመነ ፡ ይላል ፤ አያስኬድም ። አገመኑ ፡ መሥዋዕተ ። ያጌምንዎ ፡ ለሥጋሆሙ ፡ (አዋል ። ፀጺጥ ፡ ፪ ፡ ፲ ። ይሁ ፡ ፰ ። ፊእ

፳፩ ፡ ፳ ። ኩፋ ፡ ፱ ። ዘኍ፳ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። አመረን ፡ አእመረ ፡ እንደሚል ፤ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

**ገማኒ** ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት) ፤ የሚያገምን ፤ የሚያሳድፍ ፡ የሚያረክስ ።

**ተገመነ** ፤ ፀረረ ፡ ገመነ ፡ ተከነ ፡ አደፈ ፡ ረከሰ ፤ ሴሰነ ። ኢተገመንኩ ፡ ነፍስየ ፡ በርኵስ ። ተገመንኩ ፡ ለከ ፡ እምኔከ ። ወተገመነ ፡ ሕዝብ ፡ (ሕዝ፬ ፡ ፲፬ ። ኩፋ ፡ ፴፫ ። ዘኍ፳ ፡ ፩) ።

**ግሙን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ምንት) ፤ የገመነ ፡ ያደፈ ፡ የረከሰ ፤ ርኩስ ። ግሙን ፡ ቍርባኖሙ ፡ ለጎጥኣን ። ልሳን ፡ ግሙን ። ግሙናን ፡ መንፈስ ። ሖሩ ፡ ፍናዊሆሙ ፡ ግሙናን ። ምድር ፡ ግምንት ፡ (ሚራ፴፩ ፡ ፳፱ ። ፺፩ ፡ ፳ ። ዳድ ፡ ፳፩ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ኩፋ ፡ ፳፱ ። ፩ ዕገ ፡ ፳ ፡ ፹) ። ሐረርም ፡ ዘማይቱን ፡ ግምንት ፡ ሲል ፡ ግሙና ፡ ይላል ።

**ግማን** ፤ (ናት) ፤ አድፍ ፡ ርስሐት ፤ ትክቶ ፤ ዝሙት ፡ ኀጢአት ፤ ገመና ፡ ነውር ፡ የሚያሳፍር ። ምድር ፡ ርኵስት ፡ ይእቲ ፡ በግማኖሙ ፡ ለአሕዛበ ፡ ምድር ፡ (ዕዝ፱ ፡ ፲፩) ።

**ግማኔ** ፤ **ግምንት** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። እምኵሉ ፡ ግማኔ ፡ ኀጢአት ። ግማኔ ፡ ነፍስ ፡ (ኩፋ ፡ ፳ ። ጥበ፲፱ ፡ ፳፯) ። ማረር ፡ መግመን ፤ ማሳረር ፡ ማግመን ፤ አገማመን ፤ ገመና ፡ ዐራራነት ፡ ጥቍረት ፤ ነውረ ፡ ኀብስት ። ለእመ ፡ ቦ ፡ ንቅዐት ፡ ውስተ ፡ ኅብስት ፡ አው ፡ ግምነት ፡ ኢታዕርግዎ ፡ (ቄድር ፡ ገ፹፱) ።

**ገምዖ** ፤ **ዖት** ፤ (ገምዐ ፡ ይጌምዕ ፡ ይግምዕ) ፤ መቍረጥ ፡ መሸለት ፤ መላጨት ፤ የጠጕር ። ገምዒ ፡ ርእሰኪ ። ወይገምዖ ፡ ጽሕሞሂ ፡ (ሚክ፩ ፡ ፲፮ ። ኢሳ፷ ፡ ፳) ። ማለዘብ ፡ መፋቅ ፡ መላግ ፡ ማስተካከል ፤ ልጩ ፡ ራስ ፡ ማስመሰል ፤ የርጥብ ፡ ሸክላ ፡ የምርግ ፡ የልስን ። ትግሬ ፡ ግን ፡ ገምዐ ፡ ብሎ ፡ መከረ ፡ ይላል ፤ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ከማለዘብ ፡ ይገባል ።

**ገማዒ** ፤ **መገምዕ** ፤ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት) ፤ የሚቈርጥ ፤ ሸላች ፡ ላጭታ ፤ ገያሪ ፡ ሸክላ ፡ ሠሪ ።

**አገምዐ** ፤ አስላጨ ፡ አስቈረጠ ፤ አስለዘበ ።

**ተገምዐ** ፤ ተላጨ ፡ ተቈረጠ ፤ ተፋቀ ፡ ለዘበ ። ከመ ፡ ይትገምዑ ፡ (ኢር፳፰ ፡ ፴፱) ።

**ግሙዕ** ፤ የተላጨ ፡ ልጩ ፡ ሽልት ፤ ልዝብ ፡ ጥሩቅ ።

**ግማዔ** ፤ መላጨት ፡ (ጥላ) መላጨት ፡ አለማጭ ፤ ቈረጣ ፡ ሽለታ ።

**ግምዔ** ፤ (ዕያት ፤ ግማዕይ ፡ ው) ፤ ምንቸት ፡ ማሰሮ ፡ ዐይኑት ፡ ጭንቀሎ ፤ ታናሽ ፡ ሸክላ ፤ ልጩ ፡ ራስ ፡ ጭንቅላት ፡ የምትመስል ፤ የዘይት ፡ ዕቃ ። (ቀረት) ፡ ጋኖች ፡ ዐስቱና ፡ ምንቸቶች ፡ ጋን ፡ ኾኑ ። ግምዔ ፡ ልሕኵት ። ግምዔ ፡ ቅብዕ ። ኵሉ ፡ ግምዐያቲሃ ፡ ዘቅብዕ ። ነሥኣ ፡ ቅብዐ ፡ በገማዕይሆን ፡ (ዘኍ፳ ፡ ፲፯ ። ዮዲ፲ ፡ ፳ ። ዘኍ፬ ፡ ፱ ። ማቴ፳፭ ፡ ፬) ።



ግምዔ ፡

**ጕማዕ** ፤ (ዓት) ፤ በቁሙ ፤ ጕማ ፡ ሙዳ ፤ የሥጋ ፡ ቍራጭ ፡ ታናሽ ፡ ክፍል ፤ ለብቻው ፡ ጕም ፡ ያለ ።

**ገሚጽ** ፤ **ጾት** ፤ (ገመጸ ፡ ይገምጽ ፡ ይግምጽ ፤ አው ፡ ገምጸ ፡ ጾት ፤ ገመጸ ፡ ይጌምጽ ፡ ይገምጽ) ፤ መግመጥ ፡ መጋጥ ፤ መዘንተር ፡ መዝብተር ፤ ማማት ፡ መንቀፍ ። በላም ፡ ለስምዖን ፡ እንተ ፡ ለሐቌሁ ፡ አጽንዖ ፡ በሐብለ ፡ በቀልት ፡ ይቡስ ፡ እንተ ፡ ይጌምጾ ፡ ወይበልዖ ። ወገሚጽኒ ፡ እምዕጸበ ፡ አስተሐቅሮ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፳ ። ማር ፡ ይሥ፳፱ ፡ ፩) ።

—፤ ማጕብጥ ፤ ማስጕንበስ ፤ ማጥመም ፡ መቈልመም ፡ መቀለስ ፡ ማጽነን ፡ ማዘንበል ፤ ወዳንድ ፡ ወገን ፡ ማድላት ፡ መድፋት ፡ ራስን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ። ዘይጌምጽ ፡ ከማይ ። እምንእሰሙ ፡ ግምጽ ፡ ከማይሰሙ ። ወርቅ ፡ ገመጸሙ ፡ ልቦሙ ፡ ለነገሥት ። ለገሚጸ ፡ ፍትሕ ። ኢትግምጽ ፡ ፍትሐ ፡ ነዳይ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ሚራ፺ ፡ ፳፫ ። ፳ ፡ ፪ ። ዘፀ፳፫ ፡ ፪ ። ዳድ ፡ ፬) ። ትግሬ ፡ ግን ፡ ገመጸ ፡ ብሎ ፡ ደኸየ ፡ ድኻ ፡ ኾነ ፡ ይላል ።

**ተገምጸ** ፤ **ተገመጸ** ፤ ተገመጠ ፤ ተቀለሰ ፡ ተጕነበሰ ፤ ጕበጠ ፤ ወትትገመጽ ፡ እምህየ ፡ መንገለ ፡ በሜን ፡ (ኩፋ ፡ ፳) ።

**ገሚር** ፤ **ሮት** ፤ (ገመረ ፡ ይገምር ፡ ይግምር ። ሱር ፡ ግማር ። ዕብ ፡ ጋማር) ፤ ማግመር ፡ መጨረስ ፡ መፈጸም ፤ መቻል ፡ መያዝ ፡ መወሰን ፤ መድፈር ፡ ጨርሶ ፡ መናገር ። (መጕምራት ። መጕመር ፤ ማደማ ። መጋመር ፤ መዳበር ፤ የሴት) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በገመረ ፡ ፈንታ ፡ አግመረ ፡ ይላል ፡ አድራጊውን ፡ ባስደራጊ ። ለእመ ፡ አግመረ ፡ ገራህተ ፡ እንዘ ፡ ይበልዕ ። ብሒእ ፡ ዘአግመሮ ፡ ለሐሪጽ ። እስ ፡ ይፈቅዱ ፡ ያግምርዋ ፡ ለምድር ፡ ባሕቲቶሙ ። እግዚ ፡ ዘያገምር ፡ ኵሎ ፡ ወኢያገምሮ ፡ መካን ። ኢታገምር ፡ ፍኖታ ፡ ዘእንበለ ፡ አሐቲ ፡ ኪደተ ፡ እግረ ፡ ብእሲ ። በከመ ፡ አግመረ ፡ አፌ ፡ ኢሳይያስ ፡ ወይቤ ፡ (ዘፀ፳፪ ፡ ፱ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ኢሳ፭ ፡ ፰ ። ግንዘ ። ሱቱ ፡ ዕዝ፳ ፡ ፯ ። ተረ ፡ ቄር ፲፯) ።

**አግመረ** ፤ አስጨረሰ ፡ አስፈጸመ ፤ አስቻለ ፡ አስወሰነ ፡ አስደፈረ ።

**ተገምረ** ፤ ተጨረሰ ፡ ተከተተ ፡ ተካተተ ፡ ተቻለ ፡ ተወሰነ ። እስከ ፡ ተገምረ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወዐደወ ። ፀርበ ፡ ተገምሩ ፡ በኵናት ። ውስተ ፡ ክርሥ ፡ ይትገ

መር ። ተገምረ ፡ በማሕፀነ ፡ ድንግል ። መሲኮተ ፡ ኢይትገመር ፡ በምንትኒ ። እፎ ፡ አግመርኪዮ ፡ ለዘ ኢይትገመር ፡ ተገምሮ ፡ (ኢያ፫ ፡ ፲፮ ። መዝ ፡ ፱ ። ማቴ፲፭ ፡ ፲፯ ። ኪዳ ። ቄር ። ድጓ) ።

**ግሙር ፤(ራን ፡ ራት ፡ ምርት)፤** የተጨረሰ ፡ የተክተተ ፤ የተቻለ ፡ የተወሰነ ፡ ውሱን ። የኰመራ ፡ ጒምር ፤ የተጐመረ ፡ ጐምሮ ፤ የጋመረ ፡ የዳበረ ።

**ትግምርት ፤** ቻይነት ፡ አቻቻል ፡ ችሎት ።

**ግሙራ ፤(ደቂቅ ፡ አገባብ)፤** ጭራሽ ፡ አካቶ ፡ ፈጽሞ ፤ ከንዱ ፡ ዘንዱ ፤ መቼም ፡ መች ። ለእግዚአብሔርሰ ፡ አልቦ ፡ ዘርእዮ ፡ ግሙራ ። ግሙራ ፡ ኢያስተርእየ ፡ ዘከመ ፡ ዝ ። ኢትምሐሉ ፡ ግሙራ ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፲፰ ። ማቴ፭ ፡ ፴፬ ። ፳ ፡ ፴፱) ። ለ ፡ ሲወድቅበት ፡ ለዘወትር ፡ ለዘላለም ፡ ያሰኛል ፤ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገባል ። ብኑ ፡ ሊግሙራ ፡ አረምም ፡ እንከ ። አሐተ ፡ መሥዋዕተ ፡ ገብረ ፡ እንተ ፡ ለግሙራ ። ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ ለግሙራ ። ትረስዕኒ ፡ ለግሙራ ፡ (ኢሳ፷፪ ፡ ፲፱ ። ዕብ፲ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፱ ። ፲፪) ።

**ገመር ፤(ብ ፡ ገመራት ፡ አግማር)፤** በቁሙ ፤ ታላቅ ፡ ዝንጀሮ ፡ ባለብዙ ፡ ጅር ፤ ጒምቱ ፡ ሽማግሌ ፡ ያገር ፡ ቀንድ ፤ መምህር ፡ አበ ፡ ማኅበር ። (ተረት) ፤ መምሩ ፡ ገመሩ ። ምስጢሩ ፡ ታላቅነት ፡ ነው ።

**ጐማሬ ፤ ጐማሬ ፤** በቁሙ ፤ የባሕር ፡ አውሬ ፡ ጒምር ፡ ተጐማሪ ፡ (መ ፡ ፈ) ።

**ጐሞር ፤ ጎሞር ፤(ጽርእ ። ዕብ ፡ ዖሜር)፤** ታናሽ ፡ ልክ ፤ የኽል ፡ መስፈሪያ ፡ እንደ ፡ ድርጎና ፡ እንደ ፡ ቍልቢጥ ፡ እንደ ፡ ቁሰምሽሽ ፡ ያለች ፤ የኢፍን ፡ ከሦር ፡ አንድ ፡ የምቲዝ ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፲፰) ። ኢፍን ፡ እዩ ።

**ጐምር ፤** በቁሙ ፤ የበሰለ ፡ የደረሰ ፡ እሸትነቱን ፡ የጨረሰ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ገሞራ ፤(ጽር ፡ ጎሞራ ። ዕብ ፡ ዐሞራ)፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ አካቶ ፡ ፈጽሞ ፡ እሳት ፡ መዐት ፡ ከዘነመባቸው ፡ ከምስቱ ፡ አህጉረ ፡ ሰዶም ፡ አንዲቱ ፡ (ዘፍ፲፫ ፡ ፲) ። ዘይገብሩ ፡ ግብረ ፡ ገሞራ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰) ።

**ገሞራዊ ፤** የገሞራን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፤ ወንድ ፡ ኹኖ ፡ ወደ ፡ ወንድ ፡ የሚኼድ ፤ በሴት ፡ ፈንታ ፡ ወንድ ፡ የሚፈልግ ፡ ከወንድ ፡ የሚዘወግ ፡ አድራጊ ፡ ወንድ ፤ ወይም ፡ ተደራጊ ፡ ወንዳገረድ ፤ ወንድነቱን ፡ ክዶ ፡ በማይገባ ፡ ለወንዶች ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ የሚኾን ፡ መቀመጫውን ፡ የሚደቅን ። ገሞራውያን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰) ።

**ጐመሮ ፤ ገመሮ ፤** የቈላ ፡ ዕንጨት ፡ ዐረጋም ፡ እሾኻም ፡ የቀንጠፋ ፡ ወንድም ፤ ወንዴና ፡ ሴቴ ፡ ያለው ።

**ገሚስ ፤ ሶት ፤(ገመሰ ፡ ይገምስ ፡ ይግምስ ። ፈተተ)፤** መግመስ ፡ መገማመስ ፡ መቍረስ ፡ መቈራረስ ፤ መሸረፍ ፡ መሸራረፍ ። መመንዘር ፤ አንድ ፡ የነበረውን ፡ ብዙ ፡ ማድረግ ፡ ሰብዙ ፡ መስጠጥ ። መግመስ ፡ መቍረስ ፡ የእንጀራ ፡ መሸረፍ ፡ የገንዘብ ፡ ለእንጀራም ፡ ይኾናል ፡ መመንዘር ፡ ግን ፡ ለገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ገማሲ ፤(ሲት ፡ ስያን ፡ ያት ፤ መስት)፤** የሚገምስ ፡ ገማሽ ፡ ቈራሽ ፤ ሰራፍ ፡ ሸራፊ ፡ መንዛሪ ፡ ዐራሽ ።

**አግመሰ ፤** አስገመሰ ፡ አስቈረሰ ፤ አሳረሰ ።

**ተገምሰ ፤** ተገመሰ ፤ ተከፈለ ፡ ተገመደሰ ።

**ግሙስ ፤(ሳን ፡ ሳት ፡ ምስት)፤** የተገመሰ ፡ የተቈረሰ ፡ ግምስ ፡ ቍርስ ።

**ግማስ ፤(ሳት)፤** ግማሽ ፡ እኩሌታ ፡ መንፈቅ ። (ተረት) ፤ ግማሹን ፡ ተሳቢታ ፤ ግማሹን ፡ ተቀብታ ። አሐደ ፡ ኅብስተ ፡ አው ፡ ግማሰ ፡ ኅብስት ፡ (አዋል) ።

**ገሚስ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ግማሽ ። ዴው ፡ መጠነ ፡ ገሚስ ፡ (መ ፡ ፈ) ።

**ገመስ ፤(ብ ፡ አግሙስ)፤** ምንዛሪ ፡ ታናናሽ ፡ ገንዘብ ፡ የተሸረፈ ፡ የተመነዘረ ፤ ከአላድ ፡ እስከ ፡ ሶልድ ፡ እስከ ፡ ቤሳና ፡ እስከ ፡ ድዋኔ ፡ ያለ ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ ሰንኬቶ ፡ ቀለበት ፡ ይሉታል ። ደኃሪተ ፡ ገመስ ፡ (ሉቃ፲፪ ፡ ፶፱) ። ዳግመኛም ፡ ድርህማት ፡ ዲናራት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አግሙስ ፡ ይላል ። ዐሥሩ ፡ አግሙስ ፡ (ሉቃ፲፭ ፡ ፰) ።

**ገሙስ ፤ ጋሙስ ፤(ሱር ፡ ጋሙሽ)፤** ጐሽ ፡ ቀንደ ፡ ኹል ፡ የበረሓ ፡ እንስሳ ፤ መልኩ ፡ የላም ፡ የበሬ ፤ ጠባዩ ፡ ያውሬ ፤ እንዳንበሳና ፡ እንደ ፡ ነብር ፡ ዐዳኙን ፡ የሚያ ፡ የሚከተል ፡ በቀንዱና ፡ በግሩ ፡ የሚበቀል ። ወይሴሰይ ፡ እምሐሊብ ፡ ገሙስ ፡ እሱ ፡ እሙ



ገሙስ ፡

ንቱ ፡ አልሕምት ፡ ጸሊማን ፡ ዘገዳም ፡ (ስንክ ፡ መስ፳) ። ዘገዳም ፡ ማለቱ ፡ ግብጦችና ፡ ህንዶች ፡ የሚያልቡትና ፡ የሚጠምዱት ፡ ጠጕረ ፡ ሥሥ ፤ ቀንደ ፡ ገባሳ ፤ ሻኛ ፡ የሌለው ፡ ገራም ፡ ጭምት ፡ የቤት ፡ ጐሽ ፡ አለና ፡ ከዚያ ፡ ሲለይ ፡ ነው ።

**ገሚት ፤ ቶት ፤(ገመተ ፡ ይገምት ፡ ይግምት)፤** መገመት ፡ መገምገም ፤ ይህን ፡ ያኽል ፡ ማለት ።

**ገመታ ፤** ግምጋሚ ፤ ግምት ፡ የጭገሬታ ፡ ለውጥ ። በእንተ ፡ ተዓስቦ ፡ ቤት ፡ ወውሂበ ፡ ንዋይ ፡ ለምድር ፡ ዘከመ ፡ ገመታ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ።

**ጐማሚት ፤** ታላቅ ፡ ጐምቱ ፡ እባብ ፡ ዐይጥ ፡ የሚውጥ ፡ የሚሰለቅጥ ፡ ባላገሮች ፡ ጐማሚት ፡ ገና ፡ የሚሉት ።

(ጥ) **ጌና ፤—ገና ፡ ልደት ፤—ገኒን ፡ ገነ ።**

**ጎን ፤—መልክ ፤—ገወን ።**

**ገነበ ፤(ዕብ ፡ ጋናብ ፤ ሰረቀ)** ፤ ገነባ ፡ ግንብ ፡ ሠራ ፤ ወይም ፡ አፈረሰ ፤ ቈፈረ ፡ ሰረሰረ ፤ ለመስረቅ ። መግንባት ፡ የሽክላንና ፡ የጡብንም ፡ ሥራ ፡ ያሳያል ። ገንቦ ፡ ገንቦኛ ፡ እንዲሉ ።

**ተገንበ** ፤ ተሠራ ፡ ተገነባ ፤ ገንቦው ፡ ግንቡ ።

**ግንበት ፤(ታት)** ፤ ገንቦ ፡ ዳብሬ ፡ ደሮ ፡ ርኮት ፡ ሬዎት ፤ ታናሽ ፡ ቀርበታ ። **ወወሀበታ ፡ ሲወለታ ፡ ትጹር ፡ ግንባተ ፡ ወይን ፡**(ዮዲ ፲ ፡ ፭) ።

**ግንቦት** ፤ ስመ ፡ ወርኅ ፤ ታስዕ ፡ እመስከረም ፡ ገቦ ፡ ክረምት ፡ ጎረ ፡ ክረምት ፤ ገቦንና ፡ ጻዲን ፡ እይ ። በግንቦ ፡ ዘይቤ ፡ ቢፈቱት ፡ ግን ፡ ወርኅ ፡ ሡራሬ ፡ ያስኛል ፤ የባቢሎን ፡ ግንብ ፡ ሳይቀር ፡ ፪ቱ ፡ መቅደሶች ፡ በግንቦት ፡ ተመሥርተዋል ፡ (፫ነገ ፡ ፮ ፡ ፩ ። ዕዝ፫ ፡ ፰—፲፫) ። ያገዳን ፡ እኽል ፡ ገነበበ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከገነበ ፡ ሥር ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ጕንባሕ ፤(ዐረ ፡ ጁንቡሕ ፤ ወፍራም ፡ ረኸም)** ፤ ጕ ፡ ንባሕ ፤ ጕ ፡ ጕ ፡ እያለ ፡ የሚጮኽ ፡ ታላቅ ፡ አሞራ ፤ ርኩም ፤ ወይም ፡ የርኩም ፡ ዐይነት ፡ ሌላ ። ያፈ ፡ ጕንባሕ ። አበ ፡ ጕንባሕ ፤ አባ ፡ ጕንባሕ ፤ የጩኽት ፡ ባለቤት ፡ (ፊላስ ፡ ገ፲፮ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፲፰) ። ትግሮች ፡ ግን ፡ አባ ፡ ጕንባሕ ፡ ማለት ፡ ጕንባሳ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። አብ ፡ አባ ፡ ካልተጨመረ ፡ ጕንባሕ ፡ ብቻ ፡ ርኩምነቱን ፡ አያሳይም ፤ ማእከላይ ፡ ስም ፡ ነው ። ስምነቱም ፡ ከገነበና ፡ ከነብሐ ፡ ከኹለቱ ፡ ሥር ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ ነብሐን ፡ እይ ።

**ገነደ ፤ዶት ፤(ገነደ ፡ ይገንድ ፡ ይጕንድ)** ፤ መጕነድ ፤ ጕንድ ፡ ጕናዲ ፡ መኾን ፤ ጕገ ፡ መውጣት ፤ ሰብቻ ፡ መቆም ፡ መተከል ፤ ራስን ፡ መቻል ፤ መወፈር ፡ መደንደን ፤ የዛፍ ፡ የሰው ።

**ጕኑድ ፤(ዳን ፡ ዳት ፡ ንድ)** ፤ የጕነደ ፤ ጕንድ ፡ የኾነ ፡ የደነደነ ። **ሕ ፡ ሕብዳን ፡ ወጕኑዳን ፡ ልብ ፡** (መጽ ፡ ምስ) ።

**ጕንድ ፤(ዳት ፡ አጕናድ)** ፤ በቁሙ ፤ ግንድ ፡ በሥርውና ፡ በዐጽቅ ፡ መካከል ፡ ያለ ፤ ሥሩም ፡ ሳይቀር ፤ ወፍራም ፡ ደንዳና ፤ የኖረ ፡ የቈየ ፤ የዘገየ ፡ ዕንጨት ። **ሥርዎ ፡ ወጕንዶ ። ጕንደ ፡ ወይን ። ጕንደ ፡ ዐፀው ። ወሰበ ፡ ሐሐቲ ፡ ጕንድ ፡ በበ ፡ ሠላሳ ፡ ወአሐጹ ፡ እ**



ጕንድ ፡

**ልፍ ፡ አዕጹቂሃ ። ጕንዳት ። አጕናደ ፡ በቀልት ፡** (ዮሐ፲፭ ፡ ፩ ። ማቴ፫ ፡ ፲ ። ቀሌ ። ሔኖ፳፫ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ ሚያ፳፫) ።

**—** ፤ ሥር ፡ መብቀብያ ፡ ወገብ ፡ አጠገብ ፤ ወይና ፡ ደጋ ። **አዘዘ ፡ ያውቅዩ ፡ ልሳና ፡ እምጕንዱ ። እምጕንደ ፡ ደብር ። አሰርዎ ፡ ጕንደ ፡ ደብር ፡** (ስንክ ፡ መስ፳ ። ጥቅ፲፰ ። ዮዲ፮ ፡ ፲፱ ። ፮ ፡ ፲፫) ።

**ጕንደ ፡ ዳዊት** ፤ ወገነ ፡ ዘር ፡ የትውልድ ፡ ሥር ፡ (አርጋ ፡ ፩) ።

**ጕንደ ፡ ማእሰር** ፤ እግር ፡ ግንድ ፡ (ግብ፲፮ ፡ ፳፬) ።

**ጕንደ ፡ ማኅፈድ** ፤ የግንብ ፡ ዐምድ ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ የቆመ ፤ ወይም ፡ ወገቡ ፡ መካከሉ ፡ (ሄርማ) ።

**ጕንዶ ፡(ዐማርኛ)** ፤ ታላቅ ፡ የማር ፡ መስፈሪያ ፡ ፲፮ ፡ ነጥር ፡ የሚይዝ ። ጕንዶ ፡ ማር ፡ እስጥ ፡ እንዲሉ ።

**ገንደበ ፤(ትግሬ)** ፤ አረጀ ፡ ገንጀበ ፡ ገንጃባ ፡ ኾነ ።

**ጕንደየ ፡(ተቀ ፡ ግ)** ፤ ቈየ ፡ ዘገየ ፡ ሰነበተ ፤ ሥር ፡ ያዘ ፤ ቀረ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አለ ፤ ኖረ ፡ ተቀመጠ ። **ጕንደየ ፡ እንዘ ፡ ይጕደጕድ ። ኢይጕንዲ ፡ ንዋዩ ። ወልድየሰ ፡ ሞተ ፡ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ጕንደየ ። ኢትጕንዲ ፡ ውስተ ፡ መካና ። ጕንደዩ ፡ አንጾኪያ ። ከመ ፡ ኢይጕንዲ ፡ ውስተ ፡ እስያ ፡** (ግብ፲፪ ፡ ፲፮ ። ኢዮ፲፭ ፡ ፳፱ ። ጦቢ፲ ፡ ፩ ። ምሳ፱ ፡ ፲፰ ። ግብ፲፬ ፡ ፳፰ ። ፳ ፡ ፲፮) ። በጕንደየ ፡ ፈንታ ፡ ተጕናደየ ፡ ይላል ። **ኢትትጕናደይ ፡ ላዕለ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ። ኢመፍትው ፡ ንትጕናደይ ፡ ተጠምቆ ። ሶበ ፡ ተጕናደየ ፡ ሞተ ፡ አቡሁ ፡ ፈቀደ ፡ ይቅትሎ ፡** (ፊላስ ። አፈ ፡ ተ፲፫ ። ዮሴፍ) ።

**ጕንዱይ ፤(ያን ፡ ያት ፡ ዲት)** ፤ የቈየ ፡ የዘገየ ፤ የሰነበተ ፡ የኖረ ፤ ዳ ፡ ያለ ፡ ዳተኛ ፤ ዝግተኛ ። **ጕንዱይ ፡ ሰነቢብ ፤ ጕንዱይ ፡ ሲመዐት ። ጕንዱየ ፡ መዐት ። ጕንዱያነ ፡ ልብ ፡**(ያዕ፩ ፡ ፲፱ ። ነሐ፱ ፡ ፲፮ ። ሉቃ ፳፬ ፡ ፳፭) ። ብዙ ፡ እጅግ ፡ ዐያሌ ። **እሕየው ፡ ጕንዱየ ፡ ዓመተ ። እምጕንዱይ ፡ ዕለት ። በጕንዱይ ፡ መዋዕል ። እምድኅረ ፡ ጕንዱይ ፡ መዋዕል ፡** (ኢዮ፳፱ ፡ ፲፰ ። ሮሜ፲፭ ፡ ፳፫ ። ኢሳ፵ ፡ ፳፯ ። ኤር፲፫ ፡ ፯) ።

**ጕንዱየ** ፤ ቈይቶ ፡ ሰንብቶ ፤ አዝግሞ ፡ ዝግ ፡ ብሎ ። **መጽአ ፡ ጕንዱየ ፤ ሖረ ፡ ጕንዱየ ።**

**አጕንደየ** ፤ አቈየ ፡ አዘገየ ፡ አስቀረ ። **ያጕንዲ ፡ ከመ ፡ ዘኢይሁብ ። አበየ ፡ ወአጕንደየ ። አንከርኩ ፡ አጕንድዮተከሙ ፡ ትእዛዘ ፡ ንጉሥ ። ኢያጕንዲ ፡ እግዚ ፡ ቃለ ፡ ዘነበበ ፡** (ቅዳ ፡ ግሩ ። ሉቃ፲፰ ፡ ፬ ። ዮሴፍ ። ፪ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፱) ። በአጕንደየ ፡ ፈንታ ፡ አስተጕናደየ ፡ ይላል ፤ አያስኬድም ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**አጕንዳዪ ፤ መጕንድይ** ፤ የሚያቈይ ፡ የሚያዘገይ ፤ ዙሪያ ፡ ጠማማ ። **እሰ ፡ የሐውሩ ፡ ጕንዱየ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ መጕንድይ ፡** (ፊልክ ፡ ፲፬) ።

**ጕንዳን** ፤ በቁሙ ፤ ዝግተኛ ፡ ታናሽ ፡ ጥቍር ፡ ትንኳሽ ፡ ተናካሽ ፡ ተቈናጣጭ ።

**ጐንደር ፤** ጕንደ ፡ ሀገር ፤ የፋሲል ፡ ከተማ ፡ ከግ ራኝ ፡ በኋላ ፡ የቀናች ፡ ባላ፴፱ ፡ ደብር ፤ ዳግም ፡ ግራኝና ፡ ግልስ ፡ ግራኝ ፡ (ቱዎ ፡ ደር) ፡ ተከታትለው ፡ እስኪያጠ ፍት ፡ ድረስ ፡ መናገሻ ፡ ታላቅ ፡ መዲና ፡ የነበረች ።

**ገንዶር ፤** ጕንደ ፡ እግር ፤ ማእሰረ ፡ እግር ፤ የ ግር ፡ ግንድ ፡ የንጨት ፡ ዛንጅር ። ወስከምት ፡ የቀንበር ፡ ዐይነት ፤ መንቁር ፡ ባላ ፡ እንዝዝላ ፡ የወይፈን ፡ መቅጫ ። አዘዘ ፡ ይደዩ ፡ ውስተ ፡ ከሣይሙ ፡ ጋጋተ ፡ ወገንዶ ራተ ፡ ውስተ ፡ እገሪሆሙ ፡ ወይሰድዎሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ። አክብድ ፡ ገንዶራቲሁ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ ፳፱ ። ሚራ፴ ፡ ፴፫) ።

**ገንዶር ፤** ግንደ ፡ ቁርቍር ፡ ጢንዝዛ ፤ በዚ ያው ፡ በግንዱ ፡ ውስጥ ፡ ማር ፡ የሚሠራ ፤ ወይም ፡ የጢ ንዝዛ ፡ ወገን ፡ ሌላ ፡ ጥቍር ፡ ደረቅ ፡ ራሰም ፡ ሸከራ ።

**ገንዎ ፤ ዎት ፤ (ገነወ ፡ ይጌኑ ፡ ይገኑ ። ዐረ ፡ ጀነ) ፤** መጀንን ፤ ጋኔን ፡ መሳብ ፤ ለጋኔን ፡ ለጣ ዖት ፡ መገዛት ፡ ማገልገል ፤ ካህን ፡ ጣዖት ፡ መኾን ፡ መ ባል ። ገንየንና ፡ ገኒንን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ናቸው ።

**ገናዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ነውት) ፤** የተጀንን ፡ የሚጀንን ፤ ጋኔን ፡ ሳቢ ፤ ዘራም ፡ ጋኔናም ፡ ካ ህን ፡ ጣዖት ፡ ነቢየ ፡ ሐሰት ። ገናዊ ፡ አማልክት ። ገነ ውቱ ፡ ለቤል ። ገነውቱ ፡ ለዳጎን ። ወገብረ ፡ ገነውተ ፡ አማልክት ፡ (ቄስጠ ፡ ፳፯ ። ዳንኢ፫ ፡ ፰ ። ፩ነገ ፡ ፰ ፡ ፰ ። ፫ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፴) ።

**ገንዜ ፤** ስመ ፡ ሀገር ፡ በኤፌሶን ፡ ውስጥ ፡ ያለች ፡ መከነ ፡ ጉባኤ ፡ (ቀረ ፡ ቄር) ።

**ገኒዝ ፤ ዘት ፤ (ገነዘ ፡ ይገንዝ ፡ ይግንዝ ። ዕብ ፡ ጋናዝ ፤ ቀበረ ፡ ሰወረ) ፤** መገንዝ ፡ መከፈን ፤ መጠቅለል ፡ መሰፈፍ ፤ ማልበስ ፡ ማጕናጠፍ ፤ ማሰር ፡ መቋጠር ፡ መከተት ፡ የሬሳ ፡ የገንዘብ ፡ (ማቴ፳፯ ፡ ፶፱ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፵) ። ገነዝ ፡ ሴት ፡ ወአንበሮ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ። ምስለ ፡ አፈዋት ፡ ገነዘ ፡ ወቀበረ ፡ በድዎ ። ኢትግን ዝዎ ፡ እስመ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ። ሶበ ፡ ሞተት ፡ ብእ ሲት ፡ በወሊድ ፡ ይኅፅብዋ ፡ ወይግንዝዋ ፡ በካልእ ፡ ልብስ ። (ግጥም) ፤ አጥበው ፡ ገንዘው ፡ ሲሰጡት ፤ ምን ፡ ይበላ ፡ መሬት ፡ (ቀሌ ። ስንክ ፡ ነሐ፳ ። ባሮክ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳፱) ።

**ገናዚ ፤ (ዚት ፡ ዝያን ፡ ያት) ፤** የሚገንዝ ፡ ገናዥ ፤ አማዋች ፡ ቀባሪ ፡ ከታች ።

**አግንዘ ፤** አስገነዘ ፡ አስከፈነ ፤ አስከተተ ። ለዐ ሩቅ ፡ ኢያልበሱ ፡ ወነዳያን ፡ እሙ ፡ ይመውቱ ፡ ኢያግ ንዘ ፡ ወኢያቀብረ ፡ (ራእ ፡ ማር) ።

**ተገንዘ ፤** ተገነዘ ፡ ተከፈነ ፤ ተሰወረ ፡ ተቀበረ ። ትግንዙ ፡ በእደ ፡ መላእክት ። ሞተኒ ፡ ወተገንዘ ፡ (ገድ ፡ ዘሚ ። ቄር) ።

**ግኑዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ንዝት) ፤** የተገነዘ ፡ ግ ንዝ ፡ ስውር ፡ ድብቅ ፡ ሽፉን ። ሶበ ፡ ታወፅእ ፡ ለግኑዝ ። ከሣቴ ፡ ትምህርት ፡ ግኑዝ ፡ (ግንዘ ። ስንክ ፡ ታኅ፳፰) ።

**ግንዘት ፤ (ዐረ ፡ ጅናዝ ፤ ፍታት) ፤** መገ ነዝ ፡ (ጥገ) መገነዝ ፡ አገናነዝ ፡ ግነዛ ፤ ግንዘት ። ግንዘተ ፡ ሥጋኪ ፡ በመዋጥሐ ፡ ክታን ። ገነዘ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ግን ዘተ ፡ ሠናየ ። ይሜኒ ፡ ግንዘተ ፡ ደናግል ፡ (ደራሲ ። ስ ንክ ፡ ሐም፮ ፡ መስ፲፱) ።

—፤ የመቃብር ፡ ሸማ ፡ ከፈን ፤ ሣጥን ፡ ስሌን ። ሬሳ ፤ የሬሳ ፡ ምስል ፡ አጐበር ፡ ዐልጋ ። የፍታት ፡ መጽሐፍ ። ያቅድም ፡ ሜጠ ፡ ግንዘቶ ። ይሕሩር ፡ ቅድመ ፡ ዐራተ ፡ ግንዘቱ ። ነሥአት ፡ ግንዘቶ ፡ ወገነዘቶ ። አሠረ ፡ ግን ዘቶ ፡ ተኀድገ ። ግንዘት ፡ ዘይትነበብ ፡ ላዕለ ፡ ሙታን ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፵፱ ፡ ፩ ። ፳፪ ። ፩ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፳፫ ። ግንዘ ፡ ገ፩) ።

**መግነዝ ፤ (ብ ፡ መጋንዝ) ፤** በቁሙ ፤ መገ ነዣ ፡ የውስጥ ፡ የአፍኣ ፡ ልብስ ፡ ፈትል ፤ ሽቱ ፡ ሣጥን ፡ ለሬሳ ፡ የሚገባ ፡ ኹሉ ። አዘዘ ፡ እስክንድር ፡ ከመ ፡ ይ ግንዝዎ ፡ ለዳራ ፡ በሠናይ ፡ መግነዝ ። ኢሠነቀ ፡ እም ንዋይከ ፡ ዘእንበለ ፡ መግነዝ ። ዠሎ ፡ መፍቅደ ፡ መግ ነዝ ። ገነዘቶ ፡ በአልባስ ፡ ሠናያት ፡ ወገብረት ፡ ሎቱ ፡ መልዕልተ ፡ መግነዙ ፡ ልብሰ ፡ ዘወርቅ ፡ ወአንበረቶ ፡ በማጹን ። ጠብለለ ፡ ልደቶ ፡ በመግነዝ ፡ ኀቡአቲሁ ፡ ከመ ፡ ኢያእምርዎ ፡ ፍጡራን ፡ (ዮሴፍ ። ግንዘ ። ገድ ፡ ላሊ ። ስንክ ፡ ሐም፳፱ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ግንዜን ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ልብስ ፡ መግነዝ ። ገር ዜንን ፡ እይ ፤ ንና ፡ ር ፡ ስለ ፡ ተዋረሱ ፡ ገረዘ ፡ ወስደታል ።

**ግንዘብ ፤ (ሱር ፡ ግኑዝበ) ፤** በቁሙ ፤ መድ ፍን ፡ የተቀበረ ፡ ወርቅ ፤ ወይም ፡ በሣጥን ፡ የሚደበቅ ፡ (ዲድ ፡ ፮) ። ብ ፡ ከዘገበ ፡ መጥቶ ፡ በገንዘ ፡ ላይ ፡ ተደ ርቢል ።

**ገኒሕ ፤ ሐት ፤ (ግንሐ ፡ ይገንሕ ፡ ይግ ናሕ ። ዕብ ፡ ጋናሕ) ፤** መገንታት ፡ መጮኽ ፡ መቈ ጣት ፤ ድምፅን ፡ ማግነን ፡ ቃልን ፡ ማበርታት ፤ መቃበይ ፡ መዥራት ፤ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ማውጣት ። ገሠጸ ፡ እግዚ ፡ ለዳዊት ፡ በቃለ ፡ ነቢይ ፡ እንዘ ፡ ይገንሕ ። ወትገን ሖሙ ፡ ለኃጥኣን ፡ በቃለ ፡ ስክየት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ቅዳ ፡ ያዕ) ። ጕሀንን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ገናሒ ፤ ግኑሕ ፤** የሚቈጣ ፡ ቍጡ ፤ ጩኺ ፡ ተሳዳቢ ።

**ግናሕ ፤ (ዕብ ፡ ግኒሓ) ፤** ጩኸት ፡ ቡታ ፡ እሪታ ፤ ታላቅ ፡ ድምፅ ፤ ቍጣ ፡ ተግሣጽ ፤ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ስድብ ፤ ብርቱ ፡ ትእዛዝ ፡ የዥራትና ፡ የትቢት ፡ ቃል ፤ የሚገባ ፡ የማይገባ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ አኮ ፡ ዘይትናገ ረክሙ ፡ በቃለ ፡ ግናሕ ፡ ከመ ፡ መኰንን ፡ ወከመ ፡ ሊቅ ፡ ዐቢይ ። ክኑ ፡ ድንዙዛነ ፡ እንዘ ፡ ይትሜከሑ ፡ ወደለዎ ፡ ከመ ፡ ይትናገሮሙ ፡ በቃለ ፡ ግናሕ ፡ ዘይ ሐምም ። በትዕቢተ ፡ ፀር ፡ ወበግናሕ ፡ (አፈ ፡ ተ፱ ። ድርሳ፳ ። ቄር ፡ ገ፯) ።

**ግናሓት ፤ አግናሕ ፤** ጩኸቶች ፡ ቍጣዎች ፡ ተግሣጾች ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ። ወይእዜኒ ፡ ኀቤከ ፡ ነገ ርየ ፡ ዘልዑለ ፡ ታሌዕል ፡ አግናሒነ ፡ ላዕለ ፡ ዠሉ ፡ (ተ

ረ ፡ ቁርጃ) ። መተርጐማን ፡ ግን ፡ አግናሒ ፡ ብለው ፡ ጥሬውን ፡ በቅጽልንት ፡ ይፈቱታል ።

**ግንታ** ፤ ቀንዳ ፡ መለከት ፡ ቱልቱላ ፡ ግንትቶ ፡ የሚሰማ ኽ ። ዐዊዶሙ ፡ ምስለ ፡ ግንታ ፡ ወግርጣጥ ፡ በክበሮ ፡ ወጸናጽል ፡ (ቃሬ ፡ እ፲) ።

**ጋን ፤ (ትግሬ)** ፤ ታላቅ ፡ እምራ ፡ ጋን ፡ የሚ ያኽል ፡ ፊሺ ፡ ልዑል ፡ ቃል ፡ (ራእ፮ ፡ ፺ ። ፳ ፡ ፲፫) ።

**አግንሐ** ፤ አስፈሰኽ ፡ አስቈጣ ፤ አናገረ ።

**አግናሒ ፤ መግንሒ ፡ ሒ** ፤ የሚያስፈስኽ ፡ የሚያስቈጣ ፤ አስቈጭ ፡ አናጋሪ ።

**ግንሕ ፤ አው ፡ ግንዕ ፤ (ዓት ፤ አግንዕት)** ፤ ጋን ፡ ገናና ፡ ታላቅ ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፤ የጠላ ፡ የጠጅ ፡ መጥ መቂያ ፤ የልብስ ፡ ማጠቂያ ። የጋን ፡ ሸማ ፡ እንዲሉ ። ግንዐ ፡ ወልጕነ ፡ (ጎድ ፡ ተክ) ።

—፤ ላመ ፡ ፈጅ ፡ ጽህርት ፤ ታላቅ ፡ የብረት ፡ ድስት ። ግንዐ ፡ ዐቢይ ፡ ዘብርት ፡ (ስንክ ፡ ሐምሮ) ። ጃን ፡ ሆይ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ጋን ፡ ጃ ፡ ማለት ፡ ያረቦች ፡ ልማድ ፡ ነው ።

**ግንይ ፤ የት ፤ (ገነየ ፡ ይገኒ ፡ ይግኒ ፤ አው ፡ ግንየ ፡ ይገኒ ፡ ይግነይ ። ዐረ ፡ ጀነአ ። ሱር ፡ ግናአ ። ዕብ ፡ ከናዕ)** ፤ መገዛት ፡ ማጕንበስ ፡ መስገድ ፤ መዋረድ ፡ መታዘዝ ፡ ማገልገል ፤ መጸለይ ፡ ማመ ስገን ፤ መየበብ ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ፤ መለማመጥ ፡ ማቈ ላመጥ ። ምስጢሩ ፡ ፱ ፡ ነው ፤ መገዛትና ፡ የመገዛት ፡ ሥራ ። ወሰጽድቀ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ ስእኑ ፡ ገንየ ። ግነዩ ፡ ወስግዱ ። እፎ ፡ ሠመርክሙ ፡ ከመ ፡ ትግነዩ ፡ ለአቢባል ። ዙሉ ፡ ልሳን ፡ ይገኒ ፡ ለእግዚ ። እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ በዙሉ ፡ ልብየ ። ወነዳይሰ ፡ ሰሲሁ ፡ ይትገፋዕ ፡ ወሰሲሁ ፡ ይገኒ ፡ (ሮሜ፲ ፡ ፲ ። ዳን፲ ፡ ፳ ። ዮሴፍ ። ኢሳ፵፭ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፱ ። ሚራ፲፫ ፡ ፲) ። በግነየ ፡ ፈንታ ፡ ተጋነየ ፡ ይላል ፤ በጕንደየ ፡ ፈንታ ፡ ቶጐናደየ ፡ እንዲል ። እትጋነይ ፡ ለብእሲትየ ። እንዘ ፡ ይትጋነይ ፡ ላቲ ። ተጋነይ ፡ ሶበ ፡ ትኤብስ ። ተጋነየ ፡ ለገጸ ፡ እግዚ ። ተጋነዩ ፡ ወስገዱ ፡ ቅድሜሁሙ ። ስኢል ፡ ወተጋንዮ ፡ (ኢዮ፲፱ ፡ ፲፯ ። አስቴ፯ ፡ ፰ ። ሚራ፲፰ ፡ ፳፩ ። ፩ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፱ ። ቀሌ ። ሕጢሞ ፡ ፱ ፡ ፭) ።

—፤ መገኘት ፡ መምጣት ፡ መፈጠር ፡ መወለድ ፡ (ዐማ ርኛ) ።

**ገናዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ነይት)** ፤ የሚገዛ ፡ ተገዥ ፡ ሰጋጅ ፡ አመስጋኝ ።

**ግኑይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ኒት)** ፤ የተገዛ ፡ ትሑት ፡ አገልጋይ ፡ (አርጋ) ።

**ግናይ ፤ (ያት)** ፤ አገልግሎት ፡ አገዛዝ ፡ ምስ ጋና ፡ ቍልምጫ ፡ ልመና ፤ የመዝሙር ፡ ስም ፡ ግነዩ ፡ ግነዩ ፡ የሚል ። ሕይት ፡ ግናይ ፡ ወሕይት ፡ ሕኰቴት ። ግናይ ፡ ለክሙ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ። ዘለከ ፡ ስብሐት ፤ በጊዜ ፡ ወግናይ ። ያቅርብ ፡ ለእግዚ ፡ መሥዋዕተ ፡ ስብሐት ፡ ወግናየ ፡ ጸሎታት ። እምድኅረ ፡ አንበቡ ፡ ወዘመሩ ፡ ግናየ ፡ ስብሐት ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ ። ደራሲ ። ቄ ድር ። ኪዳ ። ፪ዜና ፡ ፳ ፡ ፳፪) ።

—፤ ረድፍ ፡ ተራ ፤ የመዘምራን ፡ ክፍል ፡ በድሩ ፡ ድር ድሩ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ኹኖ ፡ ግናያትን ፡ እየደገመና ፡ እያ ዜመ ፡ እያስተዛዘለ ፡ የሚኼድ ፡ የሚያውድ ። ወአቀምኩ ፡ ክልኤተ ፡ ግናያተ ፡ ዐበይተ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ ይምነ ፤ ወካልእ ፡ ግናያት ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ ፀግመ ፤ ወአነ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ (ነሐ፲፪ ፡ ፴፩ ፡ ፴፰) ። መዘምራኑን ፡ ግና ያት ፡ ያሰኛ ፡ የመዝሙሩ ፡ ስም ፡ ነው ።

**ግናይ ፤ (ዕብራ ፡ ወትግሬ)** ፤ ጕድ ፡ ድ ንቅ ፤ ጕባጣ ፡ ተርከሳ ፤ ፀጕር ፡ ግጕር ፡ ድንክ ፡ ኩሳሳ ፤ ልምሾ ፡ ዐንካሳ ፤ ዕውር ፡ ጠንባሳ ፤ ምንጕግ ፡ ጎሱር ፡ ሕ ሡምም ፡ ጥፉ ፤ መልክ ፡ ክፉ ። (ግጥም ፡ ትግሪኛ) ፤ ሰበ ይቲ ፡ እንግዳ ፡ ግናይ ፡ ወሊዳ ። ጕድ ፡ ለክፋም ፡ ለበ ጎም ፡ ለብርቅና ፡ ለድንቅ ፡ ይነገራል ፤ እንደ ፡ ታም ራት ፡ ነው ። (ግጥም) ፤ የሚጣቅ ፡ ዐማኒል ፡ ያንተ ፡ ጕድ ፡ አያልቅም ፤ የፈረስ ፡ ገባ ፡ እንደ ፡ ጨርቅ ፡ ስትጠቅም ።

**አግነየ** ፤ አስገዛ ፡ አሳመነ ፤ አሰገደ ፡ አስመሰገነ ። (አገኘ ፡ አስገኘ) ። አግነዮሙ ፡ ለትእዛዘ ፡ ሮም ። ወል ድኒ ፡ ይገኒ ፡ ለዘአግነየ ፡ ሎቱ ፡ ዙሉ ። ዘአናብስተ ፡ ታገኒ ፡ ወአራዊተ ፡ ትቀኒ ፡ (ዮሴፍ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፳፰ ። ስንክ ፡ መጋ፳) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአግነየ ፡ ፈንታ ፡ አስ ተጋነየ ፡ ይላል ። ምሉአ ፡ ሞገስ ፡ ዮሐንስ ፡ እንተ ፡ ታስ ተጋኒ ፡ ድበ ፡ (ደራሲ) ።

**ተጋነየ ፤ (ገነየ)** ፤ ተገዛ ፡ ታዘዘ ፤ ተለማመጠ ። ተገናኘ ፤ እጅ ፡ ነሣ ፡ ሰገደ ፤ ጨማማ ፡ ሳመ ። ተገናኘ ፡ ከማ ለት ፡ በቀር ፡ ሌላው ፡ አፈታት ፡ ለገነየ ፡ እንጂ ፡ ለተጋነየ ፡ አይስማማም ።

**አስተጋነየ** ፤ አገናኘ ፡ አገናኛኘ ።

**ጐንከ ፤ ከት ፤ (ጐነከ ፡ ይጔንክ ፡ ይጐ ንክ)** ፤ መሰብሰብ ፤ መጐቶት ፡ መሰንደቅ ፤ መከመር ፡ መቈለል ፡ ቤት ፡ ማስመሰል ፤ ወይም ፡ እያሰሩ ፡ መሸ ከም ፡ መደብለል ፤ የነዶ ፡ የማር ። ያከይዱ ፡ ወይነ ፡ ወይጔንኩ ፡ ክላስስተ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ (ነሐ፲፫ ፡ ፲፭) ።

**ጐናኪ ፤ (ኪት ፡ ካያን ፡ ያት)** ፤ ሰብሳቢ ፡ ሰንዳቂ ፤ ከማሪ ፡ ቈላይ ፡ ተሸካሚ ።

**ተጐነከ** ፤ ተከመረ ፡ ተቈለለ ። ተጐነኩ ፡ ክ ምረ ፡ ሥርናይ ። ይዌግርዎ ፡ እስከ ፡ ይትጔነኩ ፡ እብን ፡ ዲበ ፡ እብን ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ግኒን ፤ (ዐረ ፡ ጀኒን)** ፤ ገል ፡ ጭንጋፍ ፤ የተ ናቀ ፡ ወራዳ ፡ ታናሽ ፡ ርካሽ ። ሊትሚጣ ፡ በሜጠ ፡ ገኒን ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፰) ።

**ጋኔን ፤ (ብ ፡ አጋንንት ። ዐረ ፡ ጂን ፤ ጃን ። ዕብ ፡ ሼድ)** ፤ በቁሙ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፤ ዲያ ብሎስ ፡ የዲያብሎስ ፡ ጭፍራ ፤ ክፉ ፡ ጨካኝ ፡ ዕቡይ ፡ የሚያሳብድ ፤ ከባሕር ፡ ከገደል ፡ የሚሰድ ፡ ከምድር ፡ የሚ ፈጭ ፡ የሚያንቈጠቍጭ ፤ ከእሳት ፡ የሚጥል ፡ የሚያን

ከባልል ፡ የሚያስፈጥጥና ፡ የሚያስገጥጥ ፤ የሚያንቅ ፡ የሚያስጨንቅ ፤ እንደንጨት ፡ የሚያደርቅ ። ምስጢሩ ፡ ትቢትና ፡ ጨክኝነት ፡ ነው ፤ ባለመጣፎች ፡ ግን ፡ ሩቅ ፡ ውዱቅ ፡ ጥንብ ፡ ሸጋታ ፡ ይሉታል ፡ (ማርኳ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ፡ ፳፪ ። ፳፬ ፡ ፲፰) ። **ጋኔን ፡ እኩይ ። ጋኔነ ፡ ቀትር ። ጋኔን ፡ ርኩስ ። በመልአከሙ ፡ ለአጋንንት ፡ ያወፅእሙ ፡ ለአጋንንት ፡** (ጦቢ ፡ ፮ ። መዝ ፡ ፺ ። ራእ ፲፰ ፡ ፪ ። ማቴ ፱ ፡ ፴፬) ።

(ጥ) **ጊኑይ ፤** ገናዊ ፤ ጋኔናም ፤ ጋኔን ፡ ያደረበት ፡ እብድ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፲፭) ። ገነወን ፡ እይ ።

**ጋኔናይ ፤ ዊ ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፤ ዘጋኔን ። **እንስሳ ፡ ጋኔናዊ ፤ ሰው ፡ ሰብድ ።** የሚወገሽ ፡ ተዋጊ ፡ ደንባሬ ፡ ጋግርታም ፡ ወይም ፡ አበያ ፡ ደደብ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፫) ።

**ገነ ፤ (ይገንን ፡ ይግንን ፤ ገኒን ። ዕብ ፡ ጋናን) ፤** ገነነ ፤ ገናና ፡ ኾነ ፤ ታበየ ፡ ኰራ ፡ ተንጠራራ ። ተከለ ፡ ጋረደ ፡ መከተ ፤ ዐጠረ ፡ ቀጠረ ። መገን ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ጋሻ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ገነገነና ፡ ጕንጕንም ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ ማስነቱ ፡ ሐውልትና ፡ ገቢር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ።

**አግነነ ፤ (ያገንን ፡ ያግንን) ፤** አገነነ ፤ አጋነነ ፤ አጋናኝ ፡ ኾነ ፤ ቃለ ፡ አጋኖ ፡ እንዲሉ ። አስተከለ ፤ አሳጠረ ፤ አስቀጠረ ፤ አስጠበቀ ።

**ተገነ ፤** ተተከለ ፡ ታጠረ ፡ ተቀጠረ ፤ ታከሉ ፡ በታው ።

**ገነት ፤ (ታት ። ዕብ ፡ ጋን ። ሱር ፡ ጋንታ ። ዐረ ፡ ጀነት) ፤** የተከል ፡ ቦታ ፡ ብዙ ፡ ዛፍና ፡ ዕንጨት ፡ ሽቱ ፡ ቅመም ፡ የሚበቅልበት ፤ ምንጭ ፡ ያለው ፡ ውሃ ፡ የሚገባው ፤ የታጠረ ፡ የተቀጠረ ። **ገነት ፡ ዕጹት ። ገነተ ፡ አቅማሕ ። ወበ ፡ ህየ ፡ ገነት ፡ ዐጺደ ፡ ሐምል ። ወውስተ ፡ ውእቱ ፡ ገነት ። ዐቃቤ ፡ ገነት ። ገበርኩ ፡ ሊተ ፡ አዕጻደ ፡ ሐምል ፡ ወገነታተ ፡ ወተከልኩ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ዕፀወ ፡ ዘይፈርዩ ፡** (ማሕ ፬ ፡ ፲፪ ። ዳን ፲፫ ፡ ፯ ። ዮሐ ፲፰ ፡ ፩ ። ፲፱ ፡ ፵፩ ። ፳ ፡ ፲፭ ። መክ ፪ ፡ ፬ ፡ ፭) ።

**—፤** ዓለመ ፡ ጻድቃን ፤ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ የነበሩበት ፤ እግዜር ፡ ያበጀው ፡ ያዘጋጀው ፤ የዕረፍትና ፡ የሕይወት ፡ የተድላ ፡ የደስታ ፡ ቦታ ፤ ስለ ፡ ልዕልናው ፡ ሰማይ ፡ የሚባል ፡ ልዑል ፡ ሀገር ፡ ልዑል ፡ ማኅደር ፡ (ዘፍ ፪ ፡ ፰ ፡ ፱ ። ፫ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ። ፲፫ ፡ ፲ ። ፪ቆሮ ፲፪ ፡ ፪ ፡ ፬) ። **ገነትሰ ፡ በእንተ ፡ ልዕልናሁ ፡ እምድር ፡ ይሰመይ ፡ ሰማየ ፤ ወሐዋርያኒ ፡ ነዋ ፡ ሰመያ ፡ ለገነት ፡ ሰማየ ፡ ሣልሲተ ። ቀዳሚ ፡ ታስ ፡ ይእቲ ፡ ምጽናዓት ፡ እንተ ፡ ይቤ ፡ በእንቲአሃ ፡ እግዚ ፡ በውስተ ፡ ኦሪት ፡ በልሳነ ፡ ሙሴ ፡ ነቢይ ፤ በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ። ወካልእታኒ ፡ ይእቲ ፡ ጠፈር ፡ ዘፈጠጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማእከለ ፡ ማያት ። ወሣልሲት ፡ ይእቲ ፡ ገነት ፡ በከመ ፡ ሰመያ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፤ ወነፍሳቲሆሙ ፡ ለጻድቃን ፡ ይከውና ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይመጽእ ፡ እግዚእ ፡ ለፍዳ ፤ ወአሜሃ ፡ ይከውን ፡ ሎሙ ፡ ተሳትፎ ፡ ምስለ ፡ ክርስቶስ ። ወያጌጹ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ቃለ ፡ እግዚእነ ፡ ለፈያታዊ ፡ ዘየማን ፡ ዮም ፡ ትሄሉ ፡ ምስሌየ ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡** (ፊልክ ፡ ፰ ። ሉቃ ፳፫ ፡ ፵፫) ።

**—፤** መጽሐፍ ፡ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ዜና ፡ አበው ፡ ገድለ ፡ መነኮሳት ። **አስመ ፡ ጸሐፈ ፡ ገነት ፡ ይቤ ። መጽሐፈ ፡ ገነት ፡ ዘጸሐፎ ፡ ጰላድዮስ ፡** (ፊልክ ፡ ፲፯ና ፡ ፴፱) ። በገነት ፡ መልክምና ፡ ክፉ ፡ የሚያሳውቅ ፡ ዕፀ ፡ አእምሮ ፡ እንዳለበት ፤ በዚህም ፡ ጽድቅን ፡ ከኀጢአት ፡ ከሐሰትና ፡ ከምትሀት ፡ የሚያስለይ ፤ ያምላክንና ፡ የመልአክን ፡ መንገድ ፡ ከሰይጣናት ፡ መንገድ ፡ ለይቶ ፡ የሚያሳይ ፡ የሚያስረዳ ፡ የገነትን ፡ ተድላ ፡ የሚያወራ ፡ እንደ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡ የጠራ ፡ ዕውቀትና ፡ ትምርት ፡ ስላለበት ፤ በምሳሌ ፡ ገነት ፡ ብለውታል ፤ ብርሃን ፡ ማለት ፡ ነው ። **አበዊነ ፡ ይሰምይዎ ፡ ለብርሃነ ፡ አእምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገነተ ። ልቡ ፡ ለባሕታዊ ፡ ገነተ ፡ ተድላ ፡ ውእቱ ፡** (አረጋ ፡ ድ ፲፯ ። ፵፯) ።

**ጌና ፤ (ጽር) ፤** ገና ፡ የልደት ፡ ዋዜማ ፤ ድራር ። ገሃድ ፡ ወይም ፡ ልደት ፤ በዓለ ፡ ልደት ። የሴቶች ፡ ገና ፡ የወንዶች ፡ ገና ፡ እንዲሉ ። **እንተ ፡ በዙሉ ፡ ክብርት ፡ ጌና ፡ ዘይእቲ ፡ ልደቱ ፡ በሥጋ ፡** (ተረ ፡ ቄር ፳፰ ። ስንክ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፱) ። ጌንሆይ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ይኸውም ፡ ሲታወቅ ፡ ጽርኡ ፡ ብእሲቶ ፡ ቢል ፡ ጊኒ ፡ ከፋም ፡ እመ ፡ ቤቱ ፡ ቢል ፡ ጌኒ ፡ ይላል ።

**ገንዕ ፤ —ጋን ፤ —ገኒሕ ፡ ገንሐ ፡ ገንሕ ፤ ዕ ።** ዐና ፡ ሖን ፡ እንዲወራረሱ ፡ አስተውል ።

**ገነፈ ፡ (ይገንፍ ፡ ይግንፍ ። ገለፈ) ፤** ጕነፈ ፡ ማለ ፡ መሰለ ፤ ቀረጸ ። ዐጠበ ፡ አጠራ ፤ ወይም ፡ ለማጠብ ፤ ባመድ ፡ በረመጥ ፡ ጕነፈ ፡ ቀቀለ ፤ የልብስ ፡ የሸክላ ። ገነፈ ፡ አገነፈ ፡ አማሰለ ። ገዘሓን ፡ በሙቅ ፡ ውሃ ፡ ዘፈቀ ፡ ነከረ ።

(ጥ) **ገናፍ ፤ ገናፊ ፤ (ጽር ፡ ግናፊስ ። ዕብ ፡ ክቤስ) ፤** ልብስ ፡ ዐጣቢ ። **ዐጺደ ፡ ገናፊ ፡** (፬ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯) ።

**ጕንፋ ፤ (ትግሬ) ፤** በቁሙ ፤ ጕንፋን ፡ ገር ፡ በሽታ ፤ ከከርፋትና ፡ ከትንፋገን ፡ ከክፉ ፡ ሽታ ፡ የሚመጣ ።

**ገንፎ ፤ (ዐማርኛ) ፤** በቁሙ ፤ ገዐት ፡ በውሃ ፡ የበሰለ ፡ዱቄት ፤ የጕንፋን ፡ መድኀኒት ። (ተረት) ፡ ለጕንፋን ፡ ምሱ ፡ ገንፎ ፡ በትኩሱ ።

**ግንፋል ፤ (ላት) ፤** የጡብ ፡ ጭቃ ፡ የተቦካ ፡ የተገነፈ ። ጡብ ፡ የሸክላ ፡ ዐይነት ፡ ደንጊያ ፤ ከጭቃ ፡ ተሠርቶ ፡ በፀሐይ ፡ ደርቆ ፡ በእሳት ፡ የሚበስል ፡ የሚፈተን ፡ ለሕንጻ ፡ የሚኾን ። **ንጥፋሕ ፡ ግንፋለ ፡ ወናብስሎ ፡ በእሳት ። በጽቡር ፡ ወበግንፋል ። ወድቀ ፡ ግንፋል ። ንሣእ ፡ ግንፋለ ፡ ወሠዐል ፡ ላዕሌሃ ፡ ሀገረ ፡** (ዘፍ ፲፩ ፡ ፫ ። ዘፀ ፩ ፡ ፲፬ ። ኢሳ ፱ ፡ ፲ ። ሕዝ ፬ ፡ ፩) ። የጡብ ፡ ዱቄት ፡ የደቀቀው ፡ የተሰለቀው ። **በቀኖስሎ ፡ ወደዩ ፡ ግንፋለ ። ደመረ ፡ ጼወ ፡ ምስለ ፡ ግንፋል ። ከመ ፡ ይቅብዕዎ ፡ በጼው ፡ ወብሒእ ፡ ወግንፋል ፡** (ስንክ ፡ ግንቦ ፡ ፳፯ ። ሐምሌ ፳፯) ።

**ግንፈለ ፤ (ገለፈ) ፤** አቦካ ፡ ለወሰ ፡ ጡብ ፡ ሠራ ፡ ተኰሰ ። **ወይገነፍሉ ፡** (ታሪ ፡ አክሱ) ። በቁሙ ፡ ግንፈለ ፡ መደ ፡ ላይ ፡ እሰ ፡ ፈላ ፡ ፈሰሰ ፡ የወጥ ፡ የመጠጥ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ገነጸ፤(ፀረ፡ከነበ)፤** ለበሰበ፡ አከበ፤ አከተ፡ ከተተ ።

**ምጕንጻ፤(ጻት)፤** ጕረንጕሬ፡ የፍላጻ፡ ቤት፤ ባለቀበት፡ ፍላጻቸን፡ አከቦ፡ ሰብስቦ፡ የሚይዝበት፡ እንደ፡ ቍናማት፡ እንደ፡ ከረጢት፡ ያለ ። ዘያወፅእ፡ አሕጻሁ፡እምጕንጻሁ፡ንሥኡ፡ምጕንጻ። ምልኡ፡ ምጕንጻክሙ። አሕጻቲሆሙ፡ ውስተ፡ ምጕንጻቲሆሙ፡ (ሚራ፳፯፡ ፲፱ ። ኢሳ፳፪፡ ፯ ። ኤር፳፰፡ ፲፩ ። መዝ፡ ፲፩) ።

**ገንጸለ፤(ተቀ፡ ግ)፤** ለወጠ፡ ገለበጠ፤ ገለባበጠ፡ (ገነበለ፤ አገነበለ፤ ገንባሌ፡ ለበሰ) ። እንዘ፡ ይገነጽሉ፡ጽድቀ፡ ውስተ፡ ዘኢመፍትው። ፈድፋደ፡ ይዲምፁ፡ በዘንቱ፡ ገንጺሎሙ፡ ጽድቀ፡ ብሐሰቶሙ። ወገንጸለ፡ መናብርቲሆሙ፡ (ቄር፡ ጸላ ። ገድ፡ ተክ) ።

**ገንጻሊ፤መገንጽል፤** የሚለውጥ፡ የሚገለብጥ፡ ለዋጭ፡ ገልባጭ ።

**ተገንጸለ፤** ተለወጠ፡ ተገለበጠ፤ ተገነበለ፤ ግንብል፡ ግንብል፡ አለ ። ወተገንጸለ፡ በዘሉ፡ ወተመይጠ፡ ዘትሥጉት፡ ምስጢር፡(ቄር፡ ጸላ) ።

**ግንጹል፤(ላን፡ላት፡ጽልት)፤** የተለወጠ፤ ልውጥ፡ ግልብጥ ።

**ግንጽሊት፤** ግልብጭ፡ የኋሊት፡ የግርንግፉት ። እመ፡ ደረስዎ፡ ግንጽሊተ፡ ይከፍእ፡ጺጋሁ፡ ለምስጢር፤መልኩ፡(ተረ፡ ቄር) ።

**ገሥገሠ፤(ጌሠ)፤** በቁሙ፤ቸኰለ፡ አረበደ፡ ፈጠነ ።

**አንገሥገሠ፤** እወከ፡ ነቀነቀ፤ ታወከ፡ ተደረጠ ። እመ፡ ኢታንገሥግሥ፡ ነፋስ፤ ለዐፀ፡(አዋል) ። አንገሸገሸ፡ ተንገሸገሸ፡ ማለት፡ ፀማርኛው፡ ከዚህ፡ የወጣ፡ ነው ።

**ነገሥጋሥ፤** ሁከት፡ ሽብር፡ ድብልቅልቅ፡ ንውጽውጽታ፤ የባሕርይ፡ ጦር ። ሰ፡ አርጌንስ፡ ሀዋኪ፡ እፎ፡ ታፈቅር፡ነገሥጋሠ፡ ከመ፡ትግበር፡ ነቀልቃለ፡ ሰቤተ፡ ክርስቲያን፡በነገሥጋሠ፡ነፍስት፡ መዋቲት፡ ዘይእቲ፡ ደዌ፡ ነፍስት፡ ኢመዋቲት፡(መጽ፡ ምስ ። ገድ፡ ኪሮ) ።

**ገሠሠ፤—ዳሰሰ፤—ገሢሥ፡ገሰ፡ ገሰሰ ።**

**ገሚዕ፤ዖት፤(ጐሥዐ፡ ይጐሥዕ፡ ይጕሣዕ ። ፀረ፡ ጀሸአ፤ጀሰዐ። ሱር፡ ግሣእ ፣ ዕብ፡ ጋዛህ፤ጋዓሀ)፤** መግሣት፡ ማግሣት፡ መጮኸ፤ አፍን፡ መክፈት፤ መትፋት፡ መቀርሸት፡ ቋቅ፡ ማለት፤ የጠብ፡ የጥጋብ ። (ግጥም)፤ ሚጣቅ፡ እሾላው፡ ሥር፡ ዐማኔል፡ ቢያገሣ፡ በሽታዬ፡ ኹሉ፡ እክቱን፡ እንሣ ። ትበ፡ነቀወ፡ ደርሆከ፡ ወጐሥዐ፡ ሶረ፡ ብዕራይከ፡ ህየ፡ ንበር ። ወእጐሥዕ፡ እምሐዘነ፡ ልብየ። ዘሉ፡ ዘይጐሥዕ፡ ማይ፡ (ታሪ፡ ነገ ። መዝ፡ ፴፯ ። ዘሌ፲፩፡ ፲) ።

**—፤** መናገር፤ ኀይለ፡ ቃል፡ ማውጣት፤ ደፍሮ፡ ተፈቶ፤ የክፉ፡ የበጎ፡ የድርሰት፡ የትንቢት ። ብ፡ እስ፡ ይጐሥዑ፡ በእንቲኣየ፡ቃላተ፡ዐመፃ። ዕለት፡ለዕለት፡ ትጐሥዕ፡ ነቢበ። ጐሥዐ፡ ልብየ፡ቃለ፡ ሠናየ። ወጐሥዐ፡ ልብየ፡ ጥቀ፡ ጥበበ። ዘጐሥዐ፡ መጻሕፍተ፡ ጥበብ፡ ዘሎ፡ (ተረ፡ ቄር፲፭ ። መዝ፡ ፲፰ ። ፵፬ ። ሉቃ፡ ዕዝ፲፬፡ ፵፪ ። ስንክ፡ የካ፲) ።

**—፤** መፍሳት፤ መገንፈል፤ መልቶ፡ ተርፎ፡ መፍሰስ ። መንፈስ፡ቅዱስ፡ ይጐሥዕ፡ ውስተ፡ልቡ፡ በከመ፡ ይጐሥዑ፡ አፍላጋት፡ ወይውሕዙ። እምነ፡ሐዋርያት፡ ጐሥዐ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ላዕለ፡ ዘሉሙ፡ ቅዱሳን፡ መሀይምናን፡(ስንክ፡ የካ፲። ጥቅ፳፩) ።

**ጐሥዖት፤** ማግሣት፤ መናገር፤ አገሣሥ፡ አንጋገር፤ ግሣት፡ ትፋት፡ ቅርሻት፤ ልብ፡ ወለድ፡ ፈጠራ፡ ነገር ። ከመ፡ ጐሥዖተ፡ ልቦሙ፡ ይትናገሩ። ጐሥዖተ፡ ኀሊና፡ ሰይጣናዊ። ሰፈላስፋ፡ ኢተትሰሐ፡ ልቦሙ፡ በሃይማኖት፡ ወኢበርሁ፡ ቤብርሃነ፡ ዜኣሃ፤ ኦላ፡ ይትአመኑ፡በጐሥዖተ፡ልቦሙ። ይሜህሩ፡ፈጠራ፡ ዘእምጐሥዖተ፡ ልቦሙ፡ (ዕር፡ ኢሳ፸፡ ፳፭ ። ቄር፡ ገ፸ ። አፈ፡ ድ፳፱፡ መጽ፡ ምስ) ።

**አጕሥዐ፤** አስገሣ፤ አናገረ ። ዘያጐሥዕ፡ ጥበበ፡ ወይሁብ፡ ሕይወተ፡(ቅዳ፡ ሕር) ።

**ገሥጸ፤ጸት፤(ገሠጸ፡ ይጌሥጽ፡ ይገሥጽ ። ዕብ፡ ያሰር)፤** መገሠጽ፤ መቅጣት፡ መቈጣት፤ አጥብቆ፡ መላልሶ፡ መምከር፡ ማስተማር፤ እንደ፡ ደንጊያ፡ መውቀር፤ በነገር፡ ባለንጋ፡ መግረፍ፡ ማሰንበር፤ ያባት፡ የመምር፡ የወዳጅ ። ገሥጽሶ፡ ገሠጸኒ፡ እግዚ፡ ወለሞትሰ፡ ኢመጠወኒ ። እመ፡ ብከ፡ ውሉድ፡ገሥጾሙ፡ ወመሀርሞሙ ። ንጉሥ፡ ጠቢብ፡ ይጌሥጽ፡ አሕዛቢሁ ። ገሥጾ፡ ሰዐርክከ ። በእንተ፡ ገሥጾቱ፡ለአብድ ። ገሠጽኮ፡ለዮናስ፡ በቀስታመ፡ ባሕር፡(መዝ፡ ፻፲፯ ። ሚራ፯፡ ፳፫ ። ፲፪ ። ፲፫ ። ፲፱ ። ፲፫ ። ማ፪፡ ፸ ። ቅኔ) ።

**ገሣጺ፤(ጺት፡ ጽያን፡ ያት)፤** በቁሙ፤ የሚገሥጽ፤ ቀጭ፡ ተቈጭ፤ መካር፡ መምር ። ገሣጼ፡ ሕዝብ፡ሕብዳን፡(ስንክ፡ ኅዳ፳፫) ።

**መገሥጽ፤(ጽት፡ ጻን፡ ጻት)፤** ገዢ፡ ከማሁ፤ ገሣጺ፡ (፩ጢሞ፡ ፫፡ ፪ ። ሆሴ፭፡ ፪) ። አብ፡ መገሥጽ ። መምህር፡ ወመገሥጽ፡ ዘአልህቀ፡ ደቂቀ፡በንጽሕ፡(ጥበ፲፩፡ ፲፭ ። ዲድ፡ ፩) ።

**ተገሥጸ፤** በቁሙ፤ ተመከረ፤ ተሠራ፡ ተቀጣ፤ ምክር፡ ሰማ፤ ቅጣት፡ ተቀበለ ። ገሥጽከኒ፡ ወተገሥጽኩ ። ዘእምንእስከ፡ኢተገሥጽከ። ወልድ፡ዘኢተገሥጸ ። ገሥጸ፡ ወኢተገሥጸ ። ከመ፡ ይትገሥጽ። ዘይትጌሥጹ፡ በሥርዐታ፡ ለቅድስት፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ (ኤር፴፩፡ ፲፰ ። ሚራ፳፮፡ ፫ ። ፴ ። ፳፫ ። ስንክ፡ ታኅ፲፱ ። ቀሌ) ።

**ግሡጽ፤(ጻን፡ ጻት፡ ሥጽት)፤** የተገሠጸ፡ የተማረ፡ የተመከረ፤ ምሁር፡ ምኩር፡ የተሠራ፡

የተቀጣ ፤ የተገሬ ፡ ሥሉጥ ፤ ሽቍጥቍጥ ። ወልድ ፡ ግሁጽ ፡ ያስተፌሥሕ ፡ አበዊሁ ፤ ሰብእ ፡ ግሁጻን ። ግሁጽ ፡ ለትምህርት ፡ መንፈስ ፡ ዐቢይ ፡ ወእከ ፡ ሕጹጽ ፡ (ፈላስ ። ስንክ ፡ ጥር፳)።

**ግሣጼ** ፤ መገሠጽ ፤ (ጥገ) መገሠጽ ፤ አገሣሠጽ ፤ ግሠጻ ፤ ተግሣጽ ፡ ቍጣ ። ነቢየ ፡ ምህሮ ፡ ወግሣጼ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳፩)።

**ተግሣጽ ፤(ጻት)** ፤ በቁሙ ፤ ስብከት ፡ ትምርት ፤ ብርቱ ፡ ምክር ፡ ምዕዳን ፤ ቍጣ ፡ ዘለፋ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፤ ከበትር ፡ የሚበልጥ ፡ የሚሻል ፡ የምስጢሩ ፡ ስሜት ፡ ልብ ፡ የሚሰብር ፡ የሚነካ ። ተግሣጸ ፡ ሰሎሞን ። በእንተ ፡ ተግሣጸ ፡ ካህናት ። በእንተ ፡ ተግሣጸ ፡ ሕዝባውያን ። ዕቀብ ፡ ተግሣጸሙ ፡ ለአእሩግ ። አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ደረሰ ፡ ድርሳናተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወተግሣጻተ ፡ ወቃላተ ፡ በቀኖት ፡ (ምሳ፳፭—፳፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፪ ። ፴፬ ። ሚራ፳ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ሐምሌ)።

**ጐዐ ፤(ብ ፡ ጐዓት ፡ ቆዐ)** ፤ ጓሚያ ፤ ቃሪያ ፡ እንጭጭ ፡ ያልበሰለ ። ጓ ፡ ድብድብ ፤ የጥጥ ፡ ያበባ ፡ እንቡጥ ።

**ገዐዘ ፤ ግዕዘ ፤—ኀቀፈ ፤ ቈጠረ ፡ አጋዘ ፤—ግኢዝ ፡ ገእዘ ፤ ግእዘ ፡ ግእዝ ።**

**ግዒዝ ፡ ዘት ፤(ግዕዘ ፡ ይግዕዝ ፡ ይግዐዝ)** ፤ መጓዝ ፤ ከሉበት ፡ መንሣት ፡ እግርን ፡ መንቀል ፡ ጕዞ ፡ መገሥገሥ ፤ ማዝገም ፡ ቀስ ፡ እያሉ ፡ መኼድ ፡ መጓዝ ። ወግዐዙ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ እምራምሴ ፡ ውስተ ፡ ሱኮት ። ወይግዐዙ ፡ ግብጽ ፡ ድኅሬሆሙ ። ወግዐዝክሙ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፴፯ ። ፲፬ ፡ ፲ ። ዘዳ፩ ፡ ፵)።

—፤ መበተን ፡ መበታተን ፤ መዘራት ፡ መሠራጨት ። ግዐዙ ፡ አሕዛብኒ ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ወአልቦ ፡ ዘያስተጋብእ ፡ (ናሖ፫ ፡ ፲፰)።

—፤ ሐራ ፡ መውጣት ፤ መፈታት ፡ መለቀቅ ፤ ነጻ ፡ መኾን ። ግዐዝክሙ ፡ እምግብርናት ። ገብር ፡ ለእመ ፡ ግዐዘ ፡ እምግብርናቲሁ ። ይግዐዝ ፡ ገብር ፡ እምእግዚኡ ፡ (ዲድ ፡ ፴፫ ። ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴)። በግዕዘ ፡ ፈንታ ፡ ተግዕዘ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ይትገዐዙ ፡ ወይፈቅዱ ፡ ይፃኡ ፡ እምኔክ ። ተግዐዝክሙ ፡ እምኀጢአት ። ግዐዛኒ ፡ ኢተግዐዘት ፡ (ሚራ፴ ፡ ፴፬ ። ሮሜ፮ ፡ ፲፰ ። ዘሌ፲፱ ፡ ፳)።

**ግዑዝ ፤(ዛን ፡ ዛት ፡ ዕዝት)** ፤ የተጓዘ ፤ ነጻ ፡ የወጣ ። ግዑዝ ፡ ውስተ ፡ ምዉታን ። እመኒ ፡ ግዕዝት ፡ ይብተራ ። ይሬስዮሙ ፡ ግዑዛነ ፡ (መዝ ፡ ፹፯ ። ዘኍ፭ ፡ ፶፩ ። ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፩)።

**ግዕዘት** ፤ መጓዝ ፡ አጓጓዝ ፤ ጕዞ ። ነጻ ፡ መውጣት ፤ ነጻነት ፡ ሐርነት ። ግዐዘት ፡ እምትዕርርት ፡ ኀበ ፡ ሰላም ፡ (ፊልክ ፡ ፲፭)።

**ግዕዝ ፤(ዛት)** ፤ ኹኔታ ፡ አኳኋን ፡ ጸንዐ ፡ ልማድ ፤ ሐሳብ ፡ ኅሊና ፡ ፈቃድ ፤ ባሕርይ ፡ ጠባይ ፤ የባሕርይ ፡ ሥራ ፡ ዐመል ፤ መንገድ ፡ ጕዞ ፡ አካኼድ ፡ አረማመድ ፡ የክፉ ፡ የበጎ ። ሰብአ ፡ ዐይን ፡ አንትሙ ፡ ወመጻእክሙ ፡ ትርአዩ ፡ ግዐዘ ፡ ብሔር ። ሰብእ ፡ ሠናያነ ፡ ግዕዝ ። ስምዐ ፡ ግዕዝነ ። ወልድከ ፡ ዘኢየሐውር ፡ በግዕዝከ ። እምከመ ፡ ዐረዩ ፡ ግዕዛቲሆሙ ። ሰማይ ፡ ጥቀ ፡ ሠናይት ፡ ወብርህት ፡ ፈድፋደ ፡ በግዕዘ ። በግዕዘ ፡ ጠባይዕ ፡ ወበባሕርይ ። ወነየ ፡ ይእቲ ፡ በዓልተ ፡ ጥዒና ፡ ሐዳስ ፤ ምስለ ፡ አራዊት ፡ ዘተኀድር ፡ ነፍስ ፤ እንዘ ፡ እምነ ፡ ሰብእ ፡ ትትገሐሥ ፤ እስመ ፡ ግዕዘ ፡ አርዌ ፡ ዐቢይ ፤ ወግዕዘ ፡ ሰብእ ፡ ንኡስ ። ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ግዕዝኪ ፡ እምንእስኪ ፡ (ዘፍ፵፪ ፡ ፱ ። ዮሴፍ ። ሚራ፴፭ ፡ ፳፪ ። ፈልክ ፡ ፱ ። እፈ ፡ ተ፲፯ ። ድር፪ ። ቅኔ ። ኤር፳፪ ፡ ፳፩)።

**ግዕዛን** ፤ ነጻ ፤ ነጻነት ። እስብክ ፡ ግዕዛነ ፡ ለፂዉዋን ። ወጸገከነ ፡ እምግብርናት ፡ ግዕዛነ ። በእንተ ፡ ግዕዛን ፡ ወግብርናት ። ወኢይዲምፅ ፡ ግዕዘ ፡ ኖሙ ፡ (ሉቃ፬ ፡ ፲፱ ። ኪዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፩ ። ፈልክ ፡ ፻፹፩)።

**ግዕዝና** ፤ ግዘኒ ፡ ከማሁ ፤ ነጻነት ፡ (ሄርማ ፡ ገ፵፱)።

**ገዓዝ ፤ ጋዕዝ** ፤ ጓዝ ፤ መንገደኛ ፤ ቤተ ፡ ሰብ ። ተቃወመከ ፡ በፍኖት ፡ ወአምተረከ ፡ ጋዕዘከ ፡ እለ ፡ ጻመዉ ፡ በድኅሬከ ። ተንሥኡ ፡ ምስለ ፡ ገዓዞሙ ፡ (ዘዳ፳፭ ፡ ፲፰ ። ዘኍ፲ ፡ ፲፪)።

**አግዐዘ** ፤ አጓዘ ፤ አስጓዘ ፤ አሸሸ ። ነጻ ፡ አወጣ ፤ አስወጣ ። ዐገዘ ፡ ረዳ ፤ አጸና ፡ አበረታ ፤ አዳነ ። ወእምዝ ፡ አግዐዙ ፡ ተዓይኒሆሙ ፡ ወንዋዮሙኒ ። አግዐዘ ፡ ዮሴፍ ፡ ሥጋሁ ፡ ለያዕቆብ ፤ ወአብጽሖ ፡ ኀበ ፡ መቃብረ ፡ አብርሃም ፤ አጓዘ ፡ (ዮዲ፯ ፡ ፲፰ ። ቀሌ ። ዘኍ፴፪ ፡ ፴)። በእንተ ፡ አግዐዘ ፡ ገብር ። ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ትትወሰብ ፡ ብእሲት ፡ ለገብር ፡ ዘአግዐዘ ፡ ምታ ። ንጉሥ ፡ ዘኢይሠይምዎ ፤ እግዚእ ፡ ዘኢያግዕዝዎ ። አግዐዘነ ፡ እምኀጢአት ፡ ወሞት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ሮሜ፰ ፡ ፪)።

**አግዓዚ ፤(ዚት ፡ ዝያን ፡ ያት ፤ ጋዕዝት)** ፤ አጓዥ ፤ እግዚእ ፡ ጌታ ፡ ባለቤት ፤ ነጻ ፡ አውጪ ፤ አሰናባች ፤ ጥሩ ፡ የሰው ፡ ልጅ ። ወዘሎ ፡ ገብር ፡ ወአግዓዚ ። ዘዘ ፡ እልፍ ፡ አግዓዚ ። ግብርናተ ፡ ዘካልኡ ፡ መድኅኔ ፡ ዓለም ፡ አግዓዚ ፡ ዲበ ፡ ግዕዛኑ ፡ ወበከ ። ለእከት ፡ ኀበ ፡ አጋዕዝቲሃ ። እግዚእ ፡ አጋዕዝት ። አኅው ፡ አጋዕዝተ ፡ ኪነት ፡ (ራእ፯ ፡ ፲፭ ። ፳ ፡ ፲፩ ። ቅኔ ። ጦቢ፪ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፻፴፭ ። ፈልክ ፡ ፻፹፱)። ግዑዝ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አግዓዚ ፡ አግዓዛይ ፡ ይባላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ትፌንዎ ፡ አግዓዜ ። ትፌንዋ ፡ አግዓዚተ ። ኢየሩሳሌም ፡ አግዓዚት ። ወረሰይካ ፡ ለሔዋን ፡ አግዓዚተ ፡ እምጻዕረ ፡ ሞት ። ወኩኑ ፡ ከመ ፡ አግዓዝያን ። ጸጋ ፡ አግዓዝያን ፡ ዘነሥኡ ። አግዓዝያንኑ ፡ እሙንቱ ። እፎ ፡ ከመ ፡ ይረሲ ፡ ርእሶ ፡ አግዓዛየ ። አግዓዛይት ፡ (ኤር፴፩ ፡ ፲፬ ። ዘዳ፳፩ ፡ ፲፬ ። ቀሌ ። ውዳ ፡ ፪ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ። ስንክ ፡ ሚያ፲፰ ። ማቴ፲፰ ፡ ፳፯ ። ቄር ፡ ጸላ ። ፩ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፳፪ ፡ ፴፱)።

—፤ ስመ ፡ ነገድ ፡ ሴማዊ ፤ የዮቅጣን ፡ ትውልድ ፤ ከየመን ፡ ፈልሶ ፡ ተጕዞ ፡ ወደ ፡ ሐበሻ ፡ ክፍል ፡ ወዳፍሪቃ ፡

የወጣ ፤ ራሱን ፡ ለዠሽ ፡ ከመገዛት ፡ ነጻ ፡ ያወጣ ፤ የዠሽን ፡ አገር ፡ ብሔረ ፡ አግዓዚ ፡ ያሰኛ ። **ለብሔረ ፡ አግዓዚ ፡ ሰበከ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ዜናሁ ፡** (ድጓ) ። በአግዓዚ ፡ ፈንታ ፡ ግዕዝ ፡ ይላል ፤ ምስጢሩ ፡ ጕዘና ፡ ስደት ፡ ነጻነት ፡ ነው ። **ብሔረ ፡ ግዕዝ ። ሰላም ፡ ለከ ፡ ቀመ ፡ ብቅልት ፡ ወአርዝ ፡ ዘፈረየተከ ፡ ግዕዝ ፡ ይሥሕቅ ፡ ጥቡዕ ፡ ሰማዕተ ፡ ዐዚዝ ። እስከ ፡ ዮም ፡ ትትፌሣሕ ፡ ግዕዝ ፡** (ስንክ ፡ መስ፳፫ ። ሐም፳፫ ። ታኅ፲፰) ። ዐምሓራን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**አጋዕዝት ፤** ስመ ፡ ነገድ ፤ መላእክት ። **መላእክቲ ፡ አጋዕዝት ፡** (ሔኖ፵፩ ፡ ፲ ። ኤፌ፩ ፡ ፳፩ ። ቈላ፩ ፡ ፲፮) ።

**ምግዓዝ ፤** መጓዣ ፡ ማጓጓዣ ፤ መዝመቻ ፡ መሰደጃ ። **ምግዓዘሙ ፡ ለእስራኤል ፡** (አዋል) ።

**ተጋዐዘ ፤** ተጓጓዘ ፤ ተከታተለ ፡ ተግተለተለ ።

**ግዒር ፤ ሮት ፤ (ግዕረ ፤ ገዐረ ፡ ይግዕር ፡ ይግዐር ። ዐረ ፡ ጀዐረ ። ዕብ ፡ ጋዓር ። ሱር ፡ ግዓር) ፤** መጋር ፡ መሮኽ ፤ መጨንቅ ፤ ማጣር ። **ገዐርኩ ፡ ኀቤከ ። ይገዐሩ ፡ እመዝራዕተ ፡ ብዙኃን ። የዐወይዉ ፡ ወይገዐሩ ። ገዐሩ ፡ እምግብሮሙ ። ገዐረ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ። ግዒሮ ፡ ሞተ ፡** (ኢዮ፴፩ ፡ ፲፱ ። ፴፰ ፡ ፱ ። ኤር፳፱ ፡ ፪ ። ዘፀ፪ ፡ ፳፫ ። ማር፲፭ ፡ ፴፯ ፡ ፴፱ ፡ ፴፱) ።

**ገዓሪ ፤ ግዑር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ዕርት) ፤** የጋረ ፡ የጣረ ፤ ጋረኛ ፡ ጣረኛ ። **ግዑራን ፡** (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ገዐር ፤ ገዓር ፤** ጩኸት ፡ ጭንቅ ፤ ጣር ፡ ጋር ፤ መራራ ፡ ቃል ፤ የሐዘን ፡ የደዌ ፡ የመከራ ፡ ስሜት ። **ገዓረ ፡ ምስኪናን ። ብካየ ፡ ገዓሮሙ ። ገዓሮሙ ፡ ለሙቁሓን ፤ ወይብጻሕ ፡ ቅድሜከ ፡ ገዐርየ ፡** (ኢዮ፴፬ ፡ ፳፰ ። ኤር፫ ፡ ፳፩ ። መዝ ፻፫ ። ፻፩) ።

**ትግዕርት ፤** ጣር ፡ ጋር ፤ ጣረኛነት ፡ ጋረኛነት ። **ሕማን ፡ ትግዐርታ ፡ ለኀጢአት ፡ አሰበለ ፡** (ቄር ፡ ጸላ) ።

**አግዐረ ፤** አስጮኸ ፡ አስጨነቀ ፤ ዋይ ፡ አሰኘ ፤ አስለቀሰ ። **አግዐሩ ፡ ነፍሰ ፡ ሕፃናት ። እለ ፡ ታግዐሩ ፡ ነዳየ ። ዕቤረ ፡ ብእሲተ ፡ እመ ፡ ቦ ፡ ዘአግዐራ ፡** (ኢዮ፳፬ ፡ ፲፪ ። ኣሞ፰ ፡ ፬ ። ሢራ፴፪ ፡ ፲፯) ።

**አግዓሪ ፤ መግዐሪ ፤ ዕር ፤** የሚያስጮኽ ፡ የሚያስጨንቅ ፤ አስለቃሽ ፤ (ግፈኛ ፡ ጨካኝ) ።

**ግዒት ፤ ዖት ፤ (ገዐተ ፡ ይግዕት ፡ ይግዐት ። ወግዐ ። ጠፍሐ) ፤** ማገንፋት ፤ መጋት ፡ ማጠጣት ፡ ማስጕነጨት ፤ በጋት ፡ በጥርኝ ፡ መስፈር ፡ መስከት ። **ኢይግዕቱ ፡ ሎሙ ፡ ወኢይፌትቱ ፡ ሎሙ ፡ ኅብስተ ።** ኢያስትይዎሙ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ኤር፲፮ ፡ ፯) ።

**ገዐት ፤** ገንፎ ፡ መንካካ ፤ አጥሚት ፡ እንቀት ፤ ያራስ ፡ የሕፃን ፡ ያሮጌ ፡ የበሽተኛ ፡ ምግብ ። (ተረት) ፤ ብኖር ፡ ዓመት ፡ ብበላ ፡ ገዐት ። **አስተዳሉ ፡ ሎሙ ፡ ኅዳጠ ፡ ገዐተ ፡ እስመ ፡ ድውያን ፡ እሙንቱ ፡** (ፈልክ ፡ ፫፻) ።

**ጋዕት ፤** ጋት ፡ ጥርኝ ፤ መጋቻ ፡ መስኪያ ። ሺቱ ፡ ጋት ፡ ፩ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ።

**ግዕት ፤** ግት ፤ ወኽ ፡ ጡት ፤ የእንስሳት ።

**ጕዕትያ ፤ (ድር ፡ ኀዒቲያ) ፤** ሐሪት ፡ ጥንቁሳ ፤ የጥንቁሳ ፡ ሥራ ፤ ጋኔን ፡ መጥራት ፡ ምትሀት ፡ ማሳየት ፤ ማታለል ፡ መሸንገል ፡ ማሞኘት ፤ ክንቱ ፡ ነገር ። ትግል ፡ ትግያ ፡ ትንንቅ ፤ ጣር ፡ ድካም ፡ ልፋት ፤ የጕልበት ፡ ሥራ ። **በከመ ፡ በርሕ ፡ በሥራያቲሁ ፡ ወበብዙኀ ፡ ጕዕትያሁ ። ስብሐትሙ ፡ ኢከነ ፡ ከመ ፡ ስብሐተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ በጕዕትያ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡** (ቀሌ) ። **ወእምድኅረ ፡ ብዙኅ ፡ ጕዕትያ ። በሀፍ ፡ በጕዕትያ ፡ ወጻማ ። በፈቃደ ፡ እግዚ ፡ ተውህበ ፡ ሎቱ ፡ መንግሥተ ፡ ዓለም ፡ ለዘርዐ ፡ ሴም ፤ ወግብርናት ፡ ለዘርዐ ፡ ካም ፤ ወጕዕትያ ፡ ለዘርዐ ፡ ያፌት ፡** (ፈልክ ፡ ፲፬ ። መቃ ፡ ገ፲፩ ። ክብ ፡ ነገ፸፫) ።

**ጕዕትየ ፤** አሞኘ ፡ አታለለ ፤ ተሞኘ ፡ ተታለለ ።

**ጕዕቱይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ቲት) ፤** የተሞኘ ፡ የተታለለ ፤ ፍጻሜው ፡ ክንቱ ፡ የኾነ ። **ኦ ፡ ጕዕቱይ ፡ ተወሲድከ ፡ ዕራቀከ ፡ ወትቀውም ፡ በከሃ ፡ ዕራቀከ ፡** (ግንዘ) ።

**ኀፍ ፤—ሀላዌ ፤—ገወፍ ።**

**ገፊዕ ፤ ዖት ፤ (ገፍዐ ፡ ይገፍዕ ፡ ይግፋዕ ። ዐረ ፡ ጀፋ ፤ ተቈጣ ፡ ሰደበ) ፤** መግፋት ፡ መገፍተር ፤ ለመጣል ፡ ለማራቅ ። ግፍ ፡ መሥራት ፡ መጨቈን ፡ ማጣበቅ ፡ ማስጠበብ ፡ ማስጨነቅ ፡ መበደል ፡ መቀማት ፡ መንጠቅ ፡ መመንጠቅ ፤ በኀይል ፡ መውሰድ ። **ገፍዕዎ ፡ ለውእቱ ፡ ቤት ፡ ወኢወድቀ ። ለሊሁ ፡ ይገፍዕ ፡ ወለሊሁ ፡ ይትመዐዕ ። ግፍዕ ፡ ዘገፋዕክሙ ። ወእመሂ ፡ ቦ ፡ ዘገፋዕክዎ ፡ እፈድዮ ፡ ትርብዕተ ። አባ ፡ ሙሴ ፡ ጻሊም ፡ ገፍዓ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡** (ማቴ፯ ፡ ፳፭ ። ሢራ፲፫ ፡ ፫ ። ሐዋ፯ ፡ ፳ ። ሉቃ፲፱ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳፬) ። ገፍትዐን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ስርጽ ፡ ነው ፤ ስርጹም ፡ ት ፡ ነው ።

**ገፋዒ ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት ፤ ዕት) ፤** የሚገፋ ፤ ግፍ ፡ የሚሠራ ፤ ገፊ ፡ ግፈኛ ፤ በዳይ ፡ ቀማኛ ። **ብእሲ ፡ ገፋዒ ። አኮ ፡ ውእቱ ፡ ገፋዒ ። መኳንንተ ፡ ገፋዕያን ። ኖሎት ፡ ገፋዕያኒ ፡ መርዔቶሙ ። ኖሎት ፡ ገፋዕተ ፡ አበግዖሙ ፡** (ምሳ፳፱ ፡ ፳፯ ። ፩ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፲፯ ። ጥበ፮ ፡ ፲ ። ቀሌ ። ዕር ፡ ኢሳ፫ ፡ ፳፱) ።

**አግፍዐ ፤** አስገፋ ፡ አስበደለ ፤ ግፍ ፡ አሠራ ፤ ግፈኛ ፡ አደረገ ፤ ገፋዒ ፡ አሰኘ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአግፍዐ ፡ ፈንታ ፡ አስተጋፍዐ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። **ለእግዚአብሔር ፡ ያስተጋፍዖ ፡ በልቡ ፡** (ምሳ፲፱ ፡ ፫) ።

**ተገፍዐ ፤** ተገፋ ፡ ተበደለ ፤ ግፍ ፡ ተቀበለ ፤ ተጠቃ ። **እትገፋዕ ፡ እምኔከ ። ናሁ ፡ ይትገፍዑ ፡ ደቂቅየ ። ተገፍዐ ፡ በዐውደ ፡ ምኵናን ፡** (ዘፀ፲፮ ፡ ፳ ። ነሐ፳ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ተ፲፩) ።

**ግፉዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ፍዕት) ፤** በቁሙ ፤ የተገፋ ፡ የተበደለ ፡ የተጠቃ ። **ዐውያተ ፡ ግፉዕ ። አድኅኖ ፡**

ግፉዐ ። ሰብአ ፡ ግፉዓን ፡ (ሚራ፴፪ ፡ ፲፮ ። ኢ.ሳ፰ ፡ ፲፯ ። ፳፰ ፡ ፫) ።

**ግፍዐት** ፤ መግፋት ፡ መገፋት ፤ አገፋፍ ።

**ግፍዕ ፤ (ዓት)** ፤ በቁሙ ፤ ግፍ ፡ በደል ፤ ቅሚያ ፤ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ሥራ ፡ ስድብ ፡ መከራ ። ዐመፃ ፡ ወግፍዕ ። ከመ ፡ ትግበሩ ፡ ላዕሌነ ፡ ዐቢየ ፡ ግፍዐ ። ወባሕቱ ፡ እ ነግረከ ፡ ግፍዐከ ። እመ ፡ ተዐገሥክሙ ፡ ግፍዐክሙ ፡ (ኩፉ ፡ ፴፰ ። ዮዲ፯ ፡ ፳፱ ። ኢዮ፴፫ ፡ ፰ ። ፳ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳) ።

**ተጋፍዐ** ፤ ተጋፋ ፡ ተጣነቀ ፤ ተጨቋቈነ ፡ ተሳ ደበ ። ወከኑ ፡ ሰብአ ፡ ይትጋፍዑ ፡ ከመ ፡ ይልክፉ ፡ ዘፈረ ፡ ልብሱ ። ዘይትጋፋዕ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፲፱ ። ቀሌ) ።

**አስተጋፍዐ** ፤ አጋፋ ፡ አጣነቀ ፤ ግፍ ፡ አሣራ ።

**ገፈፍ ፤ ፎት ፤ (ገፈ ፡ ይገፍፍ ፡ ይግፍፍ)** ፤ መግፈፍ ፡ መገልፈፍ ፤ መጋፈፍ ፡ (፩ማርኛ) ። ኹለተኛም ፡ ገፍገፈ ፡ አንገፍገፈ ፡ ብሎ ፤ ገፈገፈ ፡ አንገፈገፈ ፡ ተንገፈገፈ ፡ ማለት ፤ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ገፈር ፤ ሮት ፤ (ገፈረ ፡ ይገፍር ፡ ይግፍር)** ፤ መገፈር ፡ መቸፈር ፤ ማጋፈር ፡ ማጕፈር ፤ ገፈራ ፡ አጋፋሪ ፡ ጕፈሬ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ገፈት ፡ ቶት ፤ (ገፈተ ፡ ይገፍት ፡ ይግ ፍት)** ፤ መገፈት ፤ ማጋፈት ፤ ገፋች ፡ አጋፋች ፡ ገፈታም ፡ መኾን ።

**ገፍትዐ** ፤ ገፈተረ ፤ ጣለ ፡ አራቀ ፤ ገለበጠ ፤ ደፋ ፤ የውስጡን ፡ በላይ ፡ የላዩን ፡ በታች ፡ አደረገ ፡ አፈረሰ ። ለወጠ ፡ ቀየረ ፤ ሌላ ፡ አደረገ ፤ አጠመመ ፡ ቈለመመ ። ትገ ፈትዕዎ ፡ ለሕዝብ ፡ እምግብሩ ፡ (አራቀ) ። እገፈትዕ ፡ መናብርተ ፡ ነገሥት ፡ ወእገፈትዕ ፡ ሠረገላተ ፡ ወመስ ተጽዕናነ ። ገፍትዎሙ ፡ ለአድባር ፡ እመሠረቶሙ ። ገፍታዕኩ ፡ ሾሎ ፡ ንዋየ ፡ አፍኣ ፤ ጣለ ። (ሐጌ፪ ፡ ፳፪ ። ኢዮ፳፰ ፡ ፱ ። ነሐ፲፫ ፡ ፰) ። አንትሙ ፡ ዘትገፈትዕዎሙ ፡ ለእ ስራኤል ። ፍትወት ፡ ገፍትዐ ፡ ልበከ ። አለ ፡ ትገፈት ዕዋ ፡ ለርትዕ ። ከመ ፡ ይገፍትዕ ፡ ፍትሐ ፡ ምስኪን ፤ ለወጠ ፡ (ፎነገ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ። ዳን፲ ፡ ፶፯ ። ሚክ፫ ፡ ፱ ። ኢሳ ፴፪ ፡ ፯) ።

**ገፍታዒ ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት)** ፤ የሚ ጥል ፡ የሚገለብጥ ፡ ገልባጭ ፡ ገላባጭ ፡ ገለባባጭ ። ገፍታዬ ፡ መናብርተ ፡ ኀያላን ፡ (መቃ ፡ ገ፲፯) ።

**ተገፍትዐ** ፤ ተገለበጠ ፡ ተደፋ ፤ ተለወጠ ፤ ል ውጥ ፡ ግልብጥ ፡ ሌላ ፡ ኾነ ፤ ፈረሰ ። ከመ ፡ ተገፍትዐት ፡ ሰዶም ፡ ወገሞራ ። ትትገፈታዕ ፡ ነነዌ ። ወተገፍትዐ ፡ ዝሙትኪ ። ኢይጐነዲ ፡ ተገፍትዖ ፡ ቤቱ ፡ (ኤር፳፱ ፡ ፲፱ ። ዮና፫ ፡ ፬ ። ሕዝ፲፯ ፡ ፴፱ ። ሚራ፳፯ ፡ ፫) ።

**ግፍቱዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ትዕት)** ፤ የተለወጠ ፡ የተገለበጠ ፤ ልውጥ ፡ ግልብጥ ፤ ጠማማ ፡ ቈልማማ ። ይ ወፅእ ፡ ሕግ ፡ ግፍቱዐ ። ትውልድ ፡ ዕሉት ፡ ወግፍት ዕት ። ግፍቱዓነ ፡ ልብ ። ዐላውያን ፡ ወግፍቱዓን ፡ (ዕን፩ ፡ ፬ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፭ ። ሔኖ፺ ፡ ፭ ። ፊልጵ፪ ፡ ፲፭) ።

**ግፍታዌ** ፤ መገልበጥ ፡ መደፋት ፡ መፍረስ ፡ ሥ ራዊ ፡ ጥፋት ። ወአውፅአ ፡ እማእከለ ፡ ግፍታዌ ። ግፍ ታዌ ፡ ሰዶም ፡ (ኩፋ ፡ ፲፯ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ገጽ ፤ (ጻት ፤ ገገጻ ። ሱር ፡ ሐዛእ ። ዕብ ፡ ሓዛሀ ፤ ሙል)** ፤ በቁሙ ፤ ፊት ፡ ግንባር ፤ ዐይንና ፡ አፍንጫ ፡ አፍ ፡ ያሉበት ፤ ከንገት ፡ በላይ ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ጠጕር ፡ ወደ ፡ ታችም ፡ እስከግር ፡ ጥፍር ፡ በስተፊት ፡ ያለው ፡ ክፍል ። ፊት ፡ ለፊት ፡ የሚታይ ፤ በፊት ፡ አንጻር ፡ ያለ ፡ ዐይን ፡ የሚያርፍበት ፡ ስማዩም ፡ ምድሩም ፡ ማና ቸውም ፡ ኹሉ ። ይከድኑ ፡ ገጸሙ ። ሰዐረ ፡ ሾሎ ፡ አን ብዐ ፡ እምኵሉ ፡ ገጽ ። ከደነኒ ፡ ኀፍረት ፡ ገጽየ ። ከመ ፡ ኣስሕት ፡ በገጽየ ። ገጹ ፡ ለማያት ፡ ተአምሩ ። አስተ ፍሥሕ ፡ ገጻ ፡ ለምድር ፡ (ኢ.ሳ፮ ፡ ፪ ። ፳፰ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፷፫ ። ዮዳ፲፫ ፡ ፲፯ ። ማቴ፲፮ ፡ ፫ ። ቅዳ) ።



ገጽ ፤

—፤ ድፍረት ፤ ቀረቤታ ፡ ሟልነት ፤ ግልጥ ፡ ገሃድ ። ገጽ ፡ ብነ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ። ከመ ፡ ንርከብ ፡ ገጸ ። ወሀበኒ ፡ እ ግዚ ፡ ገጸ ፡ ወሞገሰ ። ዘእንበለ ፡ ኀፍረት ፡ ትቤሎ ፡ በ ገጽ ፡ (፩ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ። ፪ ፡ ፳፰ ። ጦቢ፩ ፡ ፲፫ ። ምሳ፯ ፡ ፲፫) ።

—፤ አካል ፡ ቁመና ፡ ቁመት ። መድኅኔ ፡ ገጽየ ። አሐዱ ፡ ገጸ ፡ ነአምኖ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ክል ኤቱ ፡ ገጻት ፡ በበ ፡ አካሎሙ ፡ (መዝ ፡ ፵፩ ። ቄር ፡ ጸላ ። አፈ ፡ ድ፫) ።

—፤ ወገን ፡ ማእዘን ፤ መንገድ ፤ ስልት ፡ ተራ ፤ ምክንያት ፡ የመጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ክፍል ፡ ምዕራፍ ። እምአርባዕቱ ፡ ገጹ ። አርባዕቱ ፡ ገጸ ፡ ምድር ። ዐርገ ፡ እንተ ፡ ካልእ ፡ ገጽ ። ወሖረ ፡ እንተ ፡ ካልእ ፡ ገጽ ። ከመ ፡ ንንግር ፡ በበ ፡ ገጹ ። በምንትኑ ፡ ገጽ ፡ ዘከነ ። በብዙኅ ፡ ገጸ ፡ መከንን ። (ሕዝ ፡ ፱ ፡ ፵፯ ። እጥል ። ዮሐ፲ ፡ ፩ ። ገድ ፡ ተክ ። ዕብ፱ ፡ ፭ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ድ፲) ። ገጽ ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ እየተናበበ ፡ ሳይናበብም ፡ ወድቆ ፡ በሚ ስማማው ፡ ይፈታል ፤ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ነው ፤ ገገጸን ፡ ተመ ልከት ።

**ገጸወ ፤ (ይጌጹ ፡ ይገጹ ። ተቀ ፡ ግ)** ፤ ታየ ፡ ተገለጠ ፤ ጐላ ፡ ተረዳ ፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ ኾነ ፡ ተንጸጸረ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በገጸወ ፡ ፈንታ ፡ ተገጸወ ፡ ይላል ፤ እያ ሰኘም ። ዘቲ ፡ ኀጢአት ፡ ትትጌጸ ፡ ኀበ ፡ ብዙኅ ፡ ጸታ ፡ ገጻት ። እንዘ ፡ ይትጌጸ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፭ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ግጽው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ጹት)** ፤ የታየ ፡ የተ ገለጠ ፤ ግልጥ ፡ ጕልሕ ፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለ ፤ ሥዕል ፡ ም ስል ፤ ባለሟል ። ግጽው ፡ መንገለ ፡ ሰሜን ። ሊተ ፡ ግ ጽው ፡ ቅድመ ፡ አዕይንትየ ፡ ኢየሱስ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

—፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ከሐዋርያት ፡ ሲኖዶስ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ። ፍትሐ ፡ ንጉሥት ፡ ረስጠብ ፡ ይለዋል ፡ ሐዋርያት ፡ ለቀሌምንጦስ ፡ የሰጡት ፡ ኹለተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ማለት ፡ ነው ። ግጽው ፡ ወሥርዐት ፡ ወአብጥሊስ ፡ (ሲኖዶ) ።

**ግጻዌ** ፤ መታየት ፡ መገለጥ ፡ መታወቅ ፡ መረዳት ፡ ባለማልነት ፤ ትርጓሜ ፡ አፈታት ። በከመ ፡ ደለዎ ፡ ግጻዌ ፡ ለዮሐንስ ። ሕእምሮትከ ፡ ዘመልዕልተ ፡ ሥሉ ፡ ግጻዌ ። ግጻዌ ፡ ትምህርተ ፡ ሕግ ፡ ወሥርዐት ፡ ወተግሣጽ ። ግጻዌ ፡ ድርሳን ፡ ዘቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ ክርስቶስ ፡ (ፊልክ ። ጥበ ፡ ጠቢ ። ሲኖዶ ። ቄር ፡ ጸሎ) ። ባለመጣፎች ፡ ግን ፡ ግጽው ፡ ብለው ፡ በቅጽል ፡ አፈታት ፡ ይፈቱታል ።

**ግጻዌ** ፤ ግጽው ፡ የንባብ ፡ መጣፍ ፡ እንደ ፡ ድጓ ፡ ክመት ፡ እስከመት ፡ የተሠራ ፡ በጾሎት ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ የሚነበብ ፡ ቃሉ ፡ ለዘመን ፡ ለበዓል ፡ የሚስማማ ፡ ከብሉይ ፡ ከሐዲስ ፡ የወጣ ። መጽሐፈ ፡ ግጻዌ ፡ ዘአባ ፡ መቃርስ ። መጻሕፍተ ፡ ግጻዌ ። በውስተ ፡ ግጻዌ ፡ (ስንክ ፡ መስ ፲ ። ኅዳ ፲፯ ። ግን ፲፱) ።

**ግጻዌ** ፤ ገጽ ፡ ያለው ፡ አካል ፡ ሀላዌ ። ነአምን ፡ አበ ፡ በአካሉ ፡ ወበግጻዌሁ ፡ ዘኢይትፈለጥ ፡ እምከዊነ ፡ አብ ፡ ንበ ፡ ከዊነ ፡ ወልድ ። አቀመ ፡ ግጻዌ ፡ ባሕቲቶ ፡ በአብ ። እመን ፡ በሥላሴ ፡ ወተጋነይ ፡ በግጻዌ ፡ መለኮት ። በስመ ፡ ግጻዌ ፡ ሠላስ ፡ ዕሩያነ ፡ ክብር ፡ ወንግሥ ። አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ ዘበሠለስቱ ፡ ግጻዌ ፡ (አትና ። መጽ ፡ ምስ ። አዋል ። ቅዳ ፡ ሕር) ።

**አግጸወ** ፤ ፈት ፡ አሳየ ፡ ገለጠ ፡ አንጐላ ፡ አስረዳ ፤ ጸላእያንየ ፡ ክህሉኒ ፡ በቀጥባበ ፡ ነገረ ፡ ሐሰት ፡ ሰሀጕልየ ፡ ወአግጸዊ ፡ ኅቤከ ፡ ፀሩዐ ፡ በገጹ ፡ ጽድቅ ። ወያጊጹ ፡ በእንቲኣሁ ፡ ከዊነ ፡ አፍቅሮ ፡ ክርስቶስ ፡ ለዮሐንስ ፡ ፈድፋደ ፡ እምጴጥሮስ ። ለእመ ፡ ጕንደየ ፡ ኀሊና ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ያጊጹ ፡ ላዕለ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ያፈቅሮ ፡ ሎቱ ፡ (ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፰ ። ፻፳፩) ። ያጊጹ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ገጽዎት ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ተጋብኦትነ ፡ ለግንዘትሙ ፡ ለምዉታን ፡ ወሐዊር ፡ ቅድሜሆሙ ፡ ውእቱኬ ፡ ገጽዎተ ፡ ሕስተፋንዎቶሙ ፡ ለእለ ፡ ይነግዱ ፡ ወጠብልሎቶሙ ፡ በአልባስ ፡ ሐዲስ ፡ ገጽዎት ፡ በእንቲኣሆሙ ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ ፡ ናሁ ፡ ይትነሥኡ ፡ በአልባስ ፡ ሐዲስ ፡ ዘኢይማስን ፡ (ግንዘ) ።

**ጐጻጕጽ** ፤ (ጻት) ፤ ጕጠጕጥ ፤ ሥርጥ ፡ ዐባባ ፡ ጕባጣ ፡ ሰንከልካላ ። ፍኖት ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ ማዕቅፍ ፡ ወአሥዋክ ፡ ወጐጻጕጽ ፡ ወአጽዳፍ ። አኮ ፡ ብነ ፡ ዝየ ፡ ሀገር ፡ አጽዳፍ ፡ ወጐጻጕጽ ፡ (ሲኖዶ ። ቅዳ ፡ አትና) ።

**ጐጽፈረ** ፤ (ዲቃ ፡ ግ ፤ ደጐጸ ፤ ጸፈረ) ፤ ጕደፈረ ፡ ማስ ፡ ቈፈረ ፡ ጫረ ፡ ማጨረ ፡ ጕፈጨረ ፡ ያውሬ ፡ በክክ ፡ ርክት ፡ የሰው ። የደጐጸና ፡ የጸፈረ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ጕጽፋር** ፤ (ራት) ፤ ዕክክ ፡ ርክት ፡ ደረሙን ፡ ፈረሳቤት ፡ የጥፍር ፡ ንኪት ።

**ጌራ** ፤—ራስ ፡ ቀኑር ፤—ገየረ ።

**ግራ** ፤ የጉብ ፡ እንጀራ ፡ ሰጬ ፡ ጕመጬ ፡ ስፈፉ ፡ ሳይቀር ፡ ከንማሩ ፡ ከነመለሳው ። የማር ፡ ስፈፍ ፡ የተነጠረ ፡ ሠም ፡ ልጥልጡ ፡ ማግሩ ፡ ነጋሪቱ ። ነገረን ፡ እይ ፡ ዘሩና ፡ ምንጬ ፡ ርሱ ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ግራ ፡ መዓር ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መዓረ ፡ ግራ ፡ ይላል ፡ መዓርን ፡ እይ ፡ (ኢሳ ፯ ፡ ፲፭ ። ዮዳ ፲፯ ፡ ፲፰ ። ሱቱ ፡ ዕዝ ፲፩ ፡ ፳፰) ። እንግር ፡ እንጀራ ፡ መጌራ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ግራ** ፤ (ዕብ ፡ ጋሩዕ ፤ ሕጽጹ) ፤ በቀመ ፡ ዐጋም ፡ ሀካይ ፡ ድኩም ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጎር** ፤—ጎረ ፡ ቤት ፤—ገወረ ።

**ግራብ** ፤ (ባት ። ዐረ ፡ ጅራብ ። ትግ ፡ ገራቢት) ፤ ቀርብ ፡ ቀርበታ ፡ ርኮት ፡ ሬምት ፡ ቈርባ ብቻ ፡ የማር ፡ የቅቤ ፡ የዘይት ፡ ስልቻ ፡ ማስሮ ፡ ግንብ ። ለእመ ፡ ኅሠሥከ ፡ ቅብዐ ፡ ዘይት ፡ ትረክብ ፡ ኀበ ፡ ግራባቲሃ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ጌርጌል** ፤—መንከራከር ፤—ጌልጌል ።

**ገርገረ** ፤ (ገሬር ፡ ገረ ፡ ገረረ ። ዕብ ፡ ጋራር) ፤ ሳበ ፡ ጕተተ ፡ ተሳበ ፡ ተጕተተ ፡ የጋሬ ። በቁሙ ፡ ገረገረ ፡ አቆመ ፤ የደጆ ፡ የንጬት ። ወገሸ ፡ አገረገረ ፡ ግር ፡ ግር ፡ አለ ፡ የክብት ። ግርግር ፡ ፍግርግር ፡ ወጋግሬ ፡ ግርግሬ ፡ ገረገሬ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**እንገርገረ** ፤ አፍገመገመ ፤ ጣለ ፡ አንከባለለ ፡ አንደባለለ ፡ አንፈራፈረ ፡ አፈራገጠ ፡ የባሪያ ፡ የጋኔን ፡ አጣጣል ። እኩይ ፡ ጋኔን ፡ አኀዞ ፡ ወያንገረግሮ ። አውደቃ ፡ ወአንገርገራ ። አንገርገሮሙ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ መሬት ፡ (ማቴ ፲፯ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ የካ ። ሠኔ ፯ ፡ ፲፭) ።

**እንገርገረ** ፤ ተፍገመገመ ፡ ወደቀ ፡ ተንከባለለ ፡ ተንደባለለ ፡ ከብለል ፡ ደብለል ፡ አለ ፡ ተንፈራፈረ ። ከመ ፡ ሐራውያ ፡ ዘይኔጽር ፡ ታሕተ ፡ ወያጸንን ፡ እመንገለ ፡ ክርሁ ፡ ወያንገረግር ፡ ውስተ ፡ ጸብር ። ወድቀ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወእንገርገረ ፡ እንዘ ፡ ይበኪ ። እንገርገረ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ። ናንገርግር ፡ በተፋቅሮ ፡ (አፈ ፡ ተ ፲፱ ። ስንክ ፡ መስ ፪ ። ገድ ፡ ተክ ። ምሳ ፲፰ ፡ ፯) ።

**እንገርጋሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤ የሚያፍገመግም ፡ የሚፍገመገም ፡ ጣይ ፡ አንከባላይ ፡ ተንከባላይ ፡ ደብለል ፡ ከብለል ፡ ባይ ። በቁሙ ፡ የመንዝሙር ፡ ስም ፡ ምልጣን ፡ ከጾምቱ ፡ የድጓ ፡ አርእስቶች ፡ አንዱ ፡ ኃኛው ፡ ርእስ ፡ መሪ ፡ ከወንጌል ፡ በኋላ ፡ መስቀል ፡ ይዞ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ብሎ ፡ የሚመራው ፡ ተቀባዮችም ፡ በዝማሜና ፡ በተሐውሶ ፡ በአንገርግሮ ፡ የሚሉት ።

**ነገርጋር** ፤ መውደቅ ፡ መንከባለል ፡ መንፈራፈር ፡ የጋኔን ፡ ትግያ ፡ ትግል ፡ በየወሩ ፡ ሬብረታ ፡ ስትበቅል ፡ የሚኾን ። ዘአኀዞ ፡ ጋኔን ፡ ወነገርጋር ። እለ ፡ ቦሙ ፡ ነውር ፡ ዘነገርጋር ፡ ወዘጋኔን ፡ ኢይሀየሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። እለ ፡ ነገርጋር ። በእንተ ፡ ዘነገርጋር ፡ (ቀሌ ። ማቴ ፬ ። ፳፬ ። ፲፯ ፡ ፲፱ ። ሉቃ ፱ ፡ ፴፱) ።

**ጕርጕረ ፤ (ዕብ ፡ ጋርጌር)** ፤ በቊሙ ፡ ጕረ ጕረ ፡ ጓንጐበ ፡ ነክ ፡ ቋቅ ፡ አስ ፡ ለማስመለስ ፤ የጕረሮ ። ጕረሮ ፡ ቅሉ ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ። ሻ ፡ በረበረ ፤ አጥብቆ ፡ ፈለገ ፡ ለማግኘት ። (ተረት) ፤ ዓማ ፡ ጕርጓሬ ፡ ዘንዶ ፡ ያወጣል ፤ የሰው ፡ ፈላጊ ፡ የራሱን ፡ ያጣል ። ጕርጕረ ፡ ከማርሻ ፡ በቀር ፡ በማእዝ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ አስልማድ ፡ አይነገርም ።

**አንጐርጐረ ፤ (ነገረ ፡ አንገረ)** ፤ አጕረመ ረመ ፡ ተጕረመረመ ፡ አንጕራጐረ ፡ ተናገረ ፡ ነቀፈ ፡ ተ ቈጣ ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ አወጣ ፡ ቋቅ ፡ አክሽ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ለክፉም ፡ ለበጎም ፡ ይኸናል ። ጕሥዐን ፡ ተመልከት ። ለምንት ፡ ያንጐረጕር ፡ ሰብእ ። ኢታንጕርጕር ፡ ላዕለ ፡ ጸጋ ፡ ዘወሀበከ ። ወአንጐርጐሩ ፡ ጸሐፍት ፡ ወ ፈሪሳውያን ። ወብዙኃ ፡ አንጕርጐሩ ፡ በእንቲአሁ ። ወሰምዑ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ከመ ፡ አንጐርጐሩ ፡ ሕዝብ ፡ (ሰቈ፫ ፡ ፴፱ ። ፈላስ ። ሉቃ፲፭ ፡ ፪ ። ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ፡ ፴፪) ።

**አንጐርጓሪ ፤ መንጐርጕር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት)** ፤ የሚያጕረመርም ፡ ተቈጭ ፡ ተናጋሪ ፡ ሐሜተኛ ፡ አንባቢተኛ ። ኢትኩኑ ፡ መንጕርጕረ ፡ (ቈስጠ ፡ ፶) ።

**ነጐርጓር ፤ (ራት)** ፤ በቊሙ ፡ ማጕረምረም ፡ መድረምረም ፤ ማንጕራጐር ፡ አንጐርጐሮ ፡ የቀጣ ፡ የን ቢታ ፡ የሐሜት ፡ የስድብ ፡ የነቀፌታ ፡ ቃል ፤ ክፉ ፡ ነገር ። ጓሮ ፡ እንባ ፡ ጓሮ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፯ ፡ ፰ ። ዘኍ፲፬ ፡ ፳፯ ። ኢሳ፶፰ ፡ ፱) ። አኅድግዎሙ ፡ እ ኩየ ፡ ነጕርጓረ ። ተዐቀቡኬ ፡ እምነጕርጓር ። ዘእን በለ ፡ ነጕርጓር ፡ ወኑፋቄ ፡ (ጥበ፩ ፡ ፪ ። ጥበ፩ ፡ ፲፩ ። ፊልጵ፪ ፡ ፲፬) ።

**ገሬድ ፤ ዶት ፤ (ገረደ ፡ ይገርድ ፡ ይግ ርድ ። ዕብ ፡ ጋራድ)** ፤ ማግረድ ፡ ማምረት ፡ ግርድ ፡ ቈንድ ፡ ማውጣት ፡ ፍሬን ፡ ከገለባ ፡ መለየት ፡ መፈልፈል ፡ ማሸት ። መጋረድ ፡ መሸፈን ። ገረድ ፡ ግሬዶ ፡ መኾን ። ከርደደን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ። ጋሬዳ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ገሬሀ ፤ ሆት ፤ (ገርሀ ፡ ይገርሀ ፡ ይግራሀ ። ገበረ ፤ ረየፀ ። ዕብ ፡ ጋሬሀ ፤ አፍርሀ ፡ አርዐዶ)** ፤ ማረስ ፡ መንገድ ፡ ማግራት ፡ መገራት ፡ ገር ፡ ማድረግ ፡ ማለስለስ ፡ ማለዘብ ፡ የመሬት ፡ የከብት ።

**ገራሂ ፤ (ሂት ፡ ሀያን ፡ ያት ፤ ሀት)** ፤ ዐራሽ ፡ ቈፋሪ ፡ ነጋዴ ፡ ዐጣሪ ፡ ፈረስ ፡ በቅሎ ፡ ገሬ ።

**ገርሀ** ፤ ገር ፡ የዋህ ፡ ገራም ፡ ቈያምት ፡ ልሙጵ ፡ ልዝብ ፡ ስስላባ ፡ ጕጣምና ፡ ሽክሩ ፡ ያይያስ ፡ የመሳል ፡ ፀይነት ። ካህን ፡ ዘያዐርግ ፡ ቍርባነ ፡ ኢይግበሮ ፡ ገርሀ ፡ ሕላ ፡ ይኩን ፡ ጽሉንታሁ ፡ ምስቁለ ፡ በማኅተም ፡ (ፈ ፡ መ) ። መደ ፡ ጣቃ ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ሸቀጥ ፡ የሚሸ ጥና ፡ የሚለወጥ ፡ አስረው ፡ አክተው ፡ በማጥን ፡ መልተው ፡ ከገር ፡ ወዳገር ፡ የሚወስዱት ። ገርሀ ፡ ማለት ፡ ሥራው ፡ ያለቀለት ፡ ዝግጁ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፳፱) ።

**ገርሃት ፤ ገራህው** ፤ ጣቆች ፡ የንግድ ፡ ዕቆች ፡ ሸቀጦች ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ገራህው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ገራውህ ፡ ይላል ፡ ባለሐዲሶችም ፡ ፍችውን ፡ ዕርሻ ፡ ይ ሉታል ፡ ጎባቡም ፡ ፍችውም ፡ ተሳስቷል ። ዘይማየጥ ፡ ሎሙ ፡ ገራውሂሆሙ ፡ (ፊአ፲፰ ፡ ፲፩) ። ገራውህ ፡ ያለ ውን ፡ ከዚያው ፡ ብ፲፱ና ፡ ብ፲፫ ፡ ቀ ፡ ዘርዝሮ ፡ ተርትሮ ፡ የንግድ ፡ ዕቃንቱን ፡ ይናገራል ።

**ገራህት ፤ ገርዋህ ፤ (ዐረ ፡ ቀራሕ ፡ ቊር ዋሕ)** ፤ ዕርሻ ፡ ቅብቅብ ፡ የለዘበ ፡ የለሰለሰ ፡ ዘር ፡ ለመ ቀበል ፡ የደረሰ ። ዕርሻ ፡ የሚመስል ፡ የበረሓ ፡ መሬት ፡ ማርና ፡ ቅጠል ፡ ዛፍ ፡ የሌለበት ፡ አሸዋ ፡ ድቡሽት ። ሠ ናየ ፡ ዘርዐ ፡ ዘራዕከ ፡ ውስተ ፡ ገራህትከ ፡ (ማቴ፲፫ ፡ ፳፯) ።

**ገራህታት ፤ ገራውህ** ፤ ዕርሾች ፡ ቅብቅቦች ። አጥረየ ፡ አባግዐ ፡ ወአልሕምተ ፡ ወገራውሀ ፡ ብዙኀ ። ውስተ ፡ ጽሉ ፡ ገራውህ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ አብራም ። መን ገለ ፡ ገራውህ ። እመ ፡ ቦ ፡ ውስተ ፡ ካልእ ፡ ብሔር ፡ ገራውህ ፡ (ዘፍ፳፮ ፡ ፲፬ ። ኩፋ ፡ ፲፫ ። ማቴ፲፱ ፡ ፳ ። ሲኖዶ) ።

**ገርዋህ ፤ (ትግሬ)** ፤ አጋዘን ፡ ዑኸር ። ገራገር ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ገረዘ ፤ (ዕብ ፡ ጋራዝ)** ፤ በቊሙ ፡ ቈረጠ ፡ ገረዘዘ ። ገዘረን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ፡ ነከሰ ፡ ነሰከ ፡ ቀሐመና ፡ ቀምሐ ፡ ፩ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ እነዚህም ፡ እንደነዚያ ፡ ናቸው ።

**ጋርዜን ፤ (ዕብ)** ፤ መግረዣ ፡ መቍረጫ ፡ የ ብረት ፡ መጣሪያ ፡ ምሳር ፡ መጥረቢያ ፡ ማጭ ፡ ምግር ።

**ገርዜን ፤ (ገንዜን ፤ ገኒዝ ፡ ገነዘ)** ፤ ቀጭን ፡ ሸማ ፡ ጥሩ ፡ በፍታ ፡ ሻሽ ፡ ሐዲስ ፡ ልብስ ፡ ከፋን ። አም ጽኡ ፡ ልብሰ ፡ ገርዜን ፡ ለግንዘተ ፡ ሥጋሁ ። በሰንዱኒ ፡ ገርዜን ፡ ተገንዘ ፡ ወተቀብረ ። ዘተጠብለለ ፡ በል ብሰ ፡ ገርዜን ። ለምሥዋዐ ፡ ይኩን ፡ መንጠላዕት ፡ ዘ ገርዜን ፡ ንጹሕ ፡ ዘአልቦ ፡ ነውር ። ከድንኒ ፡ ገርዜነ ፡ ጸጋ ፡ ዘኢሕነፃምዎ ፡ ጠቢባን ፡ በኪን ፡ (ቅዳ ፡ አፈ ። ተረ ፡ ቊርጎ፳ ። አርጋ ። ኪዳ ። ደራሲ) ።

**ገሬዛን ፤ (ጽር ፡ ጋሬዚን ። ዕብ ፡ ግሪ ዚም)** ፤ የተራራ ፡ ስም ፡ ቍርጥ ፡ ያኾኑ ፡ የፁራኪ ፡ ቃ ሎች ፡ የሚነገሩበት ፡ ተራራ ። ጌባልን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ወ ንድም ፡ ነው ፡ (ዘዳ፳፯ ፡ ፲፪) ።

**ግርጣጥ** ፤ ታናሽ ፡ መዘቃ ፡ የዘፈን ፡ ዕቃ ፡ የ መዘቃ ፡ ወይነት ። ግንታ ፡ ወግርጣጥ ፡ (ሶር ፡ አዝ) ።

**ኀርየመ ፤—ዐገመ ፤—ጕር ፡ ገወረ ።**

**ገሬም ፤ ሞት ፤ (ገረመ ፡ ይጌርም ፡ ይግ ርም ። ዕብ ፡ ጋራም ፤ ሰበረ ፡ ጐረመመ)** ፤ መግረም ፡ መድነቅ ፡ መፈረት ፡ መፈራት ፡ ግሩም ፡ መ ኾን ፡ ማስገረም ፡ ማስደነቅ ፡ ማስፈረት ፡ ሌላውን ፡ የመ ልክና ፡ የክብር ፡ የቃላቅንት ፡ ወይም ፡ የክፋት ። ገረሞሙ ፡ ዘኢከነ ፡ ግሩመ ። ወይጌርም ፡ እምነገሥት ፡ ም

ደር ። ትገርሞ ፡ ወታደነግፆ ። ሰፈራሂ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ አልቦ ፡ ዘይገርሞ ። መንግሥት ፡ እንተ ፡ ትገ ርም ፡ እምዝሉ ፡ መንግሥት ፡ (መዝ ፡ ፺፫ ። ፻፫ ። ሚ ራ፱ ፡ ፲፮ ። ፴፩ ፡ ፲፰ ። ሉቃ ፡ ሰዝ፲፱ ፡ ፲፯) ።

**ተገርመ ፤ ተገረመ ፤** ታበየ ፡ ኰራ ፤ ገረመመ ፤ ተገራመመ ። ኢይምጽኡ ፡ በተገርሞ ። ኢይስምዕ ፡ ድምፀ ፡ ዘይትገረም ። ኢትትገረመኒ ፡ እ ፡ ፀረ ፡ እ ግዚ ፡ በዘተነኪክ ። ተገረሞሙ ፡ ወፀረፎሙ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ቀሌ ። ኢዮ፴፱ ፡ ፯ ። ዮሴፍ) ።

**ግሩም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ርምት) ፤** በቁሙ ፡ የተፈራ ፡ የሚያስፈራ ፤ አስፈሪ ፡ ገናና ፡ ታላቅ ፤ ውብ ፡ ድንቅ ። እስመ ፡ ልዑል ፡ ወግሩም ፡ እግዚ ። ግሩመ ፡ ገጽ ። ኢኮኑ ፡ ግሩማነ ፡ ለዘይገብር ፡ ሠናየ ። ሚ ፡ መ ጠን ፡ ግርምት ። ወለብሰት ፡ አልባሰ ፡ ክብራ ፡ ወክ ነት ፡ ግርምት ፡ (መዝ ፡ ፵፯ ። ዘዳ፳፰ ፡ ፶ ። ሮሜ፲፫ ፡ ፫ ። ቅዳ ። አስቴ ፡ ፭) ።

**ግርማ ፤** በቁሙ ፤ ማስፈረት ፡ አስፈሪነት ፡ የመፈ ረት ፡ የመወደድ ፡ ሀብት ፤ ክብር ፡ ባለሟልነት ፤ የመልክ ፡ ውበት ፡ ደም ፡ ግባት ፤ ደመ ፡ ግቡነት ። ዘበዝኀ ፡ ሠ ሐቅ ፡ የሐጽጽ ፡ ግርማሁ ። አንበረ ፡ ግርማሁ ፡ ዲበ ፡ ዙሉ ፡ አሕዛብ ። ብኪ ፡ ግርማ ፡ ራእይ ፡ ዘየዐቢ ፡ እ ምግርማ ፡ ሱራፌል ። ኢትርአይ ፡ ግርማ ፡ ርእየቱ ፡ ለሐልያብ ፡ (ፈላስ ፡ ገጽ፩ ፡ ፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ። ውዳ ፡ ፩ ። ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፯) ።

**ትግርምት ፤** ግርማ ፡ አስፈሪነት ፤ ተፈሪነት ። እሰሰ ፡ ኢይፈርሁ ፡ ትግርምቶ ፡ ለውእቱ ፡ ንጉሥ ። ትግርምቱ ፡ ያወድቆ ። ኢትፍርሁ ፡ ትግርምቶሙ ፡ (ቀሌ ። ኢዮ፲፭ ፡ ፳፩ ። ኢሳ፰ ፡ ፲፪) ።

**መግረምት ፤** ማስፈሪያ ፡ ማስፈራሪያ ፤ መስፈ ራቻ ። ወይከውኖሙ ፡ ለግብጽ ፡ መግረምቶሙ ፡ ብሔረ ፡ ይሁዳ ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፲፯) ።

**ግራም ፤** የሚዛን ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ ታናሽ ፡ ክ ፍል ፡ የኪሎ ፡ ሺሕኛ ።

**ገረማ ፤** በቁሙ ፡ ሲናር ፡ ጌንጭ ፤ የገብስ ፡ ዐ ረም ፡ (ዐማርኛ) ።

**ገሬማ ፤** የሰው ፡ ስም ፡ ገባሬ ፡ ቀኣምር ፡ ግሩም ፡ ከተሰበቱ ፡ ቅዱሳን ፡ አንዱ ፡ ይሥሐቅ ። ገሪማ ፡ የግብር ፡ ስም ፡ ነው ። ገሪማ ፡ ገረምከኒ ፡ (ድጓ) ።


**ጕርን ፤ (ዕብ ፡ ጎሬን ። ዐረ ፡ ጁርን) ፤** ምክያድ ፤ ዐውድማ ፡ የበሬ ፡ የገበሬ ፡ ሸንጎ ፤ አዝመራ ፡ መከር ፡ ታጭድ ፡ ተሰብስቦ ፡ የሚወቃበት ፡ የሚበራይበት ፡ ተመዝኖ(ንሽቶ) ፡ የሚመረትበት ። ጕርኒ ፡ ኦርና ። ኦርና ፡ የሰው ፡ ስም ፡ (፩ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ፡ ፪ዜና ፡ ፫ ፡ ፩) ።

**ገረሠ ፤ (ዐረ ፡ ጀረሰ ፤ ከካ ። ዕብ ፡ ጋ ራስ ፤ ተከከ) ፤** ጐረሠ ፡ ቃመ ፡ አላመጠ ፡ ቈረጠመ ፤ ሰለቀ ፡ አላመ ፤ አለዘበ ። ገረሽ ፡ አገረሽ ፤ የደቁ ። ባለቅኔ ዎች ፡ ግን ፡ ሠራ ፡ ይሉታል ። ገረሠሠ ፡ ቀገረሠሠ ፡ ማ ለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ገርሣ ፤** ልዝብ ፡ ለስላሳ ፡ ሣር ፡ ልሻ ፡ የጠጕር ፡ ዐይነት ፤ እንደ ፡ ጭድ ፡ እንደ ፡ ገለባ ፡ ከጭቃ ፡ የሚለ ማማ ፤ ጕርሻ ፡ ጕርሣ ፤ ግርሻ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጋርሣ ፤ (ገዐት ፤ ገርህ) ፤** የላመ ፡ የጣመ ፡ ምግብ ፤ ገንፎ ፡ መንክክ ፤ ወይም ፡ ወፍራም ፡ ትኩስ ፡ ለስላሳ ፡ ዳቦ ። ባለመጣፎች ፡ ግን ፡ እንባዘ ፡ ዓሣ ፡ ይሉ ታል ። ውስተ ፡ መካነ ፡ አኀው ፡ ድዉያን ፡ አልቦ ፡ ዘይበልዕ ፡ ጋርሣ ፡ ወኢዘይሰቲ ፡ ወይነ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይደዊ ። አው ፡ ጸብኀ ፡ አው ፡ ጋርሣ ፡ (ሥር ፡ ጳኵ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**ገርሦ ፤ (ሣት) ፤** የመዝጊያ ፡ ብረት ፡ ሳንቃ ውን ፡ ከመቃን ፡ የሚያዛውግ ፤ የሚያቈራኝና ፡ እንደ ፡ የሚያደርግ ፤ ወንዴና ፡ ሴቴ ፡ ብረት ፤ ወንደው ፡ በመ ቃን ፡ ላይ ፡ ሴቴው ፡ በመዝጊያ ፡ ላይ ፡ ተቸንክሮ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ የሚሳከና ፡ የሚጓረሥ ፤ ወይም ፡ በሳንቃው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሳንቃ ፡ ኹኖ ፡ የሚለበጥና ፡ የሚጠረቅ ። ወካ ዕበ ፡ አስተዳለወ ፡ ብርተ ፡ ብዙኀ ፡ ዘአልቦ ፡ መድ ሎት ፡ ለገርሣተ ፡ ኆዋኅው ፤ ወሰባዕድኒ ፡ ግብር ፡ (፩ዜና ፡ ፳፪ ፡ ፫) ። ባለብሎዎች ፡ ግን ፡ ሰንሰለት ፡ ይሉታል ።





ገርሦ ፡

**ገርማኒ ፤** ያርብሓዊ ፡ ሬዐይታዊ ፤ ኀይለኛ ፡ ጣሽ ፡ ጠምሳሽ ። ኀኢናዊ ፡ ማሕረጻዊ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ጕራሽነትንም ፡ ያሳያል ፡ (ገድ ፡ አዳ) ። ለሽጕጥና ፡ ለነፍ ጥም ፡ ይስማማል ፤ ፯ ፡ ጕራሽ ፡ ፱ ፡ ጕራሽ ፡ እንዲሉ ።

**ጕርዒ ፤ (ብ ፡ ጕራዒት ። ዕብ ፡ ጋሮን) ፤** ዐንገት ፡ ማንቍርት ፤ ጕረሮ ፡ የሆድ ፡ ደጃፍ ፡ ውስጠ ፡ ከናፉ ፤ መዋጫ ፡ መሰልቀጫ ፤ ማግቢያ ፡ ማውጫ ፤ መሮ ኺያ ፤ የዜማ ፡ የንባብ ፡ የምግብ ፡ ጣዕም ፡ የሚታወቅበት ። መተረ ፡ ጕርዒ ። ጥዑም ፡ ለጕርዒየ ። ጕርዒ ፡ ይፈ ልጦ ፡ ለዙሉ ፡ ጣዕመ ፡ እክል ። ጕርዒየ ፡ ይነብብ ። ኢትክሉ ፤ ነቢበ ፡ በጕርዒክሙ ። ከመ ፡ መቃብር ፡ ክሡት ፡ ጕራዒትሙ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፯ ። መዝ ፡ ፻፲፰ ። ሚራ ፡ ፳፮ ፡ ፳፱ ። ኢዮ፯ ፡ ፴ ። ቀሌ ። ሮሜ፫ ፡ ፲፫) ።

**ጕርዒያዊ ፤** ጨኺ ፡ ቀባጣሪ ፤ ሆዳም ፡ ኹ ሉን ፡ ውጬው ፡ የሚል ።

**ጕርዐየ ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤** ዐነቀ ፡ ፈጠረቀ ፡ ጕ ረሮ ፡ ያዘ ። ጕርጕረን ፡ እይ ።

**ተጕርዐየ ፤** ታነቀ ፤ ጕረሮው ፡ ተያዘ ፡ ተሰ ቀዘ ፤ በገዛ ፡ እጁ ፡ ወይም ፡ በጠላት ፡ እጅ ። እምፈተ ውኩ ፡ ለልየ ፡ እትጕርዐይ ፡ (ኢዮ፯ ፡ ፳፱) ።

**ጕርዑይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ዒት) ፤** የታነቀ ፡ የተሰረነቀ ፡ ታኝቆ ፡ የሞተ ።

**ጕርዒት ፤** ዕንቂት ፡ ዕንቂያ ፡ ጕሬሮ ፡ አያያዝ ፡ አስተናንቅ ፤ የማነቅና ፡ የመታነቅ ፡ ሥራ ።

**ገሬፍ ፤ ፎት ፤ (ገረፈ ፡ ይገርፍ ፡ ይግርፍ ። ዕብ ፡ ጋራፍ ፤ ሳበ) ፤** መግረፍ ፤ መሸንቈጥ ፤ በጅራፍ ፡ ባለንጋ ፡ መቅጣት ። መማለብ ፡ መሥራት ፤ የተሠራውን ፡ መውገር ፡ መጣል ፡ ከባሕር ፡ ማግባት ፤ ዓሣው ፡ ሲመላ ፡ መሳብ ፡ መጕተት ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ ማውጣት ።

**ጐሬፍ ፤ ፎት ፤ (ጐረፈ ፡ ይጐርፍ ፡ ይጕርፍ) ፤** በቁሙ ፤ መጕረፍ ፡ መፍሰስ ።

**ግሬፍ ፤** ወጥመድ ፤ ዘረ ፡ መቅር ፤ መረብ ፡ መማለቢያ ፡ መያዣ ፤ መጋረፊያ ፡ (ማቴ ፲፫ ፡ ፵፯) ። ኀሠሠ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ሎሙ ፡ ገሬፈ ። መሥገርት ፡ ገሬፍ ፡ እንተ ፡ ታስተጋብእ ፡ ዘመደ ፡ ኵሎን ፡ ዓሣት ፡ (ፊልክ ፡ ፻፳፰ ። አርጋ ፡ ፫) ። ዓምና ፡ ያለፈው ፡ ዓመት ።

**ግረፋ ፤ ጐረፋ ፤** የፍርድ ፡ ቅጣት ፤ ግርፋት ፡ እስራት ። ፍዳ ፡ መርገም ፤ ፍትወት ፤ የአዳም ፡ ኀጢአት ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ከባት ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ የሚወርድ ። ባልሐነ ፡ እምጐረፋነ ፡ ወእምቀዳሚት ፡ አበሳነ ፡ (ቄር) ።

**ምግራፍ ፤ (ፋት) ፤** መግረፊያ ፡ በታ ፡ ወይም ፡ ጅራፍ ፡ ባንባ ፡ ጠለፍ ። መጅረፊ ፡ አካፊ ፡ የብረት ፡ ሳይዳ ፤ መጋፊያ ፡ መጥረጊያ ።

**ጐሬጽ ፤ ጻት ፤ (ጐረጸ ፡ ይጐርጽ ፡ ይጕርጽ) ፤** መብጣት ፡ መፍቃት ፤ መቀረጥ ፡ መሠንበጥ ፤ መውጋት ፡ መጋረጥ ፤ መሰርሰር ፡ መንደፍ ፤ ደም ፡ ለማውጣት ፤ የማንባር ፡ ያፍንጫ ። ማጕረጥ ፡ ማፍጠጥ ፡ ያይን ። ጕርጥ ፡ ጕረጥ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**መጕረጽ ፤ (ጻት ፤ መጓርጽ) ፤** መብሓ ፡ መጋረጫ ፤ ጋሬጣ ፡ ሥንጥር ። ማጕርጥ ፡ የጥፍር ፡ ዐይነት ፡ ሹል ፡ ስል ፤ መውጊያ ፡ ቸክ ፡ ጠቅ ፡ ማድረጊያ ። አራዊት ፡ መሣጥያን ፡ እለ ፡ ብሙ ፡ ጽፍራት ፡ ወመጕረጽ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫) ።



መጕረጽ ።

**ገሬር ፤ ሮት ፤ (ገረ ፤ ገረረ ፡ ይገርር ፡ ይግርር ። ገነየ) ፤** መገዛት ፡ መታዘዝ ፤ ዜጋ ፡ ገባር ፡ መኾን ። ለሊሆሙ ፡ ገረሩ ። ፈቀዱ ፡ ይግረሩ ፡ ሎቱ ። ኢይግርር ፡ ኤጺስቀጸስ ፡ ዘኢየኑሳቤም ፡ ለካልኡ ፡ እምኤጺስቀጸሳት ። ኢይገርር ፡ ለሕገ ፡ እግዚ ፡ (ኢያ ፡ ፳ ። ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ። ሮሜ ፰ ፡ ፯) ። ገርገረን ፡ እዩ ፡ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ገራሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤** የሚገዛ ፡ ተገዥ ፡ ታዛዥ ። አማንያን ፡ ለቃለ ፡ እግዚ ፡ ወገራርያን ፡ ለነገረ ፡ አኀው ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ።

**ግሩር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ርርት) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ የተገዛ ፡ ተገዥ ። ግሩር ፡ ታሕተ ፡ መከየድ ፡ (አርጋ ፡ ፩ ። ግብጽኽ ፡ ፯) ።

**ግረት ፤** መገዛት ፤ አገዛዝ ፤ ሥጋዊ ፡ ሥራ ። እስመ ፡ ግረትሰ ፡ በሥጋ ፡ ለኀዳጥ ፡ ዘመን ፡ ትበቍዕ ። (፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፰ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።


**ግረት ፤** ስመ ፡ ዕፅ ፤ ግራር ፡ የግራር ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ፤ ቀንበር ። ዕፀ ፡ ግረት ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፯ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**አግረረ ፤** ገዛ ፤ ዜጋ ፡ አደረገ ። አስገዛ ፡ አስደረገ ። ይመውእ ፡ ወያገርር ፡ ኵሎ ፡ መንግሥት ። ወኵሎ ፡ በሓውርተ ፡ አግረርየ ። አልቦ ፡ ዘይክል ፡ አግርሮታ ፡ ለልሳን ፤ ገዛ ፡ (ዳን ፪ ፡ ፵፬ ። አስቴ ፡ ፫ ። ያዕ ፫ ፡ ፯) ። ወኵሎ ፡ አግረርከ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ። አግርር ፡ ርእሰከ ፡ ለጽድቅ ፤ አስገዛ ፡ (መዝ ፡ ፰ ። ፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፯) ።

**አግራሪ ፤ መግረሪ ፤ መግረር ፡ ርር ፤** የሚገዛ ፤ የሚያስገዛ ፤ ገዥ ፡ አስገዥ ። መግረሬ ፡ ፀርየ ። መግረሬ ፡ አናብስት ፡ (ግንዘ ። አርጋ ፡ ፬) ።

**ግሬጳ ፤ (ጽር ፡ ግሬፕስ ። ዕብ ፡ ፔሬስ) ፤** ታላቅ ፡ አሞራ ፡ ግድንግዲ ፤ ነጣቂ ፡ ግልገል ፡ አንሣ ፤ ቅልጥም ፡ ሰባሪ ፤ የሎስ ፡ ጕሤ ፡ ጆሬ ። ጕሤ ፡ ያንሣኽ ፡ እንዲሉ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዘማች ፡ አሞራ ፡ ይሉታል ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፲፫ ። ዘዳ ፲፬ ፡ ፲፪) ።

**ግስላ ፤** (ዐማርኛ) ፡ ያውሬ ፡ ስም ፡ ቍጡ ፡ ብስሬጭ ፡ ግልፍተኛ ። ተገስሊብኝ ፡ ይገስላል ፡ እንዲሉ ፤ ተቈጣ ፡ ሲሉ ።



ግስላ ።

**ጌሰም ፤—ነገ ፡ ነገታ ፤—ገይሥ ፡ ጌሠ ፤ ጌሠም ።**

**ጌሴራሴም ፤ (ዕብ ፡ ጌእ ፡ ሐራሽም) ፤** ያናጠኞና ፡ የጠራቢዎች ፡ የጠቢቦች ፡ በታ ፡ በተራሮች ፡ ማኸል ፡ ያለ ፡ ቈላ ፡ ሸለቆ ፡ ወንዛወንዝ ፡ (፩ዜና ፡ ፬ ፡ ፲፬) ።

**ገሲስ ፤ ሶት ፤ (ገሰ ፤ ገሰሰ ፡ ይገስስ ፡ ይግስስ ። ዕብ ፡ ጋሻሽ ። ሱር ፡ ጋሽ ፤ ግሻ ። ዐረ ፡ ጀሰ) ፤** መግሰስ ፤ መዳሰስ ፡ መዳበስ ፡ በእጅ ፡ መንካት ፡ ማባበስ ፡ መያዝ ፡ መጨበጥ ። ወዘገሰሳሁ ፡ እደዊነ ። ዘኢይክውኖሙ ፡ ለገሲስ ፡ በእደዊሆሙ ። ኢትግስሱ ፡ መሲሓንየ ። ኢትግስስ ፡ ወኢትልክፍ ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፩ ። ዮዲ ፲፭ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፻፭ ። ቈላ፪ ፡ ፳፩) ።

—፤ ግስ ፡ መግሰስ ፤ አንዱን ፡ ቃል ፡ ማርባት ፡ ማብዛት ፤ የሩቁን ፡ ለቅርብ ፡ የወንዱን ፡ ለሴት ፤ ያንዱን ፡ ለብዙ ፡ መስጠት ፡ ማመራረስ ፡ የቅኔ ፡ የዚቅ ፡ የወረብ ፡ የለዘብ ።

—፤ መፋቅ ፡ መፈቅፈቅ ፡ መሞነስ ፡ ማጥፋት ፡ መደምሰስ ፡ መለወጥ ፡ መገልበጥ ፡ የጥፋት ፡ የፍርድ ፡ ለገንዘብና ፡ ለክብርናም ፡ ጥፋት ፡ ይነገራል ። ፈኑ ፡ እዴከ ፡ ወግስስ ፡ ኵሎ ፡ ዘቦ ፡ (ኢዮ ፲ ፡ ፲፭ ፡ ፲፪) ፡ ፈሐቀ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ገሰሰ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ገሰገሰ ፡ ይላል ፡ አጥብቆ ፡ መላልሶ ፡ ለማለት ። እምድኅረ ፡ ገሰገስዎ ፡ ለውእቱ ፡ ቤት ፡ (ዘሌ ፲፬ ፡ ፵፫) ።

ገሳሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት) ፤ የገሰሰ ፡ የሚገስ ፡ ገሳሽ ፡ ዳሳሽ ። ማቴዎስ ፡ ገባሲ ፡ ቍስልክ ። ገሳሲት ፡ (አሞል ። አርጋ ፡ ፭) ።

አግሰሰ ፤ አስገሰሰ ፡ አስዳሰሰ ፡ አስያዘ ፡ አስፈጠጠ ። አግስስኒ ፡ አዕማደ ፡ እለ ፡ ዲቤሆን ፡ ይቀውም ፡ ዝንቱ ፡ ቤት ፡ (መሳ ፲፮ ፡ ፳፮) ።

ተገሰ ፤ ተዳሰሰ ፡ ተዳበሰ ፡ ተነካ ፡ ተያዘ ። ቶገሰ ፡ እምቶማስ ። እሳተ ፡ ሕይወት ፡ ዘኢይትገሰስ ፡ (ኪዳ ። ባታት ። ቂር) ።

ግሱስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ስስት) ፤ የተያዘ ፡ የተዳሰሰ ፡ የተደመሰሰ ።

ግሰት ፤ መዳሰስ ፡ (ጥዳ) መዳሰስ ፡ አዳሳሰስ ፤ ዳሰሳ ፡ ዳበሳ ። ኢልኩፋን ፡ በግሰተ ፡ አጻብዕ ። በግሰተ ፡ ከናፍሪሁ ፡ ለዳንኤል ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

ግስ ፤ ጓዝ ፡ እክት ፤ ግስንግስ ፡ ዕቃ ፡ ግሰት ፡ የሚያገዙና ፡ የሚዳሰስ ፡ ኹሉ ። ሰማይ ፡ ከነግሱ ፡ ምድር ፡ ከነልብሱ ፡ እንዲሉ ፡ ከነጓዙ ፡ ቢሉ ። ጋሰሰ ፡ አጋሰሰ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

—፤ በቁሙ ፡ የቋንቋ ፡ መጣፍ ፡ የዘርና ፡ የነባር ፡ መድበል ፡ መዝገበ ፡ ቃል ፡ ንባቡ ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ የታከተ ፡ የተከተተ ። ምስጢሩ ፡ ግን ፡ ተወራራሽ ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አንዱ ፡ አንቀጽ ፡ እስከ ፡ ሰማንያ ፡ ነባሩና ፡ ጥሬው ፡ እስከ ፡ ሦር ፡ መርባት ፡ በመወራረስ ፡ ነውና ።

ጋስ ፤ አው ፡ ጋሶ ፤ ዝንጉርጉር ፡ ነጭና ፡ ጥቍር ፡ ጕራዝማ ፤ የበዳ ፡ አህያ ፡ ዐይነት ፡ ሽልምልም ፡ ወይም ፡ ዒሐ ፡ ቡሕማ ። ጋስ ፡ ወጸዐዳ ፤ ወይወልዳ ፡ ኵሎን ፡ አባግዕ ፡ ጋሶ ፡ ወኵሎ ፡ ዘቦ ፡ ትእምርት ፡ ወኵሳኵስ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫) ።

(ጥ) ገት ፤—ብዕል ፡ ሀብት ፤—ገዪት ፡ ጌተ ።

ጌቴሴማን ፤ (ጽር ፤ ጌትሲማኒ ። ዕብ ፡ ጋት ፡ ሽማኔይ) ፤ የቦታ ፡ ስም ፡ የደብረ ፡ ዘይት ፡ እግር ፡ የዐጸደ ፡ ሐምል ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ። ግበ ፡ ዘይት ፡ ምክያደ ፡ ዘይት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ማቴ ፳፮ ፡ ፴፮) ።

ገቲት ፤ ቶት ፤ (ገተ ፤ ገተተ ፡ ይገትት ፡ ይግትት) ፤ መጕተት ፡ ማንገላታት ፡ እንዳለወገን ፡ ማድረግ ። ገትገተ ፡ ብሎ ፡ ገተገተ ፡ ገትጋታ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

ተገተ ፤ ተጐተተ ፡ ዐለቀ ፡ አረጀ ፡ ግትቻ ፡ ኾነ ።

ግቱት ፤ ያረጀ ፡ ያለቀ ፡ የተጠገን ፡ የተናቀ ፡ (ኢያ ፱ ፡ ፭) ።

ግትት ፤ ግትቻ ፡ ስባሪ ፡ የማይረባ ፡ ሥራ ፡ የማይገዝ ፡ ዕላቂ ፡ ውዳቂ ፡ ውራጅ ፡ አሮጌ ፡ ዕቃ ። ወከነ ፡ ከመ ፡ ግትት ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ። ግትተ ፡ ዘሰምን ፡ ትሂ ፡ ኢይበቍዕ ፡ (ሆሴ ፰ ፡ ፰ ። ኤር ፳፪ ፡ ፳፰) ።

ጊጳ ፤ (ጽር ፡ ጊፓ ። ትግ ፡ ጋብ) ፤ የጥንብ ፡ አሞራ ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፲፬ ። ዘዳ ፲፬ ፡ ፲፪) ።

# ደ

ደ ፤ አራተኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፋ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፡ ስሙ ፡ ድል(ን)ት ፡ ቍጥሩ ፡ አራት ፡ አ፡ንዝ ፡ ሲኾን ፡ ደ ፡ እርባዕት ፡ ቱ ፡ ይባላል ። ዕብራውያን ፡ ግን ፡ አራትን ፡ መደብ ፡ አድርገው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነቍጣ ፡ እየ ጨመሩ ፡ አራት ፡ አልፍ ፡ ይሉታል ። ምስጢሩ ፡ ረቡንና ፡ የረቡን ፡ ፍጥረት ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ምስጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ ያሳያል ። (ዘፍ ፩ ፡ ፲፱ ። ዮሐ ፩ ፡ ፫–፭) ።

ድኢም ፤ ሞት ፤ (ደአመ ፡ ይድእም ፡ ይድአም ፡ ዐረብ) ፤ መቅክል ፡ ማቆም ፡ ማጥናት ፡ ማሸራሸት ፡ ማጥበቅ ፡ እንዳይወድቅ ፡ እንዳይነቃነቅ ፡ ማድረግ ፡ መመሥረት ፡ የማብር ፡ የነገር ፡ ከጥሬው ፡ በቀር ፡ እንቀጹ ፡ አይገኝም ።

ዳእሙ ፤ (ትግ ፡ ደአም) ፤ ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ። እንጂ ፡ ግን ፡ ብቻ ፡ ይልቅ ፡ ይኾናል ፤ እንጂና ፡ ግን ፡ ብቻና ፡ ይልቅ ፡ አንዳንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ቢገባም ፡ እንደ ፡ ባሕቱ ፡ በፊት ፡ በኋላ ፡ ይገባል ፡ አሳንና ፡ ባሕቱን ፡ ተመልከት ። ኃጥኣንሰ ፡ አኮ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ዳእሙ ፡ ከመ ፡ መሬት ፤ እንጂ ። ኵሎ ፡ ዘቦ ፡ መጠውኩክ ፤ ዳእሙ ፡ ኪያሁ ፡ ኢትግስስ ፤ ግን ። እሉኑ ፡ ዳእሙ ፡ ደቂቅከ ፤ ብቻ ። ወይቤሎ ፡ አልቦ ፡ ዳእሙ ፡ ፈንወኒ ፤ ይልቅ ፡ ብቻም ፡ ይኾናል ፡ (መዝ ፩ ። ኢዮ ፩ ፡ ፲፪ ። ሳሙ ፲፮ ፡ ፲፩ ። ጦቢ ፲ ፡ ፱) ። (ዕር ፲፱ ፡ ቍ ፹፭) ።

ዲበ ፤—ላዩ ፡ ወደ ፤—ደይብ ፡ ደየበ ፤ ዲብ ።

**ድብ ፤—በቁሙ ፤—ደቢው ፡ ደበወ ።**

**ደቢብ ፤ ቦት ፤(ደበ ፡ ደበበ ፡ ይደብብ ፡ ይድብብ ። ዕብ ፡ ዳበብ ፤ ኀለየ ፡ ነበበ)** ፤ መደበብ ፡ መዘርጋት ፡ መወጠር ፡ መገተር ፡ የጥላ ፡ ያጐበር ። መይብብ ፡ መጥቈር ፡ ደባባ ፡ መኾን ፡ የመልክ ፡ የሕብር ፡ ድባ ፡ መዳብ ፡ እንዲሉ ። ወደ ፡ ደቡብ ፡ መኼድ ፡ ደቡብ ፡ ደቡብ ፡ ማየት ፡ ደቡባዊ ፡ መኾን ። ደብደበን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ድብብ** ፤ በቁሙ ፡ ጃን ፡ ጥላ ፡ የሚደበብ ፡ የሚዘረጋ ፡ የሚታጠፍ ፡ የሚጠቀለል ፡ ጌጥና ፡ ሽልማት ፡ መረሻት ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ሌጣ ። **ጸዋሬ ፡ ድባብ** ፡ (ታሪ ፡ አክ) ።

**ደቡብ** ፤ የማእዝን ፡ ስም ፡ ዐቢይ ፡ ማእዝን ፡ የሰሜን ፡ ትይዩና ፡ አንጻር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሊባና ፡ በአዜብ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ የምዕራብ ፡ ቀኝ ፡ የምሥራቅ ፡ ግራ ። ሰሜንን ፡ ተመልከት ። **ዘሎ ፡ ገጽ ፡ እምደቡብ ፡ እስከ ፡ ሰሜን** ፡ (ሕዝ፳ ፡ ፵፰) ። ደቡብ ፡ የምሥራቅ ፡ ግራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሰሜንም ፡ የምዕራብ ፡ ግራ ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተሳስቶ ፡ በደቡብ ፡ ፈንታ ፡ ሰሜን ፡ በሰሜን ፡ ፈንታ ፡ ደቡብ ፡ እያለ ፡ ቡበዙ ፡ ቦታ ፡ ተጥፎ ፡ ይገኛል ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፲፫ ፡ ፴፭ ። ፵፭ ፡ ፳፰ ። ፵፱ ፡ ፲፪) ።

**ተደበ** ፤ ተደበበ ፡ ተዘረጋ ፡ ተዋቀረ ።

**ድቡብ ፤(ባን ፡ ባት ፡ ብብት)** ፤ የተደበበ ፡ የተዘረጋ ፡ ገዝርግ ። ደባባ ፡ መዳበማ ።

**ተድባብ ፤(ባት)** ፤ ጣራ ፡ ባጥ ፡ ጠፈር ፡ መዋቅር ፡ መከደኛ ፡ ክዳን ፡ ጥላ ፡ ከለላ ፡ ዳስ ፡ ጕዝ ። **ተሞቅሑ ፡ መትሕተ ፡ ተድባበ ፡ ቤት ። ወትገብር ፡ ላቲ ፡ መልዕልቴሃ ፡ ተድባበ ፡ ዘወርቅ ። ይትጌገሥ ፡ ቍረ ፡ ክረምት ፡ ወሐሩረ ፡ ሐጋይ ፡ ታሕተ ፡ ሰማይ ፡ ዘእንበለ ፡ ተድባብ** ፡ (ጥበ፲፯ ፡ ፲፯ ። ዘፀ፳፭ ፡ ፲፯—፳፪ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፳፭) ። የማእዝን ፡ ራስ ፡ ሩጋፍ ፡ የቤት ፡ የቅጽር ፡ መስኮት ፡ ቅስት ፡ ዝንቦ ፡ ቀጸላ ፡ ደርብ ፡ ሰንቀባል ፡ ማነብ ፡ ስገንት ፡ ዘውድ ፡ አክሊል ፡ ጕልላት ፡ የመርከብ ፡ ሰንሰለት ፡ በኋላና ፡ በፊት ፡ በማእዝኑ ፡ ራስ ፡ የሚኾን ። በስተላይ ፡ ስለሚኾን ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። **አውረድዎ ፡ እንተ ፡ ተድባበ ፡ ቅጽር ። ተድባበ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ። ወይደንን ፡ እንተ ፡ ተድባብ ። ወለእመ ፡ ሐነጽከ ፡ ቤተ ፡ ሐዲስ ፡ ትገብር ፡ ሎቱ ፡ ተድባበ ፡ ለናሕስክ ። ለእመ ፡ አረፍት ፡ ይእቲ ፡ ንሕንጽ ፡ ዲቤሃ ፡ ተድባበ ፡ ዘብሩር ። ትምህሩ ፡ ይግበሩ ፡ ተድባበ ፡ አሕማር ። ወከኑ ፡ ይገብሩ ፡ ተድባባተ ፡ አሕማራት** ፡ (ግብ፲ ፡ ፴፫ ። ማቴ፬ ፡ ፭ ። ማሕ፪ ፡ ፱ ። ዘዳ፳፪ ፡ ፰ ። ማሕ፰ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ጥር ፲፯ ። የካ፪) ።

**ዲባግ ፤(ጋት ። ዐረ ፡ ዲባጅ)** ፤ ልብስ ፡ ሐር ፡ ዝንጕርጕር ፡ ባለብዙ ፡ ሕብር ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ። **ሢራዮት ፡ ወዲባጋት ። አልባሰ ፡ ዲባጋት ። ቀጠንት ፡ ወአዲባጋት ። ጸውዖ ፡ ብእሲ ፡ ባዕል ፡ ለዲዮጋንስ ፡ ጠቢብ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ወከነ ፡ ስርግወ ፡ በዲባጋት ፡ ወብእሲሁሰ ፡ ኢከነ ፡ ግሁዳ** ፡ (መቃ ። ስንክ ፡ መስ፲፯ ። አፈ ፡ ተ፳፰ ። ፈላስ) ።

**ደብደበ ፤(ደበ ። ዐረ ፡ ዘበ ፤ ዘብዘበ)** ፤ ፈራ ፡ ዐሰበ ፡ ተጨነቀ ፡ የሚመጣበትን ፡ ስላወቀ ። **ዪሐዝን ፡ ወይደበድብ** ፡ (ሬልክ ፡ ፻፳፭ ። ቀሌ) ።

—፤ ፈዘዘ ፡ ተንፋ ፡ ዱባ ፡ መሰለ ፡ የሆድ ፡ የሰውነት ፡ እብጠቱ ፡ ከመብላት ፡ የተነሣ ። **ወሶበ ፡ ይነቅህ ፡ ኢይደበድብ ፡ ነፍስቱ** ፡ (ሢራ፴፱ ፡ ፳) ።

—፤ በቁሙ ፡ ደበደበ ፡ መላልሶ ፡ መታ ፡ ቀጠቀጠ ፡ ደብዳቢ ፡ እንዲሉ ። አረገዘ ፡ ድብድብ ፡ ኾነ ፡ የስብል ፡ ምስጢሩ ፡ ማበጥ ፡ መንዘርጠጥ ፡ ነውና ፡ ተንፋ ፡ ካለው ፡ ይገባል ።

—፤ ጣፈ ፡ ሰጠፈ ፡ ሰፋ ፡ ጠቀመ ፡ ደረተ ። ደብዳቢ ፡ ድብዳብ ፡ ደባደበ ፡ እንዲሉ ፡ ድብድብ ፡ ዳቦ ፡ ዱባ ፡ ማለትም ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ። (ግጥም ፡ ድኻ ፡ ተማሪ) ፡ ጋቢዬ ፡ አትለቂ ፡ ተዩ ፡ ይሻልሻል ፡ መርፌች ፡ ተሰብስበው ፡ ይደበድቡሻል ።

**አደብደበ** ፤ አስደበደበ ። አስጨነቀ ፡ አፈዘዘ ፡ አደከመ ። **ለእመ ፡ አደብደበታ ፡ ኀጢአት ፡ ለነፍስ** ፡ (ሬልክ ፡ ፺፭) ።

**አንደብደበ** ፤ አንደበደበ ፡ ተንደበደበ ፡ ደበደበ ፡ ኾነ ፡ መሰለ ፡ የገላ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዲብዲቆን ፤(ጽር ፡ ዲፕቲኮን)** ፤ ሰሌዳ ፡ መጽሐፈ ፡ ተዝካር ፡ የሙታን ፡ ወይም ፡ የሕያዋን ፡ የማኅበርና ፡ የመምህራን ፡ የጳጳሳትና ፡ የቅዱሳን ፡ ስም ፡ በቅሎ ፡ የሚጣፍበት ፡ የባለልዮስን ፡ ቅዳሴና ፡ ወዕቀበመውን ፡ በእንተ ፡ ብፁዕን ፡ የመሰለ ፡ መግዘገበ ፡ አስማት ። **መጽሐፈ ፡ ዲብዲቆን ፡ ዘቅዱሳን ። ኀበ ፡ ተለክአ ፡ ዲብዲቆን ፡ ዘማኅበረ ፡ ነቢያት** ፡ (መጽ ፡ ምስ ። አርጋ ፡ ፬) ።

**ደቢው ፡ ዎት ፤(ደበወ ፤ ይደቡ ፡ ይድቡ ። ደበየ ፤ ዴገ)** ፤ ማድባት ፡ መሸመቅ ፡ ቀስ ፡ ገዝግ ፡ ማለት ፡ መደበት ፡ መሠዋን ፡ መፈለቁን ፡ መደቈቆስ ፡ ያውሬ ፡ የጠላት ፡ የንቅልፍ ።

**ድቡት** ፤ ሽመቃ ፡ ቀስታ ፡ ዝግታ ፡ ድቢታ ፡ አደባበት ። **ርቱዕ ፡ በድቡት ፡ ንግበሮ ፡ ለዝ ። ከመ ፡ ዘበድቡት ፡ ወበቀሊል ፡ ያሐምመከ** ፡ (ግብ፳፱ ፡ ፴፯ ። ሄርማ ። ፪ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፪) ።

**ድቡተ** ፤ ቀስ ፡ ብሎ ፡ በቀስታ ፡ በሹልክታ ፡ ሳይታይ ፡ ሳይሰማ ። **ዐርገ ፡ ድቡተ ፡ እንተ ፡ ካልእ ፡ ገጽ ። ወፅአ ፡ ድቡተ ። ወሶበ ፡ ስእነ ፡ ሠገረ ፡ ድቡተ ፡ ሖረ** ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ድጓ) ።

**ድብ ፤(ባት ። ዕብ ፡ ዶብ ። ሱር ፡ ዶባ ። ዐረ ፡ ዱብ ፤ ዱበት)** ፤ በቁሙ ፡ አውሬ ፡ የጎሬብ ፡ ወገን ፡ የሚያደባና ፡ የሚያሸምቅ ፡ አድብቶ ፡ የሚይዝ ፡ የሚነጥቅ ፡ ጥላው ፡ የሚያፈዝ ፡ የሚያድብት ፡ ጠጕራም ፡ ዐመድማ ፡ (ወና ፡ ሴ) ። **ድብ ፡ ኀራስ ። ድብ ፡ ርኁብ ። ድብ ፡ እንተ ፡ ትንዑ ። ቤተ ፡ አናብስት ፡ ወድባት ። ከመ ፡ ትፈኑ ፡ ድባተ ፡ ብዙኀ** ፡ (፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፰ ። ሆሴ ፲፫ ፡ ፰ ። ሰቈ፫ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ መስ፳፯ ። ጥበ፲፩ ፡ ፲፰) ።

—፤ ስመ ፡ ከዋክብት ፡ እንስሳዊ ፤ ከመንፈቀ ፡ ሰማይ ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወገን ፡ ጅብ ፡ ብለው ፡ ታፍገ ውና ፡ ተመስገው ፡ ድርገት ፡ ኹነው ፡ የሚታዩ ፤ ባለመር ከቦች ፡ የሚመሩባቸው ። ዮትያዊ ፤ ይኔጽር ፤ ኀበ ፤ ከዋ ክብት ፤ አመ ፤ የሐውር ፤ ውስተ ፤ ባሕር ፤ ዘከመ ፤ ይ መርሓ ፤ ወይከይዳ ፤ ለሐመሩ ፤ (ማር ፡ ይሥ፳፰) ።



ድብ ፡

**ደብይ፤ዮት ፤(ደበየ፡ይደቢ፡ይድቢ። ደበወ)** ፤ ማደባየት ፡ ከፈር ፡ ከመሬት ፡ ከድቤ ፡ ላይ ፡ መጣል ፡ ማንከባለል ፤ ደባ ፡ መሥራት ፤ ሳይታሰቡ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ ዘው ፡ ጥልቅ ፡ ዠቅ ፡ ማለት ፤ መውረር ፡ መዝረፍ ፤ መቀማት ፡ መመንተፍ ። ደበዩኒ ፤ እለ ፤ አልቦሙ ፤ ምሕረት ። ሮዱኒ ፤ ወደበዩኒ ። ይ ደቢ ፤ እብያተ ፤ ሰብእ ። ከመ ፤ ኢይድብያ ፤ ለቤተ ፤ ክርስቲያን ፤ (ኢዮ፴ ፡ ፳፩ ። መዝ ፡ ፴፯ ። ግብ፰ ፡ ፫ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ደባዪ ፤(ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ በይት)** ፤ ወራሪ ፡ ዘራፊ ፤ ቀማኛ ። ደባዩ ፤ አባግዐ ፤ (አዋል) ።

**ድቤ ፤(ዐማርኛ)** ፤ ዐፈር ፡ መሬት ፤ ትቢያ ፡ ዐቧራ ። ደባ ፡ ደበ ፡ ደባይ ፡ ደባያት ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ደቢል ፤ ሎት ፤(ደበለ ፡ ይደብል ፡ ይ ድብል)** ፤ መደበል ፡ ማዳበል ፤ መሸረብ ፡ መደረብ ፤ የሐብል ፡ የፈደል ። መስከት ፡ ማሳከት ፤ በፈትል ፡ ወይም ፡ ርስ ፡ በርሱ ፤ ደድባ ፡ የበለስ ፡ የዋንጫ ።

—፤ ማከብ ፡ መሰብሰብ ፡ ማከማቸት ፤ የሸንጎ ። መጽ ሐፍ ፡ ማን ፡ በደበለና ፡ በተደብለ ፡ ፈንታ ፡ አመድብለ ፡ መድብለ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ሰላም ፤ ሰላም ፤ ለእንድራኒቆስ ፤ እብሎ ፤ ውሒዘ ፤ መንፈስ ፤ ዘሰተየ ፤ ምስለ ፤ ሐዋርያት ፤ በአመድብሎ ። ሰቍስጥንጥ ንያ ፤ ዘመድብሉ ፤ (ስንክ ፡ ግንቦ፱ ። ጥር፲፭) ።

**መድበል** ፤ ማከማቻ ፡ መከማቻ ፤ መሰብሰ ቢያ ፡ መድለቻ ፤ ሸንጎ ፡ ጉባኤ ፡ የሰው ፡ መንጋ ። መድ በለ ፤ ማኅበር ። መድብለ ፤ ቅዱሳን ፤ እንተ ። አዘዘ ፤ ይግበሩ ፤ መድብለ ። ለእለ ፤ ምስሌሁ ፤ መድበል ፤ (ማሕ፯ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፯ ። ሚያ፲፯ ። መስ፱) ። የቅ ጽል ፡ ስም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ የሚያስተባብር ፤ ቅደ ምት ፤ ደንርት ፤ ገበርት ፤ ቀተልት ፤ ይህን ፡ የመሰለ ።

**ተዳበለ** ፤ በቁሙ ፡ ተባበረ ፡ ተጨፋፈረ ፡ ተሸ ረበ ፡ ተደራረበ ። ተዳበለ ፤ ፀራዊ ፤ ወተመዊእ ፤ ጕየ ፤ (ተረ ፡ ቁር፲) ።

**ዱብል ፤(ላቲን)** ፤ ደባል ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ መንታ ፡ ፈደል ፡ ደጊመ ፡ ቃል ። የበበ ፤ ነበበ ፤ ደሰለ ፤ ከለለ ፤ ሐተተ ፤ ፈተተ ፤ ይህን ፡ የመሰለ ። ደበሎ ፡ ዐጕዚ ፡ ለምድ ፡ በላይ ፡ የሚደረብ ። (ትረት) ፡ ሁብታም ፡ ይኼ ዳል ፡ በበቅሎ ፤ ድኻ ፡ ይለብሳል ፡ ደበሎ ።

**ድብል ፤(ትግሬ)** ፤ ልብስ ፡ ዒሊ ፤ የደንገ ያና ፡ የቀንድ ፡ ያጥንት ፡ ዐይነት ፡ ከራራ ፡ ጠንካራ ። ጥኑ ፡ ክባድ ፡ ሸክም ፤ ጭነት ፡ ውድን ፡ ወዲላ ። በቁሙ ፤ ድ በላ ፡ ያበባ ፡ እኽል ፡ ሲከኩት ፤ ፪ንት ፡ ያለው ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዳቤላ ፤(ላት)** ፤ ደቦል ፤ ታላቅ ፡ የፍየል ፡ አ ውራ ፤ የሚደረብና ፡ የሚታዘል ፡ የሚንጠላጠል ፤ የላም ፡ አውራ ፡ ኰርማ ፡ ወይፈን ። ዳቤላ ፤ ዘጠሊ ። ሰብዐቱ ፤ ዳቤላት ። ንስሐቦ ፤ ለዳቤላ ፤ ዘላሕም ፤ (ዳን፰ ፡ ፭ ። ኩፋ ፡ ፲፮ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ዳቤላም ፤(ዕብ፡ ድቤሊም)** ፤ የበለስ ፡ ቋን ጦች ፡ ቍጥራቶች ፤ እንደ ፡ መቍጠሪያ ፡ የተሰኩ ። አን ዱን ፡ ስከ ፡ ድቤላ ፡ ይሰዋል ፤ እኔላን ፡ ተመልከት ፤ ከ ዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዕፀ ፡ ጕ ርደ ፡ የወጣለት ፡ ደቂት ፡ ይሉታል ፡ (፩ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፵) ።

(ጥ) **ድበን ፤(ዐረ)** ፤ ዝንብ ፤ ደበን ፡ አደበን ፡ ድ ብን ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።


**ድብዕንኵል ፤ ድንብዕኵል ፤(ላት)** ፤ ያን በሳ ፡ ወጥመድ ፡ እንደ ፡ ቀፎ ፡ ያለ ፡ (ሕዝ፲፱ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ደቢቅ ፤ ቆት ፤(ደበቀ፡ ይደብቅ፡ ይድ ብቅ ። ዕብ፡ ዳባቅ ፤ ለጠቀ፡ ተጠጋ)** ፤ መደበቅ ፡ መደባበቅ ፤ መሸጐጥ ፡ ማስጠጋት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ደቢር ፤ ሮት ፤(ደበረ ፡ ይደብር ፡ ይድ ብር)** ፤ መደበር ፡ መገደም ፤ ደብር ፡ ገዳም ፡ መሥራት ፡ ማዘጋጀት ፤ ለንግድ ፡ ዕቃም ፡ ሳይቀር ፡ ለታሪክ ፡ ለመጽ ሐፍ ፡ ይኾናል ።

**ደባሪ ፤ መደብር** ፤ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፤ ባለቤት ። ዮሐንስ ፤ መደብር ፤ ዘውእቱ ፤ ሠራዒ ፤ ብሂል ።

**ደብር ፤(ብ ፡ አድብር ፤ ራት)** ፤ ተራራ ፡ ጋራ ፡ ገመገም ፤ የምድር ፡ ዕንብርት ፡ ጉብር ፡ ታላቅ ፡ ረኀርም ፤ ከወገር ፡ የሚበልጥ ። ደብረ ፤ ሲና ። ደብረ ፤ ዘይት ። ደብረ ፤ ታቦር ። አድባረ ፤ እስራኤል ፤ (ሕዝ፮ ፡ ፪) ። የተራራ ፡ ተራራ ፤ ከተራራ ፡ ኹሉ ፡ የሚበልጥ ፤ በረደ ፡



ደብር ፡

የሚፈሳበት ፡ ሰው ፡ የማይደርስበት ፤ እንደ ፡ ዳሸን ፡ እ ንደ ፡ ሄርሞን ፡ ያለ ፡ የሰማይ ፡ ጎረ ፡ ቤት ። አድባረ ፤ አራ ራት ። አድባር ፤ ነዋኃት ፤ ዘመትሕተ ፤ ሰማይ ፤ (ኩፋ ፡ ፰ ። ዘፍ፰ ፡ ፲፱ ። ፰ ፡ ፬) ።

—፤ ወሰን ፡ ደንበር ፤ መዲና ፡ ከተማ ፡ ታላቅ ፡ አገር ። ወኮነ ፡ አድባሪሆሙ ፡ ለከነዓን ፡ እምነ ፡ ሲዶን ፡ እስከ ፡ ጌራራ ። ደብረ ፡ አህጉር ። ዲበ ፡ ሖሉ ፡ አድባሪከ ። አድባረ ፡ ግብጽ ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፲፱ ። ኢ.ያ፲፬ ፡ ፲፭ ። ዘፀ፲ ፡ ፬ ፡ ፲፱ ። ኢሳ፳ ፡ ፳፮) ።

—፤ ገዳም ፡ ቤተ ፡ ክሲያን ፡ ታላቁም ፡ ታናሹም ። ደብረ ፡ ሊባኖስ ። ደብረ ፡ ዐስቦ ። አድባራት ፡ ወገዳማት ። አበ ፡ መቃርስ ፡ ዘደብረ ፡ አስቄጥስ ፤ መዳልወ ፡ አልባብ ፡ ተሰምየት ፡ እስከ ፡ ዮም ፡ ደብሩ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ስንክ ፡ መጋ፳፯) ። ደብር ፡ ማለት ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ የሚሠራ ፤ ተራራ ፡ የሚያኽል ፡ ታላቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የምኵራብን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። (ሙሾ ፡ ስለ ፡ ድምፀ ፡ መልካም ፡ ደብተራ) ፤ ካህን ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ አይንግሩም ፡ ዐዋጅ ፤ እንዲያው ፡ በየደብሩ ፡ መላክ ፡ ነበረ ፡ እንጅ ።

**ዳባር ፤ (ዕብራ)** ፤ ነገር ፡ ቃል ፤ ባህል ፡ ብሂል ፤ እንዳች ፡ ጕዳይ ፡ መፍቅድ ።

**ዳቤር ፤ (ጽር ፡ ዳቢር ። ዕብ ፡ ድቢር) ፤** መቅደስ ፤ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፤ ባርባው ፡ ከንድ ፡ ፊት ፡ ያለ ፡ ኸያው ፡ ክንድ ፤ መክነ ፡ ታቦት ፤ ቃለ ፡ እግዚ ፡ የሚሰማበት ፤ የሚነገርበት ፡ (፩ነገ ፡ ፮ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱—፳፪ ። ፰ ፡ ፮ ፡ ፰ ። ዘፀ፳፭ ፡ ፳፪) ።

—፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ ታናሽ ፡ ከተማ ፤ በይሁዳ ፡ ክፍል ፡ ያለች ፤ ካሌብ ፡ የወረሳት ። እስ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ዳቤር ፤ ወስማ ፡ ለዳቤር ፡ ሀገረ ፡ መጽሐፍ ፡ (ኢ.ያ፲፭ ፡ ፲፭) ። ዳቤር ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ መጽሐፍ ፡ ብሎ ፡ ፈታው ፤ መጽሐፍን ፡ ዳቤር ፡ ድቢር ፡ ማለት ፡ በፋርስ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ (ረበናት) ።

**ደበርቢር ፤ (ዐረ ፡ ዱብር ፤ ዘባን ፡ ድኅር) ፤** ታናሽ ፡ ድንኳን ፡ አጕብር ፤ ማረፊያ ፡ መጠጊያ ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ወንበርና ፡ እንዳትሮንስ ፡ ያለ ፤ ሲጠጉት ፡ ገርባ ፡ የሚጐንጥ ፤ የሚጐረብጥ ፤ መንኮባት ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ዐርፈው ፡ ርሱን ፡ ተደግፈው ፡ እንቅልፋቸውን ፡ የሚያሳልፉበት ። ይኑሙ ፡ እንዘ ፡ ኢይሰክቡ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ አትራዮስ ፡ ዘንድቅ ፡ ይግበሩ ፡ ደበርቢረ ፡ ወቦቱ ፡ ይንጽፉ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ወይስክቡ ፡ ንቡረ ፡ (ሥር ፡ ጳኵ) ።

**ደብረወ ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤** ዳበረ ፡ አደገ ፡ ላቀ ፡ ባለቀ ፡ ለዘር ፡ በቃ ፤ ባለገ ፡ ማገጠ ።

**ደበራ ፤** የብልግና ፡ ሥራ ፤ ገዘሙት ፡ ሴሰን ፤ ቅንዝር ፡ ምንዝር ።

**እንደበራ ፤ እንደባራ ፤ (ርው) ፤** ዲቃላ ፡ በዝሙት ፡ የተወለደ ፡ ያመንዝራ ፡ ልጅ ፤ ያልተሠራ ፡ ያልተቀጣ ፤ ሕገ ፡ ወጥ ፤ መረን ፡ አግድሞ ፡ አደግ ፤ ደፋር ፡ ዳንደ ፤ ጣፎርደ ። ወእመሰ ፡ ኢገሠጹክሙ ፡ እንደበራ ፡ አንትሙ ። ወልድ ፡ ዘኢተገሥጸ ፤ ፈረስ ፡ ዘኢተረየፀ ፡ እንደባራ ፡ (ዕብ፲፪ ፡ ፰ ። አዋል) ።

**መድበራ ፤ (ዕብ ፡ ሚድባር) ፤** ዱር ፡ የከብት ፡ መሰምሪያ ፡ ብዙ ፡ ሣር ፡ ቅጠል ፡ ውሃ ፡ ያለበት ። ወይም ፡ በጭራሽ ፡ ምናምን ፡ የሌለው ፡ ደረቅ ፡ በረሓ ፤ ምድረ ፡ በዳ ። ገዳም ፡ ዘመድበራ ። ማእከላ ፡ ለደብረ ፡ መድበራ ፡ (ኢ.ያ፳ ፡ ፮ ። ሔኖ፳፱ ፡ ፩) ።

—፤ መድበል ፡ ማኅበር ፤ ጉባኤ ፡ አንድነት ። ይገብሩ ፡ መድበራ ፡ (ሔኖ፹፯ ፡ ፲) ።

**መድብራይጥስ ፤ (ጽር ፡ ማብዳሪቲስ ። ዕብ ፡ ሚድባራ) ፤** ጠፍ ፡ ባድ ፡ ባድማ ፤ የዱሮ ፡ ከተማ ፤ የተፈታ ፡ አገር ፤ ዱር ፡ ጣሻ ፤ በረሓ ፡ የኾነ ። መድብራይጥስ ፡ ዘቤቶን ፡ (ኢ.ያ፲፰ ፡ ፲፪) ።

**ደብራን ፤ (ዐረ ፡ እደበራን ። ዕብ ፡ ክሲል) ፤** ጕባኤን ፡ ከዋክብት ፡ ባንድነት ፡ የተደበሩ ፤ በጕሽ ፡ ስም ፡ የሚጠሩ ፤ ፈላስፎች ፡ ጕሽ ፡ የሚሏቸው ፡ እንንትምስቶ ፤ ወይም ፡ ክምስቱ ፡ አንዱ ፡ ታላቁ ፡ ብጣም ፡ የሚያበራው ። ባለብሎዮች ፡ ዳተኛ ፡ ይሉታል ። ወአስተጋብእሙ ፡ ለደብራን ። ርኢከኑ ፡ ፍኖቶ ፡ ለደብራን ፡ ወመፃእ ፡ (ኢዮ፶ ፡ ፱ ። ፴፰ ፡ ፴፩) ።

**ድቡስ ፤ ድንቡስ ፤ (ሳት ። ዐረ ፡ ዲቡስ ፤ ብ ፡ ደባቢስ) ፤** ሩባም ፡ ችንካር ። የብረት ፡ በሎታ ፤ ወይም ፡ ዘንግ ፡ ወፍራም ፡ ሽቦ ፡ ቋራም ፡ ስስታም ። አዘዘ ፡ ይዝብጥዎ ፡ በድቡሳት ፡ ዘትጺን ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፳ ። ጥር፩ ። ሐም፳ ። ሠኔ፳፯) ። ቀሠፍዎ ፡ በድንቡሳት ፡ በሲኃት ፡ እስከ ፡ ተሰብሩ ፡ ገበዋቲሁ ፡ ወቦኡ ፡ ውስተ ፡ ከርሡ ። ድንቡስ ፡ ክቡድ ፤ ድንቡሳት ፡ ዘብርት ፡ (ስንክ ፡ ሚ.ያ፲፪ ። ፳፯) ።

(ጥ) **ድቡት ፤ —ሽመቃ ፡ ቀስታ ፤ —ደቢው ፡ ደበወ ።**

**ደብተር ፤ ፤ (ዕብ ፡ ዲፍታር ። ዐረ ፡ ዲፍትር) ፤** በቁሙ ፤ መጣፊያ ፡ መክተቢያ ፤ የብራና ፡ የወረቀት ፡ መዝገብ ፤ ነጋዶች ፡ ጠርዘው ፡ አፍፈው ፡ መጣፍ ፡ አስመስለው ፡ ለየጻሓፊው ፡ የሚሸጡት ። የገንዘብ ፡ ቍጥር ፡ ዘወፅአ ፡ ዘገብአ ፡ የሚጣፍበት ። ደብተር ፡ ማለት ፡ ቃሉ ፡ የፋርስ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

**ደብተራ ፤ (ጽር ፡ ዲፍቴራ) ፤** የምሣዕ ፡ የሠረገላ ፡ ተድባብ ፤ የመንበረ ፡ ታቦት ፡ አጕበር ፤ በስተላይ ፡ እንደ ፡ ድባብ ፡ እንደ ፡ ጃን ፡ ጥላ ፤ እንደ ፡ ባጥና ፡ እንደ ፡ ጣራ ፡ ኹና ፡ የሚሠራ ። ድንኳን ፡ መላጃን ፡ በዲፍቴራ ፡ አምሳል ፡ የተሠራ ፤ እንደ ፡ ብራና ፡ የሚወጠርና ፡ የሚገተር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ። ጸሓፊ ፤ ባለደብተር ፡



ደብተራ ፤

ባለብራና ። (ቀረት) ፤ ኢይጥፍ ፡ ደብተራ ፤ ክንፉ ፡ የለው ፡ አሞራ ። ተከለ ፡ አብራም ፡ ደብተራሁ ። መትሕተ ፡ ደብተራ ፡ ሠቅ ። በውስተ ፡ ደብተራሁ ፡ ቅዱስ ። ከመ ፡

ትትሐነጽ ፡ ደብተራሁ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፫ ። ሄኖና ፡ ፲፯ ፡ ፩ ። ሚራሽ፱ ፡ ፲ ። ጦቢ፲፫ ፡ ፲) ።

**ደብተራት ፤ ደባትር ፤** ደብተሮች ፡ መዝገ በኞ ፡ የሚጣፍባቸው ፡ ወይም ፡ የሚጥፉ ፡ ጣፎች ፡ ባለ ደብተሮች ። ድንኳኖች ፡ አጉብሮች ። **ጥዓት ፡ ደባትሪ ሆሙ ። ደበትር ፡ ዘነደ ፡ እሳት ። ደብተራት ፡** (ዘፀ፴፫ ፡ ፲ ። ቅዳ ፡ ሕር ። መቃ ፡ ገ፩) ።

**ደብተራዊ ፤** ድንኳን ፡ ተካይ ፡ የድንኳን ፡ አገ ልጋይ ፡ ባለድንኳን ፡ ሌዋዊ ፡ (እሬ ፡ ተ፲፯) ። መዘምርን ፡ ደብተራ ፡ ማለት ፡ ከሌዋውያን ፡ ስም ፡ የመጣ ፡ ነው ።



ደብተራ ፡

**ደብተረ ፤** ደበተረ ፡ ዘረጋ ፡ ነጠበ ፡ ወጠረ ፡ ገተረ ፡ በደብተረ ፡ ፈንታ ፡ አደብተረ ፡ ይላል ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**ተደብተረ ፤** ተደበተረ ፡ ተተከለ ፡ ተዘረጋ ፡ ተ ወጠረ ፡ እንደ ፡ ድንኳን ፡ ኾነ ። **ወተደብተረት ፡** ሎሙ ፡ **ደኢቲ ፡ እብን ፡** (ገድ ፡ አዳ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ድብቱር ፤** የተዘረጋ ፡ የተተከለ ። **ንብ ፡ ድብ ቱር ፡ ደባትረ ፡ እሳት ፡** (መጽ ፡ ምስ) ።

**ድብታሬ ፤** መተከል ፡ መዘርጋት ፡ ድብትርና ፡ ደብተርንት ።

**ድጓ ፤—የዜማ ፡ መጽሐፍ ፤—ደጊግ ፡ ደገ ፡ ደግደገ ።**

**ደጎብያ ፡ (ዕብ ፡ ጎበይ ። ዐረ ፡ ጃቢእ) ፤** ደጎብ ፡ አንበጣ ፡ ያንበጣ ፡ ወገን ፡ ኮብኮባ ፡ ፌንጣ ፡ ሉ ላውም ፡ ኹሉ ፡ አናኮስን ፡ እይ ። ለሰው ፡ ሲኾን ፡ ጉብዝ ፡ ወጣት ፡ ሦታ ፡ ደበል ፡ ረድ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ መሐገዝን ፡ ተው ፡ (ዮኤል ፩ ፡ ፬ ። ፪ ፡ ፳፭ ። ናሖ፫ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯) ። **እመ ፡ በ ፡ ዘበልዐ ፡ አንበጣ ፡ ወደጎብዮ ፡ አው ፡ ገመሰ ፡** (ቀሌ) ።

**ደጊግ ፤ ጎት ፤ (ደገ ፡ ይደግግ ፡ ይድግግ ። ዕብ ፡ ዳጋህ ፤ በዝ ፡ ረበ) ፤** መደገግ ፡ መኰረፋት ፡ ማደግ ፡ መመንደግ ፡ ደግ ፡ ደገኛ ፡ ታላቅ ፡ ምጡቅ ፡ መኾን ። ደጋ ፡ (ማድጋ) ፡ ደደክ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡ አዳጋ ፡ ቍ ሊልታ ፡ ተራራ ፡ ኰረብታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ልዕልናውን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ደግነቱን ፡ ጤና ማነቱን ፡ ያሳያል ። ደንገገን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ስሯሽ ፡ ነው ። በጋልኛም ፡ ዝናብን ፡ ደጋጋ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ ነጊን ፡ እይ ።

**ደግደገ ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ግ ። ዕብ ፡ ዳግዶግ ፤ ነከ ፡ ዳሰሰ) ፤** ከሳ ፡ ቀጠነ ፡ ደቀቀ ፡ ረቀቀ ፡ ማግ ። ማ ሰደ ፡ ገሠገሠ ፡ ማሰዳ ፡ ተንግ ፡ ታጠቀ ፡ ተጣጠቀ ፡ ለበሰ ፡ ተላበሰ ፡ አደገደገ ።

**ድግዱግ ፤ (ጋን ፡ ጋት ፡ ድግት) ፤** የከሳ ፡ የ ቀጠነ ፡ ቀጭን ፡ ደግዳጋ ፡ ኰሳሳ ፡ ከሻዋ ። **ድግዱግ ፡ ሥ ጋሆሙ ። ድግዱጋኒክሙ ። እስክንድር ፡ ድግዱግ ፡ መልክኡ ። ከነ ፡ አባ ፡ ብሶይ ፡ ድግዱግ ፡** (ዘዳ፳፰ ፡ ፫ ። ዳን፩ ፡ ፲ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ሐም፳) ።

**ድግዳጌ ፤** መክሳት ፡ መቅጠን ፡ እክሳስ ፡ ክሳት ፡ ደግዳግነት ፡ (ስንክ ፡ የካ፳፰) ። መታጠቅ ፡ መልበስ ፡ አለ ባበስ ፡ አስተጣጠቅ ፡ ትጥቅ ፡ ድግድጋት ። ዱግ ፡ ደግ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

(ጥ) **ድግ ፤** በቁሙ ፡ መቀንት ፡ የሆድ ፡ ክሳ ፡ የወገብ ፡ ምሳ ፡ ወገብ ፡ የሚያጠና ፡ የሚደግፍ ።

**ደግደግ ፤ ደግዲግ ፤** ጎሕ ፡ ንጋህ ፡ ጧት ፡ ማ ለዳ ፡ ንጋት ፡ ሳኒታ ፡ ማግስት ። **እፎ ፡ ወድቀ ፡ እምሰ ማይ ፡ ኮክበ ፡ ጽባሕ ፡ ዘበደግደግ ፡ ይሠርቅ ። ወኢ ታትርፉ ፡ እምኔሁ ፡ ለደግደግ ፡** (ተረ ፡ ቁር፳ ። ዘፀ ፲፪ ፡ ፲) ።

**አደግደገ ፤** አከሳ ፡ አቀጠነ ፡ አጕሰቈለ ። አማ ሰደ ፡ አስማሰደ ፤ አስገሠገሠ ። አስታጠቀ ፡ አስደገደገ ። **ደዌ ፡ አደግደገ ፡ ሥጋሁ ። ወያደገድጎ ፡ ከመ ፡ ላ ሕም ። አርባዕቱ ፡ ግብራት ፡ ያደገድጉ ፡ አባለ ፤ ሐ ዋረ ፡ ፍኖት ፡ ወትጋህ ፡ ዘልፈ ፡ ወጸዊም ፡ ወጽምእ ፡ በሐኑር ፤** አከሳ ፡ (ዮሴፍ ። መገ ፡ ሸ፳ ። ፈላስ) ። **ም ንት ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ያደገድገከ ፤** አማሰደ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፬) ።

**አንደግደገ ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ግ) ፤** በቁሙ ፡ አንደ ገደገ ፡ ተንደገደገ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ድጓ ፤** የዜማ ፡ መጽሐፍ ፡ ስም ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ባዱ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘመን ፡ ያዜመውና ፡ የገጠመው ። የኋላም ፡ ሰዎች ፡ በየጊዜው ፡ ለጠምረውበታል ፡ ጀሃው ፡ መዝሙር ፡ የዳዊት ፡ ብቻ ፡ እንዳይደለ ፡ ድጓም ፡ የያ ሬድ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ድግዱግ ፡ ድግዱገ ፡ ጽሕፈት ፡ ጥፈቱ ፡ የከሳ ፡ የቀጠነ ፡ ደቂቅ ፡ ረቂቅ ፡ የኾነ ፡ እሸዋ ፡ እብቅ ፡ ወይም ፡ ዜማ ፡ ቍዘማ ፡ ግጥምና ፡ ዜማ ፡ ማ ለት ፡ ነው ። ድጕጓን ፡ ተመልከት ። በደገ ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈ ቱት ፡ ግን ፡ ደግ ፡ ደገኛ ፡ አሰኝቶ ፡ የመጽሐፉን ፡ መጠን ፡ ታላቅነቱን ፡ ያሳያል ፡ በርቀቱ ፡ ላይ ፡ የመንፈቅ ፡ ስንክ ሳር ፡ ያኽላልና ። ፪ኛም ፡ ምእላድ ፡ መድበል ፡ እስትጉ ቡእ ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ፡ ቃሉ ፡ ከገድል ፡ ከታምር ፡ ከአዋልድ ፡ ሳይቀር ፡ ከብሉይ ፡ ከሐዲስ ፡ ከሊቃውንት ፡ ተሰቅሞ ፡ ተቀምሞ ፡ የወጣ ፡ ድርሳን ፡ ጎጤ ፡ መዝ ሙር ፡ ሐዲስ ፡ ማለት ፡ ነው ። ፫ኛም ፡ በፊደል ፡ ቍጥር ፡ ሲፈቱት ፡ ደ ፡ ፬ ፡ ገ ፡ ፫ ፡ ድጓ ፡ ፯ ፡ ይኾናል ፡ **እስመ ፡ ጕልቊ ፡ ሳብዐ ፡ ፍጹም ፡ ውእቱ ፡** ይላልና ፡ (ሃይ ፡ አበ) ፡ ፯ ፡ ፍጹም ፡ ቍጥር ፡ ነው ። ድጓ ፡ ማለትም ፡ እንደ ፡ ስንክሳር ፡ ከመት ፡ እስከመት ፡ የተሠራ ፡ በየስብሐቱ ፡

ከሐውድ ፡ እስከ ፡ ቀዳም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ቢት ፡ ማታ ፡ የሚቀርብ ፡ ፍጹም ፡ ድርሰት ፡ መሚሰት ፡ ስብሐት ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፡ ዋዜማ ፡ ዘሠርክ ፡ ዕዝል ፡ ዘነግህ ፡ ስብሐተ ፡ ነግህ ፡ ይባልና ። እየብቻውም ፡ ነጥሎ ፡ ቢፈቱት ፡ ይ ፡ የከፍሉን ፡ ትርጓሜት ፡ እንደ ፡ ወንጌል ፡ ፬፱ ፡ ዐቢይ ፡ ክፍል ፡ ተከፍሎ ፡ ዮሐንስ ፡ አስተምሕሮ ፡ ጾም ፡ ፋሲካ ፡ መብሉን ፡ ኅ ፡ ምስራፋን ፡ ዝማሬንና ፡ መዋሥዕትን ፡ ሦስቱን ፡ ያሳያል ። ዳግመኛም ፡ ዋይ ፡ ዜማ ፡ ዘሰማዕኩ ፡ በሰማይ ፡ እመላእክት ፡ ይባልና ፡ ሰባትነትን ፡ ለዜማው ፡ ብቻ ፡ ቢሰጡት ፡ ይ ፡ የስልቱን ፡ ትርጓሜት ፡ ቁምን ፡ ዝማሜን ፡ መረግድን ፡ ጽፋትን ፡ ያሳያል ፤ እሊህ ፡ አራቱ ፡ የኪሩቤል ፡ አምሳል ፡ ናቸውና ። ቁም ፡ ከመ ፡ ኪደተ ፡ ብእሲ ፤ ዝማሜ ፡ ከመ ፡ ኪደተ ፡ አንበሳ ፤ መረግድ ፡ ከመ ፡ ኪደተ ፡ ላሕም ፤ ጽፋዐት ፡ ከመ ፡ ኪደተ ፡ ንስር ፡ ወእሉ ፡ ይትሜሰሉ ፡ በአርባዕቱ ፡ እንስሳ ፤ (ገድለ ፡ አብርሃ ፡ ወአጽብሐ) ። ኅ ፡ የዜማውን ፡ ትምልስት ፡ ዜማው ፡ ግእዝና ፡ ዕዝል ፡ አራራይ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ። ዜማ ፡ ጠቅላይ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ያንድነት ፡ ስሙ ፡ የሦስትነት ። ምልክቱ ፡ ግን ፡ የኋላ ፡ ሰዎች ፡ ያበጁት ፡ ነው ፡ የያሬድ ፡ አይደለም ። ወበመዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ንጉሥ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ተንሥኡ ፡ አዛዥ ፡ ጌራ ፡ ወአዛዥ ፡ ራጉኤል ፡ ካህናት ፡ ማእምራን ፡ ዜማ ፡ ወወጠኑ ፡ አውፅኦ ፡ ምልክት ፡ ዘድጓ ፤ (ታሪ ፡ ነገ) ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ የድጓን ፡ ዘይቤ ፡ ምስጢርና ፡ አፈታት ፡ ከድጓ ፡ መምህራን ፡ ይጠይቋል ።

**ደጊም ፡ ሞት ፤ (ደገመ ፡ ይደግም ፡ ይድግም)** ፤ መድገም ፡ መደጋገም ፡ ቀድሞ ፡ የሠሩትን ፡ ፪ኛ ፡ መሥራት ። ገሥጽ ፡ ለዐርክከ ፡ ዮጊ ፡ ኢገብረ ፡ ወእመኒ ፡ ገብረ ፡ ከመ ፡ ኢይድግም ። ለእመ ፡ ቦ ፡ ዘአበስከ ፡ ኢትድግም ። ድገሙ ፡ ዓዲ ፡ ወአበሱ ። ኢይደግሙ ፡ አበሳ ፤ (ሢራ ፲፱ ፡ ፲፫ ። ፳፩ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፸፯ ። ሔኖ ፳ ፡ ፵) ።

—፤ ማንበብ ፡ ማንበንበብ ፡ መጸለይ ፡ መድገም ፡ መናገር ፡ መለፍለፍ ። ነሥአ ፡ መጻሕፍተ ፡ አበዊሁ ፡ ወደገሞን ። ወትደግም ፡ ምእተ ፡ ወኀምሳ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ። ኢይደግሙ ፡ ነገረ ፡ በደቢ ፡ ነገርየ ፤ (ኩፋ ፡ ፲፪ ። ግንቦ ። ኢዮ ፳፱ ፡ ፳፪) ።

**ደጋሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት)** ፤ በቁሙ ፡ የሚደግም ፡ የሚያነብ ፡ አንባቢ ። ዳዊት ፡ ደጋሚ ፡ እንዲሉ ።

**ምድጋም ፤ (ማት)** ፤ መድገሚያ ፡ ቦታ ፡ መጣፍ ፡ ጊዜ ። ድጋም ፡ ንባብ ፡ ዜማ ፡ የሌለው ፡ ቃል ።

**አድገመ** ፤ አስደገመ ፡ አስነበበ ፡ ድጋም ፡ አስተማረ ።

**ተደግመ** ፤ ተደገመ ፡ መጣፉ ። ፪ኛ ፡ ጊዜ ፡ ተደረገ ፡ ሥራው ። ዘኢኮነ ፡ ከማሁ ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ ወኢይደገም ፡ እንከ ፡ እምድኅሬሁ ፤ (ዮኤ ፪ ፡ ፪) ።

**ድጉም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ግምት)** ፤ የተደገመ ፡ የተደጋገመ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ። የተደገመበት ።

**ዳግም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት)** ፤ ድጋሚ ፡ ዳግምሽ ፡ ዳግመኛ ፡ ኹለተኛ ። ዳግም ፡ ልደት ። ዳግም ፡ ሞት ። ዳግም ፡ እሬት ። ዳግም ፡ ብእሲ ። አዕቀጸኒ ፡ ወናሁ ፡ ዳግሙ ፡ ዮም ። ሰላም ፡ ለክልኤት ፡ ደዎስ ፡ ለዋናክንዲስ ፡ ዳግሙ ፤ (ማቴ ፲፱ ፡ ፳፰ ። ራእ ፪ ፡ ፲፩ ። ዘዳ ፲፯ ፡ ፲፰ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፵፯ ። ዘፍ ፳፯ ፡ ፴፮ ። ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

**ዳግመ** ፤ ደግሞ ፡ መልሶ ፡ ተመልሶ ፡ ዳግመኛ ። እንከ ፡ ዳግመ ። ዓዲ ፡ ዳግመ ። ወካዕበ ፡ የሐውር ፡ የአብስ ፡ ዳግመ ። ዳግመ ፡ ይመጽእ ፤ (ኢሳ ፲፫ ፡ ፩ ። መሳ ፲፫ ፡ ፱ ። ሢራ ፴፩ ፡ ፴፩ ። ቅዳ) ።

**ዳግማዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ ዳግማይ ፤ (ዪት ፡ ሚት ፡ ይያን ፡ ያት)** ፤ በቁሙ ፡ ኹለተኛ ፡ ታናሽ ፡ ተከታይ ፡ ምክትል ። አባ ፡ ማርቆስ ፡ ዳግማዊ ። ወልደ ፡ ዳግማዊት ፡ ብእሲት ። ዳግማይ ፡ አዳም ። ሰማይ ፡ ዳግሚት ፤ (ስንክ ፡ ጥቅ ፳፱ ። መስ ፬ ። ሙዳ ፡ ፬ ። ቅዳ ። ድጓ) ።

**ድጋም** ፤ በቁሙ ፡ መድገም ፡ መደገም ፡ አደጋገም ፡ ደገማ ፡ ድግሚያ ፡ ጸሎት ።

**ደጋን ፤—በቁሙ ፤—ዴግኖ ፡ ዴግን ።**

**ዳጎን ፤ (ዕብራ)** ፤ ስሙ ፡ ጣዖት ፡ የባሕር ፡ ዳር ፡ ሰዎች ፡ ኢሎፍላውያን ፡ የሚያመልኩት ፡ ፊቱና ፡ ራሱ ፡ የሰው ፡ ግንዱና ፡ ገላው ፡ መስመላው ፡ የደራትን ፡ ያማ ፡ ዐይነት ፡ ሦርዣና ፡ ጉርዣ ፡ ወይም ፡ አንባዛና ፡ ዐሣ ፡ የሚመስል ። ዳግ ፡ ዓሣ ፡ ዳጎን ፡ ዓሣዊ ፡ ዓሥማ ፡ ዓሣ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ዥብ ፡ ጉብር ፡ እንደ ፡ ማለት ፤ (፩ነገ ፡ ፭ ፡ ፪) ።

**ድጕዓ ፤ (ሐማሴን)** ፤ አልቃሽ ፡ አሞሽ ፡ ገጣሚ ። ቍዘማ ፡ የልቅሶ ፡ ዜማ ፡ ሙሾ ፡ ግጥም ። ድጓን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ። ድጕዓ ፡ ደግሞ ፡ ከጕድዐ ፡ ወጥቷል ።

**ደጕዓሊ ፡ ደጓዕሊ ፤ (ዕብ ፡ ዴቄል ። ሱር ፡ ዴቅላ ። ዐረ ፡ ደቀል)** ፤ የሰሌን ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ፡ ተምር ፡ ግንዱ ፡ ቁመቱ ፡ የበቀልት ፡ ቅጠሉ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ እንደ ፡ ውስጥ ፡ እጅና ፡ እንደ ፡ ጣት ፡ ያለ ፡ ዲቃላ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።



ደጕዓሊ ፡

—፤ ሰሌን ፡ የሰሌን ፡ ቅጠል ፡ ዘንባባውና ፡ ዝንጣፊው ፡ በመርቱ ፡ ሙሽራው ፡ የተሠራ ፡ ወይም ፡ ያልተሠራ ። ወአንበረ ፡ በውሳጢታ ፡ ታቦተ ፡ አንጦሊያ ፡ ደጕዓሊ ። ነጸረ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ ቈጽለ ፡ ደጕዓሊ ። ነሥአ ፡ ኀደጠ ፡ ደጓዕሊ ፡ ወሠረቀ ፡ ወበዕለት ፡ ካልእ ፡ አር

ሐሰ ። ፀፍረት ፡ ዘደኀዐሌ ። ፀፊረ ፡ ደኀዐሌ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ገድ ፡ ዮሐ ። ፊልክ ፡ ፵፰ ። ፻፫ ። በንክ ፡ ኀዳ፲፯) ።

**ደጊፍ ፡ ፎት ፤ (ደገፈ ፡ ይደግፍ ፡ ይድግፍ ። ትግ ፡ ደግፈ)** ፤ መደገፍ ፡ መደጋገፍ ፤ ማጽናት ፡ ማበርታት ፡ እንዳይወድቅ ፡ ማድረግ ፤ አይዞኽ ፡ ማለት ። ገደፈ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ የዚህ ፡ ግልባጭ ፡ ነው ። ሰቀንና ፡ ዐመደን ፡ ተመልከት ፤ ደገፈ ፡ ያማርኛና ፡ የትግሬ ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ብርዕ ፡ ሲሉ ፡ ብዕር ፡ እንደሚሉት ፡ ደገፈ ፡ ሲሉ ፡ ገደፈ ፡ ይላሉ ፤ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ደጕጽ ፤ ጾት ፤ (ደጐጸ ፡ ይደጕጽ ፡ ይድጕጽ ። ዕብ ፡ ዳጋሽ ፤ አጠበቀ ፤ የማጥበቅ ፡ ምልክት ፡ አደረገ ፤ የፊደል)** ፤ መውጋት ፡ መጠቈም ፡ ጠቅ ፡ ማድረግ ፤ መኀጐጥ ፡ መነካት ፡ መጐንጥ ፤ መጕሰም ፡ መደሰቅ ፤ መምታት ። መጐጸን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። አሚኪላ ፡ ለእመ ፡ አንዝኪ ፡ በእዴኪ ፡ ይደጕጽ ። አሕጻከ ፡ ደጕጻኒ ። ዘደጕጸ ፡ ዐይኖ ፡ ያወርድ ፡ አንብዐ ። ዘይደጕጸኒ ፡ ሥጋየ ። ደጕጸ ፡ እንግድዓሁ ። ወገረ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ አሐደ ፡ ዐጽቀ ፡ ወደጕጸ ፡ ገጸ ፡ ንጉሥ ፤ (አፈ ፡ ድ፲ ። መዝ ፡ ፴፺ ። ሢራ፳፪ ፡ ፲፱ ። ፪ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፯ ። ገድ ፡ ተክ ። ዮሴፍ) ።

—፤ መደጕስ ፤ መደገስ ፡ ማሰናዳት ፤ ማሥመር ፡ ማሳመር ፤ ማሰንበር ፡ ማስመጥ ፡ ማሳበጥ ፤ መሸለም ፡ ማስጌጥ ፤ መልክ ፡ ማውጣት ፤ ያንቀልባ ፡ የብራና ፡ ገለደን ፡ እይ ።

—፤ መዳጕስ ፤ ደኀሳ ፡ መኾን ፤ ወይም ፡ ማድረግ ። ምስጢሩ ፡ ማሳበጥ ፡ ካለው ፡ ይገባል ። ደንገፀን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ደኀጺ ፤ (ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት)** ፤ የሚወጋ ፡ የሚጐነጥ ፤ ደኀሽ ፡ አሥማሪ ።

**መድጐጽ ፤ (ብ ፡ መዳጕጽ)** ፤ መውጊያ ፡ መኀጐጫ ፡ አርቃሽ ፡ ኹንካር ፡ የእንስሶች ፡ መነኪያ ፡ መጠቈሚያ ። ነገረ ፡ ጠቢባን ፡ ከመ ፡ መድጕጸ ፡ ባሕም ፡ (መክ፲፪ ፡ ፲፩) ።

—፤ በቁመ ፤ ማሥመሪያ ፤ ማሰንበሪያ ፡ አፈ ፡ ዱልዱም ፡ ወስፌ ፤ መድጕስ ፡ የድጕስ ፡ መሣሪያ ፡ በየስሙና ፡ በያይነቱ ። መግለድን ፡ ተመልከት ።

**ተደጕጸ** ፤ ተወጋ ፡ ተነካ ፡ ተጐነጠ ፡ ተደጕሰ ፡ ተሠመረ ።

**ድጉጽ ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ጕጽት)** ፤ የተወጋ ፡ የተነካ ፡ የተደጕሰ ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፯) ።

**ድጕጻት** ፤ መውጋት ፤ መወጋት ፡ መነካት ፡ ንኪት ፡ ሰንበር ፡ ዕበጥ ፤ ድጕስ ፡ ድጕሰት ። እንበለ ፡ ሕማም ፡ ወእንበለ ፡ ድጕጻት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተዳጐጸ** ፤ ተጣለ ፡ ተኀነጠ ፡ ተጐናነጠ ።

**አስተዳጐጸ** ፤ አጣላ ፡ አነካካ ፤ አኀነጠ ። ያስተዳጕጽ ፡ ማእከለ ፡ አዕርክት ። ልሳን ፡ ዐማፂ ፡ ዘያስተዳጕጽ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ። እስ ፡ ኢያስተዳጕጻ ፡ (ሢራ ፳፰ ፡ ፱ ። ፶፩ ፡ ፯ ። ፩ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፩) ።

**መስተዳጕጽ** ፤ የሚያጣላ ፡ አጣይ ፤ አሳባቂ ፡ ነገረ ፡ ሠሪ ። ልሳን ፡ መስተዳጕጽ ፡ ሆከሙ ፡ ለብዙኃን ። ኢይኩና ፡ መስተዳጕጻተ ፡ (ሢራ፳፰ ፡ ፲፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳ ፡ ፩) ።

**ደጕር ፤ ሮት ፤ (ደጐረ ፡ ይደጕር ፡ ይድጕር ። ዕብ ፡ ዳጋር)** ፤ ማሞቅ ፡ መታቀፍ ፤ ማመስ ፡ መቀፍቀፍ ፤ የንቍላል ። መዘርጋት ፡ ማርገብገብ ፤ የክንፍ ፤ ለመብረር ። ኹሉም ፡ የወፍ ፡ ሥራ ፡ ነው ። መስካት ፡ ክልክ ፡ ማግባት ፤ መስፈር ፡ መመዘን ፡ ማስተካከል ።

**ደጕር ፤ ድጕር ፤ (ዐረ ፡ ደጅር)** ፤ ድግር ፡ የሞፈር ፡ ክንፍ ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ የሚቀጠል ፤ ስረረን ፡ እይ ። በአንጻረ ፡ ድጕር ፡ ዕርፈ ፡ ወበአንጻረ ፡ ዕርፍ ፡ ድጕረ ። አርውተ ፡ ብዕራ ፡ ወጸሪበ ፡ ድጕር ፡ (ኩፋ ፡ ፲፩ ። አዋል) ። ደንጐራ ፡ አዳጕራ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ዶግሬ ፤ (ላቲን ፡ ግራዱስ)** ፤ ደረጃ ፡ ዕርከን ፤ ልክ ፡ ሚዛን ፡ እንደ ፡ ድግር ፡ የተከከለ ።

**ደጕስ ፤ (ትግሬ)** ፤ ዳጕሳ ፤ የድግስ ፡ እኽል ፤ የጤፍ ፡ ዐይነት ፤ ዐረቂና ፡ ጠላ ፡ እንጀራ ፡ የሚኾን ።

**ዱድ ፤—ስመ ፡ ነገድ ፤—ደዊድ ፡ ዶደ ፤ ዶድ ።**

**ዶዶ ፤—ደጆ ፤—ደይደየ ፤ ዶደየ ።**

**ድድ ፤—መሠረት ፤—ወዲድ ፡ ወደ ።**

**ደደክ ፤ (ደግ ፤ ደግደግ)** ፤ ደጋ ፡ ሙቄ ፡ ገማም ፡ ብርዳም ፡ ውርጫም ፡ ነፋሳም ። ወምድረ ፡ ቤምስ ፡ ኢመርቄ ፡ ወኢደደክ ። ይበርክዎ ፡ ደደክ ፡ ወመርቄ ። ገነት ፡ ዘኢያየብሳ ፡ ነፋስ ፡ መርቄ ፡ ወደደክ ፡ (ኩፋ ፡ ፳ ። ዳንኤ ፡ ፵፰ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፩) ።

—፤ ቀቅ ፡ ቈሪር ፡ ነፋስ ፤ በደጋ ፡ የሚወርድ ፡ የብርድ ፡ ዐይነት ፡ ኹሉ ። አስሐትያ ፡ ወቍር ፡ ወሐመዳ ፡ ወደደክ ። ዘየዐርግ ፡ እምኔሁ ፡ ከመ ፡ ጢስ ፡ ውእቱ ፤ ወስሙ ፡ ደደክ ፡ (ሔኖ፷፯ ፡ ፲፪ ። ፳ ፡ ፲፰) ።

**ዲዲሞስ ፤—መንቲያ ፤—ዶደየ ።**

**ዶዳን ፤—ስመ ፡ ነገድ ፤—ደይዳን ።**

**ደዲቅ ፤ ቆት ፤ (ደደቀ ፡ ይደድቅ ፡ ይደድቅ ። ወድቀ ፤ ወገበ)** ፤ መደንገት ፡ ድንገት ፡ መኾን ፡ መደረግ ፤ የሥራ ። ሳይታሰቡ ፡ መድረስ ፡ መምጣት ፡ ከተፍ ፡ ማለት ፤ በድንገት ፡ ማግኘት ፡ መገኘት ፡ ግጭት ፡ መግጠም ። ደደቀ ፡ በውእቱ ፡ አዝማን ፡ ባእስ ፡ ማእከለ ፡ አይሁድ ፡ ወማእከለ ፡ አርማንያ ። እመ ፡ ደደቀ ፡ ብጽሐተ ፡ ነግድ ። እመ ፡ ቦ ፡ ካህን ፡ ዘደደቆ ፡ በንዋም ፡ ዝንየት ። ጽኑዐ ፡ ልብ ፡ ኢይደድቅ ፡ ሠናየ ። ወደደቆ ፡ ለአብ ፡ መምህረ ፡ (ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፸፱ ። ቄድር ። ምሳ፲፯ ። ተረ ፡ ቄር) ።

—፤ መደደቅ ፥ መውጋት ፥ መደንጐር ፥ መፈንቀል ፥ መገልበጥ ፤ መቈፈር ፥ መመንቀር ፥ (ዐማርኛ) ። አንዳንድ ፥ መጽሐፍ ፥ ግን ፥ በደደቀ ፥ ፈንታ ፥ ተዳደቀ ፥ ይላል ፤ አ ያሰኝም ። እንተ ፡ ኢኀሰይኩ ፡ ተዳደቀትኒ ። በከመ ፡ ይዳደቅ ፡ ሰአብድ ፡ ከማሁ ፡ ሊተኒ ፡ ይዳደቀኒ ። ለአብዳን ፡ ይዳደቅሙ ፡ ሞት ። አልቦ ፡ ዘይዳደቃ ። ወተዳደቀ ፡ አሕዱ ፡ ካህን ። ከመ ፡ ይዳደቅዋ ፡ ለሀገር ፡ (ኢዮ፲ ፥ ፳፰ ። መክ፱ ፥ ፲፭ ። ምሳ፳፬ ፥ ፰ ። ጥበ፮ ፥ ፳፰ ። ሉቃ፲ ፥ ፴፭ ። ዮሴፍ) ።

**ተዳደቀ** ፤ ተገናኘ ፥ ተገናኘኘ ፥ ተጋጠመ ። ተዳደቁ ፡ ዠሎሙ ፡ ውስተ ፡ ጸብእ ። ኢይደሉ ፡ ንዳደቃ ፡ ለጸብእ ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዘ ፡ እግዚ ፤ አባ ፡ በተዳድቆ ፡ ግብት ፡ (ዮሴፍ ። ፈ ፡ መ ፥ ፱ ፥ ፲፪) ።

**ድድቅ** ፤ (**ቃት**) ፤ ድንገት ፤ ድንገተኛ ፥ ያልታሰበ ፡ አደጋ ፥ ሞት ፥ ጥፋት ፤ ክፉ ፥ ነገር ፥ ኹሉ ። አሕዱ ፡ ድድቅ ፡ ይዳደቆሙ ፤ ለክልኤሆሙ ። ተዳደቆ ፡ ድድቅ ፡ ለውእቱ ፡ ንዋይ ። ምንዳቤያት ፡ ወድድቃት ። እምዠሉ ፡ ድድቅ ፡ ዘይደንሖ ፡ ለዕጓለ ፡ መሕያው ። እምድድቅ ፡ ዘውስተ ፡ ማያት ፡ (መክ፱ ፥ ፲፬ ። ፍ ፥ ነ ፥ ፶፩ ፥ ፳ ። መቃ ፥ ገ፳፬ ። አርጋ ፥ ፫ ። ደራሲ ። መዝ ፥ ፺) ።

**ዳድርክም** ፤—**የገንዘብ ፡ ስም** ፤—**ደይ ደር** ።

**ዳድስቅልያ** ፤—**የመጣፍ ፡ ስም** ፤—**ደ ይደስ** ።

**ደሀለ** ፤—**ሸሸ** ፤—**ደሐለ** ።

**ዳህምሞ** ፤ **ሞት** ፤ (**ዳህመመ ፡ ይዳህ ምም ፡ ይዳህምም ። ዕብ ፡ ዳህም ፤ ብህመ**) ፤ መቈፈር ፥ መኰትኰት ፤ ዐፈር ፥ ማስታቀፍ ። መቈለል ፥ መደመም ፤ መመደብ ፥ መደብ ፥ መሥራት ፥ ሳታክልት ። ደመመን ፥ እይ ፤ የዚህ ፥ ገር ፥ ነው ።

**ዶድ** ፤ (**ዕብራ ። ሱር ፡ ዶዳ**) ፤ አጐት ፥ ያባት ፥ የናት ፥ ወንድም ፤ ያክሥት ፥ ባል ። ወዳጅ ፥ ዘመድ ፥ ባልንጀራ ፥ እኩያ ፥ አምሳያ ፥ ዐብሮ ፥ አደግ ፥ ወንድም ፥ እኩል ።

**ዶዲ** ፤ የሰው ፥ ስም ፤ ወዳጄ ፥ ዘመዴ ፥ ማለት ፥ ነው ፥ (፪ነገ ፥ ፳፫ ፥ ፱ ፥ ፳፬) ። አንዳንድ ፥ መጣፍ ፥ ግን ፥ ዱድ ፤ ደዳኢ ፤ ይላል ፤ ስሕተት ፥ ነው ። ዱድ ፤ ታላቅ ፥ ድስት ፥ ቅርጫት ፤ ዱዳኢም ፤ የሽቱ ፥ ቅጠል ፥ ነው ፥ ዕንጐትን ፥ ተመልከት ።

**ጀውዛ** ፤—**ስመ ፡ ከከብ** ፤—**ገውዛ** ።

**ዶሐን** ፤ (**ዕብ ፡ ወሱር ። ዐረ ፡ ዱኻን**) ፤ ስመ ፥ እክል ፤ አንድ ፥ ዐይነት ፥ እኽል ፤ አገዳው ፥ ሳንፉው ፥ የማሽላ ፤ ዐጭሞር ፥ ቀጭጭን ፥ ፍሬው ፥ የዳጐሳ ፥ ዐይነት ፥ (ሕዝ፬ ፥ ፱) ።

**ደውዩ** ፤ **ዮት** ፤ (**ደወየ ፡ ይደዊ ፡ ይድ ወይ ። ዐረ ፡ ደዊየ ። ዕብ ፡ ዳዋህ ። ሱር ፡ ድ ዊይ**) ፤ መደወይ ፥ መታመም ፥ መበሸት ፤ ድውይ ፥ መኾን ፤ በኬና ፥ ማጣት ፤ በደዌ ፤ ዳኛ ፤ ባልጋ ፤ ቍራኛ ፤ መያዝ ። እመሂ ፡ ደወየ ፡ ኢይሴፎ ፡ ሐዩወ ። ደወዩ ፡ ከመ ፡ አባግዕ ። ደወየ ፡ ልብየ ። ደወይኩ ፡ ወሐወጽ ክሙኒ ፡ (ኢዮ፳፱ ፥ ፳፫ ። ዘካ፲ ፥ ፪ ። ሰቈ፮ ፥ ፲፯ ። ማቴ ፳፭ ፥ ፴፯) ።

**ድዉይ** ፤ (**ያን ፡ ያት ፤ ዱያን ፤ ድው ይት ፡ ዊት**) ፤ በቁሙ ፤ የተደወየ ፤ ደዌ ፥ ያደረበት ፤ ታማሚ ፥ በሽተኛ ። ኢትትሀከይ ፡ ሐውጾ ፡ ድዉይ ። ዘድዉይ ፡ ሥጋሁ ። በእንተ ፡ ድዉያን ። መጋቤ ፡ ዱያን ። ነፍስ ፡ ድውይት ፡ (ሢራ፯ ፥ ፴፭ ። ፴ ፥ ፲፬ ። ፍ ፥ ነ ፥ ፳፩ ። ሲኖዶ) ።

**ደዋ** ፤ (**ትማ ፡ ወዐረ**) ፤ መድኀኒት ፥ የሚያም ፥ የሚገድል ፥ ደዌ ፥ የሚኾን ፤ ወይም ፥ የሚያድን ።

**ደዌ** ፤ (**ያት**) ፤ በቁሙ ፤ በሽታ ፥ ሕማም ፥ የቈየ ፥ የዘገየ ፥ ዐብሮ ፥ የሚኖር ፤ ወይም ፥ ዐልፎ ፥ ኻያጅ ፤ ኀጢአት ፥ ፍትወት ፤ ደዌ ፥ ነፍስ ። ደዌ ፡ መሬር ፡ ወእኩይ ፡ ደዌ ፡ ክርሥ ። ለእመ ፡ አሐዩ ፡ እምዛቲ ፡ ደዌ ። ሐይወ ፡ እምደዌሁ ። ደዌ ፡ ሲሕ ። ነበረት ፡ ይእቲ ፡ ደዌ ፡ ውስተ ፡ ልብ ፡ (፪ዜና ፥ ፳፩ ፥ ፲፭ ። ፪ነገ ፥ ፩ ፥ ፪ ። ኢሳ፴፰ ፥ ፱ ። ሢራ፴ ፥ ፲፯ ። ሉቃ ፥ ዕገሥ ፥ ፳፱) ።

**አድወየ** ፤ አደወየ ፥ ድውይ ፥ አደረገ ፤ ደዌ ፥ አሳደረ ። መጽአ ፡ ላዕለ ፡ ርእሱ ፡ ሐፋር ፡ ወአድወዮ ፡ ወሞተ ። ለእሉ ፡ አድወዮሙ ፡ ፍርሀት ። እንተ ፡ አድወያ ፡ ጋኔን ። መከራት ፡ እለ ፡ ያደውያ ። ምርዓይ ፡ ማየ ፡ ዘያደዊ ፡ (ዮዲ፰ ፥ ፫ ። ጥበ፲፯ ፥ ፰ ። ሉቃ ፲፫ ፥ ፲፩ ። ማር ፥ ይሥ፪ ፥ ፲፩ ። ፍ ፥ ነ ፥ ፴፯) ።

**ደዊል** ፤ **ሎት** ፤ (**ዶለ ፤ ደወለ ፡ ይደ ውል ፡ ይዱል ። ዕብ ፡ ዳዌል ፤ አከበ ፡ ደወረ ፡ ጠመጠመ ፤ የፈትል**) ፤ መወሰን ፥ መክለል ፤ የቦታ ። መደወል ፤ ማቃጨል ። መደል ፥ ማግባት ፤ መክተት ። ዱላ ፥ ዳውላ ፥ ደልዷላ ፥ ዱለት ፥ ማለት ፥ የዚህ ፥ ዘር ፥ ነው ።

**ደወል** ፤ (**ብ ፡ አድዋል**) ፤ ዙሪያ ፥ ዳርቻ ፥ ጫፍ ፥ ወሰን ፥ ደንበር ፤ ቀበሌ ፥ አውራጃ ። ኢታፍልስ ፡ ደወለ ፡ ገራህት ፡ ዘአንበሩ ፡ አበው ። ዠሉ ፡ ደወሉ ፡ ዘዐውዱ ። ደወለ ፡ ጢሮስ ። ደወለ ፡ ፋርስ ። ተጋብኡ ፡ እምአድዋለ ፡ ብሔሮሙ ፡ (ምሳ፳፫ ፥ ፲ ። ሕዝ፵፯ ፥ ፳ ። ዘካ፱ ፥ ፪ ። ኢሳ፯ ፥ ፲፰ ። ኑሐ፲፪ ፥ ፳፰) ።

**ደወል** ፤ (**ላት**) ፤ በቁሙ ፥ መጥቅ ፥ መረዋ ፥ ቃጭል ፤ የደንጊያ ፥ የንሐስ ፥ የብረት ፤ ሲደወል ፥ በዙሪያው ፥ ባውራጃው ፥ የሚሰማ ። ከመ ፡ ድምፀ ፡ ብርት ፡ ዘይነቁ ፡ ባሰው ፥ ደወል ፥ እንዲል ፥ (፩ቆሮ ፥ ፲፫ ፥ ፩) ።

**ተዳወለ** ፤ ተዋሰነ ፤ ተወሳሰነ ፥ ተዳከ ። እለ ፡ ይዳወልዎ ፡ እለ ፡ ዐውዱ ፡ (፫ነገ ፥ ፴ ፥ ፲፯) ።

**ደዊር** ፤ **ሮት** ፤ (**ዶረ ፡ ይደውር ፡ ይዱር ። ዕብ ፡ ዳር**) ፤ መማገድ ፥ መረብረብ ፤ ማንደድ ፥ መቈስቈስ ፤ እሳት ፥ መለኰስ ።

**ዱር** ፤ በቁሙ ፡ ደን ፡ ሰማክ ፡ ምማ ፡ ብዙ ፡ ዘ ፋና ፡ ዕንጨት ፡ ያለበት ። **ታሕተ ፡ ዱር ፡ ተኀብእኩ ፡** (አዋል) ።

**ዶር ፤ (ዐረ ፡ ዱር ፡ ዶረ ፡ ጠራ ፡ በራ) ፤** ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ዕንቍ ፡ ፈርጥ ፡ በወርቅ ፡ ጎርወት ፡ የሚ ሰክ ። **ወማእከሌሆሙ ፡ ታቦት ፡ ዶር ፡ ዘስርጉት ፡ በሁ ራኂ ፡ ጸዳል ፡፡ ታቦት ፡ ዘዶር ፡** (መጽ ፡ ምስ ። ቅዱ ፡ ሕር) ።

**ዶር ፤ (ዕብራ) ፤** ትውልድ ፡ ዘመን ፡ የትውል ድን ፡ ፋኖች ፡ ቀመልክት ። **በዶሮሙ ፡** (ዘፀ፴ ፡ ፲) ። በዐ ረብ ፡ ግን ፡ ያር ፡ ተራ ፡ ዱራ ፡ ዑደት ፡ ይኾናል ።

**ደውርሀ ፤ (ይደወርህ ፡ ይደውርሀ ፥ ደ ውርሆ ፡ ኢው ፡ ዶርሀወ ፡ ይዶርሁ ፥ ዶርህዎ ፤ ተቀ ፡ ግ) ፤** በዘ ፡ ተባዘ ፡ ረባ ፡ ተንሸሸ ።

**ዶርሆ ፤ (ብ ፡ ደዋርህ) ፤** ዶሮ ፡ ብዙ ፡ የሚ ወልድ ፡ የሚዋስድ ፡ ለማዳ ፡ የቤት ፡ ወፍ ። ምስጢሩ ፡ መርባት ፡ ነው ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ያስተባብራል ። **በድ ምፀ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ለሱራፌል ፡ ይነቅ ፡ ዶርሆ ፡፡ ዶርሆ ፡ ተባዕት ፡፡ ከመ ፡ ዶርሆ ፡ እንተ ፡ ታስተጋብእ ፡ ዕጕ ሊሃ ፡ ታሕተ ፡ ክነፊሃ ፡፡ መጋዝእ ፡ ደዋርህ ፡፡ ክልኤቱ ፡ እልፈ ፡ ደዋርህ ፡** (ቀሴ ። ምሳ፳፱ ፡ ፴፩ ። ማቴ፳፫ ፡ ፴፯ ። ፫ነገ ፡ ፬ ፡ ፳፫ ። ገድ ፡ ተክ) ።



ደዋርህ ፡

**ዳዊት ፤ (ዕብ ፡ ዳዊድ) ፤** የሰው ፡ ስም ፡ የእ ስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ፍቁር ፡ መፍቀሬ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፪) ።

**ዳዊት ፤ (ዕብ ፡ ትሂሊም) ፤** የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ መጽሐፈ ፡ መዝሙር ፡ ዳዊትና ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ያሉ ፡ ንጉሣውያን ፡ የመሰሉ ፡ የሚዘምሩ ፡ መዘምራን ፡ የደረ ሱት ። ብዙው ፡ የዳዊት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በዳዊት ፡ ስም ፡ ተ ጠርቷል ፡ እንጂ ፡ ጀሚው ፡ ኹሉ ፡ የርሱ ፡ አይደለም ፡ ይ ኸውም ፡ በደርእስቱ ፡ ይታወቃል ፡ ከምርኮም ፡ በኋላ ፡ የተደረሰ ፡ አለ ። ይልቁንም ፡ እግዚእ ፡ ጸወን ፡ የንከን ፡ ከሰው ፡ ዠምሮ ፡ ምሕረተ ፡ ወፍትሐ ፡ እስከሚለው ፡ ድረስ ፡ ፲፭ ፡ መዝሙር ፡ የመሰ ፡ ይባላል ። **ምእት ፡ ወኀምሳ ፡ ዳዊት ፡፡ ጸሎት ፡ ዘእምዳዊት ፡ በዜማ ፡** (ግንዘ) ።

**ዶታይም ፡ ን ፤** ስመ ፡ ሀገር ፡ የኢይዝራኤል ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ፡ (ዘፍ፴፯ ፡ ፲፯) ።

**ድሒዩ ፡ ዮት ፤ (ደሐየ ፡ ይድሒ ፡ ይድ ሐይ ። ዐረ ፡ ደሐ ። ሱር ፡ ዳሒሓ) ፤** መፍጨት ፡ ማድቀቅ ፡ መገርደፍ ፡ መሰለቅ ፡ ማዘር ፡ ማሽክርከር ፡ መግፋት ፡ መመሰስ ፡ የመጅ ።

**ደሓዪ ፡ መድሐዪ ፡ ሐይ ፤** የሚፈጭ ፡ ፈ ጫታ ፡ ባለወፍጮ ።

**መድሖ ፤ (ብ ፡ መዳሕይ) ፤** መፍጨ ፡ መጅ ፡ የወፍጮ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ግልገል ። **መድሖ ፡ ማሕረጽ ፡፡ እመ ፡ ኮነ ፡ በማይ ፡ መድሖ ፡ ወምድ ርኒ ፡ ማሕረጸ ፡** (ዘዳ፳፬ ፡ ፮ ። አርጋ ፡ ፫) ።

**ደሐየ ፤ — ቈፈረ ፤ — ደኀየ ፤ ደኃነ ።**

**ድሒክ ፤ ኮት ፤ (ድሕከ ፡ ደሐከ ፡ ይድ ሕክ ፡ ይድሐክ) ፤** መዳኸ ፡ አጕንብሶ ፡ በእጅና ፡ በእ ግር ፡ መኼድ ፡ ወይም ፡ እጅን ፡ ተይዞ ፡ በእግር ፡ ብቻ ፡ መወናከር ፡ አኳኼድና ፡ አረማመድ ፡ መማር ፡ ለፈደልም ፡ ይኾናል ። **በድሒክ ፡ ውስተ ፡ መርሕብ ፡፡ ሐንካስ ፡ ድሕከ ፡ እስከ ፡ ይበጽሕ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ይ ድሕክ ፡ ወይስእል ፡፡ ወድሕከ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡፡ ይድ ሕክ ፡ በነቢብ ፡ ፊደላት ፡** (መጽ ፡ ምስ ። ገድ ፡ ሳሙ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ። አፈ ፡ ተኛ፯) ። ድኻ ፡ ዳክዬ ፡ ድኽ ፡ ድ ኩት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ድሑክ ፤** የዳኸ ፡ የሚድኸ ፡ ታናሽ ፡ እግረ ፡ ኩ ንትሽ ፡ ደካማ ፡ እንዳሽኮኮና ፡ እንደ ፡ ሳጵቁት ፡ ያለ ፡ ማናቸውም ፡ ፍጥረት ።

**አድሐከ ፤** አዳኸ ፡ አስዳኸ ፡ መዳኸ ፡ አስተማረ ። **በበ ፡ ንስቲት ፡ ይድሕክ ፡** (አፈ ፡ ድ፭) ።

**ምድሓክ ፤** መዳኺያ ፡ ደጁ ፡ ወለወል ፡ መር ሕብ ።

**ድሒል ፤ ሎት ፤ (ድሕለ ፡ ይድሕል ፡ ይድሐል ። ዐረ ፡ ደሐለ) ፤** ድል ፡ መኾን ፡ መሸሽ ፡ መኰብለል ፡ ማምለጥ ፡ መራቅ ፡ መደበቅ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በድሕለ ፡ ፈንታ ፡ ተድሕለ ፡ ይላል ። **እመ ፡ ተድ ሕሉ ፡ ወጕዩ ፡፡ እምኅጸ ፡ ሄሮድስ ፡ ዘተድሕለ ፡፡ እ መንግሥተ ፡ ዓለም ፡ ዘተድሕለ ፡** (አዋል ። ስንክ ፡ ሚ ያዝ ። መስ፱) ።

**ዳሕል ፤** ድል ፡ ሽሽት ፡ ኰብለላ ።

**ዳሕመመ ፤ — ቈፈረ ፤ — ዳሀምሞ ፡ ዳ ሀመመ ።**

**ድሕነ ፤ — ዳነ ፤ — ድኀነ ፡ ድኃነ ።**

**ድሕንጻ ፤ (ድ ፡ ሕንጻ) ፤** በቁሙ ፡ እደ ፡ ሕ ንጻ ፡ የከራርና ፡ የበገና ፡ የመሰንቆ ፡ መምቻ ፡ እድ ፡ ልጅ ፡ ሕንጻ ፡ እናቱ ። ኀብሩ ፡ ሐንጻን ፡ ምስጢሩ ፡ ደጕጻንና ፡ ደነጻን ፡ ይመስላል ፡ ጥሬነቱ ፡ ግን ፡ የሐንጸ ፡ ነው ። እድ ፡ ውእቱ ፡ ቀብሎ ፡ ወደ ፡ ወ ፡ እንደ ፡ ኬደ ፡ ሕንጻም ፡ ድ ሕንጻ ፡ ተብሎ ፡ ወደ ፡ ደ ፡ መጥቷል ። **በድሕንጻ ፡ መ ንፈስ ፡ ዘብጠ ፡ አውታረ ፡ መሰንቆሁ ፡ ለልብየ ፡፡ እ ብል ፡ ሰላመ ፡ በልሳንየ ፡ ድሕንጻ ፡፡ ጳ ፡ ፎጢኖስ ፡ ክ ንክ ፡ እንዘ ፡ ሪሁ ፡ ለመንፈስ ፡ ሰይጣን ፡ ወመሰንቆሁ ፡ ለመንፈስ ፡ ሐሰት ፡ ወደጕጻከ ፡ በድሕንጻሁ ፡** (ሳታት ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፯ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ድሒፍ ፡ ፎት ፤ (ደሐፈ ፡ ይድሕፍ ፡ ይድሐፍ ። ዕብ ፡ ዳሐፍ)** ፤ መግፋት ፡ ማዳፋት ፡ መገፍተር ፡ ማጣደፍ ፡ ማበረር ።

**ዳሕፍ** ፤ ጻፋ ፡ ግፍ ፡ ግፊ ፡ ድቀት ፡ ፍዳ ፡ ጠ-ር ፡ የክፉ ፡ ብድር ። (ተረት) ፡ የኋጥኤ ፡ ዳፋ ፡ ጻድቁን ፡ አዳፋ ። ኢየመሥጥ ፡ ኃጥእ ፡ እምነ ፡ ዳሕፍ ፡ (ሚል ፲፮ ፡ ፲፫) ።

**ድሕጸ ፤— ዳጠ ፤— ድኂፅ ፡ ድኅፀ ።**

**ድሒር ፡ ሮት ፤ (ደሐረ ፡ ይድሕር ፡ ይድሐር ። ዐረ ፡ ደሐረ)** ፤ ማበረር ፡ መስደድ ፡ መፋታት ፡ መልቀቅ ፡ ከቤት ፡ ማስጣት ፡ ማሰናበት ፡ (ማቴ ፲፱ ፡ ፱ ። ማር ፲ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ። ሉቃ ፲፮ ፡ ፲፰) ፡ ዘይድሕር ፡ ብእሲቶ ፡ ዘእንበለ ፡ ትዘሙ ። ኢይድሐር ፡ ብእሲ ፡ ብእሲቶ ፡ (ቀሌ ። ዲድ ፡ ፴፫) ።

—፤ መዳር ፡ ማጋባት ፡ ሴት ፡ ልጅን ፡ በሕግ ፡ በሥርዐት ፡ ለሬሚኛዋ ፡ መስጠት ፡ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ማስጣት ፡ ነው ። ለወንድ ፡ ልጅም ፡ ይነገራል ። (ግጥም ፡ ልጃገረድ ፡ በባቷ ፡ ሰርግ) ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ዘመን ፡ የተበላሌሌ ፡ አባቱ ፡ ተዳሩ ፡ እኔ ፡ ተቀምሬ ።

—፤ ማዘዝ ፡ መፍቀድ ፡ እድርግ ፡ ማለት ፡ ምስጢሩ ፡ ከማሰናበት ፡ ይገባል ፡ ሙሴሰ ፡ በከመ ፡ እከየ ፡ ልብክሙ ፡ ደሐረክሙ ፡ ትኅድጉ ፡ አንስቲያክሙ ፡ (ማቴ ፲፱ ፡ ፰) ።

**ደሓሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፡ ሐርት)** ፤ የሚድር ፡ የሚፈታ ፡ የሚሰድ ፡ የሚያብርር ።

**ተድሕረ** ፤ ተዳረ ፡ ተፈታ ፡ ተለቀቀ ።

**ድሑር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ሕርት)** ፤ የተዳረ ፡ የተፈታ ፡ ገለሞታ ። ዘአውሰበ ፡ ድሕርተ ፡ አርኰሰ ፡ ሥጋሁ ፡ (ዲድ ፡ ፴፫) ።

**ደሐረ ፤— መረቀ ፤— ድኂር ፡ ደኀረ ።**

**ድሕር ፤— ኋላ ፤— ድኅር ።**

**ደሐሰ ፤— ዳሰ ፡ ፈፀጠ ፡ ረገጠ ፤— ዕሒስ ፡ ፀሐሰ ።**

**ድኂኅ ፡ ኆት ፤ (ደኀኀ ፡ ይድኅኅ ፡ ይድኅኅ)** ፤ መፋር ፡ መፈርፈር ፡ መጥረብ ፡ መውቀር ፡ የጥሻ ፡ የኮረ ።

**ድኁኅ ፤ (ኃን ፡ ኃት ፡ ኅኅት ፤)** የተፋረ ፡ የተጠረበ ፡ የተወቀረ ፡ ጥርብ ፡ ውቅር ። ኢይብር ፡ ድኁኃን ፡ (ድጓ ። ማሕ፪ ፡ ፲፯ ። ፰ ፡ ፲፱) ። ጥሻ ፡ ፍርኩታ ፡ እንባንት ፡ ሰርድንት ፡ ያላቸው ፡ ደንጊያ ፡ የመላባቸው ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለብሶዎች ፡ ግን ፡ ጽንጉግን ፡ ይሉታል ። ባለቅኔዎችም ፡ ደኅን ፡ ጸና ፡ ይባሉ ።

**ደኀየ ፤ (ደኅን)** ፤ ቈፈረ ፡ ማሰ ፡ አጠለቀ ፡ የጉድጓድ ። ግበ ፡ ከረየ ፡ ወደኀየ ። ጸናሐ ፡ ግበ ፡ ዘይድኂ ። ወይድኅይዎሙ ፤ (መዝ ፡ ፯ ። ደራሴ ። ዲድ ፡ ፲፯) ።

**ተድኅየ** ፤ ተቈፈረ ፡ ተማሰ ፡ ጠለቀ ፡ ጕድጓድ ።

**ድኁይ** ፤ የተቈፈረ ፡ የተማሰ ፡ ጥልቅ ። ጉገድፈ ፡ ሥጋከ ፡ ውስተ ፡ ከርየት ፡ ግብ ፡ ድኁይ ፡ (ደራሲ) ።

**ድኂን ፡ ኖት ፤ (ደኅነ ፡ ይድኅን ፡ ይድኅን ። ዕብ ፡ ያሾዕ ፡ ሂዋሼዕ)** ፤ መዳን ፡ ማምለጥ ፡ መውጣት ፡ ከተያዙ ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ ሳይያዙ ፡ መቅረት ፡ መትረፍ ፡ እንዳይያዙ ፡ መኾን ፡ መጠንቀቅ ፡ መጠበቅ ፡ በሕይወት ፡ መኖር ፡ መቃየስ ፡ መለምለም ። (ዐጋዥ ፡ ረዳት ፡ ጠበቃ ፡ ወባት ፡ ዋስና ፡ መድኅን ፡ ተያዥ ፡ ማግኘት) ፡ እንደ ፡ አዳም ። ሕይወትን ፡ ቀመ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ፡ ሕይወ ፡ የማእገዘ ፡ ድኅነ ፡ ያማርኛ ። ሕልቦ ፡ ድኂን ። መዋዕለ ፡ ድኂን ። ድኂኖ ፡ እምባሕር ። ወድኅነ ፡ ጢጦስ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ እምቀትል ፡ ሠለስተ ፡ ጊዜያተ ። ወሊደተ ፡ ዓለም ፡ ለድኂን ። ይእቲ ፡ ዕፀ ፡ ድኅነት ፡ (ክፋ ፡ ፵፱ ። አስቴ ፱ ፡ ፳፱ ። ጥበ ፳፫ ፡ ፱ ። ዮሴፍ ። ጥበጽ ፡ ፲፱ ። ሂርማ) ።

**ዳኅን ፤ (ኅት ፡ ናን ፡ ናት)** ፤ የዳነ ፡ የሚድን ፡ ደኅና ፡ ባለጤና ፡ ንጹሕ ፡ ጽሩይ ። ዳኅንኑ ፡ አባ ፡ እወ ፡ ዳኅን ። ዳኅንኑ ፡ ማኅትም ። ርእ ፡ ለእመ ፡ ዳኅናንኑ ፡ አኀዊከ ፡ ወአባግዒሆሙኒ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ዳን ፲፫ ፡ ፲፯ ። ዘፍ ፴፯ ፡ ፲፬ ። ፩ነገ ፡ ፳፯ ። ማቴ ፳፫ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰) ። በዳኅና ፡ ፈንታ ፡ ዳኅን ፡ ይላል ። ወከነ ፡ ሰላም ፡ ወዳኅን ፡ ባዕለ ፡ ጸሎ ፡ በሓውርት ። ዳኅን ፡ ወሰላም ፡ (ገድ ፡ ተክ ። አ ተስ ፡ ፳ ፡ ፫ ። ቀሌ) ።

**ድኁን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ኅንት)** ፤ የዳነ ፡ ያመለጠ ፡ ደኅና ፡ የኾነ ፡ የተፈወሰ ፡ ጥዑይ ፡ ንጹሕ ፡ ጽሩይ ፡ ያልተነካ ። ኢድኁን ፡ አንተ ፡ በሞት ፡ ኢያሰስ ። ይረስዮ ፡ ምስለ ፡ ድኁናን ። ድኁን ፡ ምስማዕ ፡ ወንጻሬ ፡ ድኁን ፡ እምነውር ። ድኁን ፡ አፉ ፡ እምሐሜት ። ክርስቶስ ፡ ድኁን ፡ ውእቱ ፡ እምኀጣውእ ። ነፍስ ፡ ድኅንት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ማኅዘ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፫ ፡ ጀ ። አፈ ፡ ድ፱ ። ፲፮ ። ድጓ) ።

**ዳኅን ፡ ድኁን** ፤ ደኅና ፡ በደኅና ፡ ወደ ፡ ደኅና ፡ ድኖ ፡ ደኅና ፡ ኹኖ ። ዳኅነ ፡ ሀሉ ። ዳኅነ ፡ ይትናገሩ ፡ ለቢጸሙ ። ትነብር ፡ ዳኅነ ። ለእመ ፡ ዳኅነ ፡ አቶክሙ ። ይሬእ ፡ ዳኅነ ። ወርእየ ፡ ዳኅነ ። መጽአ ፡ ድኁነ ፡ (ግብ ፳፫ ፡ ፴ ። ኤር፱ ፡ ፳ ። ኢዮ ፲፭ ፡ ፲፯ ። ሶቤ ፲ ፡ ፲፮ ። ፲፭ ፡ ፲፬ ። ማር፫ ፡ ፳፭ ። ዘረፋ) ።

**ድኅነት** ፤ መዳን ፡ መፈወስ ፡ ደኅንነት ፡ ጤና ። ወአንከሩ ፡ እም ፡ ድኅነቱ ። እምአይቴ ፡ ተሰፈወ ፡ እሉ ፡ ድኅነተ ፡ ሕፃን ። ድኅነተ ፡ ልብ ፡ ወአባል ። ድኅነት ፡ እምደዌ ፡ ዴዌ ። ጸመ ፡ ድኅነት ፡ ምሕላ ፡ ድኅነት ፡ (በንክ ፡ ሐምሽ፱ ። አፈ ፡ ድ፳፯ ። ፍ ፡ ን ፡ ፱ ። መር ፡ ዕጠ ። ድጓ) ።

**ዳኅና** ፤ ደኅንነት ፡ ጤና ፡ ሰላም ፡ ትንሣኤ ፡ ሕይወት ። ሕልቦ ፡ ዘይስእል ፡ ዳኅናኪ ። ተስእሎ ፡ በእንተ ፡ ዳኅናሁ ። ይኬንጢከ ፡ ዳኅና ፡ ብሔር ። እነግር ፡ ጽድቀከ ፡ በዳኅናየ ። በእንተ ፡ መንክር ፡ ዳኅናሁ ፡ (ኢሳ፲፰ ፡ ፳ ። ፪ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፯ ። ፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፱ ። ኢሳ፴፰ ፡

፳ ። ጥበ፳ ፡ ፱) ። በዳኅን ፡ ፈንታ ፡ ዳኅና ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ነበረት ፡ ሀገር ፡ ዳኅና ፡ (፱ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፳) ።

**አድኅነ** ፤ አዳነ ፡ አስዳነ ፡ ታደገ ፡ አወጣ ፡ ረዳ ፡ ዐገዘ ። ያድኅን ፡ በዕለተ ፡ ምንዳቤ ። ስእኑ ፡ አድኅኖ ። አድኅኑ ፡ ግፉዐ ። አድኅነኒ ፡ ርእሰከ ፡ (ሚራ፪ ፡ ፲፭ ። ኢዮ፱ ፡ ፳ ። ኢሳ፩ ፡ ፲፯ ። ማቴ፳፯ ፡ ፵) ።

**አድኅኖ ፡ ት** ፤ ማዳን ፤ መታደግ ፡ መቤዠት ፤ ነጻ ፡ ማውጣት ፤ ትድግና ። በእንተ ፡ ሕቢት ፡ ወአድኅኖ ፤ አድኅኖስ ፡ ዘነፍስ ፡ ውእቱ ፡ ወተሐብየ ፡ ዘንዋይ ። ዘእግዚ ፡ አድኅኖ ። ወንትፌሣሕ ፡ በአድኅኖትከ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯ ። መዝ ፡ ፫ ። ፲፱) ።

**አድኃኒ ፤ መድኅኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፤ የሚያድን ፡ የሚቤዥ ፡ የሚታደግ ፤ ታዳጊ ። የሰው ፡ ስም ። መድኅኔ ፡ ዅሉ ። መድኅንየ ። መድኅኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። መድኅኔ ፡ ዓለም ። መድኅኒት ፡ መቤዝዊት ። አብ ፡ አድኃኒ ፡ (ጥበ፲፯ ፡ ፺ ። መዝ ፡ ፲፯ ። ፊልጵ፫ ፡ ፳ ። ቀሌ ። ድጓ ። ስንክ ፡ ጥር፲) ።

**መድኅን** ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፤ የሚያድን ፡ አዳኝ ፤ በቁሙ ፡ መድኅ ፡ ዋስ ፡ ተያዥ ፡ ቤዛ ፡ ነጻ ፡ አውጭ ። እምጽዮን ፡ ይወፅእ ፡ መድኅን ። መድኅነ ፡ ዓለም ። ተወልደ ፡ ለክሙ ፡ ዮም ፡ መድኅን ። ውስተ ፡ ዘመድኅን ፡ መርሶ ። ወልቃሕስ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ በአኅዝ ፡ አው ፡ በትሕቢት ፡ አው ፡ በመድኅን ፤ አው ፡ በመጽሐፍ ፡ እንተ ፡ ውስቴታ ፡ በማዕት ። መድኅነ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ። ወለብእሲት ፡ ኢይትወከፉ ፡ እምኔሃ ፡ መድኅነ ፡ ወኢተሐብየ ፡ (ሮሜ፲፩ ፡ ፳፯ ። ዮሐ፬ ፡ ፵፪ ። ሉቃ፪ ፡ ፲፩ ። ስንክ ፡ ጳጉ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯) ።

**መድኅኒት ፤ (ታት)** ፤ በቁሙ ፤ መዳኛ ፡ ማዳኛ ፡ መዳኒት ፡ ፈውስ ፤ የሚያድን ። መድኅኒት ፡ በዘ ይትፌወስ ፡ ቍስል ። ጸሎትሰ ፡ መድኅኒት ፡ ይእቲ ። መድኅኒተ ፡ ዓለም ፡ ኮነ ፡ ደመ ፡ ጽጌኪ ፡ ክርስቶስ ። ጌራ ፡ መድኅኒት ። መድኅኒታት ፡ (አርጋ ። አፈ ፡ ተ ፳፯ ። ደራሲ ። ኢሳ፶፱ ፡ ፲፯ ። ግንዘ) ። ድኅነ ፡ ድኅነት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መድኅኒት ፡ ይባላል ፡ (፩ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፱ ። ፩ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፱) ። መሥዋዕተ ፡ መድኅኒት ። ዘይፈቅድ ፡ መድኅኒተ ፡ እምነጣውኢሁ ፡ (ዓሞ፭ ፡ ፳፪ ። ፈ ፡ መ ፡ ፪ ፡ ፳) ።

**ተድኅነ** ፤ ተዳነ ፡ ተዋሰ ፤ መድን ፡ ተያዥ ፡ ኾነ ፤ እዳናለኹ ፡ አለ ። ወመድኅነ ፡ ነፍስኪ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያምጽእ ፡ ዘተድኅነ ፤ ወይኩን ፡ ቃለ ፡ ዛቲ ፡ ተድኅኖ ፡ ከመ ፡ ይበል ፡ ተድኅንኩ ፡ ለአብጽሖተ ፡ እገሌ ፡ ለእገሌ ፤ አው ፡ ተድኅንኩ ፡ ለእገሌ ፡ ገጸ ፡ እገሌ ፤ አው ፡ ተድኅኖተ ፡ እገሌ ፡ ሳዕሌየ ። ኢይደሉ ፡ ተድኅኖቱ ፡ ለዘይደሉ ፡ ሳዕሌሁ ፡ ቀትል ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯) ።

**ድኅንጻ ፤—በቁሙ ፤—ድሕንጻ ።**

**ድኀፀ ፤ ፆት ፤ ( ድኅፀ ፡ ይድኅፅ ፡ ይድኅፅ ። ዐረ ፡ ደሐፀ)** ፤ መዳጥ ፡ መሰናከል ፡ መውደቅ ፤ የእግር ፡ የቃል ። ከመ ፡ ኢይድኅፀ ፡ ሰኰናየ ። ይጔይስ ፡ ትድኅፀ ፡ ወትደቅ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ እምትድኅፀ ፡ በልሳን ። ትድኅፅ ፡ ምክሩ ። ኢንድኅፀ ፡ በኃጢአት ። ከመ ፡ ኢንድኅፀ ፡ እምርትዕት ፡ ሃይማኖት ፡ (መዝ ፲፯ ። ሢራ፳ ፡ ፲፰ ። ኢዮ፲፰ ፡ ፯ ። ዲድ ፡ ፱ ። ፳፭) ። (ጥጨ) መጨንገፍ ፡ መውረድ ፤ ጭንጋፍ ፡ መኾን ፤ የዕንስ ፡ የሽል ። መዳጥ ፡ መደፍጠጥ ፤ መርገጥ ፡ መዠለጥ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ድኁፅ ፤ ድኁፅ ፤ ( ፃን ፡ ፃት ፡ ኃፅት)** ፤ የዳጠ ፡ የተሰናከለ ። የተዳጠ ፡ የተደፈጠጠ ። የሚድጥ ፡ ዳጭ ፡ (ገቢር) ።

**ድኅፀት** ፤ መዳጥ ፡ (ጥዳ) መዳጥ ፡ አዳዳጥ ፡ ድጠሽ ፤ መሰናከል ፡ (ፊልክ ፡ ፻፳፲ ። ፈላስ) ።

**ዳኅፅ ፤ ( ፃት)** ፤ ዳጭ ፡ ድጥ ፡ መሰናከል ፡ ዕንቅፋት ፤ ኀጢአት ፤ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ሥራ ። ጭንጋፍ ፡ ውርጃ ፡ ሽል ። ዳኅፀ ፡ ወጽልመት ። ያመጽኡ ፡ ዳኅፀ ፡ ለሕዝብ ። አበሳነ ፡ ስረይ ፡ ወዳኅፃቲነ ፡ እምሕግ ። ይጔይስ ፡ እምኔሁ ፡ ዳኅፅ ፡ (መዝ ፡ ፹፱ ። ዳን፲፩ ፡ ፲፬ ። መክ፯ ፡ ፫) ።

**አድኀፀ** ፤ አዳጠ ፡ አስዳጠ ፤ ዐነቀፈ ፡ አሰናከለ ፡ ሰረጀ ፡ ዘረጠጠ ፤ ለመጣል ። አድኅፆ ፡ ለሳእክ ። ኢይደግም ፡ አድኅፆተ ፡ እግርሙ ። ትዐቀባ ፡ ኢታድኅፀከ ፡ ልሳንከ ። ኵሎሙ ፡ ዘያድኅፀ ። አድኅፀክዎ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ወነሣእክዎ ፡ እመንበሩ ፡ (ዮሴፍ ። ፬ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፰ ። ሢራ፳፰ ፡ ፳፯ ። ኢሳ፰ ፡ ፲፱ ። ቀሌ) ።

——፤ ጨነገፈ ፡ አስጨነገፈ ፡ አሶረደ ፤ ከመ ፡ ፃእፃእ ፡ ዘአድኅፀት ፡ ማሕፀን ፡ እሙ ። ብእሲት ፡ ዘትስቲ ፡ ፈውስ ፡ ከመ ፡ ታድኅፅ ፡ ፃእፃአ ፡ እማሕፀና ፡ (ኢዮ፫ ፡ ፲፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፬ ፡ ፱ ። ዘዐቅ፳፩ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰) ። በአድኅፀ ፡ ፈንታ ፡ ድኅፀ ፡ ይባላል ፤ አያስኬድም ፡ (ኢዮ ፳፩ ፡ ፲) ።

**መድኅፂ ፤ ኃፅ** ፤ የሚያድጥ ፡ የሚያሰናክል ፡ አሰናካይ ። እሬእ ፡ መድኅፂነ ፡ (ሱቱ ፡ ዕገዜ ፡ ፳፪) ።

**ምድኃፅ ፤ ( ፃት)** ፤ (ጥዳ) መዳጫ ፡ መሰናከያ ፤ ቦታ ፡ ምክንያት ።

**ድኂር ፤ ሮት ፤ ( ደኀረ ፡ ይድኅር ፡ ይድኅር ። አኀረ ። ዐረ ፡ ደኀረ ፤ ንእሰ)** ፤ መቈየት ፡ መዘግየት ፤ ማፈግፈግ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማለት ፡ በኋላ ፡ መቅረት ፤ ኋለኛ ፡ መጨረሻ ፡ መኾን ፤ በግብር ፡ በነገር ፡ በማናቸውም ። ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ ወኢይድኅር ። ሰእመ ፡ ነበረ ፡ ሕዝባዊ ፡ ሠለስተ ፡ ሰንበተ ፡ ድኂሮ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይክልእዎ ፡ ትድምርተ ፡ (ዮሴፍ ። ቀኖና ፡ ግንር) ። ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ በደኀረ ፡ ፈንታ ፡ ተድኅረ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ተድኅሮ ፡ መጽአ ። ኢይበድሩ ፡ ወኢይደኀሩ ፡ አሐደ ፡ ዕለተ ። በእንተ ፡ እለ ፡ ተድኅሩ ። እመሂ ፡ ኢጸስቀጸስ ፡ ተድኃረ ፡ እምስብሐተ ፡ ነግህ ። ወኢተድኃረ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሰገቢረ ፡ ዝንቱ ። እንበለ ፡ ተድኅሮ ፡ (ኪዳ ። ሐዋ፳፱ ፡ ፲፪ ። ቅዳ ። ቀሌ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲) ።

—፤ መመረቅ ፤ መባረክ ፤ ማመስገን ። ሰበ ፡ አሐዱ ፡ ይድኅር ፡ ወካልኡ ፡ ይረግም ። በጸጋዊ ፡ ይድኅርዎ ፡ በሥነ ፡ ምግባሩ ። ድኅረኒ ፡ ዘይመውት ። ይድኅሩኒ ፡ ስሑናን ። ይድኅሩኒ ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ። ይረግሙነ ፡ ወንሕነ ፡ ንድኅሮሙ ። በአፉሆሙ ፡ ይድኅሩ ፡ ወበልቦሙ ፡ ይረግሙ ፡ (ሢራ ፴፰ ፡ ፳፱ ። ፴፱ ፡ ፳፫ ። ኢዮ ፳፱ ፡ ፲፫ ። ፴፩ ፡ ፲፱ ። ኢሳ ፷፫ ፡ ፳ ። ፩ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፷፩ ። ፻፰) ።

**ደኃሬ** ፤ (ሬት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ኅርት) ፤ ኋለኛ ፡ የኋላ ፡ መጨረሻ ፤ ታናሽ ፡ ተከታይ ። አግሪጳስ ፡ ውእቱ ፡ ደኃሬ ፡ እምእለ ፡ ነግሡ ፡ በይሁዳ ። ደኃሬ ፡ ጸላኢ ። ደኃሪት ፡ ገመስ ። እሙንቱ ፡ ደኃርያን ። ቀደምት ፡ ወደኃርት ፡ (ዮሴፍ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ። ማቴ ፡ ፳፯ ። ዘኁ ፳ ፡ ፴፭ ። ፳፱ ፡ ፳፯ ፡ ፳፱) ።

**ደኃራዊ** ፤ **ይ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ህርቃኖስ ፡ ደኃራዊ ። ከመ ፡ ያቅም ፡ ደኃራዌ ፡ (ዮሴፍ ። ዕብ ፲ ፡ ፱) ።

**ድኅር** ፤ (ራት) ፤ ኋላ ፡ ዠርባ ፤ ከማኽራት ፡ እስከ ፡ ተረከዝ ። በዠርባ ፡ አንጻር ፡ ያለ ፡ ቦታ ፤ የኋላ ፡ ኋላ ፡ ጓሮ ። ድኅሬሆሙ ፡ ለእልክቱ ፡ አልሕምት ፡ ይኤጽር ፡ ውስጠ ። ገቦሃ ፡ ዘድኅር ። ዘባን ፡ እንተ ፡ ድኅር ፡ (፩ዜና ፡ ፬ ፡ ፱ ። ግብ፳፯ ፡ ፴፭ ። ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ድኅረ** ፤ (ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ) ፤ ኋላ ፡ በኋላ ፤ ወደ ፡ ኋላ ። ምክጢሩ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ እም ፡ በ ፡ እንተ ፡ ይስማሙታል ። ዐቢይ ፡ ሲኾን ፤ እምድኅረ ፡ ተደሩ ፤ ወእምድኅረ ፡ መስሑ ፡ እያለ ፡ በቀዳማይ ፡ ይገባል ። ደቂቅ ፡ ሲኾን ፡ በቦታ ፡ በጊዜ ፡ ይገባል ። በማዕኩ ፡ በድኅሬየ ። ቀመት ፡ እንተ ፡ ድኅሬሁ ። ድኅረ ፡ ማዕጸ ። ፈረሱ ፡ ለፈርዖን ፡ ይቤ ፡ ድኅረ ፡ ድኅረ ፤ እስመ ፡ እግሩ ፡ ኢለመደ ፡ ባሕረ ፤ ቦታ ፡ (ሕዝ፵፩ ፡ ፲፱ ። ሉቃ፳ ፡ ፵፬ ። ኢሳ፶፯ ፡ ፰ ። ቅኔ) ። እምድኅረ ፡ ሐቅ ። እምድኅረ ፡ ፍልሰተ ፡ ባቢሎን ። ወድኅረ ፡ ኵሉሙ ፡ አስተርአየኒ ፡ ሊተ ። ቅድመ ፡ ጠይቅ ፡ ወድኅረ ፡ ትጌሥጽ ፤ ጊዜ ፡ (ማር፲፬ ፡ ፮ ። ማቴ፩ ፡ ፲፪ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፰ ። ሢራ፲፩ ፡ ፯) ። (ዕር፲፱ ፡ ቍ፫፱) ።

**ድኅሬት** ፤ ኋሊት ፤ የኋሊት ፤ ኋላ ፤ እንግሊላ ። የሐርስ ፡ ድኅሬተ ። እሱራን ፡ ድኅሬተ ። ኢገብኡ ፡ ድኅሬተ ። ከመ ፡ ይደቁ ፡ ድኅሬተ ፡ (ሉቃ፱ ፡ ፷፪ ። መቃ፫ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፳፰ ። ኢሳ፳፰ ፡ ፲፫) ።

**ድኅርና** ፤ ደኃራዊነት ፤ ኋለኛ ፡ መጨረሻ ፡ መኾን ። ለቅድምናከ ፡ ወለድኅርናከ ፡ (ፋ ፡ ኑ ፡ መቅ) ።

**አድኅረ** ፤ (አስመረቀ ፡ አስመሰገን) ፡ አቈየ ፡ አስቈየ ፤ አዘገየ ። አስከተለ ፤ በኋላ ፡ አደረገ ። አድኅሩ ፡ ፍትሐ ፡ ላዕሌሁ ። እመ ፡ አድኅርከኒ ። አድኅርከዋ ፡ እምተበሥሮ ፤ አቈየ ፡ (ዮሴፍ ። አዋል) ። ሞተ ፡ በሃይማኖት ፡ ወአድኅረ ፡ ሰብአ ፡ ድኅሬሁ ። አድኅረ ፡ መብዝኅተ ፡ ሰብኡ ፡ ምስለ ፡ እኁሁ ። አ ፡ አብዳን ፡ እፎ ፡ አድኅርክምዎ ፡ ለመለኮተ ፡ አምላክነ ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ እምጥንተ ፡ ህላዌሆሙ ፡ ለፍጡራን ፡ (ዮሴፍ ። መጽ ፡ ምስ) ። በአድኅረ ፡ ፈንታ ፡ አስተደ(ድ)ኅረ ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አድራጊና ፡ አስደራጊ ፡ ነው ፤ ዳ ፡ ካሳለ ፡ አደራራጊነት ፡ የለውም ። ለእመ ፡ አንተ ፡ አስተደኅርከ ፡ ቀቲሎታ ። አስተድኅረ ፡ ወልዶ ፡ ጢጦስ ፡ ይዕግታ ፡ ለሀገር ። ኢታስተድኅሮ ፡ እስከ ፡ ጌሠም ። ወያስተድኅሩ ፡ መብልዖሙ ፡ እስከ ፡ ይመሲ ፡ (ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፫ ። አቡሻ ፡ ፲፱ ። ዮሐ፱ ፡ ፲) ።

**አስተዳኅረ** ፤ አከታተለ ፡ አራደፈ ። አስተዳኅረ ፡ መጸዝኒሃ ፡ (ቅዳ ፡ ኤጲ) ።

**ተድኅረ** ፤ ተመረቀ ፤ ተባረከ ፤ ተመሰገነ ።

**ድኁር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ኅርት) ፤ የተመረቀ ፡ ምሩቅ ። የቈየ ፡ የዘገየ ።

**ድኁር** ፤ (ዐማርኛ) ፤ ዐጭር ፡ ግጭር ፤ ድንክ ፡ ጕባጣ ፤ ሕጹጽ ፡ ታናሽ ። ማናይን ፡ ተመልከት ።

**መድኅር** ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤ ቅጽልና ፡ ጥሬ ። የሚመርቅ ፡ መራቂ ፤ የሚያቈይ ፡ የሚያዘገይ ፡ ቅጽል ። ምርቃት ፡ በረከት ፡ ምስጋና ፡ ብፅዓን ፤ ጥሬ ። መድኅረ ፡ አብ ። መርገም ፡ ወመድኅር ። አቅረብነ ፡ ለክሙ ፡ መርገመ ፡ ወመድኅረ ፡ (ሢራ፫ ፡ ፱ ። ፪ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፰ ። ቀሌ) ።

**ደይበ** ፤ **በት** ፤ (ደየበ ፡ ይደይብ ፡ ይደይብ ። ትግሬ) ፤ ማረግ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ መውጣት ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ማለት ፤ በላይ ፡ መኾን ። መመደብ ፤ መደብ ፡ ዕርከን ፡ መሥራት ። ዐርገንና ፡ ለፀለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ አግዋር ፡ ናቸው ።

**ዲብ** ፤ **ዲበ** ፤ (ደቂቅ ፡ አገባብ) ፤ ላይ ፡ በላይ ፤ ወደ ፤ ስለ ፡ ይኾናል ፤ ላይናበብ ፡ ላይዘረዘር ፡ እንደ ፡ ላዕለ ፡ ብቻውን ፡ አይነገርም ። ዘሐነጸ ፡ ቤቶ ፡ ዲበ ፡ ኰኵሕ ። ኢይትነደግ ፡ እብን ፡ ዲበ ፡ እብን ። ሀሎ ፡ ዲቤሁ ፡ ልብስ ፡ ጥቀብ ። ከልብ ፡ ይገብእ ፡ ዲበ ፡ ቅያኡ ። ዲበ ፡ ሀጕለ ፡ ውሉዶሙ ፡ ይግዕዙ ፡ (ማቴ፯ ፡ ፳፬ ። ፳፬ ፡ ፪ ። ፪ ። ራእ፲ ፡ ፲፬ ። ምሳ፳፮ ፡ ፲፩ ። ሔኖ፲፪ ፡ ፮) ። ንበና ፡ ዲበ ፡ ይወራረሳሉ ፤ ስለዚህ ፡ በንበ ፡ ፈንታ ፡ ዲበ ፡ ይላል ። ነበረ ፡ ዲበ ፡ ዐዘቅት ፡ (ዘፀ፪ ፡ ፲፭) ። የወዲያኛው ፡ ትግሬም ፡ ወደ ፡ ሲል ፡ ዲብ ፡ ይላል ። ባማርኛ ፡ ግን ፡ ጉብ ፡ ጕብታ ፡ ታናሽ ፡ ቍሊልታ ፡ አዳጋ ፡ ቦታ ፤ እንዳርባጫ ፡ ያለ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ተረት) ፤ የወዳጅ ፡ ኾርብ ፤ ልጅን ፡ ከዲብ ። ድብኝትም ፡ የዚሁ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**መደብ** ፤ (ሰብ ፡ ዐሩጋ ፤ ዐዛራ) ፤ በቁሙ ፤ ዕርከን ፡ ምዕራግ ፤ መውጫ ፡ መወጣጫ ፡ ስፋትና ፡ ከፍታ ፡ ያለው ፤ ላታክልትም ፡ ይነገራል ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፲ ። ማር፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ፡ ፳) ። ደመ ፡ ቅሥፈቱ ፡ ያርሕስ ፡ መደበ ። ተፈትሑ ፡ ኵሉ ፡ አራዊት ፡ ወበልዑ ፡ ስጕርንደ ፡ ስማንያ ፡ መደበ ፡ (ስንክ ፡ ጳጉ፭ ። ገድ ፡ ተክ) ።

—፤ የርባታ ፡ ክፍል ፡ ዐሥሩ ፡ ስራዊት ፡ ወይም ፡ መራሕያን ።

**መደብዊ** ፤ **ይ** ፤ መደበኛ ፡ መደባም ፡ ባለመደብ ፡ የመደብ ። ባላባት ፡ ዋና ፡ ደቀ ፡ መደባይ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**መደቤና** ፤ (ዕብ ፡ ማድሜና) ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ የብንያም ፡ ክፍል ፡ (ኢሳ፲ ፡ ፴፩) ።

**ጀይብ** ፤ (ዐረብ) ፤ የቀሚስ ፡ ሕፅን ፡ ስባጤ ፤ በስባጤው ፡ ላይ ፡ የሚሰፋ ፡ ኪስ ፡ ከረጢት ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ ኹኖ ፡ ማረሚያ ፡ ገንዘብ ፡ የሚከት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፴፩ ፡ ፳) ። ምስጢሩ ፡ የጂብና ፡ የድብኝት ፡ ነው ።

**ዲያብሎስ** ፤ (ጽር ፡ ዲያቦሎስ ። ዐረ ፡ ኢብሊስ) ፤ በቁሙ ፤ ሰይጣን ፡ ጋኔን ፡ ኵፉ ፡ መልአክ ፤ የሰይጣንን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ባስመጣሮች ፡ ግን ፤ ዐማፂ ፡ ገፋዒ ፡ ጸናኒ ፡ ፈታዊ ፤ ጎማሜ ፡ አምላክና ፤ ነገድ ፡ ውዑይ ፡ ያፍ ፡ ስራሪ ፡ ይሉታል ፤ ዘይቤው ፡ ከደየበና ፡ ከደበወ ፤ ምስጢሩ ፡ ከሰይጣን ፡ ይስማማል ፡ (ጥበ፱ ፡ ፳፬ ። ማቴ፬ ፡ ፩ ። ፲፪ ፡ ፴፱) ።

**ዴግኖ** ፤ ኖት ፤ (ዴገነ ፡ ይዴግን ፡ ይዴግን ። ትግ ፡ ዳገነ ። ዕብ ፡ ዳዮግ ፤ አሥገሮ ፡ ዓሣ) ፤ መከተል ፡ ማባረር ፤ መሻት ፡ ማደን ፤ ማጥመድ ፡ ማስገብ ፡ መደገን ፤ ስመያዝ ፡ ስመግደል ፡ ስመግረክ ። ዴግንዩ ፡ እኢኀዞሙ ። ዴግንዎ ፡ ወትእኅዝዎ ። ይዴግንዋ ፡ ለእሪትሙ ። ለእመ ፡ ዴገንከ ፡ ለጽድቅ ፡ ትረክብ ። ይዴግን ፡ ኀበ ፡ ሐመልማል ፡ (ዘፀ፲፭ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፸ ። ሮሜ፱ ፡ ፴፩ ። ሢራ፳፯ ፡ ፰ ። ኢዮ፴፱ ፡ ፰) ።

**ዴጋኒ** ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት ፤ ዴግንት) ፤ ደጋኝ ፡ አጥማጅ ፤ ዐዳኝ ። የሚከተል ፡ ተከታይ ፤ ፈላጊ ፡ አባራሪ ፡ ገዳይ ፤ ሯጭ ፡ ገሥጋሽ ። ኤዎስጣቴዎስ ፡ አሠረ ፡ ትማሰ ፡ ዴጋኒ ። ዴጋኔ ፡ ፀሩ ፡ (ድጓ ። ስንክ ፡ ሚያ፳፰) ።

**ዴጋን** ፤ ደጋን ፤ (ናት) ፤ በቁሙ ፤ ቀስት ፡ የነጨት ፡ የብረት ፤ ጕባባ ፡ ጕባጣ ፤ ጠማማ ። ደጋን ፡ ያማርኛ ፡ ቀስት ፡ የግእዝ ፡ ነው ። እሰ ፡ ፍናዊሆሙ ፡ መብእስ ፡ ወደጋን ፡ መንኲራኵሮሙ ፡ (ምሳ፱ ፡ ፲፭) ።



ደጋን ፡

**አዴገነ** ፤ አስደገነ ፤ አስከተለ ፡ ተከታይ ፡ ላከ ። ወአዴገንዎ ፡ ውስተ ፡ ለኪስ ፡ ወቀተልዎ ፡ (፬ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፲፱) ።

**ዴድዮ** ፤ ዮት ፤ (ዴደየ ፡ ይዴዲ ፡ ይዴዲ ። ዕብ ፡ ዳዴሀ ፤ ሂዳዴ) ፤ መዝለል ፡ መፈንጨት ፤ እንጥር ፡ ፍንጥር ፡ ድቅ ፡ ድቅ ፡ ማለት ፡ የግልገል ፡ የጥጃ ። አክኼድ ፡ አረማመድ ፡ መማር ፤ ማስተማር ፤ ዳዴ ፡ ዳዴ ፡ ወይም ፡ አቱ ፡ ሥግሬ ፤ ታቱ ፡ ሥግሬ ፡ ማለት ፡ የሕፃን ፡ የሞግዚት ።

**ዴዴ** ፤ (ብ ፡ ዴዴያት ፤ ዴዳያት ፤ ዴድያት) ፤ ደጃፍ ፡ በረንዳ ፡ ወልወል ፤ የቤት ፡ መዠመሪያ ፡ ክፍል ፤ ከበር ፡ ከቅጥር ፡ በውስጥ ፡ ያለ ፡ በታ ፤ ወይም ፡ ታላቅ ፡ የውጭ ፡ በር ፤ ደጀ ፡ ሰላም ። ዴዴሁ ፡ ለባዕል ። እለ ፡ ውስተ ፡ ዴዴ ፡ ቤት ፡ ክር ። በዴዴያተ ፡ አብያት ። ዴድያተ ፡ አንቀጽ ። ወዴዳያቲሃ ፡ (ሉቃ፲፮ ፡ ፳ ። ቀሌ ። ሕዝ፵፫ ፡ ፴ ። ኤር፳ ፡ ፲፩ ። ራእ፳፩ ፡ ፳፩) ።

**ዲዲሞስ** ፤ (ጽርእ ። ዕብ ፡ ቶማእ) ፤ መንታዊ ፤ መንቲያ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቶማስን ፡ እይ ፡ (ዮሐ፲፩ ፡ ፲፯) ።

**ዴዳን** ፤ (ዕብ ፡ ድዳን) ፤ ስመ ፡ ነገድ ፤ የኵሽ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፤ የሸባእ ፡ ወንድም ፤ ዐደንን ፡ ያቀና ፡ ያረበች ፡ አባት ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፯ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፲፭) ። የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ ከኬጡራ ፡ የተወለደ ፡ (ዘፍ፳፭ ፡ ፫) ።

**ዲድርከም ፡ ሚ** ፤ (ጽር ፡ ዲድራኽሞን) ፤ የገንዘብ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ሩብና ፡ እንደ ፡ ፈረንክ ፡ ያለ ፤ አንዱ ፡ ዲድርከም ፡ ኻያ ፡ አበሊ ፡ ነው ። የአበሊን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፡ (ዘሌ፳፯ ፡ ፫—፯) ።

**ዲድስቅልያ** ፤ (ጽር ፡ ዲዳስካሊያ) ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ፫ኛው ፡ የሐዋርያት ፡ መጽሐፍ ፤ ትምርት ፡ ማለት ፡ ነው ። ወሣልስ ፡ መጽሐፍ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ዘውእቱ ፡ ትምህርት ፤ ወኍላቄሁ ፡ አርብዓ ፡ ወሠለስቱ ፡ አንቀጽ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ።

**ደይኖ** ፤ ኖት ፤ (ደየነ ፡ ይዴይን ፡ ይደይን ፤ ዳነየ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ዳን ። ዐረ ፡ ዳነ) ፤ መዳኘት ፤ መፍረድ ፡ መቅጣት ፤ መገሠጽ ፡ መቈጣት ። ወይዴይኖሙ ፡ በዐቢይ ፡ (ሉቱ ፡ ዕዝ፲፱ ፡ ፵፩) ።

**ደያኒ** ፤ **መደይን** ፤ የሚዳኝ ፡ ዳኛ ፤ ፈራጅ ፡ ቀጭ ። ደያኔ ፡ ጽድቅ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፷፱) ።

**ተደየነ** ፤ ተዳኘ ፡ ተቀጣ ፤ ተፈረደበት ፤ ፍርድ ፡ ለበሰ ፤ ቅጣት ፡ ተቀበለ ። ወዘሰ ፡ ኢአምነ ፡ ይደየን ። ከመ ፡ ይደየኑ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ። ዘከመ ፡ ይደየኑ ፡ ኃጥአን ፡ በዝንቱ ፡ እሳት ፡ (ማር፲፮ ፡ ፲፮ ። ራእ፳ ፡ ፲ ። ቀሌ) ።

**ድዩን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ይንት) ፤ የተዳኘ ፡ የተቀጣ ፤ ፍርድ ፡ የለበሰ ፤ የተፈረደበት ።

**ደይን** ፤ (ናት) ፤ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፤ የማይላጥ ፡ የማይለወጥ ፤ የማይመለስ ፡ ቃል ፤ ንዑ ፡ ኀቤየ ፡ ሑሩ ፡ እምኔየ ፤ ይህን ፡ የመሰለ ። ኢትግበር ፡ ዘንተ ፡ ደይነ ። ትንሣኤ ፡ ዘለደይን ፡ ዕለተ ፡ ደይን ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፳፭ ። ዮሐ፭ ፡ ፳፱ ። ማቴ፲ ፡ ፲፭) ።

—፤ ፍዳ ፡ ቅጣት ፤ መከራ ፡ ሥቃይ ፤ የሥቃይ ፡ በታ ። መካነ ፡ ደይን ። ጢስ ፡ ደይኖሙ ። ዕዘቅተ ፡ ደይን ። ይጼዐሩ ፡ ውስተ ፡ ደይን ። አንቀጸ ፡ ደይን ፡ (ኩፋ ፡ ፯ ። ራእ፲፬ ፡ ፲፩ ። ሉቱ ፡ ዕዝ፯ ፡ ፳ ፡ ፶ ። አርጋ ፡ ፬) ። ዲን ፡ ድኝ ፡ ማለት ፡ ደይን ፡ ከማለት ፡ ወጥቷል ፤ ክብሪትን ፡ እይ ።

**መዲና** ፤ (ናት) ፤ በቁሙ ፤ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ መናገሻ ፤ ፍርድ ፡ የሚቈረጥበት ፤ በደግባኝ ፡ የሚኬድበት ። ቆሮንቶስ ፡ ልህቀተ ፡ አካይያ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ መዲና ።

ወኀብረ ፡ መዲናሁ ፡ በጐንደር ፡፡ ወኢወፅአ ፡ እመዲ ናሁ ፡ (አዋል ። ታሪ ፡ ነገ) ።

**ዲና ፤ (ዕብራ) ፤** ስመ ፡ ብእሲት ፤ ወለተ ፡ ያዕቆብ ፡ ፍርዲ ፡ ፍርዲቴ ፡ ማለት ፡ ነው ። ወንድሞቿ ፡ ስምዖንና ፡ ሌዊ ፡ በርሷ ፡ ምክንያት ፡ የሴኬምን ፡ ሰዎች ፡ ለለ ፡ ዘረፉና ፡ ለለ ፡ ፈጁ ፤ ሽፍታ ፡ ኹሉ ፡ በነዚህ ፡ አምሳል ፡ ዲና ፡ ይባላል ፤ የዲና ፡ ወንድም ፡ ማለት ፡ ነው ። ሴኬም ፡ ህየ ፡ ብዴና ፡ ተሀጕለ ፤ ወበሳራ ፡ አቤሜሌክ ፡ ቈስለ ፡ (ቅኔ ። ዘፍ፴፬ ፡ ፳፭ ። ፴፬ ፡ ፩—፫ ፡ ፳፱—፴) ።

**ዲኖ ፤ (ትግሬ) ፤** ዐጕዛ ፡ ሌጦ ፡ ደበሎ ፡ ፍርድ ፡ ልብስ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ዐድልን ፡ ተመልከት ። ባማርኛ ፡ ግን ፡ ጅን ፡ ጅናም ፡ የባሕር ፡ ጕሽ ፡ የጋኔን ፡ በሬ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከባሕር ፡ እየወጣ ፡ ሣር ፡ ይበላል ፡ ከየብስ ፡ እንስሳትም ፡ ይወልዳል ፤ ከርሱ ፡ የሚወለድ ፡ ላም ፡ ኹሉ ፡ በጣም ፡ ብርቱ ፡ ነው ፤ በገር ፡ አይያዝም ፡ አይጠመድም ፤ ብሂሞትን ፡ እይ ።

**ዳን ፤** የዲና ፡ ወንድም ፤ ስመ ፡ ነገድ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፤ ፈረደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሰመዮቶ ፡ ስሞ ፡ ዳን ፡፡ ተሰምየ ፡ እስከ ፡ ዳን ፡፡ እምዳን ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ (ዘፍ፴ ፡ ፮ ። ፲፬ ፡ ፲፬ ። ፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፩) ።

**ዳይቅ ፤ (ዕብ ፡ ዳየቅ) ፤** መታከሻ ፡ ግንብ ፤ የውጭ ፡ ጠላት ፡ በቅጥር ፡ ዠርባ ፡ የሚሠራው ፤ ወይም ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ኹኖ ፡ እንዳንደርቢ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ የሚሰደው ፡ የሚወረውረው ፡ ደንጊያ ። ኪመ ፡ ይሕንጽ ፡ ዳይቀ ፡ (ሕዝ፳፩ ፡ ፳፪) ።

**ዲያቆን ፤ (ናት ። ጽር ፡ ዲያክኖስ) ፤** በቁሙ ፤ አገልጋይ ፡ የቄስ ፡ ተወራጅ ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ የሚሾም ። ሶበ ፡ ትሰይሞ ፡ ለዲያቆን ፡ አንብር ፡ እዴከ ፡ ላዕሌሁ ፡፡ ሊቀ ፡ ዲያቆናት ፡፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆን ፤ የዲያቆን ፡ ተወራጅ ፡ ምክትል ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፯ ። ፰) ።

**ዲያቆናይ ፤ ዊ ፤ (ይያን ፡ ውያን) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ። እስጢፋኖስ ፡ ዲያቆናይ ፡ ምእመን ፡ በሰማይ ፡ (ድጓ) ።

**ዲያቆናይት ፤ (ዊት ፤ ይያት ፡ ውያት) ፤** ሴት ፡ ዲያቆን ፤ የ፷ ፡ ዓመት ፡ ባልቴት ፤ በሴቶች ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ዲያቆን ፡ ኹና ፡ የምትላክ ፡ የምታገለግል ። ወዲያቆናዊት ፡ ትገሥጾን ፡ ለአንስት ፡ ወታዐርፎን ፡ ወትርድኦን ፡፡ እለ ፡ ያወስቡ ፡ መነከሳይያት ፡ ወዲያቆናይያት ፡ (ሲኖዶ ፡ ፳ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፯ ። ማ፳) ።

**ዲቁና ፤** በቁሙ ፤ ዲያቆንነት ፡ ዲያቆን ፡ መኾን ፤ የዲያቆን ፡ ሹመት ፡ ማዕርግ ። ሢመተ ፡ ዲቁና ፡፡ መልእክተ ፡ ዲቁና ፡፡ ግብረ ፡ ዲቁና ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲) ።

**ዴቆን ፤ (ይዴቁን ፡ ይዴቁን) ፤** ዲያቆን ፤ ዘቆን ፤ ዲያቆን ፡ ኾነ ። ዜቆንን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ምክኼና ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ዶር ፤ (ሱር ፡ ዳይራ ። ዐረ ፡ ደይር) ፤** ገዳም ፡ ዱር ፤ የመነኮሳት ፡ ቦታ ፡ ሰፈር ። ዘሩ ፡ ደዊር ፡ ነው ፤ ወና ፡ የ ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በየ ፡ ምክንያት ፡ ወደዚህ ፡ መጥቷል ፤ ዱርና ፡ ዶር ፡ ፩ ፡ ስም ፡ ናቸው ። ኀበ ፡ ተሐንጸ ፡ ተዝኪር ፡ ወኀበ ፡ ተማረረ ፡ ዶር ፡ (ስንክ ፡ የካ፲) ።

**ዳየር ፤** አንካ ፡ ኩረብታ ፤ ዙሪያው ፡ ገደል ፤ የማሸና ፡ የማሸን ፡ ተራራ ፤ ምስጢሩ ፡ ገዳምነት ፡ ነው ።

**ድያስ ፤ ድዮስ ፤ ድያ ፤ (ጽር ፡ ዲዎስ) ፤** ወፍራም ፡ ረዥም ፡ ጣዖት ፤ አምላክ ፡ ዐቢይ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዜውስን ፡ እይ ፡ (ግብ፲፬ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፱) ።



ድያ ፡

**ዲዮስቆሪዶስ ፤ (ጽር ፡ ዲዎስኩሮን) ፤** መንታ ፡ ጣዖት ፡ ወንድማማች ፤ የድያስ ፡ ልጆች ፡ የሚባሉ ። ባሲሐዲሶች ፡ ግን ፡ መስቀል ፡ ይሉታል ፡ (ግብ፳፰ ፡ ፲፩) ።

**ዲዮስቆሮስ ፤ (ጽር ፡ ወቅብጥ) ፤** የሰው ፡ ስም ፤ በዳኬዎስና ፡ በመርቅያን ፡ ዘመን ፡ የነበረ ፡ ስማዕት ፤ ያምላክ ፡ ወገን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤ ልደ ፡ ቤት ፡ አገልጋይ ፡ (ቅዳ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**ዲዮስጶራ ፤ (ጽር ፡ ዲያስፖራ) ፤** ዝርዋን ፡ ዘበዝርወት ፡ ዘበስደት ፡ ዘበፍልሰት ፡ (ያዕ፩ ፡ ፩) ።

**ዴፐ ፤ ዴየፐ ፤ (ደበወ ፤ ደበየ) ፤** ሸመቀ ፡ አሸመቀ ፤ አደባ ፡ ደፈጠ ፡ ተደበቀ ፤ ለመግደል ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ። ዘዴፐ ፡ ለከ ፡ ይቅትልከ ፡፡ ዴፑ ፡ በፍኖት ፡ (ዮሴፍ) ።

—፤ ጦር ፡ ወጥመድ ፤ አኖረ ፤ ደበቀ ፡ ሸሸገ ። ዴፐ ፡ ሎቱ ፡ ዕደወ ፡ ኪመ ፡ የኀይል ፡ ቦቱ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ዲፓ ፤ (ዲባ) ፤** ሽመቃ ፡ ሽመቃ ፤ ደበቅ ፡ ጦር ፡ ደባ ፡ ተንኰል ። ነበረ ፡ ዲፓ ፡፡ ቀመ ፡ ዲፓ ፡፡ ጸንሐቶ ፡ ዲፓ ፡ ለንጉሥ ፡፡ ወይጸንሕዎ ፡ ሎቱ ፡ በዲፓ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፭ ። መሳ፱ ፡ ፴፱ ። ዮሴፍ) ።

**ደኪም ፤ ሞት ፤ (ደክመ ፡ ይደክም ፡ ይድክም) ፤** መድከም ፡ መታከት ፤ መዛል ፡ መስነፍ ፡ መላም ፡ መለስለስ ፤ ማነስ ፡ መኰስስ ። እገሪከ ፡ ይረውዳ ፡ ወይደክማከ ፡፡ ወደኪሞ ፡ በሐዊረ ፡ ፍኖት ፡ ነበረ ፡፡ ደክመት ፡ ነፍስየ ፡ (ኤር፲፪ ፡ ፭ ። ዮሐ፬ ፡ ፮ ። ሉቃ ፡ ዕዝ ፲፪ ፡ ፳) ።

—፤ መፍዘዝ ፤ መሰለል ፤ የዐይን ፡ የቃል ፡ ማርጀት ፡ መታመም ፤ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ድካም ፡ ነው ። ደክማ ፡ አዕ

ይንትየ ፡ በአንብዕ ። ቃለ ፡ ወለተ ፡ ጽዮን ፡ ደክመ ። ኢ.ደክመት ፡ እምነ ይላ ። ደክመ ፡ አቡከ ። ዘእንበለ ፡ ትድክም ፡ (ስቈ፪ ፡ ፲፬ ። ኢር፴ ፡ ፴፯ ። ኩፋ ፡ ፴፯ ። ዘፍ ማ፳ ፡ ፩ ። ሚራ፲፰ ፡ ፳፩) ። ደክተመን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ስ ሯጽ ፡ ነው ።

**ድኩም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ክምት) ፤** የደከመ ፡ ደካማ ፡ ኰሳሳ ፤ ታናሽ ፡ ወራዳ ፤ አሮጌ ፡ በሽተኛ ፤ ልም ፡ ልምሎም ፤ ርጥብ ፡ ለጋ ፡ ጨቅላ ። ድኩም ፡ ወጽኑስ ። መንግሥት ፡ ድኩም ። ልደትኪ ፡ እማሕፀኒ ፡ ድክ ምት ፡ ሥጋ ። አዕይንቲሃ ፡ ድኩም ። ልሳን ፡ ድክ ምት ። ድኩማን ፡ ደቂቅ ፡ (ገላ፬ ፡ ፱ ። ሕዝ፲፯ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ ማንሸ ። ኩፋ ፡ ፳፰ ። ምሳ፳፭ ፡ ፲፭ ። ዘፍ፴፫ ፡ ፲፫) ።

**ድክመት ፤** መድከም ፡ አደካከም ፤ ድካም ፡ ደካምነት ። እምድኅረ ፡ ርሥአኑ ፡ ወድክመቱ ፡ (ፊ ልክ ፡ ፶፩) ።

**ድክምና ፤** ደካምነት ፤ ድካም ። እንዘ ፡ ሀለው ክኒ ፡ እንቲ ፡ ለድክምና ፡ መጽንዒ ፡ (አዋል) ።

**ድካም ፤ (ማት) ፤** በቁሙ ፤ ስንፍና ፡ ሀኬት ፤ ልፋት ፡ ጥረት ፡ አገልግሎት ። እንበለ ፡ ድካም ። ከመ ፡ ያእምር ፡ ድካሞ ። ድካመ ፡ ፍጥረቱ ፡ ወአእምሮቱ ። ሑጻጼ ፡ ወድካም ። ዕሴተ ፡ ገድላቲሆሙ ፡ ወድካ ማቲሆሙ ፡ (ስንክ ፡ ጳግ፪ ። ኢዮ፴፯ ፡ ፯ ። ፊልክ ፡ ፻፰ ። ዮሴፍ ። ፊ ፡ መ ፡ ፩ ፡ ፪) ።

**አድከመ ፤** አደከመ ፤ አለፋ ፡ አታከተ ፡ አሰለቸ ፤ አሰነፈ ። ያደክም ፡ ቃሎ ፡ ወይዌውሀኪ ። ያደክም ፡ ኀይሎ ፡ እንዘ ፡ ይትቀነይ ። ስካር ፡ ያደክም ፡ ኀሊና ፡ (ሚራ፳፱ ፡ ፳ ። ፴፰ ፡ ፴ ። ቀሌ) ።

**መድክም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤** የሚያደ ክም ፤ አድካሚ ። ዛቲ ፡ ግብር ፡ መድክምት ፡ ጥቀ ፡ (ፊልክ ፡ ፳፫) ።

**ድኰዐ ፤ (ይደኵዕ ፡ ይድኰዕ ፤ ደኵዖ) ፤** ወደቀ ፡ ተጣለ ፡ ተረፈ ።

**ድኵዕ ፤ (ዕብ ፡ ዳከእ ፡ ዐፈር ፡ ትቢያ) ።** ፍግ ፡ ፋንድያ ፡ በጠጥ ፤ ዐዘባ ። ደከይ.ድዎሙ ፡ ከመ ፡ ድኵዕ ። እክው ፡ ድኵዐ ። ተግሣጽ ፡ ለሕፃን ፡ ያሤንዮ ፡ በከመ ፡ ያሤንዮ ፡ ድኵዕ ፡ ለምድር ፡ (ኢር፰ ፡ ፪ ። ሉ ቃ፲፫ ፡ ፰ ። ፊላስ ፡ ፺፰) ።

**ደኵስበተሬ ፤ (ጽር ፡ ዶክሳ ፡ ፓቴሪ) ፤** ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ማለት ፡ ነው ። አርቆዶክስን ፡ እይ ። ወ ትብል ፡ ደኵስበተሬ ፡ አርባዕተ ፡ ጊዜ ፡ (ማንዘ) ።

**ደክተመ ፤ (ደክመ ፤ ተ ፡ ስሯጽ ። ዕብ ፡ ያቱም) ፤** ደኸየ ፤ የሙት ፡ ልጅ ፡ ኾነ ። አባት ፡ እናት ፡ ዐጣ ። ድኻ ፡ ማለት ፡ ቅሎ ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ዕብራይስ ጥም ፡ ድኻ ፡ ሲል ፡ ዳኻ ፡ ይላል ። ደክተመት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ለእለ ፡ ተርፉ ፡ ድኅሬሁ ፡ ርድእሙ ፡ ወለእለሂ ፡ ደክተሙ ፡ ሕፀምሙ ፡ (አቡሻ ፡ ፶ ። ማንዘ) ።

**ድክቱም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ትምት) ፤** የደኸየ ፡ የተጣለ ፤ አባት ፡ እናቱ ፡ የሞቱበት ። ድክት ምት ፡ ይእቲ ፡ እምአቡሃ ፡ ወእማ ። ድክቱማን ፡ (አ ዋል ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፫) ።

**ደክታም ፤ (ብ ፡ ደክትም) ፤** ድኻ ፡ አደግ ፡ ድኻ ፡ የሙት ፡ ልጅ ። እሮ ፡ ኢይፈደፍድ ፡ ሐዘንየ ፡ እንዘ ፡ እኤጽር ፡ አንስቲያሆሙ ፡ ከዊኖን ፡ ደክታመ ፡ ወውሉዶሙ ፡ ዕጓለ ፡ ማውታ ። ደክታም ፡ ነፍስየ ፡ እምእማ ፡ ወአባ ። ንዋየ ፡ ደካትም ፡ (ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ታኅሣ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፱) ።

**ድክታሜ ፤ ድክትምና ፤** ድኻነት ፡ አደጎ ፡ ዐጣነት ፤ የሙት ፡ ልጅነት ። በእንተ ፡ ዕጓለ ፡ ማውትና ሆሙ ፡ ወድክትምናሆሙ ፡ (ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፮) ።

**አደክተመ ፤** አደኸየ ፡ ድኻ ፡ አደረገ ፤ አባት ፡ እናት ፡ አሳጣ ። አደክተመኒ ፡ እምአቡየ ፡ ወእምየ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ደልኀ ፤ ኀት ፤ (ደለገ ፡ ይደልግ ፡ ይደ ልግ ። ዕብ ፡ ዳላግ ፤ ዳላቅ) ፤** መዝለል ፡ (ጥወ) መ ወርወር ፤ ዘሎ ፡ ተራምዶ ፡ ማለፍ ፤ መፍጠን ፡ መቃል ጠፍ ፤ መናር ፡ መጓን ፤ ሳም ፡ እንዳየ ፡ አንበሳ ፡ መኾን ፤ ያርበኛ ። ማዝለል ፡ መወርወር ፡ አርቆ ፡ መጣል ፤ የፍላጻ ፡ የጦር ። ንኅረይ ፡ ለርእስነ ፡ ኀኑያነ ፡ በብእ ፡ እለ ፡ ይ ደልጉ ፡ ውስተ ፡ ቀትል ፡ ወንሑር ፡ ላዕሌሁ ፡ ወንት ቃተል ፡ ምስሌሁ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፯) ።

**ተዳለገ ፤** ተወራወረ ፤ ተመካከተ ። ዕደው ፡ ኀ ያላን ፡ ወእለሂ ፡ ይዳለጉ ፡ ጠፍኡ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፰) ።

**ድላግ ፤** ዝላይ ፡ ውርወራ ፡ መክታ ፤ የሰልፍ ፡ ሥራ ። ከመ ፡ ያእትት ፡ እምላዕሌየ ፡ ዘቀትለ ፡ ፀራዊ ፡ ድላገ ፡ ውሒዘ ፡ ረድኤትከ ፡ ይኩን ፡ በዐውድየ ፡ ፀ ይገ ፡ (ደራሲ) ።

**ዳልጋ ፤ (ዐማርኛ) ፤** የባሕር ፡ በሬ ፤ ጅን ። የ በሬ ፡ ዐንገት ፡ ትርፋ ፡ እንጥልጥሉ ፡ ቈርበት ፤ ደላጎ ፤ የ ጤፍ ፡ ዛላ ። ማናቸውም ፡ ትርፍ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ።

**ድልጐማ ፤ (ዐረ ፡ ዱምሉጅ) ፤** የእጅ ፡ የ ማት ፡ ጌጥ ፡ ጥምዝ ፡ የወርቅ ፡ አንባር ፤ ኀቲም ፡ ቀለበት ፡ ወይም ፡ ባለስንቅ ፡ ፈርጥ ። ወከመ ፡ ድልጐማ ፡ ው ስተ ፡ እደ ፡ የማን ። ሕልቀትየ ፡ ዘአጽባዕትየ ፡ ወድ ልጐማየ ፤ አንባር ፡ (ሚራ፳፩ ፡ ፳፩ ። ኩፋ ፡ ፴፰) ። ከመ ፡ በዝግና ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ ክሣድ ፡ ወከመ ፡ ድልጐማ ፡ ዘውስተ ፡ አጻብዕ ፡ (ፊላስ ፡ ፲፰ ። ደልጎን ፡ ማለት ፡ ከ ዚህ ፡ ይሰማማል ።


**ደሊው ፤ ዎት ፤ (ደለወ ፡ ይደሉ ፡ ይ ድሉ ። ዐረ ፡ ደላ ። ሱር ፡ ድላ ። ዕብ ፡ ዳላህ ፤ ሒብ) ፤** መጥለቅ ፡ መቅዳት ፤ መሳብ ፡ መጉተት ፤ ከጉድ ጓድ ፡ ከጥልቅ ፡ ከዐዘቅት ፡ ማውጣት ። ማንሣት ፡ መስ ቀል ፡ ማንጠልጠል ፤ መመዘን ፡ መለካት ፡ ማስተካከል ። (ማዘጋጀት ፤ ማሰናዳት) ። ወደለዊ ፡ ዐስብየ ። ደለ ውኩ ፡ ሎቱ ፡ ወርቀ ። ወደለውኩ ፡ ሎሙ ፡ ወርቀ ፡ ወብሩረ ። እመ ፡ ደለውከ ፡ ቃለከ ፡ በመዳልው ። ወ ትደልዎ ፡ (ዘካ፲፩ ፡ ፲፪ ። ኢር፴፱ ፡ ፲ ። ዕዝ፰ ፡ ፳፮ ።

ሚ.ራ፳፰ ፡ ፳፩ ። ሕዝ፳ ፡ ፰) ። ዳግመኛም ፡ በቀደስ ፡ ቤት ፡ ደልዎ ፤ ደሰወ ፡ ይደሎ ፡ እያለ ፡ በ፪ ፡ መንገድ ፡ ይኬዳል ። ተደሰወና ፡ መደልው ፡ የዚህ ፡ አንጻር ፡ ናቸው ።

**ደላዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ የሚመዝን ፡ መዛኝ ፤ ውሃ ፡ ቀጅ ፡ ባለማሕየብ ።

**ደለው** ፤ (ዐረ ፡ እደለው) ፤ ስመ ፡ ኮከብ ፤ ደላዊ ፡ ማይ ፡ ሐያቢ ፡ በዓለ ፡ ማሕየብ ፡ ማለት ፡ ነው ። መልኩ ፡ በሥዕል ፡ ሲያዩት ፡ ውሃ ፡ ቀጅ ፡ ይመስላል ፡ ኮከብነቱም ፡ የጥር ፡ ነው ፤ ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ ፳፱ ፡ ዕለት ፡ ፴፰ ፡ ኬክሮስ ፡ ይመግባል ፡ (አቡሻ ፡ ፬) ።

**መድለው** ፤ (ብ ፡ መዳልው) ፤ **አው ፡ መድሎት** ፤ (ታት) ፤ መመዘኛ ፡ ማስተካከያ ፤ ሚዛን ፡ ደንጊያ ፡ ልክ ፤ ብዙ ፡ ስምና ፡ ክፍል ፡ ያለው ። መድሎተ ፡ ሰቅል ። መድሎተ ፡ ልጥር ። ወተረክበ ፡ መድሎተ ፡ ውእቱ ፡ አክሲል ፡ መክሲተ ። መዳልው ፡ ዐቢይ ፡ ወንኡስ ። መዳልወ ፡ አልባብ ። መዳልወ ፡ ፀሓይ ፡ (ዘዐ፴፱ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ሚያ፫ ። ፩ዜና ፡ ፳ ፡ ፪ ። ምሳ፳ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ጥቅ፩ ። ክብ ፡ ነገ) ።



መድሎት ፤

**ደለወ** ፡ (ዐጕል) ፤ ኾነ ፡ ተገባ ፤ ደላ ፡ ተመቸ ፡ ተስማማ ። (ገበዘ ፡ ተገበዘ ፡ ግብገዘ ፡ ኾነ) ። ዘይደሉ ፡ ለመልእክት ፡ ዘሉ ። ለከ ፡ ይደሉ ፡ ስብሐት ። ወደለዎ ፡ ብሔር ፡ (ጥበ፲፰ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፳፬ ። ሉቃ፲፱ ፡ ፲፯) ።

**አድለወ** ፤ አስመዘነ ። አደላ ፤ አስደላ ፤ አስመቸ ፡ ደሉ ፡ አስኘ ፡ ግቡ ፡ አደረገ ፡ አበቃ ። ታደሉ ፡ ሲተ ፡ መክሲተ ፡ ብሩር ። ኢታድሉ ፡ ለሰብእ ፡ እንበይነ ፡ ላሕዩ ። ለእግዚ ፡ አድልዎ ፡ ኢይክሉ ። ዘንተ ፡ ሕዝበ ፡ አድሉ ፡ ለነሚአ ፡ ምስጢርከ ፡ (፪ነገ ፡ ፳ ፡ ፴፱ ። ሚራ፲፩ ፡ ፪ ። ሮሜ፰ ፡ ፰ ። ቅዳ ፡ ሕር) ።

**አድላዊ ፤ መድልው ፤ መደልው** ፤ (ዋን) ፤ የሚያስመዝን ፤ አስመዛኝ ። በቁሙ ፤ የሚያደላ ፤ የሚያስመች ። ግብዝ ፡ ሰነፍ ፤ ሞኝ ፡ ዋቻ ። ብእሲ ፡ መደልው ። ኦ ፡ መደልው ። ፈሪሳውያን ፡ መደልዋን ። ረበናት ፡ መደልዋን ፡ (ኢዮ፴፬ ፡ ፴ ። ማቴ፮ ፡ ፭ ። ፳፫ ፡ ፲፫ ። ዳንኤ ፡ ፳) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ አመድለወ ፡ ብለው ፡ ይገሩና ፡ መደልውን ፡ ከዚህ ፡ ያወጣሉ ።

**አስተደለወ** ፤ (ያስተዴሉ ፡ ያስተደሉ ፤ **አው ፡ አስተዳለወ** ፡ ያስተዳሉ ፡ ያስተዳሉ) ፤ የደሰወና ፡ የአድለወ ፡ ድርብ ፡ አድራጊና ፡ አስደራጊ ። አዘጋጀ ፡ አሰናዳ ። አደላደለ ፡ አስመቸ ፡ አመቻቸ ። ያስተዴሉ ፡ ለዓለም ፡ መፍቅዶ ። ወያስተዴሉ ፡ ክረምተ ፡ ለምድር ። አስተዳለወ ፡ መንበሮ ። አስተደለወ ፡ ሀገረ ፡ (ሚራ፴፱ ፡ ፴፰ ። መዝ ፡ ፻፵፯ ። ፻፪ ። ዕብ፲፩ ፡ ፲፯) ።

**ተደልወ** ፤ ተመዘነ ፤ ተካከለ ፡ (ሔኖ፵፰ ፡ ፰ ። ፵፫ ፡ ፪) ። እስመ ፡ በመዳልው ፡ ተደልወ ፡ ዓለም ። ሶበ ፡ ተደልወት ፡ ምስለ ፡ ብርሃን ፡ (ሱቱ ፡ ዕዝ፪ ፡ ፵፮ ። ጥበ፯ ፡ ፳፱) ።

**ተደለወ** ፤ ተዘጋጀ ፡ ተደራጀ ፤ ተሰናዳ ። ተደላደለ ፡ ተቀማጠለ ፤ ተድላ ፡ አደረገ ፡ በተድላ ፡ ኖረ ፤ ተደሉተ ። ተደለዉ ፡ አሕዛብ ፡ ለጸብእ ። ተደለው ፡ ከመ ፡ ትሑር ። ወመጽአ ፡ ሳኦል ፡ ተደሊዎ ። ባዕድ ፡ ይዴሉ ፡ በንዋየ ፡ ዚኣሁ ። ከመ ፡ ትደሉ ፡ አመ ፡ ተድላሁ ። እምተደለው ፡ ወትትፈጋዐ ፡ በንዋየ ፡ ነኪር ፡ (አስቴ፩ ፡ ፯ ። ጦቢ፰ ፡ ፲፯ ። ፩ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፬ ። ኢዮ፲፰ ፡ ፳ ። ሚራ ፡ ፳፱ ፡ ፪ ፡ ፳፪) ።

(ሀ) **ድልው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሉት) ፤ የተመዘነ ፡ የተካከለ ፡ ልክኛ ፤ እንሰ ፡ በዛ ፡ የማይባል ። ቃሎሙ ፡ ለጠቢባን ፡ ድልው ፡ በመዳልው ። ድልወ ፡ ዕርየት ፡ (ሚ.ራ፳፩ ፡ ፲፭ ። ፊልክ ፡ ፫) ።

(ለ) **ድልው** ፤ የተገባ ፤ የተዘጋጀ ፡ የተሰናዳ ፡ ዝግጁ ። ዘድልው ፡ ለክብር ። ድልው ፡ መንበርከ ። በዓልየ ፡ ድልው ። ድልዋኒክሙ ፡ ሀልዉ ። እልኩ ፡ እለ ፡ ድልዋት ። ወድሉት ፡ ይእቲ ፡ (ሚራ፴፱ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፺፪ ። ማቴ፳፪ ፡ ፰ ። ፳፬ ፡ ፵፬ ። ፳፭ ፡ ፲ ። ራእ፳፩ ፡ ፪) ። ድልኽ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ድልወት** ፤ (ታት) ፤ መመዘን ፡ (ጥመ) መመዘን ፡ መዛኝና ፡ ተመዛኝ ፡ መኾን ፤ አመዛዘን ፡ ምዘና ፡ ሚዛን ፤ ልክ ፡ መጠን ፡ (ዘፍ፳፬ ፡ ፳፪ ። ዘፀ፴ ፡ ፴፬ ። መሳ፰ ፡ ፳፯) ። ወድልወቱ ፡ ለዘሉ ፡ ብርት ፡ ወኀጺን ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ኀምሳ ፡ ምእት ፡ ሰቅሎን ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ። ፪ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፳፮) ።

—፤ አገባብ ፡ ርቱዕ ፡ እውነት ፡ የተገባ ፡ የሚገባ ። በጽድቅ ፡ ተኰነኑ ፤ ዘከመ ፡ ድልወተ ፡ እከዮሙ ። እንዘ ፡ አከ ፡ ድልወት ፡ ሲተ ፡ አድኀንከኒ ፤ አከ ፡ ድልወት ፡ ሲተ ፡ ኣንቃዕዶ ። በበ ፡ ድልወታት ። ነበብከ ፡ ድልወተ ፡ (ጥበ፲፱ ፡ ፲፰ ። ዲድ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ፡ ፪ ። ቁር ፡ ጸላ) ።

**ተድላ** ፤ በቁሙ ፡ ደስታ ፡ ድሎት ፡ ምቾት ፡ ምቹ ፡ ፍራሽ ፡ ፈርሽ ፡ የዙፋን ፡ የኮር ። ኢያፍቀከ ፡ ተድላሆሙ ፡ ለረሲዓን ። ገነተ ፡ ተድላ ። ተድላ ፡ ርእስየ ። ፍትሐ ፡ ወርትዐ ፡ ተድላ ፡ መንበሩ ፡ (ሚራ፴፱ ፡ ፲፪ ። ዘፍ፪ ፡ ፳፫ ። ሰቆቃ ፡ ፲ ፡ ፴፫ ። መዝ ፡ ፹፰) ።

—፤ አገባብ ፡ ክብር ፡ ገንዘብ ። እስመ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ተድላ ፡ ለነ ። ተድላ ፡ መለኮት ። መዛግብቲሆሙ ፡ ከመ ፡ እምላእ ፡ ተድላ ፡ (ማቴ፫ ፡ ፲፭ ። ቁር ። ምሳ፳ ፡ ፳፩) ።

**ተዳለወ** ፤ (ይዳለው) ፤ ተደራረገ ፡ ተዘገጃጀ ፡ ተሰነዳዳ ፡ ተመቻቸ ።

**ዳሌጥ** ፤(ዕብ፡ ዳሌት ። ጽር፡ ዴልታ ። ግእ፡ ድልት) ፤ ስመ፡ ፊደል፡ ራብዕ፡ ደ፡ መዝገቢያ፡ ሳንቃ፡ ማለት፡ ነው፡ (መዝ፡ ፻፲፰፡ ፳፭—፴፪ ። ሰቈ፡ ፩ ። ፪ ፡ ፬ ። ፫፡ ፲ ። ፬፡ ፬) ።

**ደልሎ** ፤ **ሎት** ፤(ደለለ፡ ይዴልል፡ ይደልል ። ዕብ፡ ዳላል ፤ ታላል) ፤ መመየድ፡ መከፍከፍ ፤ ጠጕርን፡ በሚዶ፡ ማበጠር፡ ማጕፈር ፤ መበተን፡ ማጕተን ፤ መንቀስ፡ መከናከን ፤ ስቤት፡ ክዳንም፡ ይኾናል ። ወይም፡ መሥራት፡ መጣስ ፤ መሸረብ፡ መጕንጐን ፤ መፍተል፡ መቈንደል ። በቁሙ፡ መደለል፡ ማታለል ፤ መሸንገል ። (ተረት) ፤ ደሮን፡ ሲደልሏት ፤ በመጫኛ፡ ጣሏት ። ደላል፡ ደላላ ፤ ድላል፡ ደለል፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ወጥቷል ።

**ተደለ** ፤ **ተደለለ** ፤ በቁሙ ፤ ተከፈከፈ፡ ተበጠረ፡ ተቈንደለ ።

**ድሉል** ፤(ላን፡ ላት፡ ልልት) ፤ የተመየደ፡ የተከፈከፈ፡ ክፍክፍ ፤ ወይም፡ ወደ፡ ታች፡ የተጣሰ፡ የተዝረፈረፈ ፤ ግልስልስ፡ ያለ ፤ የተቈናዘለ ፤ የተጋመደ፡ የተመሳቀለ ። ድምድማሁ፡ ድሉል ። ሥዕርተ፡ ርእስኪ፡ ድሉላት ። ላሕይት፡ ይእቲ፡ ብእሲት ፤ ድምድማሃ፡ ድሉል ፤(ማሕ፩፡ ፲፩ ። አርጋ፡ ፯ ። ገድ፡ ተክ) ።

**ድላሌ** ፤ (ላ፡ ጥ፡ ክ) መከፍከፍ ፤ አከፋከፍ ፤ ክፍከፋ ፤ ክፍክፋት ፤ የጠጕር፡ ሥራ ፤ ዐይነቱ፡ መልኩ ፤ ጠባዩ፡ አኳኋኑ ። ርእሱ፡ ወርቅ፡ ቈፋዝ፡ ወድላሌሁ፡ ጸሊም፡ ከመ፡ ቋዕ ። ለሥዕርትኪ፡ ሰላም፡ ዘድላሌሁ፡ ጸሊም ፤(መጽ፡ ምስ ። ደራሲ) ።

**ደሊላ** ፤(ዕብ፡ ድሊላ) ፤ ቀጭን፡ ክር ፤ ገመድ፡ ፈትል ፤ ወይም፡ ሥሥ፡ ረቂቅ፡ መንዲል ፤ የጠጕር፡ ማስረያ፡ መሸፈኛ ። የሶምሶን፡ ሚስት፡ (መሳ፲፮፡ ፬) ። ስሟ፡ እንደ፡ ትንቢት፡ ኹኖ፡ ተነግሯል ።

**ድልማኑታ** ፤ ስመ፡ ሀገር፡ የገሊላ፡ ምዕራብ፡ (ማር፡ ፰፡ ፲) ።

**ደሊቅ** ፤ **ቆት** ፤(ደለቀ፡ ይደልቅ፡ ይድልቅ ። ዐረ፡ ደሊቀ ። ዕብ፡ ዳላቅ ፤ ነደ) ፤ መታወክ፡ መናወጥ ፤ መጋለብ፡ መውለብለብ ፤ የባሕር፡ የእሳት ። በቁሙ ፤ መደለቅ፡ መምታት ፤ የከበሮና፡ የርግጫ ።

**አድለቀ** ፤ አወከ፡ አናወጠ ፤ አስመታ፡ አስደለቀ ። መጽሐፍ፡ ግን፡ በደለቀና፡ በአድለቀ፡ ፈንታ፡ ኹለቱን፡ አዕማድ፡ ደርበ፡ አድለቅለቀ፡ ይላል ።

**አድለቅለቀ** ፤ አንዋወጠ ፤ ተንዋወጠ፡ (መዝ፡ ፳፰ ። ፶፱ ። ፺፰) ። አነ፡ ኣድለቀልቃ፡ ለምድር ። ወኣድለቀልቆን፡ ለአህጉር ። ዘያድለቀልቃ፡ እመሠረታ ፤ ገቢር፡ (ዕብ፲፪፡ ፳፮ ። ኢሳ፲፡ ፲፬ ። ኢዮ፱፡ ፮) ። ያድለቀልቅ፡ ሰማየ፡ ወምድረ ። አድለቅለቀ፡ አድባር፡ እምኔሁ ። ርዕደት፡ ወአድለቅለቀት፡ ምድር ፤ ተገብሮ፡ (ዮኤ፪፡ ፲፯ ። ናሖ፩፡ ፭ ። መዝ፡ ፲፯) ።

**ድልቅልቅ** ፤(ቃት) ፤ ሁከት፡ ንውጽውጽታ ፤ ሽብር፡ ድብልቅልቅ ። አድለቅለቀ፡ ዐቢየ፡ ድልቅልቀ ። ወናሁ፡ ኮነ፡ ዐቢይ፡ ድልቅልቅ ። ወይከውን፡ ዐቢይ፡ ድልቅልቅ፡ ወረኀብ፡ በበ፡ ብሔሩ፡ (ግብ፲፮፡ ፳፮ ። ማቴ፳፰፡ ፪ ። ሉቃ፳፩፡ ፲፩) ።

**ዲሎሳን** ፤(ጽር፡ ዲሎሲስ ። ዕብ፡ ኡሪም) ፤ የበዓል፡ መብራቶች ፤ ለደስታና፡ ለክብር፡ የሚበሩ ። ቃላት፡ ነገራት፡ ክሊቅ፡ ክህናት፡ ልብስ፡ የሚሰሙ ። አልባስ፡ ተክህኖ፡ ሊቀ፡ ክህናት፡ ቃለ፡ እግዚ፡ ሲጠይቅ፡ የሚለብሳቸው ። ካህን፡ ዘይለብስ፡ ዲሎሳነ ። ልብሰ፡ ዲሎሳን፡ (ዕዝ፪፡ ፷ ። ፳፡ ፵) ።

**ድልት** ፤ (ድንት) ፤ ስመ፡ ፊደል፡ ራብዕ ፤ የግእዝ፡ አራተኛ፡ ፊደል፡ ደ ። ፍችውን፡ በዳሌጥና፡ በድንት፡ ተመልከት ።

**ደምዎ** ፤ **ዎት** ፤(ደመወ፡ ይዴሙ፡ ይደሙ) ፤ መድማት ፤ ደም፡ መኾን ፤ ደም፡ መልበስ ፤ መምሰል ።

**አድመወ** ፤ አደማ፡ አስደማ ፤ ደም፡ አደረገ ፤ በደም፡ በከለ ። አ፡ ሔዋን፡ ናሁ፡ ይበክያ፡ ሹሎን፡ አዋልድኪ ፤ ወይዴምዋ፡ በከመ፡ አድመውኪያ፡ አንቲ፡ ለእንትኩ፡ ዕፀ፡ (ቅዳ፡ አት) ።

**ደም** ፤(ማት ። ዕብ፡ ዳም ። ሱር፡ ድማ ። ዐረ፡ ደም) ፤ በቁሙ ፤ ቀይ፡ ፈሳሽ፡ ከሕያው፡ ከሥጋው፡ የሚገኝ፡ (ዘፍ፱፡ ፬—፮) ። ሥጋ፡ ወደም ። እምነ፡ ዘደም ። ደማቲሆሙ፡ ወደምየ ። በእንተ፡ ክዒወ፡ ደማቲሆሙ ። ርቱዕ፡ ንክዐው፡ ደማቲነ፡ በእንተ፡ ክርስቶስ፡ አምሰለ፡ ማየ፡ (ሚራ፲፬፡ ፲፫ ። ዮሐ፩፡ ፲፫ ። ዮሴፍ ። ፊልክ፡ ፲፴ ። አፈ፡ ተ፳) ። ዘር ፤ ወገን ። ተደምሮ፡ በደም ። ዘተርፈ፡ እምነ፡ ደሞሙ፡ ለእለ፡ ያርብሕ፡ (ፈ፡ መ፡ ፳፡ ፩ ። ኢያ፲፫፡ ፲፪) ።

**ደማዊ** ፤(ዊት፡ ውያን፡ ያት) ፤ የደም፡ ደማም፡ ደመ፡ ነፍስ፡ ያለው፡ ደም፡ የሚወጣው ፤ ደሙ፡ ሲያልቅና፡ ሲደርቅ፡ የሚሞት ፤ በባሕርና፡ በየብስ፡ የሚኖር፡ ሕያው፡ ሥጋው ፤ ተባዕት፡ ተንቀሳቃሽ፡ ያሙስና፡ ያርብ፡ ፍጥረት ፤ ለማግኛም፡ ፍጥረት፡ ይነገራል ። ደመ፡ አስካል ። ደመ፡ በለስ ። ደመ፡ ዕጕሥታር፡ (ዘፍ፵፱፡ ፲፩ ። መጽ፡ ምስ) ።

**ደመ፡ ኪዳን** ፤ የማዝረት፡ የመሥዋዕት፡ ደም ፤ ኪዳን፡ ስለ፡ ማጥናት፡ የሚፈስ ።

**ደመ፡ ነፍስ** ፤ የሰው፡ የንስሳ፡ ደም ፤ ከዕፀዋት፡ ደም፡ የተለየ ። በደም፡ የሚሣል፡ እንስሳዊ፡ አእምሮ ።

**ደመ፡ ሰማዕት** ፤ ስለ፡ ሃይማኖት፡ በግፈኞች፡ እጅ፡ የሚፈስ፡ የምእመናን፡ ደም ።

**ደመ፡ ትክቶ** ፤ የሴቶች፡ ግዳጅ ፤ ባሕርያዊ፡ ምንጭ፡ አበባ፡ በየወሩ፡ ፯፡ ፯፡ ቀን፡ የሚታይ ።

**ድምድማ ፤—ጕተና ፤—ደሚኅ ፡ ደምኅ ።**

**ደሚሕ ፤ ሖት ፤ ( ደምሐ ፡ ይደምሕ ፡ ይድማሕ ። ዕብ ፡ ዳማህ ፤ መሰለ ) ፤** መጥለቅ ፡ መስመጥ ፤ ወደ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፤ ጠልቆ ፡ ማወቅ ፡ መመርመር ። መቅዳት ፡ መጨለፍ ። **ኢታአምርኑ ፡ እግዚእ ፡ አልባበ ፡ ሰብእ ፡ ዘአንተ ፡ ትደምሕ ፡ ኅሊናነ ፡** (ተረ ፡ ቄርⷎ) ። ደምዐን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**መድምሕ ፤ ሕት ፤ ( ብ ፡ መዳምሕ ፤ ሕት ) ፤** መጥለቂያ ፡ መቅጃ ፡ መጨለፊያ ፤ ማጥሪያ ፤ ታናሽ ፡ ጻሕል ፤ መንካ ፡ ዕርፈ ፡ መስቀል ፡ የማእድና ፡ የምሂዐ ፡ መማሪያ ። **ወገብረ ፡ ንዋየ ፡ ማእድ ፡ አጽሕለ ፡ ወመደምሐ ። መደምሕት ፡ ዘቤተ ፡ ምሥዋዕ ። መጥዎተ ፡ ደሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ በመዳምሐ ፡ ወይን ፡ ዘውእቱ ፡ መንካ ፡** (ዘፀ፴፰ ፡ ፫፱ ። ፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፲፩ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ደምኅ ፤ ( ዐረ ፡ ደመኅ ፤ ኖኅ ) ፤** አደገ ፡ ላቀ ፤ ረዘመ ። አንጣ ፡ አቀና ፤ የጠጕር ፡ የራስ ።

**ድማኅ ፤ ( ኃት ) ፤** ራስ ፡ ጭንቅላት ፤ የራስ ፡ ቅል ፡ ቍብቍበ ፤ ክንንቱ ፡ በላይ ፡ ያለው ። (ግጥም) ፤ ዋርሳ ፡ እታግቡ ፡ ብሎ ፡ የገዘተ ፡ ማንው ፤ ዮሐንስ ፡ እንደኾን ፡ ክንንቱ ፡ በላይ ፡ ነው ፡ (መዝ ፡ ፷ ። ኩፋ ፡ ፳፪) ። **በከመ ፡ በካፊ ፡ እምሐፉረ ፡ ወይን ፡ እንተ ፡ ተዐርግ ፡ ዲበ ፡ ድማኁ ፡ ይሬእ ፡ ዘሉ ፡ ወኢየአምራ ፡** (ፈልክ ፡ ፶፯) ።

**—፤** በናት ፡ ማኽል ፡ ራስ ፤ የናላ ፡ ርግብግቢት ፡ ሜዳው ፡ ስጡሑ ፡ በስተላይ ፡ ያለው ፤ ለተራራና ፡ ለዛፍም ፡ ይኾናል ፡ (ሔኖ፳ ፡ ፯ ። ፲፰ ፡ ፰) ። **ሥዕርተ ፡ ድማኅ ፤** ቍንሮ ፡ ብርንገ ፡ ከብቶ ፡ በማኽል ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የሚበቅል ፡ የሚከበስ ፡ (ሕዝ ፡ ፰ ፡ ፫ ። ዳንⷎ ፡ ፴፯ ። ኢዮ፲፯ ፡ ፲፪) ።

**ድምድማ ፤ ( ማት ) ፤** ጕተና ፡ ጕፈሬ ፤ የራስ ፡ ጠጕር ፡ (ማሕ፩ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬) ። **ቈናዝዐ ፡ ወድምድማት ፡ ርእስ ፡** (አዋል) ። ማፍ ፡ መጨረሻ ፡ መደምደሚያ ፤ ክዳን ፡ ክፍክፋት ፤ ቍንሮ ፡ ጕልላት ። ድምድማት ፡ እንዲሉ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ደማሊ ፤ ( ጽር ፤ ዳማሊስ ) ፤** ጥጃ ፡ እንቦሳ ፤ በጥጃ ፡ አምሳል ፡ የተሠራ ፡ ጣዖት ። ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ የእንቦሳ ፡ ምስል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ የእንቦሳ ፡ ምስል ፡ ይሉታል ። **ወዘሉ ፡ ሕዝብ ፡ እለ ፡ ክሕዱ ፡ ሦዑ ፡ ለበዓል ፡ ወለደማሊ ፡** (ጦቢ፩ ፡ ፭) ።

**ደሚም ፤ ሞት ፤ ( ደመ ፤ ደመመ ፡ ይደምም ፡ ይድምም ። ዕብ ፡ ዳማም ) ፤** መድመም ፡ (ጥደ) መደመም ፤ መደነቅ ፡ መገረም ፤ መደንገጥ ፡ መፍራት ፤ ዝም ፡ ዕክም ፡ ጸጥ ፡ ማለት ፤ መፍዘዝ ፡ አፍን ፡ መያዝ ፤ የክፉ ፡ የበጎ ። (ድም ፡ ማለት ፤ መጮኽ ፡ መፈንዳት) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በደመ ፡ ፈንታ ፡ ተደመ ፡ ይላል ፤ ተ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። **አንከረ ፡ ወተደመ ። ታንክር ፡ ወትዴመም ። ተደሙ ፡ እምነ ፡ ሥና ። እንዘ ፡ ይዴመሙ ፡ ጥቀ ፡** (ዮሴፍ ። አፈ ፡ ተ፳፰ ። ዮዲ፲ ፡ ፲፱ ። ጥበ፲፱ ፡ ፫) ።

(ጥ) **ደመመ ፤ ( ይዴምም ፡ ይደምም ፤ ደምሞ ፤ ዐማርኛ ) ፤** ዘጋ ፡ መረገ ፤ ደፈነ ፤ መላ ፡ ቈለለ ፡ አስተካከለ ፤ ደመደመ ። የመቃብርና ፡ ያቀባበር ፡ ደምመው ፡ እንዲሉ ፡ ድፈነው ፡ አስተካክለው ፡ ሲሉ ። (ሙሾ ፤ መንኰሲት ፡ በወሊድ ፡ ሙታ ፡ ስትቀበር ፤ እኅቷና ፡ አክሥቷ) ፤ እንቺ ፡ ሞኝ ፡ እንቺ ፡ ሞኝ ፡ እንቺ ፡ ሞኝ ፡ ተላላ ፤ የኋላዉን ፡ በፊት ፡ የፊቱን ፡ በኋላ ። ያማወቷን ፡ ነገር ፡ ምን ፡ አጠያይቋችኹ ፤ እንዲያው ፡ ቅበሩ ፡ እንጂ ፡ እየደመማችኹ ።

**አድመመ ፤** አስደመመ ፤ አስደነቀ ፡ አስገረመ ፤ ዝም ፡ አሰኘ ። **አድመሞሙ ፡ ግብሩ ። ፈድፋደ ፡ ያደምመኒ ። ብርእየ ፡ መንክራት ፡ ዘታደምም ፡** (ዮሴፍ ። አፈ ፡ ተ፲፭ ። አረጋ ፡ ድ፯) ።

**መደምም ፤ ( ምት ፡ ማን ፡ ማት ) ፤** የሚያስደምም ፡ የሚያስገርም ፤ አስደናቂ ። ከርሠ ፡ መቃብር ፡ ታችኛው ፡ ውስጡ ፡ የሬሳው ፡ ቤት ። ሺዎች ፡ ግን ፡ መደንን ፡ ይሉታል ፤ ራስ ፡ የሚያስደንን ፤ ቀባሮችና ፡ አስቀባሮች ፡ በአድንኖተ ፡ ርእስ ፡ የሚያዩት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዐማርኛ) ።

**መድምም ፤ ( ማት ) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ቅጽልና ፤ ጥሬ ። እጅግ ፡ የሚደንቅ ፤ የሚደነቅ ፤ የሚያስደንቅ ፡ ታላቅ ፡ ድንቅ ፡ ግሩም ፤ ታምር ፡ አምላካዊ ፡ ግብር ። **መድምም ፡ ውእቱ ፡ ሥና ፡ ፈድፋደ ፡ ቅድሜሆሙ ። መድምም ፡ ኃይሉ ። እስመ ፡ መድምም ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ። ገበርከ ፡ ዘሉ ፡ መድምመ ፡ ዘመትሕተ ፡ ሰማይ ። በዘሉ ፡ መድምምየ ፡ ዘእገብር ። ዝኩ ፡ ቶአምር ፡ ወመድምም ፡ ዐቢይ ። መድምማት ፡** (ዮዲ፲ ፡ ፲፬ ። መላ፲፰ ፡ ፲፫ ። አስቴ፭ ፡ ፪ ። ፬ ፡ ፲ ። ዘፀ፫ ፡ ፳ ። ዘዳ፳፱ ፡ ፪ ። ቅዳ ፡ ኤጲ) ።

**ድማም ፤** ድንቅ ፤ ድንቂያ ፡ ዝምታ ፡ እንክሮ ። **ወተደመ ፡ ይሥሐቅ ፡ ዐቢየ ፡ ድማመ ፡** (ኩፋ ፡ ፳፮) ።

**ድመት ፤** መደመም ፡ መደነቅ ፤ አደናነቅ ፤ ድንቂያ ። ጩኽት ፡ ድምታ ፤ ድም ፡ ማለት ።

**ድመት ፤ ( ታት ። ዐረ ፡ ዲመት ። ጽር ፡ ኤሉሬ ) ፤** በቁሙ ፤ ብስ ፡ ብሴ ፤ ውር ፡ ውሮ ፡ የሚባል ፤ ታናሽ ፡ የቤት ፡ አውሬ ፡ ያይጦች ፡ ደመኛ ፤ ግርማው ፡ የሚደም ፡ የሚያስደምም ፤ ያንበሳ ፡ ወገን ፡ ዐዳኝ ፡ ወሮ ፡ በላ ። የዱር ፡ የባሕር ፡ ድመት ። **ደጐረ ፡ ድመት ። አና ብስት ፡ ክኑ ፡ ከመ ፡ ድመታት ። ወረውዎ ፡ ውስተ ፡ ማዕበለ ፡ ባሕር ፤ ከመ ፡ ይብልዕዎ ፡ ዓሣት ፡ ወዐናብርት ፡ ወድመታት ፡** (መ ፡ ፈ ። ስንክ ፡ መጋ፳፫ ። ጥቅ፯) ።

**ደማሚት ፤ ( ደማሚ ፡ ምያን ፡ ያት ) ፤** በቁሙ ፤ የሚደም ፡ የሚጮኽ ፡ ድም ፡ የሚል ፡ ባሩድ ። ደማሚት ፡ የቤት ፡ እንቅጽ ፡ ነው ፤ ስዱስ ፡ ብሎ ፡ ስድስት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ደምኖ** ፤ **ኖት** ፤ (**ደመነ ፡ ይዴምን ፡ ይደምን ፤ ደምሰ ። ዕብ ፡ ዳሜን ፤ ዘበለ**) ፤ መዳመን ፡ መጥቈር ፡ መጨለም ፤ ደመና ፡ መምሰል ፤ ደመና ፡ መልበስ ፤ በጉም ፡ መታፈን ፡ መሸፈን ። እምከመ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ እዝኑ ፡ ሰሰብእ ፡ ነገረ ፡ ሕሡም ፡ ይዴምን ፡ ገጽ ። ፀሓየ ፡ ጽድቅ ፡ ዘኢይዴምን ። ጸዳል ፡ ዘኢይዴምን ። መጽሔት ፡ እንተ ፡ ኢትዴምን ፡ (ቀሌ ። ቄር ። አፈ ፡ ተ፱ ። ጥበ፯ ፡ ፳፯) ።

**ድሙን** ፤ (**ናን ፡ ናት ፡ ምንት**) ፤ የዳመነ ፡ የጨለመ ፡ የጠቈረ ፤ ጥቍር ። ያቅየሐይሕ ፡ ሰማይ ፡ ድሙን ። ከነ ፡ ገጹ ፡ ድሙነ ፡ ወሕብሩ ፡ ጽምሑየ ፡ (ማቴ፲፮ ፡ ፫ ። ፊልክ ፡ ፻፶፬) ።

**ድማኔ** ፤ መደመን ፡ አደማመን ፤ ድመና ፡ ጥቍረት ፡ ጨለማ ። ሰማይ ፡ ንጽሕት ፡ ይእቲ ፡ ወኢይረክባ ፡ ርስሐት ፡ ወኢድማኔ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፯) ።

**ደመና** ፤ (**ናት**) ፤ በቁሙ ፤ ከርጥብ ፡ ምድር ፡ የሚወጣ ፡ ጢስ ፡ ላበት ፤ ተሰብስቦ ፡ ክጠፈር ፡ በታች ፡ በጎዋ ፡ የሚታይ ፤ ጠፈርን ፡ የሚሸፍንና ፡ የሚጋርድ ። ደመና ፡ ዐቢይ ። ደመና ፡ ሰማይ ። ደመና ፡ ዝናም ። ደመናት ፡ ያውሕዙ ፡ ጠላተ ፡ (ሕዝ ፡ ፩ ፡ ፬ ። ዳን፯ ፡ ፲፫ ። ሚራ፴፪ ፡ ፳፯ ። ምሳ፫ ፡ ፳) ።

—፤ ብዙ ፤ ብዛት ፡ መዐት ። ደመና ፡ ቋዓት ። ደመና ፡ ዘናቢር ፡ ወትንንያ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፩ ። ስንክ ፡ ጥር፲፰) ።

**ደመንሚን** ፤ ጨለማ ፡ ድማዝታ ፤ ምሼት ፡ ማታ ፤ የጉም ፡ ያፈና ፡ ጊዜ ፡ ቦታ ፤ የማይታይ ። ዝ ፡ ነገር ፡ ደመንሚን ፡ ይመስል ፡ ለብዙኃን ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፱) ።

**አደመነ** ፤ አጨለመ ፡ አጠቈረ ፡ አሳዘነ ። እፎ ፡ አደመና ፡ እግዚ ፡ ለወለተ ፡ ጽዮን ። ያዴምኖ ፡ ለገጽ ፡ ከመ ፡ ጸሊሎ ፡ መቅፀት ። ብእሲት ፡ መንጐርጐርት ፡ ታዴምን ፡ ገጾ ፡ ምታ ፡ (ሰቈ፪ ፡ ፩ ። አርጋ ፡ ፪ ፡ ፈላስ) ።

**ደምዐ** ፤ (**ደምዐ** ፤ **ትግ ፡ በጨበጣ ፡ ወጋ ። ዕብ ፡ ዳማዕ ፤ አነባ**) ፤ ቆሎ ፡ አገኘ ፤ በቆሎ ፡ ዐወቀ ፤ የሰውን ፡ ልብ ፡ ምስጢርና ፡ ሐሳብ ። ደምዐና ፡ ደምሐ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በደምዐ ፡ ፈንታ ፡ አድምዐ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ሲወጉና ፡ ሲያገኙ ፡ ደምና ፡ እንባ ፡ በቆሎ ፡ እንዲገኝ ፤ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። ኢያደምዕ ፡ ፍትወተ ። ቢደኃሪ ፡ ያደምዑ ፡ ኀይለ ፡ እምጸጋ ። እመሰ ፡ አድምዐተከ ፡ ኢታወፅአከ ። ጽዕልት ፡ ብእሲት ፡ ለእመ ፡ አድምዐት ፡ ብእሴ ፡ ኄረ ፡ (ኢዮ፳ ፡ ፳ ። ፊልክ ፡ ፹፫ ። ሚራ፳፩ ፡ ፪ ። ምሳ፳፱ ፡ ፶፰) ።

**አድምዐ** ፤ አስገኘ ፡ አስመረመረ ፡ በቆሎ ፡ እንዲገኝ ፡ አደረገ ።

**ደሚፅ** ፤ **ፆት** ፤ (**ደምፀ ፡ ይደምፅ ፡ ይድምፅ ። ዕብ ፡ ሻሜጽ ፤ ሰደበ ፡ አሽሟጠጠ**) ፤ መድመፅ ፡ መሬኘት ፤ ድምፅ ፡ መስጠት ፤ መሰማት ፡ መደመጥ ፡ ድምጣም ፡ መኾን ። (መዳመጥ ፡ መርገጥ ፡ መደፋጠጥ ፤ መራመም ፡ መፈግፈግ) ። ይደምፅ ፡ ማዕበሉ ። ዘእንበለ ፡ ይድምፅ ፡ ነጐድጓድ ። በቃለ ፡ አሚን ፡ ወበትፍሥሕት ፡ ደምፁ ። ደምፀ ፡ ወተሰብከ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ (ኤር፳ ፡ ፳፪ ። ቡቱ ፡ ሰገ፱ ፡ ፳ ። መገ ፡ ማ፩ ። ድጓ) ።

**ድሙፅ** ፤ (**ፃን ፡ ፃት ፡ ምዕት**) ፤ የተሰማ ፡ የተደመጠ ፤ ጢኺ ፡ ድምጣም ፡ (ስንክ ፡ ሐም፲፰) ።

**ድምፅ** ፤ (**ፃት**) ፤ በቁሙ ፤ ድምጥ ፡ ጓታ ፡ ጩኸት ፡ አጢጪኽ ፤ የጩኸት ፡ ቃል ። ድምፅ ፡ ተሰሚው ፡ ቃል ፡ ፍሬው ። ሰማዕኩ ፡ ድምፀ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ከመ ፡ ድምፀ ፡ ማይ ፡ ብዙኅ ። ድምፀ ፡ አራዊት ። ድምፀ ፡ ጸሎት ፡ ሐዋዝ ። ድምፀ ፡ ንባቢሆሙ ። ድምፃት ፡ መደንግፃት ፡ (ሕዝ፩ ፡ ፳፬ ። ስንክ ፡ ማያ፲፯ ። ጥቅ፯ ። ጥበ፩ ፡ ፲፱ ። ፊልክ ፡ ፻፲፯) ።

**አድመፀ** ፤ አስሬኘ ፡ አሰማ ፤ አስደመጠ ። (አስዳመጠ ፡ አስራመመ) ። አነ ፡ እግዚ ፡ ዘአደምፆ ፡ ለማዕበላ ። እማት ፡ ያደምፃ ፡ ቃለ ፡ ለቊቃው ። ሰብሔረ ፡ እግዚ ፡ አድያሚሃ ፡ አድመፅከ ፡ (ኢሳ፶፩ ፡ ፲፭ ። ጥበ፲፰ ፡ ፲ ። ድጓ) ።

**መድመፅ** ፤ በቁሙ ፤ መዳመጫ ፡ መራመሚያ ፤ የደንጊያ ፡ የገል ፤ ሲዳምጥ ፡ ድምጥ ፡ የሚሰጥ ።

**ደሚቅ** ፤ **ቆት** ፤ (**ደመቀ ፡ ይደምቅ ፡ ይድምቅ ። ዐረ ፡ ደመከ ፡ ቀ**) ፤ መጨፍለቅ ፡ መሰበር ፡ ማድቀቅ ፤ መቀጥቀጥ ፡ መፍጨት ፤ መምታት ፡ መግጨት ፡ (ማቴ፳፩ ፡ ፵፬ ። ኢሳ፵፩ ፡ ፲፯) ። ደመቀቶ ፡ መልታሕቶ ። በውግረተ ፡ እብን ፡ ደመቁ ፡ ሥጋሁ ። እብን ፡ ለእብን ፡ ሶበ ፡ ይደምቆ ፡ ይወፅእ ፡ እሳት ፡ (መሳ፳ ፡ ፳፯ ። ስንክ ፡ ጥቅ፴ ። አፈ ፡ ድ፲፱) ። በቁሙ ፤ መድመቅ ፡ ማማር ፤ የልብስ ፡ የግምጃ ። (ተረት) ፤ ማቅ ፡ ይሞቃል ፤ ሸሽ ፡ ይደምቃል ፤ ገቢውን ፡ ባለቤት ፡ ያውቃል ።

**ድሙቅ** ፤ የደመቀ ፡ ደማቅ ፤ ቀለሙ ፡ ዕዳያቱ ፡ ጽዕዳዊው ፡ ቅላቱ ፡ ክሩቅ ፡ የሚታይ ። ወይትኄጣእ ፡ ቅድው ፡ ወድሙቅ ፡ አልባስ ፡ (ፍካሬ ፡ እየስ) ።

**ድምቀት** ፤ መድመቅ ፡ አደማመቅ ፤ የማሕሌት ፡ የዘፈን ። ምስጢሩ ፡ ልብሱን ፡ አይለቅም ፤ ሲዘምሩና ፡ ሲዘፍኑ ፡ ለብሰው ፡ አጊጠው ፡ ነውና ።

**ደመቅ** ፤ ድቃቂ ፡ ስባሪ ፡ እንክትካች ። ወትገብር ፡ ደቃቀ ፡ ወደመቀ ፡ (ኢሳ፵፩ ፡ ፲፱) ።

**ደምሮ** ፤ **ሮት** ፤ (**ደመረ ፡ ይዴምር ፡ ይደምር ፤ ፀመረ ። ዐረ ፡ ደመረ ፤ ገባ**) ፤ መደመር ፡ መጨመር ፡ ማግባት ፤ መግጠም ፡ ማገናኘት ፤ ማዋሐድ ፡ አንድ ፡ ማድረግ ፤ መቀላቀል ፡ መደባለቅ ። ትደምር ፡ ኆጻዳተ ፡ ውስተ ፡ መማሥጥ ። ኢትደምሩ ፡ ዕጣነ ፡ ዘካልእ ፡ ቅታሬሁ ። ደምር ፡ አዕጻደ ፡ አሐተ ፡ ምስለ ፡ ካልእታ ። ደመረ ፡ ሥጋነ ፡ ምስለ ፡ መለኮቱ ። ይዴምሩ ፡ ደመ ፡ ምስለ ፡ ደም ። ኢትደምር ፡ ንዋየከ ፡ ምስለ ፡ ዘይኄይሰከ ። ሥላሳ ፡ ወአሐዱ ፡ ወዕሥራ ፡ ወተስዐቱ ፡ ለእመ ፡ ደመርከ ፤ ክል

ኢሆመ ፡ ይክውኑ ፡ ስሳ ፤ (ዘፀ፳፰ ፡ ፲፩ ። ፴ ፡ ፱ ። ፳፯ ፡ ፮ ። ዮሴ ። ሆሴ፬ ፡ ፱ ። ሚልኪ፫ ፡ ፪ ። አቡሻ ፡ ፲፩) ።

**ደማሪ ፤ መደምር** ፤ በቁሙ ፡ የሚደምር ፡ የሚጨምር ፤ አዋሓጅ ፡ ቀላቃይ ።

**ተደመረ** ፤ በቁሙ ፤ ገባ ፡ ተጨመረ ፤ አንድ ፡ ኾነ ፡ ተዋሐደ ፤ ገጠመ ፡ ተገናኘ ። ኢይደሜመር ፡ ኀጺን ፡ ምስለ ፡ ልሕኵት ። ኤፍሬም ፡ ተደመረ ፡ ምስለ ፡ አሕዛብ ። እምክልኤቱ ፡ ህላዌ ፡ ተደመረ ፡ አሐዱ ፡ ክርስቶስ ። አንትሙ ፡ ይደመሩ ፡ ምስለ ፡ አዋልደ ፡ ሰብእ ፤ (ዳን፪ ፡ ፵፫ ። ሆሴ፯ ፡ ፰ ። ቄር ። ክፋ ፡ ፱) ።

**ተዳመረ** ፤ ተገናኘ ፡ ተጣመረ ። በተዳመረ ፡ ፈንታ ፡ ተደማመረ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ተባዕት ፡ ወአንስት ፡ ዘይደማመሩ ፤ (ፊልክ ፡ ፻፶፰) ።

**ድሙር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ምርት)** ፤ በቁሙ ፡ የተደመረ ፡ ድምር ፡ ጭምር ፡ ቅልቅል ። ኀጺን ፡ ድሙር ፡ ምስለ ፡ ልሕኵት ። ኢኮኑ ፡ ድሙራነ ፡ ዝንቱ ፡ ምስለ ፡ ዝንቱ ። ባሕር ፡ ድምርት ፡ በእሳት ፤ (ዳን፪ ፡ ፵፩ ፡ ፵፫ ። ራእ፲፭ ፡ ፪) ።

—፤ የቍጥር ፡ ስም ፤ አንድነት ፡ ጅምላ ። ወክነ ፡ ኵሉ ፡ ድሙር ። ወድሙር ፡ ኵሉ ፡ ንዋዮሙ ፤ (ነሐ፯ ፡ ፷፮ ። ግብ፪ ፡ ፵፩) ።

**ድማሬ ፤ (ሬያት)** ፤ መደመር ፤ (ጥይ) መደመር ፡ አደማመር ፡ ድመራ ፡ ደመራ ። ኅብረት ፡ አንድነት ፤ ተዋሕዶ ። ህበነ ፡ ለኵልነ ፡ ድማሬ ። እንዘ ፡ ኢይዜሮ ፡ እምድማሬሁ ። ድማሬ ፡ ዘህላዌ ፡ ጽድቅ ፤ (ኪዳ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ቄር) ።

—፤ መቀላቀል ፤ (ጥቀ) መቀላቀል ፤ አቀላቀል ፡ ቅልቀላ ፡ ድብለቃ ፡ ቅልቅልነት ። ኢድማሬ ፡ ህላውያት ፤ የባሕርያት ፡ አለመቀላቀል ፤ (ሃይ ፡ አበ) ።

**ትድምርት** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ጋብቻ ፡ ሩካቤ ፡ ሰምረት ፡ ተዋሕዶ ፡ አንድነት ፤ (ጥቀ) መቀላቀል ፤ ቅልቅልነት ። ለበጎም ፡ ለክፉም ፡ ይነገራል ፤ ሰምረት ፤ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ተዋሕዶ ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ መለኮት ፡ እንደ ፡ ትስብእት ፤ አንድነት ፡ ለኹሉም ፡ ይኾናል ። መቀላቀል ፡ እንደ ፡ ዶቄትና ፡ እንደ ፡ ዶሮት ፡ እንደ ፡ ሞራና ፡ እንደ ፡ መሬት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ መንጋና ፡ እንደ ፡ መንጋ ። ትድምርት ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ። ነፍሱ ፡ እንተ ፡ ለብሳ ፡ በትድምርት ። ዘእንበለ ፡ ቱስሕት ፡ ወኢትድምርት ። ይትዐቀቡ ፡ እምትድምርት ፡ እኩያን ፡ ሰብእ ። ይሰደዱ ፡ እምትድምርት ፡ ምእመናን ፤ አንድነት ፡ ሱታፌ ፡ ኅብረት ፤ (ዲድ ፡ ፴፫ ። ቄር ። ቅዳ ። ዲድ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፩) ። ለቍጥርም ፡ ይኾናል ፤ (አቡሻ ፡ ፲፩) ።

**ደመራ ፤ ድምር ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፡ የበዓለ ፡ መስቀል ፡ ዋዜማ ፤ ዕንጨቶች ፡ የሚደመሩበት ።

**ደሚስ ፤ ሶት ፤ (ደምሰ ፡ ይደምስ ፡ ይድምስ ። ዐረ ፡ ደመሰ ። የደመነ ፡ ሞክሼ)** ፤ መጥቈር ፡ መጨለም ፡ መክበድ ።

**ድሙስ** ፤ ጥቍር ፡ ጠቋራ ፡ ጽልመታዊና ፡ ቅላት ፡ የሌለው ። ብድሙስ ፡ ሰማይ ፤ ሰብሩህ ፡ ሰማይ ፤ (ቄድር) ።

**ደምሰሰ ፤ (ተቀ ፡ ማ)** ፤ በቁሙ ፡ ደመሰሰ ፡ አጠፋ ፡ አበላሸ ፡ ፋቀ ፡ ሠረዘ ፤ ደቀቀ ፡ አለ ፤ የጥፈት ፡ የሥዕል ፡ የማኅተም ። ወደምሰሰ ፡ ኵሎ ፡ ዘጽሑፍ ፡ ውስቴታ ፡ ለይእቲ ፡ ክርታስ ። አነኬ ፡ ዘእደመስሶን ፡ ለኃጣውኢከ ። ወደምሰሰ ፡ ሰነ ፡ መጽሐፈ ፡ ዕዳነ ። ደምስሰ ፡ አሠርየ ፤ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፪ ። ኢሳ፵፫ ፡ ፳፭ ። ቈላ፪ ፡ ፲፬ ። ኢዮ፴ ፡ ፲፫) ።

**ደምሳሲ ፤ መደምስስ** ፤ የሚደመስስ ፡ ደምሳሽ ፡ አጥፊ ። እግዚ ፡ ደምሳሴ ፡ አበሳየ ። መልአከ ፡ መደምስስ ፤ (ቄድር ። ቅዳሴ ፡ ፳፩ ፡ ፲፫) ።

**ተደምሰሰ** ፤ ተደመሰሰ ፡ ተፋቀ ፡ ጠፋ ፡ እንዳልነበረ ፡ ኾነ ። ይደመስሱ ፡ እመጽሐፈ ፡ ሕይዋን ። ኢይደመሰስ ፡ ነገርየ ፡ እምልብክሙ ። ብዕል ፡ ዘይዘገብ ፡ በዐመፃ ፡ ይደመሰስ ። በእንተ ፡ ተደምስሶቱ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፤ (ክፋ ፡ ፴ ። ሔኖ፺፱ ፡ ፳ ። ኢዮ፳ ፡ ፲፭ ። ዕር ፡ ኢሳ ፡ ፳) ። ተቃተሉ ፡ ተጋብኡ ፡ ተጣፍኡ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተደምሰሱ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ተደምሰሱ ፡ በበይናቲሆሙ ፤ (ዮሴፍ) ።

**ድምሱስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ስስት)** ፤ የጠፋ ፡ የተደመሰሰ ፡ ድምስስ ፡ ያለ ፡ ዐይን ፡ የሌለው ።

**ድምሳሴ** ፤ ማጥፋት ፡ መደምሰስ ። መጥፋት ፡ መደምሰስ ፤ አጠፋፍ ፡ ጥፋት ። ደመ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘይትከዐው ፡ ለድምሳሴ ፡ ኃጣውአ ፡ ዓለም ። ድምሳሴ ፡ እደመስሶሙ ። ድምሳሴ ፡ ኃጥኣን ፡ ሰብእ ። ማየ ፡ ድምሳሴ ፤ (መጽ ፡ ምስ ። ዘፀ፲፯ ፡ ፲፬ ። ፪ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፮) ።

**ደማስቆ ፤ (ሰብ ፡ ዳሜሴቅ)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ የአራም ፡ መዲና ፤ ደማስ ፡ ግምኛ ፡ የሚሠራበት ፡ የሐርና ፡ የዐምር ፡ የልብስ ፡ የፈትል ፡ አገር ። አምሳለ ፡ ሠቅ ፡ በዓለ ፡ ሠቅ ፡ ማለት ፡ ነው ። ማየ ፡ ደም ፡ አምሳለ ፡ ፍሕም ፡ የሚሉም ፡ አሉ ፤ (፩ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፳፬) ።

**ድመት ፤—በቁሙ ፤—ደሚም ፡ ደመመ ።**

**ዳን ፤—ስመ ፡ ነገድ ፤—ደይኖ ፡ ደየነ ።**

**ዳንኤል ፤ (ሰብ ፡ ዳኒኤል)** ፤ ስመ ፡ ሰብእ ፤ ጻድቅ ፡ ነቢይ ፡ ፈላስፋ ። አምላክ ፡ ደያኒየ ፡ መደይንየ ፡ የሚፈርድል(ብ)ኝ ፡ ፈራጄ ፡ ዳኛዬ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ (ዳን፩ ፡ ፮ ። ሕዝ፲፬ ፡ ፲፬ ። ፳፰ ፡ ፫) ። ደየነን ፡ እይ ።

**ድንባዝ ፤ (ዛት ። ድ ፡ ንባዝ ፤ ነበዘ)** ፤ መጸር ፡ ምዝባል ፤ መሶጊያ ፡ ወፍራም ፡ ደጋፍ ፡ ደልዳላ ፤ እንደ ፡ ዐርፍና ፡ እንዳልጋ ፡ ዘንግ ፡ እንደ ፡ ሸማኔ ፡ መጠቅለያ ፡ ያለ ፡ የወሰከ ፡ ዕንጨት ፡ የሳንሳ ፡ የሚያዙበት ፤ የታቦት ፡ ጽዋን ፡ መሸከሚያ ፤ (ዘፀ፳፭ ፡ ፲፫—፲፭) ። የመሰንቆና ፡ የበገና ፡ የክራር ፡ ዕንጨት ፤ (፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፲፩) ።

ዘሩ ፡ ነበዘ ፡ ነው ፡ ሕንጻ ፡ ድሕንጻ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ ንብዝም ፡ ድንባገ ፡ ተብሎ ፡ ወደዚህ ፡ መጥቷል ፡ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ደንበዘ ፡ ደንፈ ፡ ብለው ፡ ደገሱና ፡ ድንባዝ ፡ ባላ ፡ ድጋፍ ፡ ወጋግራ ፡ ይላሉ ።

**ድንብዕኵል** ፤—ያንበሳ ፡ ቀፎ ፤—ድብዕኵል ።

**ደንበር** ፤ (ትግ ፤ ክንፍ ፡ ላባ ፡ ቍንጮ) ፤ በቁሙ ፡ ወሰን ፡ ዳርቻ ፡ ጽንፍ ፡ ሓፍ ፡ (በማርኛ) ። ደንበረ ፡ ተደናበረ ፡ ደንባራ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ድንቡስ** ፤—ችንክር ፡ ሽበ ፤—ድቡስ ።

**ደንገገ** ፤ (ደገገ ፤ ደግደገ) ፤ ደነገገ ፡ ወሰነ ፡ ፀገገ ፤ ገደበ ፡ ወደበ ፤ የሕግ ፡ የፈለግ ።

**ተደንገገ** ፤ ተደነገገ ፡ ተወሰነ ፡ ተወደበ ። ስፍሕት ፡ በሥለሄ ፡ ዘኢትደነገግ ፡ (አትና) ።

**ድንጉግ** ፤ (ጋን ፡ ጋት ፡ ግግት) ፤ የተወሰነ ፡ የተደነገገ ፤ ውሱን ። ኢድንጉግ ፡ መለኮቱ ፡ በግብረት ፡ ዓለም ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ድንጋጌ** ፤ ውሳኔ ፡ አወሳሰን ፡ ውስና ። ወሰን ፡ ደንበር ፤ አሸዋ ፡ ደንጊያ ። ባሕረ ፡ ውቅያኖስ ፡ ውሱን ፡ በድንጋጌሁ ፡ (አርጋ ፡ ፪) ።

**ድንጋግ** ፤ ዳርቻ ፡ ዳር ፤ ወሰን ፡ ደንበር ፤ ወደብ ፡ ገደብ ፤ አፋፍ ፡ ጠረፍ ። ሞጺ ፡ ዘድንጋግ ፡ ባሕር ። አልቦ ፡ ድንጋግ ፡ ለባሕረ ፡ ጥበቡ ። ወሚጠኒ ፡ ኀበ ፡ ድንጋገ ፡ ፈለግ ። ኀበ ፡ ድንጋገ ፡ ማይ ፡ (ዘፍ፴፪ ፡ ፲፯ ። ቅዳ ፡ ኢ.ጲ. ። ሕዝ፵፯ ፡ ፯ ። ሚራ፳፬ ፡ ፲፬) ።

**ደንገዘ** ፤ (ደነዘ ፤ ደንዘዘ) ፤ አረጀ ፡ ደከመ ፡ መሸ ፡ ፊሰመ ፡ (በማርኛ) ።

**ደንጎዘ** ፤ ሠረ ፡ ቈነነ ፤ ጐቸ ፡ ጐነጐነ ፤ ከፈለ ፡ ፈተለ ፤ ቈነጣጠረ ።

**ድንጉዝ** ፤ (ዛት) ፤ የጭራ ፡ የጠጕር ፡ ሥራ ፤ ቍንናት ፤ ያሠራሩ ፡ ዐይነት ፤ የሥራው ፡ ስም ። ጕቾ ፡ ብርንን ፡ ቍንጥርጥር ፤ እንደ ፡ ማህሌ ፡ ሥላሴ ፡ ጠጕር ። (ማጥም ፡ መጥፎ ፡ ተንሳሐ ፡ ጠጠቱ ፡ የደሁዳን ፡ ጠጠት ፡ የመሰለ) ፡ የወንድሜ ፡ ራሱ ፡ ጕተናመ ፡ አማሪ ፡ እኔም ፡ ባልተሠራኹ ፡ ይሻለኝ ፡ ነበረ ። ድንጉዛት ፡ (ፍ፡ ፡ ነ ፡ ፶፩) ።

**ደንጎላ** ፤ (ላት ። ዕብ ፡ ሐባጺሌት) ፤ የዱር ፡ የበረሓ ፡ ሽንኵርት ፡ በቁላ ፡ በደጋ ፡ የሚበቅል ፡ የኽብ ፡ ሽንኵርት ፡ ዐይነት ፡ መልክም ፡ አበባ ፡ የሚሰጥ ፤ አበባው ፡ መረዋ ፡ ቃጭል ፡ የሚመስል ፡ ጥሩ ፡ ሽታ ፡ ያለው ። ጽጌ ፡ ደንጎላት ፡ ዘውስተ ፡ ቈላት ። ወከመ ፡ ጽጌ ፡ ደንጎላት ፡ በማእከለ ፡ አሥዋክ ፡ (ማሕ፪ ፡ ፩ ፡ ፪) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ማእከለ ፡ አሥዋክን ፡ ሲያዩ ፡ ሱፍ ፡ ይሉታል ፡ ፍችው ፡ አይደለም ።

**ደንገለ** ፤ (ዐረ ፡ ደገለ ፤ ሸሸገ ፡ ደበቀ) ፤ ደነገለ ፡ አጥብቆ ፡ ጠበቀ ፡ ከለከለ ፡ ከሴት ፡ አራቀ ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ። የደንጎላ ፡ ምስጢር ፡ አብዝቶ ፡ አለማፍራት ፡ ነውና ፡ ደንገለም ፡ የደንጎላ ፡ ዘር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ይህን ፡ ያሳያል ። እምአይቴ ፡ ረከብከ ፡ ዘከመ ፡ ዝ ፡ ብሥራት ፤ እንበለ ፡ ዘርዐ ፡ እምድር ፡ እትወተ ፡ ወእንበለ ፡ ምት ፡ እምድንግል ፡ ፀንሰተ ፡ (ድጓ) ።

**ተደንገለ** ፤ ተደነገለ ፡ ድንግል ፡ ኾነ ፡ ተጠበቀ ፡ ተጠንቀቀ ። ወለነፍሳትኒ ፡ እለ ፡ ተደንገላ ። ተደንግሎ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ ለመኑ ፡ ተውህበ ፡ (አፈ ፡ ተሸ፰ ። ደራሲ) ።

**ድንጉል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ግልት) ፤ የደነገለ ፡ የተደነገለ ፡ ድንግል ፡ ጥብቅ ፡ ሴት ፡ የማያውቅ ። ቅድስት ፡ ወብፅዕት ፡ ወድንግልት ፡ ኢዮጸራቅስያ ። ነበርኪ ፡ ድንግልተ ። ደቂቅት ፡ ድንግልት ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳፯ ። አርጋ ፡ ፬ ። ፈልክ ፡ ፶፰) ። ባማርኛ ፡ ግን ፡ ድንጉል ፡ ላ ፤ የንብ ፡ ውሃ ፡ ቀጆ ፤ ያልተሰነጋ ፡ ፈረስ ፡ ማለት ፡ ነው ። ክበገና ፡ አውታርም ፡ አንዱ ፡ ድንጉል ፡ ይባላል ።

**ድንግል** ፤ (ብ ፡ ደናግል) ፤ በቁሙ ፡ ጥሬ ፡ ቅጽል ፤ ፍችው ፡ እንደ ፡ ድንጉል ፡ ነው ። ዮሐንስ ፡ ድንግል ። አሞንዮስ ፡ ድንግል ። አባ ፡ ኖብ ፡ ድንግል ፡ (ድጓ ። ፈልክ ። ቅዳ) ። ቅጽልነቱና ፡ ስምነቱ ፡ የወንድ ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጣሮች ፡ ስሕተት ፡ ለወንድም ፡ ለሴትም ፡ ያደርገዋል ። ብእሲት ፡ ድንግል ። ወለት ፡ ድንግል ። ወለማ ፡ ለይእቲ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ (ዘሌ፳፩ ፡ ፲፫ ። ዘዳ፳፪ ፡ ፳፫ ። ሉቃ፩ ፡ ፳፯) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ብእሲ ፡ ድንግል ፡ ወብእሲት ፡ ድንግልት ፡ ብሎ ፡ ይለያል ፡ (ፍ፡ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፳) ።

**ደናግል** ፤ ድንግሎች ፡ ደናግሎች ፡ የወንድ ፡ የሴት ፤ ጕብዛገት ፡ ቈንጃጅት ፡ ያልዳሰሱ ፡ ያልተዳሰሱ ። ደናግል ፡ ወመንከሳት ። በእንተ ፡ ደናግል ፡ ዐደው ። ደናግል ፡ ንጹሓን ፤ ወንዶች ፡ (ቅዳ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፯ ። አርጋ ፡ ፭) ። ደናግል ፡ አፍቀራከ ። አዋልድ ፡ ደናግል ። ወራዙትኒ ፡ ወደናግል ። ዐሥሮን ፡ ደናግል ፡ (ማሕ፩ ፡ ፫ ። መሳ፳፩ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፻፵፰ ። ማቴ፳፭ ፡ ፩) ።

**ድንጋሌ** ፤ መደንገል ፡ ድንገላ ፡ ጥበቃ ፡ ድንግልና ። ድንጋሌ ፡ ሥጋ ። ኅይለ ፡ ድንጋሌሁ ። መሀሮሙ ፡ ለደናግል ፡ በእለ ፡ ኢያውሰቡ ፡ ከመ ፡ ይዕቀቡ ፡ ድንጋሌሆሙ ፡ ከመ ፡ ብንተ ፡ ዐይን ፡ (አፈ ፡ ተሸ፰ ። ስንክ ፡ መጋ፲፪ ። ቀሌ) ።

**ድንግልና** ፤ በቁሙ ፡ ድንግልነት ፡ ድንግል ፡ መኾን ፡ ክብርና ፡ ማኅተመ ፡ ሥጋ ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ። በእንተ ፡ ምታ ፡ ዘድንግልናሃ ። አርከሰ ፡ ድንግልናሃ ። ዮሐንስ ፡ ቅኑት ፡ በድንግልና ። ዐቀበ ፡ ኖኅ ፡ ርእሶ ፡ በድንግልና ፡ ኀምስተ ፡ ምእተ ፡ ዓመተ ፡ (ዮኤል፩ ፡ ፰ ። ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፱ ። ድጓ ። ቀሌ) ።

**ድንግልናዊ** ፤ ድንግላይነት ፡ ድንግላይ ፡ ባለድንግልና ። በዓለ ፡ ልደት ፡ ድንግልናዊ ። እም ፡ ድንግልናዊት ፡ (አቡሻ ፡ ፴፱ ። አርጋ ፡ ፪) ።

**ደንገፀ** ፤ ጸ ፡ (ደጎጸ ፤ ደነጸ) ፤ ደነገጠ ፡ ፈራ ፡ ተንቀጠቀጠ ። ምስጢሩ ፡ ልብን ፡ በፍርሀት ፡ መድ

ጉጽ ፡ መንካት ፡ ነው ፡ ከማየት ፡ ከመስማት ፡ የተነሣ ። ኵሉ ፡ ነፍስ ፡ ይደነግፅ ። ደንገፀኒ ፡ ነፍስየ ። ይደነ ግፅ ፡ ልብኪ ። ደንገፁ ፡ በበይነ ፡ ዘኮነ ፡ (ኢሳ ፲፫ ፡ ፯ ። ፳፩ ፡ ፬ ። ፳ ፡ ፭ ። የዳ ፲፭ ፡ ፭) ።

—፤ ራጎኘ ፡ አስተጋባ ፡ ተሠነጠቀ ፡ የምድር ፡ የተራራ ። ድንገፀት ፡ ምድር ፡ እምቃሎሙ ። ወይደነግፁ ፡ አ ድባር ፡ ነዋኃት ፡ (፪ነገ ፡ ፳ ፡ ፵ ። ፩ነገ ፡ ፬ ፡ ፭ ። ሔኖ ፩ ፡ ፯) ።

**ድንጉፅ ፤ (ፃን ፡ ፃት ፡ ግፅት) ፤** የደነገጠ ፡ ድንጉጥ ፡ ፈሪ ፡ ፍሩት ፡ የያዘው ፡ ያፈዘዘው ። ሀሎኩ ፡ ድንጉፀየ ። ኀሰፉ ፡ ድንጉፃኒሆሙ ። አህጉር ፡ ድንጉ ፃት ። ንበሪ ፡ ድንግፅተኪ ፡ (ሱቱ ፡ ፅገዘ ። ኤር ፱ ፡ ፲ ። ኢሳ ፲፱ ፡ ፴፩ ። ማ፯ ፡ ፭) ።

**ድንጋፄ ፤** በቁሙ ፡ መደንገጥ ፡ አደናጋገጥ ፤ ድን ጋጤ ፡ ፍራት ። ድንጋጤ ፡ የልብ ፡ የልቡና ፡ ፍራት ፡ ያን ጎል ፡ የናላ ። ያመጽእ ፡ ድንጋፄ ፡ ላዕለ ፡ አሕዛብ ። ፀቢይ ፡ ድንጋፄ ፡ አንዘሙ ። ድንጋፄ ፡ ልብ ፡ (ኤር ማሕ ፡ ፬ ። ዳን ፲ ፡ ፯ ። ፍሉ፱ ፡ ፲) ።

—፤ እንቅልፍ ፡ ራእይ ፡ እንክሮ ፡ ተደሞ ፡ ተመሥጦ ። ወድቀ ፡ ድንጋፄ ፡ ላዕለ ፡ አብራም ። መጽአ ፡ ድን ጋፄ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወርእየ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፬ ። ግብ ፲ ፡ ፲) ።

**አደንገፀ ፤** አስደነገጠ ፡ አስፈራ ፡ አሳዘነ ። ም ንት ፡ ያደነግፀኪ ። ሕልም ፡ ያደግፆ ፡ ለአብድ ። እ ብድከ ፡ አደንገፀኒ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ ፳፩ ፡ ፲ ። ሚራ፴፩ ፡ ፩ ። ማ፯ ፡ ፳) ።

**መደንግፅ ፤ (ቅጽልና ፡ ጥሬ) ፤** የሚያስደ ነግጥ ፡ የሚያስፈራ ፤ አስፈሪ ፡ አስደንጋጭ ። ወይን ፡ መ ደንግፅ ። መብረቅ ፡ መደንግፅ ። ፀዓዕ ፡ መደንግፅ ። መኳንንት ፡ ምድር ፡ መደንግፃን ፡ (መዝ ፶፱ ። የሉፍ ። ኢዮ፴፯ ፡ ፬ ። ጥበ፳ ፡ ፲፬ ። ማሕ፯ ፡ ፬ ፡ ፲) ።


—፤ ማደንገጫ ፡ ማስደንገጫ ፤ ማስፈሪያ ፡ ማስፈራሪያ ። በመደንግፅ ፡ ፀቢይ ፡ (ዘዳ፱ ፡ ፴፬) ።

**ተደናገፀ ፤** ተደናገጠ ፡ ተደነጋገጠ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ (ፀማርኛ) ።

**ድንግት ፤ (ፀማርኛ) ፤ በቁሙ ፡ ድን ቀት ፤—ደኒቅ ፡ ደነቀ ።**

**ደንዳና ፤ (ዕብ ፡ ዳንዳና) ፤** የቅጠል ፡ ስም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ቅጠል ፡ ጥሩ ፡ ሽታ ፡ ያለው ፡ መድኀ ኒት ፡ የሚኾን ። በቁሙ ፡ ጠፍራም ፡ ግዙፍ ፡ (ፀማ ርኛ) ። ደኒን ፡ ደነ ፡ ደንደነ ።

**ደንደር ፤ (ዕብ ፡ ዳርዳር) ፤** እሾኻም ፡ ቅጠል ፡ የሱፍና ፡ የኩሸሽላ ፡ ዐይነት ፡ ኹለንተናው ፡ እሾኽ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሊያዝ ፡ ሊጨበጥ ፡ የማይቻል ። በቁሙ ፡ ደንደሮ ፡ እ ሾኽ ፡ ጋሬጣ ፡ ወይም ፡ በደንደር ፡ አምሳል ፡ የሚሠራ ፡ የስ ልክና ፡ የብረት ፡ እሾኽ ፡ የዱሮ ፡ ሰዎች ፡ እግረኛ ፡ ፈረሰኛ ፡ ጠላት ፡ በሚመጣበት ፡ መንገድ ፡ ወጥመድ ፡ አድርገው ፡ የሚቀብሩት ፡ የሚሰውሩት ፡ አውሬ ፡ የሚያጠምዱበት ። ይቤ ፡ እንጦንዮስ ፡ አንሰ ፡ ርኢኩ ፡ ኵሎ ፡ መሣግረ ፡ ሰይጣን ፡ ትክልተ ፡ ደበ ፡ ምድር ፡ ....በከመ ፡ ተጽ ሕፈ ፡ እስመ ፡ ኅብኡ ፡ ሊተ ፡ በውስተ ፡ ፍኖት ፡ ምሕ ዋርየ ፡ መሣግረ ፡ ወአሕባለ ። ወሶበ ፡ ርእየ ፡ እንከረ ፡ እምብዝኀ ፡ አሥዋከ ፡ ወደንደር ፡ እንተ ፡ ቍጽርት ፡ ውስቴታ ፡ ወአራዊት ፡ እንተ ፡ ትወድቅ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፲፯) ።



ደንደር ፤

**ደንደስ ፤ (ፀማርኛ) ፤** በቁሙ ፡ ማንቃ ፡ ት ከሻ ፡ ደንደሳም ፡ እንዲሉ ።

**ደኒዝ ፤ ዘት ፤ (ደንዘ ፡ ደነዘ ፡ ይደንዝ ፡ ይድንዝ ። ፀሪስ ፡ ፀርሰ) ፤** መደንዘዝ ፡ መጥረስ ፡ ደ ነዘ ፡ መኾን ፡ የስለት ። ደንዛዝነና ፡ ደንዙዛን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ስርጽ ፡ ነው ። ደንዘ ፡ ያማርኛ ፡ ፀርሰ ፡ የግእዝ ።

**ደንዘዘ ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤** በቁሙ ፡ ፈዘዘ ፡ ዳተኛ ፡ ቸልተኛ ፡ ኾነ ።

**ድንዙዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ዝዝት) ፤** የፈዘዘ ፡ ፈዛዛ ፤ ደንዛዛ ፡ ደብዛዛ ፤ እንቅልፋም ፤ ስንፍ ፡ ታካታ ፡ ደካማ ። ወሀበሙ ፡ መንፈሰ ፡ ድንዙዘ ፡ (ሮሜ ፲፩ ፡ ፰ ። ዕብ፭ ፡ ፲፩ ። ፮ ፡ ፲፪) ። ሊትኩኑ ፡ ድንጉፃነ ፡ ወድንዙ ዛነ ። ድንዙዛነ ፡ ልብ ። ፍካሬሁ ፡ ሊኮነ ፡ ቀሊለ ፡ ወ ፈድፋደሰ ፡ ለእለ ፡ ኢይሌብዉ ፡ ወኮኑ ፡ ድንዙዛነ ፡ ለሰሚዐ ፡ (ኪዳ ። መቃ ። ተረ ፡ ቁርጽ፳) ።

**ድንዛዜ ፤** መደንዘዝ ፡ መፍዘዝ ፤ ፈዛዝነት ። ድንዛዜ ፡ ወሀኬት ፡ እምሰሚዐ ። ሀኬት ፡ ወድንዛዜ ፡ (አፈ ፡ ድ፲ ፡ ቀሌ) ።

**ዳነየ ፤ (ደየን) ፤** ዳኘ ፡ ፈረደ ። ኢይዳንየነ ፡ ንጉሥ ፡ (ታሪ ፡ ነገ ፡ ኢያ) ።

**ዳናዪ ፤ ዳኒ ፤** ደያኒ ፡ የሚዳኝ ፡ ዳኚ ፡ ዳኛ ፤ እ ውነተኛ ፡ መካከለኛ ፡ የፍርድ ፡ ሚዛን ። (ተረት) ፤ ዳኛ ፡ የወል ፡ ምሰሶ ፡ የመካከል ። ዳኛ ፡ ቢያደላ ፡ በዳኛ ፤ እ ህያ ፡ ቢያጋድል ፡ በመጫኛ ። ዳኒና ፡ ደኃኒ ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ። (ግጥም ፡ በቴዎ ፡ ጊዜ) ፤ ይልማናና ፡ ደ ጎሳ ፡ ቁሞ ፡ ይሟገታል ፡ ይህን ፡ በጌምድርን ፡ ማን ፡ ዳኛ(ኝ) ፡ አድርጎታል ። ዳነየ ፡ ያማርኛ ፡ እንጂ ፡ የግእዝ ፡ አይደለም ።

**ዳንዮት ፤** መዳኘት ፡ ዳኝነት ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ።

**ደኒክ ፤ ኮት ፤ (ደንከ ፡ ይደንክ ፡ ይድንክ) ፤** መዘልዘል ፡ መቅለቅል ፡ የሥጋ ፡ የቈርበት ።

**ደነክ ፤** ዝልዝል ፡ ቅልቅል ፡ ቋንጣ ፡ ያልጋ ፡ ጠፍር ።

**ድንክ** ፤ በቁሙ ፡ ታናሽ ፡ ዐጭር ፡ ዐልጋ ። ለሰ ውም ፡ ይኾናል ።

**ደኒን ፡ ኖት** ፤ (ደነ ፡ ደነነ ፡ ይደንን ፡ ይ ድንን ። ዐረ ፡ ደኒን) ፤ መድነን ፡ መጐንበስ ፤ ራስን ፡ መቀለስ ፡ ዐንገትን ፡ መድፋት ፡ መስበር ፡ ማቀርቀር ። አድንን ፡ ወእፍታሕ ። ደነነ ፡ ሥዕል ፡ ከመ ፡ እሆ ፡ ዘ ይብል ። ትደንኑ ፡ ወትሰግዱ ፡ ሎቱ ። ድንኒ ፡ ወንትዐ ይኪ ፤ (ማርቆ ፡ ፯ ። ድጓ ። ኢሳይ ፡ ፯ ። ሄኖ ፡ ፳፫) ።

—፤ መጕብጥ ፡ መታጠፍ ፡ በጭራሽ ፡ እንደ ፡ ደጋን ፡ መ ኾን ፡ የደዌ ፡ የርግና ። ኮነ ፡ ነዊኅ ፡ በቆሙ ፡ አላ ፡ ው እቱ ፡ ይደንን ፡ በእንተ ፡ ርሥእናሁ ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ) ።

**አድነነ** ፤ አደነነ ፡ አስደነነ ፡ አጕንበሰ ፡ አስጕን በሰ ፡ ሰገደ ፡ አሰገደ ። አድነነ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ያጥምቆ ፡ እደ ፡ ገብር ። አድንኑ ፡ አርእስቲክሙ ። ፀሚደ ፡ አር ዑት ፡ ያደንኖ ፡ ለክሣድ ። አድንኑ ፡ አርእስቲሆሙ ፡ ወሰገዱ ፡ ለአዳም ፡ (ቅዳ ። ሚሬ ፡ ፴፭ ። ቀሌ) ።

**አድናኒ ፤ መድንኒ** ፤ የሚያጕንብስ ፡ የሚያስ ጐነብስ ፡ አጕንባሽ ፡ አስጐንባሽ ። (ተረት) ፤ ዐፋሽ ፡ አጕ ንባሽ ። መንኰራኵረ ፡ ሠረገላ ፡ መድንኒ ፡ ክሣድ ፡ (ስንክ ፡ ጥር ፳፱) ።

**ድኑን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ንንት) ፤ የደነነ ፡ ያደ ነነ ፡ የተጕነበሰ ፤ ጕንብስ ፡ ጐንባሳ ፡ ቀርክሳ ። ሰይጣን ፡ ጕየ ፡ በኀፍረት ፡ ወበኀሳር ፡ ድኑነ ። ወርእየ ፡ ዘሎ ፡ ኀይላት ፡ ሰማይ ፡ ድኑናነ ፡ በዐውደ ፡ መስቀል ፡ ቅ ዱስ ፡ (ስንክ ፡ የካ ፲ ። መቅ ፡ ወን) ።

**ድናኔ** ፤ መጕንበስ ፡ አጕንባበስ ፤ ጐንባሳነት ፡ መ ቅለስለስ ፡ (ገድ ፡ አዳ) ። አውሥአ ፡ ወድናኔ ፡ (ማር ፡ ይ ሥሽ ፡ ፱) ።

**ምድናን** ፤ (ናት) ፤ ማጕንበሻ ፡ መጕንበሻ ። አኮ ፡ ዘበቱ ፡ ለመለኮት ፡ ምድናን ፡ ወአትሕቶ ፡ ር እስ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ እምድር ፡ ዘኮነ ፡ ውስቴታ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

(ጥ) **ደን** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፡ ዱር ፡ ጫካ ፡ ብዙ ፡ ዛፍ ፡ ዘፋም ፡ የዛፍ ፡ ዐታ ። ደን ፡ ጠባቂ ፡ የደን ፡ ሹም ፡ እንዲሉ ፡ ሲባኖስን ፡ እይ ።

**ደንደነ** ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ በቁሙ ፡ ወፈረ ፡ ገዘፈ ፡ ዛኑ ፡ ለሰውም ፡ ይኾናል ። ደንዳና ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ደነፈ** ፤ (ትግ ፡ ደንፈ) ፤ ጠውዐ ፡ ደነፉ ፡ ፈ ከረ ፡ ተንደቀደቀ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ደኒጽ ፤ ጾት** ፤ (ደነጸ ፡ ይደንጽ ፡ ይድ ንጽ) ፤ አጥብቆ ፡ መደንገጥ ፡ መሸበር ፡ መቀየም ፡ የጠ ላት ፡ የፍንዝዝ ።

**ደንጽ** ፤ ቂም ፡ በቀል ፡ ትግል ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ ፍጅት ። ምንት ፡ ውእቱ ፡ ዝ ፡ ደንጽ ። ሰደንጽ ፡ ሀ ለዉ ፡ አሐዱ ፡ ለአሐዱ ፡ ይትቃተሉ ። ደንጽ ፡ ዘበኀ ደጥ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ ፡ ፲፭ ። ፲ ፡ ፳፱) ።

**ደንጸወ** ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ ነፈገ ፡ ቤሰ ፡ ማማ ፡ ቈጠበ ፡ ሬሰበጭ ፡ ኾነ ፡ ቀና ፡ ተመቀኘ ። ኢትደንጹ ፡ ዐ ይንከ ፡ ሶበ ፡ ትገብር ፡ ምጽዋተ ። ጸጋዊ ፡ ዘእንበለ ፡ ደንጽዎ ። ይደነጹ ፡ ባቲ ፡ ላዕለ ፡ ነዳያን ። ይደነጹ ፡ በውስቴቱ ፡ ማእድ ። ትደነጹ ፡ ዐይኑ ፡ በእኍሁ ፡ (መ ቢ ፴ ፡ ፯ ። ቅዳ ፡ ኢጲ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲ ። ሚሬ ፲፬ ፡ ፲ ። ዘዳ፳፰ ፡ ፶፬ ፡ ፶፮) ።

**ደንጻዊ ፤ ድንጽው** ፤ ንፉግ ፡ ሬሰባጭ ፡ ሥሡ ፡ ሥሥታም ፡ (ሚሬ ፲፰ ፡ ፲፰ ። ፳፰ ፡ ፪) ። ሰደን ጻዊ ፡ ይረግምዎ ፡ በእከየ ፡ ግዕዙ ። ኢትትማከር ፡ ም ስለ ፡ ደንጻዊ ፡ እንበይነ ፡ ውሂብ ፡ ምጽዋት ፡ (፴፬ ፡ ፳፫ ። ፴፯ ፡ ፲፩) ። ድንቅው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ድንጽው ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ኢትኩኑ ፡ ድንጽዋነ ፡ ወድንዙ ዛነ ፡ ልብ ፡ ለአሚን ፡ (መቃ ፡ ፲፰) ።

**ተደናጸወ** ፤ ተናፈገ ፤ ተጣላ ፡ ተቃና ፤ ተሬ ሬጸ ። ይደናጸዉ ፡ ከመ ፡ አክልብት ። አሐዱ ፡ ለካ ልኡ ፡ ይደናጸዉ ፡ (ገድ ፡ ተክ ፡ ስር ፡ ኢሳ፯ ፡ ፱) ።

**ደኒቅ ፤ ቆት** ፤ (ደነቀ ፡ ይደንቅ ፡ ይድ ንቅ ። ደደቀ) ፤ መድነቅ ፡ መደነቅ ፡ ድንቅ ፡ መኾን ፡ መደንገጥ ። ደደቀንና ፡ ወገበን ፡ እይ ።

**ድንቀት** ፤ ገዚኢ ፡ ከማሁ ፤ አደናንቅ ፡ ድንቂያ ፤ ድንቅነት ። ድንቅ ፡ ብርቅ ፤ የሚያስደንቅ ። እምእይቴ ፡ አምጽእት ፡ ዛቲ ፡ ብእሲት ፡ ዘከመ ፡ ዝ ፡ ድንቀተ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ድንቀት** ፤ (ድድቀት) ፤ ድንገት ፡ ቶሎ ፡ ወ ዲያው ። ምስጢሩ ፡ ድንቂያን ፡ አይለቅም ።

**ድንቀተ** ፤ (ግብተ) ፤ ድንገት ፡ በድንገት ፡ ሳ ይታሰብ ። ድንቀተ ፡ ግብተ ፡ እንዘ ፡ ኢተአምር ። በ ጽሑ ፡ ኀበ ፡ በራዊተ ፡ ዳራ ፡ እምቅድመ ፡ ጽባሕ ፡ ድ ንቀተ ። እለ ፡ ይነግሩ ፡ እምአፉሆሙ ፡ ድንቀተ ፡ ወ ኢቀደሙ ፡ ጽሒፈ ፡ (ቀሌ ። ዮሴፍ ። ተረ ፡ ቄር) ።

**ደንቀወ** ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ ደነቈረ ፡ ተደፈነ ፡ አልሰማ ፡ አለ ፡ የገባር ። አ ፡ ዘአሜሃ ፡ ትውልድ ፡ ደን ቀዋ ፡ እዘኒሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይስምዕዎ ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ) ። ደንቀረ ፡ በግድ ፡ አገባ ፡ ቀረቀረ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ደንቃዊ ፤ ድንቅው** ፤ የደነቈረ ፡ ደንቈሮ የማይሰማ ። ወይም ፡ መከክለኛ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ የሚ ሰማ ። ነፍሳት ፡ ደንቃውያት ። አ ፡ ድንቅው ፤ ድንቅ ዋነ ፡ እዝነ ፡ (ቂር ፡ ጲላ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ድንቃዌ** ፤ መደንቈር ፡ ድንቍርና ፡ ደንቈሮ ነት ። ዐጸወ ፡ እዝና ፡ በድንቃዌ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አደንቀወ** ፤ አደነቈረ ፡ ደንቈሮ ፡ አደረገ ፡ አስኘ ።

**ዲናር** ፤ (ራት ። ጽር ፡ ዲናሪዮን) ፤ የገንዘብ ፡ ስም ፡ ጽርኣዊ ፡ ሮማዊ ፤ ታናሽ ፡ የብር ፡ ገን ዘብ ፤ የሰቅል ፡ እኩሌታ ፡ የዲድርክም ፡ አሳድ ፤ ወርቅም ፡ ይኾናል ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፳፰ ። ፳ ፡ ፪ ። ፳፪ ፡ ፲፱) ። ዲናረ ፤

ብሩር ፡፡ ዲናረ ፡ ወርቅ ፡፡ ዲናራተ ፡ ብሩር ፡ ወወርቅ ፡፡ ዲናራት ፡ ወጠፋልሐ ፡ ብሩር ፡፡ ዲናር ፡ ግብጻዊ ፡ ዲናር ፡ ጤሮሳዊ ፡ (ዘሌዋ ፡ ፭ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፲፩ ። ጥር ፲፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፰ ። ፀ፲) ። ዴናሪ ፡ ማለት ፡ በማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ይሰማማል ።

**ደንሰ ፡ ሰት ፡ (ደነሰ ፡ ይዴንስ ፡ ይደንስ ። ዐረ ፡ ደኒሰ)** ፡ ማደፍ ፡ መርከስ ። ማሳደፍ ፡ ማርከስ ፡ ማባበል ። መለመን ፡ በስበ ፡ ዝሙት ፡ መስጠት ። እስመ ፡ ደነስኪ ፡ ወኢደነሱኪ ፡ (ሕዝ ፡ ፲፮ ፡ ፴፬) ። በደነስ ፡ ፈንታ ፡ ተደንስ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ይረኵሱ ፡ ብቲ ፡ ወይዴንሱ ፡፡ እመ ፡ ቦ ፡ ዘአበሰ ፡ ወተደንሰ ፡ በብቲ ፡ ኀጢአት ፡፡ እመሂ ፡ በቃል ፡ አበሱ ፡ ወእመሂ ፡ በገቢር ፡ ረኰሱ ፡ ወእመሂ ፡ በክሁት ፡ ተደነሱ ፡ (አፈ ፡ ድሜጥ ፡ ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፱ ። ማኅዘ) ።

**ድኑስ ፡ (ሳን ፡ ሳት ፡ ንስት)** ፡ ያደፈ ፡ የረከሰ ፡ እድፋም ። ኢበላዕኩ ፡ አነ ፡ ግሙራ ፡ ርኩሰ ፡ ወድኑሰ ፡፡ ንሕነሰ ፡ ንሬኢ ፡ ከሎ ፡ ርኩሰ ፡ ወድኑሰ ፡፡ ዘማዊ ፡ ወድኑስ ፡፡ ኅሊና ፡ ድንስት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫ ። አፈ ፡ ድሜጥ ። ፀ፲ ። ፊልክ ፡ ፻፳፭) ።

**ደነስ ፡ (ሳት)** ፡ እድፍ ፡ አደፍ ፡ ትክቶ ፡ ዝሙት ፡ ኀጢአት ፡ የዝሙት ፡ ሥራ ፡ ምኞት ፡ ፀስበ ፡ ዝሙት ። መዋዕለ ፡ ደነስ ፡፡ አኮ ፡ በፍትወተ ፡ ደነስ ፡ ዘተፀነስኪ ፡፡ አንጽሐነ ፡ እምዙሉ ፡ ደነስ ፡ ወእምዙሉ ፡ ርኩስ ፡፡ ያነጽሕ ፡ ልቦ ፡ እምደነሳት ፡ (አዋል ። ቅዳ ። ፊልክ ፡ ፻፳፯) ። ሀበኒ ፡ ደነስየ ፡፡ ደነስ ፡ ዘማ ፡፡ ደነሰ ፡ ዝሙት ፡ ዋጋ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፭ ። ዘዳግ ፡ ፳፫ ። ሚክ ፡ ፩) ።

**ደነሳዊ ፡ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፡ ዘማዊ ፡ ሴሰኛ ፡ ያመንዝሮች ፡ ቢሳይ ። ይትወደዩ ፡ ውስተ ፡ ሖኔ ፡ ደነሳውያን ፡ በርኵሰ ፡ ዝሙት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፭) ።

**ዳንስ ፡ (ሮማይ)** ፡ ዘፈን ፡ እስክስታ ፡ የዝሙት ፡ ዋዜማ ። እንስሳውን ፡ ገፊም ፡ ጭምት ፡ ሲሉ ፡ ደንሴ ፡ ማለት ፡ በማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ይሰማማል ።

**ዳናት** ፡ ስመ ፡ ቀሚስ ፡ ማለስ ፡ የግራ ፡ እጅ ። ዳናት ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ማልስ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ዳኑተ ፡ (ዐማርኛ)** ፡ በቀደሙ ፡ ሰዎች ፡ ተቈጣ ፡ ነደደ ፡ ቃል ፡ አወጣ ። ነገሩ ፡ ችንክር ፡ ነው ፡ እንዲሉ ።

**ድንት ፡ (ድልት)** ፡ ስመ ፡ ፊደል ፡ ራብዕ ፡ ደ ፡ ለዓለም ፡ ዘለዓለም ። ድንት ፡ ያኮርኽ ፡ እንዲሉ ። አውነተኛ ፡ ስሙ ፡ ድልት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ድንት ፡ አይደለም ፡ ል ፡ በን ፡ ተለውጧል ፡ ዳሌጥንና ፡ ድልትን ፡ እይ ።

**ድንት ፡ (ታት)** ፡ ድንች ፡ ነዋሪ ፡ የምድር ፡ ፍሬ ፡ ከተዘራበት ፡ የማይጠፋ ፡ የማይታጣ ።

**ድንታር ፡ ዲንታር** ፡ የሱሪ ፡ መሸቀቅ ፡ ጥብጣብ ። ማንቆ ፡ ሸምቀቆ ፡ (ጥሬ ፡ ስዋ) ። ምስጢሩ ፡ ዘልፋዊ ፡ ማለት ፡ ነው ። ወክመ ፡ ቅናት ፡ ዘይቀንት ፡ ዘልፈ ፡ (መዝ ፡ ፻፳) ።

**ዳዕሙ ፡—እንጂ ፡—ድኢም ፡ ደአመ ፡ ዳእሙ ።**

**ዳዕሮ** ፡ የዛፍ ፡ ስም ፡ ወርካ ፡ ዋርካ ፡ የሾላ ፡ የባንባ ፡ ዐይነት ፡ ወፍራም ፡ ደንዳና ፡ ታላቅ ፡ ግዙፍ ፡ በጽቁ ፡ ግድም ፡ የሚኼድ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ የሚወርድ ፡ የሚሰፋ ፡ የሚንሰራፋ ። እንደ ፡ ወርካ ፡ ይሰፋኽ ፡ እንዲሉ ። (ግጥም ፡ ስደተኛ ፡ ጠላቱ ፡ ብዙም ፡ ስለ ፡ ተሻረና ፡ ስለ ፡ ሞተ) ፡ ወርካ ፡ ምድር ፡ ነካ ፡ ደረሰ ፡ ንግሬ ፡ እንግዲህ ፡ ልመለስ ፡ ልግባ ፡ ወደገሬ ። ወይጼልሎ ፡ ፆመ ፡ ዳዕሮ ፡ (ኢዮብ ፡ ፲፮) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ አርዘ ፡ ሊባኖስ ፡ ይላል ።



ዳዕሮ ፡

**ደፍደፍ ፡—ክርክሪ ፡—ደፈዐ ፡ ደፍዐ ።**

**ደፈን ፡ ኖት ፡ (ደፈነ ፡ ይደፍን ፡ ይድፍን ። ዐረ ፡ ደፈነ ። ዕብ ፡ ዳፉን ፡ ግሩ ፡ ደፋ)** ፡ መድፈን ፡ መምረግ ፡ መዝጋት ። ዘይደፍን ፡ ዐዘቅተ ፡፡ አዘዘሙ ፡ ይድፍኑ ፡ ውእተ ፡ መቃብረ ፡፡ አዘዘ ፡ ይድፍኑ ፡ ግበባተ ፡ (ምሳሌ ፡ ፳፮ ። ጦቢ ፡ ፲፰ ። ዮሴፍ) ።

—፡ መቅበር ፡ መሸሸግ ፡ መሰወር ፡ ከፈር ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ ማግባት ፡ መክተት ፡ ከእሳት ፡ ከፍሕም ፡ መረመጥ ፡ መሸጐጥ ። ድፍኑ ፡ ደመ ፡፡ ይደፍንኑ ፡ ምሕረቶ ፡ በመዐቱ ፡፡ ቀተሎ ፡ ወደፈኖ ፡ ውስተ ፡ ኖዳ ፡፡ እመ ፡ ደፈንኩ ፡ ወርቅየ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡፡ ደፈነቶ ፡ ውስተ ፡ ሐፅጽ ፡፡ ደፈነት ፡ ናእተ ፡ (ኩፋ ፡ ፯ ። ዘፀ ፪ ፡ ፲፪ ። ኢዮ ፴፩ ፡ ፳፬ ። ሉቃ ፲፫ ፡ ፳፩ ። ሄኖ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬) ።

—፡ መሸፈን ፡ ማልበስ ፡ መክደን ። ደፈነኒ ፡ ቀባር ፡፡ ይደፍነኪ ፡ ጸበል ፡፡ ደፈኖሙ ፡ ማዕበል ፡፡ ደፈነ ፡ ጽላሎተ ፡ ሞት ፡ (ኢዮ ፳፫ ፡ ፲፯ ። ሕዝ ፳፮ ፡ ፲ ። ዘፀ ፲፭ ፡ ፲ ። መዝ ፡ ፵፫) ። ማስታጐል ፡ ማስቀረት ፡ የግብር ፡ የጸሎት ። ምስጢሩ ፡ ከመዝጋት ፡ ይገባል ።

**ደፋኒ ፡ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፡ የሚደፍን ፡ ደፋኝ ፡ ቀባሪ ፡ ሸሻጊ ። ገብር ፡ ደፋኔ ፡ ወርቀ ፡ እግዚኡ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፱) ።

**አድፈነ** ፡ አስደፈነ ፡ አስቀበረ ፡ የድፍኖት ፡ አበላ ።

**ተደፍነ** ፡ ተደፈነ ፡ ተዘጋ ፡ ተቀበረ ፡ ዐፈር ፡ ለበሰ ። ተደፍኑ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡፡ ዐይንየ ፡ ተደፍነት ፡፡ ማይ ፡ ይደፈን ፡ በማእከለ ፡ ምድር ፡፡ ንደፈ

ንኑ ፡ ኀቡረ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡፡ እስከ ፡ ኀቡረ ፡ ተደፍኑ ፡ (ሰቈ፪ ፡ ፱ ፡፡ ፫ ፡ ፶፰ ፡፡ ኢ.ዮ፲፱ ፡ ፲፱ ፡፡ ፲፯ ፡ ፲፮ ፡፡ ሰንክ ፡ ጥቅ፲፱) ፡፡

**ድፉን ፤ (ፉን ፡ ፉት ፡ ፍንት)** ፤ የተደፈነ ፡ የተቀበረ ፡ በውር ፡ ድብቅ ፡ (ኢ.ያ፳ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪) ፡፡ ያልተ ቈረሰ ፡ ያልተከፈተ ፡ ድፍን ፡ ምሉ ፡ ፍጹም ፤ እንጀራ ፡ ቅል ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡፡ ለሀገርና ፡ ለሕዝብም ፡ ይኾ ናል ፡ ድፍን ፡ በማሪ ፡ ድፍን ፡ ትግሬ ፤ መላው ፡ ጠቅ ላላው ፡ ፩ ፡ ሳይቀር ፡፡

**ድፍንት** ፤ መድፈን ፡ መደፈን ፤ አደፋፈን ፡ አ ቀባበር ፡፡ ድፍነተ ፡ ምጧት ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ከመ ፡ ዘሬዐ ፡ ዘርዐ ፡ ውስቴታ ፡፡ እምቅድመ ፡ ድፍነተ ፡ ም ጧታን ፡ (ግንዘ) ፡፡

**ዳፍንት** ፤ በቁሙ ፤ የዐይን ፡ በሽታ ፡ ከማታ ፡ እስከ ፡ ጧት ፡ የሚያሳውር ፡፡ ዳፍንታም ፡ እንዲሉ ፡፡

—፤ ቂጣ ፡ ብርኸታ ፡ ርሚጠ ፤ እንባሻ ፡ ሽልጦ ፤ በረመጥ ፡ በፍሕም ፡ ተቀብረው ፡ አዳፍነው ፡ የሚያበስሉት ፡ የባላገር ፡ ኅብዝት ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፮ ፡፡ ፲፱ ፡ ፫ ፡፡ ዘፀ፲፪ ፡ ፴፱) ፡፡ ግበሪ ፡ ዳፍንተ ፡ ወአምጽኢ ፡ ሊተ ፡፡ ከመ ፡ ይግበራ ፡ ዳፍ ንተ ፡ (፫ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፫ ፡፡ ኤር፯ ፡ ፲፰) ፡፡

**መድፍን ፤ (ብ ፡ መዳፍንት)** ፤ የተቀበረ ፡ ወርቅ ፡ ገንዘብ ፡፡ ከመ ፡ መድፍን ፡ ክቡት ፡፡ ረኪብ ፡ መድፍን ፡፡ መድፍን ፡ ኅቡእ ፡ ውስተ ፡ ገራህት ፡ (ሚልክ ፡ ፴ ፡፡ ፵ ፡ ፲፰ ፡፡ ማቴ፲፫ ፡ ፵፬) ፡፡

**ዳፈን ፤ (ዐማርኛ)** ፤ ያዳፋኝ ፤ መቀፊያ ፡፡

**ዶፎኒ ፤ (ሱር ፡ ዱፍና)** ፤ የሬሳ ፡ ማጥን ፡ እ ስከሬን ፡፡ ዶፎኒ ፡ ጸበተ ፡ (ሰንክ ፡ መጋ፳) ፡፡

**ዳፍን ፤ (ጽር ፡ ዳፍኒ)** ፤ የዛፍ ፡ ስም ፡ ሽቱን ትና ፡ ቅመምነት ፡ ያለው ፤ ቅጠሉን ፡ ስለ ፡ ክበሬታ ፡ ቈ ሳሮች ፡ የሚቀዳጁት ፡፡ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ጥድ ፡ ይሉ ታል ፡ (ክሩ ፡ ፳፩) ፡፡

**ደፈዐ ፤ ፆት ፤ (ደፍዐ ፡ ይደፍዕ ፡ ይድ ፍዕ ፡፡ ዐረ ፡ ደፈዐ ፡፡ ዕብ ፡ ዳፋ)** ፤ መድፋት ፡ መከንበል ፤ መግፋት ፡ መጣል ፤ መገልበጥ ፡፡ ደፍዐ ፡ ገጾ ፡፡ ሖ ፡ ገባሬ ፡ ብርሃናት ፡ ዘደፍዖ ፡ ለጽልመት ፡፡ አባ ፡ ታድራ ፡ ወአባ ፡ ሉቃ ፡ አዝለፉ ፡ ኅምሳ ፡ ዓመተ ፡ እ ንዘ ፡ ይደፍዑ ፡ ኀሊናቲሆሙ ፤ እስመ ፡ ኮኑ ፡ ይፈ ቅዱ ፡ ፈሊሰ ፡ እመካኖሙ ፡ ወኮኑ ፡ ይብሉ ፡ እስከ ፡ ክረምት ፡ ነሐውር ፤ ወሶበ ፡ ይበጽሕ ፡ ክረምት ፡ ይ ብሉ ፡ እስከ ፡ ሐጋይ ፡ ነሐውር ፡ (ገድ ፡ ተክ ፡፡ ቅዳ ፡ ያዕ ፡፡ ፊልክ ፡ ፸፫) ፡፡

**መድፍዕ ፤ (ብ ፡ መዳፍዕ)** ፤ በቁሙ ፤ መ ድፍ ፡ ታላቅ ፡ ሰውቅ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፤ ሲተኰስ ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ የሚጮኽ ፡ የሚንጐድ ፤ ዐረሩ ፡ ሩቅ ፡ የሚኼድ ፡፡ ወትንሥእ ፡ ግራኝ ፡ በእግረ ፡ ትዕቢት ፡ እንዘ ፡ ይትአ መን ፡ በመድፍዕ ፡ ወበቱርክ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ፡፡ የምጣድ ፡ ሞግድ ፡ አክንባሎ ፡ መክደኛው ፡፡

—፤ መዳፍ ፡ የእጅ ፡ ተረከዝ ፡፡ (ትረት) ፡ አሬኛ ፡ ባፉ ፤ ኀይለኛ ፡ በመዳፉ ፡፡



መድፍዕ ፡

**ድፍዕ** ፤ ድፋት ፡ አደፋፍ ፡ ድፎ ፡፡

**ደፍዕ** ፤ የመዝጊያ ፡ ደፍ ፤ ጕበን ፡ በመቃኖች ፡ ላይ ፡ የሚኾን ፡፡

**ደፍደፍ** ፤ ከርከሬ ፡ የእድሞ ፡ ቤት ፡ ጣራ ፡ ሱሕ ፡ ጠርብ ፡ መረባርብ ፡፡ ደፍደፈ ፡ ናሕስ ፡፡

**ደፍደፈ** ፤ አገደመ ፡ ረበረበ ፤ ደፈደፈ ፤ መረገ ፡ አለበሰ ፡ ደመደመ ፤ ኹሉም ፡ የእድሞ ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ እ ድሞን ፡ እይ ፡፡ ይደፈድፉ ፡ ናሕሰ ፡ (ታሪ ፡ እሾ) ፡፡

**ድፍድፍ** ፤ ጭቃ ፡ የጠላ ፡ ቡሖ ፡፡ ተሰብረ ፡ ገ ንዐ ፡ ወኢተክዕወ ፡ ድፍድፍ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ፡፡

**እንደፍደፈ** ፤ እንደፋደፈ ፤ ተንደፋደፈ ፡ ደፍ ደፍ ፡ አለ ፡ (ዐማርኛ) ፡፡

**ደፈር ፤ ሮት ፤ (ደፈረ ፡ ይደፍር ፡ ይድ ፍር ፡፡ ዐረ ፡ ደፈረ ፤ ግፋ ፡ አራቀ ፤ ወዳያ ፡ አለ)** ፤ መድፈር ፡ መጨከን ፤ አለመፍራት ፡ አለማፈር ፤ መናቅ ፡ ማቃለል ፡ ማዋረድ ፡፡ ደፈርከ ፡ ትስተይ ፡ በንዋየ ፡ ቅድ ሳት ፡፡ ኢኮኑ ፡ አይሁድ ፡ ይደፍሩ ፡ ይስዐሩ ፡ ካህነ ፡ እ ምሂመቱ ፡ እስከ ፡ ይመውት ፡፡ ወኢክህሉ ፡ አሐዱሂ ፡ ይድፍር ፡ ባዕሌሁ ፡ (ዮሴፍ) ፡፡ ኢይድፍር ፡ ወኢይ ትናገር ፡ መኑሂ ፡፡ ይደፍር ፡ ለምህሮ ፡፡ ዘንተ ፡ ደፈ ርከ ፡ በትዕቢትከ ፡፡ ሐሰወ ፡ ወደፈረ ፡ መሐላ ፡፡ ደፈሮ ፡ ለእግዚእ ፡ (ሰንክ ፡ ጥር፳ ፡፡ ፊልክ ፡ ፻፶፱ ፡፡ መቃ ፡ ገ፮ ፡፡ ቀሌ ፡፡ ቄድር) ፡፡

**ደፋሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት)** ፤ በቁሙ ፡ የሚ ደፍር ፡ ደፋር ፡ ጨካኝ ፡ ትቢተኛ ፡፡ ጽኑዐ ፡ ወደፋሪ ፡ እምንእሱ ፡፡ ደፋሪ ፡ ወኢንፉዕ ፡፡ ደፋርያን ፡ (ዮሴፍ ፡፡ ግንዘ ፡፡ ፊልክ ፡ ፻፶፫) ፡፡

**አድፈረ** ፤ አስደፈረ ፡ ድፍረት ፡ አስተማረ ፡፡

**ተደፍረ** ፤ በቁሙ ፤ ተደፈረ ፡ ተናቀ ፡፡ ግሩም ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይደፈር ፡፡ ሖ ፡ ዘኢትደፈር ፡ ይሁዳ ፡ ደ ፈረከ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ፡፡ ያዕ) ፡፡

**ድፉር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ፍርት)** ፤ የተደፈረ ፡ የተናቀ ፡ የተጠቃ ፡ ጥቁ ፡፡

**ድፍረት** ፤ በቁሙ ፡ መድፈር ፤ መደፈር ፡ አደ ፋፈር ፡ የትቢትና ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡፡ ዝንቱ ፡ ይከውን ፡ ድፍረተ ፡ ወተንብሎ ፡፡ ያሴስል ፡ ድፍረተ ፡ ዝንጉራን ፡፡ ይትናገሮ ፡ ለንጉሥ ፡ በድፍረት ፡ ዘእንበለ ፡ ፍርሀት ፡፡ በድፍረትክሙ ፡ ለእመ ፡ ቀረብክሙ ፡፡ ነሚአ ፡ ሥ ጋሁ ፡ በድፍረት ፡፡ ወድፍረት ፡ ውስተ ፡ ሀርብዶ ፡

(አፈ ፡ ተ፳ ። ቁስጠ ፡ ፶፭ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፭ ። ቅዳ ። አፈ ፡ ወር ። ማር ፡ ይስሐቅ ፡ ፫) ።

**ደፈር ፤** ቀራሩ ፡ ኩረብታ ፡ ንመገም ።

**ዳፍራን ፤(ሱር ፡ ዳፍራና) ፤** ጥድ ፡ የጥድ ፡ ዐይነት ፡ ዝፍ ። ባለብርቱዎች ፡ ማን ፡ ቀረጥ ፡ ይስታል ፡ (ኩፋ ፡ ፳፭) ።

**ደፍተር ፤—በቁሙ ፤—ደብተር ።**

**ደቅሐ ፤(ቀድሐ) ፤** በቁሙ ፡ ደቃ ፡ ደሰቀ ፡ መታ ፡ ቸንከረ ፡ በሳ ፡ ንደለ ፡ ሰረሰረ ፡ ወገን ፡ ዐደለ ፡ ባረከ ፡ መረቀ ፡ ቀደሰ ። በመድቅሒሁ ፡ ደቅሖሙ ፡ ወበንደሎ ፡ መገዘራዕቱ ፡ አጽንዖሙ ፡ (ኢሳ፵፬ ፡ ፲፪) ።

**መድቅሕ ፤(ብ ፡ መዳቅሕ) ፤** መዶቂያ ፡ መደሰቂያ ፡ መዶሻ ፡ መዶሻ ፡ መብሻ ። ማደሻ ፡ መቀደሻ ፡ መመረቂያ ፡ ቅዳሴ ፡ በዓል ፡ (ዘኍ፳ ፡ ፲ ። ዘዳ፳ ፡ ፳ ። ዳ ኅ፫ ፡ ፪ ። ፩ነገ ፡ ፰ ፡ ፳፩) ። ወገብሩ ፡ መድቅሐ ፡ ቤቱ ፡ እግዚ ፡ በትፍሥሕት ። ወአብኡ ፡ ለመድቅሐ ፡ ቤት ፡ ምእተ ፡ አልሕምተ ፡ (ዕዝ፯ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯) ።

**ምዳቍ ፤** ምዳቋ ፡ ሚዳቋ ፡ የዱር ፡ እንስሳ ፡ የ ሥጋ ፡ ወገን ፡ ቂጠ ፡ ወፍራም ፡ እግረ ፡ ቀጭን ፡ ዐንገተ ፡ ረጅም ፡ ምድርን ፡ በእግሯ ፡ የምትደቃ ፡ የምትደቅድቅ ። አምሥጦተ ፡ ምዳቍ ፡ እማዕገት ፡ (ሚራ፳፯ ፡ ፳) ።



ምዳቍ ፤

**ድቀንዱቅ ፤** ምድቃሕ ፡ ፋስ ፡ ምማር ፡ መጥ ረቢያ ። መፍጽሕ ፡ ወድቀንዱቅ ፡ (፫ነገ ፡ ፮ ፡ ፯) ።

**ድቃል ፤(ብ ፡ ደቃልው ። ዕብ ፡ ዴቄል ። ሱር ፡ ዴቅላ ። ዐረ ፡ ደቀል ፤ ተምር) ፤** ዲቃላ ፡ የዝሙት ፡ ልጅ ፡ ከሚመሳሰል ፡ ከማይመሳሰል ፡ የተወ ለደ ። በቅልን ፡ ተመልከት ።

**ደቂቅ ፤ቆት ፤(ደቀ ፤ደቀቀ ፡ ይደቅቅ ፡ ይድቅቅ ። ዕብ ፡ ዳቃቅ) ፤** መድቀቅ ፡ መላም ፡ ደ ቂት ፡ መኾን ፡ መርቀቅ ፡ መቅጠን ፡ ማነስ ፡ መኰሰስ ፡ ታናሽ ፡ መኾን ። ደማደግን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ድቁቅ ፤(ቃን ፡ ቃት ፡ ቅቅት) ፤** የደቀቀ ፡ ደቃቅ ፡ የተወገጠ ፡ የተቀጠቀጠ ፤ የተደቈሰ ፡ የተፈጨ ፤ ታ ናናሽ ፡ ቅንጣት ። ዕጣን ፤ ዘድቁቅ ። ተሐርጽ ፡ ድቁቀ ። ወይከውኑ ፡ ድቁቀ ፡ አግልዕተ ፡ (ዘሌ፲፮ ፡ ፲፪ ። ዘዐ፴ ፡ ፴፯ ። ኢሳ፴ ፡ ፲፬) ። ድቁቅ ፡ ቃሉ ፤ የደከመ ፡ የሰለለ ፡ ቀ ጭን ፡ (ስንክ ፡ ኅሐ፲፰) ።

**ደቂቅ ፤(ቅት ፡ ቃት ። ደቃቅ ፡ ቃት) ፤** ቅጽልና ፡ ጥሬ ። በቁሙ ፡ የደቀቀ ፡ ደቃቅ ፡ አሸዋ ፡ እ ብቅ ፡ ደቂት ፡ ውጣጥ ፡ የሚበን ፡ የሚተን ፡ የሚበተን ። ዕጣን ፡ ዘቅታሬ ፡ ደቂቅ ። ትገብር ፡ ደቃቀ ። ጼው ፡ ደ ቃቅ ፡ (ዘፀ፴ ፡ ፯ ። ኢሳ፴ ፡ ፳፱ ። ስንክ ፡ ኅዳ፭) ።

—፤ ታናናሽ ፡ ጥቃቅን ፤ ቀጣጣ ፡ ቀጣጣዎን ። ክንፍ ፡ ደቃቅ ። አስናኒሁ ፡ ደቃቅ ፡ ወበሊኃት ፡ ከመ ፡ አስናኒ ፡ ከልብ ። ይማርር ፡ ደበ ፡ ማይ ፡ ወየሐንጽ ፡ በደቃቅ ። እንስሳ ፡ ዐበይት ፡ ምስለ ፡ ደቃቅ ። አራዊት ፡ ደቃቅ ። አብትር ፡ ደቃቅ ፤ እለ ፡ ደቃቅ ፡ ንቅዐቶሙ ። እለ ፡ ደ ፈጽሙ ፡ ታሕጻጺተ ፡ ደቂቃት ፡ ኀጣውእ ። አሕባለ ፡ ሥርው ፡ ደቃቃት ፡ (ሔኖ ፡ ዕ፲፫ ፡ ፱ ። ዮሴፍ ። ቅዳ ። መዝ ፡ ፶፫ ። ስንክ ፡ የካ፳ ። ሄርማ ። ቀሌ ። መቃ ፡ ገ፳) ።

—፤ ልጅ ፡ ዕንል ፡ ሕፃን ፡ ደበል ፤ አሽከር ፡ ጕብል ። ው ስጠ ፡ ብዙኅት ፡ ሰባለሙ ፡ እንደ ፡ ሰብእ ፡ ሳንይም ፡ ስብ ዙም ፡ ይኾናል ። ወሊድየ ፡ ዓዲሁ ፡ ደቂቅ ። ደቂቅት ፡ ድንግል ። ደቂቅ ፡ ድኩማን ። አዳም ፡ ወደቂቀ ። ወ ርእየ ፡ ኢዮብ ፡ ደቂቀ ፡ ወደቂቀ ፡ ደቂቁ ፡ (፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፩ ። ፊልክ ፡ ፶፰ ። ዘፍ፴፱ ፡ ፲፫ ። አርጋ ። ኢዮ፵፪ ፡ ፲፮) ።

—፤ ሕዝብ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤ አሽከሮች ፡ አርድእት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ምስጢሩ ፡ ታናሽነት ፡ ነው ። ደቂቀ ፡ እስ ራኤል ። ደቂቀ ፡ ለንጉሥ ። ደቂቀ ፡ አቤሴሎም ። ደ ቂቀ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ። ደቂቀ ፡ ነቢያት ። ደቂቀ ፡ ጥበብ ፡ (ዘፀ፩ ፡ ፩ ። እስቴ፪ ፡ ፪ ። ፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፳፱ ። ገድ ፡ ተክ ። ፬ነገ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ማቴ፲፩ ፡ ፲፱) ።

**ደቂቅና ፤** ልጅነት ፡ ታናሽነት ። በደቂቅናሁ ። ኢክልአ ፡ ደቂቅናሃ ፡ (ፊልክ ፡ ፀ፰ ። ፶፱) ።

**ደቃውቅ ፤(ቃት) ፤** ልጆች ፡ ታናናሾች ። ዕ ቀብ ፡ አንስቲያሆሙ ፡ ወተማሕፀን ፡ ደቃውቂሆሙ ። ደቃውቃት ፡ (ቅዳ ፡ ያዕ ። ኪዳ) ።

**ደቅ ፤** (ግእዝ ፡ ከማሁ) ፤ ልጆች ፡ አሽከሮች ፡ ወሽ ከሮች ። አንስት ፡ ወደቅ ። አምጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ደቀ ። ወ ረከበ ፡ ደቀ ፡ ንኡሳነ ፡ (ማቴ፲፱ ፡ ፳፭ ። ፲፱ ፡ ፲፫ ። ፪ነገ ፡ ፪ ፡ ፳፫) ።

—፤ ኅያላን ፡ ጕበዛዝት ፡ ወጣቶች ። ወጸውዐ ፡ ዳዊት ፡ አሐደ ፡ እምውስተ ፡ ደቁ ፡ ወይቤሎ ፡ ሑር ፡ ቅትሎ ። ለይትነሥኡ ፡ ደቅነ ። ደቀ ፡ ብንያም ፡ ወደቀ ፡ ዳዊት ፡ (፪ነገ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። ፪ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭) ።

—፤ ስሙ ፡ በገር ፡ በጣና ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ደሴት ። ስሙ ፡ ልሕኮት ፡ የደቅ ፡ ሰዎች ፡ የሚሠሩት ፡ ጥሩ ፡ ሸክላ ። (ማጥም ፤ ያጤ ፡ ቴ ፡ ገረድ ፡ ኰብልላ ፡ ደቅ ፡ ስትገባ ፡ ያደት ፡ አገዛማሪ ፡ ላጤ ፡ ቴ ፡ ሲያወራ) ፤ እጅጉን ፡ ተሰብራ ፡ በሙሉ ፡ ኂሩት ፡ ደቃስኝ ፡ አሉ ።

**ደቀ ፡ መዝሙር ፤(መዛሙርት) ፤** በቁሙ ፡ ተማሪ ፡ ዳዊት ፡ ደጋሚ ።

**ደቀ ፡ ጽርሕ ፤** ዙፋን ፡ ጠባቆች ፡ የልፋኝ ፡ አሽ ከሮች ፡ (ኢሳ ፡ ፴፱ ፡ ፯) ።

**ደቂቃ ፤(ብ ፡ ደቃይቅ ። ዐረ ፡ ደቂቀት) ፤** በቁሙ ፡ ታናሽ ፡ የጊዜ ፡ ክፋል ፡ የሰዓት ፡ ወይም ፡ የኬክ

ሮስ ፡ ፳፫ ፤ ከሥልሳው ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ (አቡሻ ፡ ፶፬) ።

**አድቀቀ** ፤ አደቀቀ ፡ አስደቀቀ ፡ ፈጨ ፡ ደቁሰ ። ያደቅቆ ፡ ለዘሎሉ ፡ (ዳንዬ ፡ ፱ ። ዘፀ፴፪ ፡ ፳) ።

**መድቀቅ** ፤ **ት** ፤ ማድቀቂያ ፤ ማላሚያ ፡ መደ ቂሻ ። ወያደቅቅዎ ፡ በመድቀቅ ፡ (ዘኍ ፲፩ ፡ ፰) ።

**ደቅደቀ** ፤ (**ተቀ ፡ ግ**) ፤ በቁመሙ ፡ ደቀደቀ ፡ (ዐማርኛ) ።

**አንደቅደቀ** ፤ አንደቀደቀ ፡ ተንደቀደቀ ፡ የመ ማሪያ ፡ የገርሮ ።

**ደቅሰ** ፤ **ሰት** ፤ (**ደቀሰ ፡ ይዴቅስ ፡ ይደ ቅስ ። ዐረ ፡ ዱከስ**) ፤ ማንቀላፋት ፡ በእንቅልፍ ፡ መ ደገፍ ፡ መድቀስቀስ ፡ እንደ ፡ ሬሳ ፡ መኾን ። **ደቀሰ ፡ ወ ኖመ ። ደቀሱ ፡ ኖሙ፡ትኪ ። ወኢይዴቅስ ፡ ዘየዐቅበከ** ፡ (ማቴ፳፭ ፡ ፭ ። ኖሑ፪ ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፻፳) ።

—፤ መተኛት ፡ መጋደም ፡ መጣመር ። **ደቀሱ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ዘይዴቅስ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ወላዕሌሃ ፡ ትክት** ፡ (አዋል ፡ ሲኖዶ) ። መደቁስ ፡ መደቋቁስ ፡ ገቢር ። ወይም ፡ ዐጉል ፡ ተገብሮ ፡ (ጥዶ) ፡ መደቁስ ፡ ተደቁሽ ፡ መኾን ።

**ድቁስ** ፤ (**ሳን ፡ ሳት ፡ ቅስት**) ፤ ያንቀላፋ ፡ እን ቅልፍ ፡ የወሰደው ፡ የደበተው ። **ዘይነግሮ ፡ ለድቁስ ። ኢ ድቁስ ፡ ወኢንዉም** ፡ (ሢራ፳፪ ፡ ፰ ። መጽ ፡ ምስ) ። በቁሙ ፡ ድቍስ ፡ ብትን ፡ ድልኽ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ድቃስ** ፤ ክቡድ ፡ እንቅልፍ ፡ እንደ ፡ ሞት ፡ ያለ ፡ ስልምታ ፡ ሽልብታ ፡ እንጕልቻ ። **ወፈነወ ፡ እግዚ ፡ ድ ቃስ ፡ ላዕለ ፡ አዳም** ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፳፩ ። መዝ ፡ ፻፴፭ ። ም ሳ፳ ፡ ፬ ። ሉቃ፱ ፡ ፴፪) ።

**ምድቃስ** ፤ ማንቀላፊያ ፡ መተኛ ፡ መኝታ ፡ የን ቅልፍ ፡ ቦታ ። **ኢይኑም ፡ ውስተ ፡ ሠናይ ፡ ምድቃስ ፡ አላ ፡ ውስተ ፡ ሐመድ** ፡ (ቄድር) ።

**ዶር ፤—ጥሩ ፡ ወርቅ ፤—ደዊር ፡ ዶረ ፡ ደወረ ።**

**ደረብ** ፤ **ቦት** ፤ (**ደረበ ፡ ይደርብ ፡ ይድ ርብ ። ከዐበ ፤ ደበለ**) ፤ መደረብ ፡ መደራረብ ። ደርብ ፡ ደረባ ፡ ድርብ ፡ እንዲሉ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ደርበየ** ፡ (**ተቀ ፡ ግ**) ። **ዕብ ፡ ዳርቤን**) ፤ ወረወረ ፡ ወጋ ፡ መታ ፤ ደራርበ ፡ መላልሶ ። **ደርቢዮ ፡ ሲኩናቶ ፡ ውስተ ፡ አረፍት ። ደርብዮ ፡ ሾ ያንው ። ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘይደረቢ ፡ ኲናተ ፡ ይወግዖ ፡ ለዘተ ፈነወ ፡ ኀቤሁ ። ለደርብዮቱ ። ይደረቢ ፡ በሾ ያንዊሁ** ፡ (ሄኖ ፡ ፲፱ ፡ ፲ ። መቃ ፡ ፲፱ ። አፈ ፡ ተ፳፪ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፰) ። እንደርቢ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ዘ ረበን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ተደራበየ** ፤ ተወራወረ ፡ ተዋጋ ፡ ተማታ ። **ወራ ዙትኒ ፡ ተደራበይዎሙ ። ይደራበዩ ፡ ዐደው ፡ በአሕ ዛት** ፡ (ዮዲ፲፯ ፡ ፲፪ ። ፊልክ ፡ ፪) ።

**ዳርበን** ፤ (**ሰብራ**) ፤ መድጕጸ ፡ ላሕም ፡ አር ቃሽ ፡ መውጊያ ፡ መንጕጫ ፡ ህየንተ ፡ ጅራፍ ።

**ደረግ** ፤ **ጎት** ፤ (**ደረገ ፡ ይደርግ ፡ ይድርግ ። ሱር ፡ ዳራግ**) ፤ ማድረግ ፤ ማደራጀት ፡ ደረጃ ፡ መሥ ራት ፤ በደረጃ ፡ መውጣት ፤ መግጠም ፡ ማዛወግ ፡ አንድ ፡ ማድረግ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በደረገ ፡ ፈንታ ፡ አድረገ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። **ኅቡረ ፡ ኢታድርግ ። ኢድሬጎ ፡ በአ ልጓሚሁ** ፡ (ሚራ፳ ፡ ፰ ። ቄር) ።

**አድረግ** ፤ አስደረገ ፤ ደረጃ ፡ አሠራ ። በቁሙ ፡ ሠራ ፡ አደረገ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ተዳርገ** ፤ ተሠራ ፡ ተደረገ ፤ ተደራጀ ፡ ገጠመ ፡ አንድ ፡ ኾነ ። **ይደረጉ ፡ ክልኤቱ** ፡ (ሕዝ፩ ፡ ፲፩) ።

**ድሩግ** ፤ (**ጋን ፡ ጋት ፡ ርግት**) ፤ የተደረገ ፡ ድ ርግ ፤ ድርጁ ፡ ዝግጁ ፤ ቅንጁ ።

**ድርገት** ፡ (**ቃት**) ፤ ማድረግ ፤ መደረግ ፡ አድር ጎት ፡ አደራረግ ፤ ድርጊያ ፡ ድርጊት ። አንድነት ፤ አንድ ፡ መኾን ፤ ማኅበር ፡ ሸንጎ ፡ ጉባኤ ። **ከመ ፡ ይውርሰ ፡ መ ንግሥተ ፡ ወድርገተ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ይነሥኡ ፡ አክሊለ ። ድርገት ፡ ምስለ ፡ መላእክት ። ድርገተ ፡ አንው ። ድ ርገቶሙ ፡ ለቅዱሳን ። ንፍረት ፡ በቂቃወ ፡ ብካይ ፡ ማእከለ ፡ ድርገት ፡ ማሕሌት** ፡ (ቀሌ ። ቄር ። ፊልክ ፡ ፺፬ ። ተረ ፡ ቄር ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ድርገት** ፤ (**ቃት ። ዐረ ፤ ደረጀት ። ሱር ፡ ዳርጋ**) ፤ ደረጃ ፡ ዕርከን ፡ ማዕርግ ፤ የቤት ፡ የሹመት ። **ዘይሴብሕዎ ፡ ድርገታተ ፡ ሐራ ። ወዠሉ ፡ ድርገታት** ፡ (ድጓ ። ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ደርግ** ፤ አንድነት ፤ አንድጋ ፤ መጋጠሚያ ። **ሐ ውጺ ፡ ማኅበረነ ፡ ወባርክነ ፤ በደርግ ። በደርገ ፡ አን ቀጸ ፡ ዐጺድ** ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፳፯ ። ዘዐ፴፯ ፡ ፲፫) ።

**ደርግ** ፤ ባንድነት ፡ አንድ ፡ ኹኖ ፤ ዐብሮ ። **ደ ርገ ፡ ይፌውስ ። ዐጠነ ፡ ደርገ ፡ ምስሌሆሙ ። ከመ ፡ ታዕርፍ ፡ ነፍሶሙ ፡ ወይኩኑ ፡ ደርገ ፡ ምስለ ፡ ሊቃ ናት ፡ ለማያውያን** ፡ (ቄር ። ገድ ፡ ተክ ። ግንዘ) ።

**ደርጕ** ፤ (**ብ ፡ ደራግሙ**) ፤ ወረንጦ ፡ መቈን ጠጫና ፡ ማጣበቂያ ። ሚደርጕ ፤ ሚ ፡ ወረንጦው ፡ ሹሉ ፡ ደርጕ ፡ መቈንጠጫው ።

**ደርግሐ** ፤ (**ተቀ ፡ ግ**) ፤ ደረተ ፡ ሰፋ ፡ ጠቀመ ። ሠራ ፡ አማገ ፤ ድርና ፡ ማጉን ፡ አዛወገ ፤ አንድ ፡ አደረገ ።

**ድርጋሕ** ፤ ድሪቶ ፡ ደባደቦ ፡ ሦስቲዮና ፡ አራቲዮ ፡ ኹኖ ፡ የተሰፋ ፡ የተጠቃቀመ ፡ ቆብ ፡ እርጎ ፡ ጋቢ ። ዐዲስ ፡ ልብስ ፡ ዐርብ ፡ ወዋ ፡ ገና ፡ ያልተሰፋ ። **አልቦ ፡ ዘይጠ ቅብ ፡ ግምደ ፡ ድርጋሐ ፡ ልብስ ፡ ውስተ ፡ ሥጠተ ፡ ልብስ ፡ ብሉይ** ፡ (ማቴ፱ ፡ ፲፯ ። ማር፪ ፡ ፳፩ ። ሉቃ፭ ፡ ፴፮) ።

**ዳርጎ** ፤ **ጎት** ፤ (**ዳረገ ፡ ይዳርግ ፡ ይዳረግ**) ፤ መዳረግ ፡ ማስተላለፍ ፤ ሰጪን ፡ ከተቀባይ ፡ መግጠም ፡

የገንዘብ ፡ የቀለብ ። ሰእመ ፡ ዳረገ ፡ ሦያጤ ፡ ባዕለ ፡ ተሣያጤ ፡ ብእሲ ፡ በንዋይ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፯) ።

**ዳራጊ ፡ (ጊት ፡ ግያን ፡ ያት)** ፤ በቁሙ ፤ የሚዳርግ ፡ ሰጭ ፡ አሰጭ ፤ ድርጎ ፡ አውጭ ፡ ባለገንዘብ ።

**ተዳረገ** ፤ በቁሙ ፤ ተደራረገ ፡ ተጋጠመ ፤ ተዋደደ ፡ ተስማማ ። ዘይዳረግ ፤ ተዳርጎ ፡ (ፍ ፡ ነ) ።

**ድሩግ** ፤ የተዳረገ ፤ ገንዘብ ፡ ሰው ። ንዋየ ፡ ድሩግ ፡ ንዋይ ፡ ድሩግ ፡ (ፍ ፡ ነ) ።

**ድርጎ** ፤ በቁሙ ፤ ጕርሻ ፡ ዳረጎት ፡ ተዳራጊ ፡ የሚቀበለው ። በእንተ ፡ ድርጎ ፡ ዘይዳረግዎ ፤ ኢትክውን ፡ አማፂ ፡ ተዳርጎ ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረተ ፡ ዳራጊ ፡ ወተዳራጊ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፯) ።

**ደራጎን** ፤ የየብስና ፡ የባሕር ፡ ዘንዶ ፡ እግርና ፡ ክንፍ ፡ ገርና ፡ ቀንድ ፡ ያለው ፤ በንጕል ፡ ከኹሉ ፡ አለኹ ፡ የሚል ። ምስጢሩ ፡ ድርገትና ፡ ባለድርጎነት ፡ ነው ፤ ድሩግ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ (ገድ ፡ ጊዮ) ።

**ድርድር ፤—በቁሙ ፡ ዐማርኛ ፤—ደራር ፡ ደረ ፡ ደርደረ ።**

**ዶርሆ ፤—በቁሙ ፡ ዶሮ ፤—ዶር ፡ ደወር ።**

**ድርሀም ፤ (ጽር ፡ ድራኽሚ ። ዐረ ፡ ዲርሀም)** ፤ የገንዘብ ፡ ስም ፤ ድሪም ፡ እንደ ፡ ዲናር ፡ ያለ ፡ የፋርስ ፡ ገንዘብ ። ዲናርና ፡ ድርሀም ፡ ትክክል ፡ ናቸው ፡ (ስንክ ፡ የካ፳ ። ግብ፲፱ ፡ ፲፱ ። ቀሌ) ።

**ድርሀማት ፤ ደራህም** ፤ ድሪሞች ። መጠነ ፡ ዐሥርቱ ፡ ድርሀማት ። ደራህም ፡ ዘሕልያን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፭ ፡ ፩) ።

**ደርዝ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ ድርብ ፡ ስፌት ፡ እንደ ፡ መከዳ ፡ ስፍ ፡ ያለ ፤ ወይም ፡ የባብ ፡ ጥርስ ፡ የጥልፍና ፡ የጥራዝ ፡ ዐይነት ።

**ደረዘን ፤ (ጽር ፡ ዲምርዘን** ፤ ንድቀ ፡ የግንብ ፡ ሥራ ፡ (ሕዝ፵፩ ፡ ፲፪) ። ጠቀመን ፡ እይ ።

**ድርያሚን ፤ ድብርያሚን ፡ (ዕብ ፡ ዲብሬይ ፡ ሀያሚም)** ፤ የብሉይ ፡ መጽሐፍ ፡ ስም ፤ እንደ ፡ ነገሥት ፡ ያለ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ማለት ፡ ነው ። ሕጹጻንን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (አቡሻ) ።

**ደረክ ፤ ከት ፤ (ደረከ ፡ ይደርክ ፡ ይድርክ ። ዕብ ፡ ዳራኽ ። ሱር ፡ ድራኽ ፤ ኬደ ፡ ረገፀ)** ፤ መጥናት ፡ መጠንከር ፤ መድረቅ ፡ መሻከር ፤ መክፋት ፡ መጨከን ። ደረቀ ፡ ማለት ፡ ቅሉ ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ትፀወግ ፡ እምሕምዘ ፡ አፍዖት ፡ ወትደርክ ፡ እምተጸላ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

—፤ መንደርከክ ፡ ሙብሰል ፡ መቅላት ፤ የፍሬ ፡ የፍሕም ።

**ድሩክ ፤ (ክን ፡ ክት ፡ ርክት)** ፤ የጠና ፡ ጥኑ ፤ ብርቱ ፡ ጠንካራ ፤ ደረቅ ፡ ሸካራ ፤ ክፉ ፡ ጨካኝ ። (የተንደረከከ ፡ ብስል ፡ ቀይ) ። ማእሰር ፡ ድሩክ ። ልሳን ፡ ድሩክ ። ቃል ፡ ድሩክ ። ወዒሳውብ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ድሩክ ፡ ወሐቃባዊ ፡ ወጸጓር ፡ ወዘሎ ፡ ግብሩ ፡ ድሩክ ። ድርክት ፡ ከመ ፡ ሲኦል ፡ ቅንአት ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ ፳፩ ። ጎዳ፳ ። ኩፋ ፡ ፲፱ ። ማሕ፰ ፡ ፯) ።

**ደርከኖ ፤ (ዕብ ፡ አርጋማን)** ፤ ኀምራዊ ፡ ቀይ ፡ ሕብር ፡ ደባባ ፡ የበሰለ ፡ ፍሬ ፡ ወይም ፡ የጥቍር ፡ ወይን ፡ ደም ፡ የሚመስል ። በርሱ ፡ የታለለ ፡ ልብስ ፡ ፈትል ። መጻሕፍት ፡ ግን ፡ በያክንት ፡ ፈንታ ፡ ደርከኖ ፡ ይላሉ ፤ መምህራንም ፡ ሰማያዩ ፡ ይሉታል ፡ (ራእ፱ ፡ ፲፰) ።

**አድረከ ፤ (አድረገ)** ፤ አጠና ፡ አበረታ ፡ መድረክ ፡ ሠራ ፡ አጋጠመ ።

**መድረክ ፤ (ብ ፡ መዳርክ)** ፤ በቁሙ ፤ መረጋገጫ ፡ ከመግቢያ ፡ በታች ፡ የሚጋደም ። መድረከ ፡ ኆኅቱ ። ኅበ ፡ መድረከ ፡ ኆኅትክሙ ። መዳርክ ፡ ወመሳክው ፡ (ሢራ፮ ፡ ፴፮ ። ያዕ፳ ፡ ፱ ። ሕዝ፵፩ ፡ ፲፮) ።

**ድርኵኵት ፤ (ታት)** ፤ የመግቢያ ፡ ቍላ ፡ ወንደ ፤ በመድረኩ ፡ ላይ ፡ የሚቆም ፡ የሚተከል ፤ ወይም ፡ ቤቱው ፡ የመድረኩ ፡ ፍልፍል ፡ መቋሚያውና ፡ መትከያው ። ከመ ፡ ማዕጾ ፡ እንተ ፡ ተዐውድ ፡ ውስተ ፡ ድርኵኵታ ፡ (ምሳ፳፮ ፡ ፲፬ ። ዘካ፲፪ ፡ ፪ ። ፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፴፩) ።

**ድርክሜ ፤ (ጽር ፡ ድራኽሚ ። ዕብ ፡ ቤቃዕ)** ፤ ድሪም ፡ ድርሀም ፤ የዲድርክም ፡ አላድ ። ድርክሜ ፡ አሐቲ ። ድርክሜኑ ፡ ለለ ፡ ዐለት ፡ (ዘፀ፴፱ ፡ ፫ ። ጦቢ፭ ፡ ፲፬) ።

**ደርከኖ ፤—ኀምራዊ ፤—ደሪክ ፡ ደረከ ።**

**ዳሮም ፤ (ዕብራ)** ፤ ደቡብ ፤ የሰሜን ፡ አንጻር ፡ (ሕዝ፳ ፡ ፵፯) ።

**ድራሞ** ፤ ደበክ ፡ የንቅልፍ ፡ ጋኔን ፡ የሚጫን ፡ የሚደብት ፤ ይልቁንም ፡ በጸሎትና ፡ በጉባኤ ፡ ጊዜ ። የመነኮሳት ፡ ደረጦኛ ፡ ጋኔን ፡ ገዘሙት ፡ የሚያሳክክ ፡ የሚያስፎክት ፡ ዕከክም ። ያስሕክ ፡ ለሥጋ ፡ ወይሬስዮ ፡ ለብእሲ ፡ ይዝሐቅ ፡ ሥጋሁ ፡ ዘእንበለ ፡ አፀርያ ፡ (አረጋ ፡ ድ፯) ።

**ደረመን** ፤ ዕክክ ፡ ፎክት ፡ ፈረሳቤት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ድርማንቅ ፤ (ቃት)** ፤ የውስጥ ፡ የገላ ፡ ልብስ ፡ ሱሪ ፡ ቀሚስ ፤ ልብ ፡ አልባ ፡ ጥብቆ ፤ ዐጭር ፡ ቍምጣ ፡ ወይም ፡ ረዥም ፡ ጠባብ ፡ የወንድ ፡ የሴት ። ድርማንቅ ፡ ዘዐጌ ። ድርማንቃቲሆሙ ፡ (ሕዝ፵፬ ፡ ፲፰ ። ዳን፫ ፡ ፳፩ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፬) ።

—፤ የመንገዝ ፡ ስም ፤ የቄስ ፡ የመነኰሴ ፡ ግንዛት ፡ አስተሳሰሩ ፡ እንዳስኬማ ፡ ያለ ፤ ፯ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ያለበት ። ድርማንቅ ፤ ፪ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ድርማ ፡ ንቅ ፡ ወይም ፡ ድር ፡ ማንቅ ፤ ድርማ ፡ ንቅ ፡ ሲኾን ፡ ድርማ ፡ ከድራሞ ፤ ንቅ ፡ ከንቅሀ ፡ የወጣ ፡ ይመስላል ፤ የሚለበስ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ነውና ። ድር ፡ ማንቅ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፤ አለጥርጥር ፡ ድር ፡ ከድርዕ ፡ ማንቅ ፡ ከዐንቀ ፡ መጥቷል ፡ ያሰኛል ። የመግንዙም ፡ ስም ፡ በቁሙ ፡ ድርን ፡ ማሰረያን ፡ ያሳያል ። (ተረት) ፡ ድር ፡ ቢያብር ፡ አንበሳ ፡ ያስር ።


**ድርሙስ**፤ (ጽር ፡ ድሪሙ) ፤ ዱር ፡ ደን ሐቅል ፡ ብዙ ፡ ዛፍና ፡ ዕንጨት ፡ ያለበት ። ሐነጸ ፡ ቤተ ፡ ድርሙስ ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፪) ። ድርሙስ ፡ ባለው ፡ ደግሞ ፡ በገዳም ፡ ይላል ።

**ድርንቅ**፤ (ዕብ ፡ ስላው) ፤ የባሕር ፡ ቆቅ ፡ ድርጭት ፤ ፍርፍርት ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ የሚኖር ፤ የሥጋ ፡ ያፈረጠመ ፡ ዐንገቱ ፡ ከክንፉ ፡ የገጠመ ። ድርንቅ ፡ ማለት ፡ ቃሉ ፡ ከደቂት ፡ ስፍር ፡ መጥቷል ፤ ፀምቆ ፡ ደርንቆ ፡ እንዲሉ ። ያንገቱን ፡ ማጠር ፡ የሥጋ ውን ፡ መጥበቅ ፡ ያሳያል ። ወሶበ ፡ ሰአሉ ፡ መብልዐ ፡



ፍግዓ ፡ ወተ ፡ ድላ ፡ ዐርገ ፡ እምውስተ ፡ ባሕር ፡ ብዙኅ ፡ ድርንቅ ፡ (ጥበ፲፱ ፡ ፲፪) ። ፍርፍርትን ፡ እዩ ።

**ድርዕ**፤ (ብ ፡ አድራዕ ። ዐረ ፡ ዲርዕ) ፤ ጥሩር ፡ የብረት ፡ ቀሚስ ፡ ሲደርያ ፡ በሰልፍ ፡ ጊዜ ፡ የሚ ለበስ ። ወልታ ፡ ወድርዐ ፡ እንግድዓ ። ዘቦ ፡ ድርዐ ። ይለብስ ፡ ድርዐ ፡ ጽድቅ ። አልባሰ ፡ ድርያሙ ። አድ ራዕ ፡ ወአቅስስት ፡ (ሔኖ፰ ፡ ፩ ። ነሐ፱ ፡ ፲፭ ። ጥበ፭ ፡ ፲፱ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፱ ። ፪ዜና ፡ ፳፯ ፡ ፲፰) ። በምስጢር ፤ ጥብ ዐት ፡ ትዕግሥት ፡ ይኾናል ። በድርዐ ፡ እንግድዓ ፡ ወበ ጽንዐ ፡ ሃይማኖት ፡ ወረሰ ፡ መኑ ፡ ሰማ ፡ (ድጓ) ።



ድርዕ ።

(ጥ) **ደርዐ**፤ ተጠረረ ፡ ጥሩር ፡ ለበሰ ። ጨከነ ፡ ታ ገሠ ። ሰማዕት ፡ ረከቡ ፡ ተስፋሆሙ ፡ ደሪዮሙ ፡ ወተ ዐጊሦሙ ፡ (ድጓ) ።

**ድርቀ**፤ (ትግ ፡ ግፋ ፡ ግፌትረ) ፤ ደረቀ ፡ ከረረ ፤ ደረቅ ፡ ኾነ ። ዘሩ ፡ ደረክ ፡ ነው ፡ (ዐማርኛ) ።

**ድሪቆን**፤ **ድርኳቆን**፤ (ዕብ ፡ ርቂዕ) ፤ የሰማይ ፡ ስም ፡ ፬ኛ ፡ ሰማይ ፡ ኢረር ፤ ፬ኛንቱ ፡ ሰጠፈር ፡ ነው ፤ ሰላይኞቹ ፡ ግን ፡ ሰሰባቱ ፡ አንደኛ ፡ ይባላል ፡ (አ ዋል ። ቀሌ) ።

**ዶርቃስ**፤ (ጽር ፡ ዶርካስ) ፤ ሬቆ ፡ ወይጠ ልንና ፡ ጠቢታን ፡ እዩ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ ድሪቶ ፡ ጿሕ ፡ ጀባ ፡ ይሉታል ፡ (ግ ብ፱ ፡ ፴፯ ፡ ፴፱) ።

**ደሪር**፤ **ሮት**፤ (ደረ ፡ ደረረ ፡ ይደርር ፡ ይድርር) ፤ ማረቅ ፤ እራት ፡ ማብላት ፡ መጋበዝ ። መ ወዘም ፤ ዋዜማ ፡ መቆም ። የደረረ ፡ ምስጢር ፡ መደበ ኛው ፤ ሰውን ፡ እንዳሞሌና ፡ እንደ ፡ ኰልኰል ፡ በሰደ ቃው ፡ ዙሪያ ፡ በድሮ ፡ ደርድሮ ፡ ማስቀመጥ ፡ ነው ፤ ደ ርን ፡ እዩ ።

**ተደረ**፤ (ይዴረር ፡ ይደረር) ፤ ታረተ ፤ እራት ፡ በላ ፡ ተጋበዘ ። እምድኅረ ፡ ተደሩ ። እንዘ ፡ ይዴረሩ ። ሶበ ፡ አኅለቁ ፡ ተደሮ ። ኖመ ፡ ዘእንበለ ፡ ይደረር ። ምንተ ፡ ተደረርከ ፡ (ሉቃ፳፪ ፡ ፳ ። ዮሐ፲፫ ፡ ፪ ። ጦቢ፰ ፡ ፩ ። ዳን፮ ፡ ፲፰ ። ሄርማ) ።

**ድራር**፤ (ራት) ፤ እራት ፤ የማታ ፡ ምግብ ። ም ሳሕ ፡ ሰው ፡ ድራር ። እመሂ ፡ በድራር ፡ ወእመሂ ፡ በምሳሕ ። ዘአሕጸጸ ፡ ድራሮ ፡ ይበይት ፡ ጥዑየ ፡ ሥ ጋሁ ። ይጸውም ፡ ድራረ ፡ (ሉቃ፲፬ ፡ ፲፪ ። ኪዳ ። ፈላስ ። ስንክ ፡ መስ፴) ።

—፤ ድሮ ፡ ዋዜማ ፤ ቅበላ ። ጾመ ፡ ድራረ ፡ ልደት ፡ ወ ጾመ ፡ ድራረ ፡ ጥምቀት ። ማዓትቲው ፡ ዘድራረ ፡ ጾም ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭ ። ድጓ) ። ዲቃላውን ፡ ደርደረ ፡ አን ደርደረ ፡ ብሎ ፤ ደረደረ ፡ አንደረደረ ፡ ተንደረደረ ፡ ማ ለት ፡ ከዚህ ፡ ይወጣል ፡ (ዐማርኛ) ።

**ደሪስ**፤ **ሰት**፤ (ደረሰ ፡ ይደርስ ፡ ይድ ርስ ። ዕብ ፡ ዳራሽ ። ሱር ፡ ድራሽ ። ዐረ ፡ ደረሰ) ፤ መድረስ ፡ በቁሙ ፤ በጽሕንና ፡ ለጸቀን ፡ ተመ ልከት ። ድርሳን ፡ መድረስ ፤ እየደረሱ ፡ መጻፍ ። ደረሱ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ወጸሐፉ ። ደሪሰ ፡ ድርሳን ። ዘደረሰ ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ ፡ (ቁር ። ስንክ ፡ ታኅ፳ ። ቅዳ) ።

—፤ መተርጐም ፡ መፍታት ፡ ማፍታታት ፤ መስበክ ፡ ማስ ተማር ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ መናገር ። አፈ ፡ ቱ ፡ ሕነ ፡ ዘይ እዜ ፡ ቶነበ ፡ በወንጌል ፡ እ ፡ ድርስ ፡ ለከሙ ። መዳሕ ፍተ ፡ ሕግ ፡ ደሪሶ ። ቀሲስ ፡ ይድርስ ፡ ድርሳነ ፡ ዘመ ፍትው ፡ (ተረ ፡ ቁር፲፱ ። ስንክ ፡ ግንቦ፳ ። ኪዳ) ።

**ደራሲ**፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት) ፤ የሚደርስ ፡ ደራሽ ፡ ባለድርሳን ፡ ተርጓሚ ፡ ሰባኪ ፡ ፍጹም ፡ ሊቅ ። ጎርጎርዮስ ፡ በዓለ ፡ መንክራት ፡ ወደራሲ ፡ ቅዳስያት ። ቤተ ፡ ደራስያን ፡ (አቡሻ ፡ ፶ ። ስንክ ፡ ሚያዝ፳፩) ።

**አድረሰ**፤ አደረሰ ፡ አስደረሰ ፤ ጨረሰ ፡ አስጨ ረሰ ። የበጋ ፡ የሥራ ፡ የድጋም ፡ የዜማ ።

**ተደርሰ**፤ ተደረሰ ፡ ተጣፈ ፡ ተተረጐመ ። ወሰ እመ ፡ ተደርሰ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፳) ።

**ድሩስ**፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ርስት) ፤ የደረሰ ፡ የተደረሰ ፡ ድርስ ፡ ፍጹም ።

**ድርሰት፤(ታት)**፤ መድረስ፤ መደረስ፤ አደ ራረስ፤ ደረሳ፤ ድርሻ። በቁሙ፥ የምስጋና፤ ቃል፤ ቅኔ፤ መልክ፤ ሰላምታ፤ ግጥም። ነባቤ፤ ዝንቱ፤ ድርሰት፤ አርብዓ፤ ወክልኤ። ድርሰታተ፤ ማሕሌት፤(ደራሲ። አርጋ)።


**ድርሳን፤(ናት)**፤ በቁሙ፤ የተደረሰ፤ የተ ጣፈ፤ ቃል፤ ነገር፤ ስራ፤ ንባብ፤ ረዥም፤ ስብከት፤ ትር ጓሜ፤ አፈታት፤ ጕሥዐተ፤ ልብ፤(ዲዝኩር)፤ መዝሙር፤ ምስጢሩ፤ የሚያጠግብ፤ ቃሉ፤ የሚያረካ፤ አነጋገሩ፤ የተ ባካ፤ ጣዕመ፤ ቃሉና፤ ኀይለ፤ ቃሉ፤ ደስ፤ የሚያሰኝ፤ ልብ፤ የሚነካ። ድርሳን፤ በእንተ፤ በነቢት፤ ዘደረሰ፤ ርቱዐ፤ ሃይማኖት። ድርሳን፤ ዘአባ፤ ያዕቆብ፤ ዘስ ሩግ፤ ዘደረሰ፤ በእንተ፤ እለ፤ ኖሙ፤ ካህናት፤ ወዲያ ቆናት። አባ፤ ኤፍሬም፤ ሶርያዊ፤ ደረሰ፤ ድርሳናተ፤ ብዙኃተ፤ ፈድፋደ፤(አዋል። ግንዘ። ስንክ፤ ሐም፲፰)። ድርሳነ፤ ማርያም፤ ድርሳነ፤ ሚካኤል፤ ቢል፤ ወግ፤ ታ ሪክ፤ ዜና፤ ማለት፤ ነው። ምስጢሩ፤ ነገር፤ ከማለት፤ ይገባል።

**ምድራስ፤(ሳት)**፤ ዝኒ፤ ከማሁ፤ ድርሳን፤ ድርሰት፤ ትርጓሜ፤ ስብከት። ዛቲ፤ መጽሐፈ፤ ምድ ራስ። ዘውእቱ፤ ሥሉጥ፤ ላዕለ፤ ቀድሶ፤ ቍርባን፤ ወላዕለ፤ ምህሮ፤ ወላዕለ፤ ምድራሳት። ወዘምድ ራሳት፤(መጽ፤ ምስ። ፩ቆሮ፤ ፲፬፤ ፳፮)።

—፤ ቤታ፤ ድርሳን፤ መድረሻ፤ መተርጐሚያ፤ ቤት፤ ክሲ ያን፤ ጉባኤ፤ የተማሪ፤ ቤት።

**ድርስ፤(ዐማርኛ)**፤ ልክ፤ እውነት፤ ርግጥ። ድርሱን፤ አገኘኹት፤ እንዲሉ። የምልክት፤ ስም፤ የዜማ፤ ምልክት፤ ፍጹም፤ ማለት፤ ነው።

**ድርስ፤ ድራይ፤(ጽር፤ ድሪስ፤ ድሪይ፤ ድሪዮስ)**፤ የዛፍ፤ ስም፤ በሉጥ። ባለብሉዮች፤ ግን ወይራ፤ ይሉታል፤(ኩፋ፤ ፲፫። ፲፱። ፴፮)። ለአብርሃም፤ አብ፤ ቀዳሚ፤ ዘአስተርአይኮ፤ ክርስቶስ፤ ቀትረ፤ ታ ሐተ፤ ዕፀ፤ ድርስ፤ ተሰቀልከ፤ ከመ፤ እቡስ፤(ደራሲ)።



ድርስ፤

**ደርሴኔ፤(ዐረ፤ ዳርሲን፤ ኒ)**፤ የሽቱ፤ ዛፍ፤ ስም፤ ዕንጨቱ፤ ብዙ፤ ዐይነት፤ ያለው፤ ቅመምና፤ መድ ኀኒት፤ የሚኾን፤ ቀናንሞን፤ እይ። ምቱረ፤ ልሳኖ፤ ኀበ፤ ህላዌሁ፤ አግብአ፤ ሶበ፤ ደርሴኔ፤ ወመዓረ፤ ቀ ብዐ፤(ስንክ፤ ጥር፳)።

**ደረት፤(ዐማርኛ)**፤ በቁሙ፤ እንግድዓ። ደ ርግሐ፤ ብሎ፤ ደረተ፤ ማለት፤ ከዚህ፤ ወጥቷል።

**ድርቲቆን፤—፪ኛ፤ ሰማይ፤—ድሪቆን።**

**ድስቡጣ፤(ጽር፤ ዴስፖታ፤ ቴ)**፤ ሊቀ፤ እግዚእ፤ ደግ፤ ገዥ። ድስቡጣ፤ ናይናን። ምንስቴ ቲሙ፤ ድስቡጣ፤(ግብ፤ ሐማ)።

**ደስዮ፤ዮት፤(ደሰየ፤ ይደሲ፤ ይድሲ። ዕብ፤ ዳሽ። ዐረ፤ ዳስ)**፤ መዳስ፤ መርገጥ፤ መደፍ ጠጥ፤ ማበራየት፤ ኬደን፤ እይ። ማስደሰት፤ ደስ፤ ማሰ ኘት፤ መጣድ፤ ማስረር። ደስታ፤ ድሰት፤ ከዚህ፤ ወጥ ቷል።

**ደሴት፤(ብ፤ ደስያት)**፤ በቁሙ፤ በባሕር፤ ውስጥ፤ ያለ፤ ባሕር፤ የከበበው፤ የብስ፤ ሀገር፤ ምድር፤ ተራራ፤ እንደ፤ ደቅ፤ እንደ፤ ሐይቅ፤ እንደ፤ ዚይ፤ ያለ። እለ፤ ይነብሩ፤ ውስተ፤ ዛቲ፤ ደሴት። ደሴተ፤ ኬጥ ኤም። አድለቅለቃ፤ ደስያት። ደስያተ፤ ዐበይት፤ (ኢሳ፳፤ ፮። ኤር፪፤ ፲። ሕዝ፳፮፤ ፲፰። ኩፋ፤ ፰)።

**ደስክ፤** ደባስ፤ ጋኒን፤ የሚፈግን፤ የሚጨቍን፤ የሚደብት፤ ድራሞን፤ ተመልከት።

**ደስክን፤ኖ፤(ብ፤ ደሳክን። ዕብ፤ ዲሾን። ሱር፤ ሬማእ። ዐረ፤ ሬእም)**፤ የዱር፤ የበረሓ፤ እን ስሳ፤ ቀንዳም፤ ቀንደ፤ ታላላቅ፤ ባለብዙ፤ ዐጽቅ፤ እንደ ርኤም፤ ያለ፤ የቀሊያና፤ የፌቆ፤ ወገን፤ ባለብሉዮች፤ ግን፤ ጐሽ፤ ይሉታል። ትራ፤ ወደስክን፤(ዘዳ፲፬፤ ፭)።



ደስክን፤

**ድስቅን፤(ጽር፤ ዲስኮስ)**፤ ታናሽ፤ ክብ፤ ጻሕል፤ የቍርባን፤ መሥሪያ፤ መቀደሻ። ኢያቅርብ፤ ቢድስቅን፤ ወኢያቅርብ፤ በጽዋዕ። ዲያቆን፤ ለቁስ፤ ማለት፤ ነው፤(ቀኖ፤ ኒቅ፲፫)።

**ደሲስ፤ ሶት፤(ደሰ፤ ደሰሰ፤ ይደስስ፤ ይድስስ። ዐረ፤ ደሰ)**፤ መሰጠር፤ መደበቅ፤ መከ ለል፤ መጋረድ። መዳሰስ፤ መዳበስ፤ በእጅ።

—፤ መንዳሰስ፤ ድሰስ፤ ማለት፤ ማጕንበስ፤ ደሳሳ፤ መ ኾን፤ የቤት፤ የጐጆ፤ ለፈስም፤ ይኾናል።

**ዳስ፤** በቁሙ፤ ጥላ፤ ከለላ፤ የሣር፤ የቅጠል፤ ጐጆ፤ ግርዶ፤ ከሐሩር፤ ከቍር፤ የሚሰውር። ዳስ፤ ዐ ቃቤ፤ ወይን። ከመ፤ ትግበር፤ ዳስ፤ ኀበ፤ ትነብር፤ (ኢሳ፩፤ ፰። ፲፮፤ ፫)።

**ደሳ፤** ዳውዝ፤ ምንጣፍ፤ የሱማሌ፤ ሥራ፤ ጭ ገራም።

**ደስጴዳ** ፤ (ጽር ፡ ዳሲፑስ ፤ ዳሲፖዳ) ፤ ጥንቸል ፡ የሽኮኮ ፡ ዐይነት ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፭ ፡፡ ዘዳ፲፬ ፡ ፯) ፡፡

**ዳታን** ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ሥርዐት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ፪ኛም ፡ ንቅዓዊ ፡ ይሉታል ፡ (ዘኊ፲፮ ፡ ፳፬) ፡፡

**ዴገ ፤ ዲጋ ፤ —ሸመቀ ፤ ሸመቃ ፤ —ደየገ** ፡፡

# ሀ

**ሀ** ፤ ፳፯ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፤ ስሙ ፡ ሆይ ፤ ሀውይ ፡፡ ቍጥሩ ፡ ዐምስት ፤ እኅዝ ፡ ሲኾን ፡ ሀ ፡ ኀምስት ፡ ቱ ፡ ይባላል ፡፡ ዕብራውያን ፡ ግን ፡ ዐምስትን ፡ መደብ ፡ አድርገው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነቍጣ ፡ እየጨመሩ ፡ ዐምስት ፡ እልፍ ፡ ይሉታል ፤ ይኸውም ፡ ኀምሳ ፡ ምእት ፡ ወይም ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ ምስጢሩ ፡ ኀሙስንና ፡ የኀሙስን ፡ ፍጥረት ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ምስጢረ ፡ ጥምቀትን ፡ ያሳያል ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፳—፳፫) ፡፡

**ሀ ፤ —አ** ፤ (ሐ ፡ ኀ ፡ ዐ) ፤ የግስ ፡ ዐመል ፤ የራብዕ ፡ የሳድስ ፡ ሥረይ ፡፡ የአን ፡ ፍች ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፤ አንድ ፡ ነው ፡፡ ፪ኛም ፡ (ዕር፪ ፡ ቍ፲፱) ፡፡

**ሀ ፤ —ሃ** ፤ የግእዝ ፡ ወራሽ ፡ ለሩቅ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፤ ግእዙ ፡ ለወንድ ፤ ራብዑ ፡ ለሴት ፡ ትራስ ፡ እየኾን ፡ በተጸውዖ ፡ ስም ፡ ሲገባ ፤ ን ፡ ወደ ፡ ይኾናል ፡፡ **ርኢ ፡ አዳምሀ ፡ ወሔዋንሃ** ፡፡ መጣፍ ፡ ግን ፡ በጣፎች ፡ ስሕተት ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ሳይለይ ፡ ለኹሉም ፡ ራብዑን ፡ ብቻ ፡ ያገባል ፡፡ **ዘካርያስሃ ፡ ወኤልሳቤጥሃ** ፡፡ ሃሌታ ፡ ሲጣፍ ፡ የሚገባው ፡ በግእዝ ፡ ሀ ፡ ሲኾን ፤ ሃሌ ፡ ተብሎ ፡ በራብዕ ፡ እንዲጣፍ ፡ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ፡፡

**ሁ** ፤ (ሁ—ኍ) ፤ ጥያቄ ፡ የጥያቄ ፡ ቃል ፤ ንኡስ ፡ አገባብ ፤ ፍችው ፡ ን ፡፡ በቃል ፡ መጨረሻ ፡ እንደ ፡ ዝርዝር ፡ ትራስ ፡ እየኾነ ፡ ይገባል ፡፡ **ኢትክነሁ ፤ ከመ ፡ ዝ ፡፡ እምኔየሁ ፡ ይሴወር ፡፡ ትሰአሉኒሁ ፡ መዳእክሙ** ፡ (ዓሞ፪ ፡ ፲፩ ፡፡ ኢዮ፴፰ ፡ ፯ ፡፡ ሕዝ፳ ፡ ፫) ፡፡ **ቦሁ ፡ አመ ፡ ነገሩክሙ ፡፡ አልቦሁ ፡ አመ ፡ አንበብክሙ ፡፡ አኮሁ ፡ አነ ፡ ዘአወልድ** ፤ እየለም ፡ በነባር ፡ አንቀጽ ፡ ይገባል ፡፡ ኍ ፡ ደግሞ ፡ ሁ ፡ በገባበት ፡ ይገባል ፤ አገባቡን ፡ በቦታው ፡ እይ ፡፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሁ ፡ ምናልባት ፡ ይኾናል ፡፡ **እመሰ ፡ ትብሉሁ ፡፡ ሶበሁ ፡ የአምር ፡ በዓለ ፡ ቤት ፡፡ እመ ፡ አንተሁ ፡ ክርስቶስ** ፡ (ኢሳ፴፮ ፡ ፯ ፡፡ ማቴ፳፬ ፡ ፵፫ ፡፡ ሉቃ፳፪ ፡ ፷፯) ፡፡

**ሁ** ፤ (ውእቱ) ፤ ባዕድ ፡ ዝርዝር ፡ ጠቃሽ ፤ ዐጸፋ ፡ ምእላድ ፡ ላንድ ፡ ለሩቅ ፡ ወንድ ፤ በሩቅ ፡ ወንድ ፡ አንቀጽ ፡ ለሚጠራ ፡ ኹሉ ፡፡ ርኡ ፡ ያ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ **ብእሲሁ** ፤ ሰውየው ፡ ያ ፡ ሰው ፡፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፡ እየለ ፡ በሩቆች ፡ ብቻ ፡ ይረባል ፡፡ ኪያ ፡ ኪያሁ ፤ ለል ፡ ለሊሁ ፤ ቅድሜሁ ፡ ድኅሬሁ ፡ ቀደሳሁ ፡ ወደሳሁ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡፡ ዝ ፡ ዝንቱ ፡ ከዘ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ውእቱም ፡ ከሁ ፡ ወጥቷል ፤ የርባታ ፡ መደቦች ፡ የሚባሉ ፡ ዐሥሩ ፡ ሰራዊት ፡ ሳይቀሩ ፡ ኹሉም ፡ የሁ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፡፡

**ሂ** ፤ (ሂ—ኂ) ፤ ቀዋሚ ፡ ፍችው ፡ ም ፡ ደግሞ ፤ ግን ፤ ስንኳ ፡፡ ሂ—ሂ ፡ ኂ—ኂ ፤ ወይም ፡ ሂ—ወ—ሂ ፡ ኂ ፡ ወ—ኂ ፡ እያለ ፡ ብቻውንም ፡ ከወም ፡ ጋራ ፡ ይገባል ፡፡ **አነሂ ፡ አንተሂ ፡፡ አቡየሂ ፡ ወአነሂ ፡፡ እመሂ ፡ ሠርከ ፡ ወእመሂ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡፡ ክሃሊ ፡ አንበ ፡ ተጸናሰሂ ፡ ወተደልዎሂ ፤ ርኂበሂ ፡ ወጸጊበሂ ፤ ሐሚመሂ ፤ ወተፈሥሖሂ** ፡ (ፊልጵ፬ ፡ ፲፪) ፡፡ ግንና ፡ ስንኳ ፡ ሲኾን ፡ አገባቡ ፡ እንደ ፡ ወ ፡ ነውና ፤ የወን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ፡፡

**ሃ** ፤ ዝርዝር ፡ ጠቃሽ ፤ ላንዲት ፡ ለሩቅ ፡ ሴት ፤ በሩቅ ፡ ሴት ፡ አንቀጽ ፡ ለሚነገር ፡ ኹሉ ፡፡

**ሄ** ፤ ጊዜ ፡ ቦታ ፡ ወገን ፡ ማእዝን ፡ ዘርፍ ፡ እየኾነ ፡ ከሆል ፡ ጋራ ፡ ይነገራል ፡፡ ሆልን ፡ ተመ ፤ ኔ ፡ ከአሐቲ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ እንዳይገኝ ፤ ሄ ፡ ደግሞ ፡ ከሆል ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ አይገኝም ፡፡

**ሄ** ፤ (ዕብ ፡ ሄእ) ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ኃምስ ፤ ሀ ፡፡ እንሆ ፡ እንካ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (መዝ፻፲፰ ፡ ፴፫—፵ ፡፡ ሰቈ፩ ፡ ፭ ፡፡ ፪ ፡ ፭ ፡፡ ፫ ፡ ፲፫ ፡፡ ፬ ፡ ፭) ፡፡ ከና ፡ ሆ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ የተለየ ፡ ሥራ ፡ የላቸውም ፡፡

**ሀብ ፤ —በል ፡ ስጥ ፤ —ውሂብ ፡ ወሀበ ፡ ይውሀብ ፡ የሀብ** ፡፡

**ሀብአ ፤ —ዐበ ፡ ሸሸገ ፤ —ኀቢእ ፡ ኀብአ** ፡፡

**ሀቢብ ፤ ቦት ፤ (ሀበ ፤ ሀበበ ፡ የሀብብ ፡ ይሀብብ ፡፡ ዐረ ፡ ሰበ)** ፤ ሀብ ፡ ሀብ ፡ ማለት ፡ መስደብ ፡ መንቀፍ ፤ ማቃለል ፡፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሀበበ ፡ ፈንታ ፡ ተሀበበ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡፡ **ይትሀበቡኒ ፡ ወይዘነጕጕኒ ፡፡ ኢትትሀበቦ ፡ ለዘይትጋነይ ፡፡ በማኅክለ ፡ ቢጹ ፡ ይትሀበብዎ ፡ ለምታ** ፡ (ኤር፳ ፡ ፯ ፡፡ ሢራ፰ ፡ ፩ ፡፡ ፳፭ ፡ ፲፰) ፡፡

**ሀባቢ ፤ መሀበቢ ፤ መሀብብ ፤ መስተሀብብ ፤ (ብት ፡ ባን ፡ ባት)** ፤ የሚሳደብ ፡ ተሳዳቢ ፤ ነቃፊ ፡ አቃላይ ፡ ሀብ ፡ ሀብ ፡ ባይ ፡፡ **ኢይኩኑ ፡ ነባብያነ ፡ ወተናጋርያነ ፡ ፀሩዐ ፡ ወመስተሀብባነ** ፡ (ኪዳ ፡፡ ሮሜ ፩ ፡ ፴) ፡፡

**ሀቢብ ፤—ወዳጅ ፤—ሐቢብ ፡ ሐበ ፤ ሐበበ ፡ ሐቢብ ።**

**ሀብሀብ ፤—ዐስበ ፡ ዝሙት ፤ —ውሂብ ፡ ወሀበ ።**

**ሀቢው ፤ ዎት ፤ (ሀበወ ፡ የሀቡ ፡ ይሀቡ ። ወሀበ ፤ ሐበበ) ፤** መወፈፍ ፡ መዝነብ ፡ መንፈስ ፡ መተግብ ። ዝናምና ፡ ጠል ፡ መስጠት ፡ ማጥገብ ፤ ወሀቡንና ፡ ሐበቡን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**ሀበ ፤** ወጨር ፡ እንዳሽዋና ፡ እንደ ፡ ጠጠር ፡ ያለ ፡ የገዘናብ ፡ ቅንጣት ፡ ጠል ፡ ጤዛ ፡ ጠፈጠፍ ፤ ከዝናም ፡ በኋላ ፡ በማር ፡ በቅጠል ፡ ላይ ፡ የሚታቈር ፡ የሚንቈረ ዘገ ፡ ሕንበበ ፡ ማይ ። (ግጥም) ፡ የተንቈረዘዘው ፡ ደምኸ ፡ እንደ ፡ ጤዛ ፤ የሰብስቱ ፡ ማንቡል ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወሬዛ ። እንዘ ፡ ይትኄደግ ፡ ሀቡ ፡፡ እምነቀዐ ፡ ቅዳሴከ ፡ እር ወይ ፡ ወእስቀይ ፡ ሀቡ ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፲፫ ። ድራሲ) ።

**ሀበየ ፤—ሾመ ፡ ጠበቀ ፤—ሐብይ ፡ ሐበየ ።**

**ሆባይ ፤—እሞራ ፤ ዝንጀሮ ፤—ሀዊብ ፡ ሆበ ።**

**ሀብለ ፤—ዋሸ ፡ ዐበለ ፤—ሐቢል ፡ ሐብለ ።**

**ሀብለየ ፤—በዘበዘ ፤—ሐብለየ ፡ ሕብልያ ።**

**ሀገየ ፤—ባጀ ፤—ሐግይ ፡ ሐገየ ፡ ሐጋይ ።**

**ሀጕል ፤ ሎት ፤ (ሀጕለ ፡ ሀጐለ ፡ የሀጕል ፡ ይሀጐል) ፤** ማጣት ፡ መቸገር ፡ የያዙትን ፡ የረዘዙትን ፤ ወይም ፡ የሹትን ፡ የተመኙትን ፡ አለማግኘት ። ከመ ፡ ኢትህጐል ፡ ርስተከ ፡፡ ህጐል ፡ ወርቀከ ፡ እምትህጐል ፡ ዐርከከ ፡፡ ሀጐለ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ጠቢት ፡፡ ሀጐሉ ፡ ዕሴቶሙ ፡፡ የሀጐሉ ፡ ተስፋሆሙ ፡ (ሢራ፲፱ ፡ ፳ ። ፳፱ ፡ ፲ ። ጠቢ፰ ፡ ፺ ። ማቴ፳ ፡ ፱ ። ዲድ ፡ ፳፫) ።

**አህጐለ ፤** አጕለ ፤ አስታጐለ ፡ አስቀረ ። አጠፋ ፤ አስጠፋ ። ንጉሥ ፡ ጸብድ ፡ ያሀጕል ፡ ሕዘቢሁ ፡፡ ያሀጕሎሙ ፡ ለረሲዓን ፡፡ ከመ ፡ ኣህጕሎሙ ፡ እምገጸ ፡ ምድር ፡፡ ኀጢአት ፡ ነፍሶሙ ፡ ታሀጕል ፡ (ሢራ፲ ፡ ፫ ። ሔኖ፷ ፡ ፱ ። ኢሳ፳ ፡ ፯ ። ምሳ፳ ፡ ፲፱) ።

**አህጓሊ ፤ ማህጐሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤** የሚያጕል ፡ አጓይ ፤ አስታጓይ ፡ አስተጓጓይ ። አጥፊ ፡ አስጠፊ ፤ ጕጂ ፡ ገዳይ ፡ አስገዳይ ። ዝንቱ ፡ ደዊ ፡ ማህጐሊ ፡፡ ዛቲ ፡ ኀጢአት ፡ ማህጐሊት ፡፡ ፍትወት ፡ እኩይ ፡ ማህጐሌ ፡ ነፍሳት ፡፡ እመ ፡ መስሕት ፡ ወማህጐሊ ፡ አንተ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ፳ ፡ ፳ ። ዲድ፲፱ ፡ ፴፪) ። ሞት ፡ ገሃነም ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ማሀጐሊ ፡ ይላል ። ቢ አል ፡ ወማህጐሊ ፡ ኢይደግቡ ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፳) ።

**ማህጕል ፤ (ላን) ፤** ገዳ ፡ ከማሁ ፡ አጥፊ ፡ መጥፎ ። እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ማህጕላን ፡ ጸላእያነ ፡ ሠናይ ፡፡ እኩያን ፡ ወማህጕላን ፡ ምሎት ፡ (ዲድ፲ ፡ ፴፰) ።

**ተሀጕለ ፤** ታጐለ ፡ ቀረ ፡ ተዳፈነ ፡ የቅዳሴ ፡ የግብር ። ጠፋ ፡ ተበላሸ ፡ ሞተ ፡ ታጣ ፡ ተጐዳ ። ቱሀጕለት ግብጽ ፡፡ ይትሀጐል ፡ አሐዱ ፡ እምኔ ፡ አባልከ ፡፡ አብግዕ ፡ ዘተሀጕላ ፡፡ ተሀጕሉ ፡ እማእከለ ፡ ትዕይንት ፡ ኢትፍቅድ ፡ ተሀጕሎቶሙ ፡ (ዘፀ፲ ፡ ፯ ። ማቴ፳ ፡ ፳፱ ። ፲ ፡ ፯ ። ዘኍ፲፯ ፡ ፴፫ ። ሉቃ ፡ ሰገ፱ ፡ ፴፱) ። በተሀጕለ ፡ ፈንታ ፡ ሀጕለ ፡ ይላል ፡ የጣፈ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ተሀጕል ፡ ህጐለ ፡ ዐቢየ ፡፡ ከመ ፡ ኢትህጐሉ ፡፡ ወናሁ ፡ ህጐሉ ፡ እሙንቱ ፡ ወዓለምኒ ፡ (ሔኖ፶፫ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፴፯ ። ሉቃ ፡ ሰገ፱ ፡ ፳፱) ።

**ህጕል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ጕልት) ፤** የታጐለ ፡ የተጓጐለ ፤ መና ፡ የቀረ ። የጠፋ ፡ ጥፉ ፡ ብልሹ ፤ ከንቱ ፡ ከበታው ፡ የታጣ ፤ የኰበለለ ። ሕዝብ ፡ ህጕላን ፡ ምክር ፡፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ህጕለ ፡ ዕሴትከ ፡፡ ዘይትአመን ፡ በብዕሉ ፡ ህጕል ፡፡ መድኅኒሆሙ ፡ ለህጕላን ፡፡ ህጕላነ ፡ ሚጥ ፡ (ዘዳ፴፪ ፡ ፳፰ ። ሢራ፹ ፡ ፲፱ ። ሲኖ ዶ ። ዮዲ፱ ፡ ፲፩ ። ኪዳ) ።

**ህጕለት ፤** መታጐል ፡ መቅረት ። መጥፋት ፡ አጠፋፍ ፤ ጥፋት ፡ (ሔኖ፰ ፡ ፱ ። ፳፱ ፡ ፲፪) ። ህጕለተ ፡ ነፍስ ፡ (ሲኖዶ) ።

**ሀጕል ፤ (ላት) ፤** ጥፋት ፡ ጕዳት ፤ ችግር ፡ ዕጦት ። ፍኖት ፡ እንተ ፡ ትወስድ ፡ ውስተ ፡ ሀጕል ፡፡ ወልደ ፡ ሀጕል ፡፡ ሀጕል ፡ ዐቢይ ፡፡ በሀጕልክሙ ፡ እሥሕቅ ፡ (ማቴ፯ ፡ ፲፫ ። ዮሐ፲፯ ፡ ፲፪ ። ግብ፳፯ ፡ ፲ ። ምሳ፩ ፡ ፳፮) ። አጥፍኦ ፡ አሀጕሎ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሀጕል ፡ ይላል ። ጊዜ ፡ ሰንሚሥ ፡ ወጊዜ ፡ ለሀጕል ፡ (መክ፫ ፡ ፮) ።

**ተሃጐለ ፤ (ይትሃጐል) ፤** ተጓጐለ ፤ ተጣፋ ፡ ተጣጣ ።

**ሀጊናህ ፤ (ዕብራ) ፤** የቀና ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፤ የተቀ ከለ ፤ ባለዕርከን ፤ ፍኖት ፡ መዘምራን ፡ (ሕዝ፵፪ ፡ ፲፪) ።

**ህጕሬ ፤—ቀይ ፡ ቀለም ፤—ሕጕሬ ።**

**ሀጌር ፤ ሮት ፤ (ሀገረ ፡ የሀግር ፡ ይሀግር ። ዕብ ፡ ሀጌር) ፤** ዐዲስ ፡ በታ ፡ መሻት ፡ መፈለግ ፤ መመርመር ፤ ማቅናት ፡ መቈርቈር ፤ ምንጩን ፡ መማስ ፡ ዱሩን ፡ መጣስ ፤ መከተም ፡ መመንደር ፤ መዲና ፡ መሥራት ።

**ሀገር ፤ (ብ ፡ አህጉ(ጕ)ር ፤ ራት) ፤** በቁሙ ፡ አገር ፡ መንደር ፤ ከተማ ፡ ገጠር ፤ ብዙ ፡ ቤቶች ፡ የተሠሩበት ፤ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሚኖሩበት ፡ በያቅኚውና ፡ በየክፍሉ ፡ ገዥ ፡ አዛዥ ፤ ዳኛ ፡ መልከኛ ፡ ያለው ፤ ታላቁም ፡ ታናሹም ። ኢትክል ፡ ተከብቶ ፡ ሀገር ፡ እንተ ፡ ተሐንጸት ፡ መልዕልተ ፡ ደብር ፡፡ ሀገር ፡ ቅድስት ፡፡ ሀገረ ፡ እስራኤል ፡፡ ውስተ ፡ አህጕር ፡ ወአዕጻዳት ፡ (ማቴ፭ ፡ ፲፬ ። ሢራ፳፱ ፡ ፲፭ ። ኤር፫ ፡ ፳ ። ማር፮ ፡ ፶፮) ።

**ሀገራዊ ፤** ያገር ፡ ባላገር ፤ ባላባት ፡ አቅኚ ፤ ሹም ፡ ሽማግሌ ፡ አውራ ፡ ቀንድ ፡ ወይም ፡ ዕድር ፤ ልማድ ። (ተረት) ፡ ያገር ፡ ዕድር ፡ ለንጉሥ ፡ ያስቸግር ። ምግብና ፡ ሀገራዊት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**ሀገሬት**፤ ያቀኗት፡ የቈረቈሯት፡ የተወለዱበት፡ አገር፡ ርስት፡ ጕልት። ወዳጅ፡ ዘመድ፤ ዐብሮ፡ አደግ፡ ያገር፡ ሰው፡ ተወራራሽ፡ ወንድም። ብላ፡ ለጥበብ፡ እኅትየ፡ አንቲ፡ ወለአእምሮ፡ ሀገሬትከ፡ ረስያ፡ (ምሳ ፯፡ ፬)።

—፤ አንባ፡ ኵረብታ፡ ዕርድ፡ ምሽግ። ሀገሬት፡ ይእቲ፡ ለኵሎሙ፡ እለ፡ ይቀርብዋ፡ (ምሳ፲፡ ፲፰)።

—፤ ማኅበር፡ ጉባኤ፡ ድርገት። እንዘ፡ ሀለዉ፡ ቤምድር፡ ሀገሬት፡ ይኩኑ፡ ምስለ፡ ሰማያውያን፡ (ቀሌ)።

—፤ ባላገር፡ ባለጌ፡ አረመኔ፡ ያልተማረ፡ ያልሠለጠነ፤ ዐጀም። ኢሐቃል፡ ወኢሀገሬት፡ (ቆላ፫፡ ፲፩)።

**ሀገሬታዊ**፤ ገዢ፡ ከማሁ፤ ዐጀም፡ አረመኔ። ጽሑፍ፡ ሕልቦ፡ ውስተ፡ ልብ፡ ንጹሓን፡ ፍልጠት፡ ማእከለ፡ አይሁዳዊ፡ ወሀገሬታዊ፡ ገብር፡ ወአግዓዚ፡ (ፊልክ፡ ፹፯)።

**ሀግረተ**፤ (ተቀ፡ ግ)፤ ተጋ፤ ዐለበ፡ ተወዘወዘ፤ በትጋት፡ በሐሳብ፡ ተያዘ፡ በሀግረተ፡ ፈንታ፡ ጋሀረተ፡ ይላል፤ የጣፊ፡ ስሕተት፡ ነው። ከመ፡ ትትጋሀረቱ፡ ለመፍቅደ፡ ልብየ፡ (አርጋ፡ ፬)።

**ሀግሩት**፤ የተጋ፡ ትጉ፤ ዐሳቢ፡ ተቈርቋሪ፡ (አርጋ)።

**ሀግርትና**፤ ትጋት፡ ሐሳብ፤ ትጉህነት፡ ዐሳቢነት፡ (መጽ፡ ምስ)።

**ሀዲእ**፤ **አት**፤ (ሀድአ፡ የሀድእ፡ ይሀዳእ። ዐረ፡ ሀደአ)፤ ዝም፡ ጸጥ፡ ዱ፡ ጫ፡ ማለት፤ ከሁከት፡ ማረፍ፤ መርጋት፡ መጨመት፤ መቆም፡ መገታት። ዝኅንኒ፡ ተመ፤ የዚህ፡ ጎር፡ ነው። ወሀድኡ፡ አይሁድ፡ በመዋዕለ፡ ስምያን። ውእቱሰ፡ ኢይትናዘዝ፡ ወኢየሀድእ። ሀድአት፡ ልባ፡ እምሐዘን። በመዋዕሊሁ፡ ሀድአት፡ ወአርመመት፡ ምድረ፡ ይሁዳ። ዝኅኑ፡ ሞገድ፡ ወሀድአ፡ ማዕበል፡ (ዮሴፍ። ስንክ፡ መስጀ፰። ፪ዜና፡ ፲፬፡ ፩። መጽ፡ ምስ። ዘፀ፪፡ ፭፰—፴፬)። ዱታ፡ ዱተኛ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ወጥቷል።

**ህዱእ**፤ (እን፡ ኣት፡ ድእት)፤ ዝም፡ ጸጥ፡ ያለ፤ ያረፈ፡ የረጋ፤ ሁከት፡ የሌለው፤ በከመ፡ መንግሥትየ፡ ህዱእ። ህዱኣን፡ ወዕፉፋን። ይኩን፡ ህዱአ፡ አዕይንት። ዘኢኮነ፡ ህዱአ፡ በቃሉ፡ ወበምግባሩ። ከመ፡ በህዱእ፡ ወበጽምው፡ ይኩን፡ ንብረትነ፡ (አስቴ፡ ፫። መሳ፲፰፡ ፯። ፈ፡ መ፡ ፰፯፡ ፰። ቀሌ፡ ድጓ)።

**ህዱኣዊ**፤ ዝምተኛ፡ ጸጥተኛ፤ ጭምት። ልብ፡ ህዱኣዊ፡ (ፊልክ፡ ፶፩)።

**ህድአት**፤ ዝም፡ ጸጥ፡ ማለት። ዝምታ፡ ጸጥታ፡ ዕረፍት፡ ርጋታ፡ ዱታ፡ ቀስታ፡ ዝግታ፤ ጭምትነት። ህድአት፡ ወአርምሞ። መፍቀሬ፡ ህድአት። መፍትው፡ ለነ፡ ንሑር፡ በህድአት። መፍትው፡ ለአንስት፡ ይትርአያ፡ በአርአያ፡ ህድአት። ፈታሒ፡ ዘአጥረየ፡ ህድአተ፡ ወትዕግሥተ፡ (ጥበ፲፰፡ ፲፬። ዮሴፍ። አፈ፡ ተ፴፬። ፈ፡ መ፡ ፴፱። ፍ፡ ነ፡ ፲፰፡ ፪)።

**አህድአ**፤ ጸጥ፡ አደረገ፡ ዝም፡ አሰኘ፡ አስታገሠ፡ አረጋጋ። በኀይሉ፡ አህድአ፡ ለባሕር። ያህድእ፡ ሀውከ፡ ሞገድ። አህድአ፡ ህርቃኖስ፡ ኵሎ፡ ሕዝበ፡ እለ፡ ይጸብኡ፡ ምድረ፡ ይሁዳ፡ ወሞእሙ። አኀዊ፡ አግብርቲሁ፡ ይናዝዝዎ፡ ወያህድእዎ። ወአህድኦሙ፡ መልአክ፡ በሰላም፡ በቃሉ፡ (ኢዮ፳፮፡ ፲፪። ተረ፡ ቄር። ዮሴፍ። አክሲ)።

**አህዳኢ**፤ **መሀድኢ፡ እ**፤ ጸጥ፡ የሚያደርግ፤ የሚያስታግሥ፡ አጽናኝ፡ መህድኢ፡ ንዴት፡ ውእቱ፡ (ፈላስ)።

**ሀደየ**፤ (ዐረ፡ ሀደይ)፤ አበሰለ፡ አሻከከ፤ የሥጋ፡ ያጥንት፡ የሚቀቀል፡ ኹሉ።

**ተሀድየ**፤ በሰለ፡ ሻከከ፤ ዝንግልግል፡ አለ። ባለብሉዮች፡ ግን፡ ተፋጨ፡ ይሉታል። ተቀጥቅጡ፡ ወተሀድየ፡ አዕፅምትየ፡ (ኢዮ፴፡ ፴)።

**ሀዲም**፤ **ሞት**፤ (ሀድመ፤ ሀደመ፡ የሀድም፡ ይሀድም። ዕብ፡ ራዳም)፤ ማንቀላፋት፤ በንቅልፍ፡ መያዝ፡ መወሰድ፤ መስነፍ፡ መታከት፡ እንቅልፋም፡ መኾን። መጨለም፡ መክበድ፡ ሌሊት፡ ውድቅት፡ መኾን፤ የጊዜ። መጽሐፍ፡ ግን፡ በሀድመ፡ ፈንታ፡ ተሀድመ፡ ይላል። ዘኢ፡ ተሀድመ። እምቅድመ፡ ይብራህ፡ ብርሃን፡ መዓልት፡ ወእምቅድመ፡ ይትሀደም፡ ሌሊት፡ (ዕዝ፯፡ ፴፰። ቅዳ፡ አፈ)።

**ህድመት**፤ ማንቀላፋት። ክቡድ፡ እንቅልፍ፤ እንደ፡ ሞት፡ ያለ። ወደየ፡ እግዚ፡ ህድመተ፡ ላዕሌሁ፡ ወኖመ። ሞት፡ ውእቱ፡ ህድመት፡ ወንዋም። ከመ፡ ሞት፡ በህድመት፡ ክቡድ። ኢወሀቡ፡ ለአዕይንቲሆሙ፡ ምንተኒ፡ ህድመተ፡ (ኩፋ፡ ፫። አፈ፡ ተ፬። አርጋ፡ ፪። ስንክ፡ ኅዳ፲፯)።

**ሀደመ**፤—**ተረተ**፤—**ሐድሞ፡ ሐደመ**።

**ሁጅራ**፤ (ዐረ፡ ሂጅረት)፤ ሠግር፤ ቀመር። ዓመተ፡ አልሁጅራ፡ (አቡሻ፡ ፲፩)።

**ሀዳር**፤—**በቁሙ**፤—**ኅዳር**።


**ሀዋርኤል**፤ ምሥዋዕ፡ የምሥዋዕ፡ ስም፤ ደብረ፡ እምላክ፡ ማለት፡ ነው፡ (ሕዝ፵፫፡ ፲፭)። አሪኤልንና፡ አርያልን፡ እይ፤ ከዚህ፡ ጋራ፡ አንድ፡ ነው።

**ሀዊብ**፤ **በት**፤ (ሆበ፡ የሀውብ፡ ይሁብ። ዕብ፡ አዊህ)፤ መፈለግ፡ መሻት፤ መዘር፡ መንከርተት፡ ለማግኘት፡ የምግብ።

**ሆባይ**፤ (**ያት**፤ **አህቡይ**)፤ እንጨት፡ አሞራ፤ ሳቢሳ፡ ጭላት፤ ጥንብ፡ ፈላጊ፡ (ዘሌ፲፩፡ ፲፬። ዘዳ፲፬፡ ፲፫። ኢዮ፴፱፡ ፳፮። ሔኖ፹፱፡ ፲፡ ፲፫፡ ፲፬፡ ፲፰፡ ፳፪)። ስምንቱ፡ አስተጋባኢ፡ ነው፤ ለሚከንፍና፡ ለሚረብ፡ ለማያንዣብብ፡ ኹሉ፡ ይኾናል።

**ሆባይ**፤ (**ዕብ፡ ቆፍ። ሱር፡ ቁፋ። ዐረ፡ ቂርድ**)፤ ዝንጀሮ፤ ጨላዳ፤ በብዙ፡ ወገን፡ ሰው፡ የሚመስል፤ ንጪና፡ ጥቍሬ፡ ፪፡ ዐይነት፡ ያለው። በእም

ሳለ ፡ ሆባይ ፡ ሆባይት ፡ አጽዐቅዎሙ ። ወይጠለ ፡ አ ስገ.ድክ ፡ ወሆባየ ፡ አክነስከ ፡ ብፁዕ ፡ አንተ ፡ አባ ፡ ዮ ሐኒ ። ወአህቡየ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። መዋሥ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፳፩) ።



ሆባይ ።

**ሆባይ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፡ ሆ ፡ ባይ ፤ ሆ ፡ አሆ ፡ የሚል ፡ ጨፋሪ ፤ እንደ ፡ ዝንጀሮ ፡ የሚያወክ ።

**ሆድ** ፤ (ዕብ ፡ ጸዳል ፡ ውበት ፤ ክብር ፡ ምስጋና) ፤ በቁሙ ፤ ከርሥ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሆሄ** ፤ (ሆይ ፡ ሄ) ፤ ስሙ ፡ ፊደል ፡ መልክአ ፡ ፊደል ፡ ሀ ። ሆይ ፡ የማእዝ ፤ ሄ ፡ የዕብራይስጥ ፡ ነው ።

**ሆህያት** ፤ ፊደሎች ፤ የፊደል ፡ ስሞችና ፡ መልኮች ፤ ከሀ ፡ እስከ ፡ ሆ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ያሉት ፡ መሳው ፡ ባንድነት ። ፊደላተ ፡ ዒበር ፡ በሥራቸውና ፡ መክብባቸው ፡ አሌፍ ፡ ስለ ፡ ኾን ፡ በመክብባቸው ፡ ስም ፡ አሌ ፋት ፡ ተብለው ፡ እንዲጠሩ ፤ ፊደላተ ፡ ግእዝም ፡ ከበሳማ ፡ ወዲህ ፡ መክብባቸው ፡ ሆሄ ፡ (ሆይ ፡ ሄ) ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በሆሄ ፡ ሆህያት ፡ ይባላሉ ። ቃሉ ፡ የብዙ ፡ ሲኾን ፡ ባንድም ፡ ስብዙም ፡ ይነገራል ፤ ባንድ ፡ ሲነገር ፡ ስባትነቱን ፤ ለብዙ ፡ ሲነገር ፡ መሳወ.ን ፡ ያሳያል ። ሆህያተ ፡ ፊደል ፡ እስመ ፡ ሆህያተ ፡ ቤት ፡ ወዋዊ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ። በከመ ፡ ሆህያተ ፡ አልፋ ፡ ትከውን ፡ ኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ ሆህያት ። ወሰሰ ፡ ማኅደር ፡ ስምዮሙ ፡ በሆህያተ ፡ ጽርእ ፡ እምአልፋ ፡ ወቤጣ ፡ ወጋማ ፤ አ ፡ በ ፡ ገ ፡ (አፈ ፡ ድ፳ ፡ ፱ ። ሥር ፡ ጳዥ) ፡ ወይቤ ፡ ጠቢብ ፡ ቀሬጦን ፤ እስመ ፡ ቤት ፡ ቀዳሚ ፡ ዘከሠተ ፡ ሆህያተ ፡ ጽሕፈት ፡ ወአ ያቀ ፡ ልሳነ ፡ ዕብራዊ ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፯) ።

**ሆሄ** ፤ (ዐረ ፡ ሁወ ፡ ሄ) ፤ ውእቱ ፡ ሄ ፡ ማለት ፡ ነው ። የአራትን ፡ ክፍልና ፡ ብሔር ፡ ከዘፍ ፡ እስከ ፡ ዘዳ ፡ በ ፊደል ፡ ቍጥር ፡ ሲቈጥር ፤ ወለመጻሕፍተ ፡ ኦሪትኒ ፡ (ት እምርታቲሆሙ) ፡ በክልኤቱ ፡ ፊደላት ፡ እሙንቱ ፤ ወፊደለ ፡ ትእምርተ ፡ ኦሪት ፡ ቀዳማዊ ፡ ትአ ፤ ወዳ ግማዊ ፡ ትቤ ፤ ወሣልስ ፡ ትጋ ፤ ወራብዕ ፡ ትዳ ፤ ወ ኃምስ ፡ ትሃ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ወውእቱ ፡ ሄ ፡ እንደ ፡ ማ ለት ፡ ወሆሄ ፡ ኍልቈ ፡ መጻሕፍት ፡ ይባል ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ። ይህም ፡ ሄ ፡ ፭ኛ ፡ ፊደል ፡ ነውና ፡ ብቻውን ፡ ያ፭ቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ቍጥር ፡ ነው ፡ ያሰኛል ። አይሁድም ፡ ፭ቱን ፡ መጻሕፍት ፡ በዝርዝር ፡ ሐማሽ ፡ በአኃዝ ፡ ሄ ፡ ይሏቸዋል ፡ ፭ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ሆይ** ፤ ሀውይ ፤ (ዕብ ፡ ሆዌ ፤ ውስጠ ፡ ዘ) ፤ ስሙ ፡ ፊደል ፡ ኃምስ ፡ ሀ ። ሀላዊ ፡ ህልው ፡ ዘሀሎ ፤ ወይም ፡ ከዋኒ ፡ ክዉን ፡ ዘኮነ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሀለወና ፡ ኮነ ፡ በዕብራይስጥ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ ሀ ፡ ህ ፡ ይህ ዌህ ፡ ብሎ ፡ ሀለወ ፡ ይሄሉ ፤ ኮነ ፡ ይከውን ፡ ያሰኛልና ፡ ሆይ ፡ ሀውይ ፡ እህያ ፡ ይሆዋ ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ሆይ** ፤ (ዐማራ ፡ ወዕብራ) ፤ በቁሙ ፤ የ ጥሪ ፡ ቃል ፡ በቅርብ ፡ ላለ ፡ ሰሚ ፤ አቤቱ ፡ ቶ ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ። ፍችው ፡ በጥራቱ ፡ እንደ ፡ ኦ ፡ ነውና ፤ ኦንና ፡ ኦኦን ፡ ተመልከት ።

**ሀዊክ** ፤ ኮት ፤ (ሆከ ፡ የሀውክ ፡ ይሁክ ። ዐከወ ፤ ሀከከ) ፤ ማወክ ፡ መነቅነቅ ፡ ማንቀሳቀስ ፡ ማ ገበር ፡ መጕሰጕስ ፡ ማንሣሣት ፤ ማሳዘን ፡ ማስጨነቅ ፡ ባለ መከፉ ፡ ማድረግ ። ሆከሙ ፡ ከመ ፡ ማዕበለ ፡ ባሕር ። ኢተክህሎሙ ፡ ከመ ፡ ይሁክዋ ፡ ለሐመር ፡ እመካና ። ተመሰሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይሰክፉ ፡ ምንተኒ ፡ በአጽባዕ ቶሙ ፡ ወየሀውኩ ፡ ኵለንታሁ ። ሆከቶ ፡ ጸጋ ፡ እግዚ ከመ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ። ፈቀድክ ፡ ትሁክ ፡ ቅድስተ ፡ ሲኖዶስ ። የሀውክሙ ፡ ለሕዝብ ፡ (ሚራ፳፱ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፰ ። አፈ ፡ ድ፪ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ተረ ፡ ቄር፲፪ ። ኢዮ፲፪ ፡ ፳፫) ። ሖለንና ፡ ኮሶን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ አግዋር ፡ ናቸው ።

**ሀዋኪ** ፤ (ኪት ፡ ክያን ፡ ያት) ፤ የሚያውክ ፡ አዋኪ ፤ ሁከተኛ ፡ ነቅናቂ ፡ በጥባጭ ። ሀዋኪ ፡ በግዕዙ ። ሞገድ ፡ ሀዋኪ ። ጸልዩ ፡ ውስተ ፡ ማኅበርነ ፡ ኢይባእ ፡ ሀዋኪ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ተረ ፡ ቄር ። ደራሲ) ።

**መሀውክ** ፤ (ክት ፡ ካን ፡ ካት) ፤ ዝኒ ፡ ከ ማሁ ፤ እኪት ፡ ይእቲ ፡ ሐሜት ፡ ወመሀውክት ። ቍ ጥዓ ፡ ወፍርሀት ፡ መሀውካን ፡ (ሄርማ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱ ፡ ፬) ።

**ሀውክ** ፤ በቁሙ ፡ ሁከት ፡ እውከታ ፡ ንውጽው ጽታ ፤ መከፉ ፡ ጭንቅ ፡ ሽብር ፡ ድብልቅልቅ ። ሀውክ ፡ ሞገድ ። ከመ ፡ ያህድእ ፡ ኵሉ ፡ ሀውክ ፡ ወሐዘነ ፡ (ተረ ፡ ቄር፩ ። ፲፬ ። ሔኖ፻፲ ፡ ፪ ። ያዕ፫ ፡ ፲፮) ።

**ተሀውከ** ፤ ታወከ ፡ ተናወጠ ፡ ተንዋወጠ ፡ ተን ሣሣ ። ወተሀውከት ፡ ኵላ ፡ ሀገር ። ባሕርሰ ፡ ይትሀ ወክ ። ተሀውኩ ፡ ከመ ፡ ዕፀ ፡ ገዳም ። ተሀውከ ፡ ልቡ ፡ ላዕሌሃ ። ኢይኩን ፡ ተሀዋኬ ፡ ወኢሰካሬ ፡ ወኢቍ ጡዐ ፡ (ማቴ፳፩ ፡ ፲ ። ዮሐ፮ ፡ ፲፰ ። ኢሳ፯ ፡ ፪ ። ዮዲ ፲፪ ፡ ፲፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**ህዉክ** ፤ (ካን ፡ ካት ፡ ውክት) ፤ የታወከ ፡ ሁ ከታም ፡ ሁከተኛ ፡ ርጋታ ፡ ጸጥታ ፡ የሌለው ። ዘክልኤ ፡ ልቡ ፡ ህዉክ ፡ ውእቱ ፡ በኵሉ ፡ ፍኖቱ ። ህዉካን ፡ ወጽሩዓን ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ (ያዕ፩ ፡ ፰ ። ቀሌ) ።

**ሁከት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፡ ማወክ ፡ መታወክ ፡ መታመስ ፡ መተራመስ ፡ ሽብር ። ሁከት ፡ ማይ ። ተሀ ውኩ ፡ ዐቢየ ፡ ሁከተ ። ሁከት ፡ ነፍስ ። ቃል ፡ ወሁከት ። ሰይጣን ፡ መፍቀሬ ፡ ሁከት ። ከመ ፡ ቢድምፀ ፡ ምጽ

አትከ ፡ ኢይኩን ፡ ሁከት ፡ (ዮሐ፳ ፡ ፲ ። ሔኖ፳ ፡ ፳ ። ጥበ፲፯ ፡ ፳ ። አስቴ ፡ ፰ ። ቀሌ ። ኪዳ) ።

ሀወለ ፤—ቀላቀለ ፤—ሐወለ ።

ሀውል ፤ (ዕብ ፡ ሄቤል) ፤ ባበት ፡ እንፋሎት ፡ ከምቀ ፡ ገላ ፡ ክፋ ፡ የሚወጣ ። ከንቱ ፡ ነገር ፡ ስብሰት ፡ ጥዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ማቅ ፡ ሥሳቅ ፡ ሰድብ ፡ ንቀፋ ።

ሀውለየ ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ አፌዘ ፡ ማቀ ፡ ተማለቀ ፡ ንቀፈ ፡ ሰደበ ፡ አረከሰ ፡ ከንቱ ፡ አደረገ ። ከመ ፡ ዝ ፡ የሀወልይዎ ፡ ለእግዚ ፤ ወእለ ፡ ጸጋ ፡ ትስብእቱ ፡ ይመይጡ ፡ ውስተ ፡ ሀውልዮ ። ተሀወልዮቱ ፡ ለእግዚ ፡ ቃል ፡ በዘሐመ ። ኢተሀውልዮ ፡ ለዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ እመ ፡ በትሕትና ፡ አሕየወ ። ኢየሀውልይዎኬ ፡ ለክርስቶስ ፡ ኃጥኣን ። ኢተሀውሊኬ ፡ ሕማማት ። እመ ፡ አረሚ ፡ ሀውለይዎ ፡ ለምስጢር ፡ (ተረ ፡ ቄርሎ ። ፳ ። ፲ ። ፲፰) ።

ሀየ ፤—በዚያ ፡ ከዚያ ፤—ሀይይ ፡ ሀየ ፤ ሀየየ ።

ሀይብ ፤—በቁሙ ፡ ዐይብ ፤—ሔበ ፡ ሐይብ ።

ሀዩድ ፤ ዶት ፤ (ሄደ ፤ ሀየደ ፡ የሀይድ ፡ ይሂድ) ፤ መቀማት ፡ መንጠቅ ፡ በምክንያት ፡ መውሰድ ። እነሥእከ ፡ ወአሀይደከ ። ወየሀይደክሙ ፡ ገራህተክሙ ። ኢትትዐገሉ ፡ ወኢትሂዱ ፡ መነሂ ፡ (፩ነገ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ። ፳ ፡ ፲፬ ። ሉቃ፫ ፡ ፲፬) ።

—፤ ማንጸብረቅ ፤ መሳብ ፡ መበዝበዝ ። ሰብሰ ፡ ዳዊት ፡ ዘየሀይድ ፡ ዐይነ ። አማእኒሃ ፡ ሀየደ ፡ አዕይንቲሁ ። ዐበየ ፡ ብርሃኑ ፡ የሀይድ ፡ አዕይንተ ፡ (፪ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ። ዮዳ፲፮ ፡ ፱ ። ቀሌ) ።

—፤ መሄድ ፡ መሬመድ ፤ እግርን ፡ ማንሣት ፡ መንጠቅ ። ምስጢሩ ፡ ያው ፡ መውሰድ ፡ ነው ፤ ኪደ ፡ መርገጥ ፡ መደፍጠጥን ፡ ሄደ ፡ አንሣሥን ፡ ያሳያል ፤ ኪደ ፡ ሖረ ፡ የማእዝ ፡ ሄደ ፡ ያማርኛ ። ነጠቀ ፡ ነጠቀ ፡ አርገ ፡ እንዲሉ ፡ ቆሎ ፡ ቆሎ ፡ ሂድ ፡ ሲሉ ።

ሀያዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤ የሚቀማ ፡ ቀማኛ ፡ ነጣቂ ፡ ወሳጅ ፡ (ሉቃ፲፰ ፡ ፲፩ ። ፩ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ። ፮ ፡ ፲) ። እምእደ ፡ ሀያዲሁ ። ሀያዲ ፡ ንዋየ ፡ ባዕድ ። ሰራቂ ፡ ወዐማፂ ፡ ወሀያዲ ፡ ወመማጢ ። ሀያድያን ፡ (ኤርሚ፱ ፡ ፲ ። ቀሌ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፭) ።

ሀይድ ፤ ቅሚያ ፤ ንጥቂያ ፤ ምክንያት ፡ ያለው ፡ አወሳሰድ ፡ (መገ ፡ ፳፩ ። ኢሳ፳፩ ፡ ፳) ።

ተሀይደ ፤ ተቀማ ፡ ተነጠቀ ፡ ተማረከ ፤ ገንዘቡ ፡ ወይም ፡ ርሱ ፡ ራሱ ። ዘያስተጋብእ ፡ ብዕሎ ፡ በዐመፃ ፡ ይትሀየድ ፡ ብዕሉ ፡ እምኔሁ ። ዘእንበለ ፡ ትትሀየድ ፡ ብእሲቱ ፡ እምኔሁ ። ሰማይ ፡ ይትሀየድ ። ተሀይዱ ፡ ደቂቅነ ፡ (ዲድ ፡ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፲፫ ። ሔኖ፹፫ ፡ ፲ ። ሉቃ ፡ ዕዝ፲ ፡ ፴፭) ።

ሀዩድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ይድ) ፤ የተቀማ ፡ የተነጠቀ ፤ ገንዘብ ፡ ሰው ።

ሂደት ፤ መቀማት ፡ (ጥቀ) መቀማት ፡ አቀማም ፡ አወሳሰድ ፤ ቅሚያ ፡ ንጥቂያ ፡ (አርጋ) ። መሄድ ፡ መራመድ ፤ አካሄድ ፡ አረማመድ ፤ እግር ፡ አነሣሥ ።

ተሃየደ ፤ ተቃማ ፡ ተሻማ ፡ ተነጣጠቀ ፤ ርስ ፡ በርሱ ።

ሀይወ ፤—ዳነ ፤—ሐዩው ፡ ሐይወ ።

ሄጠ ፤—ሸነገለ ፤—ኀዩጥ ፡ ኄጠ ።

ሀይይ ፤ ዮት ፤ (ሀየ ፤ ሀየየ ፡ የሀይይ ፡ ይሀየይ ። ሀከየ) ፤ ቸል ፡ ማለት ፤ መናቅ ፡ ማቅለል ፤ መቀው ፡ መጣል ። መጽሐፍ ፡ ማን ፡ በሀየየ ፡ ፈንታ ፡ ተሀየየ ፡ ይላል ፤ አያስኬም ። ኢትትሀየይ ፡ ትእዛዘ ፡ እምከ ። ተሀየዩ ፡ ሥርዐቶ ። እሙንቱ ፡ ቲሀየዩ ፡ ወኀለፉ ። ትትሄየይ ፡ ኀጢይኣ ፡ ሰብእ ። ለዕቡያን ፡ ይትሄየዮሙ ፡ እግዚ ፡ (ምሳ፩ ፡ ፯ ። ቀሌ ። ማቴ፳፫ ፡ ፳ ። ጥበ፲፩ ፡ ፳፬ ። ያዕ፬ ፡ ፯) ።

ሀያዩ ፤ (ተሀያዪ) ፤ ቸል ፡ ባይ ፡ ቸልተኛ ፤ ታጋሽ ። ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ከነ ፡ ተሀያዪ ፡ ስብሐተ ፤ ኀሳረ ፡ ወጽዕለተ ፡ (ፊልክ ፡ ፵፯ ። ፶፬ ። ፶፮) ።

አህየየ ፤ ቸል ፡ አሰኘ ፤ አስናፈ ፡ አስተወ ፤ አስጣለ ። ኢፈቀደ ፡ አምላክ ፡ ይርኢከ ፡ ሙስናሃ ፡ ለሀገር ፡ ወአምጽአ ፡ ኑዛዜ ፡ ላዕሌከ ፡ ወአህየየከ ፡ (ራእ ፡ ባሮ) ።

ተሀየ ፤ ተሀየየ ፤ ቸል ፡ ተባለ ፤ ተተወ ፡ ተጣለ ። ብእሲ ፡ ዐማፂ ፡ ይትሄየይ ፡ (ምሳ፲፱ ፡ ፱) ።

ህዩይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ይይት) ፤ ቸል ፡ የተባለ ፤ የተናቀ ። ቸል ፡ ያለ ፡ ቸልተኛ ፤ ሰነፍ ። መንዘህልልለ ፤ ወህዩይ ። ፍናዊሆሙ ፡ ለህዩያን ፡ (ፊልክ ፡ ፶፬ ። ምሳ፲፫ ፡ ፲፰) ።

(ጥ) ህየት ፤ ቸል ፡ ማለት ፤ ቸልታ ፡ ስንፍና ። እምህየት ፡ ወእምፀርዐት ፡ (ሲጦን) ።

ህየ ፤ የበታ ፡ ዐጸፋ ፤ በዚያ ፡ ከዚያ ፡ ወደዚያ ፤ ሩቅን ፡ ያሳያል ፤ እንደ ፡ ከዣ ፡ ነው ። ትከለ ፡ ገነተ ፡ ወሜሞ ፡ ህየ ። ህየ ፡ ይሠየማ ፡ ወህየ ፡ ይትዐቀብ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ለጻድቃን ። ቦ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምሥራቅ ፡ ወየሐውር ፡ ለምዕራብ ፡ ከመ ፡ ይስቲ ፡ በህየ ። ተንሥእ ፡ ወፃእ ፡ ሐቅለ ፡ ወበህየ ፡ እነግረከ ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፰ ። ቅዳ ፡ ግሩ ። አት ። ሕዝ፫ ፡ ፳፪) ።

ህየንተ ፤ (ህየ ፡ እንተ) ፤ ወዚይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ። ህየና ፡ እንተ ፡ ቶጋጥሞ ፡ አንድ ፡ ኅርመት ፡ ኹኗል ፤ እ ፡ ስለ ፡ ተጕረደ ፡ መጋጠሚያው ፡ አያስታውቅም ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ አለ ። ስለ ፡ በ ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ ይኾናል ፤ ስለና ፡ በ ፡ ፈንታ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ ምስጢሩ ፡ እንደ ፡ ፍዳ ፡ ነው ፤ ለውጥ ፡ ሤጥ ፡ በዛ ፡ ካሳ ፡ ዕዳ ፡ ብድር ፡ ያሳያል ። በአንቀጽ ፡ ሲገባ ፡ ዘን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ያደርጋል ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ብቻውን ፡ ይገባል ። ምንተ ፡ ተዐስዮሙ ፡ ህየንተ ፡ ዘገብሩ ። ህየንተ ፡ ዘትረድኦ ፡ አቅበጽካሁ ። ህየንተ ፡ ተቀንዩ ። ህየንተ ፡ ጻመወ ፡ (ሚራሺ ፡ ፳፫ ። ቀሌ ። ኩፋ ፡ ፵፰ ። ስንክ ፡ ጥቅ፴) ። በዘርና ፡ በስም ፡ ሲገባ ፤ ፈደዩኒ ፡ እኪተ ፡ ህየ

ንተ ፡ ሠናይት ። ህየንተ ፡ አበውኪ ፡ ተወልዱ ፡ ለኪ ፡ ደቂቅ ። ተቀንየ ፡ ያዕቆብ ፡ ህየንተ ፡ ራሔል ፡ ይላል ። እንደ ፡ ሊኾን ፡ ህየንተ ፡ ቈፀለ ፡ ዕፀ ፡ ከማሁ ፡ አነ ። አሕመልምል ፡ ሊተ ፡ ነፍስየ ፡ ህየንተ ፡ ዕፀ ፡ ትክልት ፡ ማእከለ ፡ ገነት ፡ ይላል ፡ (አርጋ) ። ህየንቴሁ ፡ ሃ ፡ ብሎ ፡ ሲዘረዝር ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ፈንታ ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያሰኛል ። ሀበሙ ፡ ህየንቴየ ፡ ወህየንቴከ ፡ (ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፳፯) ። (ዕር ፲፱ ፡ ቍ ፴፱) ።

**ሄከ፤—አላመጠ፤—ሐዩከ ፡ ሔከ ።**

**ሀይከል፤(ዕብ ፡ ሄካል ፡ ሱር ፡ ሄክላ ። ዐረ ፡ ሀይከል)፤** ታላቅ ፡ ቤት ፡ አዳራሽ ፡ ሰቀላ ፤ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ከዚያውም ፡ ዓው ፡ ክንድ ፡ መካከለኛው ፡ ክፍል ፤ ጽርሕ ። ሀይከለ ፡ ቍድስ ፡ (ዮሴፍ) ።

—፤ መቅደስ ፡ ምሥዋዕ ፡ መንበረ ፡ ታቦት ፤ በተገናኝ ፡ ማደሪያ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሲያበዛ ፡ ሀይከላት ፤ ሀያክል ፡ ይላል ።

**ሀየለ ፤—በረታ ፤—ኀይሎ ፡ ኀየለ ።**

**ሀየል ፤ (ላት ። ዕብ ፡ አያል ። ሱር ፡ አያላ ። ዐረ ፡ ኢየል)፤** ዋሊያ ፡ ዋላ ፡ ቀንዳም ፡ ቀንደ ፡ ገባባ ፤ ባለብዙ ፡ ዐጽቅ ፡ ባለተቀጥላ ፡ ነዊን ፡ ዐፅም ፡ እግረ ፡ ሽመላ ፤ የፌቆ ፡ ወገን ፡ የበረሓ ፡ እንስሳ ። ዘይረትዖን ፡ ከመ ፡ ሀየል ፡ ለእገርየ ። ወከመ ፡ ወሬዛ ፡ ሀየል ። ህየ ፡ ተጋብአ ፡ ሀየላት ፡ እስመ ፡ ሀየል ፡ ቀታሊሁ ፡ ለከይሲ ። ሀየላት ፡ ወለዳ ፡ በውስተ ፡ ገዳም ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። ማሕ፪ ፡ ፱ ። ተረ ፡ ቄር፰ ። ኤር፲፬ ፡ ፭) ።



ሀየል ፤

**ሄላ ፤** የወይን ፡ ዘለላ ፤ የበሰለ ፡ ደሙ ፡ የመላ ። አጥባትኪ ፡ ከመ ፡ ሄላ ፡ ዘእምኔሆን ፡ ይውሕዝ ፡ ሐሊብ ፡ (አርጋ ። ማሕ፯ ፡ ፰) ። እኔላን ፡ ተመ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ፡ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ምንጭ ፡ የበሰለ ፡ ቋንጣ ፡ የሰሌን ፡ ፍሬ ፡ ይሉታል ። ንባቡ ፡ ሀየላዊ ፡ ምስጢሩ ፡ መስተፍሥሒ ፡ ከመ ፡ ሀየል ። አስከል ፡ ሄላ ፡ መባሉ ፡ በምሳሌ ፡ እንጂ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ አይደለም ።

**ሄላንሳን፤—ክቡር ፡ ልብስ፤—ቂላኖስ።**

**ሀይመነ ፤ (ሱር ፡ ሃይሜን ። ዐረ ፡ ሀይመነ)፤** አመነ ፡ ታመነ ። ንባቡ ፡ ከየማን ፡ ፍችው ፡ ከአማን ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ የመነንና ፡ አይመነን ፡ ተመልከት ።

**ሀይማኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)፤** ያመነ ፡ የሚያምን ፡ የሚታመን ፡ እማኒ ፡ ተአማኒ ።

**መሀይምን ፤ (ንት ፡ ናን ፡ ናት)፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፤ ምእመን ፤ ያመነ ፡ የታመነ ፤ አማኒ ፡ እሙን ፡ የማይጠረጠር ። መሀይምን ፡ ውእቱ ፡ በዂሉ ። ስምዕ ፡ መሀይምን ። ክርስቲያናዊት ፡ መሀይምንት ። ማሕየዊ ፡ ለዂሉ ፡ ለብእ ፡ ወፈድፋደ ፡ ለመሀይምናን ፡ (ኊል ፡ ፲፯ ። ራእ፩ ፡ ፭ ። ኪዳ ። ፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲) ። በቁሙ ፡ ማይምን ፡ ያልተማረ ፡ ያልተካነ ፡ ሕዝባዊ ፡ ሐገዋ ። (ተረት) ፤ ከማይምን ፡ ባለጌ ፡ የተማረ ፡ አርጌ ።

**ሃይማኖት፤(ሱር ፡ ሃይማኑታ)፤** የውዳሴ ፡ የምሕላ ፡ ጸሎት ፡ ከቤተ ፡ ክሲያን ፡ ውጭ ፡ በዙሪያው ፡ በገረገራው ፡ የሚባል ፡ እንደ ፡ ጥምቀት ፡ እንደ ፡ ጕዞ ፡ ፍታት ፡ ያለ ፤ ወረብ ፡ ለዘብ ፤ የታቦት ፡ ዘፈን ። ሀይመና ፡ ሀይመን ፡ እንዲል ፡ (ያረርጌ ፡ ዉፋሬ) ።

—፤ በቁሙ ፤ ማመን ፡ መታመን ፤ እምነት ፡ ጽኑ ፡ ተስፋ ፤ የአምልኮት ፡ ባህል ፤ በልብ ፡ በረቂቅ ፡ ሐሳብ ፡ የሚማል ። ሃይማኖተ ፡ ዕቀብ ፡ ምስለ ፡ ቢጽከ ። ብእሲ ፡ ዘተአምር ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ ሃይማኖት ። እለ ፡ አዕረፉ ፡ በሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ (ሢራ፳፪ ፡ ፳፫ ። ፳፯ ፡ ፲፱ ። ዲድ ፡ ፴፱) ።

**ሃይማኖት ፡ ቅድስት ፤** ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፤ ምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ (ይሁ ፡ ፫) ።

**ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፤** ኦርቶዶክሳዊት ፤ የኦርቶዶክስ ፡ ባህል ፡ (ቅዳ) ።

**ሃይማኖተ ፡ አበው ፤** የሊቃውንት ፡ መጽሐፍ ፤ ድርሳን ፡ መልእክት ፤ የጉባ ፡ ሰዎች ፡ ከየመጣፋና ፡ ከየቋንቋው ፡ ለቅመው ፡ ተርጕመው ፡ እንደ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ለብቻው ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ መጣፍ ፡ ያደረጉት ፡ ታላቅ ፡ ምእላድ ፤ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ የሚነበብ ።

**ሃይማኖተ ፡ እስላም ፤** እስላማዊ ፡ ባህል ፤ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ትምርት ፡ ከኦሪት ፡ ከወንጌል ፡ የማይገጥም ፡ (አቡሻ ፡ ፶) ።

**ሃይማኖተ ፡ ንስጡር ፤** ንስጥሮሳዊ ፡ ባህል ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ እንደ ፡ ሙሐመድ ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከኖን ፡ የሚንቅፍና ፡ የሚያጸይፍ ፤ ቃል ፡ በሰው ፡ ዐደረ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ አልኾነም ፡ ሰው ፡ ኹኖ ፡ አልተቀባም ፡ ብሎ ፡ የቃልን ፡ ሰው ፡ መኾን ፡ መሲሕነቱን ፡ የሚክድ ፡ (ቄር) ።

**ሀየንተ ፤—ስለ ፡ ፈንታ ፤—ሀየየ ፡ ህየ ።**

**ሀዩጽ ፤ ጾት ፤ (ሄጿ ፡ የሀይጽ ፡ ይሂጽ ። ዐረ ፡ ሀበ ፤ ሀፈ)፤** መንቅንቅ ፡ መስበቅ ፡ የሾተል ፡ የጦር ። መሳብ ፡ መንደፍ ፤ መወርወር ፡ ማወንጨፍ ፤ መውጋት ፡ መግመስ ፡ መፈንከት ። ሀይጾተ ፡ ቀስት ፡ ወደርብዮ ፡ ኰይንው ። ነደፈ ፡ ወሄጾ ፡ ለንጉሥ ፡ ማእከለ ፡ ስንብው ። ፈነወ ፡ ሐጾ ፡ ወሄጾ ፡ ጥቦ ። የሀይጹ ፡ ሥዕርተ ፡ ወኢይስሕቱ ። ወፀፎ ፡ በእብን ፡ ወሄጾ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሙ ፡ (መቃ ፡ ገ፲፱ ። ፪ዜና ፡ ፲፰ ፡ ፴፫ ። ኩፋ ፡ ፴፰ ። መሳ፳ ፡ ፲፮ ። ሢራ፵፯ ፡ ፬) ።

**ተሀይጸ ፤** ተነደፈ ፡ ተወረወረ ፡ ተወጋ ፡ ተገመሰ ። ከመ ፡ ሀየል ፡ ዘተነደፈ ፡ ወተሀይጸ ፡ ክብዶ ።

ኢተሀይጽ፡ ውስተ፡ ሕማም ። ተሀይጽ፡ በሐጹ፡ ቃሉ፡ ለጳውሎስ፡ (ምሳ፡ ፯፡ ፳፫ ። ተረ፡ ቄር፲፯ ። ገድ፡ ተክ) ።

**ሂጽት**፤ መንደፍ፡ መነደፍ፡ አንዳደፍ፡ ንደፈ፡ ውርወራ፡ ንድፈያ፡ ውጊያ፡ ውግታት፡ ግምሳት ። እኩ፡ በዘቀስት፡ ሂጽት፡ (ቄር፡ ገ፯) ።

**ሀከየ፤ ዮት፤ (ሀከየ፡ የሀኪ፡ ይሀኪ ። ሀየየ፤ አከየ)**፤ መሰንፋ፡ መታከት፡ መድከም፡ መሰልቸት፤ ሥራ፡ መተው፡ መጥላት፤ መስገም፡ ቸል፡ ማለት ። መጽሐፍ፡ ግን፡ በሀየየ፡ ፈንታ፡ ተሀየየ፡ እንዲል፤ በሀከየም፡ ፈንታ፡ ተሀከየ፡ ይላል ። ዘይጸመው፡ በሥጋሁ፡ ወይትሀከይ፡ በነፍሱ ። ኢናፀርዕ፡ ቅኔ፡ እደዊነ፡ ወኢንትሀከይ ። ኢትትሀከዩ፡ ለንስሓ ። ኢትትሀከይ፡ ገቢረ፡ ሠናይ ። ኢይትሀከይ፡ መዊተ፡ (አርጋ ። ዲድ፡ ፲፫ ። ቀሌ ። ምሳ፫፡ ፳፯ ። ማቴ፳፭፡ ፲፩) ።

(ጥ) **ሀከይ፤ (ያን፡ ያት)**፤ የታከየ፡ ሀኬተኛ፤ ሰነፍ፡ ታካታ፡ ሥራ፡ ፈች፡ (ምሳ፮፡ ፮ ። ፲፡ ፬ ። ማቴ፳፭፡ ፳፮) ። በሀከይ፡ ፈንታ፡ ተሀካዪ፡ ይላል ። ኢትኩን፡ ተሀካዬ፡ (ምሳ፳፡ ፫) ።

**ሀኬት**፤ በቁመው፡ ሰንፍና፡ ቸልታ፡ ንዝህላልነት፡ ተንኰል፡ ክፋት ። በሀኬት፡ ወበፅርዐት፡ ዕደው፡ ይወድቅ፡ ናሕስ ። እመ፡ ዘረከባ፡ እምሕሠማት፡ ኮነ፡ በሀኬት፡ ዚኣሁ ። ሶበ፡ ተሀጕለ፡ ንዋየ፡ አመጋቢ፡ በእደ፡ መጋቢ፡ ዘእንበለ፡ ጽልሑት፡ ወኢሀኬት፡ (መክ፲፡ ፲፰ ። ፍ፡ ነ፡ ፳፰፡ ፴) ።

**አሀከየ**፤ አሰነፈ፡ አታከተ፡ አሰለቸ ። እስመ፡ በአኅጽሮ፡ ይኄይስ፡ ድርሳን፡ ከመ፡ እምብዝኁ፡ ኢያሀኪክሙ፡ (ተረ፡ ቄር፳፩) ። በአሀከየ፡ ፈንታ፡ አስተህከየ፤ አስተሀከየ፡ ይላል፡ ፍችው፡ አንድ፡ ነው ። ዛቲ፡ መጽሐፍ፡ መዜንው፡ ሠናይ፡ ኢያዐቅፉ፡ ትጋሀ፡ ሌሊት፡ ወኢያደክማ፡ ወኢያስተሀክያ፡ ብዝኀ፡ ነጽሮ፡ (ፈላስ) ።

**አሀካዪ፤ መሀክይ**፤ የሚያሰንፍ፡ አስናፊ ። ጽሒፍ፡ ሊተሰ፡ ኢመሀክይ፡ ወለክሙሰ፡ ጽኑዕ፡ (መጽ፡ ምስ) ።

**ተሃከየ፤ (ይትሃከይ)**፤ ተሳነፈ፤ ተሰናነፈ፤ ተደራረገ ።

**አስተሃከየ**፤ አሳነፈ፤ አሰናነፈ፤ አደራረገ ።

**መስተሃክይ**፤ የሚያሳንፍ፡ አሳናፊ፤ አሰናናፊ ።

**ሀከከ፤ (ሆክ)**፤ አወከ፤ አሸበረ ። ሆከንና፡ ዐከውን፡ ተመልከት ።

**ሀከክ**፤ ሁከት፡ ሽብር፡ ጠብ፡ ክርክር፤ ቱማታ፡ ፍጅት ። ዕለተ፡ ሀከክ ። ማየ፡ ሀከክ ። እኩ፡ በሀከክ፡ ወበትዝልፍት ። እለ፡ ይገብሩ፡ ሀከክ ። እስመ፡ በሀከክ፡ ኀደርክሙ፡ ወበሀከክ፡ ይወድቁ፡ ይቀቅክ፡ (ኢሳ፳፱፡ ፭ ። ሙዝ፡ ፻፳፫ ። ግብ፲፱፡ ፴፯ ። ሮሜ፲፯፡ ፲፯ ። ክፋ፡ ፲) ።

**ተሀከከ፤ (ተሀውክ)**፤ ታወከ፡ ተሸበረ፡ ዐዘነ፡ ተቈረቈረ ። እስመ፡ ኦኅው፡ ሶበ፡ ዘርከይዎ፡ ለአባ፡ ሙሴ፡ ተብህለ፡ ሎቱ፡ ኢተሀከከኑ፡ ልብከ፤ ወይቤ፡ ተሀከኩ፡ ወባሕቱ፡ ኢተናገርኩ፡ (ፊልክ፡ ፻፱) ።

**ህኩክ፤ (ካን፡ ክት፡ ክክት)**፤ ሀዉክ፡ ወፊዉ፡ ወሬኛ፡ ወላዋይ ። ኅሊና፡ ህክክት፡ (ፊልክ፡ ፻፲) ።

**ሀከከ፤ — ዐከከ፤ ፎከተ፤ — ሐኪክ፡ ሐከክ ።**

**ሁል፤ — ርኩስ፤ — ሐዊል፡ ሐለ፡ ሐወለ፤ ሐውል ።**

**ሀላ፡ ሀሊብ፤ — ድንኳን፤ — አሆላ፡ አሆሊብ ።**

**ሀለደ፤ — ጨረሰ፤ — ኀልዶ፡ ኀለደ ።**

(ጥ) **ሀልዎ፤ ዎት፤ (ሀለወ፤ ሀሎ፤ ይሄሉ፡ የሀሉ ። ዕብ፡ ሀያህ)**፤ መኖር፡ መገኘት፡ መኾን፡ መፈጠር ። ኮንንና፡ መጽእን፡ ተመ፤ የዚህ፡ አግዋር፡ ናቸው ። እግዚአብሔር፡ አምጻኤ፡ ኵሉ፡ ዓለም፡ እምኀበ፡ ኢሀልዎ፡ ኀበ፡ ሀልዎ ። ሀለወ፡ ወኢሀለወ ። ዘሀሎ፡ ወይሄሉ ። ወሀሎ፡ አሐዱ፡ ብእሲ፤ አለ፡ ኖረ፡ ነበረ፡ (ፈላስ ። ራእ፲፯፡ ፰ ። ፭፡ ፬ ። ዮሐ፫፡ ፩) ።

**ሀላዊ፤ (ዊት፡ ውያን፡ ያት)**፤ የሚኖር፤ ነዋሪ፤ ኗኝ ። ነፍስሰ፡ ሀላዊት፡ ይእቲ፡ ወኢትትዌለጥ፡ (ፈላስ) ።

**ህልው፤ (ዋን፡ ዋት፡ ሉት)**፤ ያለ፡ የኖረ፡ የነበረ፤ የሚኖር፡ ነባር፤ ቀዋሚ፡ እውነት ። ፈጠረ፡ ፍጥረተ፡ ይኩን፡ ህልወ ። መድኅኒነ፡ ዘህልው፡ እምቅድመ፡ ዓለም ። ብዕል፡ ህልው ። ንርአይ፡ ለእመ፡ ነገሩ፡ ህልው ። ህልወ፡ ቃለ ። አማን፡ ህልወ፡ እብለክሙ፡ (ጥበ፪፡ ፲፯ ። ዲድ፡ ፴፯ ። ዮሴፍ ። ምሳ፳፪፡ ፳፩ ። ዮሐ፲፯፡ ፯) ።

**ህላዌ፤ (ውያት)**፤ መኖር፡ መኾን፤ አኗኗር፤ ኑሮ ። ንዜኑ፡ ህላዌሁ፡ ለአብ፡ ምስለ፡ ወልዱ፤ ወህላዌሁ፡ ለወልድ፡ ምስለ፡ አቡሁ ። ሠለስቱ፡ ህላዌ፡ በአካላት፡ ወአሐዱ፡ ህላዌ፡ በመለኮት፡ (ቅዳ፡ ግሩ ። ሃይ፡ አበ፡ ባስ) ። ይህ፡ ቃል፡ ለሦስቱ፡ ኹሉ፡ የተለየ፡ የአካል፡ ህላዌና፡ ግብር፡ እንዳላቸው፡ ያሳያል፤ ትርጓሜውም፡ ይህ፡ ነው ። ወላዲ፡ የአብ፡ አካል፡ መውለድ፡ ማሥረጽ፡ ግብሩ፤ ከዊን፡ ወላዲ፡ ወይም፡ ወላዲነት፡ ህላዌው፤ ባማርኛ፡ ባሕርይ፡ ይባላል፤ ልዩነት፡ ያለው፡ ገጽ፡ ቁመት፡ አቋቋም፡ መልክ፡ ማለት፡ ነው ። ተወላዲ፡ የወልድ፡ አካል፤ መወለድ፡ ግብሩ፤ ተወላዲነት፡ ህላዌው ። ሠራጺ፡ የመንፈስ፡ ቅዱስ፡ አካል፤ መሥረጽ፡ ግብሩ፤ ሠራጺነት፡ ህላዌው፤ ሠለስቱ፡ ህላዌ፡ ይህ፡ ነው ። ወአሐዱ፡ ህላዌ፡ ያለውም፤ መውለድና፡ ማሥረጽ፡ መወለድ፡ መሥረጽ፡ በዚያው፡ ባንዱ፡ ባሕርይ፡ ባንዱ፡ መለኮት፡ ነውና፤ ባሕርይ፡ የሦስቱ፡ መሣሪያ፡ መኾኑንና፡ አንድነቱን፡ መደብ፡ አድርጎ፡ እንደ፡ አካላት፡ ወላዲ፡ ተወላዲ፡ ሠራጺ፡ አለመባሉን፡ ያሳያል ። ምስጢሩ፤ ባሕርይ፡ ሳይከፋፈል፤ አካል፡ ሳይቀላቀል፤ ስምና፡ ግብር፡ ሳይፋለስ፡ የአካል፡ ህላዌ፡ ሳይፈርስ፤ ባን

ይንትና ፡ በሦስትነት ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ ነው ። ፫ ፡ መለኮት ፡ የሚሉ ፡ ግን ፤ ወላዲ ፡ ባሕርይ ፡ ተወላዲ ፡ ባሕርይ ፡ ሠራጺ ፡ ባሕርይ ፡ እያሉ ፤ የአካላትን ፡ ስምና ፡ ግብር ፡ በባሕርይ ፡ ሰጥተው ፡ ይፈታሉ ።

**ህላዌ ፤** አካል ፡ ገጽ ፤ አቋቋም ፡ ቁመት ፤ አኳኋን ፡ ኹነታ ። አካል ፡ ማለት ፡ ባሕርይና ፡ ግብርን ፡ መልክንና ፡ ስምን ፡ ኹሉን ፡ ሰብስቦ ፡ የሚይዝ ፤ ሰብሳቢ ፡ ገዥ ፡ አዛዥ ፡ ባለቤት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የአካልን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። **እግዚአብሔር ፡ በዓለ ፡ ሠለስቱ ፡ ህላዌ ፡ አሐዱ ፡ በባሕርይሁ ፡ ወሥልጣኑ ፡ ወመለኮቱ ። እስመ ፡ አበዊነ ፡ ሰመይዎ ፡ በዝንቱ ፡ ገጸ ፡ መካን ፡** (በአንቀጸ ፡ ተዋሕዶ) ፡ **ለህላውያት ፡ አካላት ፤ አትናቴዎስኒ ፡ ረሰዮ ፡ ህላዌ ፡ አሐደ ፡ አካለ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተሠገወ ። እስመ ፡ ህላዌ ፡ ይትበሀል ፡ በእንተ ፡ ክዋኔ ፡ ወአካል ፤ ወክዋኔሂ ፡ ይትበሀል ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ህላዌ ፡ ዘያስተጋብእ ፡ ኵሉ ፤ ወአካልሰ ፡ ዘአሐዱ ፡ ህላዌ ፡ ውእቱ ።** ተውሕደ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ አካል ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ገጽ ፡ አቋቋም ፡ ቁመት ፡ ያልነው ፡ የአካል ፡ ባሕርይ ፡ ይባላል ፤ አካል ፡ ያለገጽ ፡ ያላቋቋም ፡ አይገኝምና ። **እስመ ፡ በዝየ ፡ ይሰመይ ፡ አካል ፡ ህላዌ ፡ አካሉ ፡ ለወልድ ፤ ወአኮ ፡ ውእቱ ፡ ህላዌ ፡ ዘያስተጋብአሙ ፡ ለሥሉስ ፡ ቅዱስ ፤ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ተሠገወ ፡ እግዚ ፡ ቃል ፡** (አክሲ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ብን ። ዲዮ ። መቃር)። ህላዌን ፡ የአካል ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ አካልን ፡ አቋቋም ፡ ብሎ ፡ ነው ።

**ህላዌ ፤** ባሕርይ ፤ ጠባይ ። ባሕረንና ፡ ጠብዕን ፡ ተመልከት ። **ጎቡረ ፡ ህላዌ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፤ ጎቡረ ፡ ህላዌ ፡ ምስሌነ ፡ በትስብእቱ ። ወኢተወለጠ ፡ ህላዊ ፡ ቃል ፡ ኀበ ፡ ህላዌ ፡ ሥጋ ፡ ወህላዌ ፡ ሥጋ ፡ ኀበ ፡ ህላዌ ፡ ቃል ፤ ዳእሙ ፡ ይሄልዉ ፡ ክልኤቱ ፡ ህላውያት ፡ በበ ፡ ህላዌሆሙ ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡** (ተረ ፡ ቄር ። ሃይ ፡ አበ ፡ መጠሊ) ። ህላዌ ፡ በአንቀጸ ፡ ተዋሕዶ ፡ አካል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አሐዱ ፡ እንዲባል ፡ በአንቀጸ ፡ ተፀቅዖም ፡ ባሕርይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ክልኤቱ ፡ ይባላል ፡ እውነተኛው ፡ የሊቃውንት ፡ ዐዋጅ ፡ ይህ ፡ ነው ። **ወኢተዋሐደ ፡ በመንፈቀ ፡ ህላዌ ፡ ወኢኮነ ፡ ካልአ ፡ እንስሳ ፡ በእንተዝ ፤ አላ ፡ ምሉእ ፡ ወፍጹም ፤ በአሐዱ ፡ ህላዌ ፡ ይገብር ፡ ዘክልኤቱ ፡ ህላውያት ፡** (ሃይ ፡ አበ ፡ ኤፍ፡) ። አሐዱ ፡ ያለው ፡ አካል ፤ ክልኤቱ ፡ ያለው ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ። ባሕርያት ፡ ፪ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ የባሕርያት ፡ ፍሬ ፡ ግብራትም ፡ ፪ ፡ ናቸው ፡ ተወላዲው ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ሲኾን ፡ ልደቱ ፡ ፪ ፡ እንዲባል ፤ ግብሩም ፡ ሠሪው ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ መሣሪያው ፡ እንደ ፡ ባሕርይ ፡ ፪ ፡ ይባላል ። ግብርን ፡ አሐዱ ፡ ማለት ፡ ልደትንም ፡ አሐዱ ፡ ያሰኛል ፤ ልደት ፡ ቅሉ ፡ ግብር ፡ ነውና ፡ ፪ ፡ መባሉ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፤ ግብር ፡ ባሕርይን ፡ ገቢር ፡ አካልን ፡ ይከተላል ። **ሶቤ ፡ መንክራት ፡ ወዓዲ ፡ ሶቤ ፡ ሕማማት ፡ ወውእቱ ፡ አሐዱ ፡ ህላዌ ፡ በመለኮቱ ፡ ይገብር ፡ መንክራተ ፡ ወበትስብእቱ ፡ ይትዌከፍ ፡ ሕማማተ ። ርኢኩ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ሎቱ ፡ ክልኤቱ ፡ ግብራት ፡ ጎቡረ ። ወሀቀበ ፡ እሎንተ ፡ ክልኤተ ፡ ግብራተ ፡ በዘሉ ፡ ዘመን ። ወኢንቤ ፡ ከመ ፡ መንክራት ፡ ለአሐዱ ፡ ወሕማማት ፡ ለካልኡ ፤ አላ ፡ እሙንቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አሐዱ ፡ ባሕቲቱ ፤ ከመ ፡ አምላክነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አሐዱ ፡ አካል ፡ ሥግው ፡ ወአሐዱ ፡ ህላዌ ፡ ዘንብረ ፡ ኵለንታሁ ፡ ለወልድ ፡ ዘውእቱ ፡ ቃል ፡ ወነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ወልቡና ፡ ወምግባር ።** ህላዌ ፡ ዘንብረ ፡ ኵለንታሁ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ነፍስ ፡ ልቡና ፡ ምግባር ፡ ብሎ ፡ ቈጠረ ፤ ልቡና ፡ ምግባር ፡ የሌለው ፡ ሌላ ፡ ህላዌ ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ ህላዌ ፡ አይባልምና ፡ (ሃይ ፡ አር ፡ ጎር ። ኤጺ ። መቃር) ።

**ህላዌ ፤** ጠቅላይ ፡ ስም ፤ ኵላዊ ፡ አስተጋባኢ ፤ ስምንቱ ፡ ክቶሊክ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ለፈጣሪ ፡ ሳይቀር ፡ በሰማይ ፡ በምድር ፡ ላለ ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። **ወእምኑ ፡ እስመ ፡ ስመ ፡ ህላዌ ፡ ይትበሀል ፡ በገጸ ፡ መካን ፡ ህየንተ ፡ ህላዌ ፡ ኵሉ ፡ ዘመድ ፡** (ሃይ ፡ አበ ፡ ዲዮ) ። አስተጋባኢ ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እንደ ፡ ጠባይዕ ፡ ለአካል ፡ በሚመችበት ፡ አካል ፤ ለባሕርይ ፡ በሚመችበት ፡ ባሕርይ ፡ ይባላል ። ባማርኛ ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ ታጥቶለት ፡ እንጂ ፡ በአካልና ፡ በባሕርይ ፡ መካከል ፡ ሌላ ፡ የተለየ ፡ ማእከላዊ ፡ ስም ፡ ያስፈልገው ፡ ነበር ። በምድር ፡ ያለ ፡ የፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ሥር ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ናቸው ፤ ማይ ፡ መሬት ፡ ነፋስ ፡ እሳት ፤ እሊህ ፡ አራቱ ፡ እየተዋሐዱ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ባሕርይ ፤ ሥጋን ፡ ዕንጨትን ፡ ያስገኛሉ ። የተለየ ፡ የባሕርይ ፡ ስሙ ፡ ሥጋ ፡ ዕንጨት ፡ ነው ፤ ከራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ተውሕደ ፡ ሥጋ ፡ ኹኖ ፡ ዕንጨት ፡ ኹኖ ፡ የቆመበት ፡ ውሳጣዊ ፡ አስተጋባኢ ፡ ስሙ ፡ ህላዌ ፡ ተብሏል ። «ጵርኣውያን ፡ ህላዌን ፡ ወለያ ፡ ባሕርይን ፡ ፊሲስ ፡ ይሉታል ። ላቲናውያንም ፡ ህላዌን ፡ ሱብስታንስያ ፤ ባሕርይን ፡ ናቱራ ፡ ይሉታል» ። አካል ፡ ለባሕርይ ፡ አይነገርም ፤ ባሕርይም ፡ ለአካል ፡ አይነገርም ፤ ህላዌ ፡ ግን ፡ ኹለቱ ፡ አንድ ፡ ኹነው ፡ የቆሙበት ፡ አስተጋባኢ ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለኹለቱ ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። የመጠበት ፡ የስምንቱ ፡ ምስጢር ፡ ግን ፡ አጥብቆ ፡ አጥልቆ ፡ ሲመረመር ፡ አኳኋንንና ፡ አቋቋምን ፡ የተዋሐደውን ፡ ጽናትና ፡ አኗኗር ፡ ያሳያል ፡ እንጂ ፡ አካልን ፡ ብቻ ፡ ባሕርይንም ፡ ብቻ ፡ አያሳይም ። የንጨት ፡ ኹሉ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ህላዌው ፡ እየቅል ፡ ነው ፡ ብርቱ ፡ አለ ፡ ግብዝ ፡ አለ ፤ ከራቱ ፡ ባሕርያት ፡ የተፈጠረ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ነው ። የመላእክትና ፡ የነፍስ ፡ ባሕርይ ፡ ግን ፡ መሠረት ፡ የለውም ፡ እምነበ ፡ አልቦ ፡ ነው ፤ መላእክትን ፡ ዘይሬስዮሙ ፡ መንፈሰ ፡ ወነደ ፡ እሳት ፡ ቢላቸው ፡ የሚራቀቁ ፡ የሚጣመቁ ፡ ተላአክያን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እኛ ፡ ከምናውቀው ፡ ነፋስና ፡ እሳት ፡ ማለት ፡ አይደለም ፤ ከዚህ ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ ባየናቸው ፡ በሰማናቸው ፡ ነበር ። አካላውያን ፡ ኹነው ፡ ተፈጥረዋል ፤ ባሕርያቸው ፡ ከአካላቸው ፡ አይቀድምም ፤ የአካላቸው ፡ አኳኋን ፡ ህላዌ ፡ ይባላል ፤ የነፍስም ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ነው ። የነፍስ ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡ ሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡ ግዘፍ ፡ ሳይሳብ ፤ የሥጋም ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡ ነፍስ ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡

ርቀት ፡ ሳይሳብ ፤ ንፍስና ፡ ሥጋ ፡ ተውሕደው ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ፩ ፡ ህላዌ ፡ ፩ ፡ ሰው ፡ ይገኛል ። **እስመ ፡ ክዋኔሁ ፡ ለሰብእ ፡ ውእቱ ፡ ግብር ፡ እለ ፡ ኢይትማሰሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወኢየኀብሩ ፡ ወቃልኒ ፡ ኢየኀብር ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ በከመ ፡ ኢተኀብር ፡ ነፍስ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ እንዘ ፡ ብእሲሁ ፡ አሐዱ ፡ እምነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ወአሐዱ ፡ ገጽ ፡ እምዘኢየኀብሩ ፡ ግብራት ።** ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ተውሕደው ፡ አንድ ፡ ኹነው ፡ የቆሙበት ፡ አካል ፡ ህላዌ ፡ ይባላል ፤ ሲቃልም ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ የተለየ ፡ ህላዌ ፡ አለው ፤ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ።

**ህላዌ ፤** መኖሪያ ፡ መኗሪያ ። ምስጢሩ ፡ እኖምር ፡ ከሰው ፡ ይገባል ። **ኅበ ፡ ህላዌሁ ፡ ተመይጠ ፡ ልሳኑ ፡ ውቂይ ፡ ኅበ ፡ ህላዌሁ ፡ አግብአ ፡** (ስንክ ፡ ጥር፳) ፡ ዳግመኛም ፡ ባሕርይ ፡ ያላካል ፤ አካል ፡ ያለባሕርይ ፡ ብቻ ፡ ብቻውን ፡ አይኖርምና ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ቦታ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ።

**ህላዌ ፤** ሥራ ፡ ግብር ። **ህላዌ ፡ ግፍዕ ፤** የግፍ ፡ ሥራ ፡ ግዙፍ ፡ ግፍ ፡ (ሔኖ፺፩ ፡ ፭) ። እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ የህላዊንና ፡ የጠባይዕን ፡ ፍች ፡ በየስልቱ ፡ ማስተዋል ፡ ይገባል ፤ ኹለቱ ፡ ኹሉ ፡ ፩ ፡ ናቸውና ።

**ህሉና ፤ ህልውና ፤** ነዋሪነት ፤ አንዋወር ፡ ኑሮ ። **ህሉና ፡ ሥላሴ ። ህሉና ፡ መለኮት ፡** (ቅዳ) ።

**አህለወ ፤** አኖረ ፤ አስኖረ ፤ አስቀመጠ ፤ ነዋሪ ፡ አደረገ ፤ አስደረገ ። **ወምስለ ፡ ብዙኅ ፡ ምሕረት ፡ ታሄልወነ ፡** (ጥበ፲፪ ፡ ፲፰) ።

**ምህላው ፤** መኖሪያ ፤ ቦታ ፡ ሀገር ። **ነፍስ ፡ እመ ፡ ተፈልጠት ፡ እምሥጋ ፡ በሞት ፡ ገብአት ፡ ኅበ ፡ ብርሃን ፤ ዘውእቱ ፡ ማኅደራ ፡ ወምህላዋ ፡ ወፍግዓሃ ፡ ወተድላሃ ። ነሥኣ ፡ ለሀገረ ፡ ባቢሎን ፡ ወተወፈየ ፡ ምህላወ ፡ ብልጣሶር ፡** (ዮሴፍ) ።

**ሀለወ ፤—ጠበቀ ፤—ኀሊው ፡ ኀለወ ።**

**ሀለየ ፤—ዘፈነ ፤—ሐልይ ፡ ሐለየ ።**

**ሀሊል ፤ (ሀለ ፡ የሀልል ፡ ይሀልል ። ዕብ ፡ ሀሎል ፡ ሄል) ፤** ማወደስ ፡ ማመስገን ፤ መዩበብ ፡ መዝፈን ።

**ሃሌ ፤ (ሀሌ ። ዕብ ፡ ሀሌል) ፤** ሃሌታ ፤ ስብሐት ፡ ውዳሴ ፤ መዝሙር ፡ ግናይ ፤ ቅኔ ፡ ሐዲስ ፡ ምስጋና ፤ መዘምራን ፡ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ብለው ፡ የሚመሩት ፤ በሃሌታ ፡ የሚዘምሩት ። እንቀጽ ፡ ሃሌታ ፡ እንዲሉ ። (ተረት) ፤ መዝሙር ፡ በሃሌ ፤ ነገር ፡ በምሳሌ ፤ ጠጅ ፡ በብርሌ ። ሃሌታና ፡ እልልታ ፡ በምስጢር ፡ አንድ ፡ ነው ፤ አለለን ፡ ተመልከት ።

**ሃሌ ፡ ሉያ ፤ (ዕብ ፡ ሀልሉ ፡ ያህ) ፤** ስብሐ ፡ እግዚአ ፤ ሀልሉ ፡ ሰብሐ ፤ ያህ ፡ እግዚእ ፡ አምላክ ። **ወርኅ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡** (ዘፀ፲፫ ፡ ፬) ። አቢብን ፡ ተመልከት ።

**ህላል ፤ (ዐረ ፡ ሂላል) ፤** ሠርቅ ፡ ወርኅ ፡ ልደተ ፡ ወርኅ ፤ ሐዲስ ፡ ለጋ ፡ ጨረቃ ።

**ህላሊ ፤** ሠርቃዊ ፡ ወርኃዊ ፤ የጨረቃ ፡ ወር ። **አውራኅ ፡ ህላል ፤ ህላሊ ፡** (አቡሻ ፡ ፳፭) ።

**ሆሙ ፤ (ሁ) ፤** የሩቅ ፡ ወንዶች ፡ ዝርዝር ፡ ጠቃሽ ። የሁን ፡ አፈታት ፡ እይ ።

**ሀሙዲዳ ፤ (ዕብ ፡ ሀሞዒድ) ፤** ዕድሜ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወራት ፡ የበዓል ፡ የቀጠሮ ፡ ቀን ። **ሄዔኬር ፡ ሀሙዲዳ ፡** (ኤር፵፮ ፡ ፲፯) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ስባሬ ፡ ምቱረ ፡ ሥርው ፡ ፈረ ፡ ይሉታል ።

**ሆሚር ፤—መስፈሪያ ፤—ሐሚር ።**

**ሆን ፤—(ሁ ፡ ሆሙ) ፤** የሩቅ ፡ ሴቶች ፡ ዝርዝር ፡ ጠቃሽ ።

**ሀኖስ ፤ (ጽር ፡ አኖስ ፡ ያኖስ) ፤** ክፍለ ፡ ስም ፡ የውቅያኖስ ፡ ክፋይ ፤ ብጥብጥ ፡ ባሕር ፤ የሚታወክና ፡ የሚናወጽ ፤ የማይደምዕና ፡ የሚደረጽ ። ይኸውም ፡ ከጠፈር ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ሚሶው ፡ ውሃ ፡ ነው ፤ እንዱ ፡ እጅ ፡ ጠፈር ፡ አንዱ ፡ እጅ ፡ ውቅያኖስ ፡ እንዲባል ፤ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ሀኖስ ፡ ይባላል ፡ (ዘፍ፲፯ ፡ ፲፩ ። ኩፋ ፡ ፳ ። ሱቱ ፡ ዕዝ፮ ፡ ፵፩) ። **ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ይወፅእ ፡ መቅሠፍቱ ፡ ለእግዚአ ፡ መናፍስት ፤ ወይትረኀዉ ፡ ኵሎሙ ፡ መዛግብተ ፡ ማያት ፡ ዘመልዕልተ ፡ ሰማያት ፡ ወዲበ ፡ አንቅዕት ፡ እለ ፡ መትሕተ ፡ ሰማያት ። ወይደመሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ማያት ፡ ዘምስለ ፡ ማያት ፤ ዘመልዕልተ ፡ ሰማያት ፤ ማይሰ ፡ ዘመልዕልተ ፡ ሰማይ ፡ ተባዕታይ ፡ ውእቱ ፤ ወማይ ፡ ዘመትሕተ ፡ ምድር ፡ አንስቲያዊት ፡ ይእቲ ፡** (ሔኖ ፡ ፶፩) ። ብዙዎች ፡ መተርጕማን ፡ ግን ፡ ፬ቱን ፡ እጅ ፡ ውሃ ፡ ጠፈር ፡ አደረገው ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፤ ከጠፈር ፡ በላይ ፡ ብጥብጥ ፡ ባሕር ፡ አለ ፡ አይሉም ።

**ሀዑቢም ፤ (ዕብራ) ፤** ወፍራሞች ፤ ደንዳኖች ። ወፍሮች ፡ ድንዳኔዎች ፡ (ሕዝ፴፩ ፡ ፳፯) ።

**ሄዔኪር ፤ (ዕብ ፡ ሄዒቢር) ፤** አሳለፈ ፡ አሻገረ ፤ አስተላለፈ ፤ የጊዜ ፡ የወራት ። ሐተታውን ፡ በቢድን ፡ ፍች ፡ እይ ፤ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ይከማ ፡ ዘበጽሐ ፡ ጊዜሁ ፡ ኅሱር ፡ ይሉታል ፡ (ኤር፵፮ ፡ ፲፯) ።

**ሀፈው ፤ ምት ፤ (ሀፈወ ፡ የሀፉ ፡ ይሀፉ ። ዐረ ፡ ሀውፍ ፤ ሁፍ ፤ ውዐይ ፡ ነፋስ) ፤** መውዘት ፡ መድከም ፤ መሞቅ ፡ በላበት ፡ መጠመቅ ። **ፈተወት ፡ ትትኀፀብ ፤ እስመ ፡ ሀፈወት ። እስከ ፡ የሀፍዉ ። ጸመ ፡ ወጸለየ ፡ ደክመ ፡ ወሀፈወ ። በጸዋሪ ፡ መስቀሉ ፡ ሀፈወ ፤ እስመ ፡ ክቡድ ፡ ውእቱ ፡** (ዳን፲ ፡ ፲፭ ። ሥር ፡ ጻጕ ። ግንዘ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ሀፍ ፤ (ዕብ ፡ ዚዓህ) ፤** ወዝ ፡ ላበት ፤ ድካም ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፲፱ ። ሉቃ፳፪ ፡ ፵፬) ። **ኢብዝኅ ፡ ስግደተ ፡ እስከ ፡ ይውሕዝ ፡ ሀፉ ፡ ከመ ፡ ማይ ። ዘእንበለ ፡ ጻማ ፡ ወሀፍ ። ፈንዉ ፡ ሲሳዮሙ ፡ እምንዋይክሙ ፡ ወሀፈ ፡ ገጽክሙ ፡** (ገድ ፡ ተክ ። አፈ ፡ ተ፫ ። ዲድ ፡ ፳፭) ።

—፤ ሙቀት ፡ ሐሩር ። **ቍር ፡ ወሀፍ ። ብሔረ ፡ ጽምእ ፡ ወሀፍ ። ሀፍ ፡ ወሞቅ ፡** (ዘፍ፰ ፡ ፳፪ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፲ ። ሔኖ፹፪ ፡ ፲፯) ።

**ሀርበደ** ፤ (አብደ ። ዐረ ፡ ዐርበደ ፤ ክፉ ፡ ክፉ ፡ ኾነ) ፤ አረበደ ፤ ቸኰለ ። ተቈጣ ፡ እብድ ፡ እብድ ፡ አለ ። ደነገጠ ፡ ደነበረ ፤ ወገሸ ፡ አገረገረ ፤ ሸሸ ፡ ሮጠ ፡ ፈረጠጠ ፡ የክብት ። ክመ ፡ ዕጐልት ፡ እንተ ፡ ተሀረብድ ፡ ሀርበደ ፡ ኤፍሬም ፡ (ሆሴ ፱ ፡ ፲፩) ።

— ፤ ተቀናጣ ፤ ተቀማጠለ ፤ ሰው ፡ ልፍጅ ፡ አለ ፤ የዘመናይ ። ወለእመ ፡ ቀተለ ፡ በሀርብዶ ፡ ኢይክውን ፡ ዘነኒሁ ፡ ክመ ፡ ዘነኑ ፡ አብዳን ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፸፩) ። አንዳንድ ፡ መጠፍ ፡ በተሀርብዶ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ሀርብዶና** ፤ መቀማጠል ፤ ቅምጥልነት ፡ የቅንጦት ፡ ሥራ ። ወለእመ ፡ ክንከ ፡ ዘመንንካሁ ፡ ለህርብዶና ፡ ጕየይ ፡ እምእለ ፡ ይነዐውዎ ፡ (ማር ፡ ይሥ፪ ፡ ፲፱) ።

**ሄሮድያኖስ** ፤ (ጽር ፡ ሄሮዲዎስ) ፤ ያሞራ ፡ ስም ፡ ሽመላ ፡ ሽመላዊ ፤ እግረ ፡ ሽመል ፡ ዐንገተ ፡ ማመል ፡ እግሩ ፡ ሽመል ፡ የሚያክክል ። (ተረት) ፤ ክህነና ፡ ሽመላ ፡ ያልዘራውን ፡ ይበላ ። ሄሮድያኖስ ፡ በሰማይ ፡ የአምር ፡ ዕድሜሁ ፡ (ኤር፰ ፡ ፯ ። ዘሌ፲፩ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፻፫ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፲፰) ።



ሄሮድያኖስ ።

**ሄሮድስ** ፤ (ዕብ ፡ ሆርዶስ) ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ኢዶማዊ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፤ በዘመኑ ፡ ልደት ፡ የነበረ ፡ (ማቴ፪ ፡ ፩) ።

**ሀረመ** ፡—ተወ ፤—ሐሬም ፡ ሐረመ ።

**ሄርማ** ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ የጣፈው ፡ እንደ ፡ ማልስ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ያለ ፡ ከቍጥር ፡ ያልገባ ፡ ትርፍ ፡ ወረደየ ፡ ብሔረ ፡ ሮሜ ፡ ብሎ ፡ የሚዠምር ። ስምነቱ ፡ ሄርሜን ፡ ከማለት ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ ሄርሜናዊ ፡ ያሰኛል ፤ ጸሐፊው ፡ ሄርሜን ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ መጽሐፉም ፡ ሄርማ ፡ ተብሏል ።

**ሄርሜን** ፤ (ጽር ፡ ሄርሚን) ፤ ጠዖት ፡ ስመ ፡ ጣዖት ፤ በመንታ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የሚቆሙት ። መሬ ፡ አስተማሪ ፤ ትርጁማን ፡ አፈ ፡ በሃማኑ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ግብ፲፬ ፡ ፲፪) ።

**ሀሴቦን** ፤ (ጽር ፡ ሄሴቦን) ፤ ውስጠ ፡ በውስጥ ፡ ውሳጣዊ ። ኵሉ ፡ ክብሩ ፡ ለወለተ ፡ ንጉሥ ፡ ሀሴቦን ፡ (መዝ ፡ ፵፬) ።

**ሄሴሮት** ፤ (ዕብ ፡ ሀአሴሮት) ፤ የጥራጊ ፡ የጕድፍ ፡ መጣያ ፤ ያዛባ ፡ የፍግ ፡ መቈለያ ፡ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ግናይ ፡ ይሉታል ። አንቀጹ ፡ ሄሴሮት ፡ (ኍሐ፲፪ ፡ ፴፭) ።

**ሆሴዕ** ፤ (ዕብ ፡ ሆሼዕ) ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ነቢይ ፡ ንጉሥ ። አድኅን ፡ ባልሐ ፤ ረድእ ፡ አውፅእ ፡ እመሥገርት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ሆሴ፩ ፡ ፩ ። ፬ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፩) ።

**ሆሳዕና** ፤ (ዕብ ፡ ሆሺዓህ—ናእ) ፤ አንቀጽና ፡ ጥሬ ፤ አድኅነነአ ፤ አድኅና ፤ አድኅንኦ ፤ እባክኽ ፡ አድኅን ፤ የአን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፡ (ማር፲፩ ፡ ፲ ። ዮሐ፲፪ ፡ ፲፫) ።

— ፤ መድኀኒትነት ፤ መድኀኒት ፡ መኾን ፤ ወይም ፡ መባል ። ሆሳዕና ፡ ለወልደ ፡ ዳዊት ። እምሆሳዕናሁ ፡ አርእየ ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡ (ማቴ፳፩ ፡ ፱ ። ቅዳ ፡ ጎር) ።

— ፤ የበዓል ፡ ስም ፤ የሰሌን ፡ በዓል ፡ ሰሌን ፡ ይዘው ፡ እያመሰገኑ ፡ የሚያውዱበት ፤ ለብሉዩ ፡ የመጸለት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፤ ለሐዲሱ ፡ ግን ፡ ከትንሣኤ ፡ በፊት ፡ ያለ ፡ እሑድ ። (የደሮች ፡ ዘፈን) ፡ በሆሳዕና ፡ ተሰበሰብና ፤ በሳምንቱ ፡ አለበን ፡ ሞቱ ። ዋዜማ ፡ ዘሆሳዕና ። በሳኒታ ፡ ሆሳዕና ፡ በበኑይ ፡ ዕለት ፡ (ድጓ ። ዲድ ፡ ፳፱) ።



ሆሳዕና ።

— ፤ ሰሌን ፡ የሰሌን ፡ ቅጠል ፤ ቈጽለ ፡ ዘይት ፤ ባርሰንት ፡ ኰሓ ፤ የመሰሰው ፡ ኹሉ ፤ የሆሳዕና ፡ ለት ፡ የሚያዝ ። ዘይትን ፡ ወሆሳዕና ። ልብሱ ፡ እምልሕጸ ፡ ሆሳዕና ፡ ወቈጽሉ ፡ ሰሌን ፡ (ስንክ ፡ መስ፲) ።

**ሁስጱ** ፤ (ጽር ፡ ሒሶፖስ) ፤ የቀንበጥ ፡ ቾበ ፡ ለባልብ ። አዛብንን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ፡ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሰይተው ፡ ስምዛ ፡ አሸክት ፡ ይሉታል ። ቈጽለ ፡ ሁስጱ ። ሐምለ ፡ ሁስጱ ፡ (ዘሌ፲፬ ፡ ፬ ፡ ፯ ። ፫ነገ ፡ ፬ ፡ ፴ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፳፱ ። ዕብ፱ ፡ ፲፱) ።

**ሆትሒላ** ፤ (ዕብራ) ፤ መዝሙር ፡ ምስጋና ። መልእክ ፡ ሆትሒላ ፡ (ኍሐ፲፭ ፡ ፲፯) ።

**ሄጸ** ፤—ወጋ ፡ ገመሰ ፤—ሀዩጽ ።

**ሄጽደጤን** ፤ (ጽር ፡ ሂፖዲቴስ ። ዕብ ፡ ምዒል) ፤ ልብስ ፡ ተክህኖ ፤ የላይ ፡ ልብስ ፡ ታላቅ ፡ ቀሚስ ፡ እጀ ፡ ሰፊ ፡ መቋረፊያ ። እደፊሉን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፴ ። ዘሌ፰ ፡ ፯) ።

**ሄጳዲያቆን ፤ (ጽር ፡ ሄፖዲያክኖስ) ፤** የዲያቆን ፡ ተጠሪ ፤ ንፍቀ ፡ ዲያቆን ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ሄጳጳ ፤ (ጽር ፡ ሄፖፓ ፤ ሄፖፕስ) ፤** ስሙ ፡ ያፍ ፡ ንኡስ ፤ መጠኑ ፡ የርግብ ፡ የዋኖስ ፤ ቍንጮዉም ፡



አፈ ፡ ረዥሙ ፡ የሾለቅ ፡ ዐይነት ፡ ዥንጕርጕር ፡ ኵሳኵስ ።

ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዐቢይ ፡ አሞራ ፡ ይሉታል ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፲፱ ። ዘዳ ፲፬ ፡ ፲፰) ።

(ተ) **ሀተለ ፤ (ዐረ ፡ አበለ ፤ ወበለ) ፤** ዐጠበ ፤ መታ ፡ ደበደበ ። በመርገጥና ፡ በመጠቅጠቅ ፡ ፈንታ ፡ በዱላ ፡ እየመቱ ፡ የሚያጥቡት ፡ ዕጥበት ፡ አለና ፤ ዕጥበቱንም ፡ አመታቱንም ፡ ባንድነት ፡ ያሳያል ።

**ሀታሊ ፤ መሀትል ፤ መሀቲል ፤** እየመታ ፡ የሚያጥብ ፡ ዐጣቢ ። **ገራህተ ፡ መሀቲል ።** ዘኢይክል ፡ **መሀቲል ፡ አጻዕድዎ ፡ ከማሁ ፡** (ኢሳ ፯ ፡ ፫ ። ፴፮ ፡ ፪ ። ማር ፱ ፡ ፫) ።

# ወ

**ወ ፤** ኻያ ፡ ፊደል ፤ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ። ስሙ ፡ ዋዊ ፤ ቍጥሩ ፡ ስድስት ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ **ወ ፡ ስድስት ፤** ስድስት ፡ ቱ ፡ ይባላል ። ዕብራውያን ፡ ግን ፡ ስድስትን ፡ መደብ ፡ አድርገው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ንቍጣ ፡ እየጨመሩ ፡ ስድስት ፡ እልፍ ፡ ይሉታል ። ኻያ ፡ ማለት ፡ ምስጢሩ ፡ ዐርብንና ፡ የዐርብን ፡ ፍጥረት ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፤ ዳግማይ ፡ አዳም ፡ ሥጋው ፡ ቃልን ፡ ምስጢረ ፡ መስቀልን ፡ ያሳያል ፤ የዋዊን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ።

**ወ ፤ (ሂ ፡ ኒ ፡ ዓዲ) ፤** ንኡስ ፡ አገባብ ። አጫፋሪ ፤ ማሰሪያ ፡ ከፋይ ፤ አጋናኝ ። ም ፤ ና ፤ ቸልታ ፡ ዘተረስዐ ፤ ውጥን ፡ ጨራሽ ፤ የአኃዝ ፡ ጠቅላይ ፡ ከ ፤ በ ፡ ጊዜ ፤ ስንኳ ፤ ግን ፤ ስ ፤ ፈጽሞ ፡ አዳማቂ ፡ ትች ፡ ይኾናል ። ም ፡ ሲኾን ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ፤ **በልዐ ፡ ወሰትየ ፡ ሰምዐ ፡ ወርእየ ።** ና ፡ ሲኾን ፡ በስም ፡ ይገባል ፤ **ጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስ ፡ ያዕቆብ ፡ ወዮሐንስ ።** በሦስት ፡ ስሞች ፡ ሲገባ ፤ መጀመሪያው ፡ ና ፡ ኹለተኛው ፡ ም ፡ ይኾናል ፤ **ጳውሎስ ፡ ወስልዋኖስ ፡ ወጢሞቴዎስ ።** በብዙ ፡ ስሞች ፡ ሲገባ ፡ ጭራሽ ፡ ም ፡ ይኾናል ፡ ወይም ፡ ጠቅላይ ፡ ኹሎ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ያሰኛል ። **ተንሥአ ፡ ወነደገ ፡ ልብሶ ፡ ተጠምቀ ፡ ወአድኀነ ፡ ርእሶ ፤** ቸልታ ፡ ልብሱን ፡ ጥሎ ፡ ራሱን ፡ አድንኖ ። ዘተረስዐ ፡ ሲኾን ፡ የኋሊት ፡ ይፈታል ፤ ወ ፡ የወደቀበት ፡ ማሰሪያ ፡ ያልወደቀበት ፡ ቸልታ ፡ ይኾናል ፤ **ይበኡ ፡ ወይርአዩ ፡** ገብቶ ፤ **ሐመ ፡ ወሞተ ፤** ታሞ ፤ **ሖረ ፡ ወመጽአ ፤** ኼዶ ፡ መጣ ። **ተሰቅለ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወከማሁ ፡ እንድርያስ ፤ ተውህበ ፡ ጳውሎስ ፡ ሙቁሐ ፡ ወካልኣንሂ ፡ ሙቁሓን ፤** ውጥን ፤ ይህ ፡ የፊቱን ፡ በኋላ ፡ ሲጨርስ ፡ ነው ። የኋላውን ፡ በፊት ፡ ሲጨርስ ፤ **ሰማይ ፡ ወምድር ፡ የኀልፍ ፤** ይላል ፤ ሰማይም ፡ ያልፋል ፡ ምድርም ፡ ታልፋለች ፡ ያሰኛል ፡ ሰማይ ፡ ምድር ፡ ያልፋል ፡ ተብሎም ፡ በጠቅላይነት ፡ ሊፈታ ፡ ይቻላል ፤ ባላገባቦች ፡ ግን ፡ ጋራ ፡ ይሉታል ። **ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ሰብዓ ፡ ወኀምስቱ ፤ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ዐሠርቱ ፡ ወሰመንቱ ፤** ጠቅላይ ። **እልፍ ፡ ወዕሥራ ፡ ምእት ፤** ከ ፡ ና ። **ወተወሊዶ ፡ ወጸቢሖ ፤** በ ፡ ጊዜ ። **ኢወሀቦ ፡ ርስተ ፡ ወኢመጠነ ፡ ምከየደ ፡ እግር ፤** ስንኳ ። **ጻድቅ ፡ ቄርሎስ ፡ ወኢጻድቅ ፡ ንስጥሮስ ፤** ግን ። እንጂም ፡ ይኾናል ፤ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ነው ። **በልዐ ፡ ወኢሰትየ ፤** ብሎ ፡ አልጠጣም ፡ እንጂ ፡ ያሰኛል ። **ምንተ ፡ ንበልዕ ፡ ወምንተ ፡ ንሰቲ ፤** ስ ። **ሖረ ፡ ወኀለፈ ፤ ከተበ ፡ ወጸሐፈ ፤** ፈጽሞ ። ፈጽሞ ፡ ያሰኘው ፡ ያናቅጽ ፡ ኅብረት ፡ የፍች ፡ አንድነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምስጢሩና ፡ ሙያው ፡ ከጫፋሪነት ፡ አይወጣም ። አዳማቂ ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ ከመ ፡ በማልሳይ ፡ አንቀጽ ፤ **ሰምዐኒ ፡ ወእንግርከ ፤ ቅረበኒ ፡ ወእግስስከ ፤ ኢትግበራ ፡ ለእኪት ፡ ወኢይርከብከ ፡ እኩይ ፤** እያለ ፡ ይገባል ። ትች ፡ ሲኾን ፡ **ምንተ ፡ ትሁበኒ ፡ ወአነ ፡ አገብኦ ፡ ለክሙ ፤** ይላል ። ወ ፡ እኹል ፡ ገብ ፡ ፊደል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ስልቱና ፡ አፈታቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፤ የቀረውን ፡ በግስ ፡ በመልና ፡ በፊደል ፡ ታሪክ ፡ በንኡስ ፡ አገባብ ፡ ተመልከት ። ኹለተኛም ፡ የግስ ፡ በመል ፡ ኹኖ ፡ ፊደልን ፡ ኹሉ ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ያደርጋል ። የካዕብ ፡ የሳብዕ ፡ ሥረያቸው ፡ ወ ፡ ነው ፤ ሥረይነቱ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በፊደል ፡ ታሪክ ፡ እዩ ። ባማርኛም ፡ እንደ ፡ መ ፡ ባዕድ ፡ ዘር ፡ ይኾናል ፤ ጠመደ ፡ ወጥመድ ። ነበረ ፡ ወንበር ። ሰፋ ፤ ወስፌ ። ነፋ ፤ ወንፊት ። ዐገመ ፡ ዋገምት ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**ዊ ፤ (ዊ—ዪ) ፤** ወገን ፡ ቅጽል ፡ የ ። ምድራዊ ፡ ሰማያዊ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ምእላድ ፡ በዓቃፍ ፡ በትራስ ፡ ይገ

ባል ። ፪ኛም ፡ ግብረ ፡ ሰብእ ፡ ያስመሰ ፡ ግብር ፡ ስብ ኢዊ ፡ ይባልና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የመሻዝር ፡ ውስጠ ፡ ዘ ፡ ይባላል ። ዊና ፡ ዪ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ።

**ዋ ፤ (ዋ—ኣ)** ፤ የራብዕ ፡ ሥረይ ፡ (ዋየል) ፡ ላ ፊቱ ፡ ዲቃሎች ፤ ጓ ፡ ኍ ፡ ኊ ፡ ቈ ፤ ጕዋ—ጓ ። በነዚህ ፡ አንጻር ፡ ስሚገኙም ፡ ለራብዖች ፡ ኹሉ ፡ ላማርኛ ፡ ፊ ደል ፡ ሥረይ ፡ ይኾናል ፤ ቡዋ—ቧ ። ባማርኛም ፡ የሐዘ ንና ፡ የንቀፌታ ፡ ቃል ፡ ይኾናል ።

**ው** ፤ አብኚ ፡ ምእላድ ። **ሰግላ ፡ ሰጋልው ፡ ሰላ ርው ፡ ወላትው** ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። የወዲያኛው ፡ ትግ ሬም ፡ ቀርቡ ፡ መጽኡ ፡ ፈርሁ ፡ ደንገፁ ፡ ሲል ፡ ቀርበው ፡ መጽአው ፡ ፈርሀው ፡ ደንገፀው ፡ ይላል ።

**ው** ፤ ያማርኛና ፡ የጥንታዊ ፡ ግእዝ ፡ ዝርዝር ፡ ግስ ፡ ቀተለው ፡ ሎ ፡ ቀተልክው ፡ ኮ ። ፀማ ፡ ገደለው ፡ ገደልክው ። ውን ፡ ጕርደ ፡ ቀተሎ ፡ ልክ ፡ ማለት ፡ የሐ ዲስ ፡ ግእዝ ፡ ነው ።

**ወእደ ፤ ውእደ ፤ (እድ ፡ ወእድ)** ፤ ዐቢ ይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ። ከ—ተ—ዘንድ ፤ የ ፡ ቅጽል ። **ወ እደ ፡ ሰልቦ ፡ ሰልሕምት ፡ ምፅንጋዕ ፡ ንጹሕ** ። ሳሞች ፡ ከሴሉ ፡ ተሴሉ ፡ ዘንድ ፤ ወይም ፡ ከ ፡ ተሴሉበት ፡ ዘንድ ። **ምኔት ፡ ውእደ ፡ ሰሊሁ ፡ ይነብር** ፤ የሚኖርበት ። **ወመ ጽአ ፡ ኀቤሃ ፡ ሰሐዱ ፡ ወሬዛ ፡ እምወእደ ፡ ይትኀ ባእ** ፤ ከተደበቀበት ፡ (ምሳ፲፱ ፡ ፬ ። ሥር ፡ ጳሾ ። ዳን፩ ፡ ፴፯ ። (ዕር፲፱ ፡ ቍ፳) ።

—፤ ደቂቅ ፡ ሲኾን ፡ ወደ ፤ አገባብ ፡ ይኾናል ፤ ወደ ፡ ወ ደት ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። **እቱ ፡ ው እደ ፡ ሐዝብከ** ፤ ወደ ። **በውእደ ፡ ማየ ፡ ባሕር** ፤ አጠ ገብ ፡ (ኩፋ ፡ ፰) ። ኀበና ፡ መንገሰም ፡ እንደዚሁ ፡ ናቸው ፡ ዘሩ ፡ አደወ ፡ ነውና ፡ የእድን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ።

**ውእቱ ፤ (ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሁ ። ዐረ ፡ ሁወ)** ፤ ነባር ፡ ቅጽልና ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ ከሁ ፡ የወጣ ፡ ያ ፡ ያኛው ፡ ርሱ ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፡ ስሩቅ ፡ ወንድ ። ይ እቲ ፡ ውእቶሙ ፡ እሙንቱ ፡ ውእቶን ፡ እማንቱ ፡ አን ፡ አንተ ፡ ንቲ ፡ ትሙ ፡ ትን ፤ ንሕነ ፡ እያለ ፡ እስከሥር ፡ ይረ ባል ፡ የሁን ፡ አፈታት ፡ እይ ። **ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት** ። **ለውእቶሙ ፡ ሰሕዛብ ፡ በውእቶን ፡ መዋ ዕል** ፤ ቅጽል ። **ውእቱ ፡ ይጸንዕ ፡ እምኔየ** ፤ ዐጸፋ ። ዝ ኩንና ፡ ዝስኩን ፡ ዝክቱን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ አንጻር ፡ ናቸው ። አንቀጽ ፡ ሲኾን ፡ ደግሞ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ኖረ ፡ ነ በረ ፡ ኾነ ፡ እስከ ፡ ንሕነ ፡ ድረስ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ነው ። ውእቱና ፡ በ ፡ ሎ ፡ ኮንና ፡ ሀሎ ፡ ሱቱፋን ፡ ናቸው ፡ ይወ ራረሳሉ ፡ ይኸውም ፡ **ቀዳሚሁ ፡ ቃል ፡ ውእቱ ፡ ወው እቱ ፡ ቃል ፡ ኀበ ፡ እግዚእ ፡ ውእቱ** ፤ ባለው ፡ ይታወ ቃል ። ውእቱ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ዐጸፋና ፡ አንቀጽ ፡ ይኾ ናል ፡ **ዘወረደ ፡ ውእቱ ፡ ወዘዐርገ ፡ ውእቱ** ። ፪ ኛም ፡ በግብር ፡ ሰውጥ ፡ ሩቁን ፡ በቅርብ ፡ ቅርቡን ፡ በ ሩቅ ፡ እንዱን ፡ በብዙ ፡ ብዙውን ፡ ባንድ ፡ ወንዱን ፡ በሴት ፡ ሴቱን ፡ በወንድ ፡ ያናገራል ። **አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘይገብር ፡ ሾሎ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ዘለብሰ ፡ ሥጋ** ። **ማርያም ፡ ይእቲ ፡ ኪሩቤል ፤ ወኪሩቤል ፡ እሙ ንቱ ፡ ማርያም ፡ ለ ፡ በ ፡ እምጸዋሪ ፡ አምላክ** ። የፊተ ኛው ፡ ኹለቱ ፡ አካልን ፡ ያመጣል ፡ የኋለኛውም ፡ ኹ ለቱ ፡ ግብርን ፡ ይገልጣል ። በአካል ፡ ሰውጥ ፡ ግን ፡ በየ ራሱ ፡ ያናግራል ፤ ወይም ፡ ተለዋጭ ፡ ይኾናል ። **እመ ፡ አምላክ ፡ ማርያም ፡ ይእቲ ፡ ማርያም ፡ እመ ፡ አም ላክ ፡ ይእቲ** ። **ድንግል ፡ ዘተናገራ ፡ ኢሳይያስ ፡ ማር ያም ፡ ይእቲ ፡ ማርያም ፡ ዘተናገራ ፡ ኢሳይያስ ፡ ድ ንግል ፡ ይእቲ ፡ እብን ፡ ዘወሀቦ ፡ ሰይጣን ፡ ለእግዚ እነ ፡ ኅብስት ፡ ውእቱ ፡ ኅብስት ፡ ዘወሀቦ ፡ ሰይጣን ፡ ለእግዚእነ ፡ እብን ፡ ውእቱ** ። ቅጽል ፡ ከባለቤት ፡ ሲ ርቅ ፡ ተለዋጭ ፡ ይባላል ፡ ተለዋጭ ፡ ደግሞ ፡ ግብር ፡ ነገር ፡ ባሕርይ ፡ ይተረጕማል ፡ አካል ፡ ያመጣል ፡ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፤ አካልም ፡ ኹና ፡ ቅጽልም ፡ ኹና ፡ ማስ ፈያ ፡ ከወደቀበት ፡ ተለዋጭ ፡ ይኾናል ። ፪ኛም ፡ በሰዋ ስው ፡ ኹሉ ፡ በጥሬ ፡ በቅጽል ፡ በሚስማማው ፡ ቃል ፡ ሳይጠፋና ፡ ሳይነገር ፡ ተደብቆ ፡ ያስራል ፡ ይልቁንም ፡ በ ቅኔ ፡ ንባብ ። **ተሠግዎቱ ፡ ለቃል ፡ ወተጸልቦቱ ፡ በሥጋ ፡ ያድኅን ፡ ዓለመ ፡ ወይቤዙ ፡ ሰብአ** ። **ዘተሰቅለ ፡ በቀ ራንዮ ፡ ሥግው ፡ አምላክ ፡ ጻድቅ ፡ ወአኮ ፡ ብእሲ ፡ ዕሩቅ** ፤ የውእቱ ፡ መመርመሪያ ፡ ያድኅንና ፡ ይቤዙ ፡ አም ላክ ፡ ጻድቅ ፡ ናቸው ።

**ወባ ፤ (ዐረ ፡ ወበእ)** ፤ የበሽታ ፡ ስም ፡ ክፉ ፡ ሽታ ፡ የሚመጣ ፡ በሽታ ፡ ምክንያት ፡ የሚጋባ ፡ እንደ ፡ ጕንፋን ፡ ያለ ። በቁሙ ፡ ወባ ፡ ንዳድ ። **ሕማመ ፡ ወባ** ፡ (ዮሴፍ) ።

**ወቦ** ፤ ስመ ፡ ኮከብ ፡ ስመ ፡ ሚፍሬ ። ወቦና ፡ በቖ ፡ እንዲሉ ።

(ጥ) **ወቢ ፤ (ወቢብ ፡ ወቦ ፤ ነጠቀ)** ፤ ያውሬ ፡ ስም ፡ የነብርና ፡ ያንበሳ ፡ ዲቃላ ። ወቢ ፡ ሽማኔ ፡ እንዲሉ ። ኹሉም ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ።

**ዌቦርከኤቦት ፤ (ጽር ፡ ዌባርክቦት ። ዕብ ፡ ኢ ክቦድ)** ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ኢስብሐት ፡ ወኢ ክብር ፤ ክብር ፡ የለውም ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለቤቶቹ ፡ ግን ፡ ትክብር ፡ ኹና ፡ ትሾም ፡ ኹና ፡ በስደት ፡ ይሉታል ። አባቱና ፡ አጎቱ ፡ ሙተው ፡ እስራኤል ፡ ድል ፡ ኹነው ፡ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ወደ ፡ ኢሎፍሊ ፡ የተማረከች ፡ ለት ፡ በስ ፡ ተወለደ ፡ ኢክቦድ ፡ ተብሏል ፡ (፩ነገ ፡ ፬ ፡ ፳፩) ።

**ወጊእ ፤ አት ፤ (ወግአ ፡ ይወግእ ፡ ዩ ጋእ ፤ አው ፡ ይውጋእ ። ዕብ ፡ ናጋሕ ። ዐረ ፡ ወጀአ)** ፤ መውጋት ፡ መደይቅ ፡ መደንጐር ፡ መዘርከት ፡ መቸብለክ ፡ መቸክቸክ ። መውጋጥ ። **ለእመ ፡ ወግአ ፡ ላሕም ፡ ብእሴ ። ወጋእክሙ ፡ ከመ ፡ አስዋር ። በ ሐጽ ፡ ይወግእ ፡ በአቅርንቲሁ ። ወግአኒ ፡ በኵያንው ። ወግአኒ ፡ ሦክ ። እለ ፡ ወግእዎ** ፡ (ዘፀ፳፩ ፡ ፳፰ ። ኤር፳፯ ፡ ፲፩ ። ዳን፰ ፡ ፬ ። ኢዮ፲፯ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፻፲ ። ራእ፩ ፡ ፯) ። ድል ፡ ማድረግ ፡ ማሸነፍ ፡ መግደል ፡ የሸሸውን ፡ ማሳ ደድ ፡ መከተል ። **ብከ ፡ ንወግአሙ ፡ ለጸሮሙ ፡ ፀርነ ፡**

(መዝ ፡ ፺፫ ። ኢያ ፤ ፲ ። ፲፮ ፡ ፲ ። ዘዳ ፳ ፡ ፺፱ ። ዮሐ ፲፮ ፡ ፲፱) ። ዋግ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ወጋኢ** ፤ (**ኢት ፡ እያን ፡ ያት**) ፤ የሚወጋ ፤ የሚወግጥ ፡ ወጊ ፡ ተዋጊ ፡ (ዘፀ ፳፩ ፡ ፴፯ ። ፍ ፡ ን ፡ ፺፭) ።

**ሞግእ ፡ መውግእ ፤ ሙጋእ** ፤ (**ብ ፡ መዋግእ**) ፤ መውጊያ ፡ መውገሪያ ፤ ማፍረሻ ፡ ቀንድ ፡ ዘ ገር ፤ ሙገሪያ ፡ የሙገሪያ ፡ ግልገል ፤ ድጅኖ ፡ ደንጐራ ። **ቀወግአ ፡ በሐሊዱ ፡ ሙጋእ ። ይጐድዕዎ ፡ ውስተ ፡ ሞግእ ። ከመ ፡ ይትከሉ ፡ ሞግአ ፡ ኅጺን ፡ ላዕለ ፡ ቅጽር ። ተከለ ፡ መዋግአ ፡ ዘነፍጥ** ፡ (ሥር ፡ አኮ ። አዋል ። ዮሴፍ) ።


ሞግእ ፡

**ተወግአ** ፤ ተወጋ ፡ ተወገጠ ። (ትረት) ፤ ያወቀ ፡ ተጠንቀቀ ፤ የዘነጋ ፡ ተወጋ ። **ሰላም ፡ ለገበዋቲከ ፡ በቅትራት ፡ ኅጺን ፡ እለ ፡ ተወግኡ** ፡ (ደራሲ) ።

**ውጉእ** ፤ (**እን ፡ ኢት ፡ ግእት**) ፤ የተወጋ ፤ ውግ ፤ የተወገጠ ፡ ውግጥ ። **እለ ፡ ውጉኣን ፡ በኵናት ። ቅብዐ ፡ ዘይት ፡ ውጉእ** ፡ (ዘፀ ፳፱ ፡ ፵ ። ዘሌ ፳፬ ፡ ፪) ።

**ውግአት** ፤ መውጋት ፡ መወጋት ፡ አወጋግ ፤ ውጊ ፡ ውጊያ ፡ ውግታት ፤ በቁሙ ፡ ውጋት ። **ውግአቱ ፡ ሦክ** ፡ (ስንክ ፡ ጥር ፳፫) ።

**ተዋግአ** ፤ ተዋጋ ፡ ተተማተመ ። **ይትዋግኡ ፡ በኵናት** ፡ (አዋል) ።

**ወግአ** ፤—**ጋተ ፡ አገነፈ** ፤—**ወጊዕ ፡ ወግዐ** ።

**ወጊብ** ፤ **ቦት** ፤ (**ወገበ ፡ ይወግብ ፡ ይገብ** ፤ **ይውግብ ። ዐረ ፡ ወጀበ**) ፤ መወገብ ፤ ድንገት ፡ መምጣት ፡ መውደቅ ። ያደጋ ፡ አመጣጥ ፤ ደደቀን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ወገብ ፡ መያዝ ፤ እስከ ፡ ወገብ ፡ መድረስ ፡ የውሃ ።

**አውገበ** ፤ አደነገተ ፤ ሥራውን ፡ በድንገት ፡ ሠራ ፡ አደጋ ፡ ጣለ ። **አውገብዎሙ ፡ ወወረዱ ፡ ላዕሌሆሙ ። ያወግቦ ፡ ወይነፅኖ ። ዕለት ፡ እኪት ፡ አውገበተኒ ። ወታወግቦሙ ፡ ዕለት ፡ እኪት** ፡ (ትበጽሖሙ ፡ ግብተ) ። **እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ያውግቡ** ፡ (ኢያ ፲፭ ፡ ፳ ። ሉቃ ፳፱ ፡ ፴፱ ። ሱቱ ፡ ዕዝ ፲ ፡ ፴፱ ። ሚክ ፪ ፡ ፫ ። ቄር) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፤ አፍርሀ ፡ አደንገፀ ፡ ይሉታል ፤ ባለቅኔዎችም ፡ አኰረፈ ፡ ይሉታል ።

»**ግብት** ፤ ድንገት ፡ ግዳጅ ፤ አደጋ ፤ አስቀድሞ ፡ ሳይታሰብና ፡ ሳይታወቅ ፡ እንዲያው ፡ ደርሶ ፡ የሚኾን ፡ ነገር ፤ እጅግ ፡ ታናሽ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ደቂቃና ፡ እንደ ፡ ሴኮንድ ፡ እንደ ፡ ቅጽበት ፡ ያለ ። **እመሰ ፡ ግብት ፡ ውእቱ ። ኀጢአት ፡ ዘግብት** ፡ (ዘኍ ፴፭ ፡ ፳፪ ። ፈ ፡ መ ፡ ፪ ፡ ፲፩) ። ባዕድ ፡ ነግድ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ **ዐርከ ፡ ግብት ፡ አምላከ ፡ ግብት** ፡ ይላል ፤ ድንገት ፡ የተገኘ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ (ሚራ ፬ ፡ ፲ ። መዝ ፡ ፹) ።

»**ግብተ** ፤ ድንገት ፡ በድንገት ፤ ወዲያው ፡ ቶሎ ፡ በቅርብ ፤ ሳይቈይ ፡ ሳይዘገይ ። **ግብተ ፡ መጽአ ። ግብተ ፡ በረቀ ። ግብተ ፡ ሀለዉ ። ሐደሰ ፡ ግብተ** ፡ (ሉቃ ፪ ፡ ፲፫ ። ግብ ፱ ፡ ፫ ። ዮዲ ፱ ፡ ፫ ። ዕብ ፲ ፡ ፳) ።

»**ግብታዊ** ፤ ድንገተኛ ፤ የድንገት ፤ በድንገት ፡ የኾነ ፡ ያልታሰበ ። **ሞተት ፡ በሞት ፡ ግብታዊ** ፡ (አዋል) ።

**ወግብ** ፤ (**ዐማርኛ**) ፤ በቁሙ ፤ ሐቋ ፡ ገቦ ፡ ጐንድ ። (ትረት) ፤ በሰማይ ፡ ቢዞር ፡ ዘመዱ ፡ አንበጣ ፤ በምድር ፡ ወገቡን ፡ ይይዛል ፡ ፌንጣ ።

**ወጊግ** ፤ **ጎት** ፤ (**ወገ** ፤ **ወገገ ፡ ይወግግ ፡ ይገግ ፡ ይውግግ**) ፤ መውገግ ፤ ወገግ ፡ ማለት ፡ የንጋት ።

**ወግግ** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ ዐለቦት ። **ሳሙኤል ፡ ዘወገግ ፡ ደብረ ፡ ወገግ** ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ውጋጋን** ፤ (**ዐማርኛ**) ፤ በቁሙ ፤ ወገግታ ፡ የፀሓይ ፡ የእሳት ፡ ጸዳል ፤ ፈገግን ፤ ጎሕንና ፡ ነግህን ፡ እይ ።

**ወጊድ** ፤ **ዶት** ፤ (**ወገደ ፡ ይወግድ ፡ ይገድ**) ፤ መወገድ ፡ መራቅ ፡ መፋለስ ፡ መጕረፍ ፤ ላይ ፡ ላዩን ፡ ማለፍ ።

**አውገደ** ፤ አሶገደ ፤ መግድ ፡ አለ ፤ አራቀ ። ወግዳ ፡ ውጋዴ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ስም ፡ ይመስላል ።

**ሞገድ** ፤ (**ዳት** ፤ **መዋግድ** ፤ **ዳት ። ዐረ ፡ መውጅ**) ፤ በቁሙ ፡ ማዕበል ፡ የባሕር ፡ ጕርፍ ፡ የውሃ ፡ ተራራ ፡ ፈረሰኛ ፤ እንደ ፡ ገመገም ፡ እየኾነ ፡ ከማኸል ፡ ወደ ፡ ዳር ፤ ከዳር ፡ ወደ ፡ ማኸል ፡ የሚኼድ ፡ የሚነጕድ ፤ ነፋሳት ፡ የሚከቡትና ፡ የሚነዱት ፡ የሚያወጡትና ፡ የሚያወርዱት ። የእሳት ፡ ላንቃ ፡ ነበልባል ። **ሞገደ ፡ ባሕር ፡ እንተ ፡ ይዘብጣ ፡ ነፋስ ፡ ወይነውኃ ። ወይትሀወክ ፡ እሞገዳት ። እምአፉሁ ፡ መዋግደ ፡ እሳት ፡ ወፅአ ። መዋግዳት** ፡ (ያዕ ፩ ፡ ፮ ። ማቴ ፲፬ ፡ ፳፬ ። ሉቃ ፡ ዕዝ ፲፫ ፡ ፲፩ ። ቀሌ) ። በሞገድ ፡ ፈንታ ፡ ሞገት ፡ ይላል ፤ ሙገት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ዐረቦ ፡ በመውጅ ፡ ፈንታ ፡ መውጀት ፡ ይላልና ፤ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ፡ (እስ ቴር ፡ ፬ ። ሱቱ ፡ ዕዝ ፬ ፡ ፶) ።

—፤ ሞገድ ፡ ልክ ፡ ያለው ፡ የበጋ ፡ ሁከት ፡ ማዕበል ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ የክረምት ፡ ጐርፉ ፡ ወይብ ፡ የሚያፈርስ ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ የሚፈስ ፡ (መዝ ፡ ፺፩) ።

**ሞገዳዊ** ፤ ሞገደኛ ፡ ሞገዳም ፡ ባለሞገድ ። ሞጋች ፡ ተሟጋች ፡ ሸፋጭ ።

**ሞገደ ፡ (ይሞግድ)** ፤ በቁሙ ፡ አወከ ፡ ደረጠ ፡ በጠበጠ ። ማገደ ፡ ገዘገደ ፡ የዕንጨት ።

**አሞገደ** ፤ አስሞገደ ፤ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ አስነሣ ። እስ ፡ ያሞግዱ ፡ ወየሀውኩ ፡ (አፈ ፡ ተ፡፴፱) ።

**ተሞገደ** ፤ ታወከ ፡ ተማገደ ።

**ተሞገደ ፤ (ይትሞገድ ፤ አው ፡ ተሞዋ ገደ ፤ ተመዋገደ)** ፤ ወቅሐን ፡ ተመልከት ።

**ሙጋድ ፤ (ዕብ ፡ ሞቄድ ፤ ሞቅዳ)** ፤ ማገጃ ፡ የመሥዋዕት ፡ ዕንጨት ፡ ጥፍ ፡ ፍልጥ ፡ መልክም ፡ ሽታ ፡ ያለው ።

**ወጊዝ ፤ ዘት ፤ (ወገዘ ፡ ይወግዝ ፡ ይገዝ)** ፤ መውገዝ ፡ መገዘት ፡ መለየት ፡ መካድ ፡ መርገም ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወገዘ ፡ ፈንታ ፡ አውገዘ ፡ ይላል ። ወኪያሁኒ ፡ ያወግዝዎ ፡ እምነ ፡ ማኅበሩ ። አውገዝዎሙ ፡ እስከ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ። ብእሲ ፡ ዘአውገዘ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለየ ፡ (ዕገ፲ ፡ ፰) ። እስ ፡ ታወግዙ ፡ ግዘታተ ፡ ከመ ፡ ኢይፍትሑ ። ዘይፈቅድ ፡ ይጠመቅ ፡ ይምሀርዎ ፡ ያውግዝ ፡ ሰይጣነ ፡ ወይእመን ፡ በክርስቶስ ፡ ኣወግዘከ ፡ ሰይጣን ፡ ወኵሎ ፡ ምግባሪከ ። አውገዘ ፡ ለከይሲ ፡ ከደ ፡ ረገመ ፡ (ሔኖ፺፰ ፡ ፬ ። ዲድ ፡ ፴፱ ፡ ስንክ ፡ የካ፪) ።

**ወገዘ ፤ (ብ ፡ አውጋዝ)** ፤ በቁሙ ፡ ደደገ ፡ ጥኝ ፡ ታናሽ ፡ ወይፈን ፡ ጊደር ፤ በመብል ፡ ጊዜ ፡ ከበሬ ፡ የሚለይ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዐማርኛ) ።

**አውግዘ** ፤ አስገዘ ፡ አስገዘተ ፤ አስለየ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ አወገዘ ፡ ነው ።

**ተወግዘ** ፤ ተወገዘ ፡ ተገዘተ ፤ በግዝት ፡ ተለየ ። ካህን ፡ ዘተወግዘ ፡ (አብጥ ፡ ፲) ።

**ውጉዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ግዝት)** ፤ በቁሙ የተወገዘ ፡ የተለየ ፤ ርጉም ። ውጉዘ ፡ ሊይኩን ፡ ኢትክውን ፡ ውግዘተ ፡ (ገላ፩ ፡ ፰ ። ዘካ፲፬ ፡ ፲፩) ።

—፤ ሕርም ፡ የተባለ ፡ የተከለከለ ፡ ሕግ ፡ የነቀፈው ፡ ያጸየፈው ፡ ሥራ ፤ ማናቸውም ፡ ኹሉ ። ቀቲልሰ ፡ እምኍልቈ ፡ ዐበይት ፡ ኀጣውእ ፡ ክሉኣት ፡ ወውጉዛት ፡ በልብ ፡ ወበሕግ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፯) ።


**ውግዘት** ፤ መውገዝ ፡ መወገዝ ፡ አወጋገዝ ፤ በቁሙ ፡ ግዝት ፤ ውጉዝነት ። ዘክልእዎ ፡ ቍርባነ ፡ በእንተ ፡ ውግዘት ። ኢይፍታሕ ፡ እምኔሁ ፡ ግዘቶ ፡ (አብጥ ፡ ፱ ። ቀኖ ፡ ኒቅ፲) ።

»**ግዘት ፤ (ታት)** ፤ ግዝኢ ፡ ከማሁ ፡ መገዘት ፡ (ጥገ) መገዘት ፡ አገዛዘት ፤ በቁሙ ፡ ግዝት ፡ ርግማን ። ግዘት ፡ ዘነበበ ፡ ባቲ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘቡርልስ ። አንቀጸ ፡ ግዘት ። ንባበ ፡ ግዘት ፡ (ሃይ ፡ አበ ። ስንክ ፡ ታኅ፳) ።

**ወግዝ ፤ (ዛት)** ፤ ሕርም ፡ ልዩ ፡ ክልክል ፤ የግዜር ፡ ገንዘብ ። ዘዐለወ ፡ በወግዝ ፡ (ኢያ፯ ፡ ፩ ፡ ፳) ።

**ተዋግዘ** ፤ በቁሙ ፡ ተገዛዘተ ፡ ተማማለ ፡ ተለያየ ፡ ተካራከረ ፡ (ሔኖ፮ ፡ ፬) ። ከመ ፡ እትዋገዝ ፡ ለልብየ ፡ ወእሬስዮ ፡ መልአክ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ግዘተ ፡ እትዋገዝ ፡ ይላል ፡ (ቄነገ ፡ ፲፭ ፡ ፴፱) ።

**ወገል ፤ (ዐረ ፡ ሽንገል)** ፤ በቁሙ ፡ ከርፈስ ፡ ዕርፍን ፡ ከሞፈር ፡ ከድግር ፡ የሚያያይዝ ። ስዕሉን ፡ እዩ ።



ወገል ፡

**ወገን ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፡ መንጋ ፡ ዘመድ ። ወገን ፡ ጠባቂ ፡ ባለወገን ፡ እንዲሉ ።

**ወግዐ ፤—በቁሙ ፡ ወጋ ፤—ወጊእ ፡ ወግአ ።**

**ወግዐ ፤ (ገዐተ)** ፤ ጋተ ፡ አስጐነጨ ፡ አስጐረጐጨ ፤ በጥርኝ ። (አወጋ ፡ ተረከ) ። ወትፈቅዱ ፡ ሐሊበ ፡ ይውግዑክሙ ። ሐሊበ ፡ ወጋዕኩክሙ ፡ (ዕብ፭ ፡ ፲፪ ። ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፪) ።

**ተወግዐ** ፤ ተጋተ ፡ ገጨ ፡ ጕርጕጨ ፡ አደረገ ። መጠጡንና ፡ ወጐንም ፡ ያሳያል ። እስ ፡ ከልእዎሙ ፡ ኢይትወግዑ ፡ ሐሊበ ። እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይትወጋዕ ፡ ሐሊበ ፡ ሕፃን ፡ ውእቱ ፡ (ኢሳ፳፰ ፡ ፱ ። ዕብ፭ ፡ ፲፫) ።

**ወግዕ** ፤ በቁሙ ፤ ወግ ፡ ታሪክ ፡ አንቂክ ፡ ወሬ ፡ ከሽማግሌዎች ፡ አፍ ፡ የሚገኝ ። ዜና ፡ ወግዕ ፡ ዘመንግሥት ፡ ሺዋ ፡ ዘሰማዕናሁ ፡ እምእለ ፡ ይዛውዑ ፡ ዜና ፡ ወግዕ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ። ልማድ ፡ ደንብ ፡ አበል ፡ ለሹም ፡ ወይም ፡ ለሴላ ፡ የሚገባ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ወግዓዊ** ፤ ወገኛ ፡ ወጋም ፤ ባለወግ ።

**ወጊር ፤ ሮት ፡ (ወገረ ፡ ይዌግር ፡ ይውግር ፤ አው ፡ ይወግር ፡ ይገር)** ፤ መወርወር ፡ ማኅን ፡ መጣል ። ውርወራ ፡ የወል ፤ ጕኖች ፡ ወደ ፡ ላይ ፤ ጥሎሽ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወይም ፡ ፊት ፡ ለፊት ። ዘገር ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ዘይትወገር ፡ ያሰኛል ። ዘይወግር ፡ እብነ ፡ ላዕሌሁ ፡ ትወርድ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ። ንግእ ፡ እብነ ፡ ወገር ፡ ላዕለ ፡ አኀነ ፡ (ሚራ፳፯ ፡ ፳፭ ። ሄርማ) ። ገርዎ ፡ ውስተ ፡ ተከዚ ። ወገሩ ፡ አብትሮሙ ። ዘያስተሐይጻ ፡ ሲሪንግል ፡ ወይወግር ፡ ዐይኖ ፡ ከመ ፡ ያርኵሳ ፡ ጣለ ፡ (ዘፀ፩ ፡ ፳፪ ። ፯ ፡ ፲፪) ።

—፤ መውገር ፡ በደንጊያ ፡ መምታት ፡ መግመስ ፡ መፈንከት ፡ መስበር ፡ መቀጥቀጥ ፡ ደንጊያን ፡ መቈለል ፡ መከመር ። ወገረቶ ፡ በስባረ ፡ ማሕረጽ ። ወገሮሙ ፡ እግዚ ፡ በእብነ ፡ በረድ ። ሊይገራ ፡ በእብን ። ወነሥኡ ፡ እብነ ፡ ከመ ፡ ይውግርዎ ፡ (መሳ፱ ፡ ፶፫ ። ኢያ፲ ፡ ፲፩ ። ዮሐ፰ ፡ ፶፱ ። ፲ ፡ ፴፩) ።

—፤ ማጠን ፡ ማጤስ ፡ ማቃጠል ፡ የዕጣንን ፡ ቈቀር ፡ ከፍሕም ፡ ላይ ፡ መጣል ። መኰንን ፡ ኀሠሠ ፡ ከመ ፡ ይክሐዶ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወይውግር ፡ ዕጣነ ፡ ለጣዖታት ። ወእምዝ ፡ ይውግር ፡ ዕጣነ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፯ ። ቅዳ) ።

የወገረ ፡ ምስጢር ፡ በትግርኛ ፡ አለሌው ፡ ባዝራይቱን ፡ መታት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ወጋሪ ፡ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፡ ግርት) ፡** የሚወረውር ፡ የሚጥል ፡ ጣይ ። ወገርተ ፡ እብን ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ።

—፡ በቁሙ ፡ ዓሣ ፡ አጥማጅ ፡ መረቡን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ዓሣውን ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ የሚጥል ። ዓሣ ፡ ወጋሪ ፡ እንዲሉ ።

**ሞግራ ፡** የሬት ፡ ሽቱ ፡ ወይም ፡ ወገርት ። ሚዐሮን ፡ ተመልከት ።

**ወግር ፡ (ብ ፡ አውግር ፡ ራት ። ዕብ ፡ ያጋር ፡ ጋል ። ሱር ፡ ያግራ) ፡** የደንጊያ ፡ ክምር ፡ ቍልል ፡ እንደ ፡ ኩረብታ ፡ ያለ ። አሰዱ ፡ እብነ ፡ ወገብሩ ፡ ወግረ ። ወሰመያ ፡ ባባ ፡ ወግረ ፡ ስምዕ ፡ ወያዕቆብኒ ፡ ሰመያ ፡ ከማሁ ። ዛቲ ፡ ወግር ፡ ወዛቲ ፡ ሐውልት ፡ (ዘፍጥረት ፡ ፴፩ ፡ ፵፯ ፡ ፶፪) ።

—፡ በቁሙ ፡ ኩረብታ ፡ ቍሊልታ ፡ ተሬ ፡ ጉባ ፡ ጉባታ ፡ አዳጋ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ደፈር ፡ ሽንተረር ፡ ከተራራ ፡ የሚያንስ ። አቀውም ፡ ዲበ ፡ ርእሰ ፡ ወግር ፡ ዐርጉ ፡ ውስተ ፡ ርእሳ ፡ ለወግር ። ወኮነ ፡ ወግረ ፡ ዐቢየ ፡ ውእቱ ፡ ጕድፍ ። ወግረ ፡ ኃጥኣን ። አውግር ፡ ልዑላት ። ወባቲ ፡ አውግራትኒ ፡ ወአድባራት ፡ (ዘፀ፲፯ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ መጋ፲ ። ኢሳ፳፰ ፡ ፴፩ ። ፴ ፡ ፳፫ ። አፈ ፡ ተ፴፱) ።

**አውገረ ፡** አሶገረ ፡ አስመታ ፡ አስጣለ ።

**ተወግረ ፡** በቁሙ ፡ በደንጊያ ፡ ተመታ ፡ ተደበደበ ፡ (ዘፀ፲፱ ፡ ፲፫ ። ዕብ ፡ ፲፪) ። ለተወግሮቱ ፡ በእብን ። ወበሕግዝብ ፡ ሠርዐ ፡ ሙሴ ፡ ከመ ፡ ትትወገር ፡ በእብን ፡ (ኩፋ ፡ ፴፫ ። ዮሐ፰ ፡ ፭) ።

**ተዋገረ ፡** ተማታ ፡ ተወራወረ ፡ ደንጊያ ፡ ተጣጣለ ፡ (ግብ ፡ ፲፬ ፡ ፭) ።

**ውጉር ፡ (ራን ፡ ራት ፡ ግርት) ፡** የተወገረ ፡ የተደበደበ ፡ ደንጊያ ፡ የተጐራበት ፡ የተከመረበት ። ረከበሙ ፡ ለጣዖታት ፡ ውጉራነ ፡ ወስቡራነ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲፯) ።

**ውግረት ፡** መውገር ፡ መወገር ፡ አወጋገር ፡ ውግራት ፡ ውርወራ ፡ ደንጊያ ፡ አጣጣል ፡ አወራወር ፡ የደንጊያ ፡ ስልፍ ፡ ጦርነት ፡ እንዳንደርቢና ፡ እንደ ፡ በረድ ፡ ያለ ። ተኰነነ ፡ ምዕረ ፡ በውግረት ፡ ወምዕረ ፡ በንድፈተ ፡ አሕጻ ። ኮነ ፡ ጸብእ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ በንዋየ ፡ ሐቅል ፡ ወበውግረተ ፡ አእባን ፡ ወበሞፀፍ ። ቀተሎ ፡ በውግረተ ፡ እብን ፡ ወበኀጺን ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ ። ዮሴፍ ። ቀሌ ። ፍ ፡ ን ፡ ፺ ፡ ፫) ።

—፡ ማጠን ፡ መታጠን ፡ አስተጣጠን ። ኢተደመረ ፡ በውግረተ ፡ ዕጣን ፡ ለአማልክት ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፳፰) ።

**ሙጋር ፡** መውገሪያ ፡ መወገሪያ ፡ መጣያ ፡ መወርወሪያ ፡ ቦታ ። ተአተተ ፡ ሕቀ ፡ እምኔሆሙ ፡ መጠነ ፡ ሙጋረ ፡ እብን ፡ (ሉቃ፳፪ ፡ ፵፩ ። ስንክ ፡ ኀሐ፲፱) ።

**ሞገር ፡** ጥና ፡ የዕጣን ፡ መውገሪያ ። ዕጣን ፡ ሞገር ፡ እንዲሉ ፡ ቅኔው ፡ በዕጣን ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ ገባ ።

**ሞገርት ፡** ውርወራ ፡ ጥሎሽ ፡ እንገዛግዛንሽ ። ዘበሞገርተ ፡ እብን ፡ ወዕፀወ ፡ ገዳም ፡ (ጽንግ ፡ ፲፬ ፡ ፲፱) ።

**ወገሬ ፡** የማሽላ ፡ ስም ፡ የደፋት ፡ ማሽላ ፡ ራሱ ፡ ምንቸት ፡ የሚያካክል ። ፍችው ፡ ደኅኒ ፡ መልክሜ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ወገሬት) ፡ ወገር ፡ ዕደር ፡ እንዲል ፡ ደኅና ፡ ዕደር ፡ ሲል ፡ (ጕራጌና ፡ እስላም) ። ፪ኛም ፡ የወገሬ ፡ ስው ፡ ማለትን ፡ ያስማል ፡ ወገሬ ፡ በጕንደርና ፡ በስሜን ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው ። (ግዋም) ፡ ወገሬ ፡ እግዚእ ፡ ዘኢፈጠሬ ፡ ከቤት ፡ ቢገቡ ፡ ጢሱ ፡ ከደጅ ፡ ቢወጡ ፡ ነፋሱ ፡ እኽሉን ፡ ቢበሉት ፡ ፈሱ ።

**ወጊስ ፡ ሰት ፡ (ወግሰ ፡ ይወግስ ፡ ይግስ ። ትግ ፡ ሐገሸ ፡ ፈሥሐ) ፡** መወማሸት ፡ መቈጣት ። ወጌሻ ፡ ሐኪም ፡ መኾን ፡ መፈወስ ፡ ማዳን ፡ ማፀን ፡ መጠገን ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ መወደድ ፡ መክበር ። መሞቀ ፡ ማማር ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ፡ የመልክ ፡ የግብር ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወገሰ ፡ ፈንታ ፡ ሞገሰ ፡ ይላል ፡ ወገደንና ፡ ወቅሐን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ አምሳል ፡ ናቸው ። ለብፁዕ ፡ ቂርቆስ ፡ አልቦ ፡ ዘይሞግሶ ፡ በክብር ፡ የሚበልጠው ፡ (መዋሥ ። ድጓ) ።

**ሞገስ ፡** በቁሙ ፡ ሞጋሳ ፡ ውድ ፡ ውዴታ ፡ ባለሟልንት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ውዳሴ ፡ ብዕዓን ፡ ግርማ ፡ ውበት ፡ ደም ፡ ግባት ፡ ጣዕም ፡ ሥን ። ቦሙ ፡ ሞገስ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ። እንተ ፡ ተዐቢ ፡ ሞገሰ ፡ ይሁበነ ። ረከብኪ ፡ ሞገሰ ። ገጽከ ፡ ምሉእ ፡ ሞገሰ ። ሞገሳ ፡ ለብእሲት ፡ ያስተፈሥሖ ፡ ለምታ ፡ (ግብ፪ ፡ ፵፯ ። ያዕ፬ ፡ ፮ ። ሉቃ፩ ፡ ፴ ። አስቴ፲ ፡ ፪ ። ሢራ፳፮ ፡ ፲፫) ።

**አሞገሰ ፡** ወደደ ፡ አከበረ ፡ ባለሟል ፡ አደረገ ፡ አወደሰ ፡ አመሰገነ ፡ በቅኔ ፡ በማጥም ። ኣሤንዩ ፡ ወኣሞግሱ ፡ (ዘካ፬ ፡ ፯) ።

**መሞግስ ፡ (ስት ፡ ሳን ፡ ሳት) ፡** የሚወድ ፡ የሚያከብር ፡ ወይ ፡ የሚያሶድድ ፡ ባለሟል ፡ የሚያደርግ ፡ የሚያስደርግ ። መሞግስት ፡ (አርጋ) ።

**ተሞገሰ ፡** ከበረ ፡ ተመሰገነ ፡ በዐ፡ስ ፡ ተባለ ፡ ባለሟል ፡ ኾነ ፡ ልጅነት ፡ አገኘ ። አባ ፡ ዮሐኒ ፡ ፈድፋደ ፡ ኀየሰ ፡ ተሞገሰ ። ዮሐንስ ፡ ተፈሥሐ ፡ ወተሞገሰ ። እመ ፡ በመንፈሱ ፡ ለኢየሱስ ፡ ንትሞገስ ፡ ወንጼውዖ ፡ ለእግዚ ፡ አቡነ ፡ (መዋሥ ። ቄር ፡ ስምዓት) ።

**ሞገት ፡—ሞገድ ፡—ወጊድ ፡ ወገደ ።**

**ወድአ ፡ አት ፡ (ወድአ ፡ ይዌድእ ፡ ይወድእ ። ዐረ ፡ ወደዐ ፡ አደረገ ፡ ላከ) ፡** መጨረስ ፡ መፍጀት ፡ መፈጸም ፡ መከተት ፡ የግብር ፡ የነገር ። ትዌድእዎ ፡ ወኢታተርፉ ፡ እምኔሁ ። እሳት ፡ ዘይዌድእ ። ሕያው ፡ ነፍስከ ፡ ከመ ፡ ኢትወድእ ፡ አመትከ ፡ ዘሀለወ ፡ ምስሌሃ ። ነጸረ ፡ ንጉሥ ፡ በዘወድኡ ፡ ማእደ ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ዘዳ፬ ፡ ፫ ። ዮዲ፲፪ ፡ ፬ ። ዳን፲፫ ፡ ፲፰) ።

**ወዳኢ ፡ መወድእ** ፡ የሚጨርስ ፡ ጨራሽ ፡ ፈጻሚ ፡ ከታች ።

**ወድአ ፡ (ንኡስ ፡ አገባብ)** ፡ ቀድሞ ፡ አስቀድሞ ፡ አካቶ ፡ ፈጽሞ ፡ ጭራሽ ፡ በጭራሽ ። **እሉ ፡ ወድኡ ፡ ሞቱ ። ወድአ ፡ ተሠይመ ። ወዳእነ ፡ ግእዝና ሆመ ። ወዳእነ ፡ ሞትነ ። ወዳእነ ፡ ቀተርነ ፡ ሞኣተ ፡** (መክ ፱ ፡ ፱ ። ማቴ ፲ ፡ ፲ ። ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፱ ። ፯ ፡ ፱ ። ሉቃ ፲፩ ፡ ፯) ።

**ተወድአ** ፡ ተጨረሰ ፡ ተፈጸመ ፡ ተፈጀ ፡ ዐለቀ ። **ይትዌዳእ ፡ ዦሉ ፡ እኩይ ። መዛግብተ ፡ እክል ፡ ወሥርናይ ፡ ይትዌዳእ ፡ በዓፄ ፡ ወበነቀዝ ። ተወድአ ፡ ወርቅነ ። ፍሥሓ ፡ ዘኢይትዌዳእ ፡** (ሔኖ ። መቃ ። ዘፍ ፵፯ ፡ ፲፰ ። ኪዳ) ።

**ውዳኤ** ፡ መጨረስ ፡ (ጥጨ) መጨረስ ፡ አጨራረስ ፡ ጭረሳ ። ጭራሽ ፡ ከታች ፡ ፍጻሜ ፡ (ፈልክ) ።

**ወደብ ፡ (ዐማርኛ)** ፡ በቁሙ ፡ የባሕር ፡ ጠረፍ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ የመርከብ ፡ መቆሚያ ።

**ወዲድ ፡ ዶት ፡ (ወደ ፡ ወደደ ፡ ይወድድ ፡ ይደድ)** ፡ መውደድ ፡ ማፍቀር ። ማግባት ፡ መጨመር ፡ አንዱን ፡ ባንዱ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በመካከል ፡ እንደ ፡ ሳጋ ፡ እንደ ፡ ሽብልቅ ፡ እንደ ፡ ስሯጽና ፡ እንደ ፡ ዚቅ ። ወደየን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**አውደደ** ፡ አዖደደ ። አዋደደ ፡ አስማማ ፡ ሰካ ፡ አሳካ ፡ ቸንከረ ፡ አንድ ፡ አደረገ ፡ የግብር ፡ የነገር ። **አግበረ ፡ አርባዕተ ፡ ምእተ ፡ ጸናጽለ ፡ ወአውደዶን ፡ ዲበ ፡ መሣግር ። አውደድዎ ፡ ውስተ ፡ ወርቅ ። አውድድ ፡ ውስተ ፡ ሥጋየ ፡ ፈሪሆተከ ፡** (፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፲፫ ። ዘፀ፴፮ ፡ ፲፫ ። መዝ፻፲፰ ፡ ፻፳) ።

—፡ ሽፈነ ፡ ለበጠ ፡ በልባጥ ፡ አስጌጠ ፡ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ማዋደድ ፡ ነው ። **ወሰቤት ፡ ዐቢይ ፡ አውደዶ ፡ ወእጽ ንያ ፡ በዕፀ ፡ ዘግባት ፡** (፪ዜና ፡ ፫ ፡ ፭) ። በአውደደ ፡ ፈንታ ፡ አስተዋደደ ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ከድራጊነት ፡ በቀር ፡ ኢደራራጊነት ፡ የለውም ፡ (ዘኍ ፱ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ። ምሳ፰ ፡ ፴) ። **ዘእንበለ ፡ ያስተዋድድ ፡ እግዚ ፡ ምቋመ ፡ ኢድባር ፡ ወአውግር ። አሠነየ ፡ ሰነ ፡ ወአስተፍሥሐ ፡ መንግሥተነ ፡ ወአስተዋደደ ፡ አህጉሪነ ፡ ወሥልጣነነ ፡ ላዕለ ፡ ብዙኃን ፡ አሕዛብ ። አስተዋድዶ ፡ መዝሙረ ፡ ማሕሌት ። አስተዋደደ ፡ መዝሙራተ ። ወአጻብዐየ ፡ ያስተዋድዳ ፡ መዝሙረ ፡** (መቃ ፡ ፯፳፫ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ የካ፳ ። ቀሌ ። መዝ ፡ ፻፵፬) ።

**ተወደ** ፡ ተወደደ ፡ ተፈቀረ ። ተሰካ ፡ ተጨመረ ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፲፫) ።

**ተዋደደ** ፡ በቁሙ ፡ ተገባ ፡ ተመቸ ፡ ተስማማ ፡ ተሳካ ፡ ተዛመደ ፡ ጸና ፡ ተደላደለ ። (ምሳ፲፯ ፡ ፯ ። ፲፱ ፡ ፲፱) ። **አሳ ፡ ተዋደደ ፡ ወተደለወ ፡ ዝንቱ ፡ ስም ፡ ለዘበሥጋ ፡ ተወልደ ። ዘቦቱ ፡ የትድር ፡ ዦሉ ፡ ሥጋ ፡ ወይትዋደድ ፡ በአሥራው ፡ ወመሌሊት ። ሠነየ ፡ ንብረትሙ ፡ ወተዋደደ ፡ ሰበ ፡ ተዋደደ ፡ ትእዛዙ ። ተዋደደ ፡ ነገርነ ፡ ወረትዐ ፡ መንግሥትነ ፡** (ቄር ፡ ጸሎ ። ቆላ፪ ፡ ፲፱ ። ዮሴፍ) ።

**ተዋድዶ** ፡ መዋደድ ፡ መስማማት ፡ በፍቅር ፡ በችንካር ፡ አንድ ፡ መኾን ።

**ውዱድ ፡ (ዳን ፡ ዳት ፡ ድድ)** ፡ የተወደደ ፡ ውድ ፡ የተዋደደ ፡ የተስማማ ፡ የማይወልቅ ፡ የማይነቃነቅ ። **ውስተ ፡ ውጽቦ ፡ ወርቅ ፡ ዕንቊ ፡ ሰርድዮን ፡ ውዱድ ። ኢድባር ፡ እሉ ፡ ውዱዳን ። እሉ ፡ ውዱዳት ፡ እማንቱ ፡** (ምሳ፳፭ ፡ ፲፪ ። ዘፍ፵፱ ፡ ፳፯ ። ደራሲ) ።

**ውዱድ** ፡ የሰማይ ፡ ስምና ፡ ቅጽል ፡ መጨረሻ ፡ ሰማይ ፡ (ሕዝ፩ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬) ። **በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ ወመልዕልተ ፡ ሰማይ ፡ ውዱድ ፡ አስተዳለወ ፡ መንበረ ፡** (ደራሲ) ።

**ሙዳድ ፡ ሞዳድ ፡ (ብ ፡ መዋድድ)** ፡ ማዋደጃ ፡ ማስማሚያ ፡ ዛቢያ ፡ ችንካር ፡ ቍልፍ ፡ የመሰሰው ፡ ኹሉ ። **ወመዋድዲሆን ፡ ዘብሩር ፡** (ዘፀ፴፯ ፡ ፲፯ ። ፴፰ ፡ ፲፯) ። የሰው ፡ ስም ፡ ሙሴ ፡ ከመረጣቸው ፡ ከሰባ ፡ ኹለቱ ፡ አንዱ ፡ (ዘኍ፲፩ ፡ ፳፯) ።

»**ድድ ፡ (ዳት)** ፡ በቁሙ ፡ ማውድ ፡ መሠረት ፡ ምዕማድ ፡ ስክተት ። **ድደ ፡ መሠረት ። ዐምዳ ፡ ወድዳ ፡ ለጽድቅ ። ይጸውር ፡ ድደ ፡ ወይነብር ፡ ጠፈረ ፡** (ቆላ፩ ፡ ፳፫ ። ፩ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ። ቅዳ) ።

—፡ ድምድማት ፡ መደምደሚያ ፡ የሕንጻ ፡ ራስ ፡ የባጥ ፡ የመዋቅር ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ መጋጠሚያ ። **ድደ ፡ ንጽሕ ፡ ወመሠረተ ፡ ቅድስና ። መስቀል ፡ ዐምዳ ፡ ወድዳ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ። አነዳሀ ፡ ዘሐቁ ፡ ወሌለዩ ፡ እምነ ፡ ድዱ ፡** (አርጋ ፡ ፫ ። ድጓ ። ስንክ ፡ ግንቦ) ።

**ወድየ ፡ ዮት ፡ (ወደየ ፡ ይወዲ ፡ ይደይ ። ወደደ)** ፡ መጨመር ፡ መደል ፡ ማግባት ፡ ማኖር ፡ ማድረግ ፡ መወርወር ፡ መጣል ። **ወደዩ ፡ ሐሞተ ፡ ውስተ ፡ መብልዕየ ። ይወዲ ፡ እዴሁ ፡ ውስተ ፡ ግበ ፡ አርዌ ፡ ምድር ። ደይ ፡ ቃሎ ፡ ውስተ ፡ ልብከ ። እወዲ ፡ እዴየ ፡ ዲበ ፡ አፉየ ። ኢትደዩ ፡ ባሕርየክሙ ፡ ቅድመ ፡ አሕርው ። ወደይዎ ፡ ውስተ ፡ ግበ ፡ አናብስት ። ወደየት ፡ አዕይንቲሃ ፡ ላዕለ ፡ ዮሴፍ ። ዘወደየ ፡ እሳተ ፡ ውስተ ፡ አህጉር ፡** (መዝ ፡ ፷፰ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፰ ። ኢዮ፳፱ ፡ ፳፪ ። ፴፱ ፡ ፴፬ ። ማቴ፯ ፡ ፮ ። ዳን፲፫ ፡ ፴፩ ። ዘፍ፴፱ ፡ ፯ ። ፋ ፡ ን ፡ ፶ ፡ ፳) ።

**ወዳዬ ፡ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፡ ደይት)** ፡ ጨማሪ ፡ ነጋሪ ፡ ሠሪ ፡ ከፋ ፡ አድራጊ ። **ወዳዬ ፡ እከይ ፡ ወጽልአ ፡ ማእከለ ፡ ሰብእ ፡** (ሲኖዶ) ።

**ሙዳይ ፡ (ያት)** ፡ በቁሙ ፡ ማኖሪያ ፡ መጨመሪያ ፡ መክተቻ ፡ ዕቃ ። **ዕፍረት ፡ ዘተሰውጠ ፡ እሙዳይ ፡ ውስተ ፡ ሙዳይ ፡** (ቀሌ) ። ለንዋያት ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ፡ ሞዳያት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ሙዳየ ፡ በለስ** ፡ የበለስ ፡ መልቀሚያ ፡ ታናሽ ፡ እንቅብ ፡ ቅርጫት ፡ (ተረ ፡ ባሮ) ።

**ሙዳየ ፡ ዘቢብ** ፤ አገልግል ፡ ቅንብቻ ፡ ቢት ፡ ኪስ ፡ ከረጢት ፡ (፩ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፲፰) ።

**ሙዳየ ፡ ማይ** ፤ የውሃ ፡ ዕቃ ፡ እንስራ ፡ ፊቀን ፡ በርሚል ፡ ጋን ፡ ቀርበታ ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፭) ።

**ሙዳየ ፡ ምጽዋት** ፤ የገንዘብ ፡ ሣጥን ፡ ምእመናን ፡ አምኃቸውን ፡ የሚያገቡበት ፡ እፈ ፡ ጠባብ ፡ ሆደ ፡ ሰፊ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያስገባ ፡ እጅ ፡ የማያስገባ ፡ ገንዘቡ ፡ ሲመላ ፡ ተከፍቶ ፡ እንደ ፡ ንፍሮ ፡ የሚዘረገፍ ፡ (፪ዜና ፡ ፳፬ ፡ ፲፩ ። ማር፲፪ ፡ ፵፩) ።

**ሙዳየ ፡ ዕጣን** ፤ በቁሙ ፡ ታኖሽ ፡ ስፌት ፡ ወይም ፡ ቢት ፡ የዕጣን ፡ ማቅረቢያ ፡ (ቅዳ) ።




ሙዳየ ፡ ዕጣን ፡

**ሙዳየ ፡ ዕፍረት** ፤ የሽቱ ፡ ዕቃ ፡ ስፌት ፡ ና ርድ ፤ ቢልቃጥ ።

**ሙዳየ ፡ ዔረግ** ፤ የበጋ ፡ እንቅብ ፤ የመከር ፡ ቅርጫት ፡ ፍሬ ፡ የተመላ ፡ (ዓሞ፰ ፡ ፩) ።

**ሙዳየ ፡ ቀለም** ፤ የቀለም ፡ ቀንድ ፡ ወይም ፡ ቢልቃጥ ፡ (ሕዝ፱ ፡ ፪) ።



ሙዳየ ፡ ቀለም ፡

**ሙዳየ ፡ ቁርጠሉን** ፤ የወይን ፡ አሽት ፡ ቅርጫት ፤ ዘለላውን ፡ የሚሸከሙበት ፡ (ዘዳ፳፮ ፡ ፪) ።

**ተወድየ** ፤ ተጨመረ ፡ ገባ ፤ ተጣለ ፡ ተጫነ ። ይነሥእ ፡ እምዘይትወደይ ፡ ውስቴቱ ። ተወድየ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ። ገሪፍ ፡ እንተ ፡ ተወድየት ፡ ውስተ ፡ ባሕር ። ኢተወድየ ፡ ላዕሌሃ ፡ አርዑት ፡ (ዮሐ፲፪፡ ፮ ። ዕር ፡ ኢሳ፪ ፡ ፲፫ ። ማቴ፲፫ ፡ ፵፯ ። ዘኍ፲፱ ፡ ፪) ።

**ውዱይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ዲት) ፤ የተጨመረ፡ ጭምር ፤ ቅልቅል ።

**ውዳይ ፡ (ትግሬ)** ፤ ግብር ፡ ሥራ ። ውዳይ ፡ ሐዋርያት ፡ (ግብ ፡ ፩) ።

**ውድየት** ፤ መጨመር ፡ (ጥሬ) መጨመር ፤ አጨማመር ፡ ጭመራ ፡ ጭምርነት ። ከመ ፡ ውድየተ ፡ ወይን ፡ ሐዲስ ፡ በሐዲስ ፡ ዝቅ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲፯) ።

**ውዴት** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ነገር ፡ መሥራት ፡ ማላበቅ ፡ ያንዱን ፡ ነውር ፡ ለሌላው ፡ መንገር ፤ በሆሮው ፡ ማግባት ፡ በልቡ ፡ መስንቀር ። ስብቅ ፡ ክስ ፡ ሐሜት ። ውዴት ፡ እኪት ። ውዴት ፡ ዘሐሰት ። ኢይስማዕ ፡ ውዴተ ፡ ሐሰት ፡ ላዕለ ፡ ካልኡ ። መጽሐፈ ፡ ውዴት ። በዓለ ፡ ውዴት ። (ዘፍ፴፯ ፡ ፪ ። ዘፀ፳፫ ፡ ፩ ። ዲድ ፡ ፬ ። ኑሐ ፱ ፡ ፳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**ተዋደየ** ፤ ነገር ፡ ተማራ ፤ ተማማ ፡ ተካሰሰ ፤ ተጣላ ።

**አስተዋደየ** ፤ አሳበቀ ፡ ነገር ፡ ሠራ ፤ ከሰሰ ፡ አካሰሰ ፡ አወናጀለ ፤ አሳጣ ። ሐሰተ ፡ አስተዋደዩ ። ኢትደጉ ፡ አስተዋድዮቶሙ ። ዮጊ ፡ በጽልእ ፡ አስተዋደይዎ ። አስተዋደዩ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ። አስተዋደደ ፡ ርእስየ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ፡ (ዳን፮ ፡ ፳፫ ። ፪ ፡ ፳፬ ። ሚራ፲፱ ፡ ፲፭ ። ጦቢ፩ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፴፩) ።

**መስተዋድይ** ፤ አሳባቂ ፡ ነገረ ፡ ሠሪ ፤ ከሳሽ ፡ አሳጭ ፤ ጠላት ፡ ባለጋራ ፤ ወድቀ ፡ መስተዋድይ ፡ ዘአስተዋደዮሙ ፡ ለአኀዊነ ። ዲድቅ ፡ መስተዋድየ ፡ ርእሱ ። አዘዝክዎሙ ፡ ለመስተዋድያንሂ ፡ ይምጽኡ ፡ ኀቤከ ፡ (ራእ፲፪ ፡ ፩ ። ምሳ፲፰ ፡ ፲፯ ። ግብ፳፫ ፡ ፫) ።

**ወደፈ ፤ (ወፀፈ)** ፤ ጣለ ፡ ወረወረ ፡ አሽቀንጠረ ፤ የማይረባን ፡ ነገር ።

**ወዳፈት ፤ (ብ ፡ ወዳፋት)** ፤ ዕላቂ ፡ ውዳቂ ፡ ጨርቅ ፡ ጭረንፎ ፡ ቅርንጥስ ። ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ ያልተከለሰ ፡ ማቅ ፡ ዳውግ ፡ ይሉታል ። ወይጠበልልዎ ፡ በወዴፈት ። ዘእንበለ ፡ ወዴፈት ፡ ወአነዳ ፡ ላሕም ፡ (ኤር፴፰ ፡ ፲፱ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ወዲቅ ፤ ቆት ፤ (ወድቀ ፡ ይወድቅ ፡ ይደቅ ። ዐረ ፡ ወደቀ)** ፤ መውደቅ ፡ (ጥጣ) መጣል ፤ ድንገት ፡ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ መውረድ ፡ እንደ ፡ ዝናም ፤ ወይም ፡ ከቁም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መደፋት ፤ ፍግም ፡ ማለት ። ወደቀ ፡ እመካናት ፡ ልዑላት ። ወድቀ ፡ እምሰማይ ። ነዳይ ፡ ለእመ ፡ ወድቀ ፡ ይክይድዎ ፡ ቢጹ ። ወድቀ ፡ በገጾሙ ፡ (ፊልክ ፡ ፺፰፪ ። ኢሳ፲፬ ፡ ፲፪ ። ሚራ፲፫ ፡ ፳፫ ። ማቴ፲፯ ፡ ፮) ።

—፤ መግባት ፤ መያዝ ። ይወድቀ ፡ ውስተ ፡ ግብ ። ከመ ፡ ኢትደቅ ፡ ውስተ ፡ መሥገርት ። እመ ፡ በዙሉ ፡ ወደቀ ፡ ኢትደቅ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ጸላኢትከ ፡ (ማቴ፲፭ ፡ ፲፬ ። ሚራ፱ ፡ ፫ ። ፳፭ ፡ ፲፱) ።

—፤ መፍረስ ፡ መናድ ፤ ድል ፡ መኾን ፡ በጦርነት ፡ መሞት ። ጥቅም ፡ ወአረፍት ፡ ዘወድቀ ። ወወድቀ ፡ እምደቂቀ ፡ ብንያም ፡ እልፍ ፡ ወሰማንያ ፡ ምእት ። ሣልስትኪ ፡ ይወድቁ ፡ በኲናት ፡ (ኩፋ ፡ ፺፯ ። መሳ፳ ፡ ፺፱ ። ሕዝ፭ ፡ ፲፪) ።

—፤ መተኛት ፡ መጋደም ፤ መጣመር ፡ ወይም ፡ መከመር ፤ የዝሙት ። እመ ፡ ብ ፤ ዘወድቀ ፡ ዐርከ ፡ ምስለ ፡ ዐርክቱ ። ዘይወድቅ ፡ ምስለ ፡ ብእሲት ። ብእሲ ፡ ዘቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ወወድቀ ፡ ላዕለ ፡ ብእሲ ፡ ተባዕት ። ዘወድቀ ፡ በእንስሳ ፡ (ቁድር ። ሲኖ) ።

—፤ መስገድ ፡ መንበርከክ ፤ በግንባር ፡ መተከል ፤ ምድርን ፡ በአፍ ፡ መሳም ። ወድቀ ፡ አብራም ፡ በገጹ ። ወ

ድቁ ፡ ወሰገዱ ፡ ሎቱ ፡፡ ወድቀ ፡ ወአስተብቍዖ ፡ (ዘፍ ፳፰ ። ፱ ። ማቴ፲፪ ፡ ፳፮ ። ፳፰ ፡ ፳፯) ።

—፤ ማዘን ፡ መፍራት ፡ ማቀርቀር ፡ ፊንገትን ፡ መድፋት ። ለምንት ፡ ይወድቅ ፡ ገጽከ ፡፡ ኢይደቅ ፡ ልቡ ፡ ለእግዚእየ ፡ (ዘፍ፬ ፡ ፮ ። ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፴፪) ።

—፤ መሻር ፡ መዋረድ ፡ ከሹመት ፡ ከክብር ፡ መውጣት ፡ መለየት ። ይደቅ ፡ እምሢመቱ ፡፡ ይደቅ ፡ እማዕርጊሁ ፡፡ ወድቀት ፡ እምክብራ ፡፡ ወደቅሙ ፡ እምጸጋሁ ፡ (አብጥ ፡ ፳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፮ ፡ ፭ ። ቀሌ ። ገላ፭ ፡ ፬) ። በ ወድቀ ፡ ፈንታ ፡ ተወድቀ ፡ ተዋደቀ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ቈጽለ ፡ ሞጋት ፡ ኢይትወደቅ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃድየ ፡፡ ሶበ ፡ ቀሠፍዎ ፡ ሥጋሁ ፡ ተበጽለ ፡ እስከ ፡ ተዋደቀ ፡ በበ ፡ ክፍል ፡ ክፍለ ፡ (ቀሌ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፳፭) ።

**ውዱቅ** ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ድቅት) ፤ የወደቀ ፡ የፈረሰ ፡ ውዳቂ ፡ ውድቃን ፡ ወዳቃ ፡ ዘቅዘቃ ፡ ውድቅ ። ናሁ ፡ ሆሎፎርኒስ ፡ ውዱቅ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ በድኑ ፡፡ ረከብዎ ፡ ውዱቀ ፡ ወምዉተ ፡፡ ያነሥኦሙ ፡ ለውዱቃን ፡፡ አረፍት ፡ ውድቅት ፡፡ ውዱቅ ፡ እማዕርግ ፡ የተሻረ ፡ ሽር ፡ (ዮዲ፲፬ ፡ ፲፰ ። ተረ ፡ ባሮ ። ሚራ፻፵፬ ፡ ፲፬ ። ቀሌ) ።

**ድቀት** ፤ (ታት) ፤ መውደቅ ፡ መሰናከል ፡ አወዳደቅ ፡ ውድቂያ ፡ መከራ ፡ ሞት ፡ ኀጢአት ። እለ ፡ ይትፌሥሑ ፡ በድቀቱ ፡ ለጻድቅ ፡፡ ድቀት ፡ ትጸንሖ ፡፡ ይከውኑ ፡ ለድቀት ፡ ኅሩር ፡፡ ታንሥኦ ፡ እምነ ፡ ድቀቱ ፡ ከመ ፡ ኢይማስን ፡፡ እስመ ፡ መተረ ፡ ግብራት ፡ ድቀታት ፡ እለ ፡ ያርሕቅዎ ፡ እምእግዚ ፡ (ሚራ፳፮ ፡ ፳፱ ። ኢዮ፲፰ ፡ ፳፫ ። ጥበ፲፬ ፡ ፲፬ ። ዲድ ፡ ፮ ። ፊልክ ፡ ፭) ። በድቀት ፡ ፈንታ ፡ ውድቀት ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። በእንተ ፡ ውድቀቱ ፡ ለሳዶቅ ፡ ካህን ፡ (ክብ ፡ ነገ) ። ፪ኛም ፡ በፃእፃእ ፡ ፈንታ ፡ ድቀት ፡ ይላል ። ለእመ ፡ ድቀት ፡ ይወርድ ፡ አባሁ ፡ (ፊልክ) ።

**ሙዳቅ** ፤ (ቃት) ፤ መውደቂያ ፡ መዘቅዘቂያ ፡ ማረፊያ ፡ ቦታ ፡ (ሔኖ፳፫ ፡ ፲፫ ። ፶ ፡ ፮) ።

**አውደቀ** ፤ ጣለ ፡ አወደቀ ፡ አዋረደ ፡ አሻረ ። አሳዘነ ፡ መታ ፡ ገደለ ። አውደቀት ፡ ቢሮሃ ፡ እምነ ፡ ምስካቡ ፡፡ ወአውደቆ ፡ ውስተ ፡ ማዕምቅ ፡፡ ለብዙኃን ፡ አውደቀሙ ፡ ትዕቢተ ፡ ልቦሙ ፡፡ በእንተ ፡ ምክንያት ፡ እንተ ፡ ታወድቆ ፡ ለቀሲስ ፡ እማዕርጊሁ ፡፡ ኢታውድቁ ፡ ልበክሙ ፡፡ ለምንት ፡ አውደቀነ ፡፡ አውደቅዎ ፡ በሰይፍ ፡ (ዮዲ፲፫ ፡ ፱ ። ሕዝ፳ ፡ ፪ ። ሚራ፫ ፡ ፳፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፯ ፡ ፲ ። ነሐ፳ ፡ ፲ ። ኤር፲፱ ፡ ፲፱ ። ፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፳፩) ። ይደቀውናና ፡ ይነቀግ ፡ እንጂ ፡ የወድቀ ፡ አማኞር ፡ ናቸው ።

**ወዳር** ፤ (ወደረ ፡ ይወድር ፡ ይደር) ፤ መወደር ፡ መወዳደር ፡ (ዐማርኛ) ።

**ወድሶ** ፡ **ሶት** ፤ (ወደሰ ፡ ይዌድስ ፡ ይወድስ ። ዕብ ፡ ሆዳህ) ፤ ማወደስ ፡ ማሞገስ ፡ ማመስገን ፡ በምስጋና ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ። ጥበብ ፡ ትዌድስ ፡ ርእሳ ፡፡ ብዙኃን ፡ ይዌድስዎ ፡ እንበይነ ፡ ጥበቢሁ ፡፡ ንወድሶሙ ፡ ለዕደው ፡ ክቡራን ፡፡ ይወድስከ ፡ አፈ ፡ ነኪር ፡ (ሚራ፳፬ ፡ ፩ ። ፴፱ ፡ ፱ ። ፵፬ ፡ ፩ ። ምሳ፳፯ ፡ ፪) ።

**ወዳሲ** ፤ **መወድስ** ፤ የሚያወድስ ፡ አወዳሽ ፡ አመስጋኝ ፡ ገጣሚ ፡ ባለቅኔ ።

**መወድስ** ፤ በቁሙ ፡ ማወደሻ ፡ ድርሰት ፡ መዝሙር ፡ ቅኔ ፡ ግጥም ። ድርሰትየ ፡ ዘውእቱ ፡ መወድስ ፡፡ ወመወድሱ ፡ ዕዝል ፡ (አዋል ። ማኅዘ) ።

**አወደሰ** ፤ አስወደሰ ፡ አስመሰገነ ፡ ብፁዕ ፡ አሰኘ ።

**ተወደሰ** ፤ በቁሙ ፡ ተሞገሰ ፡ ተመሰገነ ፡ አበ ፡ አበ ፡ ተባለ ። አብደሩ ፡ በኀበ ፡ በብእ ፡ ተወድሶ ፡ ወአከ ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡፡ እስመ ፡ ይትዌደስ ፡ ኃጥእ ፡ በፍትወተ ፡ ነፍሱ ፡ (ዲድ ፡ ፳፰ ። መዝ ፡ ፱) ።

**ውዱስ** ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ድስት) ፤ የተወደሰ ፡ የተመሰገነ ፡ ምስጉን ። ነበር ፡ ምስለ ፡ ኄራን ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ውዱሰ ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡፡ ኮነ ፡ ነሃቤ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ፡ ወውዱስ ፡ ውእቱ ፡ በግብረ ፡ እደዊሁ ፡፡ ወዛ ፡ እምግባሩ ፡ ውድስት ፡ ዘዘክርናሃ ፡፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ መሥዋዕት ፡ ውድስት ፡ (ፈላስ ፡ ገ፹፰ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ። ዮሴፍ ። አፈ ፡ ተ፲፩) ።

**ውዳሴ** ፤ (ስያት) ፤ በቁሙ ፡ ማወደስ ፡ መወደስ ፡ አወዳደስ ፡ ውደሳ ፡ ምስጋና ። ዘሎ ፡ ዘነገርነ ፡ ዝ ፡ ውዳሴ ፡ ይውኅድ ፡ እምክብርክን ፡፡ ዝክረ ፡ ጻድቃን ፡ ምስለ ፡ ውዳሴ ፡፡ ፍቅረ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ውዳሰያት ፡ (ቄር ። ምሳ፲ ፡ ፯ ። አፈ ፡ ተ፳፯) ።

**ውዳሴ ፡ አምላክ** ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ከብዙ ፡ ድርሳናት ፡ የተሰቀመ ፡ የሲቃውንት ፡ ቃል ፡ ባለ፯ ፡ ክፍል ፡ ከሰኞ ፡ እስከ ፡ እሑድ ፡ የሚነበብ ።

**ውዳሴ ፡ ማርያም** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ኤፍሬም ፡ ስለ ፡ ክብረ ፡ ድንግል ፡ የደረሰው ፡ የ፯ ፡ ቀን ፡ ድርሰት ፡ በኋቱ ፡ ዕለታት ፡ የሚደገምና ፡ የሚዜም ፡ የዜማ ፡ ትምርት ፡ መገመሪያ ።

**ተውዳስ** ፤ (ሳት) ፤ ውዳሴ ፡ ምስጋና ፡ የሚገባ ፡ የማይገባ ።

**ምውዳስ** ፤ ማወደሻ ፡ መወደሻ ፡ ቦታ ፡ መሣሪያ ፡ ጊዜ ፡ ምክንያት ፡ (አዋል) ።

**ውሂብ** ፤ **ቦት** ፤ (ወሀበ ፡ ይውሁብ ፡ የሀብ ። ዕብ ፡ ያሀብ ። ሱር ፡ ይሃብ ። ዐረ ፡ ወሀበ) ፤ በይውሁብ ፡ ፈንታ ፡ ይሁብ ፡ ይላል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ ሁብን ፡ እይ ። መስጠት ፡ መናኘት ፡ ማደል ፡ ማሳለፍ ፡ የያዙትን ፡ ከሌላ ፡ እጅ ፡ ማግባት ፡ ማሲያዝ ፡ ማስጨበጥ ፡ ማስረከብ ፡ ዕንክ ፡ ተቀበል ፡ ማለት ፡ ማቅረብ ፡ በእጅ ፡ በቃል ። ቃል ፡ ሠናይ ፡ ይኄይስ ፡ እምውሂብ ፡፡ በእንተ ፡ ሁብት ፡ ወወሃቢ ፡ ወዘይሁብዎ ፡ ሎቱ ፡ ወንዋይ ፡ ዘይሁቡ ፡ ኪያሁ ፡፡ ሀቡ ፡ አኰቴተ ፡ ለእግዚ ፡ (ሚራ፲፰ ፡ ፲፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯ ። መዝ ፡ ፳፯) ።

—፤ ማዘዝ ፡ ማስናበት ፡ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ መስጠት ፡ ነው ። ለአዳም ፡ ባሕቲቱ ፡ ወሀቦ ፡ ይክድን ፡ ኀፍረቶ ፡፡

ወኢወሀበ ፡ ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ ቤተ ፡ አቡሁ ፡ (ኩፋ ፡ ፫ ። ሽንገ ፡ ፲፰ ፡ ፱) ።

—፤ ማድረግ ፡ ማኖር ፡ ማሳደር ፡ ምስጢሩ ፡ የረሰየና ፡ የሤመ ፡ ነው ፤ ዕብራይስጥም ፡ ናታን ፡ ብሎ ፡ ወሀበ ፡ ረስየ ፡ ሤመ ፡ ይላል ፡ ረስየን ፡ እይ ። እሁብ ፡ ኪዳነ ፡ ምስሌክሙ ። ቀስትየ ፡ ወሀበ ፡ ውስተ ፡ ደመና ፤ ፍርሀተ ፡ ክሙ ፡ እሁብ ፡ ኀበ ፡ ኵሉ ፡ ዘውስተ ፡ ምድር ። ዘሕይው ፡ የሀብ ፡ ሡናየ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ። ወእሁብ ፡ መንፈስየ ፡ ውስቴትክሙ ፡ (ዘፍ፱ ፡ ፱ ። ኩፋ ፡ ፯ ። መክ፮ ፡ ፫ ። ሕዝ፴፯ ፡ ፳፯) ። ማስዋብ ፡ ማሳመር ፡ ማስጌጥ ፡ ውብ ፡ ማድረግ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ወሃቢ** ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት) ፤ የሚሰጥ ፡ ሰጭ ፡ ዐዳይ ፡ አሳላፊ ፤ ለጋስ ፡ እጀ ፡ ሰፊ ። ወሃቢሃ ፡ ለሕግ ። ወሃቤ ፡ ሕይወት ። እግዚ ፡ ወሃቤ ፡ ዕሴት ፡ ወመክፈልት ፡ ለዘገብረ ፡ ፈቃዶ ። ብእሲ ፡ ፍሡሕ ፡ ወወሃቢ ፡ (ያዕ፱ ፡ ፲፪ ። ኪዳ ። ዮሴፍ ። ምሳ፳፪ ፡ ፰) ።

—፤ ዋቢ ፡ ዐላፊ ፡ በሰጠው ፡ ነገር ፡ የሚያልፍ ፡ የሚጣድ ፡ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ሰጭነት ፡ ነው ፤ (ተረት ፡ ዋቢ ፡ ያለው ፡ ይወጣል ፡ ዋቢ ፡ የሌለው ፡ ይሰምጣል ።

**ወሀብት** ፤ ወሃብያን ፡ ወሃብያት ።

»**ሀብ** ፤ (ቡ ፡ ቢ ፡ ባ) ፤ ንኡስ ፡ አገባብ) ፤ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፤ (ወሀብከ ፡ ትውህብ) ፡ ስጥ ፡ ዐድል ፡ አሳልፍ ፤ አምጣ ። እስኪ ፤ ና ፤ በል ። ሀቡ ፡ ንበል ። ሀቡ ፡ ንረድ ። ሀቡኬ ፡ ንግባእ ። ሀብኬ ፡ ንትኃሠሥ ፡ በአይ ፡ ፍኖት ፡ ተወልደ ። ሀባ ፡ ናመክሮን ፤ ሀባ ፡ ንፍትኖን ፡ (ዕገሪ ፡ ፳ ። ፴ነገ ፡ ፫ ፡ ፳፱ ። ክብ ፡ ነገ ። ቄር ፡ ጸሳ ። ሄርማ) ።

**አውሀበ** ፤ አሰጠ ፡ አስቀበለ ። ኢያውሀበከ ፡ እግዚ ፡ ክብረ ፡ (ዘኍ፳፬ ፡ ፲፩) ።

**ተውህበ** ፤ ተሰጠ ፡ ታደለ ፤ ዐለፈ ። ወልድ ፡ ተውህበ ፡ ለነ ። ዝናም ፡ አበየ ፡ ተውህቦ ፡ ለምድር ። ተውህበ ፡ መብልዐ ፡ ለአንበርት ። ተውህቦ ፡ ትትወሀብ ፡ ዛ ፡ ሀገር ፡ (ኢሳ፱ ፡ ፮ ። ኩፋ ፡ ፵፱ ። ኢዮ፲፭ ፡ ፲፫ ። ኤርም፴ ፡ ፱) ።

—፤ ኾነ ፡ ተደረገ ። ተውህቡ ፡ ታሕተ ፡ እደዊሁ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፩) ። ተዋበ ፡ አማረ ፡ ውበት ፡ አገኘ ።

**ውሁብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ህብት) ፤ የተሰጠ ፤ ተሰጭ ፡ የኾነ ። ውሁባን ፡ ሌዋ ፡ (ዘኍ፫ ፡ ፱) ። የተሰጠው ፡ የታደለ ፡ ሀብታም ፡ ዕድላም ። ውብ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ደመ ፡ ግቡ ፡ ደማም ፡ ውበት ፡ ደም ፡ ግባት ፡ የተሰጠው ፡ በተፈጥሮ ።

»**ሀብት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፡ አሰጣጥ ፡ ስጦታ ፤ ዕድል ፡ ፈንታ ፤ ጸጋ ፡ ብዕል ፤ ምጽዋት ፡ ዳረጎት ፤ ጕርሻ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ በክንቱ ፡ የሚሰጥ ። ወሀበሙ ፡ ሀብተ ፡ ወፈነዎሙ ። ሀብትከ ፡ ለከ ፡ ይኩንከ ። ኵሉ ፡ ሀብት ፡ ሠናይ ፡ እምላዕሉ ። ሀብታተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። በእንተ ፡ ሀብታት ፡ (ዘፍ፳፭ ፡ ፮ ። ዳን፭ ፡ ፲፯ ። ያዕ፩ ፡ ፲፯ ። ፊልክ ፡ ፻፸፱ ። ፋ ፡ ን ፡ ፳፯) ። ውበት ፡ ውብነት ፤ መልክ ፡ ደም ፡ ግባት ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ።

»**ሀብሀብ** ፤ (ዕብ ፡ ሀብሃብ ፤ ጥብስ ፡ ሥጋ) ፤ የዝሙት ፡ ዋጋ ፡ ለጋለሞታ ፡ የሚሰጥ ፡ (ሕዝ ፲፮ ፡ ፴፫ ። መጽ ፡ ምስ) ። ወይም ፡ ጋለሞታ ፡ ና ፡ ና ፡ ስጥ ፡ ስጥ ፡ አምጣ ፡ ጨምር ፡ የምትል ።

**ተዋሀበ** ፤ ተሰጣጠ ፤ ተቀባበለ ። ሕዝብ ፡ ይትዋሀቡ ፡ ሰላመ ፡ በበይናቲሆሙ ፤ ብእሲ ፡ ለብእሲ ፡ ወአንስት ፡ ለአንስት ፡ (ኪዳ) ።

**አስተዋሀበ** ፤ አሰጣጠ ፤ አቀባበለ ፡ አስተላለፈ ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፴፩) ።

**ዋህድ** ፤—አንድ ፡ ብቻ ፤—ዋሕዶ ፡ ዋሐደ ፡ ዋሕድ ።

**ውሂህ** ፤ (ወህሀ ፡ ይወህህ ፡ የሀህ ። ምህወ ፤ መየ) ፤ መወህየት ፤ ውሃ ፡ ውሀማ ፡ ውሃማ ፡ መኾን ፤ መቅለጥ ፡ የምህወንና ፡ የመየን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ።

**ወህውሀ** ፤ (ይወህውህ ፡ ይዋህውህ ፤ ወህውሆ ፤ ተቀ ፡ ግ) ፤ ውሃ ፡ ውሃ ፡ አለ ፡ የጣዕም ፡ የሕመም ።


**ተወህውሀ** ፤ (ይትወህዋህ ፡ ይትዋህዋህ) ፤ ጠራ ፡ በራ ፡ ጸደለ ፤ ውሃ ፡ መሰለ ፤ በረቀ ፡ አሸበረቀ ፤ አማረ ፡ ተዋበ ፤ የመልክ ፡ የኀብር ። ጸጋ ፡ ክብር ፡ አገኘ ፤ ተደሰተ ፡ በደስታ ፡ ኖረ ፤ ተመላለሰ ፤ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ ጥምቀትና ፡ ህብተ ፡ ልደት ፡ ነው ። ጻድቃንኒ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ይትፌሥሑ ፡ ወይትወህውሁ ፡ በአዝማን ፡ ዘእልበ ፡ ኍልቍ ። ደቂቃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይዕቀቡ ፡ ሥርዐታ ፡ ወይትዋህውሁ ፡ ውስቴታ ፡ ወያሠንዩ ፡ ግበሪሃ ። ይትወህውሁ ፡ በኵሉ ፡ ክብር ፡ ወፍሥሓ ፡ ዘእንበለ ፡ ጻማ ፡ ወሕማም ፡ (ድጓ ። ቀሌ) ። እለ ፡ ቀደሙ ፡ የዐይሉ ፡ ገዳመ ፡ ወአድባረ ፡ ወድኅረ ፡ ይትወህውሁ ፡ በአዕጻደ ፡ ነገሥት ። ይሰግዱ ፡ ላቲ ፡ ወይትወህውሁ ፡ በቅድሜሃ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ነሐ፳፩) ።

**ውህዋሄ** ፤ የመልክና ፡ የክብር ፡ ብርሃን ፤ ሥን ፡ ላሕይ ፡ ጸጋ ፡ ዕበይ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ የዋሐየ ፡ ዘር ፡ አድርገው ፡ (ውሕየት) ፡ መጕብኘት ፡ ይሉታል ። ዘረከበ ፡ ብእሲተ ፡ ኄርተ ፡ ረከበ ፡ ሞገሰ ፤ ወነሥአ ፡ እምኀበ ፡ እግዚ ፡ ውህዋሄ ፡ (ምሳ፲፰ ፡ ፳፪) ።

**ወዎ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ ደጀን ፡ የኋላ ፡ ጦር ፤ የፊታውራሪ ፡ አንጻር ። ወዎነት ፡ ተኾመ ፡ እንዲሉ ።

**ዋዌ** ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ባድስ ፤ ፮ኛው ፡ የግእዝ ፡ ፊደል ፡ ወ ፤ በአበገደ ። ወገል ፡ ሸንገል ፤ ሜንጦ ፡ ቈላፋ ፡ ብረት ፤ ቍልፍ ፡ ዘለበት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሸንገል ፡ እንደ ፡ ሜንጦ ፡ ያለ ፡ የመስኮት ፡ ስናግ ፡ ነው ። ቍልፍ ፡ ማእከል ፡ ኾኖ ፡ ግራና ፡ ቀኙን ፡ እንዲያያይዝ ፤ አጫፋሪነቱን ፡ ያሳያል ። ዘለበት ፡ ማለትም ፡ በግብሩ ፡ ላይ ፡ መልኩን ፡ ጨምሮ ፡ ያስረዳል ። ሆህያተ ፡ ቤት ፡ ወዋዌ ፡ (አፈ ፡ ድጓ) ።

**ዋው ፤ (ዕብ ፡ ወሱር ፡ ወዐረ) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ። ዋው ፡ ይዕማጺእ ፡ ምሕረትከ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ዓ፯ ‥ ዓ፰ ። ሰቈ፭ ፡ ፯ ። ፱ ፡ ፯ ። ፫ ፡ ፲፭ ። ፱ ፡ ፯) ።



ዋዌ ፡

**ወውዖ ፤ ዖት ፤ (ወውዐ ፡ ይዌውዕ ፡ ይወውዕ ። ዐረ ፡ ወዕውዐ) ፤** መራኘ ፡ ማውካት ፤ መደንፋት ፤ እልል ፡ ማለት ። ወውዐ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ። ወውዑ ፡ ላዕሌሁ ። ይዌውዕ ፡ ዴቢ ፡ ፀሩ ። ወውዑ ፡ ሎቱ ፡ አቢሳ ። ወውዑ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ (ዳንኤ፫ ፡ ፲፰ ። ኢሮ፪ ፡ ፲፭ ። ኢሳ፵፪ ፡ ፲፫ ። ፪ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፲፯ ። ዮሴ ፲፱ ፡ ፱) ።

**ውውዓ ፤** ጩኸት ፡ ውካታ ፤ እልልታ ፡ ድንፋታ ፤ ቡታ ፡ ዋይታ ። ውውዓ ፡ ቀትል ። ውውዓሆሙ ፡ ለበብእ ፡ አፍራስ ። ውውዓ ፡ ከነ ። ውውዓ ፡ እምውስጥ ፡ (ኤር፱ ፡ ፲፱ ፡ ፳፱ ። ማቴ፳፭ ፡ ፯ ። ሶሮ፮ ፡ ፲) ።

**ውዋዔ ፤** መራኘ ፤ አጨጫጩኸ ፤ ጩኸት ። በባም ፡ እብል ፡ በቃለ ፡ ስብሐት ፡ ወውዋዔ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፯) ።

**ወዚዝ ፤ (ወዘ ፤ ወዘዘ ። ወዝወዘ) ፤** በቁሙ ፤ ዐማርኛ ።

**ዋዜማ ፤—በቁሙ ፤—ዜመ ፤ ወዝየመ ።**

**ወዘነ ፤—መዘነ ፤—ሚዛን ፤ መዝኖ ፡ መዘነ ።**

**ወዚፍ ፤ ፎት ፤ (ወዘፈ ፡ ይወዝፍ ፡ ይዘፍ ። ሱር ፡ ያዘፍ ፤ ተለወጠ) ፤** ማጌጥ ፡ መለወጥ ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ ማውጣት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወዘፈ ፡ ፈንታ ፡ ተወዝፈ ፡ ይላል ። እምተወዘፎቱ ፡ (አዋል) ። በቁሙ ፡ መወዘፍ ፡ ማስቀመጥ ፡ ማስቀረት ። ውዝፍ ፡ እንዲሉ ።

**ትውዝፍት ፤** ትዕቢት ፡ ኵራት ፤ ከልብስና ፡ ከጌጥ ፡ የተነሣ ። የምንዝር ፡ ጌጥ ፡ መልክ ፡ የሚያድስ ፡ የሚለውጥ ፡ (ቀሌ) ።

—፤ ውዝፍንት ፡ ቀሪነት ። ዘወፈን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ምንጩ ፡ ነው ። ትውዝፍት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ትዝውፍት ፡ ይላል ፡ (ገላ፭ ፡ ፳) ።

**ወዘረ ፤ (ዐረብ) ፤** ለበጠ ፡ ሸለመ ፡ አስጌጠ ፤ የሕንጻ ። ወወዘሩ ፡ ኵሎ ፡ ንድቀ ፡ ማኅፈድ ፡ በዕፀ ።

—፤ አወየዘረ ፡ ሾመ ፡ አከበረ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ አደረገ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወዘረ ፡ ፈንታ ፡ አስተውዘረ ፡ ይላል ። እስመ ፡ አክሳይሮስ ፡ አስተውዘረ ፡ ብእሴ ፡ ዘይብልዎ ፡ ሀማን ፡ (ዮሴፍ) ።

**ወዚር ፤** ወይዘር ፡ ታላቅ ፡ መኰንን ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ባለሟል ። ሶበ ፡ ተሠይመ ፡ ሀማን ፡ ወዚረ ፡ ለአክሳይሮስ ፡ (ዮሴፍ) ። ተወዘረ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ዋሕዶ ፤ ዶት ፤ (ዋሐደ ፡ ይዋሕድ ፡ ይዋሕድ ። ዕብ ፡ ያሐድ) ፤** መዋሐድ ፤ አንድ ፡ መኾን ፡ መተባበር ፤ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ። አሐድን ፡ እይ ፤ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዋሐደ ፡ ፈንታ ፡ ተውሕደ ፡ ተወሐደ ፡ ይላል ። ይትወሐዱ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ይኩኑ ፡ አሐደ ፡ ሥጋ ። ናሁ ፡ ተዋሐደ ፡ ወተሰውጠ ፡ ቦቱ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፳ ፡ ፬ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፯) ።

**ዋሕድ ፤ ወሐድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፤ ሕድ ፤ ድት ፤ ውሕድ ። ዕብ ፡ ያሒድ ። ዐረ ፡ ዋሒድ) ፤** የተዋሐደ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ የተባበረ ። አንድ ፡ ወጣት ፡ አንድ ፡ ቅንባት ፡ ምንታዌ ፡ መንቲያ ፡ ወይም ፡ ተቀዳሚና ፡ ተከታይ ፡ የሌለው ፡ ፍጹም ፡ አንድ ። ውኅደን ፡ እይ ። ትቀትል ፡ ወልዳ ፡ ዋሕደ ። ወቦቱ ፡ ወለት ፡ ዋሕድ ፡ ት ። ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ሕፅነ ፡ አቡሁ ። ክርስቶስ ፡ ዋሕድ ፡ (ዮሴፍ ። ሉቃ፯ ፡ ፲፪ ። ዮሐ፩ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ የካ፱) ።

**ዋሕድ ፡ ወበኵር ፤** ምግው ፡ ቃል ፤ የምግው ፡ ቃል ፡ ስም ። ይሰመይ ፡ ዋሕደሂ ፡ ወበኵረሂ ፡ (ቄር) ። ዋሕድ ፡ በወዲያኛው ፡ በአምላክነት ፡ በባሕርይ ፡ ልደት ፤ ወልድየ ፡ አንተ ፡ በተባለበት ። ወበኵር ፡ በወዲህኛው ፡ በሰውነት ፡ ሰው ፡ ኹኖ ፡ በንግው ፡ በቅባት ፡ በግብር ፡ ልደት ፡ ወአነ ፡ ዮም ፡ ወለድኩከ ፤ አነ ፡ እከውኖ ፡ አባሁ ፡ ወውእቱ ፡ ይከውነኒ ፡ ወልድየ ፡ በተባለበት ። ውእቱ ፡ ይብለኒ ፡ አቡየ ፡ አንተ ፡ ወአነሂ ፡ በኵርየ ፡ እሬስዮ ። በኵረ ፡ ልደት ፡ ለኵሉ ፡ ፍጥረት ። በኵረ ፡ ልደት ፡ ኵሉ ፡ ተግባሩ ፡ (መዝ፹፰ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ኄሬ ። ቄር) ።

**ዋሕድና ፤** አንድነት ፡ አንድ ፡ ልጅነት ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ መኾን ።

**አዋሐደ ፤ አስተዋሐደ ፤** በቁሙ ፡ አዋሐደ ፡ አወሐሐደ ፤ አስማማ ፡ አንድ ፡ አደረገ ። በበ ፡ አሐዱ ፡ ታዋሕድ ። ዘያስተዋሕደከ ፡ ምስለ ፡ እግዚ ። ወአስተዋሐደ ፡ ሥጋ ፡ እንተ ፡ ነሥአ ፡ ቃል ፡ እምኔሃ ፡ (አዋል ። አረጋ ፡ ድሽ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ጎር) ።

**መዋሕድ ፤ መስተዋሕድ ፤** የሚያዋሕድ ፡ አዋሐጅ ፡ አንድ ፡ አድራጊ ።

**ሙሓድ ፤ ምስትውሓድ ፤** መዋሐጃ ፡ ማዋሐጃ ፡ ቦታ ፡ መዛሪያ ።

**ተዋሐደ ፤ (ተደራራጊ) ፤** በቁሙ ፡ ተወሐሐደ ፡ ተገናዘበ ፤ አንድ ፡ ኾነ ፡ ምንታዌ ፡ ዐጣ ። መዋሐድ ፡ ለኹለት ፡ ለሦስት ፡ ከዚያም ፡ ለሚበዛ ፡ ይነገራል ። ወተዋሕዶሂ ፡ ውእቱ ፡ ዘክልኤሆሙ ። ወኢክነ ፡ ክርስቶስ ፡ እኅወ ፡ በግብር ፡ ሐዲስ ፡ አላ ፡ ለቢሶ ፡ ሥጋ ፡ ዚአነ ፡ በተዋሕዶ ፡ ዘኢይትነገር ። እስመ ፡ ተዋሕዶ ፡

ሕእተታ ፡ ለምንታዌ ። ይሜለሱ ፡ በአካላት ፡ ወይት ዋሐዱ ፤ በመለኮት ፡ (ሃይ ፡ አበ) ። ግስንቱ ፡ በጕልናን ፡ ሐ ውልት ፡ የባረከ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ።

**ተዋሕዶ** ፤ መዋሐድ ፡ አንድ ፡ መኾን ፡ ኅብ ረት ፡ አንድነት ። እግዚ ፤ ዘይሜለስ ፤ በአካሉ ፤ እንዘ ፡ ተዋሕዶ ፤ ያጸንዕ ፡ በመለኮቱ ፡ ወኅይሉ ። ተዋሕዶ ፡ አምሳከ ፤ ወሰብእ ፤ ለክልኤ ፤ ነፈቀ ። አሚን ፤ ተዋ ሕዶት ፡ አምሳካዊት ። በእንተ ፡ ተዋሕዶ ፤ (ደራሲ ። ስንክ ፡ መስ፳ ። ፍ ፡ ን ፡ ፻፳ ። አቡሻ ፡ ፶) ።

—፤ ስመ ፡ ጉባኤ ፡ የኤፌሶን ፡ ማኅበር ፡ ኹለቱ ፡ መቶ ፡ ጳጳሳት ። ኦርቶዶክስ ፡ የኒቅያ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተዋ ሕዶም ፡ የኤፌሶን ፡ ስም ፡ ነው ። የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ኅድረት ፡ ማለትን ፡ ነቅፈው ፡ አጸይፈው ፡ ስላወገዙ ፡ ባህ ላቸውና ፡ ስማቸው ፡ በኅድረት ፡ አንጻር ፡ ተዋሕዶ ፡ ተብ ሏል ። የኦርቶዶክስና ፡ የተዋሕዶም ፡ ባህል ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ቃልና ፡ ሥጋ ፡ በተዋሕዶ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ፍጹም ፡ አምላ ክና ፡ ፍጹም ፡ ሰብእ ፤ በተፀቅቦ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፤ ኹለት ፡ የባሕርይ ፡ ልደታት ፤ ኹለት ፡ ግብራት ። መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ በቅብዐት ፡ መንፈስ ፡ መሲሕ ፡ ወበ ኵር ፡ ዳግማይ ፡ አዳም ፡ ንጉሥ ፡ ካህን ፡ ነቢይ ፡ ሐዋርያ ፡ ማለት ፡ ነው ። የኢትዮጵያም ፡ እምነትና ፡ ትምርት ፡ ከ አብርሀ ፡ አጽብሐ ፡ እስከ ፡ ሱስንዮስ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነ በረ ፤ በሱስንዮስና ፡ በፋሲል ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ካራና ፡ ቅ ባት ፡ የሚባሉ ፡ እናዛኹ ፡ ዘይትነግል ፡ እንዘኢየሱስ ፡ ኹ ለት ፡ ወገኖች ፡ ተነሥተው ፡ የተዋሕዶን ፡ ስም ፡ ቀም ተው ፤ ተዋሕዶና ፡ ኦርቶዶክስ ፡ እኛ ፡ ነን ፡ ብለው ፡ እው ነተኛውን ፡ ተዋሕዶ ፡ ጸጋ ፡ የሚሉ ፡ ስም ፡ ቀብተውታል ። ከነዚሁ ፡ ደግሞ ፡ ካራው ፡ እስካሁንም ፡ ቅባቱ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ተከፍለዋ ፤ ባህላቸው ፡ ፫ ፡ ዐይነት ፡ ነው ። ዐሥራ ፡ ስድስትም ፡ የሚሉ ፡ አሉ ፤ መዋዕሕትንና ፡ ቅብዐትን ፡ ተመልከት ። (መወድስ ፡ ዘኦርቶዶክሳዊ ፡ ክፍለ ፡ ዮሐንስ) ፤ ሃይማኖት ፡ ቄርሎስ ፡ ክነት ፡ ግማዳተ ፡ አ ብይ ፤ ወንጕልቂ ፡ ተመትሮ ፡ አብዝኀት ፡ ኀበ ፡ ኢሀሎ ፡ ንጉሥ ፤ ካህነ ፡ ደብረ ፡ ሱፍሬም ፡ ቅድመ ፡ እምዘ መተራ ፤ ነሳስ ። ወአመ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ለምሳሌ ፡ በ እደ ፤ ነቢይ ፡ ዘተሠጠት ፡ ልብስ ፤ (መሳ፲፱ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ። ፫ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፴ ፡ ፴፩) ።

**ውሕደ** ፤—አነሰ ፤ ጐደለ ፤—ውኂድ ፡ ውኀደ ።

**ወሕውሐ** ፤—በራ ፤ ተመላለሰ ፤—ወ ሂሀ ፡ ወህሀ ፤ ወህውሀ ።

**ውሒዝ** ፤ ዘት ፤ (ውሕዘ ፡ ይውሕዝ ፡ የሐዝ ። ዐረ ፡ ወዘዐ ። ዕብ ፡ ያዛዕ ፤ ወዛ) ፤ መፍ ለቅ ፡ መፍሰስ ፡ መውረድ ፡ መጕረፍ ። ይውሕዝ ፡ ማይ ። ፈለግ ፤ ዘይውሕዝ ። የሐዝ ፡ ማየ ፡ ቀራንብቲክሙ ። ብእሲት ፡ እንተ ፡ ደም ፡ ይውሕዝ ፡ (ኢሳ፴ ፡ ፳፭ ። ፴፫ ፡ ፪ ። ኤር፱ ፡ ፲፰ ። ማርቆ ፡ ፳፭) ።

—፤ ማፍለቅ ፡ ማፍሰስ ፡ ማውረድ ፡ ማጕረፍ ። እደ ውየ ፡ ይውሕዛ ፡ ከርቤ ። ምድር ፤ እንተ ፡ ትውሕዝ ፡ ሐሊበ ፡ ወመዓረ ። ዐይንየ ፡ ውሕዘት ፡ ማየ ፡ (ማሕ፭ ፡ ፭ ። ዘፀ፫ ፡ ፰ ። ሰቆ፩ ፡ ፲፮) ። ግስንቱ ፡ ዐጕልና ፡ ገቢር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ።

**ወሓዚ** ፤ (ዚት ፡ ዝያን ፡ ያት ፤ ሐዝት) ፤ የሚፈስ ፡ ፈሳሽ ፡ የሚያፈስ ፡ አፍሳሽ ።

**ውሑዝ** ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ሕዝት) ፤ የፈለቀ ፡ የሚፈልቅ ፡ ፈሳሽ ፡ ወራጅ ። አንብዕ ፡ ውሕዝት ፡ (ፊልክ ፡ ፶፲) ።

**ውሕዘት** ፤ መፍሰስ ፤ አፈሳሰስ ፤ ፈሳሽነት ። ው ሕዘቱ ፡ መንገለ ፡ ሰሜን ። በውሕዘተ ፡ አንብዕ ። ወቆ መ ፡ ሶቤሃ ፤ ውሕዘተ ፡ ደማ ፤ (ሔኖ፳፯ ፡ ፱ ። ሥር ፡ ጳኵ ። ሉቃ፰ ፡ ፵፬) ።

**ወሒዝ** ፤ **ውሒዝ** ፤ (ዛት ፤ ወሓይዝት) ፤ ወንዝ ፡ የወንዝ ፡ ውሃ ፡ ፈሳሽ ፡ ጐርፍ ። ውሒዝ ፡ ዐ ቢይ ። ውሒዝ ፡ ኀያል ። ከመ ፡ ውሒዛተ ፡ ማይ ። ውሕዙ ፡ ወሓይዝት ። ወሓይዝተ ፡ አፍላግ ፡ ቅኑያ ቲሁ ፡ (ኢሳ፲፯ ፡ ፲፫ ። ፶፱ ፡ ፲፱ ። ምሳ፳፭ ፡ ፩ ። ማቴ፯ ፡ ፳፭ ። ቅዳ ፡ ኤጲ) ።

**ወሕዝ** ፤ (ዕብ ፡ ዚዓ) ፤ ወዝ ፡ ላብት ፤ ሀፍ ፡ ራሕፀ ፡ ከገላ ፡ የሚፈልቅ ፡ የሚፈስ ።

**አውሐዘ** ፤ አፈለቀ ፡ አፈሰሰ ፤ አስፈሰሰ ፤ አዘነመ ። አውሕዘ ፡ ማየ ፡ በብሔረ ፡ ጽምእ ። ደመናት ፡ ያው ሕዙ ፡ ጠላተ ። ሊአመ ፡ አውሐዘ ፡ እግዚ ፡ አስራበ ፡ እ ክል ፡ እምሰማይ ። ጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስ ፡ አውሐዙ ፡ ምህሮ ፡ ወንጌል ፡ (ኢሳ፵፰ ፡ ፲፰ ። ምሳ፫ ፡ ፳ ። ፪ነገ ፡ ፯ ፡ ፱ ። አርጋ) ።

**አውሓዚ** ፤ **መውሐዚ** ፤ **መውሕዝ** ፤ (ዝት ፡ ዛን ፡ ዛት) ፤ የሚያፈስ ፡ የሚያስፈስስ ።

**ሙሓዝ** ፤ (ዛት) ፤ መፍሰሻ ፡ ማፍሰሻ ፡ ማስፈ ሰሻ ፤ ወንዝ ፡ ዐይ ፡ መትረብ ፡ አሸንዳ ። ኢትግበር ፡ ሎቱ ፡ ሙሓዘ ፡ ለማይ ። ሙሓዘ ፡ ማየ ፡ ግብጽ ። የነድሩ ፡ ውስተ ፡ ሙሓዛተ ፡ ማይ ። ዕፀ ፡ ዘበቈለት ፡ ኀበ ፡ ሙሓዘ ፡ ማይ ፡ (ሢራ፳፭ ፡ ፳፭ ። ኩፋ ፡ ፲ ። ኤር፲፯ ፡ ፱ ። ድጓ) ።

**ውሕጠ** ፤—ዋጠ ፤—ውኂጥ ፡ ውኅጠ ።

**ዋሕየ** ፤ ዮት ፤ (ዋሐየ ፡ ይዋሒ ፡ ይ ዋሒ ። ዐረ ፡ ወሐይ) ፤ መጐብኘት ፡ መፍቀድ ፤ መ ላልስ ፡ ተመላልስ ፡ ማየት ፡ እየዞሩ ፡ መሰለል ፡ መጠበቅ ። እመ ፤ ዋሐይኩ ፡ ኖኅተ ፡ ቤታ ። የሐውር ፤ ይሥሐቅ ፡ ወይዋሒ ፤ ጥሪቶ ፤ (ስ ፡ ሌጺስቀጾስ) ፤ ዋሕዮሙ ፤ ለ ኃጥኣን ፤ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ። እስመ ፤ ይዋሒ ፡ በ ጸዓዕ ፡ ወበድልቅልቅ ። እዋሕዮ ፡ በበትር ፡ ለኀጢአ ቶሙ ፡ (ኢዮ፴፩ ፡ ፱ ። ኩፋ ፡ ፳፱ ። ቀሌ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፮ ። መዝ ፡ ፹፰) ። ሐወጸን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ዋሓዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤ የሚጐበኝ ፤ ፈቃጅ ፡ ጠባቂ ። ከሃሊ ፡ ኵሉ ፤ ወዋሓዪ ፡ ኵሉ ፤ (ቄር) ።

**አዋሐየ ፤ አውሐየ ፤ አስተውሐየ ፤** አስጐበኘ ፡ አስጠበቀ ፤ አስጠየቀ ።

**አስተዋሐየ ፤** አስጐበኘ ፤ አጐበኛኘ ። ዘያስተዋ(ዐ)ሕያ ፡ ለእከይ ፡ ይትሀጐል ፡ ብቲ ፡ (ምሳ ፲፱ ፡ ፴) ።

**ተዋሐየ ፤** ተጐበኘ ፤ ተጐበኛኘ ።

**ዉሑይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሒት) ፤** የተጐበኘ ፡ ጐብኙ ፡ ጥብቅ ።

**ዉሓዩ ፤ ዋሕይ ፤ ሕየት ፤** መጐብኘት ፤ (ጥጐ) መጐብኘት ፡ አጐበኛኘት ፤ ጐብኝታ ፡ ጥየቃ ፡ ስለላ ፡ ጥበቃ ። እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ዋሕየ ። ዋሕይ ፡ ወሐተታ ፡ (አፈ ፡ ተጸ፱ ። ጥበ ፲፱ ፡ ፲፱) ።

**ሙ(ሞ)ሓዪት ፤** መጐብኛ ፡ መሰለያ ። በቁሙ ፤ ታፋ ፡ ሙሳ ፡ ማውድ ፡ ዳሌ ።

**ውሒክ ፤ ክት ፤ (ወሐከ ፡ ይዌሕክ ፡ የሐክ) ፤** ማወክ ፡ ማንሣሣት ፤ መንገዝገዝ ፡ መጐትጐት ፤ በግብር ፡ በነገር ፡ ማስቸገር ፤ ዕንቅፋት ፡ የክፉ ፡ አብነት ፡ መኾን ። ሆክን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ወሐከ ፡ ሰፀርክከ ፡ ዘተሐበይኮ ። ይዌሕኮ ፡ ለፈጣሪሁ ። ወሐኮ ፡ ኃጥእ ፡ ለእግዚ ። ውሒክ ፡ ወሐክሙ ፡ ለፀረ ፡ እግዚአብሔር ። አነ ፡ አአምር ፡ ውሒኮተከ ፡ (ምሳ ፳ ፡ ፫ ። ፲፱ ፡ ፴፭ ። መዝ ፡ ፱ ። ፪ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፲፱ ። ዘዳ፴፩ ፡ ፳፯) ።

**ወሓኪ ፤ (ኪት ፡ ክያን ፡ ያት) ፤** የሚያነሣሣ ፤ አንሣሽ ፡ ጐስጓሽ ።

**ውሒስ ፤ ሶት ፤ (ወሐሰ ፡ ይዌሕስ ፡ የሐስ ፡ ዐረ ፡ ወሰ) ፤** ማዋስ ፤ ዋስ ፡ ጠበቃ ፤ ተመላሽ ፡ ዕቃ ፡ መስጠት ፤ እገሌ ፡ ተዋስኝ ፤ ዕንካ ፡ ውሰድ ፡ ማለት ። ምስጢሩ ፡ መስጠት ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወሐሰ ፡ ፈንታ ፡ አውሐሰ ፡ ይላል ፤ አ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያውሕስ ፡ ንዋዮ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፰) ።

**ወሓሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት ፤ ሐስት) ፤** የሚያውስ ፡ አዋሽ ፤ ሰጭ ፡ ባለገንዘብ ። ወኢሀሎ ፡ ወሓሲ ፡ ለግዚአ ፡ ንዋይ ፡ (ዘፀ፳፪ ፡ ፲፫) ።

**አውሐሰ ፤** አስዋሰ ፤ ዋስ ፡ አስጠራ ፤ ውሰት ፡ አስጠ ።

**አውሓሲ ፤ መውሐሲ ፤ መውሕስ ፤** የሚያስውስ ፡ ዋስ ፡ የሚያስጠራ ፤ ዋስ ፡ የሚል ። ከአውሓሲ ፡ በቀር ፡ መውሐሲና ፡ መውሕስ ፡ ፪ኛ ፡ እንደ ፡ ወሓሲ ፡ ባድራጊነት ፡ ይፈታል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ አውሓሲንም ፡ በወሓሲ ፡ ፈንታ ፡ ይጥፋል ። የሀብ ፡ ለአውሓሲ ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለአውሓሲ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፰) ።

**ተውሕሰ ፤ ተወሐሰ ፤** ተዋሰ ፤ ዋስ ፡ ኾነ ፡ አዋሳለኹ ፡ አለ ። አልቦ ፡ ዘይትወሐሰክሙ ። ኢይደልዎ ፡ ለካህን ፡ ከመ ፡ ይትወሐስ ፡ አሐደሂ ፡ ወየአኀዝ ፡ ንዋየ ፡ (ቀሌ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፺) ።

—፤ አውሱኝ ፡ አለ ፤ ተዋሰ ፡ ወሰደ ። ተወሐሲ ፡ ለኪ ፡ ንዋየ ፡ ልሕዛት ፡ እምኅብ ፡ ጎርኪ ። ዕሴት ፡ ተወሓሲ ። ለእመ ፡ ተውሕሰ ፡ ብእሲ ፡ እምቢጹ ፡ እንስሳ ፡ (፪ነገ ፡ ፬ ፡ ፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ። ፵፳) ።

—፤ ተሰጠ ፤ ከዋሽ ፡ ወደ ፡ ተዋሽ ፡ ኼደ ፡ ዐለፈ ፤ ዕቃው ፡ ከብቱ ። ንዋይ ፡ ዘይትወሐስ ፡ ለእመ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ አሐዱ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመተ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ። ዳግመኛም ፡ በወሐሰ ፡ ፈንታ ፡ አውሐሰ ፡ እንዳል ፤ በተውሕሰም ፡ ፈንታ ፡ አስተውሐሰ ፡ ይላል ፤ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ወአስተውሐሱ ፡ እምግብጽ ፡ ንዋየ ፡ ብሩር ፡ ወወርቅ ፡ ወልብስ ፡ (ዘፀ ፲፪ ፡ ፴፭) ።

**ውሑስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ሕስት) ፤** የተዋሰ ፡ ዋስ ፡ የኾነ ፤ ውሰት ፡ የወሰደ ፤ የተሰጠ ።

**ውሕሰት ፤** ማዋስ ፤ መዋስ ፡ አዋዋስ ፡ ውሰት ፤ ዋስትና ፡ ዋስነት ፤ ውሰትነት ። አው ፡ በአኀዝ ፤ አው ፡ በውሕሰት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፱) ።

**ትውሕስት ፤ (ታት) ፤** በቁሙ ፡ ትውስት ፡ መዋስ ፡ ውሰት ፤ ዋስትና ፡ ዋስነት ። በእንተ ፡ ትውሕስታት ፡ ወሤጥ ፡ ወተዓስቦ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፯) ።

**ተዋሐሰ ፤** ተዋዋሰ ፡ ተሰጣጠ ፤ ዋስ ፡ ተጣራ ።

**አስተዋሐሰ ፤** አዋዋሰ ፤ ዋስ ፡ አጣራ ፡ አካሰሰ ።

**ዋሕስ ፤** በቁሙ ፤ ዋስ ፡ መድን ፡ ተያዥ ፡ ተጠሪ ፤ ቶፋ ፡ ገባሪ ። ነሣኢ ፡ ዋሕስ ። ወበዋሕስ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፺ ። ፴፱) ።

»**ሕስት ፤ (ታት) ፤** ውሰት ፡ ትውስት ፤ የተውሶ ፡ ዕቃ ፡ ከብት ። በእንተ ፡ ሕስት ፤ ሕስትሰ ፡ ነሚአ ፡ በቀዉዓት ፡ ውእቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ቤዛ ፡ በኀጽ ፡ እሙር ። ዘከመ ፡ ዲናራት ፡ ወጠፋልሐ ፡ ብሩር ፡ ወዘይሰፈር ፡ ወዘይትሜዘን ፡ ልቃሕ ፡ ውእቱ ፡ ወአኮ ፡ ሕስት ። በከመ ፡ ልብሰ ፡ ሕስት ፡ ከማሁ ፡ ብዕሎሙ ፡ ለኃጥአን ፡ በቅድመ ፡ እግዚ ። ነሳፊ ፡ ንብረት ፡ ከመ ፡ ጽላሎት ፡ ወከመ ፡ ልብሰ ፡ ሕስት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፰ ። መቃ ፡ ገ፲ ። ድጓ) ።

**ውኂድ ፤ ዶት ፤ (ውኀደ ፡ ይውኅድ ፡ ይውኀድ ፤ የኀድ) ፤** መጐደል ፡ ማነስ ፡ መቀነስ ፤ አንዳንድ ፡ እያሉ ፡ ጥቂት ፡ መኾን ፤ ብቻ ፡ መቅረት ፤ ማጠር ፡ መቅጠን ። ዋሐደን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ብዝኅ ፡ ወኢትውኅዱ ። እለ ፡ ይውኅዱ ፡ የአክሉ ፡ እልፈ ። ዓመተ ፡ ረሲዓን ፡ ይውኅድ ። ሚመተ ፡ ክህነቱ ፡ ይውኅድ ፡ እምዓመት ። ዝ ፡ ውዳሴ ፡ ይውኅድ ፡ እምክብርክን ። ተሰዓሳ ፡ ይንእስ ፡ እምነ ፡ ሐርጌ ፤ ወአንበሳ ፡ ይውኅድ ፡ እምነጌ ፡ (ኤር ፴፱ ፡ ፮ ። ኢሳ፳ ፡ ፳፪ ። ምሳ፲ ፡ ፳፯ ። ዮሴፍ ። ቈር ። ቅኔ) ።

**ውሑድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ኀድ) ፤** ያነሰ ፤ የጐደለ ፤ ታናሽ ፡ ጐደሎ ፤ ጥቂት ። ውሑድ ፡ አነ ፡ በኍልቍየ ። ውሑድ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወትየ ። ጥፊትከ ፡ እመኒ ፡ ብዙኅ ፡ ወእመኒ ፡ ውሑድ ። ውሑዳን ፡ ምድር ። ዘእንበለ ፡ ውሑዳት ፡ መካናት ። ውኁድ ፡ አንቲ ፡ (ዘፍ፴፬ ፡ ፴ ። ኢዮ፲ ፡ ፳ ። ሢራ፵፪ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፲፯ ። ኩፋ ፡ ፴፭ ። ሚክ፭ ፡ ፩) ።

**ውሑደ ፤** ጥቂት ፤ በጥቂት ። ውሑደ ፡ ጻመውኩ ። አክአብ ፡ ውሑደ ፡ ተቀንየ ፡ ለበዓል ፤ ወኢዩስ ፡

ብዙኃ ፡ ይትቀነይ ፡ ሎቱ ። ዘሰ ፡ ውኁደ ፡ አፍቀረኒ ፡ ውኁደ ፡ ይትኀደግ ፡ ሎቱ ፡ (ሚራ ፻፳ ፡ ፳፮ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፰ ። ሉቃ ፯ ፡ ፵፯) ። በውኁድ ፡ ፈንታ ፡ ዋኅድ ፡ ይላል ፤ ሳናችው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ሂሮማ) ።

**ውኅደት** ፤ መጕደል ፡ ማነስ ፡ አነኦዳደል ፡ ጕድለኝነት ። ውኅደተ ፡ ሕዝብ ። በውኅደተ ፡ እጥርየ ፡ (ምሳ ፲፬ ፡ ፳፰ ። ፊልክ ፡ ፳፱) ። በውኅደት ፡ ፈንታ ፡ ውኀድ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ውኅድ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ፡ (መዝ ፡ ፻፩) ።

**አውኀደ** ፤ አጐደለ ፡ አስጐደለ ፡ አሳነሰ ፡ ከፈለ ፤ ጥቂት ፡ አደረገ ። ታውኅዶን ፡ ለኀጣውኢክ ። ቅንአት ፡ ወመዐት ፡ ያውኅዱ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወት ። አውኅዶ ፡ ጥሪት ። እኩ ፡ በአብዝኆ ፡ አላ ፡ በአውኅዶ ። በአልዎ ፡ ያውኅድ ፡ እምነ ፡ ብዙኅ ፡ ሥቃዩ ። አዘዘ ፡ ያውኅዱ ፡ አንድዶ ፡ እምታሕተ ፡ መቅፀት ፡ (ሚራ ፳፰ ፡ ፳ ። ፴ ፡ ፳፱ ። ፊልክ ፡ ፳፱ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ፳፪ ። ዮሴፍ) ።

**መውኅዲ ፤ መውኅድ** ፤ የሚያጐድል ፡ አጓዳይ ፡ አሳናሽ ፡ ማጐደያ ።

**ዋኅደ ፤—ተዋሐደ ፤—ዋሕዶ ፡ ዋሐደ ።**

**ውኂጥ ፡ ጦት ፡ (ውኅጠ ፤ ወኀጠ ፡ ይውኅጥ ፡ የኅጥ ። ዐረ ፡ ሐጠ)** ፤ መዋጥ ፡ መስልቀጥ ፡ ወደ ፡ ሆድ ፡ መሳብ ፡ በጕረሮ ፡ መቅሰብ ፤ ማግባት ፡ መክተት ፡ መጕረስ ፡ መብላት ። ከመ ፡ ያሰምድ ፡ ውኂጠ ። ብቅው ፡ ለውኂጥ ። አዘዘ ፡ ዐንበሬ ፡ የኅጦ ፡ ለዮናስ ። ወውኂጦ ፡ ነቅዐ ። ነኀጦ ፡ ሐደዎ ። እለ ፡ ይውኅጥዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ (ኪዳ ። አርጋ ፡ ፯ ። ዮና ፩ ፡ ፲፯ ። ዳን ፲፫ ፡ ፳፯ ። ምሳ ፩ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፲፫) ።

**ወኃጢ ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት ፡ ኀጥ)** ፤ የሚውጥ ፡ ዋጭ ። ጠብቆ ፡ ቀለም ፡ የሚያስቀር ፡ ፊደል ፡ በርባታ ፡ ጊዜ ። ግ ፡ ክ ፡ ቀ ፡ ን ፡ ኀደግ ፡ ባረክ ፡ ያቀ ፡ አንተ ፡ ኩነ ፡ ንሕነ ።

**ተውኅጠ** ፤ ተዋጠ ፡ ሰጠመ ፡ ዘቀጠ ። ዘኢይትወኀጥ ፡ (ኢዮ ፡ ፲፰ ። ሔኖ ፹፫ ፡ ፬) ።

**ውኁጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ኅጥ)** ፤ የተዋጠ ፡ የሰጠመ ፡ የተጐረሰ ፡ የተበላ ።

**ውኅጠት ፤ (ኣ ፡ ጥ)** ፤ መዋጥ ፡ አዋዋጥ ፡ ውጦሽ ።

**ወኀየ ፤—ኀበኘ ፤—ዋሕየ ፡ ዋሐየ ።**

(ጥ) **ወጥሐ ፤ ሖት ፤ (ወጥሐ ፡ ይዌጥሕ ፡ ይወጥሕ ። ዐረ ፡ ጠሐ)** ፤ መከመር ፡ መቈለል ፡ ማስተካከል ፡ መሰደር ፡ መደርደር ፡ ማነባበር ፡ አንዱን ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ማኖር ፡ ማድረግ ። ወጣሕክ ፡ ዕፀወ ፡ ዲበ ፡ እሳት ። ይዌጥሑ ፡ ዝክተ ፡ ዘነመዱ ፡ ወርእሰኒ ፡ ወሥብሐኒ ፡ ላዕለ ፡ ዕፀው ። ወጥሕዎሙ ፡ ምክዕቢተ ። ይዌጥሕ ፡ ሎሙ ፡ ፍዳሆሙ ፡ ቅድሜሆሙ ። ትዌጥሕ ፡ ተደርባበ ፡ ደበ ፡ ታቦት ፡ (ሚራ ፳ ፡ ፫ ። ዘሌዋ ፡ ፩ ፡ ፰ ። ፬ነገ ፡ ፲ ፡ ፰ ። ሱቱ ፡ ሰብ ፲፬ ፡ ፴፰ ። ዘፀ ፳፮ ፡ ፳፭) ።

**አወጥሐ** ፤ አስከመረ ፡ አስቈለለ ።

**ተወጥሐ** ፤ ተከመረ ፡ ተቈለለ ። ወተወጥሐ ፡ ካዕበ ፡ እመት ፡ (ዘኍ ፲፭ ፡ ፴፭) ።

**ውጡሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ጥሕት)** ፤ የተከመረ ፡ ክምር ፡ ቍልል ፡ ድርድር ፡ ድርብርብ ፡ ንብብር ፡ (ኢያ ፯ ፡ ፳ ። መሳ ፲፭ ፡ ፳) ። ዕፀው ፡ ውጡሓን ። ርቡዕ ፡ ውጡሕ ፡ (ኢሳ ፴ ፡ ፴፫ ። ዘፀ ፴፯ ፡ ፲፰) ።

**ተዋጥሐ** ፤ ተከመረ ፡ ተከማመረ ፤ ተነባበረ ። አሐቲ ፡ ውስተ ፡ ክልኤት ፡ ይትዋጣሕ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ሞጥሕ ፤ ሞጣሕት ፤ (ታት ፤ መዋጥሕ)** ፤ የከምር ፡ ቍንጮ ፡ ከዳን ፤ የላይ ፡ ልብስ ፡ መደረቢያ ። በቁሙ ፡ ልብስ ፡ ተክህኖ ፡ ዝናር ፡ ካባ ፡ ላንቃ ፡ መጐና ጠፊያ ፤ ሠርመዲ ፡ ቀጸላ ፡ (ና ፡ ን ፡ ፰ ፡ ፫) ። መዋጥሕየ ። መዋጥሕ ፡ ዘሰንዱናት ። ወከመ ፡ ሞጣሕት ፡ ትዌልጦሙ ፡ (ሆሴ ፪ ፡ ፫ ። ሉቃ ፳፱ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፻፩) ።

**ሞጥሐ ፤ (ይሞጥሕ)** ፤ አለበሰ ፡ አጐናጠፈ ፡ ሸፈነ ፡ ደረበ ፡ አከናነበ ።

**አሞጥሐ** ፤ አስለበሰ ፤ አስጌጠ ።

**ተሞጥሐ** ፤ ለበሰ ፡ ተጐናጠፈ ፡ ተሸለመ ፡ አጌጠ ። ተሞጥሐ ፡ ሞጣሕተ ፡ ፍዳ ። በጻሕኩ ፡ ኀበ ፡ ዘይለብስ ፡ ልብሰ ፡ ፍዳ ፡ ወይትሞጣሕ ፡ ሞጣሕተ ፡ በቀል ። ንትሞጣሕ ፡ ሞጣሕተ ፡ ብርሃን ፡ (ኢሳ ፶፱ ፡ ፲፯ ። ፲፰ ። ግንዘ ። አፈ ፡ ተ ፲፯ ። አርጋ ፡ ፬) ።

**ሙጣሔ** ፤ መልበስ ፡ መጐናጠፍ ፡ መደረብ ፡ መከናነብ ፤ አለባበስ ፡ ልብሳት ፤ ልባስ ፡ ሽፋን ።

**ወጢጥ ፤ ጦት ፤ (ወጠ ፤ ወጠጠ ፡ ይወጥጥ ፡ ይጠጥ)** ፤ መወጠጥ ፡ (ጥጠ) መወጠጥ ፤ ወጠጤ ፡ ጦ ፡ መኾን ።

**ወጥወጠ** ፤ በቁሙ ፡ ወጠወጠ ፡ ወጥዋጣ ፡ ለማላጋ ፡ ኾነ ። ወጥ ፡ ሠራ ፤ ወጥ ፡ አጠጣ ፡ አሳለፈ ፡ ጠለቀ ፤ ኹሉም ፡ ፀማርኛ ፡ ነው ። (ተረት) ፤ ወጡ ፡ ሳይወጠወጥ ፡ ወገዝክንባቱ ፡ ቂጥ ።

**ወጢን ፤ ኖት ፤ (ወጠነ ፡ ይዌጥን ፡ ይውጥን ፤ እው ፡ ይወጥን ፡ ይጠን ። ዐረ ፡ በደአ)** ፤ መወጠን ፡ መጀመር ፡ አንዘን ፡ እይ ። ወወጠነ ፡ ጸውዖ ፡ ስመ ፡ እግዚ ። እምቅድመ ፡ ትውጥኑ ፡ ዐሊወ ። ንዌጥን ፡ በጽሒፈ ፡ መጽሐፍ ። ንጠንኪ ፡ ዘለፋ ። ኢብዉሕ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይውጥን ፡ ጸሎተ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ፡ (ኩፋ ፡ ፱ ። ዮሴፍ ። ፈላስ ፡ ገ፭ ። መጽ ፡ ምስ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፭ ፡ ፱) ።

**ወጣኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት ፡ ጠንት)** ፤ በቁሙ ፤ የሚጀምር ፡ ጀማሪ ። ወጣኒ ፡ ወፈጻሚ ። መምለኪ ፡ ወጣኒ ። ወጠንት ፡ (መዋሥ ። ቅዳ ። ፊልክ ፡ ፳ ። ደራሲ) ። በወጣኒ ፡ ፈንታ ፡ ውጡን ፡ ይላል ፤ አያስኝም ፡ (ፊልክ ፡ ፯ ። ፶)።

**አውጠነ** ፤ አሶጠነ ፤ አዠመረ ። ተአምኖ ፡ ደቄጥን ፡ ወተወክሶ ፡ ያፈጽም ፡ (አርጋ ፡ ፫) ።

**ተወጥነ** ፤ በቁሙ ፤ ተወጠነ ፡ ተዠመረ ፤ ተበገረ ። ግብአት ፡ ሀገር ፡ በእደ ፡ ፀር ፡ ተወጥነ ፡ በመንግሥት ፡ ልብነ ፡ ድንግል ። ተግሣጽ ፡ ትትዌጠን ፡ እም አስተሐምሞ ። ሐሳብ ፡ ይትዌጠን ፡ እምጥንተ ፡ ተውት ፡ (ታሪ ፡ ግሬ ። አፈ ፡ ድ፴ ። አቡሻ ፡ ፵፯) ።

**ውጡን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ጥንት) ፤ የተወጠነ ፡ የተዠመረ ፡ ኹምር ፡ ውጥን ።

**ውጥንት** ፤ መወጠን ፡ መዠመር ፡ (ጥወዠ) መወጠን ፡ መዠመር ፤ አወጣጠን ፡ አዠማመር ፤ ኹመራ ፤ ዠማሪነት ፡ ኹምርነት ። ለእመ ፡ ኢፈጸሙ ፡ ውጥነቶሙ ፡ በሠናይ ። ውጥነተ ፡ አጽባእ ። እመ ፡ ኮነ ፡ ሞቱ ፡ በውጥነቱ ፡ (አፈ ፡ ተሸ፱ ። ፊልክ ፡ ፻፬ ። ፱) ።

**ውጣኔ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ኹመራ ፡ አዠማመር ፤ (ሙጣን) ፤ መዠመሪያ ። ውጣኔሁ ፡ ለጾም ፡ (አቡሻ ፡ ፴፰) ።

»**ጥንት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፤ ሥር ፡ መሠረት ፡ ምንጭ ፡ መንሻ ፡ መዠመሪያ ፤ አበገኝ ፡ መገኛ ፤ ምክንያት ። ጥንተ ፡ ሖሩ ። ለልብነ ፡ ጥንት ፡ ወኢተፍጻሜት ። በጥንተ ፡ ነገር ፡ ወበደኃሪታ ። ጥንተ ፡ ሕይወቶሙ ፡ (ጥበ፲፱ ፡ ፳፯ ። ቀሌ ። አፈ ፡ ተ፲፫ ። ድ፴) ።

»**ጥንትዮን** ፤—አበቅቴ ፡ ፀሓይ ፤—ሆ ፡ ኘሊንቲዮን ።

**ወጠሰ** ፤ (ጤሰ ፤ ጠየሰ) ፤ አቃጠለ ፡ አንደደ ፡ ለኰሰ ። ነደደ ፡ ተቃጠለ ፤ በግ ፡ ቱግ ፡ አለ ፡ (ገድ ፡ አዳ ፡ ገ፻፴፰ና ፡ ፱) ።

**ወጥስ** ፤ (ዐረ ፡ ወጢስ) ፤ ምድጃ ፡ እቶን ፡ ፉርን ።

**ወይ** ፤ (ዐረ ፡ ዋእ ፤ ወይ ። ሱር ፡ ዋይ ። ዕብ ፡ አይ) ፤ ኀኢስ ፡ አገባብ ። በቁሙ ፤ ወዮ ፡ ወየው ፤ ዋይ ፡ ውይ ፡ አወይ ። የልቅሶ ፡ የሐዘን ፡ የቍጣ ፡ የኀደት ፡ የብስጭት ፡ ቃል ፡ ነው ። ወይ ፡ ሊተ ፤ ወይ ፡ ልየ ፤ ወይ ፡ ለክ ፡ እየለ ፡ እንደ ፡ አሌ ፡ በለ ፡ ይዘምታል ። ኢይብልዎ ፡ ወይ ፡ እግዚእየ ፤ ወይ ፡ እኁየ ፡ (ኤርምያ ፡ ፳፪) ። አሌንና ፡ ሰይን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**ወይ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፤ (ዋዊ ፡ አው) ፡ የሚያማርጥ ፡ ቃል ፤ አውን ፡ እይ ። (ግጥም ፤ ሐዲ ፡ ቴ ፡ ባሲን ፡ የሰቀሉባት) ፡ ወይ ፡ አልተቀደሰ ፤ የባረኩት ፡ ሰው ፡ ንጉሥ ፡ መስቀልዎን ፡ ቢተዉት ፡ ምነው ። ፪ኛም ፡ የምኞትና ፡ የፍላጎት ፤ የአንክሮ ፡ ቃል ፡ ይኾናል ፤ (ግጥምና ፡ ሙሾ ፡ ስለ ፡ ጐንደር ፡ ጥፋት) ፤ ቴዎድሮስ ፡ መጣ ፡ ፀይጉን ፡ አፍጦ ፤ ወይ ፡ መሸሸጊያ ፡ ታናሽ ፡ ቍጥቋጦ ። ተከተሰኝ ፡ ብዬ ፡ ዙሬ ፡ ዙሬ ፡ ሳይ ፤ ወይ ፡ ጥጋብ ፡ ወይ ፡ ኩራት ፡ ጐንደር ፡ ቀረ ፡ ወይ ። ፫ኛም ፡ ያቤቱታ ፡ ቃል ፡ የጥሪ ፡ ተሰጦ ፡ ይኾናል ፤ (ግጥም ፤ የበለው ፡ እንት ፡ ቶማርክ ፡ በመተማ ፡ ሳለች) ፤ ጐዝም ፡ አፋፉ ፡ ላይ ፡ የሚጣራው ፡ ማንው ፤ ወንድሜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወይ ፡ በለው ፡ ወይ ፡ በለው ። ምስጢሩ ፡ እንደ ፡ ላይኛው ፡ ነው ። ፬ኛም ፡ የጥያቄ ፡ ቃል ፡ ይኾናል ፤ ኼደ ፡ ወይ ፡ መጣ ፡ ወይ ።

**ዋየየ** ፤ አዋየ ፡ አስተዛዘነ ፡ አሳወተ ።

**ዋይ** ፤ በቁሙ ፤ ጉዳይ ፡ ግዳጅ ፤ ዋይ ፡ የለሽ ፡ እንዲሉ ። በግእዝ ፡ ግን ፡ እንክሮና ፡ አጋኖ ፡ ምኞት ፡ ይኾናል ። ዋይ ፡ ዜማ ፡ ዘሰማዕኩ ፡ በሰማይ ፡ እመላእክት ፡ (ድጓ) ።

**ወይጦ** ፤ ስመ ፡ ነገድ ፡ በጣና ፡ ዙሪያ ፡ የሚኖር ፡ ጕማሬ ፡ የባሕር ፡ አውሬ ፡ የሚያድን ።

**ወይጠል** ፤ (ላት) ፤ ፊቆ ፡ የፊቆ ፡ ወገን ፡ የበረሓ ፡ እንስሳ ። ድርቃስንና ፡ ጣቢታን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ወይጠል ፡ ወትራ ፡ ወሀየላት ። ወይጠላት ፡ (መቃ ፡ ገ፳ ። ሥር ፡ ጳጕ) ።



ወይጠል ፡

**ወይሌ** ፤ (ዐረ ፡ ወይል ። ሮማ ፡ ዋየል ፤ ድምፅ) ፤ ወይ ፡ ሊቱ ። አደጋ ፡ መቅሠፍት ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ ሐዘን ፡ መርዶ ፤ ልቅሶ ፡ ዋይታ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ዋ ፡ ዋ ፡ ማለት ፤ የልቅሶ ፡ ጩኸት ። ወይሌ ፡ በዲበ ፡ ወይሌ ። ወይሌ ፡ ባዕለ ፡ ናባው ። ሰመኑ ፡ ወይሌ ፡ ወሰመኑ ፡ ሀክክ ። ኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ ይሁበሙ ፡ ወይሌ ፡ ለሰካርያን ፡ ወይቤ ፡ አሌ ፡ ሎሙ ፡ (ሕዝ፯ ፡ ፳፯ ። ኢር፴፭ ፡ ፭ ። ምሳ፳፫ ፡ ፳፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፶) ።

**ወይል** ፤ ስመ ፡ ዕፅ ፡ ሕፃናት ፡ የጠመንዣ ፡ ዕንጨት ፡ የሚሉት ፡ ቁርበቱን ፡ እንደ ፡ ጅና ፡ አውጥተው ፡ ክንጨቱ ፡ ጫፍ ፡ ቈርጠው ፡ እንደ ፡ በሽ ፡ ወትፈው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሲገፉት ፡ እንደ ፡ ቢሩና ፡ እንደ ፡ ሽጉጥ ፡ ቅዛግ ፡ ዷ ፡ ን ፡ የሚል ፤ የሚፈነዳ ።

**ወይለየ** ፤ ጮኸ ፡ አለቀሰ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፤ ውይ ፡ ውይ ፤ ወይለይ ፡ ወይ ፡ ልየ ፡ ዋ ፡ ዋ ፡ አለ ።

**ወይን** ፤ (ብ ፡ አውያን ። ዕብ ፡ ያይን ። ዐረ ፡ ወይን ፤ ጠጅ) ፤ በቁሙ ፡ የተክል ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፡ ሐረጋም ፡ ፍሬው ፡ ከንጨት ፡ ኹሉ ፡ ፍሬ ፡ የሚከብር ፡ ጠጅና ፡ ዐረቂ ፡ የሚኾን ። በግእዝና ፡ ባማርኛ ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ ጫፉ ፡ ዕንጨቱም ፡ ፍሬውም ፡ ጠጁ ፡ ሳይቀር ፡ ኹለንተናው ፡ ኹሉ ፡ ወይን ፡ ተብሎ ፡ ባንድ ፡ ስም ፡ ይጠራል ፤ በዐረብና ፡ በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ወይን ፡ የሚባል ፡ ጠጁ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ተከሉ ፡ ወይነ ። ሐልቦ ፡ አስካል ፡ ውስተ ፡ ወይን ። አውያን ፡ ጸገዩ ። ገብረ ፡ ወይነ ፡ እምፍሬ ። ወይን ፡ ዘገቡር ፡ በእሳት ፤ ጠጅ ፡ (መዝ ፡ ፻፮ ። ኢር፫ ፡ ፲ ። ማሕ፪ ፡ ፲፫ ። ኩፋ ፡ ፯ ።

አብዋ፡ ፫) ። ወይኒ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ የወጣ፡ ስም፡ ይመስላል ።



ወይን፡

**አውየነ**፡ ጠጀ፡ ጠመቀ፡ ረገጠ፡ ወይን፡ አደረገ፡ ዘለሳውን፡ ወይም፡ በታምራት፡ ውሃውን ። ከመ፡ ታውይን፡ ማየ፡ (ስንክ፡ ጥር፳፫ ። ዮሐ፪፡ ፯—፱) ።

**ወክአ**፡—ደከመ፡—ወኪዐ፡ ወክዐ ።

**ወኪብ**፡ ቦት፡ (ወከበ፡ ይወክብ፡ ይክብ ። ዐረ፡ ወከበ)፡ መትጋት፡ መቸኰል፡ ማዘውተር፡ የገመሩት፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፡ አለማቋረጥ፡ ወይም፡ ሌላ፡ ሥራ፡ ጣልቃ፡ አለማግባት ። በኢወኪቦ ቶሙ፡ (ዕር፡ ኢሳ፫፡ ፳፱) ።

**አውከበ**፡ አዋከበ፡ አተጋ፡ አታጋ፡ አስቸኰለ፡ አቻኰለ ።

(ተ) **ወክሐ**፡ ሖት፡ (ወክሐ፡ ይዌክሕ፡ ይወክሕ ። ዕብ፡ ያክሕ)፡ ማውካት፡ ወካም፡ ወከ፡ ወከ፡ ማለት፡ ማቅራራት፡ መደንፋት፡ መፎከር፡ መድረቅረቅ፡ መፈክር፡ መንደቅደቅ ። ይዌክሑ፡ ወይዌውዑ፡ ዘሎ፡ ሰራዊተ፡ መንግሥት፡ (ሥር፡ አዥ) ። ወከተን፡ እይ፡ የዚህ፡ መንቲያ፡ ነው ።

**ወክሕ**፡ ውካታ፡ ድንፋታ፡ ጩኸት፡ ፍጅት፡ ክርክር፡ ሙግት ። ወክሕ፡ ብዙኅ ። መሐደምት፡ ወወክሕ፡ (ዕር፡ ኢሳ፫፡ ፳፪ ። ቲቶ፫፡ ፱) ።

—፡ ትማግጽ፡ ስብከት፡ ኅይለ፡ ቃል ። ዮሐንስ፡ አህድአ፡ እምካልኣኒሁ፡ አንተ፡ ወክሐ፡ እንዘ፡ ይብል፡ እምሳዐሉ፡ ወረደ፡ ቃለ፡ አብ፡ (ድጓ) ።

**አውክሐ**፡ አስደነፋ፡ ውካታ፡ አስደረገ ።

**ተዋክሐ**፡ ተዋካ፡ ተደናፋ፡ ተጯጯኸ፡ ተሟገተ፡ ተከራከረ፡ ተወዳደረ ። ማኅበረ፡ አጋንንት፡ እለ፡ ይትዋክሑ ። ወተዋክሑ፡ በበይናቲሆሙ ። መኑ፡ እንከ፡ ተረፈ፡ ተዋካሒ ። ይትዋክሑኑ፡ ማኅትት፡ ለፀሓይ፡ (ገድ፡ ተክ፡ ሱቃ፡ ፳፪፡ ፳፱ ። ቄር) ።

**ዋክዮ**፡ ዮት፡ (ዋከየ፡ ይዋኪ፡ ይዋኪ ። ወህውሀ)፡ መብራት፡ መጽደል፡ ቦግ፡ ማለት ። እምብዝኃ፡ ብርሃኑ፡ ዋክየት፡ ሀገር፡ (ገድ፡ ተክ) ።

**ውኩይ**፡ (ያን፡ ያት፡ ኪት፡ ክይት)፡ የበራ፡ ብሩህ፡ ጽዱል ። ልብሰ፡ ብርሃን፡ ውኩይ፡ (ገድ፡ ተክ) ።

**አዋከየ**፡ አበራ፡ አስበራ፡ አጸደለ ። በራ፡ ብሩህ፡ ኾነ ። ከዋክብት፡ ዘአዋከዩ፡ አድያማተ ። ሰላም፡ ለሥንኪ፡ ዘአዋከየ፡ መብረቃ፡ ለብሔረ፡ ጽልመት፡ ወጣቃ ። ዘበሥነ፡ ስብከቱ፡ ገዳም፡ ታዋኪ፡ (ገድ፡ ተክ ። ደራሲ ። ድጓ) ።

**ዋካ**፡ ብርሃን፡ ውጋጋን፡ ወገግታ፡ ቦግታ፡ ጸዳል፡ ምዕዛር ። እስመ፡ ፈድፋደ፡ ሠናይ፡ ዋካሁ ። ኢጸዳል፡ ወኢዋካ ። ብርሃን፡ ዘያንጸበርቅ፡ ዋካሁ ። ር እየ፡ ዋካ፡ ወኢርእየ፡ ማኅትተ ። እስመ፡ ዋካ፡ ይእቲ፡ ብርሃን፡ ዘቀዳሚ፡ (ሢራ፴፫፡ ፲፯ ። ሱቱ፡ ዕገዝ፡ ፲፱ ። ፈላስ፡ ገ፳፰ ። አርጋ፡ ፱ ። ጥበ፯፡ ፳፮) ። ስሙ፡ ሀገር፡ በሙንዝ፡ ውስጥ፡ ያለ ።

**ወኪክ**፡ ኮት፡ (ወከ፡ ወከከ፡ ይወክክ፡ ይውክክ፡ ይክክ)፡ መውከክ፡ ወከከ፡ ማለት፡ መደንገጥ፡ መፍራት፡ ማፈግፈግ፡ መራቅ፡ ወደ፡ ኋላ፡ ማለት ። መሳት፡ መሳሳት፡ የማያውቁትን፡ ደፍሮ፡ መናገር፡ መቀባጠር ። መጽሐፍ፡ ግን፡ በወከከ፡ ፈንታ፡ አውከከ፡ ይላል ። አውከኩ፡ እምሃይማኖት ። አውከኩ፡ እምጽድቅ፡ (፩ጢሞ፡ ፩፡ ፮ ። ፪ጢሞ፡ ፪፡ ፲፰) ።

**አውከከ**፡ አስፈራ፡ አስጨነቀ፡ መከራ፡ አሳየ ። ያወከክሙ፡ ለሕዝብ፡ (ኢዮ፲፪፡ ፳፫) ።

—፡ አስቀረ፡ አስታጉለ፡ አስትግሁ፡ እለ፡ አውከኩ፡ (ድጓ) ።

**አውክክና**፡ ስሕተት፡ ድፍረት፡ ደፋርነት ። እስመ፡ በደኃሪ፡ አዝማን፡ ይርሕቁ፡ አሐዱ፡ አሐዱ፡ እምሃይማኖት፡ ወየሐውሩ፡ ድኅረ፡ መንፈሰ፡ እውክክና፡ ወድኅረ፡ ትምህርተ፡ ሰይጣናት፡ (ፊልክ፡ ፻፺፰) ።

**ወክሎ**፡ ሎት፡ (ወከለ፡ ይዌክል፡ ይውክል ። ዐረ፡ ወከለ)፡ መወከል፡ ወኪል፡ ጠበቃ፡ ማድረግ፡ እምኖ፡ መሾም፡ እንደራሴ፡ ማለት ። ተከለን፡ እይ፡ የዚህ፡ ጎር፡ ነው ።

**አወከለ**፡ አዕከለ፡ ወኪል፡ አስደረገ ።

**ተወከለ**፡ በቁሙ፡ ወኪል፡ ኾነ፡ ታመነ፡ ለሺሚው፡ ለወካዩ ። አመነ፡ ታመነ፡ እምነቱን፡ ጣለ፡ በወኪሉ፡ ተስፋ፡ አደረገ፡ ወካዩ፡ ወኪሉን ። ታመነ፡ ማለት፡ ባማርኛ፡ እንደ፡ ሳቢ፡ ዘር፡ ነው፡ ኹለት፡ ያሳያል፡ ለሌላ፡ መታመንንና፡ በሌላ፡ ማመን ። ኪያከ፡ ተወከልኩ፡ እግዚኦ ። ሀሉ፡ ተወኪለከ፡ በእግዚ ። ንሕነ፡ ተወከልናሆሙ ። በተወክሎተ፡ መጻሕፍት፡ (መዝ፡ ፴ ። ምሳ፫፡ ፭ ። ኢሳ፰፡ ፮ ። ሮሜ፲፭፡ ፬) ።

**ውኩል**፡ (ላን፡ ላት፡ ክልት)፡ የተወከለ፡ የታመነ፡ እሙን፡ ሥልጡን፡ ሹም፡ ወኪል፡ ባለቤት፡ አክል ። ውኩላን፡ ሀገር ። መላእክት፡ እለ፡ ውኩላን፡ ብ፡ (ሕዝ፱ ። አፈ፡ ተ፳፫) ።

—፡ ያመነ፡ እማኒ፡ ተአማኒ፡ ተዘላይ፡ ምን፡ አለብኝ፡ ባይ፡ ተስፋዊ፡ ባለፍጹም፡ ተስፋ ። ጻድቅ፡ ከመ፡ አንበሳ፡ ውኩል ። ውኩላን፡ ኢይረሲክሙ፡ በእላንቱ

ቃላት ፡፡ ሰይጣን ፤ ውኩል ፤ በዝንቱ ፤ ግብር ፡፡ ውእቱ ፤ ከነ ፤ ውኩለ ፤ ዲበ ፤ ምግባሩ ፤ (ምሳ፳፰ ፡ ፭ ። ፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፲፭ ። ቀኖ ፡ ኒቅ፱ ። ፈልክ ፡ ፺፻፱) ።

**ትውክልት ፤ ቱክልት ፤ (ቃት)** ፤ በቁሙ ፤ መታመን ፤ እምነት ፤ ትምክሕት ፤ ጽኑ ፤ ተስፋ ፤ አለኝታ ፤ የማይታበል ፤ የማይጠረጠር ፤ የሃይማኖት ፤ ፍሬ ። ትውክልተ ፤ ተስፋ ፡፡ ትውክልተ ፤ ክብሮሙ ፡፡ አኀደግዎ ፤ ትውክልቶ ፡፡ ሃይማኖት ፤ ወቱክልት ፤ ወተፋቅሮ ፡፡ እስመ ፤ ቱክልታ ፤ እግዚ ፤ ውእቱ ፡፡ በእንተ ፤ ሕጹተ ፤ ቱክልቱ ፤ ላዕለ ፤ እግዚ ፤ (ግብ፳፯ ፡ ፯ ። ኢሳ፳፰ ፡ ፱ ። ሚክ፪ ፡ ፳ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ። ፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፭ ። ዮሴፍ) ።

**ትውክልና** ፤ ጥብቅና ፤ ወኪልነት ። ትክልነት ፤ ባለርስትነት ፤ ባለሐዲስኝ ፤ ግን ፤ ቀሩኝነት ፤ ይሉታል ። ወኀደጎሙ ፤ ለእኩያን ፤ ህየ ፤ ውስተ ፤ ትውክልና ፤ እስከ ፤ ዐለተ ፤ ደይን ፤ (መቅ ፡ ወን) ።

**አስተወከለ ፤ (አወከለ)** ፤ አሳመነ ፤ አስታመነ ፤ በተስፋ ፤ አጸና ፤ አቈራኝ ። ተፋቅሮ ፤ በዘሎ ፤ ያስተአምን ፤ ወበዘሎ ፤ ያስተዌክል ፤ (፩ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፯) ።

**አስተዋከለ** ፤ አዋከለ ፤ አወካከለ ፤ አስተማመነ ፤ አጸናና ።

**ወኪ.ዕ ፤ ዖት ፤ (ወክዐ ፡ ይወክዕ ፡ ይክዕ ። ዕብ ፡ ያጋዕ)** ፤ መድከም ፤ መታከት ፤ በሥራ ፤ ብዛት ። ከዐወን ፤ እይ ፤ የዚህ ፤ ጎር ፤ ነው ።

**አውክዐ** ፤ አደከመ ፤ አታከተ ፤ አስቸገረ ፤ አሰለቸ ። አውክዑኒ ፤ እሉ ፤ መስሕታን ፤ (መቃ ፡ ገ፪) ።

**ወኪ.ፍ ፤ ፎት ፤ (ወከፈ ፡ ይዌክፍ ፡ ይክፍ)** ፤ ማውከፍ ፤ እጅ ፤ በጅ ፤ መስጠት ፤ ማቀበል ፤ ማሲያዝ ፤ ማስጨበጥ ፤ ማቅረብ ፤ ማስረከብ ። መጽሐፍ ፤ ግን ፤ በወከፈ ፤ ፈንታ ፤ አውከፈ ፤ ይላል ፤ አያስኝም ። ገልዕ ፤ በዘያወክፉ ፤ ማየ ፤ ኅጻጠ ፡፡ አውክፉ ፤ አይሁድ ፤ ላዕሌሆሙ ፤ ወለዘርዖሙ ፤ ከመ ፤ ኢይፍልሱ ፡፡ ወአውከፈት ፤ አንብዐ ፤ ወሰኃ ፤ (ኢሳ፴ ፡ ፲፬ ። አስቴ፱ ፡ ፳፯ ። ጦቢ፯ ፡ ፲፯) ። ከፍን ፤ እይ ፤ የዚህ ፤ ዘር ፤ ነው ።

**አውከፈ ፤ አስተውከፈ** ፤ አስጠ ፤ አስቀበለ ።

**ተወከፈ** ፤ ተሰጠ ፤ ቀረበ ፤ ተሰጠው ፤ ተቀበለ ። ተሰጭውን ፤ መደብ ፤ አድርጎ ፤ ተቀባዩንም ፤ ያሳያል ። መዐዛ ፤ ሠናይ ፤ ዘይትዌከፍ ፤ ቅድሜሁ ፡፡ ተወከፍነ ፤ እምእዴሁ ፤ ቍርባነ ፡፡ ዘኪያክሙ ፤ ተወክፈ ፤ ኪያየ ፤ ተወከፈ ፤ ወዘኪያየ ፤ ተወክፈ ፤ ተወከፎ ፤ ለዘፈነወኒ ፤ (ኩፋ ፡ ፬ ፡ ፱ ። ማቴ፲ ፡ ፵ ፡ ፵፩) ።

—፤ ወደደ ፤ በቀፈ ፤ ቃቀፈ ። ተወክፈቶ ፤ ነፍስየ ፡፡ ዐይ ፤ ኢይትወከፍ ፤ ወለተ ፤ በጥምቀት ፤ (ኢሳ፵፪ ፡ ፩ ። ፊ ፡ መ ፡ ፭ ፡ ፪) ።

—፤ ሰማ ፤ አመነ ፤ ዕሺ ፤ አለ ፤ ታገሠ ፡፡ ምስጢሩ ፤ ያው ፤ መቀበል ፤ ነው ፤ አይለወጥም ። ይትወከፍ ፤ እዝንክሙ ፤ ቃለ ፤ አፉሁ ፡፡ ተወከፍ ፤ ቃለ ፤ አመትከ ፡፡ እለ ፤ ይትዌከፍዎ ፤ ለአርጌንስ ፡፡ እኪተ ፤ ኢንትዌከፍ ፡፡ ተወከፍ ፤ ሖሮ ፤ ዘመጽአከ ፤ (ኤር፱ ፡ ፳ ። ዮዲ፲፩ ፡ ፭ ። ቄር ፡ እስት ። ኢዮ፪ ፡ ፲ ። ሢራ፪ ፡ ፬) ።

**ተወካፊ** ፤ የሚቀበል ፤ ተቀባይ ። ተወካፊ ፤ ነግድ ፡፡ ተወካፊ ፤ ንስሓ ፤ (ዲይ ፡ ፲ ። ፈ ፡ መ ፡ ፩ ፡ ፯) ።

**ውኩፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ክፍት)** ፤ የተሰጠው ፤ የተቀበለ ፤ ተቀባይ ። የተሰጠ ፤ የተወደደ ፤ ወደው ፤ አሜን ፤ ብለው ፤ የሚቀበሉት ፤ ተሰጭ ። አእመርነ ፤ ከመ ፤ ውኩፍ ፤ ስእለትከ ፡፡ ኢይኩን ፤ ውኩፈ ፤ ቍርባኖሙ ፡፡ በእንተ ፤ ኍልቈ ፤ መጻሕፍት ፤ ውኩፋት ፡፡ ጉባኤያት ፤ ውኩፋት ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፪ ፡ ፶፩) ።

**ውካፌ** ፤ መቀበል ፤ አቀባበል ፤ ቅበላ ። የእምሩ ፤ ውካፌ ፤ ነገሩ ፤ ብዙኃ ፤ ጊዜያተ ፤ (ዮሴፍ) ።

**ሙክፍ ፤ (ፋት)** ፤ መስጫ ፤ ማቅረቢያ ፤ ማቀበያ ፤ መቀበያ ። ሙካፈ ፤ ስእለቱ ፤ ለኢዮብ ፤ (ደራሲ ። አርጋ ፡ ፫) ።

**ተዋከፈ** ፤ ተቀባበለ ፤ ተሰጣጠ ።

**አስተዋከፈ** ፤ አወካከፈ ፤ አሰጣጠ ፤ አቀባበለ ፤ አረካከበ ።

**መስተዋክፍ ፤ (ፍት ፡ ፋን ፡ ፋት)** ፤ የሚያቀባብል ፤ አቀባባይ ። የሚቀባበል ፤ ተቀባባይ ፤ (፩ዜና ፡ ፳፯ ፡ ፲፰) ።

**ወከተ ፤ (ወክሐ)** ፤ ፎከ ፤ ተንጫጫ ፤ አወከ ፤ ውካታ ፤ አደረገ ፤ ግር ፤ ግር ፤ አለ ። መጽሐፍ ፤ ግን ፤ በወከተ ፤ ፈንታ ፤ አውከተ ፤ ይላል ። ወአዘዘሙ ፤ ለሕዝብ ፤ ከመ ፤ ኢያውክቱ ፤ (ኢያ፯ ፡ ፲) ።

**አውከተ** ፤ አስፎከ ፤ አሸበረ ፤ ግር ፤ ግር ፤ አሰኘ ።

**ተዋከተ** ፤ ተጫጨኸ ፤ ተዋከ ፤ ተተራመሰ ። ኢትትዋከት ፤ ምስለ ፤ ሰብእ ፡፡ ኢትትዋከቱ ፤ እስከ ፤ ንሥወጥ ፤ ኀቤክሙ ፤ (አረጋ ፡ ድ፭ ። ዘፀ፳፬ ፡ ፲፬) ።

**ውካታ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፤ የብዙ ሰው ፤ ድምፅ ፤ ቱማታ ፤ ጩኸት ።

**ወለበ ፤ (ትግ ፡ ዘረ ፡ ተመለሰ)** ፤ በቁሙ ፤ ታሸ ፤ ተፈለፈለ ፤ ውልብኝ ፤ ኸነ ፤ ተጠረጠረ ፤ የእሸት ፤ ያሹቅ ። ውልብ ፤ አለ ፤ ዐልም ፤ አለ ፤ ቃይቶ ፤ ጠፋ ፤ ታባ ። ተውለበለበ ፤ የጨርቅ ፤ የምላስ ፤ የገለባ ፤ (ዐማርኛ) ።

**አውለበ** ፤ አወለበ ፤ ዐሸ ፤ ፈለፈለ ። አሳሸ ፤ አስፈለፈለ ።


**ወልብ** ፤ ውልብኝ ፤ የእሸት ፤ ፍሬ ፤ ታሽቶ ፤ ተፈልፍሎ ፤ የማይቃወም ፤ የሚጠረጠር ። የአዕዋፍ ፤ ዘር ፤ ዐንቀኍላል ፤ ከዚያውም ፤ ውስጡ ፤ ፍሬው ፤ እስኪሉ ። ከመ ፤ አንቆቅሖ ፤ ባለው ፤ ከመ ፤ ተረፈ ፤ ወልብ ፤ እንዴል ፤ (ኢሳ፲ ፡ ፲፬) ።

**ወለባ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፤ የእሸት ፤ ገለባ ፤ ፍልፋይ ፤ ጥርጣሬ ፤ ቁረቁንዳ ።

—፤ የራስ ፤ ጌጥ ፤ ማክኪያ ። (ተረት) ፤ ራስ ፤ ተላጭቶ ፤ ወለባ ፤ ልባልባ ፤ ታጥቆ ፤ ዐዘባ ።

**ወሊግ ፡ ጎት ፡** (ወለገ ፡ ይወልግ ፡ ይ ለግ ። ዐረ ፡ ወለጀ) ፡ መውለግ ፡ ማውለግ ፡ መሹለክ ለክ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ መግባት ። ዋልጋ ፡ ዋልጌ ፡ ውላጋ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ልገት ፡ (ታት) ፡** ጉገር ፡ ቅልስ ፡ መተሜታ ፡ ቆሻ ፡ ጉሬ ፡ ሾልክ ፡ ተጉንብሶ ፡ የሚገቡበት ። ልገተ ፡ ዐቃቤ ፡ ቀምሕ ። ወገብረ ፡ ሎቱ ፡ ልገተ ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፰ ። ዮናፀ ፡ ፭) ።



ልገት ፡

**ወሊድ ፡ ዶት ፡** (ወለደ ፡ ይወልድ ፡ ይ ለድ ። ዕብ ፡ ያላድ ። ሱር ፡ ዩሌድ ። ዐረ ፡ ወ ለደ) ፡ መውለድ ፡ ማውጣት ፡ መፍጠር ፡ ማምጣት ፡ ማስገኘት ፡ በባሕርይ ፡ በግብር ። ጊዜ ፡ ለፀኒስ ፡ ወጊዜ ፡ ለወሊድ ። ምድር ፡ ትወልድ ፡ ማዕረ ። ቊጥዓ ፡ ወ መዐት ፡ ይወልዱ ፡ ካሕደ ፡ (መክ፫ ፡ ፪ ። ዕብ፮ ፡ ፯ ። አፈ ፡ ድ፯) ።

—፡ ማደስ ፡ ልጅ ፡ ማድረግ ፡ ልጂ ፡ ማለት ፡ የግብር ፡ የቃል ፡ (፩ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፫ ። ፩ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፭ ። ፊልሞ ፡ ፲) ። ደግመ ፡ ወለዱክሙ ፡ እማይ ፡ ወእመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ቀሌ) ።

**ወላዲ ፡ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፡** የሚወልድ ፡ ወላጅ ፡ አስገኝ ፡ አባት ፡ ፈጣሪ ። ወላዲሃ ። ወላዴ ፡ ሕ ይወት ። ወላዲ ፡ ሥን ። ወላዲትክሙ ። ወላዲተ ፡ አ ምላክ ፡ እናት ። ወላድያን ፡ (ሚራ፳፪ ፡ ፬ ። ኪዳ ። ጥ በ፲፫ ፡ ፫ ። ኤር፳፯ ፡ ፲፪ ፡ ቁር ። ዘዳ፳፱ ፡ ፲፯) ።

**ወላድ ፡ (ዳት) ፡** በብዙ ፡ የምትወልድ ፡ ሴት ፡ መካን ፡ ያይደለች ። ወላድ ፡ ስእነት ፡ ወሊደ ። ወላድ ፡ ተቀሥፎቱ ፡ ዘትነብር ፡ በምንዳቤ ፡ (፩ነገ ፡ ፪ ፡ ፭ ። ቅኔ) ።

**አውለደ ፡** አስወለደ ፡ አዋለደ ፡ እርጉዚቱን ፡ ዐ ገዛ ፡ ረዳ ። አኮሁ ፡ አነ ፡ ዘአወልድ ። ሶበ ፡ ታወልዳ ሆን ፡ ለዕብራውያት ፡ ወእመሰ ፡ አንስት ፡ አውልደሃ። ኢመፍትው ፡ ውስተ ፡ ዳዕረ ፡ ወላዲት ፡ ናውልዶ ፡ ለ እግዚ ፡ ቃል ። አዳም ፡ አውለደ ፡ ሴትሀ ፡ (ኢሳ፷፯ ፡ ፱ ። ዘፀ፩ ፡ ፲፯ ። ቁር ። ዮሴፍ) ።

**መወልድ ፡ (ድት ፡ ዲት ፡ ዳን ፡ ዳት) ፡** የሚያስወልድ ፡ አዋላጅ ፡ አዋላጅ ፡ ሐኪም ፡ (ዕር ፡ ኢሳ ፷፩ ፡ ፲፱) ። ስሎሟ ፡ መወልዲት ። መወልዳተ ፡ ዕብራ ውያት ፡ (ታም ፡ እየ ። ዘፀ፩ ፡ ፲፭—፳፩) ።

**ሙላድ ፡ (ዳት) ፡** መውለጃ ፡ ማስለጃ ፡ ማዋ ለጃ ፡ መወለጃ ፡ መገኛ ፡ መውጫ ፡ ቤታ ፡ ማሕፀን ፡ መ ገምሬያ ፡ ካባት ፡ ኹለተኛ ፡ ከናት ፡ የሚወለዱበት ። ብ ሔረ ፡ ሙላድኪ ። ምድረ ፡ ሙላዱ ። ዘርዐ ፡ ሙ ላድ ። ሙላዳት ፡ (ሩት፱ ፡ ፲፩ ። ኤር፳፱ ፡ ፲ ። ቅዳ ፡ ቁር ። ሔኖ፸፪ ፡ ፩) ።

**ተወልደ ፡** ተወለደ ፡ ከባት ፡ ከናት ፡ ወጣ ፡ ተ ከፈለ ። ዘተወልደ ፡ ወአኮ ፡ ዘተገብረ ። ሕፃን ፡ ተወ ልደ ፡ ለነ ። ወተወሊዶ ፡ (ኒቅ ። ኢሳ፱ ፡ ፯ ። ማቴ፪ ፡ ፩) ።

—፡ ልጅ ፡ ኾነ ፡ ተባለ ፡ በልጅ ፡ ስም ፡ ተጠራ ፡ ታደሰ ። እምእግዚአብሔር ፡ ተወልዱ ። ዘኢተወልደ ፡ ዳ ግመ ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፲፫ ። ፫ ፡ ፫) ።

—፡ ተገኘ ፡ መጣ ፡ ተፈጠረ ። ይትወለድ ፡ ብሩር ፡ እ ምጸበለ ፡ ምድር ። በተካሕዶ ፡ ይትወለድ ፡ ለነ ፡ ብ ቍዕ ። እምስካር ፡ ይትወለድ ፡ ምርዓት ፡ ወዘሙት ። እምልብ ፡ ይትወለድ ፡ ኀጢአት ። እምዘቲ ፡ ግብር ፡ ይትወለድ ፡ ቀትል ። ሰዓል ፡ ይትወለድ ፡ እምነ ፡ ቍር ፡ (ሔኖ፷፭ ፡ ፯ ። ቁር ፡ ጸላ ። ቀሌ ። ፈ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ። ፳፱ ፡ ፩ ። አዋል) ።

**ተወላዲ ፡** የተወለደ ፡ ተወላጅ ፡ ልጅ ። አይ ቴኬ ፡ ሀሎ ፡ ዝየ ፡ ፍቁር ፡ ወላዲ ፡ ወአይቴ ፡ ሀሎ ፡ ዘ መድ ፡ ወላድያን ፡ ወተወላዲ ። አብ ፡ ወላዲ ፡ ወኢ ተወላዲ ፡ ወልድ ፡ ተወላዲ ፡ ወኢወላዲ ፡ (ግንዘ ። አትና) ።

**ውሉድ ፡ (ዳን ፡ ዳት ፡ ልድ) ፡** የተወለደ ፡ ውልድ ፡ ልጅ ፡ ውላጅ ፡ ከባሕርይ ፡ የተከፈለ ። እሁብ ፡ ውሉደ ፡ እምኔክ ። ትረክብ ፡ ሳራ ፡ ውሉደ ። መኑ ፡ ውሉድ ፡ ዘኢይጌሥጾ ፡ አቡሁ ። ውሉዳነ ፡ ልሂቃነ ፡ ሰብእ ። ወትክውን ፡ ከመ ፡ ውሉደ ፡ ልዑል ። ዘያፈ ቅር ፡ ውሉዶ ፡ ልጁን ፡ (ዘፍ፲፯ ፡ ፲፮ ። ፲፰ ፡ ፲ ። ዕብ ፲፪ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ሠኔ፫ ። ሢራ፱ ፡ ፲ ። ፴ ፡ ፩) ። ልዑል ፡ ምጡቅ ፡ ረዥም ፡ ታላቅ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ውሉድ ፡ እምአእላፍ ፡ ይላል ፡ (ማሕ፭ ፡ ፲) ። ባለቅኔዎችም ፡ ባለ ብሉዮችም ፡ ኀባቡን ፡ እንደ ፡ ቀደስ ፡ ቤት ፡ አዋብቀው ፡ ፍችውን ፡ ጎሩይ ፡ ይሉታል ፡ ሰብራይስጡ ፡ ግን ፡ ዳጉል ፡ ሜርባባ ፡ ዐረቡም ፡ ሙዕሊሞን ፡ በይን ፡ ሬብወቲን ፡ ይ ላል ፡ እንደ ፡ ባንዲራና ፡ እንዳላማ ፡ በብዙ ፡ ሰራዊት ፡ መካከል ፡ በተራዳ ፡ ላይ ፡ የቆመ ፡ የተንጠለጠለ ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የተሰቀለ ፡ ስቁል ፡ ማለት ፡ ነው ። ኋለ ታሊን ፡ እይ ።

**ወልድ ፡ (ብ ፡ አውላድ ፡ ውሉድ ፡ ደ ቂቅ) ፡** ልጅ ፡ ተባት ፡ ወንድ ። ድንግል ፡ ትፀንስ ፡ ወ ትወልድ ፡ ወልደ ። ኢያእመራ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ወለ ደት ፡ ወልደ ፡ ዘበኵራ ። ሀበኒ ፡ ውሉደ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ እመውት ፡ (ማቴ፩ ፡ ፳፫ ፡ ፳፭ ። ዘፍ፴ ፡ ፩) ። ስም ነቱ ፡ ማእከላዊ ፡ ነው ፡ ሳይገነውም ፡ ሳላይገነውም ፡ ይነገ ራል ። ወልድ ፡ መባል ፡ ግን ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ በባሕርይ ፡ በግብር ፡ ወይም ፡ በጸጋ ፡ ግብርና ፡ ጸጋ ፡

አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። እንዳረቡ ፡ ውሳድ ፡ አውሳድ ፡ በ ማለት ፡ ፈንታ ፡ ውሉድ ፡ ብሎ ፡ ልጆች ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ደቂቅ ፡ በልማድ ፡ ነው ። እንጂ ፡ ንባቡም ፡ ፍችውም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ እያሰኘም ፡ አንስትን ፡ ቢጸና ፡ ፀርን ፡ እያ ፤ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

**ወልደ ፡ እግዚ** ፤ ሥግው ፡ ቃል ፡ ክርስቶስ ። መልአክ ፡ (ማቴ፩ ፡ ፪ ። ዳን፫ ፡ ፳፭) ።

**ውሉደ ፡ እግዚ** ፤ መላእክት ፡ ጻድቃን ፡ ምእመናን ፡ (ኢዮ፩ ፡ ፮ ። ሮሜ፰ ፡ ፲፬) ።

**ውሉደ ፡ አዳም** ፤ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ (ሚራ፵ ፡ ፩) ።

**ውሉደ ፡ አቡነ ፡ ተክ ፡ ሃይ** ፤ መነኮሳት ፡ አርድእት ፡ በዶብ ፡ በትምርት ፡ የተወለዱ ፡ (ስንክ ፡ ሐም ፲፱) ።

**ውሉደ ፡ አርጤምስ** ፤ መምለክያን ፡ ጣዖት ፡ አርጤምስን ፡ ብቻ ፡ የሚያመልኩ ።

**ውሉደ ፡ ቤት** ፤ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ አሽከሮች ፡ አገልጋዮች ፡ የቤት ፡ ውልዶች ።

**ውሉደ ፡ ብርሃን** ፤ ፀዋቶች ፡ ጻድቃን ፡ መናኒያን ፡ (ሉቃ፲፮ ፡ ፰) ።

**ወልደ ፡ ሀጕል** ፤ ጥፋት ፡ የሚገባው ፡ ለጥፋት ፡ የተገባ ፡ መጥፎ ፡ ርጉም ፡ (ዮሐ፲፯ ፡ ፲፪) ።

**ውሉደ ፡ ሕይወት** ፤ መውተው ፡ በክብር ፡ የሚነሡ ፡ ዳግመኛ ፡ ሊሞቱ ፡ የማይቻሉ ፡ (ሉቃ፳ ፡ ፴፮) ።

**ወልደ ፡ ኀይል** ፤ ኀይለኛ ፡ ፀዋቂ ፡ ባለአእምሮ ፡ የጦር ፡ ሰው ፡ (፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯) ።

**ውሉደ ፡ ጥምቀት** ፤ ክርስቲያኖች ፡ ሀብተ ፡ ወልድና ፡ ስመ ፡ ክርስትና ፡ ያላቸው ፡ (አርጋ) ።

**ውሉደ ፡ መንግሥት** ፤ ክብርቴዎች ፡ ባላባቶች ፡ መደበኞች ፡ (ማቴ፰ ፡ ፲፪) ።

**ወልደ ፡ ሞት** ፤ ሞት ፡ የሚገባው ፤ ይሞት ፡ በቃ ፡ የተፈረደበት ፡ (፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፴፩) ።

**ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው** ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሰው ፡ የአዳም ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ (ሕዝ፪ ፡ ፩) ።

—፤ ሥግው ፡ ቃል ፡ ዳግማይ ፡ አዳም ፡ (ማቴ፲፩ ፡ ፲፱ ። ፳፭ ፡ ፴፩) ። ዳግመኛም ፡ ገብር ፡ ቍልዔ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ወልድ ፡ ይላል ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ግብ፫ ፡ ፲፫ ፡ ፳፮ ። ፬ ፡ ፳፯ ፡ ፴) ።

» **ልድ** ፤ ውላጅ ፡ የቤት ፡ ውልድ ፡ የባሪያ ፡ ልጅ ። **ልደ ፡ ቤቱ** ፡ (ዘፍ፲፯ ፡ ፳፫ ። ኤር፪ ፡ ፲፬) ።

° **ልድ** ፤ (**ዐረብ**) ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ ልዳ ፡ የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መቃብር ።

**ወለድ** ፤ **ወለት** ፤ (**ብ ፡ አዋልድ**) ፤ ሴት ፡ ልጅ ፡ ልጃገረድ ፡ ወይም ፡ የተዳረች ። **በከመ ፡ እም ፡ ከማሁ ፡ ወለታ ። ወለተ ፡ ወልድከ ፡ አው ፡ ወለተ ፡ ወለትከ ። አዋልደ ፡ አዋልዲሁ** ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፵፬ ። ዘሌ ፲፰ ፡ ፲ ። ዘኍ፳፯ ፡ ፯) ።

—፤ ሕዝብ ፡ ባላገር ፡ ያገር ፡ ልጅ ፡ ተቀማጭ ፤ **ወለተ ፡ ጽዮን ። ይንግል ፡ ወለተ ፡ ግብጽ** ፡ (ኢሳ፲ ፡ ፴፪ ። ኤር ፵፮ ፡ ፲፩) ።

—፤ ገጠር ፡ ታናሽ ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ሰበካ ። **ቄናት ፡ ወአዋልዲሃ** ፡ (፩ዜና ፡ ፪ ፡ ፳፫ ። መሳ፩ ፡ ፳፯) ።

—፤ ገረድ ፡ ደንገጥር ፡ ሴት ፡ አሽከር ፡ ብላቴና ፡ ባሪያ ። **አንሶበዋ ፡ አዋልዲሃ ፡ ወፈነወት ፡ ወለታ ። ትልዊየን ፡ ለአዋልድየ** ፡ (ዘፀ፪ ፡ ፭ ። ሩት፪ ፡ ፰) ።

**አዋልድ** ፤ የሊቃውንት ፡ መጻሕፍ ፡ ድርሳናት ፡ ተግሣጻት ፤ ንባባቸውና ፡ ምስጢራቸው ፡ እንደ ፡ ዐጽቅ ፡ ኹሉ ፡ ከብሉይ ፡ ከሐዲስ ፡ የወጣ ፡ (ማሕ፮ ፡ ፰) ።

**ወልድና** ፤ ልጅነት ፡ ልጅ ፡ መኾን ። **ዝግም ደተ ፡ ለብና ፡ ወወልድና** ፡ (ፋ ፡ ን ፡ ፳፱ ፡ ፮ ። አፈ ፡ ድ፱ ፡ ፀ) ።

» **ልደት** ፤ (**ታት**) ፤ በቁሙ ፡ ውልደት ፡ መውለድ ፡ መወለድ ፡ አወላለድ ፡ ትውልድ ። **ዕለተ ፡ ልደቱ ። በልደቱ ፡ እምብእሲት ። ከመ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ልደቶሙ ፡ ለደቂቅ ፡ ኖኅ** ፡ (ማቴ፲፱ ፡ ፮ ። ቈር ። ዘፍ፲ ፡ ፩) ።



ልደት ፡

—፤ መውጣት ፡ መብቀል ፡ መገኘት ፡ መፈጠር ፡ ፍጥረት ። **ልደተ ፡ ወርኅ ። ከመ ፡ ልደተ ፡ ንጻሬ ፡ እምዐይን ፡ ወከመ ፡ ልደተ ፡ አምሳለ ፡ መልክእ ፡ እመጽሔት ። ወልደተ ፡ ዓለም ፡ ሲድኒን ። ሕሪት ፡ ዘልደት** ፡ (መር ፡ ዕው ። ያስ ፡ ዘእል ። ጥበ፩ ፡ ፲፱ ። ዘፋ ፡ ፩) ።

—፤ ዘር ፡ የትውልድ ፡ ሥር ፡ ሐረግ ። **መጽሐፈ ፡ ልደት ። ኍልቈ ፡ ልደት** ፡ (ማቴ፩ ፡ ፩ ። ፩ዜና ፡ ፯ ፡ ፱) ።

**ልደት** ፤ ልጅነት ፡ ልጅ ፡ መኾን ፡ ልጅ ፡ መባል ፡ መታደስ ። **ዳግም ፡ ልደት** ፡ (ቲቶ፫ ፡ ፭ ። ማቴ፲፱ ፡ ፳፰) ። የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሊቃውንት ፡ ልደትን ፡ አምልተው ፡ አስፋትው ፡ ሲተረጕሙና ፡ ሲፈቱት ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ይዘረዝሩታል ። ልደት ፡ በ፪ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ በባሕርይ ፡ በግብር ፡ የባሕርይ ፡ ልደት ፡ የባሕርይ ፡ አባትን ፡ የባሕርይ ፡ እናትን ፡ መስሎ ፡ ተካክሎ ፡ ነው ፡ መብለጥና ፡ ማነስ ፡ የለበትም ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ጌታችንም ፡ በባሕርይ ፡ ልደቱ ፡ መንቲያና ፡ ታናሽ ፡ መባይ ፡ ተከታይ ፡ ወንድም ፡ ስለሌው ፡ ላባቱም ፡ ለናቱም ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ እንጂ ፡ በኵር ፡ አይባልም ፡ በሰውነቱም ፡ በምላክነቱም ፡ ባሕታዊ ፡ ልደት ፡ ነውና ፡ ከዋሕድና ፡ በቀር ፡ ብኵርና ፡

የሰውም ፤ ብንሰጠውም ፡ እንደ ፡ ዋሕድናው ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘቡ ፡ ስላልኾነ ፡ ዕሺ ፡ ብሎ ፡ አይቀበለንም ። የግብር ፡ ልደት ፡ ግን ፡ ለባሕርይ ፡ ልደት ፡ ምሳሌ ፡ ነውና ፤ ምሳሌ ፡ ከአማናዊ ፡ እንዲያንስ ፡ እንዳይተካከል ፡ የግብር ፡ ልደትም ፡ ከባሕርይ ፡ ልደት ፡ አይተካከልም ፤ በስም ፡ ብቻ ፡ ልደት ፡ በመባል ፡ ይተካከለዋል ። አወላለዱም ፡ ወዘእኔ **በሰ ፡ ካሕድ ፡ ዘየዐቢ ፡ ይባርክ ፡ ለዘይንእስ ፤** እንዳለው ፡ ኹሉ ፡ (ዕብ ፯ ፡ ፯) ፤ ከሚበልጠውና ፡ ከሚቀድመው ፡ ተባርኮ ፡ ተሹሞ ፤ ሀብተ ፡ ወልድና ፡ ስመ ፡ ወልድና ፡ ተቀብሎ ፡ መውለዱና ፡ መወለዱ ፡ ሳይኖር ፡ በመስጠትና ፡ በመቀበል ፡ ብቻ ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ መባባል ፡ ነው ። ናታንና ፡ ዳዊት ፡ በትንቢት ፤ **ለኔ ፡ እከውኖ ፡ አባሁ ፡ ወውእቱ ፡ ይከውነኒ ፡ ወልድየ ፡፡ (ወልድየ ፡ አንተ) ፡ ወአነ ፡ ዮም ፡ ወለድኩከ ፡፡ ውእቱ ፡ ይብለኒ ፡ አቡየ ፡ አንተ ፡ ወአነሂ ፡ በኵርየ ፡ እሬስዮ ፡** ያሉት ። መልአኩም ፡ በብሥራት ፤ **ዘኒ ፡ ይትወለድ ፡ እምኔኪ ፡ ቅዱስ ፡ ውእቱ ፡ ወይሰመይ ፡ ወልደ ፡ እግዚ ፡ ልዑል ፡** ያለው ። ሊታወቁትም ፡ ከዚህ ፡ አያይዘው ፡ **ወንሰምዮ ፡ ወልደ ፤ ናሁ ፡ ከነ ፡ ለነ ፡ ወልደ ፡ በሀብተ ፡፡ ወተሠርዐ ፡ ወልደ ፡ እግዚ ፡ በኀይል ፡ ቅብዐ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡፡ እመበ ፡ ኵበይነ ፡ ልደቶ ፡ እንተ ፡ ከማነ ፡ በመኑ ፡ ተመሲለነ ፡ ንከውን ፡ ውሉደ ፡ እግዚ ፡ በመንፈስ ፡** ያሉት ፡ በዚህ ፡ በግብር ፡ ልደት ፡ ነው ። የግብር ፡ ወይም ፡ የጸጋ ፡ ልደት ፡ ከጸጋ ፡ ወንድሞች ፡ ከተወራራሾች ፡ ቢያስተካክል ፡ እንጂ ፡ ከወላጁና ፡ ከሠያሚ ፡ አያስተካክልም ፤ ይኸውም ፡ **ዘቀደሶ ፡ አብ ፡ ወፈነዎ ፡፡ እስመ ፡ አብ ፡ የዐብየኒ ፡** ባለው ፡ ይታወቃል ፡ (ሮሜ ፰ ፡ ፲፬—፲፯ ። ዮሐ ፲ ፡ ፴፮ ። ፲፬ ፡ ፳፰ ። ፳ ፡ ፲፯) ። **ወረሰየነ ፡ ዕሩያነ ፡ ምስሌሁ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡፡ ይቤ ፡ እነግሮሙ ፡ ስመከ ፡ ለአኀውየ ፤ ዝኒ ፡ ከመ ፡ ያግህድ ፡ ዕበየ ፡ ክብር ፡ ዘወሀቦሙ ፡ ከመ ፡ ይትዓረይዎ ፡፡ ሰሊሁ ፡ ርእሰ ፡ ወንሕነ ፡ አባል ፡ ወሱቱፋኒሁ ፡ በተዋርሶ ፡** (ቄር ። አፈ ፡ ድ፱ ። ፯) ። የግብር ፡ ልደትም ፡ የሚፈጸም ፡ ኋላ ፡ በትንሣኤ ፡ ነው ፤ እስከዚያ ፡ ዐረቦን ፡ ይባላል ፡ (ሮሜ ፰ ፡ ፳—፳፬ ። ፪ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ። ፭ ፡ ፭) ። ይኸውም ፡ ሲታወቅ ፡ ሐዋርያው ፡ ዮም ፡ ወለድኩከን ፡ ኹለተኛ ፡ ስለ ፡ ትንሣኤ ፡ ጠቅሶታል ። ሊቁም ፡ **ወውእቱ ፡ ቀዳሚ ፡ ዘተወልደ ፡ እሙታን ፡** ብሎታል ፡ (ግብ ፲፫ ፡ ፴፫ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ቄር) ። ዐረቦንና ፡ የትንሣኤው ፡ ልደት ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አይባልም ፤ ትርጓሜ ፡ ወንጌል ፡ ግን ፡ እየብቻው ፡ ቈጥሮ ፡ **አርባዕቱ ፡ ልደታቲሁ ፡ ለክርስቶስ ፡** ይላል ። ይኸውም ፡ ቢኾን ፡ የትንሣኤን ፡ ልደት ፡ መባል ፡ እንጂ ፡ አራተኛነትን ፡ አያሳይም ፤ ዐረቦን ፡ እንደ ፡ ፅንስ ፤ ትንሣኤ ፡ እንደ ፡ ልደት ፡ ነውና ።

**ትውልድ ፤ (ዳት) ፤** በቁሙ ፡ ዘር ፡ ልጅ ፡ ባላገር ፡ ተወላጅ ። ሾሉ ፡ **ትውልድ ፡ ዘሥጋ ፡ ወደም ፡፡ ትውልደ ፡ ቃግስት ፡፡ ትውልደ ፡ ሐርቶማን ፡፡ ትውልደ ፡ ዘመድየ ፡፡ ትውልደ ፡ ምድር ፡** (ሚራ ፲፱ ፡ ፲፰ ። ኢሳ ፲፱ ፡ ፳፱ ። ሣ፯ ፡ ፱ ። ዘኍ ፲፯ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ዘዐ ፲፪ ፡ ፵፰) ።

—፤ ወገን ፡ ነገድ ፤ ሐረግ ። በሾሉ ፡ ትውልዶሙ ፡ (፩ዜና ፡ ፯ ፡ ፱) ።

—፤ የሰው ፡ አወላለድ ፡ የዘር ፡ አወራረድ ፡ ኹቅብና ፡ ቍልቍል ፡ የሚቈጠር ፤ በተራ ፡ የሚጣፍ ፡ የሚነገር ፤ የሰው ፡ ዕድሜ ፡ ዘመን ፡ መዋዕል ፤ ተወልዶ ፡ እስኪሞትና ፡ እስኪቀበር ፡ ተሹሞ ፡ እስኪሻር ፡ የሚኖረው ። **እስከ ፡ ሣልስ ፡ ወራብዕ ፡ ትውልድ ፡፡ ትውልድ ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ፡፡ ለብዙኅ ፡ ትውልድ ፡፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡፡ ለትውልዳት ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡** (ዘፀ፳ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፸፩ ። ኢሳ፶፱ ፡ ፳፩ ። ሚራ፴፱ ፡ ፱ ። ሔኖ፹፪ ፡ ፱) ።

**ተዋለደ ፤** በቁሙ ፤ ተራባ ፡ ተባዛ ። **ይትባዝኁ ፡ ወይትዋለዱ ፡፡ ኢይትዋለዱ ፡** (ኢዮ፴፱ ፡ ፬ ። ገድ ፡ ተክ) ። በወለደ ፡ ፈንታ ፡ ተዋለደ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ንእሳትኒ ፡ ያውስባ ፡ ወይትዋለዳ ፡፡ ወእትዋለድ ፡ እምኔሃ ፡** (፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ። ዘፍ፴ ፡ ፫) ።

**አስተዋለደ ፤** አዋለደ ፡ አወላለደ ፤ አባዛ ፡ አራባ ። **ወያስተዋልዶ ፡ ለእንስሳከ ፡** (ዘዳ፳፰ ፡ ፲፩ ። ፴ ፡ ፱) ።

**ወልውሎ ፤ ሎት ፤ (ወልወለ ፡ ይወለውል ፡ ይወልውል ። ወሊል ፡ ወለ ፤ ወለለ) ፤** በቁሙ ፤ መወልወል ፤ መሰንገል ፡ (ዐማርኛ) ። ወልወል ፡ ወለል ፤ ወልታ ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

—፤ መዋለል ፡ መገፋት ፡ መናጥ ፤ መወዘወዝ ፤ ውል ፡ ውል ፡ ኸው ፡ ኸው ፡ ማለት ፤ የውሃ ፡ የዛፍ ፡ የነፋስ ። መወላወል ፡ መጠራጠር ፤ ምልስ ፡ ቅልስ ፡ ማለት ፤ መውሰብሰብ ፤ የኅሊና ፡ የእግር ፡ የምላስ ፤ ሎለወን ፡ እይ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወልወለ ፡ ፈንታ ፡ ተወላወለ ፡ ይላል ፤ ባማርኛ ፡ ጠረጠረና ፡ ተጠራጠረ ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ግእዙን ፡ እንዳማርኛው ፡ አስኪደታል ። **ዝንጉዓን ፡ እለ ፡ ይትወላወሉ ፡፡ ኅሊና ፡ ዘይትወላወል ፡፡ እእጋር ፡ እለ ፡ ይትወላወላ ፡ ለገቢረ ፡ እከይ ፡፡ ላህበ ፡ ነድ ፡ እንዘ ፡ ይትወላወል ፡ ወያንሶሱ ፡ ውስቴቶሙ ፡** (አፈ ፡ ተ፳፫ ። አርጋ ። ምሳ፮ ፡ ፲፰ ። ጥበ፲፱ ፡ ፳) ።

**ወልዋሊ ፤** ወልዋይ ፤ ወላዋይ ፤ ወለብላባ ።

**አወልወለ ፤** አዖለወለ ፤ አስጠረጠረ ። አወላወለ ፡ አጠራጠረ ፤ አወጣ ፡ አወረደ ፡ አመላለሰ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአወልወለ ፡ ፈንታ ፡ አስተወላወለ ፡ ይላል ። **ያስተወላውላ ፡ ለምክረ ፡ ልቡ ፡፡ ወውእቱ ፡ ገጾ ፡ አስተወላወለ ፡** (ሚራ፴ ፡ ፯ ። መክ፲ ፡ ፲) ።

**አወልዋሊ ፤ መወላውል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤** የሚያወላውል ፡ አወላዋይ ፤ አጠራጣሪ ። **ኢይሔር ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፤ ወኢይባእ ፡ ውስተ ፡ አብያት ፤ ከመ ፡ ኢይምሳእ ፡ ራእዩ ፡ ወእዘኒሁ ፡ እምነ ፡ መወላውላተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡** (ፊልክ ፡ ፲፻፲) ።

**ተወልወለ ፤** ተወለወለ ፡ ተሰነገለ ፤ ጠራ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ውልዉል ፤** የተወለወለ ። የሚቀልል ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ የሚል ፡ ቅብዝብዝ ። **ውልዉለ ፡ ነፋስ ፡** (አቋል) ።

**ውልዋሌ**፤ ውልወላ። መዋለል፤ መወላወል፡ ጥርጥር፤ ውዝወዛ፡ ውዝውዝታ፡ ፍርሀት፡ ፍጥንት። ውልዋሌ፡ ወሑሰት፡ ነፍስ። እስመ፡ ሰዛቲ፡ በዓል፡ በውልዋሌ፡ ገበርክምዋ። በደመ፡ በግዕ፡ ዘበል ዕዎ፡ ደቂቀ፡ እስራኤል፡ በውልዋሌ፡ አመ፡ ሌሊተ፡ ፀአቶሙ፡ (ፊልክ፡ ፶፱። ኩፋ፡ ፵፱። መጽ፡ ምስ። ዘ፶፻፪፡ ፻፵)።

**ወልጦ፤ ጦት፤ (ወለጠ፡ ይዌልጥ፡ ይወልጥ)**፤ መለወጥ፡ መተካት፡ አንዱን፡ በሌላ፡ ወይም፡ ሌላ፡ ማድረግ። ኢትወልጥ፡ ዐርከ። ኢትወልጥ፡ ግዕዘከ። ወልጡ፡ አልባሲክሙ። እመ፡ ይዌልጥ፡ ሐራውያ፡ ማእሰ፡ ወጸጕሮሂ፡ ከመ፡ ፀምር፡ (ሚራጺ፡ ፻፳። ፴፡ ፳፱። ዘፍ፴፭፡ ፪። ኩፋ፡ ፴፯)።

**ወላጢ፤ (ጢት፡ ጥያን፡ ያት)**፤ የሚለውጥ፡ ለዋጭ፤ መንዛሪ፡ ቸርቻሪ።

**መወልጥ፤(ጣን፡ ጣት)**፤ ዝኒ፡ ከማሁ፤ መንዛሪ፤ አንዱን፡ ሰብዙ፡ ብዙውን፡ ባንድ፡ የሚለውጥ። ገፍትዐ፡ ማእዳቲሆሙ፡ ለመወልጣን፡ (ማቴ፳፩፡ ፲፪። ማር፲፩፡ ፲፭። ዮሐ፪፡ ፲፬)።

**ተወለጠ**፤ተለወጠ፡ ተተካ፤ ሌላ፡ ኾነ። ተወለጠ፡ ርእየተ፡ ገጹ። ተወለጠ፡ ወክነ፡ ከመ፡ መልአክ። ያንሶሱ፡ ማእከለ፡ ሰብእ፡ ተወሊጦ፡ (ዳን፫፡ ፲፱። ዕር፡ ኢሳ፲፱፡ ፴። ዮሴፍ)።

**ውሉጥ፤(ጣን፡ ጣት፡ ልጥ)**፤ የተለወጠ፡ ልውጥ፤ ልዩ፡ ሌላ። ኢውሉጥ፡ እምኔነ፡ ዘእንበለ፡ ኀጢአት። በቀኖናት፡ ውሉጣት፡ (ተረ፡ ቄር። ፈ፡ መ፡ ፳፡ ፫)።

**ውላጤ**፤ (ጥ፡ ለ፡ ወ) መለወጥ፤ አለዋወጥ፡ ልወጣ፤ ልውጥንት። ውፁእ፡ እሚጠት፡ ወእምውላጤ። ንሕነ፡ ክሃሊያን፡ ለውላጤሁ፡ (ቄር። ዮሴፍ)።

**ተዋለጠ**፤ ተላወጠ፡ ተለዋወጠ፤ ተወኻጀ። በእንተ፡ ተዋልጦ። እስመ፡ እግዚ፡ ተዋለጠ፡ ዓለመ፡ በክርስቶስ። ቦቱ፡ ተዋለጠነ፡ (ፋትፀ፡ ፯። ፪ቆሮ፡ ፭፡ ፲፱። ቄር፡ ጸላ)።

**ተዋልጦ**፤ መለዋወጥ፡ መቀያየር፤ መፈራረቅ። በእንተ፡ ምክንያተ፡ ተዋልጦ፡ ጠባይዐ፡ ዕጓለ፡ መሕያው፡ (ፈ፡ መ፡ ፳፡ ፫)።

**ተውላጥ፤(ጣት)**፤ መለወጥ፡ መለዋወጥ፤ ውላጤ፡ (ያዕ፩፡ ፲፯)። ከመ፡ ተውላጥ፡ ዘረከባ። ተውላጣት። አልቦቱ፡ ቱስሕት፡ ወኢተውላጥ፡ ግሙራ፡ (አፈ፡ ተ፲፯። ፴፪። ሃይ፡ አበ፡ ብን)።

—፤ለውጥ፡ ዋጋ፡ ቤዛ። ለዐርክ፡ ምእመን፡ አልቦቱ፡ ተውላጥ። ኢወርቅ፡ ሤጡ፡ ወኢብሩር፡ ተውላጡ። ረሰይኩ፡ ለከ፡ ተውላጠከ፡ ግብጸ። ተውላጠ፡ ዓለም፡ (ሢራ፮፡ ፲፭። ድጓ። ኢሳ፵፫፡ ፫። ሔኖ፳፡ ፩)።

**ተውላጠ፤(ዐቢይና፡ ደቂቅ፡ አገባብ)**፤ ስለ፤ ምስጢሩ፡ ስውጥን፡ አይለቅም። ተውላጠ፡ ሴሰይዎ፤ ስለ፡ መገቡት፡ (ስንክ፡ መጋ፳)። ደቂቅ፡ ሲኾን፡ በብትን፡ ይገባል። ተለዐለ፡ ሞገስ፡ ስሙ፡ ተውላጠ፡ ጻማሁ፡ ወሕማሙ። ተውላጠ፡ ዝ፡ (ስንክ፡ ነሐ፲፮። ዮሴፍ። (ዕር፲፱፡ ቍ፰፱)።

(ጥጥ) **ወለጥ**፤ ቀስት፤ ወስፈንጠር፡ የሚለጠጥ። ወለጠ፡ ወመቅልዐ፡ (ገድ፡ አዳ)።

**ወሊል፤ ሎት፤ (ወለ፤ ወለለ፡ ይወልል፡ ይለል)**፤ መውለል፡ መዋለል፤ ወለል፡ ወለል፡ ማለት፤ ወለላ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ወጥቷል፤ ወልወለ፡ የዚህ፡ ዲቃላ፡ ነው።

**ወለት፤—ብንት፡ ሴት፡ ልጅ፤—ወሊድ፡ ወለደ፤ወለድት።**

**ወልታ፤(ታት፤ወላትው። ወልወለ)**፤ ታላቅ፡ ጋሻ፡ አላባሽ፡ አግሬ፤ ክብ፡ ወይም፡ ሞላላ፡ ከጕሽ፡ ከውፈሪም፡ ከዝሆን፡ ቍርበት፡ የሚሠራ፡ ፍችው፡ የወል፡ የመከከል፡ ማለት፡ ነው፤ ዋልታ፡ እንደ፡ ማለት፤ ዋልታ፡ ቅሉ፡ ከዚህ፡ ወጥቷል። ከመ፡ ወልታ፡ ሥሙር፡ ከለልከነ። ወልታ፡ ብርሃን። ወልታት። ይጸውሩ፡ ወላትወ፡ (መዝ፡ ፭። ሮሜ፲፫፡ ፲፪። ዮሴፍ። ኩፋ፡ ፴፯)።



ወልታ፡

**ወልተወ**፤ አጌጠ፡ ለበሰ፡ ተጠረረ፤ መከተ፡ ከለለ፡ ጋረደ። መጽሐፍ፡ ግን፡ በወልተወ፡ ፈንታ፡ ተወልተወ፡ ይላል። ንትወልተው፡ ብንዋየ፡ ሐቅል፡ ዘሃይማኖት። ንትወልተው፡ ሃይማኖቶሙ። ተወልተዉ፡ በይእቲ፡ ኀሲና፡ (አፈ፡ ተ፳፱። መዋሥ። ፳ጴጥ፡ ፱፡ ፩)።

**ወልታዊ**፤ የሚመክት፡ መካች፤ ጋሸኛ፡ ባለ ጋሻ፤ ጋሻ፡ ያዥ፡ ጋሻ፡ ዠግሬ።

**አወልተወ**፤ አስጌጠ፡ አስመከተ፤ አስለፈ፡ አስጠረረ፤ ጋሻ፡ አለበሰ፤ አስለበሰ። ይደልወነ፡ ከመ፡ ናወልቱ፡ ነፍሳቲነ፡ (አፈ፡ ተ፳)።

**ተወልተወ**፤ ተለበሰ፤ ተመከተ፡ ተነገበ፤ ጌጡ፡ ጋሻው።

**ውልትው**፤ የመከተ፤ የተመከተ፤ ምክት።

**ውልታዌ**፤ መመከት፡ አመካከት፤ ምክታ፡ (አፈ፡ ተ፳)።

**ተወላተወ**፤ ተመካከተ፤ ተሳለፈ።

**ምውልታው**፤ መመከቻ፡ መመከከቻ፡ መለሳለፊያ፡ (አር፡ ፳)።

**ወማይ**፤ ጥቋቊር፡ ወፍ፤ አረንጓዴ፡ መሳይ፤ የማኻላ፡ ተባይ፡ (ዕማርኛ)።

**ወናግ፤(ሐረር)**፤ እንበላ። ወናግ፡ በገድ፡ ዘውእቱ፡ ሚናስ፡ (ታሪ፡ ነገ)። ስምንቱ፤ ወንጎ፡ ወነገ፡ ከማለት፡ ከሩካቤ፡ ሥጋ፡ ከሩዊት፡ እሮት፡ የወጣ፡ ነው።

**ወንጌል ፡(ትግሬ)፡** ወንጀል ፡ ስልጦት ፡ በደል ፤ ጥፋት ፡ ክፋት ፡ ነውር ።

**ወንጌላዊ ፡** ወንጀለኛ ፤ ባለወንጀል ። ወንገለ ፤ ወነጀለ ።

**ወንጌል ፡(ላት ። ጽር ፡ ሄዋንጌሊዎን ። ዐረ ፡ ኢንጂል)፡** በቁሙ ፤ ብሥራት ፡ ምሥራች ፤ ሐዲስ ፡ ዜና ፡ መልክም ፡ ወሬ ፤ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ስብከት ፤ እምላካዊ ፡ ሰማያዊ ፡ ነገር ፤ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ምስጢረ ፡ ሥጋዌ ። ወንጌል ፡ ብሂል ፡ በልሳነ ፡ ጽርእ ፡ ወትርጓሜሁ ፡ ስብከት ። ወይሰበክ ፡ ዝ ፡ ወንጌለ ፡ መንግሥት ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ (መቅ ፡ ወን ። ማቴ፳፬ ፡ ፲፬) ።

—፡ መጽሐፍ ፡ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ የሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ነገሥት ፡ ፬ ፡ ክፍል ፡ ያለው ፡ ፬ ፡ ሰዎች ፡ የጣፉት ፤ ፍችው ፡ ያው ፡ ብሥራት ፡ ነው ። በከመ ፡ ይቤ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ። አርባዕቱ ፡ መጻሕፍተ ፡ ወንጌል ። ዘኢየአምር ፡ ነገረ ፡ መጻሕፍት ፡ ወፈድፋደሰ ፡ አርባዕተ ፡ ወንጌላተ ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፳፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፬ ። ፯) ።

**ወንጌላዊ ፡** የወንጌል ፡ መምር ፤ ሰባኪ ፡ ጸሓፊ ፡ እማኒ ፤ ክርስቲያን ። ማቴዎስ ፡ ወንጌላዊ ። አርባዕቱ ፡ ወንጌላውያን ። ዘወንጌላውያን ፡ ትምህርት ። ሃይማኖት ፡ ወንጌላዊት ። ጸሎት ፡ ወንጌላዊት ፡ (ቅዳ ። ቄር ። አፈ ፡ ድ፴፩ ። ፊልክ ፡ ፻፸፩) ።

**ዋንይ ፡ ዩት ፡(ዋነየ ፡ ይዋኒ ፡ ይዋኒ ። ትግ ፡ ወነሰ ፤ ተጫወተ)፡** መዋኘት ፤(ጥና) ዋና ፡ ዋነኛ ፡ ዋነተኛ ፡ መኾን ፤ መጫዎት ፡ መዝፈን ፡ መወሳወስ ። ጸብጥ ፡ መስፈፍ ፡ መንከፈፍን ፤ ዋነየ ፡ ውስወሳን ፡ ያሳያል ፤ ዘፈንና ፡ ዋና ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ወኒ ፡ ወና ፡ ዋኖስ ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**አዋነየ ፡ አስተዋነየ ፡** አጫወተ ፤ አጨዋወተ ።

**አስተዋናዪ ፡ መስተዋንይ ፡** የሚያጫውት ፡ አጫዋች ፡ አጨዋዋች ። መስተዋንያን ፡ (ሲኖ ፡ ዶ) ።

**ተዋነየ ፡** ተጫወተ ፤ ተጨዋወተ ፡ ተነጋገረ ። ደቅ ፡ ወአዋልድ ፡ ዘይትዋነዩ ። እንዘ ፡ ይትዋነይ ፡ በመሰንቆ ። እምከመ ፡ ተዋነይከ ፡ ምስሌሁ ፡ (ዘካ፰ ፡ ፭ ። መሳ፳፩ ፡ ፳፩ ። ሢራ ፡ ፴፱) ።

**ተዋናዪ ፡** የሚጫወት ፡ ተጫዋች ፡ ፌዘኛ ፡ ዐዋቂ ።

**ተውኔት ፡** ጨዋታ ፡ ዘፈን ፤ ብዙ ፡ ስምና ፡ ስልት ፡ መጣሪያ ፡ ያለው ። ቃለ ፡ ተውኔት ። ንዋየ ፡ ተውኔት ። ቤተ ፡ ተውኔት ። መካነ ፡ ተውኔት ። ዘከመ ፡ ተውኔቶሙ ። ወትያላን ፡ ተውኔቱ ፡ (ኤርሚ፳ ፡ ፲፱ ። ዳንኤ ፡ ፯ ። ዲድ ፡ ፳፯ ። ግብ፲፱ ፡ ፳፱ ። ጥበ፲፪ ፡ ፳፭ ። ስንባ፩ ፡ ፲) ።

**ዋኔ ፡ ዋኖስ ፡** በቁሙ ፡ ተጫዋች ፡ ወፍ ፡ ማስነቅ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ወሣእ ፡ አት ፡(ወሥአ ፡ ይወሥእ ፡ ይሣእ ። ግሥዐ)፡** ማውሣት ፡ ማሰብ ፡ መናገር ፡ መጠየቅ ፡ መመለስ ፡ ምላሽ ፡ መስጠት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወሥአ ፡ ፈንታ ፡ አውሥአ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ኢታውሥእ ፡ ሕሡመ ፡ በአፉከ ። ሙሴ ፡ ይወሥእ ፡ ወእግዚ ፡ ይሰጠዎ ። ወአውሥኡ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ በይእቲ ፡ ሰብሐት ። ከመ ፡ ታውሥእዎሙ ፡ ቃለ ፡ ሰእሰ ፡ ይሴእሉክሙ ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ (ኢሳ፶፰ ፡ ፲፫ ። አርጋ ፡ ፮ ። ዮዲ፲፭ ፡ ፲፱ ። ፩ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፭) ።

**አውሥአ ፡** አሰማ ፡ አናገረ ፡ አስጠየቀ ፡ አስመለሰ ፤ አሳሰበ ፡ አስታወሰ ። የልማድ ፡ ፍችው ፡ ግን ፡ አድራጊ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ አእመረ ፡ ተበላሽቷል ።

**አውሣኢ ፡(ኢት ፡ እያን ፡ ያት)፡** የሚያሰማ ፤ መላሽ ፡ ምላሽ ፡ ሰጪ ፤ ጠበቃ ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ። አንትሙ ፡ አውሣእያን ፡ በእንቲአሆሙ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**ተወሥአ ፡** ተወሣ ፡ ታሰበ ፤ ተባለ ፡ ተነገረ ፡ ተሰጠ ፤ ቃሉ ፡ ምላሹ ።

**ተዋሥአ ፡** ተመላለሰ ፡ ተከራከረ ፤ ተሟገተ ፡ ተባባለ ። አልቦ ፡ ዘይትዋሥአኒ ። ኢትትዋሣእ ፡ በኀበ ፡ ጸዓሊ ። ወተዋሥአ ፡ እለእስክንድሮስ ፡ (ኢሳ፲ ፡ ፲፬ ። ሢራ፰ ፡ ፲፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ።

**ተዋሣኢ ፡** ተሟጋች ፤ ተከራካሪ ። ሰብ ፡ ይትዋሣእ ፡ ተዋሣኢ ፡(አፈ ፡ ድ፳፯) ።

**ሞሣእ ፡ ት ፡** መመለሻ ፡ ምላሽ ፡ መስጫ ፡ መነጋገሪያ ፤ ቦታ ፡ መጽሐፍ ።

**መዋሥእት ፡(ብዙ)፡** መመለሾች ። የዜማ ፡ መጽሐፍ ፡ ስም ፤ ቃሉ ፡ በመዝሙር ፡ መካከል ፡ እየገባ ፡ የሚመላለስ ፤ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ኹነው ፡ መዘምራን ፡ የሚቀባበሉት ፤ ለሙታን ፡ ለበዓል ፡ የተሠራ ። መዋሥእት ፡ ዘፈላስያን ፡ (ማኅዘ) ።

»**ሣእሣእ ፡** መልስ ፡ ምላሽ ፡ የሚበቃ ፡ አፍ ፡ የሚያሲዝ ፡ ቃል ፤ ጕንደልና ፡ ጣዕም ፡ ያለው ፡ የሚደነቅ ፡ የነገር ፡ ጣዕም ፡ ለዛ ፡ አጣጣል ፡ አሰካክ ። ወሰው ፡ ውሸት ፤ ዋሸንት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ምገበ ፡ ቃሉ ፡ ወጣዕመ ፡ ነገሩ ፡ ወሣእሣአ ፡ አፉሁ ። ወአንከሩ ፡ ሣእሣኦ ። ሣእሣአ ፡ ቃልክሙ ። ጥበብ ፡ ሰርኢይ ፡ አዳም ፡ ለሰሚዐ ፡ ጥዑም ፡ ለአፍ ፡ ሣእሣእ ፡ ለከናፍር ፡ ባሕይ ፡ ለአዕይንት ፡ (ሉቃ፬ ፡ ፳፪ ። ፳ ፡ ፳፮ ። ኢዮ፮ ፡ ፳፮ ። ቀሌ) ።

»**ሣእሥአ ፡(ተቀ ፡ ግ)፡** ሰበቀለ ፤ ቀለጠፈ ፡ ቅልጥፍጥፍ ፡ አለ ፡ ተባ ፡ ረታ ፡ ኸለ ፡ ለሳ ፡ ያንደበት ።

»**ሥእሡእ ፡(ኢን ፡ አት ፡ ሥእት)፡** የሰበቀለ ፡ ስብቅል ፡ ትብ ፡ ቀልጣፋ ፤ በሊን ፡ ልሳን ። ከናፍሪሁ ፡ ጥዑም ፡ ወአፉሁ ፡ ሥእሡእ ፡ (ደራሲ) ።

»**ሥእሣኤ ፡** መሰብቀል ፡ አሰበቃቀል ፤ ስብቀላ ፡ ቅልጠፋ ፡ ያንደበት ።

»**ሥእሥእና ፡** ስብቅልነት ፡ ቀልጣፋነት ።

**ወሠቀ ፡—ዐሰበ ፡ ደከረ ፡—ወሰቆ ፡ ወሰቀ ።**

**ወሥሮ ፤ ወሣር ፤ ሮት ፤** (ወሠረ ፡ ይዌሥር ፡ ይወሥር ። ዕብ ፡ ናሣር ። ዐረ ፡ ነሸረ ፤ ወሸረ) ፤ መወሠር ፡ መገዝገዝ ፡ መከርከር ፡ መቍረጥ ፡ መሠንጠቅ ፡ መተርተር ፡ በመጋዝ ። ወሠረ ፡ ዕፀ ። ወሠርዎን ፡ በሞሠርት ፡ ነጺን ፡ ለፀኑሳት ። ወሠሮ ፡ ለኢሳይያስ ፡ በሞሠርተ ፡ ዕፀ ። ወቦ ፡ እለ ፡ ወሠርዎሙ ፡ በሞሠርት ፡ (ጥበ፲፫ ፡ ፲፰ ። ዓሞ፩ ፡ ፫ ። ዕር ፡ ኢሳ፳ ፡ ፩ ። ዕብ፲፩ ፡ ፴፯) ።

**ወሣሪ ፤ መወሥር ፤** የሚቈርጥ ፡ የሚሠነጥቅ ፡ ባለመጋዝ ።

**ተወሥረ ፤** ተቈረጠ ፤ ተሠነጠቀ ። እስከ ፡ ተወሥረ ፡ ለክልኤ ። እለ ፡ በሞሠርት ፡ ተወሥሩ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ፳ ፡ ፲፱ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፯) ።

**ተዋሠረ ፤** ተሳሳበ ፡ ተገዘገዘ ፡ አንዱን ፡ መጋዝ ፡ ለኹለት ፡ ይዞ ።

**ውሡር ፤ (ሩን ፡ ሩት ፡ ሥርት) ፤** የተቈረጠ ፡ ቍርጥ ፡ ሥንጥቅ ፡ ትርትር ።

**ውሣሬ ፤** መቍረጥ ፡ መቈረጥ ፡ አቈራረጥ ፤ ቈረጣ ፡ ግዝገዛ ፡ ትርተራ ፡ ሥንጠቃ ።

**ሞሠር ፡ ት ፤ (ብ ፡ መዋሥር ፡ ት) ፤** መጋዝ ፡ ጥርሳም ፡ ብረት ፡ መቍረጫ ፡ መሠንጠቂያ ። ይትሌዐልኑ ፡ ሞሠርት ። መዋሥረ ፡ ነጺን ። መዋሥርተ ፡ ዕፀ ፡ (ኢሳ፲ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፳ ። ቢ.ኖ.ደ) ።



ሞሠርት ፡

**ምሣር ፤ (ራት) ፤** በቂሙ ፡ ፋስ ፡ መቍረጫ ፡ መፍለጫ ፡ መጥረቢያ ። ከመ ፡ ምሣር ፡ ዘይሜጽር ። ምሣረ ፡ ጸራቢ ፡ ዘጸረበ ፡ ግልፎ ። ጸረቦሙ ፡ በምሣራት ፡ ነጺን ፡ (ዲድ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ ሚያ፳፯ ። ፩ዜና ፡ ፳ ፡ ፫) ። ሞሠርና ፡ ምሣር ፡ ይሞክሻሉና ፡ በሞሠር ፡ ፈንታ ፡ ምሣር ፡ ይላል ።



ምሣር ፡

**ውሥት ፤—ወደ ፤—ውስተ ።**

**ወዕደ ፤—ወደ ፤ ዘንድ ፤—ወእደ ።**

**ውዕይ ፤ (ውዕየ ፤ ወዐየ ፡ ይውዒ ፡ የዐይ) ፤** መንደድ ፡ መቃጠል ፡ መጋም ፡ መጋል ፡ መሞቅ ፤ መተኰስ ፡ መፋጀት ፡ መቈጣት ፡ ማዘን ። እስከ ፡ በሕቁ ፡ ይውዒ ። ኢይውዐያ ፡ አልባሲሁ ። ከመ ፡ ኢትዐይ ፡ በነደሙ ። ምድር ፡ ትውዒ ፡ እሙቀተ ፡ ፀሓይ ። ውዐየ ፡ ልብየ ፡ (ዳንኤ ፡ ፲፱ ። ምሳ፳ ፡ ፳፯ ። ሚራ፫ ፡ ፲ ። ሔኖ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፴፱) ። መሬሳኽ ፡ ዋይ ፡ ማለት ፡ ቡቃ ፡ መሰደድ ፡ (ትግሬ) ።

**ወዓዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤** የሚነድ ፡ የሚቃጠል ፡ ተቃጣይ ።

**ውዑይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ዪት) ፤** የነደደ ፡ የተቃጠለ ፡ ሙቅ ፡ ትኩስ ፡ የሚፋጅ ። ውዑየ ፡ ነድ ። ውዑይ ፡ ፍቅር ። አንብዕ ፡ ውዑይ ። ነፋስ ፡ ውዑይ ። ይከውኑ ፡ ውዑያነ ። ውዒት ፡ በእሳት ፡ (ስንክ ፡ ነሐሴ፱ ። አርጋ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ተወ፩ ። ሕግ፲፯ ፡ ፲ ። ኢሳ፴፫ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፸፱) ።

**ውዕየት ፤ ዕየት ፤** መቃጠል ፡ መሞቅ ፡ መተኰስ ፡ መናደድ ። ውዕየተ ፡ ሀገር ። ውዕየተ ፡ ቤተ ፡ እግዚ ። ውዕየት ፡ ዘፍትወት ። በውዕየተ ፡ ልብ ። በልባዌ ፡ ወበውዕየተ ፡ ነፍስ ፡ (ራእ፲፰ ፡ ፲፰ ። አቡሻ ፡ ፷ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፮ ። ፊልክ ፡ ፻፵፫) ።

»**ዕየት ፤** ትኩስ ፡ ትኩሳት ፤ እሳት ፡ የፈጀው ፡ ገላ ፡ ቍስሉ ፡ ዕትራቱ ። ዕየተ ፡ ህየንተ ፡ ዕየት ፡ (ዘፀ፳፩ ፡ ፳፭ ። ዘሌ፲፫ ፡ ፳፰) ።

—፤ ሙቀት ፡ የሚያሞቅ ፡ ልብስ ፡ በላይ ፡ የሚደረብ ። ወዕዬያት ፡ ዕየትከ ። ልብሶቹ ፡ መሸፈኛኹ ፡ ትኩሶቹ ፡ ናቸው ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፲፭) ።

**ዋዕይ ፤** ቃጠሎ ፡ ሙቀት ፡ ትኩሳት ፤ ሐሩር ፡ ድርቅ ፡ በጋ ። ከመ ፡ ዋዕየ ፡ እሳት ። ዋዕየ ፡ ፀሓይ ። ዋዕየ ፡ ፍትወት ፡ (ኢሳ፱ ፡ ፲፱ ። ሔኖ ፡ ፬ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፳) ።

**አውዐየ ፤** አቃጠለ ፡ ተኰሰ ፤ ለበለበ ። አውዐይናሃ ፡ በእሳት ። ክልኤሙ ፡ አውዕዮተ ፡ መቅደስ ። ዐቀብተ ፡ ሥራይ ፡ ሶበ ፡ ይፈቅዱ ፡ በጢሐ ፡ ወአውዕዮ ፡ በእሳት ። ፀሓይ ፡ ኢያውዒከ ። ኅጠተ ፡ ስናፔ ፡ ሶበ ፡ ጥዕማ ፡ ብእሲ ፡ ታውዕዮ ፡ (ኤሶፕ ፡ ፴ ፡ ፲፱ ። የሔና ። አፈ ፡ ተ፴ ። ዲድ ፡ ፲፱) ።

**መውዕይ ፤ (ያን ፡ ያት ፤ ዪት ፡ ዒት) ፤** የሚያቃጥል ፡ አቃጣይ ፡ ተኳሽ ። እሳት ፡ መውዒት ፡ (ፊልክ ፡ ፻፴፫) ።

**ሙዓይ ፤ (ያት ፤ መዋዕይ) ፤** መቃጠያ ፡ ማቃጠያ ፡ መተኰሻ ።

**አስተዋዐየ ፤** አቀጣጠለ ፡ አያያዘ ፡ እሳቱን ። ዘያስተዋዕዩ ፡ ለእከይ ፡ (ምሳ፲፱ ፡ ፱) ።

**ውዕላ ፡ (ዕብ ፡ ያዒል ። ሱር ፡ ያዕላ ። ዐረ ፡ ወዕል ፤ የበዳ ፡ ፍየል) ፤** ዋሊያ ፡ የዋሊያ ፡



ውዕላ ፡

ወገን ፤ ቦኽር ፤ ተባት ፡ ወይጠል ። ዐየልን ፡ እይ ፡ (ዘዳ፲፬ ፡ ፭) ።

**ውዒል ፤ ሎት ፤ (ውዕለ ፤ ወዐለ ፡ ይው ዕል ፡ የዐል)** ፤ መዋል ፤ ውሎ ፡ ውለታ ፡ ማድረግ ፤ ቀኑድ ፡ ቦታ ፡ ባንድ ፡ ሥራ ፤ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፤ መኖር ፡ መቈየት ፤ ወይም ፡ መዋልና ፡ ማደር ፡ መሰንበት ። እስ ፡ ይውዕሉ ፡ በስታይ ። ዘኀቤሁ ፡ ወዐልኩ ፡ ዮም ። ወዐሉ ፡ ኀቤሁ ፡ ይእተ ፡ ዕለተ ። ይውዕል ፡ ወይትቀ ፃይ ፡ እስከ ፡ ይመሲ ። ንውዕል ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ እ ንዘ ፡ ንሐውር ። ኃበረ ፡ ትዕይንት ፡ ወውዕለ ፡ እስከ ፡ ሕመ ፡ ሐይዉ ፡ (ኢሳ፳ ፡ ፲፩ ። ሩት፪ ፡ ፲፱ ። ዮሐ፩ ፡ ፴፱ ። መገ ፡ ፲፫ ። ዘፍ፴፫ ፡ ፲፱ ። ኢያ፭ ፡ ፰) ። ሰበወ ፡ ብሎ ፡ እስተዋለ ፡ ማለት ፡ በማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ወዓሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ዐልት)** ፤ የሚውል ፡ ሙያተኛ ፤ ሎሌ ፡ አሽከር ፡ ወታደር ። ወዓሊ ፡ ዘምስሌየ ። እምተባእሱ ፡ ሊተ ፡ ወዓልያንየ ። ይጸ ውርዎ ፡ ወዐልት ፡ (ፊልጵ፪ ፡ ፳፭ ። ዮሐ፲፰ ፡ ፴፮ ። ግ ብ፳፰ ፡ ፴፰) ።

**ውዑል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ዕልት)** ፤ የዋለ ፤ ባለ ውለታ ፡ ሙያተኛ ። በጥቃ ፡ ገቦከ ፡ ዘልፈ ፡ ስእኩን ፡ ውዑለ ፡ (ደራሲ) ።

***ዕለት ፤ (ታት)** ፤ መዋል ፡ አዋዋል ፤ ውሎ ፡ ውለታ ። ቀን ፤ ጊዜ ። በዕለተ ፡ ምንዳቤ ። በዕለት ፡ ኀፊት ። ኅጹር ፡ ዕለትየ ። ዕለተ ፡ ነግህ ፡ ወሠርክ ፡ (ሚራ፪ ፡ ፲፩ ። ኢሳ፷፱ ፡ ፰ ። ዕብ፲፩ ፡ ፴፪ ። ኩፋ ፡ ፯) ።

—፤ መዓልት ፡ ከንግሀ ፡ እስከ ፡ ሠርክ ። ሣልስተ ፡ እዴ ሆሙ ፡ ሰዕለት ፡ ወሰሌሊት ። በእፎ ፡ ዕለት ፡ እም ዕለት ፡ ትነውኅ ። ዕለታት ፡ ወሰያልይ ፡ (ራእ፰ ፡ ፲፪ ። ሚራ፴፯ ፡ ፯ ። ቅዳ) ።

—፤ በቁሙ ፤ የጊዜ ፡ ክፍል ፡ ከ፳ ፡ አንዱ ፤ መዓልትና ፡ ሌሊት ፡ ፳፬ ፡ ሰዓት ። ዕለት ፡ ብሂል ፡ ዘያስተዘውጎሙ ፡ ለሌሊት ፡ ወለመዓልት ። ወኮነ ፡ ምሴተ ፤ ወኮነ ፡ ጽ ባሕ ፤ አሐደ ፡ ዕለተ ። ሰቡዐ ፡ ዕለታተ ። በዕለት ፡ ሳ ምንት ፡ (አዋል ። ዘፍ፩ ፡ ፭ ። ሕንን ፡ ፲፩ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፲፰) ።

—፤ ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ሲኾን ፤ ሰዓ ፡ ሰዓተ ፡ እን ደሚገቡት ፡ ይገባል ። በዕለተ ፡ ተወልደ ፤ በዕለተ ፡ ተሰ ቀለ ፤ እምዕለተ ፡ ትበልዑ ፤ እምዕለተ ፡ ከደነ ፡ ኀፍ ረተ ። ሕመ ፡ ዕለተ ፡ ዕጼውዐከ ፡ እያለ ፡ ከገባብ ፡ ጋራ ፡ በኀሳፊና ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ። ደቂቅ ፡ ሲኾን ፡ በዕለተ ፡ ቀተል ፡ እያለ ፡ በጥሬ ፡ ይገባል ፤ ፍችው ፡ ቀንና ፡ ጊዜን ፡ አይለቅም ። ዘሎ ፡ ዕለተ ፤ ዘወትር ፡ ኹል ፡ ቀን ፡ ዕለት ፡ ዕለት ። በዕለቱ ፤ ዕለቱን ፡ በዚያው ፡ ቀን ፤ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ወዲያው ፡ ቶሎ ፡ ሳይመሽ ፤ ወይም ፡ ሳይነጋ ፡ ያሰኛል ። በግእዝ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ዕለት ፡ የሚባለው ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ነውና ፤ (መዝ ፡ ፹፱ ። ፪ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፰) ። ፷፻ው ፡ ዓመት ፡ እኩል ፡ ቀን ፡ ይባላል ። «ይቤሎ ፡ መንፈስ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ዘውእቱ ፡ ቃል ፡ ዘአስተርአየ ፡ በአምሳለ ፡ መልአክ» ፡ ለእስክንድር ፤ ለእመ ፡ በጽሐ ፡ ዘመኑ ፡ ሰዕለትየ ፡ በኀሙስ ፡ ዕለት ፡ ወበመንፈቀ ፡ ዕለት ፡ እ ለብስ ፡ ሥጋሁ ፡ ለአዳም ፡ አቡከ ፡ በእንተ ፡ ዕልወቱ ፡ (ዜና ፡ እስ ፡ ክ፯) ።

**አውዐለ** ፤ አዋለ ፤ ጠበቀ ። ዘአውዐልከኒ ፡ ዘሎ ፡ ኑኀ ፡ ዕለት ። አውዐልዎሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞ ቅሕ ። ወአውዐሉ ፡ አፍራሲሆሙ ፡ (ድጓ ። ግብ፭ ፡ ፲፰ ። ፵፫ ፡ ፴፪) ።

—፤ አስዋለ ፤ አስጠበቀ ። እስመ ፡ አፈቅድ ፡ አውዕል ፤ ምንት ፡ ውእቱ ፡ አውዕሎ ፡ (ሄርማ ፡ ገ፶፪ ፡ ፶፫) ።

—፤ አዋለ ፤ አሰረ ፤ አጠበቀ ፡ ከግዞት ፡ አገባ ። አውዐ ልዎ ፡ ውስተ ፡ ሙዓል ። አውዐልዎሙ ፡ ሙዓለ ፡ (ዘኍ ፲፭ ፡ ፴፬ ። ግብ፬ ፡ ፫) ።

**አውዓሊ ፤ መውዐሊ ፤ ዕል** ፤ የሚያውል ፡ አዋይ ፡ ጠባቂ ፤ አሳሪ ፤ ባለውል ።

**ሙዓል ፤ (ላት)** ፤ መዋያ ፡ ውሎ ፡ ማድረጊያ ፡ ቦታ ፤ የቀን ፡ ሐብስ ፤ ወይም ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ እስኪፈ ረድበት ፡ በደለኛ ፡ የሚውልበትና ፡ የሚያድርበት ። ምስ ክሩ ፡ ቀድሞ ፡ ቀነማሯል ።

—፤ በቁሙ ፡ ሙያ ፤ ጥሩ ፡ ሥራ ፡ ተግባረ ፡ እድ ። ባለ ሙያ ፡ እንዲሉ ፡ (በማርኛ) ።

**ሞዐልት ፤ መዓልት ፤ (ብ ፡ መዋዕል ፡ ላት)** ፤ በቁሙ ፡ ቀን ፤ ፀሓይ ፡ ወጥቶ ፡ እስኪገባ ፡ ያለ ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ። ዘሌሊት ፡ መዓልተ ፡ ይከ ውኖ ። አርብዓ ፡ መዋዕለ ፡ ወአርብዓ ፡ ሰያልየ ፡ (ሚራ ፴፰ ፡ ፳፰ ። ማቴ፬ ፡ ፪) ።

—፤ ጊዜ ፡ ዘመን ፡ ወራት ። ተዘከር ፡ መዋዕለ ፡ ረኃብ ፡ ሕመ ፡ መዋዕለ ፡ ጽጋብ ። መዋዕል ፡ ወአዝማን ። በእ ማንቱ ፡ መዋዕል ፡ (ሚራ፲፰ ፡ ፳፭ ። ግብ፭ ፡ ፯ ። ዘፍ ፴፰ ፡ ፩) ። መዋዕል ፡ በዕለትና ፡ በዕለታት ፡ ፈንታ ፡ እየ ገባ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ኹኖ ፡ ላንድም ፡ ለብዙም ፡ ይነገ ራል ። በዝ ፡ መዋዕል ፤ በዝሉ ፡ መዋዕል ፤ በእማንቱ ፡ መዋዕል ፤ ሰዱሰ ፡ መዋዕለ ። መዋዕል ፡ እኩያት ፤ መ ዋዕል ፡ ሠናያት ። በአንቀጽ ፡ ሲገባ ፡ እንደ ፡ ዕለት ፡ ዐ ቢይ ፡ አገባብ ፡ ይኾናል ። በመዋዕለ ፡ ተወልደ ፡ ዮሴፍ ። በመዋዕለ ፡ ትሔብስ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፰ ። ሚራ፲፰ ፡ ፳፯) ።

**መዓልታዊ** ፤ የቀን ፡ የሙያ ፡ ቀን ፡ የሚመ ግብ ። ፀሓይ ፡ መዓልታዊ ፡ (ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**መዋዕልና** ፤ ዘመንንት ። ብሉየ ፡ መዋዕልና ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**ተዋዐለ** ፤ ተዋዋለ ፡ ተሰማማ ። ተካሀለን ፡ እይ ።

**ውዕል ፤ (ላት)** ፤ በቁሙ ፤ ውል ፡ ኪዳን ፡ የታ ሰረ ፡ ነገር ። (ተረት) ፤ ውል ፡ አያወሳውል ፡ (በማርኛ) ።

**ውዒር ፤ ሮት ፤ (ወዐረ ፡ ይዌዕር ፡ የዐር ፤ ይውዐር ። ዐረ ፡ ወዐረ)** ፤ መሻከር ፡ ማስቸገር ፤ ሻ ካራ ፡ ጠዋይ ፡ መኾን ፤ የግብር ፡ የነገር ። ማይነቅ ፡ ማን ከር ፤ ዕጹብ ፡ ዕጹብ ፡ ማለት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወዐረ ፡ ፈንታ ፡ ተወዐረ ፡ ይላል ። አንስ ፡ እትዌዐር ፡ ጥበቦ ፡ (ተረ ፡ ቁር) ።

**ወዓሪ ፤ መውዕር** ፤ የሚሻክር ፡ ሻካራ ። እድ ናቂ ፡ አዳናቂ ።

**ወዐር ፤ (ዐረ ። ዕብ ፡ ያዓር) ፤** ዱር ፡ ገደል ፡ ደንጊያማ ፡ ድንኮር ፡ ሰንከልካላ ፡ ቦታ ፤ ሰው ፡ የማይደ ርስበት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወዕር ፡ ፈንታ ፡ ወርዕ ፡ ይ ላል ። ወእምዝ ፡ ወፅኡ ፡ በሌሊት ፡ እም ይእቲ ፡ ደ ብር ፡ እንዘ ፡ ኢየአምሩ ፡ ፍኖቶ ፡ ወበጽሑ ፡ ውስተ ፡ ወርዐ ፤ ወእንዘ ፡ የኅሥሡ ፡ ፍኖተ ፡ ኀጥኡ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ።

**አውዐረ ፤** አስደነቀ ፡ ዕጹብ ፡ አሰኘ ።

**ተውዐረ ፤** ተደነቀ ፡ ዕጹብ ፡ ተባለ ።

**ውዑር ፤ ዋዕር ፤** ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ልዩ ፡ ል ውጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፤ ሊያምኑት ፡ እንጂ ፡ ደርሶ ፡ ሊያውቁት ፡ ሊመረምሩት ፡ የማይቻል ። ወአማን ፡ ነኪር ፡ ወዋዕር ፡ ውእቱ ፡ ዘክርስቶስ ፡ ምስጢር ። ው ስተ ፡ ቅድስት ፡ ወመንክርት ፡ ወዋዕር ፡ በአማን ፡ ል ደት ። ኮነ ፡ ዋዕረ ፡ ወነከራ ፡ (ቁር ፡ ጳላ) ።

**ትውዕርት ፤** ድንቂያ ፡ ድንቅነት ፡ ልዩነት ፡ ል ውጥነት ። በትውዕርቱ ፡ ወበመንክሩ ፡ ለዘክርስቶስ ፡ ምስጢር ፡ (ቁር ፡ ጳላ) ።

**ወፊጥ ፡ ጦት ፤ (ወፈጠ ፡ ይወፍጥ ፡ ይ ፊጥ) ፤** መተኰስ ፡ ማብሰል ፤ የልብስ ፡ የሸክላ ፡ ለንፍ ጥም ፡ ይኾናል ። ወበሱባዔ ፡ ራብዕ ፡ ወፈጡ ፡ በእሳት ፤ ወኮኖሙ ፡ ግንፋል ፡ ከመ ፡ እብን ፡ (ኩፋ ፡ ፲) ።

**ወፉጢ ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት ፤ ፊጥ) ፤** የሚተኰስ ፡ ተኳሽ ፤ ተኰስ ፡ ዐዋቂ ።

**ሞፍጥ ፤ (ብ ፡ መዋፍጥ) ፤** መተኰሻ ፡ ማ ብሰያ ፤ ምድጃ ፡ እቶን ። ዘከመ ፡ ያዐውድ ፡ ሞፍጦ ፡ (ሚ ፊ፴፫ ፡ ፴) ።

**ወፍይ ፤ (ወፈየ ፡ ይወፊ ፡ ይወፊ ። ዐረ ፡ ወፈይ) ፤** ዐጉልና ፡ ገቢር ፤ የጠፈረ ፡ ቤት ። ፍጹም ፡ ጥዑይ ፡ መኾን ፤ አለመጉደል ፡ አለመንከት ። መስጠት ፡ ማሲያዝ ፡ ማስጨበጥ ፤ ዐደራ ፡ ማለት ፤ ዐደራን ፡ ዕዳን ፡ መመለስ ፡ መክፈል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወፈየ ፡ ፈንታ ፡ አወፈየ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ዘሎ ፡ አወፈየ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ። አወፈይዋ ፡ ለዮሴፍ ። ትጉጉአ ፡ ምድር ፡ ታውፊ ፡ ማሕፀንታ ። አወፈየት ፡ ዕዳ ፡ ዘላዐለ ፡ ምታ ፡ (ዮሐ፲ ፡ ፴፯ ። ንን ፡ ማር ። ሱቱ ፡ ፅገ፪ ፡ ፶፭ ። ስንክ ፡ ሠ ኔ፳) ። ዳግመኛም ፡ በአዘዘ ፡ ፈንታ ፡ አወፈየ ፡ ይላል ፡ ምስጢሩ ፡ ዐደራ ፡ ከሰው ፡ ይገባል ። ወአወፈየ ፡ ከመ ፡ ይሕንጽ ፡ ቤተ ፡ (፩ዜና ፡ ፳፪ ፡ ፮ ፡ ፲፯) ።

**አወፈየ ፤** (ባጉልነቱ ፡ አድራጊ ፤ በገቢርነቱ ፡ አ ስደራጊ) ፤ አሰጠ ፡ አሰሜ ፡ ኾነ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ ሰጠ ፤ ሰጭ ፡ ኾነ ፡ ነው ። እመ ፡ ፈቀደ ፡ ያወፊ ፡ ነፍሶ ። ያ ወፍይዎን ፡ ሊኅጽወ ፡ ንጉሥ ። አወፈየ ፡ ምሕፀና ፡ (ቀሌ ። አስቴ፪ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ መስ፳) ።

**ተወፈየ ፤** ተሰጠ ፤ ተሰጭ ፡ ኾነ ። ተቀበለ ፡ እጅ ፡ አደረገ ። ሃይማኖት ፡ እንተ ፡ እምትካት ፡ ተወፈየት ፤ ተሰጠች ። (ቁር ፡ እስ) ። ተወፈያ ፡ ሰርብቃ ። አመ ፡ ተ ወፈየ ፡ መንግሥት ። ምድረ ፡ ጽጌ ፡ ተወፈየ ፡ ዕሴበ ፤ ተቀበለ ፡ (ዘፍ፳፱ ፡ ፳፭ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፳፱ ። ስንክ ፡ ጥ ቅ፱) ።

**ውፉይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ፊት) ፤** የተሰጠ ፡ ተ ሰጭ ፤ የተሰጠው ፡ ተቀባይ ።

**ውፉዬ ፤ ወፍየት ፤** መስጠት ፤ መቀበል ፤ እ ሰጣጥ ፡ አቀባበል ፤ ስጦታ ፡ ቅበላ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፵፱) ።

**ትውፊት ፤** ስጦታ ፤ ልማድ ፡ ትምርት ፤ ወግ ፡ ታሪክ ፡ ሃይማኖት ፡ ሥርዐት ፤ ከጥንት ፡ ከአበው ፡ ሲያ ያዝ ፡ ሲወርድ ፤ ቃል ፡ በቃል ፡ ሲነገር ፡ የመጣ ። ዘርት ዕት ፡ ወእንተ ፡ ሐዋርያት ፡ ሃይማኖት ፡ ትውፊት ። ትውፊተ ፡ ቅዱሳን ፡ መምህራን ። ትውፊቶሙ ፡ ለ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ። ትውፊተ ፡ መጻሕፍቲሆሙ ፡ (ቁር ፡ እስ ። ጳላ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ወፊፍ ፤ ፎት ፤ (ወፈ ፤ ወፈፈ ፡ ይወፍፍ ፤ ይፊፍ) ፤** ወፈፍ ፡ ወፈፍ ፤ አፈፍ ፡ አፈፍ ፡ ማለት ፤ መ ንማማት ፤ ወፈፍተኛ ፡ መኾን ፤ (ዐማርኛ) ። ያፈን ፡ ተመ ልክት ።

**ወፊር ፤ ሮት ፤ (ወፈረ ፡ ይወፍር ፡ ይ ፊር) ፤** መወፈር ፡ መደንደን ፤ መሰፋት ፡ መዘርጋት ። ይወፍር ፡ አዕጹቂሁ ፡ (ሆሴ፲፬ ፡ ፮) ።

—፤ መሰምረት ፤ ዕዳሪ ፡ መውጣት ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ወደ ፡ ተግባር ፡ መኼድ ፡ ማለፍ ። በረዘን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ንር ፡ ነው ። ወፈረ ፡ ሐቅለ ። ወፈረ ፡ ኀበ ፡ አቡሁ ፡ ውስተ ፡ ማእረር ። ይወፍር ፡ ውስተ ፡ ተግባሩ ። ኦፈር ፡ ወን እቱ ። ፈር ፡ ኀቤሃ ፡ ከመ ፡ ዘየሐርስ ። ወፈረ ፡ በሰን በት ፡ (ዳን፲፫ ፡ ፴፫ ። ፬ነገ ፡ ፬ ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፻፫ ። ድጓ ። ሚራ፺ ፡ ፲፱ ። ሉቃ፺ ፡ ፳) ።

**ወፋሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ፈርት) ፤** የሚሰመር ፡ ተሰምሪ ፤ ዐራሽ ፡ ቈፋሪ ፤ ማር ፡ ዐማጅ ፡ ቆ ንጫት ፡ ሰባሪ ። ወፋርያነ ፡ ዕፀው ፡ (ኢያ፱ ፡ ፳፫) ።

**ውፍረት ፤** በቁሙ ፤ መወፈር ፡ አወፋፈር ፤ ው ፋሬ ፡ ግዘፍ ፤ ወፍራምነት ። መሰምረት ፤ አሰመራር ፡ ሰ ምሪት ። ቡሩክ ፡ ይኩን ፡ ውፍረትክሙ ፡ ወእትውኘ ክሙ ፡ (ግንዘ) ።

**ወፍር ፤** ወፍራም ፡ መሬት ፡ ዕርሻ ፤ የከብት ፡ መሰምሪያ ፡ ዱር ፡ መስክ ። ዘይትቃነይ ፡ ወፍረ ። ወ ፍረ ፡ ሐረስት ። ዐጺደ ፡ ወፍር ። ዐብረ ፡ ዘሎ ፡ ወ ፍር ፡ ዘውስተ ፡ ገዳም ። አዕጻዳተ ፡ ወፍርነ ፡ (ኩፋ ፡ ፶ ። መክ፳ ፡ ፴ ። ፩ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፮ ። ኤር፴፫ ፡ ፲ ። ዮዲ፫ ፡ ፫) ።

—፤ ጉዳይ ፡ ተግባር ፤ መፍቅድ ፤ ገንዘብ ፡ የሚያስፈልግ ። ዘይዘሩ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለወፍረ ፡ ቤቱ ፡ (ቀሌ) ።

**አውፈረ ፤** አሰማራ ፤ ነዳ ፡ ወሰደ ። ይጉብር ፡ ነግሀ ፡ ወያወፍሮ ፡ ለሰብእ ፡ ውስተ ፡ ተግባሩ ። ዘያ ወፍር ፡ እክለ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ (ቀሌ ። ሚራ፴ ፡ ፲፰) ።

**መሑፈር ፡** (ራት) ፡ መስምሪያ ፡ ማስምሪያ ፡ በታ ። ስምድሮሙ ፡ ወበሙፋሮሙ ። ሚጥ ፡ ልበክ ፡ ለመርዓትከ ፡ ወበሙፋረ ፡ ዚአከ ፡ (ሔኖ ፳ ፡ ፪ ። ምሳ ፳፮ ፡ ፳፫ ። መገ ፡ ፳፬፻) ።

**ሞፈር ፡ ት ፡ (ብ ፡ መዋፍር ፡ ት) ፡** በቁሙ ፡ የርሻ ፡ የስምሪት ፡ ዕቃ ፡ ገበሬ ፡ ይዞት ፡ የሚሰመር ፡ ወፍራም ፡ ረዥም ። ለነ ፡ ጸራቢ ፡ ወእጸርብ ፡ መዋፍረ ፡ ወመናብርተ ፡ ወካልኣኒ ። መዋፍርት ፡ ዘየሐርሱ ፡ ወይመልኍ ፡ አሥዋከ ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ ፡ ጥቅ፲) ።



ሞፈር ፡

**ተዋፈረ ፡** ተስማሬ ፡ ተስመፈፈ ፡ እየብቻው ፡ ኼደ ፡ ተሠራጨ ፡ ዕዳሪ ፡ ለመውጣት ፡ ወንብ ፡ ለመሞከር ። ወቦአ ፡ ይትዋፈር ፡ (፩ነገ ፡ ፳፬ ፡ ፬) ።

(ጥ) **ወጽአ ፡ ኢት ፡ (ወጽአ ፡ ይዌጽእ ፡ ይወጽእ ። ወፅኦ)** ፡ ማየል ፡ መበርታት ፡ ማሸነፍ ፡ ድል ፡ መንሣት ። ነፅንንና ፡ ወይአን ፡ እይ ። ሶበ ፡ ያሌዕል ፡ ሙሴ ፡ እደሁ ፡ ይዌጽእ ፡ እስራኤል ፡ ወሶበ ፡ ያቴሕት ፡ እደሁ ፡ ይዌጽእ ፡ ዐማሌቅ ፡ (ዘፀ፲፯ ፡ ፲፩) ።

**ወጻኢ ፡ መወጽእ ፡** የሚያሸንፍ ፡ አሸናፊ ፡ ኀይለኛ ።

**ተወጽአ ፡** ተሸነፈ ፡ ድል ፡ ኾነ ፡ ተረታ ።

**ወጽአ ፡—ወጣ ፡—ወፂእ ፡ ወፅአ ።**

**ወጺብ ፡ ቦት ፡ (ወጸበ ፡ ይወጽብ ፡ ይውጽብ ። ዐረ ፡ ዐጸበ)** ፡ መሥራት ፡ መቀልበት ፡ ማፍሰስ ፡ ማቅለጥ ፡ መቀጥቀጥ ፡ የወርቅ ፡ የብር ። ዐነገንና ፡ ዐጸበን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ግር ፡ ነው ፡ በሥራው ፡ መጨነቅና ፡ መደንቅ ፡ አለበት ።

**ወጽብ ፡ ውጽብ ፡ ውጽቦ ፡ (ብ ፡ አውጻብ ፡ ባት)** ፡ ቀለበት ፡ ጕትቻ ፡ የዠሮ ፡ ወይም ፡ ያፍንጫ ፡ ጌጥ ። ውስተ ፡ ውጽቦ ፡ ወርቅ ፡ ዕንቁ ፡ ሰርድዮን ። ከመ ፡ ውጽብ ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ አንፈ ፡ ሐራውያ ። ወአምጽኡ ፡ አውጻበ ። እንበለ ፡ አውጻባት ፡ ወባዝግናት ፡ (ምሳ፲፩ ፡ ፳፪ ። ፳፭ ፡ ፲፪ ። ዘፀ፴፭ ፡ ፳፪ ። መሳ፰ ፡ ፳፮) ።

**ወጺሕ ፡ ሐት ፡ (ወጽሐ ፡ ይወጽሕ ፡ ይጻሕ ። ዕብ ፡ ያጻቅ)** ፡ ማፍሰስ ፡ ማፍሰቅ ፡ መቅዳት ፡ መጨመር ፡ ጠብ ፡ ጠብ ፡ ማድረግ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወጽሐ ፡ ፈንታ ፡ አውጽሐ ፡ ይላል ። አውጻሕከ ፡ ሎቱ ፡ ወይነ ። አውጽሐ ፡ ቢደመ ፡ አስካል ። ሶበ ፡ ኀደግነ ፡ አውጽሖ ፡ ሞጻሕት ። ይወድቅ ፡ ናሕስ ፡ ወያወጽሕ ፡ ቤት ፡ (ሚክ፪ ፡ ፲፩ ። ሚራ፵ ፡ ፲፰ ። ኤር፵፬ ፡ ፲፰ ። መክ፲ ፡ ፲፰) ። ማዋቀር ፡ መሳግ ፡ መማገር ፡ ጣራ ፡ ባጥ ፡ መሥራት ።

**አውጽሐ ፡** (አስደራጊ) ፡ አስፈሰሰ ፡ ባጥ ፡ አሠራ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ አድራጊ ፡ ነው ።

**ተወጽሐ ፡** ፈሰሰ ፡ ተቀዳ ፡ ገባ ፡ ተጨመረ ። እስመ ፡ ተወጻሕከ ፡ በምግባር ፡ እኩይ ፡ (ሂርማ ፡ ገ፳) ። በተወጽሐ ፡ ፈንታ ፡ ተዋጽሐ ፡ ይላል ፡ አያስኼም ።

**ሞጻሕ ፡ ት ፡ (ብ ፡ መዋጽሕ ፡ ት)** ፡ የመጠጥ ፡ መሥዋዕት ፡ ወይን ፡ ሥልስ ፡ ስለ ፡ ክብረ ፡ አምላክ ፡ የሚረጭ ፡ የሚፈስ ። ወአውጽሖ ፡ ሞጻሕተ ። አንሥአ ፡ እደሁ ፡ በሞጻሕት ። መሥዋዕት ፡ ወቍርባን ፡ ወሞጻሕት ፡ (፪ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፲፮ ። ሢራ፶ ፡ ፲፭ ። ሕዝ፵፭ ፡ ፲፯) ።

—፡ ማፍሰሻ ፡ መቅጃ ፡ ዋንጫ ፡ ጻሕል ፡ ጽዋ ፡ ፍንጃል ፡ የሥልስ ፡ ወጭት ። መዋጽሕ ፡ በዘየወጽሑ ፡ ቦቱ ። ቤተ ፡ መዋጽሕት ፡ (ዘፀ፴፯ ፡ ፲፪ ። ፳፭ ፡ ፳፱) ።

—፡ መዋቅር ፡ የጣራ ፡ የባጥ ፡ ዕንጨት ፡ ክርክራ ። ወመዋጽሕተ ፡ ቤትነ ፡ ዘአርዝ ፡ (ማሕ፩ ፡ ፲፯) ።

»**ጻሕጻሕ ፡** የቤት ፡ ውስጥ ፡ ፍሳሽ ፡ የጣራ ፡ ነጠብጣብ ፡ ጠፈጠፍ ። ጻሕጻሕ ፡ ይወፅእ ፡ ሰብእሲ ፡ እምቤቱ ፡ በመዋዕለ ፡ ክረምት ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፲፭) ። በዚያው ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ካንዱ ፡ ወዳንዱ ፡ ማለት ፡ መንቈራጠጥ ፡ ስፍራ ፡ መለወጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከቤት ፡ መውጣት ፡ የለም ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ጕርፍ ፡ ተቅማጥ ፡ ይሉታል ። (ተረት) ፡ እግዜር ፡ ሲቈጣ ፡ በዝናም ፡ ጊዜ ፡ ፀር ፡ ያመጣ ።

**ወጽሐ ፡—አስማጠ ፡—ወፅኖ ፡ ወፅን ።**

**ወጸፈ ፡—ወጨፈ ፡ ወነጨፈ ፡—ወፂፍ ፡ ወፀፈ ።**

**ወፂእ ፡ ኢት ፡ (ወፅአ ፡ ይወፅእ ፡ ይፃእ ። ዕብ ፡ ያጻእ)** ፡ መውጣት ፡ ከውስጥ ፡ ወደ ፡ አፍኣ ፡ ከሉብት ፡ ወደ ፡ ሌላ ። መብቀል ፡ መወለድ ፡ መፍለቅ ፡ መፍሰስ ፡ መገኘት ። እም ፡ ነበ ፡ ግእዝ ፡ ይስማሙታል ። ወፃእኩ ፡ እምከርሠ ፡ እምየ ። ወፅአ ፡ ኀበ ፡ አንዊሁ ። ንፃእ ፡ ሐቅለ ። ዘይወፅእ ፡ ጺብአ ። እምኔኪ ፡ ይወፅእ ፡ ንጉሥ ። ወፅአ ፡ እምኔሁ ፡ ደም ፡ ወማይ ፡ (ኢዮ፩ ፡ ፳፩ ። ዘፀ፪ ፡ ፲፩ ። ማሕ፯ ፡ ፲፪ ። ዘኍ፳፮ ፡ ፪ ። ሚክ፭ ፡ ፩ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፴፬ ። መሳ፲፬ ፡ ፲፬) ።

—፡ መዳን ፡ መራቅ ፡ መለየት ። ይወፅእ ፡ እምዠሎ ። ዘይወፅእ ፡ እምዓለም ። ወፅአ ፡ እምዜሉ ፡ ጥበብ ፡ (መክ፯ ፡ ፲፰ ። ፊልክ ። ሚራ፴፯ ፡ ፳፩) ።

—፡ መጥፋት ፡ መታጣት ። ምስጢሩ ፡ መራቅ ፡ መለየት ፡ ከለው ፡ ይገባል ። ኢትርሳዕ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ወኢይፃእ ፡ እምልብከ ። ኢታንብር ፡ ዕፀ ፡ ብሉየ ፡ እስመ ፡ ወፅአ ፡ መፀዛሁ ፡ (ዘዳ፬ ፡ ፱ ። ኩፋ ፡ ፳) ። በኮነ ፡ ፈንታ ፡ ወፅአ ፡ ይላል ፡ አያስኼም ። ፈረስ ፡ ዘኢተረየፀ ፡ ይወፅእ ፡ እኩየ ፡ ወልድ ፡ ዘኢተገሠጸ ፡ ይወፅእ ፡ ዝሉፈ ፡ (ሚራ፴ ፡ ፰) ።

**ወፃኢ ፡ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት)** ፡ የሚወጣ ፡ ወጭ ፡ ጪ ። በእንተ ፡ ብዝኀ ፡ በዋእያን ፡ ወወፃእያን ፡ (ፊልክ ፡ ፻፳፱) ።

**ውፁእ ፤(ኢን ፡ ኢት ፡ ፅእት)፤** የወጣ ፡ የራቀ ፡ የተለየ ፡ ልዩ ፡ ትርፍ ። ውፁኣን ፡ እምጽድቅ ። ኮኑ ፡ ውፁአ ፡ እምጸጋሁ ። ውፁእ ፡ እምኵልቍ ፡ (ሺጢኖ ፡ ፩ ፡ ፱ ። መቃ ፡ ፻፳ ። መገ ፡ ፺፯፳) ።

»**ፀአት ፤** መውጣት ፡ አወጣጥ ፤ መለየት ፡ መኼድ ። ተፈሥሑ ፡ ግብጽ ፡ በፀአቶሙ ። ሰበ ፡ በጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ፀአቱ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ። ትትፈሣሕ ፡ ነፍስ ፡ ኃርት ፡ በፀአታ ፡ እምሥጋ ፡ (መገ ፡ ፺፱ ። ቀሌ ። ዮሴፍ) ።

—፤ ዘር ፡ ትውልድ ። እምሀገረ ፡ መኑፍ ፡ ፀአቱ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፳፭) ።

—፤ ፍታት ፡ ልቅሶ ፤ ለሙታን ፡ የሚገባ ፡ ነገር ። ወኢገብረ ፡ ሕዝብ ፡ ፀአተ ፡ ቀበረ ፡ ዚኣሁ ፡ በላዕሌሁ ፡ (፪ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፲፱) ። ውጤት ፡ ውጤታ ፤ ምርት ፡ ደቄት ፡ (ዐማርኛ) ።

»**ፃት ፡ (ታት) ፤** ጣት ፡ የእጅና ፡ የእግር ፡ ቅጥይ ። የዘፍ ፡ ስም ፤ ጣት ። ሕፃን ፡ ልጠቅላ ፡ ርጥብ ፡ ስጋ ፡ ቀንበጥ ፤ ዐሩስ ፡ ወጣት ፤ ልጅ ፡ ጳጹት ። እመ ፡ ፃት ፤ እመጫት ፡ የልጠቅላ ፡ እናት ። እመጫት ፡ ደሮ ፤ እመጫት ፡ ዝንጀሮ ፡ እንዲሉ ። (ተረት) ፤ እመጫት ፡ ሆዷ ፡ ቅርጫት ።

**ሙፃእ ፤ (ኢት) ፤** መውጫ ፡ ቀዳዳ ፡ በር ፡ ደጃፍ ፡ መስኮት ፤ ዳገት ፡ ሥርጥ ፤ መሽለኪያ ፡ ስርቆሽ ፡ ሠገራ ፤ ምንጭ ። ሕልቡ ፡ ሙፃእ ፡ እማእከሎሙ ። እንተ ፡ አልባቲ ፡ ሙፃእ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ። ሙባኣቲሁ ፡ ወሙፃኣቲሁ ። ሙፃአ ፡ ሰሰሕ ። ከመ ፡ ዘይደፍኑ ፡ ዐዘቅተ ፡ ወይማስኑ ፡ ሙፃአ ፡ ማይ ። አስተርአዩ ፡ ሙፃኣተ ፡ ማያት ፡ (ዮዲ፯ ፡ ፲፫ ። ቀሌ ። ሕዝ፵፪ ፡ ፲፩ ። ስንክ ፡ ነሐ፲፰ ። ምሳ፳፭ ፡ ፳፮ ። ፪ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፲፮) ። መውጫ ፡ ነጭ ፡ ቀይ ፡ የዕጣንና ፡ የጸቃውዕ ፡ ዐይነት ፤ ከቃወቱ ፡ ዕንቁላቶች ፡ የሚወጣ ፡ መጣብቅ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሞፃእት ፤** ግዜ ፡ ከማሁ ፤ መውጫ ፡ መዝለቂያ ፡ ብቅ ፡ መባያ ፤ ጣፍ ፡ መጨረሻ ፡ ፍጻሜ ፡ (ዘኍ፴፬ ፡ ፬) ። መብእስ ፡ እበሂሃ ፡ ለፍኖተ ፡ ኃጥኣን ፡ ወጺድፍ ፡ ሞፃእታ ። ሞፃእቱ ፡ ለቅሥት ፡ የኀልቅ ፡ በመሐላ ፡ (ሢራ፳፩ ፡ ፲ ። ዕብ፮ ፡ ፲፮) ።

**አውፅአ ፤** አወጣ ፡ አሶጣ ፡ ሰደደ ። አዳነ ፡ አግዘረ ፡ አወጣኝ ፡ እንዲሉ ። አውፅኦሙ ፡ ኀቤነ ። ተፋቅሮ ፡ ታወፅእ ፡ ለፍርሀት ። አውፃእክን ፡ ዕራቃን ፡ ለዕቤራት ፡ (ዘፍ፲፱ ፡ ፭ ። ፩ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፲፰ ። ኢዮ፳፪ ፡ ፱) ።

—፤ ገፈፈ ፡ አፈሰሰ ። አውፅኡ ፡ እምእስቲሆሙ ። ኢያወፅአ ፡ ደመ ፡ (ሚክ፫ ፡ ፫ ። ጦማ) ።

**አውፃኢ ፤** የሚያወጣ ፡ አውጭ ፡ አሶጭ ፡ አስገኝ ። አውፃኢሁ ፡ ለዘእንተ ፡ ውስጥ ። አውፃኢሃ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ። ፈላስ ፡ ገ፵፱) ።

**መውፅኢ ፤** ግዜ ፡ ከማሁ ፤ የሚያወጣ ፡ አውጭ ። ማውጫ ፡ መሣሪያ ። መውፅኤ ፡ ዐይን ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፳) ።

**ተዋፅአ ፤** ተዋጣ ፡ ተወጣጣ ፤ የድግስ ፡ የገንዘብ ፡ የቃል ።

**አስተዋፅአ ፤** አዋጣ ፤ አወጣጣ ። ንብቡ ፡ የማደራረግ ፡ ሲኾን ፡ ፍችው ፡ እንደ ፡ አውፅአ ፡ ነው ፤ ማድረግና ፡ ማስደረግ ፡ አለበት ። አስተዋፅኡ ፡ ወገደፉ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ንዋዮሙ ። አስተዋፅአ ፡ ኪን ፡ ወተግባር ። ከመ ፡ ያስተዋፅኡ ፡ መጽሐፈ ፡ ፍትሕ ፡ እምብሔር ፡ ወሐዲስ ። ዘአስተዋፃእኮ ፡ ሎቱ ፡ (ዮናል ፡ ፩ ። መጽ ፡ ምስ ። ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ። ሉቃ፲ ፡ ፴፭) ። ወአሐውር ። አስተዋፅአ ፡ ምጽዋተ ። አስተዋፅአ ፡ ለመድፍንክ ፡ በእንተ ፡ ትእዛዙ ፡ ለልዑል ። እለ ፡ ያስተዋፅኡ ፡ ብዑሎሙ ፡ በሠናይ ፡ ለእመ ፡ ቦ ፡ ምንትኒ ፡ ዘአጥረይነ ፡ ናስተዋፅእ ፡ በዘይደልዎ ። ወአስተዋፅአት ፡ ዘሎ ፡ ንዋያ ፡ ወአኅለቀት ፡ (ጦቢ፩ ፡ ፯ ። ሢራ፳፱ ፡ ፲፩ ። አፈ ፡ ተ፱ ። ማር፭ ፡ ፳፮) ። ይህ ፡ የተጠቀሰ ፡ ጥቅስ ፡ ኹሉ ፡ በአውፅአ ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፡ ነው ፤ መሳሾች ፡ አበላሽተውታል ።

»**ፃእፃእ ፤ (ዕብ ፡ ጼኤጻኢም ። ሀረ ፡ ፂእፂእ ፤ ልጆች) ፤** ፍንጋፍ ፡ ውርጃ ፡ ሽል ፡ አለቀኑ ፡ ከ፱ ፡ ወር ፡ በፊት ፡ የወጣ ። ዝብጠታተ ፡ ፃእፃእ ፡ በማሕፀን ። ከመ ፡ ፃእፃእ ፡ ዘአድኀፀቶ ፡ ማሕፀኑ ፡ እሙ ። ብእሲት ፡ ዘትበቲ ፡ ፈውሰ ፡ ከመ ፡ ታድኅፅ ፡ ፃእፃኣ ፡ እማሕፀና ፡ (ሔኖ፷፱ ፡ ፲፪ ። ኢዮ፫ ፡ ፲፮ ። ፈ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፱) ።

—፤ ጣጣ ፤ ጕዳይ ፡ መፍቅድ ፤ ዕዳ ፡ ግብር ፤ ገንዘብ ፡ የሚያሻ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነገር ። ወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ቤት ፡ ሠራ ፡ ለሠራተኞች ፡ የሚሰጠው ፤ ለኖራ ፡ ለንጨት ፡ ለደንጊያ ፡ ለብረት ፡ የሚያወጣው ፤ ወይም ፡ ሕዝብ ፡ የሚያዋጣው ፡ ግብር ፡ የመዋጮ ፡ ገንዘብ ፡ (ሉቃ፲፬ ፡ ፳፰ ። ፪ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪) ። አብኡ ፡ እመዝገብ ፡ ለፃእፃአ ፡ ግብር ። የሀብዎሙ ፡ እምቤተ ፡ ንጉሥ ፡ ለፃእፃእሙ ። እንዘ ፡ መጠኑ ፡ ዝ ፡ ፃእፃኡ ። ዘላዕሌሁ ፡ ፃእፃአ ፡ ቤቱ ፡ (ዕዝ፪ ፡ ፷፱ ። ፯ ፡ ፱ ፡ ፰ ። ነሐ፳ ፡ ፲፰ ። ጦቢ፩ ፡ ፳፪) ።

»**ፃእዕአ ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤** ጨነገፈ ፤ አሶረደ ።

**አፃእዕአ ፤** አስጨነገፈ ። አብቃቃ ፡ አኮላሸ ። ወእምነሁ ፡ ያፃአፅኡ ፡ ለነደቅት ፡ ወለጸረብት ፡ (፪ዜና ፡ ፳፬ ፡ ፲፪) ።

**ተፃእዕአ ፡ ተፀአዕአ ፤** አነሰ ፡ ተቀነሰ ፡ እንስንስ ፡ አለ ፡ ጭንጋፍ ፡ ኾነ ። ሰገደ ፡ ተዋረደ ፤ ለጣዖት ፡ ተገዛ ። ወተፀአፀኡ ፡ ተግባሮ ፡ (ሮሜ፩ ፡ ፳፫) ። ፍጡር ፡ ኹሉ ፡ ፈጣሪ ፡ አለኝ ፡ ማለቱ ፡ እንደ ፡ መዕንስና ፡ እንደ ፡ መፀንስ ፡ ነው ፤ በፈጣሪ ፡ ፈንታ ፡ ፍጥረትን ፡ ማምለክ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ መውረድ ፡ እንደ ፡ ማሶረድ ፤ ዘርፉ ፡ እንዳለመቃም ፡ ወልድ ፡ እንዳለመሳም ፡ ነውና ፤ ምስጢሩ ፡ የውቀትን ፡ ሕጸጽ ፡ ተፀንሶ ፡ በቅሎ ፡ አለማደግን ፡ ባጭር ፡ መቀጨትን ፡ በዝርዝር ፡ መቅረትን ፡ ያሳያል ።

(ጥ) **ወዕኖ ፤ ኖት ፤ (ወዕነ ፡ ይዌዕን ፡ ይወዕን ። መንፀ) ፤** ማስማጥ ፡ ማስጨነቅ ፡ መፍጨት ፡ መቀጥቀጥ ፤ የሆድ ። መንፀንና ፡ ወዕኦን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**ተወዕነ ፤** አማጠ ፡ በምጥ ፡ ተያዘ ፡ ተጨነቀ ፡ ተፈጨ ፡ ተቁላ ። ወይትዌፃን ፡ ከመ ፡ ማሕምም ፡ እ


ንተ ፡ ትወልድ ፡ ሕፃን ፡፡ (ሚራ ፲፱ ፡ ፲፰ ። ኦሬ ፡ ተ፳፭ ። አርጋ ፡ ፭) ።

**ትውፅኅት** ፤ ምጥ ፡ ጭንቅ ፤ አህታ ፡ የሆድ ፡ በሽታ ፡ (ቂድር ፡ ገ፶፱) ።

**ወፂፍ ፤ ፎት ፤ (ጺ.) (ወፀፈ ፡ ይዌፅፍ ፡ ይውፅፍ ፤ አው ፡ ይወፅፍ ፡ ይፀፍ)** ፤ መወጨፍ ፡ መርጨት ፤ የዝናም ። መወንጨፍ ፡ ማወንጨፍ ፤ መወርወር ፤ መምታት ፤ የድንጊያ ፡ (፭ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፵፱) ። ትዌፅፍ ፡ አእባነ ፡ ቢሥረዊሃ ፡፡ ወፀፎ ፡ በእብን ፡ ወሄደ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሙ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ሢራ፵፯ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፻፵፭) ።

**ወፃፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ፀፍት)** ፤ የሚወረውር ፡ የሚወነጭፍ ፤ ወንጫፊ ፡ ወርዋሪ ፤ ባለወንጭፍ ። ወፃፍያን ፡ በሞፀፍት ፡ እብን ፡፡ ወፀፍት ፡ ወነደፍት ፡ (፭ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፪ ። ፪ዜና ፡ ፲፬ ፡ ፰) ።

**ሞፀፍ ፤ ት ፤ (ብ ፡ መዋፅፍ ፡ ት)** ፤ ማወንጨፊያ ፤ ብድል ፡ ነጉድ ፡ ወንጭፍ ። ንፍጥ ፤ መድፍ ። ዘይወዲ ፡ እብነ ፡ ዲበ ፡ ሞፀፍ ፡፡ እብነ ፡ ሞፀፍ ፡፡ ሰብአ ፡ ሞፀፍ ፡፡ ሞፀፍት ፡ እብን ፡፡ መዋፅፍት ፡ እብን ፡ (ምሳ፳፮ ፡ ፰ ። ዘካ፱ ፡ ፲፭ ። ዮዲ፯ ፡ ፲፪ ። መሳ፳ ፡ ፲፮ ። ፪ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፲፬) ። መዋጽሕት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ የመጽሐፍ ፡ ጥፋ ፡ ለወፀፈ ፡ ሰጥቶ ፡ መዋጽፍት ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። እኩ ፡ በአሕባል ፡ ዘይጠፍሮን ፡ ወእኩ ፡ በመዋጽፍት ፡ ወበማዕር ፡ ዘይከድኖን ፡፡ ዘእንበለ ፡ ዕፀ ፡ ወመሬት ፡ ወዘእንበለ ፡ አሕባለ ፡ ጠፈር ፡ ወመዋጽፍት ፡፡ መዋጽፍት ፡ ዘዕፀ ፡ (ገድ ፡ ላሊ) ።



ሞፀፍ ።

**ተወፅፈ** ፤ ተወነጨፈ ፡ ተጣለ ፤ ተወረወረ ። ወነፍስ ፡ ጸላእትከሰ ፡ ተወፅፈት ፡ በማእከለ ፡ ሞፀፍ ፡፡ ሊይትወፀፉ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፳፱ ። ዘዐ፲፱ ፡ ፲፫) ።


**ውፁፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ፅፍት)** ፤ የተወነጨፈ ፡ የተጣለ ፡ የተወረወረ ።

**ተዋፀፈ** ፤ ተወናጨፈ ፡ ተወንጫጨፈ ፡ ተወራወረ ።

**ወፅፍ ፤ ወፀፍ** ፤ ወጨፎ ፡ ስረይ ፡ ውሽንፍር ፤ የወንጭፍ ፡ ድንጊያ ፤ ጥይት ፡ ዐረር ።

**ወቂሕ ፤ ሖት ፤ (ወቅሐ ፡ ይወቅሕ ፡ ይቃሕ ። ዐረ ፡ ወክ)** ፤ ማሰር ፡ ማጥበቅ ፤ ማስተሳሰር ፤ ማቈራኘት ፤ ማቋለፍ ፡ ማቈላለፍ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወቅሐ ፡ ፈንታ ፡ ሞቅሐ ፡ ይላል ፡ ወገደኛና ፡ ወገስን ፡ ነሰውን ፡ እይ ፤ አካኼዳቸው ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ሞቅሕ ፤ (ብ ፡ መዋቅሕት)** ፤ ማሰሪያ ፡ ማቈራኛ ፤ ሰንሰለት ፡ እግረ ፡ሙቅ ፡ ወይም ፡ እግር ፡ ብረት ፤ ቀንበር ፡ መንቈር ፤ ዛንጅር ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ወድቃ ፡ መዋቅሕት ፡ እምእደዊሁ ፡፡ ሰበርኩ ፡ መዋቅሕቲክሙ ፡፡ መዋቅሕቲሃ ፡ ዘብርት ፡፡ አሕመምዎሙ ፡ በመዋቅሕት ፡ (ግብ፲፪ ፡ ፯ ። ዘሌ፳፮ ፡ ፲፫ ። ሚራ፳፯ ፡ ፳ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፫) ።



ሞቅሕ ።

—፤ ግዞት ፡ እስራት ፤ የግዞት ፡ ቤት ፤ ሐብስ ፡ ወህኒ ። ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡፡ ህለወ ፡ ውስተ ፡ ሞቅሕ ፡፡ ወደዮሙ ፡ ውስተ ፡ ሞቅሕ ፡ (ማቴ፲፩ ፡ ፪ ። ኩፋ ፡ ፴፱ ። ዘፍ፵ ፡ ፫) ።

**ሞቅሐ ፤ (ወቅሐ)** ፤ ያዘ ፡ አሰረ ፡ አጋዘ ፤ አቈራኘ ፡ ከወህኒ ፡ አገባ ። ሙኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘይሞቅሖ ፡ ለእዴየ ፡፡ ሞቅሕዎ ፡ ብንዲን ፡፡ አዘዘ ፡ ይደዩ ፡ ጋጋ ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ፡ ወይሞቅሕዎ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡፡ ዕደው ፡ እለ ፡ ሞቃሕክምዎሙ ፡ (ኢዮ፲፯ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ሚያ፳ ። ጎዳ፳፯ ። ግብ፭ ፡ ፳፭) ።

**ሞቃሒ ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት)** ፤ የሚያስር ፡ አሳሪ ፤ እስር ፡ ጠባቂ ፡ ዘበኛ ። ሰገደ ፡ ሞቃሒ ፡ ለሙቁሓን ፡ (ኦሬ ፡ ተ፳፮) ።

**አሞቅሐ** ፤ አሳሰረ ፡ አስጋዘ ፤ ያዙት ፡ እሰሩት ፡ አለ ። ወአሞቅሖ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይፌድዮ ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፴) ።

**ተሞቅሐ** ፤ ታሰረ ፡ ተጋዘ ። እገሪከ ፡ ኢተሞቅሓ ፡፡ ዘኢተሞቅሐ ፡ በማእሰሩ ፡፡ ተሞቂሖክ ፡፡ በተቀሥፎ ፡ ወበተሞቅሖ ፡፡ ወለጠ ፡ ልብሰ ፡ ተሞቅሖቱ ፡ (፪ነገ ፡ ፫ ፡ ፴፬ ። ሚራ፳፫ ፡ ፲፱ ። ማቴ፳፭ ፡ ፴፱ ። ፪ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፭ ። ኤር፶፪ ፡ ፴፫) ።

**ሙቁሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ቅሕት)** ፤ የታሰረ ፡ የተጋዘ ፤ እስር ፡ ግዞተኛ ። እግር ፡ ሙቁሕ ፡፡ ሙቁሓን ፡ እደዊሆሙ ፡፡ እለ ፡ ሙቅሕታ ፡ ትነብር ፡ ነፍሶሙ ፡ (ሚራ፳፩ ፡ ፲፱ ። ኢሳ፵፭ ፡ ፲፱ ። ፩ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፱) ።

**ሙቃሔ ፤ (ሕያት)** ፤ ማሰር ፡ መታሰር ፡ አስተሳሰር ። እስራት ፡ ግዞት ፤ የግዞት ፡ ቤት ። እመ ፡ ሙቃሔሁ ፡፡ ሙቃሔ ፡ ጽኑዕ ፡፡ አ ፡ ዘረታሕከ ፡ እሙቃሔ ፡ እግሩ ፡ ወእዴ ፡፡ ውስተ ፡ ሙቃሔሁ ፡ ኢትደገቶ ፡ (ስንክ ፡ ግን፲፱ ። መስ፯ ። ጥብ ፡ ጠቢ ። ጥበ፲ ፡ ፲፬) ።

**ተሟቅሐ ፤ (ይትሟቃሕ ፤ አው ፡ ተም(መ)ዋቅሐ ፡ ይትመዋቃሕ)** ፤ ተሳሰረ ።

**አስተሟቅሐ ፤ (ያስተሟቅሕ ፤ አው ፡ አስተም(መ)ዋቅሐ ፡ ያስተመዋቅሕ)** ፤ አስተሳሰረ ።

**ወቅይ ፤ ዮት ፤ (ወቀየ ፡ ይወቂ ፡ ይቀይ ። ዐረ ፡ ወቀይ)** ፤ መጠበቅ ፤ መጠባበቅ ፤ ድውይን ፡ በጊዜ ፡ ሞት ። ከመ ፡ ይናዝዝዎ ፡ ወይወቅይዎ ፡ ፍልሰቶ ፤ (ስንክ ፡ ጥቅ፳) ።

—፤ መቍረጥ ፡ መቀርጠፍ ፡ መቅፅፅት ፡ መዘለፍ ። ወቅዐን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በወቀየ ፡ ፈንታ ፡ አውቀየ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ኢይወቅዮ ፡ ርእሶ ። ኣወቂ ፡ ቍልፈተ ፡ ልቦሙ ። አውቀዮ ፡ ክሣዶ ፡ በአሐቲ ፡ ዝብጠት ። አዘዘ ፡ ያውቅዩ ፡ ልሳና ፡ እምጕንዱ ፤ (ዘሌ፳ ፡ ፴ ። ክብ ፡ ፭ ። መቃ ፡ ገ፺ ። ስንክ ፡ መስ፺ ። ሮሜ፲፭ ፡ ፳፪) ።

**አውቀየ** ፤ አስቈረጠ ፤ አስቀረጠፈ ፤ ልማዱ ፡ ግን ፡ አድራጊንት ፡ ነው ።

**ሞቀይ ፤ ት ፤ (ብ ፡ መዋቅይ)** ፤ መቍረጫ ፡ መቀርጠፊያ ፤ መዘለፊያ ። መዋቅየ ፡ ኣምትንት ፡ ወሥርው ፤ (ስንክ ፡ ጥር፲፩) ።

**ተወቅየ** ፤ ተቈረጠ ፤ ተቈራረጠ ፤ ተገዘረ ፡ ተቀረጠፈ ። በሰይፍ ፡ ተወቅየ ። ጕንደ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘኢይትወቀይ ። ኢፈርሀ ፡ ሕማመ ፡ ተወቅዮ ፡ ቍልፈተ ፡ ነፍስቱ ፤ (ስንክ ፡ ሚያ፳፯ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ውቁይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ቅይት ፡ ቂት)** ፤ የተቈረጠ ፤ ቍርጥ ። አርዮስ ፡ ውቁይ ፡ በሰይፈ ፡ መርገም ፤ (ስንክ ፡ ነሐ፲፰) ።

**ውቅየት ፤ (ቃት)** ፤ መቍረጥ ፡ መቈረጥ ፡ አቈራረጥ ፤ ቁረጣ ፡ ቅርጠፋ ። ዐሜር ፡ ቈራጣ ፡ ስናፈል ፡ ቍምጣ ፡ ሱሪ ፡ ግልድም ፡ ሽርጥ ፤ የወንድ ፡ የሴት ። ክቡራት ፡ ቀማይሳቲ ፡ ወውቅየታተ ፡ ህናያቲ ። ወገብሩ ፡ ውቅየተ ፡ ጎጺን ፡ ዘአምሳለ ፡ ግላ ፤ (አዋል ። ስንክ ፡ ሐም፳) ።

**ወቄት ፤ (ብ ፡ አውቅያት ። ዐረ ፡ ወቂየት)** ፤ በቁሙ ፤ የሚዛን ፡ ስም ፡ የልጥር ፡ ፲፪ኛ ፤ አንዱ ፡ ወቄት ፡ ፲ ፡ ድሪም ፤ አላዱ ፡ ወይም ፡ እክሌታው ፡ ፲፰ ፡ ድሪም ፡ ይኸናል ፤ ልጥርን ፡ እይ ። ወክ፩ ፡ ሄጠ ፡ ሕልቅ ፡ ሠላሳ ፡ አምሌ ፡ ወወቄት ፡ ለአሐዱ ፡ ብዕራይ ። ወብየ ፡ አውቅዮተ ፡ ወርቅ ፤ (ሥር ፡ አክ ። ፈላስ) ።

**ወቅት ፤ (ብ ፡ አውቃት ። ዐረብ)** ፤ ጊዜ ፡ ወራት ። ዓመታት ፡ ወአውቃት ፤ (ስንክ ፡ ግን፳፪) ።

**ውቅያኖስ ፤ (ጽር ፡ ዖኬያኖስ)** ፤ በቁሙ ፤ ዓለሙ ፡ ማይ ፤ ዐቢይ ፡ ባሕር ፡ ሰፊ ፡ ጥልቅ ፡ ዕሙቅ ፤ ባሕቱ ፡ ማእዘን ፡ የመላ ፤ ከየብስ ፡ ፫ ፡ እጅ ፡ የሚበልጥ ፡ እንደ ፡ የብስ ፡ ፭ ፡ ክፍል ፡ ያለው ። ባሕር ፡ ለታላቅ ፡ ለታናሽ ፡ ይኸናል ፤ ውቅያኖስ ፡ ግን ፡ ለታላቅ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ባሕረ ፡ ውቅያኖስ ፤ (ዮሴፍ ። አርጋ ፡ ፩) ።

**ወቂሥ ፤ ሦት ፤ (ወቀሠ ፡ ይወቅሥ ፡ ይውቅሥ ፤ አው ፡ ይቀሥ)** ፤ መውቀሥ ፡ መክሰስ ፡ መንቀፍ ፡ መዝለፍ ፡ መገሠጽ ፡ መምከር ፡ መንገር ፡ መናገር ፤ ቃልን ፡ ማፍሰስ ፡ መዘርዘር ። ምንተ ፡ ንብል ፡ ወምንተ ፡ ንወቅሥ ። አኀዘ ፡ ይውቅሣ ፤ (ይቀሣ) ። አልብነ ፡ በዘ ንወቅሥ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ሀከክ ። ፈቀደ ፡ ይውቅሥ ፡ ለዐውድ ። እወቅሥ ፡ ጽድቀኪ ፡ ወተግባረኪ ፤ (ኪሩ ፡ ሚ፳ ። ዮሴፍ ። ግብ፲፱ ፡ ሚ ፡ ፴፫ ። ኢሳ፶፯ ፡ ፲፪) ።

**ወቃሢ ፤ (ሢት ፡ ሥያን ፡ ያት)** ፤ የሚወቅሥ ፡ ወቃሽ ፡ ከሳሽ ። ወቃሥያን ፡ ዘእንበለ ፡ ፍትሕ ። ላዕለ ፡ ወቃሢ ፡ ይደሉ ፡ አቅሞተ ፡ ለማዕት ፤ (መቃ ፡ ገ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱) ።

**ሙቃሥ ፤ (ሣት)** ፤ መውቀሻ ፡ መወቀሻ ፡ መዋቀሻ ፡ መክሰሻ ፡ ቦታ ። በአሐዱ ፡ ዐውድ ፡ ወበአሐቲ ፡ ሙቃሥ ፤ ዐውደ ፡ ሙቃሥ ። አሐዱ ፡ ክብር ፡ ወመንግሥት ፡ ወምኵናን ፡ ወሙቃሥ ፤ (መጽ ፡ ምስ ። ድራሴ) ።

**ተወቅሠ** ፤ ተወቀሠ ፡ ተመከረ ፤ ተገሠጸ ። ይትወቀሥ ፡ እምሰብአ ፡ ሀገር ፡ እስከ ፡ አሆ ፡ ይቤ ፡ ወይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ መንበሩ ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**ውቁሥ ፤ (ሣን ፡ ሣት ፡ ቅሥት)** ፤ የተወቀሠ ፤ የተነቀፈ ፡ የተዘለፈ ።

**ተዋቀሠ** ፤ በቁሙ ፤ ተሟገተ ፡ ተከራከረ ። ንዑ ፡ ንትዋቀሥ ። ኵሉ ፡ ይትዋቀሥ ፡ ለእኁሁ ። ኢክህለት ፡ ተዋቅሦተክሙ ፤ (ኢሳ፩ ፡ ፲፰ ። ሚ፮ ፡ ፪ ። ዳንኤ ፡ ፶፪) ። በወቀሠ ፡ ፈንታ ፡ ተዋቀሠ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ተዋቀሥዋ ፡ ለእምክሙ ። መኑ ፡ ይትዋቀሦሙ ፤ (ሆሴ፪ ፡ ፪ ። ሮሜ፰ ፡ ፴፫) ።

**አስተዋቀሠ** ፤ አዋቀሠ ፡ አወቃቀሠ ፤ አሟገተ ፡ አከራከረ ። ሶበሁ ፡ ያስተዋቅሥዎ ፡ ለሰብእ ፡ ምስለ ፡ እግዚ ። አስተዋቅሦሙ ፡ ለኵሉ ፡ አሕዛብ ፤ (ኢዮ፲፮ ፡ ፳፩ ። ዮኤ፬ ፡ ፲፪) ።

**መስተዋቅሥ** ፤ የሚያዋቅሥ ፡ የሚያከራክር ፤ ዳኛ ። የሚዋቀሥ ፡ ተዋቃሽ ፡ ተከራካሪ ፤ ባለጋራ ። እስመ ፡ መስተዋቅሥ ፡ ጽኑዕ ፡ ውእቱ ፤ (ቅዳ) ።

**ቅሥት ፤ (ቃት)** ፤ ወቀሣ ፡ ክሰሳ ፤ ጠብ ፡ ክርክር ፤ ሙግት ፡ ፍርድ ። ቅሥተ ፡ ጊጉይ ። ማየ ፡ ቅሥት ። ንግር ፡ ቅሥተከ ። ኢመፍትው ፡ ትግበሩ ፡ ቅሥተ ፡ በሰንበተ ፡ ክርስቲያን ። አልቦ ፡ ዘይክውን ፡ ቅሥት ፤ (ሚራ፲፭ ፡ ፱ ። ዘኁ፳ ፡ ፲፫ ። ማቴ፳፯ ፡ ፭ ። ዲድ ፡ ፲ ። መክ፰ ፡ ፲፭) ።

**ወቂዕ ፤ ዖት ፤ (ወቅዐ ፡ ይወቅዕ ፡ ይቃዕ ። ዐረ ፡ ወቀዐ)** ፤ መውቃት ፡ መምታት ፡ መደብደብ ። በሙቃዕ ፡ ይወቅዕዎ ፤ (ኢሳ፳፰ ፡ ፳፯) ።

—፤ መግፈፍ ፡ መላጥ ። ወይወቅዕዎ ፡ ወይፈልጡ ፡ መለያልዮ ፡ ዘዘ ፡ ዚኣሁ ፤ (ዘሌ፩ ፡ ፮) ። ቈርበቱን ፡ ከሥጋው ፡ ለመለየት ፡ እግሩን ፡ ሠንብጠው ፡ በታናሽ ፡ ሸንበቆ ፡ እየነፉ ፡ ይመቱታልና ፤ ዘይቤው ፡ ውቂዖን ፡ አይለቅም ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ ወይወቅይዎ ፡ ይላል ፡ ማረድ ፡ ማጠራረድን ፡ መቍረጥ ፡ መክትክትን ፡ ያሳያል ፤ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ አይወጣም ።

**ወቃዒ ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት ፤ ዕት)** ፤ የሚወቃ ፡ ወቂ ፤ ነፊ ፡ ገፋፊ ።

**ተወቅዐ** ፤ ተወቃ ፡ ተመታ ፡ ተገፈፈ ።

**ውቁዕ**፤(ዓን፡ ዓት፡ ቅዕት)፤ የተወቃ፡ የተገፈፈ፡ የተላጠ ።

**ሙቃዕ፤ ሞቅዕ**፤(ብ፡ ሙቃዓት፤ መዋቅዕ ። ዐረ፡ ሚቀዐት፤ መዶሽ)፤ መውቂያ፡ መግፈፊያ፤ ፍሬን፡ ከገለባ፡ ሥጋን፡ ከቈርበት፡ ዕንጨትን፡ ከቅርፊት፡ የሚለዩበት፡ መሣሪያ፡ ቦታ ።

**ወቀፈ**፤(ዐረ)፤ ቆመ፤ የሐቀፈ፡ ሞክሸና፡ መንቲያ፡ ሐቀፈን፡ እይ ።

**ወቅፍ**፤(ብ፡ አውቃፍ፤ ፋት ። ዐረብ)፤ አንባር፡ ቀለበት፡ እጅን፡ ጣትን፡ ዐቅፎና፡ ከቦ፡ የሚይዝ፡ ቀዋሚ፡ የእጅ፡ ጌጥ ። ኢኀሥሣ፤ አውቃፈ፤ ብሩር፤ ወወርቅ፤ ለስርጋዌሆን ። ወደይኩ፤ አውቃፋተ፤ ውስተ፤ እደውኪ ። አርባዕቱ፤ አውቃፋት፤(ደራሲ ። ሕዝ፲፮፡ ፲፩ ። ዘፀ፳፮፡ ፲፱) ።

**ወቂር**፤ ሮት፤(ወቀረ፡ ይወቅር፡ ይቅር ። ዐረብ)፤ መውቀር፡ ማስዘብ፤ መቈፈር፡ መጥረብ፡ የደንጊያ፡ የገደል፡ የዋሻ፡ የጕድጓድ ። ወቀረ፤ ውስተ፤ ኰኵሕ፤ ግበበ፤ ብዙኃ ። ዘይወቅርሂ፤ ወዘይጸርብ ። እንዘ፤ ይወቅር፤ ረከበ፤ አእባነ፤ ወርቅ ። ርእይዎ፤ ለኰኵሕ፤ እንተ፤ ወቀርክሙ ። መካን፤ ዘወቀረ፤ ሎቱ ። ቀር፤ ለከ፤ ክልኤ፤ ጽላተ፤ ዘእብን፤(፪ዜና፡ ፳፮፡ ፲ ። ገድ፡ ላሊ ። ስንክ፡ ግንቦ ። ኢሳ፶፩፡ ፩ ። ጥበ፲፫፡ ፲፩ ። ዘፀ፴፬፡ ፩) ። ማዋቀር፡ መቋጠር፡ በግንብ፡ በግድግዳ፡ ላይ፡ ጣራ፡ ባጥ፡ መሥራት ።

**ወቃሪ**፤(ሪት፡ ርያን፡ ያት፤ ቀርት)፤ በቁሙ፡ የሚወቅር፤ የሚያዋቅር፤ ጠራቢ ። ወቀርተ፤ እእብን፤ ወፈሐቅት፤(፩ዜና፡ ፳፪፡ ፪ ። ፪ነገ፡ ፭፡ ፲፭) ።

**አውቀረ**፤ አሶቀረ፡ አስቈፈረ፤ አስጠረበ፤ ውቅር፡ አሠራ ። አውቀረ፤ ኰኵሐ፤ በኀጺን ። አውቀርከ፤ ለከ፤ ዝጎረ፤ ውስተ፤ ኰኵሕ ። አውቀረ፤ ላቲ፤ መንፈስ፤ ቅዱስ፤ ጥምቀተ፤ መቃብረ፤ ነፍስ፤ ወንተማ፤ በአእባን፤ ሠላስ፤(ሚራግ፰፡ ፲፯ ። ኢሳ፳፪፡ ፲፮ ። ቅኔ) ።

**ተወቅረ**፤ ተወቀረ፡ ተጠረበ፡ ተቈፈረ፡ ተዋቀረ ። እብን፤ ዘኢተወቅረ ። ጽኑዓት፤ እማንቱ፤ ለተወቅሮ፤(ኢያ፰፡ ፴፫ ። ሄርማ፡ ገ፹፩) ።

**ውቁር**፤(ራን፡ ራት፡ ቅርት)፤ የተወቀረ፡ የተዋቀረ፡ ውቅር፡ ጥርብ፡ ልዝብ ። እብን፤ ውቁር ። እበን፤ እለ፤ ኢኮና፤ ውቁራት፤(፬ነገ፡ ፲፪፡ ፲፪ ። ዘዳ፳፯፡ ፮) ።

**ውቅሮ**፤ ዋሻ፡ ፍርኩታ፡ ጕድጓድ፡ መቃብር፡ ተጠርቦ፡ ተወቅሮ፡ ታንጾ፡ ተቈፍሮ፡ የተሠራ ። ዐዘቅተ፤ ውቅሮ ። ቤት፤ ዘውቅሮ ። ርእስ፤ ዘውቅሮ ። እብነ፤ ውቅሮ፤(ነሐ፱፡ ፳፭ ። ጥበ፲፫፡ ፲፭ ። ዘዳ፫፡ ፳፮ ። ፬ነገ፡ ፳፱፡ ፮) ።

—፤ ጥርብ፡ ደንጊያ፡ ገንቢዎች፡ በየረድፉ፡ የሚሰድሩት፡ የሚደረድሩት ። አረፍት፤ ዘኢኮነ፤ በውቅሮ ። ወበዐውዱ፤ ሠለስቱ፤ ጾታ፤ ዘኢኮነ፤ ውቅሮ፤ ወአርባዕቱ፤ ጾታ፤ በውቅሮ ። አብያተ፤ ዘውቅሮ፤ መኒኒክ፤(፫ነገ፡ ፯፡ ፲፫ ። ፯፡ ፲፱ ። ድጓ) ። በውቁር፡ ፈንታ፡ ውቅሮ፡ ይላል፡ አያስኬድም ። ማእዳት፤ ዘእብን፤ ውቅሮ፤(ሕዝ፵፡ ፵፪) ።

**ሞቀር**፤ ርት፤(ብ፡ መዋቅር)፤ መውቀሪያ፡ መጥረቢያ፤ የደንጊያ፡ መሣሪያ፡ የነጠረ፡ ብረት ። መዋቅረ፤ እብን፤(አዋል) ።

**ወቀሰ**፤—በቁሙ፤—ወቂሶ፡ ወቀሠ ።

**ወቄት**፤ ወቅት፤—በቁሙ፤—ወቅይ፡ ወቀየ ።

**ወሪእ**፤ ኦት፤(ወርአ፡ ይወርእ፡ ይራእ ። ዐረ፡ ወረ)፤ መስወር፡ መደበቅ፤ መሸፈን፡ መጋረድ፡ የንፍረት፡ ስሌሳም፡ ይኾናል ።

**ሞራእ**፤(ብ፡ መዋርእት)፤ ግልድም፤ ሽርጥ፡ ማጠቆ፤ መታጠቂያ ። ተሣየጥ፤ ለከ፤ ሞራአ ። ስፈይ፤ ቈጽለ፤ በለስ፤ ወገብሩ፤ ሎሙ፤ መዋርእተ፤(ኤር፲፫፡ ፩ ። ዘፍ፫፡ ፯ ። ኩፋ፡ ፫) ።

—፤ በቁሙ፡ ሞራ፤ የኀዋየ፡ ውስጥ፡ ልብስ፡ የሆድ፡ ዕቃ፡ ሽፋን፤ ሥሥ፡ እንደ፡ ክርታስ፡ ያለ፤ ጋሎች፡ የሚያሟርቱበት፡(በማርኛ) ።

**ወሪድ**፤ ዶት፤(ወረደ፡ ይወርድ፡ ይረድ ። ዐረብ ። ዕብ፡ ያራድ)፤ መውረድ፡ መቈልቈል፤ ከላይ፡ ወደ፡ ታች፡ መውደቅ፡ መዝነም፡ መፍሰስ ። እምና፡ ውስተ፡ ዲበ፡ ላዕለ፡ ይስማሙታል ። ጕንደየ፤ ወሪደ፤ እምደብር ። ወረደ፤ እምሰማይ ። ረድ፤ እመስቀልከ ። እንዘ፤ ማይ፤ ይረድ፤ ውስተ፤ ቀላይ ። ወረደ፤ ዐፃ፤ ላዕለ፤ ዮናስ ። ፍርሀት፤ ወረዓድ፤ ወረደ፤ ላዕሌሁ፤(ዘፀ፴፱፡ ፩ ። ማቴ፳፯፡ ፱ ። ማር፲፭፡ ፴ ። ኩፋ፡ ፳ ። ዮናእ፡ ፯ ። ሉቃ፩፡ ፲፪) ።

—፤ መዋረድ፡ ትሑት፡ መኾን ። መጽሐፍ፡ ግን፡ በወረደ፡ ፈንታ፡ ተወርደ፡ ተወረደ፡ ተዋረደ፡ ይላል፡ አያስኬድም፡ ተ፡ ያማርኛ፡ ነው ። ተወርዶቱ፤ ለእግዚ፤ ኀበ፤ ከዊነ፤ ብብእ ። ለቀሲስ፤ ብዉሕ፤ ሎቱ፤ ከመ፤ ይትወረድ፤ ኀበ፤ መልእክተ፤ ካህናት፤ እለ፤ እምታሕቴሁ ። ነቢያትኒ፤ ይትዌረዱ፤ ለበዓል ። በፍትወተ፤ ነፍሳ፤ ትትዌረድ ። ነጽርኬ፤ ዘከመ፤ እፎ፤ ይትዋረድ፤ ርኢክኑ፤ ከመ፤ ዝንቱ፤ ሐገ፤ ተዋርደ ። ወለተ፤ እንተ፤ ይትዋረዳ፤ ጋኔን፤(መጽ፡ ምሥ ። ኤር፪፡ ፰፡ ፳፱ ። አፈ፡ ድ፪፡ ፰ ። ግብ፲፯፡ ፲፯) ። እንደ፡ ዘንመ፡ ዐጕል፡ ስለ፡ ኾነ፡ ሌላ፡ ተገብሮ፡ የለውም ።

**ወራዲ**፤(ዲት፡ ድያን፡ ያት)፤ የሚወርድ፡ ወራጅ፡ ፈሳሽ፡ የሚዋረድ፡ ተዋራጅ ።

**ውሩድ**፤(ዳን፡ ዳት፡ ርድ)፤ የወረደ፡ የተዋረደ፡ ወደ፡ ታች፡ ያለ፤ ወራዳ፡ ትሑት ። ውሩድ፤ ግልባቤሃ፤ ውስተ፤ ገጻ፤(ሄርማ፡ ገ፳፩) ።

**ርደት**፤ መውረድ፡ መዋረድ፤ አወራረድ፡ ትሕትና፡ ውርደት ። ወራድነት ። ርደቱ፤ ለወልድ፤ እም

ሰማይ ። ከመ ፡ ርደት ፡ ንስር ። ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ርደተከ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ በእንተ ፡ ፍቅረ ፡ ሰብእ ። ርደተ ፡ ዝናማት ። ወከመ ፡ ርደት ፡ አንበጣ ፡ ርደቱ ፤ (ቀሌ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፲፪ ። ማንዘ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፪ ። ሚራ፲፫ ፡ ፲፯) ።

**ሙራድ ፤ (ዳት)** ፤ መውረጃ ፡ ቊልቊለት ፤ ዕርከን ፡ መሰላል ። ሙራደ ፡ ደብር ። ሙራደ ፡ ዐቀብ ፡ ዘደብረ ፡ ዘይት ። ይውሕዝ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ውስተ ፡ ሙራድ ። በበ ፡ ሙራዶሙ ፤ (ኢያ፰ ፡ ፳፱ ። ሉቃ፲፱ ፡ ፴፯ ። ኢሳ፴ ፡ ፳፰ ። ፍ ፡ ን ፡ ፶፪) ።

**አውረደ** ፤ አወረደ ፡ አዋረደ ፤ ሻረ ፤ አሶረደ ። አወርዶሙ ፡ ቈላተ ፡ ዮሳፍጥ ። አውረደቶሙ ፡ በሐብል ፡ እንተ ፡ መስኮት ። አውረዶሙ ፡ ለነገሥት ፡ ውስተ ፡ ሞት ፡ ወሰከቡራን ፡ እምነ ፡ ዐራታቲሆሙ ። አውረድዎሙ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ለመሳፍንት ፤ (ዮኤ፫ ፡ ፪ ። ኢያ፪ ፡ ፲፭ ። ሚራ፻፺ ፡ ፯ ። ሰቈ፪ ፡ ፲) ።

—፤ አዘነመ ፡ አፈሰሰ ። እግዚ ፡ ያወርድ ፡ ጠለ ፡ ወዝናመ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ። አውረደት ፡ አንብዐ ። አውረደ ፡ እሳተ ፡ እምሰማይ ፤ (ኩፋ ፡ ፲፪ ። ሚራ፴፪ ፡ ፲፰ ። ዮ፰ ፡ ፲) ።

—፤ ዘረጋ ፡ ላከ ፡ ሰደደ ፡ የእጅ ። አውረደ ፡ እዴሁ ፡ ወነሥአ ። ኢትቅድም ፡ አውርዶ ፡ እዴከ ። ደይዎ ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅት ፡ ወእደዊክሙ ፡ ባሕቱ ፡ ኢታውርዱ ፡ ላዕሌሁ ፤ (፪ነገ ፡ ፯ ፡ ፪ ። ሚራ፴፱ ፡ ፲፰ ። ዘፍ፴፯ ፡ ፳፪) ።

—፤ ጣለ ፡ ጐዘ ፤ የመረብ ፡ የመልሕቅ ። እስ ፡ ያወርዱ ፡ መሣግሪሆሙ ፡ ውስተ ። ወአውረዱ ፡ ሐብለ ፤ (ኢሳ፲፱ ፡ ፰ ። ግብ፳፯ ፡ ፲፯) ።

—፤ ከሳ ፡ አወጣ ፤ አወለቀ ፡ አስለበ ፤ አራገፈ ፡ አሳረፈ ፤ የልብስ ፡ የጭነት ፡ የሸክም ። ወአውረደ ፡ ዮናታን ፡ ዐጽፈ ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ወወሀቦ ፡ ለዳዊት ። ያውርዱ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ዘተልእኩ ፡ ቦሙ ። ወአውረዱ ፡ ሾሎ ፡ ዘውስተ ፡ ሐመር ፤ (፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፬ ። ሕዝ፵፬ ፡ ፲፱ ። ግብ፳፯ ፡ ፲) ። ምንም ፡ ያማርኛው ፡ ስልት ፡ ቢበዛ ፡ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ከማውረድ ፡ አይወጣም ።

**ተወርደ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ ተወረደ ፤ ሰዳውን ፡ ግብሩን ፡ ተወጣ ። ውርደ ፡ ኸን ፡ ቂጥኝ ፡ ወጣለት ።

**ተዋረደ ፤ (ወረደ)** ፤ በቊሙ ፡ ወረደን ፡ እይ ። ተወራረደ ፡ እሰጥ ፡ አገባ ፡ ተባባለ ፡ ውርድ ፡ ተናዘ ።

**አስተዋረደ** ፤ (አድራጊና ፡ አደራራጊ ፤ ባድራጊነቱ ፡ የአውረደ ፡ ድርብ) ፤ አዋረደ ፡ አወራረደ ። አፋለሰ ፡ አስተፋለሰ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ያስተዋርድዎ ፡ ውስተ ፡ እምጣነ ፡ ገብር ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ (ተረ ፡ ቄር) ።

**ወርድ ፤ (ዐረ ፡ ዐርድ)** ፤ በቁሙ ፤ ስፋት ፡ ርሕብ ፡ ጐን ። ወይኩን ፡ ዐጽፍ ፡ ዘእመት ፡ ኑኁ ፡ ወእመት ፡ ወርዱ ፤ (ዘፀ፳፰ ፡ ፲፮ ። ፴፯ ፡ ፲፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፩ ፡ ፭) ። ወረዳ ፡ አውራጃ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ወረው ፤ ዎት ፤ (ወረወ ፡ ይዌሩ ፡ ይውሩ ። ዕብ ፡ ያራህ)** ፤ መወርወር ፡ መጣል ፡ ማሽቀንጠር ። ወሬወ ፡ እብነ ። ይዌርዊ ፡ አልባሲሆሙ ። ትዌርዎሙ ፡ ማእከለ ፡ እሳት ። እዌሩ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መሥገርትየ ። ወረወ ፡ ነፍሶ ፡ እመልዕልተ ፡ ሉዓሌ ፡ ወሞተ ፤ (መክ፫ ፡ ፭ ። ግብ፳፪ ፡ ፳፫ ። ሕዝ፭ ፡ ፬ ። ሆሴ፯ ፡ ፲፪ ። ዮሴፍ) ።

**ወራዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ረውት)** ፤ የሚወረውር ፡ ወርዋሪ ። ወራዌ ፡ ረምሕ ፤ (ፊልክ ፡ ፻፶፰) ።

**ተወርወ** ፤ ተወረወረ ፡ ተጣለ ፡ ተምዘገዘገ ፤ ዘለለ ፡ መር ፡ ቸር ፡ ዱብ ፡ አለ ፡ ወረደ ፡ ወደቀ ። ተወረው ፡ ታሕት ። ተወርዉ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ውስተ ፡ እሳት ። ፈቃዱ ፡ ተወርወት ፡ ኀበ ፡ ዐጸደ ፡ ወይን ። ተጋብኡ ፡ ውስተ ፡ አህጉር ፡ ጽኑዓት ፡ ወንትወሮ ፤ (ማቴ፬ ፡ ፮ ። ፳፩ ፡ ፳፩ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ታኅ፩ ። ኤር፰ ፡ ፲፬) ።

**ውርው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሩት)** ፤ የተወረወረ ፡ የተጣለ ፡ የወደቀ ። ወቆብዑ ፡ ውሩት ፡ ዲበ ፡ መታክፍቲሁ ። ውርዋት ፤ (ፊልክ ፡ ፶፯ ። አዋል) ።

**ወራውር** ፤ ውርወራ ፡ የወንጭፍ ፡ ድንጊያ ፡ መርማ ፡ ናደት ።

**ወራውሬ** ፤ እብን ፡ በረድ ፡ ነጭ ፡ ድንጊያ ። ሾሎ ፡ እብነ ፡ ክቡረ ፡ ወዕንቈ ፡ ወራውሬ ፡ ብዙኀ ፤ (፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፪) ።

—፤ ብልጭልጭ ፡ ዕንቍ ፡ ወርቅ ፡ የሚመስል ። ወታስዕት ፡ በወራውሬ ፤ (ራእ፳፩ ፡ ፳ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፲፯) ።

**ወሬዝ ፡ ዘት ፤ (ወረዘ ፡ ይወርዝ ፡ ይረዝ)** ፤ መወርዘት ፡ መርጠብ ፡ የሸከላ ፡ የማንብ ።

**ወርዘወ ፤ (ተቀ ፡ ማ)** ፤ ጕለ(ረ)መሰ ፡ አደገ ፡ ጐበዘ ፤ ሬዝ ፡ አወጣ ፡ አቀመቀመ ፤ ጸና ፡ በረታ ። ልሕቀ ፡ በበ ፡ ሕቅ ፤ ወወርዘወ ፡ በአምጣነ ፡ ብእሲ ። ወርዘውኩሂ ፡ ወረሣእኩ ። አመ ፡ ወርዘወ ። ጽናዕ ፡ ወወርዙ ፡ በእንተ ፡ ሕዝብ ፡ ዚአነ ፤ (መጽ ፡ ምስ ። መዝ፴፮ ። ገድ ፡ ላሊ ። ፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፲፫) ። በወርዘወ ፡ ፈንታ ፡ ተወርዘወ ፡ ይላል ፡ አያስኬድም ። ላዕለ ፡ ሞት ፡ ተወርዘወ ። እንዘ ፡ ይትወረዘው ፡ በኀይለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ (ድጓ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ውርዘው ፤ (ውት ፡ ዙት ፤ ዋን ፡ ዋት)** ፤ ያደገ ፡ የጐለመሰ ፡ ብርቱ ። ብእሲት ፡ ውር(ዘው)ዙት ። ውርዘዋት ፡ አንስት ። ደናግል ፡ ርሱያት ፡ ወሰርጎዋት ፡ ወውርዘዋት ፡ በሃይማኖት ፤ (ስንክ ፡ ግንቦ ። ዲድ ፡ ፲፱ ። መዋሥ) ።

**ወሬዛ ፤ (ብ ፡ ወራዝው ፤ ወራዙት)** ፤ ጕልማሳ ፡ ጐበዝ ፡ ሰጋ ፡ ወጣት ፤ ሶብ ፡ ሦስት ፡ ከሠላሳ ዓመት ፡ በላይ ፡ ያለ ፤ ለዘር ፡ የበቃ ፡ ለማግባት ፤ ሬዝ ፡ ቀምቀሞ ። ወሬዛ ፡ ወሐፃን ። ልሂቅ ፡ ወወሬዛ ። ወልድ ፡ ወሬዛ ። ከመ ፡ ወሬዛ ፡ ሀየል ። ወራዙትኒ ፡ ወደናግል ፤ (፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፩ ። ሕዝ፱ ፡ ፮ ። ዳን፩ ፡ ፲፫ ። ማሕ፪ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፻፵፰) ።

**ወሬዛዊ** ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ። ወሬዛዊት ፡ ድንግል ፤ (ፍ ፡ ን ፡ ፲) ።

**ውርዙት**፤ ጎልማሳ፡ ሕፃንነት፡ ጕልማስነት፡ ጕብዝና፡ በፍኖ። ኀሠሥክዋ፡ እምነ፡ ውርዙትየ። ኅሰሩ፡ ውርዙቱ። መዋዕሊ፡ ውርዙትሙ። እንዘ፡ ሀለዋ፡ በኀይሊ፡ ውርዙትን፤ (ጥበ፰፡ ፪። ሱቱ፡ ዕ፻፲፩፡ ፰። ሔኖ፲፡ ፲፯። ዲድ፡ ፲፬)።

**ውርዛዌ**፤ ዝኒ፡ ከማሁ። መዋዕሊ፡ ውርዛዌ። አልቦ፡ ርሥአን፡ ለውርዛዌሁ፤ (ጥበ፱፡ ፯። ቅዳ)። ፱ኛም፡ መጐልመስ፡ አጐለማመስ፤ ጐልመሳ፡ ይኾናል።

**ውርዝውና**፤ ዝኒ፡ ዓዲ፡ ከማሁ፡ ጐልማስነት፡ (አፈ፡ ተጂ። ፊልክ፡ ፱። ፍ፡ ነ፡ ፳)።

**አወርዘወ**፤ አሳቀ፡ አሳደገ፤ ጐበዘ፡ አደረገ። ኢያወርዘውኩ፤ (ኢሳ፳፫፡ ፬)።

»**ሬዝ**፤ በቁሙ፤ ከራስ፡ እስከ፡ ጽሕም፡ በግ ራና፡ በቀኝ፡ የሚወርድ፡ ጠጕር። የታናሽ፡ በግ፡ የጠ በት፡ ጠጕር፡ መዠመሪያ፡ የሚሸለተው። በጕም፡ ወ ሬዝ፡ እንደ፡ መባል፡ ሬዝ፡ ይባላል፤ ሬዝ፡ በግ፡ የሬዝ፡ በግ፡ ጠጕር፡ እንዲሉ።

**ወርኅ**፤ (ብ፡ አውራኅ፤ ኀት። ዕብ፡ ያሬሐ፡ ዩራሕ። ሱር፡ ያርሓ)፤ ጨረቃ፡ የፀሓይ፡ ታናሽ። ፀሓይኒ፡ ይጸልም፡ ወወርኅኒ፡ ኢይሁብ፡ ብርሃኖ። የሐጽጽ፡ ልቡ፡ ከመ፡ ወርኅ። ወርኅ፡ ምልእት። ሠርቀ፡ ወርኅ፤ (ማቴ፳፬፡ ፳፱። ማሬ፳፯፡ ፲፭። ሃ፡ ፯። ኢሳ፶፡ ፲፱)።

—፤ በቁሙ፤ የጨረቃ፡ ወር፤ ተወልዶ፡ ጠፍ፡ እስክት ኾን፡ የምታበራው፤ ፳፱፡ ቀን፤ ፲፪፡ ሰዓት፡ ፯፻፶፫፡ ክ ፍል። የክፍሉ፡ መጠን፡ እጅግ፡ ስላነስ፡ ፫ቱ፡ ክፍል፡ ፲፡ ሴኮንድ፡ ፲፰ቱ፡ ክፍል፡ ፩፡ ደቂቃ፡ ነው። ፫፻፷ቱ፡ ክፍል፡ ፳፬፡ ደቂቃ፡ ኹኖ፡ ፩፡ ክፍል፡ ይተርፋል። ሺሕ፡ ከዃው፡ ክፍል፡ ፰፡ ደቂቃ፡ ወይም፡ ፩፡ ሰዓት፡ ይኾናል። የፀሓይ፡ ወር፡ ሲኾን፡ ፴፡ ቀን፡ ነው፤ ሕ ጸጽ፡ የለበትም። ዝንቱ፡ ወርኅ፡ ይኩንክሙ፡ ቀዳ ማየ፡ አውራኅ። ዐሠርቱ፡ ወክልኤቱ፡ ወርኅ። በአ ውራኅ፡ እሙራት። ወርኅ፡ ወርኃዊ፤ ወርኅ፡ ፀሓ ያዊ። ኍሉን፡ አውራኅ፤ (ዘፀ፲፪፡ ፪። ዳን፬፡ ፳፮። ሔ ኖ፸፰፡ ፱። አቡሻ፡ ፫። ፍ፡ ነ፡ ፴፯)።



ወርኅ፡

—፤ ጊዜ፡ ዘመን፡ ወራት። ወበጽሐ፡ ወርኃ፡ ለኤል ሳቤጥ። በወርኅ፡ ቀላውዴዎስ። ዘመነ፡ መንግሥት፡ ወወርኅ፡ ተከውሰ። በወርኅ፡ ምግቡ፡ ለያሬድ፤ (ሉቃ፩፡ ፶፯። ስንክ፡ ሚያ፲፭። ጽ፪፡ ጥበ፡ ጠቢ)።

**ወርኃዊ**፤ ወረኛ፡ ወራተኛ፤ ወረተኛ፤ ቶሎ፡ የሚያልፍ። በየወሩ፡ ጨረቃ፡ ሲወጣ፡ የሚጥል፡ ጋኔን። ወርኃውያን፤ (ማቴ፬፡ ፳፬)። የጨረቃ፡ ቍጥር። ወ ርኅ፡ ወርኃዊ። ዓመት፡ ወርኃዊ፤ (አቡሻ)።

**ወረኀ**፤ በቁሙ፡ እግረ፡ ወንካራ፤ ወይም፡ እ ግረ፡ ማቋድ፤ እግሩ፡ ለጋ፡ ጨረቃ፡ የሚመስል፤ ሲ ቆም፡ በመካከሉ፡ ልጅ፡ የሚያሾልክ፤ (በማርኛ)።

**ወረየ**፤ (ይወሪ፡ ይረይ)፤ አወራ፡ አሳየ፡ ገለጠ፤ የነገር፡ የምስጢር።

**ወራዪ**፤ ወሬኛ፡ አውሪ፡ ወሬ፡ ነጋሪ።

**ወሬ**፤ በቁሙ፤ (በማርኛ)።

**ወረቀ**፤ **ቆት**፤ (ወረቀ፡ ይወርቅ፡ ይ ረቅ። ዕብ፡ ያራቅ)፤ መትፋት፡ አክ፡ ትፍ፡ ማለት፤ ከአፍ፡ ምራቅ፡ ማውጣት። ኢይትሀከዩ፡ ወሪቀ፡ ው ስተ፡ ገጽየ። ኢይውርቅ፡ ምራቀ። ለምንት፡ ዘኢ ወረቀ፡ አቡ፡ መቃራ፤ (ኢዮ፴፡ ፲። ፍ፡ ነ፡ ፲፱። ፊ ልክ፡ ፲)።

—፤ ቅጠል፡ መኾን። መርቀቅ፡ መሣሣት፤ መወረቅ፡ መወየብ፤ ወርቅ፡ የበሰለ፡ ቅጠል፡ መምሰል። ረቀቀን፡ እይ፡ የዚህ፡ ጎር፡ ነው።

»**መረቅ**፤ (ዐረ። ዕብ፡ ማራቅ)፤ በቁሙ፤ የሥጋ፡ ውሃ፡ የበሰለበት፡ የተቀቀለበት። (ተረት)፤ ው ምና፡ ወርቅ፡ እንጀራና፡ መረቅ። ከሥጋው፡ ጠመኛ፡ ነኝ፡ ከመረቁ፡ አውጡልኝ፤ (መጽ፡ ፈው)። መረቃ፡ አመረቃ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ወጥቷል፤ ፍችው፡ ጣፈጠ፡ ማለት፡ ነው።

»**ምራቅ**፤ በቁሙ፤ ትፋት፡ ትፍታ፤ አክታ፡ ጢቅታ። ኢሜጥኩ፡ ገጽየ፡ እምነፍረተ፡ ምራቅ። ለእመ፡ መጽአ፡ ምራቅ። ጽቡረ፡ ገብረ፡ በምራቁ፤ (ኢሳ፶፡ ፯። ፊልክ፡ ፲። ዮሐ፱፡ ፯)። በምራቅ፡ ፈንታ፡ ረቅ፡ ይላል። በረቅ፡ አፋሆሙ፤ (አዋል)። መረቀ፡ ማ ለት፡ ከምራቅ፡ ወጥቷል፤ መርቀኝ፡ ሲል፡ እንትፍትፍ፡ በልብኝ፡ እንዲል፤ (ባላገር)።

**ወረቀት**፤ (ዐረ፡ ወረቅ። ዕብ፡ የሬቅ፤ ቅጠል)፤ በቁሙ፤ ክርታስ፡ መጣፊያ፤ ሥሥ፡ ይከማ። ከማርኛ፡ በቀር፡ በግእዝ፡ ቃል፡ ውስጥ፡ አይገኝም።

**ወርቅ**፤ በቁሙ፡ ከማዕድን፡ ኹሉ፡ የሚበልጥ፡ ልዩ፡ ክቡር፡ ገንዘብ፤ ሕብሩ፡ ብጫ፡ ቀይ፡ ሐመልሚል፤ አንጥረኞችና፡ ጃን፡ ሸላሞች፡ ሌሎች፡ ንዋያትን፡ በ ርሱ፡ ለማስጌጥ፡ ለመለበጥ፡ እንደ፡ ቀለም፡ በላይ፡ የ ሚቀቡትና፡ የሚያፈሱት፤ እንደ፡ ወረቀት፡ የሚያማ ሡት። ስለ፡ መልኩና፡ ስለ፡ ግብሩ፡ ስሙን፡ ከቅጠል፡ ወስዷል። ወርቅ፡ የገንዘብ፡ ኹሉ፡ ራስ፡ ስለ፡ ኾነ፡ ማኅተመ፡ ንጉሥ፡ ያለበት፡ መዳብም፡ ብሩም፡ ማናቸ ውም፡ ኹሉ፡ በርሱ፡ በመክብቡ፡ ስም፡ ወርቅ፡ ይባላል። ወርቀ፡ ሜጥ። ደፈነ፡ ወርቀ፡ እግዚኡ። ወሀብ ዎሙ፡ ብዙኀ፡ ወርቀ፡ ለሠገራት፡ ብር፡ ገንዘብ፡ ማ ለት፡ ነው፤ (ዘሌ፳፭፡ ሃ። ማቴ፳፭፡ ፲፰። ፳፰፡ ፲፪)።

**ወርቃዊ**፤ ወርቃም፡ ባለወርቅ፡ ወርቅማ፡ ወ ርቅ፡ የሚመስል፡ የወርቅ፡ ዐይነት፤ ቍጥር፡ ሚዛን። ንልቈ፡ ወርቃዊ፤ (አዋል)።

**ወረረ** ፤ (ትግ ፡ ወዐም ። ወሬር ፡ ወረ) ፤ በቁሙ ፤ ዘረፈ ፡ በዘበዘ ፤ አደጋ ፡ ጣለ ። (ተረት) ፤ ክጭር ፡ ምክር ፡ ከረኸርም ፡ ውረር ። ዩቶን ፡ ወሬሬ ፡ የሴት ፡ ስባሪ ።

**ወረሰ** ፤ ሶት ፤ (ወረሰ ፡ ይወርስ ፡ ይረስ ። ዕብ ፡ ያራሽ ። ሱር ፡ ዩሬት ። ዐረ ፡ ወሬሰ ፡ ተ) ፤ መውረስ ፡ መውረት ፡ እጅ ፡ ማድረግ ፤ የሙትን ፡ ይዞታ ፡ ርስትና ፡ ገንዘብ ፡ በሻቹ ፡ ፈቃድ ፡ መውሰድ ፡ መያዝ ። ወይም ፡ ሳይሞት ፡ በግድ ፡ መቀማት ፤ እንደ ፡ እስራኤል ። በእንተ ፡ ዘይወርሰ ፡ ብእሲ ፡ እምብእሲቱ ፡ ወብእ ሲት ፡ እምብእሲሃ ። ንዋይ ፡ ብዙኀ ፡ ዘወረሰት ፡ እ ምታ ። ከመ ፡ ይረሳ ፡ ለምድር ። ይወርስ ፡ ኵሎ ፡ መ ንግሥተ ፡ ምድር ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፯ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ጳጉ ፫ ። ቀሌ) ። በወረሰ ፡ ፈንታ ፡ ተወርሰ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። (ኢያ፲፰ ፡ ፱) ።

**ወራሲ** ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት) ፤ የሚወርስ ፡ ወራሽ ፤ ዋርሳ ። ዘረሰዮ ፡ ወራሴ ፡ ለኵሉ ። ወራሲ ፡ ጠባይዓዊ ። ብእሲት ፡ ዘትወልድ ፡ ወራሴ ። ወራስያ ኒሃ ፡ ለምድረ ፡ ሕያዋን ። ወራስያነ ፡ ክብር ፡ (ዕብ፩ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፶፱ ፡ ፫ ። ሚራ፳፫ ፡ ፳፱ ። ቀሌ ። ዮሴፍ) ። በወራሲ ፡ ፈንታ ፡ ዋርስ ፡ ይባል ፡ (ማቴ፳፩ ፡ ፴፰ ። ስንክ ፡ ኅዳ፴) ።

**አውረሰ** ፤ አወረሰ ፤ አስወረሰ ። ያወርስ ፡ እ ግዚ ፡ ለይሁዳ ፡ መክፈልቶ ። ሕገ ፡ ዘያሐይዎሙ ፡ አውረሶሙ ። ከመ ፡ ትረሱ ፡ ምድረ ፡ ወእምድኅሬ ክሙኒ ፡ ታውርሱ ፡ ለደቂቅክሙ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ (ዘካ፪ ፡ ፲፪ ። ሚራ፲፯ ፡ ፲፩ ። ዕዝ፱ ፡ ፳፰ ፡ ፰) ።

**ተወርሰ** ፤ ተወረሰ ፤ ርስቱን ፡ ገንዘቡን ፡ ተቀማ ፤ ለውዩው ። ወይም ፡ ርስቱ ፡ ለሌላ ፡ ዐለፈ ፤ እንደ ፡ ከነ ዓን ። ከመ ፡ ኢትትወረስ ፡ ለካልአን ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፮) ።

**ተዋረሰ** ፤ ተወራረሰ ፤ ተካፈለ ፡ ተከፋፈለ ፤ ተተ ናተን ። ኢይበአ ፡ ውስተ ፡ ተዋርሶ ። ለተዋርሶ ፡ ዘኢ ይበሊ ። ተዋረሱ ፡ ኵሎ ፡ ይወሉሙ ። ወሱቱፋኒሁ ፡ በተዋርሶ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፫ ። ቀሌ ፡ ፳ ፡ ፱ ። ዮዲ ፡ ፲፰ ። አፈ ፡ ድ፯) ።

**ተዋራሲ** ፤ ሞረስ ፤ (ብ ፡ መዋርስት) ፤ የሚዋረስ ፡ የሚወራረስ ፤ ተዋራሽ ፡ ተወራራሽ ፤ ድፍን ፡ አቋራሽ ፡ ርቢት ፡ አጋማሽ ፡ ተካፋይ ፡ ባላንጣ ፡ ባለጢንጦ ፤ አለቃና ፡ ምንዝር ፡ ተነኃታይና ፡ በዥር ። ተዋራሴ ፡ ስሙ ። ኵሎ ፡ ተግባረክ ፡ ይትካፈሉ ፡ መዋርስቲከ ። እሁብ ፡ ገራውሂሆሙ ፡ ለመዋርስት ። ወእምከመሰ ፡ ው ሉደ ፡ እግዚ ፡ ንሕነ ፡ ወራስያኒሁ ፡ ንሕነ ፤ ወእምከ መሂ ፡ ወራስያነ ፡ እግዚ ፡ ንሕነ ፡ መዋርስቲሁ ፡ ለክር ስቶስ ፡ ንሕነ ፤ ወእምከመ ፡ ዐረይነ ፡ ሕማመ ፡ ንዔሪ ፡ ክብረ ፡ ምስሌሁ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲፫ ። ሚራ፲፬ ፡ ፲፰ ። ሮሜ፰ ፡ ፲፯ ። ኤፌ፫ ፡ ፮) ።

**አስተዋረሰ** ፤ አዋረሰ ፡ አወራረሰ ፤ አከፋፈለ ። አድራጊና ፡ አደራራጊ ፡ ነው ፤ አስተዋረደኝ ፡ እይ ። ለመ ፡ ያስተዋርሶሙ ፡ ንዋዮ ፡ ለደቂቁ ። እምርስቱ ፡ ያስ ተዋርስ ፡ ለውሉዱ ። አስተዋርስ ፡ ንዋየከ ። መባሕት ፡ ለአቡሁ ፡ ከመ ፡ ኢያስተዋርሶ ፡ ርስተ ፡ ዚኣሁ ። እ ዴሁ ፡ አስተዋረሰቶሙ ፡ (ዘዳ፳፩ ፡ ፲፮ ። ሕዝ፵፮ ፡ ፲፰ ። ሚራ፴ ፡ ፴፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፬ ። ኢሳ፴፬ ፡ ፲፯) ።

»**ርስት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፡ ቦታ ፡ መሬት ፡ የሚወርሱትና ፡ የሚያወርሱት ። ወሀቦን ፡ አቡሆን ፡ ርስ ቶን ። ሰአሊ ፡ እምኔየ ፡ ወእሁበከ ፡ አሕዛበ ፡ ለርስትከ ፡ እስራኤል ፡ ርስትየ ። ዐረብነ ፡ ርስትነ ። ወጸውዖሙ ፡ ውስተ ፡ ርስቱ ፡ ዘለዓለም ፡ (ኢዮ፵፪ ፡ ፲፭ ። መዝ ፡ ፪ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፳፭ ። ኤሬ፲ ፡ ፲፬ ። ዕብ፱ ፡ ፲፭ ። ፲፭ ፡ ፳) ።

**ወረስ** ፤ ወረት ፤ ገንዘብ ፡ ጥሬት ፡ ረኀት ። ግብዝ ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ገንዘብ ፡ ካንዱ ፡ ወዳንዱ ፡ ፈ ጥኖ ፡ የሚያልፍ ። ወረታም ፡ ባለወረት ፡ ወረተኛ ፡ እን ዲሉ ።

**ወሲብ** ፤ ቦት ፤ (ወሰበ ፡ ይወስብ ፡ ይ ሰብ ። ዕብ ፡ ያሻብ ፤ ተቀመጠ) ፤ መዳበል ፡ መ ደረብ ፤ ካንድ ፡ ከሌላ ፡ መጠጋት ፤ ደባል ፡ ድልባን ፡ ኹኖ ፡ መቀመጥ ። መወሰብ ፡ መጥለፍ ፡ መቈለፍ ፤ የፈትል ፡ ያ ረግ ፤ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ነው ፡ ከደባልነት ፡ አይወጣም ። ወሸባ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**አውሰበ** ፤ አስጠጋ ፡ አዳበለ ፡ ሰበሰበ ፤ ከቤቱ ፡ አስቀመጠ ። ሚስት ፡ አገባ ፤ ቈበተ ፡ ገረድ ፡ ቀጠረ ። ኢ ታውስብ ፡ ብእሲተ ። ዘአውሰበ ፡ ብእሲተ ፡ ኄርተ ። እለ ፡ ያወስቡ ፡ ዳግመ ፡ ይክውኑ ፡ ውፁኣነ ፡ እምሕግ ፡ (ኤር፲፮ ፡ ፩ ። ሚራ፴፮ ፡ ፳፬ ። ዲድ ፡ ፲፬) ።

—፤ ወደ ፡ ቤት ፡ ገባ ፡ ቀረበ ፤ ተራከበ ። አውስቦ ፡ በአ ሐዱ ፡ ሌሊት ፡ ሠለስተ ፡ ጊዜ ፤ አውስቦ ፡ እንስሳ ፤ አ ውስቦ ፡ አውናኝ ፡ (አንቀጸ ፡ ንስሓ) ። ለሴትም ፡ ይነገ ራል ። አውሰበት ፡ ካልአ ፡ ብእሴ ። እምድኅረ ፡ አው ሰበት ። እንተ ፡ ኢያውሰት ፡ (ኤር፫ ፡ ፩ ። ዓዘ ፡ ፱ ። ፩ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፴፱) ።

**ተወሰበ** ፤ ተዳረ ፤ ለሚስት ፡ ተሰጠ ፤ ገቢ ፡ ኾነ ። ወተወሰበት ፡ ለመርቅያን ። ለእመ ፡ ተወሰበት ፡ ለብ እሲ ፡ (ዮሐ ፡ መደ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፩) ።

**ውሱብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ስብት) ፤ ያገባ ፡ የተ ገባ ፡ የተዳረ ፤ ጕጕ ፡ ወጥ ። ትከውን ፡ እምኍልቈ ፡ መ በለታት ፡ ውሱባት ። እንስት ፡ ውሱባት ። ማእከለ ፡ ውሱባን ፡ ወደናግል ፡ ሀሎ ፡ ፍልጠት ፡ ክሡት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ። ፯ ፡ ፲፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**ተዋሰበ** ፤ በቁሙ ፤ ተወሳሰበ ። ተጋባ ፡ ተዛመደ ፡ ተገናዘበ ። ትትዋሰቡ ፡ ምስሌሆሙ ። ኢያወስቡ ፡ ወ ኢይትዋሰቡ ። እመ ፡ ኮነ ፡ አሐዱ ፡ እምተዋሳብያን ፡ ድንግለ ። እሎን ፡ ተዋሰቦታት ፡ (ኢያ፳፫ ፡ ፲፪ ። ማቴ ፳፪ ፡ ፴ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፲፯) ። በተዋሰቦ ፡ ፈንታ ፡ አውሰቦ ፡ ይባል ፤ አያሰኝም ። ክቡር ፡ አውስቦ ፡ በዅሉሂ ፡ (ዕብ ፲፫ ፡ ፬) ።

**አስተዋሰበ** ፤ አዋሰበ ፤ አወሳሰበ ። አጋባ ፡ አዛ መደ ፤ አጣመረ ፡ አጣመደ ፤ አቆናጀ ፡ አራከበ ፤ የወንድና ፡ የሴት ። ወአስተዋሰቡ ፡ ደቂቆሙ ። ለብእሲ ፡ ጠቢብ ፡

አስተዋስባ ፡፡ አስተዋሰብዋ ፡ ለሰብዐቱ ፡ ዕደው ፡፡ አነ ፡ ፈቀድኩ ፡ ከመ ፡ አስተዋስብ ፡ ወለተከ ፡ ለወልደ ፡ እስክንድር ፡፡ ፈቀዱ ፡ አበዊሁ ፡ ከመ ፡ ያስተዋስብዎ ፡ ሎቱ ፡ ብእሲተ ፡ (ስንክ ፡ ፪ ። ሚያዝ ፡ ፳፭ ። ጦቢ ፡ ፫ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ መጋ፳፯) ።

» **ሰብሳቢ** ፤ ጋብቻ ፡ ማቢ ፡ ተክሊል ፤ ሰምረት ፡ ፋካቤ ። ዝሙት ፡ ኢኮነ ፡ ሰብሳበ ፡ ወኢይትኌለቍ ፡ በሰብሳብ ፡፡ ቀዳሚ ፡ ሰብሳብ ፡ ንጹሕ ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡፡ ሰብሳብ ፡ ዘሕግ ፡፡ ቀኖና ፡ ሰብሳብ ፡፡ አለ ፡ ውስተ ፡ ሰብሳብ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፫ ። ዲድ ፡ ፲፱ ። ቄድር ። ቀሌ ። መቃ ፡ ፻፲፯) ።

» **ሰብሰበ** ፤ (በማርኛ) ፤ ሰበሰበ ። ሰብሳብ ፡ ሰበሰብ ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ አገባ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ አውሰበ ፡ ይፈቱታል ፡ ወሥእን ፡ እይ ።

**አሰብሰበ** ፤ አሰበሰበ ፡ ሰብሰበ ፡ አሰረ ፡ ማገረ ፤ የማርኛ ፡ የንፊልት ። ሠብሠብንና ፡ ሰበበን ፡ እይ ።

**ወሲድ ፤ ዶት ፤ (ወሰደ ፡ ይወስድ ፡ ይሰድ ። ሰብ ፡ ያሰድ ፤ መሠረተ)** ፤ መውሰድ ፡ ይዞ ፡ መኼድ ፡ ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ። ወሰደኒ ፡ ኢየሩሳሌም ፡፡ ወሰደኒ ፡ መንፈስ ፡ ገዳመ ፡፡ ወሰደኒ ፡ ውስተ ፡ አየር ፡ ዘሳብዕ ፡ ሰማይ ፡፡ ፍኖት ፡ እንተ ፡ ትወስድ ፡ ውስተ ፡ ሀጕል ፡ (ሕዝ ፡ ፰ ። ራእ ፡ ፲፯ ። ዕር ፡ ኢሳ ፡ ፳ ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፫) ።

**ወሳዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት)** ፤ የሚወስድ ፡ ወሳጅ ፡ ይዞ ፡ (ሀ)ኺያጅ ።

**መውስድ ፤ (ብ ፡ መዋስድ)** ፤ መውሰጃ ፤ ዋስዳ ፡ ዕቃ ፡ መሣሪያ ።

**ተወስደ** ፤ ተወሰደ ፡ ተይዞ ፡ ኼደ ፡ በግድ ።

**ወሲጥ ፤ ጦት ፤ (ወሰጠ ፡ ይወስጥ ፡ ይሰጥ ፡ ይውስጥ ። ዐረብ)** ፤ መወሰጥ ፡ በውስጥ ፡ መኾን ፡ ከውስጥ ፡ መግባት ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ማግባት ፡ መክበብ ፡ ማማከል ። ሦጠን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ወሳጢ ፤ ውሳጢ ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት)** ፤ የውስጥ ፡ ውስጠኛ ። አንቀጽ ፡ ውሳጢ ፡፡ ዐጺድ ፡ ውሳጢ ፡፡ ወውስተ ፡ ውሳጢትሰ ፡፡ ውሳጢቱ ፡ ጽርሕ ፡፡ መዘግብት ፡ ውሳጥያን ፡፡ አዕይንት ፡ ልብነ ፡ ውሳጥያት ፡ (ሕዝ ፡ ፵ ። ፲ ፡ ፱ ። ሰብዐ ፡ ፳ ። ፬ንግ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ፩ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፲፩ ። ቅዳ ፡ ኪዳ) ።

**ውስጥ ፤ ውሳጥ ፤ (ብ ፡ ውስጣት ፤ ውሳጣት)** ፤ በቁሙ ፡ ሆድ ፡ ልብ ፡ መካከል ፡ ጓዳ ፡ ማጀት ። ዝንቱሰ ፡ ውስጡ ፡ ጽቡር ፡፡ ወሞቀኒ ፡ ልብየ ፡ በውስጥየ ፡፡ ንዋየ ፡ ውስጥ ፡፡ ትበውእ ፡ እምውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ (ዳን ፡ ፲፬ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፴፰ ። ዘሌ ፡ ፲፮ ። ፪ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፳፱) ።

**ውስጠ** ፤ በውስጥ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ግቢ ፡ ወደ ፡ ማኸል ። ወደየን ፡ ውስጠ ፡፡ ይኔጽር ፡ ውስጠ ፡፡ ወቦአ ፡ ውስጠ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡፡ ውስጠ ፡ እምነ ፡ መንጦላዕት ፡ (ዘፀ ፡ ፲፰ ። ፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፱ ። ሕዝ ፡ ፲፰ ። ዘሌ ፲፮ ፡ ፲፪) ።

**ውስጣዊ ፤ ውሳጣዊ ፡ ይ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ለውሳጢ ። እንተ ፡ ውሳጣይ ፡ ኆኅት ፡፡ ሕዋሳት ፡ ውሳጣውያት ፡፡ አእምሮተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውሳጣዊት ፡ ዘትሰመይ ፡ መንፈሳዊት ፡ (፪ዜና ፡ ፳፫ ፡ ፫ ። ፈላስ ፡ ገጽ ። ፈልክ ፡ ፲፻፴፬) ።

**ውሳጤ ፤ (ጥያት)** ፤ ውስጥ ፡ ውሳጥ ፡ የውስጥ ፡ ውስጥ ፤ ዋሻ ፡ ጕስጕሻ ፤ ውስጥነት ፡ ያለው ፡ ኹሉ ። በውሳጤ ፡ ሀገር ፡ ወአፍኣሃ ፡፡ እምውሳጤሁ ፡ ወአፍኣሁ ፡፡ ኵሉ ፡ ውሳጥያቲሁ ፡ ለደቡብ ፡፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ውሳጥያተ ፡ ጽርሑ ፡፡ ውስተ ፡ አብያት ፡ ወውስተ ፡ ውሳጥያት ፡፡ አልቦሙ ፡ መዘግብት ፡ ወኢውሳጥያት ፡ (ዮሴፍ ። ዘፀ ፳፰ ፡ ፲፰ ። ኩፋ ፡ ፱ ። ፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፴ ። ኢሳ ፳፮ ፡ ፳፩ ። ሉቃ ፲፪ ፡ ፳፬) ።

**ውስጠ ፡ ዘ** ፤ የቅጽል ፡ ስም ፡ በውስጡ ፡ ያ ፡ የሚሰማበት ፤ ቀታሊ ፤ ቅቱል ፤ አዳም ፡ ሠናይ ፤ ይህን ፡ የመሰለ ።

**ውስጠ ፤ ወይራ** ፤ የቅኔ ፡ መንገድ ፡ ስም ፡ በዘና ፡ በዊ ፡ በተናባቢና ፡ በዝርዝር ፡ በአኔንዘ ፡ ውስጥ ፡ የሚሰማ ፡ ቃል ። ናዝሬት ፡ ዘገሊላ ፤ የገሊላ ፡ ክፍል ። ኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ፤ የናዝሬት ፡ ሰው ። ብእሲተ ፡ ፒየርፒስ ፡ ወለደት ፡ ሠለስተ ፤ (ክዋደ ፡ ፒየ ፡ አውሐዘት ፡ ደመ ፡ ወማየ ፡ ወሐሊበ) ፡፡ ጳውሎስ ፡ እሳተ ፡ ወንጌል ፡ (ሐዋርያ ፡ ወ) ፡ ምሕራበ ፡ አይሁድ ፡ አውዐየ ፡ በነበልባሉ ፡ (በስብከቱ) ፡፡

**ውስት ፤ ውስቴት ፤ ውስተ ፤ (ውስጥ ፡ ውሳጤ ፡ ውስጠ)** ፤ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ውስጥ ፤ ማኸል ፤ ጋራ ፤ ወደ ፡ ይኾናል ፤ ፍችው ፡ በን ፤ ምስጢሩ ፡ ውስጥን ፡ አይለቅም ፤ በ ፡ እም ፡ እንተ ፡ ይስማሙታል ። በውስተ ፡ ባሕር ፡ እምውስተ ፡ አፍ ፤ ኢየኀልፍ ፡ እንተ ፡ ውስቴታ ፡ እያለ ፡ ይገባል ። ምስክሩን ፡ እንደ ፡ ተራው ፡ እይ ። ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡፡ ከመ ፡ እንበሳ ፡ ውስተ ፡ እንስሳ ፡፡ ኢይትኌለቍ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ፡፡ ሚጥዎ ፡ ውስተ ፡ ላሕ ፡ ወአግብእዎ ፡ ውስተ ፡ ትካዝ ፡ (ማቴ ፡ ፬ ፡ ፲፮ ። ሚክ ፡ ፭ ፡ ፰ ። ዘኍ ፡ ፳፫ ፡ ፱ ። ዮሴፍ ፡ ፱) ። በ ፡ ዲበ ፡ ላዕለ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ውስተ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ ውስጥነት ፡ ማእከልነት ፡ እንጂ ፡ ላዕልነት ፡ አይስማማውም ። ዘመሥዋ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡፡ ኢሀሎ ፡ ውስተ ፡ መካኑ ፡፡ ይኩኑ ፡ ውስተ ፡ ጠፈረ ፡ ሰማይ ፡ ፩ ፡ (ማቴ ፡ ፲፪ ። ፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፳፭ ። ዘፍ ፡ ፲፬) ። ወረደት ፡ እምውስተ ፡ ገመላ ፡፡ ያሴስል ፡ ሐመደ ፡ እምውስተ ፡ ምሥዋዕ ፡፡ ወድቀ ፡ እምውስተ ፡ መንበሩ ፡፡ ይሰክቡ ፡ ውስተ ፡ ዐራታት ፡ ዲበ ፡ ላዕሉ ፡ (ዘፍ ፡ ፳፬ ፡ ፷፬ ። ዘሌ ፡ ፮ ። ፩ነገ ፡ ፬ ፡ ፲፰ ። ዓሞ ፡ ፮) ። ዳግመኛም ፡ በማእዝ ፡ ፈንታ ፡ ገቢር ፡ ለማድረግ ፡ ውስተ ፡ ይላል ፡ ይህም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ አያሰኝም ። እሬስየከ ፡ ውስተ ፡ ሕዝብ ፡ ዐቢይ ፡፡ ይእቲ ፡ ኮነት ፡ ው-

ስተ ፡ ርእሰ ፡ ማእዘንት ፡፡ ዘበጡት ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ፡፡ አንብብ ፡ ውስተ ፡ ወንጌል ፤ (ዘፀ ፴፫ ፡ ፲ ፡፡ መኃ ፡ ፻፲፯ ፡፡ ዮዲ ፲፫ ፡ ፰ ፡፡ ማር ፡ ደሮሥ) ፡፡ በውሳጢት ፡ አንጻር ፡ ውስቴቱ ፡ ታ ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ፡ ወና ፡ የ ፡ እንዲወራረሱ ፡ ጠና ፡ ተም ፡ ይዋረሳሉና ፤ ውስጠ ፡ የነበረው ፡ ውስተ ፡ መባሉ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡፡

**ወሳይድ ፤ (ዐረ ፡ ወሳኢድ) ፤** የራስ ፡ ድጋፍ ፡ ትራስ ፡ ብርኩማ ፡ መከዳ ፤ መሬርጊያ ፡፡ በወሳይድ ፡ ዘማኅላት ፡ (ዮሴፍ) ፡፡ ሶፋና ፡ ምንጣፍ ፡ ሰደየና ፡ ስዐደ ፡ ናቸው ፤ ኹሉቱንም ፡ እዩ ፡፡

**ወስከ ፤ ከት ፤ (ወሰከ ፡ ይዌስክ ፡ ይወስክ ፡፡ ዐረ ፡ ወሸቀ ፡ ከመረ) ፤** መጨመር ፡ መደመር ፡ ማብዛት ፡፡ ትዌስኩ ፡ ኃጢአተ ፡ በደቡ ፡ ኃጢአት ፡፡ ጠቢብ ፡ ይዌስክ ፡ ጥበበ ፡፡ ባዕል ፡ ይዌስክ ፡ አዕርክተ ፡፡ ወወሰከ ፡ ዓዲ ፡ ፈሪሆተ ፡ ለእግዚ ፡ (ኢሳ ፳ ፡ ፳ ፡፡ ምሳ ፳ ፡ ፳ ፡፡ ፲፱ ፡ ፬ ፡፡ ጦቢ ፲፬ ፡ ፱) ፡፡ ወሸቀ ፡ ወሰከ ፡ ወሰየ ፡ ወስከምት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡፡

**ተወሰከ ፤** ተጨመረ ፡ (ለት ፡ በት) ፡ በዛ ፡፡ ይትዌሰኩ ፡ ደቢ ፡ ፀርነ ፡፡ ወይትዌሰኩ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ፈላስያን ፡፡ ወተወሰከ ፡ ውስተ ፡ እስራኤል ፡፡ ወኮኑ ፡ ሰራዊተ ፡ ሮም ፡ ይትዌሰኩ ፡ ለለ ፡ ሾሉ ፡ ዕለት ፡ (ዘፀ ፩ ፡ ፲ ፡፡ ኢሳ ፲፬ ፡ ፩ ፡፡ ዮዲ ፲፬ ፡ ፲ ፡፡ ዮሴፍ) ፡፡

**ውሱክ ፤ (ክን ፡ ክት ፡ ስክት) ፤** የተጨመረ ፡ ጭምር ፡ ብዙ ፡፡ ዐፀም ፡ ውሱክ ፡፡ አስተብቍዖት ፡ ውሱክ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ፡፡ ስንክ ፡ ሐምሌ) ፡፡

**ውሳኬ ፤ ውሳክ ፤ (ክት) ፤** መጨመር ፤ (ጥጨ) መጨመር ፤ አጨማመር ፤ ጭመራ ፡ ጭማሪ ፡፡ ሰላም ፤ ለኀሲናክ ፡ ዘክነ ፡ መምሰኬ ፡ ሥሳሴ ፡ ዕሩየ ፡ እንበለ ፡ ውሳኬ ፡፡ ውሳኬ ፡ መልእክቱ ፡፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ሥርዐተ ፡ ውሳኬ ፡፡ ጠፈሮንሂ ፡ ቀመሮንሂ ፤ ውሳካቲሆንሂ ፡ እብን ፡ (ደራሲ ፡፡ ስንክ ፡ ጥቅ ፲ ፡፡ አፈ ፡ ተ ፳ ፡፡ ገድ ፡ ላሊ) ፡፡

**ተውሳክ ፤ (ክት) ፤** ጭማሪ ፡ ተጨማሪ ፡ የስፍር ፡ የቍጥር ፡ ማማያ ፡ ማስተካከያ ፡፡ ዘእንበለ ፡ ተውሳክ ፡ ወኢሕጸት ፡፡ ወተውሳክክሙ ፡ ሰመንቱ ፡፡ ተውሳካት ፡ (ዮሴፍ ፡፡ ስንክ ፡ መጋ ፲ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ ፻፲) ፡፡

— ፤ ትርፍ ፡ ተረፍ ፡ ቀሪ ፤ ከስፍር ፡ ከቍጥር ፡ ያልገባ ፡፡ እነግሥኑ ፡ ዐሠርተ ፡ ዓመታተ ፤ ወይቤሎ ፡ እወ ፡ ዐሥራ ፡ ዓመተ ፡ ወሠላሰ ፡ ዓመተ ፡ ወተውሳከ ፡ ወይቤሎ ፡ ሚ ፡ መጠን ፡ ተውሳኩ ፡ (ዮሴፍ) ፡፡

— ፤ ብዛት ፡ ብዙኀነት ፡፡ በእንተ ፡ ተውሳከ ፡ መብልዕ ፡ ወመስቴ ፡፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ፈጽሞ ፡ ጽድቀ ፡ ወተውሳከ ፡ ትሩፋት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ፡፡ ፴፫ ፡ ፳) ፡፡ ባማርኛ ፡ ግን ፡ በሽታ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ተውሳክም ፡ እንዲሉ ፡፡

**ውስኪ ፤** የመጠጥ ፡ ስም ፡ ውሱክ ፡ መቃስም ፡ ጽሩይ ፡ ወጥዑም ፡ የንግሊዞች ፡ መጠጥ ፤ ዋጋው ፡ ድኻ ፡ የማይነካ ፡ ልብስ ፡ የማያሽጥ ፡፡ (ተረት) ፡ ዛሬም ፡ ውስኪ ፡ ነገም ፡ ውስኪ ፡ ተነንዲያ ፡ እስኪ ፡፡

**ወስኖ ፤ ኖት ፤ (ወሰነ ፡ ይዌስን ፡ ይወስን ፡፡ ዐረ ፡ ወዘነ ፤ መዘነ) ፤** መወሰን ፡ መደንገግ ፤ መቁረጥ ፡ መከለል ፡ ማመልከት ፡ ምልክት ፡ ማድረግ ፤ የበታ ፡ የሕግ ፡፡ ወሰነ ፡ ሲተ ፡ መካነ ፡ ዘአንድር ፡ ውስቴቱ ፡፡ ይዌስን ፡ በኖዳ ፡፡ አከ ፡ ዳሕቅከ ፡ ወትጋህከ ፡ በዓለም ፡ ዘይዌስከከ ፡ እምዘወሰነ ፡ ለከ ፡ ፈጣሪከ ፡ ወኢተሀከየትከ ፡ ዘየሐጽጸከ ፡ እምዘዐቀመ ፡ ለከ ፡፡ ሠርዑ ፡ ወወሰኑ ፡ በቀኖናሆሙ ፡ (ስንክ ፡ መጋቢት ፡፡ ቅዳ ፡ ግሩ ፡፡ ፈላስ ፡ ገ፳፯ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ፡፡

**ወሳኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት) ፤** የሚወስን ፡ ወሳኝ ፡ ሐጋጊ ፡ ደንጋጊ ፡፡ ፈጣሬ ፡ አዝማን ፡ ወወሳኒ ፡ ዓመታት ፡፡ ወሳኒ ፡ ሀልዎታት ፡ ከመ ፡ ኢይትዐደዉ ፡ እምዘአዘዘ ፡ (መጽ ፡ ምስ ፡፡ አፈ ፡ ድ፱) ፡፡

**አወሰነ ፤** አዮሰነ ፡ አስደነገገ ፡ ወሰን ፡ አስደረገ ፡፡

**ተወሰነ ፤** በቂመ ፡ ታገገ ፡ ተደነገገ ፡ ተቈረጠ ፡፡ መካን ፡ ዘተወሰነ ፡ ዕድሜ ፡ ዘተወሰነ ፡፡ መጠን ፡ ዘተወሰነ ፡፡ ተወሰነ ፡ ወተፈትሐ ፡ ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ምእመናን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፰ ፡፡ ፴፯ ፡፡ ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፫) ፡፡

**ውሱን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ስንት) ፤** በቂሙ ፤ የተወሰነ ፡ የተቈረጠ ፡ ቍርጥ ፡ ወሰን ፡ ደንበር ፡ ልክ ፡ መጠን ፡ ያለው ፡፡ መካን ፡ ውሱን ፡፡ ኵሎ ፡ ሥሩዐ ፡ ወዕቁመ ፡ ወውሱነ ፡ ግበሩ ፡፡ እግዚ ፡ ረሰየ ፡ ለክሙ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ መዋዕለ ፡ ውሱነ ፡፡ መዓርጋት ፡ ዘውሱን ፡ ሎቱ ፡፡ ጊዜ ፡ ዘውሱን ፡ ሎቱ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫ ፡፡ ፩ ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፵ ፡፡ ዮሴፍ ፡፡ ፈ ፡ መ ፡ ፬ ፡ ፪ ፡፡ ፲ ፡ ፩) ፡፡

**ውሳኔ ፤ (ንያት) ፤** መወሰን ፤ (ጥወ) መወሰን ፡ አወሳሰን ፡ ውስና ፡፡ ገዢነቱ ፡ ውሳኔ ፡ ሕግ ፡ ይደሉ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡፡ ውሳኔያተ ፡ ሕግ ፡፡ ውሳኔያት ፡ እንተ ፡ ወሰንዋ ፡ አበው ፡ ቀደምት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፳ ፡፡ ገድ ፡ ኪሮ ፡፡ ያዕ ፡ ዘእል) ፡፡

— ፤ በቂሙ ፤ ፍጻሜ ፡ ወሰን ፡ ደንበር ፡፡ በእንተ ፡ ውሳኔ ፡ አውስቦ ፡፡ ውሳኔያተ ፡ አምዳር ፡፡ ለሕገ ፡ አሪት ፡ ቦቱ ፡ ወሰን ፡ ወሰዛቲስ ፡ አልባቲ ፡ ውሳኔ ፡፡ በጽሒት ፡ በምዕር ፡ ኀበ ፡ ውሳኔ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፬ ፡፡ መቅ ፡፡ አፈ ፡ ድ፲፱ ፡፡ ፲፫) ፡፡

**ወሰን ፤ (ናት ፡ ነታት) ፤** በቂሙ ፡ ዳርቻ ፡ ዳር ፡ ደንበር ፤ ምልክት ፡ ወደብ ፡ ገደብ ፤ ፍጻሜ ፡፡ አመ ፡ ያነብር ፡ ወሰነ ፡ ለባሕር ፡፡ ገበርኩ ፡ ላቲ ፡ ወሰነ ፡፡ እስከ ፡ ወሰንከ ፡ ሰደዱከ ፡፡ ወሰን ፡ ሰማኒናዊ ፡፡ ዘይትዐዶ ፡ ወሰነ ፡፡ አልቦ ፡ ለዝ ፡ ሕግ ፡ ወሰነ ፡ መዋዕል ፡ (ምሳ ፰ ፡ ፳፱ ፡፡ ኢዮ ፴፰ ፡ ፲ ፡፡ ዓብድ ፡ ፯ ፡፡ ሕዝ ፵፫ ፡ ፳ ፡፡ ሆሴ ፭ ፡ ፲ ፡፡ ኩፋ ፡ ፲፯) ፡፡

**ተዋሰነ ፤** በቂሙ ፡ ተወሳሰነ ፡ ተዳከ ፡ ተካለለ ፡ ተደናበረ ፡፡ ኤማት ፡ እንተ ፡ ትትዋሰና ፡ (ዘካ ፲ ፡ ፱) ፡፡

**አስተዋሰነ ፤** አዋሰነ ፡ አወሳሰነ ፡ አካፈለ ፡ አካለለ ፡፡

**ወስቆ ፤ ቆት ፤ (ወሰቀ ፡ ይዌስቅ ፡ ይወስቅ ፤ ዐሰቀ ፡፡ ዕብ ፡ ናሻቅ) ፤** መወሰቅ ፡ መለጠጥ ፡

መቀፈር፤ መሳብ፡ መገተር፤ ማለብ፡ መደከር፤ መደገን፡ ማከናወን፤ የቀስት፡ የንዋየ፡ ሐቅል። መለከን፡ እዴ፤ የዚህ፡ ወንድም፡ ነው። ወሰቀ፡ ቀስቶ። እሰ፡ ወሰቁ፡ አቅስስቲሆሙ፡ ወሰቀ፡ ልሳኖሙ፡ ከመ፡ ቀስት፡ ለ ሐሰት። ወይዌስቅ፡ ቀስቶ፡ (ኩፋ፡ ፴፰። ኤር፱፡ ፫፱። ፱፡ ፫። መዝ፡ ፶፯፡ ፯)።

**ተወሰቀ**፤ ታለበ፡ ተደገነ፡ ተዘጋጀ።

**ውሱቅ**፤ (ቃን፡ ቃት፡ ስቅት)፤ የታለበ፡ የተደገነ፡ ድግን። ሐጽ፡ ውሱቅ፡ በአንጻረ፡ ጸላኢ። ውሱቃን፡ አቅስስቲሆሙ፡ (ማር፡ ይሥኗ፡ ፳። ኢሳ፭፡ ፳፰። ፳፯፡ ፲፭)።

**ወሰረ**፤—ገዘገዘ፤—ወሥሮ፡ ወሠረ።

**ወሲስ**፤ ሶት፤ (ወሰ፡ ይወስስ፡ ይሰስ)፤ መወስስ፤ ማነስ፡ መኰስስ፤ ሥሥ፡ ወሰስ፡ መኘን፤ የከብት፡ የቅንጣት። ፪ኛም፤ ወስወሰ፡ ብሎ፡ ወሰወሰ፡ ተወሳወሰ፤ ውስወሳ፡ ወስዋሳ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ይወጣል፡ (ዐማርኛ)።

**ውስተ**፤—ወደ፡ በ፤—ወሲዋ፡ ወሰጠ።

(ጥ) **ወተገ**፤ (ይዌትግ፡ ይወትግ፤ ወትጎ፤ ነትገ)፤ ሸሸ፡ ኰበለለ፤ ተሰደደ። እሰ፡ ወተጉ፡ እምነ፡ ሞአብ። ወተገ፡ ዝሉ፡ በሓውርት፡ (ኢሳ፲፮፡ ፱። ኤር፴፡ ፳፱)። ባለቅኔዎች፡ ግን፡ ቀማ፡ ይሉታል።

**ወተን**፤ **አውታን**፤ (ዐረብ)፤ ጠያት፡ የጠያት፡ ስም። ቀይጠነ፡ አውታን፡ (አቡሻ፡ ፯)።

**ወተፈ**፤ (ትግ፡ ወዐም)፤ በቁሙ፤ ዘጋ፡ ደፈነ፡ አኰረሠ።

**ወቲር**፤ ሮት፤ (ወተረ፡ ይወትር፡ ይትር)፤ መወ(ጠ)ተር፡ መገተር፤ መሳብ፡ መዘርጋት። ወተረ፡ ቀስቶ፡ (ዕንባ፡ ፲፱። መዝ፡ ፯)።

—፤ መትኰር፤ ማዘውተር፤ የዐይን፡ የኅሊና። ማብዛት፡ መደጋገም፤ መመላለስ። መውደድ፡ ማሰብ። መጽሐፍ፡ ግን፡ በወተረ፡ ፈንታ፡ አውተረ፡ ይላል፤ አያሰኝም። ኢታውትር፡ እደከ፡ ለዘኢኮነት፡ እንቲኣከ፤ ዘረጋ፡ (ምሳ፳፡ ፳)። አወትር፡ አዕይንትየ፡ ላዕሌሆሙ። ኢታውትር፡ ዐይነከ፡ ኀቤሃ። ዘየወትር፡ አዕይንቲሁ፡ ይኄሊ፡ ጠዋየ። እመ፡ አውተርከ፡ ዐይነከ፡ ኀቤሁ፤ ተኰረ፡ (ዓሞ፱፡ ፬። ምሳ፱፡ ፲፰። ፲፯፡ ፴። ፳፫፡ ፭)። አውተረ፡ ጸልዮ። አውትሮ፡ ጸሎት። ጳውሎስ፡ ኢያውተረ፡ ነጊረ፡ ትሕትናሁ፤ አበዛ፡ (ሉቃ፳፪፡ ፵፬። አፈ፡ ተ፱። ድ፪)። ኢልፀስ፡ ከነ፡ ያወትር፡ ህይድአት፡ ወብሕታዌ። እንዘ፡ ያወትራ፡ ይሕየዋ፡ በንጽሕ። ኢታውትር፡ ስማዬ፤ ወደደ፡ (ፊልክ፡ ፳። ፲፭። ፪፻ ፵፪)።

**አውተረ**፤ (አስደራጊ)፤ አስወተረ፡ አስገተረ፡ አዘወተረ። ልማዱ፡ ግን፡ አድራጊ፡ ነው።

**አውታሪ**፤ **መውተሪ**፤ (ሬት፡ ርያን፡ ያት)፤ የሚያዘወትር፡ አዘውታሪ፤ ተኳር። እስመ፡ ኮነ፡ ውእቱ፡ ጻድቀ፡ ወመውተሬ፡ ለህይድአት፡ (ፊልክ፡ ፲፭)።


**ተዋትረ**፤ ተወተረ፡ ተገተረ፤ ተዘወተረ።

**ውቱር**፤ (ራን፡ ራት፡ ትርት)፤ የተወተረ፡ የተዘወተረ፤ የዘወትር።

**ውቱረ**፤ ወትሮ፡ አዘውትሮ፤ ሁሉ፡ ወገን፡ በውስጥ፡ በአፍኣ። ውቱረ፡ ይዋሕየኒ፡ ነያራር። ይከድንዋ፡ በወርቅ፡ ውቱረ፡ (ኢዮ፴፡ ፲፭። ዕብ፱፡ ፬)።

**ወትር**፤ **ወትረ**፤ ዘልፍ፡ ዘልፈ፤ ወትሮ፡ ዘወትር፡ ዕለት፡ ዕለት፤ በየቀኑ። ፍርየታ፡ ዘወትር። ሀበነ፡ ዘወትር፡ ጸሎተነ፤ ዘወትረ፡ ይሴብሑ። በከመ፡ ልማድ፡ ዘወትር። ወትረ፡ ይጌሥጽ። ወትረ፡ በኵሉ፡ ጊዜ፡ ወበኵሉ፡ ሰዓት፡ (ዘፀ፳፱፡ ፴፰። ኪዳ። አፈ፡ ድ፲፰። ምሳ፲፫፡ ፳፬። ድጓ)።

**ወትር**፤ (ብ፡ አውታር። ዕብ፡ የቴር። ሱር፡ ያትራ። ዐረ፡ ወትር)፤ በቁሙ፤ ኹማት፡ ገመድ፤ የክራር፡ የበገና፡ የደጋን፡ የድንኳን። ቃለ፡ አውታረ፡ መሰንቆ። መዝሙር፡ ዘዐሥርቱ፡ አውታሪሁ። እመ፡ አሰሩኒ፡ በሰብዐቱ፡ አውታር፡ ሐዳሳት፡ እለ፡ አልቦሙ፡ ብትክት፡ (ቀሌ። መዝ፡ ፴፪። መሳ፲፮፡ ፯)።



ወትር፡

**ወቲት**፤ ቶት፤ (ወተ፡ ወተተ፡ ይወትት፡ ይትት)፤ ማውተት፡ መዋተት፤ አውታታ፡ ክርታታ፡ መኸን፤ ወተተ፡ ማለት፡ ከወተትና፡ ከውሃ፤ ከገፋፋ፡ ከጕሬረፋ፡ የወጣ፡ ነው። ፪ኛም፤ ወትወተ፡ ብሎ፡ ወተወተ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ይወጣል፤ ኹሉም፡ ዐማርኛ፡ ነው።

**ወተት**፡ (ዐማርኛ)፤ በቁሙ፤ ሐሊብ። (ተረት)፡ የረጋ፡ ወተት፡ ቅቤ፡ ይወጣዋል።

# ዘ

ዘ ፤ ፯ኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፋ ፡ ቤት ፡ በአ በገደ ። ስሙ ፡ ዘይ ፤ ቀጥሩ ፡ ፯ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ ዘ ፡ ሰብዐት ፡ ቱ ፡ ይባላል ። ዕብራውያን ፡ ግን ፡ ሰባትን ፡ መ ደብ ፡ አድርገው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነቊጣ ፡ እየጨመሩ ፡ ሰባት ፡ እልፍ ፡ ይሉታል ። ምስጢሩ ፡ ምስጢረ ፡ ስንበት ፡ ነው ፤ ፍጻሜንና ፡ ዕረፍትን ፡ ፍጹም ፡ ጌጥን ፡ ፍጹም ፡ ሽልማ ትን ፡ ያሳያል ። ዘየነን ፡ ተመልከት ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ዘሌ ፳፫ ፡ ፪) ።

ዝ ፤ (ዘ ፤ እሉ ፤ እላ) ፤ የቅርብ ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፤ ይህ ፡ ይኸ ። ቅጽል ፡ ሲኾን ፡ ስሙ ፡ ጫብጥ ፡ ወ ይም ፡ እጅታ ፡ ይባላል ። ዝ ፡ ብእሲ ፤ ዝ ፡ ሕዝብ ፤ ዝ ፡ ቃል ፤ ዝ ፡ መጽሐፍ ። ዝኑ ፡ ዝኒ ፡ ዝስ ፡ ዝኬ ። በዝ ፡ እ ምዝ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ በእንተ ፡ ዝ ። ዘ ፡ ይኸን ፡ ይህን ፡ ይህ ንን ፤ ትማልም ፡ ዘ ፡ ጊዜ ። እመ ፡ ገብረ ፡ ዘ ፡ ቃለ ። ስምዑ ፡ ዘ ፡ ነገረ ። ወባረኩ ፡ ዘ ፡ ቡራኬ ።


ዛ ፤ ይች ፡ ቺ ፤ ይህች ፡ (ይችን) ። ዛ ፡ አንቀጽ ፤ እስከ ፡ ዛ ፡ ዕለት ፤ ምስለ ፡ ዛ ፡ ትውልድ ። ርባታው ፡ እንደ ፡ አንና ፡ እንደ ፡ ንሕነ ፡ መደብ ፡ ስምንት ፡ ብቻ ፡ ኹኖ ፡ ይቀራል ፤ አንና ፡ ንሕነ ፡ የለውም ፤ ያውም ፡ እን ዲህ ፡ ነው ። ዝ ፡ ዝንቱ ፤ ይህ ። እሉ ፡ እሎንቱ ፤ እሊህ ፡ እኒህ ። ዛ ፡ ዛቲ ፤ ይች ። እላ ፡ እሎን ፡ እላንቱ ፤ እሊህ ፡ ሴቶች ። ይህ ፡ አራቱ ፡ መደብ ፤ አንተ ፡ አንቲ ፡ አንትሙ ፡ አንትን ፡ በማለት ፡ አንጻር ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ የቅርብ ፡ ቅርብ ፡ ይባላል ። ዝኩ ፡ ዝስኩ ፡ ዝክቱ ፤ ያ ፡ ያኛው ። እልክቱ ፤ እሊያ ፡ እኒያ ። እንትኩ ፡ እንታክቲ ፤ ያች ። እልኩ ፤ እሊያ ፡ ሴቶች ። ይህ ፡ አራቱ ፡ ደግሞ ፤ ውእቱ ፡ ይእቲ ፡ እሙንቱ ፡ እማንቱ ፡ በማለት ፡ አንጻር ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ የቅ ርብ ፡ ሩቅ ፡ ይባላል ። የክ ፡ ጠባይ ፡ ማቅረብ ፡ እንጂ ፡ ማራቅ ፡ አልነበረም ፤ ክ ፡ ክሃ ፡ ክማለት ፡ መጥቶ ፡ በዝ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተደረበ ፡ ምስጢሩ ፡ ዘክሃ ፡ ኹኗል ፤ ይሆን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ቃል ፡ አለ ። ፍቻቸውን ፡ በየቦታቸው ፡ ተመልከት ።

ዘ ፤ (እንተ ፤ እለ) ፤ ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ቅጽልና ፡ በቂ ፤ ፍችው ፡ የ ። ዘ ፡ ያንድ ፡ አንተ ፡ ያንዲት ፤ እለ ፡ የብዙ ። ኢየሱስ ፡ ዘተብህለ ፡ ክርስቶስ ። ድንግል ፡ እ ንተ ፡ ተፍኀረት ፡ ለብእሲ ። ሕዝብ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ምስሌሁ ። አዋልድ ፡ እለ ፡ አልቦን ፡ ኍልቍ ፡ (ማቴ፳ ፡ ፲፮ ። ሉቃ፩ ፡ ፳፯ ። ዮሐ፲፪ ፡ ፲፯ ። ማሕ፮ ፡ ፰) ። መጽ ሐፍ ፡ ግን ፡ ዐዋጅ ፡ አፍርሶ ፡ ዘን ፡ ላንድም ፡ ለብዙም ፡ ለሴትም ፤ እንተን ፡ ለሴትም ፡ ለወንድም ፡ ይቀጽላል ፡ ባለቅኔዎችም ፡ ያደርጉታል ፡ እያሰኛም ። አንስትያ ፡ ዘኀረዩ ። አባግዕ ፡ ዘአልቦ ፡ ኖላዊ ። በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዘልህቀት ፡ ወለተ ፡ ዳዊት ። አቃርዮስ ፡ እንተ ፡ ደለዎ ፡ ርእይ ። ዮሐንስ ፡ ወአቡቂር ፡ እንተ ፡ ነበሩ ፡ ኅቡአ ፡ በእስክንድርያ ፡ ሀገር ። ብእሲ ፡ ምእመን ፡ እንተ ፡ ይሰመይ ፡ ጕልያን ፡ (ዘፍ፮ ፡ ፪ ። ዘኍ፳፯ ፡ ፲፯ ። ድጓ ። ስንክ ፡ ታኅሣ፱ ። ሐምሌ ፡ ፲) ። ዘርፍ ፡ እያያዥ ፡ ኹኖም ፡ ሲነገር ፡ ብዙርና ፡ ዘያዕቆብ ፤ ክህነት ፡ እንተ ፡ ሌዊ ፤ ነገ ሥታት ፡ እለ ፡ ይሁዳ ፤ አንስትያ ፡ እለ ፡ ዳዊት ፡ ወዕቁ ባት ፡ እለ ፡ ሰሎሞን ፡ እያለ ፡ በየጕንዘቡ ፡ ይገባል ፤ ፍች ውም ፡ ያው ፡ የ ፡ ነው ። ሲዘረዘርም ፡ ኣን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ አድርጎ ፤ ዚኣ ፡ እንቲኣ ፡ እሊኣሁ ፡ ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፤ ከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ የ ፡ ነ ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ ሥር ፡ ይዘምታል ፤ ፍችውም ፡ የርሱ ፡ የርሷ ፡ የርሳቸው ፡ ያሰኛል ። በዚኣ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ዘዚኣሁ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ዘክመና ፡ እንደ ፡ ዘእንበለ ፡ አዳማቂ ፡ ኹኖ ፡ ይገባል ፤ የርሱ ፡ የኾን ፡ ተብ ሎም ፡ የቅጽል ፡ አፈታት ፡ ይፈታል ። ዘዘ ፡ ዚኣሁ ፡ ሲል ፡ ግን ፡ እየራሱ ፡ እየቅሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ያሰኛል ፡ ምስክሩን ፡ በየቦታው ፡ እይ ። በር ፡ ከፋች ፡ ሲኾን ፡ በእንተ ፡ ዘ ፤ ህየንተ ፡ ዘ ፤ ከመ ፡ ዘ ፤ እምዘ ፡ በዘ ፡ እያለ ፡ ይገባል ። አንዳንድ ፡ ሰዋሰዋውያን ፡ ዘ ፤ ስለ ፡ ና ፡ ይኾናል ፡ ይላሉ ፡ ምክንያቱም ፡ በእስመና ፡ በእንተ ፡ ፈንታ ፡ ተጥሮ ፡ ስላ ገኙት ፡ ነው ። ነስሐ ፡ እግዚ ፡ ዘአንገሦ ፡ ለሳኦል ። ሰይ ፡ ልየ ፡ ዘርሕቀ ፡ ማኅደርየ ። አአኰትከ ፡ እግዚኦ ፡ ዘአ ረሰይከኒ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ሀያድያን ፡ (፩ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፴፭ ። መዝ ፡ ፻፲፱ ። ሉቃ፲፰ ፡ ፲፩) ። ዘ ፡ እንተ ፡ እለ ፡ በቅጽል ፡ በዘርፍ ፡ ሲፈቱ ፡ የሚስማማቸው ፡ ቃል ፡ ይሻሉ ፡ እንጂ ፡ ወትሮ ፡ የ ፡ አይባሉም ። ይህም ፡ ብእሲ ፡ ዘለምጽ ፤ ለም ጻም ። ዘጋኔን ፤ ጋኔናም ፡ ጋኔን ፡ ያደረበት ። ዘሚበት ፤ ሽ በታም ፡ ሽበቶ ። እንተ ፡ ዕፍረት ፤ ባለሽቱ ። እለ ፡ ዐመፃ ፤ ዐመፀኞች ፡ እያሰኘ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። እንትና ፡ እለ ፡ ዘዘ ፡ ከዝ ፡ በሚለዩበት ፡ በልዩነታቸው ፡ ለየብቻ ቸው ፡ ተጽፈዋልና ፤ ፍቻቸውን ፡ በየቦታቸው ፡ እይ ፡ (ዕ ርር፱ ፡ ቀ፲) ።

ዚአ ፤ (ዚ ፡ አ) ፤ ዚ ፡ ቅጽል ፤ አ ፡ አካል ፤ በር ፡ ከፋች ፡ ከውእቱ ፡ ርባታ ፡ ከሥሩ ፡ መደብ ፡ የመጣ ። ሲዘ ረዝር ፡ ዚኣየ ፡ (ከ ፡ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ ፡ ነ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ሆሙ ፡ ሆን) ፡ ይላል ፡ የኔ ፡ ማለት ፡ ነው ። እንቲኣ ፡ እሊኣ ፡ ያለ ውም ፡ እንደዚሁ ፡ ይዘረዝራል ፡ (ዚ ፡ ቲ ፡ ሊ ፡ በያሪች ፡ ናቸው ፡ ወደ ፡ ኃምስ ፡ ሳይለወጡ ፡ ገቢር ፡ ተገብሮ ፡ ይከ ታሉ) ። ዘሉ ፡ ዘታሕተ ፡ ሰማይ ፡ ዚኣየ ፡ ውእቱ ። ም ድር ፡ እንተ ፡ ኢኮነት ፡ እንቲኣከ ። ነአምር ፡ ከመ ፡ እ ሊኣከ ፡ ንሕነ ። ውስተ ፡ ዚኣሁ ፡ መጽአ ፡ ወእሊኣሁሰ ፡ ኢተወክፍዎ ፡ (ኢዮ፵፩ ፡ ፪ ። ኩፋ ፡ ፲ ። ጥበ፲፭ ፡ ፪ ። ዮሐ፩ ፡ ፲፩) ።

ዝእብ ፤ (ብ ፡ አዝእብት ። ዕብ ፡ ዝኤብ ። ሱር ፡ ዚእባ ። ዐረ ፡ ዚእብ) ፤ ኝብ ፡ ነጣቂ ፡ አ

ውሬ ፡ መልኩ ፡ ውሻ ፡ የሚመስል ፡ የጽዕብ ፡ ወገን ፤ ሆዳም ፡ ያህዮች ፡ ጠላት ። (ተረትና ፡ ግጥም) ፡ ኸ-ብ ፡ ሲወጉ ፡ ባህያ ፡ ይወጉ ። ያህያ ፡ ባል ፡ ተኸ-ብ ፡ አያስጥል ። ባህያ ፡ ቁዳ ፡ የተሠራ ፡ ቤት ፡ ብትንትን ፡ ይባል ፡ ኸ-ብ ፡ የሬሳ ፡ ሌት ። ግብ ፡ ዝእብ ፡፡ ክሰባት ፡ ወአዝእብት ፤ (ኢርሚ ፡ ፭ ። ፫ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፲፬ ። ፳፬ ፡ ፴፰ ። ሚልክ ፡ ፲፰ ። ሔኖ ፡ ክ፹) ። በግእብ ፡ ፈንታ ፡ ተኵላ ፡ እንዲል ፤ በጽዕብም ፡ ፈንታ ፡ ዝእብ ፡ ይላል ፤ ጽዕብንና ፡ ተኵላን ፡ እይ ። ተፃቱና ፡ እንስቱ ፡ ባንድና ፡ በብዙ ፡ ሲለዩ ፤ ዝእብ ፤ ዝእባን ፤ አዝኣብ ፡፡ ዝእብት ፤ ዝእባት ፤ አዝእብት ፤ ያሰኛል ። መምህራን ፡ ግን ፡ ኸ-ብ ፡ ፈናፍንታም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አይለዩለትም ፤ መጽሐፍም ፡ እሙ ፡ ዝእብ ፡ ወይእቲ ፡ ዝእብ ፡ እያለ ፡ ይገኛል ፡ (አዋል ። ስንክ ፡ ግንቦ) ። በተረትም ፡ ኸ-ብ ፡ ሲሰር ፡ ኪዳ ፡ ተሰሮ ፡ ገባ ፡ ይባላል) ።



ዝእብ ፡

**ዚአሁ ፤ (ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን)** ፤ ዚአ ፡ ሁ ፡ ዘ ፡ የርሱ ።

**ዚአየ ፤ (ከ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡ ና)** ፤ ገነኢ ፡ ከማሁ ፤ ዘ ፡ የኔ ።

**ዘእንበለ ፤—ዘ—እንበለ** ፤ ያለ ።

**ዘቢብ ፤ ቦት ፤ (ዘበ ፡ ይዜብብ ፡ ይዝብብ)** ፤ መዝርበብ ፡ ዝርበብ ፡ ማድረግ ፡ የንቅልፍ ። መንዝርበብ ፡ ማንዝርበብ ፡ ያሞራ ፡ የወፍ ፡ የባለክንፍ ፤ ይኸውም ፡ ሲታወቅ ፡ ዕብራይስጡ ፡ ዝንብ ፡ ዝንቦች ፡ ሲል ፤ ዝቡብ ፡ ዝቡቢም ፡ ይላል ፤ ዘብዘበን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ዘቢብ ፤—በቁሙ ፤—ዘብይ ፡ ዘበየ ።**

**ዝብድ ፤ (ዐረ ። ትማ ፡ ዚብደት ። ዕብ ፡ ዚብዳ)** ፤ ስብድ ፡ ስብታ ፡ ቅቤ ፡ ትኵሱ ፡ ስጋው ፡ ሽፍታው ። (ግጥም ፡ የራብ ፡ ዐሊ ፡ እናት ፡ የገፉትና ፡ የበደለት ፡ ቋረኛው ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ እናትና ፡ ልጁን ፡ ለመውጋት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ይዞ ፡ በሸፈተ ፡ ጊዜ) ፡ ተገፍቶ ፡ ተገፍቶ ፡ በታላቅ ፡ ሰቀቃ ፡ ካሳ ፡ ሽፍታ ፡ ኾነ ፡ ስራብ ፡ የሚበቃ ።

**ዝብድይ ፤ (ፀማርኛ)** ፤ የቅቤ ፡ ወቀት ፡ ማውጫው ፡ መቀበያው ።

**ዝባድ ፤ (ዕብ ፡ ዜቤድ)** ፤ የዝባድ ፡ አውሬ ፡ ጥርኝ ፡ መጠኗ ፡ የድመት ፡ ያህል ፡ ነብርማ ፡ ዝንጉርጉር ፤ በኋላዋ ፡ ወይም ፡ በሆዷ ፡ በጕያዋ ፡ ታናሽ ፡ ማቈሪያ ፡ ያላት ፡ ላብታና ፡ ወዚ ፡ በዚያ ፡ እየመላ ፡ እንደ ፡ ቅቤ ፡ ረግቶ ፡ የሚገኝ ፡ ዝባድ ፡ የሚባለው ፡ ርሱ ፡ ነው ። ጽርኒን ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ዘብድ ፤ ዘብድው ፤ (ብ ፡ ዘባድው ። ዐረ ፡ ሰበድ)** ፤ ዐጥፍ ፡ ሌጦ ፡ ዳባ ፡ ነት ፡ እንቀልባ ፡ የመናኒ ፡ ካባ ፤ እንደ ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ ያለ ። ሰሌልያስ ፡ ኢሀሰዎ ፡ ዘእንበለ ፡ አሐዱ ፡ ዘብድ ፡፡ አልባሲሁ ፡ ዘዘብድወ ፡ ጠሊ ፡፡ በዘብድወ ፡ ጠሊ ፡ ወበሐሜለት ፡፡ ዘባድወ ፡ ጠሊ ፡፡ ዘባድው ፡ (አፈ ፡ ተ፲፰ ። ስንክ ፡ ጥር፳፱ ። ድጓ ። ዕብ፲፩ ፡ ፴፯ ። ሥር ፡ ጳጕ) ።

**ዘብዘበ ፤ (ዐረብ ። ዘቢብ ፡ ዘበ)** ፤ ከለከለ ፡ አሶጣ ፡ አባረረ ። ሰበከ ፡ በህየ ፡ በወንጌለ ፡ ኢየሱስ ፡ ወዘብዘብዎ ፡ ወሰደድዎ ፡ እምዝሉ ፡ አህጉሪሆሙ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲፩) ።

—፤ በቁሙ ፤ ዘበዘበ ፡ አስቸገረ ፡ በነገር ። ዘብዘባ ፡ እንዲሉ ፡ (በማርኛ) ።

**አዘብዘበ** ፤ አዘበዘበ ፤ አረገዘ ፡ ተንጠረዘዘ ፡ ሲናድ ፡ ቀረበ ፤ የካብ ፡ የግንብ ።

**ዘቢሕ ፤ ሖት ፤ (ዘብሐ ፡ ይዘብሕ ፡ ይዝባሕ ። ዕብ ፡ ዛባሕ)** ፤ ማገዝባት ፡ ማዘባት ፤ ጠልፎ ፡ መጣል ፤ ማሰር ፡ መኰድኰድ ፤ ቈልምሞ ፡ ማረድ ፡ መሠዋት ። ጠብሐን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ዘብሖት ፡ ዘዚኣሃ ፡ ጥብሖ ፡፡ ዘቢሖ ፤ መሥዋዕት ፡ ዘብሑ ፡ ደቤላ ፡ ጠሊ ፡፡ ዘብሑ ፡ ደቂቀሙ ፡ ወአዋልዲሆሙ ፡ ለአጋንንት ፡ (ምሳ፱ ፡ ፪ ። ፲፮ ፡ ፳ ። ኩፋ ፡ ፴፱ ። መዝ ፡ ፻፭) ።

—፤ በቁሙ ፤ መዝባት ፡ መዛባት ፡ መውደቅ ፤ መታሰር ፡ መቈልመም ፡ ለመታረድ ። ግስንቱ ፡ ገቢርና ፡ ሰገል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ።

**ዘባሒ ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት)** ፤ የሚያርድ ፡ የሚሠዋ ፤ ዐራጅ ፡ ሰጋሚ ።

**ዝቡሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ብሕት)** ፤ የዘባ ፡ የተዘባ ፤ የታረደ ፡ የተሠዋ ፤ ዕርድ ። ዝቡሕ ፡ ለአማልክት ፡፡ ወበልዐ ፡ ዝቡሓቲሆሙ ፡፡ ኢፈቀዱ ፡ ይብልዑ ፡ እምዝቡሓተ ፡ ባዕዳን ፡ ዘእንበለ ፡ ዝቡሓተ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ (ራእ፪ ፡ ፲፬ ። ፊ ፡ መ ፡ ፲፮ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ግንቦ) ።

**ዝብሐት ፤ (ታት)** ፤ ማረድ ፡ መታረድ ፡ አስተራረድ ። ዝብሐተ ፡ በግዕ ፡ ለእግዚ ፡፡ ይሥሐቅ ፡ ተቤዘወ ፡ በዝብሐተ ፡ በግዕ ፡ (አርጋ ፡ ፭ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ዝብሕ ፤ (ሓት)** ፤ ዕርድ ፡ መሥዋዕት ፤ ቍርባን ፡ ፍሬዳ ። ዝብሐ ፡ ለአምልክ ፡፡ ይዝብሑሑ ፡ ሎቱ ፡ ዝብሐ ፡፡ ዝብሓት ፡ (ሲኖዶ ። ዮሴፍ ። ዘፀ፳፱ ፡ ፳፰) ።

**መዝብሕ ፤ (ብ ፡ መዛብሕ)** ፤ ማረጃ ፡ ስለት ፡ የብረት ፡ መግፊያ ። የሚያርድ ፡ ዐራጅ ። የታረደ ፡ ዕርድ ፡ ፍሪዳ ፡ መሥዋዕት ። ወብሂሎቱስ ፡ ስጡሕ ፡ አምጽአ ፡ ዘንተ ፡ እምሥርዐተ ፡ መዝብሕ ፡ ዘመሥዋዕት ፡ (አፈ ፡ ድኀ) ።

**ምዝባሕ** ፤ ማረጃ ፡ መሠዊያ ፡ ቦታ ፤ ምሥዋዕ ፡ መንበረ ፡ ታቦት ።

**ዘቢጥ ፤ ጦት ፤** (ዘበጠ ፡ ይዘብጥ ፡ ይዝብጥ ። ዕብ ፡ ሻባጥ) ፤ መዝበጥ ፡ መምታት ፡ ማስተካከል ፤ የሽማኔ ። መደብደብ ፡ መውቃት ፤ መጠዘል ፡ መንረት ፤ ማፍሠል ፡ መጽፋት ። በበትር ፡ ይዘብጠከ ። ዘይዘብጥ ፡ ሕባሁ ፡ ወእም ። ዝብጦ ፡ ለወልድከ ። ይዘብጡክሙ ፡ መላትሒክሙ ፤ (ኢሳ፲ ፡ ፳፬ ። ዘፀ ፳፩ ፡ ፲፰ ። ምሳ፲፱ ፡ ፲፰ ። ሚክ፬ ፡ ፲፬) ። ጕድዐንና ፡ ጠቅዐን ፡ ወገረን ፡ እይ ።

**ዘባጢ ፤** (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት ፤ ዘበጥ) ፤ የሚዘብጥ ፡ ዘባጭ ፡ ተማች ፡ በበትር ፡ አቅላጭ ። ይቅትልዎ ፡ ለዘባጢ ። እምእደ ፡ ዘባጢሁ ። ዘባጥያት ፡ ክበሮ ፡ (ዘኍ፴፭ ፡ ፳፭ ። ዘዳ፳፭ ፡ ፲፭ ። መዝ ፡ ፳፯) ።

**መዝበጥ ፤** (ብ ፡ መዛብጥ) ፤ መዝበጫ ፡ መምቻ ፡ መንረቻ ፡ በትር ፡ ቅጠት ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**አዝበጠ ፤** አስመታ ፡ አስደበደበ ።

**ተዘብጠ ፤** ተዘበጠ ፡ ለጥ ፡ አለ ፡ ተካከለ ። ተመታ ፡ ተወቃ ፡ ተደበደበ ። ሥልስ ፡ ተዘበጥኩ ፡ በእብትር ። ሰገም ፡ ተዘብጠ ። ክበሮ ፡ ዘይዘበጥ ፡ (ተረ ፡ ቄር ። ፪ቆ፲፩ ፡ ፲፭ ። ሸቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፭) ።

**ዝቡጥ ፤** (ጣን ፡ ጣት ፡ ብጥ) ፤ የተዘበጠ ፡ የቀመታ ፡ ምት ፡ ፍንከት ። ዝቡጥ ፡ በእርእስተ ፡ ኀጺን ። ይሬሲ ፡ ዝቡጠ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፭ ። ጥበ፰ ፡ ፲፭) ።

**ዝብጠት ፤** (ታት) ፤ መምታት ፤ መመታት ፤ አመታታት ፤ ምት ፡ ውቂያ ፤ በትር ፡ ቅጣት ፡ ማርፋት ። ዝብጠት ፡ ወቅጥቃጤ ። ከመ ፡ ዝብጠቱ ፡ መሰንቆ ፡ ወእንዚራ ። ሞተ ፡ ፊልጶስ ፡ በውእቱ ፡ ዝብጠት ። ይደልዎ ፡ አርብዓ ፡ ዝብጠት ፡ (ምሳ፳ ፡ ፲፭ ። መቃ ፡ ፲፰ ። ዮሴፍ) ።

**ዝብጦ ፤** (ዝቡጥ) ፤ ሥሥ ፡ ረቂቅ ፡ ተመትቶ ፡ ተቀጥቅጦ ፡ የተሠራ ። ቀርነ ፡ ዝብጦ ። መጣቅዕት ፡ ዘብሩር ፡ ዝብጦ ። ወላትው ፡ ዘወርቅ ፡ ዝብጦ ፡ (መዝ ፡ ፺፯ ። ዘኍ፲ ፡ ፪ ። ዘሌዋ ፡ ፬ ፡ ፲፭) ።

**ዘብጥ ፤** (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፡ ሜዳ ፡ ረባዳ ፡ የዳገት ፡ የተራራ ፡ ሥር ።

**ተዛበጠ ፤** ተማታ ፡ ተደባደበ ፡ ተቀናደበ ። እለ ፡ ይትላሀዩ ፡ ወይዛበጡ ፡ ወይትጋደሉ ። ኅሊናት ፡ እለ ፡ ይዛበጡ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፱ ። አረጋ) ።

**አስተዛበጠ ፤** አማታ ፡ አጋጨ ፡ አዋጋ ፡ አናከሰ ። ያስተዛብጡ ፡ አባግዐ ፡ ወዶርሆ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፡ (ቄለመ ፡ ፲፫) ።

**ዘብዮ ፤ ዮት ፤** (ዘበየ ፡ ይዘቢ ፡ ይዝቢ ። ትግ ፡ ዘቤ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ዛቤን) ፤ መግዛት ፡ መዋጀት ። ይፈኑዎ ፡ እለእስክንድርያ ፡ ይሚጥ ፡ ሎሙ ፡ ግብረ ፡ ወይዘቢ ፡ ሎሙ ፡ መፍቅዶሙ ፡ (ሥር ፡ ጳኮ) ። ማዋደድ ፡ ማስማማት ፡ ዕንቢትን ፡ ክብረት ፡ ማሳከት ። ዛቢያ ፡ እንዲሉ ።

**ዘቢብ ፤** (ብ ፡ ዘባይብ ። ዐረብ) ፤ በቁሙ ፤ የወይን ፡ ቋንጣ ፡ በበሎ ፡ የደረቀው ። አስካለ ፡ ወዘቢብ ፡ ኢይብላዕ ። ሙዳየ ፡ ዘቢብ ። ፀጽቀ ፡ ዘቢብ ፡ (ዘኍ፮ ፡ ፫ ። ፩ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፲፰ ። ፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፩) ።

**ዘቢል ፤ ሎት ፤** (ዘበለ ፡ ይዘብል ፡ ይዝብል ። ዕብ ፡ ዛባል) ፤ መዝበልበል ፡ ማፋግ ፡ ፍግ ፡ መጣል ።

**ዝብል ፤** (ሉር ፡ ዚብላ ። ዕብ ፡ ዜቢል ። ዐረ ፡ ዚብል) ፤ ሐሠር ፡ አተላ ፡ ፋንድያ ፡ እበት ፡ ፍግ ፡ በጠጥ ፤ ዐዛባ ፡ ኵስ ፡ ከሰው ፡ ከእንስሳ ፡ ሆድ ፡ የሚወጣ ። እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ውስቴታ ፡ ኵስሐ ፡ ወዝብለ ፡ ወኵሎ ፡ ምግባረ ፡ ፅግ ። ዝብለ ፡ ብርት ፡ ወኀጺን ፡ ዐር ፡ (መቃ ፡ ፲፱ ። አዋል) ። ሲያበዛ ፡ ዝብላት ፡ ዝብለታት ፡ ይላል ። ከንክሙ ፡ ዝብለታተ ፡ (ሕዝ፳፪ ፡ ፲፱) ።

**መዝበል ፤** (ልት ፡ ታት) ፤ ፍግ ፡ ማፈሻ ፡ ማትቻ ፡ ወይም ፡ መጣያ ፡ መቈለያ ።

**ዜቡል ፤** (ጽርእ ። ዕብ ፡ ዝቡል) ፤ መንገድ ፡ ቤት ፡ ቦታ ። ብዔል ፡ ዜቡል ፡ (ማቴ፲፪ ፡ ፳፬) ።

**ዘበነ ፤** (ይዘብን ፡ ይዝብን ። ዘቢን) ፤ ታዘለ ፡ ታዛይ ፡ ዝርባ ፡ ደጀን ፡ ኋን ።

**ዘባን ፤** (ናት) ፤ በቁሙ ፡ ዝርባ ፡ ኋላ ፤ ከማኅራት ፡ እስከ ፡ መንበርት ፡ ያለው ፡ የሆድና ፡ የደረት ፡ ምስራብ ፡ ጎሮ ። ሆድና ፡ ዝርባ ፡ እንዲሉ ። መጠውኩ ፡ ዘባንየ ፡ ለመቅሠፍት ። እመ ፡ ይጥ ፡ ዘባንክሙ ። ዘባኖሙ ፡ መንገለ ፡ ቤተ ፡ እግዚ ። ወዘባናቲሆሙ ፡ ምሉኣን ፡ አዕይንት ፡ (ኢሳ፶ ፡ ፮ ። ሚል፪ ፡ ፫ ። ሕዝ፰ ፡ ፲፮ ። ፲ ፡ ፲፪) ። ዘባነ ፡ ባሕር ፡ ሜዳ ፡ ሰጡሕ ።

**ዘባናዊ ፤** ዘበኛ ፡ ደጀን ፡ ዝርባ ፡ ሰፋሪ ።

**ዘቢር ፤ ሮት ፤** (ዘበረ ፡ ይዘብር ፡ ይዝብር ። ሰበረ) ፤ መቈረጥ ፡ መስበር ፡ መክፈል ፡ መቈንጸል ። መዘበር ፡ መወዘበር ፡ መዝበራታ ፡ መናገር ፡ መንዝባረር ፡ ያሮጌ ፡ የሰከር ።

**ዘብርት ፤** (ታት ። ዐረ ፡ ዙብረት) ፤ ቁራጭ ፡ ቍራሽ ፡ ስባሪ ፡ እንክትክች ፡ ሥራ ፡ የማይገዛ ። ይኄይስከ ፡ ትጹር ፡ ሞጻ ፡ ወጼወ ፡ ወዘብርታተ ፡ ኀጺን ፡ እምትንበር ፡ ምስለ ፡ አብድ ፡ (ሢራ፳፪ ፡ ፲፭) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዘብርታት ፡ ፈንታ ፡ ዝብለታት ፡ ይላል ።

**መዝበር ፤** (ራት ፡ መዛብርት) ፤ ባድማ ፡ ባዶ ፡ ፍራሽ ፡ ጠፍ ፤ የተፈታና ፡ የፈረሰ ፡ አገር ፡ መንደር ። ይትሐነጽ ፡ መዝበርከ ። ንሕንጽ ፡ መዝበራ ። እንግብሮን ፡ ለአህጉሪክሙ ፡ መዝበረ ፡ (ኢሳ፶፰ ፡ ፲፪ ። ሚል፩ ፡ ፬ ። ዘሌዋ፳፮ ፡ ፴፩) ።

**መዝበሬ ፤** (ዳ ፡ ቃ ፡ ግ) ፤ ፈረስ ፡ ተናጋ ፡ ተበተነ ። መዝበረ ፡ ዦሉ ፡ አህጉር ። መዝበርኪ ፡ ወወድቂ ፡ ወማሰንኪ ። አሕየወ ፡ ምሥዋዐ ፡ ዘመዝበረ ፡ (ኢሳ፵፱ ፡ ፲ ። ማ፲፱ ፡ ፲፱ ። ፫ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፴፱) ። በመዝበረ ፡ ፈንታ ፡ ተመዝበረ ፡ ይላል ፡ አያስኬድም ። ወተሐንጻ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘተመዝበራ ፡ (ስንክ ፡ መጋ ፳፯) ።

**ምዝቡር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ብርት) ፤ የፈረሰ ፡ የተናደ ። ቤትየሰ ፡ ምዝቡር ። አንኳሰ ፡ ዙሉ ፡ አብያተ ፡ ጣያታት ፡ ወረሰየሙ ፡ ምዝቡራነ ፡ (ሐጌ፩ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ሡኔ፱) ።

**ምዝባሬ** ፤ መፍረስ ፡ አፈራረስ ፡ ፍርሻ ፤ ጠፍንት ። ምዝባሬ ፡ ዳግም ፡ ዘቤተ ፡ መቅደስ ፡ (አቡሻ) ።

**አመዝበረ** ፤ አፈረሰ ፤ አስፈረሰ ፤ አስጠፋ ። አህጉረ ፡ ጽኑዓተ ፡ አመዝበረት ። ደማስኖ ፡ ወደመዘብሮ ፡ ነኪር ። ግፍዐ ፡ ደመዘብር ፡ አብያተ ፡ ወደሐጽጽ ፡ መዋዕለ ፡ (ሚራ፳፰ ፡ ፲፩ ። ኢሳ፲ ፡ ፳ ። ፈላስ ፡ ገ፴፱) ።

**ዘቢት** ፤ ቶት ፤ (ዘበተ ፡ ይዘብት ፡ ይዝብት) ፤ መዝበት ፡ ማፌዝ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዜጋ** ፤—በቁሙ ፤—ዘዊግ ፡ ዜግ ።

**ዘጊብ** ፤ ቦት ፤ (ዘገበ ፡ ይዘግብ ፡ ይዝግብ ። ጸግበ) ፤ መሰብሰብ ፡ ማድለብ ፤ መከተት ፡ ማከማቸት ። ከመ ፡ ጽቡር ፡ ወርቀ ፡ ዘገበ ። የዐውድ ፡ ባዕል ፡ ከመ ፡ ይዝግብ ፡ ንዋየ ፤ ይጼይስ ፡ ውሂበ ፡ ምጽዋተ ፡ እምዘጊቦቱ ፡ ለወርቅ ። ይዘግቡ ፡ ለርእሶሙ ፡ እኩየ ፡ (ኢዮ፳፯ ፡ ፲፮ ። ሚራ፴፱ ፡ ፫ ። ጠቢ፲፱ ፡ ፳ ። ምሳ፲ ፡ ፲፬) ። በልዐንና ፡ ጸግበን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**ዘጋቢ** ፤ መዝግብ ፤ የሚዘግብ ፤ ሰብሳቢ ፡ ከታች ፤ ሆዳም ።

**መዝገብ** ፤ (ብ ፡ መዛግብት) ፤ መገንበያ ፡ መከተቻ ፡ ማከማቻ ፤ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ሣጥን ፡ ጉታ ፡ ጉተራ ፡ ጉርጆ ፤ ደልገን ፡ ድብኝት ፡ ጉስጉሻ ፤ ማድጋ ፡ ፈቀን ፡ ገንቦ ፡ ጋን ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። መዝገበ ፡ ንጉሥ ። አርኀው ፡ መዛግብቲሆሙ ። ደስተጋብእ ፡ ሥርናየ ፡



መዝገብ ።

ውስተ ፡ መዝገቡ ። ወአባእክሙ ፡ ኵሎ ፡ ማእረረክሙ ፡ ውስተ ፡ መዛግብት ። ምእት ፡ መዛግብተ ፡ ወይን ፡ ወመዛግብተ ፡ ቅብዕ ፡ (አስቴ፫ ፡ ፱ ። ማቴ፲፪ ፡ ፲፭ ። ፫ ፡ ፲፬ ። ሚልክ ፡ ፫ ። ዕዝ፯ ፡ ፳፪) ።

—፤ ድልብ ፤ ቅምጥ ፡ ገንዘብ ፤ የተደበቀ ፡ የተጠበቀ ። ብክ ፡ መዝገብ ፡ ዘሥዩም ፡ ለከ ፡ ኀበ ፡ ልዑል ። ረክበ ፡ መዝገበ ። መዝገብ ፡ ኅቡእ ፡ ወክቡት ፡ (ሉቃ ፡ ዕገዜ ፡ ፺ ። ሚራ፯ ፡ ፲፱ ። ኢሳ፵፭ ፡ ፫) ።

—፤ በቁሙ ፡ ደብተር ፡ የገንዘብ ፡ ወጪና ፡ ገቢ ፡ የሚጣፍበት ። መዝገብ ፡ ይታይ ፡ እንዲሉ ።

—፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ታላቅ ፡ መጽሐፍ ፤ ብዙ ፡ ነገር ፡ የተጣፈበት ፡ እንደ ፡ ድጓ ፡ ያለ ። ይቤ ፡ ቴርሎስ ፡ በውስተ ፡ መጽሐፉ ፡ ዘይሰመይ ፡ መዝገብ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**መዝገበ ፡ ቃላት** ፤ የቋንቋ ፡ መጽሐፍ ፤ ግስና ፡ ነባር ።

**ተዘግበ** ፤ ተዘገበ ፡ ተሰበሰበ ፤ ደለበ ፡ ተጠበቀ ። በኀቤከ ፡ ተዘግበት ፡ ጥበብ ። ብዕል ፡ ዘይዘገብ ፡ በዐመፃ ። ይዘገብ ፡ ለጻድቃን ፡ ብዕሎሙ ፡ ረሲዓን ፡ (ኢዮ፳፰ ፡ ፳ ። ፳ ፡ ፲፰ ። ምሳ፲፫ ፡ ፳፪) ።

**ዝጉብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ግብት) ፤ የተዘገበ ፡ የተደለቀ ፡ የተጠበቀ ። ኀጢአቱ ፡ ለኤፍሬም ፡ ዝጉብ ። ዝጉባን ፡ ለእሳት ፡ (ሆሴ፲፫ ፡ ፲፪ ። ፪ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፯) ።

**ዘግባ** ፤ (ባት) ፤ በቁሙ ፡ ዝግባ ፤ የደጋ ፡ ዛፍ ፡ ታላቅ ፡ ረዥም ፡ ገናና ፡ ወፍራም ፤ የማጥን ፡ ዕንጨት ፡ እንደ ፡ ዘግባና ፡ እንደ ፡ ጥንዝ ፡ ያለ ፤ የዘግባ ፡ ዐይነት ፡ አርዘ ፡ ሊባኖስ ። ዘግባ ፡ ይትመሳኅ ፡ እምሥርዌ ። ከመ ፡ ዘግባ ፡ ዘሊባኖስ ። እስመ ፡ ወድቀ ፡ ዘግባ ። ወዕፀወ ፡ ዘግባት ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ ፡ (መቃ ፡ ገ፳ ። መዝ ፡ ፺፩ ። ዘካ፲፩ ፡ ፪ ። ፩ዜና ፡ ፳፪ ፡ ፬) ። አርዘን ፡ እይ ።

**ዝጋግ** ፤ (ትግሬ) ፤ ምሽሮ ፡ ነቀርሳ ፤ ዕንገት ፡ የሚያዝግ ፡ የሚበሳሳ ። ፪ኛም ፡ ዘጊግ ፡ ዘገ ፡ ብሎ ፡ ሲገሉት ፡ ዝግ ፡ አለ ፡ ዝግግግ ፡ ያለኛል ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዘጊድ** ፤ ዶት ፤ (ዘገደ ፡ ይዘግድ ፡ ይዝግድ) ፤ መዝገድ ፡ አብዝቶ ፡ መጨመር ፡ መማገድ ፤ የኀፍረት ።

**ዘግዴየ** ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ አዘጋጀ ፤ አሰናዳ ። ደሰወን ፡ እይ ።

**ተዘግደየ** ፤ **ተዘጋደየ** ፤ ተዘጋጀ ፤ ተዘገጃጀ ። ተሰካተዩ ፡ ወተዘጋደዩ ፡ ለመዊት ፡ (ንግሥ) ።

**ዝግዱይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ዲት) ፤ የተዘጋጀ ፡ ዝግጁ ፤ ስንዱ ፡ ልባም ።

**ዘጊሕ** ፤ ሖት ፤ (ዘግሐ ፡ ይዘግሕ ፡ ይዝጋሕ ። ዘግዐ ፤ ሠገረ) ፤ መዝጋት ፡ መግጠም ፡ መቈለፍ ፤ ማጉር ፡ ማጠር ፡ መድፈን ፤ መውጫ ፡ መግቢያ ፡ መንሣት ። ዘግሐ ፡ ኆኃወ ፡ ቤት ፡ እግዚ ። የዐቅቡ ፡ ዘጊሖሙ ፡ ጽኑዐ ። ዝጋሕ ፡ ኆኅተ ፡ ወኅትም ። ዘግሖ ፡ መጽሐፍ ፡ ለዙሉ ፡ ውስተ ፡ ኀጢአት ። ዘግሖሙ ፡ ወሞቅሖሙ ፡ (፪ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፳፬ ። ተረ ፡ ቄር ፳፬ ፡ ዳን፲፫ ፡ ፲ ። ገላ፫ ፡ ፳፪ ። ስንክ ፡ መጋ፲፫) ። ዝሓ ፡ ማዝጋት ፡ ወይም ፡ ድር ፡ ማድራት ፤ ዝሓውን ፡ ይዞ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ማለት ። ዝሓ ፡ አዝጊ ፡ እንዲሉ ።

**ዘጋሒ** ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት) ፤ የሚዘጋ ፡ ዘጊ ፤ በረኛ ።

**አዝግሐ** ፤ አ(ስ)ዘጋ ፡ አሲያዘ ፡ አስጨበጠ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአዝግሐ ፡ ፈንታ ፡ ዘግሐ ፡ ይላል ። ወኢዘጋሕከኒ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ፀርየ ፡ (መዝ ፡ ፴) ።

**ተዘግሐ** ፤ ተዘጋ ፤ ተዘጋበት ። ተዘግሖ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ። ሶበ ፡ ወፅአ ፡ እምተዘግሖ

ቅመ ፡፡ ፍኖት ፡ ተዘግሖ ፡ በውስተ ፡ ገዳም ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳ ፡ ፊልክ ፡ ፺፳፱ ፡ ገድ ፡ ኪሮ) ፡፡


**ዝጉሕ** ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ግሕት) ፤ የተዘጋ ፡ ዝግ ፡ ቤት ፡ ሞቅሕ ፡ ንሥግ ፡ ወቅቱር ፡ ወዝጉሕ ፡፡ አንቀጸ ፡ መቃብር ፡ ዝጉሕ ፡ (ግብጽ ፡ ፳፫ ፡ ደራሲ) ፡፡ —፤ የተዘጋበት ፤ ደጃፍ ፡ ዘግቶ ፡ በውስጥ ፡ ያለ ፤ የዘጋ ፡ ብሕታዊ ፡፡ ዝጉሕ ፡ ውስቴ ፡ ምኔት ፡፡ ውእቱ ፡ ዝጉሕ ፡ (ፊልክ ፡ ፺፱፫ ፡ ፺፯፭) ፡፡

**ዝጉሓዊ** ፤ ዝጊ ፡ ከማሁ ፡ የዘጋ ፡ የተዘጋ ፤ ተዘግቶ ፡ የሚኖር ፡፡ ወውእቱ ፡ ሥርዐተ ፡ ትሩፋን ፡ ዘዘጉሓውያን ፡ ወፈላስያን ፡፡ ዝጉሓውያን ፡ ወባሕታውያን ፡ (ፊልክ ፡ ፩ ፡ ፶፱) ፡፡

**ዝግሐት** ፤ (ቃት) ፤ መዝጊት ፡ መዘጋት ፡ አዘጋግ ፡ ዝግንነት ፡ የተዘጋ ፡ መኾን ፡፡ ኢታግብእ ፡ አንዊክ ፡ ዘበሥጋ ፡ ኀበ ፡ ማእሰርት ፡ ወዝብጠት ፡ ወዝግሐት ፡ ወሥቃይ ፡፡ በዝግሐታት ፡ መዋቅሕት ፡ አመንደብዎ ፡፡ ዝግሐታት ፡ መዋቅሕት ፡ ዘጸረ ፡ (ፊልክ ፡ ፺፫፭ ፡ መጽ ፡ ምስ ፡ ቅዳ ፡ ግሩ) ፡፡

**መዝግሕ** ፤ (ብ ፡ መዛግሕ ፡ ት) ፤ መዝጊያ ፡ መቈለፊያ ፡፡ ኀበ ፡ ብዙኀ ፡ በዋኢቱ ፡ በመዝግሕ ፡ አንብር ፡፡ ይዘግሑ ፡ መዛግሐ ፡፡ መዛግሕት ፡ ድንግልና ፡ ኢብተክ ፡ (ሚራ፥፱ ፡ ፮ ፡ ኪዳ ፡ ገ፱ ፡ ተረ ፡ ቄር ፡ ፲፰) ፡፡ —፤ ቢተዋ ፡ ማልደያ ፡ የጅ ፡ ቡሬ ፡፡ መዝግሕ ፡ ዘበመዝራዕቱ ፡ (፱ነገ ፡ ፩ ፡ ፲) ፡፡ —፤ ጋሻ ፤ አግሬ ፡፡ መዛግሕተ ፡ ወርቅ ፡ (፱ነገ ፡ ፰ ፡ ፯) ፡፡

**ዘጐል** ፤ (ላት ፡ ፅብ ፡ ሽሒሌት) ፤ በቁሙ ፤ ከባሕር ፡ የሚገኝ ፡ የዘጐል ፡ ልብስ ፡፡ እንደ ፡ ተሳቦና ፡ እንደ ፡ ዔሊ ፡ ያለ ፤ ስሙ ፡ ዘጐል ፡ ወይም ፡ ዛጐል ፡ ልብሱ ፡ የሚባል ፡ ታናሽ ፡ የባሕር ፡ ትል ፡፡ እለ ፡ ይትፋወሱ ፡ በሐመድ ፡ ወፍሬ ፡ ዕፀው ፡ ወዘጐል ፡፡ ኅጠታት ፡ ዘጐል ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፩ ፡ ፵፯) ፡፡



ዘጐል ፡

**ዘጐለ** ፤ ዘጐለ ፡ ዛጐል ፡ ኾነ ፤ ዛጐል ፡ መሰለ ፤ የመልክ ፡፡ ዛጐል ፡ በርበሬ ፡ እንዲሉ ፡፡

**መዝጐል** ፤ ዛጐልማ ፡ ዝንጕርጕር ፡፡ ዛጐልማ ፡ ደሮ ፡ እንዲሉ ፡፡

**መዝጐለ** ፤ **ተመዝጐለ** ፤ ተዘናጐለ ፤ ተዘንጐለ ፡፡ ተቃወመ ፡ ተከራከረ ፤ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ በጣ ፡፡ ደቤ ፡ ለአርድእት ፡ እንዘ ፡ ይምዕድ ፡ ሰላመ ፡ እንቲአየ ፡ አኀድግ ፡ ለክሙ ፤ ከመ ፡ ወኢመኑሂ ፡ ኀበ ፡ ካልኡ ፡ ኢይትመዝጐል ፡ በሥርዐት ፡ ሠናየ ፡ አምልኮ ፡ አባ ፡ ዕሩየ ፡ ዘበአማን ፡ ይርአዩ ፡ ስብሐተ ፡፡ ወዘሎ ፡ ይትመዘጐል ፡ ቃለ ፡ በበይናቲሁ ፡ በሃይማኖት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ፡፡

**ዘጊን** ፤ **ኖት** ፤ (ዘገነ ፡ ይዘግን ፤ ይዝግን) ፤ መዝገን ፡ መዸቦን ፡ መጨበጥ ፡ ማፈን ፤ ባንድ ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ በ፪ ፡፡ ሐፈነ ፡ እደ ፡፡ ዘዘገነ ፡ አብሕርት ፡ ዓለም ፡ በሕፍኑ ፡፡ ይዘግን ፡ እምኔሁ ፡ ምልአ ፡ ሕፍኑ ፡ (ቅዳ ፡ ቄር ፡፡ ዘሌ፱ ፡ ፪ ፡፡ ፳ ፡ ፲፱ ፡፡ ዘኍ ፳ ፡ ፳፮) ፡፡ —፤ መማረክ ፤ መያዝ ፤ ምርኮውን ፡ ማፈሥ ፡ እጅ ፡ ማድረግ ፡፡ ዝግና ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡፡

**ዝግን** ፤ (ናት) ፤ ዝግኝ ፡ ጥርኝ ፡ ጭብጥ ፡፡ በቁሙ ፡ መተሮ ፡ የሥጋ ፡ ንፍሮ ፤ የወጥ ፡ ፍሬ ፡፡ የማናይ ፡ ርግ ፡ ፀጋማይ ፡ ጕመን ፡ ወማእከሎሙ ፡ ኢየሱስ ፡ ዝግን ፡ (ቅኔ) ፡፡

**መዝገን** ፤ (ብ ፡ መዛግን ፡ ት) ፤ መዝገኛ ፡ ማፈኛ ፤ ዕፍኝ ፡ ጥርኝ ፡ ውስጥ ፡ እጅ ፡፡

**መዝገነ** ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ግ) ፤ አመሰገነ ፤ አሸገነ ፡ አዝገነ ፤ ዝግና ፡ አደረገ ፤ በቃል ፡፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመዝገነ ፡ ፈንታ ፡ አመዝገነ ፡ ይላል ፤ ኢ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ፡፡ ንጉሥ ፡ ዐማፂ ፡ እመ ፡ ገበርከ ፡ ሠናየ ፡ ኢያመዘግንከ ፤ ወለእመ ፡ አበስከ ፡ ይቀትለከ ፡፡ ሑር ፡ ኀበ ፡ ካህን ፤ ወአመዝግኖ ፡፡ ኢያመዝገነ ፡ ጽጋዌ ፡ ላዕሌሁ ፡ (ፈላስ ፡ ገ፹ ፡፡ ዮሴፍ) ፡፡ ዘና ፡ ስ ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ዐማርኛው ፡ ስ ፡ ይላል ፡፡ ሚዝትንና ፡ ኀብዝ(ስ)ትን ፡ ስገንንና ፡ መስገንን ፡ እይ ፡፡

**አመዝገነ** ፤ (አስደራጊ) ፤ አስመሰገነ ፤ ምስጉን ፡ አሰኘ ፡፡

**አመዝጋኒ** ፤ የሚያስመሰግን ፤ አስመስጋኝ ፡፡ ልማዱ ፡ ግን ፡ አድራጊነት ፡ ነው ፡፡ ሰብእ ፡ አመዝጋንያን ፡ (ፈላስ ፡ ገ፷፱) ፡፡


**ተመዝገነ** ፤ ተመሰገነ ፤ ምስጋና ፡ አገኘ ፡፡ ይትመዘገን ፡ በዘይትከሀሎ ፡፡ አልቦ ፡ ዘይትመዘገን ፡ ከመ ፡ ምግባረ ፡ ትሩፋት ፡፡ ሰላም ፡ ለጦር ፡ ኀበ ፡ እግዚኡ ፡ ዘተመዝገነ ፡ (፱ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፲፱ ፡፡ አፈ ፡ ድ፲ ፡፡ ስንክ ፡ ሐምሌ፲፱) ፡፡

**ምዝጉን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ግንት) ፤ የተመሰገነ ፤ ምስጉን ፡፡

**ምዝጋና** ፤ (ናት) ፤ ምስጋና ፡ ክብር ፤ ትምክሕት ፡፡ ኢታፅርዐ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ፤ እስመ ፡ ገባሪሁ ፡ ኢየኀጥእ ፡ ምዝጋና ፡ በውስተ ፡ ዓለም ፡፡ ከመ ፡ ይርከቡ ፡ ምዝጋና ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ዘአምንዎ ፡፡ ምዝጋናየ ፡፡ ኢይከውኑ ፡ ምዝጋና ፡፡ ወእመኒ ፡ መስተጋድል ፡ ኢይከውኖ ፡ ምዝጋና ፡ እመ ፡ ዘበሕጉ ፡ ኢተጋደለ ፡ (ፈላስ ፡ ገ፶፯ ፡፡ መቃ ፡ ገ፲፱ ፡፡ ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ፡፡ ፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፭ ፡፡ ፪ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፲፰) ፡፡

**ማዝግና** ፤ ባዝግና ፤ (ናት) ፤ ዝርግፍ ፤ የወርቅ ፡ የብር ፡ ደቃ ፤ ድብ ፡ ማርዳ ፡ ሰደፍ ፤ የሚዘገን ፤ በፈትል ፡ ተሰክቶ ፡ ባንገት ፡ የሚታሰር ፡ ያንገት ፡ የደረት ፡ ጌጥ ፤ የሴቶች ፡ የወንዶች ፡ ሽልማት ፡፡ ቃማን ፡ ተመል

ክት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ትረስዕኑ ፡ መርዓት ፡ ሰርጓ ፡ ወይንግል ፡ ባዝግናሃ ። ወአዕፃቂ ፡ ባዝግና ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ። ባዝግናት ፡ ዘውስተ ፡ ክሣደ ፡ አግማል ፡ (ኢሮ፪ ፡ ፲፱ ። ዘፍ፡፴፭ ፡ ፬ ። መሳ፰ ፡ ፳፮ ፡ ፳፮) ። መን ፡ ፬ ፡ ስለ ፡ ጠረሰው ፡ በማግዝግና ፡ ፈንታ ፡ ባዝግና ፡ ይባላል ፤ ዘና ፡ ባ ፡ እንደ ፡ ተዋረሱ ፡ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።



ማግዝግና ፡

**ዘግዐ ፤ (ዘግሐ ። ሰኰዐ) ፤** ዘጋ ፤ ሰነገ ፡ ዐፈነ ፡ ወተፈ ፡ ጠቀጠቀ ፡ ደፍኖማ ። ዘንግዐን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ስርጽ ፡ ነው ።

**ተዘግዐ ፤** ተዘጋ ፤ ተሰነገ ፡ ተወተፈ ። ዘግሐን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ዝጉዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ግዕት) ፤** ዝጉሕ ፡ የተዘጋ ፡ ዝግ ፤ የተዘጋበት ፡ ከሰው ፡ የተለየ ። ቀንኑ ፡ ባዕለ ፡ ብእሲት ፡ ዝግዕት ፡ ዘቦአት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እምቅድመ ፡ ትትኀፀብ ፡ ኀምሳ ፡ ዕለተ ፡ (ሲኖ ፡ ዶ) ።

**ዝግራ ፤ (ራት) ፤** በቁሙ ፤ ኸርግራ ፡ ዝጉርጉር ፡ ዝንጉርጉር ፡ ጠቃጠቆም ፡ የዱር ፡ የበረሓ ፡ ወፍ ፡ እንደ ፡ ቆቅ ፡ ያለ ። (ተረት) ፤ አሞራን ፡ ሲበሉ ፡ ስሙን ፡ ኸርግራ ፡ ይሉ ፡ (አዋል) ።



ዝግራ ፡

**ዝርዶይ ፤ (ዐረ ፡ እልጀድይ ። ዕብ ፡ ግዲ) ፤** የፍየል ፡ ጠቦት ፡ ወጠጤ ። ከ፲፪ቱ ፡ መናዝል ፡ አንዱ ፡ የታኅሣሥ ፡ ኮከብ ። ከዐሐይ ፡ ጋራ ፡ ፳፱ ፡ ዕለት ፡ ፳፫ ፡ ኬክሮስ ፡ ይመግባል ፡ (አቡሻ ፡ ፱) ። አቡ ፡ ጀዲ ፤ (ዐረብ) ፡ የልብስ ፡ ጣቃ ፡ ፍየል ፡ የተማለበት ፡ ባለፍየል ፡ ጠቦት ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ዛህልሎ ፤ ሎት ፤ (ዛህለለ ፡ ይዛህልል ፡ ይዛህልል) ፤** መንዘልዘል ፡ ሞኝ ፡ ዘባ ፡ ተላላ ፡ ዘላላ ፡ መኾን ፤ ብዙ ፡ መብላት ፤ መሴሰን ፤ በውቀት ፡ በሥራ ፡ ማነስ ፡ መጉደል ።

**አንዛህለለ ፤** አሰል ፡ ዘለል ፡ አለ ፤ ዘረ ፡ ባከነ ፡ ደከመ ፤ በሴሰን ፡ በቀንጣን ። ታበየ ፡ ኰራ ። ዘያንዛህልል ፡ ምስለ ፡ አብዳን ። አንዛህለሉ ፡ በአብዝኆ ፡ መብልዕ ። አልባሰ ፡ ቀጠንት ፡ ይመስዋ ፡ ለነፍስ ፡ ወይሬስያ ፡ ታንዛህልል ። ኢታንዛህልል ፡ ሶበ ፡ ገሠጸከ ። አንዛህልሎታ ፡ ለነፍስ ፡ (ምሳ፲፫ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ተ፳፱ ። ድ፳፱) ። ገቢርም ፡ ይኾናል ። መፍትው ፡ ለነ ፡ ኢንረስዮ ፡ ለሥጋ ፡ ዘእንበለ ፡ ረባሕ ፡ ወኢናንዛህልሎ ፡ በትፈግዖ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፱) ።

**እንዝህሉል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ልልት) ፤** አሰል ፡ ዘለል ፡ የሚል ፤ አውታታ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ሲል ፡ ዘሲል ፤ ስካር ፡ ሞኝ ፡ ዘባ ፡ ተላላ ፡ ዘላላ ። እመ ፡ ከነ ፡ እንዝህሉለ ፡ በግብሩ ፡ ዝንቱ ፡ እንዝህሉል ፡ ውእቱ ፡ በሥርዐቱ ፡ ወንዋዩ ፡ ወይትዐቀብ ፡ በጽኑዕ ፡ ከመ ፡ ካዕበ ፡ እንዝህሉለ ፡ ኢይኩን ፡ በሃይማኖቱ ፡ ወዜናሁ ፡ ለእንዝህሉል ፡ ይትናጸር ፡ ምስለ ፡ ዜናሁ ፡ ለልብው ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱) ። በእንዝህሉል ፡ ፈንታ ፡ ንዝህሉል ፡ ነዘህሊል ፡ ይባላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። ተደመረ ፡ ምስለ ፡ አንው ፡ ንዝህሉላን ። ነዘህሊል ፡ ብእሲ ፡ እምንእሱ ፡ ገብረ ፡ ይከውን ፡ (ፊልክ ፡ ፻፱ ። ምሳ፳፱ ፡ ፳፮) ።

**መንዘህልል ፤ መንዛህልል ፤** ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ። ወልድ ፡ መንዘህልል ፡ ዘይዘብጥ ፡ ወላዲያኒሁ ፡ ወይፀርፎሙ ። ህዩይ ፡ ወመንዘህልል ። በእንተ ፡ ሀካያን ፡ ወመንዛህልላን ። ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሐምት ፡ ዘውእቱ ፡ ቤተ ፡ ዘማውያን ፡ ወመንዛህልላን ። ኢይሑር ፡ ኀበ ፡ መካናት ፡ ዘይትጋብኡ ፡ ውስቴቶን ፡ መንዛህልላን ፡ ወእለ ፡ ይሰክሩ ፡ ተባዕተ ፡ ወአብዛኀ ፡ ሠሐቅ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱ ፡ ፲፫ ። ፊልክ ፡ ፲፻፫ ። አፈ ፡ ድ፫ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፱ ፡ ፰ ። ፴፱ ፡ ፱) ።

**ንዝህላል ፤** ዘባንት ፡ ንዝህላልነት ፡ አሰል ፡ ዘለልታ ፤ ዝሙት ፤ ትዕቢት ፡ ክፋት ። ሀኬት ፡ ወንዝህላል ። ንዝህላል ፡ ወትዝኅርት ። ኢይሑራ ፡ ውስተ ፡ ሐውዝ ፡ መባልዕት ፡ ወንዝህላል ። እለ ፡ ወድቁ ፡ ውስተ ፡ ንዝህላል ። ናሁ ፡ ተበየነ ፡ ንዝህላልከ ፡ (አፈ ፡ ድ፴፱ ። ፊልክ ፡ ፳ ። ዲድ ፡ ፲፱ ። ቄር ፡ ጸላ ። ዮሴፍ) ። በንዝህላል ፡ ፈንታ ፡ ነዘህላል ፡ ይባላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። ነዘህላለ ፡ ፍትወት ፡ ያፈልስ ፡ ልበ ፡ የዋሃን ፡ (ጥበ፬ ፡ ፲፪) ።

**ዘሀረ ፤ (ዐረ ፡ ወዕብ) ፤** በራ ፡ አበራ ፡ ብሩህ ፡ ኾነ ፡ የከብር ፡ ብርሃን ፡ (ዘፀ፴፬ ፡ ፴) ።

**ዝሁራ ፤ ዝሆራ ፤ (ዐረ ፡ ዙሀረት) ፤** ብሩህ ፡ ጽዱል ፡ ኮከብ ፤ ስሙና ፡ ክብሩ ፡ ለዝሙት ፡ ማያት ፡ የተሰጠ ፡ የአምልኮው ፡ ሥርዐት ፡ ዝሙት ፡ የኾነ ። ዝሆራ ፡ ኮከብ ። ሐነጹ ፡ ምሥራብ ፡ በስመ ፡ ኮከብ ፡ ዝሁራ ፡ (ስንክ ፡ የካ፳፰ ። ሚያ፫ ። ዮሴፍ) ።

**ዙሀር ፤ ዘውሀር ፤ (ብ ፡ ዘዋህር ። ዐረ ፡ ጀውሀር) ፤** ኮከባዊ ፡ ዕንቍ ፤ ባሕርይ ። ዘውሀር ፡ ወበሉር ። ዘዋህር ፡ ዘእምአዕናቁ ፡ ህንደኬ ፡ ዘያበርህ ፡ (ኪብ ፡ ነገ፲፯ ። እርጋ ፡ ፯) ።

**ዘሀረ ፤—ሰፋ ፡ ረዘመ ፤—ዝኀር ፡ ዘኀረ ።**

**ዝሄት ፤ ቶት ፤ (ዝህተ ፡ ይዝህት ፡ ይዝሀት ። ዕብ ፡ ዛሄት ፤ ገሠጸ ፡ ነቀፈ) ፤** መዛት ፡ መ

ፈክር ፡ ቈይማ ፡ ቈይ ፡ ብቻ ፡ ማለት ። (ተረት) ፤ አላቻ ፡ ጋብቻ ፡ ቈይ ፡ ብቻ ፡ ቈይ ፡ ብቻ ።

**ዘፀት** ፤ ዘቻ ፡ ፍካሬ ፡ ድንፋታ ፡ ጕራ ፤ የትቢትና ፡ የጕጠኛ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ መሐላ ፡ ያለ ።

**ዘዊግ ፤ ጎት** ፤ (ዘገ ፡ ይዘውግ ፡ ይዙግ ። ዕብ ፡ ዛዌግ ። ዐረ ፡ ዘወጀ) ፤ ማዛወግ ፡ ማጋባት ፡ መጥመድ ፡ ማቀናጀት ፡ ጥንድ ፡ ጥንድ ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ማድረግ ። ምስጢሩ ፤ ወፈንዎሙ ፡ በበ ፡ ክልኤቱ ። ተባዕተ ፡ ወአንስተ ፡ ፈጠሮሙ ፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡ ነው ።

**አዝወገ ፡ አዘገ** ፤ (ጥዘ) ፡ አዘወገ ፡ አስጠመደ ፡ ጥንድ ፡ ዘውግ ፡ አስደረገ ።

**ተዘውገ** ፤ ተዘወገ ፡ ተጠመደ ፡ ዘውግ ፡ ኾነ ፡ ተባለ ።

**ተዛወገ** ፤ በቊሙ ፤ ተጋባ ፡ ተጣመደ ፡ ተዛመደ ፡ ተመሳሰለ ፤ ተካከለ ፡ ተዋገነ ። ዘይሬእዩ ፡ ለዘማ ፡ ይዛወጋ ፡ ለሙስና ። ዛቲ ፡ ንጢአት ፡ ትዛወግ ፡ ምስለ ፡ ዘይክው ። በዘይዛወገ ፡ ለግብር ። በላም ፡ ለአስና ንኪ ፡ ሐሊብ ፡ ዕጕልት ፡ ዘተዛወጋ ፡ (ምሳጅ፳ ፡ ፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፫ ። አፈ ፡ ተ፲፫ ። ደራሲ) ።

**ዝዉግ** ፤ (ጋን ፡ ጋት ፡ ውግት) ፤ የተዛወገ ፡ የተዛወገ ፡ የተመሳሰለ ።

**ዘውግ** ፤ (ብ ፡ አዝዋግ ። ዕብ ፡ ዘግ ። ሱር ፡ ዛውጋ ። ዐረ ፡ ዘውጅ ። ጽር ፡ ዜውጎስ) ፤ ኹለት ፤ ጥንድ ፡ መንታ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ጣምራ ፡ ባልና ፡ ሚስት ። ዘውገ ፡ መዓንቅ ። ዘውገ ፡ አልባስ ። ወዘውግ ፡ እሙንቱ ፡ (ሉቃ፪ ፡ ፳፬ ። መሳ፲፬ ፡ ፲ ። ፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፵፫) ።

—፤ ወገኑ ፡ እኩያ ፡ መሰል ፡ አምሳያ ፤ ባልንጀራ ። ዘውገ ፤ አርዌ ፡ ወዘውገ ፡ እንስሳ ። ሥዕርተ ፡ ርእስኪ ፡ ዘፈትለ ፡ ሚላት ፡ ዘውጋ ፡ (አዋል ። ደራሲ) ።

**አስተዛወገ** ፤ (ዘገ ፤ ዘወገ) ፤ አዋገነ ፡ አዛመደ ፡ አስማማ ፡ አንድ ፡ አደረገ ። አድራጊና ፡ አደራራጊ ፡ ነው ። ወያስተዛውግ ፡ በቃለ ፡ ትስፋ ። ዕለት ፡ ብሂል ፡ ዘያስተዛውጎሙ ፡ ለሌሊት ፡ ወለመዓልት ፡ (አፈ ፡ ድ፰ ፡ አዋል) ።

**ዘውሀር ፤—ዕንቍ ፤—ዘሀረ ፡ ዙሀር ።**
**ዝውዛ፤—ከከብ፤—ጀውዛ ፡ ገ ።**

**ዘዌ፤ ሂይ ፤ ዝዋይ** ፤ (ያት ። ዕብ ፡ ዛዊት ። ዐረ ፡ ዛውያ) ፤ መጋጠሚያ ፤ የፄ ፡ ማእዝን ፡ ጫፍ ፡ ሽ ለቆው ፡ ስብራቱ ። ፬ኛም ፤ ዘዌ ፡ ስሙ ፡ ዕፅ ፡ ዝዋይ ፡ ስሙ ፡ ሀገር ፡ ይኾናል ። ዕፀ ፡ ዘዌ ፤ ባሕረ ፡ ዚይ ፡ እንዲሉ ። የዚይ ፡ ምስጢር ፡ ወሰንነት ፡ ነው ። ዕፀ ፡ ዘዌም ፡ በሙ ገር ፡ ቈላ ፡ ይገኛል ፤ የባብ ፡ መድኀኒት ፡ ነው ፤ ጥላው ፡ እንደ ፡ ትንባኾ ፡ ውሃና ፡ ጢስ ፡ ቶሎ ፡ ይገድለዋል ፡ ቢነ ክስም ፡ መርዙን ፡ ይሽርበታል ። ዘዌ ፡ ዘይቀትል ፡ አርዌ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ዕፁ ፡ የሙስቀል ፡ ኀይሉ ፡ የሥግው ፡ ቃል ፡ እባብ ፡ የሳጥናኤል ፡ ምሳሌ ።

**ዘዊዕ ፡ ዖት** ፤ (ዘዐ ፡ ይዘውዕ ፡ ይዛዕ ፤ ይ ሂዕ ፤ ይዝዋዕ ። ዕብ ፡ ዙዕ) ፤ መደንገጥ ፡ መራድ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ መላብ ፡ መውዛት ፡ ወዝ ፡ ማፍሰስ ። ዋዛ ፡ መናገር ፡ ዋዘኛ ፡ መኾን ። ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ማለት ፡ መመ ሳወስ ፡ እስኪወዛ ፡ ድረስ ፡ ማሽብሸብ ፡ መርገጥ ፡ መኼድ ፡ መራመድ ፡ መንጐራደድ ፡ መቅመድመድ ፡ መዝለል ፡ እ ስኪታ ፡ መውረድ ፡ የዘፈን ፡ የማሕሌት ። መታበይ ፡ መ ኵራት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ማለት ፡ ምስጢሩ ፡ ከዝላይ ፡ ይገባል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዘዐ ፡ ፈንታ ፡ ተዛውዐ ፡ ይላል ። ኢይ ዛውዓ ፡ አዕይንትየ ፡ (መዝ ፡ ፴) ።

**ዛውዕ** ፤ (ዓት) ፤ ጨዋት ፡ ጨዋታ ፤ ዘፈን ፡ እ ስኪታ ፡ ሽፋሮ ፡ ሆታ ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ወዘበሬታ ፡ ቧልት ፡ ለግጥ ። ዛውዐ ፡ ነገር ፡ ዘይፈጥሩ ። እክሕደከ ፡ ሰይ ጣን ፤ ወኵሎ ፡ ሥልጣነከ ፡ ወኵሎ ፡ ዛውዐከ ፡ ወፍት ወተከ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘይትረከብ ፡ በሠሐቅ ፡ ወበዛ ውዕ ፡ ይገሥጾ ፡ ዲያቆን ፡ ወይረስዮሙ ፡ ያርምሙ ። እንዘ ፡ ኢያበዝኁ ፡ ሠሐቀ ፡ ወዛውዐ ፡ (ሃጢ.ሞ ፡ ፳ ፡ ፬ ። ኪዳ ። ዲድ ፡ ፲፪ ። ቀሌ) ።

—፤ ጣያት ፡ ቤተ ፡ ጣያት ፡ የሣቅ ፡ የጨዋታ ፡ ቦታ ። ነገ ሩኒ ፡ ኃጥአን ፡ ዛውዐ ፡ ወአኮሰ ፡ ከመ ፡ ሕግከ ። ወይ ማስነ ፡ አውግረ ፡ ዛውዕ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ። ዓሞ፯ ፡ ፱) ።

**ተዛውዐ** ፤ ተጫወተ ፡ ተጨዋወተ ፤ ተናገረ ፡ ተ ከራከረ ፡ በጨዋታ ፡ ቃል ። ኢትዛዋዕ ፡ ምስለ ፡ መስነ ቃዊት ። ቢከ ፡ ይዛዋዕ ። ተዛውዖ ፡ ደቂቅ ። ዘፈቀድኩ ፡ እምእሉ ፡ ኵሎሙ ፡ ይዛዋዕ ፡ ምስሌየ ፡ ወእዛዋዕ ፡ ምስሌሁ ፤ ተዛውዖ ፡ ምስለ ፡ አንው ፡ በቃለ ፡ መጻሕ ፍት ፡ ትጥዕሞሙ ፡ ለለባውያን ፡ እምኵሉ ፡ ጣዕ ማት ፡ (ሢራ፱ ፡ ፬ ። ፬ነገ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ። አፈ ፡ ተ፲፭ ። ፈላስ ፡ ገ፴፫) ።

**ዝዉዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ውዕት) ፤ የታበየ ፡ ዕ ቡይ ፡ ኵሩ ። ዋዘኛ ፡ ዝንጉዕ ። እ ፡ ዕዩይ ፡ ወዝዉዕ ፡ ዕዩየ ፡ ኅሊና ፡ ወዝዉዕ ፡ ልብ ፡ (ሲኖ ዶ) ።

**አስተዛውዐ** ፤ አዋዛ ፡ አጫወተ ፡ አጨዋወተ ። ፊልሞን ፡ መአንዝር ፡ ያስተዛውዖ ፡ ለአርያኖስ ፡ መ ኰንን ፡ (ስንክ ፡ የካ፳) ።

**መስተዛውዕ** ፤ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት) ፤ የሚጫ ወት ፡ የሚያጫውት ፡ ተጫዋች ፡ አጫዋች ። ኢትኹሉ ፡ ኅሊና ፡ መስተዛውዐ ፡ (ኪዳ) ።

**ዛወፈ** ፤ (ዐረ ፡ ዛፈ) ፤ ታበየ ፡ ኰራ ፡ ተመካ ። ኢይዛወፍ ፡ ባዕል ፡ በብዕሉ ፡ (ኤር፱ ፡ ፳፫) ። ወዘፈንና ፡ ዘፍዘፈን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ አማዋር ፡ ናቸው ።

**ዛውፍ** ፤ (ቅጽልና ፡ ጥሬ) ፤ ትቢተኛ ፡ ኵሩ ፡ ተመካሒ ። ትዕቢት ፡ ትምክሕት ። በዘውፍና ፡ በትውዝ ፍት ፡ ፈንታ ፤ ትዝውፍት ፡ ይላል ፡ (ገላ፭ ፡ ፳) ።

**ዘውሮ ፤ ሮት** ፤ (ዘወረ ፡ ይዜውር ፡ ይዘ ውር ፤ አው ፡ ዘዊር ፡ ዘረ ፡ ይዘውር ፡ ይዙር) ፤ መዞር ፡ መክበብ ፤ መጠበቅ ፡ ዘበኛ ፡ መኾን ። ጸጋሁ ፡ ለእግዚ ፡ ትዜውሮሙ ፡ ለጻድቃን ፡ (ሢራ፲፩ ፡ ፲፯) ።

ማዞር ፡ መዘወር ፡ ማሽከርከር ፤ የመኪና ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዘዋሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ ጠባቂ ፡ ከባቢ ፤ የሚዞር ፡ የሚያዞር ፤ የሚዘውር ።

**መዘውር** ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ዘዋሪ ። በቁሙ ፤ መኪና ፡ የሚዘወር ።

**ተዘወ(ው)ረ** ፤ ተዞረ ፡ ተከበበ ፡ ተጠበቀ ። ይዜወሩ ፡ ከመ ፡ አባግዕ ። ነፍስ ፡ ዝልፍት ፡ ኢትዜወር ፡ (ኢዮ፳፫ ፡ ፲፭ ። ሚራ፲፱ ፡ ፲፫) ።

**ዘውር** ፡ (ራት) ፤ ዙሪያ ፤ ከበብ ። ሠረገላሁ ፡ በረድ ፡ ወራሕበ ፡ ዘውሩ ፡ በእሳት ፡ ሕጹር ። ወይኩን ፡ ዘውረ ፡ አክሊሉ ፡ ስፋሐ ፡ ወስፋሑ ፡ በሠላስ ፡ ማዕርጋት ፡ ስፍየት ። አምጣኑ ፡ ባዕል ፡ አነ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ በዘውራ ፤ ንዴት ፡ ውስተ ፡ ቤትየ ፡ ኢይበውእ ፡ ለግሙራ ፡ (ቅዳ ፡ ጎር ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፭ ፡ ፳ ። ቅኔ) ፡ ይህን ፡ ቅኔ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አምኃየስ ፡ ንዴት ፡ በሚባል ፡ ሰው ፡ የዘረፉት ፡ ነው ፡ ይባላል ።

**ዜዉስ** ፤—ስመ ፡ ጣዖት ፤—ዘየዉስ ።

**ዘዘ** ፤ (ደቂቅ ፡ አገባብ) ፤ እየ ፤ እየቅል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ። በዚኣ ፡ ዝርዝር ፡ እየገባ ፡ እንደሚስማማው ፡ ይፈታል ። ለለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ዘዘ ፡ ዚኣሁ ፤ እየራሱ ፡ እየቅሉ ፡ እየብቻው ፡ እያንዳንዱ ። ይፈልጠሙ ፡ ዘዘ ፡ ዚኣሆሙ ። ተፋለጡ ፡ ዘዘ ፡ ዚኣሆሙ ። አስተራሕቅዎሙ ፡ ዘዘ ፡ ዚኣሆሙ ፡ (ማቴ፳፭ ፡ ፴፪ ። ግብ ፲፭ ፡ ፴፱ ። ዳን፭ ፡ ፶፭) ። ዘዘ ፡ ዚኣሁ ፡ ትምህርት ። ዘዘ ፡ ዚኣሁ ፡ ጸጋሁ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፴፯ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፯) ።

**ዘሐብ** ፤ (ትግ ። ዕብ ። ዐረ) ፤ ወርቅ ፡ የወርቅ ፡ ገንዘብ ፡ ዕቃ ፡ መሣሪያ ።

**ዘሕዝሐ** ፤ ሐት ፤ (ዘሕዝሐ ፡ ይዘሐዝሕ ፡ ይዘሕዝሕ) ፤ መዘክዘክ ፡ መዘርገፍ ፤ ማራገፍ ።

**ዛሕዝሐ** ፤ ሐት ፤ (ዛሕዝሐ ፡ ይዛሐዝሕ ፡ ይዛሕዝሕ) ፤ መንዛዛት ፡ መብዛት ፤ መልቶ ፡ መትረፍ ፡ ከልክ ፡ ማለፍ ፤ መፍሰስ ፡ መዝረብረብ ፡ መንጠባጠብ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዛሕዝሐ ፤ ፈንታ ፡ አዛሕዝሐ ፡ ይላል ። ወያዛሕዝሕኒ ፡ በሕቁ ፡ ማእሰየ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፴) ። ፍሕንሐን ፡ እይ ።

**ዝሕዙሕ** ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ዝሕት) ፤ የተንዠዠ ፤ የተትረፈረፈ ፤ ጠብ ፡ ጠብ ፡ ርግፍ ፡ ርግፍ ፡ ያለ ፤ ከልክ ፡ ያለፈ ። መስፈርት ፡ ምሉእ ፡ ወዝሕዙሕ ፡ ወንሕኑሕ ። ትሰረይ ፡ ሎቱ ፡ ጌጋዩ ፡ ዝሕዝሕተ ፡ ወምልእተ ፡ (ሉቃ፮ ፡ ፴፰ ። ቄድር) ።

**ዝሕዛሔ** ፤ መትረፍረፍ ፡ አተራረፍ ፤ ትርፍቻ ፡ ተረፍ ።

**ዝሒሕ** ፤ (ዘሕሐ ፡ ይዘሕሕ ፡ ይዝሐሕ) ፤ መስፈር ፡ መስፋፈር ፤ ዘሕዝሐ ።

**ዝሒል** ፤ ሎት ፤ (ዝሕለ ፡ ይዝሕል ፡ ይዝሐል ። ዕብ ፡ ዛሐል ፤ ዳኸ ፡ ፈሰሰ) ፤ መዛግ ፡ መመረት ፡ ማደፍ ፡ ዐፈር ፡ መራት ፡ ቅጠል ፡ መምሰል ። ወርቅክሙኒ ፡ ወብሩርክሙኒ ፡ ዝሕለ ። ህጉል ፡ ወርቀክ ፡ እምትህጉል ፡ ዐርክክ ፡ ወእምይዝሐል ፡ ውስተ ፡ መድፍን ፡ (ያዕ፭ ፡ ፫ ። ሚራ፳፱ ፡ ፲) ። በቁሙ ፤ መዛል ፡ መድከም ፡ መዝለፍለፍ ። (ግጥም ፤ በቴዎ ፡ ጊዜ) ፤ ብርቱ ፡ ነው ፡ ስትሉት ፡ ከውቤ ፡ ይልቅ ፤ ይኸው ፡ አ(ዐ)ሊዛለ ፡ የጁን ፡ እስኪለቅ ።

**ዘሓሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ይት) ፤ የሚዝግ ፤ ል ፤ ዝገታም ። እምወርቅ ፡ ዘሓሊ ፡ ወእምብሩር ፡ ማሰኒ ፡ (ድጓ) ።

**ዝሑል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ሕልት) ፤ የዛገ ፡ የመረተ ፤ የተበላሸ ፡ እድፋም ። ጽህርት ፡ ዝሕልት ። መጽሔት ፡ ዝሕልት ። ዝሑላኒ ፡ አእምሮ ፤ (ሕዝ፳፬ ፡ ፮ ። ሚራ፲፪ ፡ ፲፩ ። አፈ ፡ ድ፴፫) ።

**ዛሕል** ፤ (ላት) ፤ በቁሙ ፤ ዝገት ፤ እድፍ ። ከመ ፡ ዛሕለ ፡ ብርት ፡ አክየ ፡ ልቡ ። አንተ ፡ ኢሐብረትዋ ፡ ዛሕላ ። እፌትን ፡ ዛሕለኪ ፡ በከውር ፡ (ሚራ፲፪ ፡ ፲ ። ሕዝ፳፬ ፡ ፮ ። ኢሳ፩ ፡ ፳፭) ።

**አዝሐለ** ፤ አዛገ ፡ አሳደፈ ። አዛለ ፡ አደከመ ።

**አዝሓሊ** ፤ መዝሕል ፤ የሚያዝግ ፤ የሚያዝል ፡ አድካሚ ።

**ዙሐል** ፤ (ዐረብ) ፤ ስመ ፡ ኮከብ ፤ ፕላኔት ፡ ከሚባሉት ፡ ከ፯ቱ ፡ ዐበይት ፡ ከዋክብት ፡ አንዱ ፤ እንደ ፡ ምድር ፡ ያለ ። ጣዖት ፤ በምሳሌው ፡ የተሠራና ፡ በስሙ ፡ የሚጠራ ። ኮኪብ ፡ ዙሐል ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፪ ። ዮሴፍ) ። ፍችውን ፡ ዳተኛ ፤ ዘአልቦ ፡ ብርሃን ፡ ይሉታል ፤ ዝሑል ፡ ከማለት ፡ ይስማማል ። በዙሐል ፡ ፈንታ ፡ ሱሐል ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ሱሐል ፡ አብርሀ ፡ ላዕሌየ ፡ ዮም ፡ (ቄድር) ።

**ዝሕነ** ፤—ዘነ ፤—ዝኒን ፡ ዝኅነ ።

**ዝሒቅ** ፤ ቆት ፤ (ዝሕቀ ፡ ዘሐቀ ፡ ይዝሕቅ ፡ ይዝሐቅ) ፤ መዛቅ ፤ አብዝቶ ፡ ማፈሥ ፡ መውሰድ ፡ (ዐማርኛ) ። መግፈፍ ፤ መላጥ ፡ መገሽለጥ ፤ መሸልቀቅ ፡ ቁርበትን ፡ ከሥጋ ፡ መለየት ፤ በልጅ ፡ ማውጣት ። ሀበኒ ፡ መጥባሕት ፡ እዝሐቅ ፡ ባቲ ፡ አነዳ ፡ ትፋሕ ። ዘባሒ ፡ ይዝሕቅ ፡ አነዳ ፡ እምዲበ ፡ ሥጋ ። አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ይዝሐቁ ፡ አምእስቲሆሙ ። ሰብአ ፡ ፀንደኬ ፡ ዘሐቁ ፡ አነዳሁ ፡ ለቅማስ ፡ (ዮሴፍ ። አፈ ፡ ድ፯ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፭ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ዝሕቅ** ፤ ዝቅ ፤ (ቃት ። ዐረ ፡ ዚቅ) ፤ የማስ ፡ የቁርበት ፡ ጋን ፡ ማድጋ ፡ ፊቀን ፡ ርኮት ፡ ራምት ፡ ቀርበታ ፤ ቀረቦ ፡ ስልቻ ፡ ዳውላ ፤ የቁርበት ፡ መሣሪያ ። ዝቀ ፡ ማይ ። ዝቀ ፡ ወይን ። ይምልኡ ፡ ኖዳ ፡ ውስተ ፡ ዝቃት ፡ (ኩፋ ፡ ፲፮ ። ፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፫ ። አፈ ፡ ተ፲፱) ።

**ዘሓቂ** ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት ፤ ሐቅት) ፤ የሚዝቅ ። የሚገፍ ፤ ገፋፊ ።

**ተዝሕቀ** ፤ ተዛቀ ። ተገፈፈ ፤ ተላጠ ። ተዝሕቀ ፡ አነዳሆሙ ፡ (ስንክ ፡ ሐም፳ ። ገድ ፡ አዳ) ።

**ዝሑቅ፤(ቃን፡ ቃት፡ ሒቅት)፤** የተዛቀ ። የተገፈፈ ፡ የተላጠ ። ዝሑቅ፡ ማእስ ። ማእስ ፡ ዝሕቅት ፡ (ስንክ ፡ የካ፲፫ ። ግንቦ፳) ።

**ምዝሓቅ፤(ቃት)፤** መዛቂያ ፤ መግፈፊያ ፤ በታ ፡ ወይም ፡ መሣሪያ ። ውስተ ፡ አስኪተ ፡ ሀገር ፡ ወቦ ፡ እለ ፡ በምዝሓቅ ፡ ወቦ ፡ እለ ፡ በመንኰራኵር ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ዝኊን ፤ ኖት ፤ (ዝኅን፡ ይዝኅን፡ ይዝኅን)፤** መዝናት ፤ ማረፍ ፡ መርጋት ፤ ጸጥ ፡ ማለት ፤ አለመታወክ ። ሀድአንና ፡ ረመመን ፡ እይ ። ዝኅን ፡ ማዕበል ። ሶበ ፡ ረከበ ፡ ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ይትፌወስ ፡ እምሕማሙ ፡ ወይዝኅን ፡ እምደዌሁ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

**ዝኁን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ኅንት)፤** የዘና ፤ ያረፈ ፡ የረጋ ፤ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ጸጥተኛ ። ዝኁን ፡ መርሶ ። ነፋስ ፡ ዝኁን ። እንዘ ፡ ዝኁናን ፡ ንሕነ ፡ እምትንሣኤ ፡ መዋግድ ። ወበትእዛዛት ፡ ዝኁናት ፡ (ቄር ። እፊ ፡ ተ፴፱ ። መጽ ፡ ምስ ። ቄር ፡ ገ፭) ።

**ዝኅነት ፤** መዝናት ፤ አዘናን ፡ ዝናት ። ዕረፍት ፡ ሀድአት ፡ ጸጥታ ፤ ዝምታ ። በዝኅነት ፡ መንግሥትክሙ ፡ (ቄር ፡ ገ፭) ።

**ዛኅን ፤** ዝናት ፤ ዕረፍት ፡ ሀድአት ፡ ጸጥታ ፤ የባሕር ፡ ወደብ ። ዛኅን ፡ ዐቢይ ። ነቢር ፡ ምስለ ፡ ጠቢባን ፡ ሰላም ፡ ወዛኅን ፡ ወሀድአት ፡ ውእቱ ። መርስ ፡ ወዛኅን ፡ ጥዑይ ። ኅድፈፈ ፡ ውስተ ፡ ዛኅን ፡ ወመርስ ። ዛኅኑ ፡ ለባሕር ፡ ወመርሶ ፡ ለአሕማር ፡ (ማቴ፰ ፡ ፳፮ ። ፊላስ ። እፊ ፡ ተ፲፰ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲ ። ድጓ) ።

**ዝኆን ፤ ዘኆን ፤ (ናት)፤** በቁሙ ፤ የታላቅ ፡ አውሬ ፡ ስም ፡ ነጌ ፤ ዝኁን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዝኆን ፡ ያማርኛ ፡ ነጌ ፡ የግእዝ ፤ ነግሀን ፡ እይ ። (ተረት ፤ ስለ ፡ ሆዳም) ፤ በዝኆን ፡ አፍ ፡ ቅርፍት ።

**አዝኀነ ፤** አዘና ፡ ዝም ፡ አሰኘ ፡ ጸጥ ፡ አደረገ ፤ አረጋ ፡ አረጋጋ ። አዝኅና ፡ ለባሕር ፡ በተግሣጸ ፡ ነፋሳት ። ዘአዝኀንከ ፡ እምኔነ ፡ ማዕበላተ ፡ ውሒዛት ፡ መናፍስት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ኪዳ) ። በአዝኀነ ፡ ፈንታ ፡ አስተዝኀነ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። ውስተ ፡ ዘመድኅን ፡ መርሶ ፡ እንዘ ፡ ታስተዝኅኑ ፡ ንግዳ ፡ ለሐመርየ ፡ (ስንክ ፡ ጳጕ፭) ። ዳግመኛም ፡ በግልብጦ ፡ አጣጣፍ ፡ ቀሐመን ፡ ቀምሐ ፡ እንደሚለው ፤ ዝኅን ፡ አዝኅን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ነዝኀ ፡ አንዝኀ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ጸጋ ፡ እንተ ፡ ታነዝኆሙ ፡ ለቅዱሳን ። ሕልቦ ፡ ዘየሐውር ፡ ውስተ ፡ ምኔተ ፡ እንስት ፡ ከመ ፡ ያንዝኆ ፡ እኅተ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፳፱ ። ሥር ፡ ጳኵ) ።

**አዝኃኒ ፤ መዝኅኒ ፤ ኅን ፤** የሚያዘና ፡ የሚያጸና ፡ የሚያጸናና ፤ የሚያረጋጋ ፤ ጸጥ ፡ የሚያደርግ ፡ ዝም ፡ የሚያሰኝ ፡ (እርጋ ፡ ፫) ።

**ዛኅንን ፤ (ተቀ ፡ ማ)፤** ዘኅንን ፤ ቀይ ፡ ቀለም ፡ አገብ ፤ የእጅና ፡ የእግር ፡ የጭራ ።

**ዝኅንን ፤** ጭብር ፡ ወይም ፡ ምንጭርር ፤ ቅጠሉ ፡ ሸክሬ ፡ ቀለሙ ፡ ጠንካራ ፤ ደብተሮች ፡ ጭራቸውን ፡ ወይዛዝሮች ፡ እጃቸውን ፡ የሚያቀልሙበት ። (ወንጌላዊ ፡ ግጥም) ፤ ይህ ፡ ነው ፡ እጅታው ፡ የወንጌል ፡ ጭራ ፤ የተቈነነው ፡ ባምስት ፡ እንጀራ ። ሐዋርያትም ፡ ታሪክ ፡ ሲዘሩ ፤ የንስንሱት ፡ በያህጕሩ ። ስማዕታትም ፡ ተቀብለው ፤ ዝኅንን ፡ ያገቡት ፡ በደማቸው ። ዐለለን ፡ እይ ።

**ዝኊር ፤ ሮት ፤ (ዝኅረ ፤ ዘኀረ ፡ ይዝኅር ፡ ይዝኅር ። ዐረ ፡ ዘኀረ)፤** መስፋት ፡ መዘርጋት ፤ ማበጥ ፡ መነፋት ፤ መዝለል ፡ መጎንፈል ፡ መፍላት ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ መውጣት ፤ ምስጢሩ ፡ ከልክ ፡ ማለፍ ፡ ነው ። ልዕልናን ፡ ማሰብ ፡ መመኘት ፤ በዚህ ፡ ደግሞ ፡ ከዘከረ ፡ ጋራ ፡ ይገጥማል ። ዘሀረንና ፡ ዘከረን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**አዝኀረ ፤** አሰፋ ፡ ዘረጋ ፤ ነፋ ። አዘረጋ ፤ አሳበጠ ፡ አስነፋ ። አኵራ ፡ አስታበየ ፤ አስመካ ።

**አዝኃሪ ፤ መዝኅር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት)፤** የሚያኰራ ፡ የሚያስታብይ ፡ አስመኪ ። በዕጺ ፡ ፈንታ ፡ መዝኅርት ፡ ይላል ፡ (እዋል) ።

**ተዝኅረ ፤ ተዘኅረ ፤** ታዠረ ፡ ታጀረ ፤ ተጓደደ ፡ ተጐላመመ ፤ ያካኼደ ፡ ያለባበሰ ። ተዝኅራ ፡ አዋልደ ፡ ጽዮን ፡ ወየሐውራ ፡ እንዘ ፡ ያገዝፋ ፡ ክሣዶን ። ኢትዘንር ፡ በሥን ፡ አልባሲከ ፡ (ኢሳ፫ ፡ ፲፮ ። ሲራ፲፩ ፡ ፬) ። ታበየ ፡ ኰራ ፡ ተመካ ፤ የግብር ፡ ያነጋገር ። ተዘንረት ፡ ልብከ ። ተዘንሩ ፡ ፀርየ ። ተዘንሩ ፡ ላዕለ ፡ ብሔርየ ። ለምንት ፡ ይዜንር ፡ ኀያል ፡ በእከዩ ፡ (ዐብድ ፡ ፫ ። ሶቁ፭ ፡ ፰ ። ዘካ፱ ፡ ፰ ። መዝ ፡ ፶፩) ።

**ዝኁር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ኅርት)፤** የታጀረ ፤ ዕቡይ ፡ ኵሩ ፤ ትዕቢተኛ ፡ ተመካሒ ። ጸዓሊ ፡ ወዝኁር ። ደቂቀ ፡ ዝኁራን ። ኢትኩኑ ፡ ዝኁራነ ፡ (ኢሳ፱ ፡ ፲፱ ። ኢዮ፴፰ ፡ ፰ ። ዲድ ፡ ፳) ።

**ዝኁራዊ ፤** ትቢተኛ ፡ ኵራተኛ ፤ ትምክሕታም ፡ (ፊልክ ፡ ፪፻፷፫) ።

**ትዝኅርት ፤ (ታት)፤** በቁሙ ፤ ትቢት ፡ ኵራት ፡ ትምክሕት ፡ ተግዳሮት ። ሊብዙኃን ፡ አስሐቶሙ ፡ ትዝኅርቶሙ ። ትምክሕት ፡ ወትዝኅርት ፡ ያማስንዎ ፡ ለባዕል ፡ (ሲራ፫ ፡ ፳፱ ። ፳፩ ፡ ፬) ።

**ዝኅር ፤ (ራት ። ዝክር)፤** መቃብር ፤ ዝርግ ፡ ሞላላ ፡ ጕድጓድ ፤ ሬሳ ፡ የሚዘረጋበት ። የሐኝ ፡ መታሰቢያ ፡ ዝክረ ፡ ስም ፤ በመቃብር ፡ ላይ ፡ የሚጣፍ ፡ ጥሬት ፤ የሚቆም ፡ ሐውልት ፤ የሚሠራ ፡ ቤት ። አውቀርከ ፡ ለከ ፡ ዝኅረ ፡ ውስተ ፡ ኰኵሕ ። ዝኅር ፡ ሐዲስ ፡ ዘአልቦ ፡ ዘተቀብረ ፡ ውስቴቱ ። ዝኅራት ፡ ይትረኀዋ ። ትነድቁ ፡ መቃብሪሆሙ ፡ ለነቢያት ፡ ወታስተማንዩ ፡ ዝኅሮሙ ፡ ለጻድቃን ፡ (ኢሳ፳፪ ፡ ፲፮ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፵፩ ። ቄር ። ማቴ፳፫ ፡ ፳፱) ።

**ዘይ ፤—ስመ ፡ ፊደል ፤—ዘዪን ፡ ዜን ።**

**ዝየ ፤ (ዝ ፡ የ)፤** የቦታ ፡ ዐጸፋ ፤ በዚህ ፡ ከዚህ ፤

ወዲህ ፡ ወደዚህ ። ፀ ፡ እም ፡ እስከ ፡ ይስማሙታል ፤ ቅር ብን ፡ አጠገብን ፡ ግፊና ፡ ቀኝን ፡ ያሳያል ፤ የህየ ፡ እንጻር ፡ ነው ፤ ህየ ፡ የሩቅ ፡ ዝየ ፡ የቅርብ ፤ የህየን ፡ ፍች ፡ እይ ። ዝየ ፡ አኀድር ። መጻእኩ ፡ ዝየ ። እምጽእዎን ፡ ሊተ ፡ ዝየ ። በዝየ ፡ ተፈጸመ ። እምዝየ ፡ ወእምዝየ ። እ ስከ ፡ ዝየ ፡ ብጽሑ ።

**ዝይ** ፤ በቁሙ ፤ ዳክዬ ፡ አፈ ፡ መሮ ፡ የባሕር ፡ ዶሮ ፤ ዋነተኛን ፡ እንሌ ፡ ዝይ ፡ ነው ፡ እንዲሉ ።

**ዘዪግ** ፤ **ጎት** ፤ **(ዜገ ፡ ይዘይግ ፡ ይዚግ)** ፤ መዜግ ፡ ዜጋ ፡ መኾን ፡ መገዛት ፡ መዋረድ ።

**ዜጋ** ፤ **(ብ ፡ አዝያግ)** ፤ በቁሙ ፤ ተገዥ ፤ ገ ብር ፡ ገባር ፡ ጢሰኛ ፡ ባላገር ። ንባቡ ፡ ለነዳይ ፡ ወግዩር ፡ ወዜጋ ፡ አስተቃበልኩ ፤ ወንባበ ፡ ባዕል ፡ አልዐልኩ ፡ (መጽ ፡ ኑዛ) ።

**ዘዪድ** ፤ **ዶት** ፤ **(ዜደ ፡ ይዘይድ ፡ ይዚድ)** ፤ መዘየድ ፤ ዘዴኛ ፡ መኾን ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዜዉስ** ፤ **(ሮማይ ፡ ዴዉስ)** ፤ ስመ ፡ ጣዖት ፤ አምላክ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዜዉስና ፡ ድዮስ ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ናቸው ። ድካምስ ፡ ለዕፀ ፡ ንጤአት ፡ ሥርዋ ፤ ባዕለ ፡ አርጤምስ ፡ ወዜዉስ ፡ ነዋ ፡ (ደራሲ) ።



ዜዉስ ፡

**ዚኽር** ፤ **(ብ ፡ አዝያኽር ። ዐረ ፡ ዚድ ፡ ግ)** ፤ ሰንጠረዥ ፡ የቍጥር ፡ መጽሐፍ ፡ የፀሓይና ፡ የጨረቃ ፡ ቀመር ፡ የከዋክብት ፡ መንገድና ፡ አካኼድ ፡ የተጣፈበት ፡ ገጽ ፡ ሰሌዳ ። ሰብአ ፡ አዝያኽር ። የቍጥር ፡ ሰዎች ፡ ባለ ሰንጠረዦች ፡ (አቡሻ ፡ ፲፩ ። ፵፮) ።

**ዘዪም** ፤ **ሞት** ፤ **(ዜመ ፡ ይዘይም ፡ ይ ዚም ። ሱር ፡ ዛም ። ዕብ ፡ ዛምዜም ። ዐረ ፡ ዘምዘመ)** ፤ ማዜም ፡ መሮኾ ፡ መትመም ፡ ማጕረምረም ። ቃሉ ፡ ከንህብና ፡ ከተርብ ፡ ከጥንዝዛ ፡ ከዝንብ ፡ እፊ፡ፊ፡ኾ ፡ የመጣ ፡ ነው ፤ ቢኼድ ፡ ዕዝ ፡ ጥዝ ፡ እያለ ፡ እንደሚፎኾ ።

**ዘያሚ** ፤ የሚያዜም ፡ አዚያሚ ፤ ፊኪ ፡ ተ ማሚ ።

**ዜማ** ፤ **(ማት)** ፤ በቁሙ ፤ ስልት ፡ ያለው ፡ ፊኸ ኽት ፡ የሐለዬት ፡ የንዋየ ፡ ማሕሌት ፡ ድምፅ ። አዕዋፍ ፡ ዘሠናይ ፡ ዜማሆሙ ። ይሴብሕዎ ፡ በሠናይ ፡ ዜማ ፡ ወማሕሌት ። ኀብረተ ፡ ዜማ ። ዜማ ፡ ግእዝ ፡ ወዕ ዝል ፡ ወአራራይ ። ዝብጠተ ፡ መሰንቆ ፡ ወእንዚራ ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ሠናይ ፡ ዜማ ፡ (ተበ ፲፯ ፡ ፲፯ ። ቀሌ ። አ ርጋ ፡ ፱ ። ግንዘ ። መቃ ፡ ገ፲) ። ዝርማ ፤ ታላቅ ፡ ወንዝ ፡ ኽረት ፤ ፊኪ ፡ ብዙ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ዐማርኛ) ።

**ዜማዊ** ፤ **(ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ ዜመኛ ፡ ባለዜማ ፡ ዜማ ፡ ዐዋቂ ፡ የዜማ ፡ ሰው ።

**ወዜመ** ፤ **(ይወዘይም ፡ ይወዚም)** ፤ ወ ዘመ ፡ ዋዜማ ፡ ቆመ ፤ ዜማ ፡ ዠመረ ። ወ ፡ ከዋይ ፡ የመጣ ፡ ባዕድ ፡ ዘር ፡ ነው ፤ ንቀወ ፡ ብሎ ፡ በእንቀወ ፡ ፈንታ ፡ ስን ቀወ ፡ እንዲል ፤ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

**ዋዜማ** ፤ በቁሙ ፤ መዠመሪያ ፡ ዜማ ፡ ከበዓሉ ፡ በፊት ፡ ማታዉን ፡ የሚዜምና ፡ የሚመራ ፡ መዝሙር ፤ ቅኔ ። ዋዜማ ፡ ዘሠርክ ። እምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡ ዋ ዜማ ፡ (ድጓ ። ገድ ፡ ተክ) ። ውኽሞ ፡ ውኽምኽም ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ይስማማል ።

—፤ ድራር ፡ ንኡስ ፡ በዓል ፤ ማኅትው ፡ የሚቆምበት ፡ ዋዜማ ፡ የሚመራበት ፡ ቀን ። ማኅትው ፡ የነግህ ፡ መዝ ሙር ፡ ነው ። ዋይ ፡ ዜማ ፡ ሲል ፡ ግን ፡ ፪ ፡ ቃል ፡ ነውና ፡ ዋይን ፡ ተመልከት ።

**ዘይን** ፤ **ኖት** ፤ **(ዜነ ፡ ይዘይን ፡ ይዚን ፤ አው ፡ ዘይኖ ፤ ዘየነ ፡ ይዜይን ፡ ይዘይን ። ዕብ ፡ ዛዬን ። ዐረ ፡ ዛነ)** ፤ ማልበስ ፡ ማስታጠቅ ፡ መሸ ለም ፡ ማስጌጥ ፤ ማሰለፍ ፡ ማስጠረር ፤ ጽሕምን ፡ ራስን ፡ መከርከም ፡ ማበጠር ።

**ዘያኒ** ፤ **መዘይን** ፤ **(ዐረ ፡ ሙዘይን)** ፤ የሚያለብስ ፡ የሚያስጌጥ ፡ አልባሽ ፤ ጽሩግ ፡ ማሰሬ ፡ ባለ ወግ ። መዘይነ ፡ ንጉሥ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ዘይ** ፤ **(ዕብ ፡ ዘይን)** ፤ ሰባተኛ ፡ ፊደል ፡ ዘ ። ንዋየ ፡ ሐቅል ፡ የበዳ ፡ ጸብት ፤ ፍጹም ፡ ጌጥ ፡ ፍጹም ፡ ሽልማት ፡ ማለት ፡ ነው ። «እስመ ፡ ኵልኬ ፡ ሳብዕ ፡ ፍ ጹም ፡ ውእቱ ፡ በኀበ ፡ ዕብራውያን» ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ ሳዊ) ። ዘይ ፡ ተዘከር ፡ ቃለከ ፡ ዘአሰፈውኮ ፡ ለገብርከ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ማዝ—፶፯ ። ሰቈ ፩ ፡ ፯ ። ፪ ፡ ፯ ። ፫ ፡ ፲፱ ። ፬ ፡ ፯) ።

**ዘዬ** ፤ **(ዐማርኛ)** ፤ የነገር ፡ ጌጥ ፡ አንዳንድ ፡ ፈሊጥ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በየጨዋታው ፡ እንደ ፡ ዚቅና ፡ እን ዳዝማች ፡ አድርጎ ፡ የሚያገባው ። እኹንም ፡ እንደኾን ፡ እንግዲህ ፡ እንሆ ፡ ታዲያ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ።

**ዜነወ** ፤ **(ተቀ ፡ ግ ፤ ዜነ ፡ ወ)** ፤ ነገረ ፡ አ ወራ ፡ አሰማ ፡ ሰበከ ፡ አስተማረ ፡ አረዳ ፡ አበሠረ ። ዜን ውምሙ ፡ ለበሓውርት ። ሠናይ ፡ እግሪሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይዜንዉ ፡ ሠናየ ፡ ዜና ። ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ዘዜነወ ፡ ማቴዎስ ። ወእንዘ ፡ ይዜንዎ ፡ መጽአ ፡ ካልእ ፡ ዘይ ዜንዎ ፡ ወይቤሎ ፡ መጻእኩ ፡ እዜኑከ ። ዜነዋ ፡ ገብር ኤል ፡ ለማርያም ፡ (ዓሞ ፫ ፡ ፱ ። ሮሜ ፲ ፡ ፲፭ ። ቅዳ ። ኢዮ ፩ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ። ድጓ) ።

**ዜናዊ** ፤ **(ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ የሚነግር ፡ የሚያወራ ፡ አውሪ ፡ ወሬ ፡ ነጋሪ ፡ ሰባኪ ፡ አስተማሪ ። ወ

ፊኛ ፡ ወሬያም ፡ ባለወሬ ፡ ባለምሥራች ፡ መልክተኛ ፤ ወግ ፡ ጠራቂ ፡ ታሪክ ፡ ዐዋቂ ፤ የወሬ ፡ ቋት ። ዜናዊ ፡ ዘነገረነ ፡ ጥበበ ። ዜናዌ ፡ ጥበብ ። ዜናዌ ፡ ትፍሥሕት ። ዜናውያን ፡ ጽዱቃን ፡ (ኪዳ ። ቅዳ ። ድጓ ። ፊልክ ፡ ፲፯) ።

**መዜንው ፤ (ውት ፡ ኑት ፤ ዋን ፡ ዋት) ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ። ዝቲ ፡ መጽሐፍ ፡ መዜንወ ፡ ዘያስተፌሥሕ ፡ ትክውን ፡ ለከ ። ክመ ፡ ንኩን ፡ መዜንዋነ ፡ ኄራን ፡ (ፈላስ ። ኪዳ) ።

**ዜና ፤ (ናት) ፤** በቁሙ ፤ ዝና ፡ ጨዎታ ፡ ወሬ ፤ የተባለ ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፤ የኾነ ፡ የተደረገ ፡ ሥራ ፤ ሰው ፡ ከሰው ፡ አፍ ፤ ወይም ፡ ከመጽሐፍ ፡ የሚሰማው ፡ የሚቀበለው ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፤ ትንቢት ፡ ብሥራት ፡ ስብከት ፤ ደኅንነት ፡ መርዶ ፡ ወግ ፡ ታሪክ ፡ ገድል ፤ ደብዳቤ ፡ መልክት ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ዜና ። ዜነዉነ ፡ ዜና ፡ ነቢያት ። እዜንወክሙ ፡ ዐቢየ ፡ ዜና ። አነ ፡ እልእክ ፡ ኀበ ፡ አቡከ ፡ ይንግርዎ ፡ ዜናከ ። በጽሐ ፡ ዜና ፡ ኀበ ፡ ዳዊት ፤ መርዶ ። ዜና ፡ እስክንድር ፤ ዜና ፡ አይሁድ ። በከመ ፡ ተጽሕፈ ፡ በዜናቲሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ (፩ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፭ ። ድጓ ። ሉቃ፪ ፡ ፲ ። ጦቢ፲ ፡ ፰ ። ፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፴ ። ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፻፺፬) ። ዜናዊ ፡ ላእክ ፡ መልእክ ፡ ሐዋርያ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዜና ፡ ይላል ፤ የመላሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ወመጽአ ፡ ዜና ፡ ኀበ ፡ ሳኦል ። ወዝንቱኒ ፡ ዜና ፡ መጽአ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፳፯ ። ፪ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፮) ።

**ተዜነወ ፤ (ይዜኖ) ፤** ተወራ ፡ ተነገረ ፤ ቃሉ ። ተረዳ ፡ ተማረ ፡ ተበሠረ ፤ ሰሙዮው ። ዐበየ ፡ ዝንቱ ፡ ጻድቅ ፡ ሰበ ፡ ተዜነወ ። ወነዳያን ፡ ይዜነዉ ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፳ ። ማቴ፲፩ ፡ ፭) ።

**ዚንው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ኑት) ፤** የተወራ ፡ የተነገረ ፡ የተረዳ ፡ ምሁር ።

**ተዝያነወ ፤ (ይዝያነው ፡ ይዝያነው) ፤** ተነጋገረ ፡ ተጨዋወተ ። እንዘ ፡ ይዝያነዉ ፡ ዐበያቲሁ ፡ ለእግዚ ። ሰበ ፡ ንዝያነው ፡ በእንተ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ። ዜና ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ፡ ወይዝያነዉ ፡ ቦቱ ፡ ትውልድ ፡ እምድኅረ ፡ ትውልድ ። ወተዝያነዉ ፡ ዳኅናሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ (ስንክ ፡ የካ፫ ። አፈ ፡ ድ፭ ። ዮሴፍ ። መገ ፡ ፲፰፭) ።


**አስተዝያነወ ፤ (ያስተዝያኑ) ፤** አዋራ ፡ አጨዋወተ ።

**ዜቄን ፤ (ዴቆን) ፤** ዘቄን ፡ ዲያቆን ፡ ኾነ ። በዜቄን ፡ ፈንታ ፡ ዝያቄን ፡ ይላል ፡ (ቀኖ ፡ ኒቅ፳፯) ።

**አዜቄነ ፤ (ያዜቀኑን ፡ ያዜቀኑን) ፤** አዘቄነ ፡ ዲቁና ፡ ሾመ ። (ተረት) ፡ ያዘቄነ ፡ ሳያቀስ ፡ አይለቅም ።

**ዝያቄን ፤ (ናት) ፤** ዘቋኝ ፡ ዲያቆን ። እስመ ፡ ዘዝያቄን ፡ ሥርዐተ ፡ ዐቀበ ፡ (ድጓ) ። ዲና ፡ ዘ ፡ በዐረብ ፡ (ዳል ፡ ዛል) ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ዝያቄን ፡ ይላል ። ዚቅ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ፍችው ፡ ተጨማሪ ፡ ተባባሪ ፡ መስል ፡ አገልጋይ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ደብተሮች ፡ በመልክ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ስሯጽ ፡ ጣልቃ ፡ እያገቡ ፡ የሚሉት ፡ ዜማ ፡ ነው ። በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ (ዚቅ ፤ ዚቃ) ፡ መብረቅ ፡ ነጸብራቅ ፤ ኸራታም ፡ ኮከብ ፡ ፍላጻ ፡ ይኾናል ።

**ዘይት ፤ (ታት ። ዕብ ፡ ዛይት ። ሱር ፡ ዛይታ ። ዐረ ፡ ዘይት) ፤** በቁሙ ፤ የተክል ፡ ስንጨት ፤ የወይራ ፡ ወገን ፤ ፍሬው ፡ መልካም ፡ ቅባት ፡ የሚሰጥ ፡ የሚበላና ፡ የሚበራ ። ተክለ ፡ ዘይት ፡ ሐዲስ ። ትተክሊ ፡ ዘይተ ። ዕፀወ ፡ ዘይት ። ሕንባባተ ፡ ዘይት ። አዕጹቀ ፡ ዘይት ። ይብረ ፡ ዘይት ፡ (መዝ ፡ ፻፳፯ ። ሚክ፮ ፡ ፲፭ ። ዕዘና ፡ ፳፯ ፡ ፳፱ ። ኢሳ፲፯ ፡ ፮ ። ዘዳ፳ ፡ ፲፩ ። ማቴ ፳፩ ፡ ፩) ።



ዘይት ፡

— ፤ ቅባቱም ፡ ለብቻው ፡ ዘይት ፡ ይባላል ። ዘይት ፡ ዘቀንዴል ። ዘይተ ፡ ማኅቶት ። ይውሕዝ ፡ እምኔሁ ፡ ቅብዐ ፡ ዘይት ፡ ወዕፍረት ። በከመ ፡ ይትርአይ ፡ ዘይት ፡ በውስተ ፡ ማየው ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፳ ። ሐም፴ ። ጥቅ ፳፱ ። ፳፯) ።

**ዘይቶን ፤ (ዐረ ፡ ዘይቱን) ፤** ዕፀ ፡ ዘይት ፤ የዘይት ፡ ዛፍ ፡ ተክል ፤ ሕንባብ ። ዘይቶን ፡ ወሆሳዕና ። ፍሬ ፡ ዘይቶን ፡ (ስንክ ፡ መስ፫) ።

**ዝኩ ፤ ዝኰ ፤ ዝክቱ ፤ ዝስኩ ፤ (ዝ ፡ ኩ) ፤** ዘከሣ ፡ የቅርብ ፡ ሩቅ ፡ ዐጸፋ ፡ እጅ ፡ የማይደርስበት ፡ ዐይን ፡ የሚያርፍበት ። ያ ፡ ያው ፡ ያኛው ፡ ርሱ ። የዝን ፡ አፈታት ፡ እይ ፡ ኩ ፡ ከሣ ፡ ከማለት ፡ መጥቷል ፤ ስለዚህ ፡ በዝ ፡ እንተ ፡ እለ ፡ እየገባ ፡ ለቅርብ ፡ ሩቆች ፡ ዐጸፋ ፡ ይኾናል ፤ በገቢርም ፡ ጊዜ ፡ ዝኰ ፡ እንትኰ ፡ እልኰ ፡ ይላል ። ነዋ ፡ ዝኩ ፡ ሐላሚ ። ዝኩ ፡ ቃለ ። እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ዝክቱ ፡ ወዝክቱ ፡ ዝንቱ ። ዳኅንኑ ፡ ዝስኩ ፡ አረጋዊ ፡ አቡክሙ ፡ (ዘፍ፴፯ ፡ ፲፱ ። ራእ፳ ፡ ፲፱ ። ቄር ፡ ጸላ ። ድጓ) ። እንትኩንና ፡ እልኩን ፡ እይ ።

**ዝኬ ፤ (ዝ ፡ ኬ) ፤** ይህ ፡ ነዋ ፤ ይህ ፡ ነው ፡ እነ ። ዝኬ ፡ ውእቱ ።

**ዘኪክ ፤ ኪት ፤ (ዘከ ፡ ይዘክክ ፡ ይዝክክ ። ዕብ ፡ ዛከኽ) ፤** መንጻት ፡ መጥራት ፡ ንጹሕ ፡ ጽሩይ ፡ ብሩህ ፡ መኾን ፡ በማብራ ፡ በነገር ። ዘካ ፡ ዘኬ ፡ ዘክዘክ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ይወጣል ። ዘካ ፡ ያረብ ፤ ፍችው ፡ ዓሥራት ፤ ዘካ ፡ ጸሐፊ ፡ እንዲሉ ። ዘኬ ፡ ያማርኛ ፡ ፍችው ፡

ኵቸሮ ፡ ተረፈ ፡ ማእድ ፡ ተማሮች ፡ ከተዝክር ፡ ዐው ድማ ፡ የሚያነሡት ፤ ዓሥራተ ፡ ኅብስት ። (ግጥም) ፤ ለመ ደችና ፡ ዘኬ ፡ ባልማ ፤ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ ኹለግዜ ፡ ሩማ ። ደብተራ ፤ የዘኬ ፡ ጕተራ ።

**ዝኩኪት ፡ (ዕብራ)** ፤ ቅዘዝ ፡ መስተዋት ፡ የሥዕል ፡ የመስኮት ፡ መዝጊያ ።

**ዘክሮ ፤ ሮት ፤ (ዘከረ ፡ ይዜክር ፡ ይዘ ክር ፤ አው ፡ ዘኪር ፤ ዘከረ ፡ ይዘክር ፡ ይገዝ ክር ። ዕብ ፡ ዛካር ። ሱር ፡ ዝካር ። ዐረ ፡ ዘከረ)** ፤ መዘክር ፤ ማሰብ ፡ መቍጠር ፤ በልብ ፡ ማኖር ፤ ባፍ ፡ ማ ውሣት ፡ መናገር ፤ ስም ፡ መጥራት ፡ እገሌ ፡ ማለት ፤ ሲ ጠብቅ ፡ የቀደሰ ፤ ሲላላ ፡ የቀተለ ፡ ቤት ፡ ነው ። ኢትዝ ክር ፡ ለነ ፡ አበሳነ ፡ ዘትካት ። ምንትኑ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ትዝክሮ ። ወኢይዜክር ፡ አስማቲሆሙ ፡ በአፉየ ። ኵሎ ፡ ዘዘክርነ ። ዘአቅደምነ ፡ ዘክሮታ ፡ በጥንተ ፡ ዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ (መዝ ፡ ፸፱ ። ፰ ። ፲፰ ። መጽ ፡ ምስ ። ፈ ፡ መ ፡ ፪ ፡ ፲፩) ። ብዙው ፡ መጣፍ ፡ በዘከረ ፡ ፈንታ ፡ ተዘከረ ፡ ይላል ፤ አድራጊውን ፡ በተደራጊ ፤ ባለቅኔዎችም ፡ እንዲሁ ፡ ብለው ፡ ይገሱታል ፤ ባለመጣፎችም ፡ ስሕተ ትነቱን ፡ አላወቁለትም ። እስ ፡ ይዜከሩ ፡ እኩየ ። ተዘ ክሮ ፡ እከይ ። ተዘከረነ ፡ እግዚኦ ። ተዘከረ ፡ በእንተ ፡ ብሩር ። ወኢተዘከረ ፡ ይግበር ። ተዘከሮ ፡ እግዚኦ ፡ ለዳዊት ፡ (ምሳ፲፪ ፡ ፳፫ ። ቅዳ ። ጦቢ፬ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፻፰ ። ፻፴፩) ።

**ዘካሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት)** ፤ በቁሙ ፤ የ ሚዘክር ፡ የሚዘክር ፡ ዐሳቢ ፤ ቁስ ።

**አዘከረ** ፤ አሳሰበ ፤ አስወሣ ፡ አስታወሰ ። በዘአ ዘከረ ፡ ሎቱ ፡ መሐላ ፡ አበው ። አዘክሪ ፡ ድንግል ፡ ል ደቶ ፡ እምኔኪ ። አዘከራ ፡ እሳተ ፡ ገሃነም ። ወነዋ ፡ አዘከረ ፡ ዮሴፍ ፡ ወልደ ፡ ኮርዮን ፡ ከመ ። አዘክሮ ፡ ሰፈርያን ፡ በእንቲአየ ፡ (ጥበ ፡ ፲፰ ፡ ፳፱ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ የካ፫ ። ዮሴፍ ። ዘፍ፵ ፡ ፲፬) ። ዳግመኛም ፡ በአዘከረ ፡ ፈንታ ፡ ዘከረ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አነ ፡ እዜ ከረከ ፡ ኵሎ ። ከመ ፡ አንቅህክሙ ፡ በዘክሮ ። ዘክ ሮሙ ፡ ከመ ፡ ይትአዘዙ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፪ ። ፪ጴጥ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ፫ ፡ ፩ ። ቲቶ፫ ፡ ፩ ። ፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፬) ።

**መዘክር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት)** ፤ የሚዘ ክር ፤ የሚያዘክር ፡ አዘካሪ ፤ ዐሳቢ ፡ አሳሳቢ ። ሹም ፤ ቈ ሳጪ ፤ ምስክር ። እ ፡ ድንግል ፡ አዘክሪ ፡ ኀበ ፡ መዘክር ፡ ዘኢይረስዕ ፡ ኵሎ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ። ጸሓፊ ፡ በማለት ፡ ፈ ንታ ፡ ጸሓፌ ፡ ታሪክ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ መዘክር ፡ ይላል ፤ ምንም ፡ ምስጢሩ ፡ ቢገጥም ፡ ንባቡ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ (፪ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፮ ። ፳ ፡ ፳፬ ። ፫ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ፡ ፴፯) ።

**መዝከር ፤ ምዝከር** ፤ ማሰቢያ ፤ ማሳሰቢያ ፤ ጊዜ ፡ ቦታ ፡ ምክንያት ። መስ(ዝ)ከረምን ፡ እይ ።

**ተዘክረ ፤ ተዘከረ** ፤ ታሰበ ፤ ትዝ ፡ አለ ፡ ተ ወሣ ፤ ተጠራ ፤ ተነገረ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዘከረ ፡ አድራጊነት ፡ ነው ። ወተዘከረ ፡ ማህሎ ። ተዘከረኒ ፡ በ መንግሥትከ ። ተዘከርኩ ፡ በሌሊት ፡ ስመከ ፡ እያሉ ፤ ገንዘቡን ፡ ተገብሮንትን ፡ ትቶ ፡ አስገንዝቦ ፡ ይነገራል ።

**ዝኩር ፤ (ራን ፡ ራት ፤ ክርት)** ፤ የታሰበ ፤ የተነገረ ፡ የተጠራ ፤ ዕውቅ ፡ ስመ ፡ ጥር ፤ እበ ፡ እገሌ ፡ የሚባል ። ቀኖና ፡ ዘዝክርት ። መምህር ፡ ዝኩር ፡ ዲበ ፡ መሥዋዕት ። አብ ፡ ዝኩር ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳፱ ። ፊልክ ፡ ፪፻፵፪) ። ዝኩር ፡ ባለው ፡ ስ ሙዕ ፡ ይላል ።

**ዝክረት ፤ (ታት)** ፤ ማሰብ ፤ መታሰብ ፤ አስ ተሳሰብ ፤ ዐሳቢነት ፡ ታሳቢነት ። ዕበባ ፡ ዐሳብ ፡ ምክር ። እምዝክረታተ ፡ ሰይጣናት ፡ እኩያት ፡ (ፊልክ ፡ ፪፴፯) ።

**ዝክር ፤ (ራት)** ፤ በቁሙ ፤ ዐሳብ ፡ ትዝታ ፤ ጥሪ ፡ አጠራር ፡ ዜና ። እግዚ ፡ ያስተስል ፡ ዝክረኪ ፡ እም ውስተ ፡ ልብየ ። ሙሴ ፡ ዘቡሩክ ፡ ዝክሩ ። ሰላም ፡ ለዝክረ ፡ ስምከ ፡ (ፊልክ ። ሚራ፵፮ ፡ ፩ ። ደራሲ) ።

—፤ መወሽ ፤ መታሰቢያ ፤ ስም ፡ የሚያስጠራ ፤ ነገር ፡ ምክ ንያት ፡ ሥራ ፤ የከፉ ፡ የበጎ ፡ (መክ፩ ፡ ፲፩ ። ፪ ፡ ፲፮ ። ፱ ፡ ፭) ። ርጉመ ፡ ይኩን ፡ ዝክሩ ። ወይጥፋእ ፡ እም ድር ፡ ዝክሩ ። ዝክረ ፡ ጻድቅ ፡ ለዓለም ፡ ይሄሉ ። ዝ ክረ ፡ ቅድሳቱ ፡ (ሚራ፳፫ ፡ ፳፯ ። መዝ ፡ ፻፰ ። ፻፲፩ ። ፳፱) ።

—፤ መቃብር ፤ የመቃብር ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ሐውልት ። ዝጎርን ፡ ተመልከት ።

—፤ የበዓል ፡ ድግስ ፤ ማኅበር ፡ ጨንቢ ፡ ባመትም ፡ በወ ርም ፡ የሚኾን ።

**ተዝክር** ፤ በቁሙ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ መታሰቢያ ፡ በዓል ፡ መሥዋዕት ፡ ጸሎት ፤ ንባብ ፡ ቃል ፡ ነገር ። ወከ መ ፡ ዝ ፡ ግበሩ ፡ ተዝካርየ ። ግበር ፡ ሎቱ ፡ ተዝካሮ ። ዘ ይሁብ ፡ ስጊነ ፡ ለተዝካርየ ። ተዝካረ ፡ ስእለት ፡ (ሉቃ ፳፪ ፡ ፲፱ ። ሚራ፴፰ ፡ ፳፫ ። ኢሳ፷፯ ፡ ፫ ። ጦቢ፲፪ ፡ ፲፪) ።

—፤ ወግ ፡ ታሪክ ፡ ዜና ። መጽሐፈ ፡ ተዝካር ። ተዝ ካረ ፡ ኖብያት ። ጸሓፌ ፡ ተዝካር ፡ (ሚልክ ፡ ፲፯ ። አስቴ ፡ ፩ ። ኢሳ፴፯ ፡ ፫) ። የገዝክርና ፤ የተገዝከር ፡ ዘይቤ ፡ በማና ቸውም ፡ ስልት ፡ ቢነገር ፡ ምስጢሩ ፡ ከመታሰቢያነት ፡ አይወጣም ።

**ተገዝኪር ፤ (ዐረብ)** ፤ ገዳም ፤ የመነኰሴ ፡ በታ ፡ ቤት ፡ በኣት ፡ (ስንክ ፡ የካ፱) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ በተገዝኪር ፡ ፈንታ ፡ ተክዚር ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ።

**ዝክቱ ፤ — ዝክ ፡ ቱ ፤ — ዝኩ ።**

**ዝልብ** ፤ ሳይቀረደድ ፡ የተቀቀለ ። ዘለበት ፤ የቀ በቶ ፡ ቈልፍ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዘሊግ ፤ ጎት ፤ (ዘለገ ፡ ይዘልግ ፡ ይገዝ ልግ ። ዕብ ፡ ዛላግ)** ፤ መገዘለግለግ ፡ መገዝረብረብ ፤ መውረድ ፡ መንጠብ ፡ መንጠባጠብ ፤ መንጠፍጠፍ ፤ ካይ ንና ፡ ከፍንጫ ፡ ከፍ ፡ ከመሊሊት ።

—፤ መዝለግ ፤ ዘለግ ፡ ማለት ፡ ዘለግተኛ ፡ መኾን ፤ መር ዘም ፡ ማደግ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዘልገሰ ፤ (ተቀ ፡ ግ)** ፤ ታመመ ፡ ተደወየ ፤ ቈሰለ ፡ ዐበጠ ፡ ተሳጠ ፤ የገላ ። ዘልገሰ ፡ ሥለንታሁ ፡ ወዐፀየ ፡ ልሳኑ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ዝልጉስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ግስት)** ፤ የታመመ ፡ የቈሰለ ፤ ድውይ ፡ ቊማጣ ። እመርዒት ፡ አባግዐ ፡ ቦ ፡ ዘይከውን ፡ ጥዑየ ፡ ወቦ ፡ ዝልጉስ ። ኖላዊ ፡ አባግዐ ፡ ሶበ ፡ ይሬኢ ፡ አሐቲ ፡ ዝልግስት ፡ አፉሃ ፡ ወሰእመ ፡ ኢክልአ ፡ ፍጡነ ፡ ይከውና ፡ ሥሎን ፡ ዝልጉሳተ ። ዝልጉሳን ፡ (ኢይባእ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ) ። በአርብዓሁ ፡ ለአውሳጋ ፡ ወበማልሱ ፡ ለዝልጉስ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፯ ። ቀሌ ። ቀሌ ። ፊልክ ፡ ፲፰) ። ገዳፍ ፤ ይልታረመ ፡ መጽሐፍ ፤ አላዋቂና ፡ ዘባሬቂ ፡ ሰካር ፡ የጣፈው ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዝልጋሴ** ፤ ቍስል ፡ ዕከክ ፤ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ ቍምጥና ፡ ኮብሽ ። ዝልጋሴ ፡ እኩይ ። ዝልጋሴ ፡ ወሲምጽ ። እምቍስለ ፡ ዝልጋሴ ፡ ኀጣውእ ፡ (ኢዮ፪ ፡ ፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፀ ። ፳፱ ። አርጋ ፡ ፮) ።

(ዋ) **ዘልሐ ፤ (ዕብ ፡ ዳላህ ፤ ዛሌሕ)** ፤ ቀዳ ፡ ጠለቀ ፡ ደነበቀ ፤ ጨለፈ ። ማይ ፡ ዕሙቅ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ብእሲ ፡ መምክር ፤ ወብእሲ ፡ ጠቢብ ፡ ይዜልሖ ፡ (ምሳሌ ፡ ፳) ። ዘለለ ፡ ጠመቀ ፡ በጠበጠ ፤ በተን ፡ ረጨ ፡ ፈነጠቀ ፤ ኹሉም ፡ የውሃ ፡ ነው ። ደለወን ፡ እይ ።

**ዘሊል ፤ ሎት ፤ (ዘለ ፡ ይዘልል ፡ ይዝልል ። ዕብ ፡ ዛላል ። ዐረ ፡ ዘልዘለ)** ፤ መንዘልዘል ፡ መንጠልጠል ፤ መነቃነቅ ፡ መወዘወዝ ፤ የዛፍ ፡ የፍሬ ። መዝለል ፡ ማለፍ ፤ መዘለል ፡ መታለፍ ፤ የተራ ። ዘለላ ፡ ዝልዝል ፡ ዝልል ፡ ዝላይ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**መዝለል ፤ ምዝላል** ፤ መሎጊያ ፡ ደጓሳ ፡ ሰንጨት ፡ የሳንሳ ፡ የሚይዙበት ። ድንባዝን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ባለብሎዮች ፡ ማን ፡ ቀፎ ፡ ባጥይ ፡ ይሉታል ። ወጸርዎ ፡ ክልኤቱ ፡ በምዝላል ፡ (ዘኍ፲፫ ፡ ፳፬) ።

**ዘሊፍ ፤ ፎት ፤ (ዘለፈ ፡ ይዘልፍ ፡ ይዝልፍ ። ዕብ ፡ ዛላፍ ፤ ረጨ)** ፤ መመንጨት ፤ ሳያቋርጡ ፡ መፍሰስ ፡ መውረድ ፤ መጕረፍ ፡ መኼድ ፤ የወንዝ ። ዘለፍ ፡ ማለት ፡ መዝለፍለፍ ። በቁሙ ፡ መዝለፍ ፤ መስደብ ፡ መንቀፍ ፤ መምከር ፡ መገሠጽ ፡ መመስከር ፡ መፍረድ ። ኢትዝልፎሙ ፡ ለእኩያን ፤ ዝልፎ ፡ ለጠቢብ ። ፈያታዊ ፡ ዘየማን ፡ ዘለፈ ፡ ርእሶ ፡ በጊዜ ፡ ሞቱ ። ይዘልፈከ ፡ ቃለ ፡ አፉከ ። ምግባራቲከ ፡ ይዘልፋከ ። ይዝልፉ ፡ ማእከሌነ ፡ (ምሳ፱ ፡ ፰ ። ፊልክ ፡ ፶፱ ። ኢዮ፲፭ ፡ ፮ ። ተረ ፡ ቄር ። ዘፍ፴፩ ፡ ፴፯) ። መዘለፍ ፤ መቍረጥ ፤ መቈጥቈጥ ፡ (ዐማርኛ) ። የመጥረቢያ ፡ ልጅ ፡ መዘለፊያ ፡ እንዲሉ ።

**ዘላፊ** ፤ በቁሙ ፤ የሚነቅፍ ፡ የሚዘልፍ ፡ የሚያጸይፍ ። ኤልያስ ፡ ዘላፊ ፡ ሐጋ ፡ ለቤተ ፡ አክአብ ። ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘላፊ ፡ ረሲዓን ፡ (ስንክ ፡ የካ፳፰ ። ደራሲ) ።

**አዝለፈ** ፤ አዘወተረ ፤ አራደፈ ፡ አከታተለ ፤ አበዛ ፤ መሳለስ ። ወተረን ፡ እይ ። ዘአዝለፈ ፡ ትዕግሥቶ ። ሶበ ፡ አዝለፈ ፡ ጸሎተ ። ከመ ፡ ያዝልፍ ፡ ገቢረ ፡ ትሩፋት ፡ (ማቴ፲ ፡ ፳፱ ። ፊልክ ፡ ፶፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፪ ፡ ፱) ። አ(ስ)ዘለፈ ፡ አሰደበ ፡ አስነቀፈ ።

**አዝላፊ** ፤ የሚያዘወትር ፡ አዘውታሪ ። ለእመ ፡ ኮነ ፡ አዝላፊ ፡ ለገቢር ። ይኩኑ ፡ አዝላፍያነ ፡ ጾም ፡ ወጸሎት ፡ (ፊልክ ፡ ፪፻፷፮ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲ ፡ ፵) ። አሰዳቢ ፤ አስነቃፊ ።

**መዝለፊ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ አዘውታሪ ። መዝለፊ ፡ ስካር ፡ ወእከይ ። መዝለፊተ ፡ ተፀምዶ ። ኩኑ ፡ ለጸሎት ፡ መዝለፍያነ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳ ። ፲ ፡ ፰ ። ፲፬) ። የሚዘልፍ ፡ የሚነቅፍ ፤ ዘላፊ ፤ አዘላፊ ። ኮነነ ፡ መዝለፊ ፡ ኀሊናነ ፡ (ጥበ፪ ፡ ፲፬) ።

**ተዘልፈ** ፤ ተዘወተረ ፡ ተለመደ ። በቁሙ ፤ ተዘለፈ ፡ ተሰደበ ፡ በገዛ ፡ አፉ ፤ ተጸጸተ ፡ ተወቀሠ ፡ በኅሊናው ። እመ ፡ ተዘከርኩ ፡ ተዘለፍኩ ። ወባሕቱ ፡ በዘተዘለፍኩ ፡ ተመሰውኩ ። ቦ ፡ እለ ፡ ይዘለፉ ፡ ወይትመውኡ ፡ (ኢዮ፳፩ ፡ ፮ ። ዓ፪ ፡ ፮ ። ቄር) ።

**ዝሉፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ልፍት)** ፤ የተዘወተረ ፤ ዝውትር ። ዘልፈ ፡ ለዝላፉ ፡ ለዓለም ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዝሉፈ ፡ ለዝሉፉ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ይትቀነይ ፡ ሎቱ ፡ ዝሉፈ ። ኢትግድፈነ ፡ ለዝሉፉ ። እስከ ፡ ለዝሉፉ ፡ (ዘፀ፳፩ ፡ ፮ ። መዝ ፡ ዓ፫ ። ኢዮ፳፫ ፡ ፫) ። ዳግመኛም ፡ መረግድ ፤ አፈው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዝሉፍ ፡ ይላል ፤ ይህ ፡ ደግሞ ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ። ዝሉፍ ፡ ወእንቡዝ ፡ ኢይዜከርዎ ። ወያመጽኡ ፡ ለኪ ፡ ዝሉፈ ፡ (ኢዮ፳፰ ፡ ፲፰ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፲፮) ።

—፤ በቁሙ ፤ የተዘለፈ ፡ የተነቀፈ ፤ አውታታ ፡ ደፋር ፤ ይሉኝ ፡ አይል ። ኢትኩን ፡ ዝሉፈ ፡ በልሳንከ ። ዝሉፍ ፡ ለይትገሠጽ ። ዝሉፋን ፡ እለ ፡ ኢይትኤዘዙ ። ነፍስ ፡ ዝልፍት ፡ ኢትዜወር ፡ (ሢራ፭ ፡ ፲፬ ። ኪዳ ። ቲቶ፩ ፡ ፲ ። ሢራ፲፱ ፡ ፫) ። ጕጕኣን ፡ ዘላፍያን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዝሉፋን ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፬ ። ሮሜ፩ ፡ ፴) ።

**ዝልፈት** ፤ ማዘውተር ፤ መዘውተር ፤ ዝውተራ ፡ አለማቋረጥ ። በዝልፈቱ ፡ ወዕጽበቱ ፡ (ፊልክ) ። መዝለፍ ፡ መዘለፍ ፤ አዘላለፍ ፡ ዘለፋ ፤ ተግሣጽ ፡ ትምርት ። በእንተ ፡ ዝልፈተ ፡ ትዝኅርትሙ ። ለዝልፈተ ፡ አበሳሆሙ ። እለ ፡ ይጸልኡ ፡ ዝልፈተ ፡ (ፊልክ ፡ ፳፲፱ ። ጥበ፩ ፡ ፱ ። ምሳ፲፭ ፡ ፲) ።

**ዚልፋ ፤ ዜልፋ ፡ (ዕብራ)** ፤ የሴት ፡ ስም ፤ አመት ፡ ልያ ፡ ብእሲተ ፡ ያዕቆብ ፡ (ዘፍ፳፱ ፡ ፳፬) ። ግእዝ ፡ ግን ፡ ዘለፋ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**ዘለፋ** ፤ በቁሙ ፤ ስድብ ፡ ነቀፋ ፡ ምክር ፡ ተግሣጽ ። ዘለፋ ፡ ክሡት ። ዘለፋ ፡ ካህናት ። ንጽሕፍ ፡ እንከ ፡ ዘለፋሁ ፡ ለንስጥሮስ ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ዓ፱ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ዘልፍ ፤ ዘልፈ** ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኹልጊዜ ፤ ወትሮ ፡ ዘወትር ፤ በየቀኑ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፤ ጧት ፡ ማታ ፤

ሥርከ ፡ ዘላለም ፡ ዘሬም ፡ ነገም ። በእንተ ፡ ደዌከ ፡ ዘ
ዘልፍ ። ወከመ ፡ ዝ ፡ ይከውን ፡ ለዘልፍ ። መሥዋ
ዕተ ፡ ዘልፍ ፡ (፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፳፫ ። ዘኊ ፲፱ ፡ ፲፯ ። ዕንባ ፡ ፳) ። ዘልፈ ፡ ለለ ፡ ዕለቱ ። እዜከረከሙ ፡ ዘልፈ ። ይእ
ዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ። ዘልፈ ፡ እሬእዮ ፡ ለእግዚ ። ወዘ
ልፈ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ውስተ ፡ አፉየ ፡ (ዘዐ፲፯ ፡ ፭ ። ሮ
ሜ፩ ፡ ፱ ። ቅዳ ። መዝ ፡ ፲፭ ። ፴፫) ።

**ዘልፋዊ ፤ ዘዘልፍ ፤** የዘወትር ፡ የዘላለም ፡
የማይቀር ፡ የማይታጐል ።

**ዝላፍ ፤** ወትሮ ፡ ዘላለም ። ዝላፍና ፡ ዘልፍ ፡
፩ ፡ ናቸው ። እስመ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ለዝላፉ ፡ ሀሎ ።
እምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ወለዝላፉ ። ወከነ ፡ ለዝላፉ ፡ ቀ
ትል ፡ (ኪዳ ። ዳንኤ ፡ ፰፱ ። ፀንገ ፡ ፫ ፡ ፩) ።

**ተዛለፈ ፤** ተዘዋተረ ፡ ተዘወታተረ ። በቁሙ ፤
ተሳደበ ፡ ተሰዳደበ ፤ ተሟገተ ፡ ተከራከረ ። መደቡ ፡ መደ
ፈረግ ፡ ሲኾን ፡ ማድረግም ፡ አለበት ። ሊትዛለፍ ፡ በ
ማእከለ ፡ ሊቃውንት ። ለማርያም ፡ እኅተ ፡ ሙሴ ፡
ሶበ ፡ ተዛለፈት ፡ አውፅእዋ ፡ እምትዕይንት ። እምድ
ኅረ ፡ ተዛለፉ ፡ በስምዕ ፡ ከመ ፡ ቀታሌ ፡ ነፍስ ፡ ው
እቱ ። ይዛለፎሙ ፡ ለብዙኃን ፡ አሕዛብ ፡ (ሚራ፯ ፡
፲፱ ። ዲድ ፡ ፴፩ ። ቀሌ ። ኢሳ፪ ፡ ፬) ።

**ትዝልፍት ፤** ዝውትራ ፡ አዘውታሪነት ፤ ተሳ
ዳቢነት ። ክርክር ፡ ስድብ ፡ ንዝንዝ ፡ ውዝግብ ፡ ኹከት ።
በእንተ ፡ ትዝልፍቱ ። አኮ ፡ በሀከክ ፡ ወበትዝልፍት ።
ትዝልፍተ ፡ ኅሊና ፡ ስሑን ፡ (ቀኖና ። ግብ፲፱ ፡ ፴፯ ።
ቄር ፡ ጸላ) ።

**ዘሊቅ ፤ (ዘለቀ ፡ ይዘልቅ ፡ ይዝልቅ) ፤**
በቁሙ ፤ መዝለቅ ፤ መዘልቀቅ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዘሊስ ፤ (ዘለሰ ፡ ይዘልስ ፡ ይዝልስ) ፤**
በቁሙ ፤ መዘለስ ፡ ዘለሳ ፡ መጣል ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዘም ፤ ዘም ፤ (ጽር ፡ ዘሞስ) ፤** ደም ፡ አ
ዝኅ ፡ መረቅ ፡ አሙክ ፡ (ሕዝ፳፬ ፡ ፲ ። መሳ፮ ፡ ፲፱ ፡ ፳) ።

**ዜመ ፤—አዜመ ፤—ዘዩም ፡ ዜመ ።**

**ዘሚድ ፤ ዶት ፤ (ዘመደ ፡ ይዘምድ ፡ ይ
ዝምድ ። ዐመደ) ፤** ማዛመድ ፡ ማዋደድ ፡ ማስማ
ማት ፤ ማጣመር ፡ ማራከብ ፡ ማገናዘብ ፤ መጥመድ ፡ ማ
ዛወግ ፡ ኹለቱን ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ማድረግ ። ዐመድን ፡
እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**አዝመደ ፤** አዘመደ ፤ አስጠመደ ።

**ተዘምደ ፤** ተዘመደ ፤ ዘመድ ፡ ኾነ ፡ ተስማማ ።
እሉ ፡ እለ ፡ ይዘመዱ ፡ ወይሰናሰሉ ፤ እስመ ፡ ተወ
ልዱ ፡ እምአበው ፡ ወእምሔዋን ። ለእመ ፡ ዘመወ ፡
ምስለ ፡ ካልእት ፡ ዘትዘመድ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፳፱ ፡ ፱ ። ፈ
መ ፡ ፭ ፡ ፫) ።

**ተዛመደ ፤** በቁሙ ፤ ተዘማመደ ፤ ተስማማ ።
መዛመድ ፡ በ፱ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ በሥጋ ፡ በነፍስ ፡ ለኹለ
ቱም ፡ ብዙ ፡ ስልት ፡ አለው ።

**ዝሙድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ምድ) ፤** የተዘ
መደ ፡ የተዛመደ ፤ የተዘማመደ ፤ ዝምድ ።

**ዝምደት ፤** መዘመድ ፡ መዘማመድ ፤ አዘማ
መድ ፡ ዘመድነት ፡ ዝምድና ። ዝምደት ፡ ዘኢትትፌ
ጸም ። ዝምደተ ፡ እምሔዋን ። ዝምደተ ፡ ሕብና ፡
(ፍ ፡ ን ፡ ፵፱ ፡ ፮) ።

**ትዝምድ ፤ (ዳት) ፤** መዘመድ ፤ ዝምድና ።
ዘመድ ፤ ወገን ፡ ነገድ ፤ ልጅ ፡ ቤት ፡ ሰብ ፤ ትውልድ ።
እምድርከ ፡ ወእምትዝምድከ ፤ ወገን ። እሉ ፡ ትዝ
ምደ ፡ ያዕቆብ ። ኢሩት ፡ ትዝምድ ። ኵሉ ፡ በበ ፡
ትዝምዱ ፡ ኵሎ ፡ መዋዕለ ። በኵሉ ፡ ትዝምዶሙ ፡
(ኩፋ ፡ ፲፱ ። ፴፱ ። ጥበ፳ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፳ ። ፮) ።

**ትዝምድና ፤** ዝምድና ፡ ዘመድነት ፡ ተወላጅ
ነት ። ትዝምድና ፡ ዘውሉድ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፵፱ ፡ ፮) ።

**አስተዛመደ ፤ (ዘመደ) ፤** አዛመደ ፡ አዘማ
መደ ፤ አስማማ ። አድራጊና ፡ አደራራጊ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡
በፍች ፡ ይተባበራል ። ተሰምዮት ፡ በመንፈስ ፡ ዘያስተ
ዛምድ ፡ ምስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ተዘም
ዶት ፡ ሥጋዊ ፡ ያስተሳትፍ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፵፩) ።

**ዘመድ ፤ (-ብ ፡ አዝማድ) ፤** በቁሙ ፤ ወ
ላጅ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ተወላጅ ፡ ወንድም ፡ እኅት ፤ አጎት ፡
አክስት ፤ ወገን ፡ ነገድ ፤ ሥነ ፡ ፍጥረት ፤ ዐይነቱና ፡ ስሙ ፡
ትውልዱና ፡ ዘሩ ፡ አንድ ፡ የኾነ ። ወገን ፡ ነገድ ፡ የሩቅ ፤
ዘመድ ፡ አዝማድ ፡ የቅርብ ። ወልድ ፡ ዘይስሕት ፡ ያ
ስተኃፍር ፡ ዘመዶ ። አክብሪ ፡ ታሕማኪ ፡ እስመ ፡
እምይእዜ ፡ ዘመድኪ ። ወአዝማዲሃኒ ፡ ጻድቃን ፡
እሙንቱ ፤ አባት ፡ እናት ፡ (ምሳ፳፱ ፡ ፲፭ ። መቃ፳ ፡
፲፱ ። ዳንኤ ፡ ፫) ። አነ ፡ ዐዘርያ ፡ ዘመደ ፡ አናንያ ።
እስመ ፡ ዘመድከ ፡ ይእቲ ፤ ወንድም ፡ እኅት ፡ (ጦ
ቢ፭ ፡ ፲፪ ። ዘሌ፲፰ ፡ ፲፬) ። ኵሉ ፡ እንስሳ ፡ ያፈቅር ፡
ዘመዶ ። እምኵሉ ፡ ዘመደ ፡ ዓሣ ። ኵሉ ፡ ዘመደ ፡
መብልዕ ፤ ወገን ፡ ነገድ ፡ ዐይነት ፡ (ሢራ፲፫ ፡ ፲፭ ።
ማቴ፲፫ ፡ ፵፯ ። ዘፍ፵ ፡ ፲፯) ። ወገብረ ፡ ዘንተ ፡ አርባ
ዕተ ፡ ዘመደ ፡ በዕለት ፡ ሳድስት ፡ ወኮነ ፡ ኵሉ ፡ ዐሠሩ ፡
ወክልኤተ ፡ ዘመደ ፤ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ (ኩፋ ፡ ፪) ።

—፤ ጥሬ ፡ ዘር ፡ ሌላ ፡ ፊደል ፡ ባዕድና ፡ ምእላድ ፡ ሳይ
ጨምር ፡ እንቀጹን ፡ መስሎ ፡ የሚገኝ ፡ ቃል ። ቀተለ ፡
ቀትል ፤ ገብረ ፡ ግብር ፤ ቀደሰ ፡ ቅዳሴ ፤ ነደ ፡ ነድ ፤
ቈረ ፡ ቍር ፤ ጾመ ፡ ጾም ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ይህን ፡ የመ
ሰለ ፡ ኹሉ ፡ ዘመድ ፡ ዘር ፡ ይባላል ፤ መሰል ፡ ማለት ፡ ነው ።

**አዝማድ ፤ (ዳት) ፤** የቅመም ፡ ስም ፡ አብ
ሱዳ ፡ አቡሱዳን ፡ ነጭና ፡ ጥቍር ፡ ዐይነት ፡ (ዐማርኛ) ።

(ጥ) **ዘምዎ ፤ ዎት ፤ (ዘመወ ፡ ይዜሙ ፡ ይ
ዘሙ ። ዘነየ) ፤** መዝመት ፡ ሰውን ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡
ሴትን ፡ መማረክ ፡ መዝረፍ ፤ መስረቅ ፡ መቀማት ። መዘ
ሞት ፡ መሰሰን ፡ ጣዖት ፡ ማምለክ ፤ ከሕግ ፡ መውጣት ፡
ማለፍ ፡ መትረፍ ። ዘምዎተ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ።
ዘዘመወ ፡ በእንስሳ ። እለ ፡ ይዜምዉ ፡ ተባዕት ፡ ምም

ስለ ፡ ተባዕት ፡ ወአንስት ፡ ምስለ ፡ አንስት ። ብእሲ ፡ ዘይዜሙ ፡ በነፍስተ ፡ ሥጋሁ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፺ ፡ ፰ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ሚ ፡ ራ ፡ ፳፫ ፡ ፲፯) ። እስመ ፡ ዘምዎ ፡ ትዜሙ ፡ ምድር ። ዘመወት ፡ በዕፀ ፡ ወበእብን ። ከመ ፡ ይብልዑ ፡ ዝቡሐ ፡ ለአማልክት ፡ ወይዘምዉ ፡ (ኢ ፡ ር ፡ ፲ ፡ ፱ ። ሆሴ ፡ ፬ ፡ ፲ ። ራእ ፡ ፲፬) ።

**ዘማዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ በቁሙ ፡ የሚሴስን ፡ ሴሰኛ ፤ አመንዝራ ። ብእሲ ፡ ዘማዊ ። አረጋዊ ፡ ዘማዊ ። ኢትደመሩ ፡ ምስለ ፡ ዘማውያን ። ትውልድ ፡ ዐማፂት ፡ ወዘማዊት ፡ (ሚ ፡ ራ ፡ ፳፫ ፡ ፲፯ ። ፳፭ ፡ ፲ ። ፩ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፱ ። ማቴ ፡ ፲፪ ። ፴፱) ።

**ዝማዌ** ፤ መሴሰን ፡ መገልሞት ፤ ግልሙትና ፡ ዘማዊነት ።

**ዝሙት** ፤ በቁሙ ፡ ሴሰኝ ፡ ቅንዝር ፡ ምንዝር ፡ ሀልኮ ፡ ያሰፈ ፡ የተረፈ ። ዝሙተ ፡ ብእሲት ፡ ምስለ ፡ ብእሲት ፤ ዝሙተ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡ ወበእንስሳ ። ቤተ ፡ ዝሙት ። ትርሲተ ፡ ዝሙት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፺ ፡ ፮ ። ሕዝ ፡ ፲፮ ፡ ፴፱ ። ምሳ ፡ ፯) ።

**ዘማ ፤ (ብ ፡ ዘማት)** ፤ በቁሙ ፤ ጋለሞታ ፡ አመንዝራ ፡ ሴት ፤ ኹሉን ፡ የምትቀበል ፡ የማትስለች ፡ ባንድ ፡ ወንድ ፡ ያልቆመች ። ብእሲት ፡ ዘማ ። ዘቲ ፡ ትውልድ ፡ ዘማ ፡ ወኃጥእት ። ዘርዐ ፡ ዘማውያን ፡ ወዘማት ። ሑር ፡ አውስብ ፡ ብእሲተ ፡ ዘማ ፡ ወአዋልደ ፡ ዘማ ። በከመ ፡ ይገብራ ፡ አንስት ፡ ዘማት ፡ (ምሳ ፡ ፫ ። ማር ፡ ፰ ፡ ፴፰ ። ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፫ ። ሆሴ ፡ ፩ ። ዲድ ፡ ፫) ።

**አዘመወ** ፤ አሴሰነ ፤ ዘማዊ ፡ አደረገ ፤ አገለሞተ ፡ አስገለሞተ ። አዘመውካ ፡ ለብእሲተ ፡ካልእከ ። ወይዜምወኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃድየ ፡ (ዲድ ፡ ፰ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**መዘምው** ፤ የሚያሴስን ፤ ዝሙት ፡ የሚያስተምር ፡ የሚያገብር ።

**ዘሚም ፤ ሞት ፤ (ዘመ ፤ ዘመመ ፡ ይዘምም ፡ ይዝምም ። ዐረ ፡ ዘመ ። ሱር ፡ ዛም)** ፤ መሸበብ ፡ መለበብ ፤ መለጐም ፡ መመንገግ ፤ እንዳይበላና ፡ እንዳይጠባ ፡ ማድረግ ። ዝም ፡ ማለት ፤ ዝም ፡ ማሰኘት ፡ አፍን ፡ መዝጋት ፡ መያዝ ፡ ማሲያዝ ። ረመመን ፡ እይ ። መዝመም ፡ ማጋደል ፡ መወዘወዝ ፡ መነዋወጥ ፤ ዜማን ፡ በቃል ፡ በበትር ፡ ማቅለጥ ።

**ዝማሜ ፤ (ምያት)** ፤ በቁሙ ፡ የዜማ ፡ ሕግ ፡ አዘማመም ፡ ከዜማው ፡ ጋራ ፡ የዘነገ ፡ የመቋሚያ ፡ እንግሮ ፡ አጣጣል ። ዝማሜ ፡ አምሳለ ፡ ኪዳን ፡ አንበሳ ፡ ውእቱ ፡ (ገድ ፡ አብርሀ) ።

**ዝማም ፤ (ማት)** ፤ ዝምታ ፡ አርምሞ ። ቃናሽ ፡ ቅርማት ፡ እንደ ፡ ከረጢት ፡ ኹና ፡ የእንስሳን ፡ አፍ ፡ የሚከት ፤ መንግን ፡ በመያዝና ፡ በማሰር ፡ ፈንታ ፡ የሚደረግ ። ተግሣጽ ፡ ወትምህርት ፡ ልጓም ፡ ወዝማም ፡ (ፈላስ) ።

—፤ ጉሮ ፡ መንደልት ፡ ያፍንጫ ፡ ቀለበት ፡ የአራዊትና ፡ የእንስሳት ፡ ስናግ ፡ ገመድ ፡ እያበቱ ፡ የሚስቡበት ። ትወዲ ፡ ሎቱ ፡ ዝማማተ ፡ ውስተ ፡ አንፉ ። እወዲ ፡ ለከ ፡ ዝማማተ ፡ ውስተ ፡ አንፍከ ፡ (ኢዮ ፡ ፵ ። ኢሳ ፡ ፴፯ ፡ ፳፱) ። ወጸበን ፡ እይ ።



ዝማም ፤

**ዘመመን ፤ ዘመሚት ፤ (ዐማርኛ)** ፤ ዘመመን ፡ የንድ ፡ ድርድር ፤ ዘመሚት ፡ ቀይ ፡ ጕንዳን ።

**ዝማሞ** ፤ ስም ፡ ዐገር ፤ የመንዝ ፡ ክፍል ፡ በሞፈር ፡ ውሃ ፡ ዳር ፡ ያለ ።

**ዘመን ፤ (ናት ፤ አዝማን ፡ ናት ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ዝማን ። ዐረ ፡ ዘመን ፤ ዝማን)** ፤ በቁሙ ፤ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ወራት ፡ በየስሙና ፡ በየክፍሉ ። ዘመን ፡ ወአዝማን ፡ ወመንፈቀ ፡ ዘመን ። ኵሉ ፡ በበ ፡ ዘመኑ ። ዘመናት ። እምቅድመ ፡ መዋዕል ፡ ወአዝማናት ፡ (ራእ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ ። ሔኖ ፡ ፪ ። ኢዮብ ፡ ፱ ። ቅዳ ፡ አፈ) ። ዘመኑ ፡ መፀው ፡ ወሐጋይ ፤ ወራት ። ዓምንና ፡ ጊዜን ፡ ተመልከት ።

**ዘመነ ፤ (ይዜምን ፡ ይዘምን)** ፤ ዘመናይ ፡ ኾነ ፤ ዘመን ፡ ወሰነ ፡ ቀጠረ ። ዐደመን ፡ እይ ።

**ዘመናዊ** ፤ ዘመናይ ፤ ባለጊዜ ፡ ባለወራት ፤ ሹም ፡ ባለጠጋ ፤ ኀላፊ ፡ ነገር ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ የሚፈለግ ። መብልዕ ፡ ማሳኒ ፡ ወዘመናዊ ። ትፍግዕት ፡ ዘመናዊት ፡ ወኀላፊት ። ሕይወት ፡ ዘመናዊት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ። አፈ ፡ ድጓ ። አቡሻ ፡ ፴፭) ።

**ዘምሮ ፤ ሮት ፤ (ዘመረ ፡ ይዜምር ፡ ይዘምር ። ዕብ ፡ ዛማር ፤ ዘሚር)** ፤ ማዝመር ፤ አዝመራን ፡ ማጨድ ፡ መቍረጥ ፤ መሰብሰብ ፡ መክተት ፤ መዝራትም ፡ ይኾናል ። አዝማሬ ፡ መኾን ፡ ሴሴ ፡ ማለት ፡ መዝፈን ። ሐሊዮሁ ፡ ወዘመራሁ ፡ በበረከተ ፡ እግዚ ፡ (ሚ ፡ ራ ፡ ፲፯ ፡ ፮) ።

—፤ መዘመር ፡ መወበን ፤ የሥራ ። መምራት ፡ መቀንቀን ፡ መዘመር ፡ ማመስገን ፡ በልዑል ፡ ዜማ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡ በክብሮና ፡ በጸናጽል ፡ በሌላውም ፡ ኹሉ ። ይዘምሩ ፡ በጊዜ ፡ ተመጥዎ ፡ ቍርባን ፡ ኵሎሙ ፡ ምእመናን ። ሶ ፡ እመላእክት ፡ ዘይዜምር ፡ ወቦ ፡ ዘይቄድስ ። ውእቱ ፡ ዝማሬ ፡ ዘኮኑ ፡ ይዜምሩ ፡ ቦቱ ። ይዜምሩ ፡ በአቅርንት ። ይዜምሩ ፡ በመሰንቆ ። ወበመዝሙር ፡ ዘዐሠርቱ ፡ አውታሪሁ ፡ ዘምሩ ፡ ሎቱ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፫ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ኅዳ ፲ ። ፩ዜና ፡ ፲፭ ፡ ፳፱ ። ፪ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፴፪) ።

—፤ ማማጠን ፡ ይገባኛ ፡ ማለት ። መጥቀስ ፤ ምስክር ፡ መጥራት ፤ ኹሉም ፡ የሙግት ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዘመረ ፡ ፈንታ ፡ ተዘመረ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ተዘ

መረ ፡ በቍሳር ፤ ወኀበ ፡ ቍሳር ፡ የሐውር ። ተዘመር ፡ በስመ ፡ ዚኣሁ ፤ እግጠን ፡ (ኀብኚ፰ ፡ ፳፰ ። ሲኖዶ) ። ያቀውሙ ፡ ቃላቲሆሙ ፡ ተዘሚሮሙ ፡ እምቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ። እላ ፡ ክልኤ ፡ ቃላተ ፡ ተዘመርኑ ፡ እንዘ ፡ ትእልፌት ፡ ዘክመ ፡ ዝ ፤ ጠቀስ ፡ (ቄር ፡ ጸላ ። ተረ ፡ ኢጲ) ። መመስከር ፡ ማወጅ ፡ መናገር ፤ መስበክ ፡ ማስተማር ። በእርእዮ ፡ መኑ ፡ ዘይዜምር ፤ ከመ ፡ ያስተርኢ ፡ እንዘ ፡ ይዜምር ፡ እምአብ ፤ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይዜምር ፡ ከመ ፡ ይሠምር ፡ አብ ፡ (ቄር ፡ ተረ ፡ ኢጲ) ። ዳግመኛም ፡ በዘመረ ፡ ፈንታ ፡ አዝመረ ፡ ይላል ፤ እያስኘም ። ሃይማኖተ ፡ መስቀል ፡ በዐውድ ፡ አዝመረ ። እንዘ ፡ ታዘምር ፡ ሃይማኖተከ ፡ በዐውድ ። አዝመረ ፡ ወልደ ፡ እግዚ ፡ በአቡሁ ፡ ሰማያዊ ፡ ወይቤ ፤ ኢያእመርክሙኑ ፡ ከመ ፡ ዘውስተ ፡ ቤተ ፡ አቡየ ፡ ሀሎኩ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ጥር፲፰ ። መጽ ፡ ምስ) ።


**ዘማሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ የሚዘምር ፡ ዜመኛ ፡ አመስጋኝ ፡ መሪ ፡ ዝማሬ ፡ ቀንቃኝ ። በአፈ ፡ ዘማሪ ፡ ዳዊት ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**መዘምር** ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ዘማሪ ፡ አዝማሪ ፤ ባለበገና ። በከመ ፡ ይቤ ፡ መዘምር ። መዘምራን ፡ ወመዘምራት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ዕዝ፱ ፡ ፷፭) ።



መዘምር ፡

**መዝሙር** ፤ (ራት ፤ መዛሙርት ። ዕብ ፡ ሚዝሞር ። ሱር ፡ ማዝሙራ ። ዐረ ፡ መዝሙር) ፤ በቁሙ ፤ ምስጋና ፡ ውዳሴ ፡ ጸሎት ፤ መጽሐፈ ፡ ዳዊት ፤ ከ፻፶ው ፡ ክፍላት ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ክፍል ። መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ትመስል ፡ ገነተ ፤ መዝሙረ ፡ ድንግል ፤ መዝሙረ ፡ ክርስቶስ ። በከመ ፡ ይቤ ፡ በውስተ ፡ መዝሙር ፡ ዘክልኤቱ ፡ (ደራሲ ። ግብ፲፫ ፡ ፴፫) ። ማመስገኛ ፡ ንዋየ ፡ ማሕሌት ፡ በገና ፡ ክራር ፡ ክበሮ ፡ ጸናጽል ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ንሥኡ ፡ መዝሙረ ፡ ወሀቡ ፡ ክበሮ ፡ መዝሙር ፡ ሐዋዝ ፡ ዘምስለ ፡ መሰንቆ ። በክበሮ ፡ ወበመዝሙር ፡ ይዜምሩ ፡ ሎቱ ፡ (መዝ ፡ ፹ ። ፻፵፱) ። ዜማ ፡ ድምፅ ፡ ከሰው ፡ ከበገና ፡ የሚወጣ ። ደረሰ ፡ ያሬድ ፡ መጽሐፈ ፡ መዝሙር ። ትረክብ ፡ መዝሙረ ፡ ነቢያት ። ወኢያጸምዕ ፡ መዝሙረ ፡ መሰንቆክሙ ፡ (ታሪ ፡ ነገ ። ፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፳ ፡ ፲ ። ዓሞ፭ ፡ ፳፫) ።



መዝሙር ፡

**አዝመረ** ፤ **አዘመረ** ፤ አስቈረጠ ፤ አሳጨደ ። አ(ስ)ዘመረ ፤ አስመሰገነ ።

**አዝመራ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፤ ዐጨዳ ፡ ስብሰባ ፤ ወይም ፡ ዝሪት ።

**አዝመር** ፤ (ዐረ ፡ አስመር) ፤ ያይነት ፡ ስም ፤ ደባባ ፡ ደባላ ፤ የበሰለ ፡ የጎተከከ ፡ ፍሬ ፡ የሚመስል ፤ ፍጹም ፡ ቀይ ፡ ወይም ፡ ፍጹም ፡ ጥቍር ፡ ያይደለ ፡ ማእከላዊ ፡ ሕብር ፡ (ራእ፲፰ ፡ ፲፪ ፡ ፲፮) ።

**እዛምር** ፤ የዳበ ፡ ቅጠል ፤ ዐይነቱ ፡ አረንጓዴ ፡ ብጫቱ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ተዘመረ** ፤ በቁሙ ፤ ተዘራ ፡ ታጨደ ። ምስክር ፡ ተጠራ ፤ ተጠቀሰ ። ተመሰገነ ፡ ተወደሰ ። ተዜመ ፡ ተቃኘ ፡ ተደረደረ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ አይራጊ ፡ ነው ።


**ዝሙር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ምርት) ፤ የታመነ ፡ የተመሰገነ ፤ እሙን ፡ ምስጉን ፤ የማይጠረጠር ፡ ምስክር ። ዝሙረ ፡ ቃላትየ ፡ ነቢይ ፡ ኤርምያስ ። ለዝንቱ ፡ ዝሙር ፡ ጳውሎስ ። ወዝሙር ፡ ጳውሎስ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ (ቄር ፡ እስት ። ጸላ) ።

**ዝማሬ** ፤ (ርያት) ፤ መዘመር ፡ አዘማመር ፡ ዝመራ ፤ ኹመራ ፡ ቅንቀና ፤ ዜማ ፡ የዜማ ፡ ምስጋና ። ዝማሬ ፡ መላእክት ፡ ቅዱሳን ። ዘምሩ ፡ በአልባቢክሙ ፡ ዝማሬያተ ፡ ወስባሔያተ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፲፭ ። ፊመ ፡ ፴፱ ፡ ፳) ። በቁሙ ፤ የዜማ ፡ መጽሐፍ ፡ ስም ፡ ከ፭ቱ ፡ ጸዋትወ ፡ ዜማ ፡ አንዱ ፡ የቅዳሴ ፡ ወንድም ፡ ከድርገት ፡ በኋላ ፡ የሚቃኝ ፡ የሚዜም ፡ የሚዘመርም ።

**ምዝማር** ፤ (ራት) ፤ ጥቅስ ፤ የመጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ምስክር ፡ የሚኾን ። ብዙኅ ፡ ምዝማር ፡ ብየ ። ዘእምቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ምዝማር ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ቄር) ።

**ዘሚር** ፤ (ዕብራ) ፤ ዜማዊ ፡ ዖፍ ፤ እጅግ ፡ ድምፀ ፡ መልካም ፤ ያሮድዮን ፡ ወንድም ፡ ወይም ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ዖፈ ፡ ያሬድ ። ተመልከት ፡ አሮድዮንን ፡ እዮ ።

**ዘመረግድ** ፤—ዕንቍ ፤—መረግድ ፡ ረገደ ።



ዘሚር ።

**ዘኒብ** ፤ ቦት ፤ (ዘነበ ፡ ይዜንብ ፡ ይዝንብ) ፤ ማወዛወዝ ፤ መቍላት ፡ መሽጐብ ፡ መነስነስ ።

**ዘነብ** ፤ (ብ ፡ አዝናብ ። ዕብ ፡ ዛናብ ። ሱር ፡ ዙንባ ። ዐረ ፡ ደነብ) ፤ ዥራት ፤ የእንስሳትና ፡ የአራዊት ፡ ቅጥያ ፡ በስተኋላቸው ፡ የሚበቅል ፤ ጫፍ ፡ ውልብልቢት ፡ ጭራ ። ዘነበ ፡ ከልብ ። ዘነበ ፡ አፍራስ ። ምቱረ ፡ ዘነብ ። ርእስ ፡ ወዘነብ ። ወበሙ ፡ ዘነብ ፡ ከመ ፡ ዘነበ ፡ ዐቅራብ ። ወአዝናቢሆሙ ፡ ከመ ፡ አራዊተ ፡ ምድር ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ መስ፳፱ ። ዘሌ፳፱ ፡ ፳፫ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፲፱ ። ራእ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፱) ። ዘነበለ ፡ አዘነበለ ፡ ዝንብ ፡ መዘነቢያ ፡ ማለት ፡ ከዘኒብ ፡ ወጥቷል ፡ (ዐማርኛ) ።




ዘነብ ።

**ዝንብ** ፤ (ዕብ ፡ ዝቡብ) ፤ በቁሙ ፡ ኹሉን ፡ የሚቀምስም ፡ የሚልስ ፡ የንብ ፡ ጐሣ ፤ ምናምንቴ ፡ እንስሳ ። ከገጠር ፡ ንብ ፡ የከተማ ፡ ዝንብ ፤ ዝንብ ፡ ቢሰበሰብ ፡ መማላሊት ፡ አይከፋት ፡ እንዲሉ ፡ (ዐማርኛ) ።



ዝንብ ።

**ዘንቢር** ፤ (ብ ፡ ዘናቢር ። ዐረ ፡ ዙንቡር ፤ ዚንብር) ፤ ቀርብ ፡ የውሻ ፡ ዝንብ ፡ የሚነድፍ ፡ የሚነክስ ፡ ተቁናጣጭ ። ወሰብ ፡ መጽአ ፡ ንጉሠ ፡ ፋርስ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ንጽቢን ፡ ወዐገታ ፡ አምጽአ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሊ ፡



ዘንቢር ።

ሰራዊቱ ፡ ደመና ፡ ዘናቢር ፡ ወትንንያ ፤ ወነደፍዎሙ ፡ ለአፍራሲሆሙ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፫) ።

**ዘንበረ** ፤ (ዕብ ፡ ዛምሬ) ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ከንገደ ፡ ስምዖን ፡ ወገን ፡ የሰሉ ፡ ልጅ ፤ ያባቱ ፡ ቤት ፡ አለቃ ፤ ከመንግዛራይቱ ፡ ከከስቢ ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ተጣምሮ ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፤ ካህኑ ፡ ፊንሐስ ፡ ያልዓዛር ፡ ልጅ ፡ በዘገሩ ፡ ባበታ ፡ ጦሩ ፡ አጣምሮ ፡ ወግቶ ፡ የገደለው ፡ የደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ዕልው ፡ (ዘኍ፳፭ ፡ ፲፬) ።

**ዝንጊብል** ፤ (ዕብ ፡ ዘንግቢል) ፤ በቁሙ ፡ የተክል ፡ ወገን ፤ ሥሩ ፡ ከቅመም ፡ የሚገባ ፤ ሽታው ፡ የሚጣፍጥ ፡ ጣዕሙ ፡ የሚሰንፍጥ ።

**ዘንጐጎ** ፤ ጎት ፤ (ዘንጐጎ ፡ ይዜንጕጕ ፡ ይዘንጕጕ) ፤ ማሽሟጠጥ ፤ በነገር ፡ መንካት ፡ መጉነጥ ፤ መስደብ ፡ መዝለፍ ፤ ማንወር ፡ መንቀፍ ፤ ማፌዝ ፡ ማላገጥ ። ይዜንጕግዎሙ ፡ በእንተ ፡ ዘገዩ ። ይዜንጕጕ ፡ በኃጢአ ፡ ሕግ ። ይጼዐሉክሙ ፡ ወይዜንጕጕክሙ ። ወከማሁ ፡ ፈያትኒ ፡ ይዜንጕግዎ ፡ (ዮሴፍ ። ጥበ፲ ፡ ፲፱ ። ማቴ፳፯ ፡ ፲፭ ። ጰጵ፮ ፡ ፵፬) ። ዘንግ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡ መንኪያ ፡ መጕንጫ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (አስቴ፱ ፡ ፲፭ ። ፳ ፡ ፲፱) ።

**ዘንጓጉ** ፤ (ጕት ፡ ጕያን ፡ ያት) ፤ የሚያሽሟጥጥ ፡ አሽሟጣጭ ፡ ዘባቴ ፡ ነቃፊ ፡ ምሳሱ ፡ እንደ ፡ ዘንግ ፡ በሩቅ ፡ የሚጠቅስ ፡ የሚነካ ። ይኪውን ፡ ዘንጓጌ ፡ (ምሳ፲፰ ፡ ፳) ።

**አዘንጐጎ** ፤ አሰደበ ፡ አስነቀፈ ። አዘንጐግዎሙ ፡ ነፍሳቲክሙ ። ቦ ፡ እስ ፡ ይክሕዱ ፡ ወያዘነጕጉ ፡ ህሉተ ፡ ሥርዐተ ፡ (ዮሴፍ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ተዘንጐጎ** ፤ ተሽሟጠጠ ፡ ተሰደበ ፡ ተነቀፈ ፤ ማላገጫ ፡ ኾነ ። ወተዘንጕጕ ፡ በኀበ ፡ ህለዉ ፡ (ዘዳ፳፱ ፡ ፴፯) ።

**ዝንጉግ** ፤ ጕ ፤ የተሰደበ ፡ ንቁፍ ፡ ምንኑን ፡ ኀሱር ። ከመ ፡ ዝንጉግ ፡ ኢትኩኑ ፡ (ምሳ፳፭ ፡ ፲) ።

**ዝንጓጌ** ፤ ስድብ ፡ ሽሙጥ ፡ ተግዳሮት ፡ ለግጥ ፡ (ዘፍ፴፩ ፡ ፳፫ ። ሉቃ፳ ፡ ፳፭) ። በባእስ ፡ ወበዝንጓጌ ፡ ይፌንዎሙ ። ነገረ ፡ ዝንጓጌ ። ኢይረክቦ ፡ ዝንጓጌ ፡ (ኢሳ፳፯ ፡ ፵ ። ጥበ፳ ፡ ፱ ። ሄኖ ፡ ፲፯ ፡ ፱) ።

**ዘንግዐ** ፤ (ዘግዐ ፤ ስሕ ፡ ግ) ፤ ዘነጋ ፡ ረሳ ፡ አጠፋ ፡ ቀድሞ ፡ ያውቀው ፡ የነበረውን ፡ ልቡ ፡ ደንግጦ ፡ አእምሮው ፡ ተናውጦ ፡ ወይም ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ አርጅቶ ፡ ገርጅቶ ፤ ራሱ ፡ ጠፍቶ ፡ ተበሳጭቶ ። ዘግዐን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ ሥር ፡ ነው ። ዘንግዐኒ ፡ ልብየ ። ሰበ ፡ አከ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ እምእቤ ፡ ዘንጋዕክ ። ከመ ፡ አብድ ፡ እዜንግዕ ፡ (ሱቱ ፡ ዕገ፲ ፡ ፯፩ ። ራእ ፡ ባሮ ። ዘቅርሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ፡ ፳፫) ።

—፤ ለፈለፈ ፡ ቀባጠረ ፡ ነገር ፡ አበዛ ፤ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገባል ። ወሰበ ፡ ትጼልዩ ፡ ኢትዘንግዑ ፡ ከመ ፡ አሕዛብ ፡ (ማቴ፮ ፡ ፯) ።

**አዘንግዐ** ፤ አዘነጋ ፡ ዝንጉ ፡ አደረገ ፤ አስረሳ ፡ ልብ ፡ አጠፋ ። ኢብዝኆ ፡ መጻሕፍት ፡ ያዜንግዕ ፡ ልበ ። ናሁ ፡ አነ ፡ አንጐግዎ ፡ ወአዘንግዖ ፡ ልበ ፡ (ግብ ፡ ፳፯ ፡ ፳፬ ። ሆሴ፪ ፡ ፲፬) ።

**ተዘንግዐ** ፤ ተዘነጋ ፡ ተረሳ ፤ ጠፋ ፡ ቀረ ።

**ዝንጉዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ግዕት) ፤ የተዘነጋ ፡ ዝንግ ፤ ውዳቂ ። የዘነጋ ፡ ዝንጉ ፤ ልበ ፡ ቢስ ፤ ተለል ፡ ተሰላ ፡ የሚል ፡ (ቋንቋውን ፡ የሚያውቅለት ፡ ሳይኖር ፡ አላስተርጓሚ ፡ የሚናገር ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፩) ። ዝንጉዕ ፡ ኢይሁዳዊ ። ኢይኩን ፡ ዕጩረ ፡ ወኢጽሙመ ፡ ወኢ ዝንጉዐ ። ዝንጉዓን ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ልብ ፡ (ቁር ፡ እ ስት ። ፍ ፡ ን ፡ ፰ ። ፳፱ ፡ ፫) ።

**ዝንጋዔ** ፤ (ዕያት) ፤ በቁሙ ፤ መዘንጋት ፡ አዘ ነጋግ ፤ ዝንጋታ ፡ ርሳታ ፤ ተረት ፡ ተርታ ፤ ከንቱ ፡ ነገር ። መንፈሰ ፡ ዝንጋዔ ። አ ፡ ለዝ ፡ ዝንጋዔ ። ወኵሉ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ከመ ፡ ዝንጋዔ ፡ ወኢአምን ዎን ፡ (ሆሴ፱ ፡ ፯ ። ቁር ፡ እስት ። ሉቃ፳፬ ፡ ፲፩) ።

**ዝንድ** ፤ (ዐረ) ፤ የብረት ፡ ዘንግ ፤ የመዝጊያ ፡ ሰናግ ፡ ረዥም ፡ ሸንገል ። የዋዊን ፡ ፍች ፡ እይ ፤ ዘንድ ፡ ዘንደ ፡ ማለት ፡ በማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ዜነወ** ፤—ነገረ ፤—ዘየነ ፤ ዘይነወ ።

**ዘንዮ** ፤ ዮት ፤ (ዘነየ ፡ ይዘኒ ፡ ይዝኒ ። ዕብ ፡ ዛናህ ። ሱር ፡ ዝናእ ። ዐረ ፡ ዘነይ ፤ ዘመወ) ፤ መዘናት ፤ መዳራት ፤ መቈላመጥ ፡ የዝሙት ፡ ጥዜማ ፡ መቆም ። መሴበን ፡ መቀንዘር ፤ ባልን ፡ ወይም ፡ ሚስትን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መኼድ ፤ በዝሙት ፡ ሥራ ፡ ማደፍ ፡ መርከስ ፡ ዘር ፡ መዝራት ፡ ማውጣት ፡ ማፍሰስ ፤ ዘመወን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ዝንየት** ፤ ዝኔት ፤ መዘሞት ፤ ዝሙት ፡ ዝና ፤ የዝሙት ፡ ሥራ ። ዘር ፡ እድፍ ፡ ርስሐት ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘወድቀ ፡ በዝንየት ፡ ወበሕልም ፡ ይትከላእ ፡ እም ቍርባን ፡ ኪያሃ ፡ ዕለተ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘወፅአ ፡ ዝንየት ፡ ወውእቱ ፡ እንዘ ፡ ንቁህ ፡ ይትገሐሥ ፡ እምቍርባን ፡ ሰሉስተ ፡ ዕለተ ። ዝኔት ፡ በኅሊና ፡ ርኩስ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘይትከዐዎ ፡ ዝንየት ፡ ለዝሉፉ ፡ (ቄድር ፡ ገ፷ ። ፻፷) ። ወከዐዉ ፡ ዝንየቶሙ ፡ ዲቤሃ ፡ (ሕዝ፳፫ ፡ ፰) ።

**ዘኒም** ፤ ሞት ፤ (ዘን(ነ)መ ፡ ይዘንም ፡ ይዝንም ። ዕብ ፡ ዛራም ፤ ዜሬም) ፤ መዝነም ፡ ከላይ ፡ ከአየር ፡ ከሰማይ ፡ መውረድ ፡ መፍሰስ ፤ በኀይል ፡ መረጨት ፡ የውሃ ፡ የእሳት ፡ የበረድ ፡ የመቅሠፍት ። ዘ ነመ ፡ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ ዐቢይ ፡ ዝናም ። ዘነመ ፡ እሳት ። ይዘንም ፡ መሣግር ፡ ላዕለ ፡ ኃጥኣን ። በረድ ፡ ይዘንም ፡ (ዮሴፍ ። ሉቃ፲፯ ፡ ፳፱ ። መዝ ፡ ፲ ። ፸፯) ።

**አዝነመ** ፤ አዘነመ ፡ አወረደ ፡ ረጨ ፡ አፈሰሰ ። አስደራጊነትም ፡ አለበት ። እኤዝዝ ፡ ደመናተ ፡ ከመ ፡ ኢያዝንሙ ፡ ላዕሌሃ ። አዘዘ ፡ ደመና ፡ ወአዝነመ ፡ መና ። ኣዘንም ፡ በረደ ። ወአዝነመ ፡ እግዚ ፡ እሳተ ፡ ወተየ ፡ እምሰማይ ፡ (ኢሳ፭ ፡ ፮ ። መዝ ፡ ፸፯ ። ዘፀ፱ ፡ ፲፰ ። ዘፍ፲፱ ፡ ፳፬) ።

**ዝናም** ፤ (ማት) ፤ በቁሙ ፡ የውቅያኖስ ፡ ውሃ ፡ በደመና ፡ ዐይበት ፡ ተቋጥሮ ፡ በነፋስ ፡ ወደልጋዝ ፡ ተጭኖ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወዳየር ፡ እየወጣ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ የሚረጭ ፡ የሚፈስ ፡ የሚንሰነስ ። የዐቈሩ ፡ ማየ ፡ በክረምሥ ፡ ደመና ፡ ወያወርድ ፡ ዝ ናመ ፡ እምክረምሥ ፡ ማሕፀና ። በእንተ ፡ ዝናማት ፡ ከመ ፡ ዝናም ፡ ይፈኑ ። ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ርደተ ፡ ዝናማት ፡ (ቅዳ ፡ ጎር ። ጸዋት) ።

**ዘናና** ፤ (ዘነ ፡ ዘነነ ፤ ዘንዘነ ፤ ዘኒን ፤ መ ውግጥ) ፤ ብስ ፡ ክብ ፡ እንክብል ፡ ደንጊያ ፤ በወይፈን ፡ ማንበር ፡ ላይ ፡ የሚታሰር ፡ መቅጫ ። በደንጐሬ ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ የሚሰካ ። በቁሙ ፡ ዘንዘና ፡ ፈሳም ፡ የመውጊያ ፡ ማልገል ። ለመርከብና ፡ ላትሮንስም ፡ መልሕቅ ፡ ይነገ ራል ፡ (አዋል) ። ጐንደሮች ፡ ግን ፡ ውሽምውን ፡ ዘን ዘና ፡ ይሉታል ። ኹሉም ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ።

**ዘኒፍ** ፤ (ዘነፈ ፡ ይዘንፍ ፡ ይዝንፍ) ፤ ማዘንፍ ፤ የልብስ ፡ የቃል ፡ (ዐማርኛ) ።

**ተዛነፈ** ፤ በቁሙ ፡ ተዛነፈ ። (ግጥም ፤ ስለ ፡ ሳ ውልና ፡ ስለ ፡ ኬፋ ፡ ሞት) ፤ ጳውሎስ ፡ ታርደ ፡ በኔሮን ፡ ሰይፍ ፤ ኹለቱ ፡ ዓመት ፡ ፈርጅ ፡ ሳይዛነፍ ፤ ስቅሎ ፡ ለመ ግደል ፡ በመጨረሻ ፤ ወሰዱት ፡ እንጂ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዋሻ ፤ ጴጥሮስን ፡ ማርከ ፡ ከባቢሎን ፤ ሮም ፡ እንድትከብር ፡ እንድትገን ።

**ዘኒቅ** ፤ (ዘነቀ ፡ ይዘንቅ ፡ ይዝንቅ ። ዕብ ፡ ዛኖቅ ፤ ቀዲም ፡ ቀኒጽ) ፤ መዘንቅ ፡ ማዘ ንቅ ፤ መቀየጥ ። መዝንቅ ፡ አብዝቶ ፡ መጨመር ፤ የግብር ፡ የነገር ። ዘንቅ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ግእዝ ፡ ከማ ርኛ ።

**ዝናር** ፤ (ራት ። ዐረ ፡ ዙናር ። ሱር ፡ ዙ ናራ ። ጽር ፡ ዘናሪዎን) ፤ በቁሙ ፡ መታጠቂያ ፡ ዐሞር ፡ የወገብ ፡ ማሰሪያ ፤ ወይም ፡ ድግ ። ምጣሕት ፤ ወርደ ፡ ጠባብ ፡ ቁመተ ፡ ረዥም ፡ እንደ ፡ ድግ ፡ ያለ ፤ ዲያቆናት ፡ የሚያጣፉት ፡ የሚያወነዝፉት ፡ በትከሻቸው ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉት ። ቀኒተ ፡ ሐቌ ፡ በዝናር ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፤ ለይኩን ፡ ሐቌክሙ ፡ ቅኑተ ። ኢይ ቅንቱ ፡ ሐቌሆሙ ፡ ዲያቆናት ፡ በዝናር ፡ በጊዜ ፡ ጸ ሎት ፡ እስመ ፡ ግዑዛን ፡ እሙንቱ ። ከመ ፡ ይዑድ ፡ ዝናረ ፡ ላዕለ ፡ ከሣዱ ፤ ወኢይግበር ፡ ዝናረ ፡ ላዕለ ፡ ሕሐዱ ፡ መትከፍቱ ። ዝናራት ፡ ዘውእቶሙ ፡ ፊቃር ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፲፬ ። ፯ ፡ ፱ ። ፊ ፡ መ ፡ ፴፭ ፡ ፫ ፡ ፭) ።

**ዝንቱ** ፤ (ዝ ፡ ንቱ) ፤ የቅርብ ፡ ዐጸፋና ፡ ቅ ጽል ፡ ይህ ፡ ይኸው ፤ ይኸኛው ። ን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ቱ ፡ አርቲክል ፡ ነው ፤ ዝን ፡ ዙ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዝንቱ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ዐቢሩ ፡ መልክኡሙ ፡ ዙ ፡ ነበረ ፤ ዝኩ ንና ፡ ዝክቱን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ አንጻር ፡ ነው ። ዝንቱሰ ፡ ይፀርፍ ፡ ዝንቱ ፡ ምስለ ፡ ዝንቱ ፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፤ ዐ ጸፉ ። ዝንቱ ፡ ሕዝብ ፡ ዝንቱ ፡ ነዳይ ፤ ዝንቱ ፡ ይስማ ኤል ፤ ቅጽል ። ዘንተ ፡ (ዘ) ፡ ይህን ፡ ይህንን ፤ ይኸውን ፡ ይኸኛውን ። ዘንተ ፡ አሕሠምከ ፡ ወዘንተ ፡ አሠነይከ ፡ (ሳታት) ።

**ዝዕላ** ፤ (ዐረ ፡ ዚር ። ዕብ ፡ ዜር) ፤ ዘርፍ ፡ ጌጥ ፡ ጕፍኝ ፡ አበባ ፡ ዐጽቅ ፡ ዛላ ፡ በቆብ ፡ በባርኔጣ ፡ ላይ ።

ወይም ፡ በዙሪያው ፡ የሚደረግ ። ሥራዐ ፡ ሎሙ ፡ ቀዋ ብዐተ ፡ ዘአልቦ ፡ ዝዐላ ፡ ዘከመ ፡ ደቂቅ ፡ (ሥር ፡ ጸሁ) ።

**ዘፈን ፤ ኖት ፤ (ዘፈነ ፡ ይዘፍን ፡ ይዝፍን ። ዐረብ)** ፤ መዝፈን ፡ መወዛወዝ ፤ ማሽብሸብ ፡ ማጋፈት ፤ መዝለል ፡ መፈንጨት ። እንዘ ፡ ይትዋነይ ፡ ወይዘፍን ። ተንሥኡ ፡ ይዝፍኑ ። ይዘፍኑ ፡ አድባር ፡ ከመ ፡ ሐራጊት ። አንኩ ፡ ይዝፍኑ ፡ በማሕሌተ ፡ እግዚአሙ ፡ (ኩፉ ፡ ፲፯ ። ፩ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፯ ። ሔኖ፺፭ ፡ ፱ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ዘፋኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፤ የሚዘፍን ፡ ዘፋኝ ፡ ተወዛዋዥ ። ከመ ፡ ያነቅሆ ፡ ለልበ ፡ ዘፋኒ ፡ ና ብሊስ ። ዘፋኒት ፡ አቅረበት ፡ ዳሕለ ፤ ሄሮድስ ፡ ለዮ ሐንስ ፡ ርእሶ ፡ አምተረ ። ኢትኩኑ ፡ ዘፋንያነ ፡ (ደራሲ ። መዋሥ ። ዲድ ፡ ፯) ።

**ዘፈን ፤ (ናት)** ፤ በቁሙ ፤ ዝላይ ፡ እስክስታ ። እለ ፡ ይጸብእሙ ፡ ሰይጣን ፡ በነገረ ፡ ዘፈን ፡ ወተው ኔት ። ካህናት ፡ ኢይነጽሩ ፡ ተውኔተ ፡ ወኢዘፈነ ፡ (ቀሌ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፱ ፡ ፯) ።

**አዝፈነ** ፤ አዘፈነ ፤ አዘለለ ፤ ዘፈን ፡ አስተማረ ። ያዘፍን ፡ አፍራሰ ፡ እንዘ ፡ ያነዝር ፡ በእንዚራ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፴) ።

**ምዝፋን ፤ (ናት)** ፤ መዝፈኛ ፤ ማዘፈኛ ፡ ቦታ ፡ መሣሪያ ። ዘበልዐ ፡ በቤተ ፡ ምዝፋናት ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፴) ።

**ዘፈፍ ፤ (ዘፈ ፤ ዘፈፈ ፡ ይዘፍፍ ፡ ይዝፍፍ ። ሰፈፈ)** ፤ ዘፍ ፡ ማለት ፤ መውደቅ ፡ መጋደም ። ዛፍ ፡ መኾን ፤ መንዛፈፍ ።

**ዙፋን ፤ (ናት)** ፤ በቁሙ ፤ ታላቅ ፡ ዐልጋ ፡ ዘፍ ፡ መባያ ፤ መንበረ ፡ መንግሥት ። ማማ ፡ ቁራ ፤ የዛፍ ፡ ላይ ፡ ሥራ ።

**ዘፍዘፈ ፤ (ዐረብ)** ፤ ሰፋ ፡ ተንሰራፋ ፤ ተዘ ረጋ ፤ የእጅ ፡ የዐጽቅ ፡ የክንፍ ። ወፈረ ፡ ገዘፈ ፡ ዘፍዛፋ ፡ ኾነ ። በቁሙ ፤ ዘፈዘፈ ፡ ዘፈቀ ፡ ነከረ ፤ ለማራስ ፡ (መ ፡ ፈ) ።

**አንዘፍዘፈ** ፤ በቁሙ ፤ ዘረጋ ፡ አራገበ ፤ አርገ በገበ ። ኪሩቤል ፡ እንዘ ፡ ያንዘፈዝፉ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ዴብ ፡ ምሥሃል ። መላእክተ ፡ እግዚ ፡ ያንዘፈዝፉ ፡ ክ ነፊሆሙ ፡ ላዕሌሁ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳) ።

**ዘፈቀ** ፤ በቁሙ ፤ ነከረ ፡ አራሰ ፤ ዘፈዘፈ ፡ (ዐ ማርኛ) ።

**ዘፈር ፤ (ብ ፡ አዝፋር ። ዐረ ፡ ሽፍር ። ሱር ፡ ስፋራ ፤ ጽንፍ)** ፤ ጫፍ ፡ ዳርቻ ፤ ዘርፍ ፡ ቅ ጽል ፡ የልብስ ። ሥፋና ፡ ምንጩ ፡ ሰፈረ ፡ ነው ፤ ዘረፈም ፡ ይኾናል ፡ (ዘኊ ፲፭ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ። ዘዳ፳፪ ፡ ፲፪) ። ዘፈረ ፡ ልብሱ ፡ አንቅዕተ ፡ ደም ፡ አይበሰ ። አዝፋረ ፡ አልባሲ ሆሙ ። አዝፋረ ፡ ወርቅ ። ይስሕባ ፡ አዝፋረ ፡ አልባሲ ሆን ፡ (ቀሌ ። ማቴ፳፫ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፵፬ ። አርጋ ፡ ፪) ።

**ዘፈቀ ፤ (ዘፈ ። ዕብ ፡ ዘፋት)** ፤ ዝፍት ፡ አ መባ ፤ በዝፍት ፡ ቀባ ፡ ለቀለቀ ፡ መረገ ፡ ዘጋ ።

**ዝፍት ፤ (ዕብ ፡ ዜፌት ። ሱር ፡ ዚፍታ ። ዐረ ፡ ዚፍት)** ፤ በቁሙ ፤ የንጨት ፡ የሙጫ ፡ ቅጥራን ፡ ከታወቁ ፡ ዛፎች ፡ የሚወጣ ፤ መጣብቅነት ፡ ያለው ፡ መ ልኩ ፡ እተላ ፡ ጭቃ ፡ የሚመስል ፡ ጥቍር ፡ ከርፋታም ፤ እንደ ፡ ጋዝ ፡ እንደ ፡ ዲን ፡ እሳት ፡ የሚቀበል ፤ ቶሎ ፡ የሚነድ ፡ የሚቃጠል ። አዘዘ ፡ ይቅብዑ ፡ ሥጋሁ ፡ ተየ ፡ ወዝፍተ ፡ ወይደይዎ ፡ ውስተ ፡ እቶነ ፡ እሳት ። ነሥአ ፡ ዳንኤል ፡ ዝፍተ ፡ ወጸጕረ ። ተይ ፡ ወዝፍት ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፳፯ ። መጋ፳፫ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ዝቅ ፤—የማስ ፡ ጋን ፤—ዝሒቅ ፡ ዘሐቀ ፤ ዝሕቅ ።**

**ዘቂቅ ፤ (ዘቀ ፡ ይዘቅቅ ፡ ይዝቅቅ ። ዕብ ፡ ዛቆቅ ፤ ዛቃቅ ፤ ነጠፈ ፤ አጽረየ)** ፤ መዝቀጥ ፡ መ ጥለቅ ፤ ዝቃጭ ፡ እተላ ፡ መኾን ። ፪ኛም ፤ ዘቅዘቀ ፡ ብሎ ፡ ዝቅዝቅ ፡ ዘቅዛቃ ፡ ዝቅተኛ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ይወጣል ፡ (ዐማርኛ) ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ ግስ ፡ ኹሉ ፡ ቃሉና ፡ ፊደሉ ፡ የግእዝ ፡ ሲኾን ፡ ወዳማርኛ ፡ ስለ ፡ ኼደ ፡ በግእዝ ፡ ቃ ላት ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም ።

**ዛር ፤ (ራት ። ዕብ ፡ ዛር ፤ ብ ፡ ዛሪም)** ፤ በቁሙ ፤ ነኪር ፡ ልዩ ፡ ባዕድ ፡ ሌላ ፤ የሌላ ፡ ወገን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፤ እንግዳ ፡ ስደተኛ ። ጣዖት ፤ መንፈስ ፡ ጋኔን ፡ በሰው ፡ እያደረ ፡ ሰው ፡ የሚያስት ፡ (ዐማርኛ) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ዛር ፡ ባዕድ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ግብት ፡ ሐዲስ ፡ ይ ላል ። ኢይኩውንከ ፡ አምላክ ፡ ግብት ። ኢይኩን ፡ ብከ ፡ አምላክ ፡ ሐዲስ ፤ አይገኝብኽ ፡ (መዝ ፡ ፹ ። ቁር) ። ይኸ ውም ፡ ሊታወቅ ፡ ግእዙ ፡ አምላክ ፡ ነኪር ፡ ባለው ፡ ዕብ ራይስጡ ፡ ኤል ፡ ዛር ፡ ይላል ።

**ዛራዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ ጣዖታዊ ፤ ዛራም ፡ ባለዛር ፤ የዛር ፡ ፈረስ ።


**ዛርት ፤ (ዕብ ፡ ዜሬት)** ፤ ዣርት ፤ ዐይነ ፡ ፈ ጣጣ ፡ ጠጕረ ፡ ጋሬጣ ፡ (ዛራም ፡ ሴት) ፡ ቅንፋዝን ፡ እይ ።

**ዘርአ ፤—ዘራ ፤—ዘረዐ ፡ ዘርዐ ፤ ዘርዕ ።**

**ዘረብ ፤ ቦት ፤ (ዘረበ ፡ ይዘርብ ፡ ይዝርብ ። ዐረ ፡ ፀረበ)** ፤ መምታት ፡ መቀጥቀጥ ። ደረበንና ፡ ጸረ በን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ናቸው ። መርገጥ ፡ መፈጋገጥ ፤ የጣማ ፡ የምንጣፍ ። በትግሪኛ ፡ ግን ፡ መንገር ፡ መና ገር ፡ ይኾናል ፡ ምስጢሩ ፡ የነገርን ፡ በትር ፡ ስድብን ፡ ያሳያል ።

**ዘርብ** ፤ ምት ፡ አመታት ፤ አንዛዘር ፤ ርግጫ ።

**መዝረብ** ፤ መምቻ ፤ መቀጥቀጫ ፤ ድሕንጻ ፡ መዶሻ ። ነሥአት ፡ መትከለ ፡ ወመዝረበ ። በሰፈልያ ፡



መዝረብ ፡

ወበመዝረብ ፡ አዕፅምቲከ ፡ ስቡር ፡ (አቡሻ ፡ ፶፯ ። ደራሲ) ።

**ዘርበን ፤ (ናት ። ዐረ ፡ ዘርዐ·ል)** ፤ ነጠላ ፡ ጫማ ፤ ክፍት ፡ መጫሚያ ፡ በስተኋላ ፡ ተረከዝ ፡ የማይከድን ፡ የማይሸፍን ። እሉ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ቀደሙ ፡ የሐርምዎ ፡ ለአሣእን ፡ ወድኅረበ ፡ የሐውሩ ፡ በዘርቦናት ፡ ወበቀጽናት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።



ዘርበን ፡

**ዘርቤት ፤ (ዐረ ፡ ዙርቢየት)** ፤ ጥሩ ፡ ልብስ ፡ ሌሐፍ ፤ ክቡር ፡ ምንጣፍ ፡ ያልጋ ፡ የዙፋን ፡ ጌጥ ። ወመንጸፊ ፡ ቤታ ፡ ውእቱ ፡ ዘርቤት ፡ ቅዳሴ ፡ ዘሱራፌል ። ዘርቤታተ ፡ ነጸፍኩ ፡ ዘእምግብጽ ። ነጸፈት ፡ ዘርቤታተ ፡ ወአልባሳተ ፡ ደርከኖ ፡ ዲበ ፡ ዐራታ ፡ (ድጓ ። ምሳ፯ ፡ ፲፮ ። ስንክ ፡ የካ፲፫) ።

**ዘርግሐ ፤ ተዘርግሐ ፤ (የዘግሐ ፡ ስሯጽ ፤ ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፤ ዘረጋ ፤ ተዘረጋ ።

**ዘሬው ፤ ዎት ፤ (ዘረወ ፡ ይዘሩ ፡ ይዝሩ ። ዕብ ፡ ዘራ·ህ)** ፤ ማዝራት ፤ መዝራት ፡ መበተን ፤ ማጥፋት ፡ ማባከን ፡ ባይ ፡ ማድረግ ፡ አብዝቶ ፡ መስጠት ፡ መመጽወት ፤ መውገዝ ፡ መለየት ፡ ማራቅ ፤ ምስጢሩ ፡ መበተን ፡ ክሰው ፡ ይገባል ። ይዘርዎ ፡ ለጊሜ ፡ ከመ ፡ ሐመድ ። ዝሩ ፡ እክለክ ፡ ባዕለ ፡ መቃብረ ፡ ጻድቃን ። እዘርዎሙ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ነፋሳት ። ዘሬዎቱ ፡ ንዋየ ፡ ለመብልዕ ፡ ወመስቴ ። ዘረወ ፡ መክፈልተ ፡ ንዋዩ ፡ ባዕለ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ። ዘረወ ፡ ኢምእመናነ ፡ እምነ ፡ ጉባኤ ፡ (መዝ ፡ ፻፵፯ ። ወቢ ፡ ፲፯ ። ሕዝ፭ ፡ ፲ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ። ፈልክ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ሐም፭) ።

**ዘራዊ ፡ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ በታኝ ፡ አጥፊ ፡ አባካኝ ። ዘራዊ ፡ መርዔቱ ፡ ለእግዚ ። ዘራዊ ፡ ንዋይ ። ዘራዊ ፡ በአስተዋፅኦታት ፡ (ቀሌ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፱ ። ፴፪) ።

**አዝረወ** ፤ አስበተነ ፤ አስጠፋ ፡ አስፈረሰ ።

**ተዘርወ** ፤ ተዘራ ፡ ተበተነ ፤ ተበታተነ ። እምህየ ፡ ተዘርዉ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ አህጉር ። ኵልክሙ ፡ ትዘረዉ ፡ በበ ፡ አሐዱ ፡ ውስተ ፡ መካኑ ። እስመ ፡ ጽሑፍ ፡ እቀትሎ ፡ ለኖላዊ ፡ ወይዘረዉ ፡ አባግዕ ፡ (ኩፋ ፡ ፲ ። ዮሐ፲፯ ፡ ፴፪ ። ማቴ፳፮ ፡ ፴፩) ።

**ዝርው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሩት)** ፤ የተዘራ ፡ የተበተነ ፡ ብትን ፤ ብትንትን ፤ አንድነት ፡ የሌለው ። ሐመደ ፡ እቶን ፡ ዝርው ፤ ረሰይኩክሙ ፡ ዝርዋነ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ። ተሰምየ ፡ ስሙ ፡ ዝሩት ፤ እስመ ፡ በህየ ፡ ዘረዎሙ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ሚል፪ ፡ ፱ ። ዘፍ፲፩ ፡ ፱) ።

**ዝርወት ፤ (ታት)** ፤ መዝራት ፤ መዘራት ፡ መበተን ፤ መለያየት ። ዝርወተ ፡ ሕዝብ ። ዝርወተ ፡ እስራኤል ። ዝርወተ ፡ ልሳን ፡ (ዳን፲፪ ፡ ፯ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፯ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ዘሮ ፤ (ሮማይ ፡ ዜሮ)** ፤ ባዶ ፡ ጠፍ ፤ የባዶ ፡ ምልክት ፤ ፊደል ፡ (0) ካንድ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ያሉትን ፡ አኃዞች ፡ (1—9) ስማቸውንና ፡ ቍጥራቸውን ፡ የሚለዋውጥ ፡ የሚያበዛ ።

**ዘርዜቅ** ፤ የድሬ ፡ ጕንጕን ፤ ትት ፤ የወንፊት ፡ ዐይነት ፤ የወርቅ ፡ ሰንሰለት ። ወፅፍሮሁ ፡ ከመ ፡ ዘርዜቅ ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፳፪) ። ከዘርዘረና ፡ ከዘረቀ ፡ ከኹለቱ ፡ የወጣ ፡ ስም ፡ ነው ።

**ዘርዘረ ፤ (ዘሬር ፡ ዘረ ። ዘረወ)** ፤ በቁሙ ፤ ዘረዘረ ፡ አፍታታ ፡ አበጠረ ፤ ለያየ ፡ በተነ ፡ በታተነ ፤ የነገር ፡ የጠጕር ፡ የርባታ ፡ የቍጥር ፡ የሸንጎ ፡ የማኅበር ፡ የጥርስ ፡ የሰብል ። አጠፋ ፡ አበላሸ ፡ ከንቱ ፡ አደረገ ፤ የሥራ ፡ የምክር ፡ (ሔኖ፶፫ ፡ ፲፭) ። ዘርዝር ፡ ምክሮሙ ። ስአሉ ፡ ከመ ፡ ይዘርዝር ፡ እግዚ ፡ ምክሮሙ ፡ ለፀላውያን ፡ (ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ታኅ፱) ።

—፤ መሸነ ፡ አመነሸ ፡ በረበረ ፡ አዘራ ፡ አንዘረዘረ ፡ ያውድማ ። ሠዐየን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ተዘርዘረ** ፤ ተዘረዘረ ፡ ተፍታታ ፡ ተለያየ ፡ ተበታተነ ፤ ጠፋ ፡ ከንቱ ፡ ኾነ ። ይትከሀሉኑ ፡ ይሕየው ፡ ዘማስነ ፡ ወዘተዘርዘረ ። አዘዘ ፡ ይሥትርዎሙ ፡ በአጽፋረ ፡ ኀጺን ፡ ከመ ፡ ይዘርዝር ፡ ሥጋሆሙ ። ወይዘርዝር ፡ ኵሉ ፡ ዘፍጥረታተ ፡ ሕምዝ ። ጸለየ ፡ ቅዱስ ፡ ማእከለ ፡ እሳት ፡ ወተዘርዘረ ፡ ውእቱ ፡ እሳት ፡ ወወፅአ ፡ ቅዱስ ፡ እምኔሁ ፡ (ኪዳ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፱ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፱) ።

**ዝርዙር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ዝርት)** ፤ የተዘረዘረ ፡ የተበተነ ፡ ብትን ፡ ጕትን ፡ ብጥር ። ኢትግበር ፡ ሥዕርተክ ፡ ፍቱሐ ፡ ወዝርዙረ ፡ ወኢፀፉረ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ መስ፲፰) ። ዘር ፡ ዘር ፡ ያለ ፤ ዘርዛራ ፤ የጥርስ ፡ የወንፊት ። ዐይን ፡ ሸውራራ ፡ እግረ ፡ ወንካራ ፡ ጥርሰ ፡ ዘርዛራ ፤ መጋዝ ፡ ጥርስ ፡ እንዲሉ ፡ (ኪዳ ፤ ስለ ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ መልክ) ። የዘረዘረ ፡ ዝርዝር ፡ ፀዱስ ፡ መጣት ፡ ሰብል ። (ትረት) ፤ ግዝግዘ ፡ ቀጭ ፤ ዐመደ ፡ ፈጭ ።

**ዘርዘር ፤ (ዘርዜቅ)** ፤ ማንዘርዘሪያ ፤ የጠፍር ፡ የኽርማት ፡ የሽቦ ፡ ወንፊት ።

**ዘሬጥ ፤ ዘረጠ ፤ አዝረጠ ፤ ዘረጦ ፡ ዝራጭ ፡ ምዝራጥ ። ዘርጠጠ ፡ ዘርጣጣ ፤ በቁሙ ፡ (ዐማርኛ) ።**

**ዘረየ ፤ (ይዘሪ ፡ ይዝሪ ። ዘረወ)** ፤ በተነ ፡ ለየ ። ወና ፡ የ ፡ ይወራረሳሉ ። ለሰባልዮስ ፡ ይዘርዮ ፡ ወለአርዮስ ፡ ይሰድዶ ፡ (ስንክ ፡ ታኅሣ፱) ። ዮም ፡ ይእዜ ፡ ብሎ ፡ ዘሬ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ዘሬክ ፤ ኮት ፤ (ዘረከ ፡ ይዘርክ ፡ ይዝርክ ። ደረከ)** ፤ መዘርከት ፡ መቅደድ ፡ ማዝረክረክ ፡ መጣል ፤ ደረከን ፡ እይ ።

**ዘርከየ ፤ (ተቀ ፡ ግ)** ፤ ሰደበ ፡ አዋረደ ፡ ተሳገደ ፡ ከፋ ፡ ስም ፡ ቀባ ። አብድ ፡ ይዘረኪ ፡ ወኢየአዙትት ። ኀፍረት ፡ ዘርከዮቱ ፡ ለዐርክከ ። ዘርከዮተ ፡

ጸላኢ ። ከመ ፡ ይጽዐላሃ ፡ ወይዘርክያሃ ፡ ለእንተ ፡ ዝሙት ፡ (ሚ.ፌ ፲፰ ፡ ፲፮ ። ማኅ ፡ ፳፱ ። ቅዳ ። የሴፍ) ።

**ዘርከየ፤ መዘርከይ**፤ የሚሳደብ ፡ ተሳዳቢ ፡ ተላጋጭ ፤ ስመኛ ።

**አዘርከየ**፤ አሰደበ ፤ ተሳዳቢ ፡ አሰነካ ።

**ተዘርከየ**፤ ተሰደበ ፤ ስሙ ፡ ጠፋ ፤ ወሬው ፡ ከፋ ።

**ዝርኩይ**፤ (ያን ፡ ያት ፡ ኪት ፡ ክይት)፤ የተሰደበ ፡ ስዱብ ፤ ስመ ፡ ጥፉ ፤ ስድብ ፡ ልብሱ ፡ ነውር ፡ ቀሚሱ ። በውነት ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ እንደ ፡ ሶስና ፡ (ዳንኤ ፡ ፴፳—፶) ።

**ዝርከዩ**፤ (ይያት)፤ መሰደብ ፡ መሰደብ ፡ አሰዳደብ ። ስድብ ፤ ሰግድ ።

**ዝርክይና**፤ ስዱብነት ፡ ስድብ ፡ የስድብ ፡ ቃል ፡ (ቀሌ) ።

**ዘረዐ፤ ዖት**፤ (ዘርዐ ፡ ይዘርዕ ፡ ይዝራዕ ። ዕብ ፡ ዛራዕ ። ሱር ፡ ዝራዕ ። ዐረ ፡ ዘረዐ)፤ መዝራት ፡ መትከል ፤ ፍሬን ፡ ቅንጣትን ፡ በርሻ ፡ ላይ ፡ መበተን ፤ መርጨት ፡ መፈንጠቅ ፡ ማፍሰስ ፡ መነስነስ ፤ ዘርን ፡ መቅበር ፡ ዐፈር ፡ ማልበስ ፡ እንዲበቅል ፡ ማድረግ ፡ ለምድርና ፡ ለሴት ፡ ዐደራ ፡ መስጠት ። በጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ዘርዕ ፡ ለዘሪዕ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ኢትዝርዑ ፡ ሰከሙ ፡ ውስተ ፡ ሦክ ። ኢትባእ ፡ ኀበ ፡ ብእሲተ ፡ ካልእከ ፡ ወኢትስክብ ፡ ምስሌሃ ፡ ወኢትዝራዕ ፡ ዘርዐከ ፡ ላዕሌሃ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፩ ። ኤር ፬ ፡ ፫ ። ዘሌ ፲፰ ፡ ፳) ። ሌለዩ ፡ ፈለጠ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዘርዐ ፡ ይላል ። አመ ፡ ክፈሎሙ ፡ ልዑል ፡ ለአሕዛብ ፡ ወዘከመ ፡ ዘርዖሙ ፡ ለደቂቀ ፡ አዳም ፡ (ዘዳ ፴፪ ፡ ፰) ። መዘርጋት ፡ መስደድ ፤ የእጅ ፡ የክንድ ። መወጠር ፡ መገተር ፡ መነጠል ፤ የመጋረጃ ፡ የድንኳን ።

**ዘራዒ**፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት)፤ የሚዘራ ፡ ዘሪ ፡ ተካይ ፡ (ገበሬ ፡ ወላጅ ፡ አባት) ። ውእቱ ፡ ይሁብ ፡ ዘርዐ ፡ ለዘራዒ ። ሰይጣን ፡ ዘራዔ ፡ እኪት ፡ ውስተ ፡ ልብ ፡ ሰብእ ። ዘራዔ ፡ ንባብ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ቀሌ ። ግብ፲፯ ፡ ፲፰) ።

**አዝርዐ**፤ አ(ስ)ዘራ ፡ አስተከለ ፤ አስበተነ ።

**ተዘርዐ**፤ ተዘራ ፡ ተበተነ ፤ ዘሩ ። ተዘራበት ፡ ተተከለበት ፤ እርሻው ። ኅቡረ ፡ ተዘርዐነ ፡ ማእከለ ፡ ክርሥኪ ። ዘርዕ ፡ ዘይዘራዕ ። ምድር ፡ ዘኢይዘራዕ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፰ ። ዘሌ ፲፰ ፡ ፴፯ ። ኤር ፡ ፪ ፡ ፪) ።


**ዝሩዕ**፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ርዕት)፤ የተዘራ ፤ የተዘራበት ፡ ዝር ። ለእመ ፡ ዐቀብነ ፡ አበሳሁ ፡ ለዘይትጋነይ ፡ ለነ ፡ ኮነት ፡ ዝርዕተ ፡ ውስተ ፡ ኵሉሕ ። ገራህት ፡ ዝሩዕ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ማን፲፱) ።


**ዝርዐት**፤ መዝራት ፡ መዘራት ፡ አዘራር ፡ ዝራት ።

**ዘርዕ**፤ (ዓት ፤ አዝርዕት)፤ በቁሙ ፤ ዘር ፡ ቅንጣት ፡ ጥሬ ፡ ፍሬ ፤ የሚበቅል ። በጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ዘርዕ ። ሀበነ ፡ ዘርዐ ፡ ምድር ። ፍሬያተ ፡ አዝርዕት ፡ (ኩፋ ፡ ፲፩ ። ዳንኤ ፡ ፲፯ ። ጥበ፲፩ ፡ ፳፪) ።

—፤ የሰው ፡ ዘር ፤ ልጅ ፡ ወገን ፡ ነገድ ፡ ትውልድ ። ከዐወ ፡ ዘርዐ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ማእከለ ፡ ዘርዕኪ ፡ ወማእከለ ፡ ዘርዓ ። ለከ ፡ ወለዘርዕከ ። እምዘርዐ ፡ ሜዶን ። ዐሠርቱ ፡ ወአርባዕቱ ፡ አዝርዕት ፡ (ኩፋ ፡ ማቴ ፩ ። ዘፍ፫ ፡ ፲፭ ። ገላ፫ ፡ ፲፮ ። ዳን፱ ፡ ፩ ። መጽ ፡ ምስ) ። ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ቀቲል ፤ ይህን ፡ የመሰለ ። ከንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ የሚወጣ ፡ ጥሬ ፤ ቀትል ፡ መቅትል ፡ ምቅታል ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**መዝርዕ**፤ (ብ ፡ መዛርዕ)፤ ቁና ፡ ቅርጫት ፤ ላዳን ፡ ታላቅ ፡ የቤት ፡ ቍና ፤ ቤድ ፡ ቀረዋ ፤ እንቅብ ፡ ጉርዝኝ ፡ ጉብ ፤ ገበሬ ፡ ዘር ፡ የሚሰፍርበት ፡ የሚያኖርበት ፤ ወይም ፡ በርሱ ፡ ይዞ ፡ የሚዘራበት ፡ የዘር ፡ መጣሪያ ፤ ለሌላም ፡ ይኾናል ። ወአግሐሡ ፡ ዘተርፈ ፡ ፍተታተ ፡ ዐሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ መዛርዐ ፡ ምሉአ ፡ (ማቴ፲፬ ፡ ፳ ። ፲፭) ።


መዝርዕ ፡


መዝርዕ ፡

**ምዝራዕ**፤ (ዓት)፤ መዝሪያ ፡ መዛሪያ ፤ ቃዳ ፡ ተሰላ ፤ እመም ፡ ገዝም ።

**መዝራዕት**፤ (ብ ፡ መዛርዕ ። ዕብ ፡ ዝሮዐ ። ሱር ፡ ዝራዕ ። ዐረ ፡ ዚራዕ)፤ ጡንቻ ፤ ከመትከፍት ፡ እስከ ፡ ክርናድ ፡ ያለው ፡ መዘርጋው ፡ ክፍል ፤ አገዳው ፡ ቅልጥሙ ። ፪ኛም ፡ የክንድ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ክንድ ፡ ወርቻ ፡ ይባላል ። እግዚኦ ፡ ልዑለ ፡ መዝራዕትከ ፡ ኢያእመሩ ። ተመጠውክዎ ፡ ዲበ ፡ መዝራዕትየ ። ምዕራፈ ፡ መዛርዕ ። መዛርዕ ፡ እለ ፡ ሥጋ ። አገዳ ፡ ወመዝራዕተ ፡ (ኢሳ፳፮ ፡ ፲፩ ። ሆሴ፲፩ ፡ ፫ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፲፰ ። ፴፪ ፡ ፳ ። ሕዝ፳፱ ፡ ፱) ። እጅጌ ፡ የቀሚስ ፡ እጅታ ። መዛርዐ ፡ ቀሚስ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፴፭ ፡ ፳) ።

**መዝርዕ**፤ (ብ ፡ መዛርዕ ፤ ዓት ። መሥርዕ ፤ ሥራዕ ፡ ዓት ። ዐረ ፡ ሺራዕ)፤ የመርከብ ፡ ሸራ ፡ ከፈትለ ፡ ከታን ፡ የሚሠራ ፤ ወፍራም ፡ ጥቅጥቅ ፡ ጥሩ ፡ ጠንካራ ፡ ረዥምም ፡ ሰፊ ፡ ታላቅ ፡ መጋረጃ ፤ ነፋስ ፡ እየሳበ ፡ መርከብ ፡ የሚያስኬድ ። ዘሩ ፡ ሠርዐ ፡ ነው ፤ ሥራዕን ፡ ተመልከት ፤ ጣፊና ፡ መላሽ ፡ ሠን ፡ በዚ ፡ ለውጠው ፡ ዘርዐ ፡ ብለውታል ። ወናሁ ፡ መዝርዐ ፡ ሐመርነ ፡ ሠናይት ፡ ወጽሪት ። ንስፋሕ ፡ እንከ ፡ መዝርዐ ፡ ሐመርነ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ኅሊናነ ። ለትኩን ፡ እንከ ፡ መዝርዕነ ፡ ንጽሕተ ፡ ወጽሪተ ፡ (አፈ ፡ ተ፴፱) ።

**ዘረፈ፤ ፎት**፤ (ዘረፈ ፡ ይዘርፍ ፡ ይዝርፍ ። ትግ ፡ ዘረፈ)፤ መዝረፍ ፡ መቀማት ፡ መንጠቅ ፤ የገንዘብ ፡ የቅኔ ። መዘረፍ ፡ መናበብ ፤ ዘረፋም ፡

ቅጥላም ፡ መኾን ፤ የቃል ። ቤተ ፡ ዳዊት ፡ ንጉሠ ፡ እስራ ኤል ፤ መምህረ ፡ ሕግ ፡ ሰባኬ ፡ ወንጌል ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

(ጥ) **ዘራፍ** ፤ በቁሙ ፤ ዘራፌ ። የድንፋታ ፡ ቃል ።

**ዘርፍ** ፤ በቁሙ ፤ ተሳቢ ፡ ተናባቢ ፡ ቃል ። ዘ ፈረ ፡ ጽንፍ ፤ ዘፈርን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ግልባጭ ፡ ነው ።

**ዘረቀ ፤ ቆት ፤ (ዘረቀ ፡ ይዘርቅ ፡ ይዝ ርቅ ። ዕብ ፡ ዛራቅ ። ዐረ ፡ ዘረቀ)** ፤ መወርወር ፡ መጣል ፤ የደንጊያ ፡ የጦር ። ማቧለት ፡ መቀሰድ ። መነ የል ፤ ልብስን ፡ በማየ ፡ ኒል ፡ በቀለመ ፡ ኒል ፡ መንከር ፤ ማስል ፤ ወይም ፡ መጥቈር ፡ ሰማይ ፡ መምሰል ።

**ዘርቅ** ፤ ቧልት ፡ ቀልድ ፤ ለግጥ ፡ ዋዛ ፡ ወዘበ ፌታ ፤ ለሰሚው ፡ ለተናጋሪው ፡ የማይጠቅም ፡ ቀርቃ ፡ ነገር ። **ወእመሂ ፡ ነገረ ፡ ዘርቅ ፡ አምጽአት ፡ ለከ ። ነ ግረ ፡ በከ ፡ ወዘርቅ ። ዓሊና ፡ ነገረ ፡ ዘርቅ ፡ ዘኢይ ደሉ ፡ ለክርስቲያን** ፡ (ምሳ፳ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ መስ፳፰ ። ኤነቀ ፡ ንስ) ።

**ምዝራቅ ፤ (ዐረ ፡ ሚዝራቅ)** ፤ ምዝራጥ ፡ ጦር ፡ ዘገር ፤ የሚወረወር ። **ደርበዮ ፡ በምዝራቅ ፡ ው ስተ ፡ ክርሁ ፡ ወቀተሎ** ፡ (ዮሴፍ) ።

**አዝረቀ ፤ (ዐረ ፡ አዝረቁ)** ፤ ጥቊር ፡ የ ኒል ፡ ዐይነት ፤ ጥቍረቱ ፡ ሰማይ ፡ የሚመስል ። **ብንተ ፡ ሕዐይንቲሁ ፡ አዝረቅ ፡ ከመ ፡ ኒል ። አልባስ ፡ ዘሕብረ ፡ አዝረቅ** ፡ (ስንክ ፡ ሐም፰ ። አቡሻ ፡ ፶) ።

**ዘረረ ፤ ሮት ፤ (ዘረ ፤ ዘረረ ፡ ይዘርር ፡ ይዝርር ። ዐረ ፡ ዘረ)** ፤ መዘረር ፡ መቈለፍ ፤ ዝራር ፡ ማግባት ። ማስጣት ፤ ለፀሓይ ፡ መስጠት ። መንዥረር ፡ መፍሰስ ፤ ዥረር ፡ ማለት ። ዘርዘረን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ቅ ጥይ ፡ ነው ። ዝራር ፡ አዝራር ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ዘረር** ፤ የቅጠል ፡ ስም ፤ የሥንቅ ፡ ቅጠል ፡ የ ወፌ ፡ የሚባል ፤ የስናፍጭ ፡ ዐይነት ። የወፍ ፡ ዘረር ፡ እን ዲሉ ።

**ዘራት ፤ ዝራት ፤ (ዐረ ፡ ዙራፈት)** ፤ ቀጭኔ ፤ ኽራት ፡ ቀጭን ፡ ነብርማ ፡ የበረሓ ፡ ግመል ። የበረሓ ፡ ጕሽ ፤ መልኩ ፡ የበሬ ፡ ጠባዩ ፡ ያውሬ ። **አራጋ ፡ ወዘራት** ፡ (ዘዳ፲፬ ፡ ፭) ።



ዘራት ።

**ዛቲ ፤ (ዛ ፡ ቲ ። ዝ ፡ ንቱ)** ፤ የቅርብ ፡ ዐጸፋና ፡ ቅጽል ፡ በሴት ፡ እንቀጽ ፤ ቲ ፡ አርቲክል ፡ ነው ። ይች ፡ ይህች ፤ ይችው ፡ ይችይቱ ፡ ይችኛይቱ ። ዝንና ፡ ዛን ፡ ዝን ቱን ፡ እይ ። **እስመ ፡ ዛቲ ፡ ትትወለድ ፡ እምእንታክ ቲ ። ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ምዕራፍየ ፡ ለዓለም** ፤ ዐጸፋ ፡ (ማር ፡ ይሖ፰ ። መዝ ፡ ፻፴፩) ። **ዛቲ ፡ ትውልድ ፡ ተኀሥ ፡ ሎቱ ። ዛቲ ፡ ባሕር ፡ ዐባይ ፡ ወረሓብ** ፡ (መዝ ፡ ፳፫ ። ፻፫) ።

**ዛተ** ፤ ይችን ፡ ይችይቱን ፤ ይችኛይቱን ። **ዛተ ፡ ሀገረ ። ዛተ ፡ ሌሊተ** ፡ (ሊጦ ። ሩትይ ፡ ፲፫) ።

**ዘትር ፤ (ሠትር ፤ ሠተረ)** ፤ በቁሙ ፤ ቀይና ፡ ሠጥቆ ፡ ሠንጥቆ ፡ በኀይል ፡ የሚወጣ ፡ ወዝ ፤ ፈሳሽ ፡ ምንጭ ፤ ወለላ ፡ ወተት ፤ ደም ፡ እንባ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ፤ ሠተረን ፡ እይ ። **ዘአንቅዐ ፡ ዘትረ ፡ ማይ ፡ እመንበከ ፡ አድግ ፡ ለሶምሶን ። ዘትረ ፡ መዓር ። ዘትረ ፡ ሐሊብ** ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ፳ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፳፮ ። አርጋ ፡ ፱) ። ምስጢሩ ፡ ፈሳሽነትን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ጥፍጥንትንም ፡ ያሳያል ፤ ስለዚህ ፡ በማር ፡ በስኳር ፡ በወተት ፡ በንቀኣል ፡ ለሚ ሠራ ፡ ምግብ ፡ ይነገራል ።

**ዘጲ ፤ (ጽር ፡ ኢቆጲ ፤ ኢቆፖስ ፤ ሄቤ ኖስ)** ፤ በቁሙ ፤ አብኖስ ፡ ጥቊር ፡ ጠቋራ ፡ ክስልማ ፡ ዕንጨት ፤ ጥቍረቱ ፡ ኹል ፡ ጥላት ፡ ሱዳን ፡ አሰሱድ ፡ አ ዝሙድ ፡ የሚመስል ፤ በኢትዮጵስ ፡ አገር ፡ በሱዳን ፡ በ ኖባ ፡ ወዲያ ፡ ማይደም ፡ በህንድ ፡ የሚገኝ ፤ የአብኖስን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። **ዕፀ ፡ ጸሊም ፡ ዘይብልዎ ፡ ዘጲ ፤ በግእዝ** ፡ (እዋል) ። በዘጲ ፡ ፈንታ ፡ ዘጲ ፡ አዘጲ ፡ ይላል ፤ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

# ሐ

**ሐ** ፤ ፰ኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአ በገደ ፡ ስሙ ፡ ሐውት ፤ ሐይት ፤ ቍጥሩ ፡ ስምንት ፤ አ ኃዝ ፡ ሲኾን ፡ ስምንት ፡ ቱ ፡ ይባላል ። ዕብራውያን ፡ ግን ፡ ስምንትኘ ፡ መደብ ፡ አድርገው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነቍጣ ፡ እየጨመሩ ፡ ስምንት ፡ እልፍ ፡ ይሉታል ። የሦስቱ ፡ ሀሐን ፡ ድምጥ ፡ እንደ ፡ መልካቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሲኾን ፡ ከስ ላማ ፡ ወዲህ ፡ ባለመለየት ፡ ይነገራል ፤ ይኸውም ፡ በቸል ታና ፡ በስንፍና ፡ በትምርት ፡ ሕጸጽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚ ገባው ፡ ኹኖ ፡ አይደለም ። ጥሩ ፡ መምህርና ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ ከሌለ ፡ የፊደልን ፡ ጠባይ ፡ በጥፈትና ፡ ባጠራር ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ አይቻልምና ።

**ሐብአ**፤—ዐባ፡ ሰወረ፤—ኀቢእ፡ ኀብአ።

**ሐበበ**፤—ሰደበ፤—ሀቢብ፡ ሀበ፡ ሀበበ።

**ሐቢብ**፤ ቦት፤ (ሐበ፤ ሐበበ፡ የሐብብ፡ ይሕብብ። ዐረ፡ ሐበ)፤ መውደድ፡ ማፍቀር፤ በፍቅር፡ መቃጠል። መጽሐፍ፡ ግን፡ በሐበበ፡ ፈንታ፡ ተሐበ፡ ተሐበበ፡ ይላል፡ አያሰኝም። እለ፡ ይትሐበቡ፡ በተባዕት፤ (ቀሌ። ፩ቆሮ፡ ፮፡ ፱)። ማፍራት፤ ፍሬ፡ መያዝ። ሐንበበን፡ እይ።

**ተሐበ**፤ **ተሐበበ**፤ ተወደደ፤ ውድ፡ ኾነ።

**ሐቢብ**፤ (ዐረ፡ እልሐቢብ)፤ ወዳጅ፡ ፍቁር።

**መሕቡብ**፤ (ዐረ)፤ ዝኒ፡ ከማሁ፤ የተወደደ፡ ውድ፤ መውደድ፡ መወደድ፡ ያለው። መሕቡብ፡ ኢጲስቆጶስ፡ ዘመንበግ፤ (አቡሻ፡ ፶፯)።

**ሐበበ**፤—ጠመቀ፡ ረገጠ፤—ኀቢብ፡ ኀበበ።

**ሐበወ**፤—ወጨፈ፤—ሀቢው፡ ሀበወ።

**ሐበዘ**፤—ጋገረ፤—ኀቢዝ፡ ኀበዘ።

**ሐቢጥ**፤ ጦት፤ (ሐብጠ፤ ሐበጠ፡ የሐብጥ፡ ይሕብጥ። ዐረ፡ ሐቢጠ)፤ ማበጥ፤ መነፋት፡ (ጥቀ) መቀብጠጥ፤ መቍሰል፡ ከበትር፡ ከደዌ፡ የተነሣ። እስከ፡ የሐብጥ፡ ሥጋሁ። ተፀምደ፡ በቀዊም፡ እስከ፡ ሐብጠ፡ እገሪሁ። ሰእመ፡ ሐበጠ፡ እባሉ፤ ሰዘሐበጠ፡ እስኪቱ፤ (ቄድር። ስንክ፡ ታኅ፲፱። ጽጌ። መ፡ ፈ)። በሐበጠ፡ ፈንታ፡ ተሐበጠ፡ ይላል፤ አያሰኝም። ሰ፡ እለ፡ ይትሐበጡ፡ በትዕቢት፤ (ተረ፡ ቄር፡ ፲፱)።

**ሐባጢ**፤ **ሕቡጥ**፤ ያበጠ፡ የተነፋ፤ ቅብጥጥ፡ ያለ። በሕቡጥ፡ ፈንታ፡ ቅቡጥ፡ ይላል፤ የጣፊ፡ ስሕተት፡ ነው። ዘይከውን፤ ጽንፈ፡ ዐይኑ፡ ቀይሐ፡ ወቅቡጠ፤ (መ፡ ፈ)።

**ሕብጠት**፤ በቁሙ፡ ዕብጠት፤ ማበጥ፡ እስተባበጥ፡ (ፈ፡ መ፡ ፫፡ ፫)።

**ሕበጥ**፤ (ጣት)፤ ዕበጥ፡ ዕባጭ፡ ቍስል፡ መግል፡ የያዘ፡ ያረገዘ። ትዕቢት፡ ኵራት። እዝልፎ፡ ስካር፡ ያመጽእ፡ ኮብስ፡ ወፈፀንተ፡ ወቍስለ፡ እማዑት፤ ወሕበጠ፡ ናላ። ቍስል፡ ወሕበጥ። ተፈወሱ፡ ዝኩ፡ ሕበጣ፤ (ፍ፡ ነ፡ ፶። ፈ፡ መ፡ ፳፡ ፱። ተረ፡ ቄር)።

**አሕበጠ**፤ (ዕብ፡ ሐባጥ፤ ወቃ፡ አረገፈ፤ የፍሬ)፤ አሳበጠ፡ ነፋ፤ አቈሰለ፤ በበትር።

**ሐብይ**፤ ዮት፤ (ሐበየ፡ የሐቢ፡ ይሐቢ። ዐረ፡ ሐባ)፤ መጠበቅ፤ መክልከል። መሸም፡ መወከል። ማዋስ፤ ዋስ፡ መድን፡ ቀብድ፡ የሚበቃ፡ ምግብ፡ መስጠት፤ ዕልፍ፡ ትርፍ፡ የሌለው፡ የሚገባ፡ ነገር፡ ሰላምታ፡ ግብር፡ ማቅረብ። መጽሐፍ፡ ግን፡ በሐበየ፡ ፈንታ፡ አሕበየ፡ ተሐበየ፡ ይላል፤ አያሰኝም። ወአሕበዩ፡ ሎቱ፡ በተአዝዞ። ክርስቶስ፡ ዘዴበ፡ ኪኑ ቤል፡ ይነብር፡ ወዘሎ፡ ዓለመ፡ ዘይትሐበይ፤ (ዮሴፍ። መዋሥ)።

**ሐባዪ**፤ (ዪት፡ ይያን፡ ያት፤ በይት)፤ ጠባቂ፡ ከልካይ፤ ሺሚ፡ ወካይ፤ አዋሽ፡ ዋስ፡ መድን፡ ሰጭ።

**ሐቢ**፤ (ቢት፡ ብያን፡ ያት፤ በይት)፤ ዋስ፡ መድን፡ ተያዥ። ጠባቂ፡ ሹም፡ አለቃ፡ ወኪል፡ ምስለኔ፡ እንደ፡ ራሱ። ሐቤ፡ ምእት። እሉ፡ እሙንቱ፡ ሐበይቶሙ፡ ለክልኤቱ፡ ምእት፡ መላእክት። ይኩኑክሙ፡ ሐበይተ፡ ወመሳፍንተ፤ (ማቴ፳፡ ፳። ሔኖ፳፡ ፳። ዘዳ፳፡ ፲፭)።

**አሕበየ**፤ አስጠበቀ፤ አሾመ፡ አስዋሰ፡ አሰጠ፡ አስገበረ።

**ተሐበየ**፤ ተሾመ፤ ተወከለ። ተዋሰ፤ ዋስ፡ መድን፡ ተያዥ፡ አበ፡ ልጅ፡ ኾነ። ገብርከ፡ ተሐበዮ፡ ለዝ፡ ሕፃን፡ እምኀበ፡ አቡሁ። ኢትትሐበዮ፡ ለዘይጸንዐከ። መኑ፡ ይትሐበዮ፡ ለበራቂ። ተሐበይኒ፡ ከመ፡ ኢይወፅእ፡ እኩይ፡ እምኔየ። ዘሂ፡ ተሐበየ፡ ወዘሂ፡ ተሐበይዎ፡ ኢይትዋሰቡ፤ (ዘፍ፵፬፡ ፴፪። ሲራ፰፡ ፲፫። ፴፯፡ ፴፰። ክፋ፡ ፴፮። ፍ፡ ነ፡ ፳፱)።

—፤ ተስፋ፡ ሰጠ፡ አማኸተ፤ አይዞኽ፡ አለ። ምስጢሩ፡ ከዚያው፡ ከመዋስ፡ ይገባል። ተሐበየ፡ ሎቱ፡ ብዙኀ፡ ንዋየ። ተሐበየ፡ ሎቱ፡ ከመ፡ የናናውያን፡ ኢይትመየጡ፡ ዳግመ፤ (ዮሴፍ)።

**ተሐባዪ**፤ የሚዋስ፤ የዕዳና፡ የክርስትና፡ የምንኵስና፡ ዋስ፡ የሚኾን። እስመ፡ ተሐባይያን፡ እለ፡ ተወክፉነ፡ በጥምቀት፡ ናሁ፡ ኮኑነ፡ አበወ፡ ወእማተ። ተሐበይት፤ (ፈ፡ መ፡ ፳። ፍ፡ ነ፡ ፳፱፡ ፪)።

**ሕቡይ**፤ (ያን፡ ያት፡ ቢት)፤ የተዋሰ፤ የውስት፡ የተውሶ። ወዝንቱኒ፡ ሕቡይ፤ (፴ነገ፡ ፯፡ ፳)።

**ሕቢት**፤ **ሕብየት**፤ መዋስ፡ መሾም፤ ዋስትና፡ ሹመት። ኢተሀብ፡ ርእሰከ፡ ለሕቢት። ከመ፡ ዘይትሐበይ፡ ሕቢተ፡ ለዐርኩ፤ (ሲራ፳፱፡ ፳፯። ምሳ፲፯፡ ፲፰)።

—፤ ሰሞን፤ ተራ፡ ፈረቃ፤ የሹመት፡ የማዕርግ፡ ሥራ። ወከመ፡ ዝ፡ ትገብር፡ ሎሙ፡ ለሌዋውያን፡ በበ፡ ሕቢቶሙ፤ (ዘኁ፰፡ ፳፮። ፳፫፡ ፴፩—፴፫። ፮፡ ፬። ፳፡ ፳፯)።

**ትሕቢት**፤ ዋስነት፡ ዋስትና፤ ዋስ፡ መኾን። ኢይባእ፡ ቀሳውስት፡ ውስተ፡ ትሕቢት፤ (ቀኖ፡ ኒቅ ፳፫)። ተሐበየ፤ አስተሐበየ፡ ብሎ፡ ተዋዋሰ፡ አዋዋሰ ያሰኛል፤ ተደራራጊና፡ አደራራጊ፡ አንቀጽ።

**ሐቢል**፤ ሎት፤ (ሐብለ፤ ሐበለ፡ የሐብል፡ ይሕ(ብ)በል። ዕብ፡ ሐባል። ዐረ፡ ሐበለ)፤ ማበል፡ መዋሸት፤ ፈጥሮ፡ መናገር፤ ማታ

ለል ፡ መሸነገል ፤ ማሳት ፡ መጐዳት ። መማመድ ፡ መፍተል ፤ በገመድ ፡ ማሰር ፤ መሳብ ፡ መጐተት ። ቀላድ ፡ መጣል ፤ በገመድ ፡ መስፈር ፡ መለካት ፡ መክፈል ፤ የምድር ። ሐንበለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ስረጅ ፡ ነው ። ሕከ ፡ ሠናይ ፡ ለመኳንንት ፡ ጽድቅ ፡ ሐቢል ። የሐብሉ ፡ አዕርክቲሆሙ ። ብእሲ ፡ እኩይ ፡ የሐብል ፡ አዕርክተ ፤ (ምሳ፲፷ ፡ ፳፯ ። ፳፯ ፡ ፲፱ ። ፲፯ ፡ ፳፱) ።

**ሐባሊ ፤(ሊት ፡ ልያን ፡ ያት)** ፤ የሚያብል ፤ ዐባይ ፡ ዋሾ ። ሐባሊ ፡ ሶበ ፡ ተአምኖ ፡ ይትኋሐሰወከ ። ሐባሊ ፡ ለይትነፃኅ ፤ (ፈላስ ፡ ገ፴፯ ። ቅዳ) ። ገማጅ ፡ አሳሪ ፤ ለፋፊ ።

**አሕበለ** ፤ አሳበለ ፡ አስገመደ ፤ ቀላድ ፡ አስጣለ ፤ አሳሰረ ።

**ተሐብለ** ፤ ተዋሸ ፡ ታበለ ፡ ተገመደ ፡ ተፈተለ ፤ ታሰረ ፡ ተሰፈረ ።

**ሕቡል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ብልት)** ፤ ያበለ ፡ የታበለ ። ክፉ ፡ መጥፎ ፤ ቀጣፊ ፡ ብስፉ ፡ ዋዘኛ ፡ ዋሾ ። ሕቡል ፡ ንጉሥ ፡ መኰንን ፡ ፀመፃ ፤ ሕቡል ፡ ምክሩ ። ወሕቡላንሰ ። ነፍሳተ ፡ ሕቡላን ። ሕቡል ፡ እንዘ ፡ ይትቀሠፍ ፤ (ኪዳ ። ምሳ፲፱ ፡ ፳፬ ። ፲፫ ፡ ፱ ። ፲፱ ፡ ፳፭) ።

**ሕብል ፤(ላት)** ፤ ዕብለት ፡ ውሸት ፡ ሐሰት ፡ ጕሕሉት ፤ ተንኰል ፡ ክፋት ፤ አሉታ ፡ ክዳት ። ዘይዘርዕ ፡ ሕብለ ፡ የአርር ፡ እከየ ። ወበክመ ፡ ብዝኆ ፡ ሕብሎሙ ፡ ስደዶሙ ። ልሳንከ ፡ ፀፈራ ፡ ለሕብል ። መጽአ ፡ እኁከ ፡ በሕብል ። ከመ ፡ የአኀዝዎ ፡ በሕብል ፤ (ምሳ ፳፪ ፡ ፰ ። መዝ ፡ ፭ ። ፶፱ ። ኩፋ ፡ ፳፯ ። ማቴ፳፯ ፡ ፬) ።

**ሐብል ፤(ብ ፡ አሕባል ፤ ላት ። ዕብ ፡ ሔቤል ። ሱር ፡ ሐብላ ። ዐረ ፡ ሐብል)** ፤ ፀቀሙ ፤ ገመድ ፡ ቀላድ ፡ ከቃጫ ፡ ከናጫ ፤ ከጓሳ ፡ ከገርማ ፤ ከጭራ ፡ ከጭረት ፡ ከቴርበት ፡ ከኽርማት ፡ ከእንስት ፡ ከልጥ ፡ ከክታን ፡ ከጥጥ ፡ ከፀምር ፡ ከሐር ፤ ከሌላውም ፡ ኹሉ ፡ ተፈትሎ ፡ ተክሮ ፡ የሚሠራ ፤ ጠፍር ፤ ሰንሰለት ፤ ወጥመድ ። ሐብል ፡ ነዋኅ ። ሐብለ ፡ ዐኄ ። ሐብለ ፡ አነዳ ። አሕባለ ፡ ሥርው ፡ ደቃቅ ። አሕባለ ፡ ቢሶንስ ። አሕባለ ፡ ጠፈር ። ኅቡእ ፡ ደበ ፡ ምድር ፡ ሐብሉ ፤ (ኢሳ፴ ፡ ፲፰ ። ሕዝ፵ ፡ ፫ ። ሰንከ ፡ ጥቅ፲፯ ። መቃ ፡ ገ፳ ። አስቴ፩ ፡ ፯ ። ገድ ፡ ላሊ ። ኢዮ፲፰ ፡ ፲) ።

—፤ ርስት ፡ ቀላድ ፡ ቦታ ፡ መሬት ፡ የርስት ፡ የመሬት ፡ ክፍል ፤ ወገን ። ወድቀ ፡ ሐብሎን ። ትኩንክሙ ፡ ሐብለ ፡ ርስትክሙ ። ወእስራኤልኒ ፡ ሐብለ ፡ ርስቱ ፤ (ኢያ፲፯ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፻፬ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፱) ።

**ሐብለት ፤(ታት)** ፤ እንጥልጥል ፡ የዝሮ ፡ ያንገት ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ ጕትቻ ፡ ድሪ ፤ የወርቅ ፡ የብር ፡ ሰንሰለት ። ሕልቀታተ ፡ ወሐብለታተ ፤ (ዘፀ፴፭ ፡ ፳፪) ። በሐብለት ፡ ፈንታ ፡ ሐብላት ፡ ይላል ፤ የሐብል ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ (መሳ፰ ፡ ፳፯ ። ሺጢሞ ፡ ፪ ፡ ፱) ።

**ሐብለየ ፤ (ተቀ ፡ ግ)** ፤ ከዳ ፡ ተተንኰለ ፡ ክፉ ፡ ዐሰበ ። ተናገሩ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በእኩይ ፡ ወሐብለይዎሙ ። ሐብለይዎ ፡ ወገብሩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ምክረ ። ከመ ፡ የሐብልይዎሙ ፡ ለአግብርቲሁ ፤ (ኩፋ ፡ ፴ ። ፴፬ ። መዝ ፡ ፻፬) ።

—፤ በዘበዘ ፤ ዘረፈ ፡ ገፈፈ ፤ ቀማ ፡ ወሰደ ፤ በተንኰል ፡ በኀይል ፤ በግድ ፡ በገመድ ። የሐብልዮ ፡ ነኪር ፡ ዘሎ ፡ ተግባሮ ። ይበርብርዎሙ ፡ ወየሐብልይዎሙ ። ወሐብለይዎሙ ፡ ለግብጽ ፤ (መዝ ፡ ፻፰ ። ኢሳ፳ ፡ ፯ ። ዘፀ፫ ፡ ፳፪ ። ፲፪ ፡ ፴፮) ። በሐብለየ ፡ ፈንታ ፡ ተሐብለየ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እነሥት ፡ ጸቄዋ ፡ ወይትሐበለይዎ ። ወእለሰ ፡ ይነብሩ ፡ ቤጤሌዋ ፡ ወረዱ ፡ ውስተ ፡ ትዕይንቶሙ ፡ ለአሶር ፡ ወተሐብለይዎሙ ፡ ወብዕሉ ፡ ፈድፋደ ፤ (ኢሳ፳ ፡ ፳ ። ዮዲ፲፭ ፡ ፯) ።

**ተሐብለየ** ፤ ተበዘበዘ ፡ ተዘረፈ ፡ ተቀማ ፤ ተማረከ ። ገንዘቡንም ፡ ባለገንዘቡንም ፡ ያሳያል ።

**ተሓብለየ** ፤ ተበዛበዘ ፡ ተዛረፈ ፤ ተሻማ ፡ ተቃማ ፡ ተናጠቀ ።

**ሕብሉይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሊት)** ፡ የተዘረፈ ፡ የተበዘበዘ ፡ ብዝብዝ ። የተዘረፈ ።

**ሕብልያ** ፤ ብዝበዛ ፡ ዘረፋ ፤ ቅሚያ ፡ ምርኮ ። እሬስዮሙ ፡ ሕብልያ ፡ ወበርበረ ። ወይከውኑ ፡ ሕብልያ ፡ ለእለ ፡ ይትቀነዩ ፡ ሎሙ ። አንስትያን ፡ ወደቂቅ ፡ ይከውኑ ፡ ሕብልያ ፤ (ዮዲ፬ ፡ ፯ ። ዘኍ፲፬ ፡ ፫ ። ዘኍ፲፬ ፡ ፫ ፡ ፴፩) ። ፍግ ፡ ፋንድያ ፡ ዐዛባ ፤ መሬት ፡ የሚያሠባ ። ይከውኑ ፡ ሕብልያ ፡ ውስተ ፡ ገጸ ፡ ምድር ፤ (ኤር፰ ፡ ፪) ።

**ሐብለ ፤—ደፈረ ፤—ኀብሎ ፡ ኀበለ ።**

**ሐብቀቀ ፤ ሐብቄቄ ፤(አብከከ ፤ በኪክ ፡ በከ)** ፤ አሳደፈ ፡ አረከሰ ፤ አበላሸ ፡ ከንቱ ፡ አደረገ ፤ በጠበጠ ፡ አደፈረሰ ፡ ቀላቀለ ፡ ደባለቀ ፡ አወከ ፡ አሸበረ ።

**ተሐብቀቀ** ፤ አደፈ ፡ ረከሰ ፡ ተበላሸ ፡ ደፈረሰ ፤ ታወከ ፡ ተሸበረ ። እለ ፡ ይትሐበቀቁ ፡ ውስተ ፡ ብዙኅ ፡ ትካዝ ። ይትሀወኩ ፡ አሕዛብ ፡ ወይትሐበቀቁ ፡ ሕዝብ ፤ (ሄርማ ። ሉቱ ፡ ዕገዘ፪ ፡ ፫) ።

**ሕብቁቅ ፤(ቃን ፡ ቃት ፤ ቅቅት)** ፤ ያደፈ ፡ የረከሰ ፤ እድፋም ፡ ነውረኛ ። ሕብቁቃን ፡ ወርኩሳን ። ሕብቁቃን ፡ ዲያቆናት ። ሕብቅቅት ፤ (፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ። ሄርማ) ።

**ሕብቃቄ** ፤ ማደፍ ፡ እድፍ ፡ ርኩስ ፡ ነውር ፡ ገመና ። ዘእንበለ ፡ ሕብቃቄ ። ንዘህላል ፡ ወፍርዛዜ ፤ ሕብቃቄ ፡ ወዘውዕ ፤ (ያዕ፩ ፡ ፳፯ ። አንቀ ፡ ንስ) ።

**ሐብረ ፤—ዐበረ ፤—ኀቢር ፡ ኀብረ ።**

**ሓብሮ ፤ ሮት ፤ (ሓበረ ፡ የሓብር ፡ የሓብር)** ፤ ማቅለም ፤ ቀለም ፡ ማግባት ፡ መንከር ፤ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ ቀለም ፡ መሸለም ፡ ማስጌጥ ፡ ማንቈጥቈጥ ፤ መልክ ፡ ማውጣት ፤ ሥዕል ፡ መሣል ፡ ሐረግ ፡ መጣል ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ቤቱ ፡ የባረከ ፡ ሲኾን ፡ ኈበረ ፡ ብለው ፡ በዋለወ ፡ ቤት ፡ በጎርም ፡ ይገሉታል ። ከጥፈውና ፡ ከቅጽሉ ፡ በቀር ፡ እንቀጹ ፡ አይገኝም ።

**ሓባሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤ የሚያቀልም ፤ የሚያልል ፤ ቀለም ፡ አግቢ ።

**አሓበረ ፤ አስተሓበረ** ፤ አስቀለመ ፡ አስነከረ ፤ ቀለም ፡ አስገባ ፡ አስቀባ ፤ አስጌጠ ።

**ተሓበረ** ፤ ቀለም ፡ ገባ ፡ ተነከረ ፤ ተጌጠ ፡ ተሸለመ ።

**ሐቡር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ብርት) ፤ ቀለም ፡ የገባ ፡ የታለለ ፤ የተሸለመ ፡ የተጌጠ ፤ ቀይ ፡ ጥቍር ፡ ዝንጕርጕር ። በአልባሰ ፡ ወርቅ ፡ ፁጽፍት ፡ ወሐብርት ። አልባሰ ፡ ቅዳሴ ፡ ይኩና ፡ ፀዓድወ ፡ ወአኮ ፡ ሐቡራተ ። ፁጽፍሃ ፡ ቃንሶሱ ፡ ወቃስተርኢ ፡ ሐብርሃ ፡ (መዝ ፡ ፵፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፪ ። ቅኔ) ።

**ሐብርቃት** ፡ (የሐብርት ፡ ብዝ) ፤ ሽልምልሞች ፤ ዝንጕርጕሮች ፡ ባለብዙ ፡ ሕብሮች ። ሀሎ ፡ ዴቤሁ ፡ ልብስ ፡ ጥቁብ ፤ ወቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ሐብርቃት ፡ ፤ ፊልክ ፡ ፻፴፯) ።

**ሕብር** ፤ (ብ ፡ ሕበር ፤ ሕብራት ። ዐረ ፡ ሒብር) ፤ በቁሙ ፤ ቀለም ፡ ስባቅ ፡ ፀለላ ፤ መልክ ፡ ዐይነት ፤ የቀለም ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ ያለው ። በዓለ ፡ ሕብር ። ጥምፀተ ፡ ሕብር ። ጸፍጸፍ ፡ ዘዘ ፡ ዚኣሁ ፡ ሕብሩ ። ጥበብ ፡ እንተ ፡ ብዙኅ ፡ ሕበሪሃ ። ሕብራት ፡ ቀይሓት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫ ። መሳ፳ ፡ ፴ ። አስቴ፳ ፡ ፮ ። ኤፌ፫ ፡ ፲ ። ፊላስ ፡ ፻፲፮) ።

**ሕብረ ፡ ክብድ** ፤ ጕበትማ ፤ የጥቍር ፡ ቀይ ፤ ደባባ ፡ ደባሳ ፡ (ዘፀ፴፭ ፡ ፳፭ ። ዘኍ፬ ፡ ፯ ፡ ፲፫) ።

**ሕብረ ፡ ሚራ** ፤ ስንጠረዥ ፤ የስንጠረዥ ፡ ዐይነት ፡ ፊደምታ ፤ መፈወቻቸው ፡ ቀለም ፡ የተቀባ ፡ እንደ ፡ ሥዕል ፡ እንዳሻንጕሊት ፡ ያለ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፲፪) ።

**ሕብረ ፡ ሰማይ** ፤ (ዐረ ፡ ሐጀር ፡ ጀሃነም) ፤ በቁሙ ፤ ሰማይ ፡ የሚመስል ፤ የኵሕል ፡ ወገን ፡ ዶንጊያ ፡ ቀለም ፡ ሰቍስል ፡ ሰቂጥኝ ፡ የሚበጅ ፡ እንደ ፡ ጎት ፡ እንደ ፡ በርበሬ ፡ የሚፈጅ ፡ የሚተኰስ ፡ ሰብልቦ ፡ አንገብግቦ ፡ የሚፈውስ ። ለዐይን ፡ ማዝም ፡ ይበጃል ፡ እዮሱ ፡ አሳርረው ፡ ከኵል ፡ ፈጨምረው ፡ ይኳሉታል ። ግእዝ ፡ የማያውቅ ፡ ባላገር ፡ ግን ፡ በሕብር ፡ ፈንታ ፡ ክብር ፡ ይላል ። (መኖ ፤ ባሷ ፡ መንኖ ፡ ጥሷት ፡ ስለ ፡ ኬደ ፤ ንዋዣጊት) ፤ እኔማ ፡ ሳልሰማ ፡ ቂጥኝ ፡ አውጥተው ፤ ክብረ ፡ ሰማይ ፡ ብለው ፡ ኬዱ ፡ አቶ ፡ ይግዛው ። (ተሰጥዎ) ፤ እሳት ፡ ነው ፡ እሳት ፡ ነው ፡ ክብረ ፡ ሰማይም ፡ ስማዕት ፡ የሚያቃጥል ፡ እንደ ፡ ቂጥኛም ።

**ሐብረተ** ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ ወለወለ ፡ ሰነገለ ፡ ሰደሰ ፡ ኰላ ፤ የማዕደናት ። ወርቅ ፡ እመ ፡ ኢሐብረትዎ ፡ ኢይበርህ ። ጽህርት ፡ እንተ ፡ ኢሐብረትዋ ፡ ዘሕላ ። ሰመኑ ፡ ዘቲ ፡ ሰይፍ ፡ ዘየሐበርትዋ ፡ (መል ፡ ኤር፳፫ ። ሕዝ፳፬ ፡ ፮ ። ፊላስ) ።

**ሐብራቲ** ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤ የሚወለውል ፡ ወልዋይ ፡ ሰንጋይ ።

**ተሐብረተ** ፤ ተወለወለ ፡ ተሰነገለ ፤ ታደሰ ፡ ተኰላ ፡ (ሕዝ፳፩ ፡ ፱) ።

**ሕብሩት** ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ርት) ፤ የተወለወለ ፡ የተሰነገለ ፤ የታደሰ ፡ የተኰላ ፡ ጥሩ ። ሕብሩት ፡ እምዛሕለ ፡ ጊጋይ ፡ (ደራሲ) ።

**ሐበሰ** ፤ (ዐረብ) ፤ ፀበሰ ፡ አጋዘ ፤ አሰረ ፡ ከወህኒ ፡ አገባ ።

**ተሐብሰ** ፤ ታበሰ ፡ ታሰረ ፤ ከግዞት ፡ ቤት ፡ ገባ ።

**ሕቡስ** ፤ (ዐረ ፡ መሕቡስ) ፤ የታበሰ ፡ ሐብስ ፡ የገባ ። ቂውው ፡ ወሕቡስ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ሐብስ** ፤ በቁሙ ፤ የግዞት ፡ ቤት ፡ ወህኒ ። ሐብስ ፡ ዘይቤ ፡ ቤተ ፡ ጽልመት ፡ (ጥሬ ፡ ሰዋ) ።

**ሐግጎ** ፤ ጎት ፤ (ሐገገ ፡ ይሔግግ ፡ የሐግግ ። ዕብ ፡ ሐቃቅ ። ዐረ ፡ ሐቀ) ፤ ማገግ ፡ መደንገግ ፤ መወሰን ፡ መቍረጥ ፤ መጣፍ ፡ ማወጅ ። የሥርዐት ፡ የትእዛዝ ፡ የፍርድ ፡ ደንዛዝ ፤ የዘመን ፡ የጊዜ ፤ ለዋጋም ፡ ይኾናል ። ሐገና ፡ ዐ(አ)ገና ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ሕግ ፡ ዘሐገገ ፡ ለክሙ ፡ እግዚ ። አሕዛብኒ ፡ የሐግጉ ፡ ሎሙ ፡ ሕገ ። ሙሴ ፡ ሐገገ ፡ ሎሙ ፡ ሕገ ፡ (ዘዐ፳፱ ፡ ፰ ። ሮሜ፪ ፡ ፲፬ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ፪) ።

**ሐጋጊ** ፤ (ጊት ፡ ግያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ የሚያግግ ፤ ሕግ ፡ ሠሪ ፡ ወሳኝ ፡ አቋሚ ፡ በቃል ፡ በመጽሐፍ ። እስመ ፡ ሐጋጊ ፡ ብሉይ ፡ ወሐዲስ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ። እንዘ ፡ ሐጋጊ ፡ ሕግ ፡ በመለኮቱ ፡ ናሁ ፡ ኮነ ፡ መትሕተ ፡ ሕግ ። ሐጋጊ ፡ አጽዋም ፡ እምስቴ ፡ (አፈ ፡ ድ፴፱ ። ሃይ ፡ አበ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፱) ።

**ተሐገገ** ፤ ታገገ ፡ ተወሰነ ፤ ተጣፈ ። ዝንቱ ፡ ሕግ ፡ ዘተሐገገ ፡ በዛቲ ፡ መጽሐፍ ። ዕድሜ ፡ ዘተሐገገ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፳) ።

**ሕጉግ** ፤ (ጋን ፡ ጋት ፡ ግግት) ፤ የታገገ ፡ የተደነገገ ፤ ውሱን ፡ ሥሩዕ ፡ ጽሑፍ ።

**ሕግ** ፤ (ብ ፡ ሕገግ ፤ ጋት) ፤ በቁሙ ፡ የተወሰነ ፡ የተጣፈ ፡ ሥርዐት ፤ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ ደገር ፡ ልማድ ፡ ለማድረግ ፡ የሚያገ ፡ ከማድረግ ፡ የሚከለክል ፤ አድርጉ ፡ አታድርጉ ፡ የሚል ። በሠርቱ ፡ ቃላት ፡ ኦሪት ፡ ስድስቱ ፡ ቃላት ፡ ወንጌል ፡ (ዘዳ፳ ፡ ፳ ። ዘፀ፳ ፡ ፳—፲፯ ። ዘሌ፲፱ ፡ ፲፰ ። ማቴ፳ ፡ ፳፭—፵፰) ። ከነዚያውም ፡ ሕግ ፡ የሚባለው ፡ አታድርግ ፡ አታድርግ ፡ የሚለው ፡ ነው ፡ አድርግ ፡ የሚለው ፡ ግን ፡ ትእዛዝ ፡ ይባላል ። ሰሌዳተ ፡ እብን ፡ ዘሕግ ፡ ወዘትእዛዝ ። ሕገገ ፡ ኦሪት ። ክልኤቱ ፡ ሕገጋት ። ዘየአምር ፡ ሕገጋተ ፡ ምኑት ፡ (ዘፀ፳፬ ፡ ፲፪ ። ሮሜ፪ ፡ ፳፭ ። ፈ ፡ መ ፡ ፪ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**ሕጋዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ የሕግ ፡ ባለሕግ ፤ ሕግ ፡ የሚጠብቅ ፡ በሕግ ፡ የተጋባ ። ሰብሳብ ፡ ሕጋዊ ። ብእሲት ፡ ሕጋዊት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፳) ።

**ሕገ** ፤ (ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አግባብ) ፤ እንደ ። ሕገ ፡ ጾመ ፡ ሙሴ ፡ ተመጣዌ ፡ ሕግ ፡ ጾመ ፡ ኢየ

ቡስኒ ፡ ሠራዒ ፡ ሕግ ፡ (ዘሬፈ) ። ኢትእምሩኑ ፡ ሕገ ፡ ንነግረክሙ ፤ እንድንነግራችኹ ። ደቂቅ ፡ ቢኾን ፡ ሕገ ፡ ሰብእ ፡ እነብብ ። ሕገ ፡ ሰብእ ፡ እብለክሙ ። ሕገ ፡ ሰብእ ፡ አናሕሲ ፡ ሰነ ፡ እያለ ፡ በብቱን ፡ ይገባል ። (ሮሜ፫ ፡ ፳፯ ። ፯ ፡ ፲፪ ። ሲኖን) ። (ዕርጀ፱ ፡ ቍ፻፳፩) ።

**ሕግ ፡ ጠባይዕ** ፤ ባሕርያዊ ፡ ሕግ ፤ ፍጡር ፡ ኹሉ ፡ በባሕርዩ ፡ ዐውቆ ፡ የሚሠራው ፤ መውሰድ ፡ መዋሰድ ፤ በየጥቂቱ ፡ ማደግ ፤ መራብ ፡ መጠማት ፡ ምግብ ፡ መሻት ፤ የመሰሰው ፡ ኹሉ ፡ (አፈ ፡ ድጓ፲ ። ሮሜ፪ ፡ ፲፭) ።

**ሕግ ፡ ሥጋ** ፤ ልማድ ፡ ፈቃድ ፤ ግዳጅ ። ይፌጽም ፡ ሕገ ፡ ሥጋ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፲፱) ።

**ሐግ** ፤ (ዕብራ) ፤ በዓል ፤ የበዓል ፡ ቀን ። ምንተ ፡ ይገብሩ ፡ በዕለተ ፡ ሐጎሙ ፡ (ሆሴ፱ ፡ ፭) ።

**ሐጌ** ፤ (ዕብ ፡ ሐጋይ) ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ነቢይ ፡ ከሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ አንዱ ። በዓላዊ ፡ ዘተወልደ ፡ በዕለተ ፡ በዓል ፡ ማለት ፡ ነው ። በእደ ፡ ሐጌ ፡ ነቢይ ፡ (ሐጌ፩ ፡ ፩) ።

**ሐጊዝ ፤ ዘት** ፤ (ሐገዘ ፡ የሐግዝ ፤ ይሕግዝ ። ዐረ ፡ ሐጀዘ) ፤ መግታት ፡ ማቆም ፤ ማስጠጋት ፡ ማስደገፍ ፤ እንዳይኼድ ፡ እንዳይወድቅ ፡ መከልከል ፡ መጠበቅ ፤ የመርከብ ፡ የፈረስ ። መሰወር ፡ መደበቅ ፤ ከብብት ፡ ከጕያ ፡ ማግባት ፡ መሸጕጥ ። በቁሙ ፤ ማገዝ ፡ መርዳት ።

**ሐግዝ** ፤ ብብት ፤ ንፍረት ፡ ጕያ ። ሐንገዝን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ስሯጽ ፡ ነው ።

**ተሐግዘ** ፤ ተገታ ፡ ቆመ ፡ ተከለከለ ። ታገዘ ፡ ተረዳ ፤ ተደገፈ ።

**ተሓገዘ** ፤ ተጋገዘ ፤ ተረዳዳ ። ወእምዝ ፡ ተሓገዝነ ፡ ወአጽናዕናሃ ፡ በሐብል ፡ (ግብ፳፯ ፡ ፲፯) ።

**ሐግዮ ፤ ዮት** ፤ (ሐገየ ፡ የሐጊ ፡ ይሕጊ) ፤ ማጋየት ፡ ማቃጠል ፤ በጋ ፡ ድርቅ ፡ መኾን ፤ የአባት ፡ የወራት ። መባጀት ፤ በጋው ፡ እስኪያልፍ ፡ መቈየት ። መጋረድ ፡ መሸፈን ፡ (ትግሬ) ። ጋየ ፡ ጋያ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ሐጋይ** ፤ በጋ ፡ ድርቅ ፤ የድርቅ ፡ ወራት ፡ ከራቱ ፡ ክፍላተ ፡ ዘመን ፡ አንዱ ፡ እጅ ፡ ፫ ፡ ወር ፡ ወይም ፡ ፺፩ ፡ ቀን ፡ ተሩብ ፤ ከታኅሣሥ ፡ ፳፮ ፡ እስከ ፡ መጋቢት ፡ ፳፭ ። ሀለዉ ፡ አርባዕቱ ፡ ዘመናት ፤ ቀዳማዊ ፡ ሆሙ ፡ ዘመኑ ፡ መፀው ። ወፈለጠ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ክረምተ ፡ ወማእረረ ፡ ወሐጋየ ፡ በበ ፡ ኍልቆሙ ፡ ወበበ ፡ ጊዜሆሙ ፡ (አዋል ። ሚራ፴፮ ፡ ፱) ። የሐጋይ ፡ ፍች ፡ በጋ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ መፀውም ፡ ጸደይም ፡ በርሱ ፡ ስም ፡ ሐጋይ ፡ ይባላሉ ። ዘጠኝ ፡ ወር ፡ በጋ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ክረምት ፡ እንዲሉ ። ክረምተ ፡ ወሐጋየ ፡ ዘአንተ ፡ ፈጠርከ ። ወከማሁ ፡ ይክውን ፡ በክረምት ፡ ወበሐጋይ ፡ (መዝ ፡ ፸፫ ። ዘካ፲፬ ፡ ፰ ። ዘፍ፰ ፡ ፳፪) ።

**ሐጋያዊ** ፤ የበጋ ፤ ለበጋ ፡ የሚኾን ፤ የበጋ ፡ ወራት ፡ ሐሩር ፡ ድርቅ ፡ የሚጠናበት ፡ (አቡሻ ፡ ፴፯) ።

**ሐጕለ** ፤—ዐጣ ፤—ሀጕል ፡ ሀጕለ ።

**ሐጊል ፤ ሎት** ፤ (ሐገለ ፤ ሐግለ ፡ የሐግል ፡ ይሕግል ። ዐረ ፡ ሐጀለ) ፤ ማሰር ፡ መሸንከፍ ፤ መቀየድ ፡ መሰንከል ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ መር ፡ መር ፡ ኾብ ፡ ኾብ ፡ ዱብ ፡ ዱብ ፡ እያሉ ፡ መኼድ ፤ የቍራ ፡ ያንካሳ ፡ የእስር ፡ አካኼድ ፡ አረማገጥ ። ከጥሬው ፡ በቀር ፡ አንቀጹ ፡ አይገኝም ።

**ሐግል** ፤ (ላት ። ዐረ ፡ ሐጅል ፤ ሒጃል) ፤ ማሰሪያ ፤ የግር ፡ ብረት ። የግር ፡ ጌጥ ፤ ግርጃ ፡ ድኵት ፡ ጥምዝ ። መንቈር ፤ ቀንበር ፡ ከነማንቆው ። ግበር ፡ ለከ ፡ ጋገ ፡ ወሐግለ ፡ ወደዮ ፡ ውስተ ፡ ክሣድከ ፡ (ኤር፳፯ ፡ ፪) ።

**ሐገመ** ፤ (ሐከመ) ፤ በገመ ፡ ዋገምት ፡ ተከለ ። ዘሩ ፡ ሐከመ ፡ ነው ፤ ከ ፡ በገ ፡ ተለውጧል ።

**ሐገን** ፤ ንፍጥ ፡ ያፍንጫ ፡ እድፍ ፡ (ትግሬ) ።

**ሐገፈ** ፤ (ዐረ ፡ ሐጀበ) ፤ መከተ ፡ አነገበ ፤ ለበሰ ፡ ያዘ ፤ የጋሻ ።

**ሐገፋ** ፤ (ፋት) ፤ ጋሻ ፡ የሰልፍ ፡ ልብስ ፤ ላዩ ፡ ብረት ፡ ውስጡ ፡ ቈርበት ፤ ከሰይፍና ፡ ከጦር ፡ የሚያድን ። ወልታን ፡ እይ ። ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ሐገፋ ፡ ዘወርቅ ። ወነሥአ ፡ ሐገፋተ ፡ ወርቅ ። ሐገፋ ፡ ወረምሕ ። ኩንኒ ፡ እግዚእትየ ፡ ቅድመ ፡ ፀርየ ፡ ሐገፋ ፡ (፩ዜና ፡ ፲ ፡ ፲፯ ። ፲፬ ፡ ፲ ። ፲፱ ፡ ፳ ። ደራሲ) ።

**ሕጕሬ** ፤ (ዐረ ፡ ሐጀሬ ፤ እብናዊ) ፤ ቀይ ፡ ቀለም ፤ ወርቅማ ፡ እንደ ፡ ኾል ፡ ደንጊያነት ፡ ያለው ፡ ሳይደቈስ ፡ ወርቅ ፡ የሚመስል ፤ ቅላቱ ፡ ፍጹም ፡ ደማቅ ። ወቀብዖ ፡ በሕጕሬ ፡ ወሜሪየ ፡ ወአቅየሐይሐ ፡ ሕብሮ ፡ (ጥበ፲፫ ፡ ፲፬) ።

**ሕጕር** ፤ (ራት) ፤ የፍሬ ፡ ፍሬ ፤ በወይኑና ፡ በተምር ፡ ሕንባብ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ቅንጣት ፤ ውስጡ ፡ ዐጥንቱ ፡ ከራራው ፡ ጠንካራው ፡ እንዳሸዋና ፡ እንደ ፡ ጠጠር ፡ ያለው ። ዘእምውስተ ፡ ዘቢብ ፡ ሕጕር ፡ (ዘኍ፮ ፡ ፬) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፤ ንባቡን ፡ ሕጕር ፡ ይሉና ፡ ፍችውን ፡ የተነጐረ ፡ ይሉታል ።

**ሐዲድ** ፤ (ዐረብ) ፤ ብረት ፡ ዘንጅር ። እምከሣድየ ፡ ሐዲደ ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፳፩) ።

**ሐደመ** ፤—እንቀላፋ ፤—ሀዲም ፡ ሀደመ ።

**ሐድሞ ፤ ሞት** ፡ (ሐደመ ፡ ይሔድም ፡ የሐድም ። ዕብ ፡ ሐድ) ፤ መተረት ፡ መመሰል ፤ በተረትና ፡ በምሳሌ ፡ መናገር ፡ ማስተማር ። ሐድም ፡ ሐድሞተ ፡ ወመስል ፡ ምሳሌ ፡ (ሕዝ፲፯ ፡ ፪) ።

**ሐዳሚ** ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት ፤ ደምት) ፤ የሚተርት ፡ ተራች ፤ ምሳሌ ፡ ዐዋቂ ፤ ተጫዋች ።

**መሐድም** ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ተረታም ።

**መሐደምት** ፤ (ታት) ፤ ተረት ፡ ምሳሌ ፤ ጨዋታ ፡ ቢልት ፤ ለማጥ ፡ (፩ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፬ ። ፬ ፡ ፯ ። ፪ጢሞ ፡

፱ ፡ ፱ ። ቲቶ፩ ፡ ፲፱ ። ፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፯) ። ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ነገረ ፡ መሐደምት ፡ ወተዛውዖ ፡ ደቂቅ ፤ እስመ ፡ ደቂቅ ፡ ይሰምዑ ፡ ብዙኀ ፡ ነገረ ፡ መሐደምት ፡ እም ኀበ ፡ ሐፃኒት ። መሐደምት ፡ ስሑን ። አነ ፡ መሐደ ምቶሙ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፩ ። ቁር ። ኢዮ፴ ፡ ፱) ።

**ሐደሠ ፤—በቁሙ ፤—ሐድሶ ፡ ሐደሰ ።**

**ሐድዐ ፤—ጸጥ ፡ አለ ፤—ሀዲእ ፡ ሀድአ ።**

**ሐዳፍ ፤ (ብ ፡ አሕዳፍ ። ዕብ ፡ ዖሬፍ) ፤** ማኅፈራት ፡ ማንቃ ፤ ያንገት ፡ ኋላ ። አጽንዑ ፡ ሐዳፎሙ ። እግዚ ፡ ሰበረ ፡ አሕዳፊሆሙ ፡ (ኤር፲፱ ፡ ፲፭ ። መዝ ፡ ፻፳፰) ።

**ሐደፈ ፤—ቀዘፈ ፤—ኀድፎ ፡ ኀደፈ ።**

**ሐደረ ፤—ዐደረ ፤—ኀዲር ፡ ኀደረ ።**

(ጥ) **ሐድሶ ፤ ሶት ፤ (ሐደሰ ፡ ይሔድስ ፡ የሐ ድስ ። ዕብ ፡ ሐዴሽ ። ሱር ፡ ሐዴት ። ዐረ ፡ ሐደሰ) ፤** ማደስ ፤ መለወጥ ፡ ሐዲስ ፡ ማድረግ ፤ ማጥ ናት ፡ ማበርታት ፤ መሥራት ፡ መጠገን ፤ ያሮጌ ፡ የሰባራ ። የሐድስዋ ፡ ለንስሓሆሙ ። ሎሙ ፡ ትሔድስ ። ይሔ ድሱ ፡ አህጉረ ፡ እለ ፡ መዝበራ ፡ (ዕብ፮ ፡ ፮ ። ጥበ፯ ፡ ፳፯ ። ኢሳ፷፩ ፡ ፬) ።

—፤ ዐዲስ ፡ ነገር ፡ ማውጣት ፡ መፍጠር ። ይሔድስ ፡ እግዚእ ፡ ሐዲሳተ ፡ (ሔኖ ፡ ፸፯ ፡ ፲፫) ።

—፤ መባረክ ፡ መቀደስ ፡ መመረቅ ፤ ያዲስ ፡ ቤት ። ደቅ ሐንና ፡ ሐንከን ፡ ተመልከት ። ወሐደሰ ፡ ቤተ ፡ እግዚ ። ሐድሶ ፡ ሕንጻታ ፡ (፪ዜና ፡ ፯ ፡ ፭ ፡ ፱ ። ዮሐ፲ ፡ ፳፪) ። በሐረስ ፡ ፈንታ ፡ ሐደሰ ፡ ይባል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ። ሐ ድሱ ፡ ሐዳሳተ ፡ (ኤር፬ ፡ ፫) ።

**ሐዳሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት ፤ ደስት) ፤** የሚያድስ ፡ የሚጠግን ፡ ወጌሻ ፡ ገንቢ ፡ ዐናጢ ። ኮነ ፡ ሐዳሲሃ ፡ ለጽድቅ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ።

**አሐደሰ ፤ አስተሐደሰ ፤** አሳደሰ ፡ አስጠገነ ፤ ሐዲስ ፡ አስደረገ ። ወአስተሐደሰ ፡ ቤተ ፡ ምሥዋዕ ፡ (፪ ዜና ፡ ፲፭ ፡ ፰) ።

**ተሐደሰ ፤** ታደሰ ፤ ተለወጠ ፡ ዐዲስ ፡ ኾነ ። ወ ናሁ ፡ ተሐደሱ ፡ ኵሉሙ ። ተሐደሰት ፡ ወሐይወት ፡ መንፈሱ ። ተሐደሰት ፡ ሕግ ፡ መንግሥት ፡ (ራእ፳፩ ፡ ፭ ። ኩፋ ፡ ፵፫ ። ክብ ፡ ነገ) ። አርመመ ፡ ዝጉን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተሐደሰ ፡ ይባል ፤ ጸና ፡ ረጋ ፡ ለማለት ። ተሐደሳ ፡ መንገሌየ ፡ ደሰያት ። ወአመ ፡ በሕፀኑ ፡ ተጸውረ ፡ ማ ዕቀበ ፡ አልፋ ፡ ሕፃን ፤ ተሐደሰ ፡ ኢያሪኮ ፡ ብሉየ ፡ መ ዋዕል ፡ ወአዝማን ፡ (ኢሳ፶፭ ፡ ፩ ። ቅኔ) ።

**ሐዲስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፤ ዳስ ፡ ሳት) ፤** በቁሙ ፤ ዐዲስ ፡ እንግዳ ፡ ቀድሞ ፡ ያልነበረ ፡ ኋላ ፡ የተገኘ ፡ የተ ፈጠረ ፤ ወይም ፡ የታደሰ ፡ የተለወጠ ፤ ብልየት ፡ የጠፋለት ። ዐርክ ፡ ሐዲስ ፡ ወይን ፡ ሐዲስ ። በእንተ ፡ ሐዲሳን ፡ ሕ ዝብ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይጠመቁ ። ብሉያት ፡ ወሐ ዲሳት ። ሐዳስ ፡ ሥርዐት ። ሐዳሳተ ፡ ሰማያተ ፡ ወሐ ዳስ ፡ ምድረ ፡ ንሴፎ ፡ (ሲራ፱ ። አርጋ ። ዕብ፰ ፡ ፲፫ ። ፪ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፫) ። ሐዲሳት ፡ ሐዳሳት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሐደስት ፡ ይባል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (መሳ፲፭ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ። ዘፀ፳፫ ፡ ፲፭) ።

**ሕዳሴ ፤** ማደስ ፡ መታደስ ፤ አስተዳደስ ፡ ዕደሳ ፤ ሐዲስነት ።

**ሐው ፤—እሳት ፤—ሐውይ ፡ ሐወየ ።**

**ሔው ፤ ሔዋ ፤—ስም ፤—ሐይው ፡ ሐ ይወ ።**

**ሐዊዝ ፤ ዞት ፤ (ሐዘ ፤ ሐወዘ ፡ የሐውዝ ፡ ይሐውዝ) ፤** ማወዝ ፤ ዐዋዜ ፡ መኾን ፤ መጣም ፡ መጣ ፈጥ ፡ መስማማት ፤ ማማር ፡ መወደድ ። ደስ ፡ ፈቅ ፡ ማ ሰኘት ፤ ማስጐምጀት ። ለሚያየውና ፡ ለሚሰማው ፡ ለሚ ቀምሰው ፤ የመልክ ፡ የዜማ ፡ የምግብ ፡ የነገር ። ኢየሐው ዘኒ ፡ ሣእሣአ ፡ ቃልክሙ ። መሰንቆ ፡ ወመዝሙር ፡ የሐውዝ ፡ ለነፍስ ። ሐወዘኒ ፡ እስመ ፡ ሞቁ ። ወባ ሕቱ ፡ ሊተሰ ፡ ኢየሐውዘኒ ፡ ዝንቱ ፡ (ኢዮ፳ ፡ ፳፪ ። ሢራ፵ ፡ ፳፩ ። ኢሳ፵ ፡ ፳፩ ። አስቴ፳ ፡ ፲፫) ። በሐወዘ ፡ ፈንታ ፡ አሐዘ ፡ አስተሐወዘ ፡ ይባል ፤ አያሰኝም ። ይገ ብር ፡ ዘከመ ፡ ያሐውዞ ። በዕፍረት ፡ ወዕጣን ፡ ወወ ይን ፡ ያስተሐ(ሔ)ውዞ ፡ ልበ ፡ (ሄርማ ፡ ገ፻፱ ። ምሳ ፳፯ ፡ ፱) ።

**ሐዋዝ ፤** ያማረ ፡ የጣፈጠ ፡ የተስማማ ፤ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መልካም ። ቅጽልነቱ ፡ ለገሩ ፡ ለለ ፡ ኾነ ፤ ወ ንድና ፡ ሴት ፡ ያስተባብራል ። ሐዋዝ ፡ ማሕሌት ፡ ወመ ሰንቆ ፡ በቤተ ፡ ስታይ ። ሐዋዝ ፡ ውእቱ ፡ ሕገ ፡ እግዚ ። ምድር ፡ ሐዋዝ ፡ ወሥብሕት ። ሐዋዚ ፡ ትንውም ። ንግበር ፡ ሐዋዘ ፡ ውስተ ፡ ፍጥረትነ ፡ (ሢራ፴፭ ፡ ፯ ። ሮሜ፯ ፡ ፳፪ ። ሔኖ፹፱ ፡ ፵ ። ምሳ፫ ፡ ፳፬ ። ጥበ፪ ፡ ፯) ። ዐዋዜ ፡ ጥሩ ፡ ድልኽ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሐውዝ ፤ (ዛት) ፤** ተድላ ፡ ደስታ ፤ ጣዕም ፡ ፍት ወት ፤ ውበት ፡ ስምምነት ። ጕየ ፡ እምሐውዝ ፡ ዓለም ። ሐውዘ ፡ መሰንቆ ፡ ወማሕሌት ። ሐውዘ ፡ መንበርት ። ሐውዘ ፡ መባልዕት ። ሐውዘ ፡ አየራት ፡ ወፍሬያተ ፡ ምድር ፡ (ድጓ ። ሢራ፵፱ ፡ ፳ ። ሉቃ፰ ፡ ፲፬ ። ዲድ ፡ ፲፱ ። ማኅዘ) ።

**አሐዘ ፤ አስተሐ(ሕ)ወዘ ፤** አጣመ ፡ አጣፈጠ ፤ አሳመረ ፡ አስማማ ።

**ተሐውዘ ፤** ተደሰተ ፤ ደስ ፡ ፈቅ ፡ አለው ፡ ተ ድላ ፡ አገኘ ። ተሐውዘ ፡ ወተደልዎ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲) ።

**ተሓወዘ ፤** ተጣጣመ ፤ ተጠፋፈጠ ፡ ተመሳሰለ ፡ ተ ከንዋወነ ፤ የሥራ ።

**አስተሓወዘ ፤** አጣጣመ ፡ አጠፋፈጠ ፤ አስማ መረ ። አስተሓዊዘከ ፡ ግስስ ። ያስተሓውዝ ፡ ሎሙ ፡ ጽሙና ። ያስተሓውዝ ፡ ፍትወተ ፡ ውስተ ፡ ልብ ፡ (ም ሳሌ ፡ ፲፯ ። ፈልክ ፡ ፶ ። አርጋ ፡ ፪) ።

**ሐውይ ፤ ዮት ፤ (ሐወየ ፡ የሐዊ ፡ ይሕ ወይ ። ዐረ ፡ ሐዊየ) ፤** መንም ፡ መቃጠል ፤ እሳት ፡

መኾን ፡ መምሰል ፤ መጥቈር ፡ መክሰል ፡ የብረት ፡ የን ጨት ። መምሸት ፡ መጨለም ፤ ድግዝ ፡ ማለት ። ፀሓይ ፡ ስትገባ ፡ የሰማይን ፡ መቅላትና ፡ መጥቈር ፡ ያሳያል ።

**ሕዋይ ፤ ሐዋይ ፤** ምሼት ፡ ድግዝታ ፡ ጭልም ልምታ ፤ የሠርክ ፡ ሠርክ ፡ የማታ ፡ ማታ ። እምከመ ፡ መሰየ ፡ ወኮነ ፡ ሕዋየ ፡ (ማቴ፲፮ ፡ ፪) ።

**ሐው ፤** እሳት ፡ የሚፋጅ ፡ የሚያቃጥል ፤ ሕብሩ ፡ ቀይ ፡ የምሼት ፡ ሰማይ ፡ የሚመስል ። በብዝኀ ፡ ትንታጉ ፡ ለሐው ፡ ይበዝኅ ፡ ፍሕሙ ። ሐወ ፡ ዘአቈርከ ። ጤ ግን ፡ ዘአፍልሕዎ ፡ በሐው ። አንዳደሙ ፡ ሐወ ፡ (ሚራ ፲፩ ፡ ፴፪ ። ድጓ ። ስንክ ፡ ኅዳ፯ ። ሠኔ፳፩) ።


**ሐዊ ፤** መጽሐፍ ፡ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ሐዊ ፡ የሚ ባል ፡ ሰው ፡ የጣፈው ፡ የሰበሰበው ፤ የአበውን ፡ ዜና ፡ የ ቅዱሳንን ፡ ገድል ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ የሚናገር ፡ መጠኑ ፡ ከመንፈቅ ፡ ስንክሳር ፡ የሚበልጥ ። ፍችው ፡ እሳታዊ ፡ ሰማያዊ ፤ መንፈሳዊ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ (ግብ፪ ፡ ፫) ።

**ሐከ ፤—አወከ ፤—ሀዊክ ፡ ሆከ ።**

**ሐዊል ፤ ሎት ፤ (ሐለ ፤ ሐወለ ፡ የሐ ውል ፡ ይሑል ። ዐረ ፡ ሐውለ ፤ ዘረ) ፤** መዞር ፡ መክበብ ። መቀላቀል ፡ መደባለቅ ፤ አንድ ፡ ማድረግ ። ሐ በለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ሐዋሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ወልት) ፤** የሚዞር ፡ የሚከብብ ፤ ቀላቃይ ።

**ሐውልት ፤ (ታት) ፤** በቁሙ ፡ ትክል ፡ ደን ጊያ ፡ እንደ ፡ ዐምድ ፡ እንደ ፡ ምሰሶ ፡ የቆመ ፡ ክብነት ፡ ምእዙንነት ፡ ያለው ፤ ለመታሰቢያ ፡ የሚተከል ፡ የሚን ደቅ ፡ ወይም ፡ ከኖራ ፡ ከሸዋ ፡ ከሸሚንት ፡ ከደንጊያ ፡ ደቂት ፡ ቀላቅለው ፡ ደባልቀው ፡ እያፈሰሱ ፡ የሚሠሩት ፡ ፍስ ፡ ደንጊያ ። አቀሙ ፡ ሐውልተ ፡ እብን ፡ ዐቢይ ። ኢታቅሙ ፡ ለክሙ ፡ ሐውልተ ፡ እብን ። ሐውልተ ፡ ጼው ። ሐውልተ ፡ ስምዕ ፡ (ዘፍ፳ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ። ዘሌ ፳፮ ፡ ፩ ። ዘፍ፲፱ ፡ ፳፮ ። ቅዳ) ።



ሐውልት ፤

—፤ የጕል ፡ ግስ ፡ ስም ፤ ናሙ ፡ ቆሙ ፡ ጥዕየ ፡ ሐሙ ፤ ጸንዐ ፡ ደከሙ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ግስ ፡ ሐውልት ፡ ይባ ላል ፡ ቅልቅል ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ተሐውለ ፤** ተጨመረ ፡ ተዘነቀ ፡ ተደባለቀ ። ኢይደመሮ ፡ መርድእ ፡ ወኢይትሐወሎ ፡ ዳማ ፡ ወድካም ፡ (ዮሴፍ) ።

**ተሓወለ ፤** ተቀላቀለ ፡ ተደባለቀ ፡ ተሳተፈ ፡ ተ ባበረ ። ይደሉ ፡ ንዕቀብ ፡ ርእሰነ ፡ ወኢንትሓወል ፡ ምስለ ፡ ኃጥኣን ። ኢትትሓወል ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡ ደም ። ኢትትሓወሉ ፡ ዕልዋነ ፡ ሃይማኖት ። ይትፈ ለጥ ፡ ወኢትትሓወልዎ ፡ (ዲድ ፡ ፱ ፡ ፯ ። ቀሌ ። ፪ተሰ ፡ ፫ ፡ ፲፬) ።

**ሕዉል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ውልት) ፤** የተቀላ ቀለ ፡ ቅልቅል ፤ ኅቡር ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፳፫ ። ጥር፳፯) ።

**ሐውል ፤ (ላት ። ዕብ ፡ ሖል ፤ አሸዋ) ፤** ያሸዋ ፡ ጭቃ ፤ ዐፈር ፡ ኩረት ፡ የተቀላቀለው ። ሸሮ ፡ እ ለት ፡ ጥርሳም ፡ ስለታም ፡ ሸካራ ፡ ደንጊያ ። ወምስካቡ ፡ ሐውላት ፡ ፀበይት ፡ (ኢዮ፵፩ ፡ ፳፭) ።

**ሐዋላ ፤ (ዐረብ) ፤** በፖስታና ፡ በባንክ ፡ የሚ ላክ ፡ ገንዘብ ።

**ሑል ፤ (ዕብ ፡ ሖል) ፤** ተርታ ፡ መናኛ ፡ መ ከከለኛ ፤ ፍጹም ፡ ርኩስ ፡ ያይደለ ፤ መሥዋዕትና ፡ ቍር ባን ፡ የማይኾን ፡ ለሕዝብ ፡ የሚገባ ፡ ሕዝብ ፡ የሚበሉት ። ይምሀሩ ፡ ለሕዝብ ፡ ማእከለ ፡ (ንጹሕ) ፡ ቅዱስ ፡ ወ ሑል ፡ (ሕዝ፵፬ ፡ ፳፫) ።

**ሐውለየ ፤—ለየ ፡ ነቀፈ ፤—ሀውለየ ።**

**ሐሠ ፤—ቀላቀለ ፤—ነዊሥ ፡ ኖሠ ።**

**ሐዊጽ ፤ ጾት ፤ (ሐጸ ፡ የሐውጽ ፡ ይ ሑጽ ፤ አው ፡ ሐውጸ ፤ ሐወጸ ፡ ይሔውጽ ፡ የሐውጽ ። ሐየጸ ። ዋሐየ) ፤** ማወጥ ፡ መጐብ ኘት ፡ መሰለል ፤ መፍቀድ ፡ መጠየቅ ፡ አሻግሮ ፡ ማየት ፤ ዐይንን ፡ ልብን ፡ ጥሎ ፡ ሥራዬ ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ መመል ከት ። አመ ፡ ሐውጸ ፡ ሐወጸክሙ ፡ እግዚእ ። ኢት ትሀከይ ፡ ሐውጾ ፡ ድዉይ ። የሐውጽዎሙ ፡ ለነዳ ያን ። ወይሔውጽ ፡ እንተ ፡ መሳክው ። እንተ ፡ ትሔ ውጽ ፡ እምርሑቅ ። ወዘሰ ፡ ሐወጸ ፡ ውስተ ፡ ሕግ ፡ ፍጹም ፡ (ዘፍ፶ ፡ ፳፭ ። ሢራ፯ ፡ ፴፭ ። ኪዳ ። ማሕ፪ ፡ ፱ ። ፯ ፡ ፩ ። ያዕ፩ ፡ ፳፭) ። ግእዝቱ ፡ ገቢርና ፡ በጕል ፡ ነውና ፤ ያለፈው ፡ ገቢር ፡ የሚመጣው ፡ በጕል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ፍች ውን ፡ አስተውል ።

**ሐዊጽ ፤ ሐውጾ ፤** መጎብኘት ፡ መጥራት ፡ ንጹሕ ፡ ጽሩይ ፡ ብሩህ ፡ መኾን ። ወከመ ፡ ርእየተ ፡ ጽንዐ ፡ ሰማይ ፡ ሶበ ፡ ሐወጼት ። መኑ ፡ ይእቲ ፡ ዛቲ ፡ እንተ ፡ ትሔውጽ ፡ ከመ ፡ ጎሕ ። ሐውጽ ፡ እምሰ ማይ ፡ ብርሃነከ ፡ ከመ ፡ ንርአይ ፡ (ዘፀ፳፬ ፡ ፲ ። ማሕ ፮ ፡ ፱ ። ድጓ) ።

**ሐዋጺ ፤ (ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት) ፤** የሚ ጐበኝ ፤ ተመልካች ፡ ጠያቂ ፡ ፈቃጅ ፤ መርማሪ ፡ በላይ ። እግዚእ ፡ ሐዋጼ ፡ ነፍስ ፡ ትሑታን ። ድዉያን ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ሐዋጺ ። ሐዋጺ ፡ ህልው ፡ ይሔ ውጽ ፡ ልቦ ፡ (ኪዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፯ ፡ ፫ ። ጥበ፩ ፡ ፮) ።

**መሐውጽ ፤ (ጽት ፡ ጻን ፡ ጻት) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ጐበኛ ፡ ሰላይ ፡ ፈላስፋ ፡ ጠንቋይ ። መሐውጻነ ፡ ኮከብ ፡ (ኪዳ ፡ ገ፳፯) ።

**ምሕዋጽ ፤ (ጻት) ፤** መጐብኛ ፡ መመልከቻ ፤ መስኮት ። ምሥሣል ፡ የታበተ ፡ ሙሴ ፡ መክደኛ ፡ በላዩ ፡

ኪሩቤል ፡ የተማለሉበት ፡ እግዜር ፡ እስራኤልን ፡ የሚጐበኝበት ፤ ቃሉን ፡ የሚያሰማበት ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፳፪) ። ማህሰን ፡ እይ ።

**ተሐወጸ** ፤ ተጐበኘ ፡ ታየ ፡ ተስለለ ፤ ተፈቀደ ፡ ተቈጠረ ። ከመ ፡ ትትሐወጽ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ። እስ ፡ የሐውፉ ፡ ከመ ፡ ይትሐወጹ ፡ (ኪዳ ። ዘፀ፴ ፡ ፲፫) ።

**ሕዉጽ** ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ውጻት) ፤ የተጐበኘ ፡ የተሰለለ ፤ ጕብኙ ።

**ሕዋጼ** ፤ (ጼያት) ፤ መጐብኘት ፡ (ጥጕ) መጐብኘት ፤ እጕብኛኘት ፡ ጕብኝታ ፡ ጥየቃ ፤ ስለላ ፡ ጥበቃ ፡ (ጥበ፫ ፡ ፳ ፡ ፱) ። ዚኣከ ፡ ጥበበ ፡ ወዘዚኣከ ፡ ሕዋጼ ። ሐውጽዎሙ ፡ በሕዋጼ ፡ እግዚአብሔራዊት ፡ (ኪዳ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳) ።

**ሐጸ ፤—እሸዋ ፤—ሐጸ ፡ ኀጠ ፡ ኆጸ ።**

**ሐዊር** ፤ **ሮት** ፤ (ሐረ ፡ የሐውር ፡ ይሑር) ፤ መኼድ ፡ መራመድ ፡ ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ መፍለስ ፤ እግርን ፡ በፈረቃ ፡ ማንሣት ፡ መጣል ፡ መንቀል ፡ መትከል ፡ ማሽቀዳደም ። በደረት ፡ በልብ ፡ መሳብ ፡ መጕተት ፡ ለመም ፡ ማለት ። ሂደንና ፡ ኬደን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ንሮች ፡ ናቸው ። ሑሩ ፡ ውስተ ፡ ዠሉ ፡ ዓለም ። ከመ ፡ ይሑር ፡ በእገሪሁ ። ሑሪ ፡ በእንግድዓኪ ፡ (ማር፲፮ ፡ ፲፭ ። ማብ፫ ፡ ፲፱ ። ዘፍ፫ ፡ ፲፬) ።

—፤ መኖር ፤ መቀመጥ ፡ የቦታ ፡ የግብር ። ሰምንት ፡ የሐውር ፡ ወልደ ፡ ብእሲት ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡ መዋዕል ። ዘየሐውር ፡ በጽድቅ ። ዘከመ ፡ ሖርኩ ፡ ቅድሜከ ። ኢሖሩ ፡ በትእዛዝከ ። ዘኢሖረ ፡ በምክረ ፡ ረሲዓን ፡ (ሔኖ ። ኢሳ፴፫ ፡ ፲፭ ። ፴፰ ፡ ፫ ። ኤር፴፱ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፩) ።

—፤ መሥራት ፡ ማድረግ ፡ መቅረብ ፡ መራከብ ። ሖሮን ፡ እግዚእ ፡ ለኀምስ ፡ ግብራት ። ሐዊረ ፡ ብእሲተ ፡ ብእሲ ። ኢትሑር ፡ ኀበ ፡ እንስሳ ። ዙሉ ፡ ዘየሐውር ፡ እንስሳ ፡ ሸነኑሁ ፡ መዊት ። እስ ፡ የሐውሩ ፡ ወእስ ፡ የሐውርዎሙ ፡ (ትር ፡ ወን ። ማር፳ ፡ ፳፩ ። ዘሌ፲፰ ፡ ፳፫ ። ዘፀ፳፪ ፡ ፲፰ ። ሰቆር ፡ ፳ ፡ ፱) ።

**ሐዋሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤ የሚኼድ ፡ ኸ(ሀ)ያጅ ፡ ተራማጅ ፡ ኋጅ ፡ ገሥጋሽ ፡ (ዘማዊ) ። ጻማዊ ፡ በገድሉ ፡ ወሐዋሪ ፡ በፍኖተ ፡ አበው ፡ ቅዱሳን ። ፈላሲ ፡ ወሐዋሪ ፡ እምኔነ ፡ ሐዋሪ ፡ ዘኢይሰፎ ፡ ተመይጦ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ግንዘ) ። ደላዊ ፡ ሐያሲ ፡ ቀዳሒ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሐዋሪ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ሐዋሬ ፡ ማይ ፡ ክሙ ። ወረበዮሙ ፡ ሐዋርያነ ፡ ማይ ፡ በዠሉ ፡ ተዓይን ። ይወፅእ ፡ ሐዋርያተ ፡ ማይ ፡ (ዘዳ፳፱ ፡ ፳ ። ኢያ፱ ፡ ፳፫ ። ዘፍ፳፱ ፡ ፲፩ ። ሕንገ ፡ ፱ ፡ ፲፩) ።

**ሐዋርያ** ፤ (ያት ። ዐረ ፡ ሐዋሪይ) ፤ መንገደኛ ፡ መልክተኛ ፡ ቀላጤ ። ከመ ፡ እኩይ ፡ ሐዋርያ ። ሐዋርያ ፡ ጠቢብ ፡ ያድኅን ፡ ርእሶ ። ፈነወ ፡ ሐዋርያተ ፡ (ምሳ፲ ፡ ፲፩ ። ፲፫ ፡ ፲፯ ። ሕዝ፲፯ ፡ ፲፭) ።

—፤ በቀሙ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሹም ፡ መምህር ፡ ዘሮ ፡ የሚሰብክ ፡ የሚያስተምር ፡ ባለምሥራች ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ። ሐዋርያ ፡ ዘተጸውዐ ፡ ወተፈልጠ ፡ ለትምህርተ ፡ ወንጌል ። ርእዩዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ሐዋርያክሙ ። ዘሎቱ ፡ ተሠየምኩ ፡ አነ ፡ ሐዋርያ ፡ ወዐዋዲ ። ጉባኤ ፡ እንተ ፡ ሐዋርያት ፡ ሐዋርያተ ፡ በግዑ ፡ (ሮሜ፩ ፡ ፩ ። ዕብ፫ ፡ ፩ ። ፪ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ። ጸሎ ፡ ሃይ ። ራእ፳፩ ፡ ፲፬) ።

**ሐዋርያዊ** ፤ የሐዋርያ ። ቀኖና ፡ ሐዋርያዊ ። መንበር ፡ ሐዋርያዊት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ። አቡሻ) ።

**አሖረ** ፤ **አስተ(ሐ)ሐወረ** ፤ አኼደ ፡ አስኼደ ፡ ነዳ ፡ ወሰደ ። ወአሖሩ ፡ ሠረገላቲሆሙ ። አነ ፡ አንጐግዋ ፡ ወአሐውራ ፡ በድው ። ያረትዕ ፡ መዝራዕተ ፡ እድ ፡ ይቡስ ፡ ወያሐውር ፡ እግረ ፡ ሐንካስ ፡ (፩ነገ ፡ ፱ ፡ ፳፭ ። ሆሴ፪ ፡ ፲፬ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ። አሠራ ፡ አስያረገ ።

**መሐውር** ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤ የሚኼድ ፡ ኸያጅ ፡ ዘዋሪ ፤ የሚያስኼድ ፤ ነጂ ፡ ወሳጅ ።

**ምሖር** ፤ **ምሕዋር** ፤ (ራን) ፤ መኼጃ ፡ ማስኼጃ ፤ መንገድ ፡ ጐዳና ። ምሕዋረ ፡ ሠሉስ ፡ ዕለት ። ምሕዋረ ፡ ሰቡዕ ፡ መዋዕል ። ወብሔሩሰ ፡ ምሕዋረ ፡ ዓመት ፡ ወመንፈቅ ፡ (ዘፀ፫ ፡ ፲፰ ። ዘኍ፴፩ ፡ ፳፱ ። ሉቃ ፡ ፩፲፭) ። ምሕዋራት ፡ ማያት ፤ መስኖ ፡ ቦይ ፡ መትረብ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ፡ ፫) ። ዕሥራ ፡ ምእት ፤ ወይም ፡ ክዕበተ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምእት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዐሠርተ ፡ ምእት ፡ ምሕዋረ ፡ ዓመት ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ መተርጕማንን ፡ ግን ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ቀጥሎ ፡ ቀጥሎ ፡ ቢኖር ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ፡ (መክ ፡ ፮ ፡ ፮) ።

**ተሖረ** ፤ **ተሐው(ወ)ረ** ፤ ተኼደ ፡ ተኼደበት ። ተሠራ ፤ ተደረገ ።

**ተሓወረ** ፤ ተኺያኺያደ ፡ ተካኺያደ ።

**ሕዉር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ውርት) ፤ የኼደ ፡ የተኼደ ፡ የተኼደበት ፤ የተካኺያደ ። የተሠራ ፡ የተደረገ ፡ ግቡር ፡ ሕኑጽ ።

**ሑረት** ፤ (ታት) ፤ መኼድ ፡ አካኼድ ፤ አኗኗር ፡ ኑሮ ። ሑረት ፡ ወግብአት ። ሑረተ ፡ ብእሲተ ፡ ብእሲ ። ሑረተከ ፡ በሰላም ፡ ይሠኒ ። መምህር ፡ ይኩን ፤ ንጹሐ ፡ በሑረታቲሁ ፡ ወጽኑዐ ፡ በፍናዋቲሁ ። በእንተ ፡ ሠናይ ፡ ሑረታቲሁ ፡ ለሕዝብ ፡ (ዘካ፮ ፡ ፲፱ ። ቀሌ ። ምሳ፴ ፡ ፳፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፩ ፡ ፭ ። ዮሴፍ) ።

**ሕዋር** ፤ (ራት) ፤ በረንዳ ፡ ወልወል ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፤ መወጣጫ ፡ መግቢያ ፡ መመላለሻ ፤ በታላቅ ፡ ቤትና ፡ በቤተ ፡ ክሲያን ፡ ደጅ ፡ አፍ ፡ ወይም ፡ በዙሪያው ፡ ግጥም ፡ ተያይዞ ፡ የሚሠራ ፤ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ ዐምድ ፡ የቆመበት ፡ ከበታቹ ፡ ዕርከኖች ፡ ያሉት ፤ ዕርከን ፡ ተረግጦ ፡ የሚገቡበት ። ኢሳምን ፡ እይ ። አንሶሰወ ፡ በሕዋረ ፡ ሰሎሞን ። ወባቲ ፡ ኀምስቱ ፡ ሕዋራት ፡ (ዮሐ፲ ፡ ፳፫ ። ፭ ፡ ፪ ። ግብ፫ ፡ ፲፩) ።


—፤ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ጓዳ ፡ ታዛይ ፡ በቤት ፡ ዙሪያ ፡ ወይም ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ከቤቱ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚኖር ፡ የሚነደቅ ፤ በላይ ፡ አንድ ፡ ኹና ፡ በውስጥ ፡ የተለየ ፡ ታናሽ ፡ ጠባብ ፡

ክፍል ፡ ዕልፍኝ ። ኤስኬደራን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ለቸኩን ፡ እንከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኑኃ ፡ መንገለ ፡ ምሥራቅ ፤ ወክልኤ ፡ ሕዋራት ፡ ውስተ ፡ ገበዋቲሃ ፡ በአምሳለ ፡ ሐመር ። ሕዋር ፡ ማእከላዊ ። ወናሁ ፡ ሕዋራት ፡ (ዲድ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ መጋ፳፫ ። ሕዝ፵፩ ፡ ፲፯) ።

**አስተሓወረ** ፤ አከኼደ ፡ አዋሰደ ፡ አኖዳ ፤ የእግር ፡ የነገር ። ያስተሓውሩ ፡ ነቢበ ። ኢያስተሓውራ ፡ ነገረ ፡ (ኑሐ፮ ፡ ፲፱ ። ቲቶ፪ ፡ ፫) ።

**መስተሓውር** ፤ የሚያከኺድ ፤ አዋሳጅ ፡ መናጀ ። አባባቂ ፤ መስተዋድይ ። ዓዲ ፡ መስተሓውራን ፡ (፪ተስ ፡ ፫ ፡ ፲፩) ።

**አሑር** ፤ አውራ ፤ ኰርማ ፤ አለሌ ። ሐርጌ ፡ አሕሩግ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አሑር ፡ አሑረ ፡ በግዕ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (ዕዝ፲ ፡ ፲፱) ።



አሑር ፡

**ሖር** ፤ (ዐረ ፡ ሐውር) ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ኽያጅ ፡ ዘዋሪ ። አባ ፡ ሖር ፡ እንዲሉ ።

**ሖር** ፤—ብስ ፡ ነዳላ ፤—ነረወ ፡ ኖር ።

**ሐዊስ** ፤ ሶት ፤ (ሐሰ ፡ የሐውስ ፡ ይሑስ ፤ ክሰ ። ዕብ ፡ ሓሽ ። ዐረ ፡ ሐሰ ፤ ሀዘ) ፤ መፍጠን ፡ መቀልጠፍ ፤ መቸኰል ። ማዘን ፡ መታወክ ፤ መዋለል ። መነቅነቅ ፡ መናጥ ፡ ማናወጥ ፡ ማንቀሳቀስ ፤ ራስን ፡ ሕዋስን ። ኮለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሖሰ ፡ ፈንታ ፡ አሖሰ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። አሖሰ ፡ ርእሶ ፡ ዲቤኪ ። አሖሱ ፡ ከናፍሪሆሙ ፡ ላዕሌየ ። በአሕውሶ ፡ ከነፊሁ ፡ (ኢሳ፴፯ ፡ ፳፪ ። ሰቈ፫ ፡ ፷፭ ። ጥበ፭ ፡ ፲፭) ።

**አሖሰ** ፤ (ያሐውስ ፤ ያሑስ) ፤ አስቸኰለ ፤ አሳዘነ ፤ አድራጊ ። አስነቀነቀ ፤ አስደራጊ ።

**ተሐሰ** ፤ ተሐውሰ ፤ ተነቃነቀ ፤ ተናወጠ ፡ ተንቀሳቀሰ ፡ ተወዛወዘ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ ፤ ዐለፈ ። ኢይትሐወስ ፡ እንከ ፡ እመንበሩ ። ዘመደ ፡ እንስሳ ፡ ወዘይትሐወስ ። ብርዕ ፡ ዘይትሐወስ ፡ እምነፋስ ። ይትሐወስ ፡ ጽላሎቱ ፡ (ኢሳ፶፯ ፡ ፯ ። ዘፍ፩ ፡ ፳፱ ። ማቴ፲፩ ፡ ፯ ። ማሕ፱ ፡ ፯) ። ታወሰ ፡ አስታወሰ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ተሐዋሲ** ፤ (ሲት ፡ስያን ፡ ያት) ፤ የሚንቀሳቀስ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ ያሙስና ፡ ያርብ ፡ ፍጥረት ። ኢይሚጥ ፡ ምንተኒ ፡ እምተሐዋስያን ፡ አው ፡ እምእለ ፡ ኢይትሐወሱ ። ነሰሳወ ፡ ተሐዋስያን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፱ ። ጥበ፲፯ ፡ ፱) ።

**ሕዉስ** ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ውስት) ፤ የተላወሰ ፡ የተንቀሳቀሰ ፤ የተነቃነቀ ፡ ንቅንቅ ።

**ሑሰት** ፤ (ታት) ፤ መፍጠን ፤ መታወክ ፡ መናወጥ ፤ መንቀሳቀስ ፤ ንቅንቃ ። ሑሰታ ፡ ለጥበብ ፡ ይፈጥን ፡ እምኵሉ ፡ ሑሰት ። በሑሰተ ፡ ልብነ ። ሑሰተ ፡ ባሕር ። ረሰይከነ ፡ ሑሰተ ፡ ርእስ ፡ ለሕዝብ ። ውልዋሴ ፡ ወሑሰተ ፡ ነፍስ ፡ (ጥበ፯ ፡ ፳፬ ። ፪ ፡ ፪ ። ሔኖ፻፩ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፵፫ ። ፊልክ ፡ ፻፱) ።

**ሐዊሳ** ፤ ፍጥነት ፡ ችኰላ ፡ ንቅንቃ ፡ ቅስቀሳ ። የደስታና ፡ የአንክሮ ፡ የሰላምታ ፡ ቃል ፤ ሐዲስ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ምስጢር ፡ ከማየት ፡ ከመስማት ፡ የተነሣ ፡ ራስን ፡ ዐንገትን ፡ በመነቅነቅ ፤ ወሰሙ ፡ ወሰሙ ፤ መልካም ፡ መልካም ፤ ይበል ፡ ይበል ፤ ዕሠይ ፡ ዕሠይ ፡ ማለት ። ሐዊሳ ፡ ሐዊሳ ፡ ሊዝንቱ ፡ ሐዋርያ ። ሐዊሳ ፡ ለምጽአትከ ፡ ወለመዊአትከ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፪ ። ዮሴፍ) ። የሰላምታ ፡ ቃል ፡ ሲኾን ፡ ፍችው ፡ እንደ ፡ በሓ ፡ ነው ። ኢይፈርህ ፡ ብሂሎተከ ፡ ሐዊሳ ፡ ሐዊሳ ፤ እስመ ፡ ባሕረ ፡ ልብየ ፡ መልአ ፡ ሰላምከ ፡ ዓሣ ፡ (ደራሲ) ።

**ሕዋስ** ፤ (ሳት ። ዐረ ፡ ሐስ ። ዕብ ፡ ሑሽ ። ሱር ፡ ሓሽ) ። በቁሙ ፤ ገላ ፡ አባል ፤ ኅሊና ፤ የአፍኣ ፡ የውስጥ ፡ የሥጋ ፡ የነፍስ ፡ መሣሪያ ፡ የሚላወስ ፡ የሚንቀሳቀስ ። ይልቁንም ፡ ዐይንና ፡ ጆሮ ፡ አፍና ፡ አፍንጫ ፡ እጅ ። ዳግመኛም ፡ በነዚህ ፡ ባምስቱ ፡ የሚሠራ ፡ ፭ቱ ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፤ ማየትና ፡ መስማት ፡ መቅመስና ፡ ማሽተት ፡ መዳሰስ ፤ በቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ ፭ ፡ ሕዋስ ፡ ይባላል ። ሕዋሳትሰ ፡ ዐሠርቱ ፡ እሙንቱ ፤ ኀምስቱ ፡ ዘአፍኣ ፡ ወኀምስቱ ፡ ዘውስጥ ። ወሕዋሳትሰ ፡ ዘውስጥ ፡ እሙንቱኬ ፡ ልቡና ፡ ወአእምሮ ፡ ወፈሊጠ ፡ እኩይ ፡ እምሠናይ ፡ ወሰብዎ ፡ ወተገሥጾ ። ወሕዋሳትሂ ፡ እለ ፡ ያስተርእዩ ፡ እሙንቱኬ ፡ ሰሚዕ ፡ ወርእይ ፡ ወአጼንዎ ፡ ወጥዒም ፡ ወገሲስ ፡ (ፈላስ ፡ ገ፻፫) ። በግእዝ ፡ ልማድ ፡ ግን ፡ እሊህን ፡ ዐሥሩን ፡ የሕዋሳት ፡ ግብር ፡ ማለት ፡ እንጂ ፡ ሕዋሳት ፡ ማለት ፡ አይመችም ፤ ጸያፍ ፡ ይኾናል ፤ ሕዋስ ፡ የሚባል ፡ መሣሪያው ፡ ብቻ ፡ ነው ። በነዚህ ፡ ባ፭ቱ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ እግርና ፡ አባለ ፡ ዘር ፡ ሲጨመሩ ፡ ሕዋሳተ ፡ አፍኣ ፡ ፯ ፡ ይባላሉ ።

**ሐሰ** ፤—ቀላቀለ ፤—ነዊሥ ፡ ኖሠ ፡ ኑሠት ።

**ሐውት** ፤ ሐይት ፤ (ዕብ ፡ ሔት) ፤ የፊደል ፡ ስም ፤ ፰ኛ ፡ ፊደል ፡ ሐ ፤ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ። ሕይወት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሐይወን ፡ እይ ። ምስጢሩ ፡ በ፰ኛው ፡ ሺሕ ፡ የሚኾን ፡ ሐዲስ ፡ ሕይወትን ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ ከስንኚው ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ያሳያል ፡ (ዮሐ፲፩ ፡ ፳፭ ። ማቴ፳፪ ፡ ፴፪) ። ጸሐፍት ፡ ግን ፡ ሐመር ፡ ሐ ፡ ይሉታል ።

**ሑት** ፤ (ዐረ ፡ እልሑት) ፤ ስመ ፡ ኮከብ ፤ ከ፲፪ቱ ፡ መናግሽል ፡ አንዱ ። በየካቲት ፡ ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ ፴፭ ፡

ዕለት ፡ ፲ ፡ ኬክሮስ ፡ ይመግባል ። ፍችው ፡ ዓሣ ፡ ማለት ፡ ነው ። (አቡሻ ፡ ፱) ።

**ሐዚእ ፡ አት ፤** (ሐዝአ ፡ የሐዝእ ፡ ይሕዛእ ። ዐረ ፡ ሐዘአ) ፤ መንዳት ፡ ማባረር ፡ ማሳደድ ፤ ሰብሰበ ፡ አስቀድሞ ፡ መከተል ፤ የረኛ ፡ ያርበኛ ። ነድአን ፡ እይ ።

**ሐዛኢ ፤** (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤ የሚነዳ ፡ ነጅ ፡ አባራሪ ፡ አሳዳጅ ።

**ሕዝእ ፤** (እት ፤ አው ፡ ሕዝአት ፤ ታት) ፤ መሰምሪያ ፡ ማሰምሪያ ፡ ማደሪያ ፡ በረት ፡ ምሳግ ፤ ዋሻ ፡ ጕሬ ። በሸሉ ፡ ፍኖት ፡ መጽዮሕት ፡ ሕዝአቶሙ ። ወይክውን ፡ ሕዝአቶሙ ፡ ህየ ። ዕጕልት ፡ በውስተ ፡ ሕዝአቶሙ ፡ ጠፍአ ። ዕርግ ፡ እምሕዝአትከ ። ቀኝ ብእ ፡ ሕዝብ ፡ ውስተ ፡ በአታት ፡ ወውስተ ፡ ሕዝአታት ፡ (ኢሳ ፵፱ ፡ ፱ ። ሕዝ ፴፬ ፡ ፲፬ ። ዮኤ ፩ ፡ ፲፯ ። ዘ ፍ ፵፱ ፡ ፱ ። ፩ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፮) ።

—፤ መግቢያ ፡ በር ፤ ወሰን ፡ ደንበር ፤ ርስት ፡ ጕልት ። ወሰምድረ ፡ ናምሩድ ፡ በውስተ ፡ ሕዝአቲ ። ወሎሩ ፡ ካም ፡ ወውሉዱ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ እንተ ፡ ሕዝአት ፡ ሎቱ ፡ ዘረከቦ ፡ በመክፈልቱ ፡ (ሚክ ፭ ፡ ፮ ። ኩፋ ፡ ፲) ።

**ሐዝቦ ፤ ቦት ፤** (ሐዘበ ፡ ይሔዝብ ፡ የሐዝብ ። ሐሰበ) ፤ ማዘብ ፡ ማሰር ፤ የሓማማ ፡ የመሓማሚያ ። መሰብሰብ ፡ መወገን ። ማሰብ ፤ መጠርጠር ፤ መፍራት ፡ ምን ፡ አልባት ፡ ማለት ። አነ ፡ አሐዝብ ፡ ከመ ፡ መልአክ ፡ ውእቱ ። ወኢሐዘብኩ ፡ እስማዕ ፡ ቃልአ ፡ ነገረ ። ኢሐዘብኩክ ፡ ትንብብ ፡ ከመ ፡ ዝ ። ሐዘብኩኑ ፡ እኩን ፡ ከማከ ። አሐዝብ ፡ ሕያዋኒነ ፡ እምውኅጡነ ። አሐዝብ ፡ ንመጽእ ፡ አነ ፡ ወእምከ ፡ ወአኀዊከ ፡ ወንሰግድ ፡ ለከ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ (ፊልክ ፡ ፶፪ ። አቅሮ ፡ ፬ ፡ ፬ ። ኢዮ ፴ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፵፱ ። ፻፳፫ ። ዘፍ ፴፯ ፡ ፲) ። ዳግመኛም ፡ በሐዘበ ፡ ፈንታ ፡ ተሐዘበ ፡ ይባል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ተሐዘበ ፡ ከመ ፡ ዘማዊት ። ብእሲ ፡ ዘይትሔዘብዎ ፡ በዝሙት ። በከመ ፡ ይትሔዘቡ ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ አእምሮ ። ምንተኑመ ፡ ትትሔዘቡኒ ። ትትሔዘብኑ ፡ ታስተአብዮ ፡ ለእግዚ ። እትሔዘብ ፡ ናስጠርዮስ ፡ ዝንቱ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፯ ። ቄለመ ፡ ፲፫ ። ፊልክ ፡ ፻፶፲፱ ። ድጓ ። ሮሜ ፪ ፡ ፱ ። ቄር ፡ ጸጓ) ።

**ሐዛቢ ፤** (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ዘብት) ፤ የሚያዝብ ፤ የሚሰበስብ ፤ ዐሳቢ ፡ ጠርጣሪ ።

**አሐዘበ ፤ አስተሐዘበ ፤** አሳሰበ ፡ አስጠረጠረ ። አንዘ ፡ አንደፊር ፡ ይድግም ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ኀበ ፡ ህርቃኖስ ፡ ወያሐዝቦ ፡ ለእንሁ ። ተዘከር ፡ ከመ ፡ ኢይጐነዲ ፡ ሞት ፡ ወኢታስተሐዝብክ ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ (ዮሴፍ ። ሢራ ፲፬ ፡ ፲፪) ።

**ተሐዘበ ፤** ታዘበ ፡ ተሰበሰበ ፤ ታሰበ ፡ ታማ ፤ ተጠረጠረ ። ባማርኛ ፡ ግን ፡ ናቀ ፡ መሰከረ ፡ ይኾናል ፤ እንዲሁ ፡ ታዘብኝ ፡ እንዲሉ ።

**ሕዙብ ፤** (ብን ፡ ብት ፡ ዝብት) ፤ የታዘበ ፡ የተሰበሰበ ፤ የታሰበ ፡ የተጠረጠረ ። ወዕለታኒ ፡ ሕዝብት ፡ እኪት ፡ (ኢሳ ፳፰ ፡ ፲፱) ።

**ትሕዝብት ፤** በቁሙ ፤ ትዝብት ። ጥርጣሬ ፡ ጥርጥር ፤ የፍርሀት ፡ ሐሳብ ። እምፍርሀት ፡ ወእምትሕዝብት ፡ ዘይመጽእ ። እምትሕዝብተ ፡ ጸላኢ ። በሰማይ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ፍርሀት ፡ ወኢትሕዝብት ። ፍርሀቱ ፡ ወትሕዝብቱ ፡ (ሉቃ ፳፩ ፡ ፳፮ ። መዝ ፡ ፶፫ ። ግንዘ ። ዮሴፍ) ።

**ተሓዘበ ፤** ተዛዘበ ፡ ተሳሰበ ፡ ተጠራጠረ ።

**አስተሓዘበ ፤** አስተዛዘበ ፡ አጠራጠረ ፡ አስተማማ ።

**ሕዝብ ፤** (ብ ፡ ሕዘብ ፤ አሕዛብ) ፤ በቁሙ ፤ ወገን ፡ ነገድ ፤ የተሰበሰበ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፤ ጉባኤ ፡ ሸንጎ ፤ ልቅዕኛ ፡ ሰርገኛ ፡ ገበያተኛ ። ያንዲት ፡ አገር ፡ ያንዲት ፡ ከተማ ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ብሔር ፡ ያንድ ፡ መንግሥት ፡ ሰው ፤ ቋንቋውና ፡ ሕጉ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፤ ባንድ ፡ ሕግ ፡ የሚኖር ። ውስጠ ፡ ብዙኅነት ፡ ስላለው ፡ ባንድም ፡ በብዙም ፡ በወንድም ፡ በሴትም ፡ ይነገራል ። ሕዝብ ፡ ዐቢይ ። ዝ ፡ ሕዝብ ፡ አብድ ፡ ወአከ ፡ ጠቢብ ። ሕዝብ ፡ ጽኑዕት ። ከመ ፡ ትፃእ ፡ የም ፡ አሐቲ ፡ ሕዝብ ፡ እምእስራኤል ። ሕዝብ ፡ ንኪራን ፡ ወእኩያን ፡ (ዘፍ ፲፪ ፡ ፪ ። ዘዳ ፴፪ ፡ ፮ ። ሚክ ፬ ፡ ፯ ። መሳ ፳፩ ፡ ፫ ። ኢሳ ፲፰ ፡ ፪) ። ስሕቱ ፡ ግብጽ ፡ በበ ፡ ሕዘቢሆሙ ። ሕትቶሙ ፡ ለአበው ፡ በበ ፡ ሕዘቢሆሙ ። ተደመሙ ፡ ሰብእ ፡ ወሕዘቢሁ ፡ አንከሩ ። ለምንት ፡ አንገለጉ ፡ አሕዛብ ። ይገንዩ ፡ ለከ ፡ አሕዛብ ፡ እግዚኦ ። አግረረ ፡ ለነ ፡ አሕዛበ ፡ ወሕዝበ ፡ ታሕተ ፡ እገሪነ ፡ (ኢሳ ፲፱ ፡ ፲፫ ። ኢዮ ፳ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ታኅ ፲ ። መዝ ፡ ፪ ። ፷፮ ። ፵፮) ።

**ሕዝባዊ ፤** (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፡ የሕዝብ ፡ ወገን ፤ ከህን ፡ ያይደለ ፡ ማይምን ፤ ሲቪል ፡ ባላገር ። በእንተ ፡ ተግሣጽ ፡ ወትእዛዝ ፡ ሕዝባውያን ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዊ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭ ። ፲፱ ። ዲድ ። ኪዳ ። ቀሌ) ።

**ሕዝብና ፤ ሕዝበት ፤** ሕዝብነት ፡ ወገንነት ፡ ሕዝብ ፡ መኾን ። እስመ ፡ ተኀድገ ፡ ሕዝብናከ ፡ (ተረስዐ ፡ ሕዝበትከ) ፡ እስራኤል ፡ (ኢሳ ፪ ፡ ፮) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ (ኪ ፡ ናጣሽታ ፡ ዐምኻ ፡ ቤት ፡ ያዕቆብ) ፡ እስመ ፡ ገደፍከ ፡ ሕዝበከ ፡ ቤተ ፡ ያዕቆብ ፡ ይላል ።

**ሐዚዝ ፤ ዝት ፤** (ሐዘ ፤ ሐዘዘ ፡ የሐዝዝ ፡ ይሕዝዝ) ፤ ማነቅ ፡ መሰርነቅ ፡ ማስፈነቅ ፡ ማስፋቅ ፡ ሕቅ ፡ ስርቅ ፡ ማሰኘት ፡ ማንዘዝ ፡ ትን ፡ ማለት ፡ ባፍንጫ ፡ መውጣት ፡ መምረር ፡ መክርከር ፡ መሎምጠጥ ፡ መጐፍነን ፡ የመጠጥ ፡ የፈሳሽ ፡ ነገር ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሐዘዘ ፡ ፈንታ ፡ አሕዘዘ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ያስትይዎ ፡ ብሒአ ፡ ዘምስለ ፡ ሐሞት ፡ ለአሕዝዞቱ ። በእንተ ፡ ጕርዔከ ፡ ለቴ ፡ ሐሞት ፡ ዘአሕዘዘ ። ዐቀቦ ፡ ለዮናስ ፡ በከርሠ ፡ ዐንበሪ ፡ ከመ ፡ ኢያሕዝዞ ፡ ሞገደ ፡ ባሕር ፡ (አር ፫ ። አ

ቀል ። መጽ ፡ ምስ) ። ዳግመኛም ፡ ዐንተ ፡ ክበበ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ አሕዘዘኒ ፡ ማይ ፡ እስከ ፡ ነፍስየ ፡ ይላል ፡ (ዮና፪ ፡ ፭) ።

—፤ መጕንፈጽት ፡ መማግ ፤ ገሞ ፡ ጕርጕሞ ፡ ማድረግ ፤ መዋጥ ፡ ማሥረግ ፤ ኹሉም ፡ የጕረሮና ፡ ያፍ ፡ ያፍንጫ ፡ ሥራ ፡ ነው ። መጥቈር ፡ መዝጕን ፡ መብሰዝ ፤ እንዝዝ ፡ መምሰል ፤ ማሳከክ ፡ መሻከር ፡ መቀንቀን ፤ የሥጋ ፡ የገላ ፡ ክደዌ ፡ ክበትር ፡ የተነሣ ። የሐዝዘኒ ፡ በሕቁ ፡ ማእስየ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፴) ። ዘሕዝሐን ፡ እይ ።

**አሕዘዘ** ፤ አስጐነጨ ፤ አስጐረጐጨ ። ነሥአ ፡ ሰፍነገ ፡ መመልእ ፡ ብሒአ ፡ ወአሰረ ፡ በኅሴት ፡ ወአሕዘዞ ፡ (ማቴ፳፯ ፡ ፵፰) ።

**ሐዝሐዝ** ፤ ኵረት ፡ ጠጠር ፡ ጭንጫ ፡ አሸዋ ። ማግጥ ፡ ረግረግ ፡ ውኃማ ፡ ቦታ ፡ ፈላ ፡ ቈጠማ ፡ ሸንበቆ ፡ መቃ ፡ የሚበቅልበት ። ማእከለ ፡ ጸላዕት ፡ ይበይት ፡ ወውስተ ፡ ሐዝሐዝ ፡ የሐዩ ። ይሰጥሞ ፡ ሐዝሐዝ ፡ ፈለግ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፯ ። ፵ ፡ ፳፫) ። ሐዘንን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ሐዚል ፤ ሎት ፤ (ሐዘ(ዝ)ለ ፡ የሐዝል ፡ ይሕዝል)** ፤ ማዘል ፡ መሸከም ፤ በገርባ ፡ በሕፅን ። ዘባንኪ ፡ እምዘባኑ ፡ ኪሩብ ፡ ዘዐብየ ፤ ሐዚሎ ፡ እሳተ ። ሐፃኒት ፡ አንተ ፡ ተሐዝል ፡ ደቂቃ ። ወሐዘሎሙ ፡ በክነፊሁ ፡ (ደራሲ ። ሽተስ ፡ ፱ ፡ ፫ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፲፩) ።

**ሐዛሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ዘልት)** ፤ የሚያዝል ፡ ዐዛይ ፤ ተሸካሚ ። ዕደው ፡ ሐዘልት ፡ (፪ዜና ፡ ፪ ፡ ፪) ።

**አሕዘለ** ፤ አሳዘለ ፡ አሸከመ ፤ ማን ፡ አስደበለለ ።

**ተሐዝለ** ፤ ታዘለ ፡ ተሰማን ፤ ሸከም ፡ ኾነ ፡ ተለጠፈ ። ተሐዚሎ ፡ በዘባንኪ ፡ (አርጋ) ።

**ሕዙል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ዝልት)** ፤ የታዘለ ፤ ዕዝል ፡ ቅጥል ። ሕዙላን ፡ በክነፊሁ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ማሕዘል ፤ ልት ፤ (ብ ፡ መሓዝል ፡ ላት)** ፤ ማዘያ ፡ መሸከሚያ ፤ አንቀልባ ።

**ተሓዘለ** ፤ ተዛዘለ ፡ ተደራረበ ፤ ተነባበረ ።

**አስተሓዘለ** ፤ አስተዛዘለ ፡ የዜማ ፡ የድጋም ። ይበል ፡ በአስተሓዝሎ ፡ (ድጓ) ።

**ምሕዛል ፤ ምስትሕዛል** ፤ ማስተዛዘያ ፤ የሚያስተዛዝሉት ፡ ዜማ ፡ ድጋም ፡ (ድጓ) ።

**ሕዝል** ፤ ስዝል ፤ የዜማ ፡ ስም ፤ የግእዝ ፡ ድርብና ፡ ታዛይ ፡ ኹለተኛ ። ስዝልን ፡ እይ ፤ ሊጣፍ ፡ የሚገባው ፡ በሐ ፡ ነበረ ፤ ሐና ፡ ፀ ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ሕ ፡ በስ ፡ ተለውጧል ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ቃል ፡ አለ ።

**ሐዚን ፤ ኖት ፤ (ሐዘ(ዝ)ነ ፡ የሐዝን ፡ ይሕዝን ። ዐረ ፡ ሐዚነ)** ፤ ማዘን ፡ መቈርቈር ፤ መቈጣት ፡ መናደድ ፤ መከፋት ። በመጥፎ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ተቀምጦ ፡ ምኝት ፡ ከማጣት ፡ የተነሣ ፤ ሐዝሐዝን ፡ እይ ። ሐዘነ ፡ መንፈሳ ፡ ለርብቃ ። ለምንት ፡ ተሐዝን ። ወሰሚያሙ ፡ ፀሐርቱ ፡ ሐዘኑ ፡ በእንተ ፡ ክልኤቱ ፡ አኃው ፡ (ኩፋ ፡ ፳፯ ። ዘፍ፵ ፡ ፯ ። ማቴ፳ ፡ ፳፬) ።

**ሐዛኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፤ የሚያዝን ፡ ዐዛኝ ፤ ተቈርቋሪ ። ብእሲ ፡ ሐዛኒ ፡ ያየብስ ፡ አዕፅምቲሁ ፡ (ምሳ፲፯ ፡ ፳፪) ።

**ሕዙን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ዝንት)** ፤ ያዘነ ፡ የተቈረቈረ ፤ የከፋው ፡ ሐዘንተኛ ። ብእሲ ፡ ሕዙን ። ልብ ፡ ሕዙን ። ጽሉ ፡ ሕዙን ፡ መንፈስ ። ሕዙን ፡ ገጽክሙ ። ሕዙናን ፡ በእንቲኣሁ ፡ (ሢራ፳ ፡ ፲፩ ። ዘዳ፳፰ ፡ ፷፭ ። ፩ነገ ፡ ፳፱ ፡ ፱ ። ዘፍ፵ ፡ ፯ ። ግንዘ) ።

**ሐዘን ፤ (ናት)** ፤ በቁሙ ፡ ዐዘን ፤ ደረቅ ፡ ሸክራ ፡ ጥኑ ፡ ጠንካራ ፡ ነገር ፤ የሚያንድ ፡ የሚያጤስ ፤ የሚያስለቅስ ፡ ሐሳብ ። ሐዘን ፡ ኢይባእኪ ፤ እስመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ሞቱ ፡ እንበይነ ፡ ሐዘን ። እስመ ፡ ሐዘኑ ፡ ለልብ ፡ ይሰብሮ ፡ ለኀይል ። ወንሬስየክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ሐዘን ። እንተ ፡ ኢፈጸመት ፡ ዕድሜ ፡ ሐዘኑ ፡ ምታ ፡ ዘሞተ ። ሐዘናት ፡ ብዙኃት ፡ (ሢራ፴፰ ፡ ፲፰ ። ማቴ፳፰ ፡ ፲፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፱ ። ፈልክ ፡ ፸፱) ።

**ሐዘንዚን** ፤ የልቅሶ ፡ ቃል ፤ ወርድ ፡ ንባብ ፤ የሐዘን ፡ ዜማ ። ካህናት ፡ ይትቀነዩ ፡ ዘንተ ፡ መዝሙረ ፡ በዜማ ፡ ሐዘንዚን ፡ (ግንዘ) ።

**አሕዘነ** ፤ አሳዘነ ፡ አስቈረቈረ ፤ አስቀየመ ፡ አስከፋ ፤ አስቈጣ ። ኢታሕዝኖ ፡ ለአቡከ ፡ በሕይወቱ ። ከመ ፡ ኢያሕዝንከ ። ኢያሕዝኖ ፡ በእንተ ፡ አባግዕ ። ወአሕዘኖ ፡ ለቃየን ፡ ጥቀ ፡ (ሢራ፫ ፡ ፲፪ ። ፫ ፡ ፲ ። ዮሐ፲ ፡ ፲፫ ። ዘፍ፬ ፡ ፭) ።

**ማሕዘኒ ፤ ማሕዝን ፤ (ቅጽልና ፡ ጥሬ)** ፤ የሚያሳዝን ፤ አሳዛኝ ። ማዘኛ ፤ ማሳዘኛ ። ሞት ፡ ማሕዘኒ ። ቃል ፡ ማሕዘኒ ። ማሕዘኒ ፡ ኮኖ ፡ ዝ ፡ ቃል ። ኅዳጥ ፡ ውእቱ ፡ ነብረትኒ ፡ ወማሕዝን ። በአርኣያ ፡ ማሕዘን ፡ (አዋል ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፰ ። ኩፋ ፡ ፲፯ ። ጥበ፪ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ተ፲፩) ።

**ሐዝዐ ፤—ነዳ ፡ አባረረ ፤—ሐዚእ ፡ ሐዝአ ።**

**ሐዙር ፤ (ዐረ ፡ እልሐዝር)** ፤ ግምት ፡ መላ ፤ ጥንቈላ ። ከታብ ፡ ሥራሥር ፤ መንድግ ፤ መስተፋቅር ። እለ ፡ ይገብሩ ፡ እልሐዙረ ፡ በሥርናዕ ፡ ወይፈቅዱ ፡ ቦቱ ፡ ይርብሐ ፡ ረባሐ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶ ፡ ፳) ።

**ሑኸራ ፤—ሠግር ፤—ሁጀ(ግ)ራ ።**

**ሐዙራን ፤ (ሱር ፡ ወዐረ ፡ ሐዚራን)** ፤ የወር ፡ ስም ፤ የሶርያ ፡ ወር ፡ ሠኔ ፡ (ገድ ፡ ላሊ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ሐሐርኤል ፤-ምሥዋዕ ፤-ሀሀርኤል ።**

**ሐጢብ ፤ ቦት ፤ (ሐጠበ ፡ የሐጥብ ፡ ይሕጥብ ። ዕብ ፡ ሐጣብ ። ዐረ ፡ ሐጠበ)** ፤ መቍረጥ ፡ መፍለጥ ፡ መከትከት ፤ መስበር ፡ መሰባበር ፤ መልቀም ፡ መሰብሰብ ፤ የንጨት ፡ የማገዶ ። ሒምናክሙ ፡ ትሕጥቡ ፤

ዕፀ ፡ ወትቅድሑ ፡ ማየ ። ዘየሐጥብ ፡ ዕፀ ። ይሐጥብ ፡ ዕፀ ። ተሐጥበ ፡ ዕፀወ ። ሶበ ፡ የሐጥብ ፡ ዕፀወ ፡ ይሜጽር ፡ በበ ፡ አርብዓ ፡ ጸረ ፡ ብእሲ ፡ እስከ ፡ ያነጢ ፡ ዘይጸውር ፡ ሎቱ ፡ (ኢያ፱ ፡ ፳፱ ፡ ፳፫ ። ዘዳ፳፱ ፡ ፲፩ ። ፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ሐጣቢ** ፤ ብ ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ጠብት) ፤ የሚቈርጥ ፡ የሚፈልጥ ፡ ሰባሪ ፡ ለቃሚ ፡ ቍራፊ ፡ ቋሚ ። እምሐጣበ ፡ ዕፀ ፡ እስከ ፡ ሐዋሬ ፡ ማይ ። ሐጣብያኒ ፡ ዕፀ ፡ ወቀዳሕያኒ ፡ ማይ ፡ (ዘዳ፳፱ ፡ ፲ ። መቃ ፡ ገ፷) ።

**ሐጥብ** ፤ (ዐረ ፡ ሐጠብ) ፤ የሙገድ ፡ የማገዶ ፡ ዕንጨት ፤ ፍልጥ ፡ ጭራሮ ፡ ጉቶ ፡ ጉልጥምት ። ሥልሰ ፡ ሌልያስ ፡ ውስተ ፡ ዕፀ ፡ ሐጥብ ፡ ወውስተ ፡ አባለ ፡ ላሕም ፡ ማየ ፡ ሰዊጦ ፡ እሳተ ፡ እምሰማይ ፡ አውረደ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ (ተረ ፡ ቁር ፡ ሳዊ) ።

**ሕጥሜ** ፤—ሥንቆ ፤—ኅጥሜ ።

**ሐዩብ** ፤ ቦት ፤ (ሔበ ፡ የሐይብ ፡ ይሒብ ። ደለወ ። ዕብ ፡ ሻአብ) ፤ ማየብ ፤ መቀዳት ፡ መጥለቅ ፡ መደንበቅ ፤ መሳብ ፡ መጐተት ፤ ከጕድጓድ ፡ ከዘቅት ፡ ከጨልፎ ፡ ማውጣት ፡ (ዘፀ፪ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱) ። ደለወን ፡ ተመልከት ።

**ማሕየብ** ፤ (ባት) ፤ መቅጃ ፡ መጥለቂያ ፤ የውሃ ፡ ዕቃ ። ማሕየብኒ ፡ አልብከ ። ከመ ፡ ነጠብጣበ ፡ ማሕየብ ። ማሕየበ ፡ ዐዘቅት ። ምልኢዮን ፡ ለዙሎን ፡ ማሕየባት ፡ (ዮሐ፬ ፡ ፲፩ ። ኢሳ፵ ፡ ፲፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳) ።



ማሕየብ ።

**ሐየብ** ፤ አው ፡ ሐበይ ፡ (ዕብ ፡ ሖቢት ፤ በርሚል ። ሱር ፡ ሓቢታ ። ዐረ ፡ ኅቢየት ፤ ኂባእ) ፤ የሸክላ ፡ ዕቃ ፤ ቡይት ፡ መንቀል ፡ ኰስኰስት ፡ የዘይት ፡ ገንቦ ፡ ማድጋ ፡ ፈቀን ፡ ዝንግሪር ፡ ጋን ፤ ሆደ ፡ ሰፊ ፡ አፈ ፡ ጠባብ ። ርእሰ ፡ ሐበይ ፡ ስሳ ፡ ምእት ፡ ዐሠርቱ ፡ ወኅምስቱ ፡ ወመሥረበ ፡ ማይሂ ፡ ተስዓ ፡ ወአሐዱ ፡ (ታሪ ፡ እኆ) ።

**ሐይብ** ፤ በቁሙ ፤ ዐይብ ፡ የላም ፡ ልጅ ፡ የርጎ ፡ ተወራጅ ። (ትረት) ፤ ዐይቡ ፡ ዳኛ ፤ ቅቤው ፡ መልከኛ ፡ (መ ፡ ፈ) ።

**ሐይድ** ፤—ቅሚያ ፤—ሀዩድ ፡ ሄደ ።

**ሐዩው** ፤ ዎት ፤ (ሔወ ፡ ሐይወ ፡ የሐዩ ፡ ይሕዩ ፤ የው ። ዕብ ፡ ሐያህ ፤ ሐይ ። ሱር ፡ ሕያእ ። ዐረ ፡ ሐየ) ፤ መዳን ፡ መፈወስ ፡ ወደ ፡ ጥንተ ፡ ሕይወት ፡ መመለስ ፤ መታደስ ፡ ዳግመኛ ፡ መሠራት ፤ ሙቶ ፡ መነሣት ፡ በሕይወት ፡ በጤና ፡ መኖር ፤ አለመታመም ፡ አለመሞት ። እመ ፡ ደወየ ፡ ኢይሴፎ ፡ ሐዩወ ። ትፌቅድኑ ፡ ትሕየው ። አመ ፡ የሐይዉ ፡ ምዉታን ። ወሐይወ ፡ አዳም ፡ እምድኅረ ፡ ወለደ ፡ ለሴት ፡ ሰብዐተ ፡ ምእተ ፡ ዓመተ ። ሕየው ፡ ለዓለም ፡ (ኢዮ፲፬ ፡ ፳፫ ። ዮሐ፭ ፡ ፮ ። ማር፲፪ ፡ ፳፫ ። ዘፍ፭ ፡ ፬ ። ዳን፫ ፡ ፱) ።

—፤ ደስ ፡ ፈቅ ፡ ማለት ፤ ደስታ ፡ መመላት ፤ ምስጢሩ ፡ መታደስ ፡ ከሰው ፡ ይገባል ። ሐይወ ፡ ልቡ ፡ ወነፍሱ ፡ ለያዕቆብ ። ተሐደሰት ፡ ወሐይወት ፡ መንፈሱ ፡ (ዘፍ፵፭ ፡ ፳፯ ። ኩፋ ፡ ፵፫) ። ሐዮኩ ፡ ከ ፡ ኪ ፡ ሐዮን ፡ ከሙ ፡ ክን ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ሀለወ ፡ በቅርብ ፡ በቅርቦች ፡ ይገኛል ። ሐውትንና ፡ ሔትን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ናቸው ።

**ሕያው** ፤ (ውት ፡ ዋን ፡ ዋት) ፤ በቁሙ ፤ ንዋሪ ፡ ደኅና ፡ ባለጤና ፡ ነፍስና ፡ ደም ፡ ነፍስ ፡ እስትንፋስ ፡ ያለው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ፍጥረት ፡ ገና ፡ ያልሞተ ፡ በሕይወት ፡ ያለ ። ኵሉ ፡ ዘሕያው ። ሕያውኑ ፡ ዓዲሁ ፡ አቡነ ፡ (ሚክ፲፪ ፡ ፱ ። ዘፍ፵፭ ፡ ፫) ። ጭራሽ ፡ ለባሕርዩ ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ ኅልፈት ፡ ጥፋት ፡ መለወጥ ፡ ማርጀት ፡ የማይስማማው ። ቅዱስ ፡ ሕያው ፡ ዘኢይመውት ። መልአክ ፡ ዘሕያው ። ነፍስ ፡ ሕያውት ፡ (አዋል) ። ሕያዋኒ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ዘኢይመውት ፡ (ሔኖ፲፭ ፡ ፬ ፡ ፯) ።

—፤ መሐላ ፤ ቃለ ፡ መሐላ ። ሕያው ፡ እግዚ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ እትሐመወኪ ። ሕያው ፡ አነ ፡ ከመ ፡ ትበረገዊ ዮሙ ። ሕያው ፡ ነፍስከ ፡ ከመ ፡ ኢትወድእ ፡ አመትከ ፡ (ሩት፫ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፲፰ ። ዮዲ፲፪ ፡ ፬) ። ሕያዉ ፡ ሕያዎ ፡ ሕያወ ፡ በሕያው ፡ እያለ ፡ ይረቅቅ ፡ ይገኛል ። ዕጓለ ፡ መሕያው ፤ ሕያው ፡ ከመሬት ፡ ያስገኘው ፡ መዋቲ ፡ ሰው ፡ አዳም ፤ ዕጓልን ፡ እይ ።

**ሕያውና** ፤ ሕያውነት ፤ ሕያው ፡ ደኅና ፡ ባለጤና ፡ መኾን ። እንዘ ፡ ሀሎከ ፡ አንተ ፡ በሕያውናከ ፡ ዝየ ፡ (አዋል) ።

**ሕይወት** ፤ ሒወት ፤ (ታት) ፤ መዳን ፡ መኖር ። በቁሙ ፡ ደኅንነት ፤ እናምር ፡ ኑሮ ፤ ዘመን ፡ ዕድሜ ፤ ተወልዶ ፡ እስኪሞቱ ፡ ተኹሞ ፡ እስኪሻሩ ፡ የሚኖሩት ። ሕይወት ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ ሞት ። ይኄይስ ፡ መዊት ፡ እመሪር ፡ ሕይወት ። ጸላእኩ ፡ ሕይወትየ ፡ ምስለ ፡ አዋልደ ፡ ከፃን ። እሴብሖ ፡ ለእግዚ ፡ በሕይወትየ ፡ (ሉቱ ፡ ዕገዘ፰ ፡ ፲፫ ። ሢራ፴ ፡ ፲፯ ። ዘፍ፳፯ ፡ ፵፮ ። መዝ ፡ ፻፵፭) ።

—፤ ትንሣኤ ፤ ተሐድሶ ፡ ጤና ፤ ምስጢሩ ፡ ደኅንነት ፡ ከሰው ፡ ይገባል ። ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ቀዳሚት ፡ ሕይወት ። ሕይወተ ፡ ሙታን ። መጻእኪ ፡ ለሕይወትኪ ፡ (ራእ፳ ፡ ፭ ። ግብ፲፯ ፡ ፴፪ ። ዮዲ፲፩ ፡ ፫) ።

—፤ ገንዘብ ፡ ጥሪት ። ይእቲ ፡ አብአት ፡ ኵሎ ፡ ሕይወታ ፡ ወካልኣንሰ ፡ እምተረፎሙ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፮) ።

—፤ መሐላ ፤ ቃለ ፡ መሐላ ፤ ምጥንታ ። ሕይወተ ፡ ፈርዖን ፡ ከመ ፡ ኢትወፅኡ ። ሕይወተ ፡ ነፍስከ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ ይእቲ ፡ (ዘፍ፵፪ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ። ፩ነገ ፡ ፩ ፡ ፳፮) ።

**አሕየወ ፤** አዳነ ፣ ፈወሰ ፣ ፀደሰ ፣ ሕያው ፣ አደረገ ፣ አስደረገ ። ጥበብ ፡ ታሐይዎ ፡ ለዘአጥረያ ። አውረሰሙ ፡ ሕገ ፡ ዘየሐይዎሙ ። ወገሰሰ ፡ እዝኖ ፡ ወአሕየዎ ። ያሐይዉ ፡ አረፍተ ፡ ወመቅደሰ ። አሕየወ ፡ ምሥዋዐ ፡ ዘመዝበረ ፡ (መክ፯ ፣ ፲፪ ። ሚራ፲፯ ፣ ፲፩ ። ሉቃ፳፪ ፣ ፶፩ ። ዕዝ፱ ፣ ፲፯ ። ፫ነገ ፣ ፲፰ ፣ ፴፪) ።

**ማሕይው ፤ ማሕየዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** የሚያድን ፣ ዐዳኝ ፣ ፈዋሽ ፣ ሕያው ፣ አድራጊ ። ማሕይዊ ፡ ሊሖሱ ፡ በብእ ። እግዚእ ፡ ማሕየዊ ። ሕማማቲሁ ፡ መድኃኒት ፡ ወማሕየዊት ፡ (፩ጢሞ ፡ ፬ ፣ ፲ ። ቅዳ) ።

**መሕየው ፤ ምሕየው ፤** መዳኛ ፡ መኗሪያ ፣ ቦታ ፤ ምድር ፣ ዓለመ ፣ ሰብእ ፤ ወይም ፣ እግዚር ፣ ዓለመ ፣ ዙሉ ፣ ፍጡር ። ዐጽሉ ፡ መሕየው ፣ የምድር ፣ ልጅ ፣ አዳም ፤ ሥጋው ፣ ካፈር ፣ ከመሬተ ፣ ምድር ፤ ነፍሱ ፣ ከሕያው ፣ ከግዚር ፣ የተገኘች ፤ ነፍስና ፣ ሥጋ ፣ ፍጹም ፣ ሰብእ ። የአዳምንና ፣ የዕጽሉን ፣ ፍች ፣ ተመልከት ። ፪ኛም ፡ መ ፡ መሬት ፣ ም ፣ ምድር ፤ ሕያው ፣ እግዚር ፤ በተገናኝ ፣ መሬተ ፣ ሕያው ፣ ምድረ ፣ ሕያው ፣ ማለት ፣ ነው ፤ ሰማየ ፣ አምሳክ ፣ እንደ ፣ ማለት ።

**ሔዋ ፤ ሔዋን ፤ (ዕብ ፡ ሐዋ) ፤** በቁሙ ፣ መጀመሪያ ፣ ሴት ፣ የአዳም ፣ ሚስት ፤ ሕያውት ፣ እመ ፣ ሕያዋን ። ወሰመየ ፡ አዳም ፡ ስመ ፡ ብእሲቱ ፡ ሔዋ ፤ እስመ ፡ ይእቲ ፡ እመ ፡ ዙሉ ፡ ሕያው ፡ (ዘፍ፫ ፣ ፳) ።

**ሔው ፤ (ዕብ ፡ ሐይ) ፤** መጀመሪያ ፣ ወንድ ፣ አዳም ፣ የሔዋን ፣ ባል ፣ ሕያው ፣ አበ ፣ ሕያዋን ። ወነፍኅ ፡ በአንፉ ፡ መንፈሰ ፡ ሕይወት ፤ ወኮነ ፡ ሕያወ ፡ በመንፈስ ፡ (ዘፍ፪ ፣ ፯) ።

**እምሔው ፤ (ውት ፡ ዋን ፡ ዋት ፤ እማሑት) ፤** ገዢ ፣ ከማሁ ፤ አዳም ። እንደ ፡ አዳም ፡ ያለ ፣ ወንድ ፣ አያት ፣ እማታ ፤ ያባት ፣ የናት ፣ ወላጅ ፣ ጉንድ ፣ ሥርው ፣ መጀመሪያ ፣ አባት ፣ ፫ኛውን ፣ ትውልድ ፣ የልጅ ፡ ልጅ ፣ ያየ ። እም ፣ አገባብ ፣ ኹኖ ፣ መነሻነትን ፣ ቀዳሚነትን ፣ ያሳያል ። እግዚ ፡ ይቤሎሙ ፡ ለእምሔው ፡ ወለእምሔውት ፡ ቀዳማውያን ፤ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ ፤ ወሳድያን ፡ ወእምሔዋን ። አሮን ፡ እምሔወ ፡ ቀደምቶሙ ። በቤተ ፡ መላልኤል ፡ እምሔውየ ። ሐና ፡ እምሔውተ ፡ እምሳክ ፡ በሥጋ ። አበዊከ ፡ ወእማሑቶሙ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ። ዕገ፳ ፣ ፳ ። ሔኖ፰ ፣ ፯ ። ስንክ ፣ ኅዳ፲፩ ። ዘፀ፲ ፣ ፯) ። እማሑት ፣ ወንድና ፣ ሴት ፣ ያስተባብራል ። አበ ፡ እምሔው ፤ ያያት ፣ አባት ፣ ቅድም ፣ አያት ። እምሔወ ፡ እምሔው ፤ ያያት ፣ አያት ፣ ምዝላት ። እግዚርም ፣ ለአዳም ፣ እምሔው ፣ ይባላል ፤ ዕጓልን ፣ እይ ። ሐፃኒ ፣ አበ ፣ ማሕፀንት ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ እምሔው ፣ አማሑት ፣ ይላል ፣ አያሰኝም ። ባዕለ ፡ እምሔው ፡ ወመግብት ። ነገሥት ፡ እማሑትኪ ፡ (ገላ፬ ፣ ፬ ። ኢሳ፵፱ ፣ ፳፫) ።

**ሐየየ ፤—ቸል ፡ አለ ፤—ሀይይ ፡ ሀየ ፤ ሀየየ ።**

**ሐዩክ ፤ ኮት ፤ (ሔክ ፡ የሐይክ ፡ ይሐክ ። ሐነከ) ፤** ማላመጥ ፣ ማኘክ ፣ በጥርስ ፣ መፍጨት ፣ መለንቀጥ ፣ ለመዋጥና ፣ ለመሰልቀጥ ፣ የምግብ ። እይ ፡ እስናን ፡ ዘየሐይክ ፡ ዘንተ ፡ ኅብስተ ። ወይሐክ ፡ በሰንሳስ ። እንዘ ፡ የሐይክ ፡ (ቅዳ ። ሥር ፣ ጳዡ) ።

**ተሐይከ ፤** ተላመጠ ፣ ተሰነቀጠ ። ጽኑዐ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይትሐየክ ፡ (ቅዳ ፣ ሕር) ።

**ሐክት ፤** ማላመጥ ፣ አስተኛኘክ ፣ አበላል ።

**ሐክ ፤ (ዕብ ፡ ሔኽ) ፤** ላንቃ ፣ ትናጋ ፤ ያፍ ፣ ውስጥ ፣ ላይኛው ፣ ክፍል ፣ ጥሻው ። የላይና ፣ የታች ፣ የማራ ፣ የቀኝ ፣ መንጋጋ ፣ መፍጫው ፣ ማላመጫው ። ሐነክን ፣ እይ ።

**ሐይል ፤—በቁሙ ፤—ኀይሎ ፡ ኀየለ ።**

**ሐይመነ ፤—አመነ ፤—ሀይመነ ፤ ሃይማኖት ።**

**ሐይመት ፤—ድንኳን ፤—ኀይመት ።**

**ሐዩጽ ፤ ጾት ፤ (ሔጸ ፤ ሐየጸ ፡ የሐይጽ ፡ ይሐጽ ። ሐወጸ) ፤** ማስተዋል ፣ መመልከት ፣ ውስጡን ፣ ምስጢሩን ፣ ማስብ ፣ መመርመር ፣ መሻት ፤ መላልቦ ፡ ቀምሎ ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ማየት ፤ የክፉ ፣ የበጎ ። ሐወጸን ፣ እይ ፤ የዚህ ፣ መንቲያ ፣ ነው ። መጽሐፍ ፣ ግን ፣ በሐየጸ ፣ ፈንታ ፡ አስተሐየጸ ፡ ይላል ፤ አስቶ ፣ አሰቦታው ፣ ገብቷል ፤ ሐቀረን ፣ እይ ፣ ይህም ፣ እንደዚያ ፣ ነው ። እምርሑቅ ፡ ያስተሐይጽ ፡ ዐይኑ ። መዳእክሙ ፡ ታስተሐይጹ ፡ አሥረ ፡ ምድር ። አስተሐይጽ ፡ በልብከ ፡ ወአእምር ፡ መኑ ፡ አንተ ። ወበአይኒ ፡ ግብር ፡ ያስተሐይጽዎ ፡ ዘልፈ ። ዘያስተሐይጻ ፡ ለድንግል ፡ (ኢዮ፴፱ ፣ ፳፱ ። ኩፋ ፣ ፵፪ ። አፈ ፣ ተ፲፰ ። ዳን፯ ፣ ፲፰ ። ቀሌ) ።

**ሐያጺ ፤ መሐይጽ ፤ መስተሐይጽ ፤** የሚያስተውል ፣ ተመልካች ፣ አስተዋይ ፤ ልባም ፣ ዐይናማ ። ዲያቆን ፡ ይኩን ፡ መስተሐይጸ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ (ኪዳ) ።

**ሑያጼ ፡ (ሕዋጼ) ፤** ማስተዋል ፣ መመልከት ፣ አስተያየት ። ግምት ፡ መላ ፡ ጥንቄላ ፤ ሕልም ፣ ቅዠት ፣ በቀን ፣ ያዩትን ፣ ወይም ፣ ያሰቡትን ፡ ሴት ፣ ማለም ። ወይክወኑ ፡ እለ ፡ ያስተሐይጹ ፡ በሑያጼ ፡ ወርኅ ፡ (ኩፋ ፣ ፮) ።

**ሐዩቅ ፤ ቆት ፤ (ሔቀ ፤ ሐየቀ ፡ የሐይቅ ፡ ይሐቅ) ፤** ማቀፍ ፣ መክበብ ፣ ዳር ፣ ድንበር ፣ ቅርብ ፣ አጠገብ ፣ መኾን ፤ የደሴትና ፣ የባሕር ፣ የየብስ ፤ ለሕንጻም ፣ ይኾናል ።

**ሔቅ ፤ (ዕብራ) ፤** ሕፅን ፣ ብብት ፤ ድልድል ፣ መሠረት ፣ በሕንጻው ፣ ዙሪያ ፣ በመብቀያው ፣ እንደ ፣ ዕርከንና ፣ እንደ ፣ መደብ ፣ እንደ ፣ ዝናር ፣ ኹኖ ፣ የሚ

ሠራ ፤ ዞሮ ፡ ተጠምጥሞ ፡ የሚገጥም ። ወሒቅ ፡ እመት ፤ ወእመት ፡ ርሕቡ ፡ እምሒቀ ፡ ምድር ፤ (ሕዝቅኤ ፡ ፵፫ ፡ ፲፬) ።

**ሐይቅ ፤ (ቃት) ፤** ዙሪያ ፡ ዳርቻ ፡ ወደብ ፡ ጎንፍ ፤ የባሕር ፡ ጠረፍ ። ታናሽ ፡ መጠነኛ ፡ ባሕር ፡ ዙሪያው ፡ ዳርቻው ፡ የሚታይ ፤ በተራራ ፡ በየብስ ፡ የተከበበ ፡ እንደ ፡ ዚዶ ፡ እንደ ፡ ሐይቅ ፡ እንደ ፡ ጣና ፡ ያለ ። ሐይቀ ፡ ባሕር ። ኀበ ፡ ሐይቀ ፡ ባሕር ። መንገለ ፡ ሐይቀ ፡ ጌንሴሬጥ ። ድንጋግ ፡ ዘሐይቅ ፡ (መሳፍ ፡ ፲፯ ። ማቴ ፲፰ ፡ ፳፬ ። ሉቃ፭ ፡ ፩ ። አርጋ ፡ ፪) ።

**ሖሮ ፤ — ቆሮ ፤ — ነዩር ፡ ኄረ ፡ ኄር ።**

**ሐየሰ ፤ — ተሻለ ፤ — ነዩስ ፡ ኄሰ ፡ ኀየሰ ።**

**ሐዩስ ፤ ሶት ፤ (ሐሰ ፤ ሐየሰ ፡ የሐይስ ፡ ይሐስ) ፤** መንቀፍ ፡ ማጸየፍ ፤ ማነወር ፡ መክሰስ ፤ መሰደብ ፡ መቈጣት ። ኢትሐስ ፡ ዘእንበለ ፡ ትሕትት ። ሶቤሃ ፡ የሐይስ ፡ ርእሶ ። ኢትሐሰኒ ፤ እስመ ፡ ኅሠሥኩ ፡ ኣእምር ። ይሐስከ ፡ እግዚ ፡ (ሢራ ፲፩ ፡ ፯ ። ኢዮ ፴፫ ፡ ፳፯ ። ዘካ ፫ ፡ ፲፪ ። ይሁ ፡ ፱) ።

**ሐያሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት ፤ የስት) ፤** የሚነቅፍ ፡ ነቃፊ ፤ ከሳሽ ፡ ወቃሽ ።

**አሔሰ ፤ አሕየሰ ፤** አስነቀፈ ፤ አስነወረ ። ኢታሐስ ፡ ርእሰከ ። ያሐይስ ፡ ርእሶ ፡ (ሢራ ፴ ፡ ፴፩ ። ምሳ ፱ ፡ ፯) ።

**ተሐይሰ ፤** ተነቀፈ ፤ ተሰደበ ፡ ተነወረ ። ከመ ፡ ኢትትሐየስ ፡ አንተ ፡ በእበደ ፡ ዚኣሁ ። ከመ ፡ ኢትርፍቀ ፡ ለዘ፡ነኒ ፡ ወኢትትሐየሱ ፡ (ሢራ ፴፱ ፡ ፲፫ ። ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፴፱) ።

**ተሓየሰ ፤** ተነቃቀፈ ፤ ተጣላ ፡ ተካሰሰ ። ኣድጉ ፡ ለቢጽክሙ ፤ ዘተሓየስክምዎ ፤ እመ ፡ ቦ ፡ ዘተሓየሰ ፡ ምስለ ፡ ቢጹ ፡ ይኅድግ ፡ ሎቱ ፡ (ማር ፲፩ ፡ ፳፭ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፫) ።

**ሕዩስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ይስት) ፤** የተነቀፈ ፡ የተነቃቀፈ ፡ ነቁፍ ፤ ስዱብ ፡ ነውረኛ ።

**ሒሰት ፤** መንቀፍ ፤ መነቀፍ ፡ እንቃቀፍ ፤ ነቀፋ ፡ ነቀፌታ ፡ ስድብ ።

**ሒስ ፤** ነውር ፡ ገመና ፡ ኀጢአት ፡ በደል ፡ የሚያስነቅፍ ፡ ነገር ፤ ነቀፋ ። ንጹሕ ፡ አንተ ፡ እምዝ ፡ ሒስ ፡ ዘኀቡአት ። እንተ ፡ እንበለ ፡ ሒስ ። ዘአልቦ ፡ ነውር ፡ ወሒስ ። ሒስ ፡ ንስቲት ፡ (ሔኖ ፳፰ ፡ ፲፬ ። ኤፌ ፭ ፡ ፳፯ ። ጥበ ፲፪ ። ፲፫ ፡ ፯) ።

**ሔት ፤ (ዕብራ) ፤** ስመ ፡ ፊደል ፡ ሳምን ፤ ሐውት ፡ ሐ ፤ ዘሩ ፡ ሐዩው ፤ ፍችው ፡ ሕይወት ። ሐውትና ፡ ሔት ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ናቸው ። ሔት ፤ ክፍልየ ፡ እግዚ ፡ (መዝ ፻፲፰ ፡ ፶፯—፷፬ ። ሰቈ ፩ ፡ ፰ ። ፪ ፡ ፰ ። ፫ ፡ ፳፱ ። ፬ ፡ ፰) ።

**ሐከየ ፤ — ሰነፈ ፤ — ሀከይ ፡ ሀከየ ።**

**ሐከከ ፤ — ክርክር ፤ — ሀኪክ ፡ ሀከከ ።**

**ሐኪክ ፤ ኮት ፤ (ሐከ ፤ ሐከከ ፡ የሐክክ ፡ ይሕክክ ። ዐረ ፡ ሐከ ። ዕብ ፡ ሐከኽ) ፤** ማከክ ፡ መሮከት ፡ ማቀኰስ ፤ መሳጥ ፡ መቅረፍ ፤ መፋቅ ፡ መሳግ ፤ መሞረድ ፡ መፈግፈግ ፤ የገላ ፡ የቈርበት ፡ የንጨት ፡ የብረት ። ነሥአ ፡ ገልዐ ፡ ወአኀዘ ፡ ይሕክክ ፡ ቍስሎ ። ኀሰቁ ፡ እንዘ ፡ አሐክክ ፡ ጺውበ ። (ኢዮ ፪ ፡ ፰ ። ፯ ፡ ፭) ። ዕከካም ፡ መኾን ፤ ዕከክ ፡ መልበስ ፤ በዕከክ ፡ ደዌ ፡ መያዝ ። ዘሐክክ ፡ አባሉ ፡ (መ ፡ ፈ) ።

**ሐካኪ ፤ (ኪት ፡ ክያን ፡ ያት ፤ ከክት) ፤** የሚያክ ፡ የሚያቈስል ፡ ጥፍሬም ፤ ዕከካም ። ፊብን ፡ ባንበሳና ፡ በነምር ፡ መስሎ ፡ ዐካኪ ፡ ዘፊፍ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

**ተሐከ ፤ ተሐከከ ፤** ታከከ ፡ ተፈገፈገ ፡ ተሳገ ፡ ተሞረደ ።

**ሕኩክ ፤ (ካን ፡ ካት ፡ ክክት) ፤** የታከከ ። ያከከ ፤ ዕከክ ፡ የወረሰው ።

**ሕክክ ፤** በቁሙ ፤ ዕከክ ፡ የገላ ፡ የቈበርት ፡ ደዌ ። በአበቅ ፡ እኩይ ፡ ወበሕክክ ፡ ዘአልቦ ፡ ፈውስ ፡ (ዘዳ፳፰ ፡ ፳፯) ።

**ሐኪም ፤ ሞት ፤ (ሐከመ ፡ የሐክም ፡ ይሕክም ። ዐረብ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሐካም) ፤** ብልኅ ፡ መኾን ፡ መፈልሰፍ ፤ በውቀት ፡ ማደግ ፤ ጥበብን ፡ ዕውቀትን ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግ ። ገዝም ፡ ዕክም ፡ ጸዋ ፡ ማለት ፤ አለመቀባጠር ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሐከመ ፡ ፈንታ ፡ ተሐከመ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። በአርምሞ ፡ ወበተሐክሞ ፡ ይመስል ፡ ጠቢበ ፡ (ምሳ፲፯ ፡ ፳፰) ። በቁሙ ፡ ማከም ፡ መፈወስ ፤ ድውይን ፡ መዳሰስ ፡ መዳበስ ፤ ማገም ፡ መብጣት ፡ መድኀኒት ፡ መስጠት ። ኪንን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ማስንቱ ፡ ዐጕልና ፡ ገቢር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባፈታቱ ፡ አስተውል ።

**ሐኪም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ሐካም) ፤** ብልኅ ፡ ዐዋቂ ፡ ፈላስፋ ፤ ኩኑይ ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ። ወስመ ፡ መምህሩ ፡ ዘመሀሮ ፡ ጥበበ ፡ አርስጣጣሊስ ፡ ሐኪም ። ወሰመየት ፡ ስሞ ፡ እብኑ ፡ ሐኪም ፡ (ዮሴፍ ። ክብ ፡ ነገ) ። በቁሙ ፤ ፈዋሽ ፡ የሰውን ፡ ደዌ ፡ ከነስሙ ፡ ከነመድኀኒቱ ፡ በየስሉ ፡ የሚያውቅ ፤ በሽተኞች ፡ እንደ ፡ ቁስ ፡ የሚኾት ።

**ሐውል ፤ - መክክለኛ ፤ - ሐዊል ፡ ሐወለ ።**

**ሐላ ፤ ሐሊብ ፤ — ድንኳን ፤ — አሀላ ፡ አሀሊብ ።**

**ሐሊብ ፤ ቦት ፤ (ሐለበ ፡ የሐልብ ፡ ይሕልብ ። ዐረብ ። ዕብ ፡ ሐላብ) ፤** ማለብ ፤ ከእንስሳት ፡ ወተት ፡ ማውጣት ። ከመ ፡ ሐሊብ ፡ ሐለብከኒ ። ሕልብ ፡ ሐሊበ ። የሐልቦሙ ፡ ለእንስሳ ፡ (ኢዮ ፲ ፡ ፲ ። ምሳ፳፱ ፡ ፴፫ ። ሰንክ ፡ መስ፲፫) ። መስረቅ ፤ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ወትትና ፡ እንደ ፡ ወተት ፡ መሳብ ፤ ሳይታዩ ፡ መውሰድ ። ሴብ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ሐላቢ ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ለብት) ፤** የሚያልብ ፡ ፀላቢ ፤ ባለጥገት ።

**ተሐልበ ፤** ታለበ ፤ ወተቱን ፡ ሰጠ ።

**ሕሉብ ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ልብት) ፤** የታለበ ፡ ዕልብ ፡ ወተት ፤ ወይም ፡ ጥገት ፤ ጡት ።

**ሐሊብ ፤** ወተት ፤ ንጭ ፡ ፈሳሽ ፡ ሴትንት ፡ ካላቸው ፡ ከሕያዋን ፡ ፍጥረት ፡ ከወላጆች ፡ ጡት ፡ የሚወጣ ፡ የሕፃናት ፡ የጎላማልት ፡ ምግብ ። **እስመ ፡ ሡሉ ፡ ዘይትወጋዕ ፡ ሐሊብ ፡ ሕፃን ፡ ውእቱ ። ወኲኡ ፡ ከመ ፡ ሕፃናት ፡ ወአፍቅሩ ፡ ሐሊብ ፡ ነባቤ ። ሐሊብ ፡ አልሕምት ፡ ወአባግዕ ፡** (ዕብ፭ ፡ ፲፫ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፪ ። ገድ ፡ ዘሚ) ። በሴት ፡ አንቀጽ ፡ ከምትጠራ ፡ ከምድር ፡ የሚወጣም ፡ ፍሬና ፡ ማዕደን ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ሐሊብ ፡ ይባላል ፤ የምድር ፡ ፀላብ ፡ እንዲሉ ። **ወቦአ ፡ ምድረ ፡ እንተ ፡ ትውሕዝ ፡ ሐሊበ ፡ ወመዓረ ፡** (ሚራ፵፯ ፡ ፫) ። ለዕፀዋትም ፡ ይነገራል ። **ወያንጸፈጽፍ ፡ ሐሊቦሙ ፡** (ራእ ፡ ባሮ) ። ሐሊብ ፡ ነባቢ ፤ ያለውም ፡ የወጣኒ ፡ የሕፃናት ፡ ትምርት ፡ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ይባላል ። የሐሊብ ፡ መሠረት ፡ ምግብነት ፡ ሲኾን ፡ ፫ ፡ ግብር ፡ አለው ፤ ሕይወተ ፡ ሕፃናት ፡ ነው ፤ ያሳድጋቸዋል ፤ ኀይል ፡ ይሰጣቸዋል ፤ ትምርትም ፡ ለነፍስ ፡ ምግብነቱ ፡ እንደ ፡ ሐሊብ ፡ ነው ።

**ሕልበት ፤** ማለብ ፤ መታለብ ፡ አስተላለብ ። አፍንጫ ፤ ያፍንጫ ፡ ጕንጭ ፡ ግራና ፡ ቀኙ ፤ ወይም ፡ መካከሉ ፡ ሹሉ ፡ የሚሰነገው ። **ተአስርኑ ፡ ሎቱ ፡ ሕልቀተ ፡ ውስተ ፡ ሕልበቱ ፡** (ኢዮ፵ ፡ ፳፩) ። በቁሙ ፤ ዕልበት ፡ አብሽ ፤ ከብሽ ፡ የሚሠራ ፡ የጦም ፡ ወጥ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ማሕለብ ፤ (ብ ፡ መሓልብ) ፤** ማለቢያ ፡ ቁጂ ፤ የወተት ፡ ዕቃ ፡ መማሪያ ።



ማሕለብ ፡

**ሐለደ ፤—ጨረሰ ፤—ኀልዶ ፡ ኀለደ ፡ ኀላዲ ።**

(ጥ) **ሐለወ ፤—ኖረ ፤—ሀልዎ ፡ ሀለወ ።**

(ሳ) **ሐለወ ፤—ጠበቀ ፤—ኀሊው ፡ ኀለወ ፡ ኀላዊ ።**

**ሐለዚዝ ፤ (ዐረ ፡ ሐለዞን) ፤** ዛጕል ፡ ልብሱ ፤ ቀንዳም ፡ ልጋጋም ፡ ትል ፤ እንደ ፡ ሔሰይ ፡ ከዛጕሉ ፡ ውስጥ ፡ የሚከተት ፤ ክረምት ፡ ሲገባ ፡ ደመና ፡ ሲዞር ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ዝናም ፡ የሚፈጠር ፤ ንፎሾችና ፡ ፀረቦች ፡ ቀቅለው ፡ አብስለው ፡ እንዳሹቅና ፡ እንደ ፡ በቈልት ፡ እንደ ፡ ሽንብራ ፡ እሸት ፡ እየጠረጠሩ ፡ የሚበሉት ። ቀርንናእን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ለውግዝ ፡ ይሉታል ፤ ዘሩ ፡ ለዚግዝ ፡ ነውና ፡ ለዘን ፡ እይ ።

**ሐልዘዘ ፤** አፈራ ፡ ሐለዞን ፡ ወለደ ፤ ዝናቡ ፡ ምድሩ ።

(ጥ) **ሐለየ ፤—ዐሰበ ፤—ኀልዮ ፡ ኀለየ ፡ ኀሊና ።**

**ሐልይ ፤ ዮት ፤ (ሐለየ ፡ የሐሊ ፡ ይሕሊ ። ዐረ ፡ ሐሊየ) ፤** መስዘብ ፡ መስስለስ ፤ መላም ፡ መጣም ፡ መጣፈጥ ፤ የግብር ፡ የነገር ። መዝፈን ፡ ማመስገን ፤ መቀኘት ፡ መኀጠም ፤ መጠረብ ፡ ማለዘብ ፤ እያዜሙ ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ። ለዘብ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ የዜማውን ፡ ጣዕም ፡ ማማሩን ፡ መተባበሩን ፡ ያሳያል ። **አሐሊ ፡ ማሕሌተ ። ንሕሊ ፡ ማሕሌተ ፡ መንፈሳዊተ ። ሕልዩ ፡ ለእግዚ ፡ በጸናጽል ። ምሕረተ ፡ ወፍትሐ ፡ አሐሊ ፡ ለከ ። ሐለይሁ ፡ ወዘመርሁ ። ኪያየ ፡ የሐልዩ ፡ እለ ፡ ይሰትዩ ፡ ወይነ ፡** (ኢሳ፳፮ ፡ ፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፻፱ ፡ ፮ ። ዮዲ፲፮ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፶ ። ሚራ፵፮ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፷፰) ።

—፤ መጕባት ፤ ጕብ ፡ ወመማለጃ ፡ መስጠት ። ምስጢሩ ፡ ማለዘብ ፡ ካለው ፡ ይገባል ፡ ያልበላ ፡ ዳኛ ፡ እውነት ፡ ለመፍረድ ፡ የማይፈራ ፡ ካክራ ፡ ሸካራ ፡ ነውና ። **ወሐሊይኪዮሙ ፡ ይምጽኡ ፡ ኀቤኪ ። ወመሰሎ ፡ ሰፊልክስ ፡ ዘይሁቦ ፡ ጳውሎስ ፡ ወየሐልዮ ፡ ንዋየ ፡** (ሕዝ፲፮ ፡ ፴፫ ። ግብ፳፬ ፡ ፳፮) ።

**ሐላዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ለይት) ፤** የሚዘፍን ፡ ዘፋኝ ፤ አመስጋኝ ፡ ገጣሚ ፤ ባለቅኔ ፡ ባለዜማ ። **ወፀአ ፡ ሐላይያት ፡ ወተቀበላሁ ። ሐሊይት ፡ ወሐላይያን ፡** (፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፯ ። መክ፪ ፡ ፰) ።

**መሕልይ ፤ መሕለዪ ፤ መሓልይ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ዘፋኝ ። መዝፈኛ ፤ ጊዜ ፡ መማሪያ ፡ ቦታ ።

**ምሕላይ ፤** መዝፈኛ ፡ ቦታ ፤ ቅኔ ፡ ማሕሌት ፡ የሰርግ ፡ ቤት ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**ማሕሌት ፤ (ታት ። አው ፡ ማሕልይ ፤ ብ ፡ መሓልይ) ፤** ዘፈን ፡ ምስጋና ፤ ጠረብ ፡ ለዘብ ፤ ቅዳሴ ፡ ውዳሴ ፤ ቅኔ ፡ ግጥም ፤ ጉማ ፡ ተመማ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ዜማ ። **ማሕሌተ ፡ አብድ ። አዋልደ ፡ ማሕሌት ። አልቦ ፡ ዘይክል ፡ አእምሮታ ፡ ለይእቲ ፡ ማሕሌት ፡ ዘእንበለ ፡ እልክቱ ። ያሰምዕከሙ ፡ ቃለ ፡ መሰናቁት ፡ ዘሕፃናት ፡ ወማሕሌተ ፡ ዘመላእክት ። ተሰእሉነ ፡ ነገረ ፡ ማሕሌት ፡ ወይቤሉነ ፡ ሕልዩ ፡ ለነ ፡ እማሕልዩሃ ፡ ለጽዮን ፤ እፎ ፡ ነሐሊ ፡ ማሕሌተ ፡ እግዚ ፡ በምድር ፡ ነኪር ። ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ፡** (መክ፯ ፡ ፭ ። ፲፱ ፡ ፱ ። ራእ፲፬ ፡ ፫ ። ቅዳ ፡ ሕር ። መዝ ፡ ፻፴፮ ። ማሕ ፡ ፩) ።


**ማሕሌታዊ ፤ (ታይ) ፤** የማሕሌት ፡ ሰው ፤ ደብተራ ፡ አወዳሽ ፤ መርቆ ፡ የሚቀኝ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ። ድምጣም ፡ ድምጠ ፡ መልካም ፤ ማሕሌት ፡ የሚያምቅ ፡ የሚያደምቅ ፤ መዝፈን ፡ መቀንቀን ፡ መጠረብ ፡ ማስረ

ገጥ ፡ ከበሮ ፡ መገበጥ ፡ የሚያውቅ ። **ማሕሌታይ ፡ ሚካኤል ፡ መዐርዒረ ፡ ዜማ ። ያሬድ ፡ ማሕሌታይ ፡** (ደራሲ ። ስንክ ፡ ግንቦ ፩ ። አፈ ፡ ተጎ፱) ።

**ተሐልየ ፤ ተሐለየ ፤** ተጉባ ፡ ተማለደ ፤ ጉቦ ፡ ተቀበለ ። **ወመኰንንኒ ፡ ይትሐለይ ፡ ሕልያነ ። ወብዙኅ ፡ ተሐልዮሙ ፡ እምኀበ ፡ ኢያሰን ፡ ወእምኀበ ፡ ቢጹ ፡ ኅደግዎሙ ፡** (ዕንኅ ፡ ፫ ። ግብ፲፯ ፡ ፱) ።

**ሕልያን ፤ (ዐረ ፡ ሑልዋን ፤ በርጢል ። ዕብ ፡ ሾሐድ ። ሱር ፡ ሾሓዳ) ፤** መማለጃ ፡ ጉቦ ፤ ክፉ ፡ ስጦታ ፤ ለመጥፎ ፡ ዳኛና ፡ ባላይ ፡ ምስክር ፡ የሚሰጥ ። **ያፈቅሩ ፡ ሕልያነ ። ይነሥኡ ፡ ሕልያነ ። አምኁ ፡ ወሕልያነ ፡ ያዐውሮሙ ፡ ለጠቢባን ፡** (ኢሳ፩ ፡ ፳፫ ። ፳ ፡ ፳፫ ። ሚራ፳ ፡ ፳፱) ።

**ሔለይ ፤** በቁሙ ፤ ዔሊ ፡ ደንጊያ ፡ ልብሱ ። ልዝብ ፡ ልሙጽ ፤ ወይም ፡ ፊኺ ፡ ድምጠ ፡ ቀፎን ።



ሔለይ ፡

**ሔልዩ ፤ (ጽር ፡ ሒሊዉ) ፤** ፀሓይ ፤ ሥዕለ ፡ ፀሓይ ። **ሀገረ ፡ ሔልዩ ፡** (ዘፍ፵፩ ፡ ፵፭ ። ሕዝ፴ ፡ ፲፯) ።

**ሐለከ ፤ (ትግሬ) ፤** ወደረ ፡ ሰንከለ ፤ ቀየደ ፡ ሸንከፈ ፡ የከብት ። በቁሙ ፡ ተሳላከ ፡ ሕልከኛ ፡ ኹን ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሐለለ ፤ (ሐረረ) ፤** ዐረረ ፡ ከሰለ ፤ ተቃጠለ ። ዘሩ ፡ ሐሬር ፡ ነው ፤ ረ ፡ ሲሉ ፡ ለ ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ የረ ፡ ጸያፎች ፡ ያገቡት ፡ ነው ። ትግሬ ፡ ግን ፡ ሐለለ ፡ ብሎ ፤ ደከመ ፡ ዛለ ፡ ጠወለገ ፡ ይላል ።

**አሕለለ ፤ (አሕረረ) ፤** አሳረረ ፤ አቃጠለ ። **ፈነወ ፡ እሳተ ፡ ወአሕለለኒ ፡ ለአዕፅምትየ ። ሶበ ፡ ሰልብየ ፡ እሳተ ፡ ሐዘን ፡ አሕለሎ ። እቶነ ፡ እሳት ፡ ኢያሕለላ ፡** (ሰቈ፩ ፡ ፲፫ ። ደራሲ ። ስንክ ፡ ሐም፳፰) ።

**መሐልል ፤ ማሕልል ፤** የሚያሳርር ፡ የሚያቃጥል ። ኸቱ ፡ የሚያበጅ ፡ የሚያወጣ ፤ ቀማሚ ፡ አንጣሪ ፤ የሚያቀልጥ ፡ የሚያጣፍጥ ። **ውእቱ ፡ ዘገብረ ፡ አፈዋተ ፡ ዕጣን ፡ በንጹሕ ፡ ግብረ ፡ መሐልል ፡** (ዘፀ ፴፰ ፡ ፳፱) ። ሐረረን ፡ እይ ።

**ሕላል ፤—ሠርቀ ፡ ወርኅ ፤—ሀላል ።**

**ሐሊም ፤ ሞት ፤ (ሐለመ ፡ የሐልም ፡ ይሕልም ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሐላም ። ዐረ ፡ ሐሉመ) ፤** ማለም ፤ በንቅልፍ ፡ ልብ ፡ ሕልም ፡ ራእይ ፡ ማየት ። **ወደገመ ፡ ሐሊመ ። ሐለምኩ ፡ ሕልመ ፡ ወደንገፀት ፡ ነፍስየ ። ወሊቃውንቲክሙ ፡ ሕልመ ፡ የሐልሙ ። ለእመ ፡ ሐለመ ፡ ኢይስቀቀስ ፡ አንስተ ፡ ኢይቅረብ ፡** (ዘፍ፴፯ ፡ ፱ ። ዳን፪ ፡ ፫ ። ዮኤ፪ ፡ ፳፰ ። ኪዳ) ። በሐለመ ፡ ፈንታ ፡ ተሐለመ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ሐላምያን ፡ እለ ፡ ይትሔለሙ ፡ ለክሙ ፡** (ኤር ፴፱ ፡ ፳ ። ፴፯ ፡ ፰) ። መወፈር ፡ መግዘፍ ፡ ታላቅ ፡ መኾን ፤ መጽናት ፡ መበርታት ። ሕልመልሜሌክን ፡ ተመልከት ።

**ሐላሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት ፤ ለምት) ፤** በቁሙ ፤ የሚያልም ፤ ሕልም ፡ ራእይ ፡ የሚያይ ፤ ሕልማም ፡ ባለሕልም ። **ነቢይ ፡ ፩ው ፡ ሐላሚ ፡ ሕልም ። ይትኀፈሩ ፡ ሐላምያነ ፡ ሕልም ፡** (ዘዳ፲፫ ፡ ፩ ። ሚክ፫ ፡ ፯) ።

**አሕለመ ፤** አሳለመ ፤ ሕልም ፡ አሳየ ።

**ተሐልመ ፤** ታለመ ፤ በሕልም ፡ ታየ ።

**ሕልም ፤ (ማት ። ብ ፡ ሕለም ፡ አሕላም ፤ ማት) ፤** በቁሙ ፤ በንቅልፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፤ እንደ ፡ ትንቢት ፡ ያለ ። ሕልም ፡ ፪ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ የነፍስ ፡ የሥጋ ፤ የነፍስ ፡ ሕልም ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ነው ፤ ትንቢት ፡ ራእይ ፡ ይባላል ፡ (ዘፍ፴፯ ፡ ፮ ። ማቴ፩ ፡ ፩ ። ዳንዬ ፡ ፩) ። የሥጋ ፡ ሕልም ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ምትሀት ፡ ኹኖ ፡ ቅዠት ፡ ይባላል ፤ ከንቱ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ለኹሉም ፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ አለው ፤ ሳሕሰሐን ፡ እይ ። **ወሕልምኒ ፡ ከንቱ ፡ ያደነግፆ ፡ ለአብድ ። እስመ ፡ ለብዙኃን ፡ አስሐቶሙ ፡ ሕልም ። ሕልም ፡ ዘዘሙት ። አሕላም ፡ እኩያት ። አሕላማት ፡ ሕሡማት ፡** (ሢራ፴፩ ፡ ፩ ፡ ፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ድ፳፱ ። ፊልክ ፡ ፲፰) ።

**ሕልመልሜሌክ ፤** ስመ ፡ ኮከብ ፡ ዐቢይ ፤ መጋቤ ፡ ሐጋይ ፤ ካሉቱ ፡ ዐበይት ፡ ከዋክብት ፡ አንዱ ። ዘይቤው ፡ ሕልመ ፡ ንጉሥ ፡ ማለት ፡ ይመስላል ፤ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ ታላቅነት ፡ ነው ። ፪ኛ ፡ ስሙ ፡ ፀሓይ ፡ ይባላል ፤ ምግብናውም ፡ ፺፩ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ (ሔኖ ፡ ፸፱) ።

**ሐለፈ ፤—ዐለፈ ፤—ኀሊፍ ፡ ኀለፈ ።**

**ሐለፈ ፤ (ዐረብ) ፤** ማለ ፡ ተረገመ ፤ ተገዘተ ።

**ተሓለፈ ፤** ተማማለ ፤ ተካየደ ።

**ትሕላፍ ፤** መሐላ ፤ ቃል ፡ ኪዳን ። **አልቦሙ ፡ ትሕላፍ ፡ ምስለ ፡ ሶርያ ፡** (መሳ፲፰ ፡ ፯) ።

**ሐለጸ ፤ (ዕብ ፡ ሐላጽ) ፤** መዘዘ ፡ አወጣ ፡ ከወገቡ ፤ የሰይፍ ፡ የዘር ፡ የአባለ ፡ ዘር ። ዐለጠ ፤ ዐልሜ ። ኾነ ።

**ሕልጽ ፤** ወገብ ፤ የትጥቅ ፡ሙያ ፤ ከጭን ፡ ማውድና ፡ ከባላው ፡ በላይ ፡ ከጕድንና ፡ ከሕንብርት ፡ በታች ፡ መካከሉ ። ሐቌን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ሰይተው ፡ ኅምስ ፡ ኃምሳይ ፡ ሕዋስ ፡ ኀፍረተ ፡ ብእሲት ፡ ይሉታል ። **እመኒ ፡ ተኀብአ ፡ ማእከለ ፡ አቍያጽ ፤ እምተረግዘ ፡ ኢያምሠጠ ፡ ሕልጽ ፡** (ቅኔ) ።


**ሐልቀ ፤—ዐለቀ ፤—ኀሊቅ ፡ ኀልቀ ።**

**ሐሊቅ ፤ ቆት ፤ (ሐለቀ ፡ የሐልቅ ፡ ይሕልቅ ። ዐረ ፡ ሐለቀ) ፤** መዞር ፡ መክበብ ፤ ዙሪያ ፡

ነብ ፡ ማድረግ ። ወይም ፡ መከበብ ፤ ክቡብ ፡ ከበባም ፡ መኾን ፤ የሥራ ።

**ሕልቅ ፤ (ብ ፡ አሕላቅ) ፤** ጕንጭ ፤ መንጋጋ ፡ ከነመላሱ ፡ ወይም ፡ ከንፊሩ ፤ ከናናቁ ፡ ከንጭንቅላቱ ። **ዘይሁብዎ ፡ ለካህን ፡ መዝራዕተ ፡ ወሕልቀ ፡** (ዘዳ ፲፰ ፡ ፫) ። ጕሮሮ ፤ ክበብ ፡ ክርክር ፡ ያለው ፡ ውስጠ ፡ ክፍት ፤ መጥሚጣውና ፡ መሰልቀጫው ።

**ሕልቀት ፤ (ቃት) ፤** ቀለበት ፤ የጣት ፡ ጌጥ ፤ ሌጣ ፡ ስንኬቶ ፡ ወይም ፡ ፈርጥና ፡ ማኅተም ፡ ያለው ። **ሕልቀትየ ፡ ዘአጽባዕትየ ። ሕልቀተ ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ አጻብዒሃ ። አውፅአ ፡ ንጉሥ ፡ ሕልቀቶ ። ሕልቀተ ፡ ማዕተብ ፡** (ኩፋ ፡ ፵፩ ። ገድ ፡ ተክ ። አስቴ ፫ ፡ ፲ ። ሚራ ጫ፱ ፡ ፲፭) ። ያፍጫ ፡ ስናግ ፡ የብረት ፡ ቀለበት ፤ እንደ ፡ ሰዓት ፡ ፍንጅ ፡ የሚከፈትና ፡ የሚዘጋ ። ሕልበትን ፡ እይ ።



ሕልቀት ፡

**ሕላቅ ፤ (ቃት) ፤** ምዕማድ ፤ የዐምድ ፡ እግር ፤ ዐምድ ፡ የሚቆምበት ፡ ስክተት ፡ መሠረት ፤ የዐምዱን ፡ ሥር ፡ ለመንከስ ፡ ለመጕረሥ ፡ አፉ ፡ እንደ ፡ ቀለበት ፡ ክብ ፡ የኾነ ። **ዴበ ፡ ምንት ፡ ስቁል ፡ ሕላቃቲሃ ፡** (ኢዮ ፴፰ ፡ ፮ ። ቅዳ ፡ ኤጲ) ።

**መሐልቅ ፤** ክብ ፡ ሥራ ፤ ምእዙን ፡ ሞላላ ፡ ያይደለ ፤ እንደ ፡ ሰፌድ ፡ እንደ ፡ ምጣድ ፡ ያለ ። **ሀሎ ፡ በአዝስም ፡ ሥዕለ ፡ ምትረተ ፡ ርእሱ ፡ ለዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ሥዑለ ፡ በመሐልቀ ፡ ብርት ፡** (ታሪ ፡ እኵ) ። በቁሙ ፤ ግርሽ ፡ የብር ፡ ገንዘብ ፡ ክብነት ፡ ያላት ፤ ዐይ ነቷ ፡ የብር ፡ መጠኗ ፡ የዝሩር ። በኑርም ፡ ኀ ፡ ሲጣፍ ፡ ግን ፡ መንልቅ ፡ ማለት ፡ ታናሽ ፡ ክፍል ፡ የብር ፡ ክፃኝ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ማኅበሩንና ፡ መከፈሏን ፡ እንጂ ፡ ክብነ ቷን ፡ አይሻም ።

**ሕልቅ ፤ (ጽር ፡ ፆልክ ። ዕብ ፡ ቤቃዕ) ።** ድሪም ፤ የዲድርክም ፡ አኅድ ፡ ወይም ፡ የሰቅል ፡ እኩሌታ ። ዲናርን ፡ ድርህምን ፡ ድርክሚን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ወቄት ፡ ይሉታል ። **ነሥአ ፡ አዕኑገ ፡ ዘወርቅ ፡ ዘዘ ፡ ሕልቅ ፡ ድልወቱ ፡ ወአውቃፈ ፡ ዘዘ ፡ ፀሥሩ ፡ ሕልቅ ፡ ድልወቱ ፡** (ዘፍ ፳፬ ፡ ፳፪) ።

**ሐለቅ ፤ (ትግሬ) ፤** የደም ፡ ሥር ፡ በሽታ ፡ እንደ ፡ ጨብጥና ፡ እንደ ፡ ቁጥኝ ፡ ደም ፡ የሚያበላሽ ።

**ሐለስ ፤—ዐጀ ፤—ዐለስ ።**

**ሐለስት ፤ ሐለስትዮ ፤ (ታት ። ዕብ ፡ ሐላሹት ። ዐረ ፡ ኀሊስ) ፤** ክልስ ፤ ቅልቅል ፡ ድብልቅ ፤ ንጭንና ፡ ጥቍር ፡ ዝንጕርጕር ፡ ኅጣቱን ፡ ጥቍረት ፡ ጥቍረቱን ፡ ኅጣት ፡ የተቀላቀለው ፤ ዝፋና ፡ ጠጕሩ ፡ ነጭ ፡ ብዥ ፡ ወይም ፡ ጥቍር ፡ ብዥ ፡ ያይደለ ፤ ዲቃላ ፤ ጦጣ ፡ ነጩ ፡ ዝንጀር ፤ የበዳ ፡ እህያ ። ቦኑ ፡ ለክንቱ ፡ ይነቁ ፡ ሐለስትዮ ፡ (ኢዮ ፵ ፡ ፳ ። ዳን ፳ ፡ ፳፯ ። መገ ፡ ፲፫) ።



ሐለስትዮ ፡

**ሕለት ፤—ዘንግ ፤—ኀሊል ፡ ኀለለ ።**

**ሐሙኢዳ ፤—ቀጠሮ ፤—ሀሙኢዳ ።**

**ሐሚግ ፤ (ሐመገ ፡ የሐምግ ፡ ይሕምግ ። ሐመቀ) ፤** ማመግ ፡ ማጥፋት ፡ ማበላሸት ፡ የምግብ ። ማደፍረስ ፡ መበጥበጥ ፤ የውሃ ፡ የመጠጥ ። **ማይ ፡ ዘሐመግሙ ፡ በእግሪክሙ ። ፈለግ ፡ ዘሐመግሙ ፡ በደመ ፡ ቅቱላን ። እንዘ ፡ የሐምጉ ፡ ማያተ ፡ ብዙኀ ፡** (ሕዝ ፴፬ ፡ ፲፱ ። ጥበ ፲፩ ፡ ፯ ። ዕን ፫ ፡ ፲፭) ። ማፍዘዝ ፡ ማደንገዝ ፡ ማበገዝ ፡ ማብለዝ ፤ ማድከም ፤ የዐይን ። ምስጢሩ ፡ ጽርየት ፡ ማሳጣት ፡ ነውና ፤ ማደፍረስ ፡ ከሰው ፡ ይገባል ።

**አሕመገ ፤** አሳመገ ፤ አስደፈረሰ ፡ አስፈዘዘ ።

**ተሐምገ ፤** ታመገ ፤ ተበላሸ ፡ ደፈረሰ ፡ ፈዘዘ ። **አልቦ ፡ ተሐምገ ፡ ውስተ ፡ ጽርየታ ። ተሐምጉ ፡ ማያቲሆሙ ። ረሥአ ፡ ወተሐምጋ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ወኢይሬኢ ፡** (አፈ ፡ ተ፳፫ ። መገ ፡ ፵፰ ። ዘፍ ፳፯ ፡ ፩ ። ፳፯ ነገ ፡ ፬ ፡ ፲፭) ።

**ሕሙግ ፤ (ጋን ፡ ጋት ፡ ምግት) ፤** የታመገ ፡ ዕምግ ፡ ክፉ ፡ ጥፉ ፡ ብልሹ ፡ ድፍርስ ። **ማይ ፡ ሕሙግ ። ወይን ፡ ሕሙግ ፡ መብልዕ ፡ ሕሙግ ፡ የሐምጉ ፡ ሰልብ ፡** (ኤር ፬ ፡ ፲፫ ። ፈላስ ፡ ገ፲፫) ።

**ሕምገት ፤** ማመግ ፡ መታመግ ፡ መደፍረስ ፡ አደፋፈረስ ፤ ድፍረሳ ፡ ድፍርስነት ፡ (ሂርማ ፡ ገ፶፭) ።

**ሕመግ ፤** እድፍ ፤ ጭቅቅት ፡ ኀጢአት ፡ የአእምሮ ፡ ዝገት ፤ ድንቍርና ። **ንጹሕ ፡ ውእቱ ፡ ወአልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ሕመግ ፡** (አፈ ፡ ድ፴፱) ።

**ሐሚድ ፤ ዶት ፤ (ሐመደ ፡ የሐምድ ፡ ይሕምድ ። ዐረ ፡ ወትግ ፡ ሐምደ ፤ ገነየ) ፤** ማመድ ፡ መብላት ፤ ማቃጠል ፡ ማመት ፤ ሐመድ ፡ ሕመት ፡ ማድረግ ፤ የእሳት ፡ የመብራት ፡ የጭስ ፡ የንፍት ። መቀረጥ ፡ መጕመድ ፡ መጕማመድ ፤ የስለት ። ገመደን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ይውኂ ፡ ይትሐመድ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ የሐምድ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ሕዝ ፲፭ ፡ ፬) ።

**አሕመደ ፤** አሳመደ ፡ አስበላ ፡ አስጠፋ ።

**ተሐምደ ፤** ታመደ ፣ ተበላ ፣ ጠፋ ። ሐመድ ፣ ኾነ ። ሰማይት ፤ ይጠበለሉ ፤ ወምድር ፤ ትትሐመድ ፤ (ኢ.ዳ) ።

**ሐሙድ ፤ (ዳን ፣ ዳት ፣ ምድ) ፤** የታመደ ፣ የተበላ ፣ የተቃጠለ ፣ ሐመድ ፣ የኾነ ፣ (መጽ ፣ ምስ) ።

—፤ ዐሻዳ ፣ አፋንጎማ ፣ ጐራዳ ፤ ዝንጀሮ ፣ ፊት ፤ ኾርፋድ ።

**ሐመድ ፤** በቁሙ ፤ ዐመድ ፣ የእሳት ፣ ብላቶ ፣ ነጭ ፣ ትቢያ ። የማር ፣ የገለባ ፣ ሲኾን ፣ ስለ ፣ ጥቍረቱ ፣ ጠለስ ፤ ይባላል ። **አውዐየ ፤ ለሀገር ፤ ወከነት ፤ ሐመደ ። ጠፍኦ ፤ ከመ ፤ ሐመደ ፤ ሡዐ ። መሬት ፤ ወሐመድ ፤** (ኢ.ያ፳ ፣ ፳፰ ። ኢ.ሳ፵፫ ፣ ፲፯ ። ዘፍ፲፰ ፣ ፳፯) ።

—፤ ደቃቅ ፣ ክሰል ፣ ጥላት ፣ ጥቀርሻ ። **ሐመደ ፤ እቶን ፤** (ዘፀ፱ ፣ ፰) ።

—፤ ዐፂፋ ፣ ትቢያ ፣ ደቃቅ ፣ ዐፈር ። **ወደዩ ፤ ሐመደ ፤ ዲበ ፤ ርእሶሙ ። ሐመደ ፤ ይቀምሑ ፤** (ኢ.ዮ፪ ፣ ፲፪ ። መዝ ፣ ፻፩) ። ማናቸውም ፣ ደቃቅ ፣ ነገር ፣ ኹሉ ፣ ሐመድ ፣ ይባላል ፤ ደቂቅ ፣ ማለት ፣ ነው ። **ሐመደ ፤ እብን ፤** ኖራ ፣ በረቅ ፣ ጠመኔ ።

**ሐመዳዊ ፤ (ዊት ፣ ውያን ፣ ያት) ፤** ዐመዳም ፤ ዐመድማ ፣ ቡላ ፣ ዐፈርቻ ፤ ዐይነቱ ፣ ሕብሩ ፣ ሐመድ ፣ የሚመስል ። **አፍራስ ፤ ሐመዳውያን ፤** (ዘካ፮ ፣ ፫) ።

**ሐመዳ ፤** ዐመዳይ ፣ ብትን ፣ ውርጭ ፤ ዐመድማ ፣ ነጭ ፤ ከውሃ ፣ ላይ ፣ ሲያርፍ ፣ የሚረጋ ፤ ዋግ ፣ እየኾነ ፣ እኽል ፣ የሚያበላሽ ። የሰሙ ፣ ምስጢር ፣ ፪ ፣ ነው ፤ ጎጣ ትና ፣ አጥፊንት ። አበሐትያን ፣ እይ ፣ ከዚህ ፣ ጋራ ፣ አንድ ፣ ነው ። **ቍር ፤ ወበረድ ፤ ወአስሐትያ ፤ ወሐመዳ ። እምእይቴ ፤ ይወፅእ ፤ ሐመዳ ፤ ወመኑ ፤ ይወልዶ ፤ ለሐመዳ ፤ ሰማይ ፤** (ሐኖ፹፱ ፣ ፪ ። ኢዮ፴፰ ፣ ፳፱ ፣ ፳፱) ። ለብትን ፣ በረዶም ፣ ይነገራል ፣ (ሲዜና ፣ ፲፩ ፣ ፳፪) ።

**ሐመድማድ ፤** ዐመዳይ ፣ ዐመድማይ ፣ ዐመድማ ፣ ቅጠል ፣ ዐመድ ፣ የነፋበት ፣ የሚመስል ።

**ሐሚው ፤ ዎት ፤ (ሐመወ ፣ የሐሙ ፣ ይሐሙ) ፤** ማመት ፣ ማመኘ ፤ መታመት ፣ መታመኘ ፣ ዐማት ፣ ዐማች ፣ ማድረግ ፣ ወይም ፣ መኾን ። መምረር ፣ መጐምዘዝን ፣ ሐሞት ፣ መኾን ፣ ወደ ፣ ሐሞት ፣ ጠባይ ፣ መለወጥ ፣ የምግብ ። ክፉ ፣ ጋብቻንም ፣ ያሳያል ።

**ተሐመወ ፤** ተማመቸ ፣ ዐማችና ፣ ዐማት ፣ ተኳኼነ ፣ ተጋባ ፣ ተዛመደ ። **ምንት ፤ አነ ፤ ከመ ፤ እትሓመዎ ፤ ለንጉሥ ። እስመ ፤ ተሓመውኑ ፤ ምስሌ ፤ አሕዛብ ። ኢትትሓመውዎሙ ። እምእለ ፤ ይትሓመዉኒ ፤ ውእቱ ፤** (፩ነገ ፣ ፲፰ ፣ ፲፰ ። ዕዝ፱ ፣ ፲፬ ። ዘዳ፯ ፣ ፫ ። ሩት፪ ፣ ፳) ።

**አስተሐመወ ፤** አስተማመቸ ፣ አስተማማለ ፣ አዛመደ ።

**መስተሐምው ፤ (ውት ፣ ዋን ፣ ዋት) ፤** አማላይ ፣ አስተማማይ ። (ተረት) ፣ አማማይን ፣ መጠር ፣ አማማይን ፣ በጠር ። የባል ፣ ወንድም ፣ ዘመዱ ፣ ጕልማው ፣ ርሱ ፣ ሲሞት ፣ ሚስቱን ፣ የሚወርስ ፣ የሚያገባ ። **ኢይርኒ ፤ ዐጽፈከ ፤ እስመ ፤ መስተሓምው ፤ አንተ ፤** (ሩት፫ ፣ ፱ ። ፲፩ ፣ ፲፪ ። ፬ ፣ ፩—፳) ። መስተሐምው ፣ ከማለት ፣ ይልቅ ፤ ወራሲ ፣ መውረስ ፣ ቢል ፣ በቀና ።

**ታሕማ ፤ (ማት) ፤** ዐምቻ ፣ ጋብቻ ፣ ዐማችነት ። **ገብረ ፤ ታሕማ ፤ ምስለ ፤ ነገሥት ፤ አሕዛብ ፤** (አርጋ ፣ ፭) ። ዐማች ፣ የሴት ፣ ልጅ ፣ ባል ። **ወይቤልዎ ፤ ለሎጥ ፤ ብከኑ ፤ ታሕማ ፤ በዝየ ። ወወፅአ ፤ ኀበ ፤ ታሕማቲሁ ፤** (ዘፍ፲፱ ፣ ፲፪ ፣ ፲፬) ።

—፤ ዐማት ፤ የባል ፣ ወይም ፣ የሚስት ፣ አባት ፣ እናት ። **አክብሪ ፤ ታሕማኪ ። ወቀበሮሙ ፤ በክብር ፤ ለታሕማቲሁ ፤** (ጦቢ፲ ፣ ፲፪ ። ፲፬ ፣ ፲፫) ።

**ሐም ፤ ሐማ ፤ ሐምው ፤ (ብ ፣ ሐማን ፤ አሕማው) ፤** ወንድ ፣ ዐማት ። **ሐመ ፤ ሙሴ ። እስመ ፤ ሐሙሁ ፤ ለቀደፉ ። አዝማዲሁ ፤ ወእምዝ ፤ ሐማን ፤** (ዘፀ፲፰ ፣ ፲፪ ። ዮሐ፲፰ ፣ ፲፫ ። ፍ ፣ ነ ፣ ፳፯) ።

—፤ ዐማች ። **እመሰ ፤ ጸባእክሙኑ ፤ ትጸብኡ ፤ ውሉደክሙ ፤ ወአሕማወክሙ ፤** (ዮሴፍ ።

**ሐማት ፤ (ብ ፣ አሕማት) ፤** ሴት ፣ ዐማት ። **ረከባ ፤ ለሐማተ ፤ ጴጥሮስ ፤** (ማቴ፰ ፣ ፲፬) ። መርጓት ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ ሐማት ፣ ይላል ፤ ስሕተት ፣ ነው ። **ዘይገብር ፤ ከመ ፤ ዝ ፤ ወይሰክብ ፤ ምስለ ፤ ሐማቱ ፤ ያውዕዮ ፤ በእሳት ፤** (ኩፋ ፣ ፴፩) ።

**ሐሞት ፤ (ብ ፣ ሐማውት) ፤** በቁሙ ፣ መራራ ፣ ፈሳሽ ፣ በፍጥረት ፣ ኹሉ ፣ ሆድ ፣ ከጕበት ፣ ጋራ ፣ እንደ ፣ ሽንት ፣ ውሃ ፣ በታናሽ ፣ ፊኛ ፣ ታቍሮ ፣ የሚገኝ ፤ ዐይነቱ ፣ የዘይት ፤ ምሬቱ ፣ የሬት ፤ ሲበዛ ፣ ደዌ ፣ የሚኾን ፤ የሚያስከር ፣ ራስ ፣ የሚያዞር ። የምሬርን ፣ ፋንት ፣ እይ ፣ ከዚህ ፣ ጋራ ፣ አንድ ፣ ነው ። **ተክዕወት ፤ ውስተ ፤ ምድር ፤ ሐሞትየ ። ምንት ፤ ውእቱ ፤ ልቡ ፤ ወከብዱ ፤ ወሐሞቱ ፤ ለዝ ፤ ዓሣ ። ወሀብዎ ፤ ይስተይ ፤ ወይነ ፤ ወሐሞተ ፤ ድሙረ ፤** (ኢዮ፲፮ ፣ ፲፫ ። ጦቢ፮ ፣ ፯ ። ማቴ፳፯ ፣ ፴፬) ። ሬትና ፣ ከርቤ ፣ ሌላውም ፣ ኹሉ ፣ ከዚህ ፣ ስም ፣ ነሥቶ ፣ ሐሞት ፣ ይባላል ፣ መራራ ፣ ማለት ፣ ነው ። **ወደዩ ፤ ሐሞተ ፤ ውስተ ፤ መብልዕየ ፤** (መራራ ፣ ቅጠል) ። **ምንት ፤ ይመርር ፤ እምሐሞት ፤** (ሬት ፣ የሬት ፣ ወገን) ። (መዝ ፣ ፷፰ ። ምሳሌ ፣ ፱) ።

**ሐሚዝ ፤ ዞት ፤ (ሐመዘ ፣ የሐምዝ ፣ ይሕምዝ ። ዐረ ፣ ሐሚፀ ። ሱር ፣ ሕማጽ ። ዕብ ፣ ሐማጽ) ፤** መሐምጠጥ ፣ መሰንፈጥ ፤ መቡካት ፣ መበላሸት ። መምረር ፣ መጐምዘዝ ፤ መኰምጠጥ ። መርዛም ፣ መርዛም ፣ መኾን ፣ በመርዝ ፣ መግደል ። መጥላት ፣ መመረዝ ፣ ቂም ፣ በቀል ፣ መያዝ ። መቈጣት ፣ መማሸት ፣ እንደ ፣ መርዝ ፣ ኹኖ ፣ ሰው ፣ እስከ ፣ መግደል ፣ እስከ ፣ ማጥፋት ። ሐመወና ፣ ሙሀ ፣ የዚህ ፣ ጎር ፣ ናቸው ፣ ባንዳንድ ፣ ወገን ፣ ይመሳሰላሉ ።

**ሕምዝ ፤ (ዛት) ፤** መርዝ ፤ የተቀመመ ፣ መድኀኒት ፣ የሚገድል ፣ የሚያድን ። ከእንስሳትና ፣ ከአራዊት ፣

ከተሐዋስያን ፤ ከዕፀው ፡ ከአዕራው ፡ ከማር ፡ ከቅጠል ፤ ከቋያና ፡ ከቡቃያ ፡ ወገን ፡ ከማማሰኛ ፡ ፍጥረት ፡ የሚገኝ፤መራራ ፡ ሐምጣጣ ፡ ጕምዛዛ ። ዘከመ ፡ እንስሳት ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ሐምዝ ፤ ወዘከመ ፡ አራዊት ፡ መሣጥያን ፡ እለ ፡ ይሴስዩ ፡ ሐምዘተ ። ወበቀላትኒ ፡ ቀታልያን ፡ እለ ፡ ያማስንዎ ፡ ለልብ ፡ ወለዘርሉ ፡ ዘሥጋ ፡ በበሊያቲሆሙ ። ወላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ፍትሕ ፤ እመ ፡ ተረክበ ፡ እምነ ፡ ዝንቱ ፡ ክፍል ፡ አሐዱ ፡ ጸጋ ፡ ዘያማስን ፡ ጥዑየ ፡ ወዘይፈውስ ፡ ድዉየ ፤ ይትገሐሥ ፡ ጥዑይ ፡ እምበሊያቲሁ ፤ ወለድዉይስ ፡ ብዉሕ ፡ ከመ ፡ ይብላዕ ፡ እመንገለ ፡ ጸጋ ፡ መድኀኒት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫) ።

—፤ ቍጣ ፡ መዐት ፤ ክሕደት ፡ ኀጢአት ። ፀቢይ ፡ ሐምዙ ። መሠረታተ ፡ ሐምዝ ፡ (ራእ፲፪ ፡ ፲፪ ። ቅዳ ፡ ዲዮ) ።

—፤ መራራ ፡ ሽካራ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፤ ሰው ፡ የሚጐዳ ፡ ቃል ። ሐምዝ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ታሕተ ፡ ከናፍሪሆሙ ፡ (መዝ ፡ ፻፴፱) ። መሪር ፤ ሐሞት ፤ ዕጕሥቋር ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሐምዝ ፡ ይላል ፤ መራራ ፡ ክፉ ፡ ማለት ፡ ነው ። እግዚ ፡ አስተየኒ ፡ ማየ ፡ ሐምዝ ። አጽገበኒ ፡ ሐምዘ ። ምረተ ፡ ሐምዝየ ፡ (ኤር፰ ፡ ፲፬ ። ሰቈ፫ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ። ዘዳ፳፱ ፡ ፲፯) ። ባወራረድና ፡ ባነጻር ፡ አፈታት ፡ ባለብሉዮች ፡ ስፊዊት ፤ ባለቅዳሴዎች ፡ ምድር ፡ ይሉታል ።

ሐምሐም ፤—ቅል ፤—ሐመመ ።

(ጥ) ሐመየ ፤—አሰረ ፤—ኀምዮ ፡ ኀመየ ።

ሐምይ ፤ ዮት ፤ (ሐመየ ፡ የሐሚ ፡ ይሕሚ ። ሱር ፡ ሐነየ) ፤ ማማት ፡ መበዝበዝ ፤ መንቀፍ ፡ መስደብ ፤ ሰውን ፡ በኋላው ፡ በክፉ ፡ ማንሣት ፤ በላዩ ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ መናገር ። ሐመይዎ ፡ ለሙሴ ። ሐመዩኒ ፡ በሐሰት ። ዘየሐሚ ፡ ቢጾ ፡ በጽሚት ። ዘየሐሚ ፡ አባሁ ። ሐመይክሙ ፡ ፀቢያተ ፡ ወድሩካተ ፡ ቃላተ ፡ ላዕለ ፡ ዕበዩ ። (ዘኍ፲፪ ፡ ፩ ። ሦሴ፮ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፻ ። ምሳ፳ ፡ ፳ ። ሔኖ፳ ፡ ፱) ። ሐመወ ፡ ሐመዘ ፡ ሐመመ ፡ ሐመየ ፡ እሊህ ፡ ፬ቱ ፡ ዘመዳሞች ፡ ናቸው ።

ሐማዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ መይት) ፤ የሚያማ ፡ (ዐሚ) ፡ ሐሜተኛ ፡ ሐሚና ፤ ሰዳቢ ፡ ነቃፊ ፤ ለፋፊ ፡ ለፍላፊ ። ሰብእሰ ፡ ሐማዪ ፡ በላዔ ፡ ሥጋ ፡ ወሰታዪ ፡ ደም ። ኢትኩን ፡ ሐማዪ ። ኢይኩና ፡ ሐማይያተ ። ወይከውኑ ፡ ሐመይት ፡ ወሐማይያን ፡ ብዙኀ ፡ (ድጓ ። ሢራ፭ ፡ ፲፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲ ፡ ፰ ። ዕር ፡ ኢሳ፫ ፡ ፳፮ ። ሮሜ፩ ፡ ፴) ።

አሕመየ ፤ አሳማ ፡ አስነቀፈ ፤ አስደበ ።

ተሐምየ ፤ ታማ ፡ ተነቀፈ ፤ ተሰደበ ። ለሊከ ፡ ዘትትሔመይ ፡ ወአኮ ፡ ውእቱ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፩) ።

ተሓመየ ፤ ተማማ ፤ ተንቃቀፈ ፤ ተቀናና ፡ ተመቀኛኘ ። ኢትትሓመዩ ፡ በበይናቲክሙ ። ተሓምዮ ፡ (ያዕ፬ ፡ ፲፩ ። ገላ፭ ፡ ፳፮ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፩) ።

ሕሙይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሚት) ፤ የታማ ፡ የተነቀፈ ፤ ስዱብ ፡ ንቁፍ ። ግብረ ፡ ሕሙይ ፤ ፍትወት ፡ ሕሙይ ። ሕሙየ ፡ ግብር ፡ (ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፻፳፭) ። የተማማ ፡ የተንቃቀፈ ፤ ንቅፍቅፍ ፤ ፍርቅርቅ ።

ሕሜት ፤ ሕምየት ፤ ማማት ፡ መንቀፍ ፤ መታማት ፡ መነቀፍ ።

ሐሜት ፤ (ሱር ፡ ሐኔት) ፤ በቁሙ ፤ ዐሚታ ፡ ነቀፋ ፡ ስድብ ፤ ክፉ ፡ ነገር ፡ ገመና ፡ ነውር ፤ ስም ፡ የሚያጠፋ ፡ የሚሰብር ፤ በውነት ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የሚነገር ። ዝንጓጔ ፡ ወሐሜት ፡ ወዝክር ፡ ሕሡም ። ዘአልቦ ፡ ሐሜት ። ቀሲስ ፡ ንጹሐ ፡ ይኩን ፡ እምሐሜት ፡ (ዮሴፍ ። ቲቶ፩ ፡ ፯ ። ቀኖ ፡ ኒቅ) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ በሐሜት ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ ሱርስቱ ፡ ሐኔት ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። ቃሕው ፡ ወሐኔት ፡ (ሢራ፵ ፡ ፭) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ንዝንዝ ፡ ዝብዝብ ፡ ይሉታል ።

ሐሚል ፤ ሎት ፤ (ሐመለ ፡ የሐምል ፡ ይሕምል ። ዐረ ፡ ሐመለ ፤ ጾረ ። ዕብ ፡ ሐማል ፤ ራራ) ፤ መፅነስ ፡ ማበብ ፤ ማፍራት ፡ መሸከም ። መማረር ፡ መልቀም ፤ መዘንጠፍ ፡ መመልመል ፤ የፍሬ ፡ የቅጠል ። ወፈረ ፡ ገዳመ ፡ ይሕምል ፡ ሐምለ ፡ ምድር ። ወበዕለተ ፡ ዐርብ ፡ የሐምል ፡ ሐምለ ፡ ገዳም ፡ ዘእንበለ ፡ ይኅሬ ፡ መሪረ ፡ ወጥዑመ ፡ (፬ነገ ፡ ፬ ፡ ፴፱ ። ገድ ፡ ተክ) ።

ሐማሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ መልት ። አው ፡ ሐማል ፤ ላን ፡ ላት) ፤ የሚሸከም ፡ ተሸካሚ ፤ ማራሪ ፡ ለቃሚ ። ሐማል ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ያስተባብራል ።

ሐምል ፤ (ብ ፡ አሕማል ፡ ላት) ፤ ቅጠል ፡ ቅጠላቅጠል ፤ ማር ፡ ቋያ ፡ ቡቃያ ፡ ተክል ፤ ሥንቆ ፡ ጐመን ፤ ሰላጣ ፡ ቅመም ፤ በየስሙና ፡ በያይነቱ ፤ የሚበላ ፡ የማይበላ ፡ ማናቸውም ፡ ኹሉ ። ፀዲደ ፡ ሐምል ። ሐምለ ፡ ገዳም ። ሐምለ ፡ ሁስጴ ፡ ዘይወፅእ ፡ ዲበ ፡ አረፍት ፡ (ዮሐ፲፰ ፡ ፩ ። ሉቃ ፡ ዕዝ፲፪ ፡ ፺፰ ። ፫ነገ ፡ ፬ ፡ ፴፫) ።

ሐምለ ፡ ብሒእ ፤ መራራ ፡ ስንፋጥ ፤ ሐዘ ፡ ሰናፍጭ ፤ አውጥ ፡ ዐሞጭ ፤ የመሰሰው ፡ ኹሉ ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፰ ። ዘኍ፱ ፡ ፲፩) ።

ሐምለ ፡ ሣዕር ፤ ፍሬ ፡ እክል ፤ እሸት ፡ ምርት ፡ (ኩፋ ፡ ፯) ።

ሐምለ ፡ ቅብዕ ፤ መሎኪ ፤ ቅባታም ፡ ማላጋ ፡ ጠውላጋ ፤ እንዳንጣሪያና ፡ እንደ ፡ ባማ ፡ ያለ ፤ የመሎኩን ፡ ፍች ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። (ኢሳ፶፭ ፡ ፰) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ከወጥመድ ፡ የገባ ፡ ብኽር ፡ አጋዘን ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ሐምለ ፡ ቅብዕ ፡ አይልም ።

አሕመለ ፤ አስረገዘ ፤ ጫነ ፡ አሸከመ ፤ አስለቀመ ።

**አሕመልመለ** ፤ (ቶቀ ፡ ግ) ፤ ለመለመ ፡ ረ ጠበ ፡ ወጣ ፡ በቀለ ፡ ተገኘ ። ተፈጠረ ፤ ቅጠል ፡ መሰለ ። ያሕመለምል ፡ አውግር ፡፡ ወእምአሐቲ ፡ መዘግብ ፡ ዘእምእስትንፋስ ፡ አፉሁ ፡ ይሠርጻ ፡ ወያሕመለ ምላ ፡ ነፍሳት ፡፡ ሕብር ፡ እንተ ፡ ታሕመለምል ፡፡ ወ ርቀ ፡ ዐረብ ፡ ዘያሕመለምል ፡ (ዓሞ፱ ፡ ፲፫ ። ቅዳ ፡ ግሩ ። ዘሌ፲፫ ፡ ፵፱ ። አር፫) ።

—፤ አለመለመ ፡ አረጠበ ፡ አበቀለ ፡ አስገኘ ። አሕመል ምል ፡ ሴተ ፡ ማዕረ ፡ ዘየብሰ ፡፡ አሕመልምል ፡ ሴተ ፡ ነፍስየ ፡፡ ያሕመለምል ፡ ማዕረ ፡ ለእንስሳ ፡ (ሉቃ ፡ ስ፲፫ ፡ ፵፰ ። ፊልክ ። ቅዳ ፡ ኤጲ) ። አመለመለ ፡ ጠቀ ለለ ፡ የጥጥ ፡ የፀምር ፡ ለመፍተል ።

**ሐመልሚል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ማል) ፤ የለመ ለመ ፡ ርጥብ ፡ ቅጠላም ፡ ቅጠልማ ፡ ቅጠልያ ፡ ቅጥል ጣል ፡ ዐይነቱ ፡ ቅጠል ፡ አረንጓዴ ፡ የሚመስል ። ወይም ፡ ብሩማ ፡ የወራ ፡ ቅጠል ፡ የበሰለ ፡ ፍሬ ፡ ሲወድቅና ፡ ሲደ ርቅ ፡ የቀረበ ፡ ወይባ ፡ ዐደይ ፡ አበባ ፡ የሚመስል ፡ የሎሚ ፡ የብርትኳን ፡ ዐይነት ። የሚያበራ ፡ የሚበርቅ ፡ የሚያብ ረቀርቅ ፡ የወርቅና ፡ የንሐስ ፡ ዐይነት ። ነሥአ ፡ በትረ ፡ ልብን ፡ ሐመልሚለ ፤ ርጥብ ። ዕንቍ ፡ ሐመልሚል ፡፡ ፈረስ ፡ ሐመልሚል ፡ (ዘፍ፴ ፡ ፴፯ ። ፪ ፡ ፲፪ ። ራእ፮ ፡ ፰) ። በሐመልሚል ፡ ፈንታ ፡ ሐመልማል ፡ ይላል ፤ አያ ሰኝም ፡ (ራእ፰ ፡ ፯) ።

**ሐመልማል** ፤ (ላት) ፤ ለምለም ፤ ቋያ ፡ ቡ ቃያ ፡ ሣር ፡ ቅጠል ፡ እኽል ፡ ተክል ፤ ዛፍ ፡ ቋጥቋጦ ፤ ሰጋ ፡ ቀንበጥ ፡ ሙሽራ ፤ ለባልብ ፡ ውልብልቢት ፡ መላው ፡ የማግስኛ ፡ ፍጥረት ። ሰታብቍል ፡ ምድር ፡ ሐመል ማለ ፡ ማዕር ፡፡ ዘሉ ፡ ሐመልማለ ፡ ሐቅል ፤ ወዘሉ ፡ ሐመልማለ ፡ ምድር ፡፡ እምቅድመ ፡ ያስተርኢ ፡ ገጸ ፡ የብስ ፡ ወእምቅድመ ፡ ይብቍሉ ፡ ሐመልማ ላት ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፲፩ ። ፪ ፡ ፭ ። ቅዳ) ። አመልማሎ ፡ የጥጥ ፡ ነዶ ፡ የንድፍ ፡ ጥቅል ፡ (ፀማርኛ) ።

**ሐመልማለ ፡ አቍጽል** ፤ ርጥበት ፡ ልም ላሜ ፡ ልብስነት ፡ (ሔኖ፳ ፡ ፩) ።

**ሐመልማለ ፡ ወርቅ** ፤ የወርቅ ፡ ሽበ ፡ ወ ይም ፡ ቅጠል ፡ ሥሥ ፡ ረቂቅ ፡ (መዝ ፡ ፵፯) ።

**ሐመልማለ ፡ ዘርዕ** ፤ ቡቃያ ፡ ተክል ፡ ተዘ ርቶ ፡ የሚበቅል ፡ ኹሉ ፡ (ሚራ፵ ፡ ፳፱) ።

**ሐመልማለ ፡ ሐምል** ፤ የበሰለ ፡ የገረጣ ፡ ቅጠል ፡ ወይም ፡ የጐመን ፡ (መገ ፡ ፴፯) ።

**ሐመልማለ ፡ ሣዕር** ፤ መስክ ፡ ሰሌ ፡ ለቆ ፡ ርጥብ ፡ ሣር ፡ (ማር፯ ፡ ፴፱) ።

**ሐምሌ** ፤ በቁሙ ፡ የወር ፡ ስም ፡ የመስከረም ፡ ፲፩ኛ ፡ ቅጠላም ።

**ሕምል** ፤ (ላት ። ዐረ ፡ ሒምል) ፤ ሸክም ፡ ሳዝነት ። ዕሥራ ፡ እልፍ ፡ ሕምለ ፡ ሥርናይ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ሐመል** ፤ (ዐረ ፡ እልሐመል) ፤ ኮከብ ፤ የኮከብ ፡ ስም ፡ እሡራ ፡ በግ ። ከፀሐይ ፡ ጋራ ፡ በመጋቢት ፡ ፴ ፡ ዕለት ፡ ገብቶ ፡ ኬክሮስ ፡ ይመግባል ፡ (አቡሻ ፡ ፱) ። የስሙ ፡ ምስጢር ፡ ማስረገዝና ፡ ማሸከም ፡ ነው ፡ መጋ ቢት ፡ በወዲያ ፡ እንደ ፡ መስከረም ፡ ነውና ፡ ቅጠሉና ፡ ለምላሜው ፡ ሳይቀር ፡ መዋዕለ ፡ ፅንስ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ።

**ሐሚለት** ፤ (ጽር ፡ ሒሚሎቲ ። ሱር ፡ ሚልታ) ፤ የላይ ፡ ልብስ ፡ ካባ ፡ በርኖስ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ደበሎ ፡ ፀጥፍ ። ሐ ፡ አርቲክል ፡ ነው ፡ ሚለት ፡ ከሜላት ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ፡ የሚላትን ፡ ፍች ፡ እዩ ፡ ባለብለቶች ፡ ግን ፡ ጎባጌ ፡ ጥምጥም ፡ ይሉታል ፡ (፩ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱ ። ፬ነገ ፡ ፪ ፡ ፰ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬) ። በሠቀ ፡ ወሰ ሐሚለት ፡ (ዕብ፲፩ ፡ ፴፯) ።

**ሐሚም** ፤ **ሞት** ፤ (ሐመ ፤ ሐመመ ፡ የሐ ምም ፡ ይሕምም ። ዐረ ፡ ሐመ ። ዕብ ፡ ወ ሱር ፡ ሐም) ፤ መሞቅ ፡ መተኰስ ፡ መፋጀት ፡ በን ዳድ ፡ በትኵሳት ፡ መያዝ ። መታመም ፡ መከራ ፡ መቀ በል ፡ ማማጥ ፡ መጨነቅ ፡ ማዘን ፡ ማልቀስ ፡ መናደድ ። ተሐምም ፡ ዐቢየ ፡ ፈፀንተ ፡፡ ዘእንበለ ፡ ትሕምም ፡ ተፈወስ ፡፡ ሰእንቲኣነ ፡ ሐመ ፡፡ ተሐምም ፡ ለወሊድ ፡፡ ሐመምኩ ፡ ላዕሌከ ፡ (ሉቃ፬ ፡ ፴፰ ። ሚራ፲፰ ፡ ፲፱ ። ኢሳ፶፫ ፡ ፬ ። ራእ፲፪ ፡ ፪ ። ፪ነገ ፡ ፩ ፡ ፳፯) ።

—፤ መመቅኘት ፡ መንፈግ ፡ መጨስ ፡ መሥሠት ። የሐ ምም ፡ አቅርቦ ፡ እዴሁ ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ (ምሳ፳፮ ፡ ፲፭) ።

**ሐማሚ** ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት ፡ መ ምት) ፤ የሚታመም ፡ ታማሚ ፡ ሕማም ፡ የሚሰማ ማው ፤ ሐዘንተኛ ፡ መከረኛ ። አንተ ፡ ሐማሚ ፡ ዘከመ ፡ ዕሪናከ ፡ ምስሌነ ፤ ወአንተ ፡ ኢሐማሚ ፡ ዘከመ ፡ ዕሪ ናከ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ እግዚ ፡ ኢ ሐማሚ ፡፡ ሐማሚት ፡ አርአያ ፡ ገብር ፡ (ሃይ ፡ አበ ። ተረ ፡ ቄር) ።

—፤ የሚመቀኝ ፡ ምቀኛ ፡ ሥሡ ፡ ንፉግ ። ዐይንከኑ ፡ ሐማሚ ፡ ውእቱ ፡፡ ዐይኑ ፡ ለሐማሚ ፡ ይጠውዕ ፡ እኩለ ፡፡ ብእሲ ፡ ሐማሚ ፡፡ ቅንአተ ፡ ሐማሚ ፡፡ ሐማ ምያን ፡ (ማቴ፳ ፡ ፲፭ ። ሚራ፲፬ ፡ ፲ ። ምሳ፳፰ ፡ ፳፪ ። ጥበ፯ ፡ ፳፭ ። ሮሜ፩ ፡ ፳፱) ።

(ጥ) **ሐማም** ፤ (ዐረ) ፤ ፍል ፡ ውሃ ፡ ማወት ፡ ቤተ ፡ ብለኔ ።

**ሕሙም** ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ምምት) ፤ የሞቀ ፡ ሙቅ ፡ የታመመ ፡ ድዉይ ፡ ሕዙን ። ማይ ፡ ሕሙም ፤ (ሙቅ ፡ ግም ፡ ደፍርስ) ። ብእሲሁ ፡ ቅሡፍ ፡ ወሕ ሙም ፡፡ ሕሙማን ፡ ይፈቅድዎ ፡ ለዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡፡ ዘሉ ፡ ዓለም ፡ ሕሙም ፡ ወትኩዝ ፡፡ ተንሣእኩ ፡ ሕ ሙምየ ፤ (ዕዝ፯) ። ሕምምት ፡ ነፍስየ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ ፳ ። ኢሳ፶፫ ፡ ፫ ። ማቴ፱ ፡ ፲፪ ። ሮሜ፰ ፡ ፳፫ ። ዕዝ፱ ፡ ፳ ። ሉቃ ፡ ዕዝ፱ ፡ ፵፯) ።

**ሕማም** ፤ (ማት) ፤ ትኵሳት ፡ ንዳድ ፤ በቁሙ ፡ በሽታ ፡ ሐዘን ፡ ጭንቅ ፡ መከራ ፡ ወይሌ ፡ ዋይታ ፡ ወዮታ ። ክቡድ ፡ ሕማም ፡፡ ኀበ ፡ አልቦ ፡ ደዌ ፡ ወአልቦ ፡ ሕ

ማም ፡፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ በሕማማት ፡፡ ሕማሙ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡፡ አሐቲ ፡ ሕማም ፤ ካልእት ፡ ሕማም ፡ (ሚራ፴፱ ፡ ፪ ። ቀሌ ። ዕብ፪ ፡ ፲ ። ሮሜ፰ ፡ ፲፰ ። ራእ፱ ፡ ፲፪ ። ፲፰ ፡ ፲፱) ።

**ሕማምት ፤ (ትግሬ) ፤** ያውሬ ፡ ስም ፡ ግስላ ፡ ቍጡ ፡ ብስጩ ፡ ተናዳጅ ።

**ሕመሜ ፤** መመቅኘት ፤ ምቀኝነት ፤ ተንኰል ፡ ሽንገላ ፡ የሚያናድድ ፡ ነገር ። **እምሕመሜ ፡ እኩይ ፡፡ ወሕመሜ ፡ ይትናገር ፡ አፉሆሙ ፡** (ቅዳ ። ምሳ፳፱ ፡ ፪) ።

(ጥ) **ሕመት ፤ (ሳቢና ፡ ጥሬ ፡ ዘር) ፤** መሞቅ ፡ አሕሕቅ ። ሙቀት ፡ ትኵሳት ። ጥቀርሻ ፡ ጥላት ፤ ከሰል ፡ የእሳት ፡ ትራፊ ፡ መልሶ ፡ እሳት ፡ የሚበላው ፤ ከንፈት ፡ ከደንጊያ ፡ የሚወጣ ፡ ፍጹም ፡ ጥቍር ። **ጸሊም ፡ እምነ ፡ ሕመት ፡ ራእዮሙ ፡፡ ጸሊም ፡ ከመ ፡ ሕመት ፡፡ ማየ ፡ ሕመት ፡** (ሰቆ፬ ፡ ፰ ። ሄርማ ፡ ገ፻፬ ። ፪ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፫) ።

**ሐመተ ፤ (ተቀ ፡ ማ) ፤** በቁሙ ፤ ዐመተ ፡ በላ ፡ አቃጠለ ፤ አከሰለ ፤ አጠቈረ ፡ ከሰል ፡ አስመሰለ ። ሐመደን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**አሕመመ ፤** ዐመመ ፤ አሳመመ ፤ አሞቀ ፡ አተኰሰ ፤ አሳዘነ ፡ አስጨነቀ ። **አሕመም ፡ ፀሓይ ፡ ርእሶ ፡፡ ኢያሕመምሙ ፡ ላህበ ፡ ፀሓይ ፡፡ ሀሎ ፡ ዘያሐምም ፡ ወያስተፌሥሕ ፡፡ ኢያሕመሞ ፡ ይሁዳ ፡ ለኤፍሬም ፡** (ዮና፬ ፡ ፰ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፲ ። ሢራ፳ ፡ ፲፭ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፲፫) ።

**አሕማሚ ፤ መሕምም ፤** የሚያሳምም ፡ አሳዛኝ ፡ አስጨናቂ ። **ደዌ ፡ ወሕማሕም ፡ አማምደን ፡** (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፱) ።

**ማሕመሚ ፤** ገዘፒ ፡ ከማሁ ። **ዝብጠት ፡ ማሕመሚ ፡** (ፈ ፡ መ ፡ ፰ ፡ ፫) ።

**ማሕምም ፤ ማሕመም ፤** (ጥሬና ፡ ቅጽል) ፤ ምጥ ፡ ጭንቅ ። **አኅዘሙ ፡ ማሕምም ፡** (ዘበ፲፭ ፡ ፲፬) ። የሚያሳምም ፡ የሚጐዳ ፤ የሚያስጨንቅ ። **ዘበጥዎ ፡ ዝብጠተ ፡ ዐቢየ ፡ ወማሕምመ ፡** (ስንክ ፡ መጋ፳፯) ።

**አስተሐመመ ፤ (አስተሕመመ) ፤** የሐመመና ፡ የአሕመመ ፡ ድርብ ፡ ገቢርና ፡ ዐጕል ። አሳመመ ፤ ለሕማም ፡ ሰጠ ። **እግዚ ፡ ፈተወ ፡ ያስተሐምሞ ፡** (ተረ ፡ ቄር፩) ።

—፤ አስታመመ ፡ ረዳ ፡ ጠበቀ ፡ ሰበሰበ ። **እሰ ፡ አስተሐመምዎ ፡ ለአትናቴዎስ ፡፡ ዘኢከሀለ ፡ ሠሪዐ ፡ ቤቱ ፡ እፎ ፡ ያስተሐምም ፡ ቤተ ፡ እግዚ ፡፡ አስተሐምም ፡ ዘውስተ ፡ ገዳም ፡ ሐመልማለ ፡** (አዋል ። ፩ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፭ ። ምሳ፳፯ ፡ ፳፬) ።

—፤ በሰበ ፡ አስተናነተ ፡ ተጋ ፡ አንቀልፍ ፡ ዐጣ ። ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ከማስታመም ፡ ይገባል ። **ያስተሐምሙ ፡ ኅበ ፡ ዘይትሌዐል ፡፡ ሙቀ ፡ እምፍትወታቲሁ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ ወአስተሐምሞቱ ፡፡ ተንሥሥ ፡ አስተሐሚማ ፡ እስከ ፡ ቀረከብ ፡** (አፈ ፡ ድ፳፯ ። ፊልክ ፡ ፫ ። ሉቃ፲፭ ፡ ፰) ።

**መስተሐምም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤** የሚያስታምም ፡ አስታማሚ ፡ ትጉህ ፡ ንቁህ ፡ ወባቢ ፡ አስተናቃኝ ። **መስተሐምማን ፡ ለግብረ ፡ ቅድስና ፡** (ቀሌ) ።

**ተሐመመ ፤** ተቃና ፡ ተመቀኘ ። **ተሐምሞ ፡ ወተቃንአ ፡፡ እስከ ፡ በተሐምሞ ፡** (፩ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፬ ። ሮሜ ፲፫ ፡ ፲፫) ።

**አስተሐመመ ፤** አስተማመመ ፤ አመቀኘ ። ነገር ፡ ሠርቶ ፤ መድኀኒት ፡ ሰጥቶ ።

**መስተሓምም ፤** ክፉ ፡ መድኀኒት ፤ የሚያም ፡ የሚገድል ፡ ሥራይ ፡ የሚኾን ። ወይም ፡ ሰውየው ፡ ባለ መድኀኒቱ ። **ብእሲ ፡ መስተሓምም ፤ አው ፡ ተጠያፊ ፡** (ቄስጠ) ።

**ሐምሐም ፤ (ዕብ ፡ ወሱር ፡ ቂቃዮን ። ዐረ ፡ የቅጢኒት) ፤** ቅልዕ ፤ ቅል ፡ የቅል ፡ ዐይነት ፡ ኹሉ ፤ በቊላ ፡ በእንቅልቅል ፡ በሙቀት ፡ አገር ፡ የሚበቅል ፤ ሐረጋም ፡ ሰፋሐ ፡ አቍጽል ፤ ፍሬው ፡ ገንቦ ፡ ማድጋ ፡ የሚያከክል ፤ የሚበላ ፡ የሚያገለግል ። **ወአዘዘ ፡ እግዚ ፡ ሐምሐመ ፡ ወበቊለ ፡፡ ዘመደ ፡ ሐምሐም ፡** (ዮና፬ ፡ ፮—፲ ። ቄስጠ) ።



ሐምሐም ፡

**ሐመጸ ፤ (ትግ ፡ ሐምጸ ። ዕብ ፡ ሐማጽ) ፤** በካ ፡ ሖመጠ ፡ ሖመጠጠ ፤ ሸመጠረ ፤ ሖምጣጣ ፡ ኾነ ።

**ሐሚቅ ፤ ቆት ፤ (ሐመቀ ። ዐረ ፡ ሐሚቀ) ፤** ማበድ ፡ መክነፍ ፤ ክፉ ፡ መጥፎ ፡ መኾን ።

**ሕሙቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ምቅት) ፤** ያበደ ፡ እብድ ፤ መጥፎ ፡ ምኑኑ ፡ ከንቱ ፡ ብልሹ ። **እፎ ፡ ትት መየጡ ፡ ዳግመ ፡ ውስተ ፡ ኅሳር ፡ ወሕሙቅ ፡ ነገር ፡** (ቄር ፡ ስም ። ገላ፬ ፡ ፱) ።

**ሕመቅ ፤** እብደት ፤ እብድነት ፤ ክፋት ፡ ቅለት ።


**አሕመቀ ፤ አስተ(ሕ)ሐመቀ) ፤** አሳበደ ፡ እብድ ፡ አደረገ ፡ አስመሰለ ፡፡ ናቀ ፡ ነቀፈ ፤ አቃለለ ። **ፍኖተ ፡ እንተ ፡ ትደሉ ፡ ለትስብእት ፡ ኢያስተሐሚቆ ፡ ልደተ ፡ ተወልደ ፡** (ቄር ፡ ጳላ) ።

**ሕምር ፤—ቀይ ፡ ዐይነት ፤—ኅምር ።**

**ሐመረ ፤ (ሐመለ ፤ ጸረ ፤ ሰከመ) ፤** ተጫነ ፡ ተሸከመ ፤ ተሸከሞ ፡ ኼደ ፡ ተጓዘ ።

**ሐመር ፤ (ብ ፡ አሕማር ፡ ራት ። ዐረ ፡ ሒማር ። ዕብ ፡ ሐሞር ፤ አህያ) ፤** መርከብ ፡ የባሕር ፡ አህያ ፡ የሚጫን ፡ የሚሸከም ፤ ተጭኖም ፡ የሚኼድ ፡ የሚጓጓድ ፡ በጢስ ፡ በነፋስ ፡ የሚነዳ ፤ ከብረት ፡ ከንፈት ፡ የተሠራ ፡ የተሰናዳ ። **ረከበ ፡ ሐመረ ፡ ዘይነግድ ፤ ወተዐሰበ ፡ ሐመረ ፡ ወዐርገ ፡ ውስቴቱ ፡፡ አሕማረ ፡ ተርሴስ ፡፡ ነገሥት ፡ አሕማር ፡** (ዮና፩ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፵፯ ።

ሔኖ ፡ ፻፭) ። ሐመረ ፡ የብስ ፤ የምድር ፡ ባቡር ፤ ሌላ ውም ፡ በእሳት ፡ ኀይል ፡ የሚኼድ ፡ ኹሉ ። ረከበንና ፡ መርከብን ፡ እይ ።



ሐመር ፡

**ሐሜር** ፤ (ዕብራ) ፤ የመስፈሪያ ፡ ስም ፤ የእ ኽል ፡ መስፈሪያ ፤ ዐሥር ፡ ኢፍ ፡ የሚይዝ ፤ ታላቅ ፡ ዐ ሥረ ፡ ፈጅ ፡ (ሕዝቅኤ ፡ ፵፭ ፡ ፲፬ ። ሆሴዕ ፡ ፫) ።

**ሐመር** ፤ (ዐረ ፡ ሐመር) ፤ የዛፍ ፡ ስም ፤ ፍሬው ፡ ጥቍር ፡ ጣፋጣ ፡ ሖምጣጣ ። ወይም ፡ የባሕር ፡ ፉል ፤ ታላላቅ ፡ ባቂላ ፤ ጠንቋዮች ፡ እንደ ፡ ጠጠር ፡ እየ በተኑ ፡ የሚያሟርቱበት ። ተጠይሮ ፤ በሕንጽፎ ፤ ሐ መድ ፤ ወፍሬ ፤ ዕፀው ፤ ወሖመር ፤ ወበቀልት ፤ ወኅጠታት ፤ ዘጕል ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፮) ። ፋመስን ፡ እይ ።

**ሐመር** ፤ እንቡጥ ፡ ከነፍሬው ። ሖሞረ ፡ ጽ ራእ ፤ የጽራእ ፡ እንቡጥ ፡ የብርብራ ፡ ዐይነት ፤ ወፍራም ፡ ረገሯሯም ፡ ጥፍጥ ፤ ሰውም ፡ እንስሳም ፡ የሚበላው ፤ ፍ ሬው ፡ እጅግ ፡ ታናናሽ ፡ ከሬራ ፡ ደረቅ ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ ቃሞ ፡ ተረር ፡ ይሉታል ። የጽራእን ፡ ፍች ፡ ተመ ልከት ፡ (ሉቃ ፲፭ ፡ ፲፮) ።



ሐመር ፡

(ጥ) **ሐምሰ** ፤ **ሰት** ፤ (**ሐመሰ ፡ ይሔምስ ፡ የሐምስ ። ዐረ**) ፤ ማመስ ፡ ማገላበጥ ፤ ለማሞቅ ፡ ለማድረቅ ። መዋኘት ፤ ባሕርን ፡ ማማሰል ። መብላት ፡ መቀለብ ፤ ለመሥባት ፡ ለመድለብ ፤ የእንስሳ ። በሙ ፤ ልማድ ፡ ለአባግዕ ፡ ይብልዑ ፡ ኀቡረ ፤ ወሶበሂ ፡ ይወ ርዱ ፡ ይስተዩ ፡ ማየ ፤ አው ፡ የሐምሱ ፡ ኢይትፈለጡ ፡ ዘዘ ፡ ዚአሆሙ ፤ አላ ፡ ኅቡራን ፡ በዅሉ ፡ ግዕዘሙ ፤ (ሥር ፡ ጳኵ) ። ሐመሰ ፡ ብሎ ፡ ዋኘ ፡ ማለት ፡ የትግሬ ፡ ነው ፡ ሙሴና ፡ ሐማሴን ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። የባሕር ፡ ዳር ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ፤ ጠረፍ ፡ ወደብ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ሐማስ** ፤ (ትግሬ) ፤ ጠይም ፡ ዳለቻ ፡ ድፍ ርስ ፤ የጠጠር ፡ ውሃ ፡ መሳይ ።

**ሕሙስ** ፤ (ዐረብ) ፤ ሽንብራ ፡ የቀይ ፡ ዳማ ። የታመሰ ፡ ዕምስ ።

**ሐምስ ፤—ዐምስት ፤—ኀመሰ ።**

**ሐሞት ፤—ዐሞት ፤—ሐመወ ፤**

**ሕመት ፤—ክሰል ፤—ሐመመ ።**


**ሐንበበ** ፤ (ስሯ ፡ ግ ። ሐበበ) ፤ አፈራ ፤ ፍሬ ፡ ያዘ ፡ ተሸከመ ። ሐንበበት ፡ ፍሬ ፡ (አርጋ ፡ ፪) ።

**ሕንቡብ** ፤ ያፈራ ፡ ፍሬያም ፡ ፍሬያማ ። ያበጠ ፤ ያፈረጠመ ፡ (ቢኖዶ) ።

**ሕንባብ** ፤ (ባት ። ዐረ ፡ ሐብ ፤ ዔናብ) ፤ የንፀት ፡ ፍሬ ፡ ሥጋማ ፤ እንደ ፡ ወይን ፡ እንደ ፡ ዘይት ፡ እንደ ፡ ተምር ፡ ያለ ፤ አጋምን ፡ እንኮሬን ፡ ቀጋን ፡ የመ ሰለ ፡ ከብ ፡ እንክብል ፤ ለፈሳሽም ፡ ቅንጣት ፡ ይነገራል ። ሕንባበ ፤ ፍሬሃ ። ኢትትቀረም ፤ ሕንባባተ ፤ ወይ ንከ ፤ ዘወድቀ ። ሕንባባት ፤ እምውስተ ፤ አስካል ። ሕንባባተ ፤ ዘይት ፤ ክልኤቲ ። ሕንባባተ ፤ ሮማን ። ሕንባበ ፤ ማይ ። ሕንባባተ ፤ ነጠብጣብ ። ሕንባባተ ፡ በረድ ፤ (አርጋ ። ዘሌ ፲፱ ፡ ፲ ። ሱቱ ፡ ዕገ ፲፪ ፡ ፳፬ ። ኢሳ ፲፯ ፡ ፮ ። ሰንክ ፡ ጥር ፲፫ ። ቅዳ ፡ ግሩ ። ኢዮ ፴፰ ፡ ፳፰ ። ሄርማ) ።

**ሐንበለ** ፤ (ስሯ ፡ ግ ። ሐበለ) ፤ ኮረቸ ፤ ማነ ፡ አመቻቸ ፤ ደበደበ ፡ ደለደለ ።

**ሕንባል** ፤ (ላት ። ዐረ ፡ ሐንበል) ፤ ኮርቻ ፡ ምቹ ፡ ድብዳብ ፤ መደላድል ። የዳባ ፡ ቀሚስ ፡ የንት ፡ በር ኖስ ፤ የቈርበት ፡ ልብስ ፤ ዐጥፍ ፡ ግላስ ። ሕንባላተ ፤ ገ መል ። ዅሉ ፤ ሕንባላት ፤ ዘላዕሌሁ ፤ ነበረ ፤ (ዘፍ ፴፩ ፡ ፴፬ ። ዘሌ ፲፭ ፡ ፱) ።



ሕንባል ፡

**ሕንብርብሬ** ፤ (ሕበር ፤ ሐበረ ። ዕብ ፡ ሐ ባርቡሮት) ፤ ለምጥ ፡ ቋቍቻ ፤ ድል ፤ ቡሬነት ፡ ዝንጕ ርጕርነት ። ብርሀት ፡ ወጸዐድዒድ ፡ ሕንብራ ፡ ይእቲ ። ወዘሕንብርብሬኒ ። የኀድግ ፡ ነምር ፤ ሕንብርብ ሬሁ ፤ (ዘሌ ፲፫ ፡ ፴፱ ። ፲፬ ፡ ፶፮ ። ኤር ፲፫ ፡ ፳፫) ። በነቢር ፡ ዘይቤ ፡ ቢፈቱት ፡ ግን ፤ ብጕር ፡ ዕትራት ፡ ኪንታሮት ፡ ጢ ፡ ያሰኛል ።

**ሕንብርት** ፤ (ነበረ ፤ ንብርት) ፤ በቁሙ ፡ ዕ ንብርት ፡ የሆድ ፡ መክከል ፡ የዕትብት ፡ ሥር ፡ መብቀያው ። ሰላም ፡ ለሕንብርትከ ፡ ማእከለ ፤ ጠባይዕ ፤ ዘተመ ልአከ ። ማእከለ ፡ ከርሥ ፡ ሀላዊ ። ሕንብርተ ፡ ከርሡ ፤ (ደራሲ ። ኢዮ ፵ ፡ ፲፭) ።

—፤ አንገቶች ፡ የሆድ ፡ ውስጥ ፡ ማሕፀን ። ኅቡረ ፡ ወፃእነ ፡ እምሕንብርትከ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፰) ።

—፤ የምድር ፡ ጐብር ፡ ተራራ ፡ ኰረብታ ፡ ገመገም ። ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ማእከለ ፡ ሕንብርታ ፡ ለምድር ። ናሁ ፡ ሕዝብ ፡ ይወርድ ፡ እምኀበ ፡ ሕንብርተ ፡ ምድር ። እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ሕንብርተ ፡ ምድር ፡ (ኩፋ ፡ ፰ ። መሳፍ ፡ ፴፯ ። ሕዝ፴፰ ፡ ፲፪) ።

ሕናግ ፤ (ትግሬ) ፤ ትናግ ፡ ትናጋ ፡ ላንቃ ። ሐኪክን ፡ እይ ።

ሐንገዘ ፤ (ሐገዘ ፤ ሐገገ ። ዐረ ፡ ሐጂብ) ፤ ሽፋል ፡ ቅንድብ ፡ ጠጕሩ ፡ የማይድግ ፡ የማይረዝም ፡ ሐገዘን ፡ እይ ። ይትላጸይ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእሱ ፡ ወጽሕሞ ፡ ወሐንገዘ ፡ (ዘሌ፲፬ ፡ ፱) ። ብብት ፡ ብልት ፡ ንፍረት ፡ ያገጭ ፡ ሥር ፡ ሽለቆው ። ጸጕር ፡ ሠርጸ ፡ ድማሕ ፡ ወሐንገዘ ። ሕንጋዙ ፡ (ጕርኄሁ) ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ገድ ፡ ላሊ) ።

ሐነወ ፤ (ዕብ ፡ ሐናሕ ። ዐረ ፡ ሐና) ፤ ሰፈረ ፡ ሰፍራ ፡ ያዘ ፡ ጕገዘ ፡ ሠራ ፡ ድንኳን ፡ ተከለ ።

ሐኖት ፤ (ዕብ ፡ ወዐረ ፡ ሐኑት ። ሱር ፡ ሓኑታ) ፤ መደብር ፡ የንግድ ፡ የገበያ ፡ ቤት ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ ጨዎታ ፡ መሸታ ፡ ያለበት ፡ ኅለማዊ ፡ እንግዳ ፡ የሚያርፍበት ። ሥጋ ፡ ሐኖት ። ኢይብልዕ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሐኖት ፤ እመ ፡ ቦ ፡ ካህን ፡ ዘበልዐ ፡ ውስተ ፡ ሐኖት ። ወኢትባእ ፡ ሐኖተ ፡ ለግሙራ ፡ (ምሳ፳፫ ፡ ፰ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፱ ፡ ፩ ። ሃይ ፡ አበ) ።

ሐንዋት ፤ (ዐረ ፡ ሐዋኒት ። ዕብ ፡ ሐኑዮት) ፤ መደብሮች ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በሐንዋት ፡ ፈንታ ፡ እንዳረበ ፡ ሐ(ከ)ዋኒት ፡ ይላል ፡ (ግብ፳፰ ፡ ፲፭) ።

ሐንዘር ፤ (ዐረ ፡ ኂንዚር ። ዕብ ፡ ሐዚር ። ሱር ፡ ሕዚራ) ፤ ሐማማ ፡ ሕሪያ ፡ ርኩስ ፡ የቤት ፡ እንስሳ ፡ እስራኤል ፡ የማጸየፉት ፡ አሕዛብ ፡ የሚነፈንፉት ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ አነር ፡ ይሉታል ፤ ሐሠመንና ፡ ሐረወን ፡ እይ ፡ (ሔኖ፹፰ ፡ ፲) ።

ሐንሐን ፤ (ትግ) ፤ ስርን ፡ ኵሸኵሽ ፡ ያፍንጫ ፡ ዐጥንት ፡ ማእከለ ፡ እስይንት ።

ሐነጠ ፤ (ዐረብ ። ዕብ ፡ ሐናጥ ። ሱር ፡ ሕናጥ) ፤ ሽቱ ፡ ቀባ ፡ ለቀለቀ ፡ በሽቱ ፡ ለወሰ ፡ ዐጀለ ፡ የሬሳ ፡ አቀባብ ፡ እንዳይፈርስ ፡ እንዳይበሰብስ ፡ በማይደርግ ፡ በታወቀ ፡ ሽቱ ። ጸዐጠን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ወሐነጠ ፡ ዮሴፍ ፡ ሥጋሁ ፡ በከርቤ ፡ ወበሰሊሖት ፡ ወአስቀጠኑ ፡ (አቡሻ ፡ ፵፰) ።

ሐኔት ፤—ሐሜት ፤—ሐመየ ፤ ሐነየ ።

ሐኒክ ፡ ኩት ፤ (ሐነከ ፡ የሐንክ ፡ ይሕንክ ። ዐረ ፡ ሐነከ ። ዕብ ፡ ሐናኽ) ፤ ጠልቆ ፡ ማወቅ ፡ ማስተዋል ። ማፈር ፡ መስቀጠጥ ። ዘየአምር ፡ ሐኒከ ። የሐንክዎ ፡ ወይፈርህዎ ። ሰላም ፡ ለከ ፡ ገብረ ፡ ዮሐንስ ፡ ቡሩክ ፤ በምግባርከ ፡ ሐኒከ ፡ (ምሳ፫ ፡ ፲፫ ። ሉቃ፱ ፡ ፵፭ ። ስንክ ፡ ኀዳ፳፯) ።

—፤ መብረክ ፡ መቀደስ ፡ የቤት ፡ የንዋየ ፡ ቅድሳት ። ማኅኽ ፡ ማላመጥ ፡ መበጠስ ፡ መቍረጥ ፡ የጥርስ ፡ የመኪና ። ዕንክ ፡ ማለት ፡ እጅ ፡ በጅ ፡ መስጠት ። መጣፍ ፡ ግን ፡ በሐንክ ፡ ፈንታ ፡ አንክዩ ፡ ይላል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ ነከየን ፡ እይ ።

ሕንከት ፤ ማፈር ፡ መቍረጥ ፡ ቁረጣ ። ዝንቱ ፡ ፍና ፡ ፈውስ ፡ ውእቱ ፡ ወእኮ ፡ ሕንከት ፡ (ተረ ፡ ቂር፩) ።

ሕንካ ፤ (ዕብ ፡ ሐኑካ) ፤ ቅዳሴ ፡ ቡራኬ ፡ ያዲስ ፡ ቤት ፡ ምረቃ ፤ የታቦት ፡ የመቅደስ ፡ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ ስቃ ፡ መሾምና ፡ መክበር ፡ የግዜር ፡ ገንዘብ ፡ መኾን ። በዓለ ፡ ሕንካ ፡ (ዮሐ፲) ።

ሐኖክ ፤ (ዕብ ፡ ሐኖኽ) ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ሐዲስ ፡ ቅዱስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፬ ፡ ፲፯ ። ፭ ፡ ፲፰ ። ይሁ፲ ፡ ፲፬) ።

ሕንክ ፤ (ነባርና ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ) ፤ ዕንክ ፡ ውሰድ ፡ ተቀበል ። ሕንክሙ ፡ ብልዑ ፡ (ማቴ ፳፯ ፡ ፳፮) ።

—፤ ስጥ ፡ ዐድል ፡ ዕንካችኹ ፡ በል ። ሀብን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

ሐኑክ ፤ (ትግ) ፤ ምግብ ፤ የሚኰረሥ ፡ የሚታኘክ ።

ማሕነክ ፤ (ብ ፡ መሐንክ) ፤ ማኘኪያ ፡ መንጋጋ ፡ የመኪና ፡ ጥርስ ፤ የሥጋ ፡ መምተሪያ ፤ የሰው ፡ ወጥመድ ፡ ሥጋን ፡ ከናጥንቱ ፡ የሚፈጭ ፡ የሚያልም ፡ የሚደቍስ ፡ የሚቈርጥ ፡ የሚበጣጥስ ። መንሰከ ፡ ወማሕነከ ። ወእንተሰ ፡ እስክንድር ፡ ንጉሥ ፡ ተዐቀብ ፤ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምድኅረ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ፡ እምነጋድያን ፡ ከመ ፡ ይንግር ፡ ዜና ፡ ለእለ ፡ ይመጽኡ ፤ ወአዝዘሙ ፡ ለሰራዊትከ ፡ ይትዐቀቡ ፤ እስመ ፡ ኀበ ፡ ኆኅትኪ ፡ ወማእከለ ፡ ቤትኪ ፡ ወማዕገትኪ ፡ ሀሎ ፡ ማሕነከ ፡ ወሠርም ፡ ወማዕምቅ ፤ ወእምድኅረ ፡ ወድቀ ፡ አልቦ ፡ ዘይትነሣእ ፤ አላ ፡ ይትከዐው ፡ አማዑቱ ፡ ወይትቀጠቀጥ ፡ አዕፅምቲ ፡ (አዋል ። ዜና ፡ እስ) ።

ሐንከሰ ፤ (ዲቃ ፡ ግ ። ሐነከ ፤ ነከሰ) ፤ ሀንከሰ ፡ ዐሞኘ ፡ ኾነ ፤ ዐፈረ ፡ ተሰቀጠጠ ፤ ተሰብሮ ፡ ተቈርጦ ፡ ተሸምቅቆ ፡ ወይም ፡ ስሎ ፡ ደርቆ ፡ የእግር ። ተጠራጠረ ፤ አወላወለ ፡ አመነታ ፤ የልቡና ። ሐንከሱ ፡ በፍኖቶሙ ። እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ተሐነክሱ ፡ በክልኤ ፡ ልብክሙ ። እስመ ፡ ሀካይ ፡ የሐነክስ ፡ በፍኖቱ ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። ፫ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ። አፈ ፡ ድጓ) ።

ሐንካስ ፤ (ሳን ፡ ሳት) ፤ ዐንካሳ ፡ ሽምድምድ ፡ እግሩ ፡ ተካክሎ ፡ የማይቆም ፡ የማይኼድ ። ዕዉር ፡ ወኢሐንካስ ። ዕዉራን ፡ ይሬእዩ ፡ ወሐንካሳን ፡ የሐውሩ ። ሐንካሳን ፡ ወይቡሳን ፡ (ዘሌ፳፩ ፡ ፲፰ ። ማቴ፲፩ ፡ ፭ ። ዮሐ፭ ፡ ፫) ። ተጠራጣሪ ፡ ወላዋይ ።

ሕንካሴ ፤ ማንከስ ፡ መጠራጠር ። ጥርጥር ፡ ጥርጠራ ። ከመ ፡ ይሕየው ፡ ሕንካሴክሙ ፡ (ዕብ፲፪ ፡ ፲፫) ።

**ሕንክስና** ፤ ፀንክስንት ፡ ተጠራጣሪነት ። ሕንክ ስናሆሙ ፡ (፪ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፵፮) ።



ሕንካስ ፡

**ሐንክሶ** ፤ ማንካስ ፡ መጠራጠር ፡ ፀንካሳ ፡ መ ኾን ።

**ሐንክሶ** ፤ (ዐረ ፡ ሐንክስ) ፤ ሽቱ ፡ የሽቱ ፡ ስንፊልት ፡ ቅጠል ፡ መፀዛው ፡ ክሩቅ ፡ የሚሸት ። ማር ደም ፡ ይንግል ፡ ምዕዝት ፡ ዘእምሐንክሶ ፡ (ደራሲ)።

**ሐንፈጠ** ፤ (ዲቃ ፡ ግ ። ነፈጠ) ፤ ጫረ ፡ ጐ ፈጨረ ፡ ላጠ ፡ መለጠ ፤ ፊቱን ፡ ነፈጨ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘሞተ ፡ ኢትሐንፍጡ ፡ ገጸክሙ ። በአምሳለ ፡ አንስርት ፡ ወ ቋዓት ፡ እንዘ ፡ የሐነፍጡ ፡ ገጸሙ ፡ በአጽፋሪሆሙ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰ ። ስንክ ፡ መስ፲፰) ። ነፈጠን ፡ እይ ።

**ሐንፈጠ** ፤—ቀረጠ ፤—ኀፈጠ ፡ ኀንፈጠ።

**ሐንፈጸ** ፤ (ዲቃ ፡ ግ ። ነፍጸ) ፤ አንፈሰ ፡ አ ንዘረዘረ ፤ አዘራ ፡ አበጠረ ፡ አጐለበ ፡ አንጓለለ ። ሰአሉ ፡ የሐንፍጽክሙ ፡ ከመ ፡ ዐሊስ ፡ ዘየሐንፍጸክ ፡ ሰይጣን ፡ (ሉቃ፳፪ ፡ ፴፩ ። አፈ ፡ ተ፴፩ ። ፊልክ ፡ ፻፹፱ ። አርጋ ፡ ፳) ። ነፍጸንና ፡ ኀንጸጸን ፡ እይ ።

**ተሐንፈጸ** ፤ ተነፈሰ ፡ ተበጠረ ፡ ተለየ ፡ ተንጓ ለለ ። ዘርዐ ፡ ሐሊስ ፡ እመ ፡ ተሐንፈጸ ፡ ይበውእ ፡ ኀበ ፡ ዘርዑ ፡ ሶበ ፡ ዘርዕዎ ፡ (አዋል) ።

**ሕንፉጽ** ፤ የተነፈሰ ፡ የተንዘረዘረ ። ስንፉጭ ፡ ግርድ ፡ ኀፋሽ ፤ ብጣሪ ።

**ሐንፈጽ** ፤ (ትግሪኛ) ፤ ቀይጥ ፡ ቅልቅል ፡ ገብስና ፡ ስንዴ ፡ ፀብሮ ፡ የሚዘራ ። ሐለስትን ፡ እይ ፤ ከ ዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ሐኒጽ** ፤ ጸት ፤ (ሐነጸ ፡ የሐንጽ ፡ ይሕ ንጽ ። ነደቀ) ፤ ማነጥ ፡ መቅረጥ ፡ መጥረብ ፡ የዋሻ ፡ የንፊልት ። መሥራት ፡ መመሥረት ፡ መንደቅ ፤ የቅጥር ፡ የቤት ። ሐኒጸ ፡ ሀገር ። ንሕንጽ ፡ በእብን ። ሕንጹ ፡ አ ብያተ ፡ (ኩፋ ፡ ፲ ። ኢሳ፱ ፡ ፲ ። ፴፯ ፡ ፳) ። መፍጠር ፡ ማ ደስ ፡ ማጽናት ፡ ማበርታት ፡ እንዳይፈርስ ፡ ማድረግ ። ከመ ፡ ይሕንጽ ፡ ለከ ፡ ዘርዐ ፡ እምኔሃ ። ከመ ፡ ይሕ ንጹ ፡ መዝበራ ፡ ለጽዮን ። ለዓለም ፡ አሐንጽ ፡ ምሕ ረተ ። ሐነጸ ፡ ሥርዐተ ፡ ማኅበር ፡ (ኩፋ ፡ ፲፱ ። ስንክ፱ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፹፰ ። ስንክ ፡ መስ፳፱) ።

**ሐናጺ** ፤ (ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት ፤ ነጽት) ፤ የሚያንጥ ፡ የሚቀርጥ ፡ ጠራቢ ፡ ፀናጪ ፡ ገንቢ ። ሐናጽ ያንኪ ፡ ፈጸሙ ፡ ሥነኪ ። አብጽሐ ፡ እልፈ ፡ ሐናጽያን ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፬ ። ዮሴፍ) ።


**አሕነጸ** ፤ አሳነጠ ፡ አሠራ ። ምሕራብ ፡ ጣዖት ፡ ዘአሕነጸ ፡ አንጥ ፡ ደኮስ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ተሐንጸ** ፤ ታነጠ ፡ ተሠራ ፤ ተዘጋጀ ። እመ ፡ ትትሐነጽ ፡ ኢየሩሳሌም ። ተሐነጽክሙ ፡ ዲበ ፡ መሠ ረተ ፡ ሐዋርያት ። ለክሙ ፡ ተሠርዐ ፡ ወተሐንጸ ፡ ትፍ ሥሕት ፡ (ድጓ ። ኤፌ፪ ፡ ፳ ። ሱቱ ፡ ዕገዛ፳ ፡ ፳፱) ።

**ሕኑጽ** ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ንጽት) ፤ የታነጠ ፡ የ ተሠራ ፤ ጥርብ ፡ ዝግጁ ። አህጉር ፡ እለ ፡ ሕኑዳት ፡ አረ ፋቲሆን ። ጥቅም ፡ ዘሕንጽት ፡ በእብን ፡ በረድ ፡ (፪ ዜና ፡ ፳፯ ፡ ፫ ። ሔኖ፲፬ ፡ ፱) ።

**ሕንጸት** ፤ ማነጥ ፡ መታነጥ ፤ አስተናነጥ ፤ ሕ ንጻ ። ፀንፊልት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ቀዳሚት ፡ ሕንጸታ ፡ ለኢየሩሳሌም ። ሥዩማን ፡ ላዕለ ፡ ግብረ ፡ ሕንጸት ። በመዋዕሊሁ ፡ ተፈጸመ ፡ ሕንጸታ ፡ ለቤት ። እምጊዜ ፡ ሕንጸተ ፡ ቤት ፡ ዳግማይ ፡ (ቀሌ ። ስንክ ፡ መስ፲፮ ። ጥቅ፲፮ ። ዮሴፍ) ።

**ሕንጻ** ፤ (ጻት) ፤ የቤት ፡ የዋሻ ፡ ሥራ ፡ መል ክና ፡ ቅርጥ ፡ ያለው ፤ ቤት ፡ ግንብ ፡ ዋሻ ። ውሉድ ፡ ወሕንጻ ፡ ሀገር ፡ ያፀብዩ ፡ ስመ ። ሕንጻሁ ፡ ለምሕ ራብ ። አኮ ፡ ለሰብእ ፡ ዛቲ ፡ ሕንጻ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእግዚ ። አንትሙ ፡ ሕንጻ ፡ እግዚ ። አዳም ፡ ሕንጻ ፡ ላሊበላ ፡ ኢይብላዕ ፡ እምዕፀ ፡ (ሢራ፵ ፡ ፲፱ ። ማቴ፳፱ ፡ ፩ ። ፩ ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፩ ። ፩ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፱ ። ቅኔ) ። ድሕንጻን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።



ሕንጻ ፡

**ሕንጼ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ሕንጻ ፡ ሕንጸት ። ሕ ንጼሃ ፡ ወሠራሪሃ ፡ አዳም ። እመ ፡ ሕንጼሃ ፡ ለኢየሩ ሳሌም ፡ (ድጓ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፯) ።

**ሕንጽዋል** ፤ ጌንዬ ፡ ገረማ ፡ ሲናር ፡ ዐረማሞ ፤ ክፉ ፡ ዐረም ። ህየንተ ፡ ሥርናይ ፡ ክርዳድ ፤ ወህየንተ ፡ ሰገም ፡ ሕንጽዋል ፡ (ኢዮ፴፩ ፡ ፵) ።



ሕንጽዋል ፡

**ሐንጸጸ** ፤—ጠረጠረ ፤—ኀንጽጸ ፡ ኀን ጸጸ ።

**ሐነቀ**፤—**ዐነቀ**፤—**ኀነቀ፡ ኀነቀ**።

**ሐንቀቆ**፤ **ቆት**፤ (**ሐንቀቀ፡ የሐንቅቅ፡ የሐንቅቅ**)፤ መዥራት፡ መንጠራራት፤ ያልተሰጠውን፡ መሻት፤ አምጡ፡ ውሰዱ፡ ማለት፤ መደላደል፡ መቀማጠል፤ መብሰክሰክ፡ መንቀባረር፤ የወይዛዝርና፡ የመኳንንት፡ የባለጠጎች፡ የሕፃናት፡ ለበሽተኞችም፡ ይኾናል። ምስጢሩ፡ ይሮ፡ ዕለቡ፡ በሐይ፡ በንቅብ፡ አግቡ፡ እንደ፡ ማለት፡ ነው። በሐንቀቀ፡ ፈንታ፡ ተሐንቀቀ፡ ይላል፤ ስሕተት፡ ነው። እምከመ፡ አጽገብኩ፡ ለነፍስከ፡ ኢትትሐንቀቅ። ነፍስ፡ እንተ፡ ተሐንቀቀት፡ ታስተጋብእ፡ ኀቤሃ፡ ሕማመ፡ ኀጢአት፡ (ማር፡ ይሥሐ፡ ፱። ፳፰፡ ፫)።

**ሕንቁቅ**፤ (**ቃን፡ ቃት፡ ቀቅት**)፤ ዥሩ፤ ድልድል፡ ቅምጥል፡ ብስክስክ፡ እንቅብር። (ተረት፡ ትግራይ)፡ ሕንቅቅት፡ መርዓቲ፡ እንተ፡ ስዐምዋ፡ ትበኪ።


**ሕንቃቄ**፤ (**ቀያት**)፤ ክፉ፡ ዐመል፤ ዥራት፤ መደላደል፡ መቀማጠል፡ መቅለጥ፡ መቅበጥ፡ በጥ፤ ተድላ፡ ሥጋንና፡ ምግብ፡ ሥጋን፡ ብቻ፡ መውደድ። አየንን፡ እይ፤ የዚህ፡ ጎር፡ ነው። ኢይኩን፡ ላዕሌክሙ፡ ነውር፡ እኩይ፡ ወሕንቃቄ፤ አፍቅሮተ፡ ተድላ፡ ወመብልዕት፡ ከመ፡ ይስሐብክሙ፡ ውስተ፡ ፍትወተ፡ ክንቱ። ንኅድግ፡ ሥላቀ፡ ወሕንቃቄ። ማዕርገ፡ ሕንቃቄ። ወይኅድግ፡ ሕንቃቅያተ፡ (መቃ፡ ገ፳፱። አፈ፡ ተ፳፱። ማር፡ ይሥሐ፡ ፲፩)።

**ሕንቅርት**፤ (**ጽር፡ ኸኔፍቲሪዮን**)፤ ከውር፡ ያንጥረኛ፡ አንጥረኛ፤ ታናሽ፡ ጕድጓድ፡ የከሰል፡ ምድጃ። ሕ፡ ባዕድ፡ ኹኖ፡ አለበታው፡ ገብቷል፤ ንቈረን፡ እይ። ደዮ፡ ውስተ፡ ሕንቅርት፡ (ዘካ፲፩፡ ፲፫)። ዕብራይስጡ፡ ግን፡ (ሀሽሊኬሁ፡ ኤል፡ ሀዮጼር)፡ ግድሮ፡ ኀበ፡ ለሐኩ፡ ይላል፤ የፈጣሪን፡ ቦታ፡ መቅደስንና፡ ዐጸደ፡ ለብሐዊን፡ ባንድነት፡ ያሳያል። ፪ኛ፡ ደግሞ፡ በለሐኩ፡ ፈንታ፡ (ሀኦጻር፡ ብሎ)፡ መዝገብ፤ ቤት፡ መዛግብት፤ ግምጃ፡ ቤት፡ ሙዳየ፡ ምጽዋት፡ ይላል፡ እንጂ፡ አንጥረኛንና፡ ከውርን፡ አያሳይም፡ (ማቴ፳፯፡ ፫—፯)። ሀዮጼር፡ ያለውን፡ ሀኦጻር፡ ማለት፤ የውድና፡ አሌፍ፡ ደዋ ረባሉና፤ ስለዚህ፡ ነው።

**ሐኔት**፤—**ሐሜት**፤—**ሐመ(ነ)የ**።

**ሐኖት**፤—**የመሸታ፡ ቤት**፤—**ሐነወ**።

**ሐንጾን**፤ (**ዐረ፡ ሐንፋእ**)፤ ገበሎ፡ ጕበና፤ የዕሥሥትና፡ የንሽላሊት፡ ዐይነት፡ ፬፡ እግር፡ ያለው፡ ኹራታም፤ በግሩና፡ በልቡ፡ የሚኼድ። ባለብሉዮች፡ ግን፡ አርጃኖ፡ እንዝዝ፡ ይሉታል። ላጽቂት፡ ወሐንጾን፡ (ዘሌ፲፩፡ ፴)።



ሐንጾን፤

**ሐሥአ**፤—**በረደ**፤—**ኀሠዐ፡ ኀሥዐ**።

(ሀ) **ሐሠየ**፤—**ዐሸ**፤—**ሐሰይ፡ ሐሰየ**።

(ለ) **ሐሥይ**፤ **ዩት**፤ (**ሐሠየ፡ የሐሢ፡ ይሕሢ**)፤ ማስደሰት፤ ማሳሠይ፤ ዕሠይ፡ ማሰኘት። መሠየት፤ መጕምዠት። ኢትሠሥዕ፡ ለዘሉ፡ መብልዕ፡ ወኢተሐሢ፡ ለዘሉ፡ ዘርኢከ፡ (ሢራ፴፯፡ ፳፱)።

**ተሐሠየ**፤ **ተሐሥየ**፤ ተደሰተ፤ ዕሠይ፡ አለ። ይትፌሣሕ፡ ሰማይ፡ ወትትሐሠይ፡ ምድር። ይትሐሠዩ፡ ብከ። እንዘ፡ ትትሐሠይ፡ (ድን። ኩፋ፡ ፳፰። ሢራ፴፪፡ ፲፩)።

**ሐሤት**፤ ዕሠይታ፡ ፍጹም፡ ደስታ፡ የልብ፡ ተድላ፡ የሚያዘልል፡ የሚያስፈንጭ፤ እልል፡ ዕሦ፡ ዕሦ፡ የሚያሰኝ፤ ዕሦ፡ ቅሉ፡ ዕሠይ፡ ማለት፡ ነው፡ (መዝ፡ ፲፭። ፳። ፶)።

**ሐሠከ**፤—**ዘነበ**፤—**ሐሲከ፡ ሐሰከ**።

**ሐሢም**፤ **ሞት**፤ (**ሐሠመ፡ የሐሥም፡ ይሕሥም። ዐረ፡ አሺመ። ዕብ፡ አሼም**፤ **አበሰ**)፤ መክፋት፡ መባስ፤ ማደፍ፡ መርከስ፤ በግብር፡ ዐማማን፡ መምሰል፡ እንዳሣማ፡ መኾን፤ ለመልክም፡ ይኾናል። እስከ፡ ሐሠመ፡ ጺአቱ፡ ሎቱ። ሐሠምሙ፡ ለሕያዋን፡ ጼና፡ አብድንት። ወሶበ፡ ሰምዐ፡ ሐሠም፡ ዝንቱ፡ (ዮሴፍ)። ቦ፡ እለ፡ የሐሥማ፡ ውስተ፡ ሕንጻ። መልክ፡ ክፉ፡ ኹነው፡ የሚፈጠሩ፡ (ሄርማ፡ ገ፴)።

**ሕሡም**፤ (**ማን፡ ማት፡ ሥምት**)፤ የከፋ፡ ክፉ፤ ጥፉ፡ መጥፎ፡ ቢስ። ሕሡም፡ ራእዮሙ። እለ፡ ይትሐወሱ፡ ሕሡማን። ምግባራት፡ ሕሡማት። ኢታውሥእ፡ ሕሡመ፡ በአፉከ። ቀአመን፡ ከመ፡ ሕሡም፡ አልቦ፡ ዘይረክበከ። ኢይረክባ፡ ምንትኒ፡ ሕሡም፡ (ዘፍ፵፩፡ ፲፱። ጥበ፲፯፡ ፭። ዮሴፍ። ኢሳ፶፰፡ ፲፫። ሢራ፲፱፡ ፲። ፍ፡ ነ፡ ፳፱፡ ፯)።

**ሕሠም**፤ (**ማት**)፤ ክፋት፤ ክፉነት፡ መጥፎነት፡ የመልክ። ኢታስተአክዮ፡ ለሰብእ፡ እንበይነ፡ ሕሠሚሁ። ኢይክሉ፡ ይኪድኑ፡ ሕሠሚሆሙ፡ በተሰርግዎ። ሕሠመ፡ ራእየ፡ ብእሲቱ፡ (ሢራ፲፩፡ ፪። አፈ፡ ተ፲፰። ፍ፡ ነ፡ ፳፱፡ ፳)። ለጠባይና፡ ለግብርም፡ ይኾናል። በእንተ፡ ሕሠመ፡ ግዕዙ። አሀ፡ እምዛቲ፡ ሕሠም። ገቢረ፡ ሕሠማት፡ (ፍ፡ ነ፡ ፳፱። አፈ፡ ተ፲፰። ፊላስ)።

—፤ ጥፋት፤ ጕዳት። ዘኢይረክቦ፡ ሕሠም። ኵሉ፡ ዘይረክባ፡ እምሕሠማት። ኵሉ፡ ግብረ፡ ሕሠም፡ (አርጋ። ፍ፡ ነ፡ ፳፰። ዮሴፍ)።

**ሕሥመት**፤ መክፋት፡ ማስከፋት፡ ክፉነት፡ መጥፎነት።

**አሕሠመ**፤ አከፋ፤ አስከፋ፤ ክፉ፡ አደረገ፡ አስደረገ። አሠንዩ፡ ወአሕሥሙ። ኢትቅናእ፡ ከመ፡ ታሕሥም። ለምንት፡ አሕሠምከ፡ በዝ፡ ሕዝብ። ኢታሕሥም፡ ዲበ፡ ነባሪከ። ኢታሕሥሙ፡ ላዕለ፡

እሉ ፡፡ ሀኬት ፡ ወድካም ፡ አሕማምያን ፡ (ኢሳ፡፴፩ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፸፮ ። ዘፀ ፳ ፡ ፳፱ ፡ ፳፫ ። ሚራ ፯ ፡ ፳ ። ዘፍ ፲፱ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፫ ፡ ፱) ።

ሐሣማ ፤ (ማት) ፤ በቁሙ ፡ ሕሪያ ፡ ሕሠመ ፡ ሠልክአ ፡ ወመብልዕ ፡ (ዐማርኛ) ።



ሐማማ ፡

ሐሥዐ ፤—በረደ ፤—ኀሥዐ ።

ሐሠፈ ፤—ሻከረ ፤—ኀሠፈ ።

ሐሥረ ፤—ጐሰቈለ ፤—ኀሥረ ።

ሐሢር ፤ ሮት ፤ (ሐሠረ ፡ የሐሥር ፡ ይሕሥር ። ቀሲስ) ፤ መሰብሰብ ፡ ማጓሰብ ፡ ማጋበስ ፤ የማር ፡ የገለባ ። መላጥ ፡ መምለጥ ፡ መቅረፍ ፡ መሽልቀቅ ፡ መፈልፈል ፡ መጠርጠር ፤ የፍሬና ፡ የንቡጥ ። ማሸት ፡ መጥመቅ ፤ የቈሎ ፡ የሽት ፤ የወይን ፡ የዘይት ፤ የድፍድፍ ።

ሐሣሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ሠርት) ፤ ገለባ ፡ አውድ ፡ ዐጺ ፡ ጕድፍ ፡ ጠራጊ ።

ሐሠር ፤ በቁሙ ፤ ዐሠር ፡ ገለባ ፡ እብቅ ፡ ንፋሽ ፤ ፍሬው ፡ የወጣለት ። ማር ፡ ድርቆሽ ፡ ቈሻሻ ፡ ጥራጊ ፡ ጕድፍ ። ከምረ ፡ ሐሠር ፡፡ ወሐሠሮሰ ፡ ያውዒ ፡ በእሳት ፡፡ ሐሠር ፡ ለገቢረ ፡ ግንፋል ፡፡ ከመ ፡ ሐሠር ፡ ዘቅድመ ፡ ገጸ ፡ ነፋስ ፡ (ሚራ፳፩ ፡ ፱ ። ማቴ፫ ፡ ፲፪ ። ዘፀ፭ ፡ ፯ ። ኢዮ፳፩ ፡ ፲፰) ።

ሐፈጠ ፤—መታ ፡ ደሰቀ ፤—ኀፈጥ ፡ ኀፈጠ ።

ሐፊን ፤ ኖት ፤ (ሐፈነ ፡ የሐፍን ፡ ይሕፍን ። ዐረብ ። ዕብ ፡ ሐፋን) ፤ ማፈን ፡ መሸፈን ፡ መገጋት ፡ መድፈን ፡ ማፈሥ ፡ መዝገን ፤ መጨበጥ ፡ መጀበን ፡ ባንድ ፡ ወይም ፡ በ፪ ፡ እጅ ፡ መታፈን ።

ሕፍን ፤ ዕፍኝ ፡ ጥርኝ ፤ ውስጥ ፡ እጅ ፡ ዝርጉ ፡ ጠፍጣፋው ፡ ጣቶች ፡ የሚያፍኑት ፡ የሚዝኑት ፡ ሳንድም ፡ ለኹለትም ፡ ይኾናል ። መኑ ፡ ዘሰፈሮ ፡ ለማይ ፡ በሕፍኑ ፡፡ ሠናይ ፡ ምልአ ፡ እዴ ፡ በዕረፍት ፡ እምነ ፡ ክልኤ ፡ ሕፍን ፡ በዐመፃ ፡፡ ምልአ ፡ ሕፍኑ ፡፡ ይንሣእ ፡ መጠነ ፡ ሠለስቱ ፡ ሕፍን ፡ እምነ ፡ ማይ ፡ ወይኅፀብ ፡ ርእሶ ፡ በስመ ፡ ሥላሴ ፡ (ኢሳ፵ ፡ ፲፪ ። መክ ፬ ፡ ፮ ። ዘሌ፲ ፡ ፲ ። ፍ ፡ ን ፡ ፫) ።

— ፤ የገንዘብ ፡ ስም ፡ ፲ ፡ ድሪም ፡ ስጢጥራን ፡ እይ ። ቀርቡ ፡ እለ ፡ ክልኤ ፡ ሕፍነ ፡ ይነሥኡ ፡ ወይቤሉ ፡ ኢይሁብኑ ፡ ክልኤ ፡ ሕፍነ ፡ (ቁር ። ማቴ፲፯ ፡ ፳፬) ።

ሐፈሠ ፤ (ሐፈነ) ፤ ዐፈሠ ፡ ተረፈሰ ፡ እብዝቶ ፡ ዘገን ፡ ዛቀ ። አንግሣ ፡ ወሰደ ፡ ጠረገ ፡ አስገደ ።

ወሐፈሥዎ ፡ ቢድዎ ፡ ለሳኦል ፡፡ ዐውሎ ፡ ዘየሐፍሦ ፡፡ ይነሥእሙ ፡ ዐውሎ ፡ ወየሐፍሦሙ ፡ ነፋስ ፡ (፩ዜና ፲ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፲፯ ፡ ፲፫ ። ፶፯ ፡ ፲፫) ።

ሐፍሥ ፤ (ሕፍን) ፤ ዝግኝ ፡ ጥርኝ ፡ ጭብጥ ። ጥቂት ፡ ታናሽ ፡ ገንዘብ ፡ በረከት ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ግብር ፡ ለጣዖት ፡ ለጠንቋይ ፡ የሚሰጥ ። ይሁቡ ፡ ሐፍሠ ፡ በእንቲአሁ ፡፡ እምዘትነሥእ ፡ ሐፍሥ ፡ (ኢሳ፳ ፡ ፰ ። ግብ፲፯ ፡ ፲፯) ። ኮባያ ፡ ጽዋ ። ሐፍሠ ፡ ወይን ፡ ዘቢብ ፡ (ሆሴ፫ ፡ ፩) ።

ሐፍሣት ፤ (ዕብ ፡ ሐፍሺት) ፤ ነጻነት ፡ ሐራነት ፡ ብቸኝነት ፡ ከሰው ፡ መለየት ። ቤተ ፡ ሐፍሣት ፡፡ የድውያን ፡ ቤት ፡ ለምጻሞችና ፡ ኮብሻሞች ፡ ደዌያቸው ፡ ከሰው ፡ እንዳይናኝ ፡ ለብቻቸው ፡ የሚኖሩበት ፡ (፪ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፳፩) ።

ሐጽ ፤—ፍላጻ ፤—ሐጺጽ ፡ ሐጸ ።

ሐጸበ ፤—ዐጠበ ፤—ኀጺብ ፡ ኀፀበ ።

ሐጸወ ፤—ሰለበ ፤—ኀጺው ፡ ኀጸወ ።

ሐጸየ ፤—ዐጨ ፤—ሐፅይ ፡ ሐፀየ ።

ሐጺን ፤—ብረት ፤—ኀጺን ።

ሐጺጽ ፤ ጾት ፤ (ሐጸ ፤ ሐጸጸ ፡ የሐጽጽ ፡ ይሕጽጽ ። ዕብ ፡ ሐጻጽ ፤ ከፈለ) ፤ መጕደል ፡ ማነስ ፤ መከፈል ፡ መቀነስ ፤ እኩሌታ ፡ እስከ ፡ መኾን ፡ ድረስ ። ኀጠጠን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ሐጸ ፡ ማይ ፡፡ የሐጽጽ ፡ ልቡ ፡ ከመ ፡ ወርኅ ፡፡ እለ ፡ የሐጽጹ ፡ አእምሮ ፡፡ ኢየሐጽጽ ፡ መዐተ ፡ ንጉሥ ፡ እመዐተ ፡ አንበሳ ፡፡ ኢይሕጽጽ ፡ እክልክ ፡፡ (ዘፍ፰ ፡ ፫ ። ሢራ፳፯ ፡ ፲፩ ። ምሳ፲ ፡ ፲ ። ፳ ፡ ፪ ። ኩፋ ፡ ፴፭) ።

ሕጹጽ ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ጽጽት ። ዕብ ፡ ሐጺ ፤ እኩሌታ) ፤ ያነሰ ፡ የጐደለ ፤ ታናሽ ፡ ጐደሎ ፡ ደካማ ፡ ምንዱን ። ሕጹጽ ፡ አነ ፡ እምነ ፡ ዕደው ፡ ጻድቃን ፡፡ ኩኑ ፡ ፍጹማነ ፡ ወአኮ ፡ ሕጹጻነ ፡፡ ብእሲት ፡ ሕጽጽት ፡ እምፍጥረተ ፡ አንስት ፡፡ አርባዕቱ ፡ ሕጹጻን ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ (ማር ፡ ይሥሐ ። ማንዘ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳፱ ፡ ፯ ። ምሳ፳፬ ፡ ፶፬) ።

ሕጹጻን ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ። ትራፋት ፡ ነገሥት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በነገሥት ፡ የሌሉ ፡ ከነገሥት ፡ የቀሩ ፡ ጥቃቅን ፡ ቃሎች ፡ ታናናሽ ፡ ታሪኮች ፡ ስላሉበት ፡ ስሙ ፡ ሕጹጻን ፡ ተብሏል ፡ ይኸውም ፡ ፪ ፡ ክፍል ፡ ነው ። ወክልኤቱ ፡ ሕጹጻን ፡፡ ሕጹጻን ፡ ቀዳማዊ ፡፡ ካልእ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፪ ። ዜና ፡ ፩ ። ፪) ።

ሕጸት ፤ ማነስ ፡ መጕደል ፡ አጕዳደል ፡ ጕደሎነት ፤ ጕድለት ። ዘእንበለ ፡ ተውሳክ ፡ ወኢሕጸት ፡፡ አልቦ ፡ ላዕለ ፡ እግዚ ፡ ተወስኮ ፡ ወኢሕጸት ፡፡ ሕጸተ ፡ አእምሮ ፡ እግዚ ፡፡ ሕጸተ ፡ ሃይማኖት ፡፡ በእንተ ፡ ሕጸተ ፡ ምክሮን ፡ ለአንስት ፡ (ዮሴፍ ። ቀሌ ። ጥበ፲፫ ፡ ፩ ። ኪዳ ። ዮሴፍ) ።

ሐጻጺ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ መጕደል ፡ ማነስ ፡ ጕድለት ፡ ነውር ። ዘአልቦ ፡ ሐጻጺ ፡፡ ፍድፋደ ፡ ወሐ

ጻጼ ። እምኢክነክሙ ፡ ሑጻጼ ፡ ወዘለፉ ፡ (አሞል ።
ፍ ፡ ን ፡ ፴፮ ። ዮሴፍ) ።

ሕጻጽ ፤ በቁሙ ፡ ጕዳይ ፡ ጕድለት ፡ ቅሬታ ፡
ቅሬት ፡ እንክን ፡ በሐ ፡ ጸያፍ ። በሕጻጸ ፡ ወርኅ ። እፎ
ጽም ፡ ሕጸጼ ፡ ሕማምሙ ። ሕጻጸ ፡ ነፍስ ፡ ይትወለድ ፡
እምሕጻጸ ፡ አሚን ። እንከሰ ፡ ሕጻጽ ፡ ውስተ ፡ ማዕ
ርግ ፡ ክህነት ፡ (ሔኖ፻፳፰ ፡ ፳ ። ቆላ፰ ፡ ፳፱ ። አፈ ፡ ድ
፲፱ ። ፲፫) ።

አሕጻጸ ፤ አጕደለ ፡ አስጐደለ ፡ አሳነሰ ፡ ከፈለ ፡
ቀነሰ ፤ ናቀ ፡ አቃለለ ። ወይቤ ፡ አሐዱ ፡ እምጸሐፍት ፡
ሐሳብ ፡ ዘሀሎ ፡ እምኑልቀሙ ፡ ለአይሁድ ፡ እለ ፡ አ
ምኑ ፡ ወተጠምቁ ፡ ብእሲ ፡ ማእምረ ፡ አሪት ፡ ወ
መጻሕፍት ፡ ነቢያት ። ወውእቱ ፡ ቦአ ፡ ኀበ ፡ ቈስጠ
ንጢኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ወአይድዖ ፡ ከመ ፡ ካህናተ ፡ አይ
ሁድ ፡ አሕጸጹ ፡ እምዓመታተ ፡ ልደቶሙ ፡ ለአበው ፡
ቀደምት ፡ ዘይትዌለክ ፡ ዐሠርተ ፡ ወኀምስተ ፡ ም
እተ ፡ (ሺሕ ፡ ከ፭፻) ፡ ዓመተ ፡ ወፈቀዱ ፡ በዝንቱ ፡ ያ
ብጥሉ ፡ ምጽአቶ ፡ ለክርስቶስ ። ሰብዓ ፡ ዓመተ ፡ አሕ
ጸጸ ፡ እምዐሠርቱ ፡ ምእት ፡ ዓመት ። ሐቀ ፡ አሕጸጽከ ፡
እመላእክቲከ ። ግፍዐ ፡ ያሐጽጽ ፡ መዋዕለ ። ተቀጸለ ፡
ጌራ ፡ ዐቢየ ፡ አሕጺጾ ፡ ጌራ ፡ ክህነት ፡ ቅዱስ ፡ (ገ ፡ ወ ፡
ሐ ፡ ገ፪፻፸፩ ። ኩፋ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፰ ። ፈላስ ፡ ገ፴፱ ። ዮሴፍ) ።


ተሐጸ ፤ ተሐጸጸ ፤ ተከፈለ ፡ ተከፋፈለ ፤ ተና
ነሰ ፡ ተቀናነሰ ።

ታሕጻጽ ፤ ታሕጻጺት ፤ ጕዳይ ፡ ሕጸጽ ፡ ማ
ነስ ፡ ታናሽነት ። በአይኑ ፡ ታሕጻጽ ፡ ወእቡይ ፡ ዘኮነ ።
እለ ፡ ይኄልዩ ፡ ይካመ ፡ ወታሕጻጸ ፡ ለወልደ ፡ እ
ግዚ ። አርጌንስ ፡ ይሜህር ፡ ታሕጻጸ ፡ ወልድ ፡ እም
አብ ። ታሕጻጺተ ፡ ደቂቃት ፡ ኅጣውእ ፡ (ፈልክ ፡ ፲
፪፲፮ ። ሃይ ፡ አበ ። መጽ ፡ ምስ ። ቀሌ) ።

ትሕጻጼ ፤ (ጽያት) ፤ መጕደል ፡ መጓደል ፤ ጕ
ድለት ፡ ጕደሎነት ። በእንተ ፡ ትሕጻጼ ፡ ራእዩ ። ኮነ ፡
ሎቱ ፡ ትሕጻጼ ፡ ኀዳጥ ፡ (ፈልክ ፡ ፯ ። ፲፫፻) ።

ትሕጽጽት ፤ ገዝኒ ፡ ከማሁ ። መዐት ፡ ምስለ ፡
ትሕጽጽት ፡ ልቡና ፡ ይወልድ ፡ ጽዕለተ ፡ ወጽልአ ፡
ወቀቲለ ፡ (ፈልክ ፡ ፳፱) ።

ሐጽ ፤ (ብ ፡ አሕጻጽ ፤ አሕጻ ፡ ጻት ።
ዕብ ፡ ሔጽ) ፤ ፍላጻ ፡ ስለቱ ፡ የሚፈልጥ ፡ የሚቈርጥ ፡
የሚከፍል ፡ የሚሠጥቅ ፤ በቀስት ፡ የሚነደፍ ፡ የሚወረ
ወር ። ፪ኛም ፡ ዐጭር ፡ ቀጭን ፡ ታናሽ ፡ ቀላል ፡ ከዘገር ፡
ካበታ ፡ ጦር ፡ የሚያንስ ፡ ሕጹጽ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይበ



ሐጽ ፤

ውእቱ ፡ በሐጽ ፡ ወበቀስት ። ፈነወ ፡ አሕጻሁ ፡ ወዘረ
ዎሙ ። እስተዳለዉ ፡ አሕጻቲሆሙ ። ይደራብዩ ፡ በ
አሕጻት ፡ (ኢሳ፯ ፡ ፳፬ ። መዝ ፡ ፲፯ ። ፲ ፡ ፱ ። ፈልክ ፡ ፶) ።

ሐጻ ፤—አሸዋ ፡ ድቡሽት ፤—ኀፂጽ ፡
ኆጻ ።

ሐጺር ፤ ሮት ፤ (ሐጸረ ፡ የሐጽር ፡ ይሕ
ጽር ። ዕብ ፡ ሐጻር ። ዐረ ፡ ሐጸረ) ፤ ማጠር ፡ መ
ቅጠር ፡ መከበብ ፡ ዙሪያውን ፡ መዝጋት ፡ መወሰን ፡ መ
ጠበቅ ፡ መሰወር ። ሐጸሩ ፡ አርእስተ ፡ አድባር ። ሐጸ
ሩኒ ፡ በሐሰት ። አሐጽር ፡ ፍኖታ ፡ በሦክ ። ሐጸሮ ፡ ለ
ማይ ፡ በትእዛዙ ። ሐጸርከዋ ፡ ለባሕር ፡ በአናቅጽ ።
ይሕጽርክሙ ፡ በሐጺረ ፡ መስቀሉ ፡ (ዮዲ፳ ፡ ፫ ። ሆሴ
፲፰ ፡ ፲፱ ። ፱ ፡ ፰ ። ኢዮ፳፯ ፡ ፲ ። ፴፰ ፡ ፰ ። ማንዘ) ።

ሐጻሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ጺርት) ፤ የሚ
ያጥር ፡ የሚከብብ ፤ ዐጣሪ ፡ ከባቢ ።

አሕጸረ ፤ አሳጠረ ፡ አስቀጠረ ፡ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡
አሠራ ፡ አስከበበ ።

ተሐጽረ ፤ ታጠረ ፡ ተከበበ ፡ ተዘጋ ፡ ተጠበቀ ።
በወላትወ ፡ ነኪር ፡ ተሐጺረከ ። ፍኖትየ ፡ ተሐጽረ ፡ በ
ሦክ ። ከመ ፡ ትትሐጸር ፡ በመስቀልከ ፡ (ተረ ፡ ቈር፰ ።
ሰንክ ፡ ኅዳ፲፯ ። ቅዳ) ።

ሕጹር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ጽርት) ፤ የታጠረ ፡
የተቀጠረ ፡ የተከበበ ። ሕጹር ፡ በጽጌ ። ሀገር ፡ ሕጽርት ፡
(ማሕ፯ ፡ ፪ ። ኢሳ፩ ፡ ፰) ።

ሐጹር ፤ (ራት ። ዕብ ፡ ሐጼር) ፤ ዐጥር ፡ ቅ
ጥር ፡ ከለላ ፤ ወልወል ፡ ከቤት ፡ ውጭ ፡ ከቅጥር ፡ ግቢ ፡
በቤት ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ራት ፡ ለፊት ፡ ያለ ፡ ደጅ ፡ ዐጥረ ፡
ገጥ ። ሐጹር ፡ የዐውዱ ። ማይ ፡ ሐጹራ ። ደስያተ ፡
ሙሴ ፡ ወአሮን ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፤ ዘሐጹረ ፡ ገጾሙ ፡
ከነ ፡ ፍቅረ ፡ አምልኮ ፡ ዐፀ ፡ አስራብ ፡ (ድጓ ። ፍሐ፫ ፡
፭ ። ቅኔ) ።

—፤ የጆሮ ፡ ዘለሳ ፤ በረት ፡ ዳስ ። ወገብረ ፡ ህየ ፡ ሐጹረ ፡
ሎቱ ፡ ወለእንስሳሁ ፡ (ዘፍ፴፫ ፡ ፲፯) ።

—፤ ዐርድ ፡ ምሽግ ፡ መታኰሻ ፡ ግንብ ። ትነድቅ ፡ ሐ
ጹረ ፡ ባዕለ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ አንተ ፡ ትገብር ፡ ጸብአ ፡
ምስሌከ ። ሕጽኑ ፡ ሐጹረ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ (ዘዳ፳ ፡
፳ ። ፪ነገ ፡ ፳ ፡ ፲፭) ።

ተሓጸረ ፤ ተጣጠረ ፡ ተከበበ ፡ ርስ ፡ በርሱ ። እ
ስመ ፡ ተሓጸራ ፡ ምስለ ፡ ቢጸን ፡ (ሂርማ ፡ ገ፱) ።

ሐጻረ ፡ ዔናን ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ የደማስቆ ፡ ክ
ፍል ፡ የምድረ ፡ እስራኤል ፡ ዳርቻ ፡ (ሕዝ፵፯ ፡ ፲፯) ።

ሐጽረ ፤—ዐጭር ፡ ኸነ ፤—ነጺር ፡ ነ
ጽረ ።

ሕጻት ፤—መጕደል ፤—ሐጺጽ ፡ ሐጸ ።

ሐፅይ ፤ ዮት ፤ (ሐፀየ ፡ የሐፂ ፡ ይሕፂ ።
ፈነረ) ፤ ማጨት ፡ ማጫ ፡ ማሥመሪያ ፡ ዐረቦን ፡ መስ
ጠት ፡ የልጃገረድ ። ለአከ ፡ ንጉሥ ፡ ይሕፅዮ ፡ ሎቱ ። የ
ሐፂ ፡ ሕፃሃ ፡ በአቡሃ ። ብእሲትየ ፡ እንተ ፡ ሐፀይክዋ ፡
በምእት ፡ ቍልፈት ፡ (ዮሴፍ ። ዘፀ፳፪ ፡ ፲፯ ። ፪ነገ ፡ ፫ ፡
፲፬) ።

**ሐፃዩ ፡ (ዩ·ት ፡ ይያን ፡ ያት ፡ ፀዩት) ።** የሚያዩ ፡ ማፋፋ ፡ የሚሰጥ ፡ ሰፊይት ።

**አሐፀየ ፤** አሳፈፈ ፡ ማፋፋ ፡ አሰጠ ።

**ተሐዕየ ፤** ታፈፈ ፡ ማፋፋ ፡ ወሰደ ፡ ተቀበለ ። ይ ነግል ፡ እንተ ፡ ተሐፀየት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፰ ። ፶፰) ።

**ተሓፀየ ፤** ተማፈፈ ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ተዋዋለ ።

**ሕፁ·ይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ፂ·ት) ፤** የታፈፈ ፡ የተ ማፈፈ ፡ ባለፋማ ። ድንግል ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሕፂት ፡ ለው ፡ ተፍኅረት ፡ ለብእሲ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፳) ።

**ሕዕየት ፤** ማፈፊት ፡ መታፈፊት ፡ መተማፈፊት ፡ አስተማፈፊት ። እለ ፡ ይመጽሙ ፡ ወለተ ፡ ሕፀየት ፡ (ሕ ፀ·ዩት) ፡ ለው ፡ ዘኢተሐፀየት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፰) ።

**ሕፄ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ማፈፊት ፡ መታፈፊት ፡ ማፋፋ ፡ መስጠት ፡ መቀበል ። ዐድሜ ፡ ሐዘን ፡ ይክልእ ፡ እም አውስቦ ፤ ወኢይክልእ ፡ እምሕፄ ፡ ወእምፍኅረት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፱) ።

— ፤ ማፋፋ ፡ መታፋፋ ፡ የጋብቻ ፡ ዐረቦን ፡ ወንድ ፡ ለሴት ፡ አባት ፡ የሚሰጠው ፡ ገንዘብ ። ሕፄሃ ፡ ለመርዓት ። እመ ፡ ፈቀደ ፡ ፈኃሪ ፡ ለው ፡ ዘተፍኅረት ፡ ምንዘሪስና ፡ እ ምድኅረ ፡ ወሀበ ፡ ሕፄ ፡ ይደልዎ ፡ ለፈኃሪ ፡ ዘወሀበ ፡ ቅድመ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፤ ወለፍኅርቱኒ ፡ ከመ ፡ ታግ ብእ ፡ ዘነሥአት ፡ ዘእንበለ ፡ ካዕበት ። ይደሉ ፡ ለው ስቦ ፡ ዘእንበለ ፡ ትልወት ፡ ወኢሕፄ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፫) ። ሴትም ፡ ወደ ፡ ባሏ ፡ የምትወስደው ፡ ገንዘብ ፡ ሕፄ ፡ ይባላል ፤ መዳረያ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዘጸሐፈ ፡ ትእዛዘ ፡ የሀብ ፡ ለአዋልዲሁ ፡ በበ ፡ አሐቲ ፡ መክፈልተ ፡ ሕፄ ሆን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰ ፡ ፱) ።

**ሐፄ ፤ (ሐፃዩ) ፤** ፀጤ ፡ የመንግሥት ፡ ዕፈማኛ ፡ በዓለ ፡ መንግሥት ፡ ሕዝብና ፡ ካህናት ፡ ዘውዱን ፡ ዙፋ ኑን ፡ እንደ ፡ ሙሽራ ፡ ባርከው ፡ መርቀው ፡ የሚሰጡት ፡ ተቀጸል ፡ ጽጌ ፡ የሚሉት ። እኮ ፡ በቃለ ፡ ሐፄ ፡ ወእኮ ፡ በ መክ·ንን ፡ (ታሪ ፡ አክ) ። የንግሥና ፡ የተከሊል ፡ ሥር ዐት ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሙሽሮችም ፡ በማጌጣቸው ፡ ወ ራት ፡ ሐፄና ፡ እቴጌ ፡ ወይም ፡ ንጉሥና ፡ ንግሥት ፡ ይ ባላሉ ። ወይወስዱ ፡ ለንጉሥ ፡ ደናግለ ፡ ድኅሬሃ ፡ ወ ያበውእዎን ፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ ንጉሥ ፤ ማኅሌ ፡ (መዝ ፡ ፵፬) ። ሐፄና ፡ ፀጤ ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ በዐረብና ፡ ባማርኛ ፡ ብዙ ፡ ተረትና ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ አለ ።

**ሐፄጌ ፤** ሐፃዬ ፡ ምድር ፡ ፈንሪሃ ፡ ለምድር ፡ ን ጉሠ ፡ ምድር ፡ እግዚአ ፡ ምድር ። ባለርስትን ፡ ባለጌ ፡ እ ንዲሉት ፡ የጌን ፡ አፈታት ፡ እይ ። ቀቀጸል ፡ ጽጌ ፡ ሐ ፄጌ ፡ (የድጓ ፡ ግስ) ።

**ሐፄጌ ፤ (ማእከላይ ፡ ስም) ፤** ዘይቤው ፡ ዕፈጤ ፡ ዕፈጤ ፡ ሱታፌ ፡ ንጉሥ ፡ ባለሚስ ፡ መንግሥት ። ምስ ጢሩ ፡ ሊቀ ፡ ሀገር ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፤ ርእስ ፡ አድባራት ፡ ወገዳማት ። ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ኒቅያ ፡ ሕግ ፡ ትምርቱ ንና ፡ ንጽሕናውን ፡ ጠባዩንና ፡ እናምሩን ፡ አስተዳደጉን ፡ አይታ ፡ መርምራ ፡ ይደልዎ ፡ ብላ ፡ መርጣ ፡ መስክራ ፡ ባልቻቸው ፡ ሊሎች ፡ ከወገናቸው ፡ መርጠው ፡ በሚ ሾሙት ፤ ቋንቋውን ፡ በማታውቀውና ፡ ቋንቋዋን ፡ በማ ያውቅላት ፡ በባዕድ ፡ በንግዳ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ጳጳስ ፡ ታዞ ፡ ተናዞ ፡ መኖርን ፡ ስለ ፡ ወደደች ፤ ፲፫ም ፡ ከብሯንና ፡ መዓበረ ፡ ክብሯን ፡ አዛታ ፡ ፈጽማ ፡ ይቅርብኝ ፡ ብላ ፡ ለ ባዕድ ፡ መስጠትን ፡ ስለ ፡ ጠላች ፤ እፍኣዊ ፡ በሙን ፡ መ ለካዊ ፡ ወይም ፡ ባስልዮስ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ሐፄጌ ፡ ብ ላዋለች ፡ እንጂ ፡ ውሳጣዊ ፡ ስሙ ፡ ጳጳስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ነው ። ጳጳስ ፡ ሲታጣም ፡ በማልዋ ፡ የጳጳስ ፡ ሥራ ፡ እየ ሠራ ፡ እቡንና ፡ ዕጨጌ ፡ ይባላል ፡ ጳጳስም ፡ ቢኖር ፡ ባ ገሩ ፡ እንግዳ ፡ ለሕዝቡ ፡ ባዳ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አፈ ፡ ድዳ ፡ ቀንደ ፡ ጉዳ ፡ መስሎ ፡ ያቀረቡለትን ፡ ቅብና ፡ ዲቁና ፡ ከ መሾም ፡ በቀር ፡ ሊፈርድና ፡ ሊተች ፡ ሊሰብክ ፡ ሊያስተ ምር ፡ አይችልምና ፤ በሕዝብና ፡ በካህናት ፡ ላይ ፡ ሥል ጣኑ ፡ መብቱ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ወትሮ ፡ የፈጤ ፡ ነው ። ወ ፈታሒስ ፡ ውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፤ ወውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፤ አው ፡ ኤጲስቆጶስ ፤ አው ፡ ዘአትለውዎ ፡ እሙ ንቱ ፡ ወረሰይዎ ፡ ህየንቴሆሙ ፡ በእንተ ፡ ፍትሕ ። ይ ኩን ፡ ድኑ·ተ ፡ ልሳን ፡ ወዘየአምር ፡ ነገረ ፡ ልሳን ፡ እ ንተ ፡ ኢትትከሀል ፤ ልሳኑ ፡ ሰብአ ፡ ሚመቱ ፡ በዘይትና ገሩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫) ። በሰማዕና ፡ በሰጋዕ ፡ ዘይቤም ፡ ሲፈቱት ፤ ወምስማካለ ፡ ለመንግሥትክሙ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዳለው ፡ ኹሉ ፡ (ቂር) ፡ መፈጤ ኂያ ፡ መከዳ ፡ ያሰኛልና ፡ ይህ ፡ ስም ፡ ዕፈጤማናን ፡ ከጽድስና ፡ አዛምዶ ፡ አዋሕዶ ፡ አጣምሮ ፡ አስተባብሮ ፡ ያሳያል ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ መከዳ ፡ ንጉሡን ፡ አማ ኽለው ፡ አቡኑ ፡ በቀኝ ፡ ዕፈጤው ፡ በግራ ፡ በመቀመጣ ቸው ፡ ይታወቃል ፡ አቡን ፡ ሲታጣ ፡ ግን ፡ ቀኙ ፡ የፈጤ ፡ ነው ። ዕጨማንትም ፡ የተገመረ ፡ ባ፲፪፻፷፫ (፶፫) ፡ ዓመት ፡ ይኩኖ ፡ አምላክን ፡ ቀብተው ፡ ባነገሡ ፡ በዳግማይ ፡ ተ ክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ ርሳቸውም ፡ በናታቸው ፡ የንገሥ ታት ፡ ወገን ፡ የይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ያክሥት ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የናት ፡ ወንድም ፡ አጎት ፡ ወዲህም ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ። ፈት ፡ በሕግ ፡ ቀስው ፡ በኋላ ፡ መንኵሰው ፡ አቡን ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ያልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ የማይገባ ፡ መስሏቸው ፤ አበ ፡ ብልንት ፡ ዕፈጤማ ንት ፡ ከሚለት ፡ ብለዋቸዋል ። ዳግማይ ፡ ማለትም ፡ በ፪ ኛው ፡ (ቤክል) ፡ መቆ ፡ ይህን ፡ ሐዲስ ፡ ስም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መባልን ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ በጌታ ፡ ቃል ፡ ለተሰየሙት ፤ ለጻድቁና ፡ ለቅዱሱ ፡ ለታላቁ ፡ ሐዋርያ ፡ እንጂ ፤ ባ፪ኛው ፡ (ቤክል) ፡ መቆ ፡ መንግሥትን ፡ ከድልን ዓድ ፡ ወስዶ ፡ መገርመሪያ ፡ ከዛጌ ፡ ወገን ፡ ለንገሠው ፡ መራ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለተባለው ፡ ለላስታው ፡ ንጉሥ ፡ አይደለም ። በጻድቁና ፡ በፈጤው ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ዘ መን ፡ ከ፳፻፶ ፡ ቢበልጥ ፡ እንጂ ፡ አያንስም ፡ (ታሪክና ፡ ገድል) ። ጳጳስን ፡ እይ ።

**ሐፂን ፤ ኖት ፤ (ሐፀነ ፡ የሐፅን ፡ ይሕፅን) ፤** ማቀፍ ፡ ማጥባት ፡ ማሳደግ ፡ የልጅ ። እንተ ፡ ተሐፀና ፡ ወታጠብዎ ። ተሐፅን ፡ ሳራ ፡ ሕፃነ ። እለ ፡ የሐፅና ።

ወለት ፡ እንተ ፡ ሐፀና ፡፡ መፍትው ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ውሉድ ፡ ይሕፀንዎሙ ፡ ለዕጓለ ፡ ማውታ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፯ ። ዘፍጽ፳ ፡ ፯ ። ማቴ፳፱ ፡ ፲፱ ። አስቴ፪ ፡ ፯ ። ዲድ ፡ ፲፰) ። ለንፌትና ፡ ለማር ፡ ለጠጕርም ፡ ይነገራል ። ማይ ፡ ሐፀኖ ፡፡ ሐፂኖቱ ፡ ወፀፊሮቱ ፡ (ሕዝ፴፩ ፡ ፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፶፩) ። በሴሰየ ፡ ፈንታ ፡ ሐፀነ ፡ ይላል ፤ ምስጢሩ ፡ ከማጥባት ፡ ይገባል ። የሐፀኖ ፡ ለሚበትኪ ፤ ያረጀ ፡ ሰውነትሽን ፡ (ሩት፬ ፡ ፲፭) ።

**ሐፃኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት ፤ ፀንት) ፤** የማይቀፍ ፡ የሚያጠባ ፤ አሳዳጊ ፡ ሞግዚት ። ሐፃንያትኪ ፡፡ ወልደ ፡ ሐፃኒቱ ፡፡ መምህር ፡ ወሐፃኒ ፡፡ ሐፀንተ ፡ ደቂቅ ፡ (ኢሳ፵፱ ፡ ፳፫ ። ማብ፲፫ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ድ፴፬ ። ፱ ነገ ፡ ፲ ፡ ፩) ።

**ተሐፅነ ፤** ጠባ ፡ ጠጣ ፤ አደገ ፤ ታቀፈ ፡ ዕቅፍ ፡ ኾነ ። ተሐፀንኩ ፡ በጥብ ፡፡ ትትሐፀኒ ፡ ሐሊበ ፡ አሕዛብ ፡፡ ደቂቅ ፡ እለ ፡ ተሐፀኑ ፡ ምስሌሁ ፡፡ ተሐፀነ ፡ በሖሩ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡፡ ዘከመ ፡ ተሐፀንኪ ፡ ውስተ ፡ እዴየ ፡ (ኢዮ፫ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፷ ፡ ፲፮ ። ፪ዜና ፡ ፲ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፫ ። አስቴ፬ ፡ ፰) ።

**ሕፁን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ፀንት) ፤** ያደገ ፡ የጠባ ፡ የታቀፈ ፡ በክንድ ፡ የተያዘ ።

**ሕፀንት ፤** ማደግ ፡ ማሳደግ ፡ እድገት ፡ አስተዳደግ ። ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ሐፀኖ ፡ ሠናየ ፡ ሕፀነተ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ እኅወ ፡ እሙ ፡፡ ዘየሜኒ ፡ ሕፀነተ ፡ ደቂቅ ፡ (ቁር ፡ ገ፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**ሕፃን ፤ (ናት) ፤** በቁሙ ፡ ዐራስ ፡ ጨቅላ ፡ ጡት ፡ ያልተወ ፡ ራሱን ፡ ያልቻለ ፡ ታናሽ ፡ ለጋ ፡ ርጥብ ፡ ልጅ ፡ ወንድ ፡ ሴት ። ያደገውም ፡ ቢኾን ፡ እስኪባልቅ ፡ ድረስ ፡ ሕፃን ፡ ይባላል ፤ ደቦል ፡ ጕብል ፡ አሽከር ፡ ብላቴና ፡ ማለት ፡ ነው ። ሕፃን ፡ ጥብሩል ፡፡ እለ ፡ ይእዜ ፡ ተወልዱ ፡ ሕፃናት ፡፡ ሕፃን ፡ ንስቲት ፡፡ ሕፃን ፡ ንኡስ ፡፡ ሕፃን ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ዓመት ፡፡ ወሬዛ ፡ ወሕፃን ፡ (ሉቃ፪ ፡ ፲፪ ። ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፪ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፯ ፡ ፰ ። ኩፋ ፡ ፲፩ ። ፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፩) ። ሕፃንና ፡ ዕጣን ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ፤ (ሙሽ ፤ በክፉ ፡ ቀን ፡ ልጇን ፡ እንደ ፡ ድመት ፡ ዐንቃ ፡ የበላች ፡ ሆዳም ፡ ቀን ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ስትቈጣም) ፤ አላስገባም ፡ ብሎ ፡ ቢያበረኝ ፡ መዳጇ ፡ ክፉ ፡ ቀን ፡ አወጣኝ ፡ የወልድኩት ፡ ልጁ ። ዝባይ ፡ ለመንገድ ፡ ከመውረድ ፡ መቀማ ፤ ዕጣኑ ፡ ይሻላል ፡ ለለት ፡ እራትማ ። ዳግመኛ ፡ ለመውጣት ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፤ ተመልሶ ፡ ገባ ፡ ልጅ ፡ ከናቱ ፡ ሆድ ። ልጅ ፡ የሚችለውን ፡ ዐዋቂ ፡ እንዳይችል ፤ በኒቆዲሞስ ፡ ፊት ፡ ይመስክር ፡ ወንጌል ። የልጆች ፡ ተረት ፡ ምን ፡ እናት ፡ ታስጠላ ፡ ድመት ።

**ሕፃንና ፤** ሕፃንነት ፤ ዐፍላ ፡ ጕብዝና ፡ ልጅነት ።

**ሕፅን ፤ (ፅብ ፡ ሐጼን ፡፡ ዐረ ፡ ሒፅን) ፤** በቁሙ ፤ ማቀፊያ ፡ መታቀፊያ ፤ ጭን ፡ ደረት ፤ የደረትና ፡ የእጅ ፡ መካከል ፡ ብብት ፡ ጕን ፡ ግብጣ ፡ እንብርቢጣ ። የቀሚስ ፡ ሠላጤ ፡ በሠላጤው ፡ ላይ ፡ የሚሰፋ ፡ ኪስ ፡ ጀብ ፡ ጥግ ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ፤ የቦታ ። ውስተ ፡ ሕፅኑ ፡ እሞሙ ፡፡ አንበሮሙ ፡ ውስተ ፡ ሕፅኑ ፡፡ ደይ ፡ እዴከ ፡ ውስተ ፡ ሕፅንከ ፡፡ ሕፅነ ፡ ልሳነ ፡ ባሕር ፡ (ሰቈ፪ ፡ ፲፪ ። ማር፲ ፡ ፲፮ ። ዘፀ፬ ፡ ፮ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፰) ።

**ማሕፀን ፤ (ናት ፤ መሓፅን) ፤** በቁሙ ፤ የሴት ፡ ሆድ ፡ ከዚያውም ፡ ለብቻው ፡ የተለየ ፡ የፅንስ ፡ የሽል ፡ ቦታ ፤ ልጅ ፡ ተፀንሶ ፡ እስኪወለድ ፡ የሚኖርበት ። ዕትብት ፡ እየጠባ ፡ የሚያድግበት ። ተዐቍረ ፡ ውስተ ፡ ማሕፀን ፡፡ ዘእንበለ ፡ ትባእ ፡ እማሕፀን ፡፡ እንዘ ፡ ባ ፡ ውስተ ፡ ማሕፀና ፡፡ ተሀውከ ፡ ማሕፀና ፡ በእንተ ፡ ወልዳ ፡ (ቅዳ ። ኤር፩ ፡ ፭ ። ማቴ፩ ፡ ፲፰ ። ፫ነገ ፡ ፫ ፡ ፳፮) ።

**አማሕፀነ ፤ (ዲ ቃ ፡ ማ) ፤** አማጠነ ፡ አረዳ ፡ ከለከለ ። ዐደራ ፡ አለ ፤ ዐደራ ፡ ሰጠ ፡ አስጠበቀ ። ብሩር ፡ ዘአማሕፀነ ፡ ኀበ ፡ ራጉኤል ፡፡ አማሕፀንኩክሙ ፡ ፌቤንሃ ፡ እኅተነ ፡፡ አባ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ አማሕፀን ፡ ነፍስየ ፡ (ጦቢ፱ ፡ ፩ ። ሮሜ፲፮ ፡ ፩ ። ሉቃ፳፫ ፡ ፵፮) ።

**ማሕፀንት ፤ (ታት) ፤** ዐደራ ፤ ያደራ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ፅንስ ፡ እንደ ፡ ሽል ፡ በፍጹም ፡ ጥንቃቄ ፡ የሚጠበቅ ። (ተረት) ፡ ዐደራ ፡ ጥብቅ ፤ ስማይ ፡ ሩቅ ። ታገብእ ፡ ምድር ፡ ማሕፀንታ ፡፡ ዕቀብ ፡ ማሕፀንተከ ፡፡ ኀፍረት ፡ ሰሪቅ ፡ እምንዋየ ፡ ማሕፀንት ፡ (ሔኖ፶፩ ፡ ፩ ። ፩ጢሞ ፡ ፯ ፡ ፳ ። ሢራ፵፩ ፡ ፲፱) ።

**ተማሕፀነ ፤** ተማጠነ ፤ ይማፀኝ ፡ አለ ። ተማሕፀንኩ ፡ ሎሙ ፡ በቈሳር ፡ (ማብ፳፰ ፡ ፲፱) ።

**—፤** ዐደራ ፡ አኖረ ፤ ዐደራ ፡ ተባለ ፤ ጠበቀ ፡ ተከናከነ ፤ ዐደራውን ። ኢይፈዴ ፡ ዘተማሕፀነ ፡፡ ተለቃሒ ፡ ወተማሕፃኒ ፡፡ ዘየዐቅብ ፡ አፉሁ ፡ ይትማሐፀን ፡ ነፍሶ ፡፡ ይትማሐፀንከ ፡ እምሖሩ ፡ እኩይ ፡ (ዘዐ፳፪ ፡ ፲ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፪ ። ምሳ፲፫ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፲፪) ።

**—፤** ሸሸ ፡ ተጠጋ ፡ የሙጥኝ ፡ አለ ፤ ራሱን ፡ ለሌላ ፡ ዐደራ ፡ ሰጠ ። ፍና ፡ ኀበ ፡ ይትማሐፀን ፡ ቀታሊ ፡፡ ኀበ ፡ መኑ ፡ ትትማሐፀኑ ፡፡ ተማሕፀነ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ዘዐ፳፩ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፲ ፡ ፫ ። ቀሌ) ። ይትጋባእ ፡ ይረውጽ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይትማሐፀን ፡ ይላል ፡ (ኢሳ፶፬ ፡ ፲፭ ። ፶፭ ፡ ፳) ።

**ምሕፁን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ፀንት) ፤** የተማጠነ ፡ ሙጥኝ ፡ የሙጥኝ ፡ ያለ ፡ የደወለ ።

**ምሕፅና ፤** ምጥንታ ፤ ዐደራ ። ቀሲሳን ፡ እለ ፡ ዐቀቡ ፡ ምሕፀናሆሙ ፡ በጽድቅ ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ) ።

**መምሕፅን ፤ (ናን) ፤** ጠባቂ ፡ ባልደረባ ፡ መልአክ ፡ ዑቃቢ ፡ (አርጋ) ።

**መምሕፃን ፤** ሙማጠኛ ፤ መሸሻ ፡ መጠጊያ ፡ የሙጥኝ ፡ መባያ ፡ ገዳም ። ድንቅ ፡ ታምራት ፡ የረዲት ፡ ምልክት ። ነደቀ ፡ ምሥዋዐ ፡ ወሰመዮ ፡ ስሞ ፡ መምሕፃን ፡ (ዘዐ፲፯ ፡ ፲፭) ። ሽቦሌት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መምሕፃን ፡ ይላል ፡ የተባባተ ፡ ነው ፤ ሰብለን ፡ እይ ፡ (መሳ፲፪ ፡ ፮) ።

**ሐፀረ ፡ — ዐጠረ ፡ — ሐጺር ፡ ሐጸረ ።**

**ሐዕረ ፡ — ዐጮር ፡ ኾነ ፡ — ኀጺር ፡ ኀጸረ ።**

**ሕቀ ፡ ሕቅ ፡ ሐቅ ፡ ሕቍ ፡ — ሐቀቀ ።**

**ሐቋ ፡ — ወገብ ፡ — ሐቀየ ።**

**ሔቅ ፡ — ሕፅን ፡ — ሐየቀ ።**

**ሐቅዩ ፡ ዮት ፡ (ሐቀየ ፡ የሐቂ ፡ ይሕቂ ። ዐረ ፡ ሐረቀ ። ሱር ፡ ሐሪቅ ። ዕብ ፡ ሐራቅ) ፡** ማፋጨት ፡ ማጋጨት ፡ ሚጢጥ ፡ ሚጢጥ ፡ ማድረግ ፡ የጥርስ ። ከቍጣ ፡ ከንደት ፡ ከመጕምዠት ፡ ከሥቃይ ፡ ብዛት ፡ የተነግ ። ሐቀዩ ፡ ስነኒሆሙ ፡ ላዕሌየ ። ከመ ፡ ዘየሐቅዩ ፡ ዘአስተዳለዉ ፡ ይብልዑ ። ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ብካይ ፡ ወሐቅየ ፡ ስነን ፡ (መዝ ፡ ፴፬ ። ሚራ፶፩ ፡ ፫ ። ማቴ፰፳ ፡ ፲፪) ።

— ፡ መቈርጠም ፡ መኰርደም ፡ መስበር ፡ ማድቀቅ ፡ ማንቀሳቀስ ። አዕፅምት ፡ ሰብእ ፡ ተሐቂ ። የሐቅየኒ ፡ አዕፅምትየ ፡ (ምሳ፳፱ ፡ ፳፫ ። ኢዮ፴፱ ፡ ፳) ።

**ሐቃዪ ፡ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፡ ቀይት) ፡** የሚያፋጭ ፡ የሚያጋጭ ፡ የሚያንቀሳቅስ ፡ ቈርጣሚ ፡ ኰርዳሚ ፡ የቈሎ ፡ ያጥንት ።

**አሕቀየ ፡** አስፋጨ ፡ አስገጠጠ ፡ እንዲያፋጭ ፡ እንዲያጋጭ ፡ አደረገ ፡ የጋጌን ፡ የደዌ ። ያሐቅየ ፡ ስነ ፡ ኒሁ ። ሕማመ ፡ አዕይንት ፡ ወርእስ ፡ ዘይቀጠቅጥ ፡ አዕፅምተ ፡ ወይቀጸቅጽ ፡ ርእሰ ፡ ወያሐቂ ፡ ስነ ፡ (ማር፱ ፡ ፲፰ ። መ ፡ ፈ) ።

**ተሐቅየ ፡** ተፋጨ ፡ ተጋጨ ፡ ጥርሱ ። ተፈጨ ፡ ተቈረጠመ ፡ ቈሎው ።

**ተሓቀየ ፡** ተፋጩ ፡ ተፈጣጩ ፡ ተፋተጉ ፡ ተፈጋፈጉ ፡ እሳት ፡ ስለት ፡ ዘር ፡ ለማውጣት ፡ የንጩት ፡ የብረት ፡ የሕያው ፡ ፍጥረት ፡ የተባት ፡ የንስት ።

**ሕቁይ ፡ (ያን ፡ ያት ፡ ቂት ፡ ቅይት) ፡** የተፋጨ ፡ የተጋጨ ፡ የተፋተገ ።

**ሐቌ ፡ ሐቋ ፡ (ብ ፡ ሐቍያት ። ዐረ ፡ ሐቅው) ፡** ወገብ ፡ የሕፅን ፡ አጠገብ ፡ የትጥቅ ፡ ሙያ ፡ ከጐድን ፡ በላይ ፡ ከሕፅን ፡ በታች ፡ መካከሉ ፡ ዙሪያው ፡ ግራና ፡ ቀኙ ። ሕልጽን ፡ እይ ፡ ምስጢሩ ፡ መፋጣ ፡ መጋጣ ፡ መወሳወሻ ፡ ማለት ፡ ነው ። ቅንት ፡ ሐቌከ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ። አ ፡ ዘታወፅእ ፡ ለሕፃን ፡ እምሐቌ ፡ ብእሲ ፡ ወትፌንዎ ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ፡ ብእሲት ። እለ ፡ ወፅኡ ፡ እምሐቌሁ ፡ ለአብርሃም ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፫ ። ቅዳ ፡ አት ። ዕብ፯ ፡ ፭) ። በሕፅን ፡ ፈንታ ፡ ሐቌ ፡ ይላል ፡ አያስኬድም ። ስምንት ፡ ተሐቅፍ ፡ ሐቌ ፡ ዘማዊት ፡ (ምሳ፳ ፡ ፳) ።

**ሐቅሎ ፡ ሎት ፡ (ሐቀለ ፡ ይሔቅል ፡ የሐቅል) ፡** መስምረት ፡ ከዱር ፡ ከበረሓ ፡ መግባት ፡ ለማረስ ፡ ለማደን ፡ ለመቀማጥ ።

**ሐቃል ፡ (ላን ፡ ላት ። ሐቃሊ ፡ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፡** ዐራሽ ፡ ዘሳኝ ፡ ባላገር ። ሰሐቃል ፡ ወሰግዩር ፡ (ዘፀ፳፪ ፡ ፴፰) ።

— ፡ ገልቱ ፡ አረመኔ ፡ ፈደል ፡ የሌለው ፡ ቋንቋው ፡ ያልጠራ ፡ በርበር ። ሐቃል ፡ ወህገሬት ፡ (ሮሜ፩ ፡ ፲፬ ። ቆላ፫ ፡ ፲፩) ።

— ፡ በረኸኛ ፡ በለድ ፡ ዐዳኝ ፡ ወንበዴ ። ዔሳው ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ድሩክ ፡ ወሐቃላዊ ፡ ወጸጓር ። እስመ ፡ ብእሲ ፡ ሐቃላዊ ፡ ውእቱ ፡ ወነዓዊ ። ዕደው ፡ ሐቃልያን ፡ ወመደንግፃን ፡ (ኩፋ ፡ ፲፱ ። መሳ፱ ፡ ፬) ።

**ሐቅል ፡ (ብ ፡ አሕቁ(ቃ)ል ፡ ላት ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሐቅላእ ። ዐረ ፡ ሐቅል) ፡** ገራህት ፡ ዕርሻ ፡ ቅብቅብ ፡ ዱር ፡ በረሓ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ ዕርሻ ፡ ያለበት ። ሐቅለ ፡ ድማኅ ፡ ገራህተ ፡ ደም ፡ ብሂል ። ሐቅል ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ። ወመጽአ ፡ ዔሳው ፡ እምሐቅል ፡ ርኁብ ። ወሖረ ፡ ይንበር ፡ ውስተ ፡ ሐቅለ ፡ ሞአብ ። ወተመይጣ ፡ እምሐቅለ ፡ ሞአብ ፡ ምድር ፡ (ግብ፩ ፡ ፲፱ ። ማር፲ ፡ ፴፰ ። ኩፋ ፡ ፳፬ ። ሩት፩ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፯) ።

— ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ ዘብጥ ፡ ረባዳ ፡ ግራ ፡ ቀኙ ፡ ተራራ ፡ የኾነ ፡ የወንዝ ፡ ዳር ፡ የተራራ ፡ እግር ። ምስጢሩ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ካለው ፡ ይገባል ። «ሐቅለ ፡ ሲና ፡ ሐቅለ ፡ ቃዴስ ፡ ሐቅለ ፡ ዱራ ፡ ሐቅለ ፡ ስናዖር» ። አሕቃሊሁ ። ወርእየ ፡ አሕቃላቲሁ ። አሕቃላተ ፡ በድው ። አሕቁል ። ኮከበ ፡ አሕቁላት ፡ ወገዳማት ፡ (ኢሳ፶፩ ፡ ፫ ። ዘፍ፲፫ ፡ ፫ ። ዮኤ፪ ፡ ፳፪ ። ዕር ፡ ኢሳ፯ ፡ ፫ ። ግንዘ) ።

**ሐቄን ፡ — አረጋ ፡ — ዐቀነ ፡ ዐቄነ ፡ ዕቁን ።**

**ሐቈፍ ፡ ፎት ፡ (ሐቀፈ ፡ የሐቅፍ ፡ ይሕቅፍ ። ዐረ ፡ ሐቀፈ ፡ ደነነ ። ዕብ ፡ ሀቈፍ) ፡** ማቀፍ ፡ የሰውን ፡ ገላ ፡ በ፪ ፡ እጅ ፡ ጠምጥሞ ፡ መያዝ ፡ መቀበል ፡ ራስን ፡ ግንባርን ፡ መደገፍ ፡ እጅን ፡ ማጣመር ፡ ማስተሳሰፍ ፡ ከሕፅን ፡ ማግባት ፡ መከበብ ፡ ማጠር ፡ ከማኸል ፡ ማግባት ። ሐቀፎ ፡ ወሰዐሞ ። የማኑ ፡ ተሐቅፈኒ ፡ ወፀጋሙ ፡ ታሕተ ፡ ርእስየ ። አብድ ፡ ሐቀፈ ፡ እደሁ ፡ ወሰልዐ ፡ ሥጋሁ ። ዕግትዋ ፡ ለጽዮን ፡ ወሐቅፍዋ ፡ (ዘፍ፴፫ ፡ ፬ ። ማሕ፪ ፡ ፮ ። መክ፬ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፵፯) ። እጅና ፡ ክንፍ ፡ ተመሳሳዮች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ለአዕዋፍም ፡ ይነገራል ። ከመ ፡ ዖፍ ፡ እንተ ፡ ተሐቅፍ ፡ አንቀቅሖ ። ወከመ ፡ ንስር ፡ የሐቅፍ ፡ ዕጕሊሁ ፡ በገበዋቲሁ ፡ (ዱድ ፡ ፯ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፲፩) ።

**ሐቃፊ ፡ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፡ ቀፍት) ፡** የሚያቅፍ ፡ ዐቃፊ ፡ ተቀባይ ።

**አሕቀፈ ፡** አሳቀፈ ፡ አስታቀፈ ፡ አሲያዘ ፡ አስቀበለ ፡ አስከበበ ። ወአሕቀፎ ፡ በዐጽፉ ፡ (ገድ ፡ ዮሐ፯) ።

**ተሐቅፈ ፡** ታቀፈ ፡ ተያዘ ፡ ዕቅፍ ፡ ኾነ ። ተሐቅፈ ፡ በአብራከ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተሓቀፈ ፡** ተቃቀፈ ፡ ተያያዘ ፡ ተጣመረ ። ጊዜ ፡ ሰተሓቅፎ ፡ ወጊዜ ፡ ሰተራሐቅ ፡ እምተሓቅፎ ። ተሓቀፉ ፡ በበይናቲሆሙ ። ተአምኑ ፡ ወተሓቀፉ ፡ (መክ፫ ፡ ፭ ። ሄኖ ፡ ፳ ፡ ፵፩ ። ዕገዝ፱ ፡ ፵፯) ።

**ሕቁፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ቅፍት)** ፤ የታቀፈ ፡ የተቃቀፈ ፡ ዕቅፍ ፡ ዕቅፍቅፍ ፡ በቅፍ ፡ የተያዘ ፡ የተያያዘ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ሕቅፌት** ፤ ማቀፍ ፡ መታቀፍ ፡ አስተቃቀፍ ። በእንተ ፡ ሕቅፌተ ፡ ሕፃን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫) ።

**ሑቃፌ** ፤ ግዜ ፡ ከማኑ ፡ በቀፈ ፡ ዕቅፌያ ፡ ቅበላ ፡ (አርጋ ፡ ፩) ።

**ምሕቃፍ ፤ (ፋት)** ፤ ማቀፊያ ፡ መታቀፊያ ፡ እጅ ፡ ክንፍ ፡ በታ ።

**አስተሓቀፈ** ፤ አስተቃቀፈ ፡ አያያዘ ፡ አጣመረ ፤ አቀባበለ ።

**ሐቂቅ ፤ ቆት ፤ (ሐቀ ፤ ሐቀቀ ፡ የሐቅቅ ፡ ይሕቅቅ ። ሐገገ)** ፤ ማብዛት ፡ ማሳነስ ፡ ጥቂቱን ፡ ብዙ ፡ ብዙውን ፡ ጥቂት ፡ ማድረግ ፡ መቀነረጥ ፡ መወሰን ። ሐገገን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ማፋቅ ፡ ሕቅ ፡ ሖቅ ፡ ማለት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሐቅ ፤ (ዐረ ፡ ወትግ ። ዕብ ፡ ሐቅ)** ፤ ሕግ ፡ እውነት ፡ ርግጥ ፡ አማን ።

**ሕቅ ፤ (ቃት)** ፤ ቅጽልና ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ። ጥቂት ፡ ታናሽ ፡ ወራዳ ፡ የተናቀ ። **አምጽኢ ፡ ሊተ ፡ ሕቀ ፡ ማየ ፡ በግምዔ ። ርእየ ፡ ሕቀ ፡ ደመና ። እምድኅረ ፡ ዘመን ፡ ሕቅ ። ሕንስ ፡ ሕቅ ፡ ወንሉስ ፡ በቅድሜከ ። ሕቀ ፡ አሕጸጽኮ ። ታዐርፉ ፡ ሕቀ ። ሕቀ ፡ ከመ ፡** (ዘኍ ፡ ፲፯ ፡ ፲ ። ፲፰ ፡ ማ፱ ። ፊልክ ፡ ፱ ። ፪ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፷ ። ማርቆ ፡ ፴፮) ።

**—** ፤ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ዐያሌ ፡ በጣም ፡ ፈጽሞ ። **ዘበሕቁ ፡ ንጹር ። ኢታስተርአ ፡ በሕቁ ። ኢትርሐቁ ፡ በሕቁ ። መስየ ፡ በሕቁ ። ጸለየ ፡ በሕቁ ። በሕቁ ፡ ጥቀ** ፤ ፈጽሞ ፡ (ዘሌዋ ፡ ፲፫ ። ፲፫ ፡ ፱ ። ኢያ ፡ ፱ ። ጦቢ ፡ ፪ ። ስንክ ። ቄር ፡ ጸላ) ።

**በሕቁ** ፤ በጥቂቱ ፡ በጅጉ ፡ ባያሌው ።

**በበ ፡ ሕቅ** ፤ ጥቂት ፡ ጥቂት ፤ በየጥቂቱ ። **በበ ፡ ሕቅ ፡ ልህቀ ፡** (ቅዳ ፡ ድን) ።

**ሕቀት** ፤ ሕቅታ ፡ ስርቅታ ፡ ፀአተ ፡ ነፍስ ፡ መፈረሻ ፡ ትንፋሽ ።

**ሕቁ ፤ (ቋት ። ዕብ ፡ አልሞግ ፤ ብ ፡ አልሙጊም ፤ አልጉሚም)** ፤ ሰንደል ፡ እጅግ ፡ ክቡር ፡ ዕንጨት ፡ ህንዳዊ ፡ ዛፍ ፡ መልክም ፡ ሽታ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ አብኖስ ፡ በውድ ፡ የሚሼጥ ፡ የሚገዛ ። **አምጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ወርቀ ፡ ወዕፀወ ፡ ሕቁ ፡** (፪ዜና ፡ ፲ ፡ ፲፩) ። ቁጽርስስ ፡ አርዝ ፡ ዕፀ ፡ መዐዛ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሕቁ ፡ ይላል ፡ የመሳሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ማሕ ፩ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ። ፪ዜና ፡ ፪ ፡ ፰ ። ራእ ፲፰ ፡ ፲፪) ፡ ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ ዘጲ ፡ አብኖስ ፡ ሰኖባር ፡ ይሉታል ።

**ሐቂር ፤ ሮት ፤ (ሐቀረ ፡ የሐቅር ፡ ይሕቅር ። ዕብ ፡ ሐቃር ። ዐረ ፡ ሐቀረ ፤ ማሰ)** ፤ መቈፈር ፡ መመርመር ፡ ምድርን ፡ ነገርን ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ። ግብሩን ፡ ምስጢሩን ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፡ ማስተሐቀር ፡ ቅር ፡ ማሰኘት ፡ መናቅ ፡ ማቃለል ፡ መንቀፍ ፡ ማጸየፍ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሐቀረ ፡ ፈንታ ፡ እንዳማርኛው ፡ አስተሐቀረ ፡ ይላል ፡ እስተ ፡ ተርጓሚና ፡ ጣፊ ፡ ፍችውን ፡ አቃለሉን ፡ ሲያዩ ፡ ያገቡት ፡ ነው ፤ ሐየጸንና ፡ ዐገሠን ፡ ፈሥሐን ፡ እይ ። ግእዝ ፡ መሀረ ፡ ያለውን ፡ ዐማርኛ ፡ አስተማረ ፡ እያለ ፡ ልማድ ፡ ይፈጽምራል ፤ የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ልማድ ፡ ከንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በቀር ፡ ወትሮ ፡ አይስማማም ። **ኢይምሰልክ ፡ ዘአስተሐቀርኩክ ። እለ ፡ ያስተሐቅሩ ፡ ሕገሙ ። ኢትትመካሕ ፡ በአስተሐቅሮ ፡ አቡክ ። አስተሐቅሮታ ፡ ለእሙ ። ብእሰ ፡ ጠቢብ ፡ ዕጹብ ፡ አስተሐቅሮ ፡** (ዘፍ፡፴፩ ፡ ፴፭ ። ዕዝ ፡ ፲፪ ። ሢራ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ። ፳፮ ፡ ፳፱) ።

**አሕቀረ ፤ (አስተሐ(ሕ)ቀረ)** ፤ አስቈፈረ ፡ አስመረመረ ፤ አስናቀ ።

**መሕቅር ፤ መስተሐ(ሕ)ቅር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት)** ፤ የሚያስተሐቅር ፡ የሚነቅፍ ፡ የሚያቃልል ፡ ነቃፊ ፡ አስነቃፊ ። **ብእሲ ፡ ነባቢ ፡ ወመስተሐቅር ። ኖሎት ፡ ገፋዕያን ፡ ወመስተሐቅራን ፡** (ሰንዩ ፡ ፮ ። ኪዳ ፡ ገ፱ ። ቄር ፡ ጸላ) ።

**ተሐቅረ** ፤ ተቈፈረ ፤ ተመረመረ ። ተናቀ ፡ ተነቀፈ ፡ ተቃለለ ።

**ሕቁር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ቅርት)** ፤ የተቈፈረ ፡ የተመረመረ ። የተናቀ ፡ የተነቀፈ ፡ ቀላል ፡ ንቁፍ ። **ወከኑ ፡ ሕቁራነ ። በእንቲኣከ ፡ ሕቁር ፡** (ዘፀ፩ ፡ ፯ ። ተረ ፡ ቄር፯) ።

**ሕቅረት ፤ ሐቅረት** ፤ መቃለል ፡ ማቃለል ፡ ማስተሐቀር ። አቀባለል ፡ ቅለት ። **በፍና ፡ ሐቅረት ፡** (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ሐቅር ፤ (ራት)** ፤ ቅርታ ፡ ነቀፌታ ፡ ንቀት ።

**ሐራ ፤ — ሼፍራ ፤ — ሐሪር ፡ ሐረረ ።**

**ሐርብ ፤ (ዐረ ። ዕብ ፡ ሔሬብ ፤ ሰይፍ)** ፤ ጦርነት ፡ ውጊያ ፡ ሰልፍ ። ዐ(ሐ)ርበኛ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።


**ሔሬቢ** ፤ ሰይፋዊ ፡ ሰይፋም ፡ ሰይፈኛ ፡ ተዋጊ ፡ ሐርበኛ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ፋቂ ፡ ዐራቢ ፤ ባለንቅ ፡ ባለቈርበት ፡ ይሉታል ፤ መጥረቢያውንም ፡ መክረቢ ፡ ይሉታል ።

**ሐሪግ ፤ ጎት ፤ (ሐረገ ፡ የሐርግ ፡ ይሕርግ ። ዕብ ፡ ሐራግ ፤ ዘለለ ፡ ፈነጨ ። አራግ ፤ ሳራግ ፤ ቃቃ)** ፤ መሳብ ፡ መምዘዝ ፡ መጠምዘዝ ፡ መጠቅለል ፡ የሐረግ ። መፍተል ፡ ማክረር ፡ ማጠንጠን ፡ የጥጥ ፡ የፀምር ፡ የክታን ። ሐረጉን ፡ ፈትሉን ፡ መታታት ፡ መሥራት ፡ ማቈላለፍ ፤ የጕታ ፡ የቅርጫት ፡ የሹራብ ፡ የወንፊት ። ሐረግ ፡ መጣል ፡ ማስመሰል ፤ በጥልፍ ፡ በስፌት ፡ በሥዕል ፡ በጽፈት ፡ መጕንጕን ፡ መሸረብ ። ጕንጕን ፡ ሐረግ ፡ እንዲሉ ።

**ሐረግ ፤ (ብ ፡ አሕራግ)** ፤ በቁሙ ፡ ዐረግ ፡ የወይን ፡ የዠንጐርቅ ፡ ያብታ ፡ የቅጠል ፡ የጠንበለል ፡ የሙ

በሰው ፡ ኹሉ ። ሐረገ ፡ ወይን ፡ ቅድሜየ ፡ ወውስተ ፡ ውእቱ ፡ ሐረግ ፡ ሠለስቱ ፡ አዕጹቅ ። ገመዱ ፡ ሐረገ ፡ ወይን ። ወሐረገሙ ፡ እምነ ፡ ገሞራ ። አሕራግኪ ። አሕራገ ፡ ወይን ፡ (ዘፍ፵ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ዘኍ፳፫ ፡ ፳፫ ። ዘዳ ፴፪ ፡ ፴፪ ። ኤር፴፭ ፡ ፴፪ ። መቃ ፡ ገ፰)። ትውልድ ፡ ዘር ፡ ሽቅብና ፡ ቍልቍል ፡ የሚቈጠር ፡ (ሉቃ፫ ፡ ፳፫—፴፰ ። ማቴ፩ ፡ ፩—፲፯)። ዐረገኽኝ ፡ ምዝዝ ፡ እንዲል ፡ (መንዙ)።


**ሐርጌ ፤ (ብ ፡ አሕሩግ ፤ ሐራጊት) ፤** የቀንድ ፡ ከብት ፡ ወጠጦ ፡ ኵርቤሳ ፡ ቍርንቢ ፡ የበግ ፡ የፍየል ፡ አውራ ፡ ሙክት ። ሐረገ ፡ ቀርን ፡ ዘቀርኑ ፡ ይመስል ፡ ሐረገ ፡ ቀንደ ፡ ጠማማ ፡ ቈልማማ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሐርጌ ፡ እምውስተ ፡ አባግዕ ። ሐርጌ ፡ እምውስተ ፡ አጣሊ ። ዘበደመ ፡ በግዐ ፡ ሐርጌ ፡ ወላሕም ፡ (ዘሌ፳ ፡ ፲፭ ። ፱ ፡ ፳፫ ። ቅዳ ፡ ሕር)። መጋዝእት ፡ ወአሕሩግ ፡ ዐቢያን ፡ አሕሩገ ፡ በግዕ ። ሐራጊት ፡ ሠናያን ። ሐራጊት ፡ ሥቡሓን ። ሐራጊተ ፡ ጠሊ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ኤር፴፱ ፡ ፳ ። ሚክ፭ ፡ ፯ ። ፪ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፳፩)። እንደ ፡ ዕብራይስጡ ፡ ሲፈታ ፡ ግን ፡ የሚዘል ፡ የሚፈነጭ ፤ ኰርማ ፡ ፈርጣማ ፡ ያሰኛል ። ፪ኛም ፡ በዞይ ፡ (ሀራግ) ፡ ሀረገ ፡ ብሎ ፡ ዐረደ ፡ ገደለ ፡ ይላልና ፤ ሀርጌ ፡ ተብሎ ፡ በሂ ፡ ሲጠፍ ፡ ፍሪዳ ፡ መሥዋዕት ፡ ያሰኛል ።


ሐርጌ ፡


ሐርጌ ፡

**ሔረግ ፤** ዔረግ ፡ የሐረግ ፡ ቅርጫት ። ሐና ፡ ዐ ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ሔ ፡ በዔ ፡ ተለውጦ ፡ ወደ ፡ ዐ ፡ ተራ ፡ ኺዷልና ፡ ዔረግን ፡ እይ ።

**ሐርገፅ ፤ (ፃት ። ረገፀ) ፤** ዐዞ ፡ የባሕር ፡ አውሬ ፡ ዶማ ፡ ዐይነት ፡ መጋዝ ፡ ጥርስ ፡ ሰው ፡ እየነጠቀ ፡ የሚጐርሥ ፡ እንቅልፋም ፡ እንጕልቻም ፡ እንቅልፍ ፡ የሚረግጠው ፡ የሚደቁተው ፡ ማለት ፡ ነው ። ተሐርገፀ ፡ እንዲል ፡ ሐባብ ፡ እንቀላፋ ፡ አንጐላጀ ፡ ቢል ። ዐዞ ፡ ማለትም ፡ ዕዙግ ፡ ዐዚግ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ረገፀንና ፡ ዐዞን ፡ እይ ። (ሙሾ ፡ ዐዞ ፡ ሰለ ፡ ነጠቀው ፡ ልጅ ፡ እናቱ ፡ እናቱና ፡ አባቱ)፡ ላንድ ፡ ቀን ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጪ ፡ ይመረራል ፡ የኔ ፡ ወንድም ፡ ታዞ ፡ አባይ ፡ ላይ ፡ ይኖራል ። ግባተ ፡ መሬቱን ፡ አትይገው ፡ እናንተ ፡ ታዞ ፡ ኺዷል ፡ እንጂ ፡ ልጁ ፡ መቼ ፡ ሞተ ። ልጁን ፡ አትጥሉብኝ ፡ ቢያዘችኙ ፡ ተሹሞ ፡ አ(ዐ)ዞ ፡ አያውቅምና ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ። መሠጠ ፡ ሐርገፀ ። አክይስት ፡ ወዐናብርት ፡ ወሐርገፃት ። ወረዱ ፡ ኀበ ፡ ፈለግ ፡ ወሀለዉ ፡ ውስቴቱ ፡ ሐርገፃት ፡ ወቆመ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ማእከሎሙ ፡ (አዙሽ ፡ ፯ ። መቃ ፡ ገ፲፱ ። ፊልክ ፡ ፺፱)። በሐርገፅ ፡ ፈንታ ፡ ሐገፅ ፡ ይላል ፡ የጣፊ ፡ ግድፈት ፡ ነው ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፳፱)።


ሐርገፃት ፡

**ሐረድ ፤ ዶት ፤ (ሐረደ ፡ የሐርድ ፡ ይሕርድ ። ዕብ ፡ ሐራድ ፤ ፈጠነ ፡ ፈራ ። ዐረ ፡ ሐረደ ፤ ወጋ ፡ በሳ) ፤** ማረድ ፡ መጕረድ ፡ በስለት ፡ መምታት ፡ መገዝገዝ ፡ መቈረጥ ፡ መበጠስ ፡ ያንገትና ፡ የራስ ፡ (ዘፍ፳፪ ፡ ፲ ። ፴፯ ፡ ፴፩ ። ዘዐ፲፪ ፡ ፮)። ወሐረደ ፡ ሎቱ ፡ አልሕምተ ፡ ወአባግዐ ፡ ብዙኀ ። የሐርዶ ፡ ከማዶ ። ሕርድ ፡ ወብላዕ ። ኢትብልዑ ፡ እንስሳ ፡ ዘእንበለ ፡ ይሕርድዎ ፡ ሕያዎ ፡ (፪ዜና ፡ ፲፰ ፡ ፪ ። ዘሌ፩ ፡ ፭ ። ግብ፲ ፡ ፲፫ ። ቄድር ፡ ገ፳፰)። መሰረቅ ፡ መቅጠፍ ፡ ማታለል ፡ መጥረውን ፡ መልከም ፡ ማስመሰል ። ጥምቀት ፡ ዐረደኝ ፡ እንዲሉ ።

**ሐራዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤** የሚያርድ ፡ ዐራጅ ፡ በጋሚች ። ፋደት ፡ ፋሮ ፡ የማር ፡ ሴባ ፤ ቀፎ ፡ እየደፋ ፡ ማር ፡ የሚበላ ፡ የውሻና ፡ የድመት ፡ ዐይነት ፡ ግም ፡ ክርፋታም ።

**አሕረደ ፤** አሳረደ ፡ መሥዋዕት ፡ አሠዋ ።

**ተሐርደ ፤** ታረደ ፡ ተሠዋ ። ተሐርደ ፡ በእንቲአነ ፡ በግዐ ፡ መሥዋዕት ፡ ክርስቶስ ፡ (ቄር ፡ ጸሎ)።

**ተሓረደ ፤** ተራረደ ፡ ተቃረደደ ።

**ሕሩድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ርድ) ፤** የታረደ ፡ የተራረደ ፡ ስርድ ፡ መሥዋዕት ፡ ምሽግ ።

**ሕርደት ፤** ማረድ ፡ መታረድ ፡ መተራረድ ፡ አስተራረድ ፡ ስርጃ ፡ ስርድነት ።

**አስተሓረደ ፤** አስተራረደ ፡ አጋደለ ፡ አቈራረጠ ።

**ሐረወ ፤—በሳ ፤—ኀረው ፡ ኀረወ ።**

**ሐረው ፤ ዎት ፤ (ሐረወ ፡ የሐሩ ፡ ይሕሩ ። ዐረ ፡ ኀረአ ፤ ዐራ) ፤** መቈፈር ፡ መማስ ፡ ለመንቀል ፡ ለማፍለስ ። ማረስ ፡ መኮሳት ፡ ዐዘዘ ፡ መዝቅ ፡ መፈልፈል ። ሕር ፡ ሕር ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ መጠማ ፡ መንደቅደቅ ፡ መንበቅበቅ ፡ የጕረሮ ።

**ሐራውያ ፤ ሐርዌ ፤ (ብ ፡ አሕርው) ፤** ሕሬያ ፡ ክርክሮ ፡ ሖር ፡ እየማሰ ፡ እያፈሰሰ ፡ የሚበላ ፡ ጥርሳም ፡ ጥቍር ፡ የበረሐ ፡ ዐሣማ ፡ ከቤት ፡ ዐሣማ ፡ የተለየ ፡ ትማሮች ፡ መፍለስ ፡ ይሉታል ። ስቤት ፡ ዐሣማም ፡ ይነገራል ፡ ሐሣማንና ፡ ሐንዘርን ፡ እይ ። ስምንቱም ፡ እንደ ፡ ይርሆ ፡ ነው ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ ያስተባብራል ። ሐራውያ ፡ ሐቅል ፡ ሰዋው ። ወአርኰሳ ፡ ሐራውያ ፡ ሐቅል ። እመ ፡ ይዌልጥ ፡ ሐራውያ ፡ ጸጕሮ ፡ ከመ ፡ ፀምር ። ወሐራውያኒ ፡ ተንፃባ ፡ ኀብሕተ ፡ ዳበ ፡ ጸብር ።

መራዕየ ፤ አሕርው ። ዘይሴስዮ ፡ አሕርው ፤ (ዘፍን ፡ ፲፯ ፡ ፳ ። መገ ፡ ፫፻ ። ኩፋ ፡ ፴፯ ። ፪ኤጥ ፡ ፱ ፡ ፳፱ ። ማር፳ ፡ ፲፭ ። ሉቃ፲፭ ፡ ፲፮) ።



ሐራውያ ፡

**ሐራጥቃ ፤ (ጽር ፡ ኤሬቲኪ) ፤** መናፍቅ ፡ ጠዋየ ፡ ሃይማኖት ፡ ባህሉና ፡ ትርጓሜው ፡ ከመጽሐፍ ፡ ክንባብ ፡ የማይገጥም ፡ መጻሕፍት ፡ እወ ፡ ያሉትን ፡ አልቦ ፤ አልቦ ፡ ያሉትን ፡ እወ ፡ የሚል ፤ የርሱን ፡ ሐሳብ ፡ ብቻ ፡ የሚከተል ፡ የፊቱቃ ፡ የወታደር ፡ ዐይነት ፤ ነገሩ ፡ ከጪዋ ፡ የሚስማማ ፡ ከሊቃውንት ፡ የማይስማማ ፤ እንዳርዮስ ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ እንዳውጣኪ ፡ ያለ ። ባለመጣፎች ፡ ግን ፡ ለይተው ፡ ተለወጠ ፡ የሚል ፡ ይሉታል ፤ እንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሚሉን ፡ ያባያል ። በእንተ ፡ ሐራጥቃ ፡ ዘተግህደ ፡ ዕልወቱ ። ዘተወክፉ ፡ ጥምቀተ ፡ እምሐራጥቃ ፡ አው ፡ ቀረቡ ፡ ቍርባኖሙ ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፫ ። ፳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፲) ።

**ሐረየ ፤—መረጠ ፤—ኀርይ ፡ ኅረየ ።**

**ሐረመ ፤—ቀረጠ ፡ ነደፈ ፤—ኀሪም ፡ ኅረመ ።**

**ሐሪም ፤ ሞት ፤ (ሐረመ ፡ የሐርም ፡ ይሕርም ። ዐረ ፡ ሐረመ ፤ ከለከለ) ፤** መተው ፡ መጾም ፡ ሕርም ፡ ማለት ፡ ሰውነትን ፡ ከሚገባ ፡ ነገር ፡ መከልከል ፡ ማራቅ ፤ ወይም ፡ መራቅ ፡ ከልካይና ፡ ተከልካይ ፡ መኾን ፡ በብዕዐት ፡ በፈቃድ ። **እስ ፡ የሐርሙ ፡ አውስቦ ። በእንተ ፡ ዘሐረመ ፡ አውስቦ ። በእንተ ፡ ዘየሐርም ፡ ንጹሐ ፤** (፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፫ ። ሲኖዶ ። አብጥ ፡ ፵፯) ።

—፤ ገንዘብን ፡ ወይም ፡ ራስን ፡ ለግዜር ፡ መለየት ፡ መቀደስ ፡ ምስጢሩ ፡ ከብዕዐት ፡ ይገባል ፤ ሪም ፡ ባለሪም ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። **ተሐርሚዮሙ ፡ ለእግዚ ። ኵሉ ፡ ዘየሐርሙ ፤** (ሚክ፬ ፡ ፲፫ ። ሕዝ፵፬ ፡ ፳፱) ።

—፤ ማገልገል ፡ ክህነ ፡ መኾን ፡ ምስጢሩ ፡ መቀደስ ፡ ከለው ፡ ይገባል ። **እለ ፡ የሐርምዋ ፡ ለደብተራ ፤** (ዕብ ፲፫ ፡ ፲) ።

—፤ ማረም ፡ መንቀል ፤ ማውገዝ ፡ መለየት ፡ ምስጢሩ ፡ መከልከል ፡ ከለው ፡ ይገባል ። **አነ ፡ ሐረምኩ ፡ ወአውገዝኩ ። ንሔርም ፡ እምቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ ዐመፃ ፤** (ቀሌ) ።

**ሐራሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት ፤ ረምት) ፤** የሚተው ፡ የማያርም ፡ ሕርም ፡ ባይ ፡ ከልካይ ፡ ተከልካይ ። ቀዳሽ ፡ አገልጋይ ። ዐራሚ ፡ ነቃይ ፡ የሚያወግዝ ፡ የሚለይ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሐረመና ፡ በሐራሚ ፡ ፈንታ ፡ ተሐረመ ፡ ተሐራሚ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ፤ (ሮሜ ፲፬ ፡ ፳ ፡ ፳) ። **ኢትበል ፡ በእንተ ፡ እግዚ ፡ ተሐረምኩ ። ኢይትሐረሙ ፡ በእንተ ፡ እግዚ ። መባልዕት ፡ ዘይትሔረሙ ፡ አይሁድ ፡ አምኔሁ ። ዘይትሔረም ፡ አውስቦ ። መነኮሳት ፡ ተሐራምያን ፤** (ሚራ፲፭ ፡ ፲፭ ። ፊልክ ፡ ፲፭ ። መቃ ፡ ገ፲፭ ። ቀኖ ፡ ግንግ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**አሕረመ ፤** አባረመ ፡ ሕርም ፡ አሰኘ ፡ አስተወ ፡ ከለከለ ፤ አስከለከለ ። **እምስቴ ፡ ማይ ፡ አሕረምከ ፡ ጕርዔከ ። አሕረመ ፡ ሕይወቶ ፡ እምነጽሮ ፡ አንስት ። ንጢአት ፡ ዘአሕረመ ፡ እግዚ ። ከማሁ ፡ ለዕደውኒ ፡ አሕረሞሙ ፡ እግዚ ፡ ቀሪበ ፡ አንስቲያሆሙ ፡ በመዋዕለ ፡ ትክቶሆን ፤** (ስንክ ፡ ነሐ፳፱ ። ታኅ፴ ። ፈ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፯ ። ፲ ፡ ፳) ። በሐረመ ፡ ፈንታ ፡ አሕረመ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ገብሩ ፡ ሎሙ ፡ ምስለ ፡ ወአሕረሙ ፡ ያመ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ አድባር ። አሕረምዎን ፡ ለርእሶሙ ፤** (ዘፍን ፡ ፲፯ ፡ ፲ ። አስቴ፱ ፡ ፴) ።

**ተሐርመ ፤** ታረመ ፤ ተተወ ፡ ሕርም ፡ ተባለ ። ተለየ ፡ ተቀደሰ ፤ ተከለከለ ። **ቲገዘሩ ፡ ወተሐርሙ ፡ በእንተ ፡ ፍርሀቶሙ ፡ ለአይሁድ ። ዘይትሔረም ፡ ለእግዚ ። ዘከመ ፡ መሀርኩክሙ ፡ ትትሐረሙ ፡ ከማሁ ፡ ተዐቀቡ ፤** (አስቴ፰ ፡ ፲፯ ። ያዕ፭ ፡ ፳፯ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፪) ።

**ሕሩም ፤ (ማን ፡ ማት ፤ ርምት) ፤** የተወ ፤ ያረመ ፡ ሕርም ፡ ያለ ፤ በገዛ ፡ እጁ ፡ የተከለከለ ። **ሕሩመ ፡ ሥጋ ፡ ወወይን ። ክርሠ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ሕርምተ ፡ ኑካቤ ፡ ወዘርዐ ። ኄራን ፡ ወሕሩማን ፡ መስተጋድላን ፤** (ስንክ ፡ መስ፪ ። ጥር ፡ ጠቢ፳፭ ። ቄድር ፡ ገ፳፯) ።

—፤ የታረመ ፡ የተተወ ፤ ሕርም ፡ የተባለ ፤ የተከለከለ ፡ ክልክል ፤ ተደራጊ ። **በስሉ ፡ እምነ ፡ ሕሩም ። ገባሬ ፡ ሕሩማት ። ዘተክልአ ፡ እምተዋስቦ ፡ ኀልዮ ፡ ከመ ፡ ሕርምት ፡ ይእቲ ። ወዝንቱ ፡ ሕሩም ፡ ባዕለ ፡ ምእመናን ፤** (ዮሴፍ ። ፈ ፡ መ ፡ ፱ ። ፊልክ ፡ ፪፻፲፩) ።

—፤ የተለየ ፡ የተቀደሰ ። ልዩ ፡ ሕርም ፡ ለግዜር ፡ የተሰጠ ። **ሕሩመ ፡ ይኩንክሙ ፡ ለእግዚ ። ንዋዩ ፡ ክነት ፡ ሕርምት ፡ ለእግዚ ። ሕሩም ፡ ዘሐረሙ ። ሀገር ፡ ሕርምት ፤** (ዘሌ፴ ፡ ፴፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲ ። ዘሌ፳፯ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፳፰) ።

—፤ የተወገዘ ፡ ውጉዝ ፤ ልዩ ፡ ርጉም ። **ይኩን ፡ ቅዉመ ፡ ወሕሩመ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፤** (ቀሌ) ።

—፤ ሹልዳ ፡ ሜሾን ፤ የሜሾን ፡ ሥጋ ፡ እስራኤል ፡ የሚያርሙት ። **ሥርወ ፡ ሕሩም ፤** (ዘፍ፴፪ ፡ ፳፰ ፡ ፴፫) ። ሐባበኞች ፡ ሕርቱም ፡ ይሉታል ።

**ሕርም ፤** በቁሙ ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሕርመት ፤ (ታት) ፤** በቁሙ ፡ መተው ፡ መከልከል ፡ ማረም ፤ ሕርም ፡ ማለት ። **ሕርመት ፡ ተዋስቦ ። ሕርመተ ፡ ሐራውያ ። በእንተ ፡ ሕርመት ፡ በሊዐ ፡ ሥጋ ፤** (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፭ ። ቀኖ ፡ ግንግ) ።

—፤ አምልኮ ፡ የአምልኮ ፡ ደንብ ፡ ሥርዐት ፡ (ቆላ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ። ያዕ፩ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯) ። **ኢይግበር ፡ በዓለ ፡ አው ፡ ሕር**

መት፡ ምስሌሆሙ። ሕርመታተ፡ አይሁድ። ወበዕደኒ፡ ብዙኅ፡ ሕርመት፡ የዐቅቡ፡ (ቀሌ። መቃ፡ ፲፭። ማርቆ፡ ፬)።

—፤ ሃይማኖት፡ ሕግ፡ ባህል፡ ምስጢሩ፡ ከአምልኮና፡ ከሥርዐት፡ ይገባል። ምንትኑ፡ ሕርመትክሙ። ታቦት፡ ዘሕርመት። ኢየብሩ፡ ሕርመተ፡ አይሁድ። በእንተ፡ ሕጉ፡ ለልዑል፡ ወበእንተ፡ ሕርመትከ። ዘሳቡእ፡ ሕርመታ። ሕርመተ፡ ትምህርት፤ ምስጢር፡ (ስንክ፡ ኅዳር፡ ፳። ዘፀአ፡ ፳። ዮሐ፡ ፬። ሚሊ፡ ፲፬። ሮሜ፡ ፲፭፡ ፳፭። ኤፌ፡ ፲፱)።

**ትሕርምት፤(ቶት)፤** በቁሙ፡ ጾም፡ ተበቅቦ፡ የትሩፋት፡ ሕግ። ምስጢሩ፡ ያው፡ መከልከል፡ ነው፡ ከሕርመት፡ ይገባል። የብሰ፡ ሥጋሁ፡ እምብዝኀ፡ ትሕርምት። ተፀራዕከ፡ እምትሕርምትከ። ሶበ፡ ይትሐረሙ፡ እምትሕርምታቲሆሙ፡ (ፊልክ፡ ፲፯። ፲፭። መጽ፡ ምስ። ቀሌ)።

**ተሓረመ፤** ተፈረመ፡ ተለየየ፡ ተገዛዘተ።

**ምሕራም፤(ማት)፤** መቅደስ፡ ምኵራብ፡ መሰጊድ፡ ለግዚር፡ ወይም፡ ለጣዖት፡ የተሠራ፡ ቤት። ኢትትነበይ፡ እንከ፡ በቤቴል፤ እስመ፡ ምሕራመ፡ ንጉሥት፡ ይእቲ፡ (ዓሞ፡ ፯፡ ፲፫። ሔኖ፡ ፺፱፡ ፯)።


—፤ ጣዖት፤ ግዝፈ፡ ጣዖት፡ የጣዖት፡ ዐምድ፡ ሐውልት፡ ወይም፡ ዐጸድ፡ አታክልት፡ በጣዖቱ፡ ዙሪያ፡ የሚበቅልና፡ የሚተከል። ለቤተ፡ ክሲያንም፡ ዛፍ፡ ይስማማል፤ ምስጢሩ፡ ከልክልነትና፡ ቅድስና፡ ነው። እገዝም፡ ምሕራማቲከ። ሐውልተ፡ ምሕራማቲሆሙ። ምሕራመ፡ ፆም። ምሕራማተ፡ ጣዖት፡ ተገዝመ፡ (ሚክ፡ ፭፡ ፲፫። ፪ነገ፡ ፲፰፡ ፳፫። ፲፭፡ ፲፫። ኢሳ፡ ፲፯፡ ፰)።

**መሐረም፤(ዐረ፡ እልሙሐረም)፤** ያረቢ፡ መጀመሪያ፡ ወር፡ የካቲት፡ በጨረቃ፡ መንገድ፡ (አቡሻ)።

**ሐርማዝ፤ ሐርመዝ፤(ዐረ፡ ሂርሚስ። ትግ፡ ሐርመስ፤ ዝሆን)፤** አውራሪም፡ ባላንድ፡ ጕጭማ፡ ቀንድ፡ ቀንዱ፡ ባፍንጫው፡ የሚበቅል፡ ራሰ፡ ጕዳ፡ አፍንጫ፡ ቀንዳ። ጕሽ፡ የበረሓ፡ በሬ። ማኅደረ፡ ሐርማዝ፡ ወደስከን። አዘዘ፡ ከመ፡ ይግበሩ፡ ሎሙ፡ ሠለስተ፡ ሣጹነ፡ እምአዕፅምተ፡ ሐርመዝ፡ ወይግን ዝዎሙ። ወገብረ፡ ሰሎሞን፡ መናብርተ፡ ብዙኃተ፡ እምአቅርንተ፡ ሐርመዝ፡ (አዋል። ስንክ፡ ግንቦ፡ ፲። ጊ፡ ወ፡ ሐ፡ ገ፻፱)።

**ሐርማዝ፤** ዝሆናማ፡ አሞራ። ያፍ፡ ዘይሰመይ፡ ያፊ፡ ሐርማዝ፡ ወበውስተ፡ ዝንቱ፡ ብሔር፡ ሐርመዛት፡ ዐቢይት፡ (ጊ፡ ወ፡ ሐ፡ ገ፻፳)።

**ሐሪሥ፤(ዐረ፡ ሐሪሽ። ዕብ፡ ሐሬስ፤ ብርቱ)፤** ዝኒ፡ ከማሁ፡ ጕሽ፡ አውራሪስ፡ ቁርበቱ፡ ጋሻ፡ የሚኾን። ማዘፈ፡ ማእስ፡ ይቡስ፡ ማእስ፡ ጽኑዕ፡ ማእስ፡ ማለት፡ ነው። ሐሪስ፡ ተብሎ፡ በላት፡ በ፡ ሰ፡ ጣፍ፡ ግን፡ ምስጢሩ፡ ዕርሻና፡ በሬንት፡ ይኾናል። ይፈቅድኑ፡ ይትቀነይ፡ ለከ፡ አርዌ፡ ሐሪሥ፡ (ኢዮብ፡ ፴፱፡ ፲)።



ሐሪሥ፡

**ሐረሠ፤—ዐረሰ፤—ሐሪስ፡ ሐረሰ።**

**ሐረሠ፤—ወለደ፤—ኀሪስ፡ ኀረሰ።**

**ሐሬፍ፤—ጸደይ፤—ኀሬፍ።**

**ሐሬፍ፤ ፎት፤(ሐረፈ፡ የሐርፍ፡ ይሕርፍ። ዕብ፡ ዓራፍ፤ ራዐፍ። ዐረ፡ ረዒፈ)፤** መንጠብ፡ መውረድ፡ መንጠፍጠፍ፡ መመንጨት፡ መፍሰስ፡ መኰረፍ። መፍሳት፡ መገንፈል፤ መኰረፍረፍ፤ ዐረፋ፡ ማውጣት። ማልገግ፡ መቁበር፡ ቁበርን፡ ዐረፋን፡ መድፈቅ፤ ከድካም፡ ከደዌ፡ የተነሣ፡ እንደ፡ በቅሎና፡ እንደ፡ በሬ፡ እንደ፡ ጋኔናም። ሠወንን፡ እይ።

**ሐረፋ፤(ፋት)፤** በቁሙ፡ ዐረፋ፡ ከርጥብ፡ ከፈሳሽ፡ ከንፃድ፡ ከሳሙና፡ የሚወጣ። ጥማቂ፡ እንጥፍጣፊ፡ መረቅ፤ ከሚቀቀል፡ ነገር፡ የሚወጣ። ይትበላዕ፡ ሐረፋ፡ ሐምል፡ ዘእንበለ፡ ጼው፡ (ኢዮ፡ ፮፡ ፮)።

**ሐሪጽ፤ ጾት፤(ሐረጸ፡ የሐርጽ፡ ይሕርጽ፡ ፀ። ጠሐነ፤ ደሐየ። ዕብ፡ ሐሬጽ፤ ቈረጠ፡ ከፈለ)፤** መፍጨት፡ መከከት፡ መገ(ከ)ርደ(ተ)ፍ፡ ማድቀቅ፡ ማላም፡ መሰለቅ፡ መቀጥቀጥ፡ መደቈስ። ሐረጸ፡ ወአድቀቀ። ተሐርጽ፡ እምኔሁ፡ ድቀቀ። አሐርጾሙ፡ ከመ፡ ጸበል። ክልኤቲ፡ የሐርጻ፡ በአሐቲ፡ ማሕረጽ። ንሣእ፡ ዐጽቀ፡ በለስ፡ ወሕርጽ፡ (ዘፀአ፡ ፴፪። ፴፡ ፴፮። መዝ፡ ፲፯። ማቴ፡ ፳፬፡ ፵፩። ኢሳ፡ ፴፰፡ ፳፩)። ማረጥ፡ ዐሬጣ፡ መስጠት፡ የድቄት። ደግም፡ መቀረጥ፡ ጽጌ፡ ማጣት፡ የሴት።

**ሐራጺ፤(ጺት፡ ጽያን፡ ያት፤ ረጽት)፤** የሚፈጭ፡ ፈጭታ፡ ባለወፍጮ፡ ደቂት፡ ሸያጭ።

**አሕረጸ፤** አስፈጨ፡ አስላመ፡ አስደቈሰ። አሕረጽዎ፡ ለሶምሶን፡ እክለ፡ ከመ፡ አመት፡ (ዮሴፍ)።

**ማሕረጽ፤(ጻን፡ ት፤ መሓርጽ)፤** መፍጫ፡ ማስፈጫ፡ ወፍጮ፡ የቅምጥ፡ የመዘውር፤ ደንጊያው፡ ፪፡ ኹኖ፡ የተካከለ፡ እንደ፡ ምንገ(ጣይ)ና፡ እንደ፡ ሞማይ፡ እንደ፡ ሰፈይና፡ እንደ፡ ሰፌድ፡ ገጥሞ፡ ላይኛው፡ ብቻ፡ የሚዞር፡ የሚሽከረከር። ወይም፡ የቁም፡ ወፍጮ፡ ማላሚያ፡ መደቈሻ፡ እናቱም፡ ማልጉሉም፡ ሞላላ፡ የኾኑ፡ ሴቶች፡ በ፪፡ እጃቸው፡ የሚገፉት፡ የሚያመላልሱት። አመት፡ እንተ፡ ትነብር፡ ደበ፡ ማሕረጽ። ንሥኢ፡ ማሕረጸ፡ ወሕርጺ፡ ሐሪጸ። የሐር

ጽዎ ፡ በማሕረጽ ። ቃለ ፡ ማሕረጽ ። በአሐቲ ፡ ማሕረጽ ፡ (ዘዐ፲፭ ፡ ፳ ። ኢሳ፵፩ ፡ ፲፭ ። ዘኍ፲፭ ፡ ፴ ። ዮሴፍ ። ሉቃ፲፯ ፡ ፴፭) ። የወፍጮ ፡ መጅ ፡ ግልገል ፡ ላይኛው ፡ ብቻ ። ማሕረጽ ፡ አይጥግ ። እብን ፡ ዐቢይ ፡ ከመ ፡ ማሕረጽ ። ስባረ ፡ ማሕረጽ ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፮ ። ራእ፲፰ ፡ ፳፩ ። መሳ፱ ፡ ፶፫) ።

**ተሐርጸ** ፤ ተፈጨ ፡ ተደቈሰ ፡ ደቀቀ ፡ ዐመድ ፡ ኾነ ። ተሐርጸ ፡ በምዕር ፡ (ዳን፪ ፡ ፴፭) ።

**ሕሩጽ ፡ (ጺን ፡ ጺት ፡ ርጽት)** ፤ የተፈጨ ፡ የተደቈሰ ፡ የደቀቀ ፡ የተሰለቀ ። ልሕሱት ፡ ሕሩጽ ። በእንተ ፡ ዐፅምከ ፡ በማሕረጽ ፡ ሕሩጽ ፡ (ሄርማ ፡ ገ፹፭ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፭) ።

**ሐሪጽ** ፤ ደቂት ፡ ዐመድ ፡ ትቢያ ፡ ከሚፈጩና ፡ ከሚደቈሱ ፡ ነገር ፡ የሚወጣ ፡ ውጤት ። ነፃሥእት ፡ ሐሪጺ ፡ ወሶበት ። ሐሪጸ ፡ ሰገም ። እምሐሪጽ ፡ ልዉስ ። ወደይክዎ ፡ ለውእቱ ፡ ሐሪጽ ፡ ውስተ ፡ ነቅዕ ፡ ዘይወርድ ፡ (ሄኖ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ። ዘኍ፲፱ ፡ ፲፯ ። ዮሴ፯ ፡ ፱ ። ዘዳ፱ ፡ ፳፩) ።

**ሐሪጽ ፡ ሐሊብ ፤ (ዕብ ፡ ሐሪጼይ ፡ ሄሐላብ)** ፤ ያይብ ፡ ልጥልጥ ፡ ድብና ፡ ከወተት ፡ ከርጎ ፡ የሚሠራ ፡ ቍራሽ ፡ ታናናሽ ፡ ክፍል ። ማብነትን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰) ።

**ሐራጺ** ፤ የደቂት ፡ ወለድ ፡ ፍድፋጅ ፡ የውጤት ፡ ትርፍ ፤ ይልቁንም ፡ የጤፍ ። ሰብር ፡ ወለድም ፡ ይኸናል ፤ ርዲ ፡ ብሎ ፡ በራጣ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ሐረቀ ፤ (ትግ ፡ ሐበብ ፡ ሔረቅረቅ)** ፤ ቃታ ፡ የሳንባ ፡ በሽታ ፡ ሰንባብ ።

**ሐረቂስ ፤ (ዐረ ፡ ረቅሽ ። ዕብ ፡ ሐራቅ ፡ ሐቀዩ)** ፤ ምግብ ፡ ፍሬ ፡ ዕፅ ፤ የሚጐረምሩና ፡ የሚነክሱ ፡ የሚጋጥና ፡ የሚገመጥ ፡ የሚታኘክና ፡ የሚላመጥ ፡ (ገድ ፡ አዳ ፡ ገ፻፵፱) ።

**ሐሪር ፡ (ዐረብ)** ፤ ሐር ፡ ጥሩ ፡ ነጭ ፡ ፈትል ፡ የሐር ፡ ትሎች ፡ ቷት ፡ የሚባል ፡ ቅጠል ፡ እየበሉ ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ የሚፈትሉትና ፡ የሚያዘጉት ። ከሐር ፡ ፈትል ፡ የተሠራ ፡ ጥሩ ፡ ልብስ ። ዘይለብስ ፡ ሠቀ ፡ ምስለ ፡ ዘይለብስ ፡ ሐሪረ ። መንጦላዕት ፡ ዘሐሪር ፡ (ፊልክ ፡ ፴፱ ። አዋል) ።

**ሐሪር ፤ ሮት ፤ (ሐረረ ፡ የሐርር ፡ ይሕርር ፤ ሐለለ ። ዐረ ፡ ሐረ ። ዕብ ፡ ሓራር)** ፤ ማረር ፡ መቃጠል ፡ መክሰል ፡ መቃጠል ፡ መሞቅ ፡ መቶስ ። መናደድ ፡ መቈጣት ። ይሕርር ፡ ሥጋሃ ፡ (ሕዝ ፳፬ ፡ ፲) ። ሐሬ ፡ መውጣት ፡ ነጻ ፡ መኾን ። ዐምሐሬን ፡ ተመልከት ።

(ጥ) **ሕራር ፤ (ራት)** ፤ ዕሩሪ ፡ ክሰል ፡ ጥቍር ፡ ዐመድ ። ንግእ ፡ ለከ ፡ ሕራረ ፡ ዕጣን ። በሕራረ ፡ ዐፅሙ ፡ ወሥጋሁ ፡ ፈወሰ ፡ (ጠቢ፳ ፡ ፲፯ ። ፰ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፳) ።

**ሐኖር** ፤ በቁመ ፡ መውቀት ፡ ላበት ። ነፋስ ፡ ሐኖር ። ጊዜ ፡ ሐኖር ፡ (ሆሴ፲፫ ፡ ፲፭ ። ፍ ፡ ኑ ፡ ፲) ።

**አሕረረ** ፤ አሳረረ ፡ አቃጠለ ። ያሐርሮ ፡ ለማዕር ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ (ሚራ፵፫ ፡ ፳፩) ።

**ሐሩ** ፤ ሐርነት ፡ ነጻ ። ጨዋ ፡ ነጻነት ፡ ያለው ። ጭፍራ ፡ ሰራዊት ። ሊቀ ፡ ሐሩ ። ሐሩ ፡ ሰማይ ።

**ሐራዊ** ፤ የጨዋ ፡ ወገን ፡ የጭፍራ ፡ ወገን ። ሐራዊ ፡ ዘክርስቶስ ፡ (ፊልክ ። ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፳፫) ።

**ሐረሰ ፤ ሶት ፤ (ሐረሰ ፡ የሐርስ ፡ ይሕርስ ። ዕብ ፡ ሐራሽ ። ሱር ፡ ሕራት ። ዐረ ፡ ሐረሰ ፡ ተ)** ፤ ማረስ ፡ ምድርን ፡ መሠንጠቅ ፡ መቅደድ ፤ የረጋውን ፡ መሬት ፡ ማማሰል ፡ ማፍረስ ፡ ማብሰል ፡ ማለስለስ ፡ ለዘርና ፡ ለተክል ፡ ማዘጋጀት ። ለርሻ ፡ ሥራ ፡ ፬ ፡ ስም ፡ አለው ፤ ገመሳ ፡ ግልጋሎ ፡ ስየማ ፡ ዘር ። ገበሬንና ፡ ተገበረን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ቦኑ ፡ ዘሎ ፡ አማሪረ ፡ የሐርስ ፡ ዘየሐርስ ። የሐርስ ፡ ለከ ፡ ትልመ ፡ ገራውሂከ ። የሐርስዋ ፡ ለጽዮን ፡ ከመ ፡ ገራህት ። ኢትሕርስ ፡ በአይጥግ ፡ ወበላሕም ፡ ኅቡረ ፡ (ኢሳ፳፰ ፡ ፳፬ ። ኢዮ፴፱ ፡ ፲ ። ሚክ፫ ፡ ፲፪ ። ዘዳ፳፪ ፡ ፲) ።

—፤ ሸክላ ፡ መሥራት ፤ ምስል ፡ ማፍሰስ ፡ መጥረብ ፡ መቅረጥ ። ክፉ ፡ ማሰብ ፡ መመኘት ፡ ማድረግ ፤ መጠንቈል ፡ ማሟረት ፡ ምትሀት ፡ ማሳየት ። ኢትሕርስ ፡ ሐሰተ ፡ ላዕለ ፡ ቢጽከ ፡ (ሚራ፯ ፡ ፲፪ ። ኢዮ፬ ፡ ፰) ።

**ሐራሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት ፤ ረስት)** ፤ የሚያርስ ፡ በራሽ ፡ ገበሬ ፤ ጀኝ ፡ ገበር ። ሐራሲ ፡ በዕርፈ ፡ መስቀል ። ተንፍሩ ፡ ሐረስት ። ዲበ ፡ ወፍረ ፡ ሐረስት ። እስመ ፡ መፍቀሬ ፡ ሐረስት ፡ ውእቱ ፡ (ድጓ ። ዮኤ፩ ፡ ፲፩ ። መክ፳ ፡ ፰ ። ፪ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፲) ።



ሐራሲ ፤

—፤ ሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ጠቢብ ፡ ብልኀተኛ ፤ መሠሪ ፡ አስማታም ፡ ሟርተኛ ። ወንብሩ ፡ ከማሁ ፡ ሐራስያነ ፡ ግብጽ ፡ በሥራያቲሆሙ ፡ (ዘፀ፯ ፡ ፲፩ ። ፰ ፡ ፯ ፡ ፲፰ ። ዘሌ፳ ፡ ፳፯) ።

**ሐረስ ፤ ሐረሳዊ** ፤ ገነኒ ፡ ከማሁ ፡ ሠሪተኛ ፡ ሠሪ ፡ በራሽ ፡ ቈፋሪ ። ሐረሳዊ ፡ ብእሲ ። ወዘኒ ፡ ይጼመው ፡ ሐረሳዊ ። ከመ ፡ ሐረሳዊ ፡ ዘይጼንሕ ፡ ፍሬሃ ፡ (ዘፍ፱ ፡ ፲፭ ። ፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፯ ። ያዕ፭ ፡ ፯) ።

—፤ ጠንቋይ ፡ መሠሪ ፡ ምትሀታም ። ሐረሳውያን ፡ (ቀሌ) ።

**አሕረሰ** ፤ አሠራ ፡ አሳረሰ ። ያሐርስሙ ፡ ገራህተ ፡ (፩ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፪) ።

**ማሕረስ ፤ (ብ ፡ መሓርስ)** ፤ ማረሻ ፡ ማሳረሻ ፡ ብረት ፡ ሰብቻው ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ ተሠርቶ ፡ ከዕ

ርሩ ፡ የሚቀደድ ። ወማሕረስክሙ ፡ ሕግብሩ ፡ ዘ፡ዖ ንወ ። ወይመትሩ ፡ ዘ፡ዖንዊሆሙ ፡ ለማሕረስ ። ግ ብረ ፡ ማሕረስ ፡ ዕርሻ ፡ ቍፋሮ ፡ (ዮኤ፫ ፡ ፲ ። ሚክ፬ ፡ ፫ ። ዘኍ፳፰ ፡ ፲፰) ።

ማሕረስ ፤

**ተሐርሰ** ፤ ታረሰ ፡ ተቈፈረ ፡ ተሠራ ። መብ እስ ፡ ዘኢተሐርሰ ፡ ወኢተዘርዐ ፡ (ዘዳ፳፩ ፡ ፬) ።

**ሕሩስ** ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ርስት) ፤ የታረሰ ፡ የ ተገመሰ ፡ የተገለገለ ፡ የታየመ ፡ የተዘራ ።

**ሕርሰት** ፤ ማረስ ፡ መታረስ ፡ አስተራረስ ፡ ዕ ርሻ ፡ ዐረሳ ።

**ሕርስ** ፤ (ሳት) ፤ ዕርስ ፡ ዕርሻ ፡ በለሳ ፡ ቅብ ቅብ ፡ ገራህት ።

**ሐርስ** ፤ ሻርት ፡ ጥንቈላ ፡ አስማት ፡ ምትሀት ፡ አፍዝ ፡ አደንግዝ ። ዘሥራይ ፡ ወዘሐርስ ። ሰብአ ፡ ሐ ርስ ፡ (ዘዳ፲፰ ፡ ፲፩ ። ዘሌ፳ ፡ ፮) ። በሐርስ ፡ ፈንታ ፡ ሐ ረስ ፡ ሐሬስ ፡ ሐራስ ፡ ይላል ፡ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ አያሰኝም ።

**ሐረሰ ፤—ወለደ ፡ ቀለበ ፤—ኀረሰ ።**

**ሐሬስ ፤—አውራሬሥ ፤—ሐሬሥ ።**

**ሐርተመ** ፤ (የረተመ ፡ ዲ ቃላ ፤ ወይም ፡ የሐረመ ፡ ስሯጽ) ፤ ጠፋ ፡ ታበላሸ ፡ ጐሰቈለ ፡ ከሳ ፡ ጠቈረ ፡ ፈቱ ፡ ተሰበረ ፡ ወረዳ ፡ ምናምንቴ ፡ ኾነ ። ሐር ተመ ፡ ተዓይን ። ኀሰርነ ፡ ወሐርተምነ ። የሐረትም ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ። ተሐረትም ፡ ምክዕቢተ ። ለአብ ፡ ኃጥእ ፡ የሐረትሙ ፡ ውሉዱ ፡ (ኤር፬ ፡ ፳ ። ሚክ፪ ፡ ፬ ። ኢሳ፳ ፡ ፲፭ ። ሢራ፳፱ ፡ ፭ ። ባኦ ፡ ፯) ።

**ሕርቱም** ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ትምት) ፤ የጐሰ ቈለ ፡ ጐስቋላ ፡ ብልሹ ፡ መጥፎ ፡ ወራዳ ፡ ምናምንቴ ፡ ልክስክስ ። ሕርቱም ፡ አነ ። ወልድ ፡ ሕርቱም ። ብ እሲ ፡ ሕርቱም ። የሐይዉ ፡ ሕርቱመ ። ውሉድ ፡ ሕ ርቱማን ። ትውልድ ፡ ሕርቱማን ፡ (ኢሳ፯ ፡ ፭ ። ዲ ድ፲ ፡ ቀሌ ። ጥበ፲፬ ፡ ፳፫ ። ሢራ፵፩ ፡ ፭ ። ኢሳ፶፯ ፡ ፬) ። የሐረመ ፡ ስሯጽ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በሕርምት ፡ ፈንታ ፡ ሕር ትምት ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ወኢሰደደ ፡ ዳግመ ፡ ዘ ይእቲ ፡ ሕርትምት ። ሰብሳብ ፡ ርኵስት ፡ ወሕርት ምት ። ረባሕ ፡ ርኩስት ፡ ወሕርትምት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፭ ፡ ፬ ። ፱ ፡ ፬ ። ፲፰ ፡ ፭) ። በትሕርምትም ፡ ፈንታ ፡ ሕርት ምት ፡ ይላል ፡ (ሰንክ ፡ ታኅ፲፫) ።

**ሕርትምና** ፤ (ናት ፤) ጐስቍልና ፡ ጐስቋልነት ፡ ምናምንቴነት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ውርደት ፡ ጥፋት ፡ ጕዳት ፡ አደጋ ፡ መከራ ። ይመጽእ ፡ ሕርትምና ፡ ላዕሌኪ ። ወ ልደ ፡ ሕርትምና ። ብክዩ ፡ ላዕለ ፡ ሕርትምናክሙ ። ዘሎን ፡ ሕርትምናት ፡ (ኢሳ፵፯ ፡ ፲፩ ። ዜተስ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ያዕ፭ ፡ ፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፪ ፡ ፭) ።

**አሐርተመ** ፤ አዋረደ ፡ አጐሰቈለ ፡ አከፋ ፡ አ ጠፋ ፡ ጐዳ ። ሕርቱም ፡ ዘአሐርተምዎ ፡ ዳኅፃኒሁ ፡ (ግንዘ) ።

(ጥ) **ሐሰ ፤ ሓሰ ፤ (ዐረ ፡ ሓሸ ። ሱር ፡ ሐስ ። ዕብ ፡ ሐሊላ)** ፤ ከሐሰወ ፡ ሥር ፡ የወጣ ፡ ንባር ፡ አን ቀጽ ፤ አሉታ ። አይገባም ፡ አይኾንም ፡ አይደለም ፡ አይ ኹን ፡ አይደረግ ፡ አይድረስ ፡ ሕርም ፡ ውሸት ። ሐሰ ፡ ኢ ትመውት ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፬ ፡ ፬ ። ሮሜ፫ ፡ ፬ ፡ ፴፩ ። ፱ ፡ ፲፬ ። ፲፭ ፡ ፭ ። ገላ፪ ፡ ፲፯) ። ሲረባም ፡ ሐሰ ፡ ሊተ ፡ ለከ ፡ ሎቱ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ወይና ፡ እንደ ፡ አሌ ፡ በለ ፡ ይዘምታል ፡ ምስጢሩ ፡ እንደ ፡ መሐላ ፡ ነው ። ሐሰ ፡ ሊተ ፡ ከመ ፡ ኢይ ግብር ፡ ዘንተ ። ሐሰ ፡ ለከ ፡ ኢታጥፍአነ ። ሐሰ ፡ ሎቱ ፡ ለእግዚአየ ፡ እምዘንቱ ፡ ርኩስ ። ሐሰ ፡ ለነ ፡ እስከ ፡ ነኀድግ ፡ (ዘፍ፵፬ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ። ዮሳ፳ ፡ ፲፱ ። ዘፍ፳ ፡ ፳፭ ፡ ፴፭ ። ኢሳ፳፪ ፡ ፳፱) ።

**ሐስአ ፤—በረደ ፤—ኀሥዐ ።**

**ሐሰበ ፤ በት ፤ (ሐሰበ ፡ የሐሰበ ፡ የሐ ሰብ ። ዕብ ፡ ሐሻብ ። ሱር ፡ ሕሻብ ። ዐረ ፡ ሐ ሰበ)** ፤ ማሰብ ፡ መመርመር ። መቍጠር ፡ መገምገም ፡ መገመት ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ማለት ። ምንት ፡ ይእቲ ፡ ትዕ ቢት ፡ ይቤ ፡ ለእመ ፡ የሐስብ ፡ ሰብእ ፡ ነፍሶ ፡ ንጹሐ ። የሐስብ ፡ ሎቱ ፡ ካህን ፡ ወርቀ ። ሐሲበከ ፡ ሐስቦ ፡ ለሊከ ። ኢየሐስብዎሙ ፡ በሐሳበ ፡ ዓለም ፡ (ፊልክ ፡ ፴፭ ። ዘሌ፳፯ ፡ ፲፰ ። ሉቃ ፡ ዕገዛ፬ ፡ ፭ ። ሔኖ፹፪ ፡ ፭) ።

**ሐሳቢ** ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ሰብት) ፤ የሚያስብ ፡ የሚቈጥር ፡ ዐሳቢ ፡ ቈጣሪ ። ሐሳብያነ ፡ ከ ዋክብት ፡ (አቡሻ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ጥር፳) ።

**መሐስብ** ፤ (ብት ፡ ቢን ፡ በት) ፤ ዝኒ ፡ ከ ማሁ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተሐሰበ** ፤ ታሰበ ፡ ተቈጠረ ፡ ተገመገመ ። እለ ፡ ኢይትሐሰቡ ፡ በሐሳበ ፡ ዓመት ። ይትሐሰብ ፡ ሎቱ ፡ ጽድቀ ። ዘከመ ፡ ዝ ፡ እምኢተሐሰበ ፡ ምስለ ፡ ኃጥ ኣን ። ዘኢተወክፈ ፡ ንስሓሁ ፡ ለኃጥእ ፡ ኀጢአተ ፡ ዚ አሁ ፡ ይትሐሰብ ፡ ላዕሌሁ ፡ (ሔኖ፸፭ ፡ ፩ ። ምሳ፲፯ ፡ ፳፰ ። ቄር ፡ ጳላ ። ቀሌ) ።

**ሕሱብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ስብት) ፤ የታሰበ ፡ የተ ቈጠረ ። መስተቃትላን ፡ እለ ፡ ሕሱባን ፡ ውስተ ፡ ሰ ርዌ ፡ (ዮዜና ፡ ፳፰ ፡ ፩) ።

**ሐሳብ** ፤ (ባት ፤ በቁሙ ፡ ዐሳብ ፡ ሥጋት ። (የታ ቡት ፡ ዘፈን) ፡ ያለው ፡ ሊኾን ፡ ያለው ፡ ሊኾን ፡ ዐሳብ ፡ አ ይቀቀው ፡ ጐኔን ፡ ዐሳብ ፡ አይቀቀው ፡ ጐኔን) ። ሒሳብ ፡ ቍጥር ፡ ግምት ፡ የሒሳብ ፡ ሥራ ፡ ስንል ፡ ጥንቈላ ። ሐሳበ ፡ ሄጦ ። በሐሳበ ፡ ሄጥ ። ሰብአ ፡ ሐሳባት ። እመ ፡ ከነ ፡ ተአማኒ ፡ በሐሳበ ፡ ከከብ ። ዘየሐስብ ፡ ሐ ሳባተ ፡ ወልድ ፡ ምስለ ፡ እም ፡ (ግብ፲፱ ፡ ፲፱ ። ዮሴፍ ። አቡሻ ፡ ፩ ። ፋ ፡ ን ፡ ፳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፭) ።

—፤ ልክ ፡ መጠን ፡ ማዕርግ ፡ ሀብት ። ዘሂ ፡ ይትነበይ ፡ በሐሳበ ፡ ሃይማኖቱ ። ዘብዙኅ ፡ ሐሳቡ ፡ (ሮሜ፲፪ ፡ ፮ ። ቭጲጥ ፡ ፫ ፡ ፬) ።

—፤ ፈቃድ ፤ ምላሽ ፡ ቍርጥ ፡ ነገር ። ምስጢሩ ፡ ከሐሳ
ብና ፡ ከቍጥር ፡ ይገባል ። በሐሳብ ፡ ዘእምነበ ፡ እግዚ ።
ያግብእ ፡ ሐሳበ ፡ ለዘሀለወ ፡ (ቂር ። ፩ጴጥ ፡ ፱ ፡ ፳) ። በ
ከመ ፡ ፈንታ ፡ ሐሳብ ፡ ይላል ፡ ምስጢሩ ፡ ልክ ፡ ነው ።
በሐሳበ ፡ መልበስቱ ። በሐሳበ ፡ ምሥዋዕከ ። በሐሳበ ፡
ሤጡ ፡ (ዘፀ፴፰ ፡ ፲፳ ። ፳፱ ፡ ፵፩ ። ዘሌ፳፯ ፡ ፲፯) ።

**ተሓሰበ** ፤ ተሳሰበ ፡ ተቈጣጠረ ፡ ተገማገመ ፡ ተ
መራመረ ። ወሰበ ፡ እንዘ ፡ ተሓስቦቶሙ ። ሰበ ፡ ትትሓ
ሰብ ፡ ምስለ ፡ ሱታፌከ ፡ በእንተ ፡ ተግባርከ ። ወዘሰ ፡
እንዘ ፡ ቦ ፡ ይነሥእ ፡ ምጽዋተ ፡ ሎቱ ፡ ይትሓሰቦ ፡ እ
ግዚ ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፳፬ ። ሢራ፵፪ ፡ ፫ ። ዲድ ፡ ፲፱) ።

**ትሕስብት** ፤ መተሳሰብ ፡ መቈጣጠር ፡ ቍጥ
ጥር ፡ ምርምር ።

**ሐሴበን ፤—ውስጥ ፡ ገጽ ፤—ሀሴበን ።**

(ላ) **ሐሲው ፤ ዎት ፤ (ሐሰወ ፡ የሐሱ ፡ ይ
ሕሱ ። ዕብ ፡ ኪሳህ ። ሱር ፡ ክሳእ ። ዐረ ፡ ከሳ) ፤**
መክደን ፡ ማልበስ ፡ መሰወር ፡ መደበቅ ። ፀሓይ ፡ ብር
ሃኖ ፡ ሐሰወ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲፬) ።

—፤ መክተት ፡ ከኪስ ፡ ከቅማዳ ፡ ከከረጢት ፡ ማግባት ፡
ማሰር ፡ መተብተብ ፡ መጠረፍ ፡ ማከት ። ወሐሰወት ፡
ዝሎ ፡ ንዋያ ፡ ወአጽረታ ፡ ለወለታ ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፭) ።

(ጥ) **ሐስዎ ፤ ዎት ፤ (ሐሰወ ፡ ይሔሱ ፡ የ
ሐሱ ። ሐሰ) ፤** መዋሸት ፤ ሐሰት ፡ መናገር ፡ ዐሎ ፡
ማለት ፡ መሸፈጥ ፡ የተናገሩትን ፡ መለወጥ ፤ መክዳት ፡
መካድ ፡ ማፍረስ ። ሐስዎ ፡ እውነትን ፡ በሐሰት ፡ መለ
ወጥ ፤ ሐቢል ፡ ማን ፡ ያልነበረውን ፡ ፈጥሮ ፡ መናገር ፡
ነው ። ይኄይስ ፡ ሰፊቅ ፡ እምሐስዎ ። ለማነ ፡ እብል ፡
ወኢይሔሱ ። ዘይምሕል ፡ ለቢጹ ፡ ወኢይሔሱ ።
ኢሐሰውኩ ፡ ቃለ ፡ አምላክ ። ሐሰወ ፡ ኪዳኖ ፡ (ሚ
ራ፳ ፡ ፳፭ ። ሮሜ፱ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፲፬ ። ኢዮ፯ ፡ ፲ ። ዮሴፍ) ።
በሐሰወ ፡ ፈንታ ፡ አስተሐሰወ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ዮጊ ፡
ቃልሂ ፡ ከመ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ያስተሐስወዎ ፡ (ቁር ፡ ጸላ) ።

**ሐሳዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ሰውት) ፤**
በቁሙ ፡ የሚዋሽ ፡ ዋሾ ፡ ሐሰተኛ ፡ ከሓዲ ። ሐሳዊ ፡ ው
እቱ ፡ ዘይሔሱ ፡ ዘልፈ ፡ ሰራቂ ፡ ይኄይስ ፡ እምሐ
ሳዊ ። ልሳን ፡ ሐሳዊት ። ሐሳውያን ፡ ነቢያት ። ሐሳው
ያነ ፡ መሲሕ ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፳፫ ። ምሳ፳፯ ፡ ፳፰ ። ማቴ፯ ፡
፲፭ ። ፩ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፰) ።

**አሕሰወ ፤ አሐሰወ** ፤ አሰኘ ፡ አሳበለ ፡ ዐሎ ፡
አሰኘ ፡ ውሸት ፡ አስተማረ ። አሕሰወ ፡ ስምዐ ፡ (አርጋ ፡ ፪) ።

—፤ አስተባበለ ፡ ዋሾ ፡ አደረገ ፡ እውነቱን ፡ ውሸት ፡ እ
ውነተኛውን ፡ ሐሰተኛ ፡ አለ ። አርመመ ፡ ወኢአሐሰ
ውዎ ፡ እስመ ፡ እሙነ ፡ ኮነ ፡ ነገሩ ። መነ ፡ እምእሉ ፡
ታጸድቅ ፡ ወመነ ፡ ታሔሱ ። ኢታሐስውዎ ፡ ለነገረ ፡
ቅዱስ ፡ (ዮሴፍ ። ሱቱ ፡ ዕገዘ፪ ፡ ፳፯ ። ሐዋ፲፬ ፡ ፲፬) ።

**ተሐሰወ** ፤ ተዋሸ ፡ ታበለ ፡ ሐሰት ፡ ኾነ ፡ ተለ
ወጠ ። ኢተሐሰወ ፡ ቃለ ፡ እግዚ ። በዘኢይትሔሰው ፡
ተስፋከ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ነገሩ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ወኢይት
ሔሰው ፡ (ሮሜ፱ ፡ ፯ ። ማኅዘ ። ዮሴፍ) ።

**ሕስው ፤ (ውት ፡ ሱት ፤ ዋን ፡ ዋት) ፤**
የተዋሸ ፡ የታበለ ፡ ውሸት ፡ የኾነ ። ሕስወ ፡ ተናገርከ ።
ይትኔበዩ ፡ ሕስወ ። ሀብት ፡ ሕስው ። ምትሀት ፡ ሕ
ስው ፡ (ኤር፶ ፡ ፪ ። ጥበ፲፬ ፡ ፳፰ ። ምሳ፳፩ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡
መስ፲፭) ።

**ሕሳዌ ፤ (ያት ፡ ውያት) ፤** መዋሸት ፡ ዋሾ ፡
መኾን ። ውሸት ፡ ሐሰት ። በኢሕሳዌ ፡ (አፈ ፡ ተ፱ ። ፍ ፡
ነ ፡ ፳) ።

**ሐሰት** ፤ በቁሙ ፤ ዐሰት ፡ ውሸት ፡ አሉታ ፡ ያወ
ኀታ ፡ ለውጥ ። ኢትኩን ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ። ውሉደ ፡
ሐሰት ። ነቢያተ ፡ ሐሰት ። ሐሰት ፡ ኢይወፅእ ፡ እም
አፉሁ ። ወባሕቱ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ሐሰተ ፡ ይመ
ስሎ ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፲፮ ። ኢሳ፴ ፡ ፱ ። ዕር ፡ ኢሳ፤ ፡ ፲፭ ። ዮ
ዲ፭ ፡ ፭ ። ገድ ፡ ተክ) ።

(ጥ) **ሐሰየ ፤—ደስ ፡ አሰኘ ፤—ሐሥየ ፡ ሐ
ሠየ ።**

(ላ) **ሐስዮ ፤ ዮት ፤ (ሐሰየ ፡ የሐሲ ፡ ይሕሲ) ፤**
ማሸት ፡ ማሻሸት ፡ ማፍተልተል ። መሐሢ ፡ ሥዊተ ፡
ወሐሰዩ ፡ በእደዊሆሙ ፡ ወበልዑ ። ሐሰየ ፡ አዕይን
ቲሁ ። እለ ፡ ይቀጠቅጡ ፡ ወየሐስዩ ፡ ነፍሰ ፡ ወሬዛ ።
ወለእመ ፡ አበየት ፡ ነፍሱ ፡ ሊይሕስዮ ፡ በግማደ ፡ ል
ብሱ ፡ (ሉቃ፮ ፡ ፩ ። ጦቢ፲፩ ፡ ፲፩ ። ኢሳ፲፫ ፡ ፲፰ ። ፊ
ልክ ፡ ፲) ።

—፤ መጣስ ፡ መጠምሰስ ፡ ማበራየት ፡ መርገጥ ፡ መጠ
ቀጠቅ ፡ ማፍረጥረጥ ፡ መጥመቅ ፤ የወይን ፡ የዘይት ፡ ያ
ዝመራ ። ወቦኡ ፡ ወሐሰዩ ፡ እልክቱ ፡ ሠለስቱ ፡ ጸና
ዕት ፡ ማእከለ ፡ ትዕይንቶሙ ፡ ለኢሎፍሊ ። እኮ ፡ በ
መንኰራኵረ ፡ ሠረገላ ፡ ዘየሐስዮዎ ፡ ለከሙን ፡ (፩
ዜና ፡ ፲፩ ፡ ፲፰ ። ኢሳ፳፰ ፡ ፳፯) ።

**ሐሳዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ሰይት) ፤**
የሚያሽ ፡ ዐሻታ ፡ ወጊሻ ፡ አልፊ ።


**አሕሰየ ፤ (ያሐሲ ፡ ያሕሲ) ፤** አሳሸ ፡ አስ
ለፋ ፡ አስረገጠ ። አስበራየ ።

**ተሐስየ** ፤ ታሸ ፡ ለፋ ፡ ተለፋ ፡ ተረገጠ ።

**ሕሱይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሲት) ፤** የታሸ ፡ የ
ለፋ ፡ ልፋ ፡ ለበባሳ ፡ ልዝብ ። ማእሰ ፡ በግዐ ፡ ሕሱይ ፡
(ዘፀ፳፱ ፡ ፳ ። ፳፯ ፡ ፲፬ ። ክብ ፡ ነገ፲፯) ።

**ሕስየት** ፤ ማሸት ፡ መታሸት ፡ አስተሻሸት ፡ ዐሸ
ታት ።

**ሐሴን ፤ (ብ ፡ ሐሳይን ። ዐረ ፡ ሐሲን ፡
ሐሱን) ፤** ውብ ፡ መልክ ፡ መልካም ፡ ዝንጕርጕር ፡ ባ
ለብዙ ፡ ሕብር ፡ የኅርማሬ ፡ የሶራ ፡ የጣዎስ ፡ ዐይነት ፡ ወፍ ፡
ብራብሮ ። በሽን ፡ ያንበጣ ፡ ወገን ፡ ከምድር ፡ የሚፈላ ።
ወይጠፍኦ ፡ ፍጡነ ፡ ከመ ፡ ሐሴን ፡ ዘወፅአ ፡ እም
ግቡ ፡ ወኢይትረከብ ፡ አሠሩ ፡ ወኢይገብእ ፡ ውስተ ፡
ቤቱ ፡ (መቃ ፡ ፲፲) ።



ሐሴን ፡

**ሐሰከ ፤ (ዐረ ፡ ሐሸከ) ፤** ዘነበ ፡ አካፋ ፡ በረደ ፡ ቀዘቀዘ ፡ ዕስከ ፡ ዕሽክ ፡ እትት ፡ አሰኘ ፤ ዝናቡ ፡ ብርዱ ፡ ውሃው ። ዕሽክ ፡ እትት ፡ አለ ፡ ሰውዮው ።

**ሐሰከ ፤ (ካት ፤ አሕሳክ ። ትግሪኛ) ፤** ተምች ፡ የመቅሠፍት ፡ ትል ፡ በገዝናብ ፡ የሚሠርጽ ፡ የሚወስድ ፡ የማር ፡ የቅጠል ፡ የቡቃያ ፡ ያገዳና ፡ ያበባ ፡ እኽል ፡ ጠላት ። (ተረት) ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ ሽንብራ ፡ እሸት ፡ በሽንብራውም ፡ ትል ፡ አሰበት ።

**ሐሲል ፤ ሎት ፤ (ሐስለ ፤ ሐሰለ ፡ የሐስል ፡ ይሕስል ። ዕብ ፡ ሐሳም ። ዐረ ፡ ሐዘመ ፤ ለጕመ) ፤** መለበብ ፡ መሸበብ ፡ በለኮ ፡ መሳብ ። ነሥኣ ፡ ምስሌሁ ፡ ወአጽዐና ፡ ላዕለ ፡ ፈረስ ፤ ወውእቱ ፡ የሐስል ፡ ላቲ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፳) ።

—፤ መሰብሰብ ፡ መከተት ፤ መጣን ፡ መሸከም ፡ መውሰድ ፡ ማንሣት ፡ ያገዘሙራ ። (የገበሬ ፡ ቃል ፤ ሮቢ ፡ ላይ ፡ ሃ ፡ ዳውላ ፡ ባር ፡ ማሽላ ፡ አምርቶ ፡ ማንሣት ፡ ስላቃተው) ፤ ዐምላ ፡ ተው ፡ በምኒልክ ፡ ተነሣ ። ሰብስቦ ፡ መንዳት ፤ ክበረት ፡ ማግባት ፤ ምስጢሩ ፡ ከመከተት ፡ ይገባል ። የሐስሎሙ ፡ ሕፃን ፡ ንኡስ ፡ (ኢሳ፲፩ ፡ ፮) ።


**ሐሳሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ሰልት) ፤** የሚለብብ ፡ ሳቢ ፡ ስብ ሳቢ ፡ ከታች ።

**አሕሰለ ፤** አስለበበ ፤ አሰበሰበ ፡ አስከተተ ፡ አስጫነ ።

**ተሐስለ ፤** ተለበበ ፡ ተሸበበ ፡ ተከተተ ፡ ተሰበሰበ ። በሕሳለ ፡ ንጢአቱ ፡ ዘሉ ፡ ይትሐሰል ፡ (ምሳ፭ ፡ ፳፪) ።

**ሕሱል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ስልት) ፤** የተለበበ ፡ ልቡብ ፡ ስሑብ ።

**ሕሳል ፤ (ላት) ፤** ልባብ ፡ ፋሎ ፡ (ጥባ) ሽባ ፡ ሰኮ ፡ የፈረስ ፡ የበቅሎ ፡ ማስፈያ ፡ መሳቢያ ፡ ገመድ ፡ ጠፍር ። እስ ፡ በሕሳል ፡ ወበልጓም ፡ ይመይጥዎሙ ፡ መላትሒሆሙ ፡ (መዝ ፡ ፴፩) ።



ሕሳል ፡

**ሐስል ፤ (ብ ፡ አሕስል ፤ አሕሳል) ፤** መያዣ ፡ መክተቻ ፡ አቅማዳ ፡ ስልቻ ፤ ዳውላ ፡ ዐይበት ፡ ቅርጫት ፤ ኪስ ፡ ከረጢት ፤ ከክታን ፡ ከፀምር ፡ የሚሠራ ፤ መፍሪያም ፡ ጥቅጥቅ ፡ ጥን ፡ ጠንካራ ። ወአዘዘ ፡ ዮሴፍ ፡ ይምልኡ ፤ አሕስሊሆሙ ፡ ወይደዩ ፡ ሎሙ ፡ እክለ ፡ ወወርቀሙኒ ፡ ውስተ ፡ አሕስሊሆሙ ። ወፈትሐ ፡ ሐስሎ ፡ ወረከበ ፡ ወርቀ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ ሐስሉ ። ሰረቅት ፡ እለ ፡ ይፈትሑ ፡ አሕሳለ ፡ (ዘፍ፵፪ ፡ ፳፭—፳፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፬) ።



ሐስል ፡

**ሐሴን ፤—ዐሸን ፤—ሐስይ ፡ ሐሰየ ።**

**ሐስዐ ፤—በረደ ፤—ኆሚዕ ፡ ኆሥዐ ።**

**ሐሲዕ ፤ ዖት ፤ (ሐስዐ ፡ የሐስዕ ፡ ይሕሳዕ ። ዐረ ፡ ጀዘዐ) ፤** ቀለብ ፡ መቍረጥ ፡ ምግብ ፡ መንማት ፡ መክልክል ፤ ጡት ፡ ማስጣል ።

**ማሕስዕ ፡ ዕት ፤ አው ፡ መሐስዕ ፤ (ብ ፡ መሓስዕ ፡ ዓት) ፤** ጠቦት ፡ ጡት ፡ የተወ ፤ ዓመት ፡ የኾነው ፡ ግልገል ፡ ወጠጤ ። ማሕስዐ ፡ በግዕ ። ማሕስዐ ፡ ጠሊ ። መሐስዐ ፡ በግዕ ፡ አሐዱ ። እምአይቴ ፡ ዘቲ ፡ መሐስዕት ፡ (ዘፍ፳፩ ፡ ፴፰ ። ፳፯ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ። ፯ ፡ ፱ ። ጦቢ፪ ፡ ፲፫) ። መሓስዐ ፡ አባግዕ ። መሓስዐ ፡ አጣሊ ። ሰረሩ ፡ ዴበ ፡ እልኩ ፡ መሓስዕ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፫ ። ሚራ፡፡፡ ፻ ። ማሕ፩ ፡ ፯ ። ሔኖ ፡ ፹፩) ።



መሐስዕ ፡

**ሕሱፍ ፤—ሸካራ ፤—ኆሚፍ ፡ ኆሠፈ ።**

**ሔሴፎት ፤— የጕድፍ ፡ መጣያ ፤—ሀሴፎት ።**

**ሐሰት ፤—ውሸት ፤—ሐስዎ ፡ ሐሰወ ።**

**ሑት ፤—ኮከብ ፤—ሐወተ ።**

**ሔት ፤—ስመ ፡ ፊደል ፤—ሐዩው ፡ ሐይወ ፤ ሐየተ ።**

**ሔትዮት ፤ (ዕብ ፡ ውሂትዊታ ፡ ታው) ፤** ምልክት ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ተ ፡ መስቀላዊ ። ወጸሐፍ ፡ ሔትዮተ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሞሙ ፡ (ሕዝ፱ ፡ ፬) ። ውሂትዊታና ፡ ወጸሐፍ ፡ ፬ ፡ ናቸውና ፤ ታው ፡ ትእምርተ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሔትዮት ፡ ይላል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ እንቁጸሩን ፡ ጥሬ ፡ አይሮንታል ።

**ሐቲት ፤ ቶት ፤ (ሐተ ፤ ሐተተ ፡ የሐ ትት ፡ ይሕትት ፤ ኀሠሠ ። ዕብ ፡ ሐታት ፤ ተ ሰበረ ፤ ፈራ ፡ ደነገጠ ። ሱር ፡ ሐቴት ፤ አስተ ክክለ)** ፤ መመርመር ፡ መፈተን ፤ መላልዮ ፡ መጠየቅ ፡ ማስመስከር ፡ ማናገር ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ መፍረድ ፡ የዳኛ ። ሕትቶሙ ፡ ለአበው ። ኢትሕትት ፡ ዘኢይትከሀለከ ። ኢትሐስ ፡ ዘእንበለ ፡ ትሕትት ። ኢትሕትቶ፤ ፡ ዘእግ ብር ። የሐትት ፡ ኅሊና ፡ እንዘ ፡ ኢይሴአል ። ሐቲተ ፡ ሕትዎ ። ሕቶ ፡ ርእሰክሙ ። ይሕትቶ ፡ ትዕይንት ፡ ማእከለ ፡ ቀታሊ ፡ ወማእከለ ፡ አበ ፡ ደም ፡ (ኢዮ፳ ፡ ፰ ። ሚራ፫ ፡ ፳፩ ። ፲፩ ፡ ፯ ። ዮዲ፰ ፡ ፴፬ ። ቅዳ ፡ ኢ.ጲ. ። ፪ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፰ ። ኪዳ ። ዘኍ፴፭ ፡ ፳፬) ። በሐተተ ፡ ፈንታ ፡ አስተሐተተ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ያስተሐይጽ ፡ ወያስተሐትት ፡ መኑ ፡ እሙንቱ ፡ (ኪዳ) ።

**ሐታቲ ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት)** ፤ የሚመረ ምር ፡ መርማሪ ፡ ጠያቂ ፤ ዳኛ ፡ ባላጋራ ። ለእመ ፡ ሐ ተተ ፡ ሐታቲ ፡ ወይቤ ። ኢይበጽሕዎ ፡ ኅሊናተ ፡ ሐታ ትያን ፡ (አፈ ፡ ድ፳፯ ። ያዕ ፡ ዘእል) ።

**አሕተተ** ፤ አስመረመረ ፡ አስጠየቀ ።

**መሐትት ፤ (ታን ፡ ታት)** ፤ የሚመረምር ፡ የማያስመረምር ፡ መርማሪ ፡ አስመርማሪ ።

**ማሕተት ፤ (ብ ፡ መሓትት)** ፤ ምስክር ፡ አ ማኝ ፡ ነባሪ ፡ ሽማግሌ ። ስምዕ ፡ አሐዱ ፡ ኢይከውን ፡ ማሕተተ ፡ ለአቅትሎ ፡ መንፈስ ። አነ ፡ ማሕተቶሙ ። ከናፍሪከ ፡ ማሕተትከ ። ማሕተቶሙ ፡ ለኃጥኣን ፡ ሞት ። መጽሐፈ ፡ ማሕተትየ ፡ ዝኩ ፡ ኅቱም ። (ዘኍ ፴፭ ፡ ፴ ። ሮሜ፲ ፡ ፪ ። ኢዮ፲፭ ፡ ፮ ፡ ፴፬ ። ኢር፴፱ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪) ። በመሓትት ፡ ፈንታ ፡ ማሕተት ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ዘኢዘለፍዎ ፡ ማሕተት ፡ በገጽ ፡ (ግብ፳፭ ፡ ፲፮) ።

**ተሐተ ፤ (ይትሐተት)** ፤ ተመረመረ ፤ ተጠየቀ ።

**ሕቱት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ትት)** ፤ የተመረ መረ ፡ የተፈተነ ፡ ዕውቅ ።

**ተሓተተ** ፤ ተመራመረ ፡ ተጠያየቀ ።

**ሐተታ** ፤ በቁሙ ፡ ምርምር ፡ አመራመር ፡ ም ርመራ ፡ ጥየቃ ፡ ፍተሻ ። አመ ፡ ዕለተ ፡ ሐተታ ። ጽኑዕ ፡ ሐተታ ፡ የሐትትዎሙ ። አመ ፡ ገብረ ፡ እግዚ ፡ ሐተ ታየ ። ሐቲቶሙ ፡ ሐተታ ፡ ጽኑዐ ፡ (ጥበ፫ ፡ ፲፰ ። ፮ ፡ ፮ ። ኢዮ፲፬ ፡ ፫ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፫ ፡ ፯) ።

# ኀ

**ኀ** ፤ ዘጠነኛ ፡ ፊደል ፡ የሆይ ፡ ሀ ፡ ሦስተኛ ፤ የ ሐውት ፡ ሐ ፡ ኹለተኛ ። ስሙ ፡ ኀርም ፤ ጸሐፍት ፡ ግን ፡ ብዙኃኑ ፡ ይሉታል ። ዘጠነኛነቱም ፡ በመልክ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ጤት ፡ በተራና ፡ በፊደልነት ፡ አይደለም ፡ ሦስተኛና ፡ ኹለተኛነቱም ፡ በድምጥና ፡ በቅርጽ ፡ ባሠራ ረዝ ፡ ነው ። ፀጸ ፡ ፀ ፡ የጸ ፡ ዲቃላ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከባቱ ፡ ከጸደይ ፡ እንዲደረብ ፡ ለብቻው ፡ እንዳይቈጠር ፡ ኀርም ፡ ኀም ፡ የሐ ፡ ዲቃላ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከሐ ፡ ቢደረብ ፡ እንጂ ፡ ለብቻው ፡ አይቈጠርም ፤ እንደ ፡ ኻያ ፡ ኹለቱ ፡ ፊደላት ፡ መደበኛነት ፡ የለውም ። በፊደል ፡ ቍጥር ፡ ግን ፡ ከታው ፡ በኋላ ፡ ሲጣፉ ፡ ኀ ፡ (ሀቀ)፳፫ ፡ ፀ ፡ (ጠቀ)፳፬ ፡ ይባላል ፡ ጸና ፡ ፐም ፡ ከነዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ይገባሉ ። ፳፫ኛነቱም ፡ ኀመሰና ፡ ኀምስት ፡ ኀምሳ ፡ የሚጣፉ ፡ በኀርም ፡ ነውና ፡ ያምስትነት ፡ ምስጢር ፡ ስላለው ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ በመልክና ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ ታስዓይ ፡ ፊደል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ኀ ፡ ከፐ ፡ በኋላ ፡ የ፳፯ ፡ አኃዝ ፡ እየ ኾነ ፡ በታስዕነት ፡ ይጣፋል ፡ ይህም ፡ ጸ ፡ ፳፯ ፡ ፐ ፡ ፳፰ ፡ ኀ ፡ ፳፱ ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ፤ አቡጊዳን ፡ እይ ። በዐረብ ፡ ፊደል ፡ ዮንና ፡ የዐ ፡ ድምፅ ፡ ከሐና ፡ ከጸ ፡ ድምፅ ፡ ልዩ ፡ ሲኾን ፡ መልካቸው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ከነቍጥ ፡ በቀር ፡ መለየ ፡ የለውም ፡ ገኑ ፡ ከኸ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። በግእዝ ፡ ፊደል ፡ ግን ፡ የመልክ ፡ እንጂ ፡ የድምፅ ፡ ልዩነት ፡ የላ ቸውም ፡ በጥሬት ፡ ብቻ ፡ ምስጢርና ፡ ቃል ፡ የቋንቋ ፡ ሞክሼ ፡ ይለያሉ ፤ ልዩነታቸውም ፡ የጠፋ ፡ ከፍሬ ፡ ምና ጦስ ፡ ወዲህ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ የኀርም ፡ ኀ ፡ ድምፅ ፡ እንደዚህ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ፡ ኀኽ ፡ ኍኹ ፡ ኂኺ ፡ (ኃኻ) ፡ ኄኼ ፡ ኅኽ ፡ ኆኾ ፡ ራብዑም ፡ ኃ ፡ እንደ ፡ መ ልኩ ፡ የድምጥና ፡ የምስጢር ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ እና ፡ ይስከፍታል ፤ ዝርዝር ፡ ያሳያል ። ኑኅ ፡ ኑኃ ። ብዝኅ ፡ ብዝኃ ። በዐረብ ፡ ግን ፡ ግእዙ ፡ ኀ ፡ ኸ ፡ ይባላል ። በዕ ብራይስጥም ፡ እንደዚህ ፡ አኹን ፡ እንደ ፡ ጣፍነው ፡ የ ከፍ ፡ ድርብ ፡ ኹኖ ፡ ይነገራል ፤ ዕብራውያን ፡ ከፍን ፡ ነቍጣ ፡ ሲጨምረው ፡ ከ ፡ ነቍጣውን ፡ ትተው ፡ ኸ ፡ ይሉ ታል ፡ መልኩም ፡ ፺ ፡ ዐይንት ፡ ነው ። ባማርኛና ፡ በትግ ሬኛ ፡ ከፍን ፡ እንደ ፡ ኀርም ፡ ኀ ፡ ኸ ፡ ማለት ፡ የዕብራይ ስጥ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የዐረብና ፡ የግእዝ ፡ አይደለም ።

**ኀበ ፤ (ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ)** ፤ ዘንድ ፡ የ ፡ በዝና ፡ ከመ ፡ እየ ፡ ቢ ፡ ይኾናል ። ወኀበ ፡ በዝኀት ፡ ኃጢአት ፡ ህየ ፡ ፈድፈደት ፡ ጸጋሁ ፡ ለእ ግዚ ፡ ኀጢአት ፡ ከበዛች ፡ ዘንድ ። ኀበ ፡ ጸንዐ ፡ ክረ

ያምር ፡ ይበዝኑ ፡ አንቅዕት ፡ (ሮሜ፲ ፡ ፯ ። ዘረፋ) ። የ ፡ ሲኾን ፡ የበታ ፡ ቅጽል ፡ ነው ፡ በቁም ፡ ይኾናል ። ወን ሰግድ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ቆመ ፡ እግረ ፡ እግዚ እ ፡፡ ዘየኀድር ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ኀበ ፡ አልቦ ፡ ዘይቀ ርበ ፡፡ ከመ ፡ ትሀልዉ ፡ ኀበ ፡ ሀሎኩ ፡ አነ ፤ (መዝ ፡ ፻ ፴፩ ። ውዳ ፡ ፫ ። ዮሐ፲፬ ፡ ፫) ። የነቱን ፡ (መኾኑን) ፡ ይ ገጥም ፡ የበታ ፡ ቅጽል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እምና ፡ እንተ ፡ በ ፡ ገብተውም ፡ ሳይገቡም ፡ ይበዘብዙታል ፡ አንዳንድ ፡ ጊ ዜም ፡ አዳማቂ ፡ ኹነው ፡ ይቀራሉ ። በ ፡ ብሔር ፡ እም ኀበ ፡ ይወፅእ ፡ብሩር ፡ የሚወጣበት ። ሲየአምር ፡ እ ንተ ፡ ኀበ ፡ አሐውር ፡ የምኼድበትን ። አልቦ ፡ በኀበ ፡ ሲይከብር ፡ ነቢይ ፡ የማይከብርበት ። በዝና ፡ ከመ ፡ ሲ ኾን ፡ በኀላፊ ፡ ይገባል ፡ (ማር፲፯ ፡ ፬ ። ሉቃ፳፬ ፡ ፬) ። እየና ፡ ሲ ፡ ሲኾን ፡ በደጊም ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ። ቤተ ፡ ሳአል ፡ ኀበ ፡ ኀበ ፡ ይትነሠት ፡ ሖረ ፡ ወቤተ ፡ ዳዊትሰ ፡ ኀበ ፡ ኀበ ፡ ይጸንዕ ፡ እየ ፡ እየ ። ኀበ ፡ ኀበ ፡ ይተነብዕ ፡ ይትቃተል ፡ ኀበ ፡ ኀበ ፡ ይፈርህ ፡ ይጕይይ ፡ ሲ ፡ ሲ ። በዚህ ፡ አፈታት ፡ መንገዱ ፡ የእንዝ ፡ ነውና ፡ በሩቅ ፡ በ ሩቁ ፡ ሲ ፡ ሲ ፡ የተባለው ፡ በቅርብ ፡ በቅርቡ ፡ ስለ ፡ ሳሳ ፡ ይኾናል ። ኀበ ፡ ኀበ ፡ እ(ት)ፈርህ ፡ ስለ ። ኀበ ፡ ኀበ ፡ እ ረክብ ፡ (ኢት) ሳሳ ። በ ፡ ማእዝ ፡ መኾኑ ፡ ሲናበብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሲረባና ፡ ሲዘረዘር ፡ ግን ፡ ነቤየ ፡ (ከ ፡ ክ ፡ ሁ ፡ ሃ) ፡ እየለ ፡ ወደ ፡ ኃምስኛት ፡ ይለወጣል ። ደቂቅ ፡ ሲኾን ፡ ደግሞ ፡ በበታ ፡ በአካል ፡ እየገባ ፡ ዘንድ ፡ አጠገብ ፡ ወደ ፡ ይኾናል ፡ ዘንድና ፡ አጠገብ ፡ በምስጢር ፡ ፩ ፡ ነው ። እ ንተ ፡ ሀለወት ፡ ኀበ ፡ አብ ፡፡ ነበረ ፡ ኀበ ፡ ዐዘቅት ፡፡ አሐ ውር ፡ ኀበ ፡ አብ ፤ (፩ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ዮሐ፬ ፡ ፯ ። ፲፯ ፡ ፲) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ለና ፡ በ ፡ አዳማቂና ፡ በቁም ፡ ቀሪ ፡ ኹነው ፡ ይጋኑታል ። ባሕታውያን ፡ ተመይጥያን ፡ ለ ኀበ ፡ ዓለም ፡ ወደ ። ተሳውያን ፡ ለኀበ ፡ ቃሉ ፡ ቃሉን ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ቃሉ ፡ ያሰኛል ። ይሠየም ፡ ለኀበ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ወደግዜር ፡ ለሚደርስ ፡ ነገር ። ብዕል ፡ ዘይትዐቀብ ፡ በኀበ ፡ ዘአጥረየ ፡ ዘንድ ። ሠረገላ ፡ በ ኀበ ፡ ይጼዐን ፡ አዳማቂ ፡ (ፊልክ ፡ ፩ ። ፪ ። ዕብ፩ ፡ ፩ ። መክ፭ ፡ ፲፪ ። ሐዋ፳፫ ፡ ፪) ። ዳግመኛም ፡ እስከ ፡ እም ቅድም ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ለኀበ ፡ በኀበ ፡ ይላል ፡ የመ ላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። መርሐ ፡ ለኀበ ፡ ክርስቶስ ፡፡ ኢ ትንሥኡ ፡ ቤዛ ፡ በኀበ ፡ ቀታሊ ፡፡ ዘበኀበ ፡ ሰብእ ፡ ዐ ቢይ ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡ ትሑት ፡ ወርኩስ ፡ (ገላ፫ ፡ ፳፬ ። ዘኍ፴፭ ፡ ፴፩ ። ሉቃ፲፮ ፡ ፲፭) ። ዕር፲፱ ፡ ቀ፡ዌ ፡ ተመልከት ።

**ነቢእ ፤ አት ፤ (ነብአ ፡ የነብእ ፡ ይነብእ ፤ ከበተ ። ዕብ ፡ ሐብእ ፤ ሐበሀ ፤ ታብ ። ዐረ ፡ ነብ) ፤** ማባት ፡ መሰወር ፡ መደበቅ ፡ መሸሸግ ፡ እንዳይታይና ፡ እንዳይገኝ ፡ እንዳይታወቅ ፡ ማድረግ ፡ መሸጕጥ ፡ መቅ በር ። እግዚ ፡ ነብኦ ፡ ለሔኖክ ፡፡ ነብአ ፡ ርእሶ ፡፡ ነ ብአ ፡ ለመለኮቱ ፡፡ ነብአ ፡ እደሁ ፡ ሀካይ ፡ ውስተ ፡ ሕ ፅኑ ፡፡ ነብእሙ ፡ ነቡረ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ (ሚሬ፹፬ ፡ ፲፯ ። ውዳ ፡ ፯ ። ድጓ ። ምሳ፳፮ ፡ ፲፭ ። ኢዮ፵ ፡ ፰) ። ከ በተንና ፡ ሰወረን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ።

**ነብኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤** የሚያባ ፡ የሚሸሽግ ፡ ሸሻጊ ፡ ታዳጊ ። መንጦላዕት ፡ ነባኢት ፡ መ ለኮት ፡ (ቅዳ) ።

**አነብአ ፤** አሳባ ፡ አስደበቀ ፡ አስወረ ።

**ተነብአ ፤** ታባ ፡ ተሸሸገ ፡ ተደበቀ ፡ ተሰወረ ፡ ራቀ ፡ ረቀቀ ። ተኀብኡ ፡ ውስተ ፡ ግበበ ፡ ምድር ፡፡ ተ ነቢአሙ ፡ ታሕተ ፡ ፆም ፡፡ ተኀብእት ፡ እምአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡፡ አልቦ ፡ ምንትኒ ፡ ዘይትኀባእ ፡ እምኔሁ ፡ (ኢ ሳ፪ ፡ ፲ ። ኩፋ ፡ ፴፬ ። ኢዮ፳፰ ፡ ፳፩ ። ፴፬ ፡ ፳፩) ።

**ነቡእ ፤ (ኣን ፡ ኢት ፡ ብእት) ፤** በቁሙ ፡ የ ታባ ፡ የተሸሸገ ፡ ሽሽግ ፡ ድብቅ ፡ ስውር ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ። መዝገብ ፡ ነቡእ ፡ ወክቡት ፡፡ ነቡእ ፡ እምዕጓለ ፡ መ ሕያው ፡፡ ምእመናን ፡ ነቡኣን ፡ ትምህርተ ፡ ነቡኣት ፡፡ በእይ ፡ ነብእት ፡፡ በዐውሎ ፡ ነቡእ ፤ (ዮሴፍ ። ሚሬ ፲፯ ፡ ፬ ። ኪዳ ። ዘፀ፲፯ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፹) ።

**ነቡእዊ ፤** የውስጥ ፡ የልቡና ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ። ነሲና ፡ ነቡእዊት ፡ (ፊልክ ፡ ፶፰) ።

**ነብእት ፤** ማባት ፡ መታባት ፡ ሽሽጋ ፡ ድብቃ ። ከመ ፡ ኢይትከሀሎ ፡ ነብእተ ፡ አበሳ ፡፡ በአሎ ፡ ነብእተ ፡ ሀገር ፡ (ጥበ፲ ፡ ፳ ። ዮሴፍ) ።

**ምነባእ ፤ (ኣት) ፤** ማቢያ ፡ መታቢያ ፡ (ላ ፡ ጥ) መሸሸጊያ ፡ መደበቂያ ፡ መሰወሪያ ። ወሰወረኒ ፡ በምነ ባእ ፡ ጽላሎቱ ፡፡ ከመ ፡ ያንብራ ፡ ውስተ ፡ ምነባእ ፡ (መዝ ፡ ፳፮ ። ሉቃ፲፩ ፡ ፴፫ ። ፪ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱ ። ሔኖ) ።

**ነበበ ፤—ሰደበ ፤—ሀቢብ ፡ ሀበበ ።**

**ነበበ ፤—ወደደ ፤—ሐቢብ ፡ ሐበበ ።**

**ነበበ ፤ (ሐንበበ) ፤** ዐፀ ፡ ረገጠ ፡ ጠመቀ ፡ የ ወይን ፡ የዘይት ፡ ኩደንና ፡ ዐጸረን ፡ እይ ።

**ማነበብ ፡ ት ፤ (ታት ። መኀብብ) ፤** የወ ይን ፡ መርገጫ ፡ ምክያድ ፡ ምዕጻር ። ወይኒ ፡ ማነበብ ትከ ፡፡ በእንተ ፡ ማነበብት ፡ (ምሳ፫ ፡ ፲ ። መዝ ፡ ፰) ።

**ነቢዝ ፤ ዘት ፤ (ነበዘ ፡ የነብዝ ፡ ይነ ብዝ ። ዐረ ፡ ነ ፡ ኸበዘ) ፤** ማበዝ ፡ መጋገር ፡ ሊጥን ፡ ወደ ፡ እቶን ፡ ማግባት ፡ በምጣድ ፡ ላይ ፡ ማፍሰስ ፡ ማብ ሰል ። ኀበዙ ፡ ኀሪጸሙ ፡፡ እቶን ፡ ዘአንደዱ ፡ ለኀቢዘ ፡ ኅብዝት ፡፡ ረበየ ፡ ሄሮድስ ፡ ሰብአ ፡ ብዙኃን ፡ ለኀቢዘ ፡ ኅብዝት ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይኅብዙ ፡ ወትረ ፡ (ዘፀ ፲፪ ፡ ፴፱ ። ሆሴ፯ ፡ ፬ ። ዮሴፍ) ።

**ነባዚ ፤ (ዚት ፡ ዝያን ፡ ያት ፡ በዝት) ፤** የሚያበዝ ፡ ዐበዛ ፡ ጋጋሪ ፡ ሊቀ ፡ ኀባዝያን ፡ (ዘፍ፵ ፡ ፩) ።

**አነበዘ ፤** አሳበዘ ፡ አስጋገረ ፡ ዐበዛ ፡ አደረገ ።

**ተነብዘ ፤** ታበዘ ፡ ተጋገረ ፡ በሰለ ፡ ተዘጋጀ ። ኅ ብዝት ፡ ዘተነብዘት ፡ በዕለቱ ፡ (፩ ፡ መ ፡ ፳፩ ፡ ፮) ።

**ነቡዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ብዝት) ፤** የታበዘ ፡ የተ ጋገረ ፡ ግግር ።

**ኅብዝ ፤ (ዛት ፤ ኅበውዝ ። ኅብ(ስ)ዝት ፤ ታት ። ዐረ ፡ ኍ ፡ ኹብዝ ፤ ዛት) ፤** እንጀራ ፡ ዳቦ ፡

ማቢታ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በኀብዝና ፡ በኅብዝት ፡ ፈንታ ፡ ኅብስት ፡ ይላል ፤ ስ ፡ በልማድና ፡ በጸሐፊ ፡ ስሕተት ፡ የገባ ፡ ነው ፤ ደነባ ፡ ገነባ ፡ ብሎ ፡ ደምብ ፡ ግምብ ፡ እንደ ፡ ማለት ። ኅብስተ ፡ ሰገም ። ኅብስተ ፡ ስንዳሴ ። ኅብስተ ፡ በረከት ። ኅባውዝ ፡ ቍርባን ፡ (መሰ፯ ፡ ፲፫ ። ዮዲ፲ ፡ ፭ ። ሲኖ ደ ። ማቴ፲፱ ፡ ፱) ።

**ማኅበዝ ፤ ምኅባዝ ፤** መጋገሪያ ፤ እቶን ፡ ማድ ፡ ቤት ። ጢስ ፡ ማኅበዝ ። ቦ ፡ ዘይትቀነይ ፡ ምድረ ፡ ወየሐርስ ፤ ቦ ፡ ዘገነት ፡ ወቦ ፡ ዘዐጸደ ፡ ሐምል ፤ ቦ ፡ ዘይጸርብ ፡ ወቦ ፡ ዘይገልፍ ፡ ወቦ ፡ ዘምኅባዝ ፤ አልቦ ፡ ዘይትናገር ፡ ውስተ ፡ ምኅባዝ ፡ እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ኅብዝተ ፡ (አዋል ። ሥር ፡ ጸሎ) ። በምኅባዝ ፡ ፈንታ ፡ ምኅማዝ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ኢውዕየተ ፡ ቀዋማ ፡ ማእከለ ፡ ውዑይ ፡ ወርሱን ፡ ምኅማዝ ፡ (ስንክ ፡ ግንቿ) ።

**ኅብዝ ፤ አው ፡ ኅንባዝ ፤** አጣብቂኝ ፡ የሥቃይ ፡ መሣሪያ ፤ እንደ ፡ ወፍጮና ፡ እንደ ፡ ምጣድ ፡ ያለ ፡ ሰባውያን ፡ ሰማዕታትን ፡ የሚሣቀዩበት ። አዘዘ ፡ ያዕርግዎሙ ፡ መልዕልተ ፡ ኅንባዝ ፡ እስከ ፡ ይውሕዝ ፡ ደምሙ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። አዘዘ ፡ ያዕርግዎ ፡ ላዕለ ፡ ኅንባዝ ፡ ወየዐጽርዎ ፡ ሥጋሁ ፡ እስከ ፡ ውሕዘ ፡ ደሙ ፡ ከመ ፡ ማይ ። አዘዘ ፡ ይስቅልዎ ፡ ዲበ ፡ ኅንባዝ ፡ ወየዐጽርዎ ፡ በመንኩራኵረ ፡ እሳት ፡ ዘትጼጌን ። ወሰበሮ ፡ መልአክ ፡ ለኅንባዝ ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፲፰ ። ግን፲፱ ። ሠኔ፱ ፡ ፳) ። ን ፡ ስርጉጽ ፡ ኹኖ ፡ ገብቷል ፤ የግእዝ ፡ መላሾች ፡ ዐረቡ ፡ ሐብ ፡ ሕቡብ ፡ ያለውን ፡ ሕባብ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሕንባብ ፡ እንዳሉት ፡ ኅባዝንም ፡ ኅንባዝ ፡ ብለውታል ።

**ኅብጠ ፤—ዐበጠ ፤—ሐቢጥ ፡ ሐብጠ ።**

**ኅበየ ፤—ጠበቀ ፤—ሐብይ ፡ ሐበየ ።**

**ኅብለ ፤—ዐበለ ፤—ሐቢል ፡ ሐብለ ።**

**ኀብሎ ፤ ሎት ፤ (ኀበለ ፡ ይኄብል ፡ የኅብል ። ዐረ ፡ ኅቢለ) ፤** መክፋት ፡ መጨከን ፤ ማበድ ፡ መወግሸት ፤ መድፈር ፡ አለማፈር ፤ የማይገባውን ፡ መናገር ፡ መሥራት ፡ ይገባኛል ፡ ማለት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በኀበለ ፡ ፈንታ ፡ ተኀበለ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። እፎ ፡ እንከ ፡ ተኀበለ ፡ ልብከ ። ተኀበሉ ፡ አግብርት ፡ ወወረዱ ፡ ላዕሌነ ። ደንገፁ ፡ ፋርስ ፡ እምተኀብሎታ ። ቀሲስ ፡ ዘተሰዐረ ፡ በርትዕ ፡ በእንተ ፡ ኀጢአቱ ፡ ወእምዝ ፡ ተኀበለ ፡ ላዕለ ፡ ግብረ ፡ መልእክት ። ዘተኀበለ ፡ ከመ ፡ ይውስብ ፡ ራብዕየ ፡ (ኢዮ፲፭ ፡ ፲፪ ። ዮዲ፲፱ ፡ ፲፫ ። ፲፭ ፡ ፲ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፭ ፡ ፲) ።

**ኀባሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤** ደፋር ፡ ጨካኝ ። ደፋሪ ፡ ወኀባሊ ። እምሰብእ ፡ ዐማፂ ፡ ወኀባሊ ፡ ባልሕነ ፡ (ቄድር ። ሲጦን) ።

**አኅበለ ፤ አስተኀበለ ፤** አስደፈረ ፡ አስጨከነ ፤ በሉ ፡ በሱ ፡ አለ ።

**መኅብል ፤ መስተኀብል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤** የሚያስደፍር ፡ የሚያስጨክን ። ምስለ ፡ መስተኀብ(ይ)ል ፡ ኢትኅበር ፡ መንገደ ፡ (ሢራ ፡ ፰ ፡ ፲፭) ።

**ተኀበለ ፤** ተደፈረ ፡ ተናቀ ፡ ተጠቃ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ አድራጊ ፡ ነው ። ተኀባሊ ፡ (አፈ ፡ ተ፱) ።

**ኅቡል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ብልት) ፤** የተደፈረ ፡ የተናቀ ፡ ጥቁ ። ክፉ ፡ እብድ ፡ ደፋር ፡ ጨካኝ ። ኅቡላን ፡ ወዝሉፋን ፡ (፪ጴጥ ፡ ፱ ፡ ፲) ።

**ኅብል ፤** ድፍረት ፡ ክፋት ፡ ጭካኔ ።

**ተኃበለ ፤** ተደፋፈረ ፡ ተጨካከነ ።

**አስተኃበለ ፤** አዳፈረ ፡ አደፋፈረ ፤ አጨካከነ ።

**መስተኃብል ፤** የሚያደፋፍር ፤ አጨካካኝ ።

**ኅቢን ፤ ኖት ፤ (ኅበነ ፡ የኅብን ፡ ይኅብን ። ዐረ ፡ ኅበነ) ፤** መሸጕጥ ፡ መክተት ፤ ክኪስ ፡ ከሴድርያ ፡ ማግባት ፤ የሰዓት ፤ የገንዘብ ፡ የማረሚያ ። ማጥለቅ ፡ መልበስ ፤ ሰውነትን ፡ በቀሚስ ፡ መክተት ። ራስን ፡ ማሰር ፤ መጠምጠም ።

(ጥ) **ኅባኔ ፤ (ኔያት) ፤** ቀሚስ ፤ ያንገት ፡ የደረት ፡ ልብስ ፤ የቀሚስ ፡ ተካሪስ ። ኅባኔ ፡ ፀፈረ ፡ ውስተ ፡ ክሣድየ ። ይኩን ፡ መልበሱ ፡ ለካህን ፡ ርሒብ ፡ ዘእንበለ ፡ ኅባኔ ። ጽሕሙ ፡ ከነ ፤ ፀዊን ፡ ወይበጽሕ ፡ እስከ ፡ ኅባኔሁ ፤ ትዋት ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፲፰ ። ሲኖ ደ ። ስንክ ፡ ግን፲፫ ። መዝ ፡ ፻፴፪) ። ልብስ ፡ ምንኩስና ፤ እንደ ፡ ሞጣሕት ፡ ያለ ፡ ባንገት ፡ ተጠልቆ ፡ ወደ ፡ ፊትና ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ የሚወርድ ። የራስ ፡ ማሰሪያ ፤ ጥምጥም ፡ መጠምጠሚያ ። የልብስ ፡ ዘርፍ ፤ የኩታ ፡ ጫፍ ፤ ጥለቱ ፡ ዕዳያቱ ፤ ወይም ፡ ጥልፍ ፡ ዝምዝማት ።

**ኅብር ፤—ቀለም ፤ ዐይነት ፤—ሐብሮ ፡ ሐበረ ።**

**ኅቢር ፤ ሮት ፤ (ኀበረ ፤ ኅብረ ፡ የኅብር ፡ ይኅበር ። ዕብ ፡ ሓቤር ። ሱር ፡ ሓባር) ፤** ማበር ፤ ማኄር ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ መግጠም ፡ መዋደድ ፡ መስማማት ፤ መሬጠር ፡ ዐብሮ ፡ መቈጠር ፤ ፩ ፡ ልብ ፡ ፩ ፡ ሐሳብ ፡ መኾን ። ኅበሩ ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ። ወአሰርኂ ፡ ኅብረ ፡ ምስሌሆሙ ። ኢትኅበር ፡ ምስለ ፡ ኃጥኣን ፡ ለእመ ፡ በዝኁ ። ሀበነ ፡ ንኅበር ፡ በዘዚኣከ ፡ መንፈስ ። እለ ፡ የኅብሩ ፡ በሕጋ ፡ ለቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ድጓ ። መዝ ፡ ፹፱ ። ሢራ፯ ፡ ፲፱ ። ቅዳ ። ቀሌ) ።

**ኅባሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤** የሚያብር ፡ ዐባሪ ፡ ኄረኛ ፡ ዐድመኛ ፤ መሳይ ።

**አኅበረ ፤** አሳበረ ፤ አስተባበረ ፤ አጋጠመ ፡ አንድ ፡ አደረገ ፤ አስማማ ። ሹሎ ፡ አኅቢሆሙ ፡ አኅበሩ ፡ ምስሌሆሙ ። ዘአኅበረነ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ሐዊረ ። አኅብር ፡ ሥቃተ ፡ መኑ ፡ ዘያኅብሮ ፡ ለክርስቶስ ፡ ምስለ ፡ ቤልሖር ፡ (ዕዝ፳ ፡ ፫ ። ዘኍ፳ ፡ ፲፩ ። ፪ቆሮ፮ ፡ ፲፭ ። ፪ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፭) ።

—፤ አማሰለ ፡ አዋሐደ ። አንብሪዮ ፡ እንዲል ፡ (ትግሬ) ።

**ተኀበረ ፤** ተባበረ ፡ ተንባበረ ፡ ተማፈረ ፡ ተጨማመረ ። ኢይትኃበር ፡ ውስተ ፡ ማኅበርሙ ፡ ዘደም ።

ወኢይትኃበር ፡ ምስለ ፡ ኀሩያኒሆሙ ። ምስለ ፡ ጻድቃን ፡ ኢይትኃበር ። ይከልእሙ ፡ እምዐቂበ ፡ ልብ ፡ ተኃብሮቶሙ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ ወተናግሮቶሙ ፡ ምስሌሆሙ ። ተኃባሬ ፡ ውስተ ፡ ግዕዙ ፡ ለቅዱስ ፡ (መገ ፡ ፲፫ ። ፺፱ ። ምሳ ፡ ፴፪ ። ፊልክ ፡ ፲፭ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

**ኀቡር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ብርት) ፤** ያበረ ፡ የተባበረ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፤ እኩያ ፡ ዐብሮ ፡ አደግ ፡ ባል ንጀራ ። ኀቡር ፡ ምስሌነ ፡ በዛቲ ፡ ጸጋ ። ኀቡረ ፡ ህላዌ ። ኀቡረ ፡ መንበር ። ኀቡረ ፡ ካህናየ ። ኀቡራነ ፡ ግዕዝ ፡ (ቄር ፡ ጸላ ። ተረ ። ስንክ ፡ ሚያዝ፳፰) ።

**ኀቡረ ፤ (ደቂቅ ፡ አግባብ) ፤** ዐብሮ ፡ አንድ ፡ ኹኖ ፤ ባንድነት ፡ አንድጋ ። ዘበልዐ ፡ ኀቡረ ፡ ይመውት ፡ ኀቡረ ። ምስሌሆሙ ፡ ኀቡረ ። ሶበ ፡ ይሄልዉ ፡ አኃው ፡ ኀቡረ ። ኢታድርግ ፡ ኀቡረ ፡ (አዋል ። መገ ፡ ፪ ። ፻፴፪ ። ሚያ ፡ ፫) ።

**ኀብረት ፤ (ታት) ፤** በቁሙ ፤ አንድነት ፤ ማበር ፡ መተባበር ፡ አንድ ፡ መኾን ፡ መስማማት ። ኀብረተ ፡ ህላዌ ። ኀብረተ ፡ ሥላሴ ። ኀብረተ ፡ ቤማ ። ኀብረተ ፡ ቃል ። ኢይፈቅዱ ፡ ኀብረተ ፡ አበዊሆሙ ፡ (ቄር ፡ ጸላ ። አርጋ ። አዋል ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬) ።

**ኁባሬ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ። ድማሬ ፡ ወኁባሬ ፡ (ቅዳ) ።

**ኀብር ፤ (ራት) ፤** ወገን ፡ ክፍል ፡ ዳርቻ ፡ የቦታ ፡ የሰፈር ። ውስተ ፡ አሕዱ ፡ ኀብር ፡ እምነ ፡ ገራህቱ ። ውስተ ፡ አሐዱ ፡ ኀብረ ፡ ሀገር ። ኀብረ ፡ ቢድው ። ኀብር ፡ ዘባሕረ ፡ ኪኔሬት ። ኀብር ፡ ዘደብረ ፡ ኤፍሬም ። ቁም ፡ መንገለ ፡ የማን ፡ አሐደ ፡ ኀብረ ፡ (ሩት፪ ፡ ፫ ። ሕዝ ፡ ፱ ፡ ፳፮ ። ዘኍ፴፫ ፡ ፺ ። ኢያ፲፫ ፡ ፳፯ ። መሳ፲፱ ፡ ፭ ። ሉቃ ፡ ዕገ፪ ፡ ፺፬) ።

**ማኅበር ፤ (ራን) ፤** በቁሙ ፤ አንድነት ፡ ጉባኤ ፡ ሸንጎ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ሥርዐተ ፡ ማኅበር ። ዕቀብ ፡ ማኅበረነ ። ማኅበሮሙ ፡ ለነቢያት ። ማኅበረ ፡ ሕዝብ ። ማኅበረ ፡ ሠለስቱ ፡ አስማት ፡ (ስንክ ፡ መስ፳፬ ። ቅዳ ። ሕዝ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። ኤር፴፫ ፡ ፲፯ ። አርጋ) ።

—፤ ወገን ፡ ነገድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ጭፍራ ፤ ሰራዊት ። ሰራዊተ ፡ ገብርኤል ፡ በበ ፡ ማኅበሮሙ ። ዳታን ፡ ወአቤሮን ፡ ወማኅበራኒሆሙ ። ማኅበሩ ፡ ለዲዮቅልጥያኖስ ፡ (ቅዳ ፡ ያዕ ። ፈ ፡ መ ፡ ፤ ፡ ፤ ። ስንክ ፡ ሐም፳) ።

**ማኅበራዊ ፤** የማኅበር ፡ ማኅበረተኛ ፡ ማኅበርነት ፡ ያለው ። አኃው ፡ ማኅበራውያን ፤ መነኮሳት ፡ ማኅበራውያን ፡ (ሥር ፡ ጳኰ) ።

**አማኅበረ ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ግ) ፤** ሰበሰበ ፡ ማኅበር ፡ ሠራ ፡ ጉባኤ ፡ አደረገ ፡ ሸንጎ ። ዘአፍጠንክሙ ፡ ለተጋብኦ ፡ ወለአማኅብሮ ። ኢያማኅበረታ ፡ አባ ፡ ረበየታ ፡ ለባሕቲታ ፡ (ስንክ ፡ ኀዳ፲ ። አዋል) ።

**ማኅበርት ፤ (ታት) ፤** ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ንብብር ። መኑ ፡ ይበውእ ፡ ውስተ ፡ ማኅበርተ ፡ እንግድዓሁ ፡ (ኢዮ፵፩ ፡ ፬) ።

—፤ የልብስ ፡ መጋጠሚያ ፤ ስፌት ፡ ዝራር ፡ ተካሪስ ። ወውስተ ፡ ክልኤሆን ፡ ማኅበርቱ ፡ (ዘፀ፴፮ ፡ ፳፩) ።

**ኀብስት ፤—የተጋገረች ፤ እንጀራ ፤—ኀቢዝ ፡ ኀበዘ ።**

**ኀጕል ፤—ጥፋት ፤—ሀጕል ፡ ሀጕለ ።**

**ኀድአ ፤—ጸጥ ፡ አለ ፤—ሀዲአ ፡ ሀድአ ።**

**ኀዲግ ፤ ጎት ፤ (ኀደግ ፡ የኀድግ ፡ ይኅድግ ። ዕብ ፡ ሐዳል ፤ ዐዛብ) ፤** መተው ፡ መጣል ፡ ይቅር ፡ ማለት ፤ መፍታት ፡ መልቀቅ ፤ ማራቅ ። ሰበቀን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ለምንት ፡ ኀደገኒ ። ኀድግ ፡ ለነ ፡ አበሳነ ። ዘሰ ፡ ዘየኀድግ ፡ ብእሲቶ ። አኀዝ ፡ ወኢትኅድጋ ። ኢትኅድግ ፡ ምሕረተከ ፡ እምነ ፡ ቤትየ ፡ (መገ ፡ ፳፩ ። ማቴ፳ ፡ ፲፪ ። ሚራ፯ ፡ ፳፯) ።

—፤ በቁሙ ፡ ማደግ ፡ ጡትን ፡ ልጅነትን ፡ መተው ። ደገገን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ልህቀ ፡ ብሎ ፡ አደገ ፡ ማለት ፡ በማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ኀዳጊ ፤ (ጊት ፡ ግያን ፡ ያት) ፤** የሚተው ፡ ይቅር ፡ ባይ ። ከነ ፡ ተሐራሚ ፡ ወከነ ፡ ኀዳጌ ። ክርስቶስ ፡ ኀዳጌ ፡ ኀጢአት ፡ (ስንክ ፡ የካ፳፭ ። ቄር ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**አኅደገ ፤** አስተወ ፡ አስጣለ ፤ ታደገ ፡ አዳነ ፤ አፋታ ። አኅደጉነ ፡ ዘንተ ፡ አሠረ ። መኑ ፡ ያኅድገነ ፡ ፍቅሮ ፡ ለክርስቶስ ። ከመ ፡ ታኅድጎ ፡ ለምታ ፡ እምኢደ ፡ ዘባጢ ። ሰአሰቶ ፡ ለእኁሃ ፡ ከመ ፡ ያኅድጋ ፡ እምታ ፡ ወአኅደጋ ፡ (ኢሳ፴ ፡ ፲፭ ። ሮሜ፰ ፡ ፴፭ ፡ ፴፰ ። ዘዳ፳፭ ፡ ፲፩ ። ዮሴፍ) ።

**ተኀድገ ፤** ተተወ ፡ ተጣለ ፤ ተፈታ ፡ ተለቀቀ ፤ ቀረ ፡ ኖረ ፤ ተከለከለ ። ተኀድገ ፡ ይሁዳ ። አህጉር ፡ እለ ፡ ተኀድጋ ። ብእሲት ፡ ዘተኀድገት ፡ በዝሙት ። ተኀድጉ ፡ ለይጣናት ፡ ባዕሌነ ። ኢይትኀደግ ፡ ዝየ ፡ እብን ፡ ዲበ ፡ እብን ። ኢንትኀደግ ፡ እምአብአ ፡ ቍርባን ፡ (ሚል፪ ፡ ፲፭ ። ሕዝ፴፯ ፡ ፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፲፯ ። ፊልክ ፡ ፺፯ ። ማቴ፳፬ ፡ ፪ ። ዘኍ፱ ፡ ፯) ።

**ኀዱግ ፤ (ጋን ፡ ጋት ፡ ድግት) ፤** የተተወ ፡ የተሰረየ ፡ የተፈታ ፡ የተለቀቀ ፤ ልቅ ፡ ስድ ። ኅጢአቲሃ ፡ ኀድግት ። ብእሲት ፡ ኀድግት ። ወዘሰ ፡ ኀድግተ ፡ አውሰበ ፡ (ፊልክ ፡ ፴፰ ። ኢሳ፶፬ ፡ ፮ ። ማቴ፭ ፡ ፴፪) ። ኀዱግ ፡ ስኩር ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ኀዳግ ፡ ይባል ፤ አያስኝም ፡ (መገ ፡ ፸፯ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፮) ።

**ኀድገት ፤ (ታት) ፤** (ባ ፡ ጥ) መተው ፡ መጣል ፡ መፍታት ፡ መፈታት ፤ አፈታት ፤ ስረየት ፡ ስሬት ። የሥራ ፤ የቤት ፡ የኀጢአት ። ከመ ፡ ትጸውዕ ፡ ኀድገተ ። ዓመተ ፡ ኀድገት ። በእንተ ፡ ክሊአ ፡ ኀድገተ ፡ ብእሲት ። ኀድገተ ፡ አበሳ ፡ (ኤርም፳ ፡ ፰ ። ዘሌዋ፳ ፡ ፲፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ። ቅዳ) ። በኀድገት ፡ ፈንታ ፡ ኀዳጋት ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወገብረ ፡ ኀዳጋቲሃ ፡ ኵሎ ፡ ደወለ ፡ መንግሥቱ ፡ (አስቴ፪ ፡ ፲፰) ። በሚገዛው ፡ አገር ፡ ላለው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ዕረፍት ፡ ነጻነት ፡ ሰጠ ፡ ግብር ፡ አቀለለ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ኀዳግ ፤ (ጋት) ፤** በቁሙ ፤ የመጽሐፍ ፤ እግር ፤ ከቀለሙ ፤ በታች ፤ እጅ ፤ የማያርፍበት ፤ ባዶ ፤ ብራና ፤ ስፋቱ ፤ ከአርእስትና ፤ ከገጽ ፤ ከማልፀት ፤ የሚበልጥ ። ሥርው ፤ ጥንት ። ንግባእኬ ፤ ኀበ ፤ ኀዳግ ፤ ነገር ፤ (መጽ ፤ ምስ) ።

**ኀድጋን ፤ ኀድግት ፤** ፍች ፤ ልቅ ፤ የባልና ፤ የሚስት ፤ መለያየት ፤ የጋብቻቸው ፤ ውል ፤ መፍረስ ። መጽሐፍ ፤ ግን ፤ ኀድጋን ፤ ግት ፤ በማለት ፤ ፈንታ ፤ ኀዳጋት ፤ ይላል ፤ የተሳሳተ ፤ ነው ። መጽሐፈ ፤ ኀዳጋት ፤ (ዘዳ፳፬ ፤ ፩ ። ኢሳ፶ ፤ ፩ ። ማቴ፭ ፤ ፴፩ ። ማር፲ ፤ ፬) ። ፍልጣኑን ፤ እዩ ፤ የዚህ ፤ ጎር ፤ ነው ።

**ተኃደገ ፤** ተፋታ ፤ ተላቀቀ ፤ ተለያየ ። ብእሲት ፤ ኢትትኃደግ ፤ ምስለ ፤ ምታ ። ኢትፍቅድ ፤ ተኃድጎ ፤ ምስሌሃ ። ኢያብዝኁ ፤ ተኃድጎ ፤ ምስለ ፤ አንስቲያሆሙ ፤ (፩ቆሮ ፤ ፯ ፤ ፲ ፤ ፳፯ ። ቀሌ) ።

**አስተኃደገ ፤** አፋታ ፤ አላቀቀ ፤ አለያየ ፤ ገላገለ ። ተባእሱ ፤ ክልኤሆሙ ፤ ወአልቦ ፤ ዘያስተኃድጎሙ ፤ በማእከሎሙ ፤ (ዘፀ፲ ፤ ፲፬ ፤ ፯) ።

**ኀዳጥ ፤—ጥቂት ፤—ኅጣጥ ፤ ኅጠ ፤ ኅጠጠ ።**

**ኀደየ ፤ አበሰለ ፤—ሀድየ ፤ ሀደየ ።**

**ኀደመ ፤—አንቀላፋ ፤—ሀዲም ፤ ሀደመ ።**

**ኀደመ ፤—ተረተ ፤—ሐድሞ ፤ ሐደመ ።**

**ኀዳፍ ፤—ማኸራት ፤—ሐዳፍ ።**

(ጥ) **ኀድፎ ፤ ፎት ፤ (ኀደፈ ፤ ይኅድፍ ፤ የኅድፍ ። ቀ(ደ)ዘፈ) ፤** መቅዘፍ ፤ ባሕርን ፤ በትርክዝ ፤ መክፈል ፤ መሠንጠቅ ፤ ታንኳን ፤ መርከብን ፤ መምራት ፤ ማስኬድ ፤ ማዝገዝ ፤ መጠበቅ ፤ እንዳይሰጥም ። ከመ ፤ ዘየኀድፍ ፤ ውስተ ፤ ብዙኅ ፤ ሞገድ ። ኀደፈት ፤ በንዋየ ፤ ዕፀ ፤ ምኑን ። ኀድፈኒ ፤ እማዕበለ ፤ ኀጢአት ፤ ዘይኀድፎ ፤ ለዓለም ፤ እማዕበለ ፤ ኀጣውእ ፤ በራግናተ ፤ ወንጌሉ ፤ ቅዱስ ፤ (ምሳ፴፫ ፤ ፴፬ ። ጥበ፲ ፤ ፬ ። አርጋ) ።

—፤ መወልወል ፤ ማደስ ፤ ማጽናት ። ከመ ፤ ይኅድፍ ፤ ልቦሙ ፤ ለመሀይምናን ። ወመንፈስ ፤ ቅዱስ ፤ ይኄድፍ ። ኀድፍ ፤ ልቦሙ ፤ በፈሪሆትከ ። ለኀድፎ ፤ ነፍስ ፤ (ቅዳ ፤ አት ። ሕር ። ቄድር ፤ ግ፲፩ ። ፶፫) ።

—፤ መምከር ፤ ማስተማር ። ምስጢሩ ፤ ከመምራትና ፤ ከማጽናት ፤ ይገባል ። ወኃጥአን ፤ ይኄድፉ ፤ ሕብለ ፤ (ምሳ፲፪ ፤ ፭) ።

**ኀዳፍ ፤ ኀዳፊ ፤ (ፊት ፤ ፍያን ፤ ያት) ፤** የሚቀዝፍ ፤ ቀዛፊ ፤ መሪ ፤ ጠባቂ ፤ መምር ። ወኮሉ ፤ ዘኀዳፍ ። ኀዳፍያንኪ ። ኀዳፌ ፤ ነፍሳት ። ኀዳፍያነ ፤ ክርስቲያን ፤ (ራእ፲፰ ፤ ፲፯ ። ሕዝ፳፯ ፤ ፰ ። ቅዳ ፤ ኪዳ) ።

**መኀድፍ ፤ (ፍት ፤ ፋን ፤ ፋት) ፤** ገዢ ፤ ከማሁ ፤ ቀዛፊ ። መኀድፋነ ፤ ፍርሀት ፤ (ማር ፤ ይሥ፷፯) ።

**ኀዳፍ ፤ (ብ ፤ አኀዳፍ) ፤** መቅዘፊያ ፤ ትርክዝ ፤ መያዣው ፤ እንደርፍ ፤ ሰፊ ፤ እንደ ፤ ድግር ፤ ያለ ፤ ገዘርግ ፤ ጠፍጣፋ ፤ ቀጫል ፤ ዐንጨት ፤ (ሕዝ፳፯ ፤ ፯) ።

—፤ የመርከብ ፤ ኸራት ፤ በስተኋላ ፤ ኹና ፤ የመርከቡን ፤ ፊት ፤ የሚመልስና ፤ የሚቀልስ ፤ ወደ ፤ ወደዱበት ፤ የሚያስኬድ ። ይመይጠን ፤ ብእሲ ፤ በንዳፍ ፤ ንኡስ ፤ ወያበውኦን ፤ ውስተ ፤ መርሶ ፤ ኀበ ፤ ፈቀደ ፤ (ያዕ፫ ፤ ፬) ።



ኀዳፍ ፤

— ፤ ዕውቀት ፤ ምክር ፤ ሥልጣን ። ዘሰ ፤ አጥረየ ፤ ኀዳፌ ። እለ ፤ አልቦሙ ፤ ኀዳፍ ። እንቲአከ ፤ ኀዳፍ ፤ አ ፤ አብ ፤ ትሠርዕ ፤ ኵሎ ፤ (ምሳ፩ ፤ ፭ ። ፲፩ ፤ ፲፬ ። ጥበ፲፬ ፤ ፫) ።

**ተኀደፈ ፤** ታደፈ ፤ ተወለወ ። ተቀዘፈ ፤ ታዘዘ ፤ ተጠበቀ ። ተኀዲፎ ፤ በእደ ፤ ዚአከ ፤ (ጥበ፲፬ ፤ ፯) ።

**ኀዱፍ ፤ (ፋን ፤ ፋት ፤ ድፍት) ፤** የታደፈ ፤ የተቀዘፈ ፤ ጥብቅ ።

**ኀዳፌ ፤** መቅዘፍ ፤ መቀዘፍ ፤ አቀዛዘፍ ፤ ቀዘፋ ። ትእዛዝ ፤ ዕውቀት ፤ ፈሊጥ ። በኀዳፌ ፤ ይከውን ፤ ጸብእ ፤ (ምሳ፳፬ ፤ ፯) ።

**ማኀደፍ ፤ (ብ ፤ መኃድፍ) ፤** መቅዘፊያ ። ማደፊያ ፤ መወልወያ ፤ መንዲል ፤ ማሠሻ ፤ ማበሻ ። በማኀደፍ ፤ ፈንታ ፤ ማኀፈድ ፤ ይላል ፤ የተሳሳተ ፤ ነው ። ወእምዝ ፤ ይትመጦ ፤ ንፍቅ ፤ በማኀፈድ ። ጸሎት ፤ ላዕለ ፤ ማኀፈዳት ፤ (ሥር ፤ ቅዳ) ።

**ምኅዳፍ ፤ (ፋት) ፤** የቀዘፉና ፤ የመቅዘፊያ ፤ የትርክዝ ፤ ቦታ ።

**ኅዲር ፤ ሮት ፤ (ኀደረ ፤ የኅድር ፤ ይኅድር ፤ ቤተ ። ዕብ ፤ ሐዳር ። ዐረ ፤ ኀደረ) ፤** ማደር ፤ ከሠርክ ፤ እስከ ፤ ነግህ ፤ ባንድ ፤ ቦታ ፤ መኖር ፤ ተኝቶ ፤ ተጋድሞ ፤ ሌሊትን ፤ በንቅልፍ ፤ ማሳለፍ ። ነሐሁ ፤ ቤተ ፤ ገብርክሙ ፤ ወኃድሩ ፤ ወይቤልዎ ፤ ነኅድር ፤ ውስተ ፤ መርሕብ ። ረቢ ፤ አይቴ ፤ ተኀድር ፤ ወርእዩ ፤ ኀበ ፤ የኅድር ፤ (ዘፍ፲፱ ፤ ፪ ። ዮሐ፩ ፤ ፴) ።

—፤ መግባት ፤ መከተት ፤ ወደ ፤ ውስጥ ፤ ማለፍ ፤ ውሳጣዊ ፤ መኾን ። ኀደረ ፤ ቤተ ፤ ነዳይ ፤ ኀደረ ፤ ውስተ ፤ ማኅፀን ፤ (ቅዳ ፤ ዮሐ) ።

—፤ ከሰው ፤ መጠጋት ፤ አሽከር ፤ ሎሌ ፤ ዐማች ፤ መኾን ። ኀደረ ፤ ኀበ ፤ አሐዱ ፤ ዐዱላማዊ ፤ (ዘፍ፴፰ ፤ ፩) ።

—፤ መኖር ፤ መጽናት ፤ መተባበር ፤ መስማማት ። ኢየኅድራ ፤ አእባን ፤ ውስተ ፤ ንድቅ ። ዘቦቱ ፤ የኀድር ፤

ሸሉ ፡ ሕንጻ ። ርእስ ፡ ዘቦቱ ፡ የኀድር ፡ ሸሉ ፡ ሥጋ ፡ ወይትዋደይ ፡ (ሄርማ ፡ ገ፱ ። ኤፌ፪ ፡ ፳፩ ። ፬ ፡ ፲፯ ። ቆላ፪ ፡ ፲፱) ። በኀደረ ፡ ፈንታ ፡ ተኀድረ ፡ ይላል ፡ አያስኝም ። አጽናፍ ፡ ዘይትኀደር ፡ እምሰማይ ፡ (ምሳ፰ ፡ ፳፯) ።

**ኀዳሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ደርት) ፤** የሚያድር ፡ ዐዳሪ ፡ እንግዳ ፡ ጥገኛ ፡ ደባል ፡ ሎሌ ፡ አሽከር ፡ ቤተ ፡ ሰብ ። ኅፍረት ፡ ለኀዳሪ ፡ ሰሪቅ ፡ ማኅደር ። ኀዳሪ ፡ ዘአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ኀደረ ። ኀደርቱ ፡ ለካህን ። ኀዳሪ ፡ ወገባኢ ። ባእ ፡ ኀዳሪነ ፤ ባእ ፡ ኀዳሪነ ፤ (ሚራ፴፭ ፡ ፲፱ ። ጥበ፭ ፡ ፲፭ ። ዘሌ፳፪ ፡ ፲ ። ዘፀ፲፪ ፡ ፵፭ ። ሚራ፳፱ ፡ ፳፯ ፡ ፳፯) ።

**ኀዱር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ድርት) ፤** ያደረ ፡ የኖረ ፡ የሰፈረ ። ወሸሉ ፡ ምግባረ ፡ መንፈስ ፡ ኀዱር ፡ ውስተ ፡ ሥጋሁ ። ኩን ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኀዱረ ። እለ ፡ ኀዱራን ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ (አፈ ፡ ድ፲፭ ። ፊልክ ፡ ፻፹፩ ። መገ ፡ ፴፪) ።

**ኀድረት ፤** ማደር ፡ መኖር ፡ አስተዳደር ። ዐዳር ፡ ቅዳር ፡ ኑሮ ። በእንተ ፡ ኀድረተ ፡ አኀው ። ወኀድረቶሙ ፡ ለእስራኤል ፡ (ፊልክ ፡ ፻፹፩ ። ዘፀ፲፪ ፡ ፵) ።

**አኀደረ ፤** አሳደረ ፡ አስገባ ፡ አኖረ ፡ አስጠጋ ፡ አስቀመጠ ። ሖብእ ፡ ነዳየ ፡ ወአኀድሮ ፡ ውስተ ፡ ጽላሎትከ ። ሎጥ ፡ አኀደሬ ፡ እንግዳ ። ለእመ ፡ አኀደርከ ፡ ነኪረ ፡ ምስሌከ ። ያኀስረከ ፡ ዘአኀደርከ ። ወአኀደሮሙ ፡ ህየ ፡ ሊደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ (ኢሳ፶፰ ፡ ፯ ። ፍ፡ ነ ፡ ፲፭ ። ሚራ፲፩ ፡ ፴፱ ። ፳፱ ፡ ፳፰ ። ፪ዜና ፡ ፰ ፡ ፪) ።

**ተኀደረ ፤** ተዳደረ ፡ ተጠጋ ፡ ተቃረበ ፡ ተጎራበተ ። አውፅእሙ ፡ እምኔከ ፡ ወኢትትኀደሮሙ ። ቦ ፡ እለ ፡ ኢተኀደራ ፡ ምስለ ፡ ካልኣቲሆን ፡ (ዘፀ፳፫ ፡ ፴፪ ። ሄርማ ፡ ገ፹) ።

**አስተኀደረ ፤** አስተዳደረ ። አስማማ ፡ አስተካከለ ፡ የሕንጻ ። መኑ ፡ አስተኀደረ ፡ ማእዘኒሃ ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፯) ።

**ማኅደር ፤ (ራት ፤ መኀድር ። ዐረ ፡ ኒድር ። ዕብ ፡ ሐዴር ፤)** ማደሪያ ፡ ሰፈር ፡ ቤት ፡ በኣት ፡ የመኝታ ፡ ቦታ ። ዕልፍኝ ፤ በታላላቅ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚሠራ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ደጃፍና ፡ መስኮት ፡ ያለው ፡ ድንኳን ፡ መቃብር ። ማደሪያነት ፡ ሳለው ፡ ስቦታ ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። ማኅደረ ፡ እንግዳ ። አቱጢ ፡ ማኅደሪ ሆሙ ። እንታክቲ ፡ ማኅደር ። በእንተ ፡ ማኅደራት ። ቢሳይ ፡ ወዐራዝ ፡ ወማኅደር ። ተከለ ፡ ማኅደረ ። ማኅደሩ ፡ ለሸሉ ፡ ዘሞተ ፡ ምድር ፡ (ኪዳ ። ዮዲ፲፫ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ተ፳፰ ። ፍ፡ ነ ፡ ፳፫ ፡ ፴፪ ። ዘፍ፴፭ ፡ ፲፯ ። ኢዮ፴ ፡ ፳፫) ።

—፤ ቀመር ፤ የቀመር ፡ ስም ፡ በውደ ፡ በሐይ ፡ ፳፰ ፡ ዓመት ፡ ዕለት ፡ ወንጌላዊ ፡ ረቡዕ ፡ ማቴዎስ ፡ የሚገናኙበት ። የ፩ሀረቀም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ (አቡሻ ፡ ፱) ።

**ኀዳር ፤ (ዕብ ፡ አዳር ፤ መጋቢት ። ቅብጥ ፡ አቶር) ፤** በቁሙ ፡ የወር ፡ ስም ፡ የመስከረም ፡ ምስተኛ ፡ ያዝመራ ፡ ወራት ፡ ጠባቆች ፡ ከዱር ፡ የሚያድሩበት ። አመ ፡ ሰሙኑ ፡ ለኀዳር ። መንፈቀ ፡ ኀዳር ። (ስንክ ፡ ኅዳ፰ ። ፲፭) ።

**ኀወ ፤ ኀወወ ፤ (ኀዊው ። ከዊው ፡ ከወ ፤ ከወወ) ፤** ከፈተ ፡ ከፋፈተ ፡ ተከፈተ ፡ ክፍት ፡ ኾነ ።

**ኀዋ ፤ (ብ ፡ ኀዋኀው ። ዕብ ፡ ሐዋሕ ፤ ሐዋሒም) ፤** ነቅ ፡ ሥንጥቅ ። በቁሙ ፡ ክፍት ፡ ባዶ ፡ ወለል ፡ የቤት ፡ የደጃፍ ። አየር ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ መካከል ፡ የርጉዕ ፡ ነፋስ ፡ ቦታ ። መጣፍ ፡ ግን ፡ በኀዋ ፡ ፈንታ ፡ ኀዋኀው ፡ ይላል ። ኀዋኀወ ፡ ሰማይ ። ኀዋኀወ ፡ ፈለክ ። ኀዋኀወ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ሔኖ ። አቡሻ ። ቅዳ) ።

**ኆኅት ፤ (ብ ፡ ኆኀት ፤ ኀዋኀው ። ዐረ ፡ ኀውኀት) ፤** ታናሽ ፡ ጠባብ ፡ መስኮት ፡ ፉካ ፡ ዐይን ፡ የሚያስልክ ፡ እጅ ፡ የሚያሾልክ ፤ ነፋስና ፡ ብርሃን ፡ የሚያገባ ። ደጃፍ ፡ በር ፤ የቤት ፡ የቅጥር ፡ መውጫ ፡ መግቢያ ፤ ባዶው ፡ ክፍቱ ፡ ሳንቃ ፡ የሚከድነው ፡ መዝጊያ ፡ የሚደፍነው ። አንቀጽን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ፡ ንቅጸ ። ኆኅተ ፡ አንቀጽ ። ለሸሉ ፡ ዘመጽአ ፡ ርኅው ፡ ኆኅትየ ። ባእ ፡ ቤተከ ፡ ወዕጹ ፡ ኆኅተከ ። ይትረኀዋ ፡ ኆኀት ፡ እለ ፡ እምፍጥረት ። አርኀወ ፡ ኆኀተ ፡ ሰማይ ። እስመ ፡ ሰበረ ፡ ኆኀተ ፡ ብርት ፡ (ኪዳ ። ኢዮ፴፩ ፡ ፴፪ ። ኢሳ፳፮ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፸፪ ። ፻፯ ። ፻፮) ።

**ኆኅ ፤ (ብ ፡ ኆኀት ። ዐረ ፡ ኀውኅ ። ሱር ፡ ሓውሓ ። ዕብ ፡ ሐዋሕ ፤ ሖኽ) ፤** የባሕር ፡ ኵክ ፤ እሾኽም ፡ ፍሬው ፡ ጥቍር ፤ ዘይቶንና ፡ ዘቢብ ፡ የሚመስል ፡ ተምር ፡ የሚያክል ። ቈጽለ ፡ ኆኀት ። ከመ ፡ ቈጽለ ፡ ኆኀት ፡ (ቀሌ ። ማንዘ) ።

**ኆኌ ፤—ስመ ፡ ፊደል ፤—ሆሄ ፡ ሀ ።**

**ኆሠ ፤—ነቀነቀ ፤—ሐዊስ ፡ ሐሰ ።**

**ኀዊሥ ፤ ሦት ፤ (ኆሠ ፤ ኀወሠ ፡ የኀውሥ ፡ ይኑሥ) ፤** መቀላቀል ፡ መደባለቅ ፤ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ መለወስ ፡ መቀመም ፤ እንደ ፡ ውሃና ፡ እንደ ፡ መሬት ፡ እንደ ፡ መድኀኒት ።

**ተኀውሠ ፤** ተቀላቀለ ፡ ተደባለቀ ። ሰበ ፡ ይትፌማሕ ፡ ኢይትኀወሦ ፡ ጸልዐ ። ተኀዊሦሙ ፡ እንጋ ፡ ወተቶሲሎ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ኮኑ ፡ አሐደ ፡ ህላዌ ፡ (ምሳ፲፱ ፡ ፲ ። ቄር ፡ ጸላ) ።

**ኀዊሥ ፤ (ሣን ፡ ሣት ፡ ውሥት) ፤** የተቀላቀለ ፡ ቅልቅል ፡ ድብልቅ ፡ ቅይጥ ። ኅጺን ፡ ወልሕኵት ፡ ኀዊሥ ፡ ከማሁ ፡ ኀዊሣን ፡ በዘርዐ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ። አምጽአ ፡ ኀዊሠ ፡ ከርቤ ፡ ወዐልወ ። አፈዋተ ፡ ከርቤ ፡ ኀዊሥ ፡ (ዳን፪ ፡ ፵፫ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፴፱ ። ቅዳ ፡ አፈ) ።

**ኅውሥት ፤** (ሳ ፡ ጥ ፡ ቀደ) መቀላቀል ፡ መደባለቅ ፤ አቀላቀል ፡ ቅልቅልነት ፡ ድብልቅነት ። ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ዘእንበለ ፡ ኅውሥት ። ቱስሕት ፡ ወኅውሥት ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ኀውሥ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ቅልቅላ ፡ ድብለቃ ፤ ቅልቅልነት ፡ የባሕርይ ፡ ፍልሰት ። ዘእንበለ ፡ ኅውሥ ፡ (ቄር ፡ ፻፳) ።

**ኀወጸ ፡—ጐበኘ ፡—ሐውጾ ፡ ሐወጸ ።**

**ኆጻ ፤ (ኀጢጥ ፡ ኀጠ ፤ ሐጻ ። ዐረ ፡ ሐጻን ። ሱር ፡ ሕጻጻ ። ዕብ ፡ ሓጻጽ)** ፤ ጠጠር ፡ አሸዋ ፤ ድቡሽት ፡ ታናናሽ ፡ ጥቃቅን ፡ የደንጊያ ፡ ቅንጣት ፡ እንደ ፡ ጤፍ ፡ ምርት ፡ እንደ ፡ ክርት ፡ ደቂት ፡ ያለ ፡ በ ወንዝ ፡ ዳር ፡ በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚገኝ ። ጥሬነቱ ፡ ከኀጢጥና ፡ ከሐጺጽ ፡ የተደቀለ ፡ ነው ፡ ኀጠ ኀና ፡ ሐጻን ፡ ረመለን ፡ እይ ። በዓለ ፡ አስፈሬዳት ፡ ወ ኆጻ ፡ ደቃቅ ። ኩነ ፡ ይወዲ ፡ ኆጻ ፡ ንስቲተ ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ። ከመ ፡ አሐቲ ፡ ኀጠተ ፡ ኆጻ ፡ እምውስተ ፡ ጽሒ ፡ ኆጻ ። ኆጻ ፡ ባሕር ። ወደፈኖ ፡ ውስተ ፡ ኆጻ ። ዘሐነጸ ፡ ቤቶ ፡ ዲበ ፡ ኆጻ ፡ (ፊልክ ፡ ፴ ። ፳፱ ። ሚሬ ፲፰ ፡ ፲ ። ፵፱ ፡ ፳፩ ። ዘፀ ፪ ፡ ፲፪ ። ማቴ ፯ ፡ ፳፮) ።

**ኀዉር ፤ (ዐረ ፡ ኀዋር)** ፤ ደካማ ፡ ድዉይ ፤ ቀጭን ፡ ኩሳሳ ። ወአነ ፡ ኀዉር ፡ እምሕል ፡ ሰክሙ ፡ (ጠማር) ።

**ኀዘዘ ፡—ዐነቀ ፡ አስጨነቀ ፡—ሐዚዝ ፡ ሐዘዘ ።**

**ኀዘለ ፡—ዐዘለ ፡ ተሸከመ ፡—ሐዚል ፡ ሐዘለ ።**

**ኀዝል ፤ (ዐረ ፡ እልኀዚል)** ፤ ጣብ ፡ የጨ ዎታ ፡ ስም ፡ በጠጠር ፡ ወይም ፡ በተነጠጠ ፡ ሰንጨት ፡ የሚጫወቱት ፡ ጨዎት ፤ እንደ ፡ ገበጣና ፡ እንደ ፡ ሰንጠ ረዥ ፡ ያለ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፲፪) ።

**ኀዘነ ፡—ዐዘነ ፡—ሐዚን ፡ ሐዘነ ።**

**ኀዝዐ ፡—ነዳ ፡ አበረረ ፡—ሐዚእ ፡ ሐ ዝአ ።**

**ኀጢእ ፤ እት ፤ (ኀጥእ ፡ የኀጥእ ፡ ይኀ ጣእ ። ዕብ ፡ ሐጣእ ። ሱር ፡ ሕጣእ ። ዐረ ፡ ኀጢእ)** ፤ ኀጢአት ፡ መሥራት ፡ መበደል ፡ ሕግ ፡ ያዘ ዘውን ፡ መተው ፡ ያላዘዘውን ፡ ማድረግ ፡ ጽድቅን ፡ መ ቃወም ። ኢትኀጣእ ፡ ፈድፋደ ። ለኀሪር ፡ ወለዘሂ ፡ የኀ ጥእ ። ከመ ፡ ይኀጣእ ። ከመ ፡ ኢይኀጥኡ ፡ ሰብ ። ነ ፍስ ፡ እንተ ፡ ኀጥአት ፡ ይእቲ ፡ ትመውት ፡ (መክ፯ ፡ ፲፯ ። ፶ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ። ፪ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፳ ። ሕዝ፲፰ ፡ ፬ ፡ ፳) ።

—፤ ማጣት ፡ መቸገር ፡ ፈልጎ ፡ አለማግኘት ፤ ዕጦተኛ ፡ አይቶ ፡ ፀጣ ፡ መኾን ። ይገዕሩ ፡ ወየኀጥኡ ፡ እክለ ። ይመውቱ ፡ በኀጢአ ፡ ማይ ። አርመሙ ፡ ወኀጥኡ ፡ ቃለ ፡ እንተ ፡ ያወሥኡ ። ማሰነ ፡ ብሔር ፡ በኀጢአ ፡ ሰብእ ፡ ወእንስሳ ፡ (ስቈ፭ ፡ ፲፭ ። ኢሳ፶ ፡ ፪ ። ኅሖ፳ ፡ ፳ ። ኤር፫ ፡ ፲፭) ።

**ኀጣኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት)** ፤ ኀጢአት ፡ ሠሪ ፡ የሚሠራ ፡ ኃጥእ ፡ ኀጢአተኛ ። ያጣ ፡ የሚያጣ ።

**ኃጥእ ፤ (እት ፡ አን ፡ አት)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ በቁሙ ፡ ኀጢአተኛ ፤ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ ተላላፊ ፡ (ዕጦተኛ ፡ አይቶ ፡ ፀጣ) ። ብእሲ ፡ ኃጥእ ። ብእሲት ፡ ኃጥእት ። ኃጥኣን ፡ ወመጸብሓን ፡ (ሉቃ፭ ፡ ፴ ። ፯ ፡ ፴፯ ። ማቴ፱ ፡ ፲) ። አነ ፡ ወወልድየ ፡ ሰሎሞን ፡ ንከውን ፡ ኃጥኣነ ። ድኾች ፡ አይቶ ፡ ፀጦች ፡ ወይም ፡ በቁሙ ፡ (፫ነገ ፡ ፩ ፡ ፳፩) ።

**ኃጥኢዊ** ፤ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ። ለእመ ፡ ር ኢክ ፡ ዘማዊ ፡ ወኃጥኣዊ ፡ (ፊልክ ፡ ፴፭) ።

**አኅጥአ** ፤ ኀጢአት ፡ አሠራ ፤ አሳተ ። አሳጣ ፡ አደኸየ ፡ ባደ ፡ አስቀረ ። ከመ ፡ ያኅጥእሙ ፡ ረበሐ ። ምንተ ፡ አኅጣእኩክ ። ወኢያኅጥእሙ ፡ እምዘፈ ቀዱ ፡ (ፊልክ ፡ ፶ ። ፫ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፳፱ ። መዝ ፡ ፸፯) ።

**ተኀጥአ** ፤ ታጣ ፡ ጠፋ ፡ ሸሸ ፡ ኰበለለ ። ተኀ ጥአ ፡ ሲሳይ ። በተኀጥአተ ፡ መምህር ። በእንተ ፡ ዘ ይትረከብ ፡ እምዘተኀጥአ ። ተኀጥአ ፡ ወአምሠጠ ። አግብርት ፡ እለ ፡ ተኀጥኡ ፡ እምአጋዕዝቲሆሙ ፡ (የ ሴፍ ። ምሳሌ፱ ፡ ፲፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵ ። ፩ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱ ። ፳፭ ፡ ፲) ።

**ኀጡእ ፤ (አን ፡ ኢት ፡ ጥእት)** ፤ ያጣ ፡ የ ተቸገረ ፡ የሌለው ፡ ድኻ ። ኀጡእኬ ፡ አንተ ፡ አሐተ ፡ ነ ገረ ። ኀጡእ ፡ ልቡና ። ኀጡእ ፡ ንዋይ ። ዲያቆን ፡ የሐውጽ ፡ ድዉየ ፡ ወኀጡኣነ ፡ (ፊልክ ፡ ፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፭ ፱ ። አፈ ፡ ተ፳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፭ ፡ ፪) ።

—፤ የታጣ ፡ የሸሸ ፤ የኰበለለ ። ወየአምሩ ፡ ከመ ፡ ኀ ጡእ ፡ ውእቱ ። እንዘ ፡ ኀጡእ ፡ እምገጸ ፡ ባኦል ፡ (፩ ነገ ፡ ፳፱ ፡ ፲፯ ። ፩ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፩) ።

**ኀጥአት** ፤ ማጣት ፡ መታጣት ። ኀጥአተ ፡ ን ጽሐ ፡ ኀሢና ፡ (ፊልክ ፡ ፪፻፫) ። ዕጦት ፡ ችግር ፡ ሽሽት ፡ ኰብለላ ።

**ኀጥእና** ፤ ኃጥእነት ፡ አይቶ ፡ ፀጣነት ፡ (ፈላስ ፡ ገ፹፪) ።

**ኀጢአት ፤ (ብ ፡ ኀጣውእ ፤ ይእ)** ፤ በ ቁሙ ፡ በደል ፡ ዐመፃ ፡ ግፍ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ሥራ ፤ በኀል ዮና ፡ በነቢብ ፡ በገቢር ፡ የሚሠራ ። ተኀድገ ፡ ለከ ፡ ኀጢ አትከ ። ወይሰረይ ፡ ለነ ፡ ኀጣውኢነ ። ክልኤቲ ፡ ኀጣ ይእ ። አአምር ፡ ሕማመከ ፡ ወኀጣይአከ ፡ (ማርቆ ፡ ፭ ። ቅዳ ። ሚራ፯ ፡ ፭ ። ራእዩ ፡ ፱) ።

**ማኅጣእ** ፤ ኀጢአት ፡ የሚያሠራ ፡ ማሠሠያ ፡ መሸፈቻ ፡ ቦታ ። ወማኅጣእ ፡ አግብርት ፡ ማእከላ ፡ እምትካት ፡ (ዕገዘ ፡ ፲፭) ።

**ኀጢጥ ፤ ጠት ፤ (ኀጠ ፤ ኀጠጠ ፡ የኀ ጥጥ ፡ ይኀጥጥ ። ሐጻ ። ዕብ ፡ ሓጣጥ ፤ ወ.ጋ ፡ በሳ ፡ ነቌረ)** ፤ ማጠጥ ፡ ጥቃቅን ፡ መኾን ፡ ማነስ ፡ መ ቅጠን ። ኀጢጥና ፡ ሐጺጽ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ። ኆጻ ፡ ከነዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ኀጠት ፤ (ታት ። ኆጻ ፤ ኆጻት)** ፤ ቅን ጣት ፡ ታናሽ ፡ ፍሬ ፤ ያሸዋ ፡ የእኽል ፡ የሌላውም ፡ ኹሉ ።

ኀጠተ ፡ ሞጻ ። ኀጠተ ፡ ጼው ። ኀጠተ ፡ ዘርዐ ፡ እኩይ ። ኀጠተ ፡ ስናፔ ። ኀጠተ ፡ ሥርናይ ፡ (ሚራ ፲፰ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ። ሉቃ ፡ ዕ፲፱ ፡ ፴፰ ። ማቴ፲፫ ፡ ፴፮ ። ዮሐ፲፪ ፡ ፳፬) ። ኀጠታተ ፡ ዐጣን ፤ እንኳር ፡ ቁቀር ። ኀጠታተ ፡ ዘጉል ፡ (ቅዳ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፯) ።

**ኀጣጥ** ፤ (ዕብ ፡ አጣድ) ፤ በቁሙ ፤ ዐጣጥ ፤ እሾኽም ፡ ዕንጨት ፡ እሾኹ ፡ ታናናሽ ።

**ኃዳጥ** ፤ (ኃጣጥ ፤ ጣን) ፤ ጥቂት ፤ ትንሽ ፤ ብዛት ፡ የሌለው ። ማእረሩሰ ፡ ብዙኃ ፡ ወገባሩ ፡ ኃዳጥ ። ወኃዳጣን ፡ ኅሩያን ። በእንተ ፡ ኃዳጥ ፡ ኀጢአት ፡ (ማቴ፱ ፡ ፴፯ ። ፳ ፡ ፲፮ ። ኢሳ፶፯ ፡ ፲፯) ። ቀሐይ ፡ ክልኤ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ኃዳጥ ፡ ይባላል ፡ ፰ ፡ ፍሬ ፡ ፱ ፡ ፍሬ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ኃዳጥ ፡ የአክል ። በኃዳጥ ፡ ዓሣ ፡ (ሉቃ፲ ፡ ፵፱ ። ቅኔ) ።

**ኀጥሚ** ፤ (ዐረ ፡ ኂጥሚይ) ፤ ሰላጣ ፡ ሥንቁ ፡ የወፍ ፡ ዘረር ፤ ማናቸውም ፡ ቅጠላቅጠል ፡ በፈጠው ፡ የሚጣፍጥ ። ባለብለዮች ፡ ማን ፡ የጉመን ፡ ዘር ፤ ጥማቂ ፡ ይሉታል ፡ (ኢዮ፳ ፡ ፳) ።

**ኀየጠ** ፤ ጠት ፤ (ኄጠ ፡ የኀይጥ ፡ ይኂጥ) ፤ መሸንገል ፡ መደለል ፡ ማባበል ፤ በምክር ፡ በነገር ፡ ማሳት ፡ ማታለል ። በመብልዑ ፡ የኀይጠከ ። ኄጥዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወአሆ ፡ አበልዎሙ ። ዑቁ ፡ ኢይኂጥክሙ ፡ በተጥባበ ፡ ነገር ። ኄጠሙ ፡ ሰሰብእ ፡ በነገረ ፡ የውሀት ፡ (ሚራ፲፫ ፡ ፯ ። ማር፲፭ ፡ ፲፭ ። ቈላ፪ ፡ ፰ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ኀያጢ** ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት) ፤ የሚሸንግል ፡ ሸንጋይ ፡ አታላይ ።

**ተኀይጠ** ፤ ተሸነገለ ፡ ተታለለ ። አዳም ፡ ተኀይጠ ፡ እምሰይጣን ። ኢተሀውከ ፡ ወኢይደንገፀ ፡ ወኢተኀይጠ ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፱ ። አፈ ፡ ድ፳፭) ።

**ኀዩጥ** ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ይጥ) ፤ የተታለለ ፡ የተሸነገለ ፤ ተላላ ፡ ሸንጋል ።

**ኂጠት** ፤ መታለል ፡ ማታለል ፤ መሸንገል ፡ አሸነጋገል ፡ ሸንገላ ። እምኂጠተ ፡ ጸላኢ ፡ ንትዐቀብ ። አእመረ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኂጠት ፡ እምሰይጣን ፡ (ኪዳ ። ስንክ ፡ መስ፳፩) ።

**ኂጣን** ፤ ሸንገላ ፡ ድለላ ፡ ጕሕሉት ፡ ተንኰል ፡ ልጉብ ፡ ጥዑም ፡ ቃል ፤ ንባብ ፡ ደማ ፡ ምስጢረ ፡ ክፉ ፤ (ፑሊቲክ) ። በኂጣን ፡ ነገር ፡ ወበተየውሆ ። አኮ ፡ በኂጣን ፡ ወተጥባበ ፡ ነገር ። በትምይንት ፡ ወኂጣን ። በኂጣን ፡ እኩይ ፡ ኄጠ ፡ (ሮሜ፲፮ ፡ ፲፰ ። ፩ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ድ፳፯ ። ቄድር ፡ ገ፳፩) ።

**ኀጠት** ፤—ቅንጣት ፤—ነጢጥ ፡ ኀጠ ፡ ኀጠጠ ።

**ኀየል** ፤—ዋሊያ ፤—ሀየል ።

**ኄላ** ፤—የወይን ፡ ዘለላ ፤—ሄላ ።

**ኀየለ** ፤ ሎት ፤ (ኄለ ፡ የኀይል ፡ ይኂል ። ዕብ ፡ ሓል ፡ ያሒል) ፤ መበርታት ፡ ቡቃ ፡ መስደድ ፡ ድረሱልኝ ፡ ማለት ፤ ከምጥና ፡ ከጭንቅ ፡ የተንሣ ። ሕዝብን ፡ ሰራዊትን ፡ በጩኸት ፡ በቀንዳ ፡ መሰከት ፡ መሰብሰብ ፡ መጥራት ፤ ወይም ፡ መጠራት ፡ ተካቶ ፡ መሰብሰብ ። ወኄሉ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወተለውዎሙ ፡ (ኢያ፰ ፡ ፲፯) ።

**ኀይሎ** ፤ ሎት ፤ (ኀየለ ፡ ይኄይል ፡ የኀይል) ፤ ማየል ፡ መበርታት ፡ መጉልበት ፡ ኀይለኛ ፡ መኾን ፤ መድፈር ፡ ማሸነፍ ። ጽንዑ ፡ ወኅይሉ ። በዘይኄይል ፡ ይካምየ ። ወሬዛ ፡ ዘይኄይላ ፡ ለይንግል ፡ (፱ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ። አርጋ ። ቀሌ) ።

—፤ መብዛት ፡ መበርከት ፤ ዐያሌ ፡ መኾን ። ይምፀ ፡ መጥቅዐ ፡ ይበልኃ ፡ ወይኄይል ፡ ጥቀ ። ወኀየለ ፡ ቃሎሙ ። እስከ ፡ ኀየሎሙ ፡ ደም ፡ (ዘፀ፲፱ ፡ ፲፱ ። ሉቃ፳፫ ፡ ፳፫ ። ፫ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፰) ። በገበረ ፡ ፈንታ ፡ ተገበረ ፡ እንዲል ፡ በኀየለም ፡ ፈንታ ፡ ተኀየለ ፡ ይባላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ተኀየሉ ፡ ከመ ፡ ትባኡ ። ጽንዑ ፡ ወተኀየሉ ። እለ ፡ ይትኄየሉ ። በፈቃድ ፤ አው ፡ በተኀይሎ ። ተኀየሉ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ሉቃ፲፫ ፡ ፳፬ ። ፱ ዜና ፡ ፴፱ ፡ ፯ ። ዘፀ፴፱ ፡ ፲፰ ። ቄድር ፡ ገ፴ ። ቀሌ) ።

**ኀያል** ፤ (ላን ፡ ላት ፤ የልት) ፤ በቁሙ ፤ ኀይለኛ ፡ ዐርበኛ ፤ ጥኑ ፡ ብርቱ ፡ ጠንካራ ፤ ጕልበታም ። ኢይዘኀር ፡ ኀያል ፡ በኀይሉ ። ነፋስ ፡ ኀያል ። እብነ ፡ አይማስ ፡ ኀያል ። እግዚእ ፡ ኀያላን ። ሠለስቱ ፡ ኀያልት ፡ (ኤር፱ ፡ ፳፫ ። ኢሳ፲፭ ፡ ፲፭ ። ቅዳ ። መዝ ፡ ፵፯ ። ፩ዜና ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ። ፱ዜና ፡ ፳፫ ፡ ፳) ።

—፤ ዐያሌ ፡ ብዙ ፤ እጅግ ። (ማጥም ፤ በራስ ፡ ዐሊ ፡ ጊዜ) ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ሞተ ፡ አሉ ፡ በጋሎች ፡ ከተማ ፤ ዐያሌ ፡ አይሞትሞይ ፡ ደስ ፡ እንዲለኝማ ፡ (አያ ፡ ዐሊ) ።

**ኃዩል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ይልት) ፤ የበረታ ፡ ብርቱ ፡ ብዙ ፡ ኀይለኛ ። ኃዩለ ፡ ማየ ፤ ኃዩል ፡ ውእቱ ። ማዐበል ፡ ኃዩል ፡ (ጥበ፲፫ ፡ ፱ ፡ ፬ ። ፲፱ ፡ ፯) ።

**ኀይል** ፤ (ላት) ፤ በቁሙ ፤ ጕልበት ፡ ብርታት ፡ ጥናት ፡ ጥንካሬ ፤ ችሎት ። እመ ፡ ይክመ ፡ ኀይሉ ፡ ወስእነ ። በኵሉ ፡ ኀይልየ ። ኀይላቲሁ ፡ ዘውስጥ ፡ (ሚራ ፲፱ ፡ ፳፰ ። ዘፍ፴፩ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፭) ።

—፤ ታምራት ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ። ኀይላተ ፡ ብዙኀ ፡ ገብርነ ። አህጉር ፡ እለ ፡ በውስቴቶን ፡ ገብረ ፡ ኀይለ ፡ ብዙኀ ። በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘርእዩ ፡ ኀይል ፡ (ማቴ፯ ፡ ፳፱ ። ፲፩ ፡ ፳ ። ሉቃ፲፱ ፡ ፴፯) ።

—፤ ብዕል ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፤ ጥሪት ፡ ድልብ ። ኀይለ ፡ ይማስቆ ። እለ ፡ በልዑ ፡ እምነ ፡ ኀይላ ። በጽንዐየ ፡ ገበርኩ ፡ ሊተ ፡ ዘንተ ፡ ኀይለ ፡ ዐቢየ ፡ (ኢሳ፰ ፡ ፬ ። ራእ ፲፰ ፡ ፫ ። ዘዳ፰ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰) ።

—፤ ዕውቀት ፤ ሰማያዊ ፡ ጸጋ ፤ መንፈሳዊ ፡ ሀብት ። ኀይል ፡ ታኄይል ። እስከ ፡ ትለብሱ ፡ ኀይለ ፡ (መክ፲ ፡ ፲ ። ግብ፩ ፡ ፰) ።

—፤ ሰራዊት ፡ ጭፍራ ፡ የጦር ፡ ሕዝብ ፤ ጓዝ ። ሊዮአብ ፡ መልአከ ፡ ኀይል ። በኀይል ፡ ክቡድ ። ኀይለ ፡ ሰማያት ። ኀይላት ፡ ዘዝ ፡ ዓለም ፡ (፫ነገ ፡ ፱ ፡ ፳፱ ። ፲ ፡ ፱ ። ማቴ፳፬ ፡ ፳፱ ። ዕር ፡ ኢሳ፱ ፡ ፬) ።

**አኀየለ ፤ አስተኀየለ ፤** አጠና ፡ አበረታ ፡ አጠነከረ ፡ ኀይለኛ ፡ አደረገ ፡ አበዛ ። ናዘዘት ፡ ወአኀየለት ፡ በውስተ ፡ መከራሁ ። ያኀይለከ ፡ እግዚ ። ያኀይልከ ፡ ለገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ (ፊልክ ፡ ፶፰ ። ዘፀ፲፰ ፡ ፳፫ ። ኩፋ ፡ ፳፱) ።

**ተኀየለ ፤** ተበረታበት ፤ ተደፈረ ፡ ተሸነፈ ፡ ተጠቃ ፡ በታች ፡ ኾነ ።

**ተኃየለ ፤** ተበራታ ፡ ተበረታታ ፡ ተጠናከረ ፡ ተጠነካከረ ፤ አይዞኝ ፡ አይዞኝ ፡ ተባባለ ። ተጋፋ ፡ ተዳፈረ ፡ ተደፋፈረ ። መኑ ፡ ይክል ፡ ምስሌሁ ፡ ተኃይሎ ። ኢይትኃየሉ ፡ ዐፊን ። ኢትትኃየል ፡ ውሒዘ ፡ ፈለግ ፡ (ኢዮ ፴፮ ፡ ፳፪ ። ዘፀ፲፱ ፡ ፳፱ ። ሢራ፬ ፡ ፳፮) ።

**ተኃያሊ ፤** ተጋፊ ፡ ግፈኛ ፡ ኀይለኛ ። ለእመ ፡ ኮነ ፡ ተኃያሊ ፡ ባዕል ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፭) ።

**ትኅይልት ፤** መበራታት ፡ ብርታት ፡ ብርቱነት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፲፱ ። ማንዘ) ።

**አስተኃየለ ፤** አበራታ ፡ አበረታታ ፤ አጠነካከረ ።

**መስተኃይል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤** የሚያበረታታ ፤ በሉ ፡ በሉ ፡ የሚል ፡ (ሢራ፵ ፡ ፲፭) ።

**ኀይመት ፤ (ታት ። ዐረ ፡ ኀይም ፤ ኀይመት) ፤** ድንኳን ፡ ማደሪያ ፡ ከፀምር ፡ ከከታን ፡ ከማእበ ፡ የሚሠራ ፤ የጓዝ ፡ የሰፈር ፡ ቤት ፡ የሚነቀል ፡ የሚተከል ፤ የሚታጠፍ ፡ የሚዘረጋ ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፩ ፡ ፮ ። ዕብ ፲፩ ፡ ፱ ። ማሕ፩ ፡ ፭) ። ጳውሎስ ፡ ኮነ ፡ መስተገብረ ፡ ኀይመት ። ዐረብ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ በኀይመታት ፡ (አፈ ፡ ተ፳፮ ። ሲኖ ይ) ።



ኀይመት ፡

**ኀየሠ ፤—ተሻለ ፤—ኀዩስ ፡ ኀየሰ ።**

**ኀዩር ፤ ሮት ፡ (ኄረ ፤ ኀየረ ፡ የኀይር ፡ ይኄር ። ዐረ ፡ ኃረ) ፤** መቸር ፡ መለገስ ፤ ራት ፡ ለራት ፡ እያዩ ፡ እያሳዩ ፡ መስጠት ፡ ማቅረብ ፤ ማደል ፡ ማሳለፍ ።

**ኄር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት ። ዐረ ፡ ኀይር ። ዕብ ፡ ጦብ) ፤** ቸር ፡ ለጋስ ፡ ደግ ፡ ቅን ፤ በጎ ፡ ደኅና ፡ መልካም ፤ ተንኰልና ፡ ክፋት ፡ ቢስነት ፡ የሌለው ። ምንት ፡ ትብለኒ ፡ ኄር ፡ በእንተ ፡ ኄር ፤ አልቦ ፡ ኄር ፡ ዘእንበለ ፡ አሐዱ ፡ እግዚአብሔር ። ጻድቅ ፡ ወኄር ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ። ብእሲት ፡ ኄርት ። እኩያን ፡ ወኄራን ። የሐውር ፡ ፍናወ ፡ ዘኢኮና ፡ ኄራተ ፡ (ማቴ፲፱ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፳፫ ፡ ፯ ። ሢራ፯ ፡ ፲፱ ። ማቴ፭ ፡ ፵፭ ። ምሳ፯ ፡ ፲፪) ። ኄራን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ኄራት ፡ ይላል ፤ የመሳሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ግብ፲፫ ፡ ፶፫ ። ፲፯ ፡ ፬) ።

**ኄረት ፤** መቸር ፡ መስጠት ፡ ቸርነት ፡ ደግነት ። ይኩን ፡ ኄረትኪ ፡ በኃሣ ፡ ግዕዝ ፡ ወይዋሂ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፯) ።

**ኄረወ ፤ (ይኄሩ ፡ ይኄሩ ። ኄረ ፤ ኀየረ) ፤** ወ ፡ ተቀጥላ ፡ ነው ። ቸረ ፡ ለገሰ ፡ ደግ ፡ ቅን ፡ መልካም ፡ ኾነ ። ሰበ ፡ ኄረወ ፡ እግዚ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ። ኄርዎተ ፡ ነፍስ ፡ ይትሌዐል ፡ ላዕለ ፡ ሥሉን ፡ ኄሩታት ። በኄሩቱ ፡ ለኖላዊ ፡ ይኄርዉ ፡ መርዔት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ፈላስ ፡ ገ፱፻ ። አዋል) ።

—፤ በለጠ ፡ ተሻለ ። ደቂቀ ፡ አቡከ ፡ እለ ፡ ይኄርዉ ፡ እምኔከ ። ዕረፍተ ፡ ሞት ፡ ይኄሩ ፡ ሲተ ፡ እምግባራ ፡ ለዛቲ ፡ ሕይወት ፡ (፪ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፲፫ ። ፊልክ ፡ ፻፸፱) ።

**ኄሩት ፤ (ታት) ፤** ቸርነት ፡ ደግነት ፡ በጎነት ። በኄሩቱ ፡ ጻድቃን ፡ ትረትዕ ፡ ሀገር ። አልቦ ፡ እኩይ ፡ ዘእንበለ ፡ ኄሩት ። ይኄይስ ፡ እከዩ ፡ ለብእሲ ፡ እምነ ፡ ኄሩታ ፡ ለብእሲት ። ርእሰ ፡ ኄሩታት ፡ (ምሳ፲፩ ፡ ፲ ። ኩፋ ፡ ፴፭ ። ሢራ፵፪ ፡ ፲፬ ። ፊልክ ፡ ፫) ።

**ኄሩና ፤ ኄርውና ፤ ኄርውና ፤** ግዜ ፡ ከማሁ ፡ ኄሩት ። በኄሩና ፡ ነፍሱ ። ምሕረተ ፡ ወኄርውና ። ኢበቍዖ ፡ ኄርውናሁ ፡ (ሢራ፴፭ ፡ ፳፫ ። አፈ ፡ ተ፲፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፱) ።

**አኄረወ ፤** አቸረ ፡ አስቸረ ፤ ቸር ፡ ገር ፡ አደረገ ፤ አለዘበ ። ያኄርዉ ፡ ኅሊናሁ ፡ (አረጋ ፡ ድ፲) ።

**ኄሰ ፤—ነቀፈ ፤—ሐዩስ ፡ ሔሰ ።**

**ኀዩስ ፤ ሶት ፤ (ኀየሰ ፡ ይኀይስ ፡ ይኄስ ። ኄረወ) ፤** መሻል ፡ መብለጥ ። ይኄይስኒ ፡ መዊት ፡ እምሐዩው ። ይኄይሰክሙ ፡ እሑር ። ፈሪሀ ፡ እግዚ ፡ እምዝሉ ፡ ትኄይስ ፡ (ጦቢ፫ ፡ ፯ ። ዮሐ፲፮ ፡ ፯ ። ሢራ፳፭ ፡ ፲፩) ።

—፤ ማማር ፡ መወፈር ፤ ማሽብረቅ ፤ ኀየሰት ፡ ነፍስቶሙ ፡ ወሆኅየት ፡ ራእዮሙ ፡ (ዳን፩ ፡ ፲፭) ። በኀየሰ ፡ ፈንታ ፡ ተኀየሰ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ኢትፍቅድ ፡ ተኄይሶ ፡ እምኔሆሙ ፤ አላ ፡ ኩን ፡ ዐሩየ ፡ ምስሌሆሙ ፡ (ሲኖ ይ) ።

**ኄሳን ፤** መሻል ፤ ብልጫ ፡ ላቂያ ። ኄሳኑ ፡ ህላዌሁ ። ብዙኅ ፡ ኄሳኑ ፡ ለእግዚ ፡ እምሰብእ ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**አኄሰ ፤ አኀየሰ ፤** አሻለ ፡ አበለጠ ፤ አሳመረ ፡ አስጌጠ ። አኀየስኩከ ፡ ወገበርኩከ ፡ ከመ ፡ ጽቡረ ፡ ሰብሓዊ ። ወኮኑ ፡ መንፈቀ ፡ ሰብእ ፡ ያኄይሱ ፡ ግብረ ፡ አሐዱ ፤ ወመንፈቆሙ ፡ ያኄይሱ ፡ ግብረ ፡ ካልኡ ። ሰይጣን ፡ ያኄይስ ፡ መልእክተ ፡ ኀቤሆሙ ። ወእምአኄስኩ ፡ ዘእነብብ ፡ (ኢሳ፵፮ ፡ ፱ ። ፊልክ ፡ ፳ ። ፶ ። ኢዮ፲፯ ፡ ፭) ።

—፤ አዳነ ፡ ተቤዠ ። ከመ ፡ ያኄስ ፡ ኃላዊነ ፡ እሞት ፡ ወእሙስና ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ። በአኀየሰ ፡ ፈንታ ፡ አስተኀየሰ ፡ ይላል ፡ ፍችሙ ፡ አንድ ፡ ነው ። አስተኄየስክሙ ፡ አነ ፡ ለእለ ፡ ሞቱ ፡ ኃቡረ ፡ እምሕያዋን ፡ (መክ፬ ፡ ፪) ።

**ተኃየሰ** ፤ ተሻሻለ ፡ ተበላለጠ ፡ ተላላቀ ።

**አስተኃየሰ** ፤ አሻሻለ ፡ አበላለጠ ። ንዑ ፡ ናስተኃይስ ፡ ነገረ ። ተቃንኦ ፡ በእንተ ፡ አስተኃይሶ ፡ ወበእንተ ፡ ክብር ፡ (ዕገዘ ፡ ፳ ። ሮሜ ፡ ፲፪) ።

**ኃል** ፤ ላን ፡ ልት ፡ ታት ። (ሐባብ ፡ ወዐረብ) ፤ እኅት ፡ (ኃልት) ፡ አክስት ፡ ያባትና ፡ የናት ፡ ወንድም ፡ እኅት ። (ተረት ፡ በቅሎ ፡ አባቷን ፡ ስትክድ) ፤ ባገሩ ፡ እናቴ ፡ ድንጉላ ፡ እኅቷ ።

**ኀልዮ** ፤ ዮት ፤ (ኀለየ ፡ ይኄሊ ፡ የኅሊ ። ትግ ፡ ሐብ ፡ ኀለነ) ፤ ማሰብ ፤ ክልብ ፡ ማንቃት ፡ ነገርን ፡ ሥራን ፡ ክነቢብ ፡ ከገቢር ፡ በፊት ፡ በሐሳብ ፡ በልብ ፡ መፍጠር ፡ ማስገኘት ፡ ማስናዳት ። መመርመር ፡ መፈለግ ፡ ማውጣት ፡ ማውረድ ። ሕልበሙ ፡ ልብ ፡ ለኀልዮ ። ልበ ፡ ወሀበሙ ፡ በዘይኄልዩ ። ኀለየ ፡ መጠነ ፡ ሕሐዱ ፡ ሰዓት ። ኢተኀልዩ ፡ ወኢምንተኒ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፪ ። ሚሬጉ ፡ ፳ ። ዳንኤ ፡ ፲፯ ። ፊልጵ ፡ ፬) ።

**ኀለደ** ፤ ዶት ፤ (ኀለደ ፡ ይኄልድ ፡ የኅልድ ። ሱር ፡ ሕላድ ፡ በልብ ፡ ተሳበ ፤ እብብኛ ፡ ኸደ ። ዕብ ፡ ሐላድ ፡ ፋረ ፡ ቈፈረ ። ዐረ ፡ ኀለደ ፤ አረጀ) ፤ ብዙ ፡ ዘመን ፡ መኖር ፡ መቈየት ፡ ዕድሜ ፡ ማግኘት ። መፍጨርጨር ፡ መፍጀት ፡ መክተት ፤ ዕድሜን ፡ ሥራን ። መቍረጥ ፡ መበጠስ ፡ ምክርን ፡ ፍርድን ። አለደን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ተኀለደ** ፤ ተፍጨረጨ ፡ ተፈጸመ ፡ ተቈረጠ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ቈራጭነት ፡ ተሾመ ፡ ይሉታል ። ወተኅልደቱሰ ፡ ሰሞት ፡ መጠውዎ ። እመ ፡ አበይነ ፡ ይትኀሊድ ፡ ብነ ፡ ቃለ ፡ አረጋዊ ፡ (ድጓ ፡ አዋል) ።

**ኅልድ** ፤ (ዳት ። ዕብ ፡ ሔሌድ) ፤ ፋሮ ፡ ታናሽ ፡ አውሬ ፡ ምድር ፡ የሚፍር ፡ የሚቈፍር ።

**ኀሊው** ፤ ዎት ፤ (ኀለወ ፡ ይኄሉ ፡ ይኅሉ) ፤ መጠበቅ ፤ ዘበኛ ፡ መኾን ፡ የሌሊት ። ሌሊተ ፡ ኅልዉ ፡ ወመዓልተ ፡ ተቀነዩ ። ይትገሀ ፡ ወይኄልዉ ። እምትገሀ ፡ ወእምኀለወ ። ክንቶ ፡ ይትገሀ ፡ እለ ፡ ይኄልዉ ። እለ ፡ ይኄልውዋ ፡ (ንሐ ፡ ፳፪ ። ሉቃ ፡ ፪ ። ፲፪ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፻፳፯ ። ሰቈ ፡ ፲፱) ።

**ኀላዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ለውት) ፤ የሚጠብቅ ፤ ጠባቂ ፡ ዘበኛ ፡ እረኛ ። ኖላዊ ፡ ዘመዓልት ፤ ኀላዊ ፡ ዘሌሊት ። ኀላዌ ፡ ብዕራይ ፡ (ድጓ ። አዋል) ።

**ኀለየ** ፤—ለዘበ ፤ ዘፈነ ፤—ሐልዩ ፡ ሐለየ ።

(ተ) **ኀልዮ** ፤ ዮት ፤ ኖ ፤ (ኀለየ ፡ ይኄሊ ፡ የኅሊ ። ትግ ፡ ሐብ ፡ ኀለነ) ፤ ማሰብ ፤ ክልብ ፡ ማንቃት ፡ ነገርን ፡ ሥራን ፡ ክነቢብ ፡ ከገቢር ፡ በፊት ፡ በሐሳብ ፡ በልብ ፡ መፍጠር ፡ ማስገኘት ፡ ማስናዳት ። መመርመር ፡ መፈለግ ፡ ማውጣት ፡ ማውረድ ። አልቦሙ ፡ ልብ ፡ ለኀልዮ ። ልበ ፡ ወሀቦሙ ፡ በዘይኄልዩ ። ኀለየ ፡ መጠነ ፡ ሕሐዱ ፡ ሰዓት ። ኢተኀልዩ ፡ ወኢምንተኒ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፪ ። ሚሬጉ ፡ ፳ ። ዳንኤ ፡ ፲፯ ። ፊልጵ ፡ ፬) ።

**ኀላዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፡ የሚያስብ ፡ ዐሳቢ ። ኀላዪ ፡ እኩይ ፡ (ሲኖዶ) ።

**አኅለየ** ፤ አሳሰበ ፡ አስመሰከተ ፡ አሳተ ፡ አንማማ ። ያኄልዩ ፡ ዘኅቡእ ፡ ያእምር ። ተፋቀሮ ፡ ኢያኄሊ ፡ እኩየ ። ነገሩ ፡ ዘሎሙ ፡ በከመ ፡ አኅለዮሙ ፡ ልቦሙ ። ሰይጣን ፡ አኅለዮ ፡ ለዳዊት ፡ ከመ ፡ ይኈልቍ ፡ እስራኤልሀ ፡ (ሚሬፀ፱ ፡ ፯ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፭ ። ገድ ፡ ላሊ ። ፩ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፩) ።

**ተኀለየ** ፤ ታሰበ ፡ ነቃ ። ውስተ ፡ ልበ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢተኀለየ ። ሰበ ፡ ተኀለየት ፡ ውስቴትከ ፡ ኅሊና ፡ ዝሙት ። ይትሐሰብ ፡ ሊተ ፡ ወይትኄለይ ፡ (ኪዳ ። ፈልክ ፡ ፺፰ ። ስንክ ፡ ጥር፳፯) ።

**ኅሉይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሊት) ፤ የታሰበ ፡ ዐሳቢ ።

**ኅሊ** ፤ ኅልያ ፤ (ያት ። ኀለየ) ፤ ኅሊና ፡ ሐሳብ ፡ ምኞት ፡ ከልብ ፡ የሚነቃ ፡ ነቅዐ ፡ ልብ ፡ ውሳጣዊ ፡ ሕዋስ ። ጽርየተ ፡ ኅሊሁ ። ንጹሐ ፡ ሥጋ ፡ ወኅልያ ። ጽዱላነ ፡ ልብ ፡ ወኅልያ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ግንቦ ። የካ፯) ።


**ኅሊና** ፤ (ናት ። ኀለነ) ፤ በቁሙ ፡ ግእዝ ፡ ከማሁ ፡ ሐሳብ ፡ ምኞት ። ዘርኦ ፡ ኅሊናሁ ፡ ዘከመ ፡ የሐርስ ፡ ትለማሁ ። ልብ ፡ እንተ ፡ ትወልድ ፡ ኅሊና ፡ እኩየ ። ኅሊናት ፡ ዘሥጋ ፡ (ሚሬፀ፰ ፡ ፳፯ ። ምሳ፮ ፡ ፲፰ ። ይሁ ፡ ፲) ።

—፤ የአፍኣ ፡ የውስጥ ፡ ሕዋስ ። ተንሣሽ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ማሰት ፡ ነው ፤ ሐሰንና ፡ ሎሰን ፡ እይ ። በእንተ ፡ ዐቂበ ፡ ኅሊናት ፡ ዘአፍኣ ፡ ወውስጥ ። ወግብረ ፡ ኅሊናት ፡ ዘውእቶሙ ፡ ነጽሮ ፡ ወሰሚዕ ፡ (አረጋ ፡ ድ፲፰ ። ማር ፡ ይሥ፳፱ ፡ ፩) ።

**ኅሊናዊ** ፤ የሐሳብ ፡ ሥራ ፡ ኅቡእ ፡ ረቂቅ ፤ ውሳጣዊ ፡ ድብቅ ፤ ክሳቢው ፡ በቀር ፡ ለሌላ ፡ የማይታወቅ ። ተውህበ ፡ ላቲ ፡ አእምሮ ፡ ግብራት ፡ ኅሊናውያት ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፲፩) ።

**ኀሊል** ፤ ሎት ፤ (ኀለለ ፡ የኅልል ፡ ይኅልል ። ዐረ ፡ ኃለ ። ሱር ፡ ወዕብ ፡ ሓላል) ፤ መብሳት ፤ መኅደል ፡ መፈልፈል ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ ባዶ ፡ ማድረግ ፤ እንደ ፡ ከበሮ ።

(ተ) **ኅለት** ፤ (ታት) ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፤ ዘንግ ፡ ብርዕ ፤ አገዳ ፡ ቅልጥም ፡ ያለው ፡ የጕሽ ፡ መቃ ፡ ወይም ፡ ቀለም ፤ ሽንበቆ ፡ ቀርከሓ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። አራዊተ ፡ ኅለት ። ኅለት ፡ ዘዐቅም ። ዐቃቤ ፡ ኅለት ። ብሔረ ፡ ኅለት ። ውስተ ፡ ኅለት ፡ ዘውጡሕ ፡ (መዝ ፡ ፷፯ ። ሕዝ፳፱ ፡ ፲ ። ኢሳ፴፯ ፡ ፱ ። ፴፭ ፡ ፯ ። ኢዮ፴ ፡ ፯) ።



ኅለት ፡

**ኀለፈ** ፤—ማለ ፡ ተረገመ ፤—ሐሊፍ ፡ ሐለፈ ።

**ኀሊፍ** ፤ ፎት ፤ (ኀለፈ ፡ የኀልፍ ፡ ይኅ

ልፍ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሐላፍ ። ዐረ ፡ ኀለፈ ) ፤ ማለፍ ፡ ፈጥኖ ፡ መኼድ ፤ መሻገር ፡ መራመድ ፡ መራቅ ፡ መወገድ ። ዘኒ ፡ ኀለፈ ፡ ወዘኒ ፡ ይመጽእ ። ወእምድኅረ ፡ ኀለፉ ፡ እሉ ። እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ኅልፍ ፡ (ሚራ ፴፱ ፡ ፲፱ ። ማቴ፳ ፡ ፲፫ ። መክ፫ ፡ ፳) ።

—፤ መሞት ፡ መለየት ፤ መቅረት ። ኀለፈ ፡ አሮን ፡ ወበክይዎ ። አሌ ፡ ለነ ፤ ካህነ ፡ አምላክ ፡ ኤርምያስ ፡ ኀለፈ ፡ እምኔነ ። ለዘከመ ፡ ዝ ፡ የኀልፎ ፡ ብዙኅ ፡ ረባሕ ፡ (ዘኍ ፳ ፡ ፳፱ ። ተረ ፡ ኤር ። ሚራ ፴፯ ፡ ፳) ።

—፤ መናፈቅ ፤ መሻት ፡ መመኘት ። ኀለፈት ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ አዕጻዲከ ፡ (መዝ ፡ ፹፫) ። ደግ ፡ መልካም ፡ ሲሉ ፡ ማለፊያ ፡ ማለት ፡ በማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ ምኅላፍን ፡ እይ ። ባለመጣፎች ፡ ኀለፈን ፡ ገባ ፡ ይሉና ፡ ምስክሩን ፡ ኀለፈት ፡ በንበት ። ወየኀልፍ ፡ ሐጽ ፡ ውስተ ፡ ሥጋሁ ፡ ይላሉ ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (ማር ፲፭ ፡ ፩ ። ኢዮ ፡ ፳፩) ። ዳግመኛም ፡ በኀለፈ ፡ ፈንታ ፡ ተኀለፈ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ዑቅ ፡ አልቦ ፡ ዘይትኀለፈከ ። ኢትትኀለፎ ፡ ለዘይስእለከ ፡ (ሮሜ ። ሚራ ፬ ፡ ፫) ።

ኀላፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ኀለፍት) ፤ የሚያልፍ ፡ መንገደኛ ፤ ዐላፊ ፡ ጠፊ ፤ ሟች ፤ ተለዋጭ ፤ ወረተኛ ። ኀላፊ ፡ ፍኖት ። ሖሩ ፡ ኀላፍያን ። ዐበጡ ፡ አሕይ ፡ እምኀለፍት ። ዓለም ፡ ኀላፊ ። መብልዕ ፡ ኀላፊ ። ዐርክ ፡ ኀላፊ ፡ (መዝ ፡ ፸፱ ። ሰቈ ፩ ፡ ፲፪ ። ቀሌ ። ዮሐ ፲፫ ፡ ፲፪ ። ሚራ ፯ ፡ ፲) ። በኀለፍት ፡ ፈንታ ፡ ኀላፊት ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ።

ኅሉፍ ፤ (ፉን ፡ ፉት ፡ ልፍት) ፤ ያለፈ ፤ የኼደ ። እሴሮ ፡ እርአይክሙ ፡ ኅሉፈ ። እስመ ፡ ኅሉፍ ፡ ገጽሙ ፡ ለኢየሩሳሌም ። ካህናትሰ ፡ ኅሉፋነ ፡ ፍኖት ፡ (ሮሜ ፲፭ ፡ ፳፱ ። ሉቃ ፲ ፡ ፴፫ ። ሆሴ ፮ ፡ ፱) ።

—፤ የተለየ ፡ ልዩ ፡ ልውጥ ። እስመ ፡ ከነ ፡ ኅላዌሁ ፡ ኅሉፈ ፡ እምኔሆሙ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ። የታለፈ ፤ የተዘለለ ።

ኅልፈት ፤ በቁሙ ፡ ማለፍ ፡ መኼድ ፤ አስተላለፍ ። በኅልፈተ ፡ ዐውሎ ። የኀልፍ ፡ ንብረትነ ፡ ከመ ፡ አሠረ ፡ ኅልፈተ ፡ ደመና ። ኅልፈትሙ ፡ ውስተ ፡ ባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ (ምሳ ፲ ፡ ፳፭ ። ጥበ ፪ ፡ ፬ ። አፈ ፡ ድ ፯) ።

—፤ መሞት ፤ መውጣት ፤ ከዓለም ፡ ከሥጋ ፡ መለየት ፤ መታጣት ፡ እንዳልነበረ ፡ መኾን ። ከመ ፡ ትዘከርዋ ፡ እምድኅረ ፡ ኅልፈትየ ። ኅልፈት ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ (፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። ስንክ) ።

—፤ መውጫ ፡ መጨረሻ ፤ ፍጻሜ ። ኅልፈተ ፡ ጊዜያት ፡ ወዓመታት ። ኅልፈተ ፡ መንግሥትከ ። እምከመ ፡ ሰምዐ ፡ ኅልፈቶ ፡ ለጊዜ ፡ ምንዳቤ ፡ (ጥበ ፰ ፡ ፰ ። ዮሴፍ ። አፈ ፡ ድ ፭) ። በኅልፈትና ፡ በፍልሰት ፡ ፈንታ ፡ ተኅልፎት ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። አ ፡ ነፍስ ፡ ናሁ ፡ በጽሐ ፡ ተኅልፎትኪ ፡ እምሥጋ ፡ (ማር ፡ ይሥ ፲፫ ፡ ፬) ።

(ጥ) ኅላፍ ፤ (ፉት) ፤ በቁሙ ፡ የብራና ፡ ስፌት ፡ ቀንጃ ፡ ኹለ ፡ ታጥፎ ፡ ተቀንሮ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፤ ወይም ፡ ተቀናጅቶና ፡ ተላልፎ ፡ በዚ ፡ ወገን ፡ በጥራዝ ፡ መካከል ፡ የሚገባ ፤ ፬ ፡ ገጽ ፡ ያለው ፡ እንዳንድ ፡ ሉሕ ፡ ወይም ፡ ቅጠል ። ቀንጃና ፡ ቅንጃም ፡ ባይኾን ፡ እንዱ ፡ ቅጠል ፡ ታጥፎ ፡ ወስፈ ፡ ያለፈበት ፡ ስንበሩ ፡ ኅላፍ ፡ ይባላል ። ሚራክን ፡ እይ ።

አኅለፈ ፤ አሳለፈ ፤ አሻገረ ። አኅለፍከነ ፡ ማእከለ ፡ እሳት ፡ ወማይ ፡ (መዝ ፡ ፷፭) ። በአኅለፈ ፡ ፈንታ ፡ አስተኅለፈ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። ይትክት ፡ ወያስተኀልፍ ፡ ዐይሜሁ ። ኢታስተኀልፍ ፡ ዐለተ ፡ እምዕለት ። ከመ ፡ ያስምዑ ፡ ወያስተኀልፉ ፡ ነገረ ፡ በሖሩ ፡ በሐውርት ፡ (ሚራ ፳፱ ፡ ፭ ። ኩፋ ፡ ፴፱ ። ኑሐ ፳ ፡ ፲፭) ።

ምኅላፍ ፤ (ፉት) ፤ ማለፊያ ፡ ማሳለፊያ ፤ መግቢያ ፡ መውጫ ፡ በር ፡ መንገድ ፤ በታ ። ኢወሀቦ ፡ ምኅላፈ ፡ እንተ ፡ ይወርሱ ። አልቦ ፡ ምኅላፍ ። ዳእሙ ፡ ምኅላፈ ፡ ክልኤቱ ፡ ዐይው ፡ ሖሰንታሁ ። ተኀጥእ ፡ ምኅላፈ ። ትገብር ፡ ለከ ፡ ምኅላፈ ፡ እንተ ፡ ይማስቀ ፡ (ዘኍ ፳፩ ፡ ፳፫ ። ኢዮ ፲፱ ፡ ፰ ። ዮዲ ፬ ፡ ፯ ። ፪ነገ ፡ ፳ ፡ ፴፬ ። ሆሴ ፪ ፡ ፳) ።

ማኅለፍት ፤ (ታት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ጸሎተ ፡ ማኅለፍተ ፡ ነፍስ ። ማኅለፍታተ ፡ ነፍሶሙ ፡ ግዑዝ ፡ ዘእንበለ ፡ ክልእት ፡ (ግንዘ) ። መንገደ ፡ ሰማይ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ተኅልፈ ፤ ታለፈ ፡ ተዘለለ ፤ ታለፈበት ፡ በላዩ ።

ተኃለፈ ፤ ተላለፈ ፡ ተሸጋገረ ፤ ዕልፍ ፡ ዕልፍ ፡ አለ ፤ የእግር ፡ የነገር ። ተመላለሰ ፤ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ ፡ ተዛወረ ። እንግዳ ፡ እለ ፡ ይትኃለፉ ፡ እምብሔር ፡ ለብሔር ። ተኃለፍኩ ፡ በሖሩ ፡ እስራኤል ። ሞዳእቱ ፡ ትትኃለፍ ፡ በሐይቀ ፡ ባሕር ፡ (ኪዳ ። ሄዜና ፡ ፲፯ ፡ ፮ ። ክብ ፡ ነገ) ።

ትኅላፍ ፤ መተላለፍ ፤ ዕልፈት ፡ ዐለፈታ ፡ ዕላፊ ፤ የነገር ። አልቦ ፡ ላዕሌየ ፡ ትኅላፍ ፡ (ቅዳ) ።

አስተኃለፈ ፤ አስተላለፈ ፤ አመሳቀለ ። አስተኃለፈ ፡ እዴሁ ፡ (ዘፍጥ ፵፰ ፡ ፲፬) ።

ኀልቅ ፤—ጕረሮ ፤ ድሬም ፤—ሐሊቅ ፡ ሐለቀ ።

ኀሊቅ ፤ ቆት ፤ (ኀልቀ ፡ የኀልቅ ፡ ይኅልቅ ። ዐረ ፡ ኀሊቀ ። ዕብ ፡ ሐላቅ ፤ ከፈለ) ፤ ማለቅ ፡ ማርጀት ፡ መጨረስ ፤ ተከቶ ፡ መጥፋት ። ሖሩ ፡ ግብር ፡ ይበሊ ፡ ወየኀልቅ ፡ ወገባሪሁ ፡ የኀልቅ ፡ ምስሌሁ ። እስከ ፡ ኀልቀ ፡ ሖሩ ፡ ክርታስ ፡ በእሳት ። ኀልቀ ፡ ወይዕዎሙ ። ኀሊቀ ፡ የኀልቅ ፡ እምገጹ ፡ ምድር ፡ (ሚራ ፲፬ ፡ ፲፱ ። ኤርሚ ፡ ፳፫ ። ዮሐ ፡ ፫ ። ዕብ ፡ ፩) ።

—፤ ማነስ ፡ መጉደል ፤ ሕጹጽ ፡ መኾን ። የኀልቅ ፡ ክብሩ ፡ ለያዕቆብ ። ኢየኀልቅ ፡ ወርኅኪ ፡ (ኢሳ ፲፯ ፡ ፬ ። ፷ ፡ ፳) ።

—፤ መከፈል ፡ መከፋፈል ፤ መለየት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መኾን ። ኢኀልቀ ፡ ሥጋ ፡ ዘተደመረ ፡ (ቄር) ።

—፤ መጨነቅ ፡ ለሞት ፡ መቅረብ ፤ ነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ ልለይ ፡ ልውጣ ፡ ማለት ፤ መቈረጥ ፤ የትንፋሽ ፡ የንገር ። ሶበ ፡ ኀ ልቀት ፡ ነፍስየ ። ይኀልቅ ፡ ነገሩ ፡ (ዮናÿ ፡ ፯ ። መዝ ፻፵፫ ። ጦቢ፰ ፡ ፱) ። ይባእ ፡ ነገረ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ኀበ ፡ ፈታሒት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ ይኀልቆሙ ፡ በበይናቲ ሆሙ ፡ ይባል ፤ የመሳሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፀ፳፪ ፡ ፱) ።

**ኀሉቅ** ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ልቅት) ፤ ያለቀ ፡ የተ ጨረሰ ፤ ቍርጥ ። ኀሉቅ ፡ ወምቱረ ፡ ነገረ ፡ ሰማዕኩ ። ኀሉቀ ፡ እነግር ፡ (ኢሳ፳፰ ፡ ፳፪ ። ፲ ፡ ፳፪ ። ኤር፲፰ ፡ ፯ ። ሮሜ፱ ፡ ፳፰) ።

**ኀልቀት** ፤ ማለቅ ፡ ተጨርሶ ፡ መጥፋት ፤ መክ ሳት ፡ ማነስ ፡ መጕደል ። ዘተነበይከ ፡ በይሁዳ ፡ ኀል ቀተ ፡ ኃጥኣን ፡ እምድር ። እምብዝኃ ፡ ኀልቀተ ፡ ሥ ጋሁ ፡ በእንተ ፡ አጽዋም ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ ። ገድ ፡ ተክ) ።

—፤ ማብቂያ ፡ መጨረሻ ፤ ፍጻሜ ። እስከ ፡ ኀልቀተ ፡ ዓለም ፡ (ዳን፲፪ ፡ ፱) ።

**ኀልቅ** ፤ ዕልቀት ፡ ዕልቂት ፡ ዕልቂያ ፡ ጥፋት ። ቀርበ ፡ ዕለተ ፡ ኀልቆሙ ፡ (ዘዳ፴፪ ፡ ፴፭) ።

**አኅለቀ** ፤ ፈጀ ፡ ጨረሰ ፡ ፈጸመ ፤ አጠፋ ። ወኢ ያኀልቀ ፡ ብዙኀ ፡ ብርተ ። እሳት ፡ አኀለቀ ፡ ሥነ ፡ ገ ዳም ። አኀለቆሙ ፡ በነደ ፡ እሳት ። አኀለቁ ፡ ኵሎ ፡ በሓውርተ ፡ አሞን ፡ (፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፲፰ ። ዮኤ፩ ፡ ፲፱ ። ሚራ ፻፰ ፡ ፲፱ ። ፩ዜና ፡ ፳ ፡ ፩) ።

—፤ አሳለቀ ፡ አስፈጀ ፡ አስጨረሰ ፤ አስደፈጊ ። አኀለቀ ፡ ዐጺደ ፡ ወይንየ ፡ በአባግዒሁ ፡ (ክብ ፡ ነገ ፡ ፸፪) ። በአኀ ለቀ ፡ ፈንታ ፡ አስተኀ(ኅ)ለቀ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ሉቃ፳፪ ፡ ፯) ።

**ማኅለቅት** ፤ ማለቂያ ፡ መጨረሻ ፤ ዳርቻ ፡ ፍ ጻሜ ። ጥንት ፡ ወማኅለቅት ። ይርአይ ፡ ማኅለቅቶ ፡ ለነገር ። ወማኅለቅቱሰ ፡ ለጽድቅ ፡ እሬት ። ወአልቦ ፡ ማኅለቅት ፡ ለመንግሥቱ ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፲፭ ። ማቴ፳፯ ፡ ፶፯ ። ሮሜ፲ ፡ ፬ ። ሉቃ፩ ፡ ፴፯) ።

**ተኃለቀ** ፤ ተላለቀ ፤ ተጫረሰ ፡ ተለያየ ፡ ተበታ ተነ ። ይትኃለቁ ፡ በበይናቲሆሙ ። ተኃለቁ ፡ በበይ ናቲሆሙ ፡ (፪ዜና ፡ ፳ ፡ ፳፫ ። ኢዮ፱ ፡ ፲፩) ።

**አስተኃለቀ** ፤ አስተላለቀ ፡ አጫረሰ ፡ አለያየ ፡ አፈራቀቀ ።

**ኈልቆ** ፤ **ቆት** ፤ (**ኈለቈ ፡ ይኄልቍ ፡ ይ ኈልቍ ። ዐረ ፡ ኀለቀ ፤ ፈጠረ ፡ ለየ ፡ አስታ ወቀ ፡ በቍጥር ። ዕብ ፡ ሐላቅ ፤ ከፈለ**) ፤ መቍ ጠር ፡ መተርተር ፡ መደመር ፤ ማብዛት ፡ መክፈል ። እን ዘኅና ፡ ሐሰበን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ አግዋር ፡ ናቸው ። ርኢ ፡ ከዋክብተ ፡ እመ ፡ ትክል ፡ ኈልቆቶሙ ። አቡ የሰ ፡ ይኄልቍ ፡ መዋዕሊ ። ኈለቍኒ ፡ ሎሙ ፡ ኵሎ ፡ ወ ደለውኒ ። ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢኈለቈ ፡ሎቱ ፡ እግዚ ኣብሔር ፡ ኀጢአቶ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፱ ። ጦቢ፱ ፡ ፬ ። ዕብ፳ ፡ ፴፱ ። መዝ ፡ ፴፩) ።

**ኈላቌ** ፤ (**ቍት ፡ ቍያን ፡ ያት**) ፤ የሚቈ ጥር ፡ ቈጣሪ ፡ ቍጥር ፡ ዐዋቂ ።

**መኈልቍ** ፤ (**ቍት ፡ ቋን ፡ ቋት**) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። መኍልቍ ፡ ከኢኍለቈም ፡ ሊወጣ ፡ ይችላል ፤ መስም ፡ ቅጽል ፡ ክድራጊና ፡ ክስደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ወጥቶ ፡ በማድረግም ፤ በማስደረግም ፡ በ፪ ፡ ስልት ፡ ይፈታል ።

**ኍልቍ** ፤ (**ቋት**) ፤ ቍጥር ፤ ሒሳብ ፤ በየስሙና ፡ በያኃዙ ፡ ልክና ፡ መልክ ፡ ውሳኔ ፡ ያለው ፡ ክንድ ፡ እስከ ፡ ምእልፊት ፡ በየቤቱ ፡ በየመክብቡ ፡ የሚጣፍና ፡ የሚነ ገር ። በዝኀ ፡ እምኍልቍ ። አልቦ ፡ ኍልቍ ፡ ለጥበ ቢሁ ። በአምጣነ ፡ ኍልቆሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ። በኍልቈ ፡ መዋዕል ፡ ዘሰከብከ ። በኍልቈ ፡ አህጉሪከ ፡ አማልክቲከ ፡ (መዝ ፡ ፴፱ ። ፻፵፯ ። ሚራ፻፵ ፡ ፲፭ ። ሕ ዝ፬ ፡ ፬ ። ኤር፪ ፡ ፳፰) ።

**አኈለቈ** ፤ አስቈጠረ ፡ አሳሰበ ፡ ቍጥር ፡ አስተ ማረ ።

**ተኈለቈ** ፡ ተቈጠረ ፤ ከቍጥር ፡ ገባ ። ተኈ ለቈ ፡ ምስለ ፡ ኃጥኣን ፡ (ኢሳ፶፫ ፡ ፲፪) ።

**ኍሉቍ** ፤ **ቅ** ፤ (**ቃን ፡ ቃት ፡ ልቍት**) ፤ የተቈጠረ ፤ ከቍጥር ፡ የገባ ። እንዘ ፡ ኍሉቅ ፡ ምስሌነ ። ወምስሌሆሙ ፡ ኍሉቍ ። እለ ፡ ተርፉ ፡ ይከውኑ ፡ ኍሉቃነ ። ሥዕርተ ፡ ርእስክሙ ፡ ኵሎን ፡ ኍሉቃት ፡ እማንቱ ፡ (ግብ፩ ፡ ፲፯ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ኢሳ፲ ፡ ፲፱ ። ማቴ ፲ ፡ ፴ ። ሉቃ፲፪ ፡ ፯) ።

**ኍላቌ** ፤ (**ቍያት**) ፤ መቍጠር ፤ መቈጠር ፡ አቈጣጠር ፡ ቈጠራ ፤ ቍጥር ። ያእምር ፡ ኍላቌሁ ፤ ወኍላቌሁኒ ፡ ስድስቱ ፡ ምእት ፡ ስሳ ፡ ወስድስቱ ፡ (ራእ፲፫ ፡ ፲፰) ።

**ኀምዝ** ፤-**መርዝ** ፤-**ሐሚዝ** ፤ **ሐመዘ** ።

**ኀመየ** ፤—**ዐማ** ፤ **ነቀፈ** ፤—**ሐምይ** ፡ **ሐመየ** ።

**ኈምዮ** ፤ **ዮት** ፤ (**ኈመየ ፡ ይኄሚ ፡ የ ኀሚ**) ፤ ማሰር ፡ መቀፈድ ። ኀመይዎ ፡ ለእግዚእነ ። አዘዘ ፡ የኀምይዎሙ ፡ ውስተ ፡ ክሣውዲሆሙ ፡ (ማር፲፭ ፡ ፩ ። ዮሐ፲፰ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፱) ።

**ኀማዪ** ፤ የሚያስር ፡ አሳሪ ፤ ባለወግ ።

**አኈመየ** ፤ (**ያኄሚ ፡ ያኀሚ**) ፤ አሳሰረ ፡ ሳ ሳሪ ፡ ሰጠ ።

**ተኀመየ** ፤ ታሰረ ፡ ተጋዘ ፤ እጅ ፡ እግሩን ፡ ተያዘ ።

**ኀሙይ** ፤ (**ያን ፡ ያት ፡ ሚት**) ፤ የታሰረ ፤ እስር ፡ እስረኛ ፡ ግዞተኛ ። ወፈነዎ ፡ ሐና ፡ ኀሙዮ ። ኢየሱስ ፡ ኀሙይ ፡ በእንቲአነ ፡ (ዮሐ፲፰ ፡ ፳፬ ። ደራሲ) ።

**ኀማዪ** ፤ ማሰር ፤ መታሰር ፤ አስተሳሰር ፡ እስ ራት ። በእንተ ፡ ኀማዪክ ፡ በእደ ፡ አይሁድ ፡ ክመ ፡ በራቂ ፡ (አዋል) ።

**ማኅሜ** ፡ (**ያት**) ፤ ማሰሪያ ፤ መታሰሪያ ። ፈ ትሐ ፡ ማኅሜሁ ፡ እመዝራዕቱ ። ወፈትሖ ፡ እማ ኅሜሁ ፡ በአክዮር ። እበትክ ፡ ማኅሜክ ፡ (መሳ፲፭ ፡ ፲፬ ። ዮዲ፮ ፡ ፲፫ ። ናሖ፩ ፡ ፲፫) ።

**ኀመለ ፤—ለቀመ ፤—ሐሚል ፡ ሐመለ ።**

**ኅምር ፤ (ዐረ) ፤** የወይን ፡ ጠጅ ፡ የጥቍር ፡ ቀይ ፡ ደባብ ።

**ኅምራዊ ፤** ዐይነቱ ፡ ወይም ፡ ቀላቱ ፡ የጥቍር ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ የሚመስል ። መሻች ፡ መሸተኛ ፡ ሸያጩና ፡ ገዥው ።

**ኀምር ፤** ገዳ ፡ ከማሁ ፡ ለኅምር ፡ ቀይ ፡ ዐይነት ።

**ኀመሰ ፤—ፀመሰ ፤ ዋና ፤—ሐምስ ፡ ሐመሰ ።**

(ጥ) **ኀምስ ፤ ሰት ፤ (ኀመሰ ፡ ይኄምስ ፡ የኀ ምስ ። ዐረ ፡ ኀመሰ ። ሱር ፡ ወዕብ ፡ ሐሜሽ) ፤** ዐምስት ፡ ማድረግ ፤ ከምስት ፡ መክፈል ፡ እስከምስት ፡ ጊዜ ፡ መመላለስ ። ዘይኄምሶን ፡ ለኬክሮሳተ ፡ በዓታት ፡ ከመ ፡ ይኩና ፡ መዓርገ ፡ ጸሎታት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ኀማሲ ፤ ሙኀምስ ፤ (ስት ፡ ሳን ፡ ሳት) ፤** ዐምስት ፡ የሚያደርግ ፡ ከምስት ፡ የሚከፍል ፡ ከፋይ ፤ ዐምስት ፡ ባይ ።

**ተኀመሰ ፤** ዐምስት ፡ ኾነ ፡ ዐምስት ፡ ተባለ ፡ ከምስት ፡ ተከፈለ ።

**ኀሙስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ምስት) ፤** ዐምስት ፡ የኾነ ፡ የተባለ ፡ ከ፭ ፡ የተከፈለ ፡ ፭ነት ፡ ያለው ።

**ኀማሴ ፤** ዐምስት ፡ መኾን ፤ ዐምስትነት ።

**ኀምስ ፤** ዐምስት ። የልክና ፡ የጊዜ ፡ ቅጽል ፤ በቁ ። ዐሥር ፡ ወኀምስ ፡ በእመት ። ኀምስ ፡ ቀሁ ፋቲ ፡ አይሁድ ፡ (ዘዐ፴፯ ፡ ፲፱ ። ፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፬) ።

**ኀምስ ፤ (ዕብ ፡ ኤምጻእ ፤ ውስጥ ፡ መካከል ። ሐሜሽ ። ሱር ፡ ሑምሻ ፤ ሆድ ፡ የወገብና ፡ የቋን ፡ መገናኛ ፡ ብሽሽት ፡ ጉያ) ፤** በቁሙ ፡ ማሕፀን ፤ እፈ ፡ ማሕፀን ፡ የሴቶች ፡ ዐምስተኛ ፡ ሕዋስ ። ፭ኛነቱም ፡ ከንገት ፡ በላይ ፡ ላሉት ፡ ላፌቱ ፡ ነው ። ኀምሳ ፡ ለወላዲትከ ። ዘይፈትሕ ፡ ዙሎ ፡ ኀምስ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፰ ። ዘፀ፲፫ ፡ ፪ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭) ።

**ኀምስ ፤** የቍጥር ፡ ስም ፡ በሴት ፡ አንቀጽ ፡ ዐምስት ፡ ማለት ፡ ነው ። ኀምስ ፡ ለዋልድ ። ኀምስ ፡ አህጉረ ፡ ግብጽ ፡ ይነብባ ። ኀምስ ፡ ኀብስት ። ዐሥሮን ፡ ደናግል ፤ ወእምኔሆን ፡ ኀምስ ፡ አብዳት ፡ ወኀምስ ፡ ጠባባት ፡ (፳ነገ ፡ ፳፭ ። ማቴ ፡ ኢሳ፲፱ ፡ ፲፰ ። ማቴ፲፬ ፡ ፲፯ ። ፳፭ ፡ ፪) ።

**ኀምስት ፡ ቱ ፤** ገዳ ፡ ከማሁ ፡ በቁሙ ፡ በወንድ ፡ አንቀጽ ። ወነበረ ፡ በዘከመ ፡ ዝ ፡ ግብር ፡ ኀምስተ ፡ ዓመተ ። ኀምስቱ ፡ ዕደው ፡ ነበሩ ፡ ምስሌሁ ። ኀምስቲነ ፡ (ፊልክ ። ዮሐ፬ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፱) ። ቱ ፡ ባርቲክልነት ፡ ወይም ፡ ባጸፋነት ፡ ሲፈታ ፡ ዐምስቱ ፡ ዐምስተኛው ፡ ከምስት ፡ አንዱ ፡ ያሰኛል ። ውስተ ፡ ኀምስቱ ፡ ለማይ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ፳ ፡ ፭) ።

**ኀሙስ ፤** የዕለት ፡ ቅጽልና ፡ ስም ፡ ዐምስት ፡ ዐምስተኛ ። ተፀገሁ ፡ ዓዲ ፡ ኀሙስ ፡ መዋዕለ ። ወእምድኅረ ፡ ኀሙስ ፡ መዋዕል ። እመ ፡ ኀሙሱ ፡ ለሠርቅ ፡ ቅጽል ፡ (ዮዲ፯ ፡ ፴ ፡ ፳ ፡ ፱ ። ሕዝ፴፫ ፡ ፳፩) ። ዕለተ ፡ ኀሙስ ፡ ምሴት ፡ ኀሙስ ፤ ስም ። (ግጥም ፡ ስባጤ ፡ ቴዎ ፡ ሞት) ፡ አምላክን ፡ መስሎ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ኀውና ፡ ሐሩ ፡ ሲል ፡ ዐሙስ ፡ ሰኞ ፡ መቅደላ ፡ ተጠንቀ ፤ ሰው ፡ መኾኑ ፡ ታወቀ ።

**ኀምሳ ፤ (ን—ዃ) ፤** በቁሙ ፡ ዐምሳ ፡ ፶ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ፡ ወይም ፡ ፲ ፡ ጊዜ ፡ ዐምስት ። ኀምሳ ፡ ወኀምስተ ፡ መዋዕለ ። ኀምሳ ፡ በእመት ። በዓለ ፡ ኀምሳ ። ወበኀምሳ ፡ ዕለት ። ኀምሳ ፡ ዓመት ፡ አልብከ ፡ (ጦቢ ፳ ፡ ፳፭ ። ሕዝ፵ ፡ ፲፭ ። ዲድ ፡ ፴ ። ቅዳ ። ዮሐ፰ ፡ ፶፯) ።

**ኃምስ ፤ (ስት) ፤** ዐምስተኛ ፡ ከምስት ፡ አንዱ ፡ ዐምኛ ። ወለደት ፡ ወልደ ፡ ኃምስ ። ወበኃምስ ፡ ትውልድ ፡ ዐርጉ ፡ እምግብጽ ። ኢዮብ ፡ ኃምስ ፡ እምአብርሃም ። በኃምስ ፡ ወርኅ ፡ (ዘፍ፴ ፡ ፲፯ ። ዘፀ፲፫ ፡ ፲፰ ። ታሪ ፡ ኢዮ ። ኤር፳ ፡ ፪) ።

**ኃምሳዊ ፤ ይ ፤ (ዊት ፡ ሲት) ፤** ገዳ ፡ ከማሁ ። ግዘት ፡ ኃምሳይ ። ዘአውሰበ ፡ ራብዒተ ፡ አው ፡ ኃምሲተ ፡ (ያዕ ፡ ዘኢል ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፱) ።

**ኃምሲት ፤** የኬክሮስ ፡ ዐምስቲያ ፡ ክፍል ፡ በራብዒትና ፡ በሳድሲት ፡ ማኽል ፡ ያለች ። አንዲቱ ፡ ኃምሲት ፡ ስሳ ፡ ሳድሲት ፡ ትኾናለች ፤ ኬክሮስን ፡ እይ ። በመካነ ፡ ሳድሲት ፡ ኍልቁ ፡ ኃምሲት ፡ (አቡሻ ፡ ፲፩) ።

**ታኅማስ ፤** ዐምስት ፤ ዐምስተኛ ። ታኅማስ ፡ ዓመታት ፡ ሠለስቱ ። ስመንቱ ፡ ሰዓት ፡ ወአርባዕቱ ፡ ታኅማስ ፡ ሰዓት ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲፰ ። ሚያ፲፭ ። አቡሻ ፡ ፲፱) ።

**ትኅምስት ፤** ዐምስትነት ። ዐምስት ፡ እጅ ፤ ዐምስት ፡ ሰጥፍ ። ህየንተ ፡ አሐዱ ፡ ላሕም ፡ ይፈዲ ፡ ትኅምስተ ። ሠለስቱ ፡ ትኅምስተ ፡ ብርሃን ፡ (ዘፀ፳፩ ፡ ፴፯ ። ሔኖ፸፰ ፡ ፯) ።

**መኅምስት ፤** ዐምስት ፡ ወገን ፡ ዐምስት ፡ ክፍል ፡ ዐምስት ፡ እጅ ፡ (ዘፍ፵፫ ፡ ፴፬) ።

**ኀነበ ፤—አንበ ፤—ነብዐ ፡ አንብዕ ።**

**ኀንባብ ፤—ፍሬ ፤—ሐንበበ ።**

**ኀንገር ፤ (ዕብ ፡ ሐጌር) ፤** ዐንካሳ ፡ ልምሻ ፡ ጥምልምል ፡ የሚድኽ ፡ የሚንፏቀቅ ። ግሒ ፡ ሽኮኮ ፡ እግረ ፡ ኮንትሽ ፤ ዐጫጭር ። ገሐየን ፡ እይ ።

**ኀንገረ ፤** ዐነከሰ ፡ ዐንካሳ ፡ ኾነ ። ተሸከመ ፡ እንኮኮ ፡ ወይም ፡ አሽኮኮ ፡ አለ ። እግር ፡ ስሌለው ፡ እግር ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በገድል ፡ በታምር ፡ በድርሰት ፡ ይገኛል ።

**ኀንንት ፤** ዕንቅርት ፤ ያንገት ፡ ደዌ ።

**ኀነፈ ፤ ሐናፊ ፤ (ዕብ ፡ ሐኔፍ ። ሱር ፡ ሐንፋእ ፤ ሐንፋዩ) ፤** ዐላዊ ፡ ከሓዲ ፡ ሸንጋይ ፡ አታላይ ፡ ግብዝ ፡ አረመኔ ፤ ስመ ፡ ነገድ ፡ ከፊቱ ፡ ነገደ ፡ ተንባላት ፡ አንዱ ፡ የቀሩትም ፡ ሦስቱ ፡ ሐንበሊ ፡ መለኪ ፡

ሽፍጮ ፡ ይባላሉ ። ሃይማኖታቸውም ፡ እንደ ፡ ስማቸው ፡ አራት ፡ ነው ፤ አይተባበርም ። እምውሉደ ፡ ኀነፌ ፡ አረማውያን ፤ (ስንክ ፡ ማንኟ) ።

**ኀነፋዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ የኀነፈ ፡ ወገን ፤ አረመኔ ፡ ተንባላታዊ ። ወበመዋዕሊሁ ፡ አስተርአየት ፡ አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ኀነፋዊት ፡፡ ንጉሠ ፡ ምስር ፡ ኀነፋዊ ፤ (ዮሐ ፡ መደ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፭) ።

**ኆኆፌ** ፤ መናፍቅ ፤ ገበር ፡ ዐንጕል ፡ ሕዝብ ፡ ሃይማኖቱ ፡ የተበላሸ ፤ እንደ ፡ ቅማንት ፡ እንደ ፡ ተንባላት ፡ ያለ ። ወደገጸመው ፡ በኀቡእ ፡ ፍኖት ፡ ለእለ ፡ ኆኆፌ ፤ (አፈ ፡ ድ፪ ። ተግ፱) ።

**ኀንፈጠ** ፤—ጫረ ፡ ጐፈጠረ ፤—ሐንፈጠ ።

**ኀንፈጠ** ፤—ቀረጠ ፤—ነፈጥ ፡ ኀፈጠ ።

**ኀንፈጸ** ፤—አጕለበ ፤—ነፍጸ ፡ ሐንፈጸ ።

**ኀንጽጸ** ፤ ጸት ፤ (ኀንጸጸ ፡ የኀነጽጽ ፡ የኀንጽጽ ። ሐንፈጸ) ፤ መጠርጠር ፡ ማውሰብ ፤ በጥርስ ። ማንጠርጠር ፡ ማበጠር ፡ ማንዘርዘር ፤ በስፌድ ፡ በወንፊት ፡ (ሉቃ፳፪ ፡ ፴፩) ። ማንጠጥ ፡ መቅረጥ ፤ የቀንድና ፡ የንጨት ።

**ተኀንጸጸ** ፤ ተጠረጠረ ፤ ተንጠረጠረ ። ይትኀንጸጹ ፡ ከመ ፡ ፀሰስ ፤ (ስንክ ፡ ጳጕ፭) ።

**ኀንጻጽ** ፤ (ጻት) ፤ ጥርጣሬ ፤ እንጥርጣሬ ፡ ንፋሽ ፡ ገለባ ፡ ልቃሚ ፡ ብጣሪ ። ንፋቂና ፡ ኀንጻጽ ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ። (ማጥም ፤ አቶ ፡ ስይፉ ፡ ከድተዋል ፡ ተብለው ፡ ከታሙ ፡ በኋላ ፡ በፍቅር ፡ መጥተው ፡ ሲገናኙ) ፤ አስጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ማን ፡ እሽት ፡ አምጥቷል ፤ በዚህ ፡ በቤታችሁ ፡ ጥርጣሬ ፡ መልቷል ። የእሳት ፡ ፍንጣሪ ፤ የምጣድ ፡ ብልጭልጭታ ። ቀለምጺጻን ፡ እይ ።

**ኀኒቅ** ፤ ቆት ፤ (ኀነቀ ፡ የኀንቅ ፡ ይኀንቅ ። ዐረ ፡ ኀነቀ ። ሱር ፡ ሕናቅ ። ዕብ ፡ ሐናቅ) ፤ ማነቅ ፡ ማስጨነቅ ፤ ጕሮሮን ፡ ዐንገትን ፡ አጥብቆ ፡ ሰቅስቆ ፡ መያዝ ፡ ማሰር ፡ ለመግደል ፤ አፍን ፡ አፍንጫን ፡ ማፈን ፡ መድፈን ፡ ትንፋሽ ፡ መከልከል ። ዐንቀን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ፤ ለክፉም ፡ ለበጎም ፡ ይኾናል ፤ ኀነቀ ፡ ግን ፡ ለክፉ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፳ ። ፲፰ ፡ ፳፰ ። ፳ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፴፭) ። ኀነቀኒ ፡ አፈ ፡ መልበስየ ፡፡ ኀነቀ ፡ መንፈስ ፡ እኩይ ፡፡ ወሰይ ፡ እንዘ ፡ የኀንቅ ፡ ከማይ ፤ ወያረውጸ ፡ ጕጕአ ፡፡ ንኀንቃ ፡ ለነፍስነ ፡ ወንሰጕማ ፡ ከመ ፡ ፈረስ ፡ ኀያል ፡ ወድሩክ ፤ (ኢዮ፴ ፡ ፲፰ ። ፳ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ። ገድ ፡ ተክ ። አፈ ፡ ተ፴፭) ።

**ኀናቂ** ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት ፤ ነቅት) ፤ የሚያንቅ ፡ ዐናቂ ፡ ዐንቆ ፡ ገዳይ ።

**መኀንቅ** ፤ (ብ ፡ መኃንቅ) ፤ የሚያንቅ ፤ ማነቂያ ፡ ማነቆ ፤ ሸምቀቆ ።

**አኀንቀ** ፤ አሳነቀ ፡ አስገደለ ።

**ተኀንቀ** ፤ ታነቀ ፡ ታንቆ ፡ ሞተ ፤ በሌላ ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ በገዛ ፡ እጁ ። እንዘ ፡ ይትኀነቁ ፡ አምታትኪ ፡፡ እስከ ፡ ትሬቱ ፡ ትትኀነቅ ፡፡ ተኀንቀ ፡ ወሞተ ፡፡ ፈቀደ ፡ ይትኀንቅ ፡ በእዴሁ ፤ (ወዐቢ ፡ ፰ ፡ ፲ ። ማቴ፳፯ ፡ ፭ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ኀኑቅ** ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ንቅት) ፤ የታነቀ ፡ የተጨነቀ ፡ ታንቆ ፡ ታፍኖ ፡ የሞተ ። ዘርዐ ፡ ትኑፋቲሆሙ ፡ ኀኑቅ ፡ በሥክ ፤ ዝ ፡ ዓለም ፡፡ ምቱረ ፡ ልሳን ፡ በመጥባሕት ፡ ወኀኑቅ ፡ ጕርዔ ፡ በእድ ፡፡ በሊዐ ፡ ደም ፡ ወኀኑቅ ፤ (ፊልክ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳ ፡ ፲፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫) ።

**ኀንቀት** ፤ ማነቅ ፡ መታነቅ ፤ አስተናነቅ ፡ ዕንቂያ ፡ ዕንቂት ፤ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ (ስንክ ፡ ሐም፪ ። መጽ ፡ ምስ) ። ኀንቀተ ፡ ፍትወት ፤ (ግንዘ) ።

**ኀንቅርት** ፤ በቁሙ ፤ ዕንቅርት ፤ ዥልዥልት ፡ ያንገት ፡ የማንቍርት ፡ ተቀጥላ ፡ ጕረሮ ፡ የሚያንቅ ፡ የሚያስጨንቅ ። (ተረት) ፤ የግፍ ፡ ግፍ ፡ በንቅርት ፡ ላይ ፡ ጆሮ ፡ ደግፍ ። ኀንቅርት ፡ ዘወፅአ ፡ በክሣዱ ፤ (መ ፡ ፈ) ። ክንንቅና ፡ ክንቀረ ፡ የተደቀለ ፡ ስም ፡ ንውና ፡ ንቀረንና ፡ አንቀረን ፡ እይ ።

**ኀንቅርት** ፤—ከውር ፤—ሕንቅርት ፡ ንቀረ ።

**ኀሠወ** ፤—ዋሸ ፡ ዐበለ ፤—ሐሰዎ ፡ ሐሰወ ።

**ኀሥል** ፤—ዳውላ ፤—ሐሲል ፡ ሐሰለ ።

**ኀሠመ** ፤—ከፋ ፤—ሐሚም ፡ ሐሠመ ።

**ኀሢሥ** ፤ ሦት ፤ (ኀሠ ፤ ኀሠሠ ፡ የኀሥሥ ፡ ይኀሥሥ ። ዕብ ፡ ሐሻሽ ፤ ሐየጸ ። ቤቄሽ ፤ ፈለገ) ፤ ማሠሥ ፡ መሻሰስ ፡ መጥረግ ፤ ማበስ ፤ ማደፍ ፡ መወልወል ፤ የምጣድ ። ኢትኀሥሥ ፡ አጽሕልተ ፡ ወኢትልሕስ ፡ መጻብኅተ ፡፡ ውሒዘ ፡ አንብዕ ፡ ኀሠሠ ፡ በአጽባዕተ ፡ እዴሁ ፡ ልምሉም ፡፡ ወኀሠሠት ፡ አንብዕየ ፡ በአጻብዒሃ ፤ (ሚሊ፬ ፡ ፲፬ ። ደራሲ ። ደር ፡ መድ) ።

—፤ መሻት ፡ መፈለግ ፡ መለመን ፤ ለማግኘት ። ኀሡ ፡ አእዱጊነ ፡፡ ተኀሥሥሙ ፡ ወኢትረክቡሙ ፡፡ ኀሡ ፡ ወአስተብቍዑ ፤ (፩ነገ ፡ ፱ ፡ ፫ ። ኢሳ፵፩ ፡ ፲፪ ። ቅዳ) ።

—፤ መጠየቅ ፡ መመርመር ፤ ለማወቅ ። እለ ፡ የኀሥሡ ፡ በእንተ ፡ ሕይወት ፡ እምነ ፡ ሙታን ፡፡ ኢትኀሥሥ ፡ እፎ ፡ ይትኼነኑ ፡፡ ለኀሢሥ ፡ ወለፈቲን ፡ በጥበብ ፤ (ኢሳ፰ ፡ ፲፱ ። ሉቱ ፡ ዕገ፬ ፡ ፲፬ ። መክ፩ ፡ ፲፫) ።

—፤ መውደድ ፡ መፍቀድ ፤ መከጀል ፡ መመኘት ። ምስጢሩ ፡ ያው ፡ መፈለግ ፡ ነው ፤ ከመሻት ፡ አይወጣም ። ኀሥሡ ፡ ትግበር ፡ ሠሎ ፡ ዘይሠምሮ ፡ ለእግዚ ፡፡ ኀሠሡ ፡ መኳንንቲ ፡ ከመ ፡ ይክሐዱ ፡ ለክርስቶስ ፤ (ዲድ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ መጋ፳) ። በኀሠሣና ፡ በተኃሥሦ ፡ ፈንታ ፡

ተኀሠሠ ፡ ይባል ፤ የጣፈና ፡ የመሳሽ ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ኢይትኀሠሥ ፡ ሎቱ ፡ እኩየ ፡ ዘሎ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወትየ ። እትኀሠሥ ፡ አባግዕየ ፡ እምእደ ፡ ኖሎት ። እለ ፡ ይትኀሠሠ ፡ በእንተ ፡ ፍልሰተ ፡ ሔኖክ ፡ ወኤልያስ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፰ ። ሕዝ፴፬ ፡ ፲ ። አፈ ፡ ድ፳፪) ።

**ኅሣሢ** ፤ (ሢት ፡ ሥያን ፡ ያት) ፤ የሚያሥሥ ፡ ዐሣሽ ። ፈላጊ ፡ መርማሪ ። ኀሣሢ ፡ ነቢብ ። በኪዩ ፡ ኀሣሢ ፡ ዕዳ ፡ ውእቱ ። ኀሣሥያነ ፡ መንግሥት ፡ በማያት ። ኀሣሥያተ ፡ ንዋየ ፡ ባዕድ ፡ (ኢዮ፲፭ ፡ ፲፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፯ ። ማን፱ ። ዲድ ፡ ፲፬) ።

**ኀሠሣ** ፤ (ሣት) ፤ ፍላጎት ፡ ፍለጋ ፤ ጥያቄ ፡ ጥየቃ ፤ ምርምር ፡ ምርመራ ፡ ፈቃድ ፡ መፍቅድ ፤ ሐሳብ ፡ ምኞት ። ብየ ፡ ኀሠሣ ፡ እምኔሬትክሙ ። ንኤሊ ፡ በእንቲኣሁ ፡ በብዙኀ ፡ ኀሠሣ ። ተተክለት ፡ ፍትወት ፡ በጠባይዐ ፡ እንስሳዊት ፤ ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ኀሠሣ ፡ ተራክቦ ፡ ዘእምኔሁ ፡ ይከውን ፡ ዘርዕ ። ይኩን ፡ ፈቃዱ ፡ ወኀሠሣሁ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ትሑታነ ፡ (ስንክ ፡ የካ፳፰ ። አፈ ፡ ድ፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፩ ። ፲ ፡ ፪) ። ጕርጕር ፡ ዐሠሣ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ማኅሠሥ** ፤ (ማሠሻ) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ። ብዙኀ ፡ ጻሕቀ ፡ ወፍድፋደ ፡ ማኅሠሠ ። እንዘ ፡ ይትሰአኩዎ ፡ ዘልፈ ፡ መላእክት ፡ ለማኅሠሠ ። ሶበ ፡ አናኅኩ ፡ ማኅሠሠ ። ማኅሠሥ ፡ ዘባዕለ ፡ እምልብ ፡ (ስንክ ፡ መስ፳ ። ግንቦ፲፩ ። ሐም፮ ። ቄር ፡ እስት) ።

**መንኮ(ኖ)ሥሥ** ፤ (ሣት ፤ **አው ፡ መኳሥሥት**) ፤ ሹካ ፡ መንካ ፡ ጭልፋ ፤ የሥጋ ፡ ማውጫ ። ጕጠት ፡ የጥርስ ፡ መንቀያ ። መንኮሥሥ ፡ ዘሠለስቱ ፡ ስነኒሁ ። መኳሥሥት ፡ ወፍያላት ። መንኮሥሠ ፡ ስነ ፡ (፩ንገ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ። ዘኍ፬ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ ጥር፲፭) ።



መንኮሥሥ ፤

**ተኀሥሠ** ፤ ታሠሠ ። ተሻ ፡ ተፈለገ ፤ ተመረመረ ። ጥበብ ፡ ተኀሠሠት ፡ በኀበ ፡ ዘሎሙ ፡ ቀደምት ። እትኀሠሥ ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ። ለእመ ፡ አነ ፡ ቀተልኩከ ፡ እትኀሠሥ ፡ በቅትለትከ ፡ (ሚራ፴፱ ፡ ፩ ። ሕዝ፴፮ ፡ ፴፯ ። ዮሴፍ) ።

**ኅሡሥ** ፤ (ሣን ፡ ሣት ፡ ሥሥት) ፤ የታሠሠ ፡ የተሻ ፡ የተፈለገ ።

**ኅሥሥት** ፤ በቁሙ ፡ ዕሥሥት ፤ የንሽላሊት ፡ ዐይነት ፤ መልኳ ፡ እንደ ፡ ሌት ፡ ቀን ፡ የሚለዋወጥ ፡ ጠንቋዮች ፡ አጥብተው ፡ የሚሸጧት ።



ኅሥሥት ፤

**ኀሣሢ** ፤ ማሠሥ ፡ መታሠሥ ። (ሳ ፡ ጥ) መሻት ፡ መፈለግ ፤ መመርመር ፡ አመራመር ። ምርመራ ፤ ምርማሪ ፤ መሳ ፡ ማምት ፤ ጥንቈላ ፡ ሟርት ፡ (ኩፋ ፡ ፲፩) ።

**ተኃሠሠ** ፤ ተፈላለገ ፡ ተመራመረ ፤ ተከራከረ ። ኢይትኃሠሡ ፡ በበይናቲሆሙ ። እኄዙ ፡ ይትኃሠሥዎ ። ወከነ ፡ ተኃሥሦ ፡ (ኢሳ፴፬ ፡ ፲፮ ። ማር፰ ፡ ፲፩ ። ዮሐ፫ ፡ ፳፭) ።

**አስተኃሠሠ** ፤ አፈላለገ ፡ አመራመረ ።

**መስተኃሥሥ** ፤ (ሥት ፡ ሣን ፡ ሣት) ፤ አመራማሪ ፤ ተመራማሪ ። መስተኅሥሥ ፡ ብሎ ፡ በግእዝ ፡ ኀ ፡ ሲጣፍ ፡ ማን ፡ አድራጊ ፡ ኹኖ ፤ ኀሣሢ ፡ መኀሥሥ ፤ ፈላጊ ፡ መርማሪ ፡ ያሰኛል ። በእመ ፡ ከነ ፡ መስተኀሥሣነ ፡ በእንተ ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ ባሕቲቱ ። መስተኀሥሣን ፡ ለእከይ ፡ (ፊልክ ፡ ፶፰ ። ሮሜ፩ ፡ ፴፩) ።

**ታኅሣሥ** ፤ ምርምር ፡ ምርመራ ፤ ፍላጎት ፡ ፍለጋ ። በቁሙ ፡ ትኅሥ ፤ የወር ፡ ስም ፤ የመስከረም ፡ አራተኛ ። ወርኀ ፡ ተኃሥሦ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ማቴ፪ ፡ ፩—፮) ።

**ታኅሣሥ** ፤ (ትግሬኛ) ፤ ስመ ፡ ዕፅ ፤ ከትክታ ፤ ቅጠሉ ፡ ቀንበጡ ፡ ለሐዲስ ፡ ምጣድ ፡ ማሰሻ ፡ ማሠሻ ፡ የሚኾን ። ዕንጨቱም ፡ እንደ ፡ ፍየል ፡ ፈጅ ፡ ተቀጥቅጦ ፡ መብራት ፡ ይኾናል ።

**ኀሢዕ** ፤ ዖት ፤ (**ኀሥዐ ፡ የኀሥዕ ፡ ይኅሣዕ ። ዐረ ፡ ኀሸዐ ። ዕብ ፡ ሐሻህ**) ፤ ማረፍ ፤ ዝም ፡ ጸጥ ፡ ማ ፡ ማለት ፤ አለመታወክ ። መብረድ ፡ መቀዝቀዝ ፤ የቍጣ ፡ የጠብ ። ኀበ ፡ ኢሀሎ ፡ መዐትም ፡ የኀሥዕ ፡ ጋእዝ ። መዐት ፡ ይኀሣዕ ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፳ ። ቅዳ ፡ ኪዳ) ።

**አኅሥዐ** ፤ አሳረፈ ፡ ዝም ፡ አሰኘ ፤ አበረደ ፡ አበ ታገሠ ። ሞገደ ፡ ባሕር ፡ አኅሥዐ ፡ ክርስቶስ ። መዐተ ፡ ብእሲ ፡ ያኀሥዕ ፡ ገብር ፡ ጠቢብ ። አኅሥዐ ፡ መቅሠፍተ ። ኢይክሉ ፡ ያኅሥዑ ፡ አጽባአ ፡ ዐጸባተ ፡ (ኪዳ ። ምሳ፲፰ ፡ ፲፬ ። ጥበ፲፰ ፡ ፳፭ ። ፊልክ ፡ ፻፶፯) ።

**ኀሢፍ** ፤ ፎት ፤ (**ኀሠፈ ፡ የኀሥፍ ፡ ይኅሥፍ ። ዐረ ፡ ኀሸፈ ። ዕብ ፡ ሐሳፍ**) ፤ ማከክ ፡ ማቍሰል ፤ መላጥ ፡ መምለጥ ፡ መቅረፍ ፡ መግፈፍ ፤ መማለጥ ።

**ተኀሥፈ** ፤ ታከከ ፡ ቈሰለ ፤ ተላጠ ፡ ተነካ ።

**ኅሡፍ** ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ሥፋት) ፤ ያከከ ፡ የታከከ ፤ ቍስላም ፡ ዕከካም ፡ (ዘሌ፳፪ ፡ ፳፪) ።

**ኀሠፍ** ፤ (ፉት) ፤ ዕከክ ፡ ብግር ፤ ኪንታሮት ፡ ቍስል ፤ የገላ ፡ ነውር ።

**ኀሠረ ፤ — ሰበሰበ ፤ — ሐሠረ ፡ ሐሠረ ።**

**ኀሥረ ፤ — ጐሰቈለ ፤ — ኀሰረ ፡ ኀሰረ ።**

**ኀፈደ ፡ ዶት ፤ (ኀፈደ ፡ የኀፍድ ፡ ይኅፍድ ። ነደቀ ፤ ሐነጸ ፤ ሣረረ)** ፤ መገንባት ፡ መናብ ፡ መቅንደቅ ፡ ቤትን ፡ ግንቡን ፡ አስፍቶ ፡ አስረዝሞ ፡ አጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ እንደ ፡ ባቢሎን ፡ ሕዝብ ።

**ማኅፈድ ፤ (ዳት ፤ አው ፡ መኃፍድ ። ዕብ ፡ አፑዶን ። ዐረ ፡ ፈደን)** ፤ ግንብ ፡ አዳራሽ ፡ ቤት ፡ መንግሥት ፡ ኑኅ ፡ ርሕብ ፡ ምጥቀት ፡ ርዝመት ፡ ያለው ። ሰርድ ፡ ምሽግ ፡ እንባ ፡ ኩሬብታ ፤ ከጠላት ፡ የሚጠበቁበት ፡ የሰላዮና ፡ የጕበኛ ፡ የዘበኛ ፡ ቤት ፤ በከተማ ፡ ዙሪያ ፡ ዐልዎ ፡ ዐልዎ ፡ በየበሩ ፡ በየማእዝኑ ፡ እንደ ፡ ሐውልት ፡ እንደ ፡ ደወል ፡ ቤት ፡ እንደበላም ፡ መርጦሺያ ፡ ረኸጥም ፡ ኸኖ ፡ የሚሠራ ፤ ጠላት ፡ ወዳጅ ፡ ከሩቅ ፡ ሲመጣ ፡ የሚያዩበት ፡ (ዘፍ ፲፩ ፡ ፬ ፡ ፭ ። ኩፋ ፡ ፲) ። **ማኅፈድ ፡ ጽኑዕ ፡ ቅድመ ፡ ገጸ ፡ ጸላኢ ። ደብ ፡ ጽሉ ፡ ማኅፈድ ፡ ነዋኅ ። ማኅፈደ ፡ ዓሎት** ፡ (መዝ ፡ ፷ ። ኢሳ ፪ ፡ ፲፭ ። ማኅ ፬ ፡ ፬) ። **ማኅፈደ ፡ ጢስ** ፤ ዐምድ ። **ማኅፈደ ፡ ሥጋ** ፤ ሰውነት ፡ ማዘፍ ፡ (መሳፍ ፡ ፶ ። መጽ ፡ ምስ) ። በማኅደፍ ፡ ፈንታ ፡ ማኅፈድ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፤ ኅደፈን ፡ እይ ። **ጸሎት ፡ ሳዕለ ፡ ማኅፈዳት** ፡ (ቅዳ) ።

**ኀፈወ ፤ — ወዘ ፤ — ሀፈው ፡ ሀፈወ ።**

**ኀፈጥ ፡ ጦት ፤ (ኀፈጠ ፡ የኀፍጥ ፡ ይኅፍጥ ። ዐረ ፡ ኀበጠ ። ዕብ ፡ ሓባጥ ። ሱር ፡ ሕባጥ)** ፤ መምታት ፡ መውቃት ፡ መደብደብ ፤ የበትር ። መደበቅ ፡ መሰጐድ ፡ መጠፍጠፍ ፤ የቡጢ ፡ የጥፊ ። **ኀፍጣ ፡ አጥባትክን** ፡ (ኢሳ ፴፪ ፡ ፲፪) ።

**ኀፋጢ ፤ መኃፍጥ** ፤ የሚመታ ፡ ተማች ፡ ደብዳቢ ፡ ወቂ ፡ ደሳቂ ።

**ኀንፈጠ ፤ (ስሕጽ ፡ ማስ)** ፤ በተመ ፤ በማኅተም ፡ መታ ፡ ረገጠ ፤ ፈረመ ። ወይም ፡ ማለ ፡ መሰለ ፤ ነደፈ ፡ ቀረጸ ፤ በማኅተም ፡ ላይ ።

**ተኀንፈጠ** ፤ ተማለ ፡ ተቀረጸ ። **ክልኤቱ ፡ ማኅተም ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘወርቅ ፡ ወካልኡ ፡ ዘንጺን ፤ ዘተኀንፈጠ ፡ ውስቴቶሙ ፡ አርእያ ፡ አሐዱ ፡ ንጉሥ** ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፱) ።

**ኀፍጠት** ፤ የማኅተም ፡ ቅርጽ ፡ ጥፈት ፡ መልክ ። **አልቦ ፡ ፍልጠት ፡ ውስተ ፡ ኅፍጠት ፡ ዘአርእያ ፡ ንጉሣዊ ፡ ማእከለ ፡ ዘተኀትመ ፡ በማኅተመ ፡ ወርቅ ፡ ወማእከለ ፡ ዘተኀትመ ፡ በማኅተመ ፡ ንጺን ፤ ወኢይትዐወቅ ፡ አይ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘኀተሞ ፡ በወርቅ ፡ እምዘኀተሞ ፡ በንጺን** ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፱) ።

**ኀፈነ ፤ — ዐፈነ ፤ — ሐፈን ፡ ሐፈነ ።**

**ኀፈሠ ፤ — ዐፈሠ ፤ — ሐፈሥ ፡ ሐፈሠ ።**

**ኀፈር ፡ ሮት ፤ (ኀፍረ ፤ ኀፈረ ፡ የኀፍር ፡ ይኅፈር ። ዐረ ፡ ኀፈረ ። ዕብ ፡ ሐፌር ። ሱር ፡ ሕፋር)** ፤ ማፈር ፡ መፍራት ፤ ከፊቀትንነት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ አዳም ። መደንገጥ ፡ መስወጥ ፤ በመድ ፡ መምሰል ፡ ከኀፍረት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ። ኀፍረትን ፡ ሰርቃንን ፡ መስወር ፡ መክደን ። **ኀፈረ ፡ ኢኀፍሩ ። ተዐቢ ፡ ኀፊሮተየ ። ዘኢየኀፍር ፡ ገጸ ፡ ክቡር ። ኢንኀፈር ፡ እምሚበተ ፡ ልሂቅ** ፡ (ኤር ፳ ፡ ፲፩ ። ዘፀ ፴፪ ፡ ፪ ። ኢዮ ፴፱ ፡ ፳፪ ። ጥበ ፪ ፡ ፲) ። በኀፍረ ፡ ፈንታ ፡ ተኀፍረ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ኢይግባእ ፡ ነዳይ ፡ ተኀፊሮ ። መኑ ፡ ተአመነ ፡ በእግዚ ፡ ወተኀፍረ ። ይሑሩ ፡ ተኀፊሮሙ ። ተኀፍሩ ፡ ጽሉ ፡ ነህብት ፡ በእንተ ፡ ግልፎሆሙ ። ይእቲ ፡ አሚረ ፡ ትትኀፈር ፡ እምኬጋይኪ** ፡ (መዝ ፡ ፸፫ ። ሢራ ፪ ፡ ፲ ። ኢሳ ፵፭ ፡ ፲፮ ። ኤር ፲ ፡ ፲፬ ። ሶፎ ፫ ፡ ፲፩) ።

**ኀፋሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት)** ፤ ያፈረ ፡ የሚያፍር ፤ ዐፋር ። **ደፋሪ ፡ ወኢኀፋሪ ። ብእሲት ፡ ኀፋሪት** ፡ (ማኅ ። ሢራ ፳፮ ፡ ፲፭) ።

**አኅፈረ** ፤ አሳፈረ ፡ አሳዘነ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአኅፈረ ፡ ፈንታ ፡ አስተኀፈረ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ ፩ ፡ ነው ፤ ካስደፋጊንት ፡ አይወጣም ። **ኢታስተኀፍረኒ ፡ እምተስፋየ ። ታስተኀፍር ፡ አባሃ ። ግብር ፡ ዘያስተኀፍር ። ገሥጽዎሙ ፡ ወአስተኀፍርዎሙ** ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ። ሢራ ፳፪ ፡ ፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፪ ። ቀሌ) ።

**አኅፋሪ ፤ ማኅፈሪ** ፤ የሚያሳፍር ፡ አሳፋሪ ፡ (ግንዘ) ።

**ተኀፍረ ፤ (ተደራጊ)** ፤ ታፈረ ፡ ተፈራ ፤ ከበረ ።

**ኀፋር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ፍርት)** ፤ የታፈረ ፡ የተፈራ ፤ ታፋሪ ፡ ተፈሪ ። ያፈረ ፡ የፈራ ፤ ኀፍረት ፡ የያዘው ። **እስመ ፡ ኀፋራን ፡ እሙንቱ ። ሑሩ ፡ ኀፋራኒሆሙ ። ዘኀፋር ፡ ገጹ** ፡ (ጽንዕ ፲ ፡ ፭ ። አፈ ፡ ተ፲፫ ። ኪዳ) ።

**ኀፋሬ** ፤ ማፈር ፡ ድል ፡ መኾን ፡ መሸነፍ ፡ ዕፍረት ፡ ፍራት ። **ይቤልዎ ፡ እንከ ፡ ለኀፋሬሁ** ፡ (ማር ፡ ይሥ፬ ፡ ፮) ።

**ኀፍረት ፤ (ታት)** ፤ በቁሙ ፤ ዕፍረት ፡ ፍራት ። **ክመ ፡ ኀፍረተ ፡ በራቂ ፡ ሶበ ፡ ይእኅዝዎ ፡ ከማሁ ፡ የኀፍሩ ። ወከደነኒ ፡ ኀፍረት ፡ ገጽየ ። ቦ ፡ ኀፍረት ፡ እንተ ፡ ታመጽእ ፡ ኀጢአተ ፡ ወቦ ፡ ኀፍረት ፡ ለክብር ። ዘአልቦ ፡ ኀፍረት** ፡ (ኤር ፪ ፡ ፳፮ ። መዝ ፡ ፷፰ ። ምሳሌ ፡ ፲፭ ። መክ ፳ ፡ ፭) ።

—፤ እድፍ ፡ ጕድፍ ፡ ገመና ፡ ነውር ፤ ስድብ ፡ ስንፍና ፡ የሚያሳፍር ፡ የሚያስነቅፍ ፡ ነገር ። **ኢሜጥኩ ፡ ገጽየ ፡ እምኀፍረተ ፡ ምራቅ ። ተዐገሠ ፡ ኀፍረተ ፡ መስቀል ። ኀፍረት ፡ ለነ ፡ እንተ ፡ ከመ ፡ ዛቲ ፡ ብእሲት ፡ ረኪበነ ፡ እመ ፡ ኢተናገርናሃ ። ገብረ ፡ ኀፍረተ ። ነገረ ፡ ኀፍረት** ፡ (ኢሳ ፶ ፡ ፮ ። ዕብ ፲፪ ፡ ፪ ። ዮዲ ፲፪ ፡ ፲፪ ። ዘፍ ፴፬ ፡ ፯ ። ቆላ ፫ ፡ ፰) ።

—፤ ስራቍት ፡ ዕርቃን ፤ የወንድ ፡ የሴት ፡ ገላ ፤ አባለ ፡ ዘር ፡ አፈ ፡ ማሕፀን ። **ኢትክሥት ፡ ኀፍረተ ፡ አቡከ ፡ ወእምከ ። ከደንኩ ፡ ኀፍረተኪ ። ከመ ፡ ኢይሑር ፡**

ዐራቂ ፡ ወኢ.ያስተርኢ. ፡ ኀፍረቱ ፤ (ዘሌ.፲፰ ፡ ፯ ። ሕ ዝ፲፯ ፡ ፰ ። ራእ፲፮ ፡ ፲፭) ።

**ተኀፈረ** ፤ ተፋፈረ ፤ ተፋራ ፡ ተፋዘዘ ። ወይም ፡ ኀፍረት ፡ ለኀፍረት ፡ ተጋለጠ ፡ ተገላለጠ ፤ ተደፋፈረ ፤ የሩ ክቤ ።

**ማኅፈር** ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤ የታመነ ፡ ጠዳጅ ፡ ባልንጀራ ፡ ዘመድ ፡ ጎረቤት ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ቂብ ፡ ሐኪም ፤ ገመናን ፡ ኀፍረትን ፡ ገልጦ ፡ የሚነግሩትና ፡ የሚያሳዩት ። ዐርክ ፡ ወማኅፈር ። ንግር ፡ ለማኅፈ ርከ ፡ ወለማኅፈረ ፡ ሕዝብከ ። እመ ፡ ኮነ ፡ እንበሳ ፡ ማኅፈሮ ፡ ለሳሕም ፡ (ሚ.ራ፵ ፡ ፳፫ ። ፵፪ ፡ ፲፭ ። ኩፋ ፡ ፴፯) ። ዐማች ፡ ያማችና ፡ የምራት ፡ ወገን ፡ የጋብቻ ፡ ዘመድ ። የወንድ ፡ ወገን ፡ ለሴት ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ ለወ ንድ ፡ ማኅፈር ፡ ይባላል ።

**ምኅፋር** ፤ (ራት) ፤ ማፈሪያ ፡ ኀፍረት ። ኢ.ይ ትከሠት ፡ ምኅፋሪከ ፤ (ዘፀ፳ ፡ ፳፮) ።

**ማኅፈሬት** ፤ ኾፌት ፤ እንደ ፡ ዘውድ ፡ ያለ ፡ ቆብ ፤ የቀድሞ ፡ ነገሥታት ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ዛሬም ፡ ጳጳሳት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ የሚደፉት ፡ የሚቀዳጁት ። በከይዎ ፡ ሕዝብ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ተቀደጸ ሎሙ ፡ ማኅፈሬተ ፡ ልብሶ ፡ ጋባት ፡ ሶበ ፡ መተሩ ፡ ክ ብርተ ፡ ርእሶ ፡ (ድጓ) ። በማኅፈሬት ፡ ፈንታ ፡ ማዕፈ ርት ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ዐፈረን ፡ ተመልከት ።

**ኆጻ** ፤—አሸዋ ፤—ኀጠ ፡ ሐጸ ፤ ኀወጸ ።

**ኀጸበ** ፤—ዐጠበ ፤—ኀፂብ ፡ ኀፀበ ።

**ኀጺድ** ፤ ዶት ፤ (ኀጸደ ፡ የኀጽድ ፡ ይኅ ጽድ ። ዐረ ፡ ሐጸደ ፤ ዐሰደ) ፤ ማጠዝ ፡ መጠም ዘዝ ፤ ማረቅ ፡ ማጉበጥ ፡ መጠቅለል ፤ የሐረግ ፡ የንጨት ፡ የሽቦ ፡ የብረት ።

**ኍጻድ** ፤ **አው** ፡ **ኆጻድ** ፤ (ዳት ። ዕብ ፡ **ቈሬስ** ፤ **ዋው**) ፤ ማንጠ ፤ ቀለበት ፤ ዘለበት ፡ የደን ኳን ፡ መግጠሚያ ፡ ማያያዣ ፤ ማቈላለፊያ ። ወግበር ፡ ኆጻዳተ ፡ ኀምሳ ፡ ዘወርቅ ፤ ወደምር ፡ አፅጻደ ፡ አ ሐተ ፡ ምስለ ፡ ካልእታ ፡ በኆጻዳት ፤ ወይኩን ፡ ደብ ተራሁ ፡ አሐደ ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፮) ።

**ኀጺው** ፤ **ዎት** ፤ (ኀጸወ ፡ የኀጹ ፡ ይ ኅጹ ። ዐረ ፡ ኀጸ ። ሱር ፡ ሕጻእ) ፤ መቍረጥ ፡ መ ስንጋት ፡ ማኰላሸት ፤ መስለብ ፡ መጕመድ ፤ ሻን ፡ ደረብ ፡ ማድረግ ፤ ራስን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፤ መሐጸን ፡ እይ ። ዘየኀጹ ፡ ርእሶ ፡ በፈቃዱ ። ብእሲ ፡ ዘኀጸወ ፡ ኀፍ ረተ ፡ ሥጋሁ ፡ በፈቃደ ፡ ርእሱ ፤ አው ፡ ጸላእቱ ፡ ኀጸ ውዎ ፡ (ቀሌ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፫ ፡ ፪ ። ማቴ፲፱ ፡ ፲፪) ።

**ኅጻዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ጸውት) ፤ የሚሰልብ ፡ ሰላቢ ፡ ቈራጭ ።

**አኅጸወ** ፤ አስጕመደ ፤ አሰለበ ፡ አሰነጋ ።

**ተኀጽወ** ፤ ተሰለበ ፤ ተሰነጋ ፤ እሰኪቱን ፡ ተ ቀማ ። ለእመ ፡ ተኀጽወ ፡ እምሰብእ ፡ በትዕግልት ፡ (ቀኖ ፡ ፲፭) ።

**ኅጽው** ፤ (ዋን) ፤ የተሰለበ ፡ ስልብ ፡ ጕማዳ ፡ ሻን ፡ ደረበ ። ከመ ፡ ኅጽው ፡ ሶበ ፡ የሐቅፋ ፡ ለድን ግል ። በእንተ ፡ ኅጽዋን ፡ ወግዙራን ። እስመ ፡ ቦ ፡ ኅ ጽዋን ፡ (ሢ.ራ፴ ፡ ፳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፫ ። ማቴ፲፱ ፡ ፲፪ ። ግብ፰ ፡ ፳፯) ።

**ኅጽወት** ፤ መስለብ ፡ መሰለብ ፡ ሻን ፡ ደረብ ፡ መ ኾን ፡ ማድረግ ። ዘፈቀደ ፡ ኅጽወተ ፡ (ፈልክ ፡ ፱፻፴) ።

**ኅጺን** ፤ (ናት ፤ ኀጻውንት) ፤ ብረት ፡ የታ ወቀ ፡ ማዕደን ፡ ከምድር ፡ የሚገኝ ፡ ከፈር ፡ ከመሬት ፡ የሚወጣ ፡ ብርቱ ፡ ከባድ ፡ ጥኑ ፡ ጠንካራ ። ብርትንና ፡ ብሩርን ፡ ተመልከት ፡ ብረት ፡ ማለት ፡ ከዚያ ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ ኅጺንም ፡ ከንጸወና ፡ ከመሐጸ ፡ ከኅፀቱ ፡ ወጥቷል ። ወንጸንኒ ፡ እምውስቴ ፡ ምድር ፡ ይትገበር ። ም ድር ፡ እንተ ፡ እበኒሃ ፡ ኅጺን ። በምንሃብ ፡ ያሜክ ርዎ ፡ ለኅጺን ፡ (ኢ.ዮ፳፰ ፡ ፪ ። ዘዳ፰ ፡ ፱ ። ሢ.ራ፴፱ ፡ ፳፯) ።

—፤ መቍረጫ ፡ መፍለጫ ፡ የብረት ፡ መሣሪያ ፡ ማናቸ ውም ፡ ኹሉ ፡ በየስሙና ፡ በየይነቱ ። እብልኑ ፡ ጸራቢ ፡ ኀ ጺን ። ወለኀጺናቲሆሙ ፡ ገብሮሙ ፡ ሰንጐጐ ። ተፈትሐ ፡ ሾሎን ፡ ኀጻውንት ። ኀጻውንተ ፡ መስቀል ፡ (ኢ.ሳ፲፬ ፡ ፲፪ ። ገድ ፡ ተክ ። ቄድር ። አርጋ ፡ ፱) ።

**ኅጸነ** ፤—አሳደገ ፤—ሐፂን ፡ ሐፀነ ።

**ኀጸረ** ፤—ዐጠረ ፡ ቀጠረ ፤—ሐጺር ፡ ሐ ጸረ ።

**ኀጺር** ፤ ሮት ፤ (ኀጽረ ፡ የኀጽር ፡ ይኅ ጽር ። ዕብ ፡ ቃጻር ። ዐረ ፡ ቀጸረ) ፤ ማጠር ፡ ማ ነስ ፤ ዐጭር ፡ መኾን ፡ የቁመት ፡ የጊዜ ። አእባን ፡ እለ ፡ የኀጽራ ። ሶበ ፡ እኩ ፡ ዘኀጽራ ፡ እማንቱ ፡ መቀዐል ፡ (ሄርማ ፡ ገ፰ ። ማቴ፳፱ ፡ ፳፱) ።

(ጥ) **ኀጺር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ጻር) ፤ ዐጭር ፡ ታ ናሽ ፤ ድንክ ፡ ኵንትሽ ። አንውዎ ፡ ለዐፅ ፡ ኀጺር ። ዘ በሐቅ ፡ ኀጺር ። ኀጺራት ፡ አጻብዒሁ ፡ (ሕዝ፲፯ ፡ ፳፱ ። ዘሌ፳፩ ፡ ፳ ። ሄርማ) ።



ኀጺር ፤

**ኀጺር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ጽርት) ፤ ያጠረ ፡ ዐ ጭር ፤ ታናሽ ፡ ጥቂት ። ዘመን ፡ ኀጺር ። ነገር ፡ ኀጺር ። እስመ ፡ ኀጺር ፡ ዕለትየ ። በኀጺር ፡ አዘዝኩክሙ ። ኀ ጺረ ፡ እነግረከ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፰ ። ፀቀሮ ፡ ፲ ፡ ፲ ። ዕብ፲፫ ፡ ፴፱ ። ፲፫ ፡ ፳፱ ። ግብ፳፱ ፡ ፱) ።

**ኅጽር** ፤ **ኅጽረት** ፤ ማጠር ፡ ዕጥረት ፡ ዐጭርነት ፡ (ሐ.ዋ፳፱ ፡ ፳፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ። በእንተ ፡ ኅጽረተ ፡ እ ደዊሆሙ ፡ ወበእንተ ፡ ዘአልቦሙ ፡ ክሂል ። ይትዔ

ረይ ፡ ሲሲት ፡ ምስለ ፡ መዓልት ፡ በኑኀት ፡ ወበኅጽ
ረት ፤ (ዮሴፍ ። አቡሻ ፡ ፲፱) ።

**አኅጸረ ፤** አሳጠረ ፡ አሳነሰ ። አነ ፡ ዘአኅጽሮ ፡
ለዕፀ ፡ ነዋኅ ። ወሶበ ፡ አኮ ፡ ዘአኅጸሮን ፡ ለእማንቱ ፡
መዋዕል ። በአኅጽሮ ፡ ይኄይሱ ፡ ድርሳናት ፤ (ሕዝ
፲፯ ፡ ፳፬ ። ማር፲፫ ፡ ፳ ። ቀረ ፡ ቄር፳፩) ።

**ኀፂብ ፤ ቦት ፤ (ኀፀበ ፡ የኀፅብ ፡ ይኅ
ፅብ ። ዐረ ፡ ኀፀበ ፤ ቀለም ፡ አገበ) ፤** ማጠብ ፡ ማ
ጥራት ፡ ማንጻት ። ይኅፅቡ ፡ አልባሲሆሙ ። ኅፅብ
ኩኪ ፡ በማይ ። ኅፀባ ፡ ለምድር ፡ እምዝሉ ፡ ርስ
ሐት ። የኀፅቦሙ ፡ እግዚ ፡ ሲደቂቀ ፡ ጽዮን ፤ (ዘፀ፲፱ ፡
፲ ። ሕዝ፲፯ ፡ ፱ ። መቃ ፡ ገ፯ ። ኢሳ፬ ፡ ፬) ። በኀፂብ ፡ ፈ
ንታ ፡ ኅፅበት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኀፀባ ፡ ይላል ። ኢታ
ስትት ፡ ኅፀባ ፡ እገሪሆሙ ፡ ለአኀው ፤ (ሲኖዶ ፡ ኒቅ) ።
በኀፀበም ፡ ፈንታ ፡ አስተኀፀበ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።
ኢታአንግዱ ፡ በአስተኅ(ዐ)ፅ(ጽ)ቦ ፡ አላ ፡ በፍቅር ፡
(አፈ ፡ ተ፴፫) ።

**ኀፃቢ ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ፀብት) ፤**
የሚያጥብ ፡ ዐጣቢ ፤ ቀለም ፡ አግቢ ። ኀፃቤ ፡ ልብስ ፡
(ፍ ፡ ን ፡ ፴፯) ።

**አኅፀበ ፤** አሳጠበ ፡ አስታጠበ ፡ ውሃ ፡ ጨመረ ፡
(፬ነገ ፡ ፫ ፡ ፲፩) ።

**ተኀፅበ ፤** ታጠበ ፡ ጠራ ፤ ከርስሐት ፡ ተለየ ። ተ
ኅፀበት ፡ ሥጋሃ ፡ በማይ ። ዘይትኀፀብ ፡ እምድኅረ ፡
ገሰሰ ፡ በድን ፤ ምንት ፡ ይበቍዕ ፡ ተኀፅቦ ። ተኀፂቦ ፡
ውእቱ ፡ ልብስ ፤ (ዮዲ፲ ፡ ፫ ። ሢራ፴፩ ፡ ፴ ። ዘሌ፲፫ ፡
፶፰) ።

**ኅፁብ ፤ (ባን ፡ ብት ፡ ዕብት) ፤** የታጠበ ፡ የ
ጠራ ፤ ንጹሕ ፡ ጥሩ ። ወኅፁብ ፡ ሥጋነ ፡ በማይ ፡ ንጹሕ ።
አልባስ ፡ ኅፁብ ፤ (ዕብ፲ ፡ ፳፪ ። ስንክ ፡ መጋ፫) ።

**ኅፅበት ፤** ማጠብ ፡ መታጠብ ፡ አስተጣጠብ ፡ ዐ
ጠባ ፡ ዕጥበት ፡ ስርየት ፡ ጥምቀት ። ኅፀበተ ፡ ሥጋ ። ኅ
ፀበተ ፡ እግር ። ኅፀበተ ፡ ኀጢአት ። ኅፀበተ ፡ ዘዳግም ፡
ልደት ፤ (ኢጲፋ ፡ ፫ ፡ ፳፭ ። ፊልክ ፡ ፻፲፱ ። ኪዳ ። ቅዳ ፡
ኢጲ) ።

**ኅፃብ ፤ (ባት) ፤** ዕጣቢ ፡ እድፍ ። ማየ ፡ ኅፃ
ቤሁ ፡ ኮዋን ፡ በቍዔት ፡ ለጸዋልደ ፡ የሴፍ ። በኅፃበ ፡
እግሩ ፤ (አረጋ ፡ ድ፳፬ ። ስንክ ፡ ግንቦ) ።

**ማኅፀብ ፤ (ባት ፤ አው ፡ መኅፅብ ። ማኅ
ፀብት ፤ ብ ፡ መኅፅብት) ፤** ማጠቢያ ፡ ማስታጠቢያ ፡
የጥበት ፡ መሣሪያ ። ነሥአ ፡ ማኅፀበ ፡ ወአስተየን ፡ ለ
እሉ ፡ አበግዐ ። ማኅፀበ ፡ አልባስ ፤ (ቀሌ ። ስንክ ፡ ሐም
፲፰) ።

**ምኅፃብ ፤ (ባት) ፤** ማጠቢያ ፡ መታጠቢያ ፡
ቦታ ፡ መሣሪያ ። መራዕይ ፡ እለ ፡ ወፅአ ፡ እምኅፃብ ።
ቤተ ፡ ምኅፃብ ። ወረደ ፡ ማየ ፡ ውስተ ፡ ምኅፃብ ፡
(ማሕ፬ ፡ ፬ ። ፯ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲፩ ። ዲድ ፡ ፲፯) ።

**ኀፀየ ፤—ዐሰበ ፤—ሐፀይ ፡ ሐፀየ ።**

**ኀፀነ ፤—አሳደገ ፤—ሐፂን ፡ ሐፀነ ።**

**ኀቀፈ ፤—ዐቀፈ ፤—ሐቂፍ ፡ ሐቀፈ ።**

**ኄር ፤—ቸር ፤—ኀዪር ፡ ኄረ ፡ ኀየረ ።**

**ኀረደ ፤—ዐረደ ፤—ሐሪድ ፡ ሐረደ ።**

**ኀረወ ፤—ቈፈረ ፤—ሐሪው ፡ ሐረወ ።**

**ኀሪው ፤ ዎት ፤ (ኀረወ ፡ የኀሩ ፡ ይኅሩ ።
ዐረ ፡ ኀረተ ። ዕብ ፡ ሓራት ። ሱር ፡ ሕራት) ፤**
መብሳት ፡ መንደል ፡ መፈልፈል ፡ መቅረጥ ፡ ማንጠጥ ፤
ማስመጥ ፡ ማሳበጥ ፡ የደንጊያና ፡ የንጨት ፡ የብረት ። ዕር
ሻና ፡ ቍፋሮም ፡ ያሳያል ። እለ ፡ ይገልፉ ፡ ወየኀርዉ ፡
ዐይነ ፤ ማኅተም ፡ ኀሪወ ፡ ማኅተም ። እብን ፡ ዘኅ
ረዎ ፡ ኬንያ ፤ (ሢራ፴፰ ፡ ፳፯ ። አዋል) ። ኀረመኑና ፡ ኀ
ኀረጠን ፡ እያ ፡ ኀረመ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ኀራዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ረውት) ፤**
የሚፈልፍል ፡ የሚቀርጥ ። ኀራዌ ፡ ማኅተም ፤ (አዋል) ።

**ተኀርወ ፤** ተበሳ ፡ ተነደለ ፡ ተፈለፈለ ። እብን ፡
ዘይትኀርዎ ። አእባን ፡ ዘይትኀረዉ ፤ (ዘፀ፳፰ ፡ ፯ ።
፴፰ ፡ ፰) ።

**ኅርው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሩት) ፤** የተበሳ ፡ የተ
ቀረጠ ፡ ያበጠ ፡ የሰመጠ ። ወኅርው ፡ በኵናሁ ፡ በአም
ሳለ ፡ ጕንድ ። ኅርው ፡ ዐይነ ፡ ማኅተም ፤ (ስንክ ፡
ሠኔ፬ ። ሢራ፵፰ ። ፲፩) ።

**ኅርወት ፤ (ታት) ፤** መብሳት ፡ መበሳት ፡ እበ
ሳስ ። ብስ ፡ ነዳላ ፡ ፍልፍል ፡ ቅርጥ ። አስርዎሙ ፡ ው
ስተ ፡ ኅርወተ ፡ ጕንድ ፡ ክቡድ ፡ እስረተ ፤ ብስ ። ኅር
ወተ ፡ ዐይነ ፡ ማኅተም ፤ ቅርጥ ፤ (መቃ ፡ ገ፪ ። ስንክ ፡
ሠኔ፲፬ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፲፩) ።

**ኅሮ ፤** መብሻ ፡ መንደያ ፡ መፈልፈያ ፡ መቅረጫ ፡
ማንጠጫ ፤ መሮ ፡ አፈ ፡ ምሣር ፡ ወስፌ ፤ የመሰለው ፡
ኹሉ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በኅሮ ፡ ፈንታ ፡ ኅርወት ፡ ይላል ።
ትስቍር ፡ እንዘ ፡ በኅርወት ፤ (ኢዮ፵ ፡ ፳፮) ።



ኅሮ ፡

**ኆር ፤ (ዕብ ፡ ሖር) ፤** ብስ ፡ ነዳላ ፡ ቃዳዳ ፡ ጠ
ባብ ፡ መስኮት ፡ (ሕዝ፰ ፡ ፯) ።

**ኄረ ፤—ቸረ ፤—ኀዪር ፡ ኄረ ፡ ኀየረ ።**

**ኀራውያ ፤—ሕሪያ ፤—ሐረወ ።**

**ኀርይ ፤ ዮት ፤ (ኀረየ ፤ ኀርየ ። ዐረ ፡
ኀረ ። ዕብ ፡ በሓር) ፤** መምረጥ ፡ ማቻቻል ፡ መው
ደድ ፡ ማቅረብ ፤ ለሹመት ፡ ለሥራ ። (ተረት) ፤ ክስው ፡
መርጦ ፡ ለሹመት ፡ ከንጨት ፡ መርጦ ፡ ለታቦት ። አኮ ፡
አንትሙ ፡ ዘኀረይክሙኒ ፤ አላ ፡ አነ ፡ ኀረይኩክሙ ፡
ወሣምኩክሙ ። ሕዝብ ፡ ዘኀረየ ፡ ሎቱ ፡ ለርስቱ ።
ዘበደዋት ፡ ተነበየ ፡ ወበየሐንስ ፡ ጥምቀት ፡ ኀረየ ፡

(ዮሐ፲፰ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፻፱ ። ድጓ) ። ኀረየ ፡ ባለው ፡ ዘን ዱን ፡ ይኅሬ ፡ ኀርየ ፡ ባለው ፡ ይኅረይ ፡ ይላል ፡ የቀተለና ፡ የገብረ ፡ አካኼድ ፡ ነው ።

**ኅሩይ** ፤ (**ዪት ፡ ዪያን ፡ ያት**) ፤ የሚመረጥ ፡ መሩጭ ። ኅሩዩ ፡ ሰዓት ፡ ወኅሩዮ ፡ ዕለታት ፡ (ቁስጠ) ።

**አኅረየ** ፤ አስመረጠ ፡ ምረጥ ፡ አለ ።

**ተኀርየ** ፤ ተመረጠ ፡ ተለየ ፡ ተወደደ ።

**ኅሩይ** ፤ (**ያን ፡ ያት ፡ ሬት**) ፤ የተመረጠ ፡ ምርጥ ፡ ዳኛ ፡ አስታራቂ ። ንዋይ ፡ ኅሩይ ። ወአልዐልኩ ፡ ኅሩይየ ፡ እምሕዝብየ ። ኅሩይ ፡ ዘይፈትሕ ፡ (ቅዳ ። መዝ ፡ ፹፰ ። ኢዮ ፡ ፴፱) ።

**ኅርየት** ፤ መምረጥ ፡ መመረጥ ፡ አመራረጥ ፡ መረጣ ፡ ምርጥነት ፡ ፈቃድ ። በብእ ፡ ኅርየት ። ኅርየት ፡ ሠያጢ ፤ ዘበቱ ፡ ኅርየት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ። ፴፫ ፡ ፬) ።

**ኅሬ** ፤ መረጣ ፡ ምርጫ ፤ ምርጥነት ። ስመ ፡ ነገድ ፤ እስራኤል ። ነገደ ፡ ኅሬ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፬) ። ዳግመኛም ፤ ኅሩይ ፡ ኅርየት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ኅሬ ፡ ይላል ፡ (ሮሜ፲፩ ፡ ፭ ፡ ፯ ፡ ፳፰) ።

**ኀረመ ፤—ተወ ፤—ሐሪም ፡ ሐረመ ።**

**ኅረመ** ፤ (**ኅረወ**) ፤ ጣፈ ፡ ነደፈ ፡ በገረ ፡ አመለከተ ፤ ከመቅረጥና ፡ ከመፈልፈል ፡ በፊት ። የኀረወን ፡ ፍቹ ፡ ተመልከት ።

**ኅርመት** ፤ የፊደል ፡ ቅንጣት ፡ አንዳንዱ ፡ ቅርጽ ፤ በየስሙና ፡ በየመልኩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኹና ፡ የሚጣፍ ፤ ብቻ ፡ ብቻውን ፡ የሚቈጠርና ፡ የሚነገር ። አ ፤ ቡ ፡ ጊ ፡ ዳ ፡ ሄ ፡ ው ፡ ዘ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ። የውጣ(ዩ—Ⅰ) ፡ እንተ ፡ አሐቲ ፡ ኅርመታ ፡ ወአሐቲ ፡ ቅርጸታ ፡ (ማቴ፭ ፡ ፲፰ ። ድጓ) ።

—፤ ብቸኛ ፡ ቃል ፡ ንባቡ ፡ ፊደሉ ፡ ከንቍጥ ፡ እስከ ፡ ንቍጥ ፡ የሚጣፍ ፡ በንቍጥ ፡ የሚወሰን ። አልፍ ፡ ቤት ፡ ገምል ፡ ድልት ፡ ሆይ ፡ ዋዌ ፡ ዛይ ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፤ ይህን ፡ የመሰለ ። ኢንኤዝዝ ፡ አሐተ ፡ ቃለ ፤ አው ፡ አሐተ ፡ ኅርመተ ፡ ይትወሰጥ ፡ እምዘሀሎ ፡ ህየ ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፭) ።

**ኅርም** ፤ የፊደል ፡ ስም ፡ ፰ኛ ፡ ኀ ፡ ልዩ ፡ ብቸኛ ፤ ኄር ፡ ኄሩት ።

**ኀረሠ ፤—ዐረሰ ፤—ሐሪስ ፡ ሐረሰ ።**

**ኀረሠ ፤—ወለደ ፤—ኀሪስ ፡ ኀረሰ ።**

**ኀረፈ ፤—ዐረፈ ፤—ሐረፈ ።**

**ኀሪፍ** ፤ **ፎት** ፤ (**ኀርፈ ፡ የኀርፍ ፡ ይኅርፍ ። ዐረ ፡ ኀረፈ ። ዕብ ፡ ሐራፍ ፤ ክረመ**) ፤ መልቀም ፡ መሰብሰብ ፡ የፍሬ ። መክረም ፤ ክረምት ፡ እስኪወጣ ፡ መቈየት ።

**ኀሪፍ** ፤ (**ዐረብ ። ዕብ ፡ ሖሬፍ**) ፤ ጸደይ ፤ ያመት ፡ ሩብ ፡ የዘመን ፡ ርበ ፡ በሐጋይና ፡ በክረምት ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ወራት ። ፪ኛም ፡ ከክረምት ፡ ደርበው ፡ መንፈቀ ፡ ዓመት ፡ ይሉታል ፡ ይኸውም ፡ ከጥቅምት ፡ እስከ ፡ ሚያዝያ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ባገራችን ፡ ግን ፡ ከሚያዝያ ፡ እስከ ፡ ጥቅምት ፡ ይኾናል ።

**ኀሪፍ** ፤ ዘንድሮ ፡ ይህ ፡ ዓመት ፤ መላው ፡ ፲፪ቱ ፡ ወር ። ኅድጋ ፡ ኀሪፈኒ ፡ (ሉቃ፲፫ ፡ ፰) ። ገሪፍ ፡ ወኀሪፍ ፤ ዓምናና ፡ ዘንድሮ ።

(ጥ) **ኀርሰ** ፤ **ሶት** ፤ (**ኀረሰ ፤ ይኄርስ ፤ የኀርስ**) ፤ ማገረስ ፤ መቀሰብ ፤ መመገብ ፤ መከባከብ ፤ ያራስ ፡ የመማት ፡ የመይዛዝር ። ሕዘዘ ፡ የኀርስዎሙ ። እሉ ፡ የኀርስዎሙ ። ኀረስኩኪ ፡ በስንዳሌ ፡ (ዳን ፡ ፩ ፡ ፭ ። ኤር ፳፯ ፡ ፳፩ ። ሕዝ፲፯ ፡ ፲፫) ።

**ኀራሲ** ፤ **መኀርስ** ፤ የሚያርስ ፡ ዐራሽ ፤ ቀላቢ ፡ መጋቢ ፤ ተከባካቢ ።

**ተኀረሰ** ፤ ታረሰ ፡ ተቀለበ ፤ ተመገበ ፤ ሳይጥር ፡ ሳያስብ ። እስመ ፡ መጠነ ፡ ዝ ፡ መዋዕል ፡ ይነብራ ፡ እንዘ ፡ ይትኄረሳ ፡ ወይሄንያ ፡ (አስቴ፪ ፡ ፲፪) ።

**ኀሪስ** ፤ **ሶት** ፤ (**ኀርሰ ፤ ኀረሰ ፡ የኀርስ ፡ ይኅ(ረ)ርስ**) ፤ መውለድ ፡ መጨቀል ፤ ዐራስ ፡ እመማት ፡ መኾን ። ኢበፀኒስ ፡ ወኢበኀሪስ ። አመ ፡ ዕለተ ፡ ኀሪሳ ፡ ለእምክ ። እማቲሆሙ ፡ እለ ፡ ኀረሳሆሙ ። አባግዐ ፡ ወዕጐላት ፡ የኀርሳ ፡ (አርጋ ። መጽ ፡ ምስ ። ኤር፲፯ ፡ ፲ ። ዘፍ፴፫ ፡ ፲፫) ። መወለድ ፤ ከማሕፀን ፡ መውጣት ፤ ርጥብ ፡ ጨቅላ ፡ መኾን ። ዐራስ ፡ ልጅ ፡ እንዲሉ ።

**አኅረሰ** ፤ አስለደ ፤ አዋለደ ። እንተ ፡ ታኀርስ ፡ (ዘፍ፴፭ ፡ ፲፯) ።

**ኅርስ** ፤ ዐራስነት ፤ ወሊድ ፡ ወሊዳ ፤ የወሊድ ፡ ወራት ፡ ከርስሐት ፡ እስኪነጹ ፡ ድረስ ፡ ፵ ፡ ወይም ፡ ፹ ፡ ቀን ፤ ፵ ፡ የወንድ ፡ ፹ ፡ የሴት ፡ ልጅ ። በመዋዕለ ፡ ትክቶሃ ፡ ወኅርሳ ፡ ኢትቅረባ ። እንዘ ፡ ውእቶን ፡ ኢንጹሓት ፡ እምኅርሰን ። ፀኑሳቲሆሙ ፡ ኢይድኅኑ ፡ ወይድኅና ፡ በኅርሰን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱ ፡ ፳ ። ፊ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፳ ። ኢዮ፳፫ ፡ ፲) ።

**ኀራስ** ፤ (**ሳት**) ፤ በቍመቱ ፡ ዐራስ ፡ ወሳድ ፤ ትኩስ ፡ እመሚማት ፤ የጨቅላ ፡ እናት ፡ የምታጠባ ። ብእሲት ፡ ኀራስ ። እምኀራስ ፡ ወትክት ። ድብ ፡ ኀራስ ። ወተመጠዎ ፡ እምድኅረ ፡ ኀራሳት ፡ (ቄድር ። ቀሌ ። ዘፍ፲፯ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፸፯) ።

—፤ ጨቅላ ፡ ርጥብ ፡ ልጅ ፡ ስጋ ፡ ቀንበጥ ፡ ቅቤ ፡ የሚውጥ ፤ ጡት ፡ የሚመጥ ፡ የሚመጠምጥ ። ባማርኛ ፡ ልማድ ፡ ለወንድም ፡ ለሴትም ፡ ይከታል ፡ በግእዝ ፡ ግን ፡ ለሴት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

» **ሮስ** ፤ (**ሳት ። ዐረ ፡ ሩስ**) ፤ ተባት ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ያላደገ ፡ ወይም ፡ ያደገ ። አመ ፡ ሰምንት ፡ ዕለት ፡ ትገዝሩ ፡ ኵሎ ፡ ሮሰ ። እምእደ ፡ ሰሎሚ ፡ ሰቤሃ ፡ ተመጠወቶ ፡ ለሮሳ ። ወለእመ ፡ ወግአ ፡ ሮሰ ፤ አው ፡ ወለተ ። ሮስ ፡ ወወለት ። ወለደት ፡ ሎቱ ፡ ሮሳተ ፡ ወአዋልደ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፭ ። ደራሲ ። ዘፀ፳፩ ፡ ፴፩ ። መጽ ፡ ምስ ። ዘዐ፳፭ ፡ ፱) ።

ኄሰ ፡—ነቀፈ ፡—ሐዩሰ ፡ ሔሰ ።

ኅሰል ፡—ዳውላ ፡—ሐሲል ፡ ሐሰለ ።

ኃሳል ፡—ልባብ ፡—ሐሲል ፡ ሐሰለ ።

ኅሰር ፡—ገለባ ፡ ጕድፍ ፡—ሐሢር ፡ ሐሠረ ።

ኅሰሰ ፡—ሻ ፡ ፈለገ ፡—ኅሢሥ ፡ ኀሠ ፡ ኀሠሠ ።

ኅሲር ፡ ሮት ፡ (ኅሰረ ፡ የኅስር ፡ ይኅሰር ። ዕብ ፡ ሐሳር ። ሱር ፡ ሕሳር ። ዐረ ፡ ኅሰረ) ፤ መጕደል ፡ ማነስ ፡ መክሰር ። መዋረድ ፡ መጕስቈል ፡ አይቶ ፡ ዐጣ ፡ አድኅ ፡ አነስ ፡ መኾን ። ኅሰረ ፡ ክብሮሙ ። ኢታዐቢ ፡ ርእሰከ ፡ ከመ ፡ ኢትኅሰር ። እስመ ፡ ዙሉ ፡ ዘአዐበየ ፡ ርእሶ ፡ የኅሰር ፡ (ኢሳ፫ ፡ ፳ ። ሢራ፯ ፡ ፴ ። ሉቃ፲፬ ፡ ፲፩) ።

ኅሱር ፡ (ራን ፡ ራት ፡ ስርት) ፡ በቈሙ ፡ ያነስ ፡ የጐደለ ፡ ሕጹጽ ። የተዋረደ ፡ ትሑት ፡ ወራዳ ፡ ጕስቍላ ፡ ምናምንቴ ። በእንተ ፡ አልባሲሁ ፡ ኅሱር ። ኃሱረ ፡ ነፍስ ። ረሰይኩክሙ ፡ ኃሱራነ ። ወለተ ፡ ባቢሎን ፡ ኃስርት ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፰ ፡ ፳ ። ሚልያ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፻፴፯) ።

ኅሳር ፡ (ራት) ፡ ሕጸጽ ፡ ክ(ኅ)ሳራ ፡ ውርደት ፡ መከራ ፡ ሰጠት ፡ ጕዳት ፡ ጕስቍልና ። ኅሳር ፡ ዐቢይ ። ኅሳርከኒ ፡ ወክብርከኒ ፡ እምቃልከ ። መዋዕለ ፡ ኅሳራ ። ጽኑሕ ፡ ሎቱ ፡ ኅሳር ፡ ዐጺብ ። ፍትወት ፡ እሞን ፡ ለኅሳራት ፡ ወለ ይክማት ፡ (ኩፋ ፡ ፲፱ ። ሢራ፰ ፡ ፲፫ ። ሰቈ፭ ፡ ፯ ። ኢዮ፲፰ ፡ ፲፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፩) ።

አኅሰረ ፡ (አክሰረ ፡ ክሳራ ፡ አመጣ) ፡ አዋረደ ፡ አጕስቈለ ፡ ሰደበ ፡ ነቀፈ ። ያኅስሮሙ ፡ ለዐቡያን ። ከመ ፡ ያኅስሩ ፡ ነፍስቶሙ ። አንዝዎ ፡ ሐራ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወአኅሰርዎ ። አኅስሮቶ ፡ ለብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ አኮ ፡ ሠናይ ፡ (፩ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፭ ። ሮሜ፩ ፡ ፳፬ ። ስንክ ፡ መጋ፲፫ ። ምሳ፲፯ ፡ ፳፮) ።

አኅሰርሰረ ፡ የውርደት ፡ ስም ፡ ቀባ ፡ ቀባባ ፡ አንከከ ፡ አብገነቶ ፡ መሳልቶ ፡ አካቶ ፡ ፈጽሞ ፡ ጥቂት ፡ ሳይተው ። ዙሎ ፡ ያኅሰረስር ፡ (ምሳ፳፪ ፡ ፲) ።

ኅሰት ፡—ውሸት ፡—ሐስዎ ፡ ሐሰወ ።


ኅቲው ፡ ዎት ፡ (ኅተወ ፡ የኅቱ ፡ ይኅቱ ። ዕብ ፡ ያቃድ ። ሱር ፡ ዩቃድ ። ዐረ ፡ ወቀደ) ፤ መቃጠል ፡ መንደድ ፡ በግ ፡ ቱግ ፡ ብልጭ ፡ ቍልጭ ፡ ማለት ፡ መብራት ፡ ብርሃን ፡ መኾን ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። ኢሳ ፶፪ ፡ ፩) ። ቅድሜሁ ፡ የኅትዉ ፡ ሰብዑ ፡ መኃትው ። ዕንቍ ፡ ዘየኅቱ ። ርእየተ ፡ ገጽከ ፡ አምሳለ ፡ መብረቅ ፡ ኅትወ ፡ (ራእ፬ ፡ ፭ ። ዘፍ፪ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ ነሐ፲፱) ።

ኃትው ፡ (ቱት ፡ ትውት ፡ ዋን ፡ ዋት) ፡ የበራ ፡ የተቃጠለ ፡ (ሉቃ፲፪ ፡ ፴፭) ። አዕናቍ ፡ ኃትዋን ፡ (ስንክ ፡ ሠኑ፳፯) ።


አኅተወ ፡ አቃጠለ ፡ ለኰሰ ፡ አያያዘ ፡ አበራ ፡ አስበራ ፡ (መሳ፲፭ ፡ ፬) ። አነ ፡ አኅኒቱ ፡ ማኅተተ ፡ ጥበብ ፡ ውስተ ፡ ልብከ ። መናረት ፡ እንተ ፡ ታኅትዉ ፡ (ሱቱ ፡ ዕዝ፲፬ ፡ ፳፭) ።

ማኅቶት ፡ ማኅ(ተ)ትው ፡ (ብ ፡ መኃትው ፡ ዋት) ፡ ፋና ፡ መብራት ፡ የሠም ፡ የዘይት ፡ የሌላውም ፡ ኹሉ ። ወማኅትት ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ። ማኅቶት ፡ ዘየ(ያ)ኅቱ ። መኃትወ ፡ ጽጕ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫ ። ዮሐ፩ ፡ ፴፭ ። ፲፰ ፡ ፫) ።

ማኅትው ፡ (ዋት ፡ አው ፡ መኃትው) ፡ ማብሪያ ፡ መቅረዝ ፡ ቀንዲል ፡ ፋኖስ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ሰብዑ ፡ መኃትዊ ፡ ዘወርቅ ። ወከልኤቱ ፡ መኃትው ፡ (ራእ፩ ፡ ፲፪ ። ፲፫ ። ፲፩ ፡ ፬) ።



ማኅቶት ፡



ማኅትው ፡

—፤ ዋዜማ ፡ ንኡስ ፡ በዓል ፡ እንደ ፡ ቀዳም ፡ ያለ ፡ መብራት ፡ የሚበራበት ። ኢትስግድ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወኢበማኅትዊሃ ። ሰንበት ፡ ማኅትወ ፡ ፋሲካ ፡ (ኒቅ ። ዲድ ፡ ፴) ። መዘምራን ፡ መዝሙር ፡ ከዋዜማ ፡ በፊት ፡ የሚጣፍ ፡ የዋዜማው ፡ ለት ፡ ጧት ፡ በነግህ ፡ የሚባል ፡ (ድጓ) ።

ኅቲም ፡ ሞት ፡ (ኅተመ ፡ የኅትም ፡ ይኅትም ። ዕብ ፡ ሐታም ። ሱር ፡ ሕታም ። ዐረ ፡ ኀተመ) ፤ ማተም ፡ መዝጋት ፡ መቈለፍ ፡ ማሸግ ። እመ ፡ ኅተምከ ፡ ወርቀከ ፡ ወብሩረከ ። ሠናይ ፡ ኅቲም ፡ ላዕለ ፡ ብእሲት ፡ እኪት ፡ (ሢራ፳፰ ፡ ፳፬ ። ፵፪ ፡ ፯) ።

—፤ መጣፍ ፡ መቍጠር ፡ ጥሮ ፡ ቈጥሮ ፡ ማኖር ። ኅተምኩ ፡ ውስተ ፡ ቍናማቲከ ፡ ጌጋይየ ፡ (ኢዮ፲፬ ፡ ፲፯) ።

—፤ መሸፈን ፡ ማልበስ ፡ መሰወር ፡ መተው ። ወገጸ ፡ ከዋክብት ፡ የኅትም ። ኃትም ፡ ለዝ ፡ ራእይ ። ኃትም ፡ ወኢትጽሐፍ ፡ ዘንተ ፡ (ኢዮ፱ ፡ ፯ ። ዳን፰ ፡ ፳፮ ። ራእ፲ ፡ ፬) ።

—፤ ስምን ፡ መጣፍ ፡ ማመልከት ፡ በብርዕ ፡ በቀለም ፡ ወይም ፡ በማኅተም ፡ ማኅተምም ፡ ባይኖር ፡ የጣፊትና ፡ ያውራ ፡ ጣት ፡ ምልክት ፡ ፊርማ ፡ ማድረግ ። ኅተመ ፡ ንጉሥ ፡ በሕልቀቱ ። ወኅተምዋ ፡ ለእብን ፡ (ዳን፮ ፡ ፲፯ ። ማቴ፳፯ ፡ ፷፮) ።

—፤ ማጥቈር ፡ መክተብ ፡ ንቅሳት ፡ ጥቍር ፡ ቀለም ፡ ቀብቶ ፡

በመርፌ ፡ በሾኽ ፡ መንቀስ ፡ መጠቅጠቅ ። ኢትኅትሙ ፡ አባለክሙ ፡ በመርፍእ ፤ (ፍ ፡ ን ፡ ፵፰) ።

—፤ መጨረስ ፡ መፈጸም ። ኢይፃኡ ፡ እምቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ዘእንበለ ፡ ይኅትም ፡ ካህን ። ይኅትሙ ፡ ጸሎቶሙ ፡ በጸሎተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፤ (ቀሌ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲፱) ።

—፤ መመስከር ፡ ማስረዳት ፡ ማጽናት ፤ የነገር ። እስመ ፡ ለዝሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀተሞ ። አኅትም ፡ ቃላትየ ፡ በጽድቅ ፡ (ዮሐ ፮ ፡ ፳፯ ። ቁር) ።

—፤ መቀባት ፡ መቀደስ ፡ ማክበር ፤ በሜሮን ። የኅትም ፡ አንፈ ፡ ወፍጽመ ፡ ልበ ፡ ወእገዚ ። እመ ፡ ቦ ፡ ቀሲስ ፡ ዘኅተማ ፡ በቅብዐ ፡ ቅዱስ ፡ (ኪዳ ። ፌ ፡ መ ፡ ፭ ፡ ፲፱) ። የኅተመን ፡ ፍች ፡ ፲፱ ፡ ብለው ፡ የሚቈጥሩ ፡ አሉ ፤ ምስክራቸው ፡ አያጠግብም ። ከተመንና ፡ ዐተበን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ኀታሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤** የሚያትም ፡ በታሚ ፤ ባለማኅተም ። ዓለመ ፡ ኀታሚ ። ፈጣሪ ፡ አስመሳይ ፤ ፍጥረቱን ፡ በፍጥረት ፡ የሚያትም ፡ (ኪዳ) ።

**አኅተመ ፤** አሳተመ ፡ አስመሰከረ ፤ ማኅተም ፡ ምልክት ፡ አስደረገ ።

**ተኀትመ ፤** ታተመ ፤ ተመለከተ ፤ ተዘጋ ፡ ተጨረሰ ፤ ተቀባ ። ይትኀተሙ ፡ ውስተ ፡ ፍጽምሙ ። ይትኀተሙ ፡ አግብርት ፡ በመላኪሆሙ ። ተሠጥቀት ፡ ምድር ፡ በአምሳለ ፡ ኆኅት ፡ ወመሠጠቶ ፡ ለውእቱ ፡ ሥጋ ፡ (አዳም) ፡ ወተኀትመት ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ። ከመ ፡ ትትኀተም ፡ ጌጋይ ። ምሥዋዕ ፡ ዘተኀትመ ፡ በሜሮን ፡ (ራእ ፯ ፡ ፫ ። ፍ ፡ ን ፡ ፶፭ ። ቀሌ ። ዳን ፱ ፡ ፳፬ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፭) ።

**ኀቱም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ትምት) ፤** የታተመ ፡ ዕትም ፤ የተጻፈ ፡ ጽሑፍ ፤ የተዘጋ ፡ ዝግ ፤ ስውር ። መጽሐፍ ፡ ኀቱም ። ዕፃ ፡ ዘኀቱም ፡ ላዕለ ፡ ዘመደ ፡ ዐጓለ ፡ መሕያው ። ዐዘቅት ፡ ኀትምት ። እስመ ፡ ዕጽው ፡

ወኀቱም ፡ ነገሩ ፡ (ኢሳ ፳፱ ፡ ፲፩ ። ሰንክ ፡ መጋ ፲፯ ። ማሕ ፬ ፡ ፲፪ ። ዳን ፲፪ ፡ ፱) ።

**ኅትመት ፤** ማተም ፡ መታተም ፡ አስተታተም ፡ ሰተማ ፤ ዕትማት ፤ ቡራኬ ። ጸሎተ ፡ ኅትመት ፡ (ቅዳ ። ስንክ ፡ የካ ፳) ።

**ማኅተም ፤ (ማት ፤ መኳትም ። ዐረ ፡ ኀትም ። ዕብ ፡ ሖታም) ፤** በቁሙ ፡ ማተሚያ ፡ መታተሚያ ፤ የበር ፡ የነገር ፡ መዝጊያ ፤ የባት ፡ የጥፈት ፡ ምልክት ፤ ኀቲም ፡ ቀለበት ፡ ፈርጡ ፡ ማኅተም ፡ የኾነ ፡ ስምና ፡ መልክ ፡ የተቀረጠበት ፤ ቀለበትነት ፡ ከማኅተምነት ፡ ያለው ፡ (ዳን ፮ ፡ ፲፯ ። አስቴ ፰ ፡ ፰) ። እንዘ ፡ ኢያርኁ ፡ ማኅተመ ፡ ድንግልናሃ ። ምጽዋቱ ፡ ለሰብእ ፡ ከመ ፡ ማኅተም ፡ ምስሌሁ ። ዘኀተመኒ ፡ በሰብዐቱ ፡ መኳትም ፡ (ቅዳ ። ሢራ ፲፯ ፡ ፳፪ ። ራእ ፡ ባሮ) ።

—፤ ማኅተም ፡ የወደቀበት ፤ ሥዕሉና ፡ ምስሉ ፡ ጥፈቱ ፤ የማኅተሙ ፡ ቅጅ ። ዳኅንኑ ፡ ማኅተም ። ወማኅተማት ፡ (ዳን ፲፫ ፡ ፲፯ ። ዘዐ ፳፰ ፡ ፳፩) ።

—፤ ጥምቀትና ፡ ሜሮን ፤ ቍርባን ። ማኅተመ ፡ እግዚ ፡ ዘውእቱ ፡ ቅብዐ ፡ ሜሮን ፡ ቅዱስ ። ኢያፍርሁኒ ፡ ቀታልያኒሃ ፡ ለነፍስ ፤ እስመ ፡ ማኅተምየ ፡ ይምክ ፡ ቅዱስ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፰ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ መጋ ፳፯) ።

—፤ የጥፈት ፡ መሣሪያ ፤ መጻሕፍት ፡ የሚታተሙበት ፡ መኪና ፡ ፊደል ፡ በየስሙና ፡ በየመልኩ ፡ ከብረት ፡ ከርሳስ ፡ የሚሠራ ። ኄሕነ ፡ ገበርነ ፡ ዘንተ ፡ ማኅቱመ ፡ ወኀተምነ ፡ መጻሕፍተ ፡ (አዋል) ። የማኅተም ፡ ሥራ ፡ የተዠመረ ፡ ባ፲፬፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ፡ ይባላል ፤ የዠመሩትም ፡ ጉተንቤርግ ፤ ፎስት ፡ የሚባሉ ፡ ፪ ፡ የጀርመን ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸው ።

—፤ የቀመር ፡ ስም ፡ ማእከላይ ፡ ቀመር ፤ ቍጥሩ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ። በዚህ ፡ አበቅቴና ፡ ወንጌላዊ ፡ ይገናኙበታል ፤ አበቅቴው ፡ አልቦ ፡ ወንጌላዊው ፡ ማቴዎስ ። ዐውደ ፡ ማኅቱም ፡ (መር ፡ ዕጨ) ።

**ኀተተ ፤—መረመረ ፤—ሐተተ ።**

# ጠ

ጠ ፤ ዘጠነኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፡ ስሙ ፡ ጠይት ፤ ቍጥሩ ፡ ዘጠኝ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ ጠ ፡ ተሰዐት ፡ ፱ ፡ ይባላል ።

**ጤአ ፤—ደፈነ ፤—ጠዩዕ ፡ ጤዐ ።**

**ጣእጥአ ፤ አት ፤ (ጣእጥእ ፡ ይጣእጥእ ፡ ይጣእጥእ ። ዕብ ፡ ጣእጤእ) ፤** መጥረግ ፡ መከወን ፡ እድፍን ፡ ጉድፍን ፡ ማሶገድ ፡ ማስገለል ፤ በታን ፡ ቤትን ፡ ንጹሕ ፡ ጥሩ ፡ ማድረግ ። መሰብቀል ፡ መቀልጠፍ ፡ ቅልጥፍጥፍ ፡ ማለት ፤ ማማር ፡ መጣፈጥ ፡ መከናወኝ ፤ የግብር ፡ የነገር ፡ ያንደበት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጣእጥአ ፡ ፈንታ ፡ አጣእጥአ ፡ ተጣእጥአ ፡ ይላል ፤ መንገዱ ፡ አይደለም ። ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ጽዱጥ ፡ ጸዐጠ ፡ ነው ፤ ጠና ፡ ጸ ፡ አና ፡ ዐ ፡ ይወራረሳሉ ፤ መዕአና ፡ ዋእዕአም ፡ ይመስሉታል ።

**አጣእጥአ ፤ (አስደራጊ)** ፤ አስጠረገ ፡ አስ ክወነ ፡ ኀጸሐ ፡ አስደረገ ።

**አጣእጥአ ፤ (አድራጊ)** ፤ አበጀ ፡ አዘጋጀ ፡ አሰናዳ ፤ አሳመረ ፡ አስጌጠ ፡ አጣፈጠ ፡ ፈጸመ ፡ ጨረሰ ፡ አከናወነ ። ያጣእጥእ ፡ በከመ ፡ ፈቀደ ። እንዘ ፡ ያጣ እጥእ ፡ ቃለ ። አምደስ ፡ ዘአጣእጥእዎ ፡ በሶከር ። አጣእጥኡ ፡ ንብረተክሙ ። ኢተክህሎሙ ፡ ያጣእ ጥኡ ፡ ሕንጻተ ፤ (ቅዳ ፡ ኢጲ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፰ ። ፈ ሙ ፡ ፳፫ ፡ ፭ ። ዮሴፍ) ። ዳግመኛም ፡ አጣእጥአ ፡ በማ ለት ፡ ፈንታ ፡ አስተጣእጥአ ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ ከማድረግ ፡ አይወጣም ። ወቀደመ ፡ አስተጣእጥአ ፤ ወከነ ፡ ው እቱ ፡ ፍኖተ ፡ ሕይወት ፡ ለነ ፤ (ቄር ፡ ጸላ) ። ጣእጥአ ፡ የማህረክ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እስቱ ፡ ሲገባበት ፡ ማድረግ ኀኛ ፡ ማስደረግኑ ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ማደራረግንም ፡ ያ ሳያል ፡ ማህረክንና ፡ ባረክን ፡ እዩ ።

**አጣእጣኢ ፤ መጣእጥኢ ፤** የማይበጅ ፡ የማያዘጋጅ ፡ አጣፋጭ ፡ አሳማሪ ፡ አስጊያጭ ። አጣእጣ ኢሆሙ ፡ ለፍጡራን ፤ (መጽ ፡ ምስ ። አርጋ ፡ ፪) ።

**ተጣእጥአ ፤** ተዘጋጀ ፡ ተሰናዳ ፡ ተከናወነ ፡ ተ ከናጥወነ ። እንበለ ፡ ይጣእጥኡ ፡ አድባር ። እምቅ ድመ ፡ ይጣእጥአ ፡ መሠረታተ ፡ አውግር ። እምድ ኅረ ፡ ጸንዐት ፡ መንግሥቱ ፡ ወተጣእጥአ ። ኢተጣ እጥአ ፡ ለአግሪጳስ ፡ ንብረቱ ። ወኢይጣእጣእ ፡ ተግ ባሮሙ ፤ (ዲድ ፡ ፴ ። መጽ ፡ ምስ ። ፪ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፮ ። ዮሴፍ) ።

**ጥእጡእ ፤ (እን ፡ እት ፡ ጥእት) ፤** የጣፈጠ ፡ የተጣፈጠ ፡ ጥፍጥ ፡ ጠፍ ፡ ያለ ፡ ያማረ ፡ የተከናወነ ፡ ውብ ፡ ስብቅል ፤ ንጹሕ ፡ ጥሩ ፡ እድፍ ፡ ጉድፍ ፡ ጸያፍ ፡ የሌለበት ። ዘአምሳክ ፡ ቃል ፡ ጥእጡእ ፡ ከመ ፡ ዝ ። ዘቦቱ ፡ ልሳን ፡ ጥእጡእ ፡ ወዘፍኖቱ ፡ ርቱዕ ። አን ስት ፡ ይሰርገዋ ፡ ጥእጥእ ፡ በዘይደሉ ፡ ስርጕ ፡ ትሕ ትና ፤ (ኪዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፯ ። ኪዳ) ።

**ጥእጣኤ ፤** መጣፈጥ ፡ መከናወን ፤ ጸያፍን ፡ መክተት ፡ ስብቅልንት ። ጣዕም ፡ ውበት ፤ ጠፍታ ፡ ቅል ጥፍና ። ዘእንበለ ፡ ዕቀፍት ፡ ውእቱ ፡ ወበጥእጣኤ ። እግዚእ ፡ ዘሠራዕከ ፡ ኵሉ ፡ በሥርዐት ፡ ወበመንክር ፡ ጥእጣኤ ፤ (ቄር ፡ ጸላ ። ኪዳ) ።

**ጥእጥእና ፤** ጥፍጥንት ፡ ጠፍተኛንት ፡ ስብቅ ልንት ፡ ያሰባዘበ ፡ ያነጋገር ። በጽሙና ፡ ወጥእጥእና ፤ (ኪዳ) ።

**አንጣእጥአ ፤ (ዲቃ ፡ ግ) ፤** ፈራ ፡ ደነገጠ ፤ ተንቀጠቀጠ ፤ ተናወጠ ፡ ተነዋወጠ ። ተንጣጣ ፡ ተፈና ጠረ ፤ ጣእ ፡ ጣእ ፡ ፍንጥር ፡ ፍንጥር ፡ አለ ። አንጣጣ ፤ አፈናጠረ ። ለምንት ፡ ታንጣእጥእ ፤ (ሉቃ ፡ ዐ፱፰ ፡ ፲፫) ።

**እንጣእጤ ፤** ተልባ ፤ የሚንጣጣ ፡ የሚፈናጠር ፤ (ትግሪኛ) ።

**ጥእመ ፤—ቀመሰ ፤—ጥዒም ፡ ጥዕመ ።**

**ጥብ ፤—ጡት ፤—ጠቢው ፡ ጠበወ ።**

**ጠቢ ፤ ጡባ ፤—ጥር ፤—ጠወበ ።**

**ጠብአ ፤—ወደደ ፤—ጠቢዕ ፡ ጠብዐ ።**

**ጠቢብ ፤ ቦት ፤ (ጠበ ፤ ጠበበ ፡ ይጠ ብብ ፡ ይጥብብ ። ዐረ ፡ ጠበ ። ሱር ፡ ጣብ) ፤** መጠበብ ፡ መፈልሰፍ ፡ መራቀቅ ፡ ልባም ፡ ጥበበኛ ፡ መ ኾን ፡ በግብር ፡ በነገር ። አልቦ ፡ ዘይጠብብ ፡ እምኔከ ። አንተኑ ፡ ትጠብብ ፡ እምዳንኤል ። አርአዩ ፡ እስኩ ፡ ዘጠበ ፡ እንዘ ፡ ሕሙም ፡ ወጽዑር ። ከመ ፡ ይጥብቡ ፡ በኪዳሙ ፤ (ዘፍጥ ፡ ፴፱ ። ሕዝ፳፰ ፡ ፫ ። አረ ፡ ተ፱ ። ሚራ ፴፰ ፡ ፴፱) ።

—፤ መዳን ፡ መፈወስ ። ጠበ ፡ ንጉሥ ፡ እምእንባለሁ ፤ (ገድ ፡ ተክ) ። ጠበ ፡ ጠበበ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተጠበበ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ይጠበቡ ፡ በነገር ። እለ ፡ ይጠበቡ ፡ ለእከይ ። ኢትጠበብ ፡ በኀበ ፡ ንጉሥ ። አሕውርኒ ፡ በተኀሕልዎ ፡ ወበተጠብቦ ። መጽአ ፡ በተጠብቦት ፤ (ሔኖ፴፮ ፡ ፯ ። ኢሳ፳ ፡ ፳፭ ። ሚራ፯ ፡ ፭ ። ዮሴፍ ። ክፋ ፡ ፴፯) ።

**ጠባቢ ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ በብት) ። አው ፡ ጠቢብ ፤ (ባን ፡ ባት ፤ ጠባብ ፡ ባት) ፤** የሚጠበብ ፡ ጥበበኛ ፡ ልባም ፡ ብልኅ ፤ በዋቂ ፡ ተራቃቂ ፤ ፈላስፋ ፡ ሐኪም ፤ ጠንቋይ ፡ መሠሪ ፡ ባለጅ ፡ የንጨት ፡ የብረት ፡ ሠራተኛ ፤ መሐንድስ ፡ ሠዓሊ ፡ ዐናጢ ፡ ገንቢ ፡ ሽማኔ ፤ ጸሓፊ ፡ ምሁር ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ንጉሥ ፡ ጠቢብ ። ወቦ ፡ እምውስተ ፡ ጠቢባን ። በከመ ፡ ይተ ግህ ፡ ጠቢብ ፡ ለፈውሶ ፡ ሥጋ ። ቤት ፡ እንተ ፡ ሐነጽዋ ፡ ኬነውት ፡ ወጠበብት ፡ ምድር ። ኅምስቱ ፡ ዕደው ፡ ጠቢባን ፡ መጻሕፍት ። ጠባብ ፡ ወትሕት ። ጠባባት ፡ አንስት ፤ (ሚራ፲ ፡ ፩ ። ግብ፲፯ ፡ ፲፰ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፯ ። ሐም፯ ። ድጓ ። ምሳ፲፬ ፡ ፩) ።

**ጠቢብና ፤** ጥበበኛንት ፡ ጥበበኛ ፡ መኾን ።

**ጥበብ ፤ (ባት) ፤** ብልሐት ፤ ዕውቀት ፡ ብልኅነት ፤ ፈሊጥ ፡ ፍልስፍና ፤ ሕክምና ፡ ጥንቈላ ፤ ምክር ፡ ተን ኰል ። ጥበብ ፡ ሐፀነተከ ፡ ከመ ፡ ጥብ ። ባሕረ ፡ ጥበ ባት ። ቤተ ፡ ጥበብ ። ተምህሩ ፡ ግብረ ፡ ጥበብ ፡ ወ ክኑ ፡ ይፌውስዎሙ ፡ ለድዉያን ። ምሁር ፡ በኵሉ ፡ ጥበበ ፡ ሥራይ ፡ ወሰገል ። ጥበበ ፡ ከዋክብት ። ፈርሁ ፡ ከመ ፡ ኢይጠብቡ ፡ ካልአ ፡ ጥበበ ፡ ዓዐሌሆሙ ። መ ክረት ፡ ጥበበ ፤ (ድጓ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ኅዳ፳፱ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ሐም፳፯ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ነሐ፲፭) ።

—፤ መጽሐፍ ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ የብሉይ ፡ መጣፍ ፤ ጠቢባን ፡ የጣፉት ፡ የተናገሩት ። ጥበበ ፡ ሰሎሞን ። ጥ በበ ፡ ሢራክ ።

**አጥበበ ፤** አለበመ ፡ አስተማረ ፡ ብልኅ ፡ አደረገ ። አብዳነ ፡ አጥብብ ። መቅሠፍት ፡ ወተግሣጽ ፡ በኵሉ ፡ ያጠብብ ። እግዚ ፡ ያጠብቦሙ ፡ ለዕዉራን ። አፍ ቅራ ፡ ወታጠብበከ ፤ (ኪዳ ። ሚራ፳፱ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፻፵፭ ። ፈልክ) ።

**አጥባቢ ፤ መጥበቢ ፤** የሚያስብም ፡ አስ ባሚ ፤ ብልኅ ፡ አድራጊ ፤ የጥበብ ፡ መሪ ፤ ጥበብ ፡ አስተ ማሪ ። መጥበቢሆሙ ፡ ለአብዳን ። መምህሮሙ ፡ ወመጥበቢሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይትቀነዩ ፡ ለእግዚ ። መ ጥበቤ ፡ ሕዛናት ፡ በስምዐ ፡ (ሮሜ፪ ፡ ፳ ። ዲድ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ግንቦ) ።

**ተጣበበ ፤** በቁሙ ፡ ተራቀቀ ፡ ተተናኰለ ፡ ተ ተንኳኰለ ።

**ተጥባብ ፤** ተንኰል ፤ ክፉ ፡ ምክር ፡ የፖሊቲክ ፡ ነገር ። ወኮነ ፡ ውስቴቱ ፡ ዐቢይ ፡ እከይ ፡ ወተኳሕ ልዎ ፡ ወተጥባብ ፡ ወተምያን ፡ (ዮሴፍ) ።

**አስተጣበበ ፤** አራቀቀ ፡ ጥበብ ፡ አዋጣ ፡ አሻ ሻለ ፤ ከራሱ ፡ ወይም ፡ ከሌላው ። እሌ ፡ ሎሙ ፡ ለመ ናፍቃን ፡ እለ ፡ ያስተጣብቡ ፡ ርእሶሙ ፡ (ዲድ ፡ ፴፫) ። ምስጢሩ ፡ አድራጊነት ፡ ከደራራጊነት ፡ ያሳያል ፡ ባድራጊ ነቱ ፡ ያጥበበ ፡ ድርብ ፡ ነው ።

**ጠብጠበ ፤ (ቀቀ ፡ ግ) ፤** በቁሙ ፤ ጠበጠበ ፤ ፈጠነ ፡ ቸኰለ ፡ ቀለጠፈ ፤ ያክኼድ ፡ የሥራ ፡ የንባብ ፡ የጥ ፈት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ አርእስቱ ፡ ጠብጥበ ፡ ሲኾን ፤ አን ቀጹን ፡ በጠብጠበ ፡ ፈንታ ፡ እንዳማርኛው ፡ ጠበጠበ ፡ ይላል ፤ የመሳሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ባለመጣፎ ችም ፡ አማረ ፡ አሳመረ ፡ ጣፈ ፡ ይሉታል ፤ እውነተኛ ፡ ፍች ፡ አይደለም ፤ መረደን ፡ እይ ። አልብየ ፡ ኀይል ፡ ከመ ፡ አርኢ ፡ ሥዕ ፡ ለፈጣሪ ፡ በጠብጥቦ ፡ ቀለማት ። ከመ ፡ ቀለመ ፡ ጸሓፊ ፡ ዘጠበጠበ ፡ ይጽሕፍ ፡ ልሳ ንየ ፡ (አረጋ ፡ መልኳ ፡ ፲፭ ። መዝ ፡ ፵፬) ።

**ጠብጠበ ፤** ገረፈ ፤ ጠበጠበ ፡ ቸበቸበ ፤ ያለንጋ ፡ የጅራፍ ፡ የለበቅ ።

**ጠብጣቢ ፤** በቁሙ ፡ ኻ(ሀ)ያጅ ፡ ፈጣን ። ገራፊ ፡ ባለጅራፍ ።

**ተጠብጠበ ፤** ተገረፈ ፤ ተጠበጠበ ። ሰላም ፡ ለጳውሎስ ፡ ቅሡፈ ፡ ዘባን ፡ ወገቦ ፡ በመኃትው ፡ ነድ ፡ ወተጠብጥቦ ፡ (ስንክ ፡ የካ፶) ።

**ጥብጡብ ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ጥብት) ፤** የተ ገረፈ ፤ ግርፍ ። ሰላም ፡ ለገቦክሙ ፡ በአሕባለ ፡ መን ፈስ ፡ ጥብጡብ ፡ (ደራሲ) ።

**ጥብጣቤ ፤ (ያት ፡ ብያት) ፤** መግረፍ ፡ መገ ረፍ ፡ አገራረፍ ፤ ግርፊያ ፡ ግርፋት ። ሰላም ፡ ለዘባንከ ፡ በጥብጣቤ ፡ ዘተኰነነ ፡ ከመ ፡ ጥብጣቤሁ ፡ ለክርስ ቶስ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ዘኮነ ። ዘተጽዕረ ፡ በምንዳቤ ፡ ወዘሐመ ፡ በጥብጣቤ ። ወለእመ ፡ ኢይገብር ፡ ዘ ንተ ፡ አሰፈዎ ፡ ጥብጣቤ ፡ ወቀትሎ ። አርብዓ ፡ ጥብ ጣቤ ፡ (ደራሲ ። ስንክ ፡ ጥር፲፰ ። ዮሴፍ ። አዋል) ።

**ጥብጣቤ ፤ (ዐረ ፡ ጠብጠቢያት) ፤** መግረ ፊያ ፡ መጠብጠቢያ ፤ ኩርባጅ ፡ ዐለንጋ ፡ ጅራፍ ፡ ሳንባ ፡ ጠለፍ ፡ ጠፍር ፡ ገመድ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ከመ ፡ ይ ዝብጥዎ ፡ በአብትር ፡ ወድኅሬሁ ፡ በጥብጣቤ ። ቀሠፍዎ ፡ በጥብጣቤ ፡ ላሕም ። ይቀሥፍዎ ፡ በጥ ብጣቤ ፡ ዐቢየ ፡ መቅሠፍተ ፡ (መቃ ፡ ገ፪ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳፯ ። ፊ ፡ መ ፡ ፩ ፡ ፰ ። ዮሐ፪ ፡ ፲፰) ።

**አንጠብጠበ ፤ - አንጠባጠበ ፤ - ነጠብ ፡ ነጥበ ።**

**ጠብደን ፤ (ብ ፡ ጠባድን ። ጽር ፡ ታባ ዲን ። ዕብ ፡ ባድ ፤ ባዲም) ፤** ልብስ ፡ ከታን ፤ ከተ ልባ ፡ እግር ፡ ፈትል ፡ የሚሠራ ፤ ጽሩይ ፡ ጸዐዳ ። ባለብሉ ዮች ፡ ግን ፡ እርድ ፡ እንቀጥቅጥ ፡ ማምጃ ፡ ይሉታል ። ብእሲ ፡ ዘይለብስ ፡ ጠብደነ ፡ (ዳንኤ ፡ ፲ ። ፲፪ ፡ ፮ ፡ ፯) ።

**ጠብሀ ፤ — ዐረደ ፤ — ጠቢሕ ፡ ጠብሐ ።**

**ጠቢው ፤ ዎት ፤ (ጠበወ ፡ ይጠቡ ፡ ይ ጥቡ) ፤** መጥባት ፡ ጡት ፡ መጉረፍ ፤ ወተትን ፡ ከጡት ፡ ባፍ ፡ መሳብ ፡ መምጠጥ ፡ መመጥመጥ ። እለ ፡ አኀደግ ዎሙ ፡ ጠቢወ ፡ ጥብ ። ጠበወ ፡ ሐሊበ ፡ እምብእ ሲት ። በግዐ ፡ ዘይጠቡ ፡ ሐሊበ ፡ እሙ ። ሕፃናት ፡ እለ ፡ ይጠብዉ ፡ ጥበ ፡ (ኢሳ፳፰ ፡ ፱ ። ሃይ ፡ አበ ። ዘፀ፴፬ ፡ ፳፮ ። ዮኤ፪ ፡ ፲፮) ።

**ጠባዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ በውት) ፤** የሚጠባ ፡ ጠቢ ፤ ጡት ፡ ያልተወ ፡ ሬሳቅላ ። በእንተ ፡ አ ሐዱ ፡ ጠባዊ ፡ ዘገደፉ ፡ ማእከለ ፡ ፈለግ ። ሕፃ ናት ፡ ወጠበውት ፡ (ኩፋ፵፯ ። ሰቈ፪ ፡ ፲፩) ።

**ጥብ ፤ (ብ ፡ አጥባት ። ዐረ ፡ ጢብይ) ፤** ጡት ፡ የወተት ፡ ዘለላ ፡ ወኽ ፡ ግት ፡ የሚታለብ ፡ የሚጠባ ። ተሐፀንኩ ፡ በጥብ ። አኀደግዎ ፡ ጥበ ፡ እሙ ። ከ ልኤ ፡ አጥባትኪ ። አጥባት ፡ ይቡሳት ፡ (ኢዮ፫ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፲፩ ። ማሕ፬ ፡ ፭ ። ሆሴ፱ ፡ ፲፬) ።

**አጥበወ ፤** አጠባ ፡ አስጠባ ፤ ጡት ፡ አጐረሠ ፤ አስጐረሠ ፡ መገበ ። ከመ ፡ ኣጥቡ ፡ ሕፃንየ ። አክይ ስት ፡ አጥበዉ ፡ ዕጐሊሆሙ ። አጥበውኩከ ፡ ወሐ ፀንኩከ ። ያጠብዎ ፡ እግዚ ፡ ሲሥረዊሃ ፡ እምክል ኤቱ ፡ አጥባት ፡ እማይ ፡ ወእመሬት ፡ (ዘኍገ ፡ ፩ ፡ ፳፯ ። ሰቈ፬ ፡ ፫ ። ዮሴፍ ። መቃ ፡ ገ፳) ።

**አጥባዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** የሚ ያጠባ ፡ አጥቢ ፤ እመጫት ፡ ሞግዚት ። ሕፃንያት ፡ ወአ ጥባውያት ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፵፪ ፡ ፲፫) ።

**ጠቢሕ ፤ ሐት ፤ (ጠብሐ ፡ ይጠብሕ ፡ ይጥባሕ ። ዕብ ፡ ጣባሕ ። ሱር ፡ ጥባሕ) ፤** ማረድ ፡ መሠዋት ፡ መቍረጥ ፡ መበለት ፤ መሰንዘር ፡ መ ብጣት ፤ መግፈፍ ፡ መላጥ ፤ ቈርበትን ፡ ከሥጋ ፡ መለየት ፤ መጥባት ፡ መጠብጠብ ፡ ማወራረድ ። ኹሉም ፡ የማረድ ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ በስተኋላ ፡ ዘብሐን ፡ ዘሐቀን ፡ እይ ። ጠ ብሐ ፡ አልሕምተ ። ከመ ፡ በግዐ ፡ የዋህ ፡ ዘይወስ ድዎ ፤ ይጥብሕዎ ። ትጠብሖ ፡ በበ ፡ መሌሊቱ ። ከመ ፡ ጠቢብ ፡ ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ዘይጠብሕ ፡ በመ ላጺ ። ጠብሑ ፡ አነዳ ፡ ርእሱ ። ጠብሕዎ ፡ ማእሶ ፡ (ኢሳ፳፱ ፡ ፲፫ ። ዘፀ፳፱ ፡ ፲፮ ። ዲድ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ ሐም ፲፫ ። ጥር፲፩) ።

**ጠባሒ** ፡ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት) ፤ የሚ ያርድ ፡ የሚባልት ፡ ዐራጅ ፡ ገፋፊ ፡ በጋማሽ ፡ ሥጋ ፡ ቤት ። ጠባሕያን ፡ አልሕምት ፡ (ማር ፡ ይሥ) ።

**አጥብሐ** ፤ አሳረደ ፡ አሸጠባ ፡ አስበጣ ፡ አስገፈፈ ።

**ተጠብሐ** ፤ ታረደ ፡ ተጠባ ፡ ተበስተ ፡ ተገፈፈ ። መጽአ ፡ ይጠባሕ ፡ ከማ ፡ በግዐ ፡፡ ከመ ፡ ባሕም ፡ ዘየሐውር ፡ ለተጠብሖ ፡ (ኢሳ፶፫ ፡ ፯ ። ምሳ፯ ፡ ፳፪ ። ዘኍ ፲፩ ፡ ፳፪) ።

—፤ ተበጣ ፡ ተተፈተፈ ፡ ተፈቃ ። ይጠባሕ ፡ ገጸሙ ፡ (ሕዝ፳ ፡ ፱) ።

**ጥቡሕ** ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ብሕት) ፤ የታ ረደ ፡ የተበሰተ ፡ የተበጣ ፡ ብጥ ።

**ጥብሐት** ፤ (ታት) ፤ ማረድ ፡ መታረድ ፡ አስ ተራረድ ፡ ዐረዳ ፡ ዕርደት ፡ ዕርድነት ። ዘየሠብሕ ፡ ላሕመ ፡ ለዕለተ ፡ ጥብሐት ፡ (ያዕ፭ ፡ ፭) ።

**ጥብሕ** ፤ (ሓት) ፤ ዕርድ ፡ ፍሪዳ ፤ መሥዕት ። ፀቢይ ፡ ጥብሕ ፡፡ ዘብሒት ፡ ዘዚኣሃ ፡ ጥብሕ ፡፡ ሰ ሐኪ ፡ ያምጽኡ ፡ ለከ ፡ ሥጋ ፡ እምጥብሕከ ፡ ዘጠ ባሕከ ፡ በውስተ ፡ ቤትከ ፡፡ ተአዘዘ ፡ በበዓል ፡ አዕ ርጊ ፡ መባእ ፡ ወጥብሕ ፡ (ኢሳ፩፱ ፡ ፯ ። ምሳ፱ ፡ ፪ ። ዮሴፍ ። አርጋ ። ዘዳ፲፰ ፡ ፫) ።

**ምጥባሕ** ፤ ማረጃ ፡ ቦታ ፤ ምሥዕ ፡ መንበረ ፡ ታቦት ። ምጥባሐ ፡ ሥጋሁ ፡ ወምቅዳሐ ፡ ደሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ (አርጋ ፡ ፯) ።

**መጥባሕት** ፤ (ብ ፡ መጣብሕ ፡ ት) ፤ ማረጃ ፡ መቍረጫ ፡ ካራ ፡ ቢላዎ ፡ ሰንጢ ፡ ስለታም ፡ ብ ረት ፡ ጐራዴ ፡ ስለቱ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ የኾነ ፤ ወ ይም ፡ ፪ ፡ አፍ ፡ ያለው ፤ ሰይፍ ፡ ሾተል ፤ አፉ ፡ ጩቤ ፤ ጐደ ፡ ዱቢት ፡ ቀጭኔ ፡ ቀልሴ ፡ ፀጥንት ፡ አይመልሴ ። መጥባሕት ፡ ዘእብን ፤ (ሱሩጭ ፡ ቡልጭት) ። መጥባ ሕት ፡ ዘጠባሕያኑ ፡ አልሕምት ፡፡ መጥባሕተ ፡ ጸ ሓፊ ፡፡ አነዳ ፡ ድማሁ ፡ በመጥባሕት ፡ ጠብሐ ፡፡ መጥባሕት ፡ ዘክልኤ ፡ አፉሁ ፡፡ ይጸውሩ ፡ መጥባ ሕተ ፡ ንኡሳነ ፡ ወበሲኃኒ ፡ ወየኀብእዎሙ ፡ ውስተ ፡ ልብሶሙ ፡፡ ነሥኡ ፡ መጣብሒሆሙ ፡ (ኢያ፭ ፡ ፪ ። እዋል ። ኤር፴፫ ፡ ፳፫ ። ስንክ ፡ ሐም፲፫ ። ምሳ፳ ፡ ፬ ። ዮሴፍ ። ዘፍ፳፪ ፡ ፳፯) ፡፡



መጥባሕት ፡

**መጥባሕታዊ** ፤ የካራ ፡ ወገን ፤ የካራ ፡ ዐይ ነት ፡ ስለታም ። ባለካራ ፤ ባለሾተል ፤ ወይም ፡ ሃይማኖቱ ፡ ካራ ፡ የሚባል ። እሉስ ፡ መጥባሕታውያን ፡ ይትና ገሩ ፡ ፈጠራ ፡ (ምእላድ) ። የካራ ፡ ባህል ፡ ስልቱ ፡ ፭ ነው ። ፩ኛው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቃል ፡ የነሣውን ፡ ሥጋ ፡ አለዘር ፡ ቢከፍልና ፡ ቢፈጥር ፡ ቅብዕ ፡ ተባለ ፡ ይላል ። ፪ኛው ፤ ከአዳም ፡ ፍዳ ፡ ስላነጻው ፡ ቅብዕ ፡ ተባለ ፡ ብሎ ፡ መጣፍ ፡ ይጠቅሳል ፡ (ሮሜ፭ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭) ። ፫ኛው ፤ የብ ሉዩ ፡ ሊቃ ፡ ካህናት ፡ ፱ቱን ፡ ሽቱ ፡ ባ፲፩ኛ ፡ ዘይት ፡ ያዋ ሕዳቸው ፡ ነበረና ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አዋሐጅ ፡ ስለ ኾነ ፡ ቅብዕ ፡ ተባለ ፡ ይላል ። ፬ኛው ፤ በሰውነቱ ፡ ለኛ ፡ አብነት ፡ ሊኾን ፡ ተቀባ ፡ እንጂ ፤ መቀባቱ ፡ ለርሱ ፡ አል ጠቀመውም ፡ ይላል ። እነዚህ ፡ አራቱ ፡ ኹሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ የሚሉ ፡ ናቸው ፤ ብህላቸው ፡ ግን ፡ ገባሬ ፤ መንጽሒ ፤ ደማሪ ፤ ዘኢይረብሕ ፡ ቢያሰኝ ፡ እንጂ ፤ ቅብዕ ፡ አያሰኘውም ። ፭ኛው ፤ ወልድ ፡ ቅብዕ ፤ በሰውነቱ ፡ አም ላክ ፤ ሥጋውን ፡ በተዋሕዶ ፡ ስላከበረ ፡ ቅብዕ ፡ ተባለ ፤ ተቀብዐ ፡ ማለትም ፡ ተዋሐደ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እንደኛ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከበረ ፡ ተሾመ ፡ ማለት ፡ አይ ደለም ፡ ይላል ። ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በሱስንዮስ ፡ ዘመን ፡ የበቀለው ፤ ኋላም ፡ በቴዎድሮስ ፡ የተሳለው ፡ ይህ ፡ ፭ ኛው ፡ ነው ፤ ያነቁትም ፡ ሰዎች ፤ አዛዥ ፡ ዘድንግል ፡ አባ ፡ ክርስቶስ ፡ ይባላሉ ፤ የተሳለበትም ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ። (ታሪክ) ፤ የጐንደሮች ፡ መንግሥት ፡ ዘውዱ ፡ ብቻ ፡ ሲ ቀር ፡ ግዛቱ ፡ ኹሉ ፡ ባ፲፯፻፵፯ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ መሳፍ ንት ፡ ከኼደ ፡ በኋላ ፡ ፊስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ትግሬን ፡ ለብቻቸው ፡ ሲገዙ ፡ በርሳቸው ፡ ዘመን ፤ ከትንቤን ፡ ከደ ብረ ፡ ዳሞ ፡ ካባ ፡ ገሪማ ፡ ከነዚህ ፡ ከሦስቱ ፡ አህጉር ፡ አባ ፡ ኪሮ ፤ ደብተራ ፡ በትሩ ፤ አለቃ ፡ ዐምደ ፡ መንሱት ፡ የሚባሉ ፡ ሦስት ፡ ሐሳውያን ፡ ተነሥተው ፡ ፲፪ ፡ ክሕደት ፡ ፈጥረው ፡ ጥፈው ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንደዚህ ፡ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ መናፍ ቃን ፡ ተነሥተው ፡ አስቸግረውናል ፡ የሊህም ፡ መረጃ ፡ አሩቸው ፡ የሚዘጋበት ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ያለዚህ ፡ አይረቱምና ፡ ይህን ፡ ሃይማኖት ፡ አጽኑልን ፤ የተላከ ፡ ክ፴፱ቱ ፡ አድባራት ፡ ከጐንደር ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ላኩ ። (ተረት) ፤ የገባያ ፡ ግርግርታ ፡ ለቀጣፊ ፡ ተመ ቸው ። ግብጦችም ፡ ያባቶቻቸው ፡ ትምርትና ፡ ቋንቋ ፡ በተንባላት ፡ ዘመን ፡ ዕልም ፡ ድርግም ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ጠፋ ፡ እውነት ፡ መስሏቸው ፡ ተቀበሉት ። «በእንተ ፡ ብዝኀ ፡ ተደምሮትሙ ፡ ምስለ ፡ ተንባላት ፡ እስመ ፡ ጠፍአ ፡ ልሳኖሙ ፡ ቅብጥ ፡ ዘእምኔሁ ፡ የአምሩ ፡ ጽድቀ ፡ ሃይማኖቶሙ ፤ ወከኑ ፡ ዘኢይሰምዑ ፡ ዝክረ ፡ ሥ ሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ኅዳጣን ፤ ወኢሰወልደ ፡ እግዚ ፡ ተዘከርዎ» ፡ (ሳዊ ፡ ዘእስ ፡ ድ፲) ። ከለማበት ፡ የተጋባበት ፡ እንደሚሉት ፡ ኹሉ ፤ ከዚያ ፡ ወ ዲህ ፡ የመጡት ፡ ጳጳሳት ፡ እናባ ፡ ኢዮሳብ ፤ ይልቁንም ፡ ጥንተ ፡ ስማቸው ፡ ሚናስ ፡ እንድራዎስ ፡ የነበረ ፡ ቄር ሎስ ፡ ሰላማ ፡ ወልድ ፡ ቅብ ፡ በማለት ፡ ጸንተው ፡ ሲሰደ ዱና ፡ ሲያስድዱ ፡ ሲያሳስሩና ፡ ሲያስገርፉ ፡ ሲያስይፉ ፡ ኖሩ ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የግብጦች ፡ ሃይማኖት ፡ ተብሎ ፡ ባዋጅ ፡ በግዛት ፡ የማርቆስን ፡ ስም ፡ ተቀብቶ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ነግሧል ፡ የትርጓሜውን ፡ መጥፎነት ፡ ወልድ ፡ ዋ ሕድ ፡ ማለትን ፡ እንዲያፈርስ ፡ በክርስቶስ ፡ ፍች ፡ ተመ

ልክት ። ምድራዊ ፡ እንጥረኛ ፡ የሠራውን ፡ መስቀል ፡ ማብሀችና ፡ አታላዮች ፡ ከሰማይ ፡ ወርዷል ፡ እንደሚሉት ፡ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። (ተረት ፤ ስለ ፡ ቅርናታም ፡ ሴት) ፤ ወይዘሮ ፡ ስሙኝ ፡ ለማያውቁሽ ፡ ታጠኝ ። ቀድሞም ፡ በ፲፰ ፡ ዓመት ፡ የሽፍቶች ፡ እናት ፡ የፈላሾች ፡ እኅት ፡ ከምትኾን ፡ ከዚያች ፡ ከመንዝሬ ፡ ከጕዲት ፡ በፊት ፡ እንደነዚሁ ፡ ሚናስ ፡ እንድራዎስ ፡ የሚባሉ ፡ ፪ ፡ ሐሳውያን ፡ ያውጣኪ ፡ ወገኖች ፡ መጥተው ፡ ጳጳሳት ፡ ሳይኾኑ ፡ ጳጳሳት ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሐሰት ፡ በስሕተት ፡ በክለዋታል ፤ በሰውነቱ ፡ አምሳክ ፡ ፭ ፡ ባሕርይ ፡ ፩ ፡ ግብር ፡ ማለትና ፡ ልደትን ፡ በ፫፫ ፡ ማክበር ፡ በነሱ ፡ ጊዜ ፡ ተዠምሯል ። በመፈረሻውም ፡ ሐሰታቸው ፡ ታውቆ ፡ በስደት ፡ ስለ ፡ ተቀጡና ፡ ወዲያው ፡ ያ ፡ ጕደኛ ፡ የጕዲት ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ተዠመረ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ክልኛቿ ፡ ይልቅ ፡ ባዕድ ፡ የንጀሬ ፡ ልጅ ፡ የምቆደው ፡ እናታችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፸ ፡ ዘመን ፡ ያኽል ፡ ያለጳጳስ ፡ ያለኤጲስቆጶስ ፡ ኑራለች ፡ (ስንክ ፡ መጋቢ) ። ፈተኞቹንና ፡ ኋለኞቹን ፡ የሚያስተባብር ፡ ሥላሴ ፤ ዘዚዩ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኵሴ ፡ ዘሃደ ፡ ኸሎ ፡ አድያማተ ፡ ግብጽ ፡ ወጽርእ ፡ ወሶርያ ። ሄሮድስ ፡ ወጲላጦስ ፡ ተንሥኡ ፡ ቅድመ ፡ እንበለ ፡ ፍትሐ ፡ ላዕለ ፡ አቡሁ ፡ ቀባዒ ፡ ወላዕለ ፡ ወልዱ ፡ ቅቡዕ ። ከማሁመ ፡ ዓዲ ፡ ተንሥኡ ፡ በግፍዕ ፤ ዘእምግብጽ ፡ ሚናስ ፡ ሐሳዊ ፡ ወእንድራዎስ ፡ ጽሉእ ። ወበከመ ፡ ተዘሃላት ፤ እምአባግዐ ፤ ይትኃጥኡ ፡ እሉ ፡ እምይትኄጣእ ፡ ሰብእ ፤ እስመ ፡ ከኑ ፡ አርኣያ ፡ ለጸብእ ።

**ጠብጠበ** ፤—ፈጠነ ፤ ገረፈ ፤—ጠቢብ ፡ ጠበ ።

**ጠብያ** ፤ **ጠቢት** ፤—የሰው ፡ ስም ፤—ጠወበ ።

**ጠባይዕ** ፤—ባሕርይ ፤—ጠቢዕ ፡ ጠብዐ ።

**ጠቢል** ፤ **ሎት** ፡ (**ጠበለ** ፡ **ይጠብል** ፡ **ይጥብል** ። **ዕብ** ፡ **ጣባል**) ፤ መንከር ፡ መዝፈቅ ፤ ገላን ፡ በውሃ ፡ ማጠብ ፡ መታጠብ ፤ ማጥመቅ ፡ መጠመቅ ። ጠመቀን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ጠበል** ፤ (**ላት**) ፤ በቁሙ ፤ የጥምቀት ፡ ውሃ ፡ የተባረከ ፡ የተጸለየበት ፤ ወይም ፡ በታምራት ፡ የፈለቀ ፡ ክደዊ ፡ የሚያድን ፡ የሚፈውስ ፤ እንዲ ፡ ሚጣቅና ፡ እንዳንበ ፡ እንዳትጋሬኝ ፡ ውሃ ፡ ያለ ። ጠበለተኛ ፤ ጠበል ፡ ረጪ ፡ እንዲሉ ።

**ጠብለለ** ፤ (**ተቀ** ፡ **ማ**) ፤ ጠቀለለ ፤ ሸበለለ ፡ አሰረ ፡ ጠመጠመ ። ጠብለሉ ፡ ልብሰ ፡ ሐመር ። ወጠብለላ ፡ ለክርታስ ፡ ወጎተማ ። ጠብልሎ ፡ ውስተ ፡ ክሚድክ ፡ (አፈ ፡ ተ፴፱ ። ስንክ ፡ ሚያ፫ ። ምሳ፮ ፡ ፳፭) ። —፤ ሸፈነ ፡ አለበሰ ፡ አጕናጠፈ ፡ በልብሰ ፡ ሰፈፈ ። በፈማ ፡ ጠብሰልክዋ ። ወጠብለሰቶ ፡ በአጽርቅት ። ጠብልሎቶሙ ፡ ለሙታን ፡ በአልባስ ፡ ሐዲሳት ፡ (ኢዮ ፴፰ ፡ ፱ ። ሉቃ፪ ፡ ፯ ። ግንዘ) ። በወግአና ፡ በበኣ ፡ ፈንታ ፡ ጠብለለ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ይጠበልሉን ፡ ምክ ፡ ወአሜክላ ፡ (ሄርማ ፡ ገ፸፫) ።

**ተጠብለለ** ፤ ተጠቀለለ ፡ ተሸፈነ ፡ ተጠመጠመ ። በማያት ፡ ይጠበለሉ ። በአጽርቅት ፡ ተጠብለለ ። ከይሲ ፡ ተጠብለለ ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ፡ (ኪዳ ። ድጓ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፱) ።

**ጥብሉል** ፤ (**ላን** ፡ **ላት** ፡ **ልልት**) ፤ የተጠቀለለ ፡ ጥቅልል ፡ ሽፍን ። ሰበን ፡ ዘደበ ፡ ርእሱ ፡ እንተ ፡ ባሕቲቱ ፡ ጥብሉል ። ወገጹኒ ፡ ጥብሉል ፡ በሰበን ። ጥብሉል ፡ በአጽርቅት ። የማኑ ፡ እዴሁ ፡ ጥብልልት ፡ ይእቲ ፡ በኩናት ፡ (ዮሐ ፳ ፡ ፯ ። ፲፩ ፡ ፵፬ ። አፈ ፡ ድ፰፫ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ጥብላሌ** ፤ (ላ ፡ ጥ) መጠቅለል ፡ መሸብለል ፡ መሸፈን ፡ መጠምጠም ። ጥብላሌከ ፡ በአጽርቅት ፡ (አርጋ ፡ ፬) ። አጠቀላለል ፡ ጥቅለላ ፡ ሽፈና ። ስንባልን ፡ እይ ፡ የጠብለለ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ ጠና ፡ በ ፡ ተቀራራቢች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ወደዚያ ፡ ኼዷል ፡ ጠንበለለም ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ሰንበል ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ጠቢዕ** ፤ **ዖት** ፡ (**ጠብዐ** ፡ **ይጠብዕ** ፡ **ይጥባዕ** ፤ **ተብዐ** ። **ዕብ** ፡ **ጣባዕ** ፤ **ሰጠመ** ፡ **አሰጠመ**) ፤ በጠባይ ፡ መውደድ ፡ መፍቀድ ፤ ቈራጥ ፡ መኾን ፡ መጨከን ፡ መድፈር ፤ መቻኮል ። ተብዐን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ጠብዑ ፡ መላእክት ። በየዋህ ፡ ልብ ፡ ጠባዕኩ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ። ተቃተሉ ፡ ጠቢዖሙ ። ንጥባዕ ፡ ለመዊት ። ጥባዕኬ ፡ እንኋ ፡ ጳውሎስ ፡ (ጸዜና ፡ ፳፱ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ። ዮሴፍ ። ድጓ) ።

—፤ ባሕርይን ፡ መመሥረት ፡ ማቆም ፡ የባሕርይን ፡ ሕግ ፡ መፈጸም ፡ ባለባሕርይ ፡ መኾን ፡ የፈጣሪና ፡ የፍጡር ። እነሱን ፡ እይ ፡ (ገድ ፡ አዳ) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጠብዐ ፡ ፈንታ ፡ አጥብዐ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወአጥብዐ ፡ ዳንኤል ፡ በልቡ ፡ ከመ ፡ ኢይብላዕ ፡ እማእደ ፡ ንጉሥ ። መኑ ፡ እንከ ፡ ዘያጠብዕ ፡ ይፈጽም ፡ እደዊሁ ። ለእመ ፡ አጥባዕከ ፡ እምነፍስከ ። አጥብዐት ፡ ለተኵንኖ ። ወአጥብዑ ፡ ሕዝብ ፡ በቃለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ (ዳን፩ ፡ ፰ ። ፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፭ ። ሢራ፮ ፡ ፴፪ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፭ ። ፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፰) ።

**ጠባዒ** ፤ **ጥቡዕ** ፤ (**ዓን** ፡ **ዓት** ፡ **ብዕት**) ፤ የወደደ ፡ የጨከነ ፡ ጨካኝ ፡ ደፋር ፡ ቈራጥ ፡ ጥኑ ፡ ጠንካራ ፡ ጠባየ ፡ ብርቱ ። ጥቡዕ ፡ ልቡ ፡ ለተወክሎ ። ብእሲ ፡ ጥቡዕ ፡ ጥቀ ። እመ ፡ ጥቡዓን ፡ አንትሙ ። ንሕነ ፡ ጥቡዓን ፡ ወኢንብል ፡ አሆ ። ለእመ ፡ ከነት ፡ ጥብዕተ ፡ ለንስሓ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፩ ። ፩ዜና ፡ ፳ ፡ ፯ ። ዳን፫ ፡ ፲፰ ። መቃ ፡ ገ፱ ። ቀሌ) ።

**ጥብዐት** ፤ (**ታት**) ፤ መውደድ ፡ መጨከን ፡ አጨካከን ። ጭከና ፡ ጭካኔ ፡ ድፍረት ፤ ቍርጥ ፡ ሐሳብ ። ተመይጠ ፡ ፍርሀቱ ፡ መንገለ ፡ ጥብዐት ። ጥብዐተ ፡ ኅሲናሁ ። ኣጸንዐ ፡ ጥብዐቶሙ ፡ ለዕቀበ ፡ ሃይማኖት ።

ሕይቴኑ ፡ ጽንዕከ ፡ ወኀይልከ ፡ ወጥብዐታቲከ ፡ ለሞት ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፳ ። ጎዳ፳፫ ። ዮሴፍ) ።

**ጥብዕና ፤** ጭከና ፡ ድፍረት ። ጨካኝነት ፡ ቈራጥነት ፡ ደፋርነት ፡ (ቁር) ።

**አጥብዐ ፤** አሶደደ ፡ አስጨከነ ፡ አስደፈረ ፤ አጸና ፡ አበረታ ። አጥብዐ ፡ አልባቢሆሙ ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አጥብዖ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ስምዐ ። ቀድሳ ፡ ወአጥብዓ ። አጥብዖሙ ፡ ለመዋእያን ፡ ለማዕተ ። አጥብዖ ፡ ልቦሙ ፡ (፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፮ ። ስንክ ፡ መስ፮ ። ኪዳ ። አርጋ ፡ ፩ ። ቀሌ) ።

**ጠባይዕ ፤ (ዓት ። ዐረ ፡ ጠቢዕ ፤ ጠቢዐት ። ዕብ ፡ ጤባዕ) ፤** በቁሙ ፡ ጠባይ ፤ ባሕርይ ፤ የፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ጥንት ፡ ሥር ፡ መሠረት ፤ አኳኋን ፡ ኹነታ ። ጠባይዕ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ሳንድም ፡ ለብዙም ፡ ይኾናል ። ተሐደሰ ፡ ጠባይዐ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ፡ በትንሣኤሁ ፡ ለመድኀኒነ ። ፍትወት ፡ እንስሳዊት ፡ እምከመ ፡ ተሠልጠት ፡ ትሬሲ ፡ ጠባይዔሁ ፡ በብእሲ ፡ ከመ ፡ ጠባይዐ ፡ እንስሳ ። አርባዕቱ ፡ ጠባይዐ ፡ ፍጥረቱ ፡ ለአዳም ፡ ዘመሬት ፡ ወማይ ፡ ዘነፋስ ፡ ወእሳት ። እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ጠባይዓቲሁ ፡ ለአዳም ፡ (አቡሻ ፡ ፬ ። ፊላስ ፡ ገ፲፭ ። ሳታት ። አዋል) ።

**ጠባይዕ ፤** አካል ፤ መልክ ፡ ቁመት ፤ የባሕርይና ፡ የሥራ ፡ ባለቤት ፤ ገዥ ፡ አዛዥ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘይብል ፡ ክልኤቱ ፡ ጠባይዕ ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ። ዘረሰዮ ፡ ለክርስቶስ ፡ ክልኤተ ፡ ጠባይዓተ ። የአምኑ ፡ በአሐቲ ፡ ጠባይዕ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተሰብአ ። ይሬእዩ ፡ ጠባይዖ ፡ ዘስጢር ፡ እምነ ፡ ሾሉ ፤ አካሉን ፡ መልኩን ፡ (ያዕ ፡ ዘእል ። ስንክ ፡ መስ፮ ። ነሐ፳፫ ። አረጋ ፡ ድ፲፱) ። የጠባይዕ ፡ ፍች ፡ በዐረብም ፡ እንደ ፡ ህላዌ ፡ ነው ፤ ለባሕርይ ፡ በሚመችበት ፡ ባሕርይ ፤ ለአካል ፡ በሚመችበት ፡ አካል ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፤ ፍችው ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ይኸውም ፡ ሲታወቅ ፤ ማእዙ ፡ ህላዌ ፡ ህላውያት ፡ የሚለውን ፡ ኹሉ ፡ የዐረቡ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ጠቢዓ ፤ ጠቢዕቱን ፡ ይለዋል ። በአንቀጸ ፡ ተዋሕዶ ፡ ፍችው ፡ አካል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አሐዱ ፡ ህላዌ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ዋሕድ ፡ ጠቢዓ ፡ ይላል ። በአንቀጸ ፡ ተፀቅቦም ፡ ፍችው ፡ ባሕርይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ክልኤቱ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ጠቢዕቱን ፡ ይለዋል ፤ ፪ ፡ ባሕርያት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ህላዌን ፡ ተመልከት ። ይችን ፡ የሊቃውንት ፡ በዋጅ ፡ ያላዩ ፡ ያልሰሙ ፡ መምሬን ፡ ማን ፡ ያፌታውያንም ፡ እንዳልማን ፡ እንኳ ፡ ሳይቀሩ ፡ ያመጣኪን ፡ አሠር ፡ ተከትለው ፡ ጠባይዕን ፡ ሲተረጒሙ ፡ በቦታው ፡ ኹሉ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ አይሉትም ። በለዚህ ፡ ነገር ፡ ባህላቸውና ፡ ትርጓሜያቸው ፡ ታሪካቸውና ፡ ፍቻቸው ፡ ከቋንቋ ፡ ከመጽሐፍ ፡ አይገጥምም ። ከለመማጠውም ፡ የተንሣ ፡ ተለያይታለች ፡ ከኒሳ ፤ ይኸውም ፡ እስመ ፡ አበዊነ ፡ ሰመይዎን ፡ በዝንቱ ፡ ገጸ ፡ መካን ፡ (ለጠባይዓት) ፡ ለህላውያት ፡ አካላተ ፤ ባለው ፡ ይታወቃል ። ጠባይዕን ፡ በአካል ፡ በታና ፡ በአካል ፡ ፈንታ ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ መፍታት ፡ በመንፈስ ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ገባው ፡ እንደ ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ምስጢራትን ፡ ኹሉ ፡ ያፈርሳል ። መገርመሪያ ፡ እንደ ፡ ሰባልዮስ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ነች ፤ ያሰኛል ፡ የሚያሰኝም ፡ ሰው ፡ ኹንኝ ፡ ያሰኛል ፤ የሦስቱ ፡ አካል ፡ ባሕርይ ፡ ምንታዌ ፡ ተከፍሎ ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ ሥር ፡ አንድ ፡ ነቅ ፡ አንድ ፡ መለኮት ፡ ነውና ። ኹለተኛም ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ በተለየ ፡ ሰው ፡ የኾን ፡ ባሕርይ ፡ ንሥኡ ፡ ከንጢአት ፡ በቀር ፡ እንደኛ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ለኾነው ፡ ለዚህ ፡ ላንዱ ፡ አካል ፡ ላንዱ ፡ ልጅ ፡ በተፀቅቦ ፡ ፪ ፡ ባሕርያት ፡ ከሌሉት ፡ ባንዲት ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ ፪ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፤ ኢመዋቲና ፡ መዋቲ ፡ ግዙፍና ፡ ረቂቅ ፡ መኾን ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ፍጹም ፡ አምላክና ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ መባል ፡ አይቻልምና ፤ በግድ ፡ እንዳውጣኪ ፤ ሥጋ ፡ ወደ ፡ ቃል ፡ ባሕርይ ፡ ተለወጠ ፡ ተቀላቀለ ፡ ያሰኛል ። ተዋሕዶ ፤ ቃልና ፡ ሥጋን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ቢያሰኝ ፡ እንጂ ፤ ባሕርያትንና ፡ ግብራትን ፡ ቀላቅሎ ፡ ደባልቆ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ግብር ፡ አያሰኝም ፤ ተፀቅቦ ፡ ይከለክለዋል ። የአካልንና ፡ የባሕርይን ፡ የተዋሕድን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። (ግጥም) ፤ በዋቆች ፡ ካልሰጡት ፡ ማረሚያና ፡ ፀራሚ ፡ ንፍጥ ፡ ይለቀልቃል ፡ አላዋቂ ፡ ሳሚ ። ምስጢሩን ፡ ሳያውቁ ፡ መተርጐም ፡ መፍታት ፡ ደፍሮ ፡ ሳይበጡ ፡ ዐግሞ ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ማውጣት ።

**ጠባይዓዊ ፤** ባሕርያዊ ፤ የባሕርይ ። ኀፍረቱ ፡ ጠባይዓዊ ። ሕግ ፡ ጠባይዓዊ ። እሙንቱ ፡ ኢገብሩ ፡ አውስቦ ፡ ጠባይዓዌ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፪ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ተ፲ ። አቡሻ ፡ ፶) ።

**ጥብዕ ፤ (ዓት) ። አው ፡ ጥብዖት ፡ (ታት) ፤** የሥራ ፡ ትእዛዝ ፤ ቍርጥ ፡ ቃል ፡ ጌታ ፡ ለሎሌው ፡ የሚሰጠው ። ኢትትማከሩ ፡ ምስለ ፡ ዐሳብ ፡ እንበይነ ፡ ጥብዓት ፡ (ሢራ ፴፯ ፡ ፲፩) ።

—፤ ጡብ ፤ የጡብ ፡ ሥራ ፤ ወይም ፡ ቍጥሩና ፡ ልኩ ። አምጣነ ፡ ጥብዖቶሙ ፡ ዘይገብሩ ። አልቦ ፡ ዘየሐጽጽክሙ ፡ እምጥብዖትክሙ ። ለምንት ፡ ኢትፈጽሙ ፡ ጥብዖተክሙ ፡ ግንፋለ ፡ (ዘፀ፭ ፡ ፰ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱) ።

**ጠቢቅ ፤ ቆት ፤ (ጠበቀ ፡ ይጠብቅ ፡ ይጥብቅ) ፤** ዐጐልና ፡ ገቢር ። መጥበቅ ፡ መታሰር ። መጠበቅ ፤ ጠባቂ ፡ መኾን ፡ ጥብቅና ፡ መሾም ፡ (ዐማርኛ) ። መጠበቅ ፤ ጥብቅ ፡ ልጥፍ ፡ ማለት ፤ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ መያያዝ ፤ በችንካር ፡ በመጣበቅ ፡ በማስሪያ ። ማጥበቅ ፤ ማጣበቅ ፡ ማስጠንቀቅ ፤ አጥብቆ ፡ አጣብቆ ፡ መያዝ ። ወይጠብቆ ፡ ውስተ ፡ ሐቌሁ ። ይጠብቆ ፡ ሕማማም ፡ ከመ ፡ ማይ ። እመ ፡ ጠበቆ ፡ ዥያንው ። ጠበቆ ፡ ሦክ ፡ ወኀነቀ ፡ (ኢዮ፲፰ ፡ ፳፯ ። ፳፯ ፡ ፳ ። ማሕ ፡ ፲፯ ። ማቴ፲፫ ፡ ፯) ።

—፤ መነበብ ፡ ማጠር ፡ ምስጢሩ ፡ ከጠባቂነት ፡ ይገባል ። ወአማዚሃ ፡ ተላጸቀት ፡ በበይናቲሃ ፡ ወጠበቀት ፡ ለሥጋ ፡ አዳም ፡ እምድኅረ ፡ ወረደ ፡ (አቡሻ ፡ ፵፯) ። በጠበቀ ፡ ፈንታ ፡ ጠበቀ ፡ ይላል ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**አጥበቀ ፤** አጠበቀ ፡ አስጠበቀ ። አጣበቀ ፡ ጣፈ ፡ ለጠፈ ፡ ቸንከረ ፡ አጣመረ ። ኢጥበቃ ፡ ለምትርት ፡ የማኑ ። ኢጥበቃ ፡ በምድር ። ውስተ ፡ አረፍት ፡ አጥበቆ ፡ ወጸንዖ ፡ በኀጺን ፡ (ስንክ ፡ ጥቅምት ፳፱ ። ሰኔ ፳ ፡ ፳ ። ጥቅ ፲፫ ፡ ፲፮) ።

**አጥበቂ ፤ መጥብቅ ፤** በቁሙ ፤ የሚያጠብቅ ፤ የሚያጣብቅ ፡ አጣባቂ ።

**መጥበቅ ፡ ት ፤ (ብ ፡ መጣብቅ ፡ ት) ፤** ማጥበቂያ ፤ ማጣበቂያ ፡ መጣብቅ ፤ ሙጫ ፡ ችንካር ። መጥበቅተ ፡ አዕማዲሆን ፡ (ዘፀዓ ፳ ፡ ፲፰ ። ኢሳ ፵፩ ፡ ፯) ።

**ተጣበቀ ፤** በቁሙ ፤ ተጠባበቀ ፤ ተያያዘ ፡ ተጣመረ ። አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፡ ተጣበቁ ፡ ይጣበቁ ፡ ወኢይትፋትሑ ። ኲናት ፡ ተጣበቀት ፡ ምስለ ፡ እራኁ ፡ (ኢዮ ፵፩ ፡ ፯ ፡ ፰ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ጥቡቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ብቅት) ፤** የጠበቀ ፤ የተጣበቀ ፤ የገጠመ ፡ የተያያዘ ፤ ልክክ ፡ ያለ ። ሥጋ ፡ ነፍስቱ ፡ ጥቡቅ ። እንዘ ፡ ጥቡቃን ፡ በከማይሙ ። ጊዜ ፡ ልደቱ ፡ ለሰብእ ፡ እደዊሁ ፡ ጥቡቃት ፡ ወዐራቁ ፡ ይትወለድ ። ከናፍሪሁ ፡ ለዘይትሜጦ ፡ ቍርባነ ፡ ይኩና ፡ ጥቡቃተ ፡ በፍርሀት ፡ ከመ ፡ ኢይደቅ ፡ እምኔሁ ፡ ምንትኒ ፡ (ኢዮ ፵፩ ፡ ፲፬ ። ራእ ፡ ማር ። ማንዘ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፯) ።

**አስተጣበቀ ፤** አጣበቀ ፡ አያያዘ ፡ አጋጠመ ፤ አገጣጠመ ። ከመ ፡ ዘያስተጣብቅ ፡ አግልዐተ ። አስተጣበቅዋ ፡ ከመ ፡ እብነ ፡ ኵዙሕ ። ግብር ፡ ዘያስተጣብቅዎ ፡ (ሚራ ፳፱ ፡ ፯ ። ኢዮ ፴፰ ፡ ፴፰ ። ኢር ፲ ፡ ፲፩) ።

**ጠቢስ ፤ ሶት ፤ (ጠበሰ ፤ አው ፡ ጠብሰ ፡ ይጠብስ ፡ ይጥብስ) ፤** መጥበስ ፡ በእሳት ፡ ማብሰል ፤ ከእሳት ፡ ላይ ፡ መጣል ፡ የሥጋ ፡ የሽት ። ይጠብሱ ፡ ሥጋ ፡ ወይበልዑ ፡ ጠቢሶሙ ፡ ጥብሶ ። ዓሣሁኒ ፡ ጠበሱ ፡ ወበልዑ ። ጠበሰቶ ፡ በእሳት ። ይጠብሱ ፡ ፍሥሐ ፡ በእሳት ። ይጥብስዎ ፡ በእሳት ፤ ወአልቦ ፡ በቢረ ፡ ዐፅም ፡ እምውስቴቱ ፡ ምንትኒ ፡ (ኢሳ ፵፬ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ። ጦቢ ፮ ፡ ፮ ። ዮሴፍ ። ፪ዜና ፡ ፴፭ ፡ ፲፫ ። ኩፋ ፡ ፵፱) ።


**ተጠብሰ ፤** ተጠበሰ ፤ ለእሳት ፡ ተሰጠ ፡ ተረመጠ ፡ እስኪበስል ።

**ጥቡስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ብስት) ፤** የተጠበሰ ፡ ጥብስ ፤ አሰውሃ ፡ በእሳት ፡ ብቻ ፡ የበሰለ ። መክፈልተ ፡ ዓሣ ፡ ጥቡስ ። ይብልዑ ፡ ጥቡሰ ፡ ወብሱለ ፡ በእሳት ፡ (ሉቃ ፳፬ ፡ ፵፪ ። ኩፋ ፡ ፵፱) ። ጠባሳ ፤ ጥብሳት ፡ ሰቅሬት ፤ ተተኰሶና ፡ እሳት ፡ በልዶት ፡ የሻረ ፡ ገላ ።

**ጥብሰት ፤** መጥበስ ፤ መጠበስ ፡ ጥብስነት ፤ አጠባበስ ፡ ጠበሳ ።

**ጥብሶ ፤** ጥብስ ፡ ጥብሱን ። ይብልዑ ፡ ሥጋሁ ፡ ጥብሶ ፡ በእሳት ፡ (ዘፀ ፲፪ ፡ ፰ ፡ ፱) ።

**መጥበስ ፡ ት ፤** መጥበሻ ፤ መጠበሻ ፡ የብረት ፡ ሠቅሠቅ ፡ ምጣድ ፡ ብረት ። መጥበስ ፡ ለአፍላም ፡ ወዐፀው ፡ ለእሳት ። ወትገብር ፡ መጥበስቶ ፡ ሠቅሠቅ ፡ ዘብርት ፡ ከመ ፡ መሥገርት ፡ ዓሣ ። ወአግብር ፡ ላቲ ፡ ለመጥበስት ፡ አርባዕተ ፡ ሕልቀታተ ፡ (ምሳ ፳፯ ፡ ፳፩ ። ዘፀ ፳፯ ፡ ፬ ፡ ፭) ።



መጥበስ ፡

**ጣቢታ ፤—ጠለየ ፤—ጣሊታ ።**

**ጣቢታ ፤—ጠወበ ፤—ጦቢት ።**

**ጤገን ፤—ምጣድ ፤—ጠየገን ።**

**ጠጊዕ ፤ ዖት ፤ (ጠግዐ ፡ ይጠግዕ ፡ ይጥጋዕ ። ፀግዐ ፤ ጠቅዐ) ፤** መጠጋት ፡ መደገፍ ፤ ጥግ ፡ ደገፈ ፡ መያዝ ፤ ልጥቅ ፡ ልጥፍ ፡ ማለት ፤ መጣበቅ ፡ አንድ ፡ መኾን ። ወጠግዐት ፡ በምድር ፡ ከርሥነ ። ይጥጋዕ ፡ ልሳንየ ፡ በጕርዔየ ። በከመ ፡ ይጠግዕ ፡ ዝ ፡ ሞራእ ፡ ውስተ ፡ ሐቌ ፡ ብእሲ ። እስከ ፡ ይጠግዕ ፡ ማእሰ ፡ ሥጋሁ ፡ ዲበ ፡ ዐፀሙ ፡ (መዝ ፻፲፰ ። ፻፴፮ ። ኤር ፲፫ ፡ ፲፩ ። ገድ ፡ ተክ) ።

—፤ መቆም ፡ መገታት ፤ መጽናት ፡ መርጋት ፡ ርጉዕ ፡ መኾን ፤ መጥበቅ ፡ መድረቅ ፤ የፈሳሽ ። ወጠግዐ ፡ ከመ ፡ አረፍት ፡ ማይ ። በረድ ፡ ወአስሐትያ ፡ ዘጠግዐ ። ከመ ፡ አስሐትያኑ ፡ ጠጋዕከ ። ወትጠግዕ ፡ እዴሁ ፡ በእደ ፡ ካልኡ ፡ (ዘፀ ፲፭ ፡ ፰ ። ኢዮ ፮ ፡ ፲፮ ። ፲፭ ፡ ፯ ። ዘካ ፲፬ ፡ ፲፫) ።

**ጠጋዒ ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት) ፤** የተጠጋ ፤ የሚጠጋ ፤ ተጠጊ ፡ ጥግ ፡ ፈላጊ ፡ ጥገኛ ።

**ጥጉዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ግዕት) ፤** የተጠጋ ፡ ጥግ ፡ የያዘ ፤ የተለበጠ ፡ ልብጥ ። ዐፀወ ፡ ለውሒ ፡ ጥጉዓን ፡ በአረፍት ፡ (ክብ ፡ ነገ ፶፯) ።

**አጥግዐ ፤** አስጠጋ ፡ አስደገፈ ፡ አጣበቀ ፡ አጸና ። ያጥግዕ ፡ ላዕሌከ ፡ ወላዕለ ፡ ዘርዕከ ፤ በከመ ፡ መዋዕለ ፡ ሰማይ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ (ኩፋ ፡ ፲፱) ።

**ተጣግዐ ፤** ተጠጋ ፡ ተጠጋጋ ፡ ተነባበረ ።

**ተጣጋዒ ፤ ጥጉዕ ፤** የተጠጋ ፡ የተጠጋጋ ፡ ስግ ስግ ፡ ንብብር ።

**አስተጣግዐ ፤** አጣጋ ፡ አጠጋጋ ፤ ሰገሰገ ፡ ጽፍቅ ፡ አደረገ ፤ አያያዘ ፡ አጣበቀ ። አስተጣግዖሙ ፡ ለዓማት ፡ ፈለግከ ፡ በቅማርከ ። ማህው ፡ ለእመ ፡ ተሰብረ ፡ አልቦ ፡ ዘያስተጣግዖ ፤ ዘእንበለ ፡ ገባሪሁ ። ከመ ፡ እብነ ፡ ጳዝዮን ፡ ዘአስተጣግዕዎ ፡ በወርቅ ፡ ጽሩይ ። አስተጣግዑ ፡ አባላቲሆሙ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ በግዕ ። ያስተጣግዕ ፡ በሾላ ፡ (ሕዝ ፳፱ ፡ ፬ ። ያዕ ፡ ዘእል ። መጽ ፡ ምስ ። አቡሻ ፡ ፶ ። ኢሳ ፵፩ ፡ ፯) ።

**ምጥጋዕ ፤ (ዓት) ፤** መጠጊያ ፡ ማስጠጊያ ፡ ቦታ ። መፈልፈያ ፡ መክዳ ፡ ድጋፍ ። ዕጋዕን ፡ ምዕጋዕን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ጠገራ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፤ ብረት ።

**ጥድ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፤ ጽሕድ ። ጽሕደን ፡ እይ ።

**ጥሂር ፤ ሮት ፤ (ጠሀረ ፡ ይጥህር ፡ ይጥሀር ። ዐረ ፡ ጠሁረ ። ዕብ ፡ ጣሄር)** ፤ መንጻት ፤ መጥራት ፤ ከርስሐቱና ፡ ከንጢአት ፡ ንጹሕ ፡ ጥሩ ፡ መኾን ፡ በውሃ ፡ በንስሓ ፡ (ሕዝ፴፮ ፡ ፳፭) ።

**ጥህረት** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ (ዮሐ፫ ፡ ፳፭) ።

**ጣህር ፤ ጥህር** ፤ ንጽሕ ፡ ጽርየት ፤ ቅድስና ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**አጥሀረ** ፤ አነጻ ፡ አጠራ ፡ ዐጠበ ፡ አጠመቀ ። በዘያጥህሩ ፡ አይሁድ ፡፡ በእንተ ፡ አጥህሮ ፡ (ዮሐ፪ ፡ ፮ ። ፫ ፡ ፳፭ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**አጥሃሪ ፤ መጥህር** ፤ የሚያነጻ ፡ የሚያጠራ ፤ ዐጣቢ ፡ አጥማቂ ፤ ወይም ፡ ውሃ ።

**ተጣህረ** ፤ ተነጻ ፡ ተጣራ ፤ ተጣጠበ ፡ ተጠማመቀ ። ኢትትኄፀቡ ፡ ሾሎ ፡ ጊዜ ፡ ወኢትግበሩ ፡ ዘከመ ፡ ያለምዱ ፡ ተጣህሮ ፡ (ዲድ ፡ ፴፫) ።

**ጥሁር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ህርት)** ፤ የነጻ ፡ የተነጻ ፤ የጠራ ፡ የተጣራ ፤ ንጹሕ ፡ ጥሩ ። እነዝሀክሙ ፡ በማይ ፡ ጥሁር ፡ ወትጥህሩ ፡ (ሕዝ፴፮ ፡ ፳፭) ።

**ጥህረ ፤ —ሞኽ ፤ —ጥሒር ፡ ጥሕረ ።**

**ጦበ ፤ ጠወበ ፤ (ጠዊብ ። ዕብ ፡ ጦብ ፤ ሠነየ)** ፤ ጡብ ፡ ሠራ ፤ መሠረተ ፡ አስጌጠ ፡ አሳመረ ፤ ሥራውን ። ጡብ ፡ ጡት ፡ ጠይት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ጦብያ ፤ ጦቢት ፤ (ዕብራ)** ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ሠናይ ፡ ልሑይ ፤ ጻድቅ ፡ ኄር ። መጽሐፈ ፡ ጦብያ ፡ ወልደ ፡ ጦቢት ፡ (ጦቢ፩ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳) ።

**ጣቢታ ፤ (ሱር ፡ ጣብያእ ። ጽር ፡ ታቢታ ፤ ዶርካስ)** ፤ ፈቶ ፡ ወይጠል ፡ እግረ ፡ ቀላል ፡ ቀንዳም ፡ ዘላይ ፡ ሯጭ ፡ ጡብ ፡ መልክ ፡ መልካም ። ሲበዛ ፡ ጣብያት ፡ ያሰኛል ፤ ድርቃስና ፡ ወይጠል ፡ ጣቢታ ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ፩ ፡ ስም ፡ ናቸው ፡ (ግብ፱ ፡ ፴፮ ፡ ፵) ። እንጀራንም ፡ ስላይናማነቱ ፡ ጣቢታ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ምስጢሩ ፡ ከጡብ ፡ ይስማማል ።

**ጡብ ፤ ጦቢ ፤ (ቅብጥ ፡ ቶባ ፡ ቶቢ ። ዕብ ፡ ጤቤት)** ፤ ወር ፡ የወር ፡ ስም ፤ ጥር ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ።

**ጡጥ ፤ (ዐረ)** ፤ ጥጥ ፤ የጥጥ ፡ ፈትል ። ጡጥ ፡ ርስሕት ፡ አው ፡ ሠናይት ፡ (ፈልክ ፡ ፳፱፴፮) ። ጠጣ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ጥጥማ ፡ ጠጕረ ፡ ጥጥ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ጠጕሯ ፡ ከርዝመቱና ፡ ከጥቅጥቅነቱ ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ጥጥ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፡ ጥጥንና ፡ ሐሰትዮን ፡ እይ ።

**ጠውይ ፤ ዮት ፤ (ጠወየ ፡ ይጠዊ ፡ ይጥወይ ። ዐረ ፡ ጠወየ ። ዕብ ፡ ጣዋህ)** ፤ ገዚርና ፡ ዐጕል ። ማክረር ፡ መፍተል ፤ ማጥመም ፡ መቈልመም ፡ ማጠፍ ፡ ማጕበጥ ፡ መጠቅለል ፡ መጠምጠም ። ይጠውይዋ ፡ ለጽድቅ ፡ በዐመፃሆሙ ፡፡ እጠዊ ፡ ኀሊናሆሙ ፡ (ኢሳ፷፬ ፡ ፳፩ ። መቃ ፡ ገ፷፪) ።

**—** ፤ መጥመም ፡ መጣመም ፤ መክፋት ፡ ጠማማ ፡ መኾን ። ትጠዊ ፡ እምአቅርንቲሁ ፡ ለሀያል ፡፡ ወምስለ ፡ ጠዋይ ፡ ትጠዊ ፡፡ እፈኑ ፡ ሎቱ ፡ ጠዋይነ ፡ ወይጠውይዎ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። መዝ ፡ ፲፯ ። ኢር፴፭ ፡ ፲፪) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጠወየ ፡ ፈንታ ፡ አጥወየ ፡ ቀጠወየ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ዘእግዚአብሔር ፡ አጥወየ ፡፡ ዘያጠዊ ፡ ፍኖቶ ፡፡ ዐውሎሁ ፡ ለነፋስ ፡ ዐረባዊ ፡ ያጠውያ ፡ ለመንፈስ ፡፡ እስከ ፡ ይጠወይ ፡ ሥጋሁ ፡ (መክ፯ ፡ ፲፱ ። ምሳ፲፱ ፡ ፪ ። ሚል፡ማ፫ ፡ ፲፮ ። ስንክ ፡ መጋ፲፮) ።

**ጠዋይ ፤ (ያን ፡ ያት)** ፤ ጠማማ ፡ ወልጋዳ ፡ ክፉ ፡ መጥፎ ። ቀስት ፡ ጠዋይ ፡፡ ዕፀ ፡ ጽኑዕ ፡ ወጠዋይ ፡፡ ጠዋያነ ፡ ሃይማኖት ፡፡ ፍናው ፡ ጠዋያት ፡፡ አእባን ፡ ጠዋያት ፡ (ሆሴ፯ ፡ ፲፮ ። ጥበ፲፫ ፡ ፲፫ ። ሲኖዶ ። ምሳ፳፫ ፡ ፲፫ ። ሔኖ፶፱ ፡ ፭) ።

**ጥውየት** ፤ መጥመም ፡ መጣመም ፤ ጥመት ፡ ክፋት ፤ ጠማምነት ። የውጣ(፲) ፡ ዘእንበለ ፡ ጥውየት ፡፡ በከመ ፡ ጥውየተ ፡ ልበሙ ፡ ይሜህሩ ፡ ቢጾሙ ፡፡ ምንተ ፡ ርኢኪ ፡ በላዕሌየ ፡ ጥውየተ ፡፡ ራትዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ጥውየት ፡፡ ኢክህለ ፡ ጥውየቱ ፡ ከመ ፡ ይማእ ፡ ርትዐተ ፡ ልቡ ፡፡ ስምዐ ፡ ክፉ ፡ ሎቱ ፤ አኮ ፡ በጥውየት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። መቃ ፡ ገ፳ ። ኩፋ ፡ ፴፫ ። ቅዳ ፡ ኤጲ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲ ፡ ፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፰ ፡ ፫) ።

**ጥዋይ** ፤ ብስና ፤ ክፉ ፡ ግማት ፡ እንደ ፡ ፈስ ፡ የሚሸት ፡ (ሚል፴፱ ፡ ፳) ።

**ጥውዮ** ፤ ጥምዝ ፡ ሥራ ፤ ጥልፍ ፡ ቍልፍ ፤ ቀለበት ። ክልኤቱ ፡ ጥበበ ፡ ጥውዮ ፡ (ዘፀ፴፮ ፡ ፳፫) ። በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፳፭) ፡ ነው ።

**አጥወየ ፤ (አስደራጊ)** ፤ አስከረረ ፡ አስጠመዘዘ ፤ አስጠመመ ፤ አስቀሰሰ ፡ አስጕነበሰ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ አድራጊነት ፡ ነው ።

**አጥዋዪ ፤ መጥወዪ** ፤ የሚያስጠምም ፡ የሚያስቈለምም ፤ ጠምዛዥ ፡ ቈልማሚ ። መጥወዪ ፡ ከጠወየና ፡ ከአጥወየ ፡ ከኹለቱ ፡ ዐምዶች ፡ ስለ ፡ ወጣ ፡ በ፪ ፡ ስልት ፡ ይፈታል ። መጥወዩ ፡ ክሣድ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፭) ።

**መጥወይ ፤ (ያት ፤ መጣውይ)** ፤ ማጥመሚያ ፡ መቈልመሚያ ፤ መጠምዘዣ ፡ ማስጠምዘዣ ። ኵነኔዎ ፡ በመጥወይ ፡ ወበመጥባሕት ፡፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ሀሎ ፡ በመጥወይ ፡ ቍሱል ፡ (ስንክ ፡ ግን፫ ። ሐም ፳፭) ። በመጥወይ ፡ ፈንታ ፡ መጥመይ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ግብር ፡ መጥመዩ ፡ ወመቃሥርት ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፭) ።

**ጦልሎ ፤ ሎት ፤ (ጦለለ ፡ ይጦልል ፡ ይጦልል ። ዕብ ፡ ጣሌል)** ፤ መክደን ፡ ማልበስ ፡ መሸፈን ፡ የብጥ ፡ የጣራ ። ዳስ ፡ መጣል ፡ በስተላይ ፡ መጋ

ረድ ፤ ጥላ ፡ አጉበር ፡ ማድረግ ። ጸለለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**አንጦለለ** ፤ ነጠለ ፡ ተረተረ ። ተንጠለ ፤ ተተረተረ ። ሲታጠፉ ፡ ሲተጠቀለሉ ፡ ይነገራል ፤ ቤትን ፡ ግራህትን ፡ ስራ ፡ በታች ፡ ኹሉ ፡ ጠላላ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ከመ ፡ ኢይንጦልል ፡ ልብስ ፡ ሎግዮን ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፴፪) ።

**ጦልዐ ፤ (ተቀ ፡ ግ ፤ ጦለለ ። ዕብ ፡ ጣላእ)** ፤ ዐ ፡ የ፪ኛው ፡ ለ ፡ ተውላጥ ፡ ነው ። ጣፊ ፡ ስገበ ፤ ብፉ ፡ ጡቀመ ፤ ቀዳዳን ፡ ነገር ፡ በሚመስለው ፡ ቍራጭ ። ለልብስና ፡ ለማእስ ፡ ለሚቀደድ ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ፤ ፪ኛም ፡ ለጌጥ ፡ ለሽልማት ፡ ለስደቃ ፡ ልብስ ፡ ዝንጕርጕር ፡ ኹኖ ፡ የሚሠራ ፡ ጥልፍን ፡ መረሻትን ፡ ግብረ ፡ መርፌን ፡ ኹሉ ፡ ይሳያል ።

**አንጦልዐ** ፤ ዘረጋ ፡ ጋረደ ፤ ሸፈነ ። ተዘረጋ ፡ ተጋረደ ፤ ተሸፈነ ። አርሕቢ ፡ መታክለኪ ፡ ወአንጦልዒ ፡ ደባትረኪ ። አንጦልዐ ፡ ውስተ ፡ ገጽየ ፡ ጽልመተ ። አንጦልዐ ፡ ደመና ፡ ወሰወሮሙ ። ሶበ ፡ ርእዮ ፡ አቡሁ ፡ አንጦልዐ ፡ ገጾ ፡ እምኔሁ ፡ ወይቤሎ ፡ ረሐቅ ፡ እምኔየ ፡ (ስንክ ፡ መጋቢ፪ ። ኢዮ፲፱ ፡ ፰ ። መዝ፻፬ ። ዮሴፍ) ። አንጐድጐደ ፡ አንበልበለ ፡ አንሶሰወ ፡ ብሎ ፡ በአ ፡ ልማድነት ፡ የሚገስስ ፡ ኹሉ ፡ በማድረግና ፡ በመደረግ ፡ በ፪ ፡ ጾታ ፡ ቢፈታ ፡ እንኳ ፤ ተንጐድጐደ ፡ ተንበለበለ ፡ ተንሶሰወ ፡ እንዳይል ፤ ተንጦልዐ ፡ አይልም ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በደራሲና ፡ በጸሓፊ ፡ ስሕተት ፡ ተንጦልዐ ፡ ይላል ፤ አያስኽም ። ሶበ ፡ ተንጦልዐ ፡ ሥጋሁ ፡ ለኢየሱስ ። በመብረቀ ፡ ስብሐት ፡ ተገልበበ ፡ ወበደመና ፡ እሳት ፡ ተንጦልዐ ። በከመ ፡ ተንጦልዐ ፡ ሥጋከ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ። ተንጦልዐ ፡ ንጢአትየ ፡ ማእከሌየ ፡ ወማእከለ ፡ እግዚ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ቅዳ ፡ ያዕ ። አርጋ ፡ ፭) ።

**እንጡሉዕ** ፤ የተሸፈነ ፡ የተጋረደ ፤ ሽፍን ። እንጡሉዓን ፡ በመብረቀ ፡ ስብሐት ፡ ወግልቡባን ፡ በነደ ፡ እሳት ። እንጡሉዕ ፡ በደመና ፡ እሳት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**እንጡላዌ** ፤ (ላ ፡ ጥ) መዘርጋት ፡ መጋረድ ፤ አዘረጋግ ፡ አገራረድ ፡ ግርዶሽ ። ክዱናን ፡ በስዋሬ ፡ ወኅቡኣን ፡ በእንጡላዌ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**መንጦላዕት ፤ (ብ ፡ መንጠዋልዕ ፡ ት ፡ ዓት)** ፤ መጋረጃ ፡ ግርዶሽ ፡ ጥላ ፡ ከለላ ፤ ልብስ ፡ ክዳን ፤ ልባጥ ፡ ሽፋን ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፴፩—፴፯) ። ውሳጤ ፡ መንጦላዕት ። ትከድኖሙ ፡ በመንጦላዕትከ ። መንጠዋልዕ ፡ ዘወርቅ ፡ (ዕብ፮ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፴ ። ቄጎ ፡ ፮ ፡ ፴፬) ።

—፤ ጕርጆ ፤ መክዘን ፡ የዕቃና ፡ የልብስ ፡ የገንዘብ ፡ ቤት ፡ ጕተራ ። ዲበ ፡ መንጠዋልዕ ፡ ወዲበ ፡ ንጽሐ ፡ ቅድሳት ። ቤተ ፡ መንጠዋልዕ ፡ (፩ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፳፰ ። ፪ዜና ፡ ፴፩ ፡ ፲፩) ።

**ጦሊት ፤ (ዕብ ፡ ጣሊት)** ፤ በቍመ ፡ መጠብር ፡ ነጠላ ፡ ያንገት ፡ ልብስ ። ንበርባሬ ፡ ባለጥቍር ፡ ጥለት ፤ አይሁድ ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ የሚለብሱት ።

**ጠዊም ፤ ሞት ፤ (ጠመ ፡ ይጠውም ፡ ይጡም)** ፤ ማጠፍ ፡ መጠቅለል ፡ መሸብለል ፡ ማዞር ፡ መጠምጠም ፤ የመጣፍ ፡ የምንጣፍ ፡ የልብስ ፡ የገመድ ፤ ጡብለሉን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ነሥአ ፡ ሐሜሊተ ፡ ወጠማ ። ወከመ ፡ ሞጣሕት ፡ ትጠውሞሙ ፡ (፬ነገ ፡ ፪ ፡ ፰ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፲፪) ። ወጠማ ፡ ባለው ፡ ወጠመ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**ጠዋሚ ፤ መጥውም** ፤ የሚያጥፍ ፡ ጠቅላይ ፡ ጠምጣሚ ።

**ተጠውመ** ፤ ታጠፈ ፡ ተጣጠፈ ፤ ዕጥፍጥፍ ፡ አለ ፡ ተጠቀለለ ። ትጠወም ፡ ሰማይ ፡ ከመ ፡ መጽሐፍ ። ወሰማይኒ ፡ ተጠውመት ፡ ከመ ፡ ክርታስ ፡ (ኢሳ፴፬ ፡ ፬ ። ራእ፮ ፡ ፲፬ ። ሔኖ፺ ፡ ፳፰) ።

**ጥዉም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ውምት)** ፤ የታጠፈ ፤ የተጠቀለለ ፡ ጥቅልል ።

**ጥዋሜ ፤ ጡመት** ፤ ማጠፍ ፡ መታጠፍ ፤ አስተጣጠፍ ፤ ዐጠፌታ ፡ ዕጥፍነት ።

**ጦማር ፤ (ራት ። ጽር ፡ ቶማሪዎን ። ዐረ ፡ ጡማር)** ፤ መጽሐፍ ፤ ደብዳቤ ፡ ክታብ ፤ የመልእክትና ፡ የትእዛዝ ፡ የሰላምታ ፡ ቃል ፡ ያለበት ፤ ካገር ፡ ወዳገር ፡ በፖስታ ፡ የሚላክ ፤ ወይም ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ የሚሰደድ ። ንሣእ ፡ ለከ ፡ ጦማረ ፡ ክርታስ ። ወአበጽሐ ፡ እምኀቤሁ ፡ ጦማረ ፡ መልእክት ። ተነበተ ፡ ጦማረ ፡ ሚመቱ ። ጦማረ ፡ ልዮን ። መጻሕፍተ ፡ ወጦማራተ ፡ እለ ፡ ነበሩ ፡ ምስሌሁ ፡ (ኢሳ፰ ፡ ፩ ። ፌ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ መስ፲፰ና ፡ ፯። ጥቅ፳፱) ። ባለቅኔዎቹ ፡ ግን ፡ ጦመረ ፡ ጣፈ ፡ ብለው ፡ ይገሱና ፤ ጦማርን ፡ ከዚህ ፡ ያወጣሉ ።

**ጠዊዕ ፤ ዖት ፤ (ጦዐ ፡ ይጠውዕ ፡ ይጡዕ ። ጠወየ)** ፤ መሠሠት ፡ መማማት ፤ መንፈግ ፡ መቈጠብ ፤ መቤስ ፡ መቀቀት ፤ ይኸን ፡ ብስጥ ፡ ምን ፡ አውጥ ፡ ማለት ። ሀለወ ፡ ዘይብዕል ፡ በብዝኀ ፡ ጠዊዐ ። ዘለነፍሱ ፡ ይጠውዕ ፡ ለመኑ ፡ ሀለዎ ፡ ይጸጉ ። አልቦ ፡ ዘየአክዮ ፡ ለዘይጠውዕ ፡ እምነፍሱ ። ዐይኑ ፡ ለሐማሚ ፡ ይጠውዕ ፡ እክለ ፡ (ሢራ፲፩ ፡ ፲፰ ። ፲፬ ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ፲ ። ፪ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፯) ። ደንጸወን ፡ እይ ።

**ጠዋዒ ፤ (ዒት ፡ ዐያን ፡ ያት)** ፤ የሚሣሣ ፤ ሥሡ ፡ ሥሥታም ፤ ቈቋይ ፡ ንፉግ ፡ ቢስ ፤ ጨባጭ ፡ ቈጣቢ ። ለብእሲ ፡ ጠዋዒ ፡ ኢይደልዎ ፡ ንዋይ ። እኩይ ፡ ዐይኑ ፡ ጠዋዒ ፡ (ሢራ፲፬ ፡ ፫ ፡ ፰) ።

**ጠዊቅ ፤ ቆት ፤ (ጦቀ ፤ ጠወቀ ፡ ይጠውቅ ፤ ይጡቅ)** ፤ ማስጨነቅ ፡ ማስጠበብ ፤ አጥብቆ ፡ ማሳዘን ፡ መሣቀይ ፤ መቅጣት ፡ መከራ ፡ ማምጣት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጦቀና ፡ በጠወቀ ፡ ፈንታ ፡ አጦቀ ፡ አጠወቀ ፡ ጠውቀየ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። አጠውቃ ፡ ለነፍስየ ፡ ወአገርሮ ፡ ለሥጋየ ። ወርእዮ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ ጥቀ ፡ ይጠውቅዎ ። ግርማከ ፡ ኢያጠውቀኒ ። ዘአ

ጦቀ ፡ ጋኔን ። እመቅሠፍት ፡ እንተ ፡ ታጠውቅ ። ለነ ፡ ያጠውቁነ ፤ (ሲቶሮ ፡ ፱ ፡ ፳፯ ። ዳንኤ፫ ፡ ፴ ። ኢዮ፲፫ ፡ ፳፭ ። ኪዳ ። አርጋ ፡ ፩ ። ቀሌ) ። የጦቀ ፡ ፍች ፡ ዐማርኛው ፡ አስ ፡ ስላለበት ፤ ምስጢሩ ፡ ማድረግ ፡ ማስደረግ ፡ ነውና ፤ ፎኛ ፡ አጥወቀ ፡ አያሰኝም ።

**ተጠው(ወ)ቀ** ፤ ተጨነቀ ፡ ተጠበበ ፡ በቦታ ፤ በሐሳብ ፡ በመከራ ። ተጠውቀኒ ፡ በጸቂን ። ትጠወቅ ፡ ነፍስየ ። ኢይጠወቅ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ። ወተጠወቀ ፡ በሕቁ ፡ እስከ ፡ ይደዊ ። ተጠውቀ ፡ ወተዐጽበ ፡ (ዘኁ፳፪ ፡ ፳፮ ። ኢዮ፲ ፡ ፩ ። ሚራ፲፯ ፡ ፳፰ ። ፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፪ ። ፊልክ ፡ ፳፫) ።

**ጥዉቅ** ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ውቅት) ፤ የተጨነቀ ፡ የጨነቀው ፡ ጭንቅ ፡ የያዘው ። ኮነ ፡ ጥዉቀ ፡ እምሕዋሳቲሁ ። ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ጥዉቃነ ፡ ወጽቡባነ ። ዕደው ፡ ጥዉቃን ። ሾላ ፡ ነፍስ ፡ ምንድብት ፡ ወጥው ት ፡ (ፊልክ ፡ ፵፯ ። ግንዘ ። ኢሳ፳፰ ፡ ፲፬ ። መስተ) ።

**ጡቀት** ፤ **ጥውቀት** ፤ (ታት) ፤ መጨነቅ ፡ ማስጨነቅ ፤ ጭንቀት ፡ ጥበት ፤ ጭንቅንት ፤ መከራ ፡ የጭንቅ ፡ ሥራ ። በእንተ ፡ ጥውቀት ፡ ዘይመጽእ ፡ ላዕሌሁ ፡ በውስተ ፡ ዓለም ። ክሠተ ፡ ሎቱ ፡ ግብረ ፡ ጥውቀቱ ፡ (ፊልክ ፡ ፭ ። ፲፴) ።


**ጥዋቄ** ፤ (ቀያት) ፤ ግዘኒ ፡ ክማሁ ። ውስተ ፡ ተቃትሎ ፡ ምስለ ፡ ጥዋቄሁ ፡ (ፊልክ ፡ ፸፱) ።

**ተጣወቀ** ፤ ተጣነቀ ፡ ተጨናነቀ ፤ ተጣበበ ። ይጣወቅኑ ፡ ዓለም ፡ (ሱቱ ፡ ዕገዘ) ። በጦቀ ፡ ፈንታ ፡ ጠውቀየ ፡ ካለ ፡ ዘንድ ፤ ይጣወቅኑ ፡ ባለው ፡ ይጠዋቀይኑ ፡ ይላል ።

**አስተጣወቀ** ፤ አጣነቀ ፤ አጨናነቀ ፤ አጋፋ ፡ አጣበበ ። (ተረት) ፤ ይጸድቅ ፡ አይጸድቅ ፡ አይታወቅ ፤ ቤተ ፡ ክሲያን ፡ ያጣንቅ ። አስተጣወቀ ፡ ባለውም ፡ አስተጠዋቀየ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ጣውር** ፤ (ዕብ ፡ ጡር) ፤ ክብ ፡ ናስ ፡ ማንብ ፤ ደንጊያው ፡ የተሰደረ ፤ ስድር ፡ ድርድር ። ወጣውር ፡ ቅድሚሆሙ ፡ ለአርባዕቲሆሙ ፡ (ሕዝ፵፯ ፡ ፳፫) ።

**ጣዎስ** ፤ (ጽር ፡ ታዎስ ። ሱር ፡ ጣውሳ ። ዕብ ፡ ጣዋስ ። ዐረ ፡ ጣዉስ) ፤ ቍንጮጴም ፡ ወፍ ፤ ላባው ፡ ዝንጉርጉር ፤ ዐይናማ ፡ ነብርማ ፡ የኾነ ፤ ጥሩ ፡ ሙብ ፡ መልክ ፡ መልካም ፤ ከመልኩ ፡ ውበት ፡ የተነሣ ፡ ግምጃ ፡ ሠሮች ፡ ኹሉ ፡ በየሥራው ፡ በየሱቲው ፡ ላይ ፡ የሚሥሉት ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ) ። ያፈ ፡ ጣዎስ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ። ጸጕረ ፡ ጣዎስ ፡ (አፈ ፡ ተ፴፪ ። ቄስጠ ፡ ፲፪) ።



ጣዎስ ።

ልጃገረዶችም ፡ የጥምቀት ፡ ለት ፡ የሥራ ፡ ላይ ፡ ወሬ ፡ የሥራ ፡ ላይ ፤ ላይ ፡ ባዶን ፡ ነይ ፡ እያሉ ፡ ይዘፍኑበታል ።

**ጣዝማ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፡ የጸደና ፡ ማር ፡ መድኀኒት ፡ የሚኾን ። (ተረት) ፡ ጣዝማ ፡ ይሰረስራል ፡ ዳኛ ፡ ይመረምራል ። ጸደናን ፡ እይ ።

**ጥሒል** ፤ ሎት ፤ (ጠሐለ ፤ አው ፤ ጥሕለ ፡ ይጥሕል ፡ ይጥሐል) ፤ መጣል ፤ ከውሃ ፡ ማግባት ፡ መበጥበጥ ፡ መዘለል ፤ መጥመቅ ፡ መጠጀት ፤ የማር ፡ የድፍድፍ ፡ የወይን ።

**ጠሓሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ሐልት) ፤ የሚጥል ፡ የሚጠምቅ ፤ ጠማቂ ።

**አጥሐለ** ፤ አስጣለ ፤ አስጠመቀ ፡ አስበጠበጠ ።

**ተጥሕለ** ፤ ተጣለ ፤ ወደቀ ፤ ተጠጀ ፡ ተጠመቀ ። ዘቀጠ ፡ አተላ ፡ ኾነ ፤ ተሰበሰበ ፡ ተከማቸ ። ውስተ ፡ መንጠፍት ፡ ይጠሐል ፡ ሐሠር ፡ (ሚራ፳፯ ፡ ፬) ።

**ጥሑል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ሕልት) ፤ የተጣለ ፡ የወደቀ ፤ ውድቃን ፡ ውዳቂ ፡ (ገድ ፡ አዳ ፡ ገ፳ ፡ ፱ ፡ ፲፰ ፡ ፳ ፡ ፶፯) ።

**ጣሕል** ፤ (ዐረ ፡ ጠሒል ፤ ጕሽ ፡ ድፍርስ) ፤ አተላ ፡ አንብላ ፤ ዝቃጭ ፡ ተራዋጭ ፤ ገፈት ፡ ፍላጭ ፤ ሐሠር ፡ ጥማጭ ፤ የጠላ ፡ የጠጅ ፡ የወይን ፡ ያረቂ ። ሞጻሕተ ፡ ወይን ፡ ዘእንበለ ፡ ጣሕል ። ወጣሕሉኒ ፡ ኢይትከዐው ፡ (መጽ ፡ ምስ ። መዝ ፡ ፸፬) ።

**ጥሕሎ** ፤ (ትግሪኛ) ፤ የበሶ ፡ ሊጥ ፤ እንደ ፡ ፍትፍት ፡ በገር ፡ የሚቃጥ ፡ የሚሰለቀጥ ፤ እንጀራ ፡ በሶ ፡ አላምጡኝ ፡ ስንቅጡኝ ፡ የሚይል ። (ግጥም) ፤ ጥሕሎ ፡ ለልብ ፡ ያጠልሎ ፤ ለረኀብ ፡ ይቀትሎ ።

**ጥሒን** ፤ ኖት ፤ (ጥሕነ ፤ ጠሐነ ፡ ይጥሕን ፡ ይጥሐን ። ዕብ ፡ ጣሐን ። ሱር ፡ ጥሓን ። ዐረ ፡ ጠሐነ) ፤ መፍጨት ፤ ማድቀቅ ፡ መሰለቅ ። ማሸት ፡ ማፍተልተል ፡ መሰበቅ ፤ ፱ ፡ እጅን ፡ እንደ ፡ ወፍጮ ፡ ገጥሞ ። የሸት ፡ የቄሎ ፡ የንዠቶ ፤ ደሐየንና ፡ ሐረጻን ፡ እይ ።

**ጠሓኒ** ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት ፤ ሐንት) ፤ የሚፈጭ ፤ ፈጫይ ፡ ፈጭታ ፤ ባለወፍጮ ።

**ጣሕን** ፤ (ናት) ፤ መፍጫ ፡ ወፍጮ ፤ መንጋጋ ።

**ጥሑን** ፤ (ዐረ ፡ ጢሒን) ፤ ጥሩ ፡ ደቂቅ ፤ ስልቅ ፡ በሶ ። ወመልእት ፡ ጽፍነታ ፡ ጥሑነ ፡ ወበሰለ ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፭) ።

— ፤ የታሸ ፡ ቄሎ ፡ ጥብስ ፡ እሸት ። ንሣእ ፡ ለእኅዊከ ፡ ዘንተ ፡ መስፈርተ ፡ ጥሑነ ፡ ቄሎ ። ኅምስተ ፡ መስፈርተ ፡ ጥሑን ። ወፀበጠ ፡ ላቲ ፡ ጥሑነ ፡ እሸት ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ። ፳፭ ፡ ፲፰ ። ሩት፪ ፡ ፲፬) ።

**ጥሒር** ፤ ሮት ፤ (ጥሕረ ፡ ይጥሕር ፡ ይጥሐር ። ሱር ፡ ጥሓር) ፤ መሥነክ ፡ ማግማት ፤ ክረንብ ፤ ከቀጣ ፡ የተነሣ ፡ የነስሳ ፡ ያነክሳ ፡ ያራዊት ፡ ኹሉ ። ጥሕሩ ፡ ላዕሌሁ ፡ አናብስት ። በከመ ፡ ይጥሕር ፡ አንበሳ ፡ ወዕጓለ ፡ አንበሳ ። አራዊት ፡ እለ ፡ ይጥሕሩ ፡ በጥ

ራእ ፡ ቃል ፡ መፍርሆ ፡ (ኤር፬ ፡ ፲፭ ። ኢሳ፴፩ ፡ ፱ ። ጥበ ፲፯ ፡ ፲፰) ።

**ጥሕረት** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ መፈጠኛ ፡ ማጣጣሚያ ፤ አፈፈጪ ፡ አገማሥ ። ግርማ ፡ ያለው ፡ ፈጪነት ፡ ግግት ። መፀተ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ ጥሕረተ ፡ አንበሳ ፡ (ምሳ፲፱ ፡ ፲፪) ።

**ጣሕር** ፤ ድምፀ ፡ አራዊት ፤ ፈጪነት ፡ ግግት ። ድምፀ ፡ ጣሕሩ ፡ ከመ ፡ ጣሕረ ፡ አንበሳ ፡ (ሕዝ፲፱ ፡ ፯) ።

**አጥሐረ ፤ አስተጥሐረ** ፤ አስፈጨ ፤ አስገማ ።

**አስተጣሐረ** ፤ አፈፈጨ ፤ አጋማ ፡ አገማማ ። ያስተጣሕር ፡ ነገሥተ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ጥጥ** ፤ በቁሙ ፤ ያታክልት ፡ ወገን ፡ ፍሬው ፡ ቅባታም ፤ ጠጕሩ ፡ ፈትልና ፡ ልብስ ፡ የሚኾን ፤ መጠኑ ፡ ከፀምር ፡ መጠን ፡ የሚያንስ ፡ የሚቀጥን ፤ ጠጕን ፡ እይ ። ዘይትዐሰብ ፡ እንስሳ ፡ ከመ ፡ ያጺሩ ፡ መክሊተ ፡ ጥጥ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያጺሩ ፡ መክሊተ ፡ ኅጺን ። ፈትለ ፡ ጥጥ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ። ስንክ ፡ መጋ፴) ።

**ጢጢ** ፤ ዐለንጋ ፡ ጅራፍ ። ቀሠፍዎ ፡ በጢጢ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ጢጤን** ፤ (ጽር ፡ ቲቴን) ፤ ደቅማ ፤ የደቅማ ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ፤ መልካም ፡ ሽታ ፡ ያለው ፡ (ኩፋ ፡ ፳፩) ።

**ጢጣኖስ ፡ ን** ፤ (ጽር ፡ ቲታኔስ) ፤ ኀያላን ፡ ኀዋኃን ፤ የሔናቅ ፡ ልጆች ፤ መጠናቸው ፡ ከሰው ፡ የሚበልጥ ፤ እንደ ፡ ዖግ ፡ ንጉሠ ፡ ባሳን ፡ ያሉ ፤ ዛፍ ፡ የሚያክሉ ። ወረዱ ፡ ውስተ ፡ ቈላተ ፡ ጢጣኖስ ። አኮ ፡ ደቂቀ ፡ ጢጣኖን ፡ ዘቀተልዎሙ ፡ (፪ነገ ፡ ፳ ፡ ፲፰ ። ዮዲ ፲፮ ፡ ፯) ።

**ጤግን** ፤ (ናት ። ሱር ፡ ጢጋና ። ዐረ ፡ ጣጂን) ፤ የብረት ፡ ሎሕ ፡ ሰሌዳ ፤ ምንገ ፡ ምጣድ ። ንሣእ ፡ ለከ ፡ ጤግነ ፡ ኀጺን ። ወአብአቶ ፡ በጤግኑ ። ዲበ ፡ ጤግናት ፡ ወዲበ ፡ ብሑእ ፡ (ሕዝ፬ ፡ ፫ ። ፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፱ ። ፩ዜና ፡ ፳፫ ፡ ፳፱) ።

**ጤግነ** ፤ (ዐረ ፡ ጠጀነ ። ሱር ፡ ወዕብ ፡ ጣጌን) ፤ አበሰለ ፡ ቈላ ፡ ጋገረ ፤ ዐመሰ ፡ ጠበሰ ። እሰ ፡ ጤግኖሙ ፡ ንጉሥ ፡ ባቢሎን ፡ በእሳት ፡ (ኤር፴፯ ፡ ፳፱) ።

—፤ ተጎነ ፡ ጋረደ ። ጠገነ ፡ ዐደሰ ፡ አጸና ፡ የሰበረና ፡ ያሮጌ ፡ የድኻ ፡ የደከማ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጤጋኒ** ፤ አብሳይ ፡ ጋጋሪ ። የሚያድስ ፤ የሚጠግን ፡ ጠጋኝ ።

**ተጤግነ** ፤ በሰለ ፡ ተቈላ ፡ ተጋገረ ። ታደሰ ፡ ተጠገነ ።

**ጢጉን ፤ ጤጉን** ፤ የበሰለ ፡ የተጋገረ ፡ አንባሻ ፡ ዳቦ ፡ ቈሎ ፡ ዕንጕቃ ። ኅብዝተ ፡ ጤጉን ፡ (፪ነገ ፡ ፮ ፡ ፲፱) ። የታደሰ ፡ የተጠገነ ፡ ጥግን ።

**ጤግሮስ** ፤ (ጽር ፡ ቲግሩስ ። ዕብ ፡ ሒዴቄል) ፤ ስመ ፡ ፈለግ ፤ ከ፬ቱ ፡ ወበይት ፡ አፍላጋት ፡ አንዱ ፡ ሦስተኛው ፡ ወንዝ ፤ በአሶር ፡ አገር ፡ በነነዌ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የሚፈስ ፡ ከኤፍራጥስ ፡ ገጥሞ ፡ ወደ ፡ ባሕረ ፡ ፋርስ ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ የሚገባ ። ሒዴቄል ፡ በሲኅ ፡ ማይ ፤ ጽሩየ ፡ ማይ ፤ ቀሊል ፡ ማይ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በሲኅ ፡ ፍጥነትን ፡ ያሳያል ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፲፬) ።

**ጢግሩስ ፤ ጢግሪስ** ፤ (ዕብራ) ፤ ታላቅ ፡ ነብር ፤ በወንዝ ፡ ዳር ፡ በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ የሚኖር ፤ ቍጡ ፡ ብስጩ ፡ ክፉ ፡ ፈጣኝ ። እንደ ፡ ሻሻቴ ፡ የሚዘል ፡ የሚወረወር ፤ ቀላልና ፡ ፈጣን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ስሙን ፡ ከውሃ ፡ ወሰዷል ። ቴግርን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ።

**ጠዪዕ ፤ ዮት** ፤ (ጤዐ ፡ ይጠይዕ ፡ ይጢዕ ። ዕብ ፡ ጡዋሕ ። ዐረ ፡ ጣኅ) ፤ መምረግ ፡ መለሰን ፤ በጭቃ ፡ መዝጋት ፡ መድፈን ፡ የገሮ ። ጤዑ ፡ እዘኒሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይስምዑ ፡ (ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፲ ። ሚክ፯ ፡ ፲፯) ።

—፤ መቅባት ፡ መለቅለቅ ፤ ማሰር ፡ ማጣበቅ ፤ የኖራ ፡ የመዳኒት ። ንሣእ ፡ ዐጽቀ ፡ በለስ ፡ ወጢዕ ፡ ቦቱ ፡ ኀበ ፡ ተንምም ። ዘይጠይዕዎ ፡ ሥራየ ፡ (፬ነገ ፡ ፳ ፡ ፯ ። ኢሳ፳ ፡ ፯) ።

**ተጤዐ** ፤ (ይጠያዕ) ፤ ተመረገ ፡ ተለሰነ ፤ ተደፈነ ፡ ተቀባ ።

**ጥዩዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ይዕት) ፤ የተመረገ ፡ ምርግ ፤ ድፍን ፡ ዝግ ፤ ደንቈሮ ። ለሕሙማን ፡ ለቈረ ፡ እዘኒሆሙ ፡ ጥዩዓተ ፡ ከመ ፡ ይስምዑ ፡ ቃለ ፡ ሃይማኖት ። ይሰቍር ፡ እዝነ ፡ ጥይዕተ ፡ (ቀሌ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ።

**ጤፍ** ፤—በቁሙ ፤—ጣፍ ።

**ጠያፌሳ** ፤ ፀሓየ ፡ ፈሳ ፤ ዕንቍ ፡ ባሕርይ ፤ ሰደፍ ፡ ከፀሓይ ፡ የምትቀልደው ። እብነ ፡ ባሕርይ ፡ ዘስሙ ፡ ጠያፌሳ ፡ (አረጋ) ።

**ጠይቆ ፤ ቆት** ፤ (ጠየቀ ፡ ይጤይቅ ፡ ይጠይቅ ። ሰአለ ፤ ሐተተ) ፤ መጠየቅ ፤ መመርመር ፤ ለማግኘት ፡ ለማወቅ ። ጠይቆ ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ መረዳት ፤ ልክን ፡ ድርሱን ፡ ርግጡን ፡ ማግኘት ። ጠየቅዎ ፡ ለአሐዱ ፡ እምእለ ፡ ይቀውሙ ። ቅድመ ፡ ጠይቅ ፡ ወድኅረ ፡ ትጌሥጽ ። ጠይቅ ፡ ነገሩ ፡ ለትምህርትከ ። ወነፍስየ ፡ ትጤይቆ ፡ ጥቀ ። ከመ ፡ ያእምሩ ፡ ወይለብዉ ፡ ወይጠይቁ ፡ ወይእመኑ ፡ (ዳንኤ ፡ ፲፮ ። ሢራ፲፩ ፡ ፯ ። ፲፮ ፡ ፳፭ ። መዝ ፡ ፻፴፰ ። ኢሳ፵፩ ፡ ፳) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ በጠየቀ ፡ ፈንታ ፡ ተጠየቀ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወተጠየቀ ፡ እምኀቤሆሙ ፡ መዋዕሊሁ ። ይፈርሁ ፡ ተጠይቆቱ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ነገር ። ወተጠየቆት ። እመ ፡ ተጠየቀ ፡ ብእሲ ፡ ደዌሁ ። በኀበ ፡ ጠቢባን ፡ ተጠየቀ ፡ በዘቲ ፡ ጊዜ ፡ (ማቴ፪ ፡ ፯ ። ሉቃ፱ ፡ ፵፭ ። ፳፱ ፡ ፶፯ ። ፪ዜና ፡ ፯ ፡ ፳፱ ። ሢራ፳፯ ፡ ፲፱) ።

**ጠያቂ** ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ የሚጠይቅ ፡ የሚመረምር ፤ መርማሪ ። (ተረት) ፤ አጥብቆ ፡ ጠያቂ ፡ እናቱን ፡ ይረዳል ።

**አጠየቀ** ፤ አስጠየቀ ፤ አስመረመረ ። አስረዳ ፡ አሳወቀ ፡ አስታወቀ ፡ ነገረ ፡ አሰማ ፡ አስተማረ ። አጠይቁኒ ፡ ኍልቈሙ ። ወአጠይቅዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ቃላተ ።

ተጋብኡ ፡ ኀበ ፡ ዕዝራ ፡ ከመ ፡ ያጠይቅሙ ፡ ዘሎ ፡ ቃለ ፡ ኦሪት ፡ (ሸዜና ፡ ፰፰ ፡ ፱ ፡፡ ፪ዜና ፡ ፴፱ ፡ ፳፰ ፡፡ ዕ ዝ፰ ፡ ፲፫) ፡፡

**አጠያቂ ፤ መጠይቅ ፤ (ቅት ፡ ቃን ፡ ቃት) ፤** የሚያስጠይቅ ፡ አጠያቂ ፡ አስመርማሪ ፡፡ የሚ ያስረዳ ፡ አስረጂ ፡ መምር ፡ አስተማሪ ፡፡ ወሌዋውያን ፡ መጠይቃን ፡ ለሕዝብ ፡ መጽሐፈ ፡ (ነሐ፰ ፡ ፯) ፡፡

**ተጠየቀ ፤** በቁሙ ፡ ተመረመረ ፡ ታወቀ ፡ ተ ረዳ ፡ ተረገጠ ፡ ታየ ፡ ተገለጠ ፡፡ በዝ ፡ ተዐውቀ ፡ ወተጠ የቀ ፡ ከመ ፡ (አቡሻ ፡ ፲፪) ፡፡ ወበዝ ፡ ተዐውቀ ፡ ሕልመ ፡ አቡሆሙ ፡፡ ለእመ ፡ ተጠየቀ ፡ ሞተ ፡ ንጉሥ ፡፡ ወተጠ የቀ ፡ ሶቤሃ ፡ ነገረ ፡ አረጋዊ ፡ (ዮሴፍ) ፡፡

**ጥዩቅ ፤** የተጠየቀ ፡ የተመረመረ ፡፡ የታወቀ ፡ የተረዳ ፡ የተረገጠ ፡፡ ዕለት ፡ ጥይቅት ፡፡ አይድዐኒ ፡ ፍ ካሬሁ ፡ ጥዩቀ ፡፡ ለአከቶ ፡ ይስማዕ ፡ ጥዩቀ ፡ ነገረ ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ ፡፡ ዳንኤ ፡ ፲፯ ፡፡ አበቄ፱ ፡ ፳) ፡፡

**ጥዩቀ ፤** ርግጥ ፡ በርግጥ ፡ እውነት ፡ በውነት ፡ በግልጥ ፡ ፈጽሞ ፡፡ ጥዩቀ ፡ እንከ ፡ ያእምሩ ፡፡ ጥዩቀኬ ፡ ወገሃደ ፡፡ ለሊክሙ ፡ ተአምሩ ፡ ጥዩቀ ፡ ከመ ፡ ዕለተ ፡ እግዚእነ ፡ ትመጽእ ፡ (ግብ፪ ፡ ፴፯ ፡፡ ቄር ፡ ጳላ ፡፡ ፩ተሰ ፡ ፭ ፡ ፪) ፡፡

**ጥያቄ ፤ (ቅያት) ፤** በቁሙ ፡ መጠየቅ ፡ (ጥ ፡ ጠ) መጠየቅ ፤ አጠያየቅ ፡ ጥየቃ ፡ ምርመራ ፡፡ መረዳት ፤ ማስረዳት ፤ መግለጥ ፡ ማስረገጥ ፡፡ በብዙኀ ፡ ጥያቄ ፡ ፈ ለጠ ፡፡ ናመጽእ ፡ ካልአ ፡ አምሳለ ፡ ለጥያቄ ፡ ዝንቱ ፡ (አፈ ፡ ድ፫ ፡፡ ተ፲፫) ፡፡ ርግጥ ፤ ርግጥነት ፡፡ ኀሥሥ ፡ በ እንተ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ እስከ ፡ ትረክብ ፡ ጥያቄሁ ፡፡ ኢ ያእመረ ፡ ጥያቄሁ ፡ ለዝንቱ ፡፡ የሀብዎ ፡ መዋዕለ ፡ ዕ ድሜ ፡ ለአብጽሖተ ፡ ጥያቄሁ ፡ (ዮሴፍ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡፡ ፃዊ ፡ ፯) ፡፡

**ጥይቅና ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ መረዳት ፡ ማስረገጥ ፤ ርግጥነት ፡፡ አእምሩ ፡ ዘንተ ፡ በጥይቅና ፡፡ ነባብያን ፡ በጥይቅና ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡፡ መቅ ፡ ወን) ፡፡

**ጠይሮ ፤ ሮት ፤ (ጠየረ ፡ ይጤይር ፡ ይ ጠይር ፡፡ ዐረ ፡ ጣረ) ፤** መብረር ፡ መክነፍ ፡ ያሞራ ፡ የወፍ ፡፡

**ተጠየረ ፤ (ዐረብ ፡፡ ዕብ ፡ ጣዩር) ፤** ተነሳ ፡ ጠነቈለ ፡ አሟረተ ፡ በወፍ ፡ ጩኸት ፡ በድምፀ ፡ አራዊት ፡ በሌላውም ፡ ፍጥረት ፡፡ ከሟርቱና ፡ ከጥንቈላው ፡ ጋራ ፡ አምልኮትንም ፡ ያሳያል ፡፡ ኢትጠየሩ ፡ በዖፍ ፡፡ ዘይጤ የሩ ፡ በሐሳበ ፡ ፀሓይ ፡ ወወርኅ ፡ (ዘሌ፲፱ ፡ ፳፮ ፡፡ አ ርጋ ፡ ፪) ፡፡ ዘይጤየር ፡ በዖፍ ፡ ወበማይ ፡ ወበእሳት ፡፡ እመ ፡ ቦ ፡ ዘተጠየረ ፡ በአዕዋፍ ፡ አው ፡ በአራዊት ፡ አው ፡ በካልእ ፡ አው ፡ በዘከነ ፡ ከዊኖ ፡ (ቀሌ) ፡፡

**ተጠያሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤** የሚያ ሟርት ፡ ሟርተኛ ፡ ጠንቋይ ፡ ወፍ ፡ ጠያቂ ፡ እንዳንገውና ፡ እንዳርማዎሴ ፡ ሰው ፡ የወፍ ፡ ቋንቋ ፡ የሚያውቅ ፡፡ ኢ ትኩን ፡ ተጠያሬ ፡ በዖፍ ፡፡ ተጠያሪ ፡ በመሬት ፡ ወበ ሐመድ ፡ ወበፍሬ ፡ ዕፀው ፡፡ ተጠያርያን ፡ (መጽ ፡ ምስ ፡፡ ሲኖዶ ፡፡ ቄድር) ፡፡

**አጠየረ ፤ አስተጠየረ ፤** አበረረ ፡ አስበረረ ፤ አከነፈ ፡ አክነፈነፈ ፡፡ አስጠነቈለ ፡ ወፍ ፡ አስጠየቀ ፤ አስ መሰከ ፡፡ አድራጊና ፡ አስደራጊ ፡ ነው ፡፡

**አጠያሪ ፤ መጠይር ፤ መስተጠይር ፤** አስጠንቋይ ፡ ወፍ ፡ አስጠያቂ ፡ (ሲኖዶ) ፡፡

**ጠያር ፤ ጥያራ ፤ (ራት) ፤** ሰው ፡ ሠራሽ ፡ አሞራ ፤ ዘመን ፡ አመጣሽ ፡ ወፍ ፡ በአየር ፡ የሚበር ፡ የሚ ክንፍ ፡ አይሮፕላን ፡ የውቀት ፡ ብዛትና ፡ የፍጻሜ ፡ ዘ መን ፡ ምልክት ፡ (ዮኤ፫ ፡ ፫—፭ ፡፡ ፩ተሰ ፡ ፬ ፡ ፲፯) ፡፡



ጠያር ፡

**ጢር ፤** ጥንቈላ ፡ ሟርት ፡ አምልኮ ፡ ባዕድ ፡፡ ፀ ጥር ፡ ቅጥርንም ፡ ያሳያል ፡፡ ጣውርን ፡ እይ ፡፡

**ጢሮት ፤** ጣራ ፡ ባጥ ፡ ጠፈር ፡ መዋቅር ፡ ድን ኳን ፡ (ሕዝ፳፭ ፡ ፱) ፡፡

**ጥር ፤** በቁሙ ፤ ስመ ፡ ወርኅ ፡ ኃምስ ፡ እመስከ ረም ፤ ጠር ፡፡ ምስጢሩ ፡ ምጥቀት ፡ ርዝመት ፡ ነው ፤ ባ ፲፭ ፡ ምዕራፍ ፡ ኑኅና ፡ ርሕብ ፡ ፃ ፡ ዘመን ፡ ምሉ ፡ ቅው ርቶ ፡ ቈመቱ ፡ ፭ ፡ ሺሕ ፡ ከ፩፻፴፫ ፡ ክንድ ፡ ከ፪ ፡ ስንዝር ፡ ሲኾን ፡ በጥር ፡ ፀ፯ ፡ ከፈረሰው ፡ ከጥቅመ ፡ ሰናዖር ፡ ይ ሰማማል ፡፡ ድርሳን ፡ ሥላሴ ፡ ተመልከት ፡ (ኩፋ ፡ ፲ ፡፡ ዘ ፍ፲፩ ፡ ፩—፯) ፡፡

**ጠዩስ ፤ ሶት ፤ (ጤሰ ፡ ይጠይስ ፡ ይ ጢስ ፡፡ ተነ) ፤** መጤስ ፤ መትነን ፡ መብነን ፡ መትጐ ልጐል ፤ ከሚነድና ፡ ከሚቃጠል ፡ ነገር ፡ ጭጋግና ፡ ጉም ፡ ጥቍር ፡ ደመና ፡ መስሎ ፡ መውጣት ፡፡ ትንቃጋት ፡ እለ ፡ ይጠይሱ ፡፡ ሥዕ ፡ ዘይጠይስ ፡፡ ዘእንበለ ፡ ይጢስ ፡ ሥብሕ ፡፡ እቶን ፡ ዘይጠይስ ፡ (ኢሳ፷ ፡ ፱ ፡፡ ዓ፪ ፡ ፫ ፡፡ ፩ነገ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ፡፡ ዘፍ፲፭ ፡ ፲፯) ፡፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡ ለሚ ነቁና ፡ ለሚፈልቁ ፡ ለኃሊናትም ፡ ይነገራል ፡፡

**ጢስ ፤** በቁሙ ፡ ጪስ ፡ ጭጋግ ፡ የሚመስል ፡፡ ላበት ፡ እንፋሎት ፡ ስልባቦት ፤ ከሙቅ ፡ ከትኵስ ፡ ነገር ፡ የሚወጣ ፡፡ ለእሳት ፡ ይቀድሞ ፡ ቶነ ፡ ጢስ ፡፡ ጢሰ ፡ ም ንሃብ ፡፡ ወዐርገ ፡ ጢስ ፡ እምቀሳይ ፡ ከመ ፡ ጢሰ ፡ እ ቶን ፡ ዐቢይ ፡፡ ወወፅአኒ ፡ ጢስ ፡ ውስተ ፡ አዕይንትየ ፡ ወተሥዐዐ ፡ እምብንተ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ዝኩ ፡ ጢስ ፡ (ሢራ፳፪ ፡ ፳፬ ፡፡ ፀ፳ ፡ ፳፰ ፡፡ ራእ፱ ፡ ፪ ፡፡ ጦቢ፪ ፡ ፲ ፡፡ ፲፩ ፡ ፲፪) ፡፡

**አጤሰ ፤** በቁሙ ፡ አጨሰ ፡ አበነነ ፤ ዐጠነ ፡፡ አ ጤሰ ፡ ልቦ ፡ ወሐሞቶ ፡ ለዓሣ ፡፡ ሰቀላ ፡ ቍልቍሊተ ፡ ወአጤሰ ፡ መትሕቲሃ ፡ እሳተ ፡፡ ለተነ ፡ ሪሚ ፡ ዘደጤ

ይሉ ፡፡ አጤስ ፡ ቦቱ ፤ (ስንክ ፡ መስከ ። ጥቅ ። መጽ ፡ ቃል ። ጠቢ ፡ ፲፯) ።

**ጤት ፤ (ዕብራ) ፤** ስመ ፡ ፊደል ፡ ታስዕ ። ሠ ናይት ፡ ላሕዩት ፡ ጠባብ ፡ ኄርት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፷፭—፸፪ ። ሰቈ ፡ ፱ ። ፱ ፡ ፱ ። ፱ ፡ ፷፭ ። ፱ ፡ ፱) ።

**ጠይት ፤ (ማእዝ) ፤** ግእዝ ፡ ከማሁ ፤ ዘጠነኛ ፡ ፊደል ፡ ጠ ። ጤትና ፡ ጠይት ፡ ጦብያና ፡ ጦቢት ፡ በዕብ ራይስጥ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ ጠወበን ፡ እይ ።

(ጥ) **ጠየተ ፤ (ይጤይት ፡ ይጠይት) ፤** በቁሙ ፡ ጥይት ፡ ሠራ ። መረጠ ፡ መራረጠ ፤ አበጀ ፡ አዘጋጀ ፤ የሽ ትን ፡ ዛላ ፡ ለመጥበስ ፡ ለማሸት ፡ (ዐማርኛ) ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ማስ ፡ ቅጥይ ፡ ተቀጥላ ፤ ወይም ፡ ክልስ ፡ ዲቃላ ፡ ይባላል ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ አለ ።

**ጠያቲ ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤** የሚጠይት ፡ ጠያቾ ፤ ጥይት ፡ ሠሪ ።


**አጠየተ ፤** አስጠየተ ፤ ጥይት ፡ አሠራ ።

**መጠይት ፤ (ታን) ፤** የሚያስጠይት ፡ አስጠ ያች ፡ ወይም ፡ ጠያች ።

**ተጠየተ ፤** በቁሙ ፤ ተመረጠ ፡ ተዘጋጀ ።

**ጥዩት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ይት) ፤** የተጠየተ ፤ የታሰረ ፡ የተዘጋጀ ።

**ጥይት ፤ (ታት) ፤** በቁሙ ፤ ጥሩ ፡ እሸት ፤ ተመ ርጦ ፡ የታሰረ ፤ ለመጠበስ ፡ የተደከረ ። ፀረር ፡ ርሳስ ፡ የሚ ፈነዳ ፡ የሚተኰስ ፡ እንደ ፡ ዛላ ፡ ኹኖ ፡ የተሠራ ፤ ዝግጁ ፡ ማለት ፡ ነው ። ወለቢናድር ፡ ኀይልከ ፡ አመ ፡ በጥይት ፡ ለጕምካ ፤ ትግራይ ፡ አሽከር ፡ ቦሬሳ ፡ በይእቲ ፡ ሕቅ መሰከ ፡ (ትግሬኛ ፡ ቅኔ) ።



ጥይት ፡


**ጠል ፤—በቁሙ ፤—ጠሊል ፡ ጠለ ።**

**ጠልጠለ ፤—ጣለ ፤—ጠሊል ፡ ጠለ ።**

**ጠልይ ፤ ዮት ፤ (ጠለየ ፡ ይጠሊ ፡ ይ ጥሊ ። ጠለ) ፤** መርጠብ ፡ መታደስ ፤ ልምላሜ ፡ ማ ማገት ፤ ርጥብ ፡ ለጋ ፡ መኾን ፡ የዐጽቅ ፡ የልጅ ። መው ጣት ፡ መብቀል ፡ ማቈጥቈጥ ፤ የሁቃያ ፡ የማር ። ፋኑ ኤል ፡ ዘክርከ ፡ እምቀናንም ፡ ዘይጠሊ ፡ (ደራሲ) ።

**ጠሊ ፤ (ዕብ ፡ ጣሌ ። ዐረ ፡ ጠሊይ ፤ ጠ ለን ። ሱር ፡ ጥላይ) ፤** ግልገል ፡ እንቦሳ ፡ ውርንጭላ ፡ ለጋ ፡ ቀንበጥ ፤ ርጥብ ፡ ጨሌ ፡ ዐራስ ፡ ጨቅላ ። ልጅነት ፡ ባለው ፡ ለታናናሽ ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ፤ በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ሰበግ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ጠሊ ፤ (ሊት ፤ ብ ፡ አጣሊ ፤ ልያት) ፤** ቀባት ፡ ፍየል ። ጸጕረ ፡ ጠሊ ፡፡ ማእሰ ፡ ጠሊ ፡፡ ደም ጽሕ ፡ በግዐት ፤ አው ፡ ጠሊቱ ፡፡ ይሬልጥ ፡ አባግዐ ፡ እምአጣሊ ፤ (ዘፀአ ፡ ፳ ። ዘኁል ፡ ፯ ። ዘሌዋ ፡ ፯ ። ማቴዎስ ፡ ፳፭) ። እንስቶቹን ፡ አጣልያት ፡ በማለት ፤ ፈንታ ፡ አጣሊ ፡ አንስት ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ፡ (መቃ ፡ ገጽ) ፡ እን ፡ ትቶ ፡ በንና ፡ በየ ፡ ሲበዛ ፡ ግን ፤ ጠሊ ፡ ጣል ያን ፤ ጣሊት ፡ ጣልያት ፡ ያሰኛል ።



ጠሊ ፡

**ጣሊታ ፤ (ሱር ፡ ጣልያታ ። ጽር ፡ ታ ሊታ) ፤** ታናሽ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፤ ለጋ ፡ ቈንጆ ፡ ድንግል ፤ ከዘጠኝና ፡ ከሥር ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ያለች ፤ ገና ፡ እኩለ ፡ መጠን ፡ ያልሞላች ። ወይቤላ ፤ ጣሊታ ፡ ቁንምአ ፤ ዘ በትርጓሜሁ ፡ ወለት ፡ (ማርቆ ፡ ፭) ። አንዳንድ ፡ መ ጣፍ ፡ ግን ፡ በጣሊታ ፡ ፈንታ ፡ ጣቢታ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ጠሊል ፤ ሎት ፤ (ጠለ ፤ ጠለለ ፡ ይጠ ልል ፡ ይጥልል ። ዐረ ፡ ጠለ) ፤** መጥለል ፡ መጥ ራት ፤ የጠላ ፡ የጠጅ ። መውረድ ፡ መረጨት ፤ የጠል ፡ የ ክረምት ። መራስ ፡ መረስረስ ፤ መርጠብ ፡ መለምለም ፤ መ ርካት ፡ ጠል ፡ መንጣት ፤ ከውሃ ፡ ከቅባት ። ትጠልል ፡ ምድር ፡ እምሥብሖሙ ፡፡ ወይጠልል ፡ በቅብዕ ፡ ሚበትየ ፡፡ ዘላ ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ ትባርክ ፡ ትጠልል ፡ (ኢሳ ፡ ፮ ። መዝ ፡ ፺፩ ። ምሳ ፡ ፲፩) ።

**ጥሉል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ልልት) ፤** የጠለለ ፡ ጥሩ ። የለመለመ ፡ የረጠበ ፤ ለምለም ፡ ርጥብ ። ብሔር ፡ ጥሉል ፡፡ ፂያት ፡ ጥሉል ፡፡ ደብር ፡ ጥሉል ፡፡ ርሥእን ፡ ጥሉል ፡ (ኢሳ ፡ ፴ ። ሕዝ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፷፯ ። ፺) ።

—፤ ሥጋ ፡ ቅቤ ፡ ዕንቍላል ፡ ወተት ፤ የብሎት ፡ ምግብ ። ትወርድ ፡ ማእድከ ፡ እንዘ ፡ ምሉእ ፡ ወጥሉል ፡፡ መባልዕት ፡ ጥሉላት ፡፡ ኢይብልዑ ፡ ጥሉላተ ፡ (ኢዮ ፡ ፴፮ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ ጥር ፲) ።

**ጠል ፤ (ላት) ፤** በቁሙ ፡ የሰማይ ፡ ወዝ ፤ የአ የር ፡ ላብት ፡ ሌሊት ፡ አለደመና ፡ የሚወርድ ፡ ምድርን ፡ የሚያርስ ፡ የሚያረሰርስ ፤ እንደ ፡ ጤዛ ፡ በማር ፡ በቅጠል ፡ ላይ ፡ የሚታቈር ፡ የሚንቈረዘዝ ። እስመ ፡ ርእስየኒ ፡ ምሉእ ፡ ጠለ ፡፡ ወይረድ ፡ ከመ ፡ ጠል ፡ ነቢብየ ፡፡ ወ ወረደ ፡ ጠል ፡ ደበ ፡ ፀምር ፡ ባሕቲቱ ፡ (ማሕ ፡ ፭ ። ዘዳ ፡ ፴፪ ። መሳ ፡ ፮) ።

—፤ ክረምት ፡ የጉም ፡ ሽንት ፡ ልዝብ ፡ ዝናም ። ደመ

ናት ፡ ያውሕዙ ፡ ጠላተ ፡ (ምሳ፲ ፡ ፳) ። ቅባት ፡ ዘይት ። እሉኬ ፡ ይቂቀ ፡ ጠላት ፡ እሙንቱ ፡ (ዘኍ፴ ፡ ፲፱) ።

**ጥላል** ፤ ርጥበት ፡ ልምላሜ ፡ ጣዕም ፡ ሥሥ ። ጥላሊሁ ፡ ለማእይ ፡ (ግድ ፡ ላሊ) ።

**አጥለለ** ፤ አበለለ ፡ አወረደ ፡ የጠላ ፡ የጠል ። አራሰ ፡ አረጠበ ፡ አለመለመ ፡ አረካ ። ያጠልል ፡ አዕፅምተ ፡ እምብዝኀ ፡ ጣዕሙ ። መሥዋዕቱ ፡ ለጻድቅ ፡ ያጠልሎ ፡ ለምሥዋዕ ። ያጥልል ፡ ለከ ፡ ቍርባንከ ። በማየ ፡ ጸሎቱ ፡ ጽምአ ፡ ነጋድያን ፡ አጥለለ ። በጠለ ፡ ምሕረቱ ፡ እግዚ ፡ ያጥልል ፡ ነፍሳቲክሙ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ። ሚሊ፴፬ ፡ ፫ ። መዝ ፲፱ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፱ ። ግንቦ) ። በሰቅየ ፡ ፈንታ ፡ አጥለለ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። እንበለ ፡ ይብልዎ ፡ እክለ ፡ ወማየ ፡ ያጥልሉ ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፱) ።

**መጥለሊ ፤ መጥልል** ፤ የሚያጠል ፡ የሚያለመልም ፡ የሚያረካ ። አስትየኒ ፡ ዘንተ ፡ ወይነ ፡ ኀይል ፡ መጥለሊ ፡ (ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**መጥለል** ፤ ማጥለያ ፡ ማጥሪያ ፡ ወንጠፍት ። ከመ ፡ ዘመጥለል ፡ ሙሓዝ ፡ (ስንክ ፡ ግንጀ) ።

**ጠልጠለ** ፤ (ተቀ ፡ ግ ። ዕብ ፡ ጣልጤል) ፤ ጣለ ፡ ወረወረ ፤ ረጨ ፡ በተን ፡ በየጥቂቱ ፡ እንደ ፡ ጠልና ፡ እንደ ፡ ጠበል ። ነቀለ ፡ አጓዘ ፡ ወሰደ ።

**አንጠልጠለ** ፤ በቁሙ ፡ አንጠለጠለ ፡ አንግ ፡ ያዘ ፤ ለመውሰድ ፡ ለመጣል ፡ ወይም ፡ ለማኖር ። ተያዘ ፡ ተንጠለጠለ ፡ ተወዘወዘ ፤ ለመውደቅ ። ተቀሥፈ ፡ አባለ ፤ እስከ ፡ ሥጋሁ ፡ አንጠልጠለ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲፯) ።

**ጠለመ** ፤ (ጸልመ ፤ ጸለመ ። ሱር ፡ ጥላም ። ዐረ ፡ ዘለመ) ፤ ከዳ ፡ ከዳ ፤ ሸፈጠ ፡ ተ ፤ ውል ፡ አፈረሰ ፤ ሰደበ ፡ ነቀፈ ። ጠለሙ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ . . . ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ይከውን ፡ ቀትል ፡ ማእከሌሆሙ ፡ (አዋል) ። ፪ኛም ፡ መስጠምንና ፡ መገዘቀጥን ፡ ይሳያል ። ጠ ፡ የጸ ፡ ለወጥ ፡ ነው ፤ ጸልመን ፡ ተመልከት ።

**ጥልማ ፤ ጥልም** ፤ (ዕብ ፡ ያሀሎም) ፤ ክቡር ፡ ደንጊያ ፡ ስንቍ ፤ ልዩ ፡ ሕብር ፡ የሌለው ፡ የውሃ ፡ ዐይነት ። ኢያስጲስን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (መቃ ፡ ገ፫ ። ክብ ፡ ነገ፲፯ ። ዘፀ፴፯ ፡ ፲፰) ። ኢያስጲስ ፡ ወጥልም ፡ አሐዱ ፡ (ጥፊ ፡ ሰዋ) ።

**ጥልማክስ ፤ ጥልምያክስ** ፤ ስመ ፡ ሰይጣን ፤ የሲኦል ፡ በረኛ ፡ አጋፋሪ ፤ ከሐዲ ፡ ግፈኛ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ፊእ ፡ ማር) ።

**ጠልዐ** ፤ (ዐረ ፡ ጠለዐ) ፤ ወጣ ፡ በቀለ ፤ አደገ ፡ ረዘመ ። ናሁ ፡ ትጠልዕ ፡ (ሕዝ፲፯ ፡ ፲) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ሸቱላ ፡ ይላል ፤ ትበቅላ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ጠሊቅ ፤ ቆት** ፤ (ጠለቀ ፡ ይጠልቅ ፡ ይጥልቅ ። ዐረ ፡ ጠለቀ ፤ አሳደፈ) ፤ መጥለቅ ፤ ጥልቅ ፡ ስሙቅ ፡ መኾን ፤ ወይም ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ መግባት ፤ መንከር ፡ መዘፈቅ ፡ ማደፍ ፡ መኾስፈስፍ ፤ መርከስ ፡ መጨማለቅ ። ኢጠለቀ ፡ ኅዳሮ ፡ ውስተ ፡ ማሕፀና ። ልቡና ፡ ሰብእ ፡ ዘኢጠለቀ ፡ በኀጢአት ፡ (ተረ ፡ ቄር) ።

—፤ መጥገብ ፡ መርካት ፡ መጥላት ፡ መሰልቸት ። ትሰክሩ ፡ ምድር ፡ እምደምሙ ፡ ወትጠልቅ ፡ እምሥብሖሙ ። ሰቂራረ ፡ ክንክሙኒ ፡ ወጠለቅክሙ ፡ (ኢሳ ፴፬ ፡ ፯ ። ፩ ፡ ፯) ።

—፤ መጥለቅለቅ ፡ መቅለሽለሽ ፡ ልውጣ ፡ ልውጣ ፡ አውጡኝ ፡ አውጡኝ ፡ ማለት ፡ የምግብ ፡ አብዝቶ ፡ ከመብላት ፡ ከመጋፈፍ ፡ ወይም ፡ ከሆድ ፡ ማደፍ ፡ የተነሣ ። እስ ፡ ጠለቀት ፡ ነፍስከ ፡ እምኔሆሙ ፡ (ሕዝ፳፫ ፡ ፳፪ ፡ ፳፰) ። በጠለቀ ፡ ፈንታ ፡ አጥለቀ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ብልዑ ፡ ሥብሐ ፡ እስከ ፡ ያጠልቀክሙ ፡ (ሕዝ፴፱ ፡ ፲፱ ። ሆሴ፲፫ ፡ ፯) ። ፪ኛም ፡ በጠቀስ ፡ ፈንታ ፡ ጠለቀ ፡ ይላል ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ክፋ ፡ ፴፱) ።

(ጥለ) **ጠለቀ** ፤ (ዐረብ) ፤ ፈታ ፡ ለቀቀ ፡ ሰደደ ፡ አወጣ ፡ አሰጣ ፤ አሰናበተ ፡ የሚስት ፡ የገረድ ። በቁሙ ፡ ነከረ ፡ ጠቀሰ ፡ እጁን ፡ አገባ ፡ የወጥ ። ቀዳ ፡ ጨለፈ ፡ ደነበቀ ፤ የውሃ ፡ የመጠጥ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጥሉቅ** ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ልቅት) ፤ የጠለቀ ፡ ጥልቅ ፡ ጠሊቅ ፡ ስሙቅ ። ያደፈ ፡ የረከሰ ፤ እድፋም ፡ ጨምላቃ ፡ የሚያስጠይፍ ። አውገዝነ ፡ ፀዋጋተ ፡ ወጥሉቃተ ፡ ትምህርታት ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፱ ። ገድ ፡ አዳ) ።

**ጥልቀት** ፤ (ቃት) ፤ መጥለቅ ፡ ጥልቅነት ፤ ማደፍ ፡ አስተዳደፍ ። አደፍ ፡ እድፍ ፡ ጭቅቅት ፤ ርኵስ ፡ ኀጢአት ፤ ውሃና ፡ ንስሓ ፡ የሚያስፈልግ ። ንጹሕ ፡ እምጥልቀት ። እምዘሉ ፡ ጥልቀተ ፡ ኀጢአት ። ጥልቀት ፡ ዝሙት ። እንዘ ፡ አልቦ ፡ ጥልቀት ፡ (ቄድር ፡ ገጅና ፡ ፲፪ ። አርጋ ፡ ፯ ። ቅዳ) ።

**ጥላቄ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ መጥለቅ ፡ አጠላለቅ ፤ ጥልቂያ ፡ ጥልቆሽ ። እድፍ ፡ ጥላቂ ፡ ጭላፊ ። ጥላቄ ፡ ኀጢአት ። ወመልአ ፡ ጥላቄ ፡ ዘሎቱ ፤ ቀለም ፡ (ቄድር ፡ ገ፴፱ ። ጥበ፲፫ ፡ ፲፬) ።

**አጥለቀ** ፤ አጠለቀ ፤ አስጠለቀ ፤ የቀሚስ ፡ የሱሪ ። አጥለቀለቀ ፡ አሳደፈ ፡ አረከሰ ። ርኩሱ ፡ ሰብእሲ ፡ ቀታሊ ፡ ያጠልቆ ፡ (ምሳ፳፱ ፡ ፲) ።

**ጠሊስ ፤ ሶት** ፤ (ጠልሰ ፤ ጠለሰ ፡ ይጠልስ ፡ ይጥልስ) ፤ መጥለስ ፡ መጥፋት ፡ መጥቈር ፡ የእሳት ፡ የከሰል ። ክንፈት ፡ ይልቅ ፡ ለማር ፡ ለገለባ ፡ ይስማማል ።

**ጠለስ** ፤ በቁሙ ፤ ጥቍር ፡ ዐመድ ፤ ጥላት ፤ የማር ፡ የገለባ ፡ የቅጠል ፡ ሕመት ፤ ቀለም ፡ የሚኾን ። ጠለሸት ፡ የደን ፡ ውስጥ ፡ ጥላ ፤ ጨለማ ፡ (ዐማርኛ) ።

**አጥለሰ** ፤ አጠለሰ ፤ አጠቈረ ፡ አከሰለ ፤ አጠላ ፡ አጨለመ ።

**አጥላስ** ፤ (ሳት) ፤ በቁሙ ፤ ጥቍር ፡ የሐዘን ፡ ልብስ ፤ ከል ፡ እማለማሚ ፤ የጠለሰና ፡ የጥላ ፡ የጨለማ ፡ ዐይነት ።

**ጠልሰም** ፤ (ማት ፡፡ ዐረ ፡ ጢልሰም ፡፡ ጽር ፡ ቴሌስማ) ፤ በቁሙ ፤ ክታብ ፤ ጠንቋዮች ፤ በጥቍር ፡ ቀለም ፡ ጥፈው ፡ ጠልስመው ፡ የሚያሲዙት ፡፡ ክታብ ፡ አስማቱ ፡ ጠልሰም ፡ በያስማቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚጣል ፡ ሥዕልና ፡ ሐረግ ፡ ስንጠረዥ ፡ ሥሜሮሜር ፡ ጥፈት ፡ ነው ፡፡ ጠልሰማት ፡ (አቡሻ ፡ ፵፩) ፡፡ አቀሙ ፡ ጠልሰማተ ፡ ዘውእቱ ፡ ግልፎ ፡ ጣዖት ፡ (ግ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ፹፩) ፡፡

**ጠሊሳን** ፤ (ዐረ ፡ ጠይለሳን) ፤ ክቡር ፡ ልብስ ፤ ልብስ ፡ ተክህኖ ፡ ታላቅ ፡ መጎናጸፊያ ፡ ወይም ፡ ሞጣሕት ፡ ክህነ ፡ ባንገቱ ፡ በራሱ ፡ የሚያደርገው ፡፡ ወጠሊሳኑኒ ፡ ይኩን ፡ ጽዕድወ ፡፡ እትሜነይ ፡ ለስዲም ፡ ጠሊሳነ ፡ ጳውሎስ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፀ፩ ፡ ፭ ፡፡ ድጓ) ፡፡

—፤ የላይ ፡ ልብስ ፤ መጐናጸፊያ ፡፡ ጠሊሳነ ፡ ንጉሥ ፡ ሶቤሃ ፡ ከደና ፡ (ድጓ) ፡፡

**ጠመ** ፤ **ጠመ** ፤—**ዐጠፈ** ፤—**ጠዊም** ፡ **ጠመ** ፡፡

**ጢሜዎስ** ፤ (ጽር ፡ ቲሜዎስ ፡፡ ዕብ ፡ ጢማይ) ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ጠንባባ ፡ ዕዉር ፤ ዐይነ ፡ ስዉር ፡ (ማር ፲ ፡ ፵፮) ፡፡

**ጤሜን** ፤ (ጽር ፡ ቴሜኒ) ፤ መስጊድ ፤ ቤተ ፡ ጣዖት ፤ ምኵራብ ፡ ጣዖት ፡ (ሆሴዕ ፡ ፲፬) ፡፡

**ጠመነ** ፤ (ዕብ ፡ ጣማን) ፤ ደፈነ ፡ ቀበረ ፤ ሸፈነ ፡ ሰወረ ፡፡ ቀባ ፤ ለቀለቀ ፡፡ ጣመነ ፤ ተጠማኝ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ኹሉም ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ፡፡

**ጠመኔ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፤ በረቅ ፡ ነጭ ፡ ደንጊያ ፤ ዐፈር ፡ የኖራ ፡ ዐይነት ፡ ለቤት ፡ የሚቀባ ፡ የሚለቀለቅ ፡፡

**ጠሚዕ** ፤ **ዖት** ፤ (**ጠምዐ** ፡ **ይጠምዕ** ፡ **ይጥማዕ** ፡፡ **ዕብ** ፡ **ጥማዕ** ፤ **ሰጠመ** ፡፡ **ጣማእ** ፤ **ረከሰ**) ፤ መጥማት ፤ መንከር ፡ መዝፈቅ ፤ ማግባት ፡ ማጥለቅ ፤ ማሳደፍ ፡ ማርከስ ፡፡ ኢትጥምዖ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡፡ ውስተ ፡ ዙሉ ፡ ዘርኢከ ፡ ኢትጥማዕ ፡ እዴከ ፡፡ ትጠምዐኒ ፡ ውስተ ፡ ርስሐት ፡፡ ይጥማዕ ፡ ካህን ፡ አጽባዕቶ ፡ ውስተ ፡ ደም ፡፡ ጠምዖ ፡ ለቤት ፡ (ኤር ፲፫ ፡ ፩ ፡፡ ሢራ ፡ ፴፱ ፡ ፲፬ ፡፡ ኢዮ ፱ ፡ ፴፩ ፡፡ ዘሌ ፬ ፡ ፮ ፡፡ ሔኖ ፹ ፡ ፰፱) ፡፡

**ተጠምዐ** ፤ ተነከረ ፡ ተዘፈቀ ፤ ገባ ፡ ጠለቀ ፡፡ በከመ ፡ ይዴመር ፡ ሠርዩ ፡ ምስለ ፡ ፀምር ፡ ተጠሚያ ፡፡ አጽፋሪ ፡ እግርከ ፡ በደመ ፡ ቅንዋት ፡ እለ ፡ ተጠምዓ ፡፡ ለእመ ፡ ተጠምዐት ፡ ነፍስከ ፡ ውስተ ፡ ኀጢአት ፡ እኪት ፡ ትክውን ፡ ጸሎትከ ፡ ዘኢንጽሕት ፡ (ቄር ፡ እስት ፡፡ ፈልክ ፡ ፲፫፩) ፡፡

**ጥሙዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ምዕት) ፤ የተነከረ ፡ የተዘፈቀ ፤ ቀለም ፡ የገባ ፡፡ ጥሙዓን ፡ ደም ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ ፳፱) ፡፡

**ጥምዐት** ፤ (ታት) ፤ መንከር ፡ መነከር ፡ መዘፈቅ ፤ ቀለም ፡ መግባት ፡ እንክክር ፡ ቀለም ፡ እገባብ ፡፡ ጥምዐተ ፡ ሕበሪሁ ፡፡ ጥምዐታተ ፡ ሕብር ፡ (መሳ ፭ ፡ ፴ ፡፡ ሔኖ ፹ ፡ ፩) ፡፡

—፤ ቀለም ፤ የቀለም ፡ ዐይነት ፡ ሴቶች ፡ የሚቀቡት ፡ የሚለቀለቁት ፡፡ አንስት ፡ ኢይግበራ ፡ ላዕለ ፡ መላትሒሆን ፡ ጥምዐታተ ፡ ቀይሓተ ፡፡ ርቱዕ ፡ ለአንስት ፡ ይትገሐሡ ባ ፡ ርእሶን ፡ በንጹሕ ፡ ወእኩ ፡ በአሠንዮ ፡ ላሕየ ፡ ገጾን ፡ ወጥምዐታት ፡ ወተዘሐሎ ፡ ወተሰርግዎ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፸፬ ፡ ፭ ፡፡ ዲድ ፡ ፫) ፡፡

**መጠማ** ፤ ምጥማዕ ፡ መንከሪያ ፤ ጢቆሽ ፡ የውሃ ፡ መርጫ ፡ መፈንጠቂያ ፡፡ ንሣእ ፡ መጠማ ፡ ዘማይ ፡ ወንፋኅ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ (ፄርማ ፡ ፲፯፱) ፡፡

**ጠሚቅ** ፤ **ቆት** ፤ (**ጠመቀ** ፡ **ይጠምቅ** ፡ **ይጥምቅ** ፡፡ **ዕብ** ፡ **ጣባል**) ፤ መጥመቅ ፡ ማጥመቅ ፤ መንከር ፡ መዝፈቅ ፤ ከውሃ ፡ ማግባት ፡ በውሃ ፡ ማጠብ ፤ ወይም ፡ ውሃውን ፡ በራስ ፡ በገላ ፡ ላይ ፡ ማፍሰስ ፡ መቸለስ ፤ መርጨት ፡ ማረብረብ ፡፡ ጠሚቅ ፡ ትጠምቅ ፡ (ቀሌ) ፡፡ ብዙው ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጠመቀ ፡ ፈንታ ፡ አጥመቀ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡፡ አንሰ ፡ አጠምቀክሙ ፡ በማይ ፤ ውእቱሰ ፡ ያጠምቀክሙ ፡ በመንፈስ ፡፡ አጥመቀ ፡ አጽርቅተ ፡ ዘሠቀ ፡ ጽኍር ፡ ውስተ ፡ ብሒእ ፡፡ አጥመቃ ፡ ለምድር ፡ በማየ ፡ አይኅ ፡ (ማቴ ፫ ፡ ፲፩ ፡፡ ስንክ ፡ ኅሐ ፭ ፡፡ መቃ ፡ ፹፯) ፡፡

—፤ መዘለል ፡ መብጥበጥ ፤ ከውሃ ፡ ማዋሐድ ፡ ማሰማማት ፤ የድፍድፍ ፡ የማር ፡ የጠላ ፡ የጠጅ ፡፡ ጠላ ፡ ጠማቂ ፡ እንዲሉ ፡፡ ጸመቀን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ፡፡

**ጠማቂ** ፤ **መጥምቅ** ፤ በቁሙ ፡ የሚጠምቅ ፡ የሚያጠምቅ ፤ አጥማቂ ፡፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡፡ ሐናንያ ፡ ለጳውሎስ ፡ መጥምቁ ፡ (ማቴ ፫ ፡ ፩ ፡፡ ስንክ ፡ ጥቅ ፱) ፡፡

**መጥምቃዊ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ያጥማቂ ፡ የጠማቂ ፡ ወገን ፤ አጥማቂነት ፡ ያለው ፡፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቃዊ ፡ (ፈልክ ፡ ፲፪፱) ፡፡

**አጥመቀ** ፤ አስጠመቀ ፡ አስነከረ ፡፡ ሰብ ፡ ተወልደ ፡ ሕፃን ፡ ጥዑየ ፡ ይትዐገሡ ፡ አጥምቆቶ ፡፡ እናት ፡ አባቱ ፡ ርቱን ፡ ከማስጠመቅ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፯) ፡፡ ለካህናት ፡ ግን ፤ ጠሚቅሁ ፡ ጠሚቆቶ ፡ እንጂ ፤ አጥምቆቶ ፡ አያሰኝም ፡፡

**አጥማቂ** ፤ **መጥምቅ** ፤ የሚያስጠምቅ ፤ አስጠማቂ ፡፡ መጥምቅ ፡ ከጠመቀና ፡ ከአጥመቀ ፡ ከኹለቱ ፡ አሶማይ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፤ ሌላውም ፡ መሰም ፡ እንዲህ ፡ እንደወጣ ፡ እስተውል ፡፡

**ምጥማቅ** ፤ (ቃት) ፤ መጥመቂያ ፡ ማጥመቂያ ፤ መጠመቂያ ፡ መታጠቢያ ፤ ቦታ ፡፡ ቤተ ፡ ምጥማቅ ፡፡ ቀፀሜማ ፡ ዘደብረ ፡ ምጥማቅ ፡፡ ወረደ ፡ ወልድ ፡ እምሰማያት ፡ ውስተ ፡ ምጥማቃት ፡፡ በኀበ ፡ ምጥማቃት ፡ እንተ ፡ ላዕላይ ፡ ፍኖት ፡፡ ምጥማቃተ ፡ ሰሊሖም ፡ (ኪዳ ፡፡ ድጓ ፡፡ ኢሳ ፯ ፡ ፫ ፡፡ ዮሐ ፱ ፡ ፯) ፡፡

**ተጠምቀ** ፤ ተጠመቀ ፤ ተነከረ ፤ ታጠበ ፡ ተጣጠበ ፡ በገላ ፡ እጁ ፤ ወይም ፡ በሰው ፡ እጅ ፤ ስርየት ፡ ልጅነት ፡ ለማግኘት ፡፡ ሖር ፡ ተጠመቅ ፡ ውስተ ፡ ተከዜ ፡

ዮርዳኖስ ። ትጠፀእ ፡ በሌሊት ፡ ወትጠመቅ ፡ ውስተ ፡ ነቅዐ ፡ ማይ ። ወተጠምቀ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ዐዘቅት ፡ ዘናጥራን ። ተጠምቀ ፡ ህየ ፡ በማይ ፡ (፬ነገ ፡ ፭ ፡ ፲ ፡ ፲፬ ። ዮዲ ፲፪ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፲፫ ። ኅዳ ፲፭) ። ወእም ድኅረ ፡ ተጠምቀ ፡ ሕዝብ ፡ ተጠምቀ ፡ ኢየሱስኒ ። አኮ ፡ ፈቂዶ ፡ ሊተጠምቆ ፤ አላ ፡ ጽሒቀ ፡ ይብርህ ፡ ማ ዮተ ፡ ወይኅይል ፡ መካናተ ፡ ለእለ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይጠ መቁ ፡ ውስቴቱ ። ወተጠሚቆ ፡ ወፅአ ፡ እማይ ። እለ ፡ ተጠመቅነ ፡ በእግዚእነ ፡ ውስተ ፡ ሞቱ ። ተጠ መቅነ ፡ በስሚነ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅ ዱስ ፡ (ሉቃ ፫ ፡ ፳፩ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ባዊ ። ተረ ፡ ቄርሎ ። ማቴ ፫ ፡ ፲፮ ። ሮሜ ፮ ፡ ፫ ። ቀሌ) ።

**ጥሙቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ምቅት) ፤** የተጠ መቀ ፡ ክርስትና ፡ ጥምቀት ፡ ያለው ፡ ፍጹም ፡ ክርስቲ ያን ። እንዘ ፡ ሀሉ ፡ በገዳም ፡ እመሂ ፡ ጥሙቅ ፤ እው ፡ ንኡስ ፡ ክርስቲያን ። እለ ፡ ጥሙቃን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፫ ። ቀሌ) ።

**ጥምቀት ፤ (ቃት) ፤** በቁሙ ፡ ማጥመቅ ፡ መ ጠመቅ ፤ አጠማመቅ ፡ ጠመቃ ፤ የማጥመቅና ፡ የመጠ መቅ ፡ ሥራ ፡ ኀሰቢት ፡ በጥሩ ፡ ውሃ ፡ የሚፈጸም ። የበ ዓል ፡ ስም ፤ ጌታችን ፡ የተጠመቀበት ፡ ቀን ። (ተረት) ፤ ለጥምቀት ፡ ያልኾነ ፡ ቀሚስ ፡ ይበጣጠስ ። ጥምቀታት ፤ ዘዘ ፡ ዚኣሁ ። በእንተ ፡ ሥርዐተ ፡ ጥምቀት ፤ ውሉድ ፤ እለ ፡ ሞቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ጥምቀት ። ጥምቀት ፡ ዘዳ ግም ፡ ልደት ። ቅዱስ ፡ ጥምቀት ። እምድኅረ ፡ ነ ሥአ ፡ ጥምቀተ ። ስመ ፡ ጥምቀትየ ። ንፅበ ፡ በማየ ፡ ጥምቀት ፡ (ዕብ ፮ ፡ ፲ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፭ ። ዲድ ፡ ፴ ። ቢዳ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ጥር ፲፭ ። ኑሐ ፱) ።



ጥምቀት ፡

## ጠማር ፤—ክታብ ፤—ጠወማር ።

**ጠኒን ፤ ኖት ፤ (ጠነ ፡ ይጠንን ፡ ይጥ ንን ። ዕብ ፡ ጣናን) ፤** መርጠብ ፡ መራስ ፤ ርጥብ ፡ መኾን ፡ መታደስ ። ጠጥናት ፡ መጠንከር ፤ ማየል ፡ መበ ርታት ፤ እያደገና ፡ ኀይል ፡ እየጨመሩ ፡ መኼድ ፤ የሕዋ ሳትና ፡ የዕፀዋት ። ጠለየን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ጥን ፤ (ብ ፡ አጥናን) ፤** ርጥብ ፡ ስጋ ፡ ወጣት ። ጥኑ ፡ ጠንካራ ፡ ኀይለኛ ፡ ጉበዝ ። ወገብረ ፡ ኀይለ ፡ ዘ አጥናን ፡ (፩ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፵፰) ። ዘአጥናን ፡ ትርፍ ፡ ንባብ ፡ ነው ፤ ከማእገዘ ፡ በቀር ፡ በጽርኢም ፡ በዕብራይስጡም ፡ አይገኝ ።

**እጥናን ፤** ቅድስት ፡ ሥላሴ ፤ ወይም ፡ ስባቱ ፡ ሀብታት ፡ (ኢሳ ፲፩ ፡ ፪) ። በኀይለ ፡ እጥናን ፡ ዘሞኦ ፡ ለሰይጣን ። ኀይልከ ፡ ኀይለ ፡ እጥናን ። ኀይል ፡ ዘእ ጥናን ፡ (ድጓ ። ስንክ ፡ ኅዳ ፳፫ ። አርጋ ፡ ፯) ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፤ ትጋት ፡ ትጉህነት ፡ ሙቀት ፤ መንፈሳዊ ፡ ቅንአት ፡ ይሉታል ፤ ምስጢሩ ፡ ከሀብታት ፡ ይገባል ።

**ጠነይ ፤** ጥሻ ፡ ጉሬ ፡ ባሕር ፡ ኵሬ ፡ ወይም ፡ ደሴት ፡ የባሕር ፡ ጎሬ ። ጣና ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ምስጢሩ ፡ ባሕርነትና ፡ ርጥበት ፡ ነው ፤ አፈትም ፡ ያሳ ያል ። ቦአ ፡ ጠነየ ፡ ወኢረከበ ፡ (አዋል) ። ዲልማን ፡ ግን ፡ ጎሠሠ ፡ ብሎታል ።

**ጥንፍ ፤ (ብ ፡ ጥንፍ ። ጽንፍ ፡ ጽነፍ ፤ ጸነፈ ። ዐረ ፡ ጠንፍ ፤ ጡንፍ ፤ የቤት ፡ አፍ ኢዊ ፡ ክፍል) ፤** የዐምድ ፡ ክባስ ፤ የባላና ፡ የወጋግራ ፡ ራስ ፤ ዘንድ ፡ ጋድም ፤ የድንኳን ፡ ዘንግ ፡ መሎጊያ ፡ ተራ ዶችን ፡ እንደ ፡ ዋልታና ፡ እንደ ፡ ጋድም ፡ ኹኖ ፡ የሚያ ያይዝና ፡ የሚያጠና ። በስተላይ ፡ ለሚኾን ፡ ለሥራ ፡ ጌጥ ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። ጠንፉ ፡ የሚሉት ፡ ስም ፡ ከዚህ ፡ ወጥ ቷል ፤ ዘሩ ፡ ጸነፍ ፡ ነው ። ጥንፌሁ ፡ ዘብሩር ፤ ጥንፌሁ ፡ ለዐምድ ፡ (ዘፀ ፳፯ ፡ ፲ ፡ ፲፩) ።

**እጥነፈ ፤** አያያዘ ፤ አዋደደ ። ወቃጠንፎ ፡ በ ጥንፍ ፡ (ዘፀ ፴ ፡ ፬) ።

**ጥንፍሕ ፤ አው ፡ ጥፍንሕ ፤ (ጸነፈ ፡ ጸፈነ) ፤** ሸውራራ ፤ ጨፍና ፤ ጨንቋራ ፡ ፅምልጨላ ፤ ዐይ ኑና ፡ አስተያየቱ ፡ የማያምር ። አዕይንቲሁ ፡ በአምሳለ ፡ ጥንፍሕ ፡ (ቄስጠ ፡ ፯) ። ባ፲ኛው ፡ ደማሞ ፡ ጥፍንሕ ፡ ይላል ።

**ጠንቈለ ፤ (ጠቀለ) ፤** ጠንቈለ ፤ ጠንቀለ ፤ በ ማር ፡ በሥንጥር ፡ በጣት ፡ ነካ ፡ ጠቈመ ። መጠንቈል ፡ መጣፍን ፡ ገልጦ ፡ ስንጠረዥን ፡ በማር ፡ እየወጉ ፡ ቍጥ ሩን ፡ ከስጠንቋዩ ፡ ስም ፡ አስማምቶ ፡ የንባቡን ፡ ነገር ፡ መፈለግ ፡ ነው ። ሥራይ ፡ ወጠንቍሎ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫) ። መጠንቀል ፡ ግን ፡ በጥቂቱ ፡ ለሚላስና ፡ ለሚቀመስ ፡ ለሚ ሸተት ፡ ነው ። (ተረት) ፡ አባርፍ ፡ ያለች ፡ ጣት ፡ ዐር ፡ ጠ ንቅላ ፡ መጣች ። ተንከለ ፤ ተንኰል ፡ ሠራ ፡ ተንኰለኛ ፡ ኾነ ። ጠና ፡ ተ ፡ ይዋረሳሉ ፤ ውስጠ ፡ ውስጥ ።

**ጠንቋሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ቈልት) ፤** የሚጠነቍል ፡ ጠንቋይ ፡ ሟርተኛ ፤ መጻእያትን ፡ የሚና ገር ፡ ሥጋዊና ፡ ሰይጣናዊ ፡ ነቢይ ፤ ተንኰለኛ ። ኵሉ ፡ ዘተለወ ፡ ማሪተ ፡ ወጠንቋሌ ። ዘየአምን ፡ ነገረ ፡ ጠንቋልያን ፡ ወመሠርያን ። እይቴ ፡ ሀለዉ ፡ ርኩ ሳን ፤ ዘማውያን ፡ ወጠንቋልያን ። ጠንቈልት ፡ (ቄ ድር ፡ ገ፳፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፭ ፡ ፳፫ ። ግንዘ ። ገድ ፡ አዳ ፡ ገ፲፱) ።

**መጠንቍል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ። እመሂ ፡ ዘያጠፋ ፤ እመሂ ፡ መጠንቍል ፤ እመሂ ፡ ዘማዊ ፡ ወሐሳዊ ፡ (ቄድር ፡ ገ፳፯) ።

**ጥንቋሌ ፤** መጠንቈል ፡ አጠንቋቈል ፤ ሟርት ፡ ጥንቈላ ፤ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**ጠንቀቀ፤(ጠቀቀ)፤** ጠነቀቀ ፡ አስተዋለ ፡ አስተካከለ ፡ ልክ ፡ አደረገ ፤ መላ ፡ ፈጸመ ፡ ጨረሰ ፡ የግ ብር ፡ የነገር ፡ የስፍር ፡ የቍጥር ። ኢጠንቀቀ ፤ ዐቂቦቶ ። ዘትወክፊ ፤ ህተ ፡ መጽሐፊ ፤ ወጠንቀቃ ። ወመጠነ ፤ ርሕበ ፤ ሐንጻ ፤ ወጠንቀቀ ፤ በኀሰተ ። ዘጠንቀቀ ፤ ኅምሳ ፤ ዓመተ ። ኢይደሉ ፤ አውስቦ ፤ ብእሲተ ፤ ዘኢ ጠንቀቀት ፤ ዐሠርተ ፤ አውራኀ ፤ እምድኅረ ፤ ሞተ ፤ ምታ ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፫ ። መጽ ፡ ጠማ ። ሕዝ፵ ፡ ፭ ፡ ፮ ። ዲድ ፡ ፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፭ ፡ ፲፮) ። በጠንቀቀ ፡ ፈንታ ፡ አጠንቀቀ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ሁሉ ፤ ምክሩ ፤ ዘከመ ፤ ያጠንቅቅ ፤ ኅሪወ ፤ ማኅተም ። አጠንቀቀ ፤ ነገረ ፤ (ሚ.ራ፴፰ ፡ ፳፮ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ጠንቃቂ፤(ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት)፤** በቁሙ ፡ የሚጠነቅቅ ፡ የሚያሳምር ፡ አስተዋይ ፡ ተመልካች ። ማእ ምር ፤ ወጠቢብ ፤ ወልብው ፤ ወጠንቃቂ ፤ መዲሕ ፍት ፤ (ዮሴፍ) ።

**አጠንቀቀ** ፤ አስጠነቀቀ ፡ አስለበመ ፤ ሠራን ፡ በሥራ ፡ ላይ ።

**አስተጠንቀቀ** ፤ ገቢ ፡ ከማሁ ። አስተጠን ቀቀ ፤ ለጦቱ ፤ ወነገሮ ፤ ዘከመ ፤ ይገብሩ ፤ (ቀሌ) ።

**ተጠንቀቀ** ፤ ተጠነቀቀ ፤ ሥራው ፡ ወይም ፡ ሠሪው ። ሰበሰ ፤ ኢተዐውቀት ፤ ወኢተጠንቀቀት ፤ ዛቲ ። ዝንቱ ፤ ተጠንቀቀ ፤ በብዙኃ ፤ ቀዋናት ፤ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፩ ፡ ፲ ። ፵፩ ፡ ፱) ።

**ተጠናቀቀ** ፤ ተራቀቀ ፡ መራቀቅ ፡ አበዛ ። ሀ ለወ ፤ ዘይጠቢብ ፤ ወይጠናቀቅ ፤ እንዘ ፤ ይጌምፅ ። ተጠናቀቀ ፤ ለገቢረ ፤ አምሳሉ ፤ በዘይሤኒ ፤ ወይኄ ይስ ። በተጠናቅቆ ፤ (ሚ.ራ፲፱ ፡ ፳፰ ። ጥበ፲፱ ፡ ፲፱ ። ቀሌ) ።

**ጥንቁቅ፤(ቃን ፡ ቃት ፡ ቅቅት)፤** በቁሙ ፤ የተጠነቀቀ ፡ ጠንቃቃ ፤ ፍጹም ። ጥንቁቅ ፤ ውስቴታ ። ጥንቁቅ ፤ በርእሱ ። ጼናከሙ ፤ ጥንቁቅ ፤ (ዮሴፍ ። ቁር ፡ ጸላ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳) ።

**ጥንቁቀ** ፤ ፈጽሞ ፡ ጠንቅቆ ፡ ጠንቃቃ ፡ ኹኖ ፤ በጥንቃቄ ፡ በሩቁራሽ ። መኑ ፤ ይክል ፤ ነጊረ ፤ ምሕረቱ ፤ ጥንቁቀ ፤ (ሚ.ራ፲፰ ፡ ፭) ።

**ጥንቃቄ** ፤ በቁሙ ፤ (ላጥጠ) መጠንቀቅ ፤ አጠ ንቃቀቅ ፡ ጥንቀቃ ፤ ጠንቃቅነት ። በጥንቃቄ ፤ ንኀሥሥ ። ይንግር ፤ ድዉይ ፤ ኅጣውኢሁ ፤ ለካህን ፤ በጥን ቃቄ ። ፈጠረ ፤ ሰማየ ፤ በጥንቃቄ ፤ (ቁር ፡ ጸላ ። ቂድር ፡ ገፀ፱ ። ደራሲ) ።

**ጥንቅቅና** ፤ ጥንቁቅነት ፤ ጠንቃቅነት ፤ ጥን ቁቅ ፡ ጠንቃቃ ፡ መኾን ፤ መተካከል ። እስመ ፤ ሁሉ ፤ ምሳሌ ፤ ዘበዝንቱ ፤ ይደክም ፤ እምጥንቅቅና ፤ ወይ ውኅድ ፤ እምአማን ፤ (ቁር ፡ ጸላ) ።

**አስተጠናቀቀ** ፤ አጠናቀቀ ፤ አራቀቀ ፤ አታጋ ጠባዩ ፡ ማደራረግና ፡ ማስደረግ ፡ ነው ፤ ባስደራጊነቱ ፡ ከአ ጠንቀቀና ፡ ከአስተጠንቀቀ ፡ ይስማማል ፤ ተደራራጊነቱ ፡ ግብራት ፡ ሕዋሳት ፡ ሲኾኑ ፡ ምስጢሩ ፡ ከማድረግና ፡ ከማስደረግ ፡ ከኹለቱ ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ። ፈድፋደ ፤ ናስ ተጠናቅቅ ፤ ኅሊናነ ፤ አልቦ ፤ ዘይክል ፤ አስተጠናቅቆ ። ያስተጠናቅቁነ ፤ ለገቢረ ፤ ሠናይ ፤ (ቁር ፡ ጸላ ። ቀሌ) ።

**ጥንቃቅ፤(ቃት)፤** የተራራ ፡ ሥር ፡ መሠ ረት ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ቁላ ፡ ማለምቅት ፡ ሰርጥ ፡ ምሽግ ፡ መቀራቅርት ። ናሁ ፤ ርእስየ ፤ ውስተ ፤ ጥንቃ ቃተ ፤ ደብር ። ፈቀደ ፤ ከመ ፤ ይጤዝ ፤ ሾሎ ፤ ነፍሳተ ፤ እለ ፤ ሙቁሓን ፤ ንበ ፤ ጽልመተ ፤ ሞት ፤ ወጥንቃቃተ ፤ ሲኦል ፤ (ዮና፪ ፡ ፯ ። መቅ ፡ ወን) ።

**ጥንቁር ፤ (ራት ። ነቍር ፡ ነቁረ) ፤** ጭንቁር ፡ የቍስል ፡ ስም ፡ ፩ ፡ ዐይነት ፡ ቍስል ፡ በሺዋ ፡ ሻሕኝ ፡ በሰብራይስጥ ፡ ሽሒን ፡ ይባላል ፤ (ዘፀ፱ ፡ ፱ ፡ ፲) ።

—፤ ያይጥ ፡ ወገን ፡ ጉርጥ ፤ ዐይጠ ፡ መጉጥ ፡ አፈ ፡ ሹል ፡ ጥርስ ፡ ስል ፡ ባፉ ፡ የሚያንቍር ፡ ያሚሸንቍር ። ከመ ፤ ኢይርከቦሙ ፤ አንጼዋ ፤ አው ፤ ጥንቁር ፤ (ቂድር) ።

**ጥንት ፤—በቁሙ ፤—ወጢን ፤ ወጠነ ።**

**ጥንትዮን ፤—አበቅቴ ፡ ፀሓይ ፤—ጥን ትዮን ፡ ፐ ።**

**ጥዒው ፤ ዎት ፤ (ጠዐወ ፡ ይጥዑ ፡ ይ ጥዐው ። ዕብ ፡ ጣዓህ ። ሱር ፡ ጥዓእ ። ዐረ ፡ ጠዓ)** ፤ መሳት ፡ መሳሳት ፤ ከመንገድ ፡ መውጣት ፤ ጣ ያት ፡ ማምለክ ፡ መቅረጽ ፡ መሥራት ። ክልኩ ፡ ያለፈ ፡ ዝሙትና ፡ ፍቅረ ፡ ንዋይም ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ይባላል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጠዐወ ፡ ፈንታ ፡ አጥዐወ ፡ ይላል ። ዘያበግል ፤ ወያጥዑ ፤ አጥዕዎ ፤ (ሲኖዶ) ። ፪ኛም ፡ በባረክ ፡ ቤት ፡ ጣዕም ፡ ጣዐወ ፡ ይጣዑ ፡ ይላልና ፤ ይህ ንን ፡ ደግሞ ፡ አጣዐወ ፡ ያጣዑ ፡ እያለ ፡ ባስደራጊ ፡ አን ቀጽ ፡ ይጥፋል ። እለ ፤ ያጣዕዉ ፤ በከርሥ ። አጣዕዎ ፤ ወሥራይ ። ይመርሕ ፤ ውስተ ፤ አጣዕዎ ፤ ኢታስግሉ ፤ ወኢታጣዕዉ ፤ (፪ዜና ፡ ፴፫ ፡ ፮ ። ገላ፭ ፡ ፳ ። ዲድ ፡ ፴፭) ።

**ጠዓዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ የሳተ ፡ የ ሚስት ፤ መምለኪ ፡ ጣዖት ። ጠዓውያን ፤ (ቀሌ) ።


**መጥዕው ፤ መጣዕው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ዐት)** ፤ ገቢ ፡ ከማሁ ። መጣዕዋን ፤ (ዲድ) ።

**መጥዐዊ** ፤ ገቢ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ። መጥዐዊ ፤ ወመጸብሓዊ ። አረሚ ፤ መጥዐውያን ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፭ ። ቅዳ ፡ ሕር) ። በመጣዕውና ፡ በመጥዐዊ ፡ ፈንታ ፡ መጠ ዓዊ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። (ቀሌ) ።

**ጣዕዋ ፤ (ዋት)** ፤ ጥጃ ፡ እንቦሳ ፡ ውርንጫ ፡ ግልገል ። ከመ ፤ ጣዕዋ ፤ ዘተፈትሐ ፤ እማእሰሩ ። ጣ ዕዋ ፤ ላሕም ፤ ወፈረስ ፤ ወአድግ ፤ ወገመል ። ኢታብ ስል ፤ ጣዕዋ ፤ በሐሊበ ፤ እሙ ፤ (ሚል፬ ፡ ፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵ ። ዘፀ፳፫ ፡ ፲፱) ።

—፤ ወይፈን ፡ ጊደር ። ጣዕዋ ፤ እምአልሕምት ። ጣ ዕዋ ፤ ዘሠለስቱ ፤ ዓመት ። ጣዕዋ ፤ አንስቲያዊት ። እ ልኩ ፤ ጣዕዋት ፤ ወአልሕምት ። በግዐ ፤ ንጹሐ ፤ ወ ልደ ፤ ቅድስት ፤ ጣዕዋ ፤ (ኩፋ፳ ፡ ፲፱ ። ሑሞ፻፭ ፡ ፫ ። ቄ፯ ፡ ፫ ። አርጋ) ።

**ጣዖት ፤ (ታት ። ዕብ ፡ ጣዑት)** ፤ ስሕተት ፡ የስሕተት ፡ ሥራ ። በቁሙ ፤ ግልፎ ፤ ስብኮ ፤ የጥጃ ፡ የን ፀሳ ፡ የሰው ፡ የንስሳ ፡ ምስል ፤ ስሒታን ፡ ሰዎች ፡ የሚያ መልኩት ። ገብረ ፡ ጣዖተ ። ቤተ ፡ ጣዖት ። ድኩም ፡ ወጽኑስ ፡ ጣዖተ ፡ ዝ ፡ ዓሰም ። ከመ ፡ ይሕንጽ ፡ ምሥዋዖ ፡ ወይሥርዖሙ ፡ ለጣዖታት ፡ (ኩፋ ፡ ፲፳ ። ፲፪ ። ገላ፬ ፡ ፱ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ።



ጣዖት ፡

**አጥዐወ ፤ አጣዐወ** ፤ አሳተ ፡ አሳሳተ ፤ ጣዖት ፡ አስመሰከ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ እድራጊነት ፡ ነው ። እመ ፡ ቦ ፡ እምእኅው ፡ ዘያጥዑ ። እለ ፡ ያስግሉ ፡ ወእለ ፡ ያጣዕዉ ። ተምዐ ፡ መንፈሱ ፡ ሶበ ፡ ርእየ ፡ ያጣዕዉ ፡ ኵሉ ፡ ሀገር ፡ (ሺቁሮ ፡ ፳ ፡ ፲፰ ። ቀሌ ። ግብ፲፯ ፡ ፲፮) ።

**አጥዓዊ ፤ መጥዐዊ ፤ መጥዕው ፤ መጣዕው)** ፤ የሚያስት ፡ አሳች ፤ ጣዖት ፡ አስመሳኪ ። ከአጥዓዊ ፡ በቀር ፡ ሦስቱ ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ባድራጊነትም ፡ ይፈታል ።

**ጣዕጥዐ ፤—ጠረገ ፤—ጣእጥአ ፡ ጣእጥአ ።**

**ጥዕየ ፤ ዮት ፤ (ጥዕየ ፡ ይጥዒ ፡ ይጥዐይ)** ፤ መጤን ፤ ጤና ፡ ማግኘት ፡ መሻር ፤ መፈወስ ፡ መዳን ፤ ጤናማ ፡ ባለጤና ፡ መኾን ። ለጥዕይ ፡ ከመ ፡ ይጥዐይ ፡ ኵሉ ፡ ዘይሠርጽ ፡ ወይልህቅ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ኢይጥዒ ፡ ቍስልየ ። ሶበ ፡ ትጥዒ ፡ እምሕማምከ ። እስከ ፡ ይጥዒ ፡ ወይትፈወስ ፡ (ኩፋ ፡ ፱ ። ኢዮ ፲፮ ፡ ፮ ። አፈ ፡ ተ፲፯ ። ዮሴፍ) ።

**ጥዑይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ዒት)** ፤ የጤነ ፤ ጤና ፡ ያገኘ ፡ ጤነኛ ፤ ጤናማ ፡ ባለጤና ፤ ታሞ ፡ የዳነ ፡ ወይም ፡ ያልታመመ ፡ ደኅና ፤ ነዳይ ፡ ጥዑይ ። ወአኮ ፡ ጥዑያን ። አዕይንት ፡ ጥዑያት ፡ (ሢራ፴ ፡ ፲፬ ። ማቴ፱ ፡ ፲፪ ። አፈ ፡ ተ፲፯) ።

**ጥዑየ** ፤ ድኖ ፡ ጤና ፡ አግኝቶ ፤ ባለጤና ፡ ኹኖ ፤ በጤና ፡ በሰላም ። ትሰፍሕ ፡ ጥዒታ ። ውሉድ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ ጥዑያኒሆሙ ። ዖመ ፡ ጥዑየ ፡ ወሰከበ ፡ ሐዋዘ ፡ (ጥዑሳ ፡ ፰ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ኅዳ፯) ።

**ጥዕየት** ፤ መዳን ፡ ጤና ፡ ማግኘት ፤ ባለጤናነት ።

**ጥዒና ፤ (ናት)** ፤ በቁሙ ፤ ጤና ፡ ደኅንነት ፡ የሕዋሳት ፡ ሰላም ፡ የምግባቦና ፡ የሆድ ፡ መስማማት ፤ ከርጎ ፡ ብስና ፡ የጕመን ፡ ጤና ፡ እንዲሉ ። ሠረቀ ፡ ፀሓይ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ለጥዒና ። ለጥዒና ፡ አዘማድየ ። እምቅድመ ፡ ይርከብ ፡ ፍጻሜ ፡ ጥዒና ። ዕቀብ ፡ በሰላም ፡ ወበጥዒና ፡ (ኩፋ ፡ ፱ ። ዮሴፍ ። አፈ ፡ ተ፳፱ ። ቅዳ) ።

**አጥዐየ** ፤ አጤነ ፡ ልብ ፡ አደረገ ፡ ፀበበ ፡ አሰቀ ዋሰ ፡ (ዐማርኛ) ። አዳነ ፡ አሻረ ፡ ፈወሰ ፡ ጤነኛ ፡ አደረገ ። አጥዕየ ፡ መፃጉዐ ። ፈውሳት ፡ እለ ፡ ያጥዕያ ፡ ቍስላተ ። ዝንቱ ፡ ደዌ ፡ ይከውን ፡ ዕጹበ ፡ ፈውሶቱ ፡ ወአጥዕዮቱ ። ሕጸጺ ፡ ቅንአት ፡ ያጥዒ ፡ ሥጋ ፡ (ማኅሃ ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ፈላስ) ።

**አጥዓዪ ፤ መጥዐዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት)** ፤ የሚያሽር ፡ አዳኝ ፤ ፈዋሽ ።

**መጥዕይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ዒት)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ።

**ምጥዓይ ፤ (ያት)** ፤ መዳኛ ፡ ጤና ፡ ማግኛ ፡ መፈወሻ ፤ ፀታ ፡ መድኀኒት ፡ ምክንያት ።

**ጥዒም ፤ ሞት ፤ (ጥዕመ ፤ ጠዐመ ፡ ይጥዕም ፡ ይጥዐም ። ዕብ ፡ ጣዐም ። ሱር ፡ ጥዔም ። ዐረ ፡ ጠዒመ)** ፤ መቅመስ ፡ መሞከር ፤ ማጣጣም ፡ ከጣዕም ፡ መድረስ ፤ ጣዕም ፡ ማወቅ ። ኢይክል ፡ ጥዒመ ፡ መብልዐ ። ዘእንበለ ፡ እጥዐም ፡ እክለ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘጥዕመ ፡ ወኢውዓጠ ። ጥዕም ፡ ለሞት ። ወጥዒሞ ፡ አበየ ፡ ሰትየ ። ጥዕመት ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ ተቀንየ ፡ (ኢዮ፴፫ ፡ ፳ ። ጦቢ፪ ፡ ፬ ። ቀሌ ። ዕብ፪ ፡ ፱ ። ማቴ፳፯ ፡ ፴፬ ። ምሳ፴፩ ፡ ፲፰) ።

—፤ መጣም ፡ መጣፈጥ ፤ ጥፍጥ ፡ መኾን ፤ ደስ ፡ ማሰኘት ። ምንት ፡ ይጥዕም ፡ እመዓር ። አልቦ ፡ ዘይጥዕም ፡ እምነ ፡ ዐቂበ ፡ ትእዛዙ ፡ ለእግዚ ። ቦ ፡ እክል ፡ ዘይጥዕም ፡ እምእክል ። ለዘማዊ ፡ ኵሉ ፡ እክል ፡ ይጥዕሞ ። ጥዕመ ፡ መዐዛየ ። ይጥዕም ፡ እመዓር ፡ ዝክርየ ። ይጥዕሞሙ ፡ ንዋም ። ጥዕመት ፡ እኪት ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ (መሳ፲፬ ፡ ፲፰ ። ሢራ ፡ ፳፫ ፡ ፳፮ ፡ ፴፮ ። ፳፫ ፡ ፳፪ ፡ ፲፯ ። ፳፬ ፡ ፲፰ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ድ፳፬ ። ኢዮ፳ ፡ ፲፪) ።

**አጥዐመ** ፤ አበላ ፡ አቀመሰ ፡ አስበላ ፡ አስቀመሰ ። አጥዐመ ፡ ሥጋ ፡ ለአኅው ። ወአጥዐሞ ፡ ሞተ ። እግዚ ፡ አጥዐሞሙ ፡ በከመ ፡ አጥዐሙ ፡ ለሰብእ ፡ ረኃበ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፶፯ ። ቀር ፡ ድ፳፬ ። ዮሴፍ) ።

—፤ አጣመ ፡ አጣፈጠ ፡ ጣፋጭ ፡ አደረገ ። ጼው ፡ ዘአጥዐም ፡ ለልሱሕ ። አጥዕሙ ፡ መዐዛክሙ ። አጥዕማ ፡ ለማሕሌትየ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ ኵሉ ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ ። ሢራ ፡ ፴፱ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ ታኅ፲) ።

**አስተጥዐመ ፤ አስተጠዐመ ፤ (ያስተጥዕም)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ አጣፈጠ ፡ አሰናዳ ፡ አደነቀ ። ዘዓቡረ ፡ አስተጠዐምከ ፡ ሌተ ፡ መበልዐተ ። በክናፍሪሁ ፡ ያስተጥዕም ፡ ለከ ፡ ቃሎ ። እመ ፡ አስተጠዐምከ ፡ ሎቱ ፡ ምግባሮ ፡ ቀተልኮ ፡ ለእኍከ ። ሥጋ ፡ ያስተጥዕም ፡ ለነፍስ ፡ ምግባረ ፡ ሕሡመ ፡ (መዝ ፡ ፶፬ ። ሢራ፲፪ ፡ ፲፯ ። ዲዮ ፡ ፯ ። ዮሴፍ) ።

—፤ ደስ ፡ ፊቅ ፡ አሰኘ ፡ አስጕመዠ ። ሰይጣን ፡ ያስተጥዕም ፡ ሎሙ ፡ በኅዳጥ ፡ ወይኬንን ፡ ሎሙ ፡ በብዙኅ ፡ (ቀሌ) ።

**ተጥዕመ** ፤ ተቀመሰ ፤ ተጣፈጠ ።

**ጥዑም** ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ዕምት) ፤ የተቀመሰ ፤ የተጣፈጠ ። በቁሙ ፤ የጣመ ፡ የጣፈጠ ፡ ጥፍጥ ፤ ውብ ፡ መልካም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ። መዓር ፡ ጥዑም ። ልሳን ፡ ጥዑም ። ጥዑማን ፡ ዜና ፡ ወዝክር ። ብልዑ ፡ ወስተዩ ፡ ጥዑማተ ። ጥዕምት ፡ በቃላ ፡ (ሕዝ፫ ፡ ፫ ። ሚሬ፮ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ መስ፲፪ ። ኑሐ፳ ፡ ፲ ። ድጓ) ።

**ጥዕመት** ፤ መቅመስ ፡ መቀመስ ፡ አቀማመስ ፡ ቀመሳ ፡ ቅምሻ ። መጣም ፡ መጣፈጥ ፡ አጠፋፈጥ ፤ ጣዕም ፡ ጥፍጥንት ። ወሀበት ፡ ፍተታተ ፡ በረከት ፡ እምኔ ፡ አውሎግያ ፤ ወሰበ ፡ በልዓ ፡ ኮነ ፡ ጥዕመታ ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ ከመ ፡ መዓር ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፱) ።

**ጣዕም** ፤ (ማት) ፤ በቁሙ ፤ ጣም ፡ ጥፍጥንት ፡ ወይም ፡ መራርነትና ፡ ጥፍጥንት ፤ የመብል ፡ የመጠጥ ፡ የነገር ፡ የምስጢር ፡ ጠባዩና ፡ ቃናው ፡ ሐሳቡና ፡ ስልቱ ፤ ጉረሮና ፡ ዝርዌ ፡ ለይቶ ፡ የሚያውቀው ። ጒርዔ ፡ ይፈልጦ ፡ ለሥሉ ፡ ጣዕመ ፡ እክል ። ፍሬያት ፡ ዘበበ ፡ ጣዕሙ ። ምግበ ፡ ቃሉ ፡ ወጣዕመ ፡ ነገሩ ። አንክረ ፡ ንጉሥ ፡ እምጣዕመ ፡ ቃሉ ፡ (ሚሬ፴፮ ፡ ፳፱ ። ቀሌ ። ድጓ ። ስንክ ፡ ኑሐ፳) ።

—፤ ጥሩ ፡ ምግብ ፤ የላመ ፡ የጣመ ፡ የሚያስጐመጅ ። ከመ ፡ ይጹም ፡ እምእሉን ፡ ጣዕማት ። ናሁ ፡ በላዕኩ ፡ ሥሎ ፡ ጣዕማተ ፡ ወኢረከብኩ ፡ ዘይጥዕም ፡ እምኔ ፡ ጥዒና ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ። ፈላስ ፡ ገ፳፭) ።

—፤ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ምቾት ፤ ብዕል ፡ ሹመት ። ኢይብልዑ ፡ ለጣዕም ። ይደሉ ፡ ሰሰ ፡ ሕሑዴ ፡ ከመ ፡ ይልበስ ፡ በጣዕመ ፡ ዘመን ። እንዘ ፡ ያአምሩ ፡ ጣዕሞ ፡ ለዓለም ፡ ወምረራ ፡ ለሞት ። መነኑ ፡ ፍትወታተ ፡ ወጣዕመ ፡ ዝ ፡ ዓለም ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲ ። ሸ፫ ። መቃ ፡ ገ፲፱ ። ቀሌ) ።

—፤ ፍትወት ፡ እንስሳዊት ፤ የፍትወት ፡ ሥራ ፤ ፈቃደ ፡ ሥጋ ። ተሰጥሞ ፡ ውስተ ፡ ጣዕማት ፡ እንስሳውያት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፱) ።

**ተጣዐመ** ፤ ተጣጣመ ፤ ተቃመሰ ።

**አስተጣዐመ** ፤ (ያስተጣዕም) ፤ አቃመሰ ፡ አቀማመሰ ፤ አጠፋፈጠ ፤ አስነዳዳ ። ኢናስተጣዕም ፡ ለክርሥነ ፤ አባ ፡ ናስተጣዕም ፡ ትምህርተ ፡ መንፈሳዌ ፡ (አጥል) ።

**ጣፍ** ፤ (ዕብ) ፤ ስመ ፡ ሕፃናት ፡ ንኢሳን ፤ ጉባኤ ፡ ሕፃናት ፤ ከቤት ፡ የሚውሉ ፡ ፊሳቸውን ፡ ያልቻሉ ፡ ታናናሽና ፡ ጥቃቅን ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ። በትግሬና ፡ በትግሪኛ ፡ ግን ፡ ጤፍ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የባሕር ፡ ጤፉንም ፡ ጤፋዊ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ጣፍጣፎ ፡ ይሉታል ፡ (ሐባበኙ) ።

**ጠፈአ** ፤ **አት** ፤ **(ጠፍአ ፡ ይጠፍአ ፡ ይጥፋእ ። ዐረ ፡ ጠፊአ)** ፤ መጥፋት ፡ መድከም ፡ ዐልም ፡ ድርግም ፡ ማለት ፤ መበላሸት ፡ ከንቱ ፡ መኾን ፤ የእሳት ፡ የመብራት ፡ የዐይን ፡ የብርሃን ፡ የልብ ፡ የገንዘብ ፡ የሥራ ፡ የመንገድ ። መሸሸ ፡ መኰብለል ፡ መሰወር ፡ መደበቅ ፤ ካይን ፡ መራቅ ፡ መርቀቅ ፡ መሞት ፡ መቃጣት ፤ መውደም ፡ መፈታት ፤ የሰው ፡ የንስሳ ፡ ያገር ። ጠፊአ ፡ ይጠፍኡ ፡ (ዮዲ፳ ፡ ፱) ።

**ጠፋኢ** ፤ **(ኢት ፡ እያን ፡ ያት)** ፤ የሚጠፋ ፡ ጠፊ ፡ ኰብላይ ።

**ጥፉእ** ፤ **(አን ፡ አት ፡ ፍእት)** ፤ የጠፋ ፡ ጥፉ ፤ ብልሹ ፡ መጥፎ ፤ ደካማ ። ኢያሴዕል ፡ ገጾ ፡ ጥፉእ ፡ ኀበ ፡ እግዚእ ፡ (ተረ ፡ ቄርሎ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፮ ። ዘዳ ፳፰ ፡ ፳፭) ።

**ጥፍአት** ፤ መጥፋት ፡ መታጣት ፤ ጥፋት ፡ አጠፋፍ ፤ አደጋ ፡ ሞት ፤ ምርኮ ፡ ስደት ፤ ኰብለላ ፡ ሽሽት ። እሳት ፡ ዘአልቦ ፡ ጥፍአት ። ጥፍአተ ፡ መሀይምናን ። ከመ ፡ ዝኬ ፡ ጥፍአቶሙ ፡ ለኃጥኣን ፡ በምዕር ። ጥፍአተ ፡ ልብ ። በጽሐቶሙ ፡ ጥፍአት ፡ ለኃጥኣን ፡ (ቀሌ ። መቃ ፡ ገ፳፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፶ ። ዕንቅ ፡ ፱) ። ጤስ ፡ ነበልባል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ጥፍአት ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (መሳ፳ ፡ ፵) ።

**ጠፍኢ** ፤ **(ኢት)** ፤ በቁሙ ፤ ጠፍ ፡ ባይ ፡ ባድማ ፤ ብርሃኑ ፡ ሕዝቡ ፡ የጠፋበትና ፡ ያለቀበት ፡ ጨረቃ ፡ ሀገር ። ከጌታው ፡ የጠፋ ፡ ባሪያ ፡ ከብት ። ወራሽ ፡ የሌለው ፡ ገንዘብ ፡ ርስት ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**አጥፍአ** ፤ አጠፋ ፡ አስጠፋ ፤ አወደመ ፡ ጠፍ ፡ አደረገ ። ለእሳት ፡ እንተ ፡ ትነድድ ፡ ያጠፍኣ ፡ ማይ ። ከመ ፡ ኣጥፍእ ፡ እምኔሃ ፡ ሰብአ ፡ ወእንስሳ ። እብነ ፡ በረድ ፡ አጥፍአ ፡ ሥሎ ፡ ዘይሠርጽ ፡ (ሚሬ፫ ፡ ፴ ። ሕዝ፲፬ ፡ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፵፰) ።

**መጥፍኢ** ፤ **እ** ፤ የሚያጠፋ ፡ አጥፊ ፤ አስጠፊ ፡ (እቡሻ ፡ ፲፫) ። መጥፊያ ፡ ማጥፊያ ፡ ማስጠፊያ ፤ መጥፊያ ፡ ምክንያት ።

**ምጥፋእ** ፤ መጥፊያ ፡ ማጥፊያ ፡ ስፍራ ፤ የጥፋት ፡ ቦታ ።

**ተጣፍአ** ፤ ተጣፋ ፤ ተጠፋፋ ፤ ተጋደለ ።

**ጠፈሐ** ፤ **ሐት** ፤ **(ጠፍሐ ፡ ይጠፍሕ ፡ ይጥፋሕ ። ዕብ ፡ ጣፋሕ ፤ ሳፋቅ ። ዐረ ፡ ጸፈሐ ፤ ጸፈቀ)** ፤ ማጨብጨብ ፡ ኹለት ፡ እጅን ፡ መጥፋት ፤ ማማታት ፡ ማጋጨት ፡ መስበቅ ፡ ማፋጨት ፤ የደስታና ፡ የዘፈን ፡ የቍጭት ፡ የሐዘን ፤ ያገና ፡ የገባያ ፤ ስክንፍም ፡ ይኾናል ። ጠፍሑ ፡ እደዊሆሙ ፡ ላዕሌኪ ። እለ ፡ ይጠፍሑ ፡ ወየንብሩ ፡ ምስለ ፡ ቃለ ፡ እንዚራ ። ጥፍሑ ፡ እደዊክሙ ፡ ወየብቡ ። ጥፋሕ ፡ እዴከ ፡ ብዴበ ፡ እዴከ ። ወጠፍሐ ፡ እደዊሁ ፡ ላሜኽ ፡ በእንተ ፡ ሐዘኑ ፡ ላዕለ ፡ ቃየል ። ብእሲ ፡ አብድ ፡ ይጠፍሕ ፡ እደሁ ። መላእክት ፡ ይጠፍሑ ፡ ክነፊሆሙ ፡ (ሰቈ፪ ፡ ፲፭ ። ዓሞ፯ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፵፮ ። ሕዝ፳፩ ፡ ፲፬ ። ቀሌ ። ምሳ፲፯ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ማን፳፩) ።

—፤ ማጠፍጠፍ ፤ መጠፍጠፍ ፡ ጠፍጣፋ ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡ መኾን ፤ የጡብ ፡ የኰበት ። ንዑ ፡ ንጥፋሕ ፡ ግንፋለ ፡ ወናብስሎ ፡ በእሳት ፡ (ዘፍ፲፩ ፡ ፫) ። መጋት ፡ በ

ጋት ፡ መስፈር ፤ በጥፊ ፡ መምታት ፡ ማገሥል ። ወግዐንና ፡ ጸፍዐን ፡ ገዐተን ፡ እይ ።

**ጠፉሒ ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት) ፤** የሚያጨበጭብ ፡ አጨብጫቢ ፤ ጠፍጣፊ ።

**ጥፍሐት ፤** ማጨብጨብ ፡ አጨባጨብ ፤ ጭብጨባ ፡ ማጭት ፤ የእጅና ፡ የክንፍ ፡ መማታት ። **ወበጥፍሐተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ሰከሮ ፡ ሰወልዱ ፡ ወቀተሎ ። ኢመጠነ ፡ ጥፍሐተ ፡ አክናፊ ፡ አንስርት ፡** (ቀሌ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ጥፍሕ ፤ (ዕብ ፡ ጠፉሕ) ፤** ጥፊ ፡ ጋት ፤ ያሬት ፡ ጣት ፡ መጠን ፤ ገዐተን ፡ እይ ። **እመት ፡ ወጥፍሕ ፡** (ሕዝ፵ ፡ ፳ ። ፵፫ ፡ ፲፫) ። በጥፍሕ ፡ ፈንታ ፡ ስዝር ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**ጣፍያ ፤** ጣፊያ ፤ የሆድ ፡ ዕቃ ፡ መጣሪያ ፡ እንደ ፡ ጉበት ፡ ያለ ፤ ሞላላ ፡ ጠፍጣፋ ፤ ምስጢሩ ፡ ጠፍጣፍነት ፡ ነው ። **የብሰ ፡ ሥጋሁ ፡ እምብዝኀ ፡ ትሕርምት ፡ እስከነ ፡ ይትሔዘብዎ ፡ ከመ ፡ ዘአልቦ ፡ ውስተ ፡ ከርሡ ፡ ልብ ፡ ወኢጣፍያ ፡** (ፊልክ ፡ ፲፯) ።

**ተጣፍሐ ፤** ተጣፋ ፤ እጅ ፡ ለጅ ፡ ተማታ ፤ ያገና ፡ የገባያ ። ሸያጭና ፡ ገዥ ፡ በዋጋ ፡ ተስማምተው ፡ ነገር ፡ ሲጨርሱ ፡ እንደ ፡ መማል ፡ እንደ ፡ መፈጣጠም ፡ ይጣፋሉ ።

**አስተጣፍሐ ፤** አጣፋ ፤ አማታ ፡ አጋጨ ። **ይስፍሑ ፡ ወያስተጣፍሑ ፡ እደዊሆሙ ። እንዘ ፡ ያስተጣፍሕ ፡ ክነፊሁ ፡** (ፍ ፡ ነ ፡ ፳ ። ገድ ፡ ተክ) ።

(ጥ) **ጥፉሕ ፤—የተክል ፡ ስም ፤—ትፉሕ ።**

**ጣፌጥ ፤ (ጽር ፡ ታፌት ። ዕብ ፡ ቶፌት) ፤** የቦታ ፡ ስም ፡ ምድጃ ፡ የልጆች ፡ ማንደጃ ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ቅርብና ፡ አጠገብ ፡ የገሃነም ፡ ክፍል ፤ እስራኤል ፡ ልጆቻቸውን ፡ ሞሎክ ፡ ለሚባለው ፡ ለዓሞናውያን ፡ ጣዖት ፡ ያቃጥሉበት ፡ የነበረ ። አፈየን ፡ እይ ፤ ቶፌት ፡ ማለት ፡ ከዚያ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ፪ኛ ፡ አፈታት ፡ ቶፍ ፡ ከበሮ ፡ ነውና ፤ ሕፃናቱን ፡ ካህናቱ ፡ ጣዖት ፡ ሲሠዉ ፡ እናት ፡ አባት ፡ የልጆችን ፡ ጩኸት ፡ እንዳይሰሙና ፡ እንዳይራሩ ፡ እንዳይጠጠቱ ፡ ከበሮ ፡ እየመቱ ፡ የሚያረግዱበት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ስሙ ፡ በሴት ፡ አንቀጽ ፡ ቶፌት ፡ ተብሏል ፤ ከበሮም ፡ ባለከበሮ ፤ ማርገጃ ፡ ከበሮ ፡ ማንጐጃ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሞሎክንና ፡ ገሃነምን ፡ እይ ፡ (፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፲ ። ኤር፲፱ ፡ ፲፬—፲፱) ።

**ጠፊል ፤ ሎት ፤ (ጠፈለ ፡ ይጠፍል ፡ ይጥፍል ። ዕብ ፡ ጣፉል) ፤** መጠመር ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ጥንድ ፡ ክዕብ ፡ ማድረግ ፤ ሥንጥቅ ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ እጅ ፡ ማትረፍ ፤ ያበዳሪና ፡ የነጋዴ ።

**ጠፍልሕ ፤ (ብ ፡ ጠፉልሕ ፤ ሓት) ፤** የገንዘብ ፡ ስም ፤ ጥሩ ፡ ብር ፤ የብር ፡ ገንዘብ ፡ ምዝምዙ ፡ ጠገራው ፤ ወይም ፡ በንጉሥ ፡ መልክ ፡ የተሠራው ፡ ታላቁም ፡ ታናሹም ። ጠፍ ፡ ያለ ፡ ጠፍጣፋ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። **ምንት ፡ ውእቱ ፡ አርባዕቱ ፡ ምእት ፡ ጠፉልሕ ። ጠፉልሐ ፡ ብሩር ። ዲናራት ፡ ወጠፉልሓት ፡** (ዘፍ፳፫ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯) ።

**ጥፍንሕ ፤—ጨፍና ፡ ሽውራራ ፤—ጥንፍሕ ፡ ጥንፍ ።**

**ጥፉንቂስ ፤ (ጽር ፡ ቲፎኒኮስ) ፤** የባሕር ፡ ዐውሎ ፡ ብርቱ ፡ ነፋስ ፤ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ የሚያስነሣ ፡ ባሕር ፡ የሚደርጥ ፡ መርከብ ፡ የሚያናውጥ ፡ (ግብ፳፯ ፡ ፲፬) ። አውራቂስን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

(ጥ) **ጠፊር ፤ ሮት ፤ (ጠፈረ ፡ ይጠፍር ፡ ይጠፍር) ፤** መጠፈር ፡ መማገር ፤ አጥብቆ ፡ ማሰር ፤ ጣራን ፡ ባጥን ፡ በግድግዳ ፡ ላይ ፡ መሥራት ፡ ማዋቀር ። **ሕኮ ፡ በዕፅ ፡ ዘትበውቀን ፡ ወትቄምሮን ፤ ወሕኮ ፡ በሕባል ፡ ዘትጠፍሮን ። ዘይጠፍር ፡ በማይ ፡ ጽርሖ ፡** (ገድ ፡ ላሊ ። መዝ ፡ ፻፫) ። መማገር ፡ ለኹሉ ፡ ይኾናል ፤ ማዋቀር ፡ ግን ፡ ለጣራ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ጠብቆ ፡ እንደ ፡ ቀተለ ፡ የሚኼድ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፤ ላልቶም ፡ እንደ ፡ ቀደሰ ፡ የሚኼድ ፡ ገረመን ፡ ጸዐለን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ግስ ፡ አለና ፤ መንገዱንና ፡ አካኼዱን ፡ ለይተኽ ፡ ጠንቅቀኽ ፡ አስተውል ።

**ጠፋሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤** በቁሙ ፤ የሚማግር ፡ የሚያዋቅር ፡ አጥብቆ ፡ የሚያስር ፡ የሚጠፍር ። ከበሮ ፡ ጠፋሪ ፡ እንዲሉ ።

**አጠፈረ ፤ አስተጠፈረ ፤** አስጠፈረ ፡ አስማገረ ፤ ጠፈር ፡ መዋቅር ፡ አሠራ ።

**ተጠፈረ ፤** በቁሙ ። አጥፈረ ፡ ተጠፍረ ፡ ቢል ፡ ግን ፡ የቀተለ ፡ ቤት ፡ ነው ።

**ጥፉር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ፍርት) ፤** የተጠፈረ ፤ የተሠራ ፤ ጥፍር ። **ይኄይስ ፡ ነቢር ፡ ውስተ ፡ ማእዘንት ፡ ዘኢኮነ ፡ ጥፉረ ። ወማኅደሩ ፡ በማይ ፡ ጥፉር ፡** (ምሳ፳፭ ፡ ፳፬ ። ቅዳ) ።

**ጠፈር ፤ (ራት) ፤** በቁሙ ፤ ሰማይ ፡ የምድር ፡ ባጥ ። **ለይኩን ፡ ጠፈር ፤ ወገብረ ፡ ጠፈረ ፡ ወሰመዮ ፡ ለውእቱ ፡ ጠፈር ፡ ሰማየ ፡** (ዘፍ፩ ፡ ፯ ፡ ፯ ፡ ፰) ።

—፤ የባጥ ፡ ማገር ፤ ጣራ ፡ መዋቅር ። **ዕፀው ፡ ለጠፈረ ፡ ቤት ፡ ወለሠራዊት ። ዐርገ ፡ ናሕሰ ፡ ወነሥቶ ፡ ጠፈረ ። ቦኡ ፡ አረዊት ፡ ታሕተ ፡ ጠፈር ። ኀበ ፡ አልቦ ፡ ጠፈር ። ውስተ ፡ ጠፈረ ፡ ጽርሕ ፡ አርድዎ ፡** (፪ዜና ፡ ፴፬ ፡ ፲፩ ። ሉቃ፳ ፡ ፲፱ ። ኢዮ፴፯ ፡ ፳ ። ኢሳ፳፰ ፡ ፱ ። አርጋ ፡ ፫) ።

**ጠፍር ፤** በቁሙ ፤ ማሰሪያ ፡ መጠፈሪያ ፡ መማገሪያ ፤ የተተለተለ ፡ ቁርበት ፡ ርጥቡ ፡ ወይም ፡ የሰፋው ፤ ቅሪላ ፡ ቅራና ፡ መጫኛ ፡ ምራን ፡ መርገጥ ፡ ማንቆ ።

**ጣቃ ፤ ጣቅ ፤ (ብ ፡ ጣቃት ። ዐረብ) ፤** በቁሙ ፤ ልብስ ፡ የልብስ ፡ መዳ ፡ ንድ ፤ የታጠፈ ፡ የተጠቀለለ ፡ (አቡሻ ፡ ፶) ። ጭጋግ ፡ ጉም ፡ ጢስ ፤ ጥቍር ፡ ደመና ፡ ጠቀርማ ፡ የቀን ፡ ጨለማ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፤ እንደ ፡ ልብስ ፡ ጣቃ ፡ የሚጋርድና ፡ የሚሸፍን ። ቆባርን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንትያ ፡ ነው ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፳፩ ። ዘዳ፬ ፡ ፲፩ ። ፳ ፡ ፲፱ ። ዕብ፲፪ ፡ ፲፰) ።

**ጥቀ** ፤—እጅግ ፡ ብዙ ፤—ጠቂቅ ፡ ጠቀ ።

**ጥቃ** ፤—ቅርብ ፡ አጠገብ ፤—ጠቂዕ ፡ ጠቅዐ ።

**ጠቂብ** ፤ ቦት ፤ (ጠቀበ ፡ ይጠቅብ ፡ ይጥቅብ ፤ ጠቀመ ። ዐረ ፡ ሰቀበ ፤ በሳ ፡ ነደለ) ፤ መጥቀም ፡ መጠቃቀም ፤ መስፋት ፡ መደረት ፤ መጣፍ ፡ መለገብ ፤ ያሮጌ ፡ ልብስ ፡ ያሮጌ ፡ ማግ ። ጠቀመን ፡ እይ ። ነሥአ ፡ ቈጽለ ፡ በለስ ፡ ወጠቀቡ ፡ ወገብረ ፡ ሎቱ ፡ ምራሐ ፡ ወከደኑ ፡ ኀፍረቶ ። አልቦ ፡ ዘይጠቅብ ፡ (ኩፋ ፡ ፫ ። ማቴ ፱ ፡ ፲፮) ።

**ጠቃቢ** ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ቀብት) ፤ የሚጠቅም ፡ የሚለግብ ፤ ጣፊ ፡ ለጣፊ ፡ ድሪቶ ፡ ሰፊ ፤ አሮጌ ፡ ጠጋኝ ፡ የጨርቅ ፡ ወጌሻ ።

**አጥቀበ** ፤ አስጠቀመ ፡ አስለገበ ፡ አስደረተ ፤ ልብሱን ፡ ማማውን ፡ አስጠገን ።

**ተጠቅበ** ፤ ተሰፋ ፡ ተጠቀመ ፤ ተጣፈ ፡ ተለገበ ፤ ታደሰ ፡ ተጠገነ ። ከመ ፡ ትትሐጸር ፡ በመስቀልከ ፡ ወትጠቀብ ፡ በመጽለብትከ ፡ እማእከለ ፡ መንቡት ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ) ። ምስጢሩ ፡ መራቅ ፡ መጠበቅ ፡ ነው ፡ አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ ትጠበቅ ፡ ትጠቀም ፡ ይላል ።

**ጥቁብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ቅብት) ፤ የተጠቀመ ፤ የተጠቃቀመ ፤ ድሪቶ ፡ ጥቅምቅም ። ዝቅ ፡ ብሉይ ፡ ወሥጡጥ ፡ ወጥቁብ ። ሀሎ ፡ ዲቤሁ ፡ ልብስ ፡ ጥቁብ ፡ (ኢዮ ፲ ፡ ፱ ። ፊልክ ፡ ፻፲፯) ።

**ጥቅበት** ፤ (ቃት) ፤ መጥቀም ፡ መስፋት ፤ መስፋት ፡ አሰፋፍ ፤ ስፌት ፡ ጥቅማት ። በህየ ፡ ተምህረ ፡ ግብረ ፡ እድ ፡ ጽሕፈት ፡ ወጥቅበት ። ያነቅዕ ፡ ጥቅበቱ ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ ፲፱ ። ማርቆ ፡ ፳፩) ።

**ተጣቀበ** ፤ ተጣቀመ ፡ ተጠቃቀመ ፡ ተሰፋፋ ።

**አስተጣቀበ** ፤ አጣቀመ ፡ አጠቃቀመ ፤ የጨርቅና ፡ የጨርቅ ፤ ለነገርና ፡ ለሰውም ፡ ይኾናል ።

**መጥቀብት** ፤ (ብ ፡ መጣቅብት) ፤ መጥቀሚያ ፡ መጠቃቀሚያ ፤ የስፌት ፡ መሣሪያ ።

**ጠቂል** ፤ ሎት ፤ (ጠቀለ ፡ ይጠቅል ፡ ይጥቅል) ፤ መጥቀል ፤ በነገር ፡ መንካት ፡ መጕነጥ ፤ ጠቅ ፡ ማድረግ ፡ ማሽሞጠጥ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፤ ወይም ፡ በስተኋላ ፡ ማማት ፡ መንቀፍ ፤ መዋሸት ፡ መቅጠፍ ፤ መክሰስ ፡ ማሳጣት ። አፍ ፡ ዘይጠቅል ፡ ወይሔሱ ። ወጠቀለቶ ፡ ቅድመ ፡ እግዚእ ። ሰበ ፡ ጠቀሊቶ ፡ (ጥበ ፳ ፡ ፲፩ ። ኩፋ ፡ ፴፱ ። መጽ ፡ ምስ) ። ጠንቈለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ስሕጽ ፡ ነው ።

**ጠቃሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ቀልት) ፤ የሚነካ ፡ ኈናጭ ፡ አሽሞጣጭ ፤ ሰብቀኛ ፡ ከሳሽ ፡ አሳጭ ፤ ቀጣፊ ፡ የሰው ፡ ስም ፡ አጥፊ ፤ ሹላፋ ፡ አሾካፍ ።

**መጥቀል** ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። የሰው ፡ ስም ፤ ምትሀታም ፡ አስማታም ፤ ጠንቋይ ፡ መሠሪ ፡ ጋኔን ፡ ጠሪ ፡ ሙት ፡ አናጋሪ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ንጉ ፡ ማር) ።

**ጠቅለለ** ፤ (ተቀ ፡ ግ ። ጠቀለ) ፤ በቁሙ ፤ ጠቀለለ ፤ ጠቀጣለለ ፡ ጠመጠመ ፤ የልብስ ፡ የገመድ ። ጠብለለን ፡ እይ ፤ ተቀጥጣንቱ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

**አጠቅለለ** ፤ **አስተጠቅለለ** ፤ አስጠቀለለ ፤ አስጠመጠመ ።

**ተጠቅለለ** ፤ ተጠቀለለ ፡ ተሸበለለ ።

**ጥቅሉል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ልልት) ፤ የተጠቀለለ ፤ ጥቅልል ፤ መዳ ፡ ጣቃ ። አልባስ ፡ ጥቅሉላት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫) ።

**ጠቂም** ፤ ሞት ፤ (ጠቀመ ፡ ይጠቅም ፡ ይጥቅም ። ጠቀበ) ፤ መጥቀም ፤ መጠገን ፡ ማደስ ፤ ያሮጌ ። ሐነጹ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ብዙኃተ ፡ ወጠቀሙ ፡ ወሐደሱ ፡ እምኔሆሙ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ ፳፯) ።

—፤ መንደቅ ፡ መገንባት ፤ ማጠር ፡ መቅጠር ፤ ቅጥር ፡ መሥራት ፡ በቅጥር ፡ መክበብ ፤ ዙሪያውን ፡ በግንብ ፡ መወሰን ፡ መክለል ፤ የከተማ ፡ የቤት ፡ የበታ ፡ የመሬት ። ከመ ፡ ይሕንጽ ፡ ውእተ ፡ መካነ ፡ ወይጥቅም ፡ ዐጸደ ። እለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ሕገ ፡ ይጠቅሙ ፡ ሰርአሶሙ ፡ ቅጽረ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፪ ። ምሳ ፳፰ ፡ ፬) ።

—፤ በቁሙ ፤ መርባት ፡ መጥቀም ፤ ሥራ ፡ መያዝ ፡ ማገልገል ፤ በቀኦብንና ፡ ረብሕን ፡ እይ ።

**ጠቃሚ** ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ (ተረት) ፤ ጠቋሚ ፡ ጠቃሚ ።

**ተጠቅመ** ፤ ተጠቀመ ፡ ተሠራ ፤ ታጠረ ፡ ተከበበ ፤ ጥቅም ፡ አገኘ ። ከመ ፡ ትጠቀብ ፤ ባሰው ፡ ትጠቀም ፡ እንዲል ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ) ።

**ጥቁም** ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ቅምት) ፤ የተገነባ ፡ የታናሰ ፤ የተቀጠረ ።

**ጥቅም** ፤ (ማት) ፤ ግንብ ፡ ናስ ፡ የግንብ ፡ ቅጥር ፡ መካበቢያ ፤ የደንጊያ ፡ ድሪቶ ፡ ጥቅምቅም ፡ በናሙ ፡ ፊትልንት ፡ የተሰፋ ፡ የተጠቀመ ፤ የተሳካ ፡ የተጋጠመ ፤ ብርቱ ፡ ሥራ ። ንቃወ ፡ ምዝባሬ ፡ ዘጥቅመ ፡ ሰናዖር ፡ ያፍ ። ሀገር ፡ ዘንኅሰ ፡ ጥቅማ ። አህጉር ፡ እለ ፡ ቦን ፡ ጥቅም ። መኑ ፡ ይወስደኒ ፡ ሀገረ ፡ ጥቅም ። በከመ ፡ አንኅልከ ፡ ጥቅማ ፡ ሰኢዮሪክ ፡ ከማሁ ፡ አንኅል ፡ ጥቅመ ፡ ኀጢአትየ ፡ (ቅኔ ። ምሳ ፳፭ ፡ ፳፰ ። ኢሳ ፴፮ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፶፱ ። ቅዳ) ።



ጥቅም ፤

**ጥቅምት** ፤ በቁሙ ፡ ስመ ፡ ወርኅ ፡ ካልእ ፡ እመስከረም ። ዘይቤው ፡ የተሠራች ፡ ሥር ፤ ሥስጢሩ ፡ ወርኅ ፡ ግብር ፡ ጥንተ ፡ ግብር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሥን ፡ ፍጥረትን ፡ ያሳያል ፤ እታማኙንን ፡ ተመልከት ። እንደ ፡ ወራቱ ፡ ማን ፡ ሲፈቱት ፡ ጽጌውን ፡ መደብ ፡ እድርን ፡ ፍሬ ፡ ወርን ፡ ፍሬ ፡ መዋዐስ ፡ ሠዊት ፡ ያስኛል ። (ተረት) ፡ ል

ጅን ፡ በጡት ፤ እኽሉን ፡ በጥቅምት ፡ (ካልጠበቁትና ፡ ካልቈጠቡት) ።

**ጠቀዐ ፤ ዖት ፤ (ጠቅዐ ፡ ይጠቅዕ ፡ ይጥቃዕ ። ዕብ ፡ ታቃዕ) ፤** መደወል ፡ ማቃጨል ፤ መምታት ፡ ማንኳኳት ፡ የንፈጠት ፡ የብረት ። ማርበብ ጩብ ፡ እጅ ፡ መጽፋት ። መንፋት ፡ ማጋፌት ፡ እፍ ፡ እፍ ፡ ማለት ፤ እየነፉ ፡ ድምጥ ፡ ማሰማት ፤ የንቢልታ ፡ የዋሽንት ፡ የቱልቱላ ፡ የቀንዳ ፡ መለከት ። ትጠቅዑ ፡ መጥቅዐ ፡ ወይትጋብኡ ፡ሕዝብ ። ካህናት ፡ አሙንቱ ፡ እለ ፡ ይጠቅዕዎ ፡ ለመጥቅዕ ፡ (ማንዘ ። ዘኍ ፲ ፡ ፫ ፡ ፰ ፡ ፲ ። ኢያ ፮ ፡ ፰—፲፮) ።

—፤ በቁሙ ፡ መጥቃት ፡ ጠቅ ፡ ማድረግ ፡ ማጥቃት ፡ ማስተወጋት ፡ ማስለቀስ ፡ ማሽነፍ ፡ በላይ ፡ መኾን ። ለወይፈንና ፡ ላሰሰም ፡ ይኾናል ፤ አጠቃ ፡ መታ ፡ እንዲሉ ። መጠጋት ፡ መቅረብ ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ፡ መኾን ፡ ለመምታት ፡ ለመጥቃት ።

**ጠቃዒ ፤ መጥቅዕ ፤ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት) ፤** የማይደውል ፡ የማነፋ ፡ ጠቂ ፡ አጥቂ ።

**መጥቅዕ ፤ (ብ ፡ መጣቅዕት) ፤** በቁሙ ፤ መዋቅ ፡ ድወል ፡ ቃጭል ፡ መረዋ ፡ ነጋሪት ፤ ቱልቱላ ፡ ዋሽንት ፤ እንቢልታ ፡ መለከት ። መጥቅዐሰ ፡ ተወጥነ ፡ በኖኅ ፤ ወገብረ ፡ መጥቅዐ ፡ እምዕፀወ ፡ሕብኖስ ፡ ዘፉኡ ፡ ሠለስቱ ፡ በእመት ፡ ወግድሙ ፡ አሐዱ ፡ በእመት ፡ ወሰበ ፡ አንዘ ፡ ይግበር ፡ ታቦተ ፡ ይጠቅዕ ፡ ኵሎሙ ፡ ዕለተ ፡ ሠለስተ ፡ ጊዜ ። ድምፀ ፡ መጥቅዕ ። ቃለ ፡ መጥቅዕ ። ሰብዐቱ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ያጸንዑ ፡ ሰብዐተ ፡ መጣቅዕተ ። ግበር ፡ ለከ ፡ ክልኤተ ፡ መጣቅዕተ ፡ ዘብሩር ፡ (ቀሌ ። ዕብ ፲፪ ፡ ፲፱ ። ራእ ፩ ፡ ፳ ። ፰ ፡ ፮ ። ዘኍ ፲ ፡ ፪) ።



መጥቅዕ ፡

—፤ በዓል ፡ የበዓል ፡ ስም ፡ የዕብራውያን ፡ በውዳሴት ፡ ቱልቱላ ፡ መለከት ፡ የሚነፋበት ፤ በ፯ኛው ፡ ወር ፡ የጥቅምት ፡ ጨረቃ ፡ በምትበቀልበት ፡ ቀን ፡ የሚውል ። አታሚንን ፡ እይ ፤ ክዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ዘሌ ፳፫ ፡ ፳፬) ።

**አጥቅዐ ፤** አስመታ ፡ አስነፋ ፡ አስጠቃ ፡ ጋ ።

**ተጠቅዐ ፤** ተመታ ፡ ተነፋ ፤ ተጠቃ ፡ ተጠጋ ።

**ጥቁዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ቅዕት) ፤** የተጠቃ ፡ ጥቁ ፤ ወሬዳ ።

**ጥቅዐት ፤** መጠቃት ፡ መሸነፍ ፡ በታች ፡ መኾን ። በቁሙ ፡ ጥቃት ፡ ውርደት ።

**ጥቅዕ ፤ ጥቃዕ ፤ ጥቃ ፤** አጠገብ ፡ ጐን ፡ ላይ ፤ ቅርብ ፡ የቅርብ ፡ ቅርብ ፡ ሊደዙት ፡ ሊነኩት ፡ ወይም ፡ በጨበጣ ፡ ሊመቱት ፡ ሊወጉት ፡ የሚቻል ። ዳርቻ ፡ ጠረፍ ፡ ወሰን ፡ ደንበር ፡ ጎር ፡ ጎረቤት ፤ የዐቃ ። አብ ፡ ጥቅዖም ፡ (ትግሬኛ) ። ጥቃሆሙ ። ጥቃ ፡ ማያት ። ጥቃ ፡ ጽህርት ፡ ዘሥጋ ። ማይ ፡ ዘጥቃ ፡ ባሕር ። በጥቃ ፡ ኵሎሕ ። በጥቃ ፡ ፍኖት ፤ ላይ ፡ (ኢዮ ፩ ፡ ፲፱ ። ዘፀ ፳ ፡ ፳፯ ። ፲፯ ፡ ፫ ። ኢሳ ፲፱ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፻፵ ። አፈ ፡ ድ፱) ።

**ጠቂቅ ፤ ቆት ፤ (ጠቀ ፡ ጠቀቀ ፡ ይጠቅቅ ፡ ይጥቅቅ ። ደቀ ፤ ደማደግ) ፤** መጠቀን ፡ ማነስ ፡ ጥቃቅን ፡ ታናናሽ ፡ መኾን ፡ ተፈጭቶ ፡ ደቆ ፡ ተሰባብሮ ፡ ወይም ፡ ተቈርጦ ፡ ተፈርፍሮ ። መቈጠብ ፡ መንፈግ ፡ ጨቅ ፡ መኾን ፡ ቈርጦ ፡ በጥዶ ፡ ቈንጥሮ ፡ አሳንሶ ፡ መስጠት ። ጠቆ ፡ ጥቂት ፡ ማለት ፡ ክዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ጠቆ ፡ ጋልኛ ፡ ነው ። አደሬ ፡ ጠቆ ፡ እንዲሉ ። መብዛት ፡ መፈድፈድ ፡ እጅግ ፡ መኾን ፡ በመስበርና ፡ በመድቀቅ ፡ በመፈለጥና ፡ በመቈረጥ ፡ እንደ ፡ ሸክላ ፡ እንደ ፡ ማንድ ። ተባረከ ፡ ዳግን ፡ ወኮነ ፡ ምእተ ፡ እስመ ፡ በዝኀ ፡ ወመልአ ፡ መሬተ ፡ (ቅኔ) ። የምስጢር ፡ ጥቅስ ፡ ነው ።

**ጥቀት ፤** መብዛት ፡ ብዙንት ። ማነስ ፤ ጥቂትነት ፡ የቍጥር ፡ የመጠን ። መንፈግ ፡ መቈስ ፤ ንፍገት ፡ ጨቅነት ። በጥቀት ፡ መብልዐ ፡ ወሀብኩ ፡ (መጽ ፡ ኑዛ) ።

**ጥቀ ፤** እጅግ ፤ ብዙ ፡ ዐይሉ ፤ ጥቃቅንነቱ ፡ እንዳሸዋ ፡ እንደ ፡ ጤፍ ፡ ቅንጣት ፡ እንዳፈርና ፡ እንደ ፡ ደቂት ፡ ያለ ፤ የብዛቱ ፡ መጠን ፡ በስፍር ፡ በሚዛን ፡ ክልኾን ፡ በቍጥር ፡ ሊታወቅ ፡ የማይቻል ፡ የማይቈጠር ።

**ጥቀ ፤ (ንኡስ ፡ አገባብ) ፤** እጅግ ፤ ብዙ ፡ እምብዛ ፡ ለክ ፡ ፈጽሞ ፡ ይልቅ ፡ በጣም ፡ እንኳን ። ትምዐ ፡ ጥቀ ። ጥቀ ፡ ተሰብሐ ፡ ስምከ ። ጥቀ ፡ ሠነይኪ ፡ ወጥቀ ፡ አደምኪ ። ኀቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ሥሙር ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡ ጥቀ ፡ እምዘቢሐ ፡ መሥዋዕት ። ማየ ፡ ጥቀ ፡ ኢያስተይኮ ፡ ለጽሙእ ። መላእክት ፡ ጥቀ ፡ ስሑቱ ፡ በሰማይ ፡ (ማቴ ፪ ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፰ ። ማሕ ፯ ፡ ፯ ። ምሳ ፲፯ ፡ ፳ ። ኢዮ ፳፪ ፡ ፯ ። ድራሲ) ። (ዕርጅ ፡ ቍ ፲፯) ።

**ጠቂር ፤ ሮት ፤ (ጠቀረ ፡ ይጠቅር ፡ ይጥቅር ። ደመነ ፤ ጸልመ) ፤** መጥቀር ፡ መጥቈር ፡ ጠቀራ ፡ መኾን ፤ ጥቀርሻ ፡ መምሰል ፤ የጣሬ ፡ የፊት ፡ የደመናት ።

**ጠቀር ፤** በቁሙ ፤ ጠቀራ ። ጥቀርሻ ፤ ጥቍር ፡ ጠቋራ ፡ ጥላት ፤ የጢስ ፡ ስልባቦት ፡ በማድ ፡ ቤት ፡ ጣራ ፡ በማሩም ፡ በንጨቱም ፡ የሚገኝ ። ማሩም ፡ ጠቀራ ፡ ጠጉብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ጠቀራ ፡ ይባላል ። (ተረት) ፤ ያፈና ፡ በሬ ፡ ጠቀራ ፡ ይጠዛል ። ረገዘዎ ፡ በኵናት ፡ ጸሊም ፤ ጠቀራ ፡ ጠጉብ ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ጠቂስ ፤ ሶት ፤ (ጠቀሰ ፡ ይጠቅስ ፡ ይጥቅስ ። ሱር ፡ ትካስ ። ዕብ ፡ ጣቄስ ፡ ሰደረ) ፤** መጥቀስ ፡ ማመልከት ፤ ባይን ፡ በጅ ፡ በቃል ፤ የሰው ፡ የመጥ ፡ የነገር ፡ (ምሳ ፮ ፡ ፲፪) ። መኰስተር ፡ መተርከስ ፤ የመብራት ፡ የቀንዲል ። መብራቱን ፡ ጥቀሰው ፡ እንዲሉ ።

**ጥቅስ፡(ሳት)፡** ጥቅሻ ፡ ምልክት ። ባይን ፡ ጥቅሻ ፡ በክንፈር ፡ ንክሻ ፡ እንዲሉ ። በቁሙ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ዐዋጅ ፡ ቍርጭኝ ፡ ንባብ ፡ ምሳሌ ፡ መስል ፡ ማስረጃ ፡ ምስክር ፡ የሚኾን ። ጉመን ፡ ጥቅስ ፡ ዐልማ ፡ ጥቅስ ፡ እንዲሉ ። ዘመረንና ፡ ቀጸበን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ጥር ፡—በቁሙ ፡ ጠር ፡—ጠይሮ ፡ ጠየረ ።**

**ጠሪእ፡ አት፡(ጠርአ ፡ ይጠርእ ፡ ይጥ ራእ ። ጸርሐ)፡** መጥራት ፡ መሰማኽ ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ ማለት ፡ ቡታ ፡ መስደድ ። ኢይኬልሕ ፡ ወኢይጠርእ ። እንዘ ፡ ይጠርኡ ፡ (ኢሳ፵፪ ፡ ፪ ። ግብ፳፭ ፡ ፲፭) ።

**ጠራኢ፡** ጠሪ ፡ ጩኺ ፡ ቡታ ፡ ሰዳጅ ።

**ጥራእ ፡ ጥርእ ፡** ጥሪ ፡ ጩኸት ፡ ቡታ ፡ እሪታ ። ጥራአ ፡ ቃል ፡ መፍርህ ፡ (ጥበ፲፯ ፡ ፲፰) ።

**ጥሬቡኖስ፡(ብ ፡ ጠርባናት ። ሮማይ ፡ ትሪቡኑስ)፡** የሹመት ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ደጅ ፡ አዝማች ፡ ራስ ፡ ቢቶደድ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያለ ። ፈነውዎ ፡ ለክቡር ፡ ጥሬቡኖስ ። ተፈነዉ ፡ ጠርባናት ፡ (ቀሌ ፡ ቄር፲፬ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ጠርቤንቶስ፡(ጽር ፡ ቴሬቢንቶስ)፡** የነፍስት ፡ ስም ፡ ቡጥም ፡ መልክም ፡ ሽታና ፡ ብዙ ፡ ቅጠል ፡ ደም ፡ ወተት ፡ ያለው ፡ ቅጠሉና ፡ ፍሬው ፡ ታናናሽ ፡ ቍንድ ፡ በርበሬ ፡ የሚመስል ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፴ ። ፮ ፡ ፲፫ ። ኩፋ ፡ ፲፫ ። ኢያ፳፬ ፡ ፳፮) ።

**ጠራው፡** ትርያ ፡ ጉቡኣን ፡ ከዋክብት ፡ እንደን ስድስቶ ፡ ያሉ ፡ ባንድነት ፡ ተጻፍቀው ፡ ተሰናስለው ፡ አበባ ፡ መስለው ፡ የሚታዩ ። ኮከብ ፡ ጠራው ፡ (ሰንክ ፡ መስ፲፰) ። ስሙ ፡ ዘገር ፡ ከዋክብት ፡ የሚመለኩበት ፡ ሥዕላቸው ፡ ምስላቸው ፡ ያለበት ፡ የኮከብ ፡ ቄጣሮች ፡ አገር ። ሀገረ ፡ ጠራው ፡ (ሰንክ) ። ትርያን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ።

**ጠሪዝ፡ ዞት፡(ጠረዘ ፡ ይጠርዝ ፡ ይጥ ርዝ ። ዐረ ፡ ጠሪዘ ። ዕብ ፡ ጣራዝ ፡ ጣራስ)፡** መጠረዝ ፡ መጥለፍ ፡ መዘምዘም ፡ ፈትልን ፡ በመርፌ ፡ ማቈላለፍ ፡ በልብስ ፡ ላይ ፡ ዘፍና ፡ ሐረግ ፡ መሣል ፡ ልብሱን ፡ በስፌት ፡ በሐር ፡ ማስጌጥ ፡ ማንቈጥቈጥ ፡ ሰራ ፡ ማስመሰል ፡ ረቀመን ፡ እይ ።

**ጠራዚ፡(ዚት ፡ ዝያን ፡ ያት)፡** የሚጠርዝ ፡ ጠራዥ ፡ ጠላፊ ፡ ጥልፍ ፡ ሰሪ ።

**ጥራዝ፡(ዛት)፡** ግብረ ፡ መርፌ ፡ ጥልፍ ፡ ዝምዝማት ፡ ቍልፍልፍ ፡ ስፌት ፡ በልብስ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ርሱን ፡ ራሱን ፡ ፈትሉን ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ወንፌት ፡ ሐረግ ፡ አበባ ፡ ዛላ ፡ ዘለላ ፡ እያስመሰሉ ፡ የሚጠልፉትና ፡ የሚታቱት ። የመጽሐፍ ፡ ስፌት ፡ ቆታን ፡ ሥራው ፡ የጥልፍ ፡ ሐረግ ፡ የሚመስል ፡ ኸርማቱና ፡ ሚፉ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ የተጣሰፈ ፡ የተቈላለፈ ። በቁሙ ፡ የመጽሐፍ ፡ ነደ ፡ ብራናው ፡ ወይም ፡ ወረቀቱ ፡ ክራትና ፡ ክምስት ፡ በመታጠፍ ፡ ሱሑ ፡ ቅጠሉ ፡ ፰ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ፡ ፲፮ ፡ ወይም ፡ ፳ ፡ ኹኖ ፡ ባንድነት ፡ የሚያዝ ፡ የሚሰፋና ፡ የሚጠረዝ ። ሰሙን ፡ ከስፌቱ ፡ ከቆታኑና ፡ ከኽርማቱ ፡ ወስዲል ። ወምስሌሃ ፡ ሕሑዱ ፡ ጥራዝ ፡ እመጽሐፈ ፡ መልእክቱ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወትቤሎ ፡ ተሣየጥ ፡ እምኔየ ፡ ወነሥኦ ፡ ለይእቲ ፡ ጥራዝ ። ሠሰስቱ ፡ ጥራዛት ፡ ካልኣን ፡ (ሰንክ ፡ መጋ፲፫) ።

**ጠርዝ፡** በቁሙ ፡ የልብስ ፡ ዳርቻ ፡ ዝሓው ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ኹና ፡ ጥራዝና ፡ ጥልፍ ፡ የሚመስል ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጠርዘዘ፡(ተቀ ፡ ግ)፡** አንጠረዘዘ ፡ የሬት ፡ የሆድ ።

**ተጠርዘዘ፡** ተንጠረዘዘ ፡ ጠርዛዛ ፡ ኾነ ።

**ጥርዙዝ፡** የተንጠረዘዘ ፡ እንጥርዝ ፡ ሬተ ፡ ከባይ ፡ ርጉዝ ፡ ጋን ፡ ሆድ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጥሬዝቢጤር ፡—ክህን ፡ ቄስ ፡—ጥሬዝ ፡ ጥ ።**

**ጠርይ፡(ዮት ፡ ጠርየ ፡ ጠረየ ፡ ይጠሪ ፡ ይጥሪ ። ጸርየ)፡** መጠረት ፡ ጥሪት ፡ ማጥራት ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ መሰብሰብ ፡ የሌላውን ፡ ጥሪት ፡ መዋጀት ፡ መግዛት ፡ መውረስ ፡ ጥሩ ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአመረ ፡ ፈንታ ፡ አአመረ ፡ እንዲል ፡ ብጠረየም ፡ ፈንታ ፡ አጥረየ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ንዋይ ፡ ዘአጥረየ ። አጥረይኩ ፡ ሠናየ ፡ ጥሪተ ። ኅሩያንየ ፡ እለ ፡ አጥረይኩ ። አንተ ፡ አጥረይከ ፡ በደምከ ። ልብየ ፡ እምከመ ፡ አጥረየ ፡ ክንፈ ፡ ወርሕቀ ፡ እምግብራት ፡ ሰብ ። ንጽሕቅ ፡ ለአጥርዮተ ፡ ዝንቱ ፡ (ኢዮ፳፯ ፡ ፳፱ ። ሚራ፴፯ ፡ ፳፩ ። ኢሳ፵፫ ፡ ፳፩ ። ግብ፳ ፡ ፳፰ ። አፈ ፡ ተ፳፪ ። ፴፱) ። ጥሬ ፡ መኾን ፡ አለመብሰል ፡ የምግብ ።

**ጠራዪ ፡ መጥረዪ ፡ መጥሪ ፡(ሪት ፡ ርያን ፡ ያት)፡** ገዥ ፡ ወራሽ ፡ ጥሪታም ፡ ባለጥሪት ።

**አጥረየ፡** ጥሪት ፡ አስገዛ ፡ አሲጀ ፡ ገንዘብ ፡ አስደረገ ።

**ተጠርየ፡** ተገዛ ፡ ተዋጀ ፡ ተገኘ ፡ ተሰጠ ፡ ጥሩ ፡ ገንዘብ ፡ ኾነ ። አንተ ፡ ኀሲይከ ፡ ከመ ፡ ጸጋ ፡ እግዚ ፡ ትጠረይ ፡ በብሩር ። ንዋይ ፡ ዘይጠረይ ፡ እምግብር ። ሃይማኖት ፡ እንተ ፡ ትጠረይ ፡ እምተምህሮ ። ትሩፋት ፡ እንተ ፡ እምኔሃ ፡ ትጠረይ ፡ ንጽሐ ፡ ልብ ። ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንተ ፡ ትጠረይ ፡ በጥምቀት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፫ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፱ ። ማር ፡ ይሥ ። ፊልክ ፡ ፱ ፡ ፳) ።

**ጥሩይ፡(ያን ፡ ያት ፡ ሪት)፡** የተገዛ ፡ ግዙ ፡ ውጁ ፡ ውርስ ።

**ጥሪት፡(ታት)፡** በቁሙ ፡ ጥሩ ፡ ገንዘብ ፡ ብዕል ፡ ሀብት ፡ ብዙ ፡ ከብት ፡ ቋም ፡ መንጋ ፡ የሚንጋጋ ። ሑር ፡ ወሢጥ ፡ ጥሪተከ ፡ ወሀብ ፡ ለምስኪናን ፡ ወሖረ ፡ ትኩዘ ፡ እስመ ፡ ብዙኅ ፡ ጥሪቱ ። አጥርዮ ፡ ጥሪታት ፡ (ማቴ፲፱ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፱) ።

**መጥረት** ፡ (ብ ፡ መጥርያት ፡ ታት) ፡ ጥራት ፡ ማጥሪያ ፡ ዕቃ ፡ መማሪያ ፡ ጠፍሮጣ ፡ መኪና ፡ ወይም ፡ የሚከራይ ፡ ገመል ፡ አህያ ፡ ፈረስ ፡ በቅሎ ፡ በሬያ ፡ የመሰሰው ፡ ኹሉ ። በእንተ ፡ አንስቲያሆሙ ፡ ወውሉዶሙ ፡ ወመጥርያታቲሆሙ ፡ ወኪነታቲሆሙ ፡ (ፊልክ ፡ ፫) ።

**ጥራይ** ፡ (ያን) ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ፍሬጣ ፡ ሩብ ፡ አላድ ፡ ቤሳ ፡ መሐለቅ ፡ ጥሬ ፡ ብር ፡ ጥሬ ፡ ወርቅ ። ወአልብክሙ ፡ ጥራያቲሆሙ ፡ (ሐዋ ፫፥ ፮) ።

**ጥራይ** ፡ (ዕብ ፡ ጣሪይ ። ዐረ ፡ ጠሪይ) ፡ ጥሬ ፡ ያልበሰለ ፡ እሳት ፡ ያልነካው ።

**ጥራዮ** ፡ ጥሬውን ፡ በጥሬው ፡ ሳይበስል ፡ ወይም ፡ ብቻውን ፡ (ዘፀ ፲፪ ፡ ፱ ። ኩፋ ፡ ፵፱) ። ከኑ ፡ ይብልዑ ፡ ኅጠተ ፡ ሥርናይ ፡ ጥራየ ። የሐምል ፡ ሐምለ ፡ ገዳም ፡ ወይበልዕ ፡ ጥራዮ ፡ እምኔሁ ፡ (ዮሴፍ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ጥሬ** ፡ በቁሙ ፡ ያልበሰለ ፡ ቅንጣት ፡ ፍሬ ፡ ያልተፈታ ፡ ቋንቋ ፡ በዚያው ፡ በበቀለበት ፡ የሚነገር ። ሃሌ ፡ ሉያ ፡ አያናይ ፡ ኤሎሄ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ። ከዘር ፡ ከአንቀጽ ፡ የሚወጣ ፡ ፍሬ ፡ ቃል ፡ ስምና ፡ ቅጽል ፡ ያውም ፡ ዘመድና ፡ ባዕድ ፡ የሚባል ። ዘመድንና ፡ ባዕድን ፡ ተመልከት ።

**ጠረቀ** ፡ ቆት ፡ (ጠረቀ ፡ ይጠርቅ ፡ ይጥርቅ ። ዕብ ፡ ጣራቅ ፡ መታ) ፡ መጠረቅ ፡ መጠርነቅ ፡ መጠርቁሽ ፡ መብሳት ፡ መንደል ፡ አጣብቆ ፡ መውጋት ፡ መቸንከር ፡ መስበጥ ፡ ማስጌጥ ። መጠርቀቅ ፡ ማስጨነቅ ፡ ማነቅ ፡ መፈጥረቅ ፡ አጥብቆ ፡ አጣብቆ ፡ መያዝ ፡ የሰው ፡ የንስሳ ፡ እስኪቱን ፡ ሲይዙት ፡ ሲያኰላሹት ፡ ሌባም ፡ ቢኾን ፡ እውነት ፡ እስኪያወጣ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ መቅዘን ፡ ይሉታል ፡ ይኸውም ፡ ወይፈን ፡ ሲቀጠቀጥ ፡ በግድ ፡ የሚቀዝን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። መጠርቃት ፡ ማገገም ፡ በመብል ፡ መታደስ ፡ ማፈርጠም ፡ ከተኰላሹና ፡ ከተቀጠቀጡ ፡ በኋላ ። በዐረብ ፡ ቋንቋ ፡ ግን ፡ ጠሬቅ ፡ ጥሬ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ መንገድ ፡ ጐዳና ፡ ጥርጊያ ፡ ይኾናል ።

**ጠራቂ** ፡ በቁሙ ፡ የሚጠርቅ ፡ የሚጠረንቅ ። (ተረት) ፡ ነገር ፡ ባዋቂ ፡ ብረት ፡ በጠራቂ ።

**አጥረቀ** ፡ አስጠረቀ ፡ አስመታ ፡ አስቀጠቀጠ ፡ እስኪቀዝን ፡ ድረስ ።


**አጥራቂ** ፡ የሚያስሞክት ፡ የሚያስነጋ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ጡርቂያም ፡ እንደ ፡ ማስት ፡ ቅዘናም ፡ ይሉታል ፡ ፍችው ፡ አይይስም ።

**ተጠርቀ** ፡ ተጠረቀ ፡ ተቀጠቀጠ ፡ ተኰላሸ ።

**ጥሩቅ** ፡ (ቃን ፡ ቃት ፡ ርቅት) ፡ የተጠረቀ ፡ ጥርቅ ፡ የተሰነጋ ፡ ፍሬው ፡ የወጣ ፡ ኩልሹ ፡ ሰነጋ ፡ ቅጥቅጥ ። ዘምቱር ፡ ወዘጥሩቅ ፡ ኢታቅርቡ ፡ ለእግዚ ፡ (ዘሌ ፳፪ ፡ ፳፬) ። ወዘጥሩቅ ፡ ባለው ፡ ወዘአጥራቂ ፡ ይላል ፡ የመላሸና ፡ የጣፉ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ጠረሰ** ፡ ሰት ፡ (ጠርሰ ፡ ጠረሰ ፡ ይጠርስ ፡ ይጥርስ ። ዕብ ፡ ጣሬሽ) ፡ መጠርሰም ፡ መሰበር ፡ መሠንጠቅ ፡ መፍለጥ ፡ መምታት ፡ መቀጥቀጥ ፡ ለማድቀቅ ፡ የደንጊያ ፡ የገል ፡ ወይም ፡ የመብል ፡ መጨረስ ፡ መጨፈረስ ፡ መፈጸም ፡ የሥራ ። ጥርስ ፡ ማውጣት ፡ ማብቀል ፡ የሕፃን ፡ (ተረት) ፡ እኔ ፡ እበላው ፡ ሳጣ ፡ ልጄ ፡ ጥርስ ፡ አወጣ ። መጥረስ ፡ መደንገዝ ፡ ወይም ፡ ጥርሳም ፡ ገጣጣ ፡ መኾን ። ፀርሰን ፡ እይ ።

**ጥርስ** ፡ (ብ ፡ ጥረስ ፡ አጥራስ) ፡ በቁሙ ፡ መንጋጋ ፡ ክራንቻ ። ወለእመ ፡ ሰበረ ፡ ጥርሰ ፡ ወስነ ፡ አንገፍክምሙ ፡ እማእከለ ፡ ጥረሲሆሙ ፡ ዘመሠጡ ። ጥረሲሆሙ ፡ ለአናብስት ። ስነ ፡ መጥባሕት ፡ ቦቱ ፡ ወጥረሲሁ ፡ መከርክር ። መሊኅ ፡ አጥራስ ፡ (ዘፀ ፳፩ ፡ ፳፯ ። ኢዮ ፳፱ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፶፯ ። ምሳ ፳፬ ፡ ፴፯ ። ስንክ ፡ መስ ፲፰) ።



ጥርስ ፡

**ጠረጴዛ** ፡ (ዛት ። ጽር ፡ ትራፔዛ) ፡ ሰደቃ ፡ ገበታ ፡ አራት ፡ እግር ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ። ምሳሌ ፡ መንበረ ፡ ታቦት ፡ ከንርክኑ ፡ ከፍጉብሩ ፡ መቅደስ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ። ኢይትወከፍዎሙ ፡ ውስተ ፡ ቅድስት ፡ ጠረጴዛ ። ኢይደልዎሙ ፡ ይባኡ ፡ ውስተ ፡ ቅድስት ፡ ጠረጴዛ ፡ ወምሥዋዒሁ ፡ ለእግዚ ። ጠረጴዛት ፡ ዘምስጢር ። ሰላም ፡ ለታእዮራ ፡ ዘሐነጸት ፡ ጠረጴዛ ። አሪታዊት ፡ ጠረጴዛ ፡ (ቀሌ ። አርጋ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ መጋ ፲፭ ። ታኅ ፫) ።

**ጠስ** ፡ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መዘመሪያ ፡ ክፍል ፡ ክራት ፡ አንዱ ። ጠስ ፡ መክ ፡ መጋ ፡ መጅ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ።

**ጠስየ** ፡ ዮት ፡ (ጠሰየ ፡ ይጠሲ ፡ ይጠሲ ። ዕብ ፡ ጣሽጤሽ) ፡ ማጥፋት ፡ መደምሰስ ፡ መፋቅ ፡ መሠረዝ ፡ የጥፋት ። መጣስ ፡ መጠምሰስ ፡ ማስተኛት ፡ መስጠስ ፡ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ማጥፋት ፡ ነው ። ቤቱ ፡ የጠፈረ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ቀተለም ፡ ይኼዳል ። ኅድገኒ ፡ እጥስዮሙ ። እከይዶሙ ፡ ወእጠስዮሙ ። ጠሰየኒ ፡ ምስሌሆሙ ። እነ ፡ ጠሰይኩምሙ ፡ በመዐትየ ። ተሀበኒ ፡ መድኅኒተ ፡ ደዌ ፡ ኀጢአት ፡ ዘይጠሲ ፡ (ዘፀ ፴፪ ፡ ፲ ። ዘኁ ፡ ፳፬ ፡ ፲፪ ። ኢሳ ፡ ፵፫ ። ክብ ፡ ነገ ፵ ። መቃ ፡ ፯፯ ። ስንክ ፡ መስ ፳፪) ። መስፈር ፡ መስከት ፡ ልክ ፡ ማድረግ ፡ ሳይተርፍም ፡ ሳይጐድልም ፡ የርጥብ ፡ የደረቅ ። ጣሳ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ማርጀት ፡ ማፍጀት ፡ መጠስጠስ ፡ የደሜሹን ፡ ልክ ፡ ማድረስ ።

**ጠሳዪ** ፡ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፡ የሚያጠፋ ፡ አጥፊ ፡ ጣሽ ፡ ጠምሳሽ ።

**ተጠስየ** ፡ ጠፋ ፡ ተደመሰሰ ፡ ተፋቀ ፡ ተጣሰ ። ተመስወ ፡ ልቦሙ ፡ ወተጠስየ ፡ ወንጥኡ ፡ ዘይጌልዩ ፡ ጠፋ ፡ (ኢያ ፭ ፡ ፩) ።

**ጥሱይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሲት) ፤ የጠፋ ፡ የተጣስ ።

**ጥስየት** ፤ መጥፋት ፤ ጥፋት ፡ አጠፋፍ ፡ ጥዕሽ ፡ አጣጣስ ።

**ጥስን** ፤ ጠብኝ ፡ የደጋ ፡ ቅጠል ፡ ከድልኽ ፡ ቅመም ፡ የሚገባ ።

**ጤት** ፤—ስመ ፡ ፊደል ፤—ጠይት ።

# የ

**የ** ፤ ፳፯ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፡ ስሙ ፡ የማን ፡ ቍጥሩ ፡ ፀሥር ፤ እንዳዝ ፡ ሲኾን ፡ የ ፡ ፀሠርት ፡ ቱ ፡ ይባላል ።

**የ** ፤ የአካል ፡ ዝርዝር ፤ እኔ ፡ ለሚል ፡ ብቻ ። **ስልየ ፤ ኪሮየ ፤ ዘጻየ ፤ ነፍስየ ።**

**የ** ፤ ሥርወ ፡ ትንቢት ፤ የካልኣይ ፡ አንቀጽ ፡ መነሻ ፡ ለሦስት ፡ ስራዊት ፤ ለሩቅ ፡ ለሩቆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ። ግእዙ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተነገረ ፡ ራብዑና ፡ ሳድሱ ፡ አይቀሩም ። ይህም ፡ ያቀ ፡ (ያቂ ፡ ያቃ) ፡ **የዐውቅ ፤ (ቂ ፡ ቃ) ፤ ይዑቅ ። አያቀ ፤ (ቀ ፡ ቃ) ፤ ያዐውቅ ፤ ያዑቅ ፤** እያለ ፡ ሴሳውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። የትንቢት ፡ አሥራው ፡ ፬ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤ የ ፡ ተ ፡ አ ፡ ን ።

**ዩ** ፤ የቅጽል ፡ ምእላድ ፤ ወይም ፡ የስም ፡ አርቲክል ፤ በሴት ፡ አንቀጽ ፡ ለሚነገር ፡ ቃል ። ሐዳስዩ ፡ ድንግልዩ ፡ ብሲትዩ ፤ ዕቤርዩ ፡ እያለ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ይገባል ። ሲፈታም ፡ ፀዳሲ ፡ ፀዳሲቱ ፤ ባልቴቷ ፡ ባልቴቲቱ ፡ ያሰኛል ። **ይዌድስዋ ፡ መላእክት ፡ ለማርያም ፡ በውስተ ፡ ውሳጤ ፡ መንጦላዕት ፡ ወይብልዋ ፡ በሓኪ ፡ ማርያም ፡ ሐዳስዩ ፡ ጣዕዋ ፡** (ሳታት) ።

**ዩ—ዩ** ፤ የማልስና ፡ የኃምስ ፡ ሥረዮች ፤ ዩ ፡ የማልስ ፤ ዩ ፡ የኃምስ ። የማልስ ፡ የኃምስ ፡ ድምፅ ፡ ኹሉ ፡ ከዩና ፡ ከዩ ፡ ወጥቷል ፤ ቅጥላቸውም ፡ ኢ ፡ ኤ ፡ የዩና ፡ የዩ ፡ ምልክት ፡ ነው ። ፊደል ፡ ኹሉ ፡ እስየ ፡ መሬንት ፡ ማልስና ፡ ኃምስ ፡ አይኾንም ።

**ዩ—ይ** ፤ የጥሬና ፡ የስም ፡ ምእላድ ፤ ወገናዊ ፡ ቅጽል ፡ የ ፡ ኛ ። ዊና ፡ ይን ፡ ተመልከት ።

**ያ** ፤ የጥሬና ፡ የስም ፡ ምእላድ ፤ ፍቹም ፡ ኛ ፡ የ ። **ኬንያ ፡ ሐዋርያ ፤** ብልኀተኛ ፡ መንገደኛ ። **ኢትዮጵያ ፡ እስክንድርያ ፤** የኢትዮጲስ ፡ የእስክንድር ፡ አገር ፤ ወይም ፡ ኢትዮጲዩት ፡ እስክንድራዩት ፡ ያሰኛል ፤ ይኸውም ፡ በተጸውዖ ፡ ስም ፡ ሲገባ ፡ ነው ።

**ያ** ፤ አብገር ፡ ምእላድ ፡ ከንና ፡ ከት ፡ እየተደረበ ፡ በማልስ ፡ ቅጽል ፡ በማልስ ፡ መሰም ፡ ይገባል ። **ቀታሊ ፡ ልያን ፡ ያት ፤ መምለኪ ፡ ክያን ፡ ያት ።** ብዙዎቹን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በሚያስተባብር ፡ በመድበል ፡ ቅጽል ፡ ግን ፡ ተውጦ ፡ ተጕርዶ ፡ ይቀራል ። **ቀተልት ፤ መምለክት ።**

**ዮ** ፤ ቃለ ፡ ብካይ ፡ ወሰቈቃው ፤ በቁሙ ፡ ዮ ፡ ወዮ ፡ ወየው ፡ ይብላኝ ። **ብክይዎ ፡ ወላሕውዎ ፡ እለ ፡ ታፈቅርዎ ፤ ዮ ፡ ዮ ፡ ዮ ፡ ዐማኑኤል ፡ አምላክነ ፡** (ቀዳ ፡ አፈ) ።

**ዮ** ፤ ቃለ ፡ ትፍሥሕት ፡ ወእንክሮ ፡ ዕሦ ፡ ዕሠይ ፡ ኢዮሃ ፡ እንሆ ። **ዮ ፡ መስቀል ፡ ጸገየ ። ዮ ፡ ዮ ፡ ዮ ፡ መንክር ፤** እንሆ ፡ ድንቅ ፡ (ድጓ) ። (ዕርጎ ፡ ቍ፫፱) ።

**ይ—ዩ** ፤ የቅጽል ፡ ምእላድ ፤ እንደ ፡ ዊ ፡ በጥሬና ፡ በስም ፡ እየገባ ፡ ወገን ፡ የሚያሳይ ። **ቅድም ፡ ቀዳማይ—ዩ ፤ (ዩት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤** ፊተኛ ፡ የፊት ። **ፊያታይ ፤** የወንበዶች ፡ ወገን ፤ ቀማኛ ። **ላዕላይ ፡ ታሕታይ ፤** ላይኛ ፡ ታችኛ ፤ የላይ ፡ የታች ፤ በላይ ፡ በታች ፡ ያለ ። **ግብጻይ ፡ ግብጻዩ ፤** የግብጽ ፡ ሰው ። **ቀርናይ—ዩ ፤** ቀንደኛ ፡ ቀንዳም ፡ ባለቀንድ ፤ የቀንድ ፡ ከብት ፡ ተዋጊ ፡ እያሰኘ ፡ እንደ ፡ ሙሻዘር ፡ እንደ ፡ ማልስ ፡ ቅጽል ፡ በሚያምርስት ፡ ስልት ፡ ይፈታል ። ምክንያቱም ፡ ዊና ፡ ዩ ፡ ማልሶች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነው ፤ በዩ ፡ ፈንታ ፡ ግን ፡ ይ ፡ መጣፉ ፡ ስለ ፡ ተለመደ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የሚገባው ፡ ኹኖ ፡ አይደለም ፤ ማልስና ፡ ሳድስ ፡ ምን ፡ ገጥሞት ። ባማርኛ ፡ ግን ፡ ሳድሱን ፡ ሲጣኑት ፡ ድምፁ ፡ እንደ ፡ ማልስ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ማልስና ፡ ሳድስ ፡ ይዋረሳሉ ፤ ስለዚ ፡ ገዢ ፤ ሰዊ ፡ ገኘ ፤ የመስለው ፡ ኹሉ ፤ የዊን ፡ ፍች ፡ እይ ።

**ዮ ፡ (ያ ፡ ዮሙ ፡ ዮን)** ፤ ድርብ ፡ ዝርዝር ፤ የገቢር ፡ በጸፋ ፡ ባሉት ፡ ስራዊት ፡ በሩቅ ፡ በሩቆች ፡ የሚነገር ። ኪያሁ ፡ (ሃ ፡ ሆሙ ፡ ሆን) ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እየገባ ፤ ያን ፡ ያንን ፡ ርሱን ፡ ያሰኛል ። **ሀበኒዮ ፡ እምውእቱ ፡ ማይ ። ክመ ፡ የሀበኒያ ፡ ሊይእቲ ፡ መጽሐፍ ። ወሊተ ፡ ወሀብክኒዮሙ ። አልቦ ፡ ዘየሀይዱደኒዮን ፤ እስመ ፡ አቡየ ፡ ዘወሀበኒዮን ፡ ውእቱ ፡ የዐቢ ፡ እምኵሉ ፡** (ዮሐ፬ ፡ ፲፭ ። ራእ፲ ፡ ፱ ። ዮሐ፲፯ ፡ ፮ ። ፲ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱) ።

**ይእዜ ፤ (ይእቲ ፡ ጊዜ)** ፤ አኹን ፡ በዚች ፡ ሰዓት ፤ ዛሬ ፡ ዘንድሮ ። አኹን ፡ ማለት ፡ ቅጽበት ፡ ደቂቃ ፡ ሳይቀር ፡ የጊዜን ፡ መቅረብና ፡ ማጠር ፡ ያስበትን ፡ ክፍል ፡ ያሳያል ። **ይእዜ ፡ ትስዕሮ ፡ ለገብርከ ። ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ። እምንእስየ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ። እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡** (ሉቃ፪ ፡ ፳፱ ። ይሁ ፡ ፳፭ ። መዝ ፻፳ ። ኢሳ ፡ ፶) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በእንከ ፡ ዘይቤ ፡ ይፈታል ፤ ዮምን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንትያ ፡ ነው ።

**ይእቲ ፤—ያች ፡ ርሷ ፤ ንች ፡ ናት ፤—ውእቱ ።**

**ይቤ ፤ (በዩል ፤ ሎት ፤ ቤለ ፡ ይበይል ፡ ይቢል ። አው ፡ ቤለ ፡ ይቤ ፡ ይበል) ፤** የቤለ ፡ ከልኢይ ፤ ትንቢት ፡ አንቀጽ ። ፍችው ፤ ይል ፤ ይላል ፤ ይል ፡ ነበር ። የቤለ ፡ ትንቢቶች ፡ ክልኣዮቹ ፡ ይቤና ፡ ይበይል ፡ ኹለት ፡ እንደ ፡ ኹኑ ፡ አስተውል ። መምህራን ፡ ግን ፡ በቤለ ፡ ፈንታ ፡ ይቤን ፡ ከብህለ ፡ ደርበው ፡ ቀዳማይ ፡ አንቀጽ ፡ ያደርጉታል ፤ ፪ኛም ፡ ዘሩና ፡ አርእስቱ ፡ በዩል ፡ ሲኾኑ ፡ አርእስት ፡ የለውም ፤ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ ይሉታል ፤ ብሂልን ፡ እዩ ።

**የብብ ፤ ቦት ፤ (የበበ ፡ ይዩብብ ፡ ይየብብ ። ዕብ ፡ ወሰ{ር} ፡ ያቤብ ፤ ጮኸ ፡ አለቀሰ) ፤** እልል ፡ ማለት ፡ በደስታ ፡ ቃል ፡ መፎከር ፡ ማመስገን ፤ የዘፈን ፡ የማሕሌት ። ብበየን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ ግልባጭ ፡ ነው ። ፄበቤት ፡ እሴኒ ። ቦ ፡ እመላእክት ፡ ዘይቤምር ፡ ወቦ ፡ ዘይዩብብ ፡ (ሩን ። ቀሌ ። መገ ፡ ፵፯ ። ፺፰) ።

**ይብቤ ፤ (ብያት) ፤** በቁሙ ፡ እልልታ ፡ ፉከት ፡ ምስጋና ፡ መዝሙር ፡ በደስታ ፡ ቃል ፡ የሚነገር ። ወእልቦ ፡ ብዝኀ ፡ ለይባቤ ። ፀርገ ፡ እግዚ ፡ በይባቤ ። ማርያም ፡ በይባቤ ፡ ትዘብጥ ፡ ከበሮ ፡ (መገ ፡ ፵፫ ። ፮ ። መዋሥ) ።

**የቢስ ፤ ሶት ፤ (የብሰ ፡ ይየብስ ፡ ይይበስ ። ዕብ ፡ ያቤሽ ። ሱር ፡ ዩቢሽ ። ዐረ ፡ የቢስ) ፤** መድረቅ ፡ መክረር ፤ ርጥበት ፡ ልምላሜ ፡ ማጣት ። ፈለግ ፡ ይነፅፍ ፡ ወይየብስ ። ወውእቱ ፡ የብሰ ፡ ከመ ፡ እብን ። ይየብስ ፡ ተክሎሙ ። የብሰ ፡ ማእረረ ፡ ምድር ፡ (ኢዮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፩ ። ሕንፃ ፡ ፳፭ ፡ ፴፮ ። ኢዮ ፡ ፳፱ ፡ ፲፱ ። ራእ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭) ።

**ይቡስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ብስት) ፤** የደረቀ ፡ የከረረ ፡ ደረቅ ፡ ክፉፉ ። ይብስት ፡ ባሕር ። አዕፅምት ፡ ይቡሳት ። ይቡሳኒ ፡ ልብ ። ዕፅ ፡ ይቡስ ። ኀብስት ፡ ይቡስ ። ክሣድ ፡ ይቡስ ፡ (ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፳፱ ። ሕዝ ፡ ፴፯ ፡ ፬ ። ሔኖ ፡ ፳ ፡ ፱ ። ሢራ ፡ ፫ ። ቄድር ። ክፉ ፡ ፭) ።

**ይብሰት ፤** መድረቅ ፡ አደራረቅ ፤ ድርቀት ፡ ድርቅና ፡ ደረቅነት ። ሐዘንክሙ ፡ በእንተ ፡ ይብሰተ ፡ ሐምሐም ። ይብሰቱ ፡ ኀብስት ፡ (ስንክ ፡ መስ፳፭ ። ፊልክ ፡ ፻፵) ።

**ይብስ ፤** ድርቅ ፤ ድርቀት ። ይበሰ ፡ ኀብስት ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፲፱) ።

**የብስ ፤** በቁሙ ፤ ደረቅ ፡ ምድር ፡ ባሕር ፡ የሌለው ፤ ውሃ ፡ ያልሸፈነው ። ይቤ ፤ ያስተርኢ ፡ የብስ ፤ ወእስተርአየ ፡ የብስ ፤ ወሰመዮ ፡ እግዚ ፡ ለየብስ ፡ ምድረ ። እለ ፡ የኀድሩ ፡ የብሰ ። በየብስ ፡ ወበባሕር ፡ (ዘፍጥ ፡ ፩ ። ሔኖ፴፯ ፡ ፫ ። ዮሴፍ) ።

**አይበሰ ፤** አደረቀ ፤ አስደረቀ ። አየብሶሙ ፡ ለአፍላግ ። ለሥርወሂ ፡ ያየብሶ ፡ ነፋስ ። አየብስ ፡ ዕፀ ፡ ርጡበ ። ያረጥባ ፡ ለምድር ፡ ወያየብሳ ፡ ለባሕር ። ያየብስዎ ፡ በፀሓይ ፡ (ኢሳ ፵ ፡ ፳ ። ኢዮ ፲፭ ፡ ፴ ። ሕዝ፲፯ ፡ ፳፬ ። ሳታት ። መ ፡ ፈ) ።

**ዮጊ ፤—እንሆ ፡ ወይ ፤—የወጊ ።**

**ዮድ ፤—ስመ ፡ ፊደል ፤—የወድ ።**

**ይዶን ፤ (ሮማይ ፡ ይዱስ) ፤** ክፍለ ፡ ወርኅ ፡ የወር ፡ እኩሌታ ፤ በዱሮ ፡ አከፋፈል ፡ የየካቲት ፡ ፲፫ኛ ፡ ወይም ፡ በመጋር ፡ ጊዜ ፡ ፲፭ኛው ፡ ቀን ። ወበወርኀ ፡ ሮሜ ፡ ቅድመ ፡ ሰማኒቱ ፡ ይዶን ፡ ፍርፍርዮን ፡ (ተረ ፡ ቄር፳፭) ።

**የዲዕ ፤ ዖት ፤ (የድዐ ፡ ይየድዕ ፡ ይይዳዕ ። ዕብ ፡ ያዳዕ ። ሱር ፡ ዩዳዕ) ፤** ማወቅ ፡ መረዳት ፡ ልቡን ፡ ርግጡን ፡ ማግኘት ፤ በጠባያዊ ፡ ዕውቀት ፡ ፈልጎ ፡ መርምሮ ፡ ተመራምሮ ፤ እንደ ፡ አብርሃም ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ጸቢያም ።

**አይድዐ ፤ (ብህለ ፤ ነበበ) ፤** አለ ፡ ነገረ ፡ አስተማረ ፡ አመለከተ ፤ አሳወቀ ፡ አስታወቀ ፡ አስረዳ ። ወሐነ ፡ ኣየድዕ ፡ ግብርየ ፡ ለንጉሥ ። መፍትው ፡ ኣይድዕ ። አይድዕ ፡ ከመ ፡ ኣሐይዋ ፡ ለምድር ። ኢያይድዐት ፡ ብሔራ ። ይእቲ ፡ አይድዐቶ ፡ ለንጉሥ ፡ ምክሮሙ ፡ (መገ ፡ ፵፬ ። ምሳ፰ ፡ ፮ ። ሔኖ፲ ፡ ፲፩ ። አስቴ፪ ፡ ፳ ፡ ፳፪) ።

**ተየድዐ ፤** ታወቀ ፡ ተረዳ ፡ ተሰማ ፡ ተባለ ፡ ተነገረ ። ከመ ፡ ይትየዳዕ ፡ ስምየ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ። ተየድዐ ፡ ነገሩ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ። በከመ ፡ ተየድዐ ፡ ወተነግረ ፡ በዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አንቀጽ ፡ (ዘፀ፱ ፡ ፲፮ ። ዮሴፍ ። ኢቡሻ ፡ ፴፱) ።

**ይዱዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ድዕት) ፤** የታወቀ ፡ የተረዳ ፤ የተነገረ ።

**ድዐት ፤** ማወቅ ፡ መታወቅ ፤ ዕውቀት ፡ አነጋገር ፤ ንግግር ።

**ዳዒ ፤ (ዕብ ፡ ደዒ ፤ ደዓ ፤ ዳዐት) ፤** ዕውቀት ፡ ዕውቂያ ፤ ማስተዋል ።

**እንዳዒ ፤ (ዕብ ፡ ኤን ፡ ደዒ ፤ አልቦ ፡ ዑቀት) ፤** አሉታ ፤ አላውቅም ፡ አላወቅኹም ፤ አላስተዋልኹም ። ወይም ፡ ጥርጥር ፡ እንጃ ፤ ምናልባት ። እንጋን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። እንዳዒ ፤ እግዚ ፡ የአምር ። እንዳዒ ፤ ኢያእመርኑ ፡ ከመ ፡ ይመልእ ፡ ኵሉ ፡ ዝቅ ፡ ወይነ ። እንዳዒ ፤ እመ ፡ ቦ ፡ ዘንለይክ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ኤር ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ። ኤርማ ፡ ፫) ። ከማሁ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ እንዳዒ ፡ ይላል ። በሌላም ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፤ እንዳዒ ፡ እንጋ ። እፈርህክሙ ፡ እንዳዒ ፡ እያለ ፡ አለ ፡ ስለቱ ፡ ገብቶ ፡ ይገኛል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፫ ። ሮሜ፳፭ ፡ ፯ ። ገላ፬ ፡ ፲፩) ።

**ያሁ ፤ (ዕብ ። ሱር ፡ ይያ) ፤** በዊር ፡ ስሙ ፡ እምላክ ፤ የይሆዋ ፡ ክፋይ ። ዘይቤው ፡ እግዚእ ፤ ምስጢሩ ፡ ምላትና ፡ ስፋት ፡ ልዕልናና ፡ ርቀት ፡ ያሳያል ። ዕብራውያንም ፡ ሲፈቱ ፤ ዐቢይ ፡ ወጽኑዕ ፡ ስፉሕ ፡ ወም

ሎእ ፤ እግዚእ ፡ ዘበአማን ፡ ዘያገምር ፡ ኵሎ ፡ ወኢያገ ምሮ ፡ መካን ፤ ይሉታል ። ሃሌ ፡ ሉያ ፡ (ዕብ ፡ ሀልሉ ፡ ያህ) ፤ የሃሌ ፡ ሉያን ፡ ፍቹ ፡ እይ ።

**የሃይድ ፤ ዶት ፤ (የሀደ ፡ ይየሀድ ፡ ይይ ሀድ ። ዕብ ፡ ያሄድ) ፤** ይሁዳ ፡ ማድረግ ፤ እሕዛብን ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ መሳብ ፤ ማስጠጋት ፡ ማቅረብ ፤ መግዘር ፡ በኦሪት ፡ ማሳመን ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ እግዜርን ፡ ማመስ ገን ፡ ማስመስገን ። ገየረንና ፡ አፍለሰን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፲፭) ።

**ይሁዳ ፤ (ዕብራ) ፤** የሰው ፡ ስም ፡ ምስጋና ፡ እምነት ፤ ወይም ፡ እማኒ ፡ ምእመን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘ ፍጥ፳፱ ፡ ፴፭) ። ስመ ፡ ነገድ ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ ይሁዳ ፡ የወለ ደውና ፡ የወረሰው ፡ የይሁዳ ፡ ዘር ፡ የይሁዳ ፡ ምድር ። ወከነ ፡ ይሁዳ ፡ መቅደሶ ፡ ወእስራኤልኒ ፡ ምዙናኖ ። በእንተ ፡ ይሁዳ ፡ ወኢየሩሳሌም ፡ (መዝ ፡ ፻፲፫ ። ኢ. ሳ፩ ፡ ፩ ። ማቴ፪ ፡ ፳፱ ። ፫ ፡ ፭ ። ፱ ፡ ፳፭) ።

**አይሁድ ፤** በቁሙ ፡ ይሁዶች ፡ የይሁዳ ፡ ዘ ሮች ። ይህ ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ባቢሎን ፡ ምርኮ ፡ ድረስ ፡ የይ ሁዳ ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፤ ከምርኮ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ድረስ ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ተሰጥቷል ። ፈላሻና ፡ እስራ ኤል ፡ ሕዝብና ፡ አሕዛብ ፡ ሲኾኑ ፡ በይሁዳ ፡ ስም ፡ አይ ሁድ ፡ መባላቸው ፡ ኋላ ፡ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ በሚመጣው ፡ በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመባል ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ (ግብ ፲፩ ፡ ፳፮) ። ወፈቀደ ፡ ያጥፍእሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አይ ሁድ ፡ ዘውስተ ፡ ደወለ ፡ መንግሥቱ ፡ ለአርጤክ ስስ ። ቦኑ ፡ ለባሕቲቶሙ ፡ ለአይሁድ ፡ እግዚ ፡ አኮኑ ፡ ለአሕዛብኒ ። እስመ ፡ መድኀኒት ፡ እምነ ፡ አይሁድ ፡ (አስቴ፫ ፡ ፮ ። ሮሜ፫ ፡ ፳፱ ። ዮሐ፬ ፡ ፳፪) ። ከክርስቶስ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ በክሕደታቸው ፡ ስለ ፡ ተነቀፉ ፡ አይሁድን ታቸው ፡ ወዳረመኔነት ፡ ተለውጧል ። ጉባኤ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ ይሰመዩ ፡ በከንቱ ፡ አይሁደ ። ፀርፈቶሙ ፡ ለ እለ ፡ ይብሉ ፡ አይሁድ ፡ ንሕነ ፡ ወኢኮኑ ፤ እላ ፡ ማኅ በሩ ፡ ለሰይጣን ፡ (ዲድ ፡ ፲፪ ። ራእ፪ ፡ ፱) ።

**አይሁዳዊ ፤ (ዊ—ይ) ፤** በቁሙ ፡ የአይሁድ ፡ ወገን ፡ ይሁዲ ፡ እስራኤላዊ ፡ ወይም ፡ ፈላሻ ፡ ግዙር ። ወነገርዎ ፡ ከመ ፡ መርዶኬዎስ ፡ አይሁዳዊ ፡ ውእቱ ። ቦኑ ፡ አነ ፡ አይሁዳዊ ። አይሁዳይ ። አይሁዳውያን ። ወእሙስ ፡ አይሁዳዊት ፡ (አስቴ፫ ፡ ፬ ። ዮሐ፲፰ ፡ ፴፭ ። ሲኖ ዶ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፭ ። ግብ፲፯ ፡ ፩) ።

**ይሁድና ፤** ይሁዲነት ፡ ይሁዲ ፡ መኾን ፡ መ ባል ፡ እምነት ። ይሁድና ፤ ዘአይሁድ ። ጾረ ፡ ንጤ እት ፤ ዘሕመ ፡ ይሁድና ፡ (ቄር ፡ ጸላ ። ተረ ፡ ፲፱) ።

**ተይሁደ ፤** ይሁዲ ፡ ኾነ ፤ በኦሪት ፡ በግዝረት ፡ አመነ ። ቦኑ ፡ ለዐይነ ፡ ሰብእ ፡ ይትየሀዱ ። እኮኑ ፡ በክ ዱን ፡ ይትየሀዱ ። ምንት ፡ ረባሁ ፡ ለተይሁደ ። እለ ፡ ይትየሀዱ ፡ ምጽአተ ፡ ዚአሁ ፡ (ሮሜ፪ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ። ፫ ፡ ፩ ። ገላ፪ ፡ ፲፬) ።

**ትይሁድና ፤** ይሁዲነት ፡ የአይሁድ ፡ እምነ ትና ፡ ሥርዐት ፡ ለሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ ኹኖ ፡ የተሰጠ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ግን፲፯) ።

**ይሆዋ ፤ (ዕብ ፡ ይሆዋህ) ፤** ስመ ፡ አም ላክ ፤ ከፍጡራን ፡ ስም ፡ የተለየ ፤ ከፈጣሪ ፡ በቀር ፡ ለማ ንም ፡ ፍጡር ፡ የማይሰጥ ፤ ፍጡራን ፡ የማይጠሩበት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በይሆዋ ፡ ፈንታ ፡ ይሆባ ፡ ይላል ። ይ ሆባ ፡ ጸባኦት ፡ አዶናይ ፡ (ድር ፡ ሚካ) ። ፍቹውም ፡ እግ ዚእ ፡ ኵሉ ፤ አምላክ ፡ ኵሉ ፤ ፈጣሬ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፤ ንጉሠ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ያሰኛል ። እግዚአብሔርን ፡ ተመ ልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ዮጊ ፤ (ንኡስ ፡ አግ) ፤** እንሆ ፡ አኹን ፡ ዛሬ ፡ (ይህ ፡ ጊዜ) ፤ ወይ ፤ ምናልባት ። ዮጊ ፤ በጽሒት ። እም ትሠዒ ፡ ለአማልክት ፡ ወእምዕጣነ ፡ ታዕርጊ ፤ ተመ ትሮት ፡ ከማድ ፡ አብደርኪ ፡ ወንረይኪ ፡ ዮጊ ። መኑ ፡ የአምር ፡ ዮጊ ፡ በዘንቱ ፡ መዋዕል ፡ ንግሥኪ ። ገሥጾ ፡ ለዐርክከ ፤ ዮጊ ፡ ኢገብረ ። ኢትፍቅድ ፡ ከዊነ ፡ መኰ ንን ፤ ዮጊ ፡ ኢትክል ፡ ተሰቅሎቶ ፡ ለዘአበሰ ፤ ወዮጊ ፡ ታደሉ ፡ ለገጸ ፡ ዐቢይ ፡ (ሉቃ፲፭ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ግን፯ ። አስቴ፬ ፡ ፲፬ ። ሢራ፯ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬) ። (ዕብ፩ ፡ ቀኑ ፯፯) ።

**ዮድ ፤ (ዕብ ፡ ዮድ) ፤** ስመ ፡ ፊደል ፡ ፲ኛ ። ፍችው ፡ እጅ ፡ (መዝ፻፲፰ ፡ ፸፫—፹ ። ሰቆ፩ ፡ ፲ ። ፪ ፡ ፲ ። ፫ ፡ ፳፱ ። ፬ ፡ ፲) ። በመዝሙር ፡ ዮድ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ዮዳሄ ፤ (ጽር ። ዕብ ፡ ይሆያዳዕ) ፤** የሰው ፡ ስም ፤ እግዜር ፡ ያውቃል ፡ (፬ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፬) ። ዳግመኛም ፡ በዮዳሄ ፡ ፈንታ ፡ ኢዮአዳ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (፪ዜና ፡ ፳፬ ፡ ፬) ።

**የውሀ ፤ ሆት ፤ (የውሀ ፤ ይዩውሀ ፡ ዩ የውሀ) ፤ (ገቢር) ፤** ማስዝብ ፡ ማለዛዘብ ፡ ማግራራት ፡ ማቁላመጥ ፤ ቅንነት ፡ ማስተማር ፤ ገር ፡ የዋህ ፡ ቅን ፡ ማ ድረግ ። ሀሎ ፡ ዘይጠብብ ፡ ለነፍሱ ፡ ወይዩውህ ፡ በቃሉ ። አንዘ ፡ ይየውሃ ፡ በቃል ፡ ሠናይ ። እትጋነይ ፡ ላቲ ፡ ወእዩውሃ ። ትዩውሆሙ ፡ ለኃጥአን ፡ ወትመይ ጦሙ ፡ በብዝኀ ፡ ምሕረትከ ። መፀተ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ መልእከ ፡ ሞት ፡ ወብእሲ ፡ ጠቢብ ፡ ይዩውሆ ፡ (ሢራ ፴፯ ፡ ፳፬ ። አስቴ ፡ ፭ ። ኢዮ፲፯ ፡ ፲፯ ። ዲድ ፡ ፴፯ ። ምሳ ፲፯ ፲፬) ። ማሞኘት ፡ ማታለል ፡ መደለል ፡ መሸንገል ፤ የክፉ ። ዘይዩውሁ ፡ ለከንቱ ። ኢየዋህናክሙ ፡ በቃል ፡ (ቆላ፪ ፡ ፰ ። ጸተሰ ፡ ፪ ፡ ፭) ። በየውሀ ፡ ፈንታ ፡ እየውሀ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እየውሀዎ ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፳፰) ።

**የዋሂ ፤ (ሂት ፡ ሀያን ፡ ያት) ፤** የሚያለዝብ ፡ የሚያግራራ ፡ የሚያሞኝ ፡ ሸንጋይ ፡ አታላይ ።

**ተየውሀ ፤ (ተገብሮ) ፤** የዋህ ፡ ኾነ ፡ ቀና ፡ ለዘበ ፡ ተገራ ፡ ለመደ ፡ የወይፈን ፡ የበቅሎ ፡ ላሙራም ፡ ይኾናል ። ተሞኘ ፡ ተታለለ ፡ ተሸነገለ ። አኮ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ዘይትዩዋህ ፡ እግዚአብሔር ። በተየውሆ ፡ (ዘኍ፳፫ ፡ ፲፱ ። ሮሜ፲፯ ፡ ፲፰) ።

**የውሀ ፤ (ሀጕል ። ዕብ ፡ ያእህ ፤ አማረ ፡ ተቀበበ) ፤** ገሪ ፡ ከማሁ ፡ የዋሀ ፡ ኾነ ፡ ለዘበ ፡ ቀና ፤ በገሃ ፡ እኝ ።

**የዋህ** ፤ (ሃን ፡ ሃት) ፤ በቁሙ ፤ የቀና ፡ ቅን ፡ ልዝብ ፤ ገር ፡ ገራም ፡ ጭምት ፡ ደግ ፡ ጥሩ ፤ እውነተኛ ። ቅጽልነቱ ፡ ዐጕል ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ያስተባብራል ፤ አዳምን ፡ እይ ። **ተመሀሩ ፡ እምኔየ ፡ እስመ ፡ የዋህ ፡ አነ ። ብእሲ ፡ የዋህ ። በየዋህ ፡ ጽነኔ ፡ ይኴንን ። ቅሩብ ፡ እግዚ ፡ ለየዋሃነ ፡ ልብ ፡** (ማቴ ፲፩ ፡ ፳፱ ። ሢራ ፳፰ ፡ ፳ ። ኢሳ ፲፩ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፴) ። **ብእሲት ፡ የዋህ ። እመሰ ፡ የዋህ ፡ ይእቲ ፡ ወሥናይ ፡ ቃላ ፡** (ሢራ ፳፮ ፡ ፲፱ ። ፴፯ ፡ ፳፫) ። ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ይህም ፡ የጠቀስነው ፡ ሢራክ ፡ ሳይቀር ፡ በየዋህ ፡ ፈንታ ፡ የዋሂት ፡ ይላሉ ፤ አያሰኝም ። **ብእሲት ፡ የዋሂት ፡ እምእከይ ። ርግብ ፡ የዋሂት ። በግዐት ፡ የዋሂት ፡** (ፍ ፡ ን ፡ ፲ ፡ ፴ ። አፈ ፡ ተ፴፪ ። ስንክ ፡ ግንቦ) ። ለከፉ ፡ ሲኾን ፡ ሞኝ ፡ አላዋቂ ፤ ያልተማረ ፡ ያሰኛል ። **የዋህ ፡ የአምን ፡ ዘሎ ፡ ነገረ ፡** (ምሳ ፲፬ ፡ ፲፭) ።

**የውሀት ፤ የውሀና** ፤ በቁሙ ፤ የዋህ ፡ መኾን ፡ የዋህነት ፤ ገርነት ፡ ቅንነት ። **በየውሀት ፡ ተናገረኒ ። ዘየሐውር ፡ በየውሀት ። ይኴንኒ ፡ በከመ ፡ የውሀትየ ። ርግብየ ፡ ይቤላ ፡ በእንተ ፡ የውሀታ ። ከመ ፡ በየውህና ፡ ንሕየ ፡** (ስር ፡ ኢሳ ፯ ፡ ፯ ። ምሳ ፲ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፯ ። ድጓ ። ቄር ፡ ጸላ) ።

**ይዋሄ** ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ። **በፍርሀት ፡ ወበይዋሂ ። ይዋሂ ፡ ወህድአት ፡ ወአርምሞ ፡** (አፈ ፡ ድ፱ ። ዮሴፍ ። አርጋ ፡ ፭) ።

**የውጣ** ፤ (**ጽር ፡ ዮታ**) ፤ ስሙ ፡ ፊደል ፡ የ ፤ ፲ኛ ፡ ዐሥር ፡ (ማቴ ፭ ፡ ፲፰) ። **ቀዳሚ ፡ ስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ የውጣ ፡ በኍልቁ ፡ (፲) ዐሥርቱ ። ፈጻሚት ፡ ቃላት ፡ የውጣ ፡** (ዲድ ፡ ፯ ። ውዳ ፡ ማርያ ። ስንክ ፡ ነሐ ፲፯) ። የሱስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ የውጣ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **መርቆሬዎስ ፡ ስማዕተ ፡ የውጣ ፡** (ስንክ ፡ መስ ፲፰) ።

**የዊም ፤ ሞት ፤** (**ዮመ ፡ ይየውም ፡ ይዩም**) ፤ ጊዜን ፡ መስፈር ፡ መቍጠር ፤ መክፈል ፡ መተንተን ፤ ቅጽበትን ፡ በክልኢት ፤ ክልኢትን ፡ በደቂቅ ፤ ደቂቅን ፡ በሰዓት ፤ ሰዓትን ፡ በሰለት ፤ ሰለትን ፡ በ፳፬ ፡ ሰዓት ፡ መወሰን ፡ መቀመር ፤ የፈጣሪ ፡ የሰዓት ፡ ሠራ ።

**ዮም ፤ (ዕብ ፡ ዮም ። ሱር ፡ ያውማ ። ዐረ ፡ የውም ፤ ዕለት ፤ መዓልት)** ፤ ዛሬ ፡ አኹን ፤ ዘንድሮ ፤ የተወሰነ ፡ ክፍል ፡ መዓልትና ፡ ሌሊት ፤ ዕለት ፡ ወርን ፡ ዓመት ፤ ቀመር ። ያሉበትን ፡ ቀን ፡ ወራትና ፡ ዘመን ፡ ከመባቻው ፡ እስከ ፡ መከተቻው ፡ ያሳያል ። የሰውም ፡ ዕድሜ ፡ ተወልዶ ፡ እስኪሞት ፡ ተሹሞ ፡ እስኪሻር ፡ የሚኖረው ፡ ዮም ፡ ይባላል ፤ ይእዜንና ፡ ዕለትን ፡ ተመልከት ። **ዘትማልም ፡ ወዮም ። ዮም ፡ ወሲድኩከ ፡ ወዮም ፡ ብሂል ፡ እኮ ፡ ዘንለፊ ፡ መዋዕለ ፡ ዘይነግር ፡ አላ ፡ ዘሀሎ ። ዮምኬ ፡ ሰብእ ፡ ወጊሠመ ፡ መሬት ። ንጉሥ ፡ ሰዮም ፡ ወጊሠመ ፡ ይመውት ፡** (ዕብ ፲፫ ፡ ፰ ። ቄር ። ድጓ ። ሢራ ፲ ፡ ፲) ።

**ዮማዊ** ፤ ሙያተኛ ፡ የዕለት ፡ ምንደኛ ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ የሚሠራ ። የዕለት ፡ መፍቅድ ፡ በየቀኑ ፡ የሚወጣ ፡ ወጪ ፤ ወይም ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ። ዮምዪ ፡ እንዲል ፡ (ዐረብ) ። **ዘመናይ** ፤ ሹም ፡ ባለጊዜ ፤ ዐፍለኛ ፡ ጐበዝ ፤ ወጣት ፡ ልጅ ፡ እግር ።

**ዮን ፤ ዮና ፤ (ዕብራ)** ፤ ርግብ ፤ ዮን ፡ ተባት ፤ ዮና ፡ እንስቲቱ ፤ ሲያበዛ ፡ ዮኒም ፡ ይላል ። ፪ኛም ፡ ዮና ፡ የነቢይ ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ይኾናል ፤ ስምነቱም ፡ እንደ ፡ ይስሐቅ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ያስተባብራል ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ ፲፱) ።

**ዮናን ፤ (ዕብ ፡ ያዋን)** ፤ ፬ኛው ፡ የያፌት ፡ ልጅ ፤ የግሪኮች ፡ አባት ። የሀገርና ፡ የሕዝብ ፡ ስም ፤ ጽርእ ፡ ግሪክ ፤ ፍችው ፡ እስሐቲ ፡ መስሕት ። በያዋን ፡ ፈንታ ፡ ይህያን ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፍ ፲ ፡ ፪) ።

**ዮናናዊ** ፤ የያዋን ፡ ዘር ፡ የግሪክ ፡ አገር ፡ ሰው ።

**ዮናኒ** ፤ ጽርእ ፡ የግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ከቅብጥ ፡ የሚስማማ ፡ የቅብጥ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ባለ፳፬ ፡ ፊደል ። ቅብጡ ፡ ፯ ፡ ፊደሎች ፡ ይጨምራል ፤ መለየው ፡ ይህ ፡ ነው ።

**ያክንት ፤ (ጽር ፡ ኢያኪንቶስ ። ዕብ ፡ ሌሼም)** ፤ ክቡር ፡ ደንጊያ ፤ ዕንቍ ፡ የቀይ ፡ ጥቍር ፡ ደምማ ፤ ቅላቱ ፡ የሮማን ፡ ፍሬ ፡ ደረቅ ፡ በርበሬ ፡ የሚመስል ፡ ደባባ ፡ (ራእ ፳፩ ፡ ፳ ። ሔኖ ፲፰ ፡ ፪ ። ሕዝ ፳፰ ፡ ፲፫) ።

—፤ ቀይ ፡ ቀለም ፤ የደም ፡ ዐይነት ። **ዘሚረቱ ፡ ሕብረ ፡ ያክንት ። ወእምሕብረ ፡ ያክንት ፡ ወሜላት ፡** (ዘፀ ፳፰ ፡ ፭ ። ፳፯ ፡ ፩) ።

**የካቲት ፤ (ከቲት ፡ ከተ ፤ ከተተ)** ፤ በቁሙ ፤ የወር ፡ ስም ፤ ፮ኛ ፡ ወር ፡ ከመስከረም ። የመከር ፡ ማፍ ፡ መከተቻ ፤ የበልግ ፡ መባቻ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ከተተን ፡ እይ ። **እመ ፡ ዐሡሩ ፡ ወስዱሱ ፡ ለየካቲት ፡ በዘወሀባ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡** (መቅ ፡ ታም) ።

**ዮም** ፤—ዛሬ ፤—የውም ።

**የመመ ፤ (ትግ ፡ ሐበ)** ፤ መላ ፡ ፈጸመ ፡ ቈረጠ ፡ ገደበ ። ዘሩ ፡ ሚመየ ፡ ነው ።

(ጥ) **ያም ፤ (ዕብ)** ፤ ባሕር ፡ ኵሬ ፤ ዐዘቅት ፡ ምንጭ ፡ ጕድጓድ ፤ ታላቅ ፡ የውሃ ፡ ዕቃ ። ምዕራብ ፡ የፀሐይ ፡ መግቢያ ፡ መጥለቂያ ። ባሕርንና ፡ ማርያምን ፡ እይ ።

**ዩም** ፤ ማምት ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡ ፍል ፡ ውሃ ።

**የሚን ፤ ኖት ፤ (የመነ ፡ ይየምን ፡ ይይምን ። ዕብ ፡ ያሚን ፡ ዐደመ)** ፤ መቅናት ፡ ቅን ፡ ቀኝ ፡ መኾን ፤ መጽናት ፡ መበርደድ ፤ መብዛት ፡ መረፍረፍ ፤ መክበር ፡ መወደድ ፤ በቀኝ ፡ መቀመጥ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ መኼድ ።

**ይሙን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ምንት)** ፤ የማናይ ፡ የቀና ፡ የጸና ፡ ብርቱ ፡ በርዳዳ ።

**ይሙኑ ፤ (ንእ ፡ አግ)** ፤ እጅግ ፡ በጅግ ፡ ብዙ ፡ በብዙ ፡ አካቶ ፡ ፈጽሞ ፤ ጭራሽ ። **እስመ ፡ አኀበርዎሙ ፡ ይሙኑ ። አበስኩ ፡ ይሙኑ ። ይከብደኒ ፡ ይሙኑ ። ብዙኀ ፡ ይሙኑ ፡** (ሐዜና ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። ፳፩ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፱) ። አንዳንድ ፡ መጻሕፍት ፡ በይሙኑ ፡ ፈንታ ፡ እሙን ፡ ይላሉ ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**የማን ፤ (ዕብ ፡ ያሚን ። ሱር ፡ ያሚና ። ዐረ ፡ የሚን)** ፤ ቀኝ ፤ የቀኝ ፡ እጅ ፤ የቀኝ ፡ ጐን ፡ ማእዝን ፤ ደቡብ ፤ የግራ ፡ ትይዩ ፡ የሰሜን ፡ አንጻር ። ዘትገብር ፡ የማንከ ፡ ኢታእምር ፡ ፀጋምከ ። ልቡ ፡ ለጠቢብ ፡ ውስተ ፡ የማኑ ። ቱፈለጥ ፡ የማኑ ፡ ሕው ፡ ፀጋመ ። መንገለ ፡ የማኑ ፡ ምሥዋዕ ፤ (ማቴ፮ ፡ ፫ ። መክ፲ ፡ ፪ ። ዘፍ፲፫ ፡ ፱ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፩) ። ኀይል ፡ ጽንዕ ፡ ብዛት ፡ እጅግነት ።

**ይምን** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ቀኝ ፡ የቀኝ ፡ ክፍል ፡ መንገድ ፤ በስተቀኝ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ማእዝን ፤ እጅ ፡ ሕዋስ ። ኅበ ፡ ይምኑ ፡ ሐመር ። ዘይምኖሙ ። እንዘ ፡ ይሰርር ፡ ይምኑ ፡ ወፅግመ ። ይምና ፡ ለበይኑ ፡ ሥጋሁ ። ነደፍ ፡ በይምን ፡ ወበፅግም ፤ (ዮሐ፳፩ ፡ ፮ ። ዘካ፲፪ ፡ ፮ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ፩ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፪) ።

**የማናዊ ፤ (ዩ ፤ ዪ)** ፤ የቀኝ ፤ በቀኝ ፡ ያለ ፡ ቅን ፡ ቀኛም ፡ ባለቀኝ ፡ ቀኝ ፡ አገዛማች ፡ ቀኝ ፡ ጌታ ፡ በቀኝ ፡ የሚቆም ። የማናዊ ፡ ፍኖት ። ፀይኑ ፡ የማናይ ። ነደፎ ፡ የማና(ዩ)ዩ ፡ ገቦሁ ። የማና(ዩ)ይ ፡ ወፀጋማይ ። እለ ፡ ክልኤሆን ፡ እደዊሆሙ ፡ የማናይ(ው)ያን ፤ (ስንክ ፡ ታኅ፳ ። ኪዳ ። ስንክ ፡ ነሐ፲፯ ። ቀሌ ። መሳ፳ ፡ ፲፮) ።

**አይመነ** ፤ አቀና ፡ ቀኝ ፡ አደረገ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ መራ ፡ አስተማረ ። ሀይመነኝና ፡ አእመነኝ ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ አማዋር ፡ ናቸው ።

**የመን ፤ (ዕብ ፡ ቴማን)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ የምድረ ፡ እስራኤል ፡ ደቡብ ፡ ምድረ ፡ ዐረብ ።

**ይንዋርዮስ ፤ (ሮማይ ፡ ዠንዋሪዉስ)** ፤ ስመ ፡ ወርኅ ፤ ጥር ፡ የኤውሮፖች ፡ መዠመሪያ ፡ ወር ። ዘይንዋርዮስ ፡ (ጥሬ ፡ ቄር፳፩) ።

**ያፌስ ፤ (ዕብ ፡ ኤፌስ)** ፤ ባይ ፡ ደካማ ፡ ልምሾ ። ባለብልዮች ፡ ግን ፡ ፋስ ፡ ምሣር ፡ ይሉታል ። ዕብራይስጡ ፡ ውብኤፌስ ፡ ያድ ፡ ይሻቤር ፡ ያለውን ፡ ወበድክምት ፡ እድ ፡ ወይም ፡ ዕብስት ፤ ዕውስት ፡ ዘእንበለ ፡ ኀይል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ ወበያፌስ ፡ ይፈጠቅጥ ፡ እደ ፡ ይሳል ፤ አንዳንዱም ፡ መጣፍ ፡ ዘእንበለ ፡ እድ ፡ ይሳል ፡ (ዳን፰ ፡ ፳፭) ።

**ዮቅጣን** ፤—የሰው ፡ ስም ፤—ቀጠነ ።

**ያቁም** ፤—የዐምድ ፡ ስም ፤—ቀዊም ፡ ቆመ ፡ አቀመ ።

**ያርብሕ** ፤—ዐርበኛ ፤—ረብሐ ።

**ያሬድ ፤ (ዕብራ)** ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ፮ኛው ፡ ትውልድ ፡ የሔኖክ ፡ አባት ። ወሪድ ፡ ርደት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ ዘመን ፡ የደቂቀ ፡ ሴት ፡ ከደቂቀ ፡ ቃየል ፡ መጋባትና ፡ መዋለድ ፤ ከደብር ፡ ቅዱስ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ፋሙድ ፡ መውረድ ፡ ተዠምሯል ። የወረዱበትም ፡ ምክንያት ፡ አዋልደ ፡ ቃየል ፡ እንደ ፡ የጁ ፡ አርኾ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በመልካቸው ፡ ውበት ፡ በድምፃቸውና ፡ በዘፈናቸው ፡ ጣዕም ፡ ተመሥጠው ፡ ነው ። ወለደቶ ፡ ሎቱ ፡ ዲና ፡ ወልደ ፤ ወጸውዐ ፡ ስሞ ፡ ያሬድሀ ፤ እስመ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ወረዱ ፡ መላእክተ ፡ እግዚ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ እለ ፡ ተሰምዩ ፡ ትጉሃነ ። በእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ተወልደ ፡ ሎሙ ፡ አዋልድ ፡ ሠናያት ፡ ወልሑያት ፤ ወርእዩ ፡ ኪያሆን ፡ መላእክት ፡ ውሉደ ፡ ሰማያት ፡ ወፈተውዎን ፤ ወይቤሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፤ ንዑ ፡ ንኅረይ ፡ ለነ ፡ አንስተ ፡ እምውሉደ ፡ ሰብእ ፤ ወንለድ ፡ ለነ ፡ ውሉደ ፤ (ኩፋ ፡ ፬ ። ሔኖ ፡ ፮ ። ዘፍ፮ ፡ ፩ ፡ ፪) ። በኢትዮጵያም ፡ በሳድሳይ ፡ ምእት ፡ (ሴክል) ፡ ተነሥቶ ፡ ፳ቱን ፡ ጾዋትወ ፡ ዜማ ፡ የደረሰ ፡ የድጓና ፡ የማሕሌት ፡ አባት ፤ አሮድዮን ፡ እንደሚባለው ፡ ወፍ ፡ ዜማው ፡ ልብ ፡ የሚመሥጥ ፤ እጅግ ፡ ድምፀ ፡ መልካም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ስሙ ፡ ዮው ፡ ያሬድ ፡ ወፉም ፡ ያሬ ፡ ያሬድ ፤ ተብሏል ፡ ምስክሩን ፡ በአሮድዮን ፡ ፋንቱ ፡ ተመልከት ። ሕእመርነሂ ፡ ክመ ፡ ሀሎ ፡ በቀራንዮ ፡ ገነት ፤ ያሬድ ፡ ዘወሰዶ ፡ ሔኖክ ፡ ማሕሌት ፡ (ጉንዠማዊ ፡ ቅኔ) ።

**ዮርዳኖስ ፤ (ጽር ፡ ዮርዳን ። ዕብ ፡ ያርዴን ። ሱር ፡ ያርድና)** ፤ ስመ ፡ ፈለግ ፤ የከነዓን ፡ ወንዝ ፤ ታላቅ ፡ ዠማ ፡ ከምድረ ፡ እስራኤል ፡ ዳርቻ ፡ ከነገደ ፡ ዳን ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ የወልና ፡ እንደ ፡ ዳሽን ፡ ከሰው ፡ ደብረ ፡ ሔርሞን ፡ ከሚባለው ፡ ከደቡብ ፡ ወገን ፡ ከተራራው ፡ እግር ፡ ከሔርሞን ፡ ሥር ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወደ ፡ ባሕረ ፡ ጨው ፡ የሚፈስ ። ዮር ፡ ወራጅ ፡ ፈሳሽ ። ዳን ፤ ደየን ፡ ዳኝ ፡ ፈረደ ፤ በተገናኝ ፡ ፈለገ ፡ ዳን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በዳኖስ ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ግን ፡ ዳናዊ ፡ ፈለግ ፤ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ዮርዳናዊ ፡ ይሰኛል ፡ (ኢያ፫ ፡ ፲፮) ። ዳን ፡ የውኃተኛው ፡ ዳኛ ፤ የውኃተኛው ፡ መጥምቅ ፡ የመሲሕ ፡ ምሳሌ ፡ ጸዋሪ ፡ ስመ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የዮርዳኖስ ፡ ንቅ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ምንጩ ፡ አውራጃውና ፡ ቀበሌው ፡ ገና ፡ ነገደ ፡ ዳን ፡ ሳይወርሱት ፡ ከሙሴና ፡ ከአብርሃም ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ባምሳያዊ ፡ ትንቢት ፡ ዳን ፡ ተብሏል ። ወሐዊርየ ፡ ነበርኩ ፡ ዲበ ፡ ማያተ ፡ ዳን ፡ በዳን ፤ እንተ ፡ ይእቲ ፡ እምየማኑ ፡ ዐረበ ፡ ሔርሞን ። ተለዎሙ ፡ እስከ ፡ ዳን ። ወአርአየ ፡ ኵሎ ፡ ምድረ ፡ ገለዓድ ፡ እስከ ፡ ዳን ፡ (ሔኖ ፡ ፲፫ ። ዘፍ፲፬ ፡ ፲፬ ። ዘዳ፴፬ ፡ ፩) ። ትርጓሜ ፡ ወንጌልም ፡ ዘአምኑ ፡ ወዘተጠምቀ ፡ ይድኅን ፤ ወዘሰ ፡ ኢአምኑ ፡ ይደየን ፤ ያለውን ፡ ሲፈታ ፤ ዳንን ፡ ደየኒ ፡ ደየን ፡ መደየን ፡ ብሎ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ፈለገ ፡ ደይን ፡ ይላል ፤ ፍርዱን ፡ እንደ ፡ ውሃው ፡ ከሰደ ፡ ምና ፡ ከገሞራ ፡ ከባሕረ ፡ ጨው ፡ ጋራ ፡ ለማያያዝ ፡ (ማር፲፮ ፡ ፲፮ ። ማቴ፲፩ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬) ። የዮርዳኖስ ፡ ራስ ፡ ንቁና ፡ ስሙ ፡ በሥላሴ ፡ አምሳል ፡ ሦስት ፡ ነው ፤ ያውም ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ሐስባኒ ፤ ተለልጋዳ ፤ ባንያስ ፡ ይባላል ። ጣዕሙና ፡ ሕብሩም ፡ እንደ ፡ ስሙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፤ መጠኑም ፡ በላይና ፡ በታች ፡ ትክክል ፡ ነው ፤ ርሕቀቱም ፡ ከንዱ ፡ ንቅ ፡ እስከንዱ ፡ ፋብ ፡ ፋብ ፡ ሰዓት ፡ ያስኬዳል ፤ ወደ ፡ ታች ፡ ደግሞ ፡ መክከለኛው ፡ በቀጥታ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በማስየፍ ፤ ኹሉም ፡ በየፈቱ ፡ አንዳንድ ፡ ፋብ ፡ ወይም ፡ እኩል ፡ ሰዓት ፡ ብቻ ፡ ብቻውን ፡ ይወርድና ፡ ሦስቱ ፡ ንቅዐ ፡ ማይ ፡ ከንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ይገናኛል ። ከተገናኙም ፡ በኋላ ፡ ፩ ፡ ወንዝ ፡ በመ

ኸካ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ፩ ፡ ሰዓት ፡ ወርዶ ፤ ማየ ፡ ማሪርም ፡ ወይም ፡ ባሕረ ፡ ሖሊ ፡ ከሚሏት ፡ ከታናሽቱ ፡ ሐይቅ ፡ ይገባና ፡ ርሷን ፡ እንደ ፡ መርከብ ፡ ማኸል ፡ ለማኸል ፡ ሠንጥቆ ፡ ዐልፎ ፤ ከርሷ ፡ በታች ፡ ደግሞ ፡ ፪ ፡ ሰዓት ፡ ኋርዶ ፡ ከኢፈራትና ፡ ጌንሴሬጥ ፡ ባሕረ ፡ ገሊላ ፡ ወይም ፡ ጥብርያዶስ ፡ ከሚባለው ፡ ከታላቁ ፡ ሐይቅ ፡ ይገባል ። ጥብርያዶስንም ፡ እባይ ፡ በጣና ፡ ላይ ፡ እንደሚያልፈው ፡ ማኸል ፡ ለማኸል ፡ ሠንጥቆ ፡ ዐልፎ ፤ ከግራና ፡ ከቀኝ ፡ ብዙ ፡ አፍላጋት ፡ እየጨመረ ፤ ሮቤልን ፡ ጋድን ፡ መንፈቀ ፡ ምናሴን ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ የቀሩትን ፡ ነገድ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ትቶ ፤ ማኸል ፡ ለማኸል ፡ አቅንቶ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ጕዳና ፡ ተጕትቶ ፡ ከባሕረ ፡ ጨው ፡ አፍ ፡ ይገባና ፡ ተውጦና ፡ ሰምጦ ፡ ይቀራል ፤ የባሕረ ፡ ጨው ፡ ዙሪያ ፡ ተራራና ፡ ገደል ፡ የቈላ ፡ ቈላ ፡ መቀራቅርት ፡ መቅሕቶ ፡ ታሕቲት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከዚያ ፡ ሲወጣ ፡ አይታይም ። የጥምቀትን ፡ ውሃ ፡ የንዋየ ፡ ቅድሳትን ፡ ዕጣቢ ፡ የተቀደሰን ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ከመሬት ፡ መቅበር ፡ የትም ፡ አለማፍሰስ ፡ የዚህ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ቀድሞ ፡ በኢያሱ ፡ እስራኤል ፡ የተሻገሩበት ፡ ኋላም ፡ በዮሐንስ ፡ ጌታችን ፡ የተጠመቀበት ፡ ወደቡ ፡ ፩ ፡ ነው ፤ ከዚያ ፡ በታች ፡ እስከ ፡ ባሕረ ፡ ጨው ፡ እኩል ፡ ሰዓት ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ ሩብ ፡ ያስኬዳል ። ጌታም ፡ በዚህ ፡ ወደብ ፡ በዮርዳኖስ ፡ እግር ፡ መጠመቁ ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ይባላል ። ፩ኛው ፡ ማራዝማች ፡ ዲያብሎስ ፡ ያዳምን ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ የላሜ ፡ ልጅ ፡ ያውራዬ ፡ ውላጅ ፡ ለማለት ፡ አዳም ፡ ገብሩ ፡ ሔዋን ፡ አመቱ ፡ ብሎ ፡ በደንጊያ ፡ የጣፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ከዚያ ፡ ነበረና ፡ ያንን ፡ ለማጥፋት ፡ ለመደምሰስ ። ፪ኛው ፡ ጥምቀት ፡ የሞት ፡ አርአያ ፡ የመቃብሩ ፡ አምሳል ፡ ነውና ፤ ከኀጥአን ፡ ጋራ ፡ ተቈጥሮ ፡ እንዲጠመቅና ፡ እንዲሰቀል ፡ የተጣፈውን ፡ ቃል ፡ ንስሓና ፡ ጥምቀት ፡ የሚሻ ፡ ፍጹም ፡ ኀጥእ ፡ መስሎ ፡ በዮሐንስ ፡ እጅ ፡ ለመፈጸምና ፡ ከላይ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ነቅ ፡ የተከተተውን ፡ የጥምቀት ፡ ቀሚስ ፡ ሽልማትና ፡ ጌጥ ፡ ምስጢረ ፡ ሥላሴን ፡ ለመግለጥ ። ፫ኛው ፡ የአዳም ፡ ኀጢአት ፡ ከናት ፡ ያፈሰስ ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ድረስ ፡ እንደሚሉት ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ወንዝ ፡ ነውና ፤ እስራኤል ፡ ዘሥጋ ፡ ከፈርዖን ፡ ባርነት ፡ ወጥተው ፡ ዮርዳኖስን ፡ በዚህ ፡ ወደብ ፡ ዐልፈው ፡ ተሻግረው ፡ ምድረ ፡ ከነዓን ፡ እንደ ፡ ገቡ ፤ እስራኤል ፡ ዘነፍስም ፡ ከሰይጣን ፡ ባርነት ፡ ወጥተው ፡ ያዳምን ፡ ኀጢአት ፡ በርሱ ፡ ጥምቀትና ፡ በክርስትና ፡ በጽድቁና ፡ በትሩፋቱ ፡ በሕማሙና ፡ በሞቱ ፡ ዐልፈው ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ ሰማያዊት ፡ ከነዓን ፡ እንዲገቡ ፡ መጠን ፤ መግባታቸውን ፡ ለመስበክ ፡ ነው ። (ሉቃ፲፱ ፡ ፳፩—፳ ። ፳፬—፳፯ ። ፬ነገ ፡ ፭ ፡ ፲፬) ። **እምጸፍላግሂ ፡ ወአብሕርት ፡ እንዘ ፡ ይእቲ ፡ ነዳስ ፤ ኢይትከሀል ፡ በበ ፡ ገጹ ፡ ነጊረ ፡ ዐበያ ፡ ለዮርዳኖስ ፤ አምጣነ ፡ ደግማይ ፡ አዳም ፡ መልክአ ፡ ዚአሃ ፡ ክርስቶስ ፤ ወከመ ፡ ትኩኖ ፡ ብእሲተ ፡ አልሀቃ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** (ቅኔ) ።

**የሱስ ፤—መድኅን ፤—ኢየሱስ ።**

**ዮቶር ፤ (ዕብ ፡ ዩቴር ፤ ይትሮ) ፤** የሰው ፡ ስም ፤ የሙሴ ፡ ዐማት ። ተረፍ ፡ ትራፊ ፡ ቅሬታ ፤ ወይም ፡ ከቍጥር ፡ ያልገባ ፡ ጭማሪ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ትርፈ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ (ዘፀ፫ ፡ ፩ ። ፬ ፡ ፲፰) ።

# ከ

**ከ ፤** ፲፩ኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፋ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፡ ስሙ ፡ ከፍ ፡ ቍጥሩ ፡ ከያ ፡ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ ከ ፡ ዕሥራ ፡ ይባላል ፤ ካያ ፡ ኻያ ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ ዐሥር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ከዕበተ ፡ የ ፡ እንደ ፡ ማለት ።

**ከ ፤ (ኩ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን) ፤** የአካል ፡ ዝር ፡ ዝር ፡ ጠቃሽና ፡ አሰሚ ፡ ወይም ፡ ምእላድ ። አንተ ፡ አንቲ ፡ አንትሙ ፡ አንትን ፡ የሚባሉትን ፡ የቅርብ ፡ የቅርቦችን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ፭ቱን ፡ ሰፊዎች ፤ **ነበብከ ፡ ኩ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ክን ፡** እያለ ፡ ዝርዝሮና ፡ ጠቅሶ ፡ ለይቶ ፡ ያሳያል ። እኔ ፡ ለሚለው ፡ ግን ፡ ከቀዳማይ ፡ በቀር ፡ በዝርዝር ፡ ኹሉ ፡ አይገባም ፡ ኩ ፡ የነበረውን ፡ የ ፡ ይወርሰዋል ፡ **ነበብኩ ፡ ንባብየ ።**

**ኬ ፤ (ኣ—መ—ሰ) ፤** የአንክሮና ፡ የአጋኖ ፡ የአስተብቍዖ ፡ ቃል ፡ በመጨረሻ ፡ ቃል ፡ እየገባ ፡ መድረሻውን ፡ ራብዕ ፡ በማድረግ ፡ ቃል ፡ ያገናኛል ፡ እኮ ፡ እንኳን ፡ ይኾናል ። ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ትርጓሜና ፡ ፍች ፡ ሳይፈልግ ፡ እንደ ፡ ከመ ፡ አዳማቂና ፡ የንባብ ፡ ጌጥ ፡ ኹኖ ፡ ይቀራል ። **ምንትኬ ፡ ሰብእ ፡ ዘይደንሶ ፡ እሳት ። ምንትኬ ፡ ዘአሜሃ ፡ ዐውያት ፡** (አንክሮ) ። **ንግባእኬ ፡ ኀበ ፡ ጥ ፡ ነ ። ውእቱኬ ። አንትሙኬ ። ዝኬ ፡ ውእቱ ፤ ዝኬ ፡ እፎ ፡** ይህ ፡ ነዋ ፡ ይህሳ ፡ (አጋኖ) ። **ወይንኬ ፡ አልቦሙ ፤** የላቸውም ፡ እኮ ፡ (ምልጃ) ። **ርእዩ ፡ እሙ ፡ ይዌልጡ ፡ አሕዛብ ፡ አማልክቲሆሙ ፡ እንዘኬ ፡ ኢኮኑ ፡ አማልክተ ፤** እንኳን ፡ (ኤር፪ ፡ ፲፩) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በቀዋ ፡ ፈንታ ፡ **አቡኬ ፡ ዐፀ ፡ ዘኢይፈሪ ። ዘኬ ፡ ፈትሐ ፡ አሐተ ፡ እምላ ። ዐሪትስኬ ፤** እያለ ፡ አስበታው ፡ ገብቶ ፡ ይገኛል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ማ ፡ ይኾናል ፡ ይኸውም ፡ በንባብና ፡ በትእዛዝ ፡ እንቅጽ ፡ ሲገባ ፡ ነው ። **ነዐኬ ፡ በሊኬ ፤** ናማ ፡ በልማ ፡ (ዕርጽ ፡ ቀ፲፱) ።

**ከእብ፤—ኹለተኛ፤—ክዒብ፡ ከዐበ።**

**ከአወ፤—አፈሰሰ፤—ክዒው፡ ከዐወ።**

**ኰኢስ፤—ታላቅ፡ ግንብ፤—ኰዒስ፡ ኰዐሰ።**

**ከበ፤—ኰበት፤—ከበወ።**

**ከቢብ፤ ቦት፤ (ከበበ፡ ይከብብ፡ ይክብብ። ዐረ፡ ከበ። ሱር፡ ክባብ)፤** መክበብ፡ ማጠር፤ መሾም፡ ማክበር፤ መጥራት፡ ማደም፤ መሰብሰብ፡ ማከብ፤ በዓል፡ ሰርግ፡ ጉባኤ፡ ማድረግ። ከመ፡ ይቁሙ፡ ክቢቦሙ፡ እሳቱ፡ ከመ፡ አረፍት። ርእየቶ፡ ለዳዊት፡ ምስለ፡ ዙሉሙ፡ ማኅበረ፡ ነቢያት፡ ወነፍሳተ፡ ጻድቃን፡ ክቢቦሙ፡ ከመ፡ አረፍት። ሐዋርያቲሁ፡ ከበበ፡ እግረ፡ አርዳኢሁ፡ ኀፀበ፡ (ገድ፡ ተክ። ስንክ፡ የካ ፲፰። ድጓ)። ማኰብ፡ ማኳስ፡ መጠምጠም፡ የፈትል። ማንከብከብ፡ ማንከብለል፤ ክብ፡ እንክብል፡ ማድረግ፤ የርጥብ፡ ነገር፡ የመድኀኒት።

**ከባቢ፤** በቁሙ፤ የሚከብ፤ ሰብሳቢ።

**አክበበ፤** አስከበበ፤ ጉባኤ፡ አስደረገ።

**መክብብ፤ (ብት፡ ባን፡ ባት)፤** የሚከብ፡ የሚያስከብብ፤ ከባቢ፡ አስከባቢ፤ ሹም፡ አለቃ፡ ሰብሳቢ። ኩን፡ መክብበ፡ አሕዛብ። በመክብበ፡ ማኅበሮሙ፡ ለቅዱሳን፡ (ኵፋ፡ ፳፯። አርጋ፡ ፱)።

—፤ የቍጥር፡ ድምር፤ ድምላ፡ ጠቅላላ፡ ቍጥር። ሰመንቱ፡ እልፍ፡ ወሰብዓ፡ ምእት፡ ኮነ፡ መክብበ፡ ኍልቆሙ። ወኮነ፡ መክብበ፡ አጿብዒሁ፡ ዕሥራ፡ ወአርባዕቱ፡ (፩ዜና፡ ፯፡ ፰። ፳፡ ፮)። ዘመን፡ መዋዕል፡ በማለት፡ ፈንታ፡ መክብብ፡ ይላል፤ ስሕተት፡ ነው። ወኮነ፡ መክብበ፡ ንግሡ፡ ለዳዊት፡ አርብዓ፡ ዓመተ፡ (፩ዜና፡ ፳፱፡ ፳፯)።

—፤ ኰሉ፡ ኵለንታ፤ መላው። መክብበ፡ ሥጋ። መክብበ፡ መጻሕፍት፡ ዘብሉይ፡ (ፊልክ፡ ፲፪። መጽምስ)።

—፤ መጨረሻ፡ መደምደሚያ፤ ጕልላት። የሐንስ፡ መክብበ፡ ነቢያት። ጴጥሮስ፡ መክብባ፡ ለስምዐ፡ ሃይማኖት፡ (አዋል። ስንክ፡ የካ፩)።

—፤ ወገን፡ ዐይነት። እብነ፡ ሰም፡ በበ፡ መክብቡ፡ (፩ዜና፡ ፳፱፡ ፪)።

—፤ የመጽሐፍ፡ ስም፤ ከመጻሕፍተ፡ ሰሎሞን፡ አንዱ። ርሱው፡ ራሱ፡ ሰሎሞን፤ ሰባኪ፡ መምህር፡ መገሥጽ፡ ማለት፡ ነው፤ ቈሀልትን፡ እይ። ቃለ፡ መክብብ፡ ወልደ፡ ዳዊት፡ (መክ፩፡ ፩፡ ፲፪። ፯፡ ፳፰። ፲፪፡ ፰፡ ፱)።

**ተከበ፤** ተከበበ፤ ተሰበሰበ፤ ተኮበ፡ ተኳሰ፤ ተንከበከበ፡ ክብ፡ እንክብል፡ ኾነ።

**ክቡብ፤ (ባን፡ ባት፡ ብብት)፤** የተከበበ፤ ክብ፡ እንክብል፤ ድንብልብል። እስመ፡ ምድር፡ ክቡብ፡ ከመ፡ ከራ። ከመ፡ ዐይኑ፡ ማኅተም፡ ክቡብ። ሕእባን፡ ክቡባት፡ ወልሙዳት፡ (አዋል። ተረ፡ ቄርሎ)። በክቡባት፡ ፈንታ፡ ክበብት፡ ይላል፤ ስሕተት፡ ነው፡ (ጊ፡ ወ፡ ሐ፡ ገ፲፬። ሄርማ፡ ገ፲፫። ፹፭)።

**ክበብ፤ (ብት)፤** በቁሙ፤ ዘውድ፡ ዙፋን፤ ክብነት። ይቁሙ፡ ካህናት፡ ክበቡ፡ ለምሥዋዕ። ክበቡ፡ ከመ፡ ፀሓይ፡ (ማንዘ። ሔኖ፲፬፡ ፲፰)።

—፤ ኰብ፤ ኳስ። ክበበ፡ አፍትልት፡ (ታሪ፡ አኰ)።

—፤ ክቡብ፡ ያለው፡ ገንዘብ፡ ብር፤ የገንዘብ፡ ቍጥር። የሐሰብ፡ ሎቱ፡ ካህን፡ ክበበ፡ ሤጡ፡ (ዘሌ፳፯፡ ፳፫)። በክበብ፡ ፈንታ፡ መክብብ፡ ይላል፡ (፩ዜና፡ ፳፡ ፯)።

**ከብከበ፤ (ተቀ፡ ግ)፤** አኰበኰበ፡ ኰብ፤ ኰብ፡ አለ፤ ያኰኰደ፡ የዘፈን፤ የዝሳይ፡ (ትግሬ)። ኰብ ኰባ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ወጥቷል። ከበከበ፤ ተከባከበ፡ አከበረ፡ (ዐማርኛ)።

**ከብካብ፤** ሰርግ፤ የመርዓዊና፡ የመርዓት፡ ጉባኤ፤ የዘፈን፡ የደስታ፡ በዓል፡ (ዮሐ፪፡ ፩። ሉቃ፲፬፡ ፰፫። ማቴ፳፪፡ ፪)። ገብረ፡ ከብካበ። መዋዕለ፡ ከብካብ። እመ፡ ከብካብ። በከመ፡ መርዓዊ፡ ይትፌሣሕ፡ በውስተ፡ ከብካቡ፡ (ዘፍ፳፱፡ ፳፪። አስቴ፪፡ ፳፪። ጦቢ፮፡ ፲፱። ቀሌ)።

**አንከብከበ፤** አንከበከበ፤ ተንከበከበ፤ የፍትፍት፡ (ዐማርኛ)።

**ከቢድ፤ ዶት፤ (ከብደ፡ ይከብድ፡ ይክበድ። ዕብ፡ ካቤድ)፤** መክበድ፡ መመንዘል፤ መብለጥ፡ መብዛት፤ በሚዛን፡ በቍጥር። ምንት፡ ይክብድ፡ እምነ፡ ዐረር። ይከብድ፡ እምኆጻ፡ ባሕር፡ (ሢራ ፳፪፡ ፲፬። ኢዮ፮፡ ፫)።

—፤ መጥናት፤ መበርታት፡ ማየል። ከብደ፡ ልቡ፡ ለፈርዖን። ወከብደ፡ ቀትል፤ ዲበ፡ ሳኦል። ከብደ፡ ደዌሁ፡ (ዘፀ፯፡ ፲፬። ፩ዜና፡ ፲፡ ፫። ፫ነገ፡ ፲፯፡ ፲፯)።

**ክቡድ፤ (ዳን፡ ዳት፡ ብድ)፤** በቁሙ፡ የከበደ፡ ከባድ፤ ጥኑ፡ ብርቱ፤ ክቡር፡ ታላቅ፤ ዐያሌ፡ እጅግ፡ ብዙ። ነገሩ፡ ለአብድ፡ ከመ፡ ጾር፡ ክቡድ። ሕማም፡ ክቡድ። ብፃው፡ ክቡድ። ብእሲ፡ ክቡድ። ትእምርቱ፡ ክቡድ፡ (ሢራ፳፩፡ ፲፯። ፴፱፡ ፱። መጽምስ። ፩ነገ፡ ፬፡ ፲፰። ስንክ፡ ነሐ፲፱)።

**ክብደ፡ ሐሪት፤** ዳተኛ፡ ዝግተኛ፤ ቀርሳሳ፡ (ማብሰ፳፯፡ ፯)።

**ክቡደ፡ መዝራዕት፤** ጡንቻም፡ እጀ፡ ወፍራም፤ ክንደ፡ በርዳዳ።

**ክቡዳን፡ አቅርንት፤** ቀንዳሞች፤ ቀንደ፡ ትልልቆች፡ (መዝ፡ ፸፱)።

**ክቡዳን፡ ጾር፤** ሸክም፡ የከበዳቸው፤ ሐማሎች።

**ከበድ፤ (ዳት)፤** መክበድ፤ አከባበድ፡ ከባድነት፤ ክብደት፤ ብዛት። ከበደ፡ ጾርነ፡ አቅለለ። ከበዱ፡ ለጸባሕት። ከበደ፡ ንዋም። ከበደ፡ ቅኑ። ከበዳ፡ ለስብሐቲከሙ። አልቦ፡ ዘይክል፡ ጸዊረ፡ ከበ

ይሙ ፡ ኢአድባር ፡ ወኢአውግር ፡ ወኢቈላት ፡ (መዋ ሥ ። ስንክ ፡ የካ፳ ፡ ቅዳ ፡ ያዕ ። ፪ዜና ፡ ፲ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ግንቦ ፡ የዲ፳ ፡ ፱) ። ሸክም ፡ ሒሳብ ፡ ሐዘን ፡ ክባድ ፡ ነገር ። ኢይወዲ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ክቡደ ። ሰምንት ፡ ይ ከውን ፡ ገብርከ ፡ ክቡደ ፡ ላዕለ ፡ እግዚእየ ። ግድፍ ፡ እምላዕሌከ ፡ ክቡደ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ። ከመ ፡ ያቀ ልል ፡ እምኔሁ ፡ ክበዳቲ ፡ (ፊልጵ ፡ ፳፱ ። ፪ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፴፭ ። ሉቃ ፡ ዕብ፲፱ ፡ ፲፪ ። ፊልክ ፡ ፲፫፭ ። ዕብ፲፪ ፡ ፩) ።

—፤ ቤት ፡ ማንባ ፤ በቤት ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፤ ብዙ ፡ ብዕል ፡ ክብር ፡ ወርቅ ፡ ብር ፤ ስባሬ ፡ ሥንዋር ፤ ደጃፍ ፡ የመለ ስው ፡ ማጀት ፡ የጐረሠው ፡ የቤት ፡ ዕቃ ። እግዚ ፡ የአ ምር ፡ ክበዳሃ ። ወትትካፈልዎ ፡ ለክበዳሃ ። ማኅ ፈደ ፡ ክበዲከ ። አስጠመ ፡ ዘሎ ፡ ክበዳሃ ፡ (መዝ ፡ ፵፰ ። ፻፭፭ ። ሰቈ፪ ፡ ፳) ። ርጉዝ ፡ ክበት ፤ ላም ፡ ባዝራ ። የሐር ፡ ገመድ ፡ የበቅሎ ፡ ክበድ ፡ እንዲሉ ፡ (ፀማርኛ) ።

**አክበደ** ፤ አክበደ ፤ አስከበደ ፡ አበዛ ፡ አጸና ። አክበድኪ ፡ አርዑቶሙ ፡ ፈድፋደ ። በኢያእምሮ ፡ ያከብድ ፡ ነገሮ ። አክበደ ፡ ሙሴ ፡ ተክዞ ፡ ጥቀ ። አለ ፡ ያከብዱ ፡ ዲበ ፡ አግብርቲሆሙ ፡ ቀኔ ፡ እኩየ ። አክበድክሙ ፡ ላዕሌየ ፡ ነገረክሙ ፡ (ኢሳ፵፯ ፡ ፮ ። ኢዮ ፴፭ ፡ ፲፯ ። ዘኍ፲፯ ፡ ፲፭ ። ዲድ ፡ ፳፭ ። ሚልኪ ፡ ፲፫) ።

—፤ ጣን ፡ ጨቈን ፡ አሸከመ ፤ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ማክ ብድ ፡ ነው ። ኢታክብድ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጾረ ፡ ክቡደ ። ይ ደሉ ፡ ከመ ፡ ያክብዱ ፡ ቀዋና ፡ ላዕሌሁ ፡ (ቀሌ ። ፈ መ ፡ ፲፩ ፡ ፱) ። በአክበደ ፡ ፈንታ ፡ አስተክበደ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ ፩ ፡ ነው ። አስተክብዶ ። ኢያስተክብድ ፡ ላዕ ሌሆሙ ፡ (ዲድ ፡ ፴፱ ። ፵፭) ።

**አስተክበደ** ፤ አክበደ ፤ አከባበደ ፤ አስተባሰ ፤ የመሞላትና ፡ የመሰቀቅ ። ማስንት ፡ በጉልና ፡ ሐውልት ፡ በለ ፡ ኾነ ፡ ፍችው ፡ እንደ ፡ አክበደ ፡ አድራጊ ፡ ነው ። ለ እመ ፡ አስተፀጸበ ፡ ወአስተካበደ ፡ ንስሓሁ ፡ ዘወሀ ብዎ ፡ ካህናት ፡ (ቀሌ) ። ይቴክዝ ፡ ወያስተካብድ ፡ ፍና ፡ መንሱት ። አስተካበደ ፡ ሐሚመ ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ክብድ** ፤ (ዕብ ፡ ካቤድ ። ሱር ፡ ካብዳ ። ዐረ ፡ ኪብድ) ፤ ጉበት ፤ ከንሞያተ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፤ የሐሞት ፡ ምንጭ ፡ በደንቱ ፡ ዳማ ። ምትሮ ፡ ለዝ ፡ ዓሣ ፡ ወንሣእ ፡ ልቦ ፡ ወክብዶ ፡ ወሐሞቶ ። ሕብረ ፡ ክብድ ፡ (ጦቢ፯ ፡ ፱ ። ዘኍ፱ ፡ ፯) ።

—፤ ሆድ ፡ ማኅደረ ፡ ክብድ ፤ ሸክም ፡ ወይም ፡ ተሸካሚ ፡ ማለት ፡ ነው ። አስክቡኪ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ በክብ ድኪ ። ገዚፍ ፡ ዐምድ ፡ ዘአንበሩ ፡ ዲበ ፡ ክብዱ ። በእንተ ፡ ሕማመ ፡ ክብድከ ፡ (ኢሳ፶፩ ፡ ፳፫ ። ስንክ ፡ ጳጕ፭ ። ፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፳፫) ።

**ከበወ** ፤ (ዕብ ፡ ካባህ) ፤ ጠፋ ፡ ጠሰሰ ፤ ፈዘዘ ፤ ዕልም ፡ ድርግም ፡ አለ ፤ የእሳት ፡ የመብራት ፡ የዐይን ።

**ክቡ** ፤ ኵበት ፡ የደረቀ ፡ እበት ፤ ፋሕምና ፡ ብር ሃን ፡ የሌለው ። ሐመደ ፡ ክቡ ፡ (ኵፋ ፡ ፳፰) ። ከበተንና ፡ ለከወን ፡ እይ ።

**ኰብኰበ** ፤— ሰርግ ፤— ከቢብ ፡ ከበበ ፡ ኰብኰበ ።

**ከበለ** ፤ (ዕብ ፡ ካቤል) ፤ አሰረ ፡ ዘነጀረ ፤ በ ብረት ። ኵንበሎን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ከበሎ** ፤ (ዕብ ፡ ኬቤል) ፤ ማሰሪያ ፤ የግር ፡ ብረትና ፡ የሰንሰለት ፡ ፍንጅ ፤ የማጥን ፡ ገርር ፡ ቀለበት ፡ ዙሪያው ፡ ክብ ፡ የኾነ ፡ ምእዙን ፡ ያደደለ ። ወትገብር ፡ ውስተ ፡ አርባዕቱ ፡ መሳምክቲሃ ፡ ለታቦት ፡ አርባዕተ ፡ ከበሎ ፡ (ኩብ ፡ ነ፻፳) ። ዕብንን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ከቢር** ፤ ሮት ፤ (ከብረ ፡ ይከብር ፡ ይክ በር ። ዐረ ፡ ከቡረ ። ዕብ ፡ ክባር ፤ ዱሮ ፡ ቀድሞ) ፤ መከበር ፡ መከበር ፤ መወደድ ፤ ማደግ ፡ መ ብለጥ ፤ መግነን ፡ ታላቅ ፡ መኾን ፤ የሀብት ፡ የዋጋ ፤ የማ ዕርግ ፡ የድግ ፤ የወርድ ፡ የቁመት ። ክቢር ፡ እንዲል ፡ ዐሪብ ፤ ታላቅ ፡ ሲል ። በክብረ ፡ አቡሁ ፡ ይከብር ፡ ሰ ብእ ። ቦ ፡ ዘይከብር ፡ በአትሕቶ ፡ ርእሱ ። ዘይው ኅድ ፡ ይከብር ፡ ወይቴሐት ፡ ዘይበዝኅ ። ብክሙ ፡ ይከብር ፡ ዘርዐ ፡ አብርሃም ። ውእቱ ፡ ይከብር ፡ እም እሆሙ ፡ (ሢራ፫ ፡ ፲፩ ። ፳ ፡ ፲፩ ። ሉቃ ፡ ዕብ፲፩ ፡ ፴፫ ። ኵፋ ፡ ፴፯ ። ዳን፲ ፡ ፱) ። በከብረ ፡ ፈንታ ፡ ተከበረ ፡ ይላል ፤ ተ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። ወእንስትኒ ፡ ይትከበራ ። ተክባሪ ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፰ ። ሲኖ ፡ ዶ) ።

**ክቡር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ብርት) ፤ በቁሙ ፤ የከበረ ፤ የተከበረ ፤ የተወደደ ፡ ውድ ። ብእሲ ፡ ክቡር ፤ ዕንቍ ፡ ክቡር ። ክቡረ ፡ ስም ፡ ክቡረ ፡ ሜጥ ። ዕደው ፡ ክቡራን ። አልባስ ፡ ክቡራት ። ሀገር ፡ ክብርት ፡ (ሚራ ፵፱ ፡ ፩ ። እርጋ ፡ ፪ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፲፯) ።

**ክብረት** ፤ በቁሙ ፤ መክበር ፤ አከባበር ፤ ክበ ሬታ ። ውድነት ፤ ክቡርነት ።

**ክብር** ፤ (ራት) ፤ በቁሙ ፤ ልዕልና ፡ ላቂያ ፡ ብልጫ ፤ ሹመት ፡ ሽልማት ፤ ታላቅነት ፤ ኀይል ፡ ብዕል ፤ ብዙ ፡ ገንዘብ ። ወድቀት ፡ እምክብራ ፡ ትካሑ ፡ እም ክብራ ። በእንተ ፡ ክብረ ፡ ዘመዱ ። ዘሎ ፡ ክብሩ ፡ ለሰብእ ፡ ከመ ፡ ፍሬ ፡ ሣዕር ። መንግሥታት ፡ ዓለም ፡ ወክብሮሙ ። ዘጌሠ ፡ ድኅሬሆን ፡ ለክብራት ፡ ይጐ ይይሁ ፡ (ቀሌ ። ስንክ ፡ ጳጕ፭ ። ኢሳ፵ ፡ ፯ ። ማቴ፬ ፡ ፰ ። ማር ፡ ይሥ) ።

**ክብርና** ፤ ክቡርነት ። በቁሙ ፤ የሴት ፡ ልጅ ፡ ክብር ፤ ማኅተመ ፡ ድንግልና ።

**ክብረ ፡ ነገሥት** ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ያኵስ ሞች ፡ መጣፍ ፤ ኑቡረ ፡ እድ ፡ ይሥሐቅ ፡ በላስቶች ፡ ዘ መን ፡ የደረሰው ፤ ወይም ፡ ከዐረብ ፡ የመለሰው ፤ የጽላተ ፡ ሙሴን ፡ አመጣጥ ፡ የአኵስምን ፡ ልዕልና ፤ የነገሥታቷን ፡ ክብር ፡ ከሰሎሞን ፡ መወለዳቸውን ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ የሚናገር ።


**አክበረ** ፤ አከበረ ፤ አላቀ ፡ አበለጠ ፤ አስከበረ ፡ አሰደደ ። አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ። አክበረ ፡ እግዚ ፡

አብ ፡ ኀዐለ ፡ ውሉዱ ። እግዚ ፡ አክበረከ ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፲፪ ። ሚራ፫ ፡ ፪ ። ኢሳ፶፰ ፡ ፲፫) ።

**አክባሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤** በቁሙ ፤ የሚያከብር ፡ የሚያስከብር ። እስመ ፡ እሙንቱ ፡ መል ክአ ፡ እግዚ ፡ አክባሬት ፡ ለሆሎሙ ፡ ሰብእ ፡ (ፊልክ ፡ ፹፯) ።

**ክብረወ ፤ (ተቀ ፡ ግ ። ዕብ ፡ ቶፈፍ) ፤** ጸፋ ፡ መታ ፡ ኩረኩረ ፤ ጐሰመ ።

**ከበሮ ፤ (ብ ፡ ከባሮው) ፤** በቁሙ ፤ ንዋየ ፡ ማሕሌት ፡ አታሞ ፡ ነጋሪት ፤ ከማዕደን ፡ ከንጨት ፡ ከቈ ርበት ፡ የሚሠራ ፤ ስለ ፡ ክብረ ፡ በዓል ፡ የሚመታ ። ክብ ራዊ ፡ ትእምርት ፡ ክብር ፤ ፎኒኬ ፡ ተሰሚ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሰብሕዎ ፡ በከበሮ ። ንሥኡ ፡ ከበሮኪ ። መሰንቆ ፡ ወከ በሮ ፡ (መዝ ፡ ፻፶ ። ኤር፴፰ ፡ ፬ ። ዳን፫ ፡ ፲) ።



ከበሮ ፡

**ክብሬት ፤ (ዐረ ፡ ኪብሬት ። ሱር ፡ ክብ ሬታ ። ዕብ ፡ ጎፍሬት) ፤** በቁሙ ፤ ዲን ፡ የእሳት ፡ ዐፈር ፡ እሳታዊ ፡ ሚቃ ፤ ዐይነቱ ፡ ብጫ ፡ ክርፋታም ፡ (መቃ ፡ ገ፪) ።

**ክብሬታዊ ፤** የዲን ፡ ዐፈር ፡ ሚቃ ፤ የዲን ፡ ውሃ ። ይነግእ ፡ ሙዳየ ፡ ልሕዙት ፡ ወይደይ ፡ ውስ ቴቱ ፡ ማየ ፡ መሪረ ፡ ክብሬታዊተ ፡ ወይነግእ ፡ መ ሬተ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፯ ። ዘኍ፳ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰) ።

**ክብሩታን ፤** ስመ ፡ ሀገር ፡ በምድረ ፡ እስራ ኤል ፡ ያለች ፡ አንዲት ፡ ገጠር ። (ኩፋ ፡ ፴፪) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ በክብሩታን ፡ ፈንታ ፡ ኬብሮን ፡ ይላል ፤ ባለብ ሉዮችም ፡ ክብሩታንን ፡ ኬብሮን ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ። በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ሔብሮንና ፡ ክብሩታን ፡ ልዩ ፡ ነው ።

**ከቢስ ፤ ሶት ፤ (ከበሰ ፡ ይከብስ ፡ ይክ ብስ ። ዕብ ፡ ካባስ ፤ ዐጠበ ፡ አጠራ ፡ ወለወለ ። ከበሽ ፤ ያዘ ፡ ግዛ ፡ ማቀየ ፡ አጠቃ) ፤** መከበስ ፡ ማከበስበስ ፤ ጠጕርን ፡ ሰብስቦ ፡ ጠምዞ ፡ በማኽል ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ መጠቅለል ፡ ማሰር ፤ በወለባና ፡ በሚይዶ ፡ መያዝ ፡ መቸንከር ። ራስን ፡ ጠጕርን ፡ በሚታሰርና ፡ በሚደፋ ፡ በሚለበስ ፡ ነገር ፡ መሸለም ፡ ማስጌጥ ፡ ማንቈጥቈጥ ።

**ተከብሰ ፤** ተከበሰ ፤ ተከበሰበሰ ፤ በራሱ ፡ ላይ ፡ ጌጥ ፡ ተሸከመ ፤ ተሸለመ ። ፀፈረት ፡ ርእሳ ፡ ወተከብ ሰት ፡ (ዮዲ፲፮ ፡ ፰) ።

**ክቡስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ብስት) ፤** የተከበሰ ፡ ክቡስ ፡ ከብስብስ ፤ ጌጥ ፡ ወዳድ ።

**ክብሶ ፤ (ብ ፡ ከባስው ፤ አው ፡ ክብሳት) ፤** ክብስ ፡ ጠጕር ፡ ክብሳት ። የራስ ፡ የጠጕር ፡ ክባስ ፤ በስተ ላይ ፡ የሚኾን ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፡ ቀጸላ ፡ ሠርመዲ ፡ ፀይን ፡ ርግብ ። ውስተ ፡ መካነ ፡ ስርጐ ፡ ዘክብሶ ፡ ሥዕርታ ፡ ወደየት ፡ ሐመደ ። ክብሶሆን ፡ ወአልባሲሆን ፡ ዘሜ ላት ፡ (አስቴ፬ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፫ ፡ ፳) ።



ክብሶ ፡

**ኩብስ ፤ ክብስ ፤** ኩብሽ ፤ የደዊ ፡ ስም ፤ ገላ ፡ የሚነፋ ፡ የሚያሳብጥ ፤ የሚያፈርስ ፡ የሚቈምጥ ፤ ቍም ጥና ፡ ቢስ ፡ ገላ ። አዝልፎ ፡ ስካር ፡ ያመጽእ ፡ ነቀጥ ቃጠ ፡ ወጥፍአተ ፡ ልብ ፤ ወኩብሰ ፡ ወሞተ ፡ ግብት ፡ ወፈፀንተ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶) ።

**ከቢት ፤ ቶት ፤ (ከበተ ፡ ይከብት ፡ ይክ ብት ። ኀብአ) ፤** መከበት ፤ መሸሸግ ፡ መሰወር ፡ መደ በቅ ፤ እንዳይገኝ ፡ ማድረግ ። ኢትረክበ ፡ እስመ ፡ ከቢቶ ፡ እግዚ ። ከበተት ፡ ርእሳ ። ኢንክል ፡ ከቢቶቶ ። ይኄ ይስ ፡ አብይ ፡ ዘየኀብእ ፡ እበደሁ ፡ እምጠቢብ ፡ ዘይ ክብት ፡ ጥበቢሁ ፤ (ዕብ፲፩ ፡ ፭ ። ሉቃ፩ ፡ ፳፬ ። ግብ፬ ፡ ፲፯ ። ሢራ፳ ፡ ፴፩) ።

—፤ ማሳደር ፤ ክቤት ፡ ከበረት ፡ ማግባት ፤ መጠበቅ ፡ መመ ልከት ፤ የንግዳ ፡ የከብት ። ክብት ፡ ማለት ፡ ቅሉ ፡ ኽበ ትም ፡ ሳይቀር ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ከባቲ ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤** የሚከብት ፡ ከባች ፤ ሸሻጊ ፡ ደባቂ ። ከባቲሁ ፡ ለሹሉ ፡ ክሡት ። አም ላክ ፡ ከባቴ ፡ አበሳ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ። ማንዘ) ።

**አክበተ ፤** አስከበተ ፤ አስደበቀ ፤ አስጠበቀ ።

**ተከብተ ፤** ተሸሸገ ፡ ተደበቀ ፤ ታባ ፡ ተሰወረ ፤ ከበታው ፡ ታጣ ። ተክብተ ፡ ሔኖክ ። ከመ ፡ ትትከበት ፡ መንፈስየ ። ስእነ ፡ ተክብቶ ፡ (ሔኖ፲፪ ፡ ፩ ። ሮ፩ ፡ ፩ ። ማር፯ ፡ ፳፬) ።

**ክቡት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ብት) ፤** የተሸሸገ ፡ ሽሽግ ፤ ክብት ፡ ስውር ፡ ድብቅ ። ጥበብሰ ፡ ክቡት ፡ ወ መዝገብ ፡ ዘኢያስተርኢ ። ኅቡእ ፡ ወክቡት ። ክቡተ ፡ ትአምር ፡ እስመ ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ሀሎከ ፡ (ሢራ፵፩ ፡ ፲፬ ። ሄቆር ፡ ፪ ፡ ፯ ። ቅዳ ፡ ሐዋ) ።

**ክቡታዊ ፤** የውስጥ ፡ የልቡና ፡ ረቂቅ ፡ መን ፈሳዊ ። ሥርዐት ፡ ክቡታዊ ፡ (ፊልክ ፡ ፫) ።

**ክብተት ፤** (ላ ፡ ጥ) መሸሸግ ፤ ሽሽጋ ፡ ሽሽግ ነት ። ክብቴት ፡ ዘኢየንልቅ ፡ (ፊአ ፡ ሲኖ) ።

**ከበታ ፤** ስዋሬ ፡ ስወራ ፤ ስውርነት ። በመንክ ራቲሁ ፡ ያርኢ ፡ ከበታሁ ። ኢይነግር ፡ ስእንተ ፡ ከበ ታየ ፤ አሳ ፡ በዘያስተርኢ ፡ (ተረ ፡ ቂርሽ ። ፲) ።

**ኬደ ፤—ረገጠ ፤—ከዪድ ፡ ኬደ ።**

**ከደዋ ፤ (ዕብ ፡ ክድክድ) ፤** ዕንቍ ፡ የዕንቍ ፡ ስም ፡ ሕብሩ ፡ የሮማን ፡ ዐይነት ፡ እንደ ፡ በረበሮ ፡ ያለ ፤ የሚፈልቅ ፡ የሚብለጨለጭ ። ሦሰስቱ ፡ አዕናቊ ፡ ዘወርቅ ፡ ወብሩር ፡ ወከደዋ ። ወርቅ ፡ ወከደዋ ፡ ወብሩር ፡ ወካልአን ፡ አዕናቊ ፡ ሀሰዉ ፡ ይትረከቡ ፡ እስከ ፡ ዮም ፡ (ታሪ ፡ አክ ፡ ፻፺፫) ።

**ከድከድ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ከደዋና ፡ ከድኮድ ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ነው ። ረሰሙት ፡ ወከድኮድ ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፲፮) ። በከድኮድ ፡ ፈንታ ፡ ከርከንድ ፡ ይላል ፤ ከርከዴን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ፍችውን ፡ በቦታው ፡ ተመልከት ።

**ከዲን ፤ ኖት ፤ (ከደነ ፡ ይከድን ፡ ይክድን ። ዕብ ፡ ከዳን ፤ አሰረ ፡ አቈራኘ ፡ የፈረስ ፡ የሠረገላ) ፤** መክደን ፡ መግጠም ፡ ማልበስ ፡ መሸፈን ፤ መሰወር ፡ መጋረድ ፤ እንዳይታይ ፡ ማድረግ ። አምጽኡ ፡ አብነ ፡ ወከደኑ ፡ ዲበ ፡ አፈ ፡ ግብ ። ከደነት ፡ ንፍረታ ፡ በቈጽል ። ፈጸምሙ ፡ ከዲኖ ፡ ዘቅድሳት ። ዘይከድን ፡ አበሳሁ ። ይከድኑ ፡ ገጾሙ ፡ (ዳን፮ ፡ ፲፯ ። ኩፋ ፡ ፫ ። ዘኍ፬ ፡ ፲፭ ። ምሳ፳፰ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፮ ፡ ፪) ።

**ከዳኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት ፤ ደንት) ፤** የሚከድን ፡ የሚያለብስ ፡ ከዳኝ ፡ ሰዋሪ ፡ ጠባቂ ፤ ጠባቂ ፡ ጠበቃ ። ልብሰ ፡ ጽድቅከ ፡ ይኩነኒ ፡ ከዳኔ ። ለመበለት ፡ ከዳኒ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳ ። ኪዳ) ።

**መክድን ፤ መክደኒ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ።

**አክደነ ፤** አስከደነ ፡ አስለበሰ ።

**ተከድነ ፤** ተከደነ ፡ ለበሰ ፡ ተሰወረ ፡ ተሸፈነ ። ትትከደኑ ፡ ወኢትመውቁ ። ከመ ፡ ትትከደኑ ፡ በዕሴተ ፡ መዐቱ ፡ ለእግዚ ። ተከድነት ፡ ገጻ ፡ (ሐጌ፩ ፡ ፮ ። ዕርገ፪ ፡ ፫ ። ዘፍ፳፱ ፡ ፳፭) ።

**ክዱን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ድንት) ፤** የተከደነ ፡ የለበሰ ፡ ስውር ፡ ሽፍን ። ክዱን ፡ እብን ፡ ዲቤሁ ። ክዱን ፡ ብከ ፡ ዐቢይከ ። ክዱን ፡ ትምህርትነ ፡ (ዮሐ፲፩ ፡ ፴፰ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ፩ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፫) ።

**ክድነት ፤** መክደን ፡ መከደን ፤ አከዳደን ፡ አለባበስ ፡ ከዱንነት ። የሴት ፡ ልብስ ፡ ሽፍን ፡ ንፍረት ። ኢይከሥት ፡ ክድነተ ፡ አቡሁ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፫) ።

**ከዳን ፤ (ናት) ፤** በቁሙ ፤ መከደኛ ፡ መግጠሚያ ፤ ልብስ ፡ ቀሚስ ፤ መጐናጸፊያ ፤ ስሐፍ ፡ ምንጣፍ ፤ መጋረጃ ፡ ድንኳን ፤ ዳስ ፡ ጥላ ፡ ክለላ ፡ ቤት ፡ ጐጆ ፤ የሚሰውርና ፡ የሚሸፍን ፡ ኹሉ ። ከዳነ ፡ ዐዘቅት ። ዘቦ ፡ ክልኤ ፡ ከዳናት ። ከዳን ፡ ዘሕብረ ፡ ዐስቅ ። ትክድዎሙ ፡ ከዳነከ ። ነሥአ ፡ ከዳነ ፡ ወጠምዐ ፡ ውስተ ፡ ማይ ። ከዳንከ ፡ ዘታሕተ ፡ ገቦከ ። ከዳን ፡ በዘይትገለበቡ ፡ እምጠል ፡ (፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ። ሉቃ፫ ፡ ፲፩ ። ዘፍ፴፪ ፡ ፫ ። ሕዝ፳ ፡ ፫ ። ፬ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፭ ። ምሳ፳፱ ፡ ፳፯ ። ኢሳ፬ ፡ ፮) ።

**መክደን ፤ (ብ ፡ መከድን) ፤** መከደኛ ፡ መሸፈኛ ፤ ከዳን ፡ ልብስ ። አልቦ ፡ ማዕር ፡ ለመከደኖን ። አምሳለ ፡ መክደን ። መከደኑ ፡ አርእስተ ፡ ዘተጼን ፤ የራስ ፡ ቍር ፡ (ገድ ፡ ላሊ ። ፈልክ ፡ ፶፩ ። ፪ዜና ፡ ፳፯ ፡ ፲፯) ።


**መክደንት ፤ (ታት) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ።

**ምክዳን ፤** ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፡ መከደኛ ፡ መከደኛ ።

**ኪዳን ፤—ውል ፤—ከዩድ ፡ ኬደ ።**

**ክሂሀ ፤ ሆት ፤ (ከህሀ ፡ ይክህሀ ፡ ይክሀሀ ። ዕብ ፡ ካሃሀ ፡ ይክሄሀ) ፤** መድከም ፡ ማነስ ፤ መጨለም ፡ መፍዘዝ ፤ መደንገዝ ፤ የኀይል ፡ የጕልበት ፡ የዐይን ፡ የብርሃን ። ከበወንና ፡ ለከወን ፡ እኒህ ፡ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ። ከሕክሐም ፡ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ካሂ ፤ አካሂ ፤ (ብ ፡ ካህያት ፤ አካህያት) ፤** ጊደርና ፡ ጥገት ። ካሂ ፡ ጊደር ፤ እንስት ፡ ጥጃ ። አካሂ ፡ ጥገት ፡ እመሖግት ፡ ላም ። ምስጢራቸው ፡ ማነስና ፡ መድከም ፡ ሕጻጽነት ፡ ነው ። በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ካሂ ፡ ማለት ፡ ከማሃ ፡ ከመ ፡ ዘ ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ካሂ ፡ የጥጃ ፡ ጕፍላ ፡ ወይም ፡ እንቡጣ ፡ ስልቻው ፡ ምስሉ ፡ ሲሞት ፡ ከሽሮፊቱ ፡ እስከፋ ፡ ሽልቅ ቀው ፡ በሥጋው ፡ ፈንታ ፡ ገለባ ፡ ጐስረው ፡ ጠቅጥቀው ፡ በግሮቹ ፡ ፈንታ ፡ ፬ ፡ ዕንጨት ፡ ስክተው ፡ ሕያው ፡ አስመስለው ፡ የፈጠው ፡ ውሃ ፡ ቀብተው ፡ የሚያቆሙት ፡ እካሂ ፡ ያንን ፡ እያዩች ፡ እየላሰች ፡ ወተቷን ፡ የምትሰጥ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ሙሾ ፡ ላምና ፡ ዐባቢ) ፡ ያስ ፡ እየመሰሰኝ ፡ ልጄ ፡ ሙቶ ፡ ላስ ፤ እንቡጣውን ፡ ባየው ፡ ልቤ ፡ ተታለለ ። እንኳን ፡ እንኝ ፡ ላሚ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ታታለል ፡ ነበረች ፡ በጥጃ ፡ ምስል ።



እካሂ ፡

**ከሃ ፤ (ብ ፡ ከሃት) ፤** ወዲያ ፡ ወደዚያ ፡ ከዚያ ፡ በዚያ ፤ የቦታን ፡ ፈቀቅታ ፡ ጥቂት ፡ ርሕቀት ፡ ያሳያል ፤ ፍችው ፡ እንደ ፡ ህየ ፡ ስልቱ ፡ እንደ ፡ ለፌ ፡ ነው ። እም ፡ እየተስማማው ፡ ከለፌና ፡ ከገዘየ ፡ ጋራ ፡ ሳይስማማውም ፡ ይነገራል ። አሐዱ ፡ እምለፌ ፡ ድንጋገ ፡ ፈለግ ፡ ወአሐዱ ፡ እምከሃ ፡ ድንጋገ ፡ ፈለግ ። ፍልስ ፡ እምዝየ ፡ ኀበ ፡ ከሃ ። አሐውር ፡ ከሃ ፡ ወእጼሊ ። ዝርዎ ፡ ከሃ ። ረሐቀ ፡ ከሃ ። በዝ ፡ ዓለም ፡ ወበከሃ ፡ በኀበ ፡ እግዚ ። ከሃ ፡ ከሃቲሆሙ ፡ (ዳን፲፪ ፡ ፭ ። ማቴ፲፯ ፡ ፳ ። ፳፮ ፡ ፴፮ ። ዘኍ፲፯ ፡ ፪ ። ፩ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፱ ። ዲድ ፡ ፲፬ ። ሔኖ፴፪ ፡ ፫) ። ከሃየ ፡ ከ ፡ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ ፤ ከሃን ፡ ከሙ ፡ ከን ፡ ሆሙ ፡ ሆን ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ። እምለፌሁ ፡ ፈለግ ፡ ወእምከሃሁ ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ (ራእ፳፪ ፡ ፪) ። (ዕር፳፩ ፡ ቍ፲፫) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ ግን ፡ በከሃ ፡ ፈንታ ፡ ከሃከ ፡ ከሃከ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ነዋ ፡ ዝየ ፡ ወነዋ ፡ ከሃከ ። እስከ ፡ እትመየጥ ፡ ለፌ ፡ ወከሃከ ። ተኃሥሥት ፡ እምጥንቃቂ ፡ ከሃከ ። ወዓዲ ፡ ዘእምዝ ፡ ከሃከ ፡ (ሉቃ፲፯ ፡ ፳፫ ። ፫ነገ ፡ ፳ ፡ ፵ ። ቄር) ።

**ከሂል፤ ሎት፤(ክህለ፡ ይክል፡ ይክ ሀል። ዕብ፡ ያክል)፤** መቻል፡ መብቃት፤ ማግመር፡ መወሰን፤በሚሠሩት፡ሥራ፡ማየል፡መበርታት፤ መብት፡ ማግኘት። ገቢረኒ፡ትገብር፤ ወክሂለኒ፡ትክል። ሖሮ፡ ዘትክል፡ እዴከ፡ ለገቢር። መኑ፡ ክነ፡ ከመ፡እክሀል፡ሐኒጸ፡ሎቱ፡ቤተ፤(፩ነገ፡ ፰፯፡ ፰፳። መክ፱፡ ፲። ፪ዜና፡ ፪፡ ፮)።

—፤ ችሎት፡ አቻቻል፤ ኀይል፡ ብርታት፤ ዐቅም፡ ጕልበት፤ሥልጣን፡መብት። ሰብሕዎ፡በክሂሎቱ። በከመ፡ ክሂሎትነ። አልብየ፡ ክሂል፡ ላዕሌሁ። ከመ፡ የሀበ፡ ክሂለ፡ላዕሌሁ፡ወላዕለ፡ንዋዩ፤(መዝ፡ ፻፶። ስንክ፡ ሠኔ፲፪። ጎድ፡ ተክ። ስንክ፡ ግንቧ)።

**ከሃሊ፤(ሊት፡ልያን፡ያት)፤** የሚችል፡ ቻይ፤ ኀይለኛ፡ ብርቱ፤ ሥሉጥ፡ ሰጕሥ። ከሃሌ፡ ኵሉ። ጽኑዕ፡ ወከሃሊ። ዘኮነ፡ከሃሌ፡በቃሉ፡ወበምግባሩ። መሥዋዕት፡ ከሃሊት፡ ከመ፡ ታስተስሪ። ንሕነ፡ ከሃልያን፡ ለውላጤሁ። ከሃሊ፡ አነ፡ ተጽናሰኒ፡ ወተደልዎኒ፤(ጥበ፳፡ ፰፫። ሩትዩ፡ ፩። ሎቃ፳፬፡ ፱። አፈ፡ ድ፲፰። ዮሴፍ። ፊልጵ፱፡ ፲፪)።

**አክሀለ፤** አስቻለ፡ አበረታ፤ አበቃ፡ መብት፡ ሰጠ፡ አስናበተ። ኵሎ፡ እክል፡ በዘውእቱ፡ አክሀለኒ። እግዚ፡ አክሀለነ፡ በኵሉ፡ ዘንፈቅድ። ያክህልክሙ፡ እግዚ፡ ለገቢረ፡ ኵሉ፡ፈቃዱ። ወኢያክህሎ፡ከመ፡ ይቅረብ፡ኀቤሆሙ፤(ፊልጵ፬፡ ፲፫። ዮሴፍ። ግንዘ። ማር፡ ይሥ፳፡ ፪)።

**አክሃሊ፤ መክህል፤** የሚያስችል፤ አስቻይ።

**ተክህለ፤** ተቻለ፤ ተመቸ። ኵሉ፡ ይትክህል። እምእደ፡ ዚአሁ፡ ጕይይ፡ ኢይትክህል፡ ወኢይደሉ። ኢይትክህል፡ ለኅልቆ። ኢይትክህል፡ ከመ፡ ዝ፡ ይኩን። በከመ፡ ይትክህለከ። እስመ፡ ቅኔ፡ መዝሙርስ፡ ተክሃሊት፡ በኵሉ፡ ጊዜ፤(ማቴ፲፱፡ ፳፮። ጥበ፲፮፡ ፲፭። መክ፫፡ ፲፱። ዘፀ፫፡ ፳፪። ሚሊዕ፫፡ ፲፭። ፊልክ፡ ፪፻፴፰)።

**ተካህለ፤** ተቻቻለ፤ ተስማማ፡ ተዋደደ፡ ተዋዋለ፡ ተዋረጠ፤የዋጋ። ተካህለ፡ምስሌሁ፡ገባእት፡በበ፡ ዲናር፡ ለዕለት። አኮኑ፡ በዲናር፡ ተካህልኩከ። መኑ፡ ውእቱ፡ ዘተካሀለኪ፤(ማቴ፳፡ ፪፡ ፲፫። ማር፡ ይሥ፲፫፡ ፪)።

**ክሁል፤ (ላን፡ ላት፡ ሀልት)፤** የተቻለ፡ የተቻቻለ፤ የተስማማ፡ ስምም።

**አስተካህለ፤** አቻቻለ፤ አስማማ፡ አዋደደ።

**መስተክህል፤ (ልት፡ ላን፡ ላት)፤** የሚያቻችል፡ አቻቻይ፤ አስማማ።

**ኳሄላ፤ (ላት)፤** የጠፍር፡ ኳስ፤ ዕሩር፡ ጥንግ፡ የተሾሰ፡ ዐላማ፡ ጊጠ፤ ክሆድ፡ የሚጠጣ፡ ሐሠር፡ ጉድፍ። ጕድ፡ እብድ፡ ልብሱን፡ የጣለ፤ ወይም፡ የእብድ፡ አሻንጉሊት፤ ክዐቢይ፡ ጾም፡ በፊት፡ ክጸመ፡ ንጋቱ፡ በኋላ፡ የእብድ፡ ዐሙስ፡ ስት፡ ርሱን፡ በየማንባራቸው፡ ለጥፈው፡ ሲሥቁ፡ ሲያሥቁ፡ የሚውሉበት። ወከመ፡ ኳሄላት፡ ክነ፡ ውስተ፡ ዓለም። ከመ፡ ኳሄላ፡ ኮንክምሙ፡ ለብዙኃን፤(፩ቆሮ፡ ፬፡ ፲፫። መዝ፡ ፳)።

—፤ መክን፡ የበረሓ፡ ዕንጨት፤ እሾኸም፡ ፍሬ፡ ቢስ። ወይም፡ ብቸኛ፡ በረኸኛ፡ እሙሬ፤ ፋይት፡ የዱር፡ ድመት። ወይከውን፡ከመ፡ ኳሄላ፡በውስተ፡ገዳም፤(ኤር፲፯፡ ፮)።

**ከሄን፤(ክህነ፡ይክህን፡ይክህን። ዕብ፡ ክሄን)፤** ክህን፡ መኾን፤ ክህነት፡ ተሹሞ፡ በማዜር፡ ፊት፡ ቁሞ፡ ማገልገል፡ የአምልኮ፡ ሥራ፡ መሥራት፤ ስለ፡ ራስና፡ ስለ፡ሕዝብ፡መሥዋዕትና፡ ጸሎት፡ ማቅረብ፤ መባረክ፡ መቀደስ፡ ማጥመቅ፡ ማቍረብ።

**ከሀን፤(ናት። ዕብ፡ ክሄን። ሱር፡ ክህና። ዐረ፡ ካሂን)፤** በቁሙ፤ ቄስ፡ ጳጳስ፡ የማዜር፡ አገልጋይ፡ የሕዝብ፡ መሪ፡ አስተማሪ፤ መንፈሳዊ፡ አባት። አንተ፡ ካህኑ፡ ለዓለም። ትቀብዖ፡ ወትቄድሶ፡ ወይከውነኒ፡ ካህነ። ካህናት፡ ወሊቃነ፡ ካህናት። ዕሥራ፡ ወአርባዕቱ፡ ካህናተ፡ ሰማይ፤(መዝ፡ ፻፱። ዘፀ፵፡ ፲፭። ቅዳ፡ ሕር። ስንክ፡ ኅዳ፳፬)።

**አክሀነ፤** አስከነ፤ ክህነት፡ ሰጠ፡ ሾመ፤ ካህን፡ አደረገ። ያክህኖሙ፡(ቀኖ፡ ኒቅ፡ ፳፯)። ክህነት፡ አሰጠ፡ አሾመ፤ ካህን፡ አስደረገ።

**ተክህነ፤** ተካነ፤ ክህነት፡ ተሾመ፡ ተቀበለ፤ ካህን፡ ኾነ፡ ካህን፡ ተባለ፤ ለማገልገል። ክሂን፡ ክሹመት፡ በኋላ፡ ማገልገልን፤ ተክህኖ፡ ክማገልገል፡ በፊት፡ መሾምን፡ የሹመትን፡ ጊዜ፡ የተቀበሉበትን፡ ዕለትና፡ ሰዓት፡ ያሣያል። መጽሐፍ፡ ግን፡ ኹለቱንም፡ ጸታ፡ አንድ፡ አድርጎ፡ ተክህነ፡ ይላል፤ አያስኼም። ይርዐይ፡ መርዓተ፡ ወይትክህን። እስመ፡ አንተ፡ አዘዝከነ፡ንቁም፡ ቅድሜከ፡ ወለከ፡ ንትክህን። እፎ፡ ተኅረይከ፡ ለተክህኖ፡(ኪዳ። ቅዳ። መጽ፡ ምስ)።

**ክሁን፤ (ናን፡ ናት፡ ህንት)፤** የተካነ፤ ክህነት፡ የተሾመ፡ የተቀበለ።

**ክህነት፤** መካን፡ ማስካን፡ ካህንነት፤ ተክኖ፡ ማገልገል። አገልግሎት፤ መንፈሳዊ፡ ሹመት፤ ፯፡ ዕርከኖች፡ ያሉት። ፫ቱ፡ ላይኞች፡ ጵጵስናና፡ ቅስና፡ ዲቁና። ፬ቱ፡ ታችኞች፡ ንፍቀ፡ ዲያቆንና፡ አንባቢ፤ መዘምርና፡ በረኛ። ጳጳስንና፡ ኤጲስቆጶስን፡ እይ። ተንሥእ፡ ዘርዐ፡ ሌዊ፡ ለክህነት። ለክህነት፡ ቅድስት፡ ወንጽሕት። ኢይግበር፡ ሕዝባዊ፡ ግብረ፡ ክህነት፡(ክሩ፡ ፴። ፩ጴጥ፡ ፪፡ ፭። ዲድ፡ ፲፯)።

**ክህነታዊ፤** የክህነት፤ ክህነታም፡ ባለክህነት። መልእክት፡ክህነታዊት። ሀብት፡ክህነታዊት፤(ፍ፡ ን፡ ፲፡ ፯። ፊልክ፡ ፲፰)።

**ከዊው፤ ዎት፤(ከወ፤ ከወወ፡ ይከውው፡ ይክውው)፤** መቅለል፡ መፍጠን፡ መቀልጠፍ፡ ያክኽድ፡ ያንጋጋር። መዋሸት፡ መቅጠፍ፡ መለፍለፍ። ኀወወን፡ እዩ፡ የዚህ፡ ዘር፡ ነው።

**ከዋው ፤ (ዋዋን ፡ ት)** ፤ ቀላል ፡ ፈጣን ፤ ቀልጣፋ ። እበን ፡ ከዋዋት ። አእጋሪሁ ፡ ከዋዋት ፡ (ኢ.ዩ ፴ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፲፰) ።

**ከዋው ፤ (ዋት)** ፤ ቅለት ፤ ውሸት ፡ ቅጥፈት ። በጠዋይ ፡ ቃል ፡ ወበከዋው ፡ ነገር ፡ (መቃ ፡ ገጽ፫) ።

**ከከወ ፤ ከውከወ ፤ (ተቀ ፡ ማ)** ፤ ዘረ ፡ ዋተተ ፡ ተንከወከወ ። ከውካዌ ፡ እንዲሉ ፤ ዘዋሪ ፡ ሲሉ ።

**አንከከወ** ፤ ነዘረ ፡ አዞረ ፡ አሽከረከረ ፤ ተሽከረከረ ።

**መንከክት ፤ (ብ ፡ መናኩክት)** ፤ እንዝርት ፡ የመንኩራኵር ፡ ብረት ፡ ተጋዳሚው ። ከመ ፡ መንከክት ፡ እንተ ፡ ተዐውድ ፡ (ሚሬ፴፮ ፡ ፳) ።

**ኮከብ ፤ (ብ ፡ ከዋክብት ። ዕብ ፡ ኮካብ ። ሱር ፡ ከውክባ ። ዐረ ፡ ከውኮብ)** ፤ በቁሙ ፤ የብርሃን ፡ ቅንጣት ፡ የጸዳል ፡ ሰሌዳ ፤ ብርሃን ፡ የተማለበት ፡ የሰማይ ፡ ጌጥ ፡ የጠፈር ፡ ፈርጥ ፡ ሌሊት ፡ እንዳሸዋና ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ በዝቶ ፡ የሚታይ ፡ የሚያበራ ፤ የፀሓይ ፡ ሰራዊት ፡ የፊርማ ፡ ጭፍራ ፡ ዘዋሪ ፡ ከባቢ ። ስምንቱ ፡ ከከወ ወና ፡ ከበበ ። ከኹለቱ ፡ የተደቀለ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ በኮከው ፡ ፈንታ ፡ ኮከብ ፡ ይባል ። አበዝኆ ፡ ዘርዐከ ፡ ከመ ፡ ኮከበ ፡ ሰማይ ። ኮከብ ፡ እምኮከብ ፡ ይኄይስ ፡ ክብሩ ። አበርሆ ፡ ሰማየ ፡ በከዋክብት ። ከዋክብተ ፡ ሰማይ ። ሰወርኋ ፡ ወለከዋክብት ፡ ዘአኰነኖሙ ፡ ሌሊተ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፵፩ ። ድጓ ። ኤር፲፱ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፻፴፭) ።



ኮከብ ፡

**ከዋክብት ፡ እለ ፡ ጽኑዓን** ፤ የማይኼዱ ፤ የማይናወጡ ፡ (አቡሻ ፡ ፴፯) ።

**ኮከበ ፡ ገዳም** ፤ ቅዱስ ፡ እንጦንዮስ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳፪) ።

**ኮከብ ፡ ዘቦቱ ፡ ዘነብ** ፤ ኹራታም ፡ ባለኹራት ፡ የክፉ ፡ ምልክት ፡ (አዋል) ።

**ኮከበ ፡ ምዕራብ** ፤ የማታ ፡ ኮከብ ፡ አስታርቦሽ ፡ (ስንክ ፡ የካ፪) ።

**ከዋክብተ ፡ ናግራን** ፤ ሰማዕታት ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፳፮) ።

**ኮከበ ፡ ጽባሕ** ፤ ያጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ ማለዳ ፡ የሚወጣ ፡ (ኢሳ፲፬ ፡ ፲፪) ።

**ከዋክብት ፡ ጽልሙታን** ፤ ስሑታን ፡ ስተው ፡ የሚያስቱ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ (ይሁ ፡ ፲፫) ።

**ኮክህ** ፤ በቁሙ ፤ ኮክ ፡ የተክል ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፤ ፍሬው ፡ የሚጥም ፡ ዐጥንታም ። ኮል ፡ ወኮክህ ። ፍሬሁ ፡ ለኮክህ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፯ ፡ ፪ ። መ ፡ ፈ) ።



ኮክህ ፡

**ኮክህ ፤—ንጥፍ ፡ ደንጊያ ፤—ኰኵሕ ።**

**ከከወ ፤—ዘረ ፡ ዋተተ ፤—ከዊው ፡ ከወ ፤ ከወወ ።**

**ከዊል ፤ ሎት ፤ (ኮለ ፡ ይከውል ፡ ይኩል) ፤ አው ፡**


**ከውሎ ፤ ሎት ፤ (ከወለ ፡ ይኬውል ፡ ይከውል)** ፤ መከወል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማድረግ ፤ የኋሊት ፡ ማስኼድ ፡ ማስፈግፈግ ፤ ወይም ፡ በኋላ ፡ ማስከተል ፡ አስከታይ ፡ መኾን ።

**ተከወለ** ፤ ወደ ፡ ኋላ ፡ አለ ፤ አፈገፈገ ። ደጀን ፡ ኾነ ፤ በኋላ ፡ ኼደ ፡ ተከተለ ፤ የሰልፍ ፡ የጕዞ ። ይትኬወል ፡ እምኔነ ። እለ ፡ ይትኬወሉ ፡ ድኅረ ፡ መስቀል ። ወእለሂ ፡ ይትኬወሉ ፡ ድኅረ ፡ ታቦት ፡ የሐውሩ ፡ እንዘ ፡ ይነፍኁ ፡ ቀርነ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ኢያ፮ ፡ ፱) ። ደንረኀና ፡ ተድኅረን ፡ እይ ።

**ከዊል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ውልት)** ፤ በኋላ ፡ ያለ ፡ የተከተለ ፡ ኋለኛ ፡ ደጀን ።

**ከዋላ** ፤ ኋላ ፡ ዠርባ ፤ ድኅር ፡ ዘባን ። ነዐቅብ ፡ ፍጽመ ፡ ወከዋላ ። ዳዊትስ ፡ ወሰብኡ ፡ የሐውሩ ፡ ከዋላ ። መንገለ ፡ ከዋላ ፡ ሐመር ፡ (ኑሐ፬ ፡ ፲፮ ። ሳሙ ፡ ፳፱ ፡ ፪ ። ማር፬ ፡ ፴፰) ።

**ኮል ፤ (ብ ፡ አክዋል)** ፤ የተክል ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፤ ትፋሕ ፡ ፍሬው ፡ ክብ ፡ እንክብል ፡ ሥጋማ ፤ ሲያዩት ፡ ሲበሉት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፤ ቶሎ ፡ የማይደርስ ፡ የማይበስል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የሚል ። ኮል ፡ ዘውስተ ፡ ዕፀወ ፡ ገዳም ። ሰደቁኒ ፡ በአክዋል ። እምኀበ ፡ ኮል ፡ አንጻ እኩክ ። ቅርፍተ ፡ ኮል ፡ (ማሕ ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ ፭ ። ፰ ፡ ፭ ። መ ፡ ፈ) ። ከወሎ ፡ የደጋ ፡ ዕንጨት ፡ ኰሸሽላ ፤ ቅጠሉን ፡ አህዮች ፡ ፍሬውን ፡ እረኞች ፡ አበባዉን ፡ ንቦች ፡ የሚወዱት ፡ ማሬም ፡ ማረ ፡ መልክም ።



ኮል ፡

**ኮለ ፡ ወርቅ** ፤ የወርቅ ፡ ትፋሕ ፤ በትፋሕ ፡ አምሳል ፡ የተሣለ ፡ የተቀረጸ ፡ (ምሳ፳፭ ፡ ፲፩) ።

**አክዋል ፡ ዘዐርሞን** ፤ ያርሞን ፡ ፍሬዎች ፤ እንደ ፡ ትፋሕ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ (መቃ ፡ ገ፫ ። ድጓ) ።

ፀርሞንንና ፡ ኤሳዉን ፡ እይ ። አክዋል ፡ ዘአርሞን ፡ ተብሎ ፡ በአልፍ ፡ ሲጣፍ ፡ ግን ፡ አርሞን ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቃል ፡ ታላቅ ፡ ቤት ፡ ምሽራብ ፡ ነውና ፤ የቤት ፡ ዙሪያ ፡ ጌጥ ፡ የጕልላት ፡ ሻኹራ ፡ መርገፍና ፡ እማዋች ፡ ያሰኛል ፤ ሕንባብን ፡ እይ ።

**ከለ ፡ ሐቅል** ፤ ዕንጕት ፡ የሽቱ ፡ ቅጠል ፡ በርሻ ፡ ብዝመራ ፡ ውስጥ ፡ የሚበቅል ፤ አበባው ፡ ጥቍር ፤ ፍሬው ፡ ታናናሽ ፤ ዐረቦች ፡ ሶፋሕ ፡ የሚሉት ። ሶፋሕና ፡ ትፋሕ ፡ አንድ ፡ መስሎ ፡ ስለ ፡ ታያቸው ፡ መላሾች ፡ ኮል ፡ ብለውታል ፤ ተርጓሞችም ፡ እንኰይ ፡ ይሉታል ፤ ዕንጕትን ፡ እይ ፡ (ዘፍ፴ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭) ። ይሰወጥ ፡ በአንፍየ ፡ ጼናከሙ ፡ ከሊ ። ቅብዐ ፡ ጽጌ ፡ ሰአንፈ ፡ ሽቱ ፡ ዘይጼኑ ፡ ከሰ ፡ (በንክ ፡ መስ፳፭ ። መጋ ፡ ፲፯) ።

**ከለለ** ፤ (ተቀ ፡ ማ) ፤ ተንኰለለ ፡ ኮለል ፡ ኮለል ፡ ዱብ ፡ ዱብ ፡ አለ ፡ የፍሬ ፡ የእንብ ፡ የደም ፡ አወራረድ ፤ ለውሃም ፡ ይኸናል ። የሞፈርንና ፡ ያባለ ፡ ዘርን ፡ ማፍ ፡ ቋሩን ፡ ክርክሩን ፡ ኮሌል ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**አንከለለ** ፤ (ንኈለለ ፡ አንኈለለ) ፡ ዘረ ፡ አዘረ ፡ አሰከረ ። ሐመር ፡ እንተ ፡ ታንከልል ፡ ማእከለ ፡ ዐውሎ ፤ ዘረ ፡ (ሚራ፴፮ ፡ ፱) ። ዘአንከለሎ ፡ ደም ። ብባው ፡ ክቡድ ፡ ዘይንከልሎ ፡ ሊድማኅ ፡ ከመ ፡ ስቴ ፡ ክርዳድ ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፲፬ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ነከላል** ፤ የራስ ፡ ብሽታ ፡ አዞሬቴ ፡ ስካር ። አንዘነ ፡ ነኮላል ፡ ወአሐምም ። እምትንታኔ ፡ ዘነኮላለ ፡ ጌጋይ ፡ እስመ ፡ በነኮላለ ፡ ጌጋይ ፡ ልብየ ፡ አንበዘ ፡ ከመ ፡ ዘሰትየ ፡ ወይነ ፡ መስያዝዘ ፡ (ኤር፳ ፡ ፳፭ ። አርጋ ፡ ፱) ።

—፤ የራስ ፡ ጠጕር ፡ ሥራ ፤ ዙሪያ ፡ ክብ ፡ ጥምጥም ፡ ሥር ። ኢታንኅ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእስከ ፡ ወኢትሕፀዮ ፡ ወኢትቅብዖ ፡ ዕፍረተ ፡ ወኢትኅድግ ፡ ስፉሐ ፡ ወኢፍቱሰ ፡ ወኢፅፉረ ፡ ወኢትረሲ ፡ ለከ ፡ ድንጉዛተ ፡ ወነኮላለ ፡ አላ ፡ ላጽዮ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭) ።

**ከሞል** ፤ (ላት) ፤ ስሙ ፡ ዕፅ ፡ ፍሬው ፡ የሚበላ ፡ የኮል ፡ ሴታፍ ፡ የተክል ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ፡ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ለይተው ፡ ሽፍ ፡ ወይም ፡ እሸ ፡ ይሉታል ። ፍሬው ፡ ከመ ፡ ኮል ፡ አምሳለ ፡ ኮል ፡ ማለት ፡ ነው ። ቀነውዎ ፡ ውስተ ፡ ሥጋሁ ፡ ምእተ ፡ ወኅምሳ ፡ ወሠለስተ ፡ ቅንዋተ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ ከሞል ። ወሀለዉ ፡ ህየ ፡ ዕፀወ ፡ ከሞል ፡ ወሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወኮኑ ፡ ድኑናነ ፡ እስከ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፭ ። ጥር፲፭ ። ግን፳፱) ።

**ከሞስ** ፤—ስሙ ፡ ጣዖት ፤—ከመወ ።

**ከዊን ፤ ኖት ፤ (ኮነ ፡ ይከውን ፡ ይኩን ። ዐረ ፡ ካነ ፤ ሀሎ ። ዕብ ፡ ካን ፤ ሀያህ)** ፤ መኾን ፡ መብል ፡ ሳይለወጡ ፡ በሱታፌና ፡ በምሳሌ ፡ በግብር ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ መቀበል ። ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ። ውእቱ ፡ አምላክ ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ፡ ወውእቱ ፡ ሰብእ ፡ ዘኮነ ፡ አምላከ ፡ በተዋሕዶተ ፡ መለኮት ፡ ምስለ ፡ ትስብእት ። ኮንኪ ፡ ዐጽቀ ፡ ንጹሐ ። እግዚአ ፡ ጸወነ ፡ ኮንከነ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ። አነ ፡ እከውና ፡ ጥቅመ ፡ እሳት ፡ ዐውዳ ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፲፬ ። ሃይ ፡ አበ ። ውዳ ፡ ማርያ ። መዝ ፡ ፹፱ ። ዘካ፪ ፡ ፭) ። ወይም ፡ በዓይነት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ባሕርይ ፡ መለወጥ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ መኾን ፡ ተለውጦና ፡ ተገልብጦ ፡ በሌላ ፡ ባሕርይ ፡ ስም ፡ መጠራት ፡ ይው ፡ ግን ፡ ሚገሬታውና ፡ ምልክቱ ፡ አውሩ ፡ ቢጋሩ ፡ ህላዊው ፡ ሳይጠፋ ፡ ሳይታጣ ። ነጸረት ፡ ብእሲቱ ፡ ሎጥ ፡ ድኅሬሃ ፡ ወኮነት ፡ ሐውልተ ፡ ጼው ። ወኮነት ፡ በትር ፡ አርዌ ፡ ምድር ። ወኮነ ፡ ሐሉ ፡ ማይ ፡ ዘውስተ ፡ ተከዚ ፡ ደመ ። ጥዒም ፡ አንከረ ፡ ሊቀ ፡ ምርፋቅ ፡ ውእተ ፡ ማየ ፡ ዘኮነ ፡ ወይነ ፡ (ዘፍ፲፱ ፡ ፳፮ ። ዘፀ፬ ፡ ፫ ። ፯ ፡ ፳ ። ዮሐ፪ ፡ ፱) ። ቀጥ ፡ ብሎ ፡ መቆም ፡ መገተር ፡ ባሉበት ፡ መጥናት ፡ አለመናወጥ ፡ የምስሶ ፡ የዐምድ ፡ የሐውልት ፤ ከዋኒትን ፡ እይ ፤ ምስክሩ ፡ ርሱ ፡ ነው ። በመቆም ፡ እንጸር ፡ መቀመጥንም ፡ ያሳያል ፤ ና ፡ ከዚህ ፡ ኹን ፡ እንዲሉ ፡ ቆቀመጥ ፡ ሲሉ ።

**ከዊን** ፤ መፈጠር ፡ መገኘት ፡ መወለድ ፡ ከማሕፀን ፡ መውጣት ፡ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ መውረድ ፡ መገኘንም ፤ መምጣት ፡ መሰማት ፡ መነገር ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ወኮኑ ። ነገር ፡ በእንተ ፡ ከዊነ ፡ ዓለም ። ሐሉ ፡ ኮነ ፡ እመሬት ። ኢይኩን ፡ ፍሬ ፡ እምኔኪ ። ወኮኑ ፡ ሊተ ፡ እምኒሃ ፡ ሠለስቱ ፡ ውሉድ ። ወኮነ ፡ አይኅ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ አርብዓ ፡ ዕለተ ። ወኮነ ፡ ቃል ፡ እመልዕልተ ፡ ጠፈር ፡ (መዝ ፡ ፻፵፰ ። ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፱ ። መክ፪ ፡ ፳ ። ማቴ፳፩ ፡ ፲፱ ። ፈልክ ፡ ፫ ። ዘፍ፯ ፡ ፲፪ ። ሕዝ፩ ፡ ፳፭) ።

—፤ መደረግ ፡ መፈጸም ፡ መክናወን ፤ የሥራ ፡ የትንቢት ፡ የትእዛዝ ። ዝ ፡ ኵሉ ፡ ይከውን ፡ ፍጡነ ። በከመ ፡ ነበብኩ ፡ ከማሁ ፡ ይከውን ። እስመ ፡ በግብር ፡ ይከውን ፡ ዘነበበ ፡ ዮናስ ፡ ነቢይ ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፭ ፡ ፳፱ ። ጦቢ፲፬ ፡ ፰) ።

—፤ ማደር ፡ መኖር ፡ በታ ፡ መያዝ ፡ ምስጢሩ ፡ ከመቆምና ፡ ከመቀመጥ ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ። ኮነ ፡ በማርያም ፡ ድንግል ። ሊይኩን ፡ ብርሃኑ ፡ ለእግዚ ፡ አምላክነ ፡ ላዕሌነ ። ከመ ፡ እኩን ፡ ቦቱ ፡ (ውዳ ፡ ማርያ ። መዝ ፡ ፹፱ ። ፊልጵ፫ ፡ ፱) ።

—፤ መገባት ፡ መመቸት ፡ መስማማት ። ኢይከውነከ ፡ ትዕጥን ። ኢይከውነነ ፡ ንደዮ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መባእ ። ዘኢይከውኖሙ ፡ ሰበሲዐ ፡ (፪ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፲፰ ። ማቴ፳፯ ፡ ፮ ። ሉቃ፮ ፡ ፬) ።

—፤ መብቃት ፡ ልክ ፡ መኾን ። ከነክሙ ፡ ዐዊደት ፡ ለዝንቱ ፡ ደብር ። ከነክ ፡ ወኢትድግም ። ይከውንክሙ ፡ ዐሪግ ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ (ዘዳ፪ ፡ ፫ ። ፫ ፡ ፳፮ ። ፫ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፳፰) ።

—፤ መጥቀም ፡ መርባት ፡ ማገልገል ። ምንተ ፡ ይከውን ፡ ዕፀ ፡ ወይን ፡ እምኵሉ ፡ ዕፀ ፡ (ሕዝ፲፭ ፡ ፪) ።

—፤ መሹም ፡ መለወጥ ፡ መገዛት ። ወኮነ ፡ ርእሰ ፡ አድግ ፡ ሰኅምሳ ፡ ሰቅለ ፡ ብሩር ። መስፈርተ ፡ ስንዳሌ ፡ በሰቅል ፡ ትከውን ፡ (፬ነገ ፡ ፯ ፡ ፳፭ ። ፯ ፡ ፩) ።

**ከዊን** ፤ (ዘርና ፡ ጥሬ) ፤ መኾን ፡ ኹነታ ፤ እንት ፡ ባሕርይ ፡ ጠባይ ። እንተና ፡ መኾን ፡ እንድ ፡ ወገን ፡

ናቸው ፤ ምስጢራቸውም ፡ ባሕርይ ፡ ነው ። እመሰኬ ፡ ክዊነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኢይትዌለጥ ፡ በከመ ፡ ይትዌለጥ ፡ ህላዌሆሙ ፡ ለፍጡራን ። እምክዊነ ፡ ካህን ፡ ይቴይስ ፡ ክዊነ ፡ ኖላዊ ፡ (ማር ፡ ይሥ፴፫ ፡ ፫ ። ቅኔ) ።

**ክነ** ፤ ኾነ ፤ ነበረ ። የንግር ፡ ጥንት ፡ የንባብ ፡ እርእስት ፡ እየኾነ ፡ እንደ ፡ ይቤ ፡ አንቀጽ ፡ ይሰባል ። ወከነ ፡ እምድኅረ ፡ ሞተ ፡ ሙሴ ፤ ተናገሮ ፡ እግዚ ፡ ለኢያሱ ። ወከነ ፡ እምድኅረ ፡ ሞተ ፡ ሳኦል ፤ ተመይጠ ፡ ዳዊት ፡ እምቀቲሎ ፡ ዐማሌቅ ። ወከነ ፡ በውእቱ ፡ መዋዕል ፤ ወፅአ ፡ ትእዛዝ ፡ እምኀበ ፡ ቄሳር ፡ ንጉሥ ፡ (ኢያ፩ ፡ ፩ ። ፪ነገ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ሉቃ፪ ፡ ፩) ። ፪ኛም ፡ በትንቢት ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ ሲደረብ ፤ ምስጢሩና ፡ ፍችው ፡ ጽንዕ ፡ ይኾናል ። ክነ ፡ ያፈቅር ፤ ክነ ፡ ይጕይይ ፤ ክነ ፡ ይትመዐዐ ፡ ቢል ፤ ይወድ ፡ ነበር ፡ ወይም ፡ ይወዳል ፡ ኾነ ፡ ያሰኛል ። ዐጺደ ፡ ወይን ፡ ክነ ፡ ሰሰሎሞን ፡ ያለውም ፤ ኮነ ፡ የሌ ፡ ጽንዕ ፡ ይባላል ፤ ኮነም ፡ ቢቀር ፡ ሎቱ ፡ ለሰሎሞን ፡ ብሎ ፤ አለው ፡ ነበረው ፡ ያሰኛል ። ፫ኛም ፡ ኢ ፡ ስቶድቅበት ፡ ዘማችንቱን ፡ አሉታ ፡ በዝብዘት ፡ በኢና ፡ በአኮ ፡ በንባርንት ፡ ይፈታል ፤ ምክንያቱም ፡ ደራሽና ፡ መላሽ ፡ አለቦታው ፡ ስላገቡት ፡ ነው ። አንሰ ፡ ኢኮንኩ ፡ ኪያሁ ። ኢኮነ ፡ ሠናየ ፡ ነሚአ ፡ ኅብስተ ፡ ውሉድ ፡ ወወሂብ ፡ ለከለባት ። ኢኮነ ፡ ለክሙ ፡ ታእምሩ ፡ መዋዕለ ፡ ወአዝማነ ። ኢኮንክሙ ፡ ነግደ ፡ ወፈላሴ ። ኢሠናይ ፡ ኢለክሙ ፤ ኢአንትሙ ፤ ወይም ፡ አኮ ፡ አንትሙ ፡ ነግድ ፡ ወፈላሲ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አኮና ፡ ኢ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ኮነ ፡ ግእዝ ፡ መሳቡ ፡ ተለዋጭና ፡ ኺኝ ፡ ሲያገኝ ፡ ነው ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በግእዝ ፡ ፈንታ ፡ ሰን ፡ ይሰባል ። ወይክውን ፡ ፍሬሁ ፡ ለሲሳይ ፤ ወቈጽሉሂ ፡ ለፈውስ ፡ (ሕዝ፵፯ ፡ ፲፪) ። የኮነን ፡ አፈታት ፡ ፴ ፡ ብለው ፡ የሚቈጥሩ ፡ አሉ ፤ ምስክራቸው ፡ አያጠግብም ፤ ብዙው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ነው ። ኮነና ፡ ሀሎ ፡ በዐረብና ፡ በዕብራይስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ ዐረብ ፡ ካነ ፡ ብሎ ፡ ኾነ ፡ አለ ፡ ነበረ ፡ ይላል ፤ ዕብራይስጥም ፡ ሀያህ ፡ ብሎ ፡ ኮነ ፡ ሀለወ ፡ ይላልና ፤ የኮነ ፡ አፈታት ፡ ስልቱ ፡ መብዛቱ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ ኮነኒ ፡ ኮነን ፡ በቍዐኒ ፡ አከለኒ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ኮንየ ፡ ይላል ፡ የመላሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ስእነት ፡ ብሂለ ፡ ኮንየ ፤ እሳት ፡ ወማይ ፡ ኢይብሉ ፡ ኮንየ ፡ (ምሳ፴ ፡ ፲፮) ። (ዕር፲ ፡ ቍ፫፯ ። ዕርጅ፫ ፡ ቍ፪፫፫)።


**ክዋኒ** ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት) ፤ የኾነ ፡ የሚኾን ፤ ኺኝ ፡ ተሰጭ ፡ ተለዋጭ ።

**ኩነት** ፤ (ታት) ፤ መኾን ፤ አኳኾን ፡ ኹኔታ ፤ አኗኗር ። እግዚእ ፡ የአምር ፡ ኅሊና ፡ ሰብእ ፡ እምቅድመ ፡ ኩነታ ። ኩነት ፡ ብሔር ፡ (አፈ ፡ ድ፫ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

—፤ ፍጥረት ፤ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሲይኩን ፡ በማለት ፡ የተገኘ ። ገባሬ ፡ ኵሉ ፡ ኩነታት ፡ (ያዕ ፡ ዘእል) ።

—፤ የአካል ፡ ህላዌ ፡ ወይም ፡ ስም ። ህላዌ ፡ ወላዲነትና ፡ ተወላዲነት ፡ ሠራጺነት ። ስም ፤ ወላዲ ፡ ተወላዲ ፡ ሠራጺ ፤ ወይም ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ መባል ፡ ነው ። እግዚ ፡ ዘይሤለስ ፡ በኩነታት ፤ ዘውእቱ ፡ ሠለስቱ ፡ አካላቲሁ ። ዘይሤለስ ፡ በአካላት ፡ ወበኩነታት ፡ (ያዕ ፡ ዘእል ። ፍ ፡ ነ ፡ ፩) ።

**ክዋን** ፤ (ናት ። አው ፡ ክዋኒት ፤ ንያት) ፤ የደንጊያ ፡ ዐምድ ፤ ሐውልት ፤ ትክል ፡ ደንጊያ ፡ ቋሚ ፡ ተገትሮ ፡ የሚኖር ። ዘአዘዝከ ፡ ክዋኒተ ፡ ወአእመንከ ፡ ሐዋርያተ ፤ በመስቀልከ ፡ ረከብነ ፡ ሕይወተ ። ወርእየ ፡ ክልኤተ ፡ ክዋንያተ ፡ አሐቲ ፡ በየማነ ፡ ቤት ፡ ወአሐቲ ፡ በፀጋመ ፡ ቤት ፤ ወይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ትሬእዩኑ ፡ አርአያ ፡ ..ወተመይጠ ፡ ኀበ ፡ ክዋኒት ፡ ወይቤላ ፡ ..በጊዜሃ ፡ ቀነጸት ፡ ክዋኒት ፡ ወነበበት ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ (መዋሥ ። ስንክ ፡ ነሐ፴) ።



ክዋኒት ።

**ክንየ** ፤ ኮነኒ ፡ ኾነኝ ፡ በቃኝ ፡ በቅቶኛል ። ኮንየ ፡ እንከሰ ፡ (፫ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፬) ።

**መካን** ፤ (ናት ። ዐረ ፡ መካን ። ዕብ ፡ ማቆም ። ሱር ፡ አታር) ፤ ቦታ ፡ ስፍር ፡ ስፍራ ። መቆሚያ ፡ መቀመጫ ፤ ቤት ፡ መሥሪያ ፡ ማደሪያ ፡ መኖሪያ ፤ መሰብሰቢያና ፡ መከማቻ ፤ ዐጸድ ፡ ወረድ ፤ አገር ፡ መንደር ፡ ከተማ ፡ ገጠር ። ለይትጋባእ ፡ ማይ ፡ ዘመትሕተ ፡ ሰማይ ፡ ውስተ ፡ አሐዱ ፡ መካን ። ከመ ፡ ኢይቁሙ ፡ ውስተ ፡ መካንከ ። እስመ ፡ አልቦሙ ፡ መካን ። መካናት ፡ ብሩሃን ። መካናት ፡ ሠናያት ። ራሕበ ፡ መካናቲሆሙ ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፱ ። ሚፈ፲፱ ፡ ፲፱ ። ሉቃ፪ ፡ ፯ ። ሔኖ፲፯ ፡ ፫ ። ፳፱ ፡ ፭ ። ማ፻ ፡ ፱) ።

—፤ ማእገረን ፤ የመጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ምዕራፍ ፡ ክፍል ። እምአርባዕቱ ፡ መካን ። ወከሚት ፡ መጽሐፈ ፡ ረከበ ፡ መካነ ፡ ዘይብል ። በዝንቱ ፡ ገጸ ፡ መካን ፤ ወበገጸ ፡ መካንኒ ፡ (ማቴ፳፬ ፡ ፴፭ ። ሉቃ፬ ፡ ፲፯ ። ሃይ ፡ አበ) ።

—፤ የቍጥር ፡ መደብ ፤ የአኃዝ ፡ ጉባኤ ፡ በየረድፉና ፡ በየተራው ፡ በየተለላው ፡ የሚጣፍበት ፡ (አቡሻ ፡ ፲፭) ። ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ከቦታነት ፡ አይወጣም ።

(ጥ) **ከውኖ** ፤ (ከወነ ፡ ይኬውን ፡ ይከውን ። ዕብ ፡ ኩዌን) ፤ መከወን ፤ ማከናወን ፡ መፈጸም ፤ ማበጀት ፡ ማዘጋጀት ፤ ማሳመር ፡ ማስጌጥ ፤ ማቅናት ፡ ማሳከት ።

**ተከወነ** ፤ (ከነ) ፤ በቁሙ ፤ ተፈጸመ ፡ ሥራው ፡ ዐለቀለት ።

**ክዋኔ** ፤ (ንያት) ፤ መከወን ፤ (ጥ ፡ ከ) መከወን ፤ አከዋወን ፡ ከወና ።

**ክዋኔ** ፤ (ኩነት) ፤ መኾን ፤ አኳኾን ፡ ኹኔታ ፡ ተፈጥሮ ፤ አኗኗር ፡ ኑሮ ። ምስጢሩ ፡ እንደ ፡ ህላዌ ፡ ነው ፤ የባሕርይንና ፡ የተረከበን ፡ ጸታ ፡ ይከልን ፡ ኸለንታ ፡ ያሳያል ። አንሥሥ ፡ እምጥንተ ፡ ክዋኔሃ ። ገባሬ ፡ ክዋ

ኔሁ ። ይቤ ፡ ፎጢኖስ ፤ ለፈ ፡ እማርያም ፡ ክዋኔሁ ፡ ለወልድ ። ኅሲና ፡ ፍጡራን ፡ ይኄሊ ፡ አእምሮ ፡ ክዋኔሁ ፤ ወባሕቱ ፡ ይስእን ። አልቦ ፡ ማኅለቅት ፡ ለክዋኔሁ ፤ (ጥበ፳ ፡ ፳፱ ። ፲፫ ፡ ፳ ። መጽ ፡ ምስ ። ፈልክ ። ቅዳ ፡ ኤጲ.) ። የህላዌን ፡ ፍች ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ተከወነ ፤** ተኳኋነ ፤ ተከዋወነ ፡ ተከንዋወነ ፤ ተቃና ፡ ተሳካ ።

**ትኳን ፤ (ናት ። ዐረ ፡ ተከዊን ፤ ፍጥረት) ፤** በቁሙ ፤ ትኳን ፡ ያልጋ ፡ ተባይ ፤ ሲበላ ፡ የሚያተኩን ፡ የሚያትክነክን ፤ ማማታም ፡ ክርፋታም ።

**ከዋኒም ፤ (ዕብ ፡ አዳርከኒም) ፤** የገንዘብ ፡ ስም ፤ ፋርሳዊ ፡ ገንዘብ ። አዳርኮኒም ፡ የብዙ ፡ ነው ። ላንድ ፡ ሲኾን ፡ አዳርኮን ፡ አዳርክሞን ፡ ይላል ፤ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሥንቅ ፡ ልብስ ፡ ተክህና ፡ ይሉታል ፡ (ዕገ፰ ፡ ፳፯) ።

**ከዌር ፤ ሮት ፤ (ከረ ፡ ይከውር ፡ ይኩር ። ዐረ ፡ ከረ) ፤** መሸከም ፡ ማሸከም ፤ (ላ ፡ ጥ ፡ ጫ) መጫን ፤ ማንገት ፡ መቀዳጀት ፤ የሸክም ፡ የጌጥ ። ለጥምጥምና ፡ ለቆብም ፡ ይኾናል ። ከረየን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ኮር ፤ (ብ ፡ አከዋር ። ዕብ ፡ ካር) ፤** በቁሙ ፤ ኮርቻ ፡ ማሳስ ፤ መከዳ ፡ ትራስ ፤ ቀንበር ። ወህለወት ፡ ሰይፍ ፡ ታሕተ ፡ ኮር ፤ ኮርቻ ፡ (ድር ፡ ሚክ) ።

**ከውር ፤ (ዕብ ፡ ኩር ። ሱር ፡ ኩራ ። ዐረ ፡ ከውር) ፤** በቁሙ ፤ አጕደ ፡ የማዕደናት ፡ ኹሉ ፡ መጥበሻ ፤ ማቅለጫ ፡ ማፍሰሻ ። በከመ ፡ ይትፈተን ፡ በከውር ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ። ማእከለ ፡ ከውር ። ይትዌለጥ ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ ከውር ፡ ኀበ ፡ ብሩር ፡ (ምሳ፲፯ ፡ ፫ ። ሕዝ ፳፪ ፡ ፳ ። ያዕ ፡ ዘእል) ።

(ጥ) **ከወረ ፤ (ይኬውር ፡ ይከውር ። ዕብ ፡ ካዌር) ፤** ጠመደ ፡ አጠመደ ፤ ጋፈፈ ፡ ያዘ ፤ የዓሣ ። ቀዘፈ ፡ ተረከዘ ፤ መርከብን ፡ ንዳ ፡ በሥራት ፡ አስኬደ ፤ በባሕር ፡ በመርከብ ፡ ሥሉጥ ፡ ኾን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በከወረ ፡ ፈንታ ፡ ተከወረ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ኖትያት ፡ እለ ፡ ይትኬወሩ ፡ ውስተ ፡ ባሕረ ፡ ዓለም ፡ ዐሥርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ሐዋርያት ። መዋግድ ፡ እለ ፡ ያስጥሙ ፡ ሐመረ ፡ ልቡ ፡ ለዘኢይክል ፡ ጸቢተ ፡ ውስተ ፡ ቀላየ ፡ መጻሕፍት ፡ ወለዘኢይትኬወር ፡ በመቅድፈ ፡ ኦሪት ፡ ወነቢያት ፡ ወበመቅድፈ ፡ ወንጌል ፡ ወሐዋርያት ፡ (መጽ ፡ ምስ ፡ ገ፳፩ ። ፶፰) ።

**ኮራ ፤ (ራት) ፤** ኵሬ ፤ ምዕቃል ፡ የውሃ ፡ መቋሚያ ፡ መጠራቀሚያ ። የውሃ ፡ ዕቃ ፡ ታናሹም ፡ ታላቁም ፤ ጽዋ ፡ ጣሳ ፡ ምንቸህ ፡ ኵስኵስት ። ኮራየ ፡ ዘብሩር ፡ ደይ ፡ ውስተ ፡ ሐሰሉ ፡ ለዘይንእስ ፡ ወሢጠ ፡ እክሉሂ ። ወይከውና ፡ ጻህራት ፡ ዘቤተ ፡ እግዚ ፡ ከመ ፡ ኮራት ፡ (ዘፍ ፵፬ ፡ ፪ ፡ ፲ ። ኩፋ ፡ ፵፬ ። ዘካ፲፬ ፡ ፳) ።

**—፤** ጋን ፡ ዝንግሪር ፤ ማድጋ ፡ ፈቀን ፡ እንስራ ፡ በሮሚል ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ትመልእ ፡ ማየ ፡ በኮራ ፡ ሐዲስ ። ምልአ ፡ ኮራ ፡ ማየ ። ይመልእሙ ፡ በኮራቲሆሙ ፡ ማየ ፡ (ቄድር ፡ ገ፩ ። ስንክ ፡ መስ፳፯ ። ሥኔ፳፬) ።

**—፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ የደብረ ፡ ሲባኖስ ፡ ገጠር ፡ ታችኛው ፡ ገዳም ፤ ውሃው ፡ የማያልቅ ፡ የማይደርቅ ፡ ጠበባም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ምስጢሩ ፡ ውሃን ፡ አይለቅም ። (የታቦት ፡ ዘፈን) ፤ ትምሩኝ ፡ እንደኾን ፡ ልም(ን)ጣ ፡ ወደ ፡ ኮራ ፤ ያባ ፡ ጠጋዛብ ፡ ልጅ ፡ የይቶት ፡ እዝጊያራ ።

**ኮሬ ፤** ኾሬ ፡ አንቦ ፤ እንብ ፡ እንብ ፡ የሚል ፡ የጨው ፡ ውሃ ፤ ለከብቶች ፡ የሚበጅ ፡ የሚያሸርና ፡ የሚያወፍር ። ወይም ፡ ግጦ ፡ ቦረቦር ፤ ጨው ፡ ጨው ፡ የሚል ፡ ዐፈር ። ይኸውም ፡ የሚገኝ ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ ከዚያው ፡ ከውሃው ፡ አጠገብ ፡ ነው ።

**ኮሬ ፤ (ጽር ፡ ኾሬ ፤ ኾራይ) ፤** ሙራደ ፡ ማይ ፤ የሰን ፡ የኵስኵስት ፡ ጡት ። የላሕመ ፡ ብርት ፡ አፍ ፡ እንደ ፡ ቦንቧ ፡ አፍ ፡ ኹኖ ፡ ጡት ፡ ያለው ፤ የሚከፈትና ፡ የሚዘጋ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ የብረት ፡ ጋን ፡ ይሉታል ፤ ፍችው ፡ አይደለም ። ወእምላዕሉሂ ፡ አናብስት ፡ ወአልሕምት ፡ ግብረ ፡ ኮሬ ፡ ሙራዱ ፡ (፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፳፱) ። ሙራድና ፡ ኮሬ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ሰብራይስጡ ፡ ሞራይ ፡ ያለውን ፡ ጽርኡ ፡ ኾሬ ፡ ብሎታል ፤ የማእገዘ ፡ መላሽ ፡ ግን ፡ ኮሬን ፡ በከንቱ ፡ አግብቶታል ። ወይም ፡ መላሽ ፡ ግብረ ፡ ኮሬሁ ፡ ያለውን ፡ ተርጓሚ ፡ ሙራዱ ፡ ብሎ ፡ በዳር ፡ አመልክቶት ፤ የኋላ ፡ ጣፊ ፡ አግብቶት ፡ ይኾናል ። በብዙ ፡ መጣፍ ፡ ውስጥ ፡ ስንኳን ፡ ትርጓሜው ፡ ጥቅሱና ፡ ሐተታው ፡ ሳይቀር ፡ ገብቶ ፡ እየተጣፈ ፡ ይገኛል ፤ ምክንያቱም ፡ ጥፈትና ፡ ትምርት ፡ ተባብረው ፡ ተጫፍረው ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ስላልተገኙ ፡ ነው ።

**ኮሬ ፡ ኤጲስቆጶስ ፤ (ጽር ፡ ኾሬፒስኮፖስ) ፤** የኤጲስቆጶስ ፡ ዐርክ ፡ ምክትል ፤ እንደራሴ ፡ ወኪል ፤ ወራሴ ፡ መንበር ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፬ ። ፯ ፡ ፫ ። ፬ ፡ ፪) ።

**ከዌስ ፤ ሶት ፤ (ከሰ ፡ ይከውስ ፡ ይኩስ ። ሐሰ) ፤** ማካወስ ፡ መበጥበጥ ፤ ማወክ ፡ መድረጥ ፤ መንቅንቅ ፡ ማናወጥ ፤ የባሕር ፡ የኮሶ ፡ የፈሳሽ ፡ ነገር ፤ ኮሶም ፡ በምሳሌ ፡ ባሕር ፡ ይባላል ። (ዕንቆቅልኽ) ፤ ታናሽ ፡ ባሕር ፡ ዐጤን ፡ ታስፈር) ። ኮሶ ፡ ማለት ፡ ቅሉ ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በኮሰ ፡ ፈንታ ፡ አኮሰ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። አነ ፡ እግዚ ፡ ዘአከውሶ ፡ ለባሕር ። አኮስካ ፡ ለባሕር ። ሰይጣናት ፡ ያከውሱ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ብዙኀ ፡ እከያተ ፡ (ኢሳ፶፩ ፡ ፲፭ ። ሱቱ ፡ ዕገ፩ ፡ ፲፱ ። ፈልክ ፡ ፴ ። ፴፯) ። ኮሰና ፡ ሖሰ ፡ ኀሠሠ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ ስልታቸው ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ፊደላቸው ፡ ልዩ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ በምስክራቸው ፡ ይታወቃል ፤ ፍቾቻቸውን ፡ በየቦታቸው ፡ ተመልከት ።

**አከሰ ፤** አስደረጠ ፡ አስበጠበጠ ፡ አስንቀነቀ ።

**ተከውሰ ፤** ተካወሰ ፡ ተናወጠ ፡ ተንዋወጠ ፡ ታወከ ፡ ተደረጠ ።

**ክዉስ** ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ውስት) ፤ የተክወሰ ፤ የተናጠ ፡ የተናወጠ ።

**ክውስ** ፤ (ዕብ ፡ ክስ ። ሱር ፡ ካሳ ። ዐረ ፡ ካስ) ፤ ጽዋ ፡ ዋንጫ ፤ የመጠጥ ፡ መሣሪያ ፤ መቅጃ ፡ መጠጫ ፤ ማደያ ፡ መስጫ ። ኮሶ ፤ የደጋ ፡ ዛፍ ፤ የኹጥ ፡ መድኀኒት ፤ ፍሬውን ፡ ደቍሶ ፡ በጥብጦ ፡ ሲጠጡት ፡ ሆድ ፡ እያክወሰ ፡ የሚያስቀምጥ ። ድፍርስ ፡ ብጥብጥ ፡ መራራ ፡ መጠጥ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ኹጡም ፡ ኮሶ ፡ የሚያስጠጣ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ኮሶ ፡ ይባላል ፤ ኮሶ ፡ ታየኝ ፡ እንዲሉ ።

**ኮፒ** ፤ (ሮማይ ፡ ኮፒያ) ፤ ብዛት ፤ የጥፈት ፡ አበዛዝ ፡ ብዥ ፡ ቅጅ ፤ አንድ ፡ የነበረው ፡ ብዙ ፡ መኾን ። የማይጠፋ ፡ ቀለምና ፡ ርሳስ ፡ የሴቴ ፡ ሬት ፡ ደም ፡ የሚመስል ።

**ክሓ** ፤—ወዲያ ፤—ክህሀ ፡ ክሃ ።

**ኰሓ** ፤—ሓያ ፡ አሓያ ፤—በኰሒ ፡ በኰሐ ።

**ክሒድ** ፤ ዶት ፤ (ክሕደ ፡ ይክሕድ ፡ ይክሐድ ። ዕብ ፡ ካሐድ ፡ ሂክሔድ ፤ ቃብ ፡ ቀካደ) ፤ መካድ ፤ መክዳት ፤ እምነትን ፡ ውልን ፡ መሐላን ፡ ማፍረስ ፤ መሸፈጥ ፤ ቃልን ፡ መለወጥ ፤ መዋሸት ፤ ዐሎ ፡ ማለት ፤ ማበል ፡ መወንጀል ። ክሒደ ፡ ትክሕዱኒ ። ክሕደ ፡ ሃይማኖቶ ። አምጽኡ ፡ ባዕሌነ ፡ መሐላ ፡ ዘኢንክል ፡ ክሒደ ። አምነ ፡ ወኢክሕደ ። ከመ ፡ ተዐልዎ ፡ ብእሲት ፡ ለምታ ፡ ከማሁ ፡ ክሕዱኒ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ (ኢሳ፷፫ ፡ ፰ ። ኤጢሞ ፡ ፭ ፡ ፰ ። ዮሐ፳ ፡ ፴ ። ዮሐ፩ ፡ ፳ ። ኤር፫ ፡ ፳) ።

**ከሓዲ** ፤ (ዲት ፤ ድያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ የሚክድ ፡ ከዳተኛ ፡ ሸፋጭ ፤ ዐባዊ ። ይዘለፈክሙ ፡ ሕግ ፡ ከመ ፡ ከሓዲ ። ወልድ ፡ ከሓዲ ። ኢትኩኑ ፡ ከሓድያነ ፡ በእግዚ ። መሳእክትኪ ፡ ከሓድያን ፡ (ያዕ፪ ፡ ፱ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፳፫ ። ዘኍ፲፱ ፡ ፱ ። ኢሳ፩ ፡ ፳፫) ።

**አክሐደ** ፤ አስካደ ፤ አስከዳ ፡ ዐሎ ፡ አሰኘ ፤ አሳበለ ፡ ከሓዲ ፡ አደረገ ። ኢትዌዊክሙ ፡ አክሒድዎ ፡ ለል ብክሙ ። አክሒድዎሙ ፡ ወይቤልዎሙ ፡ ንሁ ፡ ናምልክ ፡ ባዕደ ፤ (ዘዳ፲ ፡ ፳፰ ። ፲፫ ፡ ፲፫) ። በክሕደና ፡ በአርሐቀ ፡ ፈንታ ፡ አክሐደ ፡ ይላል ፤ የመሳሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ኢአምንዎን ፡ ወአክሒድዎን ። አይድዐተነ ፡ ወአክሒድናሃ ። ይቤ ፡ መኑ ፡ አክሐደከ ፡ (ሉቃ ፳፬ ፡ ፲፩ ። ኪዳ ። ቄር ፡ ጸላ) ። እስመ ፡ ያክሕዶ ፡ ለወልድከ ፡ እምኔየ ፤ ወይመልክ ፡ ባዕደ ። ትዐቢት ፡ ታክሕዶ ፡ እምነ ፡ ፈጣሪሁ ፡ (ዘዳ፯ ፡ ፬ ። ሚራ፲ ፡ ፲፪) ። በአክሐደ ፡ ፈንታ ፡ አስተክሐደ ፡ አስተክሐደ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። ከመ ፡ ያስተክሕዶ ፡ ጸጋ ፡ እግዚ ፡ እንተ ፡ ነበረት ፡ ባዕሌሁ ። ቶማስ ፡ አስተክሐዶሙ ፡ ለአኃዊሁ ፡ (ቀሌ ፡ ገ፭ ። መጽ ፡ ምስ ፡ ገ፳፰) ።

**አክሓዲ** ፤ **መክሐዲ** ፤ **መክሕድ** ፤ የሚያስክድ ፡ አስካጅ ፤ አስካጅ ።

**ተክሕደ** ፤ ተካደ ፡ ተጣለ ፡ ተተወ ፡ ተከዳ ፡ ዐሎ ፡ ተባለ ። እለ ፡ ኵሎሙ ፡ ይትከሐዱ ፡ ወይትሀጐሉ ፡ (ሔኖ፶፪ ፡ ፰) ።

**ተካሐደ** ፤ ተካካደ ፡ ተከራከረ ፡ ተሟገተ ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፲፭ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ። ፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፫) ። ትረፈቅዱኑ ፡ ንትካሐደሙ ፡ ለቃላቲከ ፡ ለነገራቶሙ ፡ ለዐልዋን ፤ እስመ ፡ ለተካሕዶ ፡ ይትወለድ ፡ ሎነ ፡ ባቍዐ ። ቦኑ ፡ እንከ ፡ ዘትትካሐደኒ ፡ በዝ ፡ ነገርየ ። ኢትትካሐድ ፡ ለእንተ ፡ ጽድቅ ፡ (ቄር ፡ ጸላ ፡ ገ፳፰ ። ፳ ። ሚራ፬ ፡ ፳፭) ።

**ክሑድ** ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ሕድ) ፤ የተካደ ፤ የተካካደ ።

**ክሕደት** ፤ (ኣ ፡ ጥ) መካድ ፤ መካካድ ፡ አካካድ ። በቁሙ ፤ ክዳት ፡ እሉታ ፤ ሸፍጥ ፡ ዐመፃ ፤ በደል ፡ ወንጀል ። ዝንቱስ ፡ ክሕደት ፡ ወእኩ ፡ ሃይማኖት ። መጽሐፈ ፡ ክሕደት ። ክሕደቶሙ ፡ ዘክሕዱከ ፡ (ታሪ ፡ ነገ ። ስንክ ፡ መስ፲፫ ። ፪ነገ ፡ ፰ ፡ ፶) ።

**ካሕድ** ፤ ጥርጥር ፡ እሉታ ፡ ጉፋቄ ፡ ክሕደት ፡ ክርክር ፡ ሙግት ፤ የነገርና ፡ የትምርት ፡ ዕንቅፋት ፡ መሰናክል ። እለ ፡ ይገብሩ ፡ ካሕደ ፡ በላዕለ ፡ ክርስቶስ ። እስመ ፡ ኵሉ ፡ ካሕድ ፡ ምግባሪሆሙ ። ዘእንበለ ፡ ካሕድ ። አልቦ ፡ ካሕድ ፡ በዝንቱ ። ያመጽኡ ፡ ካሕደ ፡ ላዕለ ፡ ትምህርትክሙ ። እብነ ፡ ካሕድ ፡ (ስንክ ፡ የካ፰ ። ኩፋ ፡ ፳፫ ። ዕብ፯ ፡ ፯ ። ቄር ። ሮሜ፲፯ ፡ ፲፯ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፰) ።

**አስተካሐደ** ፤ አካካደ ፡ አሟገተ ፡ አከራከረ ።

**መስተካሕድ** ፤ (ዳን) ፤ የሚያሟግት ፡ የሚያከራክር ፤ ዳኛ ። ተሟጋች ፡ ተከራካሪ ፤ መናፍቅ ፡ ከሓዲ ። ለመስተካሕድ ፡ ብእሲ ፡ (ቲቶ፫ ፡ ፲ ። መጽ ፡ ምስ ። አፈ ፡ ድ፲፫) ።

**ክሕክሐ** ፤ (ክሂህ ፡ ክህሀ ። ዐረ ፡ ክዕከዐ) ፤ ቀላቀለ ፡ ደባለቀ ፡ አንድ ፡ አደረገ ፡ ቀምሞ ። ክካ ፡ ፈንከተ ፡ ፈንካከተ ፡ ፈጨ ፡ ደቈሰ ፡ ጨፈለቀ ፡ የወፍጮ ፡ የናዳ ፡ የመርግ ።

**ኮኵሕ** ፤ (ሓት ። ዕብ ፡ ኮሕ ፤ ጥንካሬ ፡ ብርታት) ፤ ጥኑ ፡ ደንጊያ ፡ ጕጥና ፡ ሀፈር ፡ ለበስ ፡ ቋጥኝ ፡ ገምጃ ፤ ተራራ ፡ ኰረብታ ፤ ጭንጫ ፡ ደረቅ ፡ ጥብቅ ፡ ጠጠራም ፡ መሬት ። አንቅዐ ፡ ኰኵሐ ፡ ዘሐነጸ ፡ ቤቶ ፡ ዲበ ፡ ኰኵሕ ። እግዚ ፡ ጸወንየ ፡ ወኰኵሕየ ። ጐዩ ፡ ውስተ ፡ ኰኵሕ ፡ ሬምን ። ቦ ፡ ዘወድቀ ፡ ውስተ ፡ ኰኵሕ ፡ ኀበ ፡ አልቦ ፡ መሬት ፡ ብዙኅ ፡ (መዝ ፡ ፸፯ ። ማቴ፯ ፡ ፳፬ ። ፪ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፪ ። መሳ፳ ፡ ፵፯ ። ማቴ፲፫ ፡ ፭ ፡ ፳) ።

**እንክሕክሐ** ፤ ፈተፈተ ፡ ተፈተፈተ ።

**ነክሕካሕ** ፤ **አው ፡ ሰክሕክሕ** ፤ ፍቅፍቅ ። እክሽ ፡ ክክ ፤ ሐሠር ፡ ዐይኑ ፡ ምድር ፤ ተቅማጥ ፡ ሽታ ፡ እሕታ ፡ የሆድ ፡ በሽታ ፡ ክብርድ ፡ የተነግ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫) ።

**ክሕለ፤—ቻለ፤—ክሂል፡ክህለ።**

**ኰሒል፤ ሎት፤ (ኰሐለ፡ ይኰሕል፡ ይኰሐል። ዕብ፡ ካሐል። ሱር፡ ክሓል። ዐረ፡ ክሐለ)፤** መኳል፡ ማስነከት፤ ዐይንን፡ በኵል፡ ደቈት፡ በመድኀኒት፡ መቅባት፤ ለጌጥና፡ ለፈውስ። በእብነ፡ ፈውስ፡ ኰሐሉኒ፡ ዐይንየ። እንተሰ፡ ኰሐሎ፡ ዝኩ፡ ሐሞተ፡ ውስተ፡ አዕይንቲሁ። ለዘተወልደ፡ ዕዉር፡ አሕየዎ፡ ክርስቶስ፡ ኰሒሎ፡ አዕይንቲሁ፡ ጽቡረ፡ (ስንክ፡ ታኅሣ፲፱። ጦቢ፲፩፡፯። ሲኖዶ)።

—፤ መተኰስ፡ አመሳቅሎ፡ መጥበስ፤ የሌባን፡ ማንባር፡ በጋለ፡ ብረት፡ ማመልከት፤ ለክብትም፡ ይኾናል። እመ፡ ቦ፡ ብእሲ፡ ዘይበውእ፡ ውስተ፡ ምሥዋዕ፡ መዓልተ፡ አው፡ ሌሊተ፡ ወይነሥእ፡ እምውስቴታ፡ ምንተኒ፡ ይኰሐልዎ፡ በኀጺን፡ ርሱን። ወተአዘዙ፡ መግብት፡ አመ፡ ሆሳዕና፡ ተዐርቀ፡ ጽልመተ፡ ይኰሐልዎ፡ ለፀሓይ፡ ዘ(ሠ)በረቀ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፵፱። ቅኔ)።

**ኰሓሊ፤ (ሊት፡ ልያን፡ ያት፤ ሐልት)፤** የኳለ፡ የሚኰል፤ ኳይ፡ ተኳሽ።

**ተኰሕለ፤** ተኳለ፡ ተቀባ፤ ተተኰሰ። ተኰሕሎት፡ ወአሠንዮ፡ ቀራንብት። በተኰሕሎትን። ተኰሕለት፡ አዕይንቲሃ፡ (ሔኖ፰፡፩። ፌ፡ መ፡ ፴፱፡፰። ፱ነገ፡ ፱፡ ፴)።

**ኰሒል፤ (ላን፡ ላት፡ ሕልት)፤** የተኳለ፤ የተቀባ፤ ተኰሳም፡ ምልክታም።

**ኰሕል፤ (ላት)፤** በቁሙ፡ ኵል፤ ጥቍር፡ ሰማያዊ፡ የቀለም፡ ደንጊያ፤ ተደቍሶ፡ ላይን፡ የሚቀባ፡ የሚኳል፡ ጌጥንት፡ ከመድኀኒትንት፡ ሰላለው፡ በኹለት፡ ወገን፡ የሚፈለግ። አዕይንት፡ እለ፡ ስርግዋን፡ በኰሕል። ብንተ፡ አዕይንቲሁ፡ ከመ፡ ኰሕል፡ ወጸሊም፡ ጽሕሙ። ተኰሕልኪ፡ ኰሕለ፡ (ማንዘ። ስንክ፡ ሐምሌ። ኢር፬፡ ፴)።

**ኰሕሊ፤ (ዐረብ)፤** ኰሕላዊ፡ ኵልማ፡ የኵል፡ ዐይነት፤ ጥቍረቱ፡ ኵል፡ የሚመስል።

**ኰሐስ፤ ሶት፤ (ኰሐሰ፡ ይኰሕስ፡ ይኰሐስ። ዕብ፡ ካሐሽ)፤** መክሳት፡ መቅጠን፤ ማነስ፡ መኰሰስ፡ ከሻዋ፡ መኾን፤ የገላ። ማቅበር፡ መስገም፤ ሳይሽር፡ የሻረ፡ መምሰል፤ ወይም፡ መሰፋት፡ መማንን፤ የቀሰል። ኰሐሰ፡ ጸልዐኪ። እምቅድመ፡ ይጸኑ፡ ወይኰሐሱ፡ ቍስላተ፡ ነፍስየ፡ (ናሖ፪፡ ፲፱። አረጋ፡ ድ፻፺)።

**ኰሕስ፤** ክሳት፡ ኰሳስነት፤ የቍስል፡ ስፋት። ኀፍረተ፡ ብእሲት።

**ኬጢአ.ም፤ (ጽር፡ ኬቴይም። ዕብ፡ ባቲም)፤** ቤቶች፡ ድንኳኖች፤ ወይም፡ የድንኳን፡ ቁር በቶች። በስተላይ፡ ጠፈር፡ መዋቅር፡ የሚኾኑ፡ (፱ነገ፡ ፳፫፡ ፯)።

**ኽጥሜ፤—ሰላጣ፡ ሥንቆ፤—ኀጥሜ።**

**ኬጥሮ.ጋውሎስ፤ (ጽር፡ ኪ.ትሮክፍሉስ። ዕብ፡ ኪ.ዮሮት)፤** የብረት፡ ጋኖች፤ ታላላቅ፡ ድስቶች፡ ለማብሰያ፡ ለመቀቀያ፤ ወይም፡ ውሃ፡ ለመያ ሊያ፡ ለመታጠቢያ፡ የተሠሩ፤ ለታናናሾችም፡ ይነገራል፡ (፫ነገ፡ ፯፡ ፴፰)።

**ኪ.ያ፤ (ዐረ፡ ኢ.ያ። ዕብ፡ ኤት፤ ኢት)፤** የገቢር፡ ፀአፋና፡ ቅጽል። ስልን፡ ተመልከት፤ ይህም፡ እንደዚያ፡ ነው፤ አለዝርዝር፡ ብቻውን፡ አይገባም። ም ንባቱና፡ ሥሩ፡ እየየ፡ ነው፤ አ፡ በክ፡ ተለውጦ፡ ኢ.ያ፡ በመባል፡ ፈንታ፡ ኪ.ያ፡ ተብሏል፤ ይኸውም፡ ባረቡ፡ ይታወቃል።

**ኪ.ያየ፤ (ከ፡ ኪ.፡ ሁ፡ ሃ። ነ፡ ክሙ፡ ክን፡ ሆሙ፡ ሆን)፤** እኔን፤ ራሴን። ቦኑ፡ ኪ.ያየ፡ ትፈርሁ። ኪ.ያከ፡ ንሴብሕ። እስመ፡ ኪ.ያኪ፡ ሠምረ። ኪ.ያሁ፡ ኀረየ። ዘኪ.ያሃ፡ አፍቀረ፡ (ኤር፭፡ ፳፪። ኪዳ። ውዳ፡ ማር፱። ሚ.ራ፵፭፡ ፱። ፱፡ ፲፱)። እፎ፡ እንከ፡ ኪ.ያነ፡ ያ ድኅኑ። እፎ፡ እንከ፡ ፈድፋደ፡ ኪ.ያክሙ። ወኪ.ያ ክንሂ። በእንተ፡ ፈጠሮትየ፡ ኪ.ያሆሙ። ወኪ.ያሆን፡ (ኢ.ሳ፳፡ ፯። ማቴ፯፡ ፴። ዘረፋ። ዘፍ፯፡ ፯። ዘሌ፳፡ ፲፱)። አንዳንድ፡ ጊዜም፡ በተገብሮ፡ ፀአፋ፡ በሰሊሁና፡ በውእቱ፡ በሎቱና፡ በቦቱ፡ ፈንታ፡ ቀጥሎ፡ ይገኛል፡ የመላሽ፡ ስሕተት፡ ነው። እወ፡ ውእቱ፡ ኪ.ያሁ። ወዘ ሎሙ፡ ርቱዓነ፡ ልብ፡ እለ፡ ኪ.ያሃ፡ ቦሙ። እለ፡ ሀ ለዉ፡ በኪ.ያሆን፡ መዋዕል። ጸውዖ፡ ኪ.ያሁኒ፡ ው ስተ፡ በዓል። ነዋ፡ አምላክነ፡ ዘኪ.ያሁ፡ ተወከልነ፡ (አፈ፡ ድ፲፩። መዝ፡ ፺፫። ዮዲ.፱፡ ፯። ጦቢ.፱፡ ፪። ኢ.ሳ ፳፭፡ ፱)። ቅጽል፡ መኾኑም፤ በዝኩና፡ በውእቱ፡ ፈ ንታ፡ ሲገባ፡ ነው። ኪ.ያሁ፡ መንፈስ፡ ነሚአሙ። ይ ሠውዕ፡ ኪ.ያሃ፡ መሥዋዕተ። እሬኢ.ኑ፡ እንጋ፡ ኪ.ያሃ፡ ዕለተ፡ ቢል፤ ያንን፡ መንፈስ፡ ያችን፡ መሥዋዕት፤ ያችን፡ ዕለት፡ ያሰኛል፡ እንጂ፤ ርሱን፡ ርሷን፡ ማለት፡ አይስማ ማም፡ (ስንክ፡ ግንቦ፳። ዕብ፲፡ ፲፩። ተረ፡ ቊር)። (ዕር ፲፬፡ ቍጽ፲፱)።

**ክዩ.ድ፤ ዶት፤ (ኬደ፡ ይክይድ፡ ይኪ.ድ። ረገፀ፡ ሄደ)፤** መኼድ፤ መርገጥ፡ መዳጥ፡ መደፍጠጥ፡ መጠቅጠቅ፡ ማጥቃት፡ በእግር፡ በሰኰና፡ በርግጫ፡ መ ምታት፤ ያውድማ፡ የነዶ፡ የወይን፡ የጭቃ፡ የልብስ፡ የ ሰው። ይክይድዋ፡ ለምእብ፡ ከመ፡ ዘይክይዱ፡ እ ክለ፡ በመንኰራኵር። ኬዱኒ፡ ከመ፡ ጽቡር። ነዳይ፡ እመ፡ ወድቀ፡ ይክይድዎ፡ ቢጹ። ወኬዱኒ፡ ፀርየ። ከመ፡ ትኪ.ድሙ፡ (ኢ.ሳ፳፭፡ ፲። ኢ.ዮ፴፡ ፲፱። ሚ.ራ፲፫፡ ፳፭። መዝ፡ ፶፯። ኩፋ፡ ፴፭)።

—፤ መሄድ፡ መራመድ፤ እግሮችን፡ እያፈራረቁ፡ ማ ንሣትና፡ መጣል፡ መንቀልና፡ መትከል፤ ምስጢሩ፡ ከ ዚያው፡ ከመርገጥ፡ አይወጣም፤ ሀይድን፡ እይ። ፍ ኖተ፡ ረሲዓን፡ ኢትኪ.ድ። ሰክዩ.ደ፡ አሠሮሙ። ወን በኒ፡ ኬደ፡ ይደምፅ፡ እግሩ፡ በቃለ፡ ፀዓዕ፡ (ምሳ፬፡ ፲፬። ኩፋ፡ ፳፩። ሚ.ራ፴፩፡ ፲)። አንዳንድ፡ መጠፍ፡

በኬደ ፡ ፈንታ ፡ እንዳማርኛው ፡ አኪደ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። ኢያከይዱ ፡ ወይነ ፡ ውስተ ፡ ምክያድ ። ያከይዱ ፡ እክለ ፡ ወወይነ ። ትንሥኢ ፡ እኪዳዮሙ ። ባሕም ፡ ዘያከይድ ፤ (ኢሳ ፳፰ ፡ ፳ ። ነሐ ፲፫ ፡ ፲፭ ። ሚክ ፮ ፡ ፲፭ ። ዘዳ ፳፭ ፡ ፬) ።

**ከያዲ** ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤ የሚረግጥ ፡ ረጋጭ ፡ አጥቂ ፡ ጠቅጣቂ ።

**አኬደ** ፤ አስረገጠ ፤ አበራየ ። ኢትፍፅም ፡ እ ፉሁ ፡ ለባሕም ፡ ሶበ ፡ ታከይድ ፡ እክለከ ። ወዘኒ ፡ ያ ከይድ ፡ እክለ ፡ (፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፰ ። ፩ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፱ ፡ ፲) ።

—፤ አስኬደ ፡ አስሮጠ ፤ ነዳ ። አኬድከ ፡ ውስተ ፡ ባ ሕር ፡ አፍራሲከ ። ወያከይዱ ፡ ለሐመሩ ፡ (ዕን ፫ ፡ ፲፭ ። ማር ፡ ይሥሓቅ) ። በዐጸደ ፡ ፈንታ ፡ አኬደ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ለእመ ፡ አኬድከ ፡ እክለ ፡ ገ ራህትከ ። ያከይድ ፡ ዘርዐ ፡ ሠዊት ፡ (ዘሌ ፳፮ ፡ ፲፱ ። ኢሳ ፲፯ ፡ ፭) ።

**ተከይደ** ፤ ተረገጠ ፡ ተጠቀጠቀ ፤ ተናቀ ፡ ተ ጠቃ ፡ ተጨቈነ ። ውስተ ፡ መካን ፡ እንተ ፡ ኢተከይደት ። መቅደስ ፡ ወኀይል ፡ ተከይደ ። አርዌ ፡ ተከይደ ፡ ወ ከይሲ ፡ ተቀትለ ፡ (ጥበ ፲፮ ፡ ፪ ። ዳን ፰ ፡ ፲፫ ። ኪዳ) ።

**ክዩድ** ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ይድ) ፤ የተረገጠ ፡ የተ ጠቃ ፡ ጥቁ ። ሕዝብ ፡ ቅጡዳን ፡ ወክዩዳን ፡ (ኢሳ ፲፰ ፡ ፪) ።

**ኪደት** ፤ መርገጥ ፤ መረገጥ ፤ አረጋገጥ ፡ ርግጫ ፤ ጫማ ፡ ስኰና ፡ (ስንክ ፡ መጋ ፲፩ ። ኢሳ ፶፪ ፡ ፯) ። ወኢታ ኀምር ፡ ፍኖታ ፡ ዘእንበለ ፡ አሐቲ ፡ ኪደተ ፡ እግረ ፡ ብእሲ ፡ (ሱቱ ፡ ዕገዛ ፡ ፯) ።

**ተካየደ** ፤ ተራገጠ ፤ ተረጋገጠ ። እስከ ፡ ይትካ የዱ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ (ሉቃ ፲፪ ፡ ፩) ። በኪደ ፡ ፈንታ ፡ ተካየደ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ይትካየድዋ ፡ አሕ ዛብ ፡ (ራእ ፲፩ ፡ ፪) ።

**መከየድ** ፤ (ብ ፡ መካይድ) ፤ መርገጫ ፡ መ ኼኛ ፡ ጫማ ፡ ውስጥ ፡ እግር ፡ ዝርጉ ፡ ጠፍጣፋው ። መ ካነ ፡ መከየደ ፡ እገርየ ። በማእከለ ፡ መከየደ ፡ እገ ሪሁ ፡ ወፅአ ፡ ቍስል ። ፍቅርኪ ፡ ሠረጸ ፡ ውስተ ፡ ል ብየ ፡ ወኮነ ፡ ሥረዊሁ ፡ እስከ ፡ መካይድየ ። ሰላም ፡ ለመካይድኪ ፡ እለ ፡ ረከቦን ፡ መከራ ፡ እንበለ ፡ አሣ እን ፡ እመ ፡ ሖራ ፡ (ሕዝ ፵፫ ፡ ፯ ። ገድ ፡ ተክ ። አርጋ ፡ ፭ ። ደራሲ) ።

—፤ ድኻ ፡ ግርንቡድ ፤ ሱሕ ፡ ምንጣፍ ፡ የእግር ፡ ድጋፍ ፡ ማረፊያ ። ሰማይ ፡ መንበርየ ፡ ወምድርኒ ፡ መከ የደ ፡ እገርየ ። ወኢተዘከረ ፡ መከየደ ፡ እገሪሁ ፡ በዕ ለተ ፡ መዐቱ ። እገብኦሙ ፡ ለጸላእትከ ፡ ታሕተ ፡ መ ከየደ ፡ እገሪከ ፡ (ኢሳ ፷፮ ፡ ፩ ። ሰቈ ፪ ፡ ፩ ። መዝ ፻፱) ።

—፤ የንጨት ፡ ሰገነት ፤ ደርብ ፡ መረባርብ ፡ እንደ ፡ ቈጥና ፡ እንደ ፡ ማማ ፡ ኹኖ ፡ ለመስበክያና ፡ ለማንበቢያ ፡ ላዋጅ ፡ መንገሪያ ፡ የተሠራ ፡ ዕርከንና ፡ መሰላል ፡ ያለው ። ወቆመ ፡ ዕዝራ ፡ ላዕለ ፡ መከየድ ፡ ዘዕፅ ፡ (ነሐ ፰ ፡ ፬) ።

—፤ ጫማ ፡ ወይም ፡ መጫሚያ ፤ የውስጥ ፡ እግር ፡ ቤዛ ። ዲበ ፡ ኤዶምያስ ፡ እሰፍሕ ፡ መከየድየ ፡ (መዝ ፶፱ ። ፻፯) ።

—፤ የጫማ ፡ ልክ ፡ መጠን ፤ ስፍሩ ፡ ወይም ፡ አሠሩ ። ዐሥርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ መከየደ ፡ እግር ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

—፤ ስከተት ፤ የዐምድ ፡ ሥር ፡ መሠረት ፤ መብቀያውና ፡ መተከያው ። አዕማደ ፡ ወርቅ ፡ እለ ፡ ይቀውሙ ፡ ዲበ ፡ መከየደ ፡ ብሩር ። ወመካይዲሆን ፡ ኀምስቱ ፡ ዘብ ርት ፡ (ሢራ ፳፮ ፡ ፲፰ ። ዘፀ ፴፮ ፡ ፺—፴) ። በመከየድ ፡ ፈንታ ፡ ምክያድ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። አሠረ ፡ ምክያደ ፡ ብእሲ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ ፲) ።

**ምክያድ** ፤ (ዳት) ፤ ዐውድማ ፡ ተረግጦ ፡ የጠ በቀ ፡ መሬት ፤ ያገዘመራ ፡ መውቂያ ፡ ማበራያ ፤ ፍሬን ፡ ከገለባ ፡ መለያ ፤ ማምረቻ ፡ ማግረጃ ። የወይን ፡ መር ገጫ ፤ የዘይት ፡ የስሊጥ ፡ የቅባኑግ ፡ ማውጫ ። ምክያደ ፡ እክል ። ምክያደ ፡ ወይን ። ትበውኡ ፡ ውስተ ፡ ምክ ያድ ፡ ትቅድሑ ። ምክያዳቲሆሙ ፡ (፫ነገ ፡ ፳፮ ፡ ፩ ። ዘኍ ፲፰ ፡ ፳፯ ። ሐጌ ፪ ፡ ፲፮ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፰) ። መዛግብት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ምክያዳት ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ተነሥቱ ፡ ምክያዳት ፡ (ዮኤ ፩ ፡ ፲፯) ።

**ኬደ** ፤ **ከየደ** ፤ (ዐረ ፡ ዐሂደ ። ዕብ ፡ ዐ ዌድ ፤ ሄዒድ) ፤ አዋለ ፡ አሰረ ፤ ውል ፡ አደረገ ፤ ነገ ርን ፡ ቈረጠ ፡ አጠበቀ ፡ አጠና ፤ በቃል ፡ በጥፈት ፤ የሥራ ፡ የንግድ ።

**ተካየደ** ፤ ተዋዋለ ፤ ተጣጣፈ ፤ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተ ጋባ ፡ ተማማለ ፤ ነገር ፡ ተቈረጠ ። ተካየዶሙ ፡ በእደ ፡ ነቢ ያት ። ተካየዱ ፡ ዮናታን ፡ ወዳዊት ፡ ኪዳነ ። ተካየድነ ፡ ምስለ ፡ ሞት ። ተካየዶ ፡ ከመ ፡ ያውስብ ፡ ወለቶ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፫ ። ፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፫ ። ኢሳ ፳፰ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ ሚያ ፳፫) ።

**አስተካየደ** ፤ አዋዋለ ፡ አማማለ ፤ ቃል ፡ ኪ ዳን ፡ አጋባ ። ወአስተካየደ ፡ ዮዳሄ ፡ ኪዳነ ፡ ማእከለ ፡ ቤተ ፡ እግዚ ፡ ወማእከለ ፡ ቤተ ፡ ንጉሥ ፡ ወማእከለ ፡ ሕዝብ ፤ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚ ። አስተካየድዎ ፡ ከመ ፡ ኢ ፡ (፬ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ ሠኔ ፲፪) ።

**ኪዳን** ፤ (ናት ። ዐረ ፡ ዐህድ ። ዕብ ፡ ብሪት ። ሱር ፡ ቅያም) ፤ በቍሙ ፤ ውል ፡ ቋም ፡ ነገር ፤ የፍቅርና ፡ ያንድነት ፡ መሐላ ፤ ሰላማዊ ፡ ሕግ ፡ ኹለቱን ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፤ ስለ ፡ ረብና ፡ ስለ ፡ ጥቅም ፡ በተሰሩ ፡ የቆመ ፡ የተጣፈ ፡ ሥርዐት ፤ ቢያፈር ሱት ፡ ጕዳትና ፡ ጠብ ፡ የሚያመጣ ፡ ጥቅም ፡ የሚያሳጣ ። ወአሖሎ ፡ ኪዳነ ፡ ዘተካየደሙ ፡ ኢዐቀቡ ። ግበሩ ፡ በ ከመ ፡ ኪዳንክሙ ። ወኢይፀራዕ ፡ ኪዳነ ፡ ጼው ። ኪ ዳን ፡ ዘጽኑዕ ። መጽሐፈ ፡ ኪዳን ። ኪዳን ፡ ብሊት ፡ ወሐዳስ ። አይሁድ ፡ እለ ፡ መነኑ ፡ ኪዳናተ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፳፮ ። ገላ ፫ ፡ ፲፭ ። ዮሴፍ ። አርጋ ፡ ፭ ። ዲድ ፡ ፴፫) ።

**ኪዳን** ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ተረፈ ፡ ወንጌል ፡ የጌታና ፡ የሐዋርያት ፡ ቃል ፡ ከትንሣኤ ፡ እስከ ፡ ዕርገት ፡

ያስተማራቸው ፤ እየጠየቁት ፤ የመለሰላቸው ። ከዕርገት ፤ በኋላ ፤ ከወንጌል ፤ በፊት ፤ በጥንት ፤ በብከት ፤ ጥፈውታል ፤ እንደ ፤ ሔሮን ፤ ፪ ፤ ክፍል ፤ አለው ፤ ማስተማሩንም ፤ ሉቃስ ፤ ይመሰክራል ፤ (ግብሐ ፤ ፪ ፤ ፫) ። መጽሐፈ ፡ ኪዳን ፡ ዘእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ጸሐፍዎ ፡ ለዝ ፡ ኪዳን ፡ ዮሐንስ ፡ ወጴጥሮስ ፡ ወማቴዎስ ፡ እንዘ ፡ ያጽሕፎሙ ፡ እግዚእነ ፡ ወፈነዉ ፡ በእርኍዩ ፡ ዝ ፡ ግጽወ ፡ እምኢየሩሳሌም ፤ (ክፍል ፤ ፩) ።

**ኪዳን ፡ ዘነግህ ፤** ከመጽሐፈ ፤ ኪዳን ፤ የወጣ ፤ የንግህ ፤ ጸሎት ፤ ቀሳውስት ፤ ጧት ፤ ጧት ፤ የሚያደርሱት ። ከዚህ ፤ ሌላ ፤ ደግሞ ፤ ፯ ፤ ክፍሎች ፤ አሉ ፤ ኹሉም ፤ በቅዳሴ ፤ ውስጥ ፤ ይገኛሉ ፤ ያንድነት ፤ ስማቸው ፤ ፯ቱ ፤ ኪዳናት ፤ ይባላል ።

**ኪዳነ ፡ ምሕረት ፤** የማርያም ፤ ስም ፤ ወይም ፤ የኪዳኗ ፤ በዓል ፤ በየካቲትና ፤ በናሴ ፤ ባ፲፮ ፤ ቀን ፤ የሚውል ፤ ትእምርተ ፤ ኪዳን ፤ ማለት ፤ ንው ፤ ቀስተ ፤ ደመና ፤ እንደ ፤ ማለት ፤ ቀስቱም ፤ ቅሱ ፤ በሐፃናት ፤ አፍ ፤ የማርያም ፤ መቀነት ፤ ይባላል ። (የታቦት ፤ ከፈን) ፤ ኪዳን ፤ ምረት ፤ ዘሳለም ፤ እመቤት ። ሰላም ፡ ለኪ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ እምነ ፤ (ደራሲ) ።

**ኪያህክ ፤ ኪያክ ፤ (ቅብጥ) ፤** ስመ ፤ ወርኅ ፤ ራብዕ ፤ ታኅሣሥ ። ወኪያህክ ፡ ይሰመይ ፡ ማኅጉን ፤ ወዓዲ ፡ ይሰመይ ፡ ሰዋዋ ፤ (አቡሻ ፤ ፳) ።

**ኪዮኪሉ ፤ (ዕብ ፡ ኪ ፡ ዮክሉ) ፤** እስመ ፡ ይንእሱ ፤ ያንሳሉና ፤ (ሕዝ፵፮ ፤ ፳) ።

**ኪማ ፤ (ዕብ ፡ ኪማህ) ፤** የ፯ቱ ፤ ከዋክብት ፤ ተራ ፤ ጸታቸውና ፤ ምግባናቸው ፤ አከኺዳቸው ። ኪማ ፡ ወኬሴላ ፤ (ዓሞ፭ ፤ ፰) ።

**ከዪን ፤ ኖት ፤ (ኬነ ፤ ከየነ ፡ ይከይን ፡ ይኪን) ፤** መኾል ፤ መስላት ፤ ኹል ፤ ስል ፤ መኾን ፤ ለመውጋት ፤ ለመቍረጥ ፤ መዘጋጀት ፤ የብረት ። ብልኅ ፤ መኾን ፤ ሥራ ፤ ማወቅ ፤ በሥራ ፤ መራቀቅ ፤ ሐዲስ ፤ ነገር ፤ መፍጠር ፤ መኪና ፤ ማውጣት ። በልጎንና ፤ ጠቢን ፤ ተመልከት ፤ የዚህ ፤ ጎሮች ፤ ናቸው ። መጽሐፍ ፤ ግን ፤ በኪነ ፤ ፈንታ ፤ ኬነወ ፤ ተኪነወ ፤ ይላል ፤ ተ ፤ ከንቱ ፤ ነው ። ተኬነዉ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ትስሕቱ ። ብተኬንዎ ፡ ምግባር ። ዘዐቢይ ፡ በተኬንዎቱ ፡ ወኀያል ፡ በምግባሩ ። ልብስ ፡ ብሩህ ፡ ዘኢተኬነዎ ፡ እደ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ፤ (ኢሳ ፵፯ ፤ ፳ ። ጥበ፲፫ ፤ ፲ ። ቅዳ) ።

**ከያኒ ፤ ኬንያ ፤ (ያት) ፤** ብልኅ ፤ ጠቢብ ፤ ብልኀተኛ ፤ ጥበበኛ ፤ ሥራ ፤ ዐዋቂ ፤ አንጥረኛ ፤ ባለመኪና ፤ ፈጣሪ ፤ ሐኪም ፤ ወጌሻ ፤ መሐንዲስ ፤ ፈላስፋ ፤ በፍጥረት ፤ በሥራ ፤ የሚራቀቅ ፤ ጥሩ ፤ ዕውቀት ፤ ያለው ፤ (ማሕ ፯ ፤ ፪ ። ዕብ፲፩ ፤ ፲ ። ጥበ፯ ፤ ፳፩) ። አንተ ፡ ኬንያሁ ፡ ለኵሉ ፡ ፍጥረት ። ኬንያ ፡ ፍጥረትነ ። ኬንያት ፤ (ድጓ ። ቅዳ ። ስንክ ፤ ኅዳ፲፰) ።

**ኬናዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ነውት ፤ ኬነወ) ፤** ዝኒ ፤ ከማሁ ። ኬነውት ፤ (ስንክ ፤ መስ፳) ።

እንዳንድ ፤ መጽሐፍ ፤ ግን ፤ በኬንያትና ፤ በኬነውት ፤ ፈንታ ፤ ኪንት ፤ ኬንት ፤ ይላል ፤ የጣፊ ፤ ስሕተት ፤ ነው ። ኪነተ ፡ ዕፀ ። ኪነተ ፡ ኣሕማር ። ያስተጋብሮሙ ፡ ለኪነት ፡ ወይሁቦሙ ፡ ብዙኀ ፡ ንዋየ ። ወያስተጋብአሙ ፡ ለኵሉ ፡ ኬነት ። ኤልያብ ፡ ሊቀ ፡ ኬነት ፡ ዘማእነም ፡ (ኩፋ ፤ ፲፩ ። ፈኢ፲፰ ፤ ፲፯ ። ግብ፲፱ ፤ ፳፬ ። ፳፭ ። ዘፀ፴፯ ፤ ፳፩) ።

**ኪነት ፤ (ታት) ፤** መጠበብ ፤ መራቀቅ ፤ ጥበበኛነት ። የእጅ ፤ ጥበብ ፤ ተግባረ ፤ እድ ። ኪነተ ፡ ንዋየ ፡ ጸብእ ። ኪነታቲሆሙ ፤ (ዮሴፍ ። ፈልክ ፤ ፫) ።

**ኪን ፤ (ብ ፡ ኪናት) ፤** ጥበብ ፤ ብልኀት ፤ ተንኰል ፤ ርቀት ። ዘእንበለ ፡ ኪን ። በሥነ ፡ ኪኑ ። ኪነ ፡ ዕንቍ ። ዘቦቱ ፡ ኪን ፡ በወርቅ ። ኪን ፡ ዘሐንጻት ። ኪነ ፡ ሥራይ ። ርእዩ ፡ ኪኖ ፡ ወምግባሮ ፡ ለሰይጣን ፤ (ጥበ፲፬ ፤ ፬ ። ፲፫ ፤ ፲፭ ። ዘፀ፴፭ ፤ ፴፫ ። አዜና ፤ ፳፫ ፤ ፲፭ ። ዮሴፍ ። ቀሌ ። ዲድ ፤ ፴፪) ።

—፤ ሥራ ፤ ተግባር ፤ በየስሙና ፤ በያይነቱ ፤ ማናቸውም ፤ ኹሉ ። ኢትትማከር ፡ ምስለ ፡ ሕብሩ ፡ እንበይነ ፡ ኪን ። ከመ ፡ ይጥብቡ ፡ በኪኖሙ ። ተምህረ ፡ ኪነ ፡ እድ ፡ ለሲሳዩ ፡ ዕለቱ ፤ (ሢራ፴፯ ፤ ፲፩ ። ፴፰ ፤ ፴፬ ። ፈልክ ፤ ፩) ።

—፤ መሣሪያ ፤ መኪና ፤ ወይም ፤ ሥራ ፤ ተደራጊና ፤ ተሠሪ ። ሕውፀዩ ፡ ምግሐ ፡ ኅጺን ፡ ወኵሎ ፡ ኪነ ፡ ዘንዋየ ፡ ጸብእ ። ይብሎኑ ፡ ኪን ፡ ለኬንያሁ ። ኵሉ ፡ ኬንያ ፡ ወኵሉ ፡ ኪን ፡ ኢይትረከብ ፤ (ዮሴፍ ። ኢሳ፳፱ ፤ ፲፮ ። ፈኢ፲፰ ፤ ፳፪) ።

**ኬነወ ፤ ተኬነወ ፤** ከዪን ፤ ኪነ ፤ ከየነ ።

**መኪና ፤ (ጽር ፡ ሚካኔ) ፤** በቁሙ ፤ መዘውር ፤ የጥበብና ፤ የብልኀት ፤ መሣሪያ ፤ ሥራን ፤ ኹሉ ፤ በፍጥነት ፤ የሚያስኪድ ።

**ኲናት ፤ (ታት ፤ ኵያንው ። ዕብ ፡ ሐኒት ። ዐረ ፡ ሐርበት) ፤** ጦር ፤ ዘገር ፤ መውጊያ ፤ መዘርጊያ ፤ በብልኀት ፤ በጥበብ ፤ የተሠራ ፤ የሰላ ፤ የኾለ ። ንግሥ ፡ ወልታ ፡ ወኲናተ ። ኲናታተ ፡ ወአርማሐ ። ወላትው ፡ ወኵያንው ፤ (መዝ ፤ ፴፬ ። ፪ዜና ፤ ፲፩ ፤ ፲፪ ። ኅ፫ ፤ ፱) ።




ኲናት ፤

**ኬፋ ፤ ኬፋስ ፤—ኰኵሕ ፤—ከፊአ ፡ ከፍአ ።**

**ኬሰ ፤ (ይከይስ ፡ ይኪስ ፤ ከዪስ ። ኰዐሰ ፤ ለወየ ፤ ጠወየ) ፤** ዐጠፈ ፤ ጠቀለለ ፤ ሰበሰበ ፤ የልብስ ፤ የገመድ ፤ የሽቦ ። ታጠፈ ፤ ተጠቀለለ ። ግስንቱ ፤ ከኰዐሰና ፤ ከለወየ ፤ የተደቀለ ፤ ነው ፤ የ ፤ ከለወየ ፤ መጥቶ ፤ በዐ ፤ ፈንታ ፤ ገብቷል ። የኹሉንም ፤ ፍቾ ፤ በየቦታው ፤ እይ ።

**ከይሲ ፤ (ብ ፡ አክ(ከ)ይስት ፤ አኪስት) ፤** አባብ ፤ ዘንዶ ። ከይሲ ፡ ተጠብለለ ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ። ስነ ፡ አክይስት ፡ ዘቦቱ ፡ ሕምዝ ። ወሀሎ ፡ ከይሲ ፡ ዐቢይ ፡ ዘያመልክዎ ፡ ሰብአ ፡ ባቢሎን ። ወትከይድ ፡ አንበሳ ፡ ወከይሴ ። ወናሁ ፡ ክልኤቱ ፡ አክይስት ፡ ዐበይት ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ ፴ ። ጥበ ፲፯ ፡ ፲ ። ዳንኤ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፺ ። አስቴ ፲፩ ፡ ፭) ።



ከይሲ ፡

—፤ ዐዘ ፡ ደራጎን ፤ የባሕር ፡ ተመን ። ሰበርከ ፡ ርእሰ ፡ ከይሲ ፡ በውስተ ፡ ማይ ። ይቀትሎ ፡ ለከይሲ ፡ ዘውስተ ፡ ባሕር ። አክይስትኒ ፡ ወዘሉ ፡ ቀላያት ፡ (መዝ ፡ ፸፫ ። ኢሳ ፳፯ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፻፵፰) ።

—፤ ዐንበሪ ፡ ሌዋታን ፡ ዲያብሎስ ፡ ሰይጣን ። ከይሲ ፡ ዘፈጠርከ ፡ ይሣለቅ ፡ ባዕሌሆሙ ፡ በምክረ ፡ ከይሲ ፡ ርጉም ፡ (መዝ ፡ ፻፫ ። ቅዳ ፡ አፈ) ። ስንን ፡ አናብስት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ግርማ ፡ አክይስት ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ብሂሞትንና ፡ ሌዋታንን ፡ እይ ፡ (ኢዮ ፱ ፡ ፲) ።

**ኪስ ፤ (ብ ፡ አክያስ ። ዕብ ፡ ወዐረ ፤ ኪስ ። ሱር ፡ ኪሳ) ፤** በቁሙ ፤ ታናሽ ፡ ከረጢት ፡ ቀናማት ፡ የገንዘብ ፡ መያዣ ፤ ማስሪያና ፡ መቈለፊያ ፡ ያለው ፡ በጀብ ፡ የሚያዝ ። ፈትሐ ፡ ኪሶ ፡ ወአውፅአ ፡ ወርቀ ፡ (ዮሴፍ) ። ጀብ ፤ በኮት ፡ በካቡት ፡ በቀሚስ ፡ በሱደርያ ፡ ላይ ፡ በውስጥ ፡ በአፍኣ ፡ የሚሰፋ ፡ የልብስ ፡ ጎዳ ። ሐስል ፤ ሥቅ ፤ ጆንያ ፡ ኪሻ ። ጆን ፡ ህንዲ ፡ ነው ።

**ኳኳ ፤ (ጽር ፡ ኮኮስ) ፤** ጥሩ ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፤ ወይም ፡ በቀይ ፡ ቀለም ፡ የታለለ ፡ ልብስ ፡ ፈትል ። ባለ ብሉዮች ፡ ግን ፡ ጥቍር ፡ ሱፋላ ፡ ለማለት ፡ በርኖስ ፡ ይሉታል ። እመኒ ፡ ኮነ ፡ ኀጢአትክሙ ፡ ከመ ፡ ኳኳ ፡ ይጸዐዱ ፡ ከመ ፡ በረድ ፤ ወእመኒ ፡ ቈሐ ፡ ከመ ፡ ለይ ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡ ፀምር ፡ (ኢሳ ፩ ፡ ፲፰) ። ቈሐና ፡ ኮነ ፡ ለይና ፡ ኳኳ ፤ ይከውንና ፡ ይጸዐዱ ፤ ከመ ፡ ፀምርና ፡ ከመ ፡ በረድ ፡ አንዳንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ።

**ኮክሀ ፤—ኮክ ፡ የኮክ ፡ ፍሬ ፤—ከወከ ።**

**ኰሱሕ ፤—ጥኑ ፡ ደንጊያ ፤—ከሕክሐ ።**

**ኰከይ ፤ (ዋከየ ፡ ውኪይ) ፤** ቡሓ ፡ ራስ ፡ ነቀይ ፤ በግ ፡ ቍራ ፡ (ትግሬ) ።

**ኰከመ ፤** ከከመ ፡ የእግር ። ኰመኰመ ፤ የምግብ ፡ የጨዎት ። በፈስ ፡ ዘቀ ፤ የምርት ።

**ኰከም ፤ (ማት) ፤** የፍም ፡ መጫሪያ ፡ መተርከሻ ፡ ያመድ ፡ ማፈሻ ። ኢያሚንን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። በለብሉዮች ፡ ግን ፡ እንቅብ ፡ ይሉታል ፤ አንኮላ ፡ ገበና ፡ የሚሉም ፡ አሉ ። ጽህርታት ፡ ወኩከማት ፡ (ኤርሚ ፶፪ ፡ ፲፰) ።



ኩከማት ፡

**ኬክሮስ ፤ (ሳት ። ጽር ፡ ኪርኮስ) ፤** የክፍለ ፡ ዕለት ፡ ስም ፤ የዕለት ፡ ፳፯ ። ፭ዱ ፡ ዕለት ፡ ወይም ፡ ፳፬ቱ ፡ ሰዓት ፡ ፷ ፡ ኬክሮስ ፤ አንዱ ፡ ኬ ፡ ፷ ፡ ክልኢት ፤ አንዱ ፡ ክ ፡ ፷ ፡ ሣልሲት ፤ አንዱ ፡ ሣ ፡ ፷ ፡ ራብዒት ፤ አንዱ ፡ ራ ፡ ፷ ፡ ኃምሲት ፤ አንዱ ፡ ኃ ፡ ፷ ፡ ሳድሲት ፡ ይኾናል ፤ ይህ ፡ ሲዘረዘር ፡ ነው ። ሲጠቀለል ፡ ደግሞ ፤ ስሳው ፡ ሳ ፡ ፩ ፡ ኃምሲት ፤ ስሳው ፡ ኃ ፡ ፩ ፡ ራብዒት ፤ ስሳው ፡ ራ ፡ ፩ ፡ ሣልሲት ፤ ስሳው ፡ ሣ ፡ ፩ ፡ ክልኢት ፤ ስሳው ፡ ክ ፡ ፩ ፡ ኬክሮስ ፤ ስሳው ፡ ኬ ፡ ፩ ፡ ዕለት ፡ ይኾናል ። እንዘ ፡ ዓመተ ፡ እልሉ ጀራ ፡ በስድስቱ ፡ መካናት ፤ በመካነ ፡ ዕለት ፡ ኍልቈ ፡ ኬክሮስ ፡ ወበመካነ ፡ ኬክሮስ ፡ ኍልቈ ፡ ካልኢት ። ዘይኄምሶን ፡ ለኬክሮሳተ ፡ በዓታት ፡ ከመ ፡ ይኩና ፡ መዓርገ ፡ ጸሎታት ፡ (አቡሻ ፡ ፲፭ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ከል ፤—ትፋሕ ፤—ከወለ ።**

**ኮሉ ፤—ኹሉ ፤—ከልሎ ፡ ከለለ ።**

(ተ) **ክልአ ፤ አት ፤ (ክልአ ፡ ይኬልእ ፡ ይክልእ) ፤ አው ፡ ከሊእ ፤ አት ፤ (ከልአ ፡ ይክልእ ፡ ይክላእ ። ዕብ ፡ ካላእ ። ሱር ፡ ክላእ ። ዐረ ፡ ከለአ) ፤** መከልከል ፡ መንሣት ፤ ማገድ ፡ ማስቀረት ፤ ማቆም ፡ መግታት ፤ ክንቢብ ፡ ክገቢር ፡ ክሐዊር ። ክሊአ ፡ መንፈስ ። ክላእ ፡ ልሳንከ ፡ እምእኩይ ። መኑ ፡ ይክልአኒ ፡ ተጠምቆ ። አንዘ ፡ ለንጉሥ ፡ ወክልአ ፡ ኢይባእ ። ኢይክልእ ፡ ምሕረቶ ፡ እምገብሩ ፡ (መክ ፳ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፴፫ ። ግብ ፰ ፡ ፴፯ ። ዳንኤ ፡ ፲፯ ። ኩፋ ፡ ፵፭) ።

—፤ መኾለት ፤ ኹለት ፡ ማድረግ ፡ ከኹለት ፡ መክፈል ።

**ክላኢ ፤ መክልኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤** የሚከለክል ፡ ከልካይ ፤ በረኛ ፡ ዘበኛ ፡ አጋፋሪ ፤ ጠላት ፡ ምቀኛ ። ፍና ፡ መክልኢት ፡ (ፊልክ ፡ ፶፰) ።

**መክልእ ፤ መከልእ ፤ (እት ፡ አን ፡ አት) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ። ይቀውሙ ፡ ቅድመ ፡ ንጉሥ ፡ መክልኣን ፡ እለ ፡ ኢያበውሑ ፡ ከመ ፡ ይቅረቡ ፡ መኑሂ ። ወባሕቱ ፡ ብዙኃን ፡ መክልኣን ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፱) ።

**ምክላእ ፤ (አት) ፤** መከልከያ ፡ ኪሳ ፡ በር ፤ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ አንጉራ ።

**ተከልአ ፤** ተከለከለ ፤ ተገታ ፡ ቆመ ። ተከልአኒ ፡ ኀቢር ፡ ዘእፈቅድ ። ተከልአ ፡ ዝናመ ፡ ሰማይ ። ተከልአ ፡ ጸብእ ፡ ኀምስተ ፡ ዕለተ ፡ (ኪዳ ። ፫ነገ ፡ ፰ ፡ ፴፭ ። ዮሴፍ) ።

**ክሉእ ፤ (አን ፡ አት ፡ ልእት) ፤** የተከለከለ ፡ ክልክል ። ቀቲልሰ ፡ እምኍልቈ ፡ ዐበይት ፡ ኀጣውእ ፡ እለ ፡ ክሉኣት ፡ ወውጉዛት ፡ በሊብ ፡ ወበሕግ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፯) ።

**ክልኣት ፤ (ታት) ፤** መከልከል ፡ (ጥ ፡ ክ) መከልከል ፡ መቅረት ፤ አከላከል ፡ ክልከላ ። ወሃቢ ፡ ዘእንበለ ፡ ክልኣት ። አልቦ ፡ ክልኣት ፡ ለሞትነ ። ዘእንበለ ፡ ምሕረት ፡ ወኢክልኣት ። ክልኣታት ፡ (ቅዳ ፡ ኢ.ኢ. ። ጥበ፱ ፡ ፳ ። ፲፮ ፡ ፲፯ ። ፊልክ ፡ ፵፰) ።

**ክልእ ፤ (ዕብ ፡ ኬሌእ) ፤** ክልክል ፤ የማዘት ፡ ቤት ፡ ዘበኛ ፡ ክልካይ ፡ የሚቆምበት ። የቍጥር ፡ ስም ፤ የጊዜ ፡ ቅጽል ፤ ባንድና ፡ በሦስት ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ቍጥር ፡ ኹለት ። ክልእ ፡ ክልእ ፤ ኹለት ፡ ጊዜ ። በበ ፡ እሑድ ፡ ወበበ ፡ ክልእ ።

**ክልኤ ፤ (ዕብ ፡ ኪልአዪም) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ኹለት ፤ ጥንድ ፡ ጣምራ ፤ የተቈራኙ ፡ የተመሳሰሉ ፤ እንደ ፡ መቀስና ፡ እንደ ፡ ጕጠት ፡ እንደ ፡ ሚዛንና ፡ እንደ ፡ ጡት ፡ ያሉ ፤ ቅጽልነቱ ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ ያስተባብራል ። ክልኤ ፡ አጥባትኪ ። ምስለ ፡ ክልኤ ፡ አዋልዲሃ ። ወፅኣ ፡ ክልኤሆን ፡ ኅቡረ ። ተወልዱ ፡ ሎቱ ፡ ክልኤ ፡ ደቂቅ ። ወነሥአ ፡ ክልኤ ፡ ደቂቆ ። ይመጽኡ ፡ እሉ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ባዕሴኪ ፡ (ማሕ፯ ፡ ፬ ። ዳን፲ ፡ ፲፰ ። ዮዲ፲፫ ፡ ፲ ። ዘፍ፲ ፡ ፵፭ ። ማር ፡ ፳ ። ኢሳ፵፯ ፡ ፱) ።

**ክልኤት ፤ ክልኤቱ ፤ (ወንዶች) ፤** ኹለት ፡ ኹለቱ ። ክልኤቱ ፡ ዕደው ፡ ዐርጉ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ። ክልኤቱ ፡ እምኔክሙ ። ተረክቡ ፡ ክልኤተ ፡ ዕደወ ፡ (ሉቃ፲፰ ፡ ፲ ። ማቴ፲፰ ፡ ፲፱ ። ኢያ፪ ፡ ፪ ፡ ፬) ።

**ክልኤቲ ፤ ክልኤ ፤ (ሴቶች) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ኹለት ። በግብር ፡ ጊዜ ፡ ክልኤ ፡ ቢል ፡ እንጂ ፡ ክልኤተ ፡ አይልም ። ክልኤቲ ፡ አንስት ። ክልኤቲ ፡ ኅጣይእ ፡ (ዘካ፭ ፡ ፱ ። ሚሬ፯ ፡ ፲፫) ። ነሥአ ፡ ክልኤ ፡ አንስትየ ፡ ወወለዳ ፡ ሎቱ ፡ ክልኤ ፡ አዋልደ ።

**ክልእ ፤ (እት ፡ አን ፡ ኣት) ፤** ሌላ ፡ ልዩ ፤ ኹለተኛ ፡ ተከታይ ፤ መሰል ፡ እኩያ ፡ መንቲያ ፤ ጓደኛ ፡ ወዳጅ ፡ ባልንጀራ ፡ ባለሟል ። ካልእ ፡ ክብሩ ፡ ለዘበሰማይ ፤ ወካልእ ፡ ክብሩ ፡ ለዘበምድር ። ሕገሙ ፡ ካልእ ፡ እምነ ፡ ዙሉ ፡ አሕዛብ ። ሶበ ፡ አሐዱ ፡ ይድኅር ፡ ወካልኡ ፡ ይረግም ። ካልኣኒሁ ፡ አርዳእ ። ካልእየ ፡ ኢገፋዕኩክ ። ዘሰ ፡ ካልኡ ፡ ለዳዊት ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፵ ። አስቴ፫ ፡ ፰ ። ሢራ፴፬ ፡ ፳፱ ። ዮሐ፳ ፡ ፳፭ ። ማቴ፳ ፡ ፲፫ ። ፪ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፴፯) ።

**ክልኣዊ ፡ ዊ ፡ ይ ፤** ኹለተኛ ፡ የኹለተኛ ፡ የዳግመኛ ።

**ክልኢት ፤** ፪ኛ ፡ ክፍል ፡ የቍጥር ፡ ቤት ፡ የኬክሮስ ፡ ፷ኛ ፡ ኬክሮስን ፡ እይ ፡ (አቡሻ ፡ ፲፭) ።

**ክልአ ፤—ከላ ፡ አወለቀ ፤—ክልዐ ፤ ቀልዐ ።**

**ክሊብ ፤ ቦት ፤ (ከለበ ፡ ይከልብ ፡ ይክልብ ። ዕብ ፡ ኬሌብ ፤ ሰፋ ፡ ጠቀመ) ፤** መክለብ ፡ መክሉብልብ ፤ መቅለል ፡ መቸኬል ፤ መክለፍለፍ ፤ ቀላል ፡ ቸኮል ፡ ክልፍልፍ ፡ መኾን ፡ (ዐማርኛ) ።

**ከልብ ፤ (ብ ፡ ከለባት ፤ አክላብ ፤ አክልብት ። ዕብ ፡ ኬሌብ ። ሱር ፡ ካልባ ። ዐረ ፡ ክልብ) ፤** ውሻ ፡ የቤት ፡ አውሬ ፡ የኛብ ፡ ወገን ፤ የክፉ ፡ ሰዎች ፡ ምሳሌ ። ውሻ ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ ዋሻም ፡ ሳይቀር ፡ ወሐሽ ፡ ውሕሽ ፡ ከማለት ፡ ከዐረብ ፡ ቃል ፡ መጥቷል ፤ ይኸውም ፡ አውሬ ፡ ያራዊት ፡ ጕሬ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከልብ ፡ ይገብእ ፡ ዲበ ፡ ቅያኡ ። ዐገቱኒ ፡ ከለባት ፡ ብዙኃን ። ኅምስቱ ፡ አክላብ ። አክልብት ፡ ወአዝእብት ፡ (፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳፪ ። መዝ ፡ ፳፩ ። ራእ፳፪ ፡ ፲፭ ። ሢራ፲፫ ፡ ፲፰) ። ያገዳ ፡ ድርቆሽ ፡ ደረቅ ፡ ሳንፋ ፡ ነፋስ ፡ የሚያከለብበው ።



ክልብ ፡

**ከልባዊ ፤** ገጸ ፡ ከልብ ፤ ውሻማ ፡ የውሻ ፡ ዐይነት ፡ ውሻ ፡ ፊት ፤ ጠባየ ፡ ውሻ ፤ ዘማዊ ፡ ወሻሚ ፡ ልክስክስ ። (ግዮም ፡ ስለ ፡ ውሻማ) ፤ ውሾ ፡ ናና ፡ ናና ፡ ዕንካ ፡ ጤፍ ፡ እንጀራ ፤ ወዳጅ ፡ መስሎ ፡ ጠላት ፡ የሴት ፡ ባልንጀራ ።

**ከሌብ ፤ (ዕብ ። ዘኍ፲፫ ፡ ፯) ፤** የሰው ፡ ስም ፤ ካ ፡ ከመ ፤ ሌብ ፡ ልብ ፤ በተገናኝ ፡ ከመ ፡ ልብ ፡ ዘከመ ፡ ልብ ፡ ማለት ፡ ነው ። ካሌብን ፡ አንቀጽ ፡ አድርጎ ፡ ሰፋ ፡ ጠቀመ ፡ ባለው ፡ ዐማርኛ ፡ ሲፈቱት ፡ ግን ፡ እንዳርጌ ፡ ያሰኛል ። እንዳርጊ ፡ መባልም ፡ ባሕር ፡ ተሻግሮ ፡ የመንግ ፡ ይገዛ ፡ ለነበረው ፡ ለትግሬው ፡ ካሌብ ፡ ይስማማል ። ክርሱም ፡ አስቀድሞ ፡ ብዙ ፡ ያበሻ ፡ ነገሥታት ፡ ፳፯ ፡ ዓመት ፡ ገዝተውታል ፡ (ታሪክ) ።

**ክልበኔ ፡ (ጽር ፡ ካልባኒ) ፤** የሙጫ ፡ ሽቱ ፡ እንደ ፡ ዕጣን ፡ ያለ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ በልብን ፡ ዘይቤ ፡ ልባንጃ ፡ ይሉታል ፡ (ሔኖ፴፩ ፡ ፩ ። ሢራ፳፬ ፡ ፲፭) ።

**ክሊሕ ፤ ሐት ፤ (ከልሐ ፡ ይከልሕ ፡ ይክላሕ) ፤ አው ፡ ከልሖ ፤ ሐት ፤ (ከልሐ ፡ ይኬልሕ ፡ ይክልሕ) ፤** መከለል ፡ መጮኽ ፤ በታላቅ ፡ ቃል ፡ መስበክ ፡ መንገር ፤ ማዜም ፤ ማጕረምረም ። ቅመ ፡ ራፋስቂስ ፡ ወከልሐ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ። ክላሕ ፡ በኀይልክ ። ከልሑ ፡ ከመ ፡ ቀርን ፡ (ኢሳ፴፮ ፡ ፲፫ ። ፵፰ ፡ ፳ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ። ሰራሕኩ ፡ በከልሖ ። ይኬልሕ ፡ ሳዕሌሆሙ ። ይኬልሑ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ። ዙላ ፡ ምድር ፡ ትኬልሕ ። እንዘ ፡ ይኬልሓ ፡ መጻሕፍት ፡ (መዝ ፡ ፳፰ ። ኩፋ ፡ ፲፰ ። ኢሳ፯ ፡ ፫ ። ፲፬ ፡ ፯ ። ቁር) ። መብጣት ፡ መፍቃት ፤ መሠንጠቅ ፡ (ትግ ፡ ሐበ) ።

**ክላሒ ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት) ፤** የሚከል ፡ የሚጮኽ ፤ ጩኸ ፤ ቍጡ ፡ ደረቅ ። ብእሲት ፡ ክላሒት ፡ ወነባቢት ፡ ታነሥእ ፡ መቀሥፍ ፡ ጸብእ ። ኢትቅረብ ፡

ኀበ ፡ ብእሲት ፡ መስተጋእዝት ፡ ወከላሒት ፡ (ፊላስ ፡ ገ፻፪ ፡ ፳፱) ።

**ከላሕ ፤** ጩኸት ፤ እሪሪሪ ፡ ዜማ ፤ ፍጅት ፡ ውካታ ። ሰምዐ ፡ ከላሐ ፡ በብእ ። ከላሖሙ ፡ ለሰይጣናት ። ያፈደፍዱ ፡ ከላሐ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀፍረት ፡ (ዮሴፍ ። ስንክ ፡ መስ፳፫ ። አፈ ፡ ድ፱) ።

**ተከልሐ ፤** ተሪሪሪኸ ፤ ተፋጀ ፡ ተዋከ ፤ ተዚያዚያመ ።

**አስተከልሐ ፤** አሪሪሪኸ ፤ አዳመቀ ፤ ጩኸት ፡ አስተማረ ። ወአስተካልሐ ፡ ደቂቃ ፡ በዜማ ፡ ሐዲስ ፡ ለሀገረ ፡ አዜብ ፡ (ገድ ፡ ዘሚ) ።

**ከለየ ፤ ዮት ፤ (ከለየ ፡ ይከሊ ፡ ይክሊ ። ዕብ ፡ ክል ። ዐረ ፡ ከለ) ፤** መስፈር ፤ መመዘን ፡ መለካት ፤ ክልክ ፡ ማግባት ፡ የሥራ ፡ የምግብ ፡ የገንዘብ ።


**ከላዩ ፤ መክለዩ ፡ (ዩት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤** የሚሰፍር ፤ ሰፋሪ ፡ መዛኝ ።

**ከሌ ፤ (ትግ ። ዕብ ፡ ክሊ ፡ ኬሊ) ፤** የቤት ፡ ዕቃ ፤ መማሪያ ፡ ቁሳቍስ ፤ ንዋየ ፡ ሐቅል ፡ ልክና ፡ መልክ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ ያለው ፤ እንትትን ፡ የሚባል ።

**ኪሎ ፤** የሚዛን ፡ ስም ፡ ፍጹም ፡ ልክ ፡ ባለሺሕ ፡ ክፍል ። ኪሎ ፡ ግራም ፤ ኪሎ ፡ መትር ፡ እንዲሉ ። ሺ ፡ ሲሉ ።

**መክልይ ፤ መክሊት ፤ (ብ ፡ መክልይ ፤ መክልያት ። መክሊታት) ፤** የሚዛን ፡ ዐዋቂ ፤ ደንጊያ ፡ ወይም ፡ ብረት ፡ ርሳስ ፤ መጠኑ ፡ ፫ ፡ ሺሕ ፡ ሰቀል ፡ የሚያኽል ። አንዱ ፡ መክሊት ፡ ስሳ ፡ ምናን ፤ አንዱ ፡ ምናን ፡ ኀምሳ ፡ ሰቀል ፡ ይኾናል ። የቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሚዛን ፡ ግን ፡ ዕጥፍ ፡ ነው ፤ መክሊቱ ፡ ቀ፱—፫፳ ፡ ምናን ፤ ምናኑ ፡ ቀ—፻ ፡ ሰቅል ፡ ይኾናል ። መክሊተ ፡ ወርቅ ፡ ትገብራ ። መክሊተ ፡ ጥጥ ፤ መክሊተ ፡ ኀጺን ። መክሊተ ፡ ዐረር ። ነሥአ ፡ ዐሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ መክሊተ ፡ ብሩር ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፴፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ። ዘካ፭ ፡ ፯ ። ፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፳) ። ዘሎ ፡ ወርቅ ፡ ዘተገብረ ፡ ዕሥራ ፡ ወተስዐቱ ፡ መካልይ ፤ ወብሩርኒ ፡ ዘመባእ ፡ ምእት ፡ መካልይ ። ዘይፈዲ ፡ እልፈ ፡ መካልየ ። በረድ ፡ ዘመጠኑ ፡ መካልይ ፡ (ዘፀ፴፱ ፡ ፳ ። ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፳፬ ። ፳፭ ፡ ፲፭—፳፰ ። ራእ፲፯ ፡ ፳፩) ።

**ኵሊት ፤ (ብ ፡ ኵልያት ። ዕብ ፡ ኪልያ ። ሱር ፡ ኩሌይታ ። ዐረ ፡ ኩልየት) ፤** በቁሙ ፡ ኵላሊት ፡ የሆድ ፡ ዕቃ ፡ ንዋየ ፡ ውስጥ ፡ ከጐበትና ፡ ከጣፊያ ፡ በታች ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ሁለት ፡ ወገን ፡ የሚገኝ ፤ ክብ ፡ እንክብል ፡ የባሕርይ ፡ ሚዛን ፤ እንደ ፡ ቍላ ፡ ፍሬ ፡ ኹለትነትና ፡ ትክክልነት ፡ ያለው ። የፍትወት ፡ ምንጭ ፡ የፈቃደ ፡ ሥጋ ፡ መንሻ ። ወንድን ፡ በሴት ፡ ላይ ፡ የሚያስገኝ ፡ የሚያቅበጠብጥ ፤ ወገብ ፡ የሚንጥ ፡ የሚያናውጥ ፡ ርሱ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ክልኤ ፡ ኵልያቲሁ ፡ ወሥብሐ ፡ ኵሊቱ ። ረገዘኒ ፡ ኵልያትየ ፡ (ዘፀ፳፱ ፡ ፲፫ ፡ ፳፪ ። ኢዮ፲፮ ፡ ፲፫) ።



ኵሊት ፤

—፤ ዕውቀት ፡ ሐሳብ ፤ ረቂቅ ፡ ምክር ፡ ውሳጣዊ ፡ ነገር ፤ ኵላሊት ፡ የሚያጤስው ፤ ልብ ፡ የሚያመላልሰው ፤ ናላ ፡ የሚወርሰው ፤ እንዚህም ፡ ፫ቱ ፡ ባንድ ፡ ሚዛን ፡ ይመስላሉ ። ዘይፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ ። ርሑቅ ፡ አንተ ፡ እምነ ፡ ኵልያቲሆሙ ። ገሠጻኒ ፡ ኵልያትየ ። ይትሀወከ ፡ ኵልያቲሁ ፡ እምዛቲ ፡ ቃል ፡ (ኤር፲፩ ፡ ፳ ። ፲፪ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፲፭ ። ሔኖ፷፰ ፡ ፫) ።

**ከልከለ ፤ (ከልአ ። ዕብ ፡ ካልኬል ፤ አበላ ፡ ረኀብን ፡ ከላ) ፤** ከለከለ ፤ ከላ ፡ ከባ ፡ አለ ፤ አገረ ፡ አስተኅጐለ ። ክልክይ ፡ እንዲሉ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ተከልከለ ፤** ተከለከለ ፤ ክልክል ፡ ኾነ ። ጺሕ ፡ ፍኖቶ ፡ ዘእንበለ ፡ ክልአት ፡ ወኢተክልክሎ ። ኢይትከሰከል ፡ (ማንዘ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

**ከለለ ፤ ሎት ፤ (ከለለ ፡ ይኬልል ፡ ይክልል ። ዕብ ፡ ካላል ። ሱር ። ካሌል ፡ ዐረ ፡ ከለ) ፤** መክለል ፡ መጋረድ ፤ ማጠር ፡ መክበብ ፡ ማጀብ ፤ ማክበር ፡ ሬዥ ፡ ማመስገን ። ግሩማን ፡ የዐውድዎ ፡ ወሱራፌል ፡ ይኬልልዎ ። እግዚኦ ፡ ከመ ፡ ወልታ ፡ ሥሙር ፡ ከለልከነ ። ተሰውዋ ፡ እንዘ ፡ ይኬልልዋ ፡ ወይሴብሕዎ ፡ በአፉሆሙ ። ሰበ ፡ ርእይዎ ፡ ተወሊዶ ፡ ከለልዎ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ስብሐት ፡ በአርያም ፡ (መዋሥ ። መዝ ፡ ፭ ። ዮሴ፲፭ ፡ ፲፪ ። ቄር ፡ ገ፳) ።

—፤ ፈጽሞ ፡ ማስጌጥ ፡ መሸለም ፤ ዘውድ ፡ መድፋት ፡ አክሊል ፡ ማቀዳጀት ፡ ለንጉሥ ፡ ለሙሽራ ። ዘከለሎ ፡ ለሰማይ ፡ በከዋክብት ፡ ምድረ ፡ በጽጌ ፡ ወበፍሬ ፡ ከለልከ ። እምዐበየ ፡ ግርማሁ ፡ ዘከለሎ ። ክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ ከለልከ ፡ (ድጓ ። ቀሌ ። መዝ ፡ ፰) ።

— ፤ መደምሰል ፡ መጠቅለል ፡ መሰብሰብ ፤ ብዙውን ፡ ባንድነት ፡ ማሰብ ፤ ኵሉ ፡ ኵለንታ ፡ ማለት ። መፈጸም ፡ መጨረስ ፡ ማከናወን ፤ የሥራ ። መቍረጥ ፡ መክፈል ፤ ያንገት ፡ የመሬት ።

**ከላሊ ፤ መከልል ፤** የሚከልል ፡ ከባይ ፡ ቈራጭ ፡ ከፋይ ።

**አከለለ ፤ አስተከለለ ፤** አስከለለ ፡ ተከሊል ። አስደረገ ፤ አክሊል ፡ አሠራ ፤ አስደፋ ።

**አክሊል ፤ (ላት ። ዐረ ፡ ኢክሊል ። ሱር ፡ ክሊላ) ፤** በቁሙ ፤ ዘውድ ፤ የራስ ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ የክብር ፡ ጕልላት ። ወድቀ ፡ አክሊለ ፡ ርእስነ ። አክሊለ ፡ ጽጌ ። አክሊል ፡ ዘሦክ ። ንሣእ ፡ ወርቀ ፡ ወብሩረ ፡ ወግበር ፡ አክሊላተ ። አክሊለ ፡ ክህነት ፡ ወመ

ንግሥት ። አክሊል ፡ ዘእምዕንቍ ፡ ክቡር ፡ (ሰቈቃ ፡ ፶፮ ። ደራሲ ። ማርያ፭ ፡ ፶፯ ። ዘካ፮ ፡ ፲፬ ። ሳታት ። መዝ ፡ ፳)።



አክሊል ፤

—፤ ዘፈት ፡ ቆብ ፡ ጥምጥም ፡ የራስ ፡ ልብስ ፡ ቀጸላ ፡ መሸፈኛ ፡ ጌጥንት ፡ ያለው ፡ (ዘሌ፰ ፡ ፱) ። መጽንፍትንና ፡ ቈዳርስን ፡ ኢይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ሚክሎል** ፤ (ዕብራ) ፤ ክቡር ፡ ልብስ ፡ ፍጹም ፡ ጌጥ ፡ ፍጹም ፡ ሽልማት ፡ (ሕዝ፳፫ ፡ ፲፪) ።

**ክላል** ፤ ከሎታ ፡ መለባ ፤ ሚዶ ፡ መሥዕርት ፡ (ትግ ፡ ሐባ) ። ክለላ ፡ ዐጥር ፤ ግርዶሽ ።

**ተከለለ** ፤ በቁሙ ፤ ተጋረደ ፡ ሰበሰ ፡ ተቀዳጀ ። ተከለሉ ፡ በፍኖቶሙ ፡ ደመና ። ተከለለ ፡ ገጹ ፡ ብርሃነ ። ክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ ዘተከለለ ፡ (ዮሴፍ ። ስንክ ፡ የካ፳፭ ። ዕብ፪ ፡ ፱) ።

**ክሉል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ልልት) ፤ የተከለለ ፡ ክልል ፤ የተጌጠ ፤ ክቡር ፡ ምስጉን ፤ ቅዱስ ፤ ዝግጁ ። ቤት ፡ ክሉል ፡ በአክዋል ። በስብሐት ፡ ልዕልት ፡ ክሉል ፡ ውእቱ ። ክሉል ፡ በትርሲተ ፡ ብርሃን ። ክሉል ፡ በጌራ ፡ መዊእ ፡ (መቃ ፡ ገ፫ ። ቄር ። ስንክ ፡ ታኅ፳ ። ጥር፳፫) ።

—፤ የተደፋ ፡ የተጐለለ ፤ ጉልል ፡ ንቡር ። አክሊሉኒ ፡ ይኩን ፡ ክሉለ ፡ መልዕልተ ፡ ርእሱ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፴፭ ፡ ፳)።

**ክላሌ** ፤ (ልያት) ፤ መክለል ፤ (ጥክ) መክሰል ፤ መቈረጥ ፡ መቀዳጀት ። ክለላ ፡ ቈረጣ ፡ ቅድጀት ፡ ምስጋና ፡ ፍጻሜ ፤ ፍጹም ፡ ክብር ። ዮም ፡ ተጽሕፈ ፡ እም ፡ ነገሥት ፡ ክላሌሁ ፡ በመጥባሕት ፡ ሰ፫ዮርጊስ ፡ ሰማዕት ። ንደሉ ፡ ክላሌሆሙ ። ክላሌ ፡ ክብር ፡ ወስብሐት ፡ ይደሉ ፡ ለባሕቲቱ ፡ (ድጓ ። ስንክ ፡ ኅዳ፯ ። አፈ ፡ ድ፱) ። ክላሌሁ ፡ በመጥባሕት ፡ ያለው ፡ የሰማዕታት ፡ ሞት ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡ ሞት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነፍሳቸውም ፡ መሸፈው ፡ ፍትና ፡ ሥጋዋ ፡ ቢሰየፍ ፡ ገድሏ ፡ መፈጸሙን ፡ የቀናጓርጉን ፡ ሥራ ፡ ጠርሳ ፡ አክሊለ ፡ ብርሃን ፡ መቀበሏንና ፡ መቀዳጀቷንም ፡ ቢያሳይ ፡ እንጂ ፤ መቈረጥን ፡ ብቻ ፡ አያሳይም ።

**ተክሊል** ፤ በቁሙ ፤ የግቢ ፡ ሥርዐት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ክህነት ፡ በመርዓዊና ፡ በመርዓት ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙት ፡ የሕግ ፡ ጋብቻ ፡ ሲፈርስ ፡ የማይቻል ። ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ተክሊል ፡ ያሰኘው ፡ የሙሽሮቹ ፡ ልብስ ፡ ጌጡ ፡ ሽልማቱ ፡ ፈርጡ ፡ ቀለበቱ ፡ ያበባው ፡ አክሊል ፡ ነው ። ሰበ ፡ ተዋሰቡ ፡ በጸሎተ ፡ ተክሊል ። እምቅድመ ፡ ይግበሩ ፡ ሎቱ ፡ ተክሊለ ፤ ወእምድኅረ ፡ ተክሊል ። አውስቦስ ፡ ዳግማዊት ፡ ተሐጽጽ ፡ እምቀዳማዊት ፤ ወለዛቲ ፡ ትሠርዐ ፡ በቀኖናት ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ላቲ ፡ በረከተ ፡ ተክሊል ፤ አላ ፡ ይግበሩ ፡ ጸሎተ ፡ አስተስርዮ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፻፺ ። ፲፱ ፡ ፳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፳) ።

**ኰል** ፤ (ዕብ ፡ ከል ። ሱር ፡ ካል ። ዐረ ፡ ኩል) ፤ ኹል ፤ (ኹል ፡ ጊዜ ፤ ኹል ፡ ቀን) ። ምሉእ ፡ ፍጹም ፡ ነገር ፡ ደምሳሳ ፡ ጠቅላላ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፤ ባንድነት ፡ የቆመ ፡ የተወሰነ ፡ ሥራ ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ ማኅበር ፡ አንድ ፡ ያልቀረው ፡ ያልጐደለው ፡ ድምር ፤ ፍጥረት ፡ ሕዋሳት ፡ እንደ ፡ ማለት ። ኰልና ፡ ኰሉ ፡ አሐድ ፡ አሐዱ ፤ ዐሥርት ፡ ዐሥርቱ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ናቸው ፤ ርባታቸውም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ኰል ፡ ለስድስቱ ፡ ቅርቦች ፡ ኰሉ ፡ ላራቱ ፡ ሩቆች ፡ ይነገራል ። ኰልየ ፡ ከ ፡ ኪ ፡ ኰልን ፡ ከሙ ፡ ክን ። ኰሉ ፡ ላ ፡ ሎሙ ፡ ሎን ። አብርሃም ፡ አበ ፡ ኰልነ ። ኰልክሙ ፡ አሕዛብ ፡ (ሮሜ፬ ፡ ፲፮ ። መዝ ፡ ፻፲፮) ። በገቢርም ፡ ጊዜ ፡ ኰልየ ፡ ካለው ፡ በቀር ፡ ባምስቱ ፡ ኹሉ ፡ ልን ፡ ለ ፡ ይወርሰዋል ። ዕቀብ ፡ ኰለነ ። ከመ ፡ ትቅትል ፡ ኰለነ ፡ (ሲጦን ። ዘፀ፲፯ ፡ ፫) ።

**ኰሉ** ፤ (ኰላ ፡ ኰሎሙ ፡ ኰሎን) ፤ ኹሉ ፡ መላው ፡ ፍጹሙ ፡ ጠቅላላው ፤ አንድ ፡ ሳይቀር ። ኰሉ ፡ ዓለም ፤ ኰላ ፡ ምድር ፤ ኰሎሙ ፡ ዕደው ፤ ኰሎን ፡ አንስት ። ኰሉ ፡ ቀላይት ፤ ኰሉ ፡ ዕፀው ፤ ኰሉ ፡ አሕዛብ ። ሉ ፡ የሩቅ ፡ ዐጸፋ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የኰሉ ፡ ርባታ ፡ ከሩቆች ፡ በቀር ፡ ለቅርቦች ፡ ስራዊት ፡ አይስማማም ፤ በገቢርም ፡ ጊዜ ፡ ከሉ ፡ በቀር ፡ ላና ፡ ሎ ፡ አይለወጡም ። ዳግመኛም ፡ ኰሉ ፤ ላ ፤ ሎሙ ፡ ሎን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ ኰሉሆ ፡ ልሃ ፤ ልሆሙ ፡ ሆን ፡ እያሉ ፡ ኰልን ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ አሐድ ፡ እስክሥር ፡ ማርባት ፡ ይቻላል ። አሐዱና ፡ ኰሉ ፡ በምስጢር ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፤ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ ኰሉ ፡ ኰሉ ፤ ወይም ፡ እያቀናጀ ፡ ኰሉ ፡ አሐዱ ፡ ይላል ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ፳፯) ። ኰሉ ፡ ከተጸውዖ ፡ ስም ፡ በቀር ፡ ውስጠ ፡ ብዙነት ፡ ላለው ፡ ሉብትን ፡ ለጥስው ፡ ኹሉ ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፡ በቂ ፡ ይኾናል ፤ ክንድ ፡ በላይ ፡ ላለ ፡ ላንዱም ፡ ሳይቀር ፡ ከኹለት ፡ እስከ ፡ ምእልፊት ፡ በተከፍሎም ፡ ያለተከፍሎም ፡ ለብዙም ፡ ለጥቂትም ፡ ይነገራል ። ኰሉ ፡ ሕዝብ ፤ ኰሉ ፡ ፍጥረት ፤ ኰሉ ፡ ነፍስ ፡ ይሴብሖ ፤ ቅጽል ። ኰልክሙ ፡ ተዐልዉኒ ፤ እመሂ ፡ ኰሎሙ ፡ ዐለዉከ ፤ ወኰሎሙ ፡ ሰማዕት ፡ ክኑ ፤ ዐጸፋ ። ኰሉ ፡ ዐረየ ፤ እግዚእ ፡ ኰሉ ፤ ወኰሉ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ ይበሊ ፤ በቂ ። ኰሉ ፡ ላንድ ፡ መነገሩ ፡ ባንድነቱ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ክፍላት ፡ ብዙ ፡ ሕዋሳት ፡ ስላሉ ፡ ነው ፤ ኰሉ ፡ ሕንጻ ፤ ኰሉ ፡ መሌሊት ፡ ኰሉ ፡ ሥጋሁ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። የግእዝ ፡ መጻሕፍ ፡ ግን ፡ በመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ኅደረ ፡ ኰሉ ፡ መሰኮቱ ፡ በሥጋ ፡ ሰብእ ፡ ይላል ፡ (ቆላ፪ ፡ ፱) ። የጽርኡ ፡ አብነት ፡ ከጽርእም ፡ የተቀዳው ፡ ኹሉ ፡ እስመ ፡ ኰሉ ፡ ምልአ ፡ መለኮት ፡ ኅደረ ፡ ቦቱ ፡ በሥጋሁ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ኰሉ ፡ መለኮቱ ፡ አይልም ። ኰሉ ፡ በማንም ፡ ቋንቋ ፡ ውስጠ ፡ ብዙነት ፡ ስሌለውና ፡ መክፈል ፡ ለማይስማማው ፡ ላንድ ፡ ብቻ ፡ አይነገርም ፤ ምልአ ፡ መለኮት ፡ ያለውም ፡ ፍጹም ፡ ጸጋ ፡ ነው ። ይህም ፡ ኅቡእ ፡ ምሉእ ፡ ጸጋ ፡ ወጽድቅ ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ እንጂ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ወኅደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ አይገጥምም ፤ በጣም ፡ ሩቅ ፡ ነው ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፲፬) ።

**ኰልሄ ፡ ኰለሄ ፤ (ኰል ፡ ሄ) ፤** ኹል ፡ ጊዜ ፡ ኹለግዜ ፡ ኹለዬ ፤ ዘወትር ። ቦታ ፡ ኹሉ ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ አራቱ ፡ ማእዝን ፡ ዐውድ ፡ ዘውር ። ል ፡ ከተገብሮ ፡ ለ ፡ ከገቢር ፡ ይስማማል ። ምሉእ ፡ እምኔሁ ፡ ኰልሄ ። አዐቅበከ ፡ በኰልሄ ። አንሶሰወ ፡ ውስተ ፡ ኰልሄ ። መሐወኒ ፡ እንተ ፡ ኰልሄ ፡ (አዋል ። ክፋ ፡ ፳፯ ። ስንክ ፡ ግንቦ፳ ፡ ኢዮ፲፱ ፡ ፲) ። ተሐውር ፡ ኰለሄ ፡ ኀበ ፡ ፈነውኩከ ። ኀበ ፡ ታንሶሱ ፡ ኰለሄ ። መላእክት ፡ ወሰብእ ፡ ዘይነብሩ ፡ ኰለሄ ፡ (ኤር፩ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፯ ። ድራሲ) ። ብዙው ፡ መጽሐፍ ፡ ገቢር ፡ ተገብሮ ፡ ሳይለይ ፡ በኰለሄ ፡ እንተ ፡ ኰለሄ ፡ ውስተ ፡ ኰለሄ ፡ ይላል ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳዕለ ፡ ምድር ፡ ኰልሄ ፡ እያለ ፡ አለበታም ፡ ገብቶ ፡ ይገኛል ፡ የሄን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ።

**ኰላዊ ፤** የኹሉ ፡ የመላው ፡ (ፈልክ ፡ ፲፱፻፱) ።

**ኰለንታ ፤** ኹለንተና ፡ ኹለመና ፡ መላው ፡ ጠቅላላው ፡ ዙሪያ ፡ ገባው ፡ አራቱ ፡ ማእዝን ፡ የገጻ ፡ የቦታ ። እንተ ፡ ኰለንታሁሙ ፡ ምሉኣነ ፡ አዕይንት ። ኰለንታኪ ፡ ሠናይት ። ኰለንታየ ፡ ተመስወ ። ወኰለንታሁ ፡ በወርቅ ፡ ወበዕንቍ ። ተቋመ ፡ ማኅቶት ፡ ዘኰለንታሃ ፡ ወርቅ ። ኰለንታሃ ፡ ለዛቲ ፡ ምድር ፡ (ራእ፬ ፡ ፰ ። ማሕ፬ ፡ ፯ ። ሔኖ፵ ፡ ፫ ። አስቴ ፡ ፭ ። ዘካ፬ ፡ ፪ ። ዘፍ፲፫ ፡ ፲፭) ።

**ኰለንታዊ ፤ (ዊት) ፤** የውስጥ ፡ የአፍኣ ፡ የነፍስ ፡ የሥጋ ፡ ፍጹም ፡ ስብእና ፡ ፍጹም ፡ ልቡና ፡ ፍጹም ፡ ኅሊና ። ኀደገት ፡ ግብራቲሁ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ ወመጽአት ፡ ምስለ ፡ ኰለንታዊታ ፡ ለኀበ ፡ ዓለም ፡ ካልእ ፤ ልብ ፡ ሳይቀሩት ፡ (ፈልክ ፡ ፫) ።

**ኰላ ፤ (ጽር ፡ ኰሊ) ፤** ቀለም ፡ መጣብቅ ፡ ሙጫ ፡ ለሚታንጥ ፡ ሰንፎት ፡ መልከና ፡ ውበት ፡ እንድንት ፡ የሚሰጥ ። ወይስተጣግዕ ፡ በኰላ ፡ (ኢሳ፵፬ ፡ ፲፫) ።

**ከለሜዳ ፤ (ዳት ። ጽር ፡ ክላሚዳ) ፤** ዐጭር ፡ ካባ ፤ የክብርና ፡ የማዕርግ ፡ ልብስ ፡ ከንገት ፡ እስከ ፡ ወገብ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ጕልበት ፡ የሚደርስ ፡ ነገሥታት ፡ መኳንንት ፡ ልጆቻቸውም ፡ የሚለብሱት ። ለምድ ፡ ለምደኛ ፡ ያርበኞች ፡ ሽልማት ፡ (ማቴ፳፯ ፡ ፳፰ ፡ ፴፩) ። በምር ፡ መንጸፍ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ከለሜዳ ፡ ይላል ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ክዑብ ፡ ከለሚዳ ፡ (ምሳ፴፩ ፡ ፳፪ ። ዲድ ፡ ፫) ። ከርቤትን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። በያክንትም ፡ ፈንታ ፡ ቀይ ፡ ለማለት ፡ ከለሜዳ ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አይደለም ። ያሰብብስዎ ፡ ከለሚዳተ ፡ ወደርክዎ ፡ (ኤር፲ ፡ ፱) ።

**ኰለንታ ፤–ኹለንተና ፤–ከልሎ ፡ ከለለ ፤ ኰል ፡ ኰሉ ።**

**ከልዐ ፤—ከለከለ ፤—ከሊእ ፡ ከልአ ።**

**ከልዐ ፤ (ቀልዐ) ፤** ከላ ፡ አወለቀ ፡ አወጣ ፡ አሰለበ ፡ የልብስ ፡ የቀሚስ ፡ የጫማ ። ቀልዐን ፡ እይ ፡ የዚሁ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ኢትክልዑ ፡ አልባስየ ። ከላዕኩ ፡ ክዳንየ ፡ ዘኢትዐጸፍ ፡ ወወገርኩ ። ከልዐ ፡ አልባሲሁ ፡ ወለብሰ ፡ ሠቀ ፡ (ገድ ፡ ዳን) ። ክላዕ ፡ አሣእኒከ ፡ እምእገሪከ ፡ (ቀሌ) ።

**ኬልቄዶን ፤ (ጽር ፡ ኻልኪዶን ። ዕብ ፡ ሽበ) ፤** ነጭ ፡ ዕንቍ ፡ በንጣቱ ፡ በማያዋዩንት ፡ ያለበት ። አከጥስን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ወሣልስት ፡ በኬልቄዶን ፡ (ራእ፳፩ ፡ ፲፱) ።

—፤ የመዲና ፡ ስም ፤ በታናሽ ፡ እስያ ፡ በቱርክ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ ባ፬፻፶፩ ፡ የግሪክ ፡ ንጉሥ ፡ መርቅያኖስና ፡ ሚስቱ ፡ ብርክልያ ፡ ስለ ፡ መንግሥታቸው ፡ ልዕልና ፡ በሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ዕጥፍ ፡ ፮፻፴፮ ፡ ጳጳሳት ፡ ሰብስበው ፡ ከጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ያቆሙበት ፤ ቀድሞ ፡ በኤፌሶን ፡ ከንስጥሮስ ፡ ጋራ ፡ በብረው ፡ ተወግዘው ፡ የነበሩ ፡ ኋላም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ጉባኤ ፡ ቢጊሊዮስ ፡ ዘሮም ፡ ከነመጻሕፍቻቸው ፡ ረግሞ ፡ አውግዞ ፡ የለያቸው ፡ እንኤባስ ፡ እንታዎድሮስ ፡ የገቡበት ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዲዮስቆሮስና ፡ መቃርዮስ ፤ ሌሎችም ፡ መምህራን ፡ ከሶርያና ፡ ከአርመን ፡ የመጡ ፡ አራት ፡ ጳጳሳት ፡ ተጨምረው ፡ እነዚህ ፡ ፮ቱ ፡ የተለዩበት ። ምክንያቱን ፡ በቤተ ፡ ክሲያን ፡ ታሪክ ፡ ተመልከት ፡ ታሪኩ ፡ ግን ፡ ፪ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ፩ኛው ፡ የግብጽ ፡ የሶርያ ፡ የአርማንያ ፤ ፪ኛው ፡ የግሪክና ፡ የሮምያ ። የግሪኮች ፡ ታሪክ ፡ በዲዮስቆሮስ ፡ እጅ ፡ ከተጣፈው ፡ ከቅዳሴውና ፡ ከድርሳኑ ፡ ቃል ፡ አይስማማም ፡ ዐይንና ፡ ዐፈር ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ፍሬ ፡ ቅዳሴውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ካቶሊኮች ፡ ከሮማ ፡ ሊቃውንት ፡ አስመርምረው ፡ ከጥፋ ፡ አስፈቅደው ፡ ሐሰትና ፡ ስሕተት ፡ ጸያፍ ፡ የሌለበት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ይቀድሱበታል ። ስሙን ፡ ብቻ ፡ በአርእስቱ ፡ እኵቴት ፡ ቍርባን ፡ ዘቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ብለውታል ፤ ይህም ፡ ቅዳሴ ፡ የተደረሰና ፡ የተጣፈ ፡ በግሪክ ፡ ባስ ፡ ነው ፤ በግእዝ ፡ ተጥፎ ፡ እንደሚገኝ ፡ በሌሎችም ፡ ቋንቋ ፡ በሶርያና ፡ በአርመን ፡ በጽርእ ፡ በላቲን ፡ ይገኛል ። ከመስማት ፡ ማየት ፡ ይበልጣልና ፡ ቅዳሴውን ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ ጫፍ ፡ ተመልከት ፤ ፩ ፡ አካል ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ ሲል ፡ ታገኛለኽ ። ፪ኛም ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ የተለየበትን ፡ ለማስረዳት ፡ ከገዛ ፡ መጽሐፉ ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ ጠቅሶ ፡ ያመጣው ፡ የድርሳኑ ፡ ቍርጠኛ ፡ ወይም ፡ መልእክቱ ፡ ስላካልና ፡ ስለ ፡ ባሕርይ ፡ ስለ ፡ ህላዌም ፡ ፍች ፡ የሚለውን ፡ ባባ ፡ ብንያሚ ፡ ድርሳን ፡ ውስጥ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፤ ዲዮስቆሮስ ፡ ተአማኒ ፡ ርእሰ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ዘእለእስክንድርያ ፡ በመልእክቱ ፡ ዘጸሐፋ ፡ ኀበ ፡ በርጠሬር ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በጋግራ ። ይቤ ፡ አንሰ ፡ ረከብኩ ፡ ነገረ ፡ እንዘ ፡ አነብብ ፡ መጻሕፍቲከ ፡ ዘፈኖከ ፡ ሊተ ፤ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ መትሕላን ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ ፍጹማነ ፡ ወአልቦሙ ፡ አእምሮ ፤ ጥዩቀ ፤ ከለው ፡ ዠምረኽ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ተመልከት ። መልእክቱም ፡ የተጣፈበት ፡ ምክንያት ፡ ግብጦች ፡ በኦርቶዶክስ ፡ ባህል ፡ ታጣልተው ፡ ፪ ፡ ወገን ፡ ኹነው ፡ የጣፉትን ፡ ከታብ ፡ በርጤር ፡ የተባለው ፡ ሰውዬ ፡ የርሱንም ፡ ከታብ ፡ ጨምሮ ፡ ፪ ፡ መነኮሳት ፡ አሲዞ ፡ ስለ ፡ ላከለት ፡ ነው ፡ ይባላል ።

**ክልስሶ፤ሶት፤**(ክልሰሰ፡ ይክለስስ፡ ይክልስስ። ዐረ፡ ክለደ፡ ክለዘ)፤ መሰብሰብ፤ መሳስስ፡ መንቀል፤ የሽት፡ የሽንብራ። እያጨዱ፡ ማሰር፤ የታጨደውን፡ መሰንደቅ፤ መጕቸት፡ መከመር፤ የንዶ፡ የማር። አሰደንና፡ ቈለዘን፡ እዩ፤ የዚህ፡ ጎሮች፡ ናቸው።

**ክልሳሲ፤**(ሲት፡ ስያን፡ ያት፤ ሰስት)፤ የሚሳስስ፡ ዐጫጅ፡ አሳሪ፤ ሰብሳቢ፡ ከማሪ።

**ተክልሰሰ**፤ተላሰሰ፤ ታጨደ፡ ታሰረ፤ ተሰበሰበ።

**ክልሱስ፤**(ሳን፡ ሳት፡ ስስት)፤ የተላሰሰ፡ የታጨደ፡ የተሰበሰበ።

**ክልሰስ፤ ክልስስት፤**(ብ፡ ክላስስት)፤ ነዶ፡ ቋጨራ፤ ስንድቅ፡ ድንክን፤ የታሰረና፡ ያልታሰረ። ታበውኡ፡ ክልስስተ፡ እምቀዳሚ፡ ማእረርክሙ። እሰ፡ የአስሩ፡ ክላስስተ። ዘወይዋ፡ እምነ፡ ክላስስት፡ ወጾሩ፡ ክላስስቲሆሙ፡ (ዘሌዋ፲፡ ፲—፲፱። ዮዲ፰፡ ፫። ሩት፪፡ ፯። መዝ፡ ፻፳፭)።



ክልስስ፡

**ኬልቲ፤**(ጽር፡ ኬሬቲ። ዕብ፡ ክሬቲ)፤ የሮፍራ፡ ስም። ቀርጤሳዊ፡ የቀርጤስ፡ ሕዝብ፡ ማለት፡ ነው፤ ጕንደሬ፡ እንደ፡ ማለት፡ (፩ነገ፡ ፩፡ ፴፰)። ል፡ በጣፉ፡ ስሕተት፡ ወይም፡ በጸሮፍ፡ እንደበት፡ የገባ፡ ነው። በሐረረ፡ ፈንታ፡ ሐለለ፡ እንዲል።

**ክልተፈ፤**(ከተፈ)፤ ኰለተፈ፡ ተኰላተፈ፤ ኰልትፍትፍ፡ አለ፡ ታሰረ፡ ኰለደፈ፡ ያንደበት፡ የስለት። ል፡ በሬጽ፡ ነው፤ ከተፈን፡ እዩ።

**ኪማ፤—፯፡ ከዋክብት፤—ከየመ።**

**ከመ፤—መቼም፡ መች፤—ከመመ።**

**ከሚው፤ ዎት፤**(ከመወ፡ ይከሙ፡ ይክሙ። ዕብ፡ ከማህ)፤ አጥብቆ፡ መውደድ፤ መሳብ፡ ማቅረብ፤ እኩያ፡ አምሳያ፡ ማድረግ፤ እንደ፡ ራስ፡ ማየት። መመዘን፡ ማስተካከል፤ አንዱን፡ ባንዱ፡ ልክ፡ መወሰን።

**ከመ፤**(ዕብ፡ ክሞ። ሱር፡ ክማእ። ዐረ፡ ከማ)፤ ዐቢይና፡ ደቂቅ፡ አገባብ፤ እንደ። በ፡ ዘ፡ እያሰመቁት፡ ሳያዳምቁትም፡ ይነገራል፤ በአንጻር፡ በውጥን፡ ይገባል፤ ምስጢሩ፡ መጠንና፡ ልክ፡ አምሳል፡ ነው። በከመ፡ ፈነወኒ፡ አቡየ፡ ከማሁ፡ አነሂ፡ እፌንወክሙ። ዐገቱኒ፡ ከመ፡ ንህብ፡ መዓረ። ፬ኛም፤ እንተ፡ እለ፡ ዘ፡ ባሉበት፡ እንቀጽና፡ ጥሬ፡ ሲገባ፡ መሰለ፡ ይኾናል። ከመ፡ ዘበኀይልኪ፡ ወከመ፡ ዘበጽድቅኪ፡ ረሰይናሁ፤ ያደረግነው፡ ይመስል፤ ወይም፡ እንዳደረግነው፡ ኹሉ። ፫ኛም፤ መሰለ፡ ሲቀድመውና፡ ሲከተለው፡ ን፡ ይኾናል። ሰብዐቱ፡ ዓመቱ፡ ዘኮነኒዎ፡ ኢመሰሎ፡ ከመ፡ አሐቲ፡ ዕለት። ወከመ፡ ገሞራ፡ እመሰልነ። ፬ኛም፤ በዘንድ፡ ላይ፡ ሲወድቅ፡ አዳማቂ፡ ኹኖ፡ ይቀራል። መኑ፡ ውእቱ፡ እግዚእ፡ ከመ፡ እእመኖ፡ ቦቱ። ፭ኛም፤ አንቀጽ፡ እያስቀረ፡ ባንቀጽ፡ ሲሳብ፡ ገቢር፡ ተገብሮ፡ ይኾናል። ተዘክር፡ እግዚኦ፡ ከመ፡ መሬት፡ ንሕነ። ርእየ፡ ከመ፡ በዝኀ። ሰምዐ፡ ከመ፡ ተፄወወ። ደቂቅ፡ አገባብም፡ ሲኾን፡ በጥሬና፡ በስም፡ እየገባ፡ አንጻር፡ ይኾናል። ተሰብረ፡ ከመ፡ ዕፀ፤ ተክዕወ፡ ከመ፡ ማይ። ፮ኛም፤ እም፡ ሲወድቅበት፡ እንደ፡ ዘ፡ በር፡ ከፋች፡ ኹኖ፡ በእምና፡ በእመ፡ በሶበ፡ በድኅረ፡ ዘይቤ፡ ይፈታል፡ ምክንያቱም፡ መሳዮች፡ በነዚህ፡ ቦታ፡ ስላገቡት፡ ነው። እምከመ፡ ገሰስኩ፡ ጽንፈ፡ ልብሱ፡ አሐዩ፤ ከዳሰስኹ፡ ብዳስስ፡ የዳሰስኹ፡ እንደኾን፡ ነ። እምከመ፡ ርእዩኪ፡ ሰብአ፡ ግብጽ፤ ቢያዩሽ፡ ካዩሽ፡ ያዩሽ፡ እንደ፡ ኾነ። እምከመ፡ ቦአ፡ ሙሴ፡ ውስተ፡ ደብተራ፤ በገባ፡ ጊዜ፡ ሲገባ። ወእምከመ፡ ወፅአ፡ መንፈስ፡ ርኩስ፡ እምሰብእ፤ ከወጣ፡ በኋላ፤ በወጣ፡ ጊዜ፡ እያሰኘ፡ በየግንዘቡ፡ በያወራረዱ፡ ይፈታል፤ እምን፡ ተመልከት፡ (ዐር፲፱፡ ቍ፫፫)።

**ከማሁ፤**(ሃ፡ ሆሙ፡ ሆን፤ ከማየ፡ ከ፡ ኪ፤ ነ፡ ክሙ፡ ክን)፤ እንዲሁ፤ እንደ፡ ርሱ።

**ክሙ፤**(ክሞው፡ ክ)፤ የቀርብ፡ ወንዶች፡ ጠቃሽ፤ ዝርዝር፤ ከን፡ ተመልከት።


**ከሙን፤**(ሱብ፡ ከሞን። ሱር፡ ከሙና። ዐረ፡ ከሙን። ጽር፡ ኪሚኖን)፤ በቁሙ፡ የቅመም፡ ስም፤ ፍሬው፡ ታናናሽ፡ ያንሰባል፡ ዐይነት፤ ጣዕምና፡ መዐዛ፡ ስላለው፡ ከንጀራና፡ ከወጥ፡ የሚገባ። ባለቅኔዎች፡ ግን፡ ቀልባ፡ ፈጦ፡ ይሉታል፡ (ማቴ፳፫፡ ፳፫። ኢሳ፳፰፡ ፳፭፡ ፳፯)። ወከነ፡ ኢይበልዐ፡ ዘእንበለ፡ ኅብስት፡ ወጼው፡ ምስለ፡ ከሙን፡ ወሐምል፡ ዘኢይብሰልዎ፡ በእሳት፡ (ስንክ፡ ሐምሌ፱)። በከሙን፡ ፈንታ፡ ከሜን፡ ከሚን፡ ከሚን፡ ይላል፤ የጣፉ፡ ስሕተት፡ ነው። ስንድሪስ፡ ወከሜን፡ እመ፡ ዘራዕከ፡ ከሚነ፡ (ስንክ፡ ሐምሮ። መቃ፡ ገ፳)።



ከሙን፡

**ከመዝ፤**(ከመ፡ ዝ)፤ እንዲህ፤ እንደዚህ። ዘከመ፡ ዝ፤ እንደዚህ፡ ያለ፡ ይህን፡ የመሰለ፤ የዝን፡ አፈታት፡ እዩ። ከመ፡ ዝ፡ ይቤ። ዘከመ፡ ዝ፡ ብሥራት።

**ከመዝ** ፤ (ዝን ፡ አትሓግን) ፤ የውሃ ፡ እናት ፡ ጥቍር ፡ ጠቋራ ፡ እንዝዝ ፡ የምትመስል ፤ በቋሚ ፡ ውሃ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ እንግዝርት ፡ ራስ ፡ የምትዞር ፡ የምትሽከረከር ፤ ፈከትምን ፡ እይ ። ዝ ፡ ከእንዝዝ ፡ ከእንዝርት ፡ መጥቶ ፡ ከከመ ፡ ጋራ ፡ ተቈራኝቷል ፤ ዘይቤው ፡ ከመ ፡ እንዝዝ ፤ ወይም ፡ ከመ ፡ እንዝርት ፡ ማለት ፡ ነው ። **ሐር ሐየ ፡ ከመዝ ፡ ሰረረ ፡ በዘባነ ፡ ዐባይ ፡ ተርሴስ ፤ ሐመ ርኑ ፡ እንተ ፡ ይነድእ ፡ ነፋስ** ፡ (ደራሲ) ።



ከመዝ ፤

**ክሞስ ፤ ከሞስ ፤ (ዕብ ፡ ክሞሽ ። ጽር ፡ ኻሞስ)** ፤ ስመ ፡ ጣዖት ፡ ሞአባዊ ፤ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፤ ሰው ፡ የሚመስል ፡ (ዘኍልቍ ፡ ፳፩፥፳፱ ። መሳፍንት ፡ ፲፩፥፳፬ ። ፩ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፯) ።

**ከሚዎን ፤ ከሚዮን ፤ (ሮማይ)** ፤ የእሳት ፡ ቦታ ፡ እሳታዊ ፡ ማኅፈድ ፤ በእሳት ፡ የሚኼድ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሠረገላ ፡ እሳት ፡ እንደ ፡ ማለት ። የከመወ ፡ ዘር ፡ አይደለም ፡ በከመ ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ግን ፡ ከሚዎን ፤ ከመ ፡ ኅስር ። ከሚዮን ፤ (ከመ ፡ ዮን) ፡ ከመ ፡ ርግብ ፡ አምሳለ ፡ ርግብ ፡ ያሰኛል ፡ ዮናን ፡ እይ ፡ (ራእ ፲፪ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፶፬) ።

**ከሞል ፤—ስመ ፡ ዕፅ ፤—ከወሞል ።**

**ከሚሌዎን ፤ (ጽር ፡ ኻሚሌዎን)** ፤ ኅብረ ብዙኅ ፤ ዕብብ ፡ የንሽላሊት ፡ ዐይነት ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፴) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ እንቁራሪት ፡ ይሉታል ። ከሚሌዎን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ገላሚዎስ ፡ ይላል ፡ በስሕተት ፡ ነው ።

**ከሚም ፤ ሞት ፤ (ከመ ፤ ከመመ ፡ ይከ ምም ፡ ይክምም)** ፤ መከምከም ፤ ማስተካከል ። መ ሸፈን ፡ ማልበስ ።

**ከመ ፡ (ንኡስ ፡ አገ)** ፤ መቼም ፤ መቼም ፡ መች ፤ ዘወትር ፡ ድንት ፡ ዘላለም ። **እመሂ ፡ ትልህቁ ፡ አነ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ። ወአንተሰ ፡ አንተ ፡ ከመ ። ወከመ ፡ ውእቱ ፡ እስከ ፡ ለዓለም** ፡ (ኢሳ ፵፮ ፡ ፬ ። ዕብ ፩ ፡ ፲፪ ። ፲፫ ፡ ፰) ። ፪ኛም ፡ እንደ ፡ ዳእሙ ፡ ብቻ ፡ ይኾናል ። **አነ ፡ ከመ ፡ ወአልቦ ፡ እንተ ፡ ከማየ ። ሕቀ ፡ ከመ ፡ ዘእ ምተንትና ፡ እገርየ ። ሐይዋን ፡ ከመ ፡ ይባርኩከ** ፡ (ዕሮ፵፯ ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፳፪ ። ቀሌ) ። ፫ኛም ፡ ባወራረድ ፡ ፍች ፡ ከቶ ፡ ፈጽሞ ፡ ይኾናል ፡ ምስጢሩ ፡ መቼም ፡ መች ፡ ካለው ፡ ይገባል ፡ (ዕርፈ ፡ ቍጽ) ።

**ከማም ፤ (ብ ፡ አከማም ። ዐረብ)** ፤ በቁሙ ፡ የክንድ ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ እጅ ፡ ቤዛ ፡ ያለ ፡ ባለ መሽቀቅ ፤ ዐጭር ፡ ቍምጣ ፡ እጅጌ ፤ ቀዳሽ ፡ ቄስ ፡ በቅ ዳሴ ፡ ጊዜ ፡ ሲለብሰው ፡ እጁ ፡ ሰፊውን ፡ ሰብስቦ ፡ ክም ከሞ ፡ እጁ ፡ ጠባብ ፡ ቀሚስ ፡ የሚያስመስል ። **ወእምዝ ፡ ይልብስ ፡ አከማመ ፤ ወይእስሮ ፡ በዝናር** ፡ (ሥር ፡ ቅዳ) ።

**ከሙን ፤—በቁሙ ፤ ከመወ ።**

**ከሙሥ ፤—ቀመሰ ፤—ከመሰ ።**

(ላ) **ከመረ ፤ (ቀመረ ። አለደ)** ፤ በቁሙ ፡ ቈ ለለ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አከበ ፤ ሰበሰበ ።

**ክምር ፤ (ብ ፡ ክምራት ፤ አክማር)** ፤ በቁሙ ፤ ቍልል ። **ከመ ፡ ክምረ ፡ እክል ። ከመ ፡ ክ ምረ ፡ ሐሠር ። በእትወተ ፡ አክማሪሁ** ፡ (ዕሮ፪ ፡ ፱ ። ሚክያስ ፡ ፬ ። መቃ ፡ ፲፱) ። ያገዳ ፡ እኽል ፡ ሲኾን ፡ ክ ምሩ ፡ ዝራማ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ዲራማ ፡ ይባላል ፤ ልዑል ፡ ማለት ፡ ነው ።



ክምር ፤

**ከማርም ፤ (ዕብ ፡ ክማሪም)** ፡ ካህናተ ፡ ጣዖት ፤ ጥምጥማቸው ፡ ክምር ፡ የሚያክል ፤ አንዳንዱ ፡ ከማር ፡ ኮሜር ፡ ይላል ። **አውዐዮሙ ፡ ለከማርም** ፡ (፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፭) ።

**ከሚስ ፤ (ከመሰ ፤ ዐረ ። ትግ ፡ ከምሽ ። ዕብ ፡ ክማሽ ፤ መጽለወ ፡ የብሰ)** ፤ መቅመስ ፤ ቀምሶ ፡ መተው ፡ ልጥገብለት ፡ አለማለት ፤ ሰውነትን ፡ በራብና ፡ በጥም ፡ በችጋር ፡ መቅጣት ።

**ከምሰሰ** ፤ ዐፈረ ፡ ተሰቀጠጠ ፤ ኰምሸሸ ፡ አለ ።

**አከሞሰሰ** ፤ በጥቂቱ ፡ ማቀ ፤ ከንፈሩን ፡ ገለጠ ፤ ጥር ሱን ፡ ፍግግ ፡ ፈቱን ፡ ወንግ ፡ አደረገ ። **ሰበ ፡ ይሥሕቅ ፡ ለብሩ ፡ ያዐቢ ፡ ቃሎ ፤ ጠቢብሰ ፡ እምዕጹብ ፡ ያከሞ ስስ ፡ ከናፍሪሁ ። ወያከሞስስሙ ፡ በየውሀት ፡ ሲአብ ዳን ። አከሞስስ ፡ በኅቡእ** ፡ (ሢራክ ፡ ፳ ። ክብ ፡ ነገ ፳፪ ። አፈ ፡ ድ፳፱) ።

**ከሙሳስ ፤ ከሞሳስ** ፤ ቃናሽ ፡ ማቀ ፡ ፍግግታ ፡ የሠሐቅ ፡ ምልክት ፤ ወይም ፡ ቅምሻ ፡ መፍነክነክ ፡ መን ከትከት ፡ ሳይናገር ፡ (ዲድ) ።

**ክን ፤—የቅርብ ፡ ሴቶች ፡ ዝርዝር ፤—(ከ ፡ ከ ፡ ክሙ) ፤ ክን ።**

**ክንበሎ ፤ (ከበለ)** ፤ ጠሰብ ፡ የራስ ፡ ማከከያ ፤ የጠጕር ፡ ችንካር ፡ እንደ ፡ ሚደ ፡ ያለ ። **ወወሀበቶ ፡ ሰዐ ዳዊ ፡ ቤታ ፡ ክንበሎሃ ፡ ዘወርቅ** ፡ (ስንክ ፡ መስከረ) ።

**ክንበለ ፤ (ተቀ ፡ ግ)** ፤ ክንበለ ፡ ደፋ ፡ አፈ ሰሰ ። ክንበሌ ፡ ዞይ ፤ ክንበል ፡ ያርገኝ ፤ አክንባሎ ፡ (ሞ ግድ) ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ክንይ ፤ ዮት ፤ (ክነየ ፡ ይክኒ ፡ ይክኒ ። ዕብ ፡ ክናህ ፤ ሰመየ)** ፤ መጋረድ ፡ መመከት ፡ እን ዲህ ፡ ነው ፡ እንዲ ፤ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፤ በው ነት ፡ ወይም ፡ በሐሰት ። ከየንን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ከናዪ ፤ መክነዪ ፤ መክንይ ፤** ጋሬጅ ፤ መ ካች ፡ ተሻጋች ።

**መክነዪ ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ማ) ፤** መክኘ ፡ ምክንያት ፡ ኾኖ ፡ የከፋ ፡ የበጎ ።

**ምክንያት ፤ (ያት) ፤** በቁሙ ፤ ሽፍጥ ፡ አ ሉታ ፤ ሐተታ ፡ የቃል ፡ መከታ ። ሰበብ ፤ መንሾ ፡ መነሾ ፤ ክርክፊሻ ፡ የነገር ፡ ማንሻ ። መገኛ ፡ ሥር ፡ ሥረ ፡ ነገር ፤ ጥንት ፡ መሠረት ። ሀቦ ፡ ዘመፍትው ፡ ወኢታብዝኅ ፡ ምክንያተ ። ሐተትሙ ፡ ምክንያተ ፡ ደዌሃ ። ከመ ፡ ኢይርከብ ፡ ምክንያተ ፡ በዘይደብእን ። ብሂሎቱሰ ፡ ጥንተ ፡ ሕይወትሙ ፡ ምክንያተ ፡ ሕይወትሙ ፡ ብ ሂል ። አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ፤ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ምክንያተ ፡ ልደትከ ፡ (አፈ ፡ ድ፲፩ ። ዮሴፍ ። ፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ። አፈ ፡ ድ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፩) ።

**አመክነዪ ፤** አመክኘ ፤ ምክንያት ፡ ሰጠ ፤ ዋሸ ። ለእመ ፡ ቦ ፡ ዘተርፈ ፡ ቦቱ ፡ ምክንያት ፡ ዘያመክኒ ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ። ምንተ ፡ ታመክንዩ ፡ ወታወሥእዎ ፡ ለእግዚ ። እስመ ፡ አልቦ ፡ ውስተ ፡ ህላዌሁ ፡ አመክ ንዮ ፡ (ዮሴፍ ። ዲድ ፡ ፲፪ ። ፪) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በአመክንዮ ፡ ፈንታ ፡ ተመክንዮ ፡ ተመካንዮ ፡ ይላል ፤ ስሕ ተት ፡ ነው ። እስመ ፡ ዕልዋን ፡ ይትመክነዩ ፡ በዝንቱ ፡ ስም ፡ (ዘውእቱ ፡ ክርስቶስ) ፡ ከመ ፡ ይኂጥዎሙ ፡ ለየዋሃን ። አየ ፡ ምክንያተ ፡ ንትመከነይ ፤ እስመ ፡ አ ልብነ ፡ ፍርሀት ። አመ ፡ ቦ ፡ ዘተጸውዐ ፡ ኀበ ፡ ጉባኤ ፡ ኢያስተቃልል ፡ ለበጺሕ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ ተደ ደቀ ፡ ተመክንዮተ ፡ ዕጢቀ ፤ ወይጽሐፍ ፡ መልእ ክተ ፡ እንዘ ፡ ይነግር ፡ ተመክንዮቶ ። ተመካነየ ፡ ላዕ ሌሁ ፡ ሰይጣን ፡ (አፈ ፡ ተ፰ ። ድ፲ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ የካ፫) ።

**ተመክነየ ፤** ተመካኘኘ ፤ ርስ ፡ በርሱ ።

**ከነነ ፤ (ዐረ ፡ ከነ) ፤** ሰወረ ፡ ደበቀ ፤ ሸፈነ ፡ ከደነ ።

**መክኑን ፤** የተሰወረ ፡ ያልታወቀ ፤ ስውር ፡ ኀ ቡእ ። እልመክኑን ፡ ዝ ፡ ብሂል ፡ ኅቡእ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ግብ፲፯ ፡ ፳፫) ።

**ክኑን ፤ (ሱር ፡ ወዐረ) ፤** ስመ ፡ ወርኅ ፡ የሶ ርያ ፡ ወር ፡ ታኅሣሥና ፡ ጥር ። ካኑን ፡ ዳግማይ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲) ።

**ኰንኖ ፤ ኖት ፤ (ኰነነ ፡ ይኴንን ፡ ይኰ ንን ። ዕብ ፡ ከኔን ፤ አዘጋጀ) ፤** መኰንን ፤ መፍ ረድ ፤ መቀጣት ፤ መበየን ፡ መጸኘት ። ይትነሣእ ፡ እግዚ ፡ ለኰንኖ ። ኢትኰንኑ ፡ ከመ ፡ ኢትትኰነኑ ። ዘይኴ ንን ፡ በጽድቅ ። ቦኑ ፡ እግዚ ፡ ይኴንን ፡ በዐመፃ ፡ (ኢ ሳ፫ ፡ ፲፫ ። ማቴ፯ ፡ ፩ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳፫ ። ኢዮ፴ ፡ ፫) ።

—፤ መግዛት ፤ መሠልጠን ። ብዙኃ ፡ አሕዛበ ፡ ኰኒንየ ። እለ ፡ እኩየ ፡ ኰነኑ ፡ ይኴንንዎሙ ። ኰነኖሙ ፡ ሞት ፡ እምአዳም ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ (አስቴ፫ ፡ ፪ ። ኢሳ፲፬ ፡ ፪ ። ሮሜ፭ ፡ ፲፬) ።

—፤ መሥራት ፡ መቅጣት ፤ መማቀቅ ። ኰነንዎ ፡ ኰነኔ ፡ ዐቢየ ። በብዙኅ ፡ ኰነኔ ፡ እምድኅረ ፡ ኰነንዎ ። ወኰ ነና ፡ ለኀጢአት ፡ በነፍስቱ ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፩ ። ኅሐ፲፩ ። ሮሜ፰ ፡ ፫) ።

**ኰናኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት) ፤** የሚኰንን ፡ ኰናኝ ፤ ገዥ ፡ ፈራጅ ፤ ዳኛ ፡ ጌታ ፡ መምር ። ፈታሒ ፡ ወኰናኒ ። ሕግ ፡ ኰናኒ ። መኑ ፡ ረሰየከ ፡ ኰናኔ ፡ ሎቱ ፡ (አፈ ፡ ድ፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፳ ። ፊልክ ፡ ፻፲፰) ።

**መኰንን ፤ (ንንት) ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፤ በቁሙ ። ኢትፍቅድ ፡ ከዊነ ፡ መኰንን ። መኰንን ፡ ጽድቅ ። መ ኰንነ ፡ ምድር ። መኰንና ፡ ለይሁዳ ። እስመ ፡ መኰ ንንትሙ ፡ ይእቲ ፡ ጥበብ ፡ (ሢራ፯ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፴ ። ኤርም፪ ፡ ፴ ። ጥበ፯ ፡ ፲፪) ።

**መኳንንት ፤ (ታት) ፤** በቁሙ ፤ መኳንንቶች ፤ ገዦች ፡ ፈራጆች ፡ ሹማምት ፡ መምራን ። መኳንንትሰ ፡ ኢኮኑ ፡ ግሩማነ ፡ ለዘይገብር ፡ ሠናየ ። ተዘከሩ ፡ መ ኳንንቲክሙ ፡ ዘነገሩክሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚ ፡ (ሮሜ፲፫ ፡ ፫ ። ዕብ፲፫ ፡ ፯) ።

**ምኵናን ፤ (ናት) ፤** መፍረጃ ፤ ሸንጎ ፡ አደባ ባይ ፤ የፍርድ ፡ የቅጣት ፡ ቦታ ። ግሩም ፡ ዐውደ ፡ ምኵ ናንከ ። መዋቅሕትየ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ ምኵናን ። በእ ንተ ፡ ሰማዕታት ፡ እለ ፡ ይወስድዎሙ ፡ ኀበ ፡ ምኵ ናን ፡ (ቀሌ ። ፊልጵ፩ ፡ ፲፫ ። ዲድ ፡ ፳፭) ።

—፤ ግዛት ፡ ሥልጣን ፡ ጌትነት ፤ የጌትነት ፡ ስፍራ ። ደ ወለ ፡ ምኵናኑ ። ምኵናነ ፡ ሄሮድስ ። ተውህበ ፡ ሎቱ ፡ ምኵናን ፤ ወምኵናኑሂ ፡ ምኵናን ፡ ዘለዓለም ፡ በኢየ ሩሳሌም ፤ ምኵናንየ ፡ ኀበ ፡ አኰነኒ ፡ (ዘኁ ፡ ፴ ፡ ፱ ። ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፯ ። ዳን፯ ፡ ፲፬ ። ሢራ፳፬ ፡ ፲፩) ።

**አኰነነ ፤** አስፈረደ ፤ አስገዛ ፤ አሠለጠነ ፤ ፈራጅ ፡ አደረገ ። ኣሜግቦ ፡ ምግብከ ፡ ወአኴንኖ ፡ ምኵናኒከ ። ለወልድከ ፡ ወለብእሲትከ ፡ ኢታኰንኖሙ ፡ ንዋየከ ። በከመ ፡ አኰነንከ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ወነፍስ ። አ ኰነኖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አይሁድ ፡ (ኢሳ፳፪ ፡ ፳፩ ። ሢራ ፴ ፡ ፳፰ ። ዮሐ፲፯ ፡ ፪ ። ዳን፫ ፡ ፴) ።

**ተኰነነ ፤** በቁሙ ፤ ተፈረደበት ፤ ተቀጣ ፡ ተማ ቀቀ ፤ ተገዛ ፡ ዚጋ ፡ ኾነ ። ዘየአምን ፡ ቦቱ ፡ ኢይትኴ ነን ፤ ወዘሰ ፡ ኢአምነ ፡ ቦቱ ፡ ወድአ ፡ ተኰነነ ። ይትኰ ነኑ ፡ በሰይፍ ። ኅዳጠ ፡ ተኰኒኖሙ ። ለኵሉ ፡ ነፍስ ፡ መኰንን ፡ ተኰነኑ ፡ (ዮሐ፫ ፡ ፲፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፶፯ ። ጥበ፫ ፡ ፭ ። ሮሜ፲፫ ፡ ፩) ።

**ትኵናን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ንንት) ፤** የተኰነነ ፤ የ ተፈረደበት ፡ የተቀጣ ። ኢኮነ ፡ ርቱዐ ፡ ሃይማኖቱ ፡ አላ ፡ ትኵናን ፡ እምቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ። ትኵናን ፡ በፍል ሐቱ ፡ ቀጥራን ። በእንተ ፡ ትኵናናን ፡ ሰማዕታቲከ ፡ (ቄር ። ስንክ ፡ ጥር፳፯ ። አዋል) ።

**ትኵናኔ ፤** መፍረድ ፡ መግዛት ፤ መገዛት ፡ አገዛዝ ፡ አቀጣጥ ።

**ኵነኔ ፤ (ያት) ፤** ፍርድ ፤ ቅጣት ፡ መቅሠፍት ፤ ግዛት ፡ አገዛዝ ፤ ሕግ ፡ ትእዛዝ ፤ ሥልጣን ፡ መብት ።

ይኩንኒ ፡ ዘነኒ ፡ ጽድቅ ። ወተመጠዋ ፡ ዘነኒሆን ። ዐ ሥሩ ፡ ዘነኒያት ፡ ዐበይት ፡ ወፀዋጋት ። እግዚኦ ፡ ዘነ ኒከ ፡ ሀበ ፡ ለንጉሥ ። ስምዐ ፡ ዘነኒሁ ፡ ወፍትሖ ። ተ ውህበ ፡ ሊተ ፡ ዘነኒ ፡ በሰማይ ፡ ወምድር ፡ (ዘዳ፲፯ ፡ ፲፰ ። ይሁ ፡ ፯ ። ክሩ ፡ ፵፯ ። መዝ ፡ ፸፩ ። ዘዳ፱ ፡ ፩ ። ማቴ፳፰ ፡ ፲፰) ።

**ተኳነነ**፤ ተፋረደ ፡ ተፈራረደ ። ተዋቀሠ ፡ ተወቃቀሠ ፡ ለመታረቅ ። ተኳነኑ ፡ ሄሮድስ ፡ ወጲላጦስ ፤ እ ስመ ፡ ጋእዝ ፡ በሙ ፡ እምቅድም ። ተደመሩ ፡ ክል ኤሆሙ ፡ ወተኳነኑ ፡ ወገብሩ ፡ ሰላመ ፡ በበይናቲ ሆሙ ፡ (ሉቃ፳፫ ፡ ፲፪ ። ዮሴፍ) ።

**ክንዐ**፤ (ዕብ ፡ ክናዕ ፤ ሂክኔዕ)፤ ተገዛ ፡ ተዋረደ ፤ ግብር ፡ ሰጠ ፡ አቀረበ ።

**ክንዓን**፤ (ዕብ ፡ ክናዓን)፤ ስመ ፡ ነገድ ፡ ስመ ፡ ትውልድ ፡ ወልደ ፡ ካም ፡ ራብዕ ፡ ስመ ፡ ሀገር ፡ የከንዓን ፡ ልጆች ፡ የወረሷት ፡ ከሲዶን ፡ በመስጴ ፡ እስከ ፡ ሰዶም ፡ ድረስ ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፮ ፡ ፲፭—፲፱) ። ፍችሙ ፡ ነጋዴ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ተገኘ ፡ አገልጋይ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ የኹሉ ፡ ታናሽ ፡ ነውና ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ንግድንና ፡ የንግድን ፡ ሥራ ፡ ያወጡ ፡ የከንዓን ፡ ልጆች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነጋዴ ፡ ኹሉ ፡ ከንዓን ፡ ይባላል ፡ (ሕዝ፲፯ ፡ ፬) ። ነጋዴም ፡ ማለት ፡ ም ስጢሩ ፡ ክነዓን ፡ ይኩን ፡ ገብረ ፡ አግብርት ፡ ለአኅዊሁ ፡ ካለው ፡ ክፉን ፡ ትንቢት ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ፡ (ዘፍ፱ ፡ ፳፭ ፡ ፳፯) ።

**ክኒፍ** ፤ **ፎት** ፤ (**ክነፈ ፡ ይክንፍ ፡ ይክ ንፍ ። ዕብ ፡ ክናፍ**)፤ መክነፍ ፡ መብረር ፡ መዘርጋት ፡ መርበብ ፡ ማቀፍ ፡ መሰብሰብ ፤ ያሞራ ፡ የሰው ። ዐጽቅ ፡ ማውጣት ፡ የዕፀው ።

**ክንፍ**፤ (**ብ ፡ ክነፍ ፤ አክናፍ ። ዕብ ፡ ክ ናፍ ። ሱር ፡ ኬንፋ ፤ ጌፋ ። ዐረ ፡ ክነፍ ፤ ጆ ናሕ**)፤ በቁሙ ፡ የአዕዋፍ ፡ ገላ ፡ መብረሪያቸው ፤ የመ ርከብ ፡ ሸራ ፡ ዐጽቅ ፡ እጅ ። መኑ ፡ ይሁበኒ ፡ ክንፈ ፡ ከመ ፡ ርግብ ። ንስር ፡ ዘዐቢይ ፡ ክነፊሁ ። አሕማር ፡ እለ ፡ ቦን ፡ ክንፍ ። ሰምጽዋት ፡ ባቲ ፡ አክናፍ ፡ ዘወ ርቅ ፡ (መዝ ፡ ፶፬ ። ሕዝ፲፯ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፲፰ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ተፀ፪) ። ሰብሐር ፡ ዓሣም ፡ ይንገፈል ። (ዘሌ፲፩ ፡ ፱—፲፪) ።

—፤ ጫፍ ፡ ዳርቻ ፡ ማእዝን ፡ የልብስ ፡ የቦታ ። ከሠትት ፡ ክንፉ ። ወተዐቍሮሙ ፡ በክነፊከ ። ክንፈ ፡ ምድር ። እ ምአርባዕቱ ፡ ክነፊሃ ፡ ለምድር ፡ (ኩፋ ፡ ፴፫ ። ሕዝ፳ ፡ ፫ ። ኢዮ፴፯ ፡ ፬ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፲፪) ።

**ክንፌፍ** ፤ **ክነፌፍ** ፤ ክንፈ ፡ ክንፍ ፤ ክንፈ ፡ ክ ንፍ ፤ የጫፍ ፡ ጫፍ ፡ የመጨረሻ ፡ መጨረሻ ፡ የማእዝን ፡ ማእዝን ፡ (ሔኖ፴ ፡ ፫) ።

**ክንፈር**፤ (**ብ ፡ ክናፍር**)፤ በቁሙ ፡ የአፍ ፡ ዙ ፊያ ፡ ማእዝን ፡ እንደ ፡ ሳንቃ ፡ የሚከፈት ፡ የሚዘጋ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ። ዘሩና ፡ እንቀጹ ፡ ክኒፍ ፡ ክነፈ ፡ ሲኾን ፡ ር ፡ ከክፈር ፡ መጥቶ ፡ ተደርቧል ፡ ክፈ ርን ፡ እይ ። ክንፈሩ ፡ ታሕታይ ። ሁናይ ፡ ሞገሰን ፡ ለክናፍረ ፡ ጠቢብ ። ንሥኢ ፡ ለቈቃወ ፡ በክናፍርኪ ፡ (ኪዳ ፡ ገ፰ ። ሚራ፳፩ ፡ ፲፯ ። ኤር፯ ፡ ፳፱) ።

—፤ ቋንቋ ፡ የቋንቋ ፡ ስልት ፡ አነጋገር ፡ ካፍና ፡ ከክንፈር ፡ የሚሰማው ። ይትናገሩ ፡ ሕሒደ ፡ ክንፈረ ፡ ወአሐደ ፡ ልሳነ ። ሕዝብ ፡ ዘዐሙቅ ፡ ክናፍሪሁ ፡ ወክቡድ ፡ ል ሳኑ ። በካልእ ፡ ልሳን ፡ ወበካልእ ፡ ክናፍር ፡ እትናገ ሮሙ ፡ (ኩፋ ፡ ፫ ። ሕዝ፫ ፡ ፭ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፳፩) ። ለ አፈ ፡ ማሕፀን ፡ ሳይቀር ፡ ክንፈር ፡ ላለው ፡ ኹሉ ፡ ይነገ ራል ። ወኢይምላእ ፡ ጽዋዐ ፡ እስከ ፡ ክንፈሩ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፫) ።

—፤ ጫፍ ፡ ጠርዝ ፡ መጋጠሚያ ፡ የልብስ ፡ የድንኳን ። ክንፈረ ፡ ዐጸድ ። ክንፈረ ፡ ሠቅ ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፱ ፡ ፲) ።

—፤ ዳር ፡ ድንበር ፡ አፋፍ ፡ ጠረፍ ፡ ወደብ ፡ ገደብ ። ከመ ፡ ኆጻ ፡ ዘውስተ ፡ ክንፈረ ፡ ባሕር ፡ (መሳ፯ ፡ ፲፪ ። ኩፋ ፡ ፴) ።

(ጥ) **ክንስ** ፤ **አው ፡ ክኒስ** ፤ (**ከነሰ ፡ ይኬንስ ፡ ይክንስ ። ዕብ ፡ ካናስ ። ሱር ፡ ክናስ ። ዐረ ፡ ከነሰ ፤ ጠረገ**)፤ መክነስ ፡ መሰብሰብ ፡ ማከብ ፤ አንድ ፡ ማድረግ ። ማዝዝ ፤ መማዝት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በክነስ ፡ ፈንታ ፡ አክነሰ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። ሆባየ ፡ አክነስኩ ፡ (መጥሥ) ።

**ክናሲ** ፤ **መክንስ** ፤ የሚክንስ ፤ ሰብሳቢ ፡ ጠ ራጊ ፡ አንድ ፡ አድራጊ ።

**ተክነ(ን)ሰ** ፤ ተሰበሰበ ፡ ተከማቸ ፡ አንድ ፡ ኾነ ፤ ተቀላቀለ ። ተቀበለቶ ፡ እንዘ ፡ ትትኬነስ ፡ ደሴተ ፡ ቆጵ ሮስ ፡ ለኤዎስጣቴዎስ ። ይባእ ፡ ወይትክነስ ፡ ወይቅ ረብ ። አልባ ፡ ተክንሶ ፡ ወተደምሮ ፡ ምስለ ፡ ሕዝብ ፡ (ደራሲ ። ኪዳ ። ቀሌ) ።

—፤ ታዘዘ ፡ ተገዛ ። ዘሆባይ ፡ ይትኬነስ ፡ ሎቱ ፡ ወወ ይጠል ፡ ይሰግድ ፡ ሎቱ ፡ (ድጓ) ።

**ክኑስ** ፤ (**ሳን ፡ ሳት ፡ ንስት**)፤ የታከበ ፡ የተ ሰበሰበ ፡ ክምችት ።

**ክናሴ** ፤ አንድነት ፡ ሱታፌ ፡ ጉባሬ ። አመ ፡ ገ ብርከ ፡ በታቦር ፡ ምስለ ፡ ሐዋርያት ፡ ክናሴ ። የሀብዎ ፡ ንስሓሁ ፡ ተስዐተ ፡ ሱባዔ ፡ ይጹም ፤ ወእምድኅሬሁ ፡ ይረክብ ፡ ክናሴ ፡ ምስለ ፡ ሕዝብ ፡ መሀይምናን ፡ (ስ ንክ ፡ ነሐ፲፫ ። ቀሌ) ።

**ክንሰት** ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፤ መሰብሰብ ፡ መሳተፍ ፤ አንድነት ። ምስለ ፡ እለ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ የአምኑ ፡ አኀብር ፡ ክንሰተ ፡ (መጽ ፡ ምሥ) ።

**ክኒሳ** ፤ (**ብ ፡ ክናይስ ። ዕብ ፡ ክኒሳ ፤ ክኔ ሴት ። ሱር ፡ ክኒሰታ ። ዐረ ፡ ክኒሰት**)፤ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ማኅበር ፡ እንግልጋ ፡ የሕዝብ ፡ መንጋ ። መካነ ፡ ጉባኤ ፡ ቤተ ፡ ክሲያን ፡ ምኵራብ ፡ አይሁድ ፤ የተጠረገ ፡ የተጌጠ ። ሰላም ፡ ለጉባኤክሙ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ክ ኒሳ ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክኒሳ ፡ እንተ ፡ አልብኪ ፡ አ በሳ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲፭ ። ታኅ፲፪ ። ደራሲ) ።

**መክነስ** ፤ (ብ ፡ መከንስ ። ዐረብ) ፤ መጥ ረጊያ ፡ መኰስተሪያ ፤ የጕድፍ ፡ መማሪያ ።

**ክነት** ፤ (ቀኒት ፡ ቀነት) ፤ ዐገዘ ፡ ረዳ ፤ ኢዮ ዘኝ ፡ አለ ። ረባ ፡ ጠቀመ ፤ አገለገለ ።

**ክናት** ፤ (ቅናት ። ዕብ ፡ ክናት) ፤ ዐጋዥ ፡ ረዳት ፤ ባልንጀራ ።

**ክንተወ** ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ ከንቱ ፡ ኾነ ፤ ጠፋ ፡ ታጣ ፤ ዐበለ ፡ ዋሸ ፤ ተበላሸ ።

**ክንቱ** ፤ በቁሙ ፤ ብላሽ ፤ ያለዋጋ ፤ የማይረባ ፡ የማይጠቅም ፤ ፈጥኖ ፡ የሚያልፍ ፡ የሚጠፋ ። እስመ ፡ በከንቱ ፡ መሀርኩክሙ ። ሕልም ፡ ወሰንል ፡ ወመቅ ስም ፡ ከንቱ ፡ ኵሉሙ ። ከንቱ ፡ ከንቱ ፡ ይቤ ፡ መክ ብብ ፡ ኵሉ ፡ ከንቱ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፯ ። ሢራ፴፩ ፡ ፭ ። መክ፩ ፡ ፪) ።

—፤ ውሸት ፡ ቧልት ፤ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ። ነቢያት ፡ ርእዩ ፡ ከ ንቶ ። እለ ፡ ይትናገሩ ፡ ከንቶ ፡ (ሰቈ፪ ፡ ፲፬ ። ኢሳ፶ ፡ ፲፱) ።

—፤ የሌለ ፡ ያልነበረ ፤ ኢምንት ። የማንክ ፡ እንተ ፡ ፈ ጠረት ፡ ዓለመ ፡ እምነ ፡ ከንቱ ፡ ዘአልቦ ፡ ገጽ ፡ (ጥበ ፲፩ ፡ ፲፰) ።

—፤ ከፉ ፡ መጥፎ ። ከመ ፡ ቀዐ ፡ ከንቱ ፡ ሰሰነ ። ከንቱ ፡ ላሕይኪ ፡ (ምሳ፲ ፡ ፳፯ ። ኤር፬ ፡ ፴) ።

**ኩናት** ፤—ጦር ፡ ዘገር ፤—ከየነ ።

**ክንተረ** ፤ (ከነተ ። ተቀ ፡ ግ) ፤ ከንተረ ፤ በ ዱላ ፡ መታ ፡ ከምድር ፡ ጣለ ፡ (በማርኛ) ። ዱላን ፡ ከንተሮ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ግዕንቱ ፡ የከንተ ፡ ቅጥያ ፤ ወይ ም ፡ የከተረ ፡ ስራ፡ ይባላል ፤ ቅጥዩ ፡ ሬ ፤ ስራው ፡ ን ።

**ክንትሮስ** ፤ (ሳት ። ዐረ ፡ ሙቀንጠረት) ፤ ክፍለ ፡ ዘመን ፤ የዓመት ፡ ርበ ፤ ፲፭ ፡ ዕለት ፡ ክ፲፭ ፡ ኪክ ሮስ ። ባለመርሐ ፡ ዕዉሮች ፡ ግን ፡ የሰዓት ፡ ፴፯ ፡ ክፍል ፡ ይሉታል ፤ አንዱን ፡ ሰዓት ፡ ፴ ፡ ክንትሮስ ፡ ለማለት ። ዘ ያስተባዕ ፡ አክራመ ፡ በሐጋይ ፡ ወመፀወ ፡ በጸደይ ፡ ክንትሮሳቲሆሙ ፡ ዘገብረ ፡ በዘይትጌረይ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ክሥዶ** ፤ ዶት ፤ (ከሠደ ፡ ይኬሥድ ፡ ይከሥድ) ፤ መክሠድ ፡ መዠመት ፡ ኹማት ፡ ማው ጣት ፡ መክሳት ፡ ኹማታም ፡ መኾን ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ኹማት ፡ መጥናት ፤ መተንን ፡ እይ ።

**ክሥዳ** ፤ (ዳት) ፤ በቁሙ ፡ ኹማት ፡ ያንገትና ፡ የግር ፡ የሽንጥ ፡ (በማርኛ) ።

**ክሣድ** ፤ (ዳት ፤ ክሣውድ ። ዕብ ፡ ኬ ሤድ ፤ ክሥዳም ፤ ስመ ፡ ነገድ ። ዐረ ፡ ቂስ ወድ ፤ ማዥራት ፡ የላይኛው ፡ በገሮ ፡ አ ኳያ ፡ ያለው) ፤ ዐንገት ፡ በፊስና ፡ በመትከፍ ፡ መካ ከል ፡ ያለ ፡ ክፍል ፤ የሥርና ፡ የኹማት ፡ ቤት ፤ የቀሚስ ፡ ዐንገትጌ ፤ ዐንገን ፡ እይ ። ክሣድከ ፡ ጽኑዕ ። ክሣዳቲ ሆሙ ። ላዕለ ፡ ክሣውዲነ ፡ (ዘዳ፴፩ ፡ ፳፯ ። ፩ዜ ፡ ፳፱ ። ሰቈ፭ ፡ ፭) ።

**ኰማኵሥ** ፤—ዝንጕርጕር ፤—ኰሳኵስ ።

**ክሢት** ፤ ቶት ፤ (ከሠተ ፡ ይከሥት ፡ ይ ክሥት ። ግለየ ፤ ቀልዐ ፤ ቀፈጸ) ፤ መክሠት ፡ መ ግለጥ ፤ መክፈት ፡ ማብራት ፤ መንገር ፡ ማውጣት ። ወከ ሢቶ ፡ መጽሐፈ ፡ ረከበ ። ከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ወመሀ ሮሙ ። ትክሥት ፡ አዕይንተ ፡ ዕዉራን ። ኀፍረት ፡ ከሢተ ፡ ምክረ ፡ ዐርክክ ፡ (ሉቃ፬ ፡ ፲፯ ። ማቴ፭ ፡ ፪ ። ኢሳ፵፪ ፡ ፯ ። ሢራ፵፩ ፡ ፳፫) ።

**ክሣቴ** ፤ (ቴት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤ የሚገልጥ ፡ ገላጭ ። ክርስቶስ ፡ ክሣቴ ፡ ብርሃን ። ክሣቴ ፡ ጽድቅ ። ክሣቴ ፡ መስቀል ፡ (ድጓ ። ስንክ ፡ የካቲ፯ ። ጥር፯) ።

**መክሥት** ፤ (ታን ፡ ታት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ የሚገልጥ ፡ ገላጭ ። መግለጫ ፤ ግላጭ ። መክሥተ ፡ አፉሁ ፡ ከመ ፡ መልአከ ፡ እግዚ ። መክሥተ ፡ አፉሁ ፡ መዐዛ ፡ ዕጣን ፤ አፉን ፡ የሚከፍትበት ፡ ወይም ፡ ከፉ ፡ የሚወጣ ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳፭ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ተከሥተ** ፤ ተገለጠ ፤ ተከፈተ ። አልቦ ፡ ክዱን ፡ ዘኢይትከሠት ። ወተከሥቱ ፡ መቃብራት ፡ (ማር፬ ፡ ፳፪ ። ማቴ፳፯ ፡ ፶፪) ።

**ክሡት** ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ሥት) ፤ በቁሙ ፤ የተገለጠ ፡ ግልጥ ፡ ክፍት ። ተወልደ ፡ እምኅቡእ ፡ ው ስተ ፡ ክሡት ። ወክሡት ፡ ገጽየ ። ከመ ፡ መቃብር ፡ ክሡት ፡ ጕረዒቶሙ ፡ (ድጓ ። ጦቢ፪ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፭) ።

**ክሡተ** ፤ ገሊጦ ፤ ተገልጦ ፡ ግልጥ ፡ ኹኖ ፡ በግ ልጥ ። ተናገረ ፡ ክሡተ ። የዐስየክ ፡ ክሡተ ፡ (ዮሐ፯ ፡ ፲፫ ። ማቴ፮ ፡ ፬) ።

**ክሥተት** ፤ መግለጥ ፤ መገለጥ ፡ አገላለጥ ፡ ግል ጥነት ። ክሥተተ ፡ ኀፍረቶን ፡ (ቀኖ ፡ ሉ ዶቅ) ። በቁሙ ፤ የያሬድ ፡ ድርሰት ፡ በታላቅ ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ የሚባል ።

**ክማቶት** ፤ (ዕብራ) ፤ የመከዳ ፡ ልብሶች ፡ አ ንዱ ፡ ኪስ ፡ ያሉ ። አንዱን ፡ ኪሜት ፡ ይለዋል ። እለ ፡ ይሰፍያ ፡ ክማቶተ ፡ (ሕዝ፲፫ ፡ ፲፰) ።

**ክዒብ** ፤ ቦት ፤ (ከዐበ ፡ ይክዕብ ፡ ይክ ዐብ) ፤ መክብ ፡ መደርደር ፤ ማነባበር ፡ አንዱን ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ማኖር ። ማጠፍ ፡ መደረብ ፤ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ማድ ረግ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በክዐበ ፡ ፈንታ ፡ አካዕበተ ፡ አመ ክዐበ ፡ ይላል ።

**ክዓቢ** ፤ **መክዕብ** ፤ የሚከብ ፡ ካቢ ፡ ዐጣፊ ፡ ደራቢ ።

**ተክዕበ** ፤ ተካበ ፡ ታጠፈ ፡ ተደረበ ። ካባ ፡ ካቡት ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ክዑብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ዕባት) ፤ የተካበ ፤ ዕ ጥፍ ፡ ድርብ ፡ ንብብር ። ልብሰት ፡ እንተ ፡ ክዑብ ፡ ፈ ትሉ ። ክዑበ ፡ ከለሚዳ ። ነተ ፡ ክዑብ ። ሜላት ፡ ክ ዑብ ። በዓሎ ፡ ክዑበ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ (ሢራ፵፭ ፡ ፲፩ ። ዲድ ፡ ፫ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፴ ። ፴፮ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ጥር፳) ።

**ክዕብ** ፤ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ ኹለት ። ካዕበ ፡ አ መት ። ያስተዋፅኦ ፡ ሎቱ ፡ ሲሳዮ ፡ ስንዳሴ ፡ ዐሥረ ፡

ወካዐበ ፡ በመስፈርተ ፡ አርጣባስ ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ። ዳን፲፫ ፡ ፫) ።

—፤ ሌላ ፡ ፪ኛ ፡ ወዳጅ ፡ ባልንጀራ ፤ እኩያ ፡ መንቲያ ። እመቃብሪሁ ፡ ቀዳሚ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ካዕብ ፤ እንዘ ፡ ያፈልስዎ ፡ ሕዝብ ። ሰላም ፡ ለአውጋንዮስ ፡ ወለአውጋንዴሮስ ፡ ካዕቡ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። መጋ፲፱) ።

**ካዕብ** ፤ ፪ ፡ ጊዜ ፡ ዳግመኛ ፡ ኹለተኛ ። ምዕረ ፡ ወካዕበ ። ካዕበ ፡ ወሥልሰ ። ወካዕበ ፡ ናስተበቍዕ ፡ (ፊልጵ፬ ፡ ፲፮ ። ሚራ፲፫ ፡ ፯ ። ቅዳ) ።

**ካዕበት ፤ ክዕበት** ፤ መካብ ፡ (ጥን) መካብ ፡ አካካብ ፡ ክበሽ ። ኹለትነት ፡ ኹለት ፡ እጅ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ። በአቱ ፡ ካዕበት ። ለይኩን ፡ ካዕበት ፡ ላዕሌየ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘደቤክ ። ወሀበ ፡ እግዚ ፡ ለኢዮብ ፡ ካዕበተ ፡ ንዋዩ ፡ እምቀዲሙ ። ይፍዲ ፡ ሀየንተ ፡ ዘሰረቀ ፡ ኅምስተ ፡ ካዕበተ ፡ (እጅ) ። ካዕበተ ፡ ሱባዔ ፡ (፲፬) ። ካዕበተ ፡ ዐሥሩ ፡ (፳) ። ካዕበተ ፡ ዐሥሩ ፡ (፻) ። ካዕቢተ ፡ ምክዕቢት ፡ የዕጥፍ ፡ ዕጥፍ ፡ ጣንድ ፡ አራት ፡ (ዘፍ፵፫ ፡ ፲ ። ፬ነገ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ኢዮ፵፪ ፡ ፲ ። ፊ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ማግ፲፱ ። ኦሪ ፡ ታኅ፲፱ ። ራእ፲፰ ፡ ፮) ።

**ካዕባዊ ፡ ይ** ፡ (ካዕቢት) ፤ ሌላ ፡ ኹለተኛ ፡ (ፊልክ ፡ ማ፹ ። ፳፩) ።

**አመክዐበ** ፤ (ክዐበ ፤ ክዒበ ፡ መክዕብ) ፤ ዐጠፈ ፡ ደረበ ፡ ዕጥፍ ፡ አደረገ ። አንተ ፡ ያመክዕቡ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጸመ ፡ ወዳሉት ። ወአመክዐብኪ ፡ ፍና ወኪ ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ኤር፪ ፡ ፴፮) ።

**ተመክዐበ** ፤ (ተክዕበ) ፤ ታጠፈ ፡ ተደረበ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ኾነ ። ወይትመክዐብ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወቱ ። በሀየ ፡ ይትመክዐብ ፡ ሎቱ ። ከመ ፡ ይትመክዐብ ፡ ሀጉልክሙ ፡ (ሚራ፳፯ ፡ ፰ ። አፈ ፡ ተ፳ ፡ ፳፱) ።

—፤ በዛ ፡ ተረባ ፡ ፈደፈደ ። ወተመክዐበ ፡ ለከ ፡ ዐ ፡ ዘምእት ፡ ወዘስሳ ፡ ወዘሠላሳ ፡ (ገድ ፡ ዮሐ ፡ ክማ) ።

**ምክዕቢት** ፤ (ታት) ፤ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ኹለት ፡ እጅ ። ምክዕቢተ ፡ ክብር ፡ ይደልዎሙ ። ምክዕቢት ፡ ውእቱ ፡ ኀይሉን ። ትሥርዐዎ ፡ ምክዕቢተ ። ኃጥእ ፡ ዘክልኤ ፡ ገዐዙ ፡ ወምክዕቢተ ፡ የሐውር ፡ (፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ። ሄርማ ፡ ገ፱፪ ። ዘሌ፳፱ ፡ ፯ ። ሚራ፪ ፡ ፲፪) ። ክእንዘ ፡ ጋራ ፡ ሲነገር ፡ እንደመራረዱ ፡ ይፈታል ። ኵሉ ፡ ምክዕቢት ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ ቅድመ ፡ ካልኡ ። ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ነው ፡ ያውም ፡ ተባትና ፡ እንስት ፡ (ሚራ፵፪ ፡ ፳፬) ። ብዙኀ ፡ ምክዕቢተ ፤ ፪ ፡ ዕጥፍ ፡ ፱ ፡ እጅ ፡ (ሉቃ፲፰ ፡ ፴) ። ሰብዐቱ ፡ ምክዕቢታተ ፡ ትምህርት ፤ ፯ ፡ ዕጥፍ ፡ ማዝ ፡ (ሔኖ፺፫ ፡ ፲) ።

**ምክዕቢት** ፤ የመስፈሪያ ፡ ስም ፤ ታላቅ ፡ ያውድማ ፡ ልክ ፡ ዳውላ ፡ ቍርጫት ፤ ፪ ፡ እጅ ፡ የሚይዝ ፡ የሚያነሣ ፡ (ዘፍ፳፭ ፡ ፲፪) ። በትግሪኛም ፡ ካዕበ ፡ የሚባል ፡ መስፈሪያ ፡ አለ ፤ እንተላምን ፡ እይ ። በማሮኛም ፡ ታላቁን ፡ ዋንጫ ፡ ክበ ፡ ማለት ፡ የክዒብ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ክዒው** ፤ **ዎት** ፤ (**ከዐወ ፡ ይክዑ ፡ ይክዐው ። ወክዐ**) ፤ ማፍሰስ ፡ መክንበል ፡ መድፋት ፡ መገልበጥ ፡ መዘርገፍ ፤ መርጨት ፡ መፈንጠቅ ፤ የፈሳሽና ፡ የርጥብ ፤ ለደረቅም ፡ ይኾናል ፤ ነገረን ፡ እይ ። ደመና ፡ ይክዑ ፡ ዝናመ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ፈለግ ፡ ይክዑ ፡ ማዮ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ። ለክዒው ፡ ደመ ፡ ሰብእ ። ከዐወ ፡ ዘርዐ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። አማዑተ ፡ ከርሡ ፡ ከዐወ ፡ ከመ ፡ ፀፍዕ ፡ ዘላሕም ። ከዐዉ ፡ ልበክሙ ፡ ቅድሜሁ ። ምስለ ፡ ገዐር ፡ ወክዒወ ፡ ልብ ፡ (መክ፲፩ ፡ ፫ ። ሔኖ፸፯ ፡ ፭ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፲፩ ። ፶፩ ። ስንክ ፡ ኅሐ፲፰ ። መዝ ፡ ፷፩ ። አፈ ፡ ተ፴፩) ። እክዑ ፡ እምነ ፡ መንፈስየ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ። ከዐወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ምሕረቶ ። እክዑ ፡ ቅድሜሁ ፡ ስእለትየ ፡ (ዮኤ፪ ፡ ፳ ። ዘፍ፴፱ ፡ ፳፩ ። መዝ ፡ ፻፵፩) ። ፍዝልል ፡ ፍንቀልቅል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ንክዐው ፡ ይባል ፡ የመሳሳሽና ፡ የጣፈ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ በለሰን ፡ እይ ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፲) ።

**ክዓዊ** ፤ (**ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፡ ዐውት**) ፤ የሚያፈስ ፡ አፍሳሽ ፡ (ዘሌ፲፯ ፡ ፬ ። አፈ ፡ ድ፳፱) ።

**ምክዓው** ፡ (**ዋት**) ፤ ማፍሰሻ ፡ መገልበጫ ። ምክዓወ ፡ ማይ ፡ ዘዙሉ ፡ ቀላይ ። ምክዓወ ፡ ሐመድ ፡ (ሔኖ፲፯ ፡ ፯ ። ዘሌ፬ ፡ ፲፪) ።

**አክዐወ** ፤ አስፈሰሰ ። ያክዑ ፡ ደመ ፡ ላኳ ሆሙ ፡ ለአብዳን ፡ (ሚራ፳፯ ፡ ፲፰) ።

**ተክዕወ** ፤ ፈሰሰ ፡ ተጨመረ ፡ ተፈሰሰ ፡ ተገርጎቶ ፡ ኹደ ። ይትክዐው ፡ ዝናም ፡ እምውስተ ፡ ደመና ። ፈለግ ፡ ይትክዐው ፡ ውስተ ፡ ባሕር ። ሰብ ፡ ተክዕዉ ፡ አሕዛብ ፡ ውስተ ፡ ሕብረ ፡ እክይ ፡ ወፀግ ፡ (ኢዮ፴፮ ፡ ፳፯ ። ሔኖ፲፯ ፡ ፭ ። ጥበ፲ ፡ ፲፭) ።

**ክዑው** ፤ (**ዋን ፡ ዋት ፡ ውት ፡ ዐት**) ፤ የፈሰሰ ፡ ፈሳሽ ፡ የተዘረገፈ ፡ ብዙ ፡ ፍጹም ። ማይ ፡ ክዑው ። ሰብእ ፡ ክዑው ፡ ከመ ፡ ማይ ። እንዘ ፡ ክዑው ፡ አማዑቱ ። በመዐት ፡ ክዑው ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ደራሲ ። መጽ ፡ ምስ ። ሕዝ፳ ፡ ፴፫ ፡ ፴፬) ።

**ክዕወት** ፤ መፍሰስ ፡ ማፍሰስ ፡ አፈሳሰስ ፡ ፈሰሱ ፡ ፈሰስ ። ክዕወተ ፡ ደም ። ክሥተት ፡ ክዕወተ ፡ ደማ ፡ (ሔኖ፲፱ ፡ ፱ ። ዘሌ፳ ፡ ፲፰) ።

**ኰዕንት** ፤—የሚበላ ፡ ሥር ፤—ኰዐተ ።

**ኰዒስ** ፤ **ሶት** ፤ (**ኰዐሰ ፡ ኰዐሰ ፡ ይኰዕስ ፡ ይኰዐስ ። ዕብ ፡ ካዐስ ፤ ተቈጣ**) ፤ ማኳስ ፡ ማካብ ፤ ወይም ፡ መኳስ ፡ ኳስ ፡ መኾን ፤ ኳስ ፡ ማኽል ፤ በኳስ ፡ መጫወት ፡ ማጓን ፡ ማንጠር ፡ መልጋት ።

**ኰዒስ** ፤ (**ጽር ፡ ኾይስ ። ዕብ ፡ ባት**) ፤ ታላቅ ፡ ገንቦ ፡ እንስራ ፡ ማድጋ ፡ የውሃ ፡ ዕቃ ፤ ክብ ፡ እንክብል ፡ የኳስ ፡ ዐይነት ። ያገምር ፡ አርብዓ ፡ በመስፈርት ፡ ኰዒስ ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፴፰) ።

**ኰዕስ** ፤ (**ብ ፡ ኰዓስው**) ፤ ኳስ ፡ ንጥየ ፡ ተውኔት ፡ ከጨርቅ ፡ ወይም ፡ ከላስቲክ ፡ የሚሠራ ። ወፈ

ነው ፡ ዳራ ፡ ለእስክንድር ፡ ኵዕሶ ፡ ወሰሊጠ ፡ (ዜና ፡ እስ) ።



ኵዕሶ ፡

**ከዕሴ ፤** ፈርስ ፤ እበት ፡ ርስሐተ ፡ ክብድ ፤ በእንስሳት ፡ ሆድ ፡ በጨጓራና ፡ በሽንፍላ ፡ ባንገት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ። ምስጢሩ ፡ የጨጓራውን ፡ ክብነት ፡ እንደ ፡ ማድጋ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፤ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ስይተው ፡ የጨጓራ ፡ ስንበር ፡ ይሉታል ፤ ፍችው ፡ አይደለም ። ኵሎ ፡ ሥጋሁ ፡ ምስለ ፡ ርእሱ ፡ ወበኵንዌሁ ፡ ወከርሦ ፡ ወካዕሴሁ ፡ (ዘሌ፱ ፡ ፲፩ ። ፩ ፡ ፲፯ ። ፲፮ ፡ ፳፯ ። ዘኍ፲፱ ፡ ፭) ። ዳግመኛም ፡ ሐመድ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ከዕሴ ፡ ይባል ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ከዕሴ ፡ ዕጕልት ፡ (ዕብ፱ ፡ ፲፫) ።

**ኰዓት ፤ ዖት ፤ (ኰዐተ ፡ ይኰዕት ፡ ይኰዐት) ፤** መኳት ፡ መቈፈር ፤ ስመንቀል ፡ ለማፍለስ ፡ ለመናድ ፡ ለማፍረስ ፤ ወይም ፡ ለማረድ ፡ ለማጐድጐድ ፡ ምሽግ ፡ ለማድረግ ። ወመጽአ ፡ ኀቡረ ፡ ወኰዐትዋ ፡ ለሀገር ፡ ወከዐው ፡ ደሞሙ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ። ፈረንጂ ፡ ለጕራዕ ፡ ምስለ ፡ ጕዳጕዲ ፡ ኰዐትካያ ፡ ቅድመ ፡ ትኩን ፡ መቃብርካ ፡ (መቃ ፡ ገ፲፱ ። ትግሬኛ ፡ ቅኔ) ።

—፤ መኰትኰት ፤ ዐፈርና ፡ ፍግ ፡ ማስታቀፍ ፡ የእክልና ፡ የተክል ።

**ኰዓቲ ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤** የሚኵት ፡ የሚኰተኵት ፡ ኳች ፡ ኰትኳች ።

**ኵዕንት ፤** ቍፋሮ ፡ ኵትኳቶ ። ችግር ፡ ሐዘን ። ዘእንበለ ፡ ጻማ ፡ ወኵዕንት ፡ (አዋል) ።

—፤ በቁሙ ፡ የሳም ፡ ጡት ፡ ወይም ፡ ሴላ ፡ እንደ ፡ ቋርፍና ፡ እንደ ፡ ድንቹ ፡ ያለ ፡ የሚበላ ፡ ሥር ። ወበጽሐ ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ ዘአልቦ ፡ ዘይነብር ፡ ውስቴቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ኵዕንት ፡ ወቀቅሕ ፡ ወማይ ፡ ብዙኅ ፡ ወሶቤሃ ፡ ኀለየ ፡ ወይቤ ፤ ሶበ ፡ እወፍር ፡ ኀበ ፡ ኵዕንት ፡ ይፀራዕ ፡ ግብርየ ፡ ወአልብየ ፡ ረድእ ፡ ዘያአቱ ፡ ሲተ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲፫) ።

**ከፍ ፤ (ወከፈ) ፤** ስመ ፡ ፊደል ፡ ፲፩ኛ ፡ ከ ፤ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፹፩—፹፰ ። ሰቈ፩ ፡ ፲፩ ። ፪ ፡ ፲፩ ። ፫ ፡ ፴፩ ። ፬ ፡ ፲፩ ። አፈ ፡ ድ፪) ። ፍችው ፡ ውስጥ ፡ እጅ ፤ መስጣ ፡ ማቀበያ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ለእግርና ፡ ለመንክም ፡ ይኾናል ። ወበመ ፡ ከፍ ፡ ከመ ፡ ካፈ ፡ ሳሕም ፡ (ሕዝ፩ ፡ ፯) ። ወከፈን ፡ እይ ፤ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

**አከፈ ፤ (የአክፍ ፡ ይእክፍ ። አውከፈ) ፤** አበበ ፡ ጠረገ ። ወእከፈት ፡ አንብዐ ፡ ወሰታ ፡፡ ዐፈመ ፡ ዘቀ ፡ ጋፈ ፡ ጠረገ ፡ የምርት ፡ የመሬት ። አካፋ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ኵፍ ፤ ኩፍ ፤ (ብ ፡ አክፋፍ ። ዐረ ፡ ኰፍ) ፤** ታላቅ ፡ መመጠሚያ ፤ መጠምጠሚያ ፡ ጉንባሌ ፡ አግርን ፡ ከማማ ፡ እስከ ፡ ጉልበት ፡ የሚያለብስ ፡ የሚከት ፡ የሚሸፍን ። እስመ ፡ እሉ ፡ ኅጽዋን ፡ ኮኑ ፡ ያስተማእንዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ኩፈ ፤ ወወደዩ ፡ ውስቴቱ ፡ አክይስተ ፡ ከመ ፡ ይንስክዎ ፡ ለንጉሥ ፤ ወነሥአ ፡ ንጉሥ ፡ አክፋፈ ፡ ወረከበ ፡ ውስቴቶሙ ፡ አክይስተ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ከፈአ ፤ አት ፤ (ከፍአ ፡ ይከፍእ ፡ ይከፋእ ። ሱር ፡ ክፋእ ፤ ገፋ ፡ ደፋ ፡ ገለበጠ ፡ አስገደደ) ፤** መክፋት ፤ ክፉ ፡ መኾን ፡ የጠባይ ። አከየንና ፡ ብእሰን ፡ ሐሠመን ፡ እይ ። መበላሸት ፤ መፍዘዝ ፤ የመልክ ፡ የዐይን ። ክፍአ ፡ አርአያሃ ፡፡ ዘክፍአ ፡ ርእየቱ ፡፡ ወእመ ፡ ደረስዎ ፡ ግንጽሊተ ፡ ይከፍእ ፡ ጸጋሁ ፡ ለምስጢር ፡፡ አዕይንትየ ፡ ክፍአ ፡ ለርእይ ፡ (አረጋ ፡ ድ፰ ። አፈ ፡ ቀ፲፱ ። ተረ ፡ ቄር፫ ። ኩፋ ፡ ፵፯) ።

—፤ መጥረስ ፡ መደንገዝ ፡ መቻምቻም ፡ የስለት ፡ የሹል ። ይከፋእ ፡ ስነ ፡ አክይስት ፡፡ እስመ ፡ ክፍአ ፡ እሉ ፡ አቅርንት ፡፡ ወይከፋእ ፡ ሦኩ ፡ ለዲዮብሎስ ፡ (ግንዘ ። ዘክ፩ ፡ ፩፳ ። ተረ ፡ ቄርሎ፭) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ በከፍአ ፡ ፈንታ ፡ (ቀከፍአ) ፡ ወይትከፋእ ፡ ሦኩ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ክፉእ ፤ (እን ፡ እት ፡ ፍእት) ፤** የከፋ ፡ ክፉ ፡ የጠፋ ፡ ጥፉ ፤ መጥፎ ፡ ብልሹ ። አምሳለ ፡ ሕሡመ ፡ ወክፉአ ፡ ንጻሬ ፡ (አረጋ ፡ መል፲፱) ።

**ክፍአት ፤** መክፋት ፡ አክፋፍ ፡ ክፋት ፡ ክፉነት ፡ መጥፎነት ፡ ደግዳግነት ፡ የመልክ ፡ የግብር ። ኢይፃምህክ ፡ ልሑየ ፡ በእንተ ፡ ርእየቱ ፡ ወኢሕሡመ ፡ ኢይሜንን ፡ በእንተ ፡ ክፍአቱ ፤ እላ ፡ ያስተጋብእ ፡ ኵሎ ፡፡ ክፍአተ ፡ አበሳ ፡፡ ወክፍአቱ ፡ ለአዳም ፡ ይሚጥ ፡ እምኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ በቅድሜሁ ፡ (ግንዘ ። ማር ፡ ይስሐ ። ፩፯) ።

**ኬፋ ፤ ኬፋእ ፤ ኬፋስ ፤ (ሱር ፡ ኬፋእ ። ጽር ፡ ኪፋስ) ፤** ድንጊያ ፡ ዐንቍ ። እብነ ፡ ኬፋስ ፡ አንቲ ፡ (አርጋ ፡ ፬) ። የሰው ፡ ስም ፤ ጴጥሮስ ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፵፫ ። ፩ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ። ፲፭ ፡ ፭ ። እብንንና ፡ ኰኵሕን ፡ ጴጥሮስን ፡ ተመልከት ። ምስጢሩ ፡ ጥንካሬና ፡ ብርታት ፡ ሸካራነት ፡ ነው ።

**አክፍአ ፤** አከፋ ፤ አስከፋ ፡ አፈዘዘ ፡ አሳወረ ፡ አበላሸ ፡ አጣመመ ። ነጽሮ ፡ ብርሃኑ ፡ ያከፍእ ፡ ዐይነ ፡፡ መብረቅ ፡ ዘበስእንበሊብሎቱ ፡ ያከፍእ ፡ ዐይኖ ፡ ለዘ ይኔጽሮ ፡፡ ያከፍእ ፡ ነገረ ፡ አምሳለ ፡ ወአርአያ ፡ (ሚራ ማር ፡ ፬ ። መጽ ፡ ምስ ። ተረ ፡ ቄርሎ፬) ።

**ተከፍአ ፤** ተከፋ ፡ ዐዘነ ፡ ተቈረቈረ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ከፈየ ፤ (ዐረ ፡ ከፈ) ፤** ከፈነ ፤ አጕናጸፈ ፡ ጠቀለለ ፤ ደፋ ፡ ጠመጠመ ።

**ከፈይ ፤** በቁሙ ፡ ጠጕራም ፡ ለስላሳ ፡ ሙዳ ፡ ለምድ ፡ ቆብ ፡ ካባ ፡ ቀሚስ ፡ የሚኾን ።

**ከፈን ፤** በቁሙ ፤ ልብስ ፡ መግነዝ ፤ የሬሳ ፡ መጐናጸፊያ ፡ የመቃብር ፡ ሽማ ። (ተረት) ፡ አለ ፡ በለኝ ፡ ቀ

ለቤን ፤ ሞተ ፡ በሰኝ ፡ ክፈኢን ። ክፈን ፡ ሳይገዙ ፣ ሬሳ ፡ እያጉዙ ።

**ኰፌት** ፤ (ዐረ ፡ ኰፈት) ፤ ቆብ ፡ ጠርቡሽ ፡ ባለሐር ፡ ጉፍታ ።

**መክፌ** ፤ (አክፈ) ፤ ማጠቆ ፡ የልብስ ፡ ቤዛ ፤ ታላቅ ፡ መንዲል ፡ እንደ ፡ ሞጣሕት ፡ ያለ ፤ ማበሻ ፡ መወልወያ ። ከክፈየና ፡ ከኢክፈ ፡ ከኹለቱ ፡ የተደቀለ ፡ ነው ። ነሥአ ፡ መክፌ ፤ ወቀነተ ፤ ወመዝመዘ ፡ በውእቱ ፡ መክፌ ፡ (ዮሐ፲፫ ፡ ፬ ፡ ፭) ።

**ከፈል** ፤ ሎት ፤ (ከፈለ ፡ ይከፍል ፡ ይክፍል ፤ ቀፈለ ። ሰብ ፡ ክፉል ፤ ቃፉል) ፤ ማክፈል ፡ ማጠፍ ፡ መደረብ ፡ ኹለቱን ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ መጦም ፤ ጊታ ፡ ከተያዘበት ፡ እስከ ፡ ተንሣበት ። መክፈል ፤ መክፋፈል ፡ መለየት ፡ አንዱን ፡ ኹለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ማድረግ ፡ መተንተን ። አበሳኬ ፡ ከፈል ፡ በክልኤ ፤ እስመ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ይከፍልዋ ፡ ለመዓልት ፡ ኀበ ፡ ሠለስቱ ፡ መክፈልት ። ከፈለ ፡ ሰራዊት ፡ አርባዕተ ፡ ክፍለ ። ትከፍሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ኀበ ፡ ስሳ ፡ (ቄር ። ፍ ፡ ን ፡ ፲ ፡ ፮ ። ዮሴፍ ። አቡሻ) ።

—፤ ብድር ፡ ወረታ ፡ መመለስ ፤ ክፍለሎ ፡ መጥፎ ፡ መስጠት ፤ ቄርቦ ፡ ማደል ፡ ማውረስ ። ወከፈሎ ፡ አብርሃም ፡ ዐሥራተ ፡ እምዙሉ ። ወዙሉ ፡ በከመ ፡ ከፈሎ ፡ እግዚ ፡ በመስፈርተ ፡ ሃይማኖቱ ። መኑ ፡ እምከፈለኒ ፡ ከመ ፡ እኩን ። ርስትየ ፡ ዘከፈልከዋ ፡ ለሕዝብየ ፡ (ዕብ፯ ፡ ፬ ። ሮሜ፲፪ ፡ ፫ ። አርጋ ፡ ፭ ። ኤር፲፪ ፡ ፲፬) ።

**ክፉሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤ የሚያከፍል ፡ አክፋይ ፡ አከፋፋይ ፡ ያዥ ፡ ሰዓት ፡ ጠመኛ ። የሚከፍል ፡ የሚያድል ፤ ክፋይ ፡ ዐዳይ ። መኑ ፡ ሢመኒ ፡ ክፉሌ ፡ ወመኰንነ ። ከነ ፡ ክፉሌ ፡ ሕዝብ ። ክፉሌ ፡ ንዋይ ፡ (ሉቃ፲፪ ፡ ፲፬ ። ገድ ፡ ኪሮ ። ስንክ ፡ ሚያዝያ) ።

**አክፈለ** ፤ አስከፈለ ፡ ኹለት ፡ አስደረገ ።

**ተከፍለ** ፤ ተከፈለ ፡ ከኹለት ፡ ከሦስት ፡ ወይም ፡ ከብዙ ። በጽሑ ፡ ውስተ ፡ ፈለገ ፡ ጤግሮስ ፡ ወተከፍለ ፡ ሎሙ ፡ ማይ ፡ ወዐደዉ ። ተደምሮ ፡ ዘመድ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ክልኤ ፡ ክፍል ። ዝንቱ ፡ ጾታ ፡ ይትከፈል ፡ ለኀበ ፡ ብዙኅ ፡ ክፍል ፡ (ስንክ ፡ የካ፲፭ ። ፈ ፡ መ ፡ ፭ ፡ ፬ ። ፳፭ ፡ ፩) ።

—፤ ታደለ ፡ ተቀበለ ፤ ተቀባዩ ፡ ኹኑ ፡ አገኘ ፡ ብድሩን ፡ ዋጋውን ፡ (ዐማርኛ) ።

**ተካፈለ** ፤ በቁሙ ፡ ተከፋፈለ ፡ ተተናተነ ። ሸሎ ፡ ተግባሪክ ፡ ይትካፈሉ ፡ መዋርስቲክ ። ተካፈሉ ፡ ምድርየ ። ተካፈሉ ፡ አልባስየ ። አበ ፡ ይትካፈሉ ፡ በርበረ ። ዘይትካፈል ፡ ምስለ ፡ ሰራቂ ፡ (ሚራ፲፬ ፡ ፲፭ ። ዮኤ፬ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፳፩ ። ኢሳ፶ ፡ ፫ ። ምሳ፳፱ ፡ ፳፬) ።

**ክፉል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ፍልት) ፤ የተከፈለ ፡ የተካፈለ ፡ የተከፋፈለ ፡ ክፍልፍል ። ዘክፉል ፡ ጽፈሪሁ ። እንዘ ፡ አሐዱ ፡ ክፍሉ ፡ ውስተ ፡ ብዙኅ ፡ ክፉል ። ልሳናት ፡ ክፉላት ፡ (ዘዳ፲፬ ፡ ፯ ። ግብ፯ ፡ ፳፱ ። ግብ፪ ፡ ፫) ።

**ክፍለት** ፤ መክፈል ፡ መከፈል ፡ አከፋፈል ፡ ክፍያ ። ውእቱመ ፡ እግዚ ፡ ወሰብእ ፡ ዘእንበለ ፡ ክፍለት ። ዘእንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወኢክፍለት ፡ (ቄር ፡ ጸላ ። ሃይ ፡ አበ) ። ክፍል ፡ መክፈልት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ክፍለት ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። በበ ፡ ክፍለቶሙ ፡ ለካህናት ፡ (፪ዜና ፡ ፰ ፡ ፲፬) ።

**ኩፋሌ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ መክፈል ፡ መገመስ ፡ መለየት ። ኩፋሌ ፡ መዋዕል ። ኩፋሌ ፡ ኅብስት ። ለይኩን ፡ ዝንቱ ፡ ኩፋሌ ፡ ማእከሌክሙ ፡ (ኩፋ ፡ ፮ ። ቄድር ፡ ገ፳፫ ። አቡሻ ፡ ፴፯) ።

—፤ መጽሐፍ ፡ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ከኹለቱ ፡ ብሔረ ፡ ኦሪት ፡ ከዘፍጥረትና ፡ ከዘፀአት ፡ የተከፈለ ፤ የዘመኑን ፡ ክፍል ፡ የሚናገር ፡ በኢዮቤልዩ ፡ የሚቈጥር ። መጽሐፈ ፡ ኩፋሌ ፡ (አቡጥ ፡ ፴፭) ።

**ክፍል** ፤ (ብ ፡ ክፍላት ፤ አክፋል) ፤ ቁመር ፡ የቍጥር ፡ መደብ ፡ መክፈያ ፡ ማክፈያ ። ዘወፅአ ፡ እምክፍል ፡ (አቡሻ ፡ ፲፭) ።

—፤ በቁሙ ፡ ክፍል ፡ ለብቻው ፡ ያለ ፡ የተለየ ፡ አንድ ፡ የሚባል ፤ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ነሲብ ፡ ሰፃ ፡ ድርሻ ፡ መቍንን ፤ ገንዘብ ፡ ርስት ። ነሥኡ ፡ አልባሲሁ ፡ ወረሰይዎ ፡ አርባዕተ ፡ ክፍለ ። አልብከ ፡ ክፍል ፡ ምስሌየ ። ክፍሎሙ ፡ ለዐደው ፡ እለ ፡ ነሥኡ ፡ ክፍሎሙ ። ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ አክፋሊሆሙ ፡ (ዮሐ፲፱ ፡ ፳፫ ። ፲፫ ፡ ፰ ። ዘፍ ፲፬ ፡ ፳፬ ። ኢያ፲፱ ፡ ፵፭) ። ከሰውና ፡ ከመጽሐፍ ፡ ዝምሮ ፡ ክፍል ፡ ሳለው ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። ክፍላተ ፡ ዐቀብት ፡ አንቀጽ ። እግዚእነ ፡ አስተጋብአ ፡ ሥርዐተ ፡ ፍድፋዴ ፡ ዓለማውያን ፡ ሳዐለ ፡ ሠለስቱ ፡ ክፍል ። ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ ይትከፈል ፡ ላዕለ ፡ ሠለስቱ ፡ አክፋል ። መዓርገ ፡ ክህነት ፡ ትትከፈል ፡ ለኀበ ፡ ብዙኃን ፡ ክፍላት ፡ (፩ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፩ ። ፈልክ ፡ ፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፭ ፡ ፩) ።

**ክፍላዊ** ፤ ክፍላም ፡ ዕድላም ፤ ክፍልነት ፡ ያለው ። ሀኬት ፡ ክፍላዊ ፡ (ፈልክ ፡ ፴፬) ።

**መክፈልት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፡ ክፍል ፡ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ ያለው ። በብዙኅ ፡ መክፈልት ። አርባዕቱ ፡ መክፈልተ ፡ ዓመታት ። ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ሰመንቱ ፡ መክፈልታት ፡ (ዕብ፩ ፡ ፩ ። ሔኖ ፡ ቍ፪ ፡ ፲፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፭) ።

—፤ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ድርሻ ፤ ሰፃ ። መክፈልትየ ፡ እምዙሉ ፡ ስራሕየ ። ምስለ ፡ አራዊት ፡ መክፈልቱ ። ዝ ፡ ውእቱ ፡ መክፈልቱ ፡ ለኃጥእ ፡ እምኀበ ፡ እግዚ ፡ (መክ፲ ፡ ፳፭ ። ዳን፬ ፡ ፲፪ ። ኢዮ፳ ፡ ፳፱) ።

**አስተካፈለ** ፤ አካፈለ ፡ አከፋፈለ ። ኖኅ ፡ አስተካፈሎሙ ፡ ሸሎ ፡ ምድረ ፡ ለደቂቁ ። ዛቲ ፡ ምድር ፡ ዘታስተካፍልዋ ፡ ርስተ ፡ ለአንጋደ ፡ እስራኤል ፡ (ስንክ ፡ ጥር፮ ። ሕዝ፵፯ ፡ ፳፱) ።

**ከፈን** ፤—በቁሙ ፡ ልብስ ፤—ከፈየ ።

**ክፍዐ** ፤—ከፋ ፡ በሰ ፤—ክፍአ ።

**ከፈረ፤** (ዕብ ፡ ከፋር ። ዐረ ፡ ከፈረ ፤ ቀፈረ) ፤ ከደነ ፡ አለበሰ ፤ ከደ ፡ ከዳ ፡ እምነቱን ፡ ተወ ፡ አፈረሰ ። ክፍር ፡ እንዲል ፡ ከሓዲ ፡ ሲል ፡ (እስላም) ። ፈራ ፤ ይቅር ፡ አለ ፡ ተወ ፡ ኀጢአትን ፡ ማረ ። ስረየትና ፡ ሠሀለን ፡ ኀደገን ፡ ተመልከት ። ኢኪፉርን ፡ እይ ።

**ኰፋር፤ ኲፋር፤** (ሩት) ፤ ልብስ ፡ ስርየት ፡ የኢጲስቆጶስ ፡ ልብስ ፡ ባለራምት ፡ ካባ ፤ ለሕዝቡም ፡ ለራሱም ፡ ፍጹም ፡ ስርየት ፡ በሚለምንበት ፡ በጸሎትና ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ የሚለብሰው ። ሰፍሐ ፡ ኰፋሮ ፡ ወነሥአ ፡ በእዴሁ ፡ እምእሳት ፡ ወረሰዮ ፡ ውስቴቱ ። አንበራ ፡ ለእሳት ፡ ውስተ ፡ ኰፋሩ ። ለጳጳስ ፡ ወለዐጪኒ ፡ አበር ገዎሙ ፡ ኰፋረ ፡ ወዘናረ ፡ ወልብሰ ፡ ቀጢንት ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ ፲፱ ። መጋ ፲፱ ። ታሪ ፡ ነገ ፡ ገ፻፱) ። ዐፈረንና ፡ ማስፈረትን ፡ እይ ።

**ክፋር፤** (ዕብራ) ፤ ገጠር ፡ ታናሽ ፡ አገር ፡ ጥቂት ፡ መንደር ፡ የገበሮች ፡ ሰፈር ።

**ከፈር፤** (ብ ፡ አክፋር ። ዐረ ፡ ክፍር) ፤ መቃብር ፡ ሞላላ ፡ ጕድጓድ ፡ ወይም ፡ የምድር ፡ ቤት ፡ የሬሳ ፡ መከተቻ ። እለ ፡ ተከይዱ ፡ ታሕተ ፡ ከፈር ፡ (ቅዳ ፡ ማሩ) ።

—፤ ቅርጫት ፡ መሶብ ፡ ሳጥን ፡ እንቅብ ፡ ባላገሮች ፡ ሠርተውና ፡ ሰፍተው ፡ ለከተማ ፡ ሰው ፡ የሚሸጡት ። ወአንበረ ፡ ውእተ ፡ ሥጋ ፡ ውስተ ፡ ከፈር ። ከመ ፡ ይንብርዋ ፡ ታሕተ ፡ ከፈር ። እሬእ ፡ ሠለስተ ፡ አክፋረ ፡ ዲበ ፡ ርእስየ ፡ (መሳ ፮ ፡ ፲፱ ። ማቴ ፳፭ ፡ ፲፭ ። ዘፍ ፵ ፡ ፲፮—፲፰) ።

**ከፉር፤** (ዐረ ፡ ከፉር) ፤ በቁሙ ፡ የብል ፡ መድኀኒት ፡ የሬሳውና ፡ የስኳር ፡ ዐይነት ፤ ልብስንና ፡ ማእስን ፡ ከብል ፡ የሚያድን ፡ የሚጠብቅ ። ለሌላም ፡ ለብዙ ፡ ነገር ፤ ይልቁንም ፡ ለዕበጥና ፡ ለወለምታ ፡ ከዘይትና ፡ ከሰቢርቶ ፡ ጋራ ፡ ይፈወሳል ፡ (ዮሴፍ) ።

**ከፈቶ፤** (ዐረ) ፤ በቁሙ ፡ ገለጠ ፡ አስጠጋ ፡ ቀደመ ፤ ወገን ።

**ከፋቲ፤** (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤ የሚከፍት ፡ ከፋች ፡ የሚገልጥ ፡ ገላጭ ።

**መክፈት፤** ወገን ፡ ነገድ ። መክፈተ ፡ እንስሳት ፡ መክፈተ ፡ ሰብእ ፡ ውእቱ ፤ ወዘይሜሂ ፡ እመክፈተ ፡ ሰብእ ፡ ነቢያት ፡ እሙንቱ ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፫) ።

**ኬፌቱሔን፤** (ዕብ ፡ ክፈትሔሄን) ፤ ክ ፡ ከመ ፤ ፌታሕ ፡ ሞኀት ፤ ሄን ፡ ሆን ፤ በተገናኝ ፡ ከመ ፡ ኅዋኅዊሆን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ሕዝ፴፱ ፡ ፲፭) ። ኤፍታሔና ፡ ፈትሐን ፡ ተመልከት ።

**ከራ፤—ኰሬ ፡ አንበ፤—ከዊር ፡ ከረ ።**

**ከር፤—በቁሙ ፡ ከርቻ፤—ከዊር ፡ ከረ ።**

**ኰር፤** (ዕብ ፡ ኮር) ፤ የመስፈሪያ ፡ ስም ፤ ሐሜር ፤ በሥረ ፡ ፈጅ ፡ ፲ ፡ ግንበ ፡ ዘይት ፡ ወይም ፡ ፲ ፡ ቍና ፡ በንዶ ፡ የሚይዝ ። ኰርና ፡ ሐሜር ፡ አ ፡ ስም ፡ ነው ፡ (ሕዝ፵፭ ፡ ፲፬) ።

**ኰርአ፤—መቻ፤ ኰራ፤—ኰርዐ ።**

**ከረበ፤** (ከሪም ፡ ከረመ) ፤ በቁሙ ፡ ሰበሰበ ፡ ተሸከመ ፡ የሳንሳ ፡ ያዘ ፤ የወይን ፡ የበለስ ፤ የሬሳ ፡ የጡርብ ፡ የከባድ ፡ ነገር ፤ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ሰቀለ ፡ ይሉታል ። ከረመን ፡ እይ ፤ በ ፡ የመ ፡ ለውጥ ፡ ነው ፤ ከተበ ፡ ብሎ ፡ ከተመ ፡ እንዲል ፡ ይኸም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

**ከርቤ፤** (ዕብ ፡ ሞር ። ዐረ ፡ ሙር ። ሱር ፡ ሚራእ) ፤ በቁሙ ፤ ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ ስንፊጥ ፡ ደም ፤ ወተት ፡ ሲደርቅ ፡ እንደ ፡ ሙጫ ፡ የሚለቀም ፤ ወይም ፡ በርጥቡ ፡ እንደ ፡ ቅንጭብና ፡ እንደ ፡ ቍልቋል ፡ ደም ፡ የሚቀዳ ፡ ሽታው ፡ ጥሩጥ ፡ ጣዕሙ ፡ መራራ ። መፈርን ፡ እይ ፡ (መዝ ፡ ፵፬ ። ማሕ ፡ ፩ ። ፫ ፡ ፭ ፡ ፮ ። ማቴ፪ ፡ ፲፩ ። ማር፲፭ ፡ ፳፫) ።

**ከረበ፤** ታናሽ ፡ ቅርጫት ፡ የወይን ፡ የበለስ ፡ መልቀሚያ ። ታላቅም ፡ ይኸናል ፡ ቀርጣለምስን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አ ፡ ነው ። ከረቦ ፡ ወይን ፡ ከመ ፡ ይምላእ ፡ ቦቱ ፡ ማየ ። ሚጥ ፡ እዴከ ፡ ከመ ፡ ዘይቀሥም ፡ ውስተ ፡ ከረቦ ፡ (ስንክ ፡ ታኅሣ ፡ ኤር፮ ፡ ፱) ።



ከረብ ።

**ኪሩብ፤** (ጽር ፡ ኼሩብ ። ዕብ ፡ ክሩብ) ፤ መልአክ ፤ የመልአክ ፡ ስም ፡ ሥዕሉ ፡ ምስሉ ፡ ነገዱ ፤ ፱ ፡ ፬ ፡ ገጽ ፡ ክንፋቸው ፡ ከራቱ ፡ አወርት ፡ መንበር ፡ አንዱ ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፲፱ ። ፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፳፫ ። ሕዝ፱ ፡ ፫ ። ፲ ፡ ፳ ፡ ፲፬) ። ፍችው ፡ ተሸካሚነት ፡ ነው ፤ መሲሑንን ፡ እይ ። በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ከሩብ ፡ ከሩቢት ፤ ጕመን ፡ የጕመን ፡ አበባ ፡ መልፉፍ ፡ ኰርንባ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አይደርቂ ፡ አባጀኸኝ ፡ እንደ ፡ ማለት ። በዚህ ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ንዊን ፡ ክንፍ ፡ ጽፉቀ ፡ አክናፍ ፡ ያሰኛል ፡ (ሬእ፬ ፡ ፰) ።

**ኪሩቤን፤ል ፡ ም፤** (ጽር ፡ ኼሩቢም ። ዕብ ፡ ክሩቢም) ፤ መላእክት ፤ ኪሩቦች ፡ መንበር ፡ ተሸካሞች ፤ በእንስሳት ፡ አምሳል ፡ የሚታዩ ፤ ስመ ፡ ነገድ ። በኪሩቤን ፡ ፈንታ ፡ ኪሩቤል ፡ ኪሩቤም ፡ ይላል ፤ ል ፡ በጣፈና ፡ በመላሽ ፡ ስሕተት ፡ የገባ ፡ ነው ፤ ሱራፌልን ፡ እይ ። ም ፡ የዕብራይስጥና ፡ የትግሬ ፡ ነው ፤ የማእዝ ፡ እይደለም ፤ ሐባቦች ፡ ዳድቃም ፡ እኩያም ፡ እያሉ ፡ እንደ ፡ ዕብራውያን ፡ በም ፡ ያበዛሉ ። ወማእከሎሙ ፡ ኪሩቤን ፡ ዘእሳት ። ይኩና ፡ ኪሩቤን ፡ እንዘ ፡ ይረብባ ፡ ክነፊሆን ። ወአዘዘሙ ፡ ለኪሩቤል ፡ (ሔኖ፲፬ ፡ ፲፩ ። ዘፀ፳፭ ፡ ፳ ። ዘፍ፫ ፡ ፳፬) ።

**ኪሩባዊ፤** የኪሩብ ፤ ወገን ፡ ነገድ ። መልአክ ፡ ኪሩባዊ ። ኪሩባውያን ፡ አፍራስ ። መንበር ፡ ኪሩባዊ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲፫ ። ኅዳ፰ ። ቅዳ) ።

**ኰረበ፤** (ዕብ ፡ ካራብ ፤ ሐራብ ፤ ከረየ ፡ ነሠተ) ፤ ቈፈረ ፡ ዐረሰ ፤ ናደ ፡ አፈረሰ ። ዐበጠ ፡ ተንፋ ፤

ተክረበ ፡ ኰረብታ ፡ ኾነ ። ኰረብታ ፡ ይድ ፡ እንዲሉ ፡ ይዳም ፡ ሲሉ ።

**መነተረቢ** ፤ ማረሻ ፡ ማፍረሻ ፡ ይማ ፡ ደንጐራ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ መጥረቢያ ፡ ይሉታል ።

**ምኵራብ** ፤ (**ብ ፡ ምኵራባት** ፤ **መኳርብት**) ፤ ታላቅ ፡ ሕንጻ ፡ ተራራ ፡ ኰረብታ ፡ የሚያኽል ፡ መስጊድ ፡ ቤት ፡ ጣዖት ፡ የአይሁድ ፡ መቅደስ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ፡ ጉባኤያቸውና ፡ ማኅበራቸው ። **ምኵራበ ፡ አይሁድ ፡ ወአረሚ ። ሐነጸ ፡ ምኵራበ ፡ ዐቢየ ፡ ለዙሉሉ ። ምኵራበ ፡ እማልክት ። ወዐርጉ ፡ ምኵራበ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወዮሐንስ ። ሕዝብ ፡ ለመርዓትከ ፡ ወኀዳጋቲሃ ፡ ለአንተ ፡ ኄሬጋ ፡ ምኵራብ** ፡ (ቀሌ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ መጋቢት ፡ ማብ፫ ፡ ፭ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ። **የዐወይዉ ፡ በምኵራባቲሆሙ ። በመኳርብት ፡ ወበአስኳት** ፡ (ኅሞፀ ፡ ፲ ። ማቴ፳ ፡ ፳ ። ግብ፲፰ ፡ ፳፩) ።



ምኵራብ ፡

**ኵርበት** ፤ (**ታት**) ፤ ወግር ፡ ኰረብታ ፡ ጉብ ፡ ጉብታ ፡ ተራ ፡ ቍሊሊታ ፡ አጸጋ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ (ትግሬኛ ፡ ሉቃ፳፫ ፡ ፴) ።

—፤ ኅዋየ ፡ ጸሎት ፡ ጠፍር ፡ ቈርበት ፡ አይሁድ ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ ከዚያው ፡ ከምኵራቡ ፡ በኛቸውና ፡ በራሳቸው ፡ የሚያስሩት ፡ የሚጠመጥሙት ፡ ምኵራባዊና ፡ ቈርበታዊ ፡ ልብስ ፡ ባገራችንም ፡ ፈላሾች ፡ በጠይቦች ፡ ገዳም ፡ ይገኛል ።

—፤ ታናሽ ፡ የጸሎት ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ልፋፈ ፡ ጽድቅ ፡ ያለ ፡ ኹሉ ። **ይሰፍሑ ፡ ኵርበታቲሆሙ ፡ ወያነውኁ ፡ አዝፋሪሆሙ** ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፭) ።

—፤ የጠንቋዮች ፡ ከታብ ፡ ልቦርቦቤ ፡ ዐይን ፡ ጥላ ፡ መፍትሔ ፡ ሥራይ ፡ መንድግ ፡ መስተፋቅር ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ መግረሬ ፡ ፀር ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ በቈርበት ፡ ተሰፍቶ ፡ ባንገትና ፡ በክንድ ፡ የሚያዝ ። **ቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ገባርያነ ፡ ኵርበት ። ኵርበታተ ፡ ኢታንብር ፡ ውስተ ፡ ሥጋከ ። ዘየአስር ፡ ባዕሊሁ ፡ ኵርበታተ ። ገባርያነ ፡ ኵርበታት** ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ቢሞ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፩ ፡ ፻፺) ።

**ኪ.ሮግልዮን** ፤ (**ጽር ፡ ኺሮግሪሊዮስ**) ፤ ግሔ ፡ ሽኮኮ ፡ አሽኮኮ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሐማማ ፡ ይሉታል ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፭ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፯) ።

**ኮርጐን** ፤ (**ረግን**) ፤ ከበበ ፡ ሰበሰበ ፡ አከማቸ ።


**ኵርጓኔ** ፤ ዙሪያ ፡ ክበብ ፡ ሸንጎ ፡ አደባባይ ። **በኵርጓኔ ፡ ትዕይንት ። አዘዘዎ ፡ ይንበር ፡ በዲዲ ፡ ቅጽር ፡ ወበኵርጓኔ ፡ ንጉሥ ። ሶበ ፡ ትበውእ ፡ ውስተ ፡ ኵርጓኔ** ፡ (ዘፀ፲፯ ፡ ፲፫ ። አፈ ፡ ተ፲፫ ። ፲፰) ።

—፤ ጉባኤ ፡ ማኅበር ፡ ሸንጎኛ ። **አሐዱ ፡ እምውስተ ፡ ኵርጓኔሁ ። በባኺ ፡ ሃይማኖት ፡ ውስተ ፡ ኵርጓኔ** ፡ (አፈ ፡ ተ፱ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፭ ። ደራሲ) ።

**ክርደደ** ፤ (**ገሬድ ፡ ገረደ**) ፤ ክረደደ ፡ ክርዳዳ ፡ ኾነ ፡ ሻከረ ።

**ክርዱድ** ፤ (**ዳን ፡ ዳት ፡ ድድ**) ፤ የከረደደ ፡ የሻከረ ፡ ክርዳዳ ፡ ሸካራ ፡ መጥፎ ። **ክርዱዳን ፡ ልብ ፡ ወክርዱዳን ፡ ኀሊና ፡ ወክርዱዳን ፡ ንባብ ፡ ወክርዱዳን ፡ ትምህርት ፡ እለ ፡ ይትካሐዱ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን** ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ክርዳድ** ፤ በቁሙ ፡ እንክርዳድ ፡ ክፉ ፡ ዐረም ፡ ከስንዴ ፡ ጋራ ፡ የሚበቅል ፤ ፍሬው ፡ ከዳቦ ፡ ከጠላ ፡ ሲገባ ፡ ራስ ፡ የሚያዞር ፡ የሚያንከረድድ ፡ መራራ ፡ ሸካራ ፡ የክፉ ፡ ትምርት ፡ ምሳሌ ። ፴ኛም ፡ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ገሬድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በክርዳድ ፡ ፈንታ ፡ ግርዳድ ፡ ይላል ፡ (ኢዮ፴፩ ፡ ፵ ። ማቴ፲፫ ፡ ፳፭—፴) ። **ክርዳድ ፡ ዘይወዕዮ ፡ በእሳት ። ዴቢ ፡ ሥርናይ ፡ ኢትኅድግ ፡ ለክርዳድ ፡ ይብቍል ። በዘረ ፡ መላኪ ፡ ይምሳኅ ፡ ክርዳደ ፡ እምሰማይ ፡ ወረደ ። ክርዳድ ፡ ወሦክ ። ስቴ ፡ ክርዳድ** ፡ (ቀሌ ። ኪዳ ። ድጓ ። ፊልክ ፡ ፻፶፵፯ ። መጽ ፡ ምስ) ።



ክርዳድ ፡

**ክራድዮን** ፤ ስመ ፡ ዖፍ ፡ ጥሩ ፡ ንጹሕ ፡ መልክ ፡ መልካም ፡ ወፍ ፡ የክርስቶስ ፡ አርኣያ ፡ የሰውነቱ ፡ አምሳል ፡ ፊሳሎግስ ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልከት ። **ሰዘተወልደ ፡ እምድንግል ፡ ምንተ ፡ ንብሎ ፡ ናስተማስሎ ፡ አርዌ ፡ ገዳምኑ ፡ አንበሳ ፡ ወሚመ ፡ ክራድዮን ፡ ዖፍ ፡ ጸዐዳ ፡ ንጉሥ ፡ ይሁዳ ፡ እምዘርዐ ፡ ዳዊት ፡ ዘመጽአ** ፡ (ድጓ) ።

**ክርደል** ፤ (**ሠረ ፡ ኀርደል ። ዕብ ፡ ሐርዳል** ፤ **ሰናፍጭ**) ፤ ዐጭር ፡ ድንክ ፡ ኵርንባጥ ፡ ታናሽ ፡ ዝሬጭ ፡ እጅግ ፡ የተናቀ ፡ ቁመተ ፡ ደሮ ፡ መልክ ፡ ገንጆሮ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ክራድርዮን** ፤ (**ጽር ፡ ኻራድሪዮስ ። ዕብ ፡ አናፋ**) ፤ ታላቅ ፡ አሞራ ፡ አግረ ፡ ሽመላ ፡ የሽመላ ፡ ወገን ፤ ባጥሽ ፡ ወንዝ ፡ የሚገኝ ። ይህ ፡ ደግሞ ፡ የክርስቶስ ፡ ምሳሌ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አንዳንድ ፡ ነርስቲያኖች ፡ ርሱን ፡ ከንልጆቹ ፡ በራሳ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ ከመስቀል ፡ ጋራ ፡ ይሥሉታል ። የሙዳሴ ፡ ማሪያም ፡ ተርጓሞች ፡ ግን ፡ ስሙን ፡ ጻልቃን ፡ ጣልቃን ፡ ይሉታል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ ጻልቃንን ፡ እይ ። **አሮድዮን ፡ ወካራድርዮን** ፡ (ዘሌ

፲፰ ፡ ፲፱) ። ክራድዮንና ፡ ክራድርዮን ፡ ስለ ፡ ተቃረቡ ፡ በካራድርዮን ፡ ፈንታ ፡ ክራድዮን ፡ ይላል ፡ (ዘዳ፲፬ ፡ ፲፰) ።



ክራድርዮን ፡

**ኰሪህ ፤ ሆት ፤ (ኰርሀ ፡ ይኰርህ ፡ ይኵራህ ። ዐረ ፡ ከሪሀ ። ዕብ ፡ ሀክሬሕ) ፤** ማስገደድ ፡ በግድ ፡ መያዝ ፡ ማሠራት ፡ አስሙድና ፡ አስፈቃድ ፡ ማኖር ። ትኰርህዎ ፡ ለኲዳይ ፡ (ሔኖ፶፩ ፡ ፯) ።

**ኵርህ ፤** ግድ ፡ ግዲታ ፡ ፈቃድና ፡ ዐሺታ ፡ የሌለበት ፡ (፩ጴ.ጥ ፡ ፭ ፡ ፪ ። ፊ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፫) ። ሐመ ፡ በፈቃዱ ፡ ወአኮ ፡ በኵርህ ፡ (አፈ ፡ ድ፴፫) ።

**ከረዘ ፤ (ዐረብ ። ዕብ ፡ ካራዝ ። ሱር ፡ ክራዝ) ፤** ዐወጀ ፡ ጨኸ ፡ ሰበከ ፡ አስተማረ ። ሾመ ፡ ቀደሰ ፡ ባረከ ፡ የክህነትና ፡ ደዱል ፡ ቤት ፡ ክሲያን ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ከረዘ ፡ ስቀለ ፤ ክሩዝ ፡ መስቀል ፡ ብለው ፡ ይፈታሉ ፡ ምስክር ፡ የለውም ።

**ክርዝ ፡ ተክረዝ ፤** ስብከት ፡ ዐዋጅ ፤ ሚመት ፡ ቅዳሴ ፡ ቡራኬ ። አንበረ ፡ እዴሁ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዲበ ፡ ርእስ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ወጸለየ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጸሎተ ፡ ተክሪዝ ፡ ዘሢመተ ፡ መጥሮጶሊስ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ብዉሕ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይስፋሕ ፡ እዴሁ ፡ ለተክሪዘ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ (መጽ ፡ ምስ ፡ ገ፺፰ ። ፫፻፶፰) ።

**ኰራዚ ፤ (ዕብ ፡ ኮራዚን) ፤** የከተማ ፡ ስም ፡ በጌንሳሬጥ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ የነበረች ፡ ከተማ ፡ (ማቴ፲፩ ፡ ፳፩ ። ሉቃ፲ ፡ ፲፫) ።

**ከርይ ፤ ዮት ፤ (ከርየ ፤ ከረየ ፡ ይከሪ ፡ ይክሪ ። ዕብ ፡ ካራህ ፤ ክራእ ። ዐረ ፡ ከራ ፡ ክረ) ፤** መቈፈር ፡ መማስ ፡ መስርሰር ፡ መፈልፈል ፤ መብሳት ፡ መንደል ። ከረየ ፡ ዐዘቅተ ። ዘይከሪ ፡ ግበ ። ይቤሰዩ ፡ ክሪ ፡ አረፍተ ፡ ወከረይኩ ። እስ ፡ ይከርዩ ፡ አብያተ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱ ። ምሳ፳፮ ፡ ፳፯ ። ሕዝ፰ ፡ ፰ ። ፊ ፡ መ ፡ ፲፭ ፡ ፯) ።

—፤ መፈለግ ፡ ማሰብ ፡ መቈስቈስ ፡ መመር ፡ ማመር ፡ የጠብ ። ብእሲ ፡ አብድ ፡ ይከሪ ፡ ለርእሱ ፡ እኩየ ። ብእሲ ፡ መዐትም ፡ ይከሪ ፡ ጋእዘ ፡ (ምሳ፲፮ ፡ ፳፯ ። ፳፱ ። ፳፱) ።

—፤ መክራየት ፡ በቍሮጥ ፡ መማዘት ፡ የቤት ፡ የከብት ። መንፋት ፡ ማቀናጣት ፤ ከመንገድ ፡ ማውጣት ፡ የዋጋብ ፡ የስክር ። (ዘዳ፴፱ ፡ ፲፭) ። በእኪት ፡ ዕለት ፡ ይከሪ ፡ ጽጋብ ። ፊሓል ፡ ኢይክርየኒ ፡ (ሚራ፲፩ ፡ ፳፯ ። ፳፫ ፡ ፮) ።

**ከራዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ረይት) ፤** የሚከራይ ። የሚቈፍር ፡ ቈፋሪ ። ክራይያን ። ክረይተ ፡ መቃብር ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፭ ፡ ፩ ። ሕዝ፴፱ ፡ ፲፭) ።

**መክሪት ፤ (ብ ፡ መከርይ) ፤ አው ፡ መክርይ ፡ (ያት) ፤** መቈፈሪያ ፡ መማሻ ፡ መኳቻ ። ፭ንዘ ፡ መክርየ ፡ በእደዊሁ ። ይክረዩ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ በእት ፡ በመክርይ ፡ ዘወርቅ ። ሶበ ፡ ተኀጥአ ፡ መጥበሕት ፡ ለክሣዶሙ ፡ ይምትሩ ፤ መክርየቲሆሙ ፡ ወሀቡ ፡ ለሐራ ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ፰ ። አዋል ። ስንክ ፡ መስ፲፩) ።



መክርይ ፡

**ክሪም ፤ (ዕብራ) ፤** ክረይት ፡ መክርየት ። የቀጥር ፡ ማፍረሻ ፡ ቀንዳም ፡ ብረት ፡ ባለመዘውር ፡ ባለመንኰራኵር ። ሞማእን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ፡ (ሕዝ፬ ፡ ፪) ።

**አክረየ ፤** (አከራየ) ፡ አስኳተ ፡ አስቈፈረ ። አክረይኩ ፡ ሎቱ ፡ ምክያዶ ። ወደዩ ፡ ሥጋሁ ፡ ውስተ ፡ ገራውህ ፡ ዘአበው ፡ አክረዩ ፡ (ኢ.ሳ፯ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ጥር፳፰) ።

**ተከርየ ፤** ተቈፈረ ፡ ተማሰ ። እስከ ፡ ይትከረይ ፡ ግብ ፡ ለኃጥኣን ፡ (መዝ ፡ ፺፫) ።

**ክሩይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሪት) ፤** የተማሰ ፤ የተቈፈረ ፡ ቍፍር ።

**ክርየት ፤** (መክራየት ፡ ክራይ) ፤ መቈፈር ፤ (ጥቈ) መቈፈር ፡ አቈፋፈር ፡ ቍፈራ ፡ ቍፋሮ ። ወሰአመ ፡ ተረክበ ፡ ሰራቂ ፡ ውስተ ፡ ክርየተ ፡ ቤት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፯ ፡ ፪) ።

**ኪርያ ፤ (ጽር ፡ ኪሪያ) ፤** እግዝእት ፤ እመቤት ፡ ወይዘሮ ።


**ኪርያላይሶን ፤ ኪራላይሶን ፤ (ጽር ፡ ኪሪዬ ፡ ኤሌይሶን) ፤** እግዚኦ ፡ ተሣሀል ። ኪሪዬ ፤ እቤቱ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ። ኤሌይሶን ፤ ይቅር ፡ በል ። ኤሌይሶንሚ ፤ ተሠሀለኒ ። ኢሌይሶን ፡ ኢማስ ፤ ተሠሀለን ። ጌርዮስን ፡ እይ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፬ ፡ ፬ ። ቅዳ ። ግንቦ) ። በኪሪዬ ፡ ፈንታ ፡ ኪርያ ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ኵርያቀ ፤ ኪርያቅ ፡ (ቅብጥ ፡ ኺያክ) ፤** ስመ ፡ ወርኅ ፡ ራብዕ ፡ ታኅሣሥ ። ኪያህክን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ተወልደ ፡ በወርኀ ፡ ጽርእ ፡ ኵርያቆ ። በወርኀ ፡ ፍሥሓ ፡ ኵርያቆ ፡ (ተረ ፡ ቄር ፳፰ ። ደራሲ) ።

**ኰራኪ ፤ (ዐረ ፡ ኩርኪይ ። ሱር ፡ ኩርክያ) ፤** ቍርጫ ፡ ታላቅ ፡ አሞራ ፡ እንደ ፡ ሬዛ ፡ ያለ ፡ ሲሶኽ ፡ ኵር ፡ ኵር ፡ የሚል ፤ በገዞ ፡ ተንጋግቶ ፡ የሚኼድ ። በለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ምሥጥ ፡ ጕንዳን ፡ ይሉታል ። ዘከመ ፡ ንህብ ፡ ወራዛ ፡ ወኰራኪ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፬ ፡ ፬) ።

**ክርክዴን ፤ (ጽር ፡ ክርኪዶኔዮስ) ፤** ቀጥር ፡ ዕንቍ ፡ ክበልማ ። አረፋትኪ ፡ ዘክርክዴን ፡ ወአናቅጽኪ ፡ ዘቢረሌ ፡ (ኢሳ፶፬ ፡ ፲፪ ። ዘዐ፴፯ ፡ ፲፱) ።


—፤ ጥቍር ፡ ሰንጨት ፡ ዘጺ ፡ ወይም ፡ የዘጺ ፡ ዐይነት ። ዘጺንና ፡ አብኖስን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ወገብረ ፡ ኖኅ ፡ መጥቅዐ ፡ እምዕፀው ፡ ክርከዴን ፡ በዘበቱ ፡ ይጠቅዕ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳) ።



ኵራኪ ፡

**ከርከንድ ፤ (ዐረብ ። ዕብ ፡ ከድከድ) ፤** ግዚ ፡ ከማሁ ፡ ከርከዴን ፡ የሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ከርከደናዊ ። ከደዋን ፡ እይ ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፲፮) ።

**ከረከንድ ፤ (ዐማርኛ) ፤** በቁሙ ፡ ባላንድ ፡ ቀንድ ፡ አውሬ ፡ ቀንዱ ፡ እንደ ፡ ቤት ፡ ቀንዳም ፡ በማኽል ፡ ራሱ ፡ የበቀለ ፤ መልኩ ፡ የፈረስ ፡ ቀንዱ ፡ ያውሬሬም ። አውሬሬምም ፡ ስለ ፡ ቀንዱ ፡ አንድነት ፡ ከረከንድ ፡ ይባላል ። ወለኵናትኒ ፡ ገብርዎ ፡ እምነ ፡ ክረከንድ ፡ ዘቀርኑ ፡ መልዕልተ ፡ ድማኁ ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፳፫) ።



ከረከንድ ፡

**ከርከዕ ፤ (ዕብ ፡ ሽቁድ ። ዐረ ፡ ለውዝ) ፤** የተክል ፡ ስንሬሰት ፡ ስም ፤ ለውዝ ፡ ፍሬው ፡ እንደ ፡ ኮክ ፡ ያለ ፡ በጥንታም ፡ አፍአውና ፡ ውስጡ ፡ የሚጥም ። ባለ ብሉዮች ፡ ግን ፡ ሰሚ ፡ ይሉታል ፡ (ዘፍ፵፫ ፡ ፲፩ ። ዘኍ፲፯ ፡ ፰ ። ኤር፩ ፡ ፲፩ ። መክ፲፪ ፡ ፭) ።

—፤ ቀርከሓ ፡ ውስጠ ፡ ከፍት ፡ ወይም ፡ ፍልፍል ፡ ሰንጨት ፡ የቀርከሓ ፡ ዐይነት ። ወግዘፉ ፡ አርባዕቱ ፡ አጻብዕ ፡ ዘከርካዕ ፡ (ኤር፶፪ ፡ ፳፩) ። ዘውእቱ ፡ ከርከዕ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ንቡዝን ፡ እይ ።

**ከርከረ ፤ (ዐረ ። ከሬር ፡ ከረ) ፤** ፈጨ ፡ አዞረ ፡ መጁን ። በቁሙ ፡ ከረከረ ፡ ገዘገዘ ። ወሠረገ ፡ እይ ፡ ኪራ ፡ ከርከሮ ፡ ከርከር ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**መከርክር ፤** ወፍጮ ፡ ከንመጁ ፡ እናትና ፡ ልጁ ። ስነኒ ፡ ሞሠርት ፡ ቦቱ ፡ ወጥረሲሁ ፡ መከርክር ፡ (ምሳ፴፩ ፡ ፴፯) ።

**ኰርኰረ ፤ (ዱ ፡ ቃ ፡ ግ ። ዕብ ፡ ክርኬር) ፤** ዘለለ ፡ ፈነጨ ፡ ዞረ ፡ ዐወደ ፡ በዙሪያ ፡ ኼደ ፡ ዙሪያውን ፡ ዞረ ፡ የበጓል ፡ ዑደት ፡ ሳውድማም ፡ ይኾናል ። በቁሙ ፡ ኰረኰረ ፡ ለማግማቅ ፡ ለማስበርን ፡ ለማስሮጥ ፡ የብብትና ፡ የክበሮ ፡ የፈረስ ፡ የበቅሎ ።


**አንኰርኰረ ፤** ገለበጠ ፡ ፈነቀለ ፡ አገለባበጠ ። ዘያንኰረኵር ፡ እብነ ፡ (ምሳ፳፮ ፡ ፳፯ ። ማቴ፳፯ ፡ ፷ ። ፳፰ ፡ ፪) ።

—፤ ጨቈነ ፡ ዳጠ ፡ ደፈጠጠ ። ናሁ ፡ አነ ፡ አንኰረኵረ ክሙ ፡ ዘከመ ፡ ያንኰረኵር ፡ ሠረገላ ፡ ብርዐ ፡ (ዓሞ፪ ፡ ፲፫) ።

—፤ ተገለበጠ ፡ ተገለባበጠ ፡ ተንከባለለ ፤ ኼደ ፡ ወይም ፡ መጣ ፤ በታውን ፡ ለቀቀ ፡ (ማር፲፮ ፡ ፬ ። ሉቃ፳፬ ፡ ፪) ። አእባን ፡ ክቡራት ፡ ያንኰረኵራ ። ያንኰረኵር ፡ መንኰራኵር ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅት ። አ ፡ እኪት ፡ ፍትወት ፡ እምአይቴ ፡ አንኰርኰርኪ ፡ (ዘካ፱ ፡ ፲፮ ። መክ፲፪ ፡ ፮ ። ሢራ፴፯ ፡ ፫) ።

**ንኩርኳር ፤** መገለባበጥ ፤ ማልብጥብጦሽ ። ዘአዕረገ ፡ ለሔኖክ ፡ በንኵርኳረ ፡ ነፋሳት ። እፎኑ ፡ አርመሙ ፡ ንኩርኳረ ፡ መባርቅት ፡ ወኢያውዐዩከ ፡ (ደራሲ ። ሔኖ፴፱ ፡ ፭ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**መንኰራኵር ፤ (ራት) ፤** በቁሙ ፤ ሠረገላ ፤ የሠረገላ ፡ እግር ፡ ተሽከርካሪው ። ቃለ ፡ መንኰራኵር ። በሠረገላ ፡ ወመንኰራኵር ። መንኰራኵረ ፡ ሠረገላቲሆሙ ፡ (ናሆ፫ ፡ ፪ ። ሕዝ፳፫ ፡ ፳፬ ። ኢሳ፳፰ ፡ ፳፯) ። ሰሙ ፡ ፭ ፡ ሲኾን ፡ ዐይነቱና ፡ ክፍሉ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ያውድማና ፡ የሰልፍ ፡ የሥቃይ ፡ አለ ፤ ያውድማውን ፡ በኬደ ፡ ተራ ፡ እይ ። አስይፍተ ፡ መንገን ፡ በሊኃት ፡ ዘመንኰራኵር ። ሰብዐቱ ፡ ምእት ፡ ወሰማንያ ፡ መንኰራኵራት ፤ የሰልፍ ፡ (ስንክ ፡ መስ፳ ። ታሪ ፡ አክ) ። ወእምዝ ፡ አምጽአ ፡ መኰንን ፡ መንኰራኵራተ ፡ ዘብርት ፡ ወአኬድዎ ፡ ለቅዱስ ። ወደይዎ ፡ ውስተ ፡ መንኰራኵራት ፡ ዘርቡብ ፡ ታሕቴሆን ፡ አፍሓመ ፡ እሳት ። አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይስቅልዎ ፡ ውስተ ፡ መንኰራኵር ፡ ወይኩንንዎ ፡ (ስንክ ፡ የካ፲፫ ። ታኅ፲፪ ። ጥር፭) ።



መንኰራኵር ፡

—፤ መንገድ ፡ ጕዳና ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ የተከከለ ፤ ሠረገላ ፡ የሚኼድበት ። ታረትዐ ፡ መንኰራኵረ ፡ ሠናይት ። መንኰራኵረ ፡ ርትዕ ። ወግበሩ ፡ መንኰራኵረ ፡ ርቱዐ ፡ ለእግሪክሙ ፡ (ምሳ፪ ፡ ፱ ። ፬ ፡ ፲፩ ። ፱ ፡ ፲፪ ። ዕብ፲፪ ፡ ፲፫) ።

**ክሬም ፤ ሞት ፤ (ከረመ ፡ ይክርም ፡ ይክርም ። ዕብ ፡ ከሬም ። ዐረ ፡ ከሩመ) ፤** ወይን ፡ መትከል ፤ የተተከለውን ፡ ማገልገል ። መገዛትም ፡ መፍሰስ ፡ ክረምት ፡ መኾን ፤ የወራት ፡ የጊዜ ። መክረም ፤ ክረምትን ፡ ማለፍ ፡ ማሳለፍ ፤ ብዙ ፡ ዘመን ፡ መኖር ፤ መቈየት ። ወውእቱ ፡ መርሶ ፡ ኢይደሉ ፡ ይክርሙ ፡ ውስቴቱ ፡ ክረምተ ። ሐመር ፡ ዘከረመት ፡ በደሴት ፡ ደሴት ። አጥባዕኩ ፡ እክርም ፡ ህየ ። እመ ፡ ከረመ ፡

ትሰትዩ ፡ በትፍሥሕት ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፲፫ ። ፳፰ ፡ ፲፩ ። ቲቶ፪ ፡ ፲፬ ። ሚራ፱ ፡ ፲) ።

**ክራሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤** በቁሙ ፡ የሚከርም ፡ የከረመ ፡ የኖረ ፡ ያምና ፡ የኻች ፡ ዓምና ፡ የወዲያኛው ፡ የብዙ ፡ ዓመት ። **እክል ፡ ክራሚ ። ኅበ ልዑ ፡ ክራሚ ፡ ወክራሚ ፡ ክራሚ ። ወይን ፡ ክራሚ ፡ ዐርክ ፡ ዘቀዳሚ ። እስመ ፡ በመከራ ፡ ወተድላ ፡ ይፌ ጽምዎ ፡ ለዕድሜ ፡ ዘይስእል ፡ ማየ ፡ ወዘይተርፍ ፡ ክራሚ ፡** (ዘሌ፳፭ ፡ ፳፪ ። ፳፯ ፡ ፲ ። አዋል ። ቅኔ) ።

**ክርም ፤ (ብ ፡ አክራም ። ዐረብ ። ዕብ ፡ ኬሬም) ፤** የወይን ፡ ቦታ ፡ ዐጸደ ፡ ወይን ፡ ሐረግ ፡ ወይን ። **ደወለ ፡ ዐይኑ ፡ ክርም ። አስተጋብኡ ፡ ዕፀወ ፡ ክርም ፡ ወአንድዱ ፡ እሳተ ፡** (ሉቃ ፡ ፳ ፡ ፱፱ ። ስንክ ፡ ንሐ፲ ። ሐምሻ) ። ዐይኑ ፡ ክርም ፡ ትርጓሜ ፡ አብነት ፡ ነው ፡ ከማእዝ ፡ በቀር ፡ በጽርእና ፡ በረብ ፡ አይገኝም ።

**ክረምት ፤ ክረም ፤ (ብ ፡ ክራማት) ፤** በቁም ፡ ዝናም ፡ የዝናም ፡ ወራት ፡ በጸደይና ፡ በመፀው ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ክፍለ ፡ ዓመት ፡ ከሠኔ ፡ ፳፭ ፡ እስከ ፡ መስከረም ፡ ፳፭ ። **ያስተዴሉ ፡ ክረምተ ፡ ለምድር ፡ ዘያበቍል ፡ ማዕረ ፡ ውስተ ፡ አድባር ። ቀስተ ፡ ደመና ፡ ዘክረምት ። ዝናመ ፡ ክረምት ። በክረምት ፡ ወበሐጋይ ። ክረምት ፡ ወመፀው ፡** (ድጓ ። ቅዳ ፡ ማሪ ። ኢዮ፴፯ ፡ ፳ ። ዘካ፲፬ ፡ ፰ ። ኩፋ ፡ ፬) ። በክረምት ፡ ፈንታ ፡ አክራም ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ከንትሮስን ፡ እይ ።

—፤ ዓመት ፡ ዘመን ፡ ዕድሜ ። **ዕጕልት ፡ እንተ ፡ ሠለስቱ ፡ ክረምታ ። ወየአክል ፡ ሠላሳ ፡ ክረምቱ ። በሠላሳ ፡ ክረምት ። ዘአብዝኖ ፡ ክራማተ ። ለብዓ ፡ ክራማት ፡** (ኢሳ፲፭ ፡ ፭ ። ሉቃ፪ ፡ ፴፪ ። ቅዳ ፡ ዲዮ ። ኢዮ ፴፪ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፺፱) ። በክራማት ፡ ፈንታ ፡ አክራም ፡ ይላል ፡ የክረምና ፡ የክርም ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ (ስንክ ፡ መስ፳ ። ጥር፳ ። አርጋ ፡ ፳) ።

**አክረመ ፤** አዘነመ ፤ አክረመ ፡ አኖረ ። **ያክርም ፡ በበ ፡ ዓመት ፡** (ማቴ፲፱ ፡ ፲፯) ። አክርማ ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ እርጋኑን ፡ እይ ።

**ምክራም ፤** መክረሚያ ፡ ማክረሚያ ፡ የክረምት ፡ ቦታ ፡ ሙቀት ፡ ያለው ፡ ቈላ ፡ የምድር ፡ ቤት ። **ቤተ ፡ ምክራም ፡ ወቤተ ፡ ሐጋይ ። ወንጕሥ ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ምክራም ። ወኀብሩ ፡ ህየ ፡ ምክራመ ፡** (ዓሞ፫ ፡ ፲፭ ። ኤር፴፮ ፡ ፳፪ ። ታሪ ፡ ነገ) ።

**መስከረም ፤ (መስ ፡ ክረም ። መዝከ ረም) ፤** በቁሙ ፡ ስመ ፡ ወርኅ ፡ ቀዳማይ ፡ የወርኅ ፡ ያመት ፡ መዠመሪያ ፡ በግብጽና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቍጥር ። ጥንትም ፡ ከሥጋዌ ፡ በፊት ፡ ለዓለም ፡ ኹሉ ፡ መዠመሪያ ፡ ወር ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ በአይሁድ ፡ በውዳሜት ፡ በበዓለ ፡ መጥቅ ፡ ይታወቃል ፤ አታንምንን ፡ እይ ። መስከረም ፡ መጥቶ ፡ በክረም ፡ ላይ ፡ ወድቋል ፡ ስለዚህ ፡ መስየ ፡ ክረምት ፡ ምሴተ ፡ ክረምት ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ፡ ምስጢሩ ፡ ፀአትና ፡ መስስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የክረምት ፡ መግና ፡ መገባቻ ፡ የመፀው ፡ መባቻ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ። በዓመት ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ግን ፡ መቅድሙ ፡ አውራኅ ፡ ርእስ ፡ ክራማት ፡ ያሰኛል ፡ ይኸውም ፡ መንና ፡ ስን ፡ እያ ብቻቸው ፡ ነጣጥሎ ፡ መቅድምና ፡ ርእስ ፡ ብሎ ፡ ነው ። ፀኛም ፡ ገዛና ፡ ስ ፡ በጣሬ ፡ ስሕተት ፡ ይዋረሳሉና ፡ (መሐዘ ፡ ሚዜ ፡ ሚስት ፡ ኀበዘ ፡ ኀበዝ ፡ ኀበስት) ፡ የዘከረ ፡ መስም ፡ መዝከርና ፡ ክረም ፤ ተጋጥመው ፡ መዝከረ ፡ ክረም ፡ በመባል ፡ ፈንታ ፡ እንዱን ፡ ከረ ፡ ጕርደ ፡ መዝከ ረም ፡ መዝከረ ፡ ዓም ፡ እንደ ፡ መባል ፡ ኹሉ ፡ ዝ ፡ ስስ ፡ ተለውጦ ፡ መስከረም ፡ ተብሏል ፡ ያመት ፡ ማስቢያ ፡ መ ታሰቢያ ፡ ወይም ፡ ዐውደ ፡ ዓመት ፡ ማለት ፡ ነው ። **ውእቱ ፡ ርእሰ ፡ ዓመት ፡ ዘግብጽ ፡ ወኢትዮጵያ ። እመ ፡ ዐሡሩ ፡ ለመስከረም ፡** (ስንክ ፡ መስ፳ ፡ ፲) ።

**ክርሚል ፤ (ዕብ ፡ ክርሚል) ፤** ዕርሻ ፡ ወዝርድ ፡ የእክልና ፡ የተክል ፡ ቦታ ፡ ወፍራም ፡ መሬት ፡ ቢያመቱ ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ፡ የማይቋርጥ ። ስመ ፡ ሀገር ፡ በይሁዳ ፡ ክፍል ፡ ያለች ፡ (ኢያ፲፭ ፡ ፶፭) ፡ ወይም ፡ መላ ይቱ ፡ ምድረ ፡ እስራኤል ፡ (ኤር፪ ፡ ፯) ። ባለትኣዎች ፡ ግን ፡ ችፍርግ ፡ ይሉታል ፡ ምስክር ፡ የለውም ። ክና ፡ ቀ ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በከ ፡ ፈንታ ፡ ቀ ፡ ይላልና ፡ ቀ ርሚሎስን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ።

**ኰርናዕ ፤—ክርን ፤—ክረዕ ፡ ክርዐ ።**

**ክሬሥ ፡ ሦት ፤ (ክረሠ ፡ ይክርሥ ፡ ይክ ርሥ) ፤** መክተት ፡ ማጣበት ፡ ማኖር ፡ ማስቀመጥ ፡ ቦታ ፡ ማሲያዝ ። ወንበሩን ፡ ኰርሲ ፡ እንዲል ፡ (ዐረብ) ።

**ክርሥ ፤ (ሣት ። ዕብ ፡ ክሬሽ ። ሱር ፡ ክ ሬስ ፤ ሆድ ። ዐረ ፡ ኪርሽ ፤ ጨጓራ) ፤** በቁሙ ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ የመብል ፡ ቋት ፡ የምግብ ፡ ስልቻ ፡ የጎዋ ያት ፡ ውስጥ ፡ መዝጊብ ፡ መክተቻ ። **ጸሎ ፡ እክል ፡ ይት ባዕ ፡ ወይወርድ ፡ ውስተ ፡ ክርሥ ። መብልዕኒ ፡ ለክ ርሥ ፡ ወክርሥኒ ፡ ለመብልዕ ፡** (ሚራ፴፯ ፡ ፳፪ ። ፩ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፫) ። ክርሠ ፡ ታቦት ፡ ክርሠ ፡ ምሥዋዕ ፡ ክርሠ ፡ ሐመር ፡ ቢል ፡ ውስጥ ፡ ማለት ፡ ነው ። ማሕፀን ፡ ሰፋድል ፡ የዕንስ ፡ የሽል ፡ ቦታ ። **ክርሠ ፡ እም ። ፍሬ ፡ ክርሥ ። ብ ፁዓት ፡ ክርሣት ፡ እለ ፡ ጸረሃምዎ ፡** (መክ፭ ፡ ፲፭ ። ኩፋ ፡ ፳፫ ። ስንክ ፡ ጥር፲) ።

—፤ ሰውነት ፡ ነፍስ ፡ ውሳጣዊ ፡ ሕዋስ ፡ አንዠት ። **መንፈስ ፡ ርቱዐ ፡ ሐድስ ፡ ውስተ ፡ ክርሥየ ። ክርሥየኒ ፡ ተ ሀውከት ፡ ላቲ ፡ ወንሥሥታ ። ክርሥየ ፡ ክርሥየ ፡ ወ ሥርወ ፡ ልብየ ፡** (መዝ ፡ ፶ ። ሚራ፶፩ ፡ ፳፩ ። ኤር፬ ፡ ፲፱) ። ቀርብንና ፡ ውስጥን ፡ ተመልከት ።

**ክሬዕ ፤ ዖት ፤ (ክርዐ ፡ ይክርዕ ፡ ይክራዕ ። ዕብ ፡ ካራዕ) ፤** መስገድ ፡ መንበርከክ ፡ ጕልበትን ፡ ማ ጠፍ ።

**ክርዕ ፤ ክርዓ ፡ (ብ ፡ ክራዕ ፡ ክርዓት ። ዕብ ፡ ኬሬዕ ። ሱር ፡ ክርዓ ። ዐረ ፡ ኩራዕ) ፤** ጕልበት ፡ የእግር ፡ ማጠፊያ ፡ መታጠፊያ ፡ ከጕልበት ፡ እስከ ፡ ቍርጭምጭሚት ፡ ያለው ፡ ክፍል ።

**ክርናዕ፤ ኵርናዕ፡ (ዓት)፤** ክርን፡ የእጅ፡ ጕልበት፡ ማጠፊያው፡ ሹሉ፡ ወይም፡ መካከሉ፡ ከክርን፡ እስከ፡ መዳፍ፡ ባንድነት። ኵርናዐ፡ እዴ። ውስተ፡ ኵርናዓቲሃ፡ (ሕዝ፲፫፡ ፲፰። ስንክ፡ መጋ፳)። በመንጋጋ፡ ፈንታ፡ ጥረስ፡ እንደ፡ ማለት፡ ኵርናዓት፡ ይላል፡ የመላሽ፡ ስሕተት፡ ነው፡ (ዮኢ፩፡ ፮)።

**ኰርዐ፤ (ቀርዐ)፤** መታ፡ ቈረመ፡ ክረና፡ ኰረኰመ፡ ደበቀ፡ ጐሰመ፡ የዘንግና፡ የክርን፡ የኵርኵም፡ የቡጢ፡ የጡጫ፡ አመታት። የክርንም፡ እንዳ፡ ቀላል፡ ውስጠ፡ ክፉት፡ ስለ፡ ኾነ፡ በሰብራይስጥ፡ ቃኔ፡ ይባላል፡ ጎሰት፡ ማለት፡ ነው። እሰ፡ ይኴርዕዎሙ፡ ለዕቡራት፡ ወለዕጓለ፡ ማውታ። ይኰርዑ፡ አርእስተ፡ ነዳያን። ወይኴርዕዎ፡ ርእሶ፡ በኀሰት፡ (ሚል፫፡ ፭። ዓሞ፪፡ ፯። ማቴ፳፯፡ ፴)።

**ኰርዐ፤** በቀለው፡ ኰራ፡ ታበየ፡ ተቈነነ፡ ተኅደደ። (ተረት)፡ ባሬያ፡ ቢኰራ፡ መድኀኒቱ፡ ዱላ። ለቤትም፡ ጣራ፡ ሰባጥ፡ ለመሞቅር፡ ይነገራል። (ግጥም፡ በቴዎ፡ ጊዜ፡ ኀይለ፡ መለኮት፡ ራስ፡ ዐሊን፡ ከደፈሙ፡ ባላበት፡ ከጥቂ፡ ዳበ፡ እጅ፡ ስላወጡቸው)፡ ኰፎቶ፡ የነበረው፡ የንጥቂ፡ ጣራ፡ ኀይሉ፡ ቢወጣበት፡ ለመጥ፡ አላ፡ ደራ።

**ተኰርዐ፤** ተመታ፡ ተቈረመ። ወንትኰራዕ። በበትረ፡ ኀሰት፡ ተኰራዕከ፡ (፩ቆሮ፡ ፬፡ ፲፩። ቅዳ፡ ደሰ)።

**ኵሩዕ፤ (ዓን፡ ዓት፡ ርዕት)፤** የኰራ፡ ኵሩ፡ ትቢተኛ። በቡጢ፡ በኵርኵም፡ የተመታ። ቅንወ፡ አእዳው፡ ወእግር፡ ስቁለ፡ አይሁድ፡ ክርስቶስ፡ ርጉዘ፡ ገቦ፡ ወኵሩዐ፡ ርእስ፡ (ደራሲ)።

**ኵርዐት፤** በቀለው፡ መኵራት፡ መታበይ፡ መቈነን፡ ኵራት፡ ትዕቢት። ኵርዐቶሙ፡ ለደቂቀ፡ ዓምን፡ (ዮሮ፪፡ ፳)።

—፤ መኰራት፡ ራስን፡ መመታት። (ግጥም)፡ የየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ኵርዐቱ፡ ባቱ፡ ነወይ፡ በናቱ፡ በናቱ፡ ነው፡ እንጂ፡ ክብነቱ፡ በቀር፡ ምን፡ አለው፡ ባቱ። ዘመልታሕተከ፡ ጽፍዐተ፡ ወዘርእስከ፡ ኵርዐተ፡ (ስንክ፡ ታኅ፳፯)።

**ኽረጺት፤ (ዐረ፡ ኍርጽ)፤** ክረጢት፡ ኪስ፡ ቍናማት፡ የገንዘብ፡ መያዣ። አምሳለ፡ ኽረጺት፡ (ፈመ፡ ፻፭፡ ፳)። ሥሩና፡ ምንጩ፡ ሐረጸ፡ ነው፡ ምስጢሩም፡ ክፍሉን፡ ክፍልነትን፡ ያሳያል፡ ሐረጽን፡ እዩ።

**ክረር፤ ሮት፤ (ክረ፤ ክረረ፡ ይክርር፡ ይክርር)፤** መክረር፡ መድረቅ፡ ክፉፉ፡ ደረቅ፡ መኾን፡ በድንገት፡ መሞት። ክር፡ ክሩር፡ ማለት፡ ክርክረም፡ ሳይቀር፡ የዚህ፡ ክር፡ ነው።

**አክረረ፤** አክረረ፡ አስከረረ፡ አደረቀ፡ በድንገት፡ ገደለ። (ግጥም፡ ድኅ፡ ገበሬ፡ በሬብ፡ ዐሊ፡ ጊዜ)፡ ዐርሼ፡ በበላኹ፡ በቀንኛ፡ በሬዬ፡ የዘንድሮን፡ ዐሊ፡ አክርሞት፡ ጌታዬ። ኦ፡ ሞት፡ እግዚእየ፡ አክርር፡ ለዐሊ፡ ማለት፡ ነው።

**ክሬር፤ (ዕብ፡ አፊቅ)፤** የወንዝ፡ ውሃ፡ ፈሳሽ፡ የፈሳሹ፡ ቦታ፡ ድንጊያው፡ አለቱ፡ አሸዋው፡ ኰረቱ፡ ውሃ፡ የሚመታው፡ በላዩ፡ የሚኼድበት፡ ፈሳሹ፡ ባሕሩ፡ ወይም፡ ጕርፉ፡ ያለበስውና፡ የሸፈነው፡ ታችኛው፡ ውስጡ። ክሬሬ፡ ደረቅ፡ ኀቋጽ፡ ይቡስ፡ ከውሃ፡ ጋር፡ ሲኖር፡ የማይርስ፡ የማይለስልስ፡ ማለት፡ ነው። ክሬር፡ ከኸሬ፡ አፊቅም፡ ክሬቀን፡ ይስማማል፡ ከወረንና፡ ኮሬን፡ እዩ። ለክሬር፡ ወለቈላት፡ (ሕዝ፫፡ ፮። ፴፮፡ ፬፡ ፮)። ክሬር፡ ባሰው፡ ደግሞ፡ አናሳግ፡ አንቅዕት፡ ይላል።

**ክርስ፤—ሆድ፡ ውስጥ፤—ክርሥ።**

**ኪራስ፤ (ጽር፡ ኽሬሲሚ)፤** ወርቅ። ኪራስ፡ ትዕሬን። ትዕሬን፡ ኪራስ፡ የወርቅ፡ ቀለበት፡ ሸልማትና፡ ጌጥ፡ ባለዕንቍ፡ ፈርጥ፡ (ስንክ፡ የካ፱)።

**ኰራሲ፤ (ጽር፡ ኽርሲት። ዕብ፡ ሐርሲት)፤** ሸክላ፡ የሸክላ፡ ዕቃ፡ ወይም፡ ያልተሠራው፡ ዐፈር፡ መሬት፡ ጭቃ፡ የገል፡ ስባሪ፡ ደቂት። እንቀጸ፡ ኰራሲ፡ (ኤር፲፱፡ ፪)።

**ክርሴምቶን፤ (ጽር፡ ኽሪሶሊቶስ)፤** ዕንቍ፡ የዕንቍ፡ ስም፡ (ሕዝ፳፰፡ ፲፫)። ክርሴምቶን፡ ባሰው፡ ክርስቲሎቤ፡ ይላል፡ በጽርእ፡ ኹለቱም፡ ፩፡ ነው፡ ኽሪሶሊቶስ፡ ይባላል፡ ይኸውም፡ ቶርቤስ፡ ነው፡ ሕብሩም፡ ሕብረ፡ ማይ። የማእዝ፡ መላኽ፡ ማን፡ ፪፡ አድርጎታል።

**ክርስቲሎቤ፤** ገዢ፡ ከማሁ፡ ወምስሌሁ፡ አለፉ። ማርያም፡ ዕንቍየ፡ ክርስቲሎቤ፡ (ደራሲ። ራእ፳፩፡ ፳። ስንክ፡ ማን፳)።

**ክርስቶስ፤ (ጽር፡ ኽሪስቶስ)፤** የሹመት፡ ስም፡ የተቀባ፡ ቅቡዕ። እንደ፡ አሮንና፡ እንደ፡ ዳዊት፡ ተመርጦ፡ ተቀብቶ፡ የተሾመና፡ የነገሠ። መቀባትም፡ ለሦስት፡ ሹመት፡ ነው፡ ክህነትና፡ ንጉሥ፡ ነቢይ፡ ለመኾን። ኢሲህን፡ ሦስቱን፡ የሚሾም፡ ሰው፡ መዠመሪያ፡ ከሕዝብ፡ ይመረጣል፡ ፪ኛ፡ ከካህን፡ ከነቢይ፡ በተቀደሰ፡ ዘይት፡ ይቀባል፡ በተቀባም፡ ጊዜ፡ የሹመቱን፡ ሥራ፡ የሚያስፈጽም፡ ሀብት፡ ሥልጣንና፡ ችሎት፡ ያድርበታል፡ ይህ፡ ለኹሉ፡ ነው፡ (ዘፀ፳፱፡ ፯። ዘሌ፬፡ ፫። ፩ነገ፡ ፲፮፡ ፲፭—፲፫። ፫ነገ፡ ፩፡ ፴፱)። ለጌታችን፡ ለመድኀኒታችን፡ ለሥጋው፡ ቃል፡ ግን፡ ቀቢውና፡ ሹሚው፡ ፈጣሪ፡ እንጂ፡ ምድራዊ፡ ፍጡር፡ ስላልኾነ፡ ግዘፍ፡ ቅባት፡ የለውምና፡ በዘይቱ፡ ፈንታ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ቀብቶ፡ ይባልለታል። ኢየሱስ፡ ዘእምናዝሬት፡ ዘቀብዖ፡ እግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ወኀይለ፡ (ግብ፲፡ ፴፰)። ከሕዝብ፡ እንደ፡ መመረጥ፡ የኛን፡ ባሕርይ፡ ነሥቶ፡ ናሁ፡ ቍልዔየ፡ ዘኀረይኩ። ወአልዐልኩ፡ ኀሩይየ፡ እምሕዝብየ፡ መባል፡ ነው፡ (ኢሳ፵፪፡ ፩። መዝ፹፰፡ ፲፱)። ተቀብቶ፡ እንደ፡ መሾም፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ተቀብሎ፡ ካህን፡ ንጉሥ፡ ነቢይ፡ ሐዋርያ፡ መኾን፡ ክርስቶስ፡ ዳግማይ፡ አዳም፡ ምስኩ፡ ጸጋ፡ ተጸጋዬ፡ ጸጋ፡ በኵረ፡ ልደት፡ በኵሉ፡ ፍጥረት፡ መባል፡ ነው፡ (ኢሳ

፲፭ ፡ ፱) ። የቡስ ፡ ፀማንኤል ፡ በተዋሕዶ ፡ የወጣለት ፡ የተ ጸውዖ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ክርስቶስም ፡ የተቀብዖ ፡ ስም ፡ ነው ። በባሕርዩ ፡ ቅባትና ፡ ኹመት ፡ ፪ኛ ፡ ልደት ፡ የማ ይሻ ፡ ቃል ፤ ዳግመኛ ፡ መወለድ ፡ ስለሚሹ ፡ ስላዳምና ፡ ስለ ፡ ሔዋን ፡ ልጆች ፤ የኆም ፡ ወሰይኩክ ፡ ተብሎ ፡ በኹረ ፡ ልደትና ፡ በኹረ ፡ ስም ፡ ዳግማይ ፡ አዳም ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ያው ፡ ማን ፡ በወልድነቱ ፡ ውሉድ ፡ በቅቡዕነቱ ፡ ቅቡዓን ፡ ክርስቲያን ፡ ለማሰኘት ፤ ሰው ፡ ኹኖ ፡ ቢቀባ ፡ ክርስቶስ ፡ ተብሏል ፡ (ዳን፱ ፡ ፳፭ ። ማቴ፩ ፡ ፲፮) ። ኢይጽሕቅ ፤ ቅብዐተ ፡ በህላዌሁ ፤ አላ ፡ በሥምረቱ ፡ ተሠገዎ ፤ ነሥአ ፡ ቅብዐተ ። እስመ ፡ በዘተሰብአ ፡ ተቀብዐ ፡ (ቄር) ። ወተሰምየ ፤ ክርስቶስሀ ፡ በእንተ ፡ ዘተቀብዐ ፤ ምስ ሌነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ዳዊት ፡ ዘይቤ ፡ በእ ንተ ፡ ክርስቶስ ፤ አፍቀርከ ፡ ጽድቀ ፡ ወፀመፃ ፡ ጸላ እከ ፤ በእንተ ፡ ዝ ፤ ቀብዐከ ፡ እግዚ ፡ አምላክከ ፡ በዘ ይተ ፡ ፍሥሓ ፤ እምዘ፡ሎሙ ፤ እሊኣከ ፤ እለ ፡ እሙ ንቱ ፤ ሱቱፋኒከ ፤ ወለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ (ሃይ ፡ አበ ፡ ቄር) ። ዘይት ፡ ፍሥሓ ፡ ያለውን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ ፡ ተረጕመው ፤ ሀብትነትና ፡ ቅብዐነት ፡ የርሱ ፡ ነውና ። መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ፀሎ ፡ ብለው ፡ ወልድ ፡ ቅ ብዕ ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ማን ፤ የተሰብእንና ፡ የተቀብዖን ፡ ምስጢር ፤ እንዳውጣኪ ፡ ቀላቅለው ፡ ደባልቀው ፤ ክርስ ቶስ ፡ ማለት ፡ ክ፪ ፡ አካል ፡ ፩ ፡ አካል ፤ ክ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ የኾነ ፡ በተዋሕዶ ፡ የከበረ ፡ ዋሕድ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተቀብዖን ፡ ተዋሐደ ፡ እያሉ ፡ አለቋንቋው ፡ አለንባቡ ፤ አለስልቱ ፡ አላገባቡ ፡ ይፈቱታል ፤ ቀብዖንና ፡ ዋሐደን ፡ ተመልከት ። ሥግው ፡ ቃል ፡ በሥግውነቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አልተቀባም ፤ ሀብታተ ፡ መንፈስን ፡ አ ልተመላም ፤ ጸጋ ፡ አልተቀበለም ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕነት ፡ ክህነትና ፡ መንግሥት ፡ አልተሾመም ፤ የሰው ነት ፡ ክብር ፡ አልከበረም ፡ ማለት ፤ ሐሰትነቱ ፡ ለማዩም ፡ ለማይ ፡ ምድሩም ፡ ምድር ፡ አይደል ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያለ ፡ ነውና ፤ እሊህንም ፡ ሰምዐ ፡ ለክርስቶስ ፤ ኢያእ መሩ ፡ ወዘኢይደሉ ፤ ይሜህሩ ። እለሰ ፡ የአምኑ ፡ ር ቱዐ ፤ ይሜህሩ ፡ ከመ ፤ በሥጋሁ ፤ ተቀብዐ ። እስመ ፤ ክርስቶስ ፡ ብሂል ፡ ቅቡዕ ፡ ብሂል ። ወእፎ ፡ ይሰመይ ፤ ክርስቶስ ፤ ዘኢተቀብዐ ፤ ብሎ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ነቅ ፏቸዋል ፡ ሐዋርያውም ፡ ዘልፏቸዋል ፡ (፩ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፳፪) ። በዘብሎይ ፡ በሐዲስ ፡ በሊቃውንት ፡ ዘይት ፡ ዘይትን ፡ ተ ቀባ ፡ እንዳይባል ፡ ኹሉ ፤ ወልድም ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ቅ ብዕ ፡ ኹኖ ፡ ወልድን ፡ ተቀባ ፡ አልተባለምና ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ተዋሕዶን ፡ ኀድረት ፤ ወልድ ፡ ዋሕድን ፡ ኹለት ፡ አስኝቶ ፤ ክርስቶስ ፡ መባልን ፡ ለሥጋ ፡ ብቻ ፡ አከናንቦ ፡ ሰጥቶ ፡ ቃልን ፡ ክር ስቶስ ፡ ከመባል ፡ ከመሲሕነት ፡ ያወጣዋል ። ቅብዕና ፡ ቅ ቡዕ ፡ ኀዳሪና ፡ ማኅደር ፡ ጥሬና ፡ ቅጽል ፡ መንፈስና ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በስምና ፡ በግብር ፡ የተለዩ ፡ ፪ ፡ ፀይነት ፡ ቃሎች ፤ ፪ ፡ ልዩ ፡ አካሎች ፡ ናቸውና ፡ እንኳን ፡ በማእዝ ፡ በማንም ፡ ቋንቋ ፡ አንድ ፡ ሊባሉ ፡ ባንድ ፡ ስም ፡ ሊጠሩ ፡ አይቻልም ፤ አፍንጫ ፡ እንደ ፡ መላስ ፡ ወይም ፡ ባንዲት ፡

ቆብ ፡ ውስጥ ፡ ፪ ፡ ራስ ፡ እንደ ፡ ማግባት ፡ ነው ። ወልድ ፡ በተዋሕዶ ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ፩ ፡ ልጅ ፡ ፍጹም ፡ አምላክና ፡ ፍ ጹም ፡ ሰው ፡ ኹኖ ፤ በቀባዒነት ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፤ በተቀባ ዒነት ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ፩ነት ፡ ስላለው ፡ ቀባዒና ፡ ቅቡዕ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ አይባ ልም ፡ አብ ፡ ቅብዕ ፡ እንዳይባል ።



ክርስቶስ፤

**ክርስቶሳዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ የክርስቶስ ፤ ሕግ ፡ ሥርዐት ፤ ወገን ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ የክርስቶስ ፡ ገንዘብ ፡ ማናቸውም ፡ ኹሉ ። ስብከት ፡ ክ ርስቶሳዊት ። ንጉሣውያን ፤ ወአኮ ፤ ክርስቶሳውያን ፤ (ፊልክ ፡ ፶፩ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ክርስቲያን** ፤ (ናት) ፤ በቁሙ ፤ ጥሙቅ ፡ ቅ ቡዕ ፡ ቅቡዓዊ ፡ መሲሓዊ ። ኣንድም ፡ ስብዙም ፡ ይኾ ናል ፤ እንደ ፡ ሰብእ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ተሰምዩ ፤ አርድእት ፤ ክርስቲያነ ። ወኮኑ ፡ አበዊሁ ፡ ክርስቲያነ ፤ (ግብ፲፩ ፡ ፳፮ ። ስንክ ፡ ነሐ፰) ።

**ቤተ ፡ ክርስቲያን** ፤ (ብ ፡ አብያተ ፡ ክር ስቲያናት) ፤ በቁሙ ፤ ቤተ ፡ ክሲያን ፤ የምእመናን ፡ መሰብሰቢያ ። ቤተ ፡ ክርስቲያንሰ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ፡ ይ እቲ ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፩) ።

—፤ የክርስቶስ ፡ መንጋ ፡ ጉባኤ ፡ ማኅበር ፡ ሕዝበ ፡ ክር ስቲያን ። ክኒሳን ፡ እየ ፤ ክዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። ንግሩ ፤ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ። ሰብዑ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፩ ። ማቴ፲፰ ፡ ፲፯ ። ራእ፩ ፡ ፬) ።

**ክርስቲያናዊ** ፤ (ዊት) ፤ ክርስትና ፡ ያለው ፡ የክርስቲያን ፡ ወገን ። አንሰ ፡ አረማዊ ፤ እንዘ ፡ ክርስቲ ያናዊ ፡ በስም ። ብእሲት ፤ ክርስቲያናዊት ፤ (ቅኔ ። ስ ንክ ፡ መጋ፲፱) ።

**ክርስቱን** ፤ የክረስተን ፤ ክርስቲያን ፡ የኾነ ፡ ጥ ሙቅ ። ዘይሜህር ፡ አሐደ ፤ ገጸ ፤ ኢጥሙቅ ፤ ወኢቅ ቡዐ ፤ ወኢክርስቱን ፡ ውእቱ ፤ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ክርስትና** ፤ በቁሙ ፤ ክርስቲያንነት ። ዘተሐ በየ ፤ ውሉዶን ፤ በክርስትና ። ወአጥመቅዎ ፤ ጥም ቀተ ፤ ክርስትና ። ክሕደ ፤ ክርስትናሁ ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፰ ። ጥር፯) ።

**ክርስጵራስስ** ፤ (ጵር ፡ ኽሪሶፕራሶስ) ፤ የሰንቀጦ ፡ ስም ፤ ቅጠልማ ፡ ሰንቀጦ ፡ (ራእ፳፩ ፡ ፳) ።

**ክረተ** ፤ (ቀረፀ ። ዕብ ፡ ካራት) ፤ ቈረጠ ፡ ክ ተከተ ፤ አፈፈ ፡ ቀረጠፈ ። ክክ ፡ ገረደፈ ፤ ክረተፈ ፡ ክርት ፡ ሽርንክት ፡ አደረገ ፡ የደቂት ።

**ክርታስ** ፤ (ሳት ። ጽር ፡ ኻርቲስ) ፤ በቁሙ ፡ ክርት ፡ ክርታ ፤ ወረቀት ፡ የሚጠረጥና ፡ የሚታፈፍ ፤ ቍርጥ ፡ ነገር ፡ የሚጣፍበት ፡ ነደው ፤ ወይም ፡ የተጣፈበት ፡ ወረቀን ፡ እይ ። ንሣእ ፡ ክርታሰ ፡ ወጸሐፍ ፡ ሎቱ ። አምጽእ ፡ ክርታሰ ፡ ወማየ ፡ ሕመት ። ጠማረ ፡ ክርታስ ። እሉ ፡ ክርታሳት ፤ (ቀሌ ። ተረ ፡ ባሮ ። ኢሳ፴ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ ጥር፲፯) ። ተጠውመ ፡ ክመ ፡ ክርታስ ። አብጽሐ ፡ ሰነ ፡ ክርታሰ ፡ መጽሐፍክሙ ። ኢታርእዮሙ ፡ ዘንተ ፡ ክርታሰ ፡ ዘጸሐፍኩ ፡ ለከ ። ወጸሐፉ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ሦለስቱ ፡ ክርታሳት ፡ ንኡሳት ፤ (ፊልጵ ፡ ፲፱ ። ተረ ፡ ቄር፲፭ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ሚያ፫) ።

**ክርተሰ** ፤ ክረተሰ ፡ በክርታስ ፡ ላይ ፡ ጣፈ ፤ ማሰ ፡ መበሰ ፡ ነደፈ ፡ በገረ ፤ አነማ ፡ የመልክ ፡ የጥፊት ። ለከ እኮ ፡ በመልክእ ፡ ጽሕፈት ፡ ወክርተስኮ ፡ በክርታስ ፤ (አሞል) ።

**ኰራፒታ** ፤ (ጽር ፡ ግራፈዳ) ፤ መጣፈያ ፡ ብርዕ ፤ ወይም ፡ ቀለም ፡ መቅቢያ ፡ በማፉ ፡ ጫሬ ፡ ጫረት ፡ ያለው ። ክርታ ፡ ስሌዳ ፡ ብሰውም ፡ የሚፈቱ ፡ እሱ ፤ ስብራይስጡ ፡ ማን ፡ ሻሻር ፡ ይላል ፤ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ማለት ፡ ነው ። አርኣያ ፡ ክሰዳውያን ፡ ሥዑላን ፡ በኰራፒታ ፤ (ሕዝ፳፫ ፡ ፲፱) ።

**ከሲብ** ፤ ቦት ፤ (ከስበ ፡ ይከስብ ፡ ይክሰብ) ፤ መክሰብ ፡ ማትረፍ ፡ ትርፍ ፡ ጥቅም ፡ ማግኘት ፤ በሥራ ፡ (ትግሬ ፡ ወበረብ) ።

**ከሰበ** ፤ (ይክ ፡ ይክስ) ፤ ቈረጠ ፡ ሸለተ ፡ ከረከመ ፤ ገዘረ ፡ ትርፉን ፡ ገላ ፡ የጠጕር ፡ የጥፍር ፡ የዋሻላ ። ትክስቡ ፡ ቍልፈተክሙ ፡ ከሰበ ፡ ሥጋሁ ። ክመ ፡ ይክስቡ ፡ ውሉደሙ ፤ (ኩፋ ፡ ፲፭ ። ፲፮ ። ፳) ።

**አክሰበ** ፤ አስቈረጠ ፡ አስገዘረ ። ለአክስቦ ፤ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተከሰበ** ፤ ተገዘረ ፡ ተከረከመ ። ዘኢተክሰበ ፡ ሥጋ ፡ ነፍስቱ ። ኢኀፈረ ፡ ከሚተ ፡ ዕርቃን ፡ ለተከስቦ ፤ (ኩፋ ፡ ፲፭ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ክሱብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ስብት) ፤ የተገዘረ ፤ ግዙር ። ዘኢኮነ ፡ ክሱበ ፤ (ኩፋ ፡ ፲፭) ።

**ክስበት** ፤ መግዘር ፡ መገዘር ፡ ግዝረት ። ወአልቦ ፡ ክስበተ ፡ መዋዕል ፤ (ኩፋ ፡ ፲፭) ።

**መክሰብ** ፤ ሸንኰፍ ፡ ዋሸላ ፡ ቍልፈት ፡ ክተማ ፡ ንፍስት ፤ በምላጭ ፡ ተቈርጦ ፡ የሚወድቀው ፡ ትርፉ ። ወገዘረ ፡ ሥጋ ፡ መክሰቦሙ ፤ (ኩፋ ፡ ፲፭) ።

**ክሳድ** ፤—ዐንገት ፤—ክሥዶ ፡ ክሡዳ ።

**ኰሲሕ** ፤ ሐት ፤ (ኰስሐ ፡ ይኰስሕ ፡ ይኵሳሕ) ፤ መኰሳት ፡ ማፊት ፡ መቅዘን ። በረዘንና ፡ ዘበለን ፡ እይ ። ፋሲካ ፡ ዘቦቱ ፡ በሲዐየ ፡ እኰስሕ ፡ ወስትይየ ፡ እሠይን ፤ ዳእሙ ፡ እውዕል ፡ ፋሲካ ፡ በማይዩ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ኵስሕ ፡ ወኢሥንት ። ተሀውክ ፡ ክርሁ ፡ ለእርዮስ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ መውፅአ ፡ ኵስሕ ፡ ክመ ፡ ይኵሳሕ ፡ ወወፅአ ፡ አማዑቲሁ ፤ (አዋል ። ስንክ ፡ ነሐ፲፰) ። ከሳ ፡ ኰበስ ፡ ማለት ፡ ፀማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ በኰስሐ ፡ ፈንታ ፡ አኰስሐ ፡ ይላል ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አኰስሐ ፡ እልኩ ፡ አዕዋፍ ፡ ውዑየ ፡ ውስተ ፡ አዕይንትየ ። ክመ ፡ መዝበር ፡ ዘኰሎ ፡ ያኵስሕ ፡ ውስቴቱ ። ነበረ ፡ ክመ ፡ ያኰስሕ ፤ (መቢ፪ ፡ ፲ ። ኤር፲፱ ፡ ፲፫ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ኵስሕ** ፤ በቁሙ ፡ ኵስ ፡ ዐር ፡ ዐይን ፡ ምድር ፤ ፋንድያ ፤ ከሆድ ፡ የሚወጣ ፡ የምግብ ፡ ሐሠር ። ክመ ፡ ይብልዑ ፡ ኵስሖሙ ። ኵስሐ ፡ ርግብ ። ኵስሐ ፡ አፍራስ ፡ ወእንስሳ ፤ (ኢሳ፴፮ ፡ ፲፪ ። ፬ነገ ፡ ፮ ፡ ፳፭ ። ዮሴፍ) ።

**ምኵሳሕ** ፤ መኵሻ ፡ ኵስ ፡ መጣያ ፡ ዐዘቅት ፡ ስዳሪ ። ዐጸደ ፡ ምኵሳሕ ፤ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አኰስሐ** ፤ አስኰሳ ፡ አሳሬ ፡ አስቀዘነ ።

**ከሰየ** ፤ (ዕብ ፡ ኬሳህ) ፤ ሸፈነ ፡ ጋረደ ፡ አለበሰ ።

**መከሴና** ፤ (ዕብ ፡ ምክሴ) ፤ መሸፈኛ ፡ መጋረጃ ፡ ልብስ ። ወገብሩ ፡ ሕዝብ ፡ መከሴና ፡ ለምሥዋዕ ፡ ዘሐነጸ ፤ (ዮሴፍ) ።

**ሜክሱት** ፤ (ዕብ ፡ ምኩሶት) ፤ የተሸፈኑ ፡ የተዘጉ ፡ የተደፈኑ ፡ መስኮቶች ፤ (ሕዝ፵፩ ፡ ፲፯) ።

**ኰሰየ** ፤ (የኰስሐ ፡ መንቲያ) ፤ ኰሸ ፡ ኵሽት ፡ ቃል ፡ አወጣ ፤ ፈጥሮ ፡ አስመስሎ ፡ ተናገረ ፡ የቅኔ ፡ የማጥም ፡ የተረት ፡ የፀዎች ። እገሌ ፡ ኳሽ ፡ ነው ፤ ኵሸት ፡ ቅኔ ፡ እንዲሉ ።

—፤ ሰየ ፡ ነጠለ ፡ ከፋፈለ ፡ አጠፋ ፡ አበላሸ ፡ ነቀፈ ፡ ከደ ። ንከፍሎ ፡ ወንኵስዮ ፡ ለዐማኑኤል ፡ እምህላዌሁ ፡ ዘውእቱ ፡ ሕይወት ። እለሰ ፡ ይብሉ ፡ አኮ ፡ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ሥጋ ፡ ወኢተወልደ ፡ በሥጋ ፡ እምብእሲት ፡ ይኵስይዋ ፡ ለአሚን ። እመሰ ፡ ኰሰይነ ፡ ልደቶ ፡ ዘከማነ ። ኵሰይካ ፡ ለሃይማኖት ፤ (ቄር ፡ እስት ። ጸላ ። ተረ) ።

—፤ ዐበረ ፡ ተባበረ ፡ ተዛመደ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኾነ ፤ በስም ፡ በግብር ፡ በርስት ፡ በነገድ ። ቅኑቡ ፡ ዘይኵስዮ ፤ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ ዘይኵስዮ ፤ (ዘሌ፳፭ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮) ። ኰሰየ ፡ በቢዘወ ፡ ፈንታ ፡ ገብቷል ፤ (ዘይኰስዮ) ፡ የሚቤዠው ፡ ዘመድ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ተኰሰየ** ፤ ተሰየ ፡ ተነጠለ ፡ ጠፋ ፡ ተበላሸ ፡ ተነቀፈ ። እስመ ፡ ኢንትዌከፍ ፡ ዘይክል ፡ ተኰስዮ ። በቍዕ ፡ ወመፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢይትኰሰይ ፤ (ቄር ፡ እስት ። ተረ) ።

**ኵስየት** ፤ መለየት ፡ መከፈል ፡ መከፈል ። ወኵስየት ፡ ዘቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፤ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**መኰስ** ፡ ሲ ፡ ስይ ፤ (ብ ፡ መኰስያት ፤ አው ፡ መኳስይ) ፤ ሞካሽ ፡ የስም ፡ ተባባሪ ፡ ስም ፡

በበር ። ሶፍያ ፡ አንጌቤናይት ፡ እስመ ፡ አ፤ ፡ መዝ ሲሃ ። ዳንኤል ፡ ብፁዕ ፡ መዝሲ ፡ ዳንኤል ፡ ነቢይ ። ወካልእስ ፡ በመዝሴ ፡ ወልድ ፡ ተሰምየ ፡ ወልደ ፡ (ስንክ ፡ መስ፳ ። ታኅ፳ ። ቂር) ።

**መኰሰየ ፤ ተመኰሰየ ፤ (ኰሰየ) ፤** ሞከሸ ፡ ተሞከሸ ፡ ሞከሼ ፡ ኾነ ፡ በስም ፡ ተባበረ ። ተመዘሰዩ ፡ መልክ ፡ ጼዴቅ ፡ ወኢያሱ ፡ ምስለ ፡ ክርስቶስ ፡ በጸዋሪ ፡ ስም ፡ ወአኮ ፡ በአማን ። ሰላም ፡ ለሱስንዮስ ፡ በምግባር ፡ ወተሰምየ ፡ ለዕጓለ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሱሲ ፡ ዘተመዘሰየ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ሐምሸ፩) ።

**አመኰሰየ ፡ (ያመኰሲ ፡ ያመኰሲ) ፤** አሞከሸ ፡ ሞከሼ ፡ አደረገ ።

**ኰስኰሰ ፤ (ዲ.ቃ ፡ ወይም ፡ ተቀ ፡ ግ) ፤** ሻከረ ፡ ኰሰኰሰ ። ዝንጕርጕር ፡ ኾነ ።

**ኰሰኰሰ ፤ (ብ ፡ ኰሳኵስ ፤ ሳን) ፤** ዝንጕርጕር ፡ ጠቃጠቆ ። ዘኵሰኵሲ ፡ ሕብሩ ፡ ወዘኢኮነ ፡ ኵሰኵሰ ። ወበግዕት ፡ ላባ ፡ ይንግል ፡ ዘኢቶአምር ፡ ተውሳከ ፡ ወሲደት ፡ ኵሳኵስ ፡ ሰብአ ፡ ወአምሳክ ። አምሳለ ፡ ወርቅ ፡ ይግበሩ ፡ ለኪ ፡ ኵሳኵስ ፡ ዘብሩር ። አፍራስ ፡ ኵሳኵሳን ፡ (ዘፍ፴ ፡ ፴፱ ፡ ፴፲ ። ቅኔ ። ማሕ፩ ፡ ፲፩ ። ዘካ፩ ፡ ፰) ።

**ኵስኵስት ፤ (ብ ፡ ኰሳኵሳት) ፤** በቁመኑ ፡ ጡታም ፡ መንቀል ፡ ገንቦ ፡ እንስራ ፡ ማድጋ ፡ ዝንጕርጕርነት ፡ ያለው ። ሲያዩት ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ ቀለም ፡ እየቀቡ ፡ ሳይደርቅም ፡ በርጥቡ ፡ ሐረግ ፡ እየጣሉ ፡ ያበጁ ጡታልና ፡ ኵስኵስት ፡ ያሰኘው ፡ ሕብሩ ፡ ነው ። ቀና ፡ ከ ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በቁ ፡ ፈንታ ፡ ኰ ፡ ይላል ፡ የ ጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ ቈሳቍስን ፡ እይ ።



ኵስኵስት ፡

**ኵስኵስ ፤ (ትግ ፡ ሐበ) ፤** ኰሸኰሽ ፡ ያፍንጫ ፡ ዐጥንት ፡ ሹሉ ፡ እንደ ፡ ጡት ፡ ያለው ።

**ከስከሰ ፤ (ዕብ ፡ ኪሽኬሽ) ፤** ከሰከሰ ፡ ሰባበረ ፡ ከፋፈለ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ካሴል ፤ (ዕብ ፡ ኪስሌው ። ጽር ፡ ኻስሌው) ፤** የዕብራውያን ፡ ፱ኛ ፡ ወር ፡ ታኅሣሥ ፡ (ዘካ፯ ፡ ፩) ።


**ኬሴላ ፤ (ዕብ ፡ ክሲል) ፤** ጕብኣን ፡ ከዋክብት ፡ አንድነት ፡ ያላቸው ። ኬሴላ ፡ ባለው ፡ ሰኪላ ፡ ይላል ፡ የተዛወረ ፡ ነው ፡ ሰከለን ፡ እይ ፡ (ዓሞ፭ ፡ ፰) ።

**ኰሰረ ፤ (ዕብ ፡ ካሺር) ፤** አማረ ፡ ተከናወነ ፡ ንጹሕ ፡ ጽሩይ ፡ ኾነ ።

**ኰስተረ ፤ (ስሪ ፡ ግ) ፤** ኰስተረ ፡ ጠረገ ፡ ጥሩ ፡ አደረገ ፡ ሰበሰበ ፡ ሰማረፊያ ፡ ቈረጠ ፡ ቈጠቈጠ ። ኵስተሩ ፡ መካነ ፡ ጎልጎታ ። ቀዲሐ ፡ ማይ ፡ ወኰስትሮ ፡ ሾስሐ ፡ አፍራስ ። አዘዘ ፡ ይኵስትሩ ፡ ዐውደ ፡ ሀገር ። ሾሉ ፡ ዕፀ ፡ ዘያስተሓምመው ፡ ቦቱ ፡ ወይዋሕይዎ ፡ እንዘ ፡ ይኵስትሩ ፡ ዐውደ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲ ። ጥቅ፱ ። የሱፍ ። አፈ ፡ ድ፳) ።

**ኰስታሪ ፤ መኰስትር ፤** የሚጠርግ ፡ የሚያጠራ ፡ ጠራጊ ። ኰስታሪት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (አዋል) ።

**ምኵስታር ፤ (ራት) ፤** መጥረጊያ ፡ መጠራረጊያ ፡ የጕድፍ ፡ መማሪያ ። ወይልሕሱ ፡ ምዝስታረ ፡ ቤት ፡ (አዋል) ።



ምኵስታር ፡

**ተኰስተረ ፤** ተጠረገ ፡ ተጠራረገ ፡ ተቈጠቈጠ ። ቤት ፡ ዘኢተኰስተረ ። እስመ ፡ በቀሓት ፡ ይትኰስተሩ ፡ በእደ ፡ መስተገብራን ፡ (መጽ ፡ ምስ ። አፈ ፡ ድ፲፱) ።

**ኵስቱር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ትርት) ፤** የተጠረገ ፡ ጥርግ ፡ ጥሩ ፡ (ሉቃ፲፩ ፡ ፳፭) ።


**ኵስታር ፡ (ራት) ፤** ጥራጊ ፡ ጕድፍ ። የቤት ፡ ትርኳሽ ፡ ኵስታሪ ።

**ከተበ ፤ (ዐረ ። ሱር ፡ ክታብ ። ዕብ ፡ ክታብ) ፤** በቁሙ ፡ ጣፈ ፡ ጻፈ ። አጋበ ፡ አራከበ ፡ ተባቱን ፡ ከንስት ፡ ደቂቁውን ፡ ከጥዑይ ፡ የተክል ፡ የፈንጣጣ ።

**ክታቢ ፡ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፡ ተብት) ፤** በቁሙ ፡ የሚጥፍ ፡ ጣፊ ። ክታብያን ፡ (ስንክ ፡ የካ፰) ።

**ክታብ ፡ (ባት) ፤** መጽሐፍ ፡ መልእክት ፡ ደብዳቤ ፡ ጦማር ። ትብህለ ፡ በክታብ ፡ ዐረቢ ። ዘየሐውር ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእንበለ ፡ የአዝዞ ፡ ዘይሠይም ፡ በቃሉ ፡ ወበክታቡ ። ጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ ክታበ ፡ በእዴሁ ፡ ከመ ፡ ይትአዘዙ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ መኳንንት ። ክታበ ፡ መልእክት ፡ (አዋል ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ የካ፱ ። መስ፳) ።

—፤ በቁሙ ፡ የጠንቋዮች ፡ ጥፈት ፡ አስጠንቋዮች ፡ የሚያንገቱት ፡ ዐሸን ፡ ክታብ ፡ የደረት ፡ መጠፍ ። (ተረት) ፤ ማተብና ፡ ዐንገት ፡ ክታብና ፡ ደረት ። እሰ ፡ ይጽሕፉ ፡ ክታባተ ፡ በምክንያተ ፡ ፈውስ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፭) ።



ክታብ ፡

**ኩቶሊክ ፡ (ጽር ፡ ካቶሊክ) ፤** የቤተ ፡ ክቢያን ፡ ስም ፡ ኵላዊ ፡ ዘኵሉ ፡ እንተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ።

**ኰቶሊክ**፤ (ጽር ፡ ካቶሊኮስ)፤ ኩቶሊካዊ ፡ የኩቶሊክ ። ሃይማኖት ፡ ኰቶሊካ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሐዋርያዊት ፡፡ ወያክብርዎ ፡ በስም ፡ ፀቢይ ፡ ዘኰቶሊካ ፡ ዘውእቱ ፡ ስመ ፡ ሊቃናት ፡ (አትና ፡ እዋል ። ፍ ፡ ን ፡ ፱) ።

**ከተመ**፤ (ኀተመ ፡ ከተበ)፤ ዘጋ ፡ አሸገ ፡ ዐተመ ፡ እንዳይከፈት ። አመለከተ ፡ ምልክት ፡ ጣለ ፡ አደረገ ፡ በቀለም ፡ በተኰስ ፡ ወይም ፡ በመብጣት ፡ እንደ ፡ ግይንቶች ፡ ተድባበ ፡ ማርያም ፡ ለማለት ፡ ተን ፡ ብቻ ፡ በየቀኝ ፡ ክንዳቸው ፡ ይበጣሉ ፡ (ሉእ፲፫ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯) ። በቁሙ ፡ ከተማ ፡ ሠራ ፡ መዲና ፡ አደረገ ።

**ተከትመ**፤ ተከተበ ፡ ተጠቈረ ፡ ተበጣ ፡ ተተኰሰ ። ዘይትሜሰል ፡ በአርአያ ፡ ዘሊክነ ፡ አርአያሁ ፡ ከመ ፡ ካህን ፡ ዘይትከተም ፡ አው ፡ ዘይለብስ ፡ አልባሰ ፡ ሐራ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፲፱) ።

**ክትመት**፤ ምልክት ፡ መለዮ ። ትሕትና ፡ ውእቱ ፡ ክትመተ ፡ ሐራዊ ፡ ክርስቶስ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፶፱) ።


**ከተማ**፤ (ማት)፤ ሰፈር ፡ ሩብ ፡ ደርቻ ፡ ጽንፍ ፡ መጨረሻ ። ከተማ ፡ ፍኖት ፡፡ ከተማ ፡ ብሔሩ ፡፡ ከተማሁ ፡ ለደብር ፡፡ ጒጠት ፡ ዘሥላስ ፡ ከተማት ፡፡ አዕይንቲሁ ፡ ለእብድ ፡ ውስተ ፡ ከተማ ፡ ምድር ፡ (ዘፍ ፡ ፴፯ ፡ ፲፯ ። ማሕ ፡ ፴፮ ። ዘዐ፲፱ ፡ ፭ ። ፊልክ ፡ ፭ ። ምሳ ፲፯ ፡ ፳፱) ።

—፤ የፍሬ ፡ በኵራት ፡ ቀዳምያት ። ከተማ ፡ ዐውድክ ፡ (ዘፀ፳፱ ፡ ፳፱) ።

—፤ በቁሙ ፡ የንጉሥ ፡ መዲና ፡ መናገሻ ፡ የአህጉር ፡ ራስ ። (ተረት)፤ የድኻ ፡ ልጅ ፡ ባውድማ ፡ የመኰንን ፡ ልጅ ፡ በከተማ ። ሰብእ ፡ ከተማ ፡፡ ወገብሩ ፡ ከተማ ፡ በህየ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ።

**ከተማዊ**፤ የከተማ ፡ የመዲና ፤ ከተሜኛ ።

**ተንከተም**፤ (ታንኳ)፤ መሸጋገሪያ ፡ ድልድይ ፡ በታላቅ ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ የሚጋደም ፡ ሐዲስና ፡ ጣፋ ፡ ከማይ ፡ እስከ ፡ ማይ ፡ የሚገጥም ፡ ዕንጨትና ፡ ብረት ፡ ግንብ ፡ ን ፡ በጀ ፡ ነው ። ወገብረ ፡ ተንከተመ ፡ ዲበ ፡



ተንከተም ፡

ባሕር ፡፡ ተበትከት ፡ ተንከተም ፡ ዘውስተ ፡ ባሕር ፡፡ ማርያም ፡ ተንከተመ ፡ ዘሉ ፡ ለእለታት ፡ (ስንክ ፡ መጋቢት ። ኑሐ፲፱ ። ግንዘ) ።

**ከታን**፤ (ዕብ ፡ ኪታን ። ሱር ፡ ኬታና ። ዐረ ፡ ከታን)፤ ተልባ ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ፈትል ፡ ልብስ ። ለቢሰ ፡ ከታን ፡፡ ልብሰ ፡ ከታን ፡፡ መዋጥሐ ፡ ከታን ፡ (ፈላስ ፡ ገጽ፷ ። አፈ ፡ ተጅ፰ ። ድራሲ) ።

**ከቲፍ**፤ ፎት፤ (ከተፈ ፡ ይከትፍ ፡ ይክትፍ ። ዕብ ፡ ካፋት)፤ ማሰር ፡ ማጣመር ፤ ማስተሳሰፍ ፡ ማቈላለፍ ፤ የእጅና ፡ የጣት ፤ እስራት ፡ ወይም ፡ ያለማሰርት ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ ለግር ፡ ተወርችም ፡ ይኸናል ። በቁሙ ፡ መከተፍ ፡ መከሸን ፡ የሥጋ ፡ የሽንኵርት ። ይኸንኑ ፡ መድረስ ፡ ከተፍ ፡ ማለት ፡ (ዐማርኛ) ። ክልተፈን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ በጐጽ ፡ ነው ።

**ተከትፈ**፤ ታሰረ ፡ ተጣመረ ፡ ተከረከመ ። ተከተፈ ።

**ክቱፍ**፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ትፍት)፤ የታሰረ ፡ እስር ። በሰብለ ፡ ማእሰር ፡ ክቱፍ ፡ (ድራሲ) ።

**ኩትፈት**፤ (ታት)፤ ማሰር ፡ መታሰር ፤ አስተሳሰር ፤ እስራት ። ኩትፈተ ፡ እደዊሁ ፡ ክልኤቱ ፡፡ ውስተ ፡ ኀሳር ፡ ዘኩትፈታተ ፡ መስቀል ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፴፭ ፡ ፭ ። ፊልክ) ።

**መክተፍ**፤ (ትማ ፡ ሐባ)፤ መትከፍ ፡ ትክሻ ፡ ጫንቃ ። መክተፈያ ፤ መክሸኛ ።

**ከተረ**፤ (ቀተረ)፤ በቁሙ ፡ ዘጋ ፡ አቆመ ፡ አገደ ፡ ከለከለ ። ከተረ ፡ መዐተ ፡ (ጥበ፲፰ ፡ ፳፭) ።

—፤ ከበበ ፡ ዐጠረ ፡ ዙሪያውን ፡ ያዘ ። ቀተረን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። (ተረት)፡ ባጠ ፡ ሞት ፡ የተከተረ ፡ በበሉት ፡ የተመተረ ።

**ከታሪ**፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፡ ተርት)፤ በቁሙ ፡ ከባቢ ፡ ወንበዴ ። ኸልተ ፡ ኸተርቲ ፡ (ትግሬኛ ፡ ማቴጅ፳ ፡ ፴፰) ።

**ከታር**፤ ከታሬት፤ (ጽር ፡ ኺታር ፤ ኺታሮት ። ዕብ ፡ ኪቴሬት ፤ ብ ፡ ኪታሮት)፤ የዐምድ ፡ ጒልላት ፡ እንደ ፡ ዘውድ ፡ ያለ ። ባለብሎቹ ፡ ግን ፡ ዋልታ ፡ ገበታ ፡ ይሉታል ፡ (፩ነገ ፡ ፯፳ ፡ ፲፯ ። ፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫) ።

—፤ ኩታሬ ፡ ታናሽ ፡ ልጅ ፡ ከጨዋታና ፡ ከንጀራ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የማይሻ ፡ ሰደታ ፡ የሚያቅፍ ፡ የሚከብ ።

**ከቲት**፤ ቶት፤ (ከተ ፡ ይከትት ፡ ይክትት ። ዕብ ፡ ካት)፤ መክትከት ፡ ማይቀቅ ፡ መውቃት ፡ ማምረት ፡ መሰብሰብ ፡ መክተት ፡ ያዘመራ ። የከቲትን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

# ለ

**ለ፤** ፲፪ኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፡ ስሙ ፡ ለውይ ፡ ላዊ ። ቍጥሩ ፡ ሠላሳ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ (ለ—፴) ሠላሳ ፡ ይባላል ።

**ለ ፡ (ደቂቅ ፡ አገ)፤** በቁም ፡ ቀሪ ፡ የ ፡ ዘርፍ ፡ አያያዥ ፤ የዘርፍ ፡ ደፊ ፤ ተጠቃሽ ፡ ን ፡ ከ ፡ ተ ፡ ወደ ፡ አዳማቂ ፡ ተቀባይ ፤ አቀብሎ ፡ ሸሽ ፤ ላይ ፡ በ ፡ ስለ ፡ በ ፡ ይኾናል ። ልየ ፡ ሊተ ፡ ለከ ፡ ለኪ ፡ ሎ ፡ ሎቱ ፡ ላ ፡ ላቲ ። ለነ ፤ ለክሙ ፡ ለክን ፡ ሎሙ ፡ ሎቶሙ ፡ ሎን ፡ ሎቶን ፡ እያለ ፤ እንደ ፡ በ ፡ ይዘረዘራል ። ለአበዊነ ፡ ለአብርሃም ፡ ወለዘርዑ ፡ በቁም ፡ ቀሪ ። ለእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ በምልአ ፡ የ ። ሐማቱ ፡ ለስምዖን ፡ ዘርፍ ፡ አያያዥ ። ለዮና ፡ ሐመሩ ፡ ለአሮን ፡ በትሩ ፡ ደፊ ። ኅድጋ ፡ ለመዐት ፡ ወግድፋ ፡ ለቍጥዓ ፡ ተጠቃሽ ፡ ን ። ተከፍለ ፡ ለክልኤ ፡ ተሠጠ ፡ ለክልኤ ፡ ከ ፡ ተ ። ሊተ በል ፡ ለየማን ፡ ወሊለፀጋም ፡ ወደ ። ለእመ ፡ ርኅበ ፡ ጸላኢከ ፡ ለኅበ ፡ ለማዮት ፡ አዳማቂ ። ስብሐት ፡ ለእግዚ ። ሽሉ ፡ ለአምላክ ፡ ማሰሪያ ፡ ሰጭ ፤ ወይም ፡ አቀባይ ። ይደሉ ፤ ይትከሀል ፡ አለበት ፤ ምስጢሩ ፡ ከየና ፡ ከበቁም ፡ ቀሪነት ፡ ይገባል ። ለይትጋባእ ፡ ማይ ፡ ለታውፅእ ፡ ባሕር ፡ አቀብሎ ፡ ሸሽ ። የዚህም ፡ ምስጢር ፡ አዳማቂ ፡ ከሰው ፡ ይገባል ። ወአምጽአ ፡ ረኀበ ፡ ለብሔር ፡ በምድር ፡ ላይ ። ኢትጸሊ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ። ለ ፡ ላዕልና ፡ በአንተ ፡ መኾኑ ፡ በመላሾች ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፍችው ፡ "ኹና" ፡ አይደለም ፤ ጽርኡም ፡ ዕብራይስጡም ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ በአንተ ፡ ገ ፡ ሕዝብ ፡ ያሉትን ፡ ለብሔር ፡ ለሕዝብ ፡ እያሉ ፡ አጣገበው ፡ ጥፈውታል ። ነገር ፡ አንቀጽ ፡ ሲኾን ፡ ወሎቱ ፡ ብእሲት ፡ ወውሉድ ፡ እያለ ፡ ይዘረዘራል ፤ ፀ ፡ ፀቱ ፡ ማሰት ፡ ነው ። ሊተ ፡ ለከ ፡ ያለውም ፡ በዚህ ፡ ኹሉ ፡ አፈታት ፡ ይፈታል ፤ ሊተ ፡ ለኔ ፡ የኔ ፡ እኔን ፡ ወደኔ ፤ ልኝ ፡ አለኝ ፡ አለልኝ ፡ ያሰኛል ። ሊተ ፡ ወሀብከኒ ፡ ሊተ ፡ ውእቱ ፡ ስምዑኒ ፡ ሊተ ፡ አምጽኡ ፡ ሊተ ፡ ወይ ፡ ልየ ፡ ለይ ፡ ልየ ፡ ወይ ፡ ሊተ ፡ አሌ ፡ ሊተ ፡ ሊተ ፡ ዐርክ ፡ ምእመን ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ገናም ፡ ለመጺእ ፡ ቢል ፡ ሊመጣ ፡ ያሰኛል ፡ የለ ፡ ስልትና ፡ አፈታት ፡ በመጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ነው ። (ዕር፳፩ ፡ ቍ፲፫ ። ዕር፲፩ ፡ ቍ፲፫) ።

**ልአከ ፤ ከት ፤ (ለአከ ፡ ይልእክ ፡ ይልአክ)።** መላክ ፡ መስደድ ። ደገመ ፡ ልኢከ ፡ ኀቤሁ ። ለአከ ፡ መጻሕፍተ ፡ ወተናብልተ ፡ ወአምኃ ፡ ኀበ ፡ ሕዝቅያስ ። አመ ፡ ለአኩ ፡ ኀቤሁ ፡ አይሁድ ። ለአከ ፡ ወነሥኣ ፡ (፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፳ ። ኢሳ፴፱ ፡ ፩ ። ዮሐ፩ ፡ ፲፱ ። ዘፍ፳ ፡ ፪) ።

**ለአኪ ፤ (ኪት ፡ ክያን ፡ ያት)፤** የሚልክ ፡ ላኪ ፡ ሰዳጅ ።

**ተልእከ ፤** ተላከ ፡ አገለገለ ። ተልኢከሙ ፡ ኀቤሁ ። ተንሥአት ፡ ወተልእከቶሙ ። ወተልእኩ ፡ ውስተ ፡ ይብተራሁ ፡ (ቀኖ ። ማር፩ ፡ ፴፩ ። ሚራ፳፱ ፡ ፩) ።

**ተለአኪ ፤** የሚላክ ፡ ተላኪ ፡ አገልጋይ ። ተለአክያን ፡ ለምሥዋዕ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፳) ።

**ልኡክ ፤ (ካን ፡ ካት ፡ እክት)፤** የተላከ ፡ መልክተኛ ፤ አገልጋይ ። ልኡክ ፡ እግዚእነ ። ግብረ ፡ ልኡካን ፡ (፩ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ግብ ፡ ፩) ።

**ላእክ ፤ (ክት ፡ ካን ፡ ካት)፤** መልክተኛ ፡ አገልጋይ ፡ ሎሌ ። አብድስ ፡ ይሬቢ ፡ ርእሰ ፡ ላእከ ። ላእካነ ፡ እግዚ ፡ (ምሳ፲ ፡ ፱ ። ሮሜ፲፫ ፡ ፬) ።

**ላእክት ፤** ገረድ ፡ ደንገጥር ። ወሀበት ፡ ላእክታ ፡ ለያዕቆብ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፰) ።

**መልእክት ፤ (ታት)፤** በቁሙ ፡ መልክት ፡ ደብዳቤ ፡ ክታብ ። ወበጽሐ ፡ መልእክት ፡ ኀበ ፡ መልአከ ፡ ሰጲራ ። በዘተርፉ ፡ መልእክታቲሁ ፡ (ግብ፳፰ ፡ ፴፩ ። አፈ ፡ ድ፴፱) ።

**መልአክ ፤ (ብ ፡ መላእክት ። ዐረ ፡ መልአክ ። ሱር ፡ ማልአካ ። ዕብ ፡ ማልአኽ)፤** በቁሙ ፡ የማይ ፡ መልክተኛ ፤ ሰማያዊ ፡ ረቂቅ ፡ የእሑድ ፡ ፍጥረት ። ወአስተርአዮ ፡ መልአክ ፡ እምሰማይ ። ፈነወ ፡ መልአኮ ፡ ወአድኀነኒ ። ተሰዓ ፡ ወተስዐቱ ፡ ነገደ ፡ መላእክት ፡ (ሉቃ፳፪ ፡ ፵፫ ። ግብ፲፪ ፡ ፲፩ ። ግንዘ) ።



መልአክ ፡

**—፤** አለቃ ፡ ሹም ፡ አበጋዝ ፡ ተሹሞ ፡ ከንጉሥ ፡ የተላከ ። መልአከ ፡ አሕዛብ ። ወንትልዎ ፡ ለፍጹም ፡ መልአክነ ። መላእክቲ ፡ ረዋጽያን ። ነገሥተ ፡ ምድር ፡ ወመላእክቲሆሙ ። ዘያወፅእ ፡ ነፍሶሙ ፡ ለመላእክት ፡ (ማቴ፳፯ ፡ ፲፩ ። ዕብ፲፪ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፪ ። ፸፭) ። ልኡክና ፡ መልአክ ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ። (ግጥም) ፡ ይድረስ ፡ አይድረስ ፡ ምን ፡ በውቃለኹ ፡ መላኩን ፡ ልኬዋለኹ ።

**መልአከ ፤ አው ፤ ተመልአከ ፤** አለቃ ፡ ኾነ ፡ ተሾመ ። ከመ ፡ ትትመልአክ ፡ ለነ ። ተመልአክ ፡ ለነ ፡ አንተ ። ወተመልአከ ፡ አቤሜሌክ ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ። ተመልአኩ ፡ ካህናት ፡ ላዕለ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ (ዘኍ፲፮ ፡ ፲፫ ። መሳ፰ ፡ ፳፪ ። ፱ ፡ ፳፪ ። ኩብ ፡ ፺፲፯) ።

**አመልአከ ፤** አለቃ ፡ ሾመ ፡ አለቃ ፡ አደረገ ፡ መልአክ ፡ አሰኘ ። መልአከ ፡ ዐሐይ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ መልአከ ፡ ገነት ፡ እንዲሉ ።

**መልአክና ፡ ምልእክና ፤** አለቃነት ፡ መልአክነት ፡ መልአክ ፡ መኾን ፡ መባል ። ኢይወፅእ ፡ ምስፍና ፡ ወምልክና ፡ እምአባቲ ፡ ባለው ፡ ምልእክና ፡ ይባል ፡ (ዘፍ ፵፱ ፡ ፲) ።

**ልሒፍ ፡ ፎት ፤ (ለሐፈ ፡ ይልሕፍ ፡ ይልሐፍ ። ዐረ ፡ ላፈ ፡ ለሐፈ) ፤** መላፍ ፡ መማግ ፡ የሙቅ ፡ ያጥሚት ። መብላት ፡ መዋጥ ፡ መስልቀጥ ፡ የጥሕሎ ፡ የፍትፍት ።

**ላእፍ ፤** ለስላሳ ፡ ምግብ ፡ የላመ ፡ የጣመ ፡ ጥሙኝ ፡ ጥጥሙኝ ፡ የሚል ። ወሰበ ፡ ተፍእማ ፡ ለላእፈ ፡ ትስብእቱ ፡ ረከበ ፡ መቃጥኒ ፡ መለኮት ፡ ዘይሰቍር ፡ አንቀጸ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ። ባለመጣፎች ፡ ግን ፡ ወላፍ ፡ ትል ፡ ይሉታል ።

**ሊባ ፤ (ጽርእ ። ዕብ ፡ ኔጌብ ፤ ዳሮም ። ዐረ ፡ ጅኑብ) ፤** የማእዘን ፡ ስም ፡ ኹለት ፡ ማእዘን ፡ ደቡብ ፡ ከዚያውም ፡ የደቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ በደቡብና ፡ በምሥራቅ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ የባሕር ፡ ትይዩና ፡ አንጻር ። ሰሜን ፡ ወሊባ ፡ ወባሕር ፡ ወጽባሕ ። ውስተ ፡ ሊባ ፡ ወጺራልያ ። ወኮነ ፡ ደወሎሙ ፡ እምነ ፡ ሊባ ፡ እስከ ፡ አሐዱ ፡ ኀብር ፡ (ኩፋ ፡ ፲፰ ። ዘዳግ ፡ ፯ ። ፀ፫ ፡ ፳፫ ። ኢያ ፲፭ ፡ ፪) ። በሊባ ፡ ፈንታ ፡ ሊብስ ፡ ይባል ፡ ደቡባዊ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ለቢብ ፤ ቦት ፤ (ለበ ፡ ይለብብ ፡ ይልብብ) ፤** መለበብ ፡ ልባብ ፡ ማግባት ፡ ሐሰስን ፡ እይ ። መገረም ፡ መፈለመት ፡ ልበ ፡ ቅን ፡ መኾን ፡ እንደ ፡ ተገሬ ፡ ከብት ።


**ልቡብ ፤ (ባን ፤ ቦት ፡ ብብት) ፤** ልበ ፡ ቅን ፡ ገር ፡ ልዝብ ፡ ገራም ፡ ሚዩምት ። ምስሊ ፡ ዖኅ ፡ ልቡብ ፡ ወኀለሙ ፡ የዋሃን ። ወአሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ኮነ ፡ ልቡበ ፡ ፍጹመ ፡ ወየዋሀ ። ወይኤምርዎሙ ፡ ፍኖተ ፡ ለልቡባን ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ ። ፊልክ ፡ ፺፯ ። መዝ ፡ ፳፬) ።

**ልቡባዊ ፤** የልብ ፡ የውስጥ ፡ ውሳጣዊ ። ንጸውዖ ፡ ለእግዚአ ፡ ለረድኤት ፡ በፀውዖት ፡ ልቡባዊ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፲) ።

**ልብብና ፤** ልበ ፡ ቅንነት ፡ ገርነት ፡ ገራምነት ፡ (ፊልክ ፡ ፻፶፱) ።

**ልባብ ፤ (ብ ፡ ልባቢት) ፤** በቁሙ ፡ ፋሎ ፡ ሐሳልን ፡ እይ ፡ (በማርኛ) ።

**ልብ ፤ (ብ ፡ አልባብ ። ዕብ ፡ ሌብ ፤ ሌባብ ። ሱር ፡ ሊባእ ። ዐረ ፡ ሉብ) ፤** በቁሙ ፡ የታወቀ ፡ ሕዋስ ፡ ከንዋያተ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ በሕይው ፡ ፍጥረት ፡ ውስጥ ፡ በየደረቱ ፡ የሚገኝ ፡ የደም ፡ መሰብሰቢያ ፡ ደም ፡ ከርሱ ፡ እየመነጨ ፡ ወደ ፡ ገላ ፡ ኹሉ ፡ የሚፈኝበት ፡ የሚወራጭበት ፡ ውስጥ ፡ ውሳጣዊ ፡ ገላ ፡ የሐሳብ ፡ የፈቃድ ፡ የዕውቀት ፡ ምንጭ ፡ ወይም ፡ ከልብ ፡ የሚወጣ ፡ ሐሳብ ፡ ፈቃድ ፡ ዕውቀት ። ልብ ፡ እንተ ፡ ትወልድ ፡ ኀሊና ፡ እኩየ ። ዘከልኤ ፡ ልቡ ። ወገብአ ፡ ልቡ ። ለምንት ፡ ትኄልዩ ፡ እኩየ ፡ በአልባቢክሙ ፡ (ምሳ ፮ ፡ ፲፰ ። ያዕ ፩ ፡ ፰ ። ሉቃ ፳፬ ፡ ፴፪ ። ማቴ ፱ ፡ ፬) ። ልበ ፡ ምድር ፡ ልበ ፡ ባሕር ፡ ቢል ፡ ውስጥ ፡ ማለት ፡ ነው ።



ልብ ፡

**ልበ ፡ እብን ፤** ጥጉ ፡ ጨካኝ ፡ ፈዛዛ ፡ ድፍን ፡ ደረቅ ፡ (ሕዝ ፲፩ ፡ ፲፱) ።

**ልበ ፡ አንስት ፤** ደካማ ፡ ሕጹጽ ፡ ፈሪ ፡ ብቡ ፡ (አዋል) ።

**ልበ ፡ አርዌ ፤** ቍጡ ፡ ብስጩ ፡ የደመ ፡ ነፍስ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ (ዳን ፬ ፡ ፲፫) ።

**ልበ ፡ ሥጋ ፤** ልሕሉሕ ፡ ርኅሩኅ ፡ ገር ፡ የዋህ ፡ (ሕዝ ፲፩ ፡ ፲፱) ።

**ልበ ፡ ፀበርት ፤ (ዕብ ፡ ሉላብ) ፤** ለጋ ፡ ቀንበጥ ፡ ሙሽራ ፤ ከውስጡ ፡ ከልቡ ፡ የሚወጣ ፡ (ሕዝ ፲፯ ፡ ፳፪) ።

**ልበ ፡ ሰብእ ፤** አስተዋይ ፡ ተመልካች ፡ የነፍስ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ (ዳን ፯ ፡ ፬) ።

**ልብ ፡ ወበልብ ፤ (ዕብ ፡ ብሌብ ፡ ዋሌብ) ፤** በልብ ፡ ወልብ ፤ ፪ ፡ ልብ ፤ ፪ ፡ ሐሳብ ፡ (መዝ ፲፩) ። ልብ ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ እየተናበበ ፡ እንደ ፡ ዘርፉ ፡ ስልት ፡ ይፈታል ፡ ለዳበያም ፡ ሳይቀር ፡ ውስጥ ፡ ላለው ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። (ተረት) ፡ በገዛ ፡ ዳቦዬ ፡ ልብ ፡ ልቡን ፡ ዐጣኹት ።

**ልባዊ ፤ (ዊት) ፤** የልብ ፡ የውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፡ ኅቡእ ። ብፁዕ ፡ ልባዊ ። ስፍጠታት ፡ ሰይጣን ፡ ልባዊት ። ጸሎት ፡ ልባዊት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፪ ። ፊልክ ፡ ፬ ። ፻፳፮) ።

**ለበወ ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ግ ። ለበበ ፤ ወ ፡ የበ ፡ ለውጥ ፡ ነው) ፤** ለበመ ፤ ልባም ፡ ኾነ ። ልብ ፡ አደረገ ፤ አስተዋለ ፡ ዐወቀ ፡ ተረዳ ፡ ጠነቀቀ ። ለበየን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ለቡ ፡ ዘትሬኢ ። ወዘአልቦ ፡ ልብ ፡ ኢይሌብዎ ፡ ለዝንቱ ። ለበውኩ ፡ ዘትቤ ። ንለቡ ፡ ኀቢረ ፡ ዕለተ ፡ ፋሲካ ፡ (ዳን ፱ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፵፩ ። ቄር ፡ ጸላ ። ዲድ ፡ ፴፪) ።

**ለባዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** ልባም ፡ ልብ ፡ አድራጊ ፡ ተመልካች ፡ አስተዋይ ፡ ብልኅ ፡ ዐዋቂ ፡ ጠንቃቃ ። ኵሉ ፡ ለባዊ ፡ ይረክብ ፡ ለጥበብ ። ፍጥረት ፡ ለባዊት ፡ ወሥጋዊት ። ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ለባውያነ ፡ ወንቁሃነ ። መናፍስት ፡ ለባውያት ፡ (ሢራ ፲፰ ፡ ፳፱ ። ግንዘ ። ዮሐፍ ። ጥበ ፯ ፡ ፳፫) ።

**ልብው፤(ዋን፡ዋት፡ቡት)፤** ልበኛ፡ ል ብም፤ ዐዋቂ፡ ልብ፡ ያደረገ፡ ያስተዋለ። ብእሲ፡ ጠቢብ፡ ወልብው። ንጉሥ፡ ልብው። ዘምሩ፡ ልበወ። ምሁራን፡ ወልብዋን፡ (ዘዳግ፡ ፩፥፲፫። ጥበ፡ ፳፯። ፩ዜና፡ ፳፭፡ ፯)።

**ልብውና፤** ልባምነት፡ አስተዋይነት።

**ልባዌ፤** ልብ፡ ማድረግ፤ ማስተዋል። ዕውቀት፡ የልብ፡ እስተያየት። ቅዱሳን፡ ሲበቁ፡ ከሚያገኟቸው፡ ክሥራ፡ ማዕርጋት፡ ንጽሕ፡ አንዱ፡ ልባዌ፡ ይባላል፡ ስማቸውና፡ ተራቸው፡ ቍጥራቸውም፡ ይህ፡ ነው። የን ጽሕ፡ ሦስ፡ መዓርግ፡ ጽማዌ፤ ልባዌ፤ ጣዕመ፡ ገዳም። የንጽሕ፡ ንዑስ፡ መዓርግ፡ አንብዕ፡ ኵነኔ፡ ፍቅር፡ ሑ ሰት። የንጽሐ፡ ልብ፡ መዓርግ፤ ንጻሬ፡ መላእክት፡ ተሰ ጥሞ፡ ከዊን፡ እሳት። ስንዚሁ፡ ደግሞ፡ ብዙ፡ ዘርፎችና፡ ቅጥዮች፡ አሏቸው፡ (አረጋ፡ መንፈሳዊ)። እምእቢሮ፡ ኀበ፡ ልባዌ። በአጽባዕት፡ ጥበብ፡ ወልባዌ። ልባ ዌሁ፡ (ጥበ፡ ጠቢ። ደራሲ። ፍ፡ ነ፡ ማ፲፡ ፭)።

**ለብዎ፤** ገዢ፡ ከማሁ። ለብዎ፡ ወአእምሮ፡ (ምሳ፳፡ ፯)።

**ልቡና፤ (ናት)፤** በቂነው፡ ዕውቀት፡ ሐሳብ፡ ማስተዋል። ልቡና፡ ረሰየተከ፡ መካና። ጸገወነ፡ ጥ በበ፡ ወንይሰ፡ ልበ፡ ወልቡና። ወሀበሙ፡ እግዚ፡ ጥበበ፡ ወአእምሮ፡ ወልቡና፡ በዘ፡ሎ፡ መጽሐፍ። ሊይበጽሕዎ፡ ልቡናት፡ (ድጓ። ቅዳ። ዳንኤ፡ ፲፯። ያዕ፡ ዘእል)። ልብ፡ ልቡና፡ አእምሮ፡ እሊህ፡ ሦስቱ፡ ባይን፡ ይመስላሉ፤ ልብ፡ በጥቅሩ፤ ልቡና፡ በብሌኑ፡ አእምሮ፡ በብርሃኑ። ወይም፡ ልብ፡ በነፊሱ፡ ልቡና፡ በጥቍሩ፤ አእምሮ፡ በብሌኑ፡ ይመስላል። ነፊቲና፡ ልብም፡ ከናላ፡ ጋራ፡ በሚዛን፡ ይመስላሉና፡ ፍላን፡ ተመልከት።

**አለበወ፤** አስበመ፤ ልብ፡ አስደረገ፤ አሳሰበ፡ አስታወቀ፤ አስተማረ። ፍኖተ፡ ጽድቅከ፡ አሌብወኒ። ዕፀ፡ እንተ፡ ታሌቡ፡ ሠናየ፡ ወእኩየ። አሌብወከ፡ ዘሀለወከ፡ ትንብብ። ከመ፡ ያለብዎሙ፡ ለእስራ ኤል፡ (መዝ፡ ፻፲፰። ዘፍ፪፡ ፱። ዘዐ፬፡ ፲፪። ሚራ ፡ ፲፯)።

**መለብው፤ (ዋን)፤ አለባዊ፤** የሚያለ ብም፡ አስተዋቂ፡ አስረጅ። መለብው። ሐዋርያት፡ መምህራኒክሙ፡ ወመለብዋኒክሙ፡ (ፉሉፍ። ቄለመ)።

**ተለበወ፤** ታወቀ፡ ተረዳ። ወሰማዩሙ፡ ብ እሲ፡ ይትሌቦ፡ ክርስቶስ፡ (ቄር፡ ጳላ)። ተለበመ፡ ተዘ ጋጀ፡ ተሰናዳ። የመሚስትን፡ ይቋት፡ ልብም፡ ማለት፡ ዐማርኛው፡ ከዚህ፡ ወጥቷል።

**ለብሐ፤ (ዐረ፡ ለበከ)፤** ቀላቀለ፡ ደባለቀ፡ የሰቃ። ለወሰ፡ አበከ፡ ሠራ፡ የዱቂ። ለሐኰን፡ እይ።

**ለብሕ፤** ቅልቅል፡ ድብልቅ፡ ዱቂ።

**ለብሐ፤** ሸክላ፡ ከተበከ፡ ዱቂ፡ የሚሠራ። ንዋየ፡ ለብሓ፡ (መዝ፡ ፪)።

**ለብሓዊ፤ (ዊት፡ ውያን፡ ያት)፤** የሸ ክላ፡ ወገን፡ የሸክላ፡ ዐይነት፡ ዕቃ። ሸክለኛ፡ ሸክላ፡ ሠሪ፡ ጠቢብ። ገራህት፡ ለብሓዊ። እሉ፡ እሙንቱ፡ ለብሓውያን፡ (ማቴ፳፯፡ ፯። ፩ዜና፡ ፬፡ ፳፫። ሮሜ ፱፡ ፳፩)።

**ለበጦ፡ ጦት፤ (ለበጠ፡ ይለብጦ፡ ይል ብጦ። ዐረ፡ ለበደ፤ ላጠ። ዕብ፡ ላጥ)፤** መለ በጥ፡ ማስጌጥ፡ ማልበስ፡ መሸፈን፤ መምረግ፡ መለሰን፡ በወርቅ፡ በጨርቅ፡ በዱቂ፡ በንሬሴት። ገለወን፡ እይ። ብእሲ፡ ዘይክል፡ ለቢጠ፡ ወርቀ፡ ወብሩረ። ወለ በጠ፡ እንተ፡ ውስጡ፡ በወርቅ፡ ጽሩይ። ወንጊላቲ፡ ለቢጦ፡ በወርቅ፡ ወበብሩር፡ (፪ዜና፡ ፪፡ ፯። ፫፡ ፬። ገድ፡ ዘሚ)። መሠንበጥ፡ ማላገጥ፡ ለበጥ፡ ማውጣት፡ (ዐማርኛ)።

**ለባጢ፤ (ጢት፡ ጥያን፡ ያት)፤** የሚለ ብጥ፡ ለባዊ።

**አልበጠ፤** አስለበጠ፡ አሸፈነ። ወአልበጠ፡ ለውእቱ፡ ቤተ፡ በወርቅ፡ ጽሩይ፡ (፪ዜና፡ ፫፡ ፯—፲። ፱፡ ፲፯)። አጽንዐ፡ ጸወናቲሁ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ አል በጠ፡ መዛግብቲሁ፡ ይላል፡ የመላሹ፡ ስሕተት፡ ነው፡ (፪ዜና፡ ፲፩፡ ፲፩)።

**ተለብጠ፤** ተለበጠ፡ ተሸፈነ። ከመ፡ ወርቅ፡ ዘተለብጠ፡ ዲበ፡ እብነ፡ ያክንት፡ (አርጋ)።

**ልቡጥ፤ (ጣን፡ ጣት፡ ብጥ)፤** የተለበጠ፡ ሉብጥ፡ ሽፍን። ልቡጥ፡ በወርቅ፡ ወእቡር፡ በወ ርቅ። ልቡጣን፡ ወቅቡዓን፡ በወርቅ። ደሙ፡ ልቡጥ፡ ውስቴቱ። ልቡጥ፡ በቅድስና፡ (ዘፀ፳፯፡ ፳። ፪ዜና፡ ፱፡ ፲፰። ዮሴፍ። ስንክ፡ ኅዳ፳፩)።

**ልብጠት፤** መለበጥ፡ (ጥለ) መለበጥ፡ አለባ በጥ፤ ልበጣ፡ ልባጥ፡ ሉብጣት።

**ለቢጦን፤ (ቅብጥ፡ ሊቢቱ)፤** ዐጭር፡ ቀ ሚስ፡ እጅጌው፡ እስከ፡ ክርን፡ የሚደርስ፡ እጁ፡ ቁራጣ፡ እንደ፡ ኪታ፡ ያለ፤ የመነኰሴ፡ ልብስ። ለቢጦን፡ ዘ ሡዐ፡ (ሥር፡ ጳኰ)።

**ለበየ፤ (የለበወ፡ መንቲያ)፤** ልበ፡ ቢስ፡ ኾነ፡ ዘነጋ፤ ተሳሳተ፤ ተደናገረ፤ ጸየፈ፡ ኰለተፈ፡ የቃል፡ ያንደበት። እመ፡ እሌቢ፡ ውስተ፡ ነገራትየ፡ ስረዩ፡ ሊተ፤ እስመ፡ እለ፡ ይነግሩ፡ እምአፉሆሙ፡ ድን ቀተ፡ ወኢቀደሙ፡ ጽሒፈ፡ ዮጊ፡ ይሌብዩ፡ ወኢ ይክሉ፡ ለብዎ፡ ወነገረ፡ አሰርግዎ፡ (ተረ፡ ቄር)።

**ለባዪ፤ (ዪት፡ ይያን፡ ያት)፤** ልበ፡ ኢ፡ ልበ፡ ቢስ፡ ደፋር፡ አፉ፡ እንዳመጣ፡ የሚናገር።

**ልቡይ፤ (ያን፡ ያት፡ ቢት)፤** ልቡና፡ የ ሌለው፡ ገንንጉስ፡ ስሑት፡ ግብዝ፡ ከፉ፡ መጥፎ። እነ ግር፡ ከመ፡ ልቡይ፡ ወህጉል፡ ከሬል፡ ለክልኤ፡ ወረ ስዮ፡ ለዘዘ፡ ዚአሁ፡ ለብሰ፡ ወአምላከ፡ (ቄር፡ እስት)።

—፤ ሐሰት፡ ስሕተት፡ ጸያፍ፡ ከስሑታን፡ አፍ፡ የሚ ወጣ፡ ክንቱ። እቡሰ፡ ወልቡየ፡ ጠብዖ። ልቡይኬ፡

ይኤዜ ፡ ኀቤነ ፡ ወዕቀፍ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ አሚን ። ይብሎ ፡ ንኤብስ ፡ ዐቢየ ፡ እመ ፡ ንቤ ፡ ሐመ ፡ ቃል ፡ ወጽሎ ፡ ክብረ ፡ ምስጢር ፡ ልቡየ ፡ ንሬሲ ፡ (ቄር ፡ ጳላ) ።

**አለበየ ፤ (ያሌቢ ፡ ያለቢ)** ፤ አሳሳተ ፡ አጠፋ ፡ አበሳሽ ፡ ክንቱ ፡ አደረገ ። እመኒ ፡ ይትቄጥዑ ፡ ዐልዋን ፡ እለ ፡ ያሌብይዋ ፡ ለሃይማኖት ፡ (ቄር ፡ ጳላ) ። አለበየ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አስተላበየ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ወዝሰ ፡ ዘይብሉ ፡ ይዌ ፡ አይሁድ ፡ ወአረሚ ፡ ዘያስተላብዩ ፡ ፍኖተ ፡ መስቀል ፡ (ቄር ፡ ጳላ) ።

**ለቢን ፤ ኖት ፤ (ለበነ ፡ ይለብን ፡ ይልብን ። ዕብ ፡ ላበን)** ፤ ማንጣት ፡ ነጭ ፡ ማድረግ ፡ ማጠብ ፡ ማጥፌት ። መጥበስ ፡ መተኩስ ፡ ማጠን ፡ ማጤስ ፡ የብረት ፡ የሸክላ ፡ የጠጣን ። ስንኝን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ልብን ፡ ኔ ፤ (ዕብ ፡ ሊብኔ ። ዐረ ፡ ሉብን)** ፤ ነጭሎ ፡ ነጭ ፡ ዛፍ ፡ ቅጠሉም ፡ ቅርፍቱም ፡ ነጭ ፡ የኾነ ። በትረ ፡ ልብን ፡ (ዘፍ፡፴ ፡ ፴፯ ። ኢ.ዮ፡፬ ፡ ፲፫) ።

**ልብን ፤ (ዕብ ፡ ልቦና ፤ ሔልብና ። ዐረ ፡ ሉብን)** ፤ ነጭ ፡ ዕጣን ፡ ልባንጃ ፡ ሽቱ ፡ ከርቤ ፡ ከወተታም ፡ ዕንጨት ፡ የሚወጣ ። ማየ ፡ ልብን ፡ (ኩፋ ፡ ፲፯ ። ዘፀ፴ ፡ ፴፬ ። ማሕ፫ ፡ ፲፫) ። በልብን ፡ ፈንታ ፡ ሊባኖስ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ኤር፲፯ ፡ ፳፮) ።

**ሊባኖስ ፤ (ጽር ። ዕብ ፡ ልባኖን)** ፤ ስሙ ፡ አድባር ፡ ነጭነት ፡ እለ ፡ በሰሜና ፡ ለከንዓን ። ደጋ ፡ ብርቱ ፡ ታላላቅ ፡ ተራራ ፡ ገመገም ፡ ከዐቢይ ፡ ባሕር ፡ በመስስ ፡ ክሲደን ፡ እስከ ፡ ኤርሞን ፡ ተያይዞ ፡ በዮርዳኖስ ፡ በምድረ ፡ እስራኤል ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ዛፉም ፡ ዕንጨታም ፡ ዱራም ፡ ደናም ፡ የተራሮች ፡ ራስ ፡ ሰማይ ፡ ጠቀስ ፡ ውርጫና ፡ በረዶ ፡ እንደ ፡ ሻሽ ፡ ሽፍኖት ፡ የሚኖር ። ፍችው ፡ ቢሔት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነጩ ፡ ነጮ ፡ ወይም ፡ ነጭማም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (መዝ ፡ ፸፩ ። ማሕ፫ ፡ ፬ ። ኢሳ፵ ፡ ፲፮) ።

—፤ የሰው ፡ ስም ፡ ሶርያዊ ፡ አንጾኪያዊ ፡ ቅዱስ ፡ ከተስዐቱ ፡ ቅዱሳን ፡ በፊት ፡ የመጣ ፡ ደብረ ፡ ዐስቦን ፡ በስሙ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ይሰኝ ። ዘኖ ፡ ስሙ ፡ መጣዕ ፡ ኖ ፡ ስሙ ፡ ይስሐቅ ፡ ይባላል ፡ (ስንክ ፡ ጥር፫ ። ድጓ ። ፊልክ ፡ ፩) ።

**ለበን ፤ (ዐማርኛ)** ፤ ለንቦጭ ፡ ታችኛ ፡ ከንፈር ። ለበናም ፡ እንዲሉ ፡ በበረብ ፡ ግን ፡ ርጎ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ላበን ፤ (ዕብ)** ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ጸዐዳ ፡ ጽዕዱው ፡ (ዘፍ፳፱ ፡ ፫) ።

**ሉባር** ፤ የተራራ ፡ ስም ፡ ታላቅ ፡ ረዥም ፡ ተራራ ፡ ሐመረ ፡ ኖኅ ፡ የቆመችበት ። ወሖረት ፡ ታቦት ፡ ወአዕረፈት ፡ ዲበ ፡ ርእሰ ፡ ሉባር ፡ አሐዱ ፡ እምአድባረ ፡ አራራት ፡ (ኩፋ ፡ ፳ ። ዘፍ፰ ፡ ፬) ።

**ሊቤርጢኖን ፡ (ጽር ፡ ሊቤርቲኖን)** ፡ ግዑዛን ፡ ነጾች ፡ ነጻዎች ፡ ነጻነት ፡ ያላቸው ። ቃሉ ፡ የሮማይስጥ ፡ ነው ፡ ሊቤርታስ ፡ ከማለት ፡ ወጥቷል ፡ ይኸውም ፡ (ግዕዛን) ፡ ነጻነት ፡ ማለት ፡ ነው ። ከክርስቶስ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ተማርከው ፡ ተሸጠው ፡ የነበሩ ፡ አይሁድ ፡ ከሮም ፡ ባርነት ፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ ወጡ ፡ ከሌሎች ፡ አይሁድ ፡ ተለይተው ፡ ሊቤርቲኖናዊም ፡ ተብለዋል ። ምኵራብ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ሊቤርጢኖን ፡ (ግብ፮ ፡ ፱) ።

**ለቢስ ፤ ሶት ፤ (ለብሰ ፡ ይለብስ ፡ ይልበስ ። ዕብ ፡ ላባሽ ፡ ላቤሽ ። ሱር ፡ ልቤሽ ። ዐረ ፡ ለቢሰ)** ፤ መልበስ ፡ መከደን ፡ በልብስ ፡ ውስጥ ፡ መኾን ፡ መጐናጠፍ ። (ተረት) ፡ ካልበሱ ፡ ሬሳ ፡ ካለበሱ ፡ እንስሳ ። እንዘ ፡ ሥቀ ፡ ይለብሱ ። ወይለብሱ ፡ ብሩሀ ፡ ወንጹሐ ፡ (ራእ፲፭ ፡ ፫ ። ፲፱ ፡ ፰) ። በለብሰ ፡ ፈንታ ፡ ተለብሰ ፡ ተላበሰ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ተሰበሲ ፡ አልባሲኪ ። አኮ ፡ በተለብሶ ፡ አልባስ ፡ ዘብዙኀ ፡ ሢጡ ፡ (ፋትድ ፡ ፫ ። ሸጹጥ ፡ ፫ ፡ ፫) ። ወተላበሰ ፡ ንጉሠ ፡ እስራኤል ። ይፈቅዱ ፡ ያንሶስዉ ፡ ተላቢሶሙ ። ይመጽኡ ፡ ተላቢሶሙ ፡ አልባሰ ፡ አባግዕ ፡ (፪ዜና ፡ ፲፰ ፡ ፳፱ ። ማር፲፪ ፡ ፴፰ ። ሉቃ፳ ፡ ፵፮ ። ቀሌ) ።

**ለባሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት)** ፤ የሚለብስ ፡ ለባሽ ። ለባሴ ፡ አምላክ ። ለባሲተ ፡ ሞገስ ፡ ወግርማ ። ለባስያነ ፡ መስቀል ፡ (አረጋ ፡ ድጓ ። ደራሲ ። ቅዳ) ።

**አልበሰ** ፤ አለበሰ ፡ ከደነ ፡ ሸፈነ ። ኣለብሶ ፡ አልባሲከ ። አልበስከኒ ፡ ማእሰ ። አልበሱ ፡ ምሥዋዐ ፡ ሠቀ ፡ (ኢሳ፳፱ ፡ ፳፩ ። ኢዮ፲ ፡ ፲፩ ። ዮዲ፱ ፡ ፲፩) ። አስለብሰ ፡ አስከደነ ። አስደረገ ።

**ተለብሰ** ፤ ተለበሰ ፡ ልብስ ፡ ኾነ ።

**ልቡስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ብስት)** ፤ የለበሰ ፡ የተከደነ ፡ ሽፍን ። እንዘ ፡ ልቡስ ፡ አልባሰ ፡ መንግሥት ። ካህናት ፡ ቀሙ ፡ ልቡሳኒሆሙ ። ይእቲ ፡ ሥዕል ፡ ትመስል ፡ ልብስተ ፡ ሥጋ ፡ (አስቴር፩ ፡ ፲፭ ። ስገዘ ፡ ፲ ። ታምር) ።

—፤ የተለበሰ ፡ ልብስ ፡ ውራጅ ። ዝንቱ ፡ ልብስ ፡ ልቡስ ፡ ወአኮ ፡ ሐዲስ ፡ (ዘረፋ) ።

**ልብሰት** ፤ መልበስ ፡ መለበስ ፡ አለባበስ ፡ ልብስነት ። እምልብሰቱ ፡ ለሰብእ ፡ ወሑረቱ ። ለብሰ ፡ ዐማኑኤል ፡ ልብሰተ ፡ ሥጋ ፡ (ሢራ፲፱ ፡ ፴ ። ቅዳ) ። ባልብስ ፡ ፈንታ ፡ ልብሰት ፡ ይላል ፡ አያስኬድም ። ግሩም ፡ በልብሰቱ ፡ (ኢሳ፷፫ ፡ ፩) ።

**ልብስ ፤ (ብ ፡ አልባስ ፡ ሳት)** ፤ በቁሙ ፡ የገላ ፡ መክደኛ ፡ መሸፈኛ ፡ በየስሙና ፡ በየመልኩ ፡ ታላቁም ፡ ታናሹም ፡ ድንኳኑና ፡ መጋረጃ ፡ ሳይቀር ። ልብስ ፡ ንጹሕ ። አልባሰ ፡ ወርቅ ፡ (ራእ፫ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፵፬) ።

**መልበስ ፤ መልበስት ፤ (ብ ፡ መላብስ ፡ ት)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ልብስ ። አፈ ፡ መልበስየ ። ኅብኑ ፡ መልበሱ ። መልበስተ ፡ እንግዲዓ ። ዘመልበስቱ ፡ መዛግብተ ፡ ብርሃን ። ወመላብሲሆሙ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፻፴፪ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፴ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፱) ።

**ተላበሰ ፤ (ተደራረበ)** ፤ በቁሙ ፡ ተለባበሰ ፡ ርስ ፡ በርሱ ። ባማርኛ ፡ ግን ፡ አደግድጎ ፡ ሲል ፡ ተላበሰ ፡ ይላል ፡ መላበስ ፡ የካህናት ፡ መታጠቅ ፡ ማሸነፈጥ ፡ የሕዝብ ፡ የሰራዊት ።


**ለቤሳት** ፤ (ጽር ፡ ሌቢሲ) ፤ ጽህርት ፡ የብረት ፡ ድስት ፡ በገ ፡ ፈጅ ፡ ወይም ፡ ሳሙ ፡ ፈጅ ፡ (፪ዜና ፡ ፴፭ ፡ ፲፫) ።

**ሌጌዎን** ፤ (ጽርእ) ፤ ሰራዊት ፡ ጭፍራ ። የጦር ፡ አበጋዝ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃ ። ስድስቱ ፡ ሺሕ ፡ ጭፍራ ፡ ከሩ ለቃው ፡ አንድ ፡ ሌጌዎን ፡ ይባላል ፡ (ማቴ ፳፮ ፡ ፶፫ ። ማርቆ ፡ ፭ ። ሉቃ ፰ ፡ ፴) ።

**ሎማዮን** ፤ **ሎማዮ** ፤ (ጽር ፡ ሎጊዎን ። ዕብ ፡ ሖሼን) ፤ ሴዴርያ ፡ የደረት ፡ ልብስ ፡ ከአልባሰ ፡ ክህነት ፡ አንዱ ። ልብሰ ፡ ሎማዮን ። ከመ ፡ ልብሰ ፡ ክህነት ፡ ሎማዮ ፡ (ዘፀ ፳፰ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ፡ ፳፪ ። ደራሲ) ። ባማርኛ ፡ መልክም ፡ ነገር ፡ ሲታይ ፡ ወሼን ፡ ወሸኔ ፡ ውሽን ፡ ማለት ፡ ሖሼን ፡ ከማለት ፡ የመጣ ፡ ነው ።

**ለጐም** ፤ ሞት ፤ (ለጐመ ፡ ይለጕም ፡ ይልጕም ። ዕብ ፡ ላጋም) ፤ መለጐም ፡ ማጕረምረም ፡ በአፍ ፡ መወተፍ ፡ አፍን ፡ መዝጋት ፡ ዝም ፡ ማሰኘት ፡ መከልከል ፡ መግታት ። ንኄንቀ ፡ ለነፍስነ ፡ ወንለጕማ ፡ ከመ ፡ ፈረስ ፡ ኁደል ፡ ወድሩክ ። ለከናፍር ፡ እለ ፡ ነበባ ፡ ስብሐታተ ፡ አርመሞን ፡ ሞት ፡ ወለጕሞን ፡ በልጓም ፡ ዘኢይትበተክ ። ልጕም ፡ ልሳነከ ፡ ከመ ፡ ኢትተክዝ ፡ ድኅረ ። ለጐመ ፡ ሰማየ ፡ ከመ ፡ ኢየሀብ ፡ ዝናሞ ፡ (አፈ ፡ ተ፴፰ ። ማንዘ ። ፊላስ ። አርጋ) ። በለጐመ ፡ ፈንታ ፡ አልጐመ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ዘኢያለጕሞ ፡ ለልሳኑ ። በንጽሕ ፡ አልጕሙ ፡ ሥጋሆሙ ፡ (ያዕ፩ ። ፳፮ ። ተረ ፡ ቄር፲፱) ። ለገመ ፡ ልግም ፡ ልግመኛ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ፈአመን ፡ እይ ።

**ልጓም** ፤ (ማት ፤ አልጓም ። ዐረ ፡ ሊጃም ። ሱር ፡ ሉግማ ። ዕብ ፡ ልጊማ) ፤ ጕርሻ ፡ ባፍ ፡ የሚመላ ፡ አንዳፋ ፡ አንድ ፡ ቢጀ ፡ በቁርሙ ፡ ቀለበታም ፡ ብረት ፤ በእንስሳት ፡ አፍ ፡ የሚጕረም ። ለአፍራስኒ ፡ ንወዲ ፡ ሎቱን ፡ ልጓመ ፡ ውስተ ፡ አፉሆን ። ይፌትሕ ፡ ልጓማተ ፡ ጽኑዓን ። በአልጓሚሁ ፡ (ያዕ፫ ፡ ፫ ። ሐዋ ፡ ፬ ። ቄር) ።



ልጓም ፡

**አልጐመ** ፤ አስለጐመ ፡ አስጐረሠ ፡ ዝም ፡ አሰኘ ፡ አፍ ፡ አሲያዘ ። ባማርኛ ፡ ግን ፡ ዐጕል ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ ዝም ፡ አለ ፡ ያሰኛል ። አልጕም ፡ ከፋ ፡ ዝምተኛ ።

**ተለጕመ** ፤ ተለጐመ ፡ ተዘጋ ፡ ዝም ፡ አለ ፡ ተገታ ። ናሁ ፡ ትለጕመ ፡ ዜማ ፡ መሰንቆ ፡ ጥዑም ። ተለጕሞ ፡ ልሳን ። ይትለጐም ፡ ጸላኢ ፡ (ማንዘ ። አፈ ፡ ተ፳፱ ። ማር ፡ ይሥ፳ ፡ ፪) ።

**ለገነ** ፤ አበከ ፡ ጋገረ ፡ አገነፋ ።

**ለግን** ፤ (ጽር ፡ ላጋኖን) ፤ ወንጕሮ ፡ እንጎደ ፡ ማቢታ ፡ ያለ ፡ ሥሥ ፡ ረቂቅ ። ባለብለቦች ፡ ግን ፡ አንባሻ ፡ ይሉታል ፡ (ዘሌ፪ ፡ ፬) ።

**ልግንት** ፤ ግንፎ ፡ መንከኮ ፡ እንቀት ፡ አዋሚት ።

**ልጕን** ፤ (ሱር ፡ ልጊና ፤ ላጊና ። ጽር ፡ ላጊኖስ) ፤ ለገን ፡ ጥዲያት ፡ ማድጋ ፡ ምንቸት ፡ መንቀል ፡ ኮስኳስት ። ግንዐ ፡ ወልጕን ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ለግርዮን** ፤ (ጽር ፡ ሊጊሪዮን) ፤ የዐንዋ ስም ፡ ሕብሩ ፡ ጥቍር ፡ ደባብ ፡ ደምማ ፡ ወይም ፡ ደመርጎማ ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፲፱ ። ፴፱ ፡ ፲፬) ። ያክንትን ፡ እይ ።

**ልጕት** ፤ — ጕንገ ፡ መተሚቃ ፤ — ወለገ ።

**ለጐተ** ፤ (ዲ.ቃ ፡ ግ ፤ ልገት ፡ ወሊግ) ፤ ሰፋ ፡ ጥልቅ ፡ ኸን ፡ ጕታ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ለገተ ፡ ደቀን ፡ አቅረበ ፡ ወይም ፡ ተለገተ ፡ ለመካተት ፡ ለመቀበል ።

**ልጕት** ፤ (ታት ። ዐረ ፡ ሉጀት) ፤ ቀላይ ፡ ጥልቅ ፡ ሰጣቅ ፡ የባሕር ፡ የወንዝ ፡ የጕድጓድ ፡ የዐዘቅት ። ያስጥምዎ ፡ ውስተ ፡ ልጕተ ፡ ባሕር ። ልጕታት ፡ አብሕርት ። ልጕታት ፡ ምድር ፡ ይሜጥ ፡ ሎሙ ፡ ንቀየሙ ፡ ወልጕተ ፡ ምድሮሙ ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፮ ። ኩፋ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፫ ። ጎዳ፲፫) ።

**ልድ** ፤ **ልደት** ፤ — ወሊድ ፡ ወለደ ።

**ላህ** ፤ — ልቅሶ ፤ — ላሕዎ ፡ ላሐወ ።

**ልሂብ** ፤ ቦት ፤ (ልህበ ፡ ይልህብ ፡ ይልህብ ። ዐረ ፡ ለሂበ ። ዕብ ፡ ላሀብ) ፤ መንደድ ፡ መቃጠል ፤ መንበልበል ፡ መሞቅ ፡ መቀኰስ ፡ መላብ ፡ መውዛት ፡ ስብ ፡ ማለት ። ወእምዝ ፡ ልህበ ፡ ልህበተ ፡ እምኔሁ ፡ (መቅ ፡ ወን) ።

**ልሁብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ህብት) ፤ የተቃጠለ ፡ የጋለ ፡ የጋመ ፡ የሞቀ ፡ ሙቅ ። የላበ ፡ የወዛ ፡ ስብ ፡ ያለ ። ኮነ ፡ ልሁበ ፡ ውስተ ፡ አፍቅሮተ ፡ እግዚ ። ዐራቱ ፡ ኅጺን ፡ ልሁብ ፡ (ፊልክ ፡ ፹፬ ። ስንክ ፡ ታኅ፱) ።

**ላህብ** ፤ (ባት) ፤ ነበልባል ፡ ወላፈን ፡ ሙቀት ፡ ትኵሳት ፡ ሰብታ ፡ ላብ ፡ ላበት ፡ ወዝ ፡ መከራ ፡ ጭንቅ ። ላህበ ፡ ነድ ። ላህበ ፡ እሳት ። ላህበ ፡ ፀሓይ ። ላህበ ፡ መዓልት ። ወሶበ ፡ ፈትሖ ፡ እማእሰሪሁ ፡ ወጠፍአ ፡ ላህቡ ፡ ቆመ ፡ ቅድመ ፡ እግዚእነ ፡ እንዘ ፡ ይገርር ፡ (ጥበ፲፮ ፡ ፲፰ ። ሔኖ ። ኢሳ፴፱ ፡ ፲ ። ኤር፵፪ ፡ ፴ ። መቅ ፡ ወን) ።

**አልሀበ** ፤ አነደደ ፡ አቃጠለ ፡ አሞቀ ፡ አቀኰሰ ፡ አላበ ፡ አወዛ ። ለተጋብኦ ፡ ብዙኃ ፡ በሙዳት ፡ ወውእቱ ፡ ዘያልህብ ፡ ለእሳተ ፡ ፍቅር ። አልህበ ፡ እቶነ ። አልሀቦቶ ፡ ፀሓይ ፡ ርእሶ ፡ ለዮናስ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፱ ። አዋል ። ስንክ ፡ መስ፳፰) ።

**ልህደ** ፤ — ተቀማጠለ ፤ — ልሕደ ።

**ላህዎ** ፤ ዎት ፤ (ላህየ ፡ ይላሂ ፡ ይላሂ ። ዐረ ፡ ለሃ ፤ ለሂየ) ፤ መላጠት ፡ ማማምት ፡ ጨምታ ፡ ማድረግ ፡ በእጅ ፡ በቃል ። ማጸናናት ፡ አይዞህ ፡ አይዞህ ፡

ማለት ። ቶጥአት ፡ ዘይላህያ ። ወአልቦ ፡ ዘይላህየኒ ፡ (ሰቈ፰ ፡ ፲፯ ፡ ፳፭) ። በላሀየ ፡ ፈንታ ፡ አልሀየ ፡ ተለሀየ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ዐራትየኑ ፡ እንጋ ፡ ይናዝዘኒ ፡ ወያላህየኒኑ ፡ ምስካይየ ። እስመ ፡ የጊ ፡ ይትለሀይ ፡ (ኢዮ፯ ፡ ፲፫ ። ፫ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፯) ።

**ተላህየ ፤ (ተደራጊና ፡ ተደራራጊ) ፤** ተጫወተ ፡ ተጫዋወተ ። ወአኅዘኩ ፡ እትላሀይ ፡ ምስሌሆን ። ከመ ፡ ዘይትላሀይ ። አ ፡ ይንግል ፡ አኮ ፡ በተላሆዮ ፡ ዘልህቀ ፡ ከመ ፡ አዋልድ ፡ ዕብራውያን ። ተላህዮብ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ተላህዮ ፡ በዕፀ ፡ ወእንዚራ ፡ ወአርጋኖን ፤ ወተረፈ ፡ ንዋዮተ ፡ ማሕሌት ፡ ዘተውኔት ፡ ሕሩም ፡ ውእቱ ፡ (ሄርማ ። ገድ ፡ ተክ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፱ ፡ ፯) ። ዝሙት ፡ ወተላህዮት ። ለእመ ፡ ተረክበት ፡ ብእሲት ፡ ምስለ ፡ ካልእታ ፡ ይትላሀያ ፡ በበይናቲሆን ፡ (ሲ.ጳፋ ፡ ሲ.ጋሬው) ። ለእመ ፡ ተላህየ ፡ ካህን ፡ በነፍስተ ፡ ሥጋሁ ፡ (ገድ ፡ አዳ ። ቁድር) ።

**ተላሃዪ ፤** ተማዋች ፡ ተጫዋዋች ፡ ጨዋተኛ ፡ ጨዎታ ፡ ዐዋቂ ። ሰካሬ ፡ ወተላሃዪ ፡ ወዘፋኜ ፡ እንዚራ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፴፬ ፡ ፩) ።

**ተላህዮ ፤** ተላህዮታ ፡ ተከውሶታ ፡ ወተሀውኮታ ፡ ሞገዳ ፡ ወማዕበላ ፡ (መዝ ፡ ፹፪) ።

**ትልሂት ፤** ጨዎታ ፡ ዋውውት ፡ ዝሙት ፡ የፍትወት ፡ ሥራ ። ትልሂት ፡ በነፍስተ ፡ ሥጋሁ ፡ (ቄድር) ። ተላህዮም ፡ ጥፊ ፡ ዘር ፡ ኹና ፡ በትልሂት ፡ አፈታት ፡ ይፈታል ።

**አስተላሀየ ፤ (አስደራጊና ፡ አደራራጊ) ፤** አስጫወተ ፡ አጫዋወተ ። እልኩ ፡ መጽአ ፡ ኀቤየ ፡ ወይስተላህዩኒ ፡ (ሄርማ ፡ ገ፹፩) ።

**መስተላህይ ፤** የሚጫዋወት ፡ ተጫዋዋች ። የሚያጫዋውት ፡ አጫዋዋች ።

**ልህየ ፤—ወዘ ፡ አማረ ፤—ልሕዩ ፡ ልሕየ ።**

**ልህኮት ፤—ሸክላ ፤—ልሒኮ ፡ ለሐኮ ።**

**ላህልሀ ፤—ራሰ ፡ ለመሸቀ ፤—ላሕልሐ ።**

**ላህልሀ ፤—ላላ ፡ ረገበ ፤—ላኅልኀ ።**

**ልህመ ፤—ላመ ፡ ጸና ፡ በሰ ፤—ልሕመ ።**

**ላህም ፤—በቁሙ ፡ ላም ፤—ልሕመ ።**

**ልሂቅ ፤ ቆት ፤ (ልህቀ ፡ ይልህቅ ፡ ይልህቅ ። ዕብ ፡ ላሀቅ ፤ ሰበሰበ)** ፤ ማደግ ፡ መጐልመስ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ማድረስ ። ብእሲንና ፡ ዕብየትን ፡ ተመልክት ፤ የዚህ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። ልህቀ ፡ ሕፃን ፡ ወኀደገ ፡ ጥበ ። እስከ ፡ አመ ፡ ይልህቅ ፡ ወልድየ ፡ ሴሎ ። አይድፅቶ ፡ አስቴር ፡ ለንጉሥ ፡ ከመ ፡ በቤቱ ፡ ልህቀት ፡ (ዘፍ፳፩ ፡ ፰ ። ፴፰ ፡ ፲፩ ። አስቴ፩ ፡ ፳) ።

—፤ መላቅ ፡ መብለጥ ፡ ታላቅ ፡ መኾን ፡ በኀይል ፡ በመጠን ፡ በብዛት ፡ በዘመን ። እንሆሙ ፡ ዘይልህቅ ። አኅትክን ፡ እንተ ፡ ትልህቅ ። ለሀቀ ፡ ወብዝኀ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፲፫ ። ሕዝ፳፫ ፡ ፵፯ ። ኩፋ ፡ ፯) ።

—፤ ማርጀት ፡ መሸምገል ፡ አሮጌ ፡ መኾን ። አብርሃምሰ ፡ ወሳራ ፡ ልህቁ ፡ ጥቀ ፡ ወኀለፈ ፡ መዋዕሊሆሙ ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፲፩ ። ሸ፱ ፡ ፩ ። ፳፯ ፡ ፩) ። በልህቀ ፡ ፈንታ ፡ ተልህቀ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እለ ፡ ይትለሀቁ ፡ እምኔሆሙ ፡ (ሸዲ.ጥ ፡ ፳ ፡ ፩ ። ኪዳ) ።

**ልሂቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ሀቅት) ፤** አሮጌ ፡ ሽማግሌ ፤ ታላቅ ። ኢይትረከብ ፡ ልሂቅ ፡ ውስተ ፡ ቤትከ ። ልሂቃን ፡ ወልሂቃት ፡ (፩ነገ ፡ ፪ ፡ ፴፪ ። ዘካ፰ ፡ ፬) ።

—፤ ቄስ ፡ ካህን ፡ መስፍን ፡ መኰንን ። ሳዕለ ፡ ልሂቅ ፡ ኢትስማዕ ፡ ውዴተ ። ልሂቃነ ፡ መንግሥቱ ። እምውሉደ ፡ ልሂቃነ ፡ ሀገረ ፡ ሮሜ ፡ (፩ጢ.ሞ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ፡ ስንክ ፡ መስ፱ ። ፲፯) ።

**ላህቅ ፤ (ቃን) ፤** ግዙ ፡ ከማው ። ወሰብ ፡ ምእሙ ፡ ለጸላእቱ ፡ ገብረ ፡ ብልጣሶር ፡ ምሳሐ ፡ ዐቢየ ፡ ለላህቃነ ፡ መንግሥቱ ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፹፯) ።

**ሊቅ ፤ (ቅት ፡ ቃን ፡ ቃት) ፤** በቁሙ ፡ አለቃ ፡ ታላቅ ፤ አባት ፡ ጌታ ፡ መምህር ፡ ሹም ፡ አሮጌ ፡ ሽማግሌ ። (ተረት) ፡ ከሊቅ ፡ እስከ ፡ ደቂቅ ። ልሂቅና ፡ ሊቅ ፡ ልዩነቱ ፡ ሂን ፡ በመጕረድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምስጢሩና ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ሊቀ ፡ ይለይቅ ፡ ብለው ፡ ይገባሉ ። ወዘሰ ፡ ብዉሕ ፡ ለሊቅ ፡ ዘውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ። ሊቅት ። ሊቃነ ፡ አሪት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፩ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፯ ። ሉቃ፳ ፡ ፲፯) ።

**ሊቃን ፤ ሊቃናት ፤ ሊቃውንት ፤ (ልሂቃን ፡ ናት) ፤** አለቆች ፤ ሹማምቶች ፤ መምራኖች ፤ ሽማግሌዎች ። ሊቃነ ፡ ሕዝብ ። ሰብእ ፡ ሊቃናት ። መንበረ ፡ ሊቃውንት ። ሊቃናቲኒ ፡ ወመሓዛት ፡ (ዘፀ፲፰ ፡ ፲፱ ። ዘኁ፲፩ ፡ ፳፭ ። መዝ ፡ ፻፯ ። ፳፫፳) ።

**ሊቅና ፤ (ልህቅና) ፤** ሊቅነት ፤ አለቅነት ፤ አቅና ፡ ሹመት ፡ እርጅና ። ሢመተ ፡ ሊቅና ፡ ዘካህናት ። ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሊቅናሁ ፡ ሳዕለ ፡ መሲሓውያን ፡ (ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፬) ።

**ሊቃኖስ ፤** ከተቀበቱ ፡ ትዱሳን ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ሊባኖስ ። ባና ፡ ቃ ፡ ተወራርሰዋል ።

**ልህቀት ፤** ማደግ ፡ እድገት ፡ አስተዳደግ ። በእንተ ፡ ልደቱ ፡ ወልህቀቱ ፡ በበ ፡ ሕቅ ፡ ወሕማማቲሁ ፡ ወሞቱ ። ልህቀቱ ፡ በበ ፡ ሕቅ ፡ እስከ ፡ ወርዘወ ። ተወከፈ ፡ እሙነ ፡ ልህቀተ ፡ ዘበበ ፡ ሕቅ ፡ (አፈ ፡ ድ፳ ። አርጋ ። ሃይ ፡ አበ) ።

—፤ ማርጀት ፡ መላቅ ፡ እርጅና ፡ ላቂያ ፡ ልቅና ፡ ብክርና ። ረከበት ፡ ወልደ ፡ በልህቀቲሃ ። አግብእ ፡ ሊተ ፡ ልህቀተከ ፡ ዘቅድመ ፡ ልደት ፡ (ሉቃ፩ ፡ ፴፮ ። ኩፋ ፡ ፳፱) ።

**ልህቃን ፤** ግዙ ፡ ከማው ፡ እድገት ፡ እድጊያ ፤ እድግ ። አየ ፡ ልህቃነ ፡ ልህቀ ። ዘትስብእት ፡ ውእቱ ፡ ልህቃን ፡ (ቄር ፡ ጳላ) ።

—፤ እርጅና ፡ የድሜ ፡ ብዛት ። ውስተ ፡ ልህቃነ ፡ ዓመታቲሁ ፡ (ፊልክ) ።

—፤ ላቂያ ፡ ልቅና ፡ ብሹርና ። ወሀብኩ ፡ ልህቃንየ ፡ ሊየዕቆብ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፮) ።

**ልህቅና** ፤ ልቅና ፡ እርግና ፡ ብሹርና ፡ ታላቅ ነት ። በልህቅናሁ ፡ ሖብደ ። ነጺሮ ፡ በናእሰ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ወልህቅናሁ ፡ (ፊልክ ፡ ፴፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፴፮ ፡ ፴፮) ።

**አልሀቀ** ፤ አላቀ ፡ አሳደገ ፡ ታላቅ ፡ አደረገ ። ውሉደ ፡ ወለድኩ ፡ ወአልሀቁ ። ቀላይ ፡ አልሀቆ ። እስመ ፡ ኪያከ ፡ አልሀቀ ፡ እግዚ ፡ (ኢሳ ፩ ፡ ፪ ። ሕዝ ፴፩ ፡ ፬ ። ዳንኤ ፡ ፵) ።

—፤ አበረዠ ፡ አሸመገለ ፡ ዕድሜ ፡ ሰጠ ። ወይእዜኒ ፡ አልሀቀኒ ፡ እግዚእ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ (ኢያ፲፬ ፡ ፲) ።

**አልሃቂ ፤ መልሀቂ ፤ መልሀቅ)** ፤ የሚያ ልቅ ፡ አሳዳጊ ።

**መልሀቅ ፤ (ብ ፡ መላህቅት ፤ ታት)** ፤ ሊቅ ፡ ታላቅ ፡ የሚበልጥ ፡ አለቃ ፡ ሹም ፡ አሮጌ ፡ ሽማግሌ ። መላህቅተ ፡ ሕዝብ ። ኢይፍታሕ ፡ ሕዝባዊ ፡ ወኢመላህቅት ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ሥዩማነ ፡ ቤተ ፡ ክር ። ደናግል ፡ ወመበለታት ፡ ወመላህቅታት ፡ (ባልቴቶች) ፡ ይቁማ ፡ ቅድመ ፡ ዣሎን ፡ አንስት ፡ (ዘዐ፲፮ ፡ ፭ ። ዲድ፲ ። ፲፱) ። መልሀቅ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ያስተባብራል ፤ ለሴት ፡ ሲነገር ፡ ቅ ፡ ይጠብቃል ።

**ተልህቀ ፤ (ይትለሀቅ)** ፤ ተላቀ ፡ ተበለጠ ፡ ላቂያና ፡ ብልጫ ፡ ሆነ ፡ አነሰ ።

**ተላሀቀ ፤ (ይትላሀቅ)** ፤ ተላላቀ ፡ ተበላለጠ ፡ እኔ ፡ እበልጥ ፡ ተባባለ ።

**አስተላሀቀ** ፤ አላላቀ ፡ አበላለጠ ።

**መልህቅ ፤—በቁሙ ፤—ለሐቀ ።**

**ልህሰ ፤ (ልሒስ ፡ ለሐሰ)** ፤ ኼደ ፡ ተጠረገ ፡ ጠፋ ፡ ታጣ ። መሬትኒ ፡ እንተ ፡ ዥለሄ ፡ ወእልህስ ። ወይልህስ ፡ እመንበሩ ። ትፍህቅ ፡ ነፍስየ ፡ ወትልህስ ፡ (ኢዮ፲፱ ፡ ፲ ። ፳፮ ፡ ፳፭ ። ፴ ፡ ፲፭) ።

**ለሀሰ ፤—ላሰ ፡ ላላሰ ፤—ለሐሰ ።**

**ለሆሳስ ፤—ሹክሹክታ ፤—ለኆሰ ።**

**ላዊ ፤—የፊደል ፡ ስም ፡ ለ ፤—ለወየ ።**

**ሌዊ ፤—የሰው ፡ ስም ፤—ለየወ ።**

**ለወወ ፤ (ለወየ ፤ ዐለወ)** ፤ ጠመመ ፡ ጠነነ ፡ ልበ ፡ ክፉ ፡ ኸን ፡ ደፈረ ፡ ተኰረ ፤ በክፉ ፡ አየ ። ከለወየና ፡ ከዐለወ ፡ ከኹለቱ ፡ የተደቀለ ፡ ነው ።

**ለዋው** ፤ ጠማማ ፡ ክፉ ፡ ደፋር ፡ ተኳር ፡ ዕቡየ ፡ ዐይን ፡ ገጽ ፡ ቢስ ። እኩይ ፡ ወሊዋው ። ሐራውያ ፡ ሐቅል ፡ ለዋው ። ከመ ፡ ሊዋው ፡ ይመስል ፡ ገጹ ፡ (ሄ ኖን ፡ ፳፭ ፡ ፫ ። ፱ኖን ፡ ፲፮ ፡ ፰ ። ሄርማ ፡ ገ፳፮) ።

**ሎዘ ፤ (ዕብ ፡ ላዝ ፡ ያሉዝ)** ፤ ከመንገድ ፡ ጠጣ ፡ ፊቀ ። ምስጢሩ ፡ የለወወ ፡ ነው ፡ ክፋትና ፡ ጥመት ፡ ያሳያል ።

**ለውዝ ፡ (ዕብ ፡ ሉዝ ። ሱር ፡ ሉዛ ። ዐረ ፡ ሎዝ)** ። በቁሙ ፡ ስመ ፡ ዕፀ ። ከርከዕን ፡ እዩ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ገውዝ ፡ ወሰውዝ ። እመ ፡ ተክልከ ፡ በለሰ ፡ ቦኑ ፡ ይበቍል ፡ ለከ ፡ ለውዝ ፡ (ሆሴ ፱ ፡ ፲፫ ። መቃ ፡ ገ፳) ።



ለውዝ ፡

**ሎዛ** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ ለውዛም ፡ የለውዝ ፡ ቦታ ፡ በኤፍሬም ፡ ዕፃ ፡ ውስጥ ፡ ያለች ፡ ደኋላውም ፡ ቤቴል ፡ ናት ፡ (ዘፍ፳፰ ፡ ፲፱) ።

**ሎዛን ፤ (ዐረ ፡ ላዝን)** ፤ ስጣን ፡ ሙጫ ፡ ከለውዝ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ዕንጨት ፡ የሚገኝ ። ክርቤ ፡ ወሚዓ ፡ ወሎዛን ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

**ሎሐ ፤ (ዕብ ፡ ላዌሕ)** ፤ ሳገ ፡ ጠረበ ፡ አለዘበ ፡ ፋቀ ፡ ፊመመ ፡ የንጨት ፡ የቁርበት ፡ የደንጊያ ፡ የብረት ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ጣፈ ፡ ይላሉ ።

**ለውሐ ፡ (ሓት ። ዕብ ፡ ሉዋሕ ። ሱር ፡ ሉሓ ። ዐረ ፡ ሉሕ)** ፤ ሉሕ ፡ ሰሌዳ ፡ ገበር ፡ ሥሥ ፡ ጠፍጣፋ ፡ ጠርብ ፡ ሳንቃ ፡ ስሌቃ ፡ ብራና ፡ ወረቀት ፡ የመጽሐፍ ፡ ገበታ ፡ ጽሌ ፡ ጽላት ። ዕፀ ፡ ለውሕ ። አሕቲ ፡ ለውሕ ፡ እምዕፀወ ፡ ሐመር ፡ (ክብ ፡ ነገ፹፮ ። ስንክ ፡ ጥር፲፱) ።

**ለዋሕቅ ፤ (ዐረብ)** ፤ ጷግሜን ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ። እንስይን ፡ እዩ ።

**ሎጠ ፡ (ወለጠ ። ዕብ ፡ ላጥ ፡ ያሉጥ)** ፤ ሸፈነ ፡ አለበሰ ፤ አጐናጠፈ ። ለወጠ ፡ ለዋወጠ ፡ የልብስ ፡ የመልክ ። ወለጠን ፡ እዩ ፡ የዚህ ፡ ሙንቲያ ፡ ነው ።

**ሎጥ** ፤ መሸፈኛ ፡ ሜላት ፡ መጐናጠፊያ ፡ የላይ ፡ ልብስ ፡ በጽፍ ፡ ግልባቤ ። የሰው ፡ ስም ፤ ወልደ ፡ እኁሁ ፡ ለአብርሃም ። ወሎጥስ ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ሰዶም ፡ (ዘፍ፲፱ ፡ ፩) ።

**ሎጣዊ** ፤ ሎጥማ ፡ የሎጥ ፡ ዐይነት ። የሎጥ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ በግብር ፡ የሎጥን ፡ ጋበኞች ፡ የሰዶምን ፡ ሰዎች ፡ የሚመስል ። ሎጣውያን ፡ ዘውእቶሙ ፡ እለ ፡ ይዜምዉ ፡ ተባዕተ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፫ ፡ ፳) ።

**ለወየ ፡ (ዐረ ፡ ለወይ)** ፤ ጠወየ ፡ ጠመጠመ ፡ ጠቀለለ ፡ ፈተለ ፡ አከረረ ፡ ቀለሰ ፡ አጐበጠ ፡ ቈለመመ ። ጠወየን ፡ ተመልከት ፡ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ርሱ ፡ ነው ፡ ለ ፡ በጠ ፡ ፈንታ ፡ ገብቷል ።

**ላዊ ፡ ላውይ ፤** ስሙ ፡ ፈደል ፡ ለ ፡ የአልፋ ፡ ጓደኛ ። ጠማማ ፡ ቈልማማ ፡ ጕብጥ ፡ ቅልስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ጠማምነቱም ፡ በኹሉ ፡ ነው ።

**ምልዋይ ፤** መጠምጠሚያ ፡ ጥምጥም ፡ ራስ ፡ ማሰሪያ ፡ መሸፈኛ ።

**ለይ ፤** ፈትል ፡ ልብስ ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ የገባ ። ሕበረት ፡ ለየ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ። እመኒ ፡ ለበስኪ ፡ ለየ ፡ (ዘፍ፴፰ ፡ ፳፰ ። ኤር፬ ፡ ፴) ።

—፤ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ከጥቍርና ፡ ከነጭ ፡ ከብጫ ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ የፈትልና ፡ የልብስ ፡ መንከሪያ ። ሕብረ ፡ ለይ ። ፈትሉ ፡ ዘለይ ። ክለሚዳ ፡ ዘለይ ፡ (፪ዜና ፡ ፪ ፡ ፯ ። ሢራ፵፭ ፡ ፲፩ ። ማቴ፳፯ ፡ ፳፰) ።


**ሎልዎ ፡ ዎት ፤ (ሎለወ ፡ ለውለወ ፡ ይሎሉ ፡ ይሎሉ) ፤** መውለብለብ ፡ ማውለብለብ ፡ ማታጠል ፡ መለብለብ ፡ የምላስ ፡ የእሳት ። ለውለወ ፡ ከይሲ ፡ ልሳኖ ። ወትሎሉ ፡ ክቡት ፡ ፍጥረተ ፤ (መጽ ፡ ምስ ። ገድ ፡ ተክ ። ያዕ፫ ፡ ፮) ። በሎለወ ፡ ፈንታ ፡ አሎለወ ፡ አለውለወ ፡ ይላል ፡ ግስነቱ ፡ በግእዝና ፡ ግቢር ፡ ነውና ፡ አያሰኝም ። ለውላዋ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ሉል ፡ (ዐረ ፡ ሉእሉእ) ፤** በቁሙ ፡ ዕንቍ ፡ የዕንቍ ፡ ስም ፡ ባሕርይ ፡ ከሰደፍ ፡ የሚገኝ ፡ ነገሥታት ፡ እንደ ፡ ሎሚና ፡ እንደንቍላል ፡ የሚጨብጡት ። በሉሉ ፡ በዘውዱ ፡ እንዲሉ ። ብሕረንና ፡ ቆቅሖን ፡ ዐንቀን ፡ እይ ፡ (አርጋ) ።



ሉል ፡

**ሎሚ ፡ ሎሚን ፤ (ብ ፡ ለዋሚን ፡ አው ፡ ሎሚናት ። ዕብ ፡ ሊሞን ። ሱር ፡ ሊሙን ። ዐረ ፡ ለይሙን) ፤** በቁሙ ፡ የታወቀ ፡ ዕፀ ፡ እሾኽም ፡ መዐዛው ፡ ጥፍጥ ፡ ፍሬው ፡ የሚመጠጥ ፡ መጣጣ ፡ ሖምጣጣ ። ዘሩ ፡ ለምለመ ፡ ነው ፡ ሎሚ ፡ ያማርኛ ፡ ሎ



ሎሚን፤

ሚን ፡ የግእዝ ፡ በትግሬኛ ፡ ማን ፡ ሎሚ ፡ የም ፡ ማለት ፡ ነው ። ማየ ፡ ሎሚ ፤ ወይመትኑ ፡ ሎሚኒ ፡ (መ ፡ ፈ) ።

**ሉጺት ፤—ቡሒ ፡ መላጣ ፤—ላጸየ ።**

**ሌውቄን ፤ (ጽር ፡ ሌፋኪ) ፤** ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ወይራ ፡ (ኢሳ፵፰ ፡ ፲፱ ። ሌዊቄን ፡ ኤሌዊቄን ፡ ይላል ፡ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ለዊስ ፡ ሰት ፡ (ሎሰ ፡ ይለውስ ፡ ይሉስ ። ዕብ ፡ ሉሽ ። ሱር ፡ ላሽ ። ዐረ ፡ ላስ) ፤** መለወስ ፡ ማቡካት ፡ መፈትፈት ፡ ማጨማለቅ ። ሰፈጸን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ነሥአት ፡ ሐሪጸ ፡ ወሎሰት ። ለዊሶሙ ፡ ያምጽእዎ ። ሎስ ፡ ጸቡረ ፡ ልምሉመ ፤ (፩ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፳፬ ። ፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፰ ። ዘሌ፯ ፡ ፲፬ ። ጥበ ፲፭ ፡ ፯) ።

**ቶሎስ ፤** ቀበኮ ፡ ቀለወስ ። ናእት ፡ ዘኢቶሎስ ፡ በብሒእ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ልዉስ ፤** የተለወሰ ፡ የተቦካ ፡ የታሸ ። ልዉስ ፡ በቅብዐ ። ሐሪጽ ፡ ልዉስ ፡ (ዘፀ፳፱ ፡ ፪ ። ዘሌ፯ ፡ ፲ ። ኩፋ ፡ ፯) ።

**ተላወሰ ፤** በቁሙ ፡ ተለዋወሰ ፡ ተንቀሳቀሰ ፡ ታወከ ፡ ተነማማ ። እስመ ፡ ትትላወስ ፡ ኀሊናሆሙ ፡ (ምሳ ፳፯ ፡ ፲) ።

**ሉሲፌር ፡ (ሮማይ) ፤** የዲያብሎስ ፡ ስም ፡ ከሹመቱ ፡ በፊት ፡ የነበረው ። ጸዋሬ ፡ ብርሀ ፡ ፍድፋደ ፡ ብርሀ ፡ ቢጉ ፡ ብሩሀ ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቤ ገዝን ፡ እይ ፡ (ኢሳ፲፬ ፡ ፲፪) ። በትቢቱና ፡ በጕሬቱ ፡ ብዛት ፡ ሳጥናኤል ፡ ከኾነ ፡ በኋላ ፡ ስመና ፡ ብርሃናው ፡ ኮከብነቱ ፡ ለዳግማይ ፡ አዳም ፡ ተሰጥቷል ፡ (ዘኍ፳፬ ፡ ፲፯ ። ማቴ፪ ፡ ፪ ። ፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፱) ።

**ሌዋታን ፤ (ዕብ ፡ ሊውያታን) ፤** የባሕር ፡ አውሬ ፡ እንስሳ ፡ ዘንዶ ፡ ታላቅ ፡ ጓማ ፡ ማናቸውም ። እንስት ፡ ዐንበሬ ፡ ምድርን ፡ እንደ ፡ ዝናር ፡ እንደ ፡ ጋን ፡ ሰንበር ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ቀለበት ፡ እንዲገነባር ፡ ዙሪ ፡ ተጠምጥሞ ፡ ዐቅፎ ፡ የያዘች ፡ የብሂሞት ፡ ዘውግ ፡ ጣምራው ፡ ኹለተኛው ፡ ዘሩ ፡ ለወየ ፡ ነው ፡ ሉዋ ፡ ዐቃፊ ፡ ተጠምጣሚ ፡ ታን ፡ ዘንዶ ፡ ወይም ፡ ጠርዶና ፡ ቁመት ፡ ግዘፈ ፡ ምድር ። በትግርኛ ፡ የምድር ፡ መታጠቂያ ፡ ቅናት ፡ መቀነት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብሂሞትንና ፡ ዐንበሬን ፡ እይ ። ወፀቀብከ ፡ ደእተ ፡ አሚረ ፡ ክልኤተ ፡ እንስሳ ፡ ወሰመይካሁ ፡ ለአሐዱ ፡ ብሂሞት ፡ ወለካልኡ ፡ ሌዋታን ። ወፈለጥኮሙ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ እስመ ፡ ኢይክል ፡ ዝኩ ፡ ሳብዕተ ፡ እዴ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ማየ ፡ ናጌብ ፡ ጸዊሮቶሙ ፡ ወወሀብካሁ ፡ ለብሂሞት ፡ አሐደ ፡ እደ ፡ የብስ ፡ ወለሌዋታን ፡ ሳብዐተ ፡ እዴሁ ፡ ስርጡብ ፡ (ሱቱኤል ፡ ፮ ፡ ፵፱—፶፪) ።

**ሌምጼጤርያ ፤ (ጽር ፡ ሌምፔትሪያ) ፤** ለውጽ ፡ ደንጊያ ፡ ስሬ ፡ ዝርግ ፡ ንጥፍ ፡ (ሕዝ፵፪ ፡ ፯ ፡ ፰) ።

**ለዚገዝ ፡ ዞት ፤ (ለዘ ፡ ይለዝዝ ፡ ይልዝዝ) ፤** መልዘዝ ፡ መራስ ፡ መለስለስ ። ለስዚገዝን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ። ለዘ ፡ ላዘ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ምስጢሩም ፡ ጣዕምና ፡ ውበት ፡ ለበጎነት ፡ ነው ፡ ለዛ ፡

የነገር ፡ ላዛ ፡ የጠጕር ፡ ላሕሟ ፡ እንደ ፡ ማለት ። ለዛ ፡ ቢስ ፡ ክፉ ፡ ደረቅ ፡ ጣዕመ ፡ በልጣ ።

**ልሕደ** ፤ (**ልሕየ**) ፤ ለደለደ ፤ ወፈረ ፤ የተልባ ፡ ያብሽ ፡ የምራቅ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። አማረ ፡ ወየዘረ ፤ ተደላደለ ፡ ተቀማጠለ ። አሻረተ ፡ ጠነቋለ ፡ በሾኽ ፡ በን ቅፋት ፡ በድምፀ ፡ አራዊት ፡ በማናቸውም ።

**ለሓዲ** ፤ (**ዲት ፡ ድያን ፡ ያት**) ፤ የሚያሻ ርት ፡ ሻርተኛ ፡ ጠንቋይ ። ለሓዲ ፡ በትእምርት ፡ ወ ዘይትኣመር ፡ በንቅወተ ፡ አርዌ ፡ (ቈስጠ ፡ ፲፫) ።

**ልሑድ** ፤ (**ዳን ፡ ዳት ፡ ሕድ**) ፤ የለደለደ ፡ ወ ፍራም ። ድልድል ፡ ቅምጥል ፡ ምሥራና ፡ መከራ ፡ የማይ ችል ። ኢትበመዩ ፡ **እንከ ፡ ልሑደ ፡ ወሥብሕተ** ። **አ ንቲ ፡ ልሕድ** ፡ (ኢሳ፵፯ ፡ ፩ ፡ ፰ ። ሚክ፩ ፡ ፲፮) ።

**ላሕም** ፤ **ዎት** ፤ (**ላሐወ ፡ ይላሑ ። ዐረ ፡ ናሐ ። ዕብ ፡ ናሃህ ። ሱር ፡ ንሃእ**) ፤ ማልቀስ ፡ ማ ዘን ፡ ማሞሽ ፡ መራኰት ፡ መንሰቅሰቅ ። **ጊዜ ፡ ለላሕዎ ፤ ወጊዜ ፡ ለዘፈን** ። **ወላሐዉ ፡ ሕዝብ** ። **እለ ፡ ይላሕ ውዋ ፡ ለጽዮን** ። **ላሑ ፡ ምስለ ፡ ዘይላሑ** ፡ (መክ፫ ፡ ፬ ። ሰንገ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ። ኢሳ፷፩ ፡ ፫ ። ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭) ።

**ልሕው** ፤ (**ዋን ፡ ዋት ፡ ሑት**) ፤ ያዘነ ፡ ያለ ቀሰ ፡ እንባ ፡ የፈሰሰበት ፡ ሐዘን ፡ የመላበት ። **ለልሕዋን ፡ ይናዝዘሙ** ፡ (ኪዳ) ።

**ላሕ** ፤ (**ብ ፡ ላሓት**) ፤ ልቅሶ ፡ ሐዘን ። **ቤተ ፡ ላሕ ። አልባሰ ፡ ላሕ ። መዋዕለ ፡ ላሕ ። ገብሩ ፡ ላሐ ። ዝንቱ ፡ ሠለስቱ ፡ ላሕ** ፡ (ሚራ፴፱ ፡ ፯ ። ፱ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ። ዘዳ፴፬ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ኩፋ) ።

**ላሓዊ** ፤ (**ላሐወ**) ፤ የሚያለቅስ ፡ የሚያዝን ፡ አልቃሽ ፡ ዐዛኝ ።

**ላሓዊ** ፤ (**ላሕ**) ፤ ልቅሰኛ ፡ ሐዘንተኛ ፡ የልቅሶ ፡ ሰው ፡ እንባም ።

**አልሐወ** ፤ **አላሐወ** ፤ አሳዘነ ፡ አስለቀሰ ። ሣቀይዋ ፡ ወአልሐውዋ ፡ (ሬእ፲፰ ፡ ፯) ።

**ልሒሕ** ፤ **ሖት** ፤ (**ለሕሐ ፡ ይለሕሕ ፡ ይ ልሐሕ ። ዕብ ፡ ሌሐ ። ሱር ፡ ላሕላሕ**) ፤ መርጠብ ፡ መለዘብ ፡ መራስ ፡ መሰስለስ ፤ የገላ ፡ የንጨት ፡ የቀርበት ።

**አልሕሐ** ፤ (**ሱር ፡ ላሕሌሕ**) ፤ አራሰ ፡ አረ ጠበ ፡ አለዘበ ። እና ፡ እፍ ፡ እንትፍ ፡ እንትፍ ፡ ወይም ፡ እፍፍ ፡ እንትፍትፍ ፡ እለ ፡ ለማብረድ ፡ ለማንደድ ። **ዘ ይልሕሓ ፡ ለትዝኅርቱ ፡ ያነድዳ ፡ ለእሳት** ፡ (ሚራ፳፰ ፡ ፲፩) ።

**ላሕልሐ** ፤ (**ለሕሐ ። ሱር ፡ ሂትላሕላሕ**) ፤ ራሰ ፡ ረጠበ ፡ ልሕሉሕ ፡ ኾነ ፡ ሎኸ ፡ ሎኸ ፡ አለ ፡ በሰለ ፡ የፍሬ ፡ የዕበጥ ። **ዘይሜህር ፡ ወኢይገብር ፡ ይመስል ፡ ገብላ ፡ ዘውስቴቱ ፡ ማይ ፡ እምነሁ ፡ ይሰትዩ ፡ ብዙ ኃን ፡ ወይትነፀሉ ፡ ወቦቱ ፡ ይላሕልሕ ፡ ግብር ፡ ወሰ ሲሁሰ ፡ ኢይሰቲ ፡ ወኢይነጽሕ ፡ እምርስሐታቲሁ ፡ ወኢይላሕልሕ ፡** (ፊልክ ፡ ፶፱) ።

**ልሕሉሕ** ፤ (**ሓን ፡ ሓት ፡ ልሕት**) ፤ በ ቁሙ ፡ የራሰ ፡ የጥብ ፡ ለስላሳ ፡ ልዝብ ። **እብሰሎ ፡ ኅ ቡረ ፡ ወገብሮ ፡ ልሕሉሐ ፡ ወአፍአሞ ፡ ለክይሲ** ፡ (ዳን ፲፫ ፡ ፳፯) ።

**ላሕልሐ** ፤—**ላላ ፡ ረገበ** ፤—**ላኅልኀ** ።

**ላሐየ** ፤—**ተፃወተ ፡ አፃወተ** ፤—**ላ ህዮ ፡ ላሀየ** ።

**ልሕይ** ፤ **ዮት** ፤ (**ልሕየ ፡ ይልሒ ፡ ይል ሐይ ። ዐረ ፡ ላሐ ። ሱር ፡ ልሓእ**) ፤ መውዛት ፡ መቅለጥለጥ ፡ ማማር ፡ ማሸብረቅ ። **እስመ ፡ ትልሒ ፡ ይእቲ ፡ በሥን ፡ እምፀሓይ ። በላዕ ፡ ለገጽኪ ፡ ዘ ጥቀ ፡ ይልሒ** ፡ (ጥበ፯ ፡ ፳፱ ። ደራሲ) ።

**ተልሕየ** ፤ ተጌጠ ፡ ተሸለመ ፡ ተኳለ ፡ ተቀባ ፡ ለማማር ፡ መልክ ፡ ለመጨመር ። **ወእንዘ ፡ አይሁድ ፡ በዝ ፡ በዓል ፡ ይትለሐዩ ፡ በአዕጹቀ ፡ በቀልት ። ወኅሩ ያን ፡ በቅድሜሁ ፡ ይትለሐዩ ፡ ከመ ፡ ብርሃነ ፡ እሳት** ፡ (ዮሴፍ ። ሔኖ፵፱ ፡ ፯) ።

**ልሑይ** ፤ (**ያን ፡ ያት ፡ ሒት**) ፤ በቁሙ ፡ ወዛም ፡ ደመ ፡ ግቡ ፡ ያማረ ፡ ያጌጠ ፡ ውብ ፡ ግሩም ፡ መልከ ፡ መልካም ። **ብእሲ ፡ ልሑይ ። ወክኑ ፡ ልሑ ያነ ፡ በብርሃነ ፡ ዐቢይ** ፡ (ዮሴፍ ። አቡሻ) ። በልሑይ ፡ ፈንታ ፡ ለሓዪ ፡ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹሉ ፡ ላሕይ ፡ ይባል ፡ የጣራና ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **ገጽከ ፡ ላሕይ ። ላሕይ ፡ አዕይንቲሁ ። ላሕይ ፡ ጥቀ ፡ ራእያ ። ሶስና ፡ ላሕይት ፡ ጥቀ ። ደናግል ፡ ላሕያት** ፡ (ማሕ፪ ፡ ፲፬ ። ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፪ ። ኩፋ ፡ ሺ፰ ። ዳን፩ ፡ ፴፩ ። ዓሞ፰ ፡ ፲፫) ።

**ላሕይ** ፤ (**ያት**) ፤ ገጽ ፡ ፊት ፤ በገጽ ፡ ላይ ፡ ያ ለው ፡ መልክ ፡ ውበት ፡ ወዝ ፡ ደም ፡ ግባት ፤ ግርማ ፡ ሞገስ ። **ኢታድሉ ፡ ለሰብእ ፡ እንበይነ ፡ ላሕዩ ። ኢያ ስሕትከ ፡ ላሕያ ፡ ለብእሲት ። ተደመ ፡ እምነ ፡ ሥና ፡ ወላሕየ ፡ ገጻ ። ላሕያ ፡ ጼወዋ ፡ ለነፍሱ** ፡ (ሢራ፲፩ ፡ ፪ ። ፳፭ ፡ ፳፩ ። ዮዲ፲ ፡ ፳፫ ። ፲፮ ፡ ፲፩) ።

**ልሒኰ** ፤ **ኰት** ፤ (**ለሐኰ ፡ ይልሕኰ ፡ ይልሐኰ ። ዕብ ፡ ላሐኽ ፡ ላሰ ። ያጺር ፡ ሠራ**) ፤ መሥራት ፡ መፍጠር ፡ መሣል ፡ መቅረጽ ፡ የጭቃ ፡ የማ ዕደን ። **ይልሕኰ ፡ እምውስተ ፡ ውእቱ ፡ ጽቡር ፡ አ ምላከ ። በእደዊሁ ፡ ለሐኰኒ ። እደዊከ ፡ ገብራኒ ፡ ወለሐኳኒ ። ንልሐኰ ፡ ውስተ ፡ ልባቢነ ፡ ተዘክሮ ፡ እግዚ ፡ ወፈሪሀ ፡ ስሙ** ፡ (ጥበ፲፭ ፡ ፰ ። መቃ ፡ ገ፳፪ ። መዝ ፻፲፰ ። አፈ ፡ ተ፳፯) ።

**ለሓኪ** ፤ (**ኩት ፡ ኰያን ፡ ያት**) ፤ የሚሠራ ፡ ሠሪ ፡ ፈጣሪ ። **ይብሎኑ ፡ ልሕኵት ፡ ለለሓኪሁ ። ለ ሓኪ ፡ ወፈጣሪ** ፡ (ኢሳ፳፱ ፡ ፲፮ ። አፈ ፡ ድ፪) ።

**አልሐኰ** ፤ አሠራ ፡ አስፈጠረ ።

**ተልሕኰ** ፤ ተሠራ ፡ ተፈጠረ ። **ዘተልሕኰ ፡ ቅድመ ። እምድር ፡ ተልሕኰ ፡ ብእሲ ። ተልሕኮተ ፡ ሥጋ ፡ ቀደመ ፡ እምንፍሃተ ፡ ነፍስ ። ዛቲ ፡ ነፍስ ፡**

እንተ ፡ ተልሕኵት ፡ በኢያምሳሊከ ፡ (ጥበ፯ ፡ ፩ ። ኪዳ ። ማር ፡ ይሥሐቅ ፡ ፱ ። ማኅቡ) ።

**ልሑኵ** ፡ (ኳን ፡ ኳት ፡ ሕኵት) ፡ የተሠራ ፡ የተፈጠረ ፡ ሥር ፡ ፍጡር ።

**ልሕኵት** ፡ (ቃት) ፡ የተሠራች ፡ የተፈጠረች ። ሸክላ ፡ ሥጋ ፡ ሰው ፡ ያሙስና ፡ ደርብ ፡ ፍጥረት ። ልሕኵት ፡ ዘቦቱ ፡ ሰብሰልዎ ። ልሕኵት ፡ ንጽሕት ። ልሕኵተ ፡ እግዚአብሔር ። ከዐወ ፡ ደሞ ፡ በሥምረቱ ፡ ላዐለ ፡ ልሕኵቱ ፡ (ዘሌዋ ፡ ፳፩ ። ውዳ ፡ ማርያ ። መቃ ፡ ገጽ፱ ። ቅዳ) ። ልኩዕትንትና ፡ ልኩዕትንትን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ላሕልሐ** ፡—ራሰ ፡ ረጠበ ፡—ልሒሐ ፡ ለሕሐ ።

**ላሕልሐ** ፡—ላላ ፡ ረገበ ፡—ላኅልኀ ።

**ልሕመ** ፡ (ሰብ ፡ ላሕም ፡ በላ ፡ ወጋ ። ሰ፡ር ፡ ልሐም ፡ ላሰ ። ዐረ ፡ ለሂመ ፡ በላ ፡ አጓመጠ) ፡ ላመ ፡ ደከመ ፡ ለዘበ ፡ ለሰለሰ ፡ የደቂት ፡ የዐይን ፡ የጠጕር ፡ የቋርበት ። ቀጥቅጥ ፡ ወሕርጽ ፡ እስከ ፡ ይልሕም ፡ (መ ፡ ፈ) ።

—፡ ጸና ፡ ባሰ ። ሰብእሰ ፡ እኩይ ፡ ወእርጉ ፡ ምድር ፡ ይልሕም ፡ እከዩ ፡ (ቄር) ።

**ልሑም** ፡ (ማን ፡ ማት ፡ ሕምት) ፡ የላመ ፡ የለዘበ ፡ ልም ፡ ልዝብ ፡ የከፋ ፡ የባሰ ።

**አልሐመ** ፡ አላመ ፡ አስላመ ፡ ሰለሰሙንና ፡ አስለመኑ ፡ እይ ።

—፡ አጸና ፡ አባሰ ። አልሐሙ ፡ በእንተ ፡ ተጻብኦቶ ፡ ክቡተ ፡ ወገሃደ ። በእንተ ፡ ዝኬ ፡ ያልሕሙ ፡ ሰይጣናት ፡ ተጻብኦቶሙ ። አልቦ ፡ ዘበቍዓ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘአልሐማ ፡ (ፊልክ ፡ ፳ ። ፴ ። ማርቆ ፡ ፳፯) ።

**ልሔም** ፡ (ማት ። ሰብ ፡ ሌሔም) ፡ ኀብስት ፡ እንጀራ ፡ ክላመ ፡ ክለዘበ ፡ ይቂት ፡ የሚሠራ ፡ ሲበሉት ፡ የሚልም ፡ የሚጥም ። ኤፍራታ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ (ዘፍጥ፴፭ ፡ ፲፱) ። ወአምጽኡ ፡ ልሔምሙ ።

**ልሔምት** ፡ (ቃት) ፡ ሲማት ፡ መብል ፡ የጎጀሬ ፡ መዝገብ ።

**ላሕም** ፡ (ብ ፡ አልሕምት ። ሰብ ፡ ልሐም ፡ ሥጋ ። ዐረ ፡ ለሕም ፡ ሥጋ) ፡ በቁሙ ፡ ላም ፡ ቋም ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፡ የላም ፡ መንጋ ፡ የቤት ፡ እንስሳ ፡ ታርዶ ፡ የሚበላ ፡ ታልብ ፡ የሚጠጣ ፡ ተጠምዶ ፡ የሚያርስ ። ሰሬር ፡ እንስሳትም ፡ ለጕሽ ፡ ላጋዘን ፡ ይነገራል ፡ ላሕም ፡ ያንድነት ፡ ስም ፡ ነው ፡ ተባቱም ፡ አንስቱም ፡ ታላቁም ፡ ታናሹም ፡ ላም ፡ ይባላል ። ዘይቤሙ ፡ ሥጋማ ፡ ሥጋም ፡ ተጥጊ ፡ ቀንዳም ፡ በላቱም ፡ ዘዳም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የጠጕሩን ፡ ልሙት ፡ የጠባዩንም ፡ ልዝብነት ፡ ገርነቱን ፡ ገራምነቱን ፡ ለዉም ፡ ያሳያል ። ላሕም ፡ አእመረ ፡ ዘአጥረዮ ። ላሕም ፡ ወሲደት ፡ በግዐ ። አባግዐ ፡ ወአልሕምተ ። አልሕምት ፡ ኢይመክና ። አልሕምት ፡ ገዳም ፡ (ኢሳ ፡ ፩ ። ዮሴፍ ። መገ ፡ ፶ ። ኢዮቤል ፡ ፲ ። ፍ ፡ ን ፡ ፶፱ ፡ ፪) ። ቁም ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ ቀጥሚ ፡ ቅዉም ፡ ቋም ፡ ነገራም ፡ ደግ ፡ ደገኛ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ሙሾ ፡ ፪ ፡ ሴቶች ፡ ስላሽ ፡ ወንድማቸው) ፡ ማ ፡ ቁም ፡ ከናውራሙ ፡ ሰጥተው ፡ ቢሮሩት ፡ እሽቱ ፡ ቀጸላ ፡ ይበላል ፡ እንገሮት ። መቼ ፡ አየሽሙና ፡ እንኝም ፡ እንደ ሴላ ፡ የት ፡ እንገሮት ፡ ይበላል ፡ እሽቱ ፡ ቀጸላ ።

**ላሕም** ፡ የባሕር ፡ ጉማሬ ፡ እንደ ፡ ዱኖ ፡ ያስ ወህሎ ፡ አሐዱ ፡ ላሕም ፡ ዘይወፅእ ፡ እምአሐዱ ፡ ባሕር ፡ ጽዩእ ፡ በሀገረ ፡ ክፊክ ፡ ወይቤሉ ፡ እስመ ፡ የዐርግ ፡ አሐዱ ፡ ላሕም ፡ በበ ፡ ዓመት ፡ ወሰበ ፡ የሐውር ፡ በሐይቀ ፡ ባሕር ፡ ይትከፈል ፡ ወይከውን ፡ ፒሳ ፡ ወይሠይጥዎ ፡ ለሰብእ ፡ አፍራጊያ ፡ ይቀብዑ ፡ ኪያሁ ፡ ቦቱ ፡ አሕማሮሙ ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፳፱) ።

**ለሐማ** ፡ (ዐረብ) ፡ በቁሙ ፡ የማስደኛት ፡ መማዘቅ ።

**ለሐፈ** ፡ (ዐረ ፡ ለሂፈ) ፡ ዐዘነ ፡ ተከዘ ፡ ተጨነቀ ፡ ዐሰበ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሌሐፈ ፡ ፈንታ ፡ ተልሕፈ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ውስተ ፡ ዘኢክነ ፡ ትካዝከ ፡ ኢትትለሐፍ ፡ (ሢራ ፡ ፲፬ ፡ ፱) ።

**አልሐፈ** ፡ **አስተልሐፈ** ፡ አሳዘነ ፡ አስጨነቀ ። ዘኅቡእስ ፡ ኢያስተልሕፍክ ፡ (ሢራ ፡ ፳፱) ።

**ተልሐፍ** ፡ ሐዘን ፡ ጭንቅ ። ወምንት ፡ ተልሓፍየ ፡ ለዘአፍአ ፡ እኳንዋ ፡ (ጸሎቶ ፡ ሐ ፡ ፲፱) ።

**ለሐጸ** ፡ (ሰብ ፡ ላሐጽ ፡ ለተመ ፡ አጣበቀ) ፡ ላጠ ፡ መለጠ ፡ ቀረፈ ፡ ገፈፈ ። ሥረዊሁ ፡ ይረምፅ ፡ በእሳት ፡ ወይልሕጹ ፡ (መ ፡ ፈ ። ዘፍጥ ፡ ፴፯) ።

**ተልሕጸ** ፡ ተላጠ ፡ ተመለጠ ። ገጹ ፡ ወሥጋሁ ፡ ተልሕጸ ፡ (ግድ ፡ አዳ) ።

**ልሑጽ** ፡ (ጻን ፡ ጻት ፡ ሕጽት) ፡ የተላጠ ፡ የተመለጠ ። ለልጥ ፡ ጉማዳ ።

**ልሕጽ** ፡ (ጻት) ፡ ልጥ ፡ ቅርፍት ፡ ቁረት ። (ቁረት) ፡ የሺ ፡ ፍልጥ ፡ ማስፈያው ፡ ልጥ ። ልሕጸ ፡ ዕፀዋም ። ልብሱ ፡ ለአባ ፡ ሙሴ ፡ እምልሕጸ ፡ ሆሳዕና ፡ ወቈጽሉ ፡ (ስንክ ፡ ሐም፲ ። መስጸ) ።

**ልሕቀ** ፡—ላቀ ፡ አደገ ፡—ልሂቅ ፡ ልሆቀ ።

**ለሐቀ** ፡ (ዐረ ፡ ለሒቀ) ፡ ለጠቀ ፡ አጣበቀ ፡ አጣብቆ ፡ ያዘ ።

**መልሕቅ** ፡ (ቃት ፡ መላሕቅ) ፡ በቁሙ ፡ የመርከብ ፡ ልጓም ፡ እንዳይኼድ ፡ እንዳይናወጥ ፡ የሚገታው ፡ እንዳልጋ ፡ እግር ፡ አራት ፡ ኹዋ ፡ ፪ቱ ፡ በፊት ፡ ፪ቱ ፡ በኋላ ፡ በፊቱ ፡ ማእዝን ፡ የሚወርድ ፡ ታላቅ ፡ ዘነና ፡ ብረት ፡ የጕዳ ፡ በሬ ፡ ቀንድ ፡ የሚመስል ። ሳትሮንክም ፡ ብረት ፡ ሰይብልብሉ ፡ ይነገራል ። ወረድኩ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ከመ ፡ መልሕቅ ፡ ታሕተ ። አውረዱ ፡ አርባ

ዕተ፡ መልሕቃተ፡፡ ወመተሩ፡ መላሕቀ፡(ዮና፪፡ ፮፡ ግብ፳፯፡ ፳፱፡ ፵፡ አፈ፡ ድ፲፩)፡፡



መልሕቅ፡

—፤ መጽሐፍ፤ የመጽሐፍ፡ ስም፡፡ እንክሮመስን፡ እይ፤ ከዚህ፡ ጋራ፡ አንድ፡ ነው፡፡ ይቤ፡(ኤጲፋንዮስ)፡ በውስተ፡ መጽሐፉ፡ ዘይሰመይ፡ መልሕቅ፡(ሃይ፡ አበ)፡፡

ልሕሰ፤—ጠፉ፡ ቃጣ፤—ልሀሰ፡፡

ለሐሰ፤(ዐረ፡ ለሐሰ፡፡ ዕብ፡ ወሱር፡ ላሓኽ)፤ ላሰ፡ ተመሰ፡ ዘላ፡ ጠጣ፡ ምላሱን፡ አንቀሳቀሰ፡ ጠረገ፡ አበሰ፡፡ ከለባት፡ ይልሕሱ፡ ቍስሊሁ፡፡ ለሐሱ፡ ከለባት፡ ደሞ፡፡ እሳት፡ በልዐት፡ መሥዋዕቶ፡ ወለሐሰት፡ መሬቶሂ፡፡ ኢትልሐስ፡ መዳብኅተ፡(ሉቃ፲፮፡ ፳፩፡፡ ፫ነገ፡ ፳፩፡ ፲፱፡፡ ፲፰፡ ፴፰፡፡ ሢራ፡ ፴፱፡ ፲፱)፡፡

—፤ መጠጠ፡ መጠመጠ፡፡ በከመ፡ ይልሕስ፡ ጽሙእ፡ ወይሰቲ፡ እምነ፡ ዠሉ፡ ማይ፡(ሢራ፡ ፳፮፡ ፲፪)፡፡

—፤ ደረቀ፡ ኩበት፡ ላሽ፡ ዘገ፡፡ ይልሕስ፡ ልሳኖሙ፡ በጽምእ፡(ኢሳ፵፩፡ ፲፯)፡፡

—፤ አሰላ፡ አሾለ፡ አሾተለ፡ ለመሳል፡ ለማልመጥ፡ ወይም፡ በነገር፡ ለመጕነጥ፤ ምስጢሩ፡ የሰንብ፡ ነው፡፡ ከልብ፡ ጥቀ፡ ኢይልሕሶሙ፡ በልሳኑ፡፡ ሊልቦ፡ ዘለሐሶሙ፡ በልሳኑ፡፡ ከልብ፡ ኢይልሕስ፡ ልሳኖ፡ በቅድሜከ፡ አሳባቂ፡ ነገረ፡ ሠሪ፡(ዘፀ፲፩፡ ፯፡፡ ኢያ፲፡ ፳፩፡፡ ዮዲ፲፩፡ ፲፱)፡፡

ምልሓስ፤ ምላስ፡ ልሳን፡ አንደበት፡ መላሻ፡ መቅመሻ፡ መናገሪያ፡፡ ለበላላ፡ ልበልበ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ የወጣ፡ ነው፡፡ (ተረት)፤ በሰምለም፡ ምላሱ፡ በሠላሳ፡ ጥርሱ፡፡

ልኅደ፤—ለደለደ፤—ልሕደ፡፡

ላኅልኀ፤—ራሰ፡ ረጠበ፤—ለሐሐ፡ ለሕሐ፡፡

ላኅልኀ፤(ራኅርኀ)፤ ላላ፡ ረገበ፡ የገመድ፡ የአውታር፡ የኀሲና፡፡ ንትዐቀብ፡ ከመ፡ ኢይላኅልኅ፡ መዝርዐ፡ ሐመርነ፡ በአፍቅሮ፡ ውሉድ፡(አፈ፡ ተ፴፱)፡፡ ላሰልዐንና፡ ራኅርኅን፡ እይ፡ የዚህ፡ መንትያ፡ ነው፡፡

ልኅሉኅ፤(ኃን፡ ኃት፡ ልኅት)፤ የላላ፡ የረገበ፡ ልል፡፡ ሰብ፡ ይከውን፡ አውታረ፡ መሰንቆ፡ ልኅሉኀ፡ ይጠፍእ፡ ቃናሁ፡ እመ፡ ኢተሰሕበ፡ ዘከመ፡ ይደሉ፡፡ እሉ፡ እንው፡ ኮኑ፡ ልኅሉኃነ፡(አፈ፡ ተ፳፱፡፡ ራእ፡ ፶፱)፡፡

ልኅላኄ፤ መላላት፡ መርገብ፡ መድከም፡ መዛል፡ መሰነፍ፡ መዝለፍለፍ፡፡ በእንተ፡ ልኅላኄ፡ ኀሲናሁ፡ ወሕከከ፡ በእንተ፡ ድካመ፡ ሥጋሁ፡፡ እምሀኬት፡ ወልኅላኄ፡ አባል፡፡ ልኅላኄ፡ ኀፍረተ፡ ሥጋሁ፡ ለብእሲ፡(ፈል፲፡ ፱፡፡ ፶፱፡፡ ፊ፡ መ፡ ፱፡ ፳)፡፡

ልኅልኅና፤ ልልነት፡ ደካምነት፡ ስንፍና፡፡ ወይቈርር፡ እንከ፡ ርስነ፡ ጥብዐቶሙ፡ በእንተ፡ ልኅልኅናሆሙ፡፡ ዝኬ፡ ውእቱ፡ ልኅልኅና፡ ወሕከ፡ ተቃትሎቶ፡(ፊልክ፡ ፱፡፡ ፻፳)፡፡

አላኅልኀ፤ አላላ፡ አረገበ፡ አሰነፈ፡፡ ያላኅልኆ፡ ለፈቃድ፡ ወለኀቢና፡(ማር፡ ይሥ፲፱)፡፡

ለኈሰ፤(ልሐስ፡ ለሐሰ፡፡ ዕብ፡ ላሐሽ)፤ ለኈሰ፡ አቃጠለ፡ ሹክ፡ አለ፡ በጆሮ፡ ነገረ፡፡ ሾከከ፡ ተንሾከከ፡ በጆሮ፡ ለመናገር፡ ወይም፡ ለመስማት፡ እንደ፡ ቅኔ፡ መሪ፡ እንደ፡ ተመሪ፡፡ ዘሩ፡ ልሒስ፡ ነው፡ አካኼዱና፡ መንገዱ፡ ሰቈረን፡ ይመስላል፡፡

አልኆሰ፡ አልኆሰሰ፤ አሾከሾከ፡ ሹክ፡ ሹክ፡ አለ፡ መላልሶ፡ አብገዞ፡፡ አብሠራ፡ ገብርኤል፡ ለማርያም፡ አልኆሲሶ፡ በእዝና፡ ወይቤላ፡ ትወልዲ፡ ወልደ፡፡ ሙባኡ፡ ለቃል፡ እዝና፡ ርኅው፡ ወሙፃኡ፡ ማኅፀና፡ ዕጽው፡(መዋሥ፡፡ ቅኔ)፡፡

—፤ ደገመ፡ ደጋገመ፡ አልከሰከሰ፡ አውተፈተፈ፡ ቃሉን፡ ሳይሰማ፡ ምላሱን፡ ከንፈሩን፡ ብማንቀሳቀስ፡ የጸሎት፡ የአስማት፡፡ (ተረት)፤ ዳዊት፡ በሹክሹክታ፡ ሳታት፡ በጋጋታ፡፡

ተልኆሰሰ፤ ተሾከሾከ፡ ሰውየው፡ ሹክሹክታ፡ ሰማ፡ ወይም፡ ሹክሹክታው፡ በጆሮ፡ ተሰማ፡፡ በእንተ፡ ዝሙት፡ ዘተልኆሰሱ፡(ማር፡ ይሥ፳)፡፡ ተደገመ፡ ተልከሰከሰ፡ አስማቱ፡ ጸሎቱ፡፡

ተልኋሰሰ፤ ተሾከሾከ፡ ርስ፡ በርሱ፡፡ ዘተልኋሰሱ፡ በእዝን፤(ሉቃ፲፪፡ ፫)፡፡ አብንቱ፡ ግን፡ ዘኒ፡ አልኆሰስክሙ፡ ነው፡፡

ለኆሳስ፤ ሹክታ፡ ሹክሹክታ፡ ምስጢር፡ ቀስታ፡፡ ይትናገሩ፡ በለኆሳስ፡፡ አርእዮሙ፡ በለኆሳስ፡ መጻሕፍቲሁ፡(ኢሳ፳፱፡ ፬፡፡ አክሲ፡ ፲፩)፡፡

—፤ ድጋም፡ ኀቡእ፡ ንባብ፡ ጽሑፍ፡ ልብ፡ ኅሊና፡ ልብ፡ ጸሎት፡ ንፍስ፡፡ ሊልቦ፡ ማኅሊቅተ፡ ቅኑ፡ በልዑል፡ ዜማ፡ ዘእንበለ፡ በለኆሳስ፡፡ ወዓዲ፡ በል፡ በለኆሳስ፡ እግዚኦ፡ መሐረነ፡ ምእተ፡ ጊዜ፡፡ ንጸመም፡ ዐውደተ፡ ልሳን፡ ከመ፡ ዘኢይሰምዕ፡ ወነሐምር፡ ለኆሳሰ፡ ልብ፡(ስንክ፡ ማን፲፩፡፡ ቄድር፡፡ ቅዳ፡ ማሩ)፡፡ አልኆምስሰ፡ ለኆሳስ፡ እያለ፡ በላብስ፡ ይጥፉል፡ ስሕተት፡ ነው፡፡ ግእዝ፡ እንዳስቈቀመና፡ እንዳስቈረረ፡ ቅጥይ፡ ተቀጥላ፡ ነውና፡ ቈቀመንና፡ ቈረን፡ እይ፡፡

ሎጣዊ፤—ሰዶማዊ፤—ሎጥ፡ ለወጠ፡፡

ለጥሐ፤(ዕብ፡ ላጣህ፡ ሰደበ፡ ረገመ)፤ ለጥ፡ አለ፡ እጅ፡ ነሣ፡ ተገዛ፡ ገበረ፡ ተኛ፡ ተጋደመ፡ ተዘረጋ፡፡ ለጥ፡ ይበሉ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ መጥቷል፡፡

**ለጠ.ን ፤ ኖት ፤ (ሊጠነ ፡ ይለጥን ፡ ይል ጥን)፤** ማመልጠን ፡ ማስተዛዘል ፡ መቀባበል ፡ መመላለስ ፡ መሪና ፡ ተመሪ ፡ ወይም ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በመኾን ፡ የዜማ ፡ የንባብ ፡፡ መላልሶ ፡ ማመስገን ፡ መለመን ፡ መለማመጥ ፡ ማቈላመጥ ፡፡ እንጠየንና ፡ አስተብቍዐን ፡ በነጠየና ፡ በበቍዐ ፡ ተራ ፡ ተመልከት ፡፡

**ምልጣን ፤ (ናት)፤** በቁሙ ፡ የዜማ ፡ ምልልስ ፡ ፊት ፡ መሪና ፡ ተመሪ ፡ ቀጥሎ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ አ ንሺዎች ፡ የሚሉት ፡ ይልቁንም ፡ በሥር ፡ በሰይት ፡ በዓላት ፡ በልደት ፡ በጥምቀት ፡ በትንሣኤና ፡ በዕርገት ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ (ድጓ) ፡፡

**ሊጦን ፤ (ጽር ፡ ሊታኒያ)፤** መስተብቍዕ ፡ ልመና ፡ ምልጃ ፡ ዝብዝባ ፡ ቍልምጫ ፡፡ ሊጦን ፡ ዘሰኑይ ፡ ወካዐበ ፡ ናስተበቍዕ ፡ (ቅዳ) ፡፡

**ልጥር ፤ (ጽር ፡ ሊትራ ፡፡ ሱር ፡ ወዕብ ፡ ሊጥራ ፡፡ ዐረ ፡ ረጥል)፤** የሚዛን ፡ ስም ፡ የታወቀ ፡ ሚዛን ፡ ንጥር ፡ ፲፪ ፡ ወቄት ፡ የሚያነማ ፡ በዱሮ ፡ ሒሳብ ፡፡ ነሥአት ፡ ዕፍረተ ፡ ልጥረ ፡፡ ምእተ ፡ ልጥረ ፡፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ልጥረ ፡ ወርቅ ፡ (ዮሐ ፲፪ ፡ ፫ ፡፡ ፲፱ ፡ ፴፱ ፡፡ አፈ ፡ ተ፳) ፡፡

**ለይ ፤—ፈትል ፡ ቀይ ፡ ልብስ ፤—ለወ ፡፡**

**ላይዳ ፤—በቁሙ ፤ ላሜዳ ፤—ለመደ ፡፡**

**ሌዊ ፤ (ዕብ)፤** የሰው ፡ ስም ፡ ፫ኛው ፡ የያዕቆብ ፡ ልጅ ፡፡ ተላዊ ፡ መትልው ፡ ልጁ.ቅ ፡ መስተላጽቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፳፱ ፡ ፴፬ ፡፡ ክፋ ፡፡ ፴፭) ፡፡

**ሌዋዊ ፤ (ው ያን)፤** የሌዊ ፡ ወገን ፡ ካህን ፡ (ሉቃ ፲ ፡ ፴፪ ፡፡ ግብ፬ ፡ ፴፮) ፡፡

**ሌዋውያን ፤** የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ፫ኛው ፡ ብሔረ ፡ ኦሪት ፡ የሌዋውያንን ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ የሚናገር ፡፡ በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ዋይቅራእ ፡ ይባላል ፡ ጸውዐ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ወጸውዖ ፡ እግዚ ፡ ለሙሴ ፡ ያለውን ፡ መዠመሪያን ፡ ቃል ፡ ያሳያል ፡፡

**ሌዌን ፤ (ዕብ ፡ ዊሎን)፤** ስመ ፡ ኃምስ ፡ ሰማይ ፡፡ ኢዮር ፡ ወይም ፡ ጠፈር ፡ ሸኛነቱ ፡ ከላይ ፡ ወደ ታች ፡ ነው ፡ (አዋል) ፡፡ ሰማይንና ፡ ምጽናዓትን ፡ እይ ፡፡

**ሌልዮ ፤ ዮት ፤ (ሌለየ ፡ ይሌሊ ፡፡ ለፊየ ፤ ፊለየ)፤** መለየት ፡ መነጠል ፡ መነጣጠል ፡፡ ይሌሊ ፡ ሥርወ ፡ እመሌሊት ፡፡ ኢፈለጠ ፡ ወኢሌለየ ፡፡ ሌለዮሙ ፡ ለሰራዊት ፡፡ ይሌሊ ፡ አዕርክተ ፡ (ዕብ፬ ፡ ፲፪ ፡፡ ፪ሜፕ ፡ ፳፫ ፡፡ ፪ዜና ፡ ፳፭ ፡ ፲ ፡፡ ምሳ፲፯ ፡ ፳፰) ፡፡

**ሌለየ ፤** ሌሊት ፡ ተነማ ፡ ነቃ ፡ ተጋ ፡ ማለደ ፡ ለሥራ ፡ ለመንገድ ፡፡ ለሰንና ፡ ለልን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ፡፡

**ተሌለየ ፤** ተለየ ፡ ተለያየ ፡፡ ተሌለይ ፡ እምኔየ ፡፡ ናሁ ፡ እትሌለይ ፡ እምዘሎሙ ፡ አዝማዲየ ፡፡ እፎ ፡ ተሌለዩ ፡ (ዘፍ፲፫ ፡ ፱ ፡፡ ማንዘ ፡፡ ሐዋ፳ ፡ ፲፱) ፡፡

**ሊሉይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሊት)፤** የተለየ ፡ የተለያየ ፡ ልዩ ፡ ልዩዩ ፡፡ ሊሉይ ፡ እምነ ፡ ብእሲቱ ፡፡ ተኣኀዎ ፡ አሐዱ ፡ ነፍስ ፡ ውእቱ ፡ በሥጋ ፡ ፍሉጥ ፡ ወሊሉይ ፡፡ ሊሉየ ፡ መልክእ ፡ ወአካል ፡ (ሰንክ ፡፡ ፈላስ ፡ ገ፹ ፡፡ ደራሲ) ፡፡

**ሊላይ ፤** ልየታ ፡ ልዩነት ፡ መለየ ፡፡ ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወሊላይ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ፡፡

**መሌሊት ፤ (ብ ፡ መለያልይ ፡ ያት) ፤** ሕዋስ ፡ ብልት ፡ አባል ፡ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ የሥጋ ፡ ዐጽቅ ፡ በየስሙና ፡ በየክፍሉ ፡ በየማውዱ ፡ ሥር ፡ ጎርማት ፡ እበኪት ፡፡ ገመዱ ፡ መሌሊቶሙ ፡ ከመ ፡ ሥጋ ፡፡ ትጠብሖ ፡ በበ ፡ መሌሊቱ ፡፡ መለያልየ ፡ አዕፅምቲሃ ፡፡ መሌሊተ ፡ ሐቌሁ ፡፡ መለያልያት ፡ ኅቡረ ፡፡ ወብከ ፡ መለያልይ ፡ ዝኩ ፡ ዘታስተሐቅሮ ፡ (ሚክ፫ ፡ ፫ ፡፡ ዘፀ፳፱ ፡ ፲፯ ፡፡ መሳ፲፱ ፡ ፳፱ ፡፡ ዳንኤ ፡ ፭ ፡፡ አፈ ፡ ተ፭ ፡፡ ፩ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፳፪—፳፬) ፡፡

**ሌሊት ፤ (ብ ፡ ለያልይ ፡፡ ዕብ ፡ ላይል ፤ ላይላ ፡፡ ሱር ፡ ሌልያ ፡፡ ዐረ ፡ ለይል ፡ ለይለት)፤** በቁሙ ፡ ሌት ፡ ሊሉይ ፡ እመዓልት ፡ ጨለማ ፡ የጨለማ ፡ ጊዜ ፡ ከሠርክ ፡ እስከ ፡ ነግህ ፡ ከማታ ፡ እስከ ፡ ጧት ፡ ከኮከብና ፡ ከጨረቃ ፡ በቀር ፡ ፀሐይ ፡ የማይታይበት ፡ የሦም ፡ እኩሌታ ፡ መንፈቀ ፡ ዕለት ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፭ ፡፡ መዝ፹፰ ፡ ፳፭)፡፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡፡ ወአርብዓ ፡ ለያልየ ፡ (ኢሳ፳፭ ፡ ፲፪ ፡፡ ማቴ፬ ፡ ፪) ፡፡

**ሊሊት ፤ (ዕብ)፤** የሌቶፍ ፡ ከቀን ፡ አዕዋፍ ፡ የተለየች ፡ ዐይጥማ ፡፡ ወይም ፡ ጉጋ ፡ ጉጉት ፤ ፊተ ፡ ክብ ፡ ድመትማ ፡ የቀን ፡ ዳፍንታም ፡ የሌት ፡ ዐይናማ ፡፡ በሊሊት ፡ ፈንታ ፡ ሌሎ ፡ ይላል ፡ ሌሊቶ ፡ ሌሊት ፡ ቀን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ጥሬ ፡ ስዋ) ፡፡



ሊሊት ፡

—፤ ግብረ ፡ ኢጋንንት ፡ ጥንቈላ ፡ ሟርት ፡ ስርቆት ፡ ዝሙት ፡ ጨለማ ፡ ለብዕ ፡ የሚሠሩት ፡ ማናቸውም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ (ዮሐ፫ ፡ ፲፱ ፡ ፳) ፡፡

**አሌለየ ፤** (አሰለየ ፡ አበነጠሰ ፡ አለያየ) ፡፡ ሌሊት ፡ አስነማ ፡ አነቃ ፡ አተጋ ፡ አማለደ ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡፡ ይሌሊ ፡ በጸሎት ፡፡ አሌለያ ፡ ገዩሆ ፡፡ አሌልዮ ፡ ጸሎት ፡፡ አሌለየ ፡ እምህየ ፡ በነግህ ፡ ወአጽዐነ ፡ አድጎ ፡፡ በጽባሕ ፡ ተንሥአ ፡ ወአሌለየ ፡ ጥቀ ፡ (ሉቃ፮ ፡ ፲፪ ፡፡ ፳፱ ፡ ፭ ፡፡ አፈ ፡ ተ፲፱ ፡፡ ክፋ ፡ ፲፰ ፡፡ ማርቆ ፡ ፴፭) ፡፡

**ለከ ፤—ላንተ ፤—ለ ፡፡**

**ለከ.እ ፤ እት ፤ (ለክአ ፡ ይለክእ ፡ ይልክእ ፡፡ ዐረ ፡ ለኪየ ፤ ቀነወ)፤** መለከት ፡፡ መላከክ ፡ መቅባት ፡ መለጠፍ ፡ ማጣበቅ ፡ መቀርቀር ፡ መቸንከር ፡ በሙጫ ፡ በምስማር ፡፡ አምጽአ ፡ ቅንዋተ ፡ ኀጺን ፡ ወለከአ ፡ ውስተ ፡ ብረኪሁ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳) ፡፡

**ለክአ ፤** ጣፈ ፡ ዐተመ ፡ ሣለ ፡ መሰለ ፡ መልክ ፡ አወጣ ፡ በቀለም ፡ በቅርጽ ፡፡ ለካእክዎ ፡ ውስተ ፡ መጽ

ሐፍ ፡፡ ወይልክእ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፍ ፡፡ ሰክኦ ፡ ዝ
ክሮ ፡ (ሚራ፡፴፱ ፡ ፵፱ ። ኢዮ፲፱ ፡ ፳፫ ። ሰንክ) ።

**ለክኢ** ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤ የሚለክ ፡ የሚላክክ ፡ ጣፊ ፡ ለጣፊ ፡ ሠዓሊ ።

**አልክአ** ፤ አስለከ ፡ አስጣፈ ፡ አሳተመ ። እመ ፡ ነታዕክሙ ፡ አልካእክሙ ፡ ለክሙ ፡ ዝንጓጔ ፡ ህልወ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ተለክአ** ፤ ተለከ ፡ ተሰፈረ ። ተጣበቀ ፤ ተቀረቀረ ፡ ተቸነከረ ። ወተለክአት ፡ ሐመር ፡ ማእከለ ፡ አእባን ፡ ልዑላት ፡፡ እስከ ፡ ተለክአ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡፡ አእጋሪከ ፡ በቅንዋት ፡ እለ ፡ ተለክኦ ፡ (ማህ፳፯ ፡ ፶፭ ። ዮሴፍ ። ዲራሲ) ።

—፤ ተጣፈ ፡ ታተመ ፡ ተቀረጸ ። ተለክአ ፡ ዲብዲቆን ፡ ዘማኅበረ ፡ ነቢያት ፡፡ ዲናር ፡ ዘተለክአ ፡ በስሙ ፡ ለቄሳር ፡ (አርጋ ፡ ፫ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ልኩእ** ፤ (እን ፡ እት ፡ ክእት) ፤ የተለከ ፡ የተላከከ ። የተጣበቀ ፡ የተቸነከረ ። ወልኩእ ፡ ዲበ ፡ መሳክዊሃ ፡ በሌዳ ፡ መጽሔት ፡፡ መልክአ ፡ ሥጋሁ ፡ ልኩእ ፡ ላዕለ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ (አዋል ። ሰንክ ፡ ጥር፳፯) ።

—፤ የታተመ ፡ የተጻፈ ። ጽሑፍ ፡ ተዝካር ፡ ውስቴቱ ፡ ወልኩእ ፡ በአምጣነ ፡ ኍልቆሙ ፡፡ ናሁ ፡ ልኩእ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ፋርስ ፡ ወሜዶን ፡ ለተዝካር ፡፡ ወነገሩ ፡ ዘተርፈ ፡ ልኩእ ፡ በመጽሐፉ ፡ (ሚራ፡፴፰ ፡ ፲፭ ። አስቴ፲ ፡ ፪ ። ዮሴፍ) ።

**ልክአት** ፤ መለከት ፡ መጣፍ ፡ ማተም ፡ መታተም ፡ (አርጋ) ።

**መልክእ** ፤ (ኣት) ፤ በቁሙ ፡ መልክ ፡ ገጽ ፡ የፊት ፡ ቅርጽ ፡ ሥዕል ፡ ምስል ፡ ልክ ፡ ያለው ፡ በልክ ፡ የተሠራ ። ዘመኑ ፡ መልክኡ ፡ ወመጽሐፉ ፡፡ መልክአ ፡ ዲናር ፡ ይዌልጡ ፡፡ መልክአ ፡ ገጹ ፡ ለኤልያብ ፡፡ እመ ፡ በጽሑ ፡ መልክኣት ፡ ተርእዩ ፡ በልቡና ፡ (ማቴ፳፱ ፡ ፮ ። ቄር ። ቅዳ ፡ ጎር ። ፈላስ) ።

—፤ አካል ፡ ቁመት ፡ የአካል ፡ ህላዌ ፡ ገላ ፡ ሕዋስ ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ ራስ ። አርአያ ፡ መልክእከ ፡፡ ገጽ ፡ ወመልክእ ፡፡ እሙንቱ ፡ ሠለስቱ ፡ አካላት ፡ ፍጹማን ፡ መልክእ ፡ ወገጽ ፡ (ጥበ፲፯ ፡ ፳፭ ። ሃይ ፡ አበ፯ ፡ ፲፭) ። እግዚ ፡ አክበሮ ፡ ለሰብእ ፡ በአስተማንዮ ፡ ሥነ ፡ መልክእ ፡ በብሉዩ ፡ እምዘመዱ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ፍጹመ ፡ መልክእ ፡ በከመ ፡ ፈጠሮ ፡ እግዚ ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፭ ፡ ፭ ። ፴፫ ፡ ፱) ።

—፤ የድርሰት ፡ ስም ፡ የመልክ ፡ ውዳሴና ፡ መገዘሙር ፡ ከራስ ፡ ጠጕር ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍር ፡ የሚቈጥር ። መልክአ ፡ ኢየሱስ ፡፡

**ምልክእ** ፤ መለኪያ ፡ ልክ ፡ ማተሚያ ፡ ማጣበቂያ ።

**ተላክአ** ፤ ተለካካ ። ተጋጠመ ፡ ተያያዘ ፡ ተጣመረ ። ይትላካእ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ እኍሁ ፡ ወይጣበቁ ፡ ወኢይትፋትሑ ፡ (ኢዮ፵፩ ፡ ፰) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ ግን ፡ ያስተላክክእ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ይትላክእ ፡ ያሰውን ፡ ይጣበቁ ፡ ብሎ ፡ ተርጕሞታል ።

**አስተላክአ** ፤ አላከ ፡ አለካከ ፡ አጋጠመ ።

**ለከወ** ፤ (ከበወ ። ዐረ ፡ ከለ ፡ ደከመ) ፤ ፈዘዘ ፡ በዘ ፡ ደነገዘ ፡ የዐይን ፡ የአእምሮ ። ወብርሃነ ፡ አዕይንትየኒ ፡ ለከወኒ ፡ (መዝ ፡ ፴፯) ።

**አልከወ** ፤ አፈዘዘ ። አልከወኒ ፡ ወጸለሰኒ ፡ አዕይንትየ ፡ (ኢዮ፲፯ ፡ ፯) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ያበሉን ፡ ብዥ ፡ አስይንቴሁ ፡ ይላል ፡ ማፍጠጥና ፡ ማጕረጥ ፡ ያሳያል ።

**ላከዮ** ፤ ዮት ፤ (ላከዮ ፡ ይላኩ) ፤ መለጕጥ ፡ መጓጐጥ ፡ መተጓኰስ ።

**ተላከዮ** ፤ ተለጐጠ ፡ ተላጐጠ ፡ ተጣላ ፡ ተዘበዘበ ፡ ተወዛገበ ፡ ተሻገተ ፡ ተከራከረ ። ኢትትላከይ ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡ ነባቢ ፡፡ ትትላከዩኒ ፡ ወኢተኀፍሩ ፡፡ ወተላኩይዎሙ ፡ ለዐበይቶሙ ፡፡ ኢትትላኩይ ፡ በግብር ፡ ዘኢይበቍዕ ፡ (ሚራ፰ ፡ ፫ ። ኢዮ፲፱ ፡ ፫ ። ነሐ፲፫ ፡ ፲፯ ። ፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፬) ።

**ላኳ** ፤ (አው ፡ ላኬ) ፤ ጠብ ፡ ክርክር ፡ ንዝንዝ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ስድብ ። ማእከለ ፡ ላኳ ፡ ወላኳ ፡፡ ለደም ፡ ይቀድሞ ፡ ላኳ ፡ ወጋእዝ ፡፡ ላኳሆሙ ፡ ለአብዳን ፡ ያጸምም ፡ እዝነ ፡፡ አብድ ፡ እምከመ ፡ ለትየ ፡ ያበዝኅ ፡ ላኳ ፡ (ዘዳ፲፯ ፡ ፰ ። ሚራ፳፪ ፡ ፳፱ ። ፳፯ ፡ ፲፬ ። ፴፱ ፡ ፯) ።

**ለኰመ** ፤ (ዐረ ፡ ለከመ) ፤ መታ ፡ ደሰቀ ፡ ጐሰመ ፡ ኰረኰመ ፡ ገፋ ፡ ገፊዐ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በለኰመ ፡ ፈንታ ፡ አልኰመ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ወግብር ፡ ስግደታተ ፡ ምስለ ፡ አልዝሞተ ፡ ርእስ ፡ ወአንገርግሮተ ፡ ገጽ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ (ፊልክ ፡ ፻፯) ።

(ጥ) **ለከመ** ፤ (ይሌክም ፡ ይለክም) ፤ ለፈለፈ ፡ አባበቀ ። ባለ ፡ ጨመረ ፡ ከንገር ፡ አገባ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ልኰንት** ፤—**ልሕኰት** ፤—**ልኰትንት** ።

**ለክዐ** ፤—**ለከ ፡ ጣፈ** ፤—**ለኪእ ፡ ለክአ** ።

**ለኪፍ** ፡ ፎት ፤ (ለከፈ ፡ ይለክፍ ፡ ይልክፍ) ፤ መልከፍ ፡ (መለኰፍ) ፡ በጥቂቱ ፡ መንካት ፡ መድረስ ፡ መቅመስ ፡ ማግኘት ። ኢይለክፍዎ ፡ በአጽባዕቶሙ ፡፡ እመ ፡ ኢለክፎ ፡ በበትሩ ፡፡ ከመ ፡ ኢይልክፉ ፡ አረፍተ ፡ ቤት ፡፡ ርእሳ ፡ ትለክፍ ፡ ሰማየ ፡፡ ወኢለከፎሙ ፡ ሥቃይ ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፬ ። አስቴ፱ ፡ ፲፭ ። ሕዝ፵፩ ፡ ፮ ። ኩፋ ፡ ፳፯ ። ጥበ፫ ፡ ፩) ።

**አልከፈ** ፤ አለከፈ ፡ አቀመሰ ። አስለከፈ ፡ አስነካ ። አልከፈኒ ፡ ውስተ ፡ አፉየ ፡ ወይቤለኒ ፡ ናሁ ፡ ለከፈከ ፡ ዝንቱ ፡ ከናፍሪከ ፡ (ኢሳ፮ ፡ ፯) ።

**ተለክፈ** ፤ ተለከፈ ፡ ተነካ ። እግዚ ፡ ዘኢይትለከፍ ፡፡ እሳት ፡ ዘኢይትለከፍ ፡ (ድጓ ። ቅዳ) ።

**ልኩፍ** ፡ (ፉን ፡ ፉት ፡ ክፋት) ፤ የተለከፈ ፡ የተነካ ፡ ንክ ። ኢልኩፋን ፡ ለግብተ ፡ አጻብዕ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ልክፈት ፤** መንካት ፡ መነካት ። አንካክ ፡ ንኪት ፡ ልክፈያ ፡ ቅምሻ ።

**ተላከፈ ፤** በቁሙ ፡ ተቃመሰ ። ተለካከፈ ፡ ተነካካ ፤ ተጋጠመ ፡ ተገናኘ ። ከነፈሆሙ ፤ ስፉሓን ፤ ወርቡ ባን ፤ ወይትላከፉ ፤ በበይናቲሆሙ ፤ (ዘዜና ፡ ፫ ፡ ፲፫) ።

**ልኹትንት ፤ ልኹንት ፤ (ለሐኰ ፡ ልሒኰ) ፤** ልሕኰት ፡ ልጉን ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ የዘይት ፡ ማሰሮ ፡ ገንቦ ፡ ማድጋ ። **ልኹንትኪ ፤ ዘቅብዕ ፤** (፫ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ። ፬ነገ ፡ ፬ ፡ ፪) ። ልኹንትና ፡ ልኹ ትንት ፡ በልሕኰት ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ስለ ኾነ ፤ አንዳንዱ ፡ መጣፍ ፡ ልሕኰት ፡ ይላል ።

(ጥ) **ለለ ፤ (ሌለየ) ፤** ይቂቅ ፡ አገባብ ፡ በበኙና ፡ ዘዘኙ ፡ የመሰለ ። ክተጸውዖ ፡ ስም ፡ በቀር ፡ በብትን ፡ ኹሉ ፡ ዘርግ ሮም ፡ ሳይዘረዝርም ፡ እየገባ ፡ እየ ፡ ይኂመ ፡ ቃል ፡ ይ ኾናል ፡ በቁም ፡ ቀሪነትም ፡ አለው ። ለለ ፤ ዕለቱ ፤ ለለ ፤ ርእሱ ፤ እየለቱ ፡ እየራሱ ፡ እየለት ፡ እየለቱ ፤ እየራስ ፡ እየ ራሱ ። ለለ ፤ አሐዱ ፤ እያንዳንዱ ፡ ለያንዳንዱ ። አንዱም ፡ አንዱም ፡ ሳንዱም ፡ ሳንዱም ። በበ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ለለ ፡ ይላል ፤ የመሳሸና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ምዕረ ፤ ለለ ፤ ዓመት ። ይበክዩ ፤ ለለ ፤ ዓመ ። ወለለ ፤ በዓል ።

**ለለ ፤** ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ አመንና ፡ እንዘን ፡ የመ ሰለ ፤ በጎላፊና ፡ በትንቢት ፡ ይገባል ። ለለ ፤ ተናገርኩ ፤ ሕፀወዩ ፤ በግፍዕ ። በተናገርኹ ፡ ጊዜ ፤ ስናገር ፡ ስናገር ፡ (ኤር፳ ፡ ፰) ። ወለለ ፤ ወለዳ ፤ ተባዕተ ፤ ቅትላሁ ፤ ወ ንድ ፡ ወንድ ፡ ሲወልዱ ፤ በወለዱ ፡ ጊዜ ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፳፫ ፡ ፪) ። ለለ ፤ ይወፅኡ ፤ ውስተ ፤ ጸብእ ። ወከኑ ፤ ለለ ፤ ይሰምዑ ፤ ነገሮ ፤ ይፈ.ደፍዱ ፤ ግዘፈ ፤ (አቡሻ ፡ ፶ ። ዮ ሴፍ) ። (ዕር፳፩ ፡ ቍ፲፪፫) ።

**ለል ፤** ርስ ፤ ራስ ፡ የራስ ፡ ቅል ፡ ባለቤት ፡ አካል ። የተጐበርሮ ፡ ፀጺፉ ፡ እየኾነ ፡ እንደ ፡ ውእቱና ፡ እንደ ፡ ኪያ ፡ እስካሥር ፡ መደብ ፡ ይረባል ።

**ለልየ ፤ (ሊከ ፡ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ) ፤** እኔ ፡ ቅሌ ፡ ራሴ ፡ ባለቤቱ ። ለልየ ፤ በእደየ ፤ (ዮ፡ን) ።

**ለሊነ ፤ (ክሙ ፡ ክን ፡ ሆሙ ፡ ሆን) ፤** እኛ ፡ ቅላችን ፤ ራሳችን ፡ ባለቤታችን ። ለሊነ ፤ ሰማዕነ ፤ ወጠ የቅነ ። ዘለሊነ ፤ ነአምር ፡ አባሁ ፡ ወእሞ ፤ (ዮሐ፬ ፡ ፵፪ ። ፯ ፡ ፵፪) ።

**ላማ ፤ (ዕብ) ፤** ለምንት ፡ ለምን ፡ ስለ ፡ ምን ፤ (ማቴ፳፯ ፡ ፵፮ ። ቅዳ ፡ እቅ) ።

**ለምእ ፤—ለማ ፡ በራ ፤—ለምዐ ።**

**ለሚድ ፤ ዶት ፤ (ለመደ ፡ ይለምድ ፡ ይ ልምድ ። ዕብ ፡ ላማድ ። ዐረ ፡ ለመደ ። ሱር ፡ ል ማድ ፤ ተማረ) ፤** መልመድ ፤ ማወቅ ፡ መውደድ ፤ ለ ማዳ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ መኾን ፡ ማዘውተር ። ዘኢትለምዱ ፤ ይበጽሐክሙ ። ደም ፤ ዘይለምዳ ፤ አንስት ። እሙ ንቱ ፤ ይለምዱ ፤ ቤቶ ፤ (ኢዮ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ። ዲድ ፡ ፴፫ ። ስንክ ፡ መስ፳፪ ። ታኅ፳ ። ፈልክ፱ ፡ ፲፱) ።

—፤ መማር ፡ ልማድ ፡ ማድረግ ፡ ፊደል ፡ መቍጠር ፡ ዕውቀት ፡ መጀመር ፡ በማየት ፡ በመስማት ፡ በንባብ ፡ በግቢር ፡ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ከመልመድ ፡ አይወጣም ። «ማጥራት ፡ ማበጠር ፡ የምርት ፡ የነገር» ። ልሳኖሙ ፤ ለ መደ ፤ ተናግሮ ፤ ሐሰተ ። ከመ ፤ ኢይልምዱ ፤ ፀሪፈ ። ዘከመ ፤ ይለምዱ ፤ ብዙኃን ። እለ ፤ ቀቲለ ፤ ለመዱ ። እስመ ፤ ኢለመዱ ፤ አፍራሲሁ ፤ ተጻብኦ ፤ ምስለ ፤ መ ስተጽዕናነ ፤ ነጌያት ። ኢለመደ ፤ ከመ ፤ ይፃእ ፤ እም በኣቱ ፤ (ኤር፱ ፡ ፭ ። ፩ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፳ ። ዕብ፲ ፡ ፳፭ ። ም ሳ፩ ፡ ፲፭ ። ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፲፲፭) ። በለመደ ፡ ፈንታ ፡ አልመደ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እለ ፤ ያለምዱ ፤ ዝ ሙተ ፤ (ፊ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፪ ። ማቴ፳፯ ፡ ፲፩) ።

**አልመደ ፤** አለመደ ፤ አስለመደ ፡ አስተማረ ፡ አ ሳወቀ ። ኢታልምዶ ፤ መሐላ ፤ ለአፉክ ። አብ ፤ ወወ ልድ ፤ ወመንፈስ ፤ ቅዱስ ፤ ያለምዱ ። አልምዳ ፤ ለነ ፍስከ ፤ ትዕግሥተ ፤ ላዕለ ፤ ኵሉ ፤ መከራት ፤ (ሢራ ፳፫ ፡ ፱ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ፊላስ ፡ ፳፯) ። በለመደና ፡ በልማድ ፡ ፈንታ ፡ አልመደ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ዘከመ ፤ ያለምድ ፤ (ዘጐ፳፬ ፡ ፳ ። ማር፲ ፡ ፩ ። ኪዳ) ። በአልመደም ፡ ፈንታ ፡ ለመደ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ንሕነሰ ፤ ኢንለምድ ፤ ወኢቤተ ፤ ክርስቲያኑ ፤ (፩ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፮) ።

**ተለምደ ፤** ተለመደ ፤ ታወቀ ፡ ተጠና ፤ ልማድ ፡ ኾነ ፤ ትምርቱ ፡ ሥራው ።

**ልሙድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ምድ) ፤** የለመደ ፤ ለ ማዳ ፡ ምሁር ፡ ሊቅ ። እስመ ፤ ላህበ ፤ ነድ ፤ ክነ ፤ ልሙደ ፤ ከመ ፤ ኢያውዒ ፤ እንስሳ ። እስመ ፡ ኢክንኩ ፡ ልሙደ ። ብእሲ ፤ ልሙደ ፤ ሥላቅ ። እመ ፤ ክነ ፤ ልሙደ ፤ በሰ ኪር ፤ (ጥበ፲፯ ፡ ፲፰ ። ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፴፱ ። ሢራ፳፫ ፡ ፲፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፯) ።

—፤ የተለመደ ፡ የታወቀ ፡ ዕውቅ ። ካልእ ፤ ረድእ ፤ ዘ ልሙድ ፤ በኀበ ፤ ሊቀ ፤ ካህናት ፤ (ዮሐ፲፰ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮) ።

**ልማድ ፤ (ዳት) ፤** በቁሙ ፡ ልምድ ፡ በመል ፡ የተለመደ ፡ ማብር ። ኢክነ ፤ ሎቱ ፤ ልማድ ፤ እምቅድመ ፤ ዝንቱ ። ኢትኅድግ ፤ ልማደከ ። ወልማዶሙ ፤ ለሕ ዝብ ፤ የዐርጉ ፤ መልዕልተ ፤ ይብር ። እኩያን ፤ ልማድ ፤ ወግዐዝ ፤ (ፊ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፪ ። ዮሴፍ ። ቀሌ ። ሮማ፭ ፡ ፳፱) ።

—፤ ትምርት ፡ ሕግ ፡ ሥርዐት ። ወላዴተ ፤ አምላክ ፤ ኮነት ፤ ልማደ ። ሀለዉ ፤ እለ ፤ በልማደ ፤ አማልክት ። በእንተ ፤ ሥነ ፤ ልማዳቲሁ ። በከመ ፤ ልማዶሙ ፤ (ቄር ። ፩ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ መስ፳) ። አል ብን ፡ ልማድ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ኢንለምድ ፡ ይላል ፤ (፩ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፮) ።

**ልማድ ፤** የግስ ፡ ተውላክ ፤ በቀዳማይ ፡ አንቀጽ ፡ እየገባ ፡ አራቱን ፡ አዕማድ ፡ የሚለይና ፡ የሚያስለይ ፡ ተ ጨማሪ ፡ ፊደል ። እሊሁም ፡ ፬ ፡ ናቸው ፡ አ ፡ አን ፡ ተ ፡ አስተ ። አገባባቸውን ፡ በየቦታቸው ፡ እይ ።

**ላሚዳ ፤** በቁሙ ፡ ላይዳ ፡ ታላቅ ፡ የንጨት ፡ መ ንክ ፡ ያውድማ ፡ መማሪያ ፡ ንደው ፡ ተበራይቶ ፡ ክተመ

ሽን ፡ በኋላ ፡ ምርቱን ፡ ከማርደና ፡ ከብቶ ፡ የሚለዩበት ። ላዳንም ፡ ይሆን ፡ ይመስላል ።

**ላሚድ ፤ (ዕብ ። ጽር ፡ ላምዳ) ፤** ስመ ፡ ፊደል ፡ ለ ፤ የአሌፋ ፡ ፲፪ኛ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፹፱—፺፮ ። ሰቈቃ ፡ ፲፪ ። ፪ ፡ ፲፪ ። ፫ ፡ ፴፫ ። ፬ ፡ ፲፪) ። ፍችው ፡ ትምርት ፡ ወይም ፡ ምሁር ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ለምድ ፤** በቁሙ ፡ ደበሎ ፡ የደበሎ ፡ ዐይነት ፡ የወታደሮች ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ። አንቀልባ ፡ ነት ፤ የልጅ ፡ ማዘያ ። (ትረት) ፤ የታዘለ ፡ በለምድ ፡ የተረገዘ ፡ በሆድ ።

**ተላመደ ፤** በቁሙ ፡ ተስማመደ ፡ ተዋወቀ ።

**ተልሚድ ፤ (ዕብ ፡ ታልሚድ ። ሱር ፡ ታልሚዳ ። ዐረ ፡ ተልሚዝ-ድ) ።** ተማሪ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ። ዘነገሮ ፡ ጴጥሮስ ፡ ለቀሌምንጦስ ፡ ተልሚዱ ፡ (ትሌ ። ስንክ ፡ ሐም፳) ።

**ለምለመ ፤ (ሐመለ ፡ አሕመልመለ ። ዕብ ፡ ላብሌብ) ፤** ለመለመ ፡ ረጠበ ፡ ቅጠል ፡ አወጣ ። እምከመ ፡ ለምለመ ፡ አዕጹቂሃ ። ከመ ፡ ይለምልሙ ፡ ዕፀው ፡ (ማር፲፫ ፡ ፳፰ ። ትረ ፡ ባሮ) ።

—፤ ራሰ ፡ ለዘበ ፡ ሰለለ ፡ ልሕሉሐ ፡ ኾነ ። ከመ ፡ እብን ፡ ዘኢይለመልም ። ልእቡን ፡ እንዘ ፡ ይለመልሙ ፡ ከመ ፡ ሠምዕ ። ኢትለመልም ፡ አልባቢሆሙ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ገድ ፡ ላሊ ። ዮሴፍ) ።

**ልምሉም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ልምት) ፤** የለመለመ ፡ የረጠበ ፡ የሰለለ ፡ ልሕሉሕ ፡ ርጥብ ፡ ደካማ ፡ ለስላሳ ፡ ልዝብ ። ዕፀ ፡ ልምልምት ፡ እንተ ፡ ኢትወዒ ። ደወየ ፡ ወፈተወ ፡ ኅብስተ ፡ ልምሉመ ። ናላ ፡ ልምሉም ፡ ውእቱ ፡ በግዕዘ ፡ ጠባይዕ ። ሎስ ፡ ጽቡረ ፡ ልምሉመ ። ፈውሳት ፡ ልምሉማት ፡ ዐቃቤ ፡ አንቀጸ ፡ ምኔት ፡ ይኩን ፡ ልምሉመ ፡ ቃል ፡ ሰርሑቃን ፡ ወለ ቅሩባን ፡ ወትሑተ ፡ ጥቀ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፳፱ ። ፊልክ ፡ ፶፬ ። አረ ፡ ተ፳ ። ጥበ፲፰ ፡ ፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**ልምላሜ ፤ (ያት) ፤** በቁሙ ፡ መለምለም ፡ መለበለብ ፡ አለሳለስ ፡ ልበሳቤ ፡ ርጥበት ፡ ርጥበነት ፡ ለምለምነት ። ውስተ ፡ ገነቱ ፡ ይዩብስ ፡ ልምላሜሁ ። ልምላሜ ፡ ኅብስት ። ልምላሜ ፡ መባልዕት ፡ (ኢዮ፲፭ ፡ ፲፯ ። ቅዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫) ።

**ለምለም ፤ (ብ ፡ ለማልም ። ዕብ ፡ ሊብሉብ) ፤** በቁሙ ፡ ሐመልማል ፡ ለጋ ፡ ቀንበጥ ፡ ቅጠል ፡ ዐጽቅ ፡ ለባልብ ፡ ሙልብልቢት ፡ ዕጣፍ ፡ ሙሽራ ። ወመ ተሮ ፡ ኀበ ፡ ለምለሙ ። ርእሰ ፡ እንደየ ፡ ለምለመ ፡ ዕፀ ፡ ተሴሰየ ፡ ጠለ ፡ ገዳም ፡ በትየ ። ሲሳይከ ፡ ለምለመ ፡ ዕፀ ፡ (ሕዝ፲፯ ፡ ፬ ። ድጓ ። መዋሥ) ።

**አለምለመ ፤** አለመለመ ፡ አረጠበ ፡ አለሰለሰ ፡ አለዘበ ። ያለምልም ፡ ሲሣጋሁ ፡ ከመ ፡ ዘሕፃን ። ወአ ለምለመት ፡ ነገራ ፡ (ኢዮ፴፫ ፡ ፳፭ ። ስንክ ፡ ሠኔ፴) ።

**መለምልም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤** የሚያለመልም ፡ አለምላሚ ። የለመለመ ፡ ለምለም ፡ ለስ ላሳ ፡ ርጥብ ፡ ጥሉላት ፡ የብሉት ፡ ምግብ ። ወኸሎ ፡ መ ለምልመ ፡ (ኪዳ) ።

**ለምንት ፤—ለምን ፤—ሚ ፡ ምንት ።**

**ለምዐ ፤ (ለሚዕ ። ዐረ ፡ ለመዐ) ፤** ለማ ፡ ለም ፡ ኾነ ፡ ያገር ። ጠራ ፡ በራ ፡ ቦለለ ፡ አለ ፡ አማረ ፡ ተከናወነ ፡ የብርሃን ፡ የማዕደን ፡ የመልክ ፡ የግብር ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በለምዐ ፡ ፈንታ ፡ ተለምዐ ፡ ተላምዐ ፡ ይላል ፡ አያሰኘም ። በእደ ፡ ኪንያሁ ፡ ይት(ለ)ላማዕ ፡ ግብሩ ፡ (ሢራ፱ ፡ ፲፯) ።

**ልሙዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ምዕት) ፤** የለማ ፡ ለም ፡ ንጹሕ ፡ ብሩህ ፡ ጽሩይ ።

**ለመጸ ፤ (ለሐጸ ፤ መለጠ) ፤** ለመጠ ፡ ለምጣም ፡ ኾነ ። ለዘበ ፡ ለሰለሰ ። እብን ፡ ይለምጽ ፡ እማይ ፡ (ኢዮ፲፬ ፡ ፲፱ ። ገድ ፡ አዳ ፡ ገ፲፮) ።

—፤ ለመጠ ፡ ለማመጠ ፡ ዐረቀ ፡ ለማስተካከል ፡ ወይም ፡ ለማጣ ፡ ጉብጣ ፡ ለማድረግ ።

**አልመጸ ፤** አለመጠ ፡ አላመጠ ። ለምጣም ፡ አደረገ ፡ አለዘበ ፡ አለሰለሰ ። መደመደ ፡ ደለደለ ፡ አስተካከለ ። ከመ ፡ ያልምጹ ፡ ጉጻጉጸ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ተለምጸ ፤** ተለመጠ ፡ ተላመጠ ፡ ተለማመጠ ።

**ልሙጽ ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ምጽት) ፤** ለምጻም ፡ በራ ። የለዘበ ፡ ልዝብ ፡ ለስላሳ ፡ ልሙጥ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ የተካከለ ፡ ዐባጣ ፡ ጉባጣ ፡ ሽካራ ፡ የሌለው ። ኩዀሕ ፡ ልሙጽ ። ፍናወ ፡ ጽድቅ ፡ ልሙጻት ። አርዌ ፡ ምድር ፡ ልምጽት ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፬ ። ምሳ፲፪ ፡ ፳ ። ገድ ፡ አዳ) ።

**ለምጽ ፤ (ዕብ ፡ ጻራዓት ። ዐረ ፡ በረጽ) ፤** በቁሙ ፡ ለምጥ ፡ የቁርበት ፡ ደዌ ፡ የቀንምጥና ፡ ወገን ፡ የተላጠ ፡ የተመለጠ ፡ ዕንፊት ፡ የሚያስመስል ። ሠረጸ ፡ ለምጽ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሙ ። ወነበረ ፡ ውስተ ፡ ለምጽ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ሞተ ። ናሁ ፡ ንጹሐ ፡ ሕብረ ፡ ለምጹ ፡ ለዘለምጽ ፡ (፪ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ። ዘሌ፲፬ ፡ ፫) ።

**ለምጻዊ ፤** ለምጣም ፡ ለምጥ ፡ የወጣበት ። (ማጥም) ፡ አትቀላጆ ፡ እንደኾነ ፡ በቀርሮ ፡ ፍርድ ፡ ያለ ምጣም ፡ ምኒልክ ፡ ብዙ ፡ ልስደብኝ ፡ (የቈለም ፡ ጣዕም) ።

**ለነ ፤—ለኛ ፡ የኛ ፡ እኛን ፤—ለ—ነ ፡ ለከ ።**

**ለንጽ ፤ ለንጺዎን ፤ (ጽር ፡ ሌንቲዎን) ፤** የሥራ ፡ ልብስ ፡ መክፈ ፡ ማጠቆ ። ከፈያን ፡ እደ ፡ ባለሐዳዮች ፡ ግን ፡ ዝናር ፡ ይሉታል ። መክፈ ፡ ለንጽ ፡ መዝመዘ ፡ በለንጽ ። ነሥአ ፡ ለንጺዎ ፡ ወኀፀበ ፡ እግረ ፡ አርዳኢሁ ፡ (ዮሐ፲፫ ፡ ፬ ፡ ፭ ። መዋሥ) ። መክፈና ፡ ለ ንጽ ፡ ፩ ፡ ስም ፡ ናቸው ፡ መክፈ ፡ ብቻ ፡ ይበቃ ፡ ነበረ ፡ ለንጽ ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡ ተፈጠምሯል ፡ ከራ ፡ ሙራዱን ፡ እደ ፡ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

**ለንጻኔ ፤ ላምጼኔ ፤ (ጽር ፡ ላምፒኒ ። ዕብ ፡ ማዕጋል) ፤** ሠረገላ ፡ ወይም ፡ ሰፈር ፡ የሰፈር ፡ በታ ፡ ሰረጋላ ፡ ንጉሡን ፡ ክብ ፡ የሚሰፍርበት ። ባለብሎቶች ፡ ግን ፡ ዐልጋ ፡ ድንኳን ፡ ይሉታል ፡ (፩ነገ ፡ ፳፮ ፡ ፭ ፡ ፯) ።

**ሌንጺስ** ፤ (ጽ'ር ፡ ላምጊስ ። ዕብ ፡ ላጊድ) ፡ የእሳት ፡ ላንታ ፡ ነበልባል ፡ ምላሱ ፡ ውልብልቢቱ ፡ ወይም ፡ ችቦ ፡ ፋና ፡ ቀንዲል ። ብርሃን ፡ ዘለንጺስ ። ምጣሕት ፡ ሠራኢ ፡ ለንጺስ ፡ (ዘፀ ፳ ፡ ፲፰ ። ዮሐ ፲፰ ፡ ፫) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ግእዝ ፡ መስሏቸው ፡ ሌንጺስ ፡ እዘሬ ፡ ሰበስ ፡ ብለው ፡ ይገብሩታል ፡ ምስክር ፡ የለውም ።

**ለዐክ ፤ — ላክ ፡ ሰደደ ፤ — ልኢክ ፡ ለእክ ።**

**ልዒል ፡ ሎት ፡ (ለዐለ ፡ ይሌ(ል)ዕል ፡ ይልዐል ። ዕብ ፡ ወዐረ ፡ ዐላ)** ፤ ላይ ፡ ላይ ፡ ማለት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አፈፍ ፡ አፈፍ ፡ ማለት ፡ መንሣት ፡ ማረግ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ መውጣት ፡ መርዘም ፡ መብለጥ ፡ መክበር ፡ ልዕልና ፡ ማግኘት ፡ በላይ ፡ መኾን ፡ ደኖቦን ፡ እይ ። **ለአሉ ፡ ባዕድ ፡ ዘይሌዕል ፡ እምኔሁ ። እንዘ ፡ ሰሌሁ ፡ ይልዕል ፡ እምሰማይ ። አጽባእ ፡ ፅጽብት ፡ ዘተልዕል ፡ እምኔ ይሴ ። ብእንተ ፡ አውብዐ ፡ ራብዕ ፡ ወዘይልዕል ፡ እምኔሃ ። ዝንቱስ ፡ ራእይ ፡ ይሌዕል ፡ ፈድፋደ ፡ እምጠቢይብ** ፡ (ኢሳ ፡ ድ፲፩ ። ተ፲፯ ። ፊልክ ፡ ፻፵ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳፬ ፡ ፱ ። አረጋ ፡ መሊግ፱ ። ማር ፡ ይሥ፳ ፡ ፲፩) ። ዳግመኛም ፡ ላዕሎ ፡ ላዐለ ፡ ይላዕል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ላሐወ ፡ በበረከ ፡ ቢት ፡ ሊገበስ ፡ ይቻላል ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በለዐለ ፡ ፈንታ ፡ ተልዕለ ፡ ተለዐለ ፡ ይላል ፡ ባለቅኔዎችም ፡ በዚሁ ፡ አከኼድ ፡ ይገቡታል ፡ ፍጹም ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **ተለዐለ ፡ ማይ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ አድባር ፡ ነዋኃት ። ተለዐለት ፡ ታቦት ፡ እምነ ፡ ምድር ። ከመ ፡ ዕፀ ፡ ቄድሮስ ፡ ተለዐልኩ ። ተልዒልየ ፡ ተኽሕትኩ ። ወቱለዐለ ፡ ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ በሕቡናሁ ፡ ወበጥበቡ** ፡ (ኩፋ ፡ ፭ ። ዘፍ፯ ፡ ፲፯ ። ሢራ ፳፬ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፹፯ ። ሰንክ ፡ ጥቅ፯) ።

**ለዓሊ ፡ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት)** ፤ ላይ ፡ ላይ ፡ የሚል ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚያርግ ፡ የሚወጣ ፡ ወጣት ።

**ልዑል ፡ (ላን ፡ ላት ፡ ዕልት)** ፤ በቁሙ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የበለጠ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ረዥም ፡ ምጡቅ ። **ልዑል ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ። አእምር ፡ ሚ ፡ መጠን ፡ ልዑል ፡ እምኔክ ፡ ደመና ። ሰማይ ፡ ልዑል ። መንበር ፡ ልዑል** ፡ (መዝ ፡ ፺፰ ። ኢዮብ፳ ፡ ፳ ። ምሳሌ፳ ፡ ፫ ። ኢሳ፮ ፡ ፩) ።

**ሉዓሊ** ፤ ልዕልና ፡ ከፍታ ፡ ምጥቀት ፡ ርዝመት ። **ሉዓሊ ፡ ዐቢይ ። ያእምር ፡ ሉዓሊሁ ፡ ለሰማይ** ፡ (መክ፲ ፡ ፯ ። ቅዳ ፡ ሕር) ።

— ፤ ላይ ፡ ላዕል ፡ መሐረሻ ፡ ደርብ ፡ ሰገነት ። **ዘወረወ ፡ ነፍሶ ፡ እመልዕልተ ፡ ሉዓሊ ፡ ይመውት ። ሁለተ ፡ ሉዓሊ** ፡ (ዮሴፍ ። ኢሳ ፡ ድ፭) ።

**ሉዓላዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ ልዕልና ፡ ያለው ፡ ላይኛ ፡ ከፍተኛ ፡ የላይ ፡ የሰማይ ። **መሐላ ፡ ሉዓላዊ ፡ ወማእከላዊ ፡ ወዘይቴሕት ፡ እምኔሆሙ ። ኢስኪዴሬዮት ፡ ሉዓላውያት ። ኅይላት ፡ ሉዓላውያን ። ረድኤት ፡ ሉዓላዊት** ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፱ ፡ ፭ ። ሕዝቅ፵፪ ፡ ፭ ። ኢሳ ፡ ድ፳ ። ተ፲፱) ። ሉዓላዊ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ላዕላዊ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ልዑላዊ ፡ ወመትሕታዊ ፡ ይላል ፡ ፍቹም ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ፊልክ ፡ ፺፱፭) ።

**ልዕልና** ፤ በቁሙ ፡ ልዑልነት ፡ ታላቅነት ፡ ከፍታ ፡ ምጥቀት ፡ ርዝመት ። **ልዕልና ፡ መዝራዕትከ ። የንበር ፡ ልዕልና ፡ ዐዲለ ፡ መሐይው ። የአምር ፡ ኅይለ ፡ ልዕልና ፡ ሰማይ ። ኀዲጎሰ ፡ በእንተ ፡ ልዕልናሁ ፡ እምድር ፡ ይሰመይ ፡ ሰማየ ። ልዕልናሁ ፡ ለውእቱ ፡ ሰማይ ፡ ከመ ፡ እምድር ፡ ለምጽናዕ** ፡ (ዘዳ፳ ፡ ፳፱ ። ኢሳ፪ ፡ ፲፩ ። ሢራ ፲፯ ፡ ፴፱ ። ፊልክ ፡ ፯ ። ዕር ፡ ኢሳ፯ ፡ ፲፫) ።

**ላዕል ፤ (ላት)** ፤ ላይ ፡ ላይኛ ፡ መሐረሻ ፡ ጣራ ፡ ቁመት ። **ላዕል ፡ ወታሕት** ፡ (ቅዳ ። ኤፌ፫ ፡ ፲፰) ። ሲና ፡ በብና ፡ ሲዘረዘር ፡ አገባቡም ፡ ሲጣነት ፡ እንዳወፈረዱ ፡ ይፈታል ፡ ስልቱ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

**ላዕለ** ፤ በላይ ፡ ወደ ፡ ላይ ። **አንበሮ ፡ ላዕለ ። ትንሥኡ ፡ ላዕለ** ፡ (አስቴር ፡ ፭ ። ኢሳ፰ ፡ ፳፭) ። **ተጽዕኑ ፡ ላዕለ ፡ ኪሩቤል ። መዋእል ፡ ምት ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ** ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። ሮሜ፭ ፡ ፲፪) ። ሲዘረዝርም ፡ በጥሬነቱ ፡ ላዕሉ ፡ ላ ፡ ልከ ፡ ኪ ፡ ልየ ፡ ሎሙ ፡ ን ፡ ልክሙ ፡ ን ፡ ልነ ፡ እያለ ፡ በዘመድነት ፡ ይረባል ። በዋም ፡ ደቂቅ ፡ አንቀጽ ፡ በስ ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ ዲበ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሃ ፡ እያለ ፡ በበዕድ ፡ ይዘምታል ፡ (ዕርዳእ ፡ ቀኖ፲፱) ።

**ላዕሉ** ፤ ላይ ፡ ላዩ ፡ ላይኛው ፡ በላይ ፡ ያለው ። **ዘወረደ ፡ እምላዕሉ ። በሰማይ ፡ በላዕሉ ። ጎሁ ፡ ዘላዕሉ** ፡ (ዮሐ ። ዮሴፍ ፡ ፫ ። ቆላ፫ ፡ ፩) ።

**ላዕላይ ፡ ዊ ፤ (ዪት ፡ ሊት ፤ ዊት)** ፤ የላይ ፡ ላይኛ ፡ ታላቅ ። **ላዕላይ ፡ ማኅደር ። ላዕላይ ፡ ቀመር ። ሀገር ፡ ታሕታዩት ፡ ወላዕላዩት ። ላዕላይ ፡ ደወለ ፡ ግብጽ** ፡ (ቀሌ ። መር ፡ ዕዉ ። ሕዚና ፡ ፯ ። ፳፱ ። ጦቢ፫ ፡ ፫) ።

**አልዐለ** ፤ አነሣ ፡ አስነሣ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አወጣ ፡ አሳረገ ፡ አላቀ ፡ አበለጠ ፡ አከበረ ፡ አገነነ ፡ አመሰገነ ። **አሌዕል ፡ እደውየ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ፡ ልዑል ። ዘያሌዕለኒ ፡ እምአናቅጸ ፡ሞት ። አሌዕለከ ፡ ኀጉሥየ ፡ ወአምላኪየ** ፡ (ዘፍ፲፬ ፡ ፳፪ ። መዝ ፡ ፱ ። ፻፵፬) ። ፈንወ ፡ በፍሐ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አልዐለ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **የኀ ፡ ያሌዕል ፡ እደሁ ፡ ወይነሥእ ። አልዐለ ፡ እደሁ ፡ ወነሥአ ፡ መጥባሕተ** ፡ (ዘሌ፰ ፡ ፳፱ ። ፳፱ ፡ ፲ ። ሰንካ ፡ ፲፱ ፡ ፳፮ ። ፳፱ ፡ ፲፮) ። ዳግመኛም ፡ በአልዐለ ፡ ፈንታ ፡ አስተል(ለ)ዐለ ፡ ይላል ፡ ፍቹም ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ከዚያው ፡ ከድርብነት ፡ አይወጣም ። **ናስተልዕል ፡ ዕበዮ ፡ ወንነግር ፡ ግብሮ** ፡ (አፈ ፡ ተ፳፰) ።

**አልዓሊ ፤ መልዐሊ ፤ መልዕል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት)** ፤ የሚያነሣ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ የሚያደርግ ፡ የሚያሳርግ ፡ አሳራጊ ። **እግዚአብሔር ፡ መልዐሊ ፡ ትሑታን ። ክብርየ ፡ ወመልዐሊ ፡ ርእስየ** ፡ (መቃ ፡ ፻፲፯ ። መዝ ፡ ፫) ። በመልዕል ፡ ፈንታ ፡ ምልዓል ፡ ይላል ፡ አያስኬድም ፡ (አርጋ) ።

**መልዕልት ፤ (ታት)** ፤ መውጫ ፡ መረማመጃ ፡ ዕርከን ፡ መሰላል ። **ወመልዕልቲሁ ፡ ገጸ ፡ ጽባሕ** ፡ (ሕዝ፵፪ ፡ ፲፭) ።

—፤ ላይ ፡ በላይ ። ላዕልና ፡ ዲበን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ወጽልመት ፡ መልዕልተ ፡ ቀላይ ። ለዘ ወረደ ፡ እመልዕልት ። አልቦ ፡ ዘይትማሰሰነ ፡ እስመ ፡ መልዕልተ ፡ አምሳል ፡ ንሕነ ፡ (ዘፍ፡፩ ፡ ፪ ። ድጓ ፡ ቀሌ) ።

**ተልዕለ ፤ ተለዐለ ፤** ልዒል ፡ ልዒሎት ፡ ለ ዐለ ።

**ተላዐለ ፤** ተናማ ፡ ተንማማ ፡ ተከባበረ ፡ ተበላ ለጠ ፡ እኔ ፡ እበልጥ ፡ እኔ ፡ እበልጥ ፡ ተባባለ ። ማእዝና ፡ ሬብዕ ፡ ከለመለየት ፡ የተንማ ፡ በተላዐለና ፡ በለዐለ ፡ ፈንታ ፡ ተለዐለ ፡ ይባል ፡ የመምርና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**አስተላዐለ ፤** አናማ ፡ አሳጣሪን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አ ዳረገ ። አስተባዕል ፡ ምስሌሁ ፡ (ዘዳ፳፰ ፡ ፵) ።

**ለዓለም ፤—ድኀት ፤—ለ ፡ ዓለም ፡ ዐ ልሞ ፡ ዐለመ ።**

**ላዕልዐ ፤ (ላኀልኀ) ፤** ለነበደ ፡ ኰበተፈ ፡ ድዳ ፡ ኾነ ። (ተረት) ፡ አፈ ፡ ድዳ ፡ ቀንደ ፡ ጉዳ ። መጽሐፍ ፡ ማን ፡ ተላዕልዐ ፡ ይባል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። እንዘ ፡ ይትላዐላዕ ፡ በልሳኑ ፡ ወይድሕክ ፡ በነቢብ ፡ ፊደላት ፡ (አፈ ፡ ተሻ፯ ። ያዕ ፡ ዘእል) ።

**ላዕላዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት) ፤** ድዳ ፡ ለፍዳዳ ፡ ለንባዳ ፡ ኰልታፋ ፡ ክቡደ ፡ ልሳን ። ጸያፍ ፡ ወላዕላዐ ፡ ልሳን ፡ አኑ ። ሰበሃማን ፡ ወለጸያፋን ፡ ወለላዕላዓን ፡ ረሰዮሙ ፡ ይትናገሩ ፡ ርቱዐ ፡ (ዘዐ፱ ፡ ፲ ። ቀሌ ። ኪዳ ። ያዕ ፡ ዘ እል) ።

**ልዒት ፤ ቶት ፤ (ለዐተ ፡ ይልዕት ፡ ይል ዐት) ፤** መላት ፡ ላት ፡ ማውጣት ። መትከል ፡ ማግባት ፡ ማዋደድ ፡ መሰካት ፡ ማስማማት ፡ ዕንጨትን ፡ ከብረት ፡ ብረትን ፡ ከንጨት ።

**ለዐት ፤ አው ፡ ላዓት ፤** በቁሙ ፡ ላት ፡ የበግ ፡ ኋላ ፡ ሥራት ። ቅጠል ፡ የበግ ፡ ላት ፡ የሚባል ። ውላጋ ፡ እጅታ ፡ የሰይፍ ፡ የካራ ፡ የነፍጥ ። ወአብአ ፡ ሎቱ ፡ እስከ ፡ ላዓታ ፡ (መሳ፫ ፡ ፳፪) ።



ለዐት ፡

**ለፈየ ፤ (ፈለየ ፡ ጠ ፤ ሌለየ) ፤** ለየ ፡ ከፈለ ፡ ኹለት ፡ አደረገ ። ኢትልፍይዎ ፡ ለአሐዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ወኢትረስይዎ ፡ ለወልድ ፡ ለፌ ፡ ወለሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ ለፌ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ። ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ ፡ ተገላመጠ ።

**ለፌ ፤ (ጽር ፡ ያደ) ፤** ወዲህ ፡ ወደዚህ ፡ ወ ዲያ ፡ ወደዚያ ፡ የጊዜ ፡ የቦታ ። ለፌ ፡ እማርያም ። ለፌ ፡ እምጥምቀት ፡ የጊዜ ። እምለፌሂ ፡ ወእምለ ፌሂ ። ነጸረ ፡ ለፌ ፡ ወለፌ ፡ የቦታ ፡ (አፈ ፡ ተጓ ። መጽ ፡ ምስ ። ዘፍ፡ ፲፬ ፡ ፲፰ ። ዘፀ፪ ፡ ፲፪) ። ግዕዝንና ፡ ከዛን ፡ ተመልከት ።

**ለፈፍ ፤ ፎት ፤ (ለፈ ፤ ለፈፈ ፡ ይለፍፍ ፡ ይልፍፍ ። ዕብ ፡ ላፌፍ ። ሱር ፡ ላፍ ። ዐረ ፡ ለፈ) ፤** መለፈፍ ፡ መሸፈን ፡ መጠቅለል ። መለፈፍ ፡ መ ለፍለፍ ፡ መለበክ ፡ ፀዋጅ ፡ መንገር ። (ተረት) ፡ የሹም ፡ ለነፍ ፡ አይለፍ ፡ አይለፈልፍ ። ባፍ ፡ ይጠፋ ፡ በለፈለፉ ። መልፈፍ ፡ መድከም ፡ የቁርበት ፡ የጉልበት ።

**ለፋፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ፈፍት) ፤** በቁሙ ፡ የሚለፍ ፡ የሚለፈልፍ ፡ ለበኪ ፡ ጠቅላይ ። ባለ ቅኔዎች ፡ ግን ፡ ለፈፊ ፡ ጻፈ ፡ ለፋፊ ፡ ጣፊ ፡ ይላሉ ።

**ልፋፍ ፤ (ዐረ ፡ ሊፋፈት) ፤** መለፈፊያ ፡ መ ሸፈኛ ፡ ሥርመዲ ። አምጽአ ፡ ልፋፈ ፡ ከመ ፡ ይክድኖ ፡ አዕይንቲሁ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳) ።

—፤ የጠንቋይ ፡ ክታብ ፤ ጠልሰም ፡ ዐይነ ፡ ጥላ ፡ እንደ ፡ ፊደል ፡ የሚጠቀለል ። የጠንቋይም ፡ ባይኾን ፡ የሚጠቀ ለል ፡ ክኾነ ፡ ማናቸውም ፡ ጥፈት ፡ ልፋፍ ፡ ይባላል ፡ ል ፋፈ ፡ ጽድቅ ፡ እንዲሉ ።

**ልፋፈ ፡ ጽድቅ ፤** መንፈሳዊ ፡ ክታብ ፤ የደ ረት ፡ መጣፍ ፤ ማኅበቡሩና ፡ መሸከሙ ፡ ብቻ ፡ የሚያጸ ድቅ ፡ ኋላም ፡ ሲሞቱ ፡ ዐብሮ ፡ የሚቀበር ። መንፈሳዊ ነቱ ፡ በአፍአ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በውስጡ ፡ ብዙ ፡ ጸያፍ ፡ ቃል ፡ ሐሰትና ፡ ስሕተት ፡ አለበት ። ከሐሰቱም ፡ አንዱ ፡ እግዜር ፡ እንዳሠርቱ ፡ ቃላት ፡ በጁ ፡ ጣፈኝ ፡ ይባል ። ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ማብዘኙና ፡ አቃላዮች ፡ ፈልሰ ፈው ፡ ያወጡት ፡ አርድእት ፡ ባርቶስ ፡ ኅቡእ ፡ ስም ፡ የሚ ሉት ፡ ልፋፍ ፡ አለ ።

**መልፋፍ ፤ (ዐረ) ፤** የተሸፈነ ፡ የተጠቀለለ ፡ ሽፋን ፡ ጉመን ፡ ኾርንባ ፡ ጭብጦና ፡ ኰባ ፡ ሬስ ፡ የሚ መስል ፡ ቆሎ ፡ የሚበስል ።

**ለፍለፈ ፤** በቁሙ ፡ ለፈለፈ ፡ ቀባጠረ ፡ ነገር ፡ አበዛ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ለፈጸ ፤ (ፈለጸ ። ሎሰ) ፤** ለፈጠ ፡ ለወሰ ፡ ዐሸ ፡ አበቀ ፡ አበሰበሰ ፡ የዶቄት ፡ የበሶ ። ከፈለጸና ፡ ከሎሰ ፡ ከኹለቱ ፡ ሥር ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ተለፍጸ ፤** ተለፈጠ ፡ ታሸ ፡ ታበቀ ፡ ተለወሰ ። ሊጥ ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ልፋጽ ፤** የተለፈጠ ፡ ልፍጥ ፡ የታሸ ፡ የታበቀ ፡ ልዉስ ፡ ፍጹም ፡ ሊጥ ፡ ቀጭን ፡ ብጥብጥ ፡ ያይደለ ፡ እን ፍርፍር ። ልፋጽ ፡ በቅብዕ ፡ (ዘዐ፳፱ ፡ ፡፫) ።

**ልፍጸት ፤** ልፋጽነት ፡ እንፍርፍርነት ፡ (መፈ) ።

**ለፈቀ ፤ (ትግ ፡ ሐበ ፡ ለፍቀ ፤ ለፋ ፡ ጠ ቀመ) ፤** ነበዘ ፡ አጥበቆ ፡ ያዘ ፡ ቀለመ ፡ ቢያጥቡ ፡ አይ ጠራ ፡ ኾነ ፡ የደም ፡ የቀለም ፡ የርስሐት ። በተነስሎቱኒ ፡ ኢተሰርየ ፡ ሎቱ ፡ ኃጢአቱ ፡ እስመ ፡ ደመ ፡ መሰኪት ፡ ዘለፈቆ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ላጽዮ ፤ ዮት ፤ (ላጸየ ፡ ይላጺ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ጋላሕ ። ዐረ ፡ ማሰ) ፤** መላጨት ፡ መለጫ ጨት ፡ ጠጉርን ፡ ከሥጋ ፡ መለየት ፡ ከሥሩ ፡ መቍረጥ ፡

መጋጠሚ ፡ ቁርበቱ ፡ እስኪታይ ፡ እስኪገለጥ ። ላጸየ ፡ ሥዐርተ ፡ ርእሱ ። ላጸየሙ ፡ መንፈቀ ፡ ጽሕሞሙ ። ርእሰ ፡ ኢይላጺ ፡ (ኢዮ፩ ፡ ፳ ። ኤዜ፵ ፡ ፲፰ ፡ ፬ ። ዘሌ፳፩ ፡ ፲)።

**አላጸየ ፤ አስተላጸየ ፤** አስላጨ ።

**ተላጸየ ፤** ተላጨ ፡ ተለማጨ ፡ (ዘሌ፲፫ ፡ ፴፫ ። ፲፬ ፡ ፰ ፡ ፱ ። ሚክ፩ ፡ ፲፮)። **ተላጸየ ፡ ርእሶ ። ለትትላጺይ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ለትትቀረፀ ፡** (ማቴ፲፰ ፡ ፲፰ ። አቆር ፡ ፲፩ ፡ ፯)።

**ሉጺይ ፡ ልጹይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ጺ.ት) ፤** የተላጨ ፡ ልጩ ። **ልጹያን ፡ አጽሓሚሆሙ ። እስመ ፡ ክመ ፡ ሉጺት ፡ ይእቲ ፡** (ኢ.ርሚ፵፰ ፡ ፴ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፭)።


**መላጺ. ፤ (ጽያት) ፤** መላጫ ፡ መቀረጫ ፡ ምላጭ ፡ በንጢ ፡ በይፍ ፡ ካራ ፡ ስለታም ፡ ብረት ፡ (ኢ.ሳ፯ ፡ ፳ ። መኀ ፡ ፶፩ ። ዘኍ፮ ፡ ፭)። **መላጺ. ፡ ኢ.ሰከፈ.ኒ. ፡ ርእስየ ፡ እስመ ፡ ናዝራዊ ፡ አነ ። ክመ ፡ ጠቢብ ፡ ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ዘይጠብሕ ፡ በመላጺ. ። ክመ ፡ መላጺ. ፡ በሲ.ኒ ፡ ዘካልኤ ፡ አፉሁ ፡** (መሳ፲፯ ፡ ፲፯ ። ዲ.ድ ፡ ፲ ። ሚ.ራ፳፩ ፡ ፫)።



መላጺ. ፡

**ለጽለጸ ፤ (ዐረብ) ፤** ተናወጠ ፡ ተውለበለበ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ላይ ፡ ታች ፡ ደፋ ፡ ቀና ፡ አለ ፡ ተቅመደመደ ፡ የሚዛን ፡ የልሳንና ፡ የሰሓን ፡ ለከይሲም ፡ ይኾናል ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ መዘን ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ። ለጠለጠ ፡ ልጥልጥ ፡ አደረገ ፡ በልክ ፡ በሚዛን ፡ (ዐማርኛ) ። ዘሩ ፡ ለሲ.ጽ ፡ ነው ።

**ለጽሊ.ጽ ፤** የሚዛን ፡ ምላስ ፡ ውልብልቢት ፡ ላንሴታ ፡ ማእከል ፡ ኹና ፡ ግራና ፡ ቀኙን ፡ የሚያስተካክል ። **ክመ ፡ ለጽሊጸ ፡ መዳልው ፡ ፍትሐ ፡ እግዚ. ፡** (ምሳ፲፮ ፡ ፲፩ ። ጥበ፲፩ ፡ ፳፪)። አንዳንዱ ፡ መጽሐፍ ፡ በለጽሊጽ ፡ ፈንታ ፡ ለጽላጺ. ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ልጽላጺ. ፡ ይላል ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።



ለጽሊ.ጽ ፡

**ለጺ.ጽ ፤ (ለጺ ፤ ለጸጸ) ፤** መለጠጥ ፡ (ጥለ) መለጠጥ ፡ ለጣጭ ፡ ተለጣጭ ፡ ልጥጥ ፡ መኾን ።

**ለጺ.ቅ ፤ ቆት ፤ (ለጸቀ ፡ ይለጽቅ ፡ ይልጽቅ ። ዐረ ፡ ለጺ.ቀ ፤ ለዚ.ቀ ፤ ለሲ.ቀ) ፤** መለጠቅ ፡ መጣበቅ ፡ መጠጋት ፡ ልክክ ፡ ልስቅ ፡ ማለት ፡ መሰማማት ። **እንዘ ፡ ይለጽቅ ። እስከ ፡ ለጸቀ ፡ ማእሰ ፡ ሥጋሁ ፡ ደቢ ፡ ዐፅሙ ። ጠማዐ ፡ ወለጸቀ ፡ ምስለ ፡ መንበሩ ፡** (ዘዐ፳፯ ፡ ፳፰ ። ስንክ ፡ መስ፲፱ ። ግንቦ)።

**—፤ መቅረብ ፡ መድረስ ፡ ለመያዝ ፡ ለመንካት ። እስከ ፡ እሙንቱ ፡ ይለጽቁ ፡ ኀበ ፡ ቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡** (ማር ፡ ይሥሐ ፡ ፩)። ብዙው ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጽሐ ፡ ቀርበ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ለጸቀ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ አልጸቀ ፡ ይላል ፡ የመላሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **አልጸቀት ፡ ሰዐቲ.ዮ ። አልጸቀት ፡ ዘነኔክሙ ። አልጸቀ ፡ ዘያጺ.ድቀኒ ። አልጸቀት ፡ ነፍሱ ፡ ለመዊት ። አልጸቀት ፡ ዕለተ ፡ እግዚ. ። አልጺ.ቀ ፡ ኢ.የሩሳሌም ፡** (ኢ.ሳ፳፮ ፡ ፲፯ ። ማቴ፳፮ ፡ ፵፮ ። ፶ ፡ ፳ ። ኢ.ዮ፴፫ ፡ ፳፪ ። ዮኤ፩ ፡ ፲፭ ። ማርቆ፲፩ ፡ ፩)።

**አልጸቀ ፤** አለጠቀ ፡ አስለጠቀ ። አበጠጋ ፡ አቀረበ ። **ታለጽቅሙ ፡ ለርሑቃን ፡** (ቅዳ ፡ ዮሐ)። ስግመኛም ፡ አብጽሐ ፡ አቅረበ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አልጸቀ ፡ አስተልጸቀ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹሉ ፡ ባደራራጊ ፡ አስተላጸቀ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **በተቃርቦ ፡ አስተላጸቀ ፡ ለርእሱ ፡ ካልእ ፡ ብእሴ ። ተዓርኩ ፡ ክመ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ዘየአምዋ ፡ ለፍቁሩ ፡ ወያስተላጽቅ ፡ በፍሥሓ ፡ ወኢይትዓበይ ፡ ላዕሌሁ ። አለ ፡ ያስተላጽቁ ፡ ሰንበታተ ፡ ሐበት ። እመ ፡ አስተላጸቅሙ ፡ ወአዝለፍክሙ ፡ ኀልዮ ፡** (ቄር ፡ ጸላ ። ፈላስ ፡ ገ፲፫ ። ዓሞ፯ ፡ ፫ ። አፈ ፡ ድ፴፫)።

**ተላጸቀ ፤** ተላጠቀ ፡ ተለጣጠፈ ፡ ተጠጋ ፡ ተያያዘ ፡ ተጣመረ ፡ ተቃረበ ። **እለ ፡ ይትላጸቃ ፡ በበይናን ። ነፍስ ፡ እንተ ፡ ትትላጸቅ ፡ ምስለ ፡ እግዚ. ። እመ ፡ ቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘተላጸቀ ፡ ወሰከበ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ በእሎን ፡ መዋዕል ። ተላጽቆተ ፡ ስኢ.ል ፡** (ዘዐ፳፰ ፡ ፯ ። አፈ ፡ ተ፳፰ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፫ ። አፈ ፡ ተ፳፯)። በቀርበና ፡ በለጸቀም ፡ ፈንታ ፡ ተላጸቀ ፡ ይላል ። **ሰበ ፡ ይትላጸቅ ፡ ብእሲ ፡ ወየሐውር ፡ በገቦሁ ፡ ይረግዞ ። ይትላጸቅ ፡ ረድእ ፡ ለመምህሩ ። ጉሩ ፡ ዘይትላጸቅ ፡** (ዮሴፍ ። ቄር ፡ ጸላ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯)።

**ልጹ.ቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ጽቅት) ፤** የለጠቀ ፡ የቀረበ ፡ የተጠጋ ፡ የገጠመ ፡ የተያያዘ ፡ ዕሙር ። **አዘዘ ፡ ጢ.ጦስ ፡ ያንኅሉ ፡ መካነ ፡ ልጹቀ ፡ ቀ.ድስ ። አግዋር ፡ እለ ፡ ልጹቃን ። እመ ፡ ኮነት ፡ ነፍስ ፡ ልጽቅተ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡** (ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ። አፈ ፡ ተ፳፯)።

**ልጽቀት ፤** መለጠቅ ፡ መጣበቅ ፡ ልጥቅ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ድጕስ ። **ቅርበት ፡ አው ፡ ልጽቀት ፡** (ቄር ፡ ጸላ)።

**ለጽቅ ፤** ማጣበቂያ ፡ መጣብቅ ፡ ሙጫ ፡ ሙቅ ።

**ልጽቅ ፤ (ብ ፡ ልጻቅ) ፤** ሳንቃ ፡ መዝጊያ ፡ ወይም ፡ የቤት ፡ ታዛይ ፡ ጕርጆ ፡ ጓዳ ። **ኖኅት ፡ ውሳጥያት ፡ እለ ፡ ያበውእ ፡ ውስተ ፡ ልጽቀ ፡ ቤት ፡** (፫ነገ ፡ ፱ ፡ ፳፰)።

**ላጽቂት ፤ (ዕብ ፡ ልጣአ) ፤** ሸለሊት ፡ እንሽላሊት ፡ የገበሎ ፡ ዐይነት ። ወይም ፡ ጣፊት ፡ ሸረሪት ። **ላጽቂት ፡ ዘበእዴሁ ፡ የሐውር ፡** (ምሳ፴ ፡ ፳፰)።



ላጽቂት ፡

**አስተላጸቀ** ፤ አሳጠቀ ፡ አጠጋ ፡ አቀረበ ። ዘቲ ፡ መጽሐፍ ፡ አስተላጸቀት ፡ ርሑቃን ። በአስተላጽቆ ፡ (ፈላስ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፱) ።

**ሊ.ቅ** ፤—በቁሙ፥፥አሮጌ ፤—ልሂቅ ፡ ልህቀ ።

**ሊ.ቃኦንስጢ.** ፤ (ጽር ፡ ሊ.ክምኒስቲ) ፤ ስሙ ፡ ሀገር ፡ በቂርቆስ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ከዚያውም ፡ በፍርግያ ፡ ክፍል ፡ ያለች ፡ ታላቅ ፡ መዲና ፡ (ግብ፲፱ ፡ ፲፩) ።

**ለቂድ** ፤ **ዖት** ፤ (**ለቀደ ፡ ይለቅድ ፡ ይልቅድ ። ሰብ ፡ ላክድ**) ፤ መያዝ ፡ እጅ ፡ ማድረግ ፡ ፈለጎ ፡ ማግኘት ፡ ደህ ፡ ማሳየት ። ዘይሊቅድ ፡ ብዕለ ፡ እንበለ ፡ ኀሞይ ፡ ወግርማ ፡ እንበለ ፡ ሂመት ፡ ወኀይለ ፡ እንበለ ፡ ዐይው ፡ (ፈላስ ፡ ገ፳፯) ።

**ለቀደ** ፤ ለቁደ ፡ አሰረ ፡ የምሳሰ ፡ ለገደ ፡ ዘጋ ፡ የጐረሮ ።

**ለቅዳ** ፤ በቁሙ ፡ ቅምሖ ፡ ምንቀር ፡ የጕሮሮ ፡ የምላስ ፡ በሽታ ፡ ሕበጥ ። ቅምሖ ፡ የቀምሖ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ለቅሀ** ፤—**አለቃ ፡ አበደረ** ፤—**ለቅሐ ፡ ለቅሐ** ።

**ለቀወ** ፤ **ለቀየ** ፡ (**በቂው ፡ በቀወ**) ፤ ለቀቀ ፡ አሳቀቀ ፡ አዘጋ ፡ አፋሸገ ፡ ከፈተ ፡ ፈታ ፡ የአፍ ፡ የቍልፍ ። መኑ ፡ ከልአክሙ ፡ አርምሞ ፡ መኑ ፡ ለቀዎ ፡ ለአፉክሙ ፡ ከመ ፡ ትንብቡ ፡ ዘንተ ፡ መኑ ፡ አገበረክሙ ፡ ለተናግሮ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ። ወና ፡ የ ፡ ተወራፊዎች ፡ ስለ ፡ ኹኑ ፡ በዘረወ ፡ ፈንታ ፡ ዘረየ ፡ እንዲል ፡ ዘለቀወም ፡ ፈንታ ፡ ለቀየ ፡ ይላል ፡ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ በቀወ ፡ ነው ። ጕድጕደ ፡ ወሰበ ፡ አልቦ ፡ ዘያወሥእ ፡ ለቀየ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ጽርሑ ፡ (ዮዲ፲፬ ፡ ፲፭) ።

**ለቀወ** ፤ አቀጠለ ፡ ቅጥይ ፡ አወጣ ፡ የማር ፡ የቀጠል ፡ የማገሳ ።

**ለቆ** ፤ (**ሰብ ፡ ሌቁሽ**) ፤ በቁሙ ፡ ደኅሬዊ ፡ ማር ፡ ዳግማይ ፡ ቡቃያ ፡ ቅጥይ ፡ ከቄረጠና ፡ ከፈሰሰ ፡ በኋላ ፡ በገፍና ፡ በብሳጊ ፡ ዝናም ፡ የሚበቅል ፡ (ዐማርኛ) ።

**ለቆታ** ፤ (**ትግረኛ**) ፤ አቅማዳ ፡ ስልቻ ፡ አፋም ፡ አፈ ፡ ሰፊ ፡ ማለት ፡ ነው ። አቅማዳ ፡ ስልቻና ፡ እንዲሉ ።

**ለቅሐ** ፤ **ሐት** ፡ (**ለቅሐ ፡ ይሌቅሕ ፡ ይለቅሕ ። ሰብ ፡ ላቃሕ** ፤ **ወሰደ**) ፤ ማለቃት ፡ ማበደር ፡ መስጠት ፡ ማስተማር ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ኋላ ፡ ለመቀበል ። በደረንና ፡ ተበድረን ፡ እይ ። እመ ፡ ሲቃሕከ ፡ ብሩረ ፡ ለነዳይ ። ኢትለቅሖ ፡ ለዘይብዕለከ ። ብዙኃን ፡ እለ ፡ ኢይሌቅሑ ። ወዘኢለቅሐ ፡ ወርቀ ፡ በርደ ፡ (ዘፀ፳፪ ፡ ፳፭ ። ሢራ፳፱ ፡ ፳፱ ። ፳፱ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፲፬) ።

**ለቃሒ.** ፤ (**ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት**) ፤ የሚያለቃ ፡ አለቂ ፡ አበዳሪ ። ወለእመ ፡ ኀሰረ ፡ ይደልዎ ፡ ለለቃሒ ፡ ከመ ፡ ይምልክ ፡ ዘእኀዘ ። በቍጔተ ፡ ለቃሒ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯) ።

**አለቅሐ** ፤ አበለቃ ፡ አስበደረ ፡ ከልቆ ፡ ከብድር ፡ አገባ ።

**ተለቅሐ** ፤ ተለቃ ፡ ተበደረ ፡ ወሰደ ፡ ተቀበለ ፡ የገንዘብ ፡ የትምርት ። እፈዲ ፡ እሎንተ ፡ ዘተለቃሕኩ ፡ ትምርት ፡ (አረጋ ፡ መልዕ፳) ። ዘይትሌቃሕ ፡ ከመ ፡ ዘይሌቅሕ ። ኢትትለቃሕ ፡ እንዘ ፡ ነዳይ ፡ አንተ ። ዘይትሌቃሕ ፡ ሥርናየ ፡ ውስተ ፡ ክምሩ ፡ (ኢሳ፳፱ ፡ ፱ ። ሢራ፲፰ ፡ ፴፫ ። ምሳ፳ ፡ ፱) ። ዐሰረ ፡ ተሰጠ ፡ ተሰጭ ፡ ኾነ ፡ ገንዘቡ ፡ ከበዳሪ ፡ ወደ ፡ ተበዳሪ ።

**ተለቃሒ.** ፤ ለቃኝ ፡ ተማሪ ፡ ተበዳሪ ። ለቃሒ ፡ ወተለቃሒ ፡ (ምሳ፳፱ ፡ ፲፫) ።

**ልቁሕ** ፤ (**ሓን ፡ ሓት ፡ ቅሕት**) ፤ የተለቃ ፡ የተበደረ ፡ ተቀባይ ፡ ወይም ፡ ተሰጭ ።

**ል ቃሕ** ፤ (**ሓት**) ፤ ልቆ ፡ ብድር ፡ ዕዳ ። ዘየሐንጽ ፡ ቤቶ ፡ በንዋየ ፡ ልቃሕ ። ምጽዋትሰ ፡ ልቃሕ ፡ እምላክዊት ። ወልቃሕሰ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ በአኀዝ ፡ አው ፡ በትሕቢት ፡ (ሢራ፳፩ ፡ ፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፯ ። ፳፯) ።

**ል ቃሒ** ፤ (**ሕያት**) ፤ ማበደር ፡ መበደር ፡ አበዳደር ፡ ብደራ ፤ ልቆ ፡ የብድር ፡ ሥራ ። እስመ ፡ አፍቅሮቱ ፡ በላዕሌከ ፡ ልቃሒ ። ፍትሐ ፡ ልቃሕያት ፡ (ማር ፡ ይሥ፴፫ ፡ ፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፱) ።

**ለቀየ** ፤—**ሊቀቀ ፡ ከፈተ** ፤—**ሊቀወ** ።

**ለቅለቀ** ፤ (**ለቂቅ** ፤ **ለቀ**) ፤ ለቀለቀ ፡ ቀባ ፡ መረገ ፡ ዘጋ ፡ ደፈነ ፡ የቤት ፡ የፀዘቅት ፡ ያውድማ ፡ የጉቅ ፡ የሥንጥቅ ። ኢ.ገብአ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ማይ ፡ ወለቅለቅዎሙ ፡ በፀረር ፡ (አሞል ፡ ትርጓሜ ። ኤር፱ ፡ ፲፫) ። ዐጠበ ፡ አጠራ ፡ የልብስ ።

**ልቅላቄ** ፤ መለቅለቅ ፡ አለቃለቅ ፡ ልቅለቃ ፡ ልቅልቃት ፡ መሬበረሻ ፡ ስጥበት ።

**ለቀመ** ፡ (**ዐረ ፡ ለቀጠ ። ሰብ ፡ ላቃጥ**) ፤ በቁሙ ፡ ሰበሰበ ፡ አከማቸ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ለቀሠ** ፤—**ዐዘነ ፡ አለቀሰ** ፤—**ለቀሰ** ።

**ለቂቅ** ፤ **ቆት** ፤ (**ለቀ** ፤ **ለቀቀ ፡ ይለቅቅ ፡ ይልቅቅ ። ለቀወ ፡ በቀወ ። ሰብ ፡ ላቃቅ** ፤ **ላቅሌቅ ፡ ላሰ ፡ ሞለቀቀ**) ፤ መልቀቅ ፡ መክፈት ። መተው ፡ መስደድ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ለቀቀ** ፤ (**ዐረ ፡ ለቀ ። ሰብ ፡ ላቃህ**) ፤ መታ ፡ ጸፋ ፡ ገረፈ ። አዘዘ ፡ ይልቅቅዎ ፡ ወይጎምድዎ ፡ ውስተ ፡ ዘነብ ፡ ፈረስ ፡ ወያዑድዎ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፱) ። ዛሬም ፡ አስረው ፡ ይቀጡት ፡ ዘንድ ፡ ያስኛል ።

**ለቀሰ** ፤ (**ትግ ፡ ለቅሰ ። ዐረ ፡ ለቂሰ**) ፤ ዐዘነ ፡ ተፀፀነቀ ፡ አለቀሰ ፡ እንባ ፡ አፈሰሰ ። ሰብራ.ይሰጡ ፡ ማን ፡ ላቂሽ ፡ ብሎ ፡ ለቀወ ፡ ቃረመ ፡ ሰበሰበ ፡ ይላልና ፡ በዚህ ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ልቅሶኝ ፡ መጥራትን ፡ አልቃሾኝ ፡ ማለትን ፡ ያሳያል ፡ በከየን ፡ እይ ።

**አልቀሰ** ፤ አስለቀሰ ፡ አሳዘነ ። ባማርኛ ፡ ግን ፡ አደራረጊ ፡ ነው ።

**ተለቅሰ**፤ ተለቀሰ ፡ ልቅሶው ፡ ሐዘንተኛው ። ተለቀሰለት ፡ ሟቹ ።

**ተላቀሰ**፤ በቁሙ ፡ ተለቃቀሰ ፡ ተዛዘነ ።

**አስተላቀሰ**፤ አላቀሰ ፡ አለቃቀሰ ፡ አስተዛዘነ ። ስሕልት ፡ ሰይፍከ ፡ ብእሲ ፡ ልሁል ፡ (የተሳለች ፡ ሰይፍኽ ፡ ታላቅሰው) ፡ ሰበብአ ፡ ሞረት ፡ ወመርሐ ፡ ቤቴ ፡ እምኃ ፡ ኢየሱስ ፡ መስተጋድሎ ፡ (ቀጠሩ ፡ ቅኔ) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በናዝዘ ፡ ፈንታ ፡ አስተላቀሰ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ አላቀሰ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ወብዙኃን ፡ እምነ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ ሖሩ ፡ ኀበ ፡ ማርያ ፡ ወማርታ ፡ ከመ ፡ ያላቅስዎን ፡ በእንተ ፡ እኁሆን ፡ (ዮሐ ፲፩ ፡ ፲፱) ።

**ለሮን**፤ (ጽር ፡ ላሮስ ። ሮማይ ፡ ላሩስ ። ዕብ ፡ ሻሐፍ) ፤ የወፍ ፡ ስም ፡ ይምፁና ፡ መልኩ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ደረቱ ፡ ብሔት ፡ ወርቅማ ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፲፮ ። ዘዳ ፲፬ ፡ ፲፭) ፡ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ይብሬ ፡ የባሕር ፡ አሞራ ፡ ይሉታል ።



ለሮን ፡

**ለሮስ** ፡ (ዕብ ፡ ላሮስ) ፤ ለማሬስ ፡ ለማረስረስ ፡ ለማበቅ ፡ ለማበስበስ ፡ ለማርጠብ ፡ ለመለወስ ፤ ለማፈርፈር ፡ ለመለፈጥ ። ዘሩ ፡ ራሰስ ፡ ራስ ፡ ያሩስ ፡ ነውና ፡ ርሕሰንና ፡ እርሐሰኝ ፡ ለፈጸን ፡ እይ ፡ (ሕዝቅ፵፯ ፡ ፲፬) ። ዳግመኛም ፤ ለሮስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ለለዊስ ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ሎሰ**፤—**ለወሰ ፡ አቦካ**፤—**ለዊስ** ።

**ለሰደ**፤ (**ዐረ ፡ ለሰደ**) ፤ ጠባ ፡ መጠጠ ፡ ጨመቀ ፡ አፈረጠ ፡ የጡት ፡ የፍሬ ። ረጋ ፡ ጸና ፡ የወተት ፡ የማር ፡ የፈሳሽ ።

**ለስድ**፤ (**ዕብ ፡ ልሳድ**) ፡ ጭማቂ ፡ ውጤት ፡ (ደም ፡ ወተት) ፤ ዕትብት ፡ አሰጅ ፡ እንግዴ ፡ ልጅ ። ለስታ ፡ ሊጋ ፡ ትኵስ ፡ ቅቤ ፡ ዘረጋ ፡ ወተት ፡ የሚወጣ ፡ ዝብድን ፡ እይ ። ሕልብ ፡ ሐሊብ ፡ ወይከውኑከ ፡ ለስደ ፡ (ምሳ፴ ፡ ፴፫) ።

**ለስሐ**፤ (**ለችሐ**) ፤ ሰፈጠቀ ፡ አፋን ፡ ምላሱን ፡ አሮኘ ፡ እንፋፏ ፡ እንፋፏ ፡ አለ ። ኢትልሳሕ ፡ እንዘ ፡ ትሜጽር ፡ (ሚራ፴፱ ፡ ፲፯) ። ለስሐና ፡ ለችሐ ፡ የልሒስ ፡ ዘር ፡ ናቸው ።

—፤ ላሸ ፡ ሰለጠ ፡ በልማ ፡ ኾነ ፡ ጣዕም ፡ ዐጣ ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ተናቀ ፡ ተጠላ ፡ ተንቀፈ ፡ የምግብ ፡ ያንደበት ፡ የነገር ። ወእመሰ ፡ ጼው ፡ ለስሐ ፡ በምንት ፡ ይቄስምዎ ። ውስተ ፡ እሳት ፡ ለአብድ ፡ ይለስሕ ፡ አምሳል ። ከመ ፡ ኢትልሳሕ ፡ በእበድከ ። ለስሐ ፡ ኀይልየ ፡ ወደከመ ፡ በጸሎትከ ፡ (ማቴ፭ ፡ ፲፫ ። ሚራ፳ ፡ ፳ ። ፳፫ ፡ ፲፬ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ልሱሕ** ፡ (**ሓን ፡ ሓት ፡ ስሕት**) ፤ የላሸ ፡ ያሰጠ ፡ በልማ ፡ ሕጹጽ ፡ ምኑን ። ልሱሕ ፡ ነገሮሙ ፡ ለአብዳን ። ጼው ፡ ዘአጥዐም ፡ ለልሱሕ ። ልሱሐ ፡ ኀይል ፡ (ሚራ፳ ፡ ፳፱ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

**ልስሐት**፤ መላሸት ፡ ማለጥ ፡ በልማ ፡ መኾን ፡ በልማነት ፡ አለመጣፈጥ ። ልስሐት ፡ ጼው ፡ ግዱፍ ። ልስሐተ ፡ ልሳንየ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲፸ ። ደራሲ) ።

**አልስሐ**፤ አላሸ ፡ በልማ ፡ አደረገ ፡ አደከመ ፡ አሰነፈ ፡ አስናቀ ፡ አስንቀፈ ። አልስሕ ፡ ሕምዘ ፡ ዘክዐወ ፡ ቀታሊ ። በሃይማኖት ፡ ዚአሁ ፡ አልስሐ ፡ ዘሎ ፡ መዋቅሕቲሁ ። ወዘሰ ፡ ይነብብ ፡ በከመ ፡ ረክበ ፡ ያለስሕ ፡ ርእሶ ፡ ወአልቦ ፡ ሞገስ ፡ ለቃሉ ። ያለስሓ ፡ ለምክሮሙ ፡ (ግንዘ ። ድጓ ። ሚራ፳ ፡ ፳፱ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፳፭) ።

**ለስኖ**፤ **ኖት**፤ (**ለሰነ ፡ ይሌስን ፡ ይለስን**) ፤ መለሰን ፡ መምረግ ፡ ምርግን ፡ ማስተካከል ፡ ምላስ ፡ የሳሰው ፡ ማስመሰል ፡ የሜቃ ። ገብበሰን ፡ እይ ፡ (በማርኛ) ።

**ለሰነ**፤ (**ዕብ ፡ ላሽን**) ፤ ሰፈለፈ ፡ ቀባጠረ ፡ አፈቻስ ፡ ተናገረ ፡ ፊት ፡ ለፊት ። ነገር ፡ ሠራ ፡ አሳበቀ ፡ ባንደበት ፡ ወይም ፡ በወረቀት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በለሰነ ፡ ፈንታ ፡ ተለሰነ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ዘእንበለ ፡ ጥበብ ፡ ይትሌሰኑ ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ። ለፀለን ፡ እይ ፡ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

**ለሳኒ** ፡ **መለስን**፤ ለፍላፊ ፡ አሳባቂ ፡ ምላሰኛ ፡ ለላኝ ።

**ተለሰነ**፤ በቁሙ ፡ ተመረገ ፡ ሜቃው ፡ ቤቱ ።

**ልሱን** ፡ (**ናን ፡ ናት ፡ ስንት**) ፤ የተለሰነ ፡ ልስን ፡ ምርግ ።

**ልሳን**፤ (**ናት ። ዕብ ፡ ላሾን ። ሱር ፡ ሊሽና ። ዐረ ፡ ሊሳን**) ፤ በቁሙ ፡ ምላስ ፡ አንደበት ፡ የአፍ ፡ ውስጥ ፡ ሕዋስ ፡ የመብል ፡ የነገር ፡ መሣሪያ ፡ (ያዕ፫ ፡ ፭ ፡ ፮ ። ሚራ፳፰ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ፡ ፳፮ ። መዝ ፡ ፭ ። ፲፩) ። በርሱ ፡ መሣሪያነት ፡ የሚነገር ፡ ቃልና ፡ ቋንቋም ፡ ከርሱ ፡ ስም ፡ ንሥቶ ፡ ልሳን ፡ ይባላል ። ዘክልኤ ፡ ልሳኑ ። ልሳን ፡ ጥዑም ። ጥዑመ ፡ ልሳን ፡ ቃል ፡ ነገር ፡ (ሚራ፮ ፡ ፩ ። ፵፭ ። ድጓ) ። ሕዝብ ፡ ዘኢተአምር ፡ ልሳኖሙ ። እለ ፡ ካልእ ፡ ልሳኖሙ ። በካልእ ፡ ልሳን ፡ ይትናገሩ ። ሰብዓ ፡ ወክልኤቱ ፡ ልሳናት ፡ ዘሴም ፡ ዐሠርቱ ፡ ወሰብዐቱ ፡ ዘካም ፡ ሠላሳ ፡ ዘያፌት ፡ ዐሥራ ፡ ወኀምስቱ ፡ (ኤር፭ ፡ ፲፭ ። ሕዝ፫ ፡ ፮ ። ማር፲፮ ፡ ፲፯ ። ትርጓ ፡ ፊደ) ።



ልሳን ፡

**ልሳን ፡ እንተ ፡ ወርቅ**፤ የወርቅ ፡ ግንዘብ ፡ በልሳን ፡ አምሳል ፡ የተሠራ ፡ (ኢያ፯ ፡ ፳፩) ።

**ልሳን ፡ እሳት**፤ የእሳት ፡ ላንቃ ፡ ነበልባል ፡ (ሐዋ፪ ፡ ፫) ።

**ልሳነ ፡ ባሕር ፤** የባሕር ፡ መሣፍ ፡ ሾለቅ ፡ አሞ ጥመጦ ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ ማኸል ፡ የሚገባ ፡ (ክፋ ፡ ፮) ። ወደ ፡ ባሕርም ፡ የሚገባ ፡ ወንዝ ፡ ልሳን ፡ ይባላል ፡ (ኢ. ሳ፲፩ ፡ ፲፭) ።

**ልሳናዊ ፤** ነዋሪ ፡ ልሳን ፡ ምላሰኛ ፡ ለፍላፊ ፡ አሳባቂ ፡ ወይም ፡ ቋንቋ ፡ ዐዋቂ ።

**ልሳነ ፡ ወርቅ ፤** ጽሩየ ፡ ቃል ፡ ንባቤ ፡ ቃል ፡ ጽሩይ ፡ እንደበቱ ፡ ጥሩ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፪ ፡ ፱) ።

**ልሳነ ፡ መድሎት ፤** የሚዛን ፡ ቀንበር ፡ ጋ ድሙ ፡ ወይም ፡ ላንቲታው ፡ (ጥበ፲፩ ፡ ፳፪) ።

**ልሳነ ፡ ዕፍረት ፤** ምዑዝ ፡ ቃል ፡ ነገሩ ፡ እንደ ፡ ሽቱ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲፪) ።

**ልሳነ ፡ ሰብእ ፤** የድርሰት ፡ ስም ፡ መልክአ ፡ ልሳን ፡ የልሳንን ፡ ጠባይ ፡ የሚናገር ።

**ሊ.ተ ፤—ለኔ ፡ የኔ ፡ እኔን ፤—ለ ።**

**ለትሐ ፤ (ለስሐ) ፤** ጉረሠ ፡ አሳመጠ ፡ ተጉ ነጨ ፡ ተጉመጠመጠ ፡ ጉንጩን ፡ ነፋ ፡ አባበጠ ። ክተተ ፡ አገባ ፡ ልብሱን ፡ በማጥን ፡ ወይም ፡ ሰውነትን ፡ በልብስ ፡ በቀሚስ ። መክተትና ፡ ማግባት ፡ ከመጉረሥና ፡ ከመጉ ንጨት ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ፡ ምስጢሩ ፡ አንድ ፡ ነው ። ለትሐና ፡ ለስሐም ፡ አንድ ፡ ናቸው ።

**ለታሒ ፤ መልትሒ ፡ ሕ ፤** የሚጉርሥ ፡ የ ሚጉነጭ ፡ ከታች ፡ አላማጭ ።

**አልትሐ ፤** አጉረሠ ፡ አስጉረሠ ፡ አስጉነጨ ፡ አስከተተ ፡ አስገባ ።

**እልታሕ ፤ (ሓት ። ዕብ ፡ ሜልታሓ) ፤** የልብስ ፡ ማጥን ፡ ወይም ፡ የክት ፡ ልብስ ፡ የጋን ፡ ሸማ ፡ በማጥን ፡ በጋን ፡ የሚከተት ። ሥሩ ፡ ወጥ ፡ ልብስ ፡ ያል ተሰፋ ፡ ትት ፡ ጥልፍ ፡ መርፌና ፡ መቀስ ፡ ያልዘረበት ፡ የሴቶች ፡ ሥራ ። **እልታሐ ፡ መንፈስ ፡ ተዐጽፈ ። ወከ ደኑኒ ፡ እልታሕ ፡** (ስንክ ፡ ጥቅ፲፱ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፳፫) ።

**መልታሕት ፤ (ብ ፡ መላትሕ ። ዕብ ፡ ማ ልታዓ ፤ ብ ፡ ማልታዖት) ፤** መንጋጋ ፡ ጉንጭ ፡ ፊት ፡ የግራ ፡ የቀኝ ፡ (ማቴ፭ ፡ ፴፱ ። ኢሳ፶ ፡ ፮ ። ፪ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፳፬) ። **ሰላም ፡ ለመላትሒክ ፡ ተጸፍዖ ፡ ዘኢኀ ፈሩ ፡** (ደራሲ) ።

**መልትሐ ፤ (ዲ.ቃ ፡ ማ) ፤** መለቃ ፡ እጅጉን ፡ ባፉና ፡ በጉንጩ ፡ አናረ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመልትሐ፡ ፈንታ ፡ ቀመላትሐ ፡ ይላል ። ትኔጽሩኒ ፡ ወታነክሩ ፡ ወ ትትመላትሑ ፡ በኢደዊክሙ ፡ (ኢዮ፳፩ ፡ ፭) ።

**አመልትሐ ፤** ፊት ፡ አስመለሰ ፡ አሳፈረ ፡ ወ ይም ፡ በጥፊ ፡ አስመታ ።

**ተመላትሐ ፤** ጉንጮቹን ፡ ያዘ ፡ ፊቶቹን ፡ ጸፋ ፡ በ፪ ፡ እጁ ፡ የሐዘን ፡ የእንክብሮ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ አ ገኖ ፡ ተጣፋ ፡ ይሉታል ፡ በጥፊ ፡ ተማታ ፡ ቢያሰኝ ፡ እንጂ ፡ አገኖ ፡ አያሰኝም ፡ እውነተኛ ፡ ፍቺው ፡ ጉንጮቹንና ፡ ፊ ትን ፡ እይለቅም ።

**ለተመ ፤ (ዐረ ፡ ለተመ ፡ ቀጠቀጠ) ፤** በቁሙ ፡ መታ ፡ ገጨ ፡ ወገጠ ፡ ፈተገ ፡ ኀሰበ ፡ ጉርደ ፡ አ ወጣ ፡ ዐሸ ፡ አበቀ ፡ የቄሎ ፡ የሽት ፡ ስያቄትም ፡ ይኸናል ፡ ስፈጸን ፡ እይ ። መለተም ፡ ከበግና ፡ ከፍየል ፡ ውጊያ ፡ የ መጣ ፡ ነው ።

**ተለትመ ፤** ተለተመ ፡ ኀሰበ ፡ ጉርደ ፡ ወጣ ፡ ታሸ ፡ ታበቀ ።

**ልቱም ፤** የተለተመ ፡ ውግጥ ፡ ፍትግ ፡ (ዘፀ፳፱ ፡ ፡፡ ። ዘሌ፪ ፡ ፲፬) ። **ሐሪጽ ፡ ልቱም ፡** ታጥቦ ፡ ተፈትጎ ፡ የተፈጨ ፡ ስንዳሴ ፡ (፪ነገ ፡ ፱ ፡ ፳፱) ።

**ሊ.ቶስጥሮስ ፤ (ጽር ፡ ሊ.ቶስትሮቶስ) ፤** የቦታ ፡ ስም ፡ ጸፍጸፍ ፡ ማለት ፡ ነው ። **መካን ፡ ዘስሙ ፡ ሊቶስጥሮስ ፡** (ዮሐ፲፱ ፡ ፲፫) ። ፀኛም ፡ ሊ.ቶዕርቶን ፡ ሊ.ቶስትሮቶን ፡ ይባል ፡ ፍቺው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (፪ዜና ፡ ፯ ፡ ፫) ።

**ለትቶ ፤ ቶት ፤ (ለተተ ፡ ይሌትት ፡ ይለ ትት ። ላዕልዐ ። ዐረ ፡ ለትለተ) ፤** መለተት ፡ መኰ ልተፍ ፡ መኰላተፍ ፡ ለታታ ፡ መኾን ፡ ያንደበት ። ለትቶ ፡ የሕፃናት ፡ ነው ፡ ከልተፈንና ፡ ላዕልዐን ፡ እይ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በለተተ ፡ ፈንታ ፡ ተለተተ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **ወዝንቱ ፡ ሕፃን ፡ ቦ ፡ አመ ፡ ይትሌተት ፡ በግዕዘ ፡ ሕፃ ናት ፡ ወቦ ፡ አመ ፡ ይትብብ ፡ በነገር ፡ ጽኑዕ ፡ ከመ ፡ ወ ሬዛ ፡ ዘዐሥሩ ፡ ዓመት ። እንዘ ፡ ይትሌተት ፡ ልሳኑ ፡ በሥርዐተ ፡ ይቂቅ ፡** (ገድ ፡ ተክ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**—፤** መለክለክ ፡ ማለክለክ ፡ ምላስን ፡ መጉልጉል ፡ ው ሃን ፡ በምላስ ፡ ማንክ ፡ መጨለፍ ፡ መጠጣት ፡ የውሻ ፡ የድመት ፡ የአራዊት ፡ (ገድ ፡ አዳ) ። መድከም ፡ መልፋት ፡ መታከት ፡ የንደል ፡ የጉልበት ፡ (ፀማርኛ) ።

**ለታት ፤ (ለታቲ ፡ ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤** በቁሙ ፡ ለታታ ፡ ኰልታፋ ፡ ከቡደ ፡ ልሳን ፡ አፈ ፡ ድዳ ፡ አጥርቶ ፡ የማይናገር ። **ወለታት ፡ ውእቱ ፡ ሙሴ ፡** (ተረ ፡ ቁር፪) ።

**—፤** ለክላኪ ፡ አለክላኪ ፡ በምላሱ ፡ ውሃ ፡ የሚልስ ፡ የሚ ጠጣ ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**ልቱት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ትት) ፤** የለተተ ፡ ድ ክመ ፡ ልሳን ፡ ድዳ ፡ ለንባዳ ፡ ወይም ፡ በፍጹሽ ፡ መና ገር ፡ የማይችል ፡ በሃም ። **አስተርአየ ፡ መድኀኒ ፡ ከመ ፡ ያርትዕ ፡ ልሳነ ፡ ልቱታ ፡ ወያፈውስ ፡ ሐንካስ ፡** (መዋሥ) ።

**ልታቴ ፤ ልቶት ፤** ልቱትነት ፡ ድካም ፡ ልስ ላሴ ።

**ልት ፤** በቁሙ ፡ የቅጠል ፡ ስም ፡ የደጋን ፡ መ ሻግሮ ፡ ደካማ ፡ ለስላሳ ፡ የወጥ ፡ ቅጠል ። (ግጥም) ፡ የ ዚህ ፡ ቤት ፡ ሴቶች ፡ እትቅብጡ ፡ ልቶጡ ፡ ናኘኹ ፡ ልቶጡ ፡ (ልት ፡ ወጡ) ። ቀንበልም ፡ ቢለግምና ፡ ቢያቀብር ፡ ልት ፡ ቀጥቅጦ ፡ ቢያበሩበት ፡ ቶሎ ፡ ንፍሮቶ ፡ ይሽራል ።

# መ

**መ** ፤ ፲፫ኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፡ ስሙ ፡ ማይ ፡ ቍጥሩ ፡ አርባ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ (መ—፵) አርብዓ ፡ ይባላል ።

**መ** ፤ የቃል ፡ አጕላማሽ ፡ አጋናኝና ፡ አዳማቂ ። መድረሻ ፡ እየኾነ ፡ በአንቀጽ ፡ ሳይቀር ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ። **መኑመ ፤ ምንትኑመ ፤ እስኩመ ፤ እፎመ ። ውእቱመ ፤ (ርሱማ) ፤ ካልእመ ፤ ባዕድመ ። መጽአመ ፤ ዘይመጽእ ።** ፍችው ፡ ራብዕ ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡ ራብዕ ፡ መኾን ፡ ነው ፤ ሳይፈታም ፡ አዳማቂ ፡ ኹኖ ፡ ይቀራል ። (ዕርሾ ፡ ቍ፲፩) ።

**መ** ፤ ባዕድ ፡ ዘር ። በዘመድ ፡ ዘር ፡ ላይ ፡ እየተጨመረ ፡ መነሻ ፡ ይኾናል ፤ ግእዙ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተነገረ ፡ ካዕቡ ፡ ራብዑ ፡ ሳድሱ ፡ ሳብዑ ፡ አይቀሩም ። ይህም ፡ **ሰፈነ ፤ መስፍን ፤ ወደየ ፤ ሙዳይ ፤ ሐበ ፡ ማሕየብ ፤ ኀሰፈ ፡ ምኅላፍ ፤ ወፀፈ ፤ ሞፀፍ ፤** እያለ ፡ መኽዱን ፡ ያሳያል ። ሙና ፡ ሞ ፡ ጕራጆች ፡ ናቸው ፤ በመ ፡ ከሚነሣ ፡ ከመ ፡ ግስ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ አይገኙም ።

**ሙ** ፤ የወንዶች ፡ አብዢ ፡ ምእላድ ፤ በሩቆችና ፡ በቅርቦች ፡ ዝርዝር ፡ የሚገባ ። **ለሊሆሙ ፤ ለሊክሙ ፤ ሎሙ ፡ ለክሙ ፤ ጸውዖሙ ፡ ጸውዐክሙ ።**

**ሚ ፤ (ሰብ ፡ ሚ ፤ ማ ፤ ሜ)** ፤ የጥያቄና ፡ የምርመራ ፤ የአንክሮ ፡ አገባብ ። ማ ፡ ማን ፤ ምን ፡ ምንድር ። **ሚ ፤ የዐቢ ፤ እምረኀብ ፡ ወሚ ፡ ይሐምም ፡ እምነ ፤ ቍር ። ምንት ፡ አነ ፡ ወሚ ፡ ዘመድየ ። ሚ ፡ ትርኅሚሁ ፡ ለቃል ፡** (አፈ ፡ ተ፳፫ ። ዮዲ፲፱ ፡ ፲፱ ። ፊልክ ፡ ፴፭) ።

—፤ ምንኛ ፤ ምን ፡ ያኽል ፡ ስንት ። **ሚ ፡ አዳም ። ሚ ፡ ብዝኁ ። ሚ ፡ መጠኑ ፡** (ማሕ፱ ፡ ፲ ። መዝ ፡ ፫ ። ቅዳ) ። ሚ ፡ ወሚ ፡ ቢል ፡ ምንና ፡ ምን ፤ ማንና ፡ ማን ፡ ያሰኛል ። በጠጠቅና ፡ በምኞት ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ ምነው ፡ ይኾናል ። **ሚ ፡ እምትነ ፡ በግብጽ ።** መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ዕብ ፡ ሞትን ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፫) ። (ዕርሾ ፡ ቍ፲፩) ።

**ሞአ ፤—አሸነፈ ፤—መዊእ ፤ መዊአት ።**

**መአደ ፤—መከረ ፤—ምዓድ ፡ መዐደ ።**

**መአደ ፤ (ዐረ ፡ ማድ ። ሰብ ፡ ማዳድ)** ፤ ሰፈረ ፡ ከነዳ ፤ አስተካከለ ፡ ወርዱን ፡ ቁመቱን ፡ የሕንጻ ፡ የንጨት ፡ የቦታ ፡ የመሬት ።

**ማእድ ፤ (ዳት ። ዐረ ፡ ማይዳ ፤ ማይደት)** ፤ በቁሙ ፡ ማድ ፡ ገበታ ፡ ሰደቃ ፡ አውራጅ ፡ የምግብ ፡ ማቅረቢያ ፡ መብሊያ ፡ መጠጫ ፤ ወይም ፡ መሸጫ ፡ መለወጫ ፡ ሰፊ ፡ ዝርግ ፡ ሞላላ ፡ ወርዳም ፡ ቁመታም ፡ ወይም ፡ ክብ ፡ እንዳመድማ ፡ ያለ ፡ እግራም ። **አስተዳለወት ፡ ዘዚአሃ ፡ ማእደ ። ማእደ ፡ መኳንንት ። ሊበልዐት ፡ አመትከ ፡ እማእደ ፡ ሐማ ። ወገፍትዐ ፡ ማእዳቲሆሙ ፡ ለመወልጣን ፡** (ምሳ፱ ፡ ፪ ። ሲራ ፡ ፴ ። አስቴ፱ ፡ ፲፯ ። ማቴ፳፩ ፡ ፲፪ ። ፳፬ ፡ ፳፯) ።

—፤ ምሥዋዕ ፡ መንበር ፤ የማዜር ፡ ማእድ ፡ ዕጣንና ፡ ቍርባን ፡ ማቅረቢያ ። **ማእደ ፡ ክህነት ፡ ዘሥሩዕ ፡ ቅድሜከ ፡** (ቅዳ ፡ ያዕ) ። **ማእዳት ፡ ዘምሥያም ፡** (ኢዜና ፡ ፳፫ ፡ ፲፯ ። ኩፋ ፡ ፴፩ ። ሚልኪ ፡ ፩) ።

—፤ ምሳ ፡ ድግስ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ እንጀራና ፡ ወጥ ። **ወገብረ ፡ ማእደ ፡ ዐቢየ ። ባርክ ፡ ማእደ ። ጸሎተ ፡ ማእድ ፡** (ዘፍ፳፮ ፡ ፴ ። ግብ፳ ፡ ፯ ። ሥር ፡ ጸሎ) ።

**ማእዜ ፤ (ዕብ ፡ ማታይ ። ሱር ፡ ኤምታይ ። ዐረ ፡ መቶ)** ፤ የጊዜና ፡ የጥያቄ ፡ አገባብ ፡ መቼ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ በምን ፡ ሰዓት ። ለ ፡ እም ፡ እስከ ፡ ይስማሙታል ። ኅብረቱ ፡ **አውራኂሁ ፡ ማእዜ ፡ ይትወለድ ። ማእዜ ፡ እበጽሕ ። ለእይ ፡ ወለማእዜ ፡ መዋዕል ። ዘኢይብልዎ ፡ እማእዜ ። እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ትላሕዎ ፡** (ኢዮ፴፱ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፵ ። ሸጺዋ ፡ ሸ ፡ ፲፰ ። ቅዳ ፡ ኤጺ ። ሸነገ ፡ ፲፰) ። ኢ ፡ ወኢ ፡ ትርጓሜ ፡ ኢ ፡ ትርአስ ፡ ሲኾኑት ፡ መቼም ፡ መች ፡ ከቶ ፡ ይኾናል ። **ኢማእዜ ፡ ኢከኑ ፡ ሕያዋነ ። ወኢማእዜ ። ኢለክፎን ፡ ፀሓይ ፡ ማእዜኒ ፡** (መቃ ፡ ገ፳ ። ቄር ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፯) ።

**ማእዝን ፤—በቁሙ ፤—አዚን ፡ አዘነ ።**

**መአከ ፤ (የመሀከ ፡ ዋርሳ)** ፤ ተቈጣ ፡ ዛተ ፡ ገላመጠ ፤ ቃጣ ፡ ሰነዘረ ፡ አስፈራራ ፡ በቃል ፡ በበትር ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመአከ ፡ ፈንታ ፡ ተምእከ ፡ ተመአከ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ወዓዲ ፡ አፍርሆ ፡ እንዘ ፡ ይትሜአክ ። ኢክነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ እግዚ ፡ ዘይትሜአክ ፡ ወኢከነ ፡ ከመ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ፡ ዘይትቈየም ። ወይትሜአክ ፡ ጌሳው ፡ ያዕቆብሁ ፡ በእንተ ፡ በረከት ፡ ዘባረከ ፡ አቡሁ ፡** (ዮሴፍ ። ዮዲ፰ ፡ ፲፮ ። ኩፋ ፡ ፳፮) ።

**ምእክ ፤ (ካን ፡ ክት ፡ እክት)** ፤ ቍጡ ፡ ዐይነ ፡ ደረቅ ፡ አፍጣጭ ፡ ገላማጭ ። **ርኩስ ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡ ምእክ ፡ ዐይን ። ኅብአኒ ፡ እምልሳን ፡ ድኑክ ፡ ወእምዐይን ፡ ምእክ ፡** (ምሳ፳፯ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳) ።

**ምእከት** ፤ መቈጣት ፡ መዛት ፡ መቃጣት ፡ ማስፈራራት ።

**ትምእክት** ፤ ቍጣ ፡ ዛቻ ፡ ፍጥጫ ፡ ግልምጫ ፡ ጕራ ፡ ፍከራ ፡ በትር ፡ ሰንዘራ ። **ይሕዝን ፡ ትምእክት ፡ ልበ ፡ ጠቢባን ። ኢይደንግፅ ፡ ትምእክቱ ፡** (ምሳ፲፯ ፡ ፲ ። ዮሴፍ) ።

**መአክቶ**፤—ምግብ፡ ቀለብ፤—አክሎ፡ አከለ ።

**ማእከል** ፤—መከከል ፤—እክሎ ፡ አ ከለ ።

**መአነ** ፤ (ዐረ ፡ መአ ። ዕብ ፡ ማኤን ፡ አንቢ ፡ አለ) ፤ ዘረጋ ፡ አበላ ፡ በሌ ፡ አደረገ ፡ የበታ ፡ የሕግጻ ። እንደ ፡ ዕብራይስጡ ፡ ቢፈቱት ፡ ማን ፡ ዘጋ ፡ ከለከለ ፡ ያሰኛል ።

**ማእን** ፤ ሰፋት ፡ ወርድ ። ባለብሉዮች ፡ ማን ፡ መማቻ ፡ መታኬሻ ፡ ቅጥር ፡ ይሉታል ። ወገብረ ፡ ቀመ ፡ አረፍቱ ፡ ሰብዓ ፡ በእመት ፡ ወማእኖ ፡ ዘኅምሳ ፡ በእመት ፡ (ዮዲ ፡ ፩) ።

**ምእኖ** ፤ **አው** ፡ **ማእኖ** ፤ ዕዘበ ፡ ሣዶቃ ፡ ማጥ ፡ ረግረግ ። እሕርው ፡ ዘውስተ ፡ ጽቡረ ፡ ማእኖ ፡ ያንገረግሩ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ሚኤፌሳይም** ፤ (ዕብ ፡ ሚይ ፡ አፍሳ ይም ፤ ጥቂት ፡ ውሆች ፡ ሰማማ ፡ የሚያለብሱ ፡ እስከ ፡ ቍርጭምጭሚት ፡ የሚደርሱ ፡ ወንዙ ፡ ባይ ፡ ኸኛ ፡ ከማንሳቸው ፡ የተነሣ ፡ እያሉ ፡ የሱም ፡ የሚሉሱ ፡ (ሕዝ ፵፯ ፡ ፫) ።

**ምእር** ፤—አንድ ፡ ጊዜ ፤—ምዕር ።

**መአስ** ፤ (ዕብ ፡ ማአስ ፤ ናቀ ፡ ነቀፈ) ፤ ገፈፈ ፡ አስፌቁት ፡ ቊርበት ፡ አወጣ ። ማስ ፡ ቈፈረ ፡ አጐደጐደ ። ማሳ ፡ ማሽ ፡ ማስት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ማእስ** ፤ (ብ ፡ **አምእስት**) ፤ በቁሙ ፡ ማስ ፡ ቊርበት ፡ ጠፍር ፡ ቈዳ ፡ አጎዳ ። ማእስ ፡ በግዕ ፡ ሕሱይ ። ማእስ ፡ ዘበኒ ። ኢይቀንቶ ፡ ማእስ ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፭ ። ኢዮ፪ ፡ ፳፭ ። ሕዝ፲፮ ፡ ፲፰) ። ትመሥጥዎሙ ፡ አምእስቲሆሙ ፡ እምላዕሌሆሙ ። በልዑ ፡ አምእስተ ፡ ሥረገላቲሆሙ ፡ ወማእስ ፡ ቀቀለ ፡ አስይፍቲሆሙ ፡ (ሚክ ፫ ። ዮሴፍ ። ዘፍ፳፯ ፡ ፲፭) ።

**መአት** ፤ (መዐት ፡ ብዛት ፤ ምዒዕ ፡ መዕዐ) ፤ በዛ ፡ ፈደፈደ ፡ ዐሥር ፡ ዕጥፍ ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ ኾነ ፡ መቶ ፡ ተባለ ።

**አምአተ** ፤ አበዛ ፡ ዐሥሩን ፡ መቶ ፡ ወይም ፡ መቶውን ፡ ሺሕ ፡ አደረገ ። አምአተ ፡ ወአመክዐበ ፡ (ድጓ ። ሉቃ፰ ፡ ፰) ።

**ምእት** ፤ (ዕብ ፡ ሜአ ። ሱር ፡ ማአ ። ዐረ ፡ ሚአት) ፤ የቍጥር ፡ ስም ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ። ምእት ፡ ክረምት ። ምእት ፡ አባግዕ ። ኅረዮ ፡ ምእተ ፡ ብእሲ ፡ (ሚሉ፲፰ ፡ ፬ ። ዘፍ፭ ፡ ፲፱ ። ዮሔ፲ ፡ ፲፪) ። ከክልኤቱ ፡ እስከ ፡ እልፍ ፡ ተስዓ ፡ ወተስዐቱ ፡ ምእት ፡ እያለ ፡ በቅጽል ፡ ይዘምታል ።

**አምእት** ፤ (ታት) ፤ መቶዎች ፡ ዐሥር ፡ መቶ ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ፡ አንድ ፡ ሺሕ ። ይገብር ፡ ማህሰ ፡ ለአምኣት ፡ ወለአእላፍ ። መሳእክተ ፡ አምኣት ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫ ። አዜና ፡ ፳፰ ፡ ፩) ።

**አምእታት** ፤ መቶ ፡ ጊዜ ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ እልፍ ።

**መብእስ** ፤—ወጥ ፡ ግብ ፡ ድንጉር ፤—ብኢስ ፡ ብእሰ ።

**ሚብዝኑ** ፤ የቅኔ ፡ ስም ፡ በ፫ኛው ፡ መዝሙር ፡ የሚገባ ፡ ፫ ፡ ቤት ፡ ያለው ።

**መበለ** ፤ (ዐበለ ፡ ማዕበል) ፤ ጌታየ ፡ ሠለጠነ ፡ ደፈረ ። በሕዝ ፡ እንዘ ፡ ይሜብል ፡ ላዕለ ፡ መርዓት ። ገብር ፡ ጠቢብ ፡ ይሜብል ፡ አጋዕዝተ ፡ አብዶን ። ወብእሲትሰ ፡ ትምህር ፡ ኢናበውሕ ፡ ወኢትመብል ፡ ላዕለ ፡ ብእሲ ፡ (ምሳ፳፱ ፡ ፳፯ ። ፲፯ ፡ ፪ ። ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፪) ።

**አመበለ** ፤ አሠለጠነ ፡ ሾመ ፡ ወከለ ። ወአመበሎ ፡ ዲበ ፡ ዙሉ ፡ ቤቱ ፡ (ኩፋ ፡ ፵) ።

**መብልዕ** ፤—መብል ፡ ምግብ ፤—በሊዕ ፡ በልዐ ።

**መበለት** ፤—በቁሙ ፡ ድኻ ፡ ሴት ፤—በልዎ ፡ በለተ ።

**መብኒም**፤-ቅዱ ማን ፡ ርቱዓን፤-መው ።

**መብዐል** ፤—መክደኛ ፤—ብዒል ፡ ብዕለ ።

**መማ** ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ፬ኛው ፡ ክፍል ፡ ፋትሐ ፡ ነገሥት ። መማ ፡ ዘውእቱ ፡ ነገሥት ፡ ራብዕ ፡ (ፋ ፡ ነ ፡ መቅ) ።

**መማበ** ፡ ብት ፡ (መገበ ፡ ይሚግብ ፡ ይመግብ) ፤ መመገብ ፡ መቀለብ ፡ ማብላት ፡ ማጠጣት ፤ ምግብ ፡ መስጠት ፡ (በማርኛ) ። መጠበቅ ፡ መከናከን ፡ መንበብ ፡ ለመጠበቅ ። ይሚግቡ ፡ በጽድቅ ፡ መንበሮ ። ኢይክል ፡ ሠሪዐ ፡ መንግሥት ፡ ወመግቦታ ። ዘይሚግብ ፡ ንዋየ ፡ ሰይክትምት ። ይሚግብዎ ፡ ወየዐውድዎ ። ማህል ፡ ይሚግቦሙ ። ይሚግብ ፡ ሕዝቦ ፡ (ምሳ፳ ፡ ፳፰ ። ዮሴፍ ። ፋ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፫ ። ፀኢና ፡ ፱ ፡ ፫ ። መገ ፡ ፴፩ ። ፲፳፱ ። ዘዳ፴፰ ፡ ፲) ።

—፤ መምራት ፡ ማስተማር ፡ በሥራት ፡ ማስኬድ ። ምዕመናን ፡ ከዚያው ፡ ከመጠበቅ ፡ ይገባል ። ነፍስ ፡ እስርት ፡ በሥጋ ፡ ከመ ፡ ትመግብ ፡ ወትሥራዕ ፡ ሕይወቶ ። ይሚግባ ፡ ሰሐመር ፡ (ዮሴፍ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**መጋቢ** ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፡ ግብት ፡ በቁሙ ፡ የሚመግብ ፡ የሚጠብቅ ፡ ጠባቂ ፡ ሹም ፡ አዛዥ ፡ ቤታባቂ ፡ ምስለኔ ፡ እንደራሴ ፡ ወኪል ፡ ሞግዚት ፡ መሪ ፡ አስተማሪ ። መጋቤ ፡ ቤት ፡ ንጉሥ ። መጋቤ ፡ ሀገር ። መጋብያን ፡ ሕግ ። መጋቤ ፡ ዙሉ ። መጋቢት ፡ (ኢሳ ፳፪ ፡ ፲፭ ። ሮሜ፲፯ ፡ ፳፫ ። ዳን፲፩ ፡ ፳፫ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ መጋ፳፯) ። መጋብት ፡ አብያት ፡ ንጉሥ ፡ ተሠይሙ ፡ መጋብት ፡ ላዕለ ፡ ዙሉ ፡ ጥሪቱ ። መጋብት ፡ ምዝራብ ፡ (ዕዝ፳ ፡ ፳፱ ። አዜና ፡ ፳፯ ። ፴፱ ። ማቴ፱ ፡ ፩) ።

**ምግብ** ፤ በቁሙ ፤ ቀለብ ፤ መብል ፤ መጠጥ ፤ እንጀራና ፤ ወጥ ። ማርያም ፤ ሀብኒ ፤ ምግበ ፤ ዕለት ፤ እስመ ፤ ተማሕፀንኩ ፤ አንስ ፤ በዘዚአኪ ፤ ስደት ፤ (ቅኔ) ።
—፤ ጥበቃ ፤ ሹመት ፤ የሹመት ፤ ሥራ ፤ አስተዳደር ። መገቦሙ ፤ ምግበ ፤ እኩየ ። ዘሀለወት ፤ ታሕተ ፤ ምግቡ ። ከመ ፤ ይፈጽም ፤ ምግቦ ። ትሰዐር ፤ እምግብከ ። በምግቡ ፤ ለቈስጠንጢኖስ ፤ (ኢሳ ፤ ይ፴፱ ። ፍ ፤ ነ ፤ ፳፱ ፤ ፫ ። ተረ ፤ ባሮ ። ኢሳጅ ፤ ፲፱ ። ስንክ ፤ መስከ ። ሉቃ ፲፯ ፤ ፱—፲) ።

**አመገበ** ፤ አስመገበ ፤ አስጠበቀ ፤ ዐደራ ፤ ሰጠ ፤ ሾመ ፤ አሡለጠነ ፤ መጋቢ ፤ አደረገ ። መጋቢ ፤ ዘአመገብዎ ። እግዚ ፤ አመገበከ ፤ ትቅትል ፤ ወታሕዩ ። አሚግቦ ፤ ምግበከ ። ኢታመግብ ፤ ነኪረ ፤ ባዕለ ፤ ቤትከ ፤ (ፈ ፤ መ ፤ ፳ ፤ ፲፱ ። መቃ ፤ ፺ ። ኢሳጅ ፤ ፳፩ ። ሚራ ፤ ፳፫) ።

**ተመገበ** ፤ በቁሙ ፤ በላ ፤ ጠጣ ፤ ተቀለበ ፤ ተጠበቀ ፤ ተሾመ ። ነፍስ ፤ እንተ ፤ ትትሜገብ ፤ በመንፈስ ፤ አምላካዊት ። ተመገበ ፤ ቦቱ ። እለ ፤ ይትሜገብዎ ፤ ግብረ ፤ መወልጣን ፤ (ኢፌ ፤ ተ፴፱ ። ፍ ፤ ነ ፤ ፵ ። ፈ ፤ መ ፤ ፲፱) ።

**ምጉብ** ፤ (ባን ፤ ባት ፤ ማብት) ፤ የተመገበ ፤ የተጠበቀ ፤ የተሾመ ። ወውእቱሰ ፤ ምጉብ ፤ በኀይለ ፤ አምላኩ ፤ (ገድ ፤ ኪሮ) ።

**ምግብና** ፤ መጋቢነት ፤ ጥበቃ ፤ ሹመት ። በእንተ ፤ ምግብና ፤ (ፍ ፤ ነ ፤ ፴) ። ምግብ ፤ ምግብና ፤ ወይም ፤ ምጋቤ ፤ በማለት ፤ ፈንታ ፤ ምግበት ፤ ይላል ፤ ቤቱ ፤ የቀደሰ ፤ ነውና ፤ አያስኛም ። ሥልጣነ ፤ ምግበት ፤ (ፍ ፤ ነ ፤ ፳፱ ፤ ፫) ።

**መጋቢት** ፤ በቁሙ ፤ ስመ ፤ ወርኅ ፤ ሳብዕት ፤ እመስከረም ፤ የመዓልትና ፤ የሌሊት ፤ ምግብና ፤ እንደ ፤ መስከረም ፤ ትክክል ፤ የሚኾንበት ፤ ወርኅ ፤ ዕሩና ፤ ማለት ፤ ነው ። እስመ ፤ ይዔሪ ፤ መዓልት ፤ ወሌሊት ፤ አመ ፤ ዕሥራ ፤ ወኀሙሱ ፤ ለወርኀ ፤ መጋቢት ፤ (ዲድ ፤ ፴) ። ነገ ፤ ዐምስት ፤ ያለው ፤ የዱሮውን ፤ ነው ፤ ዛሬ ፤ ግን ፤ በዲቃይቅ ፤ ቍጥር ፤ ፱ ፤ ቀን ፤ ወደ ፤ ታች ፤ ወርዷ ፤ አመ ፤ ዕሥራ ፤ ወእሚሩ ፤ ኹኗል ። በኛም ፤ ብትት ፤ አመ ፤ ዐሡሩ ፤ ወሠሉሱ ፤ ወይም ፤ ወረቡዑ ፤ ይኾናል ።

**ሞገድ** ፤—በቁሙ ፤ ማዕበል ፤—ወጊድ ፤ ወገደ ።

**መግዌ** ፤—ጥራዝ ፤ የመጣፍ ፤ ነዶ ፤—ጎግዎ ፤ ጎገወ ።

**መግዝእ** ፤—ገች ፤ ፍሬዳ ፤—ገዚእ ፤ ገዝአ ።

**ምጕሕያ** ፤—ዐረም ፤ ቋያ ፤—ጐሐየ ።

**ምጕጣይ** ፤—መኀንኰል ፤—ጐጥይ ፤ ጐጠየ ።

**ምጕያይ** ፤—መሸሻ ፤ መጠጊያ ፤—ጐይይ ፤ ጐየ ።

**መግለ** ፤ አው ፤ መገለ ፤ (ዐረ ፤ መጀለ ። ዕብ ፤ ማጌል) ፤ መግል ፤ ያዘ ፤ ዐበጠ ። መገለ ፤ ፈረጠ ። ጸልዕ ፤ ዘይመግል ፤ (ኢሳጅ ፤ ፳) ።

**አምገለ** ፤ አመገለ ፤ አፈረጠ ። ያመግል ፤ (መ ፤ ፈ) ።

**መግል** ፤ (ብ ፤ አምግልት) ፤ በቁሙ ፤ ከበጠ ፤ ከቍስለ ፤ ገላ ፤ የሚፈስ ፤ ነጭ ፤ እድፍ ። ለእመ ፤ ኮነ ፤ ቍስል ፤ ዕሙቀ ፤ ወምሉአ ፤ መግል ፤ (ፍ ፤ ነ ፤ ፳፬ ። ስንክ ፤ ነሐሴ) ። ቍስለ ፤ መቅሠፍት ፤ ይገብር ፤ አምግልተ ፤ (ሚራ ፳፫ ፤ ፲፯) ።

**መገን** ፤ (ብ ፤ አምጋን ። ዕብ ፤ ማጌን) ፤ ጋሻ ፤ አግሬ ። በዳዊት ፤ ጋሻ ፤ እምሳል ፤ የተሠራ ፤ የአይሁድ ፤ ንሻን ፤ ማኅተመ ፤ ሰሎሞን ። የኢትዮጵያም ፤ ሽልማትና ፤ ትእምርተ ፤ መንግሥት ፤ ከዚህ ፤ ጋራ ፤ አንድ ፤ ነው ።

**ምጕንጳ** ፤—ጐረንጐሬ ፤—ገነጸ ።

**መጐጸ** ፤ (ደጐጸ ፤ መድገጽ) ፤ ተቈጣ ፤ ዘለፈ ፤ ነጠበ ፤ ነቀፈ ። መጽሐፍ ፤ ግን ፤ በመጕጸ ፤ ፈንታ ፤ አመጕጸ ፤ ይላል ፤ አያስኛም ። ሊቃናት ፤ ኢታመጕጽ ። ዘያመጕጽ ፤ ሊቃናተ ፤ (፩ጢሞ ፤ ፭ ፤ ፩ ። ቀሌ) ።

**አመጐጸ** ፤ (ያሜጕጽ ፤ ያመጕጽ) ፤ አስቈጣ ፤ አስነቀፈ ። አስደራጊ ፤ ነው ፤ ፪ኛ ፤ አካል ፤ ያሳያል ።

**መጕረጽ** ፤—ማጕርጥ ፤—ጐሪጽ ፤ ጐረጸ ።

**ሞገስ** ፤—በለሟልነት ፤—ወጊስ ፤ ወገሰ ።

**ሞገት** ፤—ሞገድ ፤—ወጊድ ፤ ወገደ ።

**መጅ** ፤ ፪ኛ ፤ ክፍል ፤ ፍትሐ ፤ ነገሥት ። መጅ ፤ ዘውእቱ ፤ ነገሥት ፤ ግልጽ ፤ (ፍ ፤ ነ ፤ መቅ) ። በቁሙ ፤ የወፍጮ ፤ ግልገል ፤ (ዐማርኛ) ።

**መደብ** ፤—በቁሙ ፤ ዕርከን ፤—ደይብ ፤ ደየበ ።

**መድበል** ፤—ክምቹ ፤—ደቢል ፤ ደበለ ።

**መድበራ** ፤—ዱር ፤ በረሓ ፤—ደቢር ፤ ደበረ ፤ ደብር ።

**ማድጋ** ፤—በቁሙ ፤ እንስራ ፤—ደጊግ ፤ ደገ ።

**መደደ** ፤ መደ ፤ (ትግ ፤ ወዐረ) ፤ ዘረጋ ፤ መደመደ ፤ አስተካከለ ፤ ያውድማ ፤ የቤት ። ሜዳ ፤ መደዳ ፤ ማለት ፤ ከዚህ ፤ ወጥቷል ። መአደን ፤ እይ ፤ የዚህ ፤ ጎር ፤ ነው ።

**ማድዮ** ፤ (ዕብ ፤ ማድ ፤ ማድያው ። ጽር ፤ ማንዲያስ) ፤ የላይ ፤ ልብስ ፤ የክብር ፤ ልብስ ፤ ነገሥታት ፤ መኳንንት ፤ ልጆቻቸውም ፤ የሚለብሱት ። ዮና ፤ ው ፤ ዝርዝሮች ፤ ናቸው ፤ ልብሰ ፤ ዕበዩ ፤ እንደ ፤

ማለት ። ወሀቦ ፡ ዐጽፈ ፡ ዘላዐሌሁ ፡ ወማድዮኒ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፷) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሰሎፋ ፡ ይሉታል ። ጽኑ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ጽርኡ ፡ ቃል ፡ በማድዮ ፡ ፈንታ ፡ መንድያ ፡ ይላል ፡ ይህንንም ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ፀሐየ ፡ ፈሳ ፡ ያለ ፡ ዘየሀይድ ፡ ዐይን ፡ ብለው ፡ ይፈቱ ታል ።

**ማዳይ። ምድያም**፤ ስመ ፡ ነገድ ፡ (ዘፍ ፡ ፲ ፡ ፬ ። ፳፭ ፡ ፪) ።

**መዲና፤—በቁሙ ፡ ከተማ፤—ደይኖ ፡ ደየነ ።**

**ምዳቀ፤—ምዳቂ፤—ደቂሕ ፡ ደቅሐ ።**

**መደረ፤ (ይመድር ፡ ይምድር ። ዐረ ፡ መዲረ)**፤ ሰፋ ፤ ረዘመ ፡ ወፈረ ። ሰፋት ፡ የወርድ ፤ ር ዝማኝ ፡ የቁመት ፤ ወፍር ፡ የወል ፡ የመካከል ። ብሕረን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ፤ ብሕረ ፡ የባሕር ፤ መደረ ፡ የየብስ ።

**መደረ፤ (ዐረ ፡ ረከዘ)**፤ በቁሙ ፤ ወጋ ፡ ቸ ከለ ፡ ምድር ፡ ያዘ ፡ ተመረኰዘ ፤ ከምድር ፡ ወረደ ፡ ተ ጠጋ ፤ የብስ ፡ ረገጠ ፡ የቀዘፈና ፡ የመርከብ ፡ የባለታንኳ ።

**ምድር፤ (ብ ፡ ምድራት፤ አምዳር፤ አምዳራት ÷ ሮት)**፤ በቁሙ ፤ ሰፊ ፡ ዝርግ ፤ ረዥም ፡ ወርዳም ፡ ቁመታም ፤ ደንዳና ፡ ወፍራም ፤ ከነባሕሩና ፡ ከነየብሱ ፡ ከነኵተናው ፡ ከነልብሱ ፡ ባንድነት ። ዘገብረ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ። ገባሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ። ሰማይ ፡ ወምድር ፡ የነልፍ ፡ (ቅዳ) ።

—፤ የብስ ፡ የባሕር ፡ ርቦ ፤ ከየብስ ፡ የተፈጠሩ ፡ የዐርብ ፡ ፍጥረቶች ፡ የሚኖሩበት ። ወሰመዮ ፡ ለየብስ ፡ ምድረ ፡ ወለምእላደ ፡ ማይ ፡ ባሕረ ። ለታብቍል ፡ ምድር ፡ ሐመልማለ ፡ ሣዕር ። ለታውፅእ ፡ ምድር ፡ ዘመደ ፡ እንስሳ ፡ ወአራዊት ፡ (ዘፍ ፩ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ። ፳፬) ።

—፤ የቦታ ፡ የርስት ፡ የመንግሥት ፡ ክፍል ፤ ሀገር ፡ ብሔር ፡ አውራጃ ፡ መንደር ፡ ከተማ ፡ ገጠር ፤ በሕዝብ ፡ በነገድ ፡ በገመድ ፡ በቀላድ ፡ የተለየ ፡ ከነሕዝቡ ፡ ከነባለቤቱ ። ኵሉ ፡ ምድር ። ምድራት ፡ ርሒባት ። አድባር ፡ ወአምዳር ። ውሳንያቲ ፡ አምዳር ። ይበውእ ፡ ው ስተ ፡ አምዳራት ። ወዘረውክዎሙ ፡ በአምዳሮት ፡ (ዮዲ ፲፩ ፡ ፲፯ ። ኢዘና ፡ ፱ ፡ ፷ ። ዘዳ፲፩ ፡ ፲፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯ ። ዳን ፲፩ ፡ ፶ ። ሕዝ፲፩ ፡ ፲፯) ።

—፤ የሰው ፡ ባሕርይ ፤ ሥጋ ፡ ዐፈር ፡ መሬት ። ዘምድረ ፡ ለብሰ ፡ (ኪዳ) ። ምድረ ፡ ግብ ፤ ምድረ ፡ ባሕር ፡ ቢል ፡ ታሕት ፡ ውስጥ ፡ ልብ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዳንኤ ፡ ፳፱ ። ኢዮ ፴፰ ፡ ፲፯) ።

**ምድራዊ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)**፤ በቁሙ ፤ የምድር ፡ ከምድር ፡ የተገኘ ፡ በምድር ፡ የሚኖር ። ወልደ ፡ ምድራዊ ። ሥጋ ፡ መሬት ፡ ምድራዊ ። ንጉሥ ፡ ምድራዊ ። ሕይወት ፡ ኀላፊት ፡ ምድራዊት ፡ (ጥበ፯ ፡ ፩ ። ዮሴፍ ። ፈልክ ፡ ፶፻፶ ። መቃ) ።

**መድረወ**፤ ከምድር ፡ አገባ ፡ ከተተ ፡ ቀበረ ፡ ፈጸመ ፡ ሰለረሰ ፡ አከናወነ ፡ ያገዘመራ ፡ የሥራ ። ገመረን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**አመድረወ**፤ ከምድር ፡ አስገባ ፡ አስከተተ ።

**እምድሩ**፤ አካቶ ፡ ፈጽሞ ፡ ጭራሽ ፤ ከንዱ ፡ ዘንዱ ። ግሙራን ፡ እዩ ። እመሰ ፡ እምድሩ ፡ ትኩሲ ፡ ሕማማት ፡ ትክሕድ ፡ ትስብእቶ ፡ (ተረ ፡ ቄርሎ) ።

**ምህወ፤ (ይምሁ ፡ ይምሀው፤ ምሂው ። መስወ፤ መሰወ)**፤ ሟሟ ፡ ቀለጠ ፤ ውሃ ፡ ኾነ ፤ ዘለ ፡ ደከመ ፡ ወዛ ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፳፩) ። ሥጋሁ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ምህወ ። ባሕር ፡ እንተ ፡ ኢተዐዱ ፡ እምወሰና ፡ ወ ምድርኒ ፡ እንተ ፡ ኢትምሁ ፡ እምዝብጠተ ፡ መዋግ ደሃ ። ይምሁ ፡ ወይትመሰው ፡ ኵሉ ፡ አባል ፡ (ስንክ ። አትና ። ግንዘ) ። ማይ ፡ ውሃ ፡ ማለት ፡ ኹለቱም ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። በምህወ ፡ ፈንታ ፡ ተምህወ ፡ ይላል ፡ ስሕ ተት ፡ ነው ። ትትመሀው ፡ አባሉ ፡ (ግንዘ) ።

**አምሀወ**፤ አሟሟ ፡ አቀለጠ ፡ ውሃ ፡ አደረገ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

**ማህው፤ (ብ ፡ ማህዋት፤ አምሃው ። ዐረ ፡ መሃት)**፤ የብርሌና ፡ የብርጭቆ ፡ የቅዝዝ ፡ የመ ስታዮት ፡ ጭቃ ፡ ዐፈሩ ፡ ደንጊያው ፡ እንደ ፡ ኖራ ፡ ፈል ቶና ፡ ቀልጦ ፡ የሚሠራ ፤ ወይም ፡ የተሠራው ። መስተ ገብራን ፡ ማህው ። አምጽኡ ፡ ሎሙ ፡ እምሀየ ፡ ሕምዘ ፡ በማህው ። ጽዋዐ ፡ ማህው ። እለ ፡ ይስ ትዩ ፡ ወይነ ፡ በማህው ፡ ወቢረሌ ። ማህው ፡ ሰእመ ፡ ቀሰብረ ፡ አልቦ ፡ ዘያስተጣግዖ ፡ ዘእንበለ ፡ ገባሪሁ ። ሰባራት ፡ ማህው ፡ በሊኍት ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፳፮ ። ዮሴፍ ። አርጋ ። ዓሞ፮ ፡ ፮ ። ያዕ ፡ ዘእል ። ሚራማር ፡ ፲፱) ።



ማህው ፤

**መሀከ፤ ምህከ፤ (መሐረ ፡ ምሕረ)**፤ ራራ ፡ ሀዘነ ፡ ማረ ፡ ይቅር ፡ አለ ። ኢመሀከተኪ ፡ ዐይን ። ወልደ ፡ ጥቀ ፡ ኢምህከ ፡ እምኔነ ። አንተሰ ፡ ትም ህክ ፡ ሐምሐመ ። መሀክ ፡ ሕዝበከ ። መሀኩ ፡ ሲተ ፡ ወልድየ ። ዘእንበለ ፡ ምሂክ ። ምሂኮትየ ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፭ ። ሮሜ፰ ፡ ፴፪ ። ዮና፬ ፡ ፲ ። ዮኤ፪ ፡ ፲፯ ። ፪ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፭ ። ስንክ ። አርጋ) ።

—፤ ገመገመ ፡ ሣሣ ፡ ቈጠበ ። ዘይምህክ ፡ በትሮ ። ዘ ይምህክ ፡ ነገረ ። ኢትምህኩ ፡ ገሥጾቶሙ ፡ (ምሳ፲፫ ፡ ፳፬ ። ኢዮ፴፪ ፡ ፫ ። ዲድ ፡ ፳፪) ።

—፤ አዳነ ፡ ተቤዠ ፡ ጠበቀ ። ይምህክ ፡ ነፍሰ ፡ እሞት ። እምእደ ፡ ሰአል ፡ መሀከ ። ወአምነኪር ፡ መሀከ ፡ ለገ ብርከ ፡ (ኢዮ፴፫ ፡ ፲፰ ። አርጋ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፲፰) ።

**መሃኪ** ፤ (ኪት ፡ ክያን ፡ ያት) ፤ የሚራራ ፡ መሐሪ ፡ ዐዛኝ ፤ ይቅር ፡ ባይ ፡ አዳኝ ፡ ፈዋሽ ። አብ ፡ መሃኪ ፡ ዘይምህክ ፡ ወልዶ ። እግዚ ፡ መሃኪክ ፡ (አፈ ፡ ተ፱ ። ዘፀ፲፭ ፡ ፳፯) ።

**ተምህከ** ፤ ተማረ ፡ ይቅር ፡ ተባለ ፡ ይቅርታ ፡ አገኘ ።

**ምሁክ** ፤ (ክን ፡ ክት ፡ ህክት) ፤ የተማረ ፡ ይቅርታ ፡ ያገኘ ።

**ምህከት** ፤ መራራት ፡ ይቅር ፡ ማለት ። ይቅር ፡ መባል ፡ ይቅርታ ፡ ማግኘት ። ይቅርታ ፡ ስርየት ፡ ርኅራኄ ። ምህከት ፡ ወምሕረት ፡ (ዮሴፍ) ።

**ማህከወ** ፤ (ተቀ ፡ ግ ። መህከ) ፤ አስፈራ ፡ አስደነገጠ ።

**ተማህከወ** ፤ ፈራ ፡ ደነገጠ ፤ ከው ፡ ከኝ ፡ አለ ። ወሶበ ፡ ይወዲ ፡ ዲቤክሙ ፡ ቃሎ ፡ ሕኩ ፡ ትትማህከዉ ፡ ወትፈርሁ ፤ ወሶበሙ ፡ ብርሃናት ፡ ይትህወኩ ፡ በፍርሀት ፡ ዐቢይ ። ወምድር ፡ ሶላ ፡ ትትማህከው ፡ ወትርዕድ ፡ ወትጌጉእ ፡ (ሔኖ፻፪ ፡ ፭ ፡ ፪) ።

**ምህላ** ፤—ልመና ፡ ምልጃ ፤—ምሒል ፡ መሐለ ።

**ማሄለክ** ፤ (ዕብ ፡ ማሃላኽ) ፤ መኼጃ ፡ መመላለሻ ፤ መንገድ ፡ ወልወል ፡ (ሕዝ፵፪ ፡ ፬) ።

**መህን** ፤—ፈገፈገ ፤—ምሒን ፡ መሐነ ።

**መህና** ፤—እጅ ፡ መንሻ ፤—መሐና ።

**ሜሄኑሀ** ፤ (ዕብ ፡ ሜሄናሀ) ፤ እምነሆን ፡ (ሕዝ፵፪ ፡ ፳) ።

**ምሂር** ፤ ሮት ፤ (መህረ ፡ ይሜህር ፡ ይምህር ። ዕብ ፡ ማህር ፤ ፈጠነ ፡ ቸኰለ) ፤ መማር ፤ መምህር ፡ መኾን ፡ መምራት ፡ ማሳየት ፤ መምከር ፡ ማስተማር ፡ ማልመድ ፡ ማስለመድ ። መህሮ ፡ ሕቡሁ ፡ መጽሐፈ ። ዘሰ ፡ ይሜህር ፡ ወይገብር ። ትሜህር ፡ እገሪሃ ፡ ሐዊረ ፡ (ኩፋ ፡ ፯ ። ማቴ፭ ፡ ፲፱ ። ዘዳ፳፫ ፡ ፶፯) ። —፤ መቅጣት ፡ መገረፍ ፡ መቈጣት ፡ መገሰፍ ። መህር ፡ ወልደከ ። መሀረኒ ፡ እግዚእ ። ገሠጸ ፡ ወመሀረ ፡ (ምሳ፳፱ ፡ ፲፯ ። ኤር፲ ፡ ፳፬ ። ሢራ፯ ፡ ፳፫) ። መርሐን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**መሃሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፡ ህርት) ፤ በቁሙ ፡ ማሪ ፡ መሪ ፡ መካሪ ፡ አስተማሪ ።

**መምህር** ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፤ በቁሙ ፡ መምር ፡ የትምርት ፡ አባት ። አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ መምህርክሙ ። መምህርት ፡ ይእቲ ። መምህራነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፳ ። ጎዳ፳፬) ። ውርወት ፡ ድቀት ፡ ፍርሀት ፡ በማስት ፡ ፈንታ ፡ መምህረ ፡ ሕግ ፡ ይባል ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (መገ፱ ፡ ፳፳) ።

**ማህር** ፤ (ብ ፡ አምህርት) ፤ ገዢ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ። አእላፍ ፡ አምህርት ፡ (አቈሮ ፡ ፬ ፡ ፲፭) ።

**አምሀረ** ፤ አስማረ ፡ አስተማረ ፤ ለመምህር ፡ ሰጠ ፤ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ አገባ ።

**ተምህረ** ፤ ተማረ ፡ ለመደ ። ተምህረ ፡ መጽሐፈ ። ተምህረ ፡ መሢጠ ። እስከ ፡ ይትሜሀሩ ፡ ብዙኃን ፡ (ኩፋ ፡ ፬ ። ሕዝ፲፱ ፡ ፫ ። ዳን፲፪ ፡ ፬) ። ነበበ ፡ ኀለየ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተምህረ ፡ ይባል ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ኢትትመሀር ፡ ነፍስየ ፡ ኀጢአተ ። ልበ ፡ ጻድቃን ፡ ይትሜሀር ፡ ሃይማኖተ ። እስመ ፡ ሐሰተ ፡ ይትሜሀር ፡ ልበሙ ፡ (ኢዮ፳፯ ፡ ፬ ። ምሳ፲፭ ፡ ፳፰ ። ፳፬ ፡ ፪) ።

**ተመሃሪ** ፤ ተማሪ ፡ ረድእ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ። ተመሃርያን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**ምሁር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ህርት) ፤ በቁሙ ፡ የተማረ ፡ ትምርት ፡ የጠገበ ፡ በዋቂ ፡ ሊቅ ፡ ልባም ፡ አስተዋይ ። ምሁር ፡ በሕሉ ፡ ጥበብ ። ምሁራን ፡ በኀበ ፡ እግዚ ። ነገሩ ፡ ኢኮነ ፡ ከመ ፡ ምሁር ። ብእሲ ፡ ምሁር ፡ (ቀሌ ። ኢሳ፶፬ ፡ ፲፫ ። ኢዮ፴፬ ፡ ፴፫ ። ሢራ፴፩ ፡ ፱) ።

**ተምሃር** ፤ ትምርት ፤ ልማድ ። ሕግከ ፡ ተምሃርየ ፡ ውእቱ ። እስመ ፡ እኩይ ፡ ተምሃሩ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ። ሄርማ ፡ ገ፴፱) ።

**ትምህርት** ፤ (ታት) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፡ በቁሙ ፡ ትምርት ፤ ዕውቀት ፤ ድርሳን ፡ ምዕዳን ። ወልድ ፡ ዘእንበለ ፡ ትምህርት ። ፍሳት ፡ እለ ፡ አልቦን ፡ ትምህርት ። በትምህርታቲሁ ። ትምህርታት ፡ ወተግሣጻት ፡ (ምሳ፲፯ ፡ ፳፭ ። ጥበ፲፯ ፡ ፩ ። ቄር ። ስንክ ፡ መስ፳) ። ልማድና ፡ ባህል ፡ ይኾናል ፡ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ትምርት ፡ ነው ።

**ማህረከ** ፤ (ይማህርክ ፡ ይማህርክ ፤ ተቀ ፡ ግ ፤ ወይም ፡ የመህክ ፡ ስሬጽ) ፤ ማረከ ፡ ዘረፈ ፡ ወሰደ ፡ ነዳ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሳበ ፡ አቀረበ ፤ በትምርት ፡ በታምራት ፤ ወይም ፡ በጦርነት ። ይማህርክሙ ፡ ለጽኑዓን ። ማህረኩ ፡ ወቀተሉ ፡ ደቂቀ ። ወማህረከ ፡ እንስሳሆሙ ። ማህረክዎሙ ፡ ምህርካ ፡ ብዙኀ ፡ (ኢሳ፶፫ ፡ ፲፪ ። ኢዮ፩ ፡ ፲፯ ። ዮዲ፪ ፡ ፳፫ ። ፪ዜና ፡ ፲፬ ፡ ፲፫) ።

**አማህረከ** ፤ (ያማህርክ) ፤ አስማረከ ፤ አዘረፈ ።

**ተማህረከ** ፤ (ይትማህረክ) ፤ ተማረከ ፡ ተዘረፈ ፡ (ወይም ፡ ተመራረከ ፤ ተዘረፈ) ። አስዋር ፡ እለ ፡ ተማህረኩ ። እስመ ፡ ተማህረካ ፡ አባግዕየ ፡ (ኢሳ፭ ፡ ፲፯ ። ሕዝ፴፬ ፡ ፰) ።

**ምህርክ** ፤ (ካት) ፤ ምህሩክ ፡ የተማረከ ፡ ምርኮ ፤ ምርኮኛ ። ዔዋ ፡ ወምህርካ ። ተካፈልኩ ፡ ምህርካ ። እንዘ ፡ ትሰመይ ፡ መምህረ ፡ ወካቶሊካ ፤ አባእከ ፡ ሎቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ምህርካ ፡ (ዘኍ፴፩ ፡ ፲፩ ። መዝ ፡ ፷፯ ። ስንክ ፡ ግንቦ፲፯) ።

**ምህርክና** ፤ ምርኮኝነት ፡ ምርኮ ፡ መኾን ። በምህርክ ፡ ፈንታ ፡ ምህርክና ፡ ይባል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (፪ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፭ ፡ ፰ ፡ ፲፫) ።

**አስተማህረከ** ፤ አማረከ ፡ አመራረከ ። እንዲሁ ፡ አማህረከም ፡ ባስደራጊነት ፡ ይፈታል ።

**መዊእ ፡ አት ፡** (ሞአ ፡ ይመውእ ፡ ይማእ) ፡ ማሸነፍ ፡ መርታት ፡ ድል ፡ መንሣት ። ትእምርት ፡ መዊእ ። ወይን ፡ ይመውእ ፡ አንስት ፡ ይመውኦ ። ሞኦ ፡ ለሞት ፡ ወተንሥአ ። ሞእክምዎ ፡ ለእኩይ ፡ (ኤፌ ፡ ተኛ ። ዕገዘ ፡ ፲ ። ድጓ ። ሸዋሐ ፡ ፬ ፡ ፲፫) ።

**መዋኢ ፡** (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፡ ያሸነፈ ፡ የሚያሸንፍ ፡ አሸናፊ ። ሰላም ፡ ለከ ፡ አባዲር ፡ መዋኢ ። ወኢሞኦ ፡ በኀይሉ ፡ መዋኢት ። በእንተ ፡ ሰማዕታት ፡ መዋእያን ፡ (ስንክ ፡ መስከረም ። መቅ ፡ ወን ። ቀዳ) ።

**አሞአ ፡** ድል ፡ አስነሣ ፡ አጸና ፡ አበረታ ፡ አሠለጠን ። ኢያመውኦ ፡ ሶበ ፡ ይትዋቀሥ ፡ (አርጋ ፡ ፩) ። ዘአሞኦ ፡ እግዚ ፡ ላዕለ ፡ ካልኡ ። ክመ ፡ ታሙኦ ፡ ለዘ ፈቀድከ ። ውእቱ ፡ ያመውአከ ፡ በጻሩ ፡ ወበመንግሥቱ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ተሞአ ፡** (ይትመዋእ) ፡ ተሸነፈ ፡ ድል ፡ ኾነ ፡ ተረታ ። ሞት ፡ ተሞአ ። ወሶበሂ ፡ ይትዋቀሥ ፡ ይፄእ ፡ ተመዊኦ ፡ (ድጓ ። መገ ፡ ፲፭) ። በተሞአ ፡ ፈንታ ፡ ተመውአ ፡ ይላል ፡ በሰብሐና ፡ በቀደሰ ፡ መንገድ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ በቀተለ ፡ ቤት ፡ አይስኝም ። ተመውአ ፡ ቀትል ፡ ብይእቲ ፡ ዕለት ፡ (፪ዜና ፡ ፲፰ ፡ ፴፬) ።

**ምዉእ ፡** (ኣን ፡ አት ፡ ውእት) ፡ የተሸነፈ ፡ ድል ፡ የኾነ ፡ የተረታ ። ትክውን ፡ ምዉእ ፡ ሎቱ ። ሕገ ፡ ጸብእ ፡ ወመዊእ ፡ ትሬስዮሙ ፡ ለምዉኣን ፡ እግብርተ ፡ ለመዋእያን ፡ (ፊላስ ፡ ገ፴፱ ። ና ፡ ን ፡ ፴፭) ።

**ሙአት ፡** ማሸነፍ ፡ መሸነፍ ፡ አሸናፊነት ፡ ድል ፡ ርቱታ ። እፎ ፡ ትኄልዩ ፡ እንትሙ ፡ ሙአትሙ ። እምድኅረ ፡ ሙአተ ፡ ዘሎሙ ፡ በይጠናት ። እምኑቤከ ፡ ሙአት ። ተበጥመ ፡ ሞት ፡ ውስተ ፡ ሙአት ፡ (ዮሴፍ ። ፈልክ ፡ ፴፱ ። ዕገዜ ፡ ፵፱ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፶፬) ።


**ምዋኤ ፡** ዝኒ ፡ ከማሁ ። ብጡል ፡ እምዋኤክሙ ፡ (አዋል) ።

**ምሟእ ፡** (ኢት) ፡ ማሸነፊያ ፡ ድል ፡ መንሻ ፡ መርቻ ፡ መረቻ ።

**ሙባኒም ፡** (ዕብ ፡ ሙካኒም) ፡ ቅዉማን ፡ ርቱዓን ፡ ወይም ፡ ቅልብሶች ፡ ቅንፎች ፡ ማለት ፡ ነው ። በዕብራይስጡ ፡ በና ፡ ክ ፡ (ቤት ፡ ካፍ) ፡ ይማስሳሉና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተሳስቶ ፡ ሙካ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሙባ ፡ ብሎታል ። ወከናፍሪሆሙ ፡ አሐዱ ፡ ጥፍሕ ፡ ሙባ (ካ)ኒም ፡ እንተ ፡ ውስጥ ፡ (ሕዝቅ ፡ ፵፫) ።

**ሞገሰ ፡**—ውድ ፡ ውዴታ ፡—ወጊስ ፡ ወገሰ ።

**ሙዝ ፡** (-ብ ፡ አሟዝ ፡ እምዋዝ ። ዐረ ፡ መውዝ ። ሱር ፡ ሙዛ) ፡ በቁሙ ፡ የታወቀ ፡ ተክል ፡ የኀሰትና ፡ የኮባ ፡ የጕናጕና ፡ ወገን ፡ ፍሬው ፡ ጥፍጥ ፡ (አዋል) ።



ሙዝ ፡

**ሞጣሕት ፡**—በቁሙ ፡—ወጥሐ ፡ ወጥሐ ።

**ሟል ፡** (ዕብ ፡ ሙል) ፡ ትይዩ ፡ አንጻር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አኳያ ፡ እኩያ ፡ አምሳያ ። ወዳጅን ፡ ባለሟል ፡ እንዲሉ ፡ በዐረብ ፡ ግን ፡ ማል ፡ ብሎ ፡ ገንዘብ ፡ ይላል ።

**መዊጽ ፡ ጾት ፡** (ሞጸ ፡ ይመውጽ ፡ ይሙጽ ። ዐረ ፡ ማጸ) ፡ መሟጠጥ ፡ መፋቅ ፡ የጥርስ ። መፈግፈግ ፡ መወልወል ፡ መጥረግ ፡ ማጥራት ፡ የድፍ ፡ የጕድፍ ። መክስ ፡ ካሳ ፡ መስጠት ፡ ቂምን ፡ በቀልን ፡ በካሳ ፡ ማጥፋት ። (ተረት) ፡ ሲታረቁ ፡ ካሶ ፡ ሲጸድቁ ፡ መንኵሶ ።

**መዋጺ ፡** (ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት) ፡ የማሟጭ ፡ ሟጪ ፡ ካሽ ፡ ካሳ ፡ ሰጪ ።

**አሞጸ ፡** አስካሰ ፡ ካሳ ፡ አሰጠ ።

**ተሞጸ ፡ ተመውጸ ፡** ተሟጠጠ ፡ ተካሰ ።

**ምዉጽ ፡** (ጻን ፡ ጻት ፡ ውጽት) ፡ የተሟጠጠ ፡ የተካሰ ።

**ተማወጸ ፡** ተካካሰ ፡ ተራረቀ ።

**አስተማወጸ ፡** አካካሰ ፡ አስተራረቀ ። ሲዘተ ጻዐሰ ፡ ያስተማውጽዎ ፡ (ሚራ ፳፮ ፡ ፳፭) ።

**ሞጸ ፡** (ጻት) ፡ ካሳ ፡ የበደል ፡ ዋጋ ፡ ሤጠ ፡ ደም ፡ መሟጠት ፡ ኀጢአት ፡ (፳ነገ ፡ ፳ ፡ ፫ ፡ ፱ ፡ ፳ ፡ ፲፪) ። መሟጫ ፡ መፋቂያ ፡ ርጥብ ፡ ዕንጨት ፡ ወይም ፡ ጭራ ።

**ሞጽ ፡** (ዕብ) ፡ ትቢያ ፡ እብቅ ፡ ቆንድ ፡ እድፍ ፡ ጕድፍ ፡ ደቃቅ ፡ ነገር ።

**ሙጽ ፡** ሙሏይ ፡ ቂጣፋ ፡ በትር ፡ የጤፍና ፡ የማሽላ ፡ መውቂያ ። ቂጣፋም ፡ ባይኾን ፡ ማናቸውም ፡ የራቻ ፡ መውቂያ ፡ ሙጫ ፡ ይባላል ።



ሙጽ ፡

**ሙጻእ ፡**—መውፅእ ፡ ቀዳዳ ፡—ወፂእ ፡ ወፅአ ።

**መዊቅ ፡ ቆት ፡** (ሞቀ ፡ ይመውቅ ፡ ይሙቅ ። ሐመ ፡ ረስነ) ፡ መሞቅ ፡ መተኰስ ፡ ሙቀት ፡ መንሣት ፡ ማግኘት ፡ ከፀሓይ ፡ ከእሳት ፡ ከልብስ ፡

ክደቱ፤ ማቅ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ወዲህ፡ ደመቀን፡ እይ። ሶበ፡ ሞቀ፡ ፀሓይ። ወእምከመ፡ ሞቀ፡ ፀሓይ፡ ይ ምህ። ሐወዘኒ፡ እስመ፡ ሞቀ። ትትከደኑ፡ ወኢ ትመውቁ። እምፀምረ፡ አባግዕየ፡ ሞቀ፡ መታክፍ ቲሆሙ፡ (፩ነገ፡ ፲፩፡ ፱። ዘፀ፲፮፡ ፳፩። ኢሳ፵፱፡ ፲፮። ሐጌ፩፡ ፮። ኢዮ፴፩፡ ፳)። በሞቀ፡ ፈንታ፡ ተማወቀ፡ ይላል፤ አያስኬድም፡ (ኢሳ፵፬፡ ፲፮)።

**ምዉቅ**፤ (ቃን፡ ቃት፡ ውቅት)፤ የሞቀ፡ ሙቅ፡ ትኩስ። ለከሰ፡ ምዉቅ፡ ውእቱ፡ አልባሲከ። ምዉቅ፡ ከመ፡ እሳት። ኅብስት፡ ምዉቅ። ማይ፡ ምዉቅ። ዐዚዝ፡ ወምዉቅ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ (ኢዮ፴፯፡ ፲፯። ሔኖ፲፱፡ ፲፫። ፩ነገ፡ ፳፩፡ ፯። ስንክ፡ የካ፲፩። ራእ፫፡ ፲፭። ቀሌ)።

**ሙቀት**፤ በቁሙ፤ መሞቅ፡ አሞቃሞቅ፡ ትኩሳት፡ ትኩስነት። እስከ፡ ሙቀተ፡ ፀሓይ። ሙቀተ፡ ሐሩር። እንዘ፡ ሀሎ፡ ሙቀት፡ ላዕሌሁ። አስሐትየ፡ ዘአልቦ፡ ሙቀት፡ (ነሐ፮፡ ፫። ሔኖ፡ ፱። ቅዳ። ቀሌ)።

**ሞቅ**፤ ሙቀት፡ ትኩሳት፡ (ሔኖ፸፭፡ ፱፡ ፮)። ነፋስ፡ ሞቅ። እሳተ፡ መለኮት፡ ዘይቄድስ፡ ነፍሰ፡ ወይጥዒ፡ ሞቅ፡ (ሔኖ፸፮፡ ፩፡ ፮። ደራሲ)።

**አሞቀ**፤ በቁሙ፤ አተኰሰ። (አስሞቀ፡ አስተ ኰሰ)። እሳት፡ ያመውቅ፡ ለኀጺን። አሐቲ፡ ኖኅት፡ ታመውቅ፡ ሞቀ። ያመውቅ፡ ፀሓይ፡ ለውእቱ፡ ዐፄ፡ ወይከውን፡ ያፈ። አሙቅ፡ ላሕዎቶ፡ (ቄር፡ ጸላ። ሔኖ፸፰፡ ፮። ዲድ፡ ፳፩። ሚራ፴፫፡ ፲፯)። በአሞቀ፡ ፈንታ፡ አስተማወቀ፡ ይላል፤ አድራጊነት፡ ከደራራጊነት፡ ያሳያል። ተሐቅፎ፡ ወታስተማውቅ። አስተማወቅዎ፡ እስትንፋሰ፡ አድግ፡ ወላሕም፡ (፫ነገ፡ ፩፡ ፪። ቅዳ፡ ሕር)።

**ተማወቀ**፤ ተሞቃሞቀ። እስመ፡ እመ፡ ኖሙ፡ ክልኤሆሙ፡ ይትማወቁ፤ ወአሐዱሰ፡ እፎ፡ ይት ማወቅ፡ (መክ፬፡ ፲፩)።

**አስተማወቀ**፤ አሞቀ፤ አሞቃሞቀ። በዝየ፡ ያስተማውቅ፡ እዴሁ፡ ካህን፡ ላዕለ፡ ማዕጠንት። እንዘ፡ ያስተማውቅዎ፡ በሕሉ፡ ምዕጻን፡ (ቅዳ። ገድ፡ ኪሮ)።

**መዊት**፤ ዎት፤ (ሞተ፡ ይመውት፡ ይ ሙት። ዕብ፡ ሚት። ሱር፡ ሚት። ዐረ፡ ማተ)፤ መሞት፡ መለየት፡ በነፍስ፡ ከሥጋ፡ በሥጋ፡ ከነፍስ፡ መራቅ፡ እየብቻ፡ መኾን፡ መድረቅ፡ መፍረስ፡ መበስበስ፡ መነቀል፡ መፍለስ፤ መጥፋት፡ መታጣት። ሐዩውኒ፡ ወመዊትኒ። ሞተ፡ ዐማኑኤል፡ ከመ፡ ሞት፡ ዚአነ፡ ዘውእቱ፡ ተፈልጦተ፡ ነፍስ፡ እምሥጋ። ሞትነ፡ እምኀጢአት። ወሙት፡ እምፍትወታቲሁ፡ ለዝ፡ ዓለም። እመ፡ ሞተ፡ አዕጹቂሁ። እለ፡ ካዕበ፡ ሞታ፡ ወተሠረዋ። ሞተት፡ ኅሊና፡ እምኔሁ፡ (ሚራ፲፩፡ ፲፱። ሃይ፡ አበ። ሮሜ፮፡ ፪። ፊልክ፡ ፫። ኢዮ፲፬፡ ፰። ይሁ፡ ፲፪። ቂድር)።

**መዊት**፤ (ቲት፡ ትያን፡ ያት)፤ በቁሙ፤ የሞተ፡ የሚሞት፡ ሟች፡ ሥጋዊ፡ ሰው። አንተ፡ መዋቲ፡ ዘከመ፡ ዕሪናከ፡ ምስሌነ፤ ወአንተ፡ ኢመዋቲ፡ ዘ ከመ፡ ዕሪናከ፡ ምስለ፡ አብ። እመ፡ ኮነ፡ መዋቲ፡ ካህን። ተናገሮ፡ በልሳነ፡ መዋቲ፡ (ሃይ፡ አበ። ፍ፡ ነ፡ ፳፪። ቀሌ)።

**ምዉት**፤ ሙት፤ (ታን፡ ታት፡ ውት)፤ በቁሙ፡ የሞተ፡ የተለየ፡ ሬሳ፡ በድን፡ አስከሬን። ምዉተ፡ ትካት። ምዉታን፡ በኀጢአት። በእንተ፡ ሙታን። ምውት፡ ይእቲ፡ ለሊሃ። (ሰቈ፫፡ ፮። ኤፌ፪፡ ፩። ፍ፡ ነ፡ ፳፪። ያዕ፪፡ ፲፯)።

**ሙቶት**፤ መሞት፡ አሟሟት። ይሬእዩ፡ ሙ ተተ፡ ጻድቅ። ወሙተትሂ፡ ምኑን። በእንተ፡ ሙተቱ፡ ለብልጣሶር፡ (ጥበ፬፡ ፲፮። ፭፡ ፬። ዮሴፍ)።

**ሞት**፤ በቁሙ፤ የሥጋዊና፡ የደማዊ፡ ሕይ ወት፡ ፍጻሜ፤ በአዳም፡ ኀጢአት፡ የመጣ፡ ጠባይዓዊ፡ ዕዳ፤ ባሕርያዊ፡ ፍዳ። (ግጥም)፤ ከጕዝምና፡ ከዳሞት፡ ማግን፡ ይበልጣለ፡ በስፋት፤ ተጨት፡ አየነው፡ ለየነው፡ ታላቁ፡ ዳሞት፡ ነው። መኑ፡ ሰብእ፡ ዘየሐዩ፡ ወኢይ ሬእዮ፡ ለሞት። ወሞተ፡ መብዝኅቶሙኒ፡ እስመ፡ ይከውን፡ በፍናው፡ ብዙኃት። ሞተ፡ ግብት። ሞት፡ ጠባይዓዊ፤ ሞተ፡ ፈቃድ። እግዚአብሔርሰ፡ ኢገ ብረ፡ ሞተ፡ ወኢይሔድም፡ ሀጕሎሙ፡ ለሕያዋን። ኮ ነኖሙ፡ ሞት፡ እምአዳም፡ እስከ፡ ሙሴ፡ ለእለሂ፡ ኢአበሱ፡ ከመ፡ አበሳሁ፡ ለአዳም፡ (መዝ፡ ፹፰። ፊ ልክ። ፍ፡ ነ፡ ፶። ፊላስ። ጥበ፩፡ ፲፫። ሮሜ፭፡ ፲፬)።

**ማውታ**፤ ሙት፡ በክት፡ ሳያርዱት፡ ታሞ፡ ወይም፡ ገደል፡ ገብቶ፡ የሞተ፡ የከብት፡ ሬሳ። ማውታ፡ ወደም፡ ወብትክ። ዘረከሰ፡ በበሊዐ፡ ማውታ። ጽ ዩእ፡ ሥጋ፡ ማውታ፡ (ቀሌ። ፈ፡ መ፡ ፮፡ ፱። ዲድ፡ ፮)። ለሰው፡ ሬሳም፡ ይኾናል። ዕጓለ፡ ማውታ፤ የሙት፡ ልጅ። በደከታም፡ ፈንታ፡ ዕጓለ፡ ማውታ፡ ይላል፤ የትርጓሜ፡ ቃል፡ ነው። አብ፡ ለዕጓለ፡ ማውታ። ኢየኀ ግኒ፡ አቡየ፡ ዕጓለ፡ ማውታ። ኢየኀድገክሙ፡ ዕጓለ፡ ማውታ፡ ትኩኑ፡ (መዝ፡ ፷፯። ጦቢ፩፡ ፰። ዮሐ፲፬፡ ፲፰)። ማውታ፡ ደካማ፡ ኰሳሳ፡ በቅመ፡ ቢስ፡ (ዐማርኛ)።

**ማውትና**፤ ሙትነት፡ በክትነት፤ ደካምነት። በእንተ፡ ዕጓለ፡ ማውትናሆሙ፡ ወድክትምናሆሙ፡ (ዮሴፍ)።

**ምሞት**፤ ምምዋት፤ መሞቻ፡ ቦታ። ምሚተቲሁ፡ ለያዘ፡ (፬ነገ፡ ፮፡ ፳)።

**አሞተ**፤ ገደለ፡ አጠፋ፡ ለየ። አሙትኒ፡ ወኢታሙቶ። ለአሙቶቱ፡ ወለቀቲሎቱ። አሙትዋ፡ ለነ ፍስክሙ፡ እምሕሉ፡ ምግባረ፡ እኩይ፡ (ዮሴፍ። ክፋ፡ ፴፫። ቀሌ)።

**መዝበር**፤—ፍራሽ፤—ዘቢር፡ ዘበረ።

**መዘገ**፤ (ዐረ፡ መዘጀ፤ አጋፀ። ዕብ፡ ማዘግ፤ ቀዳ፡ ቀላቀለ)፤ አስቀና፤ አፈነከረ። በማ ሕዘ፡ ዚአክሙ፡ ምዝጉ፡ ሕልክሙ፡ (፬ቆሮ፡ ፱፡ ፱)።

—፤ ነጠቀ ፡ መንጠቅ ፡ ነቀለ ፡ ሳበ ፡ ቡንይል ፡ ወሰደ ። ጸሎቱ ፤ ብሔልያስ ፡ ሰማየ ፡ መዘገ ። ረድኤትከ ፡ ወ ለተ ፡ ክሰባት ፡ መዘገ ፡ (ድጓ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፪) ። መሠ ጠንና ፡ መጠቀን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**መዝጎል ፤—ዘጎልማ ፤—ዘጎል ፡ ዘ ጎለ ።**

**መዝገን ፤ ምዝጋና ፤—ዘጊን ፡ ዘገነ ።**

**መዚግዝ ፤ ዘት ፤ (መዘ ፤ መዘዘ ፡ ይመ ዝዝ ፡ ይምዝዝ) ፤** መምዘዝ ፡ መንቀል ፡ መንጠቅ ፤ የሰይፍ ፡ የዱላ ፤ ለሥርም ፡ ይኸናል ፤ መልጎን ፡ እይ ፤ ከ ዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። መዝመዘም ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**መዘዝ ፤** ክፉ ፡ ነገር ፡ ያንደበት ፡ መርዝ ፡ ሰይ ፍና ፡ ዱላ ፡ የሚያማዝዝ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ምዙዛት ፤ (ዕብራ) ፤** ፈማዛት ፤ የማራና ፡ የ ቀኝ ፡ መቃኖች ። አንዲቱን ፡ ምዙዛ ፡ ይላታል ፤ ኹሉም ፡ የቤት ፡ እንቀጽ ፡ ነው ፡ (ሕዝ፡ማ፳ ፡ ፳፩) ።

**መዝሐ ፤ (ዐረ ፡ መዘሐ) ፤** ተላፋ ፡ ተዳራ ፤ ተቃበጠ ፡ ተቀማጠለ ። መሐዘንና ፡ ሐንቀቀን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመዝሐ ፡ ፈ ንታ ፡ አስተማዝሐ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። **እምከመ ፡ አስ ተማዛሕከ ፡ ለወልድከ ፡ (ሢራ፴ ፡ ፱) ።**

**ምዙሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ዝሕት) ፤** ድል ድል ፡ ቅምጥል ፡ ቀለሌ ፡ ቀበጥ ፤ ቅብጥብጥ ። **ከረየ ፡ ጽጋብ ፡ ለምዙሕ ፡** (ዘዳ፴፪ ፡ ፲፭) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በምዙሕ ፡ ፈንታ ፡ ምንዙሕ ፡ ይላል ፤ ባለቅኒዎችም ፡ መንዝሐ ፡ ብለው ፡ ይገሳሉ ፡ ነገዘና ፡ መዝሐ ፡ ተዛንቆ ንፈ ፡ ከነገዘ ፡ መስም ፡ ከምንዛህ ፡ መጥቷል ።

**መዛሕም ፤ (ዐረ ፡ መዛሒም) ፤** ጽፉቅ ፡ ጽፍቀት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የሰውን ፡ ብዛት ፡ የቦታን ፡ ጥበት ፡ መላፋትንና ፡ መፋቱግንም ፡ ያሳያል ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፱) ።

**ምዝላል ፤—መሎጊያ ፤—ዘሊል ፡ ዘለ ።**

**መዝመዘ ፤ (መዚግዝ ፡ መዘ ። ዕብ ፡ ማዝ ሚዝ) ፤** መዘመዝ ፡ ዐሸ ፡ አሰፋ ፡ አለሰለሰ ፡ ዐደፈ ፡ ወለ ወለ ፡ (ዮሐ፲፭ ፡ ፪ ። ፲፪ ፡ ፫ ። ፲፫ ፡ ፳) ። **ይመዘምዝ ዝዎሙ ፡ እምጺበለ ፡ ቤት ። መዝመዙ ፡ ሥጋሆሙ ፡ በአጽርቅት ፡** (ተረ ፡ ኤር፲፪ ። ስንክ ፡ ኅዳ፭ ። ታኅ፲፪) ።

**ተመዝመዘ ፤** ተመዘመዘ ፡ ታሸ ፡ ተወለወለ ። **በከመ ፡ ይትመዘመዝ ፡ ጻሕል ። አለ ፡ ተመዝመዙ ፡ በዐጌ ፡** (፬ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፲፫ ። ኪዳ ። አርጋ) ።

**ምዝሙዝ ፤** የተመዘመዘ ፡ ምዝምዝ ፡ የታሸ ፡ የተወለወለ ፡ ጥሩ ፡ ደረቅ ።

**መዝሙር ፤—ምስጋና ፡ በገና ፤—ዘ ምሮ ፡ ዘመረ ።**

**መዝኖ ፤ ኖት ፤ (መዘነ ፡ ይሚዝን ፡ ይመ ዝን ። ዐረ ፡ ወዘነ ። ዕብ ፡ አዜን) ፤** መመዘን ፡ መ ለካት ፡ ነገርን ፡ መሞከር ፡ በሚዛን ፡ ዕውቀት ፡ ማነጻ ጸር ፡ ደለወን ፡ እይ ። መዝኖት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫) ።

**ተመዝነ ፤** በቁሙ ፤ ተለካ ፡ ከሚዛን ፡ ገባ ። **ዘ ይሰፈር ፡ ወዘይትሜዘን ፡** (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፰) ።

**ምዙን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ዝንት) ፤** የተመዘነ ፡ የተለካ ፡ ምዝን ፡ ምእዙን ። እዝንና ፡ ማእዘንን ፡ በእ ዘን ፡ ተራ ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ሚዛን ፤ (ዐረ ፡ አልሚዛን) ፤** በቁሙ ፤ መ ድሎት ፡ መመዘኛ ፡ ልክ ። **ዘይሰርቅ ፡ በሚዛን ። አለ ፡ ይዔምፁ ፡ በሚዛን ፡** (ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ። ፳፯ ፡ ፫ ። መቃ ፡ ፲፲) ።



ሚዛን ፤

—፤ የኮከብ ፡ ስም ፡ መልኩ ፡ ሚዛን ፡ የሚመስል ፡ የመ ስከረም ፡ ኮከብ ። ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ ፴ ፡ ዕለት ፡ ፲ ፡ ኬክ ሮስ ፡ ይመግባል ፡ (አቡሻ ፡ ፱) ። ሚዛን ፡ ያሰኘው ፡ መልኩ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ግብሩም ፡ ተጨምሯል ፤ በርሱ ፡ ምግ ብና ፡ ውስጥ ፡ በመስከረም ፡ ባ፲፭ኛ ፡ ቀን ፡ መዓልትና ፡ ሌሊት ፡ ይተካከላሉ ።

**መዘረ ፤ (መዚር ፤ ሜስ ፤ ዐጸረ) ፤** ጠመቀ ፡ ዘለለ ፡ ዐሸ ፡ አማሰለ ፤ በጠበጠ ፡ ጣለ ፤ የድፍድፍ ፡ የማር ። መጸረን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ፤ መዘረ ፡ የጅ ፡ የመዳፍ ፡ መጸረ ፡ ያፍ ።

**መዛሪ ፤ (ሬት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ዘርት) ፤** የጠ መቀ ፤ የሚጠምቅ ፤ ጠማቂ ፤ ጠላ ፡ ቤት ፤ ጠጅ ፡ ቤት ፤ መሻት ፡ መሻቶኛ ፡ ቀጅ ፡ ጂ ፤ አሳላፊ ። **መዛርያን ፡ ወ መዛርያት ። ሊቀ ፡ መዘርት ፡** (መክ፪ ፡ ፰ ። ክፋ ፡ ፴፱) ።

**ምዝር ፤ (ዐረ ፡ ሚዝር ፡ መዘር) ፤** ዝልል ፡ ጥሩ ፡ ጠላ ፡ ከእኽል ፡ ከጌሾ ፡ የሚሠራ ፡ ዐረቂ ፡ ጠጅ ፡ የማያሰክር ፡ መጠጥ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**መዝራዕት ፤—ክንድ ፡ ጡንቻ ፤—ዘ ሪዕ ፡ ዘርዐ ።**

**ማዙሮት ፤ (ጽር ። ዕብ ፡ ማዛሎት) ፤** መ ናዝል ፡ ከዋክብት ፡ መገብት ፡ አውራኅ ፤ የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ በየወሩ ፡ የሚያመልኳቸው ፤ ዛሬም ፡ ጠንቋዮች ፡ ለየሰዉ ፡ የሚያድሉቸው ፡ ነዘለን ፡ እይ ፡ (፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፭) ።

**መዝሮስጢ ፤ (ጽር ፡ ሜጊስቲ) ፤** የልዕልና ፡ የክብሬታ ፡ ስም ፤ ልዑል ፡ ዐቢይ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ቢቶደድ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ (አቡሻ ፡ ፰) ። ያሜጋ ፡ እንዲል ፡ ታ ላቅ ፡ ያ ፡ ሲል ።

**ምሕወ ፤—ሻሻ ፡ ቀለጠ ፤—ምህወ ።**

**መሐወ ፤ (ዕብ ፡ መሐህ ። ዐረ ፡ መሓ) ፤** አጠፋ ፡ ደመሰሰ ፡ በውሃ ፡ በምራቅ ፡ የርስሐት ፡ የጥፋት ።

ምህውና ፡ መሐው ፡ መስወ ፡ እንዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ፩ ፡ ዘር ፡ ናቸው ።

**መሐወ** ፤ ነቀለ ፡ መዘዘ ፡ ከሥሩ ፡ አፈለሰ ፡ ቀጨ ፡ ዐሸ ፡ ደታከልት ፡ የሸት ። እግዚ ፡ ይተክል ፡ ወይምሑ ። መሐወኒ ፡ እንተ ፡ ጽለሂ ። ይየብስ ፡ ዘእንበለ ፡ ይምሐውዎ ። እንዘ ፡ ይምሐዉ ፡ ሠዊተ ። ወመሐዋ ፡ በእዴሁ ፡ (ቀሌ ። ኢዮ ፲፱ ፡ ፲ ። መዝ ፡ ፻፳፰ ። ማቴ ፲፭ ፡ ፳ ። ስንክ) ።

**መሓዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ሐውት) ፤ የሚያጠፋ ፡ ነቃይ ፡ አጥፊ ።

**ተምሕወ** ፤ ጠፋ ፡ ተደመሰሰ ፡ ተነቀለ ። ወይትመሐዉ ፡ ምግባራቲክሙ ። ሥርወ ፡ ጻድቃን ፡ ኢይትመሐው ። ማዕር ፡ ዘተምሕወ ። ይቀድም ፡ ተምሒዎ ፡ እምነ ፡ ሽሉ ፡ ማዕር ፡ (ሕዝ፳ ፡ ፯ ። ምሳ ፲፪ ፡ ፫ ። ሄርማ ፡ ገ፲፱ ። ሚራ ፡ ፲፯) ።

**ምሕው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሑት) ፤ የጠፋ ፡ የተነቀለ ፡ ጥፉ ፡ ንቁል ።

**መሐዘ** ፤ (ምሒዝ ፡ ምዕዘ) ፤ ጐለመሰ ፡ ጐበዘ ፡ አደገ ፡ ሚዝት ፡ ፈለገ ፡ ወሸመ ፡ ውሽማ ፡ ያዘ ። ማዜ ፡ ሚዝ(ስ)ት ፡ ሚያገዞ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**መሓዝ** ፤ (ዛን ፡ ዛት) ፤ ደጐብ ፡ ጐልማሳ ፡ ጐበዝ ፤ ውሽማ ፡ የሰው ፡ ሴት ፡ የሚሰርቅ ፡ የሚያማግጥ ። ሲቃናትኒ ፡ ወመሓዛት ። ተንሥኡ ፡ መሓዛት ። ወመሓዝሰ ፡ በንዴተ ፡ አእምሮ ፡ ህጉለ ፡ ነፍሱ ፡ ይገብር ። ብእሲት ፡ እንተ ፡ ተንድግ ፡ ምታ ፡ ወትወልድ ፡ ወራሴ ፡ እምዲበ ፡ መሓዚ ። መሓዛንኪ ፡ እለ ፡ ይሰክቡ ፡ ምስሌኪ ፡ (መዝ ፡ ፸፰ ። ማሕ፫ ፡ ፯ ። ምሳ፯ ፡ ፴፪ ። ሚራ፳፫ ፡ ፳፪ ። ኢሳ፶፯ ፡ ፰) ።

**መሓዝ** ፤ ጐልማስነት ፡ ልጅነት ፤ ዐፍላ ፡ ጉብዝና ፡ ቀውንዥና ። ተሐራሚት ፡ እምወይኑ ፡ መሓዚ ፡ ወእምእክሉ ፡ ውርዙት ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳፱) ።

**ተማሐዘ** ፤ (ይትማሐዝ) ፤ ተጐላመሰ ፤ ተዳራ ፡ ተቃበጠ ፡ ተዋዛ ፡ ተማወተ ። ይትማሐዛ ፡ መራዕዊክሙ ፡ (ሆሴ፬ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬) ። ኢትትማሐዝ ፡ ምስለ ፡ ብእሲት ። ኢትትማሐዝ ፡ ምስለ ፡ መኳንንት ። ዘይትማሐዝ ፡ ምስለ ፡ ጸላእቱ ፡ ይፈቅድ ፡ ከሚተ ፡ ኀጢአቱ ፡ እስመ ፡ ተማሕዞሰ ፡ መራኁት ፡ ተጻልእ ፡ ለጸላእቱ ፡ (ፈላስ ፡ ገ፶፰ ። ፳፫ ። ፳) ። ቀዛ ፡ ለቁም ፡ ነገር ፡ ብላቴን ፡ ጌታው ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ማሕየብ** ፤—መቅጃ ፤—ሐየብ ፡ ሔበ ።

**መሐከ** ፤—ራራ ፡ ዐዘነ ፤—ምሂክ ፡ መሀከ ።

**መሐለ** ፤ (ብሂል ፡ ብህለ ። ዐረ ፡ በሀለ) ፤ ማለ ፡ ተረገመ ፤ ተፈጠመ ፡ ነገርን ፡ ለማጽደቅ ፡ ለማጽናት ። ኢትምሐሉ ፡ ግሙራ ። እለ ፡ ይምሕሉ ፡ በጽድቅ ፡ እው ፡ በሐሰት ። መሐልኩ ፡ በርእስየ ። ዘብዙኅ ፡ ይምሕል ፡ (ማቴ፭ ፡ ፴፬ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፱ ። ኤር ፳፪ ፡ ፭ ። ሚራ፳፫ ፡ ፲፬) ። ተሳለ ፡ ብፅዐት ፡ ገባ ፤ ውል ፡ አደረገ ። ብፅዐንና ፡ ኪዳን ፡ ብሀለን ፡ ተመልከት ።

**መሓሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤ የማለ ፤ የሚምል ፡ ማይ ፡ ማለኛ ። ብእሲ ፡ መሓሊ ። ለእመ ፡ አእመረ ፡ መሓሊ ። ሐሳዊ ፡ ወመሓሊ ፡ በሐሰት ፡ (ሚራ፳፫ ፡ ፲፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፳ ። ቀሌ) ።

**መሐላ** ፤ በቁሙ ፡ ማላ ፡ ፍጥም ፤ የውል ፡ ነገር ፡ ማጽደቂያ ፤ በፈጣሪ ፡ ወይም ፡ በፍጡር ፡ ስም ፡ በሚወዱትና ፡ በሚያከብሩት ፡ ነገር ፡ የሚደረግ ። መሐላ ፡ በሐሰት ። መሐላ ፡ ጽድቅ ። ከመ ፡ አቅም ፡ መሐላየ ፡ (ቀሌ ። ኩፋ ፡ ፴፰ ። ኤር፲፩ ፡ ፭) ።

—፤ ስለት ፡ ብፅዐት ፤ ወይም ፡ የስለትና ፡ የብፅዐት ፡ ቃል ፡ ውል ፡ ኪዳን ። በመሐላሆሙ ፡ ለማርያም ፡ ወለወልዳ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፱) ።

**አምሐለ** ፤ አማለ ፡ አስማለ ፡ አማጠነ ። አምሐሎ ፡ በደመ ፡ አቤል ፡ ከመ ። አምሐልኩሙ ፡ በእንተ ፡ አዕፃምቲሁ ። አምሐለከ ፡ በእግዚ ፡ ከመ ፡ ኢትማቅየኒ ። ይክውን ፡ ጌጋዩ ፡ ላዕለ ፡ ዘአምሐሎ ፡ (ቀሌ ። ኩፋ ፡ ፵፯ ። ማር፭ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫) ።

**ተምሕለ** ፤ ተማለ ፤ ተማለበት ።

**ተማሐለ** ፤ ተማማለ ፤ ተፈጣጠመ ፤ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተጋባ ። ተማሐልኒ ፡ ክልኤነ ። ተማሐልነ ፡ ምስለ ፡ ሲኦል ። ዐደው ፡ እለ ፡ ተማሐልክ ፡ (፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፵፪ ። ኢሳ፳፰ ፡ ፲፭ ። ዓብድ ፡ ፯) ።

**ተማሕለለ** ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ ተማለለ ፤ ለመነ ፡ ማለደ ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ አለ ፡ መሐላና ፡ ኪዳን ፡ በማላሰብ ። ይትማሐለል ፡ አሮን ፡ በዲበ ፡ አቅርንቲሁ ። እንዘ ፡ ይትማሐለል ፡ ቅድመ ፡ እግዚ ፡ በእንተ ፡ አበሳ ። ወሰገደ ፡ ሎቱ ፡ እንዘ ፡ ይትማሐለል ። ኀበ ፡ መኑ ፡ እትማሐለል ፡ (ዘፀ፴ ፡ ፲ ። ኩፋ ፡ ፵፰ ። ማቴ፲፰ ፡ ፲፱ ። አርጋ) ።

**ምሕላ** ፤ ምሕላል ፤ በቁሙ ፡ ልመና ፡ ምልጃ ፤ የማኅበር ፡ የሕዝብ ፡ ጸሎት ፡ እግዚኦታ ። እመኒ ፡ አብዛኅክሙ ፡ ምሕላክሙ ። ቀድሱ ፡ ጾመ ፡ ወሰብኩ ፡ ምሕላ ። በሽሉ ፡ ምሕላ ፡ ወበዙሉ ፡ ጸሎት ። ተወከፍ ፡ ምሕላነ ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፲፭ ። ዮኤ፩ ፡ ፲፬ ። ፫ነገ ፡ ፰ ፡ ፴፰ ። ድጓ) ። መሐለ ፡ ከብህለ ፡ የወጣ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ተማህለለ ፡ ምህላ ፡ እያለ ፡ በሀ ፡ ሀ ፡ ይጥፋል ፤ ገንዘቡ ፡ አይደለም ።


**ማሕሌት** ፤—በቁሙ ፡ ምስጋና ፤—ሐለይ ፡ ሐለየ ።

**ምሒን** ፤ ኖት ፡ (መሐነ ፡ ይምሕን ፡ ይምሐን ። ዐረ ፡ መሐነ) ፤ መፈገፈግ ፡ ማሸት ፡ ማልፋት ፤ ማለስለስ ፤ የቁርበት ፤ ለልብስና ፡ ለፈትልም ፡ ይኾናል ። መስጠት ፡ ማስረከብ ፡ እንዠ ፡ ማለት ።

**መሓን** ፤ ማሻ ፡ ማልፊያ ፤ ወይም ፡ አልፊ ፡ ዐሻታ ፡ ዐፊቢ ። ማእሰ ፡ በግዕ ፡ ሕሡይ ፡ ግቡረ ፡ መሓን ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፭ ፡ ፳፫) ።

**ምሕን** ፤ በቁሙ ፡ መነ ፡ የሸማ ፡ መሥሪያ ፡ ርስ ፡ በርስ ፡ የሚፋተግ ፡ የሚፈገፈግ ። እንመሥ ፡ እይ ።

ወምሕኑሂ ፡ ዘእምኀበ ፡ ጽላሎተ ፡ እግዚ ፤ (ቅዳ ፡ ሕር ። ተረ ፡ ቁር) ።



ምሕን ፡

**መሐና ፤ (ዕብ ፡ ሚንሓህ) ፤** እጅ ፡ መንሻ ፤ በረከት ፤ የፍቅር ፡ ስጦታ ። ንሣእ ፡ መሐና ። ወአብእ ፡ ሎቱ ፡ መሐና ፡ (፩ነገ ፡ ፴ ፡ ፴ ። ፲፯ ፡ ፫ ፡ ፩ ። ፳ ፡ ፲፱) ።

**ማሕፈድ ፤—ማንብ ፤—ኅፈድ ፡ ኀፈደ ።**

**ማሕፈር ፤—ወዳጅ ፤—ኀፈር ፡ ኀፍረ ።**

**መሐጸ ፤ (ምሒጽ ። ዐረ ፡ መሐጸ ። ዕብ ፡ ማሐጽ) ፤** መታ ፤ ፈለጠ ፡ ቈረጠ ፤ ሰበረ ፡ አደቀቀ ፤ ገደለ ፡ አጠፋ ። የይፋት ፡ እስላም ፡ መታ ፡ አስመታ ፡ ሲል ፡ ማጠ ፡ አስማጠ ፡ ይላል ። ፪ኛም ፡ ማኢዞ ፡ አሐርጸሙ ፡ ከመ ፡ ጸበል ፡ ባለው ፡ ዕብራይስጡ ፡ ኢምሐጹም ፡ ከዓፋር ፡ እንዲል ፡ (መዝ ፲፯) ። ከመ ፡ ይምሐጸሙ ፡ በሰይፍ ። መሐጸሙ ፡ ወቀተሎሙ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫ ፡ ፺፰) ።

**መሓጺ ፤ (ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት) ፤** የሚመታ ፡ ተማች ፤ ፈላጭ ፡ ቈራጭ ፤ ገዳይ ፡ አጥፊ ። ለሆሎፎርኒስ ፡ ግብተ ፡ በሰይፈ ፡ ዮዲት ፡ መሓጺሁ ፡ (ደራሲ) ።

**ማሕጼ ፤** ማጫ ፡ ምሣር ፡ መቍረጫ ፡ መፍለጫ ፤ መምቻ ፡ መከትከቻ ፡ (መዝ ፡ ፸፫ ፡ ፮ ። ማቴ ፡ ፫ ። ፬ነገ ፡ ፮ ፡ ፭ ፡ ፮) ።



ማሕጼ ፡

**ተምሕጸ ፤** ተመታ ፡ ተቈረጠ ፤ ሞተ ፡ ጠፋ ።

**ምሑጽ ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ሑጸት) ፤** የተመታ ፡ የተቈረጠ ፤ የሞተ ፡ የጠፋ ። ወትከውን ፡ ምሑጸ ፡ በምርሖየ ፡ እዕይንቲከ ፡ (ዘዳግ ፡ ፳፱) ። ዕብራይስጡ ፡ ማን ፡ ምሹጋስ ፡ ይላል ፤ እብድ ፡ እንቡዝ ፡ ቅብዝብዝ ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለብሉዮችም ፡ ዐይንን ፡ ተከትለው ፤ ዕውር ፡ ጨምጫማ ፡ ይሉታል ፤ ፪ኛም ፡ ምሕጸ ፡ ሸሸ ፡ ብለው ፡ ምሑጽ ፡ የሸሸ ፡ ይላሉ ። ዘይቤው ፡ አይደለም ። ፫ኛም ፡ በምሑጽ ፡ ፈንታ ፡ ምሑስ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ከመ ፡ እይሁድ ፡ ምሑሳን ፡ (ሲኖ) ።

**ምሕጸት ፤** መምታት ፡ መቍረጥ ፤ መመታት ፡ መቈረጥ ፤ ሞት ፡ ጥፋት ። ኢመጽእሙ ፡ መቅሠፍት ፡ ለቀቲል ፡ ወለምሕጸት ፡ (ኩፋ ፡ ፺፱) ።

**ምሕጸ ፤ መሐጸ ፤—አማጠ ፡ ተጨነቀ ፤—ምኅዕ ፡ መኀፀ ።**

**ማሕጸን ፤—በቁሙ ፡ ማጠን ፤—ሐፂን ፡ ሐፀነ ።**

**መሐረ ፤—አስተማረ ፤—ምሂር ፡ መሀረ ።**

**ምሒር ፤ ሮት ፤ (ምሕረ ፤ መሐረ ፡ ይምሕር ፡ ይምሐር ። ዕብ ፡ ማሐል ፤ ራሐም ። ሱር ፡ ርሔም ። ዐረ ፡ ረሒመ) ፤** መማር ፡ ይቅር ፡ ማለት ፤ ዕዳን ፡ በደልን ፡ መተው ። ለዘሂ ፡ መሐርከዎ ፡ እምሕሮ ። መፍትው ፡ አንትሂ ፡ ትምሐር ፡ ቢጸከ ፡ በከመ ፡ አነ ፡ መሐርኩከ ። አሐዱ ፡ ዘመሐሮ ፡ መንፈቀ ፡ ዕዳሁ ፡ (ሮሜ ፱ ፡ ፲፭ ። ማቴ ፲፰ ፡ ፴፫ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭) ።

—፤ መውደድ ፡ ማፍቀር ፤ ከፍቅር ፡ የተነሣ ፡ ማዘን ፡ መራራት ፤ መስጠት ፡ መመጽወት ። በከመ ፡ ይምሕር ፡ አብ ፡ ውሉዶ ፡ ከማሁ ፡ ይምሕሮሙ ፡ እግዚ ፡ ለእለ ፡ ይፈርህዎ ። ሰበ ፡ መጽወትኒ ፡ ወመሐርኒ ። ርእዮ ፡ ወምሕሮ ። ደቂቅ ፡ ዘምሕሮ ፡ እግዚ ፡ ለገብርከ ። በምሒረ ፡ ነዳይ ፡ (መዝ ፡ ፻፪ ። አፈ ፡ ተ ፴፩ ። ሉቃ ፲ ፡ ፴፫ ። ዘፍ ፴፫ ፡ ፭ ። ዳን ፬ ፡ ፳፬) ። በምሕረ ፡ ፈንታ ፡ አስተምሐረ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ነጽር ፡ ላዕሌየ ፡ ወአስተምሕረኒ ። አስተምሕር ፡ ሕማሞሙ ፡ ለዘመድነ ፡ (ጦቢ ፫ ፡ ፲፭ ። ዮዲ ፰ ፡ ፲፱) ።

**መሓሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤** በቁሙ ፤ የሚምር ፡ ማሪ ፤ ይቅር ፡ ባይ ፡ ዐዛኝ ፡ ርኅሩኅ ፤ ሰጭ ፡ መጸች ፤ ለጋስ ፡ ሰው ፡ ወዳጅ ። መሓሪ ፡ ብዙኃን ፡ እምዕዳ ። መሓሪ ፡ ለዐጓለ ፡ መሕየው ። ዐይንከ ፡ መሓሪት ። ወኩኑ ፡ መሓርያነ ፡ ቢጽክሙ ። አንስት ፡ መሓርያት ፡ (ሲንክ ፡ ጥቅ ፱ ። ጎዳ ፲፱ ። አርጋ ። ኢሳ ፱ ፡ ፩፲ ። ሰቈ ፬ ፡ ፲) ። መሐርና ፡ መዓር ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ። (ግጥም ፤ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ በተያዙ ፡ ጊዜ ፡ ታስረው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎቻቸው ፡ አንዱ) ፤ ጠጅም ፡ አልቀመስን ፡ ከተለየናችኹ ፤ አውራው ፡ ከተያዘ ፡ ማሩን ፡ እባካችኹ ።

**አምሐረ ፤** አስማረ ፤ ይቅር ፡ አሰኘ ። አራራ ፡ አሳዘነ ። ያምሕሩኒ ፡ እሉ ፡ አሕዛብ ። ወአምሐርዎ ፡ ለኢየሱስ ፡ (ማቴ ፲፭ ፡ ፴፪ ። ፳ ፡ ፴፬ ። ማር ፰ ፡ ፪) ።

**ተምሕረ ፤** ተማረ ፡ ይቅር ፡ ተባለ ፤ ይቅርታ ፡ አገኘ ። ዘይምሕር ፡ ይትመሐር ። ብፁዓን ፡ መሓርያን ፤ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይትመሐሩ ፡ (ምሳ ፲፯ ፡ ፭ ። ማቴ ፭ ፡ ፯) ።

**ምሑር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ሕርት) ፤** የተማረ ፤ ይቅር ፡ የተባለ ። ኢኮንክሙ ፡ ምሑራነ ፡ (፩ጴጥ ፪ ፡ ፲) ።

**ምሕረት ፤ (ታት) ፤** በቁሙ ፤ ይቅር ፡ ማለት ፡ መባል ። ይቅርታ ፡ ቸርነት ፤ ርኅራኄ ፡ ፍቅር ፡ ምጽዋት ። እለ ፡ ትፈርህዎ ፡ ለእግዚ ፡ ጽንሕዋ ፡ ለምሕረቱ ፤ እስመ ፡ በከመ ፡ ዕበዩ ፡ ከማሁ ፡ ዕበየ ፡ ምሕረቱ ። አበ ፡ ምሕረታት ። የዐጼ ፡ ምሕረት ። እለ ፡ አልቦሙ ፡ ምሕረት ። ምሕረት ፡ ነዳያን ፡ (ሢራ ፪ ፡ ፯ ፡ ፲፰ ። ኪዳ ። ፪ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱) ።

—፤ ልብ ፡ ሆድ ፡ አንጀት ፡ የርኅራኄ ፡ ምንጭ ። ተፈሥሐ ፡ ምሕረቱ ፡ ወልቡ ፡ ላዕሌሁ ። ምሕረትየ ፡ ይ

ባርከከ ። አሕዘኑ ፡ ምሕረቶ ፡ አቡሆሙ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱ ። ፳፰ ። ፴፬) ።

**ምሕረት ፤ (ዕብ ፡ ሬሔም ፤ ራሓም) ፤** ማሕፀን ፤ አፊ ፡ ማሕፀን ፤ የፅንስ ፡ የሽል ፡ ቦታ ። ምስጢሩ ፡ ከሆድ ፡ ይገባል ። ኅቡረ ፡ ተዘራዕነ ፡ በውስተ ፡ ከርሥኪ ፡ ወኅቡረ ፡ ወፃእነ ፡ እምሕረትኪ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፰) ።

**አስተምሐረ ፤** ለመነ ፡ ማለደ ፤ አማለደ ፡ አስማረ ፤ ማረኝ ፡ ማርልኝ ፡ አለ ። አስተምሕር ፡ ለነ ፡ ሚካኤል ። ሰአሉ ፡ ለነ ፡ አስተምሕሩ ፡ ለነ ፡ (መሥዋ ። ድጓ) ።

**አስተማሐረ ፤** አማማረ ፡ አሳመነ ፤ አመሳለደ ፡ አስተዛዘነ ። ተፋቅሮ ፡ ያስተማሕር ፡ (ፊቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፱) ።

**መስተምሕር ፤ ማሕር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤** የሚያስምር ፡ የሚያማልድ ፡ አማላጅ ፤ አስተዛዛኝ ። እ ፡ መስተምሕርት ፡ አስተምሕሪ ፡ ኀበ ፡ ወልድኪ ፡ (ቅዳ) ።

**ማሕረከ ፤—ማረከ ፤—ምሂር ፡ መሀረ ፡ ማህረከ ።**

**መሐረም ፤—ያረቦች ፡ መገመሪያ ፡ ወር ፤—ሐረመ ።**

**መሐስዕ ፤—ጠቦት ፤—ሐሲዕ ፡ ሐስዐ ።**

**ማኅደፍ ፤—ማደፊያ ፡ መወልወያ ፤—ኀድፎ ፡ ኀደፈ ።**

**ማኅፈድ ፤—ግንብ ፤—ኀፊድ ፡ ኀፈደ ።**

**ማኅፈር ፤—እሙን ፡ ወዳጅ ፤—ኀፊር ፡ ኀፍረ ።**

**ምኒዕ ፤ ዖት ፤ (መንፀ ፡ ይምኅዕ ፤ ይምኀፅ ። ዐረ ፡ መኒፀ) ፤** ማማጥ ፡ መጨነቅ ፤ በምጥ ፡ መያዝ ፤ ስመውለድ ፤ የሆድን ፡ ለማውጣት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በምኅፀ ፡ ፈንታ ፡ እንዳማርኛው ፡ እምኀፀ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ፲፪ዜ ፡ ታምኅፅ ፡ ትኬልሕ ፡ (አዋል) ።

**ምኅዕ ፤** ምጥ ፡ ጭንቅ ፤ እሕታ ። ሐመመን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። (ተረት) ፤ ምጡን ፡ ርሺው ፤ ልጁን ፡ አንሺው ። የልጅ ፡ ደፋር ፡ ምጥ ፡ ለናቷ ፡ ታስተምር ።

**እምኅፀ ፤** አስማጠ ፡ አስጨነቀ ፤ እሕ ፡ አሰኘ ።

**ማኅዕ ፤** ማጥ ፡ ረግረግ ፤ አረንቋ ፡ የሚያሰ(ስ) ምጥ ፡ የሚያስጨንቅ ።

**ማጣ ፤ (ዕብ ፡ ሚጣ) ፤** ዐልጋ ፡ ዙፋን ። እግረ ፡ ማጣ ፡ (ድጓ ። መዋሥ) ።

**መጥበስ ፤—መጥበሻ ፤—ጠቢስ ፡ ጠበሰ ።**

**መጥዎ ፤ ዎት ፤ (መጠወ ፡ ይሜጡ ፡ ይመጡ ። ሰጠወ ፤ ወሀበ ፡ ወከፈ ፡ ወፈየ ። ዐረ ፡ አዕጣ) ፤** መመጥወት ፤ ምጽዋት ፡ መስጠት ፡ ማደል ፤ ማጉረሥ ፡ ማቀበል ፡ ማሳለፍ ፡ ማቅረብ ፤ ማሲያዝ ፡ ማስጨበጥ ፡ ማስረከብ ። ዘመጠወ ፡ ርእሶ ፡ በእንቲአነ ። መጠዎ ፡ ቍርባነ ። ከመ ፡ ይመጥውዎ ፡ ጽዋዐ ። መጥወኒ ፡ እሜጥወከ ፡ (ቲቶ፪ ፡ ፲፬ ። ቀሌ ። ራእ፲፯ ፡ ፲፱ ። አዋል) ።

**መጣዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** የሚሰጥ ፡ የሚያድል ፡ የሚያቀብል ፤ በአፍ ፡ በእጅ ። መጣዊ ፡ አሪት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተመጠወ ፤** ተሰጠ ፤ ተሰጠው ፡ ተቀበለ ፤ ተመጠወተ ፡ ምጽዋተኛ ፡ ኾነ ። ተመጠዋ ፡ እምነ ፡ የማኑ ፤ ወሰበ ፡ ተመጠዋ ። ዘይትሜጦ ፡ ቍርባነ ፡ ምዕረ ፡ በበ ፡ ዓመት ። ተመጠው ፡ እምኃየ ፡ እምእዴየ ፡ (ራእ፷ ፡ ፯ ፡ ፰ ። አፈ ፡ ተ፲፯ ። ዘፍ፴፫ ፡ ፲) ።

**ተመጣዊ ፤** የሚሰጥ ፡ ተሰጭ ። ተቀባይ ፡ ተመጥዋች ። ሙሴ ፡ ተመጣዌ ፡ ኦሪት ። ተመጣዌ ፡ ቍርባን ። ተመጣዌ ፡ ኅብስት ፡ ወማይ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፰ ። ደራሴ) ።

**ምጥው ፤ (ውት ፡ ጡት ፤ ዋን ፡ ዋት) ፤** የተሰጠ ፤ የተሰጠው ፡ ተሰጭ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ተቀባይ ፡ ሰው ። ሰበ ፡ ነጸረ ፡ ርእሶ ፡ ምጥወ ፡ ለሞት ፡ መከራ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፬ ፡ ፩) ።

**ምጣዌ ፤** አሰጣጥ ፤ አቀባበል ፡ ስጦታ ፡ ምጽዋት ።

**መጥለውዝ ፤—መጥረቢያ ፤—ጸለወ ፡ መጽለውዝ ።**

**መጢማ ፤—ጢቆሽ ፤—ጠሚዕ ፡ ጠምዐ ።**

**መጥኖ ፤ ኖት ፤ (መጠነ ፡ ይሜጥን ፡ ይመጥን ። መአደ) ፤** መመጠን ፡ መለካት ፤ መስፈር ፡ መክንዳት ፡ ልክ ፡ ማወቅ ፡ መገመት ፤ ይኸን ፡ ያኽል ፡ ማለት ፤ መወሰን ፡ ማስተካከል ። ዐቀመንና ፡ ወሰነን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንደር ፡ ናቸው ። ይሜጥንዋ ፡ በሐብለ ፡ መስፈርት ። ወመጠነ ፡ ርሕበ ፡ ሕንጻ ፡ አሐደ ፡ ኀለተ ። አሚሃ ፡ ይሜጥን ፡ ድካመ ፡ ዚአሁ ። ይፈቅድ ፡ ይትአመንዎ ፡ ወአከ ፡ ከመ ፡ ይመጥንዎ ፤ ወእስመ ፡ ኢይትከሀሎ ፡ ለኅሊና ፡ ይመጥን ፡ ባሕርየ ፡ ዚአሁ ፡ (ኢሳ፵፬ ፡ ፲፭ ። ሕዝ፵ ፡ ፭ ። ማር ፡ ይሥ፯ ፡ ፮ ። አፈ ፡ ድ፳፱) ።

**መጣኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት) ፤** የሚመጥን ፡ መጣኝ ፤ ሰፋሪ ፡ ልክ ፡ ዐዋቂ ። ወሊኅሊና ፡ መጣንያን ፡ (ያዕ ፡ ዘእል) ።

**መጠን ፤ (ብ ፡ አምጣን ፤ ናት) ፤** በቁሙ ፤ ልክ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፤ ሚዛን ፡ ገመድ ፤ ዐቅም ፡ ማዕርግ ። መጠኑ ፡ ለረድእ ፡ ከመ ፡ ሊቁ ። ለአሳትሰ ፡ ቦቱ ፡ መጠን ። ወዘሎ ፡ ክብር ፡ ኢመጠና ። ክቡራት ፡ መጠን ፡ (ማቴ፲ ፡ ፳፭ ። ቅዳ ። ምሳ፳ ፡ ፲፭ ። ማር ፡ ይሥ፯ ፡ ፱) ። መኑ ፡ ሠርዐ ፡ አምጣኒሃ ። በከመ ፡ አምጣኒሁ ፡ ለዝኩ ። ወእሉ ፡ አምጣናት ፡ ምሥዋዕ ፡ በእመታት ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፭ ። ሕዝ፵ ፡ ፳፱ ። ፵፫ ፡ ፲፫) ። ፈትል ፡ ሐብል ፡

በማለት ፡ ፈንታ ፡ አምጣን ፡ ይላል ፡ ምስጢሩ ፡ እንጂ ፡ ዘይቤው ፡ አይደለም ። ሰሐበ ፡ አምጣነ ፡፡ አምጣን ፡ ዘየዐውዶ ፡ (ሰቈ፱ ፡ ፳ ። ኤር፵፱ ፡ ፳፩) ።

**መጠን ፤ አምጣን ፤** ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ የ ፡ እንደ ፤ ያኽል ፡ ጊዜ ፡ ዘመን ፡ ሳ ፡ ይኾናል ፤ ጊዜና ፡ ሳ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ነው ። መጠነ ፡ ገብረ ፡ ሳቲ ፡ ለነፍስየ ፡፡ ተእምር ፡ መጠነ ፡ ተልእከኒ ፡፡ መጠኑ ፡ ብኪ ፡ የ ፡ (መዝ ፡ ፳፭) ። ፈሰግየ ፡ ክነኒ ፡ መጠነ ፡ ባሕር ፡፡ ኢትሬኢኑ ፡ መጠነ ፡ ይበልዕ ፡ ወይሰቲ ፡፡ ወአምጣነ ፡ ገፍዐት ፡ ወሣቀየት ፤ ክማሁ ፤ እንደ ፡ (ሚራ፳፱ ፡ ፴፩ ። ዳን፲፫ ፡ ፮ ። ራእ፲፰ ፡ ፯) ። ሚ ፡ መጠን ፡ ኑኃ ፡ ወሚ ፡ መጠን ፡ ርሕባ ፡፡ መጠነ ፡ ጸሐቲ ፡ ሰዓት ፡፡ መጠነ ፡ ዝ ፡ መዋዕል ፤ ያኽል ፡ (ዘካ፪ ፡ ፪ ። ዳን፱ ፡ ፲፮ ። አስቴ፪ ፡ ፲፪) ። አምጣነ ፡ ትበልዕዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ኅብስት ፡፡ አምጣነ ፡ ሐያው ፡ ውእቱ ፡፡ አምጣነሰ ፡ ሕፃን ፡ ውእቱ ፡ ወራሲ ፡፡ አምጣነ ፡ ሀሎ ፡ መርዓዊ ፡ ምስሌሆሙ ፤ ጊዜ ፡ ሳለ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፮ ። ሮሜ፯ ፡ ፩ ። ገላ፬ ፡ ፩ ። ማቴ፱ ፡ ፲፭) ። አምጣን ፡ ለብቻው ፡ ተለይቶ ፡ እንደ ፡ እስመ ፡ ና ፡ ስለ ፡ ይኾናል ። እፈርህ ፡ ሞተ ፤ አምጣነ ፡ ደወይኩ ፤ ታምሚያለኹና ፡ ስለ ። መጠንና ፡ አምጣን ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ ሲኾኑ ፡ ውስጠ ፡ ብዙነት ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ ይገባሉ ፤ ልክና ፡ ሚዛን ፡ ሲኾኑ ፡ ግን ፡ ውስጠ ፡ ብዙነት ፡ አያሳዩም ። አምጣን ፡ የመጠን ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ አምሳል ፡ የምስል ፡ ብዙ ፡ እንደ ፡ ኾነ ። አምጣንና ፡ አምሳል ፡ ሳንድ ፡ መንገሩ ፡ በልማድ ፡ እንጂ ፡ በሰዋስው ፡ ሕግ ፡ አይደለም ፡ (ዕር፲፱ ፡ ቍ፸፪) ።

**ተመጠነ ፤** በቁሙ ፡ ተለካ ፡ ተመዘነ ፤ ከልክ ፡ ገባ ። ዘይትሜጠን ፡ በእመት ፡፡ ክበደ ፡ ብዕሉ ፡ ዘኢይትሜጠን ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፴፫ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ምጡን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ጥንት) ፤** የተመጠነ ፡ የተለካ ፤ ምጥን ፡ ልከኛ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ምጣኔ ፤ (ገቢር ፡ ወተገ) ፤** መመጠን ፡ መለካት ፡ አመጣጠን ፡ አለካክ ፤ ምጠና ፡ ግምገማ ፤ ልክ ፡ መጠን ፤ ስፍር ፡ ቍጥር ፤ የወርድ ፡ የቁመት ፡ የስፋት ። ወእምነ ፡ ምጣኔ ፡ ልቡና ፡፡ አምጽአ ፡ ሥርዐተ ፡ ምጣኔ ፡ እምርሑቅ ፡፡ ሄሮድስ ፡ አስተናደፈ ፡ መሠረታቲሁ ፤ ኑኆ ፡ ወግድሞ ፡ በምጣኔ ፡ ቀደማዊ ፡፡ ይሬእዩ ፡ ዕድሜ ፡ ወርኆሙ ፡ በምጣኔ ፡ ምሕዋረ ፡ ፀሓይ ፡ ውስተ ፡ ጸሐቲ ፡ ኆኅት ፡፡ ውፁእን ፡ እምጣኔ ፡ (ፊልክ ፡ ፯ ። አፈ ፡ ድ፰ ። ዮሴፍ ። አቡሻ ፡ ፲፱ ። አዋል) ።

**መጠንጢን ፤** መጠነኛ ፤ ታናሽ ፡ ልክ ፡ መተንተኛ ፤ ወይም ፡ ጢንጦ ፡ የክፍል ፡ ክፍል ፡ ሢሶ ፡ ርቢት ፡ ዐምሻ ፡ ትሙን ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ (ሄርማ) ።

**መጠቀ ፤ (መጢቅ ። ዐርገ ፡ ለዐለ ፤ ኖኀ) ፤** በቁሙ ፡ ምድር ፡ ለቀቀ ፡ ከምድር ፡ ራቀ ፡ ረዘመ ። ምድር ፡ መልቀቅ ፡ ያሞራ ፡ የወፍ ፡ መርከም ፡ የሕንጻ ፡ የዛፍ ።

**መጠቀ ፤ (መዘገ ፤ መሠጠ) ፤** ነጠቀ ፡ መነጠቀ ፤ ክፍ ፡ አደረገ ፡ አንሣ ፡ ሳበ ፡ ጉተተ ፤ አዳነ ፡ አወጣ ፡ ራቁን ፡ ወይም ፡ ሲሳውን ። ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ከፊተኛው ፡ ይገባል ። ከመ ፡ ኢይረድ ፡ ታሕቲተ ፡ ምጥቀኒ ፡ ላዕለ ፡፡ እምግበ ፡ ሙስና ፡ ምጥቀኒ ፡ (ደራሲ) ። እግዚ ፡ መጠቀኒ ፡፡ ዘይመጥቃ ፡ ወያሌዕላ ፡፡ ይመጥቆ ፡ እምነ ፡ ዝንቱ ፡ መከራ ፡ (ዘፍ፴፬ ፡ ፰ ። ዮና ፡ ፯ ፡ ፳፬ ። ማር ፡ ይሥ፲፪ ፡ ፪) ።

**መጣቂ ፤ መምጠቂ ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት) ፤** የሚነጥቅ ፡ ነጣቂ ።

**አምጠቀ ፤** አመጠቀ ፡ አረዘመ ፤ አስመጠቀ ፡ አስረዘመ ፤ ምጡቅ ፡ ረዥም ፡ አደረገ ፤ ወይም ፡ አስደረገ ። አብድ ፡ ሶበ ፡ የሐንጽ ፡ ቤተ ፡ ያመጥቅ ፡ ሕንጻሁ ፡ እምአግዋሪሁ ፡ ከመ ፡ ይትመካሕ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ (ፊላስ ፡ ገ፺፱) ።

**ተመጥቀ ፤** ተነጠቀ ፡ ተመነጠቀ ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ ተሳበ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ። ዘተመጥቀ ፡ በደመና ፡ ሰማይ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲፱) ።

**ምጡቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ጥቅት) ፤** በቁሙ ፡ የመጠቀ ፡ ከምድር ፡ የራቀ ፤ ከፍተኛ ፡ ረዥም ፤ ሩቅ ፡ ረቂቅ ። እግዚ ፡ ዘዲበ ፡ ልዑል ፡ ወምጡቅ ፡ የኀድር ፡፡ መንበር ፡ ልዑል ፡ ወምጡቅ ፡፡ ሰማይ ፡ ምጡቅ ፤ ደመና ፡ ምጡቅ ፡፡ ምጡቃነ ፡ ስረት ፡ (ቄድር ። ቄር ። አዋል) ።


**ምጥቀት ፤** ምጡቅነት ፡ ርዝማን ፡ ርዝመት ፤ ዘለግታ ፡ ቁመት ።

**ምጥቅ ፤** ርቀት ፤ አራራቅ ፤ ልዕልና ፡ ከፍታ ። ምጥቆሙ ፡ ለአየራት ፡ (አርጋ) ።

**መምጠቅ ፤ (ቅት) ፤** ኩረጅ ፡ ቍናማት ፡ የግልገል ፡ ስልቻ ፤ ወይም ፡ ከንት ፡ ከቈርበት ፡ የሚሠራ ፡ የረኞች ፡ ኩፈዳ ፤ ወንጭፍና ፡ ደንጊያ ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ የሚከቱበት ። ኀረየ ፡ ኀምስተ ፡ አእባነ ፡ እምውስቴ ፡ ፈለግ ፡ ወወደየ ፡ ውስተ ፡ መምጠቂሁ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፵) ።

**መጠቀ ፤—ጣፈጠ ፡ ጥፍጥ ፡ ኾነ ፤—መተቀ ።**

**መጠራ ፤ (ዕብ ፡ ማጣራ) ፤** ማነጣሪያ ፡ ማነጣጠሪያ ፡ የቀስተኛና ፡ የነፍጠኛ ፡ ዐላማ ፡ ወይም ፡ ዒላማ ፡ ፍላጻው ፡ ዐረሩ ፡ ሲነደፍ ፡ ሲተኰስ ፡ የሚያርፍበት ፤ እንደ ፡ ጊጡ ፡ ያለ ፡ በሩቅ ፡ በአንጻር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የቆመ ፡ የተተከለ ። ባለብልዮች ፡ ግን ፡ ሲይተው ፡ ትክሻ ፡ ብራዪ ፡ መጋፊያ ፡ ይሉታል ። እኢሮፍ ፡ አሕጺ ፡ ኀበ ፡ መጠራ ፡ (፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፳ ። ሰቈ፫ ፡ ፲፪ ። ኢዮ፲፮ ፡ ፲፪) ።



መጠራ ፡

**መጠር ፤ (ዐረ ። ዕብ ፡ ማጣር ። ሱር ፡ ምጣር)** ፤ ዝናብ ፡ የውሃ ፡ ሕንብብ ፡ ነጠብጣብ ፤ ከላይ ፡ ከአየር ፡ ከቀስተ ፡ ደመና ፡ የሚነደፍ ፡ የሚወንፈፍ ።

**ሜጥራ ፤ (ጽር ፡ ሚትራ ። ዕብ ፡ ኔዜር)** ፤ የተቀደሰ ፡ አክሊል ፡ ዘውድ ፤ ሦሬውና ፡ ጌጡ ፡ ከነገሥታት ፡ ዘውድ ፡ የተለየ ፡ ቀድሞ ፡ በብሉይ ፡ ሊቃን ፡ ካህናት ፡ ዛሬም ፡ በሐዲስ ፡ ሊቃን ፡ ጳጳሳት ፡ የሚለብሱት ። ኢያሬርን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፴፱ ፡ ፴፰) ። በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ምዕ፲፱ ፡ ቍ፴ና ፡ ፴፮ ፡ ነው ፡ ፀማርኛውን ፡ እይ ።

**ሙጥራን ፤ (ዐረብ)** ፤ ጳጳስ ፡ ሜጥራ ፡ የሚለብስ ።

**መጥሮጶሊስ ፤ (ጽር ፡ ሚትሮፖሊስ)** ፤ እመ ፡ አህጉር ፤ ታላቅ ፡ መዲና ፡ ከተማ ፡ መናገሻ ። ዮሐንስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘቍስጥንጥንያ ፡ መጥሮጶሊስ ፡ (ራእ ፡ ፩) ።

**መጥሮጶሊስ ፤ (ጽር ፡ ሚትሮፖሊቲስ)** ፤ ፀሊይ ፡ ጳጳስ ፡ ወይም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በታላቅ ፡ መዲና ፡ የተሾመ ። መጥሮጶሊስ ፡ ዘውእቱ ፡ ጳጳስ ፤ (ሲኖዶ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፬) ።

**ሚጠት ፤—መመለስ ፤—መዩጥ ፡ ሜጠ ።**

**ማይ ፤ (ብ ፡ ማያት ። ዕብ ፡ ማይም ። ሱር ፡ ማያእ ። ዐረ ፡ ማእ)** ፤ በቁሙ ፡ ውሃ ፡ የታወቀ ፡ ፈሳሽ ፡ ከምድር ፡ ሆድ ፡ የሚፈልቅ ፡ የሚወጣ ፤ በባሕር ፡ በየብስ ፡ በጕድጓድ ፡ በዐዘቅት ፡ በአፍላግ ፡ በአንቅዕት ፡ በኹሉ ፡ የሚገኝ ፤ ለባሕርዩና ፡ ለባሕርያነቱ ፡ የተለየ ፡ ሕብር ፡ ጣዕምና ፡ መዐዛ ፡ የሌለው ፡ ጽሩይ ፡ ንጹሕ ፡ ቈሪር ፤ ከራቱ ፡ ባሕርያት ፡ አንዱ ፡ በርጥበቱ ፡ ከመሬት ፡ በጽርየቱ ፡ ከእሳት ፡ በቍረቱ ፡ ከነፋስ ፡ የሚስማማ ፡ ለሚጠጣው ፡ ኹሉ ፡ ልምላሜ ፡ የሚሰጥ ፡ የሚያቀዘቅዝ ፡ የሚያረካ ፡ ባሕርያዊ ፡ መጠጥ ፤ ዝናምም ፡ ጠል ። ዘይቤው ፡ ምህው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ምህውን ፡ እይ ። ማይ ፡ ብዙኀ ። አንቅዕተ ፡ ማያቲሆሙ ። ማያተ ፡ አፍላግ ። ኢትስተይ ፡ ማየ ፡ ዕራቀ ። ስቁለ ፡ አመ ፡ ርእዩከ ፡ አርዳኢከ ፡ ከኑ ፡ መዐዛ ፡ ማይ ፡ (ኢሳ፲፩ ፡ ፱ ። ዮሓ፳ ፡ ፲፱ ። ቅዳ ። ፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፳፫ ። ቅኔ) ። ማይ ፡ መሬር ፡ ጥዑም ፡ ምዉቅ ፡ ቢል ፤ ምረቱና ፡ ጣዕሙ ፡ ሙቀቱ ፡ ከመሬት ፡ እንጂ ፡ ከባሕርዩ ፡ አይደለም ። ከሥጋ ፡ ባሕርይም ፡ የሚወጣ ፡ እንባ ፡ ደም ፡ ዘር ፡ ሌላውም ፡ ኹሉ ፡ ማይ ፡ ይባላል ፤ ፈሳሽ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይውሕዝ ፡ አንብዕ ፡ ከመ ፡ ማይ ። ከዐዉ ፡ ደሞሙ ፡ ከመ ፡ ማይ ። ወእንዘ ፡ ማይ ፡ ውእቱ ፡ ታረግዕ ፡ በጥበብከ ፡ (ቅዳ ፡ ያዕ ። መዝ ፡ ፸፰ ። ቅዳ ፡ አት) ። ስመ ፡ ፊደል ፡ መ ፤ የአልፋ ፡ ፲፫ኛ ።

**ማያዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ ውሀማ ፡ ውሃም ፡ ውሃማ ፤ የውሃ ። ጠባይዕ ፡ ማያዊ ፤ ነፋሳዊ ፡ መሬታዊ ፡ እሳታዊ ፡ (ፈላስ ፡ ገ፲፯) ።

**ሚዜ ፤ (ትግ ፡ ማዘይ ። ዕብ ፡ ሚይ ፡ ዜ ፤ መኑ ፡ ዝ)** ፤ በቁሙ ፡ ፀማርኛ ። ዐርክ ፡ መርዓዊ ፤ ግልገል ፡ ሙሽራ ፤ የመርዓዊ ፡ አሳሳች ፡ እኩያው ፡ አምሳያው ፤ ከማሳሳቱም ፡ የተነሣ ፡ የመርዓት ፡ ወገኖች ፡ መኑ ፡ ዝንቱ ፡ ብለው ፡ የሚያደንቁት ፡ የሚጠይቁት ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፲፱ ። ፫ ፡ ፳፱) ።

**ሚዝት** ፤ በቁሙ ፤ ሴት ፡ ሙሽራ ፤ የመርዓዊ ፡ ጣምራ ፤ ሚዝ(ስ)ቱ ። መሐዘን ፡ እይ ፤ የሚዜና ፡ የሚዝት ፡ ሥር ፡ መሠረት ፡ ርሱ ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ስን ፡ ተክትለው ፡ ሚስት ፡ ማለት ፡ የሜስ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ ይላሉና ፤ በኀብዝዝ(ስ)ት ፡ ንባብ ፡ ይረታሉ ።

**ሚያዝያ** ፤ በቁሙ ፤ ማዚያ ፤ ስመ ፡ ወርኅ ፡ ባምን ፡ እመስከረም ፤ የሚዘገዝትና ፡ የሙሽሮች ፡ ወር ፡ መኑ ፡ መኑ ፡ የሚባሉበት ፡ (መዝ ፡ ፸፫ ። ኪዳ) ። በግንቦት ፡ ወር ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ባገራችን ፡ ልማድ ፡ ጋብቻና ፡ ሰርግ ፡ የለምና ፤ ሚያዝያን ፡ የሚዘገዝት ፡ ወር ፡ ማለት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ግንቦት ፡ ግን ፡ የዛር ፡ የቡዳ ፡ የደበል ፡ እንግ ፡ ወር ፡ ይባላል ፤ ይኸውም ፡ የመባቻው ፡ ስት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ይታወቃል ፤ አቢብንና ፡ ኤምንን ፡ እይ ። በወርኀ ፡ ሚያዝያ ። በቀዳሚ ፡ ወርኅ ፡ ብሩህ ፡ ዘውእቱ ፡ ሚያዝያ ፡ (ዘፀ፴፬ ፡ ፲፰ ። ዲድ ፡ ፳፱) ።

**መዩጥ ፤ ጦት ፤ (ሜጠ ፡ ይመይጥ ፡ ይሚጥ ። ሦጠ ፤ ሜሰ ፤ ወለጠ)** ፤ መመለስ ፡ መቀለስ ፤ ማዞር ። ኢትሚጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔየ ። ሜጡ ፡ ዘባኖሙ ፡ ኀቤየ ። ሚጥ ፡ ሎቱ ፡ ካልእታሂ ፡ (ጦቢ፫ ፡ ፮ ። ኤር፪ ፡ ፳፯ ። ማቴ፭ ፡ ፴፱) ።

—፤ መለወጥ ፡ መገልበጥ ፤ ሌላ ፡ ማድረግ ፤ የባሕርይ ፡ የግብር ። ኢትሚጥ ፡ ብፀዐተከ ። ኢትሚጥ ፡ ፍትሐ ። እመሂ ፡ መከርክሙ ፡ ምክረ ፡ ይመይጦ ፡ እግዚ ። ዘሜጦ ፡ ለማይ ፡ ወረሰዮ ፡ ዴወ ። ሚጦ ፡ ለዝንቱ ፡ ኀብስት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሥጋከ ፡ (ሚራ፯ ፡ ፲፬ ። ዘፀ ፳፫ ፡ ፮ ። ኢሳ፰ ፡ ፲ ። ሚራ፴፱ ፡ ፴፫ ። ቅዳ) ። ይመውእ ፡ ያደክም ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይመይጥ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፀ፲፯ ፡ ፲፫) ።

**መያጢ ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት)** ፤ የመለሰ ፡ የሚለውጥ ፤ መላሽ ፡ ለዋጭ ፡ ገልባጭ ። መያጢሃ ፡ ለነፍስ ። መያጢሆሙ ፡ ለዲውዋን ። መያጤ ፡ ልሳን ፡ (ኪዳ ። ሃይ ፡ አበ ። ምሳ፲፯ ፡ ፳) ።

**አሜጠ ፤ (ያመይጥ ፡ ያሚጥ)** ፤ አስመለሰ ፡ አስለወጠ ።

**ተመይጠ** ፤ ተመለሰ ፡ ታጠፈ ፡ ተቀለሰ ፡ ዞረ ፡ ተገለበጠ ። ተመየጡ ፡ ኀቤየ ፡ ወእትመየጥ ፡ ኀቤክሙ ። ተመየጥ ፡ ድኅሬከ ። ክመ ፡ ኢትትመየጥ ፡ እምገቦከ ፡ ኅበ ፡ ገቦከ ፡ (ዘካ፩ ፡ ፫ ። ቀሌ ። ሕዝ፱ ፡ ፰) ።

—፤ ተለወጠ ፡ ሌላ ፡ ኾነ ። ተመይጠ ፡ ልቡ ፡ ለፈርዖን ። ይትመየጥ ፡ ቈላቲሃ ፡ ወይከውን ፡ ፒሳ ። ይመስሎሙ ፡ ክመ ፡ ህላዌ ፡ ቃል ፡ ተመይጠ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ሥጋ ። እስመ ፡ ኅብስት ፡ ይትመየጥ ፡ ለክዊኔ ፡ ሥጋሁ ፡ (ዘፀ፲፬ ፡ ፭ ። ኢሳ፴፬ ፡ ፱ ። ቄር ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ተመያየጠ** ፤ (የተመይጠ ፡ ድርብ) ፡ ተመላለሰ ፤ ተዛወረ ፡ ተገላበጠ ፡ ተለዋወጠ ። ማእከለ ፡ አሠረ ፡ ጽ

ድቅ ፡ እትመያየጥ ። እንዘ ፡ ይትመያየጥ ፡ በዐራቱ ። ሕማመ ፡ ፈፀንት ፡ ዘይትመያየጥ ፡ በበ ፡ ራብዕት ፤ እስመ ፡ ግብር ፡ ዘልፈ ፡ ይትመያየጥ ፡ ወይትዌለጥ ፡ (ምሳሌ ፡ ፳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ። ዮሴፍ) ።

**ተማየጠ** ፤ ተማሰለ ፡ ተላወጠ ፤ ተዛወረ ።

**ተመያጠ ፤ ተማያጠ ፤** የተመ (ማ)ሰለ ፤ የሚለወጥ ፡ ተለዋጭ ፤ ተመሳሽ ፡ ተመላላሽ ። ተመይጥ ያን ፡ ኀበ ፡ እግዚ ። ባሕታውያን ፡ ተመይጥያን ፡ ለኀበ ፡ ዓለም ። እንሰ ፡ ከመ ፡ እሑዱ ፡ እምአርድእ ቲክሙ ፡ ወተመ (ማ)ያጢ ፡ ለነገርክሙ ፡ (ፊልክ ፡ ፪፻ና ፡ ፳ ። ዮሴፍ) ።

**ምዩጥ ፤ (ጣን ፤ ጣት ፡ ዩጥ)** ፤ የተመለሰ ፤ የተማለሰ ፤ ምልስ ፡ ልውጥ ። ምዩጠ ፡ ገጽ ፡ እምስእ ለትየ ። እስመ ፡ ምዩጥ ፡ ገጾሙ ። ሰብእ ፡ ምዩጣን ፡ ኀቤከ ፡ (አርጋ ፡ ፫ ። ሄርማ ፡ ገ፲፯ ። ዮሴፍ) ።

**ሚጠት ፤ (ታት)** ፤ መመለስ ፤ መዞር ። እሬ ስየ ፡ ኅቡረ ፡ ለሚጠቶሙ ። ሚጠተ ፡ ብርሃናት ፡ ሰማይ ። እምቅድመ ፡ ሚጠታት ፡ ዘብርሃናት ። በሚጠተ ፡ ገጺ ፡ እግዚ ፡ እምኔነ ፡ (ሚክ፪ ፡ ፲፪ ። ሔኖ፸፪ ፡ ፭ ። ቅዳ ፡ ዲዮ ። ዮሴፍ) ።

—፤ መለወጥ ፤ ውላጤ ። ሚጠተ ፡ የአምኑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ለዘኢየአምር ፡ ሚጠተ ። ዘእንበለ ፡ ሚጠት ፡ (ቁር ። ቅዳ) ።

—፤ መልስ ፡ ምላሽ ፡ የጥያቄና ፡ የወረቀት ። ሰድ ፡ መ ጽሐፈ ፡ ኀበ ፡ ንጉሠ ፡ ምዕራብ ፤ ወሰእመ ፡ ነሣእከ ፡ ሚጠተ ፡ እምኔሁ ፡ ትመየጥ ፡ ኀቤየ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ምያጤ ፤ ሙያጤ ፤ (መዊጥ ፡ ሞጠ ፡ ይመውጥ ፡ ይሙጥ)** ፤ ግእዝ ፡ ከማሁ ፤ መመለስ ፤ ምለሳ ። መለወጥ ፤ መለዋወጥ ፡ መዛወር ። ወና ፡ የ ፡ ተወ ራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በምያጤ ፡ ፈንታ ፡ ሙያጤ ፡ ይላል ። ዘእንበለ ፡ ሙያጤ ። ሙያጤ ፡ ልደት ። ሙያጤ ፡ መዋዕል ፡ ወተፋልሶ ፡ ጊዜያት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ጥበ፯ ፡ ፲፰ ። ፲፱ ፡ ፳፯) ።

**ሚጣን** ፤ ግእዝ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፤ መለወጥ ፡ ልው ጥነት ። ጽዱቅ ፡ ወክቡር ፡ ነገረ ፡ እግዚ ፤ ወአልቦ ፡ ወኢምንትኒ ፡ ሚጣን ፡ በኀበ ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ አእምሮ ፡ (መቃ ፡ ገ፲) ።

**ተምያጥ** ፤ መመሳሰል ፤ ምልልስ ፤ ተለዋዋጭ ፡ ተገላባጭ ፡ መኾን ፤ እንደ ፡ ኅሥሥት ። የተምያጥና ፡ የተ ውላጥ ፡ ምስጢር ፡ ጥቂት ፡ ይለያያል ። ተውላጥ ፡ እንደ ፡ ብእሲተ ፡ ሎጥ ፡ እንደ ፡ ማየ ፡ ቃና ፡ ተለውጦ ፡ አለመመ ለስ ፡ ነው ። ተምያጥ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ማየ ፡ ግብጽ ፡ እ ንደ ፡ በትረ ፡ ሙሴ ፡ መመላለስ ፡ ነው ። ተምያጠ ፡ ወተውላጠ ፡ ህላውያት ። ዘእንበለ ፡ ተምያጥ ፡ ወ ኢተውላጥ ፡ (ሃይ ፡ አበ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፯ ። አርጋ ፡ ፩ና ፡ ፯) ።

**መስተመይጥ ፤ (ተመይጠ ፡ ተመያ የጠ)** ፤ ተመያጢ ፤ የተመለሰ ፡ የሚመለስ ፡ ምልስ ፤ ገር ፡ የዋህ ፡ ኅዳጌ ፡ በቀል ። ብዙኀ ፡ ሣህል ፡ ወመስተመ ይጥ ፡ ላዕለ ፡ ጌጋዮሙ ፡ (፪ዜና ፡ ፴፫ ። ነቢ ፡ ፯) ።

**መስተማይጥ ፤ (ተማየጠ ፡ አስተማ የጠ)** ፤ ተማያጢ ፤ አስተማያጢ ፤ የተማለሰ ፤ የሚያማ ልስ ፤ ተማላሽ ፡ አማላሽ ።

**ሚል ፤ (ላቲን)** ፤ የመንገድ ፡ ስፍር ፡ በቁመት ፤ ሺሕ ፡ ርምጃ ፤ ሺሕ ፡ መትር ፡ ወይም ፡ ፩ ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ፩ ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ማለት ። ርምጃ ፡ የዱሮ ፤ መትር ፡ የዛሬ ፡ ነው ። (ሚልዮን ፤ ሺ ፡ ጊዜ ፡ ሺ ፤ መቶ ፡ ፻፻) ። የወሰኑም ፡ ደንጊያ ፡ በሺሕ ፡ በሺሑ ፡ መ ትር ፡ የሚቆመው ፡ ሚል ፡ ይባላል ።

**ሜም ፤ (ዕብ)** ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ መ ፤ ማይ ፡ ማያት ፡ ማለት ፡ ነው ። ደምፁ ፡ ወተሐምኑ ፡ ማያቲሆሙ ፡ ባሰው ፤ ዕብራይስጡ ፡ ዩሄሙ ፡ የሐምሩ ፡ ሜማው ፡ እን ዲል ፡ (መዝ ፡ ፵፭) ። ሜም ፡ ጥቀ ፡ አፍቀርኩ ፡ ሕገከ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፺፯—፻፬ ። ሰቈ፭ ፡ ፲፫ ። ፬ ፡ ፲፫ ። ፫ ፡ ፅ፲፫ ። ፬ ፡ ፲፫) ።

**ሜመየ ፤ (ምህወ ፤ የመመ)** ፤ ውሃ ፡ ኾነ ፡ ቃሰሰ ፡ ቀለጠ ፡ ውሃ ፡ መሰለ ፡ ውሃ ፡ ውሃ ፡ አለ ። ባሌ ቅኔዎች ፡ ግን ፡ ለየ ፡ ለያየ ፡ ይሉታል ፡ ምስክር ፡ የለውም ።

**መዩን ፤ ኖት ፤ (ሜነ ፡ ይመይን ፡ ይ ሚን ። ዐረ ፡ ማነ)** ፤ አው ፤

**መይኖ ፤ ኖት ፤ (መየነ ፡ ይሜይን ፡ ይ መይን ። መነየ)** ፤ መተንኰል ፡ መጠበብ ፤ ማወቅ ፡ መራቀቅ ፡ ለማብር ፡ ለነገር ፡ መልክ ፡ ማውጣት ፡ ምሳሌ ፡ መስበት ። መክዳት ፡ መዋሸት ፡ ማበል ፡ ማታለል ፡ መሸ ንገል ። መተንኰል ፡ ለክፉም ፡ ለበጎም ፡ ይኾናል ፤ ማእ ከላዊ ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመየነ ፡ ፈንታ ፡ እንዳ ማርኛው ፡ ተመየነ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ተ ፡ አለበ ታው ፡ ገብቷል ። ቦ ፡ ሰብእ ፡ ዘበጽሉ ፡ ይትሜየን ፡ ወ ብዙኀ ፡ የአምር ። ተመይኖ ፡ ግብር ፤ ተተንኰሉ ፡ ተጠ በበ ፡ (ሢራ፲፱ ፡ ፳፭ ። ፊላስ ፡ ገ፲፯) ። ይትሜየኑ ፡ ወይ ገብሩ ፡ ትምይንተ ። ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘይትሜየን ፡ ላ ዕለ ፡ ዳንኤል ። ተመየኖሙ ፡ ከመ ፡ ይቅትሎሙ ። በብዙኀ ፡ ተመይኖ ። እለ ፡ ይትሜየንዎ ፡ ለቃለ ፡ እ ግዚ ፤ ከዳ ፡ ሸነገለ ፡ (ኤር፱ ፡ ፰ ። ዳን፮ ፡ ፲፯ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ። አስቴ፰ ፡ ፲፫ ። ቀሌ) ።

**አመየነ ፤ አስተመየነ** ፤ አስተነኰለ ፤ ተን ኰል ፡ አስተማረ ።

**ተመየነ** ፤ ተታሰለ ፡ ተሸነገለ ፤ ተንኰል ፡ ተሠ ራበት ።

**ተመያኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፤ ተታላይ ፡ ተሸንጋይ ፤ ተላላ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ መያኒ ፡ እንደ ፡ ማለት ፤ የሚተነኩል ፤ ተንኰለኛ ፤ ሸንጋይ ፡ አታላይ ። ትምይ ንተ ፡ ሐሰቶሙ ፡ ለተመያንያን ፡ (አቡሻ ፡ ፴፯) ።

**መስተመይን ፤ (ንት ፡ ናን ፡ ናት ። መ መይን)** ፤ ግእዝ ፡ ከማሁ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ። ሮሜ፩ ፡ ፳፱ ። አፈ ፡ ድ፴፫) ።

**ምዩን** ፤ የተቃለለ ፤ የተሸነገለ ፡ ተላላ ፡ ሽንግል ፤ ሌሎች ፡ ያቃለሉት ፡ የተተነኰሉት ። **እስመ** ፡ ውስተ ፡ ምይንት ፡ ነፍስ ፡ ኢትበውእ ፡ ጥበብ ፡ (ጥበ፩ ፡ ፬) ።

**ምያኔ** ፤ መተንኰል ፡ መተናኰል ፡ ተንኰለኛ ነት ፡ ትንኰላ ፡ ሽንገላ ። **ምያኔ** ፡ ወጕሕሉት ፡ (አዋል) ።

**ሚን** ፤ ክዳት ፡ ክፋት ፡ ተንኰል ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ ሽንገላ ፡ (ፑሊቲክ) ። **ቅንአት** ፡ ወቃሕው ፡ ወሚን ፡፡ ሰይጣን ፡ ስብሐት ፡ ብጡል ፡ ብዙኅ ፡ ሚን ፡ ወእከይ ፡ (ፊልክ ፡ ፵፮) ። አይቴ ፡ ሀሎ ፡ ኀይልከ ፡ ወሚንከ ፡ ዘትገብሮ ፡ በላዕለ ፡ በብእ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ትምይንት** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ኢንሕር ፡ በትምይንት ፡፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በትምይንት ፡፡ ወአእመረ ፡ ትምይንቶሙ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፪ ። ፪ተሰ ፡ ፫ ፡ ፮ ። ሉቃ፳ ፡ ፳፫) ።

**ተምያን** ፤ ተንኰል ፡ ውሸት ፡ ማብዝነት ። ተቀትለ ፡ በተምያን ፡ ነገር ፡ ወተኃሕልዎ ፡ (ዮሴፍ) ።

—፤ ግብዝ ፡ ቅልቅል ፡ ጥሩ ፡ ጠንካራ ። ያይደለ ፡ የተንኰልና ፡ የማታለል ፡ ሥራ ፤ ያንጥረኛ ፡ የመሸተኛ ፡ የሌላውም ፡ ኹሉ ። **ወርቅ** ፡ ጽሩይ ፡ ወፍቱን ፡ ዘኢኮነ ፡ ተምያን ፡፡ ወርቅክሙ ፡ ተምያን ፡፡ ብሩረ ፡ ተምያን ፡፡ መዳልወ ፡ ተምያን ፡፡ ጽሩይ ፡ ውእቱ ፡፡ ዘእንበለ ፡ ተምያን ፡ (፳ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፲፰ ። ኢሳ፳ ፡ ፳፪ ። ምሳ፳፮ ፡ ፲፫ ። ሚክ፮ ፡ ፲፩ ። ቅዳ ፡ ጎር) ።

**ሚዐ** ፤ (**መዩሰ** ። **ዐረ** ፡ **መዐ** ፡ **ማዐ** ፤ **ደከመ** ፡ **ፈሰሰ**) ፤ ቀለጠ ፡ ውሃ ፡ ኾነ ፤ ነጠረ ፡ ተጣፈጠ ። ምህወንና ፡ መስወን ፡ ጸዐጠን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**ሚዓ** ፡ **ሚዓ** ፤ (ብ ፡ **ሚዓት** ፤ **እምያስ**) ፤ ጥሩ ፡ ሹቱ ፡ የነጠረ ፡ የቀለጠ ፡ የተጣፈጠ ። **ክርቤ** ፡ ሰሊክ ፡ ሚዓ ፡፡ **ማርያም** ፡ ገነት ፡ ሚዓ ፡ ወሰሊክ ፡፡ ስኂን ፡ ወሚዓ ፡ ወሰሊኖት ፡ (ገድ ፡ አዳ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፳፭ ። አርጋ ፡ ፯) ።

**መዩስ** ፤ **ሰት** ፤ (**ሚሰ** ፡ **ይመይስ** ፡ **ይሚስ** ፤ **ሚጠ** ። **ዐረ** ፡ **ማሰ**) ፤ መመሸት ፡ መስወስ ፡ ማሸት ፡ መበጥበጥ ፡ ማማስል ፡ መበጀት ፡ መዘለል ፡ የወይን ፡ የማር ፡ የድፍድፍ ፡ የቡሖ ። ማዘንበል ፡ ማስኰን በስ ፡ መመሰስ ፡ የጋን ፡ የመስኖ ፡ ሲሐሳብና ፡ ስልብም ፡ ይኾናል ። መሰስን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**መያሲ** ፤ (**ሲት** ፡ **ስያን** ፡ **ያት**) ፤ መሻች ፡ መሸተኛ ፡ የሚጠጅ ፡ የሚጠምቅ ፡ የሚዘልል ፡ በጥባጭ ፡ በረቂ ፡ አውጭ ። **እለ** ፡ ይገይሡ ፡ በጽባሕ ፡ ቤተ ፡ መያሲ ፡፡ ወኢይጸድቅ ፡ መያሲ ፡ እምዐመፃ ፡፡ መያስያን ፡ እለ ፡ ይትስሕቡ ፡ ማየ ፡ በወይን ፡፡ ለብሰ ፡ ልብሰ ፡ መያስያን ፡ (ኢሳ፭ ፡ ፲፩ ። ሢራ፳፮ ፡ ፳፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፪ ። ዮሴፍ) ። **መይስ** ፤ መላሽ ፡ አስመላሽ ።

**አሚሰ** ፤ (**ያመይስ** ፡ **ያሚስ**) ፤ አስመሸተ ፡ አስጠጀ ፡ አስመሰለ ።

**ተመይሰ** ፤ ተመሸተ ፡ ተጠጀ ፡ ተማሰ ፡ ተዘለለ ። ተዘነበለ ፤ ተመለሰ ። **ከመ** ፡ ውሒዘ ፡ ማይ ፡ ከማሁ ፡ **ልበ** ፡ ንጉሥ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚ ፡ ኀበ ፡ ፈቀደ ፡ ህየ ፡ ይመይሰ(ጣ) ፤ ወህየ ፡ ትትመየስ ፡ (ምሳ፳፩ ፡ ፩) ።

**ምዩስ** ፤ (**ሳን** ፡ **ሳት** ፡ **ዩስት**) ፤ የተጠጀ ፡ የተማሰ ፤ የተዘነበለ ፡ ዝንብል ፡ ምልስ ።

**ሚስ** ፤ (ብ ፡ **እምያስ**) ፤ መሸታ ፡ ጠጅ ፡ ዐረቂ ፡ የወይን ፡ የማር ፡ የሌላውም ፡ ኹሉ ፤ የሚያሰክር ፡ መጠጥ ። ስታዩ ፡ ሚሰ ፡ ወይን ፡፡ ኢይሰቲ ፡ ወይነ ፡ ወሚሰ ፡፡ ጻዐፈ ፡ ወይን ፡ ወሚስ ፡ ወምዝር ፡፡ **እምያስ** ፡ ዘግቡር ፡ በእሳት ፡፡ ወኢምንትኒ ፡ እምዘመደ ፡ አምያስ ፡ ዘአጣእጥእዎ ፡ በመዓር ፡ አው ፡ በሶከር ፡ (ቀሌ ። ሉቃ፩ ፡ ፲፭ ። ገድ ፡ ተክ ። አብጥ ፡ ፪ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፩) ።

**ሚሽሑ** ፤ (**ዕብ** ፡ **ሚይ** ፡ **ሳሑ**) ፤ ሚ ፡ ማይ ፤ ሽሑ ፡ ሳሑ ፡ ዋናተኛ ፤ በተንናኝ ፡ ማየ ፡ ሐማሲ ። እግረኛ ፡ የማይደፍረው ፡ ዋናተኛ ፡ የሚሻገረው ፡ ዕሙቅ ፡ ጥልቅ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ሕዝ፵፯ ፡ ፭) ።

**ሚሶር** ፤ (**ዕብ** ፡ **ሚሾር**) ፤ ሜዳ ፡ ለጥ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ የተካከለ ፤ እንዳውድማ ፡ ያለ ፡ ርቱዕ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ተረት) ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ እንደ ፡ ወግዳ ፡ (ኢ.ያ፲፫ ፡ ፲፯) ።

**መክ** ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ፪ኛው ፡ ክፍል ፡ ፋትሐ ፡ ነገሥት ። መ ፡ መሰክ ፤ ክ ፡ ክልእ ፡ ወይም ፡ ክልኤት ፡ ከማለት ፡ መጥቶ ፡ ፩ ፡ ስም ፡ ኾኗል ። ዳግመኛም ፡ በዕብራይስጥ ፡ ፊደል ፡ ቤትና ፡ ካፍ ፡ (በ ፡ ክ) ፡ እንደ ፡ ፪ና ፡ እንደ ፡ ፳ ፡ ይማሰላሉና ፡ ዳግምና ፡ ክልእ ፡ ለማለት ፡ መብ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መክ ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሚፈቱ ፡ አሉ ። **መክ** ፡ ዘውእቱ ፡ ነገሥት ፡ ዳግም ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ። መግና ፡ መጅም ፡ (ገ ፡ ደ) ፡ ዐረቡ ፡ ጋሜልን ፡ ጂም ፡ እያሉ ፡ አጠራሩን ፡ ስለ ፡ ለወጠው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተዛውረው ፡ አለቦታቸው ፡ ተጥፈዋል ፤ ፍቻቸውን ፡ በየቦታቸው ፡ እይ ።

**ሚካኤል** ፤ (**ዕብ**) ፤ የመልአክ ፡ ስም ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ሚ ፡ መኑ ፡ ካ ፡ ከመ ፡ **ኤል** ፡ አምላክ ፡ በተገናኝ ፡ መኑ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሚክያስ ፡ (ጽር ። ዕብ ፡ ሚካህ) ፡ ማለት ፡ መኑ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ (ሐዋ ። ዳን ፡ ፲፪ ፡ ፩ ። ይሁ ፡ ፱ ። ራእ፲፪ ፡ ፯) ።



ሚካኤል ፤

**መክሐ፤ ሐት፤** (መክሐ፡ ይሜክሕ፡ ይመክሕ)፤ መመካት፤ መታበይ፡ መኵራት፡ መክበር፡ መከበር፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ተከባሪ፡ መኾን፤ እኔ፡ እገሌ፡ ማለት። መጽሐፍ፡ ግን፡ በመየን፡ ፈንታ፡ ተመየን፡ እንዲል፡ በመክሐም፡ ፈንታ፡ ተመክሐ፡ ይላል፤ ተ፡ ያማርኛ፡ ነው፡ አያሰኝም። ትትሜካሕ፡ በማእከለ፡ አሕዛብ፡፡ መኑ፡ ተመክሐ፡ ከማከ፡፡ ወይትሜካሕ፡ ከመ፡ እግዚአብሔር፡ አቡሁ፡፡ ኢትትመክሑ፡ በቅትለትየ፤ (ሚራ፳፱፡ ፭። ፵፰፡ ፱። ጥበ፪፡ ፲፮። ዮሴፍ)።

**መካሒ፤ መካሕ፤** የሚመካ፤ ትምክሕተኛ፡ ኵሩ፡ ተከባሪ። አይ፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፡ ብእሲ፡ መካሕ፡ (ኢሳ፳፫፡ ፩)።

**አመክሐ፤ አስተመክሐ፤** አስመካ፤ አስከበረ፡ አኰራ፡ አስታበየ። አልበሶ፡ ወአስተመክሖ፡ በዘሉ፡፡ አንስት፡ ኢይልበሳ፡ ወርቀ፡ ዘተገብረ፡ በልብስ፡ ዘያስተሜክሕ፡ (ሚራ፵፰፡ ፰። ፍ፡ ነ፡ ፳፫)።

**መምክሕ፤ መመክሕ፤** መመኪያ፤ የሚያስመካ፡ አስመኪ፤ አስከባሪ። ከመ፡ ኢይበሉኒ፡ ፀር፡ አይቴኑ፡ መምክሑ፡ (አይቴኑመ፡ ምክሑ)፡ (ደራሲ)።

**ተመክሐ፤** ተመካበት፡ ተከበረበት፤ መመኪያ፡ መከበሪያ፡ ኾነ፤ ለሌላው።

**ምኩሕ፡ (ሓን፡ ሓት፡ ክሕት)፤** በቁሙ፤ መካሕ፤ የተመካ፡ ትምክሕተኛ፤ ተመኪና፡ አስመኪ፡ መመኪያ፡ የኾነ፡ ክቡር፡ ምስጉን። አልባስ፡ ክህነት፡ ምኩሕ፡፡ አልባስ፡ ክቡራት፡ ወምኩሓት፡ (ስንክ፡ ጥቅ፲፱። አፈ፡ ተ፳፫)።

**ምክሕ፤** መመኪያ፤ ትምክሕት፤ ክብር፡ ምስጋና፤ ሞገስ፡ ልዕልና፡ ጌጥ፡ ሽልማት፤ የሚያስመካ፡ ነገር፡ ማናቸውም፡ ኹሉ። ኢይከውነከ፡ ምክሐ፡፡ በፍርሀተ፡ እግዚ፡ ይኩን፡ ምክሕከ፡፡ ምክሖሙ፡ ፈሪሀ፡ እግዚ፡፡ ይከውኖ፡ ምክሐ፡ በኀበ፡ ማኅፈሩ፡፡ አክሊለ፡ ምክሕ፡ (ሚራ፫፡ ፲። ፲፡ ፲፱። ፵፭፡ ፲። ፵፰፡ ፱። ሕዝ፲፯፡ ፲፪)።

**ትምክሕት፤** በቁሙ፤ መመኪያ፡ ክብር፤ ተመካሒነት፡ ትዕቢት፡ ኵራት። ትምክሕቶሙ፡ ለረሲዓን፡ ትጠፍእ፡፡ ተኀፈርክሙ፡ በትምክሕትክሙ፡፡ ዘላ፡ ትምክሕት፡ እንተ፡ ከመ፡ ዝ፡ እኪት፡ ይእቲ፤ (ምሳ፲፩፡ ፯። ኤር፲፪፡ ፲፫። ያዕ፬፡ ፲፮)።

(ጥ) **መኰየ፤** (ይሜኵ፡ ይመኵ፤ መኵዮ፤ የመክሐ፡ ቅጥያ። ዐረ፡ መቀየ፤ መቃዐቀበ)፤ መከተ፤ ጠበቀ፤ ጋሻኛ፡ ዘበኛ፡ ኾነ። ተአዘዝኩ፡ እፈኑ፡ በብእ፡ አፍራስ፡ ወእግር፡ እለ፡ ያጸንዑ፡ ብሔረ፡ ወይሜኵዩ፡ እምነ፡ ፀርነ፡፡ አሕዛብ፡ እለ፡ ይሜኵዩ፡ ለእለ፡ ውስተ፡ ይሁዳ፡ (፩ዕዝ፡ ፰፡ ፳፱። ፭፡ ፵፩)። ሞከተ፡ ሰነገ፡ መኩት፡ አደረገ፤ (በማርኛ)።

**ሚክሎል፤—**ፍጹም፡ ጌጥ፤—ከልሎ፡ ከለለ።

**መክሊት፤—**የሚዛን፡ ዐዋቂ፤—ከልይ፡ ከለየ።

**መኪና፤—**በቁሙ፡ መዘውር፤—ከዪን፡ ኬነ፡ ኬነወ።

**መክን፤—**በታ፡ ሰፈር፤—ከዊን፡ ኮነ።

**መኪን፤ ኖት፤** (መከነ፤ አው፡ መክነ፡ ይመክን፡ ይምክን)፤ መምከን፤ መካን፡ መኾን፤ አለመውለድ፤ አለማፍራት፤ ወይም፡ ወልዶ፡ መቅበር፡ ልጅ፡ ማጣት፤ መጨንገፍ፡ ማስረድ፤ አብቦ፡ መቅረት። ርእየት፡ ልደ፡ ከመ፡ መክነት፡፡ አንስት፡ ይመክና፡፡ ትመክን፡ ብሔረ፡ ሃይማኖት፡፡ አልሕምቲሆሙ፡ ኢይመክና፡ (ኩፋ፡ ፳፰። ፩ነገ፡ ፪፡ ፲። ሉቃ፡ ዕገዛ፡ ፪። ኢዮ፳፩፡ ፲)። በመክንና፡ በመክን፡ ፈንታ፡ ተመክነ፡ ይላል፡ ስሕተት፡ ነው።

(ጥ) **መከን፤ (ናት)፤** በቁሙ፡ የማየ (ቶ) ልደ፡ የማያ(ታ) ፈራ፤ መሲና። ወሰራበ፡ መካን፡ ይእቲ፡ ወኢትወልድ፡፡ እስመ፡ መካን፡ ይእቲ፡ ኤልሳቤጥ፡፡ ብፁዓት፡ መካናት፡ እለ፡ ኢወለዳ፡ (ዘፍ፲፩፡ ፴። ሉቃ፩፡ ፯። ፳፫፡ ፳፱)።

**ምክነት፤** መምከን፤ መካንነት። ምክነትሰ፡ ኢተውህበ፡ ለብእሲት፡ (ሔኖ)።

**አምከነ፤** አመከነ፤ መካን፡ አደረገ፤ መውለድ፡ ከለከለ፡ ወይም፡ ልጅ፡ አሳጣ፡ ሾተላይ፡ ኾነ። አምክነተኪ፡ መጥባሕት፡፡ በከመ፡ አምክነቶን፡ ኲናትከ፡ ለአንስት፡ ከማሁ፡ ትምክን፡ እምከ፡፡ ወኢትደግም፡ እንከ፡ አምክኖቶሙ፡ (ሱቴ፩፡ ፳። ፩ነገ፡ ፲፭፡ ፴፫። ሕዝ፴፮፡ ፲፬)።

**መምክን፤ ክኒ፤** መምከኛ፡ የሚያመክን፡ አምካኝ። መምክኒተ፡ ሕዝብ፡ (ሕዝ፴፮፡ ፲፬)።

**ማኹን፤ (ቅብጥ)፤** ስመ፡ ወርኅ፤ ታኅሣሥ፡ ማኅበት። ኪያሆከኑና፡ በሽንበን፡ እይ፡ ለኹሉቱ፡ ወሮች፡ ፪፡ ፪፡ ስም፡ አላቸው፡ (አቡሻ፡ ፳)።

**መክኑን፤—**ኀቡእ፤—ከኒን፡ ከነ፤ ኢልመ።

**ሜክኖት፤ (ጽር፡ ሰብ፡ ምክኖት)፤** ድጋፎች፡ ተሸካሞች፡ መሠረቶች፡ ወይም፡ ስክተቶች፡ ጕልቶች። አንዳቸውን፡ ምክና፡ ይላል፡ ኹሉም፡ የሴት፡ አንቀጽ፡ ነው። ለበ፡ አሐቲ፡ ሜክኖት፡ አሐዱ፡ ኬጥሮጋውሉስ፡ ወከማሁ፡ ለዐሠርቱ፡ ሜክኖት፡ (፫ነገ፡ ፯፡ ፴፰)።

**ምክዕቢት፤—**ዕጥፍ፡ ድርብ፤—ከዒብ፡ ከዐበ።

**መክፌ፤—**ማበሻ፡ ማጠቂ፤—ከፊየ።

**መክፈልት፡ ዕድል፡ ፈንታ፤—**ከፊል፡ ከፈለ።

**መኪ.ር ፤ ሮት ፤** (መከረ ፡ ይመክር ፡ ይምክር ። ዐረ ፡ መከረ ፤ አቃለለ ። ዕብ ፡ ማካር ፤ ሼጠ) ፤ መምከር ፡ ማሰብ ፡ ማውጣት ፡ ማውረድ ፡ ሐሳብን ፡ ማሻሻል ፡ መምረጥ ፡ ማበላለጥ ፡ መወሰን ፡ መቍረጥ ፡ ለማድረግ ፡ ለመተው ። ምክሩ ፡ ምክረ ፡ ዘንገብር ። ምንተ ፡ መከረ ፡ እግዚ ፡ ላዕለ ፡ ግብጽ ። ምክር ፡ እምውስተ ፡ ሕዝብ ፡ ዕደው ፡ ጻድቃነ ፡ ምረጥ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፲፪ ። ዘፀ፲፰ ፡ ፳፩) ።

—፤ መስጠት ፡ ማቅረብ ፤ የምክር ፡ የገንዘብ ፡ ማስተማር ፡ ማመልከት ፤ ለሌላው ፡ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ከመምከር ፡ ይገባል ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመክረ ፡ ፈንታ ፡ አምከረ ፡ ተማከረ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። መኑ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ አምከረ ፡ ላዕለ ፡ ጢሮስ ። መኑ ፡ መማከርቲሁ ፡ ዘአምክሮ ። ዙሉ ፡ መምክር ፡ ያመክር ፡ ምክረ ። ንዒ ፡ አምክርኪ ፡ ምክረ ። እንዘ ፡ ያመክርዎ ፡ በግዐ ፡ ከመ ፡ ካህን ፤ ወሐሲበ ፡ ከመ ፡ ሕፃን ፤ ወርቀ ፡ ከመ ፡ ንጉሥ ፡ ወዕጣነ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ (ኢሳ፳፫ ፡ ፰ ። ፴ ፡ ፲፫ ። ሚራ፴፯ ፡ ፯ ። ፩ነገ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ። አዋል) ። ተማከሩ ፡ ምክረ ፡ እኩየ ፡ ላዕሌከ ። መኑ ፡ ተማከሮ ፡ (ኢሳ፯ ፡ ፭ ። ሮሜ፲፩ ፡ ፴፬) ።

**መከረ ፤ መምከረ ፤** (ሬት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፡ የሚመክር ፡ መካሪ ። አስተዋይ ፡ ምክር ፡ ዐዋቂ ፡ አማካሪ ። ልብ ፡ መካርያን ። ኅሊና ፡ መካርያን ። ልብ ፡ መካሪት ። መምክሪሁ ፡ ለንጉሥ ። መምክሬ ፡ ሠናይ ፡ (ምሳ፲፭ ፡ ፳፱ ። ቅዳ ፡ ኢ.ጲ. ። ምሳ፳፱ ፡ ፯ ። ፩ዜና ፡ ፳፯ ፡ ፴፫ ። ዲ.ድ) ።

**መምክር ፤** (ርት ፡ ራን ፡ ራት ፤ መማክርት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። እሙ ፡ ከነቶ ፡ መምክረ ። እስመ ፡ መምክርት ፡ ይእቲ ። መማክርቲሁ ፡ ለዳዊት ፡ (፪ዜና ፡ ፳፪ ፡ ፫ ። ጥበ፰ ፡ ፱ ። ፪ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፲፪) ።

**አምከረ ፤** አስመከረ ፡ ምክሩ ፡ አለ ፡ ስሞታ ፡ ነገረ ። መምክሪና ፡ መምክር ፡ ከዚህም ፡ ይወጣሉና ፡ እንደዚህ ፡ ደግሞ ፡ ባስደራጊነት ፡ ይፈታሉ ።

**ተመክረ ፤** ተመከረ ፡ ምክር ፡ ሰማ ፡ ተቀበለ ።

**ምኩር ፤** (ራን ፡ ራት ፡ ክርት) ፤ የተመከረ ፡ ዕድሜኛ ፡ መጠና ፡ መከራ ፡ ወይም ፡ ባልንጀራ ፡ የመከረው ።

**ምክር ፤** (ራት) ፤ በቁሙ ፡ ቍርጥ ፡ ሐሳብ ፡ ፈቃድ ፡ ትምርት ፡ ዕውቀት ፡ ምስጢር ፡ ኅቡእ ፡ ነገር ። መንፈሰ ፡ ኀይል ፡ ወምክር ። ኢኮነ ፡ ምክርየ ፡ ከመ ፡ ምክርክሙ ። ኀበ ፡ ክልኤቱ ፡ ምክራት ። ምክሮሙ ፡ ለሊቃውንት ። ዘየወፅእ ፡ ምክረ ፡ ቢጹ ፡ (ኢሳ፲፩ ፡ ፪ ። ፶፭ ፡ ፰ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳፱ ፡ ፱ ። ኢ.ዮ፲፪ ፡ ፰ ። ሚራ፲፫ ፡ ፲፪) ።

**ተማከረ ፤** በቁሙ ፡ ተመካከረ ፡ ምክር ፡ አዋጣ ፡ አሻሻለ ። ኢ.ትትማከር ፡ ምስለ ፡ አብድ ። ወጸቢሖ ፡ ተማከሩ ፡ ወተማከሮሙ ፡ (ሚራ፰ ፡ ፲፭ ። ማቴ፳፯ ፡ ፩ ፡ ፯) ።

**አስተማከረ ፤** አማከረ ፡ አመካከረ ፡ ተማከሩ ፡ አለ ፡ ምክር ፡ አካፈለ ።

(ጥ) **መክሮ ፡ ሮት ፤** (መከረ ፡ ይሜክር ፡ ይመክር ። ነሰወ ፤ ፈተነ) ፤ መሞከር ፡ መፈተን ፡ መመርመር ፡ ማስፈለግት ፡ ጠባዩንና ፡ ምስጢሩን ፡ ለማወቅ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመክረ ፡ ፈንታ ፡ አመከረ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። በእሳት ፡ ያሜክርዎ ፡ ለወርቅ ። በብዙኅ ፡ ነገር ፡ ያሜክረከ ። አመክሮሙ ፡ ለአግብርቲከ ፡ ዐሠሩ ፡ መዋዕለ ። ወቀርበ ፡ ዘያሜክሮ ፡ (ሚራ፪ ፡ ፭ ። ፴፩ ፡ ፲፩ ። ዳን፩ ፡ ፲፪ ። ማቴ፬ ፡ ፫) ።

**አመከረ ፤** አስሞከረ ፡ አስፈተነ ።

**ተመከረ ፤** ተሞከረ ፡ ተፈተነ ፡ ተመረመረ ። መኑ ፡ ተመከረ ፡ ቦቱ ፡ ወኢ.ስሕተ ። ተመከሩ ፡ ሰማዕት ፡ ከመ ፡ ወርቅ ፡ በእሳት ። ተመኪሮ ፡ ይነሥእ ፡ አክሊለ ። እምኀበ ፡ ዲያብሎስ ፡ ተመክረ ፡ (ሚራ፴፩ ፡ ፲ ። መዋሥ ። ያዕ፩ ፡ ፲፪—፲፬ ። ቅዳ ፡ ዲ.ዮ) ።

**ምኩር ፤** የተሞከረ ፡ ሙኩር ፡ ፍቱን ። ምኩር ፡ በዙሉ ፡ (ዕብ፬ ፡ ፲፭ ። ዲ.ድ ፡ ፬ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲) ።

**መክራ ፤** (ራት) ፤ በቁሙ ፡ ፈተና ፡ ጭንቅ ። እብነ ፡ መክራ ። መክራሆሙ ፡ ለወርቅ ፡ ወለብሩር ፡ ርስነት ። መናስው ፡ ወመከራት ። መከራት ፡ ሰይጣናት ፡ (ሚራ፯ ፡ ፳፯ ። ምሳ፳፯ ፡ ፳፩ ። አፈ ፡ ተ፪ ። ፊልክ ፡ ፳፯) ።

**መክር ፤** በቁሙ ፡ የእክልና ፡ የተክል ፡ አዝመራ ፡ ምድር ፡ ለገበሬ ፡ የምትሰጠው ፡ ፍሬ ፡ ተዘርቶ ፡ እስኪ.ታጨድ ፡ እስኪ.መረትና ፡ እስኪ.ከተት ፡ እንደ ፡ ለማስታት ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ያለበት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሜኪ.ር ፤** (ቅብጥ ፡ ሜ ኺ.ር) ፤ ስሙ ፡ ወርኅ ፡ የካቲት ፡ (አቡሻ) ።

**መከርከር ፤**—ወፍጮ ፤—ከርከረ ።

**መኮሴ ፤**—ሞክሼ ፤—ኰሰየ ።

**መከሴና ፤ ሜክሱት ፤**—መሸፈኛ ፤—ከሰየ ።

(ጥ) **መልአ ፤**—ያዘ ፡ ገዠመረ ፤—መልዖ ፡ መልዐ ።

**መሊ.እ ፤ አት ፤** (መልአ ፡ ይመልእ ፡ ይምላእ ። ዕብ ፡ ማሌእ ። ሱር ፡ ምላእ ። ዐረ ፡ መለአ ፤ መሊ.አ) ፤ በጐልና ፡ ገዚ.ር ፡ ሳዕለና ፡ ውስጥ ፡ ብ ፡ ግእዝ ፡ ይስማሙታል ። መምላት ፡ መንተርፈፍ ፡ ጢ.ም ፡ ማለት ፡ ማደር ፡ መከተት ፤ የጎዳሬ ፡ (ማር፪ ፡ ፴፯ ። ሉቃ፭ ፡ ፲፰ ። ፱ ፡ ፭ ። ዮሐ፲፪ ፡ ፫) ።

—፤ መመላት ፡ በውስጥና ፡ በሆድ ፡ እስካፍ ፡ እስከ ፡ ክንፈር ፡ መያዝ ፡ ጉደሎ ፡ አለመኾን ፡ የማጎደር ። መልአት ፡ ምድር ፡ ደመ ፡ ወመልአት ፡ ሀገር ፡ ዐመፃ ። ይመልእ ፡ ወይነ ፡ ዙሉ ፡ ዝቅ ። ኢ.ይመልእ ፡ ዐይኑ ፡ ብዕለ ። መልአ ፡ ደመና ፡ ዝናመ ፡ (ሕዝ፱ ፡ ፱ ። ኤር፲፫ ፡ ፲፪ ። መክ፬ ፡ ፰ ። ፲፩ ፡ ፫) ።

—፤ መምላት ፡ እስከ ፡ ልክ ፡ መድረስ ፤ ማለቅ ፡ መፈጸም ፤ መተካከል ፤ አለማነስና ፡ አለመጕደል ፤ ምሉእ ፡ ፍጹም ፡ ትክክል ፡ መኾን ፤ የስፍር ፡ የቍጥር ፡ የሥራ ፡ የስፍራ ። **እመ ፡ መልአት ፡ ዓመት ። መልአ ፡ ጽሕፈተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ። ሾሉ ፡ ማዕምቅ ፡ ይምላእ ፡** (ኤርሚ፴ ፡ ፳፱ ። ፍ ፡ ን ። ኢሳ፵ ፡ ፬) ።

—፤ መብዛት ፡ መርባት ፡ መበርከት ፡ መትረፍ ፡ ዐቃሌ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ መኾን ፡ ከልክ ፡ ማለፍ ፡ (ዘፍ፴፩ ፡ ፴ ። ማሕ ፡ ፳፯ ። ማሕ ፡ ፲፯ ። ዘፀ፩ ፡ ፯ ፡ ፳) ። እስከዚህ ፡ ዐጕል ፡ ነው ።

—፤ ማግባት ፡ መጨመር ፡ አብዝቶ ፡ መክተት ፡ ጎዳሬውን ፡ በማጎደር ፡ መምላት ፡ ገቢር ። **መልአ ፡ አሕስሊሆሙ ፡ ሥርናየ ። ምልእዎንኬ ፡ ለእላ ፡ መሳብክት ፡ ማየ ። መልእዎ ፡ ደመ ፡ ለዝንቱ ፡ ቤት ። ከመ ፡ ናእክ ፡ መላእክቲሁ ፡ ለብሩር ፡** (ኩፋ ፡ ፶፪ ። ዮሐ፪ ፡ ፯ ። ኤር፲፱ ፡ ፬ ። ሚሌ፶፯ ፡ ፲፰) ።

**መላኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤** የመላ ፡ የሚመላ ፡ መዩ ፡ ተመዩ ። **መላኢ ፡ ንትጋ ። መላኢ ፡ ሾሉ ፡ ዓለም ፡** (ጥበ ፡ ጠቢ ። አርጋ ፡ ፭) ። በመላኢ ፡ ፈንታ ፡ መምልእ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። **መምልአ ፡ ዐሥር ፡** (አዋል) ።

**ተመልአ ፤** ተመላ ፡ ጠገበ ፡ ውስጡ ፡ ኹሉ ፡ ያዘ ፡ ተመላበት ፡ በገዝቶ ፡ ዐደረበት ፡ ጎዳሬው ። **ተመልአት ፡ ደብተራ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚ ። ኢየሱ ፡ ተመልአ ፡ መንፈሰ ፡ ጥበብ ። ተመልአት ፡ አየር ፡ እምነ ፡ መላእክት ፡** (ዘፀ፵ ፡ ፴፭ ። ዘዳ፴፬ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፯) ።

**ምሉእ ፤ (እን ፡ እት ፡ ልእት) ፤** የመላ ፡ የተመላ ፡ ምሉ ፡ ፍጹም ፡ ትክክል ። **ወርኅ ፡ ምሉእ ፡ ብርሃን ። ዐይው ፡ ምሉኣነ ፡ ጥበብ ። እኩ ፡ በምልእት ፡ ልብ ፡** (አቡሻ ፡ ፲፫ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፯ ። ፪ዜና ፡ ፳፭ ፡ ፪) ።

**ምልአት ፤** መምላት ፡ መመላት ፡ አመላል ፡ ምሉንት ፡ ምላት ፡ ፍጻሜ ። **ወሰሰ ፡ ምልአቱ ፡ ለክራ ። ምልአተ ፡ ከርሥ ፡ ዘእንበለ ፡ ዐቅም ። ወሰምልአተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** (ቄድር ። መቃ ፡ ገ፳፱ ። ቅዳ) ።

**ምልአ ፤** ምላት ፡ ምሉ ፡ ፍጹም ፡ ክፍል ፤ ልክኛ ፡ ሕጸጽና ፡ ተውሳክ ፡ የሌለው ። **ንሥኡ ፡ ምልአ ፡ እደዊክሙ ፡ ሐመደ ። ምልአ ፡ ሕፍኑ ። ምልአ ፡ ቤት ፡ ወርቀ ፡ እመ ፡ ወሀበኒ ። ሾሉ ፡ ዓለም ፡ በምልኡ ፡** (ዘፀ፱ ፡ ፰ ። ዘሌ፲ ፡ ፲ ። ዘኍ፳፪ ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፵፱) ።

**መልአክ ፤—በቁሙ ፡ መላክ ፤—ልአክ ፡ ለአከ ።**

**ሚ(ም)ልኤል ፤** ስመ ፡ ኮከብ ፡ ዐቢይ ፡ መጋቤ ፡ ጸደይ ፡ (ሔኖ) ።

**መለገ ፤ (ዕብ ፡ ማላግ ፤ ንፍስ ፡ መለጠ) ፤** ማለግ ፡ ምልግልግ ፡ አለ ፤ ማላጋ ፡ ኾነ ፡ የፈሳሽ ፤ ለሰውም ፡ ይኾናል ። ታገሠ ፡ ቻለ ።

**መልጕ ፤ (ብ ፡ መላግው) ፤** ማላጋ ፡ ምልግልግ ። ዕጕሥ ፡ ታጋሽ ፡ ትዕግሥተኛ ፡ ቻይ ፡ ልበ ፡ ሰፊ ፡ (ሲኖዶ ፡ ገ፲፱፻፲) ።

**መለንስ ፤ (ጽር ፡ ማላክስ) ፤** ለምለም ፡ ለስላሳ ፡ ዝልፍልፍ ፡ የሚል ፡ የሚተጣጠፍ ፡ የሰፋ ፡ ወይም ፡ የራስ ፡ ርጥብ ፡ ትክስ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፫) ።

(ጥ) **መልሐ ፤ ሐት ፤ (መልሐ ፡ ይሜልሕ ፡ ይመልሕ ። ዐረ ፡ መለሐ ። ዕብ ፡ ማላሕ ። ሱር ፡ ምላሕ) ፤** ማጨውየት ፡ ጨው ፡ ማውጣት ፡ ውሃውን ፡ ጨው ፡ ማድረግ ፤ ወይም ፡ ጨው ፡ መጨመር ፡ በጨው ፡ ማጣፈጥ ፡ ማጀል ፤ የምግብ ፡ የሕፃን ፡ የሥጋ ፡ የኅሣ ፡ የቁርበት ። መቁረን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ተመልሐ ፤** ተጨወየ ፤ ጨው ፡ ኾነ ፡ በጨው ፡ ተጣፈጠ ። **ሾሉ ፡ በጼው ፡ ይትሜላሕ ፡** (ቀሌ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ። ማር፱ ፡ ፵፱ ። ሕዝ፲፮ ፡ ፬) ።

**ማልሕ ፤ (ዐረ ፡ ማሊሕ) ፤** ጨዋማ ፡ ጨው ፡ ጨው ፡ የሚል ፡ የጨው ፡ ውሃ ። **ባሕረ ፡ ማልሕ ፡** (አቡሻ ፡ ፶) ። ባሕረ ፡ ጼው ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ምልሕ ፤ ምልሓ ፤ (ዐረ ፡ ሚልሕ) ፤** ጨው ፡ ጨውነት ። አልቦሙ ፡ ምክር ፡ ወኢለብዎ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ አልቦሙ ፡ ምልሕ ፡ ወኢሃይማኖት ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘዳ፴፪ ፡ ፳፰) ። ባለብሉዮችም ፡ ከሃይማኖት ፡ ስለ ፡ ተጣፈረ ፡ ምግባር ፡ ይሉታል ፤ ባለቅኔዎችም ፡ መልሕ ፡ ምግባር ፡ ሠራ ፡ ብለው ፡ ይገሉታል ።

**ሞሎሕ ፤—ስመ ፡ ጣዖት ፤—ሞሎኽ ፡ መሊክ ፡ መለከ ።**

**መልሕቅ ፤—በቁሙ ፤—ለሐቀ ።**

**መሊ.ኅ ፤ ኖት ፤ (መልኀ ፡ ይመልኅ ፡ ይምላኅ ። ዐረ ፡ መለኀ) ፤** መንቀል ፡ መምዘዝ ፤ ማፍለስ ፡ ማውጣት ፡ ማጥፋት ፡ ማራቅ ፡ በቃ ፡ ማስለቀቅ ፡ ነቀለኝና ፡ ሠረወን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ። **ጊዜ ፡ ለተኪል ፡ ወጊዜ ፡ ለመሊኅ ፡ ዘተክሉ ። ሰይፎ ፡ ይመልኅ ። እመልኖሙ ፡ እምድሮሙ ። ከመ ፡ ይምላኅ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዛተ ፡ ልማደ ፡ እኪተ ፡** (መክ፫ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፳ ። ኤር፲፪ ፡ ፲፬ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፱ ፡ ፭) ። ባልሐ ፡ አውፅአ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መልኅ ፡ ይላል ፤ የጣፊና ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ አያሰኝም ። **እግዚ ፡ መልኆሙ ፡ እምቅኔ ፡ መሬር ፡** (ሲኖዶ) ።

**መላኂ ፤ (ኂት ፡ ኅያን ፡ ያት) ፤** የሚነቅል ፡ የሚመዝ ፡ ነቃይ ፡ መዛዥ ። **ሰበር ፡ ወልደ ፡ ሐርመዝ ፡ ዘይሰመይ ፡ መላኄ ፡ መትከፍት ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ከነ ፡ ሰበ ፡ ይመውእ ፡ ለካልእ ፡ ንጉሥ ፡ የአስሮ ፡ ወይመልኅ ፡ መታክፍቲሁ ፡** (ስንክ ፡ ሚያ፲፱) ።

**አምልኀ ፤** አስነቀለ ፡ አስመዘዘ ።

**ተመልኀ ፤** ተነቀለ ፡ ተመዘዘ ። **ወበንይሉ ፡ ነፋስ ፡ ይትመላኅ ። እምቅድመ ፡ ይትመልኑ ፡ መባርቅት ። በይፍ ፡ እንተ ፡ ተመልኅት ፡** (ጥበ፬ ፡ ፬ ። ቅዳ ፡ አፈ ። ሕዝ፳፩ ፡ ፳፰) ። ታረመ ፡ ተነጨ ፡ ተመለጠ ፡ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ መንቀል ፡ ነው ። **ተመልኆ ፡ ክነፊሆ ። ይበኪ ፡ እስከ ፡ ተመልኑ ፡ ሥዕርተ ፡ አዕይንቲሁ ፡** (ዳንኤ ፡ ፬ ። ፊልክ ፡ ፶፭) ።

**ምሉኅ** ፤ (ኃን ፡ ኃት ፡ ልኅት) ፤ የተነቀለ ፡ የተመዘዘ ፡ ንቅል ። ሰይፍ ፡ ምሉኅ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ። ምሉኀ ፡ ሕጽፍር ። ሕዝብ ፡ ትሑታን ፡ ወምሉኃን ። ከመ ፡ ዐቃብ ፡ ምልኁት ፡ (ዘኍልቍ ፳፪ ፡ ፳፫ ። ስንክ ፡ የካ ፲፫ ። ኢሳ ፲፰ ፡ ፯ ። ፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፮) ።

**ምልኅት** ፤ መምዘዝ ፤ መንቀል ፤ አንቀሳቀስ ፡ ንቀላ ።

**ተማልኀ** ፤ ተማዘዘ ፡ የሰይፍ ፡ የበትር ።

**አስተማልኀ** ፤ አማዘዘ ፤ አናቀለ ። ወይን ፡ ያስተማልኆሙ ፡ መጣብሒሆሙ ፡ (ሶዝ፪ ፡ ፳፰) ።

**መለጠ** ፤ (መሊጥ ። ዐረ ፡ መሊጠ ። ዕብ ፡ ማራጥ ። ሱር ፡ ምራጥ) ፤ በቁሙ ፤ ላጠ ፡ ቀረፈ ፡ ገጠበ ፡ ነጨ ፡ ላጨ ፡ የቁርበት ፡ የጠጕር ። ስሐጸ ኀና ፡ ቀረፈን ፡ ነጸየን ፡ እይ ። መሰጠቶ ፡ እግሮ ፡ ለበለዓም ፡ (ዘኍ ፳፪ ፡ ፳፭) ። ሞለጨ ፡ ሙልጭ ፡ አለ ፤ አመለጠ ። ሻለጠ ፡ ሻላጣ ፡ ኸነ ፡ ከሙላጥና ፡ ከመመለጥ ፡ ብዛት ።

**አምለጠ** ( (ዕብ ፡ ሂማሌጥ) ፤ አስመለጠ ፡ አመለጠ ፤ አዳነ ፡ አወጣ ፤ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ሙልጭልጭ ፡ ከማለት ፡ የተነሣ ። መሠጠን ፡ እይ ።

**ተመልጠ** ፤ ተመለጠ ፤ ተመላለጠ ፤ ምልጥልጥ ፡ አለ ፤ ተላጠ ፡ ተገጠበ ። ተመልጠ ፡ ርእሱ ። ወተመልጠ ፡ ሥሉ ፡ መትከፍት ፡ (ዘሌ ፲፫ ፡ ፵ ፡ ፵፩ ። ሕዝ ፳፱ ፡ ፲፰) ።

**ምሉጥ** ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ልጥ) ፤ የተመለጠ ፡ ምልጥ ፡ መላጣ ፡ በራ ፡ ቡሓ ፡ ገጣባ ፡ ንክ ፤ የዳን ፡ ያመለጠ ፡ ሙላጭ ፡ ሻላጣ ።

**ጸምላጥ** ፤ ጨምጫማ ፡ በልጣጣ ፡ ማዝ ፡ የያዘው ፡ ዐይን ፡ ቅንድቡ ፡ የተመለጠ ፡ የተገለበጠ ፡ በውስጡ ፡ የጕሽ ፡ ጠጕር ፡ የሚወጣበት ። ጸ ፡ ከነጸየና ፡ ከሐሐጸ ፡ መጥቶ ፡ ተደርቧል ። ዘጸምላጥ ፡ አዕይንቲሁ ። ጸምላጠ ፡ ዐይን ፡ (ዘሌ ፳፩ ፡ ፳ ። ቀሌ) ።

**መሊጥ** ፤ ዐጥፍ ፡ ሌጦ ፡ ዘብድው ፡ ጠጕር ፡ የሌለው ፡ የላይ ፡ ልብስ ። እስከ ፡ ኢኀደጉ ፡ መሊጦሁ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ።

**መሊጦን** ፤ (ዕብ ፡ ሜሌጥ ፤ ምሰሶ ፡ በላ ፤ ጋይም ፡ ሠረገላ) ፤ የኪሩቤል ፡ ስም ፡ ከርበቶቱ ፡ እንስሳ ፡ አንዱ ። ዐምዳዊ ፡ ዘዐምድ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ መላጥነት ፡ ሳይቀር ፡ ተሸክሚነትን ፡ ያሳያል ። በሬ ፡ መሬ ፡ መሊጦን ፡ (መዋሥ) ።

**ምልጣን** ፤—በቁሙ ፤—ለጢን ፡ ለጠነ ።

**መለየ** ፤ (ሌለየ ፤ መሰወ) ፤ መላ ፡ መታ ፡ በመላ ፡ ዐወቀ ፡ መለኛ ፡ ኾነ ። (ተረት) ፤ ከጕል ፡ ጥንቁላ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መላ ፡ አፈረሰ ፤ ፈታ ፡ ለያየ ፡ አውሰቀሰቀ ። አሻሻ ፡ አቀሰጠ ፡ አፈሰሰ ፤ ምስጢሩ ፡ ከማፍረስ ፡ ይገባል ። ማስነቱ ፡ ከመሰወና ፡ ከሌለየ ፡ የተደቀለ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የኹሉቱንም ፡ ስልት ፡ ያሳያል ። ፪ኛም ፡ በመላዊ ፡ ፈንታ ፡ መላዩ ፤ በመላይ ፡ ፈንታ ፡ መላዊ ፡ ይባላል ።

**መላዩ** ፤ (ዩት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤ መለኛ ፡ መላ ፡ ዐዋቂ ። የሚያፈርስ ፡ የሚለያይ ፤ አቅላጭ ፡ አፍሳሽ ። መላዩ(ላዊ) ፡ ኀዳውንት ፡ አድማስ ፡ (ስንክ ፡ ኀዳ፲፱) ።

**መሊክ** ፤ ከት ፤ (መለከ ፡ ይመልክ ፡ ይምልክ ። ዐረ ፡ መለከ ። ዕብ ፡ ማላኽ ። ሱር ፡ ምላኽ) ፤ መምለክ ፤ ማሸነፍ ፡ መግዛት ፡ መያዝ ፡ መውረስ ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግ ። ዘይመልክ ፡ ሀገረ ። እለ ፡ ይመልክዋ ፡ ለየብስ ። የሐናን ፡ ወእሊአሁ ፡ ተጻወኑ ፡ ኀበ ፡ ቅድስ ፡ ወመለክዋ ። ለዛቲ ፡ ምድር ፡ ከመ ፡ ይምልክዋ ፡ ለዓለም ። ይሁቡ ፡ ሥሉ ፡ ዘይመልኩ ፡ ለነዳያን ፡ (ምሳ ፲፯ ፡ ፴፱ ። ሔኖ ፳፪ ፡ ፱ ። ዮሴፍ ። ዘፍ ፶፰ ፡ ፬ ። ኢፌ ፡ ተ፲፫) ።

—፤ መንገሥ ፡ መሠልጠን ፡ ጌታ ፡ ዳኛ ፡ ሠሬ ፡ ቀሬ ፡ መሬ ፡ ጠባቂ ፡ መኾን ። ይመልከ ፡ እቡድ ። መለከ ፡ ላዕሌነ ፡ ሀኬት ። ዘየዐቢ ፡ ብርሃን ፡ ከመ ፡ ይምልክ ፡ መዓልተ ። እንስ ፡ ኢይመልክ ፡ ለክሙ ፡ ወወልድየኒ ፤ እግዚ ፡ ይመልክ ፡ ለክሙ ። መለከ ፡ እምታሕቴሁ ፡ ለንጉሥ ፡ (ምሳ ፲፰ ፡ ፱ ። ኢፌ ፡ ድ፳፱ ። ዘፍ ፩ ፡ ፲፮ ። መሳ ፰ ፡ ፳፫ ። አዋል) ። ዘይክል ፡ ዘይእኅዝ ፡ እግዚእ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ፡ (ኢዮ ፲፭ ፡ ፳፭ ። ሚልጽ ፡ ፱ ። ዘካጽ ፡ ፫) ።

**መላኪ** ፤ (ኪት ፡ ክያን ፡ ያት) ፤ የመለከ ፡ የሚመልክ ፤ ገዥ ፡ ሠራዊ ፡ መጋቢ ፤ ነጋሚ ፡ ወራሲ ፤ ባለቤት ፡ ጌታ ፤ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፱ ። ፴፩ ፡ ፴፯ ። ኢፌ ፡ ተ፲፱) ። እግዚ ፡ መላኬ ፡ ነፍሳቲነ ፡ ወፈጣሬሃ ፡ ውስተ ፡ ሥጋነ ። እግዚ ፡ መላኬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ። ክርስቶስ ፡ መላኬ ፡ ሥሉ ፡ አጽናፍ ። በሥረ ፡ መላኪ ፡ (ዮሴፍ ። መቃ ፡ ገ፲ ። ስንክ ፡ መስ፱ ። ድጓ) ።

**መለክ** ፤ አው ፡ መልክ ፤ (ብ ፡ መለከን ፤ አው ፡ አምላክ ፤ አማልክት ። ዐረ ፡ መሊክ ። ዕብ ፡ ሜሌኽ ። ሱር ፡ ማልክ) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፡ የመለከ ፡ መላኪ ፡ ንጉሥ ፡ ባለዘውድ ። መሰከ ፡ ሰገድ ። መልክ ፡ ጼዴቅ ፡ (ታሪ ፡ ነገ ። ዕብ፯ ፡ ፩ ፡ ፪) ።

**መለከዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ ንጉሣዊ ፡ የንጉሥ ፡ ወገን ፡ ንጉሥ ፡ የሾመው ፡ ሬስ ፡ ደጃዝማች ፤ ባለንቢልታ ፡ ባለመለክት ፡ መልክኛ ፡ ከኢደሬ ፡ እስከ ፡ ንጉሥ ፡ ያለው ፡ ሹም ፡ ኹሉ ። የጉባኤ ፡ ስም ፡ ማኅበረ ፡ ኬልቂዶን ፤ ንጉሥ ፡ ያቆመው ፡ የሰበሰበው ፡ የንጉሡን ፡ ፈቃድ ፡ የሚፈጽም ። ወሰስመ ፡ ንጉሥ ፡ ሰመዮሙ ፡ መለካውያነ ፤ ፈጻምያነ ፡ ፈቃደ ፡ ንጉሥ ፡ ብሂል ። ወተርጐምዎ ፡ ኀበ ፡ ዐረቢ ፡ መለካውያን ፡ ወንስጥሮሳውያን ፡ (ፊሀሪ ። ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ።

**አምለከ** ፤ አስመለከ ፡ አስገዛ ፤ አስያራጊ ። አነገሠ ፡ አጌተየ ፡ አሠለጠነ ፡ ሌላውን ፡ በሌላ ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ አድራጊ ። ኢያኴንንዎሙ ፡ ወኢያመልክዎሙ ፡ (ሚራ ፴፫ ፡ ፴፫) ።

—፤ አመለከ ፡ አምላክ ፡ አደረገ ፡ አምላኬ ፡ አምላኩ ፡ አለ ፡ ፈጣሪውን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ። እስመ ፡ ጽሑፍ ፡ ለእግዚ ፡ አምላክከ ፡ ትስግድ ፡ ወኪያሁ ፡ ባሕቲቶ ፡ ታምልክ ። ከመ ፡ ታምልኩ ፡ ዕፀ ፡ ወእብነ ። እለ ፡ ያመልኩ ፡ ጣዖተ ፡ (ማቴ፬ ፡ ፲ ። ሕዝ፳ ፡ ፴፪ ። ራእ፱ ፡ ፳፰) ።

—፤ አክበረ ፡ አመሰገነ ፡ የአምላክ ፡ ወገን ፡ አደረገ ። ሀለዉ ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ ለዕፀ ፡ ታመልኩ ፡ ወለዕፀ ፡ በዓለ ፡ ትገብሩ ፡ ኢቀደሱ ፡ ደሙ ፡ ክቡር ፡ ለዕፀ ፡ መስቀል ፡ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ንሕነ ፡ ናመልኮ ፡ ናከብሮ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ድጓ) ።

**አምልኮ** ፤ በቁሙ ፡ ሃይማኖት ፡ ማምለክ ፡ ማስመለክ ፡ አምላክ ፡ ማድረግ ። አትናቴዎስ ፡ ስሙይ ፡ በሥነ ፡ አምልኮ ፡ (ቁር ፡ እስት) ።

**መምለክ** ፤ ያመለከ ፡ የሚያመልክ ፡ የሚያስመልክ ፡ አምላኪ ፡ አስመላኪ ። መምለኬ ፡ እግዚ ። መምለኪያነ ፡ ጣዖት ፡ (ቂድር ። በንክ) ። ባሕታዊ ፡ መናኒ ፡ መነኵሴ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋውን ፡ የሚገዛ ፡ ነፍሱን ፡ ለማዜር ፡ ሥጋውን ፡ ለማኅበር ፡ የሚያስገዛ ። መምለኪ ፡ ፍጹም ፡ መምለኪ ፡ ማእከላዊ ፡ መምለኪ ፡ ወጣኒ ፡ (ፊልክ ፡ ፴) ።

**አምላክ** ፤ (ብ ፡ አማልክት) ፤ በቁሙ ፡ ፈጣሪ ፡ ገዥ ፡ ፈራጅ ፡ ዳኛ ፡ ሠሪ ፡ ቀጭ ፡ ፈላጭ ፡ ቈራጭ ፡ መልአክ ፡ ጣዖት ። አምላክ ፡ የመለከ ፡ ብዝር ፡ ሲኾን ፡ ላንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ መነገሩ ፡ በልማድ ፡ አፈታት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሰዋስው ፡ ሕግ ፡ አይደለም ፤ አማልክትም ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ኤሎሄን ፡ እዩ ። እወ ፡ እግዚእ ፡ አምላክ ፡ ዘሉ ። ወአምላክ ፡ ዓለም ። አምላኪየ ፡ ወአምላክክሙ ። ረሰይኩከ ፡ አምላከ ፡ ለፈርዖን ። ከሞስ ፡ አምላክክ ፡ (ቅዳ ፡ ኢዲ ። ሐዋ፲ ፡ ፫ ። ዮሐ፳ ፡ ፲፯ ። ዘፀ፯ ፡ ፩ ። መሳ፲፩ ፡ ፳፬) ። አምላክ ፡ አማልክት ። ማኅበረ ፡ አማልክት ፡ አንበ ፡ እቤ ፡ አማልክት ፡ አንትሙ ። ይሰግዱ ፡ ኀበ ፡ አማልክት ። ኢትትልዉ ፡ አማልክተ ፡ (መዝ ፡ ፹፩ ። ፺፮ ። ዘፀ፳፫ ፡ ፳ ። ዘሌ፲፱ ፡ ፬) ።

**አምላክና** ፤ አምላክነት ፡ አምላክ ፡ መኾን ። እንሰየ ፡ ለአዳም ፡ አምላክና ። ንብሎ ፡ ሰብአ ፡ በሰብእናሁ ፡ ወአምላክ ፡ በአምላክናሁ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፫ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**አምላካዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ ያምላክ ፡ ወገን ፡ ገንዘብ ፡ አምላክነት ፡ አምላካም ፡ ባላምላክ ። ፈቃድ ፡ አምላካዊ ። ጳውሎስ ፡ አምላካዊ ። ንድገ ፡ ጽዋዒሆሙ ፡ አምላካዊተ ። መጻሕፍት ፡ እምላካውያት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፬ ፡ ፳ ። ፲ ፡ ፩ ። ፊልክ ፡ ፳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፬) ።

**ተመልከ** ፤ ተመለከ ፡ ተገዛ ። ዘኢይትመለክ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፱ ፡ ፫) ።

—፤ አምላክ ፡ ኾነ ፡ አምላክ ፡ ተባለ ። በተመልኮ ፡ ፈንታ ፡ ተአምልኮ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አምላክ ፡ ዘተሰብአ ፡ ዐሚ ፡ መሐያው ፡ ዘተአምለከ ። ሲይሰብሕ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚ ፡ ስቡሕ ፡ ወይትአምለክ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚ ፡ አምላክ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ምሉክ** ፤ (ካን ፡ ካት ፡ ካት) ፤ የተመለከ ፡ ምልክ ፡ የተገዛ ፡ ግዛ ፡ እጅ ፡ ፀደር ። ከመ ፡ ይኩን ፡ ምሉከ ፡ ለተአማኒ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፱ ፡ ፫) ።

—፤ የመለከ ፤ የነገሠ ፡ ንጉሥ ፡ ሥሉጥ ፡ ሥልጡን ፡ ባለ ምሉ ፡ ሥልጣን ። በትእዛዘሙ ፡ ለምሉካን ፡ ነገሥት ። ዘቲ ፡ ክብርት ፡ ወምልክት ፡ ማኅበረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፱ ፡ ፫) ።

**ምልክት** ፤ መምለክ ፡ መግዛት ፡ መመለክ ፡ መገዛት ፡ አገዛዝ ፡ አምላክ ፡ መኾን ። ምልክ ፡ ግዛት ፡ ርስት ፡ ጕልት ፡ ድርሻ ፡ ይዞታ ። እመ ፡ አገበርዎ ፡ ከመ ፡ ይትዐሰብ ፡ ምልክተ ፡ ካልኡ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፰) ።

**ምልክና** ፤ መልክኛነት ፡ ገዥነት ፡ ጌትነት ፡ ሹመት ፡ አገዛዝ ፡ ግዛት ፡ ጥበቃ ። ቅንየትከ ፡ ወምልክናከ ፡ ሹሎ ። ፈጠርነ ፡ ዓለመ ፡ ከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ምልክናነ ፡ ወዕበየ ፡ ኀይልነ ። ዘታሕተ ፡ ምልክናሁ ። አሰስሎተ ፡ ምልክናሁ ፡ (ጥበ፲ ፡ ፲፱ ። ቀሌ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱) ።

**ትምልክት** ፤ ተገዥነት ፡ አገዛዝ ፡ ሞግዚና ። አውፃእኮሙ ፡ ለእስራኤል ፡ እምትምልክተ ፡ ፈርዖን ፡ (ዲድ ፡ ፴፰) ።

**ምልክ** ፤ በቁሙ ፡ ምሉክ ፡ ግዙ ፡ ርስት ፡ ቦታ ፡ የተያዘ ፡ የተረከበ ፡ እጅ ፡ ፀደር ።

**ምልክኤል** ፤ (ምሉክ ፡ ኤል) ፤ ስመ ፡ ካህን ፡ ዐቢይ ፡ መጋቤ ፡ መፀው ፡ ክራሙ ፡ መራሕያን ፡ አንዱ ፡ (ሔኖ ፡ ፹፪) ።

**መለኩት** ፤ (ዐረ ፡ መለኩት ። ዕብ ፡ ማልኩት ። ሱር ፡ ማልኩታ) ፤ ግዛት ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ። ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሓውርት ፡ መለኩቱ ። መለኩትከ ፡ ወመንግሥትከ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ፡ (መዝ ፡ ፻፪ ። ሔኖ፹፬ ፡ ፪) ።

**መለኮት** ፡ (ዕብ ፡ ኤል ፤ ኤሎሂ ። ሱር ፡ ኤላሃ ። ዐረ ፡ ኢላህ) ፤ በቁሙ ፡ ልዩ ፡ ክቡር ፡ ስም ፡ ከፈጣሪ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ፍጡር ፡ የማይጠራበት ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ባሕርያዊ ፡ ንጉሥ ፡ ጥንትና ፡ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ ዘላለማዊ ፡ ገዥ ፡ ገዛሪ ፡ ኵሉ ፡ መላኬ ፡ ኵሉ ፡ ምሉእ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከባሕርይ ፡ ከግብር ፡ የሚወጣ ፡ ባሕርያዊ ፡ ስምና ፡ ቅጽል ፡ የአካልን ፡ ባለቤትነት ፡ ልኩንና ፡ መልኩን ፡ ግብሩንም ፡ እንደ ፡ መስታዎት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያሳያል ። መለኮት ፡ ስም ፡ ዘአልቦ ፡ ብዕሪና ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፱) ። አኮ ፡ ዘቦቱ ፡ ለመኮት ፡ ክበብ ፡ ከመ ፡ ፀሓይ ፡ ወወርኅ ፡ ወዐቅም ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ አላ ፡ ምሉእ ፡ ውእቱ ፡ በዙሉሂ ፡ ወመለኮትስ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ (ቅዳ ሕር) ። ስለ ፡ ሥጋዊም ፡ ወተወልደ ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ። ክቡር ፡ አንተ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ወክቡር ፡ ዘቀደስከ ፡ ደመ ፡ መለኮት ፡ ቃል ። መልዕልተ ፡ ዝንቱ ፡ መስቀል ፡ አመ ፡ ሞተ ፡ መለኮት ፡ በትስብእቱ ። እስመ ፡ እምንእስከ ፡ ልዩን ፡ መፍቀሬ ፡ ነገር ፡ አንተ ፡ ክሬ

ልክ ፡ ኀበ ፡ ክልኤ ፡ ሥግወ ፡ መለኮተ ፡ ቢል ፡ ፍችው ፡ አምላክ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንዱን ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ያሳያል ።

**መለኮት ፤ (ዕብ ፡ ኤላሁት ። ዐረ ፡ ላሁት ። ጽር ፡ ቲዎቲስ ። ሮማይ ፡ ዲዊኒታስ) ፤** አምላክነት ፡ ፈጣሪነት ፤ እምላክ ፡ መኾን ፤ ፈጣሪ ፡ መኾን ፤ መደም ፡ የእምላክ ፡ ባሕርይ ፤ ጠባዩ ፡ ኹንታው ፤ ቅድስት ፡ ሥላሴን ፡ የሚያዋሕድ ፡ የሚያስተባብር ፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ የሚያሰኝ ። ፈጥሮ ፡ መግዛትና ፡ መፍጠር ፡ ማስገኘት ፡ የባሕርያቸው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ባሕርያቸው ፡ በግብር ፡ በሙ ፡ መለኮት ፡ ይባላል ፤ እንትና ፡ መኾንም ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ ትርጓሜያቸው ፡ ባሕርይ ፡ ከማለት ፡ ይገባል ። ምስጢራተ ፡ መለኮትከ ፡፡ ኢይደሉኬ ፡ ናስተማስል ፡ መለኮቶ ፡፡ ይሜስሉ ፡ በአካላት ፡ ወይትዋሐዱ ፡ በመለኮት ፡፡ መለኮትኒ ፡ ይትዐወቅ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ያገብር ፡ ቅድስተ ፡ ሥላሴ ፡ (ጥበ፲፱ ፡ ፳ ። ግብ፲፯ ፡ ፳፱ ። ሃይ ፡ አበ) ። ዳግመኛም ፡ ያካልና ፡ የግብር ፡ የስም ፡ መሠረት ፡ የአንድነትና ፡ የሦስትነት ፡ የነገር ፡ ኹሉ ፡ ጥንት ፡ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ባሕርይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከዚህ ፡ ከአንዱ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ነሥተው ፡ ሦስቱ ፡ ኹሉ ፡ ህላዌ ፡ ህላዌ ፡ እንዲባሉ ፡ መለኮት ፡ መለኮት ፡ ይባላሉ ፤ እምላክ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ምስጢሩ ፡ ከ፪ኛው ፡ ፍች ፡ ይገባል ። ቦሙ ፡ አእምሮ ፡ ወእትአመን ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ መለኮት ፡ ወህላዌ ፡ ወኢሙ ፤ እብል ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ መለኮት ፤ ወለለ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምአካላተ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ይበጽሕ ፡ ፍጹመ ፡ መለኮተ ፡ ምስለ ፡ ዘዚአሁ ፡ አካል ፡ ወስም ፤ ወዝኤ ፡ ዘመለኮተ ፡ ዚአሁ ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ ባስ ፡ ጸክ) ። ሦስተኛም ፤ አካላት ፡ ከባሕርያቸው ፡ ከመለኮት ፡ ስምን ፡ የሚነሡ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሊቃውንት ፡ ኹሉ ፡ በየድርሳናቸው ፡ አካል ፡ ሲሉ ፡ መለኮት ፡ ይላሉ ። መሐልቦ ፡ ኄውሥ ፡ ውስተ ፡ መለኮቱ ፤ አላ ፡ ሥላሴ ፡ ፍጽምት ፡፡ እስመ ፡ ሠለስቱ ፡ ኵሉቄ ፡ መለኮቱ ፡፡ ትሥልስተ ፡ መለኮት ፡ (ተረ ፡ ቄር ፡ ኤጲ ፲፯ ። ባዊ፲፱ ። መጽ ፡ ምስ) ። «ማስረጃ ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ባሕርዩም ፡ ሰው ፡ ኹኗል ፤ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ ወልድ ፡ ቅብ ፡ ለማለት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴን ፡ የብዕልና ፡ የባሕርይ ፡ አንድነት ፡ በሌላቸው ፡ በ፫ ፡ ባለጠጎች ፡ መመሰለው ፡ ፫ ፡ አካል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ፫ ፡ መለኮት ፡ ፫ ፡ ልዩ ፡ አማልክት ፡ በለሚሉ ፡ ስለ ፡ ሐዲስ ፡ ክሮች ፡ ባህልና ፡ አፈታት ። ሥሩ ፡ አንድ ፡ ለኾነ ፡ ላንድ ፡ በቀል ፡ ዛፍ ፡ ከላይ ፡ ሦስት ፡ አዕጹቅ ፡ ቢኖሩት ፡ ሥሩና ፡ ጕንዱ ፡ ወይም ፡ ዛፍነቱ ፡ በአዕጹቅ ፡ ምክንያት ፡ ሦስት ፡ ሊባልና ፡ ከሦስት ፡ ሊከፈል ፡ እንዳይቻል ። ደግሞም ፡ ላንድ ፡ ምንጭ ፡ ውሃ ፡ ከታች ፡ ሦስት ፡ መትረብ ፡ ቢኖረው ፤ ውሃው ፡ በሦስት ፡ መትረብ ፡ ተከፍሎ ፡ ቢኼድ ፡ ነቁ ፡ በመትረቦቹ ፡ ምክንያት ፡ ሦስት ፡ ሊባልና ፡ ከሦስት ፡ ሊከፈል ፡ እንዳይቻል ፡ መለኮትም ፡ ለሦስቱ ፡ አካላት ፡ እንደ ፡ ሥር ፡ እንደ ፡ ነቅ ፡ ነውና ፤ በአሐዱነቱ ፡ አካላትን ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ ቢያሰኝ ፡ እንጂ ፡ አካላት ፡ በሦስትነታቸው ፡ እሱን ፡ አንዱን ፡ ነቅ ፡ ሦስት ፡ መለኮት ፡ ሊያሰኙት ፤ ከሦስት ፡ ሊከፍሉት ፡ አይቻልም ። እንዘ ፡ በፀምረተ ፡ አሐዱ ፡ መለኮት ፤ ዘውእቱ ፡ አሐዱ ፡ ብርሃን ፡ ዘይሠርቅ ፡ እምኔሁ ፡ ሥላሴ ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ አግና) ። አካላትን ፡ በባሕርያቸው ፡ በመለኮት ፡ አሐዱ ፡ ማለት ፤ መለኮትን ፡ እንደ ፡ ቢዘኖች ፡ ባህል ፡ ዐጥር ፡ መልዕ ፡ በአካል ፡ ሥወስት ፡ አያሰኝም ፤ ፭ነቱ ፡ ይከለክላል ። ሦስት ፡ ዕጽቅ ፡ ያለው ፡ ዛፍ ፡ ባለሦስት ፡ ዕጽቅ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ ጕንዱ ፡ በዕጽቅ ፡ ሠወስት ፡ እንዳይባል ፤ ሦስት ፡ መትረብ ፡ ያለው ፡ ምንጭ ፡ ባለሦስት ፡ መትረብ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ ነቁ ፡ በመትረብ ፡ ሠወስት ፡ እንዳይባል ፤ መለኮትም ፡ ለሦስቱ ፡ አካላት ፡ ጕንዳቸው ፡ ነቃቸው ፡ አስተጋባኢያቸው ፡ ነውና ፡ ባሕርይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ባለሦስት ፡ አካል ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ በአካል ፡ ሠወስት ፡ አይባልም ፤ ከአሐዱ ፡ በቀር ፡ ሠለስቱ ፡ አይነካውም ፤ አይቀርበውም ፤ ቅጽል ፡ አይኾነውም ። እመሰ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ መለኮት ፡ ተዋሕዶቶሙ ፡ ውእቱ ፡ መለኮት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፤ ወበዝንቱ ፡ አእመርነ ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ መለኮት ፡ ዘቦቱ ፡ ሠለስቱ ፡ አካላት ፡፡ ንሕነሰ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ንሰግድ ፡ ለአሐዱ ፡ አምላክ ፡ ባሕቲቱ ፤ ወንትአመን ፡ በአሐዱ ፡ መለኮት ፡ ዘሠለስቱ ፡ አካላት ፤ ወኢንበውእ ፡ ኀበ ፡ ክፍለ ፡ መለኮት ፡ ወመንግሥት ፤ ወሶበሂ ፡ ንሬሲ ፡ ቅድስተ ፡ ሥላሴ ፡ ፍሉጣነ ፡ መለኮት ፡ ዘከመ ፡ አካላቲሆሙ ፡ ንትአመን ፡ እምነተ ፡ ሰይጣናዊ ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ አትና ። ዲዮና ፡ ጸክ) ። የባሕርይንና ፡ የህላዌን ፡ የጠባይዕን ፡ ፍች ፡ በየቦታው ፡ እይ ።

**መለኮታዊ ፤** በቁሙ ፡ ባሕርያዊ ፤ አምላክነት ፡ ያለው ፡ የእምላክ ፡ የመለኮት ። መለኮታዊ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘለብሰ ፡ ትስብእተ ፡፡ ዝንቱ ፡ ኅብስት ፡ መለኮታዊ ፡፡ ትምህርታት ፡ መለኮታውያት ፡ (ስንክ ። አርጋ ። ቅዳ ። ቄር) ።

**መለከት ፤** በቁሙ ፤ የመንግሥትና ፡ የሹመት ፡ ምልክት ፡ ነጋሪት ፡ መኳንንት ፡ የሚያስነፉት ። ቡቅኝና ፡ መጥቅዕን ፡ እይ ፡ ቀንዳ ፡ መለከት ፡ እንዲሉ ።



መለከት ።

**መልከተ ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤** አመለከተ ፡ አሳየ ፡ ምልክት ፡ ጣፈ ፡ አደረገ ። መለከት ፡ ንፋ ፡ አስነፋኸ ።

**ተመልከተ ፤** ተመለከተ ፡ ባለምልክት ፡ ኾነ ፡ ለራሱ ። ጠበቀ ፡ አስተዋለ ፡ ሌላውን ። ወበእንተ ፡ ብዝኃ ፡ ሰዋእያን ፡ ወወባእያን ፡ ኄደገ ፡ ተመልክቶ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ኢያእምር ፡ እኩያነ ፡ እምኔሆሙ ፡ (ፊልክ ፡ ፶፯) ።

**ምልክት ፤** በቁሙ ፤ የዜማ ፡ የንባብ ፤ የትርጓሜ ፡ የስም ፡ የቍጥር ፤ በፊደል ፡ በነቍጣ ፡ የሚደረግ ። ወጠኑ ፡ አውፅአ ፡ ምልክተ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ። ድጓን ፡ እይ ።

**ሞሎክ**፤(ጽር፡ሞሎኽ። ዕብ፡ሞሌኽ)፤ የደቂቀ፡ዓሞን፡ጣዖት፤ እስራኤል፡ያመልኩት፡የነበረ፤ ፊቱ፡የጥጃ፡እጁና፡ግንዱ፡የሰው፤ እጆቹ፡ሕፃን፡ለመቀበል፡የተዘረጉ፤ በስተፊቱና፡በአንጻሩ፡ወደ፡ምሥራቅ፡ወገን፡በሰባቱ፡ሰማያት፡አምሳል፡፯፡ቅጥርና፡፯፡ደጃፍ፡ያለው። መላኪ፡መሬ፡ጠባቂ፡ንጉሥ፡ማለት፡ነው፡(ዘሌ፲፰፡፳፩። ፳፡፪፡፬። ግብ፯፡፵፫)። ያምልኩቱም፡ሥራት፤ ስንዴሌና፡ዘይት፡ለሚያቀርብ፡፩ኛው፡በር፤ ርግብና፡ዋኖስ፡ለሚያቀርብ፡፪ኛው፤ በግ፡ለሚያቀርብ፡፫ኛው፤ ፍየል፡ለሚያቀርብ፡፬ኛው፤ ጥጃ፡ለሚያቀርብ፡፭ኛው፤ በሬ፡ለሚያቀርብ፡፮ኛው፡ይከፈትለታል፤ ልጁን፡ለሚያቀርብ፡ግን፡፯ቱ፡ኹሉ፡ተከፍቶለት፡ለጣዖቱ፡እጅ፡በጅ፡ይሰጣል። ከዚያ፡በኋላ፡ክህናቱ፡ሕፃኑን፡ከሞሎኽ፡እጆች፡ተቀብለው፡በ፬፡ወገን፡እሳት፡ያነዱና፡ከማኽል፡አግብተው፡ተወክፍ፡ለን፡እያሉ፡ያሳልፉታል፤ ከዚህ፡የቀረውን፡ሐተታና፡ታሪክ፡በጣፈጥና፡በገሃነም፡ፍች፡ተመልከት።

**መሎኬ**፤(ጽር፡ማላኺ፤ ሞሎኺ። ዐረ፡ምሉኅያ፤ ምሉኅዩት)፤ ሙሉክዬ፡ጥሩ፡ሐምል፡የወጥ፡ቅጠል፤ ለግላጋ፡ጠውላጋ፤ እንደ፡ልቅና፡እንደ፡ሳማ፡የሚማልግ፡የሚያምለገልግ፤ ለንጉሥ፡የሚገባ፡የንጉሥ፡ወጥ፡ማለት፡ነው፤ ባንዱራውን፡ያፁን፡ወጥ፡እንዲሉት። እንዳረቡ፡ግን፡በመልኑ፡ዘይብ፡ሲፈቱት፡የሚንቀልና፡የሚላስስ፡ያሰኛል። ወይጸመሒ፡ከመ፡መሎኬ፡በውስተ፡ሐሩር። ውዕየ፡በነደ፡ቃሉ፡ከመ፡እርየተ፡ሐምሰ፡መሎኬ፡(ኢዮ፴፱፡፳፱። ስንክ፡የካ፲፫። መጽ፡ምስ)። ባለብሉዮች፡ግን፡ሐመድማይ፡ይሉታል፤ ፍችው፡አይደለም።

**መልክእ**፤—መልክ፡ፊት፤—ለኪእ፡ለክአ።

**ምልክኤል**፤—ምልክ፡ኤል፤—መሊክ፡መለከ።

**መለለ**፤(ዕብ፡ማላል፤ ዐሽ፡ፈለፈለ፤ ሳበ፡መዘዘ፤ አለ፡ተናገረ፥ቃል፡አወጣ)፤ ገቢርና፡ዐጉል፤ መለመለ፡ላጠ፡ላገ፤ መለሎ፡አደረገ፡ዐረቀ፡አስተካከለ። መለል፡አለ፤ ረዘመ፡መለሎ፡ኾነ፤ የጉልበት፡የፊትል፡ለሰውም፡ይኾናል።(የስድብ፡ግጥም)፤ እየው፡መለል፡ብሎ፤ የወንዝ፡ዳር፡ጕሎ፤ ቂል፡ነው፡የገዛም፡ብሎ። ሰላላ፡መላላ፡ዱርና፡ማማ፡ፈትላ፡ሸማኔ፡አስቸገረች፡ወይዘሮ፡ውንዲላ። ሜላትን፡እይ፤ የዚህ፡ዘር፡ነው።

**መላልኤል**፤(ዕብ፡ማሃላልኤል)፤ የሰው፡ስም፤ ፭ኛው፡ትውልድ፡ከአዳም፤ ቀዳማዊ፡በኵረ፡አምላኪ፤ ስብሐተ፡አምላክ፤ ዘይሴብሕ፡አምላክ፡(ዘፍ፭፡፲፪)።

**መለምልም**፤—ለስላሳ፡ርጥብ፤—ለምለመ።

**መለንስ**፤(ጽር፡ሜላንሲዎን)፤ ጥቍር፡ከሙን፡ኑግ፡የሚመስል፡(ኢሳ፳፰፡፳፭፡፳፯)።

—፤ ኑግ፡መጭ፡የከሙን፡ዐይነት። ቅብዐ፡መለንስ፤ ኅብስተ፡መለንስ፤ ቅብኑግ፡የኑግ፡ልጥልጥ፡ቂጣ፡ጭፍቆ፡(ገድ፡ተክ)፡ከሙንን፡እይ።

**ሜላንትራ**፤—ጸፍጸፍ፤—ሜላትራ።

(ላ) **መልዐ**፤—መላ፡ተመላ፤—መሊእ፡መልአ።

(ጥ) **መልዖ**፤ ዖት፤(መልዐ፡ይሜልዕ፡ይመልዕ። ዐረ፡መለዐ)፤ መንገድ፡መገሥገሥ፤ መምራት፡ፈጥኖ፡መንሣት፡እግርን፡መንቀል፡በችኰላ፡መኼድ፡መሬመድ። መልዐ፡ንሕር። መልዐ፡ፍኖተከ። ቅድሜየ፡እሜልዐ፡ወድኅሬየ፡እደግን። ደመ፡ትዝምድክን፡እምትካት፡ዘመንግሥት፡ወይሜልዕኒ፡ዘእምይእዜ፡(ሄኖ፡፳፯፡፲፩። ስንክ፡መስ፲። ፊልጵ፫፡፲፬። ቂር)። አንዳንድ፡መጣፍ፡በመልዐ፡ፈንታ፡አምልዐ፡አመልዐ፡ይላል፤ ስሕተት፡ነው። ገብኡ፡ድኅሬሆሙ፡ወኢያመልዑ፡ቅድሜሆሙ። ርቱዓን፡የሐውሩ፡ቦቱ፡ወያሜልዑ፡ቅድመ። ወዘንተ፡ብሂሎ፡አመልዐ፡ቅድመ፡ወዐርገ፡ኢየሩሳሌም፡(ኤር፯፡፳፬። ሚክ፪፡፲፫። ሉቃ፲፱፡፳፰)።

**አመልዐ**፤ አስኬደ፡አስቸኰለ፡አንሣሣ።

**ተማልዐ**፤ ተማላ፡ወሰደ፤ ይዞ፡ኼደ። ዲይብሎስ፡ተማልዖሙ፡ለአዳም፡ወለሔዋን፡ውስተ፡ስሕተተ፡ዚአሁ፡እንዘ፡የኀይጦሙ። ወእምኔሆሙ፡ተዐቀቡ፡ከመ፡ኢይትማልዑክሙ፡ምስሌሆሙ፡ውስተ፡ገሃነም። ተማልዒ፡ሊተ፡ምስሌኪ፡ፍተ፡ኅብስት፡(መቃ፡ገ፰። ቀሌ። ፫ነገ፡፲፯፡፲፩)።

**አስተማልዐ**፤ አዋሰደ፡አወሳሰደ፤ አናዳ፡አካኼደ። ማእዜ፡ይሠርቅ፡ወርኅ፡ንምላዕ፡ወናስተማልዕ፡(ዓሞ፰፡፭)።

**መላጺ**፤—ምላጭ፤—ላጸዮ፡ላጸየ።

**መለጸ**፤(መሊጽ። ዕብ፡ማሎጽ፤ ሂማሌጽ)፤ ጣፈጠ፡እጅ፡አስመጠጠ፤ ላመ፡ጣመ፡ደስ፡አሰኘ፤ የምግብ፡ያንደበት፡የቃል። ጥዑመ፡ልሳን፡እንዲሉ። ለመጸን፡እይ፤ የዚህ፡ጎር፡ነው።

**ምላጺ**፤ ጺ፤(ብ፡ምላጽያን። ዕብ፡ሚሊጽ፤ አምጃር)፤ የንብ፡እንጀራ፡ሰፈፉ፡ጠቃጠቆው፡ወይም፡ቀፎው፡ማንቱ፡የንቡ፡መዝገብ። መለላውንም፡ያሳያል። ንብ፡ምላጽያኒሁ፡ውስተ፡ገዳም፡(አዋል። ገድ፡ላሊ)። በምላጺ፡ፈንታ፡የላጸየ፡ዘር፡መስሎት፡መላጺ፡ይላል፤ ስሕተት፡ነው።

**መለቀ**፤(መሊቅ። ዕብ፡ማላቅ)፤ ቈረጠ፡ቀጨ፡ነጨ፡የራስና፡ያንገት፡የጠጕር። ለማርና፡ለንፈልት፡ለሸትም፡ይኾናል። መለጠን፡እይ፤ የዚህ፡ጎር፡ነው።

**ሜላቅ ፤ (ቃት) ፤** ቅርጫት ፤ ታናሽ ፤ አበራ ሬድ ፤ ወይም ፤ እንቅብ ፤ ጕርገኝ ። ቦ ፤ **ዘይፀፍር ፤ ሜላቃተ ፤ እሰ ፤ እሙንቱ ፤ አስፈሬዳት ፤ ደቃቃት ፤** (ሥር ፤ ጳክ) ።

**መሊስ ፤ ሶት ፤ (መለሰ ፤ ይመልስ ፤ ይ ምልስ) ፤** መመለስ ፤ መለወጥ ፤ የቃል ፤ የነገር ፤ ለውሃና ፤ ለእግርም ፤ ይኾናል ። **ወመለሱ ፤ ቃሎሙ ፤** (ማብ፳፰ ፤ ፮) ።

—፤ መመላለስ ፤ መደጋገም ፤ እየመላለሱ ፤ መወልወል ፤ መሰንገል ፤ መሞረድ ፤ መሳል ፤ የግብር ። **ሰይፎ ፤ ይመ ልስ ፤** (መዝ ፤ ፯) ።

—፤ መፍለቅ ፤ ማንጸብረቅ ፤ መንቦግቦግ ፤ መብራት ፤ መ ጽደል ፤ ከውልወላና ፤ ከሰንገላ ፤ ብዛት ። **ኩናት ፤ ዘይ መልስ ። ሰይፍ ፤ ተንሥኢ ፤ ወምልሲ ። እንተ ፤ ትዌ ጥን ፤ ከመ ፤ ትብራህ ፤ ወትምልስ ፤** (ናሖ፫ ፤ ፫ ። ሕዝ ፳፩ ፤ ፳፰ ። ፊልክ ፤ ፺፯) ።

**አምለሰ ፤** አስመለሰ ፤ ቋቅ ፤ አሰኘ ፤ አስተፋ ፤ አ ስቀረሸ ።

**ተመልሰ ፤** ተመለሰ ፤ ተወለወለ ፤ ተሰንገለ ።

**ምሉስ ፤ (ሳን ፤ ሳት ፤ ልስት) ፤** የተመለሰ ፤ ምልስ ፤ ቅልስ ። የተሳለ ፤ የተሰንገለ ፤ ብሩህ ፤ ጽዱል ፤ መ ፍርህ ፤ ዘያንበለብል ። መጽሐፍ ፤ ግን ፤ በምሉስ ፤ ፈንታ ፤ ሜሎስ ፤ ይላል ። **ወይትፌኖ ፤ ሜሎስ ፤ ሰይፈ ፤ እሳት ። ኀጺክ ፤ ሜሎስ ፤ እሳት ፤ ዘይነድድ ፤** (ቅዳ ፤ ያዕ ። ቄር ። ዘ ፍ፫ ፤ ፳፱) ።

**ሜሎስ ፤ (ጽርእ) ፤** ዜማ ፤ ተሰጥ ፤ የዜማ ፤ ምስጋና ፤ ግሩና ፤ ቀኝ ፤ የሚመላለስ ። እሳታዊ ፤ ሰንቆ ፤ የሚበርቅ ፤ የሚያንጸበርቅ ። **ከርሆሙ ፤ ወእንግድዓሆሙ ፤ ዘዐንቈ ፤ ኢያበጺ ፤ ወበርዲኖ ፤ ከማሁ ፤ ብርሃን ፤ ዘ ሰንጳስ ፤ ገጹ ፤ ዘሜሎስ ፤ ወአዕይንቲሆሙ ፤ ዘጳዝዮን ፤** (መጽ ፤ ምስ) ።

**መልስ ፤** በቁሙ ፤ ለጣዊ ፤ ቃል ፤ ምላሽ ፤ የጥ ያቄ ፤ ፍሬ ።

**ተምላስ ፤** በቁሙ ፤ ምላሽ ፤ ትፋት ፤ ቅርሻት ፤ ባፍ ፤ ገብቶ ፤ ባፍ ፤ የሚወጣ ።

**ተመላለሰ ፤** (የተመልሰ ፤ ድርብ) ፤ በቁሙ ፤ ዘረ ፤ ወዲያ ፤ ወዲህ ፤ አለ ፤ የእግር ። **ባሕታዊ ፤ እኩይ ፤ ዘይ ትመላለስ ፤ ውስተ ፤ አ.ድዋል ፤** (ፊልክ ፤ ፳) ። እንቶስ ወን ፤ እይ ።

**ተማለሰ ፤** በቁሙ ፤ ተመላለሰ ፤ የገጽ ፤ የቃል ።

**አስተማለሰ ፤** አማለሰ ፤ አመላለሰ ፤ (አደራራገ) ።

**ሜላት ፤ (መለለ ፤ ለትሐ ። ዕብ ፤ ሚ ላት) ፤** ጥሩ ፤ ፀምር ፤ ጥሩ ፤ ሐር ፤ ጥሩ ፤ የከት ፤ ልብስ ፤ ማምጃ ፤ ከፀምር ፤ ከሐር ፤ ከከታን ፤ ከጥጥ ፤ የሚሠራ ። ስምንቱ ፤ ከመለሰና ፤ ከለትሐ ፤ የተደቀለ ፤ ነው ፤ ሜላት ፤ ጽርየቱን ፤ ንጣቱን ፤ ማምጃ ፤ ቀለሙን ፤ ዐይነቱን ፤ ያሳ ያል ፤ እልታሕን ፤ እይ ፤ (ዘፍ፵፩ ፤ ፵፪ ። ዘፀ፳፭ ፤ ፬ ። ሉቃ፲፮ ፤ ፲፱) ።

**መልታሕት ፤—ጕንጭ ፤ ፊት ፤—ለ ትሐ ።**

**ሜላትሩ ፤ ሮን ፤ (ጽርእ) ፤** ጸፍጸፍ ፤ ብ ላጥ ፤ በቤት ፤ ዙሪያ ፤ የሚሠራ ፤ ጊጥ ፤ እንደ ፤ ዐምድና ፤ እንደ ፤ ዝናር ፤ ያለ ፤ ሥረ ፤ ወጥ ፤ ወይም ፤ የኋላ ፤ ቅ ጥል ፤ ልብጣት ፤ ልባጥ ። ዳግመኛም ፤ ጊጥነቱን ፤ ሲያይ ፤ በከታር ፤ ፈንታ ፤ ሜላትሩ ፤ ይላል ፤ ባለብሉዮችም ፤ ጸፍ ጸፍና ፤ ልባጥ ፤ በማለት ፤ ፈንታ ፤ መደብ ፤ ልዝብ ፤ ጠርብ ፤ ይሉታል ፤ (፫ነገ ፤ ፯ ፤ ፱ ፤ ፶፩) ። **ሰሎሞን ፤ አስተቀጸላ ፤ ለመቅደስ ፤ በሜላትሮን ፤** (አርጋ) ። ንባቡም ፤ ምስጢ ሩም ፤ ከሜላት ፤ ጋራ ፤ ይስማማል ።

**መልጸጸን ፤ (ዕብ ፤ ማልፖን ፤ ምላፕ ፖን) ፤** ዱባ ፤ የባር ፤ ቅል ፤ ቃላቅ ፤ ከብ ፤ ወይም ፤ ሞ ላላ ፤ ሳይቀቀል ፤ የማይበላ ፤ ዐይነቱ ፤ ብዙ ። (ተረት) ፤ ዱባና ፤ ቅል ፤ ፀብሮ ፤ ይበቅል ፤ አበላሉ ፤ እየቅል ።

**መልጸጸን ፤ (ጽር ፤ ፖፖናስ ። ዕብ ፤ እ በጢሕ) ፤** በጢሕ ፤ ብርጭቅ ፤ የዱባ ፤ ዐይነት ፤ ጥሬው ፤ የሚበላ ፤ የማይቀቀል ። ባለቅኔዎች ፤ ግን ፤ ጕመን ፤ ይሉ ታል ፤ በጢሕን ፤ እይ ። **መልጸጸን ፤ ወስጕርንድ ፤** (ዘኍ ፲፩ ፤ ፭) ።

**ሚመ ፤ (ሚ ፤ መ) ፤** ንኡስ ፤ አገባብ ፤ የማገሻ ልና ፤ የማማረጥ ፤ የጥያቄ ፤ ቃል ። ወይ ፤ ወይስ ። ሚና ፤ መ ፤ ተጋጥመው ፤ አንድ ፤ ወገን ፤ ኹነዋል ፤ አውንና ፤ የ ጊን ፤ ሚንና ፤ መን ፤ እይ ። **እምበማይኑ ፤ ወሚመ ፤ እምሰብእ ። ምንት ፤ እምኀየሰሙ ፤ ለእለ ፤ ተፈ ጥሩ ፤ ሚመ ፤ ተፈጥሮ ፤ ወሚመ ፤ ኢተፈጥሮ ። አ የኬ ፤ ዘወለደት ፤ ድንግል ፤ ሚመ ፤ ትስብእተ ፤ ወ ሚመ ፤ መለኮተ ፤** (ማቴ፳፩ ፤ ፳፭ ። ቄር ፤ እስት) ። (ዕርጅ ፤ ቀኍ፲፩) ።

**ሚም ፤—ስመ ፤ ፊደል ፤ ዕብራዊ ፤ መ—መዩም ።**

**ምምባሬ ፤ (ጽር ፤ ማምብሬ ። ዕብ ፤ ማምሬ) ፤** የመረ ፤ ጥሬ ፤ የሰው ፤ ስም ፤ የአብርሃም ፤ ወዳጅ ፤ ባለቃል ፤ ኪዳን ፤ ሽፍታ ፤ እንቢተኛ ፤ አሳዛኝ ፤ ማለት ፤ ነው ፤ መረንና ፤ እምረረን ፤ እይ ። መሬርና ፤ ን ቢር ፤ ልዩ ፤ ሲኾን ፤ መምረሪ ፤ መምርር ፤ ወይም ፤ ማ ምሬ ፤ በማለት ፤ ፈንታ ፤ ምምባሬ ፤ ምንባሬ ፤ ር ፤ ማለት ፤ የመላሽና ፤ የጣፊ ፤ ስሕተት ፤ ነው ፤ (ዘፍ፲፬ ፤ ፲፫ ፤ ፳፬ ። ፲፰ ፤ ፩ ። ቅዳ ፤ ጎር) ።

**ሜመየ ፤—ወኸየ ፤ ውሃ ፤ ኾነ ፤—መይ መየ ።**

**ማሞን ፤ (ጽር ፤ ማሞና) ፤** ገንዘብ ፤ ጥሪት ፤ ብዕል ። ጣዖት ፤ አሸንክሊት ፤ ከወርቅና ፤ ከብር ፤ የተሠራ ፤ (ማቴ፮ ፤ ፳፬) ፤ ወለንዋይ ፤ ባለው ፤ ወለማሞን ፤ ይላል ። ሕፃናትን ፤ ማሞ ፤ ማሚት ፤ ማለት ፤ ከዚህ ፤ የወጣ ፤ ስም ፤ ይመስላል ።

**መምዐ ፤ (መዩ.ዕ ፤ ሜዐ ። ምዒው ፤ መ ዐወ) ፤** ፈራ ፤ ደነገጠ ፤ ከልብ ፤ ከንገሮት ፤ ታወከ ፤ ተሸ

በረ ፡ ሸሸ ፡ ደነበረ ። ከመዐወና ፡ ከሜዐ ፡ ከኹሉቱ ፡ የተ ደቀለ ፡ ነው ። መምዑ ፡ ወጉዩ ። መምዑ ፡ መሳፍንት ፡ ኢይምም ። ኢትፍርሁ ፡ ወኢትመምዑ ። ይሜምዑ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምእት ፡ እምድምፀ ፡ አሐዱ ፡ (ዮዲ፲፭ ፡ ፫ ። ዘፀ፲፭ ፡ ፲፭ ። ዘዳ፳ ፡ ፫ ። ኢሳ፴ ፡ ፲፯) ።

**ምሙዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ምዕት) ፤ የታወከ ፡ የተሸበረ ፡ ፈሪ ፡ ድንጉጥ ።

**ምማዔ** ፤ መሸበር ፡ መታወክ ፤ ሽብር ፡ ሁከት ። ፍርሀት ፡ ወምማዔ ። እንበለ ፡ ምማዔ ፡ (ሰንክ ፡ ጥር ፲፫ ። ሐም፯ ። ነሐ፳፱) ።

**ምምዓ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ሽብር ፡ ሁከት ፡ ጭ ንቅ ። ዕለተ ፡ ምምዓ ፡ ወሙስና ። ረዓድ ፡ ወም ምዓ ፡ (ሶፎ፩ ፡ ፲፭ ። ኤር፲፭ ፡ ፰) ።

**አመምዐ** ፤ አሸበረ ፡ አስጨነቀ ። እፎ ፡ ተስ ዕረ ፡ ዘያሜምዕ ፡ (ኢሳ፲፬ ፡ ፬) ።

**መምዕ** ፤ የሚያሸብር ፡ አሸባሪ ፡ ማሸበሪያ ። ኢእቢድኑ ፡ ወኢመምዕ ፡ ዝንቱ ፡ ዘይነግሩ ፡ (ቄር ፡ እ ስት ፡ ፳፲) ።

**መምዕል** ፤—ወንጀለኛ ፤—ምዒል ፡ መዐለ ።

**መመተ** ፤ (መምቶ ። ዕብ ፡ ሁሜም) ፤ ጕደለ ፡ አነሰ ፤ ሕጹጽ ፡ ጎሰር ፡ ነውረኛ ፡ ኾነ ፤ የመልክ ፡ የሕዋስ ፡ የጠባይ ፡ የግብር ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ እንደ ፡ መምዐ ፡ ተሸበረ ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ፤ ከጥሬው ፡ በቀር ፡ አንቀጹ ፡ አይገኝም ፤ ጎርንቱ ፡ የመምዐ ፡ ነው ።

**ምማቴ** ፤ (ዕብ ፡ ወዐረ ፡ ሙም ። ሱር ፡ ሙማ) ፤ ሕጸጽ ፡ ሕጹጽነት ፤ ነውረ ፡ ሥጋ ፡ የሕዋሳት ፡ መጕደል ፡ ወይም ፡ አለመተካከል ፡ ፀንካሳ ፡ ጠንባሳ ፡ ወንካራ ፡ ሸውራራ ፡ ደፍጣጣ ፡ ገጣጣ ፤ ድንክ ፡ ጉባጣ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡ (ምሳ፳ ፡ ፴) ።

—፤ ቍጣ ፡ ብስጭት ፡ የጠባይ ፡ ክፋት ፤ ዐመለ ፡ ታናሽ ፡ መኾን ። በእንተ ፡ ዘውስቴቶሙ ፡ ምማቴ ፡ ወጽነት ፡ ወውኅደተ ፡ አእምሮ ፡ ወይካመ ፡ ጠባይዕ ፡ ወብ ዝኀ ፡ ሕማማት ፡ (ፈልክ ፡ ፶፰) ።

**መኑ** ፤ (ሱር ፡ ማኑ ። ዐረ ፡ ሚን ፤ መን) ፤ መ ፡ ኑ ፡ መ ፡ ማ ፡ ማን ፤ ኑ ፡ ነው ፤ በተገናኝ ፡ ማነው ። በጥያቄንት ፡ ላይ ፡ ስምና ፡ አንቀጽ ፡ ኹኖ ፡ አክልን ፡ ሌላ ውንም ፡ ግብር ፡ ያሳያል ፤ መና ፡ ሚ ፡ ኧ ፡ ወገን ፡ ኹነው ፡ ከኑ ፡ ጋራ ፡ ገጥመዋል ፡ የሦስቱንም ፡ ፍች ፡ በየቦታው ፡ እይ ። አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ መጥበቁን ፡ ሲያዩ ፡ ደ ጊመ ፡ ቃል ፡ ያለበት ፡ መሰሏቸው ፡ የመንን ፡ ዘር ፡ ነው ፡ ይላሉ ። መኑ ፡ የዐቢ ፡ መንግሥት ፡ ሰማይትኑ ፡ ወ ሚመ ፡ ገነት ። መኑ ፡ ወመኑ ፡ አንትሙ ። መኑ ፡ ስሙ ፡ ወመኑ ፡ ስመ ፡ አቡሁ ፡ (ቀሌ ። ዘፀ፫ ፡ ፲፫ ። ቅዳ ፡ አፈ) ። መኑና ፡ ምንት ፡ በወንድና ፡ በሴት ፡ ሲለዩ ፡ መኑ ፡ የወ ንድ ፡ ምንት ፡ የሴት ፡ ይኾናል ። ሲበዙና ፡ ሲዘረዘሩም ፡ መኑ ፡ ምኖት ፡ ምኑ ፡ ምኖቱ ፡ ምንት ፡ ምንታት ፡ ም ንቱ ፡ ምንታቲሁ ፡ ያሰኛሉ ። መጻሕፍትና ፡ መምህራን ፡ ግን ፡ ሲይተው ፡ አብዝተው ፡ በርባታ ፡ አልጠነቀቁትም ።

**መነ** ፤ **መነሃ** ፤ ማን ፡ ማንን ። መነ ፡ እፌኑ ። መነ ፡ ትብል ፡ ርእሰከ ። መነሃ ፡ ትሳተፉ ፡ በቅድሳት ፡ (ኢሳ፮ ፡ ፰ ። ዮሐ፩ ፡ ፳፱ ። ኪዳ) ።

**ምንት** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ጥያቄና ፡ የጥያቄ ፡ ስም ፡ የባሕርይንና ፡ የግብርን ፡ የተጸውዖን ፡ ስም ፡ የሚያስጠ ይቅ ፡ የሚያስመረምር ፤ ስም ፡ ባለው ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። (ማንች ፡ ማናት) ፤ ምን ፡ ምንድር ፡ ን ፤ ምኖች ፡ ምን ድሮ(ና)ች ። ምንት ፡ አነ ። ምንት ፡ ሕዝብከ ። ምን ትከ ፡ እሙንቱ ። ምንት ፡ ብየ ፡ ምስሌኪ ። ምንት ፡ ዕፀ ፡ በኀበ ፡ ረከብክሙ ፡ (ኢዮ፱ ፡ ፳፱ ። ዮና፩ ፡ ፰ ። ዘፍ፴፫ ፡ ፰ ። ዮሐ፪ ፡ ፬ ። ዳን፩ ፡ ፶፰) ። ኒ ፡ ኒ ፡ ትራስ ፡ ሲኾኑት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አንዳች ፡ ከቶ ፡ ያሰኛል ። ባለ ቤት ፡ ሲኖር ፡ ቅጽል ፡ ሳይኖር ፡ በቂ ፡ ይኾናል ። ኢታ ንሥኡ ፡ ምንትኒ ፡ ጾረ ። ምንትኒ ፡ ሐሰተ ። ኢነኙ ድግ ፡ ወኢምንተኒ ፡ (ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፳፩ ። ምሳ፳፬ ፡ ፳፫ ። ዘፀ፲ ፡ ፳፯) ። መንተወን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ኢምንት** ፤ በቁሙ ፡ ባይ ፡ የሌለ ፡ ያልነበረ ፡ ያልተፈጠረ ፡ ወይም ፡ የተናቀ ፡ ከንቱ ፡ ብላሽ ፡ እይለ ፡ መኖሩ ፡ የማይታሰብ ። ወ ፡ በር ፡ ከፋችና ፡ አዳማቂ ፡ ይ ኾንለታል ። በፍሖ ፡ ብመስዕ ፡ ደበ ፡ ወኢምንት ። ከመ ፡ ወኢምንት ፡ እሙንቱ ፡ (ኢዮ፳፮ ፡ ፯ ። ኢሳ፵ ፡ ፲፯) ።

**መና** ፤ (ጽር ፡ ማና ። ዕብ ፡ ማን) ፤ በቁሙ ፡ መና ፡ ምግብ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለብ ፤ እግዜር ፡ ለእስራኤል ፡ ፵ ፡ ዘመን ፡ ምሉ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ከሰማይ ፡ ጕተራው ፡ እያወጣ ፡ በሙሴ ፡ በመጋቢው ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ገዳም ፡ ኀፍሮ ፡ ይሰፍረውና ፡ ይቈንነው ፡ ያድለው ፡ የነበር ፡ የድ ንብሳል ፡ ዐይነት ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፲፭ ፡ ፴፩ ። መዝ ፡ ፸፯) ። ሙጫ ፡ እንደ ፡ ደሮ ፡ ማር ፡ ያለ ፤ በሲና ፡ በረሓ ፡ ከሚ በቅሉ ፡ ዕንጨቶች ፡ የሚገኝ ። የኹለቱም ፡ ፍች ፡ ማ ፡ ምንት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እንግድነቱን ፤ ሐዲስ ፡ ምግብነ ቱን ፤ በሌላ ፡ ቦታ ፡ አለመገኘቱን ፡ ያሳያል ።

**ማኒ** ፤ (ጽር ። ሱር ፡ ምኔእ ፡ ምናህ ። ዕብ ፡ ማናህ) ፤ በፈረ ፡ ቈጠረ ፡ ፈጸመ ፡ (ዳን፭ ፡ ፳፮) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ መስፈሪያ ፡ ድርን ፡ ይሉታል ። ዐይን የሂ ፡ ሶበ ፡ ተሰፍረ ፡ በጽልመተ ፡ ሌሊት ፡ ማኒ ፡ እ ስከ ፡ ኤዶምያስ ፡ ሀገርየ ፡ መኑ ፡ ይመርሐኒ ፡ (የውር ፡ ቅኔ) ።

**ማኒ** ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ፩ኛው ፡ በዘመን ፡ ብሉይ ፡ የነበረ ፡ ይሁዲ ፡ ፍጹም ፡ ከሓዲ ፤ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ ፈ ጣሪ ፡ የለም ፡ የሚል ፡ የፍራማሶኖች ፡ አባት ። እልፍ ፡ ዐላውያን ፤ ማኒስ ፡ ክነ ፡ የዐብዮሙ ፡ (ቅኔ) ። ፪ኛው ፡ በዘመን ፡ ሐዲስ ፡ የተነሣ ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነን ፡ ምትሀት ፡ ጽላሎት ፡ የሚል ፡ (ቄር ፡ እስት) ።

**መንገለ** ፤ መንግል ፤—ወደ ፡ ጌጥ ፤—ነ ገለ ።

**መንግን** ፡ (ብ ፡ መናግንት ። ጽር ፡ ማጋኖን ። ሱር ፡ ማንጋኖን ። ዐረ ፡ መንገኑን) ፤ መዘውር ፡ መኪና ፤ የመዘውሩ ፡ ውስጥ ፡ ጥርሱና ፡ ሆዱ ። ወገብረ ፡ ሠረገላተ ፡ እለ ፡ በመንግን ፡ ይትነድፉ ፡ ከመ ፡ ይኩና ፡ መልዕልተ ፡ ማኅፈድ ፡ ወማእዝን ፡ ወይነድፉ ፡ በሐጽ ፡ ወበእብን ። መንግን ፡ ሶበ ፡ ነጸረ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ለስምዐ ፡ መዊት ፡ ጥሕረ ። መናግንት ፡ ኀጺን ፡ (፪ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፲፭ ። ድጓ ። ገድ ፡ ኪሮ) ። —፤ አሸክላ ፡ ወጥመድ ፡ ተንኰል ፡ ክፉ ፡ ምክር ። መናግንት ፡ ሰይጣን ፡ (ኤፌ፮ ፡ ፲፩ ። ዲድ ፡ ፲፪ና ፡ ፲፱ ። ኄርማ ፡ ገ፳፰ ። ማንዘ) ። ክንቱ ፡ በክ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መንግን ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (፩ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፳፱) ።

**መንግን ፡ አው ፡ አመንግን** ፤ ዘወረ ፡ መኪና ፡ አስኬደ ። አጠመደ ፡ ወጥመድ ፡ አኖረ ።

**ተመንግን** ፤ ተዘወረ ፡ ተጠመደ ፤ መኪናው ፡ ወጥመዱ ። ተተንኰለ ፡ ተንኰል ፡ ሠራ ፡ አታለለ ፤ ሰውየው ። ኢበክሁት ፡ ወኢበተመንግኖ ፤ ወተመንግኖት ፡ ኢልዛቤል ፡ ለቀቲሎቱ ። እለ ፡ ይትመነገኑ ፡ በጕሕሎቶሙ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፃ፱ ፡ ፱ ። ኢፌ፬ ፡ ፲፬) ።

**መንግኒቅ** ፤ (ዐረ ። ሱር ፡ ማንጋኒቃ) ፤ የዱሮ ፡ መድፍ ፤ የመዘውር ፡ ወንጭፍ ፡ እንዳንደርቢ ፡ ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ደንጊያ ፡ አርቆ ፡ የሚጥል ፡ የሚወረውር ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ነፍጥ ፡ ጠመንጃ ፡ ሽጕጥ ፡ ይሉታል ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ። መንገኒቅ ፡ ባለው ፡ አብዝቶ ፡ መናግኒቅ ፡ ይላል ፡ ወሠርዑ ፡ ሰብአ ፡ ፋርስ ፡ መናግኒቀ ፡ ዘውእቱ ፡ መዋግረ ፡ እብን ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፪፻፳) ።

**መንግሥት** ፤—በቁሙ ፤—ነጊሥ ፡ ነግሠ ።

**ምንዳቤ** ፤—በቁሙ ፡ ጭንቅ ፤—ነዲብ ፡ ነደበ ።

**መንዲያ** ፤ (ጽር ፡ ማንዲያስ ። ዕብ ፡ ማድ) ፤ ክቡር ፡ ልብስ ። የማድየሙ ፡ ፍች ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፬) ።

**መንዲል** ፤—በቁሙ ፤—ነዲል ፡ ነደለ ።

**ምንሃር** ፤—መስኖ ፤—ንሂር ፡ ነሀረ ።

**መንዝ** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ የሺዋ ፡ ክፍል ። መንዝ ፡ ማለት ፡ ነው ። መንዜ ፤ መን ፡ ዚ ፡ (ትግሪኛ) ። ፪ኛም ፡ መንዝህ ፡ መንዝሃዊ ፡ ብሎ ፡ በንዝሀ ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ከምንዝሀ ፡ ጋራ ፡ ይስማማልና ፡ ንዝሀን ፡ እይ ።

**ምንዙግ** ፤—የተዛቀየ ፤—ነዚግ ፡ ነዘ ።

**ምንዙሕ** ፤—ምዙሕ ፤—መዝሐ ።

**መንዝር** ፤-አመንዝራ ፤-ነዚር ፡ ነዘረ ።

**ሙናሕ** ፤—ማረፊያ ፤—ነዊኅ ፡ ኖኀ ።

**መንጢጥ** ፤—የወፍ ፡ ስም ፤—ነጢጥ ፡ ነጠ ።

**ማንጦን** ፤ (ጽር ፡ ፕኔፍማቶን) ፤ የተሳሳተ ፡ ከፊስ ፡ ስም ፡ መንፈስ ፡ ማለት ፡ ነው ። አግዮስ ፡ ማንጦን ፡ (አጊዮስ ፡ ፕኒፍማቶስ) ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ (ቅዳ) ።

**መንጠፍት** ፤—ማጥሪያ ፤—ነጢፍ ፡ ነጠፈ ።

**መነየ** ፤ (ይመኒ ፡ ይምኒ ፡ መንይ ። ዕብ ፡ ማናዕ ። ዐረ ፡ መነዐ) ፤ ለየ ፡ ከለለ ፡ ወሰነ ፤ ዐጠረ ፡ ቀጠረ ፤ ዙሪያውን ፡ ዘጋ ፡ ከለከለ ፤ የገዳም ፡ የቤተ ፡ ክሲያን ።

**ምኔት** ፤ (ታት) ፤ ገዳም ፤ ልዩ ፡ ክል ፡ ክልክል ፤ የመነኮሳት ፡ ሀገርና ፡ መንደር ፡ ከንቤተ ፡ ክሲያን ። ሐነጸ ፡ ምኔተ ፡ ወአስተጋብአ ፡ አኀወ ። ምኔታተ ፡ መነኮሳት ። ሊቀ ፡ ምኔት ። አበ ፡ ምኔት ። እመ ፡ ምኔት ፡ (ፊልክ ፡ ፳ ። ገድ ፡ ተክ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲) ።

**መንዮ ፤ ዮት** ፤ (መነየ ፡ ይሜኒ ፡ ይመኒ) ፤ መመኘት ፡ ምኞት ፡ ማድረግ ፤ መሻት ፡ መፈለግ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመነየ ፡ ፈንታ ፡ ተመነየ ፡ ይላል ፤ አድራጊውን ፡ በተደራጊ ፤ አያሰኝም ።

**አመነየ** ፤ አስመኘ ፡ አስጐመዠ ። ኪያሁ ፡ አመነየት ፡ ወአነበየት ። ዘያሜኒ ፡ ኵሎ ፡ ወያስተቤፉ ፡ (ቅዳ ፡ አት ። ደራሲ) ።

**ተመነየ** ፤ ምኞት ፡ ኾነ ፤ ታሰበ ፡ ተከጀለ ፡ ተሻ ፡ ተፈለገ ። ልማዱ ፡ ግን ፡

**ተመነየ** ፤ (ዐረ ፡ ተመነ ። መነየ) ፤ ተመኘ ፡ ሻ ፡ ፈለገ ፤ ወደደ ፡ ለመነ ። ተመነየ ፡ ይርአይ ፡ ዕለተየ ፤ ርእየሂ ፡ ወተፈሥሐ ። ብሔር ፡ እንተ ፡ ትትሜነይ ፡ ነፍስክሙ ። ኢብጻሕክዎ ፡ ኀበ ፡ ዘተመነየ ፤ ጸልአ ፡ ሕይወተ ፡ ወተመነዩ ፡ መዊተ ። ከመ ፡ ይትመነይ ፡ እምኔሁ ፡ ዘፈቀደ ፡ (ዮሐ፰ ፡ ፶፮ ። ኤር፳፪ ፡ ፳፯ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ታኅ፳) ።

**ተምኔት** ፤ (ታት) ፤ ምኞት ፡ ፈቃድ ፡ ልመና ፡ (መዝ ፡ ፻ ። ኢዮ፳፱ ፡ ፳፯) ። አነ ፡ እሁበከ ፡ ተምኔተ ፡ ልብከ ። ረከቡ ፡ ተምኔቶሙ ፡ ብነ ፡ (ቀሌ ። ዮሴፍ) ።

**መንከ** ፤—በቁሙ ፤—ንከይ ፡ ነከየ ።

**መንኩብ** ፤—አውራ ፡ ጣት ፤—ንኪብ ፡ ነከበ ።

**መንከክት** ፤—እንዝርት ፤—ከክዎ ፡ ከከወ ።

**መንከስ** ፤—መንከሻ ፡ ጥርስ ፤—ነኪስ ፡ ነከሰ ።

**መነከስ** ፤ (ስት ፡ ሳን ፡ ሳት ። ጽር ፡ ሞናኽስ ። ትግ ፡ ሐባ ፡ ሙንኩስ ፤ ነዳይ) ፤ መነኵሴ ፡ መናኝ ፡ ድኻ ፡ ለማኝ ፤ ከዓለም ፡ ከዘመድ ፡ ከሕዝብ ፡ ከገንዘብ ፡ የተለየ ። መጻሕፍትና ፡ መምሬን ፡ ግን ፡ ወንድና ፡ ሴቱን ፡ አይለዩትም ። መነከስ ፡ ባሕታዊ ። መነኮሳት ፡ ገዳማውያን ። መነከሳተ ፡ ምኔት ። ወከነት ፡ መነከሰ ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፪ ፡ ፲፰ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲ ። አዋል) ።



መነኮስ ፡

**መነከሳዊ** ፤ ዪ ፡ ይ ፤ (ውያን ፡ ይያን) ፤ የመነኰሴ ፡ ወገን ፡ የገዳም ፡ ሰው ፡ ገና ፡ ቆብ ፡ ያልጫነ ፡ ረድ ፡ እመክሬ ፡ አናኮ ፡ ደጕብ ፤ ወይም ፡ ቆብ ፡ የጫነ ፡ ተራ ፡ መነኰሴ ፤ ብቻውን ፡ የሚኖር ፡ ባተሌ ፡ ድንግል ።

**መነከሳዊት** ፤ (ዪት ፡ ውያት ፡ ይያት) ፤ መነኮስት ፡ መነኰሲት ፡ የሴት ፡ መናኝ ፡ መበለት ፡ ባሕታዊት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፱ ። ቄድር ። ገ፳፱) ። በእንተ ፡ መነከሳይያት ፡ ወመበለታት ። እልፍ ፡ ባሕታውያን ፡ ወክልኤቱ ፡ እልፍ ፡ መነከሳይያት ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፲ ። ፊልክ ፡ ፴፯) ።

**መንኰሰ** ፤ (ትግ ፡ ሐባ ፡ መንከሰ ፤ ነድየ) ፤ መነኰሰ ፤ አስኬማ ፡ ለበሰ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባ ፡ ደኸየ ፡ ድኻ ፡ ኾነ ። ብዉሕ ፡ ሎሙ ፡ ይመንኵሱ ። ይመንኵስ ፡ በፈቃደ ፡ ርእሱ ። ለእመ ፡ መንኰሱ ፡ ክልኤሆሙ ። ይሑር ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወይመንኵስ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፱ ። ፲፱ ፡ ፱ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ መስ፲፬) ።

**አመንኰሰ** ፤ አመነኰሰ ፡ አስኬማ ፡ አለበሰ ። ሰብእሲተ ፡ ከመ ፡ ያመንኵሳ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲ ። ሚያ፲፭) ።

**ምንኵስና** ፤ በቁሙ ፡ መነኵሴነት ፡ መነኰሴ ፡ መኾን ። ኢይፃእ ፡ እምንኵስና ። በጊዜ ፡ ምንኵስና ሆሙ ። እምድኅረ ፡ ምንኵስናሁ ። ሥርዐተ ፡ ምንኵስና ። ለብሰት ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፱ ። ፲፱ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲ ። ፊልክ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ጥቅ፭) ።

**ምንኵስናዊ** ፤ የምንኵስና ፡ ግብር ፡ አኗኗር ። ሕይወት ፡ ምንኵስናዊት ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፶፱) ።

**መኒን** ፤ ኖት ፤ (መነ ፤ መነነ ፡ ይመንን ፡ ይምንን) ፤ ማነስ ፡ መጕደል ፤ መቅለን ፡ መመንመን ፡ መናኛ ፡ ምናኝ ፡ መኾን ፤ የትምርት ፡ የውቀት ፡ የገላ ፡ የናላ ። ቅጥነት ፡ ለፈትልም ፡ ይኾናል ፤ መነን ፡ ድር ፡ እንዲሉ ።

**መንኖ** ፤ ኖት ፤ (መነነ ፡ ይሜንን ፡ ይመንን) ፤ መመነን ፡ መናቅ ፡ መጥላት ፡ ማኰስስ ፡ ማርከስ ፡ መንቀፍ ፡ ማጸየፍ ፤ መካድ ፡ መጣል ፤ ከሕጹጽነቱ ፡ የቀነሣ ። ሕጹጽነት ፡ ለመናኙም ፡ ለተመናኙም ፡ ይኾናል ። ዒሳው ፡ መነነ ፡ ቀደመ ፡ ተወልዶ ። ይሜንን ፡ እኩየ ፤ ወየኀሪ ፡ ሠናየ ። መንኖ ፡ መነንከኒ ። እግዚ ፡ መነኖሙ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱ ። ኢሳ፯ ፡ ፲፭ ። ስቈ፳ ፡ ፳፱ ። ኤር፯ ፡ ፴) ። መስፈር ፡ መቍጠር ፡ መመዘን ፤ ስቅሉን ፡ ምናን ፤ ምናኑን ፡ መክሊት ፡ ማድረግ ፤ የገንዘብ ። ማኒን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**መናኒ** ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፡ የሚንቅ ፡ ናቂ ፡ መናኝ ። መናኒተ ፡ ዓለም ። መናኔ ፡ ዓለም ። ልብሰ ፡ መናንያን ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲፯ ፡ ፲፱ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲ ፡ ፯) ።

**አመነነ** ፤ አስመነነ ፡ አስናቀ ። ዘያሜንን ፡ ወይነ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፭) ።

**ተመነነ** ፤ ተናቀ ፡ ተነቀፈ ፡ ተጠላ ፡ ረከሰ ። እምጽቡር ፡ ይትሜነን ፡ ንብረቱ ። ተትሕትኩ ፡ ወተመነንኩ ። እፎ ፡ እብዳን ፡ ይትሜነኑ ፡ (ጥበ፲፭ ፡ ፲ ። መዝ፹፯ ። ምሳ፲፪ ፡ ፰) ።

**ምኑን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ንንት) ፤ የተናቀ ፡ የተጠላ ፡ የረከሰ ፡ ከንቱ ። ወራእዩ ፡ ምኑን ። ምኑነ ፡ ረሰይክሙ ፡ ትእዛዝየ ። ምኑናን ፡ ከነ ፡ በኀቤሁ ፡ (ኢሳ፶፫ ፡ ፫ ። ምሳ፩ ፡ ፳፭ ። ጥበ፱ ፡ ፲፱) ።

**ምናኔ** ፤ በቁሙ ፤ (ላ ፡ ጥ) መመነን ፡ መናቅ ፤ ምነና ፡ ንቀት ፡ አናናቅ ። ወሎቱ ፡ ምናኔ ። ርኵስ ፡ ወምናኔ ። እመ ፡ ሖረ ፡ በትምይንት ፡ ወምናኔ ፡ (ምሳ፲፰ ፡ ፲፫ ። ኩፋ ፡ ፴፩ ። ዲድ ፡ ፱) ።

**ምናን** ፤ (ብ ፡ ምናናት ። ጽር ፡ ምና ። ዐረ ፡ መናን ። ዕብ ፡ ማኔ ። ሱር ፡ ማንያ) ፤ በቁሙ ፤ የሚዛንና ፡ የገንዘብ ፡ ስም ፤ አንዱ ፡ ምናን ፡ ፶ ፡ ሰቅል ፡ ነው ፤ ፷ው ፡ ምናን ፡ ፩ ፡ መክሊት ፡ ይኾናል ፤ የመክሊትን ፡ ፍች ፡ እይ ፡ (ሕዝ፵፭ ፡ ፲፪ ። ፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ። ሉቃ፲፱ ፡ ፲፫) ። እሁበከ ፡ ሠለስተ ፡ ምእተ ፡ ምናናተ ፡ ወርቅ ፤ ወድልወቱ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ምናናት ፡ (ዮሴፍ) ።

**መነን** ፤ (ዐማርኛ) ፤ የሴት ፡ ልጅ ፡ ስም ፤ ቀጭን ፡ ፈታይ ፡ ባለሻሽ ፤ ወይም ፡ መልክ ፡ መልካም ፡ ትክክል ፡ ፍጽምት ፡ ሕጸጽ ፡ የሌለባት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እግዝእትን ፡ እይ ፡ (ገዝአ ፡ አግዝአ) ።

**መንፈስ** ፤—በቁሙ ፤—ነፈሰ ፡ ነፍሰ ።

**መንጸፍ** ፤—ምንጣፍ ፤—ነጺፍ ፡ ነጸፈ ።

**መናረት** ፤—ማብሪያ ፤—ነዊር ፡ ኖረ ፡ ነወረ ።

**መንሱት** ፤—ፈተና ፤—ነሲው ፡ ነሰወ ።

**ምንት** ፤—ምን ፡ ምንድር ፤—መኑ ፡ መ ፡ ኑ ።

**መነተ** ፤ (ይመንት ፡ ይምንት ፤ ጥያቄ) ፤ ምን ፡ ኾነ ፡ ምን ፡ ተባለ ፤ ምን ፡ አ(ተ)ደረገ ።

**መንተወ** ፤ (ተቀ ፡ ግ ፤ ምላሽ) ፤ መነታ ፡ መንታ ፡ ኾነ ፤ መንታ ፡ ወለደ ። ኢመንተወ ፡ በግጻዌ ፡ ወኢተወሰከ ፡ በህላዌ ። ኵሎን ፡ እለ ፡ ይመነትዋ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ማሕ፬ ፡ ፱ ። ፯ ፡ ፮) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ በመንተወ ፡ ፈንታ ፡ ተመንተወ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**ምንትው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ቱት) ፤ የመነታ ፤ መንታ ፡ የኾነ ፤ መንታ ፡ የወለደ ። ምንትወ ፡ ልደት ። ምንትዋት ፡ (ደራሲ ። ገድ ፡ ተክ) ።


**ምንታዌ** ፤ መንታነት ፤ ኹለትነት ። ተዋሕዶ ፡ ያግሕሥ ፡ ኵነኔሁ ፡ ለምንታዌ ። ኅጡአ ፡ ምንታዌ ፡ ክርስቶስ ፡ (ሃይ ፡ አበ ። ደራሲ) ። ማመንታት ፤ ኹለት ፡ ልብ ፡ መኾን ።

**ምንትውና ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ መንታንት ።

**መንታ ፤ (ብ ፡ መናትው) ፤** በቁሙ ፡ ኹለት ፡ ጥንድ ፡ ዘውግ ፤ የተካከለ ፡ የተመሳሰለ ። መንታ ፡ ሀለወ ፡ ውስተ ፡ ከርሣ ። ከመ ፡ ክልኤ ፡ ዕጕለ ፡ መንታ ፡ ዘወይጠል ። እንተ ፡ ወለደት ፡ መንታ ። ወለደ ፡ እምርብቃ ፡ ክልኤ ፡ ደቂቀ ፡ መናትወ ፡ (ዘፍ፳፭ ፡ ፳፬ ። ማሕ፬ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፩ ፡ ፫ ፡ መጽ ፡ ምስ) ።

**አመንተወ ፤** አመንታ ፡ አስመንታ ፡ መንታ ፡ አሶለደ ።

**መንተሌ ፡ ሌ ፤ (ሊት) ፤** ጥንቸል ፡ የጥንቸል ፡ ወገን ። ፌልፌል ፡ ወመንተሌ ። መንተሌት ፡ ተቃሐወት ፡ ምስለ ፡ ምድር ፡ እንዘ ፡ ትብል ፤ እበጽሕ ፡ ንበ ፡ ኢ.ህሎኪ ፡ አንቲ ፡ (ፍከሬ ፡ እየ ። ገድ ፡ ፊል ፡ ገ፪፻፵፫) ።



መንተሌ ፡

**መሠግር ፤—አጥማጅ ፤—ሠገር ፡ ሠገረ ።**

**መሢሕ ፤—በቁሙ ፡ ቅቡዕ ፤—መሲሕ ፡ መስሐ ።**

**መሢጥ ፤ ጦት ፤ (መሠጠ ፡ ይመሥጥ ፡ ይምሥጥ ። መለጠ ፤ መዘገ ፤ መጠቀ) ፤** መንጠቅ ፡ መቀማት ፡ በኀይል ፡ መውሰድ ፤ መዝረፍ ፡ መግፈፍ ። ተምህረ ፡ መሢጠ ። መሠጠ ፡ ምላዌ ፡ ምስለ ፡ መርዔቱ ። ትመሥጥዎሙ ፡ እምእስቲሆሙ ፡ እምላዕሌሆሙ ፡ (ሕዝ፲፬ ፡ ፫ ። ኢዮ፳፬ ፡ ፪ ። ሚክ፫ ፡ ፪) ።

—፤ ሸሸ ፡ ሮጠ ፤ ዳነ ፡ ወጣ ፡ አመለጠ ፤ እንዳይደገዝ ፤ ወይም ፡ ነጥቆ ፡ እንደ ፡ በቅሎ ። መንጠቅ ፤ ፪ ፡ ይሳይል ፡ ራብን ፡ ገንዘብን ፡ ከሌላው ፡ እጅ ፤ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመሠጠ ፡ ፈንታ ፡ አምሠጠ ፡ ይላል ፡ ግስነቱ ፡ ገቢርና ፡ ብኵል ፡ ነውና ፡ አይሰኝም ። አምሠጡ ፡ ውስተ ፡ ጽዮን ። ወይጠል ፡ ዘያመሥጥ ። አምሠጠ ፡ በፈረስ ፡ ረዋጺ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘአምሠጠክሙ ። ከመ ፡ ትክሀሉ ፡ አምሥጦ ፡ (ኢሳ፴፫ ፡ ፲፬ ። ፫ነገ ፡ ፳ ፡ ፳ ። ፬ነገ ፡ ፲ ፡ ፳፬ ። ሉቃ፳፩ ፡ ፴፮) ።

**መሣጢ ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት ፤ ሠጥ) ፤** የነጠቀ ፡ የሚነጥቅ ፡ ነጣቂ ፡ ቀማኛ ። አንበሳ ፡ መሣጢ ። ተዘሳ ፡ መሣጢ ። አራዊት ፡ መሣጥያን ። ተዝላት ፡ መሠጥ ፡ (ዮሴፍ ። ቀሌ ። ፍ ፡ ን ፡ ፴፫ ፡ ፬ ። ማቴ፯ ፡ ፲፭) ።

**አምሠጠ ፤** አስነጠቀ ፡ አስቀማ ፡ አሶለደ ፡ የያዘውን ፡ ወይም ፡ ራሱን ።

**ተመሥጠ ፤** ተመሠጠ ፡ ተነጠቀ ፡ ተቀማ ፡ ተማረከ ፡ ተዘረፈ ፡ ጠፋ ፡ ታጣ ። ተመሠጥኩ ፡ በነኪር ኳረ ፡ ነፋሳት ። ንትመሠጥ ፡ በደመና ። ኢትትመሠጥ ፡ በቀራንብቲሃ ። ተመሥጠ ፡ ንዋም ፡ እምአዕይንቲሆሙ ፡ (ሔኖ፲፬ ፡ ፰ ። ፩ተሰ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ። ምሳ፮ ፡ ፳፭ ። ፬ ፡ ፲፮) ።

**ምሡጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ሥጥ) ፤** የተመሠጠ ፡ የተነጠቀ ። ምሡጠ ፡ ልብ ፡ ወኅሊና ። ንሕነ ፡ በዐይነ ፡ ሃይማኖት ፡ ምሡጥ ፡ ፍጹመ ፡ ሥጋዌከ ፡ ንሬኢ ፡ እምውስጥ ፡ (ስንክ ፡ ግን፳፭ ። ደራሲ) ።


**ምሥጠት ፤** መንጠቅ ፡ መነጠቅ ፡ አነጣጠቅ ፡ ንጥቂያ ፡ ቅሚያ ፤ ሽሽት ፡ ሩጫ ። አይድኃሙ ፡ ፍኖተ ፡ አስትርብሎስ ፡ ወምሥጠተ ፡ መንግሥተ ፡ ዘልሂቅ ፡ እንሁ ። ያፈጥን ፡ ፍጻሜ ፡ ኀልፈተ ፡ ምሥጠትሙ ፡ (ዮሴፍ ። ጥበ፲፬ ፡ ፲፬) ።

**ተማሠጠ ፤** ተናጠቀ ፡ ተነጣጠቀ ፡ ተቃማ ፡ ተሻማ ፡ (መዝ ፡ ፵፪ ። ፹፫ ። ኢሳ፶፪ ፡ ፰፬ ። ሆሴ፲፫ ፡ ፲) ። ከኑ ፡ ይትማሠጡ ፡ እምሲሳይ ፡ ለእመ ፡ ረከቡ ፡ ንስቲተ ፡ ይመሥጥ ፡ አብ ፡ እምወልዱ ፡ ወወልድኒ ፡ እምአቡሁ ፡ (ዮሴፍ) ።

**መምሠጥ ፤ (ብ ፡ መማሥጥ) ፤** መንጠቂያ ፡ መንጠቆ ፡ መኖሥሥ ፡ ሜንጦ ። የድንኳን ፡ ቀሎፍ ፡ ቀለበት ፡ ዘለበት ፡ ወይም ፡ በየጠርዙና ፡ በየመጋጠሚያው ፡ ያለው ፡ ብስ ፡ ንዳላ ፡ ማያያዣው ፡ ገመዱና ፡ ቀሎፉ ፡ የሚገባበት ። ግእዙን ፡ እዩ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ወግበር ፡ መምሠጢሆን ፡ ዘሕብረ ፡ ያክንት ፡ ኀምስ ፡ መማሥጠ ። መማሥጠ ፡ መናሥግት ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፬ ፡ ፳ ፡ ፳፱) ። ገመዱና ፡ ፈትሉም ፡ መምሠጥ ፡ ይባላል ።

**ምምሣጥ ፤ (ጣት) ፤** መቀሚያ ፡ የቅሚያ ፡ ቦታ ።

**ምሥጥ ፤** በቁሙ ፡ ነጭ ፡ የቁላ ፡ ተባይ ፡ የጕንዳን ፡ ዐይነት ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ የሚኼድ ፡ መሣጢ ፤ የክፉ ፡ ምሳሌ ። አገሌ ፡ ምሥጥ ፡ ነው ፡ እንዲሉ ። (ተረት) ፤ ጕራጊና ፡ ምሥጥ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ።



ምሥጥ ፡

**ምሥጢር ፤—በቁሙ ፤—ሰጢር ፡ ሰጠረ ።**

**መሥከዐ ፤—መሰኳ ፡ አመሰኳ ፤—ሰከዐ ፤ መሰከ ።**

**መሥዔ ፤—መንሽ ፤—ሥዕይ ፡ ሠዐየ ።**

**መሠረት ፤—በቁሙ ፤—ሣርሮ ፡ ሣረረ ።**

**ሜዕ ፤—ቍጣ ፡ ሽቱ ፤—መዒዕ ፡ ሜዐ ።**

**ማዕበል ፤—በቁሙ ፤ ብልሄት ፤—ዐበለ ።**

**ማዔጌላህ ፤ (ዕብ ፡ ማዕጋላህ ፤ ማዕጋል) ፤** የሠረገላ ፡ መንገድ ፤ የሰራዊት ፡ ሰፈር ፤ ክቢ ፡ ክባቢ ፡ መከበቢያ ። ወበጽሐ ፡ ውስተ ፡ ማዔጌላህ ፤ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳) ።

**ማዕድ ፤—ማድ ፡ ሰደቃ ፤—መእደ ፤ ማእድ ።**

**ምዒድ ፤ ዶት ፤ (መዐደ ፤ አው ፡ ምዕደ ፡ ይምዕድ ፡ ይምዐድ ። ዕብ ፡ ያዐድ ፤ መከረ ። ሀምዒድ ፡ አሰናከለ) ፤** መምከር ፡ ማስተማር ፡ አብገዞ ፡ መላልሶ ፡ ምክር ፡ መስጠት ፤ ክፉውን ፡ ምክር ፡ በምክር ፡ መለወጥ ፡ ማፍረስ ፡ ማሰናከል ። መከረ ፡ ለክፉም ፡ ለበጎም ፡ ይኾናል ፤ መዐደ ፡ ግን ፡ ለበጎ ፡ ብቻ ፡ ነው ። መዐድዎ ፡ ለዘጊገየ ፡ ከመ ፡ ይኅድግ ፡ ኪያሃ ፡ ፍኖተ ። ይምዐድዎሙ ፡ ወይግበሩ ፡ ንስሓ ። እግዚ ፡ መዐዶ ፡ ሰበብእ ፡ ከመ ፡ ኢይዕልዎ ። መዐደኒ ፡ ነገረ ፡ ሕይወት ። ምሂር ፡ ወምዒድ ፡ (ቅዳ ፡ አት ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፮ ። ዮሴፍ ። ገድ ፡ ተክ ። አርጋ) ።

**መዓዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤** የሚመክር ፡ መካሪ ፤ መጣፍ ፡ አሰሚ ። ንሣእ ፡ መዓዴ ። መዓድያኒሁ ፡ (ፊልክ ፡ ፶፬ ። ፩፻፵፮ ። ሥር ፡ ጳኵ) ።

**ተምዕደ ፤** ተማረ ፤ ተመከረ ፤ ምክር ፡ ሰማ ፡ ተቀበለ ። ይትመዐዱ ፡ ወይጠናቀቁ ፡ በእንተ ፡ ግብራ ፡ ለቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክር ፡ (ቀሌ) ።

**ምዑድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ዕድ) ፤** የተማረ ፤ የተመከረ ፡ ምክር ፡ የገባው ።

**ምዕደት ፤** መምክር ፡ መመከር ፡ አመካከር ፡ መካሪነት ፤ ተመካሪነት ።

**ተማዐደ ፤** ተማከረ ፡ ተመካከረ ። ተማዐዱ ፡ በበይናቲክሙ ። ከንቱ ፡ ዘተማዐዱ ፡ (ኪዳ ። ኢሳ ፴ ፡ ፯) ።

**ምዕዳን ፤ (ናት) ፤** ምክር ፡ ተግሣጽ ፡ ስብከት ፡ ትምርት ፤ መንፈሳዊ ፡ ጨዎት ። ሰሚዐ ፡ ነገረ ፡ ምዕዳን ። ቃለ ፡ ምዕዳን ። ምዕዳኑ ፡ ጽድቅክሙ ፡ በሊኅ ። ኢይመይጦን ፡ ለአልባቢክሙ ፡ ምዕዳን ፡ እምግዘፉሆን ። መጻሕፍተ ፡ ምዕዳናት ፡ (ፊልክ ፡ ፵፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰ ። ስንክ ፡ ሠኔ ፲፯ ። ዮሴፍ ። ገድ ፡ ኪሮ ። አፈ ፡ ድ፲) ።

**ማዕደን ፤ (ብ ፡ መዓድን ፤ አው ፡ ማዕደናት) ፤** በቁሙ ፡ የብረት ፡ መገኛ ፡ የሚጠበስና ፡ የሚቀልጥ ፡ የሚቀጠቀጥ ፡ ከወርቅ ፡ እስከ ፡ ርሳስ ፡ ፯ ፡ ዐይነትና ፡ ፯ ፡ ስም ፡ ያለው ።

**መዓድናት ፤** የብዙ ፡ ብዙ ። ንጽሕፍ ፡ ነገረ ፡ ንጻውንት ፡ ወመዓድናት ፡ (ጥፉ ፡ ስጥ) ።

**መዐወ ፤ (ሜዐ ። ሜመየ ፤ ምሀወ) ፤** ረጠበ ፡ ራሰ ፡ ለዘበ ፡ ለሰለሰ ፡ ላመ ፡ ጣመ ። ሰፈረ ፡ በታ ፡ ያዘ ። ጋላም ፡ ጣፈጠ ፡ ሲል ፡ ሚዐዊ ፡ ይላል ፡ ከመላም ፡ ከመጣም ፡ ይስማማል ።

**አምዐወ ፤** አረጠበ ፡ አራሰ ፡ አለሰለሰ ። አገባ ፡ ከተተ ፡ ሰፍረ ፡ አሲያዘ ።

**ማዕው ፤ ማዐውት ፤ (ብ ፡ አማዑት ። ዕብ ፡ ሜዒም ፤ ሜዖት ። ሱር ፡ ምዓያ ። ዐረ ፡ መዕይ ፤ ብ ፡ አምዓእ) ፤** አንጀት ፡ ሆድ ፤ የሆድ ፡ ዕቃ ፡ የመብል ፡ መሚሪያ ፤ ከንጀት ፡ ጋራ ፡ በብር ፡ ተያይዞና ፡ ተገናኝቶ ፡ ያለው ፡ ኋዋየ ፡ ውስጥ ። ማዕውና ፡ ማዑት ፡ ስላልተለመዱ ፡ አማዑት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሰብእ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ኹኖ ፡ ላንድም ፡ ይነገራል ። እስከ ፡ ይወፅእ ፡ አማዑቲከ ። ቦአት ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ውስተ ፡ አማዑቱ ። ሥብሕ ፡ ዘውስተ ፡ አማዑቱ ። ሕማመ ፡ አማዑት ። እምብካዮሙ ፡ ይትመሰዉ ፡ አማዑቲከ ፡ (፪ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፲፭ ። መዝ ፡ ፻፰ ። ዘሌ ፫ ፡ ፫ ። ማቴ ፳፰ ፡ ፫ ። ሚራ ፴ ፡ ፯) ። የብዙ ፡ ብዙ ፡ ሲኾን ፡ አማዕዋት ፡ ይሰኛል ፡ (ዘፍ ፵፫ ፡ ፴) ።

**ማዖን ፤ (ዕብራ) ፤** ቤት ፡ በታ ፤ የቤት ፡ ማእገዝን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፤ ጐን ፡ ጥግ ፤ አጠገብ ፡ ስብሳብ ።

**ምዕዋን ፤ (ናት) ፤** ሰሜን ፡ ግራ ፤ የደቡብ ፡ አንጻር ። መንገለ ፡ ምዕዋን ። መንጸረ ፡ ምዕዋን ፡ (ዘፀ ፳፯ ፡ ፴፩ ። ፳፯ ፡ ፲፩) ። ባሌብሌቶች ፡ ግን ፡ መስዕ ፡ ይሉታል ፤ የመስዕን ፡ ፍች ፡ እዩ ። ዳግመኛም ፡ በደቡብ ፡ ፊንታ ፡ ምዕዋን ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ገጸ ፡ ምዕዋን ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፲፰) ።

**ምዒዝ ፤ ዞት ፤ (ምዕዘ ፡ ይምዕዝ ፡ ይምዐዝ) ፤** መሸተት ፡ መልካም ፡ ሽታ ፡ መስጠት ፡ ላፍንጫ ፡ መጣፈጥ ፡ ጥሩ ፡ ሽቱ ፡ መኾን ። ዘይምዕዝ ፡ እምዘሉ ፡ መዐዛ ። ጽጌ ፡ ዘሠናየ ፡ መዐዛ ፡ ይምዕዝ ። ቤተ ፡ ክር ፡ እንተ ፡ ትምዕዝ ፡ ቅዐ ፡ ጽጌ ፡ ዘዕፀ ፡ ወይን ፡ (ሔኖ፳፬ ፡ ፬ ። እንቀ ፡ ብር ። ተረ ፡ ቄር ፡ ኤጲ፲፮) ። ዐዘዘን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ፤ በመዐዛው ፡ የዕዝዝ ፡ ምስጢር ፡ አለበት ።

**መዓዚ ፤ (ዚት ፡ ዝያን ፡ ያት) ፤** የሚሸት ፡ ሽታች ፡ ምዑዝ ፡ ባሕርይ ፤ ዕዙዝ ፡ መዐዛ ።

**አምዐዘ ፤** አማዘ ፤ አሸተተ ፡ ሸቱ ፡ ቀባ ፡ ረጨ ፡ ረበረበ ፡ ቀመመ ፡ አጣፈጠ ። ብእሲት ፡ እንተ ፡ ትሰድድ ፡ ባዔ ፡ ከመ ፡ ኢያማስኑ ፡ አልባሲሃ ፡ ወታምዕዞሙ ፡ በአፈዋት ። አምዐዝዎ ፡ በዮኅ ፡ ወቀበርዎ ። ሐዋርያት ፡ አምዐዙ ፡ ሾሎ ፡ ዓለመ ። አምዕዘኒ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፰ ። አቡሻ ፡ ፵፯ ። ቀሌ ። ቅዳ) ።

**ተምዕዘ ፤** ተሸተተ ፡ ተጣፈጠ ፡ ተቀመመ ፡ ተንጠረ ፡ ሽቱው ። ሽቱ ፡ ተቀባ ፡ ዘነበ ፡ ተረጨ ፡ ተረበረበ ፡ ሰውየው ፡ ወይም ፡ ልብሱ ። ዘተሰርገወት ፡ ሰርጓተ ፡ ወርቅ ፡ ወተምዕዘት ፡ አፈዋተ ። በዊአ ፡ ቤተ ፡ ብሰኔ ፡ ወተምዕዘ ፡ በዕፍረት ። በመዐዛሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ተምዕዙ ፡ ሐዋርያት ። ከመ ፡ እትመዐዝ ፡ በጼና ፡ አልባስኪ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፴፱ ፡ ፳ ። አቡሻ ፡ ፶ ። ቀሌ ። አርጋ ፡ ፫) ።

**ምዑዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ዕዝት) ፤** የሸተተ ፡ የተሸተተ ፡ የጣፈጠ ፡ የተጣፈጠ ። ሽቱ ፡ የተቀባ ፡ ቅቡዕ ።

ዕፍረት ፡ ምዑዝ ። ዘምዑዝ ፡ ጼናሁ ። ጽጌ ፡ ገነት ፡ ምዕዝት ። ዕፀዊሃ ፡ ምዑዛን ፡ (ቅዳ ። ዮሴፍ ። ፊላስ ። ድጓ) ። ሐዋዝ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ወዝንቱ ፡ ምዑዝ ፡ ለመትልወ ፡ ወይን ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ምሳ፲፪ ፡ ፲፩) ፡ በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ዝንቱና ፡ ምዑዝ ፡ የለም ፡ ለመትልወ ፡ ወይን ፡ ያለውም ፡ (ምራይፍ ፡ ሬቂም) ፡ ዘይደማን ፡ ክንቶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወይን ፡ አያሰኝም ።

**መዐዛ** ፤ (ዛት) ፤ በቁሙ ፡ ሽታ ፡ ሽቱ ፡ ሽቶ ። ጥዕመ ፡ መዐዛየ ፡ ከመ ፡ ቀናንሞ ። መዐዛ ፡ ሠናይ ። መዐዛ ፡ እኩይ ። ዕፀወ ፡ መዐዛ ። ኢትቀብዐት ፡ መዐዛተ ፡ (ሚራ፳፱ ፡ ፲፰ ። ዘሌ፳ ፡ ፱ ። መጽ ፡ ምስ ። ሐዋ፳፬ ፡ ፫ ። መቃ ፡ ፯፲፭) ። መዐዛ ፡ ማይ ፤ ስትይ ፡ ረውይ ፡ ጠል ፡ (ኢዮ፲፬ ፡ ፱) ።

**ምዕዛር** ፤—የብርሃን ፡ ጮራ ፤—ዐዚር ፡ ዐዘረ ።

**መዐክ** ፤—ተቈጣ ፤ ጨከነ ፤—ምኢክ ፡ መአከ ።

**ማዕከክ** ፤—ድስት ፡ ማሰሮ ፤—ዐኪክ ፡ ዐከከ ።

**ማዕከል** ፤—መካከል ፤—አኪል ፡ አከለ ፡ ማእከል ።

**መዐለ** ፤ (ይምዕል ፡ ይምዐል ፡ ምዒል ። ዕብ ፡ ማዐል) ፤ ታበየ ፡ ወነጀለ ፡ ከደ ፡ ከዳ ፡ ዐበለ ። መሐለን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ፡ መአከ ፡ የመሀከ ፡ ወንድም ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

**መዓሊ** ፤ **መምዐሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤ የሚታበይ ፡ ወንጀለኛ ፡ ዐባይ ፡ ከሓዲ ፡ ከዳተኛ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲፪ ። ኀሐ፳፰) ።

**መምዕል** ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። አይቴ ፡ ሀለዉ ፡ ነገሥት ፡ መምዕላን ፡ ወመዋእያን ። መምዕላን ፡ ነገሥት ፡ (ማንዘ ። ቀሌ) ። ለዐለ ንና ፡ ዐለወን ፡ ዐለየን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ፤ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ በመዐስ ፡ ፈንታ ፡ መስሙን ፡ መምዐስ ፡ ብለው ፡ ይገቡታል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ።

**አምዐለ** ፤ አዮነጀለ ፡ አስካደ ፡ አስከዳ ።

**ማዕሴት** ፤—ወንጀል ፡ ዐመፅ ፤—ዐለየ ።

**መዓልት** ፤—በቁሙ ፡ ቀን ፤—ውዒል ፡ ወዐለ ።

**ማዕምቅ** ፤—ጥልቅ ፡ ዐዘቅት ፤—ዐሚቅ ፡ ዐመቀ ።

**ማዕኖ** ፤—ዐዘባ ፡ ጭቃ ፤—ምኢን ፡ መአነ ።

**ማዕነፍ** ፤—የሥልስ ፡ ወጭት ፤—አኒፍ ፡ አነፈ ።

**ማዕነቅ** ፤—ቡላል ፤—ዐኒቅ ፡ ዐነቀ ።

**መዐንስብ** ፤—ሻርተኛ ፤—ዐሰበ ፤ ዐንሰበ ።

**ምዒዕ** ፤ ዖት ፤ (መዐዐ ፡ ይምዕዕ ፡ ይምዐዕ ። መዐወ ፤ ማዑት) ፤ መቈጣት ፤ መበሳጨት ፤ ማዘን ፤ መናደድ ፤ ከልብ ፡ ካንገት ። ምዒውና ፡ ምዒዕ ፡ ሱቱፋን ፡ ናቸው ። (ተረት) ፤ ካንገት ፡ ካዘኑ ፡ እንባ ፡ አይጠፋም ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመዐዐ ፡ ፈንታ ፡ ተምዐ ፡ ተምዕዐ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ባለቅኔዎችም ፡ ተምዐን ፡ ተቈጣ ፡ ተምዕዐን ፡ ተበሳጨ ፡ ብለው ፡ ብቻ ፡ ብቻውን ፡ ይገቡታል ። ተምዐ ፡ እግዚ ፡ ዐቢየ ፡ መዐተ ። ሶበ ፡ ትትመዐዕ ፡ ተዘከር ፡ ዕለተ ፡ ሞትከ ። ወሶበ ፡ አነ ፡ ተማዕኩ ፡ ኅዳጠ ። ተምዒዐከ ፡ (ኢሳ፳ ፡ ፳፰ ። ሚራ፲፰ ፡ ፳፱ ። ዘካ፳ ፡ ፲፰ ። መገ ፡ ፳፯) ።

**ምዑዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ዕዕት) ፤ የተቈጣ ፡ ቍጡ ፡ ብስጩ ፤ ተናዳጅ ፡ ጠበኛ ። መፍትው ፡ ትትዐገሥዎሙ ፡ ለምዑዓን ። ወገብረ ፡ ሰላመ ፡ ማእከለ ፡ ምዑዓን ፡ (ዲድ ፡ ፲ ። ፊልክ ፡ ፵፩) ።

**መዐት** ፤ **አው** ፡ **መዓት** ፤ በቁሙ ፤ መቈጣት ፡ መበሳጨት ። ማት ፡ ቍጣ ፡ ተግሣጽ ፤ ብስጭት ፤ ንደት ፡ ጩኸት ። ኢይቄርር ፡ መዓትየ ፡ ላዕለ ፡ ፀርየ ። ወነዳይሰ ፡ ኢይሰምዕ ፡ መዐተ ። በእንተ ፡ መዐት ፡ ወቍጥዓ ። መዐትኒ ፡ ወቍጥዓኒ ፡ ርኩሳን ፡ እሙንቱ ፡ (ኢሳ፳ ፡ ፳፱ ። ምሳ፲፫ ፡ ፰ ። ፊ ፡ መ ፡ ፳፭ ። ሚራ፳፯ ፡ ፴) ።

—፤ ብዛት ፤ ብዙኅት ፡ እጅግነት ። (ማጥም ፤ መርድ ፡ አምኃየስ ፡ ወጥ ፡ ቤታቸውን ፡ አሸክሬቸው ፡ ቢባለማት ፡ አይተው) ፤ ዓሣ ፡ የምትዘ ፡ መረብ ፡ የያዛቸኹ ፡ ያማማት ፡ ያማማት ፡ እኔ ፡ ላሳያችኹ ። ወሀቡ ፡ ህየ ፡ መዓተ ፡ ቍርባኖሙ ፡ (ሕገዝ፳ ፡ ፳፫) ።

**አምዐዐ** ፤ አስቈጣ ፡ አበሳጨ ፤ አሳዘን ፡ አናደደ ፤ አስቆጣ ፡ አስወገሸ ። ኵሉ ፡ ዘያምዕዕ ፡ እኂሁ ፡ በከንቱ ። ኢቀንእሙ ፡ ወኢያምዕዕሙ ። እንተ ፡ አምዐዐቶሙ ፡ ለነገሥት ፡ (ማቴ፭ ፡ ፳፪ ። ሮሜ፲ ፡ ፲፱ ። ኢሳ፳፫ ፡ ፲፩) ። በአድኅሮ ፡ ፈንታ ፡ አምዕዐ ፡ ይላል ፡ (ሚልዩ ፡ ፲፯) ።

**ተማዐዐ** ፤ ተጣላ ፡ ተቋጣ ፡ ተበሳጨ ። ተማዐዑ ፡ ወተፋለጡ ፡ (ግብ፲፭ ፡ ፴፱) ።

**ትምዕዕት** ፤ ቍጣ ፡ ብስጭት ፡ ብስጩነት ። ትምዕዕት ፡ ፍጥረታዊት ፡ (ፊልክ ፡ ፶፫) ።

**አስተማዐዐ** ፤ አጣላ ፡ አጋጨ ፡ አቋጣ ፡ አበሳጨ ። ኢያስተማዕዕ ፡ (አቄር ፡ ፲፫ ፡ ፳) ።

**ምዒር** ፤ ሮት ፤ (ምዕረ ፤ መዐረ ፡ ይምዕር ፡ ይምዐር ። ዐረ ፡ መረ) ፤ ፈጥኖ ፡ ማለፍ ፡ መር ፡ ቶር ፡ ማለት ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፤ ለማለፍና ፡ ለመሻገር ። መጣፈጥ ፡ መምተቅ ፤ ጥፍጥ ፡ መኾን ፡ ለጊዜው ፤ አፍን ፡ ዐልፎ ፡ ከጕረሮ ፡ እስኪወርድ ። ምስጢሩ ፡ ጊዜን ፡ አይለቅም ። መርዐን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ምዕር** ፤ (ብ ፡ ምዕራት ፤ የብ ፡ ብ ፡ ምዕራታት ። ዐረ ፡ መረት) ፤ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ፉት ፡ መዝ

መሬያ ፤ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ደቂቃ ፡ ቅጽበት ፤ ቆሎ ፡ እኹን ፤ ድንገት ፡ ወዲያው ። ምዕረ ፡ ለለ ፡ ዓመት ። ንጠይቅ ፡ ምዕረ ። ምዕረ ፡ ወካዕበ ። ብላዕ ፡ ወስተይ ፡ ምዕረ ፡ ወተፈማሕ ። ሖሩ ፡ ፍጡነ ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡ ለእንተ ፡ ምዕር ። ተኀባእ ፡ ኅዳጠ ፡ ምዕረ ። ወይከውን ፡ በጊዜሃ ፡ ለምዕር ። ይጤስ ፡ ምዕረ ፤ እኹን ፡ (ዘፀ፴ ፡ ፲ ። ዮዲ፳ ፡ ፳ ። ቲቶ፫ ፡ ፲ ። ጦቢ፮ ፡ ፲ ። ሚራ፲፰ ፡ ፳፮ ። ኢሳ፳፮ ፡ ፳ ። ፳፱ ፡ ፳ ። ፩ነገ ፡ ፱ ፡ ፲፮) ። በበ ፡ ምዕር ። ምዕራተ ፡ ብዙኃተ ። ምዕራትት ፡ (ኢያ፮ ፡ ፫ ። ፊ ፡ መ ፡ ፲፬ ፡ ፲ ። ፊልክ ፡ ፶፳) ።

**መዓር ፤ (ዕብ ፡ ያዓር ፤ ድብሽ) ፤** በቁሙ ፡ ማር ፡ የሚጣፍጥ ፤ እጅ ፡ የሚያስመጥጥ ፤ የንህብ ፡ ሥራ ። ምንተ ፡ ይጥዕም ፡ ዕመዓር ። ዐገቶ ፡ ከመ ፡ ንህብ ፡ መዓረ ፡ (መሳ፲ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፻፲፯) ።

**መዓረ ፡ ገዳም ፤** የ(ቀፎ)ማኅ ፡ ማር ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ (ማቴ፫ ፡ ፬) ።

**መዓረ ፡ ግራ ፤** የንጀራ ፡ መዓር ፤ እንጀራንት ፡ ያለው ፤ ወይም ፡ ግራ ፡ መዓር ፤ የማር ፡ እንጀራ ። መዓር ፤ ወለላው ፤ ግራ ፡ እንጀራው ፡ ማግሩ ፡ ዐይኑ ፡ ጠቃጠቆው ፡ ሰፈፉ ፡ ሠሙ ፡ የነጠረው ፡ የተጋገረው ፤ ሲቀላጥ ፡ ወለላ ፡ መስሎ ፡ የሚፈሰው ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሠሙን ፡ አይሮማል ፡ ብለው ፡ ይጨምሩበታል ፤ ግራን ፡ እይ ። ወይትመሰጠ ፡ ከመ ፡ መዓረ ፡ ግራ ። በከመ ፡ መዓረ ፡ ግራ ፡ የኀትም ፡ ሰብእ ፡ በማኅተመ ፡ ወርቅ ፡ (ሔኖ፰ ፡ ፯ ። ቄር) ።

**መዓረ ፡ ዕፅ ፤** ሠሙ ፡ የይሮ ፡ ማር ፡ ወይም ፡ አይሮማል ፡ ከንጨት ፡ የሚገኝ ።

**መዓረ ፡ ጸደና ፤** የጣዝማ ፡ ማር ፡ ከምድር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ (ማር፩ ፡ ፯) ።

**መዐርዒር ፤** መዓራዊ ፡ የሚጣፍጥ ፡ ጣፋጭ ፡ ጥፍጥ ፡ ማር ። ማር ፡ የሚል ፡ የማር ፡ ወገን ። መሬር ፡ ወመዐርዒር ። ማየ ፡ ሰርቅ ፡ መዐርዒረ ፡ ስተይ ። ነገረ ፡ ገድሉ ፡ መዐርዒር ፡ ለተናግሮ ፡ (ሔኖ ። ምሳ፱ ፡ ፲፯ ። ድጓ ። ማሕ፳ ፡ ፲፯) ።

**ምዕርዕርና ፤** ማርነት ፡ ጥፍጥነት ፤ ማር ፡ ማር ፡ ማለት ፡ መጣፈጥ ። ጣዕመ ፡ ምዕርዕርናከ ፡ (ጥበ፲፮ ፡ ፳፩) ።

**አምዐረ ፤ አምዐርዐረ ፤** አጣፈጠ ፡ አጠፋፈጠ ፡ ማር ፡ አደረገ ፤ ማር ፡ አላሰ ፡ በማር ፡ ለወሰ ። እንተ ፡ ለጊዜሃ ፡ ታመዐርዕሮ ። ከመ ፡ ኢያምዐርዕር ፡ ጕርዔከ ፡ (ምሳ፭ ፡ ፫ ። ቀ፱ ፡ ፲፫) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ አመርዐረ ፡ ብሎ ፡ ምርዕርና ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**ማዕስ ፤—ማስ ፡ ቈርበት ፤—መአሰ ፡ ማእስ ።**

**መዐስብ ፤—ፈት ፡ ብቸኛ ፤—ዐሰበ ።**

**መዐት ፤—በቁሙ ፥ ቍጣ ፤—ምዒዕ ፡ መዕዐ ።**

**ማዕተብ ፤—ምልክት ፤—ዐተበ ፡ ዐተበ ።**

**ምዕትዝላ ፤ (ዐረ ፡ እልመተዚለት) ፤** ሊሉያን ፤ ፍልስጣን ። በባህል ፡ በትምርት ፡ ከፈሪሳውያን ፡ ተለይተው ፡ ለብቻቸው ፡ ማኅበር ፡ ያቆሙ ፡ ከስምንቱ ፡ ክፍል ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ አንዱ ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ እልመተዝዕላን ፡ ይሏቸዋል ፡ (ዮሴፍ ፡ ገ፫፶) ።

**መዐትም ፤—ቍጡ ፡ ክፉ ፤—ዐተመ ።**

**ሞፍጥ ፤—መተኰሻ ፤—ወፈጥ ፡ ወፈጠ ።**

**ሞፈር ፤—በቁሙ ፤—ወፈር ፡ ወፈረ ።**

**ሜፎቲ ፤ (ዕብ ፡ ሚፎ(ፔ)ቲ) ፤** ማ ፡ እም ፡ ፎቲ ፡ ምኝ ፡ የቀሀ ፤ ሕጹጸ ፡ እእምሮ ፡ ሰሑት ፤ ፈታዊ ። እምብእሲ ፡ ሾጌ ፡ ወሜፎቲ ፡ (ሕዝማ፳ ፡ ፳) ።

**መጺእ ፤ እት ፤ (መጽአ ፡ ይመጽእ ፡ ይምጻእ ። ዕብ ፡ ማጻእ ። ሱር ፡ ምጻእ ፤ ረከበ) ፤** መምጣት ፤ መገኘት ፡ መኾን ። ዘመጽአ ፡ ወካዕበ ፡ ይመጽእ ። እምአይቴ ፡ መጻእነ ፡ ወመኑ ፡ ፈጠረነ ። ወመጽአ ፡ ረኀብ ፡ ውስተ ፡ ብሔር ፡ (ውዳ ፡ ማር፱ ። አክሲማ ። ሩትኛ ፡ ፩) ።

**መጻኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤** የሚመጣ ፡ የሚገኝ ፤ መፊጪ ፡ ኋኝ ፤ መጪ ፡ መጣተኛ ። ኀቀየ ፡ መጻኢ ፡ ዓለም ። ኀሊናት ፡ ወጠባይዓት ፡ ወመጻእያት ፡ ዘውስጥ ፡ (ደራሲ ። ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ። አፈ ፡ ድ፲) ።

**ምጹእ ፤ (አን ፡ ኢት ፡ ጽእት) ፤** የመጣ ፡ የተገኘ ፡ የኾነ ፤ መጥቶ ፡ ያለ ።

**ምጽአት ፤** መምጣት ፤ አመጣጥ ። አሐቲ ፡ ይእቲ ፡ ምጽአቱ ፡ ለኵሉ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ። በምጽአትየ ፡ ካዕበ ፡ ኅቤክሙ ። ሠናይ ፡ ምጽአትከ ፡ (ጥበ፯ ፡ ፭ ። ፊልጵ፩ ፡ ፳፮ ። ገድ ፡ ተክ) ።

—፤ በቁሙ ፡ ምጣት ፤ ድንገተኛ ፡ ነገር ፥ አደጋ ፡ መቅሠፍት ፡ ራብ ፡ ችጋር ፡ (በማርኛ) ። ምጣት ፡ ያምጣብኽ ፡ እንዲሉ ።

**ምጽአታዊ ፤** የምጽአት ። ምጣታም ፡ ምጣተኛ ፡ ሆዳም ፡ (በማርኛ) ።

**አምጽአ ፤** አመጣ ፤ አስመጣ ፤ አስገኘ ። ኣመጽእ ፡ እኪተ ፡ እምደቡብ ። በእንተ ፡ ዘፈጠረነ ፡ ወአምጽአነ ፡ (ኤር፬ ፡ ፮ ። አፈ ፡ ድ፬) ። በአምጽአ ፡ ፈንታ ፡ አስተማጽአ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እመጻሕፍቶሙ ፡ ዘይበቍዕ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ አስተማጺእየ ፡ ምዝማሬ ፡ (ቄር ፡ እስት) ። ዳግመኛም ፡ አንሥአ ፡ ፈነወ ፡ ረሰየ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አምጽአ ፡ ይላል ፤ ምስክሩን ፡ በተራው ፡ እይ ። ኣመጽእ ፡ ላዕሌከ ፡ እኪተ ፡ እምነ ፡ ቤትከ ። አምጽአ ፡ ነፋስ ። ታመጽእ ፡ ጽልመተ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፲፩ ። ዮና፩ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፻፫) ።

**አምጻኢ ፤ መምጽኢ ፤ እ ፤** የሚያመጣ ፡ አምጭ ፤ አስመጭ ፡ አስገኝ ። አምጻኤ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ። መምጽ(ኢ)እ ፡ ምስጢር ፡ (ፈላስ ። ቄር) ።

**ምምጻእ** ፤ (ኢት) ፤ መምጫ ፤ መገኛ ፡ ቦታ ። ወምምጻኢ ፡ አፍራቢሁ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ። ይወፅኡ ፡ አርባዕቱ ፡ ዕደው ፡ ወኢይትአመር ፡ ምምጻአሙ ፡ (፩ዜና ፡ ፳ ፡ ፲፯ ። ፱ ፡ ፳፰ ። ሳቤላ) ።

**ተማጽአ** ፤ ተማጣ ፡ ተመጣጣ ፤ ተሳሳበ ፡ ተጓተተ ።

**አስተማጽአ** ፤ አማጣ ፡ አመጣጣ ፤ አናዳ ፡ አማሟ ፡ ኾነ ፤ በእግር ፡ በነገር ። ወልድየ ፡ ኢትደመር ፡ ለአስተማጽኦ ፡ ብእሲት ፡ (ፈላስ) ።

**መጽአሞ** ፤—ድምፅ ፡ ጩኸት ፤—ጽኢም ፡ ጸአመ ።

**ምጽዋት** ፤—በቁሙ ፤—ጸዊት ፡ ጸተ ።

**መጽሔት** ፤—መስታዮት ፤—ጸሐየ ።

**መጽለወ** ፤—ጠወለገ ፤—ጸሊው ፡ ጸለወ ፡ መጽልው ።

**መጺጽ** ፤ ጺት ፤ (መጺ ፡ ይመጽጽ ፡ ይምጽጽ ። ዕብ ፡ ማጸጽ ። ሱር ፡ ማጽ ። ዐረ ፡ መጺ) ፤ መምጠጥ ፡ መመጥመጥ ፤ መጥበት ፡ በክንፈር ፡ መሳብ ፤ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ መጠጣት ፡ መጕንጨት ። ስትየ ፡ ብሎ ፡ ጠጣ ፡ ማለት ፡ በማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። መፀን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**መጺረ** ፤ ፀነከ ፡ አሳመጠ ፡ አመሰኳ ፡ ኰረጠመ ፡ በጥርስ ፤ ለመምጠጥ ፡ ወይም ፡ ለመዋጥ ፤ ያገዳ ፡ የምግብ ። መጸና ፡ መጸረ ፡ ፩ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ ጸና ፡ ረ ፡ ስለ ፡ ተዋረሱ ፡ መንታ ፡ ኹነዋል ። ኢትልሳሕ ፡ እንዘ ፡ ትሜጽር ። እለ ፡ ሥርወ ፡ ዕፀ ፡ ይሜጽሩ ፡ እምዐቢይ ፡ ረኃብ ። እስከ ፡ ይሜጽሩ ፡ ልሳናቲሆሙ ፡ (ሢራ፴፬ ፡ ፲፯ ። ኢዮ፴ ፡ ፬ ። ራእ፲፮ ፡ ፲) ።

**መጸር** ፤—መሸከሚያ ፤—ጸዊር ፡ ጸረ ።

**መጽርይ** ፤—ጥሩ ፡ አበባ ፤—ጸርይ ፡ ጸርየ ።

**መፃጕዕ** ፤—በቁሙ ፡ ገቦጣ ፤—ፀጊዕ ፡ ፀግዐ ።

**መፀወ** ፤ (ጸገየ ፤ ጼነወ ፤ መጠወ) ፤ አበበ ፡ አበባ ፡ ያዘ ፤ አረገዘ ፡ ደበደበ ፡ ለማፍራትና ፡ ለመውለድ ፡ ለመዘርዘር ። ምስጢሩ ፡ መፀዘ ፡ መስጠት ፤ እንቡጥና ፡ ፍሬ ፡ ማሳየት ፡ ነው ፤ ከጥሬው ፡ በቀር ፡ አንቀጹ ፡ አይገኝም ።

**መፀው** ፤ የክፍለ ፡ ዓመት ፡ ስም ፡ ያመት ፡ ርቦ ፤ ወይም ፡ ሩብ ፡ ጸአ—፲፭ ፡ ቀን ፡ ከመስከረም ፡ ፳፮ ፡ እስከ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፯ ። ወርኀ ፡ ጽጌ ፡ ዘመነ ፡ ጽጌ ፡ ማለት ፡ ነው ። ክረምት ፡ ወመፀው ፡ ማእረር ፡ ወሐጋይ ። ያዘንም ፡ ለክሙ ፡ ጸደየ ፡ ወመፀወ ። ይሁበነ ፡ ዝናመ ፡ ተወን ፡ ወመፀው ፡ (ኩፋ ፡ ፲ ። ዮኤ፪ ፡ ፳፫ ። ኤርሚ ፡ ፳፬) ።

**መፀ** ፤ መፀፀ ፤ መጠጠ ፤ ሖመጠጠ ፤ መጣጣ ፡ ኾነ ፡ ያበባው ፡ ፍሬ ፡ ቃሪያው ። (የገና ፡ ስድብ) ፤ ሳይነኩኝ ፡ አልነካም ፡ ሲነኩኝ ፡ አልሸሽም ፤ እኮማጠጣለኹ ፡ እንደ ፡ ቃሪያ ፡ ኩሽም ። ቦካ ፤ በሰለ ፤ ሟከከ ፡ ተንደረከከ ፤ የርሾና ፡ የመጠጥ ፡ የፍሬ ፤ መብሰል ፡ ለኹሉ ፡ ይኾናል ።

**መፂፅ** ፤ (ፃን ፡ ፃት ፡ ፃፅ) ፤ መጣጣ ፡ ሖምጣጣ ፤ ቃሪያ ፡ እንጭጭ ፡ ጨርቋ ፤ ወይም ፡ የቦካ ፡ የበሰለ ፡ ብስል ። ቃሪያንና ፡ ብስልን ፡ መሖምጠጥ ፡ ያገናኛቸዋል ። ብሒእ ፡ ወመፂፅ ። ተሠላት ፡ መሪራን ፡ ወመፂፃን ። ወይፈሪ ፡ ፍሬ ፡ መፂፀ ፤ ብስል ፡ (ቅዳ ፡ አፈ ። ቄር ፡ ጸላ ። ኢሳ፲፰ ፡ ፭) ።

**ምፀት** ፤ መጣጥነት ፤ መጣጣ ፡ ሖምጣጣ ፡ መኾን ። በቁሙ ፤ የተሣልቆ ፡ ቃል ፤ ሰሚውን ፡ የሚያሥቅና ፡ የሚያስደንቅ ፤ ተቀባዩን ፡ ግን ፡ የሚያሳዝን ፡ የሚያኮማጥጥ ፡ ልውጥና ፡ ግልብጥ ፡ አነጋገር ። ጋን ፡ ታረደ ፤ ሙክት ፡ ተዘነበለ ፤ ጊዮርጊስ ፡ ሊቀ ፡ መሳእክት ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ ሰማዕታት ፤ ይህን ፡ የመሰለ ። ለዳዊት ፡ ወሬዛ ፡ ፋሲለደስ ፤ ፈረሱ ፡ ቀዋሚ ፡ ከመ ፡ ነፋስ ፡ ወፈረስ ፡ ፀሩ ፡ ረዋጺ ፡ ከመ ፡ አድማስ ፡ (ቅኔ) ።

**መዓዊት** ፤ (ዕብ ፡ ተሓሽ ። ዐረ ፡ ቱኅሽ) ፤ ያውሬ ፡ ስም ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ አውሬ ፡ እንደ ፡ ተኵላና ፡ እንደ ፡ ነብር ፡ ያለ ፡ ነጣቂ ፤ ጠጕረ ፡ ልም ፡ ቴርበተ ፡ መልካም ። መጣጡ ፡ ሖምጣጡ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ስሙ ፡ የጠባዩን ፡ ክፋት ፡ ያሳያል ፤ ተሓሽ ፡ ያለውም ፡ በሖስ ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፤ ተሐዋሲ ፡ ቀበጥ ፡ ቅብጥብጥ ፡ ያሰኛል ። ቄርበቱ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ የከበረ ፡ ጥኑ ፡ ጠንካራ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሙሴ ፡ ለድንኳኑና ፡ ለመጋረጃ ፡ ኹሉ ፡ ልብሰና ፡ ክዳን ፡ አድርጎታል ፤ የግእዝ ፡ አረቅ ፡ መዓዊት ፡ ማእስ ፡ መዓዊት ፡ የሚለው ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ አውሬ ፡ ነው ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ስማያዊ ፡ ጥቍር ፡ ይሉታል ፡ (ዘፀ ፳፭ ፡ ፭ ፡ ፳፫ ። ፴፱ ፡ ፲፰ ። ዘኍ፬ ፡ ፮ ፡ ፰—፲፬ ፡ ፳፭) ።



መዓዊት ፡

**ሞቀ** ፤—በቁሙ ፤—መዊቅ ፡ ቆት ።

**ሞቅሐ** ፤—አሰረ ፤—ወቂሕ ፡ ወቅሐ ።

**መቃይጽ** ፤—የጭን ፡ ብረት ፤—ቀየጽ ።

**መቅለድ** ፤—ዳካ ፡ ኰስኰስት ፤—ቀለደ ።

**መቀኵዐል** ፤—ሥብ ፡ ሬጫ ፡ ወረሞ ፤—ቄዐለ ።

**ማቂፈም** ፤ (ዕብራ) ፤ የሚያቅፉ ፡ የሚነቡ ፡ ዙሪያዎች ። ዘሩ ፡ ሐቀፈ ፡ ነው ፡ (፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፳፱) ።

**መቅፀ·ት ፤-ድስት ፤-ቀዊ·ው ፡ ቀፀወ ።**

**መቀቀ ፤(መቂቅ ፡ መቀ ። ዕብ ፡ ማቆቅ ፡ ሂሞቅ)** ፤ ማቀቀ ፤ ማቅ ፡ ሰበሰ ፡ ባለመከራ ፡ ኾን ፤ ቀለጠ ፡ ሖሖ ፤ አነሰ ፡ ኰሰሰ ፤ አረጀ ፡ ተበላሸ ። ጣጣ ፡ አንጣጣ ፤ የጕረሮ ። **ወመቀቀ ፡ ጕርዔሁ ፡**(ታም ፡ ማር ፡ የካ፲፰) ።

**መቄረ ፤ (ይሜቀ·ር ፡ ይመቀ·ር ፤ መቀ·ሮ ። ዐረ ፡ መቀረ)** ፤ ዐጀለ ፡ ነከረ ፡ ዘፈዘፈ ፡ አጣፈጠ ፡ በጨው ፡ በመጣጣ ፤ የዓሣ ፡ የዘይት ፡ የቃሪያ ፡ የልፍት ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**ተመቄረ** ፤ ታጀለ ፡ ተነከረ ፤ ተጣፈጠ ።

**ምቁር ፤(ራን ፡ ራት ፡ ቀ·ርት)** ፤ የታጀለ ፡ የተነከረ ፡ የተዘፈዘፈ ። **ምቁረ ፡ ኤልያስ ፡**(ምቁር ፡ ኤልያስ) ፤ የተጣፈጠ ፡ ዘይቶን ፡ የወይራ ፡ ፍሬ ፡ (ሥር ፡ ጸሎ) ።

**መቀ·ስ ፤ ሰት ፤ (መቂስ ፡ ይሜቀ·ስ ፡ ይመቀ·ስ)** ፤ መቀ·ረጥ ፤ መለየት ፡ ማጥፋት ። መቀስ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። (ተረት) ፤ ቀስ ፡ በመቀስ ። **ይሜቀ·ስ ፡ እግዚ ፡ እምሀብቱ ፡ እንተ ፡ አሰፈወ ፡ ሰኔራን ፡ ሥዩማነ ፡ ቤተ ፡ ክር ፡**(ቀሌ ። መቃ ፡ ፻፰) ።

—፤ ማገበል ፡ መክዳት ፡ ቃልን ፡ መለወጥ ። **ኢይሜቀ·ስ ፡ እግዚ ፡ ዘወፅአ ፡ እምአፉሁ ፡፡ ኢይሜቀ·ስከ ፡**(መዋሥ ። ሄርማ ፡ ፻፴፯) ።

**መቋሲ ፤ መመቀ·ስ** ፤ የሚቈርጥ ፡ የሚለይ ፡ አጥፊ ፤ ፀባይ ፡ ዋሻ ፡ ቀጣፊ ።

**ተመቄሰ** ፤ ተቈረጠ ፡ ተለየ ፤ ተከለከለ ፡ ፀጣ ፡ ተቸገረ ። **ሖሎ ፡ ዘሰአሳ ፡ አዕይንትየ ፡ ኢተመቄሰኩ ፡፡ ሰእሰቱ ፡ ዚአነ ፡ አብአ ፡ ኅበ ፡ አቡሁ ፡ ምእመን ፡ ወኢይትሜቄስ ፡**(መክ፪ ፡ ፲ ። ተረ ፡ ቄር፲፰) ።

**ማር ፤ ማሪ ፤ (ሱር)** ፤ እግዚእ ፤ ጌታ ። ለግዜርም ፡ ለሰውም ፡ ይነገራል ፡ ስምንቱ ፡ ግን ፡ ያምላክ ፡ ነው ። ማር ፡ ኤፍሬም ፡ ሶርያዊ ፡ ማሪ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘስሩግ ፡ ቢል ፤ የኔታ ፡ (የኔ ፡ ጌታ) ፡ እገሌ ፤ ጌታዬ ፡ እገሌ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ሃይ ፡ አበ) ። ማርታም ፡ ማለት ፡ እንደዚሁ ፡ እግዝእት ፡ እመቤት ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ማራን ፤ ማራና** ፤ እግዚእነ ፡ ጌታችን ። በምራን ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ግን ፡ የሚማርን ፡ ማራኝ ፡ የሚያስር ፡ የሚያቈራኝ ፡ ኹሉን ፡ የሚዳኝ ፡ ሰው ፡ አይፈሬ ፡ መልአክ ፡ አያፍሬ ፡ የፍርድ ፡ ገበሬ ፡ ያሰኛል ። (ማቴ፲፫ ፡ ፬ ፡ ፴፪—፵፪) ።

**ማራን ፡ አታ ፤ (እግዚእ ፡ መጽአ)** ፤ የሐዲስ ፡ መላሽ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፳፪) ፡ እስከ ፡ ምጽአቱ ፡ ለእግዚእን ፡ ያለውን ፡ የቁርሎስ ፡ መላሽ ፡ እንደ ፡ ጽርኡና ፡ እንዳረቡ ፡ ሐዲስ ፡ ማራን ፡ አታ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ፩ ፡ ቃል ፡ አድርጎ ፡ መራናታ ፡ ይላል ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ ባለቢቃውንትም ፡ ሳይቀሩ ፡ የቁርሎስ ፡ ቃል ፡ መስሏቸው ፡ ለርሱ ፡ ሰጥተው ፡ ይፈታሉ ፡ ፍችውንም ፡ መቅረዚ ፡ መብራቷ ፡ ይሉታል ። ባለቅኔዎችም ፡ መረን ፡ አበራ ፡ ብለው ፡ ይገሉታል ፤ የኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ያማርኛውን ፡ ሐዲስና ፡ መናረትን ፡ እይ ፡ ነዊር ፡ ኖረ ፡ (ዕብ፱ ፡ ፪) ።

**ማራ** ፤ የኪሩቤል ፡ ስም ፡ ገዢ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፤ እግዚእ ፤ እግዚአዊ ፡ ዘእግዚእ ። ምስጢሩ ፡ ገጸ ፡ ሰብእን ፡ ያያል ፡ መደበኛው ፡ ርሱ ፡ ነውና ። **በራ ፡ ማራ ፡**(መዋሥ) ።

**ሞራእ ፤—ግልድም ፥ ሞራ ፤—ወሪእ ፡ ወርአ ።**

**መረብ ፤—በረሐ ፥ ወጥመድ ፤—ረቢብ ፡ ረበ ፤ ረበበ ።**

**መረግ ፤ ጎት ፤ (መረገ ፡ ይመርግ ፡ ይምርግ ። ዕብ ፡ ማራግ ፤ ነቀለ ፡ አፈለሰ ። ማራሕ ፤ መረገ ፡ ለሰነ)** ፤ መምረግ ፤ መለጠፍ ፡ መለሰን ፤ መግዝጋት ፡ መድፈን ፤ መቅባት ፡ መለቅለቅ ፤ የጭቃ ፡ የበት ፡ የሞራ ፡ የሺሚንት ። **ይመርግዎ ፡ ለውእቱ ፡ ቤት ፤ ወእምድኅረ ፡ መረግዎ ፡፡ ጽቡር ፡ በዘይመርጉ ፡ ቦቱ ፡፡ ወትመርጎ ፡ መሬተ ፡ ጸዐዳ ፡** (ዘሌ፲፬ ፡ ፵፪ ፡ ፵፫ ። ኩፋ ፡ ፲ ። ዘዳ፳፯ ፡ ፪ ፡ ፬) ።

**አምረገ** ፤ አስመረገ ፡ አስለሰን ፡ አስቀባ ፡ አስለቀለቀ ።

**ተመርገ** ፤ ተመረገ ፤ ተለሰነ ፡ ተለቀለቀ ።

**ምሩግ ፤ (ጋን ፡ ጋት ፡ ርግት)** ፤ የተመረገ ፡ ምርግ ፤ ልስን ፡ ልቅልቅ ። **ቤት ፡ ምሩግ ፡፡ ይረክቦ ፡ ምሩገ ፡**(ምሳ፳፭ ፡ ፬ ። ማቴ፲፱ ፡ ፳፬) ።

**ምረግ ፤ (ጋት ፡ አምራግ)** ፤ ምርግ ፡ ምርጊት ፤ ልስናት ፡ ልቅልቃት ። **ከመ ፡ ምረገ ፡ አረፍት ፡፡ አይቴመ ፡ ምረግ ፡ ዘመረግሙ ፡፡ ምረገ ፡ ኆዳ ፡ ውስተ ፡ አረፍት ፡**(ኢዩ፴፫ ፡ ፳፬ ። ሕዝ፲፫ ፡ ፲፪ ። ሢራ፳፪ ፡ ፲፯ ። ዳን፭ ፡ ፭) ።

**መርግግ** ፤ መረገገ ፡ ጐመዘዘ ፡ መርጋጋ ፡ ኾነ ፡ አፍ ፡ ያዘ ፡ እንደ ፡ ጭቃ ፡ (ፀማርኛ) ።

**መረግድ ፤—በቁሙ ፤ ርግዶ ፤—ረገደ ፡ ፀ ።**

**መረግድ ፤ ዘመረግድ ፡ (ጽር ፡ ስማራግዶስ ። ዕብ ፡ ባሬቄት ፤ ዝማርጋድ ። ሱር ፡ ዝማርግዳ ። ዐረ ፡ ዘበርጀድ ፤ ዙሙሩድ)** ፤ ዕንቍ ፤ የዕንቍ ፡ ስም ፤ ሕብሩ ፡ ሐመልሚል ፤ ወይም ፡ የባሕር ፡ ውሃ ፡ የሚመስል ፤ የሚበርቅ ፡ የሚያብረቀርቅ ። በዐረቡ ፡ ዘበርጀድና ፡ ዙሙሩድ ፡ ልዩዎች ፡ ናቸው ፤ ዘበርጀድ ፡ ተርሴስና ፡ ክርስቲሎቤ ፡ ክርሴምቶን ፡ ከሰው ፡ ይስማማል ። **እብን ፡ ዘሕብረ ፡ መረግድ ፡፡ ይመስል ፡ ሕብሩ ፡ ከመ ፡ መረግድ ፡፡ ወንግእ ፡ ክልኤ ፡ እብነ ፡ መረግድ ፡**(አስቴ፩ ፡ ፮ ። ራእ፬ ፡ ፫ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፱ ፡ ፲፰) ። **ወገብሩ ፡ ሖሎ ፡ እብነ ፡ ዘመረግድ ፡፡ ወራውሬ ፡ ወዘመረግድ ፡፡ ወራብዐት ፡ በዘመረግድ ፡**(ዘፀ፴፮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ። ራእ፳፩ ፡ ፲፱) ።

**ምርጉዝ**፤—በቁሙ፤—ረጊዝ፡ረጊዝ።

**መርግሕ**፡—መርግ፤—ረግሐ።

**መርዶ**፤ዶት፤(መረደ፡ይሜርድ፡ይመርድ። ዕብ፡ማራድ። ሱር፡ምራድ። ዐረ፡መሩደ)፤ መሞረድ። መሸፈት፡ማመጥ፡መውረር፡መዝረፍ፡ማሸበር። መረደ፡ሀገሮሙ፡ለሳምራውያን፡ወአንኀለ፡መቅደሶሙ፡(ዮሴፍ)።

—፤ መጠብጠብ፡መሮጥ፡መንምገም፡ቶሎ፡ቶሎ፡መኼድ፡ቸኩሎ፡መራመድ። ዘይሜርድ፡ፍኖተ። መረዱ፡ይደግንዎሙ። ውስተ፡አርእስተ፡አድባር፡ይሜርዱ። ለእመ፡መረድከ፡ላዕሌሆሙ፡(መዝ፡፻፰። ጥበ፲፱፡፪። ዮኤ፲፡፰። ዘፍ፴፫፡፲፫)። ሮደንና፡ደጋንን፡እይ፡የዚህ፡ጎሮች፡ናቸው።

**መራዲ**፤(ዲት)፡አው፡**መራድ**፤(ያን፡ያት)፤ የመረደ፡መራጅ፤ ሽፍታ፡ወራሪ፡ጠባጣቢ፡ገምጋሚ፡ሰራዊት፡ጭፍራ፡የጦር፡ሕዝብ፡ዘማች። ፈኖከ፡መራደ፡ትንንየ፡ይቅድሙ፡ተዓይኒከ። በእንቲአከሙ፡አፈኑ፡ባቢሎን፡መራደ። ወሰአሎ፡ለፍምፍምዮስ፡ከመ፡ይፈኑ፡ሎቱ፡መራደ፡መርድአ፡ላዕለ፡አንሡሁ፡(ጥበ፲፪፡፰። ኢሳ፵፫፡፲፬። ዮሴፍ)። ሀጕል፡ቀትል፡መበት፡ስደት፡በማለት፡ፈንታ፡መራድ፡ይላል፤የመሳሽ፡ስሕተት፡ነው። መራደ፡ረሲዓን። እለ፡ይትቃተሉ፡ውስተ፡መራድ። ወዐቀበ፡መራደ። አንሥኡ፡መራደ፡(ምሳ፲፡፳፫። ዮኤ፪፡፳። ዓሞ፩፡፲፭። ማብ፲፫፡፲)።

**መራድ**፤የሚሞርድ፡ሞራጅ፤ሰው፡ወይም፡ሞረድ፤መራጃ፡ታላቅ፡መይሻ። የዕቡይ፡ሞረድ፡እንዲሉ። በረደንና፡በርደደን፡እይ። መና፡በ፡ይዋሩሳሉ፡ዝናም፡ብ።

**ተመረደ**፤ተሞረደ፤ተወረረ።

**ምሩድ**፤(ዳን፡ዳት፡ርድ)፤ የተሞረደ፡ሙርድ፡የተወረረ፡የተዘረፈ።

**መርድ**፤ የከበሬታ፡ስም፡ከራሶች፡በላይ፡ከንጉሦች፡በታች፡መካከለኛ፤የሺዋ፡ባላልጋ፡ወይም፡ዐልጋ፡ወራሽ፡የንጋሢ፡ዘር፡የሚጠራበት። መርድ፡አምኃየስ፡መርድ፡ኀይሉ፡እንዲሉ።

**መርደደ**፤(ተቀ፡ግ)፤ ደፈረ፡ጨከነ፡ተጋፈጠነ።

**ምርዱድ**፤ ደፋር፡ጨካኝ፤ትጉ፡ፈጣን፡ሥራጠን፡መንገዱን፡የማይቆም፡የማይቋርጥ፡(ኄርማ፡ገጺና፡፲)።

**መረሐ**፤ሐት፤(መርሐ፡ይመርሕ፡ይምራሕ። ዕብ፡ማራሕ፤ቀባ፡መረገ፡ዐሸ)፤ መምራት፤ራት፡ፋት፡መኼድ፡መሳብ፡መውሰድ፤የመንገድ፡የትምርት፡የዜማ፡የጸሎት። መረየን፡እይ፤የዚህ፡መንቲያ፡ነው። መሪሐ፡ይመርሐሙ። መልአክ፡ዘይመርሐኒ። እለ፡ይመርሑ፡ወእለ፡ይትልዉ። ዘመርሐኒ፡ውስተ፡ብሔረ፡ቢድው፡(፩ነገ፡፲፡፳። ሰር፡ኢሳ፷፫፡፲፬። ማርቆ፲፮፡፲። ኤርሚ፡፳)።

—፤ ማሳየት፡ማስረዳት፤መግለጥ፡ማስረገጥ፡የነገር፡የምስጢር። ወይመርሕ፡ኀበ፡ዝንቱ፡ቃሉ፡ለልዑል። ተወክፎተ፡ሠያጢ፡ዐረቦነ፡እምእደ፡ተማያጢ፡ይመርሕ፡ኀበ፡ፍጻሜ፡ሠዩጥ፡ወተማይጦ፡(ፍ፡ነ፡፳፱፡፩። ፀሐ)። በመርሐ፡ፈንታ፡አምርሐ፡ይላል፡ስሕተት፡ነው። አንተ፡አምራሕከ፡ጽድቀ፡ወኀጢአተ፡ወፈለጥከ፡ብርሃነ፡ወጽልመተ፡እኩየ፡ወሠናየ፡(ኪዳ)።

**መርሕ**፤ **መራሒ**፤(ብ፡ አምርሕት)፤ የሚመራ፡መሪ፤መምር፡አብነት። አንተ፡መርሖሙ፡ለዕዉራን። ፈጺስቆጵስ፡ውእቱ፡መርሖሙ፡ለሕዝብ። አንትሙሂ፡መርሐ፡ኩንዎሙ። እስመ፡ውእቱ፡መርሕ፡ውስተ፡ጥበብ፡(ሮሜ፪፡፲፱። ዲድ፡፬። ኪዳ። ጥበ፯፡፲፭)። ንትሉ፡አምርሕተ፡ሠናይ፡ፍኖት። ዕዉራን፡አምርሕተ፡ዕዉራን፡(ቅዳ፡ሕር። ማቴ፲፭፡፲፬። ሽ፤ ፲፮፡፭፬)።

**መራሒ**፤(ሒት፡ሕያን፡ያት፤ሕት)፤ ገዢ፡ከማሁ፡መሪ፡አስተማሪ። መራሒ፡ሕይወት። መራሒ፡ዘሉ፡እኩይ። ዛቲ፡መጽሐፍ፡መራሒት፡ልቡና፡ይእቲ። መራሕያነ፡ብርሃን፡(ኪዳ። ቀሌ። ፈላስ። ቅዳ፡መስተ)።

**መራሕያን**፤ የርባታ፡መደቦች፡ዐሥሩ፡ሰራዊት፤አነ፡አንተ፡ቲ፤ውእቱ፡ይእቲ፤ንሕነ፡አንትሙ፡ን፤ውእቶሙ፡ን። ቀተልኩ፡ከ፡ኪ፡ሰ፡ሰት፡ቀተልነ፡ክሙ፡ን፡ሉ፡ላ፡የውእቱንና፡የሁን፡አፈታት፡እይ።

**አምርሐ**፤ አመራ፡አስመራ፤መሪ፡ሰጠ፡ሰተመሪ።

**ተመርሐ**፤ ተመራ፡ተከተለ። ተመራሕነ፡ውስተ፡ዛቲ፡ጸጋሁ። ተመሬሐነኬ፡ውስተ፡ጽድቅ። ከመ፡ንትመራሕ፡በትእዛዙ። ይደልወነ፡ከመ፡ንትመራሕ፡በምግባራቲሆሙ፡ወንትመሰል፡በሙ፡(ሮሜ፭፡፪። ቄር። ፊልክ። ዮሴፍ)።

**ምሩሕ**፤(ሓን፡ሓት፡ርሕት)፤ የተመራ፡ተመሪ፡ተማሪ፡ተከታይ።

**ምርሐት**፤ መምራት፡መመራት፡መሪነት፡ተመሪነት፤አመራር፡ምሬት፤ምሪት። ዘወሀቦ፡ጥበበ፡ምርሐት፡(ፊልክ፡፻፲)።

**መሪኅ**፤(ዐረ፡እልምሪኅ)፤ ኮከብ፡የኮከብ፡ስም፤የፀሓይን፡ብርሃን፡ከሚነሡ፡ከሰምንቱ፡ዐበይት፡ከዋክብት፡አንዱ።

**መረጠ**፡(ዕብ፡ማራጥ)፤ ላለ፡ሰነገለ፡ነጨ፡ነቀለ። በቁሙ፤ለየ፡ሸመ፡አከበረ። (ተረት)፤ከንጨት፡መርጠ፡ለታቦት፡ከሰው፡መርጠ፡ለሹመት። ሙርጥ፡ማስት፡ከዚህ፡ወጥቷል።

**መርጡር ፡ ል ፤ (ጽር ፡ ማርቲሪዮን ፤ ማርቲሪዩ ። ዕብ ፡ ዔዱት ። ሱር ፡ ሰሀዱታ ። ዐረ ፡ ሽሀደት)** ፤ አሪት ፡ ሕግ ፤ ጽላት ፡ ስምዕ ። ታቦት ፡ ዘመርጡር ፡ ል ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፳፪ ። ፳፯ ፡ ፴፫) ። መካኑ ፡ መርጡል ። በቅድመ ፡ መርጡል ፡ (፪ዜና ፡ ፳፬ ፡ ፯ ። ዘፀ፲፯ ፡ ፴፱) ።

**ማርቲሬ ፤ (ጽር ። ዕብ ፡ ሄዒድ ። ዐረ ፡ ሽሂደ)** ፤ ስምዐ ፡ መሰከረ ፤ በማዕት ፡ ኾነ ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፲፩) ።

**መርጡል ፤ (ዕብ ፡ ሞዔድ ። ሱር ፡ ዚ ምና ። ዐረ ፡ እሊጆቲማዕ)** ፤ ዕድሜ ፡ የበዓልና ፡ የቀጠሮ ፡ ቀን ፤ የጉባኤ ፡ ቦታ ፡ ዐውደ ፡ ስምዕ ፤ ሕዝብ ፡ ለጸሎትና ፡ ለመሚዕት ፡ ወይም ፡ ለክርክርና ፡ ለሙግት ፡ ለዘፈን ፡ ለጨዎት ፡ ለምስክርነት ፡ የሚሰበሰብበት ። ደብተራ ፡ ዘመርጡል ፡ (ዘፀ፳፱ ፡ ፬ ፡ ፲ ። ፴ ፡ ፲፰ ። ፳፯ ፡ ፴፯) ። በዕብራይስጡ ፡ ዔዱትና ፡ ሞዔድ ፡ ልዩ ፡ ሲኾን ፡ ጽርኡ ፡ አንድ ፡ አድርጎታል ። ባለቅኔዎችም ፡ መርጡልን ፡ ተራዳ ፡ ድንኳን ፡ አዳራሽ ፡ ይሉታል ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዘመርጡል ፡ ያለውን ፡ ዘዘመን ፡ ዘብዑድ ፡ ዘስምዕ ፡ ይሉታል ። አዳራሽ ፡ ከተባለ ፡ ዘንድ ፡ መቅደስ ፡ ቤተ ፡ ክር ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መርጡል ፡ ይላል ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፯ና ፡ ፳፰) ። እምኔታት ፡ በውስተ ፡ አሐቲ ፡ መርጡል ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳ና ፡ ፲፱ ። ገድ ፡ ተክ) ። መርጡሰ ፡ ማርያም ፡ ሥዕርተ ፡ ርእስ ፡ በመልዕልተ ፡ ድማኅ ፡ ዘበቁለት ፡ (ቅኔ) ።

**መርጡላዊ** ፤ አሪታዊ ፡ ዘአሪት ፡ ስምዓዊ ፡ ዘስምዕ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**መረየ ፤ (መርይ ። ዕብ ፡ ያሞር ፤ ሄሚር)** ፤ ለወጠ ፡ ቀየረ ፤ አስተሳሰፈ ፡ አሠገረ ፤ የብትት ፡ የቀን ፤ የጊዜ ፡ የዘመን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመረየ ፡ ፈንታ ፡ አሜረየ ፡ አምረየ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ዛቲ ፡ ዕለት ፡ አሜረየት ፤ እንዘ ፡ ታመሪ ፡ (መጽ ፡ ምስ ፡ ገ፪፻ ፡ ፳፰) ። ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ መሪሕ ፡ ነው ።

**ምርያ** ፤ ሠግር ፤ የሱባዔ ፡ ቍጥር ፡ ዐውደ ፡ ዕለት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የእውራኅንና ፡ ያመታትን ፡ ብተትና ፡ በዓል ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ የሚያሻግር ፡ የሚያዘዋውር ። ዕለተ ፡ ምርያ ፡ ዘያጠውዮን ፡ ለመዋዕለ ፡ ዓመታት ፡ ወያዐውዶን ፡ እምዝ ፡ ውስተ ፡ ዝ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ። ከዕንስ ፡ እስከ ፡ ልደት ፡ ያለውም ፡ የጌታችን ፡ መዋዕለ ፡ ፅንስ ፡ ፱ ፡ ወር ፡ ከ፭ ፡ ቀን ፡ ዮም ፡ ወለድኩከ ፡ የተባለበት ፡ ለብሉዩና ፡ ለሐዲሱ ፡ ዘመን ፡ ሠግር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ እንደዚሁ ፡ ምርያ ፡ ይባላል ፤ ዕለት ፡ ኀሪት ፡ ዕለተ ፡ መድኀኒት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ኢሳ፶፱ ፡ ፩ ፡ ፳ ፡ ፯ ፡ ፰) ።

**ማረየ ፤ (ይማሪ ፤ ማርዮ)** ፤ ሻረተ ፡ አሻረተ ፤ ጠንቈለ ፤ ወር ፡ አጓደለ ፤ በፊደል ፡ ቍጥር ፡ በግድፈት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በማረየ ፡ ፈንታ ፡ ተመርየ ፡ ተማረየ ፡ ተማረተ ፡ ይላል ፤ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ አያሰኝም ። ሰተመርዮ ፡ ወሰተሰግሎ ። ዘያሰግል ፡ ወዘይትሜረይ ። ዘይትማረይ ፡ ወዘያበውእሙ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ለማርያን ። ኵሉ ፡ ተማርዮ ፡ እምኀይሉ ፡ ለጋንንት ፡ ወኵሉ ፡ ቱነብዮ ፡ እምኀይሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ብእሲት ፡ ዘትትማረት ፡ ሰው ፡ ለካልእታ ፡ ትብል ፡ ትትማረት ፡ በእንቲ ፡ ፍቅረ ፡ ምታ ፤ ሰው ፡ በእንቲ ፡ ፍቅረ ፡ ካልእ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፩ ። ቀሌ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፩ ። መጽ ፡ ምስ ። ሲኖዶ) ።

**ማሪ ፤ ማሪ ፤ ማሬ ፤ (ዪት ፡ ሪት ፤ ርያን ፡ ያት ፤ ረይት)** ፤ የሚያሻርት ፡ የሚጠነቍል ፡ ማርተኛ ፡ ጠንቋይ ፤ ነቢየ ፡ ሐሰት ፡ ካህን ፡ ጣዖት ። ጺጥፋራ ፡ ማሪ ፡ ዘሀገረ ፡ ሔልዩ ። ዮቶር ፡ ማሬ ፡ ምድያም ። ወአምጽኡ ፡ ማሬ ፡ ዘደዮስ ፡ (ዘፍ፵፩ ፡ ፵፭ ። ዘፀ፪ ፡ ፲፯ ። ግብ፲፱ ፡ ፲፫) ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘሐተተ ፡ ማሪት ። ማርያን ፡ ወሰብአ ፡ ሰገል ። ውእቱ ፡ ይገብር ፡ ግብረ ፡ ሥራይ ፡ ወዘማርያት ፡ (ቀሌ ። ዳንኤ ፡ ፳ ። ፪ዜና ፡ ፴፫ ፡ ፯) ። በማረይት ፡ ፈንታ ፡ ማሪታት ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ፤ ማረይት ፡ ቅጽልንቱ ፡ መድበል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ብዙዎቹን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ያስተባብራል ፤ ማሪታት ፡ ግን ፡ ለሴቶች ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሐሳውያን ፡ ማሪታት ፡ (ቄር ፡ ገ፩) ።

**አማረየ ፤ አስተማረየ** ፤ አስጠንቈለ ፡ አስሻረተ ፡ ማርተኛ ፡ ጠየቀ ። አናገረ ፡ አስለፈለፈ ፤ ሻርተኛ ፡ አደረገ ። ሰይጣን ፡ ይጼዐን ፡ በሰብእ ፡ ለአስተማርዮ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ። ማረየ ፡ የባረከ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ አስተማረየ ፡ ከአማረየ ፡ ተለይቶ ፡ ባደራራጊነት ፡ ሲፈታ ፤ አጠናቈለ ፡ አጠንቋቈለ ፤ አሞራረተ ፡ ያሰኛል ።

**ተማረየ** ፤ ተሻረተ ፡ ተጠንቈለ ፤ ሻርቱ ፡ ጥንቈላው ፡ ተደረገ ። ተደራራጊ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፤ ተሞራረተ ፡ ተጠናቈለ ፤ ተጠንቋቈለ ፡ ያሰኛል ።

**ማርያም ፤—መራረ ፡ መዋዕል ፤—መሪር ፡ መረ ።**

**መርመሬ ፤—ከሐፊዳ ፡ ከረጆ ፤—ረመለ ፡ መርመሌ ።**

**መርመር ፤ (ዐረ)** ፤ ነጭ ፡ ደንጊያ ፡ እብነ ፡ በረድ ። አዕማደ ፡ መርመር ፡ (ስንክ ፡ ታኅ) ።

**ሜሮን ፤ (ጽር ፡ ሚሮን)** ፤ የከርቤ ፡ ሽቱ ፤ ወይም ፡ ሴላ ፡ ያልተቀደሰ ፤ ማንም ፡ የሚቀባው ፤ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ መሪር ፡ መረ ፡ ነው ። ዕጣነ ፡ ወሜሮነ ፡ (ራእ ፲፰ ፡ ፲፫) ።

—፤ በቊጠው ፤ ቅብዐ ፡ ቅዱስ ፡ የተባረከ ፡ ሽቱ ፤ ጳጳሳት ፡ ከበለሳንና ፡ ከዕፀወ ፡ ዕጣን ፡ ከእስጳዳቶስ ፡ ከሌላም ፡ ከብዙ ፡ ዐይነት ፡ ሽቱ ፡ የሚያወጡት ። መደበኛው ፡ ግን ፡ በለሳን ፡ ነው ፤ ፍሬውን ፡ በቦታው ፡ ተመልከት ። በለሳን ፡ ከነ ፡ ሀፈ ፡ ሥጋሁ ፡ በቀሎ ፡ ሜሮነ ፡ ቅብዑ ፡ ዘይቄድስ ፡ ኵሎ ፡ ለትእምርት ፡ በኀቤነ ፡ እስከ ፡ ዮም ፡ ሀሎ ። ወይትዓትም ፡ ኪያሃ ፡ በሜሮን ፤ እስመ ፡ ማኅተመ ፡ እግዚ ፡ ውእቱ ፡ (ደራሲ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፩) ።

**መራናታ** ፤—ጌታ ፡ መጣ ፤—ማር ፡ ማሬ ፡ ማራን ።

**መራናት** ፤—ማብሪያ ፤—ነዊር ፡ ኖረ ፡ መናረት ።

**መርሠሠ** ፤—ዳሰሰ ፡ ዳበሰ ፤—መርሰሰ ።

**መሪዕ** ፤ ዖት ፤ (መርዐ ፡ ይመርዕ ፡ ይምራዕ ። ዕብ ፡ ማራእ) ፤ መጕምዠት ፡ መሻፈድ ፤ መድራት ፡ መዳራት ፤ የንስት ። መዝለል ፡ መክመር ፤ መስረር ፡ መውጣት ፡ ፈጥ ፡ ማለት ፤ የተባት ። ንባቡም ፡ ምስጢሩም ፡ ምዒር ፡ ምዕረ ፡ ከለው ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ መዐረንና ፡ ፈሐስን ፡ እይ ። ብእሲት ፡ እንተ ፡ ትመርዕ ፡ በብእሲት ፤ አው ፡ ብእሲ ፡ ዘይመርዕ ፡ በደቂቅ ። እመ ፡ ቦ ፡ ብእሲት ፡ ዘትመርዐ ፡ በሥጋሃ ። እመ ፡ ቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘደፈቅር ፡ ደቂቀ ፡ ከመ ፡ ይምራዐ ፡ ቦሙ ፡ (ቀድር) ። ኰነን ፡ ደየን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መርዐ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። መራዕኪዮን ፡ ለአኃትኪ ፡ (ሕዝ ፲፮ ፡ ፶፪) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በመርዐ ፡ ፈንታ ፡ ተመርዐ ፡ ይባል ፤ አያሰኝም ። ዘይረክስ ፡ በተመርዖ ፡ ውስተ ፡ ፍትወት ። እስመ ፡ ይትመራዐ ፡ ነፍስቶሙ ፡ (መጽ ፡ ቄስጠ ። ሄርማ ፡ ገ፲፮) ።

**ምሩዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ርዕት) ፤ የሻፈደ ፡ ጕምዠ ፤ ሴሰኛ ፡ ድራተኛ ፤ ዘማዊ ። ምሩዕ ፡ በፍትወተ ፡ ፍሩ ። ምርዕት ፡ ይእቲ ፡ በመይዋ ፡ ምርዕተ ፡ (ቀኖ ኒቅ ። ምሳ፳ ፡ ፲፭ ። ቀድር) ።

**ምርዐት** ፤ መጕምዠት ፤ መዳራት ፡ መቃበጥ ፤ መቈናጠጥ ፤ በውስጥ ፡ በአፍኣ ፡ መታወክ ፡ መቅበጥበጥ ። ዝሙት ፡ ወምርዐት ። ፈቲው ፡ ምርዐት ፡ ወዝሙት ። ገብረ ፡ ዝሙተ ፡ ወምርዐተ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፭ ። ኪዳ ፡ ገ፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፲፭) ።

**ምርዕ ፤ ምርዓ ፤ ምርዓት** ፤ (ታት) ፤ ሴስን ፡ ድራት ፡ እንስሳዊ ፡ ፍትወት ፤ ልፊያ ፡ ቍልመማ ፡ የዝሙት ፡ ቀዜማ ። እምስካር ፡ ይትወለድ ፡ ምርዓት ። ርኵስ ፡ ወምርዓት ። ዘኢያስተዋድድይዎሙ ፡ በምርዓት ፡ (ቀሌ ። ገላ፭ ፡ ፲፱ ። ቲቶ፩ ፡ ፯) ።

**መርዓ ፡ ት ፡ ዊ** ፤—ሰርግ ፤ ሙሽራ ፤—ረዐወ ።

**መርዔት** ፤—መንጋ ፤—ርዕይ ፡ ረዐየ ።

**መረቅ** ፤—በቁሙ ፤—ወረቀ ፡ ምራቅ ።

**መርቄ** ፤—ቄላ ፡ በረሓ ፤—ረቅይ ፡ ረቀየ ።

**ሜሩቃዕ** ፤ (ዕብ ፡ ራቃዕ ፤ ዘረጋ ፡ አሣሣ ፤ ምሩቃዕ) ፤ ሥሥ ፡ ረቂቅ ፤ ዝርግ ፡ ጠፍጣፋ ፤ ልብስን ፡ ዕንፈቶትን ፡ ለማስጌጥና ፡ ለመለበጥ ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ኹኖ ፡ የተሠራ ። ባሉበሉዮች ፡ ግን ፡ ጽርየት ፡ ንጣት ፡ ይሉታል ። ብሩር ፡ ሜሩቃዕ ፡ (ኤር፲ ፡ ፱) ።

**መሪር** ፤ ሮት ፤ (መረ ፤ መረረ ፡ ይመርር ፡ ይምርር ። ዕብ ፤ ማራር ። ሱር ፡ ማር ። ዐረ ፡ መረ) ፤ መምረር ፤ መጐፍነን ፤ ከጣፋጣና ፡ ከሐምጣጣ ፡ ልዩ ፡ ክፉ ፡ መኾን ፤ የጣዕም ፡ የጠባይ ። ይመርር ፡ ጣዕሙ ፡ ለመዓር ፡ በዕጕሥታር ። ዘይመርር ፡ እምሐሞት ። ለትምረራ ፡ ለከርሥከ ። ወይመርሮሙ ፡ ምግባሩ ፡ ለጽድቅ ፡ (ሄርማ ፡ ገ፴ ። ምሳ፳ ፡ ፱ ። ራእ፲ ፡ ፱ ። ቀሌ) ።

—፤ ማዘን ፡ መትከንከን ፤ መቈጣት ፡ መበሳጨት ፤ ዕርር ፡ ምርር ፡ ማለት ። መሪረ ፡ መረርኩ ። መረረተኒ ፡ ነፍስየ ፡ እምኔክን ። ወምንትኑ ፡ ዘመደ ፡ መዋቲ ፡ ከመ ፡ ትምርር ፡ በእንቲኣሁ ፡ (ሰቈ፩ ፡ ፳ ። ሩት፩ ፡ ፲፫ ። ሲራ ፡ ዕገዛ ፡ ፵) ። መር ፡ ማለት ፡ መናር ፤ ዘሎ ፡ ማለፍ ። መረመርና ፡ መረመረ ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**መሪር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ራር) ፤ በቁሙ ፡ መራራ ፡ ክፉ ፤ ቍጡ ፡ ብስጩ ፤ ዐመፀኛ ። እሰ ፡ ይብልዎ ፡ ለጥዑም ፡ መሪረ ፡ ወለመሪር ፡ ጥዑመ ። መሪረ ፡ ከነ ፡ ሜስ ። ይኄይስ ፡ መዊት ፡ እመራር ፡ ሕይወት ። ትውልድ ፡ ዕሉት ፡ ወመራር ። መሪራነ ፡ ነፍስ ። ሕዝብ ፡ መሪራን ። ቤተ ፡ መሪራን ፡ (ኢሳ፭ ፡ ፳ ። ፳፱ ፡ ፱ ። ሚራ፴ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፸፯ ። መሳ፲፰ ፡ ፳፭ ። ዕንቅ ፡ ፯ ። ሕዝ፪ ፡ ፭) ።

**ምሩር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ርርት) ፤ የመረረ ፤ የተመረረ ፡ ያዘነ ፡ የተከፋ ። ለምንት ፡ ወሀብከሙ ፡ ብርሃነ ፡ ለምሩራን ። ከማሁ ፡ ለምሩራን ፡ (ኢዮ፫ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፳፯) ።

**ምረት** ፤ በቁሙ ፤ መምረር ፡ ማዘን ፤ አመራረር ፡ መራርነት ፡ ክፋት ። ምረተ ፡ ሕምዝየ ። በምረተ ፡ ነፍሱ ። አእመረ ፡ ምረቶሙ ፡ (ሰቈ፫ ፡ ፳ ። ሚራ፬ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፭) ። ሬት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ምረር** ፤ (ራት) ፤ በቁሙ ፤ ምረት ፡ መራርነት ፤ ሐዘን ፡ መከራ ፡ ቍጣ ። ምረሩ ፡ ለማይ ። ምረሩ ፡ ለሞት ። እክሥት ፡ ምረረ ፡ ነፍስየ ። እለ ፡ ተዐገሁ ፡ ምረራተ ፡ ብዙኃተ ፡ (ራእ፰ ፡ ፲፩ ። መቃ ፡ ገ፲፱ ። ኢዮ፯ ፡ ፲፩ ። አፈ ፡ ድ፴፩) ።

**ምረር** ፤ (ዕብ ፡ ምሬራ ። ሱር ፡ ምሬራ ። ዐረ ፡ መራረት) ፤ መሪር ፡ መራራ ፤ በጠባዩ ፡ ምረት ፡ መራርነት ፡ ያለው ፤ ሐሞት ፡ ከርቤ ፡ ሬት ፡ ኮሶ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፤ መደበኛው ፡ ግን ፡ ሐሞት ፡ ነው ። ጥዕምኩ ፡ ዕጕሥታረ ፡ ወዘሎ ፡ ምረራተ ፤ ወኢረከብኩ ፡ ዘይመርር ፡ እምንዴት ፡ (ፈላስ ፡ ገ፳፭) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ በምረር ፡ ፈንታ ፡ መሪር ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ምረት ፡ ይላል ፡ (ዘዳ፴፪ ፡ ፲፫ ። ጥበ፰ ፡ ፲፯) ።

**ማራ** ፤ (ዕብ ፡ ማራህ ፤ ማራታ) ፤ የቦታ ፡ ስም ፡ መራራ ፡ ውሃ ፡ ያለበት ። ኢረከቡ ፡ ማየ ፡ ከመ ፡ ይስተዩ ፡ በማራ ። ወግዕዙ ፡ እምነ ፡ ማራ ፡ (ዘፀ፲፭ ፡ ፳፫ ። ዘኍ፴፫ ፡ ፰) ። ዳግመኛም ፡ በማራ ፡ ፈንታ ፡ ምረት ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**አምረረ** ፤ አመረረ ፤ አስመረረ ፡ አሳዘነ ፡ አስቈጣ ። ወበሕምዘ ፡ መቅሠፍት ፡ ጸስከራዊ ፡ አም

ረኑ፡ መዓረ፡ ዘባኑ፡ ለኤርምያስ፡ ንህብ። አምረራ፡ ለነፍስየ። እስመ፡ አምረሩከ፡ እግዚኦ። ወእለ፡ መኑ፡ እሙንቱ፡ እለ፡ ሰምዑ፡ ወአምረርዎ፡ (ቅኔ። ኢዮ፳፯፡ ፪። መዝ፡ ፸። ዕብ፫፡ ፲፮)።

**አመራሮ፤** መራራ፡ የደጋ፡ ዕንጨት፤ ወይም፡ ቀላዋ፡ ውስጠ፡ ክፍት።

**ማርያም፤ (ዕብ፡ ሚርያም)፤** ነቢይት፡ የሙሴና፡ የአሮን፡ እኅት፡ (ዘፀ፲፭፡ ፳)። ቃሉ፡ ፪፡ ነው፤ ማር፡ ሚር፡ ፩፡ ወገን፤ መራራ፡ መሪር። ያም፡ የም፡ ዕለት፡ ዘመን፡ መዋዕል፤ በተገናኝ፡ ምርርተ፡ የም፡ ወይም፡ መሪረ፡ መዋዕል፡ ዘመሪር፡ መዋዕሊሃ። ዘመኗ፡ ዘመን፡ ልደቷ፡ ማሩር፡ የተባለው፡ ማለል፡ ፈርዖን፡ በእስራኤል፡ ላይ፡ ክፉ፡ ምክር፡ መክሮ፡ ወንድ፡ ወንዱ፡ ለሞት፡ ሴት፡ ሴቱ፡ ለትሎት፡ ብሎ፡ መራራ፡ ዐዋጅ፡ ያስነገረበት፤ እስራኤልም፡ ዕርር፡ ምርር፡ ብለው፡ ያዘኑበት፡ ያለቀሱበት፡ የሐዘን፡ የመከራ፡ ወራት፡ ስለ፡ ኾነ፡ አባት፡ እናቷ፤ ዘበመዋዕሊሃ፡ አምረሩ፡ ግብጽ፡ ሕይወተ፡ እስራኤል፡ ሲሉ፡ እንደዚህ፡ ያለ፡ ስም፡ ሰጥተዋታል፡ (ዘፀ፩፡ ፰—፲፯)። ፪ኛም፡ ኮከብ፡ ዐቢይ፡ ወረደ፡ እምሰማይ፡ ወስሙ፡ ለውእቱ፡ ኮከብ፡ ዕጐ ሥታር፡ ይባልና፡ (ራእ፰፡ ፲፡ ፲፩)። ማር፡ ሚር፡ ፊቶ፡ ሐሞቶ፡ የሚባል፡ ኮከብ፤ ያም፡ ባሕር፡ ይኾናል፤ ያም፡ ሱፍ፡ እንዲል፡ ባሕረ፡ ኤርትራ፡ ሲል፡ (ዕብራ)። በተገናኝ፡ ኮከበ፡ ባሕር፤ መራሒት፡ ለእለ፡ ውስተ፡ ባሕር፡ ማለት፡ ነው። ባሕርም፡ የዘመን፡ ምሳሌ፡ ነውና፡ የባሕሩና፡ የኮከቡ፡ ስም፡ ጣዕም፡ ምሬት፡ ስለ፡ ኾነ፡ ምስጢሩ፡ ከዚያው፡ ከፊተኛው፡ ይገባል፤ የመርሐ፡ ዕዉር፡ እርእሰት፡ ጉልቄ፡ ዘመን፡ ሲል፡ ሐሳበ፡ ባሕር፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ባሕረ፡ ሐሳብ፡ እንዲል። ስላዴሱም፡ ዘመን፡ ቡራኬ፡ እንኳን፡ ከዘመን፡ ወደ፡ ዘመን፡ አሻገረኽ፡ ማለት፡ ዘመንን፡ በባሕርና፡ በወንዝ፡ መስሎ፡ ነው፤ መመሳሰል፡ የጋራ፡ ነውና፡ (ሕገ፳፰፡ ፪—፸)። በፈርዖን፡ ዐዋጅ፡ ከባሕር፡ ከጀደባ፡ ሥር፡ ለሚወድቁ፡ ለእስራኤል፡ ልጆች፡ ናሁ፡ ወልድ፡ ይትወለድ፡ ለነ፤ ቤዘ፡ ወመድኅን፡ እምግብጽ፡ ያወፅአነ፡ እያለች፡ በደረቅ፡ ትንቢቷ፡ እንደ፡ ኮከብ፡ የምታበራ፡ ኋላም፡ በኤርትራ፡ ከበሮዋን፡ ነጥቃ፡ ሰብሐዎ፡ እያለች፡ የምትቀኝትን፡ የምትመራ፡ ነቢዩት፡ ማሕሌታዊት፡ ልዕልተ፡ ቃል፡ እርኢያ፡ ድንግል፡ ስለ፡ ኾነች፡ አስቀድሞ፡ ይህ፡ ሱግ ላዊ፡ ስም፡ ኮከበ፡ ባሕርነት፡ ተሰጥቷታል፤ ትንቢቷም፡ በአይሁድ፡ ክፋሌ፡ ይገኛል። ኖትያዊ፡ ይፈጽር፡ ኀበ፡ ከዋክብት፡ (እለ፡ በሚን)፡ አመ፡ የሐውር፡ ውስተ፡ ባሕር፡ ዘከመ፡ ይመርሖ፡ ወያከይዶ፡ ለሐመሩ፡ እስከ፡ ይበጽሕ፡ ኀበ፡ መርሶ፡ (ማር፡ ይሥ፳፰)። ማርያም፡ ብሎ፡ ዘበዕብራይስጢ፡ ሚርያም፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ማሪሃም፡ ማለት፡ የተሳሳተ፡ ነው፡ (አርጋ። ታምረ፡ ማር)። በዚህም፡ ስም፡ ብዙ፡ ሴቶች፡ ተጠርተውበታል፡ እስከዚህ፡ ሥምና፡ ብሉይ፡ ነው። ስወርቱና፡ ስሐዲሱ፡ ግን፡ የኮከብ፡ ልጅ፡ ኮከብ፡ ነውና፡ በርሷ፡ ኮከብነት፡ የርሱን፡ ኮከብነት፡ መናገር፡ ነው፡ (ዘኍ፳፬፡ ፲፯። ፪ጴጥ፡ ፩፡ ፲፱)። ብሉይ፡ ማርያም፡ የብሉይ፡ ኪዳን፡ ጥንት፡ እንደ፡ ኾነች፡ ሐዲስ፡ ማርያምም፡ የሐዲስ፡ ኪዳን፡ ጥንት፡ ናትና፡ አስቀድሞ፡ በማርያም፡ ዘመን፡ የኾነው፡ ግፍና፡ መከራ፡ ድንቅ፡ ሥራ፡ ኹሉ፡ ኋላ፡ በድንግል፡ ማርያም፡ ለሚኾነው፡ አምሳል፡ መርገፍ፡ ኹኖ፡ ተጥፏል፡ (ዕብ፲፡ ፩)። ማርያሞች፡ እንዲንጸጸሩ፡ ፈርዖንና፡ ሄሮድስ፡ ሙሴና፡ ክርስቶስ፡ ንሴብሖና፡ ታዐብዮ፡ ይነጻጸራሉ፡ (ዘፀ፲፭፡ ፩—፳፩። ሉቃ፩፡ ፵፯—፶፭)። ብሊት፡ ማርያም፡ በልደተ፡ ሥጋ፡ እኅተ፡ ሙሴ፡ እንደ፡ ተባለች፡ ሐዲስ፡ ማርያምም፡ ስሥማው፡ ቃል፡ ልጇ፡ በልደተ፡ ነፍስ፡ እኅት፡ ትባላለች። ማስተባበር፡ ልማዱ፡ እንጂ፡ ነው፤ ድንግልናን፡ ከወሊድ፡ እንዳስተባበረች፡ እኅትነትንም፡ ከናትነት፡ አስተባብራለች፤ በስንበት፡ ላይ፡ ደብረ፡ ዘይት፡ እንዲሉ። ይኸውም፡ የም፡ ወሰይኩክ፡ በተባለበት፡ በበኵርነቱ፡ በግብር፡ ልደቱ፡ ነውና፤ የበኵርን፡ ፍች፡ እይ። የጕንደሩም፡ ሊቅ፡ አጥልደ፡ ሉጥን፡ ከእሪት፡ ጠቅሶ፡ በሚበዝኍ፡ ቅኔው፡ እንዲህ፡ ይላል፡ (ዘፀ፲፱፡ ፴፯—፴፰)። በዘርዐ፡ አቡሆን፡ ኮና፡ አኃተ፡ ውሉዶን፡ አኃት፡ አመ፡ ወርኁ፡ ሕጸጽ፡ ወንትጋ፤ ለከሰ፡ አምላክ፡ ክርስቶስ፡ ቀዳሚ፡ ጸጋ፡ ወለተ፡ ሐና፡ ጠባብ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ እኅትከ፡ እንዘ፡ እምከ፡ በሥጋ።



ማርያም፡

**መርስ፤—ወደብ፡—ረሲው፡ ረሰወ።**

**መረስ፤ (መረሰ፤ ዐረ። ዕብ፡ ማራስ)፤** መንከር፡ መዘፍዘፍ፡ ማጀል፡ በሬነው፡ በውሃ፡ በቅጠል፡ ለማራስ፡ ለማበስበስ።

**ተመርሰ፤** ተነከረ፡ ተዘፈዘፈ፡ በሰበሰ፡ ገማ፡ ተበላሸ፡ ዘጼአ፡ ወተመርሳ፡ እምአባላት፡ ይትመተራ፡ ወሲሲተ፡ ዕፄ፡ ይከውና፡ (ተረ፡ ቄርሏ)።

**መርሰሰ፤ (ተቀ፡ ግ)፤** ዳሰሰ፡ ዳበሰ፡ ነካ፡ ፀሻሸ፡ የተነከረውን። ሻ፡ ፈለገ፡ ተም፡ ተም፡ አለ፡ ተደናበረ። ወትገብእ፡ ትመርስስ፡ መዓልተ፡ ዘከመ፡ ይመረስስ፡ ዕዉር፡ በውስተ፡ ጽልመት፡ (ዘዳ፳፰፡ ፳፱)። በመርሰሰ፡ ፈንታ፡ አመርሰሰ፡ ይላል፡ ስሕተት፡ ነው። ወይመረስሱ፡ ውስተ፡ አረፍት፡ ከመ፡ ዕዉር።

ይመረስሱ፡ቀትረ፡ ከመ፡ ሌሊት፡ (ኢ.ሳ፶፱ ፡ ፲ ። ኢ.ዮ፳ ፡ ፲፱) ። ከዚህ ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ ፈደል ፡ አዛውሮ ፡ ረምሰሰ ፡ አረምሰሰ ፡ ይላል ፤ ቀሐመንና ፡ ዕጕሥታ(ዕጕትግ)ርን ፡ እይ ። ታረመስስ፡ዲበ፡አባሳቲከ፡(አረጋ፡ ድ፯) ።

**መርሰስ** ፤ ዳሰሳ ፡ ዳበሳ ። ዕዉር፡ውእቱ፡ዘ የሐውር፡በመርሰስ፡(፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፱) ።

**ምርስኔ** ፤ (ጽር ፡ ሚርሲኒ) ፤ የሽቱ ፡ ዕን ፈጨት ፤ ባርስንት ፡ ወይም ፡ አደስ ። አዲሽምን ፡ እይ ፤ ከ ዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። ዕፀ፡ጺቅሶን፡ወምርስኔ፡(ኢ. ሳ፵፩ ፡ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፳፩) ።

**ማሬት** ፤—**ሻርተኛ** ፤—**መረየ፡ማረየ** ።

**መሬት** ፤ **ቶት** ፤ (**መረተ ፡ ይመርት ፡ ይ ምርት**) ፤ መምረት ፤ ከገለባና ፡ ከእበቅ ፡ መለየት ፡ እ ንዳፈር ፡ መቈለል ። መመረት ፡ መዛግ ፤ ዐፈር ፡ መሬት ፡ መኸን ፤ ወዳፈርንት ፡ መመለስ ፤ የማዕደናትና ፡ የሥጋ ፡ የንጨት ።

**አምረተ** ፤ አመረተ ፤ አስመረተ ፡ አዛገ ።

**ምርት** ፤ በቁሙ ፤ የመረተ ፡ የተመረተ ፡ ባው ድማ ፡ መካከል ፡ የተሸመ ፡ የተሸለመ ፡ ቍልል ፡ ጥሩ ፡ እኽል ።

**መሬት** ፤ በቁሙ ፤ ዐፈር ፡ ትቢያ ፡ ዐመድ ፡ እ ንደ ፡ ምርት ፡ የሚዛቅ ፡ የሚታፈሥ ፤ የብስ ፡ ገራህት ፡ ኀል ፡ ጕሊት ፡ መኰሳ ፤ የምድር ፡ ገላ ፤ የሚረጥብ ፡ የሚደርቅ ፡ የሚፈርስ ፡ የሚደቅ ፤ ከራቱ ፡ ባሕርዮት ፡ አንዱ ፤ ጽል መትና ፡ ውዕየት ፡ ርጥበት ፡ ያለው ፤ በጽልመቱ ፡ ከነፋስ ፡ በውዕየቱ ፡ ከእሳት ፤ በርጥበቱ ፡ ከውሃ ፡ የሚስማማ ። ኵ ሉሕ፡ኀበ፡ አልቦ፡መሬት ። ወደዩ፡መሬተ፡ዲበ፡ ርእሰሙ ። መሬት፡አንተ፡ ወትገብእ፡ ውስተ፡መ ሬት ። እለ፡ ይነውሙ፡ ውስተ፡መሬተ፡ምድር፡ (ማቴ፲፫ ፡ ፳ ። ሰቈ፪ ፡ ፲ ። ዘፍ፫ ፡ ፲፱ ። ዳን፲፪ ፡ ፪) ። ጽቡር ፡ ጭራ ፡ ድኾስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መሬት ፡ ይላል ። አብዮተ፡መሬት።መሬት፡ጸዐዳ።መሬተ፡ምድር፡ (ኢ.ዮ፻ ፡ ፲፱ ። ዘዳ፳፯ ፡ ፪ ። መገ ፡ ፹፰) ።

**መሬታዊ** ፤ በቁሙ ፤ ምድራዊ ፡ ግዙፍ ፤ ከ ፈር ፡ ከመሬት ፡ የተገኘ ፡ ሾኝ ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ። በከመ፡ ዝኩ፡ መሬታዊ፡ ከማሁ፡ መሬታውያን፡(፩ቆሮ፡ ፲፭ ፡ ፵፰) ።

**መሶብ** ፤—**በቁሙ** ፤—**ሰዊብ ፡ ሶበ ፡ ሰ ወበ** ።

**ማሴዔሬት** ፤—**ሰንበር** ፤—**ሠገረ** ።

**ማሲው** ፤ (**ጽር ፡ ሚሶ**) ፤ ማእከል ፡ ማእ ከላይ ። አንቀጹ፡ማሴው፡(ኤር፴፱ ፡ ፫) ። መስኤጦም ያን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**መሲው** ፤ **ዎት** ፤ (**መሰወ** ፤ **መሰወ ፡ ይ መሱ ፡ ይምሱ ። መለየ ፡ አምሀወ**) ፤ ማቅለጥ ፡ ማፍሰስ ፤ ውሃ ፡ ማድረግ ፤ ማጥፋት ፡ ማፍረስ ፤ የረጋውን ። ከመ ፡ ይመስዎ ፡ ፀሓይ ፡ ለበረድ ። ነደ ፡ እሳት ፡ ይ መስዋ ፡ ለነፍሱ ። መቅሠፍት ፡ ይመስዎሙ ። ዝ ንቱ፡ማይ፡ይምሱ፡ኵሎ፡አባላቲኪ፡(ሚራ፫ ፡ ፲፰ ። ፴፰ ፡ ፳፰ ። ፳፯ ፡ ፳፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፯) ። ኢ.ከላእኩ ፡ ኢ.ያጽለምኩ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ኢ.መሰውኩ ፡ ዐይነ ፡ ዕ ቤር ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ አላስለቀስኩም ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ፡ (ኢ.ዮ፴፩ ፡ ፲፯) ።

**መሳዊ** ፤ (**ዊት ፡ ውያን ፡ ያት**) ፤ የሚያቀ ልጥ ፤ አቅላጭ ፡ አጥፊ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ) ።

**ተመስወ** ፤ ቀለጠ ፡ ሟሟ ፤ ዛለ ፡ ደከመ ፤ ጠፋ ፡ ፈሰሰ ። ከመ፡ይትመሰ፡መዓረ፡ግራ፡እምገጸ፡እ ሳት ። ተመስወት፡ነፍስየ፡ወኀጣእኩ፡ኀይለ ። ወይ ትመሰዋ፡አዕይንቲ፡ረሲዓን፡(ኢ.ሳ፷፬ ፡ ፪ ። ዳን፲ ፡ ፲፫ ። ኢ.ዮ፲፩ ፡ ፳) ።

**ምስው** ፤ (**ዋን ፡ ዋት ፡ ሱት**) ፤ የቀለጠ ፡ የዛለ ፡ የደከመ ፡ የፈሰሰ ። አብራኪ፡ ምስዋት፡(አፈ ፡ ድ፴) ። ዕዉስ ፡ ሐንካስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዕብ፲፪ ፡ ፲፪) ።

**ትምስውና** ፤ ዝለት ፡ ድካም ፤ ዝልፍልፍነት ፡ (ፈልክ ፡ ፻፹፩) ።

**መሲሕ** ፤ **ሐት** ፤ (**መስሐ ፡ ይመስሕ ፡ ይምሳሕ ። ዕብ ፡ ማሻሕ ። ሱር ፡ ምሻሕ ። ዐረ ፡ መሰሐ ፤ ቀባ**) ፤ መቅባት ፤ ቅባት ፡ መጨመር ፤ በቅባት ፡ ማሸት ፡ ማባፈጥ ። ዘቀብዖ ፡ ባሰው ፡ ዘመስሖ ፡ እንዲል ፡ (ግብ፲ ፡ ፴፰) ።

—፤ መምሳት ፤ ምሳ ፡ መብላት ። (ተረት) ፤ ታልመሱ ፡ አያነሡ ። እምድኅረ፡አኀሰቁ፡መሲሐ ። ወቦኡ፡ ንጉሥ ፡ ወሐማ ፡ ይምስሑ ፡ ምስለ ፡ ንግሥት ። ንዑ፡ንምሳሕ ። ወእምድኅረ፡መስሑ፡(፫ነገ ፡ ፩ ፡ ፵፩ ። አስቴ፯ ፡ ፩ ። ዮሐ፳፩ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭) ።

**መሳሒ** ፤ (**ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት** ፤ **ሕት**) ፤ የመሳ ፡ የሚመሳ ፤ ምሳ ፡ በል ፤ ቀቢ ።

**አምስሐ** ፤ አመሳ ፤ ምሳ ፡ አበላ ። አእምር፡ ኵሎ፡ዘአምስሐከ፡ቢጽከ ። ወአምስሐ፡ መኳንን ቲሁ፡(ሚራ፴፱ ፡ ፲፰ ። ማር፮ ፡ ፳፩) ።

**ተመስሐ** ፤ ተቀባ ። ተመሳ ፤ ተበላ ፡ ምሳ ፡ ኾነ ፤ ምግብ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ምሱሕ** ፤ የመሳ ፤ ምሳ ፡ የበላ ። የተመሳ ፡ የተ በላ ። የተቀባ ፤ ቅቡዕ ።

**ምሳሕ** ፤ (**ሓት**) ፤ ምሳ ፡ የቀን ፡ ምግብ ፡ ድ ግስ ፡ በቀትር ፡ በተሲያት ፡ የሚበላ ፤ እንጀራው ፡ ወዛም ፡ ወጡ ፡ ቅባታም ። ምስጢሩ ፡ ቅባትን ፡ አይለቅም ። ገ ብሩ፡ሎቱ፡ምሳሐ ። እስከ፡ጊዜ፡ምሳሕ ። አው፡ እምድኅረ፡ምሳሕ ። በውስተ፡ምሳሓት፡(፪ነገ ፡ ፫ ፡ ፳ ። ፳፬ ፡ ፲፰ ። ሥር ፡ ጸሎ ። ማቴ፳፫ ፡ ፯) ።

**ምስሕ** ፤ ምስ ፡ ዳረጎት ፤ ጕርሻ ፡ ቅምሻ ፡ ለዛር ፡ ለጋኔን ፡ ለቡዳ ፡ የሚሰጥ ፡ የሚፈነጠቅ ። ለበትርና ፡ ለጥ ፊም ፡ ይኾናል ፡ ምሱን ፡ ስጠው ፡ እንዲሉ ።

**መሲሕ** ፤ (ሓን) ፤ ዐረ ። ዕብ ፡ ማሽያሕ ። ሱር ፡ ምሺሓ) ፤ በቁሙ ፤ ምሱሕ ፡ የተቀባ ፡ ቅቡዕ ፤ ለሹመትና ፡ ለምግብነት ፡ የተዘጋጀ ፤ ንጉሥ ፡ ካህን ፡ ወይም ፡ ነቢይ ፤ ሲቀባ ፡ ዕብታት ፡ መንፈስ ፡ የመሉበት ። የክርስቶስን ፡ ፍች ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። ሰመሲሒየ ፡ ቂሮስ ። ኢትግስሱ ፡ መሲሓንየ ። መኑ ፡ ውእቱ ፡ ሐሳዊ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይክሕድ ፡ ወይብል ፤ እስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ኢኮነ ፡ መሲሐ ፤ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ሐሳዌ ፡ መሲሕ ፡ (ኢሳ፵፭ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፻፬ ። ፩ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፳፪) ። መሲሕ ፡ ማለት ፡ በሦስቱ ፡ ቋንቋዎች ፡ በዐረብ ፡ በሱርስት ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቅቡዕነት ፡ ብቻ ፡ ያሳያል ፤ በግእዝ ፡ ግን ፡ ቅቡዕነትን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ምሳሕነትንም ፡ ከንጊዜው ፡ ከናቀፉረበ ፡ ያሳያል ፡ (ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፲፬ ። ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ማ፳ ፡ ማ፳) ።

**መሲሓዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ የመሲሕ ፤ በመሲሕ ፡ የሚያምን ፡ መሲሕን ፡ የመሳ ፡ ክርስቲያን ። ሕግ ፡ መሲሓዊት ። በዓሳት ፡ መሲሓውያት ። ሕዝብ ፡ መሲሓውያን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፬ ። ፳፫ ። አቡሻ ። ስንክ ፡ መስ፱) ።

**መሲሕና** ፤ መሲሕነት ፡ መሲሕ ፡ መኾን ።

**ሞሳሕ** ፤—ስመ ፡ ነግድ ፤—መሰከ ፡ ሞሳኽ ።

**ምስሓግ** ፤—ምሳግ ፤—ስሒግ ፡ ሰሐገ ።

**መሰጠ** ፤—ነጠቀ ፤—መሢጥ ፡ መሠጠ ።

**መስጦ** ፤ **እልመስጦ** ፤ (ጽር ፡ ፒስቲስ) ፤ እምነት ፤ ሃይማኖት ። እልመስጦ ፡ አግያ ፤ ወይእቲ ፡ ሃይማኖት ፡ ቅድስት ፡ እንተ ፡ መሀሮሙ ፡ እግዚእነ ፡ (ሃይ ፡ አበ፩) ። እል ፡ የዐረብ ፡ ተውላክ ፡ ነው ፤ መስጦ ፡ አግያ ፡ ያለውን ፡ ሃይማኖት ፡ ቅድስት ፡ ብሎ ፡ ተረጕመው ፤ መምህራን ፡ ግን ፡ እልም ፡ ትምርት ፤ ስጦ ፡ ምልአተ ፡ ንባብ ፤ አግያ ፡ ኅቡእ ፡ ብለው ፤ ሌላም ፡ ብዙ ፡ አፈታት ፡ ይፈቱታል ። እንተ ፡ መሀሮሙ ፡ ያለውንም ፡ አንቀጹ ፡ ምኅሳፍ ፡ ብሎታል ፤ የፊት ፡ በር ፤ ቀዳማይ ፡ አንቀጽ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ምስጢር** ፤—በቁሙ ፤—ሰጢር ፡ ሰጠረ ።

**መስይ** ፤ ዮት ፤ (መስየ ፤ መሰየ ፡ ይመሲ ፡ ይምሰይ ፤ ይምሲ) ፤ መምሸት ፤ መሥረክ ፤ ሠርክ ፡ ማታ ፡ መኾን ፤ የጊዜ ። እፎ ፡ እንጋ ፡ ይመሲ ። እምከመ ፡ መስየ ። ዘኀበ ፡ መስየ ፡ ይበይት ። እስመ ፡ መስየ ፡ ብሔር ። ይውዕል ፡ ወይትቀነይ ፡ እስከ ፡ ይመሲ ፡ (ዘዳ፳፰ ፡ ፷፯ ። ማቴ፲፮ ፡ ፪ ። ሚራ፴፮ ፡ ፴፩ ። ገድ ፡ ተክ ። መዝ ፡ ፻፫) ።

**ምሴት** ፤ (ዐረ ፡ መሳ ። ዕብ ፡ ኤሜሽ) ፤ ምሽት ፡ ማታ ፤ ከሠርክ ፡ እስከ ፡ ንዋም ። ምሴተ ፡ ኀሙስ ፡ ሰጸቢሐ ፡ ዐርብ ። በምሴት ፡ ይደምፅ ፡ ብካይ ። በፀሎቱ ፡ ወሰቡዑ ፡ ምሴት ። ይመና ፡ ምሴት ፡ (ቅዳ ፡ ኤጲ ። መዝ ፡ ፳፱ ። ኩፋ ፡ ፳፫ ። ምሳ፲፯ ፡ ፲፰) ።

**አምሰየ** ፤ አመሸ ፤ አስመሸ ፤ እስከ ፡ ማታ ፡ ቈየ ፤ አስቈየ ። ተጊሀ ፡ ወአምሲዮ ፡ (ማቴ፳፰ ፡ ፲፪) ።

**ማስያስ** ፤ (ዕብ ፡ ማሽያሕ) ፤ መሲሕ ፡ ምሱሕ ፤ ቅቡዕ ። ማስያስ ፡ ዘይሰመይ ፡ ክርስቶስ ። ማስያስ ፡ ናይናን ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳ ። ግብ ፡ ሕማ) ።

**መሲክ** ፤ ኮት ፤ (መሰከ ፡ ይመስክ ፡ ይምስክ ። ዕብ ፡ ማሻኽ ። ዐረ ፡ መሰከ) ፤ መያዝ ፡ መጨበጥ ፤ መሳብ ፡ መጐተት ፤ መለጠጥ ፡ መዘርጋት ፤ ለመንደፍ ፡ የቀስት ፡ የፍላጻ ። ምስክ ፡ አባ ፡ ቀስተከ ፡ ወፈኑ ፡ ሐጸከ ። ወሰቀ ፡ ወመሰከ ፡ ቀስቶ ። እስመ ፡ መሰኩከ ፡ መንግሌየ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፫ ። ፬ነገ ፡ ፲ ፡ ፳፱ ። ዘካ፱ ፡ ፲፫) ። ወሰቀ ፡ ማለብ ፡ መደገንን ፤ መሰከ ፡ አቤማምቶ ፡ ይዞ ፡ መሳብ ፡ መንደፍን ፡ ያሳያል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ኹሉም ፡ በኹሉ ፡ አለ ፤ ይወራረሳሉ ። ወስቅ ፡ ቀስተከ ፡ ወምስክ ፡ አሕጻከ ፡ (፬ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯) ።

**መሰከ** ፤ አመሸከ ፡ እምሽክ ፡ አደረገ ፤ ቈረጠ ፡ ፀጨደ ። ነጨ ፡ ጋጠ ፡ አመሰኳ ፤ ሰዥዑን ፡ እይ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ አቀጠን ፡ ይሉታል ፤ መሰከ ፡ መሰከ ፡ ማሸንክ ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ምስክ** ፤ (ፋርስ ፡ ሙሽክ ። ዐረ ፡ ሚስክ ። ሱር ፡ ሙሳክ ። ዕብ ፡ ሙሻቅ ። ጽር ፡ ሞስኮስ) ። የሽቱ ፡ አውሬ ፤ ዝባድ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ዝባድ ፡ ያለ ፡ ሌላ ። ጥሩ ፡ ሽቱ ፡ ከዚያው ፡ ከውሬው ፡ ገላ ፡ የሚገኝ ። ምስክ ፡ ዘውስተ ፡ ቢረሌ ። ጼናሁ ፡ ይምዕዝ ፡ እምስክ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፬ ። አረጋ ፡ ድ፲፫) ።

**ሞሳኽ** ፤ (ጽር ፡ ሜሴኽ ። ዕብ ፡ ሜሼኽ) ፤ ስመ ፡ ነገድ ፤ ከሰባቱ ፡ ደቂቀ ፡ ያፌት ፡ አንዱ ፡ ፮ኛው ፡ የመስኮቦች ፡ አባት ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፪ ። ፩ዜና ፡ ፩ ፡ ፭ ። ሕዝ፴፰ ፡ ፪) ። ሳቢ ፡ ጕታኙ ፡ መሪ ፤ ወይም ፡ የታደመ ፡ የተቀጠረ ፤ ዕድመኛ ፡ ባለቀጠሮ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ጎግ ፡ ማጎግን ፡ እይ ፡ (ሕዝ፴፰ ፡ ፯—፲ ፡ ፲፯—፲፱) ።

**ምስኪን** ፤—በቁሙ ፤—ሰኪን ፡ ሰከነ ።

**መስከረም** ፤—የወር ፡ ስም ፤—ከሪም ፡ ከረመ ።

**መስኩት** ፤—በቁሙ ፤—ሰኪው ፡ ሰከወ ።

**መሲል** ፤ ሎት ፤ (መሰለ ፡ ይመስል ፡ ይምስል ። ዕብ ፡ ማሻል ። ሱር ፡ ምታል ። ዐረ ፡ መሰ(ተ)ለ) ፤ መምሰል ፤ መስሎ ፡ መታየት ፤ ባሕርይ ፡ ሳይለወጥ ፡ ሌላ ፡ መባል ፤ በውነት ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፤ ያውም ፡ በመልክና ፡ በግብር ፡ በነገር ፡ ብቻ ። ይመስሎ ፡ ዝንቱ ፡ ወልድ ፡ ሰጦቢት ። አርዌ ፡ ዘይመስል ፡ ድብ ። ወይመስሎሙ ፡ ወልደ ፡ ዮሴፍ ። ነገርየ ፡ ይመስል ፡ ሐሰተ ። እመኒ ፡ ኀዳጠ ፡ ወሀበከ ፡ ብዙኀ ፡ ይመስሎ ። ቦ ፡ ፍናው ፡ ዘይመስላሁ ፡ ሰብእሲ ፡ ርቱዓተ ፡ (ጦቢ፯ ፡ ፪ ። ዳን፯ ፡ ፭ ። ሉቃ፫ ፡ ፳፫ ። ኢዮ፳ ፡ ፫ ። ሢራ፳ ፡ ፲፬ ። ምሳ፲፬ ፡ ፳፭) ። በመሰለ ፡ ፈንታ ፡ ተመሰለ ፡ ተማሰለ ፡

ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ተመሰሊ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ። ተመሰሎ ፡ ኪያየ ፤ በከመ ፡ አነ ፡ እትሜሰሎ ። መነ ፡ ትትሜስል ፡ (ፊልጵ፪ ፡ ፯ ። ጸቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፩ ። ሕዝ፴፩ ፡ ፪) ። ከመ ፡ ዘኢይትማሰል ፡ ገጽ ፡ ገጸ ። ይትማሰሎሙ ፡ ለገብርየ ፡ ብርት ። መኑ ፡ ይትማሰሎ ፡ ለጣዕመ ፡ ዚአሁ ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፲፱ ። ጥበ፲፭ ፡ ፱ ። ቀሌ) ። አርእስቱ ፡ የቀተስና ፡ የቀደሰ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ በመሳሳትና ፡ በመጥበቅ ፡ በቱሱሕንት ፡ ይገባል ።

**መስሎ** ፤ **ሎት** ፤ (**መሰለ ፡ ይሜስል ፡ ይመስል**) ፤ መመሰል ፡ መተረት ፡ ነገርን ፡ ከነገር ፡ ማስጠጋት ፡ ማመሳሰልና ፡ ማነጻጸር ፤ በቃል ። መስል ፡ ምሳሌ ። እሜስል ፡ ባዕሌከሙ ፡ አምሳለ ። ውስተ ፡ መስሎ ፡ ነገር ፡ ኢይሄልዉ ። ወመሰለ ፡ ሎሙ ፡ ወመሀሮሙ ፡ (ሕዝ፲፯ ፡ ፪ ። መሳ፲፬ ፡ ፲፱ ። ሚ.ራ፴፯ ፡ ፴፫ ። ሉቃ፲፱ ፡ ፯) ።

——፤ መሣል ፡ መንደፍ ፡ መበገር ፤ መልክ ፡ ማውጣት ፡ በቀለም ፡ በርሳስ ። ምስል ፡ ማፍሰስ ፡ ጣዖት ፡ መሥራት ፤ ማንጠጥ ፡ መቅረጥ ፡ የሸክላ ፡ የማዕደን ፡ የዕፀ ፡ የቀርን ፤ ምንም ፡ ስልቱ ፡ ቢለይ ፡ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ከመስሎ ፡ አይወጣም ። ገብሮ ፡ ወመሰሎ ። ይሜስል ፡ ጽቡረ ፡ በእደዊሁ ። ገለፎ ፡ ወመሰሎ ፡ በአምሳለ ፡ ሰብእ ፡ (ኢሳ፵ ፡ ፲፱ ። ፴፰ ፡ ፴ ። ጥበ፲፫ ፡ ፲፫) ። ዳግመኛም ፡ በመሰለ ፡ ፈንታ ፡ አስተማሰለ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። በመኑ ፡ ታስተማስልዎ ፡ ለእግዚ ። በመኑ ፡ አስተማስላ ፡ ለዛቲ ፡ ትውልድ ። አው ፡ አስተማሰሎ ፡ በእንስሳ ። ከመ ፡ ታመክሮ ፡ በአስተማስሎ ፡ (ኢሳ፵ ፡ ፲፰ ። ማቴ፲፩ ፡ ፲፮ ። ጥበ፲፫ ፡ ፲፬ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፩) ። ሐቀረንና ፡ ዐገሠን ፡ እይ ፤ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ።

(ሳ ፡ ጥ) **መሳሊ** ፤ **መምሰሊ** ፤ (**ሊት ፡ ልያን ፡ ያት**) ፤ የሚመስል ፡ መሳይ ፡ ተራች ፡ ሠዓሊ ፡ ምስል ፡ አፍሳሽ ። ምድር ፡ መምሰሊተ ፡ ሕማምየ ። ኩኑ ፡ መምስልያነ ፡ እግዚ ። መምሰሌ ፡ ርጢን ፡ (ጥበ፯ ፡ ፫ ። ቄር ፡ ጸላ ። አዋል) ። በመሳሊና ፡ በመምሰሊ ፡ ፈንታ ፡ ተመሳሊ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። አፍቅሮተ ፡ ሰብእ ፡ ተመሳሊት ፡ ለአፍቅሮተ ፡ እግዚ ። ተመሳልያን ፡ ቦሙ ፡ ውስተ ፡ ምግባራቲሆሙ ። ይኩኑ ፡ ተመሳልያነ ፡ በምግባራቲሁ ። ተመሳሌ ፡ ንኡስ ፡ ቀርን ። ተመሳሌ ፡ አብ ፡ ይስሬን ፡ (ፊልክ ፡ ፶፲፱ ። ፶፻፱ ። ፋ ፡ ን ፡ ፩ ፡ ፲፩ ። ጥበ ፡ ጠቢ ። ደራሲ) ።

**መመስል** ፤ (**ልት ፡ ላን ፡ ላት**) ፤ ተራች ፡ ምስል ፡ አፍሳሽ ።

**አምሰለ** ፤ አመሰለ ፤ አስመሰለ ። ብዕልክሙ ፡ ይመስለክሙ ፡ ጻድቃነ ። ከመ ፡ ዘአምካልእ ፡ ሕዝብ ፡ ያመስሉኒ ። ዐርክ ፡ አምስልዎ ። እንዘ ፡ ታመስሉኒ ፡ ኤርምያስሀ ፡ (ሔኖ፺፯ ፡ ፱ ። ኢዮ፲፱ ፡ ፲፩ ፡ ጥበ፭ ፡ ፲፯ ። ተረ ፡ ባሮ) ። ፪ኛም ፡ በመሰለና ፡ በሐሰበ ፡ ፈንታ ፡ አምሰለ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ያመስል ፡ ለሰብእ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ያፈቅረኒ ። ወአምሰላ ፡ ዔሊ ፡ ከመ ፡ ስክርት ፡ (ዮሴፍ ። ፩ነገ ፡ ፩ ፡ ፲፫) ።

**ተመሰለ** ፤ በቁሙ ፡ ሠሠ ፡ በወርቅ ፡ ወርቀ ፡ በሠም ፡ ምሳሌው ፡ ተረቱ ፡ ተነገረ ፤ ሥዕሉ ፡ ምስሉ ፡ ጣዖቱ ፡ ተሠራ ። ሸሉ ፡ ዘይትዓበይ ፡ ይትሜሰል ፡ በሰይጣን ። ዘእንዘ ፡ በ ፡ ንዋይ ፡ ይትሜሰል ፡ ከመ ፡ ነዳይ ። ሰይጣን ፡ ይትሜሰል ፡ በሥሉ ፡ አራዊት ። ወደራሩ ፡ ውእቱ ፡ ዘተመሰለ ፡ በበግዕ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ተ፲፭ ። ቀሌ ። ዮሴፍ) ። ተመሰለ ፡ ብሎ ፡ ከመና ፡ በ ፡ ካልተከተሰት ፡ ተደራጊ ፡ አይኾንም ፤ ግእዝም ፡ ቢሰብ ፡ አድራጊ ፡ ኹኖ ፡ ከመሰለ ፡ መንገድ ፡ ይገባና ፡ ተ ፡ ጸያፍ ፡ ይኾናል ። ዳግመኛም ፡ በኮነ ፡ ፈንታ ፤ ተመሰልኪ ፡ ብእሲተ ፡ ዘማ ። ተመሰለ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ። ወተመሰለ ፡ ሙሴ ፡ ከመ ፡ ሊቀ ፡ ጸጸሳት ፡ ይላል ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፴፪ ። ፊልጵ፪ ፡ ፯ ። ቀሌ) ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ የጣፊና ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

(ሳ ፡ ጥ) **ምሱል** ፤ (**ላን ፡ ላት ፡ ስልት**) ፤ የመሰለ ፤ የተመሰለ ፤ ፅንስ ፡ ሽል ፡ (ዘፀ፳፩ ፡ ፳፪) ።

**ምሳሌ** ፤ (**ልያት**) ፤ በቁሙ ፤ ማስረጃ ፡ አንጻር ፡ ተረት ፤ ፍሬ ፡ ነገር ። ናመጽእ ፡ ምሳሌ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ። ዝ ፡ ምሳሌ ፡ ይውኅድ ፡ እምአማን ። ምሳልያተ ፡ ሰሎሞን ። ወኮኑ ፡ ብየ ፡ ሠለስቱ ፡ ምሳልያት ፡ (አፈ ፡ ተ፪ ። ቄር ፡ ጸላ ። ምሳ ፡ ፩ ። ሔኖ) ።

**መምሰ(ስ)ል** ፤ መሰል ፡ አካል ፤ አምሳያ ፡ እኩያ ፤ ሱታፌ ፡ አንጻር ። አልባቲ ፡ መምሰል ፡ እምአንስት ። ሀገር ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ መምሰል ። እስመ ፡ መምስልከ ፡ ውእቱ ፡ (ዮሴፍ ። መዋሥ ። ኩፉ ፡ ፴፰) ። ቅድም ፡ ጥቃ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መንጸር ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ መምስል ፡ ይላል ፡ (መክ፯ ፡ ፲፱) ።

**ምስል** ፤ (**ብ ፡ ምሰል** ፤ **ምስላት** ፤ **አምሳል ፡ ላት**) ፤ በቁሙ ፡ ጣዖት ፡ መታሰቢያ ፤ ግልፍ ፡ ቅርጽ ፡ ተመሳሳይ ፡ መልክ ፡ ያለው ፤ የነገር ፡ ምሳሌ ፡ ተረት ፡ ስንቁቅልሽ ። ምስል ፡ ዐቢይ ፡ ርእሱ ፡ ዘወርቅ ። ግነዩ ፡ ወስግዱ ፡ ለምስል ። ምስሊሆሙ ፡ ትስብሩ ። ወሰበረ ፡ ምስላቲሆሙ ። እሜሩ ፡ ግልፎከ ፡ ወአምሳሊከ ። አምሳላተ ፡ እንስሳ ። ልብ ፡ ጠቢብ ፡ ይፌክር ፡ አምሳለ ። ይፈትን ፡ ሰርጐ ፡ ምስል ፡ (ዳን፪ ፡ ፴፰ ። ፫ ፡ ፭ ። ዘፀ፴፱ ፡ ፲፫ ። ዮዲ፫ ፡ ፰ ። ሚክ፭ ፡ ፲፱ ። ጥበ፲፫ ፡ ፲ ። ሢራ፫ ፡ ፳፱ ። መክ፲፪ ፡ ፱) ።

**አምሳል** ፤ መልኮች ፡ ዐይነቶች ፡ ባንድ ፡ አካልና ፡ ባንድ ፡ ገላ ፡ ያሉ ፡ የብዙ ፡ ሕዋሳት ፡ አርአያዎች ። በአምሳለ ፡ ዚአሁ ፡ ገብሮሙ ። ተመሰለ ፡ በአምሳለ ፡ ንስር ። በበ ፡ ዘመዶሙ ፡ ወበበ ፡ አምሳሎሙ ። አነ ፡ ሰይጣን ፡ እትሜሰል ፡ በሥሉ ፡ አምሳል ፡ (ሢራ፲፯ ፡ ፫ ። ተረ ፡ ባሮ ። ኩፉ ፡ ፫ ። ቀሌ) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ሊኪይ ፡ የማይቻል ፡ ብዙነቱን ፡ ከደው ፡ ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ አንባብ ፡ እያሉ ፡ በከመ ፡ ዘይቤ ፡ ይፈቱታል ፤ እውነተኛ ፡ የመጽሐፍ ፡ ምስክር ፡ የለውም ።

**ምስለ** ፤ (**ደቂቅ ፡ አገ**) ፤ ከ—ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ ከነ ፡ ቸልታ ፡ ቢ ፡ እንደ ። ኢታማስን ፡ ጻድቃነ ፡ ምስለ ፡ ኃጥኣን ። መጽአ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ወው

ሉዱ ፤ ከነ ። ሰረረ ፤ ንስር ፡ ምስለ ፡ መጽሐፍ ። ተሰ ውዋ ፡ ዕደው ፡ ምስለ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅሎሙ ፤ ይዘው ። በጽባሕ ፡ ምስለ ፡ ትንሣኤ ፡ ፀሓይ ፤ ሲ ። አበስኒ ፡ ምስለ ፡ አበዊነ ። ወኢተቀሥፉ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፤ እንደ ፡ (ዘፍ፡፲፰ ፡ ፳፫ ። አሞ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ተረ ፡ ባሮ ። ዮሴ፡፲፰ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፻፭ ። ፳፱) ። ምስሌሁ ፡ ሃ ፡ ከ ፡ ኪ ፡ የ ፤ እያለ ፡ እንደ ፡ ጎበ ፡ በ፫ንምበ ፡ ይዘረዝራል ። በወ ፡ ፈንታ ፡ ምስለ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ኣፈልሰከ ፡ ሰከ ፡ ምስለ ፡ አኅዊከ ፡ (ኤር፡፳ ፡ ፬) ። (ዕር፡፳፩ ፡ ቀ፡፲፯፱) ።

**ምስሌሁ** ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፤ እንደ ፡ ርሱ ። ምስሉ ፡ ሥዕሉ ፡ መልኩ ።

**ተማሰለ** ፤ በቁሙ ፤ ተመሳሰለ ፤ ተነጻጸረ ። ኢይትማሰላ ፡ ወርቅ ። ወኢይትማሰል ፡ ምስለ ፡ ባዕድ ፡ ንብረቱ ፡ (ኢዮ፡፳፰ ፡ ፲፯ ። ጥበ፡፯ ፡ ፲፱) ። ለወጥም ፡ ይኾናል ።

**አስተማሰለ** ፤ አማሰለ ፤ አመሳሰለ ፤ አነጻጸረ ። ምስጢሩ ፡ ማድረግና ፡ ማደራረግ ፡ ነው ፤ ባድራጊነቱ ፡ ከመዠመሪያው ፡ ዐምድ ፡ ይደረባል ። ረድኦ ፡ ሰሲቀ ፡ ምኔት ፡ ይኩን ፡ አስተማሳሌ ፡ ግብረ ፡ ኤልሳዕ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**መስልም ፤—እስላም ፤—ሰሊም ፡ ሰለመ ።**

**መስም ፤—ባዕድ ፡ ዘር ፤—ሰምይ ፡ ሰመየ ።**

**መስኖ ፤—በቁሙ ፤—ሰኒው ፡ ሰነወ ።**

**ማስኖ ፤ ኖት ፤ (ማሰነ ፡ ይማስን ፡ ይማስን ። መንሰወ ፤ ነሰወ ። ዕብ ፡ ናሻም ፤ ሕቅ ፡ እለ)** ፤ መማስን ፤ መድከም ፡ መልፋት ፡ (ዐማርኛ) ። መጥፋት ፡ መሞት ፡ መበላሸት ፤ መፍረስ ፡ መበስበስ ። ማሕፀንት ፡ ዘማሰነት ፡ ማስኖ ፡ ፍጥረታዊ ። ዘማሰነ ፡ ልቡ ። ወርቅ ፡ ዘይማስን ። ሰብሰ ፡ ሥጋ ፡ ዘይማስን ፡ ወረበየ ፡ ዘኢይማስን ። ይማስን ፡ ቤቶሙ ፡ ለዕቡያን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፫ ። ፴፪ ። ኪዳ፡ጥ ፡ ፩ ፡ ፮ ። ቅዳ ። ሢራ፡፳፩ ፡ ፱) ።

**ማሳኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፤ ማሳኝ ፤ የሚጠፋ ፡ ጠፊ ፤ ፈራሽ ፡ በስባሽ ። መብልዕ ፡ ማሳኒ ። ጥሪት ፡ ማሳኒ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ጥቅ፴) ።

**ሙሱን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ስንት)** ፤ የማሰነ ፤ ጥፉ ፡ መጥፎ ፡ ብልሹ ፤ ግም ፡ ድፍርስ ። ዕጽው ፡ በሰስ ፡ ሙሱን ፡ ጥቀ ። ሙሱናን ፡ ልብ ። ማይ ፡ ሙሱን ። ሙሱነ ፡ ይሰትዩ ፡ (ኤር፡፳፱ ፡ ፪ ። ፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፰ ። መጽምስ ። ሕዝ፴ ፡ ፲፯) ።

**ሙስና ፤ (ናት)** ፤ ጥፋነት ፡ ጥፋት ፡ መፍረስ ፡ መበስበስ ፡ መከራ ፡ መቅሠፍት ። ሙስናሃ ፡ ለነኒዊ ። ትዘከሮ ፡ ለሞት ፡ ወለሙስና ። ወተጋብኡ ፡ አርባዕቱ ፡ ሙስናት ፤ ዘውእቶሙ ፡ ቀትል ፡ ወዋዕይ ፡ ወጸብእ ፡ ወረኃብ ፡ (ጦቢ፲፬ ፡ ፲፫ ። ሢራ፲፰ ፡ ፳ ። ዮሴፍ) ።

የንጨት ፡ ስም ፤ ፩ ፡ ዐይነት ፡ ዕንጨት ፤ ቅርፍቱን ፡ ድቀሎ ፡ በበሶ ፡ ሲበሉት ፡ ኮሶ ፡ የሚያመክን ፡ የትማሮች ፡ መዳኒት ።

**መሲና ፤ (ናት)** ፤ በቁሙ ፤ የማቶልይ ፡ ከብት ፡ መካን ፡ ሙስንት ፡ ማሕፀን ።

**አማሰነ** ፤ በቁሙ ፤ አጠፋ ፡ አስጠፋ ፡ አበላሸ ። ሞት ፡ ዘዘሎ ፡ ያማስን ። በአማስኖ ፡ ናላሁ ። እንስሳት ፡ አማሳንያን ። አማሳኒሃ ፡ ለነፍስ ፡ (ሔኖ፹፱ ፡ ፲፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፪ ። ፫፯ ። ቅዳ ፡ ያዕ) ።

**መስዕ ፤ (ዐረ ፡ ሚስዕ)** ፤ የማእዝን ፡ ስም ፤ ንኡስ ፡ ማእዝን ፤ በሰሜንና ፡ በምሥራቅ ፡ መካከል ፡ ያለ ፤ የሰሜን ፡ ምሥራቅ ፤ የአዜብ ፡ ትይዩና ፡ አንጻር ፤ አፋዛዥ ። ባርክ ፡ መስዐ ፡ ወአዜበ ፡ (ቅዳ) ። ማእዝንነቱ ፡ የሰሜን ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሰሜንም ፡ በርሱ ፡ ስም ፡ መስዕ ፡ ይባላል ። እብሎ ፡ ለመስዕ ። ሰፍሖ ፡ ለመስዕ ፡ ዲበ ፡ ወኢምንት ። ገቦ ፡ መስዕ ። ንጉሠ ፡ መስዕ ፡ (ኢሳ፵፫ ፡ ፮ ። ኢዮ፳፮ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፵፯ ። ዳን፲፩ ፡ ፮) ። ኹለተኛም ፡ በመላሾች ፡ ስሕተት ፤ ምሥራቅን ፡ አዜብ ፤ ደቡብን ፡ ጽላሎትን ፡ መስዕ ፡ ይላል ። አንሥአ ፡ አዜበ ፡ እምሰማይ ፡ ወአምጽአ ፡ መስዐ ፡ በኀይሉ ። ዘይመይጦ ፡ ለብርሃን ፡ መንገለ ፡ መስዕ ፡ (መዝ ፡ ፸፯ ። ዓሞ፰ ፡ ፰) ።

**መስፍሕ ፤—መስፍ ፤—ሰፊሕ ፡ ሰፍሐ ።**

**መስፈርስ ፤—የበሽታ ፡ ስም ፤—እስፋር ።**

**መስፌቶም ፤ (ጽር ፡ ሞስፌታም ። ዕብ ፡ ሚሽፋታይም)** ፤ ከንፈሮች ፤ ዳር ፡ ደንበሮች ። ለምንት ፡ ትነብር ፡ ማእከለ ፡ መስፌቶም ፡ (ምሳ፷ ፡ ፲፮) ።

**ምሱቅ ፤—ጥርብ ፤—ነሲቅ ፡ ነሰቀ ፡ ንሱቅ ።**

**መስቄ ፤—ማጠጫ ፤—ሰቅይ ፡ ሰቀየ ።**

**መስቀል ፤—በቁሙ ፤—ሰቂል ፡ ሰቀለ ።**

**መስቄሎን ፤ (ጽር ፡ ሜስካሎን)** ፤ የሽማኔ ፡ ዕንጨት ፡ መጠቅለያው ፤ ደልዳላ ፡ ወፍራም ፡ ምእዙን ፡ ራሳም ፡ አራት ፡ ብስ ፡ ያለው ። ወዕፀ ፡ ኩናቱ ፡ ከመ ፡ መስቄሎነ ፡ እነምት ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፯) ።

**መስቀር ፤—ታቦተ ፡ ኖኅ ፤—ሰቁር ፡ ሰቈረ ።**

**ማስረ ፤ (ዕብ ፡ ማሳር)** ፤ እጅ ፡ በጅ ፡ ሰጠ ፤ አስጨበጠ ፤ አሲያዘ ፡ አስረከበ ። ሙሽራ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ በሕግ ፡ የተሰጠ ፡ ለጋ ፡ ቀንበጥ ፡ ወጣት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ለሰሌንና ፡ ለኮባም ፡ ይኾናል ።

**ምስራ ፤ ማሱራ ፤ (ቅብጥ ፡ ሜሱሪ)** ፤ የወር ፡ ስም ፡ ነሐሴ ፡ (አቡሻ) ።

(ጥስ) **ምስር** ፤ በቁሙ ፡ ብርስን ፡ (መ ፡ ፈ) ።

(ላስ) **ምስር ፤(ዐረ ፡ ሚጽር ፤ መጽር)፤** በቁሙ ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ ግብጥ ፡ የሚጽራይም ፡ ክፍል ፡ ሚጽር ። ሲጣፍ ፡ የሚገባው ፡ በጸደ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሳት ፡ ሰ ፡ አይደለም ። ደወለ ፡ ምስር ። ማዕልቃ ፡ ዘምስር ።

**ምሳር ፤—በቁሙ ፤—ወሥሮ ፡ ወሠረ ፡ ሞሠር ።**

**መሰረት ፡—በቁሙ ፤—ሣርሮ ፡ ሣረረ ።**

**መስቴ ፤—መጠጥ ፡ ጫ ፤—ሰትይ ፡ ሰ ትየ ።**

**መስተአድ ፤(ጽር ፡ ሚስታኢል)፤** ዕቃ ፡ ቤት ፡ ገበዝ ፡ የአልባሳትና ፡ የንዋያት ፡ ሹም ፡ ጠባቂ ፡ (፱ኑ፻ ፡ ፲ ፡ ፳፱) ።

**መስቴማ ፤(ዕብ ፡ ማስቤማህ ፤ ሳጣም)፤** ጠብ ፡ ጥል ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ጠላትንት ፡ ወቀሣ ፡ ክስሳ ። ጠላት ፡ ጠበኛ ፤ ከሳሽ ፡ አሳጭ ፡ ሰይጣን ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ የመየን ፡ ዘር ፡ መስሏቸው ፤ ተመያኒ ፡ መስተመ ይን ፡ ይሉታል ፡ (ኩፋ ፡ ፲ ። ፲፯ ። ፲፰) ።

**መሽተሪ ፤(ዐረ ፡ እልሙሽተሪ)፤** ኮከብ ፤ የኮከብ ፡ ስም ፡ (አፈ ፡ ቀ፳፯) ።

**መስጼጠምያ ፤(ጽር ፡ ሚሶፖታሚያ)፤** ማእከለ ፡ አፍላግ ፤ ሚሶ ፡ ማእከል ፤ ፖታሚያ ፡ አፍ ላግ ፡ ጤግሮስና ፡ ኤፍራጥስ ፡ (ግብ፪ ፡ ፱ ። ፯ ፡ ፪) ።

**ምት ፤—ባል ፡ ወንድ ፤—መቲህ ፡ መ ትሀ ።**

**መታግር ፤—ገመድ ፡ አውታር ፤—ተ ጊር ፡ ተገረ ።**

**መቲህ ፤ ሆት ፤(መትሀ ፡ ይመትሀ ፤ ይ ምታሀ ። ዐረ ፡ መቲሀ)፤** መሳት ፤ ማሳት ፡ ምት ሀት ፡ ማድረግ ፡ ማሳየት ። እሰ ፡ ይመትሁ ፡ (አርጋ) ። መምታት ፤ መማታት ፤ ያለሌ ፡ የበትር ፡ የቸንፈር ። መሣ ሣት ፡ መንፈግ ፡ የሆዳም ።

**መታሂ ፤ (ሂት ፡ ሀያን ፡ ያት)፤** ስሑት ፡ መስሐቲ ፤ ምትታታም ፡ ምታተኛ ። ተማች ፡ አጥቂ ፤ አለሌ ፡ ዱለኛ ። ሥሠ ፡ ንፉግ ፡ ሆዳም ፡ በላተኛ ። ኢትደረር ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡ መታሂ ፡ (ምሳ፳፫ ፡ ፮) ።

**መትህ ፤ (ሃት)፤** ምትሀት ፡ ምትሀትንት ፤ ሳይ ኾን ፡ መስሎ ፡ መታየት ። እስመ ፡ መልአክ ፡ ዘበመ ትህ ፡ (ሐኪም ፡ መስሎ) ፡ ሠጠጠ ፡ ከርሦ ፡ ለፈላሲ ፡ ወአርአየ ፡ ሕማመ ፡ ልቡ ፤ ወአግብኦ ፡ በከመ ፡ ሀሎ ። ተርእዩ ፡ ሎሙ ፡ ሰይጣናት ፡ ዘበመትህ ፡ መንክር ፡ (ምድርን ፡ እንደ ፡ ሰፌድ ፡ እያንቀረቀቡ) ። ፈቃድ ፡ ዘይወልድ ፡ መትህ ፡ (ፊልክ ፡ ፳፰ና ፡ ፳፱ ። ማር ፡ ይ ሥ፲፱ ፡ ፪) ።

**አምትሀ ፤** አስመታ ፤ ምትሀት ፡ አስደረገ ።

**ተመትሀ ፤** ተመታ ፡ ተጠቃ ፤ ምትሀት ፡ ኾነ ፤ ታበ ፡ ታይቶ ፡ ጠፋ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ተመትሀተ ፡ ይ ላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ገድ ፡ አዳ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ምቱህ ፤(ሃን ፡ ሃት ፡ ትሀት)፤** የተመታ ፤ ምትሀት ፡ የኾነ ።

**ምትሀት ፤ (ታት)፤** መምታት ፤ መመታት ፤ አመታት ። ምታት ፤ ምች ፤ ቸንፈር ፤ በትሩና ፡ መችው ፡ የማይታይ ፡ ጓቡእ ፡ ረቂቅ ፡ ሕማም ፡ መቅሠፍት ፡ (፪ ነገ ፡ ፳፬ ፡ ፲፭—፲፯ ። ዘዐ፲፪ ፡ ፳፱ ፡ ፴) ።

—፤ በቁሙ ፤ ሳይኾን ፡ የኾነ ፡ መስሎ ፡ ግዘፍ ፡ ነሥቶ ፡ መልክ ፡ ገዝቶ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፤ እንደ ፡ ሕልምና ፡ እ ንደ ፡ ጥላ ፡ እንደ ፡ ስዒማ ፡ ያለ ፤ ሰይጣናዊ ፡ ሐሰት ፤ ወ ይም ፡ መልአካዊ ፡ እውነት ። ራእየ ፡ ምትሀት ፡ ፀዋግ ። ምትሀት ፡ ሕሓላም ። ምትሀት ፡ ዓለማዊ ። ምትሀት ፡ ፀይን ። እስ ፡ ምትሀተ ፡ የአምኑ ፡ (ጥበ፲፯ ፡ ፱ ። ፲፰ ፡ ፲፯ ። አፈ ፡ ተ፳፰ ። ዕን፪ ፡ ፲፰ ። ቄር) ። ይቤሉ ፡ አኀው ፤ እስመ ፡ ሠለስቱ ፡ ሰይጣናት ፡ ቦኡ ፡ ኀበ ፡ ማር ፡ ወቅሬስ ፡ በአምሳለ ፡ ሠለስቱ ፡ ቀሳውስት ፡ (አ ርዮስና ፡ ንስጥሮስ ፡ መቅዶንዮስ) ፡ ወተዋቀሁ ፡ ምስ ሌሁ ። ወመላእክትኒ ፡ ሖሩ ፡ በአምሳለ ፡ ዓሊማው ያን ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ በኣታት ፡ በእንተ ፡ በዓለ ፡ አስፈሬ ዳት ፡ ውኖዳ ፤ ወክኑ ፡ ይሰግዱ ፡ ለመስቀል ፡ ወይኤ ምኅዎ ፡ ወይጼልዩ ። ቦኑ ፡ ከኑ ፡ ውእቱ ፡ ጥዩቀ ፤ አው ፡ አልቦ ። ይቤ ፡ መተርጕም ፤ ወመላእክ ትሰ ፡ ኮኑ ፡ ይሰግዱ ፡ ወይኤምኁ ፡ ወይጼልዩ ፡ በርእ ሰሙ ፤ በከመ ፡ ይጼልይ ፡ ወይኤምኅ ፡ ወይሰግድ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ለፍጹማን ፡ ምስለ ፡ ሥጋቲሆሙ ። ወሰይጣናትሰ ፡ ኮኑ ፡ ይገብሩ ፡ ውእተ ፡ በምትሀታቲ ሆሙ ፡ ሕስውት ፤ እስመ ፡ አልቦሙ ፡ ሥልጣን ፡ ለሰ ይጣናት ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ምትሀተ ፡ ዘበአማን ፡ ዘእ ምጠባይዕ ፡ በከመ ፡ ይገብሩ ፡ መላእክት ፡ (ፊልክ ፡ ፴፫) ።

**ምትሀታዊ ፤** ምትሀታም ፤ የምትሀት ፡ ሥራ ፤ ኀላፊ ፡ ጠፊ ፡ አታላይ ። (ት ፡ አንስት) ፡ ኀይጋ ፡ ስር ጋዊ ፡ ወፍኖተ ፡ ምትሀታዊ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፰) ።

**ምት ፤(ብ ፡ አምታት ። ዕብ ፡ ማታህ ፤ ምቴም)፤** ባል ፡ ዕሩማ ፤ ሚስት ፡ ያለችው ፡ ወንድ ፤ ጕልማሳ ። ሥሡ ፡ ንፉግ ፡ ቀናኢ ፡ ተማች ፡ ማለት ፡ ነው ። (ተረት)፤ ንጉሥ ፡ በመንግሥቱ ፡ ጕልማሳ ፡ በሚስቱ ። በሸንጎ ፡ ቢረታ ፡ ከቤት ፡ ሚስቱን ፡ መታ ። ርእሳ ፡ ለብ እሲት ፡ ምታ ። ምትኪ ፡ ዘንእስኪ ። እንተ ፡ ባቲ ፡ ምት ። አንትንኒ ፡ አንስት ፡ ተኰነና ፡ ለአምታቲክን ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፫ ። ኤፌ፭ ፡ ፳፪ ። ኢሳ፶፬ ፡ ፭ ። ፩ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፩) ።

**መትከል ፤—ኵላብ ፤—ተኪል ፡ ተከለ ።**

**መትከፍ ፤—ትከሻ ፡ ጫንቃ ፤—ተከፈ ።**

**መተነ ፤(ከሠደ ። ዐረ ፡ መተነ ፤ ረዘመ)፤** ተሳበ ፡ ተገተረ ፤ ጸና ፡ ጠነከረ ፡ ገረመተ ።

**መትን ፤ (ዕብ ፡ ማታን ፡ ይምቶን)፤** ለዘበ ፤ ፊስ ፡ ረጠበ ።

**መትን ፤ (ብ ፡ አምትንት)፤** ሻምማት ፡ ክ ሥዳ ። ከብዙ ፡ በቀር ፡ ባንድ ፡ አይገኝም ። የአስር ፡ በአ

ሥራው ፡ ወደጸነዐ ፡ በአምትንት ፡፡ ነፍስ ፡ እስርት ፡ በሥጋ ፤ ወሙቅሕት ፡ በዐፀም ፡ ወአምትንት ፡ ወአሥራው ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ ፡፡ የ፡ሲ፡ና) ፡፡

**መተቀ** ፤ (መቲቅ ፡፡ ዕብ ፡ ማታቅ) ፤ ጣፈጠ ፤ ጥፍጥ ፡ ኾነ ፤ ማር ፡ ማር ፡ አለ ፤ ደስ ፡ አሰኘ ፤ ያታክልት ፡ ያገዳ ፡ የፍሬ ፤ ለወሬም ፡ ይኾናል ፡፡

**ምቱቅ** ፤ ጥዑም ፤ ጥፍጥ ፤ መዐርዒር ፤ ላይ ጉና ፡ ለዦሮም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ምቱቅ ፡ ይባላል ፡፡ ዘእምልደቱ ፡ ዕዉረ ፡ አሕየወ ፤ ወምቱቀ ፡ ብርሃነ ፡ አብቊለ ፡ ሎቱ ፡ ወዘሎሙ ፡ አንከሩ ፡ (ቁር ፡ እስት) ፡፡

**ምትቀት** ፤ መጣፈጥ ፤ ጥፍጥንት ፡፡ ይቤልዋ ፡ ዕፀው ፡ ለበለስ ፡ ንዒ ፡ ንግሢ ፡ ላዕሌነ ፤ ወትቤሎሙ ፡ በለስ ፡ እኅድግኑ ፡ ምትቀትየ ፡ ወፍሬየ ፡ ቡሩከ ፡ ወእንግሥ ፡ ላዕለ ፡ ዕፀው ፡ (መሳ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፩) ፡፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ በጣፎች ፡ ስሕተት ፡ ያንንም ፡ ይኸንም ፡ ምጡቅ ፡ ምጥቀት ፡ ይላሉ ፤ መምህራንም ፡ ሥሩን ፡ ስላላገኙት ፡ በምጡቅ ፡ ዘይቤ ፡ ይፈቱታል ፡፡

**መቲር** ፤ ሮት ፤ (መተረ ፡ ይመትር ፡ ይምትር ፡፡ ዕብ ፡ ባታር) ፤ መምተር ፤ መቍረጥ ፡ መቈራረጥ ፡ መበጠስ ፤ መለየት ፡ መሻር ፤ ጨርሶ ፡ ማጥፋት ፡፡ እመትር ፡ ርእሰከ ፡ እምኔከ ፡፡ ወመተሩ ፡ ዐሥርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ክፍለ ፡፡ መቲረ ፡ ሥርው ፡፡ ምትሩ ፡ እምኔከ ፡፡ ይመትርዎ ፡ እመዓርጊሃ ፡ ለቤተ ፡ ክር ፡፡ ክልአታት ፡ ወመቲሮታት ፡ እምነ ፡፡ መተረ ፡ እግዚ ፡ እምእስራኤል ፡ ርእሰ ፡ ወዘነበ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፶፩ ፡፡ መሳ፲፱ ፡ ፳፱ ፡፡ ሔኖ፺ ፡ ፩ ፡፡ ሚራ፳፭ ፡ ፳፮ ፡፡ ቀሌ፡ ፈልክ ፡ ፶፭ ፡፡ ኢሳ፱ ፡ ፲፱) ፡፡ በቀጥቀጠና ፡ በረስየ ፡ ፈንታ ፡ መተረ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ኢሳ፱ ፡ ፱ ፡ ሚክ፱ ፡ ፫) ፡፡

**መታሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ተርት) ፤ በቀሙ ፡ የሚመትር ፤ ቈራጭ ፡ በጣሽ ፡፡ ሰይፍ ፡ መታሪ ፡፡ መታርያነ ፡ ሥርዋት ፡ (ጥበ፳ ፡ ፳፩ ፡፡ አቡሻ ፡ ፶ ፡፡ ሔኖ፳ ፡ ፫ ፡፡ ፳፩ ፡ ፯) ፡፡

**መተሬ** ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ቅጠል ፡ ፍሬው ፡ እንደ ፡ ሙስና ፡ ኮሶ ፡ የማያመክን ፡፡

**መምተርት** ፤ መምተሪያ ፤ መቍረጫ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ፱ ፡ ፳፭ ፡፡ ሔኖ፳፩ ፡ ፯) ፡፡

**አምተረ** ፤ አስመተረ ፤ አስቈረጠ ፡፡ አስቀረ ፤ አስታጕለ ፤ አቋረጠ ፡፡ ሄሮድስ ፡ ለዮሐንስ ፡ ርእሶ ፡ አምተረ ፡፡ ታመትርኑ ፡ ዕጣና ፡ ለገበዝ ፡ (መዋሥ) ፡፡


**ተመትረ** ፤ ተመተረ ፤ ተቈረጠ ፤ ተለየ ፡ ተሻረ ፤ ተጨርሶ ፡ ጠፋ ፡፡ ተመትሩ ፡ አርእስቲሆሙ ፡፡ ሊተ ፡ ሠላስ ፡ ዓመት ፡ እምዘተመተርኩ ፡ እመፃምርትየ ፡፡ ለይትመተር ፡ እመዓርጊሁ ፡፡ ኢይትመተር ፡ ብእሲ ፡ (ቀሌ ፡፡ ፈልክ ፡ ፫ ፡፡ ፈ ፡ መ ፡ ፮ ፡ ፩ ፡፡ ኢ፻፩ ፡ ፶፮) ፡፡

**ምቱር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ትርት) ፤ የተመተረ ፤ የተቈረጠ ፡ ቍርጥ ፤ የተሻረ ፡ ሽር ፡፡ ምቱረ ፡ እድ ፡፡ ምቱራን ፡ በሰይፍ ፡ እምሳለ ፡ ዕፀው ፡፡ ምቱርኑ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡፡ ምቱር ፡ እመዓርጊሁ ፡ (ማር፱ ፡ ፶፫ ፡፡ ስንክ ፡ ጥቅ፳፪ ፡፡ ኪዳ ፡፡ ቀሌ) ፡፡

**ምትረት** ፤ መቍ(ቈ)ረጥ ፤ አቈራረጥ ፡ ቈረጣ ፡ ቍርጠት ፡፡ ምትረተ ፡ ርእስ ፡፡ ምትረተ ፡ ተስፋ ፡፡ ምትረተ ፡ ኅሊና ፡ (አዋል ፡፡ ፈልክ ፡ ፶፱ ፡፡ ስንክ ፡ ጥቅ፩) ፡፡ በስብረትና ፡ በንሥተት ፡ ፈንታ ፡ ምትረት ፡ ይላል ፡ ጥፋት ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ ምትረተ ፡ ዖዚ ፡፡ ምትረተ ፡ ዋራሲን ፡ (፩ዜና ፡ ፲፫ ፡ ፲፩ ፡፡ ፲፱ ፡ ፲፩) ፡፡

**ምታር** ፤ (ራት) ፤ ምታሬ ፡ ቍራጭ ፡ ብጣሽ ፡ ክፍል ፡፡ መተሩ ፡ ሥጋሃ ፡ በበ ፡ ምታር ፡፡ ወመተርዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ኅበ ፡ ሠለስቱ ፡ ምታራት ፡፡ ምታር ፡ ዐቢይ ፡ (ስንክ ፡ መስ፳፪ና ፡ ፳፱ ፡፡ የ፡ሲ፡ፍ) ፡፡ ምታሮ ፡ የሥጋ ፡ ኅፍሮ ፤ ዝግን ፡ ሥቅሥቅ ፡፡

**መትር** ፤ (ብ ፡ እምታር) ፤ የልክ ፡ ስም ፡ ኹለቱን ፡ ክንድ ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፡ በትር ፡ ወይም ፡ ዘንግ ፤ በተራን ፡ እይ ፡፡ ማተረ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡ ሻ ፡ ፈለገ ፡ ጕበኘ ፡ ቈጠረ ፡ ገመተ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡



መትር ፡

**መተርእስ** ፤—የራስጌ ፡ ሰይፍ ፤—ር ኢ.ስ ፤ ርእሰ ፡፡

**ሜትራይቂይ** ፤ የሳይፍራ ፡ ስም ፡፡ ጋላትን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (መጽ ፡ ምስ) ፡፡

# ነ

**ነ** ፤ ፲፬ኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአ በገደ ፤ ስሙ ፡ ነሐስ ፡ ቍጥሩ ፡ ፶ምሳ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ (ነ—፶)ኀምሳ ፡ ይባላል ።

**ነ** ፤ ንባር ፡ አንቀጽ ፤ የ ፡ (ሀ ፡ ወ) ፡ መሪና ፡ በር ፡ ከፋች ፡ እየኾነው ፡ እንደ ፡ በና ፡ እንደ ፡ ለ ፡ ባሥር ፡ መደብ ፡ ይዘረዘራል ። ነየ ፤ (ነየከ ፡ ነየኪ ፡ ነዮ ፡ ነየ ፤ ናሁ ፡ ነው ፡ ነዋ) ፤ ነኝ ፡ እንሆኝ ፤ ከዚህ ፡ አለኹ ። ነ ፡ መኖርንና ፡ መኾንን ፤ የ ፡ በታንና ፡ የቀጠረን ፡ አከል ፡ ያሳያል ፤ የጥሪ ፡ ተሰጠ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፤ ወይ ፡ አቤት ፡ እ ሜት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አሆ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ (ዘፍ፳፪ ፡ ፩ ። ኢሳ፶፰ ፡ ፱ ። ግብ፱ ፡ ፲) ። ነዮና ፡ ናሁ ፡ ነው ፡ ነዋ ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ ነው ፡ ላማርኛ ፡ ብቻ ፡ ተሰጥቷል ፤ ፍቻቸውን ፡ በየበታቸው ፡ እይ ። ነየ ፡ አነ ፡ ወደቂቅ ። ነዮ ፡ ብእሲትከ ። ነዮ ፡ እምከ ። ነየ ፡ (ኢሳ፰ ፡ ፲፰ ። ዘፍ፲፱ ፡ ፲፱ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ ሠኔ፱) ። ነየነ ፤ (ከሙ ፡ ክን ፡ ዮሙ ፡ ዮን) ፤ ነን ፡ ነን ፤ እንሆን ፡ ከዚህ ፡ አለን ። ነየነ ፡ ንሕነ ፡ አግብርቲከ ። ነዮሙ ፡ እምከ ፡ ወአኀዊከ ። ነዮን ፡ ጽሑፋት ፡ (ኩፋ ፡ ፵፫ ። ማር፫ ፡ ፴፬ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፳፱) ።

**ነ** ፤ የእስክና ፡ የእም ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ወይም ፡ መሪ ። እምሥራቅ ፡ ፀሓይ ፡ እስከነ ፡ ዐረብ ። እምነ ፡ መኑ ፡ ፀነስኪ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፪ ። ነገረ ፡ ማር) ። ሲዘረዝር ፡ ግን ፡ እስከኔሁ ፤ እምኔሁ ፡ እያለ ፡ ማእዝንቱን ፡ እንደ ፡ ኀበና ፡ እንደ ፡ ምስለ ፡ ወደ ፡ ኋምስንት ፡ ይለውጣል ።

**ነ** ፤ የንሕነ ፡ ዝርዝር ፤ አቅራቢና ፡ ጠቃሽ ። ሰሊነ ፤ ኀቤነ ፤ ምስሌነ ፤ ከማነ ። ሥርወ ፡ ትንቢት ፡ ለንሕነ ፡ ብቻ ፤ ሳድሱም ፡ ን ፡ ሳይቀር ። ሐዮነ ፡ ነሐዩ ፤ ምትነ ፡ ንመውት ።

**ኑ** ፤ (ሁ) ፤ ጥያቄና ፡ አንክሮ ፡ የሁ ፡ መንቲያ ፤ ፍቾው ፡ ን ። ዘንቱኑ ፡ ገበርኪ ። ዳኅንኑ ፡ አቡክሙ ፤ እወ ፡ ዳኅን ። አንትኑ ፡ ዘይመጽእ ። ዘወድቀ ፡ ኢይትነሣእኑ ። ዘኖመሰ ፡ ኢይነቅህኑ ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፲፫ ። ፵፫ ፡ ፳፯ ። ማቴ፲፩ ፡ ፫ ። ኤር፰ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፵) ። መ ፡ ሲጨ መርበት ፡ በጥያቄነት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ይኾናል ፤ መኑን ፡ ተመልከት ።

**ኒ** ፤ (ወ ፡ ሂ) ፤ ቀዋ ፤ ም ፡ ደግሞ ፡ ኹም ፤ ስ ንኳ ፡ ግን ። ዘበሰማይኒ ፡ ወዘበምድርኒ ። እመ ፡ ኀደግሙ ፡ ለሰብእ ፡ አበሳሆሙ ፡ የኀድግ ፡ ለክሙኒ ፡ አቡክሙ ። በቃልክኒ ፡ ወበምግባርክኒ ፡ አክብሮ ፡ ለ አቡከ ። ወሚካኤልኒ ፡ ሊቀ ፡ (ጸሎ ፡ ሃይ ። ማቴ፮ ፡ ፲፬ ። ሢራ፫ ፡ ፰ ፡ ይሁ ፡ ፱) ። የወንና ፡ የሂን ፡ አፈታት ፡ እይ ።

**ኒ** ፤ የአነ ፡ ዝርዝር ፡ ወይም ፡ ጠቃሽ ፤ ፍቾው ፡ ኝ ። ኅፀበኒ ፡ ወአንጽሐኒ ። ቀተለኒ ፤ ገደለኝ ፤ ገደለልኝ ፡ ገደለብኝ ፡ (ልኝ ፡ የበን ፡ ብኝ ፡ የከፋ) ።

**ና** ፤ የጥሬና ፡ የስም ፡ ምእላድ ፤ ፍቾው ፡ እን ትና ፡ መኾን ፤ ምስጢሩ ፡ ባሕርይ ፤ ወይም ፡ የባሕርይ ፡ ኹንታ ፡ አኳኾን ። ቅድም ፡ ቅድምና ፤ ሰብእ ፡ ሰብ እና ። ወልድ ፡ ወልድና ፤ ልጅነት ፡ ልጅ ፡ መኾን ፡ ያሰኛል ።

**ኔ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ እንት ። አሐተኔ ፤ አንድነት ። አሐቲን ፡ እይ ፤ ከአሐቲ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ አይገኝም ።

**ን** ፤ አብዝ ፡ ምእላድ ፤ ፍቾው ፡ ዎች ። ኪሩብ ፡ ኪሩቤን ፤ ሱራፊ ፡ ሱራፌን ፤ ኪሩቦች ፡ ሱራፎች ። ጻ ድቅ ፡ ቃን ፤ ኃጥእ ፡ አን ። ንጹሕ ፡ ሓን ፤ ቅዱስ ፡ ሳን ፡ እያለ ፡ በወንድ ፡ አንቀጽ ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ፤ የአንና ፡ የያን ፡ የትን ፡ አፈታት ፡ እይ ። የዋሪ ፡ ምእላድ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ ጌጥንት ፡ እንጂ ፡ አብዝኀንት ፡ የለውም ። በርሀ ፡ ብርሃን ፤ በፀፀ ፡ ብፀፃን ፤ ግዕዘ ፡ ግዕዛን ፤ ፈረቀ ፡ ፍርቃን ፤ ቀረበ ፡ ቍርባን ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**ኔአ ፤—ቀረበ ፡ ተዘጋጀ ፤—ነየአ ።**

**ንእ፡ድ ፤ ዶት** ፤ (ንእደ ፡ ይንእድ ፡ ይን እድ ። ዐረ ፡ ነሀደ) ፤ ማክበር ፡ ማመስገን ፤ ማላቅ ፡ ማድነቅ ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ማድረግ ። ሰሊከ ፡ ትንእድ ፡ ርእ ሰከ ። ይንእዱ ፡ ርእሰሙ ፡ ከመ ፡ ጠቢባን ፡ እሙ ንቱ ። ርቱዐ ፡ ንንአዶሙ ፡ ለእልክቱ ። ሰነዳይ ፡ ይን እድዎ ፡ በጥበቢሁ ፡ (ዮሐ፰ ፡ ፲፫ ። ሄርማ ፡ ፵፯ ። አፈ ተ፱ ። ሢራ፲ ፡ ፴) ። በንእደ ፡ ፈንታ ፡ አንአደ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። አክ ፡ በእንእዶ ፡ አቡከ ፡ (፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፫) ።

**ነአዲ ፤ መንእድ** ፤ የሚያከብር ፤ አመስጋኝ ።

**አንእደ** ፤ አስከበረ ፤ አስመሰገነ ።

**ተንእደ** ፤ ከበረ ፡ ተመሰገነ ፤ ተደነቀ ። ኢይ ኩን ፡ አሐዱሂ ፡ ቀሲስ ፡ ዘኢተንእደ ፡ በስምዐ ፡ ኀም ስቱ ፡ ዐይው ። ዘተንእዱ ፡ በበ ፡ አስማቲሆሙ ። ሥዕ ርተ ፡ ርእስኪ ፡ ዘተንእደ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ኅዳር፱ ። ደራሲ) ።

**ንእ፡ድ** ፤ (ዳን ፡ ዳት ፤ እድ ፡ ድት) ፤ የከበረ ፡ ምስጉን ፤ ድንቅ ።

**ንእደት** ፤ መክበር ፡ ማክበር ፡ ማመስገን ፤ ክ ብር ፡ ምስጋና ። ኀሢሥ ፡ ክብረ ፡ ወንእደተ ፡ በእንተ ፡ ንጽሑ ፡ (ቀኖ ፡ ስርድ ፡ ፲፩) ።

**ንእክ** ፤ (ዕብ ፡ አናሕ ፤ ናአቅ) ፤ አናኘ ፡ አቃሰተ ፤ ጮኸ ፡ ተንሰቀሰቀ ፤ ከሩጫ ፡ ከሽክም ፡ ከደዌ ፡ ከሥቃይ ፡ ከሐዘን ፡ ከብካይ ፡ የተነሣ ። ንህክን ፡ እይ ፤

የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ይንእኩ ፡ ዲቤክሙ ፡ (ሔኖ ፺፯ ፡ ፪) ።

**ነእከ ፤** ዐየረ ፡ ከለሰ ፡ ቀላቀለ ፤ ማዕደንን ፡ ከማ ዕደን ።

**ናእክ ፤** ኖኽ ፡ ቃታ ፤ ከቡድ ፡ ሐዘን ፤ መራራ ፡ ጨኸት ። ንደገኒ ፡ ውስተ ፡ ናእክ ። ሕማመ ፡ ልብ ፡ ወገዐር ፡ ወናእክ ። እምብዙኅ ፡ ናእክ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፳፪ ። መስተ ። ደራሲ) ።

**ናእክ ፤ (ዕብ ፡ አናኽ ። ሱር ፡ አንክ ። ዐረ ፡ አኑክ) ፤** ዐረር ፡ ጥቍር ፡ ርሳስ ፤ የርሳስ ፡ ደን ጊያ ፡ ከባድ ፤ ዕይር ፡ ቅልቅል ። እብኒ ፡ ናእክ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ። ብርት ፡ ወናእክ ። ዐረር ፡ ወናእክ ። ወላሴ ስል ፡ ሖሎ ፡ ናእክኪ ፡ (ዘኅ፴ ፡ ፳ ። ሕዝ፳፪ ፡ ፲፰ ። ዘኍ ፴፩ ፡ ፳፪ ። ኢሳ፩ ፡ ፳፭) ።

—፤ ዛሕል ፡ ዝገት ፤ እድፍ ። ንጽሕ ፡ ዘእንበለ ፡ ናእክ ፡ ወደነስ ፡ (ደራሲ) ።

**ናእክ ፤ (ዕብ ፡ ብዲል) ፤** ኑሮ ፡ ርሳስ ፡ ቀ ላል ፡ ለማዕደናት ፡ ኹሉ ፡ መጣብቅ ፡ የሚኾን ፡ የሚያን ጣና ፡ የሚያጠራ ፡ ብር ፡ የሚያስመስል ። የርሳስ ፡ ዐይነት ፤ ታኒክ ፡ ቈርቈሮ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ዘገብካሁ ፡ ለወ ርቅ ፡ ከመ ፡ ዐረር ፤ ወከመ ፡ ናእክ ፡ መላእካሁ ፡ ለብ ሩር ፡ (ሢራ ፡ ፵፯ ፡ ፲፰) ።

**ንኤጼል ፤ (ዕብ ፡ ኔእጻል) ፤** ተለየ ፡ ልዩ ፡ ኾነ ፤ በሥራ ፡ በልክ ፡ (ሕዝ፵፪ ፡ ፯) ።

**ንኢስ ፤ ሶት ፤ (ንእሰ ፡ ይንእስ ፡ ይን እስ ። አኒስ ፡ አነሰ) ፤** ማነስ ፡ መጕደል ፡ ትንሽ ፡ መ ኾን ። ዘይንእስ ፡ ብርሃን ። ዘይንእሶ ፡ የዐብዮ ። ንእ ሰት ፡ መንፈስነ ። ዘላ ፡ እኪት ፡ ትንእስ ፡ እምእኪት ፡ ብእሲት ፡ (ዘፍ፳ ፡ ፲፯ ። ማቴ፲፩ ፡ ፲፩ ። ሔኖ ። ሢራ፳፭ ፡ ፳፯) ። በንእስ ፡ ፈንታ ፡ ተንእሰ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እሰ ፡ ይትነእሱ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፱) ። አኒስን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ንኡስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ እስት) ፤** ያነሰ ፡ ታናሽ ፡ ትንሽ ። ሕፃን ፡ ንኡስ ። ቈናጽል ፡ ንኡሳን ። ንኡሳት ፡ መበለታት ። ነያ ፡ ድንግል ፡ ንእስት ፡ በአካል ፡ (ኢሳ ፲፩ ፡ ፰ ። ማሕ፪ ፡ ፲፭ ። ዲድ ፡ ፲፬ ። ድጓ) ። በዐረብ ፡ ማን ፡ እኩሌታ ፡ መንፈቅ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ነኣስ ፤** ያነሰች ፡ ትንሽ ፡ አነስተኛ ። ነኣስ ፡ መ ርዔት ። ንህብ ፡ እንዘ ፡ በአካል ፡ ነኣስ ። ወለት ፡ ነኣስ ። (ሉቃ፲፪ ፡ ፴፪ ። ድጓ ። ፪ነገ ፡ ፭ ፡ ፪) ።

**ንስቲት ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ንእስት ፡ ትንሽ ፡ ጥ ቂት ። ሀገር ፡ ንስቲት ። ሕፃን ፡ ንስቲት ። በግዐት ፡ ን ስቲት ። ንስቲተ ፡ ከመ ፡ ተርፎሙ ። ንስቲተ ፡ ኅሊ ፍየ ፡ እምኔሆሙ ። አሥረቀ ፡ ንስቲተ ፡ መለኮቶ ። ኀ ሰፈ ፡ በበ ፡ ንስቲት ፡ (መክ፱ ፡ ፲፬ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፮ ። ፪ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፫ ። ዘዐ፲፯ ፡ ፱ ። ማሕ፫ ፡ ፬ ። ቅዳ ፡ ግሩ ። ግብ ፲፰ ፡ ፳፫) ።

**ንእስ ፤ ንእስና ፤** ማነስ ፡ ታናሽነት ፡ ሕፃንነት ፡ ጕልማስነት ። እምንእስየ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ። ኀጢአተ ፡ ንእስየ ። ብእሲተ ፡ ንእስከ ፡ (መዝ ፡ ፳ ። ኢዮ፲፫ ፡ ፳፮ ። ምሳ፭ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ጥር፲፭) ።

**ናእስ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ታናሽነት ፡ እንሽ ፤ ሕጻጽ ፡ ቅሰት ። በእንተ ፡ ራሐብ ፡ ብሔር ፡ ወናእስ ፡ ዚኣሃ ። አው ፡ በናእስ ፡ ልብ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፭ ። ቅዳ) ።

**አንአሰ ፤** አሳነሰ ፤ አዋረደ ፡ ታናሽ ፡ አደረገ ። አክ ፡ ከመ ፡ ዘንክሒድ ፡ ወዘናንእስ ። ወለእመኒ ፡ አ ንአስክ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘያንእስ ፡ አካለ ፡ ወልድ ፡ በእንተ ፡ ተሠግዎቱ ፡ (ኪዳ ። ፈላስ ። ያዕ ፡ ዘ እል) ። በአንአሰ ፡ ፈንታ ፡ አስተንአሰ ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። ቦኑ ፡ እምኔነ ፡ ዘያስተንእሶ ፡ ለወልድ ፡ እምኒሩት ፡ አብ ። እንዘ ፡ ታስተንእስ ፡ ርእሰከ ። ያ ስተንእስ ፡ ሲሳዮ ፡ (ቄር ፡ ጸላ ። አፈ ፡ ተ፴ ። አረጋ ፡ ፩) ።

**አንአሲ ፤ መንአሲ ፡ እስ ፤** የሚያሳንስ ፡ አሳ ናሽ ፤ አቃላይ ፡ አዋራጅ ።

**መንእስ ፤ (ስት ፡ ሳን ፡ ሳት) ፤** ያነሰ ፡ ታ ናሽ ፤ አነስተኛ ፡ ሕጹጽ ። አኔ ፡ ጴጥሮስ ፡ መንእስ ፡ በ ሥጋ ፡ ወዐዚዝ ፡ በመንፈስ ። ደቂቅክሙ ፡ መንእሳን ፡ (ቀሌ ። ክብ ፡ ነገ) ።

**ተናእሰ ፤** ተናነሰ ፤ እንሰንስ ፡ አለ ። የንእሰ ፡ ድርብ ።

**አስተናአሰ ፤** አስተናነሰ ። የአንአሰ ፡ ድርብ ።

**ናእት ፤—ቂጣ ፤—ነዩእ ፡ ኔአ ።**

**ንቤ ፤—እንባለን ፤—ቤልነ ፡ ብሀልነ ።**

**ነቢብ ፤ ቦት ፤ (ነበ ፤ ነበበ ፡ ይነብብ ፡ ይ ንብብ ። ዐረ ፡ ነበ ፤ ነብነበ) ፤** መንበብ ፤ መፍጨኽ ። ከበሮው ፡ ይነባል ፡ እንዲሉ ። ከመ ፡ ርግብ ፡ እነብብ ። ኢነቀዉ ፡ ወኢነበቡ ፡ (ኢሳ፴፰ ፡ ፲፬ ። ጸቀሮ ፡ ፲፬ ፡ ፯) ።

—፤ መናገር ፡ መቀባጠር ፤ መድገም ፡ ማነብነብ ። መቀ ባጠርና ፡ ማነብነብ ፡ የክፉ ፡ ናቸው ፤ ነበየን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ነቢበ ፡ ብዙኅ ፡ ነገር ። ሶበ ፡ አኃለቀ ፡ ነቢበ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ። ንብብ ፡ ለእመ ፡ አብሑክ ። አ ፉሁ ፡ ለእግዚ ፡ ነበበ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ (ኢዮ፴፱ ፡ ፴፯ ። ሉቃ ፡ ሰብዝ፭ ፡ ፮ ። ሢራ፴፭ ፡ ፯ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፫) ። በነበበና ፡ በለ ብሐ ፡ ፈንታ ፡ አንበበ ፡ ተናበበ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወአንበበት ፡ ዮዲት ፡ በዛቲ ፡ ስብሐት ። ኣነብብ ፡ ለስ ምከ ። መንፈስ ፡ እግዚ ፡ ይትናበብ ፡ በላዕሌከ ። ወይ ትናበብ ፡ በእሳት ። ኢይደሉ ፡ ለባሕታዊ ፡ ተናብቦ ፡ ቃለ ፡ ስርግው ፡ (ዮዲ፲፯ ፡ ፭ ። ኢሳ፳፭ ፡ ፭ ። መቃ ፡ ገ፳፭ ። ሳታት ፡ ፊልክ) ።

**ነቢብ ፤ (ጥሬ ፡ ዘር) ፤** ንባብ ፡ ጩኸት ፡ ነገር ፤ ለፈፋ ፡ ልፍለፋ ፡ ድጋም ። ዕለት ፡ ለዕለት ፡ ትጐሥዕ ፡ ነቢበ ። ከመ ፡ ትጽድቅ ፡ በነቢብከ ። ዐቃቤ ፡ ነቢብ ። ሴዘደብዝኅ ፡ ነቢበ ፡ ይትቋጥዐዎ ፡ (መዝ ፡ ፲፰ና ፡ ፶ ። ማብ፳፱ ፡ ፭ ። ሢራ፳ ፡ ፳) ።

**ነባቢ ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት) ፤** በቁሙ ፡ የ ሚነብ ፡ የሚፈጩኽ ፡ ተናጋሪ ፡ ቀባጣሪ ፡ አፈኛ ፡ ምላሰኛ ፤ ለፍፊ ፡ ለፍላፊ ። ብእሲ ፡ ነባቢ ። ነፍስ ፡ ነባቢት ። ል

ባን ፡ ነባቢት ፡ ዘታወፅእ ፡ ቃለ ። ነባብያነ ፡ ሐሰት ፡ (መግ ፡ ፻፴፱ ። ቅዳ ። ፈላስ ። ሸጢሞ ፡ ፱ ፡ ፪) ።

**አንበበ** ፤ አነበበ ፡ አስነበበ ፤ አስሰማ ፡ አናገረ ። ከመ ፡ ይዘምሩ ፡ ወያንብቡ ። ያንብቡ ፡ ደቂቀ ፡ አሮን ፡ ወይነፍኁ ፡ በቀርነ ፡ ዝብጦ ። ስእኑ ፡ አንብቦታ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ። ለበሃማን ፡ ያነብቦሙ ። ዘአንበበ ከሙ ፡ ሶቤሃ ፡ ንቡ ፡ (ሸዜና ፡ ፯ ፡ ፴፩ ። ሚራ፲ ፡ ፲፯ ። ዳንኤ ፡ ፳ ። ማርቆ ፡ ፴፩ ። ፲፫ ፡ ፲፫) ።

**አንበቢ** ፤ በቁሙ ፤ አናጋሪ ፡ አስጨኺ ፤ አስነባቢ ። በቀዌተ ፡ አንባቢ ፡ ወሰማዒ ። አንባብያኒሁ ፡ ለዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ (ፊልክ ። አዋል) ።

**ተነበ** ፤ ተነበበ ፡ ተደገመ ፤ ተነገረ ፤ ተሰማ ፡ ተዜመ ። መጽሐፍ ፡ ዘተነበ ፡ ቅድመ ፡ ንጉሥ ። በእንተ ፡ ጸሎት ፡ ዘይትነበብ ፡ ዲበ ፡ ማይ ። ዘኢይትነበብ ፡ ኅቡአ ። እምነግህ ፡ ይትነበብ ፡ ቅድሳቶ ፡ (፴ዜና ፡ ፴፱ ፡ ፳፱ ። ዲድ ፡ ፡ ፡ ። መግ ፡ ፶ ። ሚራ፴፯ ፡ ፲) ።

**ንቡብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ብብት) ፤ የነበበ ፡ የተነበበ ፡ የተነገረ ።

**ንቡብ** ፤ (ዕብ ፡ ናቡብ) ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፤ ባዶ ፡ ፍልፍል ፤ የሚነፋና ፡ የሚመታ ፡ ጎዋየ ፡ ማሕሌት ፤ እንቢልታ ፡ ዋሽንት ፤ ቱልቱላ ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፤ ከበሮ ፡ ነጋሪት ።

**ንበት** ፤ መንበብ ፤ መነበብ ፤ አነባበብ ፤ ንባብ ። ጽንዐ ፡ ንበቱ ፤ ተሊወ ፡ ንበቱ ። በመትልወ ፡ ንበቱ ፡ (መቅ ፡ ወን ። ሄርማ) ።

**ንባብ** ፤ በቁሙ ፤ ነገር ፡ ቃል ፤ ጩኸት ። ንባብከ ፡ አዳም ። ንባበ ፡ እግዚ ። ተወከፍ ፡ ንባበ ፡ ዚአየ ። በአብዝኆ ፡ ንባቦሙ ፡ (ማሕ፱ ፡ ፫ ። ክፋ ፡ ፳ ። ምሳ፱ ፡ ፲፱ ። ማቴ፯ ፡ ፯) ። በፍጻሜ ፡ ፊንታ ፡ ንባብ ፡ ይባል ፡ (መክ፲፪ ፡ ፲፫) ።

**ምንባብ** ፤ (ባት) ፤ ማንበቢያ ፡ የንባብ ፡ ቦታ ። ምንባበ ፡ መጻሕፍት ፡ ይኩን ፡ እቱተ ፡ ሕቀ ፡ እምሥዋዕ ። መጻሕፍተ ፡ ምንባብ ፡ (ኪዳ ። ቅዳ) ።

—፤ የንባብ ፡ መጽሐፍ ። ግጽው ፡ ስንክሳር ፤ ገድል ፡ ታምር ፤ በየውስጡ ፡ ያለው ፡ ምዕራፉ ፡ ክፍሉ ። ተፈጸመ ፡ ምንባብ ፡ ዘወርኁ ፡ ሠኔ ። አርእስተ ፡ ምንባብ ፡ ዘይትነበብ ፡ ባዕለ ፡ ሙታን ፡ (ስንክ ። ሠኔ፴ ። ግንዘ) ።

**ተናበበ** ፤ በቁሙ ፤ ተነጋገረ ። መላእክት ፡ ተናበቡ ፡ ምስለ ፡ አይሁድ ። ኢይትናበቡ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ በነገረ ፡ ሥላቅ ፡ ወኀፍረት ፡ (አፈ ፡ ድጓ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**አስተናበበ** ፤ አናበበ ፤ አነጋገረ ፤ አዛረፈ ፡ ዘርፍና ፡ ባለቤት ፡ አደረገ ፤ መጽሐፍን ፡ ከመጽሐፍ ፤ ሰውን ፡ ከሰው ፤ ስምን ፡ ከስም ።

**ነበዘ** ፤ (ይነብዝ ፡ ይንብዝ ፤ ነቢዝ) ፤ በቁሙ ፤ ሰረቀ ፡ ወሰደ ፤ አበፋ ፡ አበሳሸ ፤ የሌባ ፡ የደባ ፡ (ዐማርኛ) ።

**አንበዘ** ፤ አስነበዘ ፤ አሶበደ ፤ ልብ ፡ አሳጣ ፤ አቅበዘበዘ ። ተነበዘ ፤ ተቅበዘበዘ ፤ ዕውቀቱ ፡ ጉልበቱ ፡ አነሰ ፡ ጉደለ ፡ ተከፈለ ፤ ተከፋ ፡ ቈረጠ ። አንበዘ ፡ ልቡ ። ያነብዝ ፡ አብድ ፡ እስከ ፡ ይነግር ፡ ቃለ ፡ ዘሰምዐ ። አንበዙ ፡ ሶበ ፡ ርኅቡ ። አንበዙ ፡ እምሥቃይ ። አንበዘት ፡ ነፍስየ ፡ በላዕሌየ ። አንበዘት ፡ ነፍሶሙ ፤ እስመ ፡ ዐገትዎሙ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ሚራ፲፱ ፡ ፲፬ ። መሳ፳ ፡ ፱ ። ፲ ፡ ፲፯ ። ስቈ፫ ፡ ፳ ። ዮዲ፯ ፡ ፲፱) ። መጣፍ ፡ ግን ፡ ዐንበዘ ፡ የዐነብዝ ፡ ዕንቡዝ ፡ ዕንባዜ ፡ እያለ ፡ በዐይን ፡ ይጥፋል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ነዘረንና ፡ እንዘረን ፡ እይ ።

**እንቡዝ** ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ብዝት) ፤ በቁሙ ፤ ልቡ ፡ የጠፋ ፤ የተነበዘ ፡ ነባዝ ፤ ንብዝ ፡ ቅብዝብዝ ፤ ሰካር ፡ እብድ ። በብእ ፡ እንቡዛን ። ብእሲት ፡ እንብዝት ። እንቡዛነ ፡ ልብ ፡ ወድንቅዋነ ፡ እዝን ፡ (ኢሳ፳፰ ፡ ፰ ። ፺፱ ፡ ፯ ። መጽ ፡ ምስ) ። ዕንቁ ፤ ወይም ፡ ሰይቶ ፡ ብሎር ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እንቡዝ ፡ ይባል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ዝብጠንን ፡ እይ ፡ (ኢዮ፳፰ ፡ ፲፰) ።

**እንባዜ** ፤ መ(ን)ነብዝ ፤ መቅበዝበዝ ፡ ድካም ፡ ሕጸጽ ፡ ስካር ፡ እብደት ፡ ልብ ፡ ማጣት ። ሕማመ ፡ እንባዜሃ ። እንባዜ ፡ ነፍስ ። እንባዜ ፡ ስካር ። እንባዜ ፡ ልብ ። ጠበ ፡ እምእንባዜሁ ፡ (ኪዳ ። መግ ፡ ፺፱ ። መጽ ፡ ምስ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፲ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**እንብዝና** ፤ ልበ ፡ ቢስነት ፤ ሞኝነት ፡ ጥበት ። እንብዝና ፡ ነፍሶሙ ፡ (ዘፀ፮ ፡ ፱) ። ድንባዝን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጥሬ ፡ ነው ፤ ድሕንጻ ፡ የሐንጸ ፡ ጥሬ ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

**ነቢሐ** ፤ ሖት ፤ (ነብሐ ፡ ይነብሕ ፡ ይንባሕ ። ዕብ ፡ ናባሕ ። ሱር ፡ ንባሕ ። ዐረ ፡ ነበሐ) ፤ መጮኽ ፤ ቡሕ ፡ ቡሕ ፡ ማለት ፤ የውሻ ፡ የጉንፋናም ። ይነብሕ ፡ ከመ ፡ ከልብ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**አንብሐ** ፤ አጮኸ ፤ አስጮኸ ። ጉንባሕን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ፤ ግንባር ፡ የነበረ ፡ ዘር ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

**አንባሕብሐ** ፤ አው ፡ አንበሐብሐ ፤ አንቢቢ ፤ ተንቢቢ ፡ ተንኰኰ ፡ ተንሺሺ ፤ የፈሳሽ ፡ ውሃ ። እምቅድመ ፡ ያንበሐብሑ ፡ ወሓይዝተ ፡ አፍላግ ። ወሓይዝት ፡ እለ ፡ ያንበሐብሑ ፡ (ቅዳ ፡ አፈ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**መንበሐብሕ** ፤ አው ፡ ምንባሐብሕ ፤ (ሓት) ፤ የሚንቢቢ ፡ የገደል ፡ ውሃ ፡ ሺሺቱ ፡ ኰኰቱ ፤ ጕርፍ ፡ ማዕበል ፡ ተወርዋሮ ፡ ከደንጊያ ፡ ላይ ፡ ሲያርፍ ፤ ወይም ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ሲዋጋ ፡ ሲላለፍ ፡ ሲጋፋ ፡ ሲተላለፍ ፡ ብዙ ፡ የሚጮኽ ፡ ከሩቅ ፡ የሚሰማ ። ድምፀ ፡ ምንባሐብሓት ፡ ማይ ፡ ዘየሐውር ፡ በኀይል ። ውሒዝ ፡ ዐቢይ ፡ ዘይወርድ ፡ በኀይል ፡ እምውስተ ፡ ምንባሐብሓት ። ጲራቅሊጦስ ፡ መንበሐብሓተ ፡ ጥምቀትነ ። ክርስቶስ ፡ አምላኪየ ፡ ወተስፋየ ፡ ወዕፀ ፡ መስቀሉ ፡ በትረ ፡ ሃይማኖትየ ፡ ወርግዘተ ፡ ገቦሁ ፡ መንበ

ሐብሓተ ፡ ጥምቀትየ ፡ (ጥበ፲፯ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፲፯ ፡ ፲፫ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ነብሐ ፤ አው ፡ ንበሐ ፤** የውሻ ፡ ጩኸት ፤ አጯጯኸ ።


**ነበሕባሕ ፤** የውሃ ፡ ጩኸት ፤ ድምጡ ፡ ተመ ማው ።

**ነበጠ ፤ (ዐረ ። ዕብ ፡ ናበጥ) ፤** ፈላ ፡ ገነ ፈለ ፤ በዝቶ ፡ ወጣ ፡ በቀለ ፤ ያንበጣ ፡ ያሸን ፡ የጉንዳን ፡ የቡቃያ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**አንበጠ ፤** አፈላ ፡ አወጣ ፤ አበቀለ ።

**እንቡጥ ፤** በቁሙ ፤ ያበባ ፡ እኽል ፡ ዛላ ፡ ከን ፍሬው ።

**አንበጣ ፤ (ብ ፡ አናብጥ) ፤** በቁሙ ፤ ክም ድር ፡ የሚፈላ ፡ ፪ ፡ እግርና ፡ ፬ ፡ ክንፍ ፡ ያለው ፤ የሣር ፡ የቅጠል ፡ ያዝመራ ፡ ጠላት ። ይቤ ፡ ወመጽአ ፡ አንበጣ ። ወራእየሙ ፡ ለእልክቱ ፡ አናብጥ ፡ (መገ ፡ ፲፱ ። ራእ ፡ ፱ ፡ ፯) ።



አንበጣ ፤

**ነበየ ፤ (ይኔቢ ፡ ይነቢ ፤ ነብዮ ። ነቢብ ፡ ነበ ፡ ነበበ) ፤** ነባ ፡ ተነባ ፡ ነቢይ ፡ ኾነ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በነበየ ፡ ፈንታ ፡ ተነበየ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወፈጸሞ ፡ ተነብዮ ። በከመ ፡ ተነበየ ፡ ሔኖክ ። ተነበይ ፡ ለነ ። ተነበየ ፡ በትንቢት ፡ መለኮታ ዊት ። ብእሲ ፡ ቀነባዪ ፡ (፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ይሁ ፡ ፲፬ ። ሉቃ፳፪ ፡ ፷፬ ። ስንክ ፡ የካ፲፭ ። ዮሴፍ) ።

**ነባዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ። አው ፡ ነቢይ ፡ ይት ፡ ያን ፡ ያት ። ዕብ ፡ ናቤእ ። ሱር ፡ ንቢያ ። ዐረ ፡ ነቢይ) ፤** በቁሙ ፤ የሚተነባ ፡ ተንቢ ፡ ነባቢ ፤ መንፈስ ፡ ትንቢት ፡ ያደረበት ፡ ራእይ ፡ የሚያይ ፤ ትንቢት ፡ የሚናገር ፤ ሰባኪ ፡ መምህር ። ነቢየ ፡ ያነሥእ ፡ ለክሙ ፡ እምአኀዊክሙ ። ኢኮንኩ ፡ ነቢየ ፡ ወኢወ ልደ ፡ ነቢይ ። ሶበሁ ፡ ነቢይ ፡ ውእቱ ፡ እምኢያእመ ረኑ ፡ ምንት ፡ ብእሲታ ፡ (ዘዳ፲፰ ፡ ፲፭ ። ዓሞ፯ ፡ ፲፬ ። ሉቃ፯ ፡ ፴፱) ። ብእሲት ፡ ነቢይት ። ሕልዳና ፡ ነቢይት ። ሐና ፡ ነቢይት ። ዜብላ ፡ ነቢይት ፡ ዘኢሖሙ ፡ ለዕል ዋን ፡ (ኢሳ፰ ፡ ፫ ። ፬ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፲፬ ። ሉቃ፪ ፡ ፴፮ ። ዲድ ፡ ፳፫) ።

**ነቢያዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** የነቢይ ፡ ወገን ፡ ነቢይ ፤ ሬድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፤ ህብተ ፡ ነቢይ ፡ የተሰጠው ፤ እንደ ፡ ኢያሱና ፡ እንደ ፡ ኤልሳዕ ፡ ያለ ። ማ ርያም ፡ ነቢያዊት ። ሴቴነዋ ፡ ነቢያዊት ፡ (ዘፀ፲፭ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ኀዳ፱) ።

**ነቢያን ፤ (ያት ። ዕብ ፡ ንቢኢም) ፤** በ ቁሙ ፤ ነቢያቶች ። ያን ፡ የወንዶች ፡ ያት ፡ የሴቶች ፡ ነው ፤ ያ ፡ በጣም ፡ ይጠብቃል ፤ ይኸውም ፡ ዐቢይ ፡ ያን ፡ ያት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ሳይለይ ፡ የሴቶቹን ፡ ለወንዶች ፡ ሰጥቶ ፡ ያንኑም ፡ እሳ ልቶ ፡ በነቢያን ፡ ፈንታ ፡ ነቢያት ፡ ይላል ፤ የመሳሽ ፡ ስሕ ተት ፡ ነው ። ዅሎሙ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ እምአመ ፡ ሳሙ ኤል ። ወቦቱ ፡ ሐሳውያነ ፡ ነቢያት ። እስመ ፡ መን ፈስ ፡ ነቢያት ፡ ይትኤዘዝ ፡ ለነቢያት ። ዐሠርቱ ፡ ወ ክልኤቱ ፡ ነቢያት ፡ (ግብ፫ ፡ ፳፬ ። ፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፩ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፴፪ ። ሚ.ራ፡፲፱ ፡ ፲) ። ዳግመኛም ፤ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ነቢያት ፡ ምብያት ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ (ነቢ)ዖብያቲሆሙ ፡ ለነገ ሥት ፡ ይሁዳ ። መጽሐፈ ፡ (ዖብ)ነቢያት ፡ መዋዕሊ ሆሙ ፡ ለነገሥት ፡ ይሁዳ ፡ (፫ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፳፱ ። ፲፭ ፡ ፯) ።

**አንበየ ፤** አስነበየ ፡ አስተነባ ፤ ትንቢት ፡ አናገረ ፤ ነቢይ ፡ አደረገ ። ኪያሁ ፡ አመነየት ፡ ወአነበየት ፡ (ቅዳ ፡ አትና) ።

**ተነበየ ፤** ተተነባ ፡ ተነገረ ፤ ትንቢቱ ፡ ከነቢዩ ፡ አፍ ፡ ወጣ ፡ ተሰማ ።

**ንቡይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ቢት) ፤** የተተነባ ፤ የተነ ገረ ፡ ንግር ።

**ትንቢት ፤ (ብ ፡ ትንቢታት ፤ አው ፡ ትን ብያት) ፤** በቁሙ ፤ ራእይ ፡ ንግር ፤ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የ ሚመጣ ፡ ነገር ፤ አስቀድሞ ፡ የሚታይና ፡ የሚገለጥ ፤ ከ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚሰጥ ። መንፈስ ፡ ትንቢት ። ወይቱ ግሩ ፡ በትንቢቶሙ ። ሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ዘንተ ፡ ትንቢተ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፭ ። ሚ.ራ፡፴፱ ፡ ፫ ። ፪ዜና ፡ ፲፭ ፡ ፰) ። በእንተ ፡ እላ ፡ ራእያት ፡ ወትንቢታት ። እንዘ ፡ ታነብቡ ፡ ወትጼ ልዩ ፡ እምነ ፡ መዝሙራት ፡ ወትንቢታት ፡ ወአፈት ። እግዚ ፡ ፈጸመ ፡ ትንብያተ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ፲፭ ፡ ዓ፳ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲፱ ። ደራሲ) ።

**ናበለ ፤ (ዕብ ፡ ናባል ፤ አረጀ ፡ ደረቀ ፡ ተ ለየ ፡ ተነጠለ) ፤** በቁሙ ፤ ሰኾ ፡ ተመመ ፤ የጉርፍ ፡ የማዕበል ።

**ኔባል ፤ (ዕብ ፡ ኔቤል) ፤** የማስ ፡ ፊቀን ፤ ቀር በታ ፡ ርኩት ፡ ራምት ። ዝቅን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አ ንድ ፡ ነው ፤ ባለቀኔዎች ፡ ግን ፡ ገንቦ ፡ በፍሻት ፡ ይሎ ታል ። በመሰፈርተ ፡ ኔባል ፡ ወይነ ፡ (፩ነገ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ። ፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ። ሆሴ፫ ፡ ፪ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ናብል ፤ ናብሊስ ፤ (ሳት ። ዕብ ፡ ኔቤል ። ጽር ፡ ናብሌስ) ፤** ነዋየ ፡ ማሕሌት ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ በቁዳ ፡ የተጠፈረ ፡ የክራርና ፡ የበገና ፡ የነጋሪት ፡ ዐይነት ። ስሙ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ዐይነቱ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ፳ና ፡ ፯ ፡ ይኾናል ። ሰላም ፡ ለቃልኪ ፡ እምድምፀ ፡ ናብሊስ ፡ አዳም ፡ (ደራሲ ፡ ፪ነገ ፡ ፯ ፡ ፭ ። ፩ዜና ፡ ፲፭ ፡ ፳፰ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፲፩) ።

**ነቢዕ ፤ ዖት ፤ (ነብዐ ፡ ይነብዕ ፡ ይንባዕ ። ዕብ ፡ ናባዕ ። ሱር ፡ ንባዕ ። ዐረ ፡ ነበዐ) ፤** መን

ባት ፤ መመንጨት ፤ መፍለቅ ፡ መፈልፈል ፤ መፍሰስ ፡ መግንፈል ፤ የውሃ ፡ የእንባ ።

**አንብዐ** ፤ እንባ ፡ አለቀሰ ፤ አፈለቀ ፡ አፈሰሰ ። አንብዐ ፡ እመ ፡ ርኢኩ ፡ ሰብአ ፡ ሕሙመ ። አንብዐ ፡ ታንብዕ ፡ ዐይንየ ። ያነብዓ ፡ አዕይንቲክሙ ፤ (ኢዮ ፲፮ ፡ ፳፩ ። ዮሴፍ ። ኤር ፱ ፡ ፲፰) ።

—፤ አስነባ ፤ አስለቀሰ ። ዐይኖ ፡ ያነብዕ ፡ ለከ ፡ ጸላኢከ ፡ (ሚራ ፲፪ ፡ ፲፯) ።

**አንብዕ** ፤ (ብ ፡ አናብዕ) ፤ እንባ ፡ እንባ ፡ የልቅሶ ፡ ፍሬ ፡ የሐዘን ፡ ጠበል ፡ ካይን ፡ የሚፈልቅ ፡ የሚፈለፍል ፤ የሚፈሳ ፡ የሚገነፍል ። እንባ ፡ ፪ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ አንብዐ ፡ ሥጋ ፡ አንብዐ ፡ ጸጋ ፤ ወይም ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ። ፈልፈለ ፡ አንብዕ ። ይውሕዝ ፡ አንብዕ ፡ ከመ ፡ ማየ ፡ ክረምት ። ዘደጐጸ ፡ ዐይኖ ፡ ያወርድ ፡ አንብዐ ። በአንብዕ ፡ ውዑይ ። ነገር ፡ በእንተ ፡ ፍልጠቱ ፡ አናብዕ ። እስመ ፡ አንብዐ ፡ አእሩግ ፡ ፍጹማን ፡ ሀብት ፡ እምግዚ ፡ በጸጋ ፤ ወኢኮነት ፡ እምፍጥረት ፤ (ኤር ፱ ፡ ፩ ። ቅዳ ፡ ያዕ ። ሚራ ፴፪ ፡ ፲፱ ። አፈ ፡ ተ ፴፩ ። ማር ፡ ይሥ ፱ ። ፊልክ ፡ ፸፯) ።

**አንበ** ፤ በቁሙ ፤ ኮሬ ፡ ኸሬ ፡ እንባ ፡ እንባ ፡ የሚል ፡ የጨው ፡ ዐፈር ፤ ወይም ፡ ውሃ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ጎምቦ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ዐዘቅተ ፡ ናጥራን ፡ ዘውእቱ ፡ ጎምቦ ፤ (ስንክ ፡ ጥቅ ፲፫) ።

**ነበጽራው** ፤ (ዕብ ፡ በጸሬት ፤ በጻር ፡ ከበበ ፡ አስጨነቀ ፡ ውሃ ፡ ነሃ) ፤ ውኅደት ፡ ዝናም ፡ ሕጸጸ ፡ ማይ ፡ ሕጸጸ ፡ ሲሳይ ፤ ጭንቅ ፡ ጥብ ፡ ዐጸባ ፤ ንዳድ ፡ ትኵሳት ፡ ወባ ። በነበጽራው ፡ ፈንታ ፡ ነበርፃው ፡ ይላል ፤ የቅምጥ ፡ እንቅልፍ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫) ።

**ነቢር** ፤ ሮት ፤ (ነበረ ፤ አው ፡ ነብረ ፡ ይነብር ፡ ይን(ብ)በር) ፤ ሀልዎ ፤ መኖር ፡ መቈየት ፡ መዘግየት ። ኢይትበደር ፡ ብዕል ፡ እምነቢረ ፡ ጥዑይ ። ነበረ ፡ ህየ ፡ አሐደ ፡ ወርኀ ። እስመ ፡ መጠነ ፡ ዝ ፡ መዋዕል ፡ ይነብሩ ፡ እንዘ ፡ ይትኄረሱ ፤ (ሚራ ፴፩ ፡ ፱ ። ዮዲ ፫ ፡ ፲ ። እስቴ ፪ ፡ ፲፪) ።

—፤ መቀመጥ ፤ ጉብ ፡ ጉች ፡ ቍጭ ፡ ዘርፈጥ ፡ ማለት ፤ በምድር ፡ ላይና ፡ በወንበር ፡ ላይ ፡ ማረፍ ፡ መተጣጠፍ ። ንበሩ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ነበረ ፡ ዲበ ፡ መንበር ። ነቢረ ፡ ፍጽም ፡ በውስተ ፡ አዕዋዳት ። ነበሩ ፡ ዐውደ ፡ ሰኩንኖቱ ፤ (ኢሳ ፵፯ ፡ ፩ ። ፩ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፳፫ ። ማቴ ፳፫ ፡ ፳ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ። ተጽሕፈ ፡ ተነግረ ፡ ተብህለ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ነበረ ፡ ይላል ። ነበረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖና ፡ ዘነገሥት ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፪) ።

**ነባሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ በርት) ፤ በቁሙ ፤ የሚኖር ፡ ኗሪ ፡ ነዋሪ ፡ ነባር ፡ ተቀማጭ ። ማኅደር ፡ ነባሪ ። ነበርተ ፡ ዐውድ ፤ (ግንዘ ፡ አዋል) ።

—፤ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ባሪያ ፡ የቤት ፡ ውልድ ፤ አሽከር ፡ ወታደር ፡ ሎሌ ። ነባሪከ ፡ ዘይትቀነይ ፡ ለከ ። ወሤመ ፡ ጳዊት ፡ ነባሬ ፡ ውስተ ፡ ሶርያ ። ነባሪ ፡ ወእግዓዚ ፤ (ሚራ ፴ ፡ ፴ ። ፪ነገ ፡ ፰ ፡ ፮ ። ገላ ፫ ፡ ፳፰) ።

**ንቡር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ብርት) ፤ ያለ ፡ የኖረ ፡ የነበረ ፤ የተቀመጠ ፡ ቅምጥ ፤ ጽሑፍ ። ትኄኀር ፡ ንቡረከ ፡ ውስተ ፡ ቤትከ ። ልማድ ፡ ንብርት ። ዘንቡር ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ አንቀጽ ፤ (፩ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲ ። መቅ ፡ ወን ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

**ንቡረ ፡ እድ** ፤ እጁን ፡ የጫነ ፡ ያኖረ ፤ ወይም ፡ እጅ ፡ የተጫነበት ፡ በሹመትና ፡ በቡራኬ ፡ ጊዜ ። ያኵስም ፡ አለቃ ፡ ንብረድ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ የተሾመና ፡ የሚሾም ፡ ጳጳስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ማለት ፡ ነው ። አ ፡ አበዊነ ፡ ንቡራነ ፡ እድ ፡ ሥዩማን ፡ እለ ፡ መትልዋነ ፡ ሐዋርያት ፤ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ንብረት** ፤ በቁሙ ፤ መኖር ፡ መቀመጥ ፡ አቀማመጥ ፤ ኗሪነት ፡ አኗዋር ፡ ኑሮ ። ኀላፊ ፡ ውእቱ ፡ ንብረተ ፡ ዝ ፡ ዓለም ። ንብረተ ፡ ከዋክብት ። ንብረተ ፡ ነፍስየ ፡ ወሥጋየ ፡ በእዴሁ ፡ እጐዝ ። እምንብረቱ ፡ ላዕለ ፡ መንበር ። ንብረተ ፡ መናቅዕትኪ ። ናሁ ፡ ንብረታ ፡ ለዛቲ ፡ ሀገር ፡ ሠናይት ፤ (፩ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፳፱ ። ጥበ ፯ ፡ ፲፱ ። ስንክ ፡ ኅዳ ፯ ። ፊልክ ፡ ፲፩ ። ማሕ ፯ ፡ ፪ ። ፬ነገ ፡ ፪ ፡ ፲፱) ።

**ኑባሬ** ፤ (ርያት) ፤ ኀኒ ፡ ከማሁ ፤ አኗዋር ፡ ኑሮ ፤ አቀማመጥ ። ተዘምዶ ፡ ዘኑባሬ ። ሥነ ፡ ሥርዐቶሙ ፡ ወኑባሬሆሙ ። ማእከለ ፡ እንስሳ ፡ ኑባሬ ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፪ ፡ ፫ ። ድጓ ። ስንክ ፡ ኅዳ፫) ።

**ነባር** ፤ (ራት) ፤ በቁሙ ፤ ብቸኛ ፡ ቃል ፡ የማስ፪ኛ ፡ ክፍል ፤ አንቀጽና ፡ ስም ፡ አገባብ ።

**ግንባር** ፤ በቁሙ ፤ ፍጽምን ፡ እይ ። ገ ፡ ከገጽ ፡ የመጣ ፡ ነው ።

**ገንበረ** ፤ ገነበረ ፡ አገነበረ ፤ ባዕድ ፡ ኸነ ።

**አንበረ** ፤ አኖረ ፡ አስቀመጠ ፤ አቈየ ፡ አዘገየ ። ታነብሮ ፡ ዲበ ፡ ገሐፍት ። ያነብሮሙ ፡ ለነገሥት ፡ ዲበ ፡ መናብርት ። አብ ፡ እግዚአ ፡ ኵሉ ፡ እምአባግዒሁ ፡ አሐደ ፡ ኤልያስሀ ፡ አንበረ ፡ ለሞት ፡ እንግዳ ፡ ዘይመጽእ ፡ ድኅረ ፤ (ዘዐ ፳፱ ፡ ፫ ። ኢዮ ፴፮ ፡ ፲፰ ። ቅኔ) ።

—፤ ጣፈ ፡ ደረሰ ፤ ጥፎ ፡ አኖረ ። አንበርዮ ፡ ቃለ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘነሥአ ፡ እመጻሕፍተ ፡ ሐሰት ፡ እንተ ፡ አንበርዋ ፡ ከሓድያን ፡ ወአብአ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክር ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ፡ ፪) ።

**አንብሮ ፡ እድ** ፤ የቡራኬ ፡ ጸሎት ፡ ከቍርባን ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡን ፡ ሲያሰናብት ፡ ቄስ ፡ የሚደግመው ። ይኸውም ፡ በየቅዳሴው ፡ ማፍ ፡ ባ፲፱ቱ ፡ ኹሉ ፡ ይገኛል ።

**መንበር** ፤ (ብ ፡ መናብርት) ፤ በቁሙ ፡ ወንበር ፡ ግርንቡድ ፤ መኖሪያ ፡ ማረፊያ ፡ መቀመጫ ፤ ዙፋን ፡ አትሮንስ ፤ ድንክ ፡ አረፍት ፡ መደብ ፤ ለመቀመጫ ፡ የተሰየ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ። ወናሁ ፡ መንበር ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ። ወሰዐውዱ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ፡ ዕሥራ ፡ ወአርባዕቱ ፡ መናብርት ። መናብርተ ፡ ቤተ ፡ ዳዊት ። መንበረ ፡ ቀሳውስት ፤ (ራእ ፬ ፡ ፪ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፻፳፩ ። ሲኖ ዶ) ።

—፤ ስመ ፡ ንጉሥ ፡ መልአክ ፤ የኪሩብ ፡ ወገን ፡ ኪሩብ ፡ ጸዋሬ ፡ መንበር ። መናብርት ፡ ወኀይላት ፤ (ቅዳ ፡ ባስ) ።



መንበር ፡

**ምንበር** ፤ (ራት) ፤ መኖሪያ ፡ መቀመጫ ፤ ቦታ ፡ ስፍራ ፡ ጉባኤ ፡ ሸንጎ ፡ አደባባይ ። እግዚ ፡ ዘተናገረ ፡ ምስለ ፡ አቡነ ፡ አብርሃም ፡ በላዕለ ፡ ዕፀ ፡ ምንባር ። ኵሎሙ ፡ ይበሊ ፡ በውስተ ፡ ምንባሩ ። ኢይትሐወስ ፡ እንከ ፡ እምንባሩ ። ምንባራተ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅል ። ሄሮድስ ፡ በንእሱ ፡ የሐውር ፡ ኀበ ፡ ምንባረ ፡ ማእምራን ፡ ከመ ፡ ይትመሀር ፡ እምኔሆሙ ፡ (ቅዳ ፡ ጎር ። ኢዮ ፴፱ ፡ ፲፰ ። ኢሳ ፶፯ ፡ ፯ ። ፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፳፯ ። ዮሴፍ) ። በምንባር ፡ ፈንታ ፡ መንበር ፡ ይባል ፤ አያሰኝም ። መንበረ ፡ መስተሣልቃን ፡ (መዝ ፡ ፩) ።

**መንበርት** ፤ (ታት) ፤ ንብረት ፤ አኗኗር ፡ ኑሮ ። እምነግህ ፡ እስከ ፡ ሠርክ ፡ ትትዐሎ ፡ መንበርት ፡ (ሚራ ፲፰ ፡ ፳፮) ።

—፤ ዕድሜ ፡ ዘመን ፡ መዋዕል ። እመኒ ፡ ኖኅ ፡ መንበርቶሙ ፡ (ጥበ ፫ ፡ ፲፯) ።

—፤ ጥሪት ፡ ገንዘብ ፤ ምግብ ፡ (ሉቃ ፳ ፡ ፲፬ ። ፩ዮሐ ፪ ፡ ፲፮ ። ፫ ፡ ፲፯ ። ማር ፲፪ ፡ ፵፬ ። ዲድ ፡ ፲፬) ። ተሀየይ ፡ ለመንበርትከ ፡ ሥጋዊት ፡ ወአስተሐምም ፡ ለመንበርትከ ፡ መንፈሳዊት ፡ (ፊልክ ፡ ፸፯) ።

**ተናበረ** ፤ ተነባበረ ፡ ተቀማመጠ ፤ ንብብር ፡ ኾነ ። አነባበር ፡ እንዲሉ ።

**አስተናበረ** ፤ በቁሙ ፤ አነባበረ ፤ አቀማመጠ ፤ አበጀ ፡ አዘጋጀ ፡ አሰናዳ ፤ ሰደረ ፡ ደረደረ ። አስተናበረ ፡ ዕፀወ ። ቅዳሕ ፡ ወይዮ ፡ ወአስተናብር ። አስተናበረ ፡ ሊድባረ ፡ ወአውግረ ። ሕበው ፡ አስተናበሩ ፡ ቀኖናሆሙ ። ወአስተናበረ ፡ ምዕራፋተ ፡ (፫ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፴፫ ። ዳን ፲፫ ፡ ፲ ። ቅዳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፫ ። አቡሻ ፡ ፪) ።

**ነበርፃው** ፤ የቅምጥ ፡ እንቅልፍ ፡ እንጉልቻ ። ፃው ፡ የብፃው ፡ ከፋይ ፡ ነው ፤ በፀወን ፡ እይ ። በነበርፃው ፡ ፈንታ ፡ ነበጽራው ፡ ይባል ፤ ፍችውን ፡ በቦታው ፡ ተመልከት ። ነበርጻው ፡ ተብሎ ፡ በጸደይ ፡ ሲጣፍ ፡ ግን ፡ የበረጸ ፡ ዘር ፡ ነውና ፡ ለምጥን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ቡሕነትንና ፡ ቋቍቻን ፡ ያባያል ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫) ።

**ነበስባስ** ፤—ያይን ፡ አገላለጥ ፤—በስበሰ ።

**ንብቲራ** ፤ (ጽር ፡ ኒፒቲር) ፤ የማጠቢያና ፡ የመታጠቢያ ፡ ዕቃ ፤ ሰገን ፡ ሞዲያት ፡ ኮስኮስት ፤ ሰኅና ፡ ብርት ። ንብቲራ ፡ ዘውስቴታ ፡ ማይ ፡ (ዮሐ ፲፫ ፡ ፭ ። ፊልክ ፡ ፸፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱ ። ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

**ነጌ** ፤—ዝኖን ፤—ነግሀ ፡ ነገየ ።

**ነጕአ** ፤—መታ ፡ ገጨ ፤—ነጕዐ ።

**ነገበ** ፤ (ዕብ ፡ ናጋብ) ፤ ደረቀ ፡ ፈረሰ ፤ ተፈታ ፤ የቦታ ።

**አንገበ** ፤ አነገበ ፡ ተሸከመ ፤ በጐን ፡ በትከሻው ። አቃሰተ ፤ በሸክም ፡ ብዛት ።

**ናጌብ** ፤ (ጽር ። ዕብ ፡ ኔጌብ) ፤ ደቡብ ፤ ደቡባዊ ፡ ቦታ ፡ የብስ ፡ ሜዳ ፡ ቈላ ፡ በረሓ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፤ የምድረ ፡ እስራኤል ፡ ዳርቻ ፡ የብንያምና ፡ የይሁዳ ፡ ክፍል ፡ ከቃዴስ ፡ በርኔ ፡ የሚዋሰን ፤ ቃዴስ ፡ በርኔም ፡ ሳይቀር ። አዜብን ፡ እይ ፡ (ኢያ ፲፱ ፡ ፰ ። ሕዝ ፳ ፡ ፵፯ ፡ ፵፰ ። ሸሸ ፡ ፱ ። ኤር ፲፫ ፡ ፲፱) ። ውቅያኖስ ፤ ግብ ፡ ማይ ፡ ምግባእ ፡ ማይ ፡ ውሆችን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ የሚስብ ፡ የሚሰበስብ ፡ የሚሸከምና ፡ የሚያንግብ ፡ ማለት ፡ ነው ። ንባቡም ፡ ምስጢሩም ፡ ለይትጋባእ ፡ ማይ ፡ ከሰው ፡ ይስማማል ፤ ጉብእና ፡ ጋብእን ፡ ገበበን ፡ እይ ፤ ምስጢሩም ፡ ጕድጓድነትና ፡ ቈላነት ፡ ነው ። ወአመ ፡ ኀሙስ ፡ ትቤሎ ፡ ለዝኩ ፡ ማየ ፡ ናጌብ ፡ ከመ ፡ ያውፅእ ፡ አዕዋፈ ፡ ወዓሣተ ። እምቅድመ ፡ ይዕምቅ ፡ ማየ ፡ ናጌብ ። አውፅአሙ ፡ ለዘመደ ፡ አዕዋፍ ፡ እማየ ፡ ናጌብ ፡ (ሉቃ ፡ ዕዝ ፱ ፡ ፶፱ ፡ ፶፰ ። መጽ ፡ ምስ ፡ ገ፳፮ ። ፳፯) ።

**ነጎጋው** ፤—መበከን ፤—ነግዎ ፡ ነገወ ።

**ነጊድ** ፤ ዶት ፤ (ነገደ ፡ ይነግድ ፡ ይንግድ ። ሱር ፡ ናጋድ ፡ ይንጎድ ፤ መራ ፡ ወሰደ ፤ ፈሰሰ ፡ ወረደ) ፤ ርቆ ፡ መኼድ ፤ መንጐድ ፤ መነገድ ፤ የብሱን ፡ ዙሮ ፡ ባሕሩን ፡ ተሻግሮ ፡ መኼጥ ፡ መለወጥ ፡ ማትረፍ ። ኢይክል ፡ ነጊደ ። እለ ፡ ይነግዱ ፡ በባሕር ፡ ወበየብስ ። ወዐርገ ፡ ውስተ ፡ ሐመር ፡ ይንግድ ፡ ምስሌሆሙ ። ጸባሕት ፡ እምኀበ ፡ እለ ፡ ይነግዱ ። ነጊደ ፡ በመክሊት ፡ (ኩፋ ፡ ፴፭ ። ኪዳ ። ዮናስ ፡ ፫ ። ፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፯) ።

**ነጋዲ** ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤ የሚኼድ ፡ ኼያጅ ፤ የሚነግድ ፡ ነጋጅ ፤ ነጋዴ ፡ መንገደኛ ። ውሉደ ፡ ብእሲ ፡ ነጋዲ ። ርእዮ ፡ ለዝክቱ ፡ ብእሲ ፡ ነጋዲ ። ወናሁ ፡ ነጋድያን ፡ (ፊልክ ፡ ፩ ። መሳ ፲፱ ፡ ፲፯ ። ዘፍ፴፯ ፡ ፳፭) ።

**ንግደት** ፤ መኼድ ፤ መነገድ ፤ እንግድነት ። ንግደትከ ፡ ወእትወትከ ። ንግደተ ፡ ኢየሩሳሌም ። ወይእቲ ፡ ንግደቱ ፡ ኀቤከ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍርሀት ፡ (መዝ ፡ ፺፰ ። ገድ ፡ ተክ ። ግንዘ) ።

**ንግድ** ፤ በቁሙ ፤ የገበያ ፡ ሥራ ፡ ገበያ ። ለእመ ፡ ሖረ ፡ ውስተ ፡ ንግድ ፤ አው ፡ ውስተ ፡ ብሔር ፡ ርሑቅ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፫ ። ስንክ ፡ የካ፲) ።

**ንግድና** ፤ ንግድ ፤ ነጋዴነት ፤ እንግድነት ፡ (ፊልክ ፡ ፺፯) ።

**ነግድ ፤ (ዳን)** ፤ እንግዳ ፡ መንገደኛ ፡ ዐድር ፡ ኸደጅ ። **አፍቅሮ ፡ ነግድ ። ተቀብሎ ፡ ነግድ ። ወነግዳን ፡ አንትሙ ፡ እምሥርዐት ፡ ተስፋ ። ፍቅረ ፡ ነግዳን** ፡ (ሮሜ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ዕብ ፲፫ ፡ ፪ ። ኤፌ ፪ ፡ ፲፱ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፳፩) ።

**መንግድ** ፤ የሚነግድ ፡ ነጋዴ ። መኼጃ ፡ መንገኛ ፤ መንገድ ፡ ገንዘብ ። **በዘከነ ፡ መንግደ ፡ ይገብሩ** ፡ (መስተ) ።

**መንገድ** ፤ በቁሙ ፤ ጥርጊያ ፡ ጐዳና ፡ መኼጃ ፡ መንጐጃ ። **ኢትሑሩ ፡ መንገደ ። ኢዴሐ ፡ መንገደ ። ወበመንገድሂ ፡ እትመነደብ ፡ ዘልፈ ። ጥቃ ፡ መንገድ** ፡ (ኤር ፭ ፡ ፳፭ ። ፲ ፡ ፳፫ ። ፪ቀሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፮ ። ማቴ ፳ ፡ ፴) ።

—፤ አካኼድ ፡ ጕዞ ፡ ርምጃ ፤ የመንገድ ፡ ሥራ ። **ምስለ ፡ መስተሣይል ፡ ኢትኅበር ፡ መንገደ ። ምረጽ ፡ ብእሲ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ መንገደ ፡ ቀዳም ። ጸሎተ ፡ መንገደ ፡ ሰማይ** ፡ (ሚራ ፳ ፡ ፲፭ ። ግብጽ ፡ ፲፱ ። ግንዘ) ።

—፤ ንግድ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ችርቻሮ ። **ስእነ ፡ ከመ ፡ ይሴሲ ፡ እሞ ፡ እመሂ ፡ በመንገድ ፡ ወእመሂ ፡ በግብር ፡ ዘይገብሩ ፡ በብእ ፡ ዓለም** ፡ (ቀሌ) ።

**አንግደ** ፤ አስኬደ ፤ አስነገደ ። ጠማማ ፡ ቢሉ ፡ አንጋዳ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ተነግደ** ፤ ተነገደ ፤ ንግዱ ፡ ተደረገ ፡ (መንገዱ ፡ ተኼደ ፡ ታለፈ ፡ ተረገጠ) ። በመጽሐፍ ፡ ፈንታ ፡ ተነግደ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ሥራዊ ፡ ረቢዓን ፡ ይትነገድ ፡ እምርሑቅ** ፡ (ምሳ፳፭ ፡ ፳) ።

**ተናገደ** ፤ በቁሙ ፡ ተነጋገደ ፤ ተመላለሰ ፡ አገር ፡ ላገር ፡ ዞረ ፤ እንግዳ ፡ ኾነ ፡ በንግድ ፡ በስደት ። **ሥርዐተ ፡ ተናግዶ ፡ ወረባሕ ። ሠየጥ ፡ እለ ፡ ይትናገዱ ፡ ወያመጽኡ ፡ ሎቱ ። ምጽዋት ፡ ተናግዶ ፡ አምሳካዊት ። ተናግዶቱ ፡ ለአብርሃም ። እለ ፡ ይትናገዱ ፡ አኀው** ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፲፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፯ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ቀሞ ፡ ፴፱) ።

**አእንገደ** ፤ (የአንገደ ፡ ድርብ) ፡ አስተናገደ ፤ እንግዳ ፡ አሳደረ ፡ ተቀበለ ። **ወበእንቲአሃ ፡ አእንገዱ ፡ ሰብእ ፡ መላእክተ ፡ እንዘ ፡ ኢየአምሩ** ፡ (አፈ ፡ ድ፴፪) ።

**ተአንገደ** ፤ (የተናገደ ፡ ድርብ) ፡ ተስተናገደ ፤ እንግዳ ፡ ኾነ ፡ እንግድነት ፡ ኼደ ፡ ተሰደደ ። **እለ ፡ ሖሩ ፡ ወተአንገዱ ። ጥበብ ፡ ዐርክ ፡ ይእቲ ፡ በውስቴ ፡ ተአንግዶ ። ተአንገደ ፡ ምስለ ፡ ያዕቆብ** ፡ (ቅዳ ። ፊላስ ። ሃይ ፡ አበ፪) ።

**እንግዳ ፤ (ብ ፡ አናግድ)** ፤ በቁሙ ፤ ነግድ ፡ መንገደኛ ፡ በደተኛ ፤ መጤ ፡ ባይተዋር ። **ዝ ፡ እንግዳ ፡ አምአይቴ ፡ ዘመጽአ ። ማኅደረ ፡ እንግዳ ። መቃብረ ፡ እንግዳ ። ዑቀኒ ፡ እስመ ፡ እንግዳ ፡ አነ** ፡ (ድጓ ። ቀኖ ፡ ኒቅያ፳ ። ማቴ፳፯ ፡ ፯ ። ሩት፪ ፡ ፲) ። **ጸሊአ ፡ አናግድ ። አክብሮ ፡ አናግድ** ፡ (ጥበ፲፱ ፡ ፲፫ ። ፊላስ) ።

«**እንግድዓ** ፤ —ደረት ፤ —ጕዲዕ ፡ ጕድዐ» ።

**ነገድ ፤ (ብ ፡ አንጋድ ። ዕብ ፡ ኔኬድ ። ዐረ ፡ ነጅል)** ፤ በቁሙ ፤ ወገን ፡ ያንድ ፡ አባት ፡ ዘር ፤ ልጅ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመድ ፡ ተወላጅ ፤ እንደ ፡ ንህብና ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ገንዘብ ፡ እየበዛ ፡ እየተረባ ፡ አውራ ፡ እያበጀ ፡ የሚኼድ ። ቤትንና ፡ በትርን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። **ወተፈልጡ ፡ በበ ፡ ነገዶሙ ። አንጋደ ፡ እስራኤል** ፡ (ኢዮ፳ ፡ ፲፰ ። ሕዝ፵፰ ፡ ፳፩) ። ስራዊትና ፡ ቤተ ፡ ሰብም ፡ ላለቃውና ፡ ለጌታው ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ነውና ፡ ነገድ ፡ ይባላል ፤ አለቆችም ፡ ላለቆቻቸው ፡ ነገድ ፡ ይባላሉ ፤ ወገን ፡ አሽቃ ፡ ማለት ፡ ነው ። **ኅዲጎ ፡ ተስዓ ፡ ወተስዐተ ፡ ነገደ ። ሰራዊተ ፡ ሚካኤል ፡ በበ ፡ ነገዶሙ** ፡ (ድጓ ። ቅዳ ፡ ያዕ) ። በአንጋድ ፡ ፈንታ ፡ አናግድ ፡ ይባል ፤ የጠፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **ሕጹጻነ ፡ አናግድ ። አናግደ ፡ ሲሞን ፡ መሠርይ ፤ አናግደ ፡ መቅዶንዮስ** ፡ (ገድ ፡ አዳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፯) ።

**ነጐድጓድ ፤ —በቁሙ ፤ —ጐድጐደ ፡ አን** ።

**ነጊሀ ፤ ሆት ፤ (ነግሀ ፡ ይነግህ ፡ ይንጋህ ። ዕብ ፡ ናጋህ ። ሱር ፡ ንጋህ ። አው ፡ ነግየ ፡ ነገየ ። ነጊው ፡ ነገወ)** ፤ መንጋት ፤ መብራት ፡ ቧት ፡ መኾን ። **ማእከ ፡ ይነግህ** ፡ (ምሳ፳፫ ፡ ፴፭) ።

**ነግህ** ፤ በቁሙ ፤ ንጋት ፡ የቧት ፡ ብርሃን ፤ ቧት ፡ ማለዳ ፤ ፀሓይ ፡ ሲወጣ ፡ ከንሕና ፡ ከጽባሕ ፡ በኋላ ፡ ከሠለስት ፡ በፊት ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፤ ቀዳማይ ፡ ሰዓት ፡ መዓልት ። **በበ ፡ ነግህ ። እምነግህ ፡ እስከ ፡ ሠርክ ። ነግሀ ፡ በጽባሕ** ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፳፩ ። ፲፰ ፡ ፲፫ ። ኩፋ ፡ ፵፪) ። ጌሠምን ፡ ነገ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**አንግሀ ፤ (አሌለየ)** ፤ አነጋ ፡ ማለደ ፡ ተጋ ፤ ሌሊት ፡ ተነሣ ። **ሖሩ ፡ በኑኝ ፡ ሌሊተ ፡ ወአንግሁ ፡ ባዐለ ፡ ቂሳርያ ። ወአንግሀ ፡ ጥቀ ፡ ሐዊረ ። ለምንት ፡ አንጋህከ ፡ ገዩሥ ፡ ዝየ ። ያንግሁ ፡ ሌሊተ** ፡ (ዮሴፍ ። ማር ፲፮ ፡ ፪ ። ሄርማ ። ኪዳ) ። አስነጋ ፡ አስማለደ ፤ ማለዳ ፡ አስነሣ ፡ (አስደራጊ) ።

**ነጌ ፤ (ብ ፡ ነግያት ፤ ነግይ ፡ ነገየ)** ፤ ዝሆን ፤ በኢስያና ፡ በአፍሪቃ ፡ ቈላ ፡ በዱሩ ፡ የሚገኝ ፡ ታላቅ ፡ አውሬ ፡ ከአራዊት ፡ ኹሉ ፡ የሚበልጥ ፤ ጤናማ ፡ ዕድሜያም ፡ እንደ ፡ ርኩምና ፡ እንደ ፡ ቍራ ፡ እስከ ፡ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ ከዚያም ፡ የሚበልጥ ፡ የሚኖር ፡ ባላራት ፡ እግር ፤ ባለረዥሙም ፡ ኵንቢ ፡ ቈርበተ ፡ ወፍራም ፡ ጥርሱ ፡ ረዥምም ፤ ብዙ ፡ ጕልበት ፡ ዕውቀትና ፡ ብልኀት ፡ ማስተዋል ፡ ያለው ፤ ማርና ፡ ቅጠል ፡ ዕንጨት ፡ የሚበላ ፤ ኹለት ፡ ጥርሶቹ ፡ ቀንድ ፡ የሚመስሉና ፡ ቀንድ ፡ የሚባሉ ፡ ወፍራሞች ፡ ረዣዥሞች ፤ በብዙ ፡ ዋጋ ፡ የሚሸጡ ፡ እንደ ፡ ቀንድ ፡ የሚነጠጡ ፡ ቤትን ፡ ንዋያትን ፡ የሚያስጌጡ ። ፍ፡ችው ፡ ንግሃዊ ፤ ሰላማዊ ። ንግሃዊ ፤ እንዳራዊት ፡ ሴት ።

አለመውጣቱን ፤ እንደ ፡ ሰው ፡ ከሥርክ ፡ እስከ ፡ ንግህ ፡ መከተቱን ፤ በንግህ ፡ መውጣቱን ፡ ያሳያል ፡፡ ሰላማዊ ፤ ከሰው ፡ ከእንስሳ ፡ አለመጣላቱን ፤ ከልንኩት ፡ አለመንከቱን ፤ ሰው ፡ መውደዱን ፡ ቶሎ ፡ መልመዱን ፤ ከለመደም ፡ ወዲያ ፡ እንደ ፡ ቤት ፡ እንስሳ ፡ ታዛዥና ፡ ቶገኸ ፡ አገልጋይ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፡፡ ይኸውም ፡ ሲታወቅ ፡



ነጌ ፡

ህንዳውያን ፡ እንዳህያና ፡ እንደ ፡ ገመል ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡ በቅሎ ፡ ይጭኑታል ፡፡ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ያሠሩታል ፤ ይልቁንም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡፡ ዝሆን ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ ዝንጉን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ህድአቱን ፡ ህዱእነቱን ፡ እንዳባት ፡ በሬ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፤ ዝጎነን ፡ እይ ፡፡ ጋሎች ፡ ሰላምታ ፡ ሲሰጡ ፡ ነጌ ፡ ነጋያ ፤ ሰም ፡ ሲያወጡ ፡ ነገዎ ፡ የሚሉት ፤ ዐማሮችም ፡ ንጋቱ ፡ ንጋቷ ፡ የሚሉት ፡ ከዚህ ፡ ይሰማማል ፡፡ ቀርነ ፡ ነጌ ፡፡ ማኅፈድ ፡ ዘቀርነ ፡ ነጌ ፡፡ አብያተ ፡ ዘቀርነ ፡ ነጌ ፡፡ ወወፅአ ፡ ኀቤሁ ፡ ንጉሠ ፡ ህንድ ፡ ምስለ ፡ ብዙኃን ፡ ነጌያት ፡፡ ወገብረ ፡ ነጌያተ ፡ ብርተ ፤ ወተቃተሉ ፡ ነጌያት ፡ ምስለ ፡ ነጌያት ፡ (ማሕ፩ ፡ ፲፱ ፡ ፯ ፡ ፱ ፡፡ ዓሞ፫ ፡ ፲፭ ፡፡ ዮሴፍ ፡፡ ዜና ፡ እስክ) ፡፡

**ነጎት** ፤ (ነጊው ፡ ነገወ ፡፡ ትግ ፡ ሐባ ፡ ኑጎት) ፤ የዝሆን ፡ ኩንቢ ፡ መሣሪያው ፡ እንደ ፡ ዘንዶ ፡ የሚስብ ፡ የሚጠልፍ ፤ ኹሉን ፡ ወዳፉ ፡ እየሳበ ፡ የሚያቀርብበት ፡፡ ሲበዛ ፡ ነጎታት ፤ ወይም ፡ ነገዋት ፡ ያሰኛል ፡፡



ኑጎት ፡

**ነጊል** ፤ **ሎት** ፤ (ነገለ ፡ ይነግል ፡ ይንግል) ፤ መንገል ፤ መፍለስ ፡ መንቀል ፡፡ መገለጥ ፡ መታየት ፤ ማጌጥ ፡ መሸለም ፤ ለመታየት ፡፡ ገለየን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ፡፡

**መንገል** ፤ መታያ ፡ መተያያ ፤ አንጻር ፡ አፋዛዥ ፡ አቅጣጫ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፤ የበታ ፡፡ ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ ኀበ ፡ ወደ ፡ ወገን ፡ አጠገብ ፡ ዘንድ ፡ ቅጽል ፡ ይኾናል ፡፡ መንገለ ፡ ምሥራቅ ፡፡ እኀትየ ፡ ይእቲ ፡ እመንገለ ፡ አቡየ ፡፡ ኢታቅም ፡ መንገሌከ ፡ (ደቂቅ) ፡፡ አልቦ ፡ ማኀተት ፡ መንገለ ፡ ተኀጥአ ፡ ሠምዐ ፡ ወዘይት ፡፡ መንገለ ፡ ፈለሱ ፡፡ መንገለ ፡ ተግሕሠ ፡፡ መንገለ ፡ ትፈቅድ ፡ ፍና ፡ (ሰንክ ፡ ኅዳ፳ ፡፡ ማን፳) ፡፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፤ ባወራረድ ፡ ፍች ፡ በ ፡ በስተ ፡ ረገድ ፡ ይኾናል ፤ ምስጢሩ ፡ ከዘንድና ፡ ከወገን ፡ ካጠገብ ፡ ይገባል ፡ (ዕር፲፱ ፡ ቀ፻) ፡፡

**መንገለ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ መነገለ ፤ አነገለ ፤ ነቀለ ፡ አፈለሰ ፡፡

**መንግል** ፤ የሚታይ ፡ ገላ ፤ ፊት ፡ ዐንገት ፡ ደረት ፤ ራስ ፡ ጠጕር ፡ እጅ ፡ እግር ፡፡ እስመ ፡ ትወድዩ ፡ ሥነ ፡ ባዕሊክሙ ፡ አንትሙ ፡ ዐደው ፡ ፈድፋደ ፡ እምአንስት ፤ ወሕብረ ፡ ፈድፋደ ፡ እምድንግል ፡ በመንግል ፡ (ሔኖ ፡ ፳፰) ፡፡ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ጌጥና ፡ ሽልማት ፡ ይሉታል ፡፡

**ንግማጢስጤ** ፤ (ጽር ፡ ኤኒግማቲስቴ ፡፡ ዕብ ፡ ሞሺሊም) ፤ መሐደምት ፤ ተራቾች ፡ ተረተኞች ፡ ባለምሳሌዎች ፡ (ዘኍ፳፩ ፡ ፳፯) ፡፡ ባለብሉይና ፡ ባለቅኔ ፡ ወግ ፡ ታሪክ ፡ ይሉታል ፡፡

**ነጊሥ** ፤ **ሦት** ፤ (ነግሠ ፤ አው ፡ ነገሠ ፡ ይነግሥ ፡ ይንግሥ ፡፡ ዕብ ፡ ናጋሽ ፤ ገፋ ፡ አዳፋ ፡፡ ዐረ ፡ ነጀ(ግ)ሸ ፤ ነዳ ፡ አባረረ) ፤ መንገሥ ፤ መምለክ ፤ በመንበረ ፡ መንግሥት ፡ መቀመጥ ፤ መሠልጠን ፡ ጌታ ፡ መኾን ፡፡ መለከን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡፡ እምቅድመ ፡ ይንግሥ ፡ ተንባላት ፡ በግብጽ ፡፡ እግዚ ፡ ነግሠ ፡፡ እመ ፡ ነግሠ ፡ በሱላ ፡፡ እመ ፡ ገብር ፡ ነግሠ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳ ፡፡ መዝ ፡ ፺፪ ፡፡ አስቴ፩ ፡ ፪ ፡፡ መክ፱ ፡ ፲፬) ፡፡

**ነጋሢ** ፤ (ሢት ፡ ሥያን ፡ ያት ፤ ገሥት ፡ ታት ፡፡ ዐረ ፡ እንጃሺ ፡፡ ዕብ ፡ ኖጌሽ ፤ ግፈኛ) ፤ በቁሙ ፤ የነገሠ ፡ ንጉሥ ፡ ነጋሽ ፡፡ ጌታ ፡ አለቃ ፡ አውራ ፤ የሕዝብ ፡ ቀንድ ፡፡ አበ ፡ ነጋሢ ፡፡ ወልደ ፡ ነጋሢ ፡፡ ነገሥት ፡ አበውኪ ፡ ወነጋሥያት ፡ ሐፃንያትኪ ፡፡ ነገሥታተ ፡ አሕዛብ ፡ (፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፳፱ ፡፡ ፪ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ፡፡ ድጓ ፡፡ ታሪ ፡ ነገ) ፡፡ ኢይትዐበይ ፡ ረድእ ፡ ባዕለ ፡ መምህሩ ፡ ወኢወዓሊ ፡ ባዕለ ፡ ነጋሢ ፡፡ ነገሥተ ፡ በራዊት ፡፡ ነገሥተ ፡ አሕማር ፤ ጌታ ፡ አለቃ ፡ (ዲድ ፡ ፰ ፡፡ ዘኍ፴፩ ፡ ፵፰ ፡፡ ሔኖ ፡ ፸፱) ፡፡

**ንጉሥ** ፤ (ሣን ፡ ሣት ፡ ግሥት ፤ ታት) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፤ በቁሙ ፡ ሐፄ ፡ ባለዘውድ ፡፡ ሹም ፡ አለቃ ፡፡ ንጉሥ ፡ ዐቢይ ፡፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ (ኢሳ፴፮ ፡ ፲፫ ፡፡ ዳን፪ ፡ ፴፯) ፡፡ እስመ ፡ ዘሜም ፡ ንጉሥ ፡ ንጉሥ ፡ ውእቱ ፡፡ ሄሮድስ ፡ ንጉሠ ፡ ገሊላ ፡፡

**ንጉሣዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ መለካዊ ፤ የንጉሥ ፡፡ ግብር ፡ ንጉሣዊ ፡፡ ሰርጐዕ ፡ ንጉሣዊ ፡፡ ንጉሣውያን ፡ (አፈ ፡ ድ፳፮ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ፡፡ መጽ ፡ ምስ) ፡፡

**ንግሥት** ፤ በቁሙ ፤ ባባቱ ፡ ፈንታ ፡ የነገሠች ፤ እንደ ፡ ማክዳና ፡ እንደ ፡ ህንደኬ ፡ እንደ ፡ ዘውዲቱና ፡ እንደ ፡ ቢክቶርያ ፡ ያሉ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡፡ ንግሥተ ፡ ሣባእ ፡፡ ንግሥቶ ፡ ኢትዮጵያ ፡፡ ንግሥታተ ፡ ፋርስ ፡ (፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፩ ፡፡ ግብ፰ ፡ ፳፯ ፡፡ መቃ ፡ ፫፲፩) ፡፡

—፤ የንጉሥ ፡ ሚስት ፡ እቴጌ ፡ ባሏ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያነገሣት ፡፡ እቤኒ ፡ ንግሥት ፡፡ አስጢን ፡ ንግሥት ፡፡ ንግሥታት ፡ ወዕቁባት ፡፡ ወትቀውም ፡ ንግሥት ፡ በየማንከ ፡ (ድጓ ፡፡ አስቴ፩ ፡ ፱ ፡፡ ማሕ፯ ፡ ፰ ፡፡ መዝ ፡ ፵፬) ፡፡

**ንግሥ** ፤ መንገሥ ፡ እንጋገሥ ፤ ንጉሥነት ፡ መንግሥት ። ዜና ፡ ንግሡ ፡ ላዕለ ፡ ዮናናውያን ። ወከነ ፡ ንግሡ ፡ ለኢዮሳፍጥ ፡ በሰላም ። መኑ ፡ የአምር ፡ ብዝ ንቱ ፡ መዋዕሊ ፡ ንግሥኪ ። በእንተ ፡ ሖሩ ፡ ንግሡ ፡ ለዳዊት ። ሶበ ፡ ጸንዐ ፡ ንግሡ ፡ (ዮሴፍ ። ፪ዜና ፡ ፳ ፡ ፴ ። አስቴ፬ ፡ ፲፬ ። ፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፴ ። ዮሴፍ) ።

**መንግሥት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፤ መንገሻ ፡ መሠልጠኛ ፡ ጌታ ፡ መኾኛ ፡ ግዛት ፤ ያው ፡ ግን ፡ ካንድ ፡ ንጉሥ ፡ በታች ፡ ያለ ፡ ባንድ ፡ ሕግ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ አገ ርና ፡ ሕዝብ ፤ በውስጡ ፡ ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ክፍል ፤ ሰፋፊ ፡ አህጉር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድ ፡ ያለበት ፡ ማኅበረ ፡ ንጉሥ ፡ መርዒት ፡ ንጉሥ ፡ እረኛውን ፡ መርጦ ፡ የሚያነግሥ ። መንግሥት ፡ ትትፋለስ ፡ እምሕዝብ ፡ ለሕዝብ ። ሖላ ፡ መንግሥት ፡ ዘትትናፈቅ ፡ በበይናቲሃ ። ለሖሩ ፡ መን ግሥታተ ፡ ምድር ። መንግሥታት ፡ ዐበይት ፡ (ሚራ፲ ፡ ፰ ። ማቴ፲፪ ፡ ፳፭ ። ዘዳ፳፰ ፡ ፳፭ ። ፴፭ ፡ ፰) ።

—፤ የንጉሥ ፡ ማዕርግ ፡ ክብር ፡ ሥልጣን ፡ ጌትነት ፤ የሕዝ ብና ፡ የሰራዊት ፡ ብዛት ፡ ኅብረት ፡ አንድነት ፤ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገባል ። ፀረፍክሙ ፡ ላዕለ ፡ መንግሥትየ ። ወመንግሥታኒ ፡ የሀብ ፡ ንጉሥ ፡ ለካልእት ፡ ብእሲት ። አስቴር ፡ ሱታፌ ፡ መንግሥትነ ። መንግሥት ፡ እንተ ፡ ኢጸውዐት ፡ ስመከ ። ቅድመኒ ፡ መንግሥተ ፡ ምድር ፡ ወመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ድኅረ ፡ ኢለዘሮጸ ፡ ወኢለዘ ብደረ ፡ (ታሪ ፡ ነገ ። አስቴ፩ ፡ ፲፱ ። ፲፯ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፸፰ ። ቅኔ) ። እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓ ለም ፡ ሀሎ ፡ እግዚ ፡ በመንግሥቱ ፡ (ባንድነቱ) ፤ እግዚ ፡ ብትሥልስቱ ፡ (በሦስትነቱ) ፤ እግዚ ፡ በመለኮቱ ፡ (በም ልአቱና ፡ በስፋቱ) ። እምቅድመ ፡ ኀሠ ፡ ወጽባሕ ፡ ወእ ምቅድመ ፡ መዓልት ፡ ወሌሊት ፡ እምቅድመ ፡ ይት ፈጠሩ ፡ መላእክት ፡ ሀሎ ፡ እግዚ ፡ በመንግሥቱ ፡ (በ ሥልጣኑ ፡ በጌትነቱ) ። የመንግሥት ፡ አፈታት ፡ እንደ ፡ መለኮት ፡ ባለብዙ ፡ ስልት ፡ ነው ፡ (ቅዳ ፡ ዲዮ) ።

**አንገሠ** ፤ አነገሠ ፡ አስነገሠ ፤ ሾመ ፡ አሠለጠነ ። አንግሥ ፡ ሎሙ ፡ ንጉሠ ። ይምሥጥዎ ፡ ወያንግሥዎ ። ዘአንገሥኩክ ፡ ላዕሌሆሙ ። አንገሠቶ ፡ ኀጢአት ፡ ለሞት ፡ (፩ነገ ፡ ፰ ፡ ፳፪ ። ዮሐ፮ ፡ ፲፭ ። ፪ዜና ፡ ፩ ፡ ፲፩ ። ሮሜ፭ ፡ ፲፯) ።

**ተናገሠ** ፤ በቁሙ ፤ ተነጋገሠ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ወይም ፡ በዘመን ። ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ትትናገሥ ፡ ለዳ ዊት ፡ አሐደ ፡ ዓመተ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ። ክብረ ፡ ነገሥቱ ፡ ግን ፡ ፳፱ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**አስተናገሠ** ፤ አናገሠ ፡ አነጋገሠ ፤ አማፈረ ፡ አዛመነ ፡ በቍጥር ፡ በታሪክ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ። ፲፯ ፡ ፩ ። ፲፰ ፡ ፩) ።

**ንጉሥ** ፤ በቁሙ ፤ የድርሰት ፡ መጽሐፍ ፡ እግ ዚር ፡ ነግሥ ፡ እንደ ፡ ስንክሳር ፡ ካመት ፡ እስካመት ፡ የተ ሠራ ፡ በማሕሌት ፡ ጊዜ ፡ የሚባል ።

**ነጕዐ** ፤ (ይነጕዕ ፡ ይንጓዕ ፤ ነጕዖ ። ዕብ ፡ ናጋዕ ፤ ነካ ፡ ገፌ) ፤ ነጓ ፡ ረመኸ ፡ ዶ ፡ ን ፡ ኳ ፡ አስ ፤ ሲማታና ፡ ሲጋጭ ። ወለቀ ፡ ተናጋ ፤ ተሰበረ ፡ ተቀለጠመ ፤ ያገዳ ፡ ያጥንት ።

**አንጐዐ** ፤ አነኀ ፡ አሬመኸ ፡ አስረመኸ ፤ አናጋ ፡ ሰበረ ፡ ቀለጠመ ። ይበልዕ ፡ ሥጋ ፡ ዘሠብሐ ፡ ወያነ ጕዕ ፡ አገዳሆን ። የሐርጽ ፡ ወያነጕዕ ፡ ወዘተርፈ ፡ ይ ከይድ ፡ በእግሩ ፡ (ዘካ፲፩ ፡ ፲፮ ። መቃ ፡ ገ፲፯) ። በአን ጕዐ ፡ ፈንታ ፡ አስተናጕዐ ፡ ይላል ፤ አያሰኛም ። መሬር ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ ለዘማዊ ፡ እስመ ፡ ያስተናጕዖ ፡ ፍት ወተ ፡ ዝሙት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አንጕዕ** ፤ (ብ ፡ አናጕዕ) ፤ አንጓ ፤ አገዳ ፡ ቅልጥም ፡ ዐጥቅ ። ባንጓው ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ የቅልጥሙ ፡ ፍሬ ፡ ሥቡ ፡ ቅባቱ ፡ አንጎሉ ። አዕፅምቲሁ ፡ ይመልእ ፡ አንጕዐ ። ወይትከዐው ፡ አንጕዑ ። ዝሙት ፡ ዘይትገ በር ፡ ውስተ ፡ አንጕዕክሙ ። ትበልዑ ፡ አንጕዓ ፡ ለም ድር ፡ (ኢዮ፳፩ ፡ ፳፬ ። ፴፫ ፡ ፳፬ ። ያዕ፬ ፡ ፩ ። ዘፍ፵፭ ፡ ፲፰ ። መገ ፡ ፳፬) ።

**ነጊፍ** ፤ ፎት ፤ (ነገፈ ፡ ይነግፍ ፡ ይን ግፍ ። ዕብ ፡ ናጋፍ) ፤ መንገፍ ፡ ማንገፍገፍ ፤ መም ታት ፡ ማርገፍ ፡ ማራገፍ ፤ ርግፍ ፡ አርጎ ፡ መተው ፤ መ ጣል ፡ ማሽቀንጠር ። ንግፉ ፡ ጸበለ ፡ እገሪክሙ ። ነገ ፍኩ ፡ ጽንፈ ፡ ልብስየ ፡ ወእቤ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ለይንግፎ ። ዕፀ ፡ ጠርቤንቶስ ፡ ዘነገፈት ፡ ቈጽላ ። ንግፍ ፡ ላሐከ ። ነገፎሙ ፡ ለግብጽ ፡ ማእከለ ፡ ባሕር ፡ (ማቴ፲ ፡ ፲፬ ። ነሐ፭ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፩ ፡ ፴ ። ሚራ፵፰ ፡ ፲፯ ። ዘፀ፲፬ ፡ ፳፯) ። በነገፈ ፡ ፈንታ ፡ ተናገፈ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ትና ገፊ ፡ ጸበለኪ ፡ (ኢሳ፶፪ ፡ ፪) ።

**አንገፈ** ፤ አስረገፈ ፤ አስተወ ፡ አስጣለ ፡ አዳን ። ናሁ ፡ አነ ፡ አነግፈክሙ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅልክሙ ። አንገ ፍዎ ፡ ላሐ ። በከመ ፡ ያነግፍ ፡ ኖላዊ ፡ እምአፈ ፡ አን በሳ ፡ እግረ ። ያነግፈኪ ፡ እምእደ ፡ ፀርኪ ። አንግፍኒ ፡ በትንባሌ ፡ እምብካይ ፡ ወወይሌ ፡ (ኤር፳፩ ፡ ፬ ። ዘፍ ፳፱ ፡ ፳፯ ። ዓሞ፫ ፡ ፲፪ ። ሚክ፬ ፡ ፲ ። ደራሲ) ።

**አንጋፌ** ፤ መንገፌ ፤ የሚያስረግፍ ፤ የሚያስ ጥል ፡ የሚያስተው ፡ የሚያስረሳ ። መንገፌ ፡ ሐዘን ። መንገፌ ፡ ለባሕየ ፡ (ዮሴፍ ። አርጋ ፡ ፬) ።

**ተነግፈ** ፤ ተነገፈ ፤ ተንገፈገፈ ። ረገፈ ፤ ደረቀ ፡ ወደቀ ። ቈጽል ፡ ዘይትነገፍ ፡ እምነፋስ ። ዘቀዳሚ ፡ ይትነገፍ ፡ ወዘደኃሪ ፡ ይሠርጽ ። ዕፀው ፡ ዘኢይትነ ገፉ ፡ (ኢዮ፲፫ ፡ ፳፭ ። ሚራ፲፬ ፡ ፲፰ ። ሔኖ ፡ ፫) ።

**ንጉፍ** ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ግፍት) ፤ የተነገፈ ፡ የ ረገፈ ፡ የወደቀ ። ንጉፈ ፡ ለይኩን ። ከመ ፡ ጽጌ ፡ ንጉፍ ፡ (ነሐ፭ ፡ ፲፫ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፪) ። ንእስ ፡ ውርዙት ፡ በማ ለት ፡ ፈንታ ፡ ንጉፋን ፡ ይላል ፡ (መገ ፡ ፲፳፯) ።

**ንጋፍ** ፤ (ፋት) ፤ ርጋፊ ፡ ትቢያ ፡ ብናኝ ፡ ጕ ድፍ ። ንጋፍ ፡ ዘይመጽእ ፡ ነፋስ ፡ (ኢሳ፳፱ ፡ ፭) ።

**ተናገፈ** ፤ ተራገፈ ፡ ተረጋገፈ ፡ ተለያየ ። ተናገፉ ፡ ለመዋቲት ፡ ሕይወት ። ሕይወተ ፡ ዓለም ፡ በተናግፎ ፡ (ሉቃ ፡ ዕብ፲፬ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ ታኅ፭) ።

**ነጊር ፤ ሮት ፤** (**ነገረ ፤ ይነግር ፡ ይንግር ። ዕብ ፡ ናጎር ፤ ሂናጌር ፡ ፈሰሰ ፡ ወረደ ። ናጌር ፤ ጠረበ ፡ ላገ**) ፤ መንገር ፤ መስበክ ፡ ማስተማር ፡ ማውራት ፡ ማብሠር ፤ ነገርን ፡ ሳያቋርጡ ፡ እንደ ፡ ውሃና ፡ እንደ ፡ ዝናም ፡ ማፍሰስ ፡ ማውረድ ፡ ማንጐድጐድ ፤ ሐሳብን ፡ ምስጢርን ፡ በቃል ፡ መግለጥ ፡ በንባብ ፡ ማስጌጥ ፤ መልክ ፡ እያወጡ ፡ ምሳሌ ፡ እየሰጡ ፡ ማንጥና ፡ መቅረጥ ፡ እንደ ፡ ቅኔ ። **ኢትኅፈር ፡ ነጊረ ፡ ጌጋይከ ፡፡ መኑ ፡ ይክል ፡ ነጊረ ፡ ምሕረቶ ፡ ጥንቁቀ ፡፡ ዘአቅደመ ፡ ነጊረ ፡ በአፈ ፡ ነቢያት ፡፡ ለምንት ፡ ትነግር ፡ ሕግየ ፡፡ ፈሪህየ ፡ ክመ ፡ እንግርክሙ ፡ ዘእኄሊ ፡** (ሢራ ፥ ፳፯ ። ፲፩ ፡ ፳ ። ሮሜ ፩ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፵፱ ። ኢዮ ፴፪ ፡ ፮) ። በነገረ ፡ ፈንታ ፡ ተናገረ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ጎርጎርዮስ ፡ ተናጋሪ ፡ መለኮት ፡፡ ነፍስ ፡ ተናጋሪት ፡፡ ዝሉ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ነባቢ ፡ ወተናጋሪ ፡፡ ተናጋርያን ፡ ፀሩዐ ፡** (ስንክ ፡ ጥር ፴ ። ቄር ። ቄድር ። ኪዳ) ።

**ነጋሪ ፤** (**ሪት ፡ ርያን ፡ ያት**) ፤ በቁሙ ፤ የሚነግር ፡ የሚያወራ ፡ የሚሰብክ ፡ የሚተርክ ፡ የሚነብ ፡ ነባቢ ። ወሬ ፡ ነጋሪ ፤ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፤ ባለነጋሪት ፡ እንዲሉ ። ዜን ወንና ፡ ነብበን ፡ እይ ።

**መንግር ፤** (**ርት ፡ ራን ፡ ራት**) ፤ ፊቢሽ ፤ ለፋፊ ፤ ነጋሪ ። (መንገሪያ ፡ ያዋጅ ፡ መግሪያ ፤ ደበሎ ፡ ነጋሪት) ። **ኢበሐሳምያን ፡ ወኢበመንግራን ፡** (፩ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፮) ።

**እንገረ ፤** አናገረ ፡ አስለፈለፈ ፤ አስነገረ ፤ አቦራ ፡ አስለፈፈ ፡ አስተነበ ። በነገረ ፡ ፈንታ ፡ ተናገረ ፡ እንዲል ፤ በአንገረም ፡ ፈንታ ፡ አስተንገረ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹሉ ፡ አስተናገረ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **መንፈስ ፡ እግዚ ፡ ዘያስተናግረኒ ፡፡ አስተናገረ ፡ በሃማኑ ፡፡ አስተናገሩ ፡ ምዉተ ፡** (ኢዮ ፳፯ ፡ ፬ ። ሲኖዶ ። መጽ ፡ ምሥ) ። ወቀትና ፡ ቅቤን ፡ አነገረ ፡ አንጐረ ፤ እንገር ፡ ንጐር ፡ ግራ ፡ እንጀራ ፡ ሙጌራ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ምስጢሩ ፡ መፍሰስና ፡ መቅለጥ ፡ መርጋት ፡ መጋገር ፡ ነው ፤ ግራን ፡ ተመልከት ። ሊጥ ፡ አፍሳሽ ፡ ወጭት ፡ ጠባሽ ፡ እንዲሉ ።

**ተነግረ ፤** ተነገረ ፡ ተወራ ፡ ተባለ ፡ ተተነበ ። **በቀኖና ፡ ዘተነግረ ፡ ቀዳሚ ፡፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡፡ ዝንቱ ፡ ባህል ፡ ቀደመ ፡ ተነግሮ ፡** (ቀሌ ። ኪዳ ። አፈ ፡ ድ፳) ።

**ንጉር ፤** (**ራን ፡ ራት ፡ ግርት**) ፤ የተነገረ ፡ የተወራ ፡ የተባለ ፡ ንግር ። **ማርያም ፡ ንግርት ፡ በነቢያት ፡** (መቅ ፡ ታም) ።

**ነገር ፤** (**ራት ፤ እንጋር**) ፤ በቁሙ ፤ ቃል ፡ ንባብ ፡ ወሬ ፡ የቃል ፡ ፍሬ ፡ ከድምፅ ፡ ጋራ ፡ የሚሰማ ፡ በጥፈት ፡ ባንደበት ፡ የሚገለጥ ፤ ከልብና ፡ ከአፍ ፡ የሚወጣ ፡ ከፉውም ፡ በጎውም ፡ ማናቸውም ፡ ኹሉ ። **በብዙኅ ፡ ነገር ፡፡ ጸሐፍ ፡ ዘሎ ፡ ነገረ ፡ ፍጥረት ፡፡ ካህናት ፡ ይዕቀቡ ፡ ነገራተ ፡ እግዚ ፡** (ዕብ ፩ ፡ ፩ ። ኩፋ ፡ ፪ ። ቀሌ ። አፈ ፡ ድ፲) ።

—፤ ቋንቋ ፤ ልሳን ። **እመኒ ፡ አእመርኩ ፡ ነገረ ፡ ሰብእ ፡ ወመላእክት ፡፡ ይትብባ ፡ በነገረ ፡ ከነዓን ፡፡ ዘይሜህሮ ፡ ለያፍ ፡ ነገረ ፡ ሰብእ ፡** (፩ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ። ኢሳ ፲፱ ፡ ፲፰ ። ቀሌ) ።

**ተናገረ ፤** (ተደራራጊ) ፤ ተነጋገረ ፡ ተባባለ ፤ ተጨዋወተ ፡ ተወያየ ። **ኢይኩን ፡ ተናግሮ ፡ እንዘ ፡ ይበልዑ ፡፡ ኢትትናገር ፡ ምስለ ፡ ብእሲት ፡ በዘታቀንእ ፡፡ ተናገረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ምስጢረ ፡ ምክሩ ፡፡ ኢተናገሩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ዘውስተ ፡ ልቦሙ ፡** (ሥር ፡ ጳኰ ። ሢራ ፴፯ ፡ ፲፩ ። ዮዲ ፪ ፡ ፪ ። ዳን ፲፩ ፡ ፲) ።

**አስተናገረ ፤** (አደራራጊ) ፤ አነጋገረ ፤ አጨዋወተ ።

**አስተናግር ፤** (**አስተንግረ**) ፤ በቁሙ ፤ አብሾ ፡ ዕፀ ፡ ፋርስ ፡ (ጫት ፤ መጠጥ) ፡ የሚያሳብድ ፡ የሚያስለፈልፍ ፡ ርጥብ ፡ ደረቁን ፡ የሚያናግር ፡ የሚያስቀባጥር ፡ (ዐማርኛ) ።

**መስተናግር ፤** የሚነጋገር ፡ የሚያነጋግር ፤ አማላጅ ፡ አምኻር ፤ ጠበቃ ፡ ወባት ፤ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ የነገር ፡ አባት ። **ይኩን ፡ መስተናግረ ፡ ምስሌከ ፡፡ ዐርከ ፡ መሀይምናን ፡ መስተናግር ፡ ለጻድቃን ፡** (ኪዳ) ።

**ኔጌር ፤ ኔጎር ፤** (**ጽር ፡ ኒጌር**) ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ጥቍር ፡ ጠቋራ ፤ ወይም ፡ ነ(ጋ)ጃር ፡ በናጢ ፡ ጠራቢ ። **ስምዖን ፡ ዘተሰምየ ፡ ኔጎር ፡** (ግብ፲፫ ፡ ፩) ።

**ናግራን ፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ ብሔረ ፡ ዐረብ ፡ በየመን ፡ ውስጥ ፡ ያለች ፡ መዲና ፤ ዛሬ ፡ ስንዓ ፡ የሚሏት ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በጥንት ፡ ስብከቱ ፡ ገብቶ ፡ ያስተማራት ፡ (ገላ፩ ፡ ፲፯—፲፰) ። ኋላም ፡ ባምስተኛው ፡ (ሌክል) ፡ መቶ ፡ ፊንሐስ ፡ አይሁዳዊ ፡ ተነሥቶ ፡ ብዙ ፡ አሕዛ ፡ ሕዝቧን ፡ በማፅታቷና ፡ ሊቃውንቷን ፡ ፈጅቶ ፡ ቢያጠፋትና ፡ ቢያቃጥላት ፤ ሐፄ ፡ ካሌብ ፡ ከዚህ ፡ ተሻግረው ፡ ርሱን ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ አባረው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መልሰው ፡ ዐድሰው ፡ ሠርተዋታል ፡ (ድጓ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፮ ። ገድ ፡ ናግ ። ታሪ ፡ ነገ) ።

**ነገርጋር ፤—የጋኔን ፡ ጥሎሽ ፤—ገሪር ፡ ገረ ።**

**ነጐርጓር ፤—ጕርምርምታ ፤—ጐርጐረ ።**

**ነገስት ፤—ንጉሦች ፤—ነጊሥ ፡ ነግሠ ፡ ነጋሢ ።**

**ነጎት ፤—ኰንቢ ፤—ነግህ ፡ ነገወ ፡ የ ።**

**ነድ ፤—በቁሙ ፤—ነዲድ ፡ ነደ ።**

**ነዲእ ፤ እት ፤** (**ነድአ ፡ ይነድእ ፡ ይንዳእ ። ዕብ ፡ ናዴህ ፤ አራቀ ፡ አሰገደ ፡ ወገዘ**) ፤ መንዳት ፤ መውሰድ ፡ መሸኘት ፡ ማጀብ ፡ መከተል ፡ ማድረስ ። **ይንድኡ ፡ እንስሳሆሙ ፡፡ እለ ፡ ይነድኡ ፡ መርዔተ ፡ ዘኢኮነ ፡ ሎሙ ፡፡ ወነድእዋ ፡ ምስለ ፡ ወለታ ፡፡ ይነድእ ፡ ቃለ ፡ ኄበ ፡ ሥርዐ ፡፡ ለዝሉ ፡ ዕለቱ ፡ ይነድእ ፡** (ዘፀ ፲፱ ፡ ፲፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱ ። ዮዲ ፲ ፡ ፲፪ ። አፈ ፡ ድ፴፫ ። ሢራ ፴፱ ፡ ፴፱) ። ከዚህ ፡ ወደዚያ ፡ መናድ ፡ መፈንቀል ፡

ማንከባለል ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ ወደዚህ ፡ እየገፋና ፡ እየ ነዱ ፡ ማምጣት ፡ ማቅረብ ። ከመ ፡ ይንዳእ ፡ ኀበ ፡ ነፍስ ፡ (ማር ፡ ይ፻፲፭) ።

**ነዳኢ** ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት ፡ እት ። ዕብ ፡ ኖጌሽ ፤ ኖግሽም) ፤ የሚነዳ ፡ ነጂ ፤ አስቸ ኳይ ፡ የሚያሮጥ ፡ የሚያጣድፍ ፡ (አረኛ ፡ ሹም ፡ ሌባ ፡ ዘራፊ) ። ነዳእተ ፡ ገባር ። ነዳእቶሙ ፡ ያኄጕዕዎሙ ፡ (ዘፀ፫ ፡ ፯ ። ፳ ፡ ፲፫) ።

**ተነድአ** ፤ ተነዳ ፤ ተነዳቶ ፡ ኼደ ። ዘሰ ፡ ዘይ ትነዳእ ፡ በበትር ። ወበኀይለ ፡ ነፋስ ፡ ይትነድኣ ። ቦ ፡ እለ ፡ በፍትወተ ፡ ዝሙት ፡ ይትነድኡ ፡ (ዘሌ፳፯ ፡ ፴፪ ። ያዕ፫ ፡ ፬ ። ተረ ፡ ቁ፫፲፱) ።

**ንዱእ** ፤ (ኣን ፡ ኣት ፡ ድእት) ፤ የተነዳ ፡ ንድ፤ ተነጅ ፡ ተነድቶ ፡ ኼያጅ ።

**ንድአት** ፤ መንዳት ፡ መነዳት ፡ አነዳድ ፤ ነድቶ ፡ መውሰድ ፤ ተነድቶ ፡ መኼድ ።

**ናዳ** ፤ **ናደት** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፤ መርግ ። ረግሐን ፡ እይ ።

**ተናድአ** ፤ ተናዳ ፡ ተነዳዳ ፤ ተያይዞ ፡ ኼደ ፡ ነጕደ ።

**አስተናድአ** ፤ አናዳ ፤ አነዳዳ ፤ አዋሰደ ። ያስ ተናድኡ ፡ ዘስርቅ ፡ (ዲድ ፡ ፳ ። ሕዝ፲፰ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯) ።

**መስተናድእ** ፤ (እት ፡ አን ፡ ኣት) ፤ የሚ ያናዳ ፡ አናጅ ፤ መናጃ ። ሱቱፋነ ፡ ሰረቅት ፡ መስተናድ ኣኒ ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፳፫) ።

**መንዳእ** ፤ አው ፡ **መንዳእት** ፤ የደረትና ፡ የትከሻ ፡ ደዌ ፤ የሚያጕብጥና ፡ የሚቀልስ ፡ የሚተረክስ ።

**ምንዳእ** ፤ (ኣት) ፤ መንጃ ፡ መነጃ ፡ በትር ፡ ጅራፍ ፡ መንገድ ። በቁሙ ፤ ምንዳ ፤ የረኛ ፡ ዋጋ ፤ ደመ ወዝ ፤ ኖል ፡ ዐበል ፡ ኖላዊ ፤ ለገበሬም ፡ ይኾናል ፤ ሲያ ርስ ፡ በሮች ፡ እየነዳ ፡ ነውና ።

**ምንዳኢዊ** ፤ ምንደኛ ፡ ባለምንዳ ፤ እረኛ ፡ ሎሌ ፡ በስጦኝ ፡ ዐርስ ።

**ነደበ** ፤ (ነዲብ ። ዕብ ፡ ናዳብ ፤ ዐሰበ ፡ ቈረጠ ፡ ለማድረግ) ፤ ጨነቀ ፡ ጠበበ ፤ ጭንቅ ፡ ጥብ ፡ ኾነ ፤ የቦታ ፡ የመንገድ ፡ የሕማም ፡ የግዞት ፡ የጊዜ ፡ የወራት ።

**ምንዳቤ** ፤ (ያት) ፤ ጭንቅ ፡ ጥብ ፤ ዐጸባ ፡ ችግር ፤ መከራ ፡ ሥቃይ ። ሀሎኩ ፡ ምስሌሁ ፡ አመ ፡ ምንዳቤሁ ። ዕለተ ፡ ሕማም ፡ ወምንዳቤ ። ተጻፈቁ ፡ ቦቱ ፡ ምንዳቤያት ፡ ብዙኃት ፡ (መዝ ፡ ፺ ። ሶፎ፩ ፡ ፲፭ ። አፈ ፡ ድ፳፯) ።

**መንደበ** ፤ መነደበ ፤ ዐረደ ፡ ጕደበ ፤ ጕነደበ ፡ ቈረጠ ፤ የመሬት ፡ የዘፍ ። ሰረቀ ፡ ቀማ ፡ ደበደበ ፤ አስ ጨነቀ ፡ አስጠበበ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመንደበ ፡ ፈንታ ፡ አመንደበ ፡ ይላል ፤ አያስኼም ። አመንደብሰሙ ፡ ወኢይ ክሉ ፡ ቀዊመ ። ያመነድብ ፡ ነፍሳተ ። ሰበ ፡ አመንደ ብዎ ፡ ፀሩ ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። ምሳ፲፪ ፡ ፲፫ ። ሚራ፵፯ ፡ ፲፯) ።

**መንደብ** ፤ ምንዳቤ ፤ የምንዳቤ ፡ ቦታ ፤ የሚያ ስጨንቅ ፡ የሚያስጠብብ ፤ ወንበዲያም ። ዐረብ ፡ የጭንቅ ፡ የመከራ ፡ በር ፡ ሲል ፤ ባብ ፡ እልመንደብ ፡ እንዲል ። ይኸ ውም ፡ በአዐክና ፡ በዓደን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ባሕር ፡ ነው ፤ ቀድሞ ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ ከእስክንድር ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ስዊስ ፡ ካናል ፡ ከፍሬቃ ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ ክፍል ፡ በእግር ፡ የሚያሳልፍ ፡ የብስ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ።

**አመንደበ** ፤ አስመነደበ ፡ አስቈረጠ ፤ አስመታ ፡ አስደበደበ ።

**ተመንደበ** ፤ ተመነደበ ፤ ተጨነቀ ፡ ተጠበበ ። ተመንደብኩ ፡ እምዝ ፡ ለሊሃ ። ይትመነደቡ ፡ ከመ ፡ ዘ ይመውት ። ዘብዙኅ ፡ ተመንደበ ፡ ብዙኅ ፡ ይትሜ የኑ ፡ (፪ነገ ፡ ፳፬ ፡ ፲፬ ። ኢሳ፶፱ ፡ ፲ ። ሚራ፴፩ ፡ ፲፭) ።

**ምንዱብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ድብት) ፤ በቁሙ ፤ የተጨነቀ ፡ የተጠበበ ፤ ከተያዘበት ፡ ጭንቅ ፡ መውጫ ፡ ማምለጫ ፡ ያጣ ፤ ድኻ ፡ ችጉር ። ዘሰ ፡ ምንዱብ ። ምንዱበ ፡ ይነብር ። ረዳኤ ፡ ምንዱባን ። ነፍስ ፡ ም ንድብት ፡ ወጥውቅት ፡ (፩ነገ ፡ ፳፱ ፡ ፪ ። ሚራ፴፯ ፡ ፴ ። ቅዳ ፡ መስተ) ።

**ናዳብ** ፤ ዐሚናዳብ ፤ (ዕብ) ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ፀሚ ፡ ሕዝቤ ፡ ወገኔ ። ናዳብ ፡ ፈቃደኛ ፡ ቅን ፡ ቸር ፤ በፈቃዱ ፡ ለግዜር ፡ አምኃና ፡ መሥዕት ፡ የሚሰጥ ፤ ከሥር ፡ አንድ ፡ አውጥቶ ፡ ደግሞ ፡ ከዘጠኙ ፡ የሚያወጣ ፡ (፩ዜና ፡ ፮ ፡ ፫ ፡ ፳፱) ።

**ነዲድ** ፤ ዶት ፤ (ነደ ፤ ነደደ ፡ ይነድድ ፡ ይንድድ ። ዕብ ፡ ናዳድ ፤ ተናደ ፡ ሸሸ ፡ ዘለለ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ ፡ ታወከ ፤ የፍርሀት ፡ የቀኑጣ) ፤ መንደድ ፡ መናደድ ፡ መቃጠል ፤ በግ ፡ ቱግ ፡ ቢ ፡ ማለት ፤ የእሳት ፡ የመዐት ፡ የፍቅር ። እመ ፡ ነፋሳ ካሣ ፡ ለፍሕም ፡ ትነድድ ። ይነድድ ፡ መዐቱ ። ይነ ድድ ፡ ፍቅሩ ፡ ከመ ፡ እሳት ። ነዱ ፡ በፍትወቶሙ ፡ (ሚራ፳፰ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፴ ፡ ፳፯ ። ሚራ፲ ፡ ፳ ። ሮሜ፩ ፡ ፳፯) ።

**ነዳዲ** ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤ ነዳጅ ፡ የሚ ነድ ፡ የሚቃጠል ፤ ነዳጅ ፡ ተቃጣይ ። ሕፍኣመ ፡ እሳት ፡ ነዳዲ ። ንባበ ፡ ግዘት ፡ በማይ ፡ እምልባንክ ፡ ነዳዲ ። ማኅቶት ፡ ነዳዲ ። ፍትወት ፡ ነዳዲት ፡ (ስንክ ፡ መስ፳ ። ታኅ፳ ፡ ፳፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፳) ።

**ንዱድ** ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ድድት) ፤ የነደደ ፡ የተቃጠለ ፤ ሙቅ ፡ ትኵስ ፤ ፍሙ ፡ ተናዳጅ ። ኩነ ፡ ን ዱደ ፡ በእሳተ ፡ መንፈስ ፡ ከመ ፡ ታውዕዮ ፡ ለፍት ወት ፡ እኪት ። ንዱዳነ ፡ ልብ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፭ ። ፩ጢሞ ፡ ፱ ፡ ፪) ።

**ንደት** ፤ መንደድ ፡ መናደድ ፤ መቃጠል ፤ መቈ ጣት ፤ ቍጣ ፡ ብስጭት ። ከመ ፡ ንደተ ፡ እሳት ። ይቈ ርር ፡ ዘውስተ ፡ ልቡ ፡ ንደት ፡ (ዘፀ፳፱ ፡ ፲፯ ። ዮሴፍ) ።

**ነድ** ፤ በቁሙ ፡ ነዲድ ፡ ነበልባል ፡ ላንቃ ፤ የእ ሳት ፡ ልሳን ፡ ወላፈን ። በአምጣነ ፡ ዕፀ ፡ ለእሳት ፡ የዐቢ ፡

ንዱ ። ቃሉ ፡ ከመ ፡ ነድ ፡ ያውዒ ። አዕይንቲሁ ፡ ከመ ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ (ሚራ፳፰ ፡ ፲ ። ፵፰ ፡ ፩ ። ራእ፩ ፡ ፲፬) ።

**ንዳድ** ፤ በቁሙ ፤ ወባ ፡ አሶ ፡ የቈላ ፡ በሽታ ፡ የሚያሞቅ ፡ የሚያተኵስ ፤ አሰውን ፡ እይ ። ሕማመ ፡ ንዳድ ፡ (ሙ ፡ ፈ) ።

**አንደደ** ፤ አነደደ ፥ አስነደደ ፤ አቃጠለ ፤ ለኰሰ ፡ አያያዘ ። ወያነድዶሙ ፡ ወይን ። ኢየአክል ፡ ሊባኖስ ፡ ለአንድዶ ። ነበልባል ፡ ዘአንደድክሙ ፡ (ኢሳ፶ ፡ ፲፩ ። ፵ ፡ ፲፮ ። ፶ ፡ ፲፩) ። እንድድ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ እሳት ፡ የማፅደናትን ፡ ዛሕል ፡ እንዲያሶግድና ፡ እንዲያጠራ ፥ ርሱም ፡ መንጽሔ ፡ አልባስ ፡ ነውና ፤ ምስጢሩ ፡ ይህን ፡ ያሳያል ።

**መንድድ** ፤ (ብ ፡ መናድድ) ፤ ማናደጃ ፡ ማቀጣጠያ ፤ ቅባትነትና ፡ መጣብቅነት ፡ ያለው ፤ እሳትን ፡ የሚያገን ፡ የሚያስቈጣ ፤ እንደ ፡ ጋዝ ፡ እንደ ፡ ዝፍት ፡ ያለ ። አዘዘ ፡ ያንድዱ ፡ እቶነ ፡ ወይደዩ ፡ ውስቴቱ ፡ መናግንተ ፡ ጽህርት ፡ ወመፍልሕተ ፡ እሳት ፤ ፒሳ ፡ ወፓፒራ ፡ ወሥብሐ ፡ ወመዓረ ፡ ግራ ፡ ወአስፈሊጠ ፡ ወክብሪተ ፡ ወሰሎ ፡ መናድደ ፡ ጽህርት ፡ (መቃ ፡ ፲፱) ።

**ምንዳድ** ፤ መንደጃ ፡ ማንደጃ ፤ የእሳት ፡ ቦታ ፡ እቶን ፡ ምድጃ ። ወደይዎሙ ፡ ውስተ ፡ ምንዳደ ፡ እሳት ፡ ወአውዐይዎሙ ። ኢይደልዎ ፡ ለአሐዱ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ እቶነ ፡ አው ፡ ምንዳደ ፡ ብለኔ ፡ ኀበ ፡ ገቦ ፡ ሐጼር ፡ በዘይነክያ ፡ እሳቱ ፡ (ስንክ ፡ ኀዳ፳፱ ። ታኅ፳ ። የካ፲፫ ። ሠኔ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

**ተናደደ** ፤ በቁሙ ፤ ተያያዘ ፡ ተቀጣጠለ ፥ ተሟሟቀ ። ትትናደድ ፡ ሐኑረ ፡ አፍቅሮ ፡ ውስተ ፡ ነፍሱ ። ወትቈርር ፡ ተናድዶቶሙ ፡ (ፊልክ ፡ ፸፯ ። ፳) ።

**ነድሐ** ፤ (ዕብ ፡ ናዳሕ) ፤ ቡንይል ፡ ገፋ ፤ ገፈተረ ። ወጋ ፡ ደደቀ ፡ አናፈረ ፤ አነካ ፡ አጓን ፤ የበሬ ፡ የጐሽ ። ወነድሖ ፡ ሳሕም ፡ (፪ነገ ፡ ፮ ፡ ፯) ፡ ነፅንን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ነድየ** ፤ ዮት ፤ (ነድየ ፤ አው ፡ ነደየ ፡ ይነዲ ፡ ይንደይ ፡ ዲ) ፤ መንደይ ፡ መደኽየት ፤ ነዳይ ፡ ድኻ ፡ መኾን ። ነድይኒ ፡ ወብዒልኒ ። ከመ ፡ ነዲይየ ፡ ኢይስርቅ ። ቦኑ ፡ ዘሎሙ ፡ ይነድዩ ፡ በሀኬቶሙ ። ዘነድየ ፡ በጊዜሁ ፡ ይብዕል ፡ ወዘብዕለ ፡ በጊዜሁ ፡ ይነዲ ፡ (ሚራ፲፩ ፡ ፲፬ ። ምሳ፳፬ ፡ ፴፬ ። አፈ ፡ ተ፲፩ ። ድጓ) ።

**ነዳይ** ፤ (ይት ፡ ያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፡ ድኻ ፡ ችጋረኛ ፤ አይቶ ፡ በጣ ፤ ዘዋሪ ፡ ቀላዋጭ ። ብፁዕ ፡ ዘይሌቡ ፡ ላዕለ ፡ ነዳይ ። ብእሲት ፡ ነዳይት ። ነዳያን ፡ በመንፈስ ፡ (መዝ ፡ ፵ ። ማር፲፬ ፡ ፵፫ ። ማቴ፭ ፡ ፫) ።

**ንዴይ** ፤ (ዲት ፡ ድይት) ፤ የደኸየ ፡ የተቸገረ ፡ ችጉር ፡ ወራዳ ። ከነ ፡ ንዴየ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ብዕልኒ ። ንዴይ ፡ ወድኩም ፡ ሥርዐት ፡ (ቄር) ።

**ንድየት** ፤ ንዴት ፤ መደኽየት ፤ ድኽነት ፡ ችጋር ፡ ዕጦት ፤ ነሳር ፡ ውርደት ። ኢተሀበኒ ፡ ብዕለ ፡ ወንዴተ ። ምንት ፡ ውእቱ ፡ ንዴት ፡ ዘእንበለ ፡ ከዊነ ፡ ሰብእ ። ንዴተሰ ፡ ወትሕትና ፡ እንቲኣሁ ፡ ንብል ፡ በተሰምዮ ፡ ሐዋርያ ፡ ወሊቀ ፡ ካህናት ።

**አንደየ** ፤ አደኸየ ፡ አስቸገረ ፤ አዋረደ ። አንደየ ፡ ርእሶ ፡ እንዘ ፡ ባዕል ። እግዚ ፡ ያነዲ ፡ ወያብዕል ። ዘርከዮቶሙ ፡ ወአንድዮቶሙ ። አፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ውእቱ ፡ አንዳዬሁ ፡ ለብእሲ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፱ ። ፩ነገ ፡ ፪ ፡ ፯ ። ፊልክ ፡ ፻፵፭ ። ፈላስ) ።

**ነዲል** ፤ ሎት ፤ (ነደለ ፡ ይነድል ፡ ይንድል) ፤ መንደል ፡ መብሳት ፡ መሸንቈር ።

**ተነድለ** ፤ ተነደለ ፡ ተበሳ ፡ ተሸንቈረ ፤ ነዳላ ፡ ኾነ ።

**ንዱል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ድልት) ፤ የተነደለ ፤ ብስ ፡ ነዳላ ፡ ሽንቍር ።

**ንድለት** ፤ (ታት) ፤ መነደል ፡ መነደል ፡ አነዳደል ፡ ንድሎሽ ። ዋሻ ፡ ፍርኵታ ፤ ሠንጣቃ ፡ ብስ ፡ ነዳላ ፡ ፪ ፡ ደጃፍ ፡ ያለው ፤ እንደ ፡ ዋልድባው ፡ ደብር ፡ እንደ ፡ ሰቋር ፡ ያለ ። ንድለታተ ፡ ምድር ፡ ወንቅዐታተ ፡ ኰኵሕ ፡ (ሔኖ፶፯ ፡ ፪) ።

**መንደል** ፤ መንደያ ፤ መብሻ ፡ መሸንቈሪያ ።

**መንደለ** ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ግ) ፤ መነደለ ፤ ፀጠበ ፡ አጠራ ፡ ወለወለ ፥ አደረቀ ፤ የወጭት ፡ የገላ ።

**መንዲል** ፤ (ላት ፤ መናዲል) ፤ በቁሙ ፤ መመንደያ ፡ ማጠቢያ ፡ ማበሻ ፡ መወልወያ ፤ ጨርቅ ፡ ቍራጭ ፡ ታላቅ ፡ ማረሚያ ፤ የሥራ ፡ ልብስ ፡ ፊደ ። መክፈንና ፡ ለንጽን ፡ እይ ። ቀነተ ፡ መንዲለ ፡ ወኀፀበ ፡ እግረ ፡ አርዳኢሁ ። ትኩን ፡ ላዕለ ፡ መታክፍቲሆሙ ፡ መንዲል ፡ ስፍሕት ። ይልበስ ፡ ካህን ፡ መንዲለ ፡ ዘቦቱ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ። ገብርኤል ፡ ዘጸዳለ ፡ ብርሃን ፡ መንዲሉ ። መንዲላት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፩ ፡ ፳ ። ደራሲ ። ስንክ ፡ ግንቦ፩) ።

**ነድዐ** ፤—ነዳ ፡ ወሰደ ፤—ነዲእ ፡ ነድአ ።

**ነዲፍ** ፤ ፎት ፤ (ነደፈ ፡ ይነድፍ ፡ ይንድፍ ። ዐረ ፡ ነደፈ ፡ አጠራ ፤ ነዲፍ ፡ ጥሩ ። ዕብ ፡ ናዳፍ ፤ አዘራ ፡ አነፈሰ) ፤ መንደፍ ፤ መጠዝጠዝ ፤ የደጋን ፡ የጥጥ ፤ የንብና ፡ የተርብ ፡ የባብና ፡ የጊንጥ ። ነደፋክሙ ፡ ከመ ፡ ንህብ ። ነደፉ ፡ አፍራሰ ። ብእሲት ፡ ትትሜሰል ፡ በዐቅራብ ፡ ዘይነድፍ ፡ ሰብአ ፡ (ዘዳ፩ ፡ ፵፬ ። ስንክ ፡ ጥር፲፰ ። ፈላስ ፡ ገ፲፮ ። ራእ፱ ፡ ፭) ።

—፤ መወርወር ፤ መሙጋት ፤ የቀስት ፡ የፍላጻ ። ኢይነድፍ ፡ ውስቴታ ፡ ሐጸ ። ነዲፍ ፡ በይምን ፡ ወበፀግም ። ነዲፈ ፡ ቀስት ፤ ውርወራ ፡ (ኢሳ፴፯ ፡ ፴፫ ። ፩ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳፱) ። ንድፍ ፡ ጸላኤ ። ኢትትሀከዩ ፡ ነዲፎታ ። ነደፈኒ ፡ ኵልያትየ ፡ በአሕጻሁ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፰ ። ኤር፳፯ ፡ ፳፱ ። ሰቈ፫ ፡ ፲፫) ።

—፤ መበገር ፡ ማመልከት ፡ መሣል ፡ ሐረግ ፡ መጣል ፤ ያናጢ ፡ የገንቢ ፡ የጣፊ ፡ ያንጥረኛ ።

**ነዳፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ደፍት) ፤** በቁሙ ፤ የሚነድፍ ፡ ወርዋሪ ፡ ወጊ ፡ ባለቀስት ። ሐጸ ፡ መስተቃትል ፡ ነዳፊ ። ረከብዎ ፡ ነዳፍያን ፡ በነዲፍ ። ወፃፍያን ፡ ወነደፍት ፡ ሐጽ ፡ (ኤርሟ፷ ፡ ፱ ። ፩ዜና ፡ ፲ ፡ ፫ ። ፪ዜና ፡ ፲፬ ፡ ፰) ።

**ምንዳፍ ፤ (ፋት) ፤** መንደፊያ ፤ መወርወሪያ ፡ ቦታ ፡ ፍላጻው ፡ ተንድፎ ፡ የሚያርፍበት ። መጠነ ፡ አሐቲ ፡ ምንዳፊ ፡ ሐጽ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፪ ። ዘፍ፳፩ ፡ ፲፮) ።

**አንደፊ ፤** አስነደፈ ፤ አሶጋ ፡ (ስንክ ፡ ሐም፳፰) ።

**ተነድፈ ፤** ተነደፈ ፤ ተወረወረ ፡ ተወጋ ። ይጌጉእ ፡ ዘተነድፈ ፡ ይምላኅ ፡ ሐጸ ። ሀየል ፡ ዘተነድፈ ፡ ወተሀይደ ፡ ክብዶ ። ተነደፎሙ ፡ በፍቅሩ ። አውፅአኒ ፡ እምውስተ ፡ ቀትል ፡ እስመ ፡ ተነደፍኩ ፡ (ሢራ ፲፬ ፡ ፲፪ ። ምላ፯ ፡ ፳፫ ። ዮሴፍ ። ፫ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፴፬ ። ማሕ፪ ፡ ፳) ።

**ንዱፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ድፍት) ፤** የተነደፈ ፡ ንድፍ ፤ የተወጋ ፡ ውጋ ። ንዱፍ ፡ በሐጽ ። ንድፍት ፡ አነ ፡ በፍቅሩ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳፭ ። ማሕ፭ ፡ ፰) ።

**ንድፍት ፤** የበቅሎ ፡ በሽታ ፡ ቆሎ ፡ የሚገድል ።

**ንድፈት ፤** መንደፍ ፡ መንደፍ ፡ አነዳደፍ ፡ አወጋግ ፤ ነደፋ ፡ ውጊያ ። ውግታት ፤ ቍስል ። ሐመ ፡ ፈድፋደ ፡ እምንድፈት ። ሀለወ ፡ ይትፌወስ ፡ ንድፈቶ ፡ ንበ ፡ ነደፍዎ ፡ ሶርያ ፡ (፩ነገ ፡ ፴፩ ፡ ፫ ። ፬ነገ ፡ ፱ ፡ ፲፯) ።

**ተናደፈ ፤** ተወራወረ ፡ ተዋጋ ፤ ተቋሰለ ። ተመዩጠከ ፡ መንጸረ ፡ ትትናደፈነ ፡ ሰእሰ ፡ ምእነ ፡ ወበአሐዳ ፡ ቅንአትከ ፡ ትፈቱ ፡ ታቍስለነ ፡ (ተረ ፡ ቄር፰) ።

**አስተናደፈ ፤** አናደፈ ፤ አስማማ ፡ አመሳሰለ ፡ አስተካከለ ፡ ሕንጻውን ፡ ከንድፉ ፡ ከቢጋሩ ፡ ጋራ ። አንኅሰ ፡ ሄሮድስ ፡ መቅደሰ ፡ እስከ ፡ መሠረቱ ፡ ወአስተናደፈ ፡ መሠረታቲሁ ፡ በምጣኔ ፡ ሕንጻ ፡ ቀዳማዊ ፡ (ዮሴፍ) ። በማረረና ፡ በመሥረት ፡ ፈንታ ፡ አስተናደፍኩ ፡ መሠረት ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ አያስኝም ፡ (፩ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲) ።

**ነዲቅ ፤ ቆት ፤ (ነደቀ ፡ ይነድቅ ፡ ይንድቅ ። ሐነጸ ፤ ጠቀመ ፤ ኀፈደ) ፤** መንደቅ ፡ መሥራት ፤ መመሥረት ፡ በመሠረት ፡ ላይ ፡ መናበ ፡ መጥቀም ፡ መገንባት ፡ ማጋጠም ፤ ድንጋዩን ፡ በኖራ ፡ በጭቃ ፡ ማዛመድ ፡ ማዋሐድ ። ነደቃ ፡ ለይእቲ ፡ ዐፀም ፡ ወረሰያ ፡ ብእሲተ ። ነደቃ ፡ ለነነዌ ። ንንድቅ ፡ ሀገረ ፡ ወማኅፈደ ። ትደጉ ፡ ነዲቆታ ፡ ለሀገር ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፳፪ ። ፲ ፡ ፲፩ ። ፲፩ ፡ ፬ ፡ ፰) ። መብሳት ፤ መንደል ።

**ነዳቂ ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት ፤ ደቅት) ፤** በቁሙ ፤ የሚነድቅ ፡ የሚገነባ ፡ ገንቢ ፤ የመሐንዲስ ፡ በታች ። እንተ ፡ አንተ ፡ ሰሊከ ፡ ኬንያሃ ፡ ወነዳቂሃ ። እብን ፡ ዘመነንዋ ፡ ነደቅት ። ነደቅተ ፡ አረፍት ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ ። መዝ ፡ ፻፲፯ ። ፩ዜና ፡ ፲፬ ፡ ፩) ።

**ተነድቀ ፤** ተነደቀ ፡ ተገነባ ፤ ታነጠ ፡ ተሠራ ። ኤብሮን ፡ ተነድቀት ። ሶበ ፡ ተነድቃ ፡ እልኩ ፡ እአብን ። ደብር ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ተነድቀት ፡ ሀገሮሙ ፡ (ዘኍ ፲፫ ፡ ፳፪ ። ሄርማ ፡ ገ፳፰ ። ሉቃ፬ ፡ ፳፱) ።

**ንዱቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ድቅት) ፤** የተነደቀ ፡ የተገነባ ፡ ግንብ ። እንበለ ፡ ንዱቅ ፡ ቤት ፡ ወእንበለ ፡ ሕኑጽ ፡ ማኅደር ፡ (ስንክ ፡ የካ፳፰ ። ዘኍ፳፭ ፡ ፰) ።

**ንድቀት ፤** መን(ነ)ደቅ ፤ አሠራር ፡ አነዳደቅ ፤ ንድቂያ ። ንድቀት ፡ ወመጋብርት ፡ ለማኅደር ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፰) ።

**ንድቅ ፤ (ቃት) ፤** በቁሙ ፤ በመሠረት ፡ ላይ ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ግንብ ፡ ናስ ፤ የቤት ፡ የቅጥር ። እሚንሰ ፡ መሠረት ፡ ይእቲ ፡ ወካልአኒሃ ፡ ሕንጻ ፡ ወንድቅ ። ይትሐነጽ ፡ ቤት ፡ እግዚ ፡ በንድቅ ፡ ክቡር ። ንድቁ ፡ ወእበኒሁ ። ክመ ፡ ንድቀ ፡ ክረምት ። ንድቅ ፡ ጽኑዕ ፡ ዘቦቱ ፡ ቅጽር ። ንድቀ ፡ ማኅፈድ ፡ (አፈ ፡ ወር ። ጦቢ፲፱ ፡ ፳ ። ማር፲፫ ፡ ፩ ። ሢራ፳፩ ፡ ፰ ። መቃ ፡ ገ፳፬ ።፡ ዮሴፍ) ።

**መንደቅ ፤ (ብ ፡ መናድቅ) ፤** ዐራዳ ፡ ሠንጣቃ ፤ ብስ ፡ ሽንተኍር ፡ ነዳላ ፤ የተራራ ፡ የንፈጣት ፡ የደንጊያ ፡ የሸክላ ፡ ወይም ፡ የሌላ ። አሴቦን ፡ ዘቦ ፡ መንደቅ ። ዘይፈኑ ፡ እስኪት ፡ ውስተ ፡ መንደቅ ። ወይወስብ ፡ ምድረ ፡ ነዲቅ ፡ (ዘዳ፱ ፡ ፵፱ ። ሲኖ ዶ ። ታምር) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በመንደቅ ፡ ፈንታ ፡ መንድቅ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፤ አያስኝም ።

**ናሁ ፤ (ነ ፡ ነዮ ፡ ነዋ ። ሰብ ፡ ሄን ፤ ሂኔህ ። ዐረ ፡ ኢነ) ፤** ንኡስ ፡ አገባብ ፤ የቅርብ ፡ ያጠገብ ፡ ያጸፋ ፡ የጨበጣ ፡ ቃል ፤ አኹን ፡ ቶሎ ፡ እንሆ ፡ ይኸው ፡ ይኸውና ። የነን ፡ አፈታት ፡ እይ ፤ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ርሱ ፡ ነው ። ናሁ ፡ ነዐርግ ፡ ኢየሩሳሌም ። ወናሁ ፡ ሳድስ ፡ ዝንቱ ፡ ወርኃ ። ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ በደመና ፡ ሰማይ ፡ (ማር፲ ፡ ፴፫ ። ሉቃ፩ ፡ ፴፮ ። ራእ፩ ፡ ፯) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በሊቃውንት ፡ ውስጥ ፡ ፍቹው ፡ እንደ ፡ እስመ ፡ ና ፡ ይኾናል ። ወሥጋሂ ፡ እምድኅረ ፡ ትንሣኤሁ ፡ ከነ ፡ ዘኢይማስን ፡ ወዘኢይመውት ፤ ናሁ ፡ ከነ ፡ አሐደ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ አትና) ። ዳግመኛም ፡ ሚ ፡ ምንት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ናሁ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ናሁ ፡ ሠናይ ፡ ወናሁ ፡ አዳም ፡ (መዝ ፡ ፻፴፪) ። ደግሞም ፡ ነያ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ናሁ ፡ አመትከ ። ናሁ ፡ ድንግል ። ወናሁ ፡ ኤልሳቤጥኒ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። ርእ ፡ ጽዋንሃ ፡ ባለውም ፡ ናሁ ፡ ጽዋን ፡ ይላል ፡ (ኢሳ፴፫ ፡ ፰) ።

**ንሂብ ፤ ቦት ፤ (ነሀበ ፡ ይነህብ ፡ ይንህብ ። ወሀበ ። ዐነገ) ፤** መናብ ፤ መሥራት ፡ መቀጥቀጥ ፤ ማፍሰስ ፡ ማቅለጥ ፤ የወርቅ ፡ የብር ፡ የማዕደናት ፡ ኹሉ ። ይነህቡ ፡ ሎሙ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅል ። ሰአሴቶ ፡ ከመ ፡ ይንህብ ፡ ላቲ ፡ አዕኑገ ፡ ለአእዛኒሃ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ሐም፲) ።

—፤ ማነብ ፤ ንቦች ፡ ማርባት ፡ የንብ ፡ ጠባይ ፡ ማወቅ ፤ ያናቢ ። መቅሠም ፡ መምጠጥ ፤ ማጣም ፡ ማጣፈጥ ፤ የን-

ህብ ። የሥራውን ፡ ስልት ፡ መለየት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምስጢሩ ፡ ከመሥራት ፡ አይወጣም ።

**ነሃቢ ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ሀብት) ፤** ባለጅ ፤ ብረት ፡ ሠሪ ፡ ቀጥቃጭ ፡ ብር ፡ አፍሳሽ ፡ አንጥረኛ ፡ ጃን ፡ ሸላሚ ፡ (አናቢ ፤ ቀጣሚ) ። ነሃቤ ፡ ኅጺን ። ነሀብተ ፡ ብሩር ፡ ወወርቅ ። ነሃቤ ፡ ምስል ፡ (፩ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱ ። ጥበ፲፭ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫) ።

**ምንሃብ ፤ (ባት) ፤** መሥሪያ ፡ ከውር ፡ አጕደ ፡ ምድጃ ፤ ወይም ፡ መግሪያ ፡ ፋብሪቃ ። ነሃቢ ፡ ዘይነብር ፡ ኀበ ፡ ምንሃብ ። ጢስ ፡ ምንሃብ ። ዘከመ ፡ ያስተማኒ ፡ ምብዓሎ ፡ ወምንሃቦ ። ከመ ፡ እሳት ፡ ምንሃብ ፡ ዘአርሰንዎ ፡ በብዙኅ ፡ ምብኳሕ ፡ (ሢራ፴፰ ፡ ፳፰ ። አርጋ ፡ ፪) ።

**አንሀበ ፤** አስናበ ፤ አሠራ ፡ አስቀጠቀጠ ። ማሕረስክሙ ፡ አንህቡ ፡ ለመጥባሕት ፡ ወማዕጺደክሙ ፡ አግብሩ ፡ ረምሐ ። ኩናት ፡ ዘሎቱ ፡ አንህቡ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ቅዳ ፡ ማሩ) ።

**ተንሀበ ፤** ተናበ ፤ ተሠራ ፡ ተቀጠቀጠ ፤ ፈሰሰ ፡ ቀለጠ ።

**ንሁብ ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ህብት) ፤** የተናበ ፡ የተሠራ ፤ ፍስ ፡ ቅጥቅጥ ።

**ንህበት ፤** መሥራት ፤ ሠሠራት ፤ አሠራር ፤ ሥራ ፡ ቅጥቀጣ ። ንዋየ ፡ ንህበት ፡ ሕው ፡ ልብስ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵) ።

**ንህብ ፤ (ብ ፡ አንሃብ ፤ አንህብት ። ዐረ ፡ ኑብ ፤ ነሕል ። ዕብ ፡ ድቦራ፡፱) ፤** በቁሙ ፡ ንብ ፡ ያበባ ፡ ዝንብ ፡ ጽጌያትን ፡ ኹሉ ፡ የምትቀሥም ፡ የማር ፡ የሰፈፍ ፡ ዐበዛ ፡ ወይም ፡ አንጥረኛ ። ሑር ፡ ኀበ ፡ ንህብ ፡ ወአእምር ፡ ከመ ፡ መስተገብርት ፡ ይእቲ ። እምዘሉ ፡ አዕዋፍ ፡ ትንእስ ፡ ንህብ ። ፀንስ ፡ እንበለ ፡ ሩካቤ ፡ ከመ ፡ ንህብ ፡ ዘእምቃለ ፡ ንባብ ። አንሃብስ ፡ ይፀንሳ ፡ በምዕር ፡ ሶበ ፡ አንዘረት ፡ ንግሥትን ፡ ወታነዝር ፡ እግዝእትን ፡ ለአንህብት ፡ (ምሳ፮ ፡ ፰ ። ሢራ ፲፩ ፡ ፫ ። ቅዳ ፡ ሕር ። አዋል) ።



ንህብ ፤

**ናህብ ፤ (ባት) ፤** ድንጋግ ፡ ወደብ ፡ ገደብ ፤ ውሃ ፡ ያረደው ፡ የጐደበው ፡ በውስጡ ፡ ማገዶማና ፡ ማን ፡ የሚገኝበት ። የወንዝ ፡ ዳር ፡ ሰብል ፡ ንቦች ፡ የሚቀሥሙት ፤ ወይም ፡ የውሃው ፡ ጐርፍ ፡ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ ጠራርጎ ፡ የሚወስድ ። እምናህብ ፡ ፈለግ ፡ (ኢሳ፳፯ ፡ ፲፪) ።

**ነሀገ ፤ (ዕብ ፡ ናሀግ ። ዐረ ፡ ነሀጀ ፡ ገ) ፤** ነዳ ፡ አስማራ ፤ ወሰደ ፡ መራ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በነሀገ ፡ ፈንታ ፡ አንሀገ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ኄርማ ፡ ገ፺፯) ። ንህክና ፡ መህክ ፡ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**ንህይ ፤ ዮት ፤ (ንህየ ፤ አው ፡ ነህየ ፡ ይንሂ ፡ ይንህይ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ናሕ) ፤** ማረፍ ፡ መርጋት ፤ መጸናናት ፤ እፎይ ፡ ማለት ፤ ከሐዘን ፡ ከሁከት ፡ ከመከራ ፡ ወይም ፡ ከሥራ ። ይንህዩ ፡ ትኩዛን ። ወትንህይ ፡ ነፍስ ፡ እምአበሳሃ ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ ። ግሩ) ።

**ነሃዩ ፤ (ዩት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤** ያረፈ ፡ የሚያርፍ ፡ ዐራፊ ፤ እፎይ ፡ ባይ ።

**ንሁይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሂት) ፤** ያረፈ ፡ የረጋ ፡ እህ ፡ እፎይ ፡ ያለ ። ከመ ፡ የዐርፍ ፡ ነፍሰሙ ፡ ንሁየ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ናህይ ፤** ፍጹም ፡ ዕረፍት ፡ እፎይታ ፤ ከህድአት ፡ በቀር ፡ ሁከት ፡ የሌለበት ። ሀባ ፡ ናህየ ፡ ወዕረፍተ ፡ ለዛቲ ፡ ነፍስ ። አልብየ ፡ ናህይ ። ወለእለሂ ፡ ይላሕዉ ፡ ናህየ ፡ ወዕረፍተ ፡ ጸጉ ፡ (ግንዘ ። ቀሌ ። ቅዳ ፡ መስተ) ።

**አንህየ ፤** አሳረፈ ፡ ዕረፍት ፡ ሰጠ ፤ እፎይ ፡ አሰኘ ። አንሂ ፡ ሎሙ ፤ አንሂ ፡ ለዘላ ፡ ነፍስ ፡ ፀብለት ። አልቦ ፡ ዘያንህየኒ ፡ አንህዮ ፡ (ቅዳ ። ሰቈ፩ ፡ ፳፩ ። አርጋ ፡ ፩) ።

**መንህዪ ፤ መንህይ ፤ መናህይ) ፤** የሚያሳርፍ ፤ አሳራፊ ፡ ዕረፍት ፡ ሰጪ ፡ አይዞኽ ፡ ባይ ፡ አጽናኝ ፡ አስተዛዛኝ ። መንሂት ፡ ለስራሕየ ። መናህየ ፡ ወመናዝዘ ፡ ለሰብእሙ ፡ ከዊነከ ፤ መንፈስ ፡ ናዛዜ ፡ ወመናህየ ፡ ለሰብእሙ ፡ ፈኑ ፡ (አርጋ ፡ ፬ ። ግንዘ) ።

**ንህክ ፤ (ንሂክ ። ንእክ) ፤** ዐዘነ ፡ ተከዘ ፤ ዐሰበ ፡ ተወዘወዘ ፤ እህህ ፡ አለ ። አልብክሙ ፡ ንሂክ ፡ እምኔነ ፤ አላ ፡ ንህክሙ ፡ በልብክሙ ። ከመ ፡ በፍሥሓ ፡ ይግበርዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ወኢይንህኩ ። ከርሥየ ፡ ንህክተ ፡ ለትካዘ ፡ ዝ ፡ ዓለም ፡ (፪ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ። ዕብ፲፫ ፡ ፲፯ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ናህክ ፤** ሐዘን ፡ ልቅሶ ፤ ሐሳብ ፡ እህህታ ። እስመ ፡ ብዙኅ ፡ ናህክየ ። ኅልቀ ፡ እንከ ፡ ሕማም ፡ ወትካዝ ፡ ወናህክ ፡ (ሰቈ፩ ፡ ፳፪ ። ኢሳ፶፩ ፡ ፲፩) ። ሀና ፡ አተወራረሾች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ በናህክ ፡ ፈንታ ፡ ናእክ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ ፩ ፡ ነው ፤ ንእክን ፡ እይ ።

**አንሀከ ፤** አሳዘነ ፡ አስተከዘ ። ሰላም ፡ ለከርሥከ ፡ ምንዳቤ ፡ ረኀብ ፡ ዘኢያንህኮ ፡ (ደራሲ) ።

**ነሀረ ፤ ንህረ ፤ (ዕብ ፡ ናሀር) ፤** ፈሰሰ ፡ ወረደ ፤ ናረ ፡ ዘለለ ፤ ሰኸ ።

**ነሃር ፤** ፈሳሽ ፡ ወንዝ ፡ ኹረት ፤ ፈለግ ፡ ባለብዙ ፡ ውሃ ። ሲያበዛ ፡ ንሃሬም ፤ ንሃሮት ፡ ይላል ። ግእዙ ፡ ውስተ ፡ አፍላግ ፡ ባቢሎን ፡ ባለው ፤ ዕብራይስጡ ፡ ዐል ፡ ንሃሮት ፡ ባቤል ፡ እንዲል ፡ (መዝ ፡ ፻፴፮) ።

**ምንሃር ፤ መንሀር ፤** መስኖ ፤ የመስኖ ፡ ውሃ ፡ ከወንዝ ፡ ተከፍሎ ፡ በቦይ ፡ በመትረብ ፡ ወደ ፡ ተክል ፡ ወደርሻ ፡ የሚገባ ። ወከመ ፡ ምንሃር ፡ ቦእኩ ፡ ውስተ ፡ ገነት ። ሰላም ፡ ለከሣድከ ፡ ዘተመሰለ ፡ ምንሃረ ፡ በ

አንቅዖ ፡ ሐሊብ ፡ ወማይ ፡ አመ ፡ በመጥባሕት ፡ ተመትረ ፤ (ሚራ፳፱ ፡ ፴ ። ደራሲ) ።

—፤ አሰጅ ፡ እንግዲ ፡ ሥጋ ፡ ልጅ ፡ ከማሕፀን ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ከደምና ፡ ከዛሕል ፡ ከርስሐት ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚወርድ ። ሰይልን ፡ ተመልከት ።

**ንህረ ፤—አንኅረፈ ፤—ንኂር ፡ ንኅረ ።**

**ነዋ ፤ (ነ ፡ ነዮ ፡ ናሁ ፤ ነው) ፤** እንሆ ፤ ይኸው ፡ ይኸውና ። ናሁን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ነዋ ፡ ንጉሥኪ ፡፡ ነዋ ፡ በግዑ ፡፡ ነዋ ፡ ወልድኪ ፡፡ ነዋ ፡ ወንጌሊ ፡ መንግሥት ፡፡ ነዋ ፡ ዝየ ፤ ወነዋ ፡ ከሃ ፡፡ ነወየና ፡ ነዋይ ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ኖብያት ፤—ዜና ፡ መዋዕል ፤—ነበየ ።**

**ነዊኅ ፤ ኖኅ ፤ (ኖኀ ፡ ይነውኅ ፡ ይናኅ ፤ አው ፡ ይንዋኅ ፤ ይኗኅ ፤ ይኑኅ ። ዕብ ፡ ኑዋሕ ። ዐረ ፡ ነሐ ። ሱር ፡ ናሕ ፤ ንህየ) ፤** ማረፍ ፡ መትረፍ ፡ መቅረት ፤ ቢታ ፡ መያዝ ፤ መስፋት ፡ መንሰራፋት ፤ ጢ ፤ ዚ ፡ ብሎ ፡ መዘርጋት ። ይምዳእ ፡ መንፈስከ ፡ ሕየው ፡ ወቅዱስ ፤ ይረድ ፡ ወይንበር ፡ ይኀድር ፡ ወይኑኅ ፡፡ ኢያረምም ፡ ወኢይነውኅ ፤ (ቀዳ ፡ ዮሐ ። ሱቱ ፡ ዕዝ ፩ ፡ ፺፩ ። መጽ ፡ ምስ) ።

—፤ መርዘም ፤ መብዛት ፡ መፈድፈድ ፤ የቁመት ፡ የቍጥር ። ኖኀኩ ፡ ከመ ፡ በቀልት ፡፡ ኖኃ ፡ አዕጹቅየ ፡፡ ከመ ፡ ይኑኅ ፡ መዋዕሊክሙ ፡፡ እመኒ ፡ ኖኀ ፡ መንበርትሙ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡፡ ኖኀ ፡ እምሥዕርት ፡ ርእስየ ፡ ጊጋይየ ፡፡ ወይነውኅ ፡ እምአርዝ ፡ ፍሬሁ ፤ (ሚራ፳፱ ፡ ፲፱ ፡ ፲፮ ። ዘዳ፱ ፡ ፴ ። ጥበ፫ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፴፯ ። ፳፭) ። በኖኀ ፡ ፈንታ ፡ ተነውኀ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ከመ ፡ ፍጹመ ፡ ይኩን ፡ ኀሊናሁ ፡ እንዘ ፡ በሥሉ ፡ በብእ ፡ ይትኔዋኅ ፤ (ኪዳ) ።

**ምንዋኅ ፤ አው ፡ ምኗኅ ፤ ሙናኅ ፤ (ዕብ ፡ ሙናሕ) ፤** ማረፊያ ፡ መጠጊያ ፡ ሰብሳቢ ፡ የቤት ፡ ዙሪያ ፡ (ሕዝ፵፯ ፡ ፲፩) ።

(ተ ፡ ዊ) **ነዊኅ ፤ (ኍን ፤ ነዋኅ ፡ ኍት) ፤** ረዥም ፡ ታላቅ ፡ ምጡቅ ፤ ሰፊ ፡ ብዙ ፡ እጅግ ፡ ሩቅ ። ነዊኅ ፡ የወንድ ፡ ነዋኅ ፡ የሴት ፡ ነው ፤ ጠቢብ ፡ ጠባብ ፡ ዐቢይ ፡ ዐባይ ፡ እንደ ፡ ማለት ። ወከነ ፡ ነዊኀ ፡ በቈሙ ፡፡ አሕባል ፡ ነዊኃን ፡፡ ነዊኀ ፡ መንፈስ ፡፡ ኢድባር ፡ ነዋኃት ፡፡ ለነዋኅ ፡ መዋዕል ፡፡ እስከ ፡ ነዋኅ ፡ ብሔር ፡፡ እስመ ፡ ነዋኅ ፡ ኀበ ፡ አምሠጥከ ፤ (ሰንክ ፡ ማን፲፫ ። ሔኖ፳፩ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ተ ፴፪ ። መዝ ፡ ፺፬ ። ፳ ። ሚክ፬ ፡ ፫ ። ሚራ፳፯ ፡ ፳) ።

**ኑኀት ፤** መርዘም ፡ አረዛዘም ፡ ርዝመት ፡ ረዥምነት ። ይትዓረይ ፡ ቦቱ ፡ ሌሊት ፡ ምስለ ፡ መዓልት ፡ በኑኃት ፡ ወበኀጽረት ፤ (አቡሻ ፡ ፲፱) ።

**ኑኅ ፤ (ኑኃት ፤ እንዋኅ) ፤** ርዝማን ፡ ርዝመት ፡ ምላልነት ፡ ምጥቀት ፡ ርሕቀት ፡ ብዛት ፡ ስፋት ። ኢይትዐወቅ ፡ ኑኃ ፡ ወግድማ ፡ ወኢቆማ ፡፡ ወይከውን ፡ ኑኃ ፡ ለይእቲ ፡ ዕለት ፡ ከመ ፡ ሰብዐቱ ፡ ዓመት ፡፡ እርአይ ፡ ኑኆ ፡ ለሰማይ ፡፡ ስማዕ ፡ ጸሎቶሙ ፡ ውስተ ፡ ኑኀ ፡ ሰማይ ፡፡ ሚ ፡ መጠን ፡ ኑኀ ፡ ትዕግሥቱ ፡ ለእግዚ ፤ (ቀሌ ። ሱቱ ፡ ዕዝ፯ ፡ ፲፯) ። ጸሎ ፡ ምና ። ማንዘ ። መጽ ፡ ምስ) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በ ፡ ሲወድቅበት ፡ ሳይወድቅበትም ፡ ኹሉ ፡ ይኾናል ። አንሰ ፡ እቤ ፡ በኑኀ ፡ መዋዕልየ ፡፡ በኑኀ ፡ ዕለት ፡፡ በኑኀ ፡ ሌሊት ፡፡ ኑኀ ፡ ሠለስቱ ፡ ዕለት ፡፡

**ኖኅ ፤** (ዘፍ፭ ፡ ፳፱) ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ወልደ ፡ ላሜኅ ፤ ዕረፍት ፡ ተረፍ ። ርሱ ፡ ከነልጆቹ ፡ ከሰብእ ፡ ትካት ፡ መከራና ፡ ጥፋት ፡ የሚያርፍ ፡ የሚተርፍ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ቅድማያቱ ፡ ሔኖክ ፡ ገና ፡ ሲወለድ ፡ አስቀድሞ ፡ በትንቢት ፡ መጽሐፉ ፡ ሰይሞታል ። እምድኅረ ፡ መዋዕል ፡ ነሥአ ፡ ወልድየ ፡ ማቱሳላ ፡ ለወልዱ ፡ ላሜኅ ፡ ብእሲተ ፡ ወፀንሰት ፡ እምኔሁ ፡ ወወለደት ፡ ወልደ ፡፡ . . . ወሶበ ፡ ተንሥአ ፡ እምእዴሃ ፡ ለመወልዲት ፡ ከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ወተናገረ ፡ ለእግዚአ ፡ ጽድቅ ፡፡ ወፈርሀ ፡ ላሜኅ ፡ አቡሁ ፡ እምኔሁ ፤ ወጐየ ፡ ወመጽአ ፡ ኀበ ፡ አቡሁ ፡ ማቱሳላ ፡ ወይቤሎ ፡ አነ ፡ ወለድኩ ፡ ወልደ ፡ ውሉጠ ፡፡ ኢኮነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ አላ ፡ ይመስል ፡ ደቂቀ ፡ መላእክት ፡ ሰማይ ፡ ወፍጥረቱ ፡ ካልእት ፡ ወኢኮነ ፡ ከማነ ፡ ወአዕይንቲሁ ፡ ከመ ፡ እግረ ፡ ፀሓይ ፡ ወገጹ ፡ ስቡሕ ፡፡ ወይመስለኒ ፡ ከመ ፡ ኢኮነ ፡ እምኔየ ፡ አላ ፡ እመላእክት ፡ ውእቱ ፤ ወእፈርህ ፡ ከመ ፡ ኢይትገበር ፡ መንክር ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡፡ ወይእዜኒ ፡ እስእል ፡ እምኀቤከ ፡ ከመ ፡ ትሑር ፡ ኀበ ፡ ሔኖክ ፡ አቡነ ፡ ወትስማዕ ፡ እምኀቤሁ ፡ አማነ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ምስለ ፡ መላእክት ፡ ንብረቱ ፡፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ማቱሳላ ፡ ነገረ ፡ ወልዱ ፡ መጽአ ፡ ኀቤየ ፡ . . . ወይቤለኒ ፡ በእንተ ፡ ዳሕቅ ፡ ዐቢይ ፡ መጻእኩ ፡ ኀቤከ ፡ ወበእንተ ፡ ራእይ ፡ ዕጹብ ፡ . . . ፡፡ ወአውማእኩ ፡ አነ ፡ ሔኖክ ፡ ወእቤሎ ፡ ይሔድስ ፡ እግዚ ፡ ሐዲሳተ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤ ወዘንተ ፡ ወዳእኩ ፡ ወርኢኩ ፡ በራእይ ፡ ወአይዳዕኩ ፤ . . . ፡፡ ወዝ ፡ ወልድ ፡ ዘተወልደ ፡ ለክሙ ፡ ውእቱ ፡ ይተርፍ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤ ወሠለስቱ ፡ ደቂቁ ፡ ይድኀኑ ፡ ምስሌሁ ፡ ሶበ ፡ ይመውቱ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ . . . ፡፡ ወይእዜኒ ፡ አይድዕ ፡ ለወልድከ ፡ ላሜኅ ፡ እስመ ፡ ዘተወልደ ፡ ወልዱ ፡ ውእቱ ፡ በጽድቅ ፤ ወጸውዕ ፡ ስሞ ፡ ኖኅ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይከውን ፡ ለክሙ ፡ ተረፈ ፤ (ሔኖ ፡ ፺) ። ፩ኛም ፡ በተረፍነት ፡ ላይ ፡ ነዊኅ ፡ ዕድሜ ፡ ዘርዕ ፡ ዝንዋኅ ፡ የሐዩ ፡ ማለትን ፡ ያሳያል ። ወሐይወ ፡ ኖኅ ፡ እምድኅረ ፡ ማየ ፡ አይኅ ፡ ሠለስተ ፡ ምእተ ፡ ወኀምሳ ፡ ዓመተ ፤ ወኮነ ፡ ኵሉ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለኖኅ ፡ ተስዐቱ ፡ ምእት ፡ ወኀምሳ ፡ ዓመት ፡ ወሞተ ፤ (ዘፍ፱ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱) ። ታላቅ ፡ ዝናም ፡ ደግሞ ፡ ኖኀ ፡ ይባላል ፤ (ዐማርኛ) ።

**አንኀ ፤ አኖኀ ፤ (ያነውኅ ፡ ያንኅ ፤ ያኑኅ) ፤** አሳረፈ ፡ አተረፈ ። አሰፋ ፡ አበዛ ፤ አረዘመ ፤ አስረዘመ ፤ አሳደገ ፤ ዘረጋ ፡ ላከ ፡ ሰደደ ። አነውኅ ፡ መንፈስየ ፡ ላዕሌሆሙ ፡፡ ትዕግሥት ፡ ወአንኆ ፡ መንፈስ ፡፡ አንኅ ፡ ነገረ ፡፡ አነውኆ ፡ ለዐፀ ፡ ኀጺር ፡፡ ኢታንኅ ፡ ሥዕርተከ ፤ አላ ፡ ቅርጽ ፡፡ አንኅ ፡ እዴከ ፡ ወአውፅእ ፡ ሎቱ ፤ አንኅ ፡

ኀቤሁ፡ ምርጕዘከ፤ ወኢታንሣ፡ ሎቱ፡ እዴከ፡ (ስንክ፡ ጳጕ፫ ። እፈ፡ ተፅ ። ማብ፳፡ ፫ ። ሕዝ፲፯፡ ፳፱ ። ዲድ፡ ፭ ። ፊልክ፡ ፻፲፫) ። ያርሕቆ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ያንውኆ፡ ይላል፤ የመላሽ፡ ስሕተት፡ ነው፡ (ኢሳ፮፡ ፲፱) ።

**ተናውኀ**፤ ተራረፈ፤ ተራዘመ፡ ተባዛ፤ ተጋነነ ። ወበጊዜ፡ ተናውኆታ፡ የሀይእ፡ ልብ ። ገሥጾ፡ ለዐርክከ፡ እንበለ፡ ይትናዋኀ፡ መዐት፡ (ማር፡ ይሥ፲፮፡ ፫ ። ሚራ፲፱፡ ፲፯) ።

**ኖጠ**፤ **(ዕብ፡ ናጥ)**፤ ናጠ፡ አናወጠ፤ ወይም፡ ተናጠ፡ ተናወጠ፤ ዞረ፡ ባከነ፤ ወዲያ፡ ወዲህ፡ አለ ። ኖትንና፡ ኖትያን፡ እይ ።

**ነወየ**፤ **(ነውይ፡ ነዋ)**፤ ገንዘበ፤ ገንዘብ፡ አገኘ፤ ገንዘብ፡ አደረገ፤ ወይም፡ ተገንዘበ፤ ገንዘብ፡ ኾነ፤ ተሰጠ፡ ታደለ፤ ነዋ፡ ተባለ ። ተሸሰመ፤ አጌጠ፡ ተጌጠ ።

**ንዋይ**፤ **(ብ፡ ንዋያት ። ዕብ፡ ኖይ፤ ርሱይ፡ ስርግው)**፤ በቁሙ፤ ገንዘብ፡ ጥሪት፡ ቅርስ፤ ወርቅ፡ ብር፡ ከብት ። ንዋየ፡ ዝ፡ ዓለም ። ንዋየ፡ ልቃሕ ። ንዋየ፡ ማሕፀንት፡ (ማቴ፮፡ ፳፱ ። ሚራ፳፭፡ ፳ ። ማ፭፡ ፲፱) ።

—፤ የቤት፡ ዕቃ፤ መማሪያ፡ ከሣር፡ ከንጨት፡ ከማዕደን፡ ከብረት፡ ከጭቃ፡ ከቈርበት፡ ከሌላውም፡ ኹሉ፡ የሚሠራ፤ በየስሙና፡ በያይነቱ፡ መልክ፡ ጌጥ፡ ያለው ። ንዋይ፡ ኅሩይ ። ንዋየ፡ ቤተ፡ እግዚ ። ንዋየ፡ ማእድ፡ (ግብ፱፡ ፲፭ ። ዳን፭፡ ፪ ። ስንክ፡ ግን፲፯) ።

**ንዋየ፡ ገሞሜእ**፤ የሸንበቆ፡ ታንኳ፡ ፍልኳ፡ (ኢሳ፲፰፡ ፪) ።

**ንዋየ፡ ወርቅ**፤ የወርቅ፡ ገንዘብ፤ ወይም፡ መሣሪያ ።

**ንዋየ፡ ውስጥ**፤ የሆድ፡ ዕቃ፤ አንዠት፡ ጕበት፡ ጨጓራ፤ ሌላውም፡ ኹሉ ።

**ንዋየ፡ ሐቅል**፤ የበዳ፡ ጸብት፤ የሰልፍ፡ ዕቃ፡ መሣሪያ ።

**ንዋየ፡ ለብሓ**፤ ሸክላ፤ የሸክላ፡ ዐይነት፡ ዕቃ፡ የሚሰበር ። ንዋየ፡ ማእስ፤ ንዋየ፡ ዕፅ፡ ቢል፤ ከቈርበት፡ ከንጨት፡ የተሠራ፡ ማለት፡ ነው ። ንዋየ፡ ተውኔት፤ ንዋየ፡ ማሕሌት፡ ቢል፡ ግን፤ የዘፈን፡ ዕቃ፤ ለዘፈን፡ ተብሎ፡ የተሠራ፡ እያሰኘ፡ ባለቤትንትን፡ ያሳያል ።

**ነዌ**፤ ንዋያም፤ ገንዘባም፤ ባለብዙ፡ ገንዘብ፤ ዘወትር፡ የሚያጌጥ፡ የሚሸለም ። ወይም፡ በጭራሽ፡ ኖኅ፡ ማለት፡ ነው፤ ይኸውም፡ ሲታወቅ፡ ጽርእና፡ ላቲን፡ ኖኅ፡ ሲሉ፤ ኖኤ፡ እንደ፡ ማለት፡ ኖዬ፡ ይላሉ፤ ኖኅን፡ እይ ። ወሀሎ፡ አሐዱ፡ ባዕል፡ ዘስሙ፡ ነዌ፡ (ማንዘ ። ሉቃ፲፮፡ ፲፱) ። የግእዝ፡ ወንጌል፡ ዘስሙ፡ ነዌ፡ የሚለው፡ ግን፡ መተርጕማን፡ ከግንዘት፡ ወስደው፡ ያገቡት፡ ነው፡ እንጂ፡ የጽርእ፡ አብንት፡ አይደለም ።

**ኖልዎ**፤ **ዎት**፤ **(ኖለወ፡ ይኖሉ ። ዕብ፡ ናሄል)**፤ ማረን፤ እረኛ፡ መኾን፤ መጠበቅ፡ መንዳት፡ ማስምረት፤ ማስቸኰል፡ ማጣደፍ፤ ማሮጥ፡ ማስሮጥ፤ ቶሎ፡ ቶሎ፡ ማስኬድ፤ የከብት፡ የባቡር፡ የሠረገላ ። ረዐየን፡ እይ ።

**ኖላዊ**፤ **(ዊት፡ ውያን፡ ያት፤ ሎት፤ ነዋልው)**፤ የሚጠብቅ፡ ጠባቂ፤ መሪ፡ ንጂ፡ እረኛ፤ ንጉሥ፡ ጳጳስ ። ኖላዊ፡ አባግዕ ። ወጸውዐ፡ ሰብዓ፡ ኖላውያነ ። ኖሎተ፡ እንስሳ ። ወወፅኡ፡ ዐሥርቱ፡ ወክልኤቱ፡ ነዋልው፡ (ዘፍ፬፡ ፪ ። ሔኖ፡ ፹፱ ። ዘኁ፴፪፡ ፩ ። ገድ፡ ተክ) ። በኖለወና፡ በኖላዊ፡ ፈንታ፡ ተኖለወ፡ ተኖላዊ፡ ይባል፤ ስሕተት፡ ነው ። ሴሲተ፡ ተኖልዎሙ ። ምሕረትከ፡ ይትኖልወኒ ። በተኖልዎ፡ ወአስተሐምሞ ። አንሰ፡ ከንኩ፡ አዐቅበከ፡ ወእትኖልወከ፡ እምዘየንሥሥ፡ ሥራዌከ ። ተኖላዊሆሙ፡ ለጸላእተ፡ ክርስቶስ ። ምጽዋት፡ ተኖላዊት፡ ይእቲ፡ ለገባሪሃ፡ (ቅዳ፡ ያዕ ። ቄድር ። እፈ፡ ተፅ፫ ። ዮሴፍ ። አብጥ፡ ፵፱ ። እፈ፡ ተፅ፪) ።

**ተኖለወ**፤ ተጠበቀ፤ ተነዳ፤ ተሰማራ ።

**ኑልው**፤ **(ዋን፡ ዋት፡ ሉት)**፤ የተጠበቀ፤ ጥብቅ፤ ባለረኛ ።

**ኖል**፤ **(ዐረ)**፤ ዐስበ፡ ኖላዊ፤ የባቡር፡ ክራይ፤ ሰውን፡ ከንጓዝ፡ ሰብስቦ፡ ጠብቆ፡ ተሸክሞ፡ የመውሰዱና፡ የመንዳቱ፡ ዋጋ ።

**ናላ**፤ ኑልው፤ በቁሙ፤ አንጎል፡ የራስ፡ ቅል፡ ፍሬ፤ ፈላስፎች፡ ነቅዐ፡ ዘርዐ፡ መካነ፡ አእምሮ፡ የሚሉት ። ሂጶ፡ ውስተ፡ ፍጽሙ፡ ወረከቦ፡ ናላሁ ። እስከ፡ ይውሕዝ፡ ናላሁ፡ እምአንፉ ። ናላ፡ ልምሉም፡ ውእቱ፡ በግዕዝ፡ ጠባይዕ፤ በእንተ፡ ዝ፡ ሐነጸ፡ ፈጣሪሁ፡ ክበበ፡ ዕፀም፡ ከመ፡ እንተ፡ እብን፡ በዲበ፡ ናላ፡ ዘይከውን፡ ጸወነ፡ ወምጽላለ፡ ወአስተጻንዖ፡ ከመ፡ ኢይበቊር ። ይቤልዎ፡ ለሰሎሞን፡ አይቴ፡ መካነ፡ ልቡና፤ ይቤ፡ በናላ ። ዝንጉዕ፡ በአማስኖ፡ ናላሁ፡ (ሚራ፵፯፡ ፱ ። ስንክ፡ ግን፲፱ ። እፈ፡ ተ፳ ። ፈላስፍ፡ ን፡ ፵፱) ። ድማኅ፡ ርእስ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ናላ፡ ይላል፤ የመላሽ፡ ስሕተት፡ ነው ። ሎዱ፡ ይቅብርዋ፡ ወኢረከቡ፡ ዘእንበለ፡ ናላሃ፡ (፱ነገ፡ ፱፡ ፴፭) ።

**ነዊም**፤ **ሞት**፤ **(ኖመ፡ ይነውም፡ ይኑም ። ዕብ፡ ኑም ። ሱር፡ ናም ። ዐረ፡ ናመ)**፤ መተኛት፤ ማንቀላፋት፤ መጋደም፡ ማረፍ፡ መሞት ። ኢንኑም፡ አላ፡ ንንቃህ ። ያፈቅሩ፡ ነዊመ ። ከመ፡ ይኑሙ፡ ንዋመ፡ ዘለዓለም ። በእንተ፡ እለ፡ ኖሙ፡ (፩ተሰ፡ ፳፡ ፮ ። ኢሳ፶፮፡ ፲ ። ኤር፳፰፡ ፴፱ ። ቅዳ) ። በኖመ፡ ፈንታ፡ ነወመ፡ ተነወመ፡ ይላል፤ ስሕተት፡ ነው፡ (ኤር፳፫፡ ፴፭) ።

**ነዋሚ**፤ **(ሚት፡ ምያን፡ ያት)**፤ የተኛ፤ የሚተኛ፤ እንቅልፋም፤ ሰነፍ ። ኵሉ፡ ነዋሚ ። ሰመየሙ፡ ለምዉታን፡ ነዋምያነ፤ እስመ፡ ይትነሥኡ፡ (ምሳ፳፫፡ ፳፭ ። ግንዘ) ።

**ንዉም**፤ **(ማን፡ ማት፡ ውምት)**፤ የተኛ፤ እንቅልፍ፡ የወሰደው፤ ያረፈ፡ የሞተ፡ ምዉት፡ (ማሕ፭፡

፪ ። ሸታስ ፡ ፳ ፡ ፲ ። ፊልክ ፡ ፯፰) ። እስመ ፡ ሰብአ ፡ አይ ሁድ ፡ ከኑ ፡ ንዉማነ ፡ በእንተ ፡ ድካሞሙ ፡ ወረኃ ብሙ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ንዋም** ፤ እንቅልፍ ፡ ሽልብታ ፡ መኝታ ፤ ሞት ፡ ፍጻሜ ፡ ዕረፍት ። አንቅሀ ፡ እምዐቢይ ፡ ንዋም ፡ ለዘ ይነውም ። ንዋመ ፡ ሞት ። ይቤ ፡ ጠቢብ ፡ ሞት ፡ ንዋም ፡ ነዊኅ ፡ ወንዋምሰ ፡ ሞት ፡ ኅዳጥ ፡ (ሚራ፳፪ ፡ ፮ ። ዮሐ፲፩ ፡ ፪ ። ግንዘ) ።

**እኖመ** ፤ አተኛ ፡ አስተኛ ፡ እንቅልፍ ፡ አሶሰደ ፤ አሳደረ ። ምንት ፡ ይነውመከ ። እኖሞሙ ፡ ለዘሎሙ ፡ ነገሥት ። አኑም ፡ ውስቴትየ ፡ አፍቅሮተከ ። አኑመነ ፡ በሰላም ፡ (ዮናኳ ፡ ፮ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፲፰ ። ማር ፡ ይሥ፲፱ ፡ ፪ ። ድጓ) ። አኖሙኑ ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ፤ አ ቀመ ፡ የአቆመ ፡ ተውላጥ ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

**ኖን** ፤ (ዕብ ፡ ኑን) ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ነ ፤ የአ ሌፍ ፡ ፲፬ኛ ። ፍችው ፡ በሱርስት ፡ ረኸ·ም ፡ ዓሣ ፤ እባብ ፡ የሚመስል ፡ የባብ ፡ ዐይነት ። ኀሐስን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። ኖን ፡ (ኔር) ማኅቶት ፡ ለእግርየ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፭—፻፲፪ ። ሰቈ፩ ፡ ፲፬ ። ፪ ፡ ፲፱ ። ፫ ፡ ፴፱ ። ፬ ፡ ፲፱) ። ባለዳዊቶች ፡ ግን ፡ ስመ ፡ አምላክ ፡ ብለው ፡ ፍች ውን ፡ ንጉሥ ፡ ይሉታል ።

**ኔዎን** ፤ (ጽር ፡ ኔዖን) ፤ መፀው ፡ የጽጌ ፡ የ ፍሬ ፡ የልምላሜ ፡ ወራት ፤ በእስያና ፡ በኤውሮፓ ። ይኸ ውም ፡ ሚያዝያና ፡ ግንቦት ፡ ነው ፤ አቢብንና ፡ መፀውን ፡ እይ ። ከመ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ በወርኀ ፡ ኔዎን ፡ (ሚራ፶ ፡ ፰ ። ፹፱ ፡ ፹፫) ።

**ኖጻ** ፤—ላብ ፤—ነጽይ ፡ ነጻየ ።

**ነዊር** ፤ ሮት ፤ (ኖረ ፤ ነወረ ፡ ይነውር ፡ ይኑር) ፤ መኖር ፡ መቀመጥ ፤ ወይም ፡ ነወር ፡ ማለት ፤ መናር ፡ ከቅምጥ ፡ መነሣት ፡ (በማርኛ) ። መብራት ፡ መ ቃጠል ፤ ወይም ፡ ማብራት ፡ መለኰስ ፡ ማቃጠል ፤ ኖራ ፡ ማውጣት ፡ (ዐረብ) ። መነወር ፡ ነውር ፡ ጸያፍ ፡ መኾን ፤ ወይም ፡ መባል ፤ የግብር ፡ የነገር ።

**እንወረ** ፤ አነወረ ፡ አስነወረ ፤ ነቀፈ ፡ አጸየፈ ፤ አስነቀፈ ፡ ነውረኛ ፡ አሰኘ ። ኢትሕሚ ፡ ወኢታንውር ። ለምንት ፡ ያነውር ፡ አረጋዊ ፡ ለብሕታን ፡ እስ ፡ ያነ ውኙ ፡ ሥዐርተ ። መተረ ፡ እዝኖ ፡ እስከ ፡ አንወሮ ። ወአንወርከ ፡ ክብረከ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፫ ። ፊልክ ፡ ፵ ። ዮሴፍ ። ሚፊ፴፯ ፡ ፷ ። ፪ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፫ ። ፹ ፡ ፷) ። አኖረ ፡ አስኖረ ።

**ተነውረ** ፤ ተነወረ ፡ ነውረኛ ፡ ኾነ ፤ ተነቀፈ ፡ ተሰደበ ። ይትነወሩ ፡ እምከመ ፡ ነትዑ ። የኀስሩ ፡ ወ ይትነወሩ ፡ (ፊልክ ፡ ፬ ። ፴፭) ።

**ንዉር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ውርት) ፤ የተነወረ ፤ የተነቀፈ ፤ ነውረኛ ፡ ነውራም ። ማእደ ፡ እግዚ ፡ ንዉር ፡ ውእቱ ፡ (ሚልኳ ፡ ፯ ፡ ፲፪) ።

**ነውር** ፤ (ራት) ፤ በቁሙ ፤ ሕጸጽ ፡ ንመና ፡ ነው ረኛነት ፡ የመልክ ፡ የሕዋስ ፡ የግብር ። ምማቱን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። አልብኪ ፡ ነውር ፡ ወኢምን ትኒ ፡ ባዕሌኪ ። ወራዙት ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ነውር ። ይገብር ፡ ለከ ፡ ነውረ ፡ በዘአልብከ ። ነውር ፡ ውእቱ ፡ ዘከመ ፡ ሰራቂ ፡ ወጉያዪ ፡ ወዘይሀይድ ፡ ባዕለ ፡ መን ጸፉ ። አብዕልተ ፡ ነውራት ። ርሕቀ ፡ እምዘሉ ፡ ነው ራት ፡ (ማሕ፬ ፡ ፯ ። ዳን፩ ፡ ፬ ። ሚራ፲፩ ፡ ፴፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፫ ። ፈ ፡ መ ፡ ፮ ፡ ፫ ። ፳ ፡ ፳) ።

**ኖራ** ፤ በቁሙ ፡ ኖራ ፡ ብሩህ ፡ ጽሑድ ፡ የደን ጊያ ፡ ዐመድ ።

**ኑር** ፤ (ዐረ ፡ ወሱር ። ዕብ ፡ ኔር) ፤ ብር ሃን ፡ ጸዳል ፤ እሳት ፡ ፋና ። ብርሃን ፡ ዘእምብርሃን ፡ ብ ለው ፡ ዐረቡ ፡ ኑር ፡ ምኑር ፡ እንዲል ፡ (ጸሎ ፡ ሃይ) ።

**መናረት** ፤ (ዐረ ። ሱር ፡ ምናርታ ። ዕብ ፡ ምኖራ) ፤ ምንዋር ፡ ማብሪያ ፡ መቅረዝ ፤ የፋና ፡ የቀንዲል ፡ ማኖሪያ ፡ የሚሰቀል ፡ ወይም ፡ የሚተከል ፡ ተቅዋም ። ወገብረ ፡ መናረተ ፡ (ዘፀ፴፰ ፡ ፲፫ ። ፵ ፡ ፬ ፡ ፳፪) ። ዳግመኛም ፡ በመናረት ፡ ፈንታ ፡ አዛውሮ ፡ መራ ናት ፡ ይላል ፤ የተባሳተ ፡ ነው ። ወደቢበ ፡ መራናት ፡ አኅ ትዉ ፡ (ዘሌ፳፬ ፡ ፬ ። ዘኁ፰ ፡ ፴፩ ። ፰ ፡ ፪—፬ ። ዕብ፱ ፡ ፪ ። ድጓ) ።

**ኖት** ፤ አው ፡ ኖታ ፤ (ላቲን) ፤ በቁሙ ፡ የ ባንክ ፡ ወረቀት ፤ ህዮንተ ፡ ብሩር ፡ ወወርቅ ። ፍችው ፡ ማ ስቢያ ፡ ማስታወሻ ፡ ምልክት ፤ ዘሩ ፡ ነዊጥ ፡ ኖጠ ፡ ነው ፡ ጠና ፡ ተ ፡ ተወራርሰዋል ፤ ኖጠን ፡ እይ ። ምስጢሩም ፡ ካንዱ ፡ ወዳንዱ ፡ ማለፍ ፡ ነው ። ባንክ ፡ ደግሞ ፡ በጀር መን ፡ ቋንቋ ፡ የሰራፎች ፡ (መንዛሮች) ፡ ማእድ ፡ የገን ዘብ ፡ ሰደቃ ፡ ይባላል ፡ (ማቴ፳፩ ፡ ፲፪ ። ዮሐ፪ ፡ ፲፭) ።

**ኖትያ** ፤ ኖትያዊ ፤ (ብ ፡ ነዋትያን ፤ አው ፡ ኖትያት ። ጽር ፡ ናውቲስ ። ዐረ ፡ ኑቲይ) ፤ መርከበኛ ፡ ባለመርከብ ፤ የመርከብ ፡ አገልጋይ ፡ መሪ ፡ ቀዛፊ ፤ ቋትለኛ ። ተመትሮ ፡ ማዕበለ ፡ ደም ፡ እንተ ፡ ኢፈርሀ ፡ ልብከ ፡ ገብረ ፡ መርዓዊ ፡ ኖትዮ ። ኖትያዊ ፡ ይኔጽር ፡ ኀበ ፡ ከዋክብት ። ፈነወ ፡ ኪራም ፡ በሐመር ፡ ዕደወ ፡ ኖትያተ ፡ እለ ፡ የአምሩ ፡ ባሕረ ። ወፈርሁ ፡ ኖትያት ፡ (ቅኔ ። ማር ፡ ይሥ ። ፫ነገ ፡ ፱ ፡ ፳፯ ። ዮናኳ ፡ ፭) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ኖተወ ፡ ዋኘ ፡ ይሉና ፡ ኖትያን ፡ ከዚህ ፡ ያወጣሉ ፤ ፍችውንም ፡ ዋናተኛ ፡ ብለው ፡ ይተ ረጕማሉ ።

**ነዚህ** ፤ ሆት ፤ (ነዝሀ ፡ ይነዝህ ፡ ይን ዛብ ። ዕብ ፡ ናዛህ ፤ ተረጨ) ፤ መንዛት ፡ መርጨት ፡ ማፍሰስ ፤ መበተን ፡ መፈንጠቅ ፡ መረብረብ ፡ መንሰንስ ። ትነዝሀኒ ፡ በአዛብ ፡ ወእነጽሕ ። እነዝሀክሙ ፡ በማይ ፡ ንጹሕ ። ነዝሀ ፡ ደመ ፡ ወወይነ ። ይነሥእ ፡ ደመ ፡ ላ ሕም ፡ ወጠሊ ፡ ምስለ ፡ ማይ ፡ ወይነዝህ ፡ (መዝ ፡ ፶ ። ሕዝ፴፮ ፡ ፳፭ ። ኩፋ ፡ ፯ ። ዕብ፱ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩) ።

**ነዛሂ** ፤ (ሂት ፡ ሀያን ፡ ያት) ፤ የሚነዛ ፡ የሚ ረጭ ፤ ነገር ፡ ረጪ ። ጭብጥ ፡ ያኸ ፡ ውርድ ፡ ነኸ ፡ እን ዲሉ ።

**አንዘሀ** ፤ አስነዛ ፡ አስረጨ ፡ አስበተነ ፡ አስፈ ነጠቀ ።

**ተነገዘሀ** ፤ ተነዛ ፡ ተረጨ ፡ ተበተነ ፡ ተፈንጠቀ ። ተነዝሀ ፡ ደማ ፡ ኀበ ፡ አረፍት ። ተነዝሀ ፡ ደምሙ ፡ ውስተ ፡ አልባስየ ። ደም ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ተነዝሃ ፡ ነፍ ሳቲነ ፡ (፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፴፫ ። ኢሳ፷፫ ፡ ፫ ። አፈ ፡ ድ፳፮) ። በተነገዘሀ ፡ ፈንታ ፡ አንዝሀ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ኢየ ንዝሀ ፡ ላዕሌሁ ፡ ማየ ፡ ምንዛህ ፡ (ዘኍ፲፱ ፡ ፲፫) ።

**ንዙህ** ፤ (ሃን ፡ ሃት ፡ ዝሀት) ፤ የተነዛ ፡ የተ ረጨ ፤ የተረጨበት ። ልብስ ፡ ዘንዙህ ፡ በደም ፡ (ራእ፲፱ ፡ ፲፫ ። አፈ ፡ ድ፲፮ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ንዝሀት** ፤ መርጨት ፡ መረጨት ፡ አረጫጨ ። ንዝሀተ ፡ ደም ፡ (ዕብ፲፪ ፡ ፳፬ ። ጰጥ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ዲ.ድ ፡ ፳) ። በቁሙ ፡ ንዛት ፡ ፳ ፡ ጊዜ ፡ የሚረጭ ፡ የሚበተን ።

**ምንዛህ** ፤ (ሃት) ፤ መርጫ ፡ መረጫ ። ምን ዛህ ፡ ደም ። ማየ ፡ ምንዛህ ፡ (አርጋ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ነዘህሊል** ፤—ንዝህላል ፤—ዛሀለለ ።

**ነዚግዝ** ፤ ዘት ፤ (ነዘ ፤ ነዘዘ ፡ ይነዝግዝ ፡ ይ ንዝግዝ ። ሐዘዘ) ፤ ማንዘግዘግ ፡ ትን ፡ ማለት ፡ ብርንጫ ፡ መውጣት ።

**ነዝነዘ** ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ ነዘነዘ ፤ ወዘወዘ ፤ ማቀየ ፡ ነዘረ ፡ የቀነሰል ፡ የነገር ።

**ተነገዝነዘ** ፤ በቁሙ ፡ ተነዘነዘ ፡ ተማቀየ ። በእ ኩይ ፡ እንዘ ፡ ይትነዘነዝ ፡ (ኪዳ) ።

**መንዝግዝ** ፤ የሚያንዘገዝግ ፤ ንዛዥ ፡ ትንታ ። ነገ ናዛ ፡ ቸኮ ፡ መንቻኮ ።

**መንዘዝ** ፤ መነቻኮ ፤ ቸኮ ፡ ምንቻኮ ፡ አስ ፤ መ ንቻኮ ፡ ኹን ።

**አመንዘዘ** ፤ አመነቻኮ ፡ አጥብቆ ፡ ያዘ ፤ አስጨ ነቀ ፡ አስቸገረ ፤ በነገር ። ያቴክዝዎ ፡ ወያመነዝዝዎ ። ወበክንቱ ፡ አመንዘዝዋ ፡ ለነፍስየ ። እንዘ ፡ ያመንዝ ዝዎ ፡ ወይትቀየምዎ ፡ (ሚራ፳፭ ፡ ፲፰ ። መገ ፡ ፴፱ ። ሉቃ፲፩ ፡ ፶፫) ።

**ተመንዘዘ** ፤ ተመነቻኮ ፤ ተጨነቀ ፡ ተቸገረ ፡ በጽኑ ፡ ተያዘ ።

**ምንዙዝ** ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ዝዝት) ፤ የተጨ ነቀ ፡ በጥኑ ፡ መከራ ፡ የተያዘ ፤ የተጠላ ፡ የተነቀፈ ። ይ ድኅኑ ፡ ምንዱባን ፡ ወያዕርፉ ፡ ምንዙዛን ። ወኅሩ ያንየሂ ፡ ምንዙዛን ፡ በቅድሜሆሙ ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ ። ኪዳ) ።

**ናዘዘ** ፤ (ይናዝዝ ፤ ናዝዝ) ፤ በቁሙ ፤ አጸ ናና ፡ አረጋጋ ፡ አይዞኽ ፡ አለ ፡ ተበሩ ፡ ሰጠ ፤ በምክር ፡ በ ነገር ፡ ደስ ፡ አሰኘ ። ኅጣእኑ ፡ ዘይናዝዘነ ። ኢይና ዝዝዎሙ ፡ በእንተ ፡ ዘሞተ ። ናዘዝካሁ ፡ ለልበ ፡ አመ ትከ ። ወአልቦ ፡ ዘይናዝዞሙ ፡ (መዝ ፡ ፷፰ ። ኤር፲፮ ፡ ፯ ። ሩት፪ ፡ ፲፫ ። መክ፬ ፡ ፩) ።

**ናዛዚ** ፤ (ዚት ፡ ዝያን ፡ ያት) ፤ የሚናዝዝ ፤ ናዛዥ ፡ አረጋጊ ፡ ጸዋ ፡ አይዶራጊ ። ናዛዚ ፡ ወመናዬይ ። ናዛዜ ፡ ሕዙናን ። ናዛዚትየ ፡ እምሕዘን ፡ (ማንዘ ። ድጓ ። ደራሲ) ።

**መናዝዝ** ፤ (ዝዝት ፡ ዝዚት ፡ ዛን ፡ ዛት) ፤ ግእዝ ፡ ከማሁ ። መናዬይ ፡ ወመናዝዝ ። መናዝዛን ፡ ለእ ኪት ። መናዝዚት ፡ (ማንዘ ። ኢዮ፲፮ ፡ ፪ ። አርጋ) ።

**ተናዘዘ** ፤ በቁሙ ፡ ንስሓ ፡ ገባ ። ተጸናና ፡ ተረ ጋጋ ፤ ሐዘኑን ፡ ተወ ፡ ተደሰተ ። ሰብ ፡ ይላሕዉ ፡ ይት ናዘዙ ፡ ብየ ። ወይትናዘዛ ፡ ክልኤሆን ፡ እምቃለ ፡ መ ጻሕፍት ። አላ ፡ ይትናዘዙ ፡ ምስሌሁ ፡ (ኢዮ፳፱ ፡ ፳፭ ። ነገረ ፡ ማር ። ስንክ ፡ ጳጕ፩) ።


**ኑዛዜ** ፤ (ያት) ፤ በቁሙ ፤ (ላ ፡ ጥ ፡ ና) ፡ መና ዘዝ ፡ ማ(መ)ረጋጋት ፡ ርጋታ ፤ የልቡና ፡ ዕረፍት ። መጽ ሐፈ ፡ ኑዛዜ ። ናዘዝከ ፡ ኑዛዜ ፡ መንፈሳዊተ ። ሠናየ ፡ ኑዛዜ ፡ ትናዝዘኒ ፡ (አዋል ። ማንዘ ። ኩፋ ፡ ፴፮) ።

**ነዝሐ** ፤—ነዛ ፡ ረጨ ፤—ነዚህ ፡ ነዝሀ ።

**ነዝነ** ፤ **እንዝነ** ፤ (ዝኖን ÷ እዝንነ ፤ ዝ ኒን) ፤ በአዝንን ፡ ፈንታ ፡ እንዝነ ፡ ይላልና ፤ ዝኖንን ፡ ተመልከት ። ጸጋ ፡ እንተ ፡ ታነዝኖ ። ከመ ፡ ያንዝኖ ፡ እኅተ ።

**ነዘለ** ፤ (ነዚል ። ዐረ ፡ ናዚለ ። ዕብ ፡ ናዘል) ፤ ፈሰሰ ፡ ወረደ ፤ ወደ ፡ ታች ፡ ኼደ ፤ ተቈለቈለ ። እንዝል ፡ እንዲል ፤ ውረድ ፡ ሲል ፡ (ዐረብ) ።

**መናዝል** ፤ (ዕብ ፡ ምዚሎት ፤ ማዛሮት) ፤ ያ፲፪ቱ ፡ ወር ፡ ኮከቦች ፤ ከእልሐመል ፡ እስከ ፡ ሑት ፡ ያሉ ፤ በእንስሳት ፡ ስም ፡ የሚጠሩ ፡ መገብተ ፡ አውራኅ ። ሐ ሳበ ፡ መናዝል ፡ ስም ፡ ወስመ ፡ እም ፡ (የጥንቲላ ፡ መጣፍ) ።



መናዝል ፤

**መንዘለ** ፤ ከበደ ፡ መነዘለ ፤ ደፋ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ አለ ፤ የሚዛን ፡ (ዐማርኛ) ።

**ነዝነዘ** ፤—በቁሙ ፤—ነዚግዝ ፡ ነዘ ።

**ነዝዐ** ፤ (ነዚዕ ። ዐረ ፡ ነዘዐ ። ዕብ ፡ ና ዛዕ ፤ ናዛሕ) ፤ ነቀለ ፡ መዘዘ ፡ አፈለሰ ፤ ከበቀለበት ፡ ከተተከለበት ፡ አነሣ ፡ ወሰደ ። ቀማ ፡ ነጠቀ ፡ (ትግ ፡ ሐብ) ።

ወነዝሀ፡ መትከለ፡ እምነ፡ አረፍት፡ (መሳ፲፯፡ ፲፬)። በነዝሀ፡ ፈንታ፡ ነጥሀ፡ አንጥሀ፡ ይላል፡ የተባሳተ፡ ነው፤ ንጥሀ፡ የዕብራይስጥ፡ እንኛ፡ የግእዝ፡ አይደለም፤ ፍችም፡ ተከለ፡ ዘራ፡ ማለት፡ ነው። እስመ፡ ያንጥዖ፡ ለልብስ፡ (ማቴ፱፡ ፲፯)።

**ነዘፈ፤** (ነዚፍ። ዐረ፡ ነዘፈ፤ ዘለለ፡ ፈነጨ)፤ ወነዘፈ፡ አወንዘፈ፡ ለበሰ፡ አጣፋ፤ ቀሚ፡ ከንዱን፡ አወጣ፤ የበሳሞችና፡ የገረዶች፡ የደንገጥሮች፡ አለባበስ።

**ነዚፍ፤** ኩታ፤ ነጠላ፡ የኩታ፡ አኩሉታ፤ የሚጣፋ፡ የሚወነዘፍ።

**ተነዝፈ፤** ተጣፋ፤ ተወነዘፈ፤ ነዚፋው፡ ልብሱ። ተነጽፈ፡ ተገድፈ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ተነዝፈ፡ ይላል፤ የጣፋ፡ ስሕተት፡ ነው። ተነግፈ፤ ወተኔዝፈ፤ (ናሖ፪፡ ፲)። ዕብራይስጡ፡ ማን፡ ቡቃህ፡ ይላል፤ ባዶ፡ ባዶማ፡ ማለት፡ ነው።

**ነዚር፤ ሮት፤** (ነዘረ፡ ይኔዝር፡ ይንዝር)፤ መንዘር፤ መንከስ፡ መቀርጨፍ፤ መዘብተር፡ መበታተን፤ በጥርስ፡ መቃወም፡ መንደፍ፡ መውጋት፡ ጠቅ፡ ማድረግ፤ በመርዝ፡ መጨቅ፤ ለሽመልና፡ ለዱላም፡ ይሆናል። ለንነና፡ ነስከን፡ እይ። እንዘ፤ ይኔዝሩ፤ በስነኒሆሙ። እለ፤ ይኔዝርዎሙ፡ (ሔኖ፹፯፡ ፭። ሚክ፫፡ ፭)። መናዝር፤ መዘዘን፡ ማመንዘር፡ መቀንዘር። ድሙቱ፡ ናዘረ፡ እንዲሉ።

**ናዛሪ፤** (ሪት፡ ርያን፡ ያት)፤ የሚነዝር፤ የሚናገዝር፤ ነዛር፡ ናዜሬ፤ ዳሞትራ፡ ጊንጥ፤ ተናካሽ፡ ነዳፊ፤ መርዛም፡ ጥርሳም። ነዛር፡ እባብ፡ እንዲሉ፡ (ዘኍ፳፩፡ ፮)።

**ነዝር፤ ንዝሮ፤** ንዝሪያ፡ እንዛዘር፤ የደምና፡ የዘር፡ የመግል፡ ቃንዛ፤ አውጡኝ፡ አውጡኝ፡ አፍር ጡኝ፡ የሚል። ነስር፡ አንሳሰር፤ የንስርና፡ የፍትታት፡ ደም፡ በሥንጥር፡ ሲትጠው፡ ነድፈውና፡ ጋርጠው፤ በምላጭ፡ ፈቅተው፡ ወይም፡ ቈርተው፡ ከፍንጫ፡ ከግንባር፡ የሚያፈሱት። ነስረን፡ እይ፤ ዘና፡ ስ፡ ይዋረሳሉ።

**ተነዝረ፤** ተነከሰ፡ ተነደፈ። እንዘ፡ ይትነ ተፍ፡ ወይትኔዘር፡ (ኪዳ)።

**መንዚር፤** (ራን። ዕብ፡ ማምዜር። ሱር፡ ማምዚራ)፤ ማንዘራ፡ዥ፡ ዲቃላ፤ ያመንዝራ፡ ልጅ፡ አመንዝራ፤ ሴሰኛ፡ ቅንዝረኛ። ሔር፡ ደቤሆሙ፤ ለመንዚራን፤ ወለምኑናን፤ ወደበ፡ ውሉደ፡ ዘማ፡ (ሔኖ፲፡ ፱)።


**መንዘረ፤** (ዘረወ)፤ መነዘረ፤ በተነ፤ ለወጠ፤ ሸረፈ፤ ወርቅን፡ ለብር፡ ብርን፡ ላሞሌ፡ ለመሐልቅ።

**ነዘረ፤** (ሱር፡ ንዛር፤ ደወለ፡ መቃ፤ አቃጠለ)፤ ፊ፡ኸ፡ ከለለ፤ ኖረ፡ ተመመ። መጽሐፍ፡ ግን፡ በነዘረ፡ ፈንታ፡ አንዘረ፡ ይላል፡ ስሕተት፡ ነው። ሰበ፤ አንዘረት፤ ወታኔዝር፤ እግዝእትን፤ ለአንሀብት። ከመ፡ ቃለ፤ አርጋኖን፤ አንዛሪ፡ (አዋል። ግንዘ)።

**አንዘረ፤** አነዘረ፡ አስነዘረ፤ መቃ፡ ነፋ፤ ደረደረ፡ አስሮ፡ኸ። ዘፈነ፡ አዘመረ፤ ቀነቀነ፡ ዐብሮ፡ ፊ፡ኸ። አንዝርኒ፤ ለከሙ፤ ወኢዘፈንከሙ። ያነዝሩ፤ ወይሰ ነቅወ። ዳዊት፡ ያኔዝር፡ ለእንዚራ። በብዕዛ፡ ያነ ዝሩ። አይቴ፤ ሀሎ፤ ልሳንከ፤ አንዛሪ፤ (ማቴ፲፩፡ ፲፯። ኢዮ፳፩፡ ፲፪። ፪ነገ፡ ፮፡ ፲፭። ፩ዜና፡ ፳፭፡ ፫፡ ፭። ግንዘ)። መጽሐፍ፡ ግን፡ አንዘረ፡ ያነዝር፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ዐንዘረ፡ የዐንዝር፤ ዐንዚራ፡ መዐንዝር፡ እያለ፡ በዐይን፡ ይጥፋል፤ የስሕተት፡ ስሕተት፡ ነው።


**አንዛሪ፤ መአንዝር፤** (ርት፡ ራን፡ ራት)፤ ፈታይ፤ ባለእንዝርት፤ ባለመሰንቆ፤ ባለክራር፤ ዘፋኝ፡ አዝማሪ፡ በገና፡ ደርዳሪ። ፈያታዊ፤ መአንዝር። ፊልሞን፤ መአንዝር። ተዋናዩት፡ አው፡ መአንዝርት፤ አው፡ ዘፋኒት፡ (ፊልክ፡ ፵፪። ስንክ፡ የካ፳። መሰ፲፰)።

**እንዚራ፤** (ራት)፤ ንዋየ፡ ማሕሌት፤ የሚነፋ፡ የሚመታ፡ የሚደረደር፤ ክራር፡ በገና፡ መዚቃ፤ የመሰለው፡ ኹሉ። በከበሮ፤ ወበእንዚራ። እንዚራሁ፤ ለበዝርኪ። እለ፤ ይነፍኑ፤ እንዚራተ፡ (ኢሳ፭፡ ፲፪። ሳታት። ፍ፡ ነ፡ ፳፫)።



እንዚራ፡

**እንዝርት፤** በቂጠው፤ የፈትል፡ መማሪያ፡ መፍተያ፡ ማንዘሪያ፤ መንከክት፡ ፀለ፫፡ ዐይነት፤ ዘንጉ፡ ከሽመልና፡ ከቀርካሓ፡ ራሱ፡ ከቀንድ፡ ወይም፡ ከወፍራም፡ ቅል፡ ቋንጣው፡ ከቀጭን፡ ሽቦ፡ የሚሠራ።



እንዝርት፡

**ናዘረ፤** (ናዝሮ። ዕብ፡ ናዛር)፤ ተሳለ፡ ብፅዐት፡ ገባ፤ የብፅዐት፡ ልጅ፡ ኾነ፡ ከሕዝብ፡ ተለየ፡ በፌቃዱ፡ ወይም፡ ከባት፡ ከናቱ፡ ለማዜር፡ ተሰጠ፤ በንጽሕና፡ በቅድስና፡ በትሕርምት፡ በተባሕትዎ፡ ለመኖር፤ እንደ፡ ዮፍታሔ፡ ልጅ፡ (መሳ፲፩፡ ፴፡ ፴፭፡ ፴፱—፵)። በዕወን፡ እይ።

**ናዛሪ፤ ንዙር፤** (ዕብ፡ ናዚር። ሱር፡ ንዚራ። ዐረ፡ ነዚር። ጽር፡ አጊዎስ)፤ የተሳለ፤ ብፅዐት፡ የገባ፤ የብፅዐት፡ ልጅ፤ ብፁዕ፡ ቅዱስ፤ ጠጉሩን፡ ምላጭና፡ መቀስ፡ የማይነካው። መጽሐፍ፡ ግን፡ ናዛሪ፡ ንዙር፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ናዝራዊ፡ ይላል፤ የመ

ላሽና ፡ የጣፈ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (መሳ፲፫ ፡ ፭ ፡ ፯ ። ፲፯ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ መጋቢ) ። የብዕዐትም ፡ ሥራ ፡ ፪ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ፩ኛው ፡ ፍጻሜና ፡ ክፉል ፡ የሌለው ፤ ፪ኛው ፡ ፍጻሜ ፡ ያለው ፡ ነው ፡ (፩ነገ ፡ ፭ ፡ ፲፭ ። ዘኍ ፡ ፮—፭ ፡ ፲፰) ። ናዚር ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ በዕብራይስጡ ፡ ከብፅዐት ፡ ልጅ ፡ ሌላ ፡ ፪ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ያሳያል ፤ ፩ኛው ፡ የሕዝብ ፡ አለቃ ፡ ንጉሥ ፡ ባለዘውድ ፤ ፪ኛው ፡ ዐጽቁ ፡ በመቀስ ፡ ያልተቈረጠ ፡ ያልተቈጠቈጠ ፡ ቅጠላም ፡ ሐረግ ፡ የወይን ፡ ጕንድ ።

**ናዝሬት ፤ (ጽር ፡ ናዝሬት ። ዕብ ፡ ንጻሬት ። ዐረ ፡ ናጺረት)** ፤ በቁሙ ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ ታናሽ ፡ ከተማ ፤ ከገሊላ ፡ አውራጃ ፡ በዛብሎን ፡ ክፍል ፡ ከንዲት ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ የተሠራች ፤ ደብረ ፡ ታቦርና ፡ ቅፍርናሖም ፡ የሚያማክሏት ፤ የቀድሞ ፡ ስሟ ፡ እጅማ ፡ የተናቁ ፡ የተዋረዱ ፤ ኋላም ፡ ጌታችን ፡ የሱስ ፡ የተፀነሰባት ፡ ያደገባትና ፡ የኖረባት ። ዘይቤው ፡ ምንነት ፡ ኅስርት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ስሟን ፡ እንደ ፡ ብፅዐት ፡ ልጆች ፡ በኅሩርነት ፡ ከሚኖሩ ፡ ከሕዝቧ ፡ ወርሳለች ። **ውእተ ፡ አሚረ ፡ ይሰምይዋ ፡ ለናዝሬት ፡ በስመ ፡ ኅሳር ። ይቲ ፡ ከሀልኑ ፡ ይፃእ ፡ ኄር ፡ እምናዝሬት ። ኅሥሥ ፡ ከመ ፡ እምገሊላ ፡ ኢይትነሣእ ፡ ነቢይ** ፡ (ትር ፡ ወን ። ዮሐ፩ ፡ ፵፯ ፡ ፵፯ ። ፯ ፡ ፶፪) ።

**ናዝራዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ። ጽር ፡ ናዞሬዎስ ። ዕብ ፡ ናጽሪ)** ፤ ናዝሬታዊ ፡ የናዝሬት ፤ በናዝሬት ፡ የሚኖር ፤ ከናዝሬት ፡ የወጣ ፤ ምንኩስ ፡ ኅሱር ፡ ወልደ ፡ ናዝሬት ፡ ብእሲ ፡ ናዝሬት ። **ከመ ፡ ናዝራዊ ፡ ይሰመይ ፡ ወልድየ ። ኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ። ምኑን ፡ በኀበ ፡ ሰብእ ፡ ወትሑት ፡ በውስተ ፡ ሕዝብ ፡** (ማቴ፪ ፡ ፳፫ ። ማር፲ ፡ ፵፯ ። መኀዛ ፡ ፳፭ ። ኢሳ፶፫ ፡ ፫) ። በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ ንጻሬት ፡ የንጸረ ፡ ዘር ፡ ነው ፤ ናጻር ፡ ብሎ ፡ ጠበቀ ፡ ሰወረ ፡ ይልና ፡ ኔጺር ፡ ንጻሬት ፡ ተክል ፡ ሐመልማል ፡ ፀጽቅ ፡ ልምሉም ፡ ይላል ። ናዝራዊን ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ አመራረድ ፡ ሲፈቱት ፡ ቸር ፡ እረኛ ፡ ያዳም ፡ ፪ኛ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ጥበቃውን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ያሳያል ፡ (ዘዐ፳ ፡ ፪ ። ኢሳ፲፭ ፡ ፩ ። ኤር፳፫ ፡ ፭ ። ፀ፫ ፡ ፲፭ ። ዘካ፫ ፡ ፰ ። ፯ ፡ ፲፪) ። ናዝሬትንም ፡ የተክል ፡ ቦታ ፡ ገነት ፡ ያሰኛል ። እንደ ፡ ፈተኛውም ፡ በንዙርና ፡ በናዚር ፡ ዘይቤ ፡ ቢፈቱት ፡ የብፅዐቱ ፡ ሥራ ፡ ንጽሕናውና ፡ ቅድስናው ፡ ብሕትውናው ፡ ሳይቀር ፡ እግዜር ፡ እንደ ፡ መለከ ፡ ጸዴቅ ፡ በመንፈሱ ፡ ቀብቶ ፡ የሾመውና ፡ የተከለው ፡ ንጉሥ ፡ ካህን ፡ ጕንደ ፡ ወይን ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፡ (ማቴ፲ ፡ ፱፫ ። መኀዛ ፡ ፪ ፡ ፯ ። ፲፱ ፡ ፬ ። ዮሐ፲፭ ፡ ፩) ። ምእመናንም ፡ ከዐጽቆቹ ፡ ከሐዋርያት ፡ ገምሮ ፡ በናዝራዊው ፡ መሲሕ ፡ ስላመኑ ፡ በአይሁድ ፡ ቋንቋ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ኖጽሪም ፡ ይባላሉ ፤ ናዝራውያን ፡ ናዝሬታውያን ፡ ማለት ፡ ነው ። **ሕዝበ ፡ ናዝራውያን ። ኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ፡ አምላክሙ ፡ ለናዝራውያን** ፡ (ግብ፳፬ ፡ ፭ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ናሕብ ፤—ድንጋግ ፤—ንሂብ ፡ ነሀበ ፡ ናሀብ ።**

**ናሕክ ፤—ሐዘን ፡ ልቅሶ ፤—ንሀክ ።**

**ንሕለ ፤—ፈረሰ ፡ ተናደ ፤—ንኂል ፡ ንኅለ ።**

**ናሖም ፤ (ዕብ ፡ ናሑም)** ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ነቢይ ፡ ከ፲፪ቱ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ አንዱ ፤ ናዛዚ ፡ መናዝዝ ፡ ወይም ፡ ኑዛዜ ፡ ዕረፍት ፡ ህይወት ። ነሐምያም ፡ ማለት ፡ ዘሩና ፡ ፍችው ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። **ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ ፈዋሲተ ፡ ቍስሉ ፡ ለናሖም** ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ። ናሖ፩ ፡ ፲፱) ። **ቅፍርናሖም ፤ (ዕብ ፡ ክፋር ፡ ናሑም)** ፤ ሀገረ ፡ ኑዛዜ ፡ መዕረፍት ፤ ከፈረን ፡ እይ ፡ (ማቴ፬ ፡ ፲፫) ።

**ንሕነ ፤ (ዕብ ፡ ናሕኑ ፤ አኑ ፤ አናሕኑ ። ሱር ፡ አናሕና ። ዐረ ፡ ነሕኑ)** ፤ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ቃል ፤ የኢነ ፡ ብዙ ፤ ወንድና ፡ ሴት ፡ የሚያስተባብር ፤ የእንት ፡ ሙና ፡ የእንትን ፡ አንጻር ፤ ከብዙዎች ፡ አንዱ ፡ ስለ ፡ ራሱና ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ የሚናገረው ። ፍችው ፡ እኛ ፡ ራሳችን ፡ ቅላችን ፡ ባለቤታችን ፤ ነን ፡ ነን ፤ አለን ፡ ነበርን ። አንንና ፡ ንን ፡ ውእቱን ፡ ተመልከት ። **ንሕነሰ ፡ ንሰብክ ፡ ክርስቶስሀ ። ንሕነ ፡ ጠፈር ፡ ወንሕነ ፡ መሠረት** ፡ (፩ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ናሕንሐ ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ግ)** ፤ ናና ፡ በዛ ፡ ከልክ ፡ ዐለፈ ፡ ተረፈ ፤ ትርፍርፍ ፡ አለ ፤ ታውክ ፡ ፈላ ፡ ገነፈለ ፤ የባሕር ፡ የፈሳሽ ፡ ነገር ። ዛሕዝሖንና ፡ ንክንክን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ትርጓሜ ፡ ፍቹው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በናሕንሐ ፡ ፈንታ ፡ ተናሕንሐ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ይትናሐናሕ ፤ ወኢይክል** ፡ (ኤር፭ ፡ ፳፪) ።

**ንሕኑሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ንሕት)** ፤ የናና ፡ የበዛ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ የተረፈ ፤ እልፍ ፡ ትርፍ ፡ ጭማሪ ፡ ያለው ። **መስፈርት ፡ ንሕኑሕ** ፡ (ሉቃ፮ ፡ ፴፰) ።

**ንሕናሔ** ፤ መብዛት ፡ መትረፍረፍ ፡ ከልክ ፡ ማለፍ ፤ ብዛት ፡ ብዙነት ።

**አናሕንሐ** ፤ አናና ፡ አበዛ ፤ አትረፈ ፡ አትረፈረፈ ፡ የጥጋብ ፡ የስፍር ።

**ንሒስ ፤ ሶት ፤ (ነሐሰ ፡ ይንሕስ ፡ ይንሐስ ። ዕብ ፡ ናሔሽ)** ፤ አባብ ፡ መኾን ፡ ከይሲ ፡ መባል ፤ በስምና ፡ በግብር ፡ ወይም ፡ በባሕርይ ፡ እንደ ፡ በትረ ፡ ሙሴ ፡ ተለውጦ ። መጠንቀል ፡ ማሸረት ፤ በድምፀ ፡ ብርት ፡ በድምፀ ፡ አራዊት ፡ ወይም ፡ በሾክሽክ ።

**ንሒሳ ፤ ንሒስ** ፤ ሟርት ፡ ጥንቈላ ። ስመ ፡ ሀገር ፡ ኄቅያ ፡ ወይም ፡ ሌላ ። **ክከበ ፡ ንሒሳ** ፡ (ደራሲ ። ያዐ ፡ ገድል) ።

**ነሐስ ፤ (ዕብ ፡ ናሓሽ ፤ አባብ)** ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ነ ፤ የአልፍ ፡ ፲፬ኛ ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ። ዘይቤው ፡ እባብ ፡ ሽብ ፡ ማለትንም ፡ ያሳያል ፤ ከይሲንና ፡ ኖንን ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ።

እባብ ፡ ያሰኘውም ፡ መልኩና ፡ ቅርጡ ፡ ነው ፡ በጽርእና ፡ በላቲን ፡ ሳይቀር ፡ በፊደላት ፡ ኹሉ ፡ እባብ ፡ ይመስላል ።

**ነሐሰ፤(ይንሕስ፡ ይንሐስ)፤** ናሰ ፡ መደበ ፤ ንሐስን ፡ መዳብን ፤ ወይም ፡ ናስን ፡ ማንቧን ፡ መደብን ፡ ሠራ ፡ ገነባ ። (ሙኾ ፡ ጕዝጕሚት ፤ ባሏ ፡ ውኻማዋን ፡ ገድሎ ፡ መደቡን ፡ አፍርሶ ፡ ቁፍሮና ፡ ቀብሮ ፡ በላዩ ፡ ሐዲስ ፡ መደብ ፡ ስለ ፡ ሠራበት) ፤ ሞጣ ፡ ቀራንዮ ፡ ጽላሎና ፡ ጕንጅ ፤ ረ ፡ ሰውናሰው ፡ ሰውናሰው ፡ እንጅ ። (የባልየው ፡ መልስ) ፤ ጫቃውም ፡ አይቡካ ፡ እንደ ፡ ፈረሰው ፤ ናሰው ፡ ብለሽ ፡ ላኪ ፡ እንድጨርሰው ፡ (ሴላውን ፡ ደግሞ) ። ነፈደኅና ፡ ነደቀን ፡ ጠቀመን ፡ እዩ ።

**ንሓስ፤(ዕብ፡ ንሖሼት ። ሱር፡ ንሓሻ ። ዐረ፡ ኑሓስ)፤** በቁሙ ፤ መዳብ ፡ ብርት ፡ ዐይነቱ ፡ ቀይ ፡ ወይም ፡ ብጫ ፡ የብር ፡ ምክትል ፡ ዕቃ ፡ መሥሪያ ፡ ገንዘብ ፡ የሚኾን ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ ብር ፡ የሚያትሙት ። መጣፍ ፡ ግን ፡ በንሓስ ፡ ፈንታ ፡ ናሕስ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። መወልጣን ፡ እለ ፡ ይትስሐቡ ፡ ላዕለ ፡ ወርቅ ፡ ብሩረ ፤ አው ፡ ናሕስ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፱) ።

**ናሕስ፤(ብ፡ አንሕስት)፤** ናስ ፡ ማንቧ ፤ መደብ ። ይደቅስ ፡ እንዘ ፡ ቅዉም ፡ ውእቱ ፡ ወታሕተ ፡ እዴሁ ፡ ናሕስ ፡ ዘየሰምክ ፡ ቦቱ ፡ (ስንክ ፡ የካ ፲) ። —፤ ደርብ ፡ ሰገነት ፤ ተሥላስ ፡ መረባ ፤ ፪ኛና ፡ ፫ኛ ፡ ፬ኛ ፡ ቤት ፤ ወደ ፡ ላይ ። የማንቧ ፡ ጣራ ፡ በጥ ፡ ጠፈር ፡ መዋቅር ፡ ቅስት ፡ ዕቅድ ፡ በስተላይ ፡ ያለው ፡ ዐፈር ፡ መሬት ፡ ኖራ ፡ ሽሚንት ፤ ወይም ፡ ማርና ፡ ገል ፡ ቁርቁሮና ፡ ርሳስ ፡ የሚከድኑት ፡ እስከ ፡ ቍንሪጣው ፡ እስከ ፡ ጕልላቱ ፡ (ግብ ፲ ፡ ፱። ማቴ ፳፬ ፡ ፲፯ ። ሉቃ ፲፯ ፡ ፴፩) ። ዐርጉ ፡ ውስተ ፡ ናሕስ ፡ ማኅፈድ ። ናሕስ ፡ ንሡት ። ማዕረ ፡ አንሕስት ። እለ ፡ ይሰግዱ ፡ በአንሕስት ፡ (መሳ ፱ ፡ ፶፩ ። ምሳ ፳፫ ፡ ፳፱ ። መዝ ፡ ፻፳፰ ። ሶፎ ፩ ፡ ፭) ። የልብስ ፡ ዘርፍ ፤ ጫፍ ፡ ክፈፍ ፡ (ዘፀ ፳፰ ፡ ፴) ። ጸናጽላተ ፡ ወርቅ ፡ የዐውደ ፡ ለናሕስ ፡ መልበስት ፡ (አርጋ ፡ ፬) ።

**ነሐሴ፤** በቁሙ ፡ ናሴ ፤ መጨረሻ ፡ ወር ፡ የመስከረም ፡ ፲፪ኛ ። ውእቱ ፡ ጾም ፤ ወጥንቱ ፡ ቀዳሚ ፡ ነሐሴ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭) ።

**ናሕሰየ፤(ቀቀ ፡ ግ ። ዐረ ፡ ነሲ ። ሱር ፡ ንሻእ ። ዕብ ፡ ናሳህ)፤** ረሳ ፡ ዘነጋ ፤ ቸል ፡ አለ ። ረስዐንና ፡ ዘንግዐን ፡ እዩ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**አናሕሰየ፤** ይቅር ፡ አለ ፤ ናቀ ፡ አቃለለ ፤ ቂምን ፡ በቀልን ፡ ዕዳ ፡ በደልን ፡ ተወ ፡ ማረ ፡ አሳሰረ ። ኢይደግም ፡ እንከ ፡ አናሕሰየ ፡ ሎሙ ። አናሕሰይኩ ፡ ለመሲሕከ ። ለዘትፈቅዱ ፡ አናሕስየ ፡ አናሕስዩ ፡ ሎሙ ። ስረይ ፡ ሎቱ ፡ ወአናሕሲ ። አናሕሲ ፡ አበሳሆሙ ፡ (ዓሞ ፯ ፡ ፰ ። መዝ ፡ ፹፰ ። ቀሌ ። ማንዝ ። ቅዳ) ። ነስሐ ፤ ተሕትና ፡ ልብ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አናሕሰየ ፡ ዲብ ፡ እኪት ። ተናሕሰየ ፡ ርእሰ ፡ ይላል ፡ (ሄኖ ፡ ፳፯ ፡ ፲፭ ። ቆላ ፡ ፲፰) ።

**አናሕሰየ፤(አስደፈገ)፤** ይቅር ፡ አሰኘ ፤ አስናቀ ፡ አስረሳ ፤ አስተወ ፡ አስማረ ።

ኖን ፤—ረዘመ ፡ በዛ ፤—ነዊኅ ፡ ኖኅ ።

**ንኂል ፤ ሎት ፤(ንኅለ ፤ አው ፡ ነገለ ። ይንኅል ፡ ይንኅል ። ዕብ ፡ ናሐል ፤ ወረሰ ፡ ያዘ)፤** መፍረስ ፡ መናድ ፤ መርከስ ፡ መዋረድ ፡ ባድ ፡ ባድማ ፡ መኾን ። ከመ ፡ ሀገር ፡ ዘንኅለ ፡ ጥቅማ ። እምቅድመ ፡ ይንኅል ፡ ዝ ፡ ቅጽር ፡ ሣልሳይ ። ንኅለ ፡ ጠፈር ፡ ላዕሌሁ ። እስመ ፡ ንኅለ ፡ ሀገረ ፡ መቅደስከ ፡ (ምሳ ፳፬ ፡ ፳፰ ። ዮሴፍ ። ሬልክ ፡ ፹፭ ። ኢሳ ፻፱ ፡ ፲) ። በንኅለ ፡ ፈንታ ፡ ወድቀ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ተንኅለ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ተንኅለ ፡ ምታር ፡ ዐቢይ ። ቅጽር ፡ ዘተንኅለ ፡ (ዮሴፍ) ። ወእምዝ ፡ ተንኅለት ፡ ወበድወት ፡ (ስንክ ፡ የካ ፳) ።

**ንኁል ፤(ላን ፡ ላት ፡ ኅልት)፤** የፈረሰ ፡ የተናደ ፤ ባድ ፡ ባድማ ፤ ወይም ፡ ሊፈርስና ፡ ሊናድ ፡ የቀረበ ፡ ያረገዘ ፡ ያዘበዘበ ። ከመ ፡ ጥቅም ፡ ዘባቤል ፡ ረስዩ ፡ ንኑለ ። አረፋት ፡ ንኑላት ። ከመ ፡ አረፍት ፡ ጽንንት ፡ ወከመ ፡ ጥቅም ፡ ንኑል ፡ (ደራሲ ። ፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፳፬ ። መዝ ፡ ፷፩) ።

**ንኅለት፤** መፍረስ ፡ አፈራረስ ፡ ፍርሻ ፡ ፍራሽ ፤ ንዳላ ፡ ብስ ። ንኅለተ ፡ ቅጽር ። ከመ ፡ ያርሕቡ ፡ ውእተ ፡ ንኅለተ ፡ (ዮሴፍ) ።

**አንኀለ፤** አፈረሰ ፡ አስፈረሰ ፤ ናደ ፡ አስናደ ። አ ፡ ዘአንኀልከ ፡ ጥቅማ ፡ ለኢያሪኮ ። አብያተ ፡ ጸዓልያን ፡ ያንኅል ፡ እግዚ ። ፈቀደ ፡ ጢጦስ ፡ ይሑር ፡ ኅበ ፡ ቅጽር ፡ ከመ ፡ ያንኅሎ ፡ (ቅዳ ። ምሳ ፲፭ ፡ ፳፭ ። ዮሴፍ) ።

**አንኂሊ ፤ መንኂሊ ፡ ኅል፤** የሚያፈርስ ፡ የሚንድ ፤ አፍራሽ ፡ አስፈራሽ ። ወይም ፡ ማፍረሻ ፡ ማስፈረሻ ፡ ነገር ፡ መሣሪያ ።

**ምንኃል ፤(ላት)፤** መፍረሻ ፡ ማፍረሻ ። ወማኅፈደኪ ፡ ያንኅል ፡ በምንኃሊሁ ፡ (ሕዝ ፳፮ ፡ ፱) ።

**ተናኀለ፤** ተፋረሰ ፡ ተፈራረሰ ፤ የዋጋ ፡ የውል ።

**ንኂር ፤ ሮት ፤(ንኅረ ፡ ይንኅር ፡ ያንኅር ። ዐረ ፡ ነኀረ ። ዕብ ፡ ናሐር ። ሱር ፡ ንሓር)፤** ማኮረፍ ፤ መቈጣት ፡ አፍንጫን ፡ መንፋት ፡ ማንኮራፋት ፡ የጠብ ። ማንኳረፍ ፡ ማላዘን ፡ እንደ ፡ ታረደ ፡ ከብት ፡ መኾን ፤ የንቅልፋም ፡ የፍርዳ ። ኖመ ፡ ወንኅረ ፡ (ዮናስ ፡ ፭) ። አንፈን ፡ እዩ ።

**ናኅር፤** ኵርፊያ ፤ እንኵርፊያ ፤ ጩኸት ፡ ያሰው ፡ ትንፋሽ ፤ ያፍንጫና ፡ የጕሮሮ ፡ ድምፅ ። መናኂር ፡ እንዲል ፤ አፍንጫ ፡ ቢል ፡ (ዐረብ) ።

**ነኃር ፤ ምንኃር ፤—ወንዝ ፡ መስኖ ፤—ነሀረ ።**

**ነጢብ ፤ ብት ፤(ነጥበ ፤ ነጠበ ፡ ይነጥብ ፡ ይንጥብ ። ዕብ ፡ ናጣፍ ። ሱር ፡ ንጣፍ)፤** መንጠብ ፤ ጠብ ፡ ኮለል ፡ ማለት ፤ ተጠቅልሎ ፡ ሕንባብ ፡ መስሎ ፡ መውረድ ፡ የውሃ ፡ የዝናም ፡ የላበት ፡ የደም ።

ማየ ፡ መቍረርኺ ፡ ኢይንጥብ ፡ እምአፍ ። ተክዕወ ፡ ወነጥበ ፡ ደሙ ። መጽለወ ፡ ሥጋሁ ፡ ወከነ ፡ ከመ ፡ ምድር ፡ ይቡስ ፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ከዐዉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ምልአ ፡ ኩራ ፡ ማየ ፤ ወኢነጥበ ፡ ዘእንበለ ፡ ንስቲት ፡ እምብዝኃ ፡ ይብሰተ ፡ ሥጋሁ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፫ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፱ ። መስ፳፯) ።

**ነጥበ** ፤ ነጠበ ፡ ሰደበ ፡ ነቀፈ ፡ ተቈጣ ፡ ዘለፈ ፡ (ዐማርኛ) ። መጕጸን ፡ እይ ።

**ነጥብ** ፤ ጠብታ ፤ የፈሳሽ ፡ ቅንጣት ፡ ክብላላ ፡ ጠቅላላ ። ነጥበ ፡ ማይ ። ነጥበ ፡ ጠል ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፲ ። ጥበ፲፭ ፡ ፳፫) ።

—፤ በቁሙ ፤ የንባብ ፡ ወሰን ፡ የቃል ፡ መለያ ፡ ታላቅ ፡ ምልክት ፤ ንኡስ ፡ ምዕራፍ ፡ ባለ፱ ፡ ነቍጣ ፡ ፱ቱ ፡ ጥ ቍር ፡ ፳ቱ ፡ ቀይ ። ፍቅደ ፡ ነጥብ ፡ በዓላተ ፡ ወሊድ ፡ ቅዱሳን ፡ ተሰምዑ ፡ (ቅኔ) ። ቀዳም ፡ ቢቀር ፡ መደበኛው ፡ ጥቍሩ ፡ ነውና ፤ አራቱ ፡ ብቻ ፡ ነጥብ ፡ ይባላል ። ነጥብ ፡ ጽኑዕ ፡ ዘኢይትፋለስ ። ወይእቲ ፡ ነጥብ ፡ ነጥበ ፡ ዕ ፊና ፡ (አቡሻ ፡ ፴፯) ። በነጥብ ፡ ፈንታ ፡ ንጥበት ፡ ይላል ። ኢይትዌረይ ፡ ንጥበተ ፡ ተድላሃ ፡ አሐቲ ፡ ከመ ፡ ተ ድላ ፡ ዓለም ፡ በምልአ ። ንጥበተ ፡ ደሙ ፡ (አፈ ፡ ተ ፳፰ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**አንጠበ** ፤ አንጠበ ፡ አስንጠበ ፤ ጠብ ፡ አደረገ ፡ አስደረገ ።

**ንጥበት** ፤ መንጠብ ፤ ማንጠብ ፡ አንጣጠብ ፡ ነጠባ ፡ ንጥቢያ ፤ ጠብታ ።

**ምንጣብ** ፤ መንጠቢያ ፤ ማንጠቢያ ።

**አንጠብጠበ** ፤ አንጠበ(ባ)ጠበ ፤ ጠብ ፡ ጠብ ፡ አደረገ ፡ አንጠፈጠፈ ። ደመናት ፡ አንጠብጠቡ ፡ ማየ ። ደመናት ፡ አንጠብጠቡ ፡ ዓሣ ። ትሬእየነ ፡ ናንጠበ ጥብ ፡ ሀፈ ፡ ዘእምባእስ ። ወሰማይኒ ፡ አንጠብጠበ ፡ መሳ፳ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳፱ ። ተረ ፡ ቂ፫፫ ። መገ ፡ ፳፯) ።

—፤ ተንጠበ(ባ)ጠበ ፤ ጠብ ፡ ጠብ ፡ አለ ፡ ፈሰሰ ፡ ተንጠ ፈጠፈ ፡ (መገ ፡ ፻፷ ። ፱ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፲) ። ወኢያንጠበ ጥብ ፡ መዐትየ ፡ ላዕለ ፡ ኢየሩሳሌም ። ዘያንጠበጥብ ፡ እምላዕሉ ፡ ይሰቍራ ፡ ለእብን ፡ (፱ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፯ ። ሄ ሮማ ፡ ገ፻፱) ፡ ጸፍጸፈንና ፡ አንጸፍጸፈን ፡ እይ ።

**ነጠብጣብ** ፤ ጠብቶች ፡ ጠብታዎች ፡ ነጥቦች ፡ ነጠብጣቦች ፤ ጠፈጠፎች ። ነጠብጣበ ፡ ዝናም ። ሐ ንባባት ፡ ነጠብጣብ ። ከመ ፡ ነጠብጣበ ፡ ማሕየብ ፡ (ኢዮ፴፯ ፡ ፳፯ ። ፴፰ ፡ ፳፰ ። ኢሳ፵ ፡ ፲፭) ። ዳግመኛም ፡ በነጥብ ፡ ፈንታ ፡ ነጠብጣብ ፡ እያለ ፡ ያንዱን ፡ ብዙ ፡ ይጥፋል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ከመ ፡ አሐቲ ፡ ነጠብጣበ ፡ ማይ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ማየ ፡ ባሕር ። አሐቲ ፡ ነጠብ ጣበ ፡ አንብዕ ። ዘንተ ፡ ፈጠርከ ፡ በንስቲት ፡ ነጠብ ጣብ ፡ ዘይትዐቈር ፡ ውስተ ፡ ማሕፀን ። ነጠብጣብ ፡ ልምልምት ፡ (ሢራ፲፰ ፡ ፲ ። ቀሌ ። ዲድ ፡ ፴፰ ። ማር ፡ ይሶ፳፰) ።

—፤ ዕይር ፡ ቅልቅል ፡ ዐይነት ፡ ኰስኰስ ፡ ዝንጕርጕር ፡ ቱሱሕ ፡ ሕብር ፤ የማዕደን ፡ የደንጊያ ፡ የጠጕር ። ይብረ ፡ ወርቅ ፡ ወይብረ ፡ ነጠብጣብ ፡ (ሔኖ፺፪ ፡ ፪) ።

**ነጠ** ፤ (**ይነጥጥ ፡ ይንጥጥ** ፤ **ነጢጥ** ። **ዐረ ፡ ነጠ**) ፤ ዘለለ ፡ ፈነጨ ፤ ባጥ ፡ እንጣጥ ፡ ፈናጥ ፡ አለ ። አነጠነጠ ፡ ተቀነጠነጠ ፤ ርግብኛ ፡ ሬሞኝ ፤ የሕፃን ፡ የጨቅላ ። ዐነጠ ፤ አነጠጠ ፡ አንጣጭ ፡ ኹን ።

**መንጢጥ** ፤ (**ጣት** ፤ **አው ፡ መናጢጥ**) ፤ ጥኖስ ፡ ቡላል ፤ ርግብ ፡ የርግብ ፡ ወገን ፡ መሣዕት ፡ የሚ ኾን ፡ አነጥናጭ ፡ ወፍ ። ነሥአ ፡ መንጢጠ ፡ ወዐጕለ ፡ ርግብ ። ያፈ ፡ መንጢጥ ፡ ዘኢነባቢ ፡ ይትገሐሥ ፡ እ ምአውስቦ ፡ ዳግማዊ ። ያፈ ፡ ነበልባል ፡ ጽዕድው ፡ እ ሰምየከ ፡ መንጢጠ ። መንጢጣት ፡ (ኩፋ ፡ ፮ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ። ደራሲ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፪) ።

**ነጠየ** ፤ (**ይነጢ ፡ ይንጢ**) ፤ ናጠ ፡ ገፋ ፡ ወ ዘወዘ ፤ የወተት ፡ የጥና ። ዐጣ ፡ ነጣ ፤ መናጢ ፡ ኹን ።

**አንጠየ** ፤ አስናጠ ፤ አስገፋ ፡ አሶዘወዘ ። ዘበዘበ ፡ ነዘነዘ ፤ አስጨንቀ ፡ አስቸገረ ፤ በነገር ፡ በልመና ። አመን ዘዘን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ፡ (ሉቃ፲፰ ፡ ፯ ። ፲፰ ፡ ፭ ። ገላ፯ ፡ ፲፯) ። ኢታንጥዮሙ ፡ ለቤተ ፡ ያዕቆብ ። አንጠይዎ ፡ ከመ ፡ አሆ ፡ ያብልዎ ። ፈድፋደ ፡ አንጠ የኒ ፤ እስመ ፡ ክልኤኒ ፡ ሲሳይየ ፡ ወዐራዝየ ። ዘያነጥ ዮሙ ፡ በዥሉ ፡ (ዓሞ፯ ፡ ፲፮ ። ዮሴፍ ። ቀሌ ። መቃ ፡ ገ፪) ።

**አንጣዪ** ፤ **መንጠዪ** ፤ (**ዪት ፡ ይያን ፡ ያት**) ፤ የሚዘበዝብ ፤ ዘብዛባ ፡ ነዝናዛ ፤ ችኮ ፡ መንቻካ ፡ መናጢ ። በእንተ ፡ ፍርፋራተ ፡ ኅብዝት ፡ ትሰምዩኑ ፡ አንጣዩ ፡ ለእኍከ ። መንጠዩ ፡ አንተ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፭ ። ሄሮማ ፡ ገ፻፰) ።

**መንጥይ** ፤ (**ያን**) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ወዓዲ ። መዘብዘቢያ ፤ ምክንያት ።

**መንጥያዊ** ፤ (**ዊት ፡ ውያን ፡ ያት**) ፤ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ። የችኮ ፡ የዘብዛባ ፡ ወገን ፤ ጕስጓሽ ፡ አነሣሽ ፤ አገባሪ ፡ አስቸጋሪ ፤ አስቸኳይ ፡ በሉ ፡ በሉ ፡ ባይ ። ወሰበ ፡ ተመውአ ፡ እምውስተ ፡ መዓርጋት ፡ መንጥ ያውያት ፤ አድርጉን ፡ አድርጉን ፡ ከሚሉ ፡ ከታላላቁ ፡ ጎ ጣውእ ፡ (ፈልክ ፡ ፺) ።


**ነጢፍ** ፤ **ፎት** ፤ (**ነጠፈ ፡ ይነጥፍ ፡ ይን ጥፍ ። ዕብ ፡ ናጣፍ** ፤ **ዘቃቅ**) ፤ ማጥራት ፤ ማፍ ሰስ ፡ መከስከስ ፡ ማንጠር ፡ ማቅለጥ ፤ ለማጥራት ። እሳ ፡ ዳጹተ ፡ ትነጥፉ ። ወይነጥፎሙ ፡ ለደቂቀ ፡ ሌዊ ። ይነጥፍዎ ፡ ለወርቅ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፳፱ ። ሚልክ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ግን፪) ። መከረንና ፡ ፈተነን ፡ እይ ።

**አንጠፈ** ፤ አስነጠረ ፤ አስኰላ ።

**ተነጥፈ** ፤ ጠራ ፡ ነጠረ ፤ ተኰላ ፡ ጥሩ ፡ ኾነ ። ኢ ዮብ ፡ ተፈትነ ፡ ወተነጥፈ ፡ ከመ ፡ ወርቅ ፡ (አርጋ ፡ ፫) ።

**ንጡፍ** ፤ (**ፋን ፡ ፋት ፡ ጥፍት**) ፤ ምኩር ፡ ፍቱን ፡ የጠራ ፡ ጥሩ ፤ ጠፍ ፡ ያለ ። ወርቅ ፡ ንጡፍ ። ጽ ሩይ ፡ ወንጡፍ ፡ እምወርቅ ። ወይን ፡ ንጡፍ ፡ (ዕ ዝ፪ ፡ ፰፱ ። ድጓ ። አብጥ ፡ ፪) ።

**መንጠፍት፤** ውንጠፍት ፡ የወንፊት ፡ ዐይነት ፡ ማጥሪያ ፡ ማጥለያ ፡ መጥመቂያ ፤ ማንጠፍጠፊያ ፡ ጠፍ ፡ ማድረጊያ ። ውስተ ፡ መንጠፍት ፡ ይጠሕል ፡ ሐሠር ፡ (ሚራጃሺ ፡ ፱) ።



መንጠፍት ፡

**ነጠቀ፤ (ዕብ ፡ ናታቅ ፤ ነቀለ)፤** በቁሙ ፤ ቀማ ፡ በኀይል ፡ ወሰደ ፡ (ዐማርኛ) ። መጠቀን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ነጢር፤ ሮት፤ (ነጥረ፤ ነጠረ ፡ ይነጥር ፡ ይንጥር ። ዐረ ፡ ወዕብ ፡ ናጣር ፤ ጠበቀ)፤** መንጠር ፡ መንጠር ፤ መቅለጥ ፡ መፍሰስ ፤ የቅቤ ፡ የማዕደን ፤ ለነገርና ፡ ለኪስም ፡ ይኾናል ። መበለጭ ፡ ብልጭ ፡ ማለት ፤ መፈንዳት ። ነጥረ ፡ እሳት ፡ ነፍጥ ፡ እምነጊያት ፡ ብርት ። መብረቅ ፡ ዘይነጥር ፡ (ዮሴፍ ። ጥበ ፡ ጠቢ ። አርጋ ፡ ፭) ።

**ንጥር፤ (ራት፤ እንጥር)፤** በቁሙ ፤ ንጡር ፤ የነጠረ ፡ የተነጠረ ፤ የጠሬ ፡ የበሬ ፡ የተጠበቀ ፤ ወርቅ ፡ ብር ። ንጥር ፡ ቅቤ ፡ እንዲሉ ። ነሥአ ፡ ዲናረ ፡ ወርቅ ፡ እምንጥረ ፡ ሕበዊሁ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲) ።

—፤ ብልጭታ ፡ ብራቅ ፡ ነጸብራቅ ፡ ጓታ ፡ ፍንዳታ ። ንጥር ፡ ዘእመብረቀ ፡ ስብሐት ፡ አይኅአ ። ንጥረ ፡ እሳት ። አንጥረ ፡ መባርቅት ። ሞቱ ፡ በንጥረ ፡ መሬት ፡ ወሐመድ ፡ (አርጋ ። ዮሴፍ ። ጠማር ። አዋል) ። ልጥሮን ፡ ነጥር ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**አንጠረ፤** አነጠረ ፡ አስነጠረ ፤ አፈሰሰ ፡ አቀለጠ ፤ አጠሬ ።

**አንጣረ፤** በቁሙ ፤ አንጥረኛ ፡ ብር ፡ አፍባሽ ፤ ጃን ፡ ሸላሚ ።

**አንጣሪያ፤ (ዐማርኛ)፤** በቁሙ ፤ የሥንቆ ፡ ቅጠል ፡ ከማሽላ ፡ ውስጥ ፡ የሚበቅል ፡ ማላጋ ፡ እንደ ፡ ሰርደ ፡ ግድም ፡ የሚኼድ ፡ የሚዘረጋ ። (ተረት) ፤ አንጣሪያ ፡ ሳንጣሪያ ፡ ቢደጋገፍ ፡ ተያይዞ ፡ ዘፍ ።

**ናጥራን፤ ናጥሮን፤ (ዐረ ፡ ነጥሩን ። ዕብ ፡ ኔቴር)፤** የደንጊያ ፡ ስም ፤ ከጨው ፡ መካከል ፡ የሚገኝ ፡ ሽክሬና ፡ ዐይናማ ፤ በውሃ ፡ የሚቀልጥ ፡ የሚሟሟ ፤ እንደ ፡ ሳሙና ፡ ልብስ ፡ የሚያሳጥብ ፡ እድፍ ፡ የሚያጠሬ ፤ ለጋዝ ፡ መብራትና ፡ ለኤሌትሪክ ፡ ብርሌ ፡ ብርጭቆ ፡ የሚኾን ። ዐዘቅተ ፡ ናጥራን ። ቀሲስ ፡ ዘይብረ ፡ ናጥሮን ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲፫ ። ሬልክ ፡ ፲፰) ። ይኸውም ፡ ዐዘቅት ፡ እስቂጥስ ፡ አጠገብ ፡ ይገኛል ።

**ነየ፤** የነ ፡ ዝርዝር ፤ እንሆኝ ። ነ ፡ እንደ ፡ በና ፡ እንደ ፡ ሰ ፡ ነባር ፡ አንቀጽ ፡ ሲኾን ፡ የሀወን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ አድርጎ ፡ እንደ፡ት ፡ እንዲረባ ፡ በመዝገመሪያው ፡ ነ ፡ ተመልክት ፤ ከዚያ ፡ ተጥፏል ።

**ነዩእ፤ (ኔአ ፡ ይነይእ ፡ ይኒእ)፤** መቅረብ ፡ መዘጋጀት ፡ ለመብሰል ።

**ኒእ፤ አው ፡ ንያእ፤ (ዐረ ፡ ወዕብ ፡ ናእ)፤** ያልበሰለ ፡ ርጥብ ፤ ሥጋ ፡ ሽክላ ፡ ሊጥ ።

**ናእት፤** በቁሙ ፤ ቂጣ ፤ ብርኮታ ፡ ርሚጠ ፡ ጥረኛ ፤ ሊጡ ፡ ሳይቦካና ፡ ርሾ ፡ ሳይገባበት ፡ ወዲያው ፡ ተሰውሮ ፡ የሚጋገር ። ናእተ ፡ ትበልዑ ። ኅብስተ ፡ ናእት ። በዓለ ፡ ናእት ። ናእት ፡ አንትሙ ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፰ ። ጃ፱ ፡ ፪ ። ዘሌ፳፫ ፡ ፮ ። ፩ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፯) ።

**ኒል፤ (ዐረ)፤** በቁሙ ፤ ህንዳዊ ፡ ቀለም ፡ ልብስ ፡ ማርያም ፤ ክንድ ፡ ዐይነት ፡ ዕንጨት ፡ የሚወጣ ፡ ሕብሩ ፡ ሰማያዊ ፤ ዘረቀንና ፡ አዝረቅን ፡ ዐለለን ፡ እይ ። (ስንክ ፡ ሐም፰ ። ኅዳ፳፭) ።

**ኒሉስ፤ (ዕብራ)፤** ፈለገ ፡ ኒል ፡ ግዮን ፡ ኤፌሶን ፡ ንጫ ፡ አባይና ፡ ጥቁር ፡ አባይ ፤ ውሃቸው ፡ ንጭ ፡ ኒል ፡ ጥቁር ፡ ኒል ፡ የሚመስል ።

**ናዪን፤ (ጽር ። ዕብ ፡ ናዒም)፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ የደብረ ፡ ታቦር ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ። ሠናይት ፡ መስተፍሥሒት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ሉቃ፯ ፡ ፲፪) ።


**ናይናን፤ (ቅብጥ ፡ ናይ ፡ ናን)፤** መሐር ፡ ኪያነ ፤ መሐረን ፡ (ግብ ፡ ሕማ) ።

**ነይሩዝ፤ (ዐረ ፡ ኒሩዝ ፤ ኑሩዝ)፤** የፋርስ ፡ በውደ ፡ ዓመት ፤ የመስከረም ፡ መባቻ ። ወረሰዩ ፡ ነይሩዘሙ ፡ ዘውእቱ ፡ ቀዳሚ ፡ ዓመቶሙ ፡ በሠርቀ ፡ ተውት ፡ (አቡሻ ፡ ፸) ።

**ኔስ፤ (ዕብ)፤** ተራዳ ፤ ረዥም ፡ ምጡቅ ፡ ያላማ ፡ ሰንደቅ ፤ የባንዲራ ፡ ዕንጨት ፤ የመርከብ ፡ ምሰሶ ።

**ኔሳን፤ (ሱር ፡ ወዕብ ፡ ኒሳን ። ጽር ፡ ኔምን)፤** ስመ ፡ ወርኅ ፤ ሚያዝያ ። ቀድሞ ፡ በዕብራይስጥ ፡ አቢብ ፡ የሚባለው ፡ ከባቢሎን ፡ ምርኮ ፡ በኋላ ፡ ኔሳን ፡ ተብሏል ፤ ምልክታም ፡ ባለምልክት ፡ ባለታምራት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ፪ኛም ፡ ፀአትንና ፡ ሽሽትን ፡ ፈተናን ፡ ያሳያል ። ንሸን ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ ከኔሳን ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ፤ ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ነሰሰና ፡ ነሰወ ፡ ናቸው ። ኔሳን ፡ ዘውእቱ ፡ ሚያዝያ ። ዐቀብ ፡ ወርኀ ፡ ኔሳን ፡ እስመ ፡ በወርኁ ፡ ኔሳን ፡ ወፃእከ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ፡ (ተረ ፡ ባሮ ። ዘዳ፲፮ ፡ ፩) ።

**ኔስታሊ፤ (ጽር ፡ ኔስታን ። ዕብ ፡ ንሐሽታን)፤** የንሓስ ፡ እባብ ፡ ሙሴ ፡ በአርዌ ፡ ምድር ፡ አምሳል ፡ የሠራው ። ነሐስን ፡ እይ ፡ (፬ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፬) ። በኔስ ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ግን ፡ ኔስታሊን ፡ ታሉ ፡ ኔስ ፤ በዕብራይስጥም ፡ ታሉይ ፡ ዐል ፡ ሀኔስ ፡ ይሰኛል ። ታሊ ፡



ኔስታሊ ፡

ታሉይ ፡ ስቁል ፤ ኔስ ፡ ተራዳ ፤ በተገናኝ ፡ ስቁለ ፡ ኔስ ፡ ዘስቁል ፡ ዲበ ፡ ኔስ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ተሰውን ፡ ከንቀራኛው ፡ እይ ፡ (ዘኍ፳፩ ፡ ፰ ፡ ፱ ። ዮሐ፫ ፡ ፲፬) ።

**ነከበ፤(ነኪ.ብ። ዐረ፡ ነከበ)፤** አስጐንበሰ፣ ዐጠፈ፣ ሳበ፣ ሰበሰበ፤ የዐጽቅና፣ የክንፍ፣ የእጅና፣ የእግር፣ የሾንቢ፤ ስጎሲናም፣ ይኾናል።

**መንኮብ፤ መንኮብያ፤(ያት)፤** ዐጽቅ፣ ክንፍ፤ እጅና፣ እግር፤ አውራ፣ ጣት፣ (ሾንቢ)። አሰረቶ፣ መንኮብያቲሁ። ዘይበትክ፣ ማእሰረ፣ ኃጢአት፣ መንኮብያቲሁ፣ ተአስረ። እገሪሁ፣ ጸፋሕት፤ መንኮብያቲሁ፣ ጽንጽዋት። ዕተብ፣ ገጸከ፣ በዘይተልዎ፣ ሰመንኮብያ። መንኮብያቲሁ፣ ጠበወ፣ (ሉቃ፲፪፡ ፯፡ ፲፱። ቄር። ኪዳ። ሲኖዶ። ደራሲ.)።

**ነክይ፤ዮት፤(ነከየ፡ ይነኪ፡ ይንኪ። ዐረ፡ ነከዐ፤ ነከይ። ዕብ፡ ናከህ። ሱር፡ ንክእ)፤** መንካት፣ መጕዳት፤ መስበር፣ ማጕደል። ነክዐን፣ እይ፤ የዚህ፣ ዘር፣ ነው፣ (ኢሳ፲፩፡ ፱። ፷፭፡ ፳፭። ማር፲፮፡ ፲፰። ሉቃ፲፡ ፲፱፡ ፲፩)። አናብስት፣ ኢነከይዎሙ። አልቦ፡ ዘይነክየኒ፡ ለእመ፡ ወሀብከዎ፡ መንፈቀ፡ (አቡሻ፡ ፶። ጦቢ፲፪፡ ፪)።

**ነካዪ፤(ዪት፡ ይያን፡ ያት)፤** የሚንካ፤ የሚጐዳ። ደዌ፡ ሥጋ፡ ፍጥረታዊት፡ ነካዪት። ረኃብ፡ ወጽምእ፡ ነካይያን፡ (ገድ፡ ኪሮ። ፍ፡ ነ፡ ፲፱፡ ፱)።

**እንከየ፤** አስንካ፤ አስጐዳ፤ ጐዳት፣ አመጣ። ኢያነክየኒ፡(፩ቆሮ፡ ፳፡ ፳)። በሐንክ፡ ፈንታ፡ ሐንክየ፣ እንደ፣ ማለት፣ እንክየ፣ ይላል፤ ስሕተት፣ ነው። እመ፡ አንከይኩ፡ እምሲሳይከ፡ ወአፍአምኩ፡ ለነዳይ፡ (ኢሳ፶፰፡ ፲)።


**ተነክየ፤** ተንካ፣ ተጐዳ፤ ጐደለ፣ ታጐለ። ኢተነክየ፡ ወኢምንተኒ። አልቦ፡ ዘተትነከይ፡ አንተ፡ በእቢደ፡ ዚአሁ። ወኢይትነከይ፡ መለኮቱ። ፈርህ፡ ከመ፡ ኢትፀራዕ፡ አው፡ ከመ፡ ኢትትነከይ፡ ተፀምዶ፡ (ዳን፮፡ ፳፫። ሚሬ፰፡ ፲፫። ቄር። ጸላ። ፊልክ፡ ፲፩)።

**ንኩይ፤** የተነካ፤ ንክ፤ ስባራ፣ ዐንካሳ፣ ጐደሎ፣ (ፊልክ)።

**ንክየት፤** መንካት፣ መንካት፤ አንካካ፤ ንኪት፣ ጕዳት፣ ጥፋት። ዘእንበለ፡ ንክየት፡ እመንገሌሁ። ዘያመጽእ፡ ንክየተ፡ ካልእ። ዘወደየ፡ እሳተ፡ ውስተ፡ ሀገር፡ አው፡ በሐቅል፡ እንዘ፡ የኀሥሥ፡ ንክየተ፡ ስብአ፡ ዚአሁ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፴፰፡ ፴፯። ፶፡ ፯)።

**ንካይ፤** ንኪት፣ ጕዳት፤ ስብራት። እምንካይ፡ ወእምበቍዔት፡ (ፊልክ፡ ፻፩፪)።

**መንካ፤(ካት)፤** በቍሙ፣ ማንካ፣ የመብል፣ የመጠጥ፣ መግሪያ፣ ዕርፈ፣ መክቀል። ወረስያ፡ ኅሪተ፡ ወንጽሕተ፡ ለዛቲ፡ መንካ፡ (ሥር፡ ቅዳ)።



መንካ፡

**ነከላል፤—እዞሪቱ፤—ከለሰ፡ አን።**

**ነክነከ፤(ተቀ፡ ግ፤ ነከየ)፤** ነክነከ፤ ነቀነቀ፣ ወዘወዘ፣ ለመንቀል፣ ለመፈንቀል። ነሥቱ፡ አናቅጺሃ። ወነክነኩ፡ አዕማዲሃ። ረከቡ፡ ርእሰ፡ ምዉት፡ ወነክነኩ፡ አባ፡ ሲኖዳ፡ በበትሩ፡ እንዘ፡ ይብል፡ ተንሥእ፡ ኦ፡ ምዉት። አጋንንት፡ እኩያን፡ እለ፡ ይሰርሩ፡ በነፋሳት፡ ወይነክንኩ፡ ነፍሳተ፡ እምሥጋ፡ ግብተ። ይነክንኩ፡ ሰጽቀዐ፡ በትእምርተ፡ መስቀል፡ (መጽ፡ ምስ። ስንክ፡ ታኅ፲፩። ግንዘ። ቅዳ)።

**ነክናኪ፤** የሚነቀንቅ፣ ወዝዋዥ፣ ነቅናቂ። ክና፣ ቀ፣ ይዋረሳሉ።

**ተነክነከ፤** ተነቀ(ቃ)ነቀ፤ ተወዘ(ዛ)ወዘ፣ ተናጠ፤ ተናወጠ። ዐምደ፡ ሃይማኖት፡ ዘኢይትነከነክ፡ እምኀይለ፡ ነፋሳት፡ (መጽ፡ ምስ። አርጋ፡ ፩)።

**ንክኑክ፤** የተናጋ፤ የተነቃነቀ።

**ንክናኬ፤(ላ፡ ጥ፡ ን)** መነቅነቅ፤ አነቃነቅ፤ ንቅንቃ፤ ውዝወዛ። አዕማድ፡ እለ፡ ኢይጸንኑ፡ በንክናኬ፡ (መጽ፡ ምስ)።

**ነክዐ፤(ዐረ፡ ነከዐ)፤** ነከየ፤ ነካ፣ ጐዳ፣ ጐነጠ። ዘሩ፣ ነከይ፣ ነው፤ የ፣ በዐ፣ ተለውጧል።

**አንኰዐ፤(ብ፡ እናኵዕ)፤** አንኮ፣ አናኮ፣ ደጕብ፤ ኰብኰብ፤ ቸግኝ፣ ፈንጣ፤ ግልግል፣ አንበጣ፣ የሚዘል፣ የሚፈናጠር። የገዳም፣ ረድ፤ አመከሬ፣ ዕንፊዐት፣ ሰባሪ። አንኮ፣ በተለይ፣ ዝንጀሮ፣ ይኾናል፤ አንኮ፣ በር፣ እንዲሉ። መጽሐፍ፣ ግን፣ በአንኰዕ፣ ፈንታ፣ እናኰዕ፣ ይላል፤ አንኰዕና፣ አንበጣ፣ ውስጠ፣ ብዙ፣ ናቸው፤ እናኰዕ፣ ግን፣ የብዙ፣ ብዙ፣ ነው፤ ከእናብጥ፣ ጋራ፣ ይስማማል። ወወሀበ፡ ለእናኵዕ፡ ፍሬሆሙ። እናኵዕ፡ ወአንበጣ። ይበልዖ፡ እናኵዕ፡ ለርስትሙ፡ (መዝ፡ ፸፯። ፪ዜና፡ ፯፡ ፳፰። ሆሴ፡ ፯)።

**ኒካዑ፤(ጽር፡ ኒካዖ። ዕብ፡ ንክ)፤** ንኩይ፣ ንኩዕ፣ ኀካ፣ ስባራ፣ ዐንካሳ። ፈርዖን፡ ኒካዑ፡ (፬ነገ፡ ፳፫፡ ፳፱)።

**ኔኪፉር፤(ክፈረ)፤** የሰው፣ ስም፤ ይቅር፣ ባይ፣ ጎዳኝ፣ በቀል፣ (ማር፡ ይሥ፡ መቅ)። ክፈረን፣ እይ፣ በነ፣ ምክንያት፣ ወደዚህ፣ መጥቷል።

**ንክፈት፤—ነቀፉ፥ንቅፈት—፤ነቀፈ።**

**ነኪር፤ሮት፤(ነከረ፡ ይነክር፡ ይንክር። ዐረ፡ ወሱር። ዕብ፡ ናኬር፤ ካደ፡ ከዳ)፤** መንከር፣ መዝለቅ፣ ክውሃ፣ ማግባት፣ (ዐማርኛ)። መለየት፣ ባዕድ፣ ማድረግ፤ እንደ፣ ሥጋና፣ እንደ፣ ቁርበት። መግረም፣ መድነቅ፤ ዕጹብ፣ ድንቅ፣ መኾን፣ የክፉ፣ የበጎ።

**ነኪር፤(ራን፡ ራት፡ ርት፡ ክር)፤** ልዩ፣ ሌላ፤ ባዕድ። ብእሲ፡ ነኪር። ሕዝብ፡ ነኪራን። አንስት፡ ነኪራት። ብእሲት፡ ነኪርት፡ (ዘዳ፲፯፡ ፲፭። ኢሳ፲፰፡ ፪። ነሐ፲፡ ፲። ምሳ፯፡ ፭)።

—፤ ግሩም፣ ድንቅ፣ ጉድ፣ ብርቅ፣ ልውጥ። በሕይወቱ፡ ገብረ፡ ነኪረ። ነኪር፡ ነገሩ፡ በእንቲአኪ። ወነ

ካር ፡ ይእቲ ፡ ለአዕይንቲነ ፡ (ሚራሟ፳ ፡ ፲፭ ፡ መገ ፡ ፹፯ ፡ ፶፲፯) ።

**ነኪራዊ** ፤ እንግዳ ፡ ባዕድ ፡ አፍኣዊ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ ፲፭ ፡ ፲፱) ። **ብእሲት ፡ ነኪራዊት** ፡ (ቀኖ ፡ ኒቅ) ።

**ነከራ** ፤ ድንቅ ፡ ታምር ፡ ድንቅነት ፡ ልዩነት ፤ ድንቂያ ፡ ኣቂያ ፡ ብልሜ ። **ቀቡዕ ፡ በቅብዐተ ፡ ነከራ ፡፡ በነከራ ፡ ተወልደ** ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ። **ሚጠተ ፡ ብርሃናት ፡ ነከራ ፡፡ በቃለ ፡ ማሕሌት ፡ ዘነከራ** ፡ (ሰንክ ፡ ሐምሌ፳፭ ፡ ጥር፲፱) ።

**አንከረ** ፤ አስለየ ፡ ልዩ ፡ አደረገ ። አነከረ ፡ አስነከረ ፤ አደነቀ ፡ አስደነቀ ። **አንከርዎ ፡ ዐበይት ፡፡ አንከርኩ ፡ ዘንተ ፡ ራእየ ፡፡ ኢታንክር ፡ እምዝንቱ ፡፡ ወዝኒ ፡ አኮ ፡ ለአንክሮ** ፡ (ኢዮ፲፰ ፡ ፳ ። ዳን፰ ፡ ፳፯ ። አፈ ፡ ተ፲፯ ። ፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬) ። በአንከረ ፡ ፈንታ ፡ አስተንከረ ፡ ቢል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ።

**አንካሪ ፤ መንከሪ ፤ መንክር** ፤ የሚያደንቅ ፡ የሚያስደንቅ ፡ አድናቂ ፡ አስደናቂ ።

**መንክር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት)** ፤ ድንቅ ፡ ታምር ፡ ልውጥ ፡ ነገር ፤ የሚደንቅ ፡ የሚያስደንቅ ፡ መደነቂያ ። **ገበርከ ፡ መንከረ ፡ ግብረ ፡፡ ናሁ ፡ እግዚ ፡ ይገብር ፡ መንከረ ፡፡ መንክርት ፡ ልደት ፡፡ ጎርጎርዮስ ፡ ገባሬ ፡ መንክራት** ፡ (ኢሳ፳፭ ፡ ፩ ። ዘጸ፴፬ ፡ ፲፭ ። መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፩) ።

**መንክራዊ ፤ (ዊት)** ፤ ታምራታም ፡ ባለታምራት ፡ አስደናቂ ። **ጎርጎርዮስ ፡ መንክራዊ ፡፡ ቅድስቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ክነት ፡ መንክራዊት ፡፡ ዐንቀ ፡ መንክራዊ** ፡ (ፈልክ ፡ ፪፻፴፱ ። አፈ ፡ ድ፴፪ ። እዋል) ።

**ተነክረ** ፤ ተነከረ ፡ ተዘረቀ ። ተለየ ፡ ተደነቀ ፡ ተመሰገነ ። **ተነከሩ ፡ ኃጥአን ፡ እማሕፀን ፡፡ ተነከርኩ ፡ በአዕይንቲሁ ፡ ኄየላን ፡፡ ይትነከር ፡ እምነበ ፡ መላእክት** ፡ (መዝ ፡ ፶፯ ። ጥበ፰ ፡ ፲፭ ። አርጋ ፡ ፫) ። ተደነቀ ፡ ማለት ፡ በማርኛው ፡ አድናቂነትንም ፡ ያሳያል ፡ ለግእዙ ፡ ግን ፡ አይስማማም ።

**ንኩር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ክርት)** ፤ የተነከረ ፤ ልዩ ፡ ድንቅ ፡ ውብ ፡ ምስጉን ። **ወንኩር ፡ ሥነ ፡ ላሕዩ ፡ ብርሃን ፡ ንኩር ፡፡ ንክርት ፡ ክብር** ፡ (ዮሴፍ ። ቄር ፡ ጸላ) ።


**ተናከረ** ፤ ተለየ ፡ ተለያየ ፤ ተላቀቀ ፡ ተፈራቀቀ ፡ እየብቻው ፡ ኾነ ፤ ተክዳ ፡ ተከካደ ። **ተናከራ ፡ ለዛቲ ፡ ዓለም ፡፡ ተናከርዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ቤት ፡፡ ተናከሮ ፡ እትናከሮሙ** ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፭ ። ኤር፲፫ ፡ ፬ ። ሆሴ ፡ ፯) ። ተዳነቀ ፡ ተደናነቀ ፡ ርስ ፡ በርሱ ።

**አስተናከረ** ፤ አናከረ ፡ አንካከረ ። አለያየ ፤ አዳነቀ ፡ አደናነቀ ። አንከረ ፡ ማድረግንና ፡ ማስደረግን ፡ ፪ቱን ፡ እንዲያሳይ ፤ አስተናከረም ፡ ማድረግን ፡ ጨምሮ ፡ ያሳያል ፡ አዳነቀ ፡ ማለት ፡ ገቢር ፡ ነውና ፤ አስተጋብሮም ፡ ይኾናል ። **ያስተናክሩ ፡ ሥነ ፡ ባህርዮሙ ፡፡ ዘአስተናከራ ፡ ለመለኮተ ፡ ወልድ** ፡ (ቄር ፡ ጸላ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ነኰርኳር ፤—ማልብጥብጦሽ ፤—ኰርኰረ ።**

**ነከሰ ፤ (ዐማርኛ ። ሱር ፡ ንካስ)** ፤ በቁሙ ፡ ነከሰ ፡ ነካከሰ ፡ ንክስ ፡ አደረገ ፡ በጥርሱ ፡ ያዘ ፤ ጋጠ ፡ ገመጠ ። ሰብራይስጡ ፡ ግን ፡ ናካሽ ፡ ብሎ ፡ ዐረመ ፡ ነቀስ ፡ ይላል ፡ ጠቅን ፡ እንጂ ፡ ጥርስን ፡ አያሳይም ።

**መንከስ** ፤ መንከሻ ፡ የፊት ፡ ጥርስ ፡ ክራንቻ ፡ መንጋጋ ። **ዐፅመ ፡ መንከስ** ፡ (መሳ፲፭ ፡ ፲፱—፲፯) ። **ተዐቀቡ ፡ እምልሳናቲክሙ ፡ እስመ ፡ ተቃትሎቱ ፡ ለብእሲ ፡ ማእከለ ፡ መንከሱ ፡ ውእቱ** ፡ (ፊላስ ፡ ገ፱፩) ። ነስክን ፡ እይ ፤ ሱርስቱ ፡ ንካስ ፡ ያለውን ፡ ሰብራይስጡ ፡ ናሻክ ፡ ይላል ፤ ግእዝ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ፪ቱም ፡ ነከሰ ፡ ነሰከ ፡ ይላል ።



መንከስ ።

**ናላ ፤—በቁሙ ፡ አንጎል ፤—ኖለወ ።**

**ኖለወ ፤—ጠበቀ ፤—ነውለወ ።**

**ኔሎቄ** ፤ ሙሎኬ ። የተሳሳተ ፡ ነው ፤ ሙለከን ፡ እይ ። **ዐፀ ፡ ሐዲስ ፡ ኔሎቄ** ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፳፱) ።

**ኖመ ፤—ተኛ ፤—ነዊም ፡ ኖመ ።**

**ነመረ ፤ (ይኔምር ፡ ይነምር ። ዕብ ፡ ናሜር)** ፤ በቁሙ ፤ አዝጕረጕረ ፤ ተዝጕረጕረ ፡ ዝንጕርጕር ፡ ኾነ ፤ ዐይነቱ ፡ መልኩ ፤ ሐበረን ፡ እይ ። ጣፈ ፡ ቈጠረ ፡ አመለከተ ፤ በፊደል ፡ በአኃዝ ፡ በንቅሳ ፤ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ማዝጕርጕር ፡ ነው ።

**ነምር ፤ (ብ ፡ አንማር ፤ አናምርት ። ዕብ ፡ ናሜር ። ዐረ ፡ ነሚር ። ሱር ፡ ኒምራ)** ፤ በቁሙ ፤ ነብር ፡ ሕንብርቡር ፤ ዝንጕርጕር ፤ ነጣቂ ፡ አውሬ ፡ የፍየል ፡ ጠላት ። **ይዌልጥኑ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ማእሶ ፡ ወነምር ፡ ሕንብርብሬሁ ፡፡ የዐርፍ ፡ ነምር ፡ ምስለ ፡ ጠሊ ፡፡ አድባረ ፡ አናምርት** ፡ (ኤር፲፫ ፡ ፳፫ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፮ ። ማሕ፬ ፡ ፰) ።



አናምርት ።

**ነምራዊ** ፤ ነብርማ ፡ የነብር ፡ ዐይነት ፡ ወገን ፡ ቀለሙ ። ነብራም ፡ ባለነብር ፤ የነብር ፡ በታ ፤ ወይም ፡ ጌታ ። **ስሳ ፡ አናብስት ፡ ግሩማን ፡ ወስሳ ፡ አናምርት ፡ ለለ ፡ ሠርቅ ፡ ይትለአኩክ ፡ ዘልፈ ፡ በብዙኅ ፡ ጻሕቅ** ፡ (ድራሲ) ።

**ንምራ ፤ አው ፡ ንምሮ ፤ (ላቲን ፡ ኑሜሩስ ፤ ኑሜሮ)** ፤ ቍጥር ፡ የቍጥር ፡ ምልክት ፡ አኃዝ ፡ ፊደል ፡ ንቅሳ ፡ ንጥብ ፡ ነጠብጣብ ፡ . . . . ።

## ኖን ፤ — ስመ ፡ ፊደል ፡ ነ ፤ — ነወነ ።

**ነነዌ ፤ (ዕብ ፡ ኒንዌ) ፤** ስመ ፡ ሀገር ፡ የአሶር ፡ መዲና ። ውቢቱ ፡ ውቢት ፡ ዐባይ ፡ ልዕልት ፡ ቀዳሚት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፲፩ ። ዮና፩ ፡ ፫) ።

**ነሢእ ፤ ኢት ፤ (ነሥእ ፡ ይነሥእ ፡ ይን ሣእ ። ዕብ ፡ ናሣእ) ፤** መንሣት ፡ መቀበል ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግ ። ንሥኡ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ። ብፁዕ ፡ ዘይ ሁብ ፡ እምዘይነሥእ ። ነሢእሰ ፡ ይትበሀል ፡ በእ ንተ ፡ ፀቅመ ፡ ትስብእቱ ፡ (ዮሐ፳ ፡ ፳፪ ። ግብ ፡ ፳ ፡ ፴፭ ። ሃይ ፡ አበ) ። የመንሣት ፡ ምስጢር ፡ ፪ ፡ ነው ፤ ከሰጪው ፡ እጅ ፡ በክፍል ፡ መቀበልና ፡ ከተቀባዩ ፡ እጅ ፡ መልሶ ፡ መውሰድ ፤ ወይም ፡ ሰጠኹ ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ መክዳት ። (ተረት) ፤ የሰጠ ፡ ቢነሣ ፡ የለበት ፡ ወቀሣ ። መክልክልና ፡ እንቢታም ፡ ነሢእ ፡ ይባላል ። (ግጥም ፡ ስለ ፡ አይሁድ) ፤ እኒህ ፡ ሥሡ ፡ ረ ፡ እኒህ ፡ ሥሡ ፡ ለዝናብ ፡ ጌታ ፡ ውሃ ፡ ነሡ ።

**ነሥእ ፤** ያዘ ፡ አነሣ ፡ ተሸከመ ፤ ወሰደ ፡ ይዞ ፡ ኼደ ። ነሥአ ፡ በእደዊሁ ፡ እሳተ ፡ ወመጥባሕተ ። ይነ ሥእዎ ፡ ፍርሀት ፡ ወረዓድ ። ንሥኡ ፡ ትእምርተ ፡ ለ አሕዛብ ። ንሥኡ ፡ አርዑትየ ፡ ላዕሌክሙ ። ነሥእ ፡ ዲያ ብሎስ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ። ነሥእዎ ፡ ኢየሱስ ፡ (ኩፋ ፡ ፳ ። ሔኖ፭ ፡ ፭ ። ኢሳ፷፪ ፡ ፲ ። ማቴ፲፭ ፡ ፳፱ ። ፱ ፡ ፭ ። ፲፯ ፡ ፮) ።

**ነሥእ ፤** አወሣ ፡ አሞሸ ፡ ቈዘመ ፡ ገሣ ፡ ቃሉን ፡ አነሣ ። ጕሥዐን ፡ እዩ ፡ የዚህ ፡ ጎሮ ፡ ነው ። ትንሥእ ፡ ቤአፉክ ፡ ሥርዐትየ ። ንሥኢ ፡ ሰቈቃወ ፡ በክናፍርኪ ። ንሣእ ፡ ሰቈቃወ ፡ ላዕለ ፡ (መዝ ፡ ፵፱ ። ኤር ፡ ፯ ፡ ፳፱ ። ሕዝ፲፱ ፡ ፩) ።

— ፤ መረጠ ፡ መርጦ ፡ ወሰደ ፡ አቀረበ ፡ ለሹመት ፡ ለባለ ሟልነት ። (ይቤ ፡ ንስጥሮስ) ፡ ኢኮነ ፡ ሥጋ ፡ ዘእግዚአ ብሔር ፡ ቃል ፤ አላ ፡ ነሥአ ፡ በብአ ፡ (ቄር ፡ እበት) ። በነ ሥአ ፡ ፈንታ ፡ አንሥአ ፡ ይላል ፤ አያስኼም ። እብነ ፡ መ ክራ ፡ ሶበ ፡ ያነሥእዎ ። ኢታንሥእ ፡ ክቡደ ። አንሥ እኒ ፡ መንፈስ ፡ ማእከለ ፡ (ሢራ፯ ፡ ፳፭ ። ፲፫ ፡ ፪ ። ሕዝ፰ ፡ ፫) ።

**ነሣኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤** የሚነሣ ፡ የሚያነሣ ፡ ነሺ ፡ አንሺ ፤ ተቀባዩ ፡ ያዥ ፡ ተሸካሚ ፡ መ ሳጅ ። ነሣኤ ፡ ዋሕስ ። ነሣኤ ፡ አክሊል ። ነሣኤ ፡ ሸጦ ። ትኩነኒ ፡ እምየ ፡ መቃብርየ ፡ ወማሕፀና ፡ ነሣኢትየ ። ነሣኢ ፡ ዘኢያገብእ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯ ። ስንክ ፡ የካ፳፭ ። ታኅ፲፰ ። ኤር፳ ፡ ፲፰ ። ግንዘ) ። ነሣኢ ፡ ገጽ ፡ ነሣኤ ፡ ገጽ ፡ ቢል ፡ (ዲድ ፡ ፱ ። ቅዳ) ፤ ዘይቤው ፡ መንሣት ፡ መቀ በል ፡ ምስጢሩ ፡ አድላዊነትና ፡ ግብዝነት ፡ ነው ፡ (ሄኖ ፡ ፲፯ ፡ ፯) ።

**አንሥእ ፤** አነሣ ፡ አቀና ፡ አስነሣ ። አንሥእት ፡ ገጸ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ። አንሥእ ፡ እገሪሁ ፡ ወሖረ ። አነሥእዎ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ሰፋርስ ። ንጉሥሙ ፡ ዘአ ሥነእ ፡ ሎሙ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፭ ። ፳፯ ። ኢሳ፲፫ ፡ ፲፯ ። ኤር ፵ ፡ ፯) ። በአንሥአ ፡ ፈንታ ፡ አስተናሥአ ፡ መኳንንተ ። ያስ ተናሥእ ፡ ጽልአ ፡ ወሀከክ ፡ ይላል ፤ አስተናሥእን ፡ እዩ ።

**እንሣኢ ፤ መንሥኢ ፤** የሚያነሣ ፡ የሚያ ስነሣ ፡ አንሽ ፡ አስነሽ ። መንሥኤ ፡ ነዳያን ፡ እምድር ። መንሥኤ ፡ ውዱቃን ። መንሥኢሆሙ ፡ ለምዉታን ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፳፰ ። መቃ ፡ ገ፲፯ ። ግንዘ) ።

**ምንሣእ ፤** መንሻ ፡ መንሾ ፡ መውሰጃ ፡ መቀ በያ ። ጕብ ፡ ማማሰጃ ። አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለመደልዋን ፡ እለ ፡ ያጸድቅዎ ፡ ለኃጥእ ፡ በእንተ ፡ ምንሣእ ፡ (ኪዳ) ።

**ተነሥአ ፤** ተወሰደ ፡ ተመረጠ ። አመ ፡ ይትነ ሣእ ፡ እምኔሆሙ ። ለዘተነሥአ ፡ እምኔሁ ፡ ብእሲ ፡ (ማቴ፱ ፡ ፲፭ ። ቄር ፡ ጳላ) ።

**ተንሥአ ፤** ተነሣ ፡ ነቃ ፡ በቃ ፡ ሰቀቀ ፡ አፍ ፡ አፈፍ ፡ በድረግ ፡ አለ ፡ ቆመ ፡ በእግር ፡ በነገር ። ተንሥእ ፡ ከመ ፡ ዘንቃህ ፡ እምንዋም ። ኢይክል ፡ ተንሥአ ፡ ቅ ድሜከ ። እለ ፡ ይትነሥኡ ፡ ላዕሌየ ። እመሰ ፡ ይክ ሕዱ ፡ ምስጢረ ፡ ትንሣኤ ፡ ይትነሥእዎሙ ፡ ሐዋ ርያት ፡ (መዝ ፡ ፸፯ ። ዘፍ፴፩ ፡ ፴፭ ። ኢዮ፳፯ ፡ ፯ ። ቄር ፡ ጳላ) ። ነቅሀንና ፡ ቆመን ፡ እዩ ፡ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**ንሡእ ፤ (እን ፡ ኢት ፡ ሥእት) ፤** የተነሣ ፡ የተወሰደ ፡ ምርጥ ፡ ምልምል ።

**ንሥኢት ፤** መንሣት ፡ መንሣት ፡ አነሣሥ ፡ አ ቀባበል ፡ ቅበላ ። ቦ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ከመ ፡ ይከውን ፡ ንሥአተ ፡ መንፈስ ፡ ሕይወት ፡ ውስተ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለሕፃናት ፡ እምንፍኀተ ፡ መንፈሱ ፡ ለእግዚ ። ንሥ አተ ፡ ቅዱስ ፡ ምስጢር ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ቅዳ ፡ ሐዋ ። ዮሐ) ።

**ትንሣኤ ፤** በቁሙ ፡ መንሣት ፡ አነሣሥ ፡ መው ጣት ፡ ብቅ ፡ ማለት ፡ መታደስ ፡ መብቀል ፡ ሐዲስ ፡ ሕይ ወት ። ትንሣኤ ፡ ፀር ። ትንሣኤ ፡ ፈያት ። ትንሣኤ ፡ መዋግድ ። ትንሣኤ ፡ ፀሓይ ። ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ትንሣኤሁ ፡ ገብረ ፡ በሰንበት ፡ (ቅዳ ። ኪዳ ። መጽ ፡ ምስ ። ኩፋ ፡ ፫ ። ማቴ፳፰ ፡ ፳፫ ። ድጓ) ።



ትንሣኤ ፡

**ተናሥአ ፤** ተናሣ ፡ ተነሣሣ ፡ ተቃወመ ፡ ተቀ ቋመ ። ጽኑዕ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይትናሥእዎ ፡ ነገሥት

(ቅዳ ፡ ኢዲ.) ። በትንሥኤ ፡ ፈንታ ፡ ተናሥኦ ፡ ይላል ፡ የተደራጊ ፡ ተደራራጊ ፡ ነው ፡ ተፋለሰ ፡ እንደ ፡ ማለት ።

እስተናሥኦ ፤ አናግ ፡ አንግግግ ፡ አወከ ። አድራጊና ፡ አደራራጊ ፡ ነው ፡ ባድራጊነቱ ፡ የአንሥኦ ፡ ድርብ ። ጸላእቶ ፡ ያስተናሥእ ። ረድኤቱ ፡ ወእስተናሥኦቱ ። ዝንቱ ፡ ግብር ፡ አስተናሥኦ ፡ ለይእቲ ፡ ብእሲት ። ያስተናሥእ ፡ ኀሊና ፡ ወየሀውክ ፡ (ኢሳ ፲፱ ፡ ፲፭ ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፮ ። አፈ ፡ ድ፹፮ ። ፊላስ ፡ ገ፶፮) ።

መስተናሥኦ ፤ (እት ፡ ኣን ፡ ኣት) ፤ አስተናግጊ ፡ የሚያናግግ ፡ የሚያነግግግ ፡ አነግግሽ ፡ ጉበኝሽ ። ሥርዐ ፡ መስተናሥኣኒ ፡ ለግብረ ፡ ቤተ ፡ እግዚ ፡ (አቡሻ ፡ ፳፫) ።

ነሥገ ፤ (ነሢግ ። ዕብ ፡ ናሣግ ፤ ተመለሰ) ፤ ሰነግ ፡ ቈለፈ ፤ ወረወረ ፡ የመዝጊያ ። የሐውር ፡ በዓለ ፡ ቤት ፡ ነሢገ ፡ ወቀቲሮ ። አንቀጸ ፡ ዝናም ፡ ኤልያስ ፡ ነሥገ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ። ድ፴) ። ንቅግን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

ተነሥገ ፤ ተሰነገ ፡ ተዘጋ ፡ ተቈለፈ ።

ንሡግ ፤ (ጋን ፡ ጋት ፡ ሥጋት) ፤ የተሰነገ ፡ ሰንግ ፡ የተቈለፈ ፡ ዝግ ። ረከብነ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ንሡገ ፡ ወቅቱረ ፡ (ግብ፳ ፡ ፳፫) ።

መንሥግ ፤ (ብ ፡ መናሥግት) ፤ መሰንጊያ ፡ ሰናግ ፡ መወርወሪያ ፤ መቈለፊያ ፡ ቍልፍ ። እደ ፡ መንሥግ ። ወመንሥግ ፡ ዘማእከለ ፡ ዐምድ ። እመ ፡ ወደይከ ፡ ማዕጾ ፡ ወመንሥገ ፡ ላዕለ ፡ አፉከ ። አቀመ ፡ ኆኅተ ፡ ወገብረ ፡ መናሥግተ ። መዓጹት ፡ ወመናሥግት ፡ (ማሕ፰ ፡ ፳ ። ዘፀ፳፯ ፡ ፳፰ ። ሢራ፳፰ ፡ ፳፭ ። ነሐ፫ ፡ ፲፫ ። ኢዮ፴፰ ፡ ፲) ።

—፤ በር ፡ ደጃፍ ፡ መዝጊያ ፤ ማገቶም ። ይሞቅሕከ ፡ ወይወሀይከ ፡ ውስተ ፡ መንሥግ ፡ ሲኦል ። ዘይንግል ፡ መናሥግተ ፡ ሲዖርኒም ፡ (ቀሌ ። ድ፴) ።

ነሠወ ፤—ፈተነ ፤—ነሲው ፡ ነሰወ ።

ኔሣን ፤—የወር ፡ ስም ፤—ኔስ ፡ ኔሳን ።

ነሥነሠ ፤—ነሰነሰ ፤—ነሲስ ፡ ነሰ ፤ ነስነሰ ።

ነሢት ፤ ቶት ፤ (ነሠተ ፡ ይነሥት ፡ ይንሥት ። ዕብ ፡ ናታሽ ፤ ናታጽ ፥ ነቀለ ፡ አፈረሰ ። ናሻት ፡ ደረቀ ፥ ፈረሰ ፡ ተናደ) ፤ ማፍረስ ፡ መስበር ፡ መናድ ፡ መቈፈር ፡ መንቀል ፡ መፈንቀል ፡ መገልበጥ ፡ ገፍቶ ፡ መጣል ። ጊዜ ፡ ለነሢት ። እመ ፡ ነሠተ ፡ መኑ ፡ የሐንጽ ። ነሠቱ ፡ ብንጺን ፡ አቅርንተ ፡ ምሥዋዒከ ። እነሥት ፡ ጸቈና ። ነሠተ ፡ አህጉረ ። ነሠተ ፡ መናብርቲሆሙ ፡ ለመላእክት ፡ (መክ፫ ፡ ፫ ። ኢዮ፲፪ ፡ ፲፬ ። ዮዲ፱ ፡ ፰ ። ኢሳ፳ ፡ ፳ ። ፲፬ ፡ ፲፯ ። ሚሬ፲ ፡ ፲፱) ። ፈትሖ ፡ ሰዐረ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ነሠተ ፡ ይላል ፡ (ግብ ፲፱ ፡ ፴፱ ፡ ፺) ።

ነሣቲ ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤ የሚያፈርስ ፡ አፍራሽ ፡ ነቃይ ፡ ፈንቃይ ፡ አጥፊ ፡ ገዳይ ። ነሣቲሃ ፡ ለሐግ ። ሳዊሮስ ፡ ዕልዋኒ ፡ በሰይፈ ፡ ሃይማኖት ፡ ነሣቲ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ታኅ፲) ።

አንሠተ ፤ አነሠተ ፡ አስነሠተ ። አንስት ፡ ማስት ፡ ክዚህ ፡ ወጥቷል ፡ (ጕራጊ) ።

ተነሥተ ፤ (ተነሠተ ፡ ተንቀለ ፡ እንስቱ) ፡ ፈረሰ ፡ ፈራረሰ ። ተነሥተ ፡ መቅደስ ። ከመ ፡ ሀለዋ ፡ ትትነሠት ። ወኢይትነሠት ፡ እንከ ፡ (ሱቱ ፡ ዕዝ፲ ፡ ፳፰ ። ጦቢ፲፬ ፡ ፬ ። ኤር፴፰ ፡ ፵) ።

ንሡት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ሥት) ፤ የፈረሰ ፡ የተፈታ ፡ ፍራሽ ፡ ጠፍ ፡ ባድማ ። ናሕስ ፡ ንሡት ። ወረከብዎ ፡ ንሡተ ፡ ለምሥዋዕ ። ተሐንጸት ፡ አረፍታ ፡ ወኢተርፈ ፡ ንሡት ፡ ላዕሌሃ ፡ (ምሳ፳፬ ፡ ፴፱ ። መሳ፮ ፡ ፳፰ ። ነሐ፮ ፡ ፩) ። ግሑሥ ፡ ርሑቅ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ንሡት ፡ ከንኤክ ፡ ይላል ።

ንሥተት ፤ መፍረስ ፤ ማፍረስ ፡ አፈራረስ ፤ ፍርሻ ፡ ፍራሽ ። እስከ ፡ ንሥቴተ ፡ መቅደስ ፡ ዳግም ። ንሥተተ ፡ ሥርዐተ ፡ ሰብሳብ ። ንሥተተ ፡ ዚአሁ ፡ (ዮሴፍ ። ጥበ፲፱ ፡ ፳፮ ። ማር ፡ ይሥ፲፪ ፡ ፪) ።

ናሥታ ፤ መጋቢያ ፤ የፍርድ ፡ ቃል ፡ በይግባኝ ፡ የሚፈርስ ፡ የሚገለስ ። አስትሞ ፤ እጅ ፡ መንሻ ፡ ግብር ፡ ወይም ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ ስትዕን ፡ እይ ። ወሤመ ፡ ውስተ ፡ መንግሥቱ ፡ ምእተ ፡ ወዕሥራ ፡ መሳፍንተ ፤ ወሠለስቱ ፡ ይትሌዐሉ ፡ እምኔሆሙ ፡ ከመ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ያግብኡ ፡ ናሥታ ፡ (ዳን፮ ፡ ፩ ፡ ፪) ።

ኔሥታሊ ፤—የባብ ፡ ምስል ፤—ኔስ ፡ ኔሳን ።

ነዐ ፤—ና ፡ ምጣ ፤—ነዐወ ።

ንዕደ ፤—አከበረ ፤—ንኢድ ፡ ንእደ ።

ነዐወ ፤ (ንዒው ። ዕብ ፡ ናዕ ፤ ናወዘ ፡ ተቅበዘበዘ) ፤ ዐደነ ፡ ከደነ ፡ ገባ ፤ ሻ ፡ ፈለገ ፤ አደባ ፡ ሸመቀ ፡ ወጥመድ ፡ አኖረ ፡ ለመያዝ ፡ ለመግደል ። ጠራ ፡ ና ፡ ወዲህ ፡ አለ ፡ ሳበ ፡ አቀረበ ፡ በቃል ፡ በፉጨት ። ባእ ፡ ሐቅለ ፡ ወነዐው ፡ ሊተ ። ንዒወ ፡ ነዐዉኒ ፡ ፀርየ ፡ ከመ ፡ ዖፍ ። ዘይነዑ ፡ ክብረ ፡ እምኀበ ፡ ሰብእ ። ይደኀሕ ፡ ወይነዑ ። ከመ ፡ ይንዐወኒ ፡ መንገሌሁ ፡ (ዘፍ፳፯ ፡ ፫ ። ሰቈ፫ ፡ ፶፩ ። ማር ፡ ይሥ፩ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፱ ። አፈ ፡ ድ፳) ።

ነዓዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ዐውት) ፤ የሚያድን ፡ ዐዳኝ ፡ ፈላጊ ። ለምንት ፡ ኮንከ ፡ ነዓዌ ፡ አራዊት ። መሥገርት ፡ ነዓዊት ። እለ ፡ ይንዕዉ ፡ ነዐውት ፡ (ገድ ፡ ተክ ። መዝ ፡ ፺፩ ። ሆሴ፭ ፡ ፱) ።

ተንዕወ ፤ ታደነ ፡ ተያዘ ፡ ከወጥመድ ፡ ገባ ። መዋኢ ፡ ተሞአ ፡ ወነዓዊ ፡ ተንዐወ ። ይትነዐዉ ፡ እመ ፡ ንኅለ ፡ ሐዘን ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ማር ፡ ይሥ፱ ፡ ፲፩) ። ተጠራ ፡ ና ፡ ወዲህ ፡ ተባለ ፡ ተሳበ ፡ ቀረበ ፤ ተጠርቶ ፡ መጣ ።

ንዑው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ዑት ፤ ዕውት) ፤ የታደነ ፡ የተያዘ ፡ ዕዱን ።

ንዕወት ፤ ማደን ፡ መታደን ፡ አስተዳደን ፡ ዕደና ፡ ዐደን ። አራዊት ፡ መማጥዮን ፡ እለ ፡ ኢይሜንዩ ፡

ለንዕወት ። መካኑ ፡ ንዕወት ። ዘይሜህር ፡ ንዕወተ ፤ ሰው ፡ ቀትለ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፬ ። ሳዊ ። ቄስጠ) ።

**ናዕዊ ፤ ንዓዊ ፤** ገዳኒ ፡ ከማሁ ፤ ዐይን ። ወመጽአ ፡ ጌሳው ፡ እምንዓዊሁ ። ንሣእ ፡ ንዋየ ፡ ናዕዌከ ። ዘነዐወ ፡ ናዕዌ ፡ ወቀተለ ፡ አርዌ ፡ (ዘፍጥረት ፡ ፳፯ ። ኩፋ ፡ ፳፯ ። ዘሌዋውያን ፡ ፲፫) ።

**ምንዓው ፤** ማደኛ ፡ መታደኛ ፤ ደን ፡ ዱር ፡ በረሓ ። ምንዓወ ፡ ሀየላት ፡ (፩ነገ ፡ ፳፬ ፡ ፫) ።

**ነዐ ፤ (ንዑ ፡ ንዒ ፡ ንዓ) ፤** ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፤ ላሬቱ ፡ ሰራዊት ፡ ለቅርቦች ፡ ብቻ ። ና ፡ ምጣ ፤ ቅረብ ። ነዐ ፡ ኀቤየ ። ንዑ ፡ ትልዉኒ ። ንዒ ፡ ዝየ ፡ ወብልዒ ። ንዓ ፡ ትርአየ ፡ መካኖ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፵፬ ። ማቴ፬ ፡ ፲፱ ። ሩት፪ ፡ ፲፬ ። ማቴ፳፰ ፡ ፮) ። የመሀበኝ ፡ ትእዛዝ ፡ ሀብ ፡ (ቡ ፡ ቢ ፡ ባ)ን ፡ እይ ፤ ይኸም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። ጎላሬውና ፡ ትንቢቱ ፡ ዘንዱ ፤ ተነዐውከ ፡ (ክሙ ፡ ኪ ፡ ክን) ፤ ትትነዐው ፡ (ዉ ፡ ዊ ፡ ዋ) ፡ ቢኾን ፤ ትእዛዛቱን ፡ ተነዐው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ቱንና ፡ ወን ፡ ጐርደ ፡ ነዐ ፡ (ንዑ ፡ ዒ ፡ ዓ) ፡ ይላል ። ዐመሎች ፡ (አዐ ፡ ሀሐን ፡ ወየ) ፡ ያሉት ፡ ግስ ፡ መጕረድና ፡ መዋጥ ፡ መንገድ ፡ መለወጥ ፡ ሕጉ ፡ ነው ።

**ነዐለ ፤ (ይንዕል ፡ ይንዐል ፤ ንዒል ። ዐረ ፡ ወዕብ) ፤** ተጫማ ፤ ጫማ ፡ ለበሰ ፡ ቈሰፈ ፡ ዘጋ ።

**ንዓል ፤ አው ፡ ናዕል ፤** ጫማ ፡ መጫሚያ ፤ የግር ፡ ልብስ ፡ የሚወልቅ ።

**ንዑልት ፤ (ትግ ፡ ሐብ ፡ ነዕልት ። ዕብ ፡ ይብማ ፤ ይቤሜት ፤ ምራት) ፤** የተጫማች ፡ ባለጫማ ፤ ጫማ ፡ የምትሬታ ፡ የምታወልቅ ፤ አይት ፤ የወንድም ፡ ሚስት ፡ ዋርሳ ፤ ባሏ ፡ ሳይወልድላት ፡ ቢሞት ፡ ወንድሙ ፡ የቅርብ ፡ ዘመዱ ፡ የሚወርሳት ። አልወርስም ፡ ቢላት ፡ ግን ፡ በአረቱ ፡ ምርዐት ፡ ጫማውን ፡ ከግሩ ፡ ታወልቅበታለች ፤ በፊቱም ፡ ትተፋበታለች ፤ ንዑልት ፡ ያሰኛት ፡ ይህ ፡ ጫማ ፡ ማውለቅ ፡ ነው ። ይቤሎ ፡ ይሁዳ ፡ ለአውናን ፡ ወልዱ ፤ ባእ ፡ ኀበ ፡ ብእሲተ ፡ እኁከ ፡ ወረስያ ፡ ንዑልተከ ፡ ወአንሥእ ፡ ዘርዐ ፡ ለእኁከ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፩ ። ዘዳግም ፡ ፳፭—፲ ። ሩት ፬ ፡ ፯ ፡ ፰) ።

**ንዕሰ ፤—እንስ ፤—ንኢስ ፡ ንእስ ።**

**ናዕት ፤—ቂጣ ፤—ነዩእ ፡ ኔእ ፡ ናእት ።**

**ነፍግ ፤ አው ፡ ነፈግ ፤** በቁሙ ፡ ማግ ፡ ሠሠት ፡ ቤስ ፤ ንፉግ ፡ ኾነ ።

**ንፍግት ፤** በቁሙ ፡ ሥሥት ፡ ቢስነት ። ንፍግት ፡ ለነዳይ ፡ ወውሂብ ፡ ለባዕል ፡ (መጽ ፡ ኑዛ) ። ደንጸወኝና ፡ ቂቀየን ፡ መትሀን ፡ እይ ።

**ተነፍገ ፤ ተንፈገ ፤ (ፈጊግ ፡ ፈገ ፡ ፈገገ) ፤** ተነፈገ ፤ ገማ ፡ ከረፋ ፡ ትንፋጋም ፡ ኾነ ።

**ናፌድም ፤—ውዱቃን ፤—ናፌሊም ፡ ናፊል ።**

**ነፍኀ ፤ (ዐረ ፡ ነፈኀ ። ዕብ ፡ ናፋሕ ። ሱር ፡ ንፋሕ) ፤** ነፋ ፡ ቀበጠጠ ፡ አባበጠ ፡ የደዊ ፡ የትንፋሽ ። ዘንቱ ፡ ማይ ፡ ይነፍኅ ፡ ኵሎ ፡ ሥጋሃ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፯ ። ዘኍል ፡ ፭፳) ።

—፤ አነፋ ፡ አናፋ ፡ ፊኸ ፡ አስፊኸ ፡ በትንፋሽ ፡ የመለከት ፤ አነፈን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ግር ፡ ነው ። ንፍኁ ፡ ቀርነ ። ይነፍኅ ፡ በቀርን ፡ ዐቢይ ፡ (ሆሴዕ ፡ ፭ ። ኢሳይያስ ፡ ፲፰) ።

—፤ እፍ ፡ አለ ፡ ተነፈሰ ፤ ትንፋሽ ፡ አወጣ ፤ ለመምላትና ፡ ለማሳደር ፡ ለመንፋት ፡ ለማንደድ ፡ ወይም ፡ ለማራቅ ፡ ለማዕገድ ፤ የአፍ ፡ የወናፍ ። እመ ፡ ነፋኅካሃ ፡ ለፍሕም ፡ ትነድድ ። ነፍኃ ፡ ላዕሌሆሙ ። እመ ፡ ኢረከቡ ፡ ማየ ፡ ይንፍኁ ፡ እደዊሆሙ ። አባእክሙ ፡ ቤተ ፡ ወነፋኅክምዎ ፡ (ሢራ ፳፰ ፡ ፲፪ ። ዮሐ ፳ ፡ ፳፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፬ ። ሐጌ ፩ ፡ ፱) ።

—፤ ነፈሰ ፡ ነፋፈሰ ፡ ሽው ፡ ሽው ፡ አለ ፤ የአየር ፡ የነፋስ ፤ ነፍሰን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ይነፍኅ ፡ ነፋስ ፡ ጽባሓዊ ። ንፍኁ ፡ ነፋሳት ። ተንሥእ ፡ ሰሜን ፡ ወነዐ ፡ ደቡብ ፡ ወንፍኅ ፡ ገነትየ ፡ (ሢራ ፵፫ ፡ ፲፮ ። ማቴ ፯ ፡ ፳፭ ። ማሕ ፬ ፡ ፲፮) ።

**ነፋኂ ፤ (ኂት ፡ ኃያን ፡ ያት ፤ ኃት) ፤** የሚነፋ ፡ ነፊ ፤ መቾ ፡ አጋፋች ። ነፋኄ ፡ ቀርን ። ነፋኄ ፡ እንዚራ ፡ ወተውኔት ፡ (ነሐ ፯ ፡ ፷፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፱ ፡ ፩) ።

**ምንፋኅ ፤ (ኃት) ፤** መንፊያ ፡ ማናፊያ ፡ እፍ ፡ እፍ ፡ መባያ ፤ እፍ ፡ ወናፍ ፡ ትንፋሽ ።

**አንፍኀ ፤** አስነፋ ፤ አስመታ ። ወአንፍኀ ፡ ቀርነ ፡ ኢዮአብ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ። ፳ ፡ ፩) ።

—፤ አነፈሰ ፤ ነፋስ ፡ አመጣ ፤ እፍ ፡ እፍ ፡ አሰኘ ፤ አስነፈሰ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአንፍኅ ፡ ፈንታ ፡ ነፍኀ ፡ ይላል ፤ የመሳሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ይነፍኅ ፡ መንፈሶ ፡ (መዝ ፡ ፻፵፯) ።

**ተነፍኀ ፤** ተነፋ ፤ ዐበጠ ፡ ታበየ ፤ ተቈጣ ፡ አኰረፈ ። ዘተነፍኀ ፡ ከርሦ ። እንዘ ፡ ትትነፋኅ ፡ ላዕሌነ ። ተነፍኆ ፡ ልብ ፡ (መ ፡ ፈ ። ተረ ፡ ቄርሎ ። ዮሴፍ) ።

—፤ ተነፋ ፤ ተመታ ፡ ጮኸ ። ኢየአምን ፡ እስከ ፡ ይትነፋኅ ፡ ቀርን ። ወይትነፋኅ ፡ ቀርን ፡ ሣልስተ ፡ ጊዜ ፡ በአፈ ፡ ሚካኤል ፡ (ኢዮ ፴፱ ፡ ፳፬ ። ቀሌ) ።

—፤ ተነፈሰ ፡ እፍ ፡ እፍ ፡ ተባለ ፡ ነፋስና ፡ ትንፋሽ ፡ ተቀበለ ። ተተነፈሰ ፡ ትንፋሹ ፤ ተተነፈሰበት ፤ ተቀባዩ ። ተነፍኀ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚ ፡ (መቃ ፡ ገ፳) ።

**ንፉኅ ፤ (ኃን ፡ ኃት ፡ ፍኅት) ፤** የተነፋ ፡ ያበጠ ፤ ዕቡይ ፡ ኵሩ ። ሥዕለ ፡ ነጌያት ፡ ዘብርት ፡ ንፉኅ ። ዕቡየ ፡ ዐይን ፡ ወንፉኅ ፡ ልብ ፡ (ዮሴፍ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ንፍኀት ፤** መንፋት ፡ መነፋት ፤ እንፋፍ ፡ ንፋት ፡ ንፍፊት ፡ ዕብጠት ። መንፈስ ፡ መተንፈስ ፤ እፍ ፡ ማለት ፡ እፍታ ፡ ትንፋሽ ፤ ጸጋ ፡ ሀብት ። በደኃሪ ፡ ንፍኀት ፡ ቀርን ። ፈትለ ፡ ሣሬት ፡ ኢይክል ፡ ተዐግሦ ፡ ንፍኀተ ፡ ነፋስ ። ወዓደ ፡ አክበሮ ፡ በንፍኀቱ ። ተውህቦ ፡ ንፍኀተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ንፍኀተ ፡ እስትንፋስ ፡ አፉሁ ። ወነሥአ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ንፍኀተ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፶፪ ። አፈ ፡ ተ፴፱ ፡ መቅ ፡ ወን ። ቀሌ ። አርጋ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

**ነፍጥ ፡ (ዕብ ፡ ኣፍጥ) ፤** ጋዝ ፤ የጋዝ ፡ ዐይነት ፤ ከምድር ፡ የሚወጣ ፡ የምድር ፡ ቅባት ፤ የሚቃጠልና ፡ የሚበራ ፡ ፈሳሽ ። ዐይን ፡ ዘታንቅዐ ፡ ነፍጠ ፤ ወነፍጥኒ ፡ ይወፅእ ፡ ላዕለ ፡ ገጸ ፡ ማይ ፡ (ዮሴፍ) ።

—፤ በቍሙ ፡ ጠመንጃ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፤ በቀስትና ፡ በፍላጻ ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፤ ብዙ ፡ ስምና ፡ ዐይነት ፡ ያለው ፤ ጪኺ ፡ ፈጣን ፡ እሳታም ። ወነደፍዎ ፡ ለግራኝ ፡ በነፍጥ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ። ያፍንጫ ፡ ዛሕል ፡ ንፍጥ ፡ ምስጢሩ ፡ ፈሳሽነት ፡ ነው ። (ስድብና ፡ ተረት) ፤ ንፍጣም ፤ የንፍጥ ፡ ዋንጫ ። አላዋቂ ፡ ሳሚ ፡ ንፍጥ ፡ ይለቀልቃል ።




ነፍጥ ፡

**ነፈጠ ፤** ጋዘ ፡ አወጣ ፤ ተኰሰ ፡ አቃጠለ ፤ እንፍ ፡ አለ ፤ ተናፈጠ ።

**ነፈየ ፤ (ነፍይ ። ዕብ ፡ ናፉሀ) ፤** ነፋ ፡ አን ዘረዘረ ፤ ነቀነቀ ፡ አዘረ ፡ ወዘወዘ ። ዘርዘረን ፡ እዩ ፡ (መ ፡ ፈ) ። ነፈየና ፡ ነፍን ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ። (ግጥም ፡ ደብተራ ፡ ሚስቱ ፡ ተቈጥታ ፡ ስላኰረፈች) ፤ እንደ ፡ ሰው ፡ ገርድፋ ፡ መች ፡ ትተወጥለች ፤ ተንፋች ፡ ደስታ ፡ ትሠልቀጥለች ።

**ነፋዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤** የሚነፋ ፡ ነፊ ፤ አጥሪ ፡ አንዘርዛሪ ።

**መንፌ ፤ (ያት ፡ ያታት) ፤** መንፊያ ፡ ማጥሪያ ፡ ማንዘርዘሪያ ፤ ወንፊት ፡ ወንጠፍት ። ይጺውር ፡ ማየ ፡ በመንፌ ። ፀቍሩ ፡ ማየ ፡ በመንፌ ፡ ወኢትክዕወ ፡ ማይ ። ወይሠይጥ ፡ መንፌያታተ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። መጽ ፡ ምስ ። ፊልክ ፡ ፻፹፱) ።



መንፌ ፡

**ናፈለ ፤ (ናፍሎ ። ዕብ ፡ ናፉል) ፤** ወደቀ ፡ ተወረወረ ፤ ወረደ ፡ ተጣለ ፡ ተምዘገዘገ ፤ በፈቃዱ ፤ የትቢትና ፡ የጥጋብ ፡ እንደ ፡ ዲያብሎስ ።

**ናፌል ፤ (ጽር ፡ ናፈሊም ። ዕብ ፡ ናፈል ፤ ንፈሊም) ፤** ናፋሊ ፡ ንፉል ፤ የወደቀ ፡ ውዱቅ ፤ ዓናቃዊ ፡ ረዐይታዊ ፤ ጋኔን ። ም ፡ አብዝ ፡ ነው ፤ ውዱቃን ፡ ያሰኛል ፤ በናፈልም ፡ ፈንታ ፡ ናፈዲ(ይ)ም ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ባስብሎዮች ፡ ግን ፡ ፪ ፡ ቃል ፡ መስሏቸው ፡ ናፌድምን ፡ ኀያላን ፤ ናፊልን ፡ ድኩም ፡ ይሉታል ፤ ዓናቅን ፡ እዩ ፡ (ፊእ፲፱ ፡ ፱) ። ወወሊዱ ፡ ውሉደ ፡ ናፌ
ድመ ፤ ወዘሎሙ ፡ ኢይትማሰሉ ፤ ወይበልዕ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ ካልአ ፤ ያርብሕ ፡ በልዖ ፡ ለናፊል ፡ ወናፊል ፡ ለኤልዩ ፡ (ኩፉ ፡ ፯) ።

**ነፍነፈ ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ማ ። ነፊፍ ፡ ነፊ ፡ ነፈፈ) ፤** ነፈነፈ ፤ አብዝቶ ፡ በላ ፤ ነፈጠ ፡ ጋጠ ፤ የንስሳና ፡ ያውሬ ፡ የሆዳም ፡ (ዐማርኛ) ። አካፋ ፡ ወረደ ፡ ተረጨ ፡ በነነ ፤ የውሃ ፤ ከዝናም ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ በጉም ፡ ጊዜ ። ወዝናምሂ ፡ ኢነፍነፈ ፡ እንከ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ኢለክፎ ፡ ዝናም ፡ ዘነፍነፈ ፡ (ዘፀ፱ ፡ ፴፫ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፱) ። አነፈን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ነፍኒፍ ፤** ካፊያ ፡ የጉም ፡ ሽንት ፤ የዝናም ፡ ተረፍ ፡ ቅሬታው ፡ ጭላጩ ፤ ልዝብ ፡ ዝናም ። ያርሕሰሙ ፡ ነፍኒፍ ፡ ወጠለ ፡ ገዳም ። ነፍኒፈ ፡ ሌሊት ። ወረደ ፡ ጠል ፡ ከመ ፡ ነፍኒፈ ፡ ዝናም ። ንሴፎ ፡ ዝናም ፡ ቶርፈ ፡ ነፍኒፍ ። ወይከውን ፡ በነፍኒፎሙ ፡ ለዝንቱ ፡ ሕዝብ ፡ (ኢዮ፴፱ ፡ ፳ ። ማሕ፭ ፡ ፪ ። ገድ ፡ ተክ ። ሱቱ ፡ ዕገ ፡ ፪ ። ሚክ፪ ፡ ፲፩) ።

**ነፌፍ ፤ (ነፈ ፤ ነፈፈ ፡ ይነፍፍ ፡ ይንፍፍ ። ዕብ ፡ ናፌፍ) ፤** ማረም ፤ መኰትኰት ። ነፋፊ ፡ መኾን ፤ ምኝንት ፡ ነፋፍነት ። ለፈፈን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ነፍጸ ፤ አው ፡ ነፈጸ ፤ (ነፊጽ ። ዕብ ፡ ናፉጽ) ፤** ሸሸ ፡ ፊቀ ፤ ኰበለለ ፡ ጠፋ ፡ ታጣ ፤ በነነ ፡ ተዘራ ፡ ተበተነ ። ነፍጹ ፡ ንዋም ፡ እምአዕይንትየ ። ነፍጸ ፡ ሕዝብ ። አይቴ ፡ ትነፍጹ ። ነፍጸ ፡ እምገጸ ፡ ሰብእ ፡ (ዘፍ፴፩ ፡ ፵ ። ዘፀ፲፬ ፡ ፳ ። ሔኖ ። ስንክ ፡ ሚያ፲) ።

**ነፋጺ ፤ (ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት) ፤** የሚሸሽ ፡ ሸሺታ ፤ ኰብላይ ፡ ፈርጣጭ ። ገብአ ፡ እምነበ ፡ ከነ ፡ ነፋጼ ። ኢያትረፈ ፡ ነፋጼ ፡ ለዝክር ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ፭ ። ሚያ፲ ። ዘዳ፫ ፡ ፯) ።

**አንፈጸ ፤** አሸሸ ፡ አፈቀ ፤ አባረረ ፡ በተነ ። ወአንፈጸ ፡ እግዚ ፡ ንዋመ ፡ እምኔሁ ። ሰደዶሙ ፡ ወአንፈጾሙ ። ብርሃኑ ፡ ያነፍጾሙ ፡ ለአጋንንት ፡ (አስቴ፯ ፡ ፭ ። ጥበ፲፯ ፡ ፱ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

—፤ አዘራ ፡ አነፈሰ ። ሚጠት ፡ ገጻ ፡ ወአንፈጸት ፡ በአጻብዒሃ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲፯) ። ሐንፈጸን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ ድርብ ፡ ነው ፤ አን ፡ ሐ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ፤ ነቀወንና ፡ ሰንቀወን ፡ ይመስላል ።

**ነፌቅ ፤ (ነፈቀ ፡ ይነፍቅ ፡ ይንፍቅ ። ፀረ ፡ ነፌቀ ። ሱር ፡ ንፉቅ ፤ ወጣ ፡ ተለየ ፡ ከቍጥር ፡ ካንድነት) ፤** መንፈቅ ፡ መሠንጠቅ ፤ አስተካክሎ ፡ መክፈል ፡ መለየት ። ሠጠቀንና ፡ ፈረቀን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ። ወነፈቀ ፡ ለሕዝብ ፡ ዘምስሌሁ ። ዘነፈቃ ፡ ለባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ወክፈላ ። ቶዋሕዶ ፡ እምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ለክልኤ ፡ ነፈቀ ። ወነፈቅን ፡ እማእከል ፡ (ዘፀ፴፬ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፻፴፭ ፡ ስንክ ፡ መስ፯ ። ኩፉ ፡ ፲፱) ። በነፈቀ ፡ ፈንታ ፡ ናፈቀ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ናፋቂ ፡ መንግሥት ፤ ዘይናፍቅ ፡ መን

ግሥተ ፡ እምደቀቀ ፡ ሴም ፡፡ ዕድወ ፡ ደም ፡ ኢይናፍቁ ፡ መዋዕሊሆሙ ፡ (ክብ ፡ ነገ ፡ ፮ ፡ ፱ ፡፡ መዝ ፡ ፶፬) ፡፡

**ነፋቂ** ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት) ፤ የሚነፍቅ ፡ የሚከፍል ፡ ክፋይ ፡ ሠንጣቂ ፡፡

**አንፈቀ** ፤ አስነፈቀ ፡ አስከፈለ ፡ መንፈቅ ፡ አስኘ ፡፡

**ተነፍቀ** ፤ ተነፈቀ ፡ ተለየ ፡ ተከፈለ ፡፡ ይትነፈቅ ፡ እስራኤል ፡ ለክልኤ ፡፡ ተነፍቀት ፡ ሥዕርታ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፳፱ ፡፡ ዮዲ ፲ ፡ ፫) ፡፡ በተነፍቀ ፡ ፈንታ ፡ ተናፈቀ ፡ ይባል ፡ አያሰኝም ፡፡ ቦኑ ፡ ተናፈቀ ፡ ክርስቶስ ፡፡ ተናፈቀ ፡ ልቦሙ ፡፡ ኢይትናፈቀ ፡ እንከ ፡ ለክልኤ ፡፡ ተናፈቀ ፡ ምክርናኒክ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡፡ ሆሴ፲ ፡ ፪ ፡፡ ሕዝ፴፯ ፡ ፳፪ ፡፡ ሢራ፶፯ ፡ ፳፭) ፡፡

**ንፉቅ** ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ፍቅት) ፤ የተከፈለ ፡ ክፉል ፡ ፍሩቅ ፡ ሥጡቅ ፡፡ መንግሥቱ ፡ ንፉቅ ፡፡ እንስሳ ፡ ዘንፉቅ ፡ ሰኰናሁ ፡ (ዳን፪ ፡ ፵፩ ፡፡ ዘሌ፲፩ ፡ ፫—፯) ፡፡

**ንፍቀት** ፤ መከፈል ፡ መከፈል ፡ አከፋፈል ፡ ክፈላ ፡ ክፍያ ፡ ክፋልነት ፡፡

**ነፍቅ** ፤ (ቃት) ፤ ቃሬዛ ፡ የሬሳ ፡ ዐልጋ ፡ ማጥን ፡ ታንኳ ፡ መርከብ ፡ ሞላላ ፡ ውስጠ ፡ ክፍት ፡፡ ቀርበ ፡ ወአኀዘ ፡ ነፍቆ ፡፡ ሞተ ፡ ዮሴፍ ፡ ወሤምዎ ፡ በነፍቅ ፡፡ ነሥአት ፡ እሙ ፡ ነፍቀ ፡ ወሰበ ፡ ርእየታ ፡ ለይእቲ ፡ ነፍቅ ፡፡ ቦአ ፡ ኖኅ ፡ ውስተ ፡ ነፍቀ ፡ ታቦት ፡ (ሉቃ፯ ፡ ፲፬ ፡፡ ዘፍ፶ ፡ ፳፮ ፡፡ ዘፀ፪ ፡ ፫ ፡ ፭ ፡፡ ማቴ፳፬ ፡ ፴፰) ፡፡ ነፍቅና ፡ ታቦት ፡ ኹለቱ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ መከፈ ፡ ለንጽ ፡ ተደርቦል ፡፡

**ነፍቅ** ፤ (ዕብ ፡ ጋዲሽ) ፤ መቃብር ፡ የመቃብር ፡ ሀፈር ፡ የደንጊያ ፡ ክምር ፡ ጉብ ፡ አጐብር ፡ ጣራ ፡ በመቃብር ፡ ላይ ፡ የሚሠራ ፡፡ ውእቱ ፡ ይትጋሀ ፡ ውስተ ፡ ነፍቂ ፡፡ ወገብሩ ፡ ሎቱ ፡ ነፍቀ ፡ (ኢዮ፳፩ ፡ ፴፪ ፡፡ ኢዮ፳ ፡ ፳፱) ፡፡

**ንፍቃ ፡ አው ፡ ንፍቅ** ፤ እኩል ፡ እኩሌታ ፡ ግማሽ ፡ አሳይ ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ መንፈቅ ፡፡ እመት ፡ ወንፍቃ ፡፡ እምንፍቃሃ ፡ ለዲድርክም ፡፡ እስከ ፡ ንፍቀ ፡ ሌሊት ፡ (ዘፀ፴፰ ፡ ፲፯ ፡፡ ፴ ፡ ፲፭ ፡፡ ግብ፳ ፡ ፯) ፡፡ ተመራጅ ፡ ምክትል ፡፡ ንፍቀ(ቅ) ፡ ዲያቆን ፡፡ ንፍቀ(ቅ) ፡ ካህን ፡፡ ንፍቅ ፡ ቀሲስ ፡ (ቅዳ) ፡፡

**መንፈቅ** ፤ ገዘ ፡ ክማሁ ፡ በቁሙ ፡ እኩሌታ ፡ ግማሽ ፡፡ መንፈቀ ፡ ነገደ ፡ ምናሴ ፡፡ መንፈቀ ፡ ዓመት ፡፡ መንፈቀ ፡ ወርኅ ፡ (ዘኁ፴፪ ፡ ፴፫ ፡፡ ዳን፯ ፡ ፳፭ ፡፡ ኩፋ ፡ ፲፱) ፡፡

**ተናፈቀ** ፤ ተለያየ ፡ ተከፋፈለ ፡፡ ወፀኡ ፡ ተናፈቀሙ ፡ ውስተ ፡ መርብዕተ ፡ ማኣፈድ ፡፡ መንግሥት ፡ እንተ ፡ ትትናፈቅ ፡ በበይናቲሃ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፫ ፡፡ ማቴ፲፪ ፡ ፳፭) ፡፡

**ናፈቀ** ፤ (ይናፍቅ ፤ ናፍቆ) ፤ በቁሙ ፡ ጠደደ ፡ ተሙኘ ፡ ሻ ፡ ፈለገ ፡ ተጠማ ፡፡ ጠረጠረ ፡ ተጠራጠረ ፡ አመንታ ፡ ኹለት ፡ ልብ ፡ ኾነ ፡ ተገበዘ ፡፡ እንዘ ፡ ንናፍቅ ፡ እመ ፡ ውእቱሂ ፡፡ ተአመነ ፡ ወኢናፈቀ ፡፡ ልብ ፡ ዘይናፍቅ ፡፡ ናፍቀ ፡ ወተሓምዩ ፡፡ ናፍቀት ፡ (ኪዳ ፡፡ ሮሜ ፬ ፡ ፲፱ ፡፡ ሢራ፪ ፡ ፲፪ ፡፡ ሽኢጥ ፡ ፪ ፡ ፩ ፡፡ ሄርማ ፡ ገ፲፯) ፡፡

**ናፋቂ** ፤ በቁሙ ፡ (በማርኛ) ፡፡ ጠርጣሪ ፡ ተጠራጣሪ ፡ የሚጠራጠር ፡፡ ኢትኩን ፡ ናፋቄ ፡ አላ ፡ እመን ፡ (ዮሐ፳ ፡ ፳፯) ፡፡ ምስጢሩ ፡ የነፈቀ ፡ ነው ፡ ፈጽሞ ፡ አለማመንና ፡ ጨርሶ ፡ አለመካድ ፡፡

**አናፈቀ** ፤ በቁሙ ፡ አስናፈቀ ፡ አነፋፈቀ ፡፡ አስጠረጠረ ፡ አጠራጠረ ፡፡ አናፈቅ ፡ እንከ ፡ ወአህጉልካሁ ፡ (ፈልክ ፡ ፶፯) ፡፡

**መናፍቅ** ፤ (ቅት ፡ ቃን ፡ ቃት) ፤ ናፋቂ ፡ አናፋቂ ፡ የሚጠራጠር ፡ የሚያጠራጥር ፡ ጠርጣሪ ፡ አጠራጣሪ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ሕጹጽ ፡ የኾነ ፡ ምሉእና ፡ ፍጹም ፡ ትክክል ፡ ያይደለ ፡ መንፈቁን ፡ አምኖ ፡ መንፈቁን ፡ የሚክድ ፡፡ ዕልዋን ፡ ወመናፍቃን ፡፡ በእንተ ፡ ዘይበውእ ፡ ውስተ ፡ ሕግነ ፡ እመናፍቃን ፡ (ቀሌ ፡፡ ሲኖዶ) ፡፡

**ተናፈቀ** ፤ በቁሙ ፡ ተሻ ፡ ተፈለገ ፡፡ ተጠረጠረ ፡ ተጠራጠረ ፡ (ተነፋፈቀ) ፡፡

**ኑፋቅ** ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ፍቅት) ፤ የተናፈቀ ፡ ተናፋቂ ፡፡ የተጠረጠረ ፡ ተጠርጣሪ ፡፡ መናፍቅ ፡ ተጠራጣሪ ፡ ልቡ ፡ ሐሳቡ ፡ ኹለት ፡ የኾነ ፡፡ ልብ ፡ እኩይ ፡ ወኑፋቅ ፡፡ ኑፋቀ ፡ ሃይማኖት ፡፡ ኢትኩኑ ፡ ኑፋቃነ ፡ (ዕብ፫ ፡ ፲፪ ፡፡ መጽ ፡ ምስ ፡ ፪ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፱) ፡፡ ናፈቀ ፡ የነፈቀ ፡ ዘር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በኑፋቅ ፡ ፈንታ ፡ ንፉቅ ፡ ይባል ፡ የበረከ ፡ ቤት ፡ ነውና ፡ አያሰኝም ፡፡ ውሂበክ ፡ ኢትናፍቅ ፡ እስመ ፡ ንፉቅ ፡ እምእግዚ ፡ ይርሕቅ ፡፡ ንፉቃነ ፡ ሃይማኖት ፡ (ገድ ፡ ተክ ፡፡ ፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፰) ፡፡

**ኑፋቄ** ፤ (ያት) ፤ በቁሙ ፡ መከፈል ፡ መከፈል ፡ ክፍያ ፡ አከፋፈል ፡፡ ጥርጥር ፡ ጥርጠራ ፡ ምንታዌ ፡፡ ዘእንበለ ፡ ኑፋቄ ፡ ወብዕድና ፡፡ እሌ ፡ እንበለ ፡ ኑፋቄ ፡፡ ዘእንበለ ፡ ኑፋቄ ፡ ልብ ፡ አመንክሙ ፡ ብየ ፡ (ቁር ፡፡ ኪዳ) ፡፡

**ነፈረ** ፤ (ነፈር ፡፡ ሱር ፡ ንፋር ፡፡ ዐረፋረ) ፤ በቁሙ ፡ እጅግ ፡ ሞቀ ፡ ፈላ ፡ ገነፈለ ፡ የውሃ ፡፡ ኣነብራ ፡ ዴቢ ፡ አፍሓም ፡ እስከ ፡ ይነፍር ፡ (ሕዝ፳፬ ፡ ፲፩) ፡፡ ተቈጣ ፡ ጠብ ፡ ፈለገ ፡ አንጕሣ ፡ ወገሸ ፡ አገረገረ ፡ የበሬ ፡፡

**አንፈረ** ፤ አነፈረ ፡ አስነፈረ ፡ ቀቀለ ፡ አስቀቀለ ፡ (መ ፡ ፈ) ፡፡ አንፍሮ ፡ አደረገ ፡፡ አናፈረ ፡ በቀንዱ ፡ ቈፈረ ፡ ለመዋጋት ፡ ጠበኛን ፡ ሰው ፡ በቀንዱ ፡ ሀፈር ፡ ይጭል ፡ እንዲሉት ፡፡

**ተነፍረ** ፤ ተነፈረ ፡ ተቀቀለ ፡፡ ቸነፈር ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ፡፡

**ንፉር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ፍርት) ፤ የነፈረ ፡ ንፍር ፡ ሙቅ ፡ ፍል ፡ ማየ ፡ አይጎ ፡፡ የተነፈረ ፡ የተቀቀለ ፡ ቅቅል ፡ ከንፍሮ ፡ ውሃ ፡ የገባ ፡፡

**ነፍሮ** ፤ ንፍሮ ፡ እንጎርጓብ ፡ አንፈላ ፡፡

**ተናፈረ** ፤ ተነፋፈረ ፡ ተዘዘተ ፡፡

**ነፈርዓጽ** ፡—ዝላይ ፡ መርታ ፡—ፈር ዐጺ ።

**ነፍሰ ፤ አው ፡ ነፈሰ ፤ (ይነፍስ ፡ ይንፈስ ፤ ይንፍስ ። ዕብ ፡ ናፎሽ)** ፤ ነፈሰ ፡ ሸው ፡ ሸው ፡ አለ ። ነፍኀን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። አርባዕቱ ፡ ነፋሳት ፡ ነፍሱ ። ነፋሳት ፡ ይነፍሱ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ነፍኑ ፡ ይነፍኑ ፡ የሚልም ፡ ይገኛል ፡ (ዳ ንኤ ፡ ፯ ። ሔኖ፸፮ ፡ ፩) ።

—፤ ዐረፈ ፡ ተንፈሰ ፡ እፍ ፡ እህ ፡ እሮይ ፡ አለ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በነፍሰ ፡ ፈንታ ፡ አንፈሰ ፡ አስተንፈሰ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። አራዊት ፡ ዘያነፍሱ ፡ እሳተ ፡ ዘይነፍሩ ፡ ወይልህብ ። ዐቢየ ፡ ግብረ ፡ ፈጸምከ ፡ ወአንፈስከ ። በእብሬትኪ ፡ አንፈሱ ፡ ሕዝበ ፡ ኢትዮጵያ ። ፈጸመ ፡ ስምዖ ፡ ወተከሰሰ ፡ ወአንፈሰ ፡ እምዝ ፡ ዓለም ፡ (ጥበ ፲፭ ፡ ፲፱ ። ሚሌ፯ ፡ ፳፭ ። ስንክ ፡ ጎዳ፲፪ ። መጽ ፡ ምስ) ። እስከ ፡ ሶበ ፡ ያስተነፍስ ፡ ዕለት ። ከመ ፡ ያስተንፍስ ፡ ወልደ ፡ አመትከ ፡ (ማሕ፬ ፡ ፲፯ ። ፪ ፡ ፮ ። ዘፀ፳፫ ፡ ፲፪) ።

**ነፍስ ፤ (ሳት)** ፤ በቁሙ ፡ ረቂቅ ፡ አካል ፡ የሥጋ ፡ ሕይወት ፡ የሥጋ ፡ ባለቤት ፡ ነባቢት ፡ ለባዊት ። ሀለወት ፡ ነፍሱ ፡ በላዕሌሁ ። አልጸቀት ፡ ትፃእ ፡ ነፍሱ ። ትግባእ ፡ ነፍሱ ፡ ላዕሌሁ ። ነፍስ ፡ ነባቢት ። ትረክቡ ፡ ክፍለ ፡ ምስለ ፡ ነፍሳተ ፡ ጻድቃን ። እስመ ፡ ክልኤቲ ፡ ነፍሳት ፡ ሀለዋ ፡ ኀበ ፡ ሰብእ ፤ አሐቲ ፡ መንፈስ ፡ ሕይወት ፡ ዘወፅአት ፡ እምአፉሁ ፡ ለእግዚ ፡ ወኢትትኌለቍ ፡ ምስለ ፡ ጠባይዕ ፡ ወኢትመውትኒ ፤ ወአሐቲመ ፡ ደመ ፡ ነፍስት ፡ ይእቲ ፡ እምጠባይዕ ፤ ወይእቲሰ ፡ መዋቲት ፡ (ግብ፳ ፡ ፲ ። ዘፍ፴፭ ፡ ፲፰ ። ፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳፯ ። ቅዳ ፡ አፈ ። ዲድ ፡ ፴፱ ። አርጋ) ።

—፤ ትንፋሽ ፡ እስትንፋስ ፤ ሕቅታ ። እምጣነ ፡ ሕያው ፡ አንተ ፡ ወሀለወት ፡ ነፍስከ ። ነፍሱሂ ፡ ፍሕም ፡ ይእቲ ። እስከ ፡ ነፍስ ፡ ደኀሪት ፡ (ሚሌ፴ ፡ ፳፱ ። ኢዮ ፵፩ ፡ ፲፫ ። ቅዳ) ።

—፤ ልብ ፡ ልቡና ። ዙሉ ፡ ነፍስ ፡ ይደነግፅ ። በዙሉ ፡ ነፍስከ ፡ አክብሮ ፡ ለአቡከ ። ወአቅም ፡ ምክረ ፡ ነፍስከ ፡ (ኢሳ፲፫ ፡ ፯ ። ሚራ፯ ፡ ፳፯ ። ፴፯ ፡ ፲፫) ።

—፤ ሰው ፡ ሰውነት ። ወተወሰኩ ፡ ሠላሳ ፡ ምእት ፡ ነፍስ ። ዕቀቡ ፡ ነፍሰክሙ ። የኀሥሥዋ ፡ ለነፍሰ ፡ ዝ ሕፃን ፡ (ግብ፬ ፡ ፵፩ ። ዘዳ፬ ፡ ፲፭ ። ማቴ፪ ፡ ፳) ።

—፤ ሕያው ፡ ፍጥረት ፡ ትንፋሽና ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ የሚላወስ ፡ ተንቀሳቃሽ ። ዙሉ ፡ ነፍስ ፡ ይሴብሖ ፡ ለእግዚ ፡ (መዝ ፡ ፻፶) ።

**ነፍሳዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ በቁሙ ፡ የነፍስ ፡ የልብ ፡ መንፈሳዊ ። ሕማም ፡ ነፍሳዊት ። ይደልዎ ፡ ዙኑ ፡ ነፍሳዊ ፡ ወሥጋዊ ። ተደምሮ ፡ ዘመድ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ክልኤ ፡ ክፍል ፡ ነፍሳዊ ፡ ወሥጋዊ ፡ (ፊልክ ፡ ፶፲፪ ። ፊ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፳ ። ፳ ፡ ፪) ።

**ነፍስት ፤ (ታት)** ፤ ሰውነት ፡ ሥጋ ፡ ገላ ፡ ሕዋስ ፡ አካል ፡ ብልት ፡ መልክ ፡ ራት ፡ ሆድ ፡ አባለ ፡ ዘር ። እንዘ ፡ ከመ ፡ ቢድን ፡ ነፍስቶሙ ። እመኒ ፡ ትቤ ፡ እግር ፡ ኢኮንኩ ፡ እምውስተ ፡ ነፍስት ። ርእሲ ፡ ነፍስተነ ፡ ወነፍስቶሙ ፡ ሊደቅ ፡ እለ ፡ ይሴስዩ ፡ እማእደ ፡ ንጉሥ ። ኢይክበይክ ፡ ነፍስትከ ። ትግዝሩ ፡ ከተማ ፡ ነፍስትክሙ ፡ (ዕብ፲፭ ፡ ፲፱ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭ ። ዳን፩ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ። ሚራ፴፱ ፡ ፲፱ ። ዘፍ፲፯ ፡ ፲፩) ።

**ነፋስ ፤ (ሳት)** ፤ በቁሙ ፡ አየር ፡ ረቂቅ ፡ ርጉስ ፡ ህዉክ ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ በላይ ፡ በምድር ፡ ባሉቱ ፡ ማእዝን ፡ በኹሉ ፡ የመላ ፡ በገዛ ፡ ኀይሉ ፡ የሚታወክና ፡ የሚናወጥ ፡ ሌላውንም ፡ ኹሉ ፡ የሚያናውጥ ፡ የሚያገዝፍ ፡ የሚያረዝም ፡ የሚያሳድግ ፡ ሕይወትና ፡ ጤና ፡ የሚሰጥ ፡ ከራቱ ፡ ባሕርያት ፡ አንዱ ፤ ጽልመትና ፡ ይብሰት ፡ ቍረት ፡ ያለው ፡ በጽልመቱ ፡ ከመሬት ፡ በይብሰቱ ፡ ከእሳት ፡ በቍረቱ ፡ ከውሃ ፡ የሚስማማ ። ረበቦ ፡ ለሰማይ ፡ ከመ ፡ ሠቅ ፡ ወበነፋስ ፡ ፀመይ ። ይዌስኑ ፡ ብሩዳ ፡ ወይዴምዱ ፡ በነፋስ ። ጠባይዕ ፡ ነፋሳዊ ። መሬት ፡ ቶሱሕ ፡ በእሳት ፡ ወነፋስ ፡ ወማይ ፡ (መቃ ፡ ገ፲ ። ቅዳ ፡ ግሩ ። ፈላስ ። ቀሌ) ። ወርኢኩ ፡ አርባዕተ ፡ ነፋሳተ ፡ እለ ፡ ይጸውርዋ ፡ ለምድር ፡ ወለጽንዐ ፡ ሰማይ ፤ ወርኢኩ ፡ ከመ ፡ ነፋሳት ፡ ይረብብዋ ፡ ለልዕልና ፡ ሰማይ ፤ ወእሙንቱ ፡ ይቀውሙ ፡ ማእከለ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ። ወበአጽናፈ ፡ ምድር ፡ ርኢኩ ፡ ዐሥርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ኆዋኀወ ፡ ርኅዋተ ፡ እለ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይወፅኡ ፡ ነፋሳት ፡ ወይነፍኑ ፤ ወበአርባዕቱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይወፅኡ ፡ ነፋሳተ ፡ በረከት ፡ ወሰላም ፤ ወእምእልኩ ፡ ሰመንቱ ፡ ይወፅኡ ፡ ነፋሳተ ፡ መቅሠፍት ፡ (ሔኖ ፡ ፲፰ና ፡ ፸፯ ፡ ክፍል) ።

—፤ ማእዝን ፡ የማእዝን ፡ በታ ። ያስተጋብእዎሙ ፡ ለኅሩያኒሁ ፡ እምአርባዕቱ ፡ ነፋሳት ፡ (ማር፲፫ ፡ ፳፯) ። ትንፋሽ ፡ ሳበት ፡ እንሻሴት ፡ ወሬ ፡ ከአፍ ፡ ከገላ ፡ የሚወጣ ።

**አንፈሰ** ፤ አነፈሰ ፡ አስነፈሰ ፡ እፍ ፡ እፍ ፡ አሰኘ ። አሳረፈ ፡ አስተንፈሰ ፡ ደስ ፡ አሰኘ ። አስተብቍዖ ፡ ለሕፃን ፡ ከመ ፡ ያንፍሶ ፡ እምዝ ፡ ዓለም ። አንፈስከምዎ ፡ ለእግዚ ። አንፍሶ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ዘበ፴፪ ፡ ፳፱ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ።

**መንፈስ ፤ (ዕብ ፡ መሱር ፡ ወዐረ ፡ ሩሕ)** ፤ ረቂቅ ፡ ነገር ፡ ትንፋሽ ፡ እፍታ ፡ ነፋስ ። በመንፈሰ ፡ ከናፍሪሁ ። ይሁቦሙ ፡ መንፈሰ ፡ ለሕዝብ ። መንፈስ ፡ ኀበ ፡ ፈቀደ ፡ ይነፍኅ ፡ (ኢሳ፲፩ ፡ ፬ ። ፵፪ ፡ ፭ ። ዮሐ፫ ፡ ፰) ።

—፤ ነፍስ ፡ መልአክ ፡ ሰይጣን ፡ ምትሀት ። ወፅአት ፡ መንፈሱ ፡ ሶቤሃ ። ዙሉ ፡ መንፈስ ፡ ዘይትለአክ ። መንፈስ ፡ እኩይ ። ወመሰሎሙ ፡ ከመ ፡ ዘመንፈስ ፡ ይሬእዩ ፡ (ማቴ፳፯ ፡ ፶ ። ኩፋ ፡ ፲ ። ጦቢ፯ ፡ ፳ ። ሉቃ፳፬ ፡ ፴፯) ።

—፤ ሰው ፡ ሰውነት ፡ ገጽ ፡ መልክ ፡ ልብ ፡ ልቡና ፡ ዕውቀት ፡ ትዕግሥት ። ዙሉ ፡ መንፈስ ፡ ዘያዐቅብ ፡ ዘበአውስቱ ፡ ግብጽ ፡ ሰብዓ ፡ መንፈስ ። መንፈስ ፡ መራዕ

ይከ ። ሐመት ፡ መንፈስየ ፡ ጥቀ ። እሁቦሙ ፡ መንፈሰ ፡ ሐዲሰ ። አንሣ ፡ መንፈስከ ፡ ላዕሌየ ፡ (ኩፋ ፡ ፡ ፱ ። ምሳ ፳፯ ፡ ፳፫ ። ሉቃ ፡ ፩፡፲፱ ፡ ፵ ። ሕዝ ፲፩ ፡ ፲፱ ። ፊልክ) ።

—፤ መምር ፡ ትምርት ፤ ፈቃድ ፡ ምክር ፡ ሐሳብ ፤ ሥልጣን ፡ ባሕርይ ። ለኵሉ ፡ መንፈስ ፡ ኢትእመንዋ ። እስመ ፡ መንፈሱ ፡ ይእቲ ፡ ሥምረቱ ። አይቴኑ ፡ አሐውር ፡ እመንፈስከ ፡ (፩ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፩ ። ትር ፡ ወን ። መዝ ፻፴፰) ።

—፤ በቊሙ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባሕርያዊ ፡ አካላዊ ፡ ሕይወት ፤ እንደ ፡ ነፍስ ፡ ፍጡር ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ዝርው ፡ ያይደለ ፡ የሥላሴ ፡ ሦስተኛ ፡ አካል ፡ ከአብ ፡ የሚሠርጽ ፡ ከወልድ ፡ የሚነሣ ፡ ለሰው ፡ ለመላእክት ፡ ጸጋ ፡ ሀብት ፡ ኹሉ ፡ የሚሰጥ ። ወመንፈሰ ፡ እግዚ ፡ ይጼልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ። ወየዐርፍ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚ ። ሀብትኬ ፡ ሠናይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፪ ። ኢሳ ፲፩ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ቄር) ። የመንፈስ ፡ አፈታት ፡ ምንም ፡ ስልቱና ፡ ፀማርኛው ፡ ቢበዛ ፡ ዘይቤው ፡ ረቂቅ ፡ ርቀት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለረቂቃን ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። እስመ ፡ እግዚ ፡ መንፈስ ፡ ውእቱ ። ዘይገብሮሙ ፡ ለመላእክቲሁ ፡ መንፈሰ ፡ እሙንቱ ። ለመንፈስሰ ፡ አልቦቱ ፡ ሥጋ ፡ ወዐፅም ፡ (ዮሐ፬ ፡ ፳፬ ። ዕብ፩ ፡ ፲፬ ። ሉቃ፳፬ ፡ ፴፱) ።

**መናፍስት** ፤ **አው ፡ መንፈሳት** ፤ ነፋሳት ፡ ነፋሳት ፤ መላእክት ፡ ሰይጣናት ። እግዚአ ፡ መናፍስት ። መንፈሳቲሆሙ ፡ ለእለ ፡ ሞቱ ። መናፍስት ፡ ንጹሓት ፡ ለባውያት ፡ ወቀጢናት ። መናፍስት ፡ ርኩሳን ፡ (ሔኖ ። ጥበ፯ ፡ ፳፫ ። ማቴ፲ ፡ ፩) ።

**መንፈሳዊ** ፤ በቊሙ ፡ የነፍስ ፡ የመንፈስ ፡ የመልአክ ። ፍትሐ ፡ መንፈሳዊ ። ሥንኑ ፡ መንፈሳዊ ። ማሕሌት ፡ መንፈሳዊት ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ። ፲፱ ፡ ፫ ። ፴፬ ፡ ፯) ። ረቂቅ ፤ ንጹሕ ፡ ቅዱስ ፤ ለነፍሱ ፡ ያደረ ፡ የግዚር ፡ ወገን ። አርባዕቱ ፡ እንስሳ ፡ መንፈሳውያን ። አዋልድ ፡ መንፈሳውያት ፡ (ቅዳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፩) ።

**አስተንፈሰ** ፤ ተነፈሰ ፡ እፍ ፡ አለ ፡ ትንፋሽ ፡ አወጣ ፤ ተናገረ ። እግዚ ፡ ዘአስተንፈሰ ፡ ቦቱ ፡ ነፍሰ ። መጻሕፍት ፡ ሐበት ፡ ዘአስተንፈሰ ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ፡ (ጥበ፲፭ ፡ ፲፩ ። መጽ ፡ ምስ) ።

—፤ አንፈነፈ ፡ ሳበ ፡ ማገ ፡ አሸተተ ። አስተንፈሰ ፡ ወአጼነወ ። ከመ ፡ ይክሀል ፡ አጼንዎ ፡ ዘያስተነፍስ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ። ቀሌ) ።

**እስትንፋስ** ፤ በቊሙ ፤ ነፍስ ፡ ትንፋሽ ፡ ሕቅታ ። እስትንፋሱ ፡ ሀለወት ፡ ላዕሌሁ ። እስትንፋስ ፡ አፉሁ ። እስከ ፡ እስትንፋስ ፡ ደኃሪት ፡ (ስር ፡ ኢሳ፳ ፡ ፲፩ ። መዝ ፡ ፻፵፪ ። ቅዳ) ። ረቂቅ ፡ ነገር ፤ ጥልቅ ፡ ምስጢር ። እነግረክሙ ፡ እስትንፋሰ ፡ ቃልየ ፡ (ምሳ፳ ፡ ፳፫) ።

**ነጸብራቅ** ፤—**ብልጭታ** ፤—**በረቀ ፡ ጸብረቀ** ።

**ነጽሐ** ፤ (**ነጺሐ ። ጥሂር ፡ ጠሀረ**) ፤ ነጻ ፡ ነጣ ፡ ነጭ ፡ ኾነ ። ታጠበ ፡ ጠራ ፤ ታደሰ ፡ ከርበሐት ፡ ተለየ ። ጠሀረን ፡ እዩ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። መኑ ፡ ይነጽሕ ፡ እምርስሐት ። ኢትክል ፡ ምድር ፡ ነጺሐ ፡ እምደም ። ንጽሑ ፡ ወወልጡ ፡ አልባሲክሙ ፡ (ኢዮ፲፬ ፡ ፬ ። ኩፋ ፡ ፳፮ ። ፀ፯) ።

**ነጺሕ** ፤ **ንጹሕ** ፤ (**ሓን ፡ ሓት ፡ ጽሕት**) ፤ የነጻ ፡ የጠራ ፤ በቊሙ ፡ ጥሩ ፡ ነጭ ፡ ብሩህ ። ዘንጹሕ ፡ ልቡ ፡ ወንጹሕ ፡ እደዊሁ ። ብፁዓን ፡ ንጹሓን ፡ ልብ ። ወይለብሱ ፡ ንጹሐ ። ሕያዋት ፡ ወንጹሓት ። ንጽሕት ፡ ወብርህት ፡ (መዝ ፡ ፳፫ ። ማቴ፭ ፡ ፰ ። ራእ፲፱ ፡ ፰ ። ዘሌ፲፬ ፡ ፬ ። ውዳ ፡ ማር) ።

**ንጽሐት** ፤ መንጻት ፡ አነጻጽ ፤ ንጹሕነት ፡ ንጣት ፡ ጥራት ። አልቦ ፡ ክቡር ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡ ከመ ፡ ንጽሐተ ፡ ልብ ፡ (ፊልክ ፡ ፲፰) ።

**ንጽሕ** ፤ ንጽሕና ፡ ጥራት ፡ ጥሩነት ፡ ከዝሙት ፡ ከርበሐት ፡ መራቅ ፡ መጠበቅ ። ንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ ወአከ ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋ ። ያገብእ ፡ ለከ ፡ ንጽሐከ ። በሃይማኖት ፡ ወበንጽሕ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ። ኢዮ፰ ፡ ፯ ። ፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፪) ።

**ንጽሕና** ፤ በቊሙ ፤ ንጹሕነት ፡ ንጹሕ ፡ መኾን ። ይኄይስ ፡ ንጽሕና ፡ ምስለ ፡ ንዴት ፡ እምብዕል ፡ ምስለ ፡ ዝሙት ። ናጥሪ ፡ እንከ ፡ ትሕትና ፡ ምስለ ፡ ንጽሕና ፡ (ፊላስ ። ቅዳ) ።

**አንጽሐ** ፤ አነጻ ፡ አጠራ ፤ ንጹሕ ፡ አደረገ ፡ አስደረገ ። አንጻሕኩ ፡ እደውየ ። ትክል ፡ አንጽሖትየ ። በአንጽሖ ፡ ርእሶን ፡ እምዝሙት ፡ (ኢዮ፱ ፡ ፴ ። ማቴ፰ ፡ ፪ ። ፩ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፱) ። በአንጽሖ ፡ ፈንታ ፡ አስተናጽሖ ፡ ይላል ፤ አያስኬድም ። ያሜክርዎ ፡ ወያስተናጽሕዎ ፡ እምአበሳሁ ። ወአስተናጽሖ ፡ ርስሐተ ፡ ስኢንዎሆሙ ። ከመ ፡ ታስተናጽሕ ፡ ቀሚሰ ። ብእሲ ፡ ጠቢብ ፡ ዘያስተናጽሕ ፡ ሦከ ፡ እምገራህቱ ፡ (ክብ ፡ ነገ ። መጽ ፡ ምስ ። ዘዳ፳፬ ፡ ፳ ። ዲድ ፡ ፴፱) ።

**አንጻሒ** ፤ **መንጽሒ** ፤ (**ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት**) ፤ የሚያነጻ ፡ የሚያጠራ ፡ አጥሪ ። ማይ ፡ መንጽሔ ፡ ዚአነ ። ሥጋ ፡ ወደም ፡ መንጽሔ ፡ ኀጢአት ። ንስሓ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ መንጽሒቶሙ ፡ ለኃጥኣን ፡ (ኪዳ ። ስንክ ፡ መጋ፲፱ ። ፊልክ ፡ ፻፳፯) ።

**መንጽሕ** ፤ **ምንጻሕ** ፤ (**ሓት**) ፤ መነጫ ፡ ማንጫ ፡ ማጠቢያ ፡ መታጠቢያ ።

**ተናጽሐ** ፤ ተናጻ ፡ ተጣጠበ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ወይም ፡ በገዛ ፡ እጁ ። ተናጻሕ ፡ እምኀጣይኢከ ፡ (ሂርማ ፡ ፲፰) ።

**አስተናጽሐ** ፤ አናጻ ፡ አጣራ ፡ አስተጣጠበ ።

**መስተናጽሕ** ፤ የሚያናጻ ። የሚያፀዳ ፡ ጥሩ ፡ ርሻ ።

**ነጽሐ** ፤—**ጣለ ፡ አንከባለለ** ፤—**ነፅኀ** ።

**ነጽየ፤ ዮት፤** (ነጸየ፡ ይነጺ፡ ይንጺ። ዕብ፡ ናጻህ። ሱር፡ ንጻእ። ዐረ፡ ነጻእ)፤ መነ ጨት፤ መንቀል፡ መምለጥ፤ መጋጥ፡ መግመጥ። ነጸ ይኩ፡ሥዕርተ፡ርእስየ፡ወጽሕምየ። ሰምንት፡ ይነ ጽዩ፡ሥዕርተ፡ርእሶሙ። ሔይንጺ፡ሥዕርተ፡ርእሱ፡ (ዕዝ፱፡ ፫። አፈ፡ ተ፱። ፍ፡ ነ፡ ፳፱። ፵፩)።

**አንጸየ፤** አስነጨ፤ አጋጠ፡ አስጋጠ።

**አንጼዋ፤**(ብ፡ አናጹት)፤ ዐይጥ፡ ታናሽ፡ አውሬ፡ አፈ፡ ሹል፡ ጥርስ፡ ስል፡ የሚግጥ፡ የሚቈርጥ፡ አጥፊ፤ በዱር፡ በቤት፡ በቈላ፡ በደጋ፡ የሚገኝ። ስእመ፡ አማስነ፡ አንጼዋ፡ ምንተኒ። አውፅአት፡ ምድሮሙ፡ አናጹተ፡(ፍ፡ ነ፡ ፴፮። ፩ነገ፡ ፮፡ ፩)።



አንጼዋ፤

**ተነጽየ፤** ተነጨ፤ ተነቀለ። ዲዮስቆሮስ፡ ቀ ናኢ፡ በእንተ፡ ሃይማኖት፡ ዘተመልጎ፡ ጥረሲሁ፡ ወተነጽየ፡ መብዝኅተ፡ጽሕሙ፡(ስንክ፡ መስ፳)።

**ንጹይ፤**(ያን፡ ያት፡ ጺት)፤ የተነጨ፡ የተ ነማጨ። ንጹይ፡ ጽሕሙ።

**ንጽየት፤** መነጨት፤ መነጨት፡ አነማጭ፡ ንጭታት።

**ንጻይ፤ ንጺ፤ አው፡ ኖጺ፤**(ዕብ፡ ኖጻህ)፤ ላባ፡ ሽገር፡ የዶሮ፡ የአዕዋፍ፡ ጠጕር፤ የሚነጭ፡ የሚ ነቀል። ምሉአ፡ ኖዒ፡ ዘሎቱ፡ ኵሳሑስ። ዘዐቢይ፡ ክነ ፊሁ፡ ወምሉእ፡ ኖጻቲሁ፡(ሕዝ፲፯፡ ፫፡ ፯)። ኖጻ ቲሁ፡ በሰው፡ ጽፈሩሁ፡ ይባል፤ የመላሽና፡ የጣፊ፡ ስሕ ተት፡ ነው።



ኖጺ፤

**ተናጸየ፤** ተናጨ፤ ተነማጨ። ተነማነጨ፤ ኖጫ፡ ነጭናጫ፡ ኸነ፤ ጠባዩ።

**አስተናጸየ፤** አናጨ፡ አነማጨ፤ አነማነጨ፤ አበሳጨ።

**ነጸለ፤**(ነጺል። ዕብ፡ ናጻል። ዐረ፡ ነጸለ)፤ ነጠለ፡ ለየ፤ መነጠለ፤ አዳነ፡ አወጣ፡ አስጣለ፤ አወለቀ፡ አስለቀቀ፤ ከመከራ፡ ከፍንጅ፡ ከጠላት፡ እጅ። ጸንጸለን፡ እዶ፡ የዚህ፡ ዲቃላ፡ ነው፤ ነቀወ፡ ብሎ፡ ብንቀወ፡ እንደ፡ ማለት።

**ተነጽለ፤** ተነጠለ፤ ተለየ፡ ወለቀ። እንዘ፡ ይገ ዝም፡ ሠርዌ፡ ተነጽለ፡ ማሕጼሁ፡ ወወድቀ፡ ው ስተ፡ ማይ፡(፬ነገ፡ ፮፡ ፭)።

**ንጹል፤**(ላን፡ ላት፡ ጽልት)፤ የተነጠለ፤ ልዩ፡ ውልቅ፡ ንቁል።

**ንጻል፤**(ላት)፤ ንጣይ፡ ነጠላ፤ የጸናጽል፡ ሽሹራ፡ አንዳንዲቱ፡ ቅጠል።

**ነጺፍ፤ ፎት፤**(ነጸፈ፡ ይነጽፍ፡ ይን ጽፍ። ዕብ፡ ያጻዕ)፤ ማንጠፍ፡ መዘርጋት፡ መጕ ዝጕዝ፡ መነስነስ፡ ማመቻቸት። ጸፍጸፈን፡ እይ፤ የዚህ፡ ዲቃላ፡ ነው። ነጸፉ፡ አልባሲሆሙ። ዘርቤታተ፡ ነጸ ፍኩ። ህየ፡ ነጸፍኪ፡ ምስካብኪ። ንነጽፍ፡ ሎቱ፡ ዐራተ። ሠቀ፡ ወሐመደ፡ ነጸፉ፡ ሎሙ፡(ማቴ፳፩፡ ፰። ምሳ፯፡ ፲፮። ኢሳ፶፯፡ ፯። ፬ነገ፡ ፱፡ ፲፫። አስቴ፬፡ ፫)። በነጸፈ፡ ፈንታ፡ አንጸፈ፡ ይባል፤ ስሕተት፡ ነው። አንጽፎ፡ ሐመደ፡ ወፍሬ፡ ዕፀው፡(ፍ፡ ነ፡ ፵፯)።

**ነጻፊ፤ መንጻፊ፤**(ፊት፡ ፍያን፡ ያት)፤ የሚያነጥፍ፤ አንጣፊ፤ ጕዝጓዥ።

**አንጸፈ፤** አስነጠፈ፤ አስጕዘጐዘ።

**አንጻፊ፤ መንጸፊ፡ ጽፍ፤** የሚያስነጥፍ፤ አስነጣፊ፡ አስጕዝጓዥ።

**ተነጽፈ፤** ተነጠፈ፡ ተዘረጋ፤ ተበጀ፡ ተዘጋጀ። ውስተ፡ ጽልመት፡ ተነጽፈ፡ ምስካብየ። ታበ፡ ተኑ ጽፈ፡ ዐረፍት። ተነጽፈ፡ ምስላግ፡ በታሕቴከ፡(ኢ ዮ፲፯፡ ፲፫። ቀሌ። ኢሳ፲፬፡ ፲፩)። ተጸንቀቀ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ተነጽፈ፡ ይባላል፡ (ዮሴ፱፡ ፫)።

**ንጹፍ፤**(ፋን፡ ፋት፡ ጽፍት)፤ የተነጠፈ፡ የተጕዘጐዘ፤ የተጸፈጸፈ። በታወቁና፡ ምንጣፉን፡ ኹሉ ቱንም፡ ባንድነት፡ ያሳያል። ፍኖተ፡ ሀካያን፡ ንጹፍ፡ በአሥዋክ። ጽርሕ፡ ንጹፍ፡ ወርቡደ። ምስካብ፡ ንጹፍ። ወንጹፍ፡ ጸፍጸፉ፡ በሕብረ፡ ወርቅ፡ ወብ ሩር። ውስጡ፡ ንጹፍ፡ በእብነ፡ ሰንፔር፡(ምሳ፲፭፡ ፲፱። ማር፲፬፡ ፲፭። ስንክ፡ መጋ፳። መቃ፡ ፶፫። ማ ሕ፫፡ ፲)።

**ነጽፍ፤**(ፋት፤ **አንጽፍት፤** ገበር፡ የላ ንክ፤ ውሳጣዊ፡ ልብስ፡ ከግምጃ፡ ጋራ፡ የሚሰፋ። ወደፍ፡ ሎቱ፡ ነጽፈ፡ ዘደርከኖ፡(ዘፀ፴፯፡ ፱)።

**መንጸፍ፤ ምንጻፍ፤**(ፋት፡ መናጽፍ)፤ ምንጣፍ፡ ዐልጋ፤ ማንጠፊያ፡ መነጠፊያ፡ ቦታ፡ መኝታ። ነጸፈ፡ ሠናየ፡ መንጸፈ። ይሰክብ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ዘእንበለ፡ መንጸፍ። መንጸፈ፡ ድንግልናሃ። እ ሞሙ፡ ይእቲ፡ ምድር፡ እምትካት፡ ወይእዜሰ፡ ክነት፡ መንጸፈ፡ ለአብድንቲሆሙ። ዐራታት፡ ወመ ንጸፋት። ሠረገላት፡ ወመናጽፍ፡ ሠናያት፡(አፈ፡ ተ፳፩። ስንክ፡ መስ፲፱። ዘዳ፳፱፡ ፲፭። ግንዘ። ፍ፡ ነ፡ ፲፯። አፈ፡ ተ፱)።

—፤ ዐዘቅት፡ ጉድጓድ፤ ታች፡ የታች፡ ታች፤ አግርጌ፡ መረጋገጫ፡ መጠቃጠቂያ፤ አንጠርጣሪ። ወድቀ፡ ዲያ

ብሎስ ፡ እምኑኅ ፡ አርያም ፡ ውስተ ፡ መንጸፈ ፡ ደይን ፡ በእንተ ፡ ትዕቢቱ ፡ ወኮነ ፡ መንጸፈ ፡ ለዙሉ ፤ ወተመነነ ፡ እምቅዱሳን ፡ መላእክት ። ደቂቀ ፡ ገሃነም ፡ ክኑ ፡ ምጥዋነ ፡ ለምንጻፈ ፡ ደይን ፡ (ቀሌ ። መጽ ፡ ምስ) ።


**መንጸፍት** ፤ -የራስ ፡ ልብስ ፡ ጌጥ ፤ -መጽንፍት ፤ ጸነፈ ።

**ነጽፈ** ፤—ነጠፈ ፡ ደረቀ ፤—ነጺፍ ፡ ነፅፈ ።

**ነጽሮ** ፤ **ሮት** ፤ (**ነጸረ ፡ ይኔጽር ፡ ይነጽር ። ዕብ ፡ ናጻር ። ሱር ፡ ንጣር ። ዐረ ፡ ነዘረ**) ፤ ተኵሮ ፡ ማየት ፤ ማስተዋል ፤ መመርመር ፤ መጠበቅ ፤ መመልከት ፤ የዐይን ፡ የልብ ። ስእንኩ ፡ ነጽሮ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ፡ ሰማየ ። ንባበ ፡ ዚኣየ ፡ ነጽር ። ነጽሩ ፡ ነፍስክሙ ። ስሕልዎ ፡ ያስተጋብእ ፡ ማኅበረ ፡ ከመ ፡ ይነጽሩ ፡ በእንተ ፡ ክሕደቶሙ ፡ ለእሉ ፡ ሠለስቱ ፡ ከሓድያን ፡ (ኢሳ፴፰ ፡ ፲፬ ። ምሳ፱ ፡ ፳ ። ኪዳ ። ስንክ ፡ የካ፴) ።

**ነጻሪ** ፤ (**ሪት ፡ ርያን ፡ ያት**) ፤ የሚያይ ፡ የሚመለከት ፡ አስተዋይ ፤ ጠባቂ ፡ ተመልካች ፤ ተኳር ፡ ዐይናማ ፡ ልባም ። ረአዩ ፡ ኀቡአት ፡ ወነጻሪ ፡ ነገር ። ዐይን ፡ ነጻሪት ፡ ተዐውር ። ይገብር ፡ ብዙኀ ፡ ግብረ ፡ በዘይደት ፡ ፈሥሑ ፡ ነጻርያን ፡ (ቅዳ ፡ ጎር ። ማንዘ ። አፈ ፡ ተ፲፮) ።

**መነጽር** ፤ (**ርት ፡ ራን ፡ ራት**) ፤ ግእዝ ፡ ከማሁ ፤ ነጻሪ ። በቁሙ ፤ ማያ ፡ መመልከቻ ፡ የዐይን ፡ ቤዛ ፤ ብርሃኑን ፡ ብሌኑን ፡ የሚጠብቅ ፡ አጕልቶ ፡ የሚያሳይ ፡ ታናሹ ፤ ወይም ፡ ታላቁ ፡ አርበጣላቢ ።



መነጽር ፡

**አነጸረ** ፤ **አው** ፡ **አንጸረ** ፤ አሳየ ፡ አመለከተ ፤ በጣት ፡ ባንደበት ። አንጸረ ፡ ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ ስትዩ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

—፤ ፊቱን ፡ መለሰ ፤ አቀና ፡ አመራ ፡ ለመኼድ ። አንጸሩ ፡ መንገለ ፡ ሰዶም ። ኀበ ፡ አንጸረ ፡ ቀዳማዊ ፡ የሐውሩ ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፲፮ ። ድጓ) ።

**አንጻሪ** ፤ **መንጽር ፡ መነጽር** ፤ የሚያሳይ ፤ አመልካች ፡ ጠቋሚ ።

**አንጻር** ፤ (**ራት**) ፤ በቁሙ ፤ አኳያ ፡ አቅጣጫ ፡ አፍዝገዝ ፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ ትይዩ ፤ ፊት ፡ ገጽ ። አንጻረ ፡ ኢየሩሳሌም ። ኀደረ ፡ አንጻረ ፡ ኬብሮን ። አንበሮሙ ፡ አንጻራቲሆሙ ፡ በበ ፡ ገጾሙ ። ሚጢ ፡ አዕይንተኪ ፡ እምአንጻርየ ፡ (ዳን፰ ፡ ፲ ። ኩፋ ፡ ፲፱ና ፡ ፲፮ ። ማሕ፮ ፡ ፭) ።

**መንጸር** ፤ ግእዝ ፡ ከማሁ ፤ አንጻር ። ንሑር ፡ እንተ ፡ መንጸር ። ኢሖረ ፡ መንጸረ ። ዝንቱ ፡ መንጸረ ፡ ዝንቱ ። መንጸረ ፡ ሙዳየ ፡ ምጽዋት ። ዘይቀውም ፡ መንጸረ ፡ (ዘፍ፴፫ ፡ ፲፱ ። ዘኍ፰ ፡ ፩ ። ኩፋ ፡ ፰ ። ማር፲፪ ፡ ፵፩ ። ፲፰ ፡ ፴፱) ።

**መንጸረ** ፤ ገሃደ ፤ ታይቶ ፡ ተገልጦ ፡ ግልጥ ፡ ኹኖ ፤ በግልጥ ፡ ፊት ፡ ለፊት ። አስተርአየ ፡ መንጸረ ። አውሥአሙ ፡ መንጸረ ። መንጸረኬ ፡ አበሳ ፡ ውእቱ ፡ ክፉል ፡ ለክልኤ ፡ (ቁር) ። ኢሖረ ፡ መንጸረ ፡ ቅድሜሁ ፡ (ዘኍ፳፬ ፡ ፩) ። መንጠረ ፡ መንጩረ ፤ ገላለጠ ፡ (ዐማርኛ) ። መንጠር ፡ ምንጣር ፡ ምንጣሪም ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ምንጽርና** ፤ አንጻርነት ፤ ተንጻጻሪነት ፡ ወደረኛነት ፡ ባላጋራነት ። ወንሕነ ፡ ንትመየጦሙ ፡ በተስእሎ ፡ ውስተ ፡ ምንጽርና ፡ (ቁር ፡ ጸላ) ።

**ተንጸረ** ፤ ታየ ፡ ተገለጠ ፤ ጕላ ፡ ተረዳ ፡ ግልጥ ፡ ኾነ ።

**ንጹር** ፤ (**ራን ፡ ራት ፡ ጽርት**) ፤ የታየ ፡ የጕላ ፡ ግልጥ ።

**ንጻሬ** ፤ (**ርያት**) ፤ ማየት ፤ መታየት ፤ አስተያየት ፤ ንጸራ ፡ የዐይን ፡ ሥራ ። ዘእንበለ ፡ ፈቲው ፡ በንጻሬ ። ሠናየ ፡ ንጻሬ ። ልደቱ ፡ ንጻሬ ፡ እምዐይን ። ንጻሬ ፡ አዕይንት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። አዋል ። ያዕ ፡ ዘእል ። ደራሲ) ።

—፤ ዐይን ፡ ብሌን ፤ የሚያይ ፡ ነጻሪ ። ንጻሬ ፡ ዘይሬኢ ፡ እምርሑቅ ፡ ተንትመ ። ከሠተ ፡ ንጻሬየ ። ፈታሒ ፡ ይኩን ፡ ድኍነ ፡ ምስማዕ ፡ ወንጻሬ ። አልዕል ፡ ንጻሬከ ፡ ወልበከ ፡ ኀበ ፡ ሰማይ ፡ (ግንዘ ። አፈ ፡ ድ፶ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፩ ። ፊልክ ፡ ፶፲) ።

**ተናጸረ** ፤ ተያየ ፡ ተንጻጸረ ፤ ተመሳሰለ ። ወእምዝ ፡ ተናጸሩ ፡ ንጉሥ ፡ ወመገብቱ ፡ በበይናቲሆሙ ። ወተናጸሩ ፡ ገጸ ፡ በገጽ ። አንቀጸ ፡ ዐጸድ ፡ ውሳጢ ፡ ይትናጸር ፡ ምስለ ፡ አንቀጽ ፡ በሜናዊ ። ሲናስ ፡ ይብር ፡ ይእቲ ፡ በብሔረ ፡ ዐረብ ፡ ወትትናጸር ፡ ምስለ ፡ ኢየሩሳሌም ። ቃሎሙ ፡ ጽዱቅ ፡ ዘኢይትናጸር ፡ ሕሳዌ ፡ ወጽልሑት ፡ (ዐዛ፱ ፡ ፴፫ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ሕዝ፵ ፡ ፵፫ ። ገላ፬ ፡ ፳፭ ። አዋል) ።

**አስተናጸረ** ፤ አስተያየ ፡ አናጸረ ፡ አነጻጸረ ።

**ነጸረ** ፤—ለየ ፡ **ነጠለ** ፤—**ነጺር** ፡ **ነፀረ** ።

**ነጸራር** ፤—**አዘራቱ** ፤—**ዖረረ** ።

**ነፀወ** ፤ (**ነፂው ። በፀወ ፤ ነቅጸ**) ፤ ደረቀ ፡ ከረረ ፤ ኳ ፡ ከው ፡ ከሸለለ ፡ አለ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በነፀወ ፡ ፈንታ ፡ አንፀወ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። በጽበሐ ፡ ይሠርጽ ፡ ወሠርከስ ፡ ይወድቅ ፡ የቢስ ፡ ወእንፂዎ ፡ (መዝ ፡ ፹፱) ።

**አንፀወ** ፤ አደረቀ ፡ አከረረ ፤ አስደረቀ ።

**ነፅሐ** ፤—**ነጣ ፡ ነጸ** ፤—**ነጽሐ** ።

**ነፅኀ** ፤ (**ዕብ ፡ ናጣሽ**) ፤ ጣለ ፡ አንከባለለ ፡ ከምድር ፡ ፈጨ ፡ አንቈጫቈጨ ፤ አፈረጠ ፡ ፈጠፈጠ ፤ ሰበረ ። ዕጉልት ፡ ሰበ ፡ ነፀኀዋ ፡ ለጠቢሕ ፡ ወለደት ፡ በማዕ ። ወይነፅኑኪ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ይነፅኑ ፡ ውሉዶሙ ፡

በቅድሜሆሙ ። ይነፅኑ ፡ አንቀቅቀሎሆሙ ። ይነፀኖሙ ፡ ውስተ ፡ ኵሎሙ ። ወነፀኑ ፡ ዝክተ ፡ መሳብክተ ፡ (ዮሴፍ ፡ ኢሳ፲ ፡ ፳፯ ። ፲፫ ፡ ፲፯ ። ፳፰ ፡ ፯ ። መገ፡ ፲፱፯ ። መሩ፯ ፡ ፲፱ ፡ ፳) ።

**ነፅኀ፤ (ዕብ ፡ ናጻሕ)፤** ድል ፡ ነሣ ፤ አሸነፈ ፡ አዋረደ ፤ አጠቃ ፡ ገዛ ፡ ረገጠ ፡ ምድር ፡ አስጋጠ ። ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገባል ። እነፅኆሙ ፡ በኲናት ። ትነፅኆሙ ፡ ለአህጉር ፡ ጽኑዓት ። ከመ ፡ ኢይንፅኅዎሙ ፡ ለሕዝብ ። ነፀኃ ፡ እግዚ ፡ ለወለት ፡ ድንግል ፡ (ኤር ፲፱ ፡ ፯ ። ኢሳ፳፯ ፡ ፳ ። ዮኤ፲ ፡ ፲፯ ። ሰቈ ፡ ፲፭) ።

**አንፅኀ፤** አስጣለ ፤ ጣለው ፡ አለ ።

**ተነፅኀ፤** ተጣለ ፡ ተወረወረ ፤ ወደቀ ፡ ተዋረደ ። ተነፀንት ፡ ለሲፃ ፡ እመካን ፡ ልዑል ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ከመ ፡ ትሙት ፡ ወኢሞተት ። ረከቦ ፡ ለአቡሁ ፡ ተነፂኖ ፡ (ዮሴፍ) ። ዲበ ፡ ምድር ፡ ትትነፃኅ ። ወመብዝኅቶሙ ፡ ተነፅኑ ፡ በገዳም ። አሜሃ ፡ ተነፅኑ ፡ አበሕፃን ፡ ወሰገደ ፡ ታሕተ ፡ እግረ ፡ አባ ፡ ዘይኑን ፡ (ኪዳ ። ፩ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ የካ፫) ።

**ንፁኅ፤ (ኃን ፡ ኃት ፡ ፅኅት)፤** የተጣለ ፡ ውዱቅ ።

**ንፅኀት፤** ተጥሎ ፡ መውደቅ ፤ መንቃት ፡ መሠንጠቅ ፤ ወይም ፡ ጥሎ ፡ መስበር ፡ ማድቀቅ ፡ ጥሎሽ ፡ አጣጣል ፤ ስብራት ። ይቀሥፎ ፡ ለዐቢይ ፡ ቤት ፡ በድቀት ፡ ወለንኡስ ፡ ቤት ፡ በንፅኀት ፡ (ዓሞ፮ ፡ ፲፩) ።

**ነፀፈ፤—ዘረጋ ፡ አነጠፈ፤—ነጺፍ ፡ ነጸፈ ።**

**ነፂፍ፤ ፎት፤ (ነፅፈ ፡ ይነፅፍ ፡ ይንፅፍ ። ዐረ ፡ ነሸፈ፤ ነፀበ)፤** መንጠፍ ፡ መድረቅ ፡ ማለቅ ፡ መሥረግ ፤ ምጥጥ ፡ ማለት ፤ የፈሳሽ ። ፈልፈል ፡ ዘኢይነፅፍ ። ፈለግ ፡ ይነፅፍ ፡ ወይየብስ ። ይነፅፍ ፡ ማየ ፡ ዮርዳኖስ ። ከመ ፡ ኢይንፅፉ ፡ ዐዘቃቲክ ፡ (አርጋ ፡ ፭ ። ኢዮ፲፬ ፡ ፲፩ ። ኢያ፫ ፡ ፲፫ ። ምሳ፱ ፡ ፳፩) ።

**ንፁፍ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ፅፍት)፤** የነጠፈ ፡ የደረቀ ፤ ምጥጥ ፡ ያለ ፡ ደረቅ ። ክረዩ ፡ ሎሙ ፡ ዐዘቅተ ፡ ንፁፈ ። ዐዘቅት ፡ ንፁፍት ፡ (ኤር፪ ፡ ፲፫ ። ፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፯) ።

**አንፀፈ፤** አደረቀ ፤ አስደረቀ ። ያነፅፍ ፡ እግዚ ፡ ባሕረ ፡ ግብጽ ። አንፀፍኩ ፡ ማየ ። ያነፅፍ ፡ ዐዘቃቲሁ ። ያነፅፎሙ ፡ ለዙሉ ፡ አፍላግ ፡ (ኢሳ፲፩ ፡ ፲፭ ። ፴፯ ፡ ፳፭ ። ሆሴ፲፫ ፡ ፲፭ ። ናሖ ፡ ፬) ።

**ነፀፍፃፍ፤—ጠፈጠፍ፤—ጸፈ ፡ ጸፍጸፈ ።**

**ነፀረ፤—አየ ፡ አስተዋለ፤—ነጽሮ ፡ ነጸረ ።**

**ነፂር፤ ሮት፤ (ነፀረ ፡ ይኔፅር ፡ ይንፅር ። ሠጸረ)፤** መለየት ፡ መክፈል ፡ መሠንጠቅ ። ነፀር ። ነፂረ ፡ እኔፅራ ፡ ለመንግሥትከ ፡ እምነ ፡ እዴከ ። ለፀኑሳት ፡ ነፀሮን ፡ (ቅዳ ። ፫ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፲፩ ፡ ፴፩ ። ፬ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮) ። በነፀገ ፡ ፈንታ ፡ ነፀረ ፡ ይባል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ትኔፅር ፡ ሕፃናቲሆሙ ፡ (፬ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፪) ።

**ነያራር፤—የራስ ፡ በሽታ፤—ያረረ ።**

**ነቂብ፤ በት፤ (ነቀበ ፡ ይነቅብ ፡ ይንቅብ፤ ነቈረ ። ዕብ ፡ ናቃብ፤ ናቃር)፤** መውጋት ፡ መብሳት ፡ መንደል ፡ መፈልፈል ፡ መሰርሰር ። መለየት ፡ ማራቅ ፤ ማውጣት ፡ ማስለቀቅ ፤ ፍልፈዩን ፡ ከውስጥ ፡ ከበታው ። ማስፋት ፡ ማበፋፋት ፤ ስፊ ፡ ማድረግ ፤ መንቀብ ፤ እንቅብ ፡ መስፋት ።

**አንቀበ፤** አስነቀበ ፤ እንቅብ ፡ አሰፋ ፤ በእንቅብ ፡ ሰፈረ ፤ አሰፈረ ።

**ተነቅበ፤** ተነቀበ ፤ ተወጋ ፡ ተበሳ ፤ ተነደለ ። ተለየ ፡ ራቀ ፤ ወጣ ፡ ለቀቀ ፤ በታውን ። ሰላም ፡ ለፀአተ ፡ ነፍስኪ ፡ በመዐዛ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተነቅበ ፤ መሰንቀ ፡ ማሕሌት ፡ ሐዋዝ ፡ ከመ ፡ ያሰርር ፡ አልባበ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳፩) ። በተነቅበ ፡ ፈንታ ፡ ነቀበ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፤ ዳግመኛም ፡ በተነቅበ ፡ ፈንታ ፡ ተቈአ ፡ ይባል ፤ እንደ ፡ ተነቅበ ፡ አያጠግብም ። ነቀበተኒ ፡ ነፍስየ ፡ እምኔሃ ፤ በከመ ፡ ነቀበታ ፡ ነፍስየ ፡ ለእኀታ ፡ (ሕዝ ፳፫ ፡ ፲፰) ።

**ንቁብ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ቅብት)፤** የተበሳ ፡ የተነደለ ፤ ብስ ፡ ነዳላ ፡ ፍልፍል ፡ ሽንቍር ። የተሰፋ ፡ ሰፍ ፤ ሰፊ ፡ እንቅብ ፡ አፍ ።

**ንቁበ፤ (ዕብራ)፤** ንቅብት ፤ ሴት ፡ እንስት ፤ ቈብ ። ነቃቢት ፤ የምትበሳ ፡ የምትቃታ ።

**ንቅበት፤ (ታት ። ዐረ ፡ ኑቅበት)፤** የሥራ ፡ ልብስ ፡ ዐጭር ፡ ቀሚስ ፡ ጌጥነት ፡ ያለው ። ድግ ፡ መቀነት ፡ ዝናር ፡ የሴቶች ፡ ሥራ ፤ እንደ ፡ ወንፊት ፡ የተበሳሳ ፡ ትት ፡ ዘርፋም ። ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ ጁኅ ፡ ጀባ ፡ ይሉታል ። ሰንዱናተ ፡ ኀብረት ፡ ወጸገወተ ፡ ሲምታ ፡ ወንቅበታተ ፡ ለከነናውያን ፡ (ምሳ፴፩ ፡ ፯፫ ። ዲድ ፫) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ሰንዱን ፡ ትገብር ፡ ወትሠይጥ ፤ ወመቅነተ ፡ ትሁብ ፡ ለከነናናዊ ፡ ይላል ፤ ለነጋዴ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ምሳ፴፩ ፡ ፳፬) ።

**ነቂሀ፤ ሆት፤ (ነቅሀ ፡ ይነቅሀ ፡ ይንቃሀ ። ዐረ ፡ ነቂሀ ። ዕብ ፡ ያቃጽ)፤** መንቃት ፡ ብንን ፡ ማለት ፤ ከእንቅልፍና ፡ ከሞት ፡ መመለስ ፤ ዐይንን ፡ መክፈት ፡ መነሣት ፡ መትጋት ፡ መቀቀር ፤ ለማየት ፡ ለመስማት ። ኖመ ፡ ባዕል ፡ ወአልቦ ፡ ነቂህ ። ነቅሀ ፡ እምንዋሙ ። ወአንተሰ ፡ ንቃህ ፡ ወጥብብ ፡ በዙሉ ። ሰበ ፡ ሰምዐት ፡ ቃሎ ፡ ነቅሀት ፡ በልባ ። ለእመ ፡ ነበርከ ፡ ምስለ ፡ ማእምራን ፡ ትጋሀኬ ፡ ወንቃህ ፡ ከመ ፡ ትስማዕ ፡ ቃሎሙ ፡ (ኢዮ፳፯ ፡ ፲፱ ። ዘፍ፳፰ ፡ ፲፯ ። ፪ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ሐም፳ ። ፈላስ) ።

**—፤** መዳን ፡ መፈወስ ፤ ማምለጥ ፡ መውጣት ። አመ ፡ ነቅሀ ፡ እምደዌሁ ፡ ዘቀብጸ ፡ እምኔሃ ፡ ተስፋ ፡ ፈውስ ። ይንቅሁ ፡ እመሥገርተ ፡ ሰይጣን ፤ እስመ ፡ ወድአ ፡ አሥገሮሙ ፡ (ፈላስ ፡ ገ፹ ። ፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፳፮) ።

**ንቃሂ** ፤ (ሂት ፡ ሀያን ፡ ያት) ፤ የነቃ ፡ የሚነቃ ፡ ንቁ ። ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ለባውያነ ፡ ወነቃህያነ ፡ (ዮሴፍ) ። በነቃሂ ፡ ፈንታ ፡ ንቁሃዊ ፡ ይባል ፡ (ፈልክ) ።

**ንቁህ** ፤ (ሃን ፡ ሃት ፡ ቁህት) ፤ የነቃ ፡ ንቁ ፤ ትጉህ ፡ ልባም ፡ አስተዋይ ። ውእቱ ፡ እንዘ ፡ ንቁህ ። አነ ፡ ንዉም ፡ ወልብየ ፡ ንቁህት ። ይኩና ፡ አዕይንቲከ ፡ ንቁሃተ ። ልቡ ፡ ንቁህ ፡ ለርእየ ፡ ኀጣይእ ። ንቁሃነ ፡ ኩኑ ፡ ወኢትትሀከዩ ፡ ለንስሓ ፡ (ቄድር ። ማሕሌ ፡ ፭ ። ፪ሴና ፡ ፯ ፡ ፵ ። ፈልክ ፡ ፶፴፭ ። ቀሌ) ።

**ንቅሀት** ፤ መንቃት ፡ አንቃቅ ፤ ንቃት ፡ ትጋት ፤ ንቅንቅ ። ፉኑ ፡ ንቅሀትከ ፡ ወኢሰኪቦትከ ። እምድኅረ ፡ ንቅሀተ ፡ ሌሊት ። ሀሉ ፡ ወትረ ፡ በንቅሀት ፡ ወተወቅቦ ፡ እንዘ ፡ ትጸንሕ ፡ ምጽአተ ፡ ቀትል ። ይቁሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በህድአት ፡ ወበንጽሕ ፡ ወበንቅሀት ፡ ሀቢይ ፡ ለሰሚዐ ፡ ነገረ ፡ እግዚ ፡ (ፊላስ ። ዮሴ ፡ ፲፪ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ተ፳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱) ።

**ንቃህ** ፤ ገዘኒ ፡ ከማሁ ። ከመ ፡ ዘንቀህ ፡ እምንዋም ፡ (መዝ ፡ ፸፪ና ፡ ፸፯) ።

**አንቅሀ** ፤ አነቃ ፡ አነቃቃ ፤ ቀሰቀሰ ፡ አስነሣ ፤ አተጋ ፡ አነሣሣ ። አንቅሆ ፡ እምዐቢይ ፡ ንዋም ፡ ለዘ ይነውም ። እለ ፡ ያነቅሁ ፡ ምዉተ ። ከመ ፡ ያንቅህ ፡ ልበሙ ። ከመ ፡ አንቅህክሙ ፡ በዘክሮ ፡ (ሢራ ፡ ፳፪ ። ፯ ። ፳ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፫ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ። ቀሌ ። ፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፫) ።

**አንቃሂ** ፤ መንቅሂ ፡ ሀ ፤ የሚያነቃ ፡ የሚያስነሣ ፡ አንቂ ፡ አስነሽ ። መንቅሄ ፡ ሙታን ። መንቅህያነ ፡ ምዉት ፡ (ቅዳ ፡ ያዕ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰ ። ዲድ ፡ ፲፫) ።

**ምንቃህ** ፤ (ሃት) ፤ መንቂያ ፤ ማንቂያ ።

**ነቂው** ፤ ምት ፤ (ነቀወ ፡ ይነቁ ፡ ይንቁ ። ዐረ ፡ ነቀ ፤ ነህቀ ። ዕብ ፡ ናሀቅ) ፤ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ መጮኽ ፡ መጓጕር ፤ ማግሣት ፡ ማናፋት ፤ መትመም ፡ መክከል ፤ በታላቅ ፡ ቃል ፡ መጥራት ፤ ታላቅ ፡ ድምጥ ፡ መስጠት ። በቀወን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ፤ ሰንቀወም ፡ የአንቀወ ፡ ድርብ ፡ ይባላል ። ነቀወ ፡ ከመ ፡ ሐራውያ ፡ ገዳም ፡ በመዐት ። ይነቅዉ ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ። ዘእንበለ ፡ ይንቁ ፡ ዶርሆ ። ይነቁ ፡ ተዝካ ፡ ወይጼውዕ ፡ አብያጺሁ ፡ ለቀቲለ ፡ እንስሳ ። እብንኒ ፡ ትነቁ ። ብርት ፡ ዘይነቁ ። ግብር ፡ ዘአልቦ ፡ ነፍስ ፡ ይነቁ ፡ (መቃ ፡ ገ፪ ። ሶፎ፪ ፡ ፲፬ ። ማቴ፳፮ ፡ ፴፬ ። ሥር ፡ ጸሎ ። ሱቱ ፡ ዕንባ፫ ፡ ፰ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ። ፲፱ ፡ ፯) ።

**ነቃዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ቀውት) ፤ የሚጮኽ ፡ ጯኺ ፤ ድምጣም ። ሰባም ፡ ለከ ፡ ነቃዌ ፡ መጽሐፍ ፡ ማዐነቅ ፡ ፊቅጦር ። ዶርሆ ፡ ነቃዊ ፡ (ስንክ ። ኅዳ ፡ ፲፩ና ፡ ፳፪) ።

**ንቅው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ቁት ፤ ቅውት) ፤ የጮኸ ፡ ጯኺ ፤ የተጮኸ ፤ የተጮኸበት ።

**ንቅወት** ፤ መጮኽ ፡ አጯጯኽ ፡ ጩኸት ። ጊዜ ፡ ንቅወተ ፡ ዶርሆ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፫) ።

**ንቃው** ፤ ጩኸት ፡ ጥሪ ፤ ታላቅ ፡ ድምጥ ። ንቃወ ፡ አዕዋፍ ፡ ወአራዊት ። ንቃወ ፡ አፍራስ ። ንቃወ ፡ ዜማ ፡ ንህብ ፡ (መቃ ፡ ገ፳፪ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ሚያ፲፯) ።

**አንቀወ** ፤ አስጮኸ ፤ ደወለ ፡ መታ ። ሰንቀወን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ነቂዝ** ፤ ዞት ፤ (ነቅዘ ፤ ነቀዘ ፡ ይነቅዝ ፡ ይንቅዝ ። ዕብ ፡ ናቆዝ ፤ ሀቄዝ ፤ በጣ ፡ ዐገመ) ፤ መንቀዝ ፤ መጠንጠን ፡ ማርጀት ፤ መሻገት ፡ መበላሸት ። ዕፀ ፡ ዘኢይነቅዝ ። ብዕልክሙ ፡ ኖኀዘ ፡ (ኢሳ፵ ፡ ፳ ። ያዕ፭ ፡ ፪) ። ጸንጸንንና ፡ ቈንቈንን ፡ እይ ።

**ንቁዝ** ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ቀዝት) ፤ የነቀዘ ፡ የጠነጠነ ፡ የሻገተ ፡ ሻጋታ ። ዘይዘርዕ ፡ ሥርናየ ፡ ንቁዘ ። ወኅብስተ ፡ ሥንቅመሙ ፡ ይቡስ ፡ ወንቁዝ ፡ (አረጋ ። ኢያ፱ ፡ ፭) ።

**ነቀዝ** ፤ (ዛት ፤ አንቃዝ) ፤ በቁሙ ፤ ታናሽ ፡ ትል ፡ ዕንጨትን ፡ እኽልን ፡ ድልብን ፡ የሚያበላሽ ፤ የሚበሳሳ ፡ የሚበላ ፡ ከዚያው ፡ ከውስጡ ፡ የሚፈላ ፤ ይልቁንም ፡ ከሰንደል ፡ ከገብስ ፡ ከማሽላ ። ከመ ፡ ቍንቍኔ ፡ ለልብስ ፡ ወነቀዝ ፡ ለዕፀ ። ኅበ ፡ ኢይክርዮ ፡ ሰራቂ ፡ ወኢያማስኖ ፡ ነቀዝ ። ብእሲት ፡ ወውሉድ ፡ ነቀዙ ፡ ለንዋይ ፡ (ምሳ፳፭ ፡ ፲፱ ። ፈልክ ። ፈላስ) ።

**ነቌጠ** ፤ አው ፡ ነቍጠ ፤ (ዐረ ፡ ነቀጠ ። ዕብ ፡ ናቃድ) ፤ ነጠበ ፤ ጠብ ፡ አለ ። ነጥበን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**አንቌጠ** ፤ አነቈጠ ፤ አስነቈጠ ፤ ነቍጣ ፡ አደረገ ።

**አንቌጥቌጠ** ፤ አንቈጠቈጠ ፤ ሸለመ ፡ አሰጌጠ ፤ ተንቈጠቈጠ ፤ በቀለም ፡ በልብስ ። ሰባውዳመት ፡ በዓል ፡ ግጫና ፡ አበባ ፡ ይዞ ፡ እንቍጣጣሽ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ምስጢሩ ፡ የምሥራች ፡ ነው ፤ ኀለፈ ፡ ክረምት ፡ ቀመ ፡ በረከት ፡ ተሰርገወት ፡ ምድር ፡ በሥነ ፡ ጽጌያት ፡ እያሰኘ ፡ ርግብ ፡ ምኅን ፡ ያሳስባል ።

**ነቍጥ** ፤ (ጣት ። ዐረ ፡ ኑቅጠት ። ዕብ ፡ ንቁዳ ። ሱር ፡ ኑቅዛ) ፤ በቁሙ ፤ ነቍጣ ፡ አንዲት ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ ጠብታ (፡) የነጥብ ፡ እኩሌታ ፤ ታናሽ ፡ ምልክት ፡ የቃል ፡ መለያ ፤ ጌጥነትና ፡ ወሰንነት ፡ ያለው ፡ በያንዳንዱ ፡ ኅርመት ፡ በየስኩ ፡ በየሣጥኑ ፡ የሚገባ ። ጥንታዊው ፡ ያሮጌው ፡ ግእዝ ፡ ነቍጥ ፡ እንደ ፡ የውጣ ፡ ዘንግ (I) ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ዜማ ፡ ይዘት ፡ አንድ ፡ ቅንጣት ፡ ብቻ (.) ነበረ ፤ ዘንጉና ፡ አንዱ ፡ ቀርቶ ፡ ኹለት ፡ የኾነ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ነው ። ቃልከ ፡ ነቍጥ ፡ እንዘ ፡ ክልኤቲ ፡ ልባንክ ፡ ሰሐቲ ፡ ይእቲ ፡ (ቅኔ) ።

**ነቀጥቃጥ** ፤—በሽታ ፤—ቀጥቀጠ ፤ አን ።

**ነቈጥሩ** ፤ (ሮማይ ፡ ኔክታር ። ዕብ ፡ ቅጦሬት ፤ ዕጣን) ፤ ጥሩ ፡ ጥፍጥ ፤ የተነጠረ ፡ ሽቱ ፡ መጠጥ ፤ ኅበቶ ፡ የሚቀመመው ፡ ያበባ ፡ ውሃ ። የሽቱ ፡ ዕንጨት ፡ የዕጣን ፡ ዘፍ ፤ ደምና ፡ ሙጫ ፡ ወለላ ፡ ያለው ።

ወይወፅእ ፡ ማይ ፡ እምኔሁ ፡ ከመ ፡ ነቂጦሩ ፡ ዘ
ሰመ ፡ ሳሬራ ፡ ወከልበኒ ፡ (ሔኖ፴፩ ፡ ፭) ።

**ነቀለ** ፤ (ነቂል ። ፀረ ፡ ነቀለ ፤ ፈለሰ) ፤ በቁሙ ፤ መዘዘ ፡ አወጣ ፡ መነገለ ፡ አፈለሰ ፤ ከበቀለበት ፡ ከተተከለበት ፡ ካለበት ፡ ቦታ ፡ ከሥሩ ። ፈንቀለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ። ትሥሩ ፡ ወትንቅል ፤ ትንሥት ፡ ወትሕንጽ ። ንቀሉ ፡ እምዕፀመ ፡ ገበሁ ፡ እሕደ ። አው ረድዎ ፡ እመስቀል ፡ ነቂሎሙ ፡ ቅንዋተ ። ንቅል ፡ ሊተ ፡ ምክ ፡ ኃጢአት ። ነቀለ ፡ ደብረ ፡ ወተከለ ፡ ደብረ ፡ (ተረ ፡ ቄር ፡ ፭ ። ኤር፩ ፡ ፲ ። ሲኖዶ ። ስንክ ፡ ነሐ፭ ። ኅዳ፲ ። ቃግ፯) ።

**ተንቅለ** ፤ ተነቀለ ፤ ተመዘዘ ። በእንተ ፡ ዘተ ነቅለ ፡ ዐፅመ ፡ ገበሁ ፡ (ቅዳ ፡ ቄር) ።

**ነቀልቃል** ፤—ንውጽውጽታ ፤—ቀል ቀለ ፤ አን ።

**ነቂዕ** ፤ ዖት ፤ (ነቅዐ ፡ ይነቅዕ ፡ ይንቃዕ ። ፀረ ፡ ነቀፀ ። ዕብ ፡ ናቃዕ ፤ ተለየ ፡ ራቀ ። ናቃቅ) ፤ መንቃት ፡ መሠንጠቅ ፤ መፈንዳት ፡ ጧ ፡ ማለት ፤ መተርተር ፤ መለየት ፡ መከፈል ። ይነቅዐ ፡ ደ ብረ ፡ ዘይት ። ትነቅዐ ፡ ኵዙሕ ። ለይንቃዐ ፡ ምሥ ዋዕ ። ኅብስት ፡ ዘተርፈ ፡ እምትማልም ፡ እው ፡ ዘነ ቅዐ ። አጽደፍዎሙ ፡ እምርእሰ ፡ ቀልቀል ፡ ወዘ ሎሙ ፡ ነቅዑ ፡ (ዘካ፲፬ ፡ ፬ ። ኢሳ፴፯ ፡ ፳፩ ። ዮናግ ፡ ፲፫ ፡ ፫ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፮ ፡ ፩ ። ፪ዜና ፡ ፳፭ ፡ ፲፪) ።

—፤ መውጣት ፡ መፍለቅ ፤ መመንጨት ፡ መፍሰስ ። ከዚ ያው ፡ ከነቁ ፡ ከምንጭቁ ። ነቅዐ ፡ ማይ ፡ በውስተ ፡ በድው ። ወነቅዐ ፡ ሎሙ ፡ ፈለግ ፡ እምእብን ። ም ክሩ ፡ ይነቅዕ ፡ ከመ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡ (ኢሳ፴፭ ፡ ፮ ። ዮሴፍ ። ሚራ፳፩ ፡ ፲፫) ። በሐብጠ ፡ ፈንታ ፡ ነቅዐ ፡ ይ ላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። እገሪሆሙ ፡ ኢነቅዓ ፡ (ነሐ፱ ፡ ፳፩) ።

**ንቁዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ቅዕት) ፤ የነቃ ፡ ንቅ ፡ ምንጥቅ ፤ ምንጣም ፡ ውሃማ ። ጸድፍ ፡ ብሔሩ ፡ ወን ቁዕ ፡ ምድሩ ፡ እምኔ ፡ ማያት ፡ (ሄርማ) ። በንቁዝ ፡ ፈንታ ፡ ንቁዕ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ዕፀ ፡ ንቁዕ ፡ ወጽንጹን ፡ (ኩፋ ፡ ፳፩) ።

**ንቅዐት** ፤ (ታት ። ዕብ ፡ ንቂቅ) ፤ መን ቃት ፡ መሠንጠቅ ፡ አንቃቅ ፤ ንቃቃት ፡ ንቅ ፡ ሥንጣቃ ፡ ሥንጥቅ ። ንቅዐተ ፡ ምድር ፡ ዕሙቅ ። ንቅዐታተ ፡ ኵዙሕ ። ለእመ ፡ ቦ ፡ ንቅዐት ፡ ውስተ ፡ ኅብስት ። ዝ ንቱ ፡ ንቅዐት ፡ (ሔኖ፲፰ ፡ ፲፩ ። ኢሳ፪ ፡ ፲፱ ። ቄድር ። ስንክ ፡ ግን፳፫) ። ነቅዐና ፡ ንቅዐት ፡ ከነቅዐና ፡ ከንቅዐት ፡ ጋራ ፡ በማርኛ ፡ እንዲተባበሩ ፡ በምስጢርም ፡ ይገራ ቢታሉ ።

**ነቅዕ** ፤ (ብ ፡ አንቅዕት ፡ ታት) ፤ በቁሙ ፡ ነቅ ፡ ምንጥቅ ። ምንጭ ፤ ዐይን ፡ ማይ ፤ ታናናሽ ፡ ወ ንዝ ። ነቅዐ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ። ንስቲት ፡ ነቅዐ ፡ ማይ ፡ እንተ ፡ ከነት ፡ ፈለገ ። ዘይፈኑ ፡ አንቅዕተ ፡ ውስተ ፡ ቈላት ። ወተዐጽወ ፡ አንቅዕተ ፡ ቀላይ ። ወነዋ ፡ አን ቅዕታት ፡ ተርኅወ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ (ኤር፪ ፡ ፲፫ ። አ ስቴ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፻፫ ። ዘፍ፯ ፡ ፲፩ ። ሔኖ፹፱ ፡ ፫) ። በምዕቃል ፡ ፈንታ ፡ ነቅዕ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ... ፡ አንቅዕተ ፡ ማያት ፡ (ሚራ፲ ፡ ፫) ።

**አንቅዐ** ፤ አነቃ ፡ ሠነጠቀ ፤ ለየ ፡ ፈለሰ ። ይመ ትሮሙ ፡ ወያነቅዖሙ ። ተአዘዘ ፡ ያንቅዕከ ፡ እማእክ ልከ ። አንቅዕዎን ፡ ለፀነሳት ። ዐውሎ ፡ ኀያል ፡ ያነቅዓ ፡ (ጥበ፬ ፡ ፲፱ ። ዳን፲ ፡ ፶፮ ። ዓሞ፩ ፡ ፲፫ ። ሕዝ፲፫ ፡ ፲፩) ።

—፤ አመነጨ ፤ አፈለቀ ፡ አወጣ ፡ አስገኘ ። አነቅዐ ፡ አፍ ላግ ፡ ውስተ ፡ አድባር ። ዐዘቃተ ፡ ምድር ፡ አንቅዑ ፡ ማያተ ፡ ብዙኀ ። ዐይን ፡ ዘታነቅዕ ፡ ነፍጠ ። ዘአን ቅዓ ፡ ለጥበብ ፡ እምልቡ ፡ (ኢሳ፵፩ ፡ ፲፰ ። አቡሻ ፡ ፵፰ ። ዮሴፍ ። ሚራ፲ ፡ ፳፯) ። ሐቀፈ ፡ አንቀቅሖ ፡ በማለት ፡ ፈ ንታ ፡ አንቅዐ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። አንቀቅሖ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ያነቅዑ ፡ (ኢሳ፶፱ ፡ ፭) ።

**አንቃዒ** ፤ መንቅዒ ፡ ዕ ፤ ት ፤ የሚያነቃ ፡ አ ንቂ ፤ ሠንጣቂ ፡ አፍላቂ ። መንቅዒት ፡ ለእንቁ ፡ ይሰ ተይ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**መንቅዕት** ፤ (ብ ፡ መናቅዕ ፡ ት) ፤ ንቅ ፤ ሥ ንጥቅ ፡ ንቃቃት ። በመንቅዐተ ፡ ደብር ፡ (መ... ፡ ገ፳፮) ።

—፤ ማውጫ ፡ ዳሌ ፡ የወገብና ፡ የጭን ፡ መጋጠሚያ ፡ ወ ይም ፡ መለያያ ። በይፉ ፡ ዲበ ፡ መንቅዐቱ ። ንብረት ፡ መናቅዐትኪ ፡ (ማሕ፫ ፡ ፳ ። ፯ ፡ ፪) ። ባለብሎች ፡ ግን ፡ መታጠቂያ ፡ መቀነቻ ፡ ወገብ ፡ ብብት ፡ ላት ፡ ይሉታል ። ፪ኛም ፡ በቍየጽ ፡ ፈንታ ፡ መናቅዕ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። እምሐቋ ፡ እስከ ፡ መናቅዕ ። ሥብሐ ፡ ዘዲበ ፡ መና ቅዕ ፡ ወከብድ ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፴፰ ። ኩፋ ፡ ፳፩) ።

—፤ ተቃዋሚ ፤ ተቃራኒ ፤ ተፃራሪ ። መናቅዐቲሃ ፡ ለእ ኪት ፡ ሠናይት ፤ ወመናቅዐቲሁ ፡ ለሞት ፡ ሕይወት ፤ ከማሁ ፡ መናቅዐቲሃ ፡ ለጽድቅ ፡ ኃጢአት ፡ (ሚራ፴፮ ፡ ፲፬) ። መንቅዕታ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ያንዱን ፡ በብዙ ፡ መናቅዕቲሃ ፡ ማለት ፡ የመላሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ነቀፈ** ፤ (ነቂፍ ፤ ነጊፍ ፡ ነገፈ ። ዕብ ፡ ናቃፍ ፤ ናጋፍ ። ፀረ ፡ ነቀፈ) ፤ በቁሙ ፤ አጸየፈ ፡ ዐ ነቀፈ ፡ ዕንቅፋት ፡ ኾነ ፤ መታ ፡ አረገፈ ፤ ጣለ ፡ ቀረፈ ። ኢትንቅፉ ፡ ግድፌተ ። ወነቀፈ ፡ ቅርፍተ ፡ ዕፀ ፡ ወወ ገረ ፡ ህየ ፡ (አዋል ። ፀንገ ፡ ፯ ፡ ፯) ። ቀረፈንና ፡ በቀፈን ፡ ነገፈን ፡ እይ ፤ ሥሩ ፡ ምንጩ ፡ ነጊፍ ፡ ሲኾን ፡ ቀና ፡ ን ፡ ተወራርሰዋል ።

**አንቀፈ** ፤ አስነቀፈ ፤ ዕንቅፋት ፡ አስመታ ።

**ተንቀፈ** ፤ ተነቀፈ ፤ ተመታ ፡ ተጣለ ፡ ተቀረፈ ።

**ንቁፍ** ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ቅፍት) ፤ በቁሙ ፡ የተ ነቀፈ ፡ ነውረኛ ፡ ስዱብ ፤ የተጣለ ፡ የተመለሰ ። ወትረ ሰየሙ ፡ ንቁፋነ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፲፫) ።

**ንቅፈት** ፤ መንቀፍ ፡ መነቀፍ ፤ አንቃቀፍ ፤ ን ቀፋ ፡ ንቀፈታ ። በቂራር ፡ ወንቅፈት ፡ ወግማኔ ። ም እመን ፡ ወጠቢብ ፡ ዘርሑቅ ፡ እምንቅፈት ፡ ወድ ኅን ፡ እምነውር ፡ (ኩፋ ፡ ፴፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፩) ።

**ነቅጸ፤** (ነቂጽ። ዐረ፡ ነቀጸ፤ ነቀሰ፥ አ ጕደለ)፤ ደረቀ፡ ከረረ፤ ነቃ፡ ተሠነጠቀ፡ ከፍት፡ ኾነ፤ ከዚህ፡ የተነሣ፡ አነሰ፡ ቀለለ፡ ጐደለ፤ ዋጋው፡ ሚዛኑ። ነቅጸ፡ ከመ፡ ሣዕር፡ አዕፅምትየ። ነቅጸ፡ አቡኑ፡ በሐ ዘን፡ ለመዊት፡ (መዝ፡ ፻፩። ኩፋ፡ ፵፫)። ነፀወንና፡ የብሰን፡ እይ፤ የዚህ፡ ጎሮች፡ ናቸው።

**ንቁጽ፤** (ጻን፡ ጻት፡ ቅጽት)፤ በቁሙ፤ የደ ረቀ፡ ደረቅ፤ ሕጹጽ። ንቁጸ፡ ወሕጹጸ፡ ይለውሱ፡ በ መዓር። ዘይምህክ፡ ሰውሥአ፡ ቃል፡ ንቁጽ፡ ማእ ምር፡ (መ፡ ፈ። ምሳ፲፯፡ ፳፯)።

**ንቅጸት፤** መድረቅ፤ ድርቅና፡ ሕጸጽ።

**ነቅጽ፤** ድርቅ፤ ነቅ፡ ሥንጥቅ፤ ከፍት፡ ባይ።

**አንቀጸ፤** አደረቀ፡ አጐደለ፡ አሳነሰ፤ አነቃ፡ ሠ ነጠቀ፡ ከፍት፡ አደረገ፤ ለየ፡ ከፈለ። አጸና፡ አበረታ፤ ምስጢሩ፡ ከማድረቅ፡ ይገባል።

**አንቀጽ፤** (ብ፡ አናቅጽ)፤ በር፡ ደጃፍ፤ መ ውጫ፡ መግቢያ፤ ከፍት፡ ጐደሎ፡ ቦታ። ኆኅትን፡ እይ፤ ኆኅው፡ ኆወ። ጸባብ፡ አንቀጽ። ረሓብ፡ አንቀጽ። አናቅ ጺሃ፡ ለወለተ፡ ጽዮን፡ (ማቴ፯፡ ፲፫፡ ፲፬። መዝ፡ ፱)።

—፤ የመጽሐፍ፡ ክፍል፤ ምዕራፍ። አንቀጽ፡ ቀዳማዊ፡ በእንተ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን። እምአናኅኩ፡ ነገረ፡ በ ዝንቱ፡ አንቀጽ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፩። አፈ፡ ተ፴፱)።

—፤ ዘማች፡ ቃል፤ የነገር፡ ማሰሪያ፡ ከዘር፡ ከነባር፡ የሚገኝ፤ ኀላፊና፡ ትንቢት፡ ትእዛዝ፡ የሚለዩበት፤ ከ ፈለ፡ ከፈለ፡ ይከፍል፡ ይክፍል፤ ቦ፡ ሎ፡ አከ፡ ይህን፡ የመሰለ።

—፤ የዜማ፡ ሥረይ፤ ብዙ፡ ድርብና፡ ዐመል፡ ያለው። አንቀጽ፡ ሃሌታ፡ (ድጓ)።

—፤ በረኛ፡ አጋፋሪ፤ ጭፍራ፡ ወታደር፡ ሰራዊት። አና ቅጸ፡ ሲኦል፡ ኢይኄይልዋ፡ (ማቴ፲፮፡ ፲፰)።

**ነቀ፟ረ፤** (ንቄረ፡ ይነቀ፟ር፡ ይንቀ፟ር። ዕብ፡ ናቃር። ሱር፡ ንቃር። ዐረ፡ ነቀረ)፤ መንቁር፤ መጠቅጠቅ፤ መጫር፡ መቈፈር። ሰቈረንና፡ ወቀረን፡ ዐቈረን፡ እይ፤ የዚህ፡ ጎሮች፡ ናቸው፤ ጥን ቁርም፡ የነቈረ፡ ዘር፡ ነው።

**ነቈረ፤** ወጣ፡ ጠፋ፤ ፈረጠ፡ ፈሰሰ፤ ጕደጕደ፡ ገበጣ፡ መሰለ። ዐይኑ፡ ዘየማን፡ ነቍረ፡ ይነቍር። ዐ ይንከ፡ እንተ፡ ነቈረት፡ (ዘካ፲፩፡ ፲፯። አዋል)።

**ንቁር፤** (ራን፡ ራት፡ ቀ፟ርት)፤ የወጣ፡ የ ጠፋ፡ የፈረጠ፡ የፈሰሰ። ዘንቁር፡ ዐይኑ። ንቁረ፡ ዐ ይን፡ ወምቱረ፡ እዝን፡ (ቀኖና። አዋል)።


**ነቋር፤** በቁሙ፤ አንድ፡ ዐይና፤ ዐይኑ፡ የወጣ፡ ገበጣ፡ ዐይን። ታመጽኡ፡ ነቋረ፡ ለመሥዋዕትየ፡ (ሚ ልክ፡ ፩። ማቴ፲፭፡ ፱። ማርቆ፡ ፵፯)።

**አንቈረ፤** አነቈረ፤ አስነቈረ፤ አስቈፈረ። አወጣ፡ ጨለጠ፡ አነቀረ፤ አጠፋ፡ አስጠፋ፡ አሳወረ። አንቈረቶሙ፡ እከዮሙ። አው፡ አንቈረ፡ ዐይኖ፡ (ጥበ፪፡ ፳፩። ገድ፡ ተክ)።

**እንቅር፤** እንቃር፡ እንጥል፡ የላይኛው፡ ክፍል፤ የጕረሮ፡ ደጃፍ። መቃጥን፡ ዘይሰቀ፟ር፡ እንቅሮ፡ (መጽ፡ ምስ)። ሕንቅርትንና፡ ኅንቅርትን፡ እይ፤ ከዚህ፡ የወጡ፡ ነው፤ አዐና፡ ሀሐን፡ ተወራራሾች፡ ስለ፡ ኾኑ፡ ወደዚያ፡ ኺዷል።

**እንቁር፤ እንቁራ፤** ጥንግ፡ ዕሩር፡ (ዐማርኛ)።

**እንቈራ፤** የንብ፡ እንጀራ፤ ጠቃጠቆው፡ ክ ፍቱ፡ ዐይኑ፡ ሰፈፉ፤ ዕሬጩና፡ ጕመሬው፡ ወለላው፡ የ ሚታቈርበት፡ አንዳንዱ፡ ጕድጓድ። እንቈራ፡ ዘይት ወሊድ፡ ቦቱ፡ ንህብ፤ ወጸቃውዕ፡ ይትዐቈር፡ ቦቱ፡ (ጥሬ፡ ሰዋ። አርጋ፡ ፩)።



እንቈራ፡

**እንቈራ፤** (ጽር፡ እንኪራ)፤ እንቆራ፤ ስመ፡ ሀገር። ቴዎዶጦስ፡ ዘእንቈራ፡ (ተረ፡ ቄር)።

**መንቁር፡** (ዕብ፡ ማቆር)፤ የአዕዋፍ፡ ሾንቢ፤ ያፋቸው፡ መንጦጥ፡ በጥርስና፡ በከንፈር፡ ቦታ፡ የበቀለው፤ መውጊያቸውና፡ ማንቈሪያቸው፡ መጠቅጠቂያቸው፤ እ ንደ፡ ጥፍርና፡ እንደ፡ ማጕርጥ፡ የሰላ፡ የሾለ፡ ያሾተለ። በቁሙ፡ የሽፍታ፡ ቀንበር፡ ረዥምም፡ ባላ፡ ዐንገቱን፡ እ ንደ፡ ወደፊን፡ ጠምዶው፡ በሥሩ፡ ይዘው፡ እየገፉና፡ እያዳፉ፡ የሚያመጡበት።



መንቁር፡

**ማንቀ፟ርት፤** በቁሙ፤ ምንገትና፡ ያገጭ፡ መ ገናኛ፡ ጕጠ፡ (ዐማርኛ)።

**ነቅሬስ፤** ነቀርሳ፡ ምሽሮ፤ ፈንጣጣ፡ ቂጥኝ።

**ነቀሰ፤** (ዐረ፡ ነጂሰ)፤ አደፈ፤ ረከሰ፤ እድ ፋም፡ ጕድፋም፡ ንቃሻም፡ ኾነ። ንቃቀሰ፤ ንቃሽ፡ አ ወጣ። አጠቈረ፡ በሾኽ፡ በቀለም። ኀተመን፡ እይ፤ ን ቅሳት፡ እንዲሉ፤ ጥቀ፟ራት፡ ሲሉ። በቁሙ፤ ቀነሰ፡ አ ሳነሰ፤ የዋጋ፤ ነቅጸን፡ እይ።

**አንቀሰ፤** አሳደፈ፡ አረከሰ፤ አጠማለቀ። አስነ ቀሰ፤ አስጠቈረ።

**እንቃስ፤** ዐዛባ፡ ጭቃ፡ ጭቅቅት፤ እድፍ፡ ጕ ድፍ፡ ንቃሽ። ይገብእ፡ ከልብ፡ ዲበ፡ ቅያኡ፤ ወሐ ራውያኒ፡ ተኀፂበ፡ ዲበ፡ እንቃሱ፡ (ቄር፡ ጳላ። ፪ጴጥ፡ ፪፡ ፳፪)።

**ነቀተ፤** (ነቂት)፤ በቁሙ፤ ነከተ፡ ደቀቀ፡ እ ንቀት፡ ኾነ።

**አንቀተ** ፤ አነቀተ ፡ አንከተ ፤ አስንቀተ ።

**እንቀት** ፤ በቁሙ ፤ የገብስ ፡ ከክ ፡ የበዕ ፡ ደቂት ፡ ክርቱ ፡ እንደ ፡ ሩገዝ ፡ ያለው ። እንቀት ፡ እንቅቼ ፡ ገንፎ ፡ አገንፍቼ ፡ እንዲሉ ፡ (ዐማርኛ) ።


**ንቁት ፡ ታ** ፤ ኒቆታ ፤ (ጽር ፡ ኔኽታ ። ዕብ ፡ ንከት) ፤ ጥሩ ፡ ሽቱ ፡ የነጠረ ፡ የተጣፈጠ ፤ ከቅባ ታም ፡ ዕንጨት ፡ የሚወጣ ፤ ወይም ፡ የሽቱ ፡ ቅመም ፡ የጢስ ፡ ዕንጨት ፡ የንከተ ፡ ነካታ ፡ ደቃቅ ፤ ንቁት ፡ የነ ቀተ ። የሐኪም ፡ መድኀኒት ፤ እንደ ፡ ሽቱ ፡ የተቀመመ ፤ የተበጀ ፡ የተዘጋጀ ፤ የኖረ ፡ ድልብ ፡ የቁየ ፡ የዘገነ ፡ መ ዝገብ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ የቃ ፡ ቤት ፡ የሥዕል ፡ ቤት ፡ ይሉታል ። ወአርአዮሙ ፡ ቤተ ፡ ኒቆታሁ ፡ (፬ነገ ፡ ፳ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፴፱ ፡ ፪) ።

**ናቀት** ፤ (ዐረ ። ዕብ ፡ ሜኒቆት) ፤ የግመል ጥገቶች ፡ እመጫቶች ፤ የሚያጠቡ ፡ የሚታለቡ ። አንዲ ቱን ፡ ናቅ ፡ ኑቅ ፡ ይባል ፡ (ዘፍ፴፪ ፡ ፲፭) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ የግመል ፡ ጊደር ፡ ይሉታል ።

**ናርኤል** ፤ ስመ ፡ ኮከብ ፡ ዐቢይ ፤ መጋቤ ፡ ክረ ምት ። ናር ፤ እሳት ፡ ብርሃን ፡ ኤል ፡ አምላክ ፤ በተገናኝ ፡ ብርሃን ፡ አምላክ ፡ (ሔኖክ) ።

**ናርዱ ፤ ናርድ** ፤ (ዕብ ፡ ኔርድ) ፤ የሽቱ ፡ ስም ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሽቱ ፡ ቅጠሉ ፡ ቡቃያው ፡ ታና ናሽ ፡ (ማር ፡ ፲፬ ፡ ፫ ። ዮሐ፲፪ ፡ ፫) ። ናርጅ ፤ የንጨት ፡ ሙዳይ ፤ የታነጠ ፡ የተነጠጠ ፤ የተሸለመ ፡ የተጌጠ ፡ ወ ሎቱ ፡ ሥራ ፡ የሽቱና ፡ የቅቤ ፡ ማኖሪያ ። ስሙን ፡ ከሽ ቱው ፡ ወስዷል ።

**ናርዶስ** ፤ (ጽር ። ዐረ ፡ ናርዲኒ ። ዕብ ፡ ናርዲኖን) ፤ ናርዳዊ ፡ ዘናርዱ ፤ የናርዱ ፡ ሽቱ ፡ መ ረቁ ፡ ቅባቱ ፡ የነጠረው ፡ የተጣፈጠው ። ከመ ፡ ናርዶስ ፡ ዘጸገየ ፡ ቧጸዐድዲድ ፡ (አርጋ ፡ ፪ ። ማሕ፩ ፡ ፲፪ ። ፬ ፡ ፲፫ ። ኩፋ ፡ ፲፮) ። ስማራግደስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ናር ደስ ፡ ይባላል ፤ የተባሳተ ፡ ነው ፤ መረግድን ፡ እይ ። ዘገ ቡር ፡ በናርዶስ ፡ (ድጓ) ።



ናርደስ ፡

**ነስአ** ፤—ወሰደ ፡ ተቀበለ ፤—ነሢእ ፡ ነ ሥእ ።

**ናሴብ** ፤—ዘበኛ ፤—ናስየብ) ።

**ነሲው ፤ ዎት** ፤ (ነሰወ ፡ ይነሱ ፡ ይንሱ ። ዕብ ፡ ኒሳህ ። ሱር ፡ ናሴይ) ፤ መፈተን ፤ መመር መር ፡ መሞከር ፤ ጠባዩን ፡ ትምርቱን ፡ ዕውቀቱን ፡ እም ነቱን ፡ ዐቅሙን ፡ ለማወቅ ።

**ነሳዊ** ፤ **መንስው** ፤ የሚፈትን ፡ ፈታኝ ፤ መር ማሪ ፡ ሞካሪ ።

**መንሰወ** ፤ (ነሰወ) ፤ ፈተነ ፡ መረመረ ፤ አስ ጨነቀ ፡ ጐዳ ፡ አጠፋ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመንሰወ ፡ ፈንታ ፡ አመንሰወ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። ይመክሩ ፡ በ ቍጽር ፡ ያመንስዉኒ ። መንሱተ ፡ ከመ ፡ ያመንስዎ ፡ (መዝ ፡ ፴፱ ። ፱ዜና ፡ ፳ ፡ ፳፱) ።

**አመንሰወ** ፤ (አንሰወ) ፤ አስፈተነ ፤ አስሞ ከረ ፤ አስጠፋ ።

**ተመንሰወ** ፤ (ተነሰወ) ፤ ተፈተነ ፡ ተመረ መረ ፤ ተጨነቀ ፡ ተማቀየ ፤ ጠፋ ፡ ተጐዳ ፤ ድል ፡ ኾነ ። ኢየኀድገክሙ ፡ ትትመንሰዉ ። ኃጥእ ፡ ይትመነሰ ፡ በሕቢት ። ኢትትመንሰዉ ፡ በፍትወት ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ሢራ፳፱ ፡ ፳፱ ። ፩ተሰ ፡ ፱ ፡ ፳) ።

**ምንስው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሱት) ፤ የተፈተነ ፡ ፍቱን ፤ ደካማ ፡ ከፉ ፡ ጥፉ ። ይሬስዮ ፡ ለመስተጋ ድል ፡ ምንስወ ። ከመ ፡ ምንስዋን ። ነፍስ ፡ ምን ሱት ። ጸላእትየ ፡ ምንስዋን ፡ (ፊልክ ፡ ፭፱ ። ፪ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፱ ። ዘዳ፳፰ ፡ ፶፰ ። መዝ ፡ ፲፯ ።

**ምንሳዌ** ፤ መጥፋት ፤ አጠፋፍ ፤ ፈተና ፡ ጥፋት ፡ ጕዳት ። ሰበረ ፡ ከመ ፡ በግዐ ፡ ዘአልቦ ፡ ምንሳዌ ፤ መራ ዕየ ፡ ይብር ፡ ዘይቀትል ፡ አርዌ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳር) ።

**መንሱት** ፤ (ብ ፡ መናስው ። ዕብ ፡ ኒሳ ዮን) ፤ ታላቅ ፡ ፈተና ፤ ፍጹም ፡ መከራ ፤ ያልታሰበ ፡ አደጋ ። ኢታብአነ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ። ጸልዩ ፡ ከመ ፡ ኢትባኡ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ። መንሱት ፡ በባሕር ፡ ወ በየብስ ። ወተዐገሡ ፡ መናስወ ፡ ሰይጣናዊተ ። መና ስወ ፡ ዓለም ፡ (ማቴ፮ ፡ ፲፫ ። ሉቃ ፡ ፳፪ ። ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፫ ። አርጋ) ። ዕቅፍት ፡ መሥገርት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መን ሱት ፡ ይባላል ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፯) ።

**ተመናሰወ** ፤ ተፋተነ ፡ ተፈታተነ ፤ ተሟከረ ፡ ተጣፋ ።

**ነስሐ** ፤ (ይኔስሕ ፡ ይነስሕ ፤ ነስሖ ። ዕብ ፡ ናሳሕ ፤ ነቀለ) ፤ ንስሓ ፡ ገባ ፤ ዐዘነ ፤ ተጠጠተ ፤ ተመ ለሰ ፤ ክፉ ፡ ዐመሉን ፡ ተወ ፤ ጠባዩን ፡ ለወጠ ። እስከ ፡ ይኔስሕ ፡ ንስሓ ፡ ፍጽምተ ። ነስሑ ፡ እምፍኖቶሙ ፡ እኩይ ፤ ወእግዚአብሔርኒ ፡ ነስሐ ፡ እምዘነበበ ። ነስሕ ፡ አበሳከ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፪ ። ዮናፎ ፡ ፲ ። ሢራ ፲፯ ፡ ፳፭) ። በነስሐ ፡ ፈንታ ፡ ተነስሐ ፡ ተናስሐ ፡ ይባል ፤ የጠፋ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ተነሳሕያን ። ገብኡ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወአውሰቡ ፤ ወእምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ ተና ስሑ ፡ ወነስሑ ፡ (ፊልክ) ። ተነስሑ ፡ እስመ ፡ ቀርበት ። ተነሢሖ ፡ (ማቴ፫ ፡ ፲፯ ። ኪዳ) ።

**ነሳሒ** ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ ንስሓ ፡ ገቢ ፤ ተጸጻች ፡ ተመላሽ ፤ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በቄስ ፡ የሚወቅሥ ፡ የሚከስ ፡ በደሉን ፡ የሚያፈስ ። ይ ቀም ፡ ምስለ ፡ ነሳሕያን ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፪ ። ዲድ ። አፈ ፡ ተ፴፩) ።

**ንሱሕ** ፡ (ሓን ፡ ሓት ፡ ስሒት) ፡ ንስሓ ፡ የገባ ፤ ያዘነ ፡ የተጠጠተ ፤ ከክፋቱ ፡ የተመለሰ ። ውእቱ ፡ ንሱሕ ፡ በእንተ ፡ ኀጣይኢሁ ። መብልዑ ፡ ለንሱሕ ፡ አልቦ ፡ ዘሕንበለ ፡ ኀብስት ፡ ወጼው ፡ (ፊልክ ፡ ፻፳፩ ። ቀሌ) ። ቍጡ ፡ ብስጩ ፤ የጠዓውን ፡ ሥራ ፡ መልሶ ፡ የሚወድ ፡ (፪ኢያ ፡ ፪ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪) ። ወይም ፡ ታስፋ ፡ ቈርጦ ፡ ፊቱን ፡ የሚገድል ፡ የሚጕዳ ፤ እንደ ፡ ይሁዳ ። ኢትኩን ፡ ንሱሐ ፡ ባዕለ ፡ ዘኀሰፈ ፡ ግብር ፡ (ቀሌ) ።

**ንሳሔ** ፤ (ሕያት) ፤ መነስሕ ፡ ንስሓ ፡ መግባት ፤ ጥጠታ ፡ ምለሳ ፤ ንስሐ ፡ አገባብ ፡ አመላለስ ፤ ንሱሕነት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ንስሓ** ፤ (ሓት) ፤ በቁሙ ፡ ሐዘን ፡ ጸጸት ፡ ቍጭት ፡ ምላሽ ፤ መቀጮ ፡ ቅጣት ፡ ቀኖና ፡ የኀጢአት ፡ ክሳ ። እምድኅረ ፡ ሞት ፡ አልቦ ፡ ንስሓ ። መፍትው ፡ ይትወከፉ ፡ ንስሓሆሙ ፡ ለእለ ፡ ተመይጡ ። ንስሓ ፡ ፍጽምት ። ሀብዎ ፡ ንስሓ ፡ ቅስፀተ ፡ ሱባዔ ፡ በኀብስት ፡ ወማይ ፡ እስከ ፡ ተስፀቱ ፡ ሰዓት ፡ (ፍ.ድ ፡ ፱ና ፡ ፲ ። ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ። ቀሌ) ። በመሥገርት ፡ ፈንታ ፡ ንስሓ ፡ ይላል ፡ (ምሳ፳ ፡ ፳፭) ።

**አነስሐ** ፤ አሳዘነ ፡ አስቈጨ ፤ አስጠጠተ ። ኢያነስሐኒ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፰) ።

**ነሲኅ** ፤ ኆት ፤ (ነስኀ ፡ ይነስኅ ፡ ይንሳኅ) ፤ መከርፋት ፡ መቀርናት ፡ መግማት ፡ መበሽቀጥ ፤ ከደዌ ፡ ከርበሐት ፡ የተነሣ ። ንጽሐን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ አፍራሽ ፡ ነው ።

**ንስኀት** ፤ ክርፋት ፡ ቅርናት ፤ ግማት ፡ ክፉ ፡ ሽታ ፡ የሚጐፈንን ፡ የሚያሰቀቅ ። እሬኢ ፡ ንስኀተ ፡ ሥጋየ ፡ ከመ ፡ ብኀባኤ ፡ አንበሳ ። ወየዐርግ ፡ ንስኀቱ ፡ (ኢዮ፮ ፡ ፳ ። ዮኤ፪ ፡ ፳) ።

**ነስየ** ፤ (ዐረ ፡ ነሲየ) ፤ ረሳ ፡ ዘነጋ ፤ ከልቡ ፡ አጠፋ ። ናሕሰየ ፡ ክንሐሰና ፡ ክንሰየ ፡ ከኹለቱ ፡ ሥር ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ ኀሒስን ፡ እይ ።

**ናሴብ** ፤ (ዕብ ፡ ንጺብ) ፤ ወታደር ፡ ጭፍራ ፡ ክበኛ ፤ ከተማ ፡ ጠባቂ ፡ ሹም ። ምስጢሩ ፡ መቆም ፡ ነው ፤ በምድና ፡ ሐውልትም ፡ ያሳያል ። ፀየ ፡ ሀሎ ፡ ናሴብ ፡ ኢሎፍላዊ ፡ (፩ነገ ፡ ፲ ፡ ፭) ።

**ነሲክ** ፤ ኮት ፤ (ነሰከ ፡ ይነስክ ፡ ይንስክ ። ዕብ ፡ ናሻኽ ። ሱር ፡ ንካስ) ፤ መንከስ ፤ በጥርስ ፡ መያዝ ፡ መውጋት ፡ ማሳመም ፤ መንጨት ፡ መበጨቅ ፡ መዘብተር ፤ መጋጥ ፡ መግመጥ ፡ ማልገጥገጥ ። አሐቲ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ነበከታ ፡ ውስተ ፡ ልባ ፡ ወአሐቲ ፡ ውስተ ፡ ገቦሃ ። ከመ ፡ ኢይንስክ ፡ ለኩና ፡ እገርየ ። ይንስክዎ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፲፩ ። ኅዳ፳ ። ዮሴፍ) ።

**ነሳኪ** ፤ መንስኪ ፤ የሚነክስ ፡ ነካሽ ።

**መንሰክ** ፤ (-ብ ፡ መናስክ) ፤ መንከሻ ፤ መንጋጋ ፡ ከፉንጭ ፡ ጥርስ ።

**ተነስከ** ፤ ተነከሰ ። ዘእምአርዌ ፡ ምድር ፡ ተነስከ ፡ (ስንክ ፡ መስ፳ ። ዘኍ፳፩ ፡ ፰) ።

**ንሱክ** ፤ (ካን ፡ ካት ፡ ስክት) ፤ የተነከሰ ፤ በጥርስ ፡ የተወጋ ፡ የቈሰለ ።

**ንስከት** ፤ መንከስ ፤ መነከስ ፡ አነካከስ ፡ ንክሻ ። ኅልቁ ፡ በንስከተ ፡ አራዊተ ፡ ምድር ። ንስከተ ፡ አንበጣ ፡ ወጽንጽንያ ። መክነ ፡ ንስከት ፡ (ጥበ፲፮ ፡ ፭ ፡ ፱ ። መ ፡ ፈ) ።

**ተናሰከ** ፤ ተናከሰ ፡ ተነካከሰ ፡ ተባላ ። አንትሙ ፡ ይትናሰኩ ፡ በበይናቲሆሙ ። ትትበልዑ ፡ ወትትናሰኩ ፡ (ሔኖ፸፪ ፡ ፲፩ ። ገላ፭ ፡ ፲፭) ።

**አስተናሰከ** ፤ አናከሰ ፤ አባላ ፡ አጣላ ። ከመ ፡ ያስተናስክሙ ፡ ለደቂቃ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ኔሳን** ፡—የወር ፡ ስም ፡ ሚያዝያ ፡—ነየሰ ።

**ነስነሰ** ፤ (ተቀ ፡ ግ ። ነሲስ ፡ ነሰ) ፤ ነሰነሰ ፤ ረጨ ፡ በተነ ፡ ፈነጠቀ ፤ አዘነመ ፡ አረበረበ ፤ አጠጣ ፡ አረካ ። ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ነሲስ ፡ ነው ፤ ለዥፈትና ፡ ለጭፈም ፡ ይኾናል ። ነስነስኩ ፡ ምስካብየ ፡ መጽርየ ። ይነሰንሱ ፡ ጽድቀ ፡ ደመናት ። ነስነሱ ፡ ባዕሌሁ ፡ ብዙኃተ ፡ ዕፍረታተ ። ነስነሰ ፡ ማየ ። በእንተ ፡ ማያተ ፡ አፍላግ ፡ ከመ ፡ ያዐርግ ፡ ማያተ ፡ ወይነስንሶን ፡ ውስተ ፡ ዙሉ ፡ ገጸ ፡ ምድር ፡ ለጽሙኣን ። ዘነስነስከ ፡ ምሕረተከ ፡ በመዋዕለ ፡ ሙሴ ፡ ከማሁ ፡ ነስንስ ፡ ምሕረተከ ፡ ባዕሌነ ፡ (ምሳ፯ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፵፭ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ ነሐ፳፱ ። ሄርማ ። ቄድር) ። ሮሐን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ነስናሲ** ፤ መነስንስ ፤ የሚነሰንስ ፡ ነሳናሽ ፤ ጭራ ፡ ያዥ ፡ ባለጭራ ።

**መነሳንስት** ፤ (ሳት) ፤ በቁሙ ፡ መነሳንስ ፤ መራውሕ ፡ የሐር ፡ ፈትል ፡ እንደ ፡ ጭራ ፡ ኹኖ ፡ የተሠራ ፤ የተቈነነ ፡ ባለወርቅ ፡ እጀታ ። በዘቲ ፡ ዕለት ፡ አዐረፈ ፡ አባ ፡ ኖብ ፡ በዓለ ፡ መነሳንስት ፡ ዘወርቅ ፤ ለሰላም ፡ ለኖብ ፡ መነሳንስቲሁ ፡ ዘወርቅ ፤ ለዳዴ ፡ አራዊት ፡ ደቃቅ ። ይትቀነዩ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ነጋሢ ፤ ወመነሳንስቲሁ ፡ ዘሐፊር ፡ ገብሩ ፡ ሎቱ ፡ (ስንክ ፡ የካ፳ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።



መነሳንስት ፡

**ተነስነሰ** ፤ ተነሰነሰ ፤ ተረጨ ፡ ተረበረበ ፤ ሽቱው ፡ በልብስ ፡ ልብሱ ፡ በሽቱ ።

**ንስኑስ** ፤ የተነሰነሰ ፤ የተረጨ ፡ ቤት ። መፀዛ ፡ ጽጌ ፡ ውስቴታ ፡ ንስኑስ ፡ (ድጓ) ።

**ነሲቅ** ፤ ቆት ፤ (ነሰቀ ፡ ይነስቅ ፡ ይንስቅ ። ዐረ ፡ ነሰቀ ። ዕብ ፡ ናሻቅ ፤ ሳመ) ፤ መስደር ፡ መደርደር ፤ ማበተባለፍ ፡ መግጠም ፡ ማሳሳም ፤ መጥረብ ፡

መውቀር ፡ ማነጥ ፡ መቅረጥ ፡ የደንጊያ ፡ የንጨት ። ንስክ ንና ፡ ወስቀን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎር ፡ ናቸው ።


**ተነስቀ** ፤ ተሰደረ ፡ ተደረደረ ፡ ተሳሰረ ፡ ተጋ ጠመ ።

**ንሱቅ** ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ስቅት) ፤ የተጠረበ ፡ የተወቀረ ፤ የታነጠ ፡ የተቀረጠ ፤ ስድር ፡ ድርድር ። ዘቀሙ ፡ ስሳ ፡ በእመት ፡ ወንድቀ ፡ በእብን ፡ ንሱቅ ፡ (፩ነገ ፯፥፱) ። በንሱቅ ፡ ፈንታ ፡ ምሱቅ ፡ ውሱቅ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**ንስቀት** ፤ መግጠም ፡ ማጋጠም ፡ የክንፈር ፡ የጠርዝ ።

**ነስረ** ፤ (ዕብ ፡ ናሻር) ፤ ነሰረ ፤ ወረደ ፤ ወደቀ ፡ ተወረወረ ፤ በፈቃዱ ።

**ንስር** ፤ (ብ ፡ አንስርት ። ዕብ ፡ ኔሼር ። ሱር ፡ ኒሽራ ። ዐረ ፡ ኒስር) ፤ በቁሙ ፡ ታላቅ ፡ ነጣቂ ፡ አሞራ ፡ ርቶ ፡ መጥቶ ፡ የሚኼድ ፡ ዐይነ ፡ ጥሩ ። የሐንስ ፡ ሰራሪ ፡ ንጉሥ ፡ አዕዋፍ ፡ ንስር ። አ ፡ ንስር ፡ ዘእሙር ፡ በብርሃነ ፡ አዕይንቲክ ። ዝኩአ ፡ ንስር ፡ ዐቢይ ። ንስር ፡ ኤኪፉር ፡ (ስንክ ፡ የካ፴ ። ተረ ፡ ባር ። ሕዝ፲፯ ፡ ፫ ። ማር ፡ ይሥ ። ማቴ፳፬ ፡ ፳፰) ።



ንስር ፡

**ነስር** ፤ በቁሙ ፤ ነዝር ፡ ያፍንጫ ፡ ደም ፤ ነዝረን ፡ እይ ። የበስለ ፡ ፍሬና ፡ ቅጠል ፤ ሳይነኩት ፡ የሚወርድ ፡ የሚወድቅ ።

**አንሰረ** ፤ አነሰረ ፤ አስነሰረ ፤ ንስር ፡ አደረገ ፤ ንስር ፡ አሰኘ ።

**ተአንሰረ** ፤ ንስር ፡ ኾነ ፤ ንስር ፡ ተባለ ። ቱአንስሮትየ ፡ (አዋል) ።

**ኔስራ** ፤ (ጽር ፡ ኔሳራን ። ዕብ ፡ ኔዕጻር ። ዐረ ፡ መሕጹረን) ፤ ደጀ ፡ ጠኒ ፤ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ብቻውን ፤ የቀረ ፤ ለጸሎት ፡ ለመሟዕት ። ወሀሎ ፡ ህየ ፡ ኔስራ ፡ ቅድመ ፡ እግዚ ። ሕጹረ ፡ ዕጉተ ፡ ክሉእ ፡ ጽኑሐ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (፩ነገ ፳፩ ፡ ፯) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ በቃ ፡ ስጉን ፡ ይሉታል ።

**ንስራኒ** ፤ (ዐረ ፡ ንጽራኒ ። ዕብ ፡ ኖጽሪ) ፤ ክርስቲያናዊ ፡ በናዝ(ጽ)ራዊው ፡ መሲሕ ፡ በየሱስ ፡ ያመነ ፤ ናዝሬትን ፡ እይ ። ንስራኒ ፡ ኩነ ፡ ስምዐ ፡ (አዋል) ። በንስር ፡ ዘይቤ ፡ ሲፈቱት ፡ ግን ፡ ንስራዊ ፡ ዘንስር ፡ ያሰኛል ።

**ነሲስ** ፤ ሶት ፤ (ነሰ ፤ ነሰሰ ፡ ይነስስ ፡ ይንስስ ። ዕብ ፡ ኖሴስ ፤ ሂትኖሴስ) ፤ ማጌጥ ፡ መጌጥ ፤ መነሰንስ ፤ ነስ ፡ ነስ ፡ ማለት ፤ መወዘወዝ ፤ መንቀሳቀስ ። ሰስወንና ፡ አንሰሰወን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ማመልከት ፡ ታምራት ፡ ምልክት ፡ ማድረግ ። ኒሳንን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ነሰሳው** ፤—ምልልስ ፤—ሰሰወ ።

**ናስታ** ፤—መጋቢያ ፤—ነሥተ ፡ ናሥታ ።

**ኔስታሊ** ፤—የንፋስ ፡ አበብ ፤—ኔስ ፡ ነየሰ ።

(ጥት) **ነት** ፤ (ቀብጥ ፡ ናት) ፤ ቀይ ፡ ቀለም ፤ የቀይ ፡ ቀለም ፡ ዘር ፡ ናሬው ፡ ቅጠሉ ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ የሚኾን ። በቁሙ ፡ ነትዕ ፡ ቀይ ፡ ቁርበት ፡ ዐረብ ፡ አንቀልባ ፤ በነት ፡ ቀለም ፡ የተነከረ ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ የገባ ፡ ልብስ ፡ ፈትል ። ኢኢን ፡ እይ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፬ ። ፳፮ ፡ ፩ ፡ ፴፩ ። ፳፰ ፡ ፭ ፡ ፰ ፡ ፲፭) ።

**ነተገ** ፤ ጎት ፤ (ነትገ ፡ ይነትግ ፡ ይንትግ ። ወተገ ፤ ነሠገ) ፤ መንተግ ፡ ተግ ፡ ማለት ፡ መቆም ፡ መገታት ፡ መቋረጥ ፡ መቅረት ፡ ማነስ ፡ መጕደል ፡ መቅለል ፡ ጥቂት ፡ መኾን ። ወተገንና ፡ ነሠገን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ። ርቱዐ ፡ ይንትጉ ፡ እሉ ፡ የሀውኩክሙ ። ነትገ ፡ ማይ ። ኢነትገ ፡ አንብዕየ ። ለዘነትገ ፡ ትክቶሃ ። መዋዕል ፡ እንዘ ፡ ይንትጉ ፡ እምዐሥርቱ ፡ ወተሰዐቱ ፡ ኢየቤልዩ ። እምውስቴቶሙ ፡ ኢይትከሀል ፡ ነቲግ ፡ (ገላ፭ ፡ ፲፪ ። ዘፍ፰ ፡ ፰ ። ግብ፳ ፡ ፴፩ ። መ ፡ ፈ ። ኩፋ ፡ ፳፫ ። መክ፫ ፡ ፲፬) ። በነትገ ፡ ፈንታ ፡ ተነትገ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፰ ፡ ፭ ፡ ፰ ፡ ፲ ፡ ፲፭) ።

**ንቱግ** ፤ (ጋን ፡ ጋት ፡ ትግት) ፤ ያነሰ ፡ የጐደለ ፤ ጕደሎ ፡ ሕጹጽ ። ኢንቱግ ፡ ወኢብዑድ ፡ እምሀላዌሁ ። ደሰወከ ፡ እግዚ ፡ ወረከበከ ፡ ሕጹጸ ፡ ወንቱገ ። ኩሉ ፡ ምሉኣነ ፡ ወአኮ ፡ ንቱጋነ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ዮሴፍ ። ግንዘ) ።

**ንትገት** ፤ ማነስ ፡ መጕደል ፡ አጕዳደል ፡ ጕድለት ፡ ጕደሎነት ፤ ሕጸጽ ፡ ጕዳይ ፡ (ሲኖዶ) ።

**ኑታጌ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ኢይትሴዐሉ ፡ በፍድፋዴ ፡ ወኢየሐጽጹ ፡ በኑታጌ ። ኢሀሎ ፡ ኑታጌ ፡ ስብሐት ፡ ሳዕለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ይሜህር ፡ ኑታጌ ፡ እምጠባይዕ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ያዕ ፡ ዘእል) ።

—፤ መቅረት ፤ መታጐል ። ሰላም ፡ ለቈመቱ ፡ ዘአልቦ ፡ ኑታጌ ፡ እስከ ፡ ተመሰለ ፡ እግሩ ፡ ከመ ፡ እግረ ፡ ነጊ ፡ (በንክ ፡ የካ፳፰) ።

**ንትግ** ፤ ንትጋ ፤ (ብ ፡ ንትጋት) ፤ ሕጸጽ ፡ ጕዳይ ፡ ቅሬታ ። ከመ ፡ ይምላእ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ውስተ ፡ ንትገ ፡ ዚኣከ ። ወልድ ፡ መላኢ ፡ ንትጋ ። አፍቅርኒ ፡ እንበለ ፡ ንትጋ ። ንትጋት ፡ (መቃ ፡ ገጽ፫ ። ጥበ ጠቢ ። ደራሲ ። ፊልክ ። ፪ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፲፬) ።

**አንተገ** ፤ አሳነሰ ፡ አጐደለ ፤ አስቀረ ፡ አስታጐለ ፤ ቈረጠ ፡ አቋረጠ ፤ አቆመ ። ያነትጉ ፡ ወይዌስኩ ። ኢታ

ንትግ ፡ እምኔሁ ፡ ቃለ ። አንተጉ ፡ ሐፊጸ ፡ ሀገር ። ኢያንተጉ ፡ እንዘ ፡ ይሴብሑ ፡ (ኪዳ ። ኤርምያ ፡ ፪ ። ክፉ ፡ ፲ ። ኪዳ) ።

ትንታግ ፤ (ጋት) ፤ በቁሙ ፡ ክፋይ ፡ ትኳሽ ፡ ትርኳሽ ፡ ባንድ ፡ ወገኑ ፡ እሳት ፡ የበላው ፡ ያጐደለው ፡ የእሳት ፡ ትራፊ ፡ ዕንጨት ። ከመ ፡ ትንታግ ፡ ዘአውፅእዎ ፡ እምእሳት ። ትንታግ ፡ እሳት ። በብዝኀ ፡ ትንታጉ ፡ ለእሳት ፡ ይበዝኅ ፡ ፍሕሙ ። ትንታጋት ፡ ዐፀው ፡ እለ ፡ ይጠይሱ ፡ (ዘካ ፡ ፫ ። ዓሞ ፡ ፬ ። ሚራ ፲፩ ፡ ፴፪ ። ኢሳ ፯ ፡ ፬) ።

ተንተገ ፤ ተተገ ፡ ተኰሰ ፡ ለኰሰ ፡ ቈለቈለ ፡ ተረኰሰ ፤ በክፋዩ ፡ መታ ። ተቈጣ ፡ ቱግ ፡ ትንትግ ፡ አለ ፤ ተቃጠለ ፡ እሳቱ ፡ ወይም ፡ ሰዉ ።

ኖትያ ፤—መርከበኛ ፤—ነወተ ።

ነቲን ፤ (ነተነ ፡ ይነትን ፡ ይንትን ። ዕብ ፡ ናታን) ፤ መስጠት ፡ ማበርከት ፡ ማሲያዝ ፡ ማስጨበጥ ፡ ማስረከብ ፡ ጥጋን ፡ ዕዳን ፡ ጨርሶ ፡ መክፈል ። መተንን ፡ እይ ።

ተነትነ ፤ ተሰጠ ፡ ተናኘ ፡ ተሰፋ ፡ ኾነ ።

ተንተነ ፤—ተፍገመገመ ፤—ተኒን ፡ ተነ ።

ናታኒም ፤ (ጽር ፡ ናቲንም ። ዕብ ፡ ንቲኒም) ፤ ንቱናን ፡ ውሁባን ፡ ላቤተ ፡ መቅደስ ፡ የተሰጡ ፡ የግዜር ፡ አገልጋዮች ፤ እስራኤል ፡ ያይ ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡ የገባዖን ፡ ሰዎች ፡ (ኢያ ፱ ፡ ፳፫ ፡ ፳፯ ፡ ፳፯) ። በናታኒም ፡ ፈንታ ፡ ንቱናን ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹሉ ፡ ናቲኒም ፡ ናታናውያን ፡ ናቲናውያን ፡ ናትናውያን ፡ ይባል ፤ ኹሉም ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዕዝ ፪ ፡ ፵ ። ፯ ፡ ፯ ። ፰ ፡ ፲፯ ፡ ፳) ። ናታናውያን ፡ ማለት ፡ ግን ፡ የናታን ፡ ወገኖች ፡ ያሰኛል ፡ (፪ነገ ፡ ፯ ፡ ፪) ።

አስተንተነ ፤ አስተንተነ ፤ ይህ ፡ ለዚህ ፡ አለ ፤ ዐሰበ ፡ ተጋ ፡ ተወዘወዘ ፡ በሐሳቡ ፡ ተያዘ ፤ ለመስጠት ፡ ለመርዳት ፡ ለማገልገል ። ባርክ ፡ ዲበ ፡ እለ ፡ ያስተነትኑ ፡ በዐጣን ፡ ወቍርባን ። ለተልእኮ ፡ ምሥዋዕ ፡ ዘጽሕቀ ፡ ወዘአስተንተነ ። እንዘ ፡ ያስተነትኑ ፡ ኲነቶሙ ፡ ዘንቢፈ ፡ ወለዘኒ ፡ ይመጽእ ፡ (ቅዳ ። ስንክ ፡ ሠኔ ፲፰ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

—፤ አሳሰበ ፡ አተጋ ፡ አገበረ ፤ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ። እለ ፡ ይገብሩ ፡ ትርፍተ ፡ በሥጋቲሆሙ ፡ ባሕቲቶ ፡ ወኢያስተንተኑ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ተጋድሎት ፡ ኅሊናት ፡ ኢይበጽሑ ፡ ኀበ ፡ ንጽሐ ፡ ልብ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፹፯) ።

ነቲዕ ፤ ዖት ፤ (ነትዐ ፡ ይነትዕ ፡ ይንታዕ ። ዕብ ፡ ናቶዕ ፡ ሂናቴዕ ፤ ከሥሩ ፡ ፈለሰ ፡ ተነቀለ) ፤ መሸሽ ፡ መሮጥ ፡ መኰብለል ፤ ለማምለጥ ። ከመ ፡ ዘይነትዕ ፡ በውስተ ፡ ቀትል ። ነትዑ ፡ እምቅድመ ፡ ገጽነ ። ወይነትዕ ፡ ሰብእ ፡ ይእቲ ፡ ብሔሮ ፡ (ሚራ ፡ ፯ ። ኢያ ፰ ፡ ፲፭ ። ኢሳ ፲፫ ፡ ፲፬) ። መተከል ፡ መዘርጋት ፤ የድንኳን ፡ የጥላ ። መቅላት ፡ ነት ፡ መኾን ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ መግባት ፤ የቈርበት ።

አንትዐ ፤ አሸሸ ፡ አሸነፈ ፤ ነዳ ፡ አባረረ ። አሐዱ ፡ ያነትዖሙ ፡ ለዐሠርቱ ፡ ምእት ። አንትዐ ፡ አፅራረ ። አንትዕዎሙ ፡ ወተለውዎሙ ፡ (ዘዳ፴፪ ፡ ፴ ። አፈ ፡ ተ፳፯ ። ዮሴፍ) ። ተከለ ፡ ዘረጋ ፤ ወጠረ ፡ ገተረ ። አቀላ ፡ ዘኾነን ፡ አነተ ፡ ነት ፡ አገባ ።

ነትዕ ፤ (ብ ፡ አንትዕት) ፤ ሽሽት ፡ ሩጫ ፡ ኰብለላ ። በቁሙ ፡ ነት ፡ ቀይ ፡ ቈርበት ፤ የድንኳን ፡ ልብስ ። አንትዕት ፡ ዘማእሰ ፡ በግዕ ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፲፬) ።

ነተፈ ፤ (ነቲፍ ። ነቀፈ ፤ ነጸየ ፤ በጸለ) ፤ አንተበ ፡ ነጨ ፡ በጨቀ ፤ ቈረጠ ፡ በጠሰ ፤ ቀማ ፡ መንተፈ ። እለ ፡ ይነትፉ ፡ በመጥባሕተ ፡ ልሳኖሙ ፡ ሥጋ ፡ ቢጾሙ ። ዘማእሰረ ፡ ኀጢአት ፡ ይነትፍ ፡ ተአሰረ ፡ በአጽርቅት ። ወለአዕዋፍሰ ፡ ኢነተፎን ፡ (ሥር ፡ ጳኰ ። መጽ ፡ ምስ ። ክፉ ፡ ፲፬) ።

ተነትፈ ፤ ነተበ ፡ ተነጨ ፡ ተበጨቀ ፡ ተበጣጨቀ ። አብድ ፡ ኢይማዩጥ ፡ አማእነ ፡ እስከ ፡ ይትነተፍ ፡ እገሪሁ ። ወተነትፈ ፡ ሥጋሆሙ ፡ (ፈላስ ፡ ገ፵ ። ስንክ ፡ ሐም፳) ።

ንቱፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ትፍት) ፤ የነተበ ፡ ንትብ ፤ የተነጨ ፡ የተበጨቀ ፤ ቍርጥርጥ ፡ ብጥስጥስ ።

ንትፈት ፤ መንጨት ፡ መንጨት ፤ አንጫጭ ፡ አቈራረጥ ፡ ቈረጣ ፡ ብጠሳ ፡ ንጥቂያ ፡ ቅሚያ ፤ ንጭታት ። ንትፈተ ፡ ሥጋሁ ፡ በኀጺን ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳) ።

ንታፌ ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ። ወንታፌ ፡ ሎቱ ። ብዕል ፡ ይትሀጐል ፡ በንታፌ ፡ እኩይ ፡ (መክ፪ ፡ ፳፫ ። ፳፩ ፡ ፲፫) ።

ነትረ ፤ (ነቲር ። ዕብ ፡ ናታር ፤ ዘለለ ፡ ታወከ) ፤ ነተረ ፡ ኀረጠ ፡ በሰለ ፤ የጠላ ፡ የወጥ ። ንጥረን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

ንቱር ፤ (ላቲን ፡ ናቱር ፡ ራ ፤ ባሕርይ ፡ ጠባይ ፥ ፍጥረት) ፤ የነተረ ፡ የኀረጠ ፤ ጥሩ ፡ ብርቱ ።

ናቱሪም ፤ (ዕብ ፡ ታኑሪም) ፤ እቶኖች ፤ ቤተ ፡ ልሔሞች ፡ የማድ ፡ ቤቶች ። ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ እንባሻ ፡ ይሉታል ። ማኅፈደ ፡ ናቱሪም ፡ (ነሐ፫ ፡ ፲፩) ።

# ሠ

**ሠ** ፤ ፳፭ኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፤ ስሙ ፡ ሠውት ፡ ቍጥሩ ፡ ስሳ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ (ሠ—፷) ስሳ ፤ ወይም ፡ ሥልሳ ፡ ይባላል ፤ ሠሰሰንና ፡ ሰደሰን ፡ እይ ። ጸሐፍት ፡ ግን ፡ ንጉሠ ፡ የሚጣፍ ፡ በርሱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ስሙን ፡ ንጉሥ ፡ ይሉታል ። በዐረብና ፡ በዕብራይስጥ ፡ አንዱ ፡ ኅርመት ፡ ፊደል ፡ ሠ ፡ በነቍጣ ፡ ምክንያት ፡ ሲን ፡ ሺን ፡ እንዲባል ፡ በጥንታዊም ፡ ግእዝ ፡ ሰና ፡ ሸ ፡ የሚባል ፡ ይህ ፡ ሠውቱ ፡ ሠ ፡ እንጂ ፡ ሳቱ ፡ ሰ ፡ አይደለም ። ሳቱ ፡ ሰ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሳምኬት ፡ ሰ ፡ በስምና ፡ በመልክ ፡ ተለይቶ ፡ ተራውና ፡ ቍጥሩ ፡ ሳይፋለስ ፡ ስባንቱን ፡ ሳይለቅ ፡ ሰ ፡ ብቻ ፡ ኹኖ ፡ ሰ ፡ ከመባል ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ሠውት ፡ ሠ ፡ ሸ ፡ መባል ፡ የለውም ፤ አልነበረውም ። ፪ ፡ ዐይነት ፡ ሠ ፡ ሰ ፡ በግእዝ ፡ በሱርስት ፡ በዕብራይስጥ ፡ እንጂ ፡ በዐረብ ፡ የለም ፤ ጻዴ ፡ ግን ፡ ሳድ ፡ እየተባለ ፡ እንደ ፡ ሰ ፡ ይጠራል ፤ ለሠና ፡ ለጸ ፡ ከመልክ ፡ በቀር ፡ የድምጥ ፡ ልዩነት ፡ የላቸውም ። ሸ ፡ ደግሞ ፡ በቅብጥ ፡ እንጂ ፡ በጽርእ ፡ አይገኝም ፤ ከግእዝም ፡ ጽርኣዊው ፡ ሰባ ፡ መጻሕፍትን ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ሲመልስ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አውጥቶት ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በግእዝ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ መጣፉና ፡ መነገሩ ፡ ቀርቷል ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ዕብራይስጥና ፡ ዐረብ ፡ ሱርስትም ፡ ሸ ፡ የሚሉትን ፤ ይልቁንም ፡ ዐረብ ፡ በሺን ፡ የሚጥፈውን ፤ ዲልማን ፡ ለይቶ ፡ በሠውት ፡ ጥፎታል ። (ዐረብ) ፡ ሻበ ፡ ሸሐጸ ፡ ሸረበ ፡ ሸረዐ ፡ ሸረጸ ፡ ሸረቀ ፡ ነገሸ ። ሜበ ፡ ሥሕጸ ፡ ሠረበ ፡ ሠርዐ ፡ ሠረጸ ፡ ሠረቀ ፡ ነግሠ ። የሳቱ ፡ ሰን ፡ ፍች ፡ እይ ።

**ሥኢብ** ፤ **በት** ፤ **(ሥእበ ፤ ሠአበ ፡ ይሥእብ ፡ ይሥአብ ። ሱር ፡ ወዕብ ፡ ሣኤብ)** ፤ ማደፍ ፡ መርከስ ፤ የሩካቤ ፡ የሕልመ ፡ ሌሊት ፡ የገቢስ ፡ በድን ። ወሰእመ ፡ ሐለመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አንበተ ፡ ኢይቅረብ ፡ ወኢይትከሃነኒ ፤ ወእኮ ፡ ዘሥእበ ፡ አላ ፡ በእንተ ፡ ክብረ ፡ ምሥዋዕ ፡ (ኪዳ ፡ ገ፲) ።

**ተሣአበ** ፤ ተዳደፈ ፤ ተራከሰ ፡ ተረካከሰ ።

**ሥኡብ** ፤ **(ባን ፡ ባት ፡ እብት)** ፤ ያደፈ ፡ የተዳደፈ ፤ እድፋም ፡ ርኩስ ፡ (ዘሌ፲፭ ፡ ፲፮ ። ፲፰ ፡ ፴፪ ። ሐጌ፪ ፡ ፲፫ ። ኩፉ ፡ ፴፪) ። ቤትኩ ፡ ሥኡብየ ። እመ ፡ ቦ ፡ ሥኡብ ፡ ወዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ። ርኩስ ፡ ወሥኡብ ፡ ውእቱ ። ሥኡባነ ፡ ነፍስ ፡ (ጠቢ፪ ፡ ፱ ። ቅዳ ። ቀሌ ። አርጋ ፡ ፬) ።

**ሥእበት** ፤ **(ታት)** ፤ ማደፍ ፡ መርከስ ፤ ርኵሰት ፡ ርስሐት ፤ እድፍ ። ዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ፡ እምነ ፡ ሥእበቱ ፡ ዘሌሊት ። አልቦቱ ፡ ሥእበት ። ዘበሥእበት ፡ (ዘዳ፳፫ ፡ ፲፩ ። ዕብ፲፫ ፡ ፬ ። ቀሌ) ።

**ሥእን** ፤— ሳነ ፡ ተሳነ ፤— ስኢን ፡ ስ…

**ሥእነ** ፤ **ሠአነ** ፤ **(ሰንአ ። ዕብ ፡ ሳአን)** ፤ ተጫማ ፤ ለበሰ ፤ እግሩን ፡ ከመጫሚያ ፡ ሰካ ፡ አገባ ፡ አዋደደ ፡ አሰማማ ። ሰንአን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሥእነ ፡ ፈንታ ፡ ተሥእነ ፡ ተሠአነ ፡ ይባላል ፤ አያሰኝም ። ተሥእነት ፡ አሣእኒሃ ። ተሠአን ፡ አሣእኒከ ። ተሥኢነክሙ ፡ ትይሉ ፡ ወንጌል ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፬ ። ማብ፲፪ ፡ ፳ ። ኤፌ፮ ፡ ፲፭) ።

**አሥአነ** ፤ **አስተሥ(ሠ)አነ** ፤ አጫማ ፤ ጫማ ፡ አለበሰ ፤ አለባበሰ ። አልበስዎሙ ፡ ወአሥአንዎሙ ፡ እምበርበረ ፡ ዚአሆሙ ። አግበረ ፡ ሎቱ ፡ አሣእነ ፡ ዘካጺን ፡ ወአስተሥአንዎ ፡ ለቅዱስ ። ገብሩ ፡ ሎቱ ፡ ቅትራተ ፡ ዘብርት ፡ ወአስተሠአንዎ ፡ እስከ ፡ ቤረረ ፡ ቅትራት ፡ ውስተ ፡ እገሪሁ ፡ (፪ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፲፭ ። ድጓ ። ስንክ ፡ ነሐ፲፱) ።

**ተሥእነ** ፤ ተለበሰ ፤ ተሰካ ፡ ገባ ፡ ተዋደደ ፤ ጫማው ።

**ተሣአነ** ፤ ተሳካ ፤ ተሰማማ ፤ ተዋደደ ፤ ጫማውና ፡ እግሩ ።

**ሥኡን** ፤ **(ናን ፡ ናት ፡ እንት)** ፤ የተጫማ ፤ ጫማ ፡ የለበሰ ፡ ወይም ፡ የተለበሰ ። ሥኡናን ፡ እገሪሆሙ ፡ ወግልቡባን ፡ አርእስቲሆሙ ፡ (ታምረ ፡ ማር) ።

**ሣእን** ፤ **(ብ ፡ አሣእን ። ዕብ ፡ ስአን ። ሱር ፡ ሴናእ)** ፤ ጫማ ፤ መጫሚያ ፤ የውስጥ ፡ እግር ፡ ቈዳ ፤ ከፍት ፡ ወይም ፡ ክፍ ። ፈትሐ ፡ ሣእኖ ። ከመ ፡ ይሑርዎ ፡ በአሣእን ። ዘእንበለ ፡ አሣእን ። ፍታሕ ፡ አሣእኒከ ። ቶታነ ፡ አሣእን ፡ (ሩት፬ ፡ ፯ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፲፭ ። ፳ ፡ ፪ ። ዘፀ፫ ፡ ፭ ። ማር፩ ፡ ፯) ።



ሣእን ፡

**ሠብእ** ፤— ሰው ፤— ሰቢእ ፡ ሰብእ ።

**ሠበ** ፤ **ሠበበ** ፤ **(ሠቢብ ። ዕብ ፡ ሾቤብ ፤ ሻቤብ)** ፤ ወጋ ፡ በሳ ፤ አሳለፈ ። ሰበረ ፡ አጕበጠ ፤ ጠመዘዘ ። ሸባ ፡ ሸቦ ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ሠብሠበ** ፤ **(ሰበበ ፤ ወሰበ ። ዕብ ፡ ሸብ ሼብ)** ፤ ታጠረ ፡ ተከበበ ፤ ተቀዳጀ ፤ በዐጽቅ ፡ በሐረግ ፤ የሥራ ፡ የጌጥ ። ሸበሸበ ፡ አሸበሸበ ፤ ሽብሸቦ ፡ ሽብሸባ ፡ አደረገ ፤ የበፈት ፡ የማሕሌት ። ሰበበንና ፡ ወሰበን ፡ እይ ።

ሠብሣብ ፤ (ባት ። ጽር ፡ ሳርጋኒ ። ዐረ ፡ ዘንቢል ። ሰብ ፡ ሳል) ፤ ታላቅ ፡ ቅርጫት ፡ አፈ ፡ ሰፊ ፡ የጕታ ፡ ዐይነት ፡ ከዐጽቅ ፡ ከሐረግ ፡ የተሠራ ። ወአውረዱኒ ፡ በሠብሣብ ፡ እንተ ፡ መስኮት ፡ እምአረፍት ፡ (፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፴፫) ።

ሠብሣብ ፡—ጋብቻ ፡ ግቢ ፤—ወሰበ ፡ ሰብሳብ ።

(ጥ) ሠብሐ፡— አመስገነ ፡—ሰብሐ ፡ ሰብሐ ።

ሠቢሕ ፡ ሐት ፡ (ሠብሐ ፡ ይሠብሕ ፡ ይሥባሕ ። ትግ ፡ ሐባ ፡ ሸብሐ) ፤ መሥባት ፡ መወፈር ፡ መደንደን ፡ ሥጋ ፡ መኾን ። ይሠብሕ ፡ መራዕይከ ። ሠብሐ ፡ ወገዘፈ ፡ ወርሐበ ። ዘሠብሐ ፡ ትጠብሑ ፡ (ኢሳ፴ ፡ ፳፫ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፲፭ ። ሕዝ፴፬ ፡ ፫) ።

ሥቡሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ብሕት) ፤ የወፈረ ፤ የወፈረ ፡ ወፍራም ፡ ደንዳና ። ከመ ፡ ዘእምሥቡሕ ። ሥቡሓኒሆሙ ። ልሒር ፡ ወሥብሕት ፡ (መዝ ፡ ፷፪ ። ዘፍ፵፩ ፡ ፬ ። ኢሳ፴፯ ፡ ፳) ።

ሥብሐት ፤ መሥባት ፡ ሥባት ፡ ሥብነት ፡ አሠባብ ፡ አወፋፈር ፡ ወፍር ፡ ድንዳኔ ።

ሥብሕ ፤ (ሓት) ፤ ሥብ ፡ ሥጋ ፡ ሞራ ፡ ትርፍ ፡ ነጭ ፡ ሥጋ ፡ ላት ። ወፍር ፡ ድንዳኔ ። ለመሥዋዕት ፡ የሚቀርብ ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ሥብሕ ፡ ይባላል ። ዘእንበለ ፡ ይጤስ ፡ ሥብሕ ። ሥብሐ ፡ ክርሙ ፡ ወሥብሐ ፡ ኵሊቱ ። ሥብሐ ፡ ሥርናይ ፡ (ኛነገ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ። ዘዐቍ፲፰ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፹) ።

አሥብሐ ፤ አሠባ ፡ አወፈረ ፡ አገዘፈ ። አሥብሕ ፡ መሥዋዕተከ ። ቦሙ ፡ አሥብሐ ፡ መክፈልቶ ። ወአሥብሐ ፡ ኪያሃ ። አሠነዩ ፡ ሥጋ ፡ ወአሥብሖቶ ፡ (ሚል ፴፭ ፡ ፲፩ ። ዕንባ ፡ ፲፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፩ ። እፈ ፡ ተ፲፫) ።

አሥባሒ ፤ መሥብሒ ፡ ሕ ፤ የሚያሠባ ፡ አሥቢ ፡ ቀላቢ ።

ምሥባሕ ፤ (ሓት) ፤ መሥቢያ ፡ ማሥቢያ ፡ ማድለቢያ ።

መሥብሕት ፤ (ብ ፡ መሣብሕት) ፤ ሥብ ፡ ሥጋ ፡ የሥጋ ፡ ክፍል ፡ መክፈልት ፡ ዕድል ፡ መቍነን ፤ ለዳቦና ፡ ለፍሬም ፡ ይኾናል ። እስ ፡ ተበልዑ ፡ መሣብሕተ ፡ መሥዋዕቶሙ ፡ (ዘዳ፴፪ ፡ ፴፰) ።

ሠበጠ ፤ (ሠቢጥ ፡ ፀበጠ ፥ ተፀብጠ) ፤ ቀረበ ፡ ተዘጋጀ ፡ ዝግጁ ፡ ኾነ ፡ ለመብላትና ፡ ለመበላት ፤ የሰውና ፡ የምግብ ። ፈንታውን ፡ ያዘ ፡ ተረከበ ፡ እጅ ፡ አደረገ ፡ ለመቍረስ ፡ ለመጕረሥ ። ዐጸጠንና ፡ ኤአን ፡ እይ ።

አሥበጠ ፤ (ትግ ፡ ሐባ ፡ ዩብጠ ፤ ቀለተ) ፤ አቀረበ ፡ አስታረበ ፡ ጋበዘ ፡ አጕረሠ ፤ አሲያዘ ፡ አስበበተ ፤ ሥንቅ ፡ ሰጠ ፤ አስቋጠረ ። አልብየ ፡ ዘአሠብጦ ። ወያሠብጦሙ ፡ ለዕሙፃን ፡ (ሉቃ፲፩ ፡ ፮ ። ፊልክ ፡ ፫) ።

ሥበጥ ፤ ሥበጥ ፤ ሽባጥ ፡ ሽብልቅ ፤ ሠላጤ ፡ ወሽመጥ ፡ (ዐማርኛ) ። ጕርሻ ፡ ምግብ ፤ የበሰለ ፡ የተዘጋጀ ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፤ የምግብ ፡ መግቦ ። ሥበጠ ፡ መብልዕ ። ኤልያስ ፡ በልዐ ፡ ሥበጠ ፡ ኅብስት ፡ ዘወሀቦ ፡ መልአከ ፡ እግዚ ፤ ወሖረ ፡ በኀይሉ ፡ ውእቱ ፡ እክል ፡ አርብዓ ፡ መዓልተ ፡ ወአርብዓ ፡ ሌሊተ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

ሣባጥ ፤ (ዕብ ፡ ወሱር ፡ ወዐረ ፡ ሸባጥ) ፤ ስሙ ፡ ወርኅ ፤ የዕብራውያን ፡ ፲፩ኛ ፡ ወር ፡ የካቲት ፡ (ዘካ፩ ፡ ፯) ።

ሠበከ ፤—አስተማረ ፤—ሰቢክ ፡ ሰበከ ።

ሠበከ ፤—ሠራ ፡ ጠፈጠፈ ፤—ሰብኮ ፡ ሰበከ ።

ሠብል ፤—በቁሙ ፤—ሰቢል ፡ ሰብለ ።

ሠበነ ፤—በቁሙ ፥ ነጭ ፡ ልብስ ፤—ሰበነ ።

ሣቤቅ ፤—ጽፍቅ ፡ ዱር ፡ ዐጽቅ ፡ ሐረግ ፤—ሰቢቅ ፡ ሰበቀ ።

ሠበረ ፤—በቁሙ ፤—ሰቢር ፡ ሰበረ ።

ሠጊው ፤ ዎት ፤ (ሠገወ ፡ ይሠጉ ፡ ይሥጉ ። ዕብ ፡ ሣጋህ) ፤ አው ፡ ሠግዎ ፡ ዎት ፤ (ሠገወ ፡ ይሤጉ ፡ ይሠጉ) ፤ መብቀል ፡ ማደግ ፤ መግዘፍ ፡ መግነን ፡ መጽናት ፡ መበርታት ፤ መብዛት ፡ መርባት ። መሥጋት ፡ ማሰብ ፡ መፍራት ፡ ሥጉ ፡ መኾን ፤ ረገዘን ፡ እይ ።

ሥጋ ፤ (ብ ፡ ሥጋው ፤ ዋት ፤ ሥጋት) ፤ በቁሙ ፡ ግዙፍ ፡ ልሕሉሕ ፡ ደማም ፡ ደም ፡ ነፍሳም ፤ የሕያዋን ፡ ገላ ፡ የነፍሱና ፡ የዐርብ ፡ ፍጥረት ፤ ባጥንትና ፡ ነሥር ፡ በኹለማት ፡ የጸና ። ለማግሰኛም ፡ ፍጥረት ፡ ይበገራል ፡ ይመወን ፡ እይ ። አምላከ ፡ ለኵሉ ፡ ዘሥጋ ። ኢይመስስ ፡ ኵሎ ፡ ዘሥጋ ። እስመ ፡ ሥጋ ፡ እሙንቱ ፡ (ኤር፴፪ ፡ ፳፯ ። ዘፍ፮ ፡ ፲፯ ። ኩፋ ፡ ፳) ።

—፤ ሰው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የአዳም ፡ ዘር ፡ በሥጋነቱ ፡ ላይ ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፡ ነባቢና ፡ ቀዋሚ ፡ ፍጥረት ፤ እከሉ ፡ ገላው ፡ እንደ ፡ ዐምድ ፡ የቆመ ፡ እንደንስሳት ፡ ያልተጋደመ ፡ ከሞተም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ግንድና ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ነገድ ፡ ወድቆና ፡ ተጋድሞ ፡ ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ የማይቀር ፡ ረቂ ፡ ታድሶ ፡ የሚነሣ ። እሰውጥ ፡ እምነ ፡ መንፈስየ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ። ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፤ ወኀደረ ፡ ላዕሌነ ። ዘይሔድስ ፡ ሥጋነ ፡ ትሐውተ ፡ ወይሬስዮ ፡ አምሳለ ፡ ሥጋ ፡ ስብሐቲሁ ፡ (ዮኤ፪ ፡ ፳ ። ዮሐ፩ ፡ ፲፬ ። ፊልጵ፫ ፡ ፳፩) ።

—፤ ወገን ፡ ነገድ ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ ልጅ ፡ ሚስት ። (ተረት) ፡ የሥጋ ፡ ቍራጭ ፡ ያጥንት ፡ ፍላጭ ። ስብሑ ፡ ወሥጋሁ ። አሐዱ ፡ ሥጋ ፡ ንሕነ ፡ በክርስቶስ ። ይኩኑ ፡ ክልኤሆሙ ፡ አሐደ ፡ ሥጋ ፡ (ዘሌ፲፰ ፡ ፮ ። ሮሜ፲፪ ፡ ፭ ። ፩ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፮) ።

—፤ ሬሳ ፡ በድን ፡ አስከሬን ፤ ነፍስ ፡ የተለየችው ፡ የሞተ ፡ የታረደ ። ግድፍ ፡ ሥጋየ ፡ ላዕለ ፡ ሥጋቲሆሙ ። እላ

ንቱ ፡ ሥጋት ፡ ኢይቢታ ፡ ዴበ ፡ መሳቅሊሆን ፡፡ ይትጋብኡ ፡ ሥጋት ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ ከመ ፡ ጸበል ፡፡ ሥጋ ፡ ዘመሥዋዕት ፡፡ ዐቃቤ ፡ ሥጋ ፡ (ዮሴፍ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፴፰ ። ቀሌ ። ሕዝ፴፯ ፡ ፯ ። ሸንገ ፡ ሸኻ ፡ ፪) ።

—፤ ግዘፍ ፡ ግዙፍንት ። እስመ ፡ አኮ ፡ አምሳለ ፡ ኅጺን ፡ ዘይትሜሰል ፡ በዙለንታሁ ፡ ትስብእት ፡ አላ ፡ በሥጋ ፡ ባሕቲቱ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**ሥጋዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፡ የሥጋ ፡ ሥጋማ ፡ ሥጋም ፡ ግዙፍ ። ሹነኔ ፡ ዝሙት ፡ ሥጋዊ ፡ ወመንፈሳዊ ፡፡ አበው ፡ ሥጋውያን ፡፡ ኅጣውእ ፡ ሥጋውያት ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፴፰ ። አፈ ፡ ድጓ፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፱) ። በግማሽ ፡ ሥጋዊ ፡ ሥጋ ፡ ሽያጭ ፡ ባለሥጋ ፡ ሥጋ ፡ ቤት ፡ ሥጋ ፡ መልክኛ ።

**አሥገወ ፤ አሠገወ ፤ አስተሠገወ** ፤ አገዘፈ ፡ አጕላ ። ሰብ ፡ ይፈቅድ ፡ ሰብእ ፡ ይክሥት ፡ ነገረ ፡ ኅሊናሁ ፡ ያሠግዎ ፡ በልሳኑ ፡ (ያዕ ፡ ዘእል) ።

**ተሠግወ ፡ ተሠገወ** ፤ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ ሥጋ ፡ ለበሰ ፡ ጐላ ፡ ገዘፈ ። ተሠግዎቱ ፡ ለወልድ ፡፡ ቃል ፡ ሶበ ፡ ይሜን ፡ በልሳን ፡፡ ተሠገዎ ፡ ነሥአ ፡ ቅብዐተ ፡፡ እመኒ ፡ ዘአልበሙ ፡ ልብ ፡ ኢይሴብዉ ፡ ዘ ፡ ሖሎ ፡ ልብ ፡ ለዘቦቱ ፡ ብሂለ ፡ ተሠገወ ፡ የአክሎ ፡ (አርጋ ፡ ፩ ። ያዕ ፡ ዘእል ። ቄር ። ቅኔ) ።

**ሥግው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ጉት) ፤ ሥጋ ፡ የኾነ ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሥጋማ ፡ ግዙፍ ። እስመ ፡ እግዚ ፡ ሥግው ፡ ውእቱ ፡፡ አብ ፡ ዘኢሥግው ፡ (ቄር ፡ ጳላ ። አፈ ፡ ድጓ) ።

**ሥጋዌ** ፤ ሥጋነት ፤ ሥግና ፡ ሥጋ ፡ መኾን ፤ የሥጋ ፡ ባሕርይ ፤ መወፈር ፡ መግዘፍ ። ምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፡፡ ዓመተ ፡ ሥጋዌ ፡፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹመ ፡ ትስብእት ፡ ወሥጋዌ ፡ (ደራሲ) ። በሥጋ ፡ ፈንታ ፡ ሥጋዌ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ አያሰኝም ። ምስለ ፡ ሥጋዌ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔሃ ፡ (አርጋ ፡ ፪) ።

**ትሥጉት** ፤ ግዝፈ ፡ ከማሁ ፤ ሥጋነት ፡ ሰውነት ፤ ሰው ፡ መኾን ፡ ሥጋ ፡ መልበስ ። ወእምቅድመ ፡ ትሥጉት ፡ አልቦ ፡ ዘይሰምዮ ፡ ለቃለ ፡ እግዚ ፡ ክርስቶስ ፡፡ በእንተ ፡ ትሥጉቱ ፡ ለመድኅኒነ ፡፡ አሚን ፡ በትሥጉተ ፡ ወልድ ፡ (ቄር ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፳ ። አርጋ ፡ ፪) ።

**መሥግው ፤ መሠግው** ፤ ሠጋዊ ፡ (ሠገወ) ። አሥጋዊ ፡ (አሥ ገወ) ።

**ምሥጋው** ፤ መሥጊያ ፡ መሠጊያ ፤ ሰው ፡ መኾኛ ፡ ሥጋ ፡ መልበሻ ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቀደሳ ፡ ለወለተ ፡ ሥጋውያን ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ምሥጋወ ፡ ለአምላክ ፡ ዙሉ ፡ ዘሥጋ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ሠገል** ፡—ጥንቈላ ፤—ሰጊል ፡ ሰገለ ።
**ሠግላ** ፤—ሸላ ፤—ሰጊል ፡ ሰገለ ።
**ሠገም** ፤—ገብስ ፤—ሰጊም ፡ ሰገመ ።
**ሠገኖ** ፤—ሰጐን ፤—ሰገኖ ፡ ሰገነ ።

**ሠጕዐ** ፤—ሳገ ፡ ሰነገ ፤—ሰጕዖ ፡ ሰጕዐ ።

**ሠጊር ፤ ሮት** ፤ (ሠግረ ፡ ይሠግር ፡ ይሥግር ። ዕብ ፡ ሻጋር) ፤ መሥገር ፡ ቆሎ ፡ ቆሎ ፡ መኼድ ፡ ሄዶ ፡ ሄዶ ፡ ድቅ ፡ ድቅ ፡ ማለት ፤ የበቅሎ ፡ የሕፃን ። መሻገር ፡ ሽግር ፡ ማለት ፡ መራመድ ፡ እያለፉ ፡ መርገጥ ፡ ሐረገኛ ፡ ሄደን ፡ ኼደን ፡ እይ ። ወሰበ ፡ ሠግረ ፡ ምዕረ ፡ ወካዕበ ፡፡ ወሖረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይሠግር ፡፡ ብህለ ፡ ሠጊረ ፡ ዘእንበለ ፡ ሰትር ፡፡ ወበዘባነ ፡ ባሕር ፡ ይሠግር ፡ ሐዊሮ ፡ ወሠጊሮ ፡ (ሸንገ ፡ ፲፯ ፡ ፴፱ ። ግብፅ ፡ ፰ ። ቀሌ ። ተረ ፡ ቄር) ።

**ሠጋሪ ፤ ሠጋር** ፤ በቁሙ ፡ ሹያጅ ፡ ተራማጅ ።

**ተሣገረ** ፤ ተሣገረ ፡ ተሠጋገረ ፡ ተሻጋገረ ፡ ተረማመደ ።

**ሥግረት** ፤ መሥገር ፤ ሥግሪያ ። መሻገር ፡ መራመድ ፡ አረማመድ ፡ እርምጃ ፤ አካኼድ ፡ እግር ፡ እንሣሥ ። ኑብቁ ፡ ሖሎ ፡ ሥግረትየ ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፰) ።

**ምሥጋር** ፤ (ራት) ፤ መሥ(ሻ)ገሪያ ፡ መራመጃ ፡ እርምጃ ። ዘይረውጽ ፡ ኢይኔጽር ፡ ኅበ ፡ ምሥጋሪሁ ፡፡ ዘኢይክል ፡ ይትሐወስ ፡ ወኢየሐውር ፡ ቶሐተ ፡ ምሥጋረ ፡፡ ወኢምሥጋረ ፡ እግር ፡ (አፈ ፡ ድጓ ። ጥበ፲፫ ፡ ፲፰ ። ዘዳ፪ ፡ ፭) ።

**አሥገረ** ፤ አሠገረ ፤ አሻገረ ፡ አራመደ ፡ አሳለፈ ፤ የቀን ፡ የብቶት ፤ አዳርን ፡ እይ ። ወሰበ ፡ ሠለስቱ ፡ ዓም ፡ ያሠግሩ ፡ እሑደ ፡ ወርኅ ፡ ወትከውኖሙ ፡ ይእቲ ፡ ዓመት ፡ ዐሠርተ ፡ ወሠለስተ ፡ ወርኀ ፡ (አቡሻ ፡ ፫) ።

**አሥጋሪ** ፤ (ሪት) ፤ መሥገሪ ፡ ግር ፤ የሚያሠግር ፤ የሚያሻግር ። ወትሰመይ ፡ ይእቲ ፡ ዓመት ፡ አሥጋሪት ፡ ወርኅ ፡ (አቡሻ ፡ ፴) ።

**ሠግር** ፤ በቁሙ ፤ የዕለት ፡ የብቶት ፡ ሥግሪያ ፡ እርምጃ ፤ የጨረቃ ፡ ወር ፡ መተላለፍ ፤ ወይም ፡ ትርፍ ፡ ፍድፋጅ ። ይገብሩ ፡ ሠግረ ፡ እሑደ ፡ ወርኀ ፡ ሰበ ፡ ሠለስቱ ፡ ዓመት ፡፡ በራብዐት ፡ ዓመት ፡ ይገብሩ ፡ ሠግረ ፡ እሐዱ ፡ ዕለት ፤ ወይሰምይዋ ፡ ለወርኅ ፡ ሠግር ፡ ጳጉሜን ፤ ወትከውን ፡ ይእቲ ፡ ዓመት ፡ ሠግረ ፡ (አቡሻ ፡ ፪) ።

**ሠግራዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ የሠግር ፡ ሠግራም ፤ ሠግር ፡ ያለበት ፡ ባለሠግር ። ዓመተ ፡ ፀሓይ ፡ ሠግራዊት ፡ (አቡሻ ፡ ፲፯) ።

**ሠገረ** ፤ (ዕብ ፡ ሳጋር ፤ ሳከር) ፤ ሸጐረ ፡ ዘጋ ፡ ቈለፈ ፤ የመዝጊያ ፡ የቅናት ። ጐተተ ፡ አሰረ ፤ ከሕብስ ፡ አገባ ። አጠመደ ፡ ወጥመድ ፡ አኖረ ፤ በወጥመድ ፡ ያዘ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሠገረ ፡ ፈንታ ፡ አሥገረ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። አሥግሩ ፡ ለነ ፡ ቈናጽለ ፡፡ አሥጋሬ ፡ ዖፍ ፡፡ ያሠግሩ ፡ ሰብአ ፡፡ ከመ ፡ ኢታሥግርከ ፡ በማሕሌታ ፡፡ አሥግረኒ ፡ እምባሕረ ፡ እሳት ፡ (ማሕ፪ ፡ ፲፭ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፱ ። ኢሳ፳ ፡ ፲፭ ። ሢራ፱ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ መጋቢ) ።

**ሠጋሬ ፤ መሠግር** ፤ (ራን) ፤ ዘጊ ፡ ሸጓሪ ፡ የሚቈልፍ ፡ አጥማጅ ፡ ወጥመድ ፡ ሠሪ ፡ ጎዣ ፡ ወጋሪ ።

መሠግር ፡ ጴጥሮስ ፡ አመ ፡ አሥገረ ። እስመ ፡ መሠግራን ፡ እሙንቱ ፡ (ቅኔ ። ማቴ፬ ፡ ፲፰ ። ማር፩ ፡ ፲፮) ።

**መሥገርት ፤ (ታት ፤ መሣግር ፤ ርት) ፤** ወጥመድ ፤ ከባቢ ፡ ጦር ፡ ክፉ ፡ ነገር ፤ መያዣ ፡ ማሰሪያ ፤ የማዘዣ ፡ ቤት ፡ ሐብስ ፡ ወህኒ ፡ በደለኛ ፡ ታስሮ ፡ ተዘግቶ ፡ የሚቀመጥበት ። መሥገርት ፡ ለአዕዋፍ ። ትወርድ ፡ እግሩ ፡ ውስተ ፡ መሥገርት ። መሥገርታተ ፡ ሰይጣን ። ብትክ ፡ እምኔነ ፡ መሣግረ ፡ ዘአስተዳለው ፡ እሥጋሬ ። መሣግርት ፡ (ምሳ፮ ፡ ፲፯ ። ኢዮ፲፰ ፡ ፰ ። ፊልክ ። ግንዘ ። አፈ ፡ ተ፴፬) ።

**ማሤጌሬት ፤ (ዕብ ፡ ሚስጌሬት) ፤** ሰንበር ፡ ዝናር ፤ እንደ ፡ ወጥመድና ፡ እንደ ፡ ማገር ፡ ዙሮ ፡ የሚገጥም ፡ የሕንጻ ፡ ጌጥ ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፴፩) ።

**አሥገረ ፤** አስጠመደ ፡ በወጥመድ ፡ አሲያዘ ፤ አሳሰረ ።

**ተሠግረ ፤** ተጠመደ ፤ ከወጥመድ ፡ ገባ ፡ ተያዘ ፡ ታሰረ ፤ ተዘጋ ። ዘሠርዐ ፡ መሥገርተ ፡ ውእቱ ፡ ይሠገር ፡ ቦቱ ። ይሠገሩ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ። ኢትሠገር ፡ በአዕይንቲሃ ፡ (ሢራ፳፯ ፡ ፳፯ ። ኤር፯ ፡ ፲፩ ። ምሳ፯ ፡ ፳፭) ።

**ሥጉር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ግርት) ፤** ከወጥመድ ፡ የገባ ፡ የተያዘ ፤ የተዘጋ ፡ ዝግ ፤ የተዘጋበት ፤ የተሸጐረበት ።

**ሥግረት ፤** መዝጋት ፤ መዘጋት ፡ ዝግንት ፡ አያያዝ ፡ አከባበብ ።

**ሠግር ፤ (ራት) ፤** ወታደር ፤ የሐብስ ፡ ዘበኛ ፤ እስሮች ፡ እንዳይወጡ ፡ እንዳያመልጡ ፡ በሩን ፡ ዘግቶ ፡ ሸጕሮ ፡ የሚጠብቅ ። ተካፈሉ ፡ አልባሲሁ ፡ ሐራ ፡ ሠግራት ። ንሥኡ ፡ ሠገራተ ፡ (ድን ። ማቴ፳፯ ፡ ፴፭) ።

**ሠግራዊ ፤ ሠግራታዊ ፤** የዘበኛ ፡ ወገን ፡ በረኛ ፡ እስር ፡ ጠባቂ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲፱ ። መጋ፯) ።

**ሠግራ ፤** በቁሙ ፤ ዐዘቅተ ፡ ኵስሕ ፤ ሰው ፡ ሲገባበት ፡ የሚዘጋና ፡ የሚሸጕር ።

**ሣህበበ ፤ (ሠዩብ ፡ ሤበ ። ዐረ ፡ ሸሂበ) ፤** ሻገተ ፡ ተበላሸ ፤ ዐመድማ ፡ ቅጠልማ ፡ ኾነ ። ሤበን ፡ እይ ፡ አባቱ ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ ከቅጽሉ ፡ በቀር ፡ አንቀጹ ፡ አይገኝም ።

**ሥህቡብ ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ብብት) ፤** የሻገተ ፡ ሻጋታ ፤ ብልሹ ፡ ዐመድማ ። ኅብስት ፡ ሥህቡብ ፡ ወንቁዝ ፡ (ኢያ፱ ፡ ፭ ። ኢዮ፰ ፡ ፲፪) ።

**ሥሂል ፤ (ሠህለ ፡ ይሥህል ፡ ይሥሀል ። ዐረ ፡ ሠሁለ) ፤ አው ፡**

**ሣህሎ ፤ (ሣህለ ፡ ይሣህል) ፤** መስፋት ፡ መዘርጋት ፤ ቀጥ ፡ ሰጥ ፡ ማለት ፡ መተካከል ፤ መለዘብ ፡ መለስለስ ፤ እንደ ፡ ነትና ፡ እንደ ፡ መሳል ፡ መኾን ። ማዘን ፤ መራራት ፤ ይቅር ፡ ማለት ፡ መታረቅ ፤ ቂምን ፡ ድርቅናን ፡ ሸካራነትን ፡ መተው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሣዘለ ፡ ፈንታ ፡ ተሠሃለ ፡ ተሣህለ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ተሠሃለኒ ፡ እግዚኦ ። ይክል ፡ ተሣህሎ ። ወለዘኒ ፡ ተማህልክዎ ፡ እሣህሎ ፡ (መዝ ፡ ፶ ። ሢራ፲፰ ፡ ፲፩ ። ሮሜ፱ ፡ ፲፭) ። መንገዱ ፡ የቀተለና ፡ የባረከ ፡ ነው ።

**ሣሃሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤** ልበ ፡ ሰፊ ፡ ነገር ፡ ሀላፊ ፤ ይቅር ፡ ባይ ፡ ዐዛኝ ፡ ርሩ ። ሥሂል ፡ ሠሀለ ፡ ባለው ፡ በቀተለ ፡ ቤት ፡ ግን ፤ ሠሃሊ ፤ ሠሀልት ፡ ያሰኛል ።

**ተሣህለ ፤** ይቅር ፡ ተባለ ፤ ተማረ ፡ ይቅርታ ፡ አገኘ ። ይቅር ፡ ተባባለ ፤ ተራረቀ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ አለ ፡ ነው ።

**ሥሁል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ህልት) ፤** ይቅር ፡ የተባለ ፤ ይቅርታ ፡ ያገኘ ፤ የተማረ ። ዕደው ፡ ሥሁላን ። ኢሥህልት ፡ (ሢራ፵፬ ፡ ፲ ። ሆሴ፩ ፡ ፮ ። ፱ ፡ ፲) ።

**ሣህል ፤ (ላት) ፤** ይቅርታ ፡ ርኅራኄ ፡ ምሕረት ፤ ዕርቅ ፡ ፍቅር ። ኢይከውን ፡ ሣህል ፡ ላዕሌሆሙ ። አልቦ ፡ ሣህል ፡ ለዘያወፅእ ፡ ምክረ ፡ ቢጹ ። ዘበእንቲአሁ ፡ ረከብነ ፡ ሣህሎ ፡ (ሔኖ፭ ፡ ፭ ። ሢራ፲፫ ፡ ፲፱ ። ሮሜ፭ ፡ ፲፩) ። ኀዲት ፡ ኀሳር ፡ ሕርትምና ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሣህል ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱) ። ፱ኛም ፡ ጽርኡ ፡ ምክንያት ፡ ያለውን ፡ ሣህል ፡ ይላል ፤ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ምግብ ፡ ይሉታል ፡ (ሢራ፵፬ ፡ ፲፯) ። እስመ ፡ ይኄይስ ፡ እምሐዪው ፡ ሣህልከ ፡ ያለውንም ፤ በሕይወት ፡ አንጻር ፡ ሞት ፡ ይሉታል ፡ (መዝ ፡ ፷፪) ።

**ምሥሃል ፤ (ዕብ ፡ ክፎሬት ። ጽር ፡ ይላስቲሪዎን) ፤** ይቅር ፡ መባያ ፤ ማስተስረያ ፤ ይቅርታ ፡ በርየት ፡ ማግኛ ፤ የታቦቱ ፡ ሙሴ ፡ መክደኛ ፤ ልባጥ ፡ መሸፈኛ ፤ ፪ቱ ፡ ኪሩቤል ፡ የተሣሉበት ። አጕበር ፡ መጋረጃ ፤ የምሥዋዕ ፡ የመንበር ፡ ያልጋ ፡ የዙፋን ። ወገብረ ፡ ምሥሃለ ፡ መልዕልተ ፡ ታቦት ፡ እምወርቅ ፡ ንጹሕ ፡ (ዘፀ፴፯ ፡ ፮—፷ ። ዕብ፱ ፡ ፭) ። ኅጢአት ፡ ጣዖት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ምሥሃል ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ምሥሃለ ፡ ሰማርያ ፡ (ዓሞ፰ ፡ ፲፬) ።

**አሥሀለ ፤ አስተሥሀለ ፤ (ሠሀለ) ፤** ይቀር ፡ አሰኘ ፤ አስማረ ።

**አሣህለ ፤ አስተሣህለ ፤ (ሣህለ) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ወዓዲ ። ይቅር ፡ አባባለ ፤ አስተራረቀ ፡ አስማማ ፡ (አደራራጊ) ።

**መስተሣህል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤** መሥሀሊ ፡ መሥሀል ፤ ይቅር ፡ ባይ ፤ ይቅር ፡ የሚል ፡ ገር ፡ ጎዳጌ ፡ በቀል ። ስምዩኒ ፡ መሓሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ (ዘፀ፴፬ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፻፶፭) ። ይቅር ፡ የሚያሰኝ ፤ አስማሪ ፡ አስታራቂ ። አደራራጊም ፡ ይኾናል ።

**ሠሀለ ፤—ሳለ ፡ አሰላ ፤—ስሒል ፡ ሰሐለ ።**

**ሠሀነ ፤—ሞቀ ፤—ስኂን ፡ ሰኀነ ።**

**ሠሀቀ ፤—ሣቀ ፤—ሥሒቅ ፡ ሠሐቀ ።**

**ሣህር ፤ (ብ ፡ አሥሀርት ። ሱር ፡ ሣህራ ።**

ዐረ ፡ ሸህር) ፤ ሠርቀ ፡ ወርኅ ፡ ልደተ ፡ ወርኅ ፡ የጨረቃ ፡ ወር ፡ መባቻ ፡ ጨረቃ ፡ የምትበቅልበት ፡ ቀን ። በበዓላቲክሙ ፡ ወበአሥህርቲክሙ ፡ (ዘኍ ፲ ፡ ፲ ። ኢሳ ፩ ፡ ፲፫ ። ሆሴ ፪ ፡ ፲፱ ። ቆላ ፪ ፡ ፲፮) ።

ሥህተ ፤—ሳተ ፤—ስሒት ፡ ስሕተ ።

ሠህተ ፤—ዐረፈ ፡ ዕረፍት ፡ አገኘ ፤—ሥኂት ፡ ሠኅተ ።

ሠዊጥ ፤ ጦት ፤ (ሦጠ ፡ ይሠውጥ ፡ ይሡጥ ። ወሰጠ ፤ ሰጠ ፤ ሠጠየ) ፤ መመለስ ፡ መቀለስ ፤ መልሶ ፡ ማምጣት ፡ ማግባት ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ መጣበት ፡ ወደ ፡ ነበረበት ። እሠውጦሙ ፡ ውስተ ፡ ዛ ፡ ምድር ። አመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ ሦጠ ፡ ለነፍሱ ፡ ውስተ ፡ ሥጋሁ ። ብዉሕ ፡ ሎቱ ፡ ሠዊጠ ፡ መንፈስ ፡ ኅበ ፡ ማኅፈደ ፡ ሥጋሁ ፡ (ኢር ፳፱ ፡ ፯ ። ቅዳ ፡ አፈ ። መጽ ፡ ምስ) ። በሦጠ ፡ ፈንታ ፡ አሦጠ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ወአሦጡ ፡ ቀሣውቲሆሙ ፡ ዕራቆ ። ወርቀ ፡ አሠጥነ ፡ እምድረ ፡ ክነዓን ። አሡጥ ፡ ለካልእከ ፡ (ኢር ፲፬ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፵፫ ። ዘዳ ፳፪ ፡ ፩) ።

ሠዋጢ ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት ፤ ሠወጥ) ፤ የሚመልስ ፡ መላሽ ፡ ቀላሽ ።

አሦጠ ፤ አስመለሰ ፡ አስቀለሰ ፤ አግባ ፡ መልስ ፡ አለ ።

ተሠውጠ ፤ ተመለሰ ፡ ምልስ ፡ ቅልስ ፡ አለ ፤ ፊቱን ፡ አዞረ ፤ ተመልሶ ፡ መጣ ። እሠወጥ ፡ ወእሐውር ፡ ቤትየ ። ይሠወጥ ፡ ብሔሮ ። ይሠወጡ ፡ እሙንቱ ፡ ኅቤከ ፡ (ሆሴ ፲፩ ፡ ፲፩ ። ኢሳ ፵፯ ፡ ፯—፱ ። ኢር ፲፩ ፡ ፲፱) ።

ሥዉጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ውጥ) ፤ የተመለሰ ፤ ምልስ ፡ ቅልስ ።

ሡጠት ፤ መመለስ ፡ አመላለስ ፡ ምለሳ ፡ ምልስነት ።

አንሦጠጠ ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ማ ፤ ከሠዊጥና ፡ ከሠጢጥ ፡ የወጣ) ፤ ቀሰቀጠ ፡ ስቅጥጥ ፡ አለ ፤ ገላው ፡ ተቈጣ ፤ ጠጕሩ ፡ ቆመ ፡ ተንጨፈረረ ፡ እንደ ፡ ገርጥና ፡ እንደ ፡ ጾሮ ፡ እንደ ፡ ነብር ፡ እንደ ፡ ግስላ ። አንሦጠጠኒ ፡ ዘሰንታየ ። ወአንሦጠጠኒ ፡ ሥዕርትየ ፡ (ኤርም ፡ ገ፳ና ፡ ፯ ። ኢዮብ ፡ ፲፭ ። ኢር ፳ ፡ ፲፰ ። ሉቃ ፡ ዕገ፫ ፡ ፳፪ ። ገድ ፡ ተክ) ።

—፤ አስቀጠጠ ፤ ስቅጥጥ ፡ አደረገ ፤ አቆመ ፡ አንጨፈረረ ። ድምፀ ፡ ቃል ፡ ልዑል ፡ ዘያንሦጠጥ ፡ ድምፀ ፡ ነበቡ ። ነገሩ ፡ ሊዘብዘን ፡ ይምሕል ፡ ያንሦጠጥ ፡ ሥዕርተ ። አንሦጠጠ ፡ ለሥዕርትየ ፡ (ጥበ ፲፯ ፡ ፱ ። ሢራ ፳፯ ፡ ፲፬ ። መጽ ፡ ምስ) ።

ነሦጣጥ ፤ መደንገጥ ፡ መስቀጥጥ ፡ ስቅጠጣ ፡ ስቅጥጥታ ፤ ኀፍረት ፡ ፍርሀት ። ድንጋጼ ፡ ወነሦጣጥ ፡ (ኢር ፳ ፡ ፴) ።

ሦጠ ፤—ጨመረ ፤—ሰዊጥ ፡ ሰጠ ።

ሠውጥ ፤—ጅራፍ ፤—ሰወጠ ።

ሠውዩ ፤ ዮት ፤ (ሠወየ ፡ ይሠዊ ፡ ይሥወይ ። ዐረ ፡ ሸወይ ፤ ጠበሰ ። ዕብ ፡ ሻዌህ ፤ መሰለ ፡ ተካከለ ፤ አማረ ፡ ተዋበ ፡ ተወደደ) ፤ መሸት ፤ መጕምራት ፡ መብሰል ፡ ሰብሉን ፡ እዪ ። አመ ፡ ይሠዊ ፡ ሥርናይ ፡ (ኢዩ ፲ ፡ ፲፰ ። ያዕ ፳ ፡ ፯ ። መጽ ፡ ምስ) ። በሠወየ ፡ ፈንታ ፡ አሥወየ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ስንክ ፡ ታኅ ፯) ።

ሠዋዪ ፤ ሥዊይ ፤ የሸተ ፡ የበሰለ ፡ ነፍስ ፡ ያጥለ ።

ሥውየት ፤ መሸት ፡ መብሰል ፡ አሸሻት ፡ አበሳሰል ፡ እሸትነት ። ሰብዐቱ ፡ ሰብል ፡ ዘሠዊት ፡ ሠረጹ ፡ እምአሐዱ ፡ ብርዕ ፤ ወንኩር ፡ ሥውየቶሙ ፡ (ዮሴፍ) ።

ሠዊት ፤ (ዕብ ፡ ሽበሌት) ፤ እሸት ፡ ጉምር ፤ ዛላ ፡ ዘለላ ፡ እንቡጥ ፡ ታሽቶ ፡ ተፈልፍሎ ፡ የሚበላ ፡ የእክልና ፡ የተክል ። ወናሁ ፡ ሰብዐቱ ፡ ሠዊት ። ወእኅዘ ፡ ይምሕዉ ፡ ሠዊተ ፡ (ዘፍ ፵፩ ፡ ፳—፯ ። ማቴ ፲፪ ፡ ፩) ። ሦታ ፡ ጠጣት ፡ ጕበግ ፡ ጕልማሳ ፡ ልጅ ፡ እግር ። እሸቱ ፤ ውብ ፡ እሸት ፡ እንዲሉ ። በእሸት ፡ በኸፈት ፡ ቀዳምያት ፡ ማእረር ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሠዊት ፡ ይላል ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አመ ፡ ዕለተ ፡ ሠዊት ፡ (ዘኍ ፳፰ ፡ ፳፯ ። ከዳ ፳፫ ፡ ፳፭ ። መሳ ፲፭ ፡ ፳) ።

ሠውት ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ሠ ፡ ሠዊት ፡ ሠዌት ፤ ሠወስት ፡ ፊስ ፡ ሦስት ፡ ዛላ ፡ ባለሦስት ፡ ጣት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ መሥሚ ፡ እንደ ፡ ማለት ። ከሠለስና ፡ ከሠወየ ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ፡ በዕብራይስጥም ፡ እንደዚሁ ፡ ሦስት ፡ ጣት ፡ አለው ።

አሥወየ ፤ አሸተ ፡ እሸት ፡ አደረገ ፡ እሸት ፡ አበላ ። አሠየ ፡ አስጕመገ ፡ ብሉኝ ፡ ብሉኝ ፡ አለ ፤ እሸቱ ፡ ፍሬው ፤ እንደ ፡ ሪሀ ፡ ገንት ፡ ሐሠየን ፡ እዩ ፡ (ዘፍ ፳፯ ፡ ፯) ።

ሠዊክ ፤ ኮት ፡ (ሦከ ፡ ይሠውክ ፡ ይሡክ ። ዕብ ፡ ሳኽ ፡ ያሱኽ ፤ ወደየ ፤ መሰሐ) ፤ መውጋት ፡ ጠቅ ፡ ማድረግ ፡ ማሳመም ። እሾኽ ፡ ማብቀል ፤ እሾኽ ፡ መባል ፡ እሾኽነም ፡ ሸውከኛ ፡ መኾን ።

ሦከ ፤ (ብ ፡ አሥዋክ ። ዕብ ፡ ሶክ ፡ ሱካ ፤ ዐጽቅ ። ዐረ ፡ ሸውክ ፡ ሸውከት) ፤ ሾኽ ፡ እሾኽ ፡ የሾኽ ፡ ዛፍ ። ወግዐኒ ፡ ሦክ ። አክሊል ፡ ዘሦክ ። ይቀሥሙሁ ፡ እምአሥዋክ ፡ አስካለ ፡ (መዝ ፡ ፴፩ ። ማር ፲፭ ፡ ፲፯ ። ማቴ ፯ ፡ ፲፮) ።

ሦከዊ ፡ ይ ፤ የሾኽ ፡ ዐይነት ፡ ወገን ፡ እሾኸም ፡ ሹክ ። ሹላላ ፡ እሾኸላ ፡ ሸውከኛ ፡ አሽዋኪ ፡ ሾካካ ።

ሠዊን ፤ ኖት ፤ (ሦነ ፤ ሠወነ ፡ ይሤውን ፡ ይሡን) ፤ ማልገግ ፡ መቈበር ፡ ማገለብለብ ፡ ልጋጉም ፡ ቈበሩም ፡ መኾን ፡ ሐረፋት ፡ መድረቅ ። ሐረፈንና ፡ ሤኔንን ፡ እዩ ። ይሤውኑ ፡ በአፉሆሙ ፡ (አዋል) ።

ሠወን ፤ ልጋግ ፡ ቈበር ፡ ሐረፋ ፡ የአፍ ፡ ዛሕል ።

አሥወነ ፤ አስለገገ ፡ ቈበር ፡ አስደረቀ ። አሥወና ፡ ለብእሲት ። ወያሤውኖ ፡ (ስንክ ፡ መስ ፳ ። ማር ፱ ፡ ፲፰ ፡ ፳ ። ሉቃ ፱ ፡ ፴፱) ።

**ምሥዋን** ፤ (ብ ፡ መሣውን ፤ ምሥዋ ናት) ፤ ማልገጊያ ፡ መትረፊያ ፡ ሌጋን ፡ መጣያ ፡ መቀበያ ፡ የድዉይ ፡ (እጥል) ፡፡



ምሥዋን ፡

**ሠዊዕ ፤ ዖት ፤ (ሦዐ ፡ ይሠውዕ ፡ ይሡዕ ፤ ይሣዕ ፤ ይሢዕ ፤ ይሥዋዕ ፡፡ ዕብ ፡ ሻዊዐ ፡ ሮኸ ፡ ጠራ ፡፡ ዐረ ፡ ሸወይ ፤ ጠበሰ)** ፤ መሠዋት ፡ መሥዋዕትና ፡ ጸሎት ፡ ማቅረብ ፤ ማረድ ፡ መግደል ፡ ማንደድ ፡ ማቃጠል ፤ ማሳረር ፡ ማጤስ ፡ መጥበስ ፡ ማንጠስጠስ ፤ ለማሳረግ ፤ ለረፈን ፡ እይ ፡፡ ሰሠዊዐ ፡ መሥዋዕተ ፤ ዘእምጽአ ፡ ለሠዊዐ ፡፡ ዐርገ ፡ ከመ ፡ ይሡዐ ፡፡ ወሦዐ ፡ መሥዋዕተ ፡፡ ሡዑ ፡ ለእግዚ ፡ መሥዋዕተ ፡ ስብሐት ፡ (ዘሌ፩ ፡ ፪ ፡ ፱ ፡፡ ፩ነገ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ፡፡ ዘፍ፰ ፡ ፳) ፡፡

**ሠዋዒ ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት ፤ ዕት)** ፤ የሚሠዋ ፡ አቃጣይ ፡ ዐጣኝ ፡ የምሥዋዕ ፡ አገልጋይ ፡፡ አብርሃም ፡ አቅረበ ፡ ወልዶ ፡ ወኢሠዖ ፡ ወተፀሰየ ፡ ዕሴተ ፡ ሠዋዒ ፡ (አፈ ፡ ተ፴፱) ፡፡ ካህን ፡ ካህናት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሠዋዒ ፡ ሠዋዕት ፡ ይላል ፡ (ዘፀ፲፰ ፡ ፩ ፡፡ ፲፱ ፡ ፳፱ ፡ ፳፱ ፡፡ ፩ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፫) ፡፡

**ሣውዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት)** ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፡ ካህን ፡ የሚጠብስ ፡ የሚያጤስ ፡ (ኩፋ ፡ ፴ ፡ ፵ ፡ ፵፬) ፡፡ ቢትረ ፡ ሌዋዊ ፡ ሣውዕ ፡፡ ሚካኤል ፡ ሣውዕ ፡ (ደራሲ) ፡፡

**ምሢዕ ፤ ምሥዋዕ ፤ (ዓት)** ፤ በቁሙ ፡ መሠዊያ ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረቢያ ፤ ማረጃ ፡ ማንደጃ ፡ በታ ፡ ምድጃ ፡ የብሉይ ፡፡ ነደቀ ፡ ኖኅ ፡ ምሢዐ ፡ ወአዕረገ ፡ ቍርባነ ፡ ዲበ ፡ ምሥዋዕ ፡፡ ጸርሐ ፡ ወይቤ ፡፡ ምሢዕ ፡ ምሢዕ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚ ፡፡ ወይትነሠቱ ፡ ምሥዋዐቲክሙ ፡ (ዘፍ፰ ፡ ፳ ፡፡ ፫ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፪ ፡፡ ሕዝ፮ ፡ ፬) ፡፡

—፤ መንበረ ፡ ታቦት ፤ ጽሌ ፡ ጽላት ፤ የሐዲስ ፡፡ ያንብሩ ፡ ዲበ ፡ ምሢዕ ፡ ወንጌለ ፡ ዮሐንስ ፡ ወለእመ ፡ ተሰብረ ፡ ምሢዕ ፡ አው ፡ ፈለሰ ፡ ይቀድሱ ፡ ዳግመ ፡፡ ክልኤቱ ፡ ምሢዓት ፡ አሐዱ ፡ ዘያፈልስዎ ፡ እመካን ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፩ ፡፡ ፈ ፡ መ ፡ ፳፱ ፡ ፱) ፡፡

**ተሦዐ** ፤ ተሠዋ ፡ ታረደ ፡ ነደደ ፡ ጤሰ ፡ ተጠበሰ ፡፡ ክርስቶስ ፡ ዘተሦዐ ፡ በምዕር ፡፡ እስመ ፡ ለሊሁ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወለሊሁ ፡ ካህን ፡ ወለሊሁ ፡ ተሠዋዒ ፡፡ ተሠውዖቱ ፡፡ ሥጋከ ፡ ለለ ፡ ጊዜ ፡ ይሠዋዕ ፡ (አፈ ፡ ድ፲፰ ፡ ፲፯ ፡፡ ፳፩ ፡፡ ደራሲ) ፡፡

**ሥዉዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ውዕት)** ፤ የተሠዋ ፡ መሥዋዕት ፡ የኾነ ፡፡

**ሠዐት ፤ (ላ ፡ ጥ ፡ ሠዋ)** መሠዋት ፤ መሥዋዕት ፡ መኾን ፤ መሥዋዕትነት ፡፡ ሥምረቱ ፡ ለአብ ፡ በሠዐተ ፡ ወልዱ ፡ (መጽ ፡ ምክ) ፡፡

**መሥዋዕት ፤ (ብ ፡ መሣውዕ ፤ ዕት)** ፤ ምሥዋዕ ፡ መሠዊያ ፡ በታ ፡፡ ወግበር ፡ ላቲ ፡ ቀጸላ ፡ ለመሥዋዕት ፡፡ ቤተ ፡ መሥዋዕት ፡ ገበዋተ ፡ መሥዋዕት ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፫ ፡ ፳—፯) ፡፡

—፤ ማረጃ ፡ ወቅለምት ፡ ማንደጃ ፡ ማቃጠያ ፡ እሳት ፡፡ ወአምጽኡ ፡ ማሬ ፡ ዘ.ድያስ ፡ ምስለ ፡ አልሕምት ፡ ወመሣውዕ ፡ (ግብ፲፬ ፡ ፲፫) ፡፡ የጽርሐ ፡ አብንት ፡ ማን ፡ ወአክሊላት ፡ ይላል ፡፡

—፤ በቁሙ ፡ መንፈሳዊ ፡ እምነት ፡ ሕርድ ፡ ቍርባን ፤ የእንስሳት ፡ ያዝርዕትና ፡ ያትክልት ፡ የስንዴ ፡ የወይን ፡ የዘይት ፡ የዕጣን ፡ የመሰሰው ፡ ኹሉ ፤ ፍጡር ፡ ለፈጣሪው ፡ ከጸሎትና ፡ ከምስጋና ፡ ጋራ ፡ የሚያቀርበው ፡ የሚያቃጥለው ፡፡ መሥዋዕተ ፡ ፋሲካሁ ፡፡ መሥዋዕት ፡ ዘልዉስ ፡ በቅብዕ ፡፡ መሥዋዕተ ፡ ወቍርባነ ፡ ኢፈቀድከ ፡፡ ኅብስተ ፡ መሥዋዕት ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፳፯ ፡፡ ኩፋ ፡ ፯ ፡፡ መዝ ፡ ፴፱ ፡፡ ማር፪ ፡ ፳፯) ፡፡ ከመ ፡ ያምጽኡ ፡ መሣውዒሆሙ ፡ ዘሎ ፡ ዘይሠውዑ ፡፡ ወባሕቱ ፡ ይትሀወኩ ፡ መሣውዕት ፡ (ዘሌ፲፯ ፡ ፭ ፡፡ ዳን፰ ፡ ፲፩) ፡፡

**ሡዕ ፤ (ብ ፡ ሥዋዕ)** ፤ ማቀጣጠያ ፡ ጭራሮ ፡ ገለባ ፡ ኰበት ፡ ጢፍ ፡ ጋዝ ፡ ክብሪት ፤ የተልባ ፡ እግር ፡ ፈትል ፡ የፋኖስ ፡ ቋድ ፡ ከጋዝ ፡ የሚዋሐድ ፡ ሁብሮ ፡ የሚነድ ፡፡ ሡዕ ፡ ዘይጠይስ ፡ ኢያጠፍእ ፡፡ ወጠፍኡ ፡ ከመ ፡ ሐመደ ፡ ሡዕ ፡፡ ይልበሱ ፡ ሰቢጠነ ፡ ዘሡዕ ፡ (ኢሳ፵፪ ፡ ፫ ፡፡ ማቴ ፡ ፲፫ ፡፡ ሥር ፡ ጳኰ) ፡፡

**ሡዕ ፤ (ሦዕከ ፡ ትሠውዕ ፡ ትሡዕ)** ፤ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፤ ለሳንድ ፡ የቅርብ ፡ ወንድ ፡፡ ሠዋ ፤ መሥዋዕት ፡ አቅርብ ፡፡ ሡዕ ፡ ሊተ ፡ ወልደከ ፡ (ዘፍ፳፪ ፡ ፪) ፡፡

**ሠውር ፤—ከከብ ፤—ተውር ፡ ቶር ፡፡**

**ሠውት ፤—ስመ ፡ ፊደል ፤—ሠወየ ፡፡**

**ሠገዩ ፤ ዩት ፤ (ሠዘየ ፡ ይሤዚ ፡ ይሥዚ ፡፡ ዐረ ፡ ሸዘ ፤ ሸዘአ)** ፤ መለየት ፡ መነጠል ፤ መክልከል ፡ ማድላት ፡፡ እንዘ ፡ ትሤዚ ፡፡ ኢይሤዚ ፡ እንበይነ ፡ ንዴቱ ፡ ለነዳይ ፡፡ ምሕረተ ፡ ነዳያን ፡ እለቡ ፡ ዘእንበለ ፡ እሥዚ ፡ (ተረ ፡ ቄር ፡፡ ሲኖዶ ፡ ፲፪ ፡፡ ሚራ፴፪ ፡ ፲፯ ፡፡ ሰንክ ፡ መጋ፲፪) ፡፡

**ተሠዝየ** ፤ ተለየ ፡ ተነጠለ ፤ ተወገዘ ፡ ከማኅበር ፡ ከንድነት ፡ ከጉባኤ ፡ ወጣ ፡፡ እለ ፡ ተሠዝዩ ፡ ለዘበፀግ ፡ ይሜህሩ ፡ ወለዘተስዕረ ፡ (ተረ ፡ ቄር ፡፡ ሲኖዶ) ፡፡

**ሠሐገ ፤—ሮኸ ፡ አሞሸ ፡ ሳገ ፤—ስሒግ ፡ ሰሐገ ፡፡**

**ሥሕወ ፤—ተሳበ ፤—ስሒው ፡ ስሕወ ፡፡**

**ሠሐጠ ፤—ነካ ፡ ጫረ ፤ ቈነጠጠ ፤—ስሒጥ ፡ ሰሐጠ ፡፡**

**ሥሕከ ፤—ሻከረ ፤—ስሒክ ፡ ስሕከ ፡፡**

**ሠሐለ ፤—ራራ ፡ ይቅር ፡ አለ ፤—ሥሂል ፡ ሠሀለ ፡፡**

**ሠሐለ** ፡—ሳለ ፡ ሰነገለ ፡—ስሒል ፡ ሰሐለ ።

**ሠሐነ** ፡—ሞቀ ፡ ተከሰ ፡—ስኂን ፡ ሰኅነ ።

**ሦሒጽ** ፡ ጾት ፡ (ሦሕጸ ፡ ይሦሕጽ ፡ ይሦሐጽ ። ዐረ ፡ ሸሐጸ ። ዕብ ፡ ሸሒጽ) ፡ መታበይ ፡ መኰራት ፡ መይፈር ፡ አላቅሙ ፡ መናገር ፡ መሰደብ ፡ ማዋረድ ፡ መናቅ ፡ መማለቅ ። ከሰው ፡ ነገር ፡ መግባት ፡ ጥልቅ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ወገሜት ፡ ዝንብ ። ሰሐጠንና ፡ ሠጠጠን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ። ይሦሕጹ ፡ ዘእንበለ ፡ ዐቅም ። እለ ፡ እንበለ ፡ ጥበብ ፡ ሦሕጹ ፡ ላዕለ ፡ ትሥጉተ ፡ መድኅኒነ ። ለምንት ፡ ይሦሕጹ ፡ ላዕለ ፡ ስብሐተ ፡ መለኮት ፡ (ቁር ፡ ጳላ ፡ ተረ) ።

**ሠሓጺ** ፡ ሦሑጽ ፡ (ጺን ፡ ጺት ፡ ሕጽት) ፡ ደፋር ፡ ዕቡይ ፡ አላጋጭ ፡ እሽሙጣጭ ፡ ተሳዳቢ ፡ (ሆሴ ፯ ፡ ፭ ። ሮሜ ፩ ፡ ፴ ። ፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፪) ። መኰንን ፡ ሦሑጽ ። ዕልዋን ፡ ወጽልሕዋን ፡ ወሦሑጻን ። ልሳን ፡ ሦሕጽት ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ ፲፱ ። ቀሌ ። ቁር) ።

**ሦሕጸት** ፡ (ታት) ፡ መናቅ ፡ ማቃለል ፡ ትዕቢት ፡ ድፍረት ፡ ቅለት ፡ ጠለቅላቅነት ፡ የስድብ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ። ቃለ ፡ ሦሕጸታት ፡ ያወፅእ ፡ እምአፉሁ ። ወበዘያነጽሕ ፡ ርእሰ ፡ እምሦሕጸታት ፡ ዘሰምዐ ። ሦሕጸታት ፡ ላዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ (ቁር ፡ እስት ። ጳላ) ።

**ሦሒቅ** ፡ ቆት ፡ (ሠሐቀ ፡ ይሦሕቅ ፡ ይሦሐቅ ። ዕብ ፡ ሣሐቅ ፡ ጸሐቅ ። ዐረ ፡ ፀሒከ) ፡ መሣቅ ፡ መፍካት ፡ ማሽካካት ፡ ከንፈርን ፡ መሰቅጠጥ ፡ ጥርስን ፡ መግለጥ ፡ ከደስታና ፡ ከረብሻ ፡ ብዛት ፡ ከማየት ፡ ከመስማት ፡ የተነሣ ። ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይበክዩ ፡ ይእዜ ፡ እስመ ፡ ይሦሕቁ ። አሌ ፡ ለክሙ ፡ እለ ፡ ትሦሕቁ ፡ ይእዜ ፡ እስመ ፡ ትበክዩ ። ኢትሦሐቅ ፡ ሎቱ ፡ (ሉቃ ፮ ፡ ፳፩ ፡ ፳፭ ። ሢራ ፴ ፡ ፲) ።

**ሠሓቂ** ፡ ሦሑቅ ፡ (ቃን ፡ ቃት ፡ ሕቅት) ፡ የሚሦቅ ፡ ሣቂ ፡ የሣቀ ፡ ሣቃም ።

**ሠሐቅ** ፡ (አው ፡ ሣሕቅ ፡ ሦሓቅ ፡ ሦሐቅ) ፡ በቁሙ ፡ ሣቅ ፡ ሦቆሽ ፡ አሣሣቅ ። መሪር ፡ ሠሐቅየ ፡ ዘእሦሕቅ ። ወለሠሐቅክሙ ፡ ሚጥዎ ፡ ውስተ ፡ ላሕ ። እምሑረቱ ፡ ወእምሠሐቁ ፡ ይትዐወቅ ፡ ግዕዙ ፡ (ኤርሚ ፡ ፳ ። ያዕ ፬ ፡ ፱ ። ሢራ ፲፱ ፡ ፴) ።

**አሦሐቀ** ፡ አሣቀ ፡ ደስ ፡ አሰኘ ። ምንት ፡ አሦሐቃ ፡ ለሳራ ፡ (ዘፍ ፲፰ ፡ ፲፫) ።

**መሦሐቂ** ፡ (ሕቅ ፡ ቅት ፡ ቃን ፡ ቃት) ፡ የሚሦቅ ፡ ሣቂ ፡ የሚያሦቅ ፡ አሣቂ ፡ አሣቃዎች ፡ ቀላጅ ፡ ቧልተኛ ፡ ዘፋኝ ፡ አዝማሪ ። መካነ ፡ መሦሕቃን ፡ (ሲኖዶ) ።

**ምሦሓቅ** ፡ (ቃት) ፡ መሣቂያ ፡ መሬሻሻም ፡ ትያጥሮን ። ሕገ ፡ ምሦሓቅ ፡ (አዋል) ።

**ሦሕተ** ፡—ሳተ ፡—ስሒት ፡ ስሕተ ።

**ሦኒት** ፡ ቶት ፡ (ሦኀተ ፡ ይሦኅት ፡ ይሦኀት ፡ አው ፡ ሠነተ ፡ ይሜኅት ፡ ይሦኅት ። ዐረ ፡ ሠከተ ። ዕብ ፡ ሣከት ። ሱር ፡ ሦከት) ፡ መሠከት ፡ ዝም ፡ ዕክም ፡ ጸጥ ፡ ሠክ ፡ ሹክክ ፡ ማለት ፡ ለመስማትና ፡ ለማይመጥ ፡ ለጕሰን ፡ እይ ። ማረፍ ፡ ዕረፍት ፡ ማግኘት ፡ ከመከራ ። እሦኅት ፡ እምሕምዝ ። ከመ ፡ ታዕርፍ ፡ ምድር ፡ ወትሦኅት ፡ እምዘሉ ፡ ሕማም ። ይሦኅታ ፡ ምድረ ፡ ሰይም ፡ ወገሞራ ፡ ፊደፋደ ፡ እምይእቲ ፡ ሀገር ፡ (ኢዮ ፴፫ ፡ ፲፫ ። ሉቱ ፡ ዕዝ ፲፩ ፡ ፵፯ ። ማቴ ፲ ፡ ፲፭) ። በሦኅተ ፡ ፈንታ ፡ ተሦኅተ ፡ ይባል ፡ አያሰኝም ። ወበዝየኒ ፡ ኢትሦኅትኩ ፡ (ጾሎ ፡ ምና) ።

**ሠኃቲ** ፡ ሦኁት ፡ (ቃን ፡ ቃት ፡ ኃት) ፡ የሠከተ ፡ ያረፈ ፡ ዐራፊ ፡ ዕረፍት ፡ ያገኘ ፡ ዝም ፡ ዕክም ፡ ያለ ፡ ጸጥተኛ ፡ (ማቴ ፲፩ ፡ ፳፱) ።

**ሣኅት** ፡ ዕረፍት ፡ ኀድአት ፡ ረድኤት ። ይረክቡ ፡ ሣኅተ ። እሁበሙ ፡ ሣኅተ ፡ ንስቲተ ፡ ለመድኅኒት ፡ (ማቴ ፳፰ ፡ ፲፯ ። ማር ፯ ፡ ፲፩ ። ሉቃ ፳፪ ፡ ፯ ። ፪ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፯) ።

**አሦኅተ** ፡ (ያሜኅት) ፡ አሳረፈ ፡ ዕረፍት ፡ ሰጠ ፡ መከራ ፡ አቀለለ ፡ ተወ ፡ ይቅር ፡ አለ ። ኦዝዜ ፡ ነገርክሙ ፡ ኢያሜኅተኒ ። እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ኢታሜኅተኒ ። ወአንተኒ ፡ ዮም ፡ ኣድግ ፡ ወአሦኅት ፡ እምክበደ ፡ ቅኑ ፡ አቡከ ፡ (ኢዮ ፯ ፡ ፳፯ ። ፯ ፡ ፲፱ ። ፪ዜና ፡ ፲ ፡ ፱) ። በአሦኅተ ፡ ፈንታ ፡ ሦኅተ ፡ ሠነተ ፡ ይባል ፡ አያሰኝም ። ሦኅተኒ ፡ ከመ ፡ ኣዕርፍ ። ኢይሦኅቶሙ ። ጾረት ፡ ክቡደ ፡ ወኢሠኅትዋ ። ሠኅተነ ፡ እምቅኑነ ። አንተ ፡ አምላክነ ፡ ሠኅትከነ ፡ እምኅጢአትነ ፡ (መዝ ፴፰ ። ኢሳ፷ ፡ ፲ ። ሰቈ ፭ ፡ ፲ ። ዕዝ ፲ ፡ ፹ ፡ ፲፫) ።

**አሦኃቲ** ፡ መሦኅቲ ፡ ኃት ፡ የሚያሳርፍ ፡ አሳራፊ ፡ ዕረፍት ፡ ሰጪ ።

**ሠጠወ** ፡—ሰጠ ፡ መለሰ ፡—ሰጢው ፡ ሰጠወ ።

**ሠጥሐ** ፡—አሰጣ ፡ ዘረጋ ፡—ሰጢሕ ፡ ሰጥሐ ።

**ሠጢጥ** ፡ ጦት ፡ (ሠጠ ፡ ሠጠጠ ፡ ይሠጥጥ ፡ ይሦጥጥ ። ዕብ ፡ ሻጥ ፡ ቀዘፈ) ፡ ሠጠጥ ፡ ማድረግ ፡ መቅደድ ፡ መሠንጠቅ ፡ መሠንተር ፡ መለየት ፡ መክፈል ። ሠጠቀን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ሠጠጠ ፡ አልባሲሁ ። ኢትሦጥጥ ፡ ልብሰተ ፡ ሦጋዊሁ ። እሠጥጥ ፡ መጽሐፈ ፡ ኅጣውኢከ ። ሠጠጡ ፡ ክርሦ ። ሠጠጣ ፡ ለመንግሥትከ ፡ (ማቴ ፳፮ ፡ ፷፭ ። ተረ ። ቁር ። ስንክ ፡ ሐምሌ ። ዮሴፍ ። ሺኖ ፲፩ ፡ ፳፫) ። ሢጥ ፡ ሢጢጥ ፡ ማድረግ ፡ ማንሣያጠጥ ። ማሽጠጥ ፡ ሽጣጣ ፡ ማድረግ ።

**ሠጣጢ** ፡ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት) ፡ የሚቀድ ፡ ቀዳጅ ፡ ሠንጣቂ ።

**ተሠጠ** ፡ ተቀደደ ፡ ተሠነጠቀ ፡ ተተረተረ ። ኢይሠጠጥ ፡ ይመናሁ ፡ በታሕቴሁ ። ወተሠጠ ፡ መን

ጦሳዕተ ፡ ምሥራብ ፡ (ኢዮ ፴፯ ፡ ፳ ። ማቴ ፳፯ ፡ ፶፮) ።

**ሥጡጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ጥጥ)** ፤ የተቀደደ ፡ ቀዳዳ ፡ ሠንጣቃ ፡ ክፍት ። ሥጡጥ ፡ አልባሲሁ ፡፡ ሥጡጥ ፡ መታክፉ ፡ በሰይፍ ፡፡ ዝቅ ፡ ሥጡጥ ፡፡ ይለብስ ፡ ሥጡጠ ፡ ወአጽርቅተ ፡ ዘሉ ፡ ፃዋሚ ፡ (፳፮ ፡ ፱ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ ጥር ፲፪ ። ኢዮ ፱ ፡ ፱ ። ምሳ ፳፫ ፡ ፳፩) ፡ የቋጠጠ ፡ ሸጣጣ ፡ ሞጥሟጣ ።

**ሥጠት ፤ (ታት)** ፤ (መቀደድ ፡ መቀደድ ፡ አቀዳደድ ፡ ቀዳድነት ፡ ቅድ ፡ ሥንጥቅ ። ሥጠተ ፡ ልብስ ፡ ብሉይ ፡ ወይከውን ፡ ሥጠቱ ፡ ዐቢየ ፡ (ማቴ ፱ ፡ ፲፮) ።

**ሠጥየ ፡ ዮት ፤ (ሠጠየ ፡ ይሠጢ ፡ ይሥጢ ። ዕብ ፡ ሣጣሀ ። ሱር ፡ ሥጣኢ)** ፤ መጸነን ፡ መሳብ ፡ መዘንበል ፡ ማድላት ፡ ማጋደል ። መሰወጥ ፡ ማበድ ፡ ክሕግ ፡ ከመንገድ ፡ መውጣት ። ባለመጽሐፎች ፡ ግን ፡ አበጣ ፡ ዘረጋ ፡ ብለው ፡ በስጥሐ ፡ ዘይቤ ፡ ይፈቱታል ። ኢይትቀነያ ፡ ለስቴ ፡ ወኢይሠጠያ ፡ ውስተ ፡ ስካር ፡ (ቲቶ ፪ ፡ ፫) ። ብዙው ፡ መጽሐፍ ፡ ደግሞ ፡ በሠጠየ ፡ ፈንታ ፡ ተሠጥየ ፡ ይላል ፡ አያስኬድም ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘተፈግዐ ፡ ወተሠጥየ ፡ ዘይፈግዕ ፡ ወይሠጠይ ፡፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ተሠጥየ ፡ ልቦሙ ፡ ብእንቲ ፡ አንስት ፡፡ ተመስወ ፡ ልቦሙ ፡ ወተሠጥየ ፡ (ፊርማ ። ፩ዕዝ ፡ ፬ ፡ ፳፯ ። ኢያ ፳ ፡ ፳) ።

**ሥጡይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ጢት)** ፤ የጸነነ ፡ የተሳበ ፡ የተሰወጠ ፡ (ፊርማ) ።

**ሥጥየት** ፤ አብደት ፡ ስካር ፡ ጥጋብ ፡ የአብደትና ፡ የስካር ፡ የጥጋብ ፡ ሥራ ። ስክረተ ፡ ወሥጥየተ ፡ (፩ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፫) ።

**ሠጠመ ፤-ብቁሙ ፤-ሰጢም ፡ ሰጠመ ።**

**ሠጠቀ ፤ (ሠጢቀ ። ሠጠጠ ። ዕብ ፡ ሳዳቅ ። ሱር ፡ ስዳቅ ። ዐረ ፡ ጺደዐ)** ፤ ሠነጠቀ ፡ ፈለጠ ፡ ተረተረ ፡ ቀደደ ፡ ዐረሰ ፡ ለየ ፡ ከፈለ ፡ በቁመት ፡ እንዳክርማ ፡ እንደ ፡ ቁጠማ ። ኢሳይያስ ፡ ዘሠጠቅዎ ፡ ለክልኤ ፡ ክፍል ፡ በምሥርት ፡ ዕፀ ፡፡ መሠርይ ፡ ተናገረ ፡ ላዕለ ፡ ክይሲ ፡ ወሠጠቆ ፡ ለክልኤ ፡፡ መባርቅት ፡ እለ ፡ ይሠጥቁ ፡ አብያተ ፡፡ ወይሠጥቅ ፡ ምድረ ፡ አፍላግ ፡፡ ሠጠቀ ፡ ትዕይንተ ፡ ኢሎፍሊ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ሠኔ ፳፮ ። ዮሴፍ ። ሰኔ ፲ ፡ ፱ ። ፪ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፲፮) ።

**ተሠጥቀ** ፤ ተሠነጠቀ ፡ ተተረተረ ፡ ነቃ ፡ ፈነዳ ፡ ተቀደደ ፡ ተከፈለ ። ጸዋልዕት ፡ ተሠጥቁ ፡፡ ተሠጥቀ ፡ ገቦሁ ፡፡ ተሠጥቀ ፡ ዘሉ ፡ ቀላይ ፡፡ ሕዝብ ፡ ዘተሠጥቀ ፡ ሎሙ ፡ ባሕር ፡፡ ነፍስ ፡ ተሠጥቀ ፡ በሐጽ ፡ (ቀሌ ። ግብረ ፡ ፲፰ ። ዘፍ ፳፯ ፡ ፲፩ ። ዮሴፍ ። ጥበ ፳ ፡ ፲፱) ።

**ሥጡቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ጥቅት)** ፤ የተሠነጠቀ ፡ ሥንጥቅ ፡ ሠንጣቃ ፡ ቀዳዳ ፡ ሥጡቅ ፡ ጽፍሩ ፡ እማእከሉ ፡፡ ምብኋሉ ፡ ነሃቢ ፡ ሥጡቅ ፡ (ሥጡጥ) ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፫ ። ኢዮ ፴፱ ፡ ፲፱) ።

**ሥጥቀት** ፤ (ላጥ ፡ ሠ) መሠንጠቅ ፡ መቀደድ ፡ ሠንጣቅነት ፡ ሥንጥቃት ፡ ንቃቃት ። ሥጥቀተ ፡ ገቦ ፡ በመጥባሕት ፡፡ እንተ ፡ ሥጥቀት ፡ አረፍት ፡፡ ከመ ፡ ሥጥቀት ፡ ፈለግ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ ፳፮ ። አቡሻ ፡ ፶ ። ኢዮ ፳፰ ፡ ፱) ።

**ሠይእ ፤—ከንቱ ፡ ሥራ ፤—ሰይእ ።**

**ሠዩብ ፤ ቦት ፤ (ሤበ ፡ ይሠይብ ፡ ይሢብ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሣብ ። ዐረ ፡ ሻበ)** ፤ መሸበት ፡ ማርጀት ፡ መፈበር ፡ ነጭ ፡ ጠጕር ፡ ማውጣት ። መሸገት ፡ መበላሸት ። ሣህበን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

(ጥ) **ሠያብ ፡ ሥዩብ** ፤ የሸበተ ፡ ሽበታም ፡ አሮጊ ፡ ሽማግሌ ፡ ሽጋታ ፡ ብልሹ ።

**ሢበት** ፤ ሽበት ፡ ነጭ ፡ ጠጕር ፡ የርጅና ፡ አበባ ፡ እርጅና ፡ ሽምግልና ። በቈብ ፡ ሢበቱ ፡፡ ሢበተ ፡ ልሂቅ ፡፡ ቅድመ ፡ ዘሢበት ፡ ተንሥእ ፡፡ ይደልዋ ፡ ኵንኖ ፡ ለሢበትከ ፡፡ ዘየሐፅኖ ፡ ለሢበትኪ ፡ (ሆሴ ፯ ፡ ፱ ። ጥበ ፬ ፡ ፲ ። ዘሌ ፲፱ ፡ ፴፪ ። ሢራ ፳፭ ፡ ፬ ። ሩት ፬ ፡ ፲፭) ።

**አሤበ ፤ አው ፡ አሥየበ** ፤ አሸበተ ፡ አስረጀ ። አሸገተ ፡ አስደፈገም ፡ ይኾናል ።

**ሠዪጥ ፤ ጦት ፤ (ሤጠ ፡ ይሠይጥ ፡ ይሢጥ ። ቅብጥ ፡ ሾት ፡ ንግድ)** ፤ መሼጥ ፡ መለወጥ ፡ መቸርቸር ፡ መሸቀጥ ፡ መስጠት ፡ መቀበል ፡ ከግዥ ። ነገደ ፡ የሩቅ ፡ ሤጠ ፡ የቅርብ ፡ የመደብር ። ሠዪጥ ፡ ወተሣይጦ ፡፡ ዘሤጠ ፡ ብኵርናሁ ፡ (ራእ ፲፫ ፡ ፲፯ ። ዕብ ፲፪ ፡ ፲፮) ። በሤጠ ፡ ፈንታ ፡ አሥየጠ ፡ ይላል ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አሢጠኒ ፡ ኪዳሁ ፡ በሣጥ ፡ (፳ዘዳ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱) ።

**ሠያጢ ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት ፤ የጥ)** ፤ የሼጠ ፡ የሚሸጥ ፡ ሸያጭ ፡ ዐጣሪ ፡ ነጋዴ ፡ ቸርቻሪ ፡ ሸቃጭ ። ሠያጢ ፡ ወተሣያጢ ፡፡ ይሁዳ ፡ ሠያጤ ፡ እግዚኡ ፡፡ ሠየጠ ፡ አሕዛብ ፡ ተፋጸዩኪ ፡፡ ሠየጥኪ ፡ ብነፍስ ፡ ሰብእ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ። መጽ ፡ ምስ ። ሕዝ ፳፯ ፡ ፴፯ ። ራእ ፲፰ ፡ ፲፫) ።

**ሤጥ ፤ (ጣት)** ፤ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ ገንዘብ ፡ ገበር ፡ ለሽያጭ ፡ የሚሰጠው ። ዘብዙኅ ፡ ሤጡ ። ዘእንበለ ፡ ሤጥ ፡፡ ወሀቦ ፡ ሤጦ ፡ ለውእቱ ፡ መካን ፡፡ ሤጠ ፡ ዚአሁ ፡፡ ሤጠ ፡ ግንዘት ፡ (ኢዮ ፴፬ ፡ ፳፱ ፡ መዝ ፡ ፵፫ ። ፩ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፳፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯ ፡ ፵፱) ።

**ምሥያጥ ፤ (ጣት)** ፤ መሸጫ ፡ መሸቀጫ ፡ ገበያ ፡ ሱቅ ፡ መደብር ። ሰብእ ፡ ምሥያጥ ፡፡ ህየ ፡ ይገብሩ ፡ ምሥያጠ ፡፡ ተፀርዐ ፡ ሤጥ ፡ ወምሥያጥ ፡፡ ዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ትመስል ፡ ምሥያጠ ፤ ወዘሉ ፡ ዘዣ ፡ ለይክ ፡ ትረክብ ፡ ውስቴታ ፡፡ ተኣምኖ ፡ በውስተ ፡ ምሥያጣት ፡ (አፈ ፡ ድ ፳ ። ነሐ ፲፫ ፡ ፳ ። ዮሴፍ ። ፊልክ ። ማቴ ፳፫ ፡ ፯) ።

**ምሥያጣዊ** ፤ ገበያኛ ፡ ገበያተኛ ፡ የገበያ ፡ ሰው ፡ ዐጣሪ ፡ ነጋዴ ። ምሥያጣዊ ፡ ዘእንበለ ፡ ንዋይ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አሤጠ ፤ አው ፡ አሥየጠ ፡** አሸጠ ፡ አገበረ ፡ አስገደደ ፡ ለመሸጥ ። ተአመነ ፡ ከመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሥየጠ ፡ በሤጥ ፡ (፲ ፡ መ ፡ ጽ፳ ፡ ፩) ።

**ተሠይጠ ፤** ተሸጠ ፡ ተለወጠ ፡ ተገዛ ፡ ተዋጀ ፡ ዐለፈ ፡ ተሰጠ ፡ ለባለዋጋ ። ተሠይጠ ፡ ዮሴፍ ፡ ወኮነ ፡ ገብረ ። ጥበብ ፡ ኢትሠየጥ ፡ በወርቀ ፡ አፉር ። ይሠየጥኑ ፡ ክቡር ፡ ለሠላሳ ፡ ብሩር ፡ (መገ ፡ ፺፱ ። ኢዮ ፳፰ ፡ ፲፮ ። ይ፣3) ።

**ሥዩጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ይጥ) ፤** የተሸጠ ፡ የተዋጀ ፡ ውጁ ፡ መሸጠ ። አንበ ፡ ሥዩጥ ፡ ለኀጢአት ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ነውር ፡ በሥዩጥ ፡ (ሮሜ፯ ፡ ፲፬ ። ፍ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፯) ።

**ሢጠት ፤** (ሳጥ ፡ ሺ) መሸጥ ፡ አሻሻጥ ፡ ሽጦሽ ። ይሁዳ ፡ መከረ ፡ ለሢጠተ ፡ እግዚእ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተሣየጠ ፤** ተሻሻጠ ፡ ተገበያየ ፡ ተወጃጀ ፡ ርስ ፡ በርሱ ። ዋጀ ፡ ገዛ ፡ ተቀበለ ፡ ከሸያጭ ፡ እጅ ። ተሣየጠ ፡ ብሎ ፡ ዋጀ ፡ ገዛ ፡ ማለት ፡ መሳሸና ፡ ጣፊ ፡ በገገዘእ ፡ ፈንታ ፡ ስላገቡት ፡ እንጂ ፡ ፍችው ፡ ኹሉ ፡ አይደለም ፡ ፍችውስ ፡ የመዠመሪያው ፡ ነው ። ዘይሠይጥ ፡ ከመ ፡ ዘይሣየጥ ። በእንተ ፡ ተሣይጦ ፡ ወሠዩጥ ። በሤጥ ፡ ብዙኅ ፡ እሣየጠከ ። ዘተሣየጠ ፡ ወዘሤጠ ፡ (ኢሳ፳፬ ፡ ፪ ። ፍ፡ ነ ፡ ፴፫ ። ፩ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፳፬ ። ሕዝ፯ ፡ ፲፪) ።

**ተሣያጢ ፤** የተሻሻጠ ፡ የተወጃጀ ። (ገዛኢ) ፡ የሚገዛ ፡ ገዥ ፡ ዋጋ ፡ ሰጪ ። ሠያጢ ፡ ወተሣያጢ ። ሠያጢ ፡ ይሁዳ ፡ ወተሣያጢ ፡ ቀያፋ ። ፍቅረ ፡ ሢመት ፡ አያረት ፡ አዕይንተ ፡ ልቡ ፡ ለተሣያጢ ። ተሣያጤ ፡ ሥጋ ፡ ሐዋት ፡ (ፍ፡ ነ ፡ ፴፫ ። ሲኖዶ ። ፲ ፡ መ ፡ ጽ፳ ፡ ፩ ። ምሳ፳፫ ፡ ፳) ።

**አስተሣየጠ ፤** አሻሻጠ ፡ አሻጠረ ፡ አገበያየ ፡ አዋጀ ፡ አወጃጀ ።

**መስተሣይጥ ፤** የሚያሻሽጥ ፡ አሻሻጭ ፡ ተሻሻጭ ። የሚገዛ ፡ ገዥ ።

**ሠዩ.ም ፤ ሞት ፤ (ሤመ ፡ ይሠይም ፡ ይሚም ። ዕብ ፡ ሢም ። ሱር ፡ ሣም ። ዐረ ፡ ሣመ ፤ አኖረ) ፤** መሾም ፡ መሸለም ፡ ማሠልጠን ፡ መቀደስ ፡ ማክበር ። እሠይመከ ፡ ውሕተ ፡ ዡሉ ፡ ምድር ። ሤሞ ፡ ለዮሴፍ ፡ ዲበ ፡ ዡሉ ፡ ንዋዩ ። አንትሙ ፡ ጳጳሳት ፡ ኢትሢሙ ፡ ዡሎ ፡ ዘረከብክሙ ። ሶበ ፡ ትሠይሞ ፡ ለጳሕል ፡ ወለጽዋዕ ፡ (ዘፍ፵፭ ፡ ፵፩ ። ኩፋ ፡ ፴፱ ። ቀሌ ። ሥር ፡ ቅዳ) ።

—፤ ማስቀመጥ ፡ ማኖር ፡ መምላት ፡ ማሳደር ፡ ማቅረብ ፡ ማዘጋጀት ፡ የምግብ ፡ የልብስ ፡ ለትንቢትም ፡ ሳይቀር ፡ ስጦታ ፡ ለምርት ፡ ይነገራል ። ህየ ፡ ይሠየማ ። ወሤሞ ፡ ህየ ። ሤመ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መንፈሶ ፡ ቅዱሰ ። ሤመ ፡ ውስቴቱ ፡ ምስጢራተ ፡ ብፅዓን ፡ (ቅዳ ፡ ማሩ ። ዘፍ፪ ፡ ፰ ። ኢሳ፷፫ ፡ ፲፩ ። ማር ፡ ይሥሐ ፡ ፮፻) ።

**ሠያሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤** የሚሾም ፡ ሿሚ ፡ አስቀማጭ ፡ አኗሪ ። ሠያሚ ፡ ካህናት ። ሠያሚ ፡ ሕግ ፡ (ሲኖዶ ። ይ፣3 ። አፈ ፡ ይ፴፱) ።

**አሥየመ ፤ አሤመ ፡** አሾመ ፡ ሹመት ፡ አሰጠ ።

**ተሠይመ ፤** ተሾመ ፡ ተቀመጠ ፡ ቀረበ ፡ ተዘጋጀ ። ተሠየምኩ ፡ ንጉሠ ፡ በላዕሌሆሙ ። ተሠይመ ፡ ማሕጼ ፡ ዲበ ፡ ሥርወ ፡ ዕፀው ፡ (መገ ፡ ፬ ። ማቴ፫ ፡ ፲) ። ኮነ ፡ ተሰማየ ፡ ተጸውዐ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተሠይመ ፡ ይባል ፡ የመሳሽ ፡ በሕተት ፡ ነው ። ዘሎቱ ፡ ተሠየምኩ ፡ ዐዋዴ ። ጳውሎስ ፡ ዘተሠይመ ፡ ሐዋርያሁ ፡ (ቆላ፩ ፡ ፳፫ ። ፩ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፩) ።

**ሥዩም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ይምት) ፤** የተሾመ ፡ ሹም ፡ ኀቡር ፡ ድልው ፡ ቅምጥ ፡ ዝግጁ ። ሥዩማነ ፡ ቤተ ፡ እግዚ ። ሊቃነ ፡ ሊጳጳሳት ፡ ወባዕዳን ፡ ሥዩማን ። በእንተ ፡ ተስፋክሙ ፡ ዘሥዩም ፡ በሰማያት ። እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ሥዩም ፡ ሲርቀቶሙ ፡ ወለተንሥኦቶሙ ፡ (ግብ፲፬ ፡ ፳ ። ዲድ ፡ ፯ ። ቆላ፩ ፡ ፭ ። ሉቃ፪ ፡ ፴፬) ።

**ሢመት ፤ (ታት) ፤** መሾም ፡ ሺሚ ፡ ወይም ፡ ተሺሚ ፡ መኾን ፡ ሹምነት ፡ አሺሺም ። ሹመት ፡ ሥልጣን ፡ ማዕርግ ። ጸሎተ ፡ ሢመት ። ከመ ፡ ኢይንሣእ ፡ ሢመተከ ። በመዋዕለ ፡ ሢመትከ ። ይሰዐር ፡ እምሢመቱ ። ሢመተ ፡ ክህነት ። አቀምክምሙ ፡ በበ ፡ ሢመቶሙ ። ሢመታት ፡ ወሥልጣናት ፡ (ኪዳ ። ሚሊ፲፬ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ ማንጀ ። ቀሌ ። ቅዳ ። ነሐ፲፫ ፡ ፲፩ ። ዲድ) ።

**መሥየምት ፤ (ብ ፡ መሣይምት ፤** መሾሚያ ፡ ማኖሪያ ፡ ማስቀመጫ ፡ መከተቻ ፡ ጋን ፡ ሣጥን ፡ ጐታ ፡ ቅርጫት ፡ ጋዘና ፡ እንቅብ ፡ አገልግል ፡ መሶብ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ቢሮነ ፡ ሕፃን ፡ በውስተ ፡ መሥየምት ፡ (ስንክ ፡ የካ፫ ። ማርቆ ፡ ፵፫ ። ሉቃ፱ ፡ ፲፯) ።

**ምሥያም ፤ (ማት) ፤** መሺሚያ ፡ መኖሪያ ፡ ማኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ስፍራ ። እስ ፡ ይትቀነዩ ፡ በውስተ ፡ ምሥያሞሙ ። ምሥያመ ፡ አስሐትዮ ። መዝገበ ፡ ረድኤት ። ወምሥያመ ፡ ትፍሥሕት ፡ (፩ዜና ፡ ፳፯ ፡ ፩ ። ኢዮ፴፰ ፡ ፳፬ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ። በመሥየምት ፡ ፈንታ ፡ ምሥያም ፡ ይባል ፤ ፍችው ፡ ፩ ፡ ነው ። ኀብስተ ፡ ምሥያም ። ማእዳተ ፡ ዘምሥያም ። ዕጣነ ፡ ምሥያም ። ኀብአቶ ፡ እሙ ፡ ለሕፃን ፡ ውስተ ፡ ምሥያም ፡ ወሰቀለቶ ፡ ላዕለ ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ (፩ዜና ፡ ፳፫ ፡ ፳፱ ። ፳፰ ፡ ፲፯ ። ፪ዜና ፡ ፲፫ ፡ ፲፩ ። ስንክ ፡ ማንጀ ። መኒ፲፱) ።

**ተሣየመ ፡** ተሺሺመ ፡ ርስ ፡ በርሱ ።

**አስተሣየመ ፡** አሺሺመ ፡ አቀማመጠ ።

**መስተሣይም ፤** የሚሺሺም ፡ ተሺሺሚ ። የሚያሺሹም ፡ አሺሺሚ ።

**ሤመት ፤ አው ፡ ሠይመት ፡ (ሤመ) ፡** ሽመት ፡ እኽል ፡ ገዛ ።

**ተሠይመት ፡ (ተሠይመ) ፡** ተሸመተ ፡ ተገዛ ፡ እኽሉ ። ሸመየ ፡ ሠለጠነ ፡ ከበረ ፡ ተሾመ ፡ ሹም ፡ ኾነ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ የሾመውና ፡ የመረጠው ፡ ያከበረው ፡ ሳይኖር ፡ (ዕብ፳ ፡ ፬ ፡ ፳) ። መምህራን ፡ ግን ፡ ቀና ፡ ተመቀኘ ፡ ይሉታል ፡ ዘይቤው ፡ አይደለም ። አኮ ፡ ተሠይሚተነ ፡ ዲበ ፡ ብእሲ ፡ ዘንትናገር ፡ እስመ ፡ መፍትው ፡ ንሕዝዘነ ፡ እስመ ፡ እኁ ፡ ማሰነ ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፩) ።

**ሠዩን ፤ ኖት ፤ (ሤን ፡ ይሠይን ፡ ይሢን ። ዐረ ፡ ሽነ ፤ አሳደፈ ። ዕብ ፡ ሀሽቴን ፡ ሽነ) ፤** መሸኘት ፤ ሽኛታ ፡ መኸን ። መሸን ፡ መሽናት ፤ ማውጣት ፡ ማፍሰስ ፡ ፈር ፡ ዠረር ፡ ፏርቅ ፡ ማድረግ ። ዘይሠይን ፤ ላዕለ ፤ መንጸሩ ። ዘይሠይን ፤ ማየ ። በሊዕየ ፤ እኵስሕ ፤ ወበትይየ ፤ እሠይን ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፫ ። ቍድር ። ፈሳሽ) ።

**ሠያን ፤ ሠያኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት ፤ ዮንት) ፤** የሚሸኝ ፤ ሽኛታ ። የሸነ ፡ የሚሸን ፡ ሽኚ ፡ ሽንታም ፤ ሽንት ፡ የማይቋጥር ፤ ፈሪ ።

**ሥንት ፤ (ዕብ ፡ ሻይን ፤ ሺታን) ፤** ሽንት ፤ የሽንት ፡ ውሃ ፡ ፈሳሽ ፤ የመጠጥ ፡ ሐሠር ፡ ከሆድ ፡ የሚወጣ ። እኂዘ ፤ ሥንት ። ይስተዩ ፤ ሥንቶሙ ፤ (ፈላስ ፡ ገ፴፯ ። ኢሳ፴፮ ፡ ፲፪ ። ፬ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፯) ። ባማርኛ ፡ ማን ፡ የቍጥር ፡ ጥያቄ ፡ ይኾናል ፤ ስንት ፡ በቁሙ ፡ ምን ፡ ይኽል ። ስፍንና ፡ እስፍንቱን ፡ እይ ።

**መሥየንት ፤ (ዐረ ፡ መሻነት) ፤** ፈኛ ፡ የሽንት ፡ ቋት ፡ ከረጢት ፤ መታቈሪያው ።

**ሤርዮ ፤ ዮት ፤ (ሤረየ ፡ ይሤሪ ፡ ይሤሪ) ፤** ማሤር ፤ ሤራ ፡ መቍረጥ ፡ ስክተተኝና ፡ ተስክተየን ፡ እይ ። ማስል ፡ ማቅለም ፤ ቀለም ፡ ማግባት ፤ መንከር ፡ ማራስ ፡ ማጥለቅ ፡ መዝፈቅ ። ቀብዖ ፤ በሕጕሬ ፤ ወሤረዮ ። ለእመ ፤ ተፀገለ ፤ ልብሰ ፤ ጸዐዳ ፤ ወሤረዮ ። ፀምር ፤ ዘተጠምዐ ፤ በሤርዮ ። ሤርዩዮን ፤ ለመላትሒኪ ፤ በአንብዕ ፤ (ጥበ፲፫ ፡ ፲፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፰ ። መጽ ፡ ምስ ። ማር ፡ ይሥ፲፫) ።

**ሤራዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ረይት) ፤** የሚያሤር ፤ ሤረኛ ፡ ዐይመኛ ። የሚያልል ፡ ዐሳይ ፤ ቀለም ፡ አግቢ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

**ተሤረየ ፤** ተሤረ ፤ ተሤረበት ። ታለለ ፡ ቀለም ፡ ገባ ፤ ተንከረ ። ኵሉ ፤ ከዳንየ ፤ ተሤረየ ። ከመ ፤ ይሤረያ ፤ እገሪከ ፤ በደም ። ተሤረየ ፤ ሥጋሁ ፤ እምጠለ ፤ ሰማይ ። ግብር ፤ ዘበተሤርዮ ፤ ይዌልጥ ፤ ኅብሮሙ ። እምድኅረ ፤ ተሤረየ ፤ ነፍሳቲነ ፤ በምግባረ ፤ ኀጢአት ፤ (ኢሳ፷፫ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፷፯ ። ዳን፬ ፡ ፴ ። ጥበ፲፰ ፡ ፱ ። አፈ ፡ ተ፲፪) ።

**ሢሩይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሬት ፡ ርይት) ፤** የታለለ ፡ ቀለም ፡ የገባ ፡ ያደረ ፡ የተዥጎረጎረ ። ሢሩያን ፤ በምሕረትከ ፤ አንጽሐ ፤ (ኪዳ) ።

**ሥርየት ፤** ማለል ፤ መታለል ፡ መንከር ፡ ማደፍ ፡ (ዘዐ፳፰ ፡ ፳ ። ፴፫ ፡ ፳፰) ።

**ሢራይ ፤ (ያት ። ሱር ፡ ሺራኢ) ፤** ጥሩ ፡ ልብስ ፡ ሐር ፤ ፀምር ፡ ከታን ፡ ቀለም ፡ የገባ ፡ የታለለ ። አልባሲሆን ፤ ዘሤላት ፤ ወሢራይ ። ሟልቡባን ፤ በሢራይት ፤ (ኢሳ፫ ፡ ፳፯—፳፫ ። መጽ ፡ ምስ) ። በሢራይ ፡ ፈንታ ፡ ሢርየን ፡ ሢራ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ ሯ ፡ ነው ፡ (ገድ ፡ አዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፲፪) ። ሢራ ፡ ዐይማ ፡ ክፋ ፡ ዱሰት ።

**ሠርዮ ፤** ቀለም ፡ ስባቅ ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ። ሠርዮ ፤ ምስለ ፤ ፀምር ፤ (ቄር) ።

**ሠከረ ፤ (ሠኪር ። ዕብ ፡ ሣካር) ፤** ተከራየ ፤ በቍርጥ ፡ ገባ ፡ ተዋዋለ ፡ የከብት ፡ የጕልበት ፡ የመሣሪያ ። በሰበንና ፡ በሰየን ፡ እይ ፤ አሽክር ፡ ማለት ፤ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ሸከረ ፤ ሸከሬ ፡ ኾነ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ተሠከረ ፤** ተገዛ ፤ ለከራይ ፡ ተሰጠ ።

**ሥኩር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ክርት) ፤** የተገዛ ፡ ግገዛ ፡ የተከራየ ፡ የከራይ ። መሳጺ ፤ ሥክርት ፤ (ኢሳ፯ ፡ ፳) ። ምሳሌ ፡ የተባለች ፡ ሰይፍ ፡ ናት ፡ (ሕገ፳ ፡ ፩) ። የሻከረ ፡ ሻክራ ።

**ሠከረ ፤—ሰከረ ፤—ሰኪር ፡ ሰክረ ።**

**ሠለበ ፤—ገፈፈ ፤—ሰሊብ ፡ ሰለበ ።**

**ሠሌዳ ፤—በቁሙ ፤—ሰለደ ።**

**ሠሊጥ ፤ ጠት ፤ (ሠለጠ ፡ ይሠልጥ ፡ ይሥልጥ ። ዕብ ፡ ሻላጥ ። ሱር ፡ ሽላጥ ። ዐረ ፡ ሠሊጠ) ፤** የጠፈረ ፡ ሰርዌ ። መሠልጠን ፤ ጌታ ፡ መኾን ፤ ማየል ፡ መበርታት ፤ ኀይል ፡ ክሂል ፤ መብት ፡ ማግኘት ፡ እንደ ፡ ወደዱ ፡ ለማድረግ ። ዐበይቶሙ ፤ ይሠልጡ ፤ ላዕሌሆሙ ። ወአልቦ ፤ ዘእሬሲ ፤ ይሠለጥ ፤ በላዕሌየ ፤ መንፈሂ ፤ (ማቴ፳ ፡ ፳፭ ። ሽቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፪) ። በሠለጠ ፡ ፈንታ ፡ ተሠለጠ ፡ ተሠሰጠ ፡ ተሠልጠን ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። አግብርት ፤ ተሠልጡ ፤ ላዕሌነ ። ወሶበ ፤ ርእዩ ፤ ከመ ፤ ዘቲ ፤ ኀጢአት ፤ ተሠልጠት ፤ ላዕለ ፤ ብዙኃን ። ዘይሤለጥ ፤ በመንፈሱ ። ለዘይሤለጥ ፤ ላዕሌከ ። ተሠለጥከ ፤ በሥጋከ ፤ (ሰቈ፭ ፡ ፰ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፫ ። ምሳ፲፯ ፡ ፴፪ ። መክ፲ ፡ ፬ ። ሢራሳ፳ ፡ ፲፬) ።

**ሠላጢ ፤ መሠልጥ ፤ ሥሉጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ልጥ) ፤** በቁሙ ፤ የሠለጠን ፡ ሥልጡን ፤ ሠልጣና ፤ ሥልጣኔ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ። ሥሉጥ ፤ ውእቱ ፤ በዘፈቀደ ። ንጉሥ ፤ ሥሉጥ ። ርእዩ ፤ ከመ ፤ ኵሉ ፤ ሥሉጥ ፤ ይሕየውኒ ፤ ወይእመንኒ ። አንትሙ ፤ ሥሉጣን ፤ ላዕለ ፤ ኵሉ ፤ ሕዝብ ፤ (ዮዲ፫ ፡ ፲፭ ። መክ፰ ፡ ፬ ። ኪዳ ። ዲድ ፡ ፯ ። ራእ፲፭ ፡ ፯) ።

**አሥለጠ ፤ አው ፡ አሠለጠ ፤** አሠለጠነ ፤ ሾመ ፡ አነገሠ ፤ ሥልጣን ፡ ሰጠ ። አሥለጠ ፤ ከመ ፤ ይብላዕ ። ወኢያሥለጠ ። ርድአኒ ፤ ለወጢኖቱ ፤ ወአሠልጠኒ ፤ ካዕበ ፤ ለፈጽሞቱ ፤ (ማር ፡ ይሥ፳፪ ፡ ፩ ። መክ፮ ፡ ፪ ። አርጋ) ።

**አሠለጥ ፤ (ዐማርኛ) ፤** የቤት ፡ ውልድ ፡ ቤት ፡ አባት ፡ አሠልጣኝ ።

**አሠልጠነ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ የአሥለጠ ፡ ድርብ ። ዳበ ፤ ዝ ፤ ኵሉ ፤ አሠልጠኖ ። እግዚ ፤ አሠልጠኖሙ ፤ ለሮም ፤ በዝ ፤ አዝማን ፤ (ኩፋ ፡ ፲ ። ዮሴፍ ። አርጋ ፡ ፩ ። ቅዳ) ።

**ሥልጣኔ ፤** በቁሙ ፡ መሠልጠን ፤ ማሠልጠን ፤ አሠለጣጠን ፤ ሥልጥንና ፡ ሥልጡንነት ፡ ጠፍተኛነት ፡ በሥራ ፡ በነገር ።

**ሥልጣን ፤ (ናት)** ፤ በቁሙ ፡ ችሎት ፡ መብት ፡ ሹመት ፡ ጌትነት ። ለሕይወት ፡ ወለሞት ፡ ሥልጣን ፡ ብከ ። ከመ ፡ ዘሥልጣን ፡ ቦ ። ወሀበሙ ፡ ሥልጣነ ። መኳንንት ፡ ወእለ ፡ በሥልጣናት ፡ (ሞብ ፲፯ ፡ ፲፫ ። ማቴ፯ ፡ ፳፱ ። ፲ ፡ ፩ ። ቅዳ ፡ ኪዳ) ።

—፤ ግዥ ፡ አለቃ ፡ ንጉሥ ፡ መልአክ ። ሥልጣናት ፡ ሰማይ ። ሥልጣናት ፡ ወዙሉ ፡ ኀይል ። መናብርት ፡ ወሥልጣናት ፡ (ሐዋሮሮ ፡ ፳ ። ፩ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፳፱ ። ዲ.ድ) ።

**ሥልጣን ፤ (ብ ፡ ሠላጢን)** ፤ ሹል ፡ ስል ፡ መውጊያ ፡ የንፌጋት ፡ የብረት ፡ ሽብዳ ፡ ፀንነሰ ፡ ምሣር ፡ ሬዋ ። ሠላጤ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡ ኩሉም ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ።

**ሥልጣናዊ** ፤ ንጉሣዊ ፡ የንጉሥ ፡ የጳጳስ ፡ ወገን ፤ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ። የሹመት ፡ ሥራ ፡ ዳኝነት ። አቅሞተ ፡ ውሳንያት ፡ ሥልጣናውያት ፡ ዘፍትሕ ፡ (ፋ ፡ ን ፡ ፲፱) ።

**ሠለጠ ፤—ፈጸመ ፡ ጨረሰ ፤—ሰልጦ ፡ ሰለጠ ።**

**ሠሊክ ፤—ሽቱ ፤—ሰሊኅ ፡ ኖት ።**

**ሠለለ ፤—በቁሙ ፤—ሰሊል ፡ ሰለ ፤ ሰለለ ።**

**ሠለመ ፤-በቁሙ ፤ ሰላምታ ፡ ሰጠ ፤-ሰሊም ፡ ሰለመ ።**

**ሠለሠ ፤—ሦስት ፡ አደረገ ፤—ሠልሰ ፡ ሠለሰ ።**

**ሠለፈ ፤—በቁሙ ፤—ሰሊፍ ፡ ሰለፈ ።**

**ሠሊቅ ፤ ቆት ፤ (ሠለቀ ፡ ይሠልቅ ፡ ይሥልቅ)** ፤ መሠለቅ ፡ ማላም ፡ ማይቀቅ ።

**ሠለቀ ፤ (ዕብ ፡ ቃሌስ)** ፤ ዘበተ ፡ አፌዘ ፡ አላገጠ ፤ በነገር ፡ መታ ፡ ሠለቀ ፤ ተሣለቀ ። ምስጢሩ ፡ እንደ ፡ ጤፍ ፡ ደቂቅ ፡ ልዝብነትና ፡ ለስላስነት ፡ ነው ፡ ማቅና ፡ ጨዎት ፡ ስላለበት ።

**ሠለቀ ፤ (ዕብ ፡ ሳሌቅ)** ፤ ላጠ ፡ መለጠ ፡ ሸለቀቀ ፤ ገፈፈ ፡ አንሣ ፡ አራቀ ። ሸልቋቋ ፡ ሸለቆ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**አሥለቀ** ፤ አሠለቀ ፡ አዘበተ ፡ አስላጠ ፡ አስመለጠ ።

**ተሠልቀ** ፤ ተሠለቀ ፡ መሣለቂያ ፡ ኾነ ፡ በስድብ ፡ ተላጠ ።

**ተሣለቀ ፤ (ተደራራጊ)** ፤ በቁሙ ፤ ተሠላለቀ ፡ ተዘባበተ ፡ ተሜጣወተ ፡ ርስ ፡ በርሱ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ተደራራጊ ፡ አንቀጽ ፡ አድራጊነትም ፡ ስላለው ፡ በሠለቀ ፡ ፈንታ ፡ እንዳማርኛው ፡ ተሣለቀ ፡ ይላል ፤ አብዝቶ ፡ መላልሶ ፡ ለማለት ፡ ምስለና ፡ ላዕለ ፡ በ ፡ ይሰማሙታል ። ኢትሣለቅ ፡ ምስለ ፡ እብድ ። ኢይሣለቅ ፡ ግሙራ ፡ ምስለ ፡ ሕፃናት ፡ ወኢይዘፍን ። ተሣሊቆሙ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሰሰብዎ ። ንሰየ ፡ ሄሮድስ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይሣለቅ ፡ ቦቱ ፡ (ሚራጅ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ጥር፳፱ ። ማቴ፳፯ ፡ ፴፩ ። ዮሴፍ) ።

**አስተሣለቀ** ፤ አሣለቀ ፡ አዘባበተ ፡ አጨዋወተ ።

**መስተሣልቅ ፤ (ቅት ፡ ቃን ፡ ቃት)** ፤ የሚሣለቅ ፡ የሚያሣልቅ ፡ አላጋጭ ፡ ተሣላቂ ። መስተሣልቅ ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ። ወመስተሣልቃን ፡ ይኬንንዎሙ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፰ ፡ ፪ ። ኢሳ፫ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፩) ።

**ሥላቅ ፤ (ቃት)** ፤ በቁሙ ፡ ማቅ ፡ ጨዎት ፡ ስግጥ ፡ ቧልት ፡ ዋዛ ፡ ፈዘዘ ፡ ዘበት ፡ ዝበታ ፡ ወዘበሬታ ። ነገረ ፡ ሥላቅ ። ሠሐቀ ፡ ወሥላቀ ፡ ክንክዎሙ ፡ (ሚራጅ፫ ፡ ፲፫ ። ኢዮ፲፯ ፡ ፯) ።

**ሥልቅ** ፤ ስሙ ፡ ሀገር ፡ በማዳይ ፡ የምትባል ፡ የባቢሎን ፡ ክፍል ፡ (ፋ ፡ ን ፡ ፱) ።

**ሠልሰ ፤ ሰት ፤ (ሠለሰ ፡ ይሜልስ ፡ ይሠልስ ። ዕብ ፡ ሻሌሽ)** ፤ መሠለስ ፡ ሦስት ፡ ማድረግ ፡ ከሦስት ፡ መክፈል ፡ ሦስት ፡ ማለት ። ይቤሎሙ ፡ ሠልሱ ፡ ወሠልሱ ። ንሜልስ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ ስብሐተ ። ለዋሕድ ፡ አምላክ ፡ እንዘ ፡ በአካል ፡ ይሜልሶ ፡ (፫ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፴፬ ። ኪዳ ። ስንክ ፡ ግንጽ፯) ።

**ሠላሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት)** ፤ የሠለሰ ፡ የሚሠልስ ፡ ሠላሽ ፡ ሦስት ፡ አድራጊ ።

**አሠለሰ** ፤ በቁሙ ፤ አሠገረ ፡ ሦስት ፡ አስደረገ ፡ ሦስት ፡ አሰኘ ።

**መሠልስ ፤ (ስት ፡ ሳን ፡ ሳት)** ፤ የሚሠልስ ፡ የሚያሠልስ ፡ አሠላሽ ።

**ተሠለሰ** ፤ ተሦሰተ ፡ ሦስት ፡ ኾነ ፡ ፫ ፡ ተባለ ፡ ፫ኛ ፡ ኾነ ። እግዚ ፡ ዘይሜለስ ፡ በአካሉ ። በከመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ይትነበር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስኒ ፡ ይሜለስ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ስብሐቲሁ ፡ (ደራሲ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ሥሉስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ልስት)** ፤ በቁሙ ፤ የተሠለሰ ፡ ሦስት ፡ የኾነ ፤ ሦስቲዮ ፡ ሥሉሱ ። ፈትል ፡ ሥሉስ ። ቅዱስ ፡ ሥሉስ ። ሥሉሰ ፡ አካል ፡ (መክ፬ ፡ ፲፪ ። ኪዳ ። ደራሲ) ።

**ሥላሴ** ፤ መሠለስ ፡ ሥለሳ ። ሦስትነት ፡ ሦስት ፡ መኾን ። ንሰ ፡ ሀለዉ ፡ ሠለስቱ ፡ ሊቃነ ፡ ሰቆቃሳት ፡ ይቄድሶ ፡ እግዚእነ ፡ ለሥላሴሆሙ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ። በቁሙ ፡ የአካላት ፡ ስም ፡ ሦስቶቹ ፡ ሦስቱ ፡ ሦስቲዮ ፡ ሦስት ፡ ብቻ ፡ ቍጥራቸውና ፡ ሕጻጽ ፡ የሌለው ፡ ዘላለማዊ ፡ ሦስት ። ባንድም ፡ በብዙም ፡ በወንድም ፡ በሴትም ፡ ይነገራል ። ዓዲ ፡ ናቄርብ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ አኰቴተ ፡ ዘለዓለም ፡ ሥላሴ ። አሰብሐ ፡ ሥላሴ ፡ ቀተለ ፡ መስተቃትል ፡ መጽሐፍ ። ሥላሴ ፡ እንተ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ሀለወት ፡ ወኢትትፈለጥ ፡ በመዋዕል ፡ (ቅዳ ፡ ኪዳ ። ደራሲ ። ተረ ፡ ቄር፲፱) ።



ሥላሴ ፡

**ትሥልስት** ፤ ሦስትነት ፡ ሦስቲዮሽ ፡ ጉንጉን ፡ ኅብረብ ፡ ሦስት ፡ እጅ ። ተዋሕዶትክሙ ፡ ኢይትነገር ፡ ወትሥልስትክሙ ፡ ኢይትሌሎ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘይፈልጦ ፡ ለእግዚ ፡ እምትሥልስቱ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ። ትርብዕት ፡ ርቡዓን ፡ ኪሩቤል ፡ ወትሥልስተ ፡ አምላክ ፡ ዋሕድ ፡ (አረጋ ፡ ድጓ ። ያዕ ፡ ዘእል ። ደራሲ ። ቅዳ ፡ ዲዮ) ።

**ተሥላስ** ፤ (ሳት) ፤ የደረብ ፡ ደርብ ፡ ፪ኛ ፡ ክፍል ፡ ሰገነት ፡ መልዕልተ ፡ መልዕልት ። እምተሥላስ ፡ ቤታ ። አኖኅዎ ፡ ጥቀ ፡ ሐነጸሙ ፡ መልዕልቴሁ ፡ ተሥላስ ፡ ልዑለ ፡ እምዕፀ ። ጸድፈ ፡ እምተሥላስ ፡ (በኀነ ፡ መስጽሐ ። ዮሴፍ ። ግብሐ ፡ ፱) ።

**ሠላስ** ፤ የቍጥር ፡ ስም ፡ ሦስት ፤ በኍለትና ፡ ባራት ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ። ወንድና ፡ ሴት ፡ ያስተባብራል ፡ መደቡ ፡ ግን ፡ የሴት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሠላስ ፡ አኃቲሆሙ ፡ ምስሌሆሙ ። ወሀሎ ፡ ህየ ፡ ሠላስ ፡ መራዕየ ፡ አባግዕ ። ሠላስ ፡ መዋዕል ። በእንተ ፡ ሠላስ ፡ ኃጢአቶሙ ። ሠላስ ፡ አርዳኢሁ ፡ (ኢዮ ፡ ፱ ። ዘፍጥ ፡ ፪ ። ሳ ፡ ፲፪ ። ዓሞ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ ጥቅምት) ።

**ሠለስ(ት)ቱ** ፤ ሦስት ፡ ሦስቱ ፡ ሦስተኛው ። ሠለስቱ ፡ አቅርንት ። በእሉ ፡ ሠለስቱ ። እንዘ ፡ አሐዱ ፡ ሠለስቱ ፡ (ዳን ፡ ፯ ። ሚል ፡ ፳፭ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**ሠለስት** ፤ የዜማ ፡ ቃል ፡ ትምርት ፡ ሦስተኛ ፡ ክፍል ፡ ከውዳሴ ፡ ማርያም ።

**ሠሉስ** ፤ የዕለት ፡ ስምና ፡ ቅጽል ፡ ማግሰኞ ፡ ማግሰኞ ፡ ሰኞ ፡ የሰኞ ፡ ማግስት ፡ የእሑድ ፡ ማልስት ፡ በሰኞና ፡ በረቡ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ዕለት ። ቅጽልም ፡ ሲኾን ፡ ሦስት ፡ ሦስተኛ ፡ ያሰኛል ። ምሕዋረ ፡ ሠሉስ ፡ ዕለት ። እስከ ፡ ሠሉስ ፡ መዋዕል ። በሠሉስ ፡ ዕለት ፡ አንሥአ ። ሠሉስየ ፡ ዮም ፡ (ዮና ፡ ፫ ። አስቴ ፡ ፲ ። ዮሐ ፡ ፲፱ ። ሉቃ ፡ ፴ ፡ ፲፫) ። ሲበዛም ፡ ሠሉሳት ፡ ያሰኛል ።

**ሣልስ** ፤ (ስት) ፤ ሦስተኛ ፡ ሦስት ፡ በሰቲያ ፡ ወዲያ ። ናሁ ፡ ሣልሰሙ ፡ ዮም ፡ እንዘ ፡ ይጸንሑኒ ። አመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ ከብካብ ፡ ኮነ ። እስከ ፡ ሣልስ ፡ ወራብዕ ፡ ትውልድ ። ትማልመኒ ፡ ወሣልስተኒ ፡ (ማርቆ ፡ ፰ ። ዮሐ ፡ ፪ ። ዘፀ ፡ ፳ ። ሐዊና ፡ ፲፫ ፡ ፱) ።

**ሣልሳዊ** ፤ **አው ፡ ሣልሳይ** ፤ (ዊት ፡ ዪት ፡ ሲት) ፤ ሦስተኛ ፡ ከሦስት ፡ አንድ ፡ ሚስ ። በሣልሳዊ ፡ ልደት ፡ እምአቡሁ ፡ ሀሰወነ ፡ ተዘምዶ ፡ ምስሌሁ ። በእንተ ፡ ተዋስቦ ፡ ሣልሲት ። ሣልሲተ ፡ ሲን ፡ (ቅኔ ። ፊ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፯ ። ሕዝቅኤ ፡ ፲፱) ።

**ሣልሲት** ፤ የቍጥር ፡ መደብ ፡ የኪክሮስ ፡ ፫ኛ ። አንዱ ፡ ሣልሲት ፡ ፳ ፡ ራብዒት ፡ ይኾናል ፡ ኪክሮስን ፡ እዩ ፡ (አቡሻ ፡ ፲፩) ።

**ሥልስ** ፤ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡ ክፍል ፡ ሦስት ፡ ብቻ ። ወሰገደ ፡ ሎቱ ፡ ሥልስ ። ትክሕደኒ ፡ ሥልስ ። ዘዘርዐ ፡ ሲሮስ ፡ ያአቱ ፡ ሥልስ ፡ (ሳሙ ፡ ፳ ፡ ማቴ ። ማር ፲፬ ፡ ፸፪ ። ኢሳ ፡ ፲) ። በቁሙ ፡ አሳት ፡ ያልነካው ፡ መባያ ፡ እንደ ፡ ሰላጣ ፡ ያለ ፡ ሹሮና ፡ ድልኽ ፡ ቅባኑማ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡ ሦስትነት ፡ ያለው ፡ (ዐማርኛ) ።

**አሥልስት** ፤ ሥልሶች ፡ ሦስት ፡ እጆች ፡ ክፍሎች ፡ ጊዜዎች ። ሠለስተ ፡ አሥልስተ ፡ ዲናር ፡ (ስንክ ፡ ኅዳር) ።

**መሥለስ** ፤ (ብ ፡ መሣልስ) ፤ መሠለሻ ፡ ሦስት ፡ ማድረጊያ ፡ ከሦስት ፡ መክፈያ ፡ ወይም ፡ ሦስቱን ፡ እጅ ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፡ ሚዛን ፡ መስፈርት ፡ የሥልስ ፡ ወፍት ፡ (ዘፍጥ ፡ ፯ ። ማቴ ፲፫ ፡ ፴፫ ። ሉቃ ፲፫ ፡ ፳፩) ።

**መሥልስት** ፤ ሦስት ፡ ወገን ፡ ሦስት ፡ ክፍል ፡ ታላቅ ፡ ሠረገላ ፡ ሦስት ፡ ፈረሶች ፡ የሚስቡት ። ወትክፍል ፡ ደወሰ ፡ ምድርከ ፡ መሥልስተ ። መስተጽዕናን ፡ በመሥልስት ፡ (ዘዳ ፲፱ ፡ ፫ ። ዘፀ ፲፬ ፡ ፯) ። ሲዘረዘርና ፡ ሲናበብ ፡ ግን ፡ ሦስተኛ ፡ ያሰኛል ። ወመሥልስታ ፡ ለፀሓይ ፡ ያውዕዮሙ ፡ ለአድባር ፡ (ሲራ ፵፫ ፡ ፬) ። መውቂቱ ፡ ቀትር ፡ በኃዋ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሦስተኛ ነቱም ፡ ከነበብ ፡ ከጸዳል ፡ ከንግህ ፡ ከሠለስት ፡ ከክረምት ፡ ከመዐው ፡ ይባላል ።

**ምሥልስት** ፤ (ሰብ ፡ ምሥላሶት) ፤ ሣልሳት ፡ ሣልሳውያት ፡ ሦስተኞች ፡ ሦስተኛ ፡ ክፍሎች ፡ ደርቦች ፡ ተሥላሶች ። እስመ ፡ ምሥልስት ፡ እማንቱ ፡ (ሕዝቅ ፵፪ ፡ ፯) ።

**ሠላሳ** ፤ (ሰብ ፡ ሸሎሽም) ፤ በቁሙ ፡ የአኃዝና ፡ የቍጥር ፡ ስም ፡ (ሰ—፴) ፫ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ፡ ወይም ፡ ፲ ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ። መዋዕለ ፡ ላሕ ፡ ለሙት ፡ የሚሰቀስበት ። (ተረት) ፤ በሠላሳ ፡ እግርኽን ፡ አታንግሣ ፡ ባርባ ፡ በረኽ ፡ ግባ ። ኢየዐርግ ፡ እምሠላሳ ፡ ወኢይወርድ ፡ እምሠላሳ ፡ ወትረ ፡ ይከውን ፡ ሠላሳ ፡ (መር ፡ ስዉ) ።

**ሣሉሲም** ፤ (ሰብ ፡ ሻሊሺም) ፤ ኀያላን ፡ ያርበኞች ፡ አለቆች ፡ የጦር ፡ ሰዎች ፡ ሦስተኛ ፡ ማዕርግ ፡ ያላቸው ፡ ወይም ፡ ኀይላቸው ፡ ሦስቲዮሽ ፡ የኾኑ ፡ የተጉነኹን ። ባለብልዮች ፡ ግን ፡ ሣሊስ ፡ ይሉታል ። ርእሰ ፡ ሣሉሲም ፡ (ነገሥ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭) ።

**ሥልሳ** ፤ (ስሳ ፡ ስድሳ ፤ ስደስ) ፤ ፪ ፡ ሠላሳ ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ ኻያ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሥላት** ፡—**ለግጥ ፡ ፊገዘ** ፤—**ሰልቶ ፡ ሰለተ** ።

**ሠመከ ፡—ተጠጋ ፤—ሰሚክ ፡ ሰመከ ።**

**ሠመነ ፡—ስምንት ፡ አደረገ ፤—ሰምኖ ፡ ሰመነ ።**

**ሠምዐ ፤—ሰማ ፡ መሰከረ ፡—ሰሚዕ ፡ ሰምዐ ።**

**ሠምዕ ፡ (ዓት ፡፡ ዐረ ፡ ሸመዐ)** ፤ ሠም ፡ ጢፉ ፡ የማር ፡ ሰፈፉ ፡ ንጥሩ ፡ ማግሩ ፡ ልጥልጡ ፡ ነጋሪቱ ፤ ፋናው ፡ መብራቱ ። ለእመ ፡ በረቀ ፡ ምንተኒ ፡ እምንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ አው ፡ ሠምዐ ፤ አው ፡ ዘይተ ፡፡ ኒይ ፡ ከመ ፡ ሠምዕ ፡፡ መኀትው ፡ ብሩሃት ፡ ወሠምዓት ፡ ንጹሓት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ። ማንዘ ፡፡ አፈ ፡ ተ፱) ።

**ሠምዐ ፤** ሠም ፡ ኾነ ፡ ጠፈ ፡ ቀሰጠ ፡ ነጠረ ። ረጋ ፡ ጸና ፡ ተጋገረ ።

**ሠምረ ፡—አፈራ ፡ በጀ ፤—ሰሚር ፡ ሰምረ ።**

**ሠሚር ፤ ሮት ፡ (ሠምረ ፡ ይሠምር ፡ ይሥመር ፡፡ ዕብ ፡ ሻማር ፤ ጠበቀ)** ፤ መሥመር ፡ መውደድ ፡ ቍርጥ ፡ ፈቃድ ፡ ማድረግ ፡ እሺ ፡ በጎ ፡ ይኹን ፡ ሠመርኩ ፡ ማለት ፤ ልመናን ፡ ነገርን ፡ ወይ ፡ መቀበል ። እመ ፡ ሠምረ ፡ እግዚ ፡፡ ሥመር ፡ እግዚኦ ፡ ከመ ፡ ታድኅነኒ ፡፡ ዘትጸልእ ፡ ሰርእስከ ፡ ጽላእ ፡ ሰካልእከ ፡ ወሥመር ፡ ሰሰብእ ፡ ዘትሠምሮ ፡ ሰርእስከ ፡፡ ነዋ ፡ ሠምረ ፡ በዝንቱ ፡ እምድኅረ ፡ ሰአልዎ ፡ ሎቱ ፡፡ መሥዋዕተ ፡ አቤል ፡ ዘሠምረ ፡ (ያዕ፱ ፡ ፲፭ ። መገ ፡ ፴፱ ። ፈላስ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ፡፡ ድጓ) ።

**ሠማሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት)** ፤ የሚሠምር ፡ የሚወድ ፡ ወዳጅ ። ንሕነ ፡ ሽልነ ፡ መዋትያን ፡ ዘጸላኢነ ፡ እምነነ ፡ ወሠማሪ ፡ (ማንዘ) ።

**አሥመረ ፤** ሠመርኩ ፡ አሰኘ ፡ አሶደደ ፡ አስፈቀደ ። አገሰገሰ ፡ ደስ ፡ አሰኘ ። አሥመሮ ፡ ሔኖክ ፡ ለእግዚ ፡፡ አ ፡ ንጉሥ ፡ ያሥምርከ ፡ ምክርየ ፡፡ ኢያሠምሮ ፡ ለጻድቅ ፡ እኩይ ፡ ምንትኒ ፡ (ዘፍ፭ ፡ ፳፬ ። ዳን፬ ፡ ፳፬ ። ምሳ፲፪ ፡ ፳፩) ። አሠመረ ፡ አስነበረ ፡ ሠራ ፡ ቀጸ ፡ የብራና ፡ የድጕስ ፡ የኅብስት ፡ መሥፈሪያ ።

**መሥመሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት)** ፤ የሚያሠምር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ አገልጋይ ። መሥመሬ ፡ እግዚ ፡፡ ይከውኑ ፡ መሥመርያነ ፡ ንቡሁ ፡፡ መሥመሪት ፡ ቅዱሳን ፡ (ጥበ፱ ፡ ፲ ። ዮሴፍ ። አጥል) ።

**ተሠምረ ፤** ተሠመረ ፡ ተዘጋጀ ። ተወደደ ፡ ተፈቀደ ።

**ሥሙር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ምርት)** ፤ የተሠመረ ፡ የተወደደ ፡ ውብ ፡ መልካም ። ሥሙር ፡ ወኅሩይ ፡፡ ሥሙር ፡ ለንጉሥ ፡፡ ዐጽቀ ፡ በሰስ ፡ ሥሙር ፡ ጥቀ ፡፡ ምድር ፡ ሥምርት ፡ (ሮሜ፲፪ ፡ ፩ ። ምሳ፲፬ ፡ ፫ ። ኢሳ፷፪ ፡ ፬ ። ሚል፫ ፡ ፲፪) ።

**ሥምረት ፤ (ታት)** ፤ መውደድ ፡ መወደድ ፡ አወዳደድ ፡ ውድነት ፡ እሺታ ፡ ውዴታ ፡ ውድ ፡ ቍርጥ ፡ ፈቃድ ። ገበርኩ ፡ ቅድሜከ ፡ ሥምረትከ ፡፡ ሥምረቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ላዕሌነ ፡፡ እንበለ ፡ ፈቃዱ ፡ አው ፡ በሥምረቱ ፡ ልቡ ፡፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ቦቱ ፡ ሥምረት ፡ (ኢሳ፴፰ ፡ ፫ ። ባሮክ፬ ፡ ፬ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፱) ።

**ተሣመረ ፤** ተዋደደ ፡ ተስማማ ፡ ተባበረ ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ ኾነ ። ኢይኩን ፡ ተዋስቦ ፡ ዘእንበለ ፡ በተሣምሮቶሙ ፡ ለክልኤሆሙ ፡፡ ወተሣመሩ ፡ በምክረ ፡ ዚአሁ ፡፡ ተሣማሪነ ፡ ምስለ ፡ አካኪዮስ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፱ ። ዘሁ፭ ፡ ፴፪ ፡ ፫ ። ተረ ፡ ቄርሎ) ።

**መሥመር ፤ (ራት)** ፤ በቁሙ ፡ ማሥመሪያ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ የተካከለ ፡ ዘንግ ፡ እሩት ፡ ገጽ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ወፍጣፋ ፡ ባለ ፬ ፡ ገጽ ። መሥመር ፡ የወደቀበት ፡ የተጋደመበት ፡ ወሰፈው ፡ ርዳሱ ፡ የኼደበት ፡ መዘረያው ፡ ትልሙ ፡ (አቡሻ ፡ ፶፮) ። የመሥመር ፡ አሠራር ፡ ጥበቡ ፡ የመጣ ፡ ከሙግዚ ፡ ቅጠልና ፡ ከንስት ፡ ከኮባ ፡ ከጕናጕና ፡ ነው ፡ ይባላል ።

**ሠመርመር ፤** መወደድ ፡ ያለው ፡ ኀብር ፡ ቀይና ፡ ጥቍር ፡ ያንዘጣ ፡ ዐር ። **ያፍ ፡ ዘይሰመይ ፡ ሠመርመር ፡ ዘባኑ ፡ ጸሊም ፡ ክርሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ቀይሕ ፡ . . . ወሶበ ፡ ይመጽእ ፡ አንበጣ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ፀዘም ፡ ይመጽእ ፡ እሙንቱ ፡ አዕዋፍ ፡ ሠመርመር ፡ ወይቀትልዎሙ ፡ ለእሙንቱ ፡ አናብጥ ፡ ወይሀጕልዎሙ** ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ፺፳፩) ።

**ሠንአ ፤—ገጠመ ፡ ተስማማ ፤—ሰኒእ ፡ ሰንአ ።**

(ጥን) **ሠንዮ ፤ ዮት ፤ (ሠነየ ፡ ይሤኒ ፡ ይሠኒ ፡፡ ዐረ ፡ ሠነዐ ፤ ሐሠነ ፡፡ ዕብ ፡ ሻናህ ፤ መልኩን ፡ ለወጠ ፤ ሌላ ፡ ኾነ)** ፤ ማማር ፡ መዋብ ፡ ሐዲስ ፡ መልክ ፡ ማውጣት ፡ ጥሩ ፡ ውብ ፡ ደም ፡ ግቡ ፡ መኾን ፡ በመልክና ፡ በጌጥ ፡ ደስ ፡ መሰኘት ። ሠባሕኪ ፡ ወሠናይኪ ፡ ጥቀ ፡ ፈድፋደ ፡፡ ሕሥምት ፡ እንተ ፡ ሠናየት ፡፡ ይሤኒ ፡ ሳሕዩ ፡፡ ሠናየት ፡ ራእዮሙ ፡ (ሕዝ፲፯ ፡ ፲፫ ። ማሕ፯ ፡ ፯ ። አርጋ ፡ ፩ ። መገ ፡ ፸፱ ። ዳን፩ ፡ ፲፭ ። መሳ፲፭ ፡ ፲፫) ።

—፤ መብሰጥ ፡ መሻል ፡ ደግ ፡ ደኅና ፡ መልካም ፡ መኾን ፡ የጠባይ ። ቦ ፡ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ትሤኒ ፡ እምብእሲት ፡፡ ዘይሤኒ ፡ ወይፋ ፡፡ ይሠርሕክሙ ፡ በእንተ ፡ ትሤኒ ፡፡ በእከየ ፡ ገጽ ፡ ይሤኒ ፡ ልብ ፡ (ሢራ፴፯ ፡ ፳፯ ። ዮሐ፲ ፡ ፲ ። ጦቢ፯ ፡ ፲፩ ። መክ፯ ፡ ፬) ።

**ተሠነየ ፤** ተጌጠ ፡ ተሸለመ ፡ ተዘጋጀ ፡ ሰማማር ። ወይእቲሰ ፡ ተሠነየት ፡ በጽሉ ፡፡ ተሠነየት ፡ ጥቀ ፡፡ ሰምንት ፡ ኢትሰረገው ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኢትሤነይ ፡ (አስቴ ፡ ፭ ። ዮዲ፲ ፡ ፬ ። ፲፪ ፡ ፲፭ ። ፀንገ ፡ ፱ ፡ ፀ ። አፈ ፡ ተ፳፰) ።

**ሥኑይ ፤** ያማረ ፡ የተዋበ ፡ ውብ ። ሥኑይ ፡ ወርጉፍ ፡ በማኅላት ፡፡ ወከመ ፡ ገ ፡ ቤቱ ፡ ሥኑይ ፡ ወአ

ዳም ፡፡ ወሚመትክሙኒ ፡ ድልው ፡ ወሥኑይ ፡ (አስ ቴር ፡ ፮ ። መቃ ፡ ፫፥ ። ቄር ፡ ፩) ። በሥኑይ ፡ ፈንታ ፡ መሠንይ ፡ ይላል ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። መሠንየ ፡ እንስሳ ፡፡ መሠንየ ፡ ማእሰር ፡፡ መሠንየ ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ (ሕንገ ፡ ፲፭ ፡ ፱ ። ሚራ፵፪ ፡ ፲፮ ። አርጋ ፡ ፭) ።

**ሠናይ** ፤ (ይት ፡ ያን ፡ ያት) ፤ መልካም ፡ ውብ ፤ ደግ ፡ በጎ ፤ ቅን ፤ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፤ የመልክ ፡ የጠባይ ። ሠናይ ፡ ለርእይ ፡፡ ሠናይት ፡ በራእይኪ ፡፡ ምግባር ፡ ሠናይ ፡፡ ሠናይት ፡ ለሠናያን ፡ ተፈጥረት ፡፡ ሠናይ ፡ ልብ ። መክፈልት ፡ ሠናይ ፡፡ ዐስብ ፡ ሠናይ ፡፡ ዜና ፡ ሠናይ ፡፡ ቃል ፡ ሠናይ ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፱ ። ዮዲ፲፩ ፡ ፳፫ ። ማቴ፭ ፡ ፲፮ ። ሚራ፴፱ ፡ ፳፱ ። ሉቃ፰ ፡ ፲፭ ። ፲ ፡ ፵፪ ። መክ፱ ፡ ፱ ። ሮሜ፲ ፡ ፲፭ ። መዝ ፡ ፵፬) ። ሠናይ ፡ ቅጽልና ፡ በቂ ፡ እየኾን ፡ እንዳወራረዱ ፡ በብዙ ፡ ዐማርኛ ፡ ይፈታል ፡ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ ከመልካምነት ፡ አይወጣም ። ውስተ ፡ እደ ፡ ሀሰወት ፡ ሠናይቶሙ ፡ ቢል ፤ ብሰል ፡ በረከት ፡ ድልብ ፡ ገንዘብ ፡ ይሰኛል ፡ (ኢዮ፳፩ ፡ ፲፮) ።

**ምሥናይ** ፤ ማማሪያ ፡ መዋቢያ ፤ መልካም ፡ ቦታ ፡ ምቹ ፡ ስፍራ ። ጌሴም ፡ ምሥናይሃ ፡ ለምድረ ፡ ግብጽ ፡፡ ንበር ፡ ዝየ ፡ ውስተ ፡ ምሥናይ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፰ ። ያዕ፪ ፡ ፫) ።

**ሠኔ** ፤ (ቅብጥ ፡ ፓዎኒ ። ዕብ ፡ ሲዋን) ፤ የወር ፡ ስም ፡ ዐሥረኛ ፡ ወር ፤ በግብጽና ፡ በኢትዮጵያ ። ሠናየ ፡ ዘርዕ ፡ ወርን ፡ ዘርዕ ፡ ሠናይ ፡ ማለት ፡ ነው ። (ተረት) ፡ ለምኝ ፡ ሠኔ ፡ በጋው ፡ መስከረም ፡ ክረምቱ ። ጋላም ፡ ዘር ፡ ቢል ፡ ሠኝ ፡ ይላል ።

**ሥን** ፤ (ናት) ፤ መልክ ፡ ውበት ፤ ደም ፡ ግባት ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፡ ጥራት ፡ ጥዳት ፡ ጠፍታ ። በሥንከ ፡ ወበላሕይከ ፡፡ ሥኑ ፡ ለብሐቲሁ ፡፡ ሥኑ ፡ ዜና ፡ ዘለዓለም ፡፡ ሥና ፡ ለብእሲት ፡፡ ኢትዘኀር ፡ በሥኑ ፡ አልባሲከ ፡ (መዝ ፡ ፵፬ ። ፵፱ ። ሚራ፱ ፡ ፰ ። ፲፭ ፡ ፱) ።

**ሥን** ፤ መልካምነት ፤ ደግነት ፡ በጎነት ። ሥኑ ፡ ምግባሩ ፡፡ ሥኑ ፡ ግዕዙ ፡ (ሚራ፯ ፡ ፲፰ ። ያዕ፫ ፡ ፲፫) ።

**ሥን** ፤ ፍጥረት ፡ አዝርዕት ፡ አትክልት ፤ እንስሳት ፡ አራዊት ። ምስጢሩ ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፡ ከለው ፡ ይገባል ። እሳት ፡ አኀለቀ ፡ ሥኑ ፡ ገዳም ፡፡ ወሥኑ ፡ ገዳም ፡ ኀቤየ ፡ ሀሎ ፡ (ዮኤ፩ ፡ ፲፱ና ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፵፱) ።

**አሠነየ** ፤ አሳመረ ፤ አስማመረ ፡ አስጌጠ ፡ አበጀ ፡ አዘጋጀ ፤ መልካም ፡ አደረገ ። ኢያሠኑይኩ ፡ ጽሒፈ ፡፡ አሠነየ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእሱ ፡ ወጽሕሞ ፡፡ ከመ ፡ ያሠኒ ፡ ሎቱ ፡ አማእኒሁ ፡፡ ያሜንዩ ፡ መሥዋዕተ ፡ ለልዑል ፡፡ ለንእስኒ ፡ ወለዐቢይኒ ፡ አሠኒ ፡ ግዕዘከ ፡ ወቃለከ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ ። ዮሴፍ ። አቡሻ ፡ ፶ ። ሚራ፶ ፡ ፲፬ ። ፳፱ ፡ ፳፫) ። በአሠነየ ፡ ፈንታ ፡ አስተ(ሠ)ማነየ ፡ ይላል ፡ አያስኝም ። ከመ ፡ ያስተሣኒ ፡ ምብዓሎ ፡፡ ወታስተሣንዩ ፡ ዝኅሮሙ ፡ ለጻድቃን ፡፡ መስተሠንይ ፡ (ሚራ፴፰ ፡ ፳፰ ። ማቴ፳፫ ፡ ፳፱ ። ማርቆ ፡ ፲፱ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳፫) ።

**መሠንይ** ፤ የሚያሳምር ፤ የሚያበጅ ፡ አስጊያጭ ። መሠንያኒ ፡ ሐተታ ፡ (አዋል) ።

**ሠኑይ** ፤—ኹለት ፤—ሰንይ ፡ ሰኑየ ።

**ሠነነ** ፤—አሾለ ፤—ሰኒን ፡ ሰነነ ።

**ሠነቀ** ፤ ቆት ፤ (ሠነቀ ፡ ይሠንቅ ፡ ይሥንቅ ። ዐረ ፡ ሽነቀ ፤ ዐነቀ ። ሱር ፡ ሥናቅ ፤ ዐጣ ፡ ተቸገረ) ፤ መሠነቅ ፡ ሥንቅ ፡ መያዝ ፤ መውሰድ ፤ ስመንገድ ፡ የሚኾንን ፡ ነገር ፡ ማከት ፤ ማሰናዳት ። ኢሠነቀ ፡ እምንዋይከ ፡ ዘእንበለ ፡ መግነዝ ፡ (ግንዝ ። ኢያ፱ ፡ ፪ ። ማር፱ ፡ ፰) ።

**ሥንቅ** ፤ በቁሙ ፡ የመንገድ ፡ መጓሪያ ፡ ልብስ ፡ ምግብ ፤ ገንዘብ ። ወአስተዳለወ ፡ ሥንቀ ፡ ለፍኖት ፡፡ ወሀቦ ፡ ክልኤተ ፡ ምእተ ፡ መካልየ ፡ ወርቅ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሥንቀ ፡ ለፍኖት ፡፡ ቊርባን ፡ ቅዱስ ፡ ሥንቀ ፡ ነፍስ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፪ ። ጦቢ፭ ፡ ፲፮ ። ቃሪ ፡ ነገ ፡ ሬ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፳) ።

**አሥነቀ** ፤ (ጥሠ) አሠነቀ ፤ ሥንቅ ፡ ሰጠ ፡ አሲያዘ ። ሥንቀ ፡ ታሠንቆ ፡፡ ወአሥነቀ ፡ ለሾሎ ፡ ለብእሴ ፡፡ አሥነቁኒ ፡ (ዘዳ፲፭ ፡ ፲፬ ። ዮዲ፱ ፡ ፲፫ ። ግብ፳፰ ፡ ፲) ።

**መሥነቂ** ፤ (ንቅ) ፤ ሥንቅ ፡ የሚያሲዝ ፡ የሚሰጥ ።

**መሥነቅ** ፤ (ቅት) ፤ ሥንቅ ፡ መያዣ ፡ መቋጠሪያ ፤ መክተቻ ፤ አቅማዳ ፡ ኪስ ፡ ከረጢት ። ዘአልቦቱ ፡ መሥነቀ ፡ ኀብስት ፡፡ መሥነቅት ፡ አሐቲ ፡ ትኩኑ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ምሳ፩ ፡ ፲፬) ።

**መሣንቅ** ፤ (ቅት) ፤ የሥንቅ ፡ መያዣዎች ፡ አቅማዳች ። አምጽአ ፡ ዝኩ ፡ መሣንቀ ፡ በማኅተሞን ፡፡ ወጾሩ ፡ መሣንቀ ፡ ብሉየ ። መሣንቂነ ፡ (ጦቢ፱ ፡ ፭ ። ኢያ፱ ፡ ፬ ። ሕንገ ፡ ፱ ፡ ፯) ። መሣንቅ ፡ ብሉ ፡ ገዙ ፤ ብሉየ ፡ ማለት ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ዘእንበለ ፡ ይቁም ፡ አ.ድባር ፡ (መዝ ፡ ፻፲፱) ።

**ሠሥዖ** ፤ ዖት ፤ (ሠሥዐ ፡ ይሜሥዕ ፡ ይሠሥዕ ። ዐረ ፡ ሸሠዐ) ፤ መሣሣት ፤ መራራቅ ፡ ዘር ፡ ዘር ፡ ማለት ፤ የቡቃያ ፡ የዘር ፤ ያታክልት ፡ የጠጕር ።

—፤ መሣሣት ፡ መርቀቅ ፤ ሥሥ ፡ ረቂቅ ፡ መኾን ፡ (ዐማርኛ) ።

—፤ መሠሠት ፡ መንፈግ ፤ ሆዳም ፡ ሥሥታም ፡ መኾን ። ኢትሠሥዕ ፡ ለሾሉ ፡ መብልዕ ፡፡ ካህናት ፡ ዘሠሥዕት ፡ ነፍሶሙ ፡ በረኀብ ፡ ርኩስ ፡፡ ይሜሥዑ ፡ ለበሊዕ ፡ (ሚራ፴፯ ፡ ፳፱ ። ቀኖ ፡ ኒቅ ። ዲድ ፡ ፺ ። ፪ተሰ ፡ ፫ ፡ ፺) ።

**ሥሡዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ሥዕት) ፤ የሣሣ ፡ ሥሡ ፤ ሆዳም ፡ ሥሥታም ። ብእሲ ፡ ሥሡዕ ፡ ዘኢይጸግብ ፡፡ ሥሡዕ ፡ ልብ ፡፡ ሥሡዓን ፡ በባዕደን ፡ (ሚራ፴፱ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፫ ። መቃ) ።

**ሥሣዒ** ፤ መሣሣት ፤ መሠሠት ፡ ሥሥ ፡ ሥሡ ፡ መኾን ፤ ሥሥት ፤ ሥሡነት ።

**ሥሥዕት** ፤ በቁሙ ፤ ሥሥት ፡ ንፍገት ፡ ሆዳምነት ። እመ ፡ ኢይፈሪፍድ ፡ ሥሥዕትከ ፡፡ ምርዓት ፡ ወዝሙት ፡ ወሥሥዕት ፡፡ ያበዝኆ ፡ ለኀብጥ ፡ ሥሥ

ዕት ፤ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ቀተሎሙ ፡ ሥሥዕት ፡ (አፈ ፡ ተ፪ ። ቀሌ ። ሚሬ፴፮ ፡ ፴፯ ፡ ፴፰) ።

**አሠሥዐ** ፤ አማማ ፤ አሠሠተ ፤ ሆዳም ፡ ሥሥታም ፡ አደረገ ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**ሥዕይ ፤ ዮት ፤ (ሥዕየ ፤ ሠዐየ ፡ ይሥዒ ፡ ይሥዐይ)** ፤ ማዝሬት ፤ መበተን ፤ መመሸን ፤ የምርት ። ማጥፋት ፡ ማባከን ፤ የገንዘብ ። ከመ ፡ ፮ፋስ ፡ ይሥዕዮሙ ። እለ ፡ ጼና ፡ ጢስ ፡ ፍጉገ ፡ ይሥዕዩ ። ትሰድዶሙ ፡ በቃልከ ፡ ወትሥዕዮሙ ፡ በመንፈስ ፡ ኀይልከ ፡ (ጥበ፳፩ ፡ ፳፱ ። ፲፩ ፡ ፲፱ና ፡ ፳፩) ።

**መሥዔ ፤ (ብ ፡ መሣዕይ)** ፤ ማዝሪያ ፤ መበተኛ ፡ መንሽ ፤ ወይም ፡ መሽን ፤ ላይዳ ። መሥዔሆሙ ፡ ለረሲዓን ፤ ንጉሥ ፡ ጠቢብ ። ዘመሥዔ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ (ምሳ፳ ፡ ፳፮ ። ማቴ፫ ፡ ፲፪) ።



መሥዔ ፡

**መሥዕ ፤—በቁሙ ፤—መስዕ ።**

**ሠዐለ ፤—ለመነ ፤—ስኢል ፡ ሰአለ ።**

**ሠዐለ ፤—ሳለ ፤—ሰዐለ ።**

**ሥዒል ፤ ሎት ፤ (ሠዐለ ፡ ይሥዕል ፡ ይሥዐል ። ዕብ ፡ ያጻር ። ዐረ ፡ ጸወረ)** ፤ መሳል ፤ ማስመሰል ፤ መንደፍ ፡ መበገር ። መፍጠር ፤ ማስገኘት ፤ መቅረጽ ። ንሣእ ፡ ግንፋለ ፡ ወሠዐል ፡ ውስቴቱ ፡ ሀገረ ፡ ኢየሩሳሌም ። ናሁ ፡ በእደውየ ፡ ሠዐልኩ ፡ አረፋቲኪ ። አዘዘ ፡ ይግበሩ ፡ ጻሕለ ፡ ዘወርቅ ፡ ወይሥዐሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሥዕለ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ፡ በምልኣ ። ለዛቲ ፡ ሥዕል ፡ ሦዐላ ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌላዊ ፤ ሣለ ፡ (ሕዝ፬ ፡ ፩ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፲፮ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ መስ፲) ። ዘይሥዕሎሙ ፡ ለሕፃናት ፡ በውስተ ፡ ማሕፀን ። እግዚ ፡ ፈጠረ ፡ ሥጋክሙ ፡ ወመንፈስክሙ ፤ ወሠዐለክሙ ፡ በክሂሎቱ ፡ (ድጓ ። ዮሴፍ) ።

**ሠዓሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት)** ፤ የሚሥል ፡ የሚፈጥር ፤ ሣይ ፡ ሣዪ ፤ ፈጣሪ ። ሠዓሊና ፡ እንዘ ፡ እሬኢ ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ። (ግጥም ፤ ሚስቱን ፡ ሠዓሊ ፡ የቀማው) ፤ ባላየው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተኝቼ ፡ ሌሊት ፤ ሚስቴን ፡ ሳይ ፡ በወሰዳት ። (የሠዓሊው ፡ መልስ) ፤ እንቅልፋምንትኸን ፡ ይልቅ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹ ፤ ብሥል ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ነኝ ፡ ምን ፡ መስዬኽ ፡ አለኹ ። ሠዓሌ ፡ ሕፃናት ፡ (ቅዳ ። ድጓ) ።

**አሥዐለ** ፤ አሣለ ፤ ሥዕል ፡ አሠራ ። ሄሮድስ ፡ አሥዐለ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ሥዕሎ ፤ ወሥዐለ ፡ ኵሎሙ ፡ ነገሥት ፡ እለ ፡ ሞእሙ ። በእደ ፡ ማርያም ፡ አሥዐለ ፡ ሥዕለ ፡ ማርያም ፡ ወሥዕለ ፡ ኢየሱስ ፡ በእደ ፡ አፍርንጅ ፡ (ዮሴፍ ። ታሪ ፡ ነገ) ።

**መሥዕል ፤ (ል ት ፡ ላን ፡ ላት)** ፤ የሚሥል ፡ የሚያሥል ፡ ሣይ ፡ አሣይ ። መሥዐለ ፡ ሕፃናት ። መሥዐል ፡ ዘትያጥሮን ፡ (መጽ ፡ ምስ ። አዋል) ።

**ተሥዕለ** ፤ ተሣለ ፤ ተቀረጸ ፡ ተፈጠረ ። አሠረ ፡ እዴሁ ፡ ውስተ ፡ ኵሉሕ ፡ ተሥዐለ ። ከመ ፡ ዘተሥዐለ ፡ በእደ ፡ ኬንያ ። በአርኣያ ፡ እግዚ ፡ ተሥዐለ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ። ተሥዐለ ፡ በማሕፀኑ ፡ ሙላድ ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፰ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ሥዑል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ዕልት)** ፤ የተሣለ ፤ የተቀረጸ ፤ የተፈጠረ ፡ ፍጡር ። ሥዑል ፡ ዲበ ፡ አረፍት ። ታስተርእዮሙ ፡ ሥዕልታ ። ህየ ፡ ሀሉ ፡ መልክአ ፡ ገጹ ፡ ሥዑል ። እለ ፡ ሥዑላን ፡ በእደ ፡ እሳት ፡ (ሕዝ፰ ፡ ፲ ። ጥበ፫ ፡ ፲፯ ። ቅዳ ። ሳታት) ።

**ሥዕል ፤ (ላት)** ፤ በቁሙ ፤ መልክ ፤ የመልክ ፡ ጥላ ፡ አምሳል ፤ ንድፍ ፡ ቢጋር ፤ በውሃ ፡ በመጽሔት ፤ በጥልፍ ፡ በስፌት ፤ ወይም ፡ በቀለም ፡ በወረቀት ፡ ገዝፎ ፡ ተጥፎ ፤ ከጽቡር ፡ ከእብን ፡ ከዕፅ ፡ ከማዕድን ፡ ታንጦ ፡ ተቀርጦ ፤ ተሸልሞ ፡ አጊጦ ፡ የሚታይ ፤ የሚዳሰስ ፡ ነገር ። ሥዕለ ፡ ኪሩብ ። ሥዕለ ፡ ቤት ። ሥዕለ ፡ ጣዖት ። ሥዕላት ፡ ወምስላት ። ይረቅሙ ፡ ሥዕላ ፡ ዲበ ፡ አልባሲሆሙ ። አስተርአየ ፡ በአየረ ፡ ሰማይ ፡ ሥዕለ ፡ መስተጽዕናን ፡ በአፍራስ ፡ እሳት ፡ (፪ነገ ፡ ፮ ፡ ፳፱ ። ሕዝ፳፫ ፡ ፲፬ ። ዲድ ፡ ፳፭ ። አፈ ፡ ድ፲፪ ። ዮሴፍ) ።

**ሣዕሥዐ ፤—ተብ ፡ ቀለጠፈ ፤—ወሣኢ ፡ ወሥአ ፤ ሣእሣእ ።**

**ሥዒዕ ፤ ዖት ፤ (ሠዕዐ ፡ ይሥዕዕ ፡ ይሥዐዕ ። ዐረ ፡ ሸዐ ፤ ነቃ ፤ ተበተነ)** ፤ መግፈፍ ፤ መቅረፍ ፤ ማብነን ፡ መበተን ፤ ለማጥራት ፡ ለመግለጥ ፤ የዐይን ፡ የብሌን ። ሠዕዮን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ተሥዕዐ** ፤ ተገፈፈ ፤ በነነ ፤ ተበተነ ። ተሥዐዐ ፡ እምአዕይንቲሁ ፡ ከመ ፡ ዘማሬት ። ወተሥዐዐ ፡ እምብንተ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ዝኩ ፡ ጢስ ፡ (ግብ፱ ፡ ፲፰ ። ጦቢ ፲፩ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ መስ፲፮) ።

**ሥዓዕ** ፤ ግፋፊ ፤ ግልፋፊ ፤ ብናኝ ፤ ርጋፊ ። ወድቀ ፡ እምነ ፡ ምጋሁ ፡ ሥዓዐ ፡ ቅርፍት ፡ (አዋል) ።

**ሠዐረ ፤—ሻረ ፤—ስዒር ፡ ሰዐረ ።**

**ሥዒር ፤ ሮት ፤ (ሥዕረ ፡ ይሥዕር ፡ ይሥዐር ። ዕብ ፡ ሣዐር ፡ ራደ ፡ ታወከ)** ፤ መብቀል ፤ ሡቃይ ፡ መኾን ፤ መለምለም ፤ ማደግ ። እምነ ፡ ዝናም ፡ ይሥዕር ፡ ሐመልማል ፡ (፪ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፬) ።


—፤ መሻር ፡ መዳን ፡ መፈወስ ፡ መታደስ ፤ ባለጤና ፡ መኾን ፤ የቍስል ፡ የደዌ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሥዑር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ዕርት)** ፤ የሻረ ፤ የዳነ ። የበቀለ ፤ የለመለመ ፡ ለምለም ፤ ሣርማ ፡ ሣራም ፤ ምቹ ፡ ቦታ ። ብሔር ፡ ሥዑር ። መካን ፡ ሥዑር ፡ (መገ፤ ፡ ፳፪ ። ኢሳ፵ ፡ ፳፫ ። ግንዘ) ። በሥዑር ፡ ፈንታ ፡ መሥዐር ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ።

**ሥዕርት ፤ (ታት ። ዕብ ፡ ሤዓር ፤ ሣዐር ። ሱር ፡ ሣዕራ ፤ ሥዓርታ ። ዐረ ፡ ሸዕር ፤ ሸዕ**

ረት) ፤ ጠጕር ፤ የሥጋ ፡ ማር ፤ ቀጫጭን ፡ ደቃቅ ፤ በቍርበቱ ፡ ላይ ፡ በገዳ ፡ ጽፍቅ ፡ ኹሉ ፡ የሚበቅል ፤ ራስን ፡ ገላን ፡ የሚሸፍን ፤ የሚያሞቅ ፡ የሚያደምቅ ፤ ጋማ ፡ ጭራ ። በዝኁ ፡ ሥዕርትኪ ። ወኢሐቲ ፡ ሥዕርትነ ። ሥዕርት ፡ ቀጣን ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፯ ። ዲድ ፡ ፳፩ ። ፲፫ ፡ ፴) ።


**መሥዕርት** ፤ ሚደ ፤ የጠጕር ፡ መማሪያ ፤ ማበጠሪያ ። ብርኵማ ፡ የንጨት ፡ ትራስ ። የማንብ ፡ ልባጥ ፤ ጥግ ፡ ጌጥ ፡ (ማሕ፭ ፡ ፲፯) ።



መሥዕርት ፡

**መሣዕርት** ፤ ሚደዎች ፤ ብርኵማዎች ።

**ሣዕር** ፤ ሣር ፤ ቡቃያ ፤ የብር ፡ ያገዳ ፡ እኽል ፤ የሚታጨድ ፡ ኹሉ ፤ ገለባ ፡ ቴሻሻ ፤ ድርቆ ፡ ድርቆሽ ፤ ነፋስ ፡ የሚወስደው ። ወብዙኅ ፡ ሣዕሩ ፡ ለውእቱ ፡ መካን ። ሣዕረ ፡ ምድር ። ሣዕር ፡ ዘያነሥእ ፡ ነፋስ ፡ (ዮሐ፮ ፡ ፲ ። ዘፀ፲ ፡ ፲፪ ። ኢዮ፲፫ ፡ ፳፭) ።



ሣዕር ፡

—፤ የስፌት ፡ ዕቃ ፤ ማለቢያ ፡ ቁኝ ፡ ሞሞ ። የውሃ ፡ የወተት ፡ የማር ፡ የቅቤ ፡ ስልቻ ፤ ጠጕሩ ፡ ያልተነጨ ፡ ያልተመለጠ ፡ ቀርበታ ። ሣዕረ ፡ ማይ ። ሣዕረ ፡ ሐሊብ ፡ (ዘፍ፳፩ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ። መሳ፬ ፡ ፲፱) ።

**አሥዕርት** ፤ ሣሮች ፤ ቡቃዮች ፤ የምድር ፡ ጠጕሮች ፡ (አፈ ፡ ተ፳፯) ።

**ሣዕሮ** ፤ (ትግሬ) ፤ ወገርት ፤ ቅጠሉ ፡ ሣር ፡ የሚመስል ።

**ሥዕር** ፤ **ሥዕርና** ፤ (ዕብ ፡ ሥዖራ ። ዐረ ፡ ሸዒር) ፤ ገብስ ፤ የገብስ ፡ ዐይነት ፡ ኹሉ ፤ ጠመዥ ፡ ሌላውም ።


**ሥርናይ** ፤ (ያት) ፤ ስንዴ ፤ የስንዴ ፡ ወገን ፤ ዐጃ ። አመ ፡ ማእረረ ፡ ሥርናይ ። እክለ ፡ ሥርናይ ። ኅጠተ ፡ ሥርናይ ። ሥርናያት ፡ (ዮዲ፪ ፡ ፳፯ ። ሚራ፴፱ ፡ ፳፯ ። ዮሐ፲፪ ፡ ፳፬ ። ስንክ ፡ ጥር፳፱) ።



ሥርናይ ፡

**ሠፈረ** ፤—በቁሙ ፤—ሰፈር ፡ ሰፈረ ።

**ሣጹን** ፤ (ናት ። ዐረ ፡ ሸጹነት ። ዕብ ፡ ጺንጼኔት ፤ የሸክላ ፡ ዕቃ) ፤ ሣጥን ፤ የልብስ ፡ የገንዘብ ፡ የሬሳ ፡ መክተቻ ፤ ማኖሪያ ፤ የንጨት ፡ የብረት ። እምወርቀ ፡ መበእ ፡ ዘሣጹን ። ገብረት ፡ ክልኤተ ፡ ሣጹነ ፡ ከመ ፡ ሣጹነ ፡ ምዉታን ፡ ወዐጸተ ፡ ውስተ ፡ አሐዱ ፤ ወወልደ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ካልኡ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፰ ። ዮሴፍ) ።



ሣጹን ፡

**ሠጺር** ፤ **ሮት** ፤ (ሠጸረ ፡ ይሤጽር ፡ ይሥጽር ። ዐረ ፡ ሸጸረ ፤ ወጋ ፡ በሳ ። ሸጠረ ፡ ከፈለ) ፤ መሠንጠር ፤ መሠንጠቅ ፤ መክፈል ፡ መፍለጥ ፡ በቁመት ። የጸዐለ ፡ ቤት ፡ ነው ። ዘይሤጽር ፡ ዕፀወ ። ምሣር ፡ ዘይሤጽር ፡ (መክ፲ ፡ ፱ ። ዲድ ፡ ፲) ።

**ተሠጽረ** ፤ ተሠነጠረ ፤ ተሠነጠቀ ፤ ተፈለጠ ። ተሠጽረ ፡ ጕንደ ፡ ጣዖት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ሥጹር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ጽርት) ፤ የተሠነጠረ ፤ የተከፈለ ፤ የተሠነጠቀ ። ሥጹር ፡ ለክልኤ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ሥጻር** ፤ (ራት) ፤ ሥንጣሪ ፤ ሥንጥር ፡ ሥንጣቂ ። ሥጻረ ፡ ዕፀ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ሠቅ** ፤—ማቅ ፤—ሠቂቅ ፡ ሠቀ ።

**ሦቅ** ፤—ደገፈ ፤—ሰዊቅ ፡ ሰቀ ።

**ሠቀየ** ፤—አጠጣ ፤—ሰቅይ ፡ ሰቀየ ።

**ሣቅዮ** ፤ **ዮት** ፤ (ሣቀየ ፡ ይሣቂ ። ዐረ ፡ ሸቂየ ፤ ተጨነቀ) ፤ መሣቀይ ፤ ማስጨነቅ ፤ ማስጠበብ ፤ ባለመከራ ፡ ማድረግ ። እለ ፡ ይሣቅዩኒ ። ሣቀይዋ ፡ ወአልሐውዋ ፡ (መዝ ፡ ፫ ። ራእ፲፰ ፡ ፯) ።

**ሣቃዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤ የሚሣቅይ ፤ መከራ ፡ የሚያሳይ ፤ አስጨናቂ ። ሣቃዪተ ፡ እህጕር ፡ (፭ዕዝ ፡ ፪ ፡ ፳፪) ።

**መሥቂ** ፤ መሣቀያ ፤ መውጊያ ፤ መጠቈሚያ ፤ ሹል ፡ ዕንጨት ፤ ምስማር ። ትግሣጽ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ መሥቂ ፡ ለነፍስ ፡ (ፍ ፡ ነ) ።

**ተሣቀየ** ፤ በቁሙ ፡ ሥቃይ ፡ ተቀበለ ፡ ተጨነቀ ፤ በለመከራ ፡ ኾነ ። ውስተ ፡ ዘነኔ ፡ ደይን ፡ ተሣቀዩ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ (መቃ ፡ ገ፳፱ ። መሳ፯ ፡ ፱ ። ዕብ ፲፫ ፡ ፫) ።

**ሥቁይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ቅይት) ፤ የተሣቀየ ፡ የተጨነቀ ፤ ሥቃይ ፡ የጸናበት ። ወትክውን ፡ ጽዑረ ፡ ወሥቁየ ፡ በዘሉ ፡ መዋዕል ፡ (ዘዳ፳፰ ፡ ፴፫) ።

**ሥቃይ** ፤ (ያት) ፤ በቁሙ ፤ ጭንቅ ፤ መከራ ፡ መቅሠፍት ፤ ማፍ ፡ ቅጣት ። ኣበዝኆ ፡ ለሕማምኪ ፡ ወለሥቃይኪ ። ወሣቀየ ፡ ሰፈርያን ፡ ዐቢየ ፡ ሥቃየ ።

ይትዌገልዎሙ ፤ ወይቀንይዎሙ ፡ በሥቃይ ። ሥቃ ያት ፡ ዘተሴ ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፲፮ ። ፲፱ ፡ ፲፮ ። ዘፀ፩ ፡ ፲፫ና ፡ ፲፬ ። አፈ ፡ ይ፲) ።

**ሣቅዕ** ፤ የምድር ፡ ማእዘን ፡ አንዲት ፡ ክፍል ፡ ምድር ። እስመ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ኢነበሩ ፡ ውስተ ፡ ዘላ ፡ ምድር ፤ ዳእሙ ፡ ውስተ ፡ ሣቅዐ ፡ ዘውእቱ ፡ ማእዘንት ። ውስተ ፡ ዘሎ ፡ ሣቅዐ ፡ (ማቦ ፡ ሕማ ፡ ገ፶ ፱ ። ፻፳) ።

**ሠቂቅ ፤ ቆት ፤ (ሠቀ ፡ ይሠቅቅ ፡ ይሥ ቅቅ ። ዕብ ፡ ሣከሀ)** ፤ ማልበስ ፤ መከደን ፡ መሸፈን ። መሠቀቅ ፤ ማሠቀቅ ።

**ሠቅ ፤ (ቃት ። ዕብ ፡ ሣቅ ። ሱር ፡ ሣ ቃእ ። ቅብጥ ፡ ሦክ)** ፤ በቁሙ ፤ ማቅ ፤ ጕራጅ ፤ ምንጣፍ ፡ ከፀምር ፡ የሚሠራ ። ሸካራ ፤ የሚኰሰኵስ ፤ የሚያሠቅቅ ፤ በሐዘን ፡ ጊዜ ፡ የሚለብሱት ፤ የሚያሸር ጡት ። ታላቅ ፡ ኪስ ፤ ከረጢት ፡ የማቅ ፡ ዐይበት ፤ ዳውላ ። ጠብለልዎ ፡ በሠቅ ። ቍሰሊሆሙ ፡ መዝመዙ ፡ በ ሠቅ ። አልበሱ ፡ ምሥዋዐ ፡ ሠቀ ። ቅንቲ ፡ ሠቀ ። እግዚ ፡ ረበቦ ፡ ከመ ፡ ሠቅ ፡ ለትባዐታይ ፡ ማይ ። ወገ ብረ ፡ ሠቃተ ፡ ምሉአ ፡ ሥዳ ፡ (ስንክ ፡ መስ፳ ። ኅዳ፳ ። ዮዲ፱ ፡ ፲ ። ኢሳ፫ ፡ ፳፬ ። መቃ ፡ ገ፳፰ ። ስንክ ፡ መጋ፰) ።

**ሠቅሠቀ ፤ (ዕብ ፡ ሣበኽ ። ዐረ ፡ ሸበከ)** ፤ ሸክሸከ ፤ ሠፈ ፤ ታታ ፤ በሳሳ ፤ የማቅ ፡ የመግለብ ፤ የወን ፈት ፡ ያይን ፡ ርግብ ፡ ሥራ ። ክዋሬው ፡ በቀር ፡ አንቀጹ ፡ አይገኝም ።

**ተሠቅሠቀ** ፤ ተሸክሸከ ፤ ተታታ ፤ ተበሳሳ ፡ ተን ዳደለ ፡ ሽክሽክ ፡ ኾነ ፤ ሥራው ።

**ሥቅሡቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ሥቅት)** ፤ የተበሳሳ ፡ የተንዳደለ ። መሳክዊሁ ፡ ሥቅሡቅ ፡ እስከ ፡ መልዕልት ። ወመሳክው ፡ ሠናያን ፡ ወሥቅሡቃን ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፮ ። ገድ ፡ ላሊ) ።

**ሠቅሠቅ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ የተበሳሳ ፡ መግለብ ፡ ዐይነ ፡ ርግብ ። በሥቅሡቅ ፡ ፈንታ ፡ ሠቅሠቅ ፡ ይላል ። ወግበር ፡ መጥበስቶ ፡ ሠቅሠቀ ፡ ከመ ፡ መሥገርተ ፡ ዓሣ ፡ ዘብርት ። እንተ ፡ ሠቅሠቅ ፡ ትሬሲ ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፱ ። መሳ፭ ፡ ፳፰) ።

**ሠር ፤—ቁመት ፤—ሰሪር ፡ ሰረረ ።**

**ሦር ፤—በሬ ፤—ሰውሮ ፡ ሰወረ ፡ ሶር ።**

**ሠረበ ፤—ፈሰሰ ፡ ጐረፈ ፤—ሰሪብ ፡ ሰረበ ።**

**ሠሪብ ፤ ቦት ፤ (ሠረበ ፡ ይሠርብ ፡ ይሥ ርብ ። ዐረ ፡ ሸረበ)** ፤ መግግ ፤ መጠጣት ፤ መሳብ ፡ መምጠጥ ። ይሠርብ ፡ ደምየ ። ይሠርባ ፡ ለንጢ አት ፡ ከመ ፡ ስታይ ። ወሠሪቦ ፡ ብሒአ ፡ (ኢዮ፮ ፡ ፱ ። ፲፭ ፡ ፲፮ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፴) ።

**ሠርብ** ፤ መጠጥ ፡ የተበጀ ፡ የተዘጋጀ ። መጽ ሐፍ ፡ ግን ፡ በሠርብ ፡ ፈንታ ፡ አሥራብ ፡ ይላል ፤ ያን ዱን ፡ በብዙ ። አሥራበ ፡ ወይን ፡ አሥራበ ፡ ሶከር ፡ (አ ብጥ ፡ ፫ ። አርጋ ፡ ፭) ።

**ሠራብ ፤ (ዐረ ፡ ሸራብ)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። እመ ፡ አዕረገ ፡ ህየንተ ፡ አሥራበ ፡ ወይን ፤ ሠራበ ፡ ሦ ከር ፡ (አብጥ ፡ ፫) ።

**መሥረብ** ፤ መሳቢያ ፡ መምጠጫ ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፤ እንደ ፡ ሳስቲክ ፤ እንደ ፡ ዋገምት ፤ እንደ ፡ ው ኻዋሞ ፡ (እንደ ፡ ዘንዘና) ፡ ያለ ፤ የመጠጥ ፡ የትንባኾ ፤ ለው ሃም ፡ ይኾናል ። ወመሥረበ ፡ ማይሂ ፡ ተስዓ ፡ ወአ ሐዱ ፡ (ታሪ ፡ አክ) ። መሽረብ ፡ መትረብ ።

**ምሥራብ** ፤ መጠጫ ፤ ብርሌ ፡ ዋንጫ ፤ የመ ሰለው ፡ ኹሉ ። ሰላም ፡ ለሰፍነግ ፤ ለብሒአ ፡ ሐሞት ፡ ምሥራቡ ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፱) ። ለቦታም ፡ ይኾናል ።

**ሣራብ ፤ (ዕብራ)** ፤ ሳማ ፤ ደቢ ፤ ፋጫ ፤ አሰብ ሳቢት ፤ ሲያበዛ ፡ ሣራቢም ፡ ይላል ። እስመ ፡ ሣራቢም ፡ ወአሥዋክ ፡ ምስሌከ ፡ (ሕዝ፪ ፡ ፮) ።

**ሠርጐ ፤—ጌጥ ፤—ሰረገ ፤ ሰርገወ ።**

**ሠርግ ፤ (ዐረ ፡ ሸርግ)** ፤ መስኖ ፡ የመስኖ ፡ ውሃ ፤ ቦዩ ፡ መትረቡ ፡ ቃናሽ ፡ ወንዝ ፤ ኵሬ ፡ ዐዘቅት ።

**አሥራግ** ፤ መስኖዎች ። ዲበ ፡ አሥራጊሆሙ ፡ (ዘፀ፯ ፡ ፲፱ ። ፰ ፡ ፭) ።

**ሠረገ** ፤ በቁሙ ፤ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፡ ተሥረገ ረገ ፡ (ዐማርኛ) ።


**ሠርገል ፤ (ዕብ ፡ ሳርጌል)** ፤ መሥመር ፤ ማሥመሪያ ፤ አራት ፡ ገጽ ፡ ያለው ፤ ቀጥ ፡ ያለ ፤ የተከከለ ፡ ዐፄር ፡ ዘንግ ።

**ሠርገለ** ፤ አጋደመ ፤ መሥመር ፡ ጣለ ፤ አሠ መረ ፤ በርሳስ ፡ በቀለም ፡ በወስፌ ፡ ንደፈ ፡ በገረ ፤ አሰን በረ ፤ የወረቀትና ፡ የብራና ።

**ሠረገላ ፤ (ላት)** ፤ ጋድም ፡ የቤት ፡ የቤት ፡ ክ ሲያን ፡ የፋ ፤ ወይም ፡ ምሰሶው ፡ ዋልታ ፡ ገበታ ፡ ተሸ ክሞ ፡ የሚቆምበት ፡ ተጋዳሚ ፡ መሥመሪዊ ፡ ዕንጨት ። ወገብረ ፡ ዐበይተ ፡ ማኅፈደተ ፡ እምዕፀ ፤ ወታሕ ቴሁ ፡ ሠረገላ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ሠረገላ** ፤ የመንኰራኵር ፡ ዘንግ ፤ ተጋዳሚው ፡ ተሸካሚው ፡ ብረት ፤ መንኰራኵሩ ፡ እንደ ፡ እንዝርት ፡ ራስ ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ የሚሰካበት ፤ የሚዋደድበት ። ከ ርሱ ፡ ጋድምነት ፡ የተነሣ ፡ ላዩም ፡ ታቹም ፤ መላው ፡ ኹ ለንተናው ፤ ፈረሶች ፡ የሚስቡት ፡ ኹሉ ፡ ሠረገላ ፡ ይባ ላል ። ፪ኛም ፡ የኼደበት ፡ መንገድ ፤ መሥመር ፡ መም ስሉ ፡ የሰውን ፡ ምስጢር ፡ ያስረዳል ። ሠረገላ ፡ ሠናይ ። በብዙኅ ፡ ሠረገላየ ። ሰብአ ፡ ሠረገላት ። በሠረገላ ፡ ይረውጹ ፡ (ኢሳ፴፪ ፡ ፲፰ ። ፴፱ ፡ ፳፱ ። ዮዲ፪ ፡ ፳ ። ድን) ። በመንኰራኵርም ፡ ፈንታ ፡ ሠረገላ ፡ ይላል ። ቃለ ፡ ነጐ ድጓድከ ፡ በሠረገላት ፡ (መዝ ፡ ፸፯) ።

**ሠረገላዊ** ፤ ባለሠረገላ ፤ ነጂ ፤ ተቀማጭ ። ሠ ረገላዊ ፡ ዘእንበለ ፡ ድርዐ ፡ ነጂን ፤ ፈረሳዊ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘያገንው ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።



ሠረገላ፡

(ሳ) **ሠሪው ፤ ዎት ፤ (ሠረወ ፡ ይሠሩ ፡ ይሥሩ) ፤ አው ፡ ሠርዎ ፤ ዎት ፤ (ሠረወ ፡ ይሜሩ ፡ ይሠሩ ፡፡ ዕብ ፡ ሻሬሽ) ፤** መንቀል ፤ ከሥር ፡ ማፍለስ ፤ ጨርሶ ፡ ማጥፋት ፤ መደምሰስ ፡፡ ትሥሩ ፡ ወትትክል ፡፡ ይሜሩ ፡ መሠረተ ፡፡ ንዑ ፡ ንሥርዎሙ ፡ እምአሕዛብ ፤ (ኤር፲፩ ፡ ፲ ፡፡ ሚራ፫ ፡ ፲ ፡፡ መዝ ፡ ፹፪) ፡፡

—፤ ሥር ፡ መስደድ ፤ ሥር ፡ መያዝ ፤ ሥሬም ፡ መኾን ፤ መጽደቅ ፤ ከፈር ፡ ከመሬት ፡ መስማማት ፤ የዛፍ ፡ የተክል ፡ የቡቃያ ፡፡

(ሳጥ) **ሠራዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** የሚነቅል ፤ የሚያጠፋ ፤ ነቃይ ፡ አጥፊ ፡፡

**ሠርዌ ፤ (ራዊት ፡፡ ሱር ፡ ሣሪታ) ፤** ጉንድ ፡ ከሥር ፡ የሚወጣ ፤ ዐምድ ፡ ምሰሶ ፤ ወጋግራ ፤ የቤት ፡ ዕንጨት ፤ የድልድይ ፡ ጋድም ፤ መሸጋገሪያ ፡ የመርከብ ፡ ምሰሶ ፤ ደንቀል ፡፡ ንግዝም ፡ ሠርዌ ፡፡ ወናሁ ፡ ሠርዌ ፡፡ ታሕተ ፡ ሠርዌ ፡ ቤትከ ፡፡ ዕፀው ፡ ለጠፈረ ፡ ቤት ፡ ወለሠራዊት ፡፡ ሠርዌ ፡ ተንከተም ፡፡ ሠርዌ ፡ ሐመር ፤ (፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፪ ፡፡ ማቴ፯ ፡ ፬ ፡፡ ሚራ፳፬ ፡ ፳፱ ፡፡ ፪ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፲፩ ፡፡ ፪ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፳፩ ፡፡ አርጋ) ፡፡

**ሠርዌ ፤** ጥራቢ ፤ ጥፊጊ ፤ ጉድፍ ፤ ቂራሮ ፡፡ ከመ ፡ ሠርዌ ፡ ይውዕዩ ፤ (ተረ ፡ ኤር) ፡፡

**ሠርዌ ፤** ሱሕ ፤ ጠርብ ፤ ዝርግ ፡ ጠፍጣፋ ፡ ዕንጨት ፤ ሳንቃ ፡፡ መስመከተ ፡ ሠርዌሁ ፡፡ ሠራዊተ ፡ ዐጺድ ፤ (ዘፀ፳፯ ፡ ፲፯ ፡፡ ፴፱ ፡ ፴) ፡፡

—፤ የሸማኔ ፡ ዕቃ ፤ መጠቅለያው ፡፡ ሠርዌ ፡ አኑምት ፤ (፩ዜና ፡ ፲፩ ፡ ፳፪) ፡፡

**ሥርው ፤ (ዕብ ፡ ሾሬሽ ፡፡ ሱር ፡ ሽርሻ ፡፡ ዐረ ፡ ሢር) ፤** ሥር ፤ ኽርማት ፡፡ ወደዩ ፡ ሥርወ ፡፡ አግዘ ፡ ሥርወ ፡፡ ዘንጺን ፡ ሥርወ ፡ ከማድከ ፡፡ ይሌሊ ፡ ሥርወ ፡ እመሊሊት ፤ (ሉቃ ፡ ዕዝ፰ ፡ ፳፯ ፡፡ ኩፋ ፡ ፴፯ ፡፡ ኢሳ፵፰ ፡ ፱ ፡፡ ዕብ፱ ፡ ፲፪) ፡፡ ሥርውና ፡ ኽርማት ፡ ልዩ ፡ ሲኾን ፤ በመትን ፡ ፈንታ ፡ ሥርው ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡፡

**ሥረው ፤** ሥሮች ፤ ኽርማቶች ፡፡ ይየብስ ፡ ሥረዊሁ ፡፡ እንተ ፡ በምድር ፡ ሥረዊሃ ፤ (ኢዮ፲፰ ፡ ፲፯ ፡፡ ሆሴ፱ ፡ ፲፯) ፡፡

**አሥራው ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፡፡ አዕፀምት ፡ ወአሥራው ፡፡ ደዌ ፡ አደግደገ ፡ ሥጋሁ ፡ ወተዐውቀ ፡ አሥራወ ፡ እንግድዓሁ ፤ (ተረ ፡ ቄር ፡፡ ዮሴፍ) ፡፡

**ሥርው ፤** መዠመሪያ ፤ መንሻ ፤ መውጫ ፤ መብቀያ ፡፡ ሥርዋ ፡ ለጥበብ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚ ፤ (ሚራ፩ ፡ ፳ ፡፡ ጥበ፲፭ ፡ ፫ ፡፡ ፩ጢሞ ፡ ፯ ፡ ፲) ፡፡

—፤ የትንቢት ፡ መንሻ ፡ ትንቢት ፡ አንቀጽ ፡ የሚነሣበቸው ፡ ፊደላት ፤ የተአን ፡፡ የ ፡ ስ፫ ፡ መደብ ፤ ተ ፡ ሳ፰ ፤ አ ፡ ለአን ፤ ነ ፡ ለንሕነ ፡ አሥራወ ፡ ትንቢት ፡ ይባላሉ ፤ የይቤ ንና ፡ የየራሳቸውን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ፡፡

**ሥርው ፤** ዘር ፤ የትውልድ ፡ ምንጭ ፤ ሐረግ ፡፡ ሥርወ ፡ እሴይ ፡፡ ሥርወ ፡ ዳዊት ፡፡ ወአንተሰ ፡ እምነ ፡ ዐቢይ ፡ ሥርው ፡፡ ሥርውኪ ፡ ወዘመድኪ ፤ (ኢሳ፲፩ ፡ ፩፣ ፡ ፲ ፡፡ ራእ፳ ፡ ፳ ፡፡ ጦቢ፳ ፡ ፲፱ ፡፡ ሕዝ፲፮ ፡ ፫) ፡፡

**ሥርው ፤** መዠመሪያ ፡ መጽሐፍ ፤ ሐዲስ ፡ የወጣ ፤ የተፈጠረ ፤ ረቂቅ ፤ መዝገብ ፤ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፤ ብሉይ ፡ ሐዲስ ፡፡ መጽሐፈ ፡ ሥርው ፤ (ዮሴፍ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ ፶፩) ፡፡

**ሥርወ ፡ ሕሩም ፤** የቾልዳ ፡ ኽርማት ፡ (ዘፍ ፴፪ ፡ ፴፫) ፡፡

**ተሠርወ ፤ ተሠረወ ፤** ተነቀለ ፤ ጠፋ ፡፡ ከመ ፡ ይሠረዉ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡፡ ረሲዓን ፡ እምሥርዎሙ ፡ እምድር ፡ ይሜረዉ ፡፡ ለትሠሮ ፡ ይእቲ ፡ ነፍስ ፡ እምእስራኤል ፤ (መዝ ፡ ፺፩ ፡፡ ምሳ፲፭ ፡ ፳ ፡፡ ዘፀ ፲፪ ፡ ፲፭) ፡፡

**ተሠርወ ፤** ተተከለ ፤ ተመሠረተ ፡ ሥር ፡ መሠረት ፡ ኾነ ፡፡ ወተሠርዉ ፡ ሎሙ ፡ በሃይማኖት ፤ (ገድ ፡ ተክ) ፡፡

**ሥርው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሩት) ፤** የተነቀለ ፡ ንቁል ፤ የጠፋ ፡ ጥፉ ፤ የተተከለ ፤ ሥር ፡ የያዘ ፤ የሰደደ ፡፡

(ጥ) **ሥራዌ ፤** መንቀል ፤ መንቀል ፡ አንቃቀል ፤ ንቀላ ፤ ጥፋት ፤ ጉዳት ፤ መቅሠፍት ፡፡ የንሥሥ ፡ ሥራዌከ ፤ (ዮሴፍ ፡፡ ጥበ፭ ፡ ፲፪ ፡፡ ምሳ፳፩ ፡ ፯ ፡፡ ኩፋ ፡ ፳፪) ፡፡

**ሠርዌ ፤—አለቃ ፤ ቄፍራ ፤ —ሰሪው ፡ ሰረወ ፤ ሰርዌ ፡፡**

**ሣሮን ፤ (ዕብ ፡ ሻሮን) ፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ የባሕር ፡ የወንዝ ፡ ዳር ፤ ሜዳ ፡ ረባዳ ፤ ከኢዮጴ ፡ እስከ ፡ ቀርሜሎስ ፡ ያለ ፤ በምሥራቅም ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ሚደ ፡ ሮቤልና ፡ ጋድ ፡ የወረሱት ፡ (ኢሳ፴፫ ፡ ፱ ፡፡ ፩ዜና ፡ ፳ ፡ ፲፰) ፡፡ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ችፍርግ ፡ ታናሽ ፡ ዛፍ ፡ ይሉታል ፤ ፍችው ፡ አይደለም ፡፡

**ሥርዋጽ ፤—ሸብልቅ ፤—ስርዋጽ ፡፡**

**ሠሬገዝ ፤ ዘት ፤ (ሠረዘ ፡ ይሠርዝ ፡ ይሥርዝ) ፤** መሠረዝ ፤ ማጠር ፤ የተጣፈን ፡ ቃል ፡ ስሕተት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ቀለም ፡ ማልበስ ፤ ወይም ፡ በላዩ ፡ እንደ ፡ መሥመር ፡ ማሳለፍ ፤ ማጋደም ፡፡

**ሠረዝ ፤** ዐጥር ፤ የስሕተት ፡ ምልክት ፤ ከማን በብና ፡ ከመንበብ ፡ የሚከለክል ፡፡

**ሠረዝ ፤** የቅኔ ፡ መንገድ ፡ ስም ፤ ኹለት ፡ አርእስት ፡ ያለው ፤ ንባቡም ፡ ምስጢሩም ፡ በዋዌ ፡ እየተጫፈረ ፡ የሚኼድ ፡፡ እምከዊኑ ፡ ካህን ፡ ይኄይስ ፡ ከዊኑ ፡ ኖላዌ ፤ ወኀሰ ፡ እንስሳ ፡ ትትበደር ፡ እምቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዐባይ ፤ እስመ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ክነት ፡ ቤተ ፡

ፈያታይ ፤ ወበሳዕሊ ፡ ኖሎት ፡ ኢሀለወ ፡ ሳዕለ ፡ ካህናት ፡ ዘሀሎ ፡ እከይ ፤ ይህን ፡ የመሰለ ። ይህ ፡ ነጠላ ፡ ነው ፤ ድርብ ፡ ሲኾን ፡ አርእስቱ ፡ ሦስት ፡ ይኾናል ። አስተብፅዑ ፡ ነፍስተ ፡ ዓሣ ፡ ኢየሱስ ፡ ወጴጥሮስ ፡ ወሩፋኤል ፤ ባሕረ ፡ ጥብርያዶስ ፡ እኮኑ ፡ እመ ፡ ኢየሱስ ፡ ወፈረ ፡ በጎዳጥ ፡ ዓሣ ፡ እጽገበ ፡ ማኅበረ ፤ ወእምከርሡ ፡ ዓሣ ፡ አውፅአ ፡ ጸባሕተ ፡ ቄሳር ፡ ዲናረ ፡ መሠግር ፡ ጴጥሮስ ፡ እመ ፡ አሥገረ ፤ ሩፋኤልኒ ፡ ሥራየ ፡ በዘአእመረ ፡ በዓሣሁ ፡ አሕየወ ፡ ዐዉረ ።

**ሠረዝ** ፤ ማእከላዊ ፡ ነቍጥ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ያለው ፡ ነጠላና ፡ ድርብ ፤ የቃል ፡ መክፈያ ፤ የምስጢር ፡ መለያ ፤ ክ(።)ነጥብ ፡ የሚያንስ ፡ የነጥብ ፡ እኩሌታ ፡ ክ(፡) ነቍጥ ፡ የሚበልጥ ፤ ኹለተኛና ፡ ሦስተኛ ፡ የጥፈት ፡ ምልክት ። ነጠላ ፡ ሠረዝ ፡ ወይም ፡ ። ድርብ ፡ ሠረዝ ፤ ። ሲመኝ ፡ እንደ ፡ አኃዝ ፡ ቀይ ፡ ይጨመራል ፤ ሳይመኝ ፡ ይቀራል ። ነጠላ ፡ ሠ ፡ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ ባለው ፡ በማይጣፈር ፡ ቃል ፡ በስም ፡ ይገባል ። ቦ ፡ ዘምእት ፡ ወቦ ፡ ዘስሳ ፡ ወቦ ፡ ዘሠላሳ ። ወናሁ ፡ እነግረክሙ ፡ ዘትብሉ ፡ በበይናቲክሙ ፡ አነ ፡ ዘጳውሎስ ፡ ወአነ ፡ ዘአጵሎስ ፡ ወአነ ፡ ዘኬፋ ፡ ወአነ ፡ ዘክርስቶስ ። ድርብ ፡ ሠ ፡ ባስረጅና ፡ በተመሳሳይ ፡ ቃልይ ፡ ይገባል ። ንበር ፡ ማእከሌነ ፤ እስመ ፡ ኪያከ ፡ አልሀቀ ፡ እግዚ ። እስመ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፤ አነ ፡ አሀጕል ፡ ጥበቢሆሙ ፡ ለጠቢባን ፤ ወእሜንን ፡ ምክሮሙ ፡ ለመካርያን ። መኑ ፡ እንከ ፡ ጠቢብ ፤ ወመኑ ፡ እንከ ፡ ጸሓፊ ፤ ወመኑ ፡ ዘየኃሥሥ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፤ እኮኑ ፡ አእበደ ፡ እግዚ ፡ ለጥበበ ፡ ዝ ፡ ዓለም ።

(ተ) **ሠርሐ** ፤ ሐት ፤ (ሠርሐ ፡ ይሤርሕ ፡ ይሠርሕ ። ዐረ ፡ ሸረሐ ፤ ክሠተ) ፤ ማበጀት ፤ ማሳመር ፤ ማቅናት ፤ ማስላት ፡ ማሳካት ፤ ማከናወን ፤ ማስናበት ። ሠርሐ ፡ ምግባሮሙ ፡ በእደ ፡ ነቢዩ ። ይሤርሕ ፡ እግዚ ፡ ፍናዊሁ ። ይሤርሐከ ፡ በዘሉ ፡ ግብርከ ። ዘእንበለ ፡ ይትፈጸም ፡ ዕርገተ ፡ ቍርባን ፡ ወበረከተ ፡ ካህን ፤ ወሠርሖት ። እምቅድመ ፡ ሠርሖቱ ፡ (ጥበ፲፩ ፡ ፩ ። ኩፋ ፡ ፳፯ ። ጦቢ ፬ ፡ ፲፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፪ና ፲፫ ። ዘኍ፮ ፡ ፳፫—፳፯) ። በሠርሖት ፡ ፈንታ ፡ ሥርሖት ፡ ይባላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ንቀድም ፡ በረድኤተ ፡ እግዚ ፡ ወበሥነ ፡ ሥርሖቱ ፡ (ያዕ ፡ ዘእል) ።

**ተሠርሐ** ፤ (ዕብ ፡ ጸላሕ ። ሱር ፡ ጽላሕ ። ዐረ ፡ ጸለሐ) ፤ ተበጀ ፤ ተዘጋጀ ፤ ተከናወነ ፤ ሰላ ፡ ተሳላ ፤ ተሳካ ፤ ተሰናበተ ። ወልድየ ፡ ተሠራሕ ። ተሠርሐ ፡ ሕዝብ ፡ በዘሉ ። ትሤራሕ ፡ በዘሉ ፡ ፍኖትከ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፭ ። መዝ ፡ ፵፬ ። ፪ዜና ፡ ፲፬ ፡ ፵ ። ጦቢ ፬ ፡ ፮) ።

**ሥሩሕ** ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ርሕት) ፤ ያማረ ፡ የበጀ ፤ የቀና ፤ የሰላ ፤ የተከናወነ ። ከመ ፡ ሥሩሐ ፡ ይኩን ፡ ፍኖትከ ። ለገባሬ ፡ ሠናይ ፡ ዘሉ ፡ ፍናዊሁ ፡ ሥሩሕ ፡ (ጦቢ ፭ ፡ ፲፱ ። ፈላስ) ።

**ሥራሕ** ፤—ድካም ፤—ሰሬሕ ፡ ሰርሐ ።

**ሣርኖ** ፤—ኖት ፤ (ሣርን ፡ ይሣርን ። ዐረ ፡ ሸረን ። ዕብ ፡ ዛራሕ) ፤ መብራት ፡ መጽደል ፤ መሸብረቅ ፤ መፍለቅ ፡ ማንጸብረቅ ፤ መንደድ ፡ መቃጠል ፤ በግ ፡ ማለት ።

**ሥሩኅ** ፤ (ኃን ፡ ኃት ፡ ኅት) ፤ የበራ ፤ ብሩህ ፤ ጽዱል ።

**ሠራኄ** ፤ (ኄያት) ፤ መብራት ፤ ብርሃን ፤ ጸዳል ፤ ክብር ፤ ጌጥ ። ወሠራኄ ፡ እግዚ ፡ ተርእየ ፡ በደመና ። ለክብር ፡ ወለሠራኄ ። በርሀ ፡ ገጹ ፡ በሠራኄ ፡ መለኮት ። ሠራኄ ፡ ወጸዳል ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፲ ። ፳፰ ፡ ፪ ። ገድ ፡ ተክ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ሣርኅ** ፤ (ኃት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ወእርኢያ ፡ ሣርኅ ፡ ለእግዚ ፡ ከመ ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ (ዘፀ፳፬ ፡ ፲፯) ።

**ሠርዮ** ፤ ዮት ፤ (ሠረየ ፡ ይሤሪ ፡ ይሠሪ) ፤ መሠረይ ፤ ሥራይ ፡ ማድረግ ፤ አስማት ፡ መድገም ፤ መጠንቈል ፡ ማሟረት ፡ ምትሀት ፡ ማሳየት ፤ የክፉ ። እንዘ ፡ ይሤርይ ፡ መሠርይ ፡ ጠቢብ ። እንትሙ ፡ መሰግላን ፡ ዘትሤርዩ ፡ ሀገረ ፡ (መዝ ፡ ፶፯ ። ስንክ ፡ ሐም፲፭) ።

—፤ ማዳን ፡ መፈወስ ፤ መድኀኒት ፡ ማድረግ ፤ ለማዳን ። ውእቱ ፡ አቍሰለነ ፡ ወይሤርየነ ። ሥረይ ፡ ላቲ ፡ ለነፍስየ ፡ (ሆሴ፮ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፵) ።

**ሠራዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤ ሥራይ ፡ የሚያደርግ ፤ ሥራየኛ ፤ አስማታም ፤ መድኀኒታም ።

**መሠርይ** ፤ (ዪት ፡ ይት ፡ ያን ፡ ያት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ መሠሪ ፤ ጠንቋይ ፤ ሟርተኛ ፤ ምትሀታም ። ሲሞን ፡ መሠርይ ። ጠባብ ፡ ይእቲ ፡ ወመሠርይት ። ሊዮሎስ ፡ ሊቀ ፡ መሠርያን ፡ (ግብ፰ ፡ ፱ ። ዮሴፍ ። ቀሌ) ።


**መሥሬ** ፤ **መሥርይ** ፤ መጽሐፈ ፡ መድኀኒት ፤ የጠንቋይ ፤ ወይም ፡ የሐኪም ። መሥሬ ፡ ውሉድ ፡ (ስንክ) ።

**ሥራይ** ፤ (ያት) ፤ መድኀኒት ፤ የሚቀጥ ፡ የሚሳመጥ ፤ የሚጠጣ ፡ የሚቀባ ። ሥራይ ፡ ዘቀብዕዎ ። ይጠይዕዎ ፡ ሥራየ ። ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ (ጥበ፲፮ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፴ ፡ ፳ ። ሚራ፲ ፡ ፲) ።

—፤ ጥንቈላ ፤ ሟርት ፤ ምትሀት ። ዘሥራይ ፡ ብእሲሁ ። እለ ፡ ሥራይ ። ሰብአ ፡ ሥራይ ። መጽሐፈ ፡ ሥራያት ፡ (ግብ፰ ፡ ፱ ። ራእ፳፪ ፡ ፲፭ ። ዘፀ፱ ፡ ፲፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፭) ።

(ሳ) **ሠረየ** ፤ ፈተለ ፤ አቀጠነ ፤ አሾረ ፤ አንሻረረ ፡ አንዝርቱን ።

**ሣሬት** ፤ (ርያት) ፤ ሸረሪት ፤ ፈታይ ፡ አቅጣኝ ። ዘሣሬት ፡ ውእቱ ፡ ተመይኖ ፡ ግብር ። ፈትለ ፡ ሣሬት ፡ እንመተ ፡ ሣሬት ። ለሣሬት ፡ ፈትለ ፡ እዴ ፡ እምነ ፡ ዕርቃን ፡ ኢይትረፍ ፡ (ፈላስ ። አፈ ፡ ተወ፬ ። ቅኔ) ።



ሣሬት ፤

**ሥርየት ፤—በቁሙ ፤—ሰርይ ፡ ሰረየ ።**

**ሠረከ ፤ (ዐረ ፡ ሸረክ)** ፤ አዋሰበ ፡ ጕንጕን ፡ አሰረ ፡ ዐዘበ ፤ የቆታን ፡ የሐማማ ፤ የወጥመድ ። አሠመረ ፤ አስነበረ ፤ የሚር ፡ የብሬና ። ኹለተኛውን ፡ ሠረቀን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ፤ ከ ፡ ሰቀ ፡ ተለውጦ ፡ ወደዚያ ፡ ኼዷል ።

**ሢራክ ፤ (ካት ። ዐረ ፡ ሺራክ ። ዕብ ፡ ሥሮኽ)** ፤ ሚር ፤ ማዘቢያ ፤ ቆታን ። መሥመር ፡ ወስፈው ፡ ርባሱ ፡ ቀለሙ ፡ ያስፈበት ፤ ንድፉ ፤ ሰንበሩ ፡ የቆመው ፡ የተጋደመው ፡ ወይም ፡ ቀለም ፡ የሚወድቅበት ፡ ተለላው ፡ መዘሬያው ። ወሰሰ ፡ ኍልቈ ፡ አኃዙ ፡ ቦቱ ፡ አኃዝ ፡ ዘበሢራኩ ፤ ዘይኤምር ፡ ውስተ ፡ አይ ። አእሚረከ ፡ አኃዘ ፡ ኍልቈ ፡ ዘበሢራኩ ፡ (መቅ ፡ ወን) ።

**ሢራክ** ፤ የጸሎት ፡ የመዝሙር ፡ ክፍል ፡ ቃሉ ፡ በመሥመር ፡ በመሥመር ፡ የተለየ ፤ የሚያዜሙት ፡ የሚያስተዛዝሉት ፤ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ያለ ። (መጽ ፡ ምስ ። ሂርማ) ።

**ሢራክ** ፤ የሰው ፡ ስም ። ጥበበ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ሢራክ ። ወኮኑ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለሰሎሞን ፡ እምነቢያት ፡ ናታን ፡ ወአኪያ ፤ ወሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሳዶቅ ። ወኮነ ፡ ሊቀ ፡ ሐራሁ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ሢራክ ፡ ወውእቱ ፡ ዘአስተጋብኦሙ ፡ ለመጻሕፍት ፡ ሰሎሞን ፡ ወረሰዮሙ ፡ ኀምስተ ፡ መጻሕፍተ ፤ ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ ምሳልያት ፡ ወተግሣጽ ፡ ወጥበብ ፡ ወጉባኤ ፡ ወማሕልየ ፡ መሓልይ ፤ ወለኢያሱ ፡ ሊቀ ፡ ሐራሁ ፡ አሐዱ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘዐዊቅ ፡ ቦቱ ፡ ምሉእ ፡ እምጥበብ ፡ ወዕንቊ ፡ ባሕርይ ፡ ነገር ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፹) ።

**ሠርክ ፤ (ዐረ ፡ ሸሪክ ፡ ሸርክ ፤ ሱቱፍ)** ፤ በቁሙ ፤ ማታ ፡ ምሽት ፡ ከ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ቀዳማይ ፡ ሰዓት ፡ ሌሊት ፤ የመዓልት ፡ ሐፍ ፡ መጨረሻ ፡ መስናበቻ ፤ የሌሊት ፡ መባቻ ፡ ሱቱፈ ፡ ጽልመት ። ዐርብን ፡ ተመልከት ። መሥዋዕተ ፡ ሠርክ ። እምነግህ ፡ እስከ ፡ ሠርክ ። ፍና ፡ ሠርክ ። በበ ፡ ሠርክ ። ሠርከ ፡ ሠርከ ፡ ትበልዕ ። ሠርከ ፡ ሠርከ ፡ ይዴረሩ ፡ (መዝ ፡ ፻፵ ። ዮዲ፲ ፡ ፳ ። ዘሌ፮ ፡ ፲፫ ። ፪ዜና ፡ ፲፫ ፡ ፲፩ ። ዮዲ፲፪ ፡ ፱ ። ሱቱ ፡ ሰገ፲፬ ፡ ፵፮) ።

**አሥረከ** ፤ ወዘመ ፤ ዋዜማ ፡ ቆመ ፡ የሠርክ ፡ ጸሎት ፡ አቀረበ ። ይሠርክ ፡ በጸሎት ፡ (ቂድር) ።

**ሠረም ፤ ሞት ፤ (ሠረመ ፡ ይሠርም ፡ ይሥርም)** ፤ ማረማረግ ፡ መቅለጥ ፡ መሳብ ፡ መዋጥ ፡ ማስጠም ፡ ማስመጥ ፡ የመሬት ፡ የውሃ ።

**ሠርም ፡ (ዐረ ፡ ሸርም)** ፤ ረግረግ ፤ ማጥ ፡ የሚያጠልቅ ፡ የሚያሰምጥ ፤ ያዘባ ፡ የጭቃ ፡ ጕድጓድ ፡ ዐዘቅት ። ለእለ ፡ ውስተ ፡ ሠርም ፡ ይትመነደቡ ፡ መድኃኒ ። ዕመቀ ፡ ሠርመ ፡ ኀጢአት ። ረዳኢ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ሠርም ፡ (ኪዳ ። ቀሌ ። ድጓ) ።

**አሥራም** ፤ ረግረጎች ፡ ጥልቆች ። እሞገደ ፡ አሥራም ፡ (አርጋ ። ቂር) ።

**ተሠርመ** ፤ ተዋጠ ፤ ሰጠመ ፡ ዘቀጠ ፡ ከረግረግ ፡ ገባ ። ወኢተሠርሙ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ (መቃ) ።

**ሥርናይ ፤—ስንዴ ፤—ሥዒር ፡ ሥዕረ ።**

**ሠረዐ ፤ ዖት ፤ (ሠርዐ ፡ ይሠርዕ ፡ ይሥራዕ ። ዐረ ፡ ሸረዐ ። ዕብ ፡ ሣራዕ)** ፤ መሥራት ፡ ማድረግ ፤ ማበጀት ፤ ማዘጋጀት ፤ መምረጥ ፤ ማቅረብ ፤ መዘርጋት ፡ መሰደር ፡ መደርደር ፤ የሥራ ፡ የማእድ ፡ የወጥመድ ፤ የሕዝብ ፡ የሰራዊት ። ሥርዑ ፡ ማእደ ። ዘሠርዐ ፡ መሥገርተ ። ብዙኀ ፡ ሠርዑ ፡ ውስቴቱ ። ይሠርዖሙ ፡ ለሕዝብ ። ሠርዐ ፡ ሰራዊተ ። ኪያሆሙ ፡ ሠርዐ ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፴፩ ። ሢራ፳፯ ፡ ፳፯ ። ፴፱ ፡ ፲፪ ። ኢዮ፲፪ ፡ ፳፫ ። ዮሴፍ ። ሮሜ፰ ፡ ፳፱) ። ዘርዐንና ፡ መዝርዕን ፡ ተመልከት ፤ ዘ ፡ በሠ ፡ ተለውጧል ።

**—** ፤ ማዘዝ ፤ መወሰን ፤ መጣፍ ፤ ማኖር ፤ የሕግ ፡ የሥርዐት ። ስንክሳር ፡ ዘሠርዑ ፡ አበዊነ ። ያሬድ ፡ ሠርዐ ፡ ማሕሌተ ፡ ለለ ፡ ዘመኑ ። ሠራዕኩ ፡ ሞጻ ፡ ወሰነ ፡ ለባሕር ፤ አንበርኩ ፡ ረሰይኩ ፡ ብሂል ፡ (ስንክ ፡ መጋቢ ። ማን፲፭) ።

**ሠራዒ ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት)** ፤ የሚሠራ ፤ የሚያዝ ፤ የሚጥፍ ፤ የሚወስን ። እግዚ ፡ ሠራዒሃ ፡ ለሰንበት ። ሠራዒ ፡ ጳውሎስ ። ሠራዕያነ ፡ ሕጋቲሃ ፡ ለቤተ ፡ ክር ፡ (ቀሌ ። ቂር ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ተሠርዐ** ፤ ተሠራ ፤ ተበጀ ፤ ተዘጋጀ ፤ ተሰናዳ ፡ ተጣፈ ፡ ተወሰነ ፤ ታገገ ፡ ተደነገገ ። አኮ ፡ ለጻድቃን ፡ ዘይሠራዕ ፡ ሕግ ። በከመ ፡ ተሠርዐ ፡ በእንቲአሁ ። እስመ ፡ ለዐሠርቱ ፡ ክፍል ፡ ወመንፈቅ ፡ ተሠርዐ ፡ ዓለም ፡ (፩ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፱ ። ሉቃ፳፪ ፡ ፳፪ ። ሱቱ ፡ ሰገ፲፬ ፡ ፱) ። ተሰምየ ፡ ተብህለ ፡ ተጸውዐ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተሠርዐ ፡ ይባል ፤ ተባለ ፡ ማለት ፡ ነው ። ወተሠርዐ ፡ ወልደ ፡ እግዚ ፡ በኀይል ፡ ቅብዐ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ቂር) ።

**ሥሩዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ርዕት)** ፤ የተሠራ ፡ የተበጀ ፡ የተዘጋጀ ፤ የቀረበ ፡ የተጣፈ ፡ የተወሰነ ፤ የቆመ ፡ የተተከለ ። ጽጌ ፡ ረዳ ፡ ሥሩዕ ። ማእድ ፡ ሥሩዕ ። ሥሩዕ ፡ ወዕቁም ። ወሥሩዕ ፡ ከመ ፡ ወርኅ ፡ ለዓለም ፡ (አስቴ፩ ፡ ፯ ። ሕዝ፵፫ ፡ ፵፩ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፵ ። መዝ ፡ ፹፰) ።

**—** ፤ የተመረጠ ፤ የተሾመ ፡ ኅሩይ ፡ ሥዩም ፡ ጽጡዕ ። ሥሩዕ ፡ ጴጥሮስ ፤ ሥሩዕ ፡ ጳውሎስ ፡ (ቂር) ።

**ሥርዐት ፤ (ታት)** ፤ መሥራት ፤ መሠራት ፤ አሠራር ፡ ሥራት ፡ ደንብ ፤ አገባብ ፡ ሕግ ፡ ትእዛዝ ፡ ዐዋጅ ፡ ፍርድ ፡ ልማድ ፡ የሥራ ፡ መንገድ ። መኰንን ፡ ለባዊ ፡ ይገብር ፡ ሥርዐተ ። ዐቃቤ ፡ ሥርዐት ። ሥርዐተ ፡ ዲያቆን ፡ ዐቀበ ፡ ወኢተዐደወ ። ንሕነ ፡ ወለጥነ ፡ ሥርዐተ ። ንሥቶተ ፡ ሥርዐት ፡ በብሰብ ። ሥርዐተ ፡ ምሥዋዕ ። ሥርዐተ ፡ አውራኅ ። ሥርዐተ ፡ አበ ፡ ጳኵሚስ ፡ (ሢራ፲፯ ፡ ፳፮ ። ፩ዜና ፡ ፲፮ ፡ ፲፭ ። መዋሥ ። እፌ ፡ ተ፫ ። ጥበ፲፱ ፡ ፳፯ ። ዕብ፱ ፡ ፩ ። ኩፋ ፡ ፱ ። ሥር ፡ ጳኮ) ።

— ፤ መናገር ፡ አናጋር ፤ ጕሮ ። ይጌይስ ፡ ሥርዐተ ፡ ብሕትውና ፡ እምሥርዐተ ፡ ማኅበር ። ቦ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ያስተካብዱ ፡ ሥርዐተ ፡ ንዴት ፡ (ፊልክ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ተ፲፰) ።

(ጥ) **ሥራዕ** ፤ (ዓት ። ዐረ ፡ ሺ.ራዕ) ፤ የመርከብ ፡ ሸራ ፤ መጋረጃ ፤ መዝርዕ ፤ አውረዱ ፡ ሥራዐ ። ወሰቀሉ ፡ ሥራዐ ፡ ዘይንእስ ። ሐመር ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ ሥራዓት ፡ (ግብጽ፳ ፡ ፲፯ ፡ ፵ ። ማር ፡ ይሥ፱ ፡ ፱) ። በመልሕቅ ፡ ፈንታ ፡ ሥራዕ ፤ ሥራዓት ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ወአልዐሉ ፡ ሥራዓተ ፡ (ግብጽ፳ ፡ ፲፱) ።

**ሠረጸ** ፤ ጾት ፤ (ሠረጸ ፡ ይሠርጽ ፡ ይሥርጽ ። ዕብ ፡ ሻራጽ) ፤ መፍላት ፤ መውጣት ፤ መብቀል ፤ ሥር ፡ መስደድ ፤ መለምለም ፤ ማፈጥፈጥ ፤ የተሐዋስያን ፡ የእዝርዕት ፡ የአትክልት ። ለታውዕእ ፡ ባሕር ፡ ባለው ፤ ዕብራይስጡ ፡ ይሸርጹ ፡ ሀማዩም ፡ እንዲል ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፳) ። ውእተ ፡ ጊዜ ፡ ሠረጸ ፤ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዕመቅ ፡ ለመሬቱ ። ይሠርጽ ፡ ሥርዎሙ ። ዕፀው ፡ ሠረጹ ። በትር ፡ ትሠርጽ ። እምሥርወ ፡ እሴይ ፡ ሠረጸ ፡ (ማቴ፲፫ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፹፱ ። ኢሳ፴፯ ፡ ፴፩ ። ሉቃ፳፩ ፡ ፴ ። ዘኍ፲፯ ፡ ፰ ። ድጓ) ።

**ሠረጸ** ፤ መሥረጽ ፤ አሥራጺውን ፡ አኸሎ ፤ በባሕርይ ፡ በመልክ ፡ መስሎ ፡ ተካክሎ ፤ ከአሥራጺው ፡ አካል ፡ መውጣት ፡ መገኘት ፤ ያው ፡ ግን ፡ ተድኅሮ ፡ ተመትሮ ፤ የባሕርይ ፡ ተከፍሎ ፡ ሳይኖር ። ወወሰኩ ፡ ላዕለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘሠርዑ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ዐሠርቱ ፡ ወሰመንቱ ፡ (፫፻ ፡ ፲ወ፰) ፡ ወይቤሉ ፡ ወነአምን ፡ በበመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘሠረጸ ፡ እምአብ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜታ ። ወእሎንቱ ፡ እለው ፡ ምእት ፡ ወኃምሳ ፡ አውገዙ ፡ ዙሎ ፡ ዘይዌስክ ፡ እምድኅረ ፡ ዝ ፡ ላዕለ ፡ ሃይማኖት ፡ አው ፡ ያሐጽጽ ፡ እምኔሃ ። ወነአምን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘሠረጸ ፡ እምአብ ። ከመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሠረጸ ፡ እምአብ ፤ ወኑሥእ ፡ እምወልድ ። ወሞገስ ፡ ኢይሠርጽ ፡ ዘእንበለ ፡ እምኄቡ ፡ ምግባራት ፡ ሠናያት ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፲፫፱ ፡ ጸሎ ፡ ሃይ ። ያዕ ፡ ዘእል ። ማር ፡ ይሥ፰ ፡ ፳) ። በሠረጸ ፡ ፈንታ ፡ ወፅአ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ ፩ ፡ ነው ። ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይሄኑ ፡ ዘከመ ፡ ወፅአ ፡ እምአብ ፤ ወዘከመ ፡ ነሥአ ፡ እምወልድ ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ሠራጺ** ፤ (ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት) ፤ የሚሠርጽ ፤ የሚወጣ ፡ ወፊ ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሠራጺ ፤ ወኢአሥራጺ ። ከዊነ ፡ ሠራጺ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባሕቲቱ ፡ (አትና ፡ ያዕ ፡ ዘእል) ። መሥረጽ ፡ ግብሩ ፤ ሠራጺ ፡ አካሉ ፤ ሠራጺነት ፡ ከዊን ፡ ሠራጺ ፡ የአካሉ ፡ ባሕርይ ፤ ወይም ፡ ህላዌ ፡ ይባላል ፤ የህላዌን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። እንትና ፡ ከዊን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ።

**ሥሩጽ** ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ርጽት) ፤ የሠረጸ ፤ የወጣ ፡ የበቀለ ፤ የለመለመ ፤ ለምለም ፡ ጨፌ ፤ መስክ ። ወተርእየት ፡ ማይ ፡ እምዘቀዲሙ ፡ ርግዕት ፡ ወሥርጽተ ፡ ምድር ፡ ይብስት ፡ (ግብ፲፱ ፡ ፯) ።

**ሥርጸት** ፤ መሥረጽ ፡ መውጣት ፤ መብቀል ፡ አበቃቀል ፤ ቡቃያነት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ሠርጽ** ፤ (ጻት ። ዕብ ፡ ሼሬጽ ፤ ተሐዋሲ) ፤ ቡቃያ ፤ ዐዲስ ፡ ወጣት ፤ ለጋ ፡ ቀንበጥ ፤ ሙሸራ ፡ ጫፍ ፤ ውልብልቢት ። ዘርዐ ፡ ምስለ ፡ ሠርጽ ። ሠርጽነ ፡ ዘእንበለ ፡ ይጸምሒ ። ሠርጸ ፡ ሊባኖስ ። ሠርጸ ፡ ገዳም ። ዘሠናይ ፡ ሠርጸ ፡ ወጽፉቅ ፡ ቈጽሉ ፡ (ዓሞ፱ ፡ ፲፫ ። ጥበ፪ ፡ ፰ ። ሢራ፶ ፡ ፰ ። ሕዝ፲፯ ፡ ፮ ። ፴፮ ፡ ፫) ። ሠርጸ ፡ ጢስ ፡ ቢል ፡ ዐምደ ፡ ጢስ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዐምደ ፡ ደመና ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ (ማሕ፫ ፡ ፯) ።

**አሥረጸ** ፤ አበቀለ ፤ አስበቀለ ፤ አወጣ ፤ አስገኘ ። ያሠርጽ ፡ ሣዕረ ፡ ለእንስሳ ። አሠርጽ ፡ ለዳዊት ፡ ሠርጸ ፡ ጽድቅ ። ዘአሥረጸ ፡ ልብ ፡ ኪያሆን ፡ (መቃ ። ኤርሚ ፡ ፲፰ ፡ ፍ ፡ ን ፡ መቅ) ።

**ሠረቀ** ፤ ቀት ፤ (ሠረቀ ፡ ይሠርቅ ፡ ይሥርቅ ። ዐረ ፡ ሸረቀ ። ዕብ ፡ ዛራሕ ። ሱር ፡ ድናሕ) ፤ መነሣት ፤ መውጣት ፤ ብቅ ፡ ማለት ፤ መብቀል ፡ መወለድ ፤ መብራት ፡ መታየት ፡ መገለጥ ፤ የፀሓይ ፡ የጨረቃ ። እምከመ ፡ ሠረቀ ፡ ፀሓይ ፡ የአትዉ ። ብርሃን ፡ ዐቢይ ፡ ሠረቀ ፡ ላዕሌሆሙ ። እግብር ፡ ሐዲሰ ፡ ዘይእዜ ፡ ይሠርቅ ። ሠረቀ ፡ በሥጋ ። ትሬእዮሙ ፡ እንዘ ፡ ይሠርቁ ፡ (መዝ ፡ ፻፫ ። ኢሳ፱ ፡ ፪ ። ፵፫ ፡ ፲፱ ። ኤፍ ። አረጋ ፡ ድ፭) ።

— ፤ መባት ፤ መግባት ፤ መዠመር ፤ የወር ፡ ያመት ። ታኅሣሥ ፡ ሰእመ ፡ ሠረቀ ፡ በሠሉስ ። በክልኤቱ ፡ ዓመት ፡ መንግሥቱ ፡ ሠረቀ ፡ መስከረም ፡ በዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ (ሥር ፡ ድ፫ ። ታሪ ፡ ነገ) ።

**ሥርቀት** ፤ መውጣት ፤ አወጣጥ ፤ መታየት ። ሥርቀተ ፡ ፀሓይ ። ሥርቀተ ፡ ከዋክብት ። ሥርቀተ ፡ ቤዝ ፡ (ዮሴፍ ። ጥበ፲ ፡ ፲፯ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ሠርቅ** ፤ መውጫ ፤ መገለጫ ፤ ምሥራቅ ። መንገለ ፡ ሠርቀ ፡ ፀሓይ ። ደብረ ፡ ዘይት ፡ ዘሀለወት ፡ በሠርቀ ፡ ኢየሩሳሌም ። በከመ ፡ ይርሕቅ ፡ ሠርቅ ፡ እምዐረብ ፡ (ዘፍ፳፭ ፡ ፮ ። ዮሴፍ ። መዝ ፡ ፻፪) ።

**ሠርቅ** ፤ መባቻ ፡ የወር ፡ መዠመሪያ ፤ ልደተ ፡ ወርኅ ፤ መብቀያዋ ፡ መወለጃዋ ፤ ወር ፤ ቀን ። ጌሠም ፡ ሠርቀ ፡ ወርኅ ። ሠርቀ ፡ ወርኅክሙ ። ዕለተ ፡ ሠርቅ ። አመ ፡ ርእሰ ፡ ሠርቅ ። በኍሙስ ፡ ሠርቅ ። በበሠርቅ ፡ ሠርቅ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፭ ። ኢሳ፩ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፹ ። ዘፀ፵ ፡ ፪ ። ሕዝ፩ ፡ ፩ ። ኤር፶ ፡ ፴) ።

**ሠርቃዊ** ፤ የጨረቃ ፡ ወር ። ወርኅ ፡ ሠርቃዊ ፡ (አቡሻ ፡ ፴፫) ።

**ሠርቃዊ** ፤ (ዕብ ፡ ቄድም) ፤ ምሥራቅ ፤ ምሥራቃዊ ። ደብር ፡ ሠርቃዊ ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፴) ።

**ሠረቃዊ** ፤ (ዕብ ፡ ጼማሕ) ፤ ሠርጽ ፤ ቡቃያ ፡ ለጋ ፡ ወጣት ፤ ገና ፡ የሚያድግ ። ገብርየ ፡ ሠረቃዊ ። ናሁ ፡ ብእሲ ፡ ሠረቃዊ ፡ ስሙ ፤ ወይሠርቅ ፡ (ዘካ፫ ፡ ፰ ። ፮ ፡ ፲፪) ።

**ምሥራቅ፤(ቃት)፤** በቁሙ፡ የፀሓይ፡ መውጫ፤ መገለጫ፤ ማእዝን፤ ሀገር፤ የምዕራብ፡ ትይዩና፡ አንጻር። እምሥራቅ ፡ ፀሓይ፡ እስከነ፡ ዐረብ። ነገሥት፡ እለ፡ እምነ፡ ምሥራቀ፡ ፀሓይ። ምሥራቃት፡ (መዝ፡ ፻፲፪። ራእ፲፮፡ ፲፪። አቡሻ፡ ፵፮)።

**ምሥራቃዊ፤** የምሥራቅ። ቴዎድሮስ፡ ምሥራቃዊ። ምሥራቃውያን፡(ስንክ፡ ጥር፲፪። ፍ፡ ነ፡ ፱)።

**አሥረቀ፤** አወጣ፤ አበቀለ፤ አበራ፤ ገለጠ፤ ብልጭ፡ አደረገ። እስመ፡ ውእቱ ፡ ያሠርቅ፡ ፀሓዮ። ያሠርቅ፡ እግዚ፡ ጽድቀ፡ ወሐሤተ። አሥረቀ፡ ንስቲተ፡ መለኮቶ፡(ማቴ፭፡ ፵፭። ኢሳ፷፩፡ ፲፩። ቅዳ)። አሠረቀ፡ አባተ።

**አሥረቀ፤** ማለደ፡ አማለደ፡ አዘወተረ፤ የጧት፡ መዝሙር፡ ስብሐት፡ ነግህ፡ ማቅረብ። በእጽዋም፡ ሰእመ፡ ሀሎ፡ አሥርቆት። አርያም፡ ዘአሥርቆት፡ (ሥር፡ ድጓ)።

**ሠረቀ፤(ዐረ፡ ሸረክ)፤** አሰረ፡ ቋጠረ፤ አዋሰበ፡ ጕንጕን። ሠረክን፡ ተመልከት።

**ሥርቅ፤** ሸምቀቆ፤ ገመድ፤ ወጥመድ። ቆቃሕ፡ ተሠግረ፡ በቈጽለ፡ አሥርቀ፡ (በቈጽለ፡ ሥርቅ)፤ ቈጽል፡ ልጡ፡ ገመዱ፤ ሥርቁ፡ ውስ፡ ሸምቀቆው፡ (ሢራ ፲፩፡ ፴)።

**ሜሬቅ፤(ዕብ፡ ሦሬቅ። ጽር፡ ሰሬክ)፤** ጥሩ፡ ወይን፤ ዘረ፡ መልካም፤ እስካሉ፡ ሕንባቡ፡ ታላላቅ፤ ጣዕሙ፡ ምቱቅ፡ የኾነ። ባለብለዎች፡ ግን፡ ስመ፡ ሀገር፤ የወይን፡ ቦታ፡ ይሉታል። ተክልኩኪ፡ ሜሬቀ። ወይን፡ ኅሩይ፡ ዘሜሬቅ። መረ፡ ወይን፡ ዘሜሬቅ፡ (ኤር፪፡ ፳፩። ኢሳ፭፡ ፪። ደራሲ)።

**ሥርቅ፤—ስርቆት፤—ሰሪቅ፡ ሰረቀ።**

**ሠረረ፤—በረረ፡ መጠቀ፤—ሰሪር፡ ሰረረ)፤**

**ሣርሮ፤ሮት፤(ሣረረ፡ ይሣርር። ዕብ፡ ሸራር፤ነግሠ፤ ኀየለ። ያሣድ)፤** መመሥረት፡ እጥልቆ፡ ቈፍሮ፡ መሠረት፡ መጣል፤ ማቆም፡ መትከል፤ ከዚያ፡ በኋላ፡ መንደቅ፤ መሥራት፤ መናስ፡ መገንባት። አቅይምከ፡ ሣርሮታ፡ ለምድር። ሣረሩ፡ ቤተ፡(መዝ፡ ፺፩። ሐጌ፪፡ ፲፱)።

**ሣራሪ፤(ሪት፡ ርያን፡ ያት)፤** የሚመሠርት፤ መሥራች፤ ሠሪ፡ ፈጣሪ። ሣራሪሃ፡ ለምድር፤ ሣራሪሃ፡ ለነፍስ፡(ኪዳ)።

**ተሣረረ፤** ተመሠረተ፤ተሠራ፤ታነጸ። እስመ፡ ደብ፡ ኵሑሕ፡ ተሣረረ። ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ዘተሣረረት፡(ማቴ፯፡ ፳፭። ዲድ፡ ፰። ቆላ፪፡ ፯)።

**ሡሩር፤ሥሩር፤** የተመሠረተ፡ የተሠራ፡ የተፈጠረ። እስመ፡ ለብእ፡ ሡሩር፡ እምነፍስ፡ ወሥጋ። ሥሩራት፡ ደብ፡ መንበረ፡ ወርቅ፡(ፊልክ። ማሕ፰፡ ፲፰)።

**ሡራሬ፤** ሥራ፡ አሠራር። ሕንጼሃ፡ ወሡራሬሃ፡ አዳም፡(ድጓ)።

**መሠረት፤(ታት)፤** በቁሙ፤ የሕንጻ፡ ሥር፤ መብቀያ፡(ኤቆር፡ ፲—፲፪። ሉቃ፮፡ ፵፰። መዝ፡ ፹፰)።

**መሥረተ፤ (ሣረረ)፤** መሠረተ፡ አጸና፤ ሠራ። መጽሐፍ፡ ግን፡ አመሥረተ፡ ይላል፤ ስሕተት፡ ነው። አመሥረታ፡ ለፍቅር። አመሥርተኒ፡ ደብ፡ መሠረተ፡ ወርቅ፡(ማር፡ ይሥ፪፡ ፱። አርጋ)።

**አመሥረተ፤** አስመሠረተ፤ መሠረት፡ አስጣለ።

**ተመሥረተ፤(ተሣረረ)፤** ተመሠረተ፡ መሠረት፡ ኾነ፤ ታነጸ፡ ተሠራ፤ ጸና። ዓዲሁ፡ ኢተመሥረተ፡(ሃይማኖትከሙ)፤ እስመ፡ ዘይትመሠረት፡ ይደልዎ፡ ይኩን፡ ጽኑዐ፡(አፈ፡ ድ፱)።

**ሣሬት፤—ሸረሬት፤—ሠረየ።**

**ሠተረ፤—ዘረጋ፤—ሰቲር፡ ሰተረ።**

**ሠጢር፤ሮት፤(ሠተረ፡ ይሠትር፡ ይሥትር። ዕብ፡ ሣታር። ዐረ፡ ሸተረ)፤** መሠንጠር፤ መቅደድ፤ መሠንጠቅ፤ መክፈል፤ መቍረጥ፡ መበጠስ፡ መቈንጸል፤ መግረፍ፡ መግጠብ፡ ማቍሰል። ለግብር፡ እኩይ፡ ሥትሮ፡ ገበዋቲሁ። አዘዘ፡ ይሥትርዎሙ፡ እስከ፡ ያስተርኢ፡ ንዋየ፡ ውስጦሙ። አዘዘ፡ ይስቅልዋ፡ በሥዕርታ፡ ወይሥትርዋ፡ ሠለስተ፡ ሰዓተ፡(ሢራ ፵፪፡ ፳። ዲድ፡ ፳፪። መቃ። ስንክ፡ ጥቅ፡ ፳፯፡ ፲፰፡ ፳፭)። ዘትርን፡ ተመልከት፤ የዚህ፡ ዘር፡ ነው።

**ተሠትረ፤** ተሠነተረ፤ ተገረፈ፤ ተገጠበ።

**ሥቱር፤(ራን፡ ራት፡ ትርት)፤** የተሠነተረ፤ ግርፍ፤ ገጣባ።

**ሥትረት፤** መቅደድ፡ መቀደድ፡ አቀዳደድ፤ ግርፋት፤ ቍስል፤ ስንበር።

**መሥተር፡ ትር፤(ሣትር)፤** መሠንተሪያ፤ መቅደጃ፤ የብረት፡ መግረፊያ፤ ጫፉ፡ የሚቈርጥ፡ የሚከትፍ። መሥተረ፡ ኀጺን። መሣትረ፡ ዘኀጺን። ሠጠቁ፡ ማእሰ፡ ሥጋሆሙ፡ በመጥባሕት፡ ዘኀጺን፡ (ስንክ፡ ሚያ፬። ታኅ፯)።

**መሥተር፤ (ዐረብ)፤** ማሥመሪያ፡ ተጋዳሚው፡ ዕንጨት፡ ወይም፡ ብረት። ሚዶ፡ ማበጠሪያ።

**ሠጠር፤** መሥመር፤ ወሰፈ፡ ርሳስ፡ ቀለም፡ ያለፈበት፤ ስንበሩ፡ ኀድፉ፡ ቢጋሩ።

# ዐ

**ዐ** ፤ ዐይን ፡ ስድስተኛ ፡ ፊደል ፤ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፤ ስሙ ፡ ዐይን ፡ ቍጥሩ ፡ ሰባ ፡ እኅኀዝ ፡ ቢኾን ፡ ፻ ፡ ሰብዓ ፡ ይባላል ።

**ዔ** ፤ (**አራም**) ፤ ስሙ ፡ ፊደል ፤ ዐይን ፡ ፀ ። በ ፀረብ ፡ በግእዝ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ዐይን ፡ የሚባለው ፤ በ አራም ፡ ቋንቋ ፡ ዔ ፡ ይባላል ። **ዔ ፡ ገበርከ ፡ ፍትሐ ፡ ወ ጽድቀ** ፡ (መዝ ፻፲፰ ፡ ፻፳፩ ። ሰቈ ፩ ፡ ፲፮ ። ፪ ፡ ፲፯ ። ፫ ፡ ፵፱ ። ፬ ፡ ፲፮) ።

**ዖ** ፤ (**ጽር ፡ ዖሜጋ**) ፤ ስሙ ፡ ፊደል ፡ ደኃ ራዊ ፤ ታላቅ ፡ ዖ ፡ የሚባል ፡ እንደ ፡ ታው ፡ ያለ ፡ የፊደ ላት ፡ ጽርእ ፡ መጨረሻና ፡ መደምደሚያ ፡ የአልፋ ፡ ትይ ዩና ፡ አንጻር ፡ የደኃራዊነት ፡ አምሳል ፡ (ራእ ፩ ፡ ፰ ። ፳፩ ፡ ፮ ። ፳፪ ፡ ፲፫) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ስመ ፡ አምላክ ፡ ይሉታል ።

**ዐብደ ፤—ሰነፈ ፤—አበደ ፡ አብደ ።**

**ዐብድ** ፤ (**ዐረ ። ዕብ ፡ ዔቤድ**) ፤ አገልጋይ ፤ ሎሌ ፤ ባሪያ ፤ የተገዛ ፡ የተማረከ ። **ዐብድ ፡ እልመሲሕ ። ዐብድ ፡ ናግ** ፡ (ዳን ፩ ፡ ፯) ።

**ዐቢጥ** ፤ **ጦት** ፤ (**ዐበጠ ፡ የዐብጥ ፡ ይዕ ብጥ ። ዕብ ፡ ዐቤጥ**) ፤ ማሰናከል ፤ ማስተጓጐል ፤ ከመንገድ ፡ ማውጣት ፤ በግድ ፡ መያዝ ፤ መሳብ ፡ መጐ ተት ፤ መግፋት ፡ ማዳፋት ። **ወለዘሂ ፡ ዐበጠከ ፡ አሐደ ፡ ምዕራፈ ፡ ሑር ፡ ምስሌሁ ፡ ክልኤተ ። ዐበጥዎ ፡ ለስ ምዖን ፡ ከመ ፡ ይጹር ፡ መስቀሎ** ፡ (ማቴ ፭ ፡ ፵፩ ። ፳፯ ፡ ፴፪ ። ማር ፲፭ ፡ ፳፩ ። ዲድ ፡ ፴፰ ። ድ ፫) ።

**ዐበየ ፤—እንቢ ፡ አለ ፤—አብይ ፡ አበየ ።**

**ዐብይ ፤ ዮት** ፤ (**ዐብየ ፡ የዐቢ ፡ ይዕበይ ። ዕብ ፡ ዐበህ ። ሱር ፡ ዐብያእ**) ፤ መወፈር ፡ መግ ዘፍ ፤ መደንደን ። ማደግ ፡ መብለጥ ፤ ታላቅ ፡ መኾን ። መክበር ፡ መግነን ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ማለት ፡ ማየል ፡ መጽ ናት ፡ መበርታት ። መብዛት ፡ መፈድፈድ ፤ መመንዘል ፡ መክበድ ። **ዐብየ ፡ በጥበብ ፡ ወበጸጋ ። እስመ ፡ አብ ፡ የዐብየኒ ። ዐብየ ፡ መርዶኬዎስ ። ዐብየ ፡ ወተሰዐለ ፡ ከመ ፡ አርዝ ። ዐብየ ፡ ማዕበለ ፡ ባሕር ። ወዐብየ ፡ ረኃብ ፡ ጥቀ ። ዐብየ ፡ ገዓሮሙ ፡ ዐብየት ፡ ኃጢአ ቶሙ** ፡ (ሉቃ ፪ ፡ ፶፪ ። ዮሐ ፲፬ ፡ ፳፰ ። አስቴ ፱ ፡ ፬ ። መዝ ፺፩ ፡ ፲፪ ። ዮናስ ፡ ፩ ። ዘፍ ፵፩ ፡ ፶፯ ። ፲፰ ፡ ፳ ። ፳፫ ፡ ፳፬) ።

**ዐቢይ** ፤ (**ያን ፡ ያት ፡ ባይ**) ፤ ታላቅ ፤ ገናና ፤ ብርቱ ፤ ብዙ ፡ ፍጹም ። **ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዐ ቢይ ፡ ኃይሉ ። ተኣምራት ፡ ዐቢያን ፡ ወስቡሓን ። አፉሁ ፡ ይነብብ ፡ ዐቢያተ ። ሀገር ፡ ዐባይ ። ዐቢይ ፡ ክርስቲያን** ፡ (መዝ ፡ ፻፵፮ ። ሔኖ ፶፯ ፡ ፱ ። ዳን ፯ ፡ ፰ ። ዮናስ ፡ ፪ ። ግብ ፳፯ ፡ ፳፰) ።

**ዐበይት** ፤ ታላቆች ፡ ታላላቆች ፤ አለቆች ፤ ሽማ ግሎች ። **ብርሃናት ፡ ዐበይት ። ዐበይት ፡ መዋቅሕት ። ዐበይት ፡ ሰብእ ። ዐበይት ፡ ነገድክሙ** ፡ (ዘፍ ፩ ፡ ፲፮ ። ራእ ፮ ፡ ፲ ። ሚክ ፯ ። ዘዳ ፳፱ ፡ ፱) ።

**ዕበይ** ፤ (**ያት**) ፤ ልዕልና ፡ ከፍታ ፡ ብልጫ ፤ ክብር ፤ ታላቅነት ፤ ገናንነት ፤ ብዛት ፤ ጽናት ። **ለዕበይ ፡ ወለክብር ። አንቲ ፡ ውእቱ ፡ ዕበዮሙ ፡ ለእስራኤል ። በከመ ፡ ዕበዩሁ ፡ ከማሁ ፡ ዕበየ ፡ ምሕረቱ ። ዕበየ ፡ ኃይሉ** ፡ (ኩፋ ፡ ፩ ። ዮዲ ፲፭ ፡ ፱ ። ሢራ ፪ ፡ ፲፰ ። ኤፌ ፩ ፡ ፲፱) ።

**አዕበየ** ፤ አሳደገ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፤ አላቀ ፤ አበ ለጠ ፤ አከበረ ፤ አገነነ ፤ አኰራ ፡ አጓደደ ፡ አስታበየ ። አበዛ ፡ አጸና ። **ጥበብ ፡ አዕበየትሙ ፡ ለደቂቃ ። አዕበዮ ፡ እ ግዚ ፡ ለሰሎሞን ። ኢታዕቢ ፡ ርእሰከ ። ታዐብዮ ፡ እ ምነ ፡ ቢጹ ። አዕበየ ፡ ምግባረ ። መጠነ ፡ አዕበየ ፡ አፉሁ** ፡ (ሢራ ፬ ፡ ፲፩ ። ፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፳፭ ። ሢራ ፯ ፡ ፬ ። ፲፩ ፡ ፳ ። መክ ፪ ፡ ፬ ። ዮዲ ፡ ፲፮) ። በአዕበየ ፡ ፈንታ ፡ አስተዐበየ ፡ ይላል ፡ እንዳማርኛው ፤ አያስኝም ። **ዘአስተ ዐበይክሙ ፡ በኃጢአትሙ ። አእምሮሰ ፡ ያስተፄቢ ። ወኢያስተፄቢ ፡ ልብ** ፡ (፩ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፩ ። ፲፫ ፡ ፬ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

(ጥ) **ተዐበየ** ፤ ታበየ ፤ ትቢተኛ ፡ ኾነ ፤ ኰራ ፡ ተጓ ደደ ፤ ተነፋ ፡ ዐበጠ ፤ ልቡ ፡ ሐሳቡ ። **በምንት ፡ ይትዔ በይ ፡ መሬት ፡ ወሐመድ ። ኢትትዐበይ ፡ በመዋዕለ ፡ ተጽናስከ ። ከመ ፡ ኢይትዐበይ ፡ ንእስ ፡ ላዕለ ፡ ዐ ቢይ ። ዲያቆናት ፡ ኢይትዐበዩ ፡ ለተልእኮ ፡ ጽኑሳን ። ተዐባዩ ፡ ላዕለ ፡ ነዳያን ። እስመ ፡ ተዐበየ ፡ ልብከ** ፡ (ሢራ ፲ ፡ ፱ና ፡ ፳፮ ። ቀሌ ። ዲድ ፡ ፲፮ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፮ ። ሕዝ፳፰ ፡ ፪) ።

**ዕቡይ** ፤ (**ያን ፡ ያት ፡ ቢት**) ፤ በቁሙ ፤ ትቢ ተኛ ፡ ኵሩ ፤ ልቡ ፡ ያበጠ ፡ የተነፋ ። **ዕቡየ ፡ ልብ ። ዕቡየ ፡ መንፈስ ። ዕቡየ ፡ ዐይን** ፡ (ምሳ ፲፮ ፡ ፲፬ ። መክ ፯ ፡ ፰ ። መዝ ፡ ፻) ።

**ትዕቢት** ፤ በቁሙ ፤ ትቢት ፤ ትቢተኛነት ፤ ኵ ራት ፡ የልብ ፡ እድገት ፡ ከፍታ ። **ኀበ ፡ ሀለወት ፡ ትዕ ቢት ፡ ህየ ፡ ሀሎ ፡ ኀሳር ። ትዕቢትሰ ፡ ጥንተ ፡ ኀጢ አት ፡ ይእቲ ፡ ዘቦአት ፡ ውስተ ፡ ፍጥረት ፤ እስመ ፡ ባቲ ፡ ወድቀ ፡ ሰይጣን ። ትዕቢተ ፡ ልቦሙ ። ዑቅ ፡ ኢትንብብ ፡ ነገረ ፡ ትዕቢት** ፡ (ጦቢ ፬ ፡ ፲፫ ። ፊ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፩ ። ሢራ ፫ ፡ ፳፬ ። ፴፰ ፡ ፲፱) ።

(ላ) **ተዓበየ** ፤ ተበላለጠ ፡ ተላላቀ ፡ ተወዳደረ ፤ እኔ ፡ እበልጥ ፡ እኔ ፡ እበልጥ ፡ ተባባለ ።

**አስተዓበየ** ፤ አበላለጠ ፤ አላላቀ ፤ አመዛዘነ ። ወአስተዓበየ ፡ አምጣነ ፡ ይፈድዮ ፡ ለወልደ ፡ እግዚ ፤ ከመ ፡ ሰማይ ፡ ወዘውስቴቱ ፤ ወምድር ፡ ወዘደቤሃ ፡ (መቃ ፡ ወን) ።

(ጥ) **ዐብሎ** ፤ ሎት ፤ (ዐበለ ፡ ይዔብል ፡ የዐብል) ፤ መሥራት ፤ መሣሪያ ፡ ማውጣት ፤ ፊት ፡ ጕጠቱን ፡ መደሻውን ፤ ቀጥሎ ፡ ሌላውን ፤ የብረት ። የተሠራውን ፡ ማደስ ፡ ማሾል ፤ መወልወል ፡ መስንገል ። መበለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ማዕበል** ፤ (ልት ። ዐረ ፡ ሚዕበለት) ፤ የብረት ፡ መሣሪያ ፤ ማረሻ ፡ ማጭድ ፤ ፍላጻ ፡ ጦር ፤ ሰይፍ ፡ ሳንጃ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ይፋቶች ፡ ሰይፋን ፡ ዐበሌ ፡ እንዲሉት ። ማዐበሉ ፡፡ ማዐበለ ፡ ኀጺን ፡ ማዐበል ፡ በሊኅ ፡ ልሳኖሙ ፡፡ ትወፅእ ፡ ማዐበልት ፡ ከመ ፡ መብረቅ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፳፩ ። ፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ። ኤር፲፱ ፡ ፰ ። ዘካ፱ ፡ ፲፱ ። ዕንባ ፡ ፲፩) ። የብዕለን ፡ ጥሬ ፡ ምብዓልን ፡ ተመልከት ።

**መዓብል** ፤ (ልት) ፤ መሣሪያዎች ፤ ፍላጾች ፤ ሰይፎች ፤ ሾተሎች ። በመዓብል ፡ ፈንታ ፡ ማዕበል ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። እሙንቱሰ ፡ ማዐበል ፡ ደሰጥሙ ፡ (መዝ ፡ ፸፱ ፡ ፳፩) ። ደሰጥሙ ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ በጽርእና ፡ በዕብራይስጥ ፡ የለም ።

(ላ) **ዐበለ** ፤ (ዕብ ፡ ያበል) ፤ ፈሰሰ ፡ ወረደ ፤ ጋለበ ፡ ኼደ ፤ ታወከ ፡ ተናጠ ፤ ተደረጠ ፤ የጐርፍ ፡ የባሕር ። ጐርፉ ፡ ይናብባል ፤ ውሃው ፡ ሣር ፡ ይበላል ፡ እንዲሉ ።

**ማዕበል** ፤ (ላት) ፤ በቁሙ ፤ የውሃ ፡ ሁከት ፤ ሞገድ ፤ ፈረሰኛ ፤ ጐርፍ ፤ የሚወስድ ፡ የሚያስጥም ፤ የሚያማታ ፡ የሚያንገላታ ። ወደፈኖሙ ፡ ማዐበል ፡፡ ማዐበለ ፡ ባሕር ፡፡ ማዐበል ፡ ዐቢይ ፡፡ ማዐበለ ፡ ማይ ፡፡ ማዐበላተ ፡ ውሒዛተ ፡ መናፍስት ፡ (ዘፀ፲፭ ፡ ፰ ። ኢዮ፴፮ ፡ ፴ ። ዮና፩ ፡ ፲፩ ። ኢሳ፶፯ ፡ ፲፱ ። ኪዳ) ።

**አማዕበለ** ፤ ማዕበል ፡ አስነሣ ፤ አወከ ፡ ደረጠ ፤ አናወጠ ፤ አጕረፈ ፤ የነፋስ ።

—፤ መላ ፤ ተማላ ፤ ወሰደ ፤ ይዞ ፡ ኼደ ። ገፋ ፡ አዳፋ ፤ ለጋ ፡ አማታ ፤ አንገላታ ፤ የማዕበል ። ይፈቅድ ፡ ኅሊናየ ፡ ይጽብት ፡ ዕመቀ ፡ አብሕርት ፤ ወያማዕብሉ ፡ መዋግድ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ዐበቅ** ፤—ዕከክ ፤—አበቅ ።

**ዐቢር** ፤ ሮት ፤ (ዐብረ ፡ የዐብር ፡ ይዕበር ። ዕብ ፡ ዐባር) ፤ ማለፍ ፤ መኼድ ፤ መሻገር ፤ የበታ ፡ የዘመን ። ማርጀት ፡ መድረቅ ፤ መምከን ፤ ርጥበት ፡ ልምላሜ ፡ ማጣት ፤ ድርቅ ፡ በጋ ፡ በና ፡ መኾን ። ዐብረ ፡ ሖሉ ፡ ወፍር ፡ ዘውስተ ፡ ገዳም ፡፡ ሖሉ ፡ ይየብስ ፡ ወየዐብር ፡፡ ኢየዐብር ፡ ወይንክሙ ፡፡ ዓመታት ፡ እንዘ ፡ ይዕበሩ ፡ (ኤር፳፫ ፡ ፲ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፯ ። ሚል፫ ፡ ፲፩ ። ኩፋ ፡ ፲፩) ።

**ዕቡር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ብርት) ፤ የደረቀ ፤ ደረቅ ። ሐምለ ፡ ቅብዕ ፡ ዕቡር ፡፡ ቀጢናን ፡ ወዕቡራን ፡ (ኢሳ፶፩ ፡ ፰ ። ዘፍ፵፩ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ፡ ፳፯) ።

**ዐባር** ፤ ድርቀት ፡ ድርቅ ፤ በጋ ፡ በና ፤ ችጋር ፡ ቀጠና ፤ ከዝናም ፡ ዕጦት ፡ የተነሣ ። ዐቢር ፡ ዐቢራ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ዐባረ ፡ ዝናም ፡፡ በዓመተ ፡ ዐባር ፡፡ ቀሠፍኩክሙ ፡ በዐባር ፡ (ኤር፲፬ ፡ ፩ ። ፲፯ ፡ ፰ ። ሐጌ፱ ፡ ፲፯) ።

**አዕበረ** ፤ አሳለፈ ፤ አሻገረ ። አደረቀ ፡ አመከነ ።

**ዕቤር** ፤ (ራት) ፤ ባልቴት ፤ ዕድሜዋ ፡ ከምሳ ፡ ዓመት ፡ ያለፈ ፤ ፈጽማ ፡ ያረጠች ፤ የመውለድ ፡ ተስፋ ፡ የቈረጠች ፤ ሙቀት ፡ ልምላሜ ፡ የተለያት ። ደራቂቻ ፡ ባልቴት ፡ እንዲሉ ። ወለእመ ፡ ኀረይከ ፡ ዕቤረ ፤ ኅረይ ፡ እንተ ፡ ስሳ ፡ ክረምታ ፡፡ መሐደምተ ፡ ዕቤራት ፡፡ ወመኳንኖን ፡ ለዕቤራት ፡ (፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፱ ። ፱ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፷፯) ።

**ዕቤራዊ** ፤ (ራይ) ፤ ሽማግሌ ፤ የባልቴት ፡ ባል ፤ ሚስቱ ፡ እኩያው ፡ የኾነች ፤ ወይም ፡ የምትበልጠው ።

**ዕቤራዊት** ፤ (ይት) ፤ አሮጊት ፤ ባልቴት ። እምከ ፡ ዕቤራዊት ፡፡ መአንዝርት ፡ ዕቤራይት ፡ (ሔኖ፴፪ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ መስ፲፰) ።

**ዔቦር** ፤ (ዕብ ፡ ዔቤር) ፤ የሰው ፡ ስም ፤ የሴም ፡ ፭ኛ ፡ ትውልድ ፡ (ዘፍ፲፩ ፡ ፲፬ ። ሉቃ፫ ፡ ፴፭) ።

**ዕብራዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ የዔቦር ፡ ዘር ፤ ወገን ፤ ከልጆች ፡ ልጆቹ ፡ አንዱ ። ዕብራዊ ፡ ዘእም ዕብራውያን ፡፡ አኮ ፡ ከመ ፡ አንስተ ፡ ግብጽ ፤ ዕብራውያት ፡ (ፊልጵ፫ ፡ ፭ ። ዘፀ፩ ፡ ፲፱) ።

**ዕብራዊት** ፤ (ጽር ፡ አንድሪያ) ፤ ወንዲላ ፤ ደረቅ ፡ ብርቱ ፤ ልባም ፤ ወንዳዊት ፡ ዐጅሬት ፡ የምትባል ፡ (ሚራ፳፯ ፡ ፱) ። ግእዝ ፡ ግን ፡ በዕብራዊት ፡ ፈንታ ፡ ብዕራዊት ፡ ይላል ፤ ብዕረን ፡ ተመልከት ።

**ዕብራይስጥ** ፤ ጢ ፤ (ጽር ፡ ሄብራዩስቲ) ፤ የዔቦር ፡ ቋንቋ ፤ እስራኤል ፡ የሚናገሩበት ፤ ኦሪት ፡ ነቢያት ፡ መዝመሪያ ፡ የተጣፉበት ፤ የብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ምንጭ ፡ የሱርስት ፡ የዐረብ ፤ የግእዝ ፡ ወንድም ። ሲቹ ንግረነ ፡ ዕብራይስጠ ፡፡ ጽሑፋት ፡ በዕብራይስጥ ፡፡ ወጸርሐ ፡ በነገረ ፡ ዕብራይስጢ ፡ (ኢሳ፴፮ ፡ ፲፩ ። ኩፋ ፡ ፲፪ ። ዮሴና ፡ ፴፱ ፡ ፲፰) ።

**ዕብሬት** ፤—ፌረቃ ፡ ተራ ፤—ባርዮ ፡ ባረየ ፤ እብሬት ።

**ዐጉል** ፤ (ዕብ ፡ ዓጎል) ፤ በቁሙ ፤ ዐጓጉል ክብ ፤ እንክብል ፤ ድንብልብል ፤ ቅርጽ ፡ ገጽ ፡ ማእዘን ፡ የሌለው ፤ የኳብ ፡ የኳስ ፡ ዐይነት ። ክኩብ ፡ አይገባ ፡ እንዲሉ ። እብነ ፡ ዘመነንዋ ፡ ኀይቅት ፡ (መዝ ፡ ፻፲፯) ።

**ዐግዋል** ፤ (ላት) ፤ አስኳል ፤ ዘለላ ፤ ሕንባቡ ፡ ፍሬው ፡ ክብ ፡ እንክብል ፡ የኾነ ። ይሁብዎ ፡ ፍሬሁ ፡ በበ ፡ ጊዜሁ ፡ ባለው ፤ በበ ፡ ዐግዋሊሁ ፡ ይላል ፡ (ማቴ ፳፩ ፡ ፵፩) ።

**ዐጌ** ፤ **(ግያት)** ፤ ተልባ ፤ የተልባ ፡ እግር ። ሐብሲ ፡ ዐጌ ። ልብሰ ፡ ዐጌ ። ልብስ ፡ ዘተአንመ ፡ በፀምር ፡ ወበዐጌ ። ወለብሰት ፡ አልባስ ፡ ዐግያት ፡ (ሕዝ ፡ ፫ ። ዘሌ ፡ ፫ ። ዘዳ፳፪ ፡ ፲፩ ። ዮዲ፲፮ ፡ ፰) ።

**ዕገሌ ፤—እከሌ ፤—እገሌ ።**

**ዐጊል** ፤ **ሎት** ፤ **(ዐገለ ፡ የዐግል ፡ ይዕግል)** ፤ ማደስ ፤ መሥራት ፤ መሰደር ፡ መደርደር ፤ መቈለል ፡ መከመር ፤ የደንጊያ ፤ የንጨት ። አዘዘ ፡ ቂርስ ፡ በእንተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ከመ ፡ ይትሐነጽ ። ወይዕግልዎ ፡ እንተ ፡ ሠለስቱ ፡ ዐግለ ፡ እብን ፤ ወእንተ ፡ አሐቲ ፡ ዐግለ ፡ ዕፀ ፡ (፩ዕዝ ፡ ፯ ፡ ፫፯ ፡ ፱) ።

—፤ መውሰድ ፡ መፈልፈል ፤ የልጅ ፡ የንቍላል ። ማገል ፤ መንቀል ፡ መትከል ፤ መቍረጥ ፡ መቈጥቈጥ ፤ መከተብ ፡ ማራኰብ ፤ ማረም ፡ መኰትኰት ፡ ዐፈር ፡ ማስታቀፍ ፤ ያታክልት ። ተክል ፡ ዐጋይ ፡ እንዲሉ ።

**ዐግል** ፤ **(ዕብ ፡ ጊል ፡ ጋል)** ፤ የደንጊያ ፡ ክምር ፤ ቍልል ፤ ስድር ፡ ድርድር ። ያታክልት ፡ ፈድፋ ፡ የዛፉ ፡ ተራ ፤ ቃዳው ፡ ተሰላው ፡ መደቡ ። ጓል ፡ ጕሊት ፡ መኰላ ፡ የረጋ ፡ መሬት ፡ ፍንቅሉ ።

**ዕጐል** ፤ **(ዕብ ፡ ዔጌል ። ሱር ፡ ዔግላእ ። ዐረ ፡ ዒጊል)** ፤ ልጅ ፤ ጥጃ ፡ እንቦሳ ፤ ግልገል ፤ ጫጩት ፤ ቡችላ ፤ ውርንጭላ ፤ ያትክልት ፡ ፍል ፤ ግልግል ፡ ችግኝ ። ምስጢሩ ፡ ስጋ ፡ ወጣት ፤ ርጥብ ፡ ጨቅላ ፤ ቡቃያ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ባላደገ ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። ዕጐለ ፡ አልሕምት ። ዕጐለ ፡ መራዕይ ። ዕጐለ ፡ አዕዋፍ ። ዕጐለ ፡ አናብስት ፡ (ዘዳ፴፪ ፡ ፲፱ ። ኛ፰ ፡ ፶፰ ። ኢዮ፳ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፶፫) ።

**ዕጕል** ፤ ልጆች ፤ እንቦሶች ፤ ግልገሎች ፤ ማጨቶች ፤ ቡችሎች ። ወንደገ ፡ ዕጐሊሁ ፡ ውሉደ ፡ ንሕሳነ ። ይትሐፀኑ ፡ ዕጐሊሆሙ ። ከመ ፡ ርግብ ፡ ምስለ ፡ ዕጐሊሃ ፡ (መቃ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፯ ። ፰ ፡ ፰) ።

**ዕጐልት** ፤ **(ላት)** ፤ ጊደር ፤ ያደገች ፤ የተጠቃች ፡ በካር ። ካዕሴ ፡ ዕጐልት ። ቅብዐ ፡ ዕጐልት ። ዕጐልተ ፡ ባሳን ። ዕጐላት ፡ እምዕጐሎን ፡ (ዕብ ፡ ፱ ፡ ፲፫ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፲፬ ። ዓሞ፬ ፡ ፩ ። ፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፯ ። ደራሲ) ።

**ዕጓል** ፤ ልጅ ፤ ወይፈን ፤ ደቦል ፡ ጠቦት ፤ ጡት ፡ የተወ ፡ ያደገ ፤ ራሱን ፡ የቻለ ። ጎትልያ ፡ ርእየት ፡ ከመ ፡ ሞተ ፡ ዕጓላ ። ዕጓለ ፡ ባሕም ፡ ሥቡሕ ። ይሁዳ ፡ ዕጓለ ፡ አንበሳ ። ዕጓለ ፡ አራዊተ ፡ ምድር ፡ (፬ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፲ ። ፩ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ። ዘፍ፵፱ ፡ ፱ ። ኢሳ፴ ፡ ፯) ።

**ዕጓለ ፡ ማውታ** ፤ የሙት ፡ ልጅ ፤ ለወንድም ፡ ለሴትም ፡ ይከታል ። ጓለይ ፡ እንዲል ፡ ትግሬ ። ኢየኀድገክሙ ፡ ትኩኑ ፡ ዕጓለ ፡ ማውታ ፡ (ዮሐ፲፬ ፡ ፲፰) ።

**ዕጓለ ፡ መሕያው** ፤ **(ምሕያው)** ፤ አዳም ፡ የአዳም ፡ ልጅ ፡ ሰው ። መሕያውን ፡ እይ ። ዕጓል ፡ ልጅ ፡ መ ፡ መሬት ፤ ሕያው ፡ ፈጣሪ ። ሕያው ፡ ከመሬት ፡ ያስገኘው ፤ ከምድር ፡ የወለደው ፡ የምድር ፡ ልጅ ፤ ምድር ፡ እናቱ ፡ ሕያው ፡ አባቱ ። አዳም ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ሉቃ፫ ፡ ፴፰) ። የአዳምን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ መሕያው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እመ ፡ ሕያው ፡ ይላል ፤ እም ፡ ሔዋን ፤ ዕጓልና ፡ ሕያው ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሰው ፤ የሔዋን ፡ ልጅ ፡ ማለት ፡ ነው ። እስመ ፡ ይእቲ ፡ እመ ፡ ኵሉ ፡ ሕያው ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፳) ። እመን ፡ ስአዳም ፤ ሕያውን ፡ ስሔዋን ፡ ሰጥቶ ፡ ቢፈቱት ፡ ግን ፤ አዳምን ፡ የሔዋን ፡ መገኛ ፤ እናቷ ፡ ወላጇ ፡ ያሰኛል ፤ ዕጓለ ፡ እመ ፡ ሕያው ፤ የአዳም ፡ ልጅ ፡ ሰው ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ መላሾች ፡ ያበጁት ፡ የቀጣጠሉት ፡ ነው ፤ ጽርኡ ፡ አንትሮፖስ ፡ ይላል ፤ ሰው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዕብራይስጡም ፡ አዳም ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ዕጓል ፡ አይልም ፤ ስንኳን ፡ የዘርፍ ፡ ዘርፍ ፡ አንድ ፡ ዘርፉ ፡ የለውም ። ሦስተኛ ፡ ደግሞ ፡ ጕርደ ፡ አሳጥሮ ፡ እምሔው ፡ ይላል ። ዕጓለ ፡ እምሔው ፤ ያያት ፡ የሚታ ፡ ልጅ ፤ አባቱና ፡ እያቱ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፤ እናቱም ፡ ታላቅ ፡ እኅቱ ፡ የኾነች ፡ ያሰኛል ። ያያት ፡ የሚታ ፡ ልጅ ፡ የሚባል ፡ እንደ ፡ ሞአብ ፡ እንደ ፡ ዓሞን ፡ ያለ ፤ እናቱ ፡ ካባቷ ፡ ወልዳ ፡ ልጅ ፡ ወንድሜ ፡ ብላ ፡ የምትጠራው ፡ የልጅ ፡ ወንድም ፡ ነው ፡ (ዘፍ፲፱ ፡ ፴፯—፴፰) ። ሎጥ ፡ ከሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ከኹለቱም ፡ ኹለት ፡ ወንዶች ፡ ወልዶ ፡ ለልጅ ፡ ልጆቹ ፡ አባትና ፡ አያት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ጌታም ፡ እንደ ፡ ኹለት ፡ ሴቶች ፡ መዠመሪያ ፡ ሰማይና ፡ ምድርን ፡ ኹለቱን ፡ ፈጥሮ ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከሰማይ ፡ ሰማያውያንን ፤ ከምድር ፡ መሬታውያንን ፡ ስላስገኘ ፤ ለፍጥረቱ ፡ እንዳባት ፡ እንዳያት ፡ ነውና ፤ እምሔው ፡ ማለት ፡ ይህንን ፡ ያሳያል ። በምሳሌም ፡ ደሮ ፡ ለልጆቿ ፡ አያት ፡ ነች ፡ ይባላል ፤ ርሱም ፡ ራሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ባባትነቱ ፡ ላይ ፡ አያትነቱን ፡ ለማስታወቅ ፤ ልዑል ፡ ራሱን ፡ በንስር ፡ በደርሆ ፡ መስሎታል ፡ (ዘዳ፴፪ ፡ ፲፩ ። ማቴ፳፫ ፡ ፴፯) ።

**ዕጓለ ፡ መሕያዊ** ፤ ሰብኣዊ ፤ አዳማዊ ፤ ምድራዊ ፤ መሬታዊ ። ፍጥረት ፡ ዕጓለ ፡ መሕየዊ ፤ በከመ ፡ ምግባረ ፡ መላእክት ፡ መንፈሳውያን ፡ ይትሌዐል ፡ እምግባረ ፡ ዕጓለ ፡ መሕየውያን ፡ (ፊልክ ፡ ፩፫ ፡ ፫) ።

**ዐገሎ** ፤ **ሎት** ፤ **(ዐገለ ፡ ይዔግል ፡ የዐግል ። ዐረ ፡ ዐጊለ)** ፤ መናጠግ ፡ መቀልጠፍ ፤ መቀማት ፡ መመንተፍ ፤ መበደል ፡ መግፋት ፤ መታገል ፡ ማጥቃት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዐገለ ፡ ፈንታ ፡ ተዐገለ ፡ ይላል ፤ በገበረ ፡ ፈንታ ፡ ተገበረ ፡ እንዲል ፤ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ለእመ ፡ ተዐገለ ፡ ልብሰ ። ዘይትዔገል ፡ ነዳየ ። ይትዔገሎ ፡ ባዕል ፡ ለነዳይ ። ተዐገለ ፡ ለነሃቂ ፡ መንግሥት ፡ እምእጒሁ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፩ ። ምሳ፳፱ ፡ ፴፩ ። ሢራ፲፫ ፡ ፲፱ ። ዮሴፍ) ።

**ዐጋሊ** ፤ **(ተዐጋሊ)** ፤ የሚቀማ ፡ ቀሚ ፤ ቀማኛ ፤ በደለኛ ። ንጉሥ ፡ ነዳየ ፡ አእምሮ ፡ ጸባሒተ ፡ ዐቢየ ፡ ተዐጋሌ ፡ ይከውን ፡ (ምሳ፳፰ ፡ ፲፮ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፭) ።

**አዐገለ** ፤ **አስተዐገለ** ፤ አስቀማ ፡ አስበደለ ፡ ግፍ ፡ አሠራ ።

**መዐግል** ፤ **መስተዐግል** ፤ የሚቀማ ፡ የሚያስቀማ ፤ አስቀሚ ፤ ቀማኛ ። ርኩስ ፡ ወመስተዐግል ።

እምብዝኆሙ ፡ ለመስተዐግላን ፡ የዐወይዉ ፡ ወይ ግዕኑ ፡ (ኤፌ፭ ፡ ፭ ። ኢዮ፴ ፡ ፲) ።

**ተዐገለ** ፤ (ተደራጊ) ፤ ተቀማ ፤ ተነጠቀ ፤ ተገፋ ፤ ተበደለ ።

**ዕጉል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ግልት) ፤ የተቀማ ፤ የተነጠቀ ፤ የጠፋ ፤ የተሰረቀ ። ደግብኡ ፡ ንዋየ ፡ ዕጉለ ፡ እምተዐጋሊ ፡ ዘሰንታሁ ። ለእመ ፡ ተወሰጠ ፡ ዐይኑ ፡ ዕጉል ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፭) ።

**ትዕግልት** ፤ በቁሙ ፤ ትግል ። ቅሚያ ፤ ስርቆት ፤ ግፍ ፡ በደል ። ወይእቲ ፡ ትዕግልት ። ዘይትዔገል ፡ ትዕግልተ ፡ እኩየ ። ዘሎ ፡ ትዕግልት ፡ ውስቴታ ፡ (ዓሞ፱ ፡ ፰ ። ሰሎ፲ ፡ ፲ ። ኤር፮ ፡ ፯) ።

**ተዓገለ** ፤ (ተደራራጊ) ፤ ታገለ ፤ ተጋገለ ፤ ተቃማ ፡ ተናጠቀ ፤ ተሳረቀ ። (ግጥም) ፤ እግዜር ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እንታገል ፡ አሰኝ ፤ ሬ ፡ እንደኢት ፡ ፈጥሮ ፡ ሲጥለኝ ፤ አስመጣሉም ፡ ታውቋል ፤ በያዕቆብ ፡ ትግል ፡ (ዘፍ፴፪ ፡ ፳፬—፳፱) ።

**አስተዓገለ** ፤ (አደራራጊ) ፤ አስተጋገለ ፤ አቀማማ ፤ አነጣጠቀ ።

**መስተዓግል** ፤ የሚያቀማማ ፤ የቀማኛ ፡ ዐጋዥ ፡ ረዳት ፤ ዐብሮ ፡ የሚሰርቅ ፡ የሚቀማ ።

(ጥ) **ዐግሠ** ፤ ሦት ፤ (ዐገሠ ፡ ይዔግሥ ፡ የዐግሥ ። ዐሬ ፡ ዐጀሰ) ፤ ማስታገሥ ፤ ማቆም ፡ መግታት ፤ ማቈየት ፡ ማሰንበት ፤ ማስቀረት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዐገሠ ፡ ፈንታ ፡ አስተዐገሠ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ፤ ፈሥሐን ፡ እይ ። እሞን ፡ ታስተዔግሦን ፡ ወትብሎን ፡ ጽንዓ ። አቡሃ ፡ ኮነ ፡ ያስተዔግሣ ። ተስፋ ፡ ያጸንዕ ፡ ወያስተዔግሥ ፡ (ስንክ ፡ መስ ፡ ፳ና ፡ ፲፫ ። አፈ ፡ ድ፲) ።

**ዐጋሢ** ፤ (መዐግሥ ፤ መስተዐግሥ) ፤ የሚያስታግሥ ፤ አስታጋሽ ፤ አስቻይ ።

**ተዐገሠ** ፤ ታገሠ ፤ ተገታ ፤ ቈየ ፤ ጠበቀ ፤ ደጀ ፡ ጠና ፤ ቻለ ፡ ተሸከመ ። ደናግል ፡ ወመዓስብ ፡ ይትዐገሣ ፤ ወእመሰ ፡ ኢክህላ ፡ ተዐግሦ ፡ ለያውስባ ። ተዐገሡ ፡ ዓዲ ፡ ኅሡሰ ፡ መዋዕለ ። ዘይትዔገሥ ፡ ለእግዚ ። እለ ፡ ይትዔገሡ ፡ ሐዘናተ ፡ ወጻዕቃተ ፡ (ቀሌ ። ዮዲ፰ ፡ ፴ ። ሚሬ፳፰ ፡ ፳ ። ማር ፡ ይሥ፲፫) ።

—፤ ተቻለ ፡ የሚቻል ፡ ተቻይ ፡ ኾነ ፤ መከራው ፡ ሸከሙ ።

**ተዐጋሢ** ፤ (ሢት ፡ ሥያን ፡ ያት) ፤ የሚታገሥ ፤ ታጋሽ ፡ ቻይ ፤ ልበ ፡ ሰፊ ፡ ነገር ፡ ዐላፊ ። ትዐጋሢ ፡ እምፀርፈት ። ኩኑ ፡ ጽኑዓነ ፡ ወኀያላነ ፡ ወተዐጋሥያነ ፡ ወማእምራነ ። ተዐጋሥያን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲ ። ዮሴፍ ። አፈ ፡ ተ፴) ።

**ዕጉሥ** ፤ (ሣን ፡ ሣት ፡ ግሥት) ፤ በቁሙ ፤ የታገሠ ፤ ቻይ ፤ ትዕግሥተኛ ። ዕጉሥ ፡ ዘእንበለ ፡ መዐት ። መምህር ፡ የዋህ ፡ ወዕጉሥ ። ጕንደዩ ፡ ዕጉሣኒሆሙ ፡ (ቅዳ ፡ ኢዲ ። ዲድ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ መጋ፲፫) ።

**መስተዐግሥ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ይኄይስ ፡ መስተዐግሥ ። ነፍስ ፡ መስተዐግሥት ። በእንተ ፡ መስተዐግማን ፡ (መክ፯ ፡ ፲ ። ሚሬ፳፯ ፡ ፲፭ ። ኪዳ) ።

**ትዕግሥት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፤ መታገሥ ፤ መቈየት ፤ ታጋሽነት ፤ አንዋ ፡ መንፈስ ። ሰማዕክሙ ፡ ትዕግሥቶ ፡ ለኢዮብ ። ዘይሰትያ ፡ ለትዕግሥት ፡ ከመ ፡ ማይ ። ዕድሜ ፡ ዘትዕግሥት ። በእንተ ፡ ትዕግሥታተ ፡ ነፍሳት ፡ ናስተበቍዕ ፡ (ያዕ፭ ፡ ፲፩ ። ኢዮ፴፬ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴ ። ኪዳ) ።

**ተዓገሠ** ፤ ተጋገሠ ፡ ተቻቻለ ፤ ርስ ፡ በርሱ ።

**አስተዓገሠ** ፤ አቻቻለ ፡ አስተጋገሠ ፤ መኾመሬያውን ፡ ዐግሦን ፡ ተመልከት ። እሞን ፡ ታስተዔግሦን ፤ ወትብሎን ፡ ጽንዓ ፡ (ስንክ ፡ መስ፳) ።

**መስተዓግሥ** ፤ የሚያቻችል ፤ የሚያስተጋግሥ ፤ አቻቻይ ።

**ዕጕሥታር** ፤—ሬት ፤—ዕጉትማር ፡ ዐገተ ።

**ዐጊት** ፤ ቶት ፤ (ዐገተ ፡ የዐግት ፡ ይዕግት) ፤ ማገት ፤ ዋስን ፡ መያዝ ፤ ማሰር ። መክበብ ፡ ማጠር ፤ መወሰን ፤ ዙሪያውን ፡ መዝጋት ፤ መግጠም ፡ የከፉ ፡ የበጎ ። ዐገቱኒ ፡ ከመ ፡ ንህብ ፡ መዓረ ። ናሁ ፡ ማይ ፡ ዐገተኪ ። ዕግትዎ ፡ ለንጉሥ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፯ ። ናሑ፫ ፡ ፲፬ ። ፬ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፳) ።

**አዕገተ** ፤ አሳገተ ፤ አስከበበ ፤ አሳጠረ ፤ ወጥመድ ፡ አኖረ ።

**ማዕገት** ፤ ከባቢ ፡ ጠር ፤ ደበቅ ፡ ሰራዊት ፤ ወጥመድ ፤ አሽክላ ። ሕንበሩ ፡ ማዕገተ ። ወማዕገቶሙ ፡ ለእስራኤል ። ወይሠግር ፡ በማዕገትየ ፡ (መሳ፱ ፡ ፳፭ ። ፳ ፡ ፴፫ ። ሕዝ፲፱ ፡ ፲፫) ።

—፤ ዕርድ ፤ ምሽግ ፤ አንባ ፤ ከተማ ፤ መክበቢያ ፤ መከበቢያ ፤ የተወሰነ ፡ ቦታ ። ይትከወሱ ፡ በውስተ ፡ ማዕገቶሙ ። ወእማዕገት ፡ ከሃከ ፡ ውእቱ ፡ መለኮት ፡ (ሚክ፯ ፡ ፲፯ ። ቁር) ።

**ተዐግተ** ፤ ታገተ ፤ ተያዘ ፡ ታሰረ ። ተከበበ ፤ ተዘጋ ፤ ታጠረ ። ተዐግተት ፡ ሀገር ። ዝንቱ ፡ መዓር ፡ ተዐግተ ፡ በንህብ ፡ (፫ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፱) ።

**ዕጉት** ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ግት) ፤ የታገተ ፤ የታሰረ ፡ የተከበበ ። እስመ ፡ አነ ፡ ዕጉት ፡ በዝንቱ ፡ ሞቅሕ ። ዕጉት ፡ ውስተ ፡ አረፋቲሃ ፡ (ግብ፳፰ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፺፭) ።

**ዕጉትማር** ፤ (ዕጉት ፡ ማዕር ፤ ሥዕረ) ፤ ቃጫ ፤ ሬት ፡ የሬት ፡ ወገን ፤ መራራ ፡ ክፉ ፡ ቅጠል ፡ ሽቱና ፡ መድኀኒት ፡ የሚኾን ። ዕዉደ ፡ ዐጽቅ ፡ ከቡበ ፡ ቈጽል ፡ ማለት ፡ ነው ። በተረትም ፡ አቀማመጡ ፡ ሰሙኛ ፡ ጥርሱ ፡ ማጭድኛ ፡ ይባላል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በቅሐመ ፡ ፈንታ ፡ ቀምሐ ፡ እንዲል ፡ በዕጉትም ፡ ፈንታ ፡ ዕጕሥት ፡ ይላል ። በከመ ፡ ያማስኖ ፡ ዕጕሥታር ፡ ለጣዕመ ፡ መዓር ፤ ከማሁ ፡ ያማስኖ ፡ ግዕዝ ፡ እኩይ ፡ ለምግባረ ፡ ሠናይ ። ደመ ፡ ዕጕሥታር ። ማየ ፡ ዕጕሥታር ፡ (ፈላስ ። መጽ ፡ ምስ ። ኤር፳፫ ፡ ፲፭ ። ራእ፰ ፡ ፲፩) ።



ዕሬትማር ፡

**ዕግተት** ፤ መከበብ ፤ መከበብ ፤ አከባበብ ፤ ከበባ ። ወሶበ ፡ ጸንዐ ፡ ባዕሴሆሙ ፡ ዕግተት ፡ ወፀኡ ፡ በሌሊት ። ለእመ ፡ አእመረ ፡ ገብር ፡ ዕግተተ ፡ በእንተ ፡ ሀዩዶተ ፡ እግዝእቱ ፡ ወኢረድኣ ፡ ያውዕይዎ ፡ (ዮሴፍ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፰) ።

**ዐድ** ፤ (ዕብራ) ፤ ዘልፈ ፤ ለዓለም ፤ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ ጊዜ ፡ ዘመን ። ይነግሥ ፡ እግዚ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ወዐድ ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ወዓዲ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፀ፲፭ ፡ ፲፰) ።

**ዓዲ** ፤—ዳግመኛ ፤—ዐድይ ፡ ዐደየ ።

**ዕዳ** ፤—በቁሙ ፤—ዐድይ ፡ ዐደየ ።

**ዕድ** ፤—እድ ፤—አዲው ፡ አደወ ።

**ዕድ** ፤—ወንድ ፤—ዐዲው ፡ ዐደወ ፤

**ዐዲድ** ፤ (ዐደ ፤ ዐደደ ፡ የዐድድ ፡ ይዕድድ ። ዐረ ፡ ዐደ ፤ ቈጠረ) ፤ ማራቅ ፡ ማስገድ ፡ ማዋረድ ፤ በፊትና ፡ በቀኝ ፡ የነበረውን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ማድረግ ። ብርሃን ፡ ዘዐ(ሰ)ደይ ፡ ለጽልመት ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ) ። የዐደደ ፡ ፍች ፡ ስለ ፡ ታጣ ፡ ዐደደ ፡ ወደ ፡ ሰደደ ፡ ተለውጧል ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ አለ ።

**ዕደድ** ፤ ኀባር ፡ ውርደት ፤ ጕስቍልና ፡ ኀዴት ። ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ እንተ ፡ አፍቀረ ፡ ዕደደ ፤ እምነ ፡ የሶ ፡ ሶበ ፡ ኢተወልደ ፤ ያግብእከ ፡ ጊዜ ፡ ፈቀደ ፡ (ደራሲ) ። ብዙው ፡ መጣፍ ፡ ግን ፡ በዕደድ ፡ ፈንታ ፡ እበድ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ዐደዳ ፡ ዲደን ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ዐደዳ ፡ ንዝንዝ ፡ ውዝግብ ፡ ጭቅጭቅ ፤ ዲደን ፡ ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ነው ።

**ዐዲው** ፤ ዎት ፤ (ዐደወ ፡ የዐዱ ፡ ይዕዱ ። ዕብ ፡ ዐዳህ ። ሱር ፡ ዐዳእ ። ዐረ ፡ ዐደእ) ፤ መሻገር ፤ ማለፍ ፤ መዝለል ፡ መራመድ ፤ ዐልፎ ፡ ዘሎ ፡ ተራምዶ ፡ መኼድ ። መብዛት ፡ መትረፍ ፤ ከልክ ፡ ማለፍ ፤ መተላለፍ ። እመኒ ፡ ዐዶከ ፡ ማየ ። ዐድዊ ፡ ፈለገ ። ዐደወ ፡ እሞት ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ። ወዐዲዎን ፡ እምተዓይን ። እስከ ፡ ዐደዉ ፡ እምደማስቆ ። ዘብዙኅ ፡ እመስፈርት ፡ የዐዱ ፡ (ኢሳ፵፫ ፡ ፪ ። ፵፯ ፡ ፪ ። ዮሐ፭ ፡ ፳፬ ። ዮዲ፲፫ ፡ ፲ ። ፲፭ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ መስ፳፰) ። በዐደወ ፡ ፈንታ ፡ ተዐደወ ፡ ይላል ፤ አድራጊውን ፡ በተደራጊ ፤ የስሕተት ፡ መንገድ ፡ ነው ፤ አያሰኝም ። እትዐደዋ ፡ ለአረፍት ። ዘይትዐዶ ፡ ወሰኖ ። ድንጊ ፡ ወንትዐዶኪ ። ጸሎተ ፡ ነዳይ ፡ ትትዐዶ ፡ እምደመና ። ኢትዐደዊ ፡ እምወሰንኪ ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። ሆሴ፭ ፡ ፲ ። ኢሳ፶፭ ፡ ፳፫ ። ሢራ፴፫ ፡ ፳፭ ። ቅዳ) ። ቃዕደውንና ፡ አንቃዕደወን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ፤ ሰንቀወ ፡ የንቀወ ፡ ዘር ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

**ዐዳዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ የሚሻገር ፤ ተሻጋሪ ፤ ዐላፊ ፡ ተላላፊ ። በዐዳዊ ፡ ፈንታ ፡ ተዐዳዊ ፡ ይላል ፤ ተ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ፤ የግእዝ ፡ አይደለም ። ተዐዳዊ ፡ ትእዛዝ ። ተዐዳዊ ፡ ሕግ ። ተዐዳዊተ ፡ ሕግ ፡ (መቃ ። ጥበ፫ ፡ ፲፬ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳፱ ፡ ፳) ።

**ምዕዳው** ፤ (ዋት) ፤ መሻገሪያ ፤ ሜዳ ፡ መልክ ፤ ድልድይ ፤ ታንኳ ። አልብየ ፡ ምዕዳው ፡ ዘእንበለ ፡ በተንከተመ ፡ ሃይማኖት ። ማርያም ፡ ምዕዳው ፡ እምሠርም ፤ ዘጽድቅ ፡ ተንከተም ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ደራሲ) ።

**አዕደወ** ፤ አሻገረ ፤ አሳለፈ ። አዕድዎ ፡ አዕደዎሙ ፡ ገብርከ ። አዕደዎቶሙ ፡ ባሕረ ፡ መፍርሀ ። ወአዕደወኒ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡ (ኢያ፯ ፡ ፯ ። ጥበ፲ ፡ ፲፰ ። ሕዝ፵፯ ፡ ፫) ።

**ማዕዶ** ፤ ማዕዶት) ፤ ማዶ ፤ አሻገር ፡ ከወንዝ ፡ ወዲያ ፡ ወይም ፡ ወዲህ ፡ ያለ ፡ በታ ፤ ትይዩ ፡ አንጻር ፤ ፊት ፡ ለፊት ፤ አቅጣጫ ፡ አፍዝዣ ። የፋሲካ ፡ ስም ። ማዕዶተ ፡ ዮርዳኖስ ። ነገሥት ፡ እለ ፡ ማዕዶተ ፡ ባሕር ። ወበጺሖ ፡ ማዕዶቱ ። ቀኔማ ፡ ዘማዕዶት ፡ (ኢሳ፰ ፡ ፳፫ ። ኤር፴፪ ፡ ፳ ። ማቴ፰ ፡ ፳፰ ። ድጓ) ።

**መዓድው** ፤ ማዶዎች ፤ አሻገሮች ፤ ወንዝና ፡ ባሕር ፡ የለያቸው ፤ የከፈላቸው ።

**ተዐድወ** ፤ ታለፈ ፤ ተዘለለ ፤ ወንዙ ፡ ሕጉ ፡ ትእዛዙ ።

**ዕድው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ዱት) ፤ የታለፈ ፡ የተዘለለ ፤ ሌሎች ፡ ያለፉት ፤ የተሻገሩት ።

**ዕድው** ፤ ያለፈ ፤ የተሻገረ ፤ ወንዝን ፡ ሕግን ፡ ዐልፎ ፡ ተሻግሮ ፡ የኼደ ።

**ዕድው** ፤ (ዋሬ ። ዐረ ፡ ዐዱው) ፤ ወደረኛ ፤ ባለጋራ ፤ ደመኛ ፤ ጠላት ። ይከውነከ ፡ ዕድወ ። ዘኢከነ ፡ ምስሌየ ፡ ዕድውየ ፡ ውእቱ ። ለእመ ፡ ረከብኩ ፡ ዕድዋኒሃ ፡ ለሃይማኖት ። ዕድዋኒነ ፡ (ሢራ፮ ፡ ፲፪ ። ማቴ፲፪ ፡ ፴ ። ተረ ፡ ኤር ። ቄር) ።

**ዕድወት** ፤ መሻገር ፤ ማለፍ ፤ መታለፍ ፤ መተላለፍ ፤ ዕልፈት ፡ ዐለፌታ ፤ እልፍ ፡ ትርፍ ። ዕድወተ ፡ ቀዳማይ ፡ ብእሲ ፤ ዕድወቱ ፡ ለአዳም ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ዕድ** ፤ (ብ ፡ ዕደው) ፤ ወንድ ፡ ተባት ፤ ብእሲ ። ዕድ ፡ ወአንስት ። ዕደው ፡ ጠቢባን ። ዕደወ ፡ ስም ፡ (ቅዳ ። ሢራ፳፮ ፡ ፳፰ ። ዘፍ፮ ፡ ፬) ።

**ዕዳው** ፤ (ዋት) ፤ መንታ ፡ መንገድ ፤ ምስቅል ፡ መንገድ ። ኀበ ፡ ዕዳዋት ፡ (ማር፲፮ ፡ ፬) ።

**ተዓደወ** ፤ (ተደራራጊ) ፤ ተሻጋገረ ፡ ተላለፈ ፤ ርስ ፡ በርሱ ።

**አስተዓደወ** ፤ አሸጋገረ ፤ አስተላለፈ ።

**ምስትዕዳው** ፤ መሸጋገሪያ ፡ መተላለፊያ ፤ ማሸጋገሪያ ፡ ማስተላለፊያ ።

**ዕዳው ፤—ጕድፍ ፤—አዲው ፡ አደወ ።**

**ዐድይ ፤ዮት ፤ (ዐደየ ፡ የዐዲ ፡ ይዕዲ ። ዐረ ፡ ዐደይ)** ፤ መክፈል ፤ ብድርን ፡ መመለስ ፤ የክፉ ፡ የበጎ ።

**ዐዳዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት)** ፤ የሚከፍል ፤ ከፋይ ።

**ዕዳ** ፤ በቁሙ ፡ ብድር ፤ ልቃ ፤ የብድር ፡ ገንዘብ ። ኅደገ ፡ ሎቱ ፡ ዕዳሁ ። ሰመኑ ፡ እፌዲ ፡ ዕዳ ። አግብእ ፡ አኅዘ ፡ ዕዳሁ ። ንቅንየ ፡ ለነዳይ ፡ በዕዳነ ፡ (ማቴ ፲፰ ፡ ፳፯ ። ኢሳ ፶ ፡ ፩ ። ሕዝ ፲፰ ፡ ፯ ። ዓሞ ፰ ፡ ፯) ።

**ዕዳ** ፤ በደል ፤ ኀጢአት ፡ ክፋት ፤ መቀሮ ፡ ቅጣት ። ሐልቦ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዕዳ ። ዳእሙ ፡ ይደንዕ ፡ ዕዳሃ ፡ ለዛቲ ፡ ኀጢአት ። ሶበ ፡ ኢሰተደይክሙ ፡ ዝናመ ፡ ትምህርት ፡ እምኢክነክሙ ፡ ዕዳ ፤ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፱ ፡ ፬ና ፡ ፲፫ ። አፈ ፡ ድ፲) ።

**ዕዳዊ** ፤ ባለዳ ፤ አበዳሪ ፤ ወይም ፡ ተበዳሪ ። ነገረ ፡ ዕዳውያን ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯) ።

**ዐደይ ፤ (ትግ ፡ ሐበ)** ፤ ሹጥ ፡ የሆድ ፡ ትል ፤ ኮሶ ፡ የሚባል ። በቁሙ ፡ ብማቴ ፡ አበባ ። (ግጥም) ፤ ዐደይ ፡ ዐደይ ፡ የመስከረም ፤ ሱስንዮስ ፡ ንጉሠ ፡ ሮም ።

**ዓዲ ፤ (ዕብ ፡ ዖድ)** ፤ ኀኢስ ፡ አገባብ ፤ ገና ፤ ደግሞ ፤ ዳግመኛ ፤ አኹን ፤ እንጂ ፤ ዋዌ ፡ ም ፡ ይኾናል ። እንጂ ፡ ም ፡ ሲኾን ፤ ዐቢይ ፡ አገባብ ፡ ነው ፤ ዳግመኛነቱን ፡ ግን ፡ አይለቅም ። ዓዲ ፡ ኢበጽሐ ፡ ጊዜሁ ። ተዐገሥ ፡ ዓዲ ፡ ኀሙሰ ፡ መዋዕለ ። እስከ ፡ ዓዲሁ ። ዓዲ ፡ ሊተ ፤ (ዮሐ ፯ ፡ ፰ ። ዮዲ ፰ ፡ ፴ ። አፈ ፡ ድ፱ ። ፊልጵ ፬ ፡ ፳፯) ።

ዓዲየ ፤ከ ፡ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ ፤ ዓዲነ ፤ እያለ ፡ እስከ ፡ ሥር ፡ ይዘረዝራል ። ዋዌ ፡ ሲኾን ፤ ሄሮድስ ፡ ወጲላጦስ ፡ ተንሥኡ ፡ ቅድመ ፡ እንበለ ፡ ፍትሕ ፡ ላዕለ ፡ አቡሁ ፡ ቀብዊ ፡ ወላዕለ ፡ ወልዱ ፡ ቅቡዕ ፤ ከማሆሙ ፡ ዓዲ ፡ ተንሥኡ ፡ በግፍዕ ። ዓዲ ፡ ኢታንክርዎ ፡ ለዘትመጽእ ፡ ኅቡአ ፤ መክራ ፡ ዘሃይማኖት ፡ እስመ ፡ ፍዳ ፡ ዕሴት ፡ አኀዊነ ፤ (ቅኔ) ። (ዐርኬ ፲፬ ፡ ቍ፳፬) ።

**ዓዶት ፤ (ትግ ፡ ሐበ ። ዕብ ፡ ዳት)** ፤ ሕግ ፡ ሥርዐት ፤ የአበው ፡ ትውፊት ፤ ልማደ ፡ ሀገር ፤ (ማር፲፩ ፡ ፫) ። ሐማሴኖች ፡ እናቴ ፡ ሲሉ ፡ ዓደይ ፤ ጋሎችም ፡ ዓደቶ ፡ የሚሉት ፡ ከዚህ ፡ ይስማማል ።

**ዐደለ** ፤ በቁሙ ፤ ሰጠ ፡ አሳለፈ ፡ (ዐማርኛ) ። ከፈለን ፡ ተመልከት ።

**ዐድል ፤ (ዐረ ፡ ፍርድ ። ዕብ ፡ ክቶኔት)** ፤ ኪታ ፡ ጥብቆ ፤ ሰበላ ፡ የውስጥ ፡ ልብስ ፤ ዐጭር ፡ የገላ ፡ ቀሚስ ፤ ኩታ ፡ መጐናጸፊያ ፤ ልግም ፡ በገላ ፤ የክት ፡ ሸማ ፡ ኮት ፤ ጀባ ፡ ካባ ፤ የሚደረብ ።

**አዕዳል ፤ (ዕብ ፡ ክትኖት ። ጽር ፡ ኪቶኔስ)** ፤ ኪቶች ፤ ቀሚሶች ፤ ኮቶች ፤ ኵታዎች ። ወገብረ ፡ ሎሙ ፡ አዕዳለ ፡ ማእሰ ፤ ወአልበሶሙ ፤ (ዘፍ፫ ፡ ፳፩) ። ማእስ ፡ የሚያሞቅ ፡ የሚለሰልስ ፤ ጠጕራም ፡ የደበሎ ፡ ቀሚስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ትርጓሜ ፡ አራት ፡ የጥንቸል ፡ ቈርበት ፡ ነው ፡ ይላል ። አልበሶሙ ፡ ማለት ፤ ልብሱ ፡ ሳይቀር ፡ ፍርዱንም ፡ ያሳያል ፤ ፍርድ ፡ ልበስ ፡ እንዲሉ ።

**ዐደመ ፤—ቀላ ፡ አማረ ፤—አዳም ፡ አደመ ።**

(ጥ) **ዐድሞ ፤ሞት ፤ (ዐደመ ፡ ይዔድም ፡ የዐድም ። ዐረ ፡ ዐደ ። ዕብ ፡ ያዓድ)** ፤ ማደም ፤ መቅጠር ፡ ጊዜ ፡ መወሰን ፤ ቀን ፡ መስጠት ፤ ሰዐርግ ፡ ለጉባኤ ፤ ለኹሉ ። ሰብዓ ፡ ሰንበታተ ፡ ዐድሞሙ ፡ ለሕዝብከ ። አኮኑ ፡ ዐደምከ ፡ ዕድሜ ። ወአስተብቍዖ ፡ ከመ ፡ የዐድሞ ፡ እስከ ፡ ሠሉስ ፡ ዕለት ። እዔድመክሙ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፤ (ዳን ፱ ፡ ፳፬ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ። ፬ ፡ ፲፯ ። ታሪ) ።

**ተዐደመ** ፤ ታደመ ፤ ተቀጠረ ፤ ተወሰነ ። በመዋዕል ፡ ዘተዐደመ ። ዐስብ ፡ ዘተዐደመት ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፬ ። ፴፯) ።

**ዕዱም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ድምት)** ፤ የታደመ ፤ የተቀጠረ ፤ ዕድመኛ ።

**ዕድሜ ፤ (ያት)** ፤ በቁሙ ፤ ቀጠሮ ፤ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፤ ዘመን ፡ ወራት ፤ የሳምንት ፡ የወር ፡ ያመት ፡ በዓል ። ሄሮድያኖስ ፡ የአምር ፡ ዕድሜሁ ። ኢኀልቀ ፡ ዕድሜሁ ፡ ለራእይ ። ዕድሜ ፡ ሐዘን ። በበዓላት ፡ ወበዕድሜያት ፤ (ኤርሚ ፰ ። ዳን፰ ፡ ፲፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፬ ። ሕዝ፵፭ ፡ ፲፯) ።

**ተዓደመ** ፤ ተቃጠረ ፤ ተቀጣጠረ ፤ ተዋዋለ ፤ ተስማማ ። ተዓደሙ ፡ እስከ ፡ ሠርቀ ፡ ወርኅ ፡ ይግበሩ ፡ ከመ ፡ ዝ ። በከመ ፡ ተደመርከ ፡ ወተዓደምከ ፡ ምስለ ፡ አካዝያስ ፤ (፩ዕዝ ፡ ፱ ፡ ፲፯ ። ፪ዜና ፡ ፳ ፡ ፴፯) ።

**ዐደን** ፤ በቁሙ ፤ ሻ ፡ ፈለገ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ዔዴን ፤ (ዕብራ)** ፤ ምቹ ፡ በታ ፤ ወፍራም ፡ ሥብ ፡ መሬት ፤ አሻል ፡ ፋልማ ። ከበታው ፡ የሚገኝ ፡ ፍጹም ፡ ተድላ ፤ ጣዕም ፡ ሥጉ ፡ መዐዛ ፤ ቈጽል ፡ ልምላሜ ። ወተከለ ፡ እግዚ ፡ አምላክ ፡ ገነተ ፡ በዔዴን ፡ እምቅድም ፤ ወሤሞ ፡ ህየ ፡ ለአዳም ፡ ዘለሐኮ ፤ (ዘፍ፪ ፡ ፰) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ኤድም ፡ ኤደም ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ኤደምን ፡ ተመልከት ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ምሥራቅ ፡ ይሉታል ። ምሥራቅ ፡ የሚባል ፡ ቅድም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዔዴን ፡ አይደለም ።

**ዐሀ ፤—አዩ ፤—አሀ ።**

**ዓው** ፤ ጫን ፤ የጫን ፡ ራስ ፤ መብቀያው ፤ ከሆድ ፡ ጋራ ፤ የተያያዘው ፤ ማጠፊያው ፡ ማውጫ ። ሥርው ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ዓወ ፡ እግሩ ፤ (ዘፍ፴፪ ፡ ፴፪) ።

**ዐዊግ ፤ጎት ፤ (ያገ ፡ የዐውግ ፡ ይዑግ ። ዐረ ፡ ዐዊገ)** ፤ መጥመም ፤ መጕበጥ ፤ መወላገድ ፡ ጠማማ ፡ ቈልማማ ፡ ዐንካሳ ፡ ወንካራ ፤ ጠንባላ ፡ ሸውራራ ፡ መኾን ፡ አለመተካከል ፤ የሕዋስ ።

**ተዐወገ ፤ (ይትዓወግ)** ፤ አጣገጠ ፤ አለመጠ ፤ ተማለቀ ፤ አፉን ፡ ከንፈሩን ፡ በማጣመም ፤ ዐይኑን ፡ በማ

ሬወንቁር ፡ በማሳጠር ፤ ይሆን ፡ በመሰሉ ፡ ነገር ። ወተዐዊ ጎሙ ፡ ኢይሁድ ፡ በክርስቶስ ። ተዐዊጎሙ ፡ ይነግሩ ፡ (ቁር ፡ እስት ። ጸላ) ።

**ዖገ** ፤ (ዕብ ፡ ዓግ ፡ ያዑግ) ፤ ጋገረ ፤ ዐነጐተ ፤ ክብ ፡ አደረገ ፤ የሲጡን ፡ ቅርጥ ።

**ተዐውገ** ፤ ተጋገረ ፤ ተነጐተ ፤ ተጠቤተ ።

**ዑጋት** ፤ ዕንጕቻ ፤ ሥሥ ፤ ክብ ፤ የጣቢታ ፡ ዐ ይነት ። ዑጋተ ፡ ሰገም ፡ (ሕዝ፬ ፡ ፲፪) ።

**ዐዊድ ፤ ዶት ፤ (ዖደ ፡ የዐውድ ፡ ይ ዑድ ። ዕብ ፡ ዒዌድ ። ዐረ ፡ ዓደ)** ፤ መዞር ፤ መ ሽክርከር ፤ መገላበጥ ፤ ለራሱ ። ማወድ ፤ በዙሪያ ፡ መኼድ ፤ መመላለስ ፤ ማጠር ፡ መክበብ ፤ ዞሮ ፡ መግጠም ። አገር ፡ ላገር ፡ መንደር ፡ ለመንደር ፡ መዞር ፤ ለማየት ፤ ለመስ ማት ፤ የሹትን ፡ ለማግኘት ። ማወጅ ፤ እየዞሩ ፡ መልፈፍ ፤ ዐዋጅ ፡ መንገር ፤ ስማ ፡ ስማ ፡ ማለት ። ባዩት ፡ በሰሙት ፡ ምስክር ፡ መኾን ፤ ተጠርቶ ፡ መመስከር ፤ ወይም ፡ ታሪክ ፡ ጥሮ ፡ ማኖር ። ከመ ፡ መንክክት ፡ እንተ ፡ ተዐውድ ። ወለሰ ፡ ዖድዎ ፡ ለውእቱ ፡ መንበር ። ከመ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ የዐውዶ ፡ ሠራዊ ። ዖድኩ ፡ እንዘ ፡ አኄሥሥ ። ዖደ ፡ ዐዋዲ ። የዐውድ ፡ ይንግር ፡ ለከ ፡ ዘወሀበከ ፡ (ሚራ፳፯ ፡ ፳ ። መክ፳፯ ፡ ፲፱ ። ቅዳ ። ሳታ ። ጥበ፳ ፡ ፲፰ ። መክ፺ ፡ ፳፳ ። ዘፍ፵፩ ፡ ፵፫ ። ሚራ፳ ፡ ፲፳) ።

**ዐዋዲ** ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤ የሚዞር ፡ ዘዋሪ ፤ ለፋፊ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ። ብእሲት ፡ ዐዋዲት ፡ ዘኢ ትከድን ፡ ኀፍረታ ። ቃለ ፡ ዐዋዲ ። ሐዋርያ ፡ ወዐዋዲ ፡ (ፊላስ ። ዮሐ፩ ፡ ፳፫ ። ፩ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፯) ።

**ዐዋድ** ፤ ዐዋጅ ፤ ለሕዝብ ፡ የሚነገር ፡ የንጉሥ ፡ ሕግና ፡ ደንብ ፡ ውሳኔ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዐዋድ ፡ ፈ ንታ ፡ ዐዋጅ ፡ ይላል ። ወእንገረ ፡ ዐዋጀ ፡ (ቃሬ ፡ ነገ) ።

**አዖደ** ፤ አዞረ ፤ አሳወደ ፤ ዐዋጅ ፡ አስነገረ ። ያዐ ውድ ፡ መንኰራኵሪሁ ። ከመ ፡ ያዑድ ፡ ዐዋዴ ፡ ቅድ ሜሁ ። አዖደ ፡ ውስተ ፡ መርሕበ ፡ ሀገር ፡ (ሚራ፴፰ ፡ ፳፱ ። ዮሴፍ ። አስቴ፮ ፡ ፲፩) ።

**ተዐውደ** ፤ ታወደ ፡ ተዞረ ፤ ዐዋጅ ፡ ተነገረ ። በዖደ ፡ ፈንታ ፡ ተዐውደ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። አኮኑ ፡ ፍጡነ ፡ ይረውጽ ፡ ፀሓይ ፡ ተዐዊዶ ፡ ሰማየ ፡ (፩ዕገ ፡ ፱ ፡ ፴፱) ።

**ዕዉድ ፤ ዕውድ** ፤ የታወደ ፡ የተከበበ ፤ ክብ ፤ የታሰረ ፡ የተጠመጠመ ፤ ጥምጥም ። ጽጌ ፡ ደንጐላ ፡ ዘ ዕዉድ ፡ በአሥዋክ ። ይኩን ፡ ቀሚስ ፡ ስፋየ ፡ ወዕ ዉደ ፤ መዝርዐ ፡ ቀሚስ ፡ ይኩኑ ፡ ዕውዳነ ። ፈቃድ ፡ ዕውድ ፡ በምግባር ። ዕውድ ፡ በሚላት ፡ ውስተ ፡ አሕ ባለ ፡ ቢሶስ ፡ (አዋል ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፩ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ተ፲፯ ። አስቴ፩ ፡ ፯) ።

**ዑደት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፡ መዞር ፤ አዟዟር ፤ ዙረት ። ዑደተ ፡ ሆሳዕና ። ዑደተ ፡ ፀሓይ ። ዘእንበለ ፡ ይግበር ፡ ዑደታተ ፡ ከዋክብት ፡ ለአዝማን ፡ (ቅዳ ። አቡሻ ፡ ፴፯ ። መቃ) ። በዑደት ፡ ፈንታ ፡ ዕዋዴ ፡ ይላል ፡ አንድ ፡ ነው ። ሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ዕዋዴሁ ፡ (አቡሻ ፡ ፲፫) ።

**ዐውድ** ፤ ዙሪያ ፤ ክበብ ፤ ከበር ፡ እስከ ፡ በር ፤ ከመት ፡ እስከመት ፡ ያለ ። ለታጠረ ፡ ለተወሰነ ፡ ክበብ ፡ ላለው ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። ወበዐውዱ ፡ ለውእቱ ፡ መ ንበር ። ይቀውሙ ፡ ዐውዶ ። ዐውደ ፡ ፀሓይ ፤ ዐውደ ፡ ወርኅ ። ዐውደ ፡ ዓመት ፡ (ራእ፬ ፡ ፱ ። ኢሳ፳ ፡ ፱ ። አ ቡሻ ፡ ፳፫ ። ድጓ) ።

**ዐውደ ፡ አበቅቴ** ፤ ፲፱ ፡ ዓመት ፤ በዚህ ፡ ጨ ረቃና ፡ ፀሓይ ፡ መንገዳቸውን ፡ እየፈጸሙ ፡ ተራክቦ ፡ ያደርጉበታል ።

**ዐውደ ፡ ወርኅ** ፤ ሠላሳ ፡ ቀን ፤ ከ(ልደታ)መ ባቻ ፡ እስከ ፡ መባቻ ።

**ዐውደ ፡ ወርኅ** ፤ የጨረቃ ፡ ዐውዳመት ፤ ፫፻ ፶፬ ፡ ቀን ።

**ዐውደ ፡ ማኅተም** ፤ ፬፻፹ ፡ ዓመት ። ማኅተ ምን ፡ ተመልከት ።

**ዐውደ ፡ ነገሥት** ፤ የጥንቄላ ፡ መጽሐፍ ፤ ፲፫ ፡ ክብ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ያለው ፤ ያቡሻህርና ፡ የመርሐ ፡ ዕዉር ፡ ወደረኛ ። በየሰንጠረዡ ፡ ፲፮ ፡ ነገር ፡ አለበት ፤ ትምርቱን ፡ ግን ፡ ከጥቂት ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ ኹሉ ፡ አያ ውቀውም ፤ መጠፋም ፡ በጠንቋይ ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ አይ ገኝም ።

**ዐውደ ፡ ዕለት** ፤ ሰባት ፡ ቀን ፤ ከእሑድ ፡ እ ስከ ፡ ቀዳም ።

**ዐውደ ፡ ዓመት** ፤ የፀሐይ ፡ ዐውዳመት ፤ ፫፻ ፷፭ ፡ ዕለት ፤ ከሩብ ።

**ዐውደ ፡ ፀሐይ** ፤ ፳፰ ፡ ዓመት ፤ በዚህ ፡ ዕ ለት ፡ ወንጌላዊ ፡ ይገናኙበታል ፤ ዕለቱ ፡ ረቡዕ ፤ ወንጌላ ዊው ፡ ማቴዎስ ።

**ዐውደ ፡ ቀመር** ፤ ፭፻፴፪ ፡ ዓመት ፤ በዚህ ፡ ዕለት ፡ ወንጌላዊ ፡ አበቅቴ ፡ ይገናኙበታል ፤ ዕለቱ ፡ ሠሉስ ፤ ወንጌላዊው ፡ ማቴዎስ ፤ አበቅቴው ፡ አልቦ ፡ ነው ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ ቃል ፡ የመርሐ ፡ ዕዉር ፡ ነው ።

**ዐውድ** ፤ ዐውድማ ፤ ሸንጎ ፤ ጉባኤ ፤ አደባባይ ። ዐውደ ፡ እክል ። ዐውደ ፡ ማእረር ። አምጽእዎ ፡ ኀበ ፡ ዐውድ ። ንጉሥ ፡ ዐውደ ፡ (ሩት፫ ፡ ፪ ። ዳን፪ ፡ ፴፭ ። ግብ፲፰ ፡ ፲፪ ። ፲፬ ፡ ፴፱) ።

**አዕዋድ** ፤ (ዳት) ፤ ዙሪያዎች ፤ ዐውድሞች ፤ ሸንጎዎች ። አውራጃች ፤ ቀበሌዎች ። ያገብኡክሙ ፡ ውስተ ፡ አዕዋድ ። ነበረ ፡ ፍጽም ፡ በውስተ ፡ አዕዋ ዳት ። ምኔታት ፡ ዘአዕዋደ ፡ እለእስክንድርያ ፡ (ማቴ ፲ ፡ ፲፯ ። ፳፫ ፡ ፯ ። ፊልክ ፡ ፲፰) ።

**ምዕዋድ** ፤ (ዳት) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፤ ዙሪያ ፡ ክበብ ። መክበቢያ ፤ መክበቢያ ፤ መዞሪያ ፡ ማወጃ ፡ ቦታ ፤ ወይም ፡ መዝሙር ፡ እያወዱ ፡ የሚዘምሩት ። ምዕዋደ ፡ ቅጽራ ፡ እምአንቀጽ ፡ ለአንቀጽ ። ሠናይ ፡ ምዕዋደ ፡ ቀስት ። ወአያደኒ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ምዕዋዳተ ። መዝ

መር ፡ ዘምዕዋድ ፡ (ዮናፔ ፡ ፫ ። ጥበ፳ ፡ ፳፱ ። ሕዝ፴፯ ፡ ፱ ። ድጓ) ።

**ዐውድ ፤ (ዐረብ) ፤** የሬት ፡ ዕንፊት ፡ ሽታው ፡ የሚያውድ ፤ ክፉቅ ፡ የሚሸት ። ቀናንሞስ ፡ ወሰሊኖት ፡ ወዑድ ፡ (ዲድ ፡ ፳፭ ። መጽ ፡ አዳር ፡ ፭ ፡ ፯) ። ዐልውን ፡ ተመልከት ።

**ዑድር ፤ (ዐረብ) ፤** ምክንያት ፡ ሰበብ ፡ ሐሳብ ፤ የነገር ፡ ማፍረሻ ፤ ፈሰን ፡ ከበደል ፡ ለማንጻት ። ነገሮ ፡ ዑድሮ ፡ ወተወክፎ ፡ ፍምፍምዮስ ። አልብክሙ ፡ ዑድር ። ኢሲተ ፡ ዑድር ፡ በሕይወትክሙ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ዐውየወ ፤ (ዐረ ፡ ዐወይ ። ሱር ፡ ዐዋእ) ፤** ጮኸ ፤ ቡታ ፡ ሰደደ ፤ ዋይ ፡ ዋይ ፡ አለ ። ዐውየወ ፡ በሕቁ ። የዐወይዉ ፡ እምብዝኀ ፡ መስተፀግላን ። ወዐውየወት ፡ በሕማማ ። አንዝኩ ፡ እብኪ ፡ ወአዐውዩ ፡ (ዮዲ፲፬ ፡ ፲፯ ። ኢየ፴፭ ፡ ፱ ። ኢሳ፷፮ ፡ ፲፯ ። ሔኖ፹፱ ፡ ፷፱) ።

**አዐውየወ ፤** አስጮኸ ፡ አስጨነቀ ፤ አስለቀሰ ። እንዘ ፡ ታግዕሩ ፡ ወታዐወይዉ ፡ ነዳየ ፡ (ኢሳ፶፰ ፡ ፬) ።

**ዐውያ ፤ (ያት) ፤** ጩኸት ፤ ቡታ ፡ እሪታ ፤ ልቅሶ ፡ ዋይታ ። ጊዜ ፡ ዐውያክ ። ዐውያተ ፡ ነዳያን ። ዐውየወት ፡ ዐውያተ ፡ ዐቢይተ ፡ (ኢሳ፶፰ ፡ ፱ ። ኢየ፴፱ ፡ ፳፰ ። ሔኖ፹፭ ፡ ፯) ።

**ዐዌት ፤ (ትግሬ) ፤** ድል ፤ አሸናፊነት ፤ አስጨኺነት ።

**ዐውከከ ፤—አስጨነቀ ፤—ወከከ ፤ አውከከ ።**

**ዐውሎ ፤ (ታት ። ሱር ፡ ዑላታእ ፤ ዐላታእ ። ዕብ ፡ ዐልዖል) ፤** በቁሙ ፤ ጥቅል ፡ ነፋስ ፤ ጦሮ ፤ ኰርፊት ፡ የትቢያ ፡ ማዕበል ፡ የሚያስነሣ ፤ ቤት ፡ የሚያናውጥ ፡ የሚገለብጥ ፤ ተግብ ፡ ከዝናብ ፡ በፊት ፡ የሚነፍስ ። ነፋስ ፡ የሚያስነሣው ፡ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ የባሕር ፡ ሁከት ። ከመ ፡ ጸበል ፡ ዘይነሥእ ፡ ዐውሎ ። ዐውሎ ፡ ኀያል ፡ ያነቅዓ ። ዐውሎ ፡ ማይ ። ተንሥአ ፡ ላዕሌየ ፡ ዐውሎታት ፡ ወመዋግድ ፡ ተሰዐሉ ፡ ላዕሌየ ፡ (ኢዮ፳፩ ፡ ፲፰ ። ሕዝ፲፫ ፡ ፲፩ ። መዝ ፡ ፷፰ ። ፊልክ ፡ ፳፰) ።

**ዕዋል ፤ (ላት ። ዕብ ፡ ዑል ፤ ዐይር) ፤** ዕንል ፤ ታናሽ ፡ ልጅ ፤ ሕፃን ፡ ግልገል ፤ ውርንጫ ። ዕዋል ፡ ዕጓለ ፡ እድግት ። ትረክቡ ፡ እድግተ ፡ ወዕዋለ ፡ (ዘካ፱ ፡ ፱ ። ማቴ፳፩ ፡ ፪) ።



ዕዋል ፡

**ዐዊም ፤ ሞት ፤ (ዖመ ፡ የዐውም ፡ ይዑም ። ዐረ ፡ ዐመ ፤ ቀመ ። ዕብ ፡ ዑብ) ፤** መሸፈን ፤ ማልበስ ፡ ማጨለም ፡ የዛፍ ፡ የቅጠል ፡ የጉም ። ከጥሬው ፡ በቀር ፡ አንቀጹ ፡ አይገኝም ።

**ዖም ፤** ለምለም ፡ ማር ፡ ቅጠል ፡ ግጫ ፡ ሸንበቆ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፤ ምድር ፡ የሚያለብስ ፡ የሚሸፍን ። ጽፍቅ ፡ ዱር ፤ ደን ፡ ወማ ፡ ጫካ ፤ ታላላቅ ፡ ዛፍ ፡ ክንፋም ፡ ቅጠላም ። ኵሉ ፡ ዖመ ፡ ብርዕ ፡ ወኅሰት ። ይበቍል ፡ ዖም ፡ ውስተ ፡ በድው ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፯ ። ፴፭ ፡ ፯) ። ኵሉ ፡ ዖም ፡ ጽሩቅ ። ታሕተ ፡ ኵሉ ፡ ዖም ፡ ዘቦ ፡ ጽላሎት ። ዖመ ፡ ባሳን ፡ (፬ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፬ ። ኤር፱ ፡ ፳ ። ዘካ፲፩ ፡ ፪) ።

**ዖማት ፤** ለምለሞች ፡ ዱሮች ፡ ዛፎች ። ዕፀው ፡ እለ ፡ ይፈርዩ ፡ ወዖማት ፡ (ኩፋ ፡ ፪) ።

**አዕዋም ፤** ግዜ ፡ ከማሁ ። ነዋኀት ፡ አዕዋም ። ውስተ ፡ አዕዋሚሃ ፡ (ኢሳ፴፯ ፡ ፳፬ ። ኤር፳፮ ፡ ፲፰) ።

**ዐዊፍ ፤ ፎት ፤ (ዖፈ ፡ የዐውፍ ፡ ይዑፍ ። ዕብ ፡ ዐፍ ፡ ያዑፍ) ፤** አፈፍ ፡ ወፈና ፡ በርደግ ፡ ማለት ፤ ክንፍን ፡ መዘርጋት ፤ ብር ፡ ቱር ፡ ማለት ፤ መብረር ፡ መስረር ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ በአየር ፡ መኼድ ፤ መክነፍ ። ወፈፍተኛ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ዖፍ ፤ (ዕብ ፡ ዖፍ ። ሱር ፡ ዓውፋ) ፤** በቁሙ ፤ ወፍ ፡ ባለክንፍ ፤ የሚበር ፡ የሚሰር ፤ ታናሹም ፡ ታላቁም ፤ ያንድነት ፡ ስም ፡ ነው ። ዖፍ ፡ ዘይሰርር ። ከመ ፡ ዖፍ ፡ አፍርኅቲሃ ፡ ዘትሴውር ፡ በክንፋ ፡ (ኢሳ፴፭ ፡ ፭ ። ደራሲ) ።

**ዖፍ ፤ (ትግሬ) ፤** አንበሳ ፤ ዕጓለ ፡ አንበሳ ።

**አዕዋፍ ፤ (ፋት) ፤** ወፎች ፡ በራሮች ። ነጽሩ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ። እምኵሉ ፡ አዕዋፍ ፡ ትንእስ ፡ ንህብ ። ዘወገሮን ፡ ለአዕዋፍ ፡ (ማቴ፮ ፡ ፳፮ ። ሢራ፲፩ ፡ ፫ ። ፳፱ ፡ ፳) ።



አዕዋፍ ፡

**ዐዊቅ ፤ ቆት ፤ (ዖቀ ፡ የዐውቅ ፡ ይዑቅ ። ዕብ ፡ ዑቅ ፤ ሣቀየ ፤ አሳመመ) ፤** ማወቅ ፤ ማስተዋል ፡ ምስጢሩ ፡ ጥበቃ ፡ ጥንቀቃ ፡ ነው ። ዑቅ ፡ ትእዛዘ ፡ ወግበር ። ዑቅዎሙ ፡ ለክለባት ። ዑቅ ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ ኢታግብኦ ፡ ለወልድየ ። ዑቁኬ ፡ ኢያስሕቱ ክሙ ። ዑቁ ፡ ርእሰክሙ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፩ ። ፊልጵ፫ ፡ ፪ ። ማቴ፳፬ ፡ ፬ ። ማር፲፫ ፡ ፱) ።

**አዖቀ ፤** አሳወቀ ፡ አስታወቀ ፤ ገለጠ ፤ አስረዳ ። ነገርከ ፡ ያዐውቀከ ። ናሁ ፡ አዖቅክሙ ፡ ከመ ፡ ኢይፈ

ቅድ ፡ ንሥተተ ፡ ወአያቁ ፡ ዕልወቶሙ ። ኢያዖቀ ፡ ፍድፋዴ ፡ ክብሮሙ ፡ (ማር ፲፱ ፡ ፸ ። ዮሴፍ ። አፈ ፡ ድ፩) ።

**ተዐውቀ** ፤ ታወቀ ፤ ተረዳ ፡ ጐላ ፡ ተገለጠ ። ይትዐወቅ ፡ እምርሑቅ ፡ ዘይክል ፡ ነቢበ ። ሕልመ ፡ ሌሊት ፡ ዘኢይትዐወቅ ። ከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ጽድቁ ። ተዐውቀ ፡ እግዚ ፡ በይሁዳ ። ዘተዐውቀ ፡ አበሳሁ ፡ በውስተ ፡ ፍትሕ ፡ (ሚራ ፳፭ ፡ ፯ ። ኢዮ ፳ ፡ ፰ ። ሚክ ፯ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፸፭ ። ዲድ ፡ ፲) ።

**ዕዉቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ውቅት)** ፤ የታወቀ ፤ የተረዳ ፤ ዕውቅ ፤ ግልጥ ። ስኮ ፡ ዲበ ፡ ሚመታት ፡ ዕዉቃት ፡ (ስንክ ፡ መጋ ፲፱) ።

**ዐውቅት** ፤ ማወቅ ፡ መታወቅ ፡ አስተዋወቅ ፡ ዕውቅንት ፤ ዕውቀት ፡ ዕውቂያ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፴፫) ።

**ዐውቅ ፤ (ቃን)** ፤ ዐውቂያ ፤ የሚያውቁት ፤ ምስጢር ፡ የሚነግሩት ፡ ወዳጅ ፤ ባልንጀራ ። ዐውቅየ ። ወከመ ፡ ዐውቃንየ ፡ ኮንኩ ፡ በማእከሎሙ ፡ (መዝ ፡ ፶፱ ። አረጋ ፡ ድ፳፩) ።

**ተዓወቀ** ፤ ተዋወቀ ፤ ተሳመደ ፡ ተወዳጀ ፡ ተዛመደ ።

**አስተዓወቀ** ፤ አስተዋወቀ ፡ አሳመደ ፤ አለማመደ ።

**ዐዊር ፤ ሮት ፤ (ዖረ ፡ የዐውር ፡ ይዑር ። ዕብ ፡ ዐዌር ። ሱር ፡ ዓዋር ። ዐረ ፡ ዐዊረ ፤ ዐወረ ፤ ነቈረ)** ፤ መታወር ፤ ዕውር ፡ መኾን ፤ ከማየት ፡ መከልከል ፤ መደናበር ፤ ዐይን ፡ ፈሶ ፡ ፈርጦ ፡ ገበጣ ፡ መስሎ ፤ ተደፍኖ ፡ ተጨፍኖ ፤ ወይም ፡ ፈጦ ፡ ጕርጦ ፤ ፈዞ ፡ በልዞ ። እቀሥፍ ፡ ዙሎ ፡ አፍራሰ ፡ አሕዛብ ፡ በዐዊር ። ዖሩ ፡ አግብርተ ፡ እግዚ ። ዖራ ፡ አዕይንትየ ፡ እምአንብዕ ። ተዐውር ፡ ወኢትሬኢ ፡ ፀሓየ ። አዕይንት ፡ ነጻርያት ፡ የዐውራ ፡ (ዘካ ፲፪ ፡ ፬ ። ኢሳ ፵፪ ፡ ፲፱ ። ኢዮ ፲፯ ፡ ፯ ። ግብ ፲፫ ፡ ፲፩ ። ግንዘ) ።

**ዐዋር ፤ (ዐረብ)** ፤ ዕውር ፡ ጠንባሳ ፡ ዐይኑ ፡ የጠፋ ፤ የፈሰሰ ፡ የዐዊር ፡ ምስጢር ፡ ከብርሃኑ ፡ ይልቅ ፡ ዐይኑ ፡ ብሌኑ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፤ ባደውን ፡ ያለ ፡ ጕድጓድና ፡ ቍርበት ፡ ያሳያል ።

**ዐዋውርት** ፤ ዕውሮች ፤ ዕውራኖች ። መርሐ ፡ ዐዋውርት ፡ (ገድ ፡ ዘማ) ።

**ዕዉር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ውርት)** ፤ በቁሙ ፤ የታወረ ፡ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ለዐዋር ። ዝ ፡ ቀትል ፡ በመጥባሕት ፡ ተሰምየ ፡ ሞተ ፡ ዕዉር ። ዕዉራን ፡ ይሬእዩ ። ብእሲ ፡ ዘዕውርት ፡ አሐቲ ፡ ዐይኑ ፡ (ዮሴፍ ። ማቴ ፲፩ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ሐም ፲፩) ።

(ሳ) **ዕወር** ፤ መታወር ፤ ዕውርነት ። ይቀሥፈከ ፡ በድቀት ፡ ወበዕወር ፡ (ዘዳ ፳፰ ፡ ፳፰) ።

**ዑረት** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ዕውርነት ። በእኪት ፡ ዑረተ ፡ ልቡ ። ዑረተ ፡ ልብ ፡ የእኪ ፡ እምዑረተ ፡ ዐይን ፤ (ዲድ ፡ ፬ ። ሲኖ ደ ። ማር ፫ ፡ ፭ ። ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭) ።

**አዕወረ ፤ አዖረ ፡ (ያዐውር ፡ ያዑር)** ፤ ዐወረ ፤ አሳወረ ፡ ዐይን ፡ አወጣ ፤ አሶጣ ፡ ዕውር ፡ አደረገ ፤ አስደረገ ። ወአዕይንቲሁ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ አዖረ ። አዑሮሙ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ወአዖሮሙ ። ሕልያን ፡ ያዐውር ፡ ዐዕይንተ ፡ (ኤር ፶፪ ፡ ፲፩ ። ፬ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፯ ። ዘፀ ፳፫ ፡ ፰) ።



ዕዉር ፤

**ተዐወረ ፤ (ይትዔወር)** ፤ ዐይኑን ፡ ጨፈነ ፡ ቻለ ፡ አለ ፤ ናቀ ፤ ዕውር ፡ መሰለ ፡ እያየ ፡ እንዳላየ ፡ ኾነ ፤ ደፈረ ። ይትዔወር ፡ ነፍሶ ። ይትዔወር ፡ ቢጾ ። ኀፍረት ፡ ተዐውሮቱ ፡ ለቢጽከ ። ኢይባእ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ፤ ወእመሰ ፡ ተዐወረ ፡ ከመ ፡ ይባእ ፡ (ሚራ ፲፱ ፡ ፳ ። ፳፱ ፡ ፲፱ ። ፵፭ ፡ ፳፭ ። ቀሌ) ።

**ተዐዋሪ** ፤ ቻል ፡ ባይ ፤ ቻልተኛ ። አይቴ ፡ ለተናስሖ ፡ ተዐዋርያን ፡ (ግንዘ) ።

**ትዕውርት** ፤ ቻልታ ፤ ቻልተኛነት ፤ ንቀት ፡ ድፍረት ።

**ዐውስት ፤—አሞራ ፤—አውስት ።**

**ዐዊት ፤—ስመ ፡ ሀገር ፤—አዊት ።**

**ዐዘበ ፤—ፈሰሰ ፤—ዐዚብ ፡ ዐዘበ ።**

**ዐዘበ ፤ (ዕብ ፡ ዐዛብ)** ፤ አዳነ ፤ ዐገዘ ፡ ረዳ ፡ አናማ ፤ የሸከም ። ነጸርኩ ፡ እመ ፡ ቦ ፡ ዘይዔዝበኒ ፡ ሰብእ ፡ ወአልቦ ፡ (ሚራ ፶፩ ፡ ፯ ። ዘፀ ፳፫ ፡ ፭) ።

—፤ ቶው ፡ ጣለ ፡ ወረወረ ። ሰበቀን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ዐዘበ** ፤ በቁሙ ፤ የበከ ፡ እበት ፡ ፍግ ፡ ፋንድያ ፤ ወደርሻ ፡ የሚባል ።

**ዐዘዘ ፤—በቁሙ ፤—አገዘ ፡ አዘዘ ።**

**ዐገዘ ፤ ዞት ፤ (ዐዘዘ ፡ ይዔዝዝ ፡ የዐዝዝ ። ዐረ ፡ ዐዘ ። ዕብ ፡ ዐዛዝ)** ፤ መጽናት ፤ መበርታት ፡ መጠንከር ፡ መሠልጠን ። ማጽናት ፤ ማበርታት ፤ ልብን ፡ ሰውነትን ። ከመ ፡ የዐዝዝ ፡ ወየኀይል ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ወዐዘዘ ፡ ላዕለ ፡ ትዕይንት ፡ ግብጽ ። ዐዝዝ ፡ ለነ ። ዘይዔዝዝ ፡ ትፍሥሕተ ፡ (ሔኖ ፶፪ ፡ ፬ ። ዘፀ ፲፬ ፡ ፳፬ ። ቅዳ ። መዝ ፡ ፵፯) ። አዘዘን ፡ ተመልከት ።

**ዐዚዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ዛዝ)** ፤ ጥኑ ፡ ብርቱ ፡ ጠንካራ ፡ ልባም ። መንፈስ ፡ ዐዚዝ ። ነገሥት ፡ ዐዚዛን ። ብእሲት ፡ ዐዛዝ ፡ (መዝ ፡ ፶ ። ሔኖ ፵፰ ፡ ፳ ። ምሳ ፲፪ ፡ ፬) ። ዐሀ ፡ ዐዛውንት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ዕዙዝ ፤ (ዝዝት)** ፤ የጠና ፡ የበረታ ፤ ብርቱ ፡ ጠንካራ ፤ የማይፈርስ ። **ዕዙዝ ፡ መንግሥት ። ጕዩ ፡ ውስተ ፡ ዕዙዝ ፡ ደብር ። ወበረድስ ፡ ብዙኅ ፡ ጥቀ ፡ ወዕዙዝ ፡** (ቅዳ ። መቃ ። ዘፀ፱ ፡ ፳፬) ።

**ዕዘዝ** ፤ ጥናት ፡ ብርታት ፡ ጥንካሬ ፡ ኀይል ፡ ሥልጣን ፡ ክብር ፡ ልዕልና ። **ዕዘዝ ፡ መዝራዕትከ ። ቀማሽ ፡ ዘአርአየ ፡ ዕዘዘ ። ሞት ፡ በዕዘዝ ፡ ይኄይስ ፡ እምሐዩው ፡ በኀሳር ። ዕዘዝክሙ ፡ ወሰርጕ ፡ ክብርክሙ ። ኀስሩ ፡ እምድኅረ ፡ ዕዘዝ ። እመ ፡ አውዐይኮ ፡ ለመቅደስ ፡ ይትአተት ፡ ዕዘዘሙ ፡** (ጥበ፲፩ ፡ ፳፬ ። ስንክ ፡ የካ፳ ። ዮሴፍ) ።

**አስዐዘዘ ፤ አስዖዘዘ** ፤ አፈዘዘ ፡ አደነዘዘ ። **አስከሮ ፡ ወአስዖዘዘ ። ወአስዖዘዘ ፡ ጸኮ ፡** (ስንክ ፡ የካ፳ ። ነሐ፳፰ ። ዘፍ፴፪ ፡ ፴፭ና ፡ ፴፪) ።

—፤ አስቈጣ ፡ አስፈዘዘ ፡ አሳዘነ ፡ አሳፈረ ፡ አስቀጠጠ ። **ልሳን ፡ ኅቡእ ፡ ያስዖዝዝ ፡ ገጸ ፡** (ምሳ፳፭ ፡ ፳፫) ።

—፤ ተከተለ ፤ ሻ ፡ ፈለገ ፡ አፈነፈነ ። **ዘያስዖዝዝ ፡ ነገረ ፡ ኢይድኅን ፡** (ምሳ፲፱ ፡ ፯) ።

**መስዖዝዝ** ፤ የሚያፈዝ ፡ የሚያደነዝዝ ፡ አፍዝ ፡ አደንግዝ ። **ወይን ፡ መስዖዝዝ ፡** (አርጋ ፡ ፬) ። አፍዝ ፡ አደንግዝ ፡ የዓሣ ፡ ስም ፡ ነው ፤ መጠኗና ፡ መልኩ ፡ ታናሽ ፡ ኹኖ ፡ ግርማም ፡ የሚያስደንግጥ ፤ ሲይዟት ፡ እጅ ፡ የምታፈዝ ፡ ሲበሏት ፡ የምታደነግዝ ፡ ዓሣ ፡ ወጋሮች ፡ ለይተው ፡ የሚያውቋት ፡ ከወንዝ ፡ ዓሣ ፡ ኹሉ ፡ የተለየች ፡ መርዛም ፡ ዓሣ ፡ አለች ፡ ይባላል ።

**ሰዖዝዝ** ፤ መፍዘዝ ፡ መሰለል ፡ ድንዛዜ ፤ የዥማት ፡ ደዌ ፤ የበሽታ ፡ ጠንክ ። ቍጣ ፡ ሐዘን ፡ ኀፍረት ፤ ስቅጥጥታ ። **ሕማም ፡ ወሰዖዝዝ ፡** (ኩፋ ፡ ፳፫) ።

**ዐዛል ፤—ብርቱ ፤—አዛል ።**

**ዕዝል ፤ (ሕዝል ፤ ሐዘለ)** ፤ የዜማ ፡ ስም ፡ ፩ኛ ፡ ዜማ ። **ሠለስቱ ፡ ዜማ ፤ ዘውእቱ ፡ ግእዝ ፡ ወዕዝል ፡ ወአራራይ ፡** (ስንክ ፡ ግን፲፩) ።

**ዕዝል ፤ (ላት)** ፤ መዝሙር ፤ የመዝሙር ፡ ስም ፡ ዜማው ፡ ዕዝል ፡ የኾነ ፤ በዕዝል ፡ ዜማ ፡ የሚያዜሙት ። **ዕዝል ፡ ዘነግሀ ፤ ዕዝል ፡ ዘማርያም ፤ ህየንተ ፡ ዕዝል ፡ ዘነግሀ ፡ ግእዝ ። ዕዝል ፡ ዘሙታን ፡** (ድጓ ። ግንዘ) ።

**ዐዝም ፤ (ዐረ ፡ ዐ፪ም)** ፤ ስመ ፡ ነገድ ፤ ፋርስ ፡ የፋርስ ፡ ሕዝብ ፡ (አቡሻ) ። ሀገሪትን ፡ ተመልከት ።

**ዕዝን ፤—ዝሮ ፤—አዚን ፡ አዘነ ።**

**ዐዚቅ ፤ ቆት ፤ (ዐዘቀ ፡ የዐዝቅ ፡ ይዕዝቅ ። ዐረ ፡ ዐዘቀ ። ዕብ ፡ ዓዚቅ)** ፤ መፋር ፡ መቈፈር ፤ መብሳት ፡ መሰርሰር ፤ ማጕድጕድ ፡ ማጥለቅ ፡ ማዘቅ ፤ ገቅ ፡ ማድረግ ፤ የዥሬ ፡ የጕድጓድ ።

**ዐዘቅት ፤ (ቃት)** ፤ በቁሙ ፡ ጕድጓድ ፡ ዥሬ ። **ከመ ፡ ዐዘቅት ፡ ዘኢይነፀፍ ፡ ማዩ ። ዐዘቅት ፡ ንፅፍት ። ወውስተ ፡ ዐዘቅታት ፡** (ኢሳ፶፰ ፡ ፲፩ ። ፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ። ጸንጋ ፡ ፲፫ ፡ ፯) ።

**ዐዘቃት** ፤ ዐዘቅቶች ፤ ጕድጓዶች ። **ሖሩ ፡ ዐዘቃት ፡ ዘከረዩ ፡ ደቀ ፡ አብርሃም ፡** (ዘፍ፳፮ ፡ ፲፰) ።


**ዐዚር ፤ ሮት ፤ (ዐዘረ ፡ የዐዝር ፡ ይዕዝር ። ዕብ ፡ ዐዛር ፤ ረዳ ፡ ዐገዘ)** ፤ መበተን ፤ መዘርዘር ፡ መርጨት ፤ መፈንጠቅ ።

**ተዐዝረ** ፤ ተበተነ ፤ ተዘራ ፡ ተረጨ ፤ ተሠራጨ ፡ ተናኘ ፡ ተወራኘ ፤ የጮራ ፡ የሞፍራ ። **ወተዐዝሩ ፡ ላዕለ ፡ ሌሊ ፡** (መሳ፲፰ ፡ ፱) ።

**ምዕዛር ፤ (ራት)** ፤ የብርሃን ፡ ወንፊት ፤ ብርሃን ፡ የሚንዛበት ፤ ብሱ ፡ ነዳላው ። **ወክሡፉሁ ፡ ዘምዕዛረ ፡ ፀሓይ ፡** (መጽ ፡ ምስ) ። ያቡሻህር ፡ የመርሐ ፡ ዕውር ፡ የሔኖክና ፡ የቍጥር ፡ መምሕራን ፡ ለፀሓይ ፡ ፻፹ ፡ ለጨረቃ ፡ ፺፰ ፡ ምዕዛር ፡ አላቸው ፡ ይላሉ ። «የትርጓሜያቸውም ፡ ምክንያት ፤ ንባቡ ፡ ምስጢሩ ፤ ሥሩ ፡ አነጋገሩ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፲፮) ። ሙሴ ፤ **ወገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክልኤተ ፡ ብርሃናተ ፡ ዐበይተ ፤ ዘየዐቢ ፡ ብርሃን ፡ ከመ ፡ ይምልክ ፡ መዓልተ ፤ ወዘይንእስ ፡ ብርሃን ፡ ከመ ፡ ይምልክ ፡ ሌሊተ ፤ ምስለ ፡ ከዋክብት ፡** ያለውን ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፤ **ካልእ ፡ ክብሩ ፡ ለፀሓይ ፤ ወካልእ ፡ ክብሩ ፡ ለወርኅ ፤ ወካልእ ፡ ክብሮሙ ፡ ለከዋክብት ፡** ብሎ ፡ ነገረን ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፵፩) ። ሊቃውንትም ፡ በቅዳሴያቸው ፤ **ወአመ ፡ ፈጠረ ፡ ፀሓየ ፡ ወወርኀ ፡ አኮ ፡ ከመ ፡ ያብርሁ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ዘጸልም ፤ አላ ፡ ጸገ ዎሙ ፡ ንስቲተ ፡ እምዘዚኣሁ ፡ ብርሃን ፤ መጠነ ፡ ኅጢተ ፡ ሥርናይ ፤ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ አብርሁ ፡ ዲበ ፡ ሰብእ ፡** ብለው ፡ አስተማሩን ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ) ። ይህንንም ፡ መጠነ ፡ ኅጠተ ፡ ሥርናይ ፡ የተባለውን ፡ ብርሃን ፤ ከሺሕ ፡ መጠን ፡ ይከፍሉታል ። ከዚህም ፡ ከሺሑ ፡ ፻፹፭ቱ ፡ ለፀሓይ ፡ ይደርሳታል ፡ በምዕዛሯ ፡ ልክ ፤ ፩፻፹ ፡ ይተርፋል ። ከዚህ ፡ ደግሞ ፡ ፺፰ቱ ፡ ለጨረቃ ፡ ፺ው ፡ ለከዋክብት ፤ ፺ው ፡ ለደመናት ፡ ፺ው ፡ ለቀላያት ፡ ይደርሳቸዋል ። ይህም ፡ ለፀሓይ ፡ የሚደርሳት ፡ ፻፹፭ቱ ፡ በ፲፰ ፡ ቢቀምሩት ፡ ፯ ፡ ክፍል ፡ ኹኖ ፡ ፯ ፡ ይተርፋል ፤ ይህም ፡ ፯ቱ ፡ ክፍል ፡ ከንግህ ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡ በየሰዓቱ ፡ ይሰጣታል ። እንዲህ ፡ ማለት ፡ የምዕዛሯን ፡ መክፈት ፡ መዘጋት ፡ መናገር ፡ ነው ፤ ፯ቱ ፡ ምዕዛሮች ፡ ግን ፡ መቼም ፡ መቼ ፡ አይዘጉም ። ከ፮ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ፺፰ቱ ፡ ይዘጋል ፤ እስከ ፡ ፯ ፡ ሰዓት ፡ ኹሉም ፡ ፈጽሞ ፡ ይዘጋል ። ባንድ ፡ ዕለት ፡ ስድስት ፡ ተውሳክ ፤ ስድስት ፡ ሕጸጽ ፡ አላት ። ለጨረቃ ፡ ይደርሳታል ፡ ያል ነው ፡ ፺፰ቱ ፡ ደግሞ ፡ ፲፬ ፡ ሱባዔ ፡ ይኾናል ፤ ይህም ፡ ከዕለተ ፡ ሠርቅ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ገሀህ ፡ በየዕለቱ ፡ ይሰጣታል ። ከ፲፬ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በየዕለቱ ፡ ፯ ፡ ፯ ፡ እጅ ፡ ይነሣታል ፤ እስከ፲፭ ፡ ቀን ። እንዲህ ፡ ማለት ፡ የምዕዛሯን ፡ መክፈት ፡ መዘጋት ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከእፍኙ ፡ የሚሰጣት ፡ ሌላ ፡ ብርሃን ፡ አለ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ለፀሓይ ፡ ምዕዛር ፡ እንዳላት ፤ ለጨረቃም ፡ አላት ፡ ብለው ፡ ይተረጕማሉ» ።

**ምዕዛር ፤ (ዕብ ፡ አሐር)** ፤ ድኅር ፡ ኋላ ፡ ኋርባ ። **ትሬኢ ፡ ምዕዛርየ ፤ ወገጽየሰ ፡ ኢያስተርኢ ፡ ለከ ፡** (ዘፀ፴፫ ፡ ፳፫) ።

**ማዕዝር** ፤ ብርሃን ፡ የሬሙ ፡ እግር ፡ ቀርኑ ፤ ጦሩ ፤ የሚዋጋው ። **እንተ ፡ ሠረቀ ፡ ማዕዘኑ** ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳) ።



ማዕዝር ፡

**መዓዝር** ፤ ብርሃኖች ፤ የብርሃን ፡ ቀርኖች ። **መዓዝረ ፡ ፀሓይ ፤ መዓዝረ ፡ ስብሐት** ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተማዕዘረ** ፤ በራ ፤ ብርሃን ፡ ኾነ ፡ ፈለቀ ፤ አን ጸበረቀ ። **እስመ ፡ በሡራኄ ፡ ገጹ ፡ ለጸራቅሊጦስ ፡ ተ ማዕዘኑ** ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ዐዜራህ ፤ (ዕብ ፡ ዐዛራህ)** ፤ የምሥዋዕ ፡ ዕርከን ፤ የሕንጻው ፡ ዝናር ፤ ዙሪያውን ፡ የሚከብ ፡ መ ደብ ፡ (ሕዝ፵፫ ፡ ፲፬) ።


**ዐጢን ፤ ኖት ፤ (ዐጠነ ፡ የዐጥን ፡ ይዕ ጥን ። ዕብ ፡ ቃጣር ፤ ቀተረ)** ፤ ማጠን ፤ ማጤስ ፤ ማ ብነን ፤ በጢስ ፡ ማፈን ፤ መሥዋዕት ፡ መጠዋት ፤ ማንደድ ፡ ማቃጠል ። **ዐጢኖ ፡ ዕጣን ፡፡ ከመ ፡ ይዕጥን ፡ ዕጣነ ፡፡ ሥዑ ፡ ወዐጠኑ ፡ ለአጋንንት ፡፡ ሶበ ፡ ነደግነ ፡ ዐጢነ ፡ ለንግሥተ ፡ ሰማይ** ፡ (ኩፋ ፡ ፶ ። ፪ዜና ፡ ፪ ፡ ፬ ። ኢሳ፷፭ ፡ ፫ ። ኤር፵፬ ፡ ፲፰) ።

**ዐጣኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፤ የሚያጥን ፤ የሚያጤስ ፤ ዐጣኝ ።

**ዐጠንት** ፤ ዐጣኞች ። **ካህናት ፡ ሰማይ ፡ ቅዉ ማን ፡ በዕበይ ፤ ዐጠንት ፡ መንበሩ ፡ ለአዶናይ** ፡ (ሳታ) ።

**ምዕጣን** ፤ ማጠኛ ፤ ማጤሻ ፤ ቦታ ። **ምሥዋዕ ፡ ዘምዕጣን** ፡ (ዘሌ፬ ፡ ፯) ።

**ማዕጠንት ፡ (ታት)** ፤ ማጠኛ ፡ ማጤሻ ፡ ጥና ። **ማዕጠንተ ፡ ወርቅ ፡፡ ወማዕጠንታቲሆ** ፡ (ራእ ፰ ፡ ፫ ። ዘኍ፬ ፡ ፲፬) ።



ማዕጠንት ፡

**ተዐጥነ** ፤ ታጠነ ፤ ተጤሰ ። ዐጠኑት ፡ ዐጤሱ ለት ።

**ዕጥነት** ፤ ማጠን ፡ መታጠን ፤ አስተጣጠን ። **ይዕጥን ፡ ውስቴቱ ፡ ዕጥነተ ፡ ዘዘልፍ** ፡ (ዘፀ፴ ፡ ፯) ።

**ዕጥነት** ፤ ሽታ ፤ መዐዛ ። **ዕጥነታ ፡ ከርቤ ፡ ወ ስኂን ፡ እምዝሉ ፡ ጸበለ ፡ አፈው** ፡ (ማሕ፫ ፡ ፮) ።

**ዕጣን ፤ (ናት)** ፤ በቁሙ ፡ ሽቱ ፡ የሽቱ ፡ ቅ መም ፡ ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ የተበጀ ፡ የተዘጋጀ ፤ መሥዋዕት ፡ ቍርባን ፡ የሚኾን ፡ የሚጤስ ፡ የሚታጠን ። **ገበርተ ፡ ዕ ጣን ፡ ወአፈው ፡፡ ጸሎተ ፡ ዕጣን ፡፡ ሰዓተ ፡ ዕጣን ፡፡ ምሥ ዋዕ ፡ ዘዕጣን ፡፡ ዕጣን ፡ ቅድው** ፡ (፩ዜና ፡ ፱ ፡ ፴ ። ቅዳ ። ሉቃ፩ ፡ ፲ ። ዘሌ፴ ፡ ፩ ። ፴፭—፴፯) ።

**ዕጣነ ፡ ሞገር** ፤ ቅኔ ፤ የቅኔ ፡ ስም ፤ ከዕጣንና ፡ ከቍርባን ፡ በኋላ ፡ የሚቀኙት ፡ (መጽ ፡ ቅኔ) ።

**ዐጢፍ ፤ ፎት ፤ (ዐጠፈ ፡ የዐጥፍ ፡ ይ ዕጥፍ ። ዐረ ፡ ዐጠፈ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ዐጣፍ)** ፤ መሥራት ፤ ማጠፍ ፤ መጠቅለል ፡ ማልበስ ፡ መሸፈን ፡ ማጕናጠፍ ፤ መጠቅለያውን ፤ የሸማኔ ። ዐጸፈን ፡ ተመል ከት ፤ የዚህ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ነው ።

**ተዐጥፈ** ፤ ተሠራ ፤ ታጠፈ ፤ ተጠቀለለ ፡ ገ ለጠ ፡ ልብሱ ።

**ዕጡፍ** ፤ የተሠራ ፡ የታጠፈ ፤ የተጠቀለለ ፤ መ ዘራገር ፡ የገባ ። **ከመ ፡ ዕጡፈ ፡ ፀምር ፡ ዘአልጸቀ ፡ ይ ግምድዎ** ፡ (ኢሳ፴፰ ፡ ፲፪) ።

**ዐጥፍ** ፤ በቁሙ ፤ የተሠራ ፡ ልብስ ። **ሠርዌ ፡ ዐጥፍ ፡ ዘመዐስቃን** ፡ (፪ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱) ።

**ዐጢቅ ፤ ቆት ፤ (ዐጠቀ ፡ የዐጥቅ ፡ ይዕ ጥቅ)** ፤ መታጠቅ ፤ መቀነት ፤ ወገብን ፡ ማሰር ፡ ማጥበቅ ፤ ማሸረጥ ፡ ማሸንፈጥ ፤ ማገልደም ። **ዕጥቅ ፡ ውስተ ፡ ሐ ቌክ ፡፡ እለ ፡ የዐጥቁ ፡ ቅናተ ፡ መንግሥት ፡፡ ገብሩ ፡ ሎሙ ፡ ምራሕ ፡ ዘየዐጥቁ** ፡ (ኤር፲፫ ፡ ፩—፪ ። አፈ ፡ ተ፳ ። ቀሌ) ።

**ዐጣቂ ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት)** ፤ የታጠቀ ፡ የሚታጠቅ ፤ ታጣቂ ። **ለሐቌክ ፡ ሰላም ፡ ቅናተ ፡ ል ቡና ፡ ዐጣቂ** ፡ (ደራሲ) ።

**ዕጠቅ** ፤ መታጠቅ ፤ አስተጣጠቅ ፡ ትጥቅ ፡ ማ ጠቆ ። **ወዕጠቆሙ ፡ ይፈትሑ ፡ ሐራ** ፡ (ደራሲ) ።

**ዐጥቅ** ፤ በቁሙ ፤ ያገዳና ፡ የቅልጥም ፡ ወሰን ፡ መገናኛው ፤ እንደ ፡ ትጥቅ ፡ ያለው ። ዐጥቅ ፡ የለሽ ፡ እን ዲሉ ፤ ወሰን ፡ የለሽ ፡ ቢሉ ።



ዐጥቅ ፡

**አዕጠቀ** ፤ አስታጠቀ ። **አዕጥቀኒ ፡ ኀይላቲ ከሙ ፡ ወአቅንቶኒ ፡ ለጸብእ** ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲፬) ።

**ዐጣርድ ፤ (ዐረ ፡ ዐጣሪድ)** ፤ ኮከብ ፤ የኮ ከብ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ሥዕሉ ፡ ምስሉ ፤ ሰብአ ፡ ልበጥራን ፡ የሚያመልኩት ። ሄርሜኔን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡

አንድ ፡ ነው ። ወሰመይዎ ፡ ሰአሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ መኸተሬ ፡ ወሲካልኡ ፡ ዐጣርድ ፡ (አፈ ፡ ተጸ፺ ። ግብ፲፱ ፡ ፲፪) ።

**ዐጢስ ፤ ሶት ፤ (ዐጠሰ ፡ የዐጥስ ፡ ይዐጥስ ። ዐረብ ። ዕብ ፡ ዐጣሽ) ፤** ማንጠስ ፤ ድንገት ፡ ባፍና ፡ ባፍንጫ ፡ መሮጫ ፤ መተንፈስ ፤ ክንንፋን ፡ ወይም ፡ ከክፉ ፡ ሽታ ፡ የተነሣ ። ማፋሸግ ፡ ማላቀቅ ፡ ማዘጋት ፡ አፍን ፡ መክፈት ፤ ዋሻ ፡ ማስመሰል ።

**ዕጠስ ፤** ዕንጥስታ ፤ ንጥሻ ፡ ፍሽጊያ ፤ ክፍት ፡ አፍንት ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ቅንድብ ፡ ይሉታል ። በዕጠሱ ፡ ይበርቅ ፡ ብርሃን ። ዕጠስ ፡ ወሀኬት ፡ (ኢዮ፵፩ ፡ ፲፰ ። አፈ ፡ ተጸ፺) ።

**ዐይ ፤—ምን ፤—አይ ።**

**ዐይግ ፤ (ጋት) ፤** ዥሬ ፡ የውሃ ፡ መቋሚያ ፤ መጠራቀሚያ ፡ ጉድጓዳ ፡ በታ ፡ ፀውደ ፡ ማይ ፤ ጉባኤ ፡ ማይ ፤ ታናሽ ፡ ባሕር ። በአሐቲ ፡ ዐይግ ፡ ማይ ፤ ወውእቱ ፡ ዐይግ ፡ ማይ ፡ ተሠጠ ፡ (ሔኖ፹፱ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬—፳፯) ።

**አዕያግ ፤ (ጋት) ፤** ዥሬዎች ፤ የውሃ ፡ መቋሞች ። አዕያጊሆሙ ። አዕያጋተ ፡ ማይ ። ዝናም ፡ መልአ ፡ ዙሎ ፡ አዕያጋተ ፡ ዘሀሎ ፡ ኀቤሆሙ ፡ (ዘፀ፯ ፡ ፲፱ ። ዘሌ፲፩ ፡ ፴፮ ። ዮሴፍ) ።

**ዐይገን ፤ (ዕብ ፡ አጋን ። ሱር ፡ አጋና ። ዐረ ፡ ኢጋንት) ፤** ጣሳ ፤ ፍንጃል ፤ ኵባያ ፤ ዳክ ፤ ለገን ። ቂጃ ፤ ማለቢያ ፤ የስፌት ፡ ዕቃ ፤ ደም ፡ ተቀብቶ ፡ እንደ ፡ ሸክላና ፡ እንደ ፡ ፍንጃል ፡ ያለ ፤ ውሃ ፡ የሚይዝ ፡ የሚቋጥር ። ዐይገን ፡ ዐቢይ ። ወመልአ ፡ ዐይገኒ ፡ (መሳ፳ ፡ ፳፰ ። ኗ ፡ ፴፰) ።

**ዐይጋን ፤** ኵባዮች ፤ ፍንጃሎች ፤ የሸክላ ፡ ጥዎች ፤ እጀታ ፡ ዦሮ ፡ ያላቸው ። አርባዕቱ ፡ ምእት ፡ ዐይጋኒ ፡ ወይን ፡ (ገድ ፡ አዳ) ። ጋን ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ይሰማማል ፤ ገንዕን ፡ ተመልከት ።

**ዐይጥ ፤ (ዕብራ ፡ ዐይጥማ ፡ አሞራ) ፤** በቁሙ ፤ የሌት ፡ ወፍ ፤ ነገደ ፡ አንጼዋ ።

**ዐየየ ፤—መሰለ ፤—አይይ ፡ አየየ ።**

**ዐይይ ፤ ዮት ፤ (ዐየየ ፡ የዐይይ ፡ ይዕየይ ፡ ይዕይይ ። ዐረ ፡ ዐዪየ) ፤** መሳት ፤ መሳሳት ፡ ከመንገድ ፡ መውጣት ፤ መዞር ፡ መባከን ፤ ፈልጎ ፡ ማጣት ። ወየዐይይ ፡ እንተ ፡ በዙሰሄ ። በአይ ፡ ፍና ፡ እስመ ፡ ዐየይኩ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ። ቄር ፡ ጳላ) ።

**ዕዩይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ይይት) ፤** ፊሉ ፡ የዞረ ፡ እንቡዝ ፤ ባካና ። አ ፡ ዘእንበለ ፡ ልብ ፡ ዕዩይ ፡ ኢሰቦከ ፡ ምስጢረ ። ዘእምባሕር ፡ ወእሞት ፡ ዕዩይ ። ዕዩያኒ ፡ ጎሲና ፡ (ተረ ፡ ቄር ። አፈ ፡ ተ፫) ።

**ዐዩል ፤ ሎት ፤ (ዔለ ፡ የዐይል ፡ ይዒል ። ዕብ ፡ ዐላህ) ፤** ላይ ፡ ላዩን ፡ መዞር ፡ መባከን ፡ መብረር ፤ ማውተት ፡ መንከርተት ፡ ያሞራ ፡ የወፍ ። ርቆ ፡ መኼድ ፤ ጋራ ፡ ዙሮ ፡ ወንዛ ፡ ተሻግሮ ፡ መሸሽ ፡ መሰደድ ። ወደ ፡ ዱር ፡ ወደ ፡ በረሓ ፤ ወደ ፡ ጋራ ፡ ወደ ተራራ ፡ መውጣት ፡ መሰምረት ፤ መናወዝ ፤ መቃበዝ ፡ ጕባውን ፡ ተሬውን ፤ ዋሻውን ፡ ጕሬውን ፡ መሰለል ፡ መጕብኘት ፡ የዐዳኝ ፡ የመናኝ ። አዐይል ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ከመ ፡ ያፍ ። እንዘ ፡ የዐይል ፡ አድባረ ፡ ወአውግረ ። በውስተ ፡ በድው ፡ ኀበ ፡ ዔልክሙ ፡ በበ ፡ መራዕይክሙ ። ንዒል ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ወበአታት ፡ ወግበበ ፡ ምድር ፡ (መዝ ፲ ። ስንክ ፡ ታኅ፲ ። ሆሴ፲፫ ፡ ፳—፳ ። ድጓ) ። በዔሉ ፡ ፈንታ ፡ ተዐየለ ፡ ይባል ፤ አያስኝም ። አሐተ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡ ይትዐየል ፡ ውስተ ፡ ቢድው ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳፱) ።

**ዐያል ፤ (ሊ ፡ ሊት) ፤** የሚዞር ፤ ዘዋሪ ፤ ቅብዝብዝ ። እንዘ ፡ ዐያሰ ፡ የሐውሩ ። ከመ ፡ ንህብ ፡ ዐያሊት ፡ ከማሁ ፡ አባ ፡ ዮሐኒ ፡ ዘዔሊ ፡ (ሄርማ ። ገድ ፡ አዳ ። ድጓ) ።

**ዒለት ፤** መዞር ፤ ዙረት ፡ አዚዚር ።

**አዔለ ፤** አዞረ ፤ አባከነ ፤ አንከረተተ ። አዔሎሙ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ። አዔልዎ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ (ዘኍ፴፪ ፡ ፲፫ ። ኢዮ፲፪ ፡ ፳፬ ። ስንክ ፡ መጋ፲፭) ።

**ዔላ ፤ (ላት) ፤** ዐዘቅተ ፡ ማይ ፤ የውሃ ፡ ጕድጓድ ፤ መከማቻ ፡ መጠራቀሚያ ። ዔላ ፡ ዘውእቱ ፡ ምእላድ ፡ ማይ ፤......ያመጽኡ ፡ ሎሙ ፡ ማየ ፡ ወይመልእዎ ፡ በዔላት ፡ (ታምረ ፡ ማር) ።

**ዐያም ፤ (ዕብራ) ፤** ብርቱ ፡ ጠንካራ ፤ ዐያሌ ፡ ብዙ ፤ የሕዝብ ፡ የመንጋ ።

**ምዕያም ፤ (ማት) ፤** በረት ፤ ጎል ፡ ምስሐግ ፤ ብዙ ፡ መንጋ ፡ የሚያድርበት ፤ የሚመሰግበት ። አይቴ ፡ ኀሰፈት ፡ እምዕያማ ፡ ማርያም ፡ ጣዕዋ ፡ (ደራሲ ። ሔኖ፹፯ ፡ ፪) ።

**ዔመ ፤** አፈገ ፤ መሰገ ፤ አገባ ፤ አጐረ ።

**ዐየነ ፤—ተከባከበ ፤—አይኖ ፡ አየነ ።**

**ዐይን ፤ (ዕብ ፡ ዐዪን ። ዐረ ፡ ዐይን ። ሱር ፡ ዐይና) ፤** በቁሙ ፤ የማየት ፡ ሕዋስ ፤ ማያ ፡ መመልከቻ ። ማኅተቱ ፡ ለሥጋ ፤ ውእቱ ፡ ዐይንከ ። ይትራአዩ ፡ ዐይነ ፡ በዐይን ፡ (ማቴ፮ ፡ ፳፪ ። ኤር፴፱ ፡ ፬) ።



ዐይን ፡

**አዕይንት ፤** ዐይኖች ፤ የሥጋ ፡ መብራቶች ። ይኤጽራ ፡ አዕይንቲሁ ። ጠፍአ ፡ አዕይንቲነ ፡ (ኢሳ፶፯ ፡ ፯ ። ሰቈ፬ ፡ ፲፯) ።

**ዐይን ፤ ሰብአ ፡ ዐይን ፤** ሰላይ ፤ ጕበኛ ፤ መልከተኛ ። ወፈነወ ፡ ዳዊት ፡ አዕይንተ ። አኩኑ ፡ አዕይንት ፡ እሙንቱ ። ፈኑ ፡ ዕደወ ፡ ሰብአ ፡ ዐይን ፡ (፩ነገ ፡ ፳፯ ፡ ፬ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**ዐይን** ፤ ዐይንት ፡ መልክ ፤ ሕብር ፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለ ፡ ትይዩ ፡ አንጻር ፤ ዐይን ፡ የሚያየው ፡ የሚያርፍበት ።

**ዐይን** ፤ ዐይነታ ፡ ዋና ፡ ጭንሬታ ። **እመ ፡ ኢተ ረከበ ፡ ዐይኑ ፡ ያገብእ ፡ አምሳሊሁ** ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፰) ።

**—** ፤ የሚዛን ፡ ምላስ ፤ ውልብልቢት ፤ ላንቤታ ። **እንተ ፡ ታገብእ ፡ ዐይነ ፡ መዳልው** ፡ (ኢሳ ፵ ፡ ፲፭) ።

**—** ፤ ብስ ፤ ነዳላ ፤ ሽንቍር ፤ ፍልፍል ፤ የገበጣ ፡ የስፌፍ ፡ ዐይንት ፤ ሽክፌ ፤ ጠቃጠቆ ። የመርፌ ፡ ዐይን ፤ ገበጣ ፡ ዐይን ፤ ዐይናማ ፡ ደንጊያ ፡ እንዲሉ ።

**ዐይነ ፤ ማዓተም** ፤ የማኅተም ፡ ዐይነት ፤ በማኅተም ፡ ላይ ፡ የተሣለ ፡ የተቀረጸ ፡ መልክ ፤ ወይም ፡ የታተመ ፡ የማኅተም ፡ ቅድ ፡ (ዘፀ ፳፰ ፡ ፲፩ና ፡ ፳፩) ።

**ዐይነ ፤ ወርቅ** ፤ የወፍ ፡ በሽታ ፤ ዐይንን ፡ ጥፍርን ፡ ሽንትን ፡ ሰውነትን ፡ ብጫ ፡ የሚያደርግ ፤ ወርቅ ፡ የሚያስመስል ። የከፋ ፡ ዐይን ፡ ደዌ ፤ አስተያየቱ ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ ኹዋ ፡ የሚወጋ ። **ተዘከር ፡ ከመ ፡ እኩይ ፡ ዐይነ ፡ ሰብእ ። ነጸሩ ፡ በመዐት ፡ ወመጽለወት** ፡ (ሢራ ፴፱ ፡ ፲፫ ። አስቴ ፰ ፡ ፩—፱) ።

**ዐይን** ፤ ምንጭ ፤ ውሃው ፡ እንደ ፡ እንባ ፡ ኹኖ ፡ ሲወጣ ፡ ሲፈልቅ ፡ የሚታይበት ። **ይትከሀሉኑ ፡ ይፃእ ፡ እምአሐዱ ፡ ዐይን ፡ ማይ ፡ መሪር ፡ ወማይ ፡ ጥዑም ። ወሀሰዉ ፡ ፀየ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ዐይን ። አቀመ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ለተክዚ** ፡ (ያዕ ፫ ፡ ፲፩ ። ዘፀ ፲፭ ፡ ፳፯ ። ሱቱ ፡ ዕዝ ፲፫ ፡ ፵፬ ። ድጓ) ።

**ዐይነ ፡ ምድር** ፤ ጕድጓድ ፡ ዐዘቅት ፡ ኵስሕ ፤ የጕድጓድ ፡ ምንጭ ፤ ውሃው ፡ ከውስጥ ፡ ከመሬት ፡ የሚ ፈልቅ ፤ እንዳዲስ ፡ አበባ ፡ ያለ ።

(ጥ) **ዐየነ** ፤ **(ዕብ ፡ ዐዬን)** ፤ ዐይናማ ፡ ኾነ ፤ ዐይን ፡ አወጣ ። ምንጭ ፡ ፈለገ ፡ በታ ፡ ሰለለ ፤ ጐበኘ ፤ ሰሰፈር ። ዐይኑን ፡ ጣለ ፤ ትክ ፡ ብሎ ፡ አየ ፤ አስተዋለ ። አጥልቆ ፡ ዐሰበ ፤ መረመረ ፤ ፈተሸ ፡ ቀመለ ፡ የነገር ። ገመተ ፤ ገመገመ ፤ ይህን ፡ ያኽል ፡ አለ ፤ የዋጋ ፡ የክሳ ። **በዕጹብ ፡ እመ ፡ ዐየነ ፤ ነረክብ ፡ ምግባረ ፡ ዘውስተ ፡ ምድር ። የዐይኑ ፡ ሎሙ ፡ ዘይሁብዎሙ** ፡ (ጥበ ፱ ፡ ፲፱ ። ዘሌ ፲፱ ፡ ፳ ። ዘፀ ፳፩ ፡ ፴፩ ። ፪ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፪) ። በዐየነ ፡ ፈንታ ፡ ተዐየነ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። **እንዘ ፡ ይት ዓየኖ ፡ ዘልፈ ፡ እመ ፡ ይፈርህ ፡ ወይደንዕ ፤ በጽኑዕ ፡ ይትዓየኖኒ** ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ። ርእየነ ፡ ተመልከት ።

**ዐየነ** ፤ **(ትግሬ)** ፤ አበደ ፡ እብድ ፡ ኾነ ፤ ልቡ ፡ ጠፋ ።

**ተዐየነ** ፤ ተጐበኘ ፤ ተሰለለ ፤ ተመረመረ ፤ ምንጩ ፡ ቦታው ። ተገመገመ ፤ ዋጋው ።

**ተዐየነ** ፤ ከተመ ፡ ምንጭ ፡ ያዘ ፡ ሰፈረ ፤ ጕዝጕ ፡ ሠራ ፤ ድንኳን ፡ ተከለ ፤ ሕዝቡ ። **እለ ፡ ይቀድሙ ፡ ተዐይኖ ። ወተዐየኑ ፡ ውስተ ፡ አቤኔዜር** ፡ (ዘኍ ፪ ፡ ፫ ። ፩ነገ ፡ ፬ ፡ ፩) ።

**—** ፤ ከበበ ፤ ዐጠረ ፤ ዙሪያውን ፡ ያዘ ፤ በዙሪያ ፡ ሰፈረ ። **ሶቤ ፡ ዖነ ፡ ተዐይኖ ፡ ላዕለ ፡ ሀገር ። ወተዐየና ፡ ለሀገር ፡ ወዐገታ ። ወይትዐየኑኪ** ፡ (ዮሴፍ ። ሉቃ ፲፱ ፡ ፵፫) ።

**ዕዩን** ፤ **(ናን ፡ ናት ፡ ይንት)** ፤ የተጐበኘ ፤ የተመረመረ ፤ የተገመገመ ፤ የተመረጠ ፡ የተለቀመ ፤ ምርጥ ። **ዕጣን ፡ ዕዩን ፡ ዘድቁቅ** ፡ (ዘሌ ፲፮ ፡ ፲፪) ።

**ትዕይንት** ፤ **(ታት)** ፤ ሰፈር ፤ ከተማ ፤ መንደር ፡ ብዙ ፡ ድንኳን ፤ ጕዝጕ ፡ ቤት ፤ ዳስ ፡ በረት ። **ቀርበ ፡ ሙሴ ፡ ኀበ ፡ ትዕይንት ፤ ወቆመ ፡ ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ትዕይንት** ፡ (ዘፀ ፴፪ ፡ ፲፱ና ፡ ፳፮) ።

**—** ፤ ሰራዊት ፡ ጭፍራ ፤ ጓዝ ፡ ወገን ፤ ሕዝብ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ። ጉባኤ ፡ ማኅበር ፤ ሸንጎ ፤ የሰው ፡ መንጋ ፤ ባንድነት ፡ የሚሰፍር ፡ የሚንጋጋ ። መንግሥትን ፡ ተመልከት ። **ወሰሰለ ፡ መልአከ ፡ እግዚ ፡ ዘየሐውር ፡ ቅድመ ፡ ትዕይንቶሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ። ወትዕይንቶሙስ ፡ ለኢሎፍሊ ፡ ተዐየኑ ፡ ፈለገ ። ትዕይንቶሙ ፡ ለእለ ፡ ቆሬ** ፡ (ዘፀ ፲፬ ፡ ፲፱—፳ ። ፩ዜና ፡ ፲፩ ፡ ፲፰ ። ሚራ ፵፰ ፡ ፲፰) ።

**ተዓይን** ፤ ሰፈሮች ፡ ድንኳኖች ፤ ከተሞች ። ሰራዊቶች ፤ ጭፍሮች ፤ ማኅበሮች ። **ተዓይኒሆሙ ፡ ለኤዶምያስ ። እምዘሱ ፡ ተዓይኒሁ ፡ ለያዕቆብ ። ወርእየ ፡ ያዕቆብ ፡ ተዓይነ ፡ እግዚ ። እመኒ ፡ ጸብአኒ ፡ ተዓይን ። ተዓይኒ ፡ ክርስቶስ** ፡ (መዝ ፡ ፹፪ና ፡ ፹፯ ። ዘፍ ፴፪ ፡ ፩—፪ ። መዝ ፡ ፳፮ ። ስንክ ፡ ሐም ፲፪) ።

**ተዓየነ** ፤ ተሳፈረ ፤ ተሰፋፈረ ፡ ጕን ፡ ለጕን ፡ ወይም ፡ ፊት ፡ ለፊት ።

(ጥ) **ዐየረ** ፤ **ሮት** ፤ **(ዐየረ ፡ ይዔይር ፡ የዐይር ። ዐረ ፡ ዐየረ ። ዕብ ፡ ሐሬፍ)** ፤ ማየር ፡ መቀላቀል ፡ የማዕደናት ። መስደብ ፡ ማዋረድ ፤ መገደር ፡ መላገድ ፡ መናቅ ፡ ማቅለል ፤ አሳልፎ ፡ መስጠት ፤ ራስን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ። **ሕዝብ ፡ ዘዐየረ ፡ ነፍሶ ፡ ለሞት** ፡ (መሳ ፭ ፡ ፲፰) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዐየረ ፡ ፈንታ ፡ ተዐየረ ፡ ይላል ፤ አድራጊውን ፡ በተደራጊ ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። **ኢይትዐየር ፡ እንዘ ፡ ይብል ፤ ኦ ፡ ዕዉር ፡ ኦ ፡ ጽሙም ፡ ኦ ፡ ሐጺጽ ፡ ኦ ፡ ገብር ፡ ኦ ፡ ፀጋማዊ ፡ ኦ ፡ ሀካይ ፤ ወዘ ቶርፉ ፡ ትዕይርታተ ። ጸሐፈ ፡ እንዘ ፡ ይትዔየሮ ፡ ለእ ግዚ ። ወእመሰ ፡ ቦ ፡ ዘተዐየሩክሙ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ። ዘይትዔየር ፡ በክብረ ፡ ርእሱ** ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ፡ ፱ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፲፯ ። ፩ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ። አርጋ ፡ ፫) ።

**ተዐየረ** ፤ **(ተደራጊ)** ፤ ተሰደበ ፤ ተዋረደ ፤ ተናቀ ፤ ተጠቃ ፤ ተግዳሮት ፡ ሰማ ።

**ዕዩር** ፤ **(ራን ፡ ራት ፡ ይርት)** ፤ የተሰደበ ፤ ስዱብ ፤ ወሪዳ ፤ ጥቁ ። **ንከውን ፡ ዕዩራነ** ፡ (ዮዲ ፰ ፡ ፳፪) ።

**ትዕይርት** ፤ **(ታት)** ፤ ስድብ ፤ ውርደት ፡ ለግድ ፤ ተግዳሮት ፡ ጡር ፡ መስቃ ። **ትዕይርተ ፡ ይከ ውኖ ። ከመ ፡ ኢይስማዕ ፡ ትዕይርተ ። ትዕይርቱ ፡ ለ ክርስቶስ ። እንዘ ፡ ንጸውር ፡ ትዕይርቶ** ፡ (ጦቢ ፫ ፡ ፱ና ፡ ፲፫ ። ዕብ፲፩ ፡ ፳፮ ። ፲፫ ፡ ፲፫) ።

**ዕይር** ፤ በቁሙ ፡ ቅልቅል ፡ ድብልቅ ፡ የታየረ ።

**ዔር** ፤ **(ዕብ ፡ ዒር)** ፤ ጠባቂ ፡ መልአክ ። ምስጢሩ ፡ ግን ፤ ነሣቲ ፡ ደይኒ ፡ ማለት ፡ ነው ። **ወናሁ ፡ ዔር ፡ ቅዱስ** ፡ (ዳን ፬ ፡ ፲) ።

**ዔረግ** ፤ (ዕብ ፡ ሄሬግ ፤ የሰይፍ ፡ ሞት ። ዐረ ፡ ሐርግ) ፤ ወጥመድ ፤ አሽክላ ፤ ያውሬ ፡ መያዣ ። እስመ ፡ ፍቅረ ፡ ወይን ፡ ተብህለ ፡ ለሰይጣን ፡ ዔረጉ ፡ (ደራሲ) ።

**ዔረግ** ፤ (ዕብ ፡ ክሉብ) ፤ ቀፎ ፤ ቅርጫት ፤ የአዕዋፍ ፡ ቤት ፤ ከቀጫጭን ፡ ሐረግ ፡ ወይም ፡ ከሽቦ ፡ የተሠራ ፤ ሐረግን ፡ ተመልክት ። ከመ ፡ ዔረግ ፡ ዘምሉእ ፡ አዕዋፈ ፡ (ኤር፭ ፡ ፳፯) ። በፍሬ ፡ ፈንታ ፡ ዔረግ ፤ በዔረግ ፡ ፈንታ ፡ ሙዳይ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ሙዳየ ፡ ዔረግ ፡ (ዓሞ፰ ፡ ፩—፪) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፤ ክሉብ ፡ ቃይጽ ፡ ይላል ፤ የበጋ ፡ ቅርጫት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ፍሬ ፡ የተመላ ፡ ማለትን ፡ ያሳያል ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ በለው ፡ ሰይፍ ፤ ጸብታ ፡ ፃማታ ፡ ይሉታል ፤ የበጋ ፡ ጸብት ፡ ንጥየ ፡ ሐቅል ፡ ማለት ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ ሙዳየ ፡ ዔረግ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ቁረጽ ፡ ይቈርጽ ፡ ይላል ፤ ይህን ፡ ደግሞ ፡ መቀስ ፡ ይሉታል ፤ ንባቡም ፡ ፍችውም ፡ አልተ ሳከም ።

**ዐኪው** ፤ **ዎት** ፤ (ዐከወ ፡ የዐኩ ፡ ይዕኩ) ፤ መከልከል ፤ ማስቀረት ፤ እንዳይገባ ፡ ማድረግ ።

**ታዕካ** ፤ (ካት) ፤ የንጉሥ ፡ ቤት ፤ ቤተ ፡ መንግሥት ፤ አዳራሽ ፡ ታላቅ ፡ ከፍተኛ ፤ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ የተሠራ ፤ ግቢ ፤ ሰፈር ፤ ከልካይ ፡ አስከልካይ ፡ ዘበኛ ፡ አጋፋሪ ፡ ያለበት ። ታዕካ ፡ ንጉሥ ። ጸግዎ ፡ በላመ ፡ ለንጉሥን ፤ ለታዕካሁ ፡ ወለሰራዊቱ ። ቈስጠንጢኖስ ፡ ታዕካ ፡ ኀበ ፡ ዘሐነጸ ፡ ሎቱ ። ማርያም ፡ ታዕካ ፡ በምድር ፡ ወታዕካ ፡ በሰማይ ፤ ታዕካ ፡ መንግሥት ፡ በማያት ፡ (አቡሻ ፡ ፺ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ ጥር፳፯። ድጓ ። መቃ) ።

**ዐኮት** ፤ (ዕብ ፡ ዐሮብ) ፤ ከልካይ ፡ አጋፋሪ ፤ የበር ፡ መቅሠፍት ። ተባይ ፤ ተናካሽ ፡ ፍጥረት ፤ በየስሙና ፡ በየመልኩ ፤ የሚነድፍ ፡ የሚቈነጥጥ ፤ የሚያቈስል ፡ የሚያሳብጥ ፤ የሚያሳክክ ፡ የሚያንገበግብ ፤ ተርብ ፡ የውሻ ፡ ንብ ፤ የበሬ ፡ የበረሓ ፡ ዝንብ ፤ ትንኝ ፡ ቅማል ፤ ቍንጫ ፡ ትኋን ፤ ዘመሚት ፡ ጕንዳን ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ፈነወ ፡ ዐኮተ ፡ ወበልዖሙ ፡ (መዝ ፡ ፸፯ና ፡ ፵፬ ። ጥበ፲፱ ፡ ፲) ።

**ዐከ** ፤—**አይዶለም** ፤—**አኪው ፡ አከወ** ፤ **አኮ** ።

**ዐከየ** ፤—**ከፋ** ፤—**አክይ ፡ አከየ** ።

**ዐኪክ** ፤ **ክት** ፤ (ዐከከ ፡ የዐክክ ፡ ይዕክክ) ፤ መጥገብ ፤ መጠገብ ፤ መሰልቸት ፤ ዕክክ ፡ ማለት ። ብዙ ፡ ውሃ ፡ መያዝ ፤ እስክፍ ፡ እስክ ፡ ከንፈር ፡ መንተርፈፍ ፡ መምላት ፤ የጋን ፡ የማድጋ ፡ (ዮሐ፪ ፡ ፯) ።

**ማዕከክ** ፤ (ዕብ ፡ ኪዮር) ፤ ድስት ፤ ማሰሮ ፡ ምንቸት ፤ የሚጣድ ። ገንቦ ፡ ማድጋ ፤ እንስራ ፡ ጋን ፡ ዝንጋሮ ፤ ዋዲያት ፡ ለገን ፤ ማጠቢያ ፡ መታጠቢያ ፤ የውሃ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፤ ክብነት ፡ ያለው ። ጣሳ ፡ ኰብያ ፡ ዋንጫ ፡ ጽዋዕ ፡ ሳይቀር ፡ መቅጃውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ኬጥሮጋ ውሎስን ፤ ንባቢራን ፡ መቀሰድን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ዘገብረ ፡ ማዕከከ ፡ ብርት ፤ ወገብሮ ፡ ለውእቱ ፡ ማዕከክ ፡ ከመ ፡ ይትኃፀቡ ፡ ውስቴቱ ። ሕንብርትኪ ፡ ከመ ፡ ማዕከክ ፤ ጽዋ ፡ (ዘፀ፴፰ ፡ ፳፯—፳፯ ። ማሕ፯ ፡ ፫) ።

**መዓክክት** ፤ ታላላቅ ፡ ድስቶች ፤ ጋኖች ፤ መታጠቢያዎች ። ወመዓክክተኒ ፡ (፪ነገ ፡ ፳ ፡ ፳) ።

**ዐከለ** ፤—**በላ** ፤ **በቃ** ፤—**አኪል ፡ አከለ** ።

**ዐልጎ** ፤ **ጎት** ፤ (ዐለገ ፡ ይዔልግ ፡ የዐልግ ። ዐረ ፡ ዐለጀ) ፤ ማሸነፍ ፤ መጣል ፤ ድል ፡ መንሣት ፤ በላይ ፡ መኾን ፤ የትግል ፡ የውጊያ ። መሸጠጥ ፤ መጋጠጥ ፤ ከሥሩ ፡ መቍረጥ ፤ የንፍረት ። ትግሬ ፡ ግን ፡ ፀለገ ፡ ብሎ ፡ ሰወረ ፡ ደበቀ ፡ ይላል ፤ ምስጢሩ ፡ ኀፍረት ፡ ነው ።

**ዕልገት** ፤ ማሸነፍ ፤ መጣል ፤ መግደል ፤ መስሉብ ፤ መግፈፍ ። የድል ፡ ምልክት ፤ ምርኮ ፡ ለበባ ፡ የደም ፡ ሽማ ፤ ትምክሕት ፤ ድንፋታ ፤ ልዕልና ፡ ከፍታ ፤ ቅርርት ፡ ፍከራ ፤ የዠግንነት ፡ ሥራ ። ዕልገተ ፡ ቈላፋን ። ዘብዙኀ ፡ ዕልገቱ ። ወሎቱስ ፡ አግብኡ ፡ ሎቱ ፡ ዕልገቶ ፡ በእልፍ ። በመጥባሕትከ ፡ ዕልገትከ ። ያነብሮሙ ፡ በዕልገቶሙ ፡ መልዕልተ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳፭ ። ፪ነገ ፡ ፳፫ ። ሚራ፹፯ ፡ ፯ ። ዘዳ፴፫ ፡ ፳፱ ። ኢዮ፴፮ ፡ ፯) ።

**ዐልጋ** ፤ በቁሙ ፤ መተኛ ፤ ትእምርተ ፡ ክብር ።

**ዐልጌን** ፤ ተራዳ ፤ ረዥም ፡ ሰንጠቅ ፤ የሰው ፡ መስቀያ ። ሕዘዘ ፡ አርያኖስ ፡ ከመ ፡ ይስቅልዎ ፡ በዐልጌን ፡ ወይንድፍዎ ፡ በአሕጻ ፤ ወአልቦ ፡ ዘለከፎ ፡ (ስንክ ፡ የካ፳) ።

**ዐለደ** ፤—**አከማቸ** ፤—**አልዶ ፡ አለደ** ።

**ዐሊው** ፤ **ዎት** ፤ (ዐለወ ፡ የዐሉ ፡ ይዕሉ ፤ ዐለየ ። ዕብ ፡ ዐዌል ። ሱር ፡ ዑል ። ዐረ ፡ ዓል) ፤ መቀበል ፤ ማስተጋባት ፤ የስሙትን ፡ ዜማ ፡ መልሶ ፡ መጮኽ ፤ መናገር ። የገደል ፡ የተራራ ፤ የተመሬ ፡ የደብተራ ። ድምፀ ፡ ቃል ፡ ዘአድባር ፡ መፍርሃን ፡ እሰ ፡ ያወሥኡ ፡ ወየዐልዉ ፡ ድምፀ ፡ በበይናቲሆሙ ። ወአክ ፡ ይባቤ ፡ አድባር ፡ (ጥበ፲፯ ፡ ፲፰ ። ሕዝ፯ ፡ ፯) ።

—፤ መወንጀል ፡ መበደል ፤ ልብን ፡ ሐሳብን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መመለስ ፤ ውልን ፡ መሐላን ፡ ቃል ፡ ኪዳንን ፡ ማፍረስ ፤ መሸፈት ፡ መሸፈጥ ፡ መክዳት ፡ መካድ ፤ ዐሎ ፡ ማለት ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ የወንጀል ፡ ስልት ፡ ነው ። ዘዐለወ ፡ በወግዘ ። ዐለዉ ፡ ልቦሙ ፡ ከመ ፡ ሊየንልዩ ። ዐለዉ ፡ ሕገከ ። ዐለዉ ፡ ኪዳንየ ። ዐለወ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ እምቤተ ፡ ዳዊት ። ዐለወቶ ፡ ለምጻ ። ዐለዎ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ለንጉሠ ፡ ባቢሎን ። ዘልክሙ ፡ ተዐልዉ ፡ (፩ዜና ፡ ፪ ፡ ፯ ። ኢሳ፶፱ ፡ ፲፭ ። ዳን፯ ፡ ፲፭ ። ሆሴ፰ ፡ ፩ ። ፪ዜና ፡ ፲ ፡ ፲፱ ። ሚራ፳፫ ፡ ፳፫ ። ኤር፶፪ ፡ ፫ ። ማቴ፳፯ ፡ ፴፩) ።

—፤ ምክርን ፡ ትምርትን ፡ መልክን ፡ ጠባይን ፡ መለወጥ ፡ መገልበጥ ። ዐልዋ ፡ እግዚእ ፡ ለምክሩ ። ይፈቅዱ ፡ ይዕልዉ ፡ ትምህርቶ ። እከዩሃ ፡ የዐልዋ ፡ ለራእዩ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፴፩ ። ገላ፩ ፡ ፯ ። ሚራ፳፩ ፡ ፲፯) ።

**ዐሊው፤** መፈጸም ፡ መምላት ፤ መተው ፤ የሥራ ፡ የሹመት ። መቅዳት ፡ መገልበጥ ፤ መተርጐም ፡ መመለስ ፤ ከመጽሐፍ ፡ ወደ ፡ መጽሐፍ ፤ ከቋንቋ ፡ ወደ ፡ ቋንቋ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዐለወ ፡ ፈንታ ፡ ኹሉንም ፡ አዕለወ ፡ ይላል ፤ አድራጊውን ፡ ባስደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ **እስ ፡ አዕለዉ ፡ ምግበሙ ፡ በንጽሕ ። አዕሉ ፡ እንከሰ ፡ ወንትሓሰብ ፡ ምግበከ ፡** (ቅዳ ፡ ዮሐ ። ሉቃ፲፯ ፡ ፱) ። **አንበበ ፡ ዘውስቴታ ፡ ወአዕለዋ ። ፈነውነ ፡ ለከ ፡ አዕሊወነ ። ሀብኒ ፡ መጽሐፈ ፡ ከመ ፡ አዕልዎ ፤** ቀዳ ። **እስተሐመመ ፡ አዕልወተ ። አዕለዋ ፡ እምልሳነ ፡ ጽርእ ፡ ኀበ ፡ ልሳነ ፡ ዐረቢ ። ወዘአዕለዋ ፡ ሕጹጽ ፡ ወኃጥእ ፡** (ኩፋ ፡ ፳ ። ተረ ፡ ቄር ። ሄርማ ። ፊልክ ። አፈ ፡ ወር ። ፍ ፡ ነ) ።

**ዐላዊ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)፤** ወንጀለኛ ፤ እንቢተኛ ፤ ሽፍታ ፤ ለዋጭ ፤ ገልባጭ ፤ መላሽ ። **ዐላዊ ፡ ነጋሢ ። ወአእመሮ ፡ ከመ ፡ ዐላዊ ። ዐላውያነ ፡ ጽድቅ ፡** (ዮሐ፲፱ ፡ ፲፪ ። ቲቶ፫ ፡ ፲፩ ። ሮሜ፱ ፡ ፳) ። በዐላዊ ፡ ፈንታ ፡ አዕላዊ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። **ወአዕላዊሁኒ ፡** (ፍ ፡ ነ) ።

**አዕለወ፤ (አስደራጊ)፤** አስወንጀለ ፤ አስከዳ ፤ አስካደ ፡ ዐሎ ፡ አሰኘ ፡ አስለወጠ ። **ዘአዕለዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ በምክሩ ። ያዐልዎሙ ፡ ለሕዝብነ ። ሶበ ፡ አዕለውዎ ፡ ለሃይማኖት ፡** (ሚራ፴፮ ፡ ፳፫ ። ሉቃ፳፫ ፡ ፪ ። ክብ ፡ ነገ) ።

—፤ አስፈጸመ ፤ አስተወ ። አስቀዳ ፤ አስመለሰ ። ምስክሩን ፡ በዐሊው ፡ ተራ ፡ ተመልከት ።

**አዕላዊ፤** የሚያስከድ ፤ የሚያስከዳ ። የሚያስተረጕም ፡ የሚያስቀዳ ።

**ተዐልወ፤** ተከዳ ፡ ተካደ ፤ ተጣለ ። **አመ ፡ ይትዐለዉ ፡ ሰብእ ፡ ኀያላን ፡** (መክ፲፪ ፡ ፫) ።

—፤ ተለወጠ ፤ ሌላ ፡ ኾነ ። **እምነግህ ፡ እስከ ፡ ሠርክ ፡ ትትዐለው ፡ መንበርት ፡** (ሚራ፲፰ ፡ ፳፮) ።

—፤ ተቀበለ ፤ የሀብት ፡ የትምርት ። **ወተዐልዉ ፡ ነቢያት ፡ እምኔሁ ። ትምህርት ፡ ዘመሀርኩክሙ ፤ ዘከመ ፡ ተዐሎክሙ ፡** (ሚራ፴፰ ፡ ፳ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፩) ።

—፤ ተቀዳ ፤ ተመለሰ ፤ ተተረጐመ ። **እምነ ፡ ዐረቢ ፡ ለግእዝ ፡ መጻሕፍት ፡ ተዐልዋ ። ወመክብበ ፡ መጻሕፍትሰ ፡ ዘብሉይ ፡ ተዐልዋ ፡ እምዕብራይስጢ ፡ ኀበ ፡ ግእዝ ፡** (ስንክ ፡ ነሐሴ ። መጽ ፡ ምስ) ። የግእዝ ፡ ብሉያት ፡ በዘመን ፡ ብሉይ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ተቀድተዋል ፡ ማለት ፤ ሳይከክና ፡ ሳይበክ ፤ ሳይጋገር ፡ ምጣድ ፡ ሳይነክ ፤ እምንበ ፡ አልበ ፡ የተገኘ ፡ የሕልም ፡ እንጀራ ፡ ነው ፤ ትምርት ፡ ቀስቅሶት ፡ ከንዋመ ፡ ሀኬት ፡ ለነቃው ፡ ለዛሬ ፡ ዘመን ፡ ልጅ ፡ አያጠግብም ።

**ዕልው፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሉት)፤** የወንጀለ ፤ ዐመፀኛ ፤ ከፉ ፤ ጠማማ ፤ ልውጥ ፤ ከሓዲ ። **ንጉሥ ፡ ዕልው ። ትውልድ ፡ ዕሉት ። ለዕልዋን ፡ ዕልወ ፡ ፍኖተ ፡ ይፌኑ ፡ ሎሙ ። ዕልዋነ ፡ ሃይማኖት ። ዕልዋን ፡ ወመናፍቃን ፡** (ስንክ ፡ መጋ፳ ። መገ፡ ፳፯ ። ምሳ፳፩ ፡ ፰ ። ዲድ ፡ ፴፫ ። ቀሌ) ።

**ዕልወት፤ (ታት)፤** መወንጀል ፡ መለወጥ ፤ ወንጀል ፤ ዐመፅ ፤ ክዳት ፤ እንቢታ ፤ አይጋ ፡ ጥፋት ። **እስመ ፡ ዕልወተ ፡ ሕግ ፡ ውእቱ ፡ ዝ ፡ ግብር ። አዝማነ ፡ ዕልወታት ። ንትሉ ፡ በዕልወትነ ። ትበጽሖሙ ፡ ዕልወቶሙ ። እምኀበ ፡ እግዚ ፡ ኮነት ፡ ዕልወተ ፡ አካዝያስ ፡** (ዲድ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ ነሐሴ ። ኤር፲፰ ፡ ፲፱ ። ኢዮ፳፩ ፡ ፲፯ ። ፱ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፯) ።

—፤ መቅጃ ፤ መዝገብ ፤ ረቂቅ ፤ መዠመሪያ ፡ የወጣ ፡ መጽሐፍ ። ወይም ፡ ቅጅ ፡ ግልባጭ ፤ ከዚያው ፡ ከም ንጩ ፡ የተቀዳ ፤ የቅጅ ፡ ቅጅ ፡ ያይደለ ። **ሀሎ ፡ ኀቤነ ፡ ዕልወቱ ፡ ለውእቱ ፡ መጽሐፍ ፡** (ተረ ፡ ቄር፲፩) ።

**ዐልው፤ ዓልዋ፤ (ጽር ፤ አልዎይ ። ሱር ፡ ዐልዋይ ። ዕብ ፡ አሃል ። ዐረ ፡ ዑድ)፤** ሽቱ ፡ የሽቱ ፡ ስም ፤ ዋግራ ፤ ሬት ። **ከርቤ ፡ ወዐልው ። ዕፀው ፡ ዘዓልዋ ፡** (ማሕ፬ ፡ ፲፬ ። ሔኖ፴፩ ፡ ፪ ። ዮሐ ፲፱ ፡ ፴፱) ።

**ዐለየ፤ (ዐለወ)፤** ወንጀለ ፤ ሸፈተ ፤ ዐሌ ፡ አለ ፤ እንቢ ፡ አለ ፤ ጠመመ ፤ ለገመ ። ወና ፡ የ ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በዐለወ ፡ ፈንታ ፡ ዐለየ ፡ ይላል ። **ዐለዩ ፡ ወሚጡ ፡ ልቦሙ ፡** (ግብ፯ ፡ ፴፱) ።

**ዕሉይ፤** ወንጀለኛ ፤ ከፉ ፡ ወስላታ ። **ኦ ፡ አብድ ፡ ወዕሉየ ፡ ኅሊና ፡** (መቃ) ።

**ማዕሌት፤** ወንጀል ፤ ግፍ ፡ በደል ፤ አሉታ ፤ እንቢታ ፤ ኀጢአት ፤ ክፋት ። **ማዕሌት ፡ ሀገር ። በማዕሌቶሙ ፡ ዘዐለዉከ ። መልአከ ፡ ማዕሌት ። ከመ ፡ ይኅብር ፡ ማዕሌቶሙ ። ማዕሌተ ፡ ይገብር ፡ ባዕሌከ ፡ ዓሞጽ ፡** (ሚራ፳፯ ፡ ፳ ። ዳን፱ ፡ ፯ ። ፫ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱ ። ሆሴ፯ ፡ ፱ ። ዓሞ፯ ፡ ፲፩) ።

**ተማዕለየ፤ (ዲ.ቃ ፡ ማ)፤** ዐለየ ፤ ዐለወ ፡ ወንጀለ ። **ተማዕለዩ ፡ ሎቱ ፤ ሖሩ ፡ ይትማዕለይዎሙ ፡** (መቃ) ።

**መምዕላይ፤** ወንጀለኛ ፡ ሽፍታ ፡ ወያኔ ፡ አረመኔ ፡ ከፉ ፡ ሪከኝ ። **ንጉሥ ፡ ዘእንበለ ፡ ሕግ ፡ ኢንጉሥ ፡ ውእቱ ፤ አላ ፡ መምዕላይ ። በበርከ ፡ ስነኒሁ ፡ ለመምዕላይ ፡ ንጉሠ ፡ ገሃነም ፡** (መጽ ፡ አዳር ፡ ፺ ። ግንዘ) ። መዐለን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ወንድም ፡ ነው ።

**ዐልሎ፤ ሎት፤ (ዐለለ ፡ ይዔልል ፡ የዐልል ። ዕብ ፡ ዐላል ፤ ጀኑ ፡ ሥራ ፡ ሠራ)፤** ማለል ፤ ዐለላ ፡ ቀለም ፡ ማግባት ፡ መንከር ። **አዘዘ ፡ ከመ ፡ ኢይልበሱ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአይሁዳውያን ፡ ልብሰ ፡ ጸዐዳ ፡ ግሙራ ፤ አላ ፡ የዐልሉ ፡ ልብሶሙ ፡ በኒል** (ስንክ ፡ ኅዳ፳፯) ።

—፤ መውጋገዝ ፤ መለየት ፤ ሕርም ፡ ማለት ፤ ለገዳም ፡ ለቤተ ፡ ክሲያን ፡ ጉልት ፡ መጕለት ። **እምዘዐሊልዎ ። አዕልሎ ፡ ሎቱ ፡ ወለአህጉሪሁ ፡** (ዘሌ፲፱ ፡ ፴፯ ። ዘኍ፳፩ ፡ ፪—፫) ።

**ተዐለለ፤ (ተዐለ)፤** ታለለ ፡ ተለየ ፤ ተጕለተ ። **እጼሊ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ እትዐለል ፡ እምክርስቶስ ፡** (ሮሜ፱ ፡ ፫) ።

**ዕሉል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ልልት) ፤ የተለየ ፤ ልዩ ፤ ውጉዝ ፤ ብቸኛ ። ይኩን ፡ ዕሉለ ። ይሰመዩ ፡ ፈሪሳው ያን ፡ ወትርጓሜሁ ፡ ለዝ ፡ ስም ፡ ዕሉላን ፡ (ዮሴፍ) ።

—፤ የታለለ ፤ ቀለም ፡ የገባ ። አልባሰ ፡ ምሥዋዕ ፡ ይኩኑ ፡ ጽዕድዋነ ፤ ወአከ ፡ ዕሉላነ ፡ በዘዘ ፡ ዚአሁ ፡ ሕብራት ፡ (፫ ፡ መ ፡ ፴፭ ፡ ፳) ።

**ማዕለል** ፤ ዐለላ ፤ ማለያ ፤ ቀለም ፤ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ያለው ። ኢትሣእን ፡ አማእነ ፡ ዕሉለ ፡ በማዕለል ፤ ወኢሕልቀተ ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ አዳብዒከ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፩) ።

**ማዕለልት** ፤ ጕልት ፡ ገንዘብ ፤ ምሎ ፡ ተፈጥሞ ፡ ሕርም ፡ ይኹንብኝ ፡ ብሎ ፡ የሰጡት ። ወሰመዩ ፡ ስሞ ፡ ለውእቱ ፡ መካን ፡ ማዕለልት ፡ (ዘኍ ፳፩ ፡ ፫) ።

**ዐልሞ** ፤ **ሞት** ፤ (**ዐለመ ፡ ይዔልም ፡ የ ዐልም** ፤ **ዐረብ**) ፤ ማለም ፤ ማመልከት ፤ ስምን ፡ መጣፍ ፡ ማተም ፤ መፈረም ። በቀድመ ፡ አሰ ፡ ቀሙ ፡ ወዐሊሙ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡ (ኤርምያ ፡ ፲፱) ።

—፤ ማስተማር ፤ መስበክ ፡ መንገር ። አበው ፡ ናሁ ፡ ዐለሙ ፤ ወሰመዩ ፡ ትሕትና ፡ በአስማት ፡ ሠናያት ፡ ወትእምርት ፡ ትርፍት ፡ (ፊልክ ፡ ፻፶፱) ።

**መዐልም** ፤ (**ዐረ ፡ ሙዐሊም**) ፤ መምህር ፤ ሰባኪ ፤ አስተማሪ ፤ ሊቅ ፡ (አዋል) ።

**ተዐለመ** ፤ ተመለከተ ፤ ባለምልክት ፡ ኾነ ። ተጣፈ ፡ ተነገረ ፤ ትምርቱ ። ተማረ ፤ ትምርት ፡ ገባው ፤ መዐልም ፡ ኾነ ፤ ሰውየው ።

**ዐላማ** ፤ (**ትግሬ ፡ ዐለመት**) ፤ በቁሙ ፤ ምልክት ፤ ባንዲራ ። ስንደቅን ፡ ተመልከት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ተዐልመ** ፤ (**ዕብ ፡ ሄዓሌም**) ፤ ዕልም ፡ አለ ፤ ታባ ፡ ተሰወረ ፤ ከመታየትና ፡ ከመታወቅ ።

**ዕሉም** ፤ ዕልም ፡ ያለ ፤ ኅቡእ ፡ ረቂቅ ፡ ስዉር ፡ ድብቅ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዕሉም ፡ ፈንታ ፡ ዓለም ፡ ይላል ። ወዓለምነሂ ፡ ውስተ ፡ ብርሃነ ፡ ገጽከ ፡ (መዝ ፡ ፹፱) ።

**ዓለም** ፤ (**ዕብ ፡ ቴቤል ። ዐረ ፡ መስኩነት**) ፤ በቁሙ ፤ ዓለመ ፡ ሰብእ ፤ ሰው ፡ የሚኖርበት ፡ ምድር ፡ መሬት ፤ የአዳም ፡ ክፍል ፤ የልጆቹ ፡ ቦታ ። ለእግዚ ፡ ምድር ፡ በምልኣ ፤ ዓለምኒ ፡ ወዙሎሙ ፡ እለ ፡



ዓለም ፤

ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡ (መዝ ፡ ፳፫ ። ኢሳ ፲፬ ፡ ፲፯ ። ፴፱ ፡ ፳ ። ኩፋ ፡ ፳) ።

**ዓለም** ፤ (**ማት**) ፤ **ዐረብ ። ዕብ ፡ ዖላም ። ሱር ፡ ዓላም**) ፤ ጊዜ ፤ ዘመን ፡ ትውልድ ፡ ያለፈ ፡ ቀድም ፤ ጥንት ፤ ትካት ፤ ወይም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚመጣ ፡ ወሬት ፡ ወትር ፤ ዘልፍ ፡ ድንት ፡ መቼም ፡ መኹ ፤ የሰው ፡ ዕድሜ ፤ መዋዕለ ፡ ሕይወት ። በከመ ፡ መዋዕለ ፡ ዓለም ። ወለዓለምኒ ፡ ቀደምት ። ኮነ ፡ አርኣያ ፡ ለዓለም ፡ ከመ ፡ ይነስሑ ። ነቢያት ፡ እለ ፡ እምዓለም ፡ (ሚክ ፯ ፡ ፲፬ ። ፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳ ። ሢራ ፵፬ ፡ ፲፮ ። ግብ ፫ ፡ ፳፩) ።

—፤ ፍጥረት ፤ ዘመደ ፡ ፍጥረት ፤ እግዜር ፡ ከእሑድ ፡ እስከ ፡ ዐርብ ፡ የፈጠረው ፤ ሰማይ ፡ ከነዚጋው ፤ ምድር ፡ ከነመንጋው ። ወይም ፡ ሰማይ ፡ ከነግሡ ፡ ከነደመናው ፤ ምድር ፡ ከነልብሱ ፡ ከንጕተናው ። እምፍጥረተ ፡ ዓለም ። እምቅድመ ፡ ዓለም ። ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ምስለ ፡ ዙሉ ፡ ዓለሞሙ ፡ (ኢዮ ፲ ፡ ፲፰ ። ቀዳ ፡ ዲዮ ። ግሩ) ።

—፤ ሰው ፡ የሰው ፡ ነገድ ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፡ ሥጋ ። ወፅአ ፡ ትእዛዝ ፡ ከመ ፡ ይጸሐፍ ፡ ዙሉ ፡ ዓለም ። ዓለምኒ ፡ ቦቱ ፡ ኮነ ፤ ወዓለምሰ ፡ ኢያእመሮ ። ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ (ሉቃ ፪ ፡ ፩ ። ዮሐ ፩ ፡ ፲ ። ሮሜ ፫ ፡ ፳) ።

—፤ ከተማ ፡ መዲና ፤ ሹመት ፡ ብዕል ፡ ሥጋዊ ፡ እናኖር ። ነበረ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፤ እምቅድመ ፡ ይመንኵስ ፤ ዕሥራ ፡ ዓመተ ። ፈለሱ ፡ ገዳመ ፡ ወመነኑ ፡ ዓለመ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ ። ቀሌ) ።

**ዓለማዊ** ፤ የዓለም ፡ ዓለመኛ ፤ ዘመናይ ፤ ሥጋዊ ፡ ሕዝባዊ ፡ ካህን ፡ መነኩሴ ፡ ያይደለ ። ብዕል ፡ ዓለማዊት ። ደብተራ ፡ ዓለማዊ ። ግብራት ፡ ዓለማውያት ። እመሂ ፡ ካህን ፡ ወእመሂ ፡ ዓለማዊ ፡ (፩ ፡ መ ፡ ፲፰ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ድ፲፭ ። ፊልክ ፡ ፪ ። ቀሌ) ።

**ገ ፡ ዓለም** ፤ ቦታ ፤ ዘመን ፤ ዓለመ ፡ ሥጋ ፤ ሰው ፡ እስከ ፡ ሞትና ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ የሚኖርበት ።

**ዓለም ፡ ዘይመጽእ** ፤ ዓለመ ፡ ነፍስ ፤ ከሞትና ፡ ከኀልፈት ፡ በኋላ ፡ የሚመጣው ። ኢበዝ ፡ ዓለም ፤ ወኢ በዘይመጽእ ፡ (ማቴ ፲፪ ፡ ፴፪) ።

**ለዓለም** ፤ (**ዕብ ፡ ልዖላም**) ፤ ለወትሮ ፤ ለዘላለም ። ለገዚሉፉ ፤ ዘልፈ ፤ ወትረ ፤ በዦሎ ፡ ጊዜ ፡ በዦሎ ፡ ዘመን ። ፍጻሜ ፡ ባለውም ፡ ለሌለውም ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ፤ እንደ ፡ እስከ ፡ ነው ። ፍጻሜ ፡ ላለው ፡ ሲነገር ፤ ምድርሰ ፡ ለዓለም ፡ ትቀውም ። ኢይትሀወክ ፡ ለዓለም ፤ እነብር ፡ ቤትከ ፡ ለዓለም ፡ ይላል ፡ (መክ፩ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፳፱) ። ፍጻሜ ፡ ለሌለው ፡ ሲነገር ፡ ቦኑ ፡ ለዓለም ፡ አሐዩ ። ቦኑ ፡ ለዓለም ፡ ይነብር ፡ መዐቱ ። አከ ፡ ለዓለም ፡ ዘእትመዐዕ ። ወይነግሥ ፡ ለቤተ ፡ ያዕቆብ ፡ ለዓለም ፡ (ኢዮ፯ ፡ ፲፮ ። ኤር፫ ፡ ፳ ። ኢሳ፶፯ ፡ ፲፯ ። ሉቃ፩ ፡ ፴፫) ።

—፤ አክቶ ፡ ፈጽሞ ፤ በውነት ፤ መቼም ፡ መኹ ። አንስ ፡ ኢየዐልወከ ፡ ግሙራ ፡ ባለው ፤ ለዓለም ፤ እንዲል ፡ (ማቴ ፳፮ ፡ ፴፫) ። ኢይትሀወክ ፡ ለዓለም ፡ ያለውም ፡ እንደዚህ ፡ ሊፈታ ፡ ይቻላል ።

**ለዓለመ ፡ ዓለም** ፤ ገነኒ ፡ ከማሁ ፡ ለዘላለም ። ይህ ፡ ግን ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ቃል ፡ ቢሰ ፡ ኾነ ፡ ተለ

ይቶ ፡ ፍጻሜ ፡ ለሌለው ፡ ለማይፈጸም ፡ ይነገራል ፡፡ ኢ ይጠፍእ ፡ ለዝሉፉ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡፡ ወደምሰስከ ፡ ስምሙ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡፡ መንበርከ ፡ እግዚኦ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ (ሚራጅ፱ ፡ ፱ ፡፡ መዝ ፡ ፱ና ፡ ፵) ፡፡


**ዘለዓለም** ፤ ገላጭ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፤ በቁሙ ፡ ዘላለም ፤ ለወትሮ ፡ የሚኖር ፤ ኅልፈት ፡ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ዘለዓለም ፡፡ መንግሥቱ ፡ ዘለዓለም ፡፡ ሕግነ ፡ ዘለዓለም ፤ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ (ቅዳ ፡፡ ዳንኤ ፡ ፴፫ ፡፡ ፲፱ ፡ ፬ ፡፡ ማቴ፳፬ ፡ ፵፯) ፡፡

**ዘለዓለማዊ** ፤ የዘላለም ፤ ቀዋሚ ፡ ነዋሪ ፤ ኀላፊ ፡ ያይደለ ፡፡ ምጽላላቲሆሙ ፡ ዘለዓለማዊት ፡ (ፊልክ ፡ ፫) ፡፡

**እስከ ፡ ለዓለም** ፤ ገላጭ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፤ እስከና ፡ ለ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ የሚመጣን ፡ ጊዜ ፡ ያሳያሉ ፡፡ እስከ ፡ ዘላለም ፤ እስከ ፡ ወትሮው ፤ እስከ ፡ መቼም ፡ መቼ ፡፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡ አንተ ፡ ከመ ፡ (መዝ ፡ ፹፱ ፡፡ ቅዳ ፡ ዲዮ) ፡፡

**ዐላሞት ፤ (ዕብራ)** ፤ ኀዋየ ፡ ማሕሌት ፤ የበገና ፡ ስም ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ በገና ፤ ባለስድስት ፡ አውታር ፡፡ ላዕለ ፡ ዐላሞት ፡ (፩ዜና ፡ ፲፭ ፡ ፳) ፡፡

**ዐለቅት ፤ (ዕብ ፡ ዐሉቃህ ፡፡ ሱር ፡ ዓላቅታእ ፡፡ ዐረ ፡ ዐለቀት)** ፤ ዐልቅት ፤ የትል ፡ ዐይነት ፤ ከውሃ ፡ ከረግረግ ፡ የሚገኝ ፤ የሚነክስ ፡ የሚጣበቅ ፤ ከያዘ ፡ የማይለቅ ፤ ደም ፡ የሚመጥ ፡ የሚመጠምጥ ፤ ውጋት ፡ ቍርጥማት ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ እንዳጋሚና ፡ እንደ ፡ ዋጋምት ፡ የሚሻው ፡ የሚያስፈልገው ፡፡ ለዐለቅት ፡ ባቲ ፡ ሠላስ ፡ አዋልድ ፡ (ምሳ፴ ፡ ፲፭) ፡፡



ዐለቅት ፡

**ዐለስ ፤ (ዐረብ)** ፤ ዐጃ ፡ የስንዴ ፡ ዐይነት ፤ ፍሬው ፡ ቀጫጭን ፤ ቅንጣቱ ፡ ቀጠጦ ፡ እንደሚባል ፡ ማሽላ ፡ በያንዳንዱ ፡ ቂንድ ፡ መንታንት ፡ ያለው ፡፡ ጣዕሙና ፡ መልኩ ፡ የስንዴ ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ መጽሐፍ ፡ በሶርያይ ፡ ፈንታ ፡ ዐለስ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ሉቃ፳፪ ፡ ፴፩ ፡፡ ዲድ ፡ ፴፩) ፡፡ ሕንፈጸን ፡ ተመልከት ፡፡

**ዓም ፤ (ዐረብ)** ፤ ዓመት ፤ ዘመን ፤ ብዙ ፡ ቀን ፡ የዕለታት ፡ ድምር ፤ በውዳቸውና ፡ ቀመራቸው ፤ ፫፻፷፭ ፡ ዕለት ፡ ከዕለት ፡ ርቦ ፤ በውስጡ ፡ አራት ፡ ክፍሎች ፤ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ወሮች ፡ ያሉት ፡፡ ሶሩና ፡ ምንጩ ፡ ዐመመ ፡ ነው ፤ በአልፍ ፡ ሲጣፍ ፡ ግን ፡ እመምና ፡ ገዝም ፡ ያሳያል ፡፡ በውእቱ ፡ ሳብዕ ፡ ዓም ፡፡ በሣልስ ፡ ዓም ፡ እም ዘነግሠ ፡፡ በኅሱ ፡ ዓም ፡ ወዓመት ፡፡ ዓም ፡ እምዓም ፡፡ ዓመ ፡ ከመ ፡ ዮም ፡፡ እመ ፡ ትፈሪ ፡ ለዓሙ ፡ (ዘሌ፳፭ ፡ ፳ ፡፡ አስቴ፩ ፡ ፫ ፡፡ ኩፋ ፡ ፳ና ፡ ፴፱ ፡፡ ዘፍ፲፰ ፡ ፲ ፡፡ ሉቃ ፲፫ ፡ ፱) ፡፡

**ዓመት ፤ (ታት)** ፤ በቁሙ ፡ ገላጭ ፡ ከማሁ ፡፡ በቀዳሚ ፡ ዓመት ፡ መንግሥቱ ፡፡ ትመውት ፡ በዝንቱ ፡ ዓመት ፡፡ ምእት ፡ ወኀምሳ ፡ ዓመት ፡ ሎቱ ፡፡ ዓመታተ ፡ ብዙኀ ፡ ሐይወ ፡፡ ኍልቈ ፡ ዓመታቲከ ፡ (ዳንኤ ፡ ፩ ፡፡ ኤር፴፰ ፡ ፲፯ ፡፡ ጦቢ፲፬ ፡ ፲፩ ፡፡ ኢዮ፴፰ ፡ ፳፩) ፡፡

**ዓመተ ፡ ዓለም** ፤ ከጥንት ፡ ከፍጥረት ፡ ከአዳም ፡ ዠምሮ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡፡

**ዓመተ ፡ ሥጋዌ** ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኹኖ ፡ ከተወለደበት ፤ ዓለም ፡ በሐዲስ ፡ ተፈጥሮ ፡ ከተፈጠረበት ፤ ከዳግማይ ፡ አዳም ፡ ከክርስቶስ ፡ ወዲህ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡፡

**ዓመተ ፡ ምሕረት** ፤ ገላጭ ፡ ከማሁ ፤ የይቅርታ ፡ ዘመን ፤ ዘመነ ፡ ሥጋዌ ፡፡

**ዐምበር ፤—ሽቱ ፤—ዐንበር ፡፡**

(ጥ) **ዐምዶ ፤ ዶት ፤ (ዐመደ ፡ ይዔምድ ፡ የዐምድ ፡፡ ዕብ ፡ ዐማድ ፤ ቆመ ÷ ቀጥ ፡ አለ)** ፤ መደገፍ ፤ ማስደገፍ ፤ ማቆም ፡ ማጽናት ፤ ማሸራሸት ፤ እንዳይወድቅ ፡ እንዳይነቃነቅ ፡ ማድረግ ፡፡ ረበቦ ፡ ከመ ፡ ሠቅ ፡ ወበነፋስ ፡ ዐመዶ ፤ በኪኑ ፡ ዐመዶ ፡ ለሰማይ ፡ በነፋስ ፡፡ ይዌስን ፡ ቡኖዳ ፡ ወይዔምድ ፡ በነፋስ ፡፡ ዘዐመድካ ፡ ለምድር ፡ በሥላሴከ ፡ (መቃ ፡፡ ቅዳ ፡ ግሩ ፡፡ ድጓ) ፡፡ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ፈጠረ ፡ ብለው ፡ ይጨምሩበታል ፡፡

**ዐማዲ** ፤ የሚደግፍ ፤ ደጋፊ ፤ የሚያቆም ፡ የሚያጸና ፡፡ ዐማዲ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ (ሲጦን) ፡፡

**ዐምድ ፤ (ዕብ ፡ ዐሙድ ፡፡ ሱር ፡ ዓሙዳእ ፡፡ ዐረ ፡ ዐሙድ ፤ ዒማድ)** ፤ በቁሙ ፤ ዋና ፤ ቀዋሚ ፤ ተሸካሚ ፤ ድጋፍ ፤ ባላ ፤ ምሰሶ ፡ ወጋግራ ፤ ተራዳ ፤ ቅልጥም ፡ አገዳ ፤ ጣዖት ፤ ሐውልት ፤ የመጽሐፍ ፡ ገጽ ፡፡ ዐምደ ፡ ኄጺን ፡፡ ዐምደ ፡ ሰዋባር ፡፡ ዐምደ ፡ ሐመር ፡፡ ዐምደ ፡ ጾም ፤ ዘውእቱ ፡ አርብዓ ፡ ዕለት ፡፡ ዐምዳ ፡ ወአብራዊሃ ፡፡ ዐምደ ፡ ሀገረ ፡ ፀሓይ ፡ (ኤር፭ ፡ ፲፰ ፡፡ ስንክ ፡ ሐም ፡ ፳ና ፡ ፳፱ ፡፡ አቡሻ ፡ ፳፯ ፡፡ ዘፀ፳፭ ፡ ፴፩ ፡፡ ኤር፵ ፡ ፲፫) ፡፡ ሉሕ ፡ ጠርብ ፡ ሳንቃ ፡ ሰሌዳ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዐምድ ፡ ይላል ፤ ቀዋሚነቱን ፡ ሲያይ ፡ (ዘፀ ፳፯ ፡ ፳፫—፳፱) ፡፡

**አዕማድ** ፤ ዐምዶች ፡ ድጋፎች ፤ ቋሞች ፡ ተሸካሞች ፤ የእግር ፡ አገዶች ፡፡ አዕማድ ፡ ዘንድቅ ፡ ወአዕማድ ፡ ዘእብን ፡፡ አዕማደ ፡ ወርቅ ፡ እለ ፡ ይቀውሙ ፡፡ ጸጸሳት ፡ ኄራን ፡ ዘይብልዎሙ ፡ አዕማድ ፡፡ አዕማደ ፡ እግር ፡ (ሥር ፡ አክ ፡፡ ሚራጅ፯ ፡ ፲፰ ፡፡ ስንክ ፡ ጥር፳ ፡፡ ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፯) ፡፡

—፤ የግስ ፡ ነገዶች ፡ ወይም ፡ ጸዋትወ ፡ ግስ ፡፡ እሊሁም ፡ አድራጊ ፡ አስደራጊ ፡ ተደራጊ ፡ ተደራራጊ ፡ አደራራጊ ፡ ናቸው ፤ ቀተለን ፡ ተመልከት ፡፡

**ዐምዳዊ ፤ ዘዐምድ ፤** የዐምድ ፡ ሰው ፤ እንደ ፡ ዐምድ ፡ ቋሚ ፡ በዐምድ ፡ ፊስ ፡ ላይ ፡ ማማ ፡ ሠርቶ ፤ ወይም ፡ ከምዱ ፡ ጋር ፡ ታስሮ ፡ ተቈራኝቶ ፡ የሚኖር ። ስምዖን ፡ ዐምዳዊ ። አጋንንት ፡ ዘዐምድ ፡ (ፊልክ ፡ ፶፰ ። ስንክ ፡ መስ፲፱) ።

**ምዕማድ ፤ (ዳት ፤ መዓምድ) ፤** ማቆሚያ ፡ የዐምድ ፡ እግር ፤ ስኩተት ፡ መሠረት ። ሰመንቱ ፡ አዕማድ ፤ ወምዕማደሙኒ ፡ ዘብሩር ፡ ዐሥርቱ ፡ ወስድስቱ ፤ ወሰለ ፡ አሐዱ ፡ ዐምድ ፡ በበ ፡ ክልኤ ፡ ምዕማዲሁ ። ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ፈቀደ ፡ ያስተጻንዕ ፡ ምዕማዲሁ ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፳፫ ። አፈ ፡ ድ፫) ።

**ዐምሐራ ፤—ዐማራ ፤—ዐመመ ።**

**ዐመ ፤ ዐመመ ፤ (ዐረ ፡ ዓመ ። ዕብ ፡ ዐሚም) ፤** ጠቈረ ፡ ጨለመ ፤ አደፈ ፡ ጕደፈ ፤ ደፈረሰ ። በዛ ፡ ጸና ፡ በረታ ፤ ጌመን ፡ እይ ።

**ዐም ፤ (ዕብ) ፤** ሕዝብ ፡ ነገድ ፡ ብዙ ፡ ሰው ። ቋንቋውና ፡ ሕጉ ፡ ግዛቱ ፡ መንግሥቱ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ ጉባኤ ፡ ሰብእ ፡ ማኅበረ ፡ ሰብእ ።

**ዐምሐራ ፤ (ዐም ፡ ሐራ) ፤** ዐማራ ፡ ጨዋ ፡ ሕዝብ ፤ ነጻነት ፡ ያለው ፡ ባለነጻ ፤ ግዑዝ ፡ እግዓዚ ። ሐረረን ፡ ተመልከት ። ወኮነ ፡ በምድረ ፡ ዐምሐራ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ዐምሐራይ ፡ ዊ ፤** የማራ ፡ ወገን ፤ ልሳን ፡ ቋንቋ ፤ ዐማርኛ ፤ ከዐረብና ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ከግእዝ ፡ ከአራም ፡ የወጣ ።

**ዐምዓም ፤ (ዐረ ፡ ዐም ፤ ጅም ፤ ቀምቃም ፤ ድፍርስ ፡ ግም ፡ እድፍ ፡ ውሃ) ፤** ውሃማ ፡ በቃ ፤ ማጥ ፤ ረግረግ ፤ ጭቃው ፡ የሚጠጥ ፤ የሚያሰምጥ ። ጽቡረ ፡ ዐምዓም ። አውፅአኒ ፡ እምውስተ ፡ ዐዘቅት ፡ ዐምዓም ። ዐምዓሙሰ ፡ ወዐዘቅቱ ። ዐምዓመ ፡ ኀጢአት ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፴፱ ። ባሮክ ። ሕዝ፵፯ ፡ ፲፩ ። ግንዘ) ።

**ዐማኑኤል ፤ (ጽር ፡ ኤማኑኢል ። ዕብ ፡ ዒማኑኤል) ፤** የሥጋው ፡ ቃል ፡ ስም ፤ በኩነት ፡ በተዋሕዶ ፡ የተሰጠው ። ዒማኑ ፡ ምስሌነ ፤ ኤል ፡ አምላክ ፡ በተገናኝ ፡ አምላክ ፡ ምስሌነ ፤ ወይም ፡ ምስሌነ ፡ አምላክ ። አምላክ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ (ማቴ፩ ፡ ፳፫ ። ኢሳ፯ ፡ ፲፬) ። ሲቃውንት ፡ ግን ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ብለው ፡ የምስጢር ፡ አፈታት ፡ ይፈቱታል ። ዐማኑኤል ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፡ በመለኮቱ ፤ ወሰብእ ፡ በትስብእቱ ፡ ዘነሥአ ። ወዝ ፡ ስም ፡ ዘውእቱ ፡ ዐማኑኤል ፡ ዐቢይ ፡ ጥቀ ፡ ወኢይደሉ ፡ ፈሊጦቱ ፤ ወውእቱ ፡ ዘበአማን ፡ ምስጢር ፡ ሰጽንዐ ፡ ሃይማኖት ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ ቴዎ ፡ ዘእ ። ሳዊ ፡ ዘአን) ። ኢየሱስን ፡ ተመልከት ።

**ዐምዓም ፤—ረግረግ ፤—ዐመመ ።**

**ዐምዖ ፤ ዖት ፤ (ዐመፀ ፡ ይዔምፅ ፡ የዐምፅ ። ዕብ ፡ ሐማስ ፤ ሐሚጽ) ፤** ግመጥ ፡ መሸፈት ፡ መበደል ፡ ከፋ ፡ መኾን ፡ ግፍ ፡ መሥራት ፡ መስረቅ ፡ መቀማት ። ኢዐመፅኩ ፡ ኪዳነከ ። ይዔምፅኑ ፡ እግዚ ። ወዐመፅክሙ ፡ ዐስበሙ ፡ (መዝ ፡ ፹፫ ። ሮሜ፫ ፡ ፳ ። ያዕ፭ ፡ ፬) ።

**ዐማፂ ፤ (ፂት ፡ ፅያን ፡ ያት) ፤** ዐመጠኛ ፡ በደለኛ ፤ ከፋ ፤ ዋሾ ። ዐማፂ ፡ ወጽልሕው ። ዐማፅያነ ፡ ጸላእኩ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ። ፻፲፰) ።

**መዐምፅ ፤ (ፅት ፡ ፃን ፡ ፃት) ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ። ኢትኩኑ ፡ መዐምፀ ፡ (ዘፀ፳፫ ፡ ፩ ። ምሳ፲፬ ፡ ፳፭) ።

**ዐመፃ ፤** ዐመጥ ፤ በደል ፤ ግፍ ፤ ኀጢአት ፡ ክፋት ፡ ውሸት ። ዐመፃ ፡ ወፀአት ፡ እመዛግብቲሃ ። ልህቀት ፡ ዐመፃ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ገበርት ፡ ዐመፃ ፡ (ሔኖ ። ኩፉ ። መዝ፻፲ ፡ ፱) ።

**ተዐመፀ ፤** ተገፋ ፤ ተበደለ ፡ ግፍ ፡ ተቀበለ ። ይትዔመፅ ፡ ከመ ፡ ሐሳዊ ፡ (ተረ ፡ ቄር) ።

**ዕሙፅ ፤ (ፃን ፡ ፃት ፡ ምዕት) ፤** የተገፋ ፤ የተበደለ ። ዘከዐወ ፡ ደመ ፡ ዐማፂ ፡ ላዕለ ፡ ደመ ፡ ዕሙፅ ። ዕሙፃን ፡ (ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፫) ።

**ተዓመፀ ፤** ተጋፋ ፤ ተገፋፋ ፤ ተጣላ ፤ ግፍ ፡ ተማራ ፤ ተበዳደለ ። ለምንት ፡ ትትዓመፁ ፡ በበይናቲክሙ ። ኀፍረት ፡ ተዓምፆ ፡ ምስለ ፡ ዐርክከ ፡ (ግብ፯ ፡ ፳፮ ። ሢራ፵፩ ፡ ፲፳) ።

**አስተዐመፀ ፤ (አዐመፀ) ፤** አሳመጠ ፤ አሸፈተ ፡ ግፍ ፡ አሠራ ።

**አስተዓመፀ ፤** አባደለ ፤ አበዳደለ ፡ አጋፋ ፤ ግፍ ፡ አሣራ ።

**ዐሚቅ ፤ ቆት ፤ (ዐመቀ ፡ የዐምቅ ፡ ይዕምቅ ። ዕብ ፡ ዐማቅ ። ዐረ ፡ ዐሙቀ) ፤** መታመቅ ፤ ሰሙቅ ፡ መኾን ፤ መጕድጕድ ፤ መጥለቅ ፡ መሰወር ፡ መረቅ ፤ ከመታየትና ፡ ከመታወቅ ። እስከ ፡ የዐምቅ ፡ ምድሩ ፡ ከመ ፡ ግብ ። የዐምቅ ፡ እምነ ፡ ቀላይ ፡ ምክሩ ። እምቅድመ ፡ ይዕምቅ ፡ ቀላያት ። እምቅድመ ፡ ይዕምቅ ፡ ባሕር ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ሢራ፳፱ ፡ ፳፱ ። ቅዳ ፡ አፈ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ዕሙቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ምቅት) ፤** በቁሙ ፡ የጠለቀ ፤ ጥልቅ ፡ ወደ ፡ ቻች ፡ የራቀ ፡ ሩቅ ፤ ኀቡእ ፡ ረቂቅ ፤ የማይታይ ፡ የማይታወቅ ፤ ጨለማ ፡ ውድቅት ። ሰማይ ፡ ልዑል ፡ ወምድር ፡ ዕሙቅ ። ቈላ ፡ ዕሙቅ ። ግብ ፡ ዕሙቅ ። ቀላይ ፡ ዕሙቅ ። ይከሥት ፡ ዕሙቃተ ፡ እምጽልመት ። ይመክሩ ፡ ዕሙቀ ፡ ምክረ ። ዘዕሙቅ ፡ ክናፍሪሁ ። ሌሊተ ፡ ዕሙቀ ፡ (ምሳ፳፭ ፡ ፫ ። ሔኖ፳፮ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፷፫ ። ኢዮ፲፪ ፡ ፳፪ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፲፭ ። ሕዝ፫ ፡ ፭ ። ኪዳ) ።

**ዕመቅ ፤ (ቃት) ፤** ጥልቀት ፤ ጥልቅነት ፡ አጠላለቅ ፡ ጥልቅ ። ዕመቀ ፡ ቀላይ ። ዕመቃቲሆሙ ፡ ለአብሕርት ። ዕመቀ ፡ ምስጢር ። ኦ ፡ ዕመቂሁ ፡ ለብዕሉ ፡ ጥበቢሁ ፡ (ኢዮ፲፰ ፡ ፰ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ቄር ። ሮሜ፲፩ ፡ ፴፫) ።

**ማዕምቅ ፤ ት ፤ (ቃት)** ፤ ጥልቅ ፡ በታ ፤ ጕድጓድ ፤ ዐዘቅት ፤ የምድር ፡ ቤት ፤ ገደል ፤ ዋሻ ፡ ቈላ ፤ መቀራቅርት ፤ ዘብጥ ፡ ዘቅዛቃ ፡ ወዳቃ ። ማዕምቀ ፡ ባሕር ። ማዕምቅቲሃ ፡ ለምድር ። ወአውረደኒ ፡ ውስተ ፡ ማዕምቅ ። ጸሎ ፡ ማዕምቅ ፡ ይጼውዕ ፤ (መዝ ፡ ፷፰ ። ኩፋ ፡ ፳፰ ። ራእያ ፡ ፲ ። ኢሳ ፡ ፶ ። ባሮክ ፡ ፫) ።

**መዓምቅ ፤ ት** ፤ ጥልቆች ፡ ጕድጓዶች ፤ መዓምቅተ ፡ ሲኦል ፡ (ምሳ፲፱ ፡ ፲፪) ።

**አዕመቀ** ፤ አጠለቀ ፤ አስጠለቀ ፤ ጥልቅ ፡ አደረገ ፡ አስደረገ ። አዕምቅ ፡ ለክሙ ፡ ኅበ ፡ ትንብሩ ። ጥቀ ፡ አዕመቀ ፡ ክርየ ፡ ግብ ። ኢይክል ፡ አዕሚቀ ፡ ኅልየ ፡ (ኤር ፳፱ ፡ ፱ ። ፴ ፡ ፳ ። ሉቃ፮ ፡ ፵፰ ። ቅዳ ፡ አፈ ። ዮሐ ። ግሩ) ። አዕምቆ ፡ (አሙቅ) ፡ ላሕዎቶ ፡ (ሚራ፴፰ ፡ ፲፮) ።

**ተዓመቀ ፤ ተዐማመቀ** ፤ ተማመቀ ፤ ተናነቀ ፡ ተጣቄኑ ፤ ተጋፋ ፡ ታገለ ፡ ለመጣል ፡ ለማውደቅ ፤ በታች ፡ ለማድረግ ። ኢትትዐማመቅ ፡ ምስለ ፡ ሰይጣናት ፤ ደረት ፡ ለደረት ፡ አትጋፋ ፡ (ፊልክ ፡ ፳) ።

**ዓመት ፤—በቍሙ ፤—ዓም ።**

**ዐንበዘ ፤—ተንበዘ ፤—ነበዘ ፤ አንበዘ ።**

**ዐንበሪ ፤ ር ፤ (ዕብ ፡ ዳግ ፤ ታኒን ፤ ሊውያታን)** ፤ ታላቅ ፡ ዓሣ ፤ እንደ ፡ ዘንዶ ፡ ያለ ። ዐንበሪ ፡ ዐቢይ ። ዐንበሬ ፡ ባሕር ። ዐንበሪ ፡ እንስቲያዊት ፡ ዘስማ ፡ ሌዋታን ። ይባርክዎ ፡ ዐንበር ፡ ወዘሎ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡ (ዮና፪ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፻፵፰ ። ሔኖ፷ ፡ ፰ ። ጸሎ ፡ ፫ ፡ ደቂ) ። ስምንቱ ፡ ከዐበረና ፡ ከነበረ ፡ ከኹለቱ ፡ የተደቀለ ፡ ነው ፤ ምስጢሩም ፡ ታላቅነትና ፡ ነባርነት ፡ ነው ፤ አንባ ፡ እንደ ፡ ማለት ።



ዐንበሪ ፡ እንስቲያዊት ።

**ዐናብርት** ፤ ዐንበሪዎች ፡ ታላላቅ ፡ ዓሦች ፡ ብሄሞትና ፡ ሌዋታን ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፳፩ ። ኩፋ ፡ ፪ ። ኢዮ፴ ፡ ፲፫) ። ብሄሞትን ፡ ተመልከት ።

**ዐንበር ፤ (ዐረ ። ዕብ ፡ ዐንበር)** ፤ የሽቱ ፡ ሜቃ ፡ ሲፈጭ ፡ ሲደቈስ ፡ ወይም ፡ በእሳት ፡ ሲጤስ ፡ ሽታው ፡ የሚገን ፡ የሚጣፍጥ ። በዐንበር ፡ ፈንታ ፡ ዐምበር ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (ዮሴፍ) ።

**ዐንበሳ ፤—በቍሙ ፤—አንበሳ ፤ በስበሰ ።**

**ዐኒግ ፤ ጎት ፤ (ዐነገ ፡ የዐንግ ፡ ይዕንግ ። ዐረ ፡ ሐነጀ)** ፤ መሥራት ፡ መጠምዘዝ ፤ ማጕበጥ ፡ የቀለበት ። ማንገት ፤ ማሰር ፡ ማንጠልጠል ፡ የጌጥ ፡ የክታብ ።

**ዐንግ ፤ (ዕብ ፡ ኔዜም ። ጽር ፡ ሄኖቲያ)** ፤ ጕትቻ ፡ ቀለበት ፤ ጕሮ ፡ መንደልት ፤ ያፍንጫ ፡ ወይም ፡ የጆሮ ፡ ጌጥ ፡ ጕሮ ፡ ያፍንጫ ፡ መንደልት ፡ የጆሮ ።

**አዕኑግ** ፤ ጕትቻች ፤ ቀለበቶች ፡ ንሮዎች ፤ መንደልቶች ፡ (ዘፍ፳፬ ፡ ፳፪ ። ኢሳ፫ ፡ ፳ ። ሕዝ፲፮ ፡ ፲፪) ።




ዐንግ ።

**ዐንገት ፤ (ዐረ ፡ ዑንጉግ)** ፤ በቍሙ ፡ ክሣድ ፡ ማንገቻ ፤ የጌጥ ፡ የሽልማት ፡ ማሰሪያ ።

**ዐንጉግ** ፤ ዐንገታም ፡ ዐንገተ ፡ ወፍራም ። የባሕር ፡ አውሬ ፤ አርጃኖ ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፴) ።

**ዐናጉግ** ፤ የባሕር ፡ አራዊት ፤ አርጃኖች ፡ (መቃ ፡ ገ፲፪) ።

**ዐንጐጕ ፤ (ጓት** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ዐንጕጓት ፡ ወብሔ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።



ዐንጉግ ።

**ዕንጐት ፤ (ታት ። ዕብ ፡ ዱዳኢም ። ዐረ ፡ ሉፋሕ ። ጽር ፡ ማንድራጐሬ)** ፤ ዕንጕቾት ፤ የሽቱ ፡ ቅጠል ፡ ሽቱነት ፡ ያለው ። ዕንጕኞት ፡ ፪ ፡ ዐይነት ፡ ነው ፤ ታላቅና ፡ ታናሽ ። ኮልን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ትርንጎ ፡ ይሉታል ። በገነቶሙ ፡ ዕንጕታት ፡ ተረክቡ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ ፳፰ ። ማሕ፯ ፡ ፲፬ ። ዘፍ፴ ፡ ፲፬) ።

**ዕንዚራ ፤—የዘፈን ፡ ዕቃ ፤—ነዘረ ፡ እንዚራ ።**

**ዐንዘረ ፤—አስረመኘ ፤—ነዘረ ፡ አንዘረ ።**

**ዐኒን ፤ (ዐረብ)** ፤ አባለ ፡ ዘርዕ ፤ ደካማ ፡ ኰሳሳ ፡ የታሸ ፡ የተኰላሸ ፤ ፍሬው ፡ የወጣ ፤ ወይም ፡ ያበጠ ፡ የተነፋ ፤ ደዌ ፡ ያደረበት ። ዘይትበሀል ፡ እልዐኒን ፤ ዘውእቱ ፡ ኅፍረተ ፡ ሥጋ ፡ ንኡስ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፪ ፡ ፳) ።

**ዕንፎራ ። (ጽር ፡ አናፎራ)** ፤ አኰቴት ፡ ኅብስተ ፡ መሥዋዕት ። ጸሎተ ፡ ዕንፎራ ፡ (ቅዳ) ።

**ዐንፀወ ፤—ደረቀ ፤—ነፀወ ፡ አንፀወ ።**

**ዐንጼዋ ፤—ዐይጥ ፤—ነጽይ ፡ ነጸየ ፤ አንጼዋ ።**

**ዐኒቅ ፤ ቆት ፤ (ዐነቀ ፡ የዐንቅ ፡ ይዕንቅ ። ዕብ ፡ ዐናቅ ። ዐረ ፡ ዐነቀ)** ፤ መነበብ ፡ ማገር ፤ ዐንገትን ፡ በጌጥ ፡ ማሰር ፡ ማንገት ፡ ባንገት ፡ መሸከም ፤ ማንጠልጠል ። መርዘም ፡ መብሰጥ ። ዕንቆ ፡ ውስተ ፡ ክ

ሣድከ ። ብፁዕ ፡ ዘጸሮ ፡ ወዘዐነቆ ፡ በክሣዱ ፡ ለዘ ንቱ ፡ ጸሎት ። ሰላም ፡ ለክሣድኪ ፡ ቆማ ፡ ንጽሕ ፡ ዘ ዐነቀ ፡ (ምሳሮ ፡ ፫ ። ማንዘ ። ደራሲ) ። በዐነቀ ፡ ፈንታ ፡ ተ ዐንቀ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወይትዐነቅ ፡ ቀጺላ ፡ ወ ርቅ ፡ (አዋል) ።

**አዕነቀ** ፤ አሸከመ ፡ ጫነ ፤ አስነገተ ፤ አሳሰረ ። አቡየ ፡ አዕነቀክሙ ፡ ጋጋ ፡ ክቡደ ። ኣዐንቆ ፡ ባዝግና ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ። አዕነቅዋ ፡ ባዝግና ፡ ወርቅ ፡ (፫ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፲፩ ። ዳንኤ ፡ ፮ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ዕንቍ** ፤ ክቡር ፡ ደንጊያ ፤ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ያ ለው ፤ ያንገት ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ ተሰክቶ ፡ ባንገት ፡ የሚ ታሰር ፤ የሚሰደር ፡ የሚደረደር ። ህየ ፡ ሀሎ ፡ ዕንቍ ፡ ዘ የኀቱ ፡ ወዕንቍ ፡ ሐመልሚል ። እማንቱ ፡ ዕንቊ ፡ ባ ሕርያት ፡ ክቡራት ። ዕንቍ ፡ ዘተሰክዐ ፡ በፈትለ ፡ ሜ ላት ። ዕንቊ ፡ ኢያሰጺድ ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ ሚያ፳ ። አርጋ ። ራእ፱ ፡ ፫) ።

**አዕናቍ** ፤ ዕንቆች ፤ የከበሩ ፡ ደንጎች ። ሰሐባ ፡ ለጥበብ ፡ እምአዕናቍ ፡ (ኢዮ፳፰ ፡ ፲፰) ።

**ማዕነቅ** ፤ ቀምበ ፤ ቡላል ፤ የርግብ ፡ ዐይነት ፡ ወፍ ፤ ዐንገቷ ፡ ሐር ፡ የታሰረበት ፡ የሚመስል ፡ (ዘፍ፲፭ ፡ ፱ ። ማሕ፩ ፡ ፲) ።

**መዓንቅ** ፤ ቀምበሮች ፤ ቡላሎች ። ያመጽእ ፡ ክልኤተ ፡ መዓንቀ ፡ (ዘሌ፭ ፡ ፯) ።

**ዓናቅ** ፤ **ዔናቅ** ፤ ረዐይታዊ ፤ ኀያል ፡ ሐርበኛ ፤ እጅግ ፡ ብርቱ ፤ መለሎ ፡ ረዥም ፡ ወርዳም ፡ ቁመታም ፤ መጠኑ ፡ ከሰው ፡ ልክ ፡ ያለፈ ። ርኢነ ፡ ትውልዶ ፡ ለዔ ናቅ ። ወኮነ ፡ ቅድሜሆሙ ፡ ከመ ፡ አናብጥ ፡ (ዘኍ ፲፫ ፡ ፳፰ ፡ ፴፫) ። ናፊልን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ።

**ዕንቈራ** ፤—የማር ፡ ሰፈፍ ፤—ነቀኈር ፡ ነቈረ ፤ እንቈራ ።

**ዐንሰበ** ፤ (ዐሰበ ፤ ሐሰበ) ፤ ነሲብ ፡ ጣለ ፡ ገመተ ፤ አሟረተ ። ስሯጽ ፡ ግስ ፡ ነው ፤ ዐሰበን ፡ ተመል ከት ።

**መዐንስብ** ፤ (ብት ፡ ባን ፡ ባት) ፤ ሟር ተኛ ፤ መለኛ ፤ በነሲብ ፡ በግምት ፡ የሚናገር ። መዐንስበ ፡ አራዊት ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ዐቃቢሆሙ ። ማርያን ፡ ወ መዐንስባን ፡ (ኪዳ ። ዲድ ፡ ፲፫) ።

**ዕንሰራ** ፤ (ዕብ ፡ ዐጺራ) ፤ የሕዝብ ፡ ስብ ሰባ ፤ ጉባኤ ፤ ዐቢይ ፡ በዓል ፤ በዓለ ፡ ሠዊት ፤ በዓለ ፡ ኀ ምሳ ፤ ጰራቅሊጦስ ። በዓለ ፡ ዕንበራ ፡ (ዮሴፍ) ። ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ዐጸረ ፡ ነው ፤ ከነሰረም ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ።


**ዐንሰር** ፤ (ዐረ ፡ ዑንጹር) ፤ የፍጥረት ፡ ጠ ባይ ፡ ባሕርይ ።

**ዐናስር** ፤ (ዐረ ፡ ዐናጺሩ) ፤ ህላውያት ፤ አ ሥራው ፡ ፍጥረት ፤ አራቱ ፡ ባሕርያት ። ደንገፀ ፡ ኵሉ ፡ ዐናስረ ፡ ፍጥረት ፤ ወአንከሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ፍጡራን ፡ (ሃይ ፡ አበ ። ገድ ፡ አዳ) ። መተርጕማን ፡ ግን ፡ አለቆች ፡ ይሉታል ።

**ዐናት** ፤ (ትግ ፡ ወዐም) ፤ በቁሙ ፤ ማኽል ፡ ራስ ፡ የናላ ፡ ርግብግቢት ።

**ዐናዶት** ፤ (ዕብራ) ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ ስጣዊ ፡ (ኤር፩ ፡ ፩) ።

**ዓሣ** ፤ ት ፤ (ዕብ ፡ ዓሽ ። ዐረ ፡ ዑሸት ፤ ዕሼ) ፤ በቁሙ ፤ የባሕር ፡ እንስሳ ፡ መልኩና ፡ ነገዱ ፡ የተ ለየ ። የስሙ ፡ ምስጢር ፡ እንደ ፡ ትልና ፡ እንደ ፡ ከይሲ ፡ አለእግር ፡ መኼድ ፡ በልብ ፡ መሳብ ፡ ነው ፤ ዋነተኛነትም ፡ አለበት ። እገሌ ፡ ዓሣ ፡ ነው ፡ እንዲሉ ። በከመ ፡ ዓሣ ፡ ሶበ ፡ ወፅአ ፡ እማይ ፡ ይመውት ፡ ፍጡነ ። ዓሣተ ፡ ባ ሕር ፡ ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ (ፊልክ ፡ ፳፩ ። ዘፍ፩ ፡ ፳፮) ።



ዓሣ ፡

**ዐሠየ** ፤—ዋጋ ፡ ሰጠ ፤—ዐስይ ፡ ዐሰየ ።

**ዐሠቀ** ፤—ሠራ ፤—ዐስቆ ፡ ዐሰቀ ።

**ዐሠር** ፤—ፍለጋ ፤—አሠረ ።

**ዐሥሮ** ፤ ሮት ፤ (ዐሠረ ፡ ይዔሥር ፡ የ ዐሥር ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ዐሣር ። ዐረ ፡ ዐሸረ) ፤ ዐሥር ፡ ማድረግ ፤ ዐሥራት ፡ ማውጣት ፤ ካሥር ፡ አንድ ፡ መስጠት ፤ ወይም ፡ መቀበል ፤ መውሰድ ። ዐሠረ ፤ እም ኵሉ ፤ ከመ ፡ የዐሥር ፤ ሰዐሥሮ ። ፈጸምከ ፡ ዐሥሮተ ፡ ኵሉ ፡ ዐሥራት ። ዐሥራተ ፡ ይዔሥር ፡ (ኩፋ ፡ ፴፫ ። ዘዳ ፳፯ ፡ ፲፪ ። መቃ) ።

—፤ መጥራት ፤ ኑልኝ ፡ ማለት ፤ ማደም ፡ መቅጠር ፤ ዐ ዋጅ ፡ መንገር ፤ ሕዝብን ፡ ሰራዊትን ፡ መሰብሰብ ፤ ማከብ ። በልዎሙ ፡ ለእለ ፡ ዐሠርናሆሙ ። ገብረ ፡ ምሳሐ ፡ ዐ ቢየ ፡ ወዐሠሮሙ ፡ ለብዙኃን ። ዐሥሩ ፡ ጸብአ ፡ (ማ ቴ፳፪ ፡ ፬ና ፡ ፰ ። ሉቃ፲፬ ፡ ፲፮—፲፯ ። ዮኤ፫ ፡ ፱) ።

**አዐሠረ** ፤ ዐሥር ፡ አስደረገ ፤ ዐሥራት ፡ አሶጣ ፤ ግብር ፡ ቀረጥ ፡ አስከፈለ ። ወአዕዲደ ፡ ወፍርክሙ ፡ ያ ዔሥረክሙ ፡ (፩ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፯) ።

**ተዐ(ሥ)ሠረ** ፤ ተጠራ ፤ ታደመ ፤ ተቀጠረ ። እለ ፡ ተዐሥሩ ፡ ለመርዓ ። እለ ፡ ተዐሠሩ ፡ ውስተ ፡ ከብካብ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲፬ ። ማቴ፳፪ ፡ ፫) ።

**ዕሡር** ፤ የተጠራ ፤ ዕድመኛ ፡ (ስንክ ፡ የካ፳) ።

**ዐሡር** ፤ ቀጠሮ ፤ የቀጠሮ ፡ ቀን ፤ ጊዜ ፡ ሰዓት ። ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ዐሡር ፡ (ሉቃ፲፬ ፡ ፲፯) ።

**ተዐሠረ** ፤ ዐሥር ፡ ኾነ ፤ ዐሥር ፡ ተባለ ፤ ካ ሥር ፡ ተከፈለ ፤ ዐሥራት ፡ ወጣለት ፤ ታሸረ ።

**ዐሥሩ** ፤ (የቤት) ፡ ዐሥር ፡ (የ ፡ ፲) ፤ የቍጥር ፡ ስም ፤ መዠመሪያ ፡ ቀመር ፤ ያንድ ፡ ቤት ፡ ፍጻሜ ፤ የዘ ጠኝ ፡ ተከታይ ፡ በዘጠኝና ፡ በካያ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ቍ ጥር ፤ ካንድ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ያሉትን ፡ አኃዞች ፡ በመሐ

ፈርና ፡ በመናበብ ፡ እስከ ፡ ፺ያ ፡ ድረስ ፡ የሚዘምት ። ሩ ፡ አርቲክል ፡ ኹኖ ፡ በቁሙ ፡ ይፈታል ። ያበስላ ፡ ዐሥሩ ፡ አንስት ፡ ኅብስተክሙ ፡ በአሐዱ ፡ እቶን ። ዐሥሩ ፡ መካልየ ፡ ብሩር ። ዐሥሮን ፡ ቃላተ ። ዐሥሮን ፡ ደናግል ። ዐሥሩ ፡ ወአሐቲ ፡ (ዘሌ ፳፮ ፡ ፳፮ ። ጦቢ ፩ ፡ ፳ ። መጽ ፡ ምስ ። ማቴ ፳፭ ፡ ፩ ። ራእ ፲፫ ፡ ፩)።

**ዐሥርቱ** ፤ ቱ ፤ (የወንድ) ፡ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ዐሥር ፤ ዐሥሩ ፤ ዐሥረኛው ፤ ቱ ፡ አርቲክል ፡ ነው ። አሠ ፡ ተርፉ ፡ ዐሥርቱ ። ዐሥርቱ ፡ ወአሐዱ ። ዐሥርቱ ፡ ምእት ። ዐሥርቲሆሙ ፡ (ዓሞ ፮ ፡ ፱ ። ዘካ ፰ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፺፩ ። ሱቱ ፡ ዕገዞ)።

**ዐሡር** ፤ ዐሥር ፤ ዐሥረኛ ፤ የዕለት ፡ ቀጽል ። እምድኅረ ፡ ዐሡር ፡ ዕለት ። በዐሡር ፡ ሠርቀ ። ዐሡረ ፡ ወረቡዐ ፡ መዋዕለ ። ዐሡረ ፡ ዕለተ ። ጾመ ፡ ዐሡር ፡ (ኤርም ፵፩ ፡ ፯ ። ፵፪ ፡ ፯ ። ጦቢ ፫ ፡ ፲፱ ። ዳን ፩ ፡ ፲፪ ። ዘካ ፰ ፡ ፲፱)።

**ዕሥር** ፤ ዐሥር ፤ የጊዜ ፡ ቀጽል ። ዕሥር ፡ ወኅምስ ፡ በእመት ፡ (ዘፀ ፳፯ ፡ ፲፬)።

**ዕሥራ** ፤ ካያ ፡ ፳ያ ፤ (ክ ፡ ፳) ፤ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ፤ ወይም ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፤ ክዕበተ ፡ ዮድ ፤ ምክዕቢተ ፡ የውጣ ። ዕሥራ ፡ በእመት ። ዕሥራ ፡ ሰቅል ። ምእት ፡ ወዕሥራ ፡ (ዘካ ፭ ፡ ፪ ። ሕዝ ፵ ፡ ፲ ። ማብ ፭ ፡ ፲፭ ። ራእ ፬ ፡ ፬)።

**ዓሥር** ፤ ዐሥረኛ ። በዓሥር ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ። በዓሥር ፡ ወኅምስ ፡ ዓመት ። ወዓሥሮሙ ፡ እነግር ፡ (ኤርም ፴፱ ፡ ፩ ። ፪ዜና ፡ ፲፭ ፡ ፲ ። ሢራ ፳፭ ፡ ፯)።

**ዓሥራይ** ፤ (ዊ ፡ ሪት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ዐሥረኛ ። በዓሥራይ ፡ ወርኅ ፡ (ሕዝ ፴፫ ፡ ፳፩)።

**ዓ(ዐ)ሥራት** ፤ በቁሙ ፤ ዐሥረኛ ፤ እጅ ፤ ክፍል ፤ ካሥር ፡ አንድ ፤ ቀረጥ ፤ ግብር ። ወሀበ ፡ ዓሥራተ ፡ እድ ። ዓሥራታ ፡ ለኤን ። ዓሥራቱ ፡ ለዓሥራት ። ዓሥራቲሁ ፡ ለባት ፡ (ዘፍ ፲፬ ፡ ፳ ። ዘፀ ፳፱ ፡ ፵ ። ዘኍ ፲፰ ፡ ፳፮ ። ሕዝ ፵፭ ፡ ፲፬)።

**ትዕሥርት** ፤ ዐሥርነት ፤ ዐሥር ፡ ዕጥፍ ፤ ዐሥረኛ ፤ ክፍል ፤ ያሥር ፡ ቤት ፤ ባሥር ፡ ባሥር ፡ የሚበዛ ፡ ቍጥር ፤ ካሥር ፡ እስከ ፡ ዘጠና ፡ ያለው ። ረከበ ፡ ትዕሥርተ ፡ እምዝሉ ። ወይከውኑ ፡ ትዕሥርተ ። አእላፍ ፡ ወአምእት ፡ ወትዕሥርት ፡ ወአሐዳት ፡ (ዳን ፩ ፡ ፳ ። ኢሳ ፮ ፡ ፲፫ ። አቡሻ ፡ ፲፭)።

**ዐፈየ** ፤ (ትማ ። ዐረ) ፤ ዳነ ፡ ተፈወሰ ፤ ጤና ፡ አገኘ ፤ ባለጤና ፡ ኾነ ።

**ዐፈር** ፤ ሮት ፤ (ዐፈረ ፡ የዐፍር ፡ ይዕፍር ። ዕብ ፡ ካፋር ። ሱር ፡ ዐፋር) ፤ መሸፈን ፡ ማልበስ ፤ መቀባት ፡ መለቅለቅ ። ከፈረን ፡ ተመልከት ።

**ዕፍረት** ፤ (ታት) ፤ ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ መረቅ ፡ ቅባት ፤ የነጠረ ፤ የተጣፈጠ ። ዕፍረት ፡ ምዑዝ ። ዕፍረት ፡ ቅድው ። ቀብዐ ፡ ዕፍረተ ። መቅድመ ፡ ዕፍረታት ፡ (ጥበ ፪ ፡ ፯ ። ዓሞ ፯ ፡ ፯ ። አስቴ ፪ ፡ ፲፪ ። ማሕ ፩ ፡ ፲፱)።

**ማዕፈርት** ፤ (ሱር ፡ ማዕፍራእ ፤ ኩፋር ። ዕብ ፡ ሚጽኔፌት) ፤ የራስ ፡ ልብስ ፤ መሸፈኛ ፡ ቆብ ፤ ኰፌት ፤ መጠምጠሚያ ። ማኅፈሪትን ፡ ተመልከት ። ትወዲ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ማዕፈርቶሙ ፡ (ዘፀ ፳፱ ፡ ፱)።

**ዐፈር** ፤ (ዕብ ፡ ዐፋር ። ሱር ፡ ዐፍራ) ፤ በቁሙ ፤ መሬት ፡ ትቢያ ፡ ዐቧራ ፡ (መ ፡ ፈ)። የመሬትን ፡ ፍቾ ፡ እይ ። (ግጥም) ፤ ከቤተ ፡ ክሲያን ፡ ጓሮ ፡ ጥቂት ፡ ጥጥ ፡ ቢኖረኝ ፤ ለልብስኹ ፡ አታስብ ፡ ዐፈራለኹ ፡ አለኝ ።

**ዕጸ ፤—ዕጣ ፤—ዐፀወ ፤ ዕፃ ።**

**ዐጸ.ብ** ፤ ቦት ፤ (ዐጸበ ፡ የዐጽብ ፡ ይዕጽብ ። ዕብ ፡ ዐጺብ) ፤ ዐጸበ ፡ መኾን ፤ መጭንቅ ፤ መክበድ ፤ መባስ ፤ መክፋት ፤ የጊዜ ፡ የሥራ ፡ የመከራ ። ለምንት ፡ ትጌልዩ ፡ ዘየዐጽብ ። ኢይዕጽብከ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ። ወዐጸቦ ፡ ለሐማን ፡ ዝንቱ ፡ ጽሑ ፡ (ሉቃ ፲፪ ፡ ፳፮ ። ፪ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ ። ዮሴፍ)።

—፤ መጨነቅ ፤ መክበድ ፤ መደነቅ ፤ በሥራ ፡ በመከራ ። ዐጸበት ፡ ሶበ ፡ ትወልድ ። ሶበ ፡ የዐጽብ ፡ ሙሴ ፡ ያወርድ ፡ እዴሁ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፱ ። ዘፀ ፲፯ ፡ ፲፩)። በዐጸበ ፡ ፈንታ ፡ ተዐጽበ ፡ ይላል ፤ አያስኼም ፤ ተ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። ተዐጽቡ ፡ ምስሌነ ። ተዐጽበ ፡ ዕጽበተ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱ ። መቅ ፡ ወን)።

**ዕጹብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ጽብት) ፤ የጨነቀ ፡ ጭንቅ ፤ አስቸጋሪ ፤ ጽኑ ፤ ከቡድ ፤ ቃለ ፡ አንክሮ ፤ ድንቅ ። እፎ ፡ ዕጹብ ። ዕጹብት ፡ ለገቢር ። ትእዛዝ ፡ ዕጹብ ። ግብር ፡ ዕጹብ ። ዕጹብ ፡ ቀሊል ፡ ለከ ። ዕጹብ ፤ ይመስሎ ፡ ዝንቱ ፡ ወልድ ፡ ለጦቢት ። ዕጹብ ፡ ለዐይን ፡ ሥን ፡ ጽዕዱ ፡ (ማር ፲ ፡ ፳፬ ። ፊልክ ፡ ፫ ። ዳን ፪ ፡ ፲፩ ። ዘፀ ፰ ፡ ፲፱ ። ድጓ ። ጦቢ ፯ ፡ ፪ ። ሢራ ፵፫ ፡ ፲፰)።

**ዕጸብ** ፤ (ባት) ፤ ጭንቀት ፤ ጭንቅ ፤ ጽናት ፤ መከራ ፤ ወጥመድ ። እመ ፡ ሶ ፡ ዘከሐደ ፡ ለእንተ ፡ ንዴት ፡ ወዕጸብ ። ዕጸብ ፡ ግብሮሙ ። ረስየ ፡ ለዕጸብየ ፡ ቀሊለ ። ዕጸቢሁ ፡ ለሞት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ። ዘፀ ፯ ፡ ፱ ። ጥበ ፡ ጠቢ ። ፪ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፯)።

**ዕጽበት** ፤ (ታት) ፤ መጨነቅ ፤ ጭንቀት ፤ ጭንቅነት ፤ ጭንቅ ። በእንተ ፡ ዕጽበተ ፡ ህድአት ። ዕጽበት ፡ ተቃትሎ ፡ (ፊልክ ፡ ፫ ፡ ፶፯)።

**ዐጸባ** ፤ (ባት) ፤ ጭንቅ ፡ መከራ ፡ ችጋር ፤ ቀጠና ፤ ዕጦት ፤ ድኽነት ። ፍቁር ፡ አማናዊ ፡ ይትአመር ፡ በጊዜ ፡ ዐጸባ ። ሶበ ፡ ረከቦሙ ፡ ዐጸባ ። ንግደት ፡ ርሕቀት ፡ እንተ ፡ ከነት ፡ በእንተ ፡ ዐጸባ ፡ (ትእ ፡ ጺዋ ። ጥበ ፲፯ ፡ ፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፫)። በዐጸባ ፡ ፈንታ ፡ ዕጽብና ፡ ይላል ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ዕጽብና ፡ ዐቢይ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ገዳም ። ዕጽብናተ ፡ ገዳም ፡ (ስንክ ፡ ጥቅም ። ጥር ፡ ፲፯)።

**ዐጸብጸ.ብ** ፤ የጭንቅ ፡ ጭንቅ ፤ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ጭንቅ ፤ ቍርጥ ፡ ነገር ፤ ትእዛዝ ፤ በኹለት ፡ ወገን ፡ የሚያስጨንቅ ፤ ቢያደርጉትም ፡ ባያደርጉትም ፡ ጕዳት ፡ ያለበት ። ተናገረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ዐጸብጸበ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፱)።

**አዕጸበ** ፤ አስጨነቀ ፤ አባሰ ፤ አጸና ፡ አበረታ ። ወለዘፈቀደ ፡ ያዐጽብ ። **አዕጸቡ** ፡ ተቃትሎ ፡ (ሮሜ፱ ፡ ፲፰ ። ፊልክ) ።

**አስተዐጸበ** ፤ አከበደ ፤ አገነነ ፤ አስተባሰ ፤ አደነቀ ፤ ዕጹብ ፡ ዕጹብ ፡ አለ ፤ የከፉ ፡ የበጎ ። **አስተዐጸቡ** ፡ ሮም ፡ ዘገብሩ ፡ አይሁድ ። ኢያስተዐጸበ ፡ ንትፈተ ፡ ሥጋሁ ። አፍቅሩ ፡ ነግደ ፡ እንዘ ፡ ኢታስተዐጽቡ ፤ የከፉ ፡ (ዮሐ ። ስንክ ፡ መጋ፳ ። ፩ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፲፪) ። ከመ ፡ ይትናጸሩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወያስተዐጽቡ ፡ ፍጥረቶሙ ። ነበሩ ፡ እንዘ ፡ ያስተዐጽቡ ፡ ግብረ ፡ እግዚ ። ኣነክር ፡ ወኣስተዐጽብ ፡ እምኔክሙ ፤ የበጎ ፡ (ቀሌ ። ገድ ፡ ተክ ። አቡሻ ፡ ፳) ።

**ዐጸ.ድ ፤ ዶ.ት ፤ (ዐጺደ ፡ የዐጽድ ፡ ይዕጽድ ። ዕብ ፡ ዐጻድ ፤ ገዘመ ። ሱር ፤ ዐረ ፡ ሐጻድ)** ፤ ማጨድ ፤ መቍረጥ ፤ መቈጥቈጥ ፤ ያዝመራ ፡ የማር ፡ የቀጠል ። መክፈል ፤ መወሰን ፤ የቦታ ፡ የርስት ፤ የዘመን ። ማእረር ፡ በጽሐ ፡ ለዐጺ.ድ ። ዘየዐጽ.ድኒ ፡ ይነሥእ ፡ ዐስቦ ። ዕጽ.ድ ፡ ማዕረ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፳፩ ። ዮሐ፬ ፡ ፴፮ ። ምሳሌ፳ ፡ ፳፱) ። ጸደየን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ዐጻዲ. ፤ (ዲ.ት ፡ ድያን ፡ ያት)** ፤ የሚያጭድ ፡ ዐማጅ ፤ ቈራጭ ፤ ከፋይ ፡ ወሳኝ ።

(ጥጸ) **ዐጸድ** ፤ የሚያጭዱ ፤ ዐማጆች ። ወበጊዜ ፡ ማእረር ፡ እብሎሙ ፡ ለዐጺ.ድ ፤ ወዐጺ.ድኒ ፡ መላእክት ፡ እሙንቱ ፡ (ማቴ፲፫ ፡ ፴ና ፡ ፴፱ ። ያዕ፭ ፡ ፬) ።

**ማዕጸድ ፤ (ዕብ ፡ ማዓጻድ ፤ ገዝሞ ፤ መጥረቢያ ፤ መላጊያ)** ፤ ማጭድ ፤ ማጨጃ ፤ መቍረጫ ። ማዕጺ.ድ ፡ በሊ.ኅ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ (ራእ፲፬ ፡ ፲፬—፲፱) ።



ማዕጸድ ፡

**መዓጽድ** ፤ ማጭዶች ። ይመትሩ ፡ ሖያን ዊሆሙ ፡ ለመዓጽ.ድ ፡ (ኢ.ሳ፲፰ ፡ ፭) ።

**ተዐጽደ** ፤ ታጨደ ፤ ተቈረጠ ፡ ተከፈለ ፡ ተወሰነ ። እመ ፡ ኢ.ተዐጽ.ደ ፡ ዘተዘርዐ ። ወተዐጽ.ደት ፡ ምድር ፡ (ሉቃ ፡ ዕዝ፱ ፡ ፳፯ ። ራእ፲፬ ፡ ፲፮ ። ያዕ፭ ፡ ፯) ።

**ዕጹ.ድ** ፤ የታጨደ ፤ ዕጭድ ፡ ነዶ. ፤ ቃርሚያ ፤ ምድሩንም ፡ እኽሉንም ፡ ያሳያል ።

**ዐጸድ** ፤ ቦታ ፡ ወልወል ፤ ደጅ ፡ ምድምድ ፤ ርስት ፤ ወገድ ፤ የምድር ፡ ክፍል ፤ ያንዳንድ ፡ ሰው ፡ ዕድል ፤ ፈንታው ፡ ድርሻው ፤ በዙሪያው ፡ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ ወሰን ፡ ደንበር ፡ ያለው ፤ የግዛት ፡ ያታክልት ፡ ስፍራ ፤ የሰው ፡ የእንስሳት ፡ ሰፈር ፤ ቤት ፡ በረት ፡ ያለበት ፡ ገጠር ፡ መንደር ። ቦቱ ፡ ዐዘቅት ፡ ውስተ ፡ ዐጸ.ድ ። ወሚጡ ፡ ዐጸደሙ ። ዐጸ.ደ ፡ ወይን ፤ ዐጸ.ደ ፡ ሐምል ። ዐጸ.ደ ፡ ዘይት ። ዝ ፡ ዓለም ፡ ውእቱ ፡ ዐጸደ ፡ ገቢር ፡ ወዘይመጽእስ ፡ ዐጸ.ደ ፡ ዕሴት ፤ ዓለምኒ ፡ ዐጸ.ደ ፡ ጻማ ፡ ወድካም ፤ ወዘይመጽእኒ ፡ ዐጸ.ደ ፡ ፍግዓ ፡ ወዕረፍት ፡ (፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ። ግብሮ ፡ ፩ ። መክ፪ ፡ ፬—፩ ። ዘዳ፳ ፡ ፲፩ ። ዮሴፍ) ። በቦታው ፡ ላይ ፡ የሚበቅለውም ፡ ዛፍ ፡ ዐጸድ ፤ ይባላል ። ዐጸደ ፡ ቤተ ፡ ክሲያን ፤ ዐጸዳም ፡ እንዲሉ ። (ተረት) ፤ ዐጸድ ፡ የሌለው ፡ ደብር ፡ ጽሕም ፡ የሌለው ፡ መምር ።

**አዕጻድ ፤ (ዳት)** ፤ ቦቶች ፡ ወገዶች ፡ ገጠሮች ። አዕጻዳቲሆሙ ፡ ለኖሎት ። ተስዕ ፡ አህጉር ፡ ወአዕጻዳቲሆን ፡ (ማሕ፩ ፡ ፯ ። ኢያ፲፭ ፡ ፴፪ ። ማቴ፲ ፡ ፲፩) ።

**ዐጸ.ው ፤ ዎት ፤ (ዐጺወ ፡ የዐጹ ፡ ይዕጹ ። ዕብ ፡ ዐጻህ)** ፤ መዝጋት ፤ መግጠም ፤ መቈለፍ ፡ ማትም ፤ ማገድ ፡ መከልከል ፤ እንዳይወጣ ፡ እንዳይገባ ፡ ማድረግ ፤ ማጠር ፡ መቅጠር ፤ ማሰር ፡ ማጋዝ ፤ መድፈን ፡ መምረግ ፤ መደበቅ ፡ ማሥረግ ። ዕጹ. ፡ ኆኅተከ ። አልቦ ፡ ዘይክል ፡ ዐጺዎታ ። ዐጺወ ፡ ላዕሌሁ ። እመ ፡ ዐጸወ ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ፡ መኑ ፡ ያርኁ ። የዐጹ ፡ ምሕረተ ፡ እምኔሁ ። ዕጽዎ ፡ ለዝ ፡ ነገር ፤ ወኅትም ፡ መጽሐፈ ፡ (ኢ.ሳ፳፮ ፡ ፳ ። ራእ፫ ፡ ፰ ። ፳ ፡ ፫ ። ኢዮ፲፪ ፡ ፲፬ ። ዮሐ፫ ፡ ፲፯ ። ዳን፲፪ ፡ ፬) ።

**ዐጻዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ የሚዘጋ ፡ ዘጊ ፤ በረኛ ። ዐጻዊኒ ፡ ያርኅዎ ። አመ ፡ ዐጻዊት ። ዐጻውያን ፡ ኆዋኅው ፡ (ዮሐ፲ ፡ ፫ ። ፲፰ ፡ ፲፯) ።

**ዐጸውት** ፤ ዘጎች ፤ ዘጊዎች ፤ በረኞች ። ዐጸውት ፡ ሲኦል ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፲፯) ።

**ማዕጾ** ፤ መዝጊያ ፤ ሳንቃ ። ከመ ፡ ማዕጾ ፡ እንተ ፡ ተዐውድ ። ይርኅዉ ፡ ማዕጾ ። ወማዕጾ ፡ ዘዐቅም ፡ (ምሳ፳፮ ፡ ፲፬ ። ዘካ፲፪ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፻፵) ።

—፤ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ ሽምጥ ። ሰበረ ፡ ማዕጾ ፡ ወጕየ ። ንግበር ፡ ላቲ ፡ ማዕጾ ፡ ዘቄድሮስ ፡ (ከፋ ፡ ፴፱ ። ማሕ፰ ፡ ፱) ።

**መዓጽው ፤ (ጹ.ት ፡ ጽዋት)** ፤ መዝጊያዎች ፤ ሳንቆች ። በበ ፡ ክልኤ ፡ መዓጽዊሁ ። መዓጹ.ት ፡ ወመናሥግት ። መዓጹ.ት ፡ ዘቅድመ ፡ ገጹ. ፡ (ሕዝ፵፩ ፡ ፳፬ ። ኢዮ፴፰ ፡ ፲ ። ፪ዜ፩ ፡ ፰) ።

**ተዐጽወ** ፤ ተዘጋ ፡ ዝግ ፡ ኾነ ፤ ተዘጋበት ። ተዐጽወ ፡ አብያት ። ተዐጽወ ፡ አህጉር ። ባእ ፡ ተዐጸው ፡ ማእከለ ፡ ቤትከ ። ወሶበ ፡ ተዐጽወ ፡ ክልኤሆሙ ፡ (ኢ.ሳ፳፬ ፡ ፲ ። ኤር፲፫ ፡ ፲፱ ። ሕዝ፫ ፡ ፳፬ ። ጦቢ.፰ ፡ ፬) ።

**ዕጽው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ጹ.ት)** ፤ የተዘጋ ፡ ዝግ ፤ ኅቡእ ። ናሁ ፡ ዕጹው ፡ ኆኅት ፡ ገነት ። መስቴማ ፡ እሱር ፡ ወዕጽው ። ዕጽው ፡ ወኅቱም ፡ ነገሩ ፡ (ዳን፳ ፡ ፳ ። ከፋ ፡ ፲፫ ። ዳን፲፪ ፡ ፱) ።

**ዕጽወት** ፤ መዝጋት ፤ መዘጋት ፤ አዘጋግ ፡ ዝግነት ። መዋዕለ ፡ ዕጽወትከ ፡ (ሕዝ፬ ፡ ፱) ።

**ዐጽም ፤—በቁሙ ፤—ዐዕም ።**

**ዐጸ.ፍ ፤ ፎ.ት ፤ (ዐጺፈ ፡ የዐጽፍ ፡ ይዕ**

ጽፍ ። ዐጠፈ) ፤ ማጠፍ ፤ መደረብ ፤ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፤ ማድረግ ። መልበስ ፡ መጐናጠፍ ። ብፁዕት ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ እምቅድመ ፡ ትዕጽፍ ፡ አብራኪሃ ፡ በውስተ ፡ ጸሎት ፡ ይሠርቅ ፡ ላዕሌሃ ፡ ጸዳል ። ወዕጽፍ ፡ ሳድስተ ፡ ሠቀ ፡ (አረጋ ፡ ድ፴፪ ። ዘፀ፳፮ ፡ ፱) ።

**ዐጻፊ** ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ጸፍት) ፤ የሚያጥፍ ፡ ዐጣፊ ፤ ተጐናጣፊ ። ዐጸፍተ ፡ ብርሃናት ፡ (ኪዳ) ።

**ተዐጽፈ** ፤ ታጠፈ ፤ ተደረበ ፤ ልብሱ ። ለበሰ ፤ ተጐናጠፈ ፤ ሰዉ ። ተዐጸፍኬ ፡ ልብሰከ ። ልብሰ ፡ ቀጤን ፡ ዘይትዐጸፍ ፡ ካህን ። ትትዐጸፍ ፡ አልባሲሃ ። ንትዐጸፍኬ ፡ አ ፡ አኃውየ ፡ በዝንቱ ፡ (ግብ፲፪ ፡ ፰ ። ሚ ራ፶ ፡ ፪ ። ዮዲ፲ ፡ ፯ ። አፈ ፡ ተ፴፱) ።

**ዕጹፍ** ፤ **ዑጹፍ** ፤ የታጠፈ ፤ ዕጥፍ ፤ ድርብ ፤ ዱብል ። ቢሶስ ፡ ዕጹፍ ፡ ወንት ፡ ዕጹፍ ። አስመ ፡ ዕጹፍ ፡ ውእቱ ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፭ ። ኢዮ፲፭ ፡ ፮) ።

—፤ የለበሰ ፤ ያጣፋ ፤ የደረበ ፤ ያጌጠ ፤ የተጐናጠፈ ። ዑጹፍ ፡ ወስርግው ። ዑጽፍት ፡ ወሑብርት ፡ (አፈ ፡ ተ፴፪ ። መዝ ፡ ፵፬) ።

**ዑጻፌ** ፤ ማጠፍ ፤ መቃጠፍ ፤ አስተጣጠፍ ፤ ዕጥፈት ፤ ዐጠፋ ። መልበስ ፤ መደረብ ። ዐጽፍ ፡ መደረቢያ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሸ፭) ።

**ዐጽፍ** ፤ (ፋት) ፤ በቁሙ ፤ መጐናጠፊያ ፤ መደረቢያ ፤ የላይ ፡ ልብስ ፤ ካባ ፤ በርኖስ ፤ ኵታ ፡ ጋቢ ፤ ሻኛ ፤ ድርብ ፤ ቂፌ ፤ ልግም ፡ በገላ ፤ የሌት ፡ ልብስ ፤ የመሰለው ፤ ኹሉ ። ልብስየ ፡ ወዐጽፍየ ። ወዳዊትኒ ፡ ቅኑት ፡ በዐጽፍ ፡ ዘዕጹብ ፡ ሤጡ ። ዘዐጽፈ ፡ ትጉሃን ፡ ዐጽፋ ። ሰላም ፡ ለበርሰማ ፡ ትርቢተ ፡ ዓለም ፡ ዘገደፈ ፤ እስከ ፡ ኢያጥረየ ፡ ዐጽፈ ፡ (ዕዝ፬ ፡ ፫ ። ሽዜና ፡ ፲፭ ፡ ፳፯ ። ስንክ ፡ ጥር፲፯ ። ጳጉ፭) ።

**አዕጽፍት** ፤ ዐጽፎች ፤ መጐናጠፊያዎች ። ወልቡሳን ፡ አዕጽፍተ ፡ (፪ዜና ፡ ፲፰ ፡ ፱) ።

**ማዕጸፍ** ፤ (ፍት) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፤ ዐጽፍ ። ሲያበዛ ፡ መዓጽፍት ፡ ይባል ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ዐጺቅ** ፤ **ቆት** ፤ (ዐጸቀ ፡ የዐጽቅ ፡ ይዕጽቅ ። ዕብ ፡ ያጺቅ ፤ ጨመረ ፡ አፈሰሰ ፤ የውሃ) ፤ ማጕምጐም ፤ ማፈጥፈጥ ፤ መብቀል ፡ መክበብ ፤ ዙሪያውን ፡ መውጣት ፤ ማደግ ፡ መርዘም ፤ ቁመት ፡ መጨመር ፡ የቅጠል ፡ የዛፍ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዐጸቀ ፡ ፈንታ ፡ አዕጸቀ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ሄርማ ፡ ገ፶) ።

**ዐጽቅ** ፤ በቁሙ ፡ ቅጥይ ፤ ክንፍ ፤ ጫፍ ፡ ቅርንጫፍ ፤ ውልብልቢት ። ለዘሉ ፡ ዐጽቅ ፡ ዘኢይፈሪ ። ኢሥርዎሙ ፡ ወኢዐጽቅሙ ፡ (ዮሐ፲፭ ፡ ፪ ። ሚል፫ ፡ ፲፱) ።

—፤ ፍሬ ፤ ሕንባብ ፤ ዛላ ፤ ዘለላ ። ንግሥ ፡ ዐጽቀ ፡ በለስ ። ምእት ፡ ዐጽቀ ፡ ዘቢብ ። ቁላቱ ፡ ዐጽቅ ፡ (ኢሳ፴፰ ፡ ፳፩ ። ፪ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ። ዘኍ፲፫ ፡ ፳፫ ። ዘዳ፴ ፡ ፴፪) ።

—፤ ዙሪያ ፡ ክበብ ፡ ዐጥር ፡ ቅጥር ፤ ዛጎጋባ ፡ የቤት ፡ ቅጥይ ። ዐጽቀ ፡ ዐጺድ ፡ (ሄርማ ፡ ገ፵) ።

**አዕጹቅ** ፤ (ቃት) ፤ ቅጥዮች ፤ ጫፎች ፤ ፍሬዎች ። አዕጹቂሃ ፡ ኢይፈርዩ ። ኖኃ ፡ አዕጹቅየ ። ክልኤ ፡ አዕጹቀ ፡ በለስ ። አዕጺቃተ ፡ ወይን ፡ (ሚራ፳፫ ፡ ፳፩ ። ፳፱ ፡ ፲፮ ። ኤር፳፱ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ መስ፭) ። አዕጹቀ ፡ ተቀዋም ፡ ቢል ፡ አገዶች ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ ከዚያው ፡ ከዐጽቅንቱ ፡ አይወጣም ፡ (ዘፀ፴፰ ፡ ፲፱—፲፭) ።

**ዐጽሮ** ፤ **ሮት** ፤ (ዐጸረ ፡ ይዔጽር ፡ የዐጽር ። ዐረ ፡ ዐጸረ ። ሱር ፡ ዐጻር) ፤ መጥመቅ ፡ መጭመቅ ፤ ማሸት ፡ መርገጥ ፤ ማፍተልተል ፡ ማፍረጥረጥ ፤ መዘለል ፤ የወይን ፡ የዘይት ፡ የድፍድፍ ፤ የልብስ ፤ ለሰውም ፡ ይኾናል ። ሶበ ፡ የዐጽርዋ ፡ ትገብር ፡ ደመ ፡ አስካል ። አስተርከቡ ፡ ወዐጸሩ ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ። ሰእመ ፡ ዐጸርከ ፡ አንፈከ ፡ ይወፅእ ፡ ደም ። ዐጸሮ ፡ ለውእቱ ፡ ፀምር ። አብእዎ ፡ ውስተ ፡ ምስካበ ፡ ንጹን ፡ ወዐጸርዎ ፡ (መቃ ፡ ገ፳ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፳፱ ። ምሳ ፳፱ ፡ ፴፫ ። መሳ፮ ፡ ፴፰ ። ስንክ ፡ ማጋ፲፱) ።

**ዐጻሪ** ፤ የሚጠምቅ ፤ ጠማቂ ። ንጉሥ ፡ ከሓዲ ፡ ዐጻሬ ፡ ሰማዕታት ፡ በምክያድ ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፰) ።

**ተዐጽረ** ፤ ተጠመቀ ፤ ተዘለለ ። ዘተዐጽረ ፡ እምአስካለ ፡ ወይን ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፮ ፡ ፭ ። መቃ) ።

**ዐጺር** ፤ የተጠመቀ ፤ ጥማቂ ፤ ውጤት ። ኢይሰቲ ፡ እንከ ፡ እምዝንቱ ፡ ዐጺረ ፡ ፍሬ ፡ ወይን ፤ እስከ ፡ አመ ፡ እሰትዮ ፡ ሐዲሰ ፡ (ማቴ፳፮ ፡ ፳፱) ።

**ዐሰ** ፤—ምድረ ፡ በዳ ፤—ዐዊዕ ፡ ዐፀፀ ።

**ዐፀደ** ፤—ዐጨደ ፤—ዐጺድ ፡ ዐጸደ ።

**ዐፀወ** ፤ (ዐጸወ) ፤ በረታ ፤ ጠጠረ ፤ ጠነከረ ። ዕፃ ፡ ጣለ ፤ አወጣ ። ዐፀፀን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ዕፅ** ፤ (ዕብ ፡ ዔፅ) ፤ ጥኑ ፤ ጠንካራ ፤ ዕንጨት ፤ ዛፍ ፤ ባለብዙ ፡ ክንፍ ፤ ዐይነቱና ፡ ስሙ ፡ ሽታውና ፡ ጣዕሙ ፡ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፤ ለሥራና ፡ ለመማሪያ ፡ ኹሉ ፡ የሚፈለግ ፤ ፍሬው ፡ የሚበላ ፤ የማይበላ ። ለታብቍል ፡ ምድር ፡ ሐመልማለ ፡ ሣዕር ፡ ዘይዘሪዕ ፡ ዘርዑ ፤ ወዕፀ ፡ መፍርየ ፡ ዘይገብር ፡ ፍሬ ፡ በበ ፡ ዘመዱ ። ዕፀ ፡ ሕይወት ። ታሕተ ፡ ዕፀ ። ኅበ ፡ አልቦ ፡ ዕፀ ። እስመ ፡ እምፍሬሁ ፡ ይትዐወቅ ፡ ዕፀ ። ዕፀ ፡ ወይን ። ዕፀ ፡ ዘይት ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፲፩ ። ፪ ፡ ፱ ። ፲፰ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፳፪ ። ማቴ፲፪ ፡ ፴፫ ። ሕዝ፲፭ ፡ ፪ ። ሚራ፳፱ ፡ ፲፱) ።

**ዕፀ** ፡ **ፋርስ** ፤ ፋርሳዊ ፡ ቅጠል ፤ ከፋርስ ፡ የመጣ ፤ ነገረን ፡ ተመልከት ።

**ዕፀው** ፤ (ዋት) ፤ ዕንጨቶች ፤ ዛፎች ። ዕፀው ፡ ዘይፈርዩ ። ዕፀወ ፡ ዖም ። ዕፀወ ፡ ገዳም ። ወጣሕከ ፡ ዕፀወ ፡ ዲበ ፡ እሳት ፡ (መክ፪ ፡ ፭ ። ኤር፫ ፡ ፮ ። ኩፋ ፡ ፲፫ ። ሚራ፰ ፡ ፫) ።

**ዕፅ** ፤ ዕፃ ፤ ዕጣ ፡ የንጨት ፡ የወረቀት ፡ የጠጠር ፤ ምልክት ፡ ያለው ፤ ስም ፡ የተጣፈበት ። ዕጣው ፡ የወደቀበት ፡ ክፍል ፡ ድርሻ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ። ዘቲ ፡ መክፈልት ፡ ወፀአት በዕፀ ፡ ለሌዎ ። ወወረደ ፡ ዕፀ ፡

ላዕለ ፡ ዐሡሩ ፡ ወረቡዑ ፡ ለሠርቀ ፡ አዳር ። እስመ ፡ ሎሙ ፡ ረከቦሙ ፡ ዕፀ ፡ (ኩፋ ፡ ፴ ። አስቴ ፫ ፡ ፯ ። ሰዜና ፡ ፯ ፡ ፶፱ ። ዘሌ ፲፯ ፡ ፴—፲) ።

**ዕፃ** ፤ በቁሙ ፤ ገለ ፡ ክማሁ ። መክፈልት ፡ ዘ ኢ.ወፅአ ፡ በዕፃሁ ። ወረደ ፡ ዕፃ ፡ ላዕለ ፡ ዮናስ ። ወበ ጽሐ ፡ ዕፃ ፡ ደበ ፡ ማትያስ ፡ (ኩፋ ፡ ፱ ። ዮናሽ ፡ ፯ ። ግብሽ ፡ ፳፯) ።

**ዕፀት** ፤ ዕንጨትንት ፤ ዕንጨት ፤ የንጨት ፡ ወ ገን ፤ ቍጥቋጦ ፤ ጫሬሮ ፤ ጫፍጫፌ ፤ ዝንጣፊ ፤ እሾኽም ፤ ቅጠላም ፤ ታናናሽ ፡ ቀጫጭን ፡ በጣም ፡ የማያድግ ፡ ዛፍ ፡ የማይኾን ፤ እንደ ፡ እንባጮ ፡ ያለ ። እምዕፀት ፡ ይነ ድድ ፡ እሳት ፤ ወዕፀታ ፡ ኢ.ተውዒ ። ዕፀት ፡ ልምል ምት ፡ (ዘፀ ፫ ፡ ፪—፱ ። ስንክ ፡ ታኅሣ፱) ።

—፤ ዛፍ ፤ የዛፍ ፡ ወገን ፡ ኹሉ ፤ ታላላቅ ፡ ወፍራም ፤ ረዣዥምም ። ቅሩብ ፡ ዕፀት ፡ ፀዋጓ ፡ (ዘዳ ፲፩ ፡ ፴) ። ዕብራ ይስጡ ፡ ግን ፤ (ኤሎኒይ ፡ ሞሬ) ፡ ዕፀወ ፡ ሞሬ ፡ ይላል ፡ (ዘፍ ፲፪ ፡ ፮) ።

**ዕፀታት** ፤ **(ዕፃት)** ፤ ዛፎች ፤ ዕንጨቶች ፤ ዕጣ ዎች ። ውስተ ፡ ዕፀታት ። ዕፃት ፡ (ሬእ ፳ ፡ ፩ና ፡ ፫ ። ሄርማ ፡ ገ፺) ።

**ተዓፀወ** ፤ ዕፃ ፡ ተጣጣለ ፤ ተካፈለ ። ንዑ ፤ ንት ዓፀው ፤ ወተዓፀዉ ። መፍትው ፡ ከመ ፡ ንትዓፀው ፡ በበ ፡ ክልኤ ፡ እምኔነ ፤ ወዘወፅአ ፡ ቦቱ ፡ ዕፃ ፡ ለቀ ቲል ፤ ይቅትል ፡ ካልኦ ። ወተዓፀዉ ፡ ዲበ ፡ ዐራዝየ ፡ (ዮናሽ ፡ ፯ ። ዮሴፍ ። መዝ ፡ ፳፩) ።

**ዑፃዌ** ፤ ዕፃ ፡ መጣጣል ፤ ዕፃ ። መጽሐፈ ፡ ዑ ፃዌ ። በጽሖ ፡ በዑፃዌ ። አንበሩ ፡ ዑፃዌ ፡ (ኩፋ ፡ ፱ ። መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ሚያ፫ ። አርጋ ፡ ፩) ።

**አስተዓፀወ** ፤ ዕፃ ፡ አጣጣለ ። ዕፀው ፡ ዘቦቱ ፡ ያስተዓፀው ። ወአስተዓፀወ ፡ ዕሴተ ፡ እምዕሴት ፡ ወወ ርኀ ፡ እምወርኅ ፡ (ዘሌ ፲፯ ፡ ፰ ። አስቴ ፫ ፡ ፯) ።

**ዐዕይ** ፤ **ዮት** ፤ **(ዐፀየ ፡ የዐፂ ፡ ይዕፂ ። ዕብ ፡ ቱሎዕ)** ፤ መትሳት ፤ ትል ፡ ማውጣት ። ዐፀየ ፡ ወጼአ ። ይጸይጽ ፡ ወየዐፅዩ ። ዘበጠ ፡ መልአከ ፡ እ ግዚ ፡ ለአግሪጳስ ፡ ወዐፀየ ፡ ወሞተ ፡ (ዘፀ ፲፯ ፡ ፳ ። ኤር ፲፫ ፡ ፫ ። ዮሴፍ ። ግብ ፲፪ ፡ ፳፫) ።

**ዕፄ** ፤ **ያት** ፤ **(ዕብ ፡ ቶላዕ)** ፤ ትል ፡ ብል ፡ ንቀዝ ፤ ተምች ፤ ፈንጣ ፡ ኾማኽ ፡ ግንደ ፡ ቈርቍር ፡ የመ ሰለው ፡ ኹሉ ። ይፈኑ ፡ እሳተ ፡ ወዕፄ ፡ ውስተ ፡ ሥጋ ሆሙ ። ብልዐተ ፡ ዕፄ ። ከመ ፡ ዕፄ ፡ ለዕፀ ። በልዑ ፡ ኀጠቱ ፡ ወዕፄ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ሾስሐ ፡ አፍራስ ። ዘአትረፈ ፡ ዕፄ ፡ በልዐ ፡ አንበጣ ። ዕፄ ፡ ሶበ ፡ ይበ




ዕፄ ፡

ውእ ፡ በእዝን ፡ (ዮዲ ፲፯ ፡ ፲፯ ። ኢዮ ፬ ፡ ፲፱ ። ምሳ ፲፪ ፡ ፬ ። ዮሴፍ ። ዮኤ ፩ ፡ ፬ ። መ ፡ ፈ) ።

**ዐፂም** ፤ **ሞት** ፤ **(ዐፀመ ፡ የዐፅም ፡ ይዕ ፅም ። ዕብ ፡ ዐጻም)** ፤ መጥናት ፤ መበርታት ፡ ዐጥ ንት ፡ መኾን ።

**ዐፅም** ፤ **(ዕብ ፡ ዔጼም ። ዐረ ፡ ዐጥም)** ፤ በቁሙ ፤ ዐጥንት ፤ የሕዋሳት ፡ ክፍል ፤ በ ሰው ፡ በእንስሳ ፡ ገላ ፡ የሚገኝ ፤ የሥጋና ፡ የደም ፡ መሠረት ፤ ደረቅ ፡ ጠንካራ ፤ የት ላጠ ፡ ዕንጨት ፡ የሚመስል ፤ ዕንጨትማ ። በየክፍሉ ፡ ብዙ ፡ ስም ፡ ያለው ። ዛቲ ፡ ዐፅም ፡ እምዐፅምየ ። ኢትስብሩ ፡ ዐ ፅሞ ፡ (ዘፍ ፪ ፡ ፳፫ ። ዘፀ ፲፪ ፡ ፵፮) ።



ዐፅም ፡

**አዕፅምት** ፤ ዐጥንቶች ፤ የገላ ፡ ክፍሎች ። ሾሉ ፡ አዕፀምት ፤ የብሱ ፡ አ ዕፅምቲነ ፡ (ሕዝ ፴፯ ፡ ፲፩) ።

**ዐፂዕ** ፤ **ዖት** ፤ **(ዐፀ ፤ ዐፀፀ ፡ የዐዕዕ ፡ ይዕ ዕዕ ። ዐፀወ)** ፤ መፈታት ፡ ዱር ፡ ደን ፡ ዕንጨታም ፡ መኾን ፤ ያገር ፡ የመንደር ።

(ጥ) **ዐዕ** ፤ **(ዓዕ)** ፤ ዱር ፡ በረሓ ፤ ባድ ፡ ባድማ ፤ ማካ ፡ ወማ ፡ የአራዊት ፡ ስፍራ ። ከመ ፡ ኢትኩን ፡ ም ድር ፡ ዐፀ ። ኮነት ፡ በድወ ፡ ወዐፀ ። በብሔረ ፡ ዐፀ ። ዐፀ ፡ ይእቲ ፡ እምሰብእ ፡ ወእምእንስሳ ፡ (ዘፀ፳፫ ፡ ፳፱ ። መቃ ፡ ፲፫ ። ኤር፷ ፡ ፯ ። ፴፱ ፡ ፵፫) ።

**ዐቂብ** ፤ **በት** ፤ **(ዐቀበ ፡ የዐቅብ ፡ ይዕ ቀብ ። ዕብ ፡ ዐቃብ ፤ አደበ)** ፤ መጠበቅ ፤ መከ ልከል ፤ ጠንቅቆ ፡ ማየት ፡ መመልከት ፡ መጐብኘት ፤ ማቈ የት ፡ ማዘግየት ። ለወለትከ ፡ አጽንዕ ፡ ዐቂቦታ ። የዐ ቅብ ፡ ገነተ ፡ እምአዕዋፍ ። ከመ ፡ ትዕቀቡ ፡ ዕጓለ ፡ ማውታ ። አብድ ፡ ኢ.ይክል ፡ ዐቂበ ፡ ነገር ፡ ዘሰምዐ ፡ (ሢራ ፳፯ ፡ ፲ ። ኩፋ ፡ ፲ ። ያዕ ፩ ፡ ፳፯ ። ሢራ ፲፱ ፡ ፲፯) ።

**ዐቃቢ** ፤ **(ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ቀብት)** ፤ የሚጠብቅ ፤ ጠባቂ ፤ ተመልካች ፤ ከልካይ ። ቦኑ ፡ ዐቃ ቢሁ ፡ አነ ፡ ለእኍየ ። ብእሲት ፡ አርማሚት ፡ ወዐቃ ቢተ ፡ ልሳን ። ካህናት ፡ ዐቃብያነ ፡ ሕጉ ፡ ለእግዚ ። ሊቀ ፡ ዐቀብተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ (ዘፍ ፬ ፡ ፱ ። ፈላስ ። ቀሌ ። ኩፋ ፡ ፴፱) ። በዐቃቢ ፡ ፈንታ ፡ ዑቃቤ ፤ ተዐቃቢ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። አዘዝከ ፡ ዑቃቤ ፡ ላዕሌየ ። ኮነ ፡ ተዐቃቤ ፡ ለሕገ ፡ እግዚ ፡ (ኢዮ ፯ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ መጋ፲፱) ።

**ዐቃቤ ፡ ሥራይ** ፤ ሐኪም ፤ ባለመድኀኒት ፤ መድኀኒቱን ፡ ጠብቆ ፡ ጠንቅቆ ፤ አጣፍጦ ፡ ቀምሞ ፡ ለሐ ኪም ፡ የሚሸጥ ። ሕሙማን ፡ ይፈቅዱ ፡ ለዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ (ማቴ፭ ፡ ፴፩) ።

**ማዕቀብ** ፤ **(ቅብ)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ለዐቃቢ ፤ ዘበኛ ፤ ወታደር ፤ አረኛ ፤ ጠባቂ ። ማረፊያ ፡ መጠበቂያ ፡ ቦታ ። እቀውም ፡ ውስተ ፡ ማዕቀብየ ፡ (ዕንባ ፡ ፩) ።

**መዓቅብ** ፤ **ብት** ፤ ዘበኞች ፤ ጠባቆች ። ረከ ብዋ ፡ መዓቅብ ፡ ፋርስ ። መዓቅብት ፡ እለ ፡ የዐቅቡ ፡

ህገረ ፡፡ ከመ ፡ መዓቅበ ፡ ሐቅል ፡ (ዮዲ ፲ ፡ ፲፩ ። ማሕ ፫ ፡ ፫ ። ኤር ፴ ፡ ፲፯) ።

**አዕቀበ** ፤ አስጠበቀ ፤ ዘበኛ ፡ አቆመ ፤ ዐደራ ፡ አለ ፤ ሰጠ ፤ አኖረ ። ወአዕቀበ ፡ አህጉሪሆሙ ፡፡ የዐቅቡ ፡ ሕገ ፤ እስመ ፡ ህርቃኖስ ፡ አዕቀቦሙ ፡ ዘንተ ፡፡ ዘአዕቀበ ፡ ንጉሥ ፡፡ አዕቀብክዎ ፡ ለጋብኤል ፡ ዐሠርተ ፡ መካልየ ፡ ብሩር ፡፡ ለዘአዕቀብዎ ፡ ብዙኀ ፤ ይትኀሠሥዎ ፡ ብዙኀ ፡ (ዮዲ ፫ ፡ ፯ ። ዮሴፍ ። ኤር ፴፱ ፡ ፫ ። ጦቢ ፩ ፡ ፲፬ ። ዲድ ፡ ፯) ።

**ማዕቀቢ** ፤ አስጠባቂ ፤ ዐደራ ፡ አኗሪ ። ካዕበተ ፡ ይፈዲ ፡ ለማዕቀቢሁ ፡ (ዘፀ ፳፪ ፡ ፱) ።

**አማዕቀበ** ፤ (**አዕቀበ**) ፤ አስጠበቀ ፤ ዐደራ ፡ አለ ፤ አማጠነ ። ብእሲት ፡ ዘአማዕቀብዎ ፡፡ ብእሲ ፡ ዘአማዕቀቡ ፡ ኪያሁ ፡፡ አማዕቀቦሙ ፡ በክርስቶስ ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፰ ፡ ፲፬ ። ፲፪ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ መስ ፱) ።

**ምዕቅብና** ፤ ዐደራ ፤ ጥበቃ ፤ ምጥንቃ ። በአንተ ፡ ምዕቅብና ፡ ንዋይ ፡፡ ወይእቲ ፡ እኅተ ፡ አቡየ ፡ በምዕቅብና ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ። ፳፬ ፡ ፱) ።

**ተዐቅበ** ፤ ተጠበቀ ፤ ተጠነቀቀ ፤ ተከለከለ ፤ ራቀ ። ተዐቀብ ፡ እምነ ፡ እኩይ ፡፡ ተዐቀብ ፡ ኢያስሕትከ ፡፡ ይትዐቀቡ ፡ እምነ ፡ ኵሉ ፡ ዝሙት ፡ ወርኵስ ፡ (ሚራ ፲፩ ፡ ፴፫ ። ፲፫ ፡ ፰ ። ክፋ ፡ ፳) ።

**ተዐቃቢ** ፤ ተጠባቂ ፤ ተጠንቃቂ ፤ ጠንቃቃ ። ዮሐንስ ፡ ተዐቃቢ ፤ ሦስት ፡ አምላክ ፡ የሚል ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡ ኪራ) ።

**ዕቁብ** ፤ (**ባን ፡ ባት ፡ ቅብት**) ፤ የተጠበቀ ፤ የተጠነቀቀ ፤ ጥብቅ ፤ ጥንቁቅ ፤ ንቡር ፤ ድልው ። መዝገብ ፡ ዕቁብ ፡ ለውሉዳ ፡፡ ዕቁበ ፡ ይትናገር ፡፡ ዘዕቁብ ፡ በቃሉ ፡፡ ዘዕቁብ ፡ ሉ ፡ ወለክሙ ፡፡ ብእሲት ፡ ዕቅብት ፡ ለብእሲ ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፰ ፡ ፱ ። ምሳ ፳፩ ፡ ፳፰ ። ቀሌ ። ፩ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፬—፭ ። ዘሌ ፲፱ ፡ ፳) ።

**ዕቅብት** ፤ (**ታት ። ዕቁባት**) ፤ ቁባት ፤ ምልምል ፤ ሥራ ፡ ቤት ፤ ገረድ ፤ ሚስትነት ፡ የሌላት ። ብእሲት ፡ ዕቅብት ፡፡ ዕቅብታት ፡፡ አንስት ፡ ዕቁባት ፡ (መሳ ፲፱ ፡ ፩ ። ዮሴፍ ። ፪ነገ ፡ ፭ ፡ ፲፫) ።

**ዕቅበት** ፤ (ላጥ) መጠበቅ ፤ አጠባበቅ ፤ ጥበቃ ። እንዘ ፡ የዐቅቡ ፡ ዕቅበተ ፡ ማኅደር ፡፡ መሀረክሙ ፡ ትእዛዛቲሁ ፡ ወዕቅበተ ፡ ሃይማኖቱ ፡፡ ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ ማኅበርነ ፡ ወዕቅበተ ፡ ለኵልነ ፡ (፩ዜና ፡ ፱ ፡ ፲፱ ። ዮሴፍ ። ሥር ፡ ቅዳ) ።

**ዑቃቤ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ መጠበቅ ፤ ጥበቃ ፤ ጥንቃቄ ። ዑቃቤ ፡ ሕግ ፡፡ ዑቃቤ ፡ ሰንበት ፡፡ ዑቃቤ ፡ ጥንቁቅ ፤ ሰብእ ፡ ዑቃቤ ፡፡ በዐቢይ ፡ ዑቃቤ ፡ (እርጋ ። መጽ ፡ ምስ ። እቡሻ ፡ ፫ ። ቀሌ) ።

—፤ ውቃቢ ፤ መንፈስ ፤ መልአክ ፤ ቆሌ ፤ በሰው ፡ ያደረ ፡ ሀብት ፤ ግርማ ፤ ሞገስ ፤ ቀልብ ፤ ለዛ ፤ ጣዕም ፤ ውበት ፤ ደም ፡ ግባት ። ባማርኛ ፡ ለክፉም ፡ ለበጎም ፡ ይነገራል ፤ ቆሌ ፡ በጭራሽ ፡ የክፉ ፡ ነው ፤ ውቃቤ ፡ ቢስ ፤ ቆሊያም ፤ ቆሌ ፡ ቢስ ፤ ቀልበ ፡ ቢስ ፤ ክፉ ። ውቃቢያም ፤ ቀልባም ፤ በርስዎ ፡ ውቃቢ ፤ በጎ ። (ተረት) ፤ ሐሰት ፡ ቢናገሩ ፡ ውቃቢ ፡ ይርቃል ።

**ተዓቀበ** ፤ ተጠባበቀ ። ከመ ፡ ይትራድኡ ፡ ኅቡረ ፡ በባሕር ፡ ወበየብስ ፡ ወይትዓቀቡ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ (ዮሴፍ) ።

**አስተዐቀበ** ፤ (**አዕቀበ**) ፤ አስጠበቀ ፤ አስጠነቀቀ ፡ ተጠበቁ ፡ ተጠንቀቁ ፡ አለ ። ወታስተዐቅቦሙ ፡ እምኔየ ፡፡ አእምር ፡ ከመ ፡ እግዚ ፡ አስተዐቀበ ፡ እምበዓለ ፡ ዕዳ ፡ (ሕገ ፴፫ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯) ።

**አስተዓቀበ** ፤ (**አደራራጊ**) ፤ አጠባበቀ ፤ ተጠባበቁ ፡ አለ ።

**ዐቀብ** ፤ (**ዕብ ፡ ዐቆብ ። ዐረ ፡ ዐቀበት**) ፤ በቁሙ ፤ ዳገት ፤ ዐቀበት ፤ ቍልቍለት ፤ የተራራ ፡ መንገድ ፤ ጠማማ ፤ ስያፍ ፤ ቀጥታ ፡ የሌለው ፤ ግድምና ፡ ሽቅብ ፡ የሚወስድ ፤ መውጫ ፡ መውረጃ ። በውስተ ፡ ዐቀቢ ፡ ለሉዊት ፡፡ አህጉር ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ዐቀብ ፡፡ ወዐርጋ ፡ ዐቀበ ፡ ቤጤሌዋ ፡፡ ዐቀበ ፡ ኖዳ ፡፡ ሙራደ ፡ ዐቀብ ፡ (ኢሳ፲፭ ፡ ፭ ። ዮዲ ፯ ፡ ፯ ። ፲፫ ፡ ፲ ። ሚራ ፳፭ ፡ ፳ ። ሉቃ ፲፱ ፡ ፴፯) ።

**ዐቃብ** ፤ (**ዕብ ፡ ዐቅበ ፤ ሸንገላ ፤ ክሕደት ፤ ጠማምነት**) ፤ እሾኽ ፤ አሜከላ ፤ ኵሸሽላ ፡ ቃናሽ ፡ ዐሬም ፤ ዐቃቅማ ፡ ኰርንችት ፤ እሾኻም ። ከመ ፡ ዐቃብ ፡ ምልኅት ፤ ከማሁ ፡ ኵሎሙ ፡ (፪ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፯) ።

**ዐቀባት** ፤ እሾኾች ። እኪያት ፡ ሥጋክሙ ፡ ምስለ ፡ ዐቀባት ፡ (መሳ ፰ ፡ ፯፣ ፲፮) ።

**ዐቂድ** ፤ ዶት ፤ (**ዐቀደ ፡ የዐቅድ ፡ ይዕቅድ ። ዕብ ፡ ዐቃድ**) ፤ መቀየድ ፤ መኰድኰድ ፤ እግር ፡ ተወርቶ ፡ ማሰር ፤ መቀፍደድ ፤ የፍሬዳ ። በቁሙ ፤ ማቀድ ፤ ማስጕብደድ ፤ መቀሰት ፤ እንደ ፡ ደጋን ፡ ማጕበጥ ፤ የሕንጻ ፡ የማንብ ። ማዋቀር ፤ መማገር ፤ መሠመር ፤ የጣራ ፡ የባጥ ።

**ተዐቅደ** ፤ ታቀደ ፤ ተቀየደ ፤ ተኰደኰደ ።

**ዕቁድ** ፤ የታቀደ ፡ የተቀየደ ፤ ቅይድ ። ዕቁደ ፡ እግር ፡ (ስንክ ፡ ሚያ ፲፯) ።

**ዕቀድ** ፤ እስራት ፡ ማገር ። መታሰር ፤ መቀየድ ።

**ዐቅድ** ፤ የሥራ ፡ መልክ ፤ አሠራር ፤ ውቅር ። ዐቅዶን ፡ (ገድ ፡ ላሊ) ።

**ማዕቅድ** ፤ ዐቃድ ፤ ቀስተ ፡ ደመና ፤ ጉበን ፤ ጣራ ፤ ባጥ ፤ መዋቅር ። ቢያብዛ ፡ መዓቅድ ፡ ይላል ። አልቦ ፡ ጠፈር ፡ ለመዓቅዶን ፤ ወአልቦ ፡ ሣዕር ፡ ለመክደኖን ፤ ኢይፈቅድ ፡ አሕባለ ፡ ለመዓቅዶን ፡ (ገድ ፡ ላሊ) ።

**ዐቂል** ፤ ሎት ፤ (**ዐቀለ ፡ የዐቅል ፡ ይዕቅል ። ዕብ ፡ ዐቄል ፤ ካበ ÷ ከበበ**) ፤ ማጕድጕድ ፤ ማጥለቅ ፤ ዙሪያውን ፡ መዝጋት ፤ መገንባት ። በውስጡ ፡ ውሃን ፡ መሰብሰብ ፤ ማከማቸት ፤ ማጠራቀም ፡ መያዝ ። ዐቀለ ፡ ብሂል ፡ ይነግግ ፡ (ጥሬ ፡ ሰዋ) ።

**ምዕቃል** ፤ (ላት) ፤ ኰሬ ፤ የውሃ ፡ መቋሚያ ፤ መጠራቀሚያ ፤ ባታክልት ፡ ውስጥ ፤ በቦይ ፡ በቦምባ ፡ ማፍ ፤ ወይም ፡ በዱር ፡ በበረሓ ፡ ያለ ፤ ታናሽ ፡ ባሕር ፤ መዋኛ ፡ መታጠቢያ ። ሐነጸ ፡ ምዕቃለ ፡ ማይ ። ለእመ ፡ አብሖከ ፡ አሐዱ ፡ ከመ ፡ ታስቲ ፡ እምዕቃለ ፡ ዚአሁ ። ዘሎ ፡ ምዕቃላተ ፡ (ሚራ፴፰ ፡ ፲፮ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፮ ። ኩፋ ፡ ፪ ። መክ፪ ፡ ፮ ። ማሕ፬ ፡ ፲፪ ። ፮ ፡ ፳) ።

**ዐቅል** ፤ (ዐረብ) ፤ ጥልቅ ፡ ጠባይዓዊ ፡ ዕውቀት ፤ ጥበብ ፤ ብልኀት ። አንደፈር ፡ አበ ፡ ሄሮድስ ፤ ቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ምክር ፡ ወዐቅል ፡ (ዮሴፍ) ።

(ጥ) **ዐቅሞ** ፤ **ሞት** ፤ (**ዐቀመ** ፤ **ይዔቅም** ፡ **የዐቅም** ። **ዐረ** ፡ **ዐቀመ** ፤ **አመከነ** ። **ዕብ** ፡ **ዐቈም** ፤ **አጣመመ**) ፤ መያዝ ፡ ማሰር ፤ ማቈየት ፡ ማባቀረት ። ወዐቀመ ፡ ስምዖንሀ ፡ ባሕቲቶ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፪) ።

—፤ መቍረጥ ፤ መፈጸም ፤ መጨረስ ። ይዔቅም ፡ ቃሎ ፡ (መዝ ፡ ፸፲፩) ።

—፤ መለካት ፤ መመጠን ፤ መደንገግ ፤ መወሰን ። ጥዑይ ፡ ንዋሙ ፡ ለዘይዔቅማ ፡ ለከርሡ ። በመስፈርት ፡ ዘዐቀመ ፡ ለነ ፡ እግዚ ። ባሕረ ፡ ዐቀመ ፡ ከመ ፡ ኢትትዐደው ፡ እምዐቅማ ፡ (ሢራ፴፱ ፡ ፳ ። ፪ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ኪዳ) ።

**ዐቃሚ** ፤ የሚወስን ፡ ወሳኝ ፤ ቈራጭ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፰) ።

**ዐቅም** ፤ ወሰን ፡ ድንበር ፤ ልክ ፡ መጠን ፤ ፍጻሜ ። አልቦ ፡ ዐቅም ፡ ለስፍሐ ፡ መንግሥቱ ። ለትየ ፡ ወይን ፡ ዘእንበለ ፡ ዐቅም ። አኮ ፡ ለዝ ፡ ሕግ ፡ ዐቅመ ፡ መዋዕል ። አልቦ ፡ ዐቅም ፡ ለመለኮትከ ፡ (ቅዳ ፡ ኤጲ ። ቀሌ ። ኩፋ ፡ ፯ ። አርጋ ፡ ፪) ።

**ተዐቀመ** ፤ ተወሰነ ፤ ተገታ ። ኢይትዔቀም ፡ ባሕረ ፡ ጸጋኪ ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፳፩) ።

**ዕቁም** ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ቅምት) ፤ የተወሰነ ፤ የተቈረጠ ፤ የተለየ ፡ የተመረጠ ፤ የተመደበ ፤ የተዘጋጀ ። ዘሎ ፡ ሥሩዐ ፡ ወዕቁመ ፡ ወውሱነ ፡ ግብሩ ። በሥምረት ፡ ዕቁም ። ሕዝብ ፡ ዘዕቁም ፡ እምዘሎሙ ፡ እለ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ሀሎ ፡ ዕረፍት ፡ ኀበ ፡ ይበውኡ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥሩዕ ፡ ወዕቁም ። ዕቁም ፡ በዘሎ ፡ ምግባር ፡ ከመ ፡ የኀሊ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፵ ። ኪዳ ። ኩፋ ፡ ፲፱ ። አፈ ፡ ድኅ ። ዘፀ፴፰ ፡ ፫) ።

**ዕቃሜ** ፤ ውሳኔ ፤ ሥርዐት ፤ ጠፍታ ፤ ክትነት ። ሥርዐተ ፡ አኀው ፡ ወዕቃሜ ። ዕቃሜ ፡ እለ ፡ ይትለአኩ ፡ (ሥር ፡ ጳኰ ። ፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፳) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ መኀማድ ፡ ይባል ፤ ምቅዋም ፡ ቁመት ፡ ማለት ፡ ነው ። በዕቃሜ ፡ ፈንታ ፡ ዕቅሞት ፡ ይባል ፡ አያሰኝም ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**ዐቀኀን** ፤ **ኖት** ፤ (**ዐቈነ** ፡ **የዐቀኀን** ፡ **ይዕቀኀን** ። **ዐረ** ፡ **ሐቀነ** ፤ **ዐጀነ**) ፤ ማርጋት ፤ መግፋት ፡ መናጥ ፤ ቅቤ ፡ ማውጣት ፤ ማቡካት ፡ ማምጠጥ ፡ የወተት ፡ ያይብ ።

**ዕቋን** ፤ ለጋ ፡ ቅቤ ፤ አንቋሊት ፤ ርጎ ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፰ ። ምሳ፳ ፡ ፳፰) ። አዘዘ ፡ ከመ ፡ ያስትዮሙ ፡ ሐሊበ ፡ ወመዓረ ፡ ወዕቋነ ፡ እስከ ፡ ለምለመ ፡ ጕርዔሆሙ ፡ ወአማዑቶሙ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ዐቂፍ** ፤ **ፎት** ፤ (**ዐቀፈ** ፡ **የዐቅፍ** ፡ **ይዕቅፍ** ። **ዐረ** ፡ **ዐቀፈ** ፤ **አጐበጠ**) ፤ ማንቀፍ ፤ ዕንቅፋት ፡ መኾን ፤ ማሰናከል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዐቀፈ ፡ ፈንታ ፡ አዕቀፈ ፡ ተዓቀፈ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ኢያዐቅፈከ ፡ እብነ ፡ ዕቅፍት ። አዕቀፈኒ ፡ ሰይጣን ። ከመ ፡ ኢያዕቅፍ ፡ ትምህርቶ ፡ ለክርስቶስ ። ዝኑ ፡ ያዐቅፈክሙ ። ተንሥአ ፡ መልአክ ፡ ይትዓቀፎ ፤ ወፃእኩ ፡ እትዓቀፍከ ፡ (ኢሳ፰ ፡ ፲፬ ። ሽተ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ። ገላ፭ ፡ ፯ ። ዮሐ፮ ፡ ፷፩ ። ዘኁ፳፪ ፡ ፳፪ና ፡ ፴) ።

**ዐቃፊ** ፤ (**ፊት** ፡ **ፍያን** ፡ **ያት**) ፤ የሚያንቅፍ ፤ ዐንቃፊ ፤ አሰናካይ ።

**አዕቀፈ** ፤ አስነቀፈ ፤ ዐንቀፈ ፡ አሰናከለ ፤ ዕንቅፋት ፡ አኖረ ።

**ማዕቀፍ** ፤ (**ቅፍ** ፤ **ቅፍት**) ፤ ዕንቅፋት ፤ መሰናክል ፤ ጠጥመድ ። ሲያበዛ ፡ መዓቅፍ ፡ ይላል ። ፍኖት ፡ መጽያሕት ፡ ዘእንበለ ፡ ማዕቀፍ ። እስመ ፡ ማዕቀፍየ ፡ ሊተ ። ወእማዕቀፎሙ ። ያመጽኡ ፡ ማዕቅፍተ ፡ (ቅዳ ፡ ኤጲ ። ማቴ፲፰ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፸፱ ። ኢሳ፷፪ ፡ ፳፩) ።

**ተዐቅፈ** ፤ ተነቀፈ ፤ ዕንቅፋት ፡ መታው ፤ አገኘው ፤ ተሰናከለ ። ዘእንበለ ፡ ይትዐቀፉ ፡ እገሪክሙ ። ከመ ፡ ኢትትዐቀፍ ፡ በእብን ፡ እግርከ ። ያትዐቀፉ ፡ ደቂቅ ፡ በልሂቅ ። ኢይትዐቀፍ ፡ በኀጢአት ፡ (ኤር፲፫ ፡ ፲፮ ። መዝ ፡ ፺ ። ኢሳ፫ ፡ ፭ ። ሢራ፳፫ ፡ ፲፪) ።

**ዕቁፍ** ፤ (**ፉን** ፡ **ፉት** ፡ **ቅፍት**) ፤ የተነቀፈ ፤ የተሰናከለ ፤ ዕንቅፋት ፡ ያገኘው ፤ ወራዳ ። ንከውን ፡ ዕቁፋነ ፡ ወዕዩራነ ፡ በቅድመ ፡ እለ ፡ ያጠርዩነ ፡ (ዮዲ፰ ፡ ፳፪) ።

**ዕቅፍት** ፤ (**ታት**) ፤ ዕንቅፋት ፤ መሰናክል ፤ ወጥመድ ፤ እክል ። ኢትደይ ፡ ዕቅፍተ ፡ ቅድመ ፡ ዕዉር ። የዐቅበከ ፡ እምዕቅፍት ። እብነ ፡ ዕቅፍት ። ትከውኖ ፡ ዕቅፍተ ፡ (ዘሌ፲፱ ፡ ፲፬ ። ሚራ፴፭ ፡ ፲፱ ። ኢሳ፰ ፡ ፲፬ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፰) ።

**ተዓቀፈ** ፤ ተነቃቀፈ ፤ ተሰነካከለ ። ኢትትዓቀፉ ፡ በትሕዝብት ፡ (ገድ ፡ ዮሐ ፡ ከማ) ።

**ዐቂጽ** ፤ **ጾት** ፤ (**ዐቀጸ** ፡ **የዐቅጽ** ፡ **ይዕቅጽ** ። **ዐቀደ** ፤ **ዐቀፈ**) ፤ መሰንከል ፤ መሸንከፍ ፤ እግርን ፡ መያዝ ፤ ማሰር ፡ መጥለፍ ፤ መዘርጠጥ ፤ ማንቀፍ ። ዐቂጾ ፡ ዐቀጽከኒ ፡ ወለትየ ። ሰይጣን ፡ ይዔቅጽ ፡ በስዉር ፡ (መሳ፲፩ ፡ ፴፭ ። ሬልክ ፡ ፲) ። በዐቀጸ ፡ ፈንታ ፡ አዕቀጸ ፡ ይባላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። አዕቀጸ ፡ ለይሥሐቅ ። ዘሎ ፡ እኁ ፡ አዕቅጾ ፡ ያዐቅጽ ። አዕቅጾትሙ ፡ እምፍኖተ ፡ ጽድቅ ። በውስተ ፡ ከርሥ ፡ አዕቀጾ ፡ ለእኁሁ ፡ (ዘፍ፳፯ ፡ ፴፮ ። ኤር፱ ፡ ፬ ። ኩፋ ፡ ፳ ። ሆሴ፲፪ ፡ ፫) ።

**አዕቀጸ** ፤ አሰነከለ ፤ አባሰረ ፤ አስቀየደ ።

**ተዐቅጸ** ፤ ተሰነ(ና)ከለ ፣ እግሩ ፣ ታሰረ ፣ ተቀየደ ። ኵሉ ፣ ንቅሃነ ፤ ወኢትትዐቀጹ ፤ በምንትኒ ። እሙንቱሰ ፣ ተዐቅጹ ፣ ወወድቁ ፣ (ዮሴፍ ። መዝ ፣ ፲፱) ።

**ዕቅጸት** ፤ መሰንከል ፤ መሰናከል ፤ ሰንከላ ። ዕቅጸቶሙ ፣ ለረሲዓን ፣ (ምሳ፲፭ ፣ ፪) ።

**ዐቃቂር ፤—ቅመሞች ፤—ዐቃር ።**

**ዐቀ[ረ] ፤ ሮት ፤ (ዐቄረ ፣ የዐቀረ ፣ ይዕቀር ። ዕብ ፣ ዐቃር ፤ ነቀለ)** ፤ ማቄር ፣ መቋጠር ፤ ማናር ፣ መኰተት ፤ መሸኰጥ ፤ መታቀፍ ። የዐቀሮ ፣ ለማይ ፣ በደመናሁ ። ወአሰርዎ ፣ ዐቀሮሙ ፣ ዘሎ ፣ ወርቀ ። መኑ ፣ የዐቍር ፣ እሳተ ፣ ውስተ ፣ ሕፅኑ ፣ (ኢዮ፳፮ ፣ ፰ ። ፱ነገ ፣ ፲፪ ፣ ፲ ። ምሳ፳ ፣ ፳፯) ።

**ተዐቍረ** ፤ ታቄረ ፤ ተቋጠረ ፤ ተፀነሰ ፤ ተወሰነ ። ፈጠርከ ፣ በንስቲት ፤ ነጠብጣብ ፤ ዘርዕ ፤ ዘይትዐቄር ፣ ውስተ ፣ ማሕፀን ። ዐእንተ ፣ ተዐቍሮ ፣ ዘርዕ ፣ በማሕፀና ። ተፀንሰ ፣ በከርሥ ፣ እንዘ ፣ ኢይትዐቄር ፣ (ዲድ ፣ ፴፯ ። አፈ ፣ ድ፳፫ ። ቅዳ ፣ ዮሐ) ።

**ዕቁር ፤ (ራን ፣ ራት ፣ ቍርት)** ፤ የታቄረ ፤ የተቋጠረ ፤ ቍጥር ። ዕቁር ፣ በአልባሲሆሙ ፣ (ዘፀ፲፪ ፣ ፴፬) ።


**ዕቍር ፤ (ብ ፣ ዕቄር)** ፤ ቋጠሮ ፤ ቍጥራት ፤ የዐጽቅ ፣ ያበባ ፣ ኾብ ፤ ማቄሪያ ፤ መቋጠሪያ ፤ ጨርት ፤ ከረጢት ፤ ማድጋ ። ዕቍረ ፣ ማየ ፣ ልብን ። ዕቍረ ፣ ወርቅ ። ዕቍር ፣ ስቁር ። ወርቀሙ ፣ በዕቂሪሆሙ ፣ (ማሕ፩ ፣ ፲፪ ። ድጓ ። ምሳ፯ ፣ ፳ ። ዘፍ፵፪ ፣ ፳፯ና ፣ ፴፭ ። ሐጌ፩ ፣ ፯ ። ኩፋ ፣ ፵፬) ።

**ዐቃር ፤ (ሱር ፣ ዐቃራ ። ዐረ ፣ ዐቃር)** ፤ ቅመም ፤ ጥርቅም ፤ የሽቱ ፤ የመድኀኒት ፤ የሌላውም ፤ ኹሉ ።

**ዐቃቂር** ፤ በቁሙ ፤ ቅመሞች ፤ ጥርቅሞች ፤ ባንድነት ፣ የሚጣፈጡ ። ዐቃቂረ ፣ ፈውስ ። በከመ ፣ ይትፈ[..] ፣ በውስተ ፣ ፈውስ ፣ ብዙኅ ፣ ዐቃቂር ፣ ሁናያት ፤ ወአሐዱ ፣ እምኔሆሙ ፣ ይኄይል ፣ ለገቢረ ፣ ፈውስ ፣ (ፈ ፣ መ ፣ ፳ ፣ ፱ ። ኦፈ ፣ ተ፱) ። ወመጽኡ ፣ ገባርያነ ፣ ዐቂቃር ፣ ወአምጽኡ ፣ መክሊተ ፣ ዐረር ፣ ወገነዐ ፣ ዐቢየ ፣ ዘብርት ፣ ወሰብዐተ ፣ ልጥረ ፣ ቅብዕ ፣ ዘሰሊጥ ፣ ወደመኑ ፣ ውስቴቱ ፣ ሥብሐ ፣ ወመዓረ ፣ ግራ ፣ ወቅብዐ ፣ ሊሑም ፣ ወዐቃቂረ ፣ ብዙኀ ፣ ዘያነድዶ ፣ ለሳህበ ፣ እሳት ፣ ዘምስለ ፣ ቃር ፣ ወፒሳ ፣ ወተይ ፣ ወቅጥራን ፣ ወሰብዐተ ፣ ልጥረ ፣ እምነ ፣ ቀልፎንያ ፣ ወልካ ፣ ወቀሰ ያሮቤዳ ፣ ወሰጣጽዮን ፣ ወዕፀወ ፣ ብዙኅ ፤ ወአምጽኡ ፣ ዐቃቂረ ፣ ዘአብሰልዎ ፣ ወአምሀውዎ ፣ ውስተ ፣ ግንዕ ፣ (ሰንክ ፣ ሐምሌና ፣ ፲፱) ።

**ዐቅራብ ፤—እንቧዮች ፤—ቀረብ ፤ አቅራብ ።**

**ዐቅራብ ፤ (ዕብ ፣ ዐቅራብ ። ሱር ፣ ዓቅርባ ። ዐረ ፣ ዐቅረብ)** ፤ ጊንጥ ፤ መርዛም ፤ ኸራታም ፤ ክፉ ፤ በኸራቱ ፣ ማፍ ፣ የሚነድፍ ፤ መርዙ ፣ የሚማቅይ ። ዘይፀብጥ ፣ ዐቅራብ ። ዐቅራብ ፣ ሶበ ፣ ይነድፍ ፣ ሰብአ ፤ ዘነበ ፣ ዐቅራብ ። ዐቅራቢሁ ፣ ይሁብ ፣ (ሚ ራ፳፯ ፣ ፯ ። ራእ፱ ፣ ፭ና ፣ ፲ ። ሉቃ፲፩ ፣ ፲፪) ።



ዐቅራብ ።

—፤ እሾኽም ፣ ዕንጨት ፣ እንዳጣጥ ፣ እንደ ፣ ዝንኪላ ፣ ያለ ፤ በወጋ ፣ ጊዜ ፣ እንደ ፣ ጊንጥ ፣ መርዝ ፣ የሚያሳምም ።

**ዐቃርብት** ፤ ጊንጦች ፤ እሾኾች ። ወሀብኩ ፣ ሥልጣነ ፣ ከመ ፣ ንኪድ ፣ ከይሴ ፣ ወዐቃርብተ ። ማእከለ ፣ ዐቃርብት ፣ ትነብር ። እቀሥፈክሙ ፣ በዐቃርብት ፣ (ቅዳ ። ሕዝ፪ ፣ ፯ ። ፫ነገ ፣ ፲፪ ፣ ፲፬) ።

**ዐቅረብ ፤ (ዐረ ፣ አልዐቅረብ)** ፤ ኮከብ ፤ የኮከብ ፣ ስም ፤ መልኩ ፣ ጊንጥ ፣ የሚመስል ። ኮከብንቱም ፣ የጥቅምት ፣ ነው ፤ ከፀሐይ ፣ ጋራ ፣ ፳፱ ፤ ዕለት ፣ ፵ ፣ ኩክርስ ፣ ይመግባል ፣ (አቡሻ) ።

**ዔር ፤—ጠባቂ ፣ መልአክ ፤—ዐየረ ።**

**ዐሪብ ፤ በት ፤ (ዐርበ ፣ የዐርብ ፣ ይዕርብ ። ዕብ ፣ ወሱር ፣ ዐራብ ። ዐረ ፣ ዐረበ)** ፤ መምሸት ፤ ሠርክ ፤ መኾን ፤ መውረድ ፣ መዘቅዘቅ ፤ መግባት ፣ መጥለቅ ፤ የፀሐይ ። እስከ ፣ የዐርብ ፣ ፀሓይ ፤ ወሶበ ፣ ዐርበ ፣ ፀሓይ ። ዘእንበለ ፣ ይዕርብ ፣ ፀሓይ ፣ (ጦቢ፪ ፣ ፬ና ፣ ፯ ። ኤፌ፬ ፣ ፳፯) ።

—፤ መንገድ ፤ መሄጥ ፣ መለወጥ ፤ መተካት ፤ ሸቀጥን ፣ ከገር ፣ ወዳገር ፣ ማውጣት ፣ ማግባት ፤ መውሰድ ፣ ማምጣት ።

**ዕርበት** ፤ ምሽት ፤ የፀሓይ ፣ ግባት ። እስከ ፣ ዕርበተ ፣ ፀሓይ ፣ (ዘፀ፲፯ ፣ ፲፪) ።

**አዕረበ** ፤ አስመሸ ፤ ፀሐይ ፣ አገባ ። ኢታዕርብ ፣ ፀሓየ ፣ በበንበት ፣ እንዘ ፣ ትጸውም ፣ (ሲኖዶ) ።

**ዐረብ** ፤ ምዕራብ ፣ ዐቢይ ፣ ማእዝን ፤ የምሥራቅ ፣ ትይዩና ፣ አንጻር ፤ የፀሓይ ፣ መግቢያ ፣ መጥለቂያ ፤ መዘቅዘቂያ ። እምሥራቀ ፣ ፀሓይ ፣ እስከነ ፣ ዐረብ ፣ (መዝ ፣ ፵፱ና ፣ ፻፲፪ ። ኢሳ፵፫ ፣ ፭ ። ማቴ፳፱ ፣ ፳፯) ።

**ምዕራብ ፤ (ዕብ ፣ ማዐራብ)** ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፣ በቁሙ ። ፀሓይኒ ፣ አእመረ ፣ ምዕራቢሁ ። ምዕራብ ፣ ፀሓይ ። ኮከበ ፣ ምዕራብ ፣ (መዝ ፣ ፻፫ ። ኢሳ፱ ፣ ፲፪ ። ስንክ ፣ የካ፱) ።

**ዐረብ ፤ (ዕብ ፣ ዐራብ)** ፤ ሜዳ ፣ ምድረ ፣ በዳ ፤ ማር ፣ ዕንጨት ፣ የሌለው ፤ የዮርዳኖስ ፣ ማያ ፣ ወረዳ ፤ ከጥብርያዶስ ፣ እስከ ፣ ባሕረ ፣ ጨው ፣ ያለ ፣ በረሓ ። መንግለ ፣ ዐረብ ፣ ለሞአብ ፣ (ዘኁ፳፪ ፣ ፩ ። ዘዳ፩ ፣ ፩ ። ኢያ፩ ፣ ፲ ። ዮዲ፩ ፣ ፳) ።

**ዐረብ** ፤ (ዕብ ፡ ዔሬብ) ፤ ሠርክ ፤ ምሴት ፤ ማታ ፤ ድግዘታ ፤ ጭልምልምታ ፤ የመዓልት ፡ መጨረሻ ፤ የሌሊት ፡ ሥር ፡ መገመሪያ ፤ ሰው ፡ እስኪከተት ፡ ኸሮብ ፡ እስኪያኩተሆት ፡ ያለው ፡ ጊዜ ። ትጕሳተ ፡ ዐረብ ፡ እስ ፡ ኢያበይቱ ፡ ለነግህ ፡ (ዕሮ፫ ፡ ፫ ። ዕን፭ ፡ ፵ ። ስንክ ፡ ታኅ፳፱) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ዝኤቢይ ፡ ዔሬብ ፡ ይላል ፤ የማታ ፡ ኸሮቦች ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ዐርብ** ፤ (ዕብ ፡ ዐሮቤት ። ሱር ፡ ዐሩብታ) ፤ ስመ ፡ ዕለት ፡ ስድስተኛ ፡ ቀን ፤ በኅሙስና ፡ በቀዳም ፡ መካከል ፡ ያለ ። የፍጥረት ፡ የሥራ ፡ የመና ፡ ፍጻሜ ፤ መካተቻ ፤ ድራረ ፡ ለንበት ፤ ዋዜማ ፡ ቅበላ ፡ ማለት ፡ ነው ። ወከነ ፡ ሳድስተ ፡ ዕለተ ። እመ ፡ ዕለተ ፡ ዐርብ ። ወበሳኒታ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ እምድኅረ ፡ ዐርብ ። ዕለተ ፡ ዐርብሰ ፡ ወሰንበት ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፴፩ ። ዘፀ ፲፮ ፡ ፳፭ ፡ ፳፱ ። ማቴ፳፯ ፡ ፷፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፩) ።

**ዐረብ** ፤ ስመ ፡ ነገድ ፤ የነገድና ፡ የቋንቋ ፡ ስም ። ብሔረ ፡ ዐረብ ። ተተርጕመ ፡ እምልሳነ ፡ ቅብጢ ፡ ለዐረብ ፡ (ገላ፩ ፡ ፳፰ ። ሃይ ፡ አበ፭) ።

**ዐረቢ** ፤ ዐረብኛ ፤ የዐረብ ፡ ቋንቋ ፤ የግእዝና ፡ የዕብራይስጥ ፡ የሱርስት ፡ ወንድም ። ወእምዐረቢ ፡ ለግእዝ ። ልሳነ ፡ ቅብጢ ፡ ወዐረቢ ፡ (ሃይ ፡ አበ ። ስንክ ፡ መስ፱ ። ታኅ፳፱) ።

**ዐረባዊ** ፤ የዐረብ ፡ ወገን ። መጽሐ ፡ ዐረባውያን ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፱) ።

—፤ ምዕራባዊ ፤ ዘምዕራብ ። ነፋስ ፡ ዐረባዊ ፡ (ሚራ፴፫ ፡ ፲፯ ። ራእ፳፭ ፡ ፲፫) ።

**ዐረቦን** ፤ (ዕብ ፡ ዔራቦን) ፤ በቁሙ ፤ መያዣ ፤ ፈለማ ፤ መገመሪያ ፤ የስጦታ ፡ ድራር ፡ የጸጋ ፡ ዋዜማ ፤ ክብዙውና ፡ ከፍጹሙ ፡ ከታላቁ ፡ ዋጋ ፡ በፊት ፡ የሚሰጡት ፡ የሚቀበሉት ። ወሀበነ ፡ ዐረቦነ ፡ መንፈስ ። ዘውእቱ ፡ ዐረቦነ ፡ ርስትነ ። ዐረቦን ፡ ዘፍኅረት ፡ (፪ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፪ ። ፭ ፡ ፭ ። ኤፌ፩ ፡ ፲፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፫ ። ፵፫) ።

**ማዕረብት** ፤ (ዕብ ፡ ማዐራብ) ፤ መናገሻ ፤ ገበያ ፤ መደብር ። የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ሸቀጥ ። ኦጋድያን ፡ ሠየጥ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ማዕረብት ፡ ይላል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ። ተርሴስ ፡ እሙንቱ ፡ ማዕረብትኪ ። አራም ፡ ማዕረብትኪ ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፲፪ና ፡ ፲፮) ።

**ዐራቦት** ፤ (ጽርእ ። ዕብ ፡ ዐራብ) ፤ ሜዳ ፤ በረሓ ። ዐረብን ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ወፅኡ ፡ እንተ ፡ ዐራቦት ፡ (፬ነገ ፡ ፱ና ፡ ፭) ።

**ዐርቦት** ፤ (ዕብራ) ፤ ኩሓ ፡ ቺባሓ ፤ ወንዝ ፡ አድምቶ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ቄዳር ፡ ዘስሙ ፡ ዐርቦት ፡ (ኩፋ ፡ ፳፭) ።

**ዐሪግ** ፤ ኀት ፤ (ዐርገ ፡ የዐርግ ፡ ይዕርግ ። ዕብ ፡ ዐራግ ፤ ፈተወ) ፤ ማረግ ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ማለት ፤ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ መውጣት ። ለዐለን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ነው ። ርቱዐ ፡ የዐርግ ፡ እምነ ፡ ምድር ። ዐርገ ፡ ናሕስ ። ዐርገ ፡ ደብረ ። ዐርገ ፡ ሰማየ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፲፬ ። ግብ፲ ፡ ፱ ። ሉቃ፱ ፡ ፳፰ ። ፳፬ ፡ ፶፩) ።

—፤ መንቃት ፡ መነግሣት ፡ መታሰብ ፤ መውጣት ፡ መውረድ ፤ መብቀል ፤ የኅሊና ፡ የዐጽቅ ። ውስተ ፡ ልበ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢተኀለየ ፡ ወኢዐርገ ። ዐርገ ፡ ደቢ ፡ ኅሊናሁ ፡ ከመ ፡ ይግበር ። ለምንት ፡ ዘከመ ፡ ዝ ፡ ኅሊና ፡ የዐርግ ፡ ውስተ ፡ ልብክሙ ። ትወፅእ ፡ በትር ፡ እምሥርወ ፡ እሴይ ፡ ወየዐርግ ፡ ዐጽቅ ፡ እምጕንዱ ፡ (መስተ ። ፪ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፱ ። ሉቃ፳፬ ፡ ፴፰ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፩) ።

—፤ በመጽሐፍ ፡ በልብ ፡ መጣፍ ፤ መቈጠር ፤ ከቍጥር ፡ መግባት ፤ የክፉ ፡ የበጎ ። ኢየዐርግ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕይወት ። ወኀጢአተ ፡ ተዐርግ ፡ በእንቲአሁ ፡ ውስተ ፡ መጻሕፍት ፡ (ኩፋ ፡ ፴፯ና ፡ ፴፱) ።

**ዐራጊ** ፤ የሚያርግ ፤ የሚወጣ ። ኤልያስ ፡ ዐራጊ ፡ ሰማያተ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፭) ።

**ዕሩግ** ፤ ያረገ ፤ ልዑል ፤ ሥሙር ፡ ውኩፍ ። ወይኩን ፡ ለሕልነ ፡ ዕሩገ ፡ ወፈውስ ፡ (ሥር ፡ ቅዳ) ።

**ዕርገት** ፤ ማረግ ፤ መውጣት ፤ አወጣጥ ። ወትፈጸም ፡ መዋዕለ ፡ ዕርገቱ ። ዕርገቱ ፡ ለኢየሱስ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ። ዐርገ ፡ ከመ ፡ ያለሉ ፡ ዕርገተ ፡ ጻድቃን ፡ (ሉቃ፱ ፡ ፶፩ ። ቀሌ ። መቅ ፡ ወን) ።

—፤ በቁሙ ፤ ዐቢይ ፡ በዓል ፤ የትንሣኤ ፡ አርባ ፤ ኀሙስ ፡ ቀን ፡ የሚውል ፤ ዐቃቦች ፡ የሚዘክሩት ። (ተረት) ፤ ባመት ፡ እንደርገት ። ዋዜማ ፡ ዘዕርገት ። ወዕርገቱ ፡ የዐም ፡ ሰማያቲ ፡ (ድጓ) ።



ዕርገት ፡

—፤ መጽሐፍ ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ የብሉይ ፡ አዋልድ ፤ ኢሳይያስ ፡ ስለ ፡ ሥጋው ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ሔኖክ ፡ በተመሥጦ ፡ ያየው ፡ ጕልሕ ፡ ራእይ ፤ ደረቅ ፡ ትንቢት ። ዕርገተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ (ገድ ፡ ፭) ።

**ዕርገተ ፡ ዕጣን** ፤ ማዕጠንትን ፡ በመሥዋዕቱ ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ማዞር ፤ ኹለተኛም ፡ ጢሱን ፡ ታናሹ ፡ መሥዋዕቱን ፡ በእጅ ፡ ማጠን ። ይንሣእ ፡ ካህን ፡ ማዕጠንተ ፡ ወያዑድ ፡ ደቢ ፡ ርእሰ ፡ ምሥዋዕ ። ሰዝየ ፡ ዕርገተ ፡ ዕጣን ፤ ወይዕጥን ፡ በእዴሁ ፡ (ቅዳ) ።

**ዕርገተ ፡ ቍርባን ፤** ቍርባንን ፡ ተቀብሎ ፡ መ ቅጠት ፤ ማቀበል ። ወኢይባእ ፡ አሐዱሂ ፡ እምቤተ ፡ ክር ፡ ዘእንበለ ፡ በግብር ፡ ዕጹብ ፤ እምድኅረ ፡ ተነበ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፤ ዘእንበለ ፡ ይትፈጸም ፡ ዕርገተ ፡ ቍርባን ፡ ወበረከተ ፡ ካህን ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፲፪) ። ይህም ፡ ዕርገት ፡ ተቀባዮቹን ፡ በማያት ፡ ያሰኛል ፤ ምስጢሩ ፡ ያው ፡ ነው ።

**አዕረገ ፤** አሳረገ ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ አወጣ ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ። አይቴ ፡ ታዐርገኒ ። አዕረጎሙ ፡ ደብረ ፡ ነዋኀ ። አዕረግዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ውስተ ፡ ሐመር ። ወሰበ ፡ መልእክት ፡ አዕረግዋ ፡ ውስተ ፡ ሐይቅ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ ። ማር ፲ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ኅዳር ፳፰ ። ማቴ ፲፫ ፡ ፵፰) ።

—፤ አቀረበ ፤ ሰጠ ፤ አበረከተ ፤ የመሥዋዕት ፡ የጸሎት ፡ የምስጋና ። አዕረጎ ፡ ለይሥሐቅ ፡ ወልዱ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ። እለ ፡ ያዐርጉ ፡ ጸሎቶሙ ፡ ለቅዱሳን ። ኪያከ ፡ ይሴብሑ ፤ ወለከ ፡ ያዐርጉ ፡ ስብሐተ ፡ (ያዕ ፪ ፡ ፳፩ ። ወቢ ፲፪ ፡ ፲፭ ። መዋሥ) ።

**ማዕርግ ፤ መዓርግ ፤ (ጋት) ፤** ማረጊያ ፤ መ ውጫ ፡ መረጋገጫ ፤ መሰላል ፡ ዕርከን ፤ ደረጃ ፤ እንደ ፡ ጣት ፡ መቀዳደምና ፡ መከታተል ፡ መበላለጥ ፡ ያለው ፤ ው ስጡ ፡ ብዙ ፤ ሥራው ፡ የመሥመር ፡ በይነት ፤ ርስ ፡ በርሱ ፡ የተያያዘ ፤ ደረጃን ፡ ተመልከት ። ማዕርግ ፡ ትክልት ፡ ው ስተ ፡ ምድር ። መዓርግ ፡ ዘይወርድ ፡ እምሀገረ ፡ ዳዊት ። መዓርገ ፡ ምሥዋዕ ። ዐሠርቱ ፡ መዓርጋት ፡ (ኩፋ ፡ ፳፯ ። ነሐ ፫ ፡ ፲፭ ። ሚራ ፵ ፡ ፲፩ ። ፱ነገ ፡ ፳ ፡ ፱—፲፩) ። ሰበሓይና ፡ ሰጨረቃም ፡ መንገድ ፡ ይነገራል ። ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ወስሳ ፡ መዓርጋት ፤ ሰአሐቲ ፡ ዮኅት ፡ ሠላሳ ፡ መዓርግ ፡ ዕኑያን ፤ (አቡሻ ፡ ፬) ። በመድረክ ፡ ፈንታ ፡ ማዕርግ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ማዕርገ ፡ ዳጎን ፡ (፩ ነገ ፡ ፭ ፡ ፭) ።

—፤ በቁሙ ፡ ሹመት ፤ ክብር ፡ ሥልጣን ፡ ከዲያቆን ፡ እ ስከ ፡ ጳጳስ ፤ ከአናጕንስጢስ ፡ እስከ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ያለ ። ወተጋብኡ ፡ ለህርቃኖስ ፡ መዓርገ ፡ መንግሥት ፡ ወ መዓርገ ፡ ክህነት ። ይትመጦር ፡ እማዕርጊሁ ። አቡሊ ናርዮስ ፡ ተአመነ ፡ ከመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሐጽጽ ፡ እምአብ ፡ ወወልድ ፡ በማዕርገ ፡ እምላክና ፡ (ዮ ሴፍ ። ቀሌ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፭) ።

—፤ ክፍል ፡ ወገን ፡ ተራ ፡ ረድፍ ። ወካዕበ ፡ ሠርዐ ፡ ፍርዳዮ ፡ በሕዝቡ ፡ ውስተ ፡ ሠለስቱ ፡ መዓር ጋት ። ሰፋይ ፡ በሠላሳ ፡ መዓርገ ፡ ስፍየት ፡ (ፊልክ ፡ ፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፭ ፡ ፩) ።

**ምዕራግ ፤ (ጋት) ፤** ዳገት ፡ ዐቀበት ፡ የቀራራ ፡ መንገድ ፤ ሽቅብ ፡ የሚወጡት ። ምዕራገ ፡ ሀገር ። እንተ ፡ ምዕራጋት ። እስመ ፡ አልቦ ፡ ምዕራግ ፡ ለኢይባሬ ሆሙ ፡ (፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፳ ። ፪ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፲፭ ። ዮዲ ፯ ፡ ፲) ።

—፤ ታላቅ ፡ መሰላል ፤ በእሥክት ፡ በላሎት ፡ እግር ፤ ብቻ ውን ፡ የሚቆም ። ፩ ፡ ምዕራግ ፡ እምድር ፡ እስከ ፡ ሰ ማይ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።



ምዕራግ ፡

**ዔረግ ፤—ወጥመድ ፤—ዐየረ ።**

**ዐርዝ ፤—ዛፍ ፤—አርዝ ።**

**ዐረዝ ፤ ዞት ፤ (ዐረዘ ፡ የዐርዝ ፡ ይዕ ርዝ ። አው ፤ ዐርዞ ፡ ይዔርዝ) ፤** ማልበስ ፤ ል ብስ ፡ መስጠት ። ይሴስዩ ፡ ወይዔርዞ ። ይዔርዙኒ ፡ አልባስየ ፡ ወመዋጥሕየ ። አውፅአ ፡ ሎሙ ፡ ዘይዔር ዞሙ ። አልባስ ፡ ወክዳናት ፡ ዘዐረዘቶን ፡ ዶርቃስ ፡ (ቀሌ ። ሆሴ ፪ ፡ ፯ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፳፪ ። ግብ ፱ ፡ ፴፱) ።

**ተዐረዘ ፤** ለበሰ ፤ ልብስ ፡ አገኘ ፤ ተቀበለ ። ል ብሰ ፡ ዚአነ ፡ ንትዔረዝ ። ሀበኒ ፡ ዘእለብስ ፡ ወእትዔ ረዝ ። ተዐሪዞ ፡ ሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ (ኢሳ ፬ ፡ ፩ ። ቀሌ ። አርጋ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ ሠኔ ፲፭) ።

(ጥ) **ዕሩዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ርዝት) ፤** የለበሰ ፤ ል ቡስ ። ሸሎሙ ፡ እሊአሃ ፡ ዕሩዛን ፡ እሙንቱ ፡ (ምሳ ፴፩ ፡ ፳፱ ። ዲድ ፡ ፪) ።

(ላ) **ዐራዝ ፤ (ዛት) ፤** ልብስ ፡ የውስጥ ፡ ቀሚስ ፤ ገላ ፡ ነክ ። ቢሳየነ ፡ ወዐራዘነ ። ተካፈሉ ፡ አልባስየ ፡ ወተዓፀዉ ፡ ዲበ ፡ ዐራዝየ ። አባ ፡ ሙሴ ፡ ረሰየ ፡ ቈ ጽለ ፡ ሆሳዕና ፡ ዐራዞ ። አልባስ ፡ ወዐራዛት ፡ (አጠ.ፋ ፡ ፮ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፳፩ ። ስንክ ፡ መስ ፪ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲ ፡ ፯) ።



ዐራዝ ፡

**ትዕርዝት ፤** ጥብቆ ፡ ቀሚስ ፤ የሚለበስ ፡ የሚ ቈለፍ ። እስመ ፡ ክነት ፡ ትዕርዝቱ ፡ ኅልቅተ ። ክነ ፡ ትዕ ርዝትሙ ፡ እምአምእስት ፡ አባግዕ ፡ (ፊልክ ፡ ፶፯ ፡ ፹፱) ።

**ዐረዘ ፤ (ዕብ ፡ ኤራዚ) ፤** በቁሙ ፡ ከባ ፡ ቀ ጠን ፡ መንመን ፤ ሰሰሰ ፡ አነሰ ፤ ኰሰሰ ፤ ማማ ። እንጀራ ፡ ዐርዟል ፡ ወጥ ፡ ዐርዟል ፡ ሰውዬ ፡ እንዲሉ ። ግስነቱ ፡ ያማርኛ ፡ እንጂ ፡ የግእዝ ፡ አይደለም ።

**ተዐርዘ ፤** ታረዘ ፡ ዕርዘተኛ ፡ ኾነ ፡ ተራቈተ ፤ ልብስ ፡ ምግብ ፡ ዐጣ ፡ ተቸገረ ።

**ዕርዝና ፤ (ዕብ ፡ ራዞን) ፤** ከሳት ፡ ቅጥነት ፤ ቀጠና ፡ ዕርዘታ ፡ ችጋር ፡ ስሶት ፡ ድኽነት ። (ተረት) ፤ በ ርግዝና ፡ ላይ ፡ ዕርዝና ።

**ዐረየ ፤—ለቀመ ፤—አርዩ ፡ አረየ ።**

**ዐርይ ፤ (ዐረየ ፡ ይዔሪ ፡ ይዕሪ)** ፤ ገቢርና ፡ ዐጕል ። መደልደል ፤ ማስተካከል ፤ ቀጥ ፡ ለጥ ፡ ማድረግ ። ጺሑ ፡ ፍኖት ፡ ወዐርዩ ፡ መጽያሕቶ ። ከመ ፡ ተዐርዩ ፡ ልበ ። ዐርዩ ፡ ግዕዘ ። እስመ ፡ ከነ ፡ ዐርዮ ፡ በማእከሎሙ ፡ (ኢሳ ፵ ፡ ፫ ። ፩ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፰ ። ሄርማ ። ኩፋ ፡ ፴፯) ።

—፤ መምሰል ፡ መተካከል ፤ ትክክል ፡ መኾን ። እስመ ፡ መልክአ ፡ ይዔሪ ፡ ለመልክኡ ፤ ወአርኣያ ፡ ለአርኣያሁ ። ይምሳእ ፡ ኵሉ ፡ ማዕምቀ ፡ ወይዕሪ ፡ ምድር ። ወይዕሪ ፡ ፍኖት ፡ መብእሰ ። እስከ ፡ ይልህቅ ፡ ወይዔሪ ፡ ጽሕምክሙ ። ይዔሪ ፡ መዓልት ፡ ወሌሊት ፡ ሕመ ፡ ዕሥራ ፡ ወኀምሙሱ ፡ ለመጋቢት ። ኵሉ ፡ ዐረየ ፡ ወኀቡረ ፡ ዐቢወ ፡ (ባሮ፳ ፡ ፯ ። ሉቃ፫ ፡ ፭ ። ፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፭ ። ዲድ ፡ ፴ ። መዝ ፡ ፲፫) ።

—፤ ማበር ፡ መተባበር ፤ መስማማት ፤ አንድ ፡ መኾን ። ተማከሩ ፡ ኅቡረ ፡ ወዐረዩ ። ኢይዔርዩ ፡ ለምክር ፡ ሠናይ ። ወምስለ ፡ ብሉይ ፡ ኢየዐሪ ፡ (መዝ ፡ ፹፪ ። ኪዳ ። ሉቃ፭ ፡ ፴፮) ።

**ዕሩይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሪት)** ፤ የተካከለ ፤ የተመሳሰለ ፤ ትክክል ፤ አንድ ፡ ዐይነት ። ለአመረ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዕሩይ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ አርድእት ። ዘዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ። መፍትው ፡ ለነ ፡ ንመጽውት ፡ ባዕለ ፡ ኵሉ ፡ በዕሩይ ፡ እንዘ ፡ ኢንሌሊ ፡ ጽኑሳነ ። ዕሩየ ፡ ተጸልኡ ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡ ረቢዕኒ ፡ ወርስዓኑ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ቅዳ ። እፈ ፡ ተ፲ ። ጥበ፲፱ ፡ ፱) ።

**ዕርየት** ፤ መተካከል ፤ እኩያ ፡ አምሳያ ፡ መኾን ። ኢይከውን ፡ ድልወ ፡ ዕርየት ፡ ምስለ ፡ ባሕታውያን ፡ (ፊልክ ፡ ፫) ።

**ዕራይ** ፤ እኩያ ፤ መሰል ፤ አምሳያ ። ወከመ ፡ ዕራይሁ ፡ ለቀዳማይ ፡ ነገር ፡ ንሌብዎ ፡ ለዝንቱኒ ፡ (ቄር) ።

**ዕሪና** ፤ መተካከል ፤ አንድነት ፤ ትክክልንት ፤ አለመበላለጥ ። ዘኢየአምን ፡ በአካላተ ፡ ሥሉስ ፤ አው ፡ ዘኢየአምን ፡ ዕሪናሆሙ ፡ በባሕርይ ፡ ወበአምላክና ። ሕዘዘ ፡ አክብሮቶሙ ፡ በዕሪና ። እፎ ፡ ትከውን ፡ ክብር ፡ በዕሪና ። ለይረሉ ፡ በዕሪና ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፯ ። ዮቤና ። እፈ ፡ ድ፴፫ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፱ ፡ ፱) ።

**ትዕሪና** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ትዕሪና ፡ ዕበያት ፡ (አቡሻ ፡ ፴፯) ።

**ትዕሪን** ፤ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ የወርቅ ፡ የብር ፡ መማሪያ ፡ ሥራው ፡ ከምሳሌው ፡ የተካከለ ። ኪራስን ፡ እይ ።

**አዕረየ ፤ አዐረየ ፤ አዔረየ ፤ (ዐረየ ፤ ግቢር)** ፤ አሳከለ ፤ አስመሰለ ፤ ወይም ፡ አስተካከለ ፤ አመሳሰለ ፤ ኹሉም ፡ አድራጊ ፡ ነው ። አዔረየ ፡ እንደ ፡ አማኄረየ ፡ በጸያፍ ፡ ገብቷል ፤ አያስኝም ። ይዔሪ ፡ ርእሶ ፡ ምስለ ፡ እግዚ ። ጳውሎስ ፡ አዔረየ ፡ ርእሶ ፡ ምስለ ፡ ሐዋርያት ። አዔረየ ፡ ምስለ ፡ አቡሁ ፡ (ዮሐ፭ ፡ ፲፰ ። እፈ ፡ ድ፴ ። ፪) ።

**አስተዐረየ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። አስተዐረይ ከሙ ፡ ምስሌነ ። ያስተዔርዮ ፡ ለአብ ፡ በወልዱ ፡ (ማቴ፳ ፡ ፲፪ ። እፈ ፡ ድ፱) ።

**ተዐረየ ፤ (ዐረየ ፤ ተገብሮ)** ፤ ተካከለ ፡ ተመሳሰለ ። በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ይትዔረይ ፡ መዓልት ፡ ምስለ ፡ ሌሊት ። አልቦ ፡ ዘይትዔረዮ ፡ ለቅንአት ። ወኢይትዔረዮ ፡ ዕፀ ፡ ቄድርስስ ፡ (ሔኖ፸፪ ፡ ፳ ። ምሳ፳፯ ፡ ፬ ። ሕዝ፴፩ ፡ ፰) ። ኹለተኛም ፡ ታከለ ፤ ተመሰለ ፡ ሌላው ፡ እኩያው ፡ አከለው ፡ መሰለው ፡ ያሰኛል ፤ መተካከል ፡ የጋራ ፡ ነውና ።

**መዐርይ ፤ (ዕሩይ)** ፤ ትክክል ፤ እኩያ ፤ አምሳያ ። በኅሊናሰ ፡ ኮኑ ፡ መዐርያነ ። ዘይሜህር ፡ ዘእንበለ ፡ ይስአሎ ፤ መዐርይ ፡ ውእቱ ፡ ምስለ ፡ ዘይዜልፎ ። አንተ ፡ መሲሑ ፡ ወመዐርዩ ፡ ለእግዚ ፡ (ፊልክ ፡ ፳ ። ፪፻፳፱ ። ስንክ ፡ ታኅሣ፱) ።

**አማዕረየ ፤ (አዕረየ)** ፤ አስተካከለ ፡ አበጃጀ ፡ አዘጋጀ ። እወ ፡ እግዚአ ፡ ፍታሕ ፡ ወአግዕዝ ፤ ቀድስ ፡ ወአምዕዝ ፤ አንጽሕ ፡ ወአጽሪ ፤ አሠኒ ፡ ወአማዕሪ ፤ አሎንተ ፡ አግብርቲከ ፡ ወአእማቲከ ፡ (ግንዘ) ።

**ዖርያ ፤—ሠናይት ፤—አርያ ።**

**ዐሪክ ፤ ክት ፤ (ዐረከ ፡ የዐርክ ፡ ይዕርክ ። ዕብ ፡ ዐራኽ)** ፤ መስደር ፤ መደርደር ፤ ማንጣጠር ፤ በየምሳያውና ፡ በየኳያው ፡ ማኖር ፤ ፊት ፡ ለፊት ፤ ጐን ፡ ለጐን ፤ ወይም ፡ ላይና ፡ ታች ።

**ተዓረከ** ፤ ተወዳጀ ፤ ተዛመደ ፤ ተቀናጀ ፤ ተጣመደ ፤ ተባበረ ፡ ተመሳሰለ ፤ በመልክ ፡ በግብር ። እመ ፡ ትትዓረክ ፡ ዐርከ ፡ ተዓረክ ፡ በመዋዕለ ፡ ተጽናስከ ። ዘተዓረከ ፡ ለዕቡይ ፡ ይከውን ፡ ከማሁ ። በአይቴ ፡ ይትዓረክ ፡ መቅፀት ፡ ምስለ ፡ ጽህርት ፤ ተኵላ ፡ ምስለ ፡ በግዕ ፡ (ሢራ፮ ፡ ፯ ። ፲፫ ፡ ፩—፲ ፤ ፲፯) ።

**ዐርክ ፤ ዓርክ ፤ (ክት ፡ ክን ፡ ክት)** ፤ ወዳጅ ፤ ባለሟል ፤ ባልንጀራ ፤ ሀብሮ ፡ አደግ ፤ እኩያ ፡ አምሳያ ፤ ጓደኛ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤ ሎሌ ፡ ገረድ ፤ መንፈሳዊ ፡ ዘመድ ፤ የጡት ፡ ያደራ ፡ የክርስትና ፡ ልጅ ፤ አበ ፡ ልጅ ። አብርሃም ፡ ዐርከ ፡ እግዚ ። ዐርክ ፡ ምእመን ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘወድቀ ፡ ዐርክ ፡ ምስለ ፡ ዐርከቱ ። ዐርካነ ፡ እግዚእ ። ዐርካት ፡ ዘጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ (ኩፋ ፡ ፲፱ ። ሢራ፮ ፡ ፱ ። ቄድር ። ቅዳ ፡ ግሩ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳፱) ።

**አዕርክት** ፤ ወዳጆች ፤ ባልንጀሮች ። ብዙኃን ፡ ይኩኑከ ፡ አዕርክተ ። ጸላእትኒ ፡ አዕርክተ ፡ ይከውኑ ። ህየንተ ፡ አዕርክቲሁ ፡ (ሢራ፮ ፡ ፮ ። ምሳ፲፮ ፡ ፯ ። ዮሐ፲፭ ፡ ፲፫) ።

**አስተዓረከ** ፤ አወዳጀ ፤ አዛመደ ፤ አመሳሰለ ፤ አስተካከለ ። መኑ ፡ ያስተዓርኮ ፡ ለነዳይ ፡ ምስለ ፡ ባዕል ፡ (ሢራ፲፫ ፡ ፲፰) ።

**ዐርኬ** ፤ የስንክሳር ፡ መርገፍ ፤ ምስጠራ ፡ ያንኑ ፡ እናቱን ፡ የሚመስል ።

**ዐርሞን** ፤ የተክል ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፡ ኢሳጦን ፡

እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። አክዋሕ ፡ ዘዐርሞን ፡ (መቃ ፡ ገ፫ ። ድ፫) ።

**ዐሬሥ ፤ (ዐረ ፡ ዐሬሽ ። ዕብ ፡ ዐሬሥ) ፤** የወይን ፡ ዳስ ፡ የዳስ ፡ ዐይነት ፡ ድንኳን ። ወገብረ ፡ ባቲ ፡ ዐሬሠ ፡ ውስተ ፡ ናሕስ ፡ ቤት ፡ (የዳ.፰ ፡ ፳) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ጕገር ፡ ምግባል ፡ በታ ፤ የጸም ፡ በኣት ፡ ይሉታል ።

**ዐሬፍ ፤ ፎት ፤ (ዐረፈ ፡ የዐርፍ ፡ ይዕርፍ ። ዕብ ፡ ራፋህ ፤ ደከመ ፡ ዛለ ፡ ዐረፈ ። ዐረ ፡ ረፋ ፤ አሳረፈ) ፤** ማረፍ ፡ መተንፈስ ፤ ጸጥ ፡ ማለት ፤ አለመታወክ ፤ በታ ፡ ይዞ ፡ መቆም ፡ መቀመጥ ፤ መደገፍ ፡ መተኛት ፤ መሞት ፡ ማንቀላፋት ፡ ሀይእንኛ ፡ ንህየን ፡ ተመልከት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በዐረፈ ፡ ፈንታ ፡ አዕረፈ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። አዕረፈ ፡ እምዝሉ ፡ ግብሩ ። ከመ ፡ ያዕርፉ ፡ እምጻማሆሙ ። እነብብ ፡ ከመ ፡ አዕርፍ ። አዕረፈት ፡ ምድር ፡ እምነ ፡ ቀትል ። አዕረፈት ፡ ታቦት ፡ ዲበ ፡ ርእሰ ፡ ሉባር ። ኖሙ ፡ ወአዕርፉ ። ወአዕረፈ ፡ ምስለ ፡ አበዊሁ ። አንዊክሙ ፡ እስ ፡ አዕረፉ ፡ በሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፪ ። ራእ፲፬ ፡ ፲፫ ። ኢዮ፴፪ ፡ ፳ ። ኢያ፲፩ ፡ ፳፫ ። ኩፋ ፡ ፭ ። ማቴ፳፯ ፡ ፵፭ ። ሚራ፵፯ ፡ ፳፫ ። ዲድ ፡ ፴፬) ።

**ዕሩፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ርፍት) ፤** ያረፈ ፤ ጸጥ ፡ ያለ ፤ የረጋ ። ዕሩፈ ፡ ይነብር ። ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ልብየ ፡ ዕሩፈ ፡ በባዕሊክሙ ፡ (ኢሳ፴ ፡ ፱ ። ሄዜና ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፺፩) ።

**ዕረፍት ፤ (ታት) ፤** በቁሙ ፤ ማረፍ ፡ ዕርፈት ፤ ሞት ። መካነ ፡ ዕረፍት ። ንባእ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍቱ ። ሠሰስቱ ፡ ዕረፍታት ። ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ዕረፍቱ ፡ ለአዳም ፡ (ሉቱ ፡ ዕዝ፮ ፡ ፭ ። ዕብ፬ ፡ ፩ ፡ ፫ ። አፈ ፡ ድ፮) ።

**አዕረፈ ፤** አሳረፈ ፤ ዕረፍት ፡ ሰጠ ፡ በታ ፡ አዘጋጀ ። ያረውጽን ፡ ወኢያዐርፎን ። አዕርፋ ፡ ለነፍስየ ። ያዐርፋ ፡ ለእሙ ። ወአዕረፈ ፡ ሲተ ፡ ፈጣሪየ ፡ መንበርየ ፡ (ሄርማ ። ፈልሞ ፡ ፳ ። ሚራ፫ ፡ ፮ ። ሲ፬ ፡ ፳) ።

**ምዕራፍ ፤ (ፋት) ፤** ማረፊያ ፤ ማሳረፊያ ፤ መኖሪያ ፤ መቀመጫ ፤ በታ ፡ ስፈር ። ወይክውን ፡ ክቡረ ፡ ምዕራፊሁ ። ይእኅዝ ፡ ጽድቅ ፡ ምዕራፈ ። ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ምዕራፍየ ። ከመ ፡ ንኩን ፡ ምዕራፈ ፡ ስሙ ፡ ለሥሉስ ፡ (ኢሳ፲፩ ፡ ፲ ። ፴፪ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፻፴፩ ። ቀሌ ። ዘጉ፲ ፡ ፴፫) ።

—፤ ገበዋተ ፡ መንበር ፤ ክንድ ፡ የሚያርፍበት ፤ የሚደገፍበት ። ክልኤቱ ፡ ምዕራፈ ፡ መዛርዕ ፡ (፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፲፰) ።

**ምዕራፍ ፤ (ጽር ፡ ስታዲዎን ። ዕብ ፡ ሪስ) ፤** የምድር ፡ ልክ ፡ የርሕቀት ፡ መስፈሪያ ፤ ፍጻሜ ፡ ተንድፎ ፡ ደንጊያ ፡ ተወንጭፎ ፡ የሚያርፍበት ፤ የፈረስ ፡ እፍታ ፡ የጕልማሳ ፡ ሩጫ ፤ እስኪደክመው ፡ ቃታ ፡ እስኪይዘው ፡ የሚሮጥበት ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ የሚለይበት ። በመትር ፡ ፻፹፭ ፤ በክንድ ፡ ፫፻፸፰ ፡ ይኾናል ፡ ይላሉ ፡ ፬፻ ፡ ክንድ ፡ የሚሉም ፡ አሉ ። ሀገር ፡ እንተ ፡ ርሕቅት ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ መጠነ ፡ ስሳ ፡ ምዕራፍ ። መጠነ ፡ ዕሥራ ፡ ወኀምስቱ ፡ ምዕራፍ ፡ አው ፡ ሠላሳ ፡ (ሉቃ ፳፬ ፡ ፲፫ ። ዮሐ፮ ፡ ፲፱ ። ፲፩ ፡ ፲፰ ። ራእ፲፬ ፡ ፳) ።


**ምዕራፍ ፤ (ጽር ፡ ሚሊዎን ። ዕብ ፡ ሚል) ፤** ገዘኒ ፡ ከማሁ ፤ ታላቅ ፡ መስፈሪያ ፤ ዐይነ ፡ ገመድ ፤ ሺሕ ፡ መትር ፤ ወይም ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ። ወሰዘኒ ፡ ዐበጠከ ፡ አሐደ ፡ ምዕራፈ ፤ ሑር ፡ ምስሌሁ ፡ ክልኤተ ። መጠነ ፡ ክልኤቱ ፡ ምዕራፍ ። ወመጠነ ፡ ውእቱ ፡ ቅጽር ፡ አርብዓ ፡ ወኀምስቱ ፡ ምዕራፍ ። ወከነት ፡ በጓቱ ፡ ርሕቅቱ ፡ መጠነ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምዕራፍ ፡ (ማቴ፭ ፡ ፵፩ ። ገድ ፡ ተክ ። ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፻፳) ።

**ምዕራፍ ፤ (ዕብ ፡ ፌሬቅ) ፤** የመጽሐፍ ፡ ክፍል ፤ አንቀጽ ፤ በውስጡ ፡ ብዙ ፡ ቃል ፡ ያበበት ። ሊተ ፡ ሴቡ ፡ እሎንተ ፡ ምዕራፋተ ። ወከመ ፡ ዝ ፡ ገብረ ፡ ውስተ ፡ ብዙኅ ፡ ምዕራፋት ፡ (አፈ ፡ ተ፱ ። ድ፷) ። ከንጥብ ፡ እስከ ፡ ንጥብ ፡ ያለውም ፡ ።—። አንዳንዱ ፡ ቍጥር ፡ ንኡስ ፡ ምዕራፍ ፤ ሠረገ ፡ ደግሞ ፡ ፤ የንኡስ ፡ ንኡስ ፡ ይባላል ።

**ምዕራፌት ፤ (ምዕፋሬት ፤ ማዕፈሬት ፤ ዐፈረ) ፤** ሐሜሴት ፤ በርኖስ ፤ የላይ ፡ ልብስ ። ኤልሳዕ ፡ ሶበ ፡ ወረወ ፡ ባዕሌሁ ፡ ምዕራፌተ ፡ ኤልያስ ፡ ኀደገ ፡ ዓለመ ፡ ወተሰዎ ፡ (ፊልክ ፡ ፳ ። ፪ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫) ። ዕራፈ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ዐረፈ ፤ (ዐረብ ። ዕብ ፡ ዐራፍ ፤ ፈሰሰ ፤ ወረደ ፤ ነጠበ ፤ መልቶ) ፤** ቀዳ ፤ ጨለፈ ፤ ጠለቀ ።

**ዕርፍ ፤** መቅጃ ፤ መጨለፊያ ፤ ማንካ ፤ ጭልፋ ። የዕጣን ፡ የቍርባን ፡ መጫሪያ ፤ ጌታ ፡ የተወጋበት ፡ የጦር ፡ ምሳሌ ፤ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ያለበት ። ግበር ፡ እደከ ፡ ላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ዕርፈ ፡ መስቀል ፡ ለሠሪዐ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ። ዲያቆን ፡ ኢያጥምቅ ፡ ወኢያቅርብ ፡ በእዴሁ ፤ ዘእንበለ ፡ እምጽዋዕ ፡ በዕርፈ ፡ መስቀል ። ዕርፍ ፡ ማንካው ፤ መስቀል ፡ መያዣው ፡ (ሥር ፡ ቅዳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፩ ፡ ፬) ።



ዕርፈ ፡ መስቀል ፡

**ዕርፍ ፤** በቁሙ ፤ የማረሻ ፡ እጀታ ፤ ዐራሹ ፡ የሚይዘው ፤ ድጕርን ፡ ተመልከት ። ዘያጸንዕ ፡ ዕርፎ ። አልቦ ፡ ዘይእኅዝ ፡ ዕርፈ ፡ ወየሐርስ ፡ ድኅሬተ ። ውሂበ ፡ ዕርፍ ፡ ለጕሕላዊ ። እለ ፡ ሐረስዋ ፡ ለምድር ፡ በዕርፈ ፡ መስቀልከ ፡ (ሢራ፴፰ ፡ ፳፭ ። ሉቃ፱ ፡ ፷፪ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ኩፋ ፡ ፲፩) ።

**አዕራፍ ፤** ዕርፈ ፡ መስቀሎች ፤ ዕርፎች ።

**ዐረፍት ፤**—ግድግዳ ፤—አረፈ ፡ አረፍት ።

**ዐሬቅ ፤ ቆት ፤ (ዐርቀ ፡ የዐርቅ ፡ ይዕ**

ርቅ ። ዕብ ፡ ዐራህ ። ዐረ ፡ ዐሪየ ) ፤ መራቈት ፤ መገፈፍ ፡ መገለጥ ፤ ባይ ፡ መኾን ፤ ብቻ ፡ መቅረት ። ዐረቍ ፡ ወአልበስክሙኒ ። ዝቃተ ፡ ወይንነ ፡ ዐርቀ ፡ ወበልየ ። ዐርቀ ፡ ሖሩ ፡ አህጉር ። ዐርቀት ፡ እንተ ፡ ሰብዐተ ፡ ወለደት ፡ (ማቴ፳፭ ፡ ፴፮ ። ኢያ፱ ፡ ፲፩ ። ኤር፲፭ ፡ ፲፱ ። ፲፩ ፡ ፱) ። በዐርቀ ፡ ፈንታ ፡ ተዐርቀ ፡ ይላል ፤ እያሰኘም ። ትሰክሬ ፡ ወትትዐረቂ ። ቀሲስ ፡ ለእመ ፡ ሰክረ ፡ ወተዐርቀ ፡ አባሉ ፡ በቅድመ ፡ ሰብእ ። ተዐርቀ ፡ እምሠናይት ፡ ዘተውህበሙ ። ተዐርቀት ፡ ሀገር ፡ እምነ ፡ ዕደው ። ከዋክብት ፡ እምዕበየ ፡ ብርሃኖሙ ፡ ተዐርቁ ፡ (ሰቈ፬ ፡ ፳፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፪ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ድ፳፪ ። ዮሴፍ ። ቅዳ ፡ ጎር) ። መዓብ ፡ መውዛት ፤ ዐረቂ ፡ ማውጣት ።

ዐረቅ ፤ (ዐረብ) ፤ ወዝ ፤ ላብት ፤ የደም ፡ ዐረቂ ። የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፤ ከበለስ ፡ ከወይን ፡ ከሌላም ፡ አትክልት ፡ የሚወጣ ፤ ወዳጆች ፡ ገዳይ ፡ ጠላቱን ፡ ፈሪ ፡ ሸይጨን ፡ አክባሪ ።

ዕሩቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ርቅት) ፤ የተራቈተ ፤ የተገለጠ ፤ የታረዘ ፤ የተገፈፈ ፤ ግንዱን ፡ መለመላውን ፡ የኾነ ። ዕሩቅ ፡ ወዕጡር ። ኢይኩን ፡ ዕሩቀ ፡ አባል ፡ ቅድመ ፡ መኑሂ ። ወልብስየኒ ፡ ለዕሩቃን ። ከኑ ፡ ዕሩቃነ ፡ እምጸጋ ፡ ዘባዕሴሆሙ ፡ (ራእ፫ ፡ ፲፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፪ ፡ ፫ ። ጦቢ፩ ፡ ፲፯ ። ቀሌ) ።

—፤ ባይ ፤ ወና ፤ ብላሽ ፤ ከንቱ ። መሳብክት ፡ ዕሩቃት ። ክርሥ ፡ ዕርቅት ፡ ኢትወልድ ፡ ፍትወተ ። በእንተ ፡ ስብሐት ፡ ዕሩቅ ፡ (መሳ፯ ፡ ፲፯ ። አፈ ፡ ቀ፳፱ ። ፊልክ ፡ ፵) ።

ዕራቅ ፤ (ዕብ ፡ ረቅ) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ዕራቀት ፤ ማንድ ፡ መለመላ ፤ ባይ ፤ ብቻ ፤ ልብስ ፡ ጭማሪ ፡ አልባ ። ዕራቅየ ፡ ወፃእኩ ፡ እምከርሠ ፡ እምየ ፤ ወዕራቅየ ፡ እገብእ ፡ ህየ ። ሑር ፡ ዕራቀከ ፡ ዘእንበለ ፡ አሣእን ። ወአሠጡ ፡ ቀማውቲሆሙ ፡ ዕራቆ ። ዘዕራቁ ፡ ለእለ ፡ ዕራቆሙ ። ኢትስተይ ፡ ማየ ፡ ዕራቆ ። ተጠምቀ ፡ በማይ ፡ ዕራቁ ። ጳውሎስ ፡ ሳሚሳጤ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ በብእ ፡ ዕራቁ ፡ ብቻ ፡ (ኢዮ፩ ፡ ፳፩ ። ኢሳ፳ ፡ ፪ ። ኤር፲፱ ፡ ፫ ። ሱቱ ፡ ዕዝ፳ ፡ ፳፭ ። ሸጠ.ሞ ፡ ፳ ፡ ፳፫ ። መጽ ፡ ምስ ። ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ። ኢያምንት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዕራቅ ፡ ይላል ፤ ምስጢሩ ፡ አንድ ፡ ነው ። በቀላ ፡ ሰምድር ፡ ዴበ ፡ ዕራቃ ፡ (ኢዮ፳፬ ፡ ፯) ።

ዕርቃን ፤ በቁሙ ፤ ዕራቀት ፡ ዕራቀትነት ። ባይነት ፡ ንጽሕና ። (ግጥም) ፤ እኔ ፡ ድኻ ፡ መስሎኝ ፡ ዕርቃኑን ፡ ባየው ፡ ርቡስ ፡ ጌታ ፡ ኮረል ፡ የተሰቀለው ። ሀበኒ ፡ እክድን ፡ ዕርቃንየ ፡ በልብስ ፡ ሰዘከደኑ ፡ ዕርቃንየ ፡ በየርደኖስ ፡ (ድጓ) ። ከመ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ፡ ዕርቃን ፡ ሰገቢረ ፡ ሖሩ ፡ ትእዛዛት ። ዕርቃኖሙ ፡ ለሕፃናት ፡ እምኀሲናት ፡ ሕሥምት ፡ (ፊልክ ፡ ፵፬ ። ፻፶፬) ።

—፤ ብልት ፤ የወንድ ፡ የሴት ፡ ኀፍረት ፤ አባለ ፡ ዘርዕ ፡ አፈ ፡ ማሕፀን ። ወኢርእዩ ፡ ዕርቃኖ ፡ ለአቡሆሙ ። ከመ ፡ ትክድን ፡ ዕርቃነከ ። ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይንጽር ፡ ብእሲ ፡ ዕርቃና ፡ ብእሲት ፡ (ዘፍ፱ ፡ ፳፫ ። ራእ፫ ፡ ፲፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፫) ።

ዕርቅና ፤ ዕራቀትነት ፤ ዕርዝት ። በረኀብ ፡ ወጽምእ ፡ ወበዕርቅና ፡ (ዘዳ፳፰ ፡ ፵፰) ።

አዕረቀ ፤ አስራቈተ ፤ ገፈፈ ፤ ባይ ፡ አደረገ ። አዘዘ ፡ ያዕርቅዎ ፡ አልባሲሁ ። ኢታዕርቀ ፡ እግዚአ ፡ ስእንተ ፡ እንግሌ ፡ እምልብስ ፡ ጥምቀት ። እቤሎሙ ፡ ያዕርቁ ፡ ሖሎ ፡ መዛግብት ፡ (ስንክ ፡ የካ፲ ። ማንዘ ። ፪ዕገዘ ፡ ፲፫ ፡ ፱) ።

ዐረቀ ፤ (ዕብ ፡ ዐራቅ) ፤ በቁሙ ፤ (ጥረ) ዐረቀ ፡ አጐበጠ ፤ አጠመመ ፤ ቀለሰ ፡ አስጐነበሰ ፤ ቀናውን ፤ የሙጥ ፡ የደጋን ፡ የክዘራ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። አቀና ፤ አረታ ፤ ቀጥ ፡ ለጥ ፡ አደረገ ፤ አስተካከለ ፤ ጕባጣውን ። ሰፈረ ፡ መጠነ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዐረቀ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ሕገዘ፵ ፡ ፳) ።

—፤ አስታረቀ ፤ አስማማ ፤ ዑቁ ፡ ፍጡነ ፡ ዕርቅዎሙ ፡ ወግበሩ ፡ ሰላመ ፡ ማእከሎሙ ። ወዐረቀ ፡ ትዝምደ ፡ ሰብእ ፡ ምስለ ፡ እግዚ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቲሁ ፡ ለአብ ። ፍቅረ ፡ ለነ ፡ ኀበ ፡ አቡከ ፡ ገበርከ ፤ ወዐረቀ ፡ ማእከሌነ ። ዕርቅ ፡ ወአርትዕ ፡ ሖሎ ፡ ጠዋየ ፡ (ዲድ ፡ ፲፯ ፡ ፴፫ ። ኪዳ ። ኢሳ፵ ፡ ፬) ።

ዐራቂ ፤ የሚያርቅ ፤ የሚያስታርቅ ፤ አስታራቂ ። ዐራቂ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ይዕርቅ ። ዐራቂ ፡ ኪዳን ፡ ሐዲስ ። ክዋኔ ፡ ዐራቂ ፡ (አፈ ፡ ድ፴፫ና ፡ ፴፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፪) ።

ዐራቅይና ፤ ዐራቂነት ፤ አስታራቂነት ። በዐራቅይናሁ ፡ ለሊቀ ፡ ካህናት ። በእደዊሆሙ ፡ ወበዐራቅይናሆሙ ፡ (አፈ ፡ ድ፴፫ ። ማር ፡ ይሥሽ ፡ ፳) ።

ተዐርቀ ፤ ታረቀ ፤ ጐበጠ ፤ ቀና ፡ ረታ ፡ ዕንፈጠ ።

ተዓረቀ ፤ ታረቀ ፤ ተራረቀ ፡ ተስማማ ፤ አንድ ፡ ልብ ፡ ኾነ ። (ቀረት) ፤ ሲታጠቡ ፡ ከካንድ ፡ ሲታረቁ ፡ ከሆድ ። ኢይትዓረቅ ፡ በብዙኅ ፡ ሀብት ። ይትዓረቅ ፡ ምስለ ፡ ቢጹ ። ለእመ ፡ አበየት ፡ ተዓርቆ ፡ ምስለ ፡ ምታ ፡ (ምሳ፮ ፡ ፴፭ ። ዲድ ፡ ፲፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፪ ፡ ፪) ።

ዕርቅ ፤ በቁሙ ፡ ሰላም ፤ መታረቅ ፡ መስማማት ፤ ስምምነት ። እስከ ፡ ይገብሩ ፡ ዕርቀ ፡ በበይናቲሆሙ ። እመ ፡ ገብረ ፡ ዕርቀ ፡ ነግሡ ፡ ምሕስ ፡ ምስለ ፡ በዓለ ፡ ዕዳ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፭ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯) ።


ዕርቃና ፤ ዕርቅነት ፡ ስምምነት ። በሰላም ፡ ወዕርቃና ፡ ወተሰናእዎ ፡ (ቀኖ ፡ ስርድ ፡ ፲፱) ።

አስተዓረቀ ፤ አስተራረቀ ፤ አስማማ ። እሊ ፡ ያስተሳልሙ ፡ ወያስተዓርቁ ፡ (ቀሌ) ።

ዐረር ፤ (ሐረር ፤ ሐረረ ። ዕብ ፡ ዖፌሬት ። ሱር ፡ አባራ ። ዐረ ፡ ረጸጽ) ፤ በቁሙ ፡ ርሳስ ፤ የማስደናት ፡ ወገን ፤ ጥቍር ፤ ከባድ ፤ ልሕሉሕነት ፡ ያለው ፤ ከቀለሕ ፡ ጋራ ፡ የሚጠየቅ ። ዘና ፡ ሐሪር ፡ ነው ፤ ሐ ፡ ለበ ፡ ተለውጧል ፤ ፍእዝን ፡ ተመልከት ። ቱሰጥሙ ፡ ከመ ፡ ዐረር ፡ ውስተ ፡ ማይ ። መክሲቱ ፡ ዐረር ። ምንት ፡ ይከብድ ፡ እምነ ፡ ዐረር ፡ (ዘፀ፲፭ ፡ ፲ ። ዘካ፭ ፡ ፯ ። ሢራ፳፪ ፡ ፲፬) ።

ዐሬስ ፤—ዳሰ ፡ ወይን ፤—ዐሬሥ ።

**ዐራት ፤ ታት ፤** (ዕብ ፡ ሚጣ ፤ ዒሬሥ ። ሱር ፡ ዓርሣ) ፤ ዐልጋ ፤ መተኛ ፤ መጋደሚያ ፤ ቁጥ ፡ የሬሳ ፡ ማንሻ ፤ አራት ፡ እግር ፡ ያለው ። አርባዕቱን ፡ አ ራት ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ዐራት ፡ ዘወርቅ ፡ ስርጉው ፡ በባሕርይ ። ዐራተ ፡ ንጹን ። ሀ ራተ ፡ ሐማም ። ዐራታት ፡ (ዮሴፍ ። በንክ ፡ ማን፲፱ ። መዝ ፡ ፵ ። ፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፷፰ ። ማርቆ ፡ ፶፭) ።



ዐራት ፡

**ዐሰበ ፤ በት ፤** (ዐሰበ ፡ ይዔስብ ፡ የዐስብ ። ዐረ ፡ ዐሰፈ) ፤ ዐሰብ ፡ ክራይ ፡ መስጠት ፤ የጕልበት ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ። መክፈየት ፤ መዋዋል ፤ መስማማት ፤ ቦ ቀ ርጥ ፡ መግዛት ። ዐሰበኒ ፡ ወኩንኩዎ ፡ ካህኑ ። ወዐሰ ብዎ ፡ ለሶርያ ። ዐሰቡ ፡ ሰብአ ፡ ባዕሌየ ። ተዐስብዎ ፡ ለነሃቢ ፡ (መሳ፲፰ ፡ ፬ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፮ ። ፪ዕዝ ፡ ፭ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፵፮ ፡ ፮) ። በዐሰበ ፡ ፈንታ ፡ ተዐሰበ ፡ ይላል ፤ የተሳ ሳተ ፡ ነው ። ተዐሰብኩ ፡ ሊተ ፡ በዐሥርቱ ፡ ወኀምስቱ ፡ ጠፋልሐ ፡ ብሩር ። ዘተዐሰበ ፡ ዐጺደ ፡ ለሰ ፡ ዘሎ ፡ አ ውራኅ ፡ በዲናር ፡ ወኢያእመረ ፡ ኍልቈ ፡ ዘሎን ፡ አ ውራኅ ፤ ይከውኖ ፡ ለተዐሳቢ ፡ እምድኅረ ፡ አሐዱ ፡ ወርኅ ፡ ከመ ፡ ያብጥል ፡ ሥርዐተ ፡ ተዐስቦ ። ረከበ ፡ ሐመረ ፡ ወተዐሰበ ፡ (ሆሴ፫ ፡ ፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ። ዮና፩ ፡ ፫) ።

**ዐሳቢ ፤** የሚከራይ ፤ ደመ ፡ ወዝ ፡ ሰጪ ። በዐ ሳቢ ፡ ፈንታ ፡ ተዐሳቢ ፡ ይላል ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

**አዐ(ዕ)ሰበ ፤** አከራየ ፤ ለክራይ ፡ ሰጠ ፤ ቤቱን ፡ ከብቱን ፤ ወይም ፡ ጕልበቱን ። እመ ፡ አገበርዎ ፡ ለብ እሲ ፡ ከመ ፡ ያዕስብ ፡ ዘይመልክ ፤ አው ፡ ይትዐሰብ ፡ ምልክተ ፡ ካልኡ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፰) ። አዐሰበ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አስተዐሰበ ፡ ይላል ፤ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ። ብእመ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይሚጥ ፡ ክፍለ ፡ ዚአሁ ፤ አው ፡ ያስተ ዐስቦ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

**ተዐ(ስ)ሰበ ፤** ተከራየ ፤ ክራይ ፡ ኾነ ፤ ለክራይ ፡ ተሰጠ ።

**ዐሳብ ፤ ዕሱብ ፤** ምንደኛ ፡ ሙያተኛ ፤ ደሞ ዘኛ ፤ ቶፋ ። ዐሳብ ፡ ዘለሰ ፡ ዕለት ። ወዐሳብሰ ፡ ይጐ ይይ ፡ እስመ ፡ ዐሳብ ፡ ውእቱ ። ተዐሳቢ ፡ ወዐሳብ ፡ (ኢዮ፯ ፡ ፩ ። ዮሐ፲ ፡ ፲፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

**ዐሳባዊ ፤** የክራይ ፤ የሙያ ፤ ሙያተኛ ፡ ባለ ደመ ፡ ወዝ ። ቱክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አሐዱ ፡ እምዐሳባ ውያን ፡ ዘሠርክ ፡ (ደራሲ ። ገድ ፡ ኪሮ ። አፈ ፡ ተ፲፪) ።

**ዐስብ ፤** በቁሙ ፤ የጕልበት ፡ ዋጋ ፤ ደመ ፡ ወዝ ፡ ምንዳ ፤ ክራይ ፤ ወይም ፡ ክርካር ። ምንት ፡ ውእቱ ፡ ዐስብከ ። ሀበሙ ፡ ዐስቦሙ ። ዐስበ ፡ ሐመር ፡ (ዘፍ ፳፱ ፡ ፲፭ ። ማቴ፳ ፡ ፰ ። በንክ ፡ ንሐ፴) ።

(ላ) **ዐሰበ ፤** (ዕብ ፡ ዐዛብ) ፤ ተወ ፤ ለቀቀ ፤ ጣለ ፤ የያዘውን ፡ የተከፈየውን ፤ ሚስት ፡ ገረድ ።

**መዐስብ ፤** (ብት ፡ ባን ፡ ባት) ፤ ፈት ፤ ብቸኛ ፤ ጋለሞታ ፤ ሚስት ፡ የሌለችው ። መዐስበ ፡ ናዝዝ ። መዐ ስበ ፡ ሐውጽ ። ረድኤተ ፡ ለመዐስባን ፤ ወኀይለ ፡ ትዕ ግሥተ ፡ ለደናግል ። ዘአውሰበ ፡ መዐስብተ ፡ (ኪዳ ። ቅዳ ። አርጋ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ፡ ፳) ።

**መዐስብ ፤ መዐንስብ ፤**—ማርተኛ ፤—ዐ ንሰበ ።

**መዓስብ ፤** ፈቶች ፤ ሚስት ፡ የሌላቸው ።

**መዓስበን ፤** (ባት) ፤ ገዚ ፡ ከማሁ ፤ የብዙ ፡ ብዙ ። መነኮሳት ፡ መዓስባን ። መበለታት ፡ ወመዓስ ባት ፡ (ኪዳ) ።

**ማዕሰበ ፤** (ዐሰበ) ፤ ፈት ፡ ኾነ ፤ ገለሞተ ፤ ብ ቻውን ፡ ኖረ ፤ ሚስቱ ፡ ሙታ ፤ ወይም ፡ በነውር ፡ ወጥታ ። ሐና ፡ ወለተ ፡ ፋኑኤል ፡ ማዕሰበት ፡ ለማንያ ፡ ወአር ባዕቱ ፡ ክረምተ ፡ (በንክ ፡ የካ፳ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፴) ። በማዕ ሰበ ፡ ፈንታ ፡ ተማዕሰበ ፡ ይላል ፤ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ። እንዘ ፡ ትትማዐሰቢ ፡ (ሉቃ ፡ ፵፬) ።

**ምዕስብና ፤** ማልሙትና ፤ ፈትነት ፤ ብቻነት ። ኢይክሉ ፡ ምዕስብና ። ከመ ፡ ሐማማት ፡ ዘምዕስ ብና ፡ ይጠይቅ ፡ (ቀኖ ፡ በርድ ። ኪዳ ። ቁድር) ።

(ሦ) **ዐሰየ ፤ ዮት ፤** (ዐሰየ ፡ የዐሲ ፡ ይዕሲ ። ዕብ ፡ ዐሳሀ ፤ ገብረ) ፤ ዋጋ ፡ መስጠት ፤ ማደል ፤ መ ክፈል ፤ ብድር ፡ መመለስ ፤ አብዝቶ ፡ አትርፎ ፡ ከልክ ፡ አሳልፎ ። እሺ ፡ ማለት ። እንዘ ፡ ተዐሲ ፡ ዕሴተ ፡ ሠናየ ። ምንተኑ ፡ አዐስዮ ፡ ለእግዚ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ ሊተ ። ዕስዮ ፡ ለገብርከ ። ዘየዐሲ ፡ እኩየ ፡ ህየንተ ፡ ሠ ናይ ። የዐስየከ ፡ ቅሥተ ፡ ወተስናነ ፡ በንዋይከ ፡ (ቅዳ ። መዝ ፡ ፻፲፭ና ፡ ፲፰ ። ምሳ፲፯ ፡ ፲፫ ። ሢራ፴፱ ፡ ፳) ።

**ዐሳዪ ፤** የሚሰጥ ፡ ሰጪ ፤ ቸር ፡ ለጋስ ፤ እጀ ፡ ሰፊ ፤ ዐጻይ ፡ አሳሳፊ ። ወፈዲዮ ፡ ውእቱ ፡ ከነ ፡ ዐሳዪ ፡ ሕይወት ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይትኤዘዙ ፡ ሎቱ ፡ (ዕ ብ፭ ፡ ፱) ።

**ተዐስየ ፤ ተዐሰየ ፤** ተሰጠው ፤ ተቀበለ ፤ ዋጋ ውን ፡ አገኘ ። ዋጋው ፡ ገንዘቡ ፡ ተሰጠ ፤ ከሰጪ ፡ ወደ ፡ ተቀባይ ፡ በለፈ ። ትትዐሰይ ፡ አመ ፡ የሐይዉ ፡ ጻድቃን ። ይትዐሰይ ፡ ብዙኀ ። ተዐስየ ፡ ምሕረተ ፡ በዝንቱ ። ተ ዐስየ ፡ ዕሴተ ፡ ሠዋዒ ፡ (ሉቃ፲፬ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፲፰ ። ቄር ። አፈ ፡ ተ፴፱) ።

**ዕሱይ ፤** የተቀበለ ፤ ዋጋውን ፡ ያገኘ ።

**ዕሴት ፤** (ብ ፡ ዕስያት) ፤ ዋጋ ፤ ደመ ፡ ወዝ ፤ ስጦታ ፤ መባእ ፤ ምጽዋት ፡ (እሺታ) ። ሀኵሉ ፡ ዕሴቶሙ ። ውእቱኬ ፡ ዘይነሥእ ፡ ዕሴቶ ። ወዕሴትየኒ ፡ ምስ ሌየ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ እፍድዮ ፡ ለኵሉ ፡ ለለ ፡ አሐዱ ፡ (ማቴ፯ ፡ ፬ ። ፩ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ። ራእ፳፪ ፡ ፲፪) ።

**ትዕሲት ፤** ስጦታ ፤ አሰጣጥ ፤ ጕርሻ ፡ በቅሽሽ ።

**ዐስቆ ፤ ቆት ፤** (ዐሰቀ ፡ ይዔስቅ ፡ የዐ ስቅ ። ዕብ ፡ ዐሻቅ ፤ ነፈገ ፡ ጨበጠ ፤ በውድ ፡

ሼጠ)፤ መሥራት፤ መታታት፤ መጥለፍ፤ ማቈላለፍ፤ ልብስን፤ በብዙ፤ ዐይነት፤ ፈትል፤ በወርቀ፤ ዘቦ፤ ማስጌጥ፤ ማንቈጥቈጥ፤ እንዲያምር፤ እንዲከብር፤ በውድ፤ እንዲሼጥ፤ ማድረግ፤ የስፌ፤ የሸማኔ ።

**ዐሳቂ፤ መዐስቅ፤** ልብስ፤ የሚሠራ፤ ጥበብ፤ ድርብ፤ ሠሪ፤ ሸማኔ፤ ጠላፊ ። ሥርዌ፤ ዐጥፍ፤ ዘመዐስቃን፤ (ዘኍ፤ ፳፩፤ ፲፱ ። ስንክ፤ ታኅ፳፫) ።

**ተዐሰቀ፤** ታሰቀ፤ ተሠራ፤ ተጠለፈ፤ ተኀርጐረጐረ ።

**ዕሱቅ፤** የታሰቀ፤ የተሰሰቀ፤ ከነታን፤ ከሐር፤ ዕጥፍ፤ ድርብ፤ ኹኖ፤ የተሠራ ። ግብረ፤ ማእነም፤ ዕሱቅ ። ወክዳኑ፤ ለአንቀጸ፤ ዐጺድ፤ ዕሱቅ፤ በደርክኖ ። ልብሰ፤ ሜላት፤ ዘወርቅ፤ ወመረግድ፤ ወዕንቍ፤ ዘብዙኅ፤ ሤጡ፤ ዕሱቅ፤ ውስቴቱ፤ (ዘፀ፴፮፤ ፲፰ ። ፴፯፤ ፲፯ ። ዮዲ፲፤ ፳፩) ።

**ዐስቅ፤** ጥሩ፤ ግምጃ፤ ክቡር፤ ልብስ፤ ዠንጕርጕር፤ ባለሬት፤ ሕብር፤ ወርቀ፤ ዘቦ፤ የተጌጠ፤ የተሸለመ ። ክዳን፤ ዘሕብረ፤ ዐስቅ ። አልባስ፤ ዘተገብረ፤ በዐስቀ፤ ሜላት ። አልባሰ፤ ወርቅ፤ ወአልባሰ፤ ዐስቅ፤ (ዘፍ፴፯፤ ፫ ። ሚራ፵፭፤ ፲ ። ኢሳ፫፤ ፳፫) ።

**ዕስቍፍ፤—ኤጲስቆጶስ፤—እስቍፍ ።**

**ዐሰረ፤—በቁሙ፤—አሰር፤ አሰረ ።**

**ዐሰረ፤—ቀጠረ፤—ዐሥሮ፤ ዐሠረ ።**

**ዐቲብ፤ ቦት፤ (ዐተበ፤ የዐትብ፤ ይዕትብ፤ ኀተመ)፤** ማተብ፤ መቍረጥ፤ መፈጸም፤ መጨረስ ። ማተም፤ ማስመሰል ። ዐተቦ፤ እግዚ ። ዘቦቱ፤ ቀብዐ፤ ወዐተበነ ። ወዐተቡክሙ፤ (ዮሐ፫፤ ፴፫ ። ፪ቆሮ፤ ፩፤ ፳፪ ። ኤፌ፩፤ ፲፫ ። ፬፤ ፴) ።

—፤ መባረክ፤ ማማተብ፤ በጣት፤ በመስቀል፤ ፊትን፤ ወይም፤ ሌላውን ። ዐተበኒ፤ በትእምርተ፤ መስቀል፤ ወአርስቶ፤ ዐቲበ፤ ገጻ ። ይዕትብ፤ አባሎሙ ። ወይዕትቦሙ፤ ሥልሰ፤ (ቀሌ ። ፍ፤ ን፤ ፫ ። ቅዳ) ።

**ተዐትበ፤** ታተበ፤ ተቈረጠ ። ተባረከ፤ ታተመ ። ሀባ፤ ናህየ፤ ለዛቲ፤ ነፍስ፤ ዘተዐትበት፤ በጥምቀትከ፤ ወተቀደሰት፤ በደምከ ። ተዐትበት፤ በዕፀ፤ መስቀሉ ። ኪመ፤ ይትዐተብ፤ ራእየ፤ ነቢያት፤ (ግንዘ ። ድጓ ። ዳን፱፤ ፳፬) ።

**ዕቱብ፤ (ኅቱም)፤** የታተበ፤ የተቈረጠ፤ ቍርጥ ። እስመ፤ ዕቱብ፤ ነገር፤ (ጥበ፲፤ ፳) ።

—፤ የተባረከ፤ የታተመ ። ዕቱባን፤ አንትሙ፤ በቅድስት፤ ጥምቀት ። ምሕባነ፤ ረቢ፤ ዕቱበ፤ (ቀሌ ። ደራሲ) ።

**ዕትብት፤** በቁሙ፤ የታተበች፤ የተቈረጠች ።

**ዕትበት፤** ማተብ፤ መታተብ፤ ማማተብ፤ በአንብሮተ፤ እድ፤ መባረክ፤ መሾም፤ ወይም፤ ቡራኬን፤ ሹመትን፤ መቀበል ። እስመ፤ ዕትበትሰ፤ ይከውን፤ ውስተ፤ ሥዩም፤ በእንተ፤ መልእክት፤ (ፍ፤ ን፤ ፲፤ ፳) ።

**ዑታቤ፤** ዝኒ፤ ከማሁ፤ ቡራኬ፤ አበራረክ ። በስመ፤ ዚአሁ፤ ይደሉ፤ ዙሉ፤ ዑታቤ፤ (መጽ፤ ምስ) ።

**ማዕተብ፤ (ዕብ፤ ሐታም)፤** ኀቲም፤ ቀለበት፤ ፈርጡ፤ ማኅተም፤ የኾነ ። ኀቲምን፤ ተመልከት ። ሕልቀቱ፤ ማዕተብ ። ከመ፤ ማዕተብ፤ (ሚራ፵፱፤ ፲፩ ። ሐጌ፪፤ ፳፫ ። ኤር፳፪፤ ፳፬) ።

—፤ ትእምርተ፤ መስቀል ። ዐጽፍ፤ ጸሊም፤ ዘምሉእ፤ ማዕተበ ። ረሰየ፤ ዐውደ፤ በአቱ፤ ማዕተበ፤ መስቀል፤ ዐውደ፤ (ገድ፤ ዳን ። ፊልክ፤ ፳፯) ።

—፤ በቁሙ፤ ማተብ፤ ምልክት፤ ዕልባት ። ማዕተበ፤ ሐፆር፤ ዘሀሎ፤ በክሣዱ ። ወግዝረትሰ፤ ማዕተበ፤ ጽድቅ ። ማዕተባ፤ (ማኅተማ)፤ ለመጽሐፍየ፤ (ስንክ፤ ሐም፲፱ ። ሮሜ፬፤ ፲፩ ። ፩ቆሮ፤ ፱፤ ፪) ።

**ማዕተበ፤ ረስን፤** መስቀላዊ፤ የተኰሰ፤ ምልክት፤ ጠባሳ፤ ዕትራት ። ቀይ፤ የመስቀል፤ ምልክት፤ ከልብስ፤ ላይ፤ በቀይ፤ ፈትል፤ የሚጣፍ፤ የሚሰፋና፤ የሚጠለፍ፤ (ሥር፤ ጳኲ) ።

—፤ አብነት፤ ምሳሌ፤ ጠንክ ። ኑደገ፤ ሰኑ፤ ማዕተቦ፤ (ድጓ ። ሹኤጥ፤ ፪፤ ፳፩) ።

**ማዕተብ፤** አንባር፤ ማልደያ፤ ቢተዋ፤ ጩሩ፤ የጅብራ፤ የልክ ። ኹሉም፤ የእጅ፤ ጌጥ፤ ነው፤ ቢተዋ፤ ይበልጣል፤ የሚያደርገውም፤ በሥር፤ ገዳይ፤ ነው፤ እገሌ፤ ቢተዋ፤ መልቷል፤ እንዲሉ ። እንብረኒ፤ ከመ፤ ሕልቀት፤ ውስተ፤ ልብከ፤ ወከመ፤ ማዕተብ፤ በመዝራዕትከ፤ (ማሕ፰፤ ፮) ።

**አማዕተበ፤ (ዐተበ)፤** አማተበ፤ አመሳቀለ፤ ጣቱን፤ እጁን ። ኦማዕቲቦ፤ በትእምርተ፤ መስቀል ። በጊዜ፤ ቅዳሴ፤ ሶበ፤ ያማዕትብ፤ እደ ። አቅረበ፤ ሎቱ፤ ዮሴፍ፤ ክልኤተ፤ ደቂቆ፤ ከመ፤ ይባርኮሙ፤ ወአማዕተበ፤ እዴሁ፤ ዲበ፤ ኣርእስቲሆሙ፤ (ገድ፤ ተክ ። ስንክ፤ ታኅ፲፱ ። ኑሶ፳፰) ።

**ተማዕተበ፤ (ተዐትበ)፤** ተማተበ፤ ተባረከ፤ ተመሳቀለ ። በአምሳለ፤ ከዋክብት፤ በተማዕትቦ፤ (ስንክ፤ ኅዳ፳ ። ቀሌ) ።

(ጥ) **ዐትሞ፤ ሞት፤ (ዐተመ፤ ይዔትም፤ የዐትም ። ዐረ፤ ዐተበ ። ዕብ፤ ዐቶብ፤ በጢስ፤ መታፈን፤ መጨለም)፤** መቈጣት፤ መናደድ፤ እንደሚጤስ፤ እሳት፤ ቱግ፤ ማለት ።

**መዐትም፤ (ምት፤ ማን፤ ማት)፤** ቍጡ፤ ብስጩ፤ ተናዳጅ ። ኢይኩን፤ አሐዱ፤ እምዘመደ፤ ካህናት፤ መዐትመ፤ ወመፍጠኔ፤ መዐት ። ነፍስ፤ መዐትም፤ ዘይነደድ፤ ከመ፤ እሳት ። ነባቢት፤ ወመዐትምት ። አናብስት፤ መዐትማን፤ (ፈ፤ መ፤ ፳፩፤ ፫ ። ሚራ፳፫፤ ፲፯ ። ምሳ፳፩፤ ፲፱ ። ጥበ፲፩፤ ፲፰) ።

**ዐተር፤** በቁሙ፤ ያበባ፤ እኽል፤ ፍሬው፤ ክብ፤ እንክብል፤ ድብልብል ። ዐተረ፤ ወስጕርንደ ። ብርስነ፤ ወዐተረ ። ዐተር፤ ይቡስ፤ (ገድ፤ ተክ ። ሕዝ፬፤ ፱ ። ስንክ፤ ጥቅ፴) ። ባማርኛ፤ ዐተረ፤ ዕትራት፤ ማለት፤ ከዚህ፤ የወጣ፤ ነው ።

# ፈ

**ፈ** ፤ ዐሥራ ፡ ሰባተኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፡ ስሙ ፡ ፈፍ ፤ ቍጥሩ ፡ ሰማንያ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ ፹ ፡ ፹ ፡ ይባላል ፤ አፈፈን ፡ እይ ።

**ፌ** ፤ (ዕብ ፡ ፌእ ። ዐረ ፡ ፈም ። ሱር ፡ ፉም ፤ ፉማእ) ፤ ገኢ ፡ ክማሁ ፤ ስሙ ፡ ፊደል ፡ ፲፯ኛ ፡ ፈ ፡ ፍችው ፡ አፍ ፡ ማለት ፡ ነው ። ፌ ፡ መንክር ፡ ስም ዕከ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፲፱ ። ሰቈ ፡ ፲፮ ። ፱ ፡ ፲፮ ። ፫ ፡ ፵፰ ። ፱ ፡ ፲፯) ። በጽርእ ፡ ፒ ፡ ይባላል ፡ ዕብራውያንም ፡ ነቍጣ ፡ እየጨመሩ ፡ ፐ ፡ ይሉታል ። አፍ ፡ በሙ ፡ ወእ ይነቡ ፡ ባለው ፡ (ፌ)ኜ ፡ ሳሃም ፡ ውሎእ ፡ ያዳቤሩ ፡ እን ዲል ፡ (ዕብ ፡ መዝ ፡ ፻፲፫ ፡ ፲፫) ።

**ፍኢም ፤ ሞት ፤ (ፈእመ ፡ ይፍእም ፡ ይፍአም ። ዐረ ፡ ፈአመ)** ፤ ማጉረም ፡ ባፍ ፡ መ ወተፍ ፤ መክተት ፡ መ ይል ፡ ማግባት ፤ ማብላት ፡ ማዋዋ ፤ ቈርሶ ፡ መስጠት ፡ መዘከር ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በፈአመ ፡ ፈንታ ፡ አፍአመ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። መብልዐ ፡ መላእክት ፡ አፍአምኮ ፡ ለሕዝብከ ። አፍአም ፡ ለክ ይሲ ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ። እመ ፡ አንከይኮ ፡ እምሲሳየ ፡ ነፍስከ ፡ ወአፍአምኮ ፡ ለነዳይ ። አፍእም ፡ እምይ እቲ ፡ ለነዳይ ፡ (ጥበ ፲፮ ፡ ፳ ። ዳን ፲፫ ፡ ፳፯ ። ኢሳ ፶፰ ፡ ፲ ። ቀሌ) ።

**ፈአሚ** ፤ የሚያጕርም ፡ አጕራሽ ።

**አፍአመ** ፤ አስጐረሠ ፡ ጐረሠ ፡ አጕረሠ ፡ አለ ፡ አስደራጊ ።

**ተፍእመ** ፤ ተጐረሠ ፡ ምግቡ ። ጐረሠ ፤ ከፉ ፡ አገባ ። ሕባ ፡ ሕጋትን ፡ ተፍእመ ፡ እብነ ፡ ከመ ፡ ኢይት ናገር ፡ ነገረ ፡ ፀሩዐ ። ዘየአክሎ ፡ ለተፍእሞቱ ። ከመ ፡ ኢይትፈአምዎ ፡ ክልኤ ፡ ጊዜ ። አይ ፡ አፍ ፡ ዘይትፈ እም ፡ ዘንተ ፡ ኅብስተ ። ይመሥጡ ፡ ኅብስተ ፡ ወይት ፈአምዎ ፡ እንበለ ፡ አእምሮ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝ ፡ ይ መውቱ ። በተፍእሞ ፡ ሣዕር ፡ ኢምሮም ፡ (ስንክ ፡ መስ ፲፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፯—፯ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ የካ ፲፯) ።


**ተፋእመ** ፤ ተጓረሠ ፡ ተጐራረሠ ።

**ፋእም** ፤ ወንገትጌ ፤ የቀሚስ ፡ አፍ ። ፋእሙ ፡ ለልብስ ፡ (ዘፀ ፴፯ ፡ (ዕብ ፴፱) ፡ ፳፫) ።

—፤ ማግ ፡ ግራ ፤ ሸማኔ ፡ ሲድር ፡ ወይም ፡ ሲገሐ ፡ የሚ ያጕርሠው ። ስፍሖ ፡ ገብረ ፡ ዘእምጥንተ ፡ ሥጋሁ ፡ ለአዳም ፡ ወፋእሙኒ ፡ ሥጋ ፡ ዚአኪ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ። ተረ ፡ ቈር ፲፰ ። ዘሌ ፲፫ ፡ ፵፰—፶፰) ።

—፤ ጕርሻ ፡ ዳረጎት ፡ ምጺት ፡ ቍራሽ ፡ አንድ ፡ አፍ ፡ እንጀራ ፡ ቢጃ ፡ እንክብክብ ።

**አፍአምት** ፤ ዝኢ ፡ ክማሁ ። ሂሩክ ፡ አፍአ ምት ፡ ለርኁብ ። ሂድዎሙ ፡ ለርኁባን ፡ አፍአም ቶሙ ። ወተሰፈወ ፡ የሀብዎ ፡ አፍአምተ ፡ (ኢዮ ፳፪ ፡ ፯ ። ፳፱ ፡ ፲ ። ግብ ፫ ፡ ፭) ።



ፋእም ፡

**ፋእማት ፤ አፍኢም** ፤ ጕርሾች ፡ ዳረጎቶች ።

**አስተፍአመ** ፤ ለመነ ፡ ቀላወጠ ፡ አጕርሡኝ ፡ መጽውቱኝ ፡ አለ ። ይፍልሱ ፡ ወያስተፍእሙ ፡ (መዝ ፡ ፻፰ ። ኢዮ ፳፯ ፡ ፲፱ ። ፴ ፡ ፫—፱) ።

**አስተፋአመ** ፤ አጓረሠ ፡ አጐራረሠ ፡ ተጓረሡ ፡ አለ ።

**ፈጊግ ፤ ጎት ፤ (ፈገ ፤ ፈገገ ፡ ይፈግግ ፡ ይፍግግ)** ፤ መተንፈግ ፤ መከርፋት ፡ መቀርናት ፤ መግ ማት ፤ መሽገት ፤ መፈግ ፤ ፍግ ፡ መኾን ። ፈርገገን ፡ እይ ፤ የዚሀ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ። በቁሙ ፡ መፍገግ ፡ መብራት ፤ ወ ገግ ፡ ፈገግ ፡ ማለት ፤ የስማይ ። ጎሐን ፡ ተመልከት ።

**ፍጉግ** ፤ የሚከረፋ ፡ ከርፋታም ፡ ሽታው ፡ የሚ ያስቅቅ ። ጼና ፡ ጢስ ፡ ፍጉግ ። ጢስ ፡ እሳት ፡ ገሃነም ፡ ፍጉግ ፡ ወጽዩእ ። ቤተ ፡ ጽልመት ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ጺ አት ፡ ፍጉግ ። አጼንዎ ፡ ጼና ፡ ፍጉግ ፡ (ጥበ ፲፮ ፡ ፲፱ ። ግንዘ ። አፈ ፡ ተ፳ ። ስንክ ፡ መስ ፲፱ ። ፈላስ) ።

**ፍግግ** ፤ ትንፋግ ፡ ከርፋት ፡ ቅርናት ፤ ግማት ፡ ክፉ ፡ ሽታ ። እምፍግግ ፡ ጺአት ።

**ፈገ** ፤ ፈጀ ፡ ጨረሰ ፡ በላ ፡ አቃጠለ ፤ ለበለበ ፡ አንገበገበ ። ፈገፈገ ፡ አፈገፈገ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

(ጥ) **ፍግ** ፤ በቁሙ ፤ ዐዛባ ፡ ኵስሕ ፤ ከሕያዋን ፡ ሆድ ፡ የሚወጣ ፤ ፍጉግ ፡ ጼና ። በፍግ ፡ ፈንታ ፡ ፍዕግ ፡ ይላል ፤ ከማርናኛ ፡ የለየኹ ፡ መስሎት ። ወሶበ ፡ ከዐጠ ፡ ዲቤሃ ፡ ፍዕገ ፡ ጊዜ ፡ ምሴት ፡ ይረክብዎ ፡ በነግህ ፡ ከዊኖ ፡ ሐመደ ፡ (ሥር ፡ እኸ) ።

**ፈግዖ ፤ ዖት ፤ (ፈግዐ ፡ ይፌግዕ ፡ ይፈ ግዕ ። ዐረ ፡ ፈኪሀ ። ዕብ ፡ ፋጋዕ ፤ አገኘ ፡ ደረሰ ፡ ነካ ፡ ዳሰሰ)** ፤ ፍጹም ፡ ተድላ ፡ ማድረግ ፤ መፍከት ፡ መፈንደቅ ፡ ደስ ፡ ፈቅ ፡ ማለት ፡ ከመብል ፡ ከመጠጥ ፡ ከምኞት ፡ ከብዕል ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ። በልዑ ፡ ወጸገቡ ፡ ወሠብሑ ፡ ወፈግዑ ፡ በበረከትከ ። ወካ ልእ ፡ ይፈግዕ ፡ በንዋዩ ። ዘኢፈጸመ ፡ ሕይወቶ ፡ በ

ዲበ ፡ ምድር ፡ ወኢፈግዐ ፡ በሥናያት ። እለ ፡ ይፈግዑ ፡ ውስተ ፡ ምስካባቲሆሙ ፡ (፪ዕዝ ፡ ፱ ፡ ፳፰ ። ሚራ፲፱ ፡ ፱ ። ግንዘ ። ዓሞ፯ ፡ ፱) ። በፈግዐ ፡ ፈንታ ፡ ተፈግዐ ፡ ይባላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እምትደሰው ፡ ወትትፈጋዕ ፡ በቤተ ፡ ባዕድ ፡ በንዋየ ፡ ነኪር ። ይትፌሥሑ ፡ ወይትሐሠዩ ፡ ወይትፌግዑ ፡ በተውኔት ። ንዑኬ ፡ ንትፈጋዕ ፡ በዘሀሎ ፡ ሠናያት ። እለ ፡ ይትፌግዑ ፡ በብዕሎሙ ፡ (ሚራ፳፱ ፡ ፳፱ ። ቀሌ ። ጥበ፪ ፡ ፮ ። ኪ.ዳ) ።

**ፍጉዕ** ፡ የደላው ፡ የተመቸው ፡ ደስ ፡ ፈቅ ፡ ያለው ፡ (ኪ.ዳ) ።

**ፈጊዕ** ፡ ጥጋብ ፤ ስካር ። በስታይ ፡ ወበፈጊዕ ፡ (ሉቃ፳፩ ፡ ፴፬ ። ዲ.ድ ፡ ፱) ።

**ፍግዕ** ፡ ተድላ ፤ ደስታ ፤ ምቾት ። ኣፈቅሮ ፡ ለፍግዕኪ ። ወደስክዋ ፡ አነ ፡ ለሐሤት ፡ ፍግዕ ። ሢሐቅሙ ፡ ፍግዐ ፡ ኃጢአት ፡ (ማሕ፯ ፡ ፯ ። መክ፰ ፡ ፲፭ ። ሚራ፳፯ ፡ ፲፫) ።

**ፍግዓ** ፡ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ፍግዓሁ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ጽላሎት ፡ የኀልፍ ። ብሔረ ፡ ፍሥሓ ፡ ወፍግዓ ፡ ወተድላ ። ፍግዓ ፡ ውሉደ ፡ ሰብእ ፡ (ቀሌ ። መክ፪ ፡ ፰) ።

**ትፍግዕት** ፡ (ታት) ፡ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ። ትፍግዕት ፡ ያማስን ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ ኅቡረ ። አፍቅሮ ፡ ትፍግዕታት ። ትፍግዕታተ ፡ ሕዋሳት ፡ (እፈ ፡ ቶ፳፱ ። ፊልክ ፡ ፵፱) ።

**አስተፈግዐ** ፡ (አፈግዐ) ፡ አስመቸ ፡ ደስ ፡ አሰኘ ። ዘያስተፌግዕ ፡ ልበ ፡ (ሢራ፲፱ ፡ ፳) ።

**ፈጊር** ፡ ሮት ፡ (ፈገረ ፡ ይፈግር ፡ ይፍግር ። ዕብ ፡ ፋጌር ፡ ደክመ ። ትግ ፡ ሐባ ፡ ፈግረ ፡ ወጣ) ፡ መኛገር ፡ መፍገርገር ፤ መፍጨርጨር ፤ ለመውጣት ። መድከም ፡ ማረፍ ፡ መሞት ፤ ፊሳ ፡ መኾን ። ወሎዎች ፡ ቂጥን ፡ ፈጋራ ፤ ሐባበችም ፡ ምሥራቅን ፡ ምፍጋር ፡ የሚሉት ፡ ከዚህ ፡ የመጣ ፡ ነው ።

**ፌኅር** ፡ (ጽርእ ። ዕብ ፡ ፍዖር) ፡ ሕገ ፡ ጣዖት ፤ መከነ ፡ ጣዖት ፤ ፍቹው ፡ ከሚት ፡ ፈቲሕ ፤ ከሚተ ፡ ፅርቃን ፤ ፈቲሐ ፡ አፍ ። ብዔል ፡ ፌኅር ፡ (ዕብራ ፤ ባዓል ፡ ፍ(ፕ)ዖር) ፡ በዓለ ፡ ከሚት ፤ እግዚእ ፡ ፈቲሕ ፤ በዓል ፡ ጣዖቱ ፡ ነው ። ከሚትና ፡ ፈቲሕ ፤ የአምልኮው ፡ ሥርዐት ፡ በፊቱ ፡ ቁሞ ፡ ዕራቍት ፡ መጣል ፤ እፍን ፡ እንዳቅማዳ ፡ መክፈት ፤ መልቀቅ ፡ ማፈሸግ ፡ ማዘጋት ፤ ዋሻ ፡ ማስመሰል ፡ ነውና ፤ ይህነን ፡ ያሳያል ፡ (መዝ ፡ ፻፭ ። ዘኍ፳፭ ፡ ፳፰ ። ፳፭ ፡ ፫) ።

**ፈድዮ** ፡ ዮት ፡ (ፈደየ ፡ ይፈዲ ፡ ይፍዲ ። ዕብ ፡ ፋዳህ ። ዐረ ፡ ፈዳ ፤ ቤዘወ) ፡ ዕዳ ፡ መክፈል ፤ ብድር ፡ መመለስ ፤ ዋጋ ፡ መስጠት ። ወኅጢአ ፡ ዘይፈዲ ። ፍድዩ ፡ ዕዳኪ ። ፈድየ ፡ ልቃሕ ። ወይፈድዮ ፡ ለኵሉ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ፡ (ማቴ፲፰ ፡ ፳፭ ። ፬ነገ ፡ ፬ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፪ ። ኢዮ፴፬ ፡ ፲፩) ።

**ፈዳዪ** ፡ የሚከፍል ፡ ከፋይ ፡ ሰጭ ። ፈዳዬ ፡ ዕዳ ። ፈዳዩሃ ፡ ለዛቲ ፡ ኀጢአት ። መኑ ፡ ውእቱ ፡ ፈዳዩ ፡ ዐስብ ፤ አኮኑ ፡ እግዚ ፡ (አርጋ ። ሐዋ፺ ፡ ፫ ። ዲ.ድ ፡ ፴፳) ።

**መፍዴ** ፡ (ዐረ ፡ ፊደት ። ዕብ ፡ ኬሴፍ) ፡ ጥሩ ፡ ብር ፤ ወርቅ ፤ ገንዘብ ፤ የሚያበድሩት ፡ የሚከፍሉት ። መፍዴ ፡ ዘኢኮነ ፡ ተምያነ ። አመ ፡ ይነሥኡ ፡ ረባሐ ፡ መክሊት ፡ መፍዴ ፤ እለ ፡ ያረብሑ ፡ ወርቀሙ ፡ በርዴ ፡ (ዘፍ፳፫ ፡ ፲፮ ። ስንክ ፡ ታኅ፫) ።

**ምፍዳይ** ፡ መክፈያ ፡ ሚዛን ፡ ቀና ፡ ሳዳን ። ወኀጢአቱ ፡ ምፍዳዩ ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፰) ።

**አፍደየ** ፡ አስከፈለ ፡ አስመለሰ ። ይዝብጥዎሙ ፡ ወያፍድዩዎሙ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፯) ።

**ተፈድየ** ፡ ተከፈለ ፤ ተቀበለ ። ዮም ፡ ለእመ ፡ ወሀብከ ፡ ጌሠመ ፡ ይትፈደየከ ። ትትፈደዩ ፡ ዕዳክሙ ፡ ወትሰክዩ ፡ (ሚራ፳ ፡ ፲፰ ። ኢሳ፶፰ ፡ ፫) ።

—፡ ተቀጣ ፡ ቅጣት ፡ ተቀበለ ። ይትፈደይ ፡ በከመ ፡ ግብረ ። ተፈድየት ፡ እምእደ ፡ እግዚ ፡ ካዕበተ ፡ ኀጢአታ ። በእፎ ፡ ኢይትፈደይ ፡ ወልድ ፡ በኀጢአተ ፡ አቡሁ ፡ (ኢዮ፳፬ ፡ ፳ ። ኢሳ፵ ፡ ፪ ። ሕዝ፲፰ ፡ ፲፱ ። ሉቃ፳፫ ፡ ፵፩) ።

**ፍድየት** ፡ መክፈል ፡ መክፈል ፡ አከፋፈል ፤ ክፍል ፡ ዕድል ፡ ዋጋ ፡ (ፊልክ ፡ ፫) ።

**ፍዳ** ፡ በቁሙ ፤ በቀል ፤ ዋጋ ፤ ብድር ፤ ብድራት ፤ ፍርድ ፤ ቅጣት ። ዓመተ ፡ ፍዳ ፡ ዘነአሃ ፡ ለጽዮን ። የዐስየከ ፡ ፍጡነ ፡ ፍዳ ፡ ጽድቅከ ። ለምንት ፡ ይፈድየኒ ፡ ዘንተ ፡ ፍዳ ። ይረክቡ ፡ ፍዳሆሙ ፡ (ኢሳ፴፬ ፡ ፰ ። ኢዮ፰ ፡ ፮ ። ፪ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፴፮ ። ፪ተሰ ፡ ፩ ፡ ፱) ።

**ፍዳ** ፡ (ዐቢይ ፡ አገባብ) ፡ ስለ ፡ ህየንተ ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። ፍዳ ፡ ዘተሠይጠ ፡ ዮሴፍ ፡ ከመ ፡ ገብር ፤ ኮነ ፡ እግዚአ ፡ (ዕር፲፱ ፡ ቀኖ፲፱) ።

**ፍዳ** ፡ (ደቂቅ ፡ አገባብ) ፡ በ ፡ ስለ ፡ ፈንታ ። ይፈዲ ፡ መንፈሰ ፡ ፍዳ ፡ መንፈስ ፤ ዐይነ ፡ ፍዳ ፡ ዐይን ። ፍዳ ፡ ወይን ፡ ይስተይ ፡ ማየ ፡ ዝናም ፡ (ዘፀ፳፩ ፡ ፳፫—፳፱ ። ቅኔ) ።

**ፈዲል** ፡ ሎት ፡ (ፈደለ ፡ ይፈድል ፡ ይፍድል ። ዕብ ፡ ባዳል ። ዐረ ፡ ፈጸለ) ፡ መለየት ፤ መምረጥ ፤ ለብቻው ፡ ማስቀመጥ ፤ የእሸት ፡ የዘር ፡ የመልካም ፡ ነገር ። ማመልከት ፤ ማለም ፤ በርሳስ ፡ በቀለም ። መፈደል ፤ የሌለ ፡ ያልነበረ ፡ ነገር ፡ እምንበ ፡ አልቦ ፡ ፈጥሮ ፡ መጣፍ ፤ ወይም ፡ መለፍለፍ ፤ መዋሸት ፡ መቀጠፍ ፤ የከፋ ። እገሌ ፡ ፈድሎ ፡ ያወራል ፤ ይህ ፡ እንት ፡ የፈደልኸው ፡ ነው ፡ እንዲሉ ።

**ፊደል** ፡ (ላት) ፡ በቁሙ ፤ ልዩ ፡ ምርጥ ፤ ዘር ፤ ቀለም ። ምልክት ፤ አምሳል ፤ የድምፅና ፡ የቃል ፡ መልክ ፡ ሥዕል ፤ መማለጫ ፡ ማስታወቂያ ። ዛቲ ፡ ፊደል ። ሆህያተ ፡ ፊደል ። ካህን ፡ ይኩን ፡ ከመ ፡ መሃሬ ፡ ጽሕፈት ፡ ዘይጽሕፍ ፡ ቅድመ ፡ ፊደላተ ፡ በእዴሁ ፡ ወእምዝ ፡ ይኤዝዞሙ ፡ ለሕፃናት ፡ ከመ ፡ ይጽሐፉ ፡ በ

አምሳሊሁ ። መምህረ ፡ ኮነ ፡ በበ ፡ ደወሉ ፤ ፊደላተ ፡ ዘጕቢቁ ፡ ሾሉ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፮ ። ድ፰ ። ፈ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፲፩ ። ቅኔ) ። ይቤ ፡ ትርጓሜ ፡ ፊደል ፤ ደቂቀ ፡ ኖኅ ፡ ሠለስቱ ፤ ሴም ፡ ወካም ፡ ወያፌት ። እምደቂቀ ፡ ሴም ፡ ተናገሩ ፡ ዕሥራ ፡ ወኀምስተ ፡ ልሳናተ ፤ ወጸሐፉ ፡ እምነ ፡ ፊደላት ፡ ሰመንተ ፤ ዘውእቶሙ ፡ ዐረቢ ፡ ሶርያ ፡ አጋዊ ፡ (ግእዝ) ፡ ዕብራዊ ፡ ፋርሳዊ ፡ ከለዳዊ ፡ ህንዲ ፡ ሲኒ ። ወእምደቂቀ ፡ ካም ፡ ተናገሩ ፡ ሠላሳ ፡ ወክልኤ ፡ ልሳናተ ፤ ወጸሐፉ ፡ እምነ ፡ ፊደላት ፡ ስድስተ ፤ ዘውእቶሙ ፡ ቅብጢ ፡ ኖቢ ፡ ባሻ ፡ ቂልቂ ፡ ፍልስጢ ፡ ቍብሻ ። ወእምደቂቀ ፡ ያፌት ፡ ተናገሩ ፡ ዐሠርተ ፡ ወኀምስተ ፡ ልሳናተ ፤ ወጸሐፉ ፡ ስድስተ ፡ ፊደላተ ፤ ዘውእቶሙ ፡ ዮናኒ ፡ ሮሚ ፡ አፍርንጊ ፡ ገርማኒ ፡ አርመኒ ፡ እንድልሺ ። ወኮና ፡ ሾሎን ፡ ልሳናት ፡ ሰብዓ ፡ ወክልኤቱ ፤ እለ ፡ ቦሙ ፡ ፊደል ፡ ዕሥራ ፡ እሙንቱ ፤ ወእለ ፡ አልቦሙ ፡ ፊደል ፡ ኀምሳ ፡ ወክልኤቱ ።

**ፈደለ** ፤ (ዐረ ፡ ፈ(θ)ደለ) ፤ በዛ ፤ ተረፈ ፤ ከልክ ፡ ዐለፈ ። ዘፍዱል ፡ ኀጢአቱ ፡ (አዋል) ።

**ፍዱል** ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ተረፍ ፤ ትሩፍ ፤ ፍጹም ፤ ብዙ ፡ ነኽ ፡ ትርፌ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ወልደ ፡ ፋድል ፡ (ማር ፡ ይሥ፩) ።

**ፈድፍዶ ፤ ዶት ፤ (ፈድፈደ ፡ ይፈደፍድ ። ዐረ ፡ ፈደ ፤ ፈድፈደ ፤ ፋደደ ፡ ፋዳዳ ፡ አለ ፤ ሮጠ ፡ በረረ)** ፤ መፈድፈድ ፤ መብዛት ፤ በልጅ ፡ መክበር ፤ ከስፍር ፡ ከቍጥር ፤ ከልክ ፡ ከመጠን ፡ ማለፍ ፡ መትረፍ ፤ መላቅ ፡ መብለጥ ፤ መጽናት ፡ መበርታት ። ፈድፈዱ ፡ ወበዝኁ ፡ ጥቀ ፤ ወከማሁ ፡ ይፈደፍዱ ። ወኮነ ፡ ሾሉ ፡ መዋዕለ ፡ ትንቢቱ ፡ ዕሥራ ፡ ዓመት ፡ ወዘይፈደፍድ ። ተወሰከ ፡ ዘመኑ ፡ ወፈድፈደ ፡ እምነ ፡ ኍልቈ ። አልቦ ፡ ዘእፈደፍደከ ፡ አነ ። ወንፈድፍድ ፡ ውስተ ፡ ትሩፋት ። ቃለ ፡ ንጉሥ ፡ ፈድፈደ ፡ እምቃለ ፡ ኢዮአብ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፮ ። ስንክ ፡ ጥር ፲፰ ። ንሐ፴ ። ዘፍ፵፭ ፡ ፵ ። ማር ፡ ይሥ፪ ፡ ፰ ። ፩ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፬) ። በፈድፈደ ፡ ፈንታ ፡ ተፈድፈደ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ከመ ፡ ይትፈድፈድ ፡ ውስተ ፡ አእምሮ ፡ ወጥይቁ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፵፫) ።

**ፍድፉድ** ፤ የበዛ ፡ ብዙ ፤ ፍጹም ፡ ትሩፍ ። ተአምሪክ ፡ ዘኍላቊሁ ፡ ፍድፉድ ። እምብዙኅ ፡ ወእምነ ፡ ፍድፉድ ፡ ገድል ። በትሕትና ፡ ፍድፉድ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳፭ ። ታኅ፳፮ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፬ ፡ ፳) ።

**ፍድፋዴ** ፤ ብዛት ፡ መብዛት ፤ አበዛዝ ፤ ብልጫ ፤ ላቂያ ፤ ትርፍ ። ፍድፋዴ ፡ መዋዕል ፤ ፍድፋዴ ፡ አእምሮ ። ፍድፋዴ ፡ ክብሩ ። በእንተ ፡ ተበይኖ ፡ ፍድፋዴ ፡ ባሕታውያን ። ምንት ፡ ፍድፋዴሁ ፡ ለሰብእ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፬ ። አፈ ፡ ድ፭ ። ፊልክ ፡ ፫ ። መክ፭ ፡ ፫) ።

**ፍድፍድና** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ብዙኅነት ፤ ታላቅነት ። ፍድፍድና ፡ ረባሒ ፡ (ፊልክ ፡ ፳፫) ።

**ፈድፋድ ፤ (ዳት)** ፤ ጽናት ፤ ብርታት ። ፍድፋጅ ፤ ትርፍ ፤ ቅሬታ ፤ ብልጫ ። ወፈድፋዶንሰ ፡ እምእላ ። ወፈድፋዳተኒ ። ምንት ፡ ፈድፋዶሙ ፡ እምኔነ ። ዛቲ ፡ ባሕቲታ ፡ ፈድፋዶሙ ፡ (መገ ፡ ቾ፱ ። ዘኍ፱ ፡ ፳፮ ። ሔኖ፲፱ ፡ ፮ ። ሄርማ) ።

**ፈድፋደ** ፤ እጅግ ፤ በጅግ ፤ ይበልጥ ፤ ይልቅ ፤ እምብዛ ። ጥቀን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ወንድም ፡ ነው ። ተከዘ ፡ ፈድፋደ ። ወፈርሆ ፡ እንከ ፡ ፈድፋደ ። ጻድቅ ፡ ወጠቢብ ፡ ፈድፋደ ። ኢየሐዩ ፡ ፈድፋደ ፡ እምእት ፡ ወዕሥራ ፡ ወኀምስቱ ፡ ዓመት ። ሀገር ፡ ዘሀሰዉ ፡ ውስቴታ ፡ ሰብእ ፡ ፈድፋደ ፡ እምዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ እልፍ ። ወፈድፋደ ፡ ጸንዑ ፡ እምቀደምቶሙ ፡ (ሉቃ፲፰ ፡ ፳፫ ። ፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፱ ። መክ፮ ፡ ፲፮ ። ኩፋ ፡ ፴፭ ። ዮና፬ ፡ ፲፩ ። መገ ፡ ፻፴፰) ። ጥቀ ፡ ሲጨመርበት ፡ እጅግ ፡ ፈጽሞ ፡ ጭራሽ ፡ በጭራሽ ፡ ይኾናል ። ሠነይኪ ፡ ጥቀ ፡ ፈድፋደ ። ወፈርሁ ፡ ጥቀ ፡ ፈድፋደ ። ወፈድፋደ ፡ ጥቀ ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፲፫ ። ዮዲ፱ ፡ ፸ ። ፰ ፡ ፲፰) ።

**አፈድፈደ** ፤ አበዛ ፤ አበለጠ ፤ አጠና ፤ አበረታ ። ኢታፈድፍድ ፡ ምስሌሁ ፡ ተናግሮ ። አፈድፈድኪ ፡ ኀጢአተኪ ፡ እምኔሆን ። ጻመውኩ ፡ ለአፈድፍዶ ፡ ፍቅረ ፡ አውግስጦስ ። ወአፈድፈዱ ፡ ጸሊአተ ፡ (ሚል ፲፫ ፡ ፲፩ ። ሕዝ፲፮ ፡ ፶፩ ። ዮሴፍ ። ዘፍ፴፯ ፡ ፰) ።

**መፈድፍድ** ፤ የሚያበዛ ፤ አብዢ ። ብዙ ፡ እጅግ ፤ በያሌ ። ወመፈድፍዶሙ ፡ የዐቅቡ ፡ ዕቅበተ ፡ ቤተ ፡ ሳኦል ፡ (፩ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፳፱) ።

**ፍሂቅ ፤ ቆት ፤ (ፈሀቀ ፡ ይፍህቅ ፡ ይፍሀቅ ። ዐረ ፡ ፋቀ ፤ ፈአቀ)** ፤ ማፋቅ ፤ ሕቅ ፡ ሕቅ ፡ ማለት ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ መተንፈስ ፤ የድሙይ ፤ ለባለሴናም ፡ ይኾናል ። ትፍህቅ ፡ ነፍስየ ፡ ወትልህስ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፲፭) ።

**ፈሃቂ** ፤ የሚያፍቅ ፤ አፋቂ ፤ ሕቅ ፡ ሕቅ ፡ ባይ ።

**ፋሀቅ ፤ ፈሀቅ** ፤ ፋቅ ፤ ሕቅታ ፤ ስርቅታ ።

**ፈሀቀ ፤—ፋቀ ፤ አነጠጠ ፤—ፍሒቅ ፡ ፈሐቀ ።**

**ፈሀረ ፤—ፋረ ፡ ቈፈረ ፤—ፍሒር ፡ ፈሐረ ።**

**ፈሀረ ፤—ዐጨ ፤—ፍኂር ፡ ፈኀረ ።**

**ፈሀረስት ፤ (ዐረብ)** ፤ የገጽና ፡ የምዕራፍ ፡ ማውጫ ፤ ምልክት ። የሃይማኖት ፡ አበው ፡ ታሪክ ፤ እንቀጽ ፡ በእንተ ፡ እገሌ ፡ እያለ ፡ ሊቃውንቱን ፡ በተራ ፡ የሚጥፍ ።

**ፈዋ ፤—የበሰበሰ ፤—ፈየወ ።**

**ፈዊዝ ፤ ዞት ፤ (ፎዘ ፡ ይፈውዝ ፡ ይፋዝ)** ፤ መወልወል ፤ መሰንገል ፤ እድፋን ፡ ዝገቱን ፡ መጥረግ ፡ መፈግፈግ ፤ ማደስ ፡ መኰላት ፤ ፈጽሞ ፡ ማጥራት ፤ የወርቅ ፡ የብር ፡ የማዕደናት ፡ (አርጋ ፡ ፫ና ፡ ፩) ።

**ፋዝ ፤ (ዕብ ፡ ፉ ፡ ፓዝ)** ፤ አፈዝ ፤ ቈፋዝ ፤

ጥሩ ፡ ወርቅ ፤ የአፈ ዝን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። ወርቅ ፡ ለገንዘብ ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ፤ ስምንቱ ፡ አስተጋባኢ ፡ ነው ፤ ፋዝ ፡ ግን ፡ ለወርቅ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ያውም ፡ ለጥሩው ፡ ለመዠመሪያው ። የማእዝ ፡ መሳሾች ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ይል ቁንም ፡ ከወርቅ ፡ ጋራ ፡ በሚማፈርበት ፤ ዕንቍ ፡ ብለ ውታል ። እምወርቅ ፡ ወእምዕንቍ ። አክሊለ ፡ ዘእ ምዕንቍ ፡ (መዝ ፡ ፲፰ ። ፳ ። ምሳ፳ ፡ ፲፱) ።

**ፋዝ** ፤ የሰው ፡ ስም ፤ (ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ማለት ፡ ይመስላል) ። ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ፋዝ ፡ ንጉሠ ፡ ህን ደኬ ፤ ወበቱ ፡ ለፋዝ ፡ ነጊያት ፡ መስተቃትላን ፡ (ዜና ፡ እስ) ።

**ፋውሎ ፤ ሎት ፤ (ፋወለ ፡ ይፋውል ፡ ይፋውል)** ፤ ማስጠንቈል ፤ ጠንቋይ ፡ መጠየቅ ።

**ተፋወለ** ፤ ጠንቈለ ፤ አሟረተ ። መሠርይ ፡ ወዘይትፋወል ፡ በፍሬ ፡ ዕፀው ፡ ወዘገሥል ፡ ዴበ ፡ ሐ መድ ። ኢትኩኑ ፡ እምእለ ፡ የዐቅቡ ፡ ለዓታተ ፡ ወኄ ራይያነ ፡ ዕለታት ፤ ወኢረኣዩ ፡ ከዋክብት ፤ ወኢእም እለ ፡ ይትፋወሉ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭ ፡ ፭፻ ፡ ፲)።

**ፋል ፤ (ላት ። ትግ ፡ ወዐረ)** ፤ ገድ ፤ መላ ፡ ጥንቈላ ፤ ሟርት ፤ በፍሬ ፡ በቅንጣት ፡ በጠጠር ፡ በዛጕል ፡ የሚኾን ፤ ሰውን ፡ ወደ ፡ አምልኮ ፡ ባዕድ ፡ የሚስብ ፡ የሰ ይጣን ፡ ፋሎ ፤ ወይም ፡ ልባብ ፤ ፋሎ ፡ ጋልኛ ፡ ነው ። ፋላ ፡ ፊት ፤ ፋሎ ፡ የፊት ። ቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሰብአ ፡ ፋል ። አድምዖ ፡ ፋል ። አሕባም ፡ ወፋላት ፡ ከንቱ ፡ እሙንቱ ፡ ወሐሰት ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ቀሌ ። ፈላስ) ።

**ፋላዊ** ፤ ፈላም ። ፈልማ ፤ ወፍሬም ፡ መሬት ።

**ፋል ፤ (ዕብ ፡ ፎል ። ሱር ፡ ፋላእ ። ዐረ ፡ ፋል)** ፤ ባቄላ ፤ የባቄላ ፡ ዐይነት ፤ መላው ፡ ያበባ ፡ እ ኽል ፡ ኹሉ ፤ በውስጥ ፡ መንታንት ፡ ያለው ፤ የሚከከ ፡ የሚገመስ ፤ የሚፈለጥ ፡ የሚፈለቀጥ ፤ ቈርበታም ፤ ሻር ተኞች ፡ እንዳሸዋና ፡ እንደ ፡ ጠጠር ፡ እያፈሡ ፡ እየበ ተኑ ፤ እየቃሙ ፡ እየገቱሙ ፡ ፋል ፡ የሚያደርጉበት ። ሖ መርን ፡ ተመልከት ፤ ፋል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ፋል ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ፋል ፡ ብሂል ፤ በቈላ ፡ (ጥሬ ፡ ሰዋ) ። ፋሲ ፡ ወብርስን ፡ (ሕዝ፬ ፡ ፱) ።

**ፋውል ፤ ፋላት** ፤ ባቄሎች ፡ ያበባ ፡ እኽሎች ።

**ፎቀ ፤ (ይፈውቅ ፡ ይፋቅ ። ዕብ ፡ ፋቅ ፡ ያፈቅ)** ፤ ዘለለ ፡ ጓን ፤ ላይ ፡ ላይ ፡ አለ ፤ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከውስጥ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጣ ፡ ገነፈለ ፤ የፈሳሽ ፤ ያውሬ ። ፎቆ ፡ ፈቀን ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ፎቃንስ ፤ (ብ ፡ ፈዋቅንስ ። ዐረ ፡ ፎቃኒ ፤ ላዕላዊ)** ፤ ጕሬዛ ፤ ጠጕራም ፡ ነጭና ፡ ጥቍር ፤ ጭራው ፡ ፍጹም ፡ ነጭ ፤ የጠጣ ፡ ወገን ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ የሚኖር ፡ ከዛፍ ፡ ወደ ፡ ዛፍ ፡ የሚዘል ፡ የሚወረወር ። የጕሬዛ ፡ ዐይነት ፡ ወፍ ፡ ጕሬዝማ ፡ አሞራ ። በፎቃንስ ፡ ፈንታ ፡ ፎንቃስ ፡ ይላል ፤ ከፈንክስ ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ። ፎንቃስ ፡ ወቋዓት ፡ (ሔኖ፹፱ ፡ ፲) ።



ፎቃንስ ፤

**ፈውሰ ፤ ሰት ፤ (ፈወሰ ፡ ይፌውስ ፡ ይፈውስ ። ዐረ ፡ ሽፋ)** ፤ መፈወስ ፤ ማዳን ፤ ማሻር ፤ መድኀኒት ፡ መስጠት ። ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ፈውስ ፡ ርእ ሰከ ። ፈነወኒ ፡ ከመ ፡ እፈውስከ ። እፌውሰክሙ ፡ ቍስለክሙ ። ፈወስናሃ ፡ ለባቢሎን ፡ ወኢሐይወት ። መኑ ፡ ይፌውሰኪ ፡ (ሉቃ፬ ፡ ፳፫ ። ጦቢ፲፪ ፡ ፲፬ ። ኤ ርም ፡ ፳፪ ። ፳፰ ፡ ፱ ። ሰቈ፪ ፡ ፲፫) ።

**ፈዋሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት)** ፤ የሚፈውስ ፤ ፈዋሽ ፤ ሐኪም ። ፈዋሲሁ ፡ ለልብየ ። ፈዋሴ ፡ ዱያን ፡ በንፍግቱ ፡ (ኪዳ ። ድራሲ) ።

**መፈውስ ፤ (ስት ፡ ሳን ፡ ሳት)** ፤ ዝኒ ፡ ከ ማሁ ። መፈውሰ ፡ ልብ ። መፈውስ ፤ ልሳን ፤ ዕፀ ፡ ሕ ይወት ። መፈውሰ ፡ ነፍስ ፡ ወመፈውሰ ፡ ሥጋ ። ክህ ናትኒ ፡ ለነፍስ ፡ መፈውሳን ፡ (ምሳ፲፬ ፡ ፬ ። ፲፭ ፡ ፬ ። ቅዳ ፡ መስተ ። ተረ ፡ ቄርሎ) ።

**ምፍዋስ** ፤ መካን ፡ ፈውስ ፤ ቤት ፡ ድውያን ፤ ቤት ፡ ክሊያን ፤ ጠበል ፡ ማምቅ ፡ ፍል ፡ ውሃ ። ቦ ፡ እለ ፡ መ ጽኡ ፡ ውስተ ፡ ምፍዋስ ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን ። ከመ ፡ ይስአሉ ፡ ዘእምኅቤክ ፡ ርቅየተ ፡ ወሕይወተ ። ወቦ ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ምጥማቃት ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፱ ። ሊጠን ። ዮሐ፭ ፡ ፪—፱) ።

**አፈወሰ** ፤ አስፈወሰ ፤ መድኀኒት ፡ አስደረገ ። አፈውሶ ፡ እምለምጹ ፡ (፬ነገ ፡ ፭ ፡ ፯) ።

**ተፈወሰ** ፤ በቁሙ ፤ ዳነ ፤ ሻረ ፤ ታከመ ፤ መድ ኀኒት ፡ ተደረገለት ። ወሰእለሂ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይትፈ ወሱ ፡ አሕየዎሙ ። ከመ ፡ ይትፈወስ ፡ እምቍስሉ ። ተፈወሰ ፡ ውእቱ ፡ ማይ ። ሀለወ ፡ ይትፌወስ ፡ ንድ ፈቶ ። እንበለ ፡ ትሕምም ፡ ተፈወሰ ፡ (ሉቃ፱ ፡ ፲፩ ። ፬ዜና ፡ ፳፱ ። ፰ ። ፬ነገ ፡ ፪ ፡ ፳፱ ። ፱ ፡ ፲፭ ። ሚራ፲፰ ፡ ፲፱) ።

**ፍዉስ** ፤ የተፈወሰ ፤ የታከመ ፤ የሻረ ፡ የዳነ ፤ ደኅና ፤ ባለጤና ።

**ፍዋሴ** ፤ ፈውስ ፡ ማግኘት ፤ መፈወስ ፤ አፈዋ ወስ ፤ ፍወሳ ።

**ፈውስ ፤ (ሳት)** ፤ በቁሙ ፤ መልካም ፡ መድን ኒት ፤ የሚያድን ፡ የሚያሽር ። ለገቢረ ፡ ፈውስ ። ፍሬሁ ፡ ለሲሳይ ፡ ወቈጽሉ ፡ ለፈውስ ። አልባቲ ፡ ፈውስ ፡ ለቍስላ ። ፈውሰ ፡ ደዌሆሙ ፡ (አፈ ፡ ተ፱ ። ሕዝ፵፯ ፡ ፲፪ ። ሚራ፳፭ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፲) ።

—፤ ክፉ ፡ መድኀኒት ፤ የሚያም ፡ የሚገድል ፡ ሥራይ ፡ የሚኾን ። ዘይገብር ፡ ሥራየ ፡ ወሰገለ ፡ ወይሰምዕ ፡ ነገረ ፡ ፈውሳት ፡ ወይትአምን ፡ (ቀሌ) ።

እብነ ፡ ፈውስ ፤ ኩል ፤ ያይን ፡ መድኀኒት ፡ (ራእ ፡ ፫፡፲፰) ። መጽሐፈ ፡ ፈውስ ፤ መጽሐፈ ፡ መድኀኒት ፤ ሥጋዊ ፤ ወይም ፡ መንፈሳዊ ፤ ንስሓ ፡ ቀኖና ፤ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ ሥርዐት ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ያለ ።

**ፈውስ ፡ መንፈሳዊ ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ የቀኖና ፡ መጽሐፍ ።

**ፎት ፤ ፈወተ ፤ (ዕብ ፡ ፋታህ) ፤** ሳቀ ፡ ከሕግ ፡ ከመንገድ ፡ ወጣ ፤ ጌገየን ፡ እየ ።

**ፎት ፤ ፈውት ፤ (ትግ ፡ ፈዊታ ። ዕብ ፡ ፈቱይ) ፤** አመንዝራ ፡ ቤት ፤ ጋለሞታ ፤ ስታ ፡ የምታስት ፤ የምታሳስት ።

**አፈዋት ፤** አመንዝሮች ፡ የሚያስቱ ፡ ልብ ፡ የሚሰልቡ ፡ ሽቱ ፡ የሚዘግቡ ፤ አፈኞች ፡ አፈ ፡ ዋኞች ። አፈውን ፡ ተመልከት ።

**ፍሕሐት ፤ (ዕብ ፡ ፋሕ ፡ ያፋሕ ፤ ሐቅ ፡ አለ) ፤** የሞቀች ፤ ነፍሷ ፡ የወጣ ፤ ሙቅ ። ይኸውም ፤ ባሕረ ፡ ኤው ፡ ናት ። እምባሕረ ፡ ፍሕሐት ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ሰን ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱) ።

**ፍሒል ፤ ሎት ፤ (ፈሐለ ፡ ይፍሕል ፡ ይፍሐል ። መሐዘ) ፤** ማፈል ፤ መጕልመስ ፤ መሴስን ፡ መቀንዘር ፤ መገሰል ፡ መከመር ፤ መፈጣት ፡ መቅበጥበጥ ፡ መፈናጠር ፤ መዳራት ፡ መቃበጥ ፡ መቀናጣት ፤ አእምሮ ፡ ማጣት ። ፈሐልክሙ ፡ ከመ ፡ አልሕምት ። ውእቱ ፡ አርዌ ፡ ይመጽእ ፡ እንዘ ፡ ይፍሕል ። ፍሒሎትከኒ ፡ ዐርገ ፡ ኀቤየ ፡ (ኤር ፳፯ ፡ ፲፭ ። ሄርማ ። ፱ ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፳፰) ።

**ፈሐል ፤ (ዐረ ፡ ፈሕል) ፤** ድንጉላ ፤ አለሌ ፤ እውራ ።

**ፈሓል ፤ ፋሕል ፤** ዝሙት ፤ ሴሰን ፤ ቅንዝር ፤ መፀት ፤ ዋዕየ ፡ ፍትወት ፤ ስካር ፤ ቀንጣን ። ሲቃ ፡ ፈሓል ። ፈሓሰ ፡ ዝሙት ፤ ኢበነፍስቱ ፡ ሥጋ ፡ ምስለ ፡ ፈሓሰ ፡ እንጐዕ ፡ ዘይክው ፡ እሳተ ፡ ዴበ ፡ አባል ። ጽጋብ ፡ ኢይምጽአኒ ፡ ወፈሓል ፡ ኢይክርየኒ ። ፋሕሎ ፡ ሰወይን ፡ (ቀኖ ፡ ሐዋ ። አርጋ ፡ ፯ ። ሚራ፳፫ ፡ ፺ ። መቃ ፡ ፯፯) ።

**ፍሒም ፤ ሞት ፤ (ፍሕመ ፡ ይፍሕም ፡ ይፍሐም ። ዕብ ፡ ጋሐል) ፤** መፋም ፤ መጋል ፤ መጋም ፤ መርሰን ፡ እሳት ፡ መኾን ፤ መንደርከክ ፤ መብሰል ፤ የንፉት ፡ የብረት ። መክሰል ፤ መጥቈር ፤ ጥቀርሻ ፡ መምሰል ። በዐረብና ፡ በትግሬ ፡ ግን ፤ ፈሀመ ፡ ብሎ ፡ ስማ ፡ ተረዳ ፡ ይላል ። ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገባል ፤ ምጣዱ ፡ ሰምቷል ፡ እንዲሉ ፤ ግሷል ፡ ቢሉ ።

**ፍሕም ፤ (ዕብ ፡ ጋሔሌት ። ዐረ ፡ ፮ምር) ፤** በቁሙ ፤ ፍም ፤ እሳታዊ ፡ ምርት ፤ ዝግን ፤ በገል ፡ የሚታፈም ፤ ክፋይ ፤ ትንታግ ። እመ ፡ ነፋኅካሃ ፡ ለፍሕም ፡ ትነድድ ። ወወሪዶሙ ፡ ምድረ ፡ ረከቡ ፡ ፍሕመ ፡ ብቁጸ ፡ ወዓሣ ፡ ጥቡሰ ። አቡየ ፡ ወእኔ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሳት ፡ ወነበልባል ፡ ወፍሕም ። ማዕጠንት ፡ ዘወርቅ ፡ አንተ ፡ ጾርኪ ፡ ፍሕመ ፡ እሳት ፡ (ሚራ፳፰ ፡ ፲፬ ። ዮሐ፳፩ ፡ ፱ ። ቅዳ ፡ ግሩ ። ኤፍ ፡ ፩) ።

**ፍሕም ፤ (ዕብ ፡ ፌሓም ። ሱር ፡ ፋሕማ ። ዐረ ፡ ፈሕም ፤ ፈሐም) ፤** ከሰል ፤ የእሳት ፡ ትራፊ ፤ መልሶ ፡ እሳት ፡ የሚበላው ፤ የንጨት ፡ የደንጊያ ፡ ማገዶ ።

**አፍሓም ፤** ፍሞች ፤ ከሰሎች ። አፍሓመ ፡ እሳት ፡ ቅድሜሁ ፤ ወወገሮ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ዘአፍሓም ። መፍርህኬ ፡ አብቅዎ ፡ ክናፍር ፡ ለውሒጠ ፡ አፍሓም ፡ ርሱን ። አፍሓም ፡ ዘይንበለብል ፡ (ኤርሚ፱ ፡ ፳፱—፳፫ ። ቅዳ ፡ ቈር ። ዳንኤ ፡ ፱) ።

**አፍሐመ ፤** አጋለ ፤ አጋመ ፤ አፋመ ፡ አከሰለ ፤ ፍሙን ፡ ከሰል ፤ ከሰሉን ፡ ፍም ፡ አደረገ ።

**ፈሐቀ ፤—ሕቅ ፡ ሐቅ ፡ አለ ፤—ፍሂቅ ፡ ፈሀቀ ።**

**ፍሒቅ ፤ ቆት ፤ (ፈሐቀ ፡ ይፍሕቅ ፤ ይፍሐቅ ። ዕብ ፡ ማሐቅ) ፤** መፋቅ ፡ መፈቅፈቅ ፤ መላግ ፤ ማንጠጥ ፡ መፈግፈግ ፤ ማለዘብ ። ዘሰረቀ ፡ ወዘፈሐቀ ፡ ወዘሄደ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ። ፈሐቁ ፡ ቍስሎ ፡ በአጽርቅተ ፡ ጸጕር ፡ (ባለመጣፍ ። ስንክ ፡ ሐም፲፱) ።

**ፈሓቂ ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት ፤ ፈሐቅት) ፤** የሚፍቅ ፤ ፋቂ ፤ አንጣፊ ፤ አለዛቢ ። ከመ ፡ ዘየኀድር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ፈሓቂ ። ወቀርተ ፡ እብን ፡ ወፈሐቅት ፡ (ማር ፡ ይሥ ። ሄዜና ፡ ፳፬ ፡ ፪) ።

**መፍሐቅ ፤** የሚፍቅ ፤ ፋቂ ፤ መፋቂያ ፡ መሣሪያ ። መፍሐቀ ፡ ኀበዋት ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፭) ።

**ምፍሓቅ ፤** መፋቂያ ፡ ማንጠፊያ ፤ ቦታ ፡ ስፍራ ።

**ተፍሕቀ ፤** ተፋቀ ፤ ለዘበ ፤ ተንጠጠ ።

**ፍሑቅ ፤** የተፋቀ ፤ የተንጠጠ ፡ ንጥ ፡ ቅርጽ ፤ ልዝብ ፡ ልሙጽ ። ከመ ፡ ማዕክክ ፡ ፍሑቅ ። እደዊሁ ፡ ፍሑቃት ፡ እለ ፡ ወርቅ ። አጻብዒሁ ፡ ፍሑቃት ፡ (ማሕ፭ ፡ ፲፬ ። ፺ ፡ ፫ ። ድጓ) ። በፍሑቅ ፡ ፈንታ ፡ ፍሕቁ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ቅፍለ ፡ ወርቅ ፡ ፍሑቅ ። እምወርቅ ፡ ንጹሕ ፡ ፍሑቅ ፡ ግበሩ ። ብሩር ፡ ዘፍሑቅ ፡ እሙንቱ ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፲፰ና ፡ ፴፩ ። ኤር፲ ፡ ፱) ።

**ፍሕቁ ፤** ፍሕቀት ፡ ፍቆሽ ፡ አፋፋቅ ፡ አቀራረጥ ፡ አንጣጠጥ ፤ ጌጥ ፡ ቅርጥ ።

**ፍሒር ፤ ሮት ፤ (ፈሐረ ፡ ይፍሕር ፡ ይፍሐር ። ዕብ ፡ ሐፋር ። ዐረ ፡ ሐፈረ) ፤** መፋር ፤ መቈፈር ፡ ማፋራት ፡ መፈለግ ፡ የጠፋን ፡ የተቀበረን ። እለ ፡ ይትሜነይዎ ፡ ለሞት ፡ ወይፍሕርዎ ፡ ከመ ፡ መድፍን ፡ (ኢዮ፫ ፡ ፳፩) ። በቀበረ ፡ ፈንታ ፡ ፈሐረ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ወይፍሕርዎሙ ፡ አሕዛበ ፡ ምድር ፡ (ሕዝ፴፱ ፡ ፲፫) ።

**ፈሓሪ** ፡ የሚፍር ፡ የሚቈፍር ፤ ፋሪ ፡ ቈፋሪ ፡ ፋሮ ።

**ፈሐረ ፡—ዐጨ ፡—ፍኂር ፡ ፈኀረ ።**

**ፍሒስ ፡ ሰት ፡ (ፈሐሰ ፡ ይፍሕስ ፡ ይፍሐስ ። ዕብ ፡ ፋሐስ)** ፡ ማሸት ፤ ማፍተልተል ፡ ማፍረጥረጥ ፤ ማዋሐድ ፡ ማዛመድ ፤ የቡሖ ፡ የቀለም ። ማቅላት ፤ በቀይ ፡ ቀለም ፡ ማለል ፤ የልብስ ፡ የፈትል ። ባለብለዮች ፡ ግን ፤ ፈተለ ፡ ገመደ ፡ ጐነጐነ ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ።

**ፈሓሲ ፡ (ዐረ ። ትግ ፡ ፈሕሰ ፤ ዐማ ፡ ነቀፈ)** ፡ ቈፋሪ ፡ መረመረ ፡ አገላበጠ ፤ መላልሶ ፡ ጠየቀ ፤ የዳኛ ፡ የሐኪም ።

**ተፍሕሰ** ፡ ታሸ ፤ ተዋሐደ ፤ ቀላ ፡ ታለለ ፤ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ገባ ፤ ልብሱ ፡ ፈትሉ ።

**ፍሑስ ፡ (ዕብ ፡ አርጋማን)** ፡ የታለለ ፡ ቀለም ፡ የገባ ። ቀይ ፡ ቀለም ፤ ደባባ ፤ የሮማን ፡ ፍሬ ፡ ዐይነት ፤ ቅላቱ ፡ በጣም ፡ ያልደመቀ ። ወዕፍሮ ፡ ርእሰኪ ፡ ከመ ፡ ሜላት ፡ ፍሑስ ፡ (ማሕ፯ ፡ ፭) ።

**ፍሕሶ ፡ (ዕብ ፡ ሻኒ ። ዐረ ፡ ቂርሚዝ)** ፡ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ቀይ ፡ ቀለም ፤ ቀይ ፡ ፈትል ፤ ቀይ ፡ ሐር ። ለይንና ፡ ኳኳን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ፡ ከመ ፡ ፍሕሶ ፡ ቀይሕ ፡ ከናፍሪሃ ፡ (ማሕ፬ ፡ ፫) ።

—፤ ደበባ ፡ ስም ፤ ፍጹም ፡ ቀይ ፡ አበባ ፤ ጕተናማ ፡ ዐይነቱ ፡ ቅላቱ ፡ ከበባ ፡ ኹሉ ፡ የተለየ ፤ እንድኪ ፡ ጃዊ ፡ የሚመስል ። ቀዮ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ፍኂር ፡ ሮት ፡ (ፈኀረ ፡ ይፍኅር ፡ ይፍኀር ። ዕብ ፡ ማሀር ፤ ዐሬስ)** ፡ ማጨት ፤ ቤት ፡ ልጅን ፡ መመኘት ፤ መፈለግ ፡ መሻት ፤ ለጡኝ ፡ ማለት ፡ ለሚስትነት ። (ተረት) ፤ ልጃገረድ ፡ ዐሥር ፡ ያጭሽ ፡ አንድ ፡ ያገባሽ ። እሺ ፡ ካሰኙ ፡ በኋላ ፡ የጋብቻውን ፡ ውል ፡ ማሰር ፡ ማቆም ፤ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መግባት ፤ መፈጣጠም ። እፍኅረኪ ፡ ለኪ ፡ ብእሲተ ። ፍኂርሰ ፡ ኪዳን ፡ ውእቱ ፡ ወተስፋ ፡ ዘይቀድም ፡ እምእውስቦ ፡ ወይከውን ፡ በመጽሐፈ ፡ መልእክት ፡ ወዘእንበለ ፡ መጽሐፍ ፡ (ሆሴ፪ ፡ ፳፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፫) ። ሐፀየን ፡ ተመልከት ።

**ፈኃሪ** ፤ የሚያጭ ፤ ዐጭታ ፤ ዕጮኛ ። ፈኃሪሃ ፡ ለማርያም ። ፈኃሪ ፡ እው ፡ ዘተፍኅረት ። ለእመ ፡ ሞተ ፡ አሐዱ ፡ እምፈኃርያን ፡ ቅድመ ፡ አውስቦቱ ፡ (ማቴ፩ ፡ ፲፮ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፪ ። ቀኖ፪ ፡ ፫) ።

**ተፍኅረ** ፡ ታጨ ፡ ተፈለገ ፤ ዕጮኛ ፡ ኾነ ፡ ለማቢ ፡ ተሰጠ ። ድንግል ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሐፀይት ፡ እው ፡ ተፍኅረት ፡ ለብእሲ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፮ ፡ ፰ ። ማቴ፩ ፡ ፲፰ ። ሉቃ፩ ፡ ፳፯) ።

**ፍኁር** ፡ የታጨ ፤ ዕጮኛ ፡ የኾነ ። ማርያም ፡ ፍኅርትከ ፡ (ማቴ፩ ፡ ፳) ።

**ፍኅረት** ፡ ማጨት ፤ መታጨት ፤ አስተማጨት ፡ የጋብቻ ፡ ውል ። በእንተ ፡ ፍኅረት ፡ ወሕጼ ። ዘሐዘነት ፡ በእንተ ፡ ሞተ ፡ ኢትትከላእ ፡ እምፍኅረት ። ፈቲሐ ፡ ፍኅረት ። ዐረቦን ፡ ዘፍኅረት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፫) ።

**እፍኅርት ፡—ማጨት ፡—እፍርኅት ፡ ፈርኀ ።**

**ፈጢን ፡ ኖት ፡ (ፈጠነ ፡ ይፈጥን ፡ ይፍጥን ። የነጠፈ ፡ ግልብጥ)** ፡ መፍጠን ፤ መቀልጠፍ ፡ መቸኰል ፤ መጣደፍ ፤ ማረበድ ፤ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ማለት ፤ ያካኼድ ፡ የሥራ ። ይፈጥን ፡ መብረቅ ፡ በፈቃዱ ። ወበቃሉ ፡ ይፈጥን ፡ ሐሪቱ ። ሐሰታ ፡ ለጥበብ ፡ ይፈጥን ፡ እምዘሉ ፡ ሐሰት ፡ (ሢራ፵፫ ፡ ፳፭ ፡ ፲፫ ። ጥበ፯ ፡ ፳፬) ።

**ፈጣን** ፤ በቁሙ ፤ ቀልጣፋ ፤ ችኩል ። እምዝኩ ፡ ሞት ፡ ፈጣን ። ፀአቱ ፡ ፈጣን ፡ (አዋል) ።

**ፍጡን** ፡ የፈጠነ ፡ የቸኰለ ፤ ፈጣን ፤ ችኩል ፡ ቅርብ ፡ ቶሎ ። ይኩን ፡ ሖሩ ፡ ብእሲ ፡ ፍጡነ ፡ ለሰሚዕ ፡ ወጕንዱየ ፡ ለነቢብ ። ዘሉ ፡ ፍጡን ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡ ለእንተ ፡ ምዕር ። መልአክ ፡ ዘፍጡን ፡ ረድኤቱ ። በፍጡን ፡ እው ፡ በዕድሜ ፡ (ያዕ፩ ፡ ፲፱ ። ሢራ ፲፰ ፡ ፳፮ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፮) ።

**ፍጡነ** ፤ ፈጥኖ ፤ ቸኵሎ ፤ እኹን ፡ ቶሎ ፤ በቶሎ ። ዘፍጡነ ፡ የአምን ፡ ቀሊል ፡ ልቡ ። ፍጡነ ፡ ይርከበነ ፡ ሣህልከ ። እመጽእ ፡ ፍጡነ ። ዘትገብር ፡ እንከ ፡ ፍጡነ ፡ ግበር ፡ (ሢራ፲፱ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፸፰ ። ራእ፳፪ ፡ ፳ ። ዮሐ፲፫ ፡ ፳፯) ።

**ፍጥንት** ፡ በቁሙ ፤ መፍጠን ፤ አፈጣጠን ፤ ችኰላ ፤ ቅልጥፍና ፤ ጥድፊያ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፪) ።

**አፍጠነ** ፡ አፈጠነ ፤ አስፈጠነ ፤ አስቸኰለ ፤ ቶሎ ፡ አደረገ ፤ አስደረገ ። አፍጥን ፡ ረዲኦትየ ። ወአፍጠኑ ፡ ረሲዐ ፡ ምግባሩ ። አፍጠነ ፡ ውሂቦታ ፡ ቅብዐ ። ዘኢያፈጥን ፡ እዴሁ ፡ ለዘቢጥ ፡ (መዝ ፡ ፷፱ ። ፻፳ ። አስ፬ ፡ ፱ ። ፩ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፫) ። በአፍጠነ ፡ ፈንታ ፡ አስተፋጠነ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፤ አያሰኝም ። አስተፋጥን ፡ ትምዳአ ፡ ኀቤየ ። ናስተፋጥን ፡ ከመ ፡ ንባእ ። አስተፋጠኑ ፡ ወአግሐሡ ፡ (፪ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፱ ። ዕብ፬ ፡ ፲፩ ። ዮዲ፲፫ ፡ ፩) ።

**መፍጠኒ** ፡ የሚያፈጥን ፤ የሚያስፈጥን ፤ አፍጣኝ ፡ አስፈጣኝ ። (ተረት) ፤ አፍጣኝና ፡ አቅጣኝ ፤ ከመዳሮ ፡ አንገናኝ ። መፍጠኔ ፡ መዐት ። ሞት ፡ መፍጠኔ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፩ ፡ ፫ ። ቁድር) ።

**ተፋጠነ** ፡ በቁሙ ፤ ተቻኰለ ፤ ተቻኳኰለ ። ኢይትፋጠነኒ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬) ።

**አስተፋጠነ** ፡ አፋጠነ ፤ አፈጣጠነ ፤ አቻኰለ ፤ አቻኳኰለ ፤ እጅ ፡ እግሩን ፡ ሕዋሳቱን ፤ ወይም ፡ ሌላውን ። እግዚአብሔር ፡ አስተፋጠኖ ፡ በሞት ፡ ለገባሬ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፤ ዘእንበለ ፡ ይብጻሕ ፡ ጊዜሁ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፩ ፡ ፪) ።

**መስተፋጥን ፡ ኒ** ፡ የሚያፋጥን ፤ የሚፋጠን ። በመስተፋጥኒት ፡ መልእክት ። ወምስለ ፡ ዝ ፡ ሖሩ ፡ ፉ

ጸቱ፡ መስተፋጥኒ። አእጋር፡ መስተፋጥኒት፡ (ስንክ፡ ጥቅ፲፬። ገድ፡ ተክ። ግንዘ)።

**ፈጢር፤ ሮት፤ (ፈጠረ፡ ይፈጥር፡ ይፍጥር። ዐረ፡ ፈጠረ፤ ፈለጠ፡ ሠነጠቀ። ዕብ፡ ፋጣር፤ ፈታ፡ ከፈተ፤ የማሕፀን)፤** መፍጠር፤ ማስገኘት፤ ከለመኖር፡ ወደ፡ መኖር፡ ማምጣት። ግብር፡ እምግብር፡ መሥራት፤ ማድረግ፤ ማበጀት፤ ማዘጋጀት፤ ዐዲስ፡ ነገር፡ ማውጣት፤ መውለድ። እስመ፡ ፈጠርክሙ። ዘእንበለ፡ እፍጥርከ፡ አእመርኩከ። ኢተፈንወት፡ ኀጢአት፡ ዲበ፡ ምድር፤ አላ፡ ሰብእ፡ እምርእሰሙ፡ ፈጠርዋ። ዘፈጠረ፡ እምልቡ። ወይትካሐዱ፡ በቃሎ፡ ዘሰሊሆሙ፡ ፈጠሩ፡ (ዘፍ፳፡ ፳። ኤር፳፭፡ ፭። ሔኖ። ፻ነገ፡ ፲፪፡ ፴፪። ፪ጴጥ፡ ፪፡ ፫)። ባለቅኔዎች፡ ወደደ፡ ብለው፡ ይፈቱና፡ ምስክሩን፡ ቅኔ፡ ይጠቅሳሉ። ሙሴ፡ ፈጠረ፡ ፈጣሬሁ፤ ወፈጣሪ፡ ፈጠረ፡ ኪያሁ። በመጻሕፍት፡ ውስጥ፡ አይገኝም።

**ፈጣሪ፤** በቁሙ፤ አስገኝ፤ አምጪ፤ ሠሪ፤ አድራጊ። ሲያማሕፀኑ፡ ነፍሰሙ፡ ኀበ፡ ምእመን፡ ፈጣሪ። ፈጣሬ፡ ሰማያት፡ ወምድር። ፈጣሬ፡ ነገር፡ (፩ጴጥ፡ ፬፡ ፲፱። ተ፡ዲ፲፫፡ ፲፰። ኪዳ)። በተረትም፡ ደሪ፡ ቅኔ፡ ፈጣሪ፤ ነገር፡ ፈጣሪውን፤ እሾኽ፡ ዐጣሪውን፡ ይባላል።

**ተፈጥረ፤** ተፈጠረ፤ ተገኘ፤ ተሠራ። እምቅድመ፡ ይትፈጠር፡ ዓለም። ኵሉ፡ እምነ፡ ምድር፡ ተፈጥረ። ሰንበትሰ፡ ተፈጥረት፡ በእንተ፡ ሰብእ፡ (ቅዳ። ሢራ፴፩፡ ፲። ማር፪፡ ፳፯)።

**ፍጡር፤ (ራን፡ ራት፡ ጥርት)፤** በቁሙ፤ የተፈጠረ፤ የተሠራ። አርዮስ፡ ይቤ፡ ወልድ፡ ፍጡር፡ በመለኮቱ። መቅዶንዮስ፡ ተአመነ፡ ከመ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፍጡር። ኢያፍለሰ፡ ፈጣሪ፡ መለኮቶ፡ ለከዊነ፡ ፍጡር፤ ወኢያፍለሰ፡ ትስብእቶ፡ ፍጡረ፡ ለከዊነ፡ ፈጣሪ፡ (መጽ፡ ምስ። ፍ፡ ነ፡ መቅ። ፈ፡ መ፡ ፳፰፡ ፩። ሃይ፡ አበ፡ ጎር)።

**ፍጥረት፤ (ታት)፤** መፍጠር፤ መፈጠር፤ አፈጣጠር፤ ፈጠራ፤ ፍጡርነት። ሐዲስ፡ ፍጥረት። እምፍጥረቱ፡ ዓለም፡ (ኩፋ፡ ፩። ሮሜ፩፡ ፳)።

—፤ ጥንት፤ ቅድም፤ ትካት። ጥንተ፡ እለ፡ እምፍጥረት። ወእምፍጥረትሰ፡ (መዝ፡ ፳፫። ማር፲፡ ፮)።

—፤ በቁሙ፤ ከእሑድ፡ እስከ፡ ዐርብ፡ የተሠራ፡ ሥራ። እግዚ፡ ገባሬ፡ ኵሉ፡ ፍጥረት። አዳም፡ ቀዳሜ፡ ኵሉ፡ ፍጥረት። ዘይእኅዝ፡ ኵሎ፡ ፍጥረታተ፡ (ሃይ፡ አበ። ቅዳ፡ ሕር። ጥበ፩፡ ፯)።

—፤ ባሕርይ፤ ጠባይ። ፍጥረተ፡ አራዊት። በሕገ፡ ፍጥረት። ገብረ፡ ሎሙ፡ ፍጥረተ፡ ሐዲሰ፡ ከመ፡ ኢየአብሱ፡ በኵሉ፡ ፍጥረቶሙ፡ (ያዕ፫፡ ፯። ቅዳ። ኩፋ፡ ፭)።

—፤ ዘር፤ ሥር፤ ምንጭ። ወይእቲ፡ ገቦ፤ ፍጥረታ፡ ሰብእሲት። ምድረ፡ ፍጥረቶሙ፡ (ኩፋ፡ ፫)።

—፤ ልደት፤ ትውልድ፤ ወገን፤ ነገድ፤ ያገር፡ ልጅ። ወከመ፡ ዝ፡ ፍጥረቱ፡ ለኖኅ። እስመ፡ ተስአሰነ፡ ብእሲ፡ ፍጥረተነ። ፍጥረት፡ ኅሩያን። ፍጥረታተ፡ ሕምዝ። ዘእምነ፡ ፍጥረቱ፡ (ዘፍ፳፡ ፬። ዓም፫፡ ፳። ዘኍ፫፡ ፩። ፩ጴጥ፡ ፪፡ ፬። ቅዳ። ዘሌ፲፯፡ ፳፬)።

—፤ ልብ፡ ወለድ፤ ፈጠራ፤ ሐሳብ። ይፈጥሩ፡ ፍጥረተ፡ ዐቢያተ፡ (ሔኖ)።

**ፍጥረታዊ፤** ባሕርያዊ፤ የባሕርይ። ደዌ፡ ሥጋ፡ ፍጥረታዊት። ማሰነት፡ ማስኖ፡ ፍጥረታዊ። ሕማማት፡ ፍጥረታውያት፡ (ግድ፡ ኪሮ። ፍ፡ ነ፡ ፳፯። ፊልክ፡ ፲፩)።

**ፈጠራ፤** በቁሙ፤ ልብ፡ ወለድ፡ ነገር። መተርጉመ፡ ፈጠራ። ሰብአ፡ ፈጠራ። ይሜህሩ፡ ፈጠራ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፲፭። መጽ፡ ምስ)።

—፤ ምልክት፤ ንቅሳት፤ ብጥ፤ ተኵስ፤ የጌጥ። ፊትን፡ ጠጕርን፡ መንፈክት፤ መሳጥ፡ መምለጥ፤ የሐዘን። የጠንቋይ፡ ክታብ፤ ሥራሥር፤ የሚነገት፡ የሚታሰር። ዘይገብር፡ ፈጠራ፡ ውስተ፡ ሥጋሁ። ኢትፍጥሩ፡ ለክሙ፡ ፈጠራ፡ (ቀሌ። ዘሌ፲፱፡ ፳፰)።

**ምፍጣር፤** መፍጠሪያ፤ መፈጠሪያ፤ ቦታ፡ ማሕፀን። ምፍጣረ፡ ጸቃውዕ፡ (አርጋ፡ ፭)።

**ፌዋ፤ (ጽር፡ ፌዎስ)፤** የበሰበሰ፤ የበነቸ፤ የሻገተ፤ ጥቁር። ኢታንብር፡ ኵሎ፡ ዕፀ፡ ንቁዐ፡ ወፌዋ፡ (ኩፋ፡ ፳፩)።

**ፍዮአዮስ፤ (ሳን)፤** መናፍቅ፡ ከሓዲ፤ ፈላሻ፡ ይሁዲ፤ ባህሉ፡ ከመጽሐፍ፡ የማይገጥም። ፍዮአዮሳን፡ እለ፡ ይኄልዩ፡ ወይብሉ፡ ከመ፡ ወልደ፡ እግዚ፡ ብእሲ፡ ውእቱ፡ ወተወልደ፡ በፍትወተ፡ ሥጋ፡ በሩካቤ፡ ዮሴፍ፡ ወማርያም፡ (ዲድ፡ ፴፩)።

**ፍያል፤ (ላት። ጽር፡ ፊአሊ)፤** ዕቃ፤ መሣሪያ፤ ታላቅ፡ ሰሐን፡ ከብ፡ ዝርግ፡ ጐድጓዳ፤ ጣሳ፡ ጽዋ፡ ኵባያ፡ ፍንጃል። አሐዱ፡ ፍያል፡ ዘብሩር። እመ፡ ውስተ፡ ፍያላት፡ ወጽዋዓት፡ (ዘኍ፯፡ ፲፫። ምሳ፳፫፡ ፴፩)።

**ፍያል፤** የእሳት፡ ቦታ፡ ጕድጓድ፤ እሳተ፡ ገሞራ፡ ያለበት፤ እንደ፡ በተሐራ፡ ያለ። የእሳት፡ መምጫ፤ ኮከም። የኮከምን፡ ፍቺ፡ ተመልከት፤ ጽርኡ፡ በኮከም፡ ፈንታ፡ ፍያል፡ ይላል፡ (ኤር፴፪፡ ፲፰)።

**ፍየል፤ (ላት)፤** በቁሙ፡ ጠሊ፡ (በማርኛ)።

**ፌራ፤ (ዕብ፡ ፈር፤ ጐድጓድ፤ ወጥመድ)፤** ቸነፈር፤ ወረድሽኝ። ፌራ፡ ወንዳድ፡ (አዋል)።

**ፈይቶ፤ ቶት፤ (ፈየተ፡ ይፌይት፡ ይፈይት። ዕብ፡ ሻላል)፤** መውረር፡ መዝረፍ፤ መቀማት፡ መመንተፍ፤ መስረቅ፡ መቀጠፍ። ለጋድ፡ ፈየትዎ፡ ፈያት፤ ወውእቱኒ፡ ፈየቶሙ፡ (ዘፍ፵፱፡ ፲፱)።

—፤ በቁሙ፤ መፈየት፤ ፊት፡ ፊተኛ፡ መኾን፤ ፊት፡ ለፊት፡ መቆም፤ መግጠም።

(ጥያ) **ፈያት** ፤ ጳጉኢ ፡ ወንበዴ ፤ ቀማኛ ፤ ወራሪ ፡ ዘራፊ ፡ ሌባ ፡ ቀጣፊ ። ለሊከ ፡ ቀተልከ ፤ ወናሁ ፡ ትትዐወቅ ፡ ከመ ፡ ፈያት ፡ አንተ ፡ (ቀ፡ነገ ፡ ፳ ፡ ፵) ።

**ፈያታዊ** ፤ **ይ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ወአሐዱ ፡ ፈያታዊ ፡ እምእለ ፡ ተሰቅሉ ፡ (ሉቃ፳፫ ፡ ፴፱) ።

(ላ) **ፈያት** ፤ ወንበዶች ፤ ቀማኞች ፤ ሌቦች ። ቦኑ ፡ በኣተ ፡ ፈያት ፡ ውእቱ ፡ ቤትየ ። ወበርባንሰ ፡ ሊቀ ፡ ፈያት ። ቦኡ ፡ ፈያት ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ወነሥኡ ፡ ንዋየ ፡ (ኤር፯ ፡ ፲፩ ። ማቴ፳፯ ፡ ፲፯ ። ቀሌ) ።

**ፈያታውያን** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ክልኤቱ ፡ ወራዙት ፡ ፈያታውያን ፡ (ስንክ ፡ ሐም ፡ ፳፭) ።

**ምፍያት** ፤ መቀሚያ ፤ የወንበዴ ፡ ቦታ ። ምፍያተ ፡ አክይስት ፡ (አዋል) ።

**ተፈየተ** ፤ ተቀማ ፤ ተሰረቀ ። ተፈይት ፡ በኃቡእ ፡ (ሲኖዶ) ።

**ፍዩት** ፤ የተቀማ ፤ የተነጠቀ ፤ የተሰረቀ ።

**ፈት** ፤ በቁሙ ፡ ግጽ ። ክፍትፍቱ ፡ ፈቱ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ፈክሮ** ፤ **ሮት** ፤ (**ፈከረ ፡ ይፌክር ፡ ይፈክር ። ዐረ ፡ ፈከረ ፤ ዐሰበ ። ዕብ ፡ ፋካር ፤ ማለ**) ፤ መፈክር ፡ መደንፋት ፤ ሙያን ፡ መናገር ፡ ማውራት ፤ በሙያ ፡ መታበይ ፤ መመካት ፤ ግዳይ ፡ መጣል ፤ ስለብ ፡ መቍጠር ።

**ፈከረ** ፤ (**ዐረ ፡ ፈሰረ ። ዕብ ፡ ፋታር**) ፤ ተረጐመ ፤ ፈታ ፤ አፍታታ ፤ ዘረዘረ ፡ ለማስረዳት ፤ የሕልም ፡ የመጽሐፍ ፡ የቋንቋ ። ሐለምነ ፡ ሕልመ ፡ ወንጣእነ ፡ ዘይፌክር ፡ ለነ ። ወይፌክር ፡ ለነ ፡ መጻሕፍተ ። ዐጺብ ፡ ነገሩ ፡ ወኢይትከሀል ፡ ይፈክርዎ ፡ (ዘፍ፵ ፡ ፰ ። ሉቃ፳፬ ፡ ፴፪ ። ዕብ፭ ፡ ፲፩) ።

**ፈካሪ** ፤ (**ሪት ፡ ርያን ፡ ያት**) ፤ በቁሙ ፡ የሚፈክር ። ተርጓሚ ፡ ፈቺ ። ሳቤላ ፡ ወለተ ፡ ሀልቃስ ፡ ፈካሪተ ፡ ሕልም ፡ (ስንክ ፡ ጥር፱) ።

**መፈክር** ፤ (**ርት ፡ ራን ፡ ራት**) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ መተርጐም ፤ ጠንቋይ ። ልሳን ፡ መፈክርት ፡ ዘትኬኑ ፡ ዘውስተ ፡ ኀሊና ። መፈክራነ ፡ ሕልም ። መፈክር ፡ በሰዓታት ፡ (ፊልክ ፡ ፶ ። ኩፋ ፡ ፵ ። ዘፍ፵ ፡ ፰ ። ሲኖዶ) ።


**ተፈክረ** ፤ ተተረጐመ ፡ ተፈታ ፡ ተመረመረ ። ዕጹብ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡ ወኢይትፌክር ። አ ፡ ዝንቱ ፡ ምስጢር ፡ ዘኢይትፌክር ፡ ወዘኢይተረጐም ፡ (ቄር ፡ ጸሎ ። ቅዳ ፡ አፈ) ።

**ፍካሬ** ፤ (**ርያት**) ፤ መተርጐም ፤ መፍታት ። ትርጓሜ ፡ አፈታት ፡ ምስጢር ፡ ምሳሌ ፡ ዕውቀት ፤ ትንቢት ። ፍካሬ ፡ ሕልሙ ። ፍካሬ ፡ አምሳል ። ወፍካሬሆሙሰ ፡ ለሰብዐቱ ፡ ኮከብ ። ፍካሬ ፡ ዘጻድቃን ፡ ወዘኃጥአን ። ፍካሬ ፡ ፍጥረተ ፡ እግዚ ። ፍካሬ ፡ ኢየሱስ ፡ (መሳ፯ ፡ ፲፭ ። ሢራ፴፱ ፡ ፫ ። ራእ፩ ፡ ፳ ። መገ ፡ ፩ ። ማር ፡ ይሥ፩ ፡ ፱ ። አዋል) ።

**ፍክሬ** ፤ አፈካከር ፡ ድንፋታ ፤ ፍክራ ፤ ግዳይ ፡ ቈጠራ ።

**ፍክሬ ፡ ኢየሱስ** ፤ መጽሐፍ ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ እንደ ፡ ታምረ ፡ እየሱ ፡ እንዳቡቀለምሲስ ፡ ያለ ፤ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚመጣን ፡ ነገር ፡ የሚያወራ ፤ ትንቢተ ፡ ኢየሱስ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ፈካትም** ፤ (**ዕብ ፡ ፋኬሀ ፤ ንቅዐ ፡ ውሒዝ**) ፤ ታላቅ ፡ ፈሳሽ ፡ ወንዝ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የሚያልፍ ፡ የሚጐርፍ ፤ እንዳባይና ፡ እንደ ፡ ጣና ። የውሃ ፡ እናት ፤ ጥቍር ፡ እንዝዝ ፡ የምትመስል ፤ በውሃ ፡ ላይ ፡ እንደንዝርት ፡ ራስ ፡ የምትሾር ፡ የምትሽከረከር ። ከመ ፡ ፈካትም ፡ ዘባሕር ። እምዝሉስ ፡ ዘይብእስ ፡ ፈካትም ፡ ሀለወት ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ቤተ ፡ ዮናስ ፡ (ደራሲ ። ቅኔ) ።



ፈካትም ፡

**ፋል** ፤—**ጥንቈላ** ፤—**ፋወለ** ።

**ፈሊግ** ፤ **ጎት** ፤ (**ፈለገ ፡ ይፈልግ ፡ ይፍልግ ። ዕብ ፡ ፋላግ ። ዐረ ፡ ፈለጀ**) ፤ መክፈል ፡ መሠንጠቅ ፤ መቅደድ ፤ ማጕድጐድ ፤ መፈልፈል ፡ የውሃ ፡ የመሬት ፡ የንፈስ ፤ ለሌላም ፡ ይኸናል ። መፈለግ ፤ ፍላጎት ፤ መሻት ፡ መከተል ፡ (ዐማርኛ) ።

**ፈለግ** ፤ ታላቅ ፡ ወንዝ ፤ ፈሳሽ ፤ ዥማ ፤ መስኖ ፤ በይ ፤ አሠረ ፡ ማይ ፤ ፈፋ ፤ ቈላ ፡ ጕድጓዳ ፤ ሸለቆ ። ፈለገ ፡ ግብጽ ። ፈለገ ፡ አርዝ ። ፈለግ ፡ ዘአንጻረ ፡ ደቡብ ፡ (ኢሳ፳ ፡ ፲፪ ። ዮሐ፲፰ ፡ ፩ ። ዜዜና ፡ ፲፬ ፡ ፲) ።

**አፍላግ** ፤ (**ጋት**) ፤ ወንዞች ፡ ፈሳሾች ። አፍላግ ፡ የሐውሩ ፡ ዐውደ ፡ ተክሉ ። ወይዘብጥ ፡ ሰብዐተ ፡ አፍላጋተ ፡ (ሕዝ፴፩ ፡ ፬ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፲፭) ።

**ፍሉግ** ፤ የተከፈለ ፤ የተፈለፈለ ፡ ፍልፍል ፤ ውስጡ ፡ ክፍት ፡ እንደ ፡ ሰምባ ፡ ያለ ። ፍሉግ ፡ ይኩን ፡ ሰሌዳሁ ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፰) ።

**ፈሊሐ** ፤ **ሖት** ፤ (**ፈልሐ ፡ ይፈልሕ ፡ ይፍላሕ ። ዐረ ፡ ፋረ**) ፤ መፍላት ፡ መፍለቅለቅ ፡ መገለል ፤ መገንፈል ፤ የፈሳሽ ። (ተረት) ፤ ተጥዶ ፡ አይፈላ ፤ ተዥሞ ፡ አይበላ ። ወይፈላሕ ፡ በሕቁ ። ፈልሑ ፡ ማያት ፡ ደበ ፡ ርእሱ ። እምቅድመ ፡ ይፍልሑ ፡ አንቀዕተ ፡ ማያት ፡ (ሕዝ፳፬ ፡ ፭ ። ድጓ ። ቅዳ ፡ አፈ) ።

**ፍሉሕ** ፤ የፈላ ፤ ፍል ፤ ሙቅ ፡ ንፍር ። ይደይዎ ፡ ውስተ ፡ ጤግን ፡ ፍሉሕ ፡ ምስለ ፡ ዘይት ። ረከቦ ፡ ለውእቱ ፡ ጸብሓ ፡ ፍሉሕ ፡ ወበሰለ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ታኅ፲፭) ።

**ፍልሐት** ፡ መፍላት ፡ አፈላል ፡ ፍላት ። ፍልሐቱ ፡ ለማይ ። ፍልሐተ ፡ ቅብዕ ። ፍልሐተ ፡ ምክሮሙ ፡ (መጽ ፡ ምስ ፡ ስንክ ፡ ግንቦ ፡ ቁር) ።

**አፍልሐ** ፡ አፈላ ፡ አስፈላ ፡ አቃለጠ ። ሰዘቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ አፍልሖተ ፡ ሜሮን ። ዘአፍልሕዎ ፡ በእሳት ። አዘዘ ፡ ያፍልሑ ፡ ናእክ ፡ ወይክዕዉ ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፳፭ ፡ ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳) ።

**መፍልሕ** ፡ መፍሊያ ፡ ማፍሊያ ፡ ማስፈሊያ ። ሲያበዛ ፡ መፋልሕት ፡ ይላል ። መናግንተ ፡ ጽህርት ፡ ወመፋልሕተ ፡ እሳት ፡ (መቃ ፡ ፺፱) ።

**ፈሊጥ** ፡ **ጦት** ፡ (**ፈለጠ ፡ ይፌልጥ ፡ ይፍልጥ ። ዕብ ፡ ፋላጥ ፡ አዳነ ፡ አስጣለ ፡ አወጣ**) ፡ መፍለጥ ፡ መሠንጠቅ ፡ የንጨት ። መለየት ፡ መነጠል ፡ መክፈል ፡ መምረጥ ፡ ማስገለል ። ዘእግዚ ፡ አስተፃመረ ፡ ሰብእ ፡ ኢይፍልጥ ። ዘፈለጠ ፡ ብእሴ ፡ እምብእሲቱ ። ወይፍልጥ ፡ መንጦላዕት ፡ ውሳጤ ፡ ወቀሠፋዊ ። ፈለጠሙ ፡ ለነገደ ፡ ሌዊ ፡ ይጹሩ ፡ ታቦተ ። ወፈለጠ ፡ ዕዝራ ፡ ዕደወ ፡ (ማቴ፲፱ ፡ ፮ ። ሚራ፴፩ ፡ ፳፫ ። ዘፀ፳፮ ፡ ፴፫ ። ዘዳ፲ ፡ ፰ ። ፩ዕዝ ፡ ፱ ፡ ፲፮) ።

— ፡ ለይቶ ፡ ማወቅ ፡ መረዳት ፡ ማስተዋል ። ጕርዔ ፡ ይፈልጦ ፡ ለዘሉ ፡ ጣዕመ ፡ እክል ። እዝን ፡ ይፈልጥ ፡ ነገረ ። እለ ፡ ኢፈለጡ ፡ የማናሙ ፡ ወፀጋሞሙ ። ወትፈልጥ ፡ ዘይኄይስ ፡ (ሢራ፴፯ ፡ ፳፱ ። ኢዮ፲፪ ፡ ፲፩ ። ዮና፬ ፡ ፲፩ ። ሮሜ፪ ፡ ፲፰) ።

**አፍለጠ** ፡ አስፈለጠ ፡ አስለየ ፡ አስረዳ ፡ አሳወቀ ፡ አስታወቀ ። ለሊሁ ፡ ጳውሎስ ፡ አፍለጠ ፡ ወአርአየ ፡ ከመ ፡ በአምሳሉ ፡ ወበአርአያ ፡ ክህነቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ውእቱ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ። አፍለጠሙ ፡ ዮሴፍ ፡ ለአኃዊሁ ፡ በነፍስቱ ፡ (ተረ ፡ ቄር ። ግብ፯ ፡ ፲፫) ።

**ተፈልጠ** ፡ ተለየ ፡ ተመረጠ ፡ ተበተነ ፡ ታወቀ ። ዘይፈቅድ ፡ ይትፈለጥ ፡ እምአዕርክት ። ዘተጸውዐ ፡ ወተፈልጠ ። ተፈልጡ ፡ አርድእት ፡ እስከ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ይስብኩ ፡ ዜና ፡ ወንጌል ። ባቲ ፡ ይትፈለጥ ፡ መዋዕል ፡ (ምሳ፲፰ ፡ ፩ ። ሮሜ፩ ፡ ፩ ። ቀሌ ። ሢራ፴፱ ፡ ፯) ።

**ፍሉጥ** ፡ (**ጣን ፡ ጣት ፡ ልጥ**) ፡ የተለየ ፡ ልዩ ፡ ባዕድ ፡ ብቻ ፡ ብቸኛ ። ሕዝብ ፡ ፍሉጥ ፡ እንተ ፡ ባሕቲቱ ። እስመ ፡ መዐዛሁ ፡ ፍሉጥ ። እመ ፡ ሰብእ ፡ ፍሉጥ ፡ ውእቱ ። እስመ ፡ ኢይትማሰል ፡ ምስለ ፡ ባዕድ ፡ ንብረቱ ፡ ወፍሉጥ ፡ ፍኖቱ ፡ (አስቴ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፳፭ ። ቄር ። ጥበ፪ ፡ ፲፭) ።

**ፍልጠት** ፡ (ጥ ፡ ለ ፡ የ) መለየት ፡ አስለየት ፡ ልዩነት ። ይቴክዙ ፡ ሐዋርያት ፡ በእንተ ፡ ፍልጠታ ፡ እምኔሆሙ ። በእንተ ፡ ፍልጠተ ፡ ዕልዋን ። ፍልጠት ፡ ዘሀሎ ፡ ማእከለ ፡ ፈጣሪ ፡ ወፍጡራን ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፲፮ ። ዲድ ፡ ፴፰ ። አፈ ፡ ድ፱) ።

**ፍልጣን** ፡ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ መለየት ፡ ልዩነት ። መፋታት ፡ ፍች ። እኩያት ፡ ካልእ ፡ ፍልጣን ፡ ዘማእከለ ፡ አሮን ፡ ወማእከለ ፡ ክርስቶስ ። ዘአልቦ ፡ ፍልጣን ። ከመ ፡ ይኩን ፡ ፍልጣን ፡ ማእከለ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ (አፈ ፡ ድ፲፫ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፲፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱) ።

**ተፋለጠ** ፡ ተለያየ ፡ ተከፋፈለ ። ተማዕዑ ፡ ወተፋለጡ ፡ ዘዘ ፡ ዘኢሆሙ ፡ (ግብ፲፭ ፡ ፴፱ ። ፫ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፯) ።

**አስተፋለጠ** ፡ (**ፈለጠ**) ፡ አለያየ ፡ አፋታ ። እምድኅረ ፡ አስተፋለጦሙ ፡ መኰንን ፡ በበይናቲሆሙ ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ፲፩) ። ኅባቡ ፡ ነው ፡ እንዲ ፡ ፍችው ፡ አደራራጊነት ፡ የለውም ፡ አድራጊ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ፈልዮ** ፡ **ዮት** ፡ (**ፈለየ ፡ ይፈሊ ፡ ይፍሊ ። ዕብ ፡ ፋላህ**) ፡ መቀመል ፡ ቅማልን ፡ ከልብስ ፡ ከጠጕር ፡ መፈለግ ፡ መልቀም ። ከፋሙን ፡ ከበግ ፡ መለየት ፡ መነጠል ፡ መምረጥ ፡ ማንጓለል ፡ ማበወገድ ፡ ማስገለል ፡ (ሄርማ ፡ ፺፲) ።

**ተፈልየ** ፡ ተለየ ፡ ተመረጠ ፡ ምራቂ ፡ ኾነ ። (ተረት) ፡ መራቂ ፡ ይወድቃል ፡ ከምራቂ ። በኢትፈልዮ ። እንዘ ፡ አልብኪ ፡ ተፈልዮ ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፱ ። ደራሲ) ።

**ተፋለየ** ፡ ተለያየ ፡ ተከፋፈለ ፡ እየብቻው ፡ ኾነ ። ተጋብኡ ፡ ኀበ ፡ ቀኑድስ ፡ ሰብእ ፡ ብዙኃን ፡ ወተፋለዩ ፡ ነገሮሙ ፡ ወበዝኁ ፡ ቀትል ፡ ማእከሌሆሙ ። ወሶበ ፡ አእመሩ ፡ ሮም ፡ ተፋልዮተ ፡ ነገሮሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ቀርቡ ፡ ኀበ ፡ ቅጽር ። ዐብየ ፡ ክላሕ ፡ ወተሀውከት ፡ ሀገር ፡ በእንተ ፡ ተፋልዮትሙ ፡ ለሰብእ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ፈለክ** ፡ (**ዐረብ ። ዕብ ፡ ፌሌኽ ። ሱር ፡ ፍላኳታ**) ፡ ጠፈር ፡ አየር ፡ በአየር ፡ በጠፈር ፡ በዙሪያው ፡ ያለ ፡ ክፍል ፡ ዕርከን ፡ ማዕርግ ፡ ምልክት ፡ የፀሐይና ፡ የጨረቃ ፡ ያሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ከዋክብት ። ኅዋኅወ ፡ ፈለክ ። ቀዳማዊ ፡ ሞኅተ ፡ ፈለክ ። ሰብአ ፡ ፈለክ ። ኢትበጽሕ ፡ ኀይሉ ፡ እስከ ፡ ፈለክ ፡ ወርኅ ። ተዐየኒ ፡ ዐውደ ፡ ነፍስየ ፡ እስከ ፡ ሜልሳዊ ፡ ፈለክ ፡ አመ ፡ ተቃወማ ፡ በአየር ፡ ቀናኢ ፡ መልአክ ፡ (አቡሻ ፡ ፫ ። ፱ ። ፳፭ ። አፈ ፡ ድ፱ ። ደራሲ) ።

**አፍላክ** ፡ አየሮች ፡ የአየር ፡ ክፍሎች ፡ ማዕርጎች ። ወይብሉ ፡ ዘበአፍላክ ፡ (ፈልክ) ።

**ፋሌክ** ፡ ሰማየ ፡ ሰማያት ፡ መጨረሻ ፡ ሰማይ ፡ ደርብ ፡ ስገንት ፡ ተሥላስ ፡ (ቀሌ ። አፈ ፡ ድ፭) ።

**ፈልኪንዶስ** ፡ (**ሮማይ ፡ ፋልኪዲያኑስ**) ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ርስትና ፡ ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ክፍል ፡ አወራረስን ፡ የጣፈ ፡ ሳውራሽ ፡ ለወራሽ ፡ ሕግ ፡ ያወጣ ። ዘይቤው ፡ ፈልኪንዶሳዊ ፡ የርሱን ፡ ትእዛዝ ፡ የፈጸመ ፡ የተቀበለ ፡ ማለት ፡ ነው ። እሙንቱስ ፡ ይሰመዩ ፡ ወራስያነ ፡ ወለሊሁ ፡ ይሰመይ ፡ ሕውራሴ ፡ ፈልኪንዶስ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፲፰) ።

**ፈልክስዩስ** ፡ (**ጽርእ**) ፡ የሰው ፡ ስም ፡ የመ

ጽሐፍ ፡ ስም ፤ የመንኮሳት ፡ መጽሐፍ ። መጥቀሬ ፡ ነግድ ፡ ተወክፈ ፡ ነግድ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ፈሎስ ፡ ወዳጅ ፤ ክቢ ኖስ ፡ ነግድ ።

**ፈሊል ፤ ሎት ፤ (ፈለ ፤ ፈለለ ፡ ይፈልል ፡ ይፍልል ። ዕብ ፡ ፋሌል) ፤** መንፋለል ፤ መውረድ ፡ መውደቅ ፤ የጡት ፡ የወተት ። ፈልፈለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ፊላሴምሴሞኒም ፤ (ዕብ ፡ ፍሎኒ ፡ አ ልሞኒ) ፤** ስውር ፤ ድብቅ ፤ ስሙን ፡ ሳይጠሩ ፡ የሚያወሩት ፡ የሚናገሩት ፤ ተናጋሪ ፡ ብቻ ፡ የሚያውቀው ፡ ሰሚ ፡ የማያውቀው ። ቃሉ ፡ ኹለት ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ያሰኛል ፡ (፩ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፪) ።

**ፈለመ ፤ (ትግሬ) ፤** ከፈለ ፡ ሠነጠቀ ። በቁሙ ፤ ፈለመ ፡ መገመሪያ ፡ ወጋ ፡ መታ ፤ ፀረቡን ፡ ሰጠ ፤ ዋጋ ፡ ገመረ ።

**ፊልሞን ፤ (ጽር ፡ ፊልሙኒ ። ዕብ ፡ ፋልሞኒ) ፤** ገዢ ፡ ከማሁ ፤ እንግሌ ፤ እንግሌያዊ ፤ የእንግሌን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ብሒረ ፡ ፊልሞን ፡ ነትድር ፡ (፬ነገ ፡ ፯ ፡ ፰) ።

**ፊልሙንጢ ፤ (ጽር ፡ ፊልሙኒ ። ዕብ ፡ ፋልሞኒ) ፤** ገዢ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፤ ስሙ ፡ ያልታወቀ ፤ ያልተጠራ ፤ ሌላ ፤ አንድ ፤ ርሱ ፤ ያ ፡ ያኛው ፤ እንግሌ ፡ ያሰኛል ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ የመላእክት ፡ ቋንቋ ፡ ይሉታል ። ወይቤ ፡ አሐዱ ፡ ቅዱስ ፡ ለፊልሙንጢ ፡ ዘይነብብ ፡ (ዳንኤ ፡ ፰፲) ።

**ፊሎን ፤ (ጽር ፡ ፊሎኒስ) ፤** ሰበን ፤ ሻል ፤ የራስ ፡ ያንገት ፡ የትከሻ ፡ ልብስ ፤ የፊትና ፡ የእጅ ፡ ማደፊያ ፡ መወልወያ ፤ የመጽሐፍ ፡ ልብስ ፡ መሸፈኛ ፡ መጠቅለያ ። ወፊሎንኒ ፡ ዘመጽሐፍ ፡ ተማላዕ ፡ ምስሌከ ፡ (፪ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፫) ።

**ፈልፈለ ፤ (ፈሊል ፡ ፈለ) ፤** ፈለፈለ ፤ በላ ፡ ነደለ ፤ ፈልፋይ ፡ ኾነ ፤ የእሸት ፡ የድጥን ፡ ዕንጨት ። መንጨ ፡ ወጣ ፡ ነባ ፡ ፈለቀ ፡ ፈሰሰ ። ይፈለፍል ፡ ነቅዕ ፡ እምቤተ ፡ እግዚ ። ፈለግ ፡ ዘይፈለፍል ። ይፈለፍል ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ጽምእት ፡ (ዮኤ ፩ ፡ ፲፰ ። ምሳ፲፰ ፡ ፬ ። ኢሳ፴፭ ፡ ፯) ።

**ፈልፈል ፤** ምንጭ ፤ ፈሳሽ ። ፈልፈለ ፡ ማይ ። ፈልፈለ ፡ አንብዕ ። ይነፀፍኑ ፡ ፈልፈለ ፡ ኩዙሕ ፡ (ቀሌ ። ኤር፱ ፡ ፩ ። ፲፰ ፡ ፲፬) ።

**ፈልፈል ፤ (ዐረ ፤ ዕብ ፡ ፊል ፤ ዠኖን) ፤** እውራሪሥ ፡ ሐርማዝ ፤ ክውሃ ፡ አጠገብ ፡ የሚኖር ። ረከበ ፡ አርዌ ፡ ዐቢየ ፡ ዘስሙ ፡ ፈልፈል ፡ ዘውእቱ ፡ ሐርማዝ ፡ ብሂል ፡ (አዋል) ። አጽንዕዎ ፡ ፈልፈል ፡ ወመንተሉ ፡ (ፍክሬ ፡ እየ) ።

**አፈልፈለ ፤** አመነጨ ፡ አፈለቀ ፡ አፈሰሰ ። ኣፈለፍል ፡ ማእከለ ፡ ገዳም ፡ (ኢሳ፵፩ ፡ ፲፰) ።

**ፍልፈል ፤** በቁሙ ፤ ያይጥ ፡ ወገን ፤ ካይጥ ፡ የሚበልጥ ፤ ልበ ፡ ምድርን ፡ የሚፍር ፡ የሚፈለፍል ፤ ዐፈሩን ፡ እንደ ፡ ምርት ፡ የሚቈልል ፡ (ዐማርኛ) ።

**ፍልፍል ፤ (ዐረ ፡ ፊልፊል ። ዕብ ፡ ፊልፊል) ፤** በርበሬ ፤ የበርበሬ ፡ ወገን ፡ በያይነቱ ፤ ቍንዶ ፤ ዱቤ ፤ ሚጥሚጣ ፤ ቡልጌ ፡ ያፋቴ ፡ ሐይቂ ፤ የሚመር ፡ የሚለበልብ ፡ የሚሰንፍጥ ። ደመረ ፡ ጼወ ፡ ምስለ ፡ ግንፋል ፡ ወፍልፍል ፡ ወብሒእ ፡ ወከዐወ ፡ ውስተ ፡ አንፎሙ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

**ፈሊጽ ፤ ጻት ፤ (ፈለጸ ፡ ይፈልጽ ፡ ይፍልጽ ። ዕብ ፡ ፋላጽ) ፤** መፍለጥ ፤ መሠንጠቅ ፤ መስበር ፡ ማድቀቅ ። ፈለጠን ፡ እይ ፤ ፍላጻ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ሰፈጻን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ተፈልጸ ፤ (ዕብ ፡ ሂትፋሌጽ ፤ ደንገፀ ፡ ተሰብረ) ፤** ተፈለጠ ፤ ተሠነጠቀ ፤ ነከተ ፡ ደቀቀ ። እምከመ ፡ ረግዐ ፡ አስሐትያ ፡ ይትፈለጽ ፡ ከመ ፡ ስባሪት ፡ ማህው ፡ በሊጎት ፡ (ሢራ፵፫ ፡ ፲፱) ።

**ፍልጽ ፤** ፍልጥ ፤ ፍላጭ ፤ ሥንጥር ፤ ሥንባጭ ፤ ስባሪ ፡ ቍራጭ ።

**ፈሊቅ ፤ ቆት ፤ (ፈለቀ ፡ ይፈልቅ ፡ ይፍልቅ ። ዐረ ፡ ፈለቀ ፤ አቀለጠ) ፤** መፍለቅ ፤ መፍሰስ ፤ መልቶ ፡ ተርፎ ፡ ከልክ ፡ ዐልፎ ፤ ወይም ፡ ፈልቶ ፡ ገንፍሎ ፡ ተትረፍርፎ ። መቅበጥ ፤ መቅለጥ ፤ መቀማጠል ፤ ቅልጣን ፡ ማድረግ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በፈለቀ ፡ ፈንታ ፡ አፍለቀ ፡ ይላል ። ክንኪ ፡ ዕሉተ ፡ ወአፍለቂ ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፴፩) ። ይኸውም ፡ መላሽ ፡ የጨመረው ፡ ትርፍ ፡ ቃል ፡ ነው ።

—፤ መፈለቅ ፤ መክርከር ፤ የጥምጥም ፡ የንጨት ።

**አፍለቀ ፤** አፈለቀ ፤ አስፈለቀ ፤ አመነጨ ፤ አፈሰሰ ፤ ፍልቅ ፡ አደረገ ፤ የጠበል ፡ የመጠጥ ።

**ፈላቅ ፤ (ቃት) ፤** ክምር ፤ ቍልል ፤ የዐሥራት ፡ የመባእ ፡ እኽል ፤ ሕዝብ ፡ ካንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የሚያፈሉት ፤ የሚቈልሉት ። ጐታ ፡ ጐተራ ፡ ሬቅ ፡ ድብኝት ፤ ጕርጅ ፤ ዛኒጋባ ፤ የእኽል ፡ ቤት ፤ የዐሥራት ፡ መከተቻ ። አምጽኡ ፡ ዐሥራተ ፤ ወአብኡ ፡ ወገብሩ ፡ ፈላቃተ ። በማልስ ፡ ወርኅ ፡ አኀዙ ፡ ይሣርርዎ ፡ ለፈላቃት ፡ ወበሳብዕ ፡ ወርኅ ፡ ተፈጸመ ፡ (፪ዜና ፡ ፴፩ ፡ ፭ና ፡ ፯) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ኹሉንም ፡ ለዐሥራቱ ፡ ብቻ ፡ ይሰጣል ፤ የጐተራን ፡ ሥራ ፡ አያሳይም ።

**ፈሊስ ፤ ሶት ፤ (ፈለሰ ፡ ይፈልስ ፡ ይፍልስ ። ዕብ ፡ ፋሌሽ) ፤** መክፈት ፤ መግለጥ ፤ የመዝጊያ ፡ የመጋረጃ ። ፈላስን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጥሬ ፡ ነው ።

—፤ መፍለስ ፤ መነቀል ፤ ከሉበት ፡ ከበቀሉበት ፡ ቦታ ፡ አገርን ፡ ሥርን ፡ ማንሣት ፡ መንቀል ፤ ወደ ፡ ሌላ ፡ ማለፍ ፡ መኼድ ፡ መስደድ ፤ ፈላሽ ፡ መኾን ። ፈሊሶ ፡ እምህየ ። ፍልስ ፡ እምዝየ ። ኢትፍልሱ ፡ እምቤት ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ (ማቴ፲፪ ፡ ፱ ። ዮሐ፯ ፡ ፫ ። ሉቃ፲ ፡ ፯) ።

—፫ መዘር፤ መቅበዝበዝ ። መማረክ፤ ምርኮ ፡ መኾን፤ መሞት፤ መለየት ፡ መጥፋት ። ይፍልሱ ፡ ወያስተፍእሙ ። ይሁዳ ፡ ፈለሰ ፡ ፍጹመ ፡ ፍልሰተ ። አመ ፡ ይፈልስ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ። ከመ ፡ የሀሉ ፡ ዝክርከ ፡ እንበለ ፡ ፈሊስ ፡ (መዝ ፡ ፶፫ ። ኤር፲፫ ፡ ፲፱ ። ዲድ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፪) ።

—፬ መንፈላሰስ፤ መንደባለል፤ መንከባለል ፡ ደብለል ፡ ክብለል ፡ ማለት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ፈላሲ**፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት)፤ የሚፈልስ፤ ፈላሽ፤ ፈላሻ፤ ዘዋሪ፤ እንግዳ፤ ምርኮኛ፤ ስደተኛ፤ መዋቲ ። ንጉድ ፡ ዘፈለሰ ፡ ፈላሲ ፡ ኅቤሁ ። እስመ ፡ ፈላሲ ፡ አነ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ፈላሴ ፡ ይከውን ፡ ዘርዕከ ። ፈላስያነ ፡ ጽዮን ። መዋሥዕት ፡ ዘፈላስያን ፡ (ሕዝ፵፯ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፻፳ ። ኩፋ ፡ ፲፱ ። ባሮ፱ ፡ ፱ ። ግንዘ) ።

—፭ መናኒ፤ መንኰሴ፤ ባሕታዊ፤ ግሑሥ፤ ብቸኛ፤ በረኸኛ ። አሐዱ ፡ እምገዳማውያን ፡ ይቤ ፡ ለእኁ ፡ ለእመ ፡ ኮንከ ፡ ዘኢትክል ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ፈላሴ ፡ ከማሁ ፡ ንበር ፡ በበኣትከ ፡ ወብኪ ፡ በእንተ ፡ ኀጢአትከ ። ኩን ፡ ፈላሴ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ (ፊልክ ፡ ፳፱ና ፡ ፶፰) ።

**ፍሉስ**፤ የፈለሰ፤ ፍልስ፤ ንቃላ ። ኢይኩን ፡ ፍሉስ ፡ ወኢዘያንጌጊ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**ፍልሰት**፤ መፍለስ፤ መፍረስ፤ መሰደድ፤ ተማርኮ ፡ መኼድ፤ መዘር ፡ መባከን፤ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ መጠጋት ። ኢሬስዮ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ለፍልሰት ። ምድረ ፡ ፍልሰትከ ። እስከ ፡ አመ ፡ ፍልሰት ። እመ ፡ ምእከ ፡ ፍልሰቱ ፡ ኅሊናት ። ፍልሰተ ፡ ሀርቃኖስ ፡ ኀበ ፡ ሰዱቃውያን ፡ (ኤር፱ ፡ ፲፭ ። ኩፋ ፡ ፳፯ ። ማቴ፩ ፡ ፲፪ ። ፊልክ ። ዮሴፍ) ።

—፪ መሞት፤ መለየት፤ ማረግ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ መውጣት፤ ከምድር ፡ ከመቃብር ። ጊዜ ፡ ፍልሰቱ ። ፍልሰት ፡ እምሥጋ ። ፍልሰተ ፡ ሥጋኪ ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ ሕይወት ። ፍልሰተ ፡ ሥጋሁ ፡ ለቅዱስ ፡ አልዓዛር ፡ (ፊልክ ፡ ፲፯ና ፡ ፺፰ ። ድራሲ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፩) ።

**አፍለሰ**፤ አፈለሰ፤ አስፈለሰ፤ ነቀለ ፡ አስነቀለ፤ ማረከ ፡ አስማረከ፤ አሰደደ፤ አራቀ፤ ካገር ፡ አስወጣ ፡ አስለቀቀ ። ወአፈልሰክሙ ፡ ውስተ ፡ ባቢሎን ። ኢይደግም ፡ አፍልሶተ ፡ እግረ ፡ እስራኤል ፡ እምዛቲ ፡ ምድር ። ወአፍለሶ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ፡ (ግብ፳ ፡ ፺፫ ። ፪ዜና ፡ ፴፫ ፡ ፰ ። ኩፋ ፡ ፲፫) ።

—፪ ለወጠ፤ ገለበጠ ። ፈነቀለ፤ አንከባለለ፤ ገፋ ፡ አስፈገፈገ ። አዞረ ፡ አዛወረ ። ያፈልስ ፡ ልበ ፡ የዋሃን ። ያፈልስዋ ፡ ለጸጋ ፡ እግዚ ፡ ውስተ ፡ ዝሙት ። ናሁ ፡ አፍለስኩ ፡ ኵሎ ፡ ወጸርኩ ፡ ኖዳ ፡ ወኢረከብኩ ፡ ዘይከብድ ፡ እምነቢር ፡ በቤተ ፡ አብዳን ። ኢታፍልስ ፡ ደወለ ፡ ገራህት ። እስክንድር ፡ አፍለሰ ፡ ጥንተ ፡ ዓመቶሙ ፡ ኀበ ፡ ጥንተ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ዘውእቱ ፡ ታስሪን ፡ ቀዳማይ ፡ (ጥበ፬ ፡ ፲፪ ። ይሁ ፡ ፬ ። ፈላስ ። ምባጽር ፡ ፲ ። አቡሻ ፡ ፴፱) ።

**ተፋለሰ**፤ (ተጓብሮ ፡ ወተጋብሮ፤ በተገብሮንቱ ፡ የፈለሰ ፡ ድርብ)፤ በቁሙ፤ ተዛወረ፤ ተዘዋወረ፤ ተገላበጠ፤ ተለዋወጠ፤ ተወራረሰ ። እለ ፡ ይትፋለሱ ፡ ውስተ ፡ ገዳማት ። ዘይትፋለስ ፡ ውስተ ፡ ምስካቢሁ ። ተፋልሶተ ፡ ጊዜያት ። ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዘ ፡ ይትፋለስ ፡ እምትውልድ ፡ ውስተ ፡ ትውልድ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ (አፈ ፡ ድ፳፰ ። ሚራ፳፰ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ሚያ፯) ።

**አስተፋለሰ**፤ (አድራጊና ፡ አደራራጊ፤ ባድራጊነቱ ፡ የአፍለሰ ፡ ድርብ)፤ አፋለሰ፤ አፈናቀለ፤ አዛወረ፤ አገላበጠ፤ አሳረገ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አወጣ ። ዘያስተፋልስ ፡ አእባነ ። ከመ ፡ ያስተፋልሶሙ ፡ በበ ፡ ንስቲት ። ያስተፋልስዎ ፡ ውስተ ፡ መዓርገ ፡ ክህነት ፡ በመዓርግ ፡ እምድኅረ ፡ መዓርግ ፡ በበ ፡ መዓርጉ ፡ (ሚራ፲ ፡ ፱ ። አፈ ፡ ድ፲ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**መፍልስ**፤ የሚያፈልስ፤ አፍላሽ ። የበረሓ ፡ ፀማማ፤ ሐሩር ፡ ሲያበዛ ፡ መፋልስ ፡ ይባላል ። ከመ ፡ መፍልስ ፡ ዘይመጽእ ፡ ውስተ ፡ ረምሕ ። ሐሩውያ ፡ ዘውእቱ ፡ መፍልስ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፯ ። አዋል) ።

**መፍልስት**፤ ስርቆሽ ፡ በር፤ መሽለኪያ ። ወፀአ ፡ እንተ ፡ መፍልስት ። ወቦአ ፡ እንተ ፡ መፍልስት ፡ (ዳንኤ ፡ ፲፰ና ፡ ፳፯ ። ስንክ ፡ መስ፳፫) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሥርዋ ፡ ጕዳና፤ ስላች ፡ መንገድ ፡ ይሉታል ።

**ፈላስ**፤ (ጽር ፡ ፒላስ)፤ መዝጊያ፤ ደጅ ፡ አፍ ። ያልጋ ፡ ላብስ፤ መጋረጃ ፡ ክዳን፤ የዙፋን ፡ አጐበር፤ ዐልጋውን ፡ እንደ ፡ ድንኳን ፡ ኹሉ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ የሚሸፍን ። ሆሎፎርኒስ ፡ ይነውም ፡ ውስተ ፡ ምስካቢሁ ፡ ፈላስ ። መፍርህኬ ፡ ነጽሮ ፡ ሐርደቱ ፡ ለመርዓዊሃ ፡ ንጹሕ ፡ በውስተ ፡ ፈላሳሁ ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፳፩ ። ቅዳ ፡ ቄር ። ገድ ፡ ተክ) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ፒ ፡ የፈ ፡ ዲቃላ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ፒላስ ፡ ይላል ። ፒላስን ፡ ተመልከት፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ።

**ፍልስጥኤም**፤ (ዕብ ፡ ፍሊሽቲም)፤ ፍልስጣውያን፤ የፍሌስት ፡ ሕዝብ ። ፍሌስት ፡ ስመ ፡ ነገድ፤ ከፋትሩሲምና ፡ ከከስሎሒም ፡ ዘር ፡ የወጣ፤ እነዚህ ፡ ኹለቱ ፡ በሚስቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ደይ ፡ እደኪ ፡ ኀበ ፡ ዘፈቀድከ ፡ እያሉ ፡ የሚተላለፉ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነገዳቸውና ፡ ሀገራቸው ፡ ፍሌስት ፡ ተብሏል፤ እለ ፡ ይትፋለሱ ፡ እምስካብ ፡ ውስተ ፡ ምስካብ ፡ ማለት ፡ ነው፤ ኢሎፍሊን ፡ ተመልከት፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፲፬) ።

**ፌልሲ**፤ **ፌልቲ**፤ የሜፍሩ ፡ ስም፤ ፍልስጥኤማዊ ። ኬልቲ ፡ ወፌልቲ ፡ (፪ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፰) ።

**ፈላስፋ**፤ (ጽር ፡ ፊሎሶፊያ)፤ መፍቀሬ ፡ ጥበብ፤ ጥበበኛ ፡ ዐዋቂ ፡ ተራቃቂ ። ላንድም ፡ ለብዙም ፡ ይነገራል፤ እንደ ፡ ሰብእ ፡ እንደ ፡ ሕዝብ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ። መጽሐፈ ፡ ፈላስፋ ፡ ጠቢባን፤ ይቤ ፡ አሐዱ ፡ እምፈላስፋ ። ጠቢባን ፡ ፈላስፋ ፡ ይቤሉ ። ቀዳምት ፡ ፈላስፋ ፡ ወጠቢባን ፡ (ፈላስ ። አፈ ፡ ድ፳፱ ። አቡሻ ፡ ፱) ።

**ፈሎሶፍ ፤** ገዳኢ ፡ ክማሁ ። ፈሎሶፊያ ፡ (ስንክ ፡ ታኅሣ) ።

**ፈልሰፈ ፤ አው ፡ ተፈልሰፈ ፤** ፈላሰፈ ፡ ኾነ ፤ ዐወቀ ፤ ተራቀቀ ። ወከነ ፡ አፍላጦን ፡ ይሜህሮሙ ፡ ለአርደኢሁ ፡ ጥበበ ፡ ተፈልስፎ ፡ እንዘ ፡ የሐውር ። ወሖረ ፡ ብፍድፋዴ ፡ ውስተ ፡ ተፈልስፎ ፡ አምሳኪዊ ፡ (ፈላስ ። ማር ፡ ይ/ሥ ፡ መቅ) ።

**ፍልሱፍ ፤** የፈለሰፈ ፤ ፈላስፋ ፡ የኾነ ። ይቤ ፡ ሔራቅሊስ ፡ ፍልሱፍ ፡ (አቡሻ ፡ ፶) ።

**ፍልሳፌ ፤** ፍልስፋ ፤ ፍልስፍና ። ምርመራ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ፈጠራ ፡ (አዋል) ።

**ፍልስፍና ፤** በቁሙ ፤ ፈላስፋነት ፡ ፈላስፋ ፡ መኾን ። ጥበብ ፡ ዕውቀት ፡ (አዋል) ።

**ፌማ ፤ (ጽር ፡ ፌሚ ። ዕብ ፡ ማሣእ) ፤** ቃል ፤ ባህል ፡ ስጋል ፤ ትንቢት ፤ ራእይ ፤ የሚመጣ ፡ ነገር ። ፌማ ፡ ውእቱ ፡ ዘመሀረት ፡ እሙ ፡ (ምሳጵ፱ ፡ ፳፱) ።

**ፌማ ፤** ስመ ፡ አምላክ ፤ ሥጋው ፡ ቃል ፤ ኃይል ፡ ክሃሊ ፤ ማእምር ፡ ጠቢብ ። ለተሰየ ፡ ክርስቶስ ፡ ፌማ ። ሰማዕተ ፡ ፌማ ። ብሕፀኑ ፡ ሐቀፋ ፡ ወበእ ፋሁ ፡ ሰዐማ ፡ ኢየሱስ ፡ ፌማ ፡ ለነፍስከ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ ፪ ። ጥቅ ፡ ፬፳ ፡ ፮ ። ታኅ፲፱ ። ድጓ) ።

**ፋሚኑት ፤ (ቅብጥ ፡ ፋሜኖት) ፤** የወር ፡ ስም ፤ መጋቢት ። በረምሐትን ፡ ተመልክት ፡ (አቡሻ ፡ ፷) ።

**ፍንጋ ፤ (ጽር ፡ ፌርጋጊ) ፤** የተበላሸ ፤ ብልሹ ፤ በበባሳ ፡ ሻጋታ ፤ ግም ። ክረዩ ፡ ዐዘቅተ ፡ በፍንጋ ፡ ወረከቡ ፡ ማየ ፡ ሕያወ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱) ።

**ፈንደደ ፤** አፈንደደ ፤ ፋንድያ ፡ ጣለ ፤ ተቀመጠ ።

**ፈንደወ ፤** ፈካ ፤ ፈነዳ ፤ የጥጥ ፡ የዕበጥ ፡ የሙ ስለው ፡ ኹሉ ።

**ፈንዶት ፤ (ብ ፡ ፈናዱት ፤ ትግሬ) ፤** ቂጥ ፤ ፈንጥጣ ፤ የፋንድያ ፡ መውጫ ፤ መቀመጫ ፡ ብሱ ፡ መደቡ ።

**ፍንድ ፤ (ብ ፡ ፈናድው) ፤** በቁሙ ፤ የጥጥ ፡ ቅንጣት ፤ ጥጥ ። ፋንድያ ፡ በጠጥ ።

**ፍንዱቅ ፤ (ጽር ፡ ፓንዶኪዮን ። ዐረ ፡ ፋንዱቅ) ፤** ቤተ ፡ ነጋድ ፤ (ሖቴል) ፡ የነጋዳ ፡ ማረፊያ ፤ መብል ፡ መጠጥ ፡ ዐልጋ ፡ ምንጣፍ ፡ ያለበት ። ሐኖትን ፡ ተመልከት ። ቤተ ፡ ፍንዱቅ ። ወእንዘ ፡ ተሐውር ፡ ውስተ ፡ ፍንዱቅ ፡ ይኩን ፡ ልብከ ፡ ትኩዘ ፡ (ትእ ፡ ጴጥ ፡ ሲኖድ ። ሕን ፡ መነኮ ፡ ሃይ ፡ አበ) ። ባማርኛ ፡ ፈንደቀ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ፈንዎ ፤ ዎት ፤ (ፈነወ ፡ ይፌኑ ፡ ይፈኑ ። ዕብ ፡ ፋናህ ። ሱር ፡ ፍናእ ፤ አዘረ ፡ መለሰ ፤ የገጽ ፡ የልብ) ፤** መላክ ፤ መስደድ ። ወፈነዎሙ ፡ በበ ፡ ክልኤቱ ። ዘቀደሶ ፡ አብ ፡ ወፈነዎ ፡ (ሉቃ ፲ ፡ ፩ ። ዮሐ ፲ ፡ ፴፮) ።

—፤ ማዘዝ ፤ ማምጣት ፤ ማኖር ፡ ማሳደር ። ፈነወ ፡ እግዚ ፡ ሞተ ፡ ላዕለ ፡ ያዕቆብ ። ወይፌኑ ፡ መቅሠፍተ ፡ ላዕሌሆሙ ። ፈኑ ፡ ላዕሌየ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ (ኢሳ ፱ ፡ ፰ ። ዘዳ፳ ፡ ፰ ። ሉቱ ፡ ዕገ፲፱) ።

—፤ መዘርጋት ፤ መወርወር ። ፈኑ ፡ እዴከ ፡ ወግስስ ። ፈኑ ፡ አሕጻከ ፡ (ኢዮ፩ ፡ ፲፩ ። መዝ ፡ ፲፯) ።

—፤ መፍታት ፤ ነጻ ፡ ማውጣት ፡ ማሰናበት ፤ መልቀቅ ፤ ማሰናበት ፤ መሸኘት ። ፈነውክዋ ፡ ለእምክሙ ። ፈነዋ ፡ ወሖረት ። ወእምድኅረ ፡ ዝ ፡ ይፌንወክሙ ። ወሖረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ይፈንዎሙ ፡ (ኢሳ ፶ ፡ ፩ ። ኩፋ ፡ ፲፯ ። ዘፀ ፡ ፰ ። ዘፍ፲፰ ፡ ፲፯) ። በፈነወ ፡ ፈንታ ፡ አስ ተፋነወ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ከመ ፡ የአዝዝ ፡ ለአስ ተፋንዎ ፡ ኵሉ ፡ ዘተፄወወ ። አስተፋነዎ ፡ ሄሮድስ ፡ እስከ ፡ መካን ፡ ርሑቅ ፡ ወተመይጠ ። ቦአ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ወቤተ ፡ እንዘ ፡ ያስተፋንዎሙ ፡ ለእሙ ፡ ወለ አዝማዲሁ ፡ (ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ነሐ፲፱ ። ግብ፲፯ ፡ ፲፭ ። ፳፩ ፡ ፭) ።

**ፈናዊ ፤** የሚልክ ፤ ላኪ ፤ ሰዳጅ ። አ ፡ ፈናዌ ፡ እሳት ፡ ዲበ ፡ አህጉር ፡ ኀምስቱ ። አብ ፡ ፈናዌ ፡ ወ ልድ ። ነአምን ፡ አበ ፡ ፈናዌ ፡ (ጥበ ፡ ጠቢ ። አፈ ፡ ድ፫ ። ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ተፈነወ ፤** ተላከ ፤ መጣ ፤ ቀረበ ፤ ተወረወረ ፤ ተሸኘ ። ተፈነወ ፡ ኀቤየ ፡ አሐዱ ፡ እምሱራፌን ። ጸ ሎት ፡ እንተ ፡ ትትፌኖ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መካን ። ወ ለከ ፡ ይትፌኖ ፡ ጸሎት ፡ በኢየሩሳሌም ። ተፈነወ ፡ ኵናት ፡ ኀቤሁ ። ወእምኀቤክሙ ፡ እትፌኖ ፡ ህየ ፡ (ኢሳ፮ ፡ ፮ ። ፫ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፷፬ ። አፈ ፡ ተ፳፪ ። ሮሜ፲፭ ፡ ፳፬) ።

**ፍኑው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ኑት) ፤** የተላከ ፡ ልኡክ ፤ መልክተኛ ። መልአክ ፡ ፍኑው ፡ እምኀበ ፡ እ ግዚ ። ፍኑው ፡ አንተ ፡ እምኀበ ፡ አቡከ ፡ (ዮሴፍ ። ቅዳ ፡ ያዕ) ።

**ፍናዌ ፤** መላክ ፡ (ጥላ) መላክ ፤ አላላክ ፤ ልኮሽ ። ሲናበብ ፡ ግን ፡ የቅጽል ፡ አፈታት ፡ ይፈታል ። ፍናዌ ፡ መልእክት ፡ ቢል ፡ ፍኑው ፡ መልእክት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (አረጋ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**ፍኖት ፤ (ፍናው ፡ ዋት) ፤** መንገድ ፤ ጐ ዳና ፤ ጥርጊያ ፤ ስላች ፤ ሥርጥ ። አስተዳልዉ ፡ ፍኖቶ ። ዘይደይሖ ፡ ፍኖተከ ። ፍናው ፡ ርቱዓት ። በእንተ ፡ ፍናዋት ፡ (ማቴ፫ ፡ ፫ ። ፲፩ ፡ ፲ ። ምሳ፪ ፡ ፲፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

—፤ መግቢያ ፡ በር ። ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ባሕር ። ርሒብ ፡ ፍኖት ፡ (ሕዝ፵፯ ፡ ፫ ። ፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፩) ።

—፤ አፍኣ ፤ ውጭ ፡ ሜዳ ፤ አደባባይ ፡ መተላለፊያ ፤ ገ ባያ ፡ ሱቅ ። ጥበብ ፡ በፍናው ፡ ትኬልሕ ። በርእሰ ፡ ኵሉ ፡ ፍናዋት ። ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ፍናዋት ። ፍናወ ፡ ሀገር ፡ (ምሳ፩ ፡ ፳ ። ሰቈ፪ ፡ ፲፱ ። ኢሳ፶፩ ፡ ፳ ። ሚራ፱ ፡ ፮) ።

—፤ ሕብር ፤ መልክ ፤ ዐይነት ። ይነቅዕ ፡ ባሕር ፡ ዘክ ልኤ ፡ ፍናዊሁ ፡ ባሕር ፡ ዘብርሃን ፡ ወባሕር ፡ ዘነፋስ ፡ (ቅዳ ፡ ማሩ) ።

—፤ አካኼድ ፤ አናዎር ፣ ሥራ ፤ ሕግ ፡ ሥርዐት ፤ ልማድ ፡ ትምርት ፤ አምልኮት ። አሜሃ ፡ ይጸድቃ ፡ ፍናዊከ ፡ ወፍናወ ፡ ውሉድከ ። ዕቀብ ፡ ፍናዊሃ ። ወአጽንዐ ፡ ፍናወ ፡ ዳዊት ፡ አቡሁ ። ኢትትመሀሩ ፡ ፍኖተ ፡ አረማውያን ፡ (ኩፋ ፡ ፳፪ ። ሢራ ፡ ፳፯ ። ዓ፰ ፡ ፳፬ ። ኤር ፲ ፡ ፪) ።

**ፍና ፤ (ናት)** ፤ መንገድ ፤ አንጻር ፡ አቅጣጫ ። ጊዜ ፤ ቅድም ። ጊዜ ፡ ሠርክ ፤ ቅድመ ፡ ሠርክ ። ከተሲያት ፡ በኋላ ፤ ከሠርክ ፡ በፊት ፤ ወደ ፡ ማታ ፡ ጊዜ ፤ ሲን ፍስ ፤ ጥላ ፡ ሲበርድ ፤ ማታ ። ወሰምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚ ፡ ፍና ፡ ሠርክ ። እስከ ፡ ፍና ፡ ሠርክ ። ወፍና ፡ ሠርክ ፡ ይበርህ ፡ ብርሃነ ፡ ፀሓይ ፡ (ዘፍጥ ፡ ፫ ። ሰንክ ፡ ፳ ፡ ፳ ። ዘካ፲፬ ፡ ፯) ።

—፤ በረሐ ፤ ባድማ ፤ ስፍራ ፡ በታ ፡ ጎን ፡ ወገን ፡ ማእዝን ። ብክዩ ፡ በውስተ ፡ ፍና ፡ ቢድው ። ዘጽድቅ ፡ ፍና ። ወተሰምየ ፡ ውእቱ ፡ ፍና ፡ መሬረ ። ውስተ ፡ ጽርባዕቱ ፡ ፍና ፡ (ኤር፱ ፡ ፲ ። አርጋ ፡ ፱ ። ዘፀ፲፭ ፡ ፳፫ ። ፲፯ ፡ ፯ ። ፳፰ ፡ ፲፫ ። ፳፭ ፡ ፳፷ና ፡ ፴፪ ። ፴ ፡ ፬) ።

—፤ ምክንያት ፤ ሰበብ ። በአይ ፡ ፍና ። በእንተ ፡ ሠባስ ፡ ፍናት ፡ (ቄር ፡ ጸላ ። ፊልክ ፡ ፸) ።

**ፈንተወ ፤ (ዲ ቃ ፡ ግ)** ፤ ለየ ፡ ከፈለ ፤ ዐደለ ። ፈንታ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ተፋነወ** ፤ ተላላከ ፡ ተሸኛኘ ፤ ተሰናበተ ። ወእምዝ ፡ ተፋነውዎ ። አንስ ፡ እትፋነወክሙ ። ሑር ፡ ተፋነዎሙ ፡ ለአዝማዲከ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፬ ። የካ፫ ። ንሐ፲፬) ።

**አስተፋነወ** ፤ አላላከ ፤ አሸኛኘ ፤ አሰነባበተ ።

**ፉና ፤—ፉኖስ ፤—ፃና ።**

**ፈንጠረ ፤ (ትግሬ)** ፤ ፈነጠረ ፤ አፈናጠረ ፡ አስፈነጠረ ፤ በተነ ፡ በታተነ ፤ ወረወረ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ፈንክስ ፤ (ጽር ፡ ፊኒክስ)** ፤ ያሞራ ፡ ስም ፤ የተረት ፡ አሞራ ፤ የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ አረማውያን ፡ የሚያምኑበት ፡ የሚተርቱበት ፤ በተረቱ ፡ ትንግሌ ፡ ሙታንን ፡ የሚያስረዳ ። ናሁ ፡ ያሌብዎሙ ፡ ለዕልዋን ፡ ዖፍ ፡ እሊ ፡ ይብልዎ ፡ አልቦ ፡ ዘከማሁ ፡ ዘአሐዱ ፡ ፍጥረቱ ፡ ዘስሙ ፡ ፊንክስ ። ወይብሉ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ዖፍ ፡ ከመ ፡ የሐዩ ፡ ኃምስተ ፡ ምእተ ፡ ዓመተ ፡ ወእምዝ ፡ ይወርድ ፡ ውስተ ፡ ግብጽ ፡ ወያመጽእ ፡ ምስሌሁ ፡ ቀናንሞስ ፡ ወሰሊኖተ ፡ ወዑደ ፡ ወይነብር ፡ ውስተ ፡ ሥዕለ ፡ ጣዖት ፡ ዘስሙ ፡ ሔዎን ፡ ወይሬኢ ፡ ውስተ ፡ ምሥራቅ ፡ ወይሰግድ ፡ ለፀሓይ ። ወእምዝ ፡ ይውዒ ፡ ወይከውን ፡ ሐመደ ፡ ወይወፅእ ፡ እምውእቱ ፡ ሐመድ ፡ ንኡስ ፡ አሐዱ ፡ ዕፄ ፡ ወይከውን ፡ ንኡስ ፡ ዖፈ ፡ ፊንክስ ፤ ወልሂቆ ፡ ይገብእ ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ ዐረብ ፡ (ዲድ ፡ ፳፭) ።

**ፈንሙ ፤ ፔንሙ ፤ (ጽር ፡ ፕኔፍማቶን)** ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ምንዋማን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ፈኒን ፤ (ፈነ ፤ ፈነነ ፡ ይፈንን ፡ ይፍንን)** ፤ መፋነን ፤ መሮንን ፤ ፋኖ ፡ ፉኖ ፡ ሮናና ፡ መኾን ፤ ወይም ፡ ማድረግ ።

**ፈንፈነ ፤ (ትግ ፡ ሐበበ)** ፤ ጠላ ፡ ነቀፈ ፤ ተጠየፈ ። አስጠየፈ ፤ ነውረኛ ፡ ኾነ ።

**ፈናፍንት** ፤ በቁሙ ፤ ጉድ ፤ ነውር ፤ ጸያፍ ፤ የሚያስጠላ ፡ የሚያስጠይፍ ።

**ፈናፍንታም** ፤ ፈናፍንታዊ ፤ ም ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። ጉደኛ ፤ ጉዳም ፤ ባንድ ፡ ዐካ ፡ የወንድና ፡ የሴት ፡ ምልክት ፡ ያለው ፤ በወንድነቱ ፡ ላይ ፡ ሴትነት ፡ የተጨመረበት ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ለወንዶች ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ ለሴቶች ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ መኾን ፡ የሚችል ። ዐንጕል ፡ ከኹሉ ፡ አለኹ ፡ የሚል ። ፈናፍንታም ፡ ውእቱኒ ፡ ዘቦቱ ፡ ኀፍረተ ፡ ተባዕት ፡ ወአንስት ፡ ኅቡረ ፡ በአሐዱ ፡ መካን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፪) ። ይኸውም ፡ በሰው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ በእንስሳትና ፡ በአራዊት ፡ ኹሉ ፡ ይገኛል ፤ ኸርብ ፡ ግን ፡ በጭራሽ ፡ ፈናፍንት ፡ ኹኖ ፡ የቀደመ ፡ ፊጥ ፡ ይልበታል ፡ ይባላል ። (ተረት) ፤ ኸርብ ፡ ሲሰር ፡ ኺደ ፡ ተሰሮ ፡ ገባ ።

**ፈንጽጸ ፤ (ፈንጸጸ ፡ ይፈነጽጽ ፡ ይፈንጽጽ)** ፤ መፈናጠጥ ፤ መጣበቅ ፤ መስጠፍ ፤ ፈጥ ፡ ማለት ፡ በስተኋላ ። ፈንጥጣ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ፈንጻጺ** ፤ ኩፍኝ ፤ ፈንጣጣ ፤ የቍስል ፡ በሽታ ፤ በዐይን ፡ ሳይቀር ፡ በሕዋሳት ፡ ኹሉ ፡ የሚወጣ ፤ ሃዕከክ ፡ ዐይነት ። በደይን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። እመሂ ፡ ፈንጻጺ ፡ ወእመሂ ፡ ብድብድ ፡ (አዋል) ። ትማሮች ፡ ግን ፡ ቂጥኝ ፡ ሲሉ ፡ ፈንጣጣ ፡ ይላሉ ፤ ዐማሮችም ፡ በሸሙር ፡ ቂጥኝን ፡ ፈንጣጣ ፡ ይሉታል ፤ እንሊት ፡ ፈንጣጣ ፡ እውጥታለች ፡ እንዲሉ ። ቂጥኝ ፡ ማለት ፡ ቅሉ ፡ ከመፈናጠጥ ፡ የሚመጣ ፡ የቂጥ ፡ የፊንጥጣ ፡ ደዌ ፡ ማለት ፡ ነውና ፤ ፈንጣጣ ፡ መባል ፡ ከኩፍኝ ፡ ይልቅ ፡ ለቂጥኝ ፡ ይስማማል ። ቂጥኝ ፡ የመጣ ፡ ከግሪኝ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፤ ያመጡትም ፡ ግሪኮች ፡ ጌቶች ፡ ናቸው ፡ ይባላል ፤ ዐይነቱና ፡ ስሙ ፡ ብዙ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ዐተሬ ፡ ምስሬ ፤ ማጭደ ፡ ዝኅኔ ፤ ወንዴ ፡ ሴቴ ፤ ቀሚሱ ፡ ድኺቱ ፤ ይሰማ ፡ ስራዊት ፡ ይሉታል ።

**ፈንቀለ ፤ (ነቂል ፡ ነቀለ)** ፤ ፈነቀለ ፤ ፈነቃቀለ ፤ አስገለለ ፡ ላጠ ፤ ቀረፈ ፤ ቁፈረ ፡ ማስ ፤ ነቀለን ፡ እይ ። ፈንገለ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ቀና ፡ ን ፡ ይወራረሳሉ ። ተሀውከ ፡ ሾሎ ፡ ዘውስተ ፡ ቤታ ፡ ወትፈንቅል ። ዘፈንቀለ ፡ አጽልዕቲሁ ፡ ወአብአ ፡ አዳብዒሁ ። እለ ፡ ይፈንቅሉ ፡ መቃብረ ፡ (ሉቃ፲፭ ፡ ፰ ። መጽ ፡ ምስ ። ኦሪ ፡ ድ፳፱) ።

**ፈንቆን ፤ ፈኒቃ ፤ (ጽር ፡ ፊኒከን ፤ ፊኒክ)** ፤ ስሌን ፤ ተምር ፤ ዘንባባ ። ወተወርሰ ፡ ሀገረ ፡ ፊንቆን ። ወደቦራስ ፡ ትነብር ፡ ኀበ ፡ ፊኒቃ ፡ (መሳ፫ ፡ ፲፫ ። ፬ ፡ ፭) ።

**ፊንቂስ ፤ (ጽር ፡ ፊኒኪስ)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ ሲደና ፤ የሲደና ፡ አውራጃ ። ደወሉ ፡ ፊንቂስ ። ፈላስያን ፡ እምፊንቂስ ፡ (ዘፀ፲፯ ፡ ፴፰ ። ኢሳ፳፫ ፡ ፪ ። ግብ፲፩ ፡ ፲፱) ። ፊንቅያ ፡ ፊንቂ ፡ ፊኒቆን ፡ ይባል ፤ ኹሉም ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ነው ፡ (ግብ፲፭ ፡ ፫ ። ፳፩ ፡ ፪ ። ኢዮ፵ ፡ ፴፩) ።

**ፎንቃስ ፤ (ጽር ፡ ፊኒክስ)** ፤ ታላቅ ፡ አሞራ ፤ ጥንብ ፡ በላ ፤ ግልገል ፡ አንሣ ፡ (ሔኖክ) ።

**ፎንቃስ ፤—ጕሬዛ ፤—ፎቃንስ ።**

**ፈሥሐ ፤ ሐት ፤ (ፈሥሐ ፡ ይፌሥሕ ፡ ይፈሥሕ ። ዐረ ፡ ፈሰሐ ፤ ሰፋ ፤ ተደሰተ ። ዕብ ፡ ፋሳሕ ፤ ዐደወ ፤ ፈሰከ)** ፤ ማስደሰት ፤ ደስ ፡ ማሰኘት ፤ ማጫዎት ፡ መናዘዝ ፡ ማረጋጋት ። ፈጽሐን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጉር ፡ ነው ፤ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በፈሥሐ ፡ ፈንታ ፡ አስተፍሥሐ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ወይን ፡ ወማሕሌት ፡ ያስተፌሥሑ ፡ ልበ ። አስተፍሥሖሙ ፡ ለእለ ፡ ይላሕዉ ፡ (ሢራ፵ ፡ ፳ ። ማ፭፳ ፡ ፳፬) ።

**ፈሣሒ ፤ መስተፍሥሒ ፡ ሒ** ፤ ደስ ፡ የሚያሰኝ ። ግብር ፡ ሠናይ ፡ ወመስተፍሥሒ ። መስተፍሥሒ ፡ አልባብ ፡ (ፈላስ ። ቄድር ። ቅዳ) ።

**ተፈሥሐ** ፤ ተደሰተ ፤ ደስ ፡ አለው ፤ ደስ ፡ ተሰኘ ። ተፈሥሐ ፡ ወሰትየ ። ተፈሥሐ ፡ ልቡ ። እለ ፡ ይትፌሥሑ ፡ በድቀቱ ፡ ለጻድቅ ፡ (ኩፋ ፡ ፳ ። ሩት፫ ፡ ፯ ። ሢራ፲ ፡ ፳) ።

**ፍሡሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ሥሕት)** ፤ ደስ ፡ ያለው ፤ ደስታ ፡ የመላው ፤ ብሩህ ፤ ቀይሕ ። አሥሩ ፡ ሰልብ ፡ ፍሡሕ ፤ ገጽ ፡ ብሩህ ። እንዘ ፡ ፍሡሕ ፡ ውእቱ ፡ ልቡ ። ገጽከ ፡ ስቡሕ ፡ ወፍሡሕ ፡ ከመ ፡ ወርኅ ፡ ዘአሚ ፡ ገሀህ ። ፍሡሓት ፡ እምወይን ፡ አዕይንቲሁ ፡ (ሢራ፲፫ ፡ ፲፯ ። ፴፱ ፡ ፴፩ ። ደራሲ ። ዘፍ፵፱ ፡ ፲፪) ። ዐይኖችን ፡ ፍሡሓት ፡ እምወይን ፡ ማለት ፤ ወይን ፡ የጠጣ ፡ ሰው ፡ ልቡን ፡ ደስ ፡ ሲለው ፡ ዐይኑም ፡ እንደ ፡ ጠጁ ፡ ይቀላልና ፤ ይህንን ፡ ያሳያል ።

**ፍሥሓ** ፤ ደስታ ፤ ኑዛዜ ፤ ሰላም ፤ ጤና ፤ መልክም ። ነዐ ፡ አምክርከ ፡ በፍሥሓ ። ብላዕ ፡ ኅብስተከ ፡ በፍሥሓ ። ወሀብከኒ ፡ ፍሥሓ ፡ ጽድቅ ። ነገረ ፡ ፍሥሓ ። አልቦ ፡ ፍሥሓ ፡ ለኃጥኣን ። ለዮሐንስ ፡ ቄርሎስ ፡ ፍሥሓ ። ሕየው ፡ በፍሥሓ ፡ (መክ፪ ፡ ፩ ። ፱ ፡ ፯ ። ኢሳ፶፯ ፡ ፲፳ ። ዘካ፩ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፵፰ ፡ ፳፪ ። ቱረ ፡ ቄር፲፰ ። መቴ፯ ፡ ፲፱) ።

**ትፍሥሕት ፤ (ታት)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ተድላ ፤ ደስታ ፤ ዕረፍት ። አልቦ ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘይኄይስ ፡ እምሐሤተ ፡ ልብ ። ወይን ፡ ለትፍሥሕት ፡ ተፈጥረ ። ለብሰት ፡ አልባሰ ፡ ትፍሥሕታ ። ትፍሥሕታተ ፡ ሰማይ ፡ (ሢራ፴ ፡ ፲፯ ። ፴፬ ፡ ፳፯ ። ዮዲ፲ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ሐም፳፭) ።

**ፍሥሕ ፤ (ዕብ ፡ ፌሳሕ)** ፤ በዓለ ፡ ናእት ፤ ስመ ፡ መሥዋዕት ፤ እስራኤል ፡ በሚያዝያ ፡ ጨረቃ ፡ ባሥራ ምስተኛው ፡ ቀን ፡ የሚያከብሩትና ፡ የሚሠዉት ። ፋሲካ ፡ ዐዲው ፡ ዕድወት ፡ ማዕደት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ፋሲካን ፡ ተመልከት ። ወበቀዳሚት ፡ ዕለተ ፡ ፍሥሕ ። አመ ፡ ይጠብሑ ፡ ፍሥሐ ። በልዑ ፡ ፍሥሐ ፡ ወገብሩ ፡ በዓለ ፡ ናእት ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፡ (ማቴ፳፮ ፡ ፲፯ ። ማር፲፬ ፡ ፳፯ ። ፩ዕዝ ፡ ፯ ፡ ፳፩—፳፪) ።

**ፍሥሐት ፤ (ታት)** ፤ ጠባብ ፡ በር ፤ ሥርጥ ፡ ዳገት ፤ መተላለፊያ ፡ ዐንገት ። ፍሥሐታተ ፡ አድባር ። ዐጸዉ ፡ ፍሥሐታተ ፡ (ዮዲ፬ ፡ ፯ ። ፭ ፡ ፩ ። ፯ ፡ ፲፱ ። ፯ ፡ ፩) ።


—፤ ጕባ ፡ ቍሊልታ ፤ ተራራ ፡ ኰረብታ ። ወገብረ ፡ ፍሥሐተ ፡ ዐቢየ ፡ ህየ ፡ ለስምዐ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ተጸውዐ ፡ ስሙ ፡ ለውእቱ ፡ መካን ፡ ፍሥሐተ ፡ ስምዐ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱) ።

—፤ ቤተ ፡ ጣዖት ፤ ምሥዋዕ ፡ ጣዖት ። ወይገብሩ ፡ ሎሙ ፡ ፍሥሐታተ ፡ ወያመ ፡ ወግልፎ ፡ ወይሰግዱ ፡ (ኩፋ ፡ ፩) ። መጋርንና ፡ ባማን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ፍዕግ ፤—ፍግ ፤—ፈጊግ ፡ ፈገገ ።**

**ፈዐወ ፤ (አፈወ ። ዕብ ፡ ፋዔህ)** ፤ ጮኸ ፡ ጠራ ፡ እፏጨ ፤ አጥብቆ ፡ ነፋ ፡ ተነፈሰ ፡ አቃሰተ ፤ ከደዌና ፡ ከጭንቅ ፡ የተነሣ ። አፈወንና ፡ ገዐረን ፡ እይ ።

**አፍዖት ፤ (ዕብ ፡ ኤፍዔ ። ዐረ ፡ አፍዐን)** ፤ እፍኝት ፡ እባብ ፡ ኰርፋፋ ፡ ዐጭር ፡ ኾራት ፡ ጕንዳ ፤ ትንፋሹና ፡ መርዙ ፡ ቶሎ ፡ የሚናኝ ፡ የሚጐዳ ። ወፀአት ፡ አፍዖት ። ሕምዘ ፡ አፍዖት ። ልሳነ ፡ አፍዖት ፡ (ግብ፳፰ ፡ ፫ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፴፫ ። ኢዮ፳ ፡ ፲፮) ።



እፍዖት ፤


**አፍዖታት ፤ አፋዕው** ፤ እፍኝቶች ።

**ፈፍ ፤—ስመ ፡ ፊደል ፤—አፈፈ ።**

**ፈጺሐ ፤ ሐት ፤ (ፈጽሐ ፡ ይፈጽሕ ፡ ይፍጻሕ ። ዕብ ፡ ፋጻሕ ። ዐረ ፡ ፈፀኀ)** ፤ መግመስ ፤ መቍረስ ፤ መፍጨት ፡ መከከት ፡ መስበር ፡ ማድቀቅ ፤ መፍለጥ ፡ መሠንጠቅ ፤ መጥረብ ፡ መውቀር ። እንተ ፡ ትፈጽሖ ፡ ለሠሩ ፡ ምድር ። ለብርት ፡ ከመ ፡ እብን ፡ ይፈጽሕዎ ። ኢትንድቀ ፡ ፈጺሐከ ፡ (ኤር፳፰ ፡ ፳፫ ። ኢዮ፵፰ ፡ ፪ ። ዘፀ፵ ፡ ፳፭ ። ሃ.ርማ) ።

**መፍጽሕ ፤ (ሕት ። መፋጽሕ ፤ ሕት)** ፤ መፍጫ ፤ መፍለጫ ፤ መቀጥቀጫ ፡ መጅ ፡ ፋስ ፤ መደሻ ፤ ድጅኖ ፤ ደንጕራ ፤ በትረ ፡ ቃታ ፤ መሮ ፡ ሽብልቅ ፤ ውሻል ። መፍጽሕ ፡ ዘይፈጽሕ ፡ ኵሎ ። በመፍጽሕ ፡ ኅጺን ፡ ዐፀመ ፡ እገሪሁ ፡ ቀጥቀጡ ። ማሕጼ ፡ ወመ

ፍጽሕ ። ብርዐ ፡ ይመስሎ ፡ መፍጽሕ ፡ (ኤር፳፫ ፡ ፳፱ ። ስንክ ፡ ነሐ፳፭ ። መዝ ፡ ፸፫ ። ኢዮ፵፩ ፡ ፳)።



መፍጽሕ ፡

**ተፈጽሐ** ፤ ተገመሰ ፤ ተፈለጠ ፤ ተፈነከተ ። ኵ ዝሕ ፡ ኢይትፈጻሕ ፡ በጕድብ ፡ ወበማሕጼ ፡ ከመ ፡ ዕፀው ። በከመ ፡ እብን ፡ እድማስ ፡ ዘኢይትፈጻሕ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። አረ ፡ ተ፳፪) ።

**ፋጽዮ ፤ ዮት ፤ (ፋጸየ ፡ ይፋጺ ። ዕብ ፡ ጻፍጼፍ)** ፤ ማፏጨት ፤ በቀጭን ፡ ቃል ፡ መጮኽ ፤ ፊውፊር ፡ ማሰት ፤ የትካዜና ፡ የእንክሮ ፤ የጥሪ ፡ ምልክት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በፋጸየ ፡ ፈንታ ፡ ተፋጸየ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፤ አያሰኝም ። መንፈስ ፡ ዘይትፋጸይ ። ቃል ፡ ቀጢን ፡ ከመ ፡ ዘይትፋጸይ ። ሠየጠ ፡ አሕዛብ ፡ ተፋጸዩኪ ። አንከረ ፡ ወተፋጸየ ፡ በርደተ ፡ መንፈስ ። ወከማሁ ፡ ዲያቆናትኒ ፡ ይትፋጸዩ ፡ (ጥበ፲፯ ፡ ፲፯ ። ፫ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፴፮ ። ቀዳ ፡ ሕር ። ቀሌ) ።

**ፋጻ ፤ ፋጽ ፤ (ጻት)** ፤ ፉጨት ፡ ወፍኛ ፡ እባብኛ ፡ ጩኸት ፤ ቀጭን ፡ ድምፅ ። ከመ ፡ ፋጻ ፡ ቀጢን ። ሰበ ፡ ንሰምዮ ፡ ፋጻ ፡ ቀጢነ ፡ ይትረከብ ፡ በኀበ ፡ ኤልያስ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ማሕ ፡ ፫) ።

**ተፋጻየ** ፤ ተፏጨ ፡ ተፎማጨ ፡ በፉጨት ፡ ተጣራ ።

**ፈጽሞ ፤ ሞት ፤ (ፈጸመ ፡ ይፌጽም ፡ ይፈጽም ። ዕብ ፡ ፋጻም ፤ ሰበረ ፡ ጣለ)** ፤ መፈጸም ፡ መምላት ፤ መጨረስ ፡ ማብቃት ፤ ማከናወን ፤ ፍጹም ፡ ምሉእ ፡ ማድረግ ። መልእክ ፡ ተመልክት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ይፈጽም ፡ ለከመ ፡ ዘሎ ፡ መፍቅደከሙ ። ፈጽሙ ፡ መስፈርተ ። ወትፌጽም ፡ እደዊሁ ፡ ለአሮን ፡ ወእደ ፡ ውሉዱ ። እደዊሁ ፡ ይፌጽማሁ ፡ (ፊልጵ፬ ፡ ፲፱ ። ማቴ፳፫ ፡ ፴፪ ። ዘፀ፳፱ ፡ ፱ ። ዘካ፬ ፡ ፱) ። ባስብስዮች ፡ ግን ፡ መላ ፡ ብማሰት ፡ ፈንታ ፡ ቀብ ፡ ይሉታል ፡ ዘይቤው ፡ አይደለም ።

**ፈጻሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት)** ፤ በቁሙ ፤ የሚጨርስ ፡ ጨራሽ ። እግዚ ፡ ወጣኒ ፡ ዘሎ ፡ ወፈጻሚ ፡ ዘሎ ፡ (ቅዳ) ።

**አፈጸመ** ፤ አስፈጸመ ፡ አስመላ ፡ አስጨረሰ ። ለአፈጽሞቱ ፡ ምግባራቲ ። ስብሐት ፡ ለእግዚ ፡ ዘአፈጸመኒ ፡ ዘወጠንኩ ፡ በጸጋሁ ፡ ፍ. ሮ. ፉ. ፈ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ማ፳ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**መፈጽም** ፤ የሚፈጽም ፡ የሚያስፈጽም ፡ ፈጻሚ ፡ አስፈጻሚ ። መፈጽመ ፡ ተስፋ ፡ ለዘአስፈወ ፡ (ፊላ ፡ ግ፫) ።

**ተፈጸመ** ፤ በቁሙ ፡ መላ ፤ ተጨረሰ ፤ ፀለቀ ፤ በቃ ፡ ፍጹም ፡ ኾነ ። ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ዘተብህለ ። ኢተፈጸመ ፡ ኀጢአቶሙ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ። እምኢተፈጸመ ፡ ሎሙ ፡ ዝ ። ወበዝንቱ ፡ ትትፌጸም ፡ ተፋቅሮ ፡ (ማቴ፩ ፡ ፳፪ ። ኩፋ ፡ ፲፬ ። ዮሴፍ ። ፩ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፲፯) ።

**ፍጹም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ጽምት)** ፤ በቁሙ ፤ የተፈጸመ ፤ ያለቀ ፤ የተጨረሰ ፤ የመላ ፡ ምሉ ፤ የበቃ ፤ ትክክል ፤ ሕጸጽ ፡ ነውር ፡ የሌለበት ። ወገብረ ፡ ኪራም ፡ ፍጹመ ፡ ዘሎ ፡ ቅኔ ። ወርኀ ፡ ፍጹመ ፡ ብርሃን ። በግዕ ፡ ፍጹም ። ሥርዐተ ፡ ፍጹማን ። አኀው ፡ ፍጹማን ፡ (፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፲፩ ። አቡሻ ፡ ፲፫ ። ዘፀ፲፪ ፡ ፭ ። ፊልክ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ማ፪) ።

— ፤ ጥሩ ፡ ብርቱ ፤ እውነተኛ ፤ ቅልቅል ፡ የሌለው ፤ ግብዝ ፡ ያይደለ ። ወርቅ ፡ ፍጹም ። ብሩር ፡ ፍጹም ፡ (፫ነገ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ። ኩፋ ፡ ፲፱) ።

**ፍጹመ** ፤ ፈጽሞ ፡ በፍጹም ፤ ጨርሶ ፤ ጭራሽ ፤ በጭራሽ ። ኢተከሥተ ፡ ሕግ ፡ ፍጹመ ። ይትጋደል ፡ ፍጹመ ። ወማየሰ ፡ ፍጹመ ፡ ኢይሰቲ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፫ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፫ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ፍጽምና** ፤ ፍጹምነት ፤ ምሉነት ። ሰበ ፡ ርእየ ፡ ቅድስናሁ ፡ ወፍጽምናሁ ፡ (ስንክ ፡ የካ፲፭ ። ፊልክ ፡ ፳፯) ።

**ፍጻሜ** ፤ በቁሙ ፡ (ሳጥ ፡ ፈ) መፈጸም ፤ መፈጸም ፡ አፈጻጸም ፡ ፍጻማ ። መፈጸሚያ ፡ መጨረሻ ፤ ማፍ ፤ ምላት ። እስመ ፡ ኀልዮ ፡ ኪያሃ ፡ ፍጻሜ ፡ ለእምሮ ። ንብጻሕ ፡ ኀበ ፡ ፍጻሜሁ ። ፍጻሜ ፡ መጠኑ ፡ አካል ፡ ዘዐይው ፡ ዕሥራ ፡ ዓመት ፤ ወእመ ፡ እኮ ፡ ዕሥራ ፡ ወኀምስቱ ፡ ዓመት ፤ ወለአንስት ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ዓመት ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡ ፀሠርቱ ፡ ወኀምስቱ ፡ ዓመት ፡ (ጥበ፯ ፡ ፲፯ ። ዕብ፯ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፫) ።

**ተፍጻም** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ መጨረሻ ፤ መደምደሚያ ፤ ምላት ። እመ ፡ ተፍጻመ ፡ ወርኀ ፡ አዕረፈ ። እፎ ፡ ፈቀደ ፡ ኀሊናየ ፡ ለውዳሴኪ ፡ ተፍጻም ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ ። ድራሴ) ።

**ተፍጻሜት** ፤ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ። ተፍጻሜተ ፡ ዓመት ። ተፍጻሜተ ፡ ሰማዕት ። ተፍጻሜቱ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ። እስከ ፡ ተፍጻሜቱ ። ወእምተፍጻሜት ፡ ዘኢሁ ፡ ለዘሎ ፡ ይሁብ ፡ (ኩፋ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፱ ። ዕር ፡ ኢሳ፲፭ ፡ ፴፯ ። መክ፫ ፡ ፲፭ ። ተረ ፡ ቄር) ።

**ፍጽም ፤ (ማት ። ዕብ ፡ ፋዳሐት ፤ ሜጻሕ)** ፤ ግንባር ፡ ፊት ። ሄደ ፡ ውስተ ፡ ፍጽሙ ። ከመ ፡ ንዕትብ ፡ ፍጽማቲነ ፡ በአምሳለ ፡ መስቀል ። አነ ፡ አሐውር ፡ ፍጽመ ፡ ቅድሜከ ። ወወፅአ ፡ ይሁዳ ፡ ፍጽመ ፡ (ሚራ፯ ፡ ፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፬ ። ኢሳ፵፰ ፡ ፬ ። ኩፋ ፡ ፴፰) ።

(ሳ) **ፈዒም ፤ ሞት ፡ (ፈፀመ ፡ ይፌዕም ፡ ይፍዕም ። ዕብ ፡ ፋጢም ፤ ቀለበ ፡ አሠበ)** ፤ መገጋት ፡ ማፈን ፤ መድፈን ፡ መወተፍ ፡ መምረግ ። እፌ

ፅም ፡ መንገደ ። ከመ ፡ ይፍፅም ፡ እናቅጺሃ ። ዘ ይፈፅም ፡ እዘዚሁ ። ፈፀመ ፡ እፈ ፡ እናብስት ። አምኃ ፡ ወሕልያን ፡ ይፈፅም ፡ አፉሆሙ ፡ (ሆሴ ፡ ፲ ። ሕዝ ፳፩ ፡ ፳፪ ። ዳን ፯ ፡ ፳፱ ። ሚራ ፳ ፡ ፳፱) ።

**ተፈፅመ** ፡ ተዘጋ ፡ ታፈነ ፡ ተደፈነ ፡ ተከለከለ ፡ ምላሽ ። ዐጣ ፡ ዝም ፡ አለ ። ተፈፀመ ፡ እንቅዕተ ፡ ቀላይ ። ተፈፀመ ፡ አፈ ፡ ኵሉ ፡ አራዊት ። እምነቢብ ፡ ይትፈፀም ፡ አፉሁ ፡ ለዐማፂ ። ኀደላን ፡ ይትፈፀሙ ፡ ወኢይነብቡ ፡ (ኩፋ ፡ ፫ና ፡ ፳ ። ኢዮ ፭ ፡ ፲፮ ። ፳፱ ፡ ፱) ።

**ፍፁም** ፡ የተዘጋ ፡ ዝግ ፡ ዕፍን ፡ ድፍን ። አፍ ፡ ፍፁም ፡ (ሚራ ፴ ፡ ፲፰) ።

**ፈፂን** ፡ ኖት ፡ (ፈፀነ ፡ ይፈፅን ፡ ይፍፅን) ፡ መናደድ ፡ መቈጣት ፡ ማዘን ፡ መታመም ፡ መሞቅ ፡ መተኰስ ፡ መርበን ፡ የወባ ። መቅዘን ፡ ማማጥ ፡ መቀመጥ ። ፈፀነ ፡ በላሐ ፡ ሞቀ ። እመ ፡ ቦ ፡ ከመ ፡ ፈፀነ ፡ በፍኖት ። ወረከባ ፡ እንዘ ፡ ትፈፅን ፡ (ኩፋ ፡ ፴፱ና ፡ ፵፪ ። ማቴ ፰ ፡ ፲፬) ።

**ፈፃኒ** ፡ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት ፡ ፀንት) ፡ ተናዳጅ ፡ ተኳሳ ፡ ንዳዳም ፡ ቅዝናም ።

**ፈፀንት** ፡ ንዳድ ፡ ወባ ፡ ትኵሳት ፡ እሕታ ፡ ተቅማጥ ፡ ሻታ ፡ ቅዘን ። በይእቲ ፡ ንስቲት ፡ ፈፀንት ፡ ሞተ ። ዘይደዊ ፡ በሕማመ ፡ ፈፀንት ። ወእምዝ ፡ አንዘ ፡ ሕማመ ፡ ፈፀንት ፡ ዘይትመየየጥ ፡ ኀቤሁ ፡ በበ ፡ ራብዕት ፡ (መቃ ፡ ፻ ። አፈ ፡ ተዩ ። ዮሴፍ) ።

**ፈቅአ** ፡—ገመሰ ፡—ፈቂዕ ፡ ፈቅዐ ።

**ፈቂድ** ፡ ዶት ፡ (ፈቀደ ፡ ይፈቅድ ፡ ይፍቅድ ። ዕብ ፡ ፋቃድ) ፡ መፍቀድ ፡ መጕብኘት ፡ መቍጠር ፡ ማሰብ ፡ መገመት ፡ መመርመር ። ኢትኅድግ ፡ ዘልፈ ፡ ፈቂደ ፡ እንስሳከ ። አሐዱ ፡ እምቅዱሳን ፡ ተስዐቶ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ (ሚራ ፯ ፡ ፳፪ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፫) ።

—፡ መውደድ ፡ መመኘት ፡ መፈለግ ፡ መሻት ። ቦኑ ፡ ፈቂደ ፡ እፈቅድ ፡ ከመ ፡ ይሙት ፡ ኃጥእ ። ኢትፍቅድ ፡ ብዙኀ ፡ ውሉደ ። እለ ፡ ኢይፈቅድዎ ፡ ለወርቅ ። ብዙኃን ፡ እለ ፡ ፈቀድዋ ፡ (ሕዝ፲፰ ፡ ፳፫ ። ሚራ፲፮ ፡ ፩ ። ኢሳ፲፫ ፡ ፲፯ ። ዮዲ፲፮ ፡ ፳፪) ።

**ፈቃዲ** ፡ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት ፡ ቀድ) ፡ የሚፈቅድ ፡ የሚወድ ፡ ፈቃጅ ፡ ወዳጅ ፡ ፈላጊ ። እስመ ፡ ፈቃዴ ፡ ምሕረት ፡ ውእቱ ። ኢይኩኑ ፡ ሐማይያነ ፡ ወኢፈቃድያነ ፡ እኪይ ፡ ለምእመናን ፡ (ሚክ፯ ፡ ፲፰ ። ፍ ፡ ን ፡ ፮) ።

—፡ ሹም ፡ ጠንቋይ ፡ ኮከብ ፡ ቈጣሪ ። ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለፈቀድ ። ለማእምራን ፡ ወለፈቃድያን ፡ (ዜና ፡ ፴፬ ፡ ፲፯ ። ፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬) ።

**አፍቀደ** ፡ አስፈቀደ ፡ አሳደደ ፡ ፍቀዱልኝ ፡ አለ ። አገበረ ፡ አስገደደ ፡ ግድ ፡ አለ ። ዘአፍቀደ ፡ ሄሮድስ ፡ ለአስተዋስዖ ። ዘአፍቀደኒ ፡ ለቀቲሎትከ ፡ (ዮሴፍ) ። በአፍቀደ ፡ ፈንታ ፡ አስተፋቀደ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አስተፋቅድዎሙ ፡ ምስሌ ፡ ኅይሎሙ ፡ (ዘኍ፳ ፡ ፫) ።

**ተፈቅደ** ፡ ተፈቀደ ፡ ተጐበኘ ፡ ተቈጠረ ፡ ተወደደ ፡ ተፈለገ ። ሰላም ፡ ለሚልክያስ ፡ እንተ ፡ አድምዐ ፡ ቲፈቅዶ ፡ ምስለ ፡ ንጉሳን ፡ ነቢያት ። ዘኢይትፈቀድ ፡ ነገር ። እንተ ፡ ትትፈቀድ ፡ በኵሉ ። ዘይትፈቀድ ፡ ለነፍስትሙ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳ ። ሚራ፳፩ ፡ ፲፭ ። ምሳ፯ ፡ ፳ ። ሮሜ፲፭ ፡ ፳፯) ። በተፈቅደ ፡ ፈንታ ፡ ተፋቀደ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ኵልክሙ ፡ እለ ፡ ተፋቀድክሙ ፡ (ዘኍ፲፬ ፡ ፳፱) ።

**ፍቁድ** ፡ (ዳን ፡ ዳት ፡ ቅድ) ፡ የተፈቀደ ፡ የተወደደ ፡ የተቈጠረ ። በፍቁድ ፡ ፈንታ ፡ ፍቅድ ፡ ይላል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (ዘኍ፩ ፡ ፵፱) ።

**ፍቅድ** ፡ (ዳት) ፡ ቍጥር ፡ ድምር ፡ የድምር ፡ አኀዝ ። ፍቅደ ፡ ዕለታተ ፡ ዓመት ። ፍቅደ ፡ ንዋይ ፡ ዘይትወሀብ ። ወከነ ፡ ፍቅዶሙ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ሐመር ፡ ክልኤቱ ፡ ምእት ፡ (አቡሻ ፡ ፳ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳፯ ። ግብ፳፯ ፡ ፴፯) ።

**ፈቃድ** ፡ (ዳት) ፡ በቁሙ ፡ ትእዛዝ ፡ ውዴታ ፡ እሺታ ፡ ሐሳብ ፡ ምኞት ፡ ፍላጎት ፡ አምሮት ። ገበርነ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋነ ። ግበር ፡ ፈቃዶ ፡ ለእምከ ። በፈቃድ ፡ ወኢበኵርህ ። ፈቃደ ፡ ኅሊናሆሙ ፡ (ኤፌ፪ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፳፳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፫ ። ዘፍ፯ ፡ ፳) ።

**አፍቃድ** ፡ ፈቃደኛ ። እንደ ፡ ድርኤ ፡ ሄርጋብ ፡ ቤርሴክታን ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ግእዝ ፡ መዝገብ ፡ ማዱን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አፍቃድ ፡ አርጋብ ፡ ይላል ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አርጋብን ፡ ተመልከት ፡ (፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፳፯ ፡ ፲፩) ።

**ፈቃዳዊ** ፡ ፈቃደኛ ፡ የፈቃድ ። ይሰምዮ ፡ ለስካር ፡ እበደ ፡ ፈቃዳዊ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፶) ።

**መፍቅድ** ፡ ቀዲ ፡ የሚወድ ፡ የሚፈቅድ ፡ ወዳጅ ፡ ፈቃጅ ። ፈቃዲን ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**መፍቅድ** ፡ (ዳት) ፡ ግብር ፡ ነገር ፡ ጕዳይ ፡ ባሕርያዊ ፡ ሥራ ፡ በግድ ፡ የሚፈለግ ፡ ለባሕርይ ፡ የሚያሻ ፡ ጋብቻ ፡ ምግብ ፡ ልብስ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ውሀባ ፡ ኵሉ ፡ መፍቅዳ ፡ ዘሰአለቶ ። ይቡሉሙ ፡ አይድዑኒ ፡ መፍቅደክሙ ። ይፈጽም ፡ ለክሙ ፡ ኵሎ ፡ መፍቅደክሙ ። መፍቅደ ፡ ሥጋሁ ፡ ረከበ ። ቀዳሚ ፡ ኵሉ ፡ መፍቅዱ ፡ ለሰብእ ፡ ማይ ፡ ወእሳት ። ዝንቱ ፡ ሳዕለ ፡ ክልኤቱ ፡ መፍቅዳት ፡ (፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፲፪ ። ዮሴፍ ። ፊልጵ፬ ፡ ፲፱ ። ስንክ ፡ መጋ፴ ። ሚራ፴፱ ፡ ፳፮ ። ፍ ፡ ን ፡ ፳፱) ።

**መፍቅዳዊ** ፡ የሚፈለግ ፡ ፈላጊ ። ድኻ ፡ ለማኝ ። ያዐርፎሙ ፡ ለመፍቅዳውያን ፡ (ፊልክ ፡ ፪) ።

—፡ የሚፈለግ ፡ ተፈላጊ ። ግብር ፡ መፍቅዳዊት ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፴፪) ።

**ተፋቀደ** ፡ ተቋጠረ ፡ ተቈጣጠረ ፡ ተጐበኛኘ ፡ ተፈላለገ ፡ ተመራመረ ። ተፋቀዱ ፡ ወአእምሩ ፡ መኑ ፡ ዘሖረ ፡ እምኔክሙ ። ወተፋቀዱ ፡ ሕዝብ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ። መሳ፳፩ ፡ ፱) ።

**አስተፋቀደ** ፤ አፋቀደ ፤ አቋጠረ ፤ አፋለገ ፤ አመራመረ ። አደራረጊ ፡ ነው ።

**ፎቃንስ ፤—ጕሬዛ ፤—ፈወቀ ።**

**ፈቂዕ ፤ ዖት ፤ (ፈቅዐ ፡ ይፈቅዕ ፡ ይፍቃዕ ። ዕብ ፡ ፋቄዕ ። ሀረ ፡ ፈቃእ)** ፤ መፍቃት ፤ መግመስ ፤ መውንጠቅ ፤ መፍለጥ ፡ መክፈል ፤ መምታት ፡ ማቍሰል ፤ መፈንከት ፤ መስበር ። ከመ ፡ ይትክሉ ፡ ሞግአ ፡ ኀጺን ፡ ባዕለ ፡ ቅጽረ ፡ ሀይክል ፡ ወይፍቅዑ ፡ ቦቱ ፡ ቅጽረ ። ይፈቅዑ ፡ ገጾ ፡ በአርማሐ ፡ እሳት ። ፈቅዐዎ ፡ ርእሶ ፡ እስከ ፡ ውሕዘ ፡ ደሙ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ (ዮሴፍ ። ራእ ፡ ማር ። አዋል ። ማሕ፳ ፡ ፯ ። ሉቃ፳ ፡ ፲፪) ።

**ተፈቅዐ** ፤ ተገመሰ ፡ ተፈንከተ ፤ ቈሰለ ።

**ፍቅዐት ፤ (ታት)** ፤ መግመስ ፤ መገመስ ፤ አገማመስ ፤ ማምሳት ፤ ፍቅታት ፤ ስብራት ፡ ቍስል ። ይኄይስ ፡ ፍቅዐት ፡ ዘዐርከ ፡ እምሥናይ ፡ ስዕመት ፡ ዘጸላኢ ። ፍቅዐት ፡ ህየንተ ፡ ፍቅዐት ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፯ ። ዘፀ፳፩ ፡ ፳፭ ። ኢሳ፩ ፡ ፯) ።

**ፌቃዕ ፤ (ዕብራ)** ፤ ያበባ ፡ ምሰል ፤ ቅርጽ ፤ አበባንቱ ፡ በጣም ፡ ያልፈካ ፡ ያልፈነዳ ፤ እንደ ፡ ጥጥ ፡ ጓ ፡ ያለ ፤ ሲያበዛ ፡ ፍቃዒም ፡ ይላል ። ወአርዘ ፡ ኀበ ፡ ቤት ፡ ውሳጤ ፡ ግሉፍ ፡ ፍቃዒም ፡ (፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፰) ።

**ፈቂቅ ፤ ቆት ፤ (ፈቀ ፡ ይፈቅቅ ፡ ይፍቅቅ ። ዕብ ፡ ፋቃቅ)** ፤ ፈቀቅ ፡ ራቅ ፡ ገለል ፡ ማለት ፤ መንሸቀቅ ።

**ፈቂር ፤ ሮት ፤ (ፈቀረ ፡ ይፈቅር ፡ ይፍቅር ። ዕብ ፡ ፋቃር)** ፤ ሕገ ፡ ወጥ ፡ መኾን ፤ ሕግን ፡ መስወጥ ፤ ማፍረስ ፤ መክድ ፤ መተው ። በዐረብ ፡ ግን ፡ ድኻ ፡ ለማኝ ፡ ቢጋች ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ፈቀረ ፤ (ዕብ ፡ ያቃር)** ፤ ከበደ ፤ ተወደደ ፤ ከበረ ፤ የሚዛን ፡ የዋጋ ። ምን ፡ ፈቀረኝ ፡ እንዲሉ ።

**አፍቀረ** ፤ ወደደ ፡ ተቀበለ ፤ አከበረ ፤ አሶደደ ፤ አስከበረ ። ጊዜ ፡ ለአፍቅሮ ፡ ወጊዜ ፡ ለጸሊእ ። አፍቅሮ ፡ ነግድ ። አፍቅሮ ፡ ለእግዚ ፡ አምላክከ ፤ አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ ። አፍቅሩ ፡ ጸላእተክሙ ። ኢታፍቅርዎ ፡ ለዓለም ፡ (መክ፫ ፡ ፰ ። ሮሜ፲፪ ፡ ፲፫ ። ማቴ፳፪ ፡ ፴፯—፴፰ ። ፭ ፡ ፵፬ ። ፩ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፭) ።

**አፍቃሪ** ፤ የሚወድ ፡ የሚያሶድድ ፤ ወዳጅ ፤ አሶዳጅ ። አፍቃሪ ፡ ወናዛዚ ፡ (ግንዘ) ።

**መፍቅር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። መፍቅረ ፡ ወርቅ ፡ መፍቅራነ ፡ ክብር ፡ ዘዝ ፡ ዓለም ፡ (ዕር ፡ ኢሳ፫ ፡ ፳፭) ።

**መፍቀሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት)** ፤ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ። መፍቀሬ ፡ ሰብእ ። መፍቀሪተ ፡ ዝሙት ። መፍቀርያነ ፡ ዐመፃ ። አኃት ፡ ክቡራት ፡ ወመፍቀርያተ ፡ እግዚ ፡ (ጥበ፩ ፡ ፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፰ ፡ ፯ ። ሮሜ፪ ፡ ፰ ። ቄር) ።

**ተፈቅረ** ፤ ተወደደ ፡ ተሳበ ፡ ቀረበ ፤ ባለሟል ፡ ኾነ ። ይትፈቀሩ ፡ በእንቲአኪ ፡ ጽሉአን ። ኮንኩ ፡ እትፈቀር ፡ በገጸ ፡ እምየ ። ተፈቀር ፡ በኀበ ፡ ብዙኃን ። ፈቀደ ፡ ይግበር ፡ ግብረ ፡ ዘይትፈቀር ፡ ቦቱ ፡ በኀበ ፡ ቄሳር ፡ (ጦቢ፲፫ ፡ ፲ ። ምሳ፬ ፡ ፫ ። ሢራ፬ ፡ ፯ ። ዮሴፍ) ።

**ፍቁር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ቅርት)** ፤ የተወደደ ፤ ውድ ፤ ክቡር ፤ መክበር ፡ መወደድ ፡ ያለው ፤ ወዳጅ ፡ ባለሟል ። ክነ ፡ ፍቁረ ፡ በኀቤሆሙ ። አንተ ፡ ኢኮንከ ፡ ፍቅርተ ። ፍቁሩ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ። አ ፡ ፍቁረ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ (ሰንክ ፡ ጥር፳፯ ። ሆሴ፪ ፡ ፳፭ ። ያዕ፬ ፡ ፬ ። ቄር) ። ፍቁርየ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ወልድ ፡ እኁየ ፡ ይላል ፤ የመሳሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ማሕ፩ ፡ ፲፫) ።

**ፍቅር ፤ (ራት)** ፤ በቁሙ ፤ ውዴታ ፤ ይቅርታ ፡ ዕርቅ ፡ ሰላም ፤ የልብ ፡ አንድነት ፤ ስምምነት ፤ ረቂቅ ፡ መጣብቅ ፤ የሐሳብና ፡ የአእምሮ ፡ ሙጫ ። አንደደኒ ፡ ፍቅርከ ። ይነድድ ፡ ፍቅሩ ፡ ከመ ፡ እሳት ። ፍቅረ ፡ ቢጽ ። ፍቅረ ፡ እንግዳ ። እስመ ፡ እግዚ ፡ ፍቅር ፡ ውእቱ ፡ (አረጋ ። ሢራ፱ ፡ ፰ ። ዲድ ፡ ፯ ። ኪዳ ። ፩ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፰) ።

**ተፋቀረ** ፤ በቁሙ ፤ ተዋደደ ፤ ተሰማማ ፤ አንድ ፡ ኾነ ። ተፋቀሩ ፡ በበይናቲክሙ ። ከመ ፡ ይትፋቀር ፡ ምስለ ፡ ውሉዱ ። ተፋቀር ፡ ምስለ ፡ ብእሲትከ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፭ ። ዮሴፍ ። ምሳ፭ ፡ ፲፱) ።

**አስተፋቀረ** ፤ አፋቀረ ፤ አፈቃቀረ ፤ አዋደደ ፤ አስማማ ። ሰይጣን ፡ ቀንአ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወአስተፋቀራ ፡ ምስለ ፡ አሐዱ ፡ መነኮስ ፡ እስከ ፡ አማሰነት ፡ ድንግልናሃ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፳) ።

**መስተፋቅር** ፤ የሚያፋቅር ፡ የሚያዋድድ ፤ ክታብ ፡ መድኀኒት ፤ ጠንቋዮች ፡ ለሴቶች ፡ የሚሸጡት ።

**ፈቃር ፤ (ራት)** ፤ ሞጣሕት ፤ ዝናር ፤ እንደ ፡ ድግ ፡ ያለ ። ዲያቆናት ፡ ኢይቅንቱ ፡ ሐቌሆሙ ፡ በፈቃር ፡ በውስተ ፡ ጸሎት ። ዝናራት ፡ ዘውእቶሙ ፡ ፈቃር ። ወተበትከት ፡ ፈቃሩ ። ረከበ ፡ ኀበ ፡ አንቀጽ ፡ ከልበ ፡ ምዉተ ፡ ወሰሐቦ ፡ በፈቃሩ ፡ (ቀኖ ፡ ኒቅ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፩ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ሐም፲፩ ። ነሐ፲፬) ።

—፤ ቍንፏዪም ፡ ልብስ ፤ ባንገት ፡ የሚጠለቅ ፡ በራስ ፡ የሚደፋ ፡ እንደ ፡ ካባ ፡ እንደ ፡ በርኖስ ፡ ያለ ። ቅናት ፡ ወፈቃር ፡ ዘመስቀል ፡ አምሳለ ፡ አስኬማ ። አስሐወ ፡ ሎሙ ፡ ፈቃሮ ፡ ቅድስተ ፡ ወመጠዎሙ ፡ ከማይ ፡ ክብርተ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳፱ ። ድን) ።

**ፈርገገ ፤ (ፈገገ ፤ ር ፡ ስሑድ ፡ ነው)** ፤ ሻረ ፡ ደረቀ ፤ ዐተረ ፡ ጠባሳ ፡ ኾነ ፤ የቍስል ። ወሰእመ ፡ ፈርገገ ፡ ሥጋሁ ፡ ውስተ ፡ ርምየተ ፡ ቍስሉ ፡ (ዘሌ፲፫ ፡ ፲፰ና ፡ ፳፬) ።

**ፈርገግ** ፤ ዕትራት ፤ የቍስል ፡ ምልክት ፤ ጠባሳ ፤ ተክሶ ።

**ፈሪድ ፤ ዶት ፤ (ፈረደ ፡ ይፈርድ ፡ ይፍርድ ። ዕብ ፡ ፋራድ)** ፤ መፍረድ ፡ መለየት ፤ መኳጠል ፤ መዘርጋት ።

**ፈራዲ፤** የሚፈርድ፡ የሚለይ፤ ፈራጅ፤ ዳኛ ።

**ተፈርደ፤** ተፈረደ፤ ተለየ፤ ተነጠለ፤ ነጠላ፡ ኾነ ።

**ፍሩድ፤** የተፈረደ፤ የተለየ፤ የተነጠለ፤ ዝርግ ። ክነፊሆሙ፡ ፍሩድ፡ እመልዕልት፡ (ሕዝ፩፡ ፲፩) ።

**ፍርድ፤** በቁሙ፤ የዳኛ፡ ቃል፤ እንደ፡ ሰይፍ፡ የሚለይ፡ የሚነጥል ። ድኄዮ፡ እምባሕር፡ ኢትደገ፡ ፍርደ፡ እግዚ፡ ከመ፡ ይሕየው፡ (ግብ፳፰፡ ፬) ።

**ተፋረደ፤** በቁሙ፤ ተፈራረደ፤ ተለያየ፤ ተነጣጠለ ። አልቦ፡ ፍዳ፡ በዘይትፋረዱ፡ ወይመጽኡ፡ ውስተ፡ ሲኦል፡ (መጽ፡ ምስ) ።

**ፈርድ፤** ፈርጅ፡ ነጠላ፤ ዕጥፍ፡ ያይደለ ።

**ፌሬድ፤** (ዕብራ) በቅሎ፤ ያህያና፡ የባዝራ፡ ዲቃላ፤ ቀንጃ፡ ነጠላ፤ ከመወለድ፡ በቀር፡ መውለድ፡ የማያውቅ ።

**ፍሪዳ፤** (ዐማርኛ) በቁሙ፤ የሚታረድ፡ ከብት፡ ከመንጋው፡ የለዩት፤ የነጠሉት ። (ግጥም)፤ ነፍሱ፡ ለሥጋ፡ ሸትማሺ፤ ፍሪዳ፡ መጣልሺ ።

**ፈሪሀ፤** ሆት፤ (ፈርሀ፡ ይፈርሀ፡ ይፍራሀ ። ዕብ፡ ፋራሀ፤ ፈረየ ። ዐረ፡ ፈረ፤ ጎየ)፤ መፍራት፤ ማክበር፡ ማምለክ ። መባባት፤ መሥጋት ። ፍርህዎ፡ ለእግዚ፡ ፀቢየ፡ ፍርሀት ። ሥርዋ፡ ለጥበብ፡ ፈሪሀ፡ እግዚ ። እመኒ፡ ጸብአኒ፡ ተዓይን፡ ኢይፈርሀኒ፡ ልብየ ። ፈርሀ፡ ላዕለ፡ ነፍሱ፡ እምእኑሁ ። ሰእመ፡ ይፈርሁ፡ በእንቲአሁ፡ ሞተ፡ (ዮናሽ፡ ፲፯ ። ሚራ፩፡ ፳ ። መዝ፡ ፳፯ ። ዮሴፍ ። ፍ፡ ነ፡ ፫) ።

**ፈራሂ፤** (ሂት፡ ሀያን፡ ያት)፤ የሚፈራ፤ ፈሪ፤ እክባሪ ። ሰፈራሂ፡ እግዚ፡ ይሜኒ፡ ይኄሪቱ፡ (ድጓ) ።

**ፈራህ፤** (ህት፡ ሃን፡ ሃት)፤ ዝኒ፡ ከማሁ፤ ፈሪ፤ ፍራቱም፡ ብዙ፤ ሥጉ ። ኅሊናሆሙ፡ ለመዋትያን፡ ፈራህ፡ ከመ፡ ይትመየጥ፡ ኵሉ፡ ፈራህ፡ ልብ ። ለምንት፡ ፈራሃን፡ አንትሙ፡ (ጥበ፱፡ ፲፬ ። ዮሴፍ ። ማቴ፰፡ ፳፮) ።

**አፍርሀ፤** አስፈራ፤ አስፈራራ፡ አስከበረ ። አኮኑ፡ ኅይሉ፡ ያፈርሀክሙ ። ቃለ፡ ፀዓዑ፡ ያፈርሃ፡ ለምድር ። ጥበብ፡ ለዘረከባ፡ ታአምኖ፡ ወታፈርሆ፡ (ኢዮ፲፫፡ ፲፩ ። ሚራ፵፫፡ ፲፯ ። ፲፭፡ ፳፰) ። በአፍርሆ፡ ፈንታ፡ አስተፋርሆ፡ ይላል፡ አያሰኝም ። እፈራ፡ ያስተፋርሆ፡ በሞቱ፡ (ቄር፡ ጸላ) ።

**መፍርህ፤** (ህት፡ ሃን፡ ሃት)፤ የሚያስፈራ፡ አስፈሪ፡ አስገራሚ ። ባሕር፡ መፍርህ ። መንበርከ፡ መፍርህ ። ወከነት፡ መፍርህተ ። መፍርሃን፡ (ጥበ፲፡ ፲፰ ። ቅዳ ። መቃ ። አርጋ፡ ፯) ።

**መፍርሂ፤** ዝኒ፡ ከማሁ፤ አስፈሪ ።

**ተፈርሀ፤** ተፈራ፡ ተፈሪ፡ ኾነ ። ዘይትፈራህ፡ በእንቲአሁ፡ ሞት ። ይትፈቀር፡ እስመ፡ መሐሪ፤ ይትፈራህ፡ እስመ፡ እግዚእ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፲፩ ። መዋሥ) ።

**ፍሩህ፤** (ሃን፡ ሃት፡ ርህት)፤ የፈራ፤ የተፈራ፤ መፍራት፡ መፈረት፡ ያለው፤ ፈሪ፡ ተፈሪ ። ፍሩህክ፡ ንበር፡ እንከ ። በእንተ፡ ዝ፡ ይደልወነ፡ ከመ፡ ንኩን፡ ፍሩሃነ፡ በኵሉ፡ ጊዜ፡ (ሮሜ፲፩፡ ፳ ። ፊልክ) ።

**ፍርሀት፤** (ታት)፤ መፍራት፤ መፈራት፤ አምልኮት፤ አፈራር፤ ፈሪነት፤ በቁሙ፡ ፍራት፡ ሥጋት፤ የክፉ፡ የበጎ ። ፍርሀተ፡ ሞት ። ፈሩ፡ ፍርሀተከ ። እወዲ፡ ፍርሀትየ፡ ውስተ፡ ልቦሙ ። ፍርሀታት፡ ወምንዳቤያት፡ (ሚራ፵፡ ፭ ። ፀሐ፡ ፱ ። ኤሳ፴፱፡ ፵ ። ፊልክ፡ ፵፯) ።

**ተፋርሀ፤** ተፋራ፤ ተፈራራ ።

**አስተፋርሀ፤** አፋራ፤ አፈራራ፤ እንዲፋሩ፡ እንዲፈራሩ፡ አደረገ ።

**ፈርዝዞ፤** ዞት፤ (ፈርዘዘ፡ ይፈረዝዝ፡ ይፈርዝዝ ። ዕብ፡ ፋራዝ፡ ዐብየ፡ ልህቀ)፤ ማንፈርዘዝ፤ ደስ፡ ማሰኘት ። አበበ፡ ፍሬ፡ መያዝ፤ ማጕምጕም፡ መንጠርዘዝ፤ መደብደብ፡ ማርገዝ፤ ለማበብ፡ ለመውለድ፡ ለመዘርዘር፡ የእክልና፡ የተክል ።

**ተፈርዘዘ፤** ተንፈረዘዘ፤ ፈካ፡ ፈነዳ፤ ወለደ፡ ዘረዘረ ። ይትፈረዘዝ፡ ቍልሑ፡ (መክ፲፪፡ ፭ ። አርጋ፡ ፯) ።

—፤ ተደሰተ፤ ደላው፡ ደስ፡ አለው፤ ሣቀ፡ ፈነደቀ፤ አመከ፡ ተቸከከ ። አኮ፡ ከመ፡ ንንበር፡ ዘሊፈ፡ በሠሐቅ፡ ወተፈርዝዞ ። አንበሳ፡ ምኩሕ፡ ልሙይ፡ ይም፡ ለተፈርዝዞ፡ (አፈ፡ ተጃ፭ ። አዋል) ።

—፤ ተበተነ፡ ተበታተነ፤ ተዛራ፡ ፀነነ፤ ጠፋ፡ እንደሌለ፡ ኾነ ። ይትፈረዘዝ፡ ከመ፡ ጊሜ፡ (ጥበ፪፡ ፬) ።

**ፍርዙዝ፤** የፈካ፤ የፈነዳ፤ ደስ፡ ያለው፡ ጥጉብ፤ ፈርዛዛ፡ ዝም፡ ዕክም፡ ጸጥ፡ ዱ፡ ያለ ። (ተረት)፤ እኽል፡ የያዘ፡ ፈርዛዛ፡ ወርቅ፡ የያዘ፡ ቀበዝባዛ ።

**ፍርዛዜ፤** መንፈርዘዝ፤ ፍንደቃ፡ ሣቅ፡ ጨዋታ፤ ተድላ፡ ደስታ ። ከመ፡ ይንእድዎ፡ ኵሉ፡ ሰብእ፡ በስርጋዌ፡ አልባስ፡ ወሰብዙኅ፡ ወሂብ፡ ወብዝኃሬዎቱ፡ ንዋየ፤ ወበእንተ፡ አብዝኖ፡ ፍርዛዜ፡ (ፈ፡ መ፡ ፲፯፡ ፬) ።

**ፍርዝ፤** የሰንጠረዥ፡ መንገድ፡ አካኼድ፤ ወይም፡ አሸንጉሊቱ፡ ፈረስ፡ ወታደር፡ የሚሉት ። ሽምሳለ፡ ፍርዝ፡ (መር፡ ስጢ) ።

**ፈርሒ፤** (ትግ፡ ወዐረ)፤ ተደሰተ፡ ደስ፡ ፈቅ፡ አለው፡ ደስታ፡ መሳሙ ።

**ፈሪን፤** (ፈርን ። ዕብ፡ ፋራሕ)፤ መፋላት፡ መውጣት፤ መብዛት፡ መርባት፡ መርመብመብ፡ መንሸሽት፤ የተሐዋስያን፡ የአዕዋፍ ።

**ፈርን፤** (ዐረብ ። ዕብ፡ ኤፍሮሕ)፤ ጫጩት፡ ዘረንበ፡ ሲውሲዋ፡ የደሮ፡ የወፍ፡ ግልገል፡ ቃናቸ፡ ሕፃን፡ ወፍ ።

**አፍሮኅት፤** (ዐረ፡ አፍራኅት ። ዕብ፡ ኤፍሮሒም)፤ ጫጩቶች፡ የወፍ፡ ገኅግልቶች ። መጽሐፍ፡ ግን፡ በአፍርኅት፡ ፈንታ፡ አፍኅርት፡ ይላል፡ የ

ተሳሳተ ፡ ነው ። ዖፍ ፡ ምስለ ፡ አፍኅርቲሃ ። ከመ ፡ ይ ሊድ ፡ አፍኅርተ ። ከመ ፡ ዖፍ ፡ አፍኅርቲሃ ፡ ትሴውር ፡ በክንፋ ፡ (መቃ ። ማር ፡ ይሥሓቅ ፡ ፱ ። ደራሲ) ።



አፍርኅት ፤

**ፈርዩ** ፤ **ዩ·ት** ፤ (**ፈርየ ፤ ፈረየ ፡ ይፈሪ ፡ ይፍረይ ። ዕብ ፡ ፋራህ ፤ ፋራሕ ። ሱር ፡ ፍ ራእ**) ፤ መፌብሬብ ፤ ማበብ ፤ ዐጽቅ ፡ አበባ ፡ ማውጣት ፤ ፍሬን ፡ ከመዕነብ ፡ የተነሣ ። ወይፈሪ ፡ ከመ ፡ ተክል ፡ ሐዲስ ። ይሠርጽ ፡ ወይፈሪ ፡ እስራኤል ። ይፈሪ ፡ ከመ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ (ኢዮ ፲፬ ፡ ፱ ። ኢሳ ፳፯ ፡ ፮ ። ፴፭ ፡ ፩) ።

—፤ ማፍራት ፤ መውለድ ፤ መብዛት ፡ መርባት ፡ መፈድ ፈድ ፤ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ መስጠት ፡ ማስገኘት ። ጸናሕክዎ ፡ ይፍረይ ፡ እስካሁ ፡ ወፈረየ ፡ አሥዋክ ። ፈረየት ፡ ምድር ፡ ግብጽ ፡ ብዙኅ ፡ ሥርናየ ። ወኢይፈርዩ ፡ አዕጹቂሃ ። መካን ፡ እንተ ፡ ፈረየት ፤ (ኢሳ ፭ ፡ ፪ ። ኩፋ ፡ ፵ ። ሚራ ፴፫ ፡ ፳፭ ። አርጋ ፡ ፲) ።

—፤ መወፈር ፡ መግዘፍ ፤ ማበጥ ፡ ማፈርጠም ፡ ሥጋማ ፡ መኾን ፤ ስራሱ ።

**ፈራዪ** ፤ (**ዪ·ት ፡ ይያን ፡ ያት**) ፤ የሚያብብ ፡ የሚያፈራ ፤ አፍሪ ፤ ፍሬያም ፤ ወላይ ።

**መፍረዪ** ፤ **መፍርይ** ፤ (**ይት ፡ ያን**) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ። መፍርይት ፡ ለእንተ ፡ ይትበላዕ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ፍሩይ** ፤ (**ያን ፡ ያት ፡ ሪት**) ፤ ያበበ ፡ ያፈራ ፤ ፍሬ ፡ የያዘ ፤ ፍሬያማ ፡ ፍሬያም ፤ ዘላው ፡ ዘለላው ፡ ሕንባቡ ፡ ፍሬው ፤ ወይም ፡ ፍሬንቱ ፡ ያበጠ ፡ ያፈረጠመ ፤ ያደገ ፡ የተንገዘረገገ ።

**ፍርየት** ፤ ማበብ ፤ ማፍራት ፤ ፍሬ ፡ መሸከም ። ማበጥ ፤ ማፈርጠም ፤ የፍሬ ። ወፈጸሞ ፡ ፍርየት ፡ (ማር ፬ ፡ ፳፱) ። መሥዋዕት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ፍርየት ፡ ፍሬ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፀ ፳፱ ፡ ፳፭ ። ፴ ፡ ፲ ። ዘኍ ፲፭ ፡ ፫) ።

**ፍሬ** ፤ (**ሬ ፡ ርያት**) ፤ በቁሙ ፤ ሕንባብ ፤ ኀጠት ፤ ዘር ፡ ቅንጣት ፤ መልዕ ፡ ሲዘሩት ፡ የሚበቅል ። ፍሬ ፡ ዘይት ። ፍሬ ፡ ማዕር ። ፍሬ ፡ አቅማሕ ። ፍሬያተ ፡ አዝርዕት ፡ (ኢዮ ፲፭ ፡ ፴፫ ። ኢሳ ፯ ፡ ፮ ። ማሕ ፡ ፬ ። ጥበ ፲፮ ፡ ፳፱) ።

**ፍሬ** ፤ አዝመራ ፤ የአዝርዕት ፡ የአትክልት ፡ የዕፀዋት ፡ ፍሬ ፤ የምድር ፤ በላባ ፡ ወርቅ ፡ ዕንቍ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። **ፍሬያተ ፡ ዘበበ ፡ ዘመዱ ፡ ወበበ ፡ ጣዕሙ** ። **ፍሬያተ ፡ ምድር** ፡ (ቀሌ ። ኤር ፯ ፡ ፳) ።

**ፍሬ** ፤ ልጅ ፤ የልጅ ፡ ልጅ ፤ ዕጓል ፤ ክባሕርይ ፡ የሚገኝ ፡ የሚከፈል ። **ፍሬ ፡ ከርሥከ ፡ ወፍሬ ፡ ምድርከ** ። **ሐቤል ፡ ወሴት ፡ ወሔኖክ ፡ ሕርአስተ ፡ አበው** ። **ምስለ ፡ ዙሉ ፡ ፍሬሆሙ** ፡ (ዘዳ ፯ ፡ ፲፫ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ፍሬ** ፤ ሥራ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፤ የሥራ ፡ ዋጋ ፤ ደመ ፡ ወዝ ። **ፍሬሃ ፡ ለንህብ** ። **ፍሬ ፡ ምግባሮሙ** ። **ቦኑ ፡ ፍሬ ፡ ለጻድቅ** ። **ፍሬ ፡ ጻማከ ፡ ተሴሰይ** ፡ (ሚራ ፲፩ ፡ ፫ ። ኤር ፯ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፶፯ ። ፻፳፯) ።

**ፍሬ** ፤ ቁም ፡ ነገር ፡ ዋና ፤ ዕይነታ ። ፍሬ ፡ ቅዳሴ ፤ ፍሬ ፡ ስሞነኛ ፡ እንዲሉ ።

**አፍረየ** ፤ አሳበበ ፤ አስፈራ ፤ አሶለደ ፤ እንዲያብብ ፡ እንዲያፈራ ፡ አደረገ ። **አፈርየ ፡ ከመ ፡ ዘይት ፡ ስሙር ። ያፈሪ ፡ ወያሰምር** ፡ (ሆሴ ፲፬ ፡ ፰ ። ግብ ፲፬ ፡ ፲፯) ።

**መፍርያን** ፤ (**ሱር ፡ ማፍርያና**) ፤ የሰው ፡ ስም ፤ የሚያፈራ ፤ የሚያስፈራ ፤ ፍሬያማ ፡ ፍሬያም ። **እል መፍርያን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ ሠርቅ** ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ ፲) ።

**ፈርተት** ፤ (**ትግሬ**) ፤ ቁስጥ ፤ የቍላ ፡ ፍሬ ። በቁሙ ፡ ፍርንትት ፤ የተበጠበጠ ፡ ዕበጥ ። ሲያበዛ ፡ ፈራተት ፡ ይላል ።

**ፈርከሊሳ** ፤ (**ዕብ ፡ ፋርኪል**) ፤ የወይን ፡ ዘለላ ፡ ክናጽቁ ፤ የሾቱ ፡ ዕንጨት ፡ ዐጽቅ ፡ ከነፍሬው ። **ማርያም ፡ ጽጌ ፡ ዘትምዕዘ ፡ እምፈርከሊሳ** ፡ (ደራሲ) ።

**ፈርሙኒ** ፤ (**ቅብጥ**) ፤ የወር ፡ ስም ፤ ሚያዝያ ። በርሙዳን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። **በርሙዳ ፡ ይሰመይ ፡ ፈርሙኒ** ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ።

**ፋርን** ፤ **ፋርና** ፤ (**ዐረብ ፡ ወዕብራ**) ፤ እቶን ፤ የማድ ፡ ቤት ፤ ማብሰያ ፡ መጋገሪያ ።

**ፈርነሰ** ፤ (**ዕብ ፡ ፋርኔስ**) ፤ ቀለበ ፡ መገበ ፤ አበላ ፡ አጠገበ ፤ አስተኛ ፡ አጋደመ ፤ ደስ ፡ አሰኘ ፤ አንፈረዘዘ ። ፈረዘዘን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ወንድም ፡ ነው ።

**ፈርናሲ** ፤ (**ዕብ ፡ ፋርናስ**) ፤ ቀላቢ ፡ መጋቢ ፤ አዛዥ ፤ ቤት ፡ አባት ፤ ዐበዛ ፡ ጋጋሪ ፤ አሳላፊ ፤ አስተኚ ፤ አንጣፊ ።

**ተፈርነሰ** ፤ በቁሙ ፤ ተፈረነሰ ፤ በላ ፡ ጠገበ ፤ ተመገበ ፤ ተኛ ፡ ተጋደመ ፤ ደስ ፡ አለው ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ልቡ ፡ ታበየ ፤ ከፋ ፡ ዐሰበ ። **ለእመ ፡ መጠውከ ፡ ርእሰከ ፡ ለተፈርንሶ** ፡ (ምሳ ፳፱ ፡ ፳፮) ።

**ፍርኑስ** ፤ ጽጉብ ፤ ስኩብ ፤ ፍሡሕ ፤ ፍርዙዝ ። ዐልጋ ፤ መኝታ ፤ መከዳ ፡ ስኪብ ። ባማርኛ ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ይኾናል ፤ ወይዘሮ ፡ ፍርኑስ ፡ እንዲሉ ።

**ፍርናሴ** ፤ መፈርነስ ። ምግብ ፡ ቀለብ ፤ መብል ፡ መጠጥ ፤ ጥጋብ ፡ ስካር ፤ ተድላ ፡ ደስታ ።

**ፍራንስ** ፤ ስመ ፡ ነገድ ፤ የሕዝብና ፡ ያገር ፡ የመዲና ፡ ስም ፤ ፋ(ፓ)ሪስ ፤ ፈረንሳዊ ። ዐረቦች ፡ ፈረንጅ ፡ ይሁዶች ፡ ጳርፋት ፡ ይሉታል ።

**ፈርዖን** ፤ (**ዕብ ፡ ፋርዖህ**) ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ግፈኛ ፤ ግፍ ፡ ሠሪ ፤ ሙት ፡ አስገባሪ ፡ ማለት ፡ ነው ። ላንድ ፡ ሰው ፡ መቃብር ፡ ፻፶ ፡ ብር ፡ ይቀበል ፡ ነበረ ፡ ይ

ብላል ። ጥንቱ ፡ ስሙ ፡ ፌቅዮን ፡ ነው ፤ ክርሱ ፡ በኋላ ፡ ፈርዖን ፡ መባል ፡ ለግብጥ ፡ ንጉሥ ፡ ተሰጥቷል ።

**ፈርዐጽ፤ (ዕብ ፡ ፋርዖሽ)፤** ቍንጽ ፡ ቍንጸ ፤ ቍንጫ ፡ የሚዘል ፡ የሚፈናጠር ።

**ፈርዐጸ፤ ፀ፤ አው ፡ አንፈርዐጸ፤** ዘለለ ፤ ፈነጨ ፤ መር ፡ መር ፤ ፍንጥር ፡ ፍንጥር ፡ አለ ፤ በረቀ ፤ ፈነደቀ ። መጽአ ፡ እንዘ ፡ ያንፈርዕጽ ፡ ከመ ፡ መፍልስ ። ያንፈርዕጹ ፡ አድባር ። እንስሳ ፡ እለ ፡ ያንፈርዕጹ ። ተፈሥሑ ፡ ወአንፈርዕጹ ። አንፈርዐጹ ፡ ሰብእ ፡ ብሄል ፡ ረኪቦሙ ፡ ሕፃነ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፯ ። ኢሳ፶፭ ፡ ፲፪ ። ጥበ፲፯ ፡ ፲፰ ። ቀሌ ። ድጓ) ።

**ፍርዑጽ፤ እንፍርዑጽ፤** ደስ ፡ ያለው ፤ ደስታ ፡ የመላው ፤ ያዘለለው ፡ (አርጋ ፡ ፩) ።

**ነፈርዓጽ፤** ዝላይ ፤ መርታ ፤ ተድላ ፤ ደስታ ፤ ሴስን ፡ ቅንዝር ። ፍሥሓ ፡ ወሐሤት ፡ ወነፈርዓጽ ። እምነይብ ፡ ነፈርዓጽ ፡ (አፈ ፡ ተ፴፪ ። ራእ፲፰ ፡ ፫) ።

**ፈርፈረ፤ (ፈረር ፡ ፈረ ። ዕብ ፡ ፋርፌር)፤** ፈረፈረ ፡ ፏፈረሰ ፤ ኰተኰተ ፡ ሰባበረ ፤ አጠቃቀነ ፤ የንጀራ ። ሥፍና ፡ ምንጩ ፡ ፈረር ፡ ነው ።

**ፍርፉር፤ (ራት)፤** ፍርፋሪ ፤ የንጀራ ፡ የዳቦ ፡ ስባሪ ፡ ትራፊ ፤ ቍርስራሽ ። በእንተ ፡ ፍርፋራተ ፡ ኅብስት ፡ (አፈ ፡ ተ፲፩ ። ማቴ፲፭ ፡ ፳፯) ።


**አንፈርፈረ፤** አንፈረፈረ ፤ ተንፈረፈረ ። አንፈራፈረ ፤ ተንፈራፈረ ፤ ፍር ፡ ፍር ፡ አለ ።

**ፍርፍርት፤ (ታት)፤** የእሳት ፡ እራት ፤ ብራብሮ ። ድርጭት ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ወፍ ፡ ከሸርግሬና ፡ ከቆቅ ፡ የምታንስ ። በእሉ ፡ ወመጽአ ፡ ፍርፍርት ። ወ ፀብኮሙ ፡ መብልዐ ፡ ፍርፍርተ ፡ (ሙ፲ ፡ ፲፱ ። ጥበ ፲፯ ፡ ፪ ። ዘፀ፲፮ ፡ ፲፫ ። ዘኍ፲፩ ፡ ፴፩) ። ድርንቅን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ፍርፍርዮን፤ (ሮማይ ፡ ፈብሩአሪውስ)፤** የካቲት ፤ የሮማውያን ፡ ፪ኛ ፡ ወር ፡ (ተረ ፡ ቁር፭፻) ።

**ፈሪጽ ፡ ጾት፤ (ፈረጸ ፡ ይፈርጽ ፡ ይፍርጽ ። ዕብ ፡ ፋራጽ)፤** መስበር ፡ ማፍረጥ ፤ መፈንከት ፡ መፍለጥ ።

**ፈርጽ፤ (ብ ፡ አፍራጽ)፤** በቁሙ ፤ ፈርጥ ፤ ጌጥ ፤ ክቡር ፡ ደንጊያ ፤ ዕንቍ ፤ የዕንቍ ፡ ስባሪ ፤ ፍንካች ፤ በወርቅ ፡ የሚያዝ ፡ የሚለበጥ ። እለ ፡ ሰርግዋን ፡ በአፍራጽ ፡ ወልቡጣን ፡ በቈጽለ ፡ ወርቅ ። ውስቴ ፡ ሣጺን ፡ ዘእብነ ፡ አፍራጽ ፡ ዘውእቱ ፡ ርኲም ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፯) ።



ፈርጽ፤

**ፈሪቅ፤ ቆት፤ (ፈረቀ ፡ ይፈርቅ ። ዕብ ፡ ፋራቅ ። ሱር ፡ ፍራቅ)፤** መክፈል ፡ መለየት ። ማዳን ፡ ማስጣል ፤ መታደግ ፤ መቤዠት ፤ ከፍንጅ ፡ ከጠላት ፡ እጅ ፡ ማውጣት ። ትግሬ ፡ ግን ፡ ፈርቀ ፡ ብሎ ፤ በሳ ፡ ነደላ ፡ ይላል ።

**ፈራቂ፤** የሚያድን ፤ የሚቤዥ ፤ ታዳጊ ። ፈራቂ ፡ እምሕማማት ። እምላኪነ ፡ ወፈራቂነ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፩) ።

**ፍርቅ፤ (ቃት)፤** እኩል ፤ እኩሌታ ፤ መንፈቅ ። ፍርቅ ፡ መዓልቲ ፡ (ትግሪኛ) ።

**ፍርቃን፤ (ዐረ ፡ ወዕብ ፡ ፉርቃን ። ሱር ፡ ፉርቃና)፤** ድኅነት ፤ መድኀኒት ፤ ትድግና ። መሥዋዕተ ፡ ፍርቃን ፡ (ዘፀ፳፱ ፡ ፳፰ ። ፴፪ ፡ ፯ ። ራእ፯ ፡ ፲ ። ፲፱ ፡ ፩) ።

**ፉርቃን፤** የሙሐመድ ፡ መጽሐፍ ፡ ቍርኣን ፤ እስላሞችን ፡ ከክርስቲያኖች ፡ የሚለይ ፡ የሚከፍል ።

**አፍረቀ፤** አስከፈለ ። አፈራረቀ ፤ አከታተለ ።

**አፍራቅያ፤** አፍሪቃ ፤ አንድ ፡ እጅ ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፤ ካምስት ፡ አንድ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ያለችባት ፡ ዓለም ፤ ዙሪያዋ ፡ ዳር ፡ ደንበሯ ፡ ኹሉ ፡ በባሕር ፡ የታጠረ ፡ የተከበበ ፤ እንደ ፡ ደሴት ፡ ያለች ፤ ሥዕሏና ፡ ምስሏ ፤ ወይም ፡ ቅርጺ ፡ አቀማመጧ ፡ የወይን ፡ ዘለላ ፡ የሚመስል ። ዮም ፡ ትዌድሶ ፡ አፍራቅያ ፡ (ድጓ) ።

**ተፈርቀ፤** ተከፈለ ፤ ዳነ ፡ ተለቀቀ ፤ ወጣ ፤ አመለጠ ።

**ፍሩቅ፤** የተለየ ፤ የተከፈለ ፤ ክፋል ፤ ድኍን ።

**ፈርቅ፤ (ዐረ ። ዕብ ፡ ፌሬቅ)፤** ልዩነት ፤ ክፍል ፤ ምዕራፍ ፤ የሕዋስ ፡ የመጽሐፍ ። ተራ ፡ ፈረቃ ።

**ተፋረቀ፤** ተካፈለ ፤ ተከፋፈለ ፤ ተፈራረቀ ፤ ተጋገዘ ። ባረየን ፡ ተመልከት ።

**ፈሪር፤ (ፈረ ፡ ይፈርር ፡ ይፍርር)፤** መፈልፈል ፤ ማሸት ፤ የፍሬ ፡ የቅንጣት ። ፈርፈረን ፡ እዩ ።

**ፈሩርም፤ (ጽር ፡ ፋሩሬም ። ዕብ ፡ ፋርዋሪም)፤** ዐቆች ፤ የበታ ፡ ስሞች ፤ የቤት ፡ መቅደስ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፤ የከተማ ፡ ዙሪያ ፤ ማእገን ። ወይም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለ ፡ አደባባይ ፤ ምሳግ ፤ ሥረጊ ፤ የጕድፍ ፡ መጣያ ። በፈሩርም ፡ (፩ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፲፩) ። አንዳንድ ፡ ፋርዋር ፡ ይላል ።

**ፈሪስ፤ ሶት፤ (ፈረሰ ፡ ይፈርስ ፡ ይፍርስ ። ዕብ ፡ ፋራስ፤ ሰበረ ፡ አፈረሰ)፤** መጋለብ ፤ መንጐድ ፤ መውጣት ፡ መውረድ ፤ መፍረስ ፡ መናድ ፤ የማዕበል ። መፈታት ፤ ባድማ ፡ መኾን ፤ መለየት ፡ መክፈል ፡ መበታተን ፤ ያገር ፡ የቤት ።


**ፍርሰት፤** መፍረስ ፤ አፈራረስ ፤ ፍርሻ ። የአምር ፡ ግብረ ፡ ፍርሰት ፡ (ፊልክ) ።

**አፍረሰ፤** አፈረሰ ፤ አስፈረሰ ፤ ሻረ ፤ ድል ፡ ነሣ ።

ዘሐነጸ፡ ቤተ፡ ወያፈርስ ። ሶበ፡ ኢያፍረስኩ፡ ርእ ስየ፡ እምኢክህልኩ፡ እሕንጻ፡ ለነፍስየ ። ያፈርሱ፡ ጣቢኖተ፡ ሰይጣናት፡ (ፊልክ፡ ፶፰፤ ፪፻፷ ፡ ፴፩) ።

**ፈርስ** ፤ (ዕብ፡ ፌሬሽ) ፤ በቁሙ፡ (ፀማ ድኛ) ።

**ፈረስ** ፤ (ብ፡ አፍራስ ። ዕብ፡ ፋራሽ ። ዐረ፡ ፈረስ) ፤ በቁሙ፤ የታወቀ፡ የቤት፡ እንስሳ፤ ጌጪ፡ ጋሳቢ፤ ሠረገላ፡ ሳቢ፤ ሰንጋ፡ ድንጉላ፡ ባዝራ ። እንደ፡ ሳሕም፡ ለሴትም፡ ለወንድም፡ ይከታል፤ እይክ ትም፡ ብለው፡ ፈረስት፡ አፍራሳት፡ የሚሉ፡ አሉ፤ ያሰኛ ቸዋል ። ፈረስ፡ ዘኢተረየፀ፡ ይወፅእ፡ እኩየ ። ረዋጺ፡ ፈረስ ። መጽእት፡ ፈረሰ፡ ንጉሥ፡ ወሰትየተ፡ እም ኔሁ፡ ወፀንሰት፤ ወይእቲኒ፡ ፈረስ፡ እንተ፡ ፀንሰት፡ ወለደት፡ ባዕለተ፡ ቱወልደ፡ እስክንድር፡ (ሚራፅ፡ ፳ ። ኢሳ፴፩፡ ፲፯ ። ዜና፡ እስ) ። አፍራስ፡ ጸብእ ። ድ ምፀ፡ ሠረገላ፡ ወአፍራስ ። አፍራስ፡ አእኑስ፡ ወአ ፍራስ፡ ቶትቡዕ፡ (ዮናን፡ ፲፡ ፳፯ ። ሚክ፩፡ ፲፫ ። ፪ዜና፡ ፴፡ ፳፭) ።



ፈረስ፡

**ፈረሳዊ** ፤ ፈረሰኛ፤ ባለፈረስ፡ ጋሳቢ፤ ማዕበል፡ ሞገድ፡ (ስንክ፡ መስ፲፫) ።

**ፈርሰወ** ፤ (ተቀ፡ ግ ። ዕብ፡ ፋርሴም) ፤ አፈርሳታ፡ አወጣ፤ ለየ፡ ገለጠ፡ አስታወቀ፤ የክፉ ። ፈር ሳም፡ ጎ፦ ።

**ፈርሳዊ** ፤ አፈርሳታ፡ አውጪ ። ፈርሳም፤ ዳውላ፡ ሆድ ።

**ፍርሳዌ** ፤ **ፈርሱት** ፤ አፈርሳታ፡ ያፈርሳታ፡ ሥራ፡ አውጣጪኝ፡ ምርመራ ።

**ፈሪሳዊ** ፤ (ዕብ፡ ፋሩሽ) ፤ ዕሉል፡ ባሕታዊ፤ ንጹሕ፡ ድንግል፤ መናኒ፤ ከሰው፡ የተለየ፡ ልዩ ። ሕነ፡ ፈሪሳዊ፡ ወልደ፡ ፈሪሳዊ ። ሕሐዱ፡ እምነ፡ ፈሪሳው ያን፡ (ግብሐ፳፫፡ ፮ ። ዮሐ፫፡ ፩) ። ባለሐዲሶች፡ ግን፡ በፋ ሬስ፡ ፈሪሳውያን፡ ተብለዋል፡ ብለው፡ ይፈታሉ፤ ፋሬስ፡ የጽርእ፡ አጠራር፡ ነው፤ ዕብራይስጡ፡ ፌሬጽ፡ ይለዋል፤ ዘፋና፡ ሥሩ፡ ፈረጸ፡ ነውና፤ ፍቻቸው፡ ጥሩ፡ እውነት፡ አይደለም ።

**ፋርስ** ፤ (ዕብ፡ ፋራስ) ፤ ያገርና፡ የነገድ፡ ስም ። ፋርስ፡ ወዠሽ፡ ወፉጥ፡ (ሕዝ፴፰፡ ፭) ።

**ፋርሳዊ** ፤ የፋርስ፡ ሰው፤ በፋርስ፡ የተወለደ ። ቂሮስ፡ ፋርሳዊ፡ (ዳን፮፡ ፳፰) ።

**ፋሬስ** ፤ (ሱር፡ ፋርሲን) ፤ ከፋለ፡ ከፈላ፡ ለመንግሥትክ፤ ወተውህበት፡ ለፋርስ፡ ወሜዶን፡ (ዳን፭፡ ፳፮—፳፰) ።

**ፈርስክ** ፤ የፋርስ፡ ቍጥር ። ፈርስክ፡ ሐሳበ፡ ፋርስ፡ ወሰብአ፡ ምሥራቅ፤ ወፈርስክስ፡ ብሂል፡ አር ባዕቱ፡ ምዕራፍ፡ (ጊ፡ ወ፡ ሐ፡ ገ፲፭) ።

**ፋስ** ፤—**ዕፃ** ፤—**ፈሲስ፡ ፈሰሰ** ።

**ፈሲው** ፤ (ፈሰወ፤ ፈስወ ። ዐረ፡ ፈሳ) ፤ መረሳኘ፤ መንጓጓት፤ የሆድ ። ቂስ፡ ቂቅ፡ ሳጥ፡ በር ቀቅ፡ ማለት፡ የፈስ፤ ሾልኮ፡ ንጥቆ፡ እንደ፡ ነፍጥ፡ ባርቆ ። ወይም፡ ኸን፡ ብሎ፡ መፍሳት፤ በቂጥ፡ በመቀ መጫ፡ መተንፈስ፤ ለመናጻት፤ ጉየጸን፡ እይ ። መቀ ረጥ፡ መፍለጥ፡ መስበር፡ መቀጥቀጥ ። ፋስ፡ ማለት፡ የዚህ፡ ዘር፡ ነው ። መቀረጥ፡ ለፈስም፡ ይኸናል፤ (ግ ጥም፡ ድሬ፡ ዳዋ) ፤ ሰው፡ ኹሉ፡ ተጣልቶ፡ በፈስ፡ ደመ፡ ወገዘ፡ የማጉስ፡ እያለ፡ ገሮ፡ ሲያያዝ፤ ነጋድ፡ ራስ፡ ድልቢ፡ የፈሱን፡ ነገር፡ ቁመው፡ ተቀምጠው፡ ይቈርጡት፡ ነበር ።

**ፈስው** ፤ **ፈሰው** ፤ ፈስ፡ ታሕታዊ፡ አስትን ፋስ ። አንዳንድ፡ መምህራን፡ የፈወሰ፡ ዘር፡ አድርገው፡ በፈውስ፡ ዘይቤ፡ ይፈቱታል፤ ይኸውም፡ መድኀኒት፡ ማለት፡ ነው ። ሰእመ፡ ወፀአ፡ እምብእሲ፡ ፈስው፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፤ ሳዕሌሁ፡ ኀምሳ፡ ስግደት፡ ወ ሠለስቱ፡ ሰቅል፡ በንድሮስ፡ (ቂድር) ።

**ፈስሒ** ፤ **ፈስሓይ** ፤ ፈሳዊ፡ የፈስ፡ ዐይነት፡ ብስና፤ የኮሶ፡ የኩረፌ፡ ግማት ። ክፉ፡ ሽታ፤ ግማት፤ ክርፋት፤ ቅርናት ። ወያወፅእ፡ ፈስሓየ ።

**ፋሲካ** ፤ (ጽር፡ ፓስኻ፤ ፋሴክ ። ዕብ፡ ፌሳሕ) ፤ በቁሙ፤ ፍሥሕ፤ የመሥዋዕትና፡ የበዓል፡ ስም፤ ዕድወት፡ ማዕደት፡ ማለት፡ ነው፤ ፍሥሕን፡ ተ መልከት ። ወጠብሑ፡ ፋሲካ ። ትበልዕዎ፡ በጕጕአ፡ እስመ፡ ፋሲካሁ፡ ለእግዚ ። ፋሲካ፡ አይሁድ ። ዕ ለተ፡ ፋሲካ ። በፋሲካ፡ ኦሪት፡ ኢይገብሩ፡ ፋሲካ፡ ወንጌል፡ (ዕዝ፮፡ ፳ ። ዘፀ፲፪፡ ፲፩ ። ዮሐ፪፡ ፲፫ ። ዲድ፡ ፳፱ ። ስንክ፡ መጋ፱) ።

**ፊሳሎንስ** ፤ (ጽርእ) ፤ ነባቤ፡ ባሕርይ፤ የፍ ጥረትን፡ ጠባይ፡ የሚናገር፡ ፍላሱፍ፤ ወይም፡ የፈላ ስፋ፡ መጽሐፍ ።

**ፍሱዕ** ፤ (ዕብ፡ ፌሻዕ፤ ክፉ፡ መጥፎ፡ ሥራ) ፤ ፈጣጣ፤ ጕረጥ፤ እንደ፡ ዕሥሥት፡ ዐይን፡ ቁብ፡ ቁበብ፡ ፍጥጥ፡ ያለ ። ልም፡ ደካማ፤ ሽውራራ ። ዐይኑ፡ የማናይ፡ ቱሱሕ፡ በደም፤ ወፀጋማይ፡ ፍ ሱዕ፡ (ኪዳን) ። በመዝመሪያው፡ ክፍል፡ ፍሱዕ፡ ያለ ውን፤ በኹለተኛው፡ ክፍል፡ ምዉት፡ ይለዋል ።

**ፈሲስ** ፤ **ሶት** ፤ (ፈሰ፤ ፈሰሰ፡ ይፈስስ፡ ይፍስስ ። ሱር፡ ፍሳስ) ፤ ዕፃ፡ መጣል፤ ማውጣት፤ በዕፃ፡ መክፈል ። ማፍሰስ፤ መፍሰስ፡ መቅለጥ ።

**ፈሳሲ፤ ፈሳሲ፤** የሚፈስ ፡ ፈሳሽ ፤ ወራጅ ፡ ቀላጭ ። ነቅዐ ፡ ፈሳሲ ፡ (ፈልክ ፡ ፴፰) ።

**ተፋሰሰ፤** ተዓፀወ ፤ ሰፃ ፡ ተጣጣለ ፤ ተሻኰተ ፤ እንሻኰት ፡ አለ ፤ በጣት ። ኢንግምድ ፡ ወኢንሥጥጥ ፤ ሕላ ፡ ንትፋሰስ ፡ ላዕሌሁ ፡ ለዘረከበ ፡ ይርከቦ ፡ (ዮሐ ፲፱ ፡ ፳፬) ።

(ጥ) **ፋስ፤** ሰፃ ፤ የሰፃ ፡ ሰንጨት ፤ ወረቀት ። ሽኵቻ ፤ የጣት ፡ ምልክት ፤ ባንድ ፡ በኹለት ፡ ወይም ፡ በጋት ፡ ባራት ፡ ጣቶች ፡ የሚኾን ። አንዱ ፡ ወስፌ ፤ ኹለቱ ፡ መቀስ ፤ አራቱ ፡ ሰይፍ ፡ ይባላል ፤ ወስፌ ፡ መቀስን ፡ መቀስ ፡ ሰይፍን ፡ ይረታል ። አራተኛ ፡ ደግሞ ፡ ዐምስቱን ፡ ጣቶች ፡ ጠቅሎ ፡ ጨብጦ ፡ ጡጫ ፡ ቡጢ ፡ ሲኾን ፡ ስሙ ፡ መደሻ ፡ ይባላል ፤ ርሱ ፡ ኹሉን ፡ ቢረታ ፡ እንጂ ፡ ሌሎቹ ፡ አይረቱትም ። ተፈጸመ ፡ ብከ ፡ እግዚኦ ፡ ቃለ ፡ ዳዊት ፡ ንጉሥ ፤ አመ ፡ ተካፈሉ ፡ በዕፃ ፡ ወፋስ ፤ ልብሰከ ፡ ልብሰ ፡ ሞገስ ፡ (ደራሲ) ።

**ፈሊስ፤ (ጽርእ)፤** ባሕርይ ፡ ጠባይዕ ። ፈሳሎ ጎስን ፡ እይ ።

**ፈቲው፤ ዎት፤ (ፈተወ ፡ ይፈቱ ፡ ይፍቱ ። ዕብ ፡ ፋታህ ። ሱር ፡ ፍታእ ። ዐረ ፡ ፈታ)፤** መመኘት ፤ ማሰብ ፤ መከጀል ፤ አይቶ ፡ መውደድ ፤ በልብ ፡ መቀበል ፤ ያዩትን ፡ የሰሙትን ፡ ነገር ፡ መከተል ፡ መሻት ፤ መሠዋት ፡ መጐምጀት ፤ በምኞትና ፡ ባምሮት ፡ መያዝ ፤ አማረኝ ፡ ውል ፡ ትዝ ፡ አለኝ ፡ ማለት ። ኢትፍቱ ፡ ብእሲተ ፡ ካልእከ ። ፈተዋ ፡ በነፍሱ ፡ ከመ ፡ ይስክብ ፡ ምስሌሃ ። ኵሉ ፡ ዘርእየ ፡ ለብእሲት ፡ ወፈተዋ ፡ ወድአ ፡ ዘመወ ፡ ባቲ ፡ በልቡ ። ኢፈተውኩ ፡ መሥዋዕተከ ። ኢትፍቱ ፡ ሀልዎ ፡ ምስሌሆሙ ። ፈተወ ፡ ይስተይ ፡ ማየ ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፲፯ ። ዮዲ ፲፪ ። ፲፯ ። ማቴ፭ ፡ ፳፰ ። ኢሳ፶፫ ፡ ፳፱ ። ምሳ፳፬ ፡ ፩ ። ኤፍ ፡ ፭) ።

**ፈታዊ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)፤** የሚመኝ ፡ የሚወድ ፡ ወዳጅ ፤ ጐምጂ ። ዕቡያን ፡ ወፈታውያን ። ፈታውያነ ፡ ጽዕለት ። ኢትኩን ፡ ፈታዌ ፡ (ቀሌ ። ምሳ ፳ ፡ ፳፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭) ።

**አፍተወ፤** አስመኘ ፤ አስጐመዠ ፡ ደስ ፡ አሰኘ ፤ አስወደደ ፤ አስፈለገ ። ኢያፍቶከ ፡ ሥና ፡ ለብእሲተ ፡ ባዕድ ። ኢያፍቶከ ፡ ተድላሆሙ ፡ ለረሲዓን ። ወአፍተዋ ፡ ከመ ፡ ትብላዕ ። ዘያፈትዎሙ ፡ ለመላእክት ፡ ከመ ፡ የሐውጽዎ ፡ (ሢራ፱ ፡ ፰ ፡ ፲፱ ። መቅ ፡ ወን ። ፩ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፪) ።

**ተፈትወ፤** ተወደደ ፡ በለጠ ፡ ከበረ ። መከፈልት ፡ ዘይትፈቶ ። ወይትፈቶ ፡ እምወርቅ ፡ ወእምዕንቍ ፡ (ጥበ፫ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፲፰) ። ወሰደ ፡ ተማሰደ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተፈትወ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ተፈቲዎ ። ተፈቲውየ ፡ (ዘፀ፳፱ ፡ ፲፭ ። ዘኍ፲፯ ፡ ፲፩) ።

**ፍትው፤** ያማረ ፤ የተወደደ ፤ ውድ ፡ ክቡር ። ዝክርክሙ ፡ ፍትው ። ፍትወ ፡ ምግባር ፡ (ስንክ ፡ ታኅሣ ። ጥር፲፭) ።

**ፍትወት፤ (ታት)፤** በቁሙ ፤ መመኘት ፤ መውደድ ፤ መወደድ ፤ አወዳደድ ፤ ውዴታ ፤ ጉምዠታ ፤ ፈቃድ ፡ አምሮት ፤ ሐሳብ ፡ ምኞት ፤ ንቅዐ ፡ ጎልዮ ፤ የኀጢአት ፡ ጠኢስ ፤ ተንታ ፤ ተድላ ፡ ደስታ ። ብእሴ ፡ ፍትወት ፡ አንተ ። ፍትወቶ ፡ ለሥጋ ፡ ወፍትወቶ ፡ ለዐይን ። እለ ፡ ይገብሩ ፡ ፍትወተ ፡ ነፍሶሙ ። ወፍትወትሰ ፡ እምከመ ፡ ፀንሰት ፡ ትወልዳ ፡ ለኀጢአት ። ፍትወታቲሁ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ (ዳን፱ ፡ ፳፫ ። ፩ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ። ኢሳ፶፱ ፡ ፱ ። ያዕ፩ ፡ ፲፭ ። ፈልክ ፡ ፫) ።

**ፍትወታዊ፤** የባሕርይ ፡ ጦር ፤ ዝሙት ። ከመ ፡ ያድክም ፡ ኀይለ ፡ ፍትወታዊት ፡ (አቡሻ ፡ ፴፰) ።

**ፍታው፤** ፍትወት ፤ ፈቃድ ፤ ምኞት ። እምፈጸምኩ ፡ ፍታውየ ፡ ላዕሌከ ፡ (ዮሴፍ) ።

**መፍትው፤** ፍትው ፤ ያማረ ፤ የተወደደ ፤ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፤ የሚያስጐመኝ ፤ የሚያስመኝ ፤ የሚያሻ ፡ የሚያስፈልግ ። ኵሉ ፡ ግብሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሠናይ ፡ ወመፍትው ። መፍትው ፡ ለዐይን ፡ ስርጕ ። ወይን ፡ መፍትው ። ስእንተ ፡ ምድረ ፡ ሕዝብየ ፡ መፍትው ። አስተዳሎኩ ፡ ለዝንቱ ፡ ሕንጻ ፡ ኵሎ ፡ ዘመፍትው ፡ (ሢራ፴፱ ፡ ፳፪ ። ማሕ ፡ ፲፪ ። ዓሞ፭ ፡ ፲፩ ። ኢሳ፴፪ ፡ ፲፪ ። ፩ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፪) ።

—፤ የተገባ ፤ የሚገባ ፤ አገባብ ፤ ርትዕ ፡ ተድላ ፡ ድልወት ። መፍትው ፡ ያንሰሱ ፡ ቀሲስ ፡ ኀበ ፡ አብያተ ፡ ድዉያን ። መፍትው ፡ ይሕየው ፡ ይስማኤል ፡ ቅድሜከ ። አመ ፡ ገብረ ፡ ዘኢመፍትው ። አኮ ፡ መፍትው ፡ (ኪዳ ። ኩፋ ፡ ፲፭ ። ቀሌ ። ማቴ፲፱ ፡ ፲፯) ።

**ፈቲሕ፤ ሐት፤ (ፈትሐ ፡ ይፈትሕ ፡ ይፍታሕ ። ዕብ ፡ ፋታሕ ። ሱር ፡ ፍታሕ ። ዐረ ፡ ፈተሐ)፤** መክፈት ፤ መግለጥ ፤ መዝጊያን ፡ መክደኛን ፡ ማስገለል ፡ ማንሣት ። ፈትሐ ፡ ኪሶ ። ኵሉ ፡ ተባዕት ፡ ዘይፈትሕ ፡ ማሕፀነ ። ፍታሕ ፡ አፉሁ ፡ ወእዘኒሁ ። ፈቲሐከ ፡ እዴከ ። ርጢናት ፡ እለ ፡ ይፈትሓ ፡ ሕብጠተ ፡ (ሉቃ፪ ፡ ፳፫ ። ኩፋ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፻፫ ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፫) ።

—፤ በቁሙ ፤ መፍታት ፤ መተርተር ፤ ማውለቅ ፤ ማሰናበት ፤ መናዘዝ ፡ እፈትሐከ ፡ ማለት ። መኑ ፡ ፈትሐ ፡ ማእሰሮ ። ኢይፈትሑ ፡ ቅናቶሙ ። አንስት ፡ ሶበ ፡ ይጠመቃ ፡ ይፍትሓ ፡ ሥዕርቶን ። ፍታሕ ፡ አሣእኒከ ፡ እምእገሪከ ። ፍትሖሙ ፡ ለአሕዛብ ። ይእስሩ ፡ ወይፍትሑ ፡ (ኢዮ፴፱ ፡ ፭ ። ኢሳ፭ ፡ ፳፯ ። ኪዳ ። ዘፀ፫ ፡ ፭ ። ማቴ፲፱ ፡ ፲፭ ። ቅዳ) ።

—፤ መሻር ፤ ማፍረስ ። ዘኬ ፡ ፈትሐ ፡ አሐተ ፡ እምእላ ፡ ትእዛዛት ። ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ግብሮ ፡ ለጋኔን ። ፈቲሐ ፡ ፍኅረት ፡ (ማቴ፭ ፡ ፲፱ ። ፩ዮሐ ፡ ፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፪) ።

—፤ መፍረድ ፤ መወሰን ፤ ማዘዝ ። ኢትፍትሑ ፡ በአድልዎ ። ፈትሐ ፡ በሕግ ፡ ብሊት ፡ ከመ ፡ ይምሐል ፡ ብእሲ ፡ በጽድቅ ። ሕግ ፡ ብሊት ፡ ፈትሐት ፡ ከመ ፡ ይቅ

ትሉ ፤ ወሕግበ ፡ ሐዳስ ፡ ኢፈትሐት ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፱ ፡ ፭ ። ፱ ፡ ፱) ።

**ፈታሒ** ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት ፤ ሕት) ፤ የሚከፍት ፤ ከፋች ፤ ፈች ፤ ፈራጅ ። ፈታሔ ፡ ማሕፀን ፡ ሩፋኤል ። ፈታሔ ፡ እሱራን ። ፈታሕት ፡ (ደራሲ ። መቃ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫) ።

**መፍትሒ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ የሚሽር ፤ የሚያፈርስ ። ስቴ ፡ ሰላም ፡ መፍትሔ ፡ ሕማምነ ፤ ዘውእቱ ፡ ደመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። መፍትሔ ፡ ሥራይ ፡ (ቀሬ ፡ ቄር ። አዋል) ።

**መፍትሕ** ፤ (ዐረ ፡ ምፍታሕ) ፤ መክፈቻ ፤ መሻሪያ ፤ ማፍረሻ ። መፍትሐ ፡ ሥራይ ፡ (አዋል) ።

**አፍትሐ** ፤ አስከፈተ ፤ አስፈረደ ። ለእመ ፡ ብእሲ ፡ አፍትሐ ፡ ደመ ፡ እምድኅረ ፡ ቍርባን ። ኢያፈትሕዎሙ ፡ ፍትሐ ፡ ዘነኔ ፡ (ቄድር ። ሚራ፴፰ ፡ ፴፫) ።

**ተፈትሐ** ፤ ተከፈተ ፤ ተፈታ ፤ ቀለጠ ፤ ፈረሰ ፤ ተለየ ፡ ተከፈለ ። ተፈትሑ ፡ መዓምቅት ። ተፈትሐ ፡ ማኅሜሁ ፡ እምነ ፡ መዝራዕቱ ። ተፈትሐ ፡ ማይ ፡ ዘረገዐ ። ወይትፈታሕ ፡ ማእሰረ ፡ ተዋስቦ ። ተፈትሐ ፡ መሌሊተ ፡ ሐቌሁ ፡ (ሔኖ ። መሳ፲፭ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ ሚያ ፳፭ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፪ ፡ ፭ ። ዳን፭ ፡ ፮) ። ተፈታሕ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ኤፍታሔ ፡ ሕ ፡ ይላል ፤ የተባሳተ ፡ ነው ፡ (ማር፯ ፡ ፴፬) ።

—፤ ተፈታ ፤ ፍትሐት ፡ ዘወልድ ፡ ተደገመለት ፤ ማንዘት ፡ መዋሥዕት ፡ ደረሰለት ፤ ኀጢአቱ ፡ ይቅር ፡ ተባለለት ፤ የተናዘዥ ፡ የሙት ። ተፈትሐት ፡ ኀጢአታ ። እምዝኒ ፡ ዘሉ ፡ ነገር ፡ ታሕዝነኒ ፡ ይሉኝታ ፤ አምጣነ ፡ ካህናት ፡ ቀተልዋ ፡ ወተቀብረት ፡ ሳትፈታ ፡ (ኢ.ባፃ ፡ ፱ ። ቅኔ) ።

—፤ ተፈረደ ፡ (ለት ፤ በት) ። ታዘዘ ፤ ተሠራ ። ተፈትሐ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍትሐ ፡ ሞት ። ተወሰነ ፡ ወተፈትሐ ፡ ላእለ ፡ ዘሎሙ ፡ ምእመናን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፫) ።

**ፍቱሕ** ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ትሕት) ፤ የተከፈተ ፡ ክፍት ፤ የተፈታ ፤ የወለቀ ፤ ደስ ፡ ያለው ፡ ጤናማ ። እንዘ ፡ ፍቱሕ ፡ ልቡ ፡ ወብሩህ ፡ ኅሊናሁ ። ዘፈታሕከ ፡ በምድር ፡ ይከውን ፡ ፍቱሐ ፡ በሰማያት ። ፍቱሐ ፡ አማእን ። ፍቱሕ ፡ ውእቱ ፡ ነፍሱ ። ቦ ፡ ኀይል ፡ ወፍቱሕ ፡ ነፍሱ ፡ ለበሊዕ ፡ (ቀሌ ። ዘዳ፳፰ ፡ ፲ ። ሚራ፴ ፡ ፲፱ ። ፵ ፡ ፭) ።

**ፍትሐት** ፤ (ታት) ፤ መክፈት ፤ መፍታት ፡ መፈታት ፡ አፈታት ፤ ፍታት ። (ማጥም) ፤ ምን ፡ ያሉ ፡ ቄስ ፡ ናቸው ፡ ተዝካር ፡ የለመዱ ፤ አስቃርቁኝ ፡ ብላቸው ፡ ፍታት ፡ ብለው ፡ ኼዱ ። ፍትሐት ፡ ዘወልድ ፡ (ቅዳ) ።

—፤ መርታት ፤ መትባት ፤ ያንደበት ። በፍትሐተ ፡ ቃል ፡ (ዘፀ፲፭ ፡ ፭) ።

**ፍትሕ** ፤ (ሓት ፡ አፍታሕ) ፤ ፍርድ ፤ ሕግ ፤ ሥርዐት ፡ ደንብ ፡ ውሳኔ ፤ ዕድር ፤ ልማድ ፤ የሚገባ ፡ ነገር ። ኢትሚጥ ፡ ፍትሐ ፡ ነዳይ ፡ ወኢተዐምፅ ፡ በፍትሕ ። ፍትኅተ ፡ ሕገጊሁ ። ትግበር ፡ ፍትሐ ፡ በአፍታሒሆሙ ። አንበሩ ፡ ፍትሐ ፡ ለዘሞአ ፡ በምሳሌሁ ፡ (ዘፀ ፳፫ ፡ ፮ ። ኩፋ ፡ ፶ ። ፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፱ ። ዲድ ፡ ፲ ። አርጋ ፡ ፱) ።

**ፍትሐ ፡ ነገሥት** ፤ የፍርድ ፡ መጽሐፍ ፤ ኹለት ፡ ክፍል ፤ ፶፩ ፡ አንቀጽ ፡ ያለው ፤ ከዚያውም ፡ መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ መንፈሳዊው ፡ ፳፪ ፤ ፪ኛው ፡ ክፍል ፡ ሥጋዊው ፡ ፳፱ ፡ ነው ።

**ተፋትሐ** ፤ ተፋታ ፤ ተፍታታ ፤ ተለያየ ፤ ተላቀቀ ፤ ተሻገተ ፤ ተፋረደ ፡ ተከሰሰ ። ይጣበቁ ፡ ወኢይትፋትሑ ። ኢትትፋታሕ ፡ ምስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ። ኢይትፋትሑ ፡ ምእመናን ፡ በኀበ ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ። ይትፋትሑ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ሥርዐተ ፡ ሠናይ ፡ አምልክ ፡ (ኢዮ፵፩ ፡ ፰ ። ዲድ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፱ ። ቀኖና) ።

**አስተፋትሐ** ፤ አፋታ ፤ አለያየ ፤ አሻገተ ፤ አፋረደ ፡ አፈራረደ ።

**ፈቲል** ፤ ሎት ፤ (ፈተለ ፡ ይፈትል ፡ ይፍትል ። ዕብ ፡ ፋታል ። ሱር ፡ ፍታል ። ዐረ ፡ ፈተለ) ፤ መፍተል ፤ ማክረር ፤ መጠምዘዝ ፡ መግመድ ፤ መሳብ ፡ መምዘዝ ። ፈተላሁ ፡ ለጸጕረ ፡ ጠሊ ። እመታ ፡ ታሕንፅ ፡ ለፈቲል ። ኢታንኅ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእስከ ፡ ኢትፍትል ፡ ወኢትፀፍር ፡ (ዘፀ፴፭ ፡ ፳፮ ። ምሳ፴፩ ፡ ፲፱ ። ዲድ ፡ ፭) ።

**ፈታሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤ የሚፈትል ፤ ፈታይ ፡ አክራሪ ፡ ገማጅ ።

**ተፈትለ** ፤ ተፈተለ ፤ ተከረረ ። ልብስ ፡ ዘኢተፈትለ ፡ ወኢተአንመ ፡ በእደው ፡ (ሲኖዶ ። ሳታ) ።

**ፍቱል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ትልት) ፤ የተፈተለ ፡ የተገመደ ። ቢሶስ ፡ ፍቱል ። ደርከኖ ፡ ፍቱል ። ድምድማሃ ፡ ድሉል ፡ ወቈናዝዊሃ ፡ ፍቱል ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፲፰ ። ዘኍ፲፭ ፡ ፴፰ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ፍትለት** ፤ መፍተል ፤ መፈተል ፤ አፈታተል ፤ ፈተላ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ) ።

**ፈትል** ፤ (ላት) ፤ በቁሙ ፤ ዝሓ ፡ ግራ ፤ ወይም ፡ ድርና ፡ ማግ ፤ ክር ፤ ገመድ ፤ ሽቦ ፤ ስልክ ። ፈትል ፡ ሥሉስ ፡ ፍጡነ ፡ ኢይትበተክ ። ልብሰት ፡ እንተ ፡ ክዑብ ፡ ፈትሉ ። ፈትለ ፡ ዐጌ ። ፈትለ ፡ ማሬት ። ፈትለ ፡ ብሩር ። ፈትለ ፡ ወርቅ ፡ ወፈትለ ፡ ሜላት ፡ (መክ፬ ፡ ፲፪ ። ሚራ፵፭ ፡ ፲፩ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። አፈ ፡ ተ፴፱ ። ዘፀ ፴፭ ፡ ፳፭ ። ደራሲ) ።

**አፍታል** ፤ (ትልት) ፤ ፈትሎች ፤ ክሮች ። አፍታል ። በበ ፡ አፍትልት ፡ (ዘፀ፴፯ ፡ ፲ ። አዋል) ።

**ፍትሎ** ፤ ፈትል ፤ ፍታል ፤ ልብስ ። ዘሕብረ ፡ ያክንት ፡ ፍትሎ ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፴፯) ።

**ፈቲን** ፤ ኖት ፤ (ፈተነ ፡ ይፈትን ፡ ይፍትን ። ዐረ ፡ ፈተን ። ዕብ ፡ በሐን) ፤ መፍተን ፤ መሞከር ። ማሰብ ፡ መመርመር ። መፈለግ ፡ መጕርጐር ፡ መበርበር ። መጠየቅ ፤ መሰለል ፤ ጠባዩን ፡ መጠጕን ፡ ለማ

ወቅ ። መከረን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። ፈተኑኒ ፡ ወርእዩ ፡ ምግባርየ ። ይፈትን ፡ ልበ ፡ ወዙ ልያተ ። እስኩ ፡ ፍትን ፡ ለሊከ ፡ በልብከ ። ወፈተነ ፡ ላባ ፡ ዙሉ ፡ ቤታ ፡ ለራሔል ፡ ወኢረከበ ። እንዘ ፡ ይፈ ትን ፡ ንዋዮሙ ። ይፍትንዎ ፡ ሕገገ ። ከመ ፡ ይፍ ትን ፡ ሀገረ ፡ (መዝ ፡ ፯ና ፡ ፲፱ ። ቀሌ ። ዘፍ፴፩ ፡ ፴፭ ። ኩፋ ፡ ፵፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ። ፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፫) ።

—፤ መጥበስ ፤ መተኩስ ፤ ማቅለጥ ፡ ማፍሰስ ፤ ማንጠር ፤ መክለስ ፤ ለማጥራት ፡ ለማደስ ። ምስጢሩ ፡ እንደ ፡ ፈ ተኛው ፡ ነው ፤ ምርመራን ፡ ያሳያል ። አረስዮሙ ፡ ወአ ፈትዮሙ ። ለንዋየ ፡ ለብሓ ፡ እሳት ፡ ይፈትኖ ። ወፈ ተንክነ ፡ ከመ ፡ ይፈትንዎ ፡ ለብሩር ። ፈተነ ፡ ከመ ፡ ወርቅ ፡ (ኤር፱ ፡ ፯ ። ሢራ፳፯ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፷፮ ። ኢዮ ፳፫ ፡ ፲) ።

**ፈታኒ** ፤ የሚፈትን ፤ ፈታኝ ፤ መርማሪ ። እግዚ ፡ ፈታኔ ፡ አልባብ ። ፈታኔ ፡ ኢዮብ ፡ በደዌ ፡ ወአበቅ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**መፍትኒ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። መፍትኔ ፡ አዕር ክት ፡ (ፊላስ) ።

**አፍተነ** ፤ አስፈተነ ፤ አስመረመረ ፤ ራሱን ፡ ወ ይም ፡ ሌላውን ። አፍትን ፡ ርእሰከ ፡ ለካህን ። ኅፍ ረት ፡ ብእሲት ፡ ከመ ፡ ታፍትን ፡ ኀጢአታ ፡ ገሃደ ፡ ለቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ (ማር፰ ፡ ፵፬ ። ስንክ ፡ ሐም፲፩) ።

**ተፈትነ** ፤ ተፈተነ ፤ ተሞከረ ፤ ተመረመረ ፤ ፈ ሰሰ ፡ ቀለጠ ። እለ ፡ ተመከሩ ፡ ወተፈትኑ ። መንፈስ ፡ ሕያው ፡ ወቅዱስ ፡ ዘኢይትፈተን ። ወርቅ ፡ ይትፈ ተን ፡ በምንሃብ ፡ (አፈ ፡ ተ፳ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ጥበ፫ ፡ ፯) ።

**ፍቱን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ትንት) ፤ በቁሙ ፤ የተፈተነ ፤ የወጣለት ፤ ጠባዩ ፡ መጠኑ ፡ የታወቀ ። ፍቱን ፡ ወርቅ ። ብሩር ፡ ዘኢኮነ ፡ ፍቱነ ። አረጋዊ ፡ ጽኑዕ ፡ ወፍቱን ። ኀይል ፡ ፍትንት ፡ ትዘልፎሙ ፡ ለአብዳን ፡ (ምሳ፳ ፡ ፲ ። ፳፭ ፡ ፱ ። ፩ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ጥበ፩ ፡ ፫) ።

**ፍትነት** ፤ መፍተን ፤ መፈተን ፤ አፈታተን ፤ ፈ ተና ፤ ፍቱንነት ።

**ፈተና** ፤ (ዕብ ፡ ፌቱን ፤ ነዘር ፡ እባብ) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ በቁሙ ፤ መከራ ፤ ሙከራ ። ወኮነ ፡ ሳዕ ሌሁ ፡ ፈተና ፡ ዐቢይ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ።

**ተፋተነ** ፤ በቁሙ ፤ ተፈታተነ ፤ ተሟከረ ። ዘእ ንበለ ፡ ይትፋተን ፡ ምስለ ፡ እግዚ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ።

**አስተፋተነ** ፤ አፋተነ ፤ አፈታተነ ፤ አሟከረ ፤ አሞካከረ ።

**ፈትፈተ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ ፈተፈተ ። ፈቲት ፡ ፈተ ፤ አው ፡ ፈትቶ ፡ ፈተተ ።

**ፈትቶ** ፤ **ቶት** ፤ (**ፈተተ ፡ ይፌትት ፡ ይ ፈትት** ። **ዕብ ፡ ፋታት**) ፤ መፈተት ፤ መቍረስ ፤ መ ግመስ ፡ መክፈል ፤ መክፋፈል ፤ መሰባበር ፤ ማጠቃቀን ። ነፋስ ፡ ዘይፈትቶ ፡ ለኵሉሙ ። ወፈቲቶ ፡ ወሀበ ። እ ንዘ ፡ ይፌትት ፡ ኅብስተ ። ጸሎተ ፡ ፈትቶ ፡ (፫ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ ። ማቴ፲፬ ፡ ፲፱ ። ሉቃ፳፬ ፡ ፴፭ ። ቅዳ) ።

—፤ መስጠት ፤ ማጉረስ ፤ ማደራጎት ። ወፈተቶ ፡ ፍተ ፡ ዘዘልፍ ። የሀቦ ፡ ንጉሥ ፡ ብዙኀ ፡ ወይፌትት ፡ ዕሴተ ፡ ዘሞአ ። ወፈተቶ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ (ኤር፶፪ ፡ ፴፬ ። ፩ዕዝ ፡ ፫ ፡ ፭ ። አስቴ፩ ፡ ፲፯) ።

**ፈታቲ** ፤ (**ቲት ፡ ትያን ፡ ያት**) ፤ የሚፈ ትት ፤ የሚቈርስ ፤ ቈራሽ ።

**ተፈተተ** ፤ በቁሙ ፤ ተቈረሰ ፤ ተገመሰ ። ወይ ትፌትት ፡ እብነ ፡ በረድ ። ዝ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋየ ፡ ዘበእን ቲአክሙ ፡ ይትፌትት ፡ ለኅድገተ ፡ ኀጢአት ፡ (ሢራ ፵፫ ፡ ፲፭ ። ቅዳ ፡ እግዚ) ።

**ፍቱት** ፤ የተፈተተ ፤ የተቈራረሰ ፤ ግማሽ ፤ እኩ ሌታ ። ፈንተት ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ፍታቴ** ፤ መፈተት ፤ አፈታተት ፤ ፍተታ ፤ ቈረሳ ። በጊዜ ፡ ፍታቴ ፡ ቍርባን ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳) ።

(ጥ) **ፍት** ፤ (**ብ ፡ ፍተት** ፤ **ፍተታት** ። **ዕብ ፡ ፋት** ፤ **ፈቲም**) ፤ ቍራሽ ፤ ቍርስራሽ ፤ ፍርፋሪ ፡ የን ጀራ ፡ ስባሪ ። ፍት ፡ ጥዑም ፡ ምስለ ፡ ሰላም ። ፍተ ፡ ኅብስት ። አስተጋብኡ ፡ ዘተርፈ ፡ ፍተታተ ። ወያወ ርድ ፡ በረደ ፡ ከመ ፡ ፍተታት ፡ (ምሳ፲፯ ፡ ፩ ። ፳፰ ፡ ፳፩ ። ዮሐ፮ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፻፵፯) ።

—፤ ጕርሻ ፤ ዳረጎት ፤ ክፍላዊ ፡ ስጦታ ፤ መቍነን ፤ ዕ ድል ፡ ፈንታ ። ፍተክሙ ፡ ትነሥኡ ። ፍተ ፡ መንግሥ ትከ ፡ ሀበ ፡ ለባዕድ ። ፍት ፡ ለእግዚ ፡ ብእሲት ፡ የዋህ ። በከመ ፡ ነሣእክሙ ፡ ፍት ፡ ለእግዚ ፡ (ዳን፪ ፡ ፭ና ፡ ፵፰ ። ሢራ፳፯ ፡ ፲፱ ። ፩ጢሞ ፡ ፱ ፡ ፲) ።

—፤ መብልዕ ፤ ምግብ ፤ ሲሳይ ፤ ዘዘልፍ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ወጥንም ፡ ብቻ ፡ ያሳያል ። ፍት ፡ ሐምል ፤ የጕመን ፡ ወጥ ፤ ቅርድ ፤ ሥንቆ ፤ ስላጣ ፤ ቅጠላቅጠል ፡ ያሰኛል ፤ (ምሳ፲፭ ፡ ፲፯) ።

# ጸ

**ጸ** ፤ ፀሥራ ፡ ስምንተኛ ፡ ፊደል ፡ በጥንታዊው ፡ ተራ ፤ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፤ ስሙ ፡ ጸደይ ፤ ቍጥሩ ፡ ዘጠና ፤ አኀዝ ፡ ሲኾን ፡ ጸ ፡ ፺ ፡ ይባላል ።

**ጼአ ፤—ገማ ፤ ሸተተ ፤—ጸዪእ ፡ ጼአ ።**

**ጸአጠ ፤—ቀመመ ÷ አጣፈጠ ፤—ጽዒጥ ፡ ጸዐጠ ።**

**ጸአለ ፤—ሰደበ ፤—ጽዒል ፡ ጸዐለ ።**

**ጽኢም ፤ ሞት ፤ (ጸአመ ፡ ይጽእም ፡ ይጽአም ። ዜመ ፡ ይዘይም)** ፤ መጮኽ ፤ ማስተጋባት ። ዜመን ፡ ተመልከት ።

**መጽአሞ** ፤ ጩኸት ፤ የናደት ፡ ድምጥ ፤ የገደል ፡ ማሚቶ ፤ ተራራ ፡ ገደል ፡ ዋሻ ፡ እያስተጋባ ፡ የሚጮኸው ፡ ጩኸት ። ወሰምዐ ፡ መጽአሞሁ ። ወይዌውዑ ፡ ማእከለ ፡ መጽአም ፡ (ፊልክ ። ኢዮ፴ ፡ ፯) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ሲሒም ፡ ይላል ፤ ቍጥቋጦ ፡ ማለት ፡ ነው ።

—፤ ደስክ ፤ ቅዝት ፤ ምትሀት ፤ በእንቅልፍ ፡ ልብ ፡ የሚታይና ፡ የሚደብት ፤ የሚጫን ፡ የሚያስጮኽ ፤ የሚያስጨንቅ ፤ የሚያስለፈልፍ ፤ የአጋንንት ፡ መልክ ፤ ለሰው ፡ የሚታዩበት ፡ አርኣያና ፡ አምሳል ። ወይመልእ ፡ ውስተ ፡ አብያቲሆሙ ፡ መጽአም ፡ (ኢሳ፲፫ ፡ ፳፩) ። ዕብራይስጡ ፡ ኦሒም ፡ ይላል ፤ አሥዋክ ፤ አራዊት ፤ አዕዋፍ ፡ ርኩሳን ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ፤ ያፍ ፡ ማለት ፡ ከአቡቀለምሲስ ፡ ይስማማል ፡ (ራእ፲፰ ፡ ፪) ።

**ጸአነ ፤—ጫነ ፤—ጽዒን ፡ ጸዐነ ።**

**ጸእጸአ ፤—ጭንጋፍ ፤—ፃእፃእ ፡ ወዕአ ።**

**ጸቢእ ፤ አት ፤ (ጸብአ ፡ ይጸብእ ፡ ይጽባእ ። ዕብ ፡ ጻባእ)** ፤ አሸከር ፡ ወታደር ፡ መኾን ፤ መፋንን ፤ በፈቃድ ፡ ወይም ፡ በግድ ፡ መዝመት ፤ ተሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ መኼድ ፤ ጠብ ፡ ማንሣት ፤ ማጫር ። ፊት ፡ ለፊት ፡ መግጠም ፤ መውጋት ፤ መዋጋት ፤ ማሸነፍ ፤ ማጥፋት ፤ መግደል ፡ መስየፍ ፤ መስለብ ፡ መግፈፍ ፡ መማረክ ፡ መዝረፍ ። ሰበክ ፡ ሳኦል ፡ ለኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ከመ ፡ ይጽብኡ ፡ ወይረዱ ፡ ውስተ ፡ ቄዐላ ። ወፀኡ ፡ ሕዝብከ ፡ ለጸቢአ ፡ ተዓይኒ ፡ ፀሮሙ ። ይሔር ፡ ይጽብአ ፡ ለካልእ ፡ ንጉሥ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፰ ። ፪ዜና ፡ ፮ ፡ ፴፬ ። ሉቃ፲፬ ፡ ፴፩) ።

—፤ መሰፈር ፤ መከተም ፤ ሰፈር ፡ ከተማ ፡ ማድረግ ። ሀገር ፡ እንተ ፡ ጸብአ ፡ ዳዊት ፡ (ኢሳ፳፱ ፡ ፩) ።

**ጸባኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት)** ፤ የሚዘምት ፤ የሚዋጋ ፤ ዘማች ፤ ጠበኛ ፤ ሐርበኛ ። ቃልከ ፡ መዋኢ ፡ ወጸባኢ ። ሰብአ ፡ ጸባእያን ፡ (ጥበ፲፰ ፡ ፲፭ ። ኤር፵፭ ፡ ፱) ።

**ጸባኢት** ፤ ሰራዊት ፤ ጭፍራ ፤ የጦር ፡ ሕዝብ ፤ ብዙ ፡ ወታደር ፤ ያርበኛ ፡ ጉባኤ ፤ የዠማና ፡ ማኅበር ። ድምፀ ፡ ጸባኢት ። ሊበጸባኢት ። ከመ ፡ ይትቃተሉ ፡ ምስለ ፡ ጸባኢት ፡ ጽንዕት ። እመኒ ፡ ሮዱኒ ፡ ጸባኢት ፡ (ዘፀ፴፪ ፡ ፲፯ ። ሆሴ፩ ፡ ፯ ። ዮዲ፭ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፳፮) ።

**ጸባኦት ፤ (ዕብ ፡ ጽባኦት ፤ ጺብኦት ። ጽር ፡ ሣባዖት)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ሰራዊት ። እግዚአብሔር ፡ ጸባኦት ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፳፬ ። ፪ ፡ ፲፩ ። ፭ ፡ ፯ና ፡ ፱ ። ፮ ፡ ፫) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ እግዚእ ፡ ጸባኦት ፡ ስላላለ ፤ ለእግዚ ፡ ስምና ፡ ቅጽል ፡ አድርገው ፡ አሸናፊ ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፤ ገዝኣን ፡ ተመልከት ። በሥጋዌሁ ፡ ለጸባኦት ፡ (አርጋ ፡ ፬) ።

**መጽብኢት** ፤ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ። መጽብኢቶሙ ፡ (፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፲፰) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ብክኢም ፡ ይላል ፤ የቱት ፡ ዐይነት ፡ ዛፎች ፡ ማለት ፡ ነው ። ቱት ፡ ዐጽቃም ፡ ቅጠላም ፤ የሐር ፡ ዛፍ ፡ ነው ፤ ቅጠሉን ፡ የሐር ፡ ትሎች ፡ ይበሉታል ፤ ፍሬውም ፡ እንዠሪ ፡ ይመስላል ።

**ምጽባእ ፤ (ኣት)** ፤ መውጊያ ፤ መዋጊያ ፤ መሳለፊያ ። ማደሪያ ፤ መሳፈሪያ ፤ ጕዝጕ ፡ መሥሪያ ፤ ድንኳን ፡ መትከያ ። ዘይሰመይ ፡ ምጽባአ ፡ ዳዊት ፡ (አቡሻ ፡ ፵፯) ።

**ጸብእ** ፤ ጠብ ፤ ጥል ፤ ሰልፍ ፤ ዘመቻ ፤ ውጊት ፤ ጦርነት ፤ አንባ ፡ ጓሮ ፤ ክርክር ፤ ሙግት ። ዘይገብር ፡ ጸብአ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ። በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ጸብእ ። ወታቀንተኒ ፡ ኀይለ ፡ በጸብእ ። መድምም ፡ እንተ ፡ በኵሉ ፡ ጸብእከ ። ክብረ ፡ ሆሳዕና ፡ ነገር ፡ ለእመ ፡ ትወጥኑ ፡ አንሥአት ፡ ጸብአ ፡ ምስለ ፡ በሉሚ ፡ አድግት ፤ እንዘ ፡ ትብል ፡ ኢይኀድር ፡ ውስተ ፡ ልብኪ ፡ ትምክሕት ፤ አምጣኒ ፡ ውእቱ ፡ ሀብትኪ ፡ ስደት ፤ ወእመ ፡ ተሐዝሊ ፡ ሆሳዕና ፡ አዕቀጹኪ ፡ አእባን ፡ ወዐገቶኪ ፡ ፈያት ። ሊተሰ ፡ እመ ፡ ሐዘልኩ ፡ ሆሳዕና ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ በስብሐት ፡ ተቀበሉኒ ፡ እእሩግ ፡ ወሕፃናት ፤ ወቴንሥኡ ፡ ሊተ ፡ አእባኒ ፡ ርሑቅ ፡ ፍኖት ፤ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ሆሳዕና ፡ መጽአ ፡ በስብሐት ፡ (ኩፋ ፡ ፶ ። ኢሳ፳፯ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፲፯ ። ዮዲ፲፩ ፡ ፰ ። ቅኔ) ።

**ጸብኣት ፤ (አጽባእ ፤ እት ፤ ኣት)** ፤ ጠቦች ፤ ሰልፎች ፤ ጦርነቶች ። ብዙኀ ፡ ደመ ፡ ከዐውከ ፡ ወዐበይተ ፡ ጸብኣተ ፡ ገብርከ ። በእንተ ፡ አጽባእ ፡ ዘዐውዱ ። የኀድጉ ፡ አጽባኢሆሙ ። አጽባእት ፡ ወድምፀ ፡ ጸባኢት ። አጽባእት ፡ ብዙኃ ፡ (፩ዜና ፡ ፳፪ ፡ ፰ ። ፩ነገ ፡ ፭ ፡ ፫ ። ሉቃ ፡ ዕዝ፲፫ ፡ ፴፰ ። ማር፲፫ ፡ ፯ ። አፈ ፡ ተ፳፯) ።

**ተጸብአ** ፤ ተወጋ ፤ ቈሰለ ፤ ተዘመተበት ። ተግማጽ ፡ ይሬስዮ ፡ ለመስተጋድል ፡ ይጽናዕ ፡ ወሊይት መዋኢ ፡ በውስተ ፡ ገድል ፡ ወይጸብእ ፡ በውስተ ፡ ጸብእ ፡ (አፈ ፡ ድ፴) ።

**ጽቡእ** ፤ (እን ፡ ኢት ፡ ብእት) ፤ የተወጋ ፤ ውግ ፤ የተዘመተበት ። ጽቡእ ፡ ብሔሩ ፡ (ሄርማ) ።

**ጽብአት** ፤ መውጋት ፤ መወጋት ፤ አወጋግ ፤ ውጋታት ። ዝክርኪ ፡ ኀሊናኪ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ጽብአትኪ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (ኢሳ፶፯ ፡ ፲፩) ።

**ተጻብአ** ፤ ተጣላ ፤ ተዋጋ ፤ ተሳሰፈ ። ወተጻብእሙ ፡ ውእቱ ፡ አርዌ ። ወይጻብኡ ፡ ምስለ ፡ በግዑ ። እጻብእ ፡ ኀሊናትየ ። ወተጻብኡሂ ፡ (ራእ፲፪ ፡ ፯ ። ፲፯ ፡ ፲፬ ። ፈልክ ። ያዕ፬ ፡ ፪) ።

**እስተጻብአ** ፤ አጣላ ፤ አዋጋ ። ምንት ፡ ያስተጻብአክሙ ፡ እንዘ ፡ አኀው ፡ አንትሙ ፡ (ማብ፯ ፡ ፳፯) ።

**አጽብእት** ፤—ጣት ፤—አጽባዕት ፤ ጸብዐ ።

**ጸቢብ** ፤ ቡት ፤ (ጸበ ፤ ጸበበ ፡ ይጸብብ ፡ ይጽብብ ። ዐረ ፡ ፀበ ፤ ጠበቀ) ፤ መጥበብ ፤ ማነስ ፤ ታናሽ ፡ ጠባብ ፡ መኾን ፤ የበታ ። ይጸብበነ ፡ ብሔር ፤ ወትጸብቢዮሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴትኪ ። ዘሰማይ ፡ ኢያገምሮ ፤ ሊጸበቦ ፡ ማኅፀነ ፡ ድንግል ። ወቦ ፡ ቅንዋት ፡ አርድእት ፡ እለ ፡ ተመይጡ ፡ እምእሉ ፤ አካልከ ፡ ማኅደር ፡ ጸበበነ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ (ኢሳ፵፱ ፡ ፲፱ና ፡ ፳ ። ተረ ፡ ቄር፲፰ ። ቅኔ ። ፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፭) ።

—፤ መጭነቅ ፡ መቸገር ፤ ጭንቅ ፡ መኾን ። ሶበ ፡ ጸበበተ ፡ ግብር ፡ (ሱንክ ፡ መስ፫) ።

**ጸቢብ** ፤ (በን ፡ በት) ፤ የጠበበ ፤ ጠባብ ። መካን ፡ ጸቢብ ። ማዕምቅ ፡ ጸቢብ ። ጸቢበ ፡ እንግድዓ ፡ (ዘኍ፳፪ ፡ ፳፯ ። ሔኖ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ጸባብ** ፤ (ባት) ፤ ገዳ ፡ ከማሁ ፤ የጠበበች ፤ ጠባባ ፤ ታናሽ ። እስመ ፡ ጸባብ ፡ ፍናዊሁ ። ዕዘቅት ፡ ጸባብ ። ባሕር ፡ ጸባብ ። ባሑ ፡ እንተ ፡ ጸባብ ፡ አንቀጽ ፡ (ዮዲ፬ ፡ ፯ ። ምሳ፳፫ ፡ ፳፯ ። ዘካ፲ ፡ ፲፩ ። ማቴ፯ ፡ ፲፫) ።

**ጽቡብ** ፤ (በን ፡ ባት ፡ ብብት) ፤ ገዳ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፤ የጠበበ ፤ የጨነቀ ። የጠበበው ፡ የጨነቀው ፤ የተጠበበ ፡ የተጨነቀ ፤ እስራት ፡ የጠበቀበት ፤ ደዌ ፡ መከራ ፡ ዕዳ ፡ የወደቀበት ። ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ጥዉቃነ ፡ ወጽቡባነ ፡ (ግንዘ) ።

**ጽበት** ፤ መጥበብ ፡ መጭነቅ ፤ መጠበብ ፡ መጨነቅ ፤ ጥበት ፡ ጭንቀት ፤ ጠባብነት ። ጽበተ ፡ ብሔር ። ጽቡተ ፡ ከርሥ ። ጒየ ፡ ኀበ ፡ ጸባ ፡ ጸሞን ፡ እምጽበተ ፡ ነፍሱ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ፈልክ ፡ ፲፬) ።

**አጽበበ** ፤ አጠበበ ፤ አስጠበበ ፤ አስጨነቀ ፤ ትብግሥት ፡ ፀጣ ። ያንብሮ ፡ ውስተ ፡ መርሕብ ፡ ወኢየጽብብ ፡ ላዕሌሁ ። አጽብቡ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ በዐመፃ ። ወያጸብብ ፡ እንግድዓሁ ፡ (ግብ፳፱ ፡ ፳፫ ። ፈልክ ፡ ፹፱ ። አፈ ፡ ድ፳) ።

— ዘጋ ፤ ገጠመ ፤ አሳነስ ። አጽብቦ ፡ ክናፍር ። አጽብብ ፡ ላዕለ ፡ ኀሊናከ ። ወአጽብብ ፡ ላዕሌከ ፡ እምስትየ ፡ ማይ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ፈልክ ፡ ፵፫ና ፡ ፳፰) ።

**መጽብብ** ፤ የሚያጠብ ፤ አጥባቢ ። ጠባብ ፤ ታናሽ ፤ ቀጭን ። መጽብበ ፡ ቦእኩ ። ከመ ፡ አበግዕ ፡ ውስተ ፡ መጽብብ ። ወእንተ ፡ መጽብብ ፡ ሙባኢሁ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፳፰ ። ሚክ፪ ፡ ፲፪ ። ሉቃ ፡ ዕዝ፲፫ ፡ ፵፬) ።

—፤ አንባ ፡ ኵረብታ ፤ ዕርድ ፡ ምሽግ ፤ ጠላት ፡ የማይደፍረው ። ወነበረ ፡ ዳዊት ፡ ውስተ ፡ መጽብብ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፲፬) ።

**ጸብሀ** ፤—ጠለቀ ፤—ጸቢሕ ፡ ጸብኀ ።

**ጸቢሕ** ፤ ሐት ፤ (ጸብሐ ፡ ይጸብሕ ፡ ይጽባሕ ። ዐረ ፡ ጸባሕ ፤ ጧት) ፤ መጥባት ፤ መንጋት ፤ ወገግ ፡ ማለት ፤ ጧት ፡ መኾን ። ሶበ ፡ ጸብሐ ። እስከ ፡ ጸብሐ ። እምከመ ፡ ጸብሐ ፡ (ሩት፫ ፡ ፲፫ ። ፩ነገ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ። ኢዮ፳፬ ፡ ፲፯) ። ለጸቢሐ ፡ ዐርብ ፤ ሳርብ ፡ አጥቢያ ፤ ንሙስ ፡ ማታ ፡ (ቅዳ ፡ ኤጲ) ። ለጸቢሐ ፡ እሑድ ፤ በጽባሐ ፡ እሑድ ፤ እሑድ ፡ ጧት ፤ ማለዳ ፡ (ማቴ፳፰ ፡ ፩) ። ወጸቢሖ ፤ እንተ ፡ ጸቢሖ ፤ በነጋ ፡ ጊዜ ፤ ሲነጋ ፤ ሲጠባ ፤ ጧት ፤ ማለዳ ፤ (ግብ፲፪ ፡ ፯ ። ፳፯ ፡ ፴፫) ።

**ጽብሐት** ፤ መጥባት ፤ መንጋት ፤ ወገግ ፡ ፈገግ ፡ ማለት ። በጽብሐት ፡ ፈንታ ፡ ጸብሐት ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**እንተ ፡ ጽብሐት** ፤ በነጋ ፡ ቍጥር ፤ እየነጋ ፤ እየጠባ ፤ ማለዳ ፡ ማለዳ ፤ ነገም ፡ ነገም ፤ ጧት ፡ ጧት ፤ ዕለት ፡ ዕለት ፤ ዘወትር ፤ በየቀኑ ። ወትትናገሮ ፡ ሰዩፍ ፡ እንተ ፡ ጸብሐት ። እንተ ፡ ጸብሐት ፡ ኢትወእጥ ፡ ዐርከ ። ወእንተ ፡ ጸብሐት ፡ ይበዝኁ ፡ ሕዝብ ፡ (ዘፍ፴፱ ፡ ፲ ። ሢራ፯ ፡ ፲፫ ። ግብ፲፮ ፡ ፭) ።

**ጽባሕ** ፤ (ሓት) ፤ ጥባት ፤ ንጋት ፤ ወገግታ ፤ ጧት ፤ ማለዳ ፤ ወፍ ፡ ሲጮኽ ። በጊዜ ፡ ጽባሕ ። ሶበ ፡ ገሐ ፡ ጽባሕ ። ኮከበ ፡ ጽባሕ ። በጽባሕ ፡ እቀውም ፡ ቅድሜከ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፲፩ ። ዘፍ፴፬ ፡ ፫ ። ኢዮ፴፰ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፭) ።

—፤ ዕለት ፤ መዓልት ፤ ቀን ። ፈጸሙ ፡ ሎቱ ፡ አርብዓ ፡ ጽባሐ ። ወገብሩ ፡ በአርብዓ ፡ ጽባሕ ፡ (ዘፍ፶ ፡ ፫ ። ዘኍ ፲፫ ፡ ፳፭) ።

—፤ ነገታ ፤ ሳኢታ ፤ ማግስት ። ዘትወልድ ፡ ጽባሕ ። ጸመ ፡ ሌደት ፡ ወተፍጻሜቱ ፡ ዘጽባሒሁ ፡ ዕለተ ፡ በዓለ ፡ ሌደት ፡ (ምሳ፳፯ ፡ ፩ ። አቡሻ ፡ ፴፯) ።

—፤ ምሥራቅ ፤ የንጋት ፡ የወገግታ ፤ በታ ፤ የፀሓይ ፡ መውጫ ፡ መገለጫ ፤ ዐቢይ ፡ ማእዝን ፤ የምዕራብ ፡ ትይዩና ፡ አንጻር ። ብሔረ ፡ ጽባሕ ። ነፋስ ፡ ጽባሕ ። መንገለ ፡ ጽባሕ ። እስመ ፡ ኢእምጽባሕ ፡ ወኢእምዐረብ ። ጽባሓቲሁ ፡ (ኢዮ፩ ፡ ፫ ። ሔኖ፳፯ ፡ ፳፫ ። ሕዝ፲፯ ፡ ፲ ። መዝ ፡ ፸፬ ። ኩፋ ፡ ፰) ።

**ጽባሓዊ** ፤ (ሓይ) ፤ የጢት ፡ የማስዳ ፤ ምሥራቃዊ ፡ የምሥራቅ ። ክከበ ፡ ብርሃን ፡ ጽባሓዊ ፡፡ አንቀጸ ፡ ቤት ፡ ጽባሓዊ ፡፡ ነፋስ ፡ ጽባሓይ ፡ (ራእ፳፱ ፡ ፲፯ ። ሕዝ፵፯ ፡ ፩ ። ሔኖ፳፮ ፡ ፳) ።

**አጽብሐ** ፤ አነጋ ፤ አስነጋ ፤ አማለደ ፤ አስማለደ ። የሰው ፡ ስም ። አብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ።

**ተጻብሐ** ፤ ተሰላለመ ፡ የጢት ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጠ ፤ ጽባሕከ ፡ ኄር ፡ ወይም ፡ እንደት ፡ ዐደርኽ ፡ ተባባለ ። ወእመ ፡ ቦ ፡ ዘተጻብሐከ ፡ ኢትጻብሖ ፡ (፬ነገ ፡ ፬ ፡ ፳፱) ።

(ጥብ) **ጸብሐ** ፤ **ሐት** ፤ **(ጸብሐ ፡ ይጼብሕ ፡ ይጸብሕ)** ፤ መገበር ፡ ማቅረጥ ፤ ግብር ፡ ቀረጥ ፡ መስጠት ። ኵነኑ ፡ ቄሴ ፡ ዘሶርያ ፡ ወጸብሑ ፡ ሎሙ ፡፡ ለዘሂ ፡ ጸባሕተ ፡ ጸብሑ ፡፡ ከመ ፡ ይጸብሑ ፡ ለያዕቆብ ፡ (፩ዕዝ ፡ ፱ ፡ ፳፯ ። ሮሜ፲፫ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፴፰) ። በጸብሐ ፡ ፈንታ ፡ አጽብሐ ፡ ይላል ፤ የተባሳተ ፡ ነው ። ለእመ ፡ አጽባሕክሙ ፡ ሊተ ፡ ጸባሕተ ፡ (መቃ ፡ ገ፯) ።

**ጸባሒ** ፤ **መጸብሒ** ፤ የሚገብር ፤ ገባሪ ፤ ግብር ፡ ሰጭ ፤ አቅራጭ ። ክንዎሙ ፡ መጸብሔ ፡፡ ወረሰዮሙ ፡ መጸብሔ ፡ (ኢያ፲፱ ፡ ፵፰ ። ፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፳፱ ። መሳ፩ ፡ ፳፰) ።

**ጸባሕት** ፤ **(ሓት)** ፤ ግብር ፤ ቀረጥ ፤ ለመንግሥት ፡ የሚገባ ፡ ገንዘብ ፤ ስጦታ ። ወሠርዐ ፡ ጸባሕተ ፡ ላዕሌሆሙ ፡፡ የሀቡ ፡ ጸባሕተ ፡ ለፈርያን ፡፡ እለ ፡ ጸባሕተ ፡ ይነሥኡ ፡፡ እስመ ፡ ጸዎ ፡ ጸባሕተ ፡ ሥጋ ፡ ውእቱ ፤ ወጸሎትኒ ፡ ጸባሕተ ፡ ነፍስ ፤ በከመ ፡ ምጽዋት ፡ ጸባሕተ ፡ ንዋይ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፱ ። ፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፴፩ ። ማቴ ፲፯ ፡ ፳፬ ። አቡሻ ፡ ፴፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭) ።

**አጸብሐ** ፤ አስገበረ ፤ ግብር ፡ አስከፈለ ፤ ገብሩ ፡ ግብር ፡ አምጡ ፡ አለ ። ወያጼብሐክሙ ፡ ዐሥራተ ፡ እደ ፡ (፩ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፭—፲፯) ።

**መጸብሕ** ፤ **(ሕት ፡ ሓን ፡ ሓት)** ፤ የሚያስገብር ፤ አስገባሪ ፤ ቀራጭ ፤ ግብር ፡ ተቀባይ ፡ (ማቴ፱ ፡ ፲—፲፩) ።

**መጸብሓዊ** ፤ ገዘኒ ፡ ከማሁ ። ማቴዎስ ፡ መጸብሓዊ ፡ (ማቴ፲ ፡ ፫ ። ፲፰ ፡ ፲፯ ። ፳፩ ፡ ፴፩) ።

**ምጽባሕ** ፤ መገበሪያ ፤ ማስገበሪያ ፤ ግብር ፡ መስጫ ፡ መቀበያ ፤ ቦታ ፡ ጕምሩክ ፡ ገባያ ፤ በር ። እንዘ ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ ምጽባሕ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳፭ ። ማቴ፱ ፡ ፱) ።

**ጸቢኅ** ፤ **ኆት** ፤ **(ጸብኀ ፡ ይጸብኅ ፡ ይጽባኅ ። ዐረ ፡ ጠበኀ)** ፤ ማወጥ ፤ ማጣፈጥ ፤ ወጥ ፡ መሥራት ፤ መቀቀል ። መጥቀስ ፤ መጥለቅ ፤ መንከር ፡ መዝፈቅ ፤ እንጀራን ፡ በወጥ ፡ በመረቅ ። ወኮነ ፡ ይትጌበር ፡ ዙሉ ፡ ግብረ ፡ ቤት ፡ እስከ ፡ ቀዲሐ ፡ ማይ ፡ ወኵስትሮ ፡ ዙስሕ ፡ ወአንድዶ ፡ እሳት ፤ ወጸቢኅ ፡ ጸብኆ ፡ ወኀቢዘ ፡ ኀብዝ(ስት) ፡፡ ዘይጸብኆ ፡ ምስሌየ ፡፡ ጸብኀ ፡ ኀብስተ ፡ ወመጠዎ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፱ ፡፡ ማቴ፳፮ ፡ ፳፫ ። ማር፲፬ ፡ ፳ ። ዮሐ፲፫ ፡ ፳፮ ። ሩት፪ ፡ ፲፬) ።

**ጸብኒ** ፤ **(ኒት ፡ ኀያን ፡ ያት)** ፤ ወጥ ፡ ሠሪ ፤ ወጥ ፡ ቤት ፤ ወጥ ፡ አውጭ ፤ አሳላፊ ፤ ጠቃሽ ፤ ጠላቂ ።

**ጸብኅ** ፤ **(ኀት)** ፤ ወጥ ፤ የተቀቀለ ፤ የበሰለ ። ጸብኆ ፡ ብርስን ፡፡ ተብሲለ ፡ ወጸብኆ ፡፡ ኢይብላዕ ፡ ጸብኆ ፡ አላ ፡ ኀብስተ ፡ ይቡሰ ፡ ወጼወ ፡፡ ኢበልዐት ፡ ምንተኒ ፡ ጸብኆ ፡ ዘአብሰልዎ ፡ በእሳት ፡ (ኩፋ ፡ ፴፮ ። ገድ ፡ ተክ ። ቄድር ። ስንክ ፡ ጥቅ፩) ።

**መጽብኅ** ፤ **(ኀት)** ፤ የወጥ ፡ ዕቃ ፤ መማሪያ ፤ ድስት ፡ ሳሕን ፡ ጭልፋ ፡ ማማሰያ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡ ውስተ ፡ መጽብኅ ፡ (ማቴ፳፮ ፡ ፳፫) ።



መጽብኅ፡

**መጻብኅ** ፤ **(ኀት)** ፤ ድስቶች ፤ ሳሕኖች ። ኢየጥረየ ፡ ምንተኒ ፡ ዘእንበለ ፡ አሐዱ ፡ ፀጽፍ ፡ ወሠቅ ፡ ወመጻብኅ ፡ ወምስሓግ ፡፡ ኢትኅሥሥ ፡ አጽሕልተ ፡ ወኢትልሐስ ፡ መጻብኅተ ፡፡ መጻብኅቲሃ ፡ ወአጽሕልቲሃ ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፳ ። ሢራ፴፱ ፡ ፲፱ ። ዘኍ፬ ፡ ፯) ።

**ምጽባኅ** ፤ **(ኀት)** ፤ የወጥ ፡ ቤት ፤ ምድጃ ፤ ቦታ ።

**ጸበጠ** ፤—**ጨበጠ** ፤—**ፀቢጥ ፡ ፀበጠ** ።

**ጸብይ** ፤ **ዮት** ፤ **(ጸበየ ፡ ይጸቢ ፡ ይጽቢ ። ጾበ ፤ ጸወበ ፤ ተጸውበ)** ፤ መፍሰስ ፤ መውረድ ፤ መንዣረር ፤ የጠተት ፡ የቅባት ። እስከ ፡ ተበጽለ ፡ ሥጋሁ ፡ እመለያልዩሁ ፤ ወአንጕዑ ፡ ይጸቢ ፡ እምአዕፅምቲሁ ፡ (ስንክ ፡ መጋ ፡ ፲፯) ፡ ጸወበንና ፡ ጸበተን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲየ ፡ ነው ።

—፤ መዋኘት ፤ መስፈፍ ፤ በባሕር ፡ ላይ ፡ መኼድ ፤ እየተሳቡ ፡ እየወሰወሱ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ማለፍ ፤ መንከፈፍ ። ውእቱ ፡ መስቀር ፡ ይጸቢ ፡ ዲበ ፡ ማይ ፡ (ሔኖ፹፱ ፡ ፯) ።

**ጸበ** ፤ **(ትግሬ)** ፤ ወተት ፤ ርጎ ፤ የላም ፡ ልጅ ፡ (፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፪) ።

**ጸቢል** ፤ **ሎት** ፤ **(ጸበለ ፡ ይጸብል ፡ ይጽብል ። ዘበለ)** ፤ መብነን ፤ ሐመድ ፡ ትቢያ ፡ መኾን ። ማደፍ ፡ መጕደፍ ፤ ዐቧራ ፡ መልበስ ።

**ጽቡል** ፤ **(ላን ፡ ላት ፡ ብልት)** ፤ ትቢያ ፡ የኾነ ፤ ትቢያ ፡ የመላበት ፡ የበነነበት ። ትሬእየኒ ፡ ጽቡላኒ ፡ እምቀትል ፡ (ተረ ፡ ቄር፸) ።

**ጸበል** ፤ **(ላት)** ፤ ብናኝ ፡ ትቢያ ፡ ዐቧራ ፤ ደቃቅ ፡ ዐፈር ። ንግፉ ፡ ጸበለ ፡ እገሪክሙ ፡፡ ይደፍነኪ ፡ ጸበል ፡ እምብዝኆ ፡ አፍራሲሁ ፡፡ ተናገፊ ፡ ጸበለኪ ፡ (ማቴ፲ ፡ ፲፬ ። ሕዝ፳፮ ፡ ፲ ። ኢሳ፶፪ ፡ ፪) ። በጸበለ ፡ ፈ

ንታ ፡ ጸብለየ ፡ ተጸብለየ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ሰላም ፡ እብል ፡ ኅሊናከ ፡ ጽኑየ ፤ ዘኢረስሐ ፡ ምንተ ፡ ወኢተጸብለየ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳) ።

**ጸቢዕ ፤ ዖት ፤ (ጸብዐ ፡ ይጸብዕ ፡ ይጽባዕ ። ዕብ ፡ ጻብዕ ፤ ጠምዐ) ፤** መጣት ፤ ጣትን ፡ ማንሣት ፤ መቀሰር ፤ ቅትርት ፡ ማስመሰል ፤ በጣት ፡ መያዝ ፡ መንካት ፤ ማመልከት ፡ መጠንቈል ፤ መሸኰት ። ፈሰሰን ፡ ተመልከት ።

**አጽባዕት ፤ (ዕብ ፡ ኤጽባዕ ። ሱር ፡ ጺብዓእ ። ዐረ ፡ ኢጽበዕ) ፤** ጣት ፤ የእጆችና ፡ የእግሮች ፡ ዐጽቅ ፤ ካምስቱ ፡ ክፍል ፡ አንዱ ። ወፀአት ፡ አጽባዕተ ፡ እደ ፡ ሰብእ ። ረቢ ፡ ሰገደ ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ለረቢ ፤ ለኮኑ ፡ አጽባዕት ፡ እምኒ ፡ አጽባዕት ፡ የዐቢ ፡ (ዳን፭ ፡ ፭ ። ቅኔ) ።

**አጻብዕ ፤ (ዓት) ፤** ጣቶች ፤ ዐምስቱ ፤ ዐሥሩ ፤ ወይም ፡ ካያው ፡ ኹሉ ። ኣምስቱ ፡ ጣት ፡ ስም ፡ ስም ፡ አላቸው ፤ መዠመሪያው ፡ አውራ ፤ ኹለተኛው ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ ማመልከቻ ፤ ማማተቢያና ፡ መባረኪያ ። ዕትብ ፡ ገጸከ ፡ በዘይተልዎ ፡ ሰመንኮብያ ፡ (ሲኖዶ) ። ሦስተኛው ፡ ረዥም ፡ ወይም ፡ መካከለኛ ፤ አራተኛው ፡ ተከታይ ፡ ወይም ፡ የቀለበት ፡ ጣት ፤ ዐምስተኛው ፡ ታናሽ ፡ ወይም ፡ መጨረሻ ፡ ይባላል ። የነዚህ ፡ ያምስቱ ፡ ስም ፡ ለኹሉ ፡ ይኾናል ። በላም ፡ ለአጻብዒከ ፡ አጻብዐ ፡ አዳም ፡ ዘተኬነዋ ፡ (ደራሲ) ።

**ጸቢር ፤ ሮት ፤ (ጸበረ ፡ ይጸብር ፡ ይጽብር ። ዕብ ፡ ጻበር) ፤** መርገጥ ፤ ማላቈጥ ፤ መሰብሰብ ፡ መቈለል ፤ አርባጣ ፡ ኵይሳ ፡ ማስመሰል ፤ የጭቃ ። በጸበረ ፡ ፈንታ ፡ አጽበረ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ዕርጊ ፡ ውስተ ፡ ጽቡር ፡ ወአጽብሪ ፡ በሐሠር ፡ (ናሆ፫ ፡ ፲፬) ። —፤ በግድ ፡ ማሠራት ፤ ረግጦ ፡ መግዛት ። አልቦ ፡ ዘይጸብር ፡ ጽቡረ ፡ ዘእንበለ ፡ ያእምር ፡ አባስ ፡ (ሥር ፡ ጸኰ) ።

**ተጸብረ ፤** ጨቀየ ፤ ጭቃ ፡ ኾነ ፤ ላቈጠ ፤ ተረገጠ ፤ ተቈለለ ።

**ጽቡር ፤** የጨቀየ ፤ የላቈጠ ፤ የተቦካ ፡ የተረገጠ ፤ ቍልል ። ጽቡረ ፡ ዐምዓም ። ከመ ፡ ጽቡረ ፡ ሊብሓዊ ፡ ዘይከይድ ፡ ጽቡሮ ። ዝንቱሰ ፡ ውስጡ ፡ ጽቡር ። ንዋየ ፡ ጽቡር ፡ (መዝ ፡ ፴፬ ። ኤር፴፰ ፡ ፳፰ ። ዳን፲፫ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ የካ፴) ። በጸብር ፡ ፈንታ ፡ ጽቡር ፡ ጽቡራዊ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ይህ ፡ የጠቀስነው ፡ ኹሉ ፤ ጸብር ፡ እንጂ ፡ ጽቡር ፡ አያሰኝም ። ሥጋ ፡ ጽቡራዊት ፡ (ማር ፡ ይሥ፪ ፡ ፫) ።

**ጸብር ፤** ጭቃ ፤ ዐዘባ ። ጸብረ ፡ ግንፋል ። ተኝፊስ ፡ ኀብአት ፡ ዲበ ፡ ጸብር ፡ (አዋል ። ፪ኤጥ ፡ ፪ ፡ ፳፪) ። ጸብር ፡ ባለው ፡ ጺላ ፤ ጺላሃ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ጸብር ፤ (ትግሬ ፡ ወዐረብ) ፤** ሬት ፤ ትዕግሥት ።

**ጸብረቀ ፤ (በረጸ ፤ በረቀ) ፤** ጸ ፡ ከበረጸ ፡ ወጥቶ ፡ በበረቀ ፡ ላይ ፡ ተደርቧል ፤ ዘሩ ፡ በሬቅ ፡ ነው ፤ የበሬጽንና ፡ የበሬቅን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ።

**አንጸብረቀ ፤ (አብረቀ) ፤** በቁሙ ፤ አንጸበረቀ ፤ አብረቀረቀ ፤ በራ ፡ ፈለቀ ፤ ተብለጨለጨ ፤ ቦግ ፡ ቦግ ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ አለ ፤ ታየ ፡ ተገለጠ ፤ ጽሩይ ፡ ኾነ ። ሰይፍ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ያንጸበርቅ ፡ ከመ ፡ መብረቅ ። ወለእመ ፡ አንጸብረቀ ፡ ወልታ ፡ ንጉሥ ። ዘበላዕሌሆን ፡ ያንጸበርቅ ፡ ብዑድ ፡ ሥነ ፡ ላሕይ ። ስኂን ፡ ዘያንጸበርቅ ፡ (ዮሴፍ ። ቄር ። ዘፀ፴ ፡ ፴፱) ።

**ንጽብሩቅ ፤ (እን) ፤** የጠራ ፤ የበራ ፤ ጽሩይ ። ንጽብሩቀ ፡ ሥን ፡ (አዋል) ።

**ነጸብራቅ ፤ (ቃት) ፤** ብልጭታ ፤ ብርሃን ፤ ጸዳል ፤ ጽርየት ። ያስተርኢ ፡ ብርሃኑ ፡ ወነጸብራቁ ፡ ወጸዳሉ ። ኢርኢኩ ፡ ነጸብራቀ ፡ ሐሤት ፡ ውስተ ፡ ገጽከ ፡ (አፈ ፡ ፴፫ ። ፈላስ) ።

**ጸበርት ፤—ዐጽቃም ፡ ቅጠላም ፡ ዛፍ ፤ ዝንጣፊ ፤—ፀበርት ።**

**ጸብሰ ፤—ደከመ ፡ ላላ ፤—ፀቢስ ፡ ፀብሰ ።**

**ጸቢት ፤ ቶት ፤ (ጸበተ ፡ ይጸብት ፡ ይጽብት ። ዕብ ፡ ጻበት ፤ ጠግዐ ፡ ኀብረ) ፤** መዋኘት ፤ በባሕር ፡ ላይ ፡ መሰፈፍ ፡ መንከፈፍ ፤ መሳብ ፡ መጕተት ፤ ጸበየን ፡ ተመልከት ። እስ ፡ የአምሩ ፡ ጸቢተ ። ወከነ ፡ ጽኑዐ ፡ በተጽዕኖ ፡ አፍራስ ፡ ወጸቢተ ፡ ማይ ። ይፈቅድ ፡ ኅሊናየ ፡ ይጽብት ፡ ዕመቀ ፡ አብሕርቲሁ ። ቀላይ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይደብትዎ ፡ ዓሣት ። ወዐልኩ ፡ እንዘ ፡ እጸብት ፡ ውስተ ፡ ዕመቀ ፡ ባሕር ። ባሕረ ፡ መጻሕፍት ፡ አመ ፡ ጸበተ ፡ ልሳኑ ፤ ተቃውሞቶ ፡ መዋግድ ፡ ስእኑ ፡ (ግብጽ፳ ፡ ፵፫ ። ስንክ ፡ ሐም፲፭ ። ቅዳሴ ፤ ኤጲ ። ፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፯) ።

**ጸባቲ ፤** የሚዋኝ ፤ ዋነተኛ ። የዕጨጌ ፡ ሹም ፤ ምስለኔው ፤ እንደ ፡ ራሴው ።

**ጸብት ፤** ዋና ፤ ውስወሳ ፤ የውሃ ፡ ላይ ፡ መንገድ ፡ አካኼድ ። ንዋየ ፡ ሐቅል ።

**አጽበተ ፤** አስዋኘ ፤ ቀዘፈ ። ወረውዋ ፡ ውስተ ፡ ማዕምቀ ፡ ማይ ፡ ዘቦቱ ፡ አራዊት ፤ ወጸርዋ ፡ ወአጽበትዋ ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ፡ ወአውፅእዋ ። አጽበቶ ፡ ለሐመርኒ ፡ ውስተ ፡ ቀላየ ፡ ሃይማኖት ፡ (ስንክ ፡ ግን፲፩ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ጸጊብ ፤ ቦት ፤ (ጸግበ ፤ ጸገበ ፡ ይጸግብ ፡ ይጽግብ ። ዘገበ) ፤** መጥገብ ፤ አብዝቶ ፡ መብላት ፤ መክተት ፤ መባልዕትን ፡ እንደ ፡ ሣጥን ፡ ኹኖ ፡ መዝገብ ፡ መሰብሰብ ። ዘገበን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ወንድም ፡ ነው ፤ ዘገበ ፡ የገንዘብ ፤ ጸግበ ፡ የምግብ ። ትበልዑ ፡ ወትጸግቡ ። ኢትኩኑ ፡ ከመ ፡ ዘኢይጸግብ ። ወጸገበሙ ። ዘካርያስ ፡ ጸግበ ፡ እስከ ፡ ክሣዱ ፤ ወአትረፈ ፡ ለዮሐንስ ፡ ወልዱ ፡ (ዘሌ፳፭ ፡ ፲፱ ። ሚራ፴፩ ፡ ፲፯ ። ዮሐ፮ ፡ ፲፪ ። ቅኔ) ።

—፤ መሰልቸት ፤ መጥላት ፤ መሰቀቅ ። ብላዕ ፡ በዐቅም ፡ ከመ ፡ ኢትጽገብ ፡ ወኢትቂእ ። አንብብ ፡ እንዘ ፡ ኢትጸግብ ። ከመ ፡ ኢይጽገብከ ፡ ወኢይጽላእከ ። እንተ ፡ ጸግበት ፡ ለምታ ፡ (ምሳ፳፭ ፡ ፲፯ ። ማር ፡ ይሥ፭ ፡ ፱ ። ሚራ፳፩ ፡ ፲፯ ። ሕዝ፲፮ ፡ ፵፭) ።

**አጽገበ** ፤ አጠገበ ፤ አረካ ፤ አብዝቶ ፡ ሰጠ ። ዘበላዕኩ ፡ ያጸግበኒ ። በክልኤ ፡ ዓሣ ፡ ወበኀምስቱ ፡ ኅብስት ፡ አጽገቦሙ ፡ ኢየሱስ ፡ ለኀምሳ ፡ ምእት ። ወአጽገቦሙ ፡ እምበረከቱ ፡ ለርኁባን ። አጽግቦ ፡ ለርኁብ ፡ እምእክልከ ፡ (ሉቱ ፡ ዕዝ፱ ፡ ፳፰ ። ዝማሬ ። ሉቃ፩ ፡ ፶፫ ። ኢሳ፶፰ ፡ ፲) ።

**ተጸግበ** ፤ ተጠገበ ፤ ተሰለቸ ፤ ተጠላ ፤ ተንቀፈ ።

**ጽጉብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ግብት) ፤ የጠገበ ፤ ጥጉብ ፤ ሆዱ ፡ የሞላ ፤ የረካ ። ጽጉብ ፡ አነ ፡ መሥዋዕተ ፡ ሐራጊት ። ጽጉባን ፡ ሐሊብ ። ጽጉባኒ ፡ ዘሎ ፡ ዐመፃ ። ጽግብት ፡ ነፍስ ፡ ጸቃውዐ ፡ መዓር ፡ ትሜንን ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፲፩ ። ሔኖ፺፩ ፡ ፱ ። ሮሜ፩ ፡ ፳፱ ። ምሳ፳፯ ፡ ፯) ።

—፤ የተጠገበ ፤ የተሰለቸ ፤ የተጠላ ።

**ጽጋብ** ፤ (ባት) ፤ በቁሙ ፤ ጥጋብ ፤ ምልአተ ፡ ከርሥ ። ጽጋብ ፡ ኢይምጽአኒ ። መዋዕለ ፡ ጽጋብ ። እለ ፡ ኢየአምሩ ፡ ጽጋበ ፡ (ሚራ፳፫ ፡ ፮ ። ዘፍ፵፩ ፡ ፳፱ ። ኢሳ፶፮ ፡ ፲፩) ።

**ተጻገበ** ፤ ተጣገበ ፤ ተሰላቸ ፤ ተሰለቻቸ ።

**ጸጕጕ ፤ ጎት ፤ (ጸጐጐ ፡ ይጸጕጕ ፡ ይጽጕጕ ። ዕብ ፡ ያጸእ)** ፤ ነጻ ፡ መውጣት ፤ ወይም ፡ ለልጅ ፡ መስጠት ፤ ልጅን ፡ ተከትሎ ፡ መኼድ ፤ የባሪያ ፡ የሎሌ ። ኢትጸጕጕ ፡ በከመ ፡ ይጸጕጓ ፡ አእማት ፡ (ዘፀ፳፩ ፡ ፯) ።

—፤ ከቤት ፡ ወደ ፡ ደጅ ፤ ወደ ፡ ጐዳይ ፡ ወዳደባባይ ፡ መውጣት ፤ የበሽተኛ ፡ የመልክተኛ ። መጨገግ ፤ ጭጋግ ፡ መኾን ፡ ጢስ ፡ መምሰል ።

**ጽጕ ፤ (ብ ፡ ጽጕጕ ፤ ጓት)** ፤ አፍኣ ፤ ደጅ ፤ ሸንጎ ፡ አደባባይ ፤ መተላለፊያ ። ያንሶሱ ፡ ጽጕ ። ፆዱ ፡ ጽጕ ። ወጽጕ ፡ ሀገራ ። ግዱፍ ፡ ውስተ ፡ ጽጕ ፡ ሀገር ። ውስተ ፡ ጽጕጕ ፡ ወምሥያጣት ። እንዘ ፡ የኀልፍ ፡ ጽጕጕ ፡ ረከበ ፡ ብእሴ ፡ ቅቱለ ። ወኢያስሕትከ ፡ ጽጕጕሃ ። በእንተ ፡ ፍናዋት ፡ ወጽጕጓት ፡ ወመራሕብት ፡ (ዘፀ፳፩ ፡ ፲፱ ። መክ፲፪ ፡ ፭ ። ራእ፳፩ ፡ ፳፩ ። ስንክ ፡ ጥቅ፱ ። አፈ ፡ ተ፳፰ ። ስንክ ፡ መስ፲፰ ። ሚራ፱ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

**ጽጕ** ፤ ሽጕ ፤ ሽግ ፤ ኾቦ ፤ ዳቦት ፤ የጭራሮ ፡ የቅጥቅጥ ፤ ፋኖስ ፤ እውጭ ፡ ቢወጡ ፡ የሚያበሩት ። አዘዘ ፡ ያውዕይዎሙ ፡ በመኀትወ ፡ ጽጕ ፤ ወይሕርር ፡ ሥጋሆሙ ። ወሖሩ ፡ ህየ ፡ በመኀትወ ፡ ጽጕ ፡ (መቃ ፡ ገ፪ ። ዮሐ፲፰ ፡ ፫) ።

**ጽንጕ ፤ ጽጋግ** ፤ በቁሙ ፤ ጭጋግ ፤ ጭጕጕት ።

**ጸግዎ ፤ ዎት ፤ (ጸገወ ፡ ይጼጉ ፡ ይጸጉ ። ዕብ ፡ ዘካህ ፤ ነጽሐ ፤ ጸርየ ፤ ጸድቀ)** ፤ መስጠት ፤ መለገስ ፤ መመጽወት ፤ መቸር ፤ ማስተማር ፤ ይቅር ፡ ማለት ፤ ስርየት ፡ መስጠት ፤ የሚበቃ ፡ ዋጋ ፡ ካሳ ፡ ሳይፈልጉ ። ለዘሞተ ፡ ኢትኅድግ ፡ ጸግዎ ። ዘለነፍሱ ፡ ይጠውዕ ፡ ለመኑ ፡ ሀለዎ ፡ ይጸጉ ። እስመ ፡ ሠናየ ፡ ጸጋ ፡ እጼግወክሙ ። ጸግዉኒ ፡ ለዛቲ ፡ አበሳየ ፡ (ሚራ፯ ፡ ፴፫ ። ፲፬ ፡ ፭ ። ምሳ፬ ፡ ፪ ። ፪ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫) ።

**ጸጋዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ የሚሰጥ ፤ ሰጭ ፤ ለጪ ፤ ለጋስ ፤ ቸር ። ብእሲ ፡ ጸጋዊ ፡ ወመሓሪ ። ለጸጋዊ ፡ ይድኅርዎ ፡ በሥነ ፡ ምግባሩ ። ይኩኑ ፡ ጸጋውያነ ። እዴሁ ፡ ጸጋዊተ ፡ ምጽዋት ፡ (ኩፋ ፡ ፴፮ ። ሚራ፴፬ ፡ ፳፫ ። ፩ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ግን፳) ።

**መጸግው** ፤ ገባሪ ፡ ከማሁ ፡ (አርጋ ፡ ፬) ።

**ተጸግወ** ፤ ተሰጠ ፤ ተሰጠው ፤ ተቀበለ ፤ አገኘ ፤ ታደለ ፡ ተመጸወተ ። አእምር ፡ ዘተጸጎከ ። ከመ ፡ ትጸገዉ ፡ ሕይወተ ፡ በቃለ ፡ እግዚ ። ዘተጸጎኩ ፡ ዘንተ ፡ ዘሎ ፡ እምኔከ ። ተጸገዉ ፡ ዘንተ ፡ ወልደ ። ዘንተ ፡ ዘሎ ፡ ተጸጊዎ ፡ (ዲድ ፡ ፱ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ሠኔ፱ ። አርጋ ፡ ፬) ።

**ጽግው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ጉት)** ፤ የተሰጠ ፤ የተሰጠው ፤ ሀብታም ፤ ዕድላም ።

**ጽጋዌ** ፤ መስጠት ፤ መለጠት ፤ አሰጣጥ ፤ ስጦታ ፤ ልገሳ ፤ ሰጭነት ፤ ለጋስነት ። ኢአመዝገነ ፡ ጽጋዌነ ፡ ላዕሌሁ ። ንመውአከ ፡ በአሠንዮትነ ፡ ወንጼግወከ ፡ ጽጋዌ ። አኮ ፡ በህባዌ ፡ አላ ፡ በጽጋዌ ፡ (ዮሴፍ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ጸጋ ፤ (ጋት)** ፤ በቁሙ ፤ ሀብት ፤ መልክም ፡ ስጦታ ፤ ዕድል ፡ ፈንታ ፤ ትምርት ፤ ስርየት ፡ ይቅርታ ፤ ብዕል ፡ ክብር ፤ ሕዋስ ፤ ሞገስ ፤ የቸርነት ፡ ሥራ ፡ አለዋጋ ፡ የሚሰጥና ፡ የሚደረግ ። ምሉአ ፡ ጸጋ ፡ ወጽድቅ ። ወእምተረፈ ፡ ዚአሁ ፡ ነሣእነ ፡ ዘልነ ፡ ጸጋ ፡ በደበ ፡ ጸጋ ። ሰብአ ፡ ጸጋ ። ኢትንሥአኒ ፡ ጸጋየ ፡ ዘእንበለ ፡ እሙት ። ረከብኪ ፡ ጸጋ ። በጸጋ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ። ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ጸጋ ፡ ኢይከውን ፡ ጸጋ ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፲፬ና ፡ ፲፮ ። ዮሴፍ ። ኤፍ ፡ ፱ ። ማቴ፲ ፡ ፰ ። ሮሜ ፲፩ ፡ ፮) ።

—፤ የሃይማኖት ፡ ስም ፤ ቅባቶች ፡ ለተዋሕዶ ፡ ባህል ፡ ያወጡት ። የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሊቃውንት ፤ በተዋሕዶ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ የሱስ ፡ ዐማኑኤል ፤ ፍጹም ፡ አምላክና ፡ ፍጹም ፡ ሰብእ ። በቅባት ፡ መሲሕ ፡ ክርስቶስ ፡ ካህንና ፡ ንጉሥ ፤ ነቢይ ፡ ሐዋርያ ፡ ዳግማይ ፡ አዳም ፤ ቀዳሚ ፡ ጸጋ ፡ በኵረ ፡ ልደት ፡ ለኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ብለው ፡ በፋሲልና ፡ በዮሐንስ ፡ ዘመን ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ረቱቸው ፤ ጠላት ፡ ይቀባል ፡ ጥላት ፡ እንደሚሉት ፡ የንስጥሮስን ፡ ስም ፡ በጸጋ ፡ ሞክሼ ፡ ለመቅባት ፡ ተዋሕዶቹን ፡ ጸጎች ፡ የጸጋ ፡ ልጆች ፡ ይሏቸዋል ።

**ተጻገወ** ፤ ተሰጣጠ ፤ ተቀባበለ ፤ ተቻቻረ ፤ ይቅር ፡ ተባባለ ፡ (ራእ፲፩ ፡ ፲ ። ኤፌ፬ ፡ ፴፪ ። ቆላ፫ ፡ ፲፫) ።

**ጸግይ ፤ ዮት ፤ (ጸገየ ፡ ይጸጊ ፡ ይጽገይ ፤**

**አው ፡ ጸገየ ፡ ይጸጊ ፡ ይጽጊ)** ፤ ማበብ ፤ አበባ ፡ ማውጣት ፤ ማፍራት ። ፈረየን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ዘ ውግ ፡ ነው ። የጸገየና ፡ የጸገወ ፡ ዘራቸው ፡ አንድ ፡ ነው ፤ በወና ፡ በየ ፡ ተለያይቷል ። **ይጸጊ ፡ ክርካዕ ። አውያን ፡ ጸገዩ ። ዩ ፡ መስቀል ፡ ጸገየ ። ጽገዩ ፡ ገዳም ። ወከመ ፡ ይጸጊ ፡ ጽጌ ፡ በውስተ ፡ ጠሊ ፡ ገዳም ፡ ጽገዩ ፡** (መክ ፲፪ ፡ ፭ ። ማሕ፪ ፡ ፲፫ ። ድጓ ። ሢራ፴፱ ፡ ፲፫) ።

**ጸጋዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት)** ፤ የሚያብብ ፤ አባቢ ፤ አበባ ፡ የሚሰጥ ።

**ጽጉይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ጊት)** ፤ ያበበ ፤ አበባ ፡ የያዘ ፤ የተሸከመ ፤ አበባማ ፤ ባላበባ ። **ሕክሊል ፡ ጽጉይ ። ጽጉያን ፡ ምዑዝ ፡ ሪዳ ። ጽጉያን ፡ በረከት ። ክዳን ፡ ጽጉይ ። ትርሲተ ፡ በማይ ፡ ጽጊት ፡** (አርጋ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ መስ፴ ። ድጓ ። ፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ታኅ፯) ።

**ጽጌ ፤ (ጌያት ፡ ገያት)** ፤ አበባ ፤ የፍሬ ፡ ምል ክት ፤ ውበት ፡ ደም ፡ ግባት ፡ ያለው ። **ጽጌየኒ ፡ ፍሬ ፡ ክብር ፡ ወስብሐት ። ጽጌ ፡ ደንጐላት ። ርእዩ ፡ ጽጌ ያተ ፡ ገዳም ። አሰርጎከ ፡ ለምድር ፡ በሥነ ፡ ጽገያት ፡** (ሢራ፳፬ ፡ ፲፯ ። ማሕ፪ ፡ ፪ ። ማቴ፯ ፡ ፳፰ ። ድጓ) ። በ ጽጌ ፡ ፈንታ ፡ ጽጋይ ፡ ጽጋያት ፡ ይላል ፤ የቀድሞ ፡ ልማድ ፡ ነው ። **ድሙረ ፡ ጽጋይ ፡** (ዘፀ፳፰ ፡ ፲፱) ። ርእስ ፡ ወይም ፡ ጽፉይ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ጽጌ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ጽጌ ፡ ክርቤ ፡** (ዘፀ፴ ፡ ፳፫) ።



ጽጌ ።

—፤ ያበባ ፡ ምሳሌ ፤ መልክ ፡ ጌጥ ፤ በሽክላ ፡ በንጨት ፡ በድንጊያ ፡ በብረት ፡ የሚቀረጥና ፡ የሚነጠጥ ፤ በጥፈት ፡ በስፌት ፤ በቀለም ፡ በግብረ ፡ ምእናም ፡ የሚሠራ ። **ወ ጽጌያቲሃ ፡ እምውስቴታ ፡ ይትገበር ፡** (ዘፀ፳፭ ፡ ፴፩) ።

—፤ መፀው ፤ ወርኅ ፡ ጽጌ ፤ ዘመነ ፡ ጽጌ ፤ ፵ ፡ ቀን ፤ ከ መስከረም ፡ ፳፮ ፡ እስከ ፡ ኅዳር ፡ ፮ ። **ማሕሌተ ፡ ጽጌ ። ዋዜማ ፡ ዘጽጌ ። ሰንበት ፡ ዘጽጌያት ፡** (አዋል) ።

**አጽገየ** ፤ አሳበበ ፤ አበባ ፡ አስመሰለ ፤ ባበባ ፡ አስ ጌጠ ፤ አበባን ፡ ሣለ ፡ ቀረጠ ። **ጠበብተ ፡ እስራኤል ፡ በ ልብሰ ፡ አሮን ፡ ካህን ፡ ደርከኖ ፡ አጽገዩ ፤ ወሮማናተ ፡ ወርቅ ፡ በዐውዳ ፡ አፍረዩ ። አጽገዩ ፡ ሕዝብ ፡ መሀይ ምናን ፡** (ስንክ ፡ ጥቅ፳፭ ። ድጓ) ።

**ጸጋም ፤—ግራ ፤—ፀጋም ፤ ፀጊም ፡ ፀ ገመ ።**

**ጽግን ፤ (ዐረ ፡ ድጅን ፤ ድጅም)** ፤ ጭጋግ ፤ ጭጋጋም ፤ ጉማም ፤ የቀን ፡ ጨለማ ፡ ያለበት ።

**ጽግነት ፤ ታት)** ፤ የሌት ፡ ወፍ ፤ የሌት ፡ አውሬ ፤ ሌሊት ፡ የሚያይ ፤ የሚወጣ ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፲፱ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፲፰) ። አክይስት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ጽግነት ፡ ይላል ፤ የ ተሳሳተ ፡ ነው ። **ኮንኩ ፡ እኁሆን ፡ ለጽግነት ፡ ወቢጾን ፡ ለአዕዋፍ ፡** (ኢዮ፴ ፡ ፳፱) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ኮንኩ ፡ እኁወ ፡ ለአክይስት ፡ ወቢጾ ፡ ለአዋልደ ፡ ሰገኖ ፡ ይላል ።

**ጸግዐ ፤—ተጠጋ ፤—ፀጊዕ ፡ ፀግዐ ።**

**ጸጕሮ ፤ ሮት ፤ (ጸጐረ ፡ ይጼጕር ፡ ይጸ ጕር)** ፤ መጠ(ጨ)ጕር ፤ ጠጕር ፡ ማውጣት ፤ ጠጕራም ፡ ጭገራም ፡ መኾን ።

**ጸጓር ፤ (ራን ፡ ራት)** ፤ ጠጕራም ፤ ጭገራም ፡ ባለብዙ ፡ ጠጕር ፤ ገላው ፡ እንደንስሳ ፡ ጠጕር ፡ የመላበት ። **ወከነ ፡ አርሕያሁ ፡ ለዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ጸጓረ ፡ ዘ ለንታሁ ፡** (ስንክ ፡ ሠኔ፪ ። ዘፍ፳፯ ፡ ፳፭ ። ፳፯ ፡ ፲፩ ። ኩፋ ፡ ፲፱ ። ፬ነገ ፡ ፩ ፡ ፰) ። ጨጓራ ፤ አባ ፡ ጨጓሬ ፡ ማ ለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ጸጕር ፤ (ዐረ ፡ ሸጀር ፤ ዛፍ)** ፤ ጠጕር ፤ ጭ ገር ፤ ጭራ ፤ ጋማ ፤ ላባ ። የገላ ፡ ግር ፤ የሥጋ ፡ ቡቃያ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሥጋ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ፤ ሥዕር ትን ፡ ተመልከት ። **ጸጕረ ፡ ርእስ ። ጸጕረ ፡ ጽሕምክ ። ጸጕረ ፡ ቀራንብቲሁ ። ኵሉ ፡ በግዐ ፡ ዘጸዐዳ ፡ ጸጕሩ ። ጸጕረ ፡ ገመል ። ጸጕረ ፡ ጣዎስ ፡** (ሔኖ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፩ ። ስንክ ፡ ግንቦ፲፫ ። ዘፍ፴ ፡ ፴፪ ። ማቴ፫ ፡ ፬ ። መጽ ፡ ቄስ) ።

—፤ ጭረት ፤ የዕፀዋት ፡ ጭገር ፤ ቃጫ ፡ ናጫ ፤ ደቢ ፤ የ መሰለው ፡ ኹሉ ። **አባ ፡ ጳውሊ ፡ ኮነ ፡ ይለብስ ፡ ልብሰ ፡ ዘጸጕረ ፡ በቀልት ። አበዊነ ፡ ይለብሱ ፡ አልባሰ ፡ ጸ ጕር ፡ ዘበቀልት ፡** (ስንክ ፡ የካ፪ ። ግንቦ፲፱) ።

**ጸደይ ፤ (ዐጻደ)** ፤ ዐጨዳ ፤ ያጨዳ ፡ ወራት ፤ ዘ መን ፡ በልግ ፤ በወዲያ ፡ መከር ፡ በወዲህ ፡ በልግ ፡ የሚ ደርስበት ፤ የሚታጨድበት ፤ ወዲያውም ፡ የሚዘራበት ፡ ወርኅ ፡ ዘርዕ ። ክፍለ ፡ ዓመት ፤ ያመት ፡ ርቦ ፤ ፺፩ ፡ ቀን ፤ ወይም ፡ ፫ ፡ ወር ፤ በሐጋይና ፡ በክረምት ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ክፍል ። **ያዘንም ፡ ለክሙ ፡ ጸደየ ፡ ወመፀወ ። ዝናመ ፡ ጸደይ ፡ ወመፀው ። እግዚ ፡ ሡርዐ ፡ ጸደየ ፡ ወመፀወ ። ማእከለ ፡ ጸደይ ፡ ወዝናም ፡** (ዮኤ፪ ፡ ፳፫ ። ዘካ፲ ፡ ፲፩ ። ቀሌ ። ኩፋ ፡ ፳፱) ።

**ጸደያዊ** ፤ ወርኅ ፡ ጸደይ ፤ መጋቢት ። **በጥንተ ፡ ሐመል ፤ ዘውእቱ ፡ ዕሪና ፡ ጸደያዊ ። ዘይከውን ፡ በ ዘመነ ፡ ተዐርዮ ፡ ጸደያዊ ፡** (አቡሻ ፡ ፴፷ና ፡ ፶፫) ።

**ጸደይ ፤ (ዐረ ፡ ጻድ)** ፤ ስመ ፡ ፊደል ፤ ዐሥር ፡ ወታስዕ ፡ ጸ ። መዝመሪያውን ፡ ጸ ፡ ተመልከት ።

**ጸዴ ፤ (ዕብራ)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ጸ ። ገቦ ፤ ሕፅን ፤ ወይም ፡ ጻድቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (መዝ ፻፲፰) ።

**ጸዲል ፤ ሎት ፤ (ጸደለ ፡ ይጸድል ፡ ይጽ ድል ። ዕብ ፡ ጸሀል)** ፤ መጽደል ፤ መብራት ፤ ብርሃን ፡ መኾን ። **አስተርአየ ፡ ኮከብ ፡ ዐቢይ ፡ ዘጸዳሉ ፡ ብሩህ ፡ ጥቀ ፡ ወቍ ድስኒ ፡ ይጸድል ፡ በውእቱ ፡ ኮከብ ፡ ከመ ፡**

ጼዳለ ፡ መዓልት ። በአንተ ፡ ምንትኑ ፡ ይጼድል ፡ ገጽ ክሙ ። ትጸድል ፡ እምሥነ ፡ አርዌብ ፡ (ዮሴፍ ። አ ርጋ ፡ ፱) ።

**ጽዱል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ድልት)** ፤ የጸደለ ፤ የበራ ፤ ብሩህ ፤ ንጹሕ ፤ ጽሩይ ። ይበርህ ፡ በበርሃን ፡ ጽ ዱል ። ማኅቶት ፡ ጽዱል ። ከዋክብት ፡ ብሩሃን ፡ ወጽ ዱላን ። ጽዱላት ፡ ከመ ፡ ሱል ። ዘቲ ፡ ሜላት ፡ ጽድ ልት ፡ ሥን ፡ (ጥበ፲፯ ፡ ፲፱ ። ስንክ ፡ ጥር፲፰ ። ድጓ ። አ ርጋ ። አፈ ፡ ተ፲፱) ።

**ጼዳል ፤ (ላት)** ፤ በቁሙ ፤ ብርሃን ፤ ውጋጋን ፤ ብልጭታ ፤ ጮራ ፡ ጨረር ፤ ምዕዛር ፤ የብርሃን ፡ ቀርን ፤ ዐይን ፡ የዐይን ፡ ብሌን ። ቈባር ፡ ይእቲ ፡ ወእልባቲ ፡ ጸዳል ። ወጸዳሉኒ ፡ ከመ ፡ ብርሃን ። ጸዳለ ፡ መብ ረቅ ። ጸዳለ ፡ ብርሃን ። ጸዳለ ፡ ስብሐቲሁ ። ወይጸ ልማ ፡ እለ ፡ ይሬእያ ፡ በጸዳል ፡ (ዓሞ፰ ፡ ፳ ። ዕንባ ፡ ፲፩ ፡ ፲፩ ። ጥበ፯ ፡ ፲ ። ዕብ፩ ፡ ፫ ። አፈ ፡ ድ፰ ። መክ፲፪ ፡ ፫) ። ደመና ፤ ቀላይ ፤ ሌላውም ፡ መልካም ፡ የኾነ ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ጸዳልና ፡ ብርሃን ፡ ይባላል ። መኑ ፡ ፈጠ ሮሙ ፡ ለፀሓይ ፡ ወለወርኅ ፡ ወለከዋክብት ፡ ወለጸ ዳላት ፡ ወለብርሃናት ፡ (ሲኖ ደ) ።

**አጽደለ** ፤ አበራ ፤ አስበራ ። ጸዳለ ፡ መብረቅ ፡ ቅድሜሃ ፡ አጽደለ ። ጽርዖሬስ ፡ አንተ ፡ ታጸድል ፡ ዳበ ፡ ርእሰሙ ። ከመ ፡ ኢያጽድሉ ፡ ብርሃኖ ፡ ለወን ጌለ ፡ ስብሐት ። ወያጸድል ፡ አንተ ፡ ውስጠ ፡ ከመ ፡ ማህው ፡ (ስንክ ፡ ንሐ፲፯ ። አርጋ ፡ ፪ ። መጽ ፡ ምስ ። ራእ፳፩ ፡ ፳፩) ።

**አጽደልደለ** ፤ አብረቀረቀ ፤ አጥበረበረ ፤ በጣ ፡ በጣ ፡ አለ ። ወሓይዝተ ፡ ብርሃን ፡ ወሥን ፡ እለ ፡ ያጽ ደለድሉ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አስተጻደለ** ፤ አጕላ ፤ አስረዳ ፤ አስታወቀ ፤ የመ ነጽር ፡ የምሳሌ ። ወዝንቱ ፡ አስተጻደለ ፡ ራእየ ፡ ለ ፍና ፡ ትስብእት ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ጸደና ፤ (ናት)** ፤ ጋገ ፤ ማራም ፡ ሣር ። የበ ረሓ ፡ ንብ ፤ ገራም ፡ ጭምት ፡ የማይናደፍ ፤ ማሩና ፡ ቤቱ ፡ ከምድር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ። ጸጅ ፡ ጠጅ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። አንበጣ ፡ ወመዓረ ፡ ጸደና ፡ ተሰሴይከ ። መ ዓረ ፡ ጸደና ፡ (ድጓ ። ማር፩ ፡ ፮) ።

**ጼዴን ፤ ጼዴንያ** ፤ ጣዝማ ፤ የጣዝማ ፡ ማር ። ጼዴን ፡ ንህቡ ፤ ጼዴንያ ፡ ማሩ ።

**ጼዴንያ** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ (መቅ ፡ ታም) ።

**ጼደኒት ፤—ዘርፍ ፡ ጋኔን ፤—ጸየደኒት ።**

**ጸዲፍ ፤ ፎት ፤ (ጸድፈ ፡ ይጸድፍ ፡ ይ ጽደፍ ። ዐረ ፡ ጸደፈ ፤ ከመንገድ ፡ ወጣ)** ፤ መጽደፍ ፤ መውደቅ ፤ ገደል ፡ መግባት ፤ ከባሕር ፡ መጥ ለቅ ፤ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ተወርውሮ ፡ መውረድ ፡ መን ከባለል ። ጸድፈ ፡ እምተሥላስ ። ጸድፉ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ። ትጸድፍ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ (ግብ፰ ፡ ፴ ። ማ ር፭ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፲፬ ፡ ፲፭) ።

—፤ መጠደፍ ፤ መቀልጠፍ ፤ መቸኰል ፡ ማረበድ ፤ የ ሥራ ፡ የመንገድ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጽዱፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ድፍት)** ፤ የወደቀ ፤ ገደል ፡ የገባ ። የቸኰለ ፤ የተጣደፈ ፤ ችኩል ።

**ጽድፈት** ፤ መውደቅ ፤ አወዳደቅ ። ጥድፈያ ፤ ቅልጠፋ ፤ ችኰላ ።

**ጸድፍ ፤ (ብ ፡ አጽዳፍ)** ፤ ገደል ፡ ተራራ ፤ የተራራ ፡ ዙሪያ ። ጕድጓድ ፤ ዐዘቅት ፤ ዕርድ ፡ ምሽግ ፤ ጕራንጕር ፤ ወጥ ፡ ገብ ፤ ጕጣጕጥ ፤ ሥርጥ ፡ መንገድ ። ወይከውን ፡ ዐቢየ ፡ ጸድፈ ። ጸድፍ ፡ ዐቢይ ፡ ይከ ልለነ ። እግዚ ፡ አውደቀ ፡ ለሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ጸ ድፈ ፡ ገሃነም ። እስመ ፡ ጸድፍ ፡ ብሔሩ ፡ ወንቁዕ ፡ ምድሩ ። ጸድፍ ፡ ምፃእታ ። አጽዳፍ ፡ ወጕጻጕጽ ፡ (ዘካ፲፬ ፡ ፬ ። ሉቃ፲፮ ፡ ፳፮ ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፩ ። ኄርማ ። ሚራ ፡ ፳፭ ፡ ፵፭ ። ቅዳ ፡ አት) ።

**አጽደፈ** ፤ ገፋ ፤ ጣለ ፤ ወረወረ ፤ ገደል ፡ አገባ ፤ ሰደደ ፤ አወረደ ። ከመ ፡ ያጽድፍዎ ፡ ታሕተ ። አጽደ ፍዎሙ ፡ እምርእሰ ፡ ውእቱ ፡ ቀልቀል ። አጽደፍዎ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ። ወታጸድፎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ በመ ዐትከ ፡ (ሉቃ፬ ፡ ፳፱ ። ፪ዜና ፡ ፳፭ ፡ ፲፪ ። ሕዝ፴፩ ፡ ፲፰ ። መገ ፡ ፶፱) ።

—፤ አጠደፈ ፤ አጣደፈ ፤ አስቸኰለ ፤ አስሮጠ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጸዲቅ ፤ ቆት ፤ (ጸድቀ ፡ ይጸድቅ ፡ ይጽ ደቅ ። ዕብ ፡ ጻዳቅ ። ሱር ፡ ዝዳቅ ። ዐረ ፡ ጸ ደቀ)** ፤ መጽደቅ ፤ እውነተኛ ፡ መኾን ፤ መርታት ፤ በፍ ርድ ፡ ከሐሰት ፡ ከበደል ፡ መንጻት ፡ መጥራት ፤ መብለጥ ፡ መሻል ። ምስለ ፡ ጻድቅ ፡ ትጼድቅ ። ከመ ፡ ትጽደቅ ፡ በነቢብከ ። ለእመ ፡ ይጼድቅ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዘ ፡ ይነ ግር ። ኢይክል ፡ መዐትም ፡ ወዐማፂ ፡ ጸዲቀ ። ኢይጸ ድቅ ፡ መያሲ ፡ እምዐምፃት ። ጸድቀት ፡ ትእማር ፡ እምኔየ ፡ (መዝ ፡ ፲፯ና ፡ ፶ ። ቄር ፡ ጸላ ። ሚራ፩ ፡ ፳፱ ። ፳፮ ፡ ፳፱ ። ዘፍ፴ ፡ ፳፮) ።

—፤ መመጻደቅ ፡ ጻድቅ ፡ ነኝ ፡ ማለት ፤ በሐሰት ። መጽ ሐፍ ፡ ግን ፡ በጸድቅ ፡ ፈንታ ፡ ተጻድቀ ፡ ይላል ፤ እያስ ኛም ። እስመ ፡ ይጼድቅ ፡ ኢዮብ ፡ በቅድሜሆሙ ። ኢትጸደቅ ፡ በቅድመ ፡ እግዚ ። ትጼደቁ ፡ ለዐይነ ፡ ሰብእ ፡ (ኢዮ፴፪ ፡ ፩ ። ሢራ፯ ፡ ፭ ። ማቴ፳፫ ፡ ፳፰ ። ሉቃ፲፮ ፡ ፲፭) ።

**ጻድቅ ፤ (ቅት ፡ ቃን ፡ ቃት)** ፤ በቁሙ ፤ እውነተኛ ፤ ቅን ፤ መልካም ፤ ደግ ፡ በጎ ፤ ንጹሕ ፤ ጥሩ ። ወዮሴፍሰ ፡ ፈኃሪሃ ፡ እስመ ፡ ጻድቅ ፡ ውእቱ ፡ (ማ ቴ፩ ፡ ፲፱) ።

**ጽዱቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ድቅት)** ፤ የጸደቀ ፤ የታመነ ፡ የተረዳ ፤ የቀና ፡ የተካከለ ። ቃል ፡ ጽዱቅ ። ዘሒኮ ፡ ጽዱቀ ። ሃይማኖቱሰ ፡ ትርፍት ፡ ወጽድ ቅት ። ወመዳልዊከኒ ፡ ርቱዐ ፡ ወጽዱቀ ፡ ይኩን ፡ (ዘፀ ፳፫ ፡ ፭ ። ቄር ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፮ ። ዘዳ፳፭ ፡ ፲፭) ።

**ጽዱቃዊ** ፤ እውነተኛ ፤ ርግጠኛ ፤ የበቃ ፤ አ መን ። ይደልወነ ፡ ንእመን ፡ ዘይትበሀል ፡ በእንተ ፡

ቅዱሳን ፡ እምዜናውያን ፡ ወጽዱቃውያን ፡ (ፊልክ ፡ ፲፰) ።

**ጽድቅ** ፤ (**ቃት**) ፤ በቁሙ ፤ እውነት ፡ ርግጥ ፤ ቅንነት ፤ የሚገባ ፡ ነገር ፤ ሕግ ፡ ትእዛዝ ፤ ባሕርያዊ ፡ መጽሐፋዊ ፡ ሥራ ። ዘየሐውር ፡ በንጹሕ ፡ ወይገብር ፡ ጽድቀ ። የዐስየኒ ፡ እግዚ ፡ በከመ ፡ ጽድቅየ ። ኢኮነ ፡ ጽድቀ ፡ በሊዕ ፡ ዘስርቅ ። ወኢያማስን ፡ ምንተኒ ፡ እምአምሳለ ፡ ጽድቅ ። ኢዐቀብክሙ ፡ ዙሎ ፡ ጽድቃቲሁ ፤ አላ ፡ አግዘፍክሙ ፡ ክሣደክሙ ። ሀበኒ ፡ ለዘ አልብየ ፡ እምጽድቃቲከ ፡ አሐደ ፤ በከመ ፡ ወሀብከ ፡ ለመካን ፡ ወልደ ፡ (መዝ ፡ ፲፬ና ፡ ፲፯ ። ጦቢ ፩ ፡ ፲፫ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ኢዲ ። ባሮክ ። ስንክ ፡ ሚያ፲፯) ።

**አጽደቀ** ፤ አጸደቀ ፤ ጻድቅ ፡ አደረገ ፤ አመጻደቀ ፤ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ። እለ ፡ ያጸድቁ ፡ ርእሶሙ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ኃጥኣን ፡ እሙንቱ ፡ በቅድመ ፡ እግዚ ። እለ ፡ ያጸድቅዎ ፡ ለኃጥእ ። ወአጽድቁ ፡ ግፉዐ ፡ ወምስኪነ ፡ (ቀሌ ። ኢሳ ፭ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፹፩) ።


—፤ አጸና ፤ አስረዳ ። ያጸድቅ ፡ ምክረ ፡ መላእክቲሁ ። ለአጽድቆተ ፡ ቃል ፡ ዘንቤ ፡ (ኢሳ፵፬ ፡ ፳፮ ። አቡሻ ፡ ፴፩) ።

**መጽደቂ** ፤ የሚያጸድቅ ፤ አጽዳቂ ። ሃይማኖት ፡ ክርስቶስ ፡ መጽደቂ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳፪) ።

**ጽህቀ ፤—ወደደ ፤—ጽሒቅ ፡ ጽሕቀ ።**

**ጸሀር** ፤ (**ዕብራ**) ፤ ፋካ ፤ ላዕላይ ፡ መስኮት ፤ አፈ ፡ ድስት ፡ የኾነ ፤ ሞራ ፡ ጨረር ፤ ጸዳል ፡ ምዕዘር ፤ የፀሓይ ፡ እግር ፡ የሚገባበት ።

**ጽህርት** ፤ ድስት ፤ ምንቸት ፤ አፍላል ፡ አፈ ፡ ነብ ፤ ማብሰያ ፤ መቀቀያ ። ይእቲ ፡ ጽህርት ፡ ወንሕነ ፡ ሥጋ ። ሰከትት ፡ ጽህርተ ። ታሕተ ፡ ጽህርት ፡ (ሕዝ ፲፩ ፡ ፫ ። ፳፬ ፡ ፫ ። መክ፯ ፡ ፯) ።



ጽህርት ፡

**ጽህርታት** ፤ **ጻህራት** ፤ ድስቶች ፤ ምንቸቶች ። ጽህርታት ፡ ወኩከማት ። ኩሳዝሳት ፡ ወጽህርታት ። ወይከውና ፡ ጻህራት ፡ ከመ ፡ ከራት ፡ (ኤር፶፪ ፡ ፲፰ ። ማር፯ ፡ ፰ ። ዘካ፲፬ ፡ ፳) ።

**ጻው** ፤ (**ዕብራ**) ፤ ክፉ ፡ ልማድ ፤ ትእዛዝ ፤ የኢዮርብዓም ፡ ሕግ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጻው ፡ ፈንታ ፡ ጻሕው ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ባለብሉዮችም ፡ የዓሣ ፡ ዐጥንት ፤ ምስል ፤ ጥርኝ ፡ ይሉታል ። አኀዘ ፡ ይትልዉ ፡ ጻሕወ ፡ (ሆሴ፭ ፡ ፲፩) ።

**ጹው ፤—ጨው ፤—ጻየው ።**

**ጻውአ ፤—ጠራ ፤—ጻውዖ ፡ ጻውዐ ።**

**ጸዊብ** ፤ **ቦት** ፤ (**ጸበ** ፤ **ጸወበ** ፡ **ይጸውብ** ፡ **ይጹብ** ። **ጸበየ** ፡ **አጽበየ**) ፤ ማፍሰስ ፡ መገልበጥ ፤ ማንቀር ፡ መጨለጥ ፤ ባዶ ፡ ደረቅ ፡ ማድረግ ። ትሰትዩ ፡ ወትጸውቢዮ ፡ (ሕዝ፳፫ ፡ ፴፬) ።

**ጸውብ** ፤ (**ባት**) ፤ እድፍ ፤ እንቃሬ ፤ እዝጎ ፤ መግል ። ወትሰቀይ ፡ ምድር ፡ እምነ ፡ ጸውብከ ፡ (ሕዝ፴፫ ፡ ፮ ። ኢዮ፯ ፡ ፭) ።

**ጸጥ** ፤ (**ዕብ** ፡ **ጢጥ** ። **ዐረ** ፡ **ፀዊጠት**) ፤ ጭቃ ፤ ዐዘባ ። አንቃህክ ፡ ቢድነ ፡ ሐራውያ ፡ እምጸጥ ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፭) ።

**ጸላዕ** ፤ (**ዐረ** ፡ **ጹላዕ** ። **ዕብ** ፡ **ሴላዕ**) ፤ ቋጥኝ ፤ ገምቦ ፤ ታላቅ ፡ ደንጊያ ፤ መርግ ፤ ዕርድ ፡ ገደል ፡ ዋሻ ። ኩኵሕን ፡ ተመልከት ። ከመ ፡ እብነ ፡ ጸላዐ ። ጸላዐኒ ፡ ሐሠረ ፡ ይመስሎ ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፲፭ ። ሚራ፳፪ ፡ ፳ ። ድጓ) ።

**ጸላዕት** ፤ **ጸዋልዕት** ፤ ዋሾች ፤ ዋሻዎች ፡ ቋጥኞች ፤ መርገጆች ፡ ገደሎች ። ወጸላዕት ፡ ምጕያዮን ፡ ለግሔ ። ጸላዕት ፡ ተሠጥቁ ። ዐርጉ ፡ ውስተ ፡ ጸዋልዕት ። ድምፀ ፡ ጸዋልዕት ፡ እለ ፡ ያንኰረኵሩ ፡ በግርማ ፡ (መዝ ፡ ፻፫ ። ቀሌ ። ኤር፬ ፡ ፳፱ ። ጥበ፲፯ ፡ ፲፰) ።

**ጸዊም** ፤ **ሞት** ፤ (**ጸመ** ፡ **ይጸውም** ፡ **ይጹም** ። **ዕብ** ፡ **ጻም** ። **ሱር** ፡ **ጻም** ። **ዐረ** ፡ **ጻመ**) ፤ መጾም ፤ ጥሉላትን ፡ ፈጽሞ ፡ መተው ፤ ሰውነትን ፡ ከመብል ፡ ከመጠጥ ፡ ከሌላውም ፡ ኹሉ ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ መከልከል ፡ መጠበቅ ። ቦኑ ፡ ጾመ ፡ ዘጾምክሙ ፡ ሊተ ። ጹምሰ ፡ አኮ ፡ ጸዊም ፡ እምኅብስት ፡ ወማይ ፡ ባሕቲቱ ። ይጹም ፡ ልሳንክሙ ፡ እምነገረ ፡ ውዴት ። ለእመ ፡ ኮንከ ፡ ዘኢትክል ፡ ትጹም ፡ እመባልዕት ፡ ጹም ፡ እንከ ፡ እምኀጢኣት ፡ እኪት ፡ (ዘካ፯ ፡ ፭ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፫ ። ፊልክ ፡ ፻፶፴) ።

**ጸዋሚ** ፤ (**ሚት** ፡ **ምያን** ፡ **ያት**) ፤ የሚጦም ፡ ጢሚ ፤ ጠመኛ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭ ። አቡሻ ፡ ፴፰) ።

**ጽዉም** ፤ (**ማን** ፡ **ማት** ፡ **ውምት**) ፤ የጦመ ፤ ጦመኛ ፤ ጦሙን ፤ የዋለ ። ተንሣእኩ ፡ ጽዉምየ ። ይእቲ ፡ ጽዉም ፡ ወኢይብላዕ ። እፈንዎሙ ፡ ጽዉማነ ፡ (፳ዕዝ ፡ ፰ ፡ ፳ ። ሥር ፡ ጸሐ ። ማቴ፲፭ ፡ ፴፪) ።

**ጾም** ፤ በቁሙ ፤ ጦም ፤ ምግብ ፡ መተው ። ጾምሰ ፡ ተከልእቶተ ፡ ብእሲ ፡ እመብልዕ ፡ በጊዜ ፡ ዕዉቅ ። ጾመ ፡ ረቡዕ ፡ ወጾመ ፡ ኀሙስ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭ ። ዘካ፰ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፻፰) ።

**አጽዋም** ፤ (**ማት**) ፤ ጦሞች ፤ የጦም ፡ ቀኖች ፤ ወራቶች ። አጽዋምሰ ፡ እለ ፡ ሥሩዓን ፡ ስርስቱ ፡ እሙንቱ ፤ ጾመ ፡ አርብዓ ፤ ጾመ ፡ ረቡዕ ፡ ወዐርብ ፤ ጾመ ፡ ልደት ፤ ጾመ ፡ ዕለት ፡ ዘጽባሒሁ ፡ ዕለተ ፡ ጥምቀት ፤ ጾመ ፡ አርብዓ ፤ ጾመ ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማት ። አጽዋማት ፡ (አቡሻ ፡ ፴፰ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፯) ።

**አጾመ** ፤ አጦመ ፤ አስጦመ ፤ አስከለከለ ። ያጸውም ፡ አፉሁ ፡ እምነገረ ፡ ዘርቅ ፡ (ስንክ ፡ መስ፳፰) ።

**ጾማዕት** ፤ (ታት ። ዐረ ፡ ጸውመዐት) ፤ ዋሻ ፤ በኣት ፤ የመነኰሴ ፡ ቤት ፤ የባሕታዊ ፡ በታ ። እለ ፡ ውስተ ፡ ጾማዕት ። ቦኡ ፡ ኀበ ፡ መነኮስ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በጾማዕቱ ። ጾማዕተ ፡ ባሕታዊ ። ወየኀሥሡ ፡ ተዘ ግሖ ፡ ውስተ ፡ ጾማዕታት ፤ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ውስቴታ ፡ ረባሕ ፡ (አርጋ ፡ ፮ ። ፊላስ ። ስንክ ፡ ሚያዝ ። ፊልክ ፡ ፻፶፱) ።

**ጸውኖ** ፤ ኖት ፤ (ጸወነ ፡ ይጼውን ፡ ይ ጸውን ። ዐረ ፡ ጻን ። ዕብ ፡ ጺ.ና ፤ ጋሻ) ፤ መጠበቅ ፤ ማዳን ፤ መጋረድ ፤ መተገን ፤ ማስጠጋት ፡ ጥግ ፡ ጋሻ ፡ መከታ ፡ መኾን ። ዘበመንፈስ ፡ ለአዳም ፡ ጸወኖ ፡ ወአሕየዎ ፡ (ኪዳ ። አርጋ ፡ ፫) ።

**ተጸወነ** ፤ ተጠበቀ ፤ ተጠጋ ፤ ጥግ ፡ ያዘ ፤ ተማ ጠነ ፤ የሙጥኝ ፡ አለ ፤ ደወለ ። ተጸወነ ፡ ህየ ። ተጸወኑ ፡ ውስተ ፡ በአታት ። ፈለጠ ፡ ስድስተ ፡ አህጉረ ፡ ከመ ፡ ይጸወን ፡ ውስቴቶሙ ፡ ዘሎ ፡ ዘቀተለ ፡ ነፍሰ ፡ (ዮ ሴፍ ። ኤር፴ ፡ ፳፱ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳፯) ።

—፤ ታጠረ ፡ ተቀጠረ ፤ አንባ ፡ ኾነ ። ተከበበ ፤ ዙሪያው ፡ ተያዘ ። ወተጸወነት ፡ ሀገር ፡ እስከ ፡ ዐሥርቱ ፡ ወአ ሐዱ ፡ ዓመት ፡ (፬ነገ ፡ ፳፱ ፡ ፲ ። ፳፭ ፡ ፩) ።

**ጽዉን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ውንት) ፤ የተጠ በቀ ፤ የተጠጋ ፤ የተከበበ ። ጽዉን ፡ አነ ፡ በጸሎትከ ፡ (አርጋ ፡ ፱) ።

**ጸወን** ፤ (ናት) ፤ ጥግ ፤ መጠጊያ ፤ አንባ ፤ ዕ ርድ ፤ ምሽግ ፤ ገዳም ። አልቦ ፡ ጸወን ፡ ኀበ ፡ ትጸወን ፡ ኤፍሬም ። ተሰብረ ፡ ጸወንክሙ ። አረፍተ ፡ ጸወ ንከ ። ሀገረ ፡ ጸወናት ፡ (ኢሳ፲፯ ፡ ፫ ። ፳፫ ፡ ፲፩ ። ፳፭ ፡ ፲፪ ። ፪ዜና ፡ ፴፪ ፡ ፩) ። ጽዮንን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**አጽዋን** ፤ (ናት) ፤ አንቦች ፤ ዕርዶች ፤ ምሽ ጎች ። አጽዋኒሆሙ ፡ ወአድባሪሆሙ ። አጽዋናት ፡ ውስተ ፡ አድባር ። ይነሥት ፡ አጽዋናተ ፡ (ዮዲ፯ ፡ ፲ ። መሳ፮ ፡ ፪ ። ፪ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፬) ።

**ምጽዋን** ፤ (ናት) ፤ መጠጊያ ፤ ማስጠጊያ ፤ በታ ፤ ከለላ ፡ መከታ ፡ ያለው ።

**ጸውዖ** ፤ ዖት ፤ (ጸውዐ ፡ ይጼውዕ ፡ ይ ጸውዕ ። ዕብ ፡ ጻዋሕ ፤ ሾዋዕ ፡ ጮኸ) ፤ መጥ ራት ፤ ናልኝ ፡ ማለት ፤ ስምን ፡ ማውሣት ፡ እገሌ ፡ ብሎ ፤ ሐዲስ ፡ ስም ፡ መስጠት ፤ ማውጣት ፡ መሰየም ። ጸው ዕዎ ፡ ይርድአነ ። ጸውዖ ፡ ኪያሁ ፡ ውስተ ፡ በዓል ። ወዘርኡ ፡ ዘጸውዐ ፡ ስመ ፡ እግዚ ፡ ይድኅን ። ወበከመ ፡ ጸውዖሙ ፡ ከማሁ ፡ ኮነ ፡ ስሞሙ ። ወጸውዐ ፡ ስሞ ፡ ሮቤል ፡ (ዮዲ፰ ፡ ፲፯ ። ጦቢ፱ ፡ ፪ ። ግብ፪ ፡ ፳፩ ። ኩፋ ፡ ፫ና ፡ ፳፰) ።

**ጸዋዒ** ፤ የሚጠራ ፤ ጠሪ ፤ ለፋፊ ፤ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ። ጳውሎስ ፡ ጸዋዒ ። እኩን ፡ ጸዋዔ ፡ ሰብአ ፡ ውስተ ፡ አ ምልኮትከ ፡ (ቅዳ ። ዮሴፍ) ።

**ተጸውዐ** ፤ ተጠራ ፤ ታደመ ፤ ተባለ ። ዘሎቱ ፡ ተጸዋዕከ ። ብፁዓን ፡ እለ ፡ ተጸውዑ ፡ ውስተ ፡ በዓለ ፡ መርዓ ፡ በግዑ ። ተጸውዐ ፡ ስሞሙ ፡ ዐረብ ፡ (፩ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ። ራእ፲፱ ፡ ፱ ። ኩፋ ፡ ፳) ።

**ጽዉዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ውዕት) ፤ የተጠራ ፤ የተሰየመ ፤ የታደመ ፡ (ሮሜ፩ ፡ ፯ ። ይሁ ፡ ፩ ። ማቴ፳ ፡ ፲፮) ።

**ጽውዓ** ፤ ጥሪ ፤ አጠራር ። ለጽውዓ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ (ፊልጵ፫ ፡ ፲፬) ።

**ጽዋዔ** ፤ መጥራት ፤ መጠራት ፤ አጠራር ፤ ጥሪ ፤ ጩኸት ፤ ስም ። ዘጽሑፍ ፡ በእንተ ፡ ጽዋዔ ፡ አሕዛብ ። ኀደጉ ፡ ጽዋዔሆሙ ። በካዕብ ፡ ጽዋዔ ። በጽዋዔሁ ፡ ቅዱስ ። ሠለስቱ ፡ ጽዋዔ ፤ ክርስቲያን ፤ መሲሓው ያን ፤ ናዝራውያን ፡ (ዲድ ፡ ፴፫ ። ፊልክ ፡ ፳ ። ግንዘ ። ፪ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፱ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ጸውዕ** ፤ (ዓት) ፤ አስማት ፤ የጥንቈላ ፡ ብረት ፡ ሻረተኞች ፡ የሚደግሙትና ፡ የሚመቱት ፡ ሙታንን ፡ ሰይጣንን ፡ የሚጠሩበት ፤ አስጠንቋዮችም ፡ የሚያምኑበ ትና ፡ የሚያመልኩት ፤ የሚማማሉበት ፤ እንደ ፡ ሺዋ ፡ ጋላ ። ዘይገብር ፡ ሰብዐ ፡ ወመቅሰመ ፡ በጻውዕ ። እለ ፡ ያነቅሁ ፡ በጻውዕ ። እለ ፡ በጻውዕ ። ዘበጻውዕ ፡ (ቀሌ ። ኢሳ፵፬ ፡ ፳፭ ። ፰ ፡ ፲፱ ። ፲፱ ፡ ፫ ። ፵፯ ፡ ፲፩ ። ዘዳ፲፰ ፡ ፲፩) ።

**መጸውዕ** ፤ (ዓት) ፤ መረዋ ፤ ቃጭል ፤ ቱል ቱላ ፤ ነጋሪት ፤ መጥቅ ፡ ድወል ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ሰበ ፡ ይመውት ፡ ሰብእ ፡ ትገንዝ ፡ ወታመጽእ ፡ መጥቅዐ ፡ ወመጸውዐ ፡ ወማኅቶተ ፡ ሠለስተ ፡ ወታነሥእ ፡ ለበ ድን ፡ (ግንዘ) ።

**ምጽዋዕ** ፤ መጥሪያ ፤ መጮኺያ ፤ የእስላም ፡ ጥሩሚድ ። የደሴት ፡ ስም ፤ የሐማሴን ፡ በር ።

**ተጻውዐ** ፤ ተጣራ ፤ ተጠራራ ። ቀላይ ፡ ለቀ ላይ ፡ ተጻውዓ ፡ በቃለ ፡ አስራብ ፡ (መዝ ፡ ፵፩) ።

**ጽዋዕ** ፡ (ዓት) ፤ በቁሙ ፤ ጥዋ ፡ ኩባያ ፤ ዋ ንጫ ፤ የመጠጥ ፡ መሣሪያ ፤ ከሸክላ ፡ ከንጨት ፡ ከቀርን ፡ ከማዕደን ፡ የሚሠራ ፤ የተጠሩ ፡ ስዎች ፡ የሚጠጡበት ። ጽዋዐ ፡ ወይን ። ጽዋዐ ፡ ማይ ፡ ቈሪር ። ጽዋዕ ፡ ዘቍ ርባን ። ወኢይምላእ ፡ ጽዋዐ ፡ እስከ ፡ ከንፈሩ ። ጽ ዋዕ ፡ ዘብሩር ። ጽዋዓት ፡ ወርቅ ፡ (ኪዳ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ጥር፳፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፫ ። ኩፋ ፡ ፵፫ ። አስቴ፩ ፡ ፯) ።



ጽዋዕ፤

—፤ መጠጥ ፤ በጽዋ ፡ ተቀድቶ ፡ የሚሰጥ ። ኢያስትይ ዎሙ ፡ ጽዋዐ ። ወሰተይኩ ፡ ጽዋዐ ። ይኅልፍ ፡ እም ኔየ ፡ ዝንቱ ፡ ጽዋዕ ። ጽዋዐ ፡ ዘወሀበኒ ፡ አቡየ ፡ ኢየኀ ድግ ፡ ዘእንበለ ፡ እስተዪ ፡ (ኤር፲፮ ፡ ፯ ። ሱቱ ፡ ስንክ ። ማቴ፳፮ ፡ ፴፱ ። ዮሐ፲፰ ፡ ፲፩) ። ኵስን ፡ ተመልከት ።

—፤ ፍያል፤ ምንዛሀ፤ ጽንሓሕ ። የፍያልን ፡ ፍቾ ፡ ተመልከት ። ጉጠታተ ፡ ሥጋ ፡ ወጽዋዓተ ፡ ወርቅ ። ወገብረ ፡ ኪዐበ ፡ ጽዋዓተ ፡ ወርቅ ፡ ምእተ ። ወያጸንዑ ፡ ጽሉሙ ፡ ጽዋዓተ ፡ ዘምሉእ ፡ ዐጣነ ፡ (፩ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፲፯ ። ፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፰ ። ራእ፭ ፡ ፰ ። ፲፭ ፡ ፯ ። ፲፯ ፡ ፩) ።

**ጸዊር፤ ሮት፤ (ጾረ ፡ ይጸውር ፡ ይጹር ። ዕብ ፡ ጻዱር፤ ሳበ፤ ጐተተ)፤** መሸከም፤ አንሥቶ ፡ መያዝ፤ መውሰድ፤ ማንገት፤ ማንጠልጠል፤ ማቀፍ፤ ማዝል፤ መዕነስ ፡ ማርገዝ ፡ በሆድ ፡ መቋጠር፤ ማገገዝ ፡ መርዳት ፡ መደገፍ ፡ መጠር፤ መታገሥ ፡ መቻል፤ መወሰን ፡ ማግመር ። ይኄይስ ፡ ትጹር ፡ ሞጻ ፡ ወጼወ ። ፤ ሥእ ፡ ደዌነ ፡ ወጾረ ፡ ሕማመነ ። እስእለከ ፡ ክመ ፡ ትጹረነ ። ዘጾሮ ፡ ወዘዐነቀ ፡ በክሣዱ ። ጾሮ ፡ በሥዕርተ ፡ ርእሱ ፡ ወአብጽሖ ። ጾሮሙ ፡ በእንግድዓሁ ። ጾርኪዮ ፡ በከርሥኪ ። ጹር ፡ ርሥኣኒሁ ፡ ለአቡከ ። ኢትክል ፡ ጸዊሮቶሙ ፡ ለእኩያን ። ኢትክሉ ፡ ጸዊሮቶ ፡ ይእዜ ፡ (ሚራ፳፪ ፡ ፲፭ ። ኢሳ፶፫ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ነሐ፴ ። ልፋ ፡ ጵድ ። ዳን፲፫ ፡ ፵፭ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፲፩ ። ኤፍ ፡ ፳ ። ሚራ፫ ፡ ፲፪ ። ራእ፪ ፡ ፪ ። ዮሐ፲፮ ፡ ፲፪) ።

**ጸዋሪ፤ (ሪት፤ ርያን ፡ ያት፤ ወርት)፤** የሚጠር ፡ ጠሪ፤ ጠዋሪ ። የሚሸከም፤ ተሸካሚ፤ ያዥ፤ ወሳጅ፤ አምጭ፤ ታጋሽ ። ጸወርተ ፡ ወላትው ። ጸዋሬ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅሉ ፡ ለሔዮአብ ። ጸዋሬ ፡ ክታብ ። ጸዋሬ ፡ ዜና ። ለውንትዮስ ፡ ጸዋሬ ፡ መቅሠፍት ፡ (አርጋ ፡ ፫ ። ፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፴፱ ። አዋል ። ደራሲ ። ስንክ ፡ ሠኔ፩) ።

(ጥ) **ጸዋር፤** ዝኒ ፡ ከማሁ፤ ገባር፤ ተገዥ፤ ዜጋ ። ከነት ፡ ጸዋረ ፡ (ሰቈ፩ ፡ ፩) ።

**ጾር፤ (ብ ፡ አጽዋር)፤** ሸክም፤ ጭነት፤ ቀንበር፤ ዕዳ ፡ ግብር፤ ግፍ ፡ ጡር፤ ቀይዝ ፡ የሚኼድ ፡ የሚወሰድ ፡ ነገር ። ጾር ፡ ክቡድ ። ጾረ ፡ ክልኤቱ ፡ አብቅል ። ትገድፍ ፡ ጾሮ ፡ እምላዕሌ ፡ ክሣድከ ። አፍኒራም ፡ ላዕለ ፡ ጾር ። ኢታንሥኡ ፡ ምንተኒ ፡ ጾረ ፡ (ሚራ፳፩ ፡ ፲፭ ። ፬ነገ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ። ዘፍ፳፯ ፡ ፵ ። ፫ነገ ፡ ፳ ፡ ፳፬ ። ኤር፲፯ ፡ ፳) ።

**ጾር፤** ጦራ፤ ጨረር፤ የፀሓይ ፡ እግር፤ ቀርን ፡ ምዕዛሩ ።

**ጾር፤** በቁሙ፤ ጦር፤ ዘገር፤ ሐርበኞች ፡ የሚሸከሙት ። ኵናትን ፡ ተመልከት ።

**ጾር፤** የሰሌን ፡ ሙሽራ፤ ጦር ፡ የሚመስል ። በቀልት ፡ ወጾር ፡ (ስንክ ፡ መጋ፪) ።

**መጸር፤ መጽወርት፤ (ብ ፡ መጻውር፤ ርት)፤** መሸከሚያ፤ መቀመጫ፤ ዐልጋ፤ ወንበር፤ መሎጊያ፤ ቀላጥም፤ ዐንገት፤ ጉሮሮ፤ እጀታ፤ ማንጠልጠያ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። መጾረ ፡ ገብረ ፡ ሰርእሱ ። ወግበር ፡ መጻውርተ ፡ እምዐፀ ፡ ዘኢይነቅዝ ፡ (ማሕ፫ ፡ ፱ ። ዘፀ ፳፯ ፡ ፯ና ፡ ፯) ።

**አጾረ፤** አሸከመ፤ አሲያዘ፤ ጫነ ። ዘአጾርከኒ ፡ እጸውር ። አጾርዎ ፡ መስቀሎ ። ያጹርዎ ፡ ቀኖና ፡ ዘማውያን ፡ (፪ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ። ቅዳ ፡ ማሩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፵) ።

**ተጸውረ፤** ተያዘ፤ ተረገዘ፤ ተጫነ፤ ሸክም ፡ ኾነ ። ተጸውረ ፡ በከርሥ ። እፎ ፡ ጾርኪዮ ፡ ለዘኢይጸወር ፡ ተጸውሮ ። ውስተ ፡ ዕፀ ፡ ተጸዊሮ ፡ (ቅዳ ። ድጓ ። ጥበ፲፬ ፡ ፯) ።

**ጽዉር፤ (ራን ፡ ራት ፡ ውርት)፤** የተጫነ፤ የተሸከመ ። ጽዉራኒሆሙ ፡ ይረውጹ ፡ (ዮኤ፪ ፡ ፰) ።

—፤ የተያዘ፤ ሸክም ፡ የኾነ ። ቲርእየ ፡ ጽዉረ ፡ ለተወድዮ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ። እግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ጽዉር ፡ ውስተ ፡ እደዊሁ ፡ (ሃይ ፡ አበ ። አቡሻ ፡ ፵፯) ።

—፤ ጡረተኛ፤ አሮጌ ፡ ሽማግሌ፤ ድውይ ፡ በሽተኛ፤ ሙሉን ፡ የጣለ ።

**ጹረት፤** መሸከም፤ ማሸከም፤ አሸካከም፤ ሸከማ ። መጦር፤ አጠጣር፤ ጡረታ ።

**ጻውር፤ (ዕብ ፡ ጻዋር)፤** ዐንገት፤ ማንገቻ፤ መሸከሚያ ። ክሣድን ፡ ተመልከት ።

**ተጻወረ፤** ተሸካከመ፤ ተቻቻለ፤ ተነባበረ ። ተጻወሩ ፡ በበይናቲሆሙ፤ በበ ፡ አሐቲ ፡ እብን ፡ ጾሩ ፡ ኅቡረ ፡ (ሂርማ) ።

**ጻወሰ፤—ለመሸ፤—ፆሰ ፡ ፀወሰ ።**

**ጸዊት፤ ቶት፤ (ጸተ፤ ጸወተ ፡ ይጸውት ፡ ይጹት ። ዕብ ፡ ጹቱት)፤** መሮጥ፤ መልፈፍ ፡ መንገር ፡ ማስታወቅ፤ ያዋጅ ፡ የትእዛዝ ። መማለድ ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ ማለት፤ የልመና ። መሣቅ ፡ መጫወት፤ መንጫጫት፤ የብዙ ፡ ሰው ። መሰደር፤ መደርደር፤ በተራ ፡ ማምር፤ መናገር ። (ተረት)፤ ነገር ፡ በተርታ፤ ሥጋ ፡ በገበታ ፡

**ጸውት፤ (ብ ፡ ጸዋት፤ አጽዋት)፤** ጩኸት፤ ልመና፤ ምልጃ፤ ጸሎት፤ መስተብቍዕ ። ወትብል ፡ ጸዋተ፤ ሠለስቱ ፡ ጸዋት፤ በእንተ ፡ እለ ፡ ይነግዱ፤ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ፤ በእንተ ፡ ሰላም ፡ ወጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ (ግንዘ) ።

—፤ ጨዎት፤ ጨዎታ፤ ጫጫታ፤ የብዙ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጸታ፤ (ታት፤ ጸዋትው ። ሱር ፡ ጺውታ፤ ጺውታ፤ ኅብረት ፡ አንድነት ፡ ጉባኤ)፤** ተራ፤ ረድፍ፤ ክፍል፤ ማዕርግ፤ ዐይነት፤ ስልት፤ ወገን፤ ነገድ፤ የቅዳሴ ፡ ጸሎት፤ ኀዝ፤ ከሚ ፡ መጠን ፡ እስከ ፡ አኰቴተ ፡ ቍርባን ፡ ያለው ። አርባዕቱ ፡ ጸታሁ፤ ጸታ ፡ ዘእብን ። ወጸታ ፡ ላእካኒሁ ። ጸዋትወ ፡ መሬር ፡ ወጣዕም ። እፈቱ ፡ አስማዕ ፡ ዐሠርተ ፡ አውታረ ፡ ዜማሆሙ ፡ ወጸታሆሙ ። በበ ፡ ጸታት ፡ ፍሉጣት ። ጸዋትዊሆሙ ፡ ለመላእክት ። ጸዋትወ ፡ ቅዳሴ ፡ (ዘፀ ፳፰ ፡ ፲፯—፳ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፬ ። ደራሲ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ፡ ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ። አርጋ ፡ ፬ ። አዋል) ።

**ምጽዋት፤ ምጹት፤ (ታት ። ዕብ ፡ ሚጽዋህ፤ ትእዛዝ ። ሱር ፡ ማጡታእ፤ ልመና ፡ ፍላጎት)፤** በቁሙ ፡ ምጢት ፡ ለድኻ ፡ ለግዜር ፡ የሚሰጥ ፡ ገንዘብ ፡ ስጦታ፤ በብሉይ ፡ በሐዲስ ፡ የታዘዘ ። ሌላ

ውም ፡ የፍቅርና ፡ የርኅራኄ ፡ ሥራ ፡ ምክርን ፡ ርዳታን ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡ የግዜር ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ምጺት ፡ ይባላል ። ስኢለ ፡ ምጽዋት ፡፡ ውሂበ ፡ ምጽዋት ፡፡ ብዙኀ ፡ ምጺተ ፡ ገበርኩ ፡ ለአኀውየ ፡፡ ሚጡ ፡ ንዋየ ከሙ ፡ ወሀቡ ፡ ምጺተ ፡ ለነዳያን ፤ ደዮ ፡ ውስተ ፡ ሙዳየ ፡ ምጽዋት ፡፡ ምጺታት ፡ (ሚራ፴፭ ፡ ፳፭ ። ፴፯ ፡ ፲፭ ። ጦቢ፭ ፡ ፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፯ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፱) ።

**መጽወተ** ፤ (መጠወ) ፤ ሰጠ ፡ መጠ(ጸ)ወተ ፤ ትእዛዝ ፡ ፈጸመ ። ይምሕሩ ፡ ወይመጽውቱ ፡፡ ኢትበል ፡ እምፈተውኩ ፡ ይኩን ፡ ሊተ ፡ ብዙኀ ፡ ንዋይ ፡ ከመ ፡ እመጽውት ፡ ላዕለ ፡ ነዳያን ፡፡ ይኩን ፡ መሓሬ ፡ ወመጽዋቴ ፡ (ምሳ፲፫ ፡ ፱ ። አፈ ፡ ተ፫ ። ዲድ ፡ ፬) ።

**ተመጽወተ** ፤ ተመጠወተ ፤ ምጺት ፡ ተቀበለ ፤ ድኻው ። ይትመጸወት ፡ በአንቀጸ ፡ ሀገር ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፱ ። ቃኅ ፡ ፲) ። ተሰጠ ፡ ዐለፈ ፤ ተናኘ ፡ ቃደለ ፤ ገንዘቡ ።

**ጽሒብ** ፤ **ቦት** ፤ **(ጸሐበ ፡ ይጽሕብ ፡ ይጽሐብ ። ዐረ ፡ ጸዐበ ፤ ዐጸበ)** ፤ መድከም ፤ መታከት ፤ መስልቸት ፤ መሰቀቅ ፤ መቸገር ፡ መጨነቅ ፤ ከገዘብዘባ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፤ ንጠየን ፡ ተመልከት ።

**አጽሐበ** ፤ አደከመ ፤ አሰለቸ ፤ ዘበዘበ ፤ ነዘነዘ ፤ ስጠኝ ፡ አድርግልኝ ፡ ብሎ ። አጽሐብ ፡ ነፍስ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡፡ ምንተ ፡ አጽሐብኩከ ፡፡ ከመ ፡ ኢያጽሕብዎ ፡ ለንጉሥ ፡፡ ኢታጽሕቦ ፡ ወኢትስአሎ ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ፲ ። ሚክ፮ ፡ ፫ ። ዳንኤ ፡ ፱ ። ሚራ፴፱ ፡ ፴፭) ።


**ጻሕብ** ፤ ዝብዝባ ፤ ንዝንዝ ፤ ጭቅጭቅ ፤ ሙግት ፤ ድካም ፤ መከራ ። ተዐቀብ ፡ ከመ ፡ ኢያብእከ ፡ ውስተ ፡ ጻሕብ ፡፡ በኢፈቂዶ ፡ ጻሕብ ፡፡ ዕቀብ ፡ ሾሎ ፡ ዘአንበለ ፡ ጻሕብ ፡፡ አዐረፈ ፡ የም ፡ እምጻሕቡ ፡ (ሚራ፳፱ ፡ ፲፫ ። ፳፱ ፡ ፯ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ ታኅ፱) ።

**ጻሕብ** ፤ **(ባት ፤ አጽሕብት)** ፤ ሸክላ ፤ የሸክላ ፡ ዕቃ ፤ ከጣባ ፡ እስከ ፡ ዋዲያት ፤ ከጋን ፡ እስከ ፡ ምንቸት ፤ ከጕልላት ፡ እስከ ፡ መግላሊት ፤ በየስሙና ፡ በየይነቱ ። ፍችው ፡ ደካማ ፤ ድኩም ፡ ማለት ፡ ነው ። የማሰፊቀን ፤ ርኩት ፤ ፊምቅ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ዝቅንና ፡ ኔባልን ፡ ተመልከት ። ጻሕብ ፡ ስቁር ፡፡ ጻሕበ ፡ ማይ ፡፡ ወድቀ ፡ ጻሕብ ፡፡ ጻሕብ ፡ ዘልሕሸት ፡፡ ነሥአት ፡ ከልኤተ ፡ አጽሕብተ ፡ ወይን ፡ (ሚራ፳፭ ፡ ፲፱ ። ማር፲፱ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፴ ፡ ፲፬ ። ሕዝ፬ ፡ ፱ ። ፩ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፲፰) ።

**ጽሒድ** ፤ **ዶት** ፤ **(ጽሕደ ፡ ይጽሕድ ፡ ይጽሐድ)** ፤ መጥዳት ፤ መለዘብ ፤ መለስለስ ፤ ልሙጽ ፡ መኾን ። ወጽሕደ ፡ እምቅብዕ ፡ ነገሩ ፡ (መዝ ፡ ፶፬) ።

**ጽሑድ** ፤ **(ዳን ፡ ዳት ፡ ሕድ)** ፤ የጠዳ ፡ ጥዱ ፤ ልዝብ ፡ ልሙጽ ፤ ለስላሳ ፤ ልም ፤ ንጹሕ ። እስመ ፡ ጽሑድ ፡ ክርስቶስ ፤ ወመንክር ፡ ጽሕደተ ፡ ሥጋሁ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

(ጥድ) **ጽሕድ** ፤ በርሚል ፤ የንፎት ፡ ጋን ፤ ከለዘበ ፡ ጠርብ ፡ የሚሠራ ፤ የሸክላ ፡ ጋን ፤ ማድጋ ፡ ፈቀን ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ ጥልቅ ፡ ልሙጽ ፡ ጕድጓድ ፡ ይላል ። ጽሕድ ፡ ስቀሩርት ፡ ዘማዊት ፡፡ በጽሕድ ፡ ፈንታ ፡ ጽዕድ ፡ ይባል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ምሳ፳፫ ፡ ፳፯) ።



(ጥድ) ጽሕድ ፡

**ጽሕደት** ፤ መለዘብ ፤ አለዛዘብ ፤ ልዝብነት ፤ ልስላሴ ፤ ጥዳት ፤ ንጽሕና ። ከመ ፡ ሜላት ፡ ንጹሕ ፡ ጽሕደተ ፡ ሥጋሃ ፡ ለማርያም ፤ እስመ ፡ ኢበቊለ ፡ ውስቴታ ፡ ሦክ ፡ ኀጣውእ ፡፡ ጽሕደተ ፡ ሜላት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። አርጋ ፡ ፪) ።

**አጽሐደ** ፤ አጠዳ ፤ አለዘበ ፤ አለሰለሰ ፤ ቀባ ፤ ሸመ ። ርጢናት ፡ እለ ፡ ይፈትሓ ፡ ሕብጠተ ፡ ወያጽሕዳ ፡ ቍስላተ ፡፡ ያጽሕዳኒ ፡ እምስሕከትየ ፡፡ ወአጽሐድከ ፡ በቅብዕ ፡ ርእስየ ፡፡ አጽሕዶሙ ፡ እደዊሆሙ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ሚያ፲፯ ። መዝ ፡ ፳፪ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፵፩) ።

**ጽሕድ** ፤ **(ዳት ፤ አጽሓድ)** ፤ አርዝ ፤ ጥድ ፡ ዘግባ ፡ የጥድ ፡ የዝግባ ፡ ዐይነት ፤ የሊባኖስ ፡ ዛፍ ፤ መዐዛው ፡ የጠዳ ፤ ሲጠርቡትና ፡ ሲያለዝቡት ፡ ስለት ፡ የሚቀበል ፤ ጽሕዳት ፡ የሚስማማው ፤ የማይፍረከረክ ። አርዝን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ። ንግዘም ፡ ሰግላ ፡ ወጽሕደ ፡፡ ዕፀ ፡ ጽሕድ ፡፡ ፍሬ ፡ ጽሕድ ፡ (ኢሳ፱ ፡ ፲ ። ዘሌ፲፬ ፡ ፬ና ፡ ፮ ። መ ፡ ፈ) ።



ጽሕድ ፡

**ጻሕው** ፤—ትእዛዝ ፤—ጻው ።

**ጽሒው** ፤ **ዎት** ፤ **(ጽሕወ ፤ ጸሐወ ፡ ይጽሑ ፡ ይጽሐው ። ሱር ፡ ጻሕዋ ። ዐረ ፡ ጸሒየ ፤ ጸሓ)** ፤ መብራት ፤ መጥራት ፤ ብሩ ፡ መኾን ፤ የሰማይ ፡ የዝናም ። አንዘ ፡ ያንጠበጥብ ፡ ዝናም ፡ ወእምዝ ፡ ጽሕወ ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፳፱) ።

—፤ መንቃት ፤ መመለስ ፤ መትጋት ፤ ከንቅልፍ ፡ ከስካር ፡ ከሀኬት ። ሶበ ፡ እጽሑ ፡ እምንዋምየ ፡፡ ሶበ ፡ ጽሕወ ፡ እምወይኑ ፡፡ ንጽሐው ፡ እምንዋመ ፡ ስካር ፡፡ ጸሐዉ ፡ እምስካረ ፡ ወይን ፡፡ ወጸሐዉ ፡ ለጸሎት ፡ (አርጋ ፡ ፬ ። ዘፍ፱ ፡ ፳፬ ። መጽ ፡ ምስ ። ቄር ፡ ጸላ ። ፩ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፯) ።

**ጽሕው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሒት) ፤** የጠራ ፤ የበራ ፤ ቀ፡ልጭ ፡ ያለ ። ጽሕው ፡ ብሔር ። አየር ፡ ጽሕው ፡ ኮነ ፡ (ማቴ፲፮ ፡ ፪ ። አፈ ፡ ድ፳፱) ።

**ጸሐየ ፤ (ዕብ ፡ ጻሐሕ) ፤** ጸሐወ ፤ በራ ፤ ጠራ ፤ ጽሩይ ፡ ኾነ ፤ ጽርየቱ ፡ መልኩ ፡ የሚያሳይ ፡ እስኪ ኾን ፡ ድረስ ፤ የውሃ ፡ የሸክላ ፡ የማዕደን ። ጽሕወና ፡ ጸሐየ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ።

**ጸሓይ ፤** በቁሙ ፡ ፀሓይ ። ኹለተኛውን ፡ ፀ ፡ ተመልከት ፤ ሊጣፍ ፡ የሚገባው ፡ በዚህ ፡ ጸ ፡ ነበረ ፤ ስለ ፡ ልማድ ፡ ወደ ፡ ፀጸ ፡ ኼዷል ።

**መጽሔት ፤ (ታት ፤ መጻሕይ) ፤** መስታዮት ፡ ንጹሕ ፡ ብሩህ ፡ ጽሩይ ፤ መልኩ ፡ የሚያሳይ ፤ ማይ ፡ ሰማይ ፡ የሚመስል ። መጽሔት ፡ ዝሕልት ። መጽሔት ፡ ብርህት ። ከመ ፡ ዘይሬኢ ፡ ፍጥረተ ፡ ገጹ ፡ በመጽሔት ፡ (ያዕ ፩ ፡ ፳፫ ። ቀሌ ። ያዕ፩ ፡ ፳፫) ።



መጽሔት ፤

**ጸሐየየ ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤** አየ ፤ ተመለከተ ፤ በመስታዮት ፤ በመነጽር ። ወንጸሕየ ፡ ከሁት ፡ ገጸ ፡ ንጸሐይይ ፡ (ድ፡ን) ። በጸሐየየ ፡ ፈንታ ፡ ተጸሐየየ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ዘኢተጻሕየይኩ ፡ በመጽሔቱ ፡ ገጹ ፡ ለኢየሱስ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

—፤ ዐረመ ፤ አጠራ ፤ የፊቱን ፡ ጕድፍ ፡ የጥርሱን ፡ እድፍ ፤ የመጽሐፍን ፡ ጸያፍ ። ለየ ፤ ነቀሰ ፤ ቈረጠ ፤ ቈጠቈጠ ። ጻሕይይ ፡ ክርዳደ ። ወንጻሕይይ ፡ እምኔሃ ፡ አሥዋክ ፡ ረሲዓን ። እንዘ ፡ ትጻሕይዩ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዅሎ ፡ ምግባራተ ፡ እኩይ ፡ (ኪዳ ። ቀሌ) ።

**ተጻሕየየ ፤** ታረመ ፤ ተነቀሰ ፤ ተለየ ፤ ዐረሙ ። ታረመለት ፤ ዐረም ፡ ጠፋለት ፤ እኽሉ ፡ ተክሉ ፡ መጽሐፉ ፤ ባለመስታዮቱ ።

**ጽሕዩይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ይይት) ፤** የታረመ ፤ ዐርም ፤ እድፍ ፤ ጕድፍ ፤ ጸያፍ ፡ የሌለበት ።

**ጽሕያይ ፤** ዐረም ፤ ዐረምቻ ፤ እድፍ ፤ ጕድፍ ።

**ጸሐለ ፤ (ጸሊሕ ፡ ጸልሐ ፤ ጸልሐወ) ፤** ጣፈ ፤ ቀረጸ ፤ በደንጊያ ፡ ላይ ፤ እንዳሥሮቱ ፡ ቃላት ።

**ምጽሓል ፤ (ዕብ ፡ ዔጥ) ፤** ብርዕ ፤ አፈ ፡ ምሣር ፤ መጣፊያ ፤ መቅረጫ ። ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ ስሌዳ ፡ ይሉታል ። በምጽሓለ ፡ ኀጺን ፡ ወዐረር ፡ እመ ፡ ጸሐፎ ፡ ውስተ ፡ ኰኵሕ ፡ (ኢዮ፲፱ ፡ ፳፬) ። ብረቱን ፡ ብርዕ ፤ ርሳሱን ፡ ቀለም ፡ አድርጎ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ጸሕል ፤ (ዕብ ፡ ጸላሐት ። ሱር ፡ ጽሊሓ) ፤** በቁሙ ፤ ወጭት ፤ ሳሕን ፤ ገበቴ ፤ ጠፍጣፋ ፤ ከቢ ፡ ወይም ፡ ሞላላ ። ስጕድጓዳውም ፡ ይነገራል ። ሀበኒ ፡ በጻሕል ፡ ርእሶ ፡ ለዮሐንስ ። እሰ ፡ ተንፀቡ ፡ ጽዋዐ ፡ ወጻሕለ ። ጻሕለ ፡ ዐቢየ ፡ ዘወርቅ ፡ ንጡፍ ፡ (ማቴ፲፬ ፡ ፰ ። ፳፫ ፡ ፳፭ና ፡ ፳ ። ዮሴፍ) ።

**ጻሕላት ፤ (አጽሓል ፤ አጽሕል ፤ ልት) ፤** ጻሕሎች ። ጻሕላት ፡ ዘብሩር ። አጽሕለ ፡ ወመዳምሐ ። ወአጽሕልት ፡ ዕሥራ ፡ ወተስዐቱ ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፫ ። ዘፀ፴፰ ፡ ፲፫ ። ዕዝ፩ ፡ ፱) ።

**ጽሒም ፤ ሞት ፤ (ጸሐመ ፡ ይጽሕም ፡ ይጽሐም ። ዕብ ፡ ጻማሕ) ፤** መብቀል ፤ መውጣት ፤ ማደግ ፡ መርዘም ፤ የጣር ፡ የጠጕር ፡ የጥርስ ፡ የቀንድ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ጸምሐን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ፤ ምስጢራቸው ፡ ፩ ፡ ወገን ፡ ሲኾን ፡ ኅባባቸው ፡ በፊደል ፡ መዛወር ፡ ተለያይቷል ፤ መዛወሩም ፡ ቀሐመን ፡ ቀምሐ ፡ ብለው ፡ እንደሚገቡት ፡ ነው ።

**ጸሓም ፤ (ማን ፤ ጸሐምት) ፤** ጢማም ፤ ሪዛም ፤ ባለጢም ፤ ጢመ ፡ ረዥም ። ጸሓም ፡ ወጸጓር ፡ (ገድ ፡ ፊቅ) ።

**ጽሕም ፤ (ማት ፤ አጽሓም) ፤** በቁሙ ፤ ጢም ፤ ሪዝ ፤ ሸንጕበት ፤ ሸፋሽፍት ፤ ባገጭ ፤ በጕንጭና ፡ በጕንጭ ፤ በከናፍር ፡ ላይ ፡ የሚበቅል ፡ ጠጕር ። ሥዕርተ ፡ ጽሕምየ ። ወኮነ ፡ ጽሕሙ ፡ ነዊኀ ፤ ወይበጽሕ ፡ እስከ ፡ ኅባኔሁ ። ሊጹ ፡ ደንያ ፡ አጽሓሚሆሙ ፡ (ዕዝ፱ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ግንቦ፲፫ ። ኤር፵፰ ፡ ፴፯) ። ምስጢሩ ፤ ከደጉ ፡ በኋላ ፡ የሚሠርጽ ፡ የኋላ ፡ ቡቃያ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ጽሒፍ ፤ ፎት ፤ (ጸሐፈ ፡ ይጽሕፍ ፡ ይጽሐፍ ። ዐረ ፡ ጸሐፈ) ፤** መጣፍ ፤ ፊደልን ፡ ከብራና ፡ ከወረቀት ፡ ላይ ፡ በቀለም ፡ መሣል ፡ መንደፍ ። ስሌዳው ፡ የዕፅ ፡ የእብን ፡ የማዕደን ፡ ቢኾን ፤ ቀለም ፡ የወደቀበትን ፡ መቈፈር ፡ መፈልፈል ፡ ለማስመጥ ፤ ወይም ፡ ዙሪያውን ፡ መንቀስ ፡ መቅረጥ ፡ ለማሳበጥ ፤ እንደ ፡ ማኅተም ። ማስብ ፡ መቍጠር ፤ በፊደል ፡ በአኃዝ ። የተጣፈውን ፡ የተቈጠረውን ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፤ በልቡና ፡ ማኖር ። ጠቢባን ፡ እሙንቱ ፡ ውስተ ፡ ጽሒፍ ። ጸሐፍኩ ፡ በእዴየ ። ጸሐፎ ፡ በጽሌ ፡ ልብከ ። ወይጽሕፎሙ ፡ ሕፃን ። ጸሐፊዮ ፡ ለዝ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ዘሞተ ፡ (ሱቱ ፡ ዕዝ፲፬ ፡ ፳፮ ። ፊልሞ ፡ ፲፱ ። ምሳ፫ ፡ ፫ ። ኢሳ፲ ፡ ፲፱) ። ከተበን ፡ ተመልከት ።

**ጸሓፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ሐፍት) ፤** የሚጥፍ ፤ ጣፊ ፤ ቈጣሪ ፤ ሹም ፤ ዐዋቂ ፡ ብልኅ ፡ ጠቢብ ። ቀለመ ፡ ጸሓፊ ። ጸሓፌ ፡ ሰራዊት ። ጸሐፍተ ፡ መባእ ። ዕዝራ ፡ ጸሓፌ ፡ ሕጉ ፡ ለእግዚ ። ጸሓፌ ፡ ሀገር ። ጸሐፍተ ፡ ሀገር ፡ (መዝ ፡ ፵፬ ። ኢሳ፴፮ ፡ ፳፪ ። ዘዳ፲፮ ፡ ፲፰ ። ዕዝ፯ ፡ ፲፩ ። ማቴ፳፯ ፡ ፴፭ ። ሉቃ፲፭ ፡ ፵፭) ።

**አጽሐፈ ፤** አስጣፈ ፤ አስቈጠረ ። ለዘጸሐፎ ፡ ወለዘአጽሐፎ ፡ ለዝንቱ ፡ መጽሐፍ ። አጽሐፈ ፡ ዅሎ ፡ ብሔሮ ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ጸባሕተ ። ዘአጽሐፉ ፡ ሎቱ ፡ ትእዛዘ ፡ (ቀሌ ። ፱ንገ ፡ ፳፫ ፡ ፴፭ ። ፍ ፡ ን ፡ ፴፫ ፡ ፬) ።

**ተጽሕፈ ፤** ተጣፈ ፤ ተቈጠረ ፤ ተጣፈበት ። ተ

ጽሒፈ፡ ዐርከ፡ እግዚ፡ ውስተ፡ ጽላት፡ ሰማይ። ለተ ጽሕፎ፡ ሀገረ፡ ዳዊት፡ ዐርገ። ጽላት፡ እለ፡ ተጽሕፋ፡ በአጻብዒሁ፡ ለእግዚ፡ (ኩፋ፡ ፲፱። ስንክ፡ ታኅሣሥ። ዘጻ፴፩፡ ፲)።

**ጽሑፍ**፤ (ፋን፡ ፋት፡ ሕፍት)፤ የተጣፈ፤ የተቈጠረ። ኵሉ፡ ዘጽሑፍ፡ ውስተ፡ ዝንቱ፡ መጽሐፍ። እለ፡ ጽሑፋን፡ በበ፡ አስማቲሆሙ። ጽሑፋት፡ በዕብራይስጥ። መጽሐፍ፡ ጽሕፍት፡ (ኤር ፳፭፡ ፲፫። ፩ዜና፡ ፬፡ ፶፩። ኩፋ፡ ፲፪። ራእ፳፡ ፭)። አገባብ፡ ሲወድቅበት፤ ባይወድቅበትም፤ ቀዳማይ፡ በዝ፡ አንቀጽ፡ ይኸናል። እስመ፡ ጽሑፍ፤ በከመ፡ ጽሑፍ፡ ቢል፤ እንደ፡ ተጣፈ፤ ተጽፎ፡ እንዳለ። ጽሑፍ፡ ለእ ግዚ፡ ቅስማድ፤ ተጥኛል፡ ያስኛል።

**ጽሕፈት**፤ (ታት)፤ መጣፍ፤ (ጥጣ)መጣፍ፤ አጣጣፍ፤ ጥፈት፤ ቍጥር። ጽሕፈተ፡ ሠናየ፡ የአምር። መሃሬ፡ ጽሕፈት። ጽሕፈታተ፡ እደዊሆሙ፡ (ስንክ፡ ኅዳ፲፱። ፈ፡ መ፡ ፪፡ ፲፭። ያዕ፡ ዘእል)።

**ጻሕፍ**፤ (ፋት)፤ ጥፈት፤ ቍጥር። ወዝንቱ፡ ጻሕፍ፡ ቀዳሚ፡ (ሉቃ፪፡ ፪)።

**መጽሐፍ**፤ (ብ፡ መጻሕፍት፤ ታት)፤ በቁሙ፤ መጣፍ፤ በላዩ፡ ቃል፡ ነገር፡ የተጣፈበት፡ ብራና፤ ወረቀት፤ ንደው፡ ባንድነት፡ የታሰረና፡ የተያዘ፤ የተሰፋ፡ የተጠረዘ፤ የታፈፈ፡ የተደጕሰ፤ ቅዱስ፡ ክታብ፤ አምላካዊ፡ ንባብ፤ ብሉይ፡ ሐዲስ፤ ሌላውም፡ ኹሉ፤ ደብዳቤ፡ ሳይቀር። በከመ፡ ይቤ፡ መጽሐፍ። ቅዱሳት፡ መጻሕፍት። መጻሕፍታቲሁ፡ ወመጻሕፍተ፡ አበዊሁ። ይምህርዎሙ፡ መጽሐፈ፡ ወነገረ፡ ፋርስ። መጽሐፈ፡ መልእክት፡ (ዮሐ፳፡ ፴፩። ሮሜ፲፭፡ ፬። ኩፋ፡ ፵፭። ዳን፩፡ ፬። ግብ፱፡ ፪)።

—፤ ወግ፡ ታሪክ፤ ትምርት፡ ዕውቀት፤ ስፍር፡ ቍጥር፤ ተርትሮ፡ ደምሮ፡ የሚጥፉት። ስማ፡ ለዳቤር፡ ሀገረ፡ መጽሐፍ። አብዝኆ፡ መጻሕፍት፡ ያዘነግዕ፡ ልበ። መጽሐፈ፡ ልደቱ፡ ለኢየሱስ፡ (ኢያ፲፭፡ ፲፭። ግብ ፳፮፡ ፳፬። ማቴ፩፡ ፩)። መጽሐፍ፡ በስምና፡ በግብር፡ እየተናበበ፡ እንዳወራረዱ፡ ይፈታል፤ ምስጢሩ፡ ግን፡ ከመጽሐፍነት፡ አይወጣም።

**ምጽሓፍ**፤ (ፋት)፤ መጣፊያ፤ መቍጠሪያ፤ መማሪያ፤ የጥፈት፡ የትምርት፡ ቤት።

**ጻሕጻሕ**፤—ፍሳሽ፤ ጠፈጠፍ፤—ወጺሕ፡ ወጽሐ።

**ጽሒቅ**፤ ቆት፤ (ጽሕቀ፡ ይጽሕቅ፡ ይጽሐቅ። ዕብ፡ ጻሔቅ፤ ሣቀ። ሹቅ፤ ፈተወ)፤ መውደድ፤ መመኘት፤ መፈለግ፡ መሻት፤ ማሰብ፡ መትጋት። ፈተወን፡ ተመልከት፤ የዚህ፡ ከተማ፡ ነው። ኀሊናሁ፡ ይጽሕቅ፡ ኀበ፡ ምንዝርና። የኑሥሁ፡ ወይጽሕቁ፡ ገጾ፡ ለሰሎሞን። እጽሕቅ፡ ለከሙ፡ ዘልፈ። ኢንጽሐቅ፡ ለግብረ፡ ዓለም፡ (ስንክ፡ መስ፲፱። ፪ዜና፡ ፱፡ ፳፫። ፪ጴጥ፡ ፩፡ ፲፪። አፈ፡ ተ፳፯)።

**ጻሓቂ**፤ (ቂት፡ ቅያን፡ ያት)፤ የሚወድ፤ የሚተጋ፤ ፀሳቢ። ጻሓቂ፡ በመንፈሱ፡ ወጻማዊ፡ በገድሉ። ለባዊ፡ ወጻሓቂ። ፊልጶስ፡ ጻሓቂ፡ ውስተ፡ ትምህርት። ጻሓቅያን፡ ለሠናይ፡ (ገድ፡ ተክ። ኪዳ። ቄር። ፍ፡ ን፡ ፲)።

**ጽሑቅ**፤ (ቃን፡ ቃት፡ ሕቅት)፤ የተጋ፤ ትጉህ፤ ንቁህ። ጽሑቅ፡ ለፍቅር። ጽሕቅተ፡ ኩኒ፡ ለውሂበ፡ መፍቅድየ። ጽሕቅት፡ ለተማህሮ፡ (አርጋ፡ ድራሲ)።

**ጻሕቅ**፤ (ቃት)፤ ፈቃድ፤ ሐሳብ፤ ትጋት። ጻሕቅክሙ፡ ላዕለ፡ ሰሚዕ። ኢይትሀከይ፡ ጻሕቆሙ፡ ለእለ፡ የኀሥሡ፡ ንስሓ። ይሚጥ፡ ጻሕቃተ፡ በአስተዳልዎ፡ ዘይትፈቀድ። ጻሕቀ፡ ጽድቅ፡ (አፈ፡ ድ፴። ዲድ፡ ፮። ፍ፡ ን፡ ፳፱፡ ፪። ቄር፡ ጸላ)።

**አጽሐቀ**፤ አስመኘ፡ አስፈለገ፤ አተጋ፤ አሳሰበ፤ አሳዘነ። ለዝንቱ፡ ብእሲ፡ ኢያጽሐቀ፡ ምርዐውና፡ ዴበ፡ ምድር። ወከመ፡ ዝ፡ አጽሐቆ፡ ኅሊናሁ፡ ለሐዋርያ፡ ወአገበሮ፤ ከመ፡ ይጽሐፍ። ሳሕምኑ፡ አጽሐቆ፡ ለእግዚ። ወአጽሐቀቶ፡ ለጳውሎስ፡ (መዋሥ። አፈ፡ ወር፡ መቅ። ፩ቆሮ፡ ፱፡ ፱። ግብ፲፮፡ ፲፯)።

**ጽሕርት**፤—ድስት፤—ጽህርት።

**ጻሕስ**፤—ሽብሸባ፤—ፅሒስ፡ ፀሐሰ።

**ጽኅድ**፤—ጥድ፡ ዛፍ፤—ጽሒድ፡ ጽሕደ።

**ጻጥ**፤ (ዐረ፡ ጻህ። ዕብ፡ ሀስ)፤ በቁሙ፤ ዝም፡ ዕክም፡ ጫ፡ ማለት፤ ጸጥታ፡ ዝምታ፤ ጭታ፡ ርጋታ፤ አለድምፅና፤ አለሁከት፡ መኾን። ወጻጥ፡ ይብል፡ እስመ፡ አልቦ፡ ድምፅ፡ ወቃል፡ (ሉቱ፡ ዕዝ፯፡ ፴፱)።

—፤ ትእዛዝ፡ አንቀጽ፤ ዝም፡ በል፤ ዕሽ፡ ዕሻ፤ እርምም፤ ተፈፀም፤ ወህዳእ፡ ብሂል።

**ጸዩእ**፤ አት፤ (ጼአ፡ ይጼይእ፡ ይጼእ። ዕብ፡ ጼአ፤ ጼአህ፤ ኵስ)፤ መግማት፤ መሽተት፤ መቈነስ፤ መበስበስ፤ እስኪተላ፡ ድረስ። ወዕአን፡ ተመልከት፤ የዚህ፡ መንቲያ፡ ነው። ይጼይእ፡ ተከዚ። ጼአት፡ ምድር። ወድአ፡ ጼአ። ዘይጼይእ፡ አፋሁ። ጼአ፡ ቍስሊሁ። ሰብእ፡ እምከመ፡ ሞተ፡ ይጼይእ። እንዘ፡ ሕያው፡ ትጼይእ፡ ነፍስቱ፡ (ዘፀ፯፡ ፲፰። ፰፡ ፲። ዮሐ፲፩፡ ፴፱። መ፡ ፈ። ዮሴፍ። ኢዮ፲፱፡ ፲። ሚራ፲፡ ፱)።

**ጽዩእ**፤ (አን፡ አት፡ ይእት)፤ የገማ፡ ግም፤ ግማታም፤ የቈነሰ፤ የበሰበሰ። ጼና፡ ጽዩእ። ደመና፡ ጽዩእ፡ ወጸሊም፡ በረድ። አይሁዳዊ፡ ዕልው፡ ወጽልሕው፡ ወጽዩእ፡ አፍ፡ ወርኩስ፡ ከናፍር። ኀልቃ፡ መዋዕልየ፡ እንዘ፡ ጽዩኣት። ኵሉ፡ ሰብእ፡ ያንሶስዉ፡ ላዕለ፡ አብድንት፡ ወላዕለ፡ ጽዩእ፤ እስከ፡ በልዑ፡ ጽዩአ፡ (ግንዘ። ስንክ፡ መስ፲፰። ሲኖዶ። ኢዮ፲፯፡ ፲፯። ዮሴፍ)።

**ጺኣት፤** መግማት፤ አገማም፤ ማምነት፤ ግማት፤ ዐይን፡ ምድር፤ እድፍ፡ ርስሐት፡ ዝገት። የዐርግ፡ ጺኣቱ። ይጼኑ፡ ጺአቶሙ። መሬት፡ ወሐመድ፡ ወዕፄ፡ ወጺአት። ጼና፡ ጺአቱ። ወርቅ፡ ዘይጸሪ፡ እምጺአቱ፤ (የኤ፪፡ ፳። ኢሳ፷፬፡ ፫። መቃ። መዋሥ። ገድ፡ አዳ። ሄርማ)።

**ጺእ፤** ግማት፤ ክፉ፡ ሽታ። ምሉእነ፡ ጺእ፡ ወርኵስ፡ ወትዕግልት፤ (መቃ)።

**ጺኣት፤—መስክ፤ ጨፌ፤—ፂዖት።**

**ጼደንት፤ (ታት። ዕብ፡ ጼዳኒ፤ ተንኮለኛ፤ አጥማጅ፤ ዐዳኝ)** የዱር፡ የበረሓ፡ ዘር፤ ጋኔን። ይትራከቡ፡ ህየ፡ አጋንንት፡ ወጼደንታት፤ ወይጸርሑ፡ ኅቡረ፤ (ኢሳ፴፬፡ ፲፬ና፡ ፲፬)። በገና፡ በማስት፡ ፈንታ፡ ጼደንት፡ ይባል፤ የተሳሳተ፡ ነው፤ ባለብሎዮች፡ ግን፡ ኹሉንም፡ ሐሰይ፤ ወይም፡ ጼሊ፡ ደንጊያ፡ ልብሱ፡ ይሉታል። አዋልደ፡ ጼደንታት። ይበክዩ፡ ከመ፡ ጼደነታት፤ (ኤር፳፯፡ ፴፱። ሔኖ፺፯፡ ፪)። መጽአሞንና፡ ጽግነትን፡ ተመልከት።

**ጼው፤ (ዐረ፡ ጸዋ። ዕብ፡ ጺያ፤ ደረቅ፡ በረሓ፤ ምድረ፡ በዳ)** ጨው፤ ዐሸቦ፡ አሞሌ፤ በቈላ፡ በረሓ፡ ከውሀማ፡ መሬት፡ የሚገኝ፤ በውሃ፡ የሚቀልጥ፡ የሚሻሻ፤ መጣጣ፡ ሖምጣጣ፤ መባልዕትን፡ ኹሉ፡ የሚያጣፍጥ፤ ከኹል፡ ገብ፤ በብዙ፡ ወገን፡ የሚፈለግ። አንትሙ፡ ጼው፡ ለምድር፤ ወእመሰ፡ ጼው፡ ለስሐ፡ በምንት፡ እንከ፡ ይቄስምዎ። ወዘርዐ፡ ውስቴታ፡ ጼወ። ሐውልተ፡ ጼው። ወረሰያ፡ ለምድር፡ ጼወ። ባሕረ፡ ጼው። ገዳመ፡ ጼው፤ (ማቴ፭፡ ፲፫። ማር፱፡ ፶። መሳ፱፡ ፵፭። ዘፍ፲፱፡ ፳፮። መዝ፻፮፡ ፴፬። ኩፋ፡ ፲፫። ስንክ፡ ማግ፳፫)።

**ጼዋት፤ ጽያው፤ አጽያው፤** ጨዎች፤ ዐሸቦዎች፤ አሞሌዎች። ዐሸቦ፡ አንኳሩ፡ ብትኑ፤ አሞሌ፡ ጥርቡ፡ ምእዙኑ። (ተረት)፤ ምላጭ፡ ዐበጠ፡ በምን፡ ይበጡ፤ ጨው፡ ዐለጠ፡ በምን፡ ያጣፍጡ። የመነኰሴ፡ ሎሌ፤ የክረምት፡ አሞሌ። ሐሩ፡ ብሎ፡ ጨዋ፡ ማለት፡ ዐማርኛው፡ ከዚህ፡ ወጥቷል፤ ምስጢሩም፡ የጨው፡ ነው።

**ጸዩሐ፤ ሐት፤ (ጼሐ፡ ይጸይሕ፡ ይጺሕ። ዕብ፡ ጻሕ፤ ጠራ፤ በራ፤ ነጣ)** መጥረግ፤ ማስወገድ፤ መደልደል፤ ማስተካከል፤ ማበጀት፡ ማዘጋጀት፤ የመንገድ። ጺሑ፡ ፍኖተ፡ ቅድመ፡ ገጹ። ጺሑ፡ ፍኖተ፡ ለሕዝብ። ሴጼሐ፡ መንገደ። ዘይጸይሕ፡ ፍኖተከ፤ (ኢሳ፶፯፡ ፲፬። ፷፮፡ ፲። ኤር፲፡ ፳፫። ማር፩፡ ፪)።

**ጸያሒ፤ (ሒት፡ ሕያን፡ ያት)፤** የሚጠርግ፤ ጠራጊ። ዮሐንስ፡ ጸያሔ፡ መብእስ፤ (ድጓ)።

**ተጺሐ፤** ተጠረገ፤ ተደለደለ፤ ተበጀ፡ ተዘጋጀ፤ ተከናወነ። ትጸየሕ፡ ፍኖት፡ ራትዓን። ይጸየሕ፡ ዐውዱ፡ ለማኅፈድ። ይጸየሕ፡ ሎቱ፡ ኵሉ፡ ግብር፤ (ኤር፳፯፡ ፯። ሄርማ። አፈ፡ ተ፳፯)።

**ጽዩሕ፤ (ሓን፡ ሓት፡ ይሕት)፤** የተጠረገ፤ የተደለደለ፤ የቀና፡ ቅን፤ ትክክል። ፍኖት፡ ጽዩሕ፡ ወርሒብ። ኵሉ፡ ግብር፡ ይኩን፡ ጽዩሐ፡ በኀቤነ። እስመ፡ ትኔፎሙ፡ ጽይሕት፡ ግብር፤ (አፈ፡ ተ፲፱ና፡ ፳፯። ፊልክ፡ ፫)።

**ጽያሕ፤ (ሓት)፤** ጥርጊያ፤ አውራ፡ መንገድ፤ ታላቅ፡ ጐዳና፤ እሾኽ፡ ዕንቅፋት፡ የሌለበት። ጽያሐ፡ ንጉሥ፤ (ቄር፡ ጸላ)።

**መጽያሕት፤** ዝኒ፡ ከማሁ። ፍኖተ፡ ጽኑዓን፡ መጽያሕት። ይኩን፡ ኵሉ፡ መብእስ፡ መጽያሕተ፡ ርቱዐ። ለእኩ፡ ሐዊረ፡ መጽያሕት፤ (ምሳ፲፭፡ ፲፱። ኢሳ፵፡ ፬። ፶፱፡ ፲፱)። ፍኖትን፡ ተመልከት።

**ጺም፤ (ዕብ፡ ጺይይ፤ ጼይም)፤** የዱር፤ የበረሓ፡ አራዊት፤ በምድረ፡ በዳ፡ የሚኖሩ። ጺም፡ ምስለ፡ ኢም፤ (ኤር፶፡ ፴፱)። ጺያ፡ ጭው፡ ያለ፡ በረሓ፤ ጺይም፡ በረኻኞች። የኢምን፡ ፍች፡ በቦታው፡ ተመልከት። ባለብሎዮች፡ ግን፡ ኢምን፡ ቀኝ፤ ጺምን፡ ግራ፤ የብስ፡ ይሉታል።

**ጽዮን፤ (ዕብ፡ ጺዮን)፤** ስመ፡ ሀገር፤ የኢያውሴዎን፡ አንባ፤ ዳዊት፡ የያዛት፤ ሀገረ፡ ዳዊት። ፍችው፡ ጸወን፤ ምልክት፡ ማለት፡ ነው፡ (መዝ፡ ፪)።

**ጼንዎ፤ ዎት፤ (ጼነወ፡ ይጼኑ፤ ምዕዘ)፤** መሽተት፤ ሽታ፡ መዐዛ፡ መስጠት፤ የክፉ፡ የበጎ። ጺእ፡ ለክፉ፡ ብቻ፤ ጼነወ፡ ለኹሉ፡ ይኾናል። ይጼኑ፡ ጺአቶሙ። ሶበ፡ ጼነዎ፡ ይጐይይ። ወሶበ፡ ጼነዎ፡ ጼናሁ፡ ለዝክቱ፡ ጋኔን፡ ጐየ፤ የክፉ፤ (ጦቢ፰፡ ፲፫። ፳፡ ፫)። ዘሠናየ፡ ይጼኑ። ዘትጼኑ፡ ቆዐ። ወጼነወ፡ ጼና፡ ምዑዝ፡ ፈድፋደ። ጼነዎ፡ ጼና፡ ዕፍረት፤ (አርጋ፡ ፩። ስንክ፡ ጥቅ፳፯። ፳። የካ፳)።

**ጼናዊ፤ (ዊት፡ ውያን፡ ያት፤ ጼነውት)፤** የሚሸት፤ የሚገማ፤ ግም፡ ግማታም፤ በሽታ። ጨናዊ፡ እንዲል፤ (ትግሬ)።

**ጺንው፤ (ዋን፡ ዋት፡ ኑት፤ ንውት)፤** የሸተተ፤ ሽታው፡ የተለወጠ፤ የገማ፡ የበሸቀጠ።

**ጼና፤ (ናት)፤** ሽታ፤ መዐዛ፤ ጠረን። ጼና፡ ሕሁም፡ ወጽዩእ፡ ወፍጉግ፡ ጥቀ። ንኩን፡ ንጹሓነ፡ እምኵሉ፡ ጼና፡ ኀጢአት። ወአልቦ፡ ላዕሌሆሙ፡ ጼና፡ ዘእሳት። ጼና፡ ተይ። ጼና፡ ዕፍረት። ጥዑም፡ ጼና፡ መዐዛሁ፤ (ግንዘ። ቅዳ። ዳን፫፡ ፳፯። ሔኖ። ስንክ፡ የካ፳። መዋሥ)።

**አጼነወ፤ (ዐረ፡ ሸመ)፤** አሸተተ፤ አነፈነፈ። ወአጼነወ፡ እግዚ፡ መዐዛ፡ ሠናየ። ሊአንፎሙ፡ ለአጼንዎ፡ ነፋስ። እምርሑቅ፡ ያጼንዎ፡ ለቀትል። ፈትል፡ ሶበ፡ ያጼኑ፡ እሳተ፤ (ዘፍ፰፡ ፳፩። ጥበ፲፩፡ ፲፰። ኢዮ፴፱፡ ፳፭። መሳ፲፮፡ ፱)።

**አጼንዎ፤** ማሽተት፤ ያፍንጫ፡ ሥራ። ሕዋስን፡ ተመልከት።

**መጼንው፤** የሚያሸት፤ የሚያነፈንፍ፤ አሽታች።

**ጼናታም** ፤ ጤናዳም ፤ የሚሸት ፤ ሽታማ ፤ ባለ ሽታ ። አዛብ ፡ ወጼናታም ፡ (ሉቃ፲፩ ፡ ፵፪) ።



ጼናታም ፤

**ጸይሮ** ፤ ሮት ፤ (ጸየፈ ፡ ይጼይፍ ፡ ይጸይፍ) ፤ (ጥየ) መጸየፍ ፤ ጸያፍ ፡ መኾን ፤ መባል ፤ መንቀፍ ፤ መኰሳተፍ ። የቅኔ ፡ የነገር ፤ የጥፈት ፤ ያንደበት ። ማጸየፍ ፤ መንቀፍ ፤ ጸያፍ ፡ መያዝ ። (ጥጸ) መጸየፍ ፤ መጥላት ።

**ጸያፍ** ፤ (ፍት ፡ ፋን ፡ ፋት) ፤ በቁሙ ፤ አለስልቱ ፡ አሳገባቡ ፡ የተጣፈ ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፤ ኵልታፋ ፤ ፈ ፡ ሲሉት ፡ ለ ፡ የሚል ። ጸያፍ ፡ ወላዕላዐ ፡ ልሳን ፡ አነ ። ልሳን ፡ ጸያፍ ። ወአፉየ ፡ ሙሴ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ጸያፌ ፤ ጰራቅሊጦስ ፡ አሮን ፡ ይኩነኒ ፡ አፈ ። በሃማን ፡ ወጺያፋን ፡ (ዘፀ፬ ፡ ፲ ። ፮ ፡ ፴ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፳፬ ። ፴፪ ፡ ፬ ። ድራቢ ። ቀሌ) ።

**አጸየፈ** ፤ (አስደራጊ) ፤ አስጠየፈ ፤ አስነቀፈ ፤ ጸያፍ ፡ አሰኘ ።

**ጺድ** ፤ (ብ ፡ ጺይድ ፡ ዕብራ) ፤ አበባ ፤ ዓ ፡ ድብድብ ፡ በጣም ፡ ያልፈካ ፡ ያልፈነዳ ፤ ወይም ፡ የእሸት ፡ ወለባ ፡ ገለባ ፡ ጥርጣሪ ። አፒልያኖስ ፡ ወሀቦ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ጺጸ ፤ ወይቤሎ ፡ ገር ፡ ውስተ ፡ ገጹ ፡ ለዝንቱ ፡ ነዳይ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

**ጸይቆ** ፤ ቆት ፤ (ጸየቀ ፡ ይጼይቅ ፡ ይጸይቅ ። ዕብ ፡ ጻቅ ፤ ያጻቅ ፤ ወደየ ፡ ከዐወ) ፤ መጤቅ ፤ መበከል ፤ ጢቅ ፡ ማለት ፤ የመርገዝ ፡ የምራቅ ፤ የስድብ ፡ የሰብቅ ፤ ከባብ ፡ ከሰይጣን ፡ ከክፉ ፡ ሰው ፡ አፍ ፡ የሚወጣ ፡ (ራእ፲፪ ፡ ፲፭ ። ኢዮ፳ ፡ ፲፭ ። ፪ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፵፫ ፡ ፲፮) ።

**ጸያቂ** ፤ የሚጤቅ ፤ ጤቀኛ ፡ መርዘኛ ፤ መስተዋድይ ፤ ሰብቀኛ ፤ አጥፊ ፤ ቀጣፊ ፤ ተንኰለኛ ። እስመ ፡ ጸያቂ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ አቡሁ ፡ ዲያብሎስ ፡ (መቃ ፡ ገ፲፯ ። ሲኖዶ ። ዮሐ፰ ፡ ፵፬ ። ዘፍ፫ ፡ ፩ ። ፫ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፲፱—፳፪) ።

**ጽያቄ** ፤ መጤቅ ፤ ጢቅታ ፤ ምራቅ ፤ መርገዝ ፤ ሰብቅ ፤ ተንኰል ።

**ጸክ** ፤ ጸኮ ፤ (ብ ፡ ጸኳት) ፤ ጭን ፤ ኵልዳ ፤ ታፋ ። ነደፍዎ ፡ በሐጽ ፡ ጸኮ ። እግዚአብሔር ፡ ተጋደሎ ፡ ወአስያዘዘ ፡ ጸኮ ፡ ወሰመዮ ፡ እስራኤል ፤ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ኢይበልዑ ፡ አይሁድ ፡ ሥርዋተ ፡ ጸኰ ፡ (፩ነገ ፡ ፴፩ ፡ ፫ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ነሐሴ፳፫) ። ባለብሉዮች ፡ ማን ፡ ትክሻ ፡ ይሉታል ። ጋላም ፡ ጨኩ ፡ ነቡኤ ፡ ይላል ፡ ትክሻ ፡ ወረደኝ ፡ ሲል ፤ ጨኩና ፡ ማንቃ ፡ ይመሳሰላሉ ፤ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ቍጽን ፡ ተመልከት ።

**ጽሌ** ፤—የመጣፍ ፡ ገበታ ፤—ጸልዮ ፡ ጸለየ ።

**ጸሊእ** ፤ እት ፤ (ጸልአ ፡ ይጸልእ ፡ ይጽላእ ። ዕብ ፡ ሳኔእ ። ሱር ፡ ስናእ ። ዐረ ፡ ሸንአ) ፤ መጥላት ፤ መጠየፍ ፤ መቈጣት ፡ መንቀፍ ፤ መቀየም ፡ መናቅ ፤ ልብን ፡ ማራቅ ። ጊዜ ፡ ለጸሊእ ። አፈድፈዱ ፡ ጸሊኦቶ ። ዘትጸልእ ፡ ለርእስከ ፡ ኢትግበር ፡ ዲበ ፡ ቢጽከ ። አፍቀሩ ፡ ዘጸላእኩ ፡ አነ ። ጣዖተ ፡ ጸልአት ፡ ነፍስየ ፡ (መክ፫ ፡ ፰ ። ዘፍ፴፯ ፡ ፰ ። ዲድ ፡ ፩ ። ኢሳ፩ ፡ ፲፬ ። ኩፋ ፡ ፳፩) ። ምግባርና ፡ ጸልእ ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ። (ግጥም) ፤ ሬማውና ፡ ጠጁ ፡ መልቶ ፡ በቤታቸው ፤ እግዚያብሔር ፡ ጠላና ፡ እንጀራ ፡ ነሣቸው ።

**ጸላኢ** ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤ የሚጠላ ፡ ጠላት ፤ ምቀኛ ፤ ባለጋራ ፤ ደመኛ ። በእንተ ፡ ጸላኢ ፤ ከመ ፡ ትንሥኦ ፡ ለጸላኢ ። ጸላእያንየ ፡ ወቀናእያንየ ። ጸላእያነ ፡ እግዚ ። አፍቅሩ ፡ ጸላእተክሙ ፡ (መዝ ፡ ፰ ። ዮሴፍ ። ሮሜ፭ ፡ ፲ ። ማቴ፭ ፡ ፵፬) ።

**ጽልእ** ፤ (እት) ፤ ጥል ፡ ጠብ ፤ ቂም ። ፍጹመ ፡ ጽልአ ፡ ጸላእክዎሙ ። በልቦሙ ፡ ይሠይሙ ፡ ጽልአ ። ኅድጋ ፡ ለጽልእ ፡ (መዝ ፡ ፻፴፰ ። ኤር፱ ፡ ፰ ። ሚራ፳፰ ፡ ፮) ።

**አጽልአ** ፤ አስጠላ ፤ አስነቀፈ ፤ አስቀየመ ። አጽላእክሙኒ ፡ በኃበ ፡ ኵሉሙ ። ቦ ፡ ዘያጸልእ ፡ ርእሶ ፡ በብዝኃ ፡ ነቢብ ። ከመ ፡ ኢታጽልእ ፡ ለቢጽከ ፡ (ዘፍ፴፬ ፡ ፴ ። ሚራ፳ ፡ ፭ ። ፴፬ ፡ ፲፮) ።

**መጽልእ** ፤ የሚጠላ ፤ የሚያስጠላ ፤ ተጠይ ፡ አስጠይ ፤ አስቀያሚ ። መጽልእ ፡ ዘከመ ፡ ዝ ፡ ብእሲ ፡ (ሚራ፳ ፡ ፲፭) ።

**ተጸልአ** ፤ ተጠላ ፤ ተነቀፈ ። ርእየ ፡ ከመ ፡ ትጸላእ ፡ ልያ ። ዘተጸልኡ ፡ በኀበ ፡ እግዚ ። እስመ ፡ ዕሩየ ፡ ተጸልኡ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፰ ። ዘፍ፳፱ ፡ ፴፩ ። ምሳ፳፱ ፡ ፴፩ ። ጥበ፲፬ ፡ ፱) ።

**ጽሉእ** ፤ (ኣን ፡ ኣት ፡ ልእት) ፤ የተጠላ ፤ የተነቀፈ ፡ ንቁፍ ። ለእመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ግብር ፡ ጽሉአ ፡ እምኢገብርዎ ። ጽሉእ ፡ በኀበ ፡ እግዚ ፡ ትዕቢት ። ትከውኑ ፡ ጽሉኣነ ፡ በእንተ ፡ ስምየ ፡ (ዮሴፍ ። ሚራ፲ ፡ ፯ ። ማቴ፲ ፡ ፳፪) ።

**ጽልአት** ፤ መጥላት ፤ መጠላት ፤ አጠላል ፤ ጠላትነት ።

**ተጻልአ** ፤ ተጣላ ፤ ተጠላላ ፤ ተነቃቀፈ ። ኢትፍቅድ ፡ ተጻልኦ ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡ (ምሳ፫ ፡ ፴) ።

**አስተጻልአ** ፤ አጣላ ፤ አጠላላ ። ዘያስተጻልእ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ (ቄድር) ።

**ጸልእ** ፤—ቍስል ፤—ጸሊዕ ፡ ጸልዐ ።

**ጸላእ** ፤—ቋጥኝ ፤—ጸውልዐ ፤ ጸላዕ ።

**ጸሊብ፤ቦት፤(ጸለበ፡ይጸልብ፡ይጽልብ፤ዐረብ። ሱር፡ጸላብ። ዕብ፡ታላህ)፤** መስቀል፤ማንጠልጠል፤በችንካር፡በሐብል፡የፈያት፡የንዋያት። ኤስታሊንና፡ስቀለን፡ተመልከት።

**ተጸልበ፤** ተሰቀለ፤ተንጠለጠለ፤ከምድር፡ከፍ፡አለ። ተጸልበ፡ምስሊ፡ዡሉ፡ቤቱ። ኅበ፡ተጸልበ፡እግዚእሙ፡(አስቴ፳፡፲፫። ራእ፲፩፡፰)።

**ጽሉብ፤(ባን፡ባት፡ልብት)፤** የተሰቀለ፡ስቁል፤ቅንው፡ቅቱል።

**ጸልበ፤(ዐረ፡ጸሊብ)፤** መስቀል፤መሰቀያ፤መሰቀያ። ሰላም፡ለስቅለትከ፡መልዕልተ፡ቅዱስ፡ጸልበ። ሶበ፡ተረክበ፡ጸልቦሁ፡ለወልድ። ሥሉጠ፡ልደት፡ክርስቶስ፡ወመሥዋዕተ፡አብ፡ዘዲበ፡ጸልቦ፡(ስንክ፡ኅዳ፰። መጋ፳፯። ድጓ። ቅኔ)።

**መጽለብት፤(ታት)፤** ዝኒ፡ከማሁ። ከመ፡ትጠቀም፡በመጽለብትከ፡እማእከለ፡መንሱት፡(ቅዳ፡ዮሐ)።

**ጸልሀወ፤—ሸነገለ፤—ጸልሐ።**

**ጸሊው፤ዎት፤(ጸለወ፡ይጸሉ፡ይጽሉ። ጸለየ)፤** መቀቀር፤ማቀርቀር፤ማዘንበል፤የጉሮሮ። መስማት፡ማድመጥ፤መታዘዝ። ወጽልዉ፡እዝነክሙ፡ኅበ፡ቃለ፡አፉየ። ጸመመት፡እዝን፡እምጸሊዎቱ። ሶበ፡ኢጸለወ፡ትእዛዘ፡ንጉሥ፡(መዝ፸፯። አዋል። ስንክ፡ሠኔ፳፭)።

**ጽልው፤(ዋን፡ዋት፡ሉት)፤** የቀቀረ፤ያዘነበለ፤የነቃ፡የተጋ። ሰላም፡ለእእዛኒከ፡ጽልዋተ፡እለ፡ኮና፤አምኃ፡ነገር፡ዖብአ፡ለመኩንን፡ውስጥ፡ኅሊና። ኢትኩን፡ነማኤ፡ገጽ፡ወኢጽልወ፡ልብ። እኅው፡መስተጋድላን፤ጽልዋን፡ለጸሎት፡ዘወትር፡(ደራሲ። ዲድ፡፴፭። ቄድር)።

**ጸሎት፤** በቁሙ፤ጸለየ። ጸልዮና፡ጸሊው፡አንድ፡ዘር፡ናቸው፤ወና፡የ፡ተወራራሾች፡ስለ፡ኾኑ፤በጸሌት፡ፈንታ፡ጸሎት፡ይላል፤ጸለየን፡ተመልከት።

**ጸለወ፤(ዐረ፡ጸላ። ዕብ፡ጸላህ)፤** ጠበሰ፤አበሰለ፤በፍም፡በነዲድ። እዘዘ፡ይጽልውዎ፡ገጾ፡ውስተ፡እቶን፡ብሰኔ፡(ስንክ፡ሠኔ፲፱)።

**ጸላዊ፤መጽልው፤** የሚጠብስ፤ጠባሽ፡አብሳይ።

**መጽለወ፤(ዲ.ቃ፡ግ። ዐረ፡መዘለ)፤** ጠወለገ፤ደከመ፡ዛለ፤ዝልፍልፍ፡አለ። ዕፀ፡ሕይወት፡እንተ፡ኢትመጸሉ። ፈርሀት፡ንግሥት፡ወመጽለወት፡ወተንተነት። ወኢይፈቅድ፡እፈንዎሙ፡ጽዉማነ፤ከመ፡ኢይመጽልዉ፡በፍኖት፡(አርጋ። አስቴ፡፩። ማቴ፲፭። ፴፪)፡በመጽለወ፡ፈንታ፡ተመጽለወ፡ይላል፤ስሕተት፡ነው። ይትመጸለዉ፡ወይፈድፉ፡ገጾሙ። ተመጽለዉ፡በ.ድንጋጼ፡እንዘ፡ይደመሙ፡ጥቀ፡(ማቴ፳፡፲፯። ጥበ፲፯፡፫)።

**ምጽልው፤(ዋን፡ዋት፡ሉት)፤** የጠወለገ፤ጠውላጋ፤ደካማ፤ዝልፍልፍ። ማዕር፡ልምሉም፡ወእክ፡ምጽልው። ወነበርነ፡ውዱቃኒነ፡ውስተ፡ምድር፡ከመ፡እንተ፡ሰብእ፡ምጽልዋን፡(ስንክ፡የካ፲፯። ኪዳ፡፩)።

**መጽ(ጥ)ለውዝ፤** መጥረቢያ፡መዘለፊያ፤ወይም፡ወቅስምት።

**አመጽለወ፤** አጠወለገ፤አሳፈረ፤አነወረ፤ነቀፈ፤አጸየፈ፤ሰደበ። አመጽሉ፡ገጾ፡ለነማኤ፡ገጽ፡(አፈ፡ተ፳)። ይኸውም፡ስለ፡ሃይማኖት፡ነው፤ስለ፡ሌላ፡አይደለም፡(ሉቃ፳፱፡፳፭። ግብ፳፡፵፭—፵፱። ፳፫፡፲)።

**ጸልሐ፤(ዕብ፡ጸላሕ)፤** ጣሰ፤ሠንጥቆ፡ዐለፈ። አማረ፤ተዋበ፤ተከናወነ፤በመልክ፡በግብር፡በነገር።

**ጸልሐወ፤(ቀቀ፡ግ)፤** ሸነገለ፤አሞኘ፤አታለለ። ጸልሐዉ፡በልሳኖሙ፡(መዝ፡፭። ቄር)።

**ጸልሓዊ፤(ዊት፡ውያን፡ያት)፤** የሚሸነግል፤ሸንጋይ፤አታላይ፤ከዳተኛ። መጽሐፍ፡ግን፡በጸልሓዊ፡ፈንታ፡ጽልሕው፡ይላል፤የጣፊና፡የመላሽ፡ስሕተት፡ነው። ብእሲ፡ዐማፂ፡ወጽልሕው። ኃጥኣን፡ወጽልሕዋን፡(ዮሴፍ። ቀሌ)።

**ተጸልሐወ፤** ተታለለ፤ተሸነገለ፤ተሞኘ፤ተበለጠ።

**ጽልሕው፤(ዋን፡ዋት፡ሑት)፤** የተሸነገለ፤ሽንግል፤ሞኝ፤ተላላ፤ዘላላ።

**ጽልሑት፤** ሽንገላ፤ክዳት፤ተንኰል፤የጥሊቱክ፡ቃል። ዐመፃ፡ወጽልሑት። ይገብሩ፡ላዕሌሁ፡ጽልሑተ። ዘእንበለ፡ጽልሑት፡ወኢሀኬት፡(ዘካ፩፡፱። ዳን፲፩፡፳፫። ፍ፡ን፡፴)።

(ሀ) **ጸለጠ፤(ዐረ፡ጸለተ)፤** ጨለጠ፤መጠጠ፤ባዶ፡አደረገ። ወይጸልጥ፡(አዋል)።

(ለ) **ጸልዮ፤ዮት፤(ጸለየ፡ይጼሊ፡ይጸሊ። ጸለወ)፤** መጸለይ፤መለመን፤መሳል፤ማመስገን፤ከእምላክ፡ጋራ፡መነጋገር። አውተረ፡ጸልዮ። እንትሙሰ፡ሶበ፡ትጼልዩ፡ከመ፡ዝ፡በሉ። ጸሎተ፡ጸለየ፡ለእግዚ፡እንዘ፡ይብል፡(ሉቃ፳፱፡፴፱። ማቴ፮፡፱። ኩፋ፡፳፪)።

**ጸላዩ፤(ዪት፡ይያን፡ያት)፤** የሚጸልይ፤ጸላይ፤ጸሎተኛ። ፈሪሳዊ፡ጸላዩ፡ወመጸብሓዊ፡ጸላዩ፡(ፊልክ፡፴፭)።

**መጸልይ፤** ዝኒ፡ከማሁ። ረከቦ፡ጽዉመ፡ወጽምወ፡ወመጸልየ፡(ፊልክ፡፻፴፯)።

**ምጽላይ፤(ያት)፤** መጸለያ፤የጸሎት፡ቦታ፤ቤት፡ክሊያን፤ምኵራብ፤መስጊድ። ምጽላየ፡መሀይምናን። ዘይጼሊ፡ኅበ፡ምጽላየ፡አይሁድ፡ወእረሚ፡(ቅዳ፡ጎር። ቀሌ)።

**ጸሎት** ፤ (ታት ። ሱር ፡ ጽሎታ ። ዐረ ፡ ጸላዋት) ፤ በቁሙ ፤ ልመና ፤ ምስጋና ። ጸሎትሰ ፡ ተናግሮተ ፡ ሰብእ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ፡ ልዑል ፤ እንዘ ፡ የአኵቶ ፡ ወይሴብሖ ፡ ወይትአመን ፡ በእግዚእናሁ ፤ ወበተአምኖ ፡ በአበሳሁ ፡ ወኀሚሥ ፡ እምኔሁ ፡ በዘያሠምሮ ፡ ቦቱ ። ወጸሎትሰ ፡ ዘተአዘዘ ፡ ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ምእመናን ፡ በኵሉ ፡ ዕለት ፡ ሰብዐቱ ፡ ጊዜያት ። ቤትየሰ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ። ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ጸሎት ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፲፱ ። ኢሳ ፶፮ ፡ ፯ ። ጦቢ ፲፪ ፡ ፰) ።

**ጸሎት** ፤ (ዕብ ፡ ኤዶር) ፤ ስለት ፤ ብፅዐት ። ብፅዐን ፡ ተመልከት ። ጸለይኩ ፡ ጸሎተ ፡ አመ ፡ ጐየይኩ ፡ እምገጸ ፡ ዔሳው ፡ እኁየ ። ጸሎታ ፡ ዘከመ ፡ ነበበት ፡ በከናፍሪሃ ። ወሀቦ ፡ ለልዑል ፡ ጸሎተከ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፩ ። ዘኍ ፴ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፵፱) ።

**ተጸለየ** ፤ በቁሙ ፤ ተጸለየለት ፤ ተጸለየበት ፤ ተለመነ ፡ ተመሰገነ ፤ ጸሎት ፡ ምስጋና ፡ ቀረበለት ። ዘአሐደ ፡ ይሰገድ ፡ ወአሐደ ፡ ይሴባሕ ፡ ወአሐደ ፡ ይጼለይ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ጽሉይ** ፤ የተጸለየበት ፤ ጸሎት ፡ የደረሰበት ። ዘይት ፡ ጽሉይ ፤ ማየ ፡ ምንዝህ ፡ ጽሉይ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ጽሌ** ፤ (ላት) ፤ የጸሎት ፡ መጣፍ ፤ እንደ ፡ ሳታትና ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፤ እንደ ፡ ቅዳሴ ፡ ያለ ።

**ጽሌ** ፤ (ለውሕ ፤ ሰሌዳ) ፤ የመጣፍ ፡ ገበታ ፤ ከመጣፉ ፡ ጋራ ፡ በቶታን ፡ በጥራዝ ፡ በድጕስ ፡ ቈርበት ፡ የሚያያዝ ፤ ከቈርበቱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ሐረግ ፤ ሥዕል ፡ መስቀል ፡ የሚሣልበት ፡ የሚታተምበት ፤ ጌጣም ፡ ሽልምልም ።

—፤ ታቦት ፤ የመጽሐፍ ፡ ዐይነት ፤ ሐረጉና ፡ ጌጡ ፡ በመጽሐፍ ፡ ድጕስ ፡ አምሳል ፡ የሚሠራ ፤ በላዩ ፡ ስመ ፡ እምላክና ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላት ፡ ብሞር ፡ ቃል ፡ የሚጣፉበት ፤ መሥዋዕት ፡ የሚሠዋበት ፤ ከዕፅ ፡ ከእብን ፡ በረድ ፡ የሚቀረጽ ። ታቦትን ፡ ተመልከት ። ወአኀዘ ፡ በጽሌ ፡ ዘእብን ፡ ዘእንበለ ፡ ጽሌ ፡ ልብ ፡ ዘሥጋ ። ወወሀቦ ፡ ለሙሴ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ክልኤ ፡ ጽላተ ፡ ሕግ ፡ ጽላተ ፡ ዘእብን ፡ (፪ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፫ ። ዘፀ፴፩ ፡ ፲፰) ። ጽሌ ፡ ጽላት ፡ ለዕፅና ፡ ለእብን ፡ ለማዕደን ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ለክርታስና ፡ ለብራና ፡ አይኾንም ። ጽላተ ፡ ሰማይ ። ጽላተ ፡ ብርት ፤ ጽላተ ፡ ብሩር ። ጽላተ ፡ ሐመር ፤ (ኩፋ ፡ ፫ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ማን፳፩) ። ጽሌ ፡ ላንድ ፤ ጽላት ፡ ለኹለት ፤ ለብዙም ፡ ይኾናል ። በማርኛ ፡ ግን ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ጽላት ፡ ይባላል ፤ ይኸውም ፡ ሥራው ፡ በመጽሐፍ ፡ አምሳል ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፤ አንድ ፡ ቅጠል ፡ ክርታስ ፡ ወይም ፡ ብራና ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ተጣፈበት ፡ ኹለት ፡ ገጽ ፡ እንዲባል ፤ ጽላት ፡ ማለትም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።

**ጸለተ** ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ግ) ፤ ጋገረ ፤ ጠፈጠፈ ፤ ኰበት ፡ አስመሰለ ፤ አሣሣ ፤ ሾለመ ፡ ጠቀጠቀ ፤ የቂጣ ፡ የመጠቃ ፡ የጥረሾ ። ሐማሴኖች ፡ ንጉ ፡ ይሉታል ።

**መጸለት** ፤ (ዕብ ፡ ማጸት) ፤ ፍጹም ፡ ናእት ፤ ቂጣ ፤ ወዲያው ፡ ተለውሶ ፡ የሚጋገር ፤ የፋሲካ ፡ ምግብ ፡ አይሁድ ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ የሚበሉት ። ናእትንና ፡ ፍሥሐን ፡ ተመልከት ። ወቀርበ ፡ በዓለ ፡ መጸለት ፡ ዘስሙ ፡ ፋሲካ ። ወበጽሐት ፡ ዕለተ ፡ መጸለት ፡ አመ ፡ ይጠብሑ ፡ ፍሥሐ ። አስትዓ ፡ ዘመጸለት ፡ (ሉቃ፳፪ ፡ ፩ና ፡ ፯ ። ማር፲፬ ፡ ፩ና ፡ ፲፪ ። ሲኖዶ) ።

(፩) **ጸሊል** ፤ ሎት ፤ (ጸለለ ፡ ይጸልል ፡ ይጽልል ። ዕብ ፡ ጻላል ። ዐረ ፡ ጸለ ። ሱር ፡ ጸሊል) ፤ መጥለል ፤ መጥራት ፤ ጥሩ ፡ መኾን ፤ መፍሰስ ፤ መቅሰጥ ፤ መንጠር ፤ ለመጥራት ። እድራጊም ፡ ይኾናል ።


—፤ መስፈፍ ፤ መንካፈፍ ፤ መንጓለል ፤ መዋኘት ። ጸለለ ፡ ዝክቱ ፡ ኀጺን ። ጸለለት ፡ ታቦት ፡ ላዕለ ፡ ማይ ። ኢተሠርሙ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፤ አላ ፡ ጸለሉ ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ፡ (፬ነገ ፡ ፮ ፡ ፯ ። ዘፍ፯ ፡ ፲፰ ። መቃ ፡ ገ፱) ። ሩፋኤል ፡ መልአከ ፡ ራማ ፡ ባሕረ ፡ ሥጋዊ ፡ አመ ፡ ጸበተ ፡ እንዘ ፡ እምነ ፡ ቈጽል ፡ ይነሥእ ፡ አርኅያ ፡ ወእምነ ፡ ሐመር ፡ አምሳለ ፤ ለባሕረ ፡ ሥጋዊ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጸለለ ። ዕመቀ ፡ ባሕርዩሰ ፡ ይርአይ ፡ ፈጣሪ ፡ አመ ፡ በእንቲኣነ ፡ ክህለ ፤ ወረደ ፡ ታሕተ ፡ ወተቈልቈለ ፤ ከመሰ ፡ እማእከል ፡ ኢተርፈ ፡ ወኢተለዐለ ፤ አርአየነ ፡ ሞዳሁ ፡ መስቀለ ፡ (ሥላሴ ፡ ቅኔ) ።

—፤ በአየር ፡ በኅዋ ፡ መርበብ ፤ መስቀል ፤ ረቦ ፡ ተዘርግቶ ፡ መኼድ ፤ ያሞራ ፡ የደመና ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ጸለለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕለ ፡ ማያት ። ወመንፈሰ ፡ እግዚ ፡ ይጸልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ፡ (ቀሌ ። ዘፍ፩ ፡ ፪) ።

—፤ (ጥጠ) መጠለል ፤ ጥላ ፡ መያዝ ፤ ከጥላ ፡ ማረፍ ፡ መጠጋት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጸለለ ፡ ፈንታ ፡ አጽለለ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ይጸልል ፡ ታሕተ ፡ ኵሉ ፡ ዕፀው ። ረከበ ፡ ዕፀ ፡ ጽፍቅተ ፡ ወአጽለለ ። ያጸልሉ ፡ ታሕቴሁ ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ፡ (ሚራ፳፯ ፡ ፲፱ ። ተረ ፡ ባሮ ። ዳን፬ ፡ ፱) ።

**ጸላሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤ የሚጠል ፤ የሚሰፍ ፤ የሚረብ ፤ የሚከንፍ ፤ የሚጠለል ፤ ከጥላ ፡ የሚያርፍ ።

**ጽላል** ፤ (ላት) ፤ ጥላ ፤ ድባብ ፤ አጐበር ፤ የሚወጠር ፡ የሚገተር ፤ ፀሐይ ፡ የሚከለክል ።



ጽላል ፤

**ጽላሎት** ፤ (ታት ። ዕብ ፡ ጼል) ፤ በቁሙ ፤ ጥላ ፤ ታች ፤ ከለፋ ፡ ጨለማ ፤ አርኣያ ፡ አምሳል ፤ የዛፍ ፡ የገደል ፡ የሌላውም ፡ ኹሉ ፤ በፀሐይ ፡ ጊዜ ፡ የሚታይ ፡

የሚለይ ፤ ብርሃን ፡ ፀሓይ ፡ የሌለበት ። ጽላሎተ ፡ ዕፀ ። ጽላሎተ ፡ ኢይብር ። ጽላሎቱ ፡ ለአምላክ ፡ ሰማይ ። እስመ ፡ ጽላሎታ ፡ ይእቲ ፡ አራት ፡ ለእንተ ፡ ትመጽእ ፡ ሠናይት ፤ (ሕዝ፳ ፡ ፲፫ ። መሳ፱ ፡ ፴፯ ። መዝ ፡ ፯ ። ዕብ፲ ፡ ፩) ።

—፤ ቤት ፤ ድንኳን ፤ ማረፊያ ፡ ማደሪያ ። እብእ ፡ ነዳየ ፡ ወአኅድሮ ፡ ውስተ ፡ ጽላሎትከ ። ጽላሎተ ፡ ቤትየ ፤ (ኢሳ፶፰ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፲፱ና ፡ ፻፴፩) ።

**ጽላሎተ ፡ ሞት ፤ (ዕብ ፡ ጻልማዌት) ፤** የሞት ፡ ጥላ ፤ ውድቅት ፤ ጽኑቅ ፡ ድቅድቅ ፡ ጨለማ ፤ ገሃነም ፡ (ኢዮ፫ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፹፯ ። ማቴ፬ ፡ ፲፯) ።

**ጸለሎ ፤** ጥላት ፤ የጥቀርሻ ፡ ዐይነት ። ከመ ፡ ጸለሎ ፡ መቅፀት ፡ ይደ፡ምዎ ፡ ለገጽ ፤ (አርጋ ፡ ፪ ። ዮኤ ፪ ፡ ፮ ። ናሖ፪ ፡ ፲) ።

**አጽለለ ፤** አጠራ ፤ አጠለለ ፤ አሰፈፈ ፡ አንጓለለ ። ለኁጺኑ ፡ ማሕጼ ፡ አጽለሎ ፡ ዲበ ፡ ማይ ፤ (አርጋ ፡ ፱) ።

—፤ አስጠጋ ፤ አስጠለለ ፤ ከጥላ ፡ አሳረፈ ፤ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ። ታጽልሉ ፡ ታሕተ ፡ ዕፀ ። መኑ ፡ ያጸልል ። ወአጽለለ ፡ ህየ ፤ (ዘፍ፲፰ ፡ ፬ ። መዝ ፡ ፲፬ ። ማቴ፳፩ ፡ ፲፯) ።

**ምጽላል ፤ (ላት) ፤** ማጥለያ ፤ ማጥሪያ ። መጠጊያ ፡ ማስጠጊያ ፤ ጥላማ ፡ ቦታ ፤ የዛፍ ፡ ሥር ፤ ዳስ ፤ ድንኳን ፤ ጕጆ ፤ ቤት ፤ ማኅደርንት ፡ ያለው ፡ ኹሉ ። ወሐነጸ ፡ ምጽላላተ ፡ ሎቱ ፡ ወለእግብርቲሁ ። ወይቴ ክሉ ፡ ምጽላሎሙ ። ከመ ፡ ምጽላላተ ፡ ቄዳር ። ለአዕዋፍኒ ፡ ምጽላል ፡ ቦሙ ። ምጽላላቲሆሙ ፡ ዘለዓለማዊት ፤ (ኩፋ ፡ ፲፯ ። ኤር፳ ፡ ፫ ። ማሕ፩ ፡ ፭ ። ማቴ፰ ፡ ፳ ። ፊልክ ፡ ፫) ።

**ምጽላል ፤ (ዕብ ፡ ሱኮት) ፤** ዳስ ፤ ጥላ ፤ ከለላ ፤ ለበዓል ፡ ለድግስ ፡ የሚሠራ ። የአይሁድ ፡ በዓል ፤ በጥቅምት ፡ እኩሌታ ፡ የሚውል ። በምጽላል ፡ ፈንታ ፡ መጸለት ፡ ይላል ፤ የመላኸና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ከመ ፡ ይንበሩ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ በመጸለት ። ወውእቱ ፡ መቅድመ ፡ ገብረ ፡ በዓለ ፡ መጸለት ። ወቀርበ ፡ በዓለ ፡ መጸለቶሙ ፡ ለአይሁድ ፤ (ዕዝ ፡ ነሐ፰ ፡ ፲፬ ። ኩፋ ፡ ፲፯ ። ዮሐ፯ ፡ ፪) ።

**መጸለት ፤—ቂጣ ፤—ጸለየ ፡ ጽሌ ፡ ጽላት ፡ ጸለተ ።**

(ጥ) **ጸልሎ ፤ ሎት ፤ (ጸለለ ፡ ይጼልል ፡ ይጸልል) ፤** መጸለል ፤ በላይ ፡ ኹኖ ፡ ማጥላት ፤ ጥላ ፡ መኾን ፤ ማልበስ ፡ መክደን ፤ መሸፈን ፤ መከለል ፡ መጋረድ ፤ ማጨለም ። ይጼልላ ፡ ደመና ፡ ለደብተራ ። ወአዘዘ ፡ እግዚ ፡ ሐምሐመ ፡ ወበቈለ ፡ ወጸለሎ ፡ መልዕልተ ፡ ርእሱ ፡ ለዮናስ ። ጸለለ ፡ ከመ ፡ ወይን ፡ ማኅደሮ ። አልከወኒ ፡ ወጸለለኒ ፡ አዕይንትየ ። ይጼልሉ ፡ ወይቀትሉ ፤ (ዘኍ፱ ፡ ፲፰ ። ዮና፬ ፡ ፮ ። ሰቈ፪ ፡ ፮ ። ኢዮ፲፯ ፡ ፯ ። ኩፋ ፡ ፱) ።

—፤ እጅን ፡ ክንፍን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በስተላይ ፡ መዘርጋት ፤ በውስጥ ፡ ማደር ፤ መምሳት ። ኀበፍሖ ፡ ለኪ ፡ አእዳወ ፡ መዝራዕት ፡ ወንጼልል ፡ ዲበ ፡ ዝንቱ ፡ መሥዋዕት ። እስመ ፡ ኪሩብ ፡ ጸለሉ ፡ ክነፊሆሙ ፡ መልዕልተ ፡ መካና ፡ ወጸለልዋ ፡ ለታቦት ። ወስእኑ ፡ ሙሴ ፡ በዊአ ፡ ውስተ ፡ ደብተራ ፤ እስመ ፡ ጸለለ ፡ ደመና ። ኀይለ ፡ ልዑል ፡ ይጼልለኪ ። ወይጼልል ፡ ዲቤሆሙ ፡ (ቅዳ ፡ ጎር ። ፫ነገ ፡ ፰ ፡ ፯ ። ዘፀ፵ ፡ ፴፬ ። ሉቃ፩ ፡ ፴፭ ። ራእ፯ ፡ ፲፭) ።

**ተጸለለ ፤** ተጋረደ ፤ ተሸፈነ ፤ ታወረ ። ተጸለለ ፡ አዕይንትየ ። ወተጸለለ ፡ ልቦሙ ፡ ከመ ፡ ኢያእምርዎ ፤ (ግብ፲፫ ፡ ፲፩ ። ፰፪ ፡ ፲፩ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ጽሉል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ልልት) ፤** የተጋረደ ፤ የተሸፈነ ፤ ሽፍን ፤ ድፍን ። ጽሉል ፡ አዕይንቲሆሙ ። ናሁ ፡ ጽሉል ፡ ልቦሙ ፡ ወእዘኒሆሙ ። አብዳን ፡ ወጽሉላነ ፡ ልብ ፤ (ሔኖ ፡ ፹፱ ። ፴፫ ። ኤር፮ ፡ ፲ ። ዲድ ፡ ፱) ።

**ጽላሌ ፤** መጋረድ ፤ (ጥጋ) መጋረድ ፤ አገራረድ ፤ ግርዶሽ ፤ ጨለማ ፤ ዕውርንት ። ጽላሌ ፡ ኀይል ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወጽላሌ ፡ ኀለፈ ፡ እምአዕይንተ ፡ ይሥሐቅ ፡ ወርእየ ። ግዝረትሰ ፡ ጽላሌ ፡ ልብ ፡ በመንፈስ ። በእበዶሙ ፡ ወበጽላሌ ፡ ልቦሙ ። ጽላሌ ፡ ዐይን ፤ (ቅዳ ፡ ሕር ። ኩፋ ፡ ፴፩ ። ሮሜ፪ ፡ ፳፱ ። ኤፌ፬ ፡ ፲፰ ። አርጋ ፡ ፩) ።

**ጸሊም ፤ ሞት ፤ (ጸልመ ፡ ይጸልም ፡ ይጽልም ። ዕብ ፡ ጼሌም ። ሱር ፡ ጸልማ ፤ ጨለማ ፤ ሥዕል ፤ ምስል) ፤** መጨለም ፤ መምሸት ፤ ውድቅት ፡ ጨለማ ፡ መኾን ፤ ጨለማ ፡ መልበስ ፤ መጥቈር ፤ ጥላት ፡ መምሰል ፤ መፍዘዝ ፤ ከማየት ፡ መከልከል ። ወድአ ፡ ጸልመ ። እስመ ፡ ጽልመትኒ ፡ ኢይጸልም ፡ በኀቤከ ። ጸልመ ፡ ሎቱ ፡ ዓለም ። ጸልመ ፡ ፀሓይ ። ጸልመ ፡ ገጹ ። ጸልመ ፡ ዐይንነ ። ተጸለለ ፡ ወጸልመ ፤ (ዮሐ፳ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፻፴፰ ። ማቴ፳፯ ፡ ፵፭ ። ራእ፰ ፡ ፲፪ ። አስቴ፲ ፡ ፰ ። ሰቈ፭ ፡ ፲፯ ። ግብ፲፫ ፡ ፲፩) ።

—፤ መክዳት ፡ መካድ ፤ ከዳተኛ ፡ መኾን ። ጠለመን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

(ጥ) **ጸሊም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ላም ፤ ለምት) ፤** ጥቍር ፤ ጠቋራ ፤ ከሰልማ ፤ ቅጽልና ፡ በቂ ፡ ይኾናል ። ዘጽሑፍ ፡ በጸሊም ። አባ ፡ ሙሴ ፡ ጸሊም ። አፍራስ ፡ ጸሊማን ። ጸላም ፡ አነ ። ይመጽእ ፡ ለቢሶ ፡ ጸሊመ ። ለምንትኑ ፡ ለበስከ ፡ ጸሊማተ ፤ (አቡሻ ፡ ፴፫ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳፰ ። ዘካ፩ ፡ ፰ ። ማሕ፩ ፡ ፭ ። ዮሴፍ ። ፊላስ) ።

**ጽሉም ፤** የጨለመ ፤ የጠቈረ ፤ ጭልም ፡ ያለ ፤ የጨለማ ፡ ቦታ ። ጽሉም ፡ ኀሊናሆሙ ። ጽሉመ ፡ ልብስ ። ጽሉማነ ፡ ምድር ፤ (ኤፌ፬ ፡ ፲፰ ። ቀሌ ። መዝ ፡ ፸፫) ።

**ጽልመት ፤ (ዐረ ፡ ዙልመት ። ዕብ ፡ ሐሼኽ) ፤** መጨለም ፤ መጥቈር ፤ አጨላለም ። ጨለማ ፤ ሌሊት ፤ የጨረቃ ፡ ጠፍ ፤ ወይም ፡ ሠርቅ ። ጥቍረት ፡ ጥቍርንት ። በምስጢር ፤ ኀጢአት ፡ ክሕደት ፤ ድንቍርና ፤ ሐዘን ፡ መከራ ፡ ይኾናል ። ጸልመት ፡ ፀሓይ ፤

ሰበ ፡ ርእየት ፡ ፈጣሪሃ ፡ ሰቀለ ፤ ወኮነ ፡ መጠነ ፡ ጽልመታ ፡ እምጊዜ ፡ ስድስቱ ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ተስዐቱ ፡ ሰዓት ። ወጽልመት ፡ መልዕልተ ፡ ቀላይ ፤ ወፈለጠ ፡ እግዚ ፡ ማእከለ ፡ ብርሃን ፡ ወጽልመት ፤ ወሰመዮ ፡ ለብርሃን ፡ መዓልተ ፡ ወለጽልመት ፡ ሌሊተ ። በካልእ ፡ ወርኅ ፡ ሶመ ፡ ዐሡሩ ፡ ወሰኑዩ ፡ ለጽልመት ። ቍስል ፡ ይእቲ ፡ ለልብ ፡ ወጽልመት ፡ ለገጽ ፡ ወሐዘን ፡ ለነፍስ ፡ ብእሲት ፡ እኪት ። ወገጹ ፡ ዘፍፁም ፡ በጽልመት ፡ (ስንክ ፡ መጋ ፳፯ ። ዘፍ ፩ ፡ ፬ና ፡ ፭ ፡ ፭ ። ፮ ፡ ፲፩ ። ፳ ፡ ፬ ። ሢራ ፳፭ ፡ ፳፫ ። ኪዳ) ።

**አጽለመ** ፤ አጨለመ ፤ ጨለማ ፡ አደረገ ፤ አጠቈረ ፤ ከሰል ፡ አስመሰለ ፤ አጠፋ ፡ ለወጠ ። ያጸልም ፡ መዓልተ ፡ ከመ ፡ ሌሊት ። ኣጸልም ፡ ደመና ፡ ላዕለ ፡ ምድር ። እከዩሃ ፡ ያጸልም ፡ ከመ ፡ ርእየተ ፡ ድብ ፡ ለገጻ ። ቅንአተ ፡ እኪይ ፡ ያጸልም ፡ ሠናያተ ። ስካር ፡ ያጸልም ፡ ልበ ። ገልዓት ፡ ዘአጽለምዎሙ ፡ በፍሕም ፡ (ዓሞ ፭ ፡ ፰ ። ዘፍ ፱ ፡ ፲፬ ። ሢራ ፳፭ ፡ ፲፯ ። ጥበ ፱ ፡ ፲፪ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ መጋ ፳፯) ።

**መጽልም** ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤ የሚያጨልም ፤ የሚያጠቍር ፤ አጥቋሪ ።

—፤ የጨለመ ፤ የጠቈረ ፤ ጽሉም ፤ ጸሊም ። በውስተ ፡ መጽልም ፡ መካን ። ኢትኅሥሥ ፡ ርእየተ ፡ ገጽየ ፡ እስመ ፡ ገጽየ ፡ መጽልም ፡ ከመ ፡ ኀጣውእየ ። አንበ ፡ መጽልመ ፡ ገጽ ፡ ወብዙኀ ፡ አበሳት ፡ (ኩፋ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ሐም ፲ ። ታኅ ፲፬) ።

**ጸልመተ** ፤ (ጽልመት ፤ ጸልመ) ፤ ጨለመ ፤ ጠቈረ ፤ ደንቈረ ። በጸልመ ፡ ፈንታ ፡ ጸልመተ ፡ እያለ ፡ ይገኛል ። ይጸለምቱ ፡ በእንተ ፡ መንሱት ። ትጸለምት ፡ ነፍሳቲሆሙ ። ይጸለምት ፡ ልቡ ፡ ወይረስዮ ፡ ለእግዚ ፡ (ፊልክ ፡ ፲፱ ። ፴፭ ። ፻፶፯) ።

**ጽልሙት** ፤ (ጽሉም) ፤ የጨለመ ፤ የጠቈረ ፤ ጥቍር ፤ ጨለማ ፡ ጥቍረት ፡ የጸናበት ። እንዘ ፡ ብሩሃን ፡ ንሕነ ፡ ዘኢጽልሙታን ። ከዋክብት ፡ ጽልሙታን ። ጽልሙታነ ፡ ራእይ ፡ ሕዝብ ። አባ ፡ ሙሴ ፡ ጽልሙት ፡ (አፈ ፡ ድ፩ ። ይሁ ፡ ፲፫ ። ራደቢ ። ፊልክ ፡ ፴፯) ።

**አጸልመተ** ፤ (አጽለመ) ፤ አጨለመ ፤ አጠቈረ ፤ ጨለማ ፡ አለበሰ ።

**ጸሊዕ** ፤ ዖት ፤ (ጸልዐ ፡ ይጸልዕ ፡ ይጽላዕ ። ጸልእ) ፤ ማቁም ፡ መለገም ፤ ማድፈን ፤ ማቅበር ፤ ማበጥ ፡ መቍሰል ፤ መፍረጥ ፡ መምገል ። ጸምአና ፡ ጸምዐ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፤ ጸልአና ፡ ጸልዐም ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ ዐ ፡ በአ ፡ መለወጡ ፡ የቍስሉን ፡ ዐይን ፡ አፋኑና ፡ ፍንጩን ፡ ያሳያል ።

**ጸልዕ** ፤ (ዐረ ፡ ሰልዐት) ፤ ቍስል ፤ ዕባጭ ፤ የበትር ፡ የደዌ ፡ የመቅሠፍት ። ችፌ ፡ ጭንቍር ፤ ዋጣ ፡ ቋጥኝ ፤ ኩብቻ ፤ ንቀርሳ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ጸልዐ ፡ ዘይመግል ። ወሰኩኒ ፡ ዲበ ፡ ጸልዕየ ፡ ቍስለ ። ወመጽአ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ጸልዐ ፡ እኩይ ፡ (ኢሳ ፩ ፡ ፮ ። መዝ ፡ ፷፰ ። ራእ ፲፯ ፡ ፪) ። ምስጢሩ ፡ ጽልእን ፡ አይለቅም ፤ የሚጠላና ፡ የሚያስጠላ ፤ የሚያስቀይም ፤ የሚያስጠይፍ ፤ ማለት ፡ ነው ።

**አጽልዕት** ፤ ቍስሎች ፤ መቅሠፍቶች ። ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘአጽልዕቲሁ ፡ ምስሌሁ ፤ ወመስቀለ ፡ ሞቱ ፡ ቅድሜሁ ። አጽልዕት ፡ ዘይፈልሕ ፡ ዲበ ፡ ሰብእ ፡ ወእንስሳ ። ሕማመ ፡ አጽልዕቲሆሙ ፡ (ደራሲ ። ዘፀ ፱ ፡ ፱—፲፩ ። ራእ ፲፮ ፡ ፲፩) ።

**ጸሎት** ፤—በቁሙ ፤—ጸለወ ፤ ጸለየ ።

**ጸለተ** ፤—ጋገረ ፤—ጸለየ ፡ ጽላት ።

**ጽመ** ፤—ዝምም ፡ ብሎ ፤—ጸመመ ።

**ጸመ** ፤—ጦመ ፤—ጸዊም ፡ ጸመ ።

**ጸሚእ** ፤ ኦት ፤ (ጸምአ ፡ ይጸምእ ፡ ይጽማእ ። ዕብ ፡ ጻሜእ) ፤ መጥማት ፤ መጠማት ፡ ውሃ ፡ መጠጥ ፡ መፈለግ ፤ መናፈቅ ። ጸምዐን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። እለ ፡ ጸምኡ ፡ ይሑሩ ፡ ኀበ ፡ ማይ ። ዘጸምአ ፡ ይምጻእ ፡ ኀቤየ ፡ ወይስተይ ። ጸምአት ፡ ነፍስየ ፡ ኀበ ፡ አምላኪየ ፡ ሕያው ። ነፍስየኒ ፡ ከመ ፡ ምድረ ፡ በድው ፡ ጸምአተከ ፡ (ኢሳ ፶፭ ፡ ፩ ። ዮሐ ፯ ፡ ፴፯ ። መዝ ፡ ፵፩ና ፡ ፻፵፪) ።

**ጽሙእ** ፤ (እን ፡ ኢት ፡ ምእት) ፤ የተጠማ ፤ የናፈቀ ። ወበከመ ፡ ጽሙእ ፡ ዘየሐልም ፡ እንዘ ፡ ይሰቲ ፡ ማየ ፡ ወነቂሆ ፡ ዓዲሃ ፡ ጽምእት ፡ ነፍሱ ። ዘእሙንቱ ፡ ጽሙኣን ፡ እምቃለ ፡ እግዚ ። ከመ ፡ ይትመርሐ ፡ በቃላቲከ ፡ እለ ፡ ጽሙኣን ፡ ለነጽሮትከ ፡ (ኢሳ ፳፱ ፡ ፰ ። መጽ ፡ ምስ ። አረጋ ፡ ድ፱) ።

**ጽምእ** ፤ (ኣት) ፤ ጥም ፤ ጥማት ፤ የውሃ ፡ ዕጦት ፤ የመጠጥ ፡ ችጋር ። ጽምአ ፡ ማይ ። ብሔረ ፡ ጽምእ ። እመውት ፡ በጽምእ ፡ (ዓሞ ፰ ፡ ፲፩ ። ዘዳ ፳፱ ፡ ፲ ። መሳ ፲፭ ፡ ፲፰) ።

**አጽምእ** ፤ አስጠማ ፤ ውሃ ፡ ንሣ ፤ ከለከለ ፤ ውሃ ፡ ውሃ ፡ አሰኘ ፤ የደዌ ፡ የምግብ ። አጽማእካሁ ፡ እምስታየ ፡ ገነት ። አርኀብዎ ፡ ወአጽምእዎ ፡ (መቃ ። ፫ነገ ፡ ፳፱ ፡ ፳፯) ።

**ምጽማእ** ፤ መጠሚያ ፤ ማስጠሚያ ፤ ደረቅ ፡ በረሓ ። ወረሰየ ፡ ምጽማአ ፡ ሙሓዘ ፡ ማይ ፡ (መዝ ፡ ፻፮) ።

**ጸምአ** ፤—ቀረበ ፤ አደመጠ ፤—ጸምዐ ።

**ጸመደ** ፤—ጠመደ ፤—ፀሚድ ፡ ፀመደ ።

**ጸምሀየ** ፤—ጠወለገ ፤—ጸምሐ ።

**ጸምዎ** ፤ ዎት ፤ (ጸመወ ፡ ይጸሙ ። ጸመ) ፤ መጣመን ፤ መድከም ፤ መሥራት ፤ መጣር ፤ መትጋት ፤ ለሥራ ። ጸመንና ፡ ደከመን ፡ ተመልከት ። በከ ፡ ጻመውኩ ። አኮ ፡ ለባሕቲትየ ፡ ዘጻመውኩ ። ሐምሐም ፡ ዘኢጻመውከ ። ጻሙ ፡ ለምህሮ ፡ (ኢሳ ፵፱ ፡ ፬ ። ሢራ ፳፬ ፡ ፴፬ ። ዮሓ ፬ ፡ ፲ ። ፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፯) ።

**ጸማዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** የሚደክም ፤ ተግቶ ፡ የሚጥር ፤ የሚሠራ ። ጻማዊ ፡ በገድሉ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ስንክ ፡ ኅዳ፱ ። መጋ፲፯) ።

**ጸማዊ ፤ (ጸማ ፡ ዊ) ፤** የድካም ፤ ባለድካም ፤ ደካማ ።

**ጻማ ፤ (ማት) ፤** ጣመን ፤ ድካም ፤ ሥራ ፤ ሥቃይ ፡ መከራ ። ጻማሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ባቍዕ ። ይሴሰዩ ፡ እምጻማ ፡ እደዊሆሙ ። የዐርፉ ፡ ጻድቃን ፡ እምጻማ ፡ ኃጥኣን ። ምግባራቲሁ ፡ ወጻማቲሁ ፡ (ጥበ ፫ ፡ ፲፩ ። ስንክ ፡ ጥር፲፯ ። ሔኖ፺፯ ፡ ፫ ። ፊልክ ፡ ፳) ።

**አጻመወ ፤** አደከመ ፤ አታከተ ፤ ማቀየ ፤ መከራ ፡ አሳየ ። ኢታጻምዎ ፡ ለሊቅ ። አጻመውት ፡ ሥጋየ ፡ በተፀምዶ ፡ ጾም ፡ ወጸሎት ። ነበረ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ወአጻመወ ፡ ሥጋሁ ፡ ፈድፋደ ፡ (ማር፳ ፡ ፴፭ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ግን፲፩) ።

(ጥ) **ጻምዎ ፤ (ጸመወ ። ዐረ ፡ ጸመተ) ፤** መጨመት ፤ ዝም ፡ ዕክም ፡ ጸጥ ፡ ማለት ፤ ሕዋሳተ ፡ አፍኣን ፡ መጠበቅ ፤ አለመታወክ ፤ ጸጥተኛ ፡ ዝምተኛ ፡ መኾን ፤ ከማስተዋል ፡ ጋራ ፤ የመነኰሴ ። ሀድአን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ከተማ ፡ ነው ።

**ጽምው ፤ (ውት ፡ ዋን ፡ ዋት) ፤** የረጋ ፡ የጨመተ ፤ ጭምት ፤ ዝም ፡ ዕክም ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፤ ዝምተኛ ፤ ህዱእ ። ጽምው ፡ በቃሉ ፡ ወራትዕ ፡ በልሳኑ ። የዋህ ፡ ወጽምው ። ውስተ ፡ መካን ፡ ግሑሥ ፡ ወጽምው ፤ ጭር ፡ ጭ ፡ ያለ ፡ (ሲኖደ ። ሄርማ ። ግንዘ) ።

**ጽማዌ ፤** መጨመት ፤ ጭምትነት ፤ ዝምታ ፤ ጭታ ፤ ርጋታ ፤ ጸጥታ ። ሶበ ፡ ይከውን ፡ ጽማዌ ። ብእሲ ፡ ጠቢብ ፡ ያመጽእ ፡ ጽማዌ ። ሰላም ፡ ወጽማዌ ። ጽማዌ ፡ ነፍስ ። ወሰደደቶ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ጽማዌ ፡ (ምሳ፲ ፡ ፱ ። ፲፩ ፡ ፲፪ ። ፩ዜና ፡ ፱ ፡ ፵ ። ስንክ ፡ ታኅ፳ ። አፈ ፡ ተ፲፱) ።

**ጽሙና ፤** ጭምትነት ፤ ድካም ፤ ጸጥታ ፤ የገዳም ፡ ሥርዐት ፤ ጾም ፡ ትሕርምት ፤ ምናኔ ፤ ብቸኝነት ። ትሜህሮ ፡ ጽሙና ፡ ወትዕግሥተ ፡ ወጸሎተ ። መፍቀሬ ፡ ጽሙና ፡ ወጸሎት ። ኅሩያን ፡ መነኮሳት ፡ ዘነበረቶሙ ፡ ጽሙና ። ፈለሰ ፡ ገዳመ ፡ ውስተ ፡ ጽሙና ፡ (ዲድ ፡ ፳፱ ። ስንክ ፡ ሚያ፲ ። ሐም፳፬ ። ፊልክ ፡ ፵) ። ጸመ ፡ ጸመወ ፤ ጸመወ ፤ እሊህ ፡ ፫ቱ ፡ ፩ ፡ ዘር ፡ ናቸው ።

**ጸሚሕ ፤ ሐት ፤ (ጸምሐ ፡ ይጸምሕ ፡ ይጽማሕ ። ዕብ ፡ ጸማሕ) ፤** መብቀል ፤ መውጣት ፤ ማደግ ፤ የቡቃያ ።

**ጸምሐየ ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤** መጽለወ ፤ ጠወለገ ፤ ፈራ ፡ ዛለ ፤ ተሸመለመለ ፤ ተለወጠ ፤ መድረቅ ፡ ገመረ ። የ ፡ ጸሐየ ፡ ካለው ፡ የመጣ ፡ ነው ። ጸምሐየ ፡ ከመ ፡ ሐምለ ፡ መሎኬ ፡ በውስተ ፡ ሐሩር ። ርእ ፡ ከመ ፡ ኢጸምሐየ ፡ በለስ ። ደቂቅኪ ፡ እለ ፡ ጸምሐዩ ። ወዘኢይጸመሒ ። ዘእንበለ ፡ ይጸምሒ ፡ (ኢዮ፳፱ ፡ ፳፱ ። ተረ ፡ ባሮ ። ኢሳ፶፩ ፡ ፳ ። ፩ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፱ ። ጥበ፪ ፡ ፰) ። በጸምሐየ ፡ ፈንታ ፡ ተጸምሐየ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። በእንተ ፡ ትሕርምቶሙ ፡ ወድካሞሙ ፡ ደግደገ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ወተጸምሐየ ። ተጸምሐይ ፡ በረኃብ ፡ አንስት ። ወሶበሂ ፡ ትጸውሙ ፡ ኢትጸምሐዩ ፡ (ፊልክ ፡ ፲፮ ። ሰቈ፭ ፡ ፲ ። ማቴ፮ ፡ ፲፮) ። ኹለተኛም ፡ ጸምሐየየ ፡ ተጸምሐየየ ፡ እያለ ፡ ኹለተኛ ፡ የ ፡ ይጨምራል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ማር ፡ ይሥ፲፫ ፡ ፩) ።

**ጽምሑይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሒት) ፤** ምጽልው ፤ የጠወለገ ። ሣዕር ፡ ጽምሑይ ። ኮነ ፡ ገጹ ፡ ድሙነ ፡ ወሕብሩ ፡ ጽምሑየ ፡ (ሄርማ ። ፊልክ ፡ ፻፹፱) ።

**አጸምሐየ ፤** አጠወለገ ፤ አሳረረ ፤ አቃጠለ ፤ አጠፋ ፤ ለወጠ ። ሳህበ ፡ ነድኒ ፡ ኢያጸምሐየ ፡ ሥጋ ፡ እንስሳ ። ፍርሀተ ፡ እግዚ ፡ እምከመ ፡ ኀደረት ፡ ውስተ ፡ ብእሲ ፡ ታየብስ ፡ ሥጋሁ ፡ ወታጸመሒ ፡ አዕፅምቲሁ ። ሐሜትሙ ፡ ታጸምሕያ ፡ ለሃይማኖቶሙ ። ኢያውሥእት ፡ ለአሐቲ ፡ እምኔሆን ፡ ወኢያጸምሐየት ፡ ገጻ ፡ ወኢተሀውከ ፡ ልባ ፡ (ጥበ፲፱ ፡ ፳ ። ፊልክ ፡ ፲፯ ። ሄርማ ። ዮሴፍ) ።

**ጸምላጥ ፤—ጨምላጫ ፤—መለጠ ።**

**ጸሚም ፤ ሞት ፤ (ጸመ ፡ ይጸምም ፡ ይጽምም ። ዐረ ፡ ጸሚመ) ፤** መዘጋት ፤ መደፈን ፤ መደንቈር ፤ የጆሮ ፡ የአፍ ። ጸሙ ፡ እዘኒሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይስምዑ ። ይትመሰው ፡ አባሉ ፡ ወይጸምም ፡ እዝኑ ፡ (መቃ ፡ ገ፳ ። ግንዘ) ።

—፤ መጥመም ፤ መለገም ፤ ዝም ፡ ቸል ፡ ችላ ፡ ማለት ፤ እያዩ ፡ እየሰሙ ፡ እንዳለየና ፡ እንዳልሰማ ፡ መኾን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ጸመ ፡ ጸመመ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተጸመመ ፡ ተጸመመ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። መኑ ፡ ጸውዖ ፡ ወተጸመሞ ። ኀፍረት ፡ ተጸምሞቶ ፡ ለዘይጼውዐከ ። እግዚኦ ፡ ኢትጸመመኒ ፡ ስእለትየ ። ይጸመም ፡ ከመ ፡ ዘኢይሰምዕ ። እመ ፡ ተጸመምኪ ፡ ዮም ፡ (ሢራ፬ ፡ ፲ ። ፵፩ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፻፳ ። ቅዳ ፡ ግሩ ። አስቴ፬ ፡ ፲፬) ።

**ጸማም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤** ጠማማ ፤ ለግመኛ ፤ ቸልተኛ ፤ ደንቈሮ ፡ (ትግሬ) ።

**ጽሙም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ምምት) ፤** ደንቈሮ ፤ ጎሮው ፡ የተዘጋ ፡ የተደፈነ ፤ ዝም ፡ ቸል ፡ ያለ ። ኢትንብብ ፡ ሕሡመ ፡ ላዕለ ፡ ጽሙም ። በሃም ፡ ወጽሙም ። ከመ ፡ ጽሙም ፡ ዘኢይሰምዕ ። ለጽሙማን ፡ መፈውስ ፡ (ዘሌ፲፱ ፡ ፲፬ ። ሉቃ፲፩ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፴፯ና ፡ ፶፯ ። ኪዳ) ።

—፤ ደረቅ ፤ ጥብቅ ። ኰኵሕ ፡ ጽሙም ፡ (ማር ፡ ይሥ፳፰ ፡ ፬) ።

**አጽመመ ፤** ዘጋ ፤ ደፈነ ፤ አደንቈረ ። አጽመሙ ፡ እዘኒሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይስምዑ ። ዘያጸምም ፡ እዘኒሁ ፡ ከመ ፡ ኢይስማዕ ፡ ዐውያተ ፡ ነዳይ ። ላኳሆሙ ፡ ለአብዳን ፡ ያጸምም ፡ እዝነ ። ድምፀ ፡ ሰፈልያ ፡ ያጸምም ፡ እዘኒሁ ፡ (ኢሳ፮ ፡ ፲ ። ዲድ ፡ ፲፬ ። ሢራ፳፯ ፡ ፲፬ ። ፴፯ ፡ ፳፰) ።

**መጽመሚ** ፤ ግሮ ፡ የሚደፍን ፤ የሚያስደፍን ፤ ከመስማት ፡ የሚከለክል ። አፍ ፡ የሚያሲዝ ፤ ዝም ፡ የሚያሰኝ ። መስም ፡ ቅጽል ፡ ከኹለት ፡ አዕማድ ፡ እንዲወጣ ፡ አስተውል ።

(ጥ) **ጽም** ፤ ድንቍርና ፤ ዝምታ ፤ ጸጥታ ፤ ከንቱ ፤ ብላሽ ፤ ኵስሕ ፤ ዐዘቅተ ፡ ኵስሕ ።

**ጽመ** ፤ ዝም ፡ ብሎ ፤ በዝምታ ፤ በጸጥታ ። ባሕቲቱ ፡ ይነብር ፡ ጽመ ፡ ውስተ ፡ ምግሓሡ ፡ ጽርሑ ። ወጽመ ፡ ይትገደፍ ፤ (መሳ፫ ፡ ፳፱ ። ማቴ፲፭ ፡ ፲፪ ። ማር፮ ፡ ፲፱) ።

**ጽሚት** ፤ **ጽምሚት** ፤ ጥመት ፤ ጠማምነት ፤ ልግም ፤ ቸልታ ። ዝምታ ፤ ቀስታ ፤ ድብቃ ። ስወራ ፤ ምስጢራዊ ፡ ሥራ ። ከመ ፡ ይቅትሉ ፡ ለንጹሕ ፡ በጽሚት ። ሀብት ፡ ዘበጽሚት ። ዘአስሐቶ ፡ ለልብየ ፡ በጽምሚት ፤ (መዝ ፡ ፲ ። ምሳ፳፩ ፡ ፲፬ ። ኢዮ፴፩ ፡ ፳፯) ።

**ጽሚተ** ፤ **ጽምሚተ** ፤ ዝም ፡ ብሎ ፤ ቀስ ፡ መስስ ፡ ብሎ ፤ በቀስታ ፤ ስውሮ ፤ ተሰውሮ ፤ በስውር ፤ በምስጢር ፤ በስርቆሽ ፤ በድብቅ ፤ በሹልክታ ፤ በሹክሹክታ ። ማይ ፡ ዘየሐውር ፡ ጽምሚተ ። መከረ ፡ ጽሚተ ፡ ይኅድጋ ። ዐርገ ፡ ጽሚተ ፡ ወእከ ፡ ገሃደ ። አልቦ ፡ ዘተናገርኩ ፡ ጽምሚተ ፡ ወኢምንተኒ ፤ (ኢሳ፰ ፡ ፮ ። ማቴ፩ ፡ ፲፱ ። ዮሐ፯ ፡ ፲ ። ፲፰ ፡ ፳) ።

**ጸመተ** ፤ ጨመተ ፡ ዝም ፡ አለ ፡ ረጋ ፤ ጭምት ፡ ኾነ ።

**ጸመመ** ፤—**አሰረ ፡ ጠቀለለ ፡ ፈወሰ** ፤—**ፀመመ** ።

**ጸምዐ** ፤ (**ጸሚእ ፡ ሰሚዕ**) ፤ መስማት ፡ ፈለገ ፤ ለሰሚዕ ፡ ቸኰለ ፤ ልስማ ፡ ልስማ ፡ አለ ። ዘሩ ፡ ጸሚእ ፡ ነው ፤ ዐ ፡ ከሰሚዕ ፡ መጥቶ ፡ በአ ፡ ፈንታ ፡ ገብቷል ፤ ምስጢሩ ፡ ጽምእን ፡ አይለቅም ፡ (ዓሞ፰ ፡ ፲፭) ።

**አጽምዐ** ፤ ቀቀረ ፡ ቀፈረ ፤ አዘነበለ ፤ ግሮውን ፡ ሰጠ ፤ አቀረበ ፤ ለመስማት ። ሰማ ፤ አደመጠ ። አሰማ ፡ አስደመጠ ፤ አስደፈገ ። ጸለወንና ፡ አዘነን ፡ ተመልከት ። **አጽምዕ ፡ እዝነከ ፡ ወስምዐኒ ። አጽምዑኒ ፡ ፍትሐ ፡ ከናፍርየ ። አጽማዕኩ ፡ ሕቀ ፡ በእዝንየ ። እዝን ፡ ያጸምዕ ፡ ነገሮ ፡ ምሳሌ** ፤ (፬ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፮ ። ኢዮ፲፫ ፡ ፮ ። ሢራ፫፩ ፡ ፲፮ ። ምሳ፲፪ ፡ ፱) ።

**አጽማዒ** ፤ **መጽምዕ** ፤ **ዒ** ፤ የሚያደምጥ ፤ አድማጭ ፤ ሰሚ ፤ አስማታም ፤ ባላሾክሺኪ ። የተማረ ፡ ሊቅ ፤ መጽሐፍ ፡ የሚያሰማ ፤ ተርጓሚ ፡ ሰባኪ ። **መጽምዔ ፡ ነገር** ፤ (ኢሳ፫ ፡ ፫) ።

**ጸማዕት** ፤—**ዋሻ ፡ በኣት** ፤—**ጸወማዕት** ።

**ጸሚቅ** ፤ **ቆት** ፤ (**ጸመቀ ፡ ይጸምቅ ፡ ይጽምቅ ። ዕብ ፡ ጸማቅ ፤ ደረቀ**) ፤ መጭመቅ ፤ መጥመቅ ፤ ውሃውን ፡ ለማውጣት ፡ ለማድረቅ ። ጠመቀን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ጽሙቂም** ፤ (**ዕብራ**) ፤ ዘቢብ ፤ ደረቅ ፡ የወይን ፡ ዘለላ ፤ የበሰሰ ፡ ቋንጣ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፲፰) ። ሙዳየ ፡ ዘቢብ ፡ ባለው ፡ ጽሙቂም ፡ እያለ ፡ ይገኛል ፤ ጸሚቅ ፡ አንድ ፤ ጽሙቂም ፡ ብዙ ።

**ጸምር** ፤—**የበግ ፡ የፍየል ፡ ጠጕር** ፤—**ፀምር** ።

**ጸመተ** ፤—**ጨመተ** ፤—**ጸሚም** ።

**ጸምቶ** ፤ **ቶት** ፤ (**ጸመተ ፡ ይጸምት ። ዕብ ፡ ጸማት ፤ አጠፋ**) ፤ ማለቅ ፤ መጣመት ፤ ተጨርሶ ፡ መጥፋት ።

**አጸመተ** ፤ አጣመተ ፤ ፈጀ ፡ ጨረሰ ፤ አጠፋ ፡ ደመሰሰ ። ያጸምቶሙ ፡ መጥባሕት ፤ (ዘዳ፴፪ ፡ ፳፭) ።

**ጸንአ** ፤—**ጠና ፡ በረታ** ፤—**ጸኒዕ ፡ ጸንዐ** ።

**ጽንጕን** ፤ (**ጸንቀቀ**) ፤ ጭቃ ። ከመ ፡ ጽንጕን ፡ ዘይከይዱ ። ጽንጕኑ ፡ ፍኖት ። ጽንጕኑ ፡ መርሕብ ፤ (ሚክ፯ ፡ ፲ ። ዘካ፱ ፡ ፫ ። ፲ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፲፰) ።

**ጽንጕፍ** ፤ (**ነገፈ**) ፤ ጥጕ ፤ ከባድ ፤ ጣሉኝ ፡ ጣለኝ ፡ የሚል ፤ ጥንብ ፤ ዐይነ ፡ ምድር ፤ ሬሳ ፤ ጭምጋፍ ፡ ሙቶ ፡ የሚወርድ ፡ የሚወለድ ። ነገፈን ፡ ተመልከት ፤ አባቱ ፡ ይሱ ፡ ነው ። ክቡድ ፡ እብን ፡ ወጽንጕፍ ፡ ጸረ ፡ ኖዳ ፤ (ምሳ፳፯ ፡ ፫) ።

**ጸንገፈ** ፤ ጨነገፈ ፤ ጣለ ፤ አሶረደ ።

**ጸኒሕ** ፤ **ሐት** ፤ (**ጸንሐ ፡ ይጸንሕ ፡ ይጽናሕ ። ዕብ ፡ ጻናሕ ፤ ጸኒ ፡ ወድቀ ። ቃዊህ ፤ ቈየ**) ፤ ደጅ ፡ መጥናት ፤ መቈየት ፤ መጠበቅ ፤ መታገሥ ፤ ተስፋ ፡ ማድረግ ፤ ማድባት ፡ ማሸመቅ ፤ ማድፈጥ ፤ መዘጋጀት ፤ የከፋ ። ጸኒሐ ፡ ጸናሕክዎ ፡ ለእግዚ ። መንግሥትከ ፡ ይጸንሐከ ። ዐይኑ ፡ ዘማዊ ፡ ይጸንሕ ፡ ጽልመተ ። እስከ ፡ እትመየጥ ፡ መንገሌከ ፡ ጽንሐኒ ፡ ጸኒሐ ፤ እስመ ፡ ይኅረ ፡ ሞቱ ፡ ለሰብእ ፡ እልቦቱ ፡ ንስሓ ። ጽንሕዋ ፡ ለምሕረቱ ። ጽናሕ ፡ ፍሬሃ ፡ ቡሩከ ። ይጸንሕ ፡ ወይትኀብእ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ። ይጸንሕ ፡ መቅሠፍት ፡ ለእኩያን ፤ (መዝ ፡ ፴፱ ። ዳን፬ ፡ ፳፫ ። ኢዮ ፳፬ ፡ ፲፭ ። ደራሲ ። ሢራ፳ ፡ ፯ ። ፯ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፱) ።

**ጸናሒ** ፤ (**ሒት ፡ ሒያን ፡ ያት**) ፤ ደጅ ፡ ጠኚ ፤ ጠባቂ ፤ ሸማቂ ። ጸናሒ ፡ ወመስተዐግሥ ። ጸናሕያን ፡ ተስፋ ፡ ክቡር ። ጸናሕያን ፡ ፍኖት ፡ (ጥበ ፡ ጠቢ ። ሰንክ ፡ የካ፳፰ ። ዮሴፍ ። ምሳ፲፱ ፡ ፳፱) ።

**ጽኑሕ** ፤ (**ሓን ፡ ሓት ፡ ንሕት**) ፤ ያደባ ፤ የሸመቀ ፤ የተዘጋጀ ፤ ዝግጁ ። አንበሳ ፡ ዘጽኑሕ ፡ ለመሚጥ ። ጽኑሕ ፡ መልአከ ፡ እግዚ ፡ በሰይፍ ፡ ይሥጽርከ ። ጽኑሕ ፡ ሎቱ ፡ ኀሳር ፡ ዐጺብ ። ወበከመ ፡ ጽኑሕ ፡ ለሰብእ ፡ ምዕረ ፡ መዊት ፤ (መዝ ፡ ፲፮ ። ዳን፩ ፡ ፶፱ ። ኢዮ፲፰ ፡ ፲፪ ። ዕብ፱ ፡ ፳፯) ።

**ጽንሐት** ፤ መቈየት ፤ መታገሥ ፤ አቈያየት ። ቈይታ ፤ ደጅ ፡ ጥናት ፤ ሽመቃ ።

**ጽንሕ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ቈይታ ፤ ሽመቃ ።

**አጽንሐ** ፤ አቈየ ፤ አስቈየ ፤ ደጀ ፡ አስጠና ፤ አዘጋጀ ። አጽናሕኩሙ ፡ ወነፃኣኩሙ ። ሰማዕተ ፡ ባልሐ ፡ ዐስቦሙ ፡ አጽንሐ ። ይቤሎሙ ፡ ያጽንሑ ፡ ሎቱ ፡ ሐመረ ፡ (መዝ ፡ ፸፪ ። መዋሥ ። ማርቆ ፡ ፱) ።

**አጽናሒ ፤ መጽንሒ** ፤ የሚያቈይ ፤ የሚያዘጋጅ ። አጽናሒ ፡ ፍዳ ፡ (ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**መጽንሕ** ፤ መጥን ፤ መቈያ ፤ መስተንግዶ ፤ መተያያ ። አውገዘ ፡ ከመ ፡ ኢያሀቡ ፡ ግብረ ፡ ወመጽንሐ ፡ በኀይል ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዶሙ ፡ ሰብ ፡ የአቱ ፡ ንጉሥ ፡ (ሥር ፡ አሾ) ።

**ተጻንሐ** ፤ ተጠባበቀ ፤ ተቈያየ ። ተጻንሑ ፡ ቢጸክሙ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፴፫) ።

**ጸንሕሐ ፤ (ተቀ ፡ ግ)** ፤ ጤስ ፡ ነደደ ፡ ተቃጠለ ፤ ሸተተ ፤ መሥዋዕት ፡ ኾነ ። በጸንሕሐ ፡ ፈንታ ፡ ተጸንሕሐ ፡ ይላል ፤ አያስኼም ፤ የጸንሐ ፡ ቅጥይ ፡ ነው ፡ (አርጋ) ።

**ጽንሓሕ ፤ (ሓሒት)** ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፤ ቍርባን ፤ ሥብሕ ፤ ዕጣን ፤ ጢሱ ፡ መዐዛው ፤ ምሥዋው ፡ ጥናው ። አዕረገ ፡ ጽንሓሐ ፡ ዲበ ፡ ምሥዋዕ ። ወጽንሓሒኒ ፡ ኢትሠምር ። ጽንሓሐ ፡ መሥዋዕት ። ተዐጥነ ፡ ጽንሓሐ ፡ ወተዐውደ ፡ ወትጸርሕ ። አዐርጎ ፡ ጽንሓሐ ፡ ለእግዚ ፡ (ኩፋ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፶ ። መዋሥ ። ማንዘ ። መጽ ፡ ምስ) ። በጽንሓሕ ፡ ፈንታ ፡ ጽንሓሒ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (፪ዜና ፡ ፯ ፡ ፯ ። ፰ ፡ ፲፱ ። ፲፫ ፡ ፲፩) ።

**አጸንሕሐ** ፤ ሠዋ ፤ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ፤ አጤስ ፤ አቃጠለ ፤ አሻተተ ። አጸንሕሐ ፡ ጽንሓሐ ። ለአጸንሕሖ ፡ ቍርባን ። ወኢኀበ ፡ ያጸንሕሑ ፡ ዕጣነ ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፳፯ ። መጽ ፡ ምስ ። ዳንኤ ፡ ፲፬) ።

**አጸንሓሒ** ፤ የሚያጤስ ፤ የሚያቃጥል ፤ አሻታች ። ሚካኤል ፡ ሣውዐ ፡ አጸንሓሒ ፡ ሠናይ ፡ ጼና ፡ መዐዛ ፡ (ደራሲ) ።

**አጽናሕንሐ ፤ (የቅጥይ ፡ ቅጥይ)** ፤ ወዘወዘ ፤ አወዛወዘ ፤ ለማጠን ፤ የጥና ፡ የማጠንት ።

**ጸኒን ፤ ኖት ፤ (ጸነ ፡ ይጸንን ፡ ይጽንን ። ደነነ ። ዕብ ፡ ጻናን ፡ ቄረ)** ፤ መጽነን ፤ መጕንበስ ፤ መዘንበል ፤ ማድላት ፡ ማጋደል ፤ ማርገዝ ፡ ማዘብዘብ ፤ የካብ ፡ የግንብ ። ኀይሉ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘኢይጸንን ፡ ወኀሲና ፡ ንጹሕ ፡ ዘኢይጸንን ፡ ጸግወኒ ። ሶበ ፡ ርእየ ፡ ከመ ፡ ጸነ ፡ ልቡ ። ኢትጽንኑ ፡ መንገለ ፡ ፍኖተ ፡ ሕገጋት ፡ አፍኣዊት ። ለእመ ፡ ጸነ ፡ እረፍት ፡ መንገለ ፡ ፍኖት ፡ (ኪዳ ። ስንክ ፡ መስ፫ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፰ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ። ጸንጸንን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ። በጸነ ፡ ፈንታ ፡ አጽንን ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። አጽንኖት ፡ ታሰት ። ታጸንን ፡ ምድር ፡ (፩ዜና ፡ ፲፫ ፡ ፱ ። ኢሳ፳፬ ፡ ፳) ።

**ጸናኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፤ የሚጸን ፤ የሚጠም ፤ ጠማማ ፤ አድላዊ ።

**ጽኑን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ንንት)** ፤ የጸነነ ፤ የዘነበለ ፤ ያረገዘ ፡ ያዘበዘበ ፤ ሊወድቅ ፡ ሊናድ ፡ የቀረበ ። ከመ ፡ እረፍት ፡ ጽንንት ፡ (መዝ ፡ ፷፩) ።

**ጽነት** ፤ መጽነን ፡ መዘንበል ፤ መጥመም ፤ መጣመም ፤ ጠማምነት ። እመ ፡ ኮነ ፡ ጽነቱ ፡ መንገለ ፡ ሐዴር ። ንዐቀብ ፡ ሃይማኖተ ፡ ርትዕተ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽነት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፮ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**ጽናኔ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። በርትዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽናኔ ፡ (አፈ ፡ ተ፴፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፮ ፡ ፱) ።

**አጽነነ** ፤ አጠነነ ፤ አጠመመ ፤ አዘነበለ ፤ አስጐንበሰ ፤ አዋረደ ። አጽንኖ ፡ ርእሶ ። ሕልያን ፡ ያዐውር ፡ ወያጸንን ፡ ነገረ ፡ ርትዕ ። መኑ ፡ አጽንኖ ፡ ለሰማይ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። አጽንኒ ፡ ቀሠተኪ ። አጽንን ፡ እዝነከ ፡ ለርእየ ፡ ሕልመ ፡ አቡከ ። አጽንኖ ፡ እንዘ ፡ ኢይዘርዑ ፡ እምድማሬሁ ፡ (ዮሐ፲፱ ፡ ፴ ። ዲድ ፡ ፱ ። ኢዮ፴፰ ፡ ፴፱ ። ዘፍ፳፱ ፡ ፲፬ ። ሔኖ፹፰ ፡ ፱ ። ቅዳ ፡ አፈ) ።

**ጸኒዕ ፤ ዖት ፤ (ጸንዐ ፡ ይጸንዕ ፡ ይጽናዕ ። ዕብ ፡ ጻናዕ ፤ ታገሠ)** ፤ መጥናት ፤ መጠንከር ፤ መበርታት ፡ ማየል ፤ መድረቅ ፡ መክረር ፤ ጸንቶ ፡ መኖር ፤ ቀዋሚ ፡ መኾን ። ጸንዐ ፡ ልቡ ። ወጸንዓ ፡ እገሪሁ ፡ ወሐቌሁ ። ጸንዐ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ቀትል ። ትጸንዕ ፡ እምኵሎሙ ። ሀገር ፡ ትጸንዕ ፡ በጥበቢሆሙ ፡ ለሊቃውንት ። ኢይጸንዕ ፡ ቃሉ ፡ (ዘፀ፯ ፡ ፲፫ ። ግብሮ ፡ ፯ ። ኢሳ፴፱ ፡ ፳፩ ። ሕዝ፫ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፭ ፡ ፱) ።

—፤ መታወቅ ፡ መታመን ፤ ርግጥ ፡ መኾን ። ማደግ ፡ መጕልመስ ፤ እካለ ፡ መጠን ፡ ማድረስ ። መብዛት ፡ መፈድፈድ ። መርቀቅ ፡ መጥለቅ ፡ መጨለም ፤ የምስጢር ። ናሁ ፡ ጸንዐ ፡ በኀበ ፡ ማእምራን ፡ ከመ ፡ ቍርባን ፡ በጸሎተ ፡ ካህን ፡ ይከውን ፡ ሥጋሁ ፡ ለኢየሱስ ። ወልድየ ፡ ዓዲሁ ፡ ደቂቅ ፡ ወኢጸንዐ ። ሶበ ፡ ጸንዐ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ዐግተት ። ነዳየ ፡ ሃይማኖት ፡ ይሁዳ ፤ ሔጦ ፡ ለወልድ ፡ ሰርጕ ፡ አቡሁ ፡ ጸዐዳ ፤ እስመ ፡ ጸንዐ ፡ ቦቱ ፡ ካሕደ ፡ ልብ ፡ ዕዳ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፯ ። ፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፳ ። ዮሴፍ ። ቅኔ) ። የጸንዐ ፡ ዐማርኛ ፡ እንደ ፡ ኮነ ፡ ብዙ ፡ ስልት ፡ አለው ፤ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ ከጽንዕ ፡ አይወጣም ፤ መንገዱም ፡ የሰብሐና ፡ የገብረ ፡ ነው ፤ ሲሳላ ፡ ገብረን ፤ ሲጠብቅ ፡ ሰብሐን ፡ ይመስላል ፤ በሰብሕ ፡ መንገድ ፡ ሲገሰስ ፡ ገቢር ፡ እንጂ ፡ ተገብሮ ፡ አይኾንም ፤ ይኸውም ፡ ለብቻው ፡ ተጥፏል ።

**ጽኑዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ንዕት)** ፤ የጠና ፤ ጥኑ ፤ ብርቱ ፤ ጠንካራ ፤ ጥብቅ ፤ ደረቅ ፡ ከራራ ። እብን ፡ ጽኑዕ ። ኵሉሕ ፡ ጽንዕት ። አመ ፡ ጽኑዐ ፡ ይገብር ፡ መሠረታተ ፡ ምድር ። አጽዋናት ፡ ጽኑዓን ። አህጉር ፡ ጽኑዓት ፡ (ጥበ፲፭ ፡ ፱ ። ኢሳ፶፩ ፡ ፩ ። ምሳ፰ ፡ ፳፱ ። ፪ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፬ ። ኩፋ ፡ ፲፩) ።

—፤ ጨካኝ ፤ ዐርበኛ ፤ ታላቅ ፤ ብዙ ። ጽኑዐ ፡ ልብ ። ጽኑዕ ፡ በውስተ ፡ ቀትል ። ሕዝብ ፡ ጽኑዕ ፡ (ምሳ፲፯ ፡ ፰ ። ሢራ፴፯ ፡ ፰ ። ኢሳ፰ ፡ ፳፱) ።

**ጽንዐት ፤ (ታት)** ፤ መጥናት ፤ መጠንከር ፤ ጥናት ፤ ጥንካሬ ፤ ጭከና ፤ ብዛት ፤ ብርታት ፤ ብርቱነት ።

ጽንዐት ፡ ልብ ። ትክለት ፡ ወጽንዐት ። ሶበ ፡ ርእየ ፡ ጽንዐቶሙ ። ጽንዐት ፡ ዝኩ ፡ ሥቃይ ። ጽንዐት ፡ ቍር ፡ (አፈ ፡ ድ፺ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፯ ። አፈ ፡ ድ፺ ። ግብ ፳፰ ፡ ፱) ።

**ጽንዕ ፤ (ዓት) ፤** ጥናት ፤ ብርታት ፤ ኀይል ፤ ጥንካሬ ፤ ጠፈር ። ጽንዐ ፡ ልብ ። በብዝኆ ፡ ጽንዑ ። ጽንዐ ፡ ሰማይ ፡ (ማር፲፰ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፴፱ ። ዘፀ፳፬ ፡ ፲) ።

**አጽንዐ ፤** አጠና ፤ አበረታ ፤ አጠነከረ ፤ መሠረተ ፤ አጠበቀ ፡ ጠረነቀ ፤ ሳበ ፡ ገተረ ፤ ዘረጋ ፡ አከረረ ፤ ያዘ ፡ ጨበጠ ። አጽንዑ ፡ ገጾሙ ፡ እምኵሎሙ ። አመ ፡ ያጸንዕ ፡ መንበሮ ፡ ላዕለ ፡ ነፋሳት ። ወአጽንዐ ፡ እገሪሆሙ ፡ ውስተ ፡ ጕንድ ። አጽንዐ ፡ አውታረ ፡ አርጋኖን ። ኢመታ ፡ ታጸንዕ ፡ ሰፈቲል ። ዘያጸንዕ ፡ ሰብዐተ ፡ ኮከበ ፡ በየማኑ ። ወያጸንዑ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ፀበርተ ፡ (ኤር፳፫ ፡ ፫ ። ምሳ፰ ፡ ፳፯ ። ግብ፲፮ ፡ ፳፬ ። ዘር፴ ፡ ያዕ ። ምሳ፳፱ ፡ ፴፯ ። ራእ፪ ፡ ፩ ። ፯ ፡ ፱) ። ያዘ ፡ ጨበጠ ፡ ማለት ፡ ጣፊና ፡ መላሽ ፡ በእንጕዝና ፡ በእንዝ ፡ ፈንታ ፡ ያጸንዕ ፡ እያሉ ፡ ስለ ፡ ጣፉት ፡ እንጂ ፡ ዘይቤው ፡ አይደለም ።

—፤ ጠበቀ ፤ አጠና ፤ ያዘ ፤ የሕግ ፡ የትምርት ። አጽንዕ ፡ ዘብከ ። አጽንዖ ፡ ሃይማኖት ። ሶበ ፡ ያነብቦ ፡ ለመጽሐፍ ፡ አሐደ ፡ ጊዜ ፡ ያጸንዖ ፡ (ራእ፫ ፡ ፲፩ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

**አጽናዒ ፤** የሚያጠና ፤ አጥኝ ፡ (ፈላስ) ።

**መጽንዕ ፤ ዒ ፤** መጥኛ ፤ ማጥኛ ። የሚያጠና ፤ መጥኒ ፤ አጥኝ ፤ ደጋፊ ። መጥኚ ፡ ይስጥኽ ፡ እንዲሉ ። ረዳኢ ፡ ወዐቃቤ ፡ ወመጽንዒ ። ኅረይ ፡ መዝሙረ ፡ መጽንዒ ፡ ወመድኅኔ ፡ (ግንዘ ። ፊልክ ፡ ፲፰፫) ።

**ተጻንዐ ፤ (ጸንዐ) ፤** ተጣና ፤ ተበራታ ፡ ተጠናከረ ፤ በገዛ ፡ እጁ ፡ ወይም ፡ ርስ ፡ በርሱ ። ተደራረጊና ፡ ተደራራጊ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ተባረከ ፡ ኹለት ፡ ያሳያል ። ተደራጊ ፡ ሲኾን ፡ የጸንዐ ፡ ድርብ ፡ ነው ። ተደራጊም ፡ ቢኾን ፡ ተደራራጊነት ፡ አይቀርም ፤ የሕዋሳትን ፡ ርስ ፡ በርስ ፡ ይሻል ። ጊዜ ፡ ተጻንዖቱ ፡ ተቃትሎተ ፡ ሰይጣናት ፡ ምስሌሆሙ ፡ (ፊልክ ፡ ፹፭) ።

**አስተጻንዐ ፤ (አጽንዐ) ፤** አጣና ፤ አበራታ ፤ አጠናና ፡ አበረታታ ፤ አይዞኽ ፡ አይዞኽ ፡ አለ ። አድራጊና ፡ አደራራጊ ፡ ነው ፤ ባድራጊነቱ ፡ የአጽንዐ ፡ ድርብ ። በምስጢር ፡ ግን ፡ አደራራጊነት ፡ አይቀርም ። አስተጻንዐ ፡ መዝራዕቶ ፡ ወአቈልቈለ ፡ ኵናቶ ። ፈቀደ ፡ ያስተጻንዖ ፡ ምዕማደሁ ። ዘንተ ፡ ይቤ ፡ ከመ ፡ ያስተጻንዖሙ ። ያስተጻንዖ ፡ ፍኅረተ ፡ በቅድመ ፡ ክልኤቱ ፡ ካህናት ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ወበመስቀል ፡ ወበሕልቀት ፡ (ገድ ፡ ተክ ። አፈ ፡ ድ፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፫) ።

(ጥ) **ጸንዖ ፤ ዖት ፤ (ጸንዐ ፡ ይጼንዕ ፡ ይጸንዕ) ፤** አጽንዖ ፤ ማጥናት ፤ ማበርታት ፤ ማጠንከር ፤ ማደስ ፡ መጠገን ። ጸንዖሙ ፡ ለአኅዊከ ። ወአስተርአዮ ፡ መልአክ ፡ ዘይጼንዖ ። ዘይጼንዎ ፡ መፍቅደ ፡ ብሔር ። በዘይጼንዎ ፡ ቤደቀ ፡ (ሉቃ፳፪ ፡ ፴፪ና ፡ ዓ፫ ። ሢራ፴፰ ፡ ፴፬ ። ፬ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፭) ።

**ጸናዒ ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት ፤ ዕት) ፤** አጽናዒ ፤ የሚያጠና ፤ የሚያበረታ ፤ አይዞኽ ፡ ባይ ፤ ኀያል ፤ ዐርበኛ ፤ የጦር ፡ አለቃ ። ምስለ ፡ ሠለስቱ ፡ ጸናዕት ። ዕደው ፡ ጸናዕት ፡ (፩ዜና ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ። ፳፩ ፡ ፩) ። ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ጸናዕት ፡ ይላል ፤ አያስኬድም ። አህጉር ፡ ጸናዕት ። ዘሎ ፡ ሰራዊት ፡ ጸናዕት ፡ (፪ዜና ፡ ፰ ፡ ፬ ። ፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፰) ።

**ተጸንዐ ፤** ተጠና ፤ ተያዘ ፤ ከልብ ፡ ገባ ፤ ተረዳ ፤ ትምርቱ ፡ ቃለሙ ።

**ጽኑዕ ፤** የተጠና ፤ የተለመደ ፤ በቃል ፡ የተያዘ ።

**ጽናዔ ፤** ማጥናት ፤ መጠናት ፤ አጠናን ፤ ጥናት ፤ ጥኑነት ። ከመ ፡ ያስተርኢ ፡ ጽናዔሃ ፡ ወአፍቅሮታ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፵) ።

**ምጽናዕ ፤ (ዓት) ፤** መጥኛ ፤ መጠንከሪያ ፤ ማጥኛ ፡ ማበርቻ ። ሰማይ ፤ ጠፈረ ፡ ሰማይ ፤ ከሀሞስ ፡ ጋራ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ የተጠናና ። ሀሞስን ፡ ተመልከት ። ወበዕለተ ፡ ሳኒት ፡ ገብረ ፡ ምጽናዓተ ፡ ማእከለ ፡ ማይ ። እፎኬ ፡ ዘኢንኅሉ ፡ ምጽናዓተ ፡ በማይ ። ለዘመጽአ ፡ ወልደ ፡ በአፈ ፡ ነቢያት ፡ ተሰቢኮ ፤ ከመ ፡ ያስተፋኑ ፡ ሐራ ፡ መልአክ ፡ እስከ ፡ ምጽንዓት ፡ ኅምስ ፡ ሚካኤል ፡ ተሰውኮ ፡ (ኩፋ ፡ ፪ ። መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፪) ።

**ጸኒፍ ፤ ፎት ፤ (ጸንፈ ፡ ይጸንፍ ፡ ይጽንፍ ። ዕብ ፡ ጻናፍ) ፤** ማልበስ ፤ ማጐናጠፍ ፤ ማጠፍ ፤ ማፍና ፡ ማፋን ፡ መግጠም ፤ ወይም ፡ መጠምጠም ፤ መጠቅለል ፤ የልብስ ፡ የፈትል ። ዳርቻ ፡ ማፍ ፡ መኾን ፤ ወደ ፡ ዳር ፡ መውጣት ፤ ዳር ፡ ዳር ፡ ማለት ።

**ጸናፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት) ፤** የሚጸንፍ ፤ ዳርቻ ፡ የሚኾን ፤ ጽንፋይ ፤ አፍኣዊ ፤ ዘአፍኣ ። ዐጺድ ፡ ጸናፊ ። ጸናፊ ፡ ጽልመት ። ጸናፊት ፡ ደብተራ ፡ (ራእ ፲፩ ፡ ፪ ። ማቴ፳ ፡ ፲፪ ። ዕብ፱ ፡ ፯) ።

**ጽንፈት ፤** ዳርቻ ፡ መኾን ፤ ዳርቻነት ። አፍኣ ፡ ዕዳሪ ፤ ከውስጥ ፡ ከቤት ፡ ከቅጥር ፡ ውጭ ። አዘዘ ፡ ያውፅእዎ ፡ ኀበ ፡ ጽንፈተ ፡ ጽልመት ፡ (ቀኖ ፡ ኒቅ ፡ ፳፱) ።

**ጽናፌ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ። ውስተ ፡ ብካይ ፡ ወሐቅየ ፡ ስነን ፡ ወጽናፌ ፡ ጽልመት ፡ (ቀሌ) ።

**ጽንፍ ፤ (ዐረ ፡ ጺንፍ) ፤** ማፍ ፤ ዘርፍ ፤ ዳርቻ ፡ ጠረፍ ፤ ወደብ ፡ ገደብ ፤ ወሰን ፡ ደንበር ። ጽንፈ ፡ ልብስ ። ጽንፈ ፡ ውሒዝ ። ጽንፈ ፡ ባሕር ። ጽንፈ ፡ ምድር ፡ (ሩት፫ ፡ ፱ ። ሢራ፴ ፡ ፲፰ ። ፪ዜና ፡ ፰ ፡ ፲፯ ። ሔኖ፲፰ ፡ ፭) ።

**ጽኑፍ ፤ አጽናፍ ፤** ማሮች ። ጽኑፊሁ ፡ ለልብስ ። ጽንፈ ፡ አልባስ ። አጽናፈ ፡ ዓለም ፤ አጽናፈ ፡ ሰማይ ። አጽናፈ ፡ ምድር ። ውስተ ፡ ዙሉ ፡ አጽናፍ ። መላኬ ፡ ዙሉ ፡ አጽናፍ ፡ (ዘፀ፴፮ ፡ ፳፱ ። ዘኍ፲፭ ፡ ፴፰ ። መዝ፲፰ና ፡ ፪ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ መስ፪) ።


**መጽንፍት ፤ (ዕብ ፡ ሚጽኔፌት) ፤** የራስ ፡ ልብስ ፤ ጌጥ ፡ መሸፈኛ ፤ ሰበን ፤ ጥምጥም ፡ ከንቶቡ ፤ ክህናት ፡ አሪት ፡ የሚለብሱት ፡ (ሕዝ፳፩ ፡ ፳፮) ።

**ጸንፈርት፤—ወፈንጠር፤—ፀንፈርት።**

**ጸንጽሎ፤ ሎት፤ (ጸንጸለ፡ ይጸነጽል፡ ይጸንጽል። ዕብ፡ ጻልጼል)፤** መጸንጸል፡ መምታት፤ ማንቧቧት፤ መደወል፡ ማቃጨል፤ ማቅጨልጨል፤ የማዕደን። ዘሩ፡ ንጻለ፡ ነው።

**ጸንጻሊ፤** የሚያቃጭል፡ የሚያንቧቧ፤ ደዋይ፡ አቃሚይ፡ (አርጋ፡ ፩)።

**ጸንጸል፤ (ብ፡ ጸናጽል፤ ላት)፤** ሻሹራ፤ ቃጭል፤ በቁሙ፡ ጸናጽል። ወገብሩ፡ ጸናጽለ፡ ዘወርቅ። አርባዕተ፡ ምእተ፡ ጸናጽለ። ጸናጽላተ፡ ብሩር። እሰሊ፡ በጸናጽል፡ ወእሰሊ፡ በከበሮ። ጸናጽል፡ ዘሠናይ፡ ቃሉ፡ (ዘፀ፴፰፡ ፴፩። ፪ዜና፡ ፬፡ ፲፫። መጽ፡ ምስ። ፩ዜና፡ ፲፫፡ ፰። መዝ፡ ፻፶)።



ጸንጸል፡

**ተጸንጸለ፤** ተመታ፤ ተቃጨለ። አንቲ፡ ተጸንጻሊ፡ (አርጋ፡ ፩)።

**ጽንጹል፤** የተመታ፡ የተቃጨለ፤ ቅጭል፡ ቅጭል፡ ቧ፡ ቧ፡ የሚል።

**ጽንጻሌ፤** መቅጨልጨል፤ መንቧቧት፤ ጸናጽል፡ አያያዝ፤ አመታት።

**ጸንጸነ፤ (ጸኒን፡ ጸነ)፤** ጠነጠነ፤ ነቀዘ፤ አረጀ፡ ተበላሸ፤ ከንቱ፡ ኾነ።

**ጽንጹን፤ (ናን፡ ናት፡ ጽንት)፤** የጠነጠነ፤ የነቀዘ፤ ያረጀ፡ ያፈጀ፤ የዣገ፡ ዥገዥ፤ የተበላሸ፡ ብልሹ፤ ጥንጣናም፡ ነቀዛም፡ ከንቱ። ብሂልስ፡ ኢሀሎ፡ ቃለ፡ እግዚ፤ ሕሰው፡ ወዘጽንጹን፡ ኅሊና፡ ነገር፡ ውእቱ። ደርኢ፡ ጳውሎስ፡ በዙሉ፡ ከመ፡ ክህነት፡ ዘኦሪት፡ እንተ፡ ሰደም፡ ወጤስ፡ ከመ፡ ጽንጽንት፡ ይእቲ፡ ወኢትበቍዕ፤ ወአልባቲ፡ ኀይል፡ ግሙራ፡ (ቄር፡ እበተ። ተረ)። ሐሳብ፡ በእንተ፡ ጽንዕት፡ ወጽንጽንት፤ ጠፈታ፡ ፅንጨት፡ የሚቈረጥበት፡ ወራት። በመስከረም፡ እስከ፡ ዐሥርቱ፡ ወኅምስቱ፡ ጽንዐት፤ ወእምዝ፡ ጽንጽት፤ በጥቅምት፡ እስከ፡ ዕሥራ፡ ወሠለስቱ፡ ጽንዐት፤ ወእምዝ፡ ጽንጽንት፡ (መ፡ ፈ)። ከኅዳር፡ እስከ፡ ነሐሴ፡ ላሉትም፡ ወሮች፡ እንደዚሁ፡ ጽንዐትና፡ ጽንጽንት፡ አላቸው።

**ጽንጽንያ፤ (ያት)፤** ጥንጣን፤ ነቀዝ፤ ዝንብ፡ ትንኝ። ጽንጽንያ፡ ምዉት። በዓለ፡ ጽንጽንያ። ጽንጽንያት፡ ንኡሳን፡ (መክ፲፡ ፩። ፬ነገ፡ ፩፡ ፪። ፍ፡ ን፡ ፲፬)።

**ጸናጺት፤** ዝኒ፡ ከማሁ፤ ዝንብ፤ የዝንብ፡ ወገን፤ ትንኝ፡ ፀኮት፤ ተቈናጣጭ፡ ፍጥረት። ጸጼትንና፡ ፀኮትን፡ ተመልከት። ይሰሕቦ፡ እግዚ፡ ለጸናጺት፡ ወለንህብ፡ (ኢሳ፯፡ ፲፰። ዘፀ፰፡ ፳፩—፳፪)። በጸናጺት፡ ፈንታ፡ ጸጼት፡ ይላል፤ ፍችው፡ ፩፡ ነው፤ ብቻ፡ ታናናሽነትን፡ ያሳያል።

**ጸንቀቀ፤ (ጠንቀቀ)፤** ነከረ፤ ዘፈቀ፤ አጨቀየ፡ አጨማለቀ፤ ለወሰ፤ በከለ፤ ፈጸሞ፡ አሳደፈ፤ አሾለፈለፈ። ዘብሑ፡ ደቤላ፡ ጠሊ፡ ወጸንቀቁ፡ ልብሶ፡ ለዮሴፍ፡ በደም፡ (ኩፋ፡ ፴፱። ዘፍ፴፯፡ ፴፩)። ዘሩ፡ ጠንቀቀ፡ ነው፤ ጠ፡ ለጸ፡ ተለውጧል፤ ምስጢሩም፡ ፈጸሞ፡ ጠንቅቆ፡ ያሰኛል። ጽንጕን፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ወጥቷል፤ ቀና፡ ን፡ በብዙ፡ ቦታ፡ ይወራረሳሉ፤ ጸና፡ ጠ፡ እንዲወራረሱ።

**ተጸንቀቀ፤** ተነከረ፤ ተጨማለቀ፤ ፈጽሞ፡ አደፈ።

**ጽንቁቅ፤ (ቃን፡ ቃት፡ ቅቅት)፤** የተነከረ፤ በርስሐት፡ በደም፡ የተበከለ፤ እድፋም፡ ጨምላቃ፤ ሥልፍልፍ። እመ፡ ከንኪ፡ ዕራቀኪ፡ ወሀሎኪ፡ ጽንቅቅተ፡ በደምኪ፡ (ሕዝ፲፮፡ ፳፪)።

**ጽንቃቄ፤** መነከር፡ መዘፈቅ፤ መጨማለቅ። እድፍ፤ ርስሐት፤ ጭቅቅት።

**ጸንሰ፤—ፀነሰ፥አረገዘ፤—ፀኒስ፡ ፀንሰ።**

(ጥን) **ጸንሶ፤ ሶት፤ (ጸነሰ፡ ይጼንስ፡ ይጸንስ)፤** መቸገር፤ ማጣት፤ መደኸየት፤ አይቶ፡ ዐጣ፡ ችጋረኛ፡ መኾን፤ መዋረድ፡ መመስከን። ዘሩና፡ ምስጢሩ፡ የፀንሰ፡ ነው፤ ፅንስ፡ እያደገና፡ እየጠና፡ እንዲኼድ፡ የችግሩን፡ ጽናት፡ ያሳያል። መጽሐፍ፡ ግን፡ በጸነሰ፡ ፈንታ፡ ተጸነሰ፡ ይላል፤ ተ፡ ያማርኛ፡ ነው፤ የጸነሰ፡ ፍች፡ ተቸገረ፡ ማለት፡ ስለ፡ ኾነ፡ ጸሓፊና፡ መላሽ፡ አላገባቡ፡ ጥፈውታል። እምከመ፡ ተጸነሰ፡ ካልእከ። ይጼንሱ፡ እክለ፡ ወማየ። እምይእኤሰ፡ ኢይጼነስ፡ እንከ፡ (ዘሌ፳፭፡ ፴፭። ሕዝ፬፡ ፲፯። ሚራ፲፩፡ ፳፱)።

**ጽኑስ፤ (ሳን፡ ሳት፡ ንስት)፤** የተቸገረ፤ ችጉር፤ አይቶ፡ ዐጣ፤ ችጋረኛ፤ ድኻ፡ ወራዳ፤ ለማኝ፡ ቧጋች፤ ጦም፡ ዐዳሪ፤ ምስኪን። ወኢትትሀከይ፡ ገቢረ፡ ሠናይ፡ ለጽኑስ። ጽኑሳን፡ እምዙሉ፡ ሠናያት። ወአልቦ፡ እምውስቴቶሙ፡ ጽኑስ፡ (ምሳ፫፡ ፳፯። ኢዮ፴፡ ፬። ግብ፬፡ ፴፬)። ዘታጼንስ፡ ዘታስተጼንስ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ ዘጽንስት፡ ይላል፤ አያሰኝም። ዘጽንስት፡ ጥቀ፡ አውፅእት፡ (ፊልክ፡ መጨ)።

**ጽናሴ፤** መቸገር፡ ማጣት፤ ችግር፡ ዕጦት፡ ድኽነት፡ (ፊልክ)።

**ተጽናስ፤** ዝኒ፡ ከማሁ፤ ችግር፤ ችጋር፡ ቀጠና፤ ረኀብ፡ ዕርዝና፤ ፍጹም፡ ድኽነት። ተጽናስከ፡ ይሰድዶሙ፡ ለአዕርክቲከ። ዘይፈቅዱ፡ ለተጽናሶሙ። ብዕልስ፡ እመ፡ በጽድቅ፡ ወበኀጢአት፡ ተጽናስ፤ አክሕብ፡ እንዘ፡ ሀሎ፡ እምኢተጸነሰ፡ ኤልያስ፡ (ሚራ፲፪፡ ፬። ያዕ፪፡ ፲፯። ቅኔ)።

**አጼንሰ ፤ አስተጼንሰ ፤** አስቸገረ ፤ ችጋር ፡ አመጣ ፤ ነማ ፡ አሳጣ ። ኢያስተጼንስ ፡ እግዚ ፡ ነፍሰ ፡ ጻድቅተ ። ኢያስተጼንሶሙ ፡ እምበረከቱ ፡ (ምሳ፲ ፡ ፫ ። መቃ ። መዝ ፡ ፴፫) ።

**ጼናታም ፤—ጤናዳም ፤—ጼነወ ።**

**ጸንጰወ ፤ (ጸነፈ ፤ ጸንፈወ) ፤** ጨቈነ ፡ ደፈጠጠ ፤ መታ ፡ ቀጠቀጠ ፤ አጠዘ ፡ ጠመዘዘ ። ከልብስ ፡ ዕጥበትና ፡ ዘፈረ ፡ ልብስን ፡ ከማከረር ፡ ከመፍተል ፡ ከመ ቋጨት ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ጸነፈን ፡ ተመልከት ። እምንእሱ ፡ አጸንጽዎ ፡ አዕፅምተ ፡ ገበዋቲሁ ። ወደ ጸነጽዉኒ ፡ አዕፅምትየ ፡ (ሚራ፴ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፵፭) ።

**ተጸንጰወ ፤** ተጨቈነ ፤ ተቀጠቀጠ ፤ ተጠመዘዘ ።

**ጽንጽው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ጺት) ፤** የተጨቈነ ፤ የተቀጠቀጠ ፤ ቅጥቅጥ ፤ ጠማማ ፡ ቈልማማ ። ዘጽንጽው ፡ ወዘጽቱም ። መንከብያቲሁ ፡ ጽንጽዋት ፡ (ዘሌ፳፪ ፡ ፳፬ ። ኪዳ) ።

**ጸንጰላዕት ፤** የእባት ፡ እራት ። ወከመ ፡ ጸንጰላዕት ፡ ትወድቁ ፡ ማእከለ ፡ እሳት ፡ (ድር ፡ ሰን) ።

**ጽዕብ ፤ ብት ፤ (ዕብ ፡ ጻቡዕ ። ዐረ ፡ ፀቡዕ) ፤** ነጣቂ ፡ አውሬ ፤ የኽርብ ፡ የውሻ ፡ ወገን ፤ ማሽ ፡ ፋሪ ፤ መቃብር ፡ ቈፋሪ ፤ ሬሳ ፡ እያወጣ ፡ የሚበላ ። ባለ ብሎዮች ፡ ግን ፡ ተቈናጣጭ ፡ ዝንብ ፡ ይሉታል ።



ጽዕብ ፡

**አጽዓብ ፤ አጽዕብት ፤** ነጣቆች ፡ አራዊት ፤ ማሾች ፡ ሬሳ ፡ አውጭዎች ፤ ከብዙ ፡ በቀር ፡ ባንድ ፡ አይገኝም ። አዝእብት ፡ ወአክልብት ፡ ወአጽዕብት ፡ (ሔኖ ፡ ከ፱) ።

**ጽዒድ ፤ ዶት ፤ (ጸዐደ ፡ ይጽዕድ ፡ ይጽዐድ ። ዕብ ፡ ጻዐድ) ፤** አጥብቆ ፡ መኼድ ፡ መራመድ ፤ በኀይል ፡ መርገጥ ፡ እግርን ፡ ማንሣት ፤ መር ፡ መር ፡ አፈፍ ፡ አፈፍ ፡ ማለት ፤ የጕብዝና ፡ የወታደር ፡ የስልፈኛ ፡ አካኼድ ፡ አረጋገጥ ። ርምጃ ፡ ርግጫ ፡ እንዲል ፡ (ሰልፍ ፡ አስተማሪ) ።

—፤ መጣድ ፡ ማስረር ፤ በምስት ፡ ጕልቻ ፡ ላይ ፡ ማኖር ። በውስጡ ፡ ያካኼድ ፡ ምስጢር ፡ እሳት ፤ ከጕልቻ ፡ እስከ ፡ ጕልቻ ፡ ያለው ፡ መጠን ፡ ምሥጋርን ፤ ቢያንስም ፡ መጠን ፡ ስኩናን ፤ የድስቱና ፡ የምጣዱ ፡ ምጥቀት ፡ በእግር ፡ እንሣሥ ፡ ልክ ፡ መኾኑን ፡ ከዚያ ፡ አለመብለጡን ፡ ያሳያል ፤ ቢበልጥም ፡ በመዝለልና ፡ በመፈንጨት ፡ ፊቤ ፡ በመምታት ፡ ይመሰላል ።

**ጸዓዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤** የሚኼድ ፤ የሚጥድ ፡ ጣጅ ። (ተረት) ፤ የቤት ፡ ጣጅ ፤ የዱር ፡ ጠማጅ ።

**ተጽዕደ ፤** ተጣደ ፤ ምድር ፡ ሰቀቀ ፤ ከጕልቻ ፡ ላቀ ፤ በላይ ፡ ኾነ ፤ ጕልቾች ፡ የሳንሳ ፡ ያዙት ፤ ተሸከሙት ።

**ጽዑድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ዕድ) ፤** የተጣደ ፡ ተጥዶ ፡ ያለ ፤ የተደላደለ ።

**ጽዕደት ፤** መጣድ ፤ (ጥጣ) መጣድ ፤ አጣጣድ ፤ ጥደሽ ፤ በቁሙ ፡ ጥደት ፤ ምጣድ ፤ ዝርግ ፡ ክብ ፤ የሸክላ ፡ የብረት ። ዲያቆናት ፡ ግን ፡ በጽዕደት ፡ ፈንታ ፡ ጽዕዱት ፡ ይሉታል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**ምጽዓድ ፤** መጣጃ ፤ ምድጃ ፤ ጕልቻ ፤ የምጣድ ፡ ቤት ፤ በቁሙ ፡ ምጣድ ፤ ምንን ፡ (ዐማርኛ) ።

**ጻዕደወ ፤ (ትማ ፡ ጸዕደ) ፤** ነጣ ፤ ነጭ ፡ ኾነ ፤ ጠራ ፡ በራ ፤ ንጣቱ ፡ ጥራቱ ፡ ከልክ ፡ ዐለፈ ። ወአልባሲሁኒ ፡ በረቁ ፡ ወጻዕደዉ ፡ ጥቀ ፡ ከመ ፡ በረድ ፡ ዘኢይክል ፡ መሀፒል ፡ አጻዕድዎ ፡ ከማሁ ። ጻዕደዉ ፡ እምበረድ ። ተኀፀበኒ ፡ ወእጻዐዱ ፡ እምበረድ ። ይጻዐዱ ፡ አርእስተ ፡ ደቂቅ ፡ በሚበት ። ወለእመ ፡ ጻዕደወ ፡ ቋዕ ፡ ከመ ፡ ራዛ ፡ (ማር፱ ፡ ፫ ። ስቈ፬ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፶ ። ኩፋ ፡ ፳፫ና ፡ ፴፯) ።

**ጻዕዳዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** የሚነጣ ፤ የሚጠራ ፤ ንጣት ፡ ጥራት ፡ የሚስማማው ። ቢያጥቡ ፡ አይጠራ ፡ እንዲሉ ።

**ጽዕድው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ዱት) ፤** የነጣ ፤ የጠራ ፤ ኖራ ፡ የመሰለ ። ጽዕድዋን ፡ አርጋብ ። አእዱግ ፡ ጽዕድዋን ። ጽዕዱት ፡ ወብርሀት ። ወጽዕዱት ፡ ይእቲ ፡ ከመ ፡ ባሕርይ ፡ (ሰንክ ፡ ጥር፲፭ ። መሳ፭ ፡ ፲ ። ማሕ፰ ፡ ፰ ። ራእ፳፭ ፡ ፲፭) ።

**ጽዕዳዌ ፤ (ውያት) ፤** መንጣት ፤ መጥራት ፤ ንጣት ፡ ጥራት ፤ አንጣጥ ፤ ነጭነት ። እግዚአብሔር ፡ አክበረከ ፡ በጽዕዳዌ ፡ ጸጕር ። ጽዕዳዌ ፡ ፀምር ። ጽዕዳዌ ፡ ወሊታ ፡ (አፈ ፡ ተጊና ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ መስ፳፱) ። በጽዕዳዌ ፡ ፈንታ ፡ ጻዕዳ ፡ ጽዕዱት ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። አስተርአየ ፡ ጻዕዳሆን ፡ ለእማንቱ ፡ አብትር ። ዕጹብ ፡ ለዐይን ፡ ሥኑ ፡ ጽዕዱቱ ፡ (ዘፍ፴ ፡ ፴፯ ። ሚራ፵፫ ፡ ፲፰) ።

**ጸዐዳ ፤ (ዓድው) ፤** ነጭ ፤ ጥሩ ። እትየሰ ፡ ጸዐዳ ፡ ወቀይሕ ። ልብሱ ፡ ጸዐዳ ፡ ከመ ፡ በረድ ። ዘጸዐዳ ፡ ጸጕሩ ። አፍራስ ፡ ጸዓድው ። አልባስ ፡ ጸዓድው ። አክሊላት ፡ ጸዓድው ፡ (ማሕ፭ ፡ ፲ ። ዳን፯ ፡ ፱ ። ዘፍ፴ ፡ ፴፪ ። ዘካ፩ ፡ ፰ ። ራእ፬ ፡ ፬ ። አርጋ) ።

**ጸዐድዒድ ፤ (ድት ፡ ዳን ፡ ዳት) ፤** ፍጹም ፡ ነጭ ፤ ነጣነጭ ፤ ጸዐዳዊ ፤ ወደ ፡ ነጭነት ፡ የሚያደላ ። ናርዶስ ፡ ዘጸገየ ፡ በጸዐድዒድ ። ሕ ፡ ጽጌያት ፡ ሥነክሙ ፡ ጸዐድዒደ ፤ እግዚ ፡ ይርአይ ፡ እምሰማይ ፡ ወረደ ። ሕብራት ፡ ጸዐድዒዳን ፡ (አርጋ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ መስ፳፰ ። ፈላስ) ።

**አጻዕደወ ፤** አነጣ ፡ አጠራ ፤ ነጭ ፡ አደረገ ። አጻዐድዎ ፡ ከመ ፡ በረድ ። በዘአጻዕደወት ፡ አዕጹቂሃ ። ኢትክል ፡ አጻዕድዎ ፡ አሐተ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእስከ ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፲፰ ። ዮኤ፩ ፡ ፯ ። ሲኖዶ) ።

**ጽዒጥ ፤ ጦት ፤ (ጽዕጠ ፤ ጸዐጠ ፡ ይጽዕጥ ፡ ይጽዐጥ ። ዐረ ፡ ሰ ፤ ጸዐጠ) ፤** መቀመም ፡

ማጣፈጥ ፤ ማንጠር ፡ ማቅለጥ ፤ መቅባት ፡ መርጨት ፡ መረብረብ ፤ የሽቱ ፡ የመድኀኒት ። ዐቀብተ ፡ ሥራይ ፡ ይጽዕጡ ፡ ፈውሰ ፡ ለቍሱላን ፡ በዘይተ ፡ ሃይማኖት ። ዕፍረት ፡ ዘእደ ፡ ዮሴፍ ፡ ጸዐጠ ። ሕእዳወ ፡ ፍቅርኪ ፡ በላዕሌየ ፡ ይጽዐጣ ፤ ዕፍረተ ፡ መዐዛ ፡ ወቅብዐ ፡ ዘብዙኅ ፡ ሤጣ ። ጸዐጡ ፡ ሥጋየ ፡ በከርቤ ፡ ወበሰሊክ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ መጋ፳፪ ። ኑሐ፲፪ ። አቡሻ ፡ ፵፪) ።

ጸዓጢ ፤ የሚቀምም ፤ የሚያጣፍጥ ፡ አጣፋጭ ፤ ሽቱ ፡ ሽያጭ ።

መጽዕጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ። መጻዕጥ ፡ ጣት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ የቤት ፡ ሲኾን ፡ ጥ ፡ ይጠብቃል ። ይነሥእ ፡ አዋልዲክሙ ፡ ለመጽዕጣት ፡ (፩ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፫) ።

ተጽዕጠ ፤ ተቀመመ ፤ ተጣፈጠ ፤ ተነጠረ ፤ ተዘጋጀ ። ተቀባ ፡ ተረጨ ፡ ተረበረበ ፤ ሽቱው ፡ ሰዉ ፡ ልብሱ ።

ጽዑጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ዕጥ) ፤ የተጣፈጠ ፤ የተነጠረ ፤ ጥሩ ፡ ዝግጁ ። የተቀባ ፡ ቅቡዕ ። ዕፍረተ ፡ መዐዛ ፡ ጽዑጥ ። አፈዋተ ፡ ርሔ ፡ ጽዑጣን ፡ ዘይትዐቀብ ፡ በቀርን ፡ ቅብዐ ፡ ዘጽዮን ፡ (ስንክ ፡ የካ፲ ። መጽ ፡ ምስ) ።

(ሳ) ጽዕጥ ፤ ጽዒጥ ፤ ጥሩ ፡ ሽቱ ። ጽዒጥ ፡ ዘጸዓጢ ። ጽዒጥ ፡ ወዕጣን ፡ (ዘፀ፴ ፡ ፳፭ና ፡ ፴፪ ። መቃ) ።

አጽዐጠ ፤ አስቀመመ ፤ አስጣፈጠ ፤ አስነጠረ ፤ ቀምሙ ፡ አጣፍጡ ፤ አንጥሩ ፡ አቅልጡ ፡ አለ ።

አጽዓጢ ፤ መጽዐጢ ፤ ዕጥ ፤ የሚያስቀምም ፤ የሚያስነጥር ፤ ሽቱ ፡ የሚያስበጅ ።

ጽዒል ፤ ሎት ፤ (ጸዐለ ፡ ይጼዕል ፡ ይጽዐል ። ዕብ ፡ ጼሌል ፤ እሾኽም ፡ የሽቱ ፡ ዕንጨት) ፤ መጣል ፡ ማጣጣል ፤ መስደብ ፡ ማርከስ ፤ ማዋረድ ፡ ማሳነስ ፤ ማቃለል ፡ ማኰሰስ ፤ መንቀፍ ፤ ማጸየፍ ፤ ሹል ፡ አፍ ፡ እሾኽ ፡ አፍ ፡ መኾን ፤ መባል ። በእንተ ፡ ፀሪፍ ፡ ወጽዒል ። ለእመ ፡ አዕበይከ ፡ አፉከ ፡ ወጸዐልካሁ ። እንዘ ፡ ይጼዕልዎ ፡ ኢጸዐለ ። ወይጼዐሉኒ ፡ ኵሎሙ ፡ ጸላእትየ ፡ (፩ ፡ መ ፡ ፳ ። ሚራ፳፱ ፡ ፳፱ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፵፩) ። ጸልእን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

ጸዓሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤ የሚጥል ፡ ጣይ ፤ የሚሰድብ ፤ ሰዳቢ ፤ ተሳዳቢ ፤ ስድብ ፡ ዐዋቂ ። ዕቡይ ፡ ወጸዓሊ ። ብእሲት ፡ ጸዓሊት ። ሕብያተ ፡ ጸዓልያን ፡ ያንኀል ፡ እግዚ ፡ (ሚራ፳፫ ፡ ፰ ። ምሳ፲፭ ፡ ፳፭ ። ፳፭ ፡ ፳፱) ። ጸዓሊና ፡ ፀሓይ ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ። (ግጥም) ፤ መሸ ፡ መሰለኝ ፡ ሲጨልም ፤ እንደ ፡ ቀን ፡ ጣይ ፡ የለም ።

አጽዐለ ፤ አሰደበ ፤ አስነቀፈ ፤ አስናቀ ፤ ወልድ ፡ ሕብድ ፡ ያጼዕል ፡ አባሁ ። ወዘኢያጽዕሎ ፡ አዝማዲሁ ። ከመ ፡ ኢያጽዕላ ፡ ርእሶን ። እስመ ፡ ተዋርዶ ፡ ኢያጼዕል ፡ (ምሳ፳፰ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፲፱ ። ፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ። ተረ ፡ ቄር፩) ።

መጽዕል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤ የሚሰድብ ፤ የሚያሰድብ ፤ አሰዳቢ ፡ አስነቃፊ ። መሰደቢያ ፡ ማሰደቢያ ።

ተጽዕለ ፤ ተጣለ ፤ ተሰደበ ፤ ተዋረደ ። ተጽዕልኩ ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ ጸላእትየ ። ንበርሕ ፡ ወንጼዕል ። ወተጽዕልክሙ ፡ (መዝ ፡ ፴ ። ፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲ ። ዕብ፲ ፡ ፴፫) ።

ጽዑል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ዕልት) ፤ የተጣለ ፤ የተሰደበ ፤ ስዱብ ፤ ነውረኛ ፤ ንቁፍ ። ዘማ ፡ ወጽዕልተ ፡ ኢያውስቡ ፡ (ዘሌ፳፩ ፡ ፯ና ፡ ፲፬ ። ኢሳ፷ ፡ ፲፭ ። ምሳ፳፱ ፡ ፲፰) ።

ጽዕለት ፤ (ታት) ፤ መስደብ ፤ መሰደብ ፤ አስዳደብ ። ስድብ ፤ የቃል ፡ በትር ፤ ቍስሉ ፡ የማይሽር ። (ተረት) ፤ የባሰኄ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፤ እንደ ፡ ሽመል ፡ ይወቃል ። እምአፈ ፡ ሕብዳን ፡ ትወፅእ ፡ በትረ ፡ ጽዕለት ። ጽዕለተ ፡ ብዑላን ። ከመ ፡ ኢይደቅ ፡ ውስተ ፡ ጽዕለት ። ክብሩ ፡ ለብእሲ ፡ ተከልኦ ፡ እምጽዕለት ፡ (ሚራ ። መዝ ፡ ፻፳፪ ። ፩ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ምሳ፳ ፡ ፫) ። ጥለት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

ተጻዐለ ፤ ተሳደበ ፡ ተሰዳደበ ። ይጻዐሉ ፡ ወይትዋገሩ ፡ (ግብ፲፬ ፡ ፭) ።

ጸዐመ ፤—ጮኸ ፤—ጽኢም ፡ ጸአመ ።

ጽዒን ፤ ኖት ፤ (ጸዐነ ፡ ይጽዕን ፡ ይጽዐን ። ዕብ ፡ ጻዐን ፤ ተጽዕነ) ፤ መጫን ፤ ማሸከም ፤ ማሳዘል ፤ መጥመድ ፤ ማስገንት ፡ ሸክምን ፡ በተሸካሚ ፡ ላይ ፡ ማስቀመጥ ፡ ማኖር ፤ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ማቈራኘት ፡ ማሰር ። ሕዘዞሙ ፡ ይማየጡ ፡ በውእቱ ፡ ንዋይ ፡ እክለ ፡ ወይጽዐንዎ ፡ በሐመር ። ለሕድግለ ፡ ጸዐኖ ። ጸዐኑ ፡ አንስቲያሆሙ ። ጸዐና ፡ ለእምከ ። ጸዐኑ ፡ ሕእዱጊሆሙ ። ጸዐነት ፡ ሕብቅሊሃ ። ወእጼዕን ፡ ሠረገላ ፡ ዲበ ፡ መሁንየ ፡ ከማዱ ፡ (ዮሴፍ ። ሚራ፴ ፡ ፴፫ ። ኩፋ ፡ ፳፱ ፡ ፴፩ ፡ ፵፫ ። ሆሴ፲ ፡ ፲፩) ። በጸዐነ ፡ ፈንታ ፡ አጽዐነ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። አጽዐኖ ፡ ዲበ ፡ ፈረስ ። ወሕጽዐንከ ፡ ሰብእ ፡ ዲበ ፡ አርእስቲነ ። ወዲበ ፡ ልዑላት ፡ ያጼዕነኒ ፡ (አስቴ፮ ፡ ፱ና ፡ ፲፩ ። መዝ ፡ ፷፭ ። ዕንባ ፡ ፲፱) ።

ጸዓኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት ፤ ዐንት) ፤ የሚጭን ፤ የሚያሸከም ፤ ጫኝ ፤ አሸካሚ ።

መጽዕን ፤ (ንት ፡ ናን ፡ ናት ፤ ዐኒ) ፤ የሚጭን ፤ ጫኝ ። መጫኛ ፤ ቅራና ፤ ማሸከሚያ ።

መጻዕን ፤ (ናት) ፤ መጫኛዎች ፤ ቅራኖች ፤ የጭነት ፡ መሣሪያዎች ።

አጽዐነ ፤ አስጫነ ፤ ጫኑ ፤ አሸከሙ ፡ አለ ። በአጽዐነ ፡ ፈንታ ፡ አስተጽዐነ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ ፩ ፡ ነው ።

ተጽዕነ ፤ ተጫነ ፤ ተቀመጠ ፤ ሸክም ፡ ኾነ ፤ በላይ ። ተጫነበት ፤ ተሸከመ ፤ ተደበለለ ፤ ጸዋሪ ፡ ኾነ ። ተጽዕነ ፡ ላዕለ ፡ ኪሩቤል ። እስመ ፡ ተጽዕንከ ፡ ዲበ ፡ አፍራሲከ ። ናሁ ፡ ፈረስ ፡ ጸዐዳ ፡ ወዘይጼዐኖ ፡ ቀስተ ፡ ያጸንዕ ። ተጽዕነ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሰይጣን ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። ዕንባ ፡ ፫ ። ራእ፮ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ መስ፲፱) ።

**ጽዑን**፤ (ናን ፡ ናት ፡ ዕንት) ፤ የተጫነ ፤ የተጫነበት ፤ ሸክም ፤ ተሸካሚ ። ዘጽዑን ፡ ዲበ ፡ አድግ ። እንዘ ፡ ጽዑን ፡ ምስሌሁ ፡ ዲበ ፡ ፈረስ ። ገመል ፡ ጽዑን ። ጽዑናን ፡ አግማሊሆሙ ፡ አፈዋተ ፡ (ስንክ ፡ የካ ፲፭ ። ኅዳ፳፭ ። ሐም፳፰ ። ዘፍ፴፯ ፡ ፳፭) ።

**መስተጽዕን**፤ **ተጻዓኒ**፤ የሚጫን ፤ ተጫኝ ፤ ተቀማጭ ። መስተጽዕነ ፡ ኪሩቤል ። መስተጽዕናነ ፡ አፍራስ ። ጎኑደነ ፡ ወመስተጽዕናነ ፡ በመሥልስት ፡ (አርጋ ፡ ፩ ። ኢዮ፩ ፡ ፲፯ ። ዘፀ፲፭ ፡ ፬) ።

**ተጻዐነ**፤ ተጫጫነ ፡ ተሸካከመ ፤ ተነባበረ ፤ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ።

**አስተጻዐነ**፤ አጫጫነ ፡ አሸካከመ ፤ አነባበረ ፤ አደራረበ ።

**መስተጻዕን**፤ የሚያጫጭን ፤ የሚያሸካክም ፤ አጫጫኝ ።

**ጸዓዕ**፤—ብልጭታ፤—ፀዓዕ ።

**ጻዕፍ**፤ (ዐረ ፡ ጻዕፍ) ፤ ጉሽ ፤ እንቡሽቡሽ ፤ ድፍርስ ፡ ብጥብጥ ፤ ገና ፡ ያልፈላ ፡ ያልበሰለ ፡ መጠጥ ፤ ዐዲስ ፡ ጠጅ ፤ የማር ፡ የወይን ። ጻዕፈ ፡ ጸግቡ ፡ ወሰክሩ ። አልቦ ፡ ዘይሰቲ ፡ ከራሚ ፡ ወይፈቅድ ፡ ጻዕፈ ። ወይሰትዩ ፡ ደሞሙ ፡ ከመ ፡ ጻዕፍ ፡ (ግብ፪ ፡ ፲፫ ። ሉቃ፭ ፡ ፴፱ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፳፮) ።

**ጽዒቅ**፤ **ቆት**፤ (ጸዐቀ ፡ ይጽዕቅ ፡ ይጽዐቅ ። ዕብ ፡ ጻዐቅ ፤ ጮኸ ፡ ከጭንቅ ፡ የተነሣ) ፤ መጭነቅ ፡ መጥበብ ፤ ጭንቅ ፡ ጥብ ፡ መኾን ፤ የቦታ ፡ የጊዜ ፤ ጸበበንና ፡ ዐጸበን ፡ ተመልከት ። ለትጽዐቆ ፡ ምድር ፡ (አርጋ ፡ ፫) ።

**አጽዐቀ**፤ (ጠዊቅ ፡ ጦቀ) ፤ አስጨነቀ ፤ አስጠበበ ፤ አጣበቀ ፡ አጣብቆ ፡ ያዘ ፤ መከራ ፡ አጸና ፡ ማቀየ ፤ አስገደደ ። ኢያገምራ ፡ ርሕብ ፡ ዓለም ፡ ወኢያጽዕቃ ፡ መጽብብ ፡ ዘመቅዐን ። ዘክርሥ ፡ ኢያጽዐቆ ። ሶበ ፡ አጽዐቆ ፡ ምንዳቤ ። እለ ፡ ያጽዕቁ ፡ ላዕለ ፡ ዕቤራት ፡ (አርጋ ፡ ፩ ። ድጓ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፪) ።

**መጽዕቅ**፤ (ቅት ፡ ቃን ፡ ቃት) ፤ የሚያስጨንቅ ፡ አስጨናቂ ። ሕማም ፡ ወጽንዐ ፡ ንዴት ፡ መጽዕቅ ፡ (ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**ተጽዕቀ**፤ ተጨነቀ ፤ ተጠበበ ፤ በቦታ ፡ በመከራ ። እንዘ ፡ ይጸዐቁ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ። ባልሖሙ ፡ እምነ ፡ ገዐር ፡ ወተጽዕቆተ ፡ ግብር ፡ ዘነበሩ ፡ ባቲ ፡ (መቃ ። አፈ ፡ ድ፳፯) ።

**ጽዑቅ**፤ የጠበበ ፤ ጠባብ ፤ ጭንቅ ። ጽዕቅት ፡ ፍኖት ፡ (ማቴ፯ ፡ ፲፬ ። አፈ ፡ ተ፳፱) ።

**—**፤ የተጨነቀ ፤ የተጠበበ ፤ መከረኛ ።

**ጻዕቅ**፤ (ቃት) ፤ ጭንቅ ፡ ጥብ ፤ ግፊ ፤ ሥቃይ ፡ መከራ ። ብዙኅ ፡ ሰብእ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ወኢመካን ፡ ዕሩቅ ፡ ዘእንበለ ፡ ጻዕቀ ፡ ሰብእ ፡ ጽፉቅ ። በዕለተ ፡ ጻዕቆሙ ፡ ወጻሕቦሙ ። ምንዳቤ ፡ ወጻዐቅ ። ሐዘናተ ፡ ወጻዕቃተ ፡ (ዮሴፍ ። ሔኖ፵፰ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፪ ። ማር ፡ ይሥ፲፫) ።

**ተጻዐቀ**፤ ተጫነቀ ፤ ተጣበበ ፤ ተጋፋ ፤ ተነባበረ ፤ ጽፍቅ ፡ ኾነ ። አከኑ ፡ ይጣወቅ ፡ ሰብእ ፡ ወይጻዐቀከ ፡ (ሉቃ፰ ፡ ፵፭) ።

**ተጻዓቂ**፤ የሚጫነቅ ፤ የሚጣበብ ፤ የሚጋፋ ፡ የሚፋተግ ፤ ተጨናናቂ ። መዘሕም ፤ ዘበትርጓሜሁ ፡ ተጻ(ጸ)ዓቂ ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፱) ። መዘሕምን ፡ ተመልከት ።

**ጽዒር**፤ **ሮት**፡ (ጽዕረ፤ ጸዐረ ፡ ይጽዕር ፡ ይጽዐር ። ሱር ፡ ጻዐር ። ዕብ ፡ ያጻር) ፤ መጣር ፤ መጋር ፤ መፍገርገር ፤ መፍጨርጨር ፤ በፍጹም ፡ ኀይል ፡ በፍጹም ፡ ትጋት ፡ መሥራት ፤ መድከም ፡ መቃተት ፡ ማቃሰት ።

**—**፤ ማዘን ፡ መተከዝ ፤ በጻዕር ፡ መያዝ ፤ መጨነቅ ፡ መዋለል ፤ ሥቃይ ፡ መቀበል ። እስመ ፡ ጽዕረ ፡ ፈድፋደ ። ወትጼዕረኒ ፡ ልብየ ፡ (ስንክ ፡ ሐም፰ ። መዝ ፡ ፲፪) ። በጽዕረ ፡ ፈንታ ፡ ተጽዕረ ፡ ይላል ፤ አያስኬድም ፤ ተ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። የጽዕረና ፡ የጸዐረ ፡ ፍች ፡ ተሠቀየ ፡ ተጨነቀ ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ማእዙን ፡ እንዳማርኛው ፡ አስኪዶታል ፤ ጭፍራንቱ ፡ የጥሕረና ፡ የጸዐለ ፡ ነው ። መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘተጽዕረ ፡ ከማየ ። ተጽዕረ ፡ በምንዳቤ ። እስመ ፡ አብ ፡ ይጼዐር ፡ ወይሳሕሉ ። እለ ፡ ይጼዐሩ ፡ በህየ ፡ (ኢዮ፲፫ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ ጥር፲፰ ። ጥበ፲፬ ፡ ፲፰ ። አፈ ፡ ተ፩) ።

**ጽዑር**፤ (ራን ፡ ራት ፡ ዕርት) ፤ የተጨነቀ ፤ የተሠቀየ ፤ የሚያጥር ፤ የሚጣጣር ፤ ጣር ፡ የያዘው ፤ ለሞት ፡ የቀረበ ፤ ያዘነ ፡ የተከዘ ። ጥቀ ፡ ጽዑር ፡ ሕሙም ፡ ወጽዑር ። ፈልጸስ ፡ ጽዑረ ፡ ሥጋ ፡ በመቅሠፍት ። ጽዑራነ ፡ ነፍስ ። ይከውኑ ፡ ጽዑራነ ። ኑዛዜ ፡ ወትፍሥሕት ፡ ለጽዑራን ፡ (ማቴ፰ ፡ ፮ ። አፈ ፡ ተ፱ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፰ ። ኢዮ፫ ፡ ፳ ። ጥበ፱ ፡ ፲፱ ። ማር ፡ ይስ፲፫) ።

**ጻዕር**፤ (ራት) ፤ ጣር ፤ ጭንቅ ፤ ሥቃይ ፤ መከራ ፤ ደዌ ፤ ሕማም ፤ የሕማም ፡ ስሜት ፤ የሞት ፡ ምዜማ ። ጻዕረ ፡ ሞት ። ጻዕረ ፡ ሕማም ። ጻዕረ ፡ ደይን ። ዘቲ ፡ ዐባይ ፡ ጻዕር ። ወርእየ ፡ ኤፍሬም ፡ ለደዌሁ ፡ ወለጻዕሩ ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። ዮሴፍ ። ፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ሔኖ፷፪ ፡ ፲፭ ። ሆሴ፰ ፡ ፲፫) ።

**አጽዐረ**፤ አጣረ ፤ አደከመ ፤ አስጣረ ፤ አስጨነቀ ፤ ማቀየ ፤ መከራ ፡ አሳየ ፤ አስመረረ ፤ አሳዘነ ። አጽዐርዋ ፡ ለነፍሶሙ ። ያጼዕረኒ ፡ ዘያወፅአ ፡ ለነፍስየ ። እስከ ፡ ምንትኑ ፡ ታጼዕርዋ ፡ ለነፍስየ ። እስመ ፡ ጥቀ ፡ ያጽዕሮን ። ወፈቀደ ፡ ያጽዕራ ፡ (ግብ፲፬ ፡ ፪ ። ኢዮ፲፱ ፡ ፩ ። ፲፱ ፡ ፪ ። ሄርማ ። ስንክ ፡ ኅዳ፯) ።

**መጽዕር**፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤ የሚያጥር ፤ የሚያስቸግር ፤ የሚሠቅይ ፤ አስጨናቂ ። መሠቀያ ፤ ማስጨነቂያ ፤ የሥቃይ ፡ መሣሪያ ።

**መጻዕር**፤ (ርት) ፤ የሚሠቅዩ ፤ ሠቃዮች ፤ ሥቃዮች ፤ የሥቃይ ፡ መሣሮች ። አዘዘ ፡ ስደተ ፡ ላዕለ ፡

ኢጲስቆጶሳት ፡ ወመጺዐርተ ፡ ዘንኔ ፡ ዐጺበ ፡ ባዕለ ፡ መሀይምናን ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

(ጥ) **ጸፈሐ ፤ (ፋሕት) ፤** ካቤላ ፤ ገልባጣ ፤ ለማጣ ፤ ደረታም ። ዘፍ ፡ ጠፈሕ ፡ ነው ፤ ጠን ፡ ጸ ፡ ስለ ፡ ወረሰው ፡ ወደዚህ ፡ መጥቷል ። ዘጸፋሕት ፡ እገሪሁ ፡ (ኪዳ) ።

**ጽፍሕ ፤—ሰፋት ÷ ወርድ ፤—ሰፍሕ ፡ ሰፍሐ ።** (ዘፀ፳፭ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ፡ ፳፫ ። ፳፯ ፡ ፪ ፡ ፴ ፡ ፲፯ ። ፳፰ ፡ ፭ ፡ ፲፪ ፡ ፴)።

**ጸፈን ፤ ኖት ፤ (ጸፈነ ፡ ይጸፍን ፡ ይጽፍን ። ዐረ ፡ ጸፈን ። ዕብ ፡ ጻፋን) ፤** ማፈን ፡ መጨፈን ፤ መዝጋት ፡ መድፈን ፤ ድዳ ፡ ደንቆሮ ፡ ዕውር ፡ ማድረግ ፤ የጋኔን ። መሰወር ፡ መደበቅ ፤ መከተት ፡ ማኖር ፤ ለመጠበቅ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጸፈነ ፡ ፈንታ ፤ አጽፈነ ፡ ይላል ፤ ባስደራጊ ። ወቦ ፡ ለዘአጽፈኑ ፤ ወቦ ፡ ለዘወርኃዊ ፡ ረሰይዎ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተጸፍነ ፤** ተጨፈነ ፤ ተደበቀ ፤ ተከተተ ።

**ጽፋን ፤** የተጨፈነ ፤ ጭፍን ፤ ጨፋና ፡ ዕውር ።

**ጸፈን ፤ ጽፍን ፤ (ዐረ ፡ ጹፍን) ፤** የውሃ ፡ ዕቃ ፤ የሸክላ ፡ የቁርበት ፤ ማድጋ ፡ ፊቀን ፤ ገንቦ ፡ መንቀል ፤ ርኩት ፡ ፉምት ፤ ቀርበታ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ፤ ጸሕብን ፡ ተመልከት ። ጸፈነ ፡ ማይ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪) ።

**ጽፈን ፤ አጽፋን ፤** የውሃ ፡ ዕቆች ።

**ጽፍንት ፤ (ታት ። ዐረ ፡ ጸፍንት) ፤** የሥንቅ ፡ አቅማዳ ፤ ቊናማት ፡ ኰፋዳ ፤ ኰረጇ ፡ ፊኛ ፡ ማፋዳ ፤ የገንዘብ ፡ መያዣ ፤ ኹለንተናው ፡ ቍርበት ፡ የኾነ ። መልአት ፡ ጽፍንታ ፡ ጥሕነ ። ወወደየቶ ፡ ውስተ ፡ ጽፍንታ ፡ ዘእክል ። ወኢጽፍንተ ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፭ ። ፲፫ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ። ማቴ፲ ፡ ፲ ። ማር፮ ፡ ፰ ። ሉቃ፱ ፡ ፫) ።

**ጸፍናት ፤ (ዕብራ) ፤** ኅቡኣት ፤ ዕሙቃት ፤ ረቂቃት ፤ ምስጢራት ፡ ራእይ ፡ ወሕልም ።

**ጸፍናት—ፋዕኔሕ ፤** ፋዕኔሐ ፡ ጸፍናት ፤ ከማቴ ፡ ኅቡኣት ፡ ብሂል ። እስፍንቶሮኔሕን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ጸፈዐ ፤ ዖት ፤ (ጸፍዐ ፡ ይጸፍዕ ፡ ይጽፋዕ ። ጠፍሐ) ፤** መጽፋት ፤ በጥፊ ፡ መምታት ፤ መጠፍጠፍ ፤ ማጮል ፤ የከበሮ ፡ የፊት ፡ ያዘባ ፡ የበት ፤ ፀፍዕን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ይመይጥ ፡ መልታሕቶ ፡ ለዘጸፍዖ ። ከመ ፡ ዘይጸፍዕዎ ፡ ለብእሲ ፡ መልታሕቶ ። ወይጸፍዕዎ ፡ ገጾ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘጸፍዐ ፡ ገጾ ፡ ዲበ ፡ ምዉት ፡ እስከ ፡ የሐብጥ ፡ ሥጋሁ ፡ ወይቈስል ። አዘዘ ፡ ይጽፍዕዎ ፡ አፉሁ ፡ (ሰቈ፫ ፡ ፳፱ ። ሆሴ፲፩ ፡ ፬ ። ማር፲፬ ፡ ፷፭ ። ቀድር ። ግብ፳፫ ፡ ፪) ። በጸፍዐ ፡ ፈንታ ፡ አጽፍዐ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ናጸፍዖ ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፰) ።

**ተጸፍዐ ፤** ተጸፋ ፤ በጥፊ ፡ ተመታ ፤ ሰውዮው ፡ ከበሮው ። መዝሙሩ ፡ በከበሮና ፡ በጸናጽል ፡ በጠፈሐ ፡ እድ ፡ ተዜመ ፡ ተባለ ። ይጸፋዑ ፡ ወይጼዐሉ ። በእደ ፡ ገብር ፡ ትጸፋዐከ ። እንተ ፡ አንተ ፡ በእንቲአሃ ፡ ተጸፋዕከ ፡ በውስተ ፡ ዐውድ ፡ ከመ ፡ ታግዕዛ ፡ (ተረ ፡ ቄር፬ ። ቅዳ ፡ ያዕ ። ዮሐ) ።

**ጽፋዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ፍዕት) ፤** የተጸፋ ፤ የተጠፈጠፈ ፤ ፊቱ ፡ በጥፊ ፡ የተመታ ።

**ጽፍዐት ፤ (ታት) ፤** መጽፋት ፤ መጸፋት ፡ አጸፋፍ ፤ ጽፋት ፤ የመዝሙር ፡ አባባል ። በጥፊ ፡ መምታት ፤ መመታት ፤ አመታት ፤ ምት ፤ ጥፊ ፤ የጥፊ ፡ በትር ። መዘምር ፡ መድኅኔ ፡ ዓለም ፡ ተምህረ ፡ ጽፍዐተ ፤ እንዘ ፡ በእዴሁ ፡ ይእኅዝ ፡ ጸናጽለ ፡ ኅጺን ፡ ቀኖተ ። ንዑ ፡ ትርአዩ ፡ ጽፍዐተ ፡ መላትሕ ፡ እምገብር ። ጽፍዐተ ፡ ወልድኪ ፡ (ቅኔ ። ቅዳ ፡ ጎር ። ኢሳ፶ ፡ ፮ ። አርጋ ፡ ፩) ።

**ጸፍዕ ፤—እበት ÷ ኩበት ፤—ፀፍዕ ።** ሊጣፍ ፡ የሚገባው ፡ በዚህ ፡ ነበረ ፤ ስለ ፡ ልማዱ ፡ ወደ ፡ ፀጺ ፡ ኼዷል ።

**ጸፍጽፎ ፤ ፎት ፤ (ጸፍጸፈ ፡ ይጸፈጽፍ ፡ ይጸፍጽፍ ። ነጺፍ ፡ ነጸፈ) ፤** መጸፍጸፍ ፤ ደንጊያን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ማንጠፍ ፤ መለጠፍ ፤ ምድርን ፡ በጠፍጣፋ ፡ ድንጋይ ፡ መምረግ ፡ መለበጥ ፤ መሸፈን ፡ ማስጌጥ ፤ በዝናብ ፡ ጊዜ ፡ ጭቃ ፡ እንዳይኾን ፤ ዐፈሩን ፡ ጐርፍ ፡ እንዳይወስደው ፤ ውሃው ፡ ወደ ፡ ዐዘቅት ፡ እንዲገባ ። ወጸፍጸፉ ፡ ሎቱ ፡ ምድረ ፡ ፌለግ ፡ በብርት ፡ (ዮሴፍ ። ሥር ፡ እኵ) ።

—፤ መጠፍጠፍ ፤ ማጠፍጠፍ ፤ ጠፍጣፋ ፡ ዝርግ ፡ መኾን ፤ ማድረግ ። መጨፍጨፍ ።

**አጸፍጸፈ ፤** አስጠፈጠፈ ፤ አስለበጠ ፤ አስነጠፈ ።

**ተጸፍጸፈ ፤** ተነጠፈ ፤ ተለጠፈ ፤ ተጸፈጸፈ ፤ ደንጊያው ። ተሸፈነ ፡ ተለበጠ ፤ ደንጊያ ፡ ለበሰ ።

**ጽፍጹፍ ፤** የተነጠፈ ፤ የተጸፈጸፈ ፤ ልቡጥ ። ወጽፍጹፍ ፡ በእብን ፡ ዘሕብረ ፡ መረግድ ። መካን ፡ ጽፍጹፍ ፡ በርኳም ፡ (አስቴ፩ ፡ ፮ ። ዮሴፍ) ።

**ጸፍጻፍ ፤** በቁመሙ ፤ ጥፍጣፍ ፤ የደንጊያ ፡ ንጣፍ ፤ ልባጥ ፤ ነጣፊ ፡ ጠፍጣፋ ፤ ጡብ ፡ ደንጊያ ። ሊቶስጥሮስ ፡ ዘውእቱ ፡ ጸፍጻፍ ። አዘዘ ፡ ይኅፅቡ ፡ ጸፍጻፎ ፡ በማይ ። ወጥቀ ፡ ሠናይ ፡ ጸፍጸፉ ። በሌዳ ፡ በረድ ፡ ጸፍጸፈ ፡ ዐውዱ ፡ (፩ዜና ፡ ፯ ፡ ፫ ። ዮሴፍ ። አስቴ፩ ፡ ፮ ። ቅዳ ፡ ኤጲ) ።

**ጸፍጸፈ ፤ (ዕብ ፡ ጹፍ ፤ ጻፍ ፤ ጻፍጼፍ) ፤** አኻጨ ፡ ወፍኛ ፡ ፊጨኽ ፤ ጺፍ ፡ ጺፍ ፡ ጭው ፡ ጭው ፡ አለ ። ፈለሰ ፡ ወረደ ፤ ተንጠፈጠፈ ።

**ጸፍጻፉ ፤** የዛፍ ፡ ስም ፤ እንደ ፡ ዘግባና ፡ እንደ ፡ በቀልት ፡ ምጥቀት ፡ ርዝመት ፡ ቀጥታ ፡ ያለው ፤ በውሃማ ፡ መሬት ፡ የሚበቅል ። ርጥብ ፤ ረግረግ ፤ ጕርፋም ፡ ጠፈጠፋም ፡ ቦታ ፡ (ሕዝ፲፯ ፡ ፭) ።

**አንጸፍጸፈ ፤** አንጠፈጠፈ ፤ ተንጠፈጠፈ ፤ ፈሰሰ ፡ ጐረፈ ። ነጥበን ፡ ተመልከት ። ታንጸፍጽፍ ፡ ዐይንየ ፡ ቅድሜሁ ። ዓዲ ፡ ሐሲቦሙ ፡ ያንጸፈጽፉ ፤ (ገ

ቢር)። ያንጸፈጽፍ፡መዓር፡እምአድባር። ወያንጸፈጽፍ፡ሐሊቦን፡(ኢዮ፲፮፡፳። ዮኤ፫፡፲፰። ዓሞ፱፡፲፫። ሱቱ፡ዕዝ፫፡፯። ተረ፡ባሮ)።

**ንጸፍጻፍ፡(ፉት)፤** ጠፈጠፍ፤ ፍሳሽ፤ ፈሳሽ፤ ጠብታ፤ እንጥብጣቢ። ወኮነ፡ሀፉ፡ከመ፡ነጸፍጻፈ፡ደም፡ዘይወርድ፡ውስተ፡ምድር። ጻዐደወት፡ምድር፡እምነጸፍጻፈ፡ሐሊብ፡አጥባተ፡እሞሙ። አምሕሰኪ፡ማርያም፡በነጸፍጻፈ፡ደም፡ዘኀልኀታ፡(ሉቃ፳፪፡፵፬። መጽ፡ምስ። አርጋ፡፩። ደራሲ)።

**ጸፈቀ፤ ቆት፤(ጸፈቀ፡ ይጸፍቅ፡ ይጽፍቅ። ዐረ፡ ጸፈቀ። ዕብ፡ ሳፋቅ፤ ጠፍሐ)፤** መጽፈቅ፤ ጽፍቅ፡ ማድረግ፤ ማብዛት፤ ማፈግ፡ መቸፈግ። የዘር፡ የተክል፡ የምሕን፡ የዐርብ፤ የመሰለው፡ ኹሉ። መጨፈቅ፤ መጀጐል፤ መዝጋት፡ መድፈን፤ መወተፍ፡ መጠቅጠቅ፤ የይሎ፡ የሽምጥ። በጸፈቀ፡ ፈንታ፡ አጽፈቀ፡ ይላል፤ ጸፈቀን፡ ሐውልት፡ አድርጎ። እለ፡ ያጸፍቁ፡ንስሓ፡(ሄርማ)።

**አጽፈቀ፤** አስጨፈቀ፤ አስጀጐለ፤ ጽፍቅ፡ አስደረገ።

**ተጸፍቀ፤** ተጨፈቀ፤ ጭፍቅ፡ አለ፤ በዛ፤ ጽፍቅ፡ ኾነ፤ ተዘጋ፡ ተወተፈ፤ ተጀጐለ። ነዋ፡ተጸፍቁ፡ቦቱ፡ምንዳቤያት፡ብዙኀት። ማሕፀነ፡ራሔል፡ተጸፍቀ፡(አፈ፡ ድ፳፮። ኩፋ፡ ፳፰)።

**ጽፉቅ፤(ቃን፡ ቃት፡ ፍቅት)፤** የተጨፈቀ፤ ጽፍቅ፡ የኾነ፤ ብዙ፤ ጭፍቅ፤ ጥቅጥቅ፡ ያለ፤ የተወሳሰበ። ታሕተ፡ዥሉ፡ፆም፡ጽፉቅ፡ዘቦ፡ጽላሎት። ዕፀ፡ዘጽፉቅ፡ቈጽሉ። አዕዋም፡ጽፉቃት፡እለ፡ያጸልሉ። ወረከበ፡ዕፀ፡ጽፍቅተ፡(፫ነገ፡፲፱፡፭። ሚራ፲፱፡፲፰። ጥበ፲፯፡፲፯። ተረ፡ባሮ)።

**ጽፉቅ፤** በዝቶ፤ ጽፍቅ፡ ኹኖ፤ ተጸፍቆ፤ ተማንቆ።

**ጽፍቀት፤** መጨፈቅ፤(ጥጨ)መጨፈቅ፤ አጨፋፈቅ፤ ጭፈቃ፤ ጨፈቃነት፤ ብዛት፤ ጽፍቅነት።

**ተጽፉቅ፤(ቃት)፤** ጽፍቅነት፤ ጨፈቃ፤ ጀጐል፤ ሽምጥ፤ ውታፍ። ይትዐጸው፡ሙሳድ፡በተጽፉቀ፡ማሕፀን። ሥብ፡ ወፍር፡(መጽ፡ ምስ)።

—፤ ምልአት፤ ምሉነት፤ ልባጥ፡ ልብጣት። ዕንቁ፡ዘተጽፉቅ፡ለዐጽፍ፡(ዘፀ፴፭፡፳፯)።

**ተጻፈቀ፤** ተጫፈቀ፤ ተጨፋፈቀ፤ ተጠጋጋ። ኢንጻፈቅ፡አላ፡ንትራሐቅ፤ብእሲ፡ብእሲ፡እምካልኡ። እስመ፡ገብኡ፡ወተጻፈቁ፡ብዙኃን፡ኀቤሁ፡(፪ዕዝ፡፲፬፡፲፱። ፪ዜና፡፲፭፡፱)።

**ጸፈር፤ ሮት፤(ጸፈረ፡ ይጸፍር፡ ይጽፍር)፤** ማጣፈር፤ እንስሳ፡ ሲወለድ፡ ጥፍሩን፡ በጥፍር፡ መቍረጥ፤ መከርከም፤ ለሰውም፡ ይኾናል። ትላጽያ፡ርእሳ፡ወትጸፍራ፡(ዘዳ፳፩፡፲፪)።

—፤ ጥፍሬም፡ መኾን፤ በጥፍር፡ መቢጠጥ፤ መጕፍጨር፤ በቃሪያ፡ ጥፊ፡ መምታት። ምስጢሩ፡ ጥፍሮችን፡ ይሻል፤ አጣፍረው፡ እንዲሉ። ጥፊው፡ ብስል፡ ሲኾን፡ ማን፡ የጣቶችን፡ እንደ፡ ጠፍር፡ መኾን፡ ዐለንጋንትን፡ ያሳያል።

**ተጸፍረ፤** ተጣፈረ፤ ጥፍሩን፡ ቈረጠ፡ ከረከመ። ኢተጸፍረ፡ ወኢተላጸየ፡(፪ነገ፡፲፱፡፳፬)። ዕብራይስጡ፡ ግን፤ ወኢገብረ፡ ጽሕሞ፡ ይላል፤ አላበጀም፡ አላዘጋጀም፤ አልነቀሰም፡ አላበጠረም፡ ማለት፡ ነው፤ ከዚህ፡ በቀር፡ ጥፍር፡ መቍረጥን፡ ራስ፡ መላጨትን፡ አያሳይም። ጐጽፈረን፡ ተመልከት፤ የዚህ፡ ዲቃላ፡ ነው።

**ጽፉር፤(ራን፡ ራት፡ ፍርት)፤** የተጣፈረ፤ ጥፍሩን፡ የቈረጠ፤ የተቈረጠ።

**ጽፍር፤(ዕብ፡ ጺፎሬን። ሱር፡ ጥፉር፤ ጢፍራ። ዐረ፡ ጡፍር)፤** ጥፍር፤ አፍኣዊ፡ ዐጥንት፤ የጣቶች፡ ቀንድ፤ ነጭ፤ ስለታም። ኢይምትር፡ጽፍሮ። ጽፍረ፡እደዊከ፡ወእገሪከ፡(ቀሌ። መቃ)።

—፤ ሰኰና፤ ሸኾና፤ ጥቍር፤ ክብ፡ ንፍቅ፤ ጽፍቅ፤ የእንስሳት። ዘኢያብቈለ፡ቀርነ፡ወጽፍረ። ጽፍረ፡ላሕም። ዘሥጡቅ፡ጽፍሩ፡(መዝ፡፷፰። ኢሳ፲፫፡፳፪። ዘሌ፲፩፡፫—፯)።

**ጽፈር፤ አጽፋር፤ ጽፍራት፤** ጥፍሮች፤ ሰኰኖች፤ ሰኰናዎች። ጽፈሪሁ፡ከመ፡ንስር። አጽፋረ፡እዴከ፡ዘሕበሪሆን፡ጸዐዳ። ጽፍራት፡እደዊሆሙ፡ወእገሪሆሙ፡(ዳን፡፬፡፴። ደራሲ። ስንክ፡ሐምሌና፡፳፭)። ሌላውም፡ በጥፍር፡ አምሳል፡ የተሠራ፡ ኹሉ፡ ጥፍር፤ ይባላል። አዘዘ፡ ይሥትርዎሙ፡ በአጽፋረ፡ ኅጺን፡ከመ፡ይዘርዝሩ፡ሥጋሆሙ፡(ስንክ፡ታኅ፲፱)።

**አጽፋር፤(ዐረ፡ አጽፈር)፤** የዐይንት፡ ስም፤ ብጫ፤ ወይባ፡ ዐደይ፡ አበባ፡ የሚመስል፡ ሕብር። አስፋርን፡ ተመልከት፤ ከዚህ፡ ጋራ፡ ፩፡ ነው። ወአቅየ፡ሐይሐ፡ሕብሮ፡በአጽፋር፡(ጥበ፲፫፡፲፬)።

**ጸፈረ፤—ታታ፤ ጐነጐነ፤—ፀፈር፡ ፀፈረ።**

**ጻጹት፤** ታናሽ፡ ዝንብ፤ ትንኝ፤ የዝንብ፡ የትንኝ፡ ማጩት፤ ዘመሚት፤ ቍጫጭ፤ የደሮ፡ የወፍ፡ ገላግልት። ምስጢሩ፡ ታናሽነት፡ ነው፤ መንጫጫትንም፡ ያሳያል። አሐቲ፡ጻጹት፡ነሰከቶ። እለ፡ ጻጹተ፡ ትነጥፉ፡ ወእለ፡ ገመለ፡ ትውኅጡ፡(ስንክ፡ ግንቦ። ማቴ፳፫፡፳፬)። ጸናጺትን፡ ተመልከት።

**ጻጼ፤—ብል፤ ትል፤—ፃፄ።**

**ጸቂው፤ ዎት፤ (ጸቀወ፡ ይጸቁ፡ ይጽቁ። ዐረ፡ ጸቀበ)፤** መምታት፤ መትከል፤ መቸከል፤ መቀብቀብ፤ ከምድር፡ ማጣበቅ፤ የካስማ፡ የችካል። ወጸቀወቶ፡(መሳ፬፡፳፩)። ጺቅ፡ ጢቅ፡ ማለት፤ መትፋት፤ የንህብ፤ ጸየቀን፡ ተመልከት።

**ጸቃውዕ፤ ዓት፤ (ቀውዕ፡ ቅያእ)፤** ወለላ፡ ማር፤ የማር፡ ወለላ፤ የንቦች፡ ትፋት፡ ከጽጌያ


ትና ፡ ከአፅጹቅ ፡ እየቀሠመ ፡ በስፈፉ ፡ ዐይን ፡ በየጕድ ጓዱ ፡ የሚተፋትና ፡ የሚመሉት ፤ ፈሳሽ ። ዕ ፡ ከቆዕ ፡ መ ጥቷል ፤ ስለዚህ ፡ ንባቡ ፡ ቀውዕን ፡ ምስጢሩ ፡ ቅያእን ፡ ይመስላል ። ጸቃውዕ ፡ የብዙ ፡ ነው ፤ ያንድ ፡ ሲኾን ፡ ጸ ቆዕ ፤ ጸቁዕ ፤ ወይም ፡ ጸቂዐት ፡ ያሰኛል ፤ ጸቃውዓት ፡ ግን ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ጸቃውዐ ፡ መዓር ። እግዚ ፡ ገብረ ፡ ጸቃውዐ ፡ እምቈጽል ፡ ወጽጌያት ፡ ጥዑ ማን ። ጸቃውዕ ፡ ዘእምኑ ፡ እንቈራ ፡ ትትቀዳሕ ። ኢ ይማዕርር ፡ ጕርዔየ ፡ ጸቃውዐ ፡ ዘማ ፡ ኅስርት ፡ (ምሳ ፲፯ ፡ ፳፬ ። ቀሌ ። አርጋ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳፱) ።

**ጸቍን ፤ ኖት ፤ (ጸቈነ ፡ ይጸቍን ፡ ይጽ ቍን ። ዕብ ፡ ያጺቅ ፤ ጸቁን ፤ ክዕው) ፤** መጨ ቈን ፤ መጨቋቈን ። መክብ ፤ መጀጐል ፤ ማጠር ፡ መቅ ጠር ፤ በቤት ፡ በተክል ፡ ዙሪያ ፡ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ ጥሬ ፡ ክብ ፡ ሽምጥ ፡ መሥራት ። ተከለ ፡ ወይነ ፡ ወጸቈኖ ። እንበለ ፡ ይጽቍን ፡ ጸቊኖ ። ገብሩ ፡ ምሕራማተ ፡ ወጸቈኑ ። ጸቈንኩ ፡ ሎቱ ፡ ጸቈነ ፡ ወአግዘዝኩ ፡ (ማር ፲፪ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ መጋ፳፱ ። ፱ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፩ ። ኢሳ፳ ፡ ፪) ።

**ጸቈን ፤ (ናት ፤ አጽቋን) ፤** ክብ ፤ ዐጥር ፤ ቅ ጥር ፤ ጀጐል ፤ ቅረገራ ። ሰፈ ፡ ጸቈን ፡ ወሰፈ ፡ ጸቈን ። ዘይነሥት ፡ ጸቈነ ፡ ይነስኮ ፡ አርዌ ፡ ምድር ። ወገብረ ፡ ሎቱ ፡ ጸቈነ ፡ (ዘኍ፳፪ ፡ ፳፬ ። መክ፲ ፡ ፰ ። ማቴ፳፩ ፡ ፴፫) ።

**ጸቍን ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ የክብ ፡ ደንጊያ ፤ ጥሬ ፡ ክብ ፤ ዐፈር ፡ ቃም ፤ ርስ ፡ በርሱ ፡ የተጨቋቈነ ።

**ጽቍንቍን ፤** በክብ ፡ በጕር ፡ የሚኖር ፤ ገበሎ ፤ ጕበና ፤ እንቃቅላ ፤ የእንሽላሊት ፡ ዐይነት ። ባለብሎዎች ፡ ግን ፡ ፍልፈል ፡ ይሉታል ። አንጼዋ ፡ ወጽቍንቍን ፡ (ዘ ሌ፲፩ ፡ ፳፱) ።



ጽቍንቍን ፡

**ጸርእ ፤ (ትግ ፡ ጸር ። ዕብ ፡ ጺርዓ ፤ ን ህብ) ፤** ማኅበረ ፡ ሕዝብ ፤ ጉባኤ ፡ ሕዝብ ፤ እንደ ፡ ንህብ ፡ አውራውን ፡ የሚከብ ፤ ሰልፍ ፡ ዐጀብ ።

**ጽርእ ፤** ያገር ፡ የቋንቋ ፡ ስም ፤ ግሬክ ፤ የኖን ። ፍችው ፡ ኅቡር ፡ እስትጉቡእ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ክብኒያ ፡ ኮ ምፓኝ ፡ እንደ ፡ ማለት ። አንዳንድ ፡ ኤውሮፖች ፡ ግን ፡ በጥንታዊው ፡ ግእዝ ፡ በሕምያር ፡ ቋንቋ ፡ ምዕራብ ፡ ም ዕራባዊ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ወቦ ፡ እምሰብአ ፡ ጽ ርእ ። ወጽሑፍ ፡ በጽርእ ። ተአምርኑ ፡ ጽርአ ፡ (ዮሐ ፲፪ ፡ ፳ ። ፲፱ ፡ ፳ ። ግብ፳፩ ፡ ፴፯) ። ጽርዕ ፡ ተብሎ ፡ በ ዐይን ፡ ቢጣፍ ፡ ግን ፡ ነጭ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዕብራይስጥ ፡ ጸራዕ ፡ ብሎ ፡ ነጣ ፡ ይላልና ።

**ጽራእ ፤ (ዐረ ፡ ኀሩብ ። ሱር ፡ ወዕብ ፡ ሐሩብ) ፤** የዛፍ ፡ ስም ፤ እንቡጣም ፤ እንቡጠ ፡ ወፍ ራም ። ሖሞርን ፡ ተመልከት ፡ (ሉቃ፲፭ ፡ ፲፮) ።



ጽራእ ፡

**ጸርእ ፤—ቦዘነ ፤—ፀርዐ ።**

**ጸሪብ ፤ ቦት ፤ (ጸረበ ፡ ይጸርብ ፡ ይጽ ርብ ። ዐረ ፡ ፀረበ ፤ መታ ። ዕብ ፡ ጸራብ ፤ ነደ ፡ ውዕየ) ፤** መጥረብ ፤ መሸለት ፤ መላግ ፤ ዕንጨትን ፡ ማ ነጥ ፡ መቅረጥ ፤ ማስጌጥ ፤ አሳምሮ ፡ መሥራት ። ዘይጸ ርብ ፡ እምውስተ ፡ ዕፀ ። ጸረቦሙ ፡ በምማራተ ፡ ኀ ጺን ። ጸረበ ፡ ሎቱ ፡ መስቀረ ፡ (ዘፀ፴፩ ፡ ፭ ። ፩ዜና ፡ ፳ ፡ ፫ ። ሔኖ፳፱ ፡ ፩) ።

**ጸራቢ ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ረብት) ፤** የሚጠርብ ፤ ጠራቢ ፤ ዐናጢ ። ዘገብሮ ፡ ጸራቢ ። ጸረ ብተ ፡ ዕፀው ። ሊቀ ፡ ጸረብት ፡ (ኢሳ፵ ፡ ፲፱ና ፡ ፳ ። ፩ ዜና ፡ ፲፬ ፡ ፩ ። ፩ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲) ።

(ጥራ) **ጸራብ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ። ብእሲ ፡ ጸራብ ፡ (አ ዋል) ።

**አጽረበ ፤** አስጠረበ ፤ አሳነጠ ።

**ተጸርበ ፤** ተጠረበ ፤ ተጠራረበ ፤ ተላገ ።

**ጽሩብ ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ርብት) ፤** የተጠረበ ፤ ጥ ርብ ፤ ልዝብ ። ወረከብናሁ ፡ ለበትር ፡ ዘይጌሥጽ ፡ ለ ሮሜ ፤ ጽሩበ ፡ በንባብ ፡ ወቅሩጸ ፡ በትርጓሜ ፡ (ቅኔ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ሳዊ ። ፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ። ፱ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪) ።

**ጽርበት ፤** መጥረብ ፤ መጠረብ ፤ አጠራረብ ፤ ጠ ረብ ፤ ልጎሽ ፤ በቁሙ ፡ ጥርበት ፤ ጥርብነት ። መሀርዎ ፡ ግብረ ፡ ጽርበት ። ወተምህረ ፡ ግብረ ፡ ጽርበት ፡ ዘም ክያደ ፡ አእባን ፡ ወምሕዋራተ ፡ ማይ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ ፳፩ ። ግን፲) ።

**ጸርብ ፤ (ብ ፡ አጽራብ) ፤** ጠርብ ፤ ፍልጥ ፤ የ ቤት ፡ ዕንጨት ።

(ጥ) **ጽራብ ፤ (ባት) ፤** ጥራቢ ፤ የንጨት ፡ ገለባ ፤ እ ብቅ ። ወድቀ ፡ ቅድሜሁ ፡ ከመ ፡ ጽራባተ ፡ ዕፀ ፡ (ስ ንክ ፡ ጥር፳) ።

**መጽረብ ፤ (ብት) ፤** መጥረቢያ ፤ መላጊያ ፤ መ ሸለቻ ። ዘረበን ፤ ተመልከት ።

**መጸርብት ፤** መጥረቦች ፤ መጥረቢያዎች ።

**ምጽራብ ፤ (ባት) ፤** መጥረቢያ ፡ ቦታ ፤ የጥር በት ፡ ቤት ። ዘያወፅኡ ፡ መሬተ ፡ እምጽራበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ገድ ፡ ላሊ) ።

**ጽራግ ፤ (ትግሬ)** ፤ ፅንገትጌ ፤ ያንገት ፡ ጌጥ ፤ ሽልማት ፤ ስራስም ፡ ይኾናል ።

**ጽራግ ፡ ማሰሬ** ፤ የንጉሥ ፡ አልባሽ ፤ መዘይን ፡ ንጉሥ ፤ ያሽከሮች ፡ አለቃ ፡ ጃን ፡ ሽላሚ ። ዘየነን ፡ ተመልከት ።

**ጸሪሕ ፤ ሖት ፤ (ጸርሐ ፡ ይጸርሕ ፡ ይጽራሕ ። ዕብ ፡ ጻራሕ ። ዐረ ፡ ጸረኅ)** ፤ መጮኽ ፤ መጥራት ፤ ማልቀስ ፤ ቡታ ፡ መስደድ ፤ መጸለይ ፤ አቤት ፡ አቤት ፡ ማለት ። ጸርሐት ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ። እጸርሕ ፡ ኪያከ ። ጸራሕኩ ፡ ጽራሐ ፡ መሪረ ። እጸርሕ ፡ ወአዐወዩ ። ሶበ ፡ እኅለቀት ፡ ጸሪሐ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ፡ (ሉቃ ፡ ፩፥፵፪ ። ፴፩፥፲ ። ስንክ ፡ ነሐ፲፫ ። ሔኖ፷፯ ፡ ፰ ። ሰቆ፫ ፡ ፰ ። ዮዲ፯ ፡ ፭) ።

**ጽራሕ ፤ (ሓት)** ፤ ጩኸት ፤ ጥሪ ፡ ልቅሶ ። ጽራሕ ፡ ወብካይ ። ወለቡ ፡ ጽራሕየ ። ጽራሓት ፡ (አስቴ፬ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፰ ። ሔኖ፱ ፡ ፱) ።

**ጽርሕ ፤ (ዐረ ፡ ጸርሕ ። ዕብ ፡ ጽሪሕ)** ፤ አዳራሽ ፤ ታላቅ ፡ ቤት ፤ ግንብ ፤ ምኵራብ ፤ ቤተ ፡ ንጉሥ ፤ ቤተ ፡ መቅደስ ፤ ጥሩ ፡ ሰፊ ፡ ረዥም ፤ ደርብ ፤ ተሥላስ ፤ ሰገነት ፤ ዕልፍኝ ፤ ዋሻ ፡ በኣት ። ምስጢሩ ፡ ጥራትና ፡ ምጥቀት ፡ ታላቅነት ፤ ጩኸትና ፡ ማስተጋባት ፡ ነው ። ጽርሐ ፡ መንግሥት ። ጽርሐ ፡ መቅደስ ። ጽርሐ ፡ አርያም ። ደቀ ፡ ጽርሕ ። ዐርጉ ፡ ጽርሐ ። ወውእቱ ፡ ያርእየክሙ ፡ ጽርሐ ፡ ዐቢየ ፡ ወንጹፈ ፡ ወርቡዐ ፡ (ኢሳ ፴፱ ፡ ፯ ። ማቴ፳ ፡ ፲፫ ። ማር ፡ ፲፬ ፡ ፲፭) ።

**አጽራሕ ፤ አጽርሕት** ፤ አዳራሾች ፤ ታላላቅ ፡ ቤቶች ፤ ደርቦች ። አጽራሐ ፡ ዴዴያት ። ምሥዋዓት ፡ ዘውስተ ፡ አንሕስት ፡ ዘአጽራሐ ፡ አካዝ ። አጽርሕት ፡ (፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ መጋ፳፯) ።

**ተጽራሕ ፤ (ሓት)** ፤ ደርብ ፤ ኹለተኛ ፡ ክፍል ። ተጽራሐ ፡ ወተሥላስ ፡ (ዘፍ፮ ፡ ፲፮) ።

**ጸርይ ፤ ዮት ፤ (ጸርየ ፡ ይጸሪ ፡ ይጽረይ ። አው ፡ ጸረየ ፡ ይጸሪ ፡ ይጽሪ)** ፤ መጥራት ፤ መንጣት ፤ ጥሩ ፡ መኾን ፤ ከርስሐት ፡ መለየት ፤ ወለል ፡ ኵለል ፡ ማለት ። ከመ ፡ ወርቅ ፡ ዘይጸሪ ፡ እምጹአቱ ፡ ይጸርዩ ፡ ቦቱ ። እምከመ ፡ ጸርየት ፡ ኅሊና ፡ (ኄርማ ። ፈላስ) ።

**ጽሩይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሪት)** ፤ የጠራ ፤ የበራ ፤ ንጹሕ ፤ ጥሩ ። ፍትዎ ፡ እመ ፡ ጽሩይ ፡ ውእቱ ። ብሩር ፡ ጽሩይ ። ወርቅ ፡ ጽሩይ ። ወይን ፡ ጽሩይ ። ማየ ፡ ትምህርት ፡ ጽሩይ ። ልብ ፡ ጽሩይ ። ኅሊና ፡ ጽሪት ። ጽሩይ ፡ እምነውር ፡ (ዘካ፲፭ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፲፬ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**ጽርየት** ፤ መጥራት ፤ አጠራር ፤ ጥራት ፡ ጥሩነት ። ወአልቦ ፡ ተሐምን ፡ ውስተ ፡ ጽርየታ ። በእንተ ፡ ጽርየተ ፡ ንጽሕ ። ከመ ፡ ይኩን ፡ አምልኮትሙ ፡ በንጽሕ ፡ ወበጽርየት ፤ ተግሒሦሙ ፡ እምእምልኮ ፡ ባዕድ ። (አፈ ፡ ተ፳፫ ። ጥበ፯ ፡ ፳፱ ። ዮ ፡ ሲፍ) ።

**አጽረየ** ፤ አጠራ ፤ ንጹሕ ፡ አደረገ ፤ ዐደሰ ፡ ኵላ ፤ ፈጸመ ። ወኢያጸሪ ፡ ርስሐተ ። አጽረይኩክሙ ፡ እምኀጢአትክሙ ። አጽርዮ ፡ ለብሩር ፡ ዘኢኮነ ፡ ፍቱነ ። ከመ ፡ ያርስሕዎሙ ፡ ወያጽርይዎሙ ። ለእመ ፡ አጽረየ ፡ ንስሓሁ ፡ በጽኑዕ ፡ ውዕየት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፩ ። ሕዝ ፴፮ ፡ ፴፫ ። ምሳ፳፭ ፡ ፱ ። ዳን፲፩ ፡ ፳፭ ። ቀድር) ።

**መጽርይ ፤ (ዕብ ፡ ከርከም ። ዐረ ፡ ኩርኩም)** ፤ የሽቱ ፡ ቅጠል ፤ ጥሩ ፡ ሽቱ ፤ አበባው ፡ ብጫቱ ፤ ዐደይ ፡ የሚመስል ፤ ሽታው ፡ ብርቱ ፤ የሚሰነፍጥ ። ባለ ብሉዮች ፡ ግን ፡ ቀጋ ፡ ይሉታል ። ናርዶስ ፡ ወመጽርይ ። ነስነስኩ ፡ ምስካብየ ፡ መጽርየ ። ይለብስ ፡ ዘሕብረ ፡ መጽርይ ፡ (ማሕ፬ ፡ ፲፬ ። ምሳ፯ ፡ ፲፯ ። ኄርማ) ።

**ጽርኒ** ፤ ጥርኝ ፡ የዝባድ ፡ አውሬ ፡ ድመት ፡ የምታኽል ፡ ድመት ፡ የምትመስል ፡ ጠረናም ፡ ጠረኑ ፡ መልካም ፡ ዝባድን ፡ እይ ።



ጽ ርኒ ፡

**ጽርንዕት ፤ (ዕብ ፡ ጸራዓት ፤ ለምጽ)** ፤ ቋቍቻ ፤ ቡሓ ፤ ቈረቈር ፤ ዕከክ ፤ ብግር ። ዘቦ ፡ ጽርንዕት ፡ ባዕሌሁ ፡ (ዘሌ፳፩ ፡ ፳ ። ፳፪ ፡ ፳፬) ።

**ጸራዒት ፤ (ዕብ ፡ ክሳሊም ። ጽር ፡ ሚሪዎን)** ፤ ብሽሽት ፤ ጭቅና ፤ የኵላሊት ፡ በታ ፤ ዙሪያው ፡ አጠገቡ ። ሥብሐ ፡ ዘውስተ ፡ ጸራዒት ፡ (ዘሌ፫ ፡ ፬ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ። ፬ ፡ ፱ ። ፯ ፡ ፬) ። ጸራዒት ፡ ዘውጣ ፡ ነው ፡ የግራና ፡ የቀኝ ፤ ጎንድ ፡ ሲኾን ፡ ግን ፡ ጽርዒ ፡ ያሰኛል ።

**ጽሩፌም ፤ (ዕብ ፡ ጹርፌም)** ፤ ብር ፡ አፍሳሾች ፤ አንጥረኞች ፡ ቀጥቃጮች ፡ (ነሐ፫ ፡ ፰) ።

**ጸሪቅ ፤ ቆት ፤ (ጸረቀ ፡ ይጸርቅ ፡ ይጽርቅ ። ዐረ ፡ ጸረቅ)** ፤ ማግማት ፤ ማርቀቅ ፤ መዘርጋት ፤ ሥሥ ፡ ዝርግ ፡ ማድረግ ፤ የቈጣ ፡ የንሓስ ። ሙጨረቅ ፡ ማስቀ ፡ ውሃ ፡ መምሰል ፤ መበጨቅ ፡ መብጫጨቅ ፤ ጨርቅ ፡ ውራጅ ፡ መኾን ፤ የልብስ ። ከጥሬው ፡ በቀር ፡ አንቀጹ ፡ አይገኝም ። ጨረቃ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ጸሪቅ ፤ (ቃት ፤ ጸራይቅ)** ፤ የንሓስ ፡ ገንዘብ ፤ ሥሥ ፤ ታናሽ ፡ መጨረሻ ፤ ወራዳ ፤ የተናቀ ፤ ስምና ፡ መልክ ፡ ያልታተመበት ፤ የአሶርዮን ፡ ሩብ ። አንዱ ፡ ጸሪቅ ፡ ሳንቲምና ፡ የሳንቲም ፡ ሩብ ፡ ይኾናል ፤ ሳንቲም ፡ መቶኛ ፡ ወይም ፡ የመቶ ፡ አንደኛ ፡ ነው ። እንተ ፡ ረሰይከ ፡ እግዚእ ፡ ጸሪቀ ፡ መበለት ፡ ውኩፈ ፤ እምእለ ፡ አብኡ ፡ ብዑላን ፡ ዘተርፈ ፡ (ደራሲ) ። ክልኤ ፡ ጸራይቅ ። በክልኤቲ ፡ ጸሪቀ ፡ አሶርዮን ፡ (ማር፲፪ ፡ ፵፪ ። ሉቃ፲፪ ፡ ፯) ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ ሻሚ ፡ መሐልቅ ፤ ኃምስ ፡ ደዋኒ ፤ ግርሽ ፤ የሙርኝ ፡ አንጀራ ፡ ይሉታል ። ሙርኝ ፡ የጤፍ ፡ ዐይነት ፡ ማር ፡ ነው ፤ ዳልጋውና ፡ ፍሬው ፡ ጥቍር ፡ ጤፍ ፡ ይመስላል ።

**ጸሪቅ ፤ (ዕብ ፡ ራቂቅ)** ፤ ሥሥ ፤ ረቂቅ ፡ ዕንጐቻ ። ለማንን ፡ ተመልከት ። ጸራይቀ ፡ ናእት ። ጸራ

ይቀ ፡ ጎብዝት ። በበ ፡ ጸሪቃት ፡ ጎብዝተ ፡ ጤጉን ፡ (ዘፀጽ፴ ፡ ፪ ። ኢዘሌና ፡ ፲፯ ፡ ፫ ። ፪ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፱) ።

**ጸርቅ ፤(ብ ፡ አጽርቅት)** ፤ ጨርቅ ፤ የልብስ ፡ ዕላቂ ፡ ውራጅ ፡ ጉራጅ ፡ ቍራጭ ፡ ዕራፊ ። **ዘጸርቅ** ። **ጸርቀ ፡ ትክቶ ። ይከድን ፡ ሥጋሁ ፡ በጸርቅ ፡ ብሉይ ። ፈሐቁ ፡ ቍስሎ ፡ በአጽርቅተ ፡ ጸጕር ። ጠብሰልዎ ፡ በአጽርቅት** ፡ ጉራጅ ፡ (ማቴ፱ ፡ ፳፱ ። ኢሳ፷፬ ፡ ፮ ። ስንክ ፡ ጥቅም ፡ ፲፱ ። ሐምሌ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ።

**ጸርሰ ፤—ጠረሰ ፤—ፀሪስ ፡ ፀርሰ ።**

**ጸቃ ፤—ተራ ፡ ረድፍ ፤—ጸዊት ፡ ጸወተ ።**

**ጼተሎ ፤(ዕብ ፡ ጺቃ ፤ ጺቴት ፤ ዲን ፡ ክብሪት)** ፤ የሚያስክር ፡ መጠጥ ፡ ስውነትን ፡ የሚያነድና ፡ የሚያቃጥል ፤ ርሱም ፡ ራሱ ፡ የሚቃጠል ። ዲናዊ ፡ ክብሪታዊ ፡ ወይም ፡ ዲኖ ፡ ክብሪቶ ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ጕሽ ፡ ጠጅ ፡ የማር ፡ ጠጅ ፡ ይሉታል ። **አውዳሕከ ፡ ሎቱ ፡ ወይነ ፡ ወጼተሎ** ፡ (ሚክ፪ ፡ ፲፩ ። ሆሴ፰ ፡ ፱) ።

**ጸቲም ፤ ሞት ፤(ጸተመ ፡ ይጸትም ፡ ይጽትም ። ጻመተ ፡ አ)** ፤ መግጠት ፤ ማጋጠት ፤ መስበር ፡ ማድቀቅ ፡ መቀጥቀጥ ፡ መስንጋት ፤ ማሸት ፤ ማኰላሸት ። **ጸተሞ ፡ ያዕቆብ ፡ ለጣዖተ ፡ ራሔል** ፤ (መጽ ፡ ምስ ። ኩፋ ፡ ፵፭) ።

—፤ ማጥመም ፡ ማግደድ ፤ ገዳዳ ፡ ወልጋዳ ፡ መኾን ፡ ማድረግ ፡ የጠባይ ፡ የመልክ ።

**ተጸትመ** ፤ ተሰበረ ፤ ተቀጠቀጠ ፤ ተሰነጋ ፤ ተሞከተ ።

**ጽቱም ፤(ማን)** ፤ የተሰበረ ፡ ቅጥቅጥ ፤ ስንጋ ፤ ሙክት ። **ዘጽቱም ፡ ወዘምቱር** ፡ (ዘሌ፳፪ ፡ ፳፬) ።

**ጸታም** ፤ ጥመት ፤ ጠማምነት ፤ ውልግድግድነት ። **የኾድግኑ ፡ ዘይት ፡ ጸታሞ** ፡ (ኤር፲፫ ፡ ፳፫) ። ዕብራይስጥና ፡ ጽርእ ፡ ዐረብ ፡ ሳይቀር ፤ ይዊልጥኑ ፡ (ኢትዮጵያዊ) ፡ ኵሻዊ ፡ ማእሶ ፡ ያሉትን ፡ የግእዝ ፡ መሳኽ ፡ ዘይት ፡ ጸታም ፡ ብሎ ፡ አለስመ ፡ አለዘይቤው ፡ ተርጕሞታል ።

**ጸጸ ፤—ስመ ፡ ፊደል ፤—ፀጸ ።**

# ፀ

**ፀ** ፤ ፲፱ኛ ፡ ፊደል ፤ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፡ የጸደይ ፡ ጸ ፡ ተወራጅ ፤ ወይም ፡ ምክትል ፤ ኹለተኛ ፤ ዲቃላ ፤ ተቀጥላ ፤ ስሙ ፡ ፀጸ ፤ በዐረብ ፡ (ፃዕ) ፡ ዳድ ፡ ይባላል ፤ ፍችውን ፡ በቦታው ፡ ተመልከት ። ፲፱ኛነቱ ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ ነው ፡ በፊደልነት ፡ ግን ፡ ፲፱ኛው ፡ የግእዝ ፡ ፊደል ፡ ቆፍ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ፀጸ ፡ አይደለም ። የጸ ፡ ኹለተኛ ፡ መባሉም ፡ በመልክና ፡ በድምጥ ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ ነው ፤ የጎርም ፡ ጎን ፡ ፍች ፡ መገርመሪያውን ፡ ጎ ፡ ተመልከት ። ጎ ፡ የሐ ፡ ዲቃላ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከሐ ፡ ቢደረብ ፡ እንጂ ፡ ለብቻው ፡ እንዳይቈጠር ፤ ፀ ፡ ደግሞ ፡ የጸ ፡ ዲቃላ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ከጸ ፡ ቢደረብ ፡ እንጂ ፤ ለብቻው ፡ አይቈጠርም ፤ እንደ ፡ ኻያ ፡ ኹለቱ ፡ ፊደላት ፡ አባትነት ፡ መደበኛነት ፡ የለውም ። በፊደል ፡ ቍጥር ፡ ግን ፡ ከታው ፡ በኋላ ፡ ከነ ፡ ቀጥሎ ፡ ሲጣፍ ፡ ፀ ፡ ፳፮ ፡ ይባላል ። በዐረብ ፡ ፊደል ፡ የፀ ፡ ድምጥ ፡ ከጸ ፡ ልዩ ፡ ሲኾን ፡ መልካቸው ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ከነቍጣ ፡ በቀር ፡ ልዩነት ፡ የለውም ፤ በግእዝ ፡ ግን ፡ መልካቸው ፡ ልዩ ፡ ኹኖ ፡ ሳለ ፡ ድምጣቸው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ የመልክ ፡ እንጂ ፡ የድምጥ ፡ ልዩነት ፡ የላቸውም ፤ ልዩነታቸውም ፡ የጠፋ ፡ በኋላ ፡ ዘመኝ ፡ ነው ። ከፍሬምናጦስ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ የፀጸ ፡ ፀ ፡ ድምጥ ፡ ገባሬ ፡ ስማይት ፡ ወምድር ፡ በከመ ፡ በሰማይ ፡ ከማሁ ፡ በምድር ፡ ወምድርኒ ፡ ትገብር ፡ ፋሲካ ፡ እንደሚባለው ፡ እንደ ፡ ድ ፡ አጠራርና ፡ ድምጥ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጸደይ ፡ ጸ ፡ አልነበረም ፤ ዛሬም ፡ በዐረብ ፡ እንደ ፡ ምድራዊ ፡ ድ ፡ ይጠራል ። በዕብራይስጥም ፡ ኹለት ፡ ጸ ፡ አለ ፤ ኹለተኛው ፡ ጸ ፡ ሳድስ ፡ እየኾነ ፡ በመጨረሻ ፡ ቃል ፡ ይገባል ፤ ድምፁ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ልዩነት ፡ የለውም ፤ በፊደልም ፡ ቍጥር ፡ መጨረሻ ፡ ኹኖ ፡ ፱፻ ፡ ይባላል ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ ሐተታ ፡ ተመልሰኽ ፡ በፊደል ፡ ታሪክ ፡ ተመልከት ።

**ፄአ ፤—ገማ ፡ ሸተተ ፤—ጸዩእ ፡ ጼአ ።**

**ፃእፃእ ፤—ጭንጋፍ ፤—ወፂእ ፡ ወፅአ ።**

**ፀብአ ፤—ወጋ ፡ አጠፋ ፤—ጸቢእ ፡ ጸብአ ።**

**ፀበበ ፤—ጠበበ ፤—ጸቢብ ፡ ጸበበ ።**

**ፀቢጥ ፤ ጦት ፤(ፀበጠ ፡ ይፀብጥ ፡ ይዕብጥ ። ዐረ ፡ ፀበጥ ። ዕብ ፡ ጻባጥ)** ፤ መጨበጥ ፤ አጥብቆ ፡ መያዝ ፤ ከእጅ ፡ ውስጥ ፡ ማግባት ። **ዘይፀብጥ ፡ ዐቅራበ ። ዘይፀብጥ ፡ ጽላሎተ ። በትረከ ፡ ፅብጥ ፡ በእዴከ ። ቆመ ፡ ኄበ ፡ ሞኅት ፡ ቀሥድስ ፤ ወፀበጥዋ** ፡ (ሚሌ፳፯ ፡ ፯ ። ፀሴ ፡ ፪ ። ዘፀ፲፯ ፡ ፭ ። ዮሴፍ) ። ሥበጠን ፡ እዩ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ፀባጢ ፤(ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት)** ፤ የሚጨብጥ ፡ ያዥ ፡ ጨባጭ ። **ፀባጤ ፡ ሸሎ** ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ። ቈ

ጣቢ ፡ ንፋግ ፡ እጅ ፡ ጥብቅ ። ሰዎችና ፡ ፈረሰኞች ፡ እንዳሉ ፡ ቸርና ፡ ዚስ ፡ ሲሉ ።

**ተፀብጠ** ፤ ተጨበጠ ፡ ተያዘ ።

**ፅቡጥ** ፤ (**ጣን ፡ ጣት ፡ ብጥ**) ፤ የተያዘ ፡ የተጨበጠ ፤ ጭብጥ ። **አስይፍቲሆሙ ፡ ምሉኃን ፡ ወፅቡጣን ፡ በእደዊሆሙ** ፡ (ስንክ ፡ ታኅሣ)።

**ፅብጠት** ፤ መጨበጥ ፤ (ጥፈ) መጨበጥ ፤ አጨባበጥ ፡ ጨበጣ ፤ ጭበጣ ፤ ጭብጥንት ። **እንተ ፡ ትትረከብ ፡ ፅብጠቱ** ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፰)።

**ፀብጥ** ፤ ጨብጥ ፤ ያመንዝራ ፡ ደዌ ፤ ከቂጥኝ ፡ የሚብስ ፡ የሚከፋ ። ጭብጥ ፤ የሙጣት ፡ የውርርድ ፡ ውል ። (ተረት) ፤ ጭብጥ ፡ ያኸር ፤ ውርድ ፡ ነኸር ።

**ዕብን** ፤ **ዕብጥ** ፤ (**ብ ፡ ዕበን ፤ አዕባን**) ፤ መያዣ ፤ መጨበጫ ፡ እጀታ ፤ ገሮ ፤ ቀለበት ፤ የሣጥን ፡ የመሣሪያ ። ፩ኛው ፡ ቅጥል ፡ ስለ ፡ ቀረ ፡ ጥ ፡ የነበረው ፡ ን ፡ ተብሏል ፡ እንጂ ፡ ዘሩ ፡ ፀቢጥ ፡ ነው ። **ፀብን ፡ አርባዕ ፡ ዘወርቅ ፤ በአፀባን ፡ ዘዲበ ፡ ታቦት** ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፲፪ና ፡ ፲፰)።

**ፀበረ** ፤— ረገጠ ፤— ጸቢር ፡ ጸበረ ።

**ፀበርት** ፤— ዝንጣፊ ፤— ፀመርት ፤ ፀመረ ።

**ፀቢስ** ፤ **ሶት** ፤ (**ፀብሰ ፡ ይፀብስ ፡ ይፅብስ ። ፀወሰ**) ፤ መድከም ፡ መዛል ፤ መፍሬት ፤ መላላት ፤ ማንከስ ፤ ፈሬ ፡ ደካማ ፡ መኾን ። **ይፀብሱ ፡ ጽኑዓን ። ኢትፀበስ ፡ በቅድመ ፡ ገጾሙ** ፡ (ኢሳ፵ ፡ ፴ ። ዘዳ ፴፩ ፡ ፮)።

**ፅቡስ** ፤ (**ሳን ፡ ሳት ፡ ብስት**) ፤ የደከመ ፡ ድኩም ፤ ልል ፤ ፈሪ ፤ ስንፍ ፤ ዐንካሳ ። **ንህብ ፡ በኀይላ ፡ ፀብስት ። እስመ ፡ ኅሊና ፡ ፀቡስ ፡ ምኑን ፡ ይትባህል ። ኢትኩን ፡ ፀቡሰ ፡ በዙሉ ፡ ዘገበርከ ። እደው ፡ ፀቡሳን** ፡ (ምሳ፳ ፡ ፰ ። ጥበ፪ ፡ ፲፭ ። ሢራ፴፪ ፡ ፳፪ ። ኢሳ፴፭ ፡ ፫ ። ዕብ፲፪ ፡ ፲፪)።

**ፅብሰት** ፤ መድከም ፤ መስነፍ ፡ ደካምነት ።

**ፅበስ** ፤ ድካም ፤ ሕማም ፤ ስንፍና ፤ ፍርሀት ። **ኅሴስል ፡ ፀበሰ ፡ እምላዕሌክሙ** ፡ (ዘፀ፳፫ ፡ ፳፭ ። ፊልክ)።

**አፅበሰ** ፤ አደከመ ፤ አዛለ ፤ አስነፈ ፤ ፍቀ ፤ አቃለለ ። **ሕምዝ ፡ እንተ ፡ ታፀብስ ፡ አብለ ። አፀበሰ ፡ ኅሊናሁ ፡ በኀይለ ፡ ወይን** ፡ (ዲድ ፡ ፳፭ ። መጽ ፡ ምስ) ። በአፅበሰ ፡ ፈንታ ፡ አስተፅበሰ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። **ቀሲልኑ ፡ በኀቤክሙ ፡ አስተፀብሶተ ፡ ሰብእ ፡ ወለእግዚአብሔርኒ ፡ ታስተፀብስዎ** ፡ (ኢሳ፯ ፡ ፲፫ ። ሉቃ፲፪ ፡ ፴፱) ። ዳግመኛም ፡ አፅበሰ ፡ አስተፅበሰ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አስተፃበሰ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ፡ ፍጹም ፡ ጸያፍ ፡ ነው ፡ (ሉቃ፲፪ ፡ ፴፱)።

**ፀበተ** ፤— ዋኘ ፤— ጸቢት ፡ ጸበተ ።

**ፀጊም** ፤ **ሞት** ፤ (**ፀገመ ፡ ይፀግም ፡ ይፅግም ። ዐረ ፡ ፀጊመ**) ፤ መጥመም ፤ መጉበጥ ፤ ጠማማ ፡ መኾን ፤ ወደ ፡ ግራ ፡ መኼድ ፤ መገልበጥ ።

**ፀጋም** ፤ (**ማት ። ዕብ ፡ ስሞል**) ፤ ግራ ፡ የቀኝ ፡ አንጻር ፤ እጅ ፤ ጐን ፤ ማእዝን ፤ ሰሜን ፤ ሰሜናዊ ፤ ግራኝ ። **ተፈለጥ ፡ የማነ ፡ አው ፡ ፀጋመ ። ልቡ ፡ ሰአብድ ፡ ውስተ ፡ ፀጋሙ ። ብእሲ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ፀጋመ ፡ እድ** ፡ (ዘፍ፲፫ ፡ ፱ ። መክ፲ ፡ ፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ፡ ፩)።

**ፀጋማዊ** ፤ **ይ** ፤ የግራ ፤ በግራ ፡ ያለ ፤ ግራኝ ፡ ጠማማ ፤ ጉባጣ ፤ ሰሜናዊ ። **ፀጋማዊ ፡ ጥቡ ። ዘቦቱ ፡ ፀጋማይ ፡ የማናየ ፡ ኮነ ። ዐይኑ ፡ ፀጋማይ ። ዐይኑ ፡ የማኒት ፡ ወፀጋሚት** ፡ (ኩፋ፴፰ ። ኪዳ ። ቀሌ)።

**ዕግም** ፤ ግራ ፤ ጐን ፤ እጅ ፤ ቦታ ፤ ስፍራ ፤ የግራ ፡ ግራ ፤ ቅርብ ፡ አጠገብ ። **ነጺፍ ፡ በይምን ፡ ወበፅግም ። ማይሰ ፡ ሎሙ ፡ አረፍተ ፡ በይምን ፡ ወአረፍተ ፡ በፅግም ። እኅትኪ ፡ ዘትነብር ፡ በፅግምኪ** ፡ (ሄዜና ፡ ፲፪ ። ዘፀ፲፬ ፡ ፳፱ ። ሕዝ፲፮ ፡ ፵፮)።

**ዕግመት** ፤ ጥመት ፤ ጠማምነት ፤ ግራኝነት ።

**ፀጊዕ** ፤ **ዖት** ፤ (**ፀግዐ ፡ ይፀግዕ ፡ ይፅጋዕ ። ዐረ ፡ ፀገዐ**) ፤ ጠጊዕ ፤ መጠጋት ፤ መደገፍ ፤ መንተራስ ፤ ጥግ ፡ ደገፋ ፡ መያዝ ፤ ማግኘት ። ጠግዐን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በፀግዐ ፡ ፈንታ ፡ ፀንግዐ ፡ ተፀንግዐ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ገል ፡ ኀበ ፡ ሰከበ ፡ ወተፀንግዐ** ፡ (አዋል) ። ጥሬውንም ፡ በምዕጋዕ ፡ ፈንታ ፡ ምዕንጋዕ ፡ ይላል ።

**ፀጋዒ** ፤ (**ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት**) ፤ የሚጠጋ ፤ ተጠጊ ፤ ተደጋፊ ፤ የሙጥኝ ፡ ባይ ።

**ፅጉዕ** ፤ (**ዓን ፡ ዓት ፡ ግዕት**) ፤ የተጠጋ ፤ የተደገፈ ፤ ጥግ ፡ የያዘ ፤ የተኛ ።

**ፅግዕ** ፤ **ፅጋዕ** ፤ (**ዓት**) ፤ ጥግ ፡ ደገፋ ፤ መጠጊያ ፤ መከዳ ፤ ትራስ ። **ወይገብራ ፡ ፀጋዐ ፡ ለዙሉ ፡ ርእስ ። ወእሠጥጥ ፡ ፀጋዓቲክሙ** ፡ (ሕዝ፲፫ ፡ ፲፰ና ፡ ፳፩)።

**አፅግዐ** ፤ አስጠጋ ፤ አስደገፈ ፤ አስተኛ ፤ አንተራሰ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በአፅግዐ ፡ ፈንታ ፡ አስተፃግዐ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **አንበርዎ ፡ ዲበ ፡ ዐራት ፡ ወአስተፃግዕዎ ፡ በወሰይድ ፡ ዘሜላት** ፡ (ዮሴፍ)።

**ምዕጋዕ** ፤ (**ዓት**) ፤ መጠጊያ ፡ ማረፊያ ፡ ቦታ ፤ ዐልጋ ፡ ሙኝታ ። ዐንግዐን ፡ ተመልከት ።

**መፃጉዕ** ፤ (**ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት**) ፤ በለብዙ ፡ መጨጊያ ፤ ድውይ ፤ ባልጋ ፡ በምንጣፍ ፡ የወደቀ ፤ የተጨነቀ ፡ የጉበጠ ፤ የተጨበጠ ፡ የሰለለ ፡ የሰለሰለ ፤ መንሣት ፡ መቀመጥ ፤ መዘር ፡ መገላበጥ ፡ የማይችል ፤ ሽባ ፡ ጉባጣ ፤ ተርካሳ ። **ትቤ ፡ ዐራት ፡ ፖዜሁ ፡ ተባርዮ ፡ አልጸቀ ፡ መፃጉዕ ፡ ከማየ ፡ ከመ ፡ ትጸረይ ፡ ሕቀ ። ወኮነ ፡ መፃጉዐ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ** ፡ (ቅኔ ። ስንክ ፡ መጋ፱ ። ማቴ፱ ፡ ፳፱ ። ፰ ፡ ፮ ፡ ፱ ፡ ፪ ። ማርቆ፪ ፡ ፫ ። ሉቃ፭ ፡ ፲፰)።

**ፀዊግ** ፡ **ጎት** ፡ (**ፆገ ፡ ይፀውግ ፡ ይፁግ**) ፤ አው ፡

(ጥወ) **ፀውን ፤ ንት ፤ (ፀወገ ፡ ይጼውግ ፡ ይፀውግ)** ፤ መክፈት ፤ መፈከን ፤ እንዳውሬ ፡ መኸን ፤ ልብን ፡ ማጥመም ፤ ሬትን ፡ ማጥቁር ፡ ማጭንግ ፤ ጭጉጉት ፡ ማስመሰል ። **ዘይፀውግ ። እለ ፡ ይጼውጉ ፡ እምኔሁ ፡** (ዘዳ፳፰ ፡ ፳ ፡ ፪ ። ማቴ፲፪ ፡ ፵፭) ። በዕገና ፡ በዐወገ ፡ ፈንታ ፡ ተፀውገ ፡ ተፀወገ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **እኩያን ፤ እለ ፤ ይፀወጉ ። ዲዮቅልጥያኖስ ፤ ቢጸ ፡ አራዊት ፤ በተፀውገ ፤** (ኩፋ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ መጋ፳) ።

**ፀዋግ ፤ (ግት ፡ ጋን ፡ ጋት) ፤** ክፉ ፡ መጥፎ ፤ ጨካኝ ፤ ጠማማ ። **ገብር ፡ ፀዋግ ። አርዌ ፡ ፀዋግ ። ፀዋጋን ፤ መላእክት ። እደው ፤ ፀዋጋት ፡** (ምሳ፳፱ ፡ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፴፱ ። ግንዘ ። ሚራ፪ ፡ ፲፱) ።

**ፅዉግ ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ። **ኅብርን ፤ ሕውግዘ ፡ ፅዉጋት ፤ ወጥሉቃት ፤ ትምህርታት ፡** (ተረ ፡ ቄር፲፱) ።

**ፅግት ፤** መክፈት ፡ መፈከን ፤ አክፋፍ ፤ አጨካከን ፤ ክፋት ፡ ጭካኔ ፤ ጥመት ፤ ጠማምነት ። **ፅገተ ፤ ሕንበሳ ፡ መንገለ ፤ የውሀት ፤ ሕግዐዘ ፤** (ስንክ ፡ ታኅ፲፱) ።

**ፅግ ፤ (ጋት) ፤** ኀጢአት ፡ ክፋት ፤ ተንኰል ፤ ጽንት ፤ ጥመት ። **ሸሱ ፤ ምግባረ ፡ ፅግ ። ሰብእ ፤ ከኑ ፤ እኩያን ፤ በምክረ ፡ ፅግ ። ሊትግበር ፤ ፅግ ። እለ ፤ ይትመየጡ ፤ ውስተ ፡ ፅግ ፤** (ቀሌ ። ኩፋ ፡ ፲ ። ፴፯ ። መዝ ፡ ፻፳፱) ።

**ጼወወ ፤—ማረከ ፤—ፀየወወ ።**

**ፀወን ፤—ጥግ ፤ እንባ ፤—ጸወን ።**

**ፆረ ፤—ተሸከመ ፤—ጸዊር ፡ ጾረ ።**

**ፆርሮ ፤ ሮት ፤ (ፆረረ ፡ ይፆርር ። ጸዐረ) ፤** መጨነቅ ፡ ማጣር ፡ መራገብ ፡ መዘበር ፡ መቀባጠር ፤ መታወክ ፡ መቅበጥበጥ ፡ መንቈራጠጥ ፤ መናወዝ ፡ መቃበዝ ፡ የሥቃይ ፡ የደዌ ፡ የሞት ፡ የሐዘን ። ፀረረን ፡ ተመልከት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በፆረረ ፡ ፈንታ ፡ እንፆረረ ፡ ይላል ። **ወሸሎ ፤ ሌሊተ ፤ ታንፆርር ፤** (ኢዮ፯ ፡ ፬) ።

**እንፆረረ ፤** እንሸዋረረ ፡ ተንሸዋረረ ፤ ዐይኑ ፡ ዞዋራ ፡ ሸውራራ ፡ ሸንዳራ ፡ ኾነ ፤ ብጭርጭርቅ ፡ ወይም ፡ ጭብርቅርቅ ፡ አለ ። ምስክር ፡ የለውም ።

**ንፆራር ፤ (ዕብ ፡ ጼር) ፤** ሸውራርነት ። ጣር ፡ ጋር ፡ ሥቃይ ፡ ሐዘን ፡ ሞት ፡ የጭንቅ ፡ ጨንቆት ። **ይዋሕዩኒ ፤ ነፆራር ። አንዘሙ ፤ ፍርሀት ፤ ወረዓድ ፤ ወድንጋፄ ፤ ወነፆራር ። አንዝ ፤ ነፆራረ ፡ ሐዘን ፤ ወሕክህለ ፤ ያርምም ፤ ወክልሐ ፤** (ኢዮ፴ ፡ ፲፰ ። ግንዘ ። ዮሴፍ) ።

**ፀዊስ ፤ ሰት ፤ (ፆሰ ፤ ፀወሰ ፡ ይፀውስ ፡ ይፁስ ። ፀብሰ) ፤** መስምሸት ፤ መሸብየት ፤ መስሰል ፤ ልምሾ ፡ ሽባ ፡ ሰላላ ፡ መኾን ።

**ፅዉስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ውስት) ፤** የለመሸ ፡ ልምሹ ፤ ሽባ ፡ ሰላላ ፤ ደካማ ። **ብእሲ ፤ ዘፅዉስ ፤ እገሪሁ ። ዘፅውስት ፡ እደሁ ። ስፍነ ፤ ዕደው ፤ ኅያላን ፤ ረሰየ ፡ ሞተ ፤ ይትዋነይዎሙ ፤ ዕጼያት ፤ ፅዉሳት ፤** (ማቴ፫ ፡ ፪ ። ማር፫ ፡ ፫ ። ግንዘ) ።

**አፅወሰ ፤** ሽባ ፡ አደረገ ፤ አካለ ፡ አጕደለ ። **እሙቦ ፤ ዘአቀሥሰ ፤ ዐይነ ፤ ገብሩ ፤ ወአፅወሰ ፤** (ዘፀ፳፩ ፡ ፳፯) ።

**ፃሕብ ፤—ዝብዘባ ፤ ሽክላ ፤—ጽሒብ ፡ ጸሐበ ።**

**ፀሓይ ፤ (ያት ። ጽሕወ ፤ ጸሐየ ፤ በራ) ፤** በቁሙ ፤ ጣይ ፤ ታላቅ ፡ ብርሃን ፤ ቀን ፡ የሚያበራ ። **ዘየዐቢ ፤ ብርሃን ፤ ከመ ፤ ይምልክ ፤ መዓልተ ። ፀሓየ ፤ ቀትር ። ፀሓይ ፤ ዘያበርህ ፤ ወይጠፍእ ፤** (ዘፍ፩ ፡ ፲፮ ። ሚራ፴፩ ፡ ፲፱ ። ኢዮ፴፩ ፡ ፳፮) ።

**ፀሓያዊ ፤** የፀሓይ ። **ዓመት ፡ ፀሓያዊ ። ዓመተ ፤ ፀሓይ ፤** (አቡሻ) ።

**ፅሒስ ፤ ሰት ፤ (ፀሐሰ ፡ ይፅሕስ ፡ ይፅሐስ ። ዕብ ፡ ዱጽ ። ሱር ፡ ዳጽ ። ዐረ ፡ ደሐጸ) ፤** ማሽብሸብ ፤ ማርገድ ፤ መንኰራደድ ፤ መዝለል ፡ መጨፈር ፡ መደንከር ፤ ዳንኪራ ፡ መምታት ፤ መርገጥ ፡ ማስረገጥ ፡ መወሳወስ ፤ የእግር ፡ የጫማ ። **ይፀሕሱ ፤ በእገሪሆሙ ፤ ውስተ ፤ እሳት ፤** (ገድ ፡ ተክ) ። በፀሐሰ ፡ ፈንታ ፡ አፅሐሰ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ያፀሕሳ ፤ በእገሪሆን ። አፀሕስ ፤ በእገሪከ ። አፀሐሰት ፤ በእገሪሃ ፤ ወጠፍሐት ፤ በእደዊሃ ። ጠፊሓ ፤ በእእዳው ፤ ወአፀሒሳ ፤ በአእጋር ፤** (ኢሳ፫ ፡ ፲፮ ። ሕዝ፮ ፡ ፲፩ ። ድጓ ። አርጋ) ።

**ፃሕስ ፤** ሽብሸባ ፡ ርግድ ፤ መረግድ ፡ ረገዳ ፤ ዝላይ ፡ ጭፈራ ፤ ርግጫ ፡ ዳንኪራ ። (ግጥም ፤ ዐዲ ፡ ቴ ፡ ውርድ ፡ ሲንዛ ፡ በንደብቴ) ፤ ቦራቂ ፡ ራሱን ፡ ታጣቂ ፤ እረግራጊ ፡ እቴና ፡ ወጊ ፤ ዘፈን ፡ ግብሩ ፡ ዳንኪራ ፡ መጥኑ ፤ የኍመን ፡ ትል ፡ ዕጥፍ ፡ ዘርጋ ፡ የሚል ። ለቋረኞች ፡ ደብተራን ፡ መስደብ ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ፤ ቀድሞም ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ዲያብሎስ ፡ ቤት ፡ አያውቅምን ፡ ብለው ፡ የሞኝ ፡ አጠያየቅ ፡ ጠየቁና ፡ እምኝ ፡ እቴጌ ፡ ሆይ ፡ ርሱማ ፡ መልአክ ፡ እንኳ ፡ አይደለ ፡ በዚህስ ፡ አይጠረጠርም ፡ ቢሏቸው ፤ እንኪያማ ፡ ደብተራን ፡ ማን ፡ ወለደው ፡ ልበል ፡ የማን ፡ ልጅ ፡ ልበለው ፡ አባቱን ፡ ንገሩኝ ፡ አሉ ፡ ይባላል ።

**አፀሐሰ ፤ (አስደራጊ) ፤** ዳንኪራ ፡ አስመታ ፤ አስጨፈረ ፤ ረገጡ ፡ ዝለሉ ፡ አሸብሽቡ ፡ አለ ፤ ወይም ፡ ርግጫ ፡ ሽብሸባ ፡ ርግድ ፡ አስተማረ ፤ እንደንጉኤ ፡ መኰንን ።

**መፅሕስ ፤ (ስት ፡ ሳን ፡ ሳት) ፤** አስረጋጊ ፤ አሸብሻቢ ፤ ዳንኪራ ፡ መቺ ።

**ጼውዎ ፤ ዎት ፤ (ጼወወ ፡ ይጼውው ። ዕብ ፡ ሻባህ ። ሱር ፡ ሸባእ ። ዐረ ፡ ሰባ) ፤** መማረክ ፤ መዝረፍ ፤ መሳብ ፡ መጐተት ፤ በግድ ፡ መውሰድ ፡ መንዳት ። **ጼዊወከ ፤ ጼዋ ። አንዘ ፤ ይጼውዉ ፤ ሀገረ ። ጼወወኒ ፤ መንገሌሁ ፤** (መዝ ፡ ፷፯ ። ኩፋ ፡ ፲፭ ። ሮሜ፯ ፡ ፳፫) ።

**ጼዋዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤** የሚማርክ ፤ ማራኪ ፤ ዘራፊ ፤ ወሳጅ ።

**ተዒወወ ፤** ተማረከ ፤ ተወሰደ ፤ ፈለሰ ። ከመ ፡ ኢይዔወዋ ፡ እንስቲያሆሙ ፡፡ ተዔወዉ ፡ ሕዝብየ ፡፡ እስከ ፡ ተዔወዉ ፡ እምነ ፡ ብሔሮሙ ፡ (ዮዲ ፲ ፡ ፲፪ ። ኢሳ ፳ ፡ ፲፫ ። ሚራ ፵፰ ፡ ፲፭) ።

**ዒውው ፤ (ውት ፡ ዋን ፡ ዋት) ፤** የተማረከ ፤ የተዘረፈ ፤ የተጋዘ ። ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ዘኮነ ፡ ዒውዋነ ፡ ወአግብኦሙ ፡ ኀበ ፡ ማኅደሪሆሙ ፡፡ አመት ፡ ዒውውት ፡፡ እስብከ ፡ ሎሙ ፡ ግዕዛነ ፡ ለዒውዋን ፡ (ማንዘ ። ዘፀ ፲፪ ፡ ፳፱ ። ሉቃ ፬ ፡ ፲፱) ።

**ዔዋ ፤** ምርኮ ፤ ምርኮኛ ፤ ማዘተኛ ፤ የምርኮ ፡ ማኅበር ፤ ምርኮነት ፤ ምርኮኛነት ። ይመይጥ ፡ ዔዋ ፡ ሕዝብየ ፡፡ ነሥኡ ፡ ብዙኀ ፡ ዔዋ ፡፡ እምሕሮሙ ፡ ለዔዋሁ ፡፡ ወሀሎኩ ፡ ማእከለ ፡ ዔዋ ፡ (ኢሳ፵፰ ፡ ፲፫ ። ፪ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፲፯ ። ኤር፴፯ ፡ ፲፰ ። ሕዝ፩ ፡ ፩) ።

**ዒዋዌ ፤ ዔዋዌ ፤** ምርኮ ፤ ማረክ ፤ ዘረፋ ፤ ስደት ፤ ግዞት ። እሜጥዎሙ ፡ ለዒዋዌ ፡፡ ወሕቡላንሰ ፡ ይከውኑ ፡ ለዔዋዌ ፡ (ኩፋ ፡ ፩ ። ምሳ፲፪ ፡ ፳፬) ።

**ዔዐ ፤— ገማ ፤ ሸተተ ፤—ጸዩአ ፡ ጼአ ።**

**ዒዖት ፤ (ታት ። ዐረ ፡ ፀይዐት) ፤** መስከ ፤ ጨረፈ ፤ ክልክል ፤ ማራም ፡ ቅጠላም ፡ ስፍ ፡ ቦታ ፤ የከብት ፡ መሰማሪያ ። ከመ ፡ ማዕረ ፡ ዒዖት ፡ ስሙር ፡፡ አክብር ፡ ዒዖተ ፡ ከመ ፡ ይብዝኃ ፡ መራዕይከ ፡፡ ዒዖተ ፡ ሐመልማል ፡፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡ ውስተ ፡ ዒዖት ፡፡ ረከቡ ፡ ዒዖታተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወስሙራተ ፡ (ኢዮ፳ ፡ ፳፭ ። ምሳ፳፯ ፡ ፳፫ ። ጥበ፲፱ ፡ ፯ ። ሆሴ፬ ፡ ፲፯ ። ፩ዜና ፡ ፬ ፡ ፵) ።

**ፀክ ፤—ፂን ፤ ሹልዳ ፤—ጸክ ።**

**ፀምዐ ፤—ጠማ ፡ ተጠማ ፤—ጸምአ ።**

**አፅምዐ፤—አደመጠ፡ሰማ፤—ጸምዐ ።**

**ፀሚድ ፤ ዶት ፤ (ፀመደ ፡ ይፀምድ ፡ ይዕምድ ። ዕብ ፡ ጻማድ ። ሱር ፡ ጽማድ ። ዐረ ፡ ፀመደ) ፤** መማዘት ፡ በታች ፡ ማድረግ ። መጥመድ ፤ ማቀናጀት ፡ ጥንድ ፡ ማድረግ ፤ ቀንበር ፡ መጫን ፤ ከቀንበር ፡ ከሠረገላ ፡ ማቈራኘት ፤ የበሬ ፤ የፈረስ ። ፀመደከ ፡ ሰይጣን ፡ ከመ ፡ አባዕር ፡ ወአንበረ ፡ አርዑቶ ፡ ውስተ ፡ ክሳድከ ፡፡ ፀሚደ ፡ አርዑት ፡ ያደንኖ ፡ ለክሳድ ፡፡ ይፀምዱኒ ፡ በአርዑቶሙ ፡ ወይቀንዩኒ ፡ ለግሙራ ፤ ከመ ፡ ይፀመዱ ፡ ተያፍን ፡ ወብዕራ ፡፡ አዘዘ ፡ ይፀምድዎሙ ፡ ለአፍራስ ፡ በሠረገላ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ሚራ፴፤ ፡ ፴፳ ። ስንክ ፡ ግንቦ፲፭ ። ኅዳ፲፰) ። ዘመደኛ ፡ ተመልክት ፡ የዚህ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ነው ፡፡

—፤ ማጥመድ ፤ በወጥመድ ፡ መያዝ ። ከመ ፡ ይፀምዱ ፡ ሰብአ ፡ በሃይማኖት ፡ (ፊልክ ፡ ፵፩) ። ወሀበ ፡ አቅረበ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ፀመደ ፡ አስተፅመደ ፡ አስተፃመደ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። (ዘሌ፲፰ ፡ ፳፫ ። ፳፬ ፡ ፲፮ ፡ ፱) ።

**ፀማዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤** የሚጠምድ ፡ የሚያጠምድ ፤ ጠማጅ ፤ አጥማጅ ።

**አፅመደ ፤** አስጠመደ ፤ ጥመዱ ፡ አጥምዱ ፡ አለ ፤ በወጥመድ ፡ አሲያዘ ፤ አሳረሰ ። (ተረት) ፤ ምንም ፡ ቢያስጠምዱ ፡ በዘጠና ፤ ቤቱን ፡ አይሰትም ፡ ቀጠና ።

**መዕመ(ም)ድ ፤ (ብ ፡ መፃምድ) ፤** መጥመጃ ፤ ማጥመጃ ፡ ማያጠመጃ ፤ መቀርቀቢያ ፤ ማቈራኛ ፤ ኹለቱን ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፤ ቀንበር ፡ ምራን ፡ ማነቆ ፡ ቅራኛ ፡ መጫኛ ፡ በንሰሰት ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ወጥመድ ፤ ሸምቀቆ ፤ ቀላድ ፤ ሽርብ ፡ ገመድ ፡ ሦስቲዮ ። ተአስሮ ፡ በመፀመድ ፡፡ መፃምድ ፡ ሐይስት ፡ (ኢዮ፴፱ ፡ ፲ ። መሳ፲፭ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ። ፲፯ ፡ ፲፭ ፡ ፲፪) ።

**ተፀምደ ፤** ተጠመደ ፤ ጥንድ ፡ ኾነ ፤ ከወጥመድ ፡ ከወስከ ፡ ገባ ፤ ተያዘ ፤ አገለገለ ። ተፀምደ ፡ ምስሌሁ ፡ በአሐዱ ፡ አርዑት ፡፡ ተፀመድ ፡ መኳንንቲከ ፡፡ ዘይፈቅድ ፡ ይፀመደኒ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፯ ። ሚራ፳፻ ፡ ፲፱ ። ማርቆ ፡ ፴፬ ። ማቴ፲፫ ፡ ፶፪) ።


—፤ ነቃ ፡ ተጋ ፡ እንቅልፍ ፡ በጣ ፤ ወደደ ፡ አፈቀረ ፤ አዘወተረ ፤ ሥራውን ፡ አገልግሎቱን ። ተፀምዶ ፡ ሊተ ፡ ድላዝ ፡ ዓለም ፡ ያማስን ፡ ነፍስ ፡፡ ይፀመዱ ፡ ጸሎተ ፡፡ ይፀመድ ፡ ጸሎታተ ፡ ወአጽዋመ ፡፡ ሐና ፡ ነቢይት ፡ እንተ ፡ ተፀምደት ፡ ጾመ ፡ ወጸሎተ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፰ ። ማብ፩ ፡ ፲፬ ። ፊልክ ፡ ፯ና ፡ ፶፩) ።

**ፅሙድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ምድ) ፤** የተጠመደ ፤ የተገዛ ፡ ትጉህ ፡ መናኝ ፡ ባሕታዊ ። ፀሙዳን ፡ ታሕተ ፡ አርዑተ ፡ እሪት ፡፡ እለ ፡ ፀሙዳን ፡ ሊከርሦሙ ፡፡ ይኩን ፡ ንቁሀ ፡ ወፀሙደ ፡ ወልብወ ፡፡ ብፁዕ ፡ ጴጥሮስ ፡ ፀሙድ ፡፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ወፀሙድ ፡ መስተጋድል ፤ አባ ፡ ሰረባሞን ፡ (አርጋ ፡ ፭ ። አፈ ፡ ተ፳፱ ። ፈላስ ። ስንክ ፡ ጥር፳፭ ። መጋ፭) ።

**ፁማዴ ፤** መጥመድ ፤ መጠመድ ፤ አጠማመድ ፤ ጠመዳ ፤ አገልግሎት ፤ ባርነት ፡ ቤተ ፡ ሰብነት ። ወዘኒ ፡ ለፁማዴ ፡ (፩ሰገ ፡ ፰ ፡ ፳፮) ።

**ፀማድ ፤ (ውስጠ ፡ ብዙ) ፤** አገልጋይ ፤ ሎሌ ፡ አሽከር ፤ ቤተ ፡ ሰብ ፤ ልደ ፡ ቤት ። እምፀማዱ ፡፡ አመ ፡ ይሔውጽ ፡ ፀማደ ፡፡ ኖላውያን ፡ ወፀማደሙ ፡ (ግብ ፲ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ሚያ፯ ። ሔኖ ፡ ፲፫) ።

**ዕምድ ፤ (ዳት) ፤** ጥማድ ፤ ጥንድ ፤ ኹለት ። ፀምደ ፡ አልሕምት ፡፡ ፀምደ ፡ ብዕራይ ፡ (ኢዮ፩ ፡ ፫ ። ፫ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱—፳፩ ። ኢሳ፳ ፡ ፲ ። ሉቃ፲፬ ፡ ፲፱) ።



ዕምድ ፡

**ተፃመደ ፤** ተጣመደ ፤ ተጠማመደ ፤ ተቈራኘ ፤ አጣማጅ ፡ ወደረኛ ፡ ኾነ ፤ ተወዳደረ ።

**አስተፃመደ ፤** አጣመደ ፤ አጠማመደ ፡ ተቈራኘ ፡ አለ ።

**ፃመወ ፤—ጣመነ ፡ ደከመ ፤—ጻምዎ ፡ ጻመወ ።**

**ፀመወ ፤—ጨመተ ፤ ዝም ፡ አለ ፤—ጸምዎ ፡ ጻመወ ።**

**ፀመመ ፤ (ጸሚም ፡ ጻመ) ፤** በከመ ፡ ጠገነ ፡ አሰረ ፡ ሸፈነ ፤ ጠቀለለ ፤ ጠመጠመ ፤ የቍስል ፡ የሰባራ ። **ኢ.ፀመ ምዎ ፡ ከመ ፡ ይትፈወስ ። ኢ.ይፀምምዎ ፡ ወኢ.ይቀብዕዎ ፡** (ሕዝ፴ ፡ ፳፩ ። ኢ.ሳ፩ ፡ ፮) ። ትመልእኑ ፡ ታጽግብኑ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ት(ታ)ፀምምኑ ፡ ንፍስ ፡ አክይስት ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ኢ.ዮ፴፰ ፡ ፴፱) ።

—፤ አዳነ ፡ ፈወሰ ፡ አሻረ ፤ አደረቀ ፡ አጠና ፡ አበረታ ፤ አጨከነ ። **ወይፀምም ፡ ሶሙ ፡ ቍስሎሙ ። ፀመመ ፡ ቍስሊሆሙ ። እንበይነ ፡ ነፍስ ፡ ወልድከ ፡ ፀምም ፡ ልበከ ፡** (መገ፣ ፻፲፯ ። መጽ ፡ ምስ ። ሚ.ራ.፵ ፡ ፯) ። በፀመመ ፡ ፈንታ ፡ አፀመመ ፡ ይባል ፤ አያሰኝም ። **ጾም ፡ ትፌውስ ፡ ቍስለ ፡ ነፍስ ፡ ወታፀምም ፡ ፍትወተ ፡ ዘሥጋ ። ፈውሳት ፡ እለ ፡ ያጥዕያ ፡ ወርጢናት ፡ እለ ፡ ያየብሳ ፤ ወቅብዐ ፡ አፈዋት ፡ እለ ፡ ያፀምማ ፡ ቍስላተ ፡** (ገድ ፡ ቀክ ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፫ ። አርጋ ፡ ፫) ።

**ፅሙም ፤** የደረቀ ፤ የጠበቀ ፤ ክራራ ፡ ጠንካራ ፤ ጽኑዕ ፤ ጎቱም ። **አውፀአ ፡ ሶሙ ፡ ማየ ፡ እምኩሕሕ ፡ ፅሙም ፡** (አፈ ፡ ድ፯) ። ጽሙምን ፡ ተመልከት ፤ ጸመና ፡ ፀመመ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ።

**ያማፅት ፡—ዋሻ ፡ በአት ፤—ጸማፅት ።**

(ጥ) **ፀምሮ ፤ ሮት ፡ (ፀመረ ፡ ይፄምር ፡ ይፀምር ። ዐረ ፡ ሰመረ ። ዕብ ፡ ሳሜር ፤ ቀነወ) ፤** መጨመር ፤ መደረብ ፤ ማጣበቅ ፡ መለጠቅ ፤ ኹለቱን ፡ ነገር ፡ ማጣመር ፡ አንድ ፡ ማድረግ ፤ አጣምሮ ፡ መያዝ ፤ መውጋት ፡ መስፋት ፡ ማሰር ፡ መቸንከር ። ደመረን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። **እፄምሮ ፡ ለዳዊት ፡ ውስተ ፡ አረፍት ። እፀምሮ ፡ በምድር ፡ ምዕረ ። ፀመረቶ ፡ ምስለ ፡ ምድር ። ኢ.ትፀምር ፡ አሲረ ፡ ክልኤቲ ፡ ኀጣይእ ፡** (፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፲፩ ። ፳፯ ፡ ፰ ። መሳ፬ ፡ ፳፩ ። ሚ.ራ.፯ ፡ ፰) ።

—፤ መሸለት ፡ መቀረጥ ፤ ማጨይድ ፡ መቈጥቈጥ ፤ የጠጉር ፡ የማር ፡ የቅጠል ፤ ቀረፀን ፡ ተመልከት ።

**ፀማሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤** የሚጨምር ፡ ጨማሪ ፤ አጣባቂ ፤ አንድ ፡ አድራጊ ።

**ተፀመረ ፤** ተጨመረ ፤ ተደረበ ፤ ተጣበቀ ፤ ተዋሐደ ፤ ፩ ፡ ኾነ ። **ተፀመረ ፡ ፀምረት ፡ ህላዌ ፡** (ተረ ፡ ቄር) ።

**ፅሙር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ምርት) ፤** የተጨመረ ፤ ጭማሪ ፤ ጭምር ፤ ያበረ ፡ የተባበረ ፤ ፩ ፡ የኾነ ። **መልእክ ፡ ዘፅሙር ፡ ምስሌሁ ፡** (አዋል) ። **ፅሙረ ፤** ተጨምሮ ፡ ፩ ፡ ኹኖ ፡ ባንድነት ፡ (ኤፍ ፡ ፬) ።

**ፅማሬ ፤ ፅምረት ፤** መጣመር ፡ መጨመር ፤ አጨማመር ፤ ጭመራ ፤ አንድነት ፤ ተዋሕዶ ። **ፅምረቱ ፡ ህላዌ ። ፀምረተ ፡ ሥላሴ ። እትኤዛዝ ፡ በፀምረት ፡** (ቀረ ፡ ቄር ። አትና) ።

—፤ ሩካቤ ፡ የሩካቤ ፡ ሥራ ። **ለእመ ፡ ወረደት ፡ ላዕሌከ ፡ በሌሊት ፡ ሕልመ ፡ ፀምረት ፡ ኢ.ትዝክራ ፡ በመዓልት ፡** (ፊልክ ፡ ፻፸፩) ።

**መፅመር ፤ መፅምር ፤ (ብ ፤ መፃምር) ፤** ፀባሪ ፡ ተባባሪ ፡ ተማፋሪ ፡ ጓደኛ ፡ ወዳጅ ፡ ባልንጀራ ፤ ሰራተኛ ፡ ባል ፡ ሙሽራ ፤ የብእሲት ፡ ጣምራ ። መጨመሪያ ፡ ማጣመሪያ ፤ መጣብቅ ፡ ችንካር ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። መጣምር ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። **ኢ.ትኩን ፡ መፀመሮ ፡ ለብእሲ ፡ መዐትም ። ምስለ ፡ ዐርክከ ፡ ወመፀመርከ ፡** (ምሳ፳፪ ፡ ፳፬ ። አዋል) ። በመፅመር ፡ ፈንታ ፡ መፃምርት ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **እኁየ ፡ ወመፃምርትየ ። ይኩን ፡ መፃምርተ ፡ ምስለ ፡ ማኅበረ ፡ ቅዱሳን ። ወረሰየ ፡ መፃምርተ ፡ ምስለ ፡ ሰማያውያን ፡** (ፊልጵ፬ ፡ ፫ ። ማንዘ) ።

**መፅ(መ)ምርት ፤ (ብ ፡ መፃምርት) ፤** ሴት ፤ ሚስት ፤ የወንድ ፡ ጣምራ ፤ ኹለተኛ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ያንዱን ፡ በብዙ ፤ መፃምርት ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። **እስመ ፡ ሊተ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ እምአመ ፡ ተመተርኩ ፡ እምነ ፡ መፃምርትየ ። ዘይፈቅድ ፡ ይዘሙ ፡ ምስለ ፡ መፃምርተ ፡ ካልኡ ፡** (ፊልክ ፡ ፫ ። ፵፩) ።

**ተፃመረ ፤** ተጋባ ፡ ተጣመረ ፤ ተባበረ ፤ ተጣፈረ ፤ ተሰማማ ፤ ተዋደደ ፡ አንድ ፡ ኾነ ። **ብእሲ ፡ ይፃመር ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ። እስመ ፡ ትፃመር ፡ ነፍስ ፡ ምስለ ፡ ሰይጣን ፤ ከመ ፡ ተፃምሮታ ፡ ለብእሲት ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ። ዘይፃመር ፡ ምስለ ፡ ጠቢብ ፡** (ክፋ ፡ ፫ ። ፈ.ልክ ፡ ፻፲ ። ምሳ፲፫ ፡ ፳) ።

**አስተፃመረ ፤** አጋባ ፤ አጣመረ ፤ አዋደደ ፤ አዋሐደ ፤ አንድ ፡ አደረገ ፤ የባልና ፡ የሚስት ። አንቀጹ ፡ የማይፈረማ ፡ ነው ፤ ፍችው ፡ ግን ፡ ማድረግ ፡ ኹኖ ፡ ከፀመረ ፡ ፍች ፡ ይገጥማል ። **ዘእግዚ ፡ አስተፃመረ ፡ ሰብእ ፡ ኢ.ይፍልጥ ። ደናግል ፡ ዘኢ.ያስተፃመርዎን ፡ አበውሆን ፡ ወእሞን ፡ በሕገ ፡ ሰብሳብ ፡** (ማር፲ ፡ ፱ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**መስተፃምር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤** የሚያጣምር ፡ የሚያጋባ ፤ አማጭ ፤ ነገር ፡ ቈራጭ ።

**ፀማመረ ፤ (የፀመረ ፡ ድርብ) ፤** ጨማመረ ፡ ደራረበ ። **ወእፀማምር ፡ ሰኑየ ፡ ወሰኑየ ፡** (ፊልክ ፡ ፻፲፭) ።

—፤ ሸላለተ ፡ ቈራረጠ ፤ በመጨደ ፡ ቈጣቈጠ ።

**ፀምር ፤ (ዕብ ፡ ጼሜር ። ሱር ፡ ጻምራ) ፤** የበግ ፡ ጠጕር ፤ ልም ፡ ልገዝብ ፡ ጥሩ ፡ ነጭ ፤ ቀጫጭን ፡ ረዣዥም ። የሰው ፡ የእንስሳ ፡ ሥዕርት ፤ እያደገ ፡ የሚሸለትና ፡ የሚቈረጥ ፤ ማር ፡ ቅጠል ፡ ዐጽቅ ። ልብስ ፡ ፀምር ፤ ከጠጕር ፡ ተፈትሎ ፡ የሚሠራ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሙስክ ፡ ብዝት ፡ ጠጕር ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ይሉታል ። **እምፀምረ ፡ አባግዕየ ፡ ወሥዕርቱ ፡ ከመ ፡ ፀምር ፡ ጸዐዳ ። ትለብሱ ፡ ፀምረ ። ወኢ.ይዕርግ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ፀምር ። ሜጠ ፡ ፀምር ፡ ግብረ ፡ እዴ ፡** (ኢ.ዮ፴፩ ፡ ፳ ። ራእ፩ ፡ ፲፬ ። ሕዝ፵፬ ፡ ፫ ። ማ፬ ፡ ፲፯ ። ሰንክ ፡ መጋ፲፰) ። እሰ

ፍሕ ፡ ፀምረ ፡ ያሰው ፡ ግን ፡ (መሳ፲ ፡ ፴፯) ፡ ነጻውን ፡ ጠጕር ፡ ነው ። ፅብሬይስጡ ፡ ቅናፀ ፡ ፀምረ ፡ ያሰውን ፡ የግእዝ ፡ መሳሽ ፡ ቅጽሉን ፡ ትቶ ፤ ልብስ ፡ አስመስሎታል ፤ እንቀጹም ፡ አቀውም ፡ አነብር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሰፍሕ ፡ አይደለም ።

—፤ የታጨደ ፡ መስክ ፤ ፀጽቁ ፡ ቅጠሉ ፡ የተቈረጠ ፡ ጕንድ ፡ ሐረግ ፤ ዝናምና ፡ ጠል ፡ የሚፈልግ ። ወይወርዱ ፡ ከመ ፡ ጠል ፡ ውስተ ፡ ፀምር ። ወከመ ፡ ጊሜ ፡ ውስተ ፡ ፀምር ፡ (መዝ ፡ ፸፩ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፪) ።

**ፀመርት** ፤ (ራት ። ፅብ ፡ ጻሜሬት) ፤ ፀጽቃም ፡ ቅጠላም ፡ ዛፍ ፤ ዘንባባ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። የዛፍ ፡ ውልብልቢት ፡ ራስ ፡ ጫፍ ፡ ፀጽቅ ፡ ክንፍ ፤ ቅጣፊ ፡ ዝንጣፊ ፤ ሰሌን ፡ የዘንባባ ፡ ቅጠል ፤ ሙሽራው ። ምስጢሩ ፡ ማደግ ፡ መቈረጥ ፡ ሳይቀር ፡ የቅጠሉን ፡ ጣም ፡ ራንትና ፡ ፅጥፍ ፡ ድርብነት ፡ ያሳያል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በፀመርት ፡ ፈንታ ፡ ፀበርት ፡ ይላል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፤ ኀበዘ ፡ ብሎ ፡ በግ ፡ ፈንታ ፡ ስ ፡ ኀብስት ፡ እንደ ፡ ማለት ። ፀበርተ ፡ ተመርት ፡ ዘበቀልት ። አባ ፡ ዳንኤል ፡ ዑጹፍ ፡ በልብሰ ፡ ፀበርት ። ወግሉፋን ፡ ኪሩቤል ፡ ወፀበራት ፡ (ዮሐ፲፪ ፡ ፲፫ ። ስንክ ፡ ታኅ፳ ። ሕዝ፵፩ ፡ ፲፰) ።

**ፅንብል** ፤ (ጠብለለ) ፤ ማንብላ ፡ የራስ ፡ የማንባር ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ የሚጠመጠም ፡ የሚታሰር ። ሐዲስ ፡ ጥሩ ፡ ልብስ ፤ መጕናጠፊያ ፤ ባለማል ፡ ሲሾም ፡ ሲሸለም ፡ የሚለብሰው ። ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ ዘቦ ፡ አክሊለ ፡ ወርቅ ፡ ወፅንብል ፡ ሚራየ ፡ ሜላት ፡ (አስቴ፰ ፡ ፲፭) ።

**ፀንግዐ** ፤ (ፀግዐ) ፤ ተጠጋ ፡ አስጠጋ ፡ ራሱን ፡ ተኛ ፡ ተጋደመ ። በፀንግዐ ፡ ፈንታ ፡ ተፀንግዐ ፡ ይላል ፡ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ፍችውና ፡ ዘሩ ፡ የፀግዐ ፡ ሲኾን ፡ ን ፡ በክንቱ ፡ ገብቷል ፤ ፀግዐን ፡ ተመልከት ። ኀሊ ፡ ኀበ ፡ ተፀንግዐ ፡ (አሞል) ። ባማርኛ ፡ አጠንጋ ፡ ጥንግ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የመጣ ፡ ነው ።

**ምፅንጋዕ** ፤ (ምፅጋዕ) ፤ መጠጊያ ፡ ፀታ ፡ ጋጥ ፡ በረት ፡ ግርግም ። ወእደ ፡ አልቦ ፡ አልሕምት ፡ ምፀንጋዕ ፡ ንጹሕ ። ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ተቀነወ ፡ ወዲበ ፡ ምፀንጋዕ ፡ ተጠብለለ ። ነደቀ ፡ ውስተ ፡ ጸላዕቱ ፡ በአምሳለ ፡ ምፀንጋዕ ፡ (ምሳ፲፬ ፡ ፬ ። ድጓ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ፀንዐ** ፤—ጠና ፡ በረታ ፤—ጸንዐ ፡ ጸንዐ ።

**ፀንፈርት** ፤ (ፀፈረ ፤ መፅፈርት) ፤ የወፍ ፡ ወጥመድ ፤ ማነቆ ፡ ሽምቀቆ ። ወፈንጠር ፤ የሚያጨናፍር ፡ ደንጊያ ፡ ጠጠር ፡ ብትን ፡ ፀረር ። ከመ ፡ ይመሥጥ ፡ ወይጠል ፡ እምነ ፡ መሥገርት ፡ ገሪፍ ፤ ወከመ ፡ ይድኅን ፡ እምፀንፈርት ፡ ዖፍ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲) ።

**ፅንፅንያ** ፤—ጥንጣን ፤ ዝንብ ፤—ጸንጸና ።

**ፅናሴ** ፤ ተፅናስ ፤—ችጋር ፤—ጸንሶ ፡ ጸነሰ ።

**ፀኒስ** ፤ ሶት ፤ (ፀንሰ ፡ ይፀንስ ፡ ይፅነስ ። ዐረ ፡ ፀኒየ ፤ ወላድ ፡ ኾነ) ፤ መፅነስ ፡ መቋጠር ፡ ማርገዝ ፡ በሆድ ፡ በማሕፀን ፡ መሸከም ፡ መያዝ ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ማበጥ ፡ መንዘርጠጥ ፡ መንጠርዘዝ ፡ እስኪወልዱ ፡ ድረስ ፡ ቀብዳዳ ፡ እንቅብ ፡ ሆድ ፡ መኾን ። ጠንሰስ ፡ ጥንስስ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ጊዜ ፡ ሰፀነስ ። ናሁ ፡ ድንግል ፡ ትፀንስ ፡ ወትወልድ ፡ ወልደ ። ዘእንበለ ፡ ትፀንሶ ፡ በከርሥ ። ፀነስኪ ፤ ሐመምኪ ፡ ወወለድኪ ፡ (መክ፫ ፡ ፪ ። ማቴ፩ ፡ ፳፫ ። ሉቃ፪ ፡ ፳፩ ። ኢሳ፳፮ ፡ ፲፰) ።

—፤ ማሰብ ፡ መመኘት ። በከርሣሙ ፡ ይፀንሱ ፡ ጻዕረ ፡ (ኢዮ፲፭ ፡ ፴፭ ። መዝ ፡ ፯ ። ኢሳ፶፱ ፡ ፬ና ፡ ፲፫) ።

**ፀናሲ** ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት) ፤ የሚፀንስ ፡ የሚያስብ ፤ ፀናሽ ፡ ዐሳቢ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፩ ፡ ፬) ።

**አፅነሰ** ፤ አስፀነሰ ፡ አሲያዘ ፡ አስረገዘ ። ብእሲሰ ፡ ይክል ፡ አፅንሶ ፡ ወአቅም ፡ ዘርዐ ፡ እምድኅረ ፡ ሰላ ፡ ዓመት ። ኢይክል ፡ ተራክቦ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ወኢአፅንሶ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፯ ። ፲፪ ፡ ፳ ። ቄድር) ።

**ተፀንሰ** ፤ ተፀነሰ ፡ ተረገዘ ። ተፀንሰ ፡ በከርሥ ። ዕለተ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ተፀነስከ ። ተፀንሶቱ ፡ እንበለ ፡ ዘርዐ ፡ (ቅዳ ። መጽ ፡ ምስ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**ፅኑስ** ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ንስት) ፤ የፀነሰ ፡ ያረገዘ ፤ እርጉዝ ። ናሁ ፡ ፀንስት ፡ አንቲ ፡ ወትወልዲ ። አሌ ፡ ሎን ፡ ለፀኑሳት ። ፀኑሳት ፡ ገበዓድ ፡ (ዘፍ፲፮ ፡ ፲፩ ። ማቴ፳፬ ፡ ፲፱ ። ዓሞ፩ ፡ ፲፫) ።

—፤ የተፀነሰ ፡ የተረገዘ ፡ የሆድ ፡ ውስጥ ፡ ልጅ ። (ተረት) ፤ የታዘለ ፡ በለምድ ፡ የተረገዘ ፡ በሆድ ።

**ፅንሰት** ፤ መፅነስ ፤ መፀነስ ፤ ፅንስነት ፡ እርጉዝነት ። መዋዕለ ፡ ፅንሰታ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲ ። ነሐ፳) ።

**ፅንስ** ፤ በቁሙ ፤ የማሕፀን ፡ ፍሬ ፡ የልጅ ፡ ቡቃያ ፡ ሽል ፡ እርግዝና ፤ ሐሳብ ፡ ምኞት ። ዘአይኑ ፡ ብእሲ ፡ ዝንቱ ፡ ፅንስ ። ፅንስ ፡ እንበለ ፡ ሩካቤ ። እምቅድመ ፡ ፅንሶን ። ፅንስ ፡ እንዘ ፡ ባቲ ። መዋዕለ ፡ ፅንሳ ፡ ኪያሁ ፡ (ዘፍ፴፰ ፡ ፳፭ ። ቅዳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲ ፡ ፳ ። ዕር ፡ ኢሳ፲፬ ፡ ፳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፬) ።

**ፀዓዕ** ፤ (ዓት) ፤ መብረቅ ፤ ነጐድጓድ ፤ የመብረቅ ፡ ጓታ ፡ ብልጭታ ። ትፈኑ ፡ ፀዓዐ ፡ ወየሐውር ። ቃለ ፡ ፀዓዑ ፡ ያፈርሃ ፡ ለምድር ። መብረቅ ፡ ወነጐድጓድ ፡ ወፀዓዕ ፡ ኀያል ። ክልሑ ፡ ፀዓዓት ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፴፭ ። ሢራ፵፫ ፡ ፲፯ ። ቅዳ ፡ ያዕ ። ደራሲ) ።

**ፀዕዐ** ፤ (ዕብ ፡ ሻአህ) ፤ ሙኽ ፡ ነጐደ ፡ ፈረሰ ፡ ተናደ ፤ ተመመ ፡ አስገመገመ ፤ በረቀ ፡ ፈለቀ ፡ ብልጭ ፡ አለ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ብልጭታን ፡ ብቻ ፡ ይፈታሉ ።

**ፂዖት** ፤—መስክ ፤—ፀየዖት ።

**ፀፍዐ** ፤—በጥፊ ፡ መታ ፤—ጸፊዕ ፡ ጸፍዐ ።

**ፅፍፅ** ፤ ፀፍፅ ፤ (ጸፍዐ ። ዐረ ፡ ፀፍፅ ። ዕብ ፡ ጻፊፅ) ፤ አበት ፡ ክብት ፤ ጥፍጥፍ ፡ ዐዘባ ፤ ፈርስ ፤

ፍግ ፡ በጠጥ ፤ ፋንድያ ። ወሀብኩክ ፡ ፀፍዐ ፡ ባሕም ፡ ህየንተ ፡ ፀፍዐ ፡ ሰብእ ። ከመ ፡ ፀፍዕ ፡ ግዱፍ ፡ (ሕ ግዘ ፡ ፲፰ ። ሚ.ሬ.፳፱ ፡ ፱) ።

**ፀፍፀፈ ፤—ጠፈጠፈ ፤—ጸፍጸፎ ፡ ጸ ፍጸፈ ።**

**ፀፈቀ ፤—ጨፈቀ ፤—ጸፊቅ ፡ ጸፈቀ ።**

**ፀፈረ ፤—ጥፍራም ፡ ኾነ ፤—ጸፈር ፡ ጸ ፈረ ።**

(ጥ) **ፀፈር ፤ ሮት ፤ (ፀፈረ ፡ ይፀፍር ፡ ይዕ ፍር ። ዐረ ፡ ፀፈረ) ፤** መታታት ፤ መሥራት ፤ መጐን ጐን ፤ ማከረር ፡ መግመድ ፤ መደረብ ፡ መሸረብ ። ፀፈ ሮቱ ፡ ለሥዕርት ። ፀፈረት ፡ ርእሳ ፡ ወተከብበት ። ፀ ፈረ ፡ ደጓዕሌ ። ወፀፈሩ ፡ ሐራ ፡ አክሊለ ፡ ዘሦክ ። ል ሳንከ ፡ ፀፈራ ፡ ለሕብል ። ጽልሑተ ፡ ይፀፍራ ፡ እደ ዊክሙ ። እለ ፡ ይፀፍርዋ ፡ ለምክር ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፭ ። ዮዲ ፡ ፲፯ ፡ ፰ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፱ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፪ ። መዝ ሙ፲፯ ፡ ፶፯ ። ኢዮ፳ ፡ ፲፫) ።

—፤ ማበር ፤ መጨፈር ፤ አንድ ፡ ቃል ፡ መኾን ፤ በዘፈን ፡ በምክር ፡ (ዐማርኛ) ።

—፤ ማጣፈር ፤ በቃዊ ፡ ማያያዝ ፡ ማቈራኘት ፡ ኹለቱን ፡ ሦስቱን ፡ ብዙውን ። ሚካኤል ፡ ወገብርኤል ። አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ። ጴጥሮስ ፡ ወዮሐ ንስ ፡ ወያዕቆብ ፡ ወእንድርያስ ፡ ወፊልጶስ ፡ ወቶ ማስ ፡ (ግብ፩ ፡ ፲፫) ።

**ፀፋሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤** የሚታታ ፡ የ ሚሠራ ፡ ጐንጓኝ ፤ ጨፋሪ ፡ ዘፋኝ ።

**ተፀፍረ ፤ ተፀፈረ ፤** ተታታ ፤ ተሠራ ፤ ተጐን ጐነ ፤ ተሸረበ ፡ ተደረበ ፡ አንድ ፡ ኾነ ። በተፀፍሮ ፡ ሥ ዕርቶን ። አክሊለ ፡ ስብሐት ፡ ዘተፀፍረ ። ወዘሰ ፡ አ ብድ ፡ ዘከመ ፡ ዝ ፡ ይፀፈር ። ተፀፈርኑ ፡ በህባዊኑ ፡ እ ምእለ ፡ ኢይትአየያ ፡ (፩ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፫ ። ኢሳ፳፰ ፡ ፭ ። ምሳ፳ ፡ ፩ ። ቁር) ። በተፀፍረ ፡ ፈንታ ፡ ተፃፈረ ፡ ይባል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አሕባለ ፡ ኃጥኣን ፡ ተፃፈራ ፡ ላዕሌየ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰) ።

**ፅፉር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ፍርት) ፤** የተታታ ፤ የ ተሠራ ፤ ጕንጕን ፤ ሽርብ ። ሥረዊሁ ፡ ፀፉር ። ኢትግ ብር ፡ ሥዕርተከ ፡ ፍቱሐ ፡ ወዝርዙረ ፡ ወኢፀፉረ ። እለ ፡ ፀፉራት ፡ በኀጢአት ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፲፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭ ። ፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፮) ።

**ፅፍረት ፤** መታታት ፤ መሥራት ፤ መሠራት ፤ አ ሠራር ፤ ሥራ ፤ ስሌን ፡ ወንሬት ። በእንተ ፡ ፀፍረት ፡ ዘደጓዕሌ ። ለዘኮነ ፡ ይፀፍር ፡ ፀፍረተ ፡ (ፊልክ ፡ ፱ ፫ና ፡ ፻፹፱) ።

**ፅፍሮ ፤** የጠጕር ፡ ሥራ ፤ ትት ፤ ጕንጕናት ፤ ሽ ርባት ፤ ሽሩባ ፤ ዐይን ፡ ርግብ ፤ የራስ ፡ የጠጕር ፡ ጌጥ ፡ ሽ ልማት ። በላዎ ፡ ለሥዕርተ ፡ ርእስኪ ፡ ዘተንእደ ፡ ፀ ፍሮሁ ። ወፀፍሮ ፡ ርእስኪ ። ሐብለት ፡ ዘፀፍሮ ፡ (ደ ራቢ ። ማሕ፯ ፡ ፮ ። ዘፀ፴፭ ፡ ፵) ።



ፅፍሮ ፡

—፤ ቍጥራት ፤ ቅጥል ፤ ቅጥልጥል ፤ የጠፍር ፡ የገመድ ፡ የልጥ ፡ የሹጥ ፤ በኮሶ ፡ ቀን ።

**አፅፉር ፤** ቅጥሎች ፤ ቅጥልጥሎች ፤ ሹጦች ፡ የሆድ ፡ ውስጥ ፡ ትሎች ። ኀምሳ ፡ አፀፉር ፡ (ገድ ፡ ላሊ) ።

**መፅፈርት ፤** ወጥመድ ፤ ጕንጕን ፤ አበታ ፡ ገ መድ ። መፀፈርተ ፡ ሲኦል ፡ (ምሳ፲ ፡ ፲፰) ። ዕብራይ ስጡ ፡ ግን ፡ መዓምቅተ ፡ ሲኦል ፡ ይላል ።

**ተፃፈረ ፤** ተጣፈረ ፤ ተባበረ ፤ በዋዊ ። አኑ ፡ ወ አብ ፡ አሐዱ ፡ ንሕነ ፡ (ዮሐ፲ ፡ ፴፩) ።

**አስተፃፈረ ፤ (ፀፈረ) ፤** አጣፈረ ፤ አጨፋፈረ ፤ ሌላውን ፡ ከራሱ ፤ ራሱን ፡ ከሌላ ፤ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ከሌላ ። አቡየ ፡ ወአኑ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ፀሓይ ፡ ወ ብርሃን ፡ ወዋዕይ ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ፃሰ ፤ ፃዔ ፤ (ዕብ ፡ ሳስ ። ሱር ፡ ሳሳ ። ዐረ ፡ ሱስ) ፤** ብል ፤ ታናሽ ፡ ትል ፤ የልብስ ፡ የቅጠል ። ከመ ፡ ልብስ ፡ ይበልዩ ፡ ወይበልያሙ ፡ ፃዔ ። ፃዔ ፡ ወቍን ቍኔ ። ከመ ፡ ብላዐ ፡ ፃዔ ፡ (ኢሳ፶ ፡ ፱ ። ማቴ፮ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። ናሖ፫ ፡ ፲) ።

—፤ ነቀዝ ፤ ጥንጣን ፤ የዕፅ ፡ የእክል ። አብትር ፡ ከመ ፡ ዘፃዔ ፡ በልያሙ ፡ (ሄርማ) ።

**ፃፁት ፤—ታናሽ ፡ ዝንብ ፤—ጻጹት ።**

**ፀቄነ ፤—ጨቄነ ፤ ከበ ፤—ጸቀነን ፡ ጸ ቄነ ።**

**ፀረዐ ፤ ዖት ፤ (ፀርዐ ፡ ይፀርዕ ፡ ይዕራዕ ። ዐረ ፡ ፀረዐ) ፤** መታከት ፡ መድከም ፤ መቶኘት ፡ መጋ ደም ፡ መስነፍ ፡ መበዘን ፤ ማረፍ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ መኾን ፤ ሥራን ፡ መተው ፤ ማቋረጥ ፡ ማቆም ፤ ማስታጐል ። መ ጽሐፍ ፡ ግን ፡ በፀርዐ ፡ ፈንታ ፡ አዕርዐ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። ዘደፈቅር ፡ ውሉዶ ፡ ኢይፀርዕ ፡ ተግሣጾ ። ኢናፀርዐ ፡ ቅኑ ፡ ግብረ ፡ እደዊነ ፡ ወኢንትሀከይ ። ከመ ፡ ኢይፀ ርዐ ፡ ተቀንዮ ፡ ቅድመ ፡ ሥጋሁ ፡ ለአዳም ። ወእምዝ ፡ አፀርዐ ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ፡ (ሢራ፴ ፡ ፩ ። ዲድ ፡ ፲፫ ። ቀሌ ። ሃይ ፡ አበ) ።

**አፅርዐ ፤ (አስደራጊ) ፤** አበዘነ ፤ ሥራ ፡ አስ ፈታ ፤ አስቀረ ፡ ከለከለ ፤ አስተጓጐለ ። ኢየሱስ ፡ አፀርዐ ፡ ምሕለ ። አፀርዐ ፡ ትእዛዘ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፬ ፡ ፭ ። አ ቡሻ ፡ ፶) ።

**ተፀርዐ ፤** ተፈታ ፤ ቀረ ፤ ታጐለ ፤ ተቋረጠ ፤ ቆመ ፤ ጠፋ ፡ ተበላሸ ፡ ከንቱ ፡ ኾነ ፤ ሥራው ። አውሰበ ፡ ይፀ

ራዕ ፡ ለእመ ፡ መንኩሱ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ። ወእምቅድመ ፡ ይፍጥር ፡ መላእክተ ፡ ለቅዳሴ ፡ አኮ ፡ ለብሐቲሁ ፡ ዘተፀርዐ ። ወተፀርዐ ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ ፡ እምዓለም ። ወእምዝ ፡ ተፀርዐ ፡ ሕንጻ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፯ ። ቅዳ ፡ ማሩ ። ዮሴፍ ። ዕገዘ፱ ፡ ፳፬) ።

**ፅሩዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ርዕት) ፤ የፀዘነ ፡ በዘንተኛ ፤ ታከታ ፡ በነፍ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፤ የተጓጉለ ። ኢታንብሮ ፡ ፀሩዐ ። ፀሩዓን ፡ ጸርሑ ። ኢኮንክሙ ፡ ፀሩዓነ ። ፀሩዕ ፡ እምነሰሳው ፡ (ሚራ፴ ፡ ፴፮ ። ዘፀ፳ ፡ ፰ ። ፀጲጥ ፡ ፩ ፡ ፰ ። ጥበ፲፩ ፡ ፲፭) ።

—፤ ከንቱ ፡ ብላሽ ፤ ፈራሽ ፤ ውሸት ፡ ቢልት ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ያለፈ ፡ የቀረ ፡ የተሻረ ፤ ውጥን ፡ ኹምር ። ምግባር ፡ ፀሩዕ ፡ ዘኢይበቍዕ ። ይኩውን ፡ ጻማሆሙ ፡ ፀሩዐ ። ኢይኩውን ፡ ፀሩዐ ፡ ሰብሳብ ፡ ዚኣሃ ። ሕንጻ ፡ ነበረ ፡ ፀሩዐ ፡ (አፈ ፡ ተ፪ ። ዮሴፍ ። ማቴ፲፪ ፡ ፴፮ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፲፪ ። ዕገዘ፱ ፡ ፳፱) ።

**ፅርዐት** ፤ (ታት) ፤ መታከት ፡ መፀዘን ፡ ሥራ ፡ መፍታት ፤ መቅረት ፡ መታጉል ፤ ማስታጉል ። ፀርዐተ ፡ ዕደው ። የሀቦ ፡ ፀርዐቲሁ ። ይግበሩ ፡ ፈቃደከ ፡ ዘእንበለ ፡ ፀርዐት ። ቅዳስያት ፡ ዘእንበለ ፡ ፀርዐታት ፡ (መክ፲ ፡ ፲፰ ። ዘፀ፳፩ ፡ ፲፱ ። ቀሌ ። ቅዳ ። ስንክ ፡ መጋ ፳፱) ።

—፤ በዘን ፤ በዓል ፤ የዕረፍት ፡ ቀን ፤ ጊዜ ፤ ጉባኤ ። በመዋዕለ ፡ ፀርዐቱ ። ቀድሱ ፡ ፀርዐተ ፡ ለጣዖት ። ጾመክሙ ፡ ወፀርዐተክሙ ፡ (ጥበ፲፫ ፡ ፲፫ ። ፀነገ ፡ ፲ ፡ ፳ ። ኢሳ፩ ፡ ፲፫) ።

—፤ ንጢአት ፤ አምልኮ ፡ ጣዖት ፤ ከንቱ ፡ ነገር ፤ ከንቱነት ፤ ምናምንቴነት ። ከመ ፡ ያእምሩ ፡ ፀርዐተ ፡ ሥርዐተ ፡ አማልክቲሆሙ ። ተከሥተ ፡ ፀርዐት ፡ ወተኀብአ ፡ ጽድቅ ። ዘይዴግን ፡ ፀርዐተ ፡ (ዮሴፍ ። ምሳ፲፪ ፡ ፲፩) ።

**አፀርዕት** ፤ በዘዎች ፡ ሀኬቶች ። ይትሜሀሩ ፡ አፀርዐተ ፡ (፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፫) ።

**ፅርዕ** ፤—ግሬክ ፤ ዮናን ፤—ጽርእ ።

**ፀራዒት** ፤—ጭቅና ፤—ጸራዒት ።

**ፀሪፍ** ፤ ፎት ፤ (ፀረፈ ፡ ይፀርፍ ፡ ይፅርፍ ። ዕብ ፡ ጻራፍ ፤ ነጠፈ ፤ አኀበረ ። ሐራፍ) ፤ መፅረፍ ፤ መስደብ ፡ ማዋረድ ፤ ማቃለል ፤ ነውረኛ ፡ ማድረግ ። በእንተ ፡ ፀሪፍ ፡ ወጽዒል ። ይፀርፉ ፡ አሕዛብ ፡ ላዕለ ፡ ስምየ ። ዘይፀርፍ ፡ ላዕለ ፡ ካህናት ። ፀረፉ ፡ በሐሰት ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ። ኢሳ፶፪ ፡ ፭ ። ቀሌ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬) ።

**ፀራፊ** ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ረፍት) ፤ ሰዳቢ ፤ ተሳዳቢ ፤ አዋራጅ ፤ ሰድብ ፡ ፀዋቂ ። ኢያንጽሕ ፡ ፀራፌ ። ኢትኩኑ ፡ መፀትማነ ፡ ወኢፀራፍያነ ፡ ወኢገዝጉራነ ፡ (ጥበ፩ ፡ ፰ ። ዲድ ፡ ፯ ። ፩ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፫) ።

**አፀረፈ** ፤ አሰደበ ፤ አስነቀፈ ፤ በደቡ ፡ አለ ።

**ተፀርፈ** ፤ ተሰደበ ፤ የሰድብ ፡ ቃል ፡ ሰማ ፤ ስድብ ፡ ተቀበለ ።

**ፅሩፍ** ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ርፍት) ፤ የተሰደበ ፡ ስዱብ ፤ ንቁፍ ፡ ነውረኛ ። መኑ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ፅሩፍ ፡ ወዘእንበለ ፡ ትምህርት ። አ ፡ ፀሩፍ ፡ ዘትሜንን ፡ ቢጸከ ፡ (ቄር ፡ ጸላ ። ቀሌ) ። በፀራፊ ፡ ፈንታ ፡ ፅሩፍ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ኢትኩኑ ፡ ፀሩፋነ ፡ (፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፪) ።

**ፅርፈት** ፤ (ታት) ፤ መስደብ ፤ መሰደብ ፤ አሰዳደብ ፡ ስድብ ፡ ውርደት ። ኢተኀበለ ፡ ይንብብ ፡ ቃለ ፡ ፀርፈት ። እመ ፡ ከነ ፡ ቃለ ፡ ፀርፈቱ ፡ እሙነ ። ፀርፈታት ፡ (ይሁ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ። ራእ፲፫ ፡ ፩) ።

**ተፃረፈ** ፤ ተሳደበ ፤ ተሰዳደበ ፤ ተደራረገ ፡ ነው ። በማርኛ ፡ ግን ፡ ተሳደበ ፡ ማለት ፡ አይራገም ፡ ይኾናል ። መታ ፡ ተማታ ፡ ተማቻ ፡ እንደ ፡ ማለት ። ኢተፃረፍክሙ ፡ (አዋል) ።

**አስተፃረፈ** ፤ አሳደበ ፤ አሰዳደበ ፤ አነቃቀፈ ።

**መስተፃርፍ** ፤ የሚያሳድብ ፤ የሚያሰዳድብ ፤ አሳዳቢ ፡ አጣይ ።

**ፀርቅ** ፤—ጨርቅ ፤—ጸሪቅ ፡ ጸረቀ ።

**ፀሪር** ፤ ሮት ፤ (ፀረረ ፡ ይፀርር ፡ ይፅርር ። ዐረ ፡ ፀረ ፤ ጕዳ ። ዕብ ፡ ጻራር) ፤ መፃረር ፤ መጠናወት ፤ ወደረኛ ፡ መኾን ፤ መበደል ፤ ግፍ ፡ መሥራት ፤ መከዳት ፡ መሸፈት ፤ ማመጥ ፡ ግብር ፡ መንሣት ፡ ማቅለጥ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በፀረረ ፡ ፈንታ ፡ አፅረረ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አፀረሩ ፡ ሰይም ። አፀረሩ ፡ ሞአብ ። አፀረሩ ፡ ኤዶም ፡ (ዘፍ፲፬ ፡ ፬ ። ፬ነገ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ፰ ፡ ፳፪ ። ፳፬ ፡ ፳፪) ።

—፤ መፀረር ፤ መሰለፍ ፡ ለጦር ፡ ለውጊያ ፡ መዘጋጀት ።

**ፀራሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤ የሚፃረር ፤ ጠላት ፤ ደመኛ ። በፀራሪ ፡ ፈንታ ፡ ፀራዊ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ ፩ ፡ ነው ።

**ፅሩር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ርርት) ፤ የተፃረረ ፤ የተፀረረ ፤ ዝግጁ ፡ ሰልፈኛ ። በቁሙ ፡ ጥሩር ፡ የራስ ፡ ቍር ፤ ድርዕ ፤ የሰልፍ ፡ ልብስ ፤ የጦር ፡ መጣሪያ ። ጌራኝና ፡ ድርዕን ፡ ተመልከት ። እስመ ፡ ፅሩራን ፡ እሙንቱ ።

**ፀር** ፤ በቁሙ ፤ ተፃራሪ ፤ ጠላት ፤ ወደረኛ ፤ ባላንት ፤ ከዳተኛ ፤ ሽፍታ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጣዖቶችና ፡ በመላሾች ፡ ስሕተት ፡ ሳንድም ፡ ለብዙም ፡ ፀር ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። ብዙ ፡ ለወንድና ፡ ለሴት ፡ ይከታል ። ክዋሙ ፡ ፀሮሙ ። ይከውነከ ፡ ፀረከ ። ሰበ ፡ አመንደብዎ ፡ ፀሩ ። እንዘ ፡ ፀሩ ፡ ንሕነ ፡ ለእግዚ ። ሚመት ፡ ለዙሉ ፡ እንዘ ፡ ፀር ፡ ይእቲ ፡ መኳንንት ፡ ይትጋደሉ ፡ ባቲ ፡ (ኢሳ፷፫ ፡ ፲ ። ሚራ፴፮ ፡ ፱ ። ዓሜ ፡ ፳ ። ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲ ። ቅኔ) ።

**ፀራዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ ፀራሪ ፤ የጠላት ፡ ወገን ፤ ጠላት ፡ ደመኛ ። ብእሲ ፡ ፀራዊ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ። ወፀራዊሰ ፡ ዲያብሎስ ፡ (ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፳፰ ። ፴፱) ።

**አፀራር ፤** ዐሮች ፤ ዝግጁ ፤ ጠላቶች ። ዐቀበቶ ፤ እምአፀራሪሁ ። አፀራርየ ፤ እለ ፤ ተንሥኡ ፤ በነገረ ፤ ክንቱ ፤ ወበክ ፤ (ጥበ ፲ ፡ ፲፪ ። ደራሲ) ።

**አፀረረ ፤** አስከፋ ፤ አሸፈተ ፤ አስጠረረ ፤ አሰለፈ ፤ ጥፋር ፤ አሰበሰ ፤ አሰለበሰ ።

**መፀርር ፤ (ብ ፡ መፃርርት) ፤** የሚፃረር ፤ ተፃራሪ ፤ የሚያስጠርር ፤ አስጠራሪ ፤ ጥፋር ፤ አልባሽ ፤ የስልፍ ፤ መምር ። መሣሪያውንም ፤ ያሳያል ።

**ተፃረረ ፤** ተጣላ ፤ ተጠጣላ ፤ ጠላት ፤ ተኳኋኝ ፤ ተሰላሰፈ ፤ ለመዋጋት ፤ ለመጋደል ። ፍችው ፤ ከፀረረ ፤ ፍች ፤ ይገጥማል ፤ ባማርኛው ፤ የማይረግም ፤ ምስጢር ፤ አለበት ። እለ ፤ ይፃረሩኒ ፤ በከንቱ ። ተፃረርዋ ፤ ሾሎሙ ፤ ፍቁራኒሃ ። አንተ ፤ ተፃረርካሁ ፤ እምትካት ። ቀተሉ ፤ ሾሎ ፤ ዘከኑ ፤ ይፃረሮ ፤ (መዝ ፡ ፫ ። ሰቈ ፩ ፡ ፪ ። መቃ ። የሲፍ) ።

**ትፀርርት ፤** ፀርነት ፤ ተፃራሪነት ፤ ጠላትነት ፤ (ፈልክ ፡ ፫፻) ።

**አስተፃረረ ፤** አጣላ ፤ አጠጣላ ፤ አሳለፈ ፤ አሰላሰፈ ።

**መስተፃርር ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤** የሚያጣላ ፤ አጣይ ። የሚጣላ ፤ ተጣይ ፤ ተቃዋሚ ። ሰትማስን ፤ ምክረ ፤ መስተፃርር ። ኀጢአት ፤ መስተፃርርት ፤ ለእግዚ ፤ አጣይ ፤ (ግንዘ ። ፈልክ) ። ለመስተፃርራን ፤ አስተሳልምዎሙ ። ኢኮኑ ፤ ቃላተ ፤ አበው ፤ መስተፃርራተ ፤ ተጣይ ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ። ፈልክ ፡ ፶) ።

**ፀረስ ፤ ሰት ፤ (ፀርሰ ፡ ይፀርስ ፡ ይፅርስ ። ጠርሰ) ፤** መጥረስ ፤ መደንዘዝ ፤ መድከም ፤ መፍዘዝ ፤ መብለዝ ፤ የጥርስ ፤ የስለት ፤ ጠርስን ፤ ተመልከት ። አበው ፤ በልዑ ፤ ቀዐ ፤ ወአስናነ ፤ ደቂቅ ፤ ፀርሰ ። እሁበክሙ ፤ ትፀርሰ ፤ ስነኒክሙ ፤ (ኤርም ፴፩ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ። ሕዝ ፲፰ ፡ ፪ ። ዓሞ ፬ ፡ ፯) ።

**አፀረሰ ፤** አጠረሰ ፤ አደነዘ ፤ ጥርስ ፤ ሰበረ ፤ አበሰዘ ። ይፀርሰከ ፤ አስናኒከ ፤ (ሚራ ፴ ፡ ፲) ።

**ፅርስ ፤ (ብ ፡ ፅረስ) ፤** ጥርስ ፤ ክራንቻ ፤ መንጋጋ ። ፀና ፤ ጠ ፤ ተወራራሾች ፤ ስለ ፤ ኾኑ ፤ ፅርስ ፤ ጥርስ ፤ እያለ ፤ በኹለቱም ፤ ይገኛል ። ፅርሰ ፤ ወስነ ። ውስተ ፤ ፀረሲሆሙ ፤ (ዘፀ ፳፩ ፡ ፳፯ ። ዘኍ ፲፩ ፡ ፴፫) ።

**ፀተመ ፤—ገጨ ፡ ሰበረ ፤—ጸቴም ፡ ጸተመ ።**

**ፀጸ ፤ (ፀጺ) ፤** ስመ ፤ ፊደል ፤ ፀ ፤ ጸ ፤ ጥንተ ፤ ስሙ ፤ ነው ። አጣጣፉም ፤ እንደዚህ ፤ ነበረ ፤ ይባላል ፤ ፀ ፤ ከግእዝ ፤ በፊት ፤ በነበረው ፤ በሳባ ፤ ፊደል ፤ የበ ፤ ድርብ ፤ ኹኖ ፤ ጸ ፤ ይባል ፤ ነበረ ፤ ጸ ፤ የሚያሰኘውም ፤ የከርሡ ፤ ሠረዝ ፤ ነው ፤ ሠረዙ ፤ ሲቀር ፤ በ ፤ ሲጨመር ፤ ፀ ፤ ጸ ፤ ይባል ፤ ነበረ ፤ ይላሉ ። የኋላ ፤ ሰዎች ፤ ግን ፤ የጸደይ ፤ ምክትል ፤ ሌላ ፤ ነበረና ፤ ያንን ፤ አውጥተው ፤ ይህንን ፤ ሲያገቡ ፤ እንደ ፤ ፀይኑ ፤ ፀ ፤ ክፍቱን ፤ ዘግተው ፤ ኹለተኛ ፤ ፀ ፤ እንደ ፤ ማለት ፤ ጥንታዊ ፤ ስሙን ፤ ሳይለቁ ፤ ፀጸ ፤ ብለውታል ፤ ፍችው ፤ ፀሓያዊ ። ዳግመኛም ፤ በፀጸ ፤ ፈንታ ፤ ፀጸ ፤ ይባል ፤ ፀፀ ፤ ጸጦስ ፤ እንደ ፤ ማለት ፤ ነው ፤ ፀ ፤ ከፀፀ ፤ ጸ ፤ ከጸጦስ ፤ መጥቶ ፤ ተገናኝቷል ፤ ኀባቡ ፤ እንጂ ፤ ምስጢሩ ፤ አንድ ፤ ነው ፤ ጸጦሳዊ ፤ እሳታዊ ፤ ማለትን ፤ ያሳያል ። ጸሐፍት ፤ ደግሞ ፤ ፀሓይ ፤ ፀ ፤ ይሉታል ። ፀጸ ፤ መባል ፤ በመልክ ፤ ቢኾን ፤ ይህ ፤ የዛሬው ፤ ጸ ፤ የጸዲቃላ ፤ ስለ ፤ ኾነ ፤ ፈጽሞ ፤ ጸን ፤ ይመስላልና ፤ ለጸደይ ፤ ጸ ፤ ይልቅ ፤ ይገባው ፤ ነበር ።

# ቀ

**ቀ ፤** ፲፱ኛ ፤ ፊደል ፤ በግእዝ ፤ እልፍ ፤ ቤት ፤ በአበገደ ፤ ስሙ ፤ ቆፍ ፤ ቍጥሩ ፤ መቶ ፤ አኃዝ ፤ ሲኾን ፤ ቀ ፤ (፻) ምእት ፤ ይባላል ። ዳግመኛም ፤ መቶንቱን ፤ ሳይለቅ ፤ ቁ ፤ ከኀሦ ፤ በኋላ ፤ ይ፲፱ ፤ አኃዝ ፤ እየኾነ ፤ ይሰ ሺሕ ፤ ይጣፋል ። ይህም ፤ ኅ፻፲፱ ፤ ቁ፲፱ ፤ እየ ፤ እያለ ፤ መኸዱን ፤ ያሳያል ፤ ያቡጊዳን ፤ አኃዝ ፤ ተመልከት ።

**ቋእ ፤—ቀኈራ ፤—ቋዕ ፡ ቀዊዕ ።**

**ቁእ ፤—ተፋ ፡ ቀረሸ ፤—ቀዩእ ።**

**ቃቡ ፤—ድርጎ ፤—ቀበወ ።**

**ቀብአ ፤—ቀባ ፡ ላከከ ፤—ቀቢዕ ፡ ቀብዐ ።**

**ቀቢው ፤ ዎት ፤ (ቀበወ ፡ ይቀቡ ፡ ይቅቡ) ፤** መንፋት ፤ መቀብተት ፤ ማሳበጥ ። ቀብተተን ፤ እይ ፤ የዚህ ፤ ክፋል ፤ ነው ።

**ተቀብወ ፤** ተነፋ ፤ ተቀበተተ ፤ ሆዱ ፤ ቂብ ፤ አለ ፤ እንቅብ ፤ መሰለ ፤ የደቂ ፤ የማውቂ ።

**ቅብው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ውት ፡ ቡት) ፤** የተነፋ ፤ ኀፉ ፤ እንቅብ ፤ ሆድ ፤ ደዊ ፤ የነፋው ፤ ሆዱ ፤ የቀደመው ። ብእሲ ፤ ቅብው ፤ ቅድሜሁ ፤ (ሉቃ ፲፬ ፡ ፪) ።

**ቃቡ ፤ (ጸር ፡ ክቡ ። ዕብ ፡ ቃብ) ፤** የመስፈሪያ ፤ ስም ፤ ታናሽ ፤ ልክ ፤ ድርጎ ፤ ቍልቢጥ ፤ ቁለም ሽሽ ። የኢሳናን ፤ ፲፰ኛ ፤ እጅ ፤ የምቲዝ ። ሀሎ ፤ ውስተ ፤ አስፈሬዳ ፤ ኅዳጥ ፤ ሥርናይ ፤ ዘየአክል ፡ መጠነ ፤ መ

ስፈርት ፡ ቃቡ ። ወራብዕተ ፡ እዴሃ ፡ ለመስፈርተ ፡ ቃቡ ፡ ሸስሐ ፡ ርግብ ፡ ኅምስቱ ፡ ብሩር ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ፬ነገ ፡ ፮ ፡ ፳፭) ።

**ቃብ** ፤ የበግ ፡ ደዌ ፤ በንገት ፡ የሚያሳብጥ ፡ (ዐማ ርኛ) ።

**ቅብጥ** ፤ ግብጽ ፤ ግብጥ ። የሚጽፉይም ፡ ቋንቋ ፤ ትውልድና ፡ ዘር ፤ ርስትና ፡ ምድር ፤ ምጽ(ስ)ር ።

**ቅብጢ** ፤ (ዐማርኛ ፡ ቀበጥ) ፤ ግብጻዊ ፤ የግብጥ ፡ ሰው ፤ ቋንቋ ፡ ከጽርእ ፡ ጋራ ፡ የሚቀረብ ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ቋንቋነቱ ፡ ጠፍቶ ፡ ፊደሉ ፡ ብቻ ፡ አለ ፤ ያንኑም ፡ ዐረብ ፡ ወርሶታል ፤ የሚማረው ፡ የለም ። በእንተ ፡ ብዝኆ ፡ ቀደምሮቶሙ ፡ ምስለ ፡ ተንባላት ፡ እለመ ፡ ጠፍአ ፡ ልሳኖሙ ፡ ቅብጥ ፡ ዘእምኔሁ ፡ የአምሩ ፡ ጽ ድቀ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ (ሳዊ ፡ ዘእ) ። ግብጾችን ፡ ተመል ከት ።

**ቀበየ** ፤ (ዐረ ፡ ቀባ) ፤ አበጀ ፤ አዘጋጀ ፡ አሰ ናዳ ።

**ተቀብየ** ፤ ተዘጋጀ ። ወተቀብየት ፡ ቀትል ፡ (ሕዝ፳፩ ፡ ፲፩) ።

**ቀበያወበጠ** ፤ (የቢልተኛ ፡ ማስ) ፤ ቀላ ወጠ ፤ አፉን ፡ ከንፈሩን ፡ ለማመጠ ፤ አቀለማመጠ ፤ ሲበላ ፡ ሲውጥ ፡ ወይም ፡ ሲቀላውጥ ። አቄለጳጳሰ ፡ እንደ ፡ ማ ለት ፡ ነው ፤ ምስክር ፡ ሳይኖረው ፡ እንዲያው ፡ በልማድ ፡ ይገሰባል ፤ መምህራንም ፡ የ፮ ፡ ፊደል ፡ ግስ ፡ ብለው ፡ ከግስ ፡ አርእስት ፡ ይቈጥሩታል ።

**ቀቢል** ፤ ሎት ፤ (ቀብለ ፡ ይቀብል ፡ ይ ቅበል ። ነትግ ፤ ሐጸ) ፤ ማነስ ፤ መጕደል ፤ መክፈል ፤ ቅምጥል ፡ ማለት ፤ ከቍጥር ፡ ከምልአት ። ይቀብላ ፡ እ ምኍልቍ ፡ አውራኂሁ ። ባሕርኒ ፡ ሶበ ፡ ይቀብል ። ትሁብ ፡ ሲሆሉ ፡ እንዘ ፡ ኢትቀብል ። አሐዱ ፡ በመለ ኮት ፡ ዘኢይትከፈል ፤ ምሉእ ፡ በሥሰሄ ፡ ዘኢይቀ ብል ፡ (ኢዮ ፲፬ ፡ ፲፰ ። ፳፭ ፡ ፳፭ ። ቅዳ ፡ የጐሐ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

**ቅቡል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ብልት) ፤ ያነሰ ፤ የ ጐደለ ፤ ጐደሎ ፤ ባይ ። አጽሕብት ፡ ቅቡላን ፡ (ሄርማ) ።

**ቅብለት** ፤ መጕደል ፤ አጐዳደል ፤ ጐደሎነት ፤ ሕጸጽ ። በቅብለት ፡ ፈንታ ፡ ቅባሌ ፡ ቅባሌ ፡ ይባል ፤ ስሕ ተት ፡ ነው ። በእንተ ፡ ስካር ፡ ወቅባሌ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፱) ።

**ቃቤላ** ፤ ማኸላ ፡ ያገዳ ፡ እኸል ።

(ጥ) **ቀብሎ** ፤ ሎት ፤ (ቀበለ ፡ ይቄብል ፡ ይ ቀብል ። ዕብ ፡ ቃባል ። ሱር ፡ ቅባል ። ዐረ ፡ ቀበለ ፤ ተቀበለ) ፤ ማቀበል ፡ መስጠት ፡ ማጕረሥ ፡ ማጥጥ ፤ ማሲያዝ ፡ ማስጨበጥ ። በተቀብለ ፡ ፈንታ ፡ ቀ በለ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፳፯ ፡ ፵፰) ።

**አቀበለ** ፤ (አስደራጊ) ፤ አስቀበለ ፡ አሰጠ ።

**ተቀበለ** ፤ በፊቱ ፡ ወሰደ ፡ እጅ ፡ አደረገ ፤ ያዘ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተረከበ ፤ የሰጡትን ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ የመ ጣውን ፡ የተቃጣውን ። ለይትቀበል ፡ ቍርባነከ ። ፈኒ ውየ ፡ እትቄበለከ ። ባእ ፡ ተቀበሎ ፡ ለአኪዝ ። ኢትር ስዑ ፡ ተቀብሎ ፡ ነግድ ፡ (፳ነገ ፡ ፳፯ ፡ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፳፯ ። ኢሳ፯ ፡ ፫ ። ዕብ፲፫ ፡ ፪) ።

—፤ ሰማ ፤ አመነ ፤ ተስፋ ፡ አደረገ ፤ ፈራ ፤ ታገሠ ፡ ይቅር ፡ አለ ። ምስጢሩ ፡ እንደ ፡ ተወከፈ ፡ ነው ፤ ቅበላን ፡ አይ ለቅም ። ዘኢተቀበላ ፡ ለመንግሥተ ፡ እግዚ ። ወበየው ሀት ፡ ተቀበልዎ ፡ ለቃሉ ። ከመ ፡ ይትቀበሎ ፡ ለገድየ ፡ በዳኅን ። ተቀበሉ ፡ አበሳየ ፡ (ማርጀ ፡ ፲፭ ። ያዕ፩ ፡ ፳፩ ። ዘፍ፴፪ ፡ ፳፩ ። ዘዐ፲ ፡ ፲፯) ።

—፤ ተሰጠ ፤ ተሰጨ ፡ ኾነ ፤ ተቀበሉት ፤ ከሰጪ ፡ ወደ ፡ ተቀባይ ፡ እጅ ፡ ዐለፈ ፤ ተወሰደ ።

**ተቀባሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤ የሚቀ በል ፤ ተቀባይ ፤ ወሳጅ ። አኀው ፡ ተቀባልያን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፪ ፡ ፯) ።

**ቅቡል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ብል) ፤ የተቀበለ ፤ የተቀበሉት ፤ ቅብል ፤ ተሰጪ ።

**ቀበላ** ፤ (ቅባሌ) ፤ ማቀበል ፤ መቀበል ፤ አቀባ በል ፤ ቅበላ ፤ ተቀባይነት ። ወፅአ ፡ ለቀበላ ፡ አሳ ። ለቀ በላሆሙ ፡ ለኢሎፍሊ ። ለቀበላ ፡ መርዓዊ ፡ (፪ዜና ፡ ፲፭ ፡ ፪ ። ፳ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፷ ። ማቴ፳፭ ፡ ፮) ።

—፤ ዋዜማ ፤ ድራር ፤ መያዣ ፤ መቀበያ ። ቀበላ ፡ ጾም ፡ (አቡሻ ፡ ፳፯) ።

**ተቃበለ** ፤ ተቀባበለ ፤ ተሰጣጠ ። ቀበሎ ፤ ቀበሌ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የመጣ ፡ ነው ። ተቀበለ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተቃበለ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ተቃበል ፡ ነግደ ፤ ተ ቃብሎ ፡ ነግድ ፡ (ሄርማ) ።

**ቀቢዕ** ፤ ዖት ፤ (ቀብዐ ፡ ይቀብዕ ፡ ይቅ ባዕ ። ዕብ ፡ ቃባዕ ፤ ሐገገ ፤ ዐደመ ፤ መልአ ፤ ሤመ) ፤ መቀባት ፡ መቀባት ፤ መላከክ ፤ መለቅለቅ ፤ ለ መሾም ፡ ለማክበር ፡ ለማሳመር ፤ ለመፈወስ ። ቀብዖ ፡ ቅ ብዐ ፡ ቅድሳት ። ቀብዖ ፡ በሕጕሬ ። ቀብዖ ፡ ወርቀ ፡ ንጹሐ ። ኢትቅብዖ ፡ ዕፍረተ ። ገብረ ፡ ጽቡረ ፡ በም ራቁ ፡ ወቀብዖ ፡ አዕይንቲሁ ፡ (ሚራ፵፭ ፡ ፲፭ ። ጥበ ፲፫ ፡ ፲፬ ። ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፰ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፶፩ ። ዮሐ፱ ፡ ፯) ። ልብስና ፡ ቀለም ፡ ሽቱና ፡ ተቀቢው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁሉ ፡ ኾኑ ፡ መጋጠማቸው ፡ ለተዋሕዶ ፡ ምሳሌ ፡ እየኾነ ፡ ይነ ገራል ። ከመ ፡ ፀምር ፡ ውስተ ፡ ሠርዌ ፡ ከማሁ ፡ ቀቢዖ ፡ ትስብእተ ፡ ቢመለኮቱ ። ዕፍረትሰ ፡ ሥጋ ፡ ዚኣኪ ፡ ወተቀብዓሁ ፡ ቃሉ ፡ ውእቱ ፡ (ኤጺ ፡ እክሲ ። አርጋ) ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ንባብ ፤ ግስ ፡ ሠምም ፡ ሰዘሰ ፡ ይባላል ፤ ከሮች ፡ ግን ፡ ሠሙን ፡ ወርቅ ፡ ምሳሌውን ፡ ጽድቅ ፡ አድርገው ፤ ቀብዐን ፡ አዋሐደ ፤ ተቀብዐን ፡ ተዋ ሐደ ፡ እያሉ ፤ አለቋንቋው ፡ እስንባቡ ፡ አሰበልቱ ፡ አሳገ ባቡ ፤ አሳንጸሩ ፡ እስምስጢሩ ፡ ይፈቱታል ። የተቀቢዐ ፡ ፍች ፡ ተዋሐደ ፡ ማለት ፡ ከኾነ ፡ ቄርሎስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፤ ኢይጽሕቅ ፡ ቅብዐተ ፡ በሀላዌሁ ። ወመለኮቱሰ ፡ ኢይ ትቀባዕ ፡ ይላሉና ፤ ይህ ፡ ንባብ ፡ ሳይወዱ ፡ በግድ ፡ በባሕ ርዩ ፡ ተዋሕዶ ፡ አይሻም ፡ መለኮቱ ፡ አይዋሐድም ፡ ያሰ

ኝባቸዋል ። ተማሪ ፡ ሳይኾኑ ፡ መምህር ፡ መኾን ፡ እው ነቱን ፡ ሐሰት ፡ ሐሰቱን ፡ እውነት ፡ እያሰኙ ፡ እንዲህ ፡ ፈራሽ ፡ ነገር ፡ ያናግራል ። የተሰብእንና ፡ የተቀብዐን ፡ ምስጢር ፡ በንኳን ፡ ልቡን ፡ ዠርባውን ፡ አላገኙትም ፤ ቅባቶቹም ፡ እንዲሁ ፡ ናቸው ።

**ቀባዒ** ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት) ፤ የሚቀባ ፤ ቀቢ ፡ ሠያሚ ። **እብ ፡ ቀባዒ ፡ ወልድ ፡ ተቀባዒ ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡** (አዕ ፡ ምስ) ።

**አቅብዐ** ፤ አስቀባ ፤ አስለቀለቀ ።

**ተቀብዐ** ፤ ተቀባ ። **ተቀብዐት ፡ ገጻ ፡ ዕፍረተ ። ሳእልሂ ፡ ተቀብዐ ፡ ለነጊሥ ፡** (ዮዲ፲፮ ፡ ፯ ። ቄር) ።

**ቅቡዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ብዕት) ፤ የተቀባ ፡ ክ ርስቶስንና ፡ መሲሕን ፡ ተመልከት ። **ቅቡዕ ፡ በቅብዕ ። ቅቡዓኒከ ። ንዋኅወ ፡ ቅቡዓተ ፡ ወርቅ ፡** (ዘሌ፪ ፡ ፬ ። ዕን፪ ፡ ፲፫ ። ፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፲) ።

**ቅብዐት** ፤ መቅባት ፡ መቀባት ፤ አቀባብ ፡ ቅብ ነት ፡ ቅባት ። **ቅብዐተ ፡ በለሳን ። በቅብዐተ ፡ ዝንቱ ፡ ዘይት ፡ ቅዱስ ፡** (ኪዳ ፡ ዲድ ፡ ፴፱) ። ቅቡዕ ፡ መሲሕ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ቅብዐት ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **ይጠፍዕ ፡ ቅብዐት ። ዝንቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ወፍካ ሬሁ ፡ ቅብዐት ፤ ወገሃደ ፡ ይሰመይ ፡ ቅብዐተ ፤ እስመ ፡ በዘተሰብአ ፡ ተቀብዐ ፡** (ዳንኤ ፡ ፳፮ ። ቄር ፡ ጸላ) ።

**ቅብዐት** ፤ የሃይማኖት ፡ ስም ፤ ዕውር ፡ ዘኢየ ሱስ ፡ ባዬ ፡ ፋሲል ፡ ዘመን ፡ ያወጣው ፤ አባኙ ፡ ዘድን ግል ፡ የክራን ፡ ባህልና ፡ ክራ ፡ መባልን ፡ በሱስንዮስ ፡ ዘ መን ፡ እንዳወጣ ። የቅባት ፡ ባህል ፡ ፫ ፡ ክፍል ፡ ነው ፤ መዠመሪያ ፡ በፋሲል ፡ ዘመን ፡ የተነሡት ፡ እነዘኢየሱስ ፤ መጽሐፍ ፡ እንደየ ፡ ርእሶ ፡ ይላልና ፡ ቃል ፡ በተዋሕዶ ፡ ዜገ ፡ ከሥጋ ፡ ሲዋሐድ ፡ የባሕርይ ፡ ክብሩን ፡ ዐጣ ፡ ለ ቀቀ ፡ ሲቀባ ፡ ወደ ፡ ጥንተ ፡ ክብሩ ፡ ተመለሰ ፡ በሰውነ ቱም ፡ ባምላክነቱም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ በቅባት ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ኾነ ፡ ብለዋል ። ምስጢሩ ፡ እንደ ፡ በትረ ፡ ሙሴ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሚጠትንና ፡ ውላጤን ፡ ባንድነት ፡ ያሳ ያል ። ፪ኛ ፡ ባንደኛው ፡ ዮሐንስ ፡ የተነሡ ፡ እናክለ ፡ ክርስቶስ ፡ ዜገ ፡ ማለትን ፡ ነቅፈው ፤ አጸይፈው ፤ መጽሐፍ ፡ እስመ ፡ ተዋሕዶ ፡ እንተ ፡ ስምንታዊ ፡ ይላልና ፤ ሥጋ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ የአምላክነት ፡ ክብር ፡ አላገኘም ። ሲቀባ ፡ ግን ፡ ክብር ፡ ተሳልፎለት ፤ ተፈጥሮ ፡ ተገብሮ ፡ ጠፍቶለት ፡ በቅባት ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ኾነ ፡ ብለዋል ። ምስጢሩ ፡ መቀባ ትንና ፡ መለወጥን ፡ ለሥጋ ፡ ብቻ ፡ መስጠት ፡ ነው ። (ተረት) ፤ አልሸሹም ፡ ዘወር ፡ አሉ ። ፫ኛ ፡ በቴዎድ ሮስ ፡ ዘመን ፡ የነበሩት ፡ እናሊቃ ፡ ጐሹ ፡ በቅባት ፡ ብቻ ፡ ማለትን ፡ ነቅፈው ፡ መጽሐፍ ፡ በኹለቱም ፡ ኹሉ ፡ በተ ዋሕዶ ፡ ክበረ ፡ በቅባት ፡ ክበረ ፡ ይላልና ፤ ቅባት ፡ ያለተ ዋሕዶ ፤ ተዋሕዶም ፡ ያለቅባት ፡ ብቻ ፡ ብቻውን ፡ አያከ ብርም ፤ በተዋሕዶና ፡ በቅባት ፡ ባንድነት ፡ የአምላክነት ፡ ክብር ፡ ከብሮ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ኾነ ፡ ብለዋል ፡ ሦስቱ ፡ ኹሉ ፡ ፍጹም ፡ ውላጤ ፡ ነው ፤ ሥጋን ፡ ከፍጡርነት ፤ ቃልን ፡ ከመሲሕነት ፡ ያወጣል ። ተቀብዐ ፡ ማለት ፡ ግን ፡ አንቀጹ ፡ የቃል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከራና ፡ ቅባት ፡ እንደሚሉት ፡ ሥጋ ፡ ከአካለ ፡ ቃል ፡ ያገኘውን ፡ የወረሰውን ፡ ሉዓላዊ ፡ ሥርዐት ፡ የባሕርይ ፡ ክብር ፡ የባሕርይ ፡ ልደት ፡ ወልድዩ ፡ አንተን ፡ ያይደለ ፤ ቄርሎስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ እንደሚሉት ፤ ቃል ፡ በሥጋ ፡ ርስት ፡ በሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ሰሎ ሞን ፡ እንደ ፡ ይሥሐቅ ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ወልደ ፡ አብ ርሃም ፤ ወልደ ፡ አዳም ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ በተባለበት ፡ በሰውነቱ ፡ በሰው ፡ ልጅነቱ ፤ ቀዳማይ ፡ አዳም ፡ ያዕለደ ውን ፡ ሀብት ፡ ከአብ ፡ ተቀብሎ ፡ የጋም ፡ ወሰደኩስ ፡ የተ ባለበትን ፡ ታሕታዊውን ፡ ሥርዐት ፤ ዳግማይ ፡ አዳም ፡ በኵረ ፡ ምእመናን ፡ ንጉሥ ፡ ካህን ፡ የኾነበትን ፤ ነቢይ ፡ ሐዋርያ ፡ መልአክ ፡ ያሰኘውን ፡ የሰውነቱን ፡ ክብር ፤ ፍ ጹም ፡ ሀብቱን ፡ ፍጹም ፡ ሹመቱን ፡ የግብር ፡ ልደቱን ፡ ቢያሳይ ፡ እንጂ ፡ የባሕርይ ፡ ልደትን ፡ የአምላክነትን ፡ አያሳይም ። በብሉይ ፡ በሐዲስ ፡ በሊቃውንት ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ። **(መወድስ ፡ ዘክፍለ ፡ ዮሐ ንስ) ፤ ሃይማኖት ፡ ቄርሎስ ፡ ኮነት ፡ ግማዳተ ፡ አብድ ፤ ወንሉልቂ ፡ ተመትሮ ፡ አብዝኀነት ፡ ኀበ ፡ ኢሀሎ ፡ ን ጉሥ ፤ ካህን ፡ ደብረ ፡ ኤፍሬም ፡ ቅድመ ፡ እምዘመ ተራ ፡ ነእስ ፤ ወአመ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ለምሳሌ ፡ በ እደ ፡ ነቢይ ፡ ዘተሠጠት ፡ ልብስ ። እንተ ፡ እምዙ ሉስ ፡ ያጠይስ ፡ ወዘያነድድ ፡ ልቡና ፡ ኢትለሲ ፡ ኢ ዶምያስ ፤ ተቀብዐ ፡ ቅብዐ ፡ ውላጤ ፡ ሕሩመ ፡ ተው ላጥ ፡ ክርስቶስ ፤ ወእከ ፡ በተቀብዖቱ ፡ በኵረ ፡ ው ሉዳ ፡ ለዮርዳኖስ ። ወእንዘ ፡ ትትናገሪ ፡ ዝንተ ፡ በአ ድንኖ ፡ ክሣድ ፡ ወርእስ ፤ ከመ ፡ አነ ፡ ሰማዕኩኪ ፡ ኢ ይስማዕኪ ፡ ጳውሎስ ።**

**ቅብዕ** ፤ (ዓት) ፤ በቁሙ ፡ ቅቤ ፤ ቅባት ፤ ሽቱ ፤ የሚቦላ ፡ የሚቀባ ፡ የሚበራ ፡ ከእንስሳትና ፡ ከዕፀዋት ፡ ከምድር ፡ የሚገኝ ፡ ፈሳሽ ። **ቅብዐ ፡ ዕጕልት ። ቅብዐ ፡ ዘይት ። ቅብዐ ፡ ዕፍረት ። ቅብዐ ፡ ማኅተት ። ምን ትኒ ፡ እምዘመደ ፡ ቅብዓት ፡** (ዘዳ፴፪ ፡ ፲፬ ። ዘፀ፳፯ ፡ ፳ ። አስቴ፪ ፡ ፲፪ ። አርጋ ፡ ፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፩) ።

— ፤ ዘይት ፤ ወይራ ፡ የቅባት ፡ ዕንጨት ። **ደብረ ፡ ቅብዕ ። ዕጸደ ፡ ቅብዕ ፡** (፪ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፴ ። ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፴) ።

**ምቅባዕ** ፤ (ዓት) ፤ መቅቢያ ፤ መቀቢያ ፤ ቦታ ። **ከመ ፡ ዝ ፡ ይትቀብዑ ፡ እምቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ በኀበ ፡ ምቅባዕ ፡** (ቄስጠ ፡ ፴፱) ።

**ቆብዕ** ፤— በቁሙ ፡ **ቆብ** ፤— **ቀወብዕ** ።

**ቀቢጽ** ፤ ጾት ፤ **(ቀብጸ ፡ ይቀብጽ ፡ ይ ቅበጽ ። ዕብ ፡ ቃባጽ ፤ ሰበሰበ)** ፤ መቅበጥ ፡ መቅ በጥበጥ ፤ መውደቅ ፡ መደንገጥ ፤ መቸገር ፡ ማጣት ፡ ተ ስፋ ፡ መቍረጥ ። **ተበገሁ ፡ ወኢትቅበጹ ። ቀብጸተኒ ፡ ነፍስየ ። አቡየ ፡ ወእምየ ፡ ቀብጹኒ ፡ ወኢይሴፈዉ ፡ እንከ ፡ ይርአዩኒ ፡** (ሄርማ ። መዝ ፡ ፷፭፪ ። ጦቢ ፲ ፡ ፯) ። በቀብጸ ፡ ፈንታ ፡ ተቀብጸ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **እለ ፡ ተቀብጹ ። ኢትትቀበጽ ፡** (ኪዳ ። ሚራ፳፪ ፡ ፳፱) ።

**ቅቡጽ** ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ብጽት) ፤ የቀበጠ ፡ ቅብጢ ፡ ቀብጭ ። ያጣ ፡ የነጣ ፤ ተስፋ ፡ የቈረጠ ፡ አለኝታ ፡

የሌለው። ስማዕ፡ ቃሎሙ፡ ለቅቡጻን። ሰብእ፡ ቅቡጻን። እሉ፡ ቅቡጻን፡ ተስፋሆሙ፡ (አስቴ፱፡ ፲፯። ኢሳ ፳፱፡ ፲፱። ሉቃስ፡ ፱፡ ፲፫)።

**ቅብጸት፤** ማጣት፤ ዕጦት፤ ተስፋ፡ መቍረጥ። ቅብጸተ፡ ተስፋ። ቅብጸተ፡ ሰላም፤ ቅብጸተ፡ ዐድሜ፤ ቅብጸተ፡ ሚመት፡ (ስንክ፡ የካ፳፡ ፍ፡ ን፡ ማ፱፡ ፪)።

—፤ መቅበጥ፡ ቅብጠት፤ ቅብጥና፤ ጨምታ፡ ፍንደቃ፤ ቅልጣን።

**አቅበጸ፤** አቀበጠ፤ አትበጠበጠ፤ አስቀበጠ። አሳጣ፡ ነሣ፡ ተስፋ፡ አስቈረጠ። አቅበጸኒ፡ እግዚአብሔር፡ ተስፋኒ። ዘኢያቅበጸከ፡ ተስፋከ፡ (ኤር፪፡ ፴፯። ስንክ፡ ሐምሌ)።

**ቀብቀበ፤ (ትግሬ)፤** ሐቀየ። በቁሙ፤ ቀብቀበ፤ ቅብቃብ፤ ተክለ፤ ቈረቈረ፡ ቀብ፡ ቀብ፡ አደረገ፤ መላልሶ፡ መታ፤ ዐረሰ፡ አሰሰሰ፡ (ዐማርኛ)። መጽሐፍ፡ ግን፡ በቀብቀበ፡ ፈንታ፡ አቀብቀበ፡ ይላል፤ ስሕተት፡ ነው። ሐራቢ፡ ያቀድም፡ አቀብቅቦታ፡ ወእስተጻልዎታ፡ (ግብ፡ ሕማ)።

**ቍብቍብ፤** በቁሙ፤ የሰሰሰ፡ ዕርሻ።

**ቀብቀሊስ፤ (ዐረ፡ እልቀብቀሊስ)፤** ሊቀ፡ ጳጳስ። ርግጡ፡ አልተገኘም፡ (ማር፡ ይሥ)።

**ቀቢር፤ ሮት፤ (ቀበረ፡ ይቀብር፡ ይቅብር። ዕብ፡ ቃበር። ሱር፡ ቅበር። ዐረ፡ ቀበረ)፤** መቅበር፡ ማጥለቅ፤ መቅበር፡ መሰወር፡ መደበቅ፤ መክተት፡ ከጕድጓድ፡ ማግባት፤ መገባት፡ መድፈን፤ በመሬት፡ የሬሳ፡ የገንዘብ። ደፈነን፡ ተመልከት። እቅብሮ፡ ለአቡየ። ይቅብሩ፡ ምዉታኒሆሙ። ወኢያበውሑ፡ ይቅብርዎሙ። ወነበሩ፡ እንዘ፡ ይቀብሩ፡ ርእሰሙ። ወቀበራ፡ ታሕተ፡ ዕፀ፡ ሕይወት፤ በወራ፡ (ማቴ፰፡ ፳፩። ፳፱። ራእ፲፩፡ ፱። አዋል)።

—፤ ማፈን፡ መሸፈን፡ መቆበር፤ ጭጋግ፡ መኾን፤ መብነን፡ መትገን፤ የትቢያ፡ ያቧራ፡ የጉም።

**ቀባሪ፤ (ሪት፡ ርያን፡ ያት፤ በርት)፤** በቁሙ፡ የሚቀብር፡ ማሽ፡ ቈፋሪ። (ተረት)፤ ቀባሪ፡ በፈጣሪ፤ ጠዋሪ፡ ቀባሪ።

**ቀብር፤** ቀበራ፡ አቀባበር፤ ማንዛት፤ አገናነዝ፤ የሬሳ፡ ሕግ፡ ሽቱ፡ መቅበት፡ ማጠን፡ ማጤስ፤ መፍታት፡ ማልቀስ፡ ርግዶ፡ ሙሾ፤ የመሰለው፡ ኹሉ። ገብሩ፡ ሎቱ፡ ሙዓለ፡ ቀብር፡ ዐቢየ፡ ጥቀ። ወኢገብረ፡ ሕዝብ፡ ፀአተ፡ ቀብረ፡ ዚኣሁ፡ በሳዕሌሁ፡ (፪ዜና፡ ፲፮፡ ፲፬። ፳፩፡ ፲፱)።

—፤ ሬሳ፡ በድን፡ አስከሬን፤ ሬሳነት፤ የሬሳ፡ ጓዝ፤ ዐጀብ፡ ልቅሶኛ፤ ከሬሳው፡ ጋራ፡ የሚንጋጋ። ሐ፡ ዘእማዕቀብከ፡ ቀብረ፡ አዳም፡ ለመልከ፡ ጼዴቅ። ለቀብርየ፡ ገብረት። እስመ፡ ተዐቀበ፡ ለዕለተ፡ ቀብርየ። ወረከበ፡ ቀብረ፡ ዘወልደ፡ መበለት፡ (ጥበ፡ ጠቢ። ማቴ፳፮፡ ፲፪። ማር፲፬፡ ፰። ዮሐ፲፪፡ ፯። ሉቃ፯፡ ፲፪)።

**ቀበሮ፤** በቁሙ፤ ቍንጽል፡ እንደ፡ ሬሳ፡ በጕድጓድ፡ የሚኖር፡ የሚከተት።

**አቅበረ፤** አስቀበረ። ታቅብሩኒ፡ በደንየ፡ (ዘፍ፵፱፡ ፳)።

—፤ አቀበረ፡ አቈመ፤ ለገመ፤ የቍስል፡ (ዐማርኛ)። ኰሕሶን፡ ተመልከት።

**ተቀብረ፤** ተቀበረ፤ ከጕድጓድ፡ ገባ፤ ተከተተ፤ ዐፈር፡ ለበሰ። (ሙሾ)፡ የሺዋ፡ መኳንንት፡ እንግዲህ፡ አትልፉ፤ ተመዘ፡ የነበር፡ ተክተተ፡ ሰይፉ። ሐመ፡ ወሞተ፡ ወተቀብረ፡ (ጸሎ፡ ሃይ)።

**ቅቡር፤ (ራን፡ ራት፡ ብርት)፤** የተቀበረ፤ ዐፈር፡ የለበሰ። ተቀብረ፡ ከመ፡ ያንሥእሙ፡ ለቅቡራን፡ (ቅዳ)።

**መቅበር፤ (ርት)፤** መቅበሪያ፤ መቀበሪያ፤ የሬሳ፡ ጕድጓድ። ህየንተ፡ መቅበርቱ፡ (ኢሳ፶፫፡ ፱)።

**መቃብር፤ (ራት)፤** መቅበሪያዎች፤ መቃብሮች። መቃብር፡ ብዙ፤ መቃብራት፡ የብዙ፡ ብዙ። መቃብረ፡ አበዊከ። መቃብር፡ ግብሱሳን። ንቅዐ፡ ኩዙሕ፡ ወተከሥቱ፡ መቃብራት፡ (ኩፋ፡ ፴፪። ማቴ፳፫፡ ፳፯። ፳፯፡ ፶፪)። መቅበር፡ መቅበርት፡ በማለት፡ ፈንታ፡ መቃብር፡ እያለ፡ ይጥፋል፤ ስሕተት፡ ነው። መቃብር፡ ክሡት። መቃብረ፡ ራሔል። ውስተ፡ አሐዱ፡ መቃብር፡ (ሮሜ፫፡ ፲፫። ኩፋ፡ ፴፪። ጦቢ፬፡ ፬)፡ አንዳንድ፡ ጕድጓድ፡ መቃብር፡ ማለት፡ ያማርኛ፡ ነው፤ የግእዝ፡ አይደለም። እንደ፡ መኳንንት፡ እንዲሉ።

**ቆባር፤ (ራት)፤** ዐቢራ፡ ትቢያ፡ በቁም፡ የሚቀብር፡ የሚደፍን፤ እንደ፡ ስሐራ፡ በረሓ፡ በነፋስ፡ ጊዜ። (ዘዳ፳፰፡ ፳፬)። ጭጋግ፤ ጉም፡ ጢስ፡ ጥቍር፡ ደመና፤ የሚያፍን፡ የሚሸፍን፤ የሚያጨልም። ወቆባር፡ ታሕተ፡ እገሪሁ። ዕለተ፡ ጽልመት፡ ወቆባር። አድባረ፡ ቆባራት፡ እለ፡ ክረምት፡ (መዝ፡ ፲፯። ሶፎ፩፡ ፲፭። ሕዝ፴፬፡ ፲፪። ሔኖ፲፯፡ ፯)። ቆበር፡ ቆበራም፡ ማለት፡ ከዚህ፡ የወጣ፡ ነው።

**ቀብተተ፤** በቁሙ፡ ቀበተተ፤ ነፋ፡ አሳበጠ። ቀበወን፡ እይ።

**ቀጋ፤ (ጋት)፤** በቁሙ፤ ስመ፡ ዕፅ፤ እሾኽም፤ አበባው፡ የሚሸት፤ ፍሬው፡ የሚጥም። (ተረት)፤ የቤት፡ ቀጋ፤ የሜዳ፡ ዐልጋ። እንተ፡ ትሰመይ፡ ባሕረ፡ ቀጋ፡ (ገድ፡ ተክ)።

**ቃግስት፤ (ታት)፤** የባብ፡ ስም፤ ክፉ፡ እባብ፤ እፍኝት፤ ጕበና። ትውልደ፡ ቃግስት፡ (ኢሳ፲፬፡ ፳፱። ምሳ፳፫፡ ፴፪)።

**ቃዲ፤ (ዐረ፡ ቃዊን። ዕብ፡ ቃዲን)፤** ፈራጅ፤ ዳኛ፤ ባለፍትሕ፡ ነገሥት፤ ገዥ፡ መስፍን፡ (ዐማርኛ)።

**ቀዲድ፤ ዶት፤ (ቀደ፡ ይቀድድ፡ ይቅድድ። ዕብ፡ ቃዶድ)፤** መቅደድ፤ መሠንጠቅ፡ ማረስ፡ መግመስ፤ የመሬት፡ የልብስ። (ተረት)፤ ከቀዳዳ፡

ይሻኀል ፡ ጨምዳዳ ። መቃድ ፡ ቅድ ፡ ቃዳ ፡ ቂዳ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ቀድሀ ፤—ቀዳ ፤—ቀዲሕ ፡ ቀድሐ ።**

**ቀዲው ፤ ዎት ፤ (ቀደወ ፡ ይቀዱ ፡ ይቅዱ ። ዕብ ፡ ቂዳ ፤ ሽቱ ፤ ቀረፋ)** ፤ ማማር ፤ መሽተት ፤ መጣፈጥ ፤ መንጻት ፡ መጥራት ፤ ንጹሕ ፡ ብሩህ ፡ ጹዐዳ ፡ መኾን ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ መወደድ ፡ መነበር ። ኢቀደወ ፡ ኅሊናሁ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ዛሕለ ፡ ብርት ፡ ከነ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ቀዳዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፡ ደውት) ፤** የሚያምር ፤ ደስ ፡ የሚያሰኝ ። አልባስ ፡ ቀደውት ፡ (ሉቃ ፯ ፡ ፳፭) ።

**ቅድው ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ዱት) ፤** ያማረ ፤ የተዋበ ፤ ውብ ፤ ምዑዝ ፡ ጥዑም ፤ ንጹሕ ፡ ጽሩይ ፡ ውድ ፡ ክቡር ። ቦ ፡ ሕሡም ፡ ወቦ ፡ ቅድው ። ዘአርሕዮከ ፡ ቅድው ። ዕፍረት ፡ ቅድው ። መዓር ፡ ቅድው ። በግዕ ፡ ቅድው ። ልብስ ፡ ቅድው ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ዐርኬ ። ዓዋዲ ፡ ፯ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፲፯ ። ፩ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ። ፩ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፱) ።

**አቅደወ ፤** አሳመረ ፤ አስጌጠ ፤ አከበረ ፤ አላቀ ፡ አበለጠ ። ለህላዌ ፡ ሰብእ ፡ ያቀድዋ ፡ በርእሱ ፡ ወይሬስያ ፡ ሱታፌ ፡ መለኮት ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ቀዲሕ ፤ ሖት ፤ (ቀድሐ ፡ ይቀድሕ ፡ ይቅዳሕ ። ዐረ ፡ ቀደሐ ። ዕብ ፡ ቃዳሕ ፤ ነደ ፡ ውዕየ) ፤** መቅዳት ፤ መጥለቅ ፤ መደንበቅ ፤ መፈልፈፍ ፤ መፈመር ፡ መገልበጥ ፤ ማኀለፍ ፤ መሰብሰብ ፤ መልቀም ፡ ማጠራቀም ። የፈሳሽ ፡ የቃል ፡ የመጣፍ ፡ የእሳት ፡ የመብራት ፡ የጢስ ። ለቀዲሕ ፡ ማይ ። እለ ፡ ይቀድሕዎ ፡ ለማይ ። ወይን ፡ ዘቀዳሕኩ ፡ ለክሙ ። መጽሐፈ ፡ ስንክሳር ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ጉባኤ ፤ ዘቀድሕዎ ፡ አበዊነ ፡ እምነቶሙ ፡ ግድላት ፡ (ኩፋ ፡ ፪ ። ኢሳ፳ ፡ ፳፱ ። ምሳ፱ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ መስ፩) ።

— ፤ መብላት ፡ መንደል ። መታመም ፡ መተኰስ ፤ መላብ ፡ መውዛት ፤ ውሃ ፡ መኾን ፤ መቅለጥ ፤ መቅዘን ።

**ቀዳሒ ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት ፤ ሕት) ፤** የሚቀዳ ፤ ቀጂ ፤ አሳላፊ ። ሐጣብያን ፡ ዐፀው ፡ ወቀዳሕያን ፡ ማይ ። ወቀዳሕትየ ። ሊቀ ፡ ቀዳሕያን ፡ (መቃ ። ፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፳ ። ዘፍ፵ ፡ ፩) ።

**መቅድሕት ፤ (ሓት) ፤** መቅጃ ፤ መጥለቂያ ፤ የውሃ ፡ ዕቃ ፤ የፍም ፡ መጫሪያ ፤ መዛቂያ ፤ ማበኛ ፡ ማጤሻ ። መቅድሕት ፡ እሳት ፡ ይክዑ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ (ቀሌ ፡ መቃ) ።

**መቅድሕ ፤ (ሓ ፡ መቃድሕ) ፤** መቅጃ ፡ መንደያ ፤ መሰርሰሪያ ። መቅድሐ ፡ እዝን ፡ (ስንክ ፡ ጥር ፲፰) ።

**ምቅዳሕ ፤ (ሓት) ፤** መቅጃ ፤ መቀጃ ፤ በታ ፡ ዕቃ ። ምቅዳሐ ፡ ፈውስ ፡ ወዐዘቅተ ፡ በረከት ። ገይበ ፡ ወርቅ ፡ ምቅዳሐ ፡ ስብሐት ፡ (አርጋ ፡ ፱) ።

**አቅድሐ ፤** አስቀዳ ፤ አስገለበጠ ። አተኰሰ ፡ አመዘ ፡ አላበ ፤ አስቀመጠ ።

**ተቀድሐ ፤** ተቀዳ ፤ ተገለበጠ ። ማይ ፡ ዘኢተቀድሐ ። መጽሐፈ ፡ በዋስው ፡ ዘተቀድሐ ፡ እምስማንያ ፡ ወአሐዱ ፡ መጻሕፍት ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ማስ) ።

**ቅዱሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ድሕት) ፤** የተቀዳ ፤ ቅድ ። ዘቅዱሕ ፡ ውስተ ፡ ጽዋዐ ፡ መዐቱ ፡ (ራእ፲፬ ፡ ፲) ።

**ቅድሐት ፤** መቅዳት ፡ መቀዳት ፤ አቀዳድ ፤ ቅድነት ። ዘምሉእ ፡ ቅድሐቱ ፡ (መዝ ፡ ፸፬) ።

**ቀድሕ ፤ ቅድሕ ። (ዐረ ፡ ቀዳሕ) ፤** መቅጃ ፤ መጠጫ ፤ ኵባያ ፤ ብርጭቆ ፤ ዋንጫ ፡ ከቦ ፡ ዐፀፌ ፡ ሽልም ። ሽጕጥ ፡ ቃናሽ ፡ ጠመንዣ ፡ ርሳስ ፡ እንዳረፈ ፡ የሚጠጡበት ፡ የሚያጠጡበት ።

**አቅዳሕ ፤ (ሓት) ፤** ኵባያዎች ፤ ብርጭቆዎች ፤ ሽጕጦች ። ይሰትዩ ፡ ሠለስተ ፡ አቅዳሐ ፡ ወይን ። ወይሰትዩ ፡ ሠለስተ ፡ አቅዳሐ ፡ በበዓላተ ፡ እግዚእነ ፡ ባሕቲቱ ፡ (ፈልክ ፡ ፸፱ ። ቄድር) ።

**ቀዲም ፤ ሞት ፤ (ቀደመ ፡ ይቀድም ፡ ይቅድም ። ዕብ ፡ ቃዳም ። ሱር ፡ ቅዳም ። ዐረ ፡ ቀደመ) ፤** መቅደም ፡ ፊተኛ ፡ መዠመሪያ ፡ መኾን ፡ መላቅ ፡ መብለጥ ፤ መዠመር ፡ መወጠን ። ሊደም ፡ ይቀድሞ ፡ ላኪ ። ይቀድመኒ ፡ ወሬዛ ። እምዝሉ ፡ ዘይቀድም ። ቀደመት ፡ ማርያም ፡ ወትቤ ። ቅድሙ ፡ እምቅዱሳንየ ፡ (ሚራ፳፱ ፡ ፳፱ ። ዮሐ፳ ፡ ፯ ። ያዕ፳ ፡ ፲፱ ። ዘዐ፲፭ ፡ ፳፩ ። ሕዝ፱ ፡ ፯) ።

— ፤ ቅድምና ፤ በኵርነት ። ቀዲም ፡ ዘከነ ፡ ሎቱ ፡ በውስተ ፡ ርስት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፪) ።

**ቀዳሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት ፤ ደምት) ፤** በቀዳሙ ፡ የሚቀድም ፤ የሚበልጥ ፡ ታላቅ ፡ ደገኛ ፤ ፊተኛ ፡ ዠማሪ ። ቀዳሚ ፡ ወደኃሪ ። ትእዛዝ ፡ ቀዳሚት ። ቀዳሚ ፡ ጸጋ ። ጽላት ፡ ከመ ፡ ቀዳምያት ። አበው ፡ ቀደምት ። ነቢያት ፡ ቀደምት ፡ (ቅዳ ። ማር፲፪ ፡ ፳፰ ። ሊጦ ። ዘፀ፴፬ ፡ ፩ ። ሐዋ ። ዘካ፩ ፡ ፬) ።

**ቀዳሚ ፤ (አገባብ) ፤** ቀድሞ ፡ ዱሮ ፤ ጥንት ፤ ፊት ፤ መዠመሪያ ። እምቀዳሚ ፡ መዋዕሊነ ። ዘቀዳሚ ፡ ወዘደኃሪ ። ቀዳሚ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ለከ ። በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚ ፡ (ዮዲ፰ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፻፩ ። ግብ ፡ ፩ ። ዘፍ፩ ፡ ፩) ።

**ቀዳም ፤** መዠመሪያ ፤ ቅዳሜ ፤ ሰንበት ፡ አይሁድ ፤ የአሑድ ፡ ምሳሌ ። መንገደ ፡ ቀዳም ። ፱ ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ግብ፩ ፡ ፲፪) ።

**ቀዳማዊ ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ አው ፡**

**ቀዳማይ ፤ (ይያን ፡ ያት ፡ ይት ፡ ዩት) ፤** የቀዳም ፤ የቅዳሜ ። በቀዳሙ ፤ ፊተኛ ፤ የፊት ፡ የዱሮ ፤ መዠመሪያ ፡ ተቀዳሚ ፤ ታላቅ ፡ በኵር ፤ ማንባር ፡ ቀደም ። መስተጽዕን ፡ መስቀል ፡ ፈረስ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፤ ዘቀዳማይሁ ፡ ጽፍዐት ፡ ወደኃራይሁ ፡ ተቀሥፎ ።

ህርቃኖስ ፡ ቀዳማዊ ፡፡ ቀዳማየ ፡ አውራኅ ፡፡ ወተወ ልደ ፡ ውእቱ ፡ ቀዳማይ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ቅኔ ፡፡ ዮሴፍ ፡፡ ዘፀ፲፪ ፡ ፪ ፡፡ ቄር ፡ ጸሎ) ፡፡

**ቀዲ.ሙ** ፤ (አገባብ) ፤ ቀድሞ ፤ አስቀድሞ ፤ ፊት ፤ ጥንት ፤ ዱሮ ፤ መዠመሪያ ፡፡ እለ ፡ የአምርዎ ፡ ቀ ዲሙ ፡፡ ቀዲሙ ፡ ዜነወ ፡፡ እምቀዲሙ ፡፡ ወቀዲሙሰ ፡ ኢነገርኩክሙ ፡፡ ቀዲሙኒ ፡ እምቅድመ ፡ ዝ ፡ መዋ ዕል ፡ (ኢዮ፴፪ ፡ ፲፩ ፡፡ ኤፍ ፡ ፩ ፡፡ ዮሐ፭ ፡ ፪ ፡፡ ፲፮ ፡ ፬ ፡፡ ማቴ፳፭ ፡ ፴፮) ፡፡

**ቅድም** ፤ ፊት ፤ ገጽ ፤ ቀድሞ ፤ ዱሮ ፤ ጥንት ፤ መዠመሪያ ፡፡ እምቅድም ፡ ወእምድኅር ፡፡ እመን ገለ ፡ ቅድም ፡፡ ዘሀሎ ፡ እምቅድም ፡፡ እክያቲሁ ፡ ዘቅድም ፡ (ራእ፬ ፡ ፳ ፡፡ ዘፀ፳፰ ፡ ፲፱ ፡፡ ሰዮሐ ፡ ፩ ፡፡ ስ ንክ ፡ ጥቅ፳) ፡፡

**ቅድመ** ፤ ቀድሞ ፡ አስቀድሞ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ፊት ፤ ፊት ፡ ፊት ፤ ሩ ፡፡ ቅድመ ፡ ጠይቅ ፡፡ ቅድመ ፡ አውፅእ ፡ ሠርዌ ፡ እምዐይንከ ፡፡ ደኅርት ፡ ይከውኑ ፡ ቅድመ ፡፡ ሑሩ ፡ ቅድመ ፡፡ እስመ ፡ ተሐውር ፡ ቅ ድመ ፡ እግዚ ፡ (ማቴ፲፩ ፡ ፯ ፡፡ ማቴ፳ ፡ ፳ ፡፡ ፲፯ ፡ ፲ ፡፡ ፲፬ ፡ ፴ ፡፡ ዘፀ፴፱ ፡ ፲፯ ፡፡ ሉቃ፩ ፡ ፸፮) ፡፡ ቅድሜየ ፡ ከ ፡ ኪ ፡ ሁ ፡ ሃ ፡ ነ ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ፡፡ ሳ ፡ ሲኾን ፡ እም ፡ እያዳመቀው ፡ ሳያዳምቀውም ፤ በማልሳይ ፡ አንቀጽ ፡ ይገ ባል ፡፡ በሰማይኒ ፡ ቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ኪሩብ ፡፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ፡ (ደራሲ ፡፡ ጸሎ ፡ ሃይ) ፡፡

**ቅድምና** ፤ ቀዳማዊነት ፤ ቅድሚያ ፤ ብልፅ ፡ ላቂያ ፡ ልቅና ፤ ብኵርና ፡፡ አልቦ ፡ ጥንት ፡ ለቅድም ናከ ፡፡ እንዘ ፡ የአምር ፡ ቅድምናሁ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ፡፡ አፈ ፡ ድ፫) ፡፡

**አቅደመ** ፤ አስቀደመ ፤ በፊት ፡ አደረገ ፤ ገሆ መረ ፡፡ አቅድሙኬ ፡ ምጽዋተ ፡ ከመ ፡ ይኩንክሙ ፡ ሥንቀ ፡፡ በከመ ፡ አቅደምኩ ፡ ነጊረ ፡፡ አቅደመ ፡ ስ ምዐ ፡ ከዊነ ፡ (ቀሌ ፡፡ ቄር ፡ ጸሎ ፡፡ ድ፫) ፡፡

**አቅዲ.ሙ** ፤ አስቀድሞ ፤ ፊት ፤ መዠመሪያ ፡፡ አቅዲሙ ፡ ነገረ ፡ ሙሴ ፡ በአፉት ፡ (ድ፫) ፡፡

**መቅድም** ፤ (ብ ፡ መቃድም) ፤ መዠመ ሪያ ፤ ታላቅ ፡፡ መቅድመ ፡ ቃሉ ፡ ለእግዚ ፡፡ መቅድመ ፡ ዕፍረታት ፡ (ዕብ፭ ፡ ፲፪ ፡፡ ማሕ፬ ፡ ፲፬) ፡፡

—፤ በቁሙ ፤ የመጽሐፍ ፡ መግቢያ ፤ በር ፡ ደጅ ፡ አፍ ፤ አስቀድሞ ፡ የመጽሐፉን ፡ ጠባይ ፤ የተጣፈበትን ፡ ምክን ያት ፡ ገልጦ ፡ የሚናገር ፡ የሚያስረዳ ፡፡ መቅድመ ፡ ወን ጌል ፡፡ መቅድመ ፡ ጳውሎስ ፡፡ መቅድመ ፡ ጉባኤ ፡፡ መቅድመ ፡ ተኣምር ፡፡

**መቅድመ** ፤ ቀድሞ ፤ አስቀድሞ ፡ በፊት ፡፡ ውእቱ ፡ መቅድመ ፡ ተቀብረ ፡፡ ወውእቱ ፡ መቅ ድመ ፡ ገብረ ፡ በዓለ ፡ መጸለት ፡፡ መቅድመ ፡ ፈድ ፋደ ፡ (ኩፋ ፡ ፱ ፡፡ ፲፯ ፡፡ ቅዳ ፡ ሕር) ፡፡

**ተቀድመ** ፤ ተቀደመ ፤ ታለፈ ፤ ቅድምናውን ፡ ብኵርናውን ፡ ጣ ፤ እንደ ፡ ዔሳው ፡፡

**ቅዱ.ም** ፡ (ማን ፡ ማት ፡ ድምት) ፤ የተቀ ደመ ፤ የታለፈ ፤ ቅድምናውን ፡ ያጣ ፡፡

**ቅድመት** ፤ መቅደም ፤ መቀደም ፤ አቀዳደም ፤ ቀደማ ፡ ቅድሚያ ፤ ቀዳማዊነት ፤ ሥልጣን ፡፡ አልቦ ፡ ቅድመት ፡ ለህልዎቶሙ ፡፡ ወቅድመት ፡ ከነ ፡ ዲበ ፡ መትከፍቱ ፡፡ አሐቲ ፡ ቅድመት ፡ ወአሐቲ ፡ ስፍነት ፡ (አዋል ፡፡ ኢሳ፱ ፡ ፯ ፡፡ ደራሲ) ፡፡

**ተቃደመ** ፤ ተቀዳደመ ፤ ተከታተለ ፡ ተጋጠመ ፤ ተሰላለፈ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡፡ ተቃደማ ፡ በይጣን ፡ ወተ ራክባ ፡፡ ተቃደምዎሙ ፡ ወተቃተልዎሙ ፡ (ግንዘ ፡፡ ፪ነገ ፡ ፲ ፡ ፲) ፡፡

(ፕ) **ቀድሞ ፡ ሞት** ፤ (ቀደመ ፡ ይቄድም ፤ ይቀድም ፡፡ አቅደመ) ፤ መቀደም ፤ ማስቀደም ፤ ቀዳማይ ፡ ማድረግ ፤ ከቀዳማይ ፡ ማግባት ፤ ማንጠልጠል ፡፡ (ማዋም ፡ ዘሬፌ ፡ የመርቆሬዎስን ፡ ጽላት ፡ በኮርቻው ፡ ራስ ፡ በቀዳማይ ፡ በጽኮ ፡ ስለ ፡ ወሰደው) ፡ ፈረሰኛ ፡ አላ ምንዎ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ቢኾን ፡ ቀደሙት ፡ ይሉኛል ፡ መር ቆሬዎስን ፡፡

**ቄዴ.ም** ፤ (ዕብራ) ፤ ቀድም ፤ ምሥራቅ ፡፡ ደቂቀ ፡ ቄዴም ፡ (ሕዝ፳፭ ፡ ፬) ፡፡

**ቀዴ.ሚን** ፤ (ጽር ፡ ክዴሚን ፡፡ ዕብ ፡ ቅዱ.ሚም) ፤ አዝማን ፡ ቀደምት ፡ መዋዕለ ፡ ቅክት ፤ አዕዋደ ፡ ቀትል ፡ (መሳ፭ ፡ ፳፩) ፡፡

**ቀዲ.ፍ ፤ ፎት** ፤ (ቀደፈ ፡ ይቄድፍ ፡ ይቀ ድፍ ፡፡ ዐረ ፡ ቀዘፈ) ፤ መቅዘፍ ፤ ባሕርን ፡ መቅደድ ፤ ታንኳን ፡ መርከብን ፡ መምራት ፡ መውሰድ ፤ ማስኬድ ፡፡ ኀደፈን ፡ ቀመልከት ፤ የዚህ ፡ ግሩ ፡ ቤት ፡ ነው ፡፡ እለ ፡ ይ ቀድፉ ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፱ ፡ ፳፯ ፡ ፳፱ ፡ ፴፩) ፡፡

**መቅደፍ** ፤ (ብ ፡ መቃድፍ) ፤ መቅዘፊያ ፤ ቅርከዝ ፤ ጎዳፍ ፡፡ አሐ ፡ ጸራቢ ፡ ወነዳቂ ፡ ወእገብር ፡ መዋፍርት ፡ ወአርፁት ፡ ወመዳልው ፡ ወመንኰራ ኵረ ፡ ወእሕማረ ፡ ወመቃድፈ ፡ ወቃዕካ ፡ ነገሥት ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲ ፡፡ መጽ ፡ ምስ) ፡፡ ኹለተኛም ፡ መቅደፍት ፡ መቃድፍት ፡ ይላል ፡ በሴት ፡ አንቀጽ ፡ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ፡፡

**ቄድር** ፤ (ዐረ ፡ ቀድር ፤ እድፍ ፡ ርኵስ) ፤ ጥምቀት ፡ ዮሐንስ ፤ የንስሓ ፡ ጥምቀት ፡፡ መጽሐፈ ፡ ቄድር ፡ ዘአንበሩ ፡ መምህራን ፡ በእንተ ፡ ዘክሕደ ፡ ሃይማኖተ ፤ አው ፡ አርኰሰ ፡ ሥጋሁ ፡ ምስለ ፡ ዘኢም እመናን ፡ አው ፡ ተባዕት ፡ አው ፡ አንስት ፤ አው ፡ መነ ኮስ ፡ አው ፡ መነኮሳይት ፡፡

**ቄዳር** ፤ ሰው ፡ ነገድ ፤ ዐረባዊ ፤ ኹለተኛው ፡ የይስማኤል ፡ ልጅ ፡ ዝላን ፡ የዘላኖች ፡ አባት ፡ (ዘፍ፳፭ ፡ ፲፬ ፡፡ መዝ ፡ ፻፲፱ ፡፡ ማሕ፩ ፡ ፭) ፡፡

**ቄዳርስ** ፤ (ጽር ፡ ኪ.ዳሪስ) ፤ ጥቀር ፡ ቆብ ፤ ኵፌት ፤ መጠምጠሚያ ፡ ጥምጥም ፤ የካህናት ፡ (ዘፀ፴፮ ፡ ፴፬ ፡፡ ዘሌ፰ ፡ ፲፫ ፡፡ ፲፮ ፡ ፬) ፡፡ በቄዳርስ ፡ ፈንታ ፡ ቄድ ራን ፡ ይላል ፡ (ሚሬ፴፭ ፡ ፲፱) ፡፡

**ቄድሮስ ፤ (ጽር ፡ ኬድሮስ ። ዕብ ፡ ኤሬዝ) ፤** አርዝ ፤ ስሙ ፡ አርዝ ፤ የሊባኖስ ፡ ዛፍ ፤ ወፍራም ፡ ረዥምም ፤ ታላቅ ፡ ምጡቅ ፤ ገናና ፡ ባለብዙ ፡ ዕጽቅ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ዋንዛ ፡ ይሉታል ። ኅሩይ ፡ ከመ ፡ ቄድሮስ ፡ (ማሕ፭ ፡ ፲፭ ። ፰ ፡ ፱ ። ሢራ፳፬ ፡ ፲፫ ። ፲፫ ፡ ፳ ፡ ፱ ። ፮ ፡ ፲፫) ። በቄድሮስ ፡ ፈንታ ፡ ቄዳር ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ቄዳር ፡ ዘስሙ ፡ ዐርቦት ፡ (ኩፋ ፡ ፳፭) ።

**ቄድሮስ ፤ (ጽር ፡ ኬድሮን ። ዕብ ፡ ቂድሮን) ፤** የቦታ ፡ ስም ፡ በደብረ ፡ ዘይትና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ቈላ ፡ ሸለቆ ፤ ዛፋም ፡ ዘይታም ፡ አታክልታም ፤ ፀሓይ ፡ ቶሎ ፡ የማይደርስበት ፡ ቢደርስ ውም ፡ ቶሎ ፡ የማይልፈው ። መካነ ፡ ጽልመት ፡ ወጽላሎት ፤ ጥላማ ፤ ጽልመት ፡ ማለት ፡ ነው ። ፈለገ ፡ ቄድሮስ ። ማዕዶተ ፡ ቄድሮስ ፡ ፈለገ ፡ አርዝ ፡ (፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፮ ። ዮሐ ፲፰ ፡ ፩) ። በቄድሮን ፡ ፈንታ ፡ ቄድሮስ ፡ ማለት ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ቀድሶ ፤ ሶት ፤ (ቀደሰ ፡ ይቄድስ ፡ ይቀድስ ። ዕብ ፡ ቂዳሽ ። ሱር ፡ ቃዲሽ ። ዐረ ፡ ቀደሰ) ፤** መቀደስ ፡ መባረክ ፡ ማመስገን ፡ ማክበር ፡ ማግነን ፤ ማንጻት ፡ ማጥራት ፡ መለየት ፤ ለእግዚር ፡ መስጠት ፤ የእግዚር ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግ ። ለቀሲስ ፡ ሎቱ ፡ አሐዱ ፡ ሥልጣን ፤ ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ይምሀር ፡ ወያጥምቅ ፡ ወይቀድስ ፡ ወይባርክ ፡ ሕዝበ ። ቀድሶ ፡ ኵሎ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘሐነጽክምዎሙ ፡ ወኅትምዎሙ ፡ በማኅተመ ፡ እግዚ ፡ ዘውእቱ ፡ ቅብዐ ፡ ሜሮን ፡ ቅዱስ ። ቀድስዎ ፡ ለእግዚ ። ባረካ ፡ ወቀደሳ ። ያነጽሕ ፡ ወይቄድስ ፡ እምኀጢአ ፡ ርኵስ ። እቄድሶሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ሊተ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፯ ። ፊ ፡ መ ፡ ፳፰ ፡ ፳ ። ኢሳ፰ ፡ ፲፫ ። ዘፍ፪ ፡ ፫ ። ዘሌ፲፯ ፡ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፪) ።

**ቀዳሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት) ፤** የሚቀድስ ፡ ቀዳሽ ፡ አክባሪ ። አምላክ ፡ ዘውእቱ ፡ ሐዋጺሆሙ ፡ ወቀዳሲሆሙ ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ።

**አቀደሰ ፤** አስቀደሰ ፡ አስባረከ ፡ አስመሰገነ ።

**ተቀደሰ ፤** በቂሙ ፡ ተባረከ ፡ ተመሰገነ ፡ ተለየ ፡ ተመረጠ ፡ ከበረ ፡ ተሾመ ፡ ነጻ ፡ ጥሩ ፡ ኾነ ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘተቀደሰት ። ሶበ ፡ ተቀደስኩ ፡ በላዕሌክሙ ። ካህናት ፡ እለ ፡ ተቀደሱ ። እምከርሥ ፡ እሙ ፡ ተቀደሰ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ነቢየ ። ትትቄደስ ፡ ምድር ፡ እምኀጢአ ፡ አበሳ ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፲፭ ። ሕዝ፴፮ ፡ ፳፫ ። ሢራ፵፱ ፡ ፲፯ ። ኩፋ ፡ ፬) ።

**ቅዱስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ድስት) ፤** በቂሙ ፡ የተቀደሰ ፡ ክቡር ፡ ምስጉን ፡ ልዩ ፡ ምርጥ ፡ ንጹሕ ፡ ጽሩይ ። ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ስሙ ። ቅዱሳን ፡ ልዑል ። መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ። ሀገር ፡ ቅድስት ፡ (ኢሳ፶፯ ፡ ፲፭ ። ዳን፯ ፡ ፳፯ ። ሮሜ፩ ፡ ፪ ። ማቴ፬ ፡ ፭) ።

**ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፤ (ዕብ ፡ ቆዴሽ ፡ ቆዳሽም) ፤** በቂሙ ፡ መቅደስ ፡ አራት ፡ መካነ ፡ ታቦት ፡ ባርባው ፡ ካንድ ፡ ፊት ፡ ያለ ፡ ኋላው ፡ ካንድ ፡ (ዕብ፱ ፡ ፳፭ ። ፲፫ ፡ ፲፩) ። ዳቤርን ፡ ተመልከት ።

**ቅዳሴ ፤ (ስያት) ፤** መቀደስ ፤ (ጥቀ) መቀደስ ፤ አቀዳደስ ፤ ቅደሳ ፤ ቡራኬ ፤ ምስጋና ፤ የቍርባን ፡ ጸሎት ። ቅዳሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። መልአክ ፡ ቅዳሴ ። ወእምቅድመ ፡ ይፍጥር ፡ መላእክተ ፡ ለቅዳሴ ። እምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡ ቅዳሴ ፡ ዘምስጢር ። በእንተ ፡ ቅዳሴ ፤ ናሁ ፡ ንቡር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅብጣዊት ፡ ሠለስቱ ፡ ቅዳስያት ፤ ዘባስልዮስ ፡ ወጎርጎርዮስ ፡ ወቄርሎስ ፡ (ኩፋ ፡ ፪ ። ኤፌ ፡ ተ፲፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱) ።

**ቅድስና ፤** ቅዱስነት ፤ ክቡርነት ፤ ንጽሕና ፡ ክብሬት ። ኵነኑ ፡ ሴት ፡ ሕዝቦ ፡ በጽድቅ ፡ ወበንጽሕ ፡ ወበቅድስና ። መንፈሰ ፡ ቅድስና ። ትጓሥሥ ፡ እምነ ፡ ቅድስናከ ፡ (ቀሌ ። ኪዳ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፱) ።

**ቅድሳት ፤** ቅድስና ፤ ክብር ፡ ንጽሕ ፤ ጸጋ ፡ ብፅዓን ፤ መሥዋዕት ፡ ቍርባን ። ከመ ፡ ንርከብ ፡ ቅድሳቲሁ ። ፈነውኩ ፡ ለቅድሳቲከ ፡ ፍቁርየ ። ቅድሳት ፡ ለቅዱሳን ፤ ቅድሳቶ ፡ ነሚአነ ፤ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ (ዕብ ፲፪ ፡ ፲ ። ተረ ፡ ቄር፲፭ ። ቅዳ) ።

**ቍድስ ፤ (ዐረብ) ፤** መቅደስ ፤ መካነ ፡ መቅደስ ፤ ኢየሩሳሌም ። ሀገረ ፡ ቍድስ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ቃዴስ ፤ (ዕብ ፡ ቃዴሽ) ፤** ሲና ፤ ደብረ ፡ ሲና ፤ የሲና ፡ በረሓ ፤ ምድረ ፡ በዳ ፤ ጌታ ፡ እስራኤልን ፡ የቀደሰበት ፤ ርሱም ፡ በሕዝቡ ፡ አፍ ፡ የተቀደሰበት ፡ ቅዱሳን ፡ ኵሉ ፡ እስመ ፡ እንዚ ፡ ቅዱስ ፡ እነ ፡ ብሎ ፡ ቅዳሴውን ፡ ቅድስናውን ፡ ፵ ፡ ዘመን ፡ ያስተማረበት ። ምስጢሩ ፡ በዚህ ፡ ወግሩም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ጽኑዕ ፡ ማለትም ፡ ይስማማዋል ። ወያድለቀልቆ ፡ እግዚ ፡ ለሐቅለ ፡ ቃዴስ ፡ (መዝ ፡ ፳፰) ።


**መቅደስ ፤ (ብ ፡ መቃድስ) ፤** በቂሙ ፤ መቀደሻ ፤ ማመስገኛ ፡ መሥዋዕትና ፡ ጸሎት ፡ ማቅረቢያ ፡ የአምልኮት ፡ ቤት ፤ ሦስት ፡ ክፍል ፡ ያለው ፤ ለብሉዩ ፡ ኢላም ፡ ሀይክል ፡ ዳቤር ፡ ወይም ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፤ ለሐዲሱ ፡ ቅኔ ፡ ማሕሌት ፡ ቅድስት ፡ መቅደስ ፡ ማለት ፡ ነው ። ጽርሐ ፡ መቅደስ ። ቤተ ፡ መቅደስ ። ሀገረ ፡ መቅደስከ ። ወያረኵሱ ፡ መቃድሲሆሙ ፡ (መዝ ፡ ፸፫ ። ኩፋ ፡ ፴፱ ። ኢሳ፷፬ ፡ ፲ ። ሕዝ፳፰ ፡ ፳፱ ። ኤፌ ፡ ድ፲፯) ። በመቅደስ ፡ ፈንታ ፡ ምቅዳስ ፡ ይላል ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፰ ። ፳፯ ፡ ፴፫ ። ፳፰ ፡ ፲) ።

**ቃዴስም ፤ (ጽር ፡ ካዲሲም ። ዕብ ፡ ቀዴሽም) ፤** አብያተ ፡ ጣዖት ፡ በቅዱስ ፡ በታ ፡ ላይ ፡ ከመቅደስ ፡ አጠገብ ፡ የተሠሩ ፡ የጣዖታት ፡ ቤቶች ። ከአምላክ ፡ መቅደስ ፡ የቀሰዩ ፡ ልዩዎች ፡ ማለት ፡ ነው ። ወነሠተ ፡ አብያተ ፡ ቃዴስም ፡ (፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፯) ።

**ቄሀልት ፤ (ዕብ ፡ ቄሄሌት) ፤** አፈ ፡ ጉባኤ ፤ ሰለ ፡ ጉባኤ ፡ በጉባኤ ፡ ላይ ፡ የሚናገር ፤ ሰሎሞን ፤ የሰሎሞን ፡ መጽሐፍ ፡ ፲፭ኛው ፡ ክፍል ፡ መክብብ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፪) ።

**ቃህም ፤ — ገብረ ፡ ጕንዳን ፤ — ቃሕም ።**

**ቆብዕ** ፤ (**ዕብ ፡ ቆባዕ ፤ ከባዕ ፡ ሚግባዓ ። ሱር ፡ ቁባዓ ። ዐረ ፡ ቁበት**) ፤ የራስ ፡ ልብስ ፤ ጊጥ ፤ ቆብ ፤ ኮፊያ ፤ ባርኔጣ ፤ ቦርቦርቴ ፤ ጠርቡሽ ፤ ረኸርም ፡ ታላቅ ፤ በራስ ፡ የሚደፋ ። ቁብ ፡ ቂብ ፡ ቆቡብ ፡ የሚል ። ቁዳርበንና ፡ ማስፈርትን ፡ እዩ ። **ቆብዑ ፡ ውፉት ፡ ዲበ ፡ መታክፍቲሁ ። ነሥአ ፡ ቆብዐ ፡ ወአስኬማ ። ደቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ቆብዐ ፡ ሰላም ፤ ኀደገኒ ፡ ዴማስ ፡ መነኮስ ፡ ሕልም ፤ ወአፍቀሮ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓለም** ፤ (ፊልክ ፡ ፶፯ ። ገድ ፡ ተክ ። ቅኔ) ።



ቆብዕ ፡

**ቀዋብዕ** ፤ (**ቀዋብዕት ፤ ቆብዓት**) ፤ ቆቦች ፤ የራስ ፡ ልብሶች ። **ሥራዕ ፡ ሎሙ ፡ ቀዋብዐተ ፡ ዘአልቦ ፡ ዝዕላ** ፤ (ሥር ፡ ጳኰ) ።

**ቀዊል** ፤ **ሎት** ፤ (**ቆለ ፤ ቀወለ ፡ ይቀውል ፡ ይቁል ። ዐረ ፡ ቃለ**) ፤ ብሂል ፤ ነቢብ ፤ ደሚስ ፤ ማለት ፡ መናገር ፤ መፎከር ፡ ቃል ፡ መስጠት ፤ ማስማት ። ከጥሬው ፡ በቀር ፡ አንቀጹ ፡ አይገኝም ። ቆሌ ፤ ቀውላላ ፡ ቂል ፤ ቃቂል ፡ ቃጭል ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ቃል** ፤ (**ላት ። ዕብ ፡ ቆል ። ሱር ፡ ቃላ ። ዐረ ፡ ቃል ፤ ቀውል**) ፤ በቁሙ ፤ ፍሬ ፡ ነገር ፤ ድምጥ ፤ ጽሩሕ ፡ ከላሕ ፡ ኀባሕ ፤ ሰኈባስ ፤ ከፎኚዎና ፡ ከተናጋሪው ፡ አፍ ፡ በጕሮሮ ፡ የሚሰማ ፡ ኹሉ ። **መጽአ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ። አንሥኡ ፡ ቃለክሙ ። ቃለ ፡ ወህቡ ፡ ደመናት ፤ ቃለ ፡ ነጐድጓድከ ፡ በሠረገላት ። ቃል ፡ ተሰምዐ ፡ በራማ** ፤ (ዳን ፱ ፡ ፳፰ ። ኢሳ ፳፫ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፸፯ ። ኤርም ፴፩ ፡ ፲፭) ።

—፤ ሕግ ፡ ትእዛዝ ፡ ትምርት ፡ በዋጅ ። **ኢይትገሐሡ ፡ እምኔ ፡ ቃሉ ። ዐሥሩ ፡ ቃላት ። ቃላተ ፡ እግዚእነ** ፤ (ሚራ ፲፯ ፡ ፳፰ ። ዘዐ፴፬ ፡ ፳፰ ። ዘዳ፬ ፡ ፲፫ ። ፊልክ ፡ ፫) ።

—፤ የአካል ፡ ስም ፤ መለኮታዊ ፡ አካል ፡ ወልድ ። **ወበዝንቱ ፡ ስም ፡ ዘውእቱ ፡ ቃል ፡ ንሌብዎ ፡ እምሠለስቱ ፡ ቃላት ፡ አተርጋዎን ፡ ብርፎሪኮን ፡ አስትሪኮን ። ወኢታምስልዎ ፡ ለዝ ፡ ቃል ፡ ከመ ፡ ቃላት ፡ እለ ፡ ዘከርናሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ህላዌ ፡ ወአካል ። ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ሥጋ ፡ በአካሉ** ፤ (ሃይ ፡ አበ ፡ ጎር ። ብንያ) ።

**ቆሎንያ** ፤ (**ጽር ፡ ኮሎኒኢ**) ፤ ግዛት ፡ ቅኝ ፡ አሰራጃ ፤ ከፍል ፡ ጭማሪ ፡ ያንድ ፡ ኹም ፡ አገር ፡ (ግብ ፲፯ ፡ ፲፪) ።

**ቀዊም** ፤ **ሞት** ፤ (**ቆመ ፡ ይቀውም ፡ ይቁም ። ዕብ ፡ ቁም ። ሱር ፡ ቃም ። ዐረ ፡ ቃመ**) ፤ መቆም ፡ መነሣት ፡ አፋፍ ፡ በርደግ ፡ ቀጥ ፡ ማለት ፤ እንደ ፡ ዐምድ ፡ መኾን ፤ መጽናት ፡ መበርታት ፡ መሸሬሸት ። **ቁሙ ፡ ወአጽምዑ ፡ ወንጌለ ። ብዙኃን ፡ ቀሙ ፡ ላዕሌየ ። ቁም ፡ በእግሪከ ። አእጋሪከ ፡ እለ ፡ ጠብዓ ፡ ለቀዊም** ፤ (ቅዳ ። መዝ ፡ ፫ ። ሕዝ፪ ፡ ፩ ። ደራሲ) ።

—፤ መገታት ፤ መከልከል ፤ ቂሞ ፡ መቈየት ፤ መጽናት ጸንቶ ፡ መኖር ፤ ቀዋሚ ፡ መኾን ፤ መተካት ፡ መውረስ ፤ ያባትን ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ ሥራና ፡ ስፍራ ፡ መያዝ ። **ቀመ ፡ ዝናም ፡ እምሰማይ ። ቀመ ፡ ውሕዘተ ፡ ደማ ። ቁመኒ ፡ ቁመኒ ፡ በእንተ ፡ እግዚ ። እሮ ፡ ይቀውም ፡ መንግሥቱ ። ወኵሉ ፡ ቦቱ ፡ ቀመ ። ሃይማኖትከ ፡ ትቀውም ፡ ለዓለም ። ኢይቀውም ፡ ትእዛዙ ። ወኢይቀውም ፡ ዘርዑ** ፤ (ዘፍ፰ ፡ ፪ ። ሉቃ፰ ፡ ፵፬ ። ገድ ፡ ተክ ። ሉቃ፲፩ ፡ ፲፰ ። ቆላ፩ ፡ ፲፯ ። ሚራ፵ ፡ ፲፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፩ ። ኤር ) ። ተወልደ ፡ ተፈጥረ ፡ ተሣረረ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ቆመ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **ዘእንበለ ፡ ትቁም ፡ ምድር ። እንበለ ፡ ይቁሙ ፡ አድባር** ፤ (ሉቱ ፡ ዕዝ፩ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፹፱) ።

**ቀዋሚ** ፤ (**ሚት ፡ ምያን ፡ ያት**) ፤ በቁሙ ፤ የሚቆም ፤ ቋሚ ፤ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፤ ጠበቃ ፤ የነገር ፡ አባት ፡ መጋቢ ፤ ሹም ። **ሱራፌል ፡ ወኪሩቤል ፡ ቀዋምያን ፡ ዐውደ ፡ መንበሩ ። ጽርሕ ፡ ቀዋሚት ፡ እንተ ፡ ኢትወድቅ ። ቀዋሚ ፡ ይረክብ ፡ ስብሐተ ። ቀዋሚሃ ፡ ለመዐስብ ። ቀዋሚ ፡ ለመበለት ፡ ወለዕጓለ ፡ ማውታ ። ወይርእይ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡ እምአኀው ፡ ኀበ ፡ ዘሎቱ ፡ ምግባር ፡ ሠናይ ፡ ወይረስዮ ፡ ቀዋሜ ፡ ላዕለ ፡ ምኔት ፡ ወላዕለ ፡ መዛግብቲሁ** ፤ (ግንዘ ። አርጋ ፡ ፫ ። ፪ ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ። ድጓ ። ኪዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**ቀዋም** ፤ ቀዋሚ ፤ ጠንካራ ፤ ቈመታም ፡ ረኸጕም ። **ኵሉ ፡ አረፍት ፡ ቀዋም** ፤ (ኢሳ፪ ፡ ፲፭) ።

**ቀዊም** ፤ (**ማን ፡ ማት ፡ ውምት**) ፤ የቆመ ፤ የጸና ፤ የተለመደ ፤ የተለየ ። **እሙንቱ ፡ ቀዊማን ፡ ላዕለ ፡ ቅጽር ። ወውእቱ ፡ ቀዊም ፡ በነበ ፡ ግብጻውያን ፡ ወመለካውያን ። ሕዱም ፡ ወቀዊም ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን** ፤ (ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ። ቀሌ) ።

**ቁመት** ፤ መቆም ፤ አቋቋም ፤ በቁሙ ፤ ቀጥታ ፤ ዘለግታ ፤ ምጥቀት ፤ ርዝመት ። **ተዘከር ፡ ቁመትየ ፡ ቅድሜከ ። ወይትሀጐል ፡ ቁመቶሙ ፡ በምንዳቤ** ፤ (ኤር፲፰ ፡ ፳ ። ኩፋ ፡ ፳፫) ።

—፤ አናምር ፤ ኑሮ ፤ ጽንዐት ፤ ልዩነት ። **እለ ፡ ይከውኑ ፡ ውስተ ፡ ቁመት ፡ ፍጽምት ። ሥርዐተ ፡ ቁመት ፡ ዓለም ። ቁመት ፡ ወሕርመት** ፤ (ፊልክ ፡ ፵፰ ። ጥበ፯ ፡ ፲፯ ። ቀሌ) ።

**ቆም** ፤ (**ብ ፡ ቆማት**) ፤ ቁመት ፤ ርዝመት ፤ የሕንጻ ፡ የገላ ፡ መጠን ፤ ከምድር ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ ጫፍ ፡ ያለ ። **ወኖኅ ፡ ቆማ ። ኢይትዐወቅ ፡ ኑኃ ፡ ወግድማ ፡ ወሊ**

ቆማ ። በአምጣነ ፡ ቆሙ ፡ ለሰብእ ፡ ኅይሉ ። ቆመ ፡ አረፍት ። ወደምሰሰ ፡ ቆምሙ ፡ በእደ ፡ ብእሲት ፡ (ሕዝ፲፱ ፡ ፲፩ ። ቀሌ ። ሚራ፳፰ ፡ ፫ ። ዮዲ፩ ፡ ፱ ። ፱ ፡ ፲) ።

**ምቅዋም ፤ (ማት) ፤** መቋሚያ ፤ በታ ፡ ስፍራ ፤ ጥግ ፡ ደገፋ ። የመነሾሱ ፡ በትር ፤ (ተረት) ፤ መቃዱኝ ፡ ታጥቆ ፤ መቋሚያውን ፡ ነጥቆ ። ምቅዋመ ፡ አጣሊ ፡ ር ጉማን ፡ ወምቅዋመ ፡ አባግዕ ፡ ሁሩካን ። ዐጸደ ፡ ም ቅዋም ፡ ለካህናት ። በበ ፡ ምቅዋማቲሆሙ ፡ (ማንዘ ። ኪዳ ። ፪ዘና ፡ ፯ ፡ ፮) ።

—፤ ኩሬ ፤ ዐይጣ ፡ ምዕራፍ ። ምዕራፍ ፡ እንቀጽ ፤ የመ ጽሐፍ ፡ ክፍል ። ምቅዋመ ፡ ማይ ። ወሳዕሊ ፡ ሸሉ ፡ ምቅዋም ፡ ኑሎቀ ፡ (፱በ፯ ፡ ፲፱ ። ቢ.ሮ.ይ ፡ ፯፩) ።

**አቆመ ፤ (ሖረ ፡ አሖረ ፤ አኖመ ፤ አፆቀ ፤ አሮጸ) ፤** በቁሙ ፡ እውነተኛው ፡ ጥሪ ፡ ይህ ፡ ነው ።

**አቀመ ፤ (በአ ፤ አብአ ። ኖኀ ፡ አንኀ) ፤** አቆመ ፡ አስቆመ ፤ ተክለ ፤ መሠረተ ፤ አጸና ፤ አበነማ ። አ ቀመኒ ፡ በእገሪየ ። ይቀውም ፡ ይብቴራሁ ። መኑ ፡ አ ቀሞሙ ፡ ለአሕጉር ። ያቀውም ፡ ቃለ ፡ ገብሩ ። አ ቅም ፡ ዘቢያተ ፡ ለስምከ ፡ (ሕዝ፳ ፡ ፪ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፳፭ ። ፅዑ ፡ ፲፱ ። ዳ፲፱ ፡ ፳፮ ። ሚራ፴፫ ፡ ፳) ። ቆመ ፡ ብሎ ፡ በ አቆመ ፡ ፈንታ ፡ አቀመ ፡ ማለት ፡ የስሕተት ፡ ናቸው ፤ ዐእና ፡ ኖኀ ፡ አብአ ፡ እንኀ ፡ ቢሉ ፤ ወና ፡ አኅ ፡ ኹለት ፡ ዐመሎች ፡ ስላሉባቸው ፡ ነው ። ቆመ ፡ ግን ፡ ከ፪ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ድርብ ፡ ዐመል ፡ የለውምና ፤ አቆመ ፡ እንጂ ፡ አ ቀመ ፡ አያሰኝም ። አቆመና ፡ ዐቀመ ፡ ይተካከሉና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተሳስቷል ፤ ዐቀመን ፡ እዩ ።

—፤ ገታ ፡ መለሰ ፡ ተወ ። አዘዘ ፡ ያቅሙ ፡ ሠረገላሁ ። አቅም ፡ እዴከ ። ወአቀሙኒ ፡ ወሊደ ፡ (ግብ፰ ፡ ፴፰ ። ፩ዜና ፡ ፳፩ ፡ ፲፭ ። ዘፍ፳፱ ፡ ፴፭) ።


**ያቁም ፤ (ጽር ፡ ያኹም ። ዕብ ፡ ያኪን) ፤** ሃዐምድ ፡ ስም ፤ በሰሎሞን ፡ እንጸር ፡ በስተቀኝ ፡ የቆመ ። ቀዋሚ ፡ ቅዉም ፡ ርቱዕ ፡ ይሉታል ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በሰ ገዝን ፡ እዩ ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፳፩) ።

**ተቃወመ ፤** በቁሙ ፡ ተቋቋመ ፤ ተሸነገተ ፡ ተ ከራከረ ፡ ተወዳደረ ፡ ተፋከከረ ። መኑ ፡ ይትቃወሞ ፡ ለሸ ፍኑሁ ። አልቦ ፡ ዘይትቃወም ፡ ለቃልከ ። ለእመ ፡ ተቃ ወሞ ፡ ዲያቆን ፡ ለቀሲስ ። ምስለ ፡ ብርሃን ፡ እንዘ ፡ ትትቃወም ፡ ትትረከብ ፡ ከመ ፡ ቀዳማዊት ፡ ይእቲ ፡ (ኢዮ፱ ፡ ፲፱ ። ዮዲ፰ ፡ ፳፰ ። ፍ፡ ፡ ነ ፡ ፱ ። ቅዳ ፡ ኪዳ.) ።

**ተቃዋሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤** በቁሙ ፡ ተጣይ ፤ ከሳሽ ፡ ቁም ፡ የሚያቆም ፡ የሚቋቋም ። ብእሲት ፡ ተቃዋሚት ። ኩነንከ ፡ ተቃዋምያነ ፡ (ፈ ላስ ። ጥበ፲፩ ፡ ፱) ።

**ቃውም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤** የሚ ቆም ፡ የሚቋቋም ፤ አለቃ ፤ ጠበቃ ፤ የነገር ፡ አባት ፤ ወ ይም ፡ ወደረኛ ፤ ከሳሽ ፡ ባለጋራ ። አነ ፡ ቃውምከ ፡ መዐ ስብከ ፡ ጥቀ ። ንጉሥ ፡ ልብው ፡ ቃውመ ፡ ሕዝብ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፱ ። ጥበ፳ ፡ ፳፮ ። አርጋ) ።

**ተቅዋም ፤ (ማት) ፤** መቅረዝ ፤ ማብሪያ ፡ የመ ብራት ፡ ዕቃ ፤ የቀንዲል ፡ የፋና ፡ ማኖሪያ ፤ የሚቆም ፡ የ ሚተከል ፡ ወይም ፡ የሚሰቀል ፡ የሚንጠለጠል ፤ ባለብዙ ፡ ዐጽቅ ። ርእዩ ፡ ተቅዋመ ፡ ማኅቶት ፡ ዘዘለንታሁ ፡ ወ ርቅ ። ማኅቶት ፡ እንተ ፡ ታበርህ ፡ ዲበ ፡ ተቅዋማ ። ወትገብር ፡ ሊተ ፡ ተቅዋመ ፡ ወርቅ ፡ ጽሩይ ፡ (ዘካ ፬ ፡ ፪ ። ሚራ፳፮ ፡ ፲፯ ። ዘፀ፳፭ ፡ ፴፩) ።



ተቅዋም ፡

**አስተቃወመ ፤** አቋቋመ ፡ አሸነገተ ፡ አከራከረ ፡ አወዳደረ ፤ አፋከከረ ።

**መስተቃውም ፤** የሚቃወም ፡ የሚያቃዋ ውም ፤ አቃዋሚ ። መስተቃውማን ፡ (አዋል) ።

**ቁማስ ፤ (ዐረ ፡ ቁማሽ) ፤** መዳ ፤ ጣቃ ፤ የል ብስ ፡ ነደ ። ቁማስ ፡ ቀራጺብ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፫ ፡ ፳) ።

**ቆሞስ ፤ (ሶት ። ዐረብ) ፤** በቁሙ ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፤ የኤጲስቆጶስ ፡ ምክትል ፡ ተወራጅ ። (ሙሻ ፡ ስለ ፡ ቁስና ፡ ስለ ፡ ቆሞስ) ፤ እንጊ ፡ ፍረድ ፡ ቢሉኝ ፡ ሞት ፡ በ ደለኛ ፡ ነው ፤ ፩ ፡ ቂስ ፡ ለፍታት ፡ ቆሞስ ፡ ቢቀር ፡ ም ንው ። ኤጲስቆጶሳት ፡ ወእልቀሞሳት ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ቆመሰ ፤ አው ፡ ተቆመሰ ፤** ቆሞስ ፡ ኾነ ፤ ተባለ ፤ ቁምስና ፡ ተሾመ ፤ ተቀበለ ።

**ቁምስና ፤** ቆሞስነት ፡ ቆሞስ ፡ መኾን ፤ የቆ ሞስ ፡ ማዕረግ ።


**ቀዊዕ ፤ ዖት ፤ (ቆዐ ፡ ይቀውዕ ፡ ይቃዕ ፤ ይቅዋዕ) ፤** መዝርዘር ፤ መውለድ ፤ መፈርጸት ፡ ፍሬ ፡ መዥመር ፡ መቋጠር ። የአዝርዕት ፡ የአትክልት ። ሙል ቀም ፡ መቃረም ፤ መቀጥቀጥ ፡ መቅሠም ። ቈሰለን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ቀውዕ ፡ ቆዕ ፤** ጪርቃ ፤ እንቀጫጭ ፡ ቃሪያ ። መከር ፡ አዝመራ ፡ (ትግሬ) ። በጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ቀውዐ ። ቆዐ ፡ ትጼኑ ፡ ቆዐ ፡ ጽጌ ፡ ወይን ። አበው ፡ በልዑ ፡ ቆዐ ። ከመ ፡ ቆዐ ፡ ቀምሐ ። ፍሬሆሙ ፡ ቆዐ ፡ ከንቱ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ድጓ ። ሕዝ፲፰ ፡ ፪ ። ሚራ፴፩ ፡ ፲፭ ። ጥ በ፬ ፡ ፭) ። ኮል ፡ ዕንጉቶት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ቆዕ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ቆዐ ፡ ምስለ ፡ ናርዶስ ፡ (ማሕ፬ ፡ ፲፫) ።

—፤ ጨቅላ ፤ ሕፃን ፤ ለጋ ፡ ቀንበጥ ፤ ዝርዝሬ ፡ ቀጭ ፡ ዐመድ ፡ ፈጭ ። እንዘ ፡ ቆዑ ፡ ተመሥጠ ፡ ሕፃኑ ፡ (ጥበ ፲፱ ፡ ፲፭ ። ምሳ፲፫ ፡ ፬) ።

**ቆዓት ፤ ቃውዕ ፤ አቅዋዕ ፤** ጪርቃዎች ፤ ጨቅሎች ፤ ሕፃናት ።

**ቋዕ ፤ (ብ ፡ ቋዓት ። ዕብ ፡ ዖሬብ ። ዐረ ፡ ቁራብ ። ጽር ፡ ከራክስ) ፤** ቍራ ፤ ጥቍር ፡ አሞራ ፤ ቀጣዊ ፡ የሚቀጥ ፡ ቀማሚ ፡ ለቃሚ ። **ፈነዎ ፡ ለቋዕ ። ጸሊም ፡ ከመ ፡ ቋዕ ። ርእዩ ፡ ቋዓተ ፤** (ዘፍጥ ፡ ፰ ። ማሕ ፡ ፭፣ ። ሉቃ ፲፪ ፡ ፳፬) ። ቍራ ፡ ከርኩም ፡ ይልቅ ፡ እንደ ፡ ዝግን ፡ ዕድሚያም ፡ ነው ፡ ይባላል ። ገላግል ቱም ፡ ሲፈለፈሉ ፡ እንደ ፡ ራዛ ፡ ነጫጮች ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ሕጕሬ ፡ እንደ ፡ በርበሬ ፡ ቀያዮች ፡ ኹነው ፡ ይወጡና ፡ በኋላ ፡ ሲያድጉ ፡ ይጠቍራሉ ፤ እናታቸውም ፡ ስለ ፡ ኀጢታቸው ፡ ፈርታ ፡ ደንግጣ ፡ እስኪጠቍሩ ፡ ድረስ ፡ ከዚያው ፡ ጥላቸው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ትኼዳለች ። የፍጥረቱ ፡ አባት ፡ እግዚር ፡ ግን ፡ ፈትፍቶ ፡ እንደ ፡ ማጕረሥ ፡ ከተሐዋስያን ፡ ታናናሹን ፡ ዝንብና ፡ ትንኝ ፡ እስከፋቸው ፡ እያቀረበ ፡ ይመግባቸዋል ። **ዘይሁቦሙ ፡ሲሳዮሙ ፡ ለእንስሳ ፡ ወለዕጕለ ፡ ቋዓት ፡ አለ ፡ ይጼውዕዎ ፤** (መዝ ፡ ፻፵፯) ።




ቋዕ ፡

**ቆፍ ፤ (ዕብ) ፤** ስመ ፡ ፊደል ፡ ቀ ፤ ዝንጀሮ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (መዝ ፡ ፻፲፱ ፡ ፻፵፭—፻፶፪ ። ሰቈ ፡ ፫፥ ። ፪ ፡ ፲፱ ። ፫ ፡ ፶፱ ። ፬ ፡ ፲፱) ።

**ቆፋዊ ፤** ዝንጀሬም ፤ ዝንጀርማ ፡ የዝንጀሮ ፡ ዐይነት ፡ ቆፍቋፋ ፡ ሥሥ ፡ ንፉግ ።

**ቆቅሐ ፤ ሐት ፤ (ቆቅሐ ፡ ይቆቅሕ ። ዐረ ፡ ቀውቀ ። ዕብ ፡ ቃዕቈዐ) ፤** ማሽካካት ፤ ማሽካክት ፤ ቃቃቃ ፡ ማለት ፤ የዶሮ ፡ ያሞራ ፤ ለመውለድ ፡ ዕንቍላል ፡ ስመጣል ። ቀሕቅሐን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ቆቅሕ ፤ (ሓት ። ዕብ ፡ ቁቂያ ፤ ቆቅማ ፡ ጠፍ) ፤** እንስት ፡ ቆቅ ። ነቃወተ ፡ **ቆቅሕ ፡ ወኢወለደት ። መቃርዮስ ፡ ዘተሴሰይከ ፡ ቆቅሐ ፡** (ኤር ፲፯ ፡ ፲፩ ። ስንክ ፡ ታኅ ፲፱) ።



ቆቅሕ ፡

**ቆቃሕ ፤ (ብ ፡ ቀዋቅሕ ። ዕብ ፡ ቆሬአ) ፤** ተባት ፡ ቆቅ ። **ቆቃሕ ፡ ይነቁ ፡ ወያስተጋብእ ፡ ዘኢወለደ ። ቆቃሕ ፡ ተሠግረ ፡** (ፊሳሎ ። ሚራ ፲፩ ፡ ፴) ።

**አንቆቅሐ ፤ (ያንቆቅሕ) ፤** አፈራ ፡ ወለደ ፤ ዕንቍላል ፡ ጣለ ። ቋቋ ፡ ቀፈቀፈ ፡ ፈለፈለ ፤ ወይም ፡ ተቋቋ ፡ ተቀፈቀፈ ፡ ተፈለፈለ ፤ ዕንቍላሉ ፡ ፍሬው ፡ ጫጩቱ ።

**አንቆቅሖ ፤ አንቆቅሖ ፤ (ሖት) ፤** ዕንቍላል ፤ የአዕዋፍ ፡ እስክል ፤ ወልደው ፡ ከማያጠቡ ፡ ከሌሎቹም ፡ ፍጥረት ፡ የሚገኝ ፡ ባሕርያዊ ፡ ፍሬ ። **ይበልዑ ፡ አንቆቅሖ ፡ ወግብነተ ። ዖፍ ፡ እንተ ፡ ተሐቅፍ ፡ አንቆቅሖ ። ወይነፅኑ ፡ አንቆቅሖሙ ። አንቆቅሖ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡** (ቄድር ። ዲድ ፡ ፳ ። ኢሳ ፶፱ ፡ ፭ ። ፶፱ ፡ ፰) ። እንቆቆ ፤ እንቆቅልሽ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ዕንቍላል ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ዕንቍ ፡ ሉል ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሉል ፡ የሚመስል ፡ የሉል ፡ ዐይነት ። ዕንቍ ፡ ከዐንቀ ፤ ላል ፡ ከሉል ፡ መጥቶ ፡ ተገናኝቶ ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ኹኗል ፤ ብሒረንና ፡ ዐንቀን ፡ ተመልከት ።

**ቆራህ ፤ (ጽር ፡ ኩራ) ፤** ገነት ፡ ያታክልት ፡ ቦታ ። **ቆራሁ ፡ ለንጉሥ ፡** (ነሐ ፫ ፡ ፲፭) ።

**ቆሮስ ፤ (ጽር ፡ ክሮስ ። ዕብ ፡ ኮር) ፤** የመስፈሪያ ፡ ስም ፤ ዐሥር ፡ ኢፍ ፡ የሚይዝ ፤ ዐሥረ ፡ ፈጅ ። ሖሜርን ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። **በመስፈርተ ፡ ቆሮስ ፤** (ዘሌ ፳፯ ፡ ፲፮ ። ዘኍ ፲፩ ፡ ፴፪ ። ሉቃ ፲፮ ፡ ፯) ።

**ቀውስ ፤ (ዐረብ) ፤** ቀስት ፡ ደጋን ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**ቀውስ ፤ (እልቀውስ) ፤** ኮከብ ፤ የኮከብ ፡ ስም ፤ መልኩ ፡ ቀስተኛ ፡ ባለቀስት ፡ የሚመስል ። ኮከቡ ነቱም ፡ የኅዳር ፡ ነው ፤ ከዐሐይ ፡ ጋራ ፡ ፳፱ ፡ ዕለት ፡ ፳፰ ፡ ኤክሮስ ፡ ይመግባል ፡ (አቡሻ ፡ ፴) ።

**ቆጽን ፤ (ናት ። ቆብዕ ፡ ዓት) ፤** ኮፍ ፡ ጠማ ፡ ገንባሌ ፡ እስከ ፡ ጕልበት ፡ ድረስ ፡ የሚገባ ። **ቆጽናቲሁ ። ቆጽናት ። ቆጽናተ ፡ ደክንተ ፤** (ሚራ ፴፰ ፡ ፭ ። አፈ ፡ ቶዘ ። አረጋ) ። ጋላ ፡ ስንዱ ፡ ዝግጁ ፡ ልባም ፡ ጠፍተኛ ፡ ፈጣን ፡ ቀልጣፋ ፡ ሲል ፡ ቆጺ ፡ የሚለው ፡ ከቆጽን ፡ ጋራ ፡ በጣም ፡ ይስማማል ።



ቆጽን ፡

**ቆጸረ ፤ (ልብ ፡ ወለደ ፡ ግስ) ፤** ቈረጠመ ፤ ቈረጣጠመ ፤ ፈጨ ፡ አንቀጣቀጨ ።

**ቆጵሮስ ፤ (ጽር ፡ ኪፕሮስ ። ዕብ ፡ ቂፍሮስ ። ዐረ ፡ ቁብሩስ) ፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ ደሴት ፤ ወይናም ፡ ዘይታም ። **ሌዋዊ ፡ ዘምድረ ፡ ቆጵሮስ ፡** (ግብ ፬ ፡ ፴፮) ።

**ቆጵሮስ ፤ (ጽር ፡ ክፕሮስ) ፡** ስም ፡ ፋን ድያ ፤ በጠጥ ፡ ዐዘብ ፡ እበት ፡ ኾበት ። አኣዳስን ፡ እይ ፡ (ሉቃ ፲፱ ፡ ፴፭) ።

**ቀዘፈ ፡ (ዐረብ) ፤** በቀዘፈው ። ዐረቦች ፡ ዳሉጥን ፡ ንቀኅባ ፡ እየጨመሩ ፡ ዘ ፡ ይሉታልና ፤ ስለዚህ ፡ ቀዘፈ ፡ ቀደፈ ፡ እያለ ፡ በኹለት ፡ ይጥፋል ። ቀደፈንና ፡ ጎደፈን ፡ እይ ።

**ቅሒው ፤ ዎት ፤ (ቀሐወ ፡ ይቅሑ ፡ ይቅሐው ። ወቅሐ ፡ አሰረ)፤** ማየል ፡ መበርታት ፡ መንቃት ፡ መትጋት ፤ አለኹ ፡ አለኹ ፡ ማለት ፤ ማሬል ፡ መገን ፈል ፤ ዐፍለኛ ፡ መኾን ፡ መፈካከር ፡ መወዳደር ፤ እኔ ፡ እበልጥ ፡ እኔ ፡ እበልጥ ፡ ወይም ፡ እታከል ፡ እታከል ፡ ማለት ። በቀሐወ ፡ ፈንታ ፡ ቀቀሐወ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**አቅሐወ ፤** አነቃ ፡ አተጋ ፡ አበረታ ፡ አፈካከረ ።

**ተቃሐወ ፤** ተፈካከረ ፡ ተቃወመ ፡ ተወዳደረ ፡ ተሻገተ ፡ ተከራከረ ። **ይትቃሐወ ፡ በምግባረ ፡ ትሩፋት ። አላ ፡ ከመ ፡ ይትቃሐዎሙ ፡ ለነሀብተ ፡ ብሩር ። ኢትትቃሐው ፡ ምስለ ፡ ዘይብዕለከ ። ለእመ ፡ ተቃሐወ ፡ በዝንቱ ። ቀቃሕዎት ፡** (አፈ ፡ ድጓ፱ ። ጥበ፲፭ ፡ ፱ ። ሢራ፰ ፡ ፱ ። አብጥ ፡ ፬ ። ፊልጵ፭ ፡ ፲፭) ።


**ቃሕው ፤ (ዋት) ፤** ፍክክር ፡ ሙግት ፡ ክርክር ፡ ንዝንዝ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ቍትቻ ፡ ውርርድ ። **ቅንአት ፡ ወቃሕው ፡ ወሚን ፡ ወአፍቅሮ ፡ መዊእ ። ፈጸምዋ ፡ ለዐመፃ ፡ በቃሕዎሙ ። ቃሕወ ፡ ገብረ ፡ ምስለ ፡** (ፊልክ ፡ ፶፯ ። ዘፍጥ፺፱ ፡ ፳ ። አርጋ ፡ ፬) ።

**ቃሕዋ ፤ (ዐረብ) ፤** ቡና ፡ የቡና ፡ ፍሬ ፡ ቈልቶ ፡ ፈጭቶ ፡ አፍልቶ ፡ ሲጠጡት ፡ የሚያነቃ ።

**ቅሒም ፤ ሞት ፤ (ቀሐመ ፡ ይቅሕም ፡ ይቅሐም ። ቀምሐ) ፤** መቃም ፡ መንተም ፡ የፍሬ ፡ የበሶ ፡ የፍርፋሪ ። (ግጥም ፡ ትግሬ ፡ ስለ ፡ ነሎች) ፤ **አዒንቶም ፡ ዚመስሉ ፡ አዒንት ፡ ደማሙ ፡ ስናዮም ፡ ዚመስሉ ፡ ብርስን ፡ ዘቀሐሙ ።** መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በቀሐመ ፡ ፈንታ ፡ ቀምሐ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። **ይቀምሕ ፡ አንበሳ ፡ ሐሠረ ፡ ከመ ፡ ላሕም ። ኢይረክቡ ፡ እልሕምት ፡ ዘይቀምሑ ። ሐመደ ፡ ይቀምሑ ። ሐመደ ፡ ከመ ፡ እክል ፡ ቀማሕኩ ። ይቀምሕ ፡ መሬት ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ። ወይቀምሑ ፡ ሐሪጸ ፡** (ኢሳ ፲፩ ፡ ፯ ። ሰንክ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፻፩ ። ፶፭ ። አፈ ፡ ድጓ ። ዮሴፍ) ።

**ቀሓሚ ፡ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት ፤ ሐምት) ፤** የሚቅም ፤ ቃሚ ፤ ጎታሚ ፡ ጥሬ ፡ በል ።

**ቃሕም ፤ (ማት) ፤** አግዝ ፡ ገብረ ፡ ጕንዳን ፡ ፍሬ ፡ እክልን ፡ እንደ ፡ ገበሬ ፡ የሚዘግብ ፡ የሚሰበስብ ። **ሑር ፡ ኀበ ፡ ቃሕም ፡ አ ፡ ሀካይ ። ንሬእዮ ፡ ለሰብእ ፡ ከመ ፡ ቃሕም ፡ ወዐዒያት ። ዘጊበ ፡ መዘግብት ፡ ዘቃሕም ፡ ወተመይዮ ፡ ግብር ፡ ዘማሬት ። ትጋሆሙ ፡ ለፅብስት ፡ ንህብ ፡ ወሀካይ ፡ ቃሕም ፡** (ምሳ፮ ፡ ፮ ። አፈ ፡ ተ፲፯ ። ፊላስ ። ስንክ ፡ መስከረም) ።



ቃሕም ፡

—፤ ቃሚያ ፡ ጕርሻ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚቃም ፡ የሚቋት ፡ የሚጕረሥ ። **ዘሉ ፡ ይትኀጣእ ፡ እመ ፡ ኀሠሥዎ ፡ እምነ ፡ ፍተ ፡ ቃሕም ፡ ኅብስት ፡ እስከ ፡ ነጥበ ፡ ማይ ፡ ቈሪር ፡** (ቀኔ) ።

—፤ ቃሞ ፤ ተረር ፡ ፍሬው ፡ የማሽላ ፡ ዐይነት ፡ ታሽቶ ፡ የሚቃም ።

**አቅሐመ ፤** አቃመ ፤ አስቃመ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ አቅምሐ ፡ ይላል ። **ለአይግከለ ፡ አቅምሐ ። ዘከመ ፡ ያቀምሕ ፡ ብዕራይሁ ። አቅምሐኒ ፡ ሐመደ ፡** (ሚራ ፴ ፡ ፴፫ ። ፴፰ ፡ ፳፯ ። ሰቈ፫ ፡ ፲፮) ።

**ምቅሓም ፤** መቃሚያ ፤ ግርግም ፡ የእንስሳት ፡ ማእድ ፤ ቤት ፡ በረት ፡ ጋጥ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጣሮች ፡ ስሕተት ፡ ምቅማሕ ፡ ይላል ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፫ ። ሰንጅ ፡ ፲፯ ። ሉቃ፲፫ ፡ ፲፭) ።

**ቀሕቅሖ ፤ ሖት ፤ (ቀሕቀሐ ፡ ይቀሐቅሕ ፡ ይቀሕቅሕ ። ዐረ ፡ ቀሕቀሐ ። ሱር ፡ ቃሕቃሕ) ፤** መቈርቈር ፡ መቀብቀብ ፤ መጠብጠብ ፤ የስደቃ ፡ የጣት ፡ ለመጥራት ፤ ወይም ፡ እገሌ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እህ ፡ ዕሽ ፡ ማለት ፤ በጣት ፡ ማመልከት ፤ ውስድ ፡ አምጣ ፡ ማለት ፤ በጸሎት ፡ በማእድ ፡ ጊዜ ። ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ቆቅሐ ፡ ነው ፤ ከቈቀወም ፡ ጋራ ፡ ይሰማማል ፤ ዐና ፡ ሐ ፡ ይዋረሳሉ ። **ወእመ ፡ ቦ ፡ ዘትፈቅድ ፡ በውስተ ፡ ማእድ ፡ ኢትንብብ ፤ ቀሕቅሕ ። አልቦ ፡ ዘይትናገር ፤ አላ ፡ ይቀሐቅሑ ፡** (ሥር ፡ ጳኰ) ።

**ቅሕቃሔ ፤** ቍርቈራ ፡ ጥብጠባ ፡ የምልክት ፡ ጥሪ ፡ ትእዛዝ ።

**ቀጣ ፤ (ዕብ ፡ ቃጥ ፤ ጥቀ) ፤** ታናሽ ፡ የወርቅ ፡ ገንዘብ ፤ የወቄት ፡ ኻያኛ ። **ተማየጠ ፡ በኀምሳ ፡ ቀጣ ፡** (አዋል) ።

**ቀጢብ ፤ ቦት ፤ (ቀጠበ ፡ ይቀጥብ ፡ ይቀጥብ ። ዕብ ፡ ቃጣብ) ፤** መቀጠብ ፤ ማለብ ፤ ማመልከት ፤ ለመቍረጥ ፡ ለመበጠስ ፤ የገዞሓ ፡ የልብስ ። መቈጠብ ፤ መንፈግ ። ቀንጠበን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ስርጽ ፡ ነው ።

**ቈጢጥ ፤ ጦት ፤ (ቈጠ ፤ ቈጠጠ ፡ ይቈጥጥ ፡ ይቀኊጥጥ ። ቀጠነ) ፤** መቀጨጭ ፡ መቅጠን ፤ ቀጨጫ ፡ ቀጭን ፡ መኾን ፤ መክሳት ፡ መመንመን ። ቀጥቀጠን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ፤ አንቀጥቀጠም ፡ ሳይቀር ።

**ቈጢጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ጣጥ) ፤** ቀጨጫ ፡ ከሻዋ ፡ ቀጭን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በገዚፍ ፡ ፈንታ ፡ ቈጢጥ ፡ ይላል ። **ወዒግሎንስ ፡ ቈጢጥ ፡ ብእሲ ፡ ውእቱ ፡ ጥቀ ፡** (መሳ፫ ፡ ፲፯) ። ቀጠጠ ፡ ቀጠጥና ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ቀጠጦ ፤ የማሽላ ፡ ስም ፡ ፍሬው ፡ ቀጨጫ ።

**ቈጠጠ፤ (ዕብ፡ ቃጻጽ)፤** ቀጠጠ፤ ቈረጠ፡ ቈጠቈጠ፤ የግር፡ የቅጠል። ቍጥቋጠ፡ ማለት፡ የዚህ፡ ዘር፡ ነው። በቁሙ፡ ቈጠጠ፡ ቍጡጥ፡ ጣሰ፤ ኰሳ።

**ቍጠጥ፤** ቀጠቀጢነት፡ ቍጢንነት፤ አቀጣጠን፤ ቀጠና፡ ቅጥነት። ቅጠንየ፡ ባለው፡ ቍጠጥየ፡ ይገዝፍ፡ እምሐቌ፡ አቡየ፡ እንዲል፡ (፫ነገ፡ ፲፪፡ ፲)፡ ባለብለ ሆች፡ ግን፡ አውሬ፡ ጣት፡ ይሉታል።

**ቍጣጥ፤** የግልገል፡ በጠጥ፡ ቍጠቋጥ፡ ጭ ለቃን፡ ቃናሽ፡ ፍጥረት።

(ጥ) **ቍጥ፤** ምዝራጥ፤ ፀንካሴ፤ ኽብዳ፡ ጅንፎ፡ በጅንፎንቱ፡ ላይ፡ ምዝራጥነት፡ ያለው። ወረገዘ፡ በቍጠ፡ ኲናቱ፡ (፪ነገ፡ ፪፡ ፳፫)።

**አቍጠጠ፤** አቀጠነ፤ አመነመነ፤ አሰለሰለ። እመ፡ አቍጠጠ፡ ክሣዶ፡ ከመ፡ ሕልቀት፡ (ኢሳ፶፰፡ ፭። ፈልክ)።

**ቀጢን፤ ኖት፤ (ቀጠነ፡ ይቀጥን፡ ይቅ ጥን። ሱር፡ ቅጢን። ዕብ፡ ቃጦን)፤** መቅጠን፡ ማነስ፤ ቀጪን፡ መኾን።

(ጥጢ) **ቀጢን፤ (ናን፡ ናት፡ ጣን፤ ጠንት)፤** የቀጠነ፤ ቀጪን፤ ሥሥ፤ ረቂቅ። ልብስ፡ ቀጢን፡ ዘይ ትፀጸፍ፡ ካህን። ሰብዐቱ፡ ሥዊት፡ ቀጢናን። አስና ኒሁ፡ ቀጢናት። በቀጣን፡ ዐይኑ፡ ልብ። በቀጠንት፡ ገበድኩ፡ ምስካብየ። ብእሲ፡ ዘርሱይ፡ በቀጠንት፡ አልባስ፤ እለሰ፡ ቀጠንተ፡ ይለብሱ፡ ውስተ፡ አብ ያተ፡ ነገሥት፡ ሀለዉ፡ (ሚራ፵፡ ፪። ዘፍ፵፩፡ ፮። ዜና፡ እበ። ቄር፡ ጴላ። ምሳ፡ ፯፡ ፲፯። ማቴ፲፩፡ ፰)።

**ቅጥንት፤** በቁሙ፤ መቅጠን፤ አቀጣጠን፡ ቀጪ ንነት፡ መርቀቅ፡ መራቀቅ። ርኢክኑ፡ ቅጥንተ፡ ልቡ፡ ለሐዋርያ። ቅጥንተ፡ ጥበብ፡ (አፈ፡ ድጓ። ፲፱። ፍ፡ ነ፡ ፵፫)።

**ቅጠን፤** ቅጥንት፡ ቀጪንነት፤ ቀጠና። ቅጠ ንየ፡ ይገዝፍ፡ እምሐቌ፡ አቡየ፡ (፫ነገ፡ ፲፪፡ ፲)።

**ቍጥን፤ (ዐረ፡ ቁጥን)፤** ጥጥ፤ ቢሬትሱት፡ የሚቀጥን። ጡጥንና፡ ጥጥን፡ ተመልከት። ጠብሰባ፡ ዘቍጥን፡ ወበአልባስ፡ ንጹሕ፡ (በንክ፡ መስ፲)። ባለቅ ኔዎች፡ ግን፡ ግምጃ፡ ይሉታል።

**አቅጠነ፤** አቀጠነ፤ አስቀጠነ፡ ቀጪን፡ አደ ረገ፡ አስደረገ፡ አረቀቀ። ያቀጥኖ፡ ለልብ፡ (ማር፡ ይሥ፲፭፡ ፭)።

**አቅጣኒ፤ መቅጠኒ፤** የሚያቀጥን፡ የሚያ ስቀጥን፤ አቅጣኝ፡ አስቀጣኝ። (ተረት)፤ አፍጣኝና፡ አቅ ጣኝ፡ ከመዳሮ፡ እንገናኝ።

**መቅጠን፤ (ብ፡ መቃጥን። ዐረ፡ ሚቅ ጠን)፤** በቁሙ፡ የዓሣ፡ ወጥመድ፤ ቀጪን፡ ሚጎጠ፤ መንጠቆ። ይውሩ፡ መቃጥነ፡ መሥገርተ፡ እንቃር፡ ውስተ፡ ልጉት፡ ወያውፅእ፡ ዓሣ፡ (ኪዳ። ማቴ፲፯፡ ፳፯)።

**ቈጥዖ፤ ዖት፤ (ቈጥዐ፡ ይቈጥዕ፡ ይቈ ጥዕ። ዐረ፡ ቀዐጠ። ዕብ፡ ቁጥ፤ ናቀ፤ ጠላ)፤** መቈጣት፤ መወግሸት፡ ቍጡ፡ ብስጩ፡ መኾን፤ መጥ ላት፡ መሰልቸት። መጽሐፍ፡ ግን፡ በቈጥዐ፡ ፈንታ፡ ተቈጥዐ፡ ይላል፡ ተ፡ ያማርኛ፡ ነው። መዐዐን፡ ተመል ከት። ኢተቈጥዐ፡ ልቡ። ይትቋጣዕ፡ ዲበ፡ ሰብእ። ኢትትቈጣዕ፡ ነባሪከ። ለዘያበዝኅ፡ ነቢበ፡ ይትቈጥ ዖዎ፡ (ስቈ፪፡ ፳፪። ፈልክ፡ ፶፰። ሚራ፬፡ ፱። ፳፡ ፰)።

**ቍጡዕ፤ (ዓን፡ ዓት፡ ጥዕት)፤** የተቈጣ፤ ቍጡ፡ ብስጩ፤ ወፈፍተኛ። ብእሲ፡ ቍጡዕ፡ ለእመ፡ አንሥአኒ፡ ምዉተ፡ ኢትአመንዎ፡ (ፈልክ፡ ፻፵፭። ምሳ፳፯፡ ፱)።

**ቍጥዓ፤** ቍጣ፡ ብስጭት፤ ወፈፍታ፤ አብ ደት። ዐለተ፡ መዐት፡ ወቍጥዓ። መዐትኒ፡ ወቍ ጥዓ፡ ርኩሳን፡ እሙንቱ። በእንተ፡ መዐት፡ ወቍ ጥዓ፡ (ኩፋ፡ ፳፱። ሚራ፳፯፡ ፴። ፈ፡ መ፡ ፳፭)።

**ትቍጥዕት፤** ዝኒ፡ ከማሁ። ሰይጣን፡ ዝ ሙት፡ ወሰይጣን፡ ትቍጥዕት፡ (ፈልክ፡ ፲፫)።

**አስተቍጥዐ፤** አስቈጣ፤ አሳዘነ፤ አበሳጨ፤ አስወገሸ። ፈድፋደ፡ አስተቍጥዑኒ፡ ሕይወቶሙ። ነገሮሙ፡ ለአብዳን፡ ያስተቈጥዕ፡ (ሚራ፳፰፡ ፪። ፳፯፡ ፲፫)። ኹለተኛም፡ አቈጥዐ፡ ያቈጥዕ፤ አስተቈጥዐ፡ ያስ ተቈጥዕ፡ ያሰኛል።

**ቀጢፍ፤ ፎት፤ (ቀጠፈ፡ ይቀጥፍ፡ ይቅጥፍ። ዕብ፡ ቃጣፍ)፤** መቅጠፍ፤ መዘንጠፍ፡ መቀንዘፍ፤ መቅሬት፡ መቀንበት፤ መሸምጠጥ፤ መቀ ረጥ፤ መንቀል፡ መላሰስ፡ የቅጠል፡ የሥዊት። ንትፈ ማሕ፡ በዕፀዊሃ፡ ወአኮ፡ ዘንቀጥፍ፡ እምፍሬሃ፡ (ቅዳ፡ አት። ሕዝ፲፯፡ ፱)።

—፤ መዋሸት፡ ነገር፡ ማበላሸት፡ (በማርኛ)። ሌብነት ንም፡ ያሳያል።

**ቀጣፊ፤ (ፊት፡ ፍያን፡ ያት)፤** በቁሙ፤ የሚቀጥፍ፤ የሚዋሽ፤ ዋሾ፤ ሌባ። ላዩ፡ ጣፊ፡ ውስጡ፡ ቀጣፊ፡ እንዲሉ።

**ተቀጥፈ፤** ተቀጠፈ፤ ተቀጨ፤ በጭር፡ ቀረ፤ አስዐይሚው፡ ሞተ፤ ተቀሠፈ።

**ቅጡፍ፤ (ፋን፡ ፋት፡ ጥፍት)፤** የተቀ ጠፈ፤ የተዘነጠፈ፤ የተቈረጠ፡ የተቀጨ።

**ቅጥፈት፤** በቁሙ፤ መቅጠፍ፤ መቀጠፍ፤ አ ቀጣጠፍ፤ ቀጠፋ፤ ውሸት፡ ኵሸት።

(ጥጣ) **ቅጣፍ፤ (ፋት። ዐረብ)፤** ቅጣፊ፤ ዝን ጣፊ፤ ቍራጭ፤ ብጣሽ፤ ዘላ፡ ዘለላ፤ ዐጽቅ፡ ሙሽራ። ለቅኒም፡ ይኾናል፤ ቀጠፋ፡ ቅኔ፡ እንዲሉ።

**ቀጥቅጦ፤ ጦት፤ (ቀጥቀጠ፡ ይቀጠ ቅጥ፡ ይቀጥቅጥ። ዕብ፡ ቃጥቄጥ)፤** መቀጥ ቀጥ፤ መጨፍለቅ፤ መውገጥ፡ ማድቀቅ፤ መላልሶ፡ መም ታት፤ መሰባበር፤ ማንከት፤ ማጥፋት። ሥሩና፡ ምንጩ፡

ቀጢጥ ፡ ቀጠ ፡ ቈጠጠ ፡ ነው ። ቀጥቅጥ ፡ መዝራዕቶ ። በመፍጽሐ ፡ ንጹን ፡ ዐፅመ ፡ እገሪሁ ፡ ቀጥቀጡ ። ቀጥቅጦ ፡ ለፀራዊ ። እግዚ ፡ ይቀጠቅጥ ፡ ጸብአ ። ወቀጥቀጦሙ ፡ እግዚ ፡ ዐቢየ ፡ ቅጥቃጤ ። ንቀጥቅጦ ፡ እምድረ ፡ ሕያዋን ፡ (መገ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ነሐ፳፰ ። ሚራ ፴፪ ፡ ፱ ። ዘፀ፲፭ ፡ ፫ ። ኢያ፲ ፡ ፲ ። ኤር፲፭ ፡ ፲፱) ።

**ቀጥቃጢ** ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት) ፤ የሚቀጠቅጥ ፤ ቀጥቃጭ ፡ አንጥረኛ ።

**ተቀጥቀጠ** ፤ ተቀጠቀጠ ፤ ደቀቀ ፤ ንክት ፤ ተሰበረ ፡ ተመታ ፡ ተደበደበ ። መሥንርትስ ፡ ተቀጥቀጠት ። ይትቀጠቀጥ ፡ ከመ ፡ ዕፀ ፡ ብንኡብንኡ ። አመኒ ፡ በንጹን ፡ ንጹን ፡ ይትቀጠቀጥ ፤ እሳት ፡ ዘየመውቆ ፡ እምተቀጥቅጦ ፡ ኢያመሥጥ ፡ (መገ ፡ ፶፳፫ ። ኢዮ፳፱ ፡ ፳ ። ቅኔ) ።

**ቅጥቁጥ** ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ቅጥ) ፤ የተቀጠቀጠ ፤ የደቀቀ ፡ ቅጥቅጥ ፤ ደቃቅ ፤ ያዘን ፡ የተከዘ ። በትረ ፡ ብርዕ ፡ ቅጥቁጥ ። ዘያነሥእ ፡ ለውዱቅ ፡ ወይፌውሶ ፡ ለቅጥቁጥ ። ቅጥቁጠ ፡ ልቡ ። ቅጥቁጣንኪ ፡ (ኢሳ፴፮ ፡ ፮ ። ቀሌ ። አፈ ፡ ተ፴፩ ። ሶፎ፫ ፡ ፲፰) ።

**ቅጥቃጤ** ፤ ቢቁመ ፤ መቀጥቀጥ ፤ (ጥቀ) መቀጥቀጥ ፤ አቀጣቀጥ ፤ ቅጥቀጣ ፤ ስብራት ፤ ሐዘን ፤ ትካዜ ። ቅጥቃጤ ፡ ዳሕብ ። ቅጥቃጤ ፡ ነፍስ ። ቅጥቃጤ ፡ ልብ ፡ (ኢሳ፴ ፡ ፲፱ ። ፳፭ ፡ ፲፱ ። ዮሴፍ) ።

**አንቀጥቀጠ** ፤ አንቀጠቀጠ ፤ ተንቀጠቀጠ ፤ ተንዘፈዘፈ ፤ የደዌ ፡ የብርድ ፡ የፍርሀት ። ሰጥፍ ፡ ሰጥፍ ፡ አለ ፤ ተብረከረከ ፤ የድካም ። ያንቀጠቅጥ ፡ በእንተ ፡ ልፃላሜ ፡ እገሪሁ ፡ (ማር ፡ ደሎ፯ ፡ ፪) ።

**አንቀጥቃጢ** ፤ የሚያንቀጠቅጥ ፤ የሚንቀጠቀጥ ፤ አንቀጥቃጭ ። የዜማ ፡ ምልክት ።

**ንቅጥቁጥ** ፤ የሚንቀጠቀጥ ፤ ተንቀጥቃጭ ፤ ቀጥቃጣ ፤ እንቅጥቅጣም ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**ነቀጥቃጥ** ፤ በሽታ ፤ እንቅጥቅጥ ፤ መንዘፍዘፍ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ መንጠርጠር ። አዝልፎ ፡ ስካር ፡ ያመጽእ ፡ ነቀጥቃጠ ፡ ወጥፍአተ ፡ ልብ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶ ። ገድ ፡ አዳ) ።

**ቅጥራን** ፤ (ዐረ ፡ ቀጥራን) ፤ በቁሙ ፤ የሙጫ ፡ ቅመም ፤ ከዛፍ ፡ የሚገኝ ፡ የሚወጣ ፤ እንደ ፡ ዝፍት ፡ የሚነድ ፡ የሚቃጠል ። አፍልሕዎ ፡ ውስተ ፡ ጻሕል ፡ በዝፍት ፡ ወበቅጥራን ። ቃር ፡ ወፒሳ ፡ ወተይ ፡ ወቅጥራን ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳፯ ። ሐም፳) ።

**ቀጠራቅጢን** ፤ (ጽር ፡ ካታራክቴስ) ፤ የባሕር ፡ ወፍ ፤ እንደ ፡ ዝይ ፡ እንደ ፡ ሶረን ፡ ያለ ። ባለ ብሉዮች ፡ ግን ፡ ድንቢጥ ፡ ይሉታል ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፲፯ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፲፯) ።

**ቅጡሮት** ፤ (ዕብራ) ፤ ጢሳሞች ፤ ጠቀራሞች ፤ ጢስና ፡ ጠቀራ ፡ ያለባቸው ፡ ቤቶች ። (ሕዝ፵፮ ፡ ፳፪) ።

**ቀዩእ** ፤ ኦት ፤ (ቂአ ፡ ይቀይእ ፡ ይቂእ ። ዕብ ፡ ቃአ ። ዐረ ፡ ቃአ) ፤ ቂቅ ፡ ማለት ፡ ማስታወክ ፤ ማስመለስ ፤ መትፋት ፡ መቀርሸት ፤ ባፍ ፡ የገባውን ፡ መልሶ ፡ ባፍ ፡ ማውጣት ፤ የሰው ፡ ነገር ፡ ትምርት ፡ ምክር ፡ አለመቀበል ። ብላዕ ፡ በዐቅም ፡ ከመ ፡ ኢትቂእ ። ቂአ ፡ እምአፉሁ ፡ ደመ ፡ ብዙኀ ። ቂአከ ፡ ሕምዘ ፡ እምአፉከ ፡ ላዕለ ፡ ሔዋን ። እምከመ ፡ ሰምዐ ፡ ይቀይአ ፡ ወያገብአ ፡ ድኅረ ፡ ዘባኑ ፡ (ምሳ፳፭ ፡ ፲፯ ። ዮሴፍ ። መቃ ። ሚራ፳፬ ፡ ፲፭) ።

**ቀያኢ** ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤ የሚተፋ ፡ ትፋታም ፤ ቅርሻታም ።

**ቅያእ** ፤ ቂቅታ ፡ ምላሽ ፤ ትፋት ፤ ቅርሻት ። ከልብ ፡ ይገብእ ፡ ዲበ ፡ ቅያኡ ፡ (ምሳ፳፮ ፡ ፲፩) ።

**አቂአ** ፤ አስተፋ ። አቀይአ ፡ እምአፉሃ ፡ ዘውኅጠት ፡ (ኤር፳፰ ፡ ፵፬) ።

**ተቀይአ** ፤ ተተፋ ፤ ወጣ ፤ ተለየ ፤ ተመለሰ ። የተንቅበ ፡ ፍቺ ፡ መለየት ፡ መውጣት ፡ ብለ ፡ ኾነ ፤ በተንቅበ ፡ ፈንታ ፡ ተቂአ ፡ ይላል ፤ ምስጢሩ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ሕዝ፳፫ ፡ ፲፰) ።

**ቀዩሕ** ፤ ሖት ፤ (ቈሐ ፡ ይቀይሕ ፡ ይቂሕ ። ዕብ ፡ አዳም ፡ የኤዳም) ፤ መቅላት ፤ ቀይ ፡ መኾን ፤ ደም ፡ መምሰል ። ለምንት ፡ ቈሐ ፡ አልባሲከ ። ቈሐ ፡ ከመ ፡ ደም ፡ ውእቱ ፡ ማይ ። ይቀይሕ ፡ እምጽጌ ፡ ረዳ ፡ (ኢሳ፷ ፡ ፲፰ ። ፫ነ ፡ ፳ ። ፱ነገ ፡ ፫ ፡ ፳፪ ። ሔኖ) ።

(ጥዩ) **ቀዩሕ** ፤ **ቀይሕ** ፤ (ሕት ፡ ሓን ፡ ሓት ፡ ያሕ) ፤ ቀይ ፤ እሳት ፡ የሚመስል ። አርዌ ፡ ቀይሕ ። ከመ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ ቀይሕት ። ዕጐልት ፡ ቀያሕ ። አፍራስ ፡ ቀይሓን ። ሕብራት ፡ ቀይሓት ፡ (ራእ፲፯ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ሠኔ፭ ። ዘኍ፲፱ ፡ ፪ ። ዘካ፩ ፡ ፰ ። ፈላስ) ።

**ቂሐት** ፤ መቅላት ፤ አቀላል ፤ ቅላት ፤ ቀይነት ። እንበይነ ፡ ቂሐተ ፡ ደሞሙ ። ቂሐተ ፡ ተምር ፡ ወጽዕዳዌ ፡ ፀምር ፡ ዘእምፍጥረቶሙ ፡ ውእቱ ፡ ወአከ ፡ ዘተሣረዩ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። አፈ ፡ ተ፲፪) ።

**ቅያሔ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ይሰወጥ ፡ ውስተ ፡ ገጽየ ፡ እንተ ፡ ገጽከ ፡ ቅያሔ ፡ (ደራሲ) ።

**አቅየሐይሐ** ፤ (የቂሐና ፡ የአቂሐ ፡ ድርብ) ፤ ቀላ ፤ ተቅላላ ፤ ቀያቀይ ፡ ኾነ ፤ ወደ ፡ ቀይነት ፡ ተለወጠ ። ያቅየሐይሕ ፡ በማይ ። ሕብር ፡ እንተ ፡ ታቅየሐይሕ ፡ (ማቴ፲፮ ፡ ፪ ። ዘሌ፲፫ ፡ ፵፱ ፡ ፵፱) ።

—፤ አቀላ ፤ አቅላላ ፤ ቀይ ፡ ቀያይ ፡ ቀያቀይ ፡ አደረገ ፤ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ቀባ ። አቅየሐይሐ ፡ ሕብሮ ፡ (ጥበ፲፫ ፡ ፲፬) ።

**ቀያሕይት** ፤ (ዕብ ፡ አዳምዳሚት) ፤ ቀያቀይ ፤ ቀያቴ ፤ ዳማ ፤ ጥቂት ፡ ቀይ ፤ ፈገግ ፡ ያሉ ፤ በጣም ፡ ያልፈኩ ፡ ያልፈነዱ ፡ የለምጽ ፡ አበባ ፤ ቡቃያ ፡ (ዘሌ፲፫ ፡ ፵፱ ፡ ፵፱ ። ፲፬ ፡ ፴፯) ።

**ቀይጡን** ፡ (ዐረብ) ፤ ጓዳ ፤ ጐድጓዳ ፤ ሰግዳዳ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ክፍል ፤ የዕቃ ፡ ማኖሪያ ፡

መሰመሪያ ፤ የቁም ፡ ማጥን ። **ቀይጡኒ ፡ አውታን ፡ ዘወ እቱ ፡ ብሂል ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡** (አቡሻ ፡ ፳) ።

(ጥ) **ቀይሞ ፤ ሞት ፤ (ቀየመ ፡ ይቄይም ፡ ይቀይም ። ዕብ ፡ ናቃም ። ሱር ፡ ንቃም ። ዐረ ፡ ንቀመ)** ፤ መቀየም ፤ መበቀል ፤ ቂም ፡ በቀል ፡ መያዝ ፤ ክፉ ፡ ማሰብ ፡ መመኘት ፤ ለክፉ ፡ የክፉቱን ፡ ዋጋ ፡ ለመመለስ ፡ ማድባት ፡ ማሸመቅ ፤ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ መፈለግ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በቀየመ ፡ ፈንታ ፡ ተቀየመ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ፤ ተ ፡ ያማርኛ ፡ እንጂ ፡ የግእዝ ፡ አይደለም ። **ቂመኑ ፡ ትትቄየማኒ ። ኢትትቀየም ፡ ቢጸከ ። ተቀደሚ ፡ ወመፍቀሬ ፡ ንዋይ ። ኢኮኑ ፡ ከመ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ፡ ዘይትቄየም ፡** (ዮኤ ፫ ፡ ፬ ። ሢራ ፳፰ ፡ ፯ ። ማር ፡ ይ፡ም ፲ ፡ ፲፫ ። ዮ ዲ ፳ ፡ ፲፰) ። በቀለን ፡ ተመልከት ።

**ቀያሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት)** ፤ የሚቀየም ፤ ተቀያሚ ፤ ቂመኛ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**ቅያሜ** ፤ መቀየም ፤ አቀያየም ፤ ቅየማ ፤ ቂመኛነት ። **ፍቅርሰ ፡ ኅጥአተ ፡ ሚን ፡ ወቅያሜ ፡** (አዋል) ።

**ቂም** ፤ በቁሙ ፤ ክፉ ፡ ሐሳብ ፤ የልብ ፡ ቍስል ። ቂሙን ፡ ቀረፈብኝ ፡ እንዲሉ ። **አልቦ ፡ ዘየአኪ ፡ እምቂመ ፡ ጸላእት ። ቂም ፡ ወቅንአት ። ኵን ፡ ጻድቀ ፡ ወመሓሬ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽልሑት ፡ ወቂም ፡** (ሢራ ፳፭ ፡ ፲፭ ። ቀሌ ። ዲድ ፡ ፯) ።

**አስተቀየመ** ፤ አስቀየመ ፤ አሳዘነ ፤ ክፉ ፡ አሳሰበ ።

**መስተቀይም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት)** ፤ የሚቀየም ፤ የሚያስቀይም ፤ ተቀያሚ ፡ አስቀያሚ ፤ አሳዛኝ ። **መስተቀይም ፡ ወመዐትም ። ኵኑ ፡ ኄራነ ፡ ወ አኮ ፡ መስተቀይማነ ፡** (ቀኖ ፡ ኒቅ ። ማንዘ) ።

**ተቀየመ** ፤ ቂም ፡ ተያዘበት ፤ ለክፉ ፡ ታሰበ ፤ ተመደበ ።

**ቄሣር ፤ ቂሣርያ ፤—የሰው ፡ ያገር ፡ ስም ፤—ቄሳር ።**

**ቄዐ ፤—ተፋ ፡ ቀረሸ ፤—ቀዩእ ፡ ቄአ ።**

**ቄፋዝ ፤ (ጽር ፡ ኬፋዝ ። ዕብ ፡ ፋዝ)** ፤ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የኡፋዝ ፡ ወርቅ ፤ ኡፋዝ ፡ ከሚባል ፡ ምድር ፡ የሚመጣ ። ፎዝንና ፡ ኡፌዝን ፡ ተመልከት ። **ርእሱ ፡ ወርቀ ፡ ቄፋዝ ፡** (ማሕ ፭ ፡ ፲፩) ።

**ቍይጽ ፤ ቍጽ ፤ (ሱር ፡ ሹቃ ። ዕብ ፡ ሾቀ ። ዐረ ፡ ሳቅ)** ፤ ቋንጃ ፤ ከጕልበት ፡ እስከ ፡ ሙሐ ዶት ፡ እስከ ፡ ታፋ ፡ ያለው ፡ ክፍል ። **ወሰበሩ ፡ ቍይጾ ፡ ለቀዳማዊ ፡** (ዮሐ ፲፱ ፡ ፴፪) ።

**ቍየጽ ፡ አቍያጽ** ፤ ቋንጃች ። **ቍየጺሁ ፡ አዕማድ ። ዘበጦ ፡ ኅዐሰ ፡ ቍየጸ ። እልባሰ ፡ አቍያጽ ። ቀፈጽኪ ፡ አቍያጽኪ ፡** (ማሕ ፭ ፡ ፲፭ ። ዮሴፍ ። ዳን ፫ ፡ ፳፩ ። ሕዝ ፲፯ ፡ ፳፭) ።

**መቃይጽ** ፤ የሎቃይ ፡ መጣሪያ ፤ መንቈር ፡ ዘንጅር ፡ የቋን ፡ እግር ፡ ብረት ። **ለገብር ፡ እኩይ ፡ ሰውጥ ፡ ወመቃይጽ ፡** (ሢራ ፴ ፡ ፴፭) ።

**ቃይጽ ፤ (ዕብራ)** ፤ በጋ ፤ ወርን ፡ ማእረር ፤ የመቀት ፡ ወራት ።

**ቄቅሕ ፤ ቄቃሕ** ፤ ጥሩ ፡ ነገር ፤ እድፍ ፡ ጉድፍ ፤ ንፉኽ ፡ ጉሰባ ፡ የሌለው ፤ ልቅም ፤ ፍትግ ፡ ክክ ፤ ኅፀበ ፤ የተነፋ ፡ ደቄት ። **ቄቅሐ ፡ ሥርናይ ፡** (ዘዳ ፴፪ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፹፩ ። ዮሴፍ ። መቃ) ።

**ቄቅሐ** ፤ አጠሩ ፤ ጥሩ ፡ አደረገ ፤ ፀጠበ ፡ ፈተገ ፤ ለቀመ ፡ አበጠረ ፤ ከካ ፡ ነፋ ፤ የእክል ።

**ቄቅየ ፤ ዩት ፤ (ቄቀየ ፡ ይቄቂ)** ፤ መቀቀት ፡ መንቀብቀብ ፤ መሠሠት ፤ መንፈግ ፡ መቤስ ፤ መቈጠብ ፡ ገንዘብን ፡ አጥብቆ ፡ መያዝ ፡ መጨበጥ ። **ዘይቄቂ ፡ አውፅአ ፡ እምንዋዩ ፡ ለዘይደልዎ ፤ ይሁብ ፡ ምክዕቢተ ፡ በከንቱ ። ዘይቄቂ ፡ ለርእሱ ፡ ይዘግብ ፡ ለባዕድ ። ዘቦቱ ፡ ንዋይ ፡ ወይቄቂ ፡** (ፈላስ ። ትእ ፡ ጴጥ ። አፈ ፡ ተ፴፱) ።

**ቂቁይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ቅይት)** ፤ በቁሙ ፤ ቅቅታም ፤ ቀብቃባ ፤ ንፉግ ፡ ቢስ ፤ ጨባጭ ። **እንዘ ፡ ይዘክሩ ፡ መሓርያነ ፡ ወቂቁያነ ፡** (ስንክ ፡ መ፲፩፳) ።

**ቂቅዮት** ፤ መቀቀት ፤ መንፈግ ፤ ቅቅት ፡ ንፍገት ፤ ንፉግነት ፡ (ፈላስ) ።

**ቄር ፤ (ዕብ ፡ ቂር)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ። **ወይፄወዉ ፡ ቂረ ፤ ሕዝቦሙ ፡ ለሶርያ ። ወአፍለሶሙ ፡ ውስተ ፡ ቂር ፡** (ዓሞ ፩ ፡ ፭ ። ፬ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፱) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ቂረ ፡ ሕዝቦሙ ፡ ብለው ፡ ያነቡና ፡ ፍችውን ፡ ጎያላን ፡ መኳንንት ፡ ደብሎች ፡ ይሉታል ። ባለሊቃውንትም ፤ ቂርሎስ ፡ ብሂል ፡ ኀያል ፡ ይሉና ፡ ምስክር ፡ ይሆን ፡ ይጠቅሳሉ ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**ቀይስ ፤—ቄስ ፤—ቀሰሰ ።**

**ቀየሰ ፤ (ትግሬ ፡ ወዐረብ)** ፤ ለካ ፤ ሰፈረ ፡ ገመተ ።

**ቄሳር ፤ (ጽር ፡ ኬሳር)** ፤ ስመ ፡ ንጉሥ ፡ ፍችው ፡ ሠጣጤ ፡ ከርሥ ። እናቱ ፡ በምጥ ፡ ጊዜ ፡ ሙታ ፤ አዋላጆች ፡ ሆዷን ፡ ሠንጥቀው ፡ ስላወጡት ። **ሀቡ ፡ ዘቄሳር ፡ ለቄሳር ። ወፅአ ፡ ትእዛዝ ፡ እምኀበ ፡ ቄሳር ፡ ንጉሥ ። ኢክንከ ፡ ዐርኮ ፡ ለቄሳር ፡** (ቀሌ ። ሉቃ ፳ ፡ ፳፭ ። ፪ ፡ ፩ ። ዮሐ ፲፱ ፡ ፲፪) ።

**ቂሳርያ** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ ቂሳራዊት ፤ ሄሮድስ ፡ ስለ ፡ ቄሳር ፡ ክብር ፡ ከባሕር ፡ አጠገብ ፡ በፍልስጥኤም ፡ የሠራት ። ልጁ ፡ ፊልጶስም ፡ ከሔርሞን ፡ አጠገብ ፡ ሌላ ፡ ኹለተኛ ፡ ከተማ ፡ ሠርቶ ፡ ቂሳርያ ፡ ዘፊልጶስ ፡ አሰኝቷታል ፡ (ግብ ፲ ፡ ፩ ። ማር ፰ ፡ ፳፯) ።

**ቃል ፤—በቁሙ ፤—ቀዊል ፡ ቀወለ ።**

**ቀሊብ ፤ ቦት ፤ (ቀለበ ፡ ይቀልብ ፡ ይቅልብ ። ዐረብ)** ፤ መቅለብ ፡ እያንን ፡ እያነጠሩ ፡ መልቦ ፡ መያዝ ፡ መቅበል ፡ መገልበጥ ፡ ማናሰስ ፡ መክንበል ፡ ማሽንፍ ፡ ይል ፡ መንሣት ፡ በላይ ፡ መኸን ። ቃለጺን ፡ እይ ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። **ምንት ፡ የዐጽብ ፡**

እምዘይቀልብ ፡ ብዙኅ ፡ አስይፍተ ፡ (አፈ ፡ ተጸ፲) ። ቀለብ ፡ ማለት ፡ ከቀለበና ፡ ከቀለጸ ፡ ከ፪ቱ ፡ ወጥቷል ።

**ቀላቤ** ፤ መቅለብ ፤ አቀላለብ ፤ ቀለባ ፡ ቅልበሽ ፤ ኀላባዊነት ፤ ጕሕሉት ፡ ጽልሑት ፤ ቀዝ ፡ ፈዘዝ ። እፌኑ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ቀላቤ ፡ አፍ ፡ (ፋኖክ ፡ እየ) ።

**ቀልብ** ፤ ሐሳብ ፡ ምኞት ፤ ውበት ፡ ደም ፡ ግባት ፤ ባለሟልነት ፡ መወደድ ፡ መክበር ፡ አቦ ፡ አቦ ፡ መባል ። ቀልባም ፡ ቀልበ ፡ ቢስ ፡ እንዲሉ ።

**ቀሊድ** ፤ (ቀለደ ። ዐረብ) ፤ መቅዳት ፤ ማከማቸት ፤ የውሃ ። መቀለድ ፤ ቀልደኛ ፡ መኾን ። መቀንደብ ፤ ቅንድብን ፡ መብጣት ፡ መፍቃት ፤ ስሳይን ፤ በሽታ ።

**መቅለድ** ፤ (ብ ፡ መቃልድ) ፤ የውሃ ፡ ዕቃ ፤ መቅጃ ፤ መገልበጫ ፤ ስገን ፡ ስንና ፡ ብርት ፡ ዥስዥስት ። ነሥአ ፡ ማየ ፡ ወወደየ ፡ ውስተ ፡ መቅሊድ ፡ ወኀፀበ ፡ እግረ ፡ አርዳኢሁ ፡ (መዋሥ ። ዘፀ፳፱ ፡ ፮) ። ንብቲራን ፡ እይ ።

**ቀልድ** ፤ **ቀላድ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ። ቀላጅ ፡ ቀላድ ፡ ጣይ ፡ እንዲሉ ።

**ቀልደድ** ፤ ቅንድብ ፤ ሽፋል ፡ የዐይን ፡ ከንፈር ፡ ወይም ፡ ጕድጓዱ ፡ ሾሬው ፤ ብርንደው ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ኵኖ ፡ የመሳበት ። ዐይንኽ ፡ ይፍስስ ፡ እንዲሉ ። ቀልደደ ፡ ዐይን ፡ (አርጋ ፡ ፱) ።

**ቀሊው** ፤ ዎት ፤ (ቀለወ ፡ ይቀሉ ፡ ይቅሉ ። ዕብ ፡ ቃላህ ። ዐረ ፡ ቀላ) ፤ መቍላት ፤ ማመስ ፤ መጥበስ ፤ መለብለብ ፤ ማንኰት ። ቀሊወከ ፡ (መ ፡ ፈ) ። በቀለወ ፡ ፈንታ ፡ ቈለወ ፡ ይላል ፡ ቈ ፡ ያማርኛ ፤ ነው ።

**ተቀልወ** ፤ ተቈላ ፤ ተንደገደገ ። ተቀሎኩ ፡ ወተሀድየ ፡ አዕፅምትየ ። ትትቀሎ ፡ ነፍሱ ፡ ውስተ ፡ አፍቅሮ ፡ እግዚ ። ሶበ ፡ ሰብሰ ፡ ባሕታዊ ፡ አስኬማ ፡ ይነሥእ ፡ እምጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተቀልዎተ ፡ መንፈሳዊተ ፡ (ኢዮ፴ ፡ ፴ ። ፈልክ ፡ ፻፷ና ፡ ፸፱) ።

**ቅልው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሉት ፤ የተቈላ ፡ ቈሎ ፡ እንኩቶ ፡ ጥብስ ፡ (ዘሌ፪ ፡ ፲፬ ። ጸ፫ ፡ ፲፱) ።

**ቈላ** ፤ (ብ ፡ ቈላት) ፤ በቁሙ ፤ ሞቃት ፤ የሙቀት ፡ ቦታ ፤ ጕድጓዳ ፤ ሽለቆ ፤ ፀሓያም ፡ ሐሩራም ። ቈላ ፡ ዕሙቅ ። እስመ ፡ መካነ ፡ ብሔሩ ፡ ቈላ ፡ ውእቱ ። ቈላተ ፡ ብካይ ፡ (ሔኖ ። አዋል ። መዝ ፡ ፹፫) ።

**ቀላውትሞኖስ** ፤ (ጽር ፡ ክላፍትሞኖስ) ፤ ብካይ ፤ ልቅሶ ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፡ የቱት ፡ ዛፍች ፡ ይላል ፤ ቱት ፡ የሐር ፡ ዛፍ ፡ ነው ፡ (፪ሳሙ ፡ ፭ ፡ ፳፫) ። ቈላተ ፡ ብካይም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ባካ ፡ ብካኢም ፡ ዛፍ ። ብኪ ፡ ቤኪ ፡ ልቅሶ ፡ ይባላል ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተሳስቷል ።

**ቈልዘ** ፤ ዘት ፤ (ቈለዘ ፡ ይቈልዝ ፡ ይቈልዝ) ፤ መኰረጥ ፤ መቈጥቈጥ ፤ መጨፍጨፍ ፤ መመልመል ፡ (አርጋ ፡ ፰) ።

**መቍለዝ** ፤ መቈጥቈጫ ፤ ፋስ ፤ መጥረቢያ ። ሲበዝ ፤ መቋልገ ።

**ቍልዝ** ፤ (ዛት) ፤ ቍጥቋጦ ፤ ቍጥቋጭ ፤ ጭፍጫሬ ።

**ቍልዝም** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ ዘበሶርያ ። ሚልኪ ፡ ቍልዝማዊ ፡ (ስንክ) ።

**ቍልሕ** ፤ (ሓት) ፤ ጓ ፤ ጓሚያ ፤ ያበባ ፡ የጥጥ ፡ እንቡጥ ፤ ድብድብ ፡ እርጕዝ ፡ ገና ፡ ያልፈካ ፡ ያልፈነዳ ፤ ያበጠ ፡ የሞጠሞጠ ፡ ያጕመጕመ ፤ ወይም ፡ መፍካት ፡ መፈንዳት ፡ የዠመረ ፡ (መክ፲፪ ፡ ፭ ። አርጋ ፡ ፯) ።

—፤ ቍላ ፤ ቈለጥ ፡ ታችኛው ፡ ቅሉ ፤ እንጥልጥሉ ፤ ፍሬው ፡ ዕንቍላሉ ፤ የተባትነት ፡ ምልክት ። እስኪትን ፡ እይ ። ወዓዲ ፡ ይወርድ ፡ ዲበ ፡ እስኪት ፡ ወቍልሕ ፡ (አረጋ ፡ ድ፯) ።

**ቀልይ** ፤ ዮት ፤ (ቀለየ ፡ ይቀሊ ፡ ይቅሊ ። ቀለወ) ፤ መጥለቅ ፡ መጕድጕድ ፤ ዕሙቅ ፡ ጥልቅ ፡ መኾን ። ይቀሊ ፡ እምቀላየ ፡ ቀላያት ፡ ወይትሌዐል ፡ እመልዕልተ ፡ ሱዓሌ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

—፤ ጠልቆ ፡ ማወቅ ፤ መዝለፍ ፡ መገሠጽ ፤ መውቀሥ ፡ መክሰስ ፤ መፍረድ ፡ መመስከር ፤ የልብ ፡ የኅሊና ። ይቀልየከ ፡ ልብከ ። ሊተሰ ፡ ፈድፋደ ፡ ያሐዝነኒ ፡ ወያቴክዘኒ ፡ ወይቀልየኒ ፡ ልብየ ፡ (፪ነገ ፡ ፱ ፡ ፵፱ ። መቃ ፡ ገ ፲፱ ። ሮሜ፪ ፡ ፲፭ ። ሸዮሐ ፡ ፫ ፡ ፳፩) ።

**ቅሉይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሊት) ፤ የጠለቀ ፤ ጥልቅ ፡ ዕሙቅ ፡ (አርጋ) ።

**ቀላይ** ፤ (ያት) ፤ በቁሙ ፤ ጥልቅ ፤ ጠሊቅ ፤ ዕሙቅ ፤ የባሕር ፡ የፈለግ ። ቀላየ ፡ ባሕር ። ቀላያተ ፡ አፍላግ ። ቀላያተ ፡ ማያት ፡ (ኢሳ፶፩ ፡ ፲ ። ኢዮ፳፰ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፸፯) ።

**ቃሊ** ፤ (ትግሬ ፡ ወዐረብ) ፤ ውድ ፡ ክቡር ፤ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ የማይገኝ ፡ ዕቃ ፡ ጣቃ ።

**አቅለየ** ፤ አጠለቀ ፤ አስጠለቀ ፡ ጥልቅ ፡ አደረገ ፤ አስደረገ ። አስወደደ ፤ በውድ ፡ ሸጠ ።

**አቅሌለየ** ፤ ጠየቀ ፡ ቈፈረ ፤ አጥብቆ ፡ አጥልቆ ፡ መረመረ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ አበዛዘበ ፡ ይሉታል ። ኑዳይ ፡ ማእምር ፡ ያቅሌልዩ ፡ (ምሳ፳፰ ፡ ፲፩) ።

**ቀሊል** ፤ ሎት ፤ (ቀለ ፡ ይቀልል ፡ ይቅልል ። ዕብ ፡ ቃላል ። ሱር ፡ ቃል ። ዐረ ፡ ቀለ) ፤ መቅለል ፤ ማነስ ፤ ከሚዛን ፡ ከእንጻር ። ቈል ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። አሰሰ ፡ ዘኢይቀልል ፡ እምዝኩ ። ምንተ ፡ ይቀልል ፡ እምብሂል ። ትቀልል ፡ ሲኦል ፡ እምኔሃ ፡ (አፈ ፡ ተጸ፯ ። ማቴ፱ ፡ ፭ ። ሚራ፳፰ ፡ ፳፯) ። ቀልቀለን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

—፤ መፍጠን ፤ መቀልጠፍ ፤ ፈጣን ፡ ፈጭ ፡ መኾን ። ይቀሉ ፡ እምንስር ። ይቀልል ፡ ሩጸቶሙ ፡ እምነፋስ ። ኀሊና ፡ ይቀልል ፡ ወይሰርር ፡ እምዙሉ ፡ ክንፍ ፡ (፪ነገ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ። ቀሌ ። አፈ ፡ ተጸ፱) ። በቀለ ፡ ፈንታ ፡ ተቀ

ለስ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ይትቀሰሉ ፡ እምኀጢአቶሙ ። ይትቀሰሉ ፡ እምጻዕር ፡ (ሱቱ ፡ ዕዝ፮ ። ኪዳ) ።

**ቀሊል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ላል) ፤ በቁሙ ፤ የሚቀል ፤ ቀላል ፤ ክፉፍ ፤ ታናሽ ፡ ጥቂት ። ጾርየ ፡ ቀሊል ። ደሰዎ ፡ ወከነ ፡ ቀሊለ ፡ እምዝሉ ፡ ማያተ ፡ አፍራቅያ ። ቀሊልኑ ፡ በኀቤክሙ ፡ አስተፀብሶተ ፡ ሰብእ ፡ (ማቴ፲፩ ፡ ፴ ። ሥሉሳ ። ኢሳ፯ ፡ ፲፫) ።

—፤ ፈጣን ፤ ቀልጣፋ ፤ ቅልጥፍ ። ይመና ፡ ቀሊል ። እከ ፡ ለቀሊላን ፡ ረዊጽ ። ቀሊላት ፡ እገሪሁ ። ቀላለ ፡ ከነት ፡ ሕይወትየ ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፩ ። መክ፱ ፡ ፲፩ ። ፪ነገ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ። ኢዮ፺ ፡ ፳) ።

**ቅለት** ፤ በቁሙ ፤ መቅለል ፤ አቀላለል ፤ ቀላልነት ፤ ቅክለት ፤ ፍጥነት ።

**አቅለለ** ፤ አቀለለ ፤ አስቀለለ ፤ ከፈለ ፡ ቀነሰ ፡ አሳነሰ ፤ ቀላል ፡ አደረገ ። ከመ ፡ ያቅልል ፡ እዴሁ ፡ እምላዕሌክሙ ። አቅለሉ ፡ ሐመሮሙ ። ከመ ፡ ያቅልሉ ፡ ንስሓ ፡ ለእለ ፡ አበሱ ። አቅልል ፡ ለነ ፡ እምነ ፡ ግብርናት ። አቅለልኩ ፡ ዘንተ ፡ ምንዳቤ ፡ በእንተ ፡ ሥምረትከ ፡ (፩ነገ ፡ ፮ ፡ ፭ ። ዮና፩ ፡ ፭ ። ቀሌ ። ፫ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፬ ። ዮሴፍ) ።

—፤ አፈጠነ ፡ አቀላጠፈ ፤ ፈጣን ፡ አደረገ ። አቅለሉ ፡ ከነፊሆሙ ፡ (ቅዳ ። ሳታት) ።

—፤ ናቀ ፤ አቃለለ ፤ ሰደበ ፡ አዋረደ ፤ አኰሰሰ ። ውሉድ ፡ እለ ፡ ያቀልሉ ፡ አበዊሆሙ ። ዘያቀልል ፡ ማኅበረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ዘመሀረ ፡ አቅልሎ ፡ ቤተ ፡ ክር ፡ (ቀኖ ፡ ማኅማ ፡ ፳ና ፡ ፲፯ ። ኒቅ ፡ ፳፱) ። በአቅለለ ፡ ፈንታ ፡ አስተቃለለ ፡ ይላል ፤ አድራጊውን ፡ ባደራራጊ ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ያስተቃልሉ ፡ ተዋሕሶቶ ። ታስተቃልልኑ ፡ ዘንተ ፡ ኀጢአቶሙ ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘያስተቃልል ፡ ምሥዋዐ ። ኢታስተቃልሎ ፡ ለጸላኢከ ፡ ወበዝንቱ ፡ ትከውን ፡ ምዉአ ፡ ሎቱ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯ ። ሕዝ፳ ፡ ፲፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፱ ፡ ፱ ። ፈላስ) ። የአቅለለ ፡ ፍች ፡ አቃለለ ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ማእዙን ፡ እንዳማርኛው ፡ አስኪይታል ፤ አስተቅለለ ፡ ቢል ፡ ግን ፡ አድራጊ ፡ ኹኖ ፡ በአቅለለ ፡ መንገድ ፡ ይኼዳል ።

**ቀሊም** ፤ ሞት ፤ (ቀለመ ፡ ይቀልም ፡ ይቅልም) ፤ መቅለም ፡ ማቅለም ፡ መጣፍ ፤ ማሳደፍ ፡ መበከል ፤ ከቀለም ፡ ማግባት ፡ መንከር ፤ ማለል ፡ ማግዘፍ ፤ የቃል ፡ የልብስ ። ሀበነ ፡ ከመ ፡ ንጽሐፍ ፡ ወጸግወነ ፡ ከመ ፡ ንቅልም ፡ (አረጋ ፡ ድጓ) ።

**ቀላሚ** ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤ የሚቀልም ፤ የሚያቀልም ፤ ጣፊ ፡ ከታቢ ፤ ቀለም ፡ አግቢ ።

**ተቀልመ** ፤ ተቀለመ ፤ ተጣፈ ፤ ከቀለም ፡ ገባ ፤ አደፈ ፡ ተበከለ ፤ ተዥለፈለፈ ።

**ቅሉም** ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ልምት) ፤ የተቀለመ ፤ የተጣፈ ፤ ያደፈ ፡ እድፉም ።

**ቅልመት** ፤ ማደፍ ፤ ማሳደፍ ፡ አስተዳደፍ ፤ እድፍ ፡ እድፈት ፡ እድፋምነት ። ኀፀብ ፡ ዘሎ ፡ ቅልመታ ፡ (አ፡፡ጋ) ።

**ቀለም** ፤ (ማት ፤ አቅላም) ፤ በቁሙ ፤ ሕብር ፤ ፈሳሽ ፡ ዐይነት ፤ መጣፊያ ፡ ማቅለሚያ ። ጽሑፍ ፡ በቀይሕ ፡ ቀለም ፡ ወበጸሊም ፡ ቀለም ። እንበለ ፡ ቀለም ። ጸሐፍ ፡ ስምየ ፡ በረቀ ፡ መርዓ ፤ ገቢረከ ፡ ፋሲሊደስ ፡ ለዘኮነኒኩ ፡ ኃጥአ ፤ ደመከ ፡ ቀለመ ፡ ወዐፅመከ ፡ ብርዐ ፡ (አቡሻ ፡ ፵፮ ። ስንክ ፡ ታኅሣ፳፫ ። ድጓ) ።

**ቀለም** ፤ (ዐረብ ። ጽር ፡ ከላሞስ ። ዕብ ፡ ቃኔ) ፤ ብርዕ ፤ የቀለም ፡ መንከሪያ ፤ መጥለቂያ ፡ ከዕፅ ፡ ከኀጺን ፡ የሚሠራ ፤ ወይም ፡ ጸሓፊው ፡ የሚቀርጠው ፡ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ መቃ ፡ ሸንበቆ ፡ ቀስተንጃ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ቀለመ ፡ ኀጺን ። ከመ ፡ ቀለመ ፡ ጸሓፊ ። በማየ ፡ ሕመት ፡ ወበቀለም ፡ (ኤር፲፯ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፵፬ ። ፫ዮሐ ፡ ፲፫) ።

**ቀለም** ፤ (ዕብ ፡ ቁሜት) ፤ የቀለም ፡ ቀንድ ፤ ቢልቃጥ ፤ መውዳየ ፡ ቀለም ። ቀለመ ፡ ጸሓፊ ፡ በሐቌሁ ፡ (ሕዝ፱ ፡ ፪) ።

—፤ መልክእ ፡ ፊደል ፤ የፊደል ፡ ቅንጣት ፤ አንዳንዱ ፡ ኅርመት ። ማእዝ ፡ ቀለም ፡ ሳድስ ፡ ቀለም ፤ ሰባት ፡ ቀለማት ፡ እንዲሉ ፡ (ባላገባቦች) ።

—፤ ትምርት ፤ ዕውቀት ፤ ከመጽሐፍ ፡ ከመምር ፡ የሚገኝ ። (መምሽ ፤ የተማሪ ፡ እናት ፤ ልጇን ፡ ዳግም ፡ ማሬኝ ፡ ቱ ፡ ስላቃጠለባት) ፤ ይማርልኝ ፡ ብዬ ፡ በጌ ፡ ምድር ፡ ሰድጄ ፤ ቀለም ፡ ገባሙ ፡ አሉ ፡ እሳት ፡ ኾነ ፡ ልጄ ። (የተማሪ ፡ እናት ፤ ሊቅ ፡ ወንድሜ ፡ መሞቱ ፡ ሲቀበር) ፤ ዐፈር ፡ መልሱ ፡ እንጂ ፡ ደንጊያ ፡ ለምኖቹኹ ፤ የቀለም ፡ ቀንድ ፡ ነው ፡ ትሰብሩታላችኹ ።

**ቀለምጤዳ** ፤ (ጽር ፡ ክሊማቲዳ) ፤ የወይን ፡ ሰንሰለት ፤ ዐጽቁ ፡ ሐረጉ ፡ ተቈርጦ ፡ የወደቀውና ፡ የደረቀው ፡ ጭራሮው ፡ ጭራንሮው ። ባለብሶዎች ፡ ግን ፡ ቍልቋል ፡ ይሉታል ፡ (ዳንኤ ፡ ፳፪ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፳) ። ቀለምጤዳ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አቅላሚዶን ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ቀለምጺጽ** ፤ (ጺጸ ፡ ቀለም) ፤ ጺጽ ፡ ከጻጹት ፡ መጥቷል ። የእሳት ፡ ብራሪ ፤ ፍንጣሪ ። የምጣድ ፡ ቂጥ ፡ እሳት ፤ ብልጭልጭታ ። ጺጽ ፡ እሳቱ ፡ ብልጭታው ፡ ጣጣቴው ፤ ቀለም ፡ ጥላቱ ፡ ሕመቱ ። ቃለ ፡ ቀለምጺጽ ፡ (ጥበ፳ ፡ ፳ ። ፫ ፡ ፯ ። ፲፩ ፡ ፲፱) ።

**ቀለምሲስ** ፤ ከፈለ ፡ ስም ፤ አቡቀለምሲስ ።

**ቅልንብትራ** ፤ (ጽር ፡ ክሊምቢትራ) ፤ ዥፋ ፤ ምዕቃል ፤ መታጠቢያ ፤ መጠመቂያ ፡ (ዮሐ፭ ፡ ፪) ።

**ቂላኖስ** ፤ (ጽር ፡ ፊሎኒስ ። ዐረ ፡ ፊቂ) ፤ ክቡር ፡ ልብስ ፤ በላይ ፡ የሚደረብ ። ፊሎንን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ዐረቦች ፡ ፈን ፡ ኹለተኛ ፡ ንቍጣ ፡ ጨምረው ፡ ቀ ፡ ይሉታልና ፤ ስለዚህ ፡ ቂላኖስ ፡ ይላል ። ኹለተኛም ፡ በቂላኖስ ፡ ፈንታ ፡ ሄላንሳን ፡ ይላል ። ለፍሐ ፡ ቂላኖሰ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤ ወወረደት ፡ ጠማር ፡ ማእከለ ፡ ሄላንሳን ፡ (ጠማ ፡ ሃይ ፡

አበ)። መምህራን ፡ ግን ፡ ሄላንሳንን ፡ ከበር ፡ ምንጣፍ ፡ ሰርፍ ፡ ወላንሳ ፡ ይሉታል ።

**ቀለንቶን ፤ (ጽር ፡ ክሌንዶ)** ፤ መባቻ ፡ የወር ፡ መዠመሪያ ፤ ሠርቀ ፡ ወርኅ ። ወበወርኀ ፡ ሮሜ ፡ ቅድመ ፡ ዕሥራ ፡ ወሰመንቱ ፡ ቀለንቶን ፡ (ተረ ፡ ቄር ፳፩) ።

**ቀሊዕ ፤ ዖት ፤ (ቀልዐ ፡ ይቀልዕ ፡ ይቅላዕ ። ዐረ ፡ ቀለዐ ። ዕብ ፡ ቃላዕ)** ፤ መቅላት ፡ መክላት ፤ መግለጥ ፡ መግፈፍ ፤ ማውለቅ ፡ የልብስ ፡ የመጋረጃ ፡ የመጠፍ ። ኦ ፡ ብእሲቶ ፡ ለምንት ፡ ትቀልዒ ፡ ግልባቤ ፡ ርእስኪ ፡ እንዘ ፡ ትሥሕቂ ። አዘዘ ፡ ይቅልዑ ፡ ግልባቤ ፡ ገጾ ። አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይቅላዕ ፡ ልብሶ ። ኀፍረት ፡ ቀሊዐ ፡ መጽሐፍ ፡ ለዘኢየአምር ፡ ሆህያቲ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፰ ። ስንክ ፡ ኅዳ፲፯ ። ታኅ፲ ። መጽ ፡ ምስ) ።

—፤ መምታት ፡ መልጋት ፡ ማጠንጋት ፤ ስመወርወር ፡ የኳስ ፡ የጥንግ ።

—፤ ማወንጨፍ ፡ መተኰስ ፤ አርቆ ፡ መጣል ፡ የደንጊያ ፡ ያረር ።

**ቀላዒ ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት)** ፤ የሚቀላ ፤ የሚያወልቅ ፡ ገላጭ ፡ ገፋፊ ። እግዚ ፡ ሰብርሃነ ፡ ልብየ ፡ ቀላዒ ፡ ግኀ ፡ (ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**መቅልዕ ፤ (ብ ፡ መቃልዕ)** ፤ በይል ፡ ነጕድ ፤ ወንጭፍ ፤ ነፍጥ ፡ መድፍ ፡ ዱላ ፡ መንደ ፤ የጥንግ ፡ መልጊያ ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**ተቀልዐ** ፤ ተቀላ ፤ ተገለጠ ። ይትቀላዕ ፡ መንጦላዕት ፡ ዘቅድመ ፡ ገጹ ፡ (ቅዳ ፡ ያዕ) ።

**ቅሉዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ልዕት)** ፤ የተቀላ ፤ የተገለጠ ፤ ግልጥ ። ብእሲት ፡ ኢትኅድግ ፡ ሥዕርታ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ቅሉዐ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፩) ።

**ቅልዓ ፤ (ዐረ ፡ ቀልዐት)** ፤ ዕርድ ፡ ምሽግ ፤ መታኰሻ ፤ መወራወሪያ ፡ (ዮ ፡ ቤፍ) ።

**ቍልዒ ፤ (ዕብ ፡ ቊላእ ፤ ቀላል ፤ ቃናሽ ። ናዐር)** ፤ ልደ ፡ ቤት ፤ ብላቴና ፤ የቤት ፡ ልጅ ፡ ከቤት ፡ ሰብ ፡ የተወለደ ፤ ታናሽ ፡ ደቦል ፡ ስጋ ፡ መጣት ፤ አሽከር ፡ ሎሌ ፡ አገልጋይ ፤ ሲጠሩት ፡ አቤት ፡ ሲልኩት ፡ ወዴት ፡ የሚል ፡ ፈጣን ፡ ቀልጣፋ ፤ እግረ ፡ ቀላል ። ወሀበ ፡ ለቍልዔሁ ፡ ወእፍጠነ ፡ ገቢሮቶ ። ረድ ፡ አንተ ፡ ወቍልዔከ ። ናሁ ፡ ቍልዔየ ፡ ዘኀረይኩ ። ወተወክፎ ፡ ለእስራኤል ፡ ቍልዔሁ ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፯ ። መሳ፯ ፡ ፲ ። ኢሳ፵፪ ፡ ፩ ። ሉቃ፩ ፡ ፶፬) ።

**ቊላዕይ ፡ ው** ፤ ብላቴኖች ፡ የቤት ፡ ልጆች ። መጠፍ ፡ ግን ፡ ቍልዒያት ፡ ይላል ፡ (ዮ ፡ ቤፍ) ።


**ቍልዒት ፤ (ብ ፡ ቍልዕያት)** ፤ ገረድ ፤ ቤት ፡ አሽከር ። አመትከ ፡ ወቍልዔትከ ። እወፅእ ፡ አነ ፡ ምስለ ፡ ቍልዔትየ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፭ ፡ ኅዳ ። ዮዲ ፡ ፀ፫ ። ፲ ፡ ፲) ።

**ቍልዕውና** ፤ ብላቴንነት ፤ የቤት ፡ ልጅነት ። ባለሟልነት ፡ (አርጋ ፡ ፯) ።

**ቈሊፍ ፤ ፎት ፤ (ቈለፈ ፡ ይቄልፍ ፡ ይቈልፍ ። ሱር ፡ ቅላፍ ። ዕብ ፡ ቃላፍ ። ዐረ ፡ ቀለፈ)** ፤ መቅረፍ ፤ መላጥ ፤ መምለጥ ፤ መሸልቀቅ ፤ መግፈፍ ፤ ማሸት ፤ መፈልፈል ፤ የውስጡን ፡ ማውጣት ።

—፤ መቈለፍ ፤ መዝጋት ፤ መግጠም ፡ ማተም ፡ ማንቀላፋት ።

**ቍልፍ ፤ (ፋት)** ፤ በቍመ ፡ መቈለፊያ ፡ ባለመክፈቻ ። እስ ፡ ያርኅዉ ፡ ቍልፈ ፡ ጸኒሖሙ ፡ ጊዜ ፡ የሐውር ፡ በዓለ ፡ ቤት ፡ ቀቲሮ ፡ ወነሚኖ ። እስ ፡ ይሰብሩ ፡ ቍልፋተ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱) ።



ቍልፍ ፡

**ተቈልፈ** ፤ ተቈለፈ ፤ በቍልፍ ፡ ተዘጋ ።

**ቈላፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት)** ፤ የተቈለፈ ፡ ቍልፍ ፡ ቈላፋ ። ያልተገዘረ ፡ ሸፍን ፡ ቍልፈታም ፤ ቈለፈታም ። ወዘሰ ፡ ቈላፍ ፡ ኢይብላዕ ፡ እምኔሁ ። ዕልገተ ፡ ቈላፋን ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፵፰ ። ፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፭) ።

**ቍልፈት ፤ (ፋት)** ፤ መቈለፍ ፤ (ጥቈ) መቈለፍ ፡ አቈላለፍ ፤ ቍለፋ ፤ ቍልፍንት ። ቍልፋት ፡ ቈለፋት ፡ ሸንኰፍ ፤ ግልባጭ ፡ ነፍስት ፤ የመሌሊት ፡ ሽፋን ። ቍልፈተ ፡ ነፍስቶሙ ። ግዝረትከ ፡ ቍልፈተ ፡ ትከውነከ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፯ ። ሮሜ፪ ፡ ፳፭—፳፯) ።

**አቈለፈ** ፤ አስቈለፈ ፤ አስለበጠ ። በእቅፈለ ፡ ፈንታ ፡ አቈለፈ ፡ ይላል ፡ (፪ነገ ፡ ፭ ፡ ፳፲) ። አቈላፈሁ ፡ ወአቍፋሊሁ ፡ የሚሉት ፡ ልብ ፡ ወሰይፍ ፡ ንባብ ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡ (ማሕ ፡ ፫) ። ፍችውም ፡ መሳቢያው ፡ መለበቢያው ፤ ትቱ ፡ ወንፊቱ ፡ ገመዱ ፡ ማሰት ፡ ነው ፤ ዝርዝሩ ፡ ዐራትን ፡ ያያል ።

**ቀልፎንያ ፤ (ሮማይ ፡ ከሎፎንያ)** ፤ ሙጫ ፤ እንደ ፡ ዕጣን ፡ ያለ ፤ የሚሸት ፡ የሚቃጠል ፤ መጣብቅ ፡ የሚኾን ። ቃር ፡ ወፒሳ ፡ ወተይ ፡ ወቅጥራን ፡ ወሰብዐቱ ፡ ልጥር ፡ እምነ ፡ ቀልፎንያ ፡ (ስንክ ፡ ሐም፳) ።

**ቀልቅሎ ፤ ሎት ፤ (ቀልቀለ ፡ ይቀለቅል ፡ ይቀልቅል ። ዐረብ ። ዕብ ፡ ቂልቃል)** ፤ መቀልቀል ፤ መደብለቅ ፡ መደበላለቅ ፤ ማማሰል ፡ መንቅነቅ ፤ መናድ ፡ ማፍረስ ፡ ማውለቅለቅ ፡ ማጥፋት ፡ ማበላሸት ።

**አንቀልቀለ** ፤ አንቀሳቀሰ ፤ ተንቀሳቀሰ ፡ ተንቀነቀ ፤ ተውለቀለቀ ። ስእኑ ፡ አንቀልቅሎቶ ። አብያቲሃ ፡

ዘኢያንቀለቅላ ፡፡ ያንቀለቅል ፡ ለፌ ፡ ወለፌ ፡፡ አር ፀተ ፡ ብዕራ ፡ ዘያንቀለቅል ፡ (ሉቃ፣ ፡ ፱፣ ፡፡ ኢሳ፴፫ ፡ ፳ ፡፡ አፈ ፡ ድ፲፩ ፡፡ ሚራ፳፮ ፡ ፯) ፡፡

—፤ ወጣ ፡ ራቀ ፤ ሸሸ ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፲፭ ፡፡ ምሳ፲፯ ፡ ፲፫ ፡፡ ማሕ፪ ፡ ፲፯) ፡፡

**መንቀልቀል** ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤ የሚያናውጥ ፤ አናዋጭ ፡ ጕሰንሽ ፡ አንሣሽ ፡፡ ሥን ፡ ራእየ ፡ አንስት ፡ መንቀልቅልት ፡ ለፍትወት ፡ (ፊልክ ፡ ፶፯) ፡፡

**ነቀልቃል** ፤ (ላት) ፤ ድብልቅልቅ ፤ ሽብር ፤ ኍውጽውጽታ ፤ ነውጥ ፡ የባሕር፡ ፡ ሞገድ ፡፡ ኃይለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እምድኅረ ፡ ተዐቅቦ ፡ ብዝኅት ፡ ለሕዋሳት ፡ ወለነቀልቃላት ፤ ትትወሀብ ፡ ለ.ድልዋን ፡ ላቲ ፡ (ፊልክ ፡ ፲፰) ፡፡

**ቈልቈለ** ፤ ቈለቈለ ፤ ደፋ ፤ ዘቀዘቀ ፤ ቃጣ ፡ ሰበቀ ፡ ወረወረ ፤ የጦር ፡ የዘገር ፡፡ ሰበ ፡ ቈልቈለ ፡ ኵናቶ ፡ ላዕለ ፡ አህጉሪሆሙ ፡ (ሚራ፡፵፮ ፡ ፪) ፡፡ በቈልቈለ ፡ ፈንታ ፡ አቈልቈለ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡፡ አስቲ፯ንዐ ፡ መዝራዕቶ ፡ ወአቈልቈለ ፡ ኵናቶ ፡ ወረገዘ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ፡፡

**ተቈልቈለ** ፤ ተቈለቈለ ፡ ተደፋ ፤ ወረደ ፤ ተዘቀዘቀ ፡፡ እስመ ፡ ተቈልቈለ ፡ ፀሓይ ፡ (ኤር፳ ፡ ፱ ፡፡ ሉቃ፱ ፡ ፲፪ ፡፡ ፳፱ ፡ ፳፱) ፡፡ ይርሕቅ ፡ ይሴስል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይትቈለቈል ፡ ይላል ፡ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘክ፲፱ ፡ ፱) ፡፡

**ቍልቁል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ቍልት) ፤ ያቈለቈለ ፤ የተቈለቈለ ፤ ወደ ፡ ታች ፡ ያለ ፤ የተዘቀዘቀ ፤ ዝቅዝቅ ፡፡ ማይ ፡ ኢይውሕዝ ፡ ቍልቁለ ፤ አላ ፡ ዐቀበ ፡ (ፍካሬ ፡ እየ) ፡፡

**ቍልቍለት** ፤ መቈልቈል ፡ መውረድ ፡ መዘቅዘቅ ፡፡ በቁሙ ፤ ወጻታ ፡ ዘቅዝቃ ፤ ሲወጡት ፡ ዳገት ፡ ዐቀበት ፡ የሚባል ፡፡

**ቍልቍሊት** ፤ በቁሙ ፤ ቍልቍል ፤ ዝቅዝቆሽ ፡ የዝቅዝቂት ፡፡

**ቍልቍሊተ** ፤ ወደ ፡ ታች ፡ ወደ ፡ ምድር ፤ አቈልቍሎ ፤ ተደፍቶ ፡ ተዘቅዝቆ ፡፡ ተሰቅለ ፡ ቍልቍሊተ ፡ መልዕልቴ ፡ አየር ፡፡ ተሰቅለ ፡ ልዑለ ፡ እገሪሁ ፡ ወቍልቍሊተ ፡ ርእሱ ፡፡ ወአስተብቍዖሙ ፡ ከመ ፡ ይስቅልዎ ፡ ቍልቍሊተ ፡ (ገድ ፡ ተክ ፡፡ ስንክ ፡ መጋ ፲፱ ፡፡ ሐምሌ፳ ፡፡ ጥቅ፲) ፡፡

**ቀልቀል** ፤ (ላት) ፤ ገደል ፤ ተራራ ፤ አንባ ፤ የተራራ ፡ ዙሪያ ፡፡ ርእሰ ፡ ቀልቀል ፡፡ ከመ ፡ ዘማእከለ ፡ ቀልቀል ፡ ታንሶሱ ፡፡ ኢትንበር ፡ ደወለ ፡ ቀልቀል ፡ ምስለ ፡ ጸላኢከ ፡ ከመ ፡ ኢያጽድፍከ ፡ (፪ዜና ፡ ፳፭ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪ ፡፡ ሚራ፲ ፡ ፲፫ ፡፡ መጽ ፡ ምስ) ፡፡ ቍልቋል ፤ ቈለቈል ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ የቈላ ፡ የቍልቍለት ፡ ዛፍ ፡ ያሰኛል ፡፡

**ቀላቂል** ፤ (ትግሬ) ፤ ቈላ ፡ ሜዳ ፤ ዘብጥ ፡ ረባዳ ፤ የገደል ፡ ሥር ፤ የተራራ ፡ እግር ፡፡

**ቍልቋስ** ፤ የኀፊደት ፡ ስም ፤ በውሃ ፡ ዳር ፡ የሚበቅል ፤ ፍሬው ፡ የሚበላ ፡ እሾኽም ፡ ወተታም ፡ እንደ ፡ ቍልቋል ፡ ቶሎ ፡ የሚጸድቅ ፤ ሥር ፡ የሚሰድ ፡፡ ረከቡ ፡ በውእቱ ፡ መካን ፡ ማየ ፡ ጽሩየ ፡ እንዘ ፡ የዐውዶ ፡ ቍልቋስ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲፯) ፡፡

**ቀሊስ** ፤ ሰት ፤ (ቀለሰ ፡ ይቀልስ ፡ ይቅልስ ፡፡ ሰብ ፡ ቃሌስ ፤ ሣቀ ፡ ተሣለቀ) ፤ መቀለስ ፤ ማስጕንበስ ፡ ማረቅ ፡ ማጕበጥ ፡፡

**ተቀልሰ** ፤ ተቀለሰ ፡ ተጕንበሰ ፤ ታጠፈ ፡ ዞረ ፡ ተመለሰ ፡ ምልስ ፡ ቅልስ ፡ አለ ፡፡

**ተቃለሰ** ፤ ታገለ ፡ ተያየዘ ፤ ተጠማዘዘ ፡ ተና ነቀ ፡፡ ይትቃለስ ፡ ምስሌሁ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳፱) ፡፡

**አስተቃለሰ** ፤ አስታገለ ፡ አዋጋ ፤ አመላለሰ ፡፡ ዲበ ፡ አርእስተ ፡ አድባር ፡ ለተነ ፡ ሂሚ ፡ ዘያጠይሶ ፤ እንበለ ፡ ረዓም ፡ ዘያግሕሦ ፤ ውስተ ፡ አየራት ፡ ዘያስተቃልሶ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ፡፡

**ቀለጸ** ፤ **ቀልጸጸ** ፤ (ዐረ ፡ ቈለብ ፡፡ ቀለበ) ፤ ነከሰ ፡ ነደፈ ፤ ዋጠ ፡ ሰለቀጠ ፤ የእባይብት ፡፡ ነጠቀ ፡ ወሰደ ፤ ጣገረ ፡ ጕፈጠረ ፡ ሰበረ ፡ ዘበተረ ፡ የአንበርት ፡ የአራዊት ፡፡ በህየ ፡ እኤዝዞ ፡ ለከይሲ ፡ ወይቀልጾሙ ፡፡ ወይደይዎሙ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ ወቀለጽዎሙ ፡ አናብስት ፡ ዘእንበለ ፡ ይብጽሑ ፡ ምድረ ፡፡ በዘኢይክሉ ፡ ቀልጸጾ ፡ መስተቃርናነ ፡ ሀገረ ፡ (ዓሞ፱ ፡ ፫ ፡፡ ገድ ፡ ተክ ፡፡ መጽ ፡ ምስ ፡፡ ቄድር) ፡፡

**ቀሚሕ** ፤ ሐት ፤ (ቀምሐ ፡ ይቀምሕ ፡ ይቅማሕ ፡፡ ሰምረ ፤ ፈረየ) ፤ ማፍራት ፤ መበጀት ፤ ፍሬ ፡ መያዝ ፡ መሸከም ፤ ማንዠርገግ ፤ ያዝመራ ፡ የተ ክል ፡፡ መቀማት ፡ መመንተፍ ፡ መንጠቅ ፡፡


**ቀምሕ** ፤ (ዐረ ፤ ስንዴ ፡፡ ሰብ ፡ ቈማሕ ፤ ዶቄት) ፤ ፍሬ ፡ ቅንጣት ፡ ምርት ፡ ዛላ ፡ ዘለላ ፡ ሕንባብ ፤ በየስሙ ፡ በየንገዱ ፡ የማማሰኛ ፡ ፍጥረት ፡ የሚያፈራው ፡፡ ፍጡነ ፡ ትበልዕ ፡ ቀምሓ ፡፡ ትጸግቡ ፡ እምነ ፡ ቀምሕየ ፡፡ ይተክሉ ፡ ወይነ ፡ ወይበልዑ ፡ ቀምሖ ፡ (ሚራ፯ ፡ ፲፱ ፡፡ ፳፱ ፡ ፲፱ ፡፡ ኢሳ፷፭ ፡ ፳፩) ፡፡

—፤ ዘርዕ ፡ ተክል ፡ ቅመም ፡ ዛፍ ፡ ዕንፊለት ፤ የሚዘራና ፡ የሚተከል ፡ የሚያፈራ ፡ ኹሉ ፡፡ ዐቃቤሁ ፡ ለቀምሕ ፡ ይሬኢ ፡ ፍሬሁ ፡፡ ዕፀወ ፡ ቀምሕ ፡፡ ልኅቀ ፡ ዐቃቤ ፡ ቀምሕ ፡ (ሚራ፳፯ ፡ ፮ ፡፡ ኑሐ፱ ፡ ፳፭ ፡፡ ኢሳ፳ ፡ ፰) ፡፡

**አቅማሕ** ፤ (ሓት) ፤ ፍሬዎች ፡ ቅንጣቶች ፤ ቅመሞች ፤ አዝርዕት ፡ አትክልት ፡ ዕፀዋት ፡፡ አቅማሐ ፡ አዝርዕት ፡፡ አቅማሐ ፡ አትክልት ፡፡ አቅማሐ ፡ አፈዋት ፡፡ ዙሉ ፡ አቅማሐ ፡ ገዳም ፡፡ ትክሉ ፡ አቅማሓተ ፡፡ አስተጋብእ ፡ ውስተ ፡ ልብየ ፡ አቅማሓተ ፡ ዙሉ ፡ ጥበብ ፡ (አርጋ ፡፡ የኤኖ ፡ ፲፪ ፡፡ ኤር፴፯ ፡ ፳ ፡፡ ድራሲ ፡፡ ራእ ፲፰ ፡ ፲፬) ፡፡

**ቅምሕ** ፤ በቁሙ ፡ የጕረሮ ፡ በሽታ ፤ እንደ ፡ ፍሬ ፡ የሚያብጥ ፡ የሚፈርጥ ፡፡

**ቃማ** ፤ (ሱር ፡ ምኒክ ። ዕብ ፡ ርቢድ) ፤ ቀምሐዊ ፤ ዝርግፍ ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ ጌታ ፡ ማገርዳ ፡ ድሪ ፤ ድንገት ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ ባዝግናን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ቃማ ፡ ፍሬነቱን ፡ ባዝግና ፡ ዝግኝነቱን ፡ ያሳያል ። ሰላም ፡ ለከማድኪ ፡ ቃማ ፡ ንጽሕ ፡ ዘዐነቀ ። አስኬማ ፡ አምሳለ ፡ ባዝግና ፡ ወቃማ ፡ (ደራሲ ። ዳንኤ ፡ ፲፯ ፡ ፳፱) ።



ቃማ ፡

**ቀምሐ** ፤— ቃመ ፡ ገተመ ፤— ቀሐመ ።
**ምቅማሕ** ፤— መቃሚያ ፤— ምቅሓም ።

(ጥ) **ቀምጠ** ፤ ጠት ፤ (ቀመጠ ፡ ይቄምጥ ፡ ይቀምጥ ። ዕብ ፡ ቃማጥ ። ዐረ ፡ ቀመጠ ። ሱር ፡ ቅማጥ) ፤ አጥብቆ ፡ መያዝ ፤ ማሰር ፡ መሸንከፍ ፤ ማጠፍ ፡ ማጣመር ። ማስቀመጥ ፡ ማኖር ፤ መጐሞት ፤ ሎጭ ፡ ጉች ፡ ማድረግ ። መቍመጥ ፡ መቍረጥ ፤ መበጠስ ።

**ተቀመጠ** ፤ በቁሙ ፡ ቍጭ ፡ አለ ፤ ጕልበቱን ፡ ጭኑን ፡ በጠረ ፡ ምድር ፡ ያዘ ፡ ተንዘራፈጠ ። ተቈመጠ ፤ ቈማጣ ፡ ሆነ ። በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ምኔት ፡ ወተቀመጠ ፡ ኀበ ፡ ዴዴ ፡ ወበከየ ። ኀበ ፡ እቀውም ፡ ወኀበ ፡ እትቀመጥ ፡ (ፊልክ ፡ ፳፫ ። ደራሲ) ።

**ተቅማጥ** ፤ በቁሙ ፤ ቅዘን ፤ ተቅጠን ፡ ዐይነ ፡ ምድር ።

(ላ) **ቅምጥ** ፤ ደይን ፡ ዐር ፤ ጭንቅ ፤ ዕጦት ፡ ችጋር ፤ ቍምጥና ፡ (ዐማርኛ) ።

**ቀምጠወ** ፤ (ተቀ ፡ ማ) ፤ አስተካከለ ፤ አለሰለሰ ፤ ቀበቀበ ፤ አንቀረቀበ ፤ መላልሶ ፡ ዐርሶ ፡ ጕሎን ፡ መኰላውን ፡ ሰብሮ ፡ ከስክሶ ። መጽሐፍ ፡ ማን ፡ አቀምጠወ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። አኮኑ ፡ አቀምጢዎ ፡ ገራህት ፡ ሰቤሃ ፡ ይዘርዕ ፡ (ኢሳ ፳፰ ፡ ፳፭) ። ባለብሰጐች ፡ ተስመ ፡ ይሉታል ።

**ቀምጠራ** ፤ (ዐረ ፡ ቀመጥር ። ዕብ ፡ ቃምጣር) ፤ ማጥን ፤ ቍናማት ፤ ከረጢት ፤ የልብስ ፡ የገንዘብ ። ያስከሬንን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። በእንተ ፡ አስከሬን ፡ ወቀምጠራ ፡ ዘሙዳየ ፡ ምጺት ። ወከነ ፡ ሰረቂ ፡ ብኑር ፡ ዘውስተ ፡ ቀምጠራ ፤ ዘአስከሬኔ ፡ እግዚኡ ፡ (ዮሐ ፲፪ ፡ ፮ ። መጽ ፡ ምስ) ።


**ቀምጠራት** ፤ **ቀማጥር** ፤ ማጥኖች ፡ ቍናማዶች ። እለ ፡ ይትፌሥሑ ፡ በብዝኀ ፡ ዕንቍሙ ፡ ክቡር ፡ ወኪያሁ ፡ ዕንቈ ፡ የዐቅቡ ፡ ውስተ ፡ ቀምጠራት ፡ ዘጊሎሙ ፡ ጽኑዐ ፡ (ተረ ፡ ቄር ፳፱) ።

**ቀሚስ** ፤ (ዐረ ፡ ቀሚጽ) ፤ በቁሙ ፤ የውስጥ ፡ የገላ ፡ ልብስ ፤ ባንገት ፡ የሚጠለቅ ፤ ታናሽ ፡ ወይም ፡ ታላቅ ። እለ ፡ ቀሚሰ ፡ ይቀጽዑ ። ወይለብስ ፡ ቀሲስ ፡ ልብሰ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀሚሰ ፡ ወሞጣሕተ ፡ ወፊቃሬ ፡ ወአክሊለ ። ወሶበ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይልበስ ፡ ቀሚሰ ፡ ይነጽር ፡ ለእመ ፡ ክነ ፡ ንፁኅ ፡ አው ፡ ኀጺረ ፡ (ዮሴፍ ። ቄድር ። ቅዳ) ።

**ቀማይስ** ፤ (ሳት) ፤ ቀሚሶች ። ለብሱ ፡ ልብሰ ፡ ኀጺን ፡ እምታሕተ ፡ ቀማይሳቲሆሙ ፡ (ዮሴፍ ። ገድ ፡ አዳ) ።

**ቀሚል** ፤ ሎት ፤ (ቀመለ ፡ ይቀምል ፡ ይቅምል ። ዕብ ፡ ቃማል ፤ የብሰ ፡ መጸለወ) ፤ መቅመል ፤ መቀማመል ፡ መላለቶ ፡ ማየት ፡ ማገላበጥ ። ወይቀምሎሳ ፡ ለምድረ ፡ ግብጽ ፡ ከመ ፡ ይቀምል ፡ ኖላዊ ፡ አልባሲሁ ። ወረከበት ፡ እንዘ ፡ ይቀምል ፡ ጸጕሮ ፡ (ኤር ፵፫ ፡ ፲፪ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ቅማል** ፤ ቍማል ፤ (ላት) ፤ በቁሙ ፤ የልብስ ፡ የጠጕር ፡ ተባይ ፤ እጅግ ፡ ታናሽ ፤ ባለ፮ ፡ እግር ፤ ደም ፡ የሚመጥ ። በአንቃል ፡ ዘውእቱ ፡ ቍማል ፡ (አዋል) ።



ቅማል ፡

**ቀምሮ** ፤ ሮት ፤ (ቀመረ ፡ ይቄምር ፡ ይቀምር ። ዕብ ፡ ቃማር ፤ ሸፈነ) ፤ መቀመር ፡ ማዘጋጀት ፤ መቍጠር ፡ ማሰብ ፤ መመደብ ፡ መዘርጋት ፡ መጋረድ ፤ መለየት ፡ መክፈል ፤ በሰፍር ፡ በቍጥር ፡ ማደላደል ። ዘዐውደ ፡ ፀሓይ ፡ ወወርኀ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ መጽሔት ፡ ቀመረ ። እደሁ ፡ ለልዑል ፡ ይቄምሮ ። አኮ ፡ በዕፀ ፡ ዘትሰውቆን ፡ ወትቄምሮን ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ሚራ ፵፫ ፡ ፲፪ ። ገድ ፡ ላሊ) ።

**ተቀመረ** ፤ በቁሙ ፤ ተዘጋጀ ፤ ተጋረደ ፡ ተዘረጋ ፡ ተቈጠረ ፡ ተከፈለ ። ይትቄመር ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወየዐውዶ ፡ ስብሐቲሁ ፡ (ሚራ ፵፫ ፡ ፲፪) ።

**ቅሙር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ምርት) ፤ የተቀመረ ፡ ቅምር ፤ የተቈጠረ ፤ የተከፈለ ። ወቅሙር ፡ ዐዘቅት ፡ ጠፈሩ ፡ መሥልስተ ፡ (ሄኖ ፡ ፯ ፡ ፺፩) ።

**ቀመር** ፤ (ራት ፤ አቅማር) ፤ መጋረጃ ፡ አጉበር ፤ ጠፈር ፡ መዋቅር ፤ ዋልታ ፡ ገበታ ። ዘሰቀሎ ፡ ለሰማይ ፡ ከመ ፡ ቀመር ፡ ዘእንበለ ፡ ዐምድ ፡ (ቅዳ ። ኢሳ ፵ ፡ ፳፪)

—፤ ክፍል ፡ ምዕራፍ ፤ ቍጥር ፡ ሒሳብ ፤ የቍጥር ፡ መደብ ። አቅማር ፡ በእንተ ፡ አኅብሮ ፡ ቃላት ፤ ቀመር ፡ ቀዳማዊ ። አንቲ ፡ ውእቱ ፡ ዳግሚት ፡ ቀመር ። ቀ

መረ ፡ ዐረብ ። ፀውደ ፡ ቀመሩ ፡ ለወርኅ ። ናሁ ፡ ኅልቀ ፡ ቀመርን ፡ ዘተውህበ ፡ ለአዳም ፡ ፸፻ ፡ ዓመት ፡ (መቅ ፡ ወን ። ሙዳ ፡ ማር ። መጽ ፡ ምስ ። አዋል) ።

**ቀመር** ፤ (ዐረብ) ፤ ጨረቃ ። ፀውደ ፡ ቀመር ፤ የጨረቃ ፡ ዙሪያ ፤ ፀውደ ፡ ወርኅ ፡ ፀውደ ፡ ጨረቃ ፤ ወይም ፡ ፀውደ ፡ አበቅቴ ፡ ማለት ፡ ነው ። የፀውድን ፡ ፍች ፡ እይ ።

**ቀመራዊ** ፤ ወርኃዊ ፡፡ ወርኅ ። ወርኅ ፡ ቀመራዊ ። ኍልቍ ፡ ቀመራዊ ፡ ወፀሓያዊ ፡ (አቡሻ ፡ ፳ና ፡ ፴፩) ።

**መቃምር** ፤ የጨዋታ ፡ ስም ፤ ቅልጥሽ ፤ ቍጥር ፡ ያለበት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፲፪) ።

**ቁማር** ፤ ግዝኢ ፡ ክማሁ ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ጨዋታ ፤ ጥቅምና ፡ ጉዳት ፡ ያለበት ።

**ቆሞስ ፤ ቁማስ ፤—በቁሙ ፤ መዳ ፤—ቀውመሰ ።**

**ቀሚስ ፤—በቁሙ ፤ ቀምየሰ ።**

**ቀኒአ ፤ አት ፤ (ቀንአ ፡ ይቀንእ ፡ ይቅናእ ። ዐረ ፡ ቀነአ ። ዕብ ፡ ቃኔእ)** ፤ መቅናት ፤ መመቅኘት ፤ ማዘን ፡ መቈጣት ፡ መበሳጨት ፤ በሌላው ፡ ዕድልና ፡ ሀብት ። ወይም ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ለመኾን ፡ መንቃት ፡ መትጋት ፤ ርሱን ፡ አብነት ፡ ማድረግ ፤ ምኑ ፡ ፈቀረኝ ፡ ማለት ። ኢትቅናእ ፡ ላዕለ ፡ እኩያን ። ተመየጥ ፡ ንበ ፡ ቃሕም ፡ ወቅናእ ፡ ርእየከ ፡ ፍናዊሁ ። ቅናእ ፡ ለንስሓ ፡ (መዝ ፡ ፴፮ ። ምሳ፳ ፡ ፮ ። ራእ፫ ፡ ፲፱) ።

**ቀኒእ ፡ (ረቲእ)** ፤ በቁሙ ፤ መቅናት ፤ ቀና ፡ ማለት ፤ ቅን ፡ እውነተኛ ፡ መኾን ፤ መመቸት ፡ መፈጠን ፡ መከናወን ፤ የሥራ ። አበያ ፡ ሲቀና ፡ ቤት ፡ ያቀና ፡ እንዲሉ ። ኢትቅንኡ ፡ ለመዊት ፡ (ጥበ፩ ፡ ፲፪) ።

**ቀናኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት)** ፤ የሚቀና ፤ ቀናተኛ ፡ ምቀኛ ። አነ ፡ እግዚ ፡ ቀናኢ ። ስምዖን ፡ ቀናኢ ። በዝኑ ፡ ቀናእያኒሁ ። ጸላእያንየ ፡ ወቀናእያንየ ። መበለታት ፡ እኩያት ፡ ቀናእያት ፡ ወመስተዋድያት ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፭ ። ሉቃ፮ ፡ ፲፭ ። ፈላስ ። ፍ፡ ሴ፡ ፍ ። ዲድ ፡ ፲)።

**ቅንአት** ፤ መቅናት ፡ መመቅኘት ። ቅናት ፡ ምቀኝነት ፤ ቍጣ ፡ ብስጭት ፡ ቀናኢነት ። ቅንአተ ፡ እግዚ ፡ ይገብር ፡ ዘንተ ። በቅንአተ ፡ ዲያብሎስ ፡ መጽአ ፡ ሞት ። በከመ ፡ ከነ ፡ ውስቴቱ ፡ ቅንአት ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፤ ከማሁ ፡ ተመክዐበ ፡ ውስቴቱ ፡ ቅንአት ፡ በሕገ ፡ ኢየሱስ ፡ (ኢሳ፱ ፡ ፯ ። ጥበ፪ ፡ ፳፬ ። ሰንክ ፡ ሐምሌ፳) ። ቅንአትና ፡ የቀንነት ፡ ዘር ፡ ቅናት ፡ ባማርኛ ፡ ይተባበራሉ ። (ማጥም) ፤ ባፋ ፡ በጕራዴ ፡ ትደንቃላችኹ ፤ ወገብ ፡ ቈርጦ ፡ እሚጥል ፡ ቅናት ፡ ባለላችኹ ። ለመንኰሴ ፡ ብቻ ፡ ማን ፡ ስጠው ፡ ቅናቱን ፤ ለዓለማዊ ፡ ነው ፡ የቀሠፈው ፡ ጥንቱን ። እስራኤል ፡ በጣዖት ፡ ስላመነዘሩ ፤ ፈጣሪም ፡ ቃጥቆታል ፡ እንዲያ ፡ ሰው ፡ ፍጡሩ ።

**ቅንእ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ቅንኡ ፡ ሊብእሲ ፡ እምንበ ፡ ቢጹ ፡ (መክ፬ ፡ ፬) ።

**አቅንአ** ፤ አቀና ፤ አመራ ፤ አስቀና ፤ ቅናት ፡ አስነሣ ፡ አሳደረ ። ሐውር ፡ ወልድየ ፡ ወአቅንእ ፡ ሀገረ ። ወያቀንኡ ፡ ለሐዊር ፡ መንገሌሆን ። ኢያቅንእከ ፡ ብዕሎሙ ፡ ለኃጥኣን ። ኢትትናገር ፡ ምስለ ፡ ብእሲት ፡ በዘታቀንኣ ፡ (ዜና ፡ ወማ ። ማር ፡ ይሥ፱ ፡ ፳ ። ሢራ፱ ፡ ፩ ። ፴፯ ፡ ፲፩) ።

**መቅንእ ፤ መቃንእ** ፤ መቃን ፤ መቃኖች ፤ የማራና ፡ የቀኝ ። ራማዘቅን ፡ እይ ።

**ተቃንአ** ፤ ተቃና ፤ ተቀናና ፤ ተፈካከረ ። ትትቃንኡ ፡ ዝንቱ ፡ ምስለ ፡ ዝንቱ ። አበስልዎ ፡ ለተሓምዮ ፡ ወለተቃንአ ። እስመ ፡ ኀበ ፡ ሀለወ ፡ ተቃንአ ፡ ህየ ፡ ሀሎ ፡ ሀውክ ፡ (ኩፋ ፡ ፯ ። ፩ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፩ ። ያዕ፫ ፡ ፲፮) ።

**አስተቃንአ** ፤ አቃና ፤ አቀናና ፤ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ታስተቃንእ ፡ (ሢራ፳፯ ፡ ፯) ።

(ጥ) **ቀንአት ፤ (ዐረ ፡ ቂነት ። ዕብ ፡ ሔልብና ። ጽር ፡ ኻልባኒ)** ፤ የሽቱ ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፤ ከዕፀው ፡ ዕጣን ፡ አንዱ ፤ በዮርዳኖስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚበቅል ፡ (ዘፀ፴ ፡ ፴፬) ።

**ቀንአት ፤ (ዐረ ፡ ዑድ ። ዕብ ፡ አሀሎት ። ጽር ፡ ስታክቲ)** ፤ ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ ስም ፤ ዕጣን ። ስኂን ፡ ወቀንአት ፡ ወማየ ፡ ልብን ፡ ወሰንበልት ፡ (ኩፋ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፵፬ ። ቅዳ) ።

**ቈንደየ ፤ (ጐንደየ)** ፤ ቆንደደ ፤ ቃበየ ፡ ኰራ ፤ ተንጠራራ ፤ ቀንድ ፡ አወጣ ፤ ወይም ፡ ቀንድ ፡ ኾነ ፤ ቀንድ ፡ ተባለ ። ያገር ፡ ቀንድ ፡ እንዲሉ ፡ (መዝ ፡ ፻፴፩ ። ሉቃ፩ ፡ ፳፱ ። ሕዝ፳፱ ፡ ፳፩) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በቈንደየ ፡ ፈንታ ፡ ተቈናደየ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ትትቈናደዩ ፡ ብየ ፡ ወትዘረክዩኒ ፡ (ኢዮ፲፱ ፡ ፭) ። ጐንደየን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ሥር ፡ ነው ።

—፤ ቈንዳ ፤ ዘለለ ፤ ቈንዳ ፡ ቈንዳ ፡ አለ ። የቍጣ ፡ የኵራት ፡ ወይም ፡ የደስታ ።

**ተቈናደየ** ፤ ተቈናዳ ፡ ተዛለለ ፤ ተቃበጠ ፤ ተዳራ ። ፍሒልን ፡ ይመስላል ።

**አስተቈናደየ** ፤ አዛለለ ፤ አቃበጠ ፤ አስቃበየ ፡ አንደደ ።

**ቀንዲል ፤ (ዐረ ፡ ቂንዲል)** ፤ መብራት ፤ ማብሪያ ፤ የዘይት ፡ የሠም ፤ መደበኛው ፡ ግን ፡ ዘይት ፡ ነው ። ለእመ ፡ ኀልቀ ፡ ቅብዕ ፡ ዘይት ፡ እምቀንዲል ። ወኢይቀርቡ ፡ በአሐዱ ፡ ሠምዕ ፡ ሻባ ፡ በክልኤቱ ፡ በገበዋቲ ፡ ምሥዋዕ ፤ አላ ፡ በቀንዲል ፡ ህየንተ ፡ ሠለስቱ ፡ ሠምዕ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ሥር ፡ ቅዳ) ። መጽሐፈ ፡ ቀንዲል ፤ መጽሐፈ ፡ ዘይት ፤ ጸሎተ ፡ ዘይት ፡ ቅብዐ ፡ ድውያን ፤ በዘይት ፡ ላይ ፡ የሚነበብ ፡ የሚጸለይ ።

**ቀንዲላት ፤ ቀናዲል** ፤ ቀንዲሎች ፤ መብራቶች ፤ ማብሪያዎች ፡ (ስንክ ፡ መስ፲ ። ጥር፴) ፡ ቈንዳላ ፡ ማለት ፡ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ቀንደራጢስ** ፤ (ጽር ፡ ክድራንተስ) ፤ የአሶርዮን ፡ ሩብ ፡ ታናሽ ፡ ወሬዳ ፤ መጨረሻ ፡ ገንዘብ ። የጸሪቅን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፡ (ማር ፲፪ ፡ ፵፪) ።

**ቀንዎ** ፤ **ዎት** ፤ (ቀነወ ፡ ይቄኑ ፡ ይቀኑ ። ፀመረ) ፤ መቸንከር ፡ ማጣመር ፤ በችንካር ፡ ማጣበቅ ፡ መጠረቅ ፡ መንኰጥ ፡ መጠቅጠቅ ፤ መውጋት ፡ ማቍሰል ፤ መብሳት ፡ መንደል ። ቀኑ ፡ ፍቅረከ ፡ ውስተ ፡ ልብየ ። ቀነዉኒ ፡ እደውየ ፡ ወእገርየ ። በቅንዋቲከ ፡ ቀነውከ ፡ ለሞት ፡ (ያዕ ፡ ዘእል ። መገ ፡ ፳፩ ። ማንዘ) ።


**ቀናዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ የሚቸን ክር ፡ የሚጠርቅ ፡ ቸንካሪ ።

**ተቀነወ** ፤ ተቸነከረ ፡ ተበሳ ፡ ተንደለ ። እንዘ ፡ ይትቀሠፍ ፡ ወይትቄኖ ፡ በቅንዋት ። ተቀነወ ፡ እደ ዊሁ ። በቀኖት ፡ ኀጺን ፡ ተቀነወ ፡ እግሩ ፡ (ሃይ ፡ አበ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ሠኔ ፳፭) ።

**ቅንው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ኑት) ፤ የተቸነከረ ፡ የተጣመረ ፤ አንድ ፡ የኾነ ። ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቅንወ ፡ ሕእጋር ፡ ወእድ ። እሑድ ፡ እሱር ፡ ወቅንው ፡ በሰን በት ፡ (ደራሲ ። ሲኖዶ) ።

**ቅናዌ** ፤ መቸንከር ፤ (ጥቅ) መቸንከር ፤ አቸንካ ክር ፤ ችንካሩ ፤ የችንካር ፡ ውጋ ፡ ቍስል ። ቅናዌ ፡ ወር ግዘት ፡ ኩናት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ቀኖት** ፤ (ታት) ፤ ችንካር ፤ ምስማር ፡ እሾኽ ፡ ጋሬጣ ፤ የብረት ፡ የንጨት ። በቀኖት ፡ ሰጽንዕዎ ። አ ይቴ ፡ ውእቱ ፡ ቀኖትከ ፡ ሞት ። ይከውኑክሙ ፡ መሥ ገርት ፡ ወዕቅፍተ ፡ ወቀኖታተ ፡ (ኤር ፲ ፡ ፬ ። ሆሴ ፲፫ ፡ ፲፬ ። ኢያ ፳፫ ፡ ፲፫) ።



ቀኖት ፡

**ቅናው** ፤ **ቅናዋት** ፤ ችንካሮች ፡ የችንካር ፡ ቍስሎች ፡ ውጋታዎች ። ውስተ ፡ ዘነበሙ ፡ ሰሙ ፡ ቅና ዋት ። ቶማስ ፡ ርእየ ፡ ሰሠሮሙ ፡ ለቅናዋት ። ርግ ዘተ ፡ ገቦሁ ፡ ወቅናዋተ ፡ እደዊሁ ። ትምህርቱ ፡ ቅና ዋት ፡ (ራእ ፱ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ ሚያ ፳፯ ። ማንዘ ። አዋል) ።

— ፤ መስቀል ፡ ነክ ፡ መዝሙር ፤ ምስጢረ ፡ መስቀል ፡ ያለበት ፤ ዐርብና ፡ ረቡ ፡ ቅዳሜ ፡ በሌሳውም ፡ ቀን ፡ የሚ ባል ፡ ክብር ፡ ይእቲ ፡ ቅኔ ፡ (ሥር ፡ ድጓ) ።

**ቀንዝዕ** ፤ ቋንዣ ፤ ባት ። ቃንዛ ፤ የበትር ፡ የቀ ስል ፡ ስሜት ። ቈንዳላ ፡ ሥዕርት ። ሥሩና ፡ ምንጩ ፡ ንዝዐ ፡ ነው ።

**ቈናዝዕ** ፤ (ዐረ ፡ ቁዘዐት ፤ ቁንዙዐት) ፤ ብርንጎ ፤ የራስ ፡ ጠጕር ፡ ሥራ ፤ ነዶው ፡ ፈትሉ ፡ ገመዱ ፡ ጕንጕኑ ፡ እንጥልጥሉ ። ቈንጮ ፡ ጋሜ ፡ ሳዱላ ፤ የዘ ሪያ ፡ ልጅነት ። ቈናዝዒሃ ፡ ፍቱል ። ሰብዑ ፡ ቈና ዝዐ ፡ ርእስየ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። መሳ ፲፮ ፡ ፲፫) ።

**ቈናዝዓት** ፤ ብርንጎዎች ። ኢትግበሩ ፡ ቈና ዝዓተ ፡ እምሥዕርተ ፡ ርእስክሙ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፩ ። ዘሌ ፲፱ ፡ ፳፯) ።

**ቈንዝዐት** ፤ ቈንጉር ፤ ሳዱላ ፤ ባለቈንዳላ ፤ ልጃ ፡ ገረድ ፡ ጕበዝ ፡ እንደ ፡ ኽብ ፡ የሚንጥቃት ። ንዝ ዐን ፡ ተመልከት ።

**ቈናዝዐት** ፤ ቈንዣዥት ፤ ሳዱሎች ፤ ደናግ ሎች ።

**ቀንጠበ** ፤ (ቀጠበ) ፤ ቀነጠበ ፤ ቈነጠበ ፤ ቈ ረጠ ፡ በጠሰ ። ይቀንጥቡ ፡ ድርያ ፡ (አዋል) ።

**ቅንጣብ** ፤ (ባት) ፤ ቅንጣቢ ፤ ቍንጣቢ ፤ ቍ ራጭ ፡ ብጣሽ ፤ ስራፊ ፤ ቅሩፊ ። ወይእዜሰ ፡ ግማዳተ ፡ ሕብድ ፡ ወቅንጣባተ ፡ ረሰይከኒ ፡ (ኢዮ ፲፮ ፡ ፳) ።

**ቀንጠ** ፤ (ዕብ ፡ ቃኖጥ ፤ ሀቅኔጥ) ፤ አስ ራመኸ ፡ አስቈጣ ፤ አስወገሸ ።

**ቀንጠወ** ፤ ቈነጠነ ፤ አስከረ ፤ አቀናጣ ፤ ጤና ነሣ ፤ ልብ ፡ አሳጣ ፤ አብገዘቶ ፡ የበሉት ፡ የጠጡት ።

**ቅንጣዌ** ፤ ቍንጣን ፤ የጥጋብ ፡ ብዛት ፤ የሆ ዳም ፡ በሽታ ። ሰብእሲ ፡ ሥሡዕ ፡ ዘኢይጸግብ ፡ ደዌሁ ፡ ቅንጣዌ ፡ ወገብጥ ። ጽጋብ ፡ ጸዋዌ ፡ ቅንጣዌ ፡ ው እቱ ፤ ወቅንጣዌ ፡ ጸዋዌ ፡ ደዌ ፤ ወደዌ ፡ ጸዋዌ ፡ ሞት ፡ (ሚራ ፴፱ ፡ ፳፯ ። ፈላስ) ። ቁንጥ ፡ መቁናጥ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ቀንጠሰ** ፤ (ቀንጠበ) ፤ ቀነጠሰ ፡ ቈረጠ ፡ በጠሰ ፤ ለቀመ ፤ የጕመን ፡ የሥንቆ ። ሕልበሙ ፡ ዘይ በልዑ ፡ ዘእንበለ ፡ ሐምለ ፡ ገዳም ፤ ይቀነጥሱ ፡ እም እ.ድባር ፡ ወይሴሰዩ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ) ።

**ቀንጠስጤ** ፤ (ጽር ፡ አከንቲስቴ) ፤ ወሬ ውያን ፤ ነዳፍያን ፤ ቀስተኞች ፡ (፩ነገ ፡ ፴፩ ፡ ፫) ።

**ቀንየ** ፤ **ዮት** ፤ (ቀንየ ፡ ይቀኒ ፡ ይቅነይ ። ዕብ ፡ ቆኔን) ፤ ገዛ ፡ ማልቀስ ፡ መቈዘም ፤ ማሞሽ ፡ መግጠም ፤ ማዜም ፡ ማጕረምረም ፤ መቀንቀን ፡ መገ ፈን ፤ መምራት ፡ መቀኘት ፤ መሪ ፡ ቀንቃኝ ፡ ባለቅኔ ፡ መኾን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በቀንየ ፡ ፈንታ ፡ ተቀንየ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ፤ ተ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። ረከብዎ ፡ ለ አበ ፡ ዮሴፍ ፡ እንዘ ፡ ይትቀኒ ፡ ምስለ ፡ ሰሐዱ ፡ መነኮስ ። ካህናት ፡ ይትቀነዩ ፡ ዘንተ ፡ መዝሙረ ፡ በዜማ ፡ ሐዘንዚን ። ወእምዝ ፡ በሊ ፡ ወተቀነይ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ። ወእንዘ ፡ ይትቀኒ ፡ በሠለስቱ ፡ ዜማ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ ፳፫ ። ማንዘ ። ድጓ ። ታምር) ።

**ቅኔ** ፤ (ዕብ ፡ ቂና) ፤ በቁሙ ፡ ሙሾ ፡ ግጥም ፤ ቅንቀና ፡ ቍዘማ ፤ የፍትሐት ፡ የልቅሶ ፡ ዜማ ፤ ማሕሌት ፡ ጉማ ። መጽሐፈ ፡ ቅኔ ። አህ ፡ አሀ ፡ ለድምፀ ፡ ቅኔ

ሆሙ ፡ ለካህናት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ ተለኰመ ፡ ዜማ ፡ መሰንቆ ፡ ጥዑም ፡ በውስተ ፡ መዝሙር ፡ ወጸሎት ፡ (አዋል ። ማንዘ) ።

—፤ የዜማ ፡ የቅኔ ፡ በታ ፡ ሥልተኛ ፡ ክፍል ፡ ከመቅደስ ። ቅኔ ፡ ማሕሌት ።

**ምቅናይ** ፤ (ያት) ፤ የድጓ ፡ ባህል ፡ የምዕራፍ ፡ ቀለም ፡ ባደራረስ ፡ ጊዜ ፡ የሚዜም ፡ የሚዘመም ።

**ቃነየ** ፤ (ዕብ ፡ ኒጌን) ፤ ቃኘ ፡ ደረደረ ፤ የመዝሙር ፡ የበገና ። ትቃኒ ፡ አውታሪሃ ፡፡ ኀበ ፡ አሳፍ ፡ ይቃኒ ፡ ወኀበ ፡ ደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ ይሴብሑ ፡ (ናሖ፫ ፡ ፶ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ቃና** ፤ ዜማ ፡ ድምፅ ፡ የዜማ ፡ በልት ፡ ጣዕም ፤ አቀናኘ ፤ አቀናቀኘ ። አውታረ ፡ መሰንቆ ፡ ፍሉጥ ፡ ወሊሉየ ፡ ቃና ፡፡ መስፍነ ፡ ትዕይንት ፤ ቃና ፡ ወኢሥርፀት ፡ (ፈላስ ። አፈ ፡ ድ፻፱) ።

**ቃና** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ በናገሬት ፡ አጠገብ ፡ ያለች ፡ (ዮሐ፪ ፡ ፩) ።

**ቀነየ** ፤ ዮት ፤ (ቀነየ ፡ ይቀኒ ፡ ይቅኒ ። ዕብ ፡ ቃናህ ። ሱር ፡ ቅናአ ። ዐረ ፡ ቀነይ) ፤ መግዛት ፡ መዋጀት ፡ መቤዠት ፤ መውሰድ ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግ ፡ በዋጋ ፤ ጠረየን ፡ ተመልከት ። መፍጠር ፡ መሥራት ፤ መግዛት ፡ መጌትየት ፤ ገዥ ፡ አዛዥ ፡ ጌታ ፡ መኾን ፤ በግድ ፡ ማሠራት ፡ ማስገበር ፤ ማሳረስ ፡ ማስቈፈር ፤ ባሪያ ፡ ማድረግ ። ውእቱ ፡ ይቀኒኪ ፡፡ ወይቀንይዎሙ ፡ አርባዕተ ፡ ምእተ ፡ ዓመተ ፡፡ እሰ ፡ እኩየ ፡ ቅኔ ፡ ይቀንይዎሙ ፡፡ ንቅንዮ ፡ ለነዳይ ፡ በዕዳነ ፡ (ዘፍ፲ ፡ ፲፯ ። ፲፭ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፲፬ ፡ ፱ ። ዓሞ፰ ፡ ፮) ።

**ቀናዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ነይት) ፤ የሚገዛ ፡ የሚነዳ ፤ ገዥ ፡ አዛዥ ፡ ጌታ ። በዓልከ ፡ ለሰሉ ፡ ነባሪ ፡ ወቀናዪ ፡ ዕረፍት ፡ ውእቱ ፡፡ ቀናይያኒሆሙ ፡፡ አይቴ ፡ ሀለዉ ፡ ቀነይት ፡ ወቅኑያን ፡ (ድጓ ። መዋሥ ። አፈ ፡ ተ፳፮ ። ማንዘ) ።

**አቅነየ** ፤ አስገዛ ። አቅነይክሙ ፡ ርእሰክሙ ፡ ለኀጢአት ፡ (ሮሜ፮ ፡ ፲፱ ። ፳ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፱ ። ፪ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፭) ።

**መቅነዪ** ፤ የሚገዛ ፡ የሚያስገዛ ፡ ገዥ ፡ አስገዥ ። ለከ ፡ ንትቀነይ ፡ ዘአንተ ፡ መቅነዪ ፡ ለሰሉ ፡ (ቅዳ) ።

**ተቀንየ** ፤ ተገዛ ፡ አገለገለ ፡ ተገዥ ፡ አገልጋይ ፡ ኾነ ፤ ተሠራ ፡ ተፈጠረ ። ተቀነዩ ፡ ለእግዚ ፡ በፍርሀት ፡፡ እስመ ፡ ለከንቱ ፡ ተቀንየ ፡ ዓለም ፡፡ ነባሪ ፡ ዘበጽድቅ ፡ ይትቀነይ ፡ ለከ ፡፡ ከመ ፡ ይትቀነዩ ፡ ለገነት ፡ (መዝ ፡ ፪ ። ሮሜ፰ ፡ ፳ ። ሚሬ፯ ፡ ፳ ። ኩፋ ፡ ፫) ።

**ቅኑይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ኒት) ፤ የተገዛ ፡ ግዙ ፡ ተገዥ ፡ ባሪያ ፡ ፍጡር ፡ ግቡር ። ሥጋ ፡ ቅኑይ ፡ ለኀጢአት ፡፡ ነባሪ ፡ ወቅኑይ ፡፡ ያግዕዞ ፡ ቅኑያነ ፡፡ ሠርዐ ፡ ሰንበተ ፡ ለዕረፍት ፡ ለቅኑያን ፡ (ጥበ፩ ፡ ፬ ። ፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፱ ። ፩ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፩ ። ፊልክ ፡ ፫ ። ድጓ) ።

**ቅንየት** ፤ **ቅኔት** ፤ መግዛት ፡ መገዛት ፡ አገዛዝ ፤ ግዛት ፡ ግዙነት ፡ ባርነት ። ወእምቅንየትሙ ፡ አድኅነክሙ ፡፡ እስከ ፡ ትቀንይዋ ፡ ለሀገር ፡ እስመ ፡ ቀርበ ፡ ቅንየታ ፡፡ ኢወፅአ ፡ እምእዴሁ ፡ ኀበ ፡ ቅንየተ ፡ ካልኡ ፡፡ ለተበርብሮ ፡ ወለቅንየት ፡ (ዘፀ፮ ፡ ፯ ። ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፳፯ ። አስቴ ፡ ፯ ፡ ፱) ።

—፤ መፍጠር ፡ አፈጣጠር ፡ ፈጠራ ። እስመ ፡ ቅንየትከ ፡ ወምልክናከ ፡ ይሬስየከ ፡ ትማሀል ፡ ባዕለ ፡ ሰሉ ፡ (ጥበ፲፪ ፡ ፲፮) ።

**ቅኔ** ፤ አገዛዝ ፡ ባርነት ። ቅኔ ፡ እኩይ ፡፡ በዝንቱ ፡ ቅኔሃ ፡፡ አርዑተ ፡ ቅኔ ፡ (ኢሳ፲፬ ፡ ፫ ። ሰቈ፭ ፡ ፫ ። ገላ ፭ ፡ ፩) ።

—፤ ንግድ ፤ ተግባረ ፡ እድ ፤ አገልግሎት ። ቅኔ ፡ እደዊነ ፡ ሐናፀርዐ ፡፡ እምቅኔ ፡ እደዊሃ ፡ ትሁብ ፡ ለነዳያን ፡፡ ሥርዐተ ፡ ቅኔ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ዲድ ፡ ፲፫ና ፡ ፱ ። ኪዳ) ። መዓልትን ፡ ቀን ፡ ማለት ። በማርኛው ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ምቅናይ** ፤ መግዣ ፡ መገዠ ፤ ማስገዣ ፤ ቦታ ፡ ገባይ ። ቤተ ፡ ምቅናይክሙ ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፪) ።

**መቃኒት** ፤ (ታት) ፤ የሥቃይ ፡ መሣሪያ ፤ መቅጫ ፤ ማሸቈጥቈጫ ፤ በየስሙና ፡ በያይነቱ ። አዘዘ ፡ ሳቦር ፡ ንጉሥ ፡ ያምጽኡ ፡ መቃኒተ ፡ ሥቃይ ፡ ከመ ፡ ያፍርሆ ፡ ለቅዱስ ፡፡ አርአዮ ፡ ሰሉ ፡ መቃኒታተ ፡ ሥቃይት ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲ ። መጋ፯) ።

**ቅኑም** ፤ (ሱር ፡ ቅኑማ ። ዐረ ፡ አቅኑም) ፤ አካል ፤ ህላዌ ፤ ፍጹም ፡ ገጽ ፡ ፍጹም ፡ መልክ ፡ ያለው ፤ እኔ ፡ የሚል ። አካልንና ፡ ጠባይዕን ፡ ህላዌን ፡ ተመልከት ።

**አቃኒም** ፤ (ማት) ፤ አካላት ፤ አካሎች ፤ አካላቶች ። አቃኒመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እሙንቱ ፡ አስማት ፤ ወአስማትሂ ፡ እሙንቱ ፡ አቃኒም ፤ እስመ ፡ ትርጓሜሁ ፡ ለአቃኒም ፡ አካላት ፡ ጽኑዓን ፡ ቀዋምያን ፡ ፍጹማነ ፡ ገጽ ፡ ወመልክእ ፡ ብሂል ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**ቀንሞን** ፤ (ዕብ ፡ ቂናሞን ። ጽር ፡ ኪናሞን ። ዐረ ፡ ቂርፈት) ፤ ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፡ ቀረፋ ። በቀንሞን ፡ ፈንታ ፡ ቀንሞስ ፡ ቀናንሞስ ፡ ወይም ፡ ኹሉን ፡ ጕርድ ፡ ቀንሞ ፡ ቀናንሞ ፡ ይላል ፡ የጠፉ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ዘፀ፴ ፡ ፳፫ ። ራእ፲፰ ፡ ፲፫ ። ማሕ፬ ፡ ፲፬ ። ሔኖ፴ ፡ ፫ ። ፴፪ ፡ ፩) ።

**ቀኍናምት** ፤ (ዐረ ፡ ቀነም ፤ በግ ፡ መንጋ) ፤ በቁሙ ፤ ኩረጂ ፡ ኪስ ፡ ከረጢት ፡ አቅማዳ ፡ ቀምጣራ ፤ ተረንተራ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በቀኍናምት ፡ ፈንታ ፡ ቀኍናማት ፡ ይላል ፡ ያንዱን ፡ በብዙ ። አሐዱ ፡ ቀኍናማት ፡ ይኩን ፡ ለሰሉነ ፡፡ አእባነ ፡ ቀኍናማት ፡፡ ኀተምከ ፡ ውስተ ፡ ቀኍናማቲከ ፡ ጌጋይየ ፡ (ምሳ፩ ፡ ፲፬ ። ፲፮ ፡ ፲፩ ። ኢዮ፲፬ ፡ ፲፯) ።

**ቀኍናማት** ፤ ቀኍናማቶች ፡ የበግ ፡ የፍየል ፡ ስልቾች ።

**ቀኖና** ፤ (ናት ። ጽር ፡ ካኖን) ፤ ሕግ ፡ ሥርዐት ፡ ደንብ ፡ ፍርድ ፡ ቅጣት ። ቀኖና ፡ ብሂል ፡ ሥርዐት ፡፡ ቀኖናተ ፡ ነገሥት ፡፡ እመ ፡ ቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘዘመወ ፡ ም

ስለ፡ ወለተ፡ ብእሲቱ፡ ቀኖናሁ፡ ዐሠርቱ፡ ወኀምስቱ፡ ዓመት። ዘዘመወ፡ ምዕረ፡ አሐተ፡ ያጼርዎ፡ ቀኖና፡ ቀሊለ፤ ወለእመ፡ ተመይጠ፡ ያክብዱ፡ ላዕሌሁ፡ ቀኖና። ወሀቡ፡ ቀኖናተ፡ ክቡዳተ፡ (ፈ፡ መ፡ ፳፡ ፫። ፯፡ ፮። ስንክ፡ ነሐ፲፰)።

**ቀንነ**፤ ዐገገ፤ ሠራ፤ ደነባ፡ ሕግ፡ ሥራት፡ ደንብ፡ አቆመ፤ ቀኖና፡ ሰጠ። ቀንኑ፡ ላዕለ፡ ብእሲት፡ ዝግዐት። እመ፡ ቦ፡ ዘቀነነ፡ ርእሶ፡ በፈቃዱ፡ (ሲኖዶ። ቄድር)።

—፤ ቄንኖ፤ መቀኑንን፡ ሰጠ፡ ዐደለ፤ ቈረሰ፡ ከፈለ፤ ተንተን፤ ዘገን፡ ቃፈን፤ የምግብ።

**ተቀንነ**፤ ቀኖና፡ ያዘ፡ ተቀበለ። ተቄንኖ፤ መቀኑንን፡ አገኘ፤ ታደለ።

**ቀንዐ**፤—**ቀና**፤—**ቀኒእ፡ ቀንአ**።

**ቅንፍዝ**፤ (**ዕብ፡ ቂፎድ። ሱር፡ ቂፉዳ። ዐረ፡ ቁንፉድ፡ ዝ**)፤ ዣርት፤ እሾኻም፡ አውሬ፤ ጠጕሩ፡ እንደ፡ ጋሬጣ፡ እንደ፡ ምስማር፡ ያለ፤ ሽመልመሌ፡ ዐይነት፡ (ኢሳ ፲፬፡ ፳፫። ፴፬፡ ፲፩)።



ቅንፍዝ፡

**ቅንፍዛት**፤ **ቀናፍዝ**፤ ዣርቶች፤ ጠጕረ፡ ክፉዎች፡ ባለሾኽ፡ ጠጕሮች።

**ቀኒጽ**፤ **ጾት**፤ (**ቀነጸ፡ ይቀንጽ፡ ይቀንጽ**)፤ መነጣት፡ መቆም፡ አፈፍ፡ በርደግ፡ ማለት፤ መዝለል፤ መፈንጨት፤ መቅበጥ፡ መቈጣት፡ መቀናጣት፤ መር፡ ቸር፡ ባጥ፡ ፊናጥ፡ ማለት፤ መንጠቅ፡ መሸሽ፤ መሮጥ፡ መፈርጠጥ። ቀነጸ፡ እምዲበ፡ ሠረገላ። ቀንጺ፡ ላዕሌሁ፡ ወቀትሎ፡ በሰይፍ። ቀነጹ፡ ላዕለ፡ በራዊተ፡ ዮናናውያን። ቀነጹ፡ እምኔሃ፡ ወወፅአ። መጽአ፡ እንዘ፡ ይቀንጽ፡ (መጽ፡ ምስ። ዮሴፍ። ማሕ፪፡ ፰)።

**አቅንጾ**፤ አዘለለ፤ አስፈነጨ፡ አቀናጣ። ፍቅር፡ አንተ፡ አቅነጽኮ፡ እምዲበ፡ ሐመር፡ (መጽ፡ ምስ)።

**ተቃንጾ**፤ ተዛለለ፡ ተፈናጨ፡ ተሯሯጠ።

**አስተቃንጾ**፤ አዛለለ፡ አፈናጨ። ፈረስከ፡ ዘትጼዐኖ፡ እንዘ፡ ያስተቃንጽ፡ እግሮ፡ (ደራሲ)።

**ቍንጽ**፤ (**ጻት**)፤ ቍንጫ፤ ፈርዐጽ፤ የሚዘልል፤ የሚፈናጠር፡ (፩ነገ፡ ፳፬፡ ፲፭)።



ቍንጽ።

—፤ ቍንጬ፤ የቤት፡ የሰው፡ (ዐማርኛ)።

**ቍንጽል**፤ (**ዕብ፡ ሹዓል**)፤ ቀበሮ፤ ወይም፡ ተኵላ፤ ነጣቂ፡ የበረሓ፡ ውሻ፤ ክፉ፡ ተንኰለኛ፡ የመኳንንትና፡ የሰይጣናት፡ አምሳል። ቀበሮና፡ ተኵላ፡ እንደ፡ ነብርና፡ እንደ፡ ጥቍር፡ ዝንጀር፡ ይመሳሰላሉ፤ ዘመዳሞች፡ ናቸው፤ ከጥቍሬው፡ ዝንጀር፡ ነጩው፡ እንዲከፋ፡ ከቀበሮ፡ ተኵላ፡ ይከፋል። ነገዳቸውና፡ ጠባያቸው፡ አንድ፡ ስለ፡ ኾነ፡ ዘተኵላ፡ ፈንታ፡ ቍንጽል፡ ይላል። ሑሩ፡ በልዎ፡ ለዛቲ፡ ቍንጽል። ይበውእ፡ አንበሳ፡ ውስተ፡ ግበ፡ ቍንጽል፡ አው፡ ቍንጽል፡ ኀበ፡ አንበሳ። ሰይጣንሰ፡ ቍንጽል፡ ኁሕላዊ፡ (ሉቃ ፲፫፡ ፴፪። አኖል። ቄድር)።



ቍንጽል፡

**ቈናጽል**፤ ተኵሎች፤ ቀበሮዎች፡ ቀበራርት። አሥግሩ፡ ለነ፡ ቈናጽለ፡ ንኡሳነ። ወአኀዘ፡ ሠለስተ፡ ምእተ፡ ቈናጽለ። ለቈናጽልኒ፡ ግበብ፡ ቦሙ፡ (ማሕ፪፡ ፲፭። መሳ፲፭፡ ፬። ማቴ፰፡ ፳)።

**ቋንቋ**፤ በቁሙ፤ ልሳን፤ የቃል፡ የነገር፡ ስልት፡ (ዐማርኛ)።

**ቍንቍኔ**፤ ቍንቍን፤ ጥንጣን፤ ማንደ፡ ቈርቍር፤ ነቀዝ፡ ብል፤ ትል፤ የዕፅና፡ የእኽል፡ የልብስ፡ ተባይ። ባዬ፡ ወቍንቍኔ። ከመ፡ ብላዐ፡ ቍንቍኔ። ልብስ፡ ዘተበልዐ፡ እምቍንቍኔ፡ (ኢሳ፶፩፡ ፰። ማቴ፮፡ ፲፱። መ፡ ፈ)።

—፤ ቅንቅን፤ የደሮ፡ ቅማል፤ ጨፍ፡ የሚያከክል።

**ቈንቈነ**፤ በቁሙ፤ ነቀዘ፤ ጠነጠነ፤ ተላ፤ አረጀ፤ አፈጀ። ወአልባሲክሙኒ፡ ቈንቈነ። ዘኢይበሊ፡ ወዘኢይማስን፤ ወዘኢይቈነቍን፡ (ያዕ፭፡ ፪። ቄድር)።

**ቀኒት**፤ **ዮት**፤ (**ቀነተ፡ ይቀንት፡ ይቅንት። ዐረ፡ ነጠቀ**)፤ መቀነት፤ መታጠቅ፤ ወገብን፡ ማሰር፤ ማጥበቅ፤ ማገልደም፡ ማሸረጥ፡ ማሸንፈጥ፤ ማሸንቀጥ፤ በትጥቅ፡ ማጌጥ። ቅንት፡ ሐቌከ፡ ከመ፡ ብእሲ። ቅንት፡ ሰይፈከ፡ ኀያል፡ ውስተ፡ ሐቌከ። ቀነተት፡ ሠቀ፡ ውስተ፡ ሐቌሃ። ቅንት፡ ስልብስ፡ ዐጌ፡ ወቀነትኩ። ህየንተ፡ ቅናትኪ፡ ዘወርቅ፡ ሐብለ፡ ቅንቲ፡ (ኢዮ፴፰፡ ፫። መዝ፡ ፵፬። ዮዲ፰፡ ፭። ኄርማ። ኢሳ፫፡ ፳)።


**ቀናቲ**፤ (**ቲት፡ ትያን፡ ያት**)፤ የሚቀንት፡ የሚያጠብቅ፤ የሚታጠቅ፤ ታጣቂ።

**ቅኑት**፤ (**ታን፡ ታት፡ ንት**)፤ የታጠቀ፤ የተቀነተ፤ ቅንት፤ ዝግጁ፤ ልባም። ቅኑት፡ ሐቌሁ፡ በወርቅ። ቅኑታነ፡ ዐስቅ። ቅኑታነ፡ አስይፍት፡ (ዳን፲፡ ፭። ሕዝ፳፫፡ ፲፭፡ ፲፭። ኩፋ፡ ፴፯)።

**ቅናት ፤ (ታት ፡ ቅናውት) ፤** በቁሙ ፤ መቀነቻ ፡ መታጠቂያ ፤ ትጥቅ ፤ የወገብ ፡ ማሰሪያ ፤ ቀበቶ ፡ ዝናር ፡ መቀነት ። በቅናቱ ፡ ዘአዲም ። በቅናት ፡ ዘወርቅ ። አልባሰ ፡ ወቅናታተ ። ወኢይፍትሑ ፡ ቅናውቲሆሙ ፤ (ማቴ፲ ፡ ፱ ። ራእ፩ ፡ ፲፫ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፴ ። ኢሳ፭ ፡ ፳፯) ።

**አቅነተ ፤** አስቀነተ ፤ አስታጠቀ ፤ አሰለፈ ። በዐድ ፡ ያቀንተከ ። አቀንተክሙ ፡ ብልባሴ ። ዘያቀንቶ ፡ ለሰማይ ፡ በደመና ፤ (ዮሐ፳፩ ፡ ፲፰ ። ዓሞ፰ ፡ ፲ ። መዋሥ) ።

**ቀሡት ፤ (ዕብ ፡ ቁሜት) ፤** የቀለም ፡ ዕቃ ፤ ቢልቃጥ ፤ ሙዳየ ፡ ቀለም ፡ የገንቦና ፡ የማድጋ ፡ ዐይነት ። ገንቦ ፡ ማድጋ ፤ እንስራ ፤ የውሃ ፡ ዕቃ ፤ ሸክላ ። ቀሡተ ፡ ጸሓፊ ። ቀሡተ ፡ ልሕዘት ። ስተይ ፡ ማየ ፡ እምቀሡትከ ፤ (ሕዝ፱ ፡ ፪ ። ኤር፲፱ ፡ ፩ ። ምሳ፭ ፡ ፲፭) ።



ቀሡት ፤

**ቀሡታት ፤ ቀሣውት ፤** ማድጎች ። ቀሡታተ ፡ ይጽዐኑ ፡ በአንበሳ ። ቀሣውቲሆሙ ፤ (ደራቢ ። ኤር፲፱ ፡ ፫) ።

**ቀሢጥ ፤ ጦት ፤ (ቀሠጠ ፡ ይቀሥጥ ፡ ይቅሥጥ ። ዐረ ፡ ቀሸጠ) ፤** መቅሠጥ ፤ ማንሣት ፡ ማንሣሣት ፤ ከፍሎ ፡ መስረቅ ፡ መደበቅ ፤ ማታለል ፡ መቅጠፍ ። ቀሢጠ ፡ ንዋየ ፡ ባዕድ ። ዘይቀሥጥ ፡ እምቤተ ፡ እግዚ ። ቀሠጡ ፡ መንፈቀ ፡ ሤጡ ። ከመ ፡ ትቅሥጠሙ ፡ በተሳልሞ ፡ ፀሮሙ ፤ (መቃ ። ቀሌ ። ግብ፭ ፡ ፪ ። ዮሴፍ) ።

**ቀሣጢ ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት ፤ ሥጥ) ፤** በቁሙ ፤ ሌባ ፡ ቀጣፊ ፤ አታላይ ። በሬቂ ፡ ወቀሣጢ ፡ ዘእንበሩ ፡ ብየ ፤ (አዋል) ።

**ቈሥጤ ፤ (ዕብ ፡ ቁባህ) ፤** ቈሽት ፤ ሸንፍላ ፡ ፊሽኝ ፤ (ዘዳ፲፰ ፡ ፫) ።



ቈሥጤ ፤

**ቀሢም ፤ ሞት ፤ (ቀሠመ ፡ ይቀሥም ፡ ይቅሥም ። ቀጠፈ) ፤** መቅሠም ፤ መልቀም ፡ መቃረም ፡ መቍረጥ ፡ ማጨድ ፡ መጨርገድ ፤ ማርገፍ ፤ መሰብሰብ ፡ ያታክልት ። በከመ ፡ ይቀሥምዎ ፡ ለዘይት ፡ ከማሁ ፡ ይቀሥምዎሙ ። ከመ ፡ ዘየአርር ፡ ድኅረ ፡ ዘይቀሥም ። ቅሥም ፡ አስካሎ ፡ ለዐጺደ ፡ ወይን ። ቀሠምነ ፡ ለከ ፡ ስምዐ ፡ እመጻሕፍት ፤ (ኢሳ፳፬ ፡ ፲፫ ። ሚክ፯ ፡ ፳፩ ። ራእ፲፬ ፡ ፲፱ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ቀሣሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት ፤ ሣም ፡ ሠምት) ፤** የሚቀሥም ፡ የሚለቅም ፤ ለቃሚ ፡ ቈራጭ ። አድኅነኒ ፡ እምቀሣሚ ፡ ወይን ፡ አመ ፡ ያሌዕል ፡ ማዕጺዶ ። ሶበ ፡ ቦኡ ፡ ቀሣም ፡ ላዕሌከ ፤ (ድራሴ ። ዐብድ ፡ ፭) ።

**መቅሠም ፤** መልቀሚያ ፡ መቍረጫ ፡ አጭዘ ፡ መቅሠሞ ፤ (ሆሴ፯ ፡ ፲) ።

**አቅሠመ ፤** አስለቀመ ፤ አስቈረጠ ። ወያቀሥሞሙ ፡ ቀሥሞ ፤ (፩ነገ ፡ ፰ ፡ ፲፪) ።

**ተቀሥመ ፤** ተለቀመ ፤ ተቈረጠ ። እንበለ ፡ ይትቀሠም ፡ ወይን ፤ (ዘኍ፲፫ ፡ ፳) ።

**ቅሡም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ሥምት) ፤** የተቀሠመ ፤ የተለቀመ ፤ ልቅም ፤ ቍርጥ ።

**ቅሥመት ፤** መልቀም ፡ መቍረጥ ፤ መቈረጥ ፤ አቈራረጥ ፤ ቈረጣ ፡ ለቀማ ። ቅብዐ ፡ ዘይት ፡ ዘቀዳሚ ፡ ቅሥመታ ፤ (ዘፀ፳፯ ፡ ፳) ።

**ቀሥም ፤ (ብ ፡ አቅሣም) ፤** የተክል ፡ መከር ፡ አዝመራ ፤ ፍሬው ፡ የሚለቀምበት ፤ የለቀማና ፡ የቈረጣ ፡ ወራት ። የኀብር ፡ ቀሥም ፡ ምስለ ፡ ማእረር ፤ (ኅሞ፱ ፡ ፲፫ ። ዘሌ፳፯ ፡ ፭ ። መሳ፰ ፡ ፪) ።

—፤ ፍሬ ፤ ሕንባብ ፤ አበባል ፤ ተለቅሞ ፡ ተቈርጦ ፡ ያለ ። በመዋዕለ ፡ ማእረረ ፡ ቀሥም ። አቅሣመ ፡ ዐጺድ ። ይሴፈዉ ፡ ቀሥሞ ፤ (ሚራ፳፱ ፡ ፳፯ ። ሥር ፡ ጳጕ ። ማር ፡ ይሥ፲፭ ፡ ፩) ።

**ተቀሣም ፤ (ማት) ፤** ለቀማ ፡ ቈረጣ ፤ አዝመራ ፤ ዐጸቅ ፡ ዘለላ ። ወተቀሣመ ፡ ፍሬሃ ፤ (አርጋ ፡ ፬) ።

**ቀሠመ ፤—አጣፈጠ ፤—ቀሰመ ።**

**አስተቃሠመ ፤—አሻረተ ፤—ቀሰመ ።**

**ቀሢፍ ፤ ፎት ፤ (ቀሠፈ ፡ ይቀሥፍ ፡ ይቅሥፍ ፤ ቀጠፈ ። ዐረ ፡ ቀጸፈ) ፤** መቅሠፍ ፤ መቅጠፍ ፡ መዘንጠፍ ፤ መቍረጥ ፡ መቅፈፍት ፤ ባጭር ፡ ማስቀረት ፤ የተክል ፡ የሰብል ፡ የሕፃን ። መግፈፍ ፡ መግለጥ ፤ ማስራቈት ፤ ዕራቍት ፡ ማስጣል ፤ ለመግረፍ ።

—፤ መግረፍ ፤ መጠብጠብ ፤ መምታት ፤ መቅጣት ፡ መዝለፍ ፡ መገሠጽ ። ዘይቀሥፍ ፡ ብዕራይሁ ። ይቀሥፎሙ ፡ ለአሕዛብ ። ቀሠፍከኒ ፡ ወተቀሠፍኩ ። እግዚኦ ፡ በመዐትከ ፡ ኢትቅሥፈኒ ፤ (ሚራ፴፰ ፡ ፳፭ ። ራእ፲፱ ፡ ፲፭ ። ኤር፳፰ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፮ ። ኢሳ፲፭ ፡ ፬) ።

**ቀሣፊ ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት) ፤** የሚገርፍ ፤ ገራፊ ፤ ቀጪ ። ኀበ ፡ ቀሣፊሁ ፤ (ኢሳ፱ ፡ ፲፫) ።

**አቀሠፈ** ፤ አስቀሠፈ ፡ አስገፈፈ ፡ አስገረፈ ፤ አስቀጣ ።

**ተቀሥፈ** ፤ ተቀሠፈ ፡ ተመታ ፡ ተቀጣ ፤ ተገረፈ ። ሕቡል ፡ እንዘ ፡ ይትቀሠፍ ። በተቀሥፎ ፡ ወበተሞቅሖ ። ወኢትቀሥፉ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ። ተቀሥፈት ፡ ፀሓይ ፤ ተመታች ፡ (ሚራ፲፱ ፡ ፳፭ ። ፪ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፸፪ ። ራእ ፰ ፡ ፲፪) ።

**ቅሡፍ** ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ሥፍት) ፤ የተቀሠፈ ፡ የተገረፈ ፤ የተመታ ፡ (መዝ ፡ ፸፪ ። ኢሳ፶፫ ፡ ፫ ፡ ፬) ።

**ቅሥፈት** ፤ (ታት) ፤ መግረፍ ፤ መገረፍ ፤ አገራረፍ ፡ ግርፊያ ፤ ግርፋት ፤ ቍስል ፤ ደዌ ፡ መከራ ። ወኀፀበሙ ፡ እምቅሥፈቶሙ ። በቅሥፈታቲሁ ። ወሐይወ ፡ ኢዮብ ፡ እምድኅረ ፡ ቅሥፈቱ ፡ (ግብ፲፮ ፡ ፴፫ ። ደራሲ ። ኢዮ፵፪ ፡ ፲፯) ።

—፤ መውጫ ፤ ውጭ ፡ ዕዳሪ ። ወቅሥፈቱ ፡ ብሔረ ፡ ምድያም ፡ (ኩብ ፡ ነገ) ።

**መቅሠፍት** ፤ (ታት) ፤ መግረፊያ ፤ ጅራፍ ፡ በለንጋ ፡ ከዘራ ፡ ጨንገር ፤ የመሰሰው ፡ ኹሉ ። መቅሠፍት ፡ ወተግሣጽ ። ቍስለ ፡ መቅሠፍት ፡ ይገብር ፡ አምግልተ ። ድምፀ ፡ መቅሠፍት ። ወገብረ ፡ መቅሠፍተ ፡ ጥብጣቤ ፡ ዘሐብል ፡ (ሚራ፳፪ ፡ ፯ ። ፳፰ ፡ ፲፯ ። ናሖ፫ ፡ ፩ ። ዮሐ፪ ፡ ፲፭) ።

—፤ ግርፋት ፤ ቍስል ፤ ሰንበር ፤ በትር ፤ ቅጣት ። መጠውኩ ፡ ዘባንየ ፡ ለመቅሠፍት ። ምንትኑ ፡ ዝ ፡ መቅሠፍት ፡ ዘማእከለ ፡ እደዊከ ። ዘየአምር ፡ ፈቃደ ፡ እግዚኡ ፡ ወኢይገብር ፡ ብዙኀ ፡ መቅሠፍቱ ፡ (ኢሳ፶ ፡ ፮ ። ዘካ፲፫ ፡ ፮ ። ሉቃ፲፪ ፡ ፵፯) ።

—፤ በቁሙ ፤ የእግዜር ፡ በለንጋ ፤ መቅሥፍያ ፡ ፍርድ ፡ ቅጣት ፤ መከራ ፡ ሥጋ ። ዓዲ ፡ አሐተ ፡ መቅሠፍተ ፡ ኣመጽእ ፡ ዲበ ፡ ፈርዖን ፡ ወዲበ ፡ ኵሉ ፡ ግብጽ ። ሰብዐቱ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ይጸውሩ ፡ ሰብዐተ ፡ መቅሠፍተ ። አርባዕቱ ፡ መቅሠፍት ፡ እኩያት ፡ (ዘፀ፲፩ ፡ ፩ ። ራእ፲፭ ፡ ፩ ። ሕዝ፲፬ ፡ ፳፩) ።

**ምቅሣፍ** ፤ (ፋት) ፤ መግረፊያ ፤ መገረፊያ ፤ ማስገረፊያ ፡ ቦታ ።

**ቀሥፍ** ፤ **ቅሥፍ** ፤ አፍኣ ፡ ዕዳሪ ፡ ገጠር ፤ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ያለ ፡ አገር ፤ ከቤት ፡ ውጭ ፡ ያለ ፡ ዐዘቅት ፡ ኵስሕ ፤ ሜዳ ። ይቁሙ ፡ ቅሥፈ ፡ እቶተ ። አይሁድ ፡ እለ ፡ ተዘርዉ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሓውርት ፡ ቀሥፍ ። ይነብር ፡ ጽሙ ፡ ቅሥፈ ፡ (ቀሌ ። አስቴ፱ ፡ ፲፱ ። መሳፍ ፡ ፳፬) ።

**ቀሠፋይ** ፤ አፍኣዊ ፤ ዘአፍኣ ። ይፍልጥ ፡ መንጠላዕተ ፡ ውሳጤ ፡ ወቀሠፋየ ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፴፫) ።

**ቀሣር** ፤ (ራት ። ዐረ ፡ ቂሽረት ። ዕብ ፡ ቃሽቋሼት) ፤ ገለፈት ፡ የዓሣ ፡ ቅርፍት ፡ ዘሶ ፡ ክንፍ ፡ ወቀሣር ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፱—፲፪ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ሕዝ፳፱ ፡ ፬) ።

**ቀሡት** ፤—ማድጋ ፤—ቀሠወ ።

**ቀሥት** ፤—በቁሙ ፤—ቀስት ።

**ቅሥት** ፤—ክርክር ፤—ወቀሠ ።

**ቋዕ** ፤—ቍራ ፤—ቀዊዕ ፡ ቀዐ ።

**ቃዕደወ** ፤ (ዐደወ ፤ ቀደወ ። ዐረ ፡ ቀዐደ ፤ ተቀመጠ) ፤ አሻግሮ ፡ አየ ፡ ተመለከተ ፤ ዐይኑን ፡ አርቆ ፡ ጣለ ፤ አሬመደ ፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ ማየ ፡ ለማየ ። ቀ ፡ ከቀደወ ፡ መጥቶ ፡ በፀደወ ፡ ላይ ፡ ተደርቧል ።

**አንቃዕደወ** ፤ አንጋጠጠ ፤ አሻቀበ ፤ ተንጋጠጠ ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አየ ፤ ዐይኑን ፡ ሰከለ ፤ ጸለየ ፡ ለመኑ ። (ተረት) ፤ ከመሮጥ ፤ ማንጋጠጥ ። ይትፌሣሕ ፡ በሰርጕ ፡ ሰማያት ፡ ሶበ ፡ ያንቃዕዱ ። ጕዩ ፡ ኀበ ፡ ታቦት ፡ ወአንቃዕደዉ ፡ ኀበ ፡ ኖኅ ፡ ከመ ፡ ይንሥአሙ ፡ ኀቤሁ ። ሳዕለ ፡ ሳዕለ ፡ እንዘ ፡ ያንቃዕዱ ፤ በነጽሮ ፡ ተሰብረ ፡ ክሣዱ ። አንቃዕደወ ፡ ሰማየ ፡ ኀቤከ ፡ ኀበ ፡ አቡሁ ። አልዐለ ፡ እደዊሁ ፡ ወአንቃዕደወ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ወኀሊናቲሁ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ቀሌ ። ቅኔ ። ቅዳ ። ፊልክ ፡ ፳፫) ።

**እንቅዕድው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ዱት) ፤ ያንጋጠጠ ፤ የተንጋጠጠ ፡ ዐይኑ ፡ ልቡ ፡ የተመሠጠ ፤ ሰማይ ፡ ለማይ ፡ የሚያይ ፡ (አርጋ) ።

**ቈዐለ** ፤ (ይቈዕል ፡ ይቈዐል ። ቀዊዕ ፡ ቀዐ) ፤ ሠባ ፡ ወፈረ ፡ ሰማ ፡ ኾነ ፤ አደገ ፡ አፈረጠመ ።

**መቍዐል** ፤ (ብ ፡ መቋዕል ፡ ልት ። ዐረ ፡ ሙካል ፤ ሙቅለት) ፤ ሥብ ፡ ወፍር ፡ ሰማ ። የሠባ ፡ የወፈረ ፡ ያፈረጠመ ፤ ወረሞ ፡ አውላዲ ፡ መሐስዕ ። መቍዐለ ፡ ጠሊ ፡ ወላሕም ። እለ ፡ ይሴስዩ ፡ መቋዕለ ። ቍርባናተ ፡ ወመቋዕልተ ፡ (ዘዳ፴፪ ፡ ፲፬ ። ዓሞ፯ ፡ ፬ ። ፪ዜና ፡ ፯ ፡ ፯) ።

**ቀዒን** ፤ ኖት ፤ (ቀዐነ ፡ ይቅዕን ፡ ይቅዐን ። ቀነየ) ፤ ማስጨነቅ ፡ ማስጠበብ ፤ ማጣበቅ ። መጨነቅ ፡ መጠበብ ፡ መጣበቅ ፤ የቦታ ።

**ተቃዐነ** ፤ ተጫነቀ ፤ ተጨናነቀ ፤ ተጣበበ ፡ (ሉቃ፰ ፡ ፵፭) ።

**መቅዐን** ፤ (ብ ፡ መቃዕን) ፤ የሚያስጨንቅ ፤ የሚያስጠብብ ፡ ጠባብ ። ጭንቅ ፡ ጥብ ፤ አጣብቂኝ ። ፍኖት ፡ እንተ ፡ ትወስድ ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፤ ጽዕቅት ፡ ወመቅዐን ፤ ይእቲ ። እስመ ፡ መቅዐን ፤ ወጠዋይ ፡ ምሕዋሪ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፬ ። ደራሲ) ።


**መቅዓን** ፤ (ናት) ፤ የሥቃይ ፡ መሣሪያ ፡ የሚያጣብቅ ፡ የሚጠረቅቅ ፤ የሚያጠግ ፡ የሚጠመዝዝ ። አዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ይደይዎ ፡ ውስተ ፡ መቅዓን ፡ እስከ ፡ ይነቅዕ ፡ መለያልዩሁ ፡ ወይጠወይ ፡ ሥጋሁ ፡ በእኩይ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲፯) ።

**ቃፍ** ፤ (ዕብ ፡ ማጣራ) ፤ ጊጤ ፡ በላማ ፤ መጋፊያ ፤ ብራኣ ። የመጠራን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ከመ ፡ ቃፍ ፡ (ኢዮ፲፯ ፡ ፲፱) ።

**ቃፍ** ፤ (ዐረብ) ፤ ስሙ ፡ ፊደል ፡ ቀ ። ጋፍ ፡ ወንቃፍ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ቀፉዲት ፤ (ጽር ፡ ኻፉሪ ። ዕብ ፡ ክፎሬይ) ፤** ምንዛህ ፤ ምግዝፉቅ ፡ የውሃ ፡ የጠበል ፡ መርጫ ። ነኀዘህንና ፡ ዘረቀን ፡ ተመልከት ፡ (፳፬ንገ ፡ ፳ ፡ ፳፺) ፡ ባለ ብሉዮች ፡ ጻሕል ፡ ጽዋ ፡ ይሉታል) ።

**ቀፎ ፤ (ዐረ ፡ ቁፈት ። ዕብ ፡ ቁፉሀ) ፤** እንቅብ ፡ ቅርጫት ፡ አገልግል ፤ ከፈር ። በቁሙ ፤ የንቦች ፡ ቤት ፡ ሣጥን ፡ ኹለት ፡ አፍ ፡ ያለው ፤ ወይም ፡ ጕድጓድ ፤ ማኅ ፡ ቀባ ፤ ሰው ፡ ያልሠራው ፤ ንባም ፡ ማራም ፡ ቦታ ፡ ዛፍ ። ቀፎ ፡ ዘመዓር ፡ (፩ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፳፭) ።



ቀፎ ፡

**ቀፈዋት ፤** ቀፎዎች ። ክልኤ ፡ ቀፈዋተ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ቈፉዝ ፤ (ጽር ፡ ኬፉዝ) ፤** አፌዝ ፤ ጥሩ ፡ ወርቅ ፤ ምዝምዝ ። ርእሱ ፡ ወርቀ ፡ ቈፉዝ ፡ (ማሕ፭ ፡ ፲፩) ። ፎዘን ፡ ተመልከት ።

(ጥሬ) **ቀፈል ፤ ሎት ፤ (ቀፈለ ፡ ይቀፍል ፡ ይቅፍል ። ዕብ ፡ ቃፉል) ፤** ማጠፍ ፡ መደረብ ፤ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ማድረግ ፤ መጠምጠም ፤ ማልበስ ፡ መሸፈን ፡ መለበጥ ፡ ማስጌጥ ። በዐረብ ፡ ግን ፡ ቀፈለ ፡ ብሎ ፡ ቈለፈ ፡ ዘጋ ፡ ያሰኛል ። ከመ ፡ ብሩሪ ፡ ተምያን ፡ ዘቀፈልዎ ፡ ባዕለ ፡ ንዋየ ፡ ሰብሓ ። ዘቀፈሎን ፡ በብሩር ። ቀፈልየ ፡ በዐረር ፡ (ምሳ፳፮ ፡ ፳፫። ዘፀ፴፰ ፡ ፲፱ ። ድር ፡ ሚክ) ።

**አቅፈለ ፤** አስለበጠ ፡ አስለበሰ ። እሴፊ ፡ አቅፈለት ፡ (መስቀለ) ፡ በወርቅ ፡ ወበዕንቍ ፡ ክቡር ፡ (ድጓ) ።

**ተቀፍለ ፤** ተለበጠ ፤ ተሸለመ ፤ ለበሰ ፡ አጌጠ ። ይትቀፈሉ ፡ ወርቀ ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፳፱ ። ፳፮ ፡ ፲፩) ።

**ቅፉል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ፍልት) ፤** የተለበጠ ፡ ልብጥ ። ቅፉለ ፡ ወርቅ ። እለ ፡ ቅፉላን ፡ በብሩር ፡ (አርጋ ፡ ፬ ። ኢሳ፴ ፡ ፳፪ ። ዘፀ፳፮ ፡ ፴፪ ። ፴፯ ፡ ፬ ፡ ፲፭) ።

**ቅፍሎ ፤ (ብ ፡ ቀፉልው ፤ ሉት) ፤** ቈጽለ ፡ ወርቅ ፤ ሥሥ ፡ ረቂቅ ፤ ልብጠት ፤ ቅባት ። ቅፍሎ ፡ ወርቅ ፡ (ዘፀ፴፰ ፡ ፲፰ ። ፴ ፡ ፫ ፡ ፳) ።

**መቅፈል ፤ ልት ፤ (ብ ፡ መቃፍልት) ፤** መለበጫ ፡ ልባጥ ፤ ሽልማት ፡ ጌጥ ። ወትገብር ፡ መቃፍልቲሃ ፡ ለታቦት ፡ በወርቅ ፡ ጽሩይ ፡ (ክብ ፡ ነገ) ።

**ቀፈፍ ፤ (ቀፈ ፡ ዐረብ ። ሱር ፡ ቃፈፍ ። ዕብ ፡ ቃፉእ) ፤** መርጋት ፤ መጽናት ፤ እንደ ፡ ዳቦና ፡ እንደ ፡ ደንጊያ ፡ መኾን ፤ የፈሳሽ ፡ ነገር ፤ የሠም ፡ የውርጭ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። መጨከን ፡ ልብ ፡ ደንጊያ ፡ መኾን ፤ አለመፈራት ፡ አለማዘን ፤ መወፈር ፡ መግዘፍ ፡ መታበይ ። በቁሙ ፤ መቅፈፍ ፡ መከርከም ፤ ማስተካከል ። (ዐማርኛ) ።

**ቀፈት ፤** ሆድ ፡ ዕቃ ፡ ደንደስ ፤ ጥናት ፤ ድርቅና ፤ ጭከኔ ፤ ትዕቢት ፡ ግዘፍ ፡ ድንዳኔ ። ቀፈቶሙ ፡ አጽንዖሙ ። ይወዲ ፡ ርእሶ ፡ ዲበ ፡ ብረኪሁ ፡ ወያደንኑ ፡ ቀፈቶ ፡ ወያቴሕት ፡ ኅሊናሁ ። ኢያትሕትከ ፡ ቀፈተ ፡ ልብከ ። ቀፈተ ፡ ልብ ፡ ዘሥጋ ፡ (ቄር ። ቄድር ። መቃ ። ቅዳ) ።

**ቀፈጽ ፤ ጾት ፤ (ቀፈጸ ፡ ይቀፍጽ ፡ ይቅፍጽ ። ዕብ ፡ ቃፉጽ ፤ ቀንጺ) ፤** መግለጥ ፤ መክፈት ፤ መግፈፍ ፤ ማስፈቴት ። ቀልዐን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ። ቀፈጽኪ ፡ አቍያጸኪ ። ቀፈጽኪ ፡ ኀፍረተኪ ። መኑ ፡ ይቀፍጽ ፡ ግልባቤ ፡ ገጹ ። ይቀፍጾን ፡ እግዚ ፡ አልባሲሆን ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፳፭ ፡ ፴፯ ። ኢዮ፵፱ ፡ ፬ ። ኢሳ፫ ፡ ፲፯) ።

**ቀፉጺ ፤ (ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት) ፤** የሚገልጥ ፤ ገላጭ ፡ ገፋፊ ።

**ተቀፍጸ ፤** ተገለጠ ፤ ተገፈፈ ፤ ተከፈተ ። ወይትቀፈጽ ፡ ኀፍረቶሙ ፡ ለግብጽ ። ተቀፈጽኪ ፡ እምድኅሬኪ ። ይትቀፈጽ ፡ ኆኅት ፡ (ኢሳ፳ ፡ ፬ ። ኤር፲፫ ፡ ፳፪ ። ቅዳ) ።

**ቅፉጽ ፤ (ጻን ፡ ጺት ፡ ፍጽት) ፤** የተገለጠ ፤ የተገፈፈ ፤ ግልጥ ፡ ክፍት ፤ ባይ ።

**ቀፈር ፤ ሮት ፤ (ቀፈረ ፡ ይቀፍር ፡ ይቅፍር) ፤** መቈፈር ፡ መፈልፈል ፤ መፈለቅ ፤ መከርከር ፤ የመሬት ፡ የንጨት ፤ የደጋን ፡ የሚዛን ። መቀፈር ፡ መቀቀር ፤ ማሰብ ፡ መደገን ፤ የገሮ ፡ የቀስት ፡ የንፍጥ ። መጠየቅ ፡ መመርመር ፤ ትንቢት ፡ መፈለግ ፤ ከነቢይ ፡ ከካህን ።

**ቀፈር ፤ ቅፍር ፤** ክርክር ፤ ፍልቅ ፤ ፍልፍል ፤ የኹርማት ፡ መግቢያ ፡ የንጨት ፡ መጋጠሚያ ። ቀፈረ ፡ ሐጽ ። ቀፈረ ፡ ዐምድ ፡ (ማር፲ ፡ ፳፭ ። ዘፀ፳፮ ፡ ፳፱ ።

**መቅፈርት ፤ (ዕብ ፡ ኤፎድ ። ጽር ፡ ኤፖሚዳ) ፤** ልብስ ፡ ኢፉድ ፤ ከአልባስ ፡ ክህነት ፡ አንዱ ፤ ትንቢት ፡ ማወቂያ ፤ መጠየቂያ ፡ መመርመሪያ ። አፈደን ፡ ተመልከት ። ትብልያ ፡ ዘመቅፈርት ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፬) ።

**ቀፈት ፤— ደንደስ ፤— ቀፈፍ ።**

**ቀጺብ ፤ ቦት ፤ (ቀጸበ ፡ ይቀጽብ ፡ ይቅጽብ ። ዐረ ፡ ቀጸበ ። ዕብ ፡ ቃጻብ ፤ ቈረጠ ፤ ወሰነ) ፤** መቅጸብ ፤ ዐይንን ፡ መክፈትና ፡ መክደን ። መጥቀስ ፤ በዐይንና ፡ በእጅ ፡ መጥራት ፡ ማመልከት ፤ ከንፈርን ፡ መንከስ ። (ተረት) ፤ ባይን ፡ ጥቅሻ ፡ በከንፈር ፡ ንክሻ ። ይቀጽብ ፡ በዐይን ። ይቀጽብ ፡ በእዴሁ ። እን

በስብሶ ፡ በቀራንብት ፡ ወቀጺብ ፡ በአዕይንት ፡ ዘእንበለ ፡ ኀፍረት ። ወቀጸባ ፡ ከመ ፡ ታምጽኢ ፡ (ምሳ፳ ፡ ፲፫ ። ኪዳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፬ ፡ ፳ ። ገድ ፡ ተክ) ።

—፤ መመስል ፡ መተረት ፤ ምሳሌ ፡ መስጠት ። መፍጠን ፤ መቀልጠፍ ፤ ማፈግ ፡ ማላገጥ ።

**ተቃጸበ** ፤ ተጣቀሰ ፡ ተጠቃቀሰ ። የሐውራ ፡ እንዘ ፡ ይትቃጸባ ፡ በአዕይንቲሆን ። ዘይትቃጸብ ፡ በአዕይንቲሁ ። ይሬእይዎ ፡ ወይትቃጸቡ ፡ ቦቱ ፡ (ኢሳ፫ ፡ ፲፮ ። ምሳ፲ ፡ ፲ ። ጥበ፬ ፡ ፲፰) ።

**ቅጽበት** ፤ መጥቀስ ፤ መጠቀስ ፤ አጠቃቀስ ፤ ጥቅሻ ፡ ንክሻ ። በቁሙ ፤ ፍጥነት ፤ ችኰላ ፤ ቅልጠፋ ፤ ወዲያው ፤ ቶሎ ፤ ድንገት ፡ ጥቂት ፡ ሳይቈይ ፡ ሳይዘገይ ። ይኤምር ፡ በቅጽበተ ፡ አጺብዕ ። ዘነበበ ፡ በጊዜሁ ፡ ይገብሮ ፡ ወዘንበየ ፡ በቅጽበት ፡ ይከውኖ ። በመጠነ ፡ አሐቲ ፡ ቅጽበት ። ኢተፈልጠ ፡ መለኮት ፡ እምትስብእት ፡ ወኢከመ ፡ ቅጽበተ ፡ ዐይን ። ወበሣልስ ፡ ንፍኃተ ፡ ቀርን ፡ ይትነሥኡ ፡ ሙታን ፡ ከመ ፡ ቅጽበተ ፡ ዐይን ፡ (ምሳ፳ ፡ ፲፫ ። ቅዳ ፡ ግሩ ። ጥበ፲፰ ፡ ፲፱ ። ሃይ ፡ አበ ። ቅዳ ፡ ያዕ) ።

—፤ ጥቅስ ፤ ምሳሌ ፤ ተረት ፤ አንጻር ። ነገረ ፡ ጠቢባን ፡ በቅጽበት ። ፈክሮ ፡ ቅጽበት ፡ (ምሳ፩ ፡ ፮ ። ጥበ፰ ፡ ፰) ።

**ቀጸበ** ፤ (ትግ ። ዕብ ፡ ቃጸፍ) ፤ ተቈጣ ፤ ተናደደ ፤ ወገሸ ፡ አበደ ፤ ቱግ ፡ አለ ፤ እሳት ፡ ኾነ ።

**ቀጸወ** ፤—ጣደ ፡ አበሰለ ፤—ቀፀወ ።

**ቈጺል** ፤ ሎት ፤ (ቈጸለ ፡ ይቈጽል ፡ ይቈጽል ። ሐመለ ፤ ለምለመ) ፤ ማቈጸል ፤ ቅጠል ፡ ማውጣት ፤ መለምለም ፤ ማቀጠል ፡ ማጀፍጀፍ ፤ ዐጽቃም ፡ ቅጠላም ፡ መኾን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በቈጸለ ፡ ፈንታ ፡ አቈጸለ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (አር.ጋ ፡ ፩) ።

**ቍጹል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ጽልት) ፤ ያጀፈጀፈ ፤ ቅጠላም ፤ ባለቅጠል ። ቈጽለ ፡ ዕፀ ፡ ቍጹል ፡ ለ ገቢረ ፡ ምጽላል ፡ (ንሐ፰ ፡ ፲፭) ።

**ቈጽል** ፤ (ላት ፤ አቍጽል) ፤ ቅጠል ፤ ቅጠላቅጠል ፤ የዛፍ ፡ የመጣፍ ፡ የወርቅ ፡ የብር ። ልጥ ፡ ሐረግ ። ከመ ፡ ቈጽለ ፡ ዕፀ ፡ ዘጽሩቅ ፡ ቈጽሉ ። በኀብስት ፡ ወማይ ፡ ወቈጽል ። ቈጽለ ፡ ወርቅ ፡ ረቃቅ ። ቈጽለ ፡ አሥርቅ ፡ (ሚራ፲፬ ፡ ፲፰ ። ቀሌ ። ዘፀ፴፱ ፡ ፴፮ ። ሚራ፲፩ ፡ ፴) ።

**አቍጸለ** ፤ አለመለመ ፤ ዐደሰ ፡ አረጠበ ፡ ዐጽቃም ፡ ቅጠላም ፡ አደረገ ። ዐምደ ፡ ቤትየ ፡ ዘአቍጸልከ ፡ (ድጓ) ።

**ቀጸለ** ፤ (ይቈጽል ፡ ይቀጽል ፤ ቀጽሎ) ፤ ቀጠለ ፡ ቀጣጠለ ፤ ጨመረ ፤ የቈመት ፡ የፍሬ ፡ የትምርት ።

**አቀጸለ** ፤ **አስተቀጸለ** ፤ አስቀጠለ ። አቀዳጀ ፤ ሾመ ፡ አሸከመ ፤ አስጌጠ ፡ ሸለመ ። አክሊለ ፡ ትፍሥሕት ፡ ታስተቍጽለከ ። ትገብር ፡ አክሊላተ ፡ ወታስተቈጽሎ ፡ ለዮሳዕ ። አስተቀጸለ ፡ አረፍተ ፡ በሜላትራ ፡ (ሚራ፮ ፡ ፴፩ ። ዘካ፮ ፡ ፲፩ ። ፎንገ ፡ ፯ ፡ ፱ ። ፯ ፡ ፵) ።

**ተቀጸለ** ፤ ተቀጠለ ፡ ተጨመረ ፡ ተቀጥላ ፡ ኾነ ፤ በሰው ፡ ራስ ፡ ላይ ፤ ያበባ ፡ ያክሊል ። ተቀዳጀ ፤ ለውጥም ፡ በራሱ ፡ ደፋ ፡ ለበሰ ፡ ተሸከመ ፤ ጠመጠመ ። እንዘ ፡ ይትቈጸል ፡ አክሊለ ፡ ዘሦክ ። ንትቀጸል ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ። ንትቀጸል ፡ አሕባለ ፡ ውስተ ፡ አርእስቲነ ፡ (ዮሐ፲፱ ፡ ፭ ። ጥበ፪ ፡ ፰ ። ፫ነገ ፡ ፳ ፡ ፴፩) ።

**ቅጹል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ጽልት) ፤ የተቀጠለ ፤ ቅጥል ። የተቀዳጀ ፡ ቅድጁ ።

**ተቅጺል** ፤ (ላት) ፤ ተቀጥላ ፤ የንጨት ፡ ዲቃላ ።

**ቀጸላ** ፤ (ላት) ፤ በቁሙ ፤ የራስ ፡ ልብስ ፡ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ ታናሹም ፡ ታላቁም ፤ ማናቸውም ፡ ኹሉ ፡ በየስሙና ፡ በያይነቱ ። ወገሮ ፡ ሥልሶ ፡ ሠርሙዱ ፡ ከሎታ ፤ አክሊል ፡ ዘውድ ፡ ሜትራ ፤ ኰፈት ፡ ቆብ ፡ መጠምጠሚያ ፤ ጠርቡሽ ፡ ባርኔጣ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ዕጨጌዎችና ፡ አበ ፡ ምኔቶች ፡ በቆባቸው ፡ ላይ ፡ የሚለብሱት ፤ የሚከናነቡት ፡ ሻሽ ፡ ነጠላ ። ወህየንተ ፡ ዘወርቅ ፡ ቀጸላሃ ፤ ብርሐት ፡ ወፀአ ፡ ላዕሌሃ ፤ ወድማኅ ፡ ኢኮነት ፡ ድማኅ ። ወደበ ፡ ርእሶሙ ፡ ቦሙ ፡ ቀጸላ ፡ በአምሳለ ፡ ወርቅ ። ሰብዐቱ ፡ ቀጸላት ። ወተቀጸሊ ፡ ቀጸላኪ ፡ ዲበ ፡ ርእስኪ ፡ ዘስብሐቲሁ ፡ ቅዱስ ። ቀጸላቲሆን ፡ ወባሕርያቲሆን ፡ (ቅኔ ። ራእ፱ ፡ ፯ ። ፲፪ ፡ ፫ ። ባሮ፭ ፡ ፪ ። ኢሳ፫ ፡ ፲፱) ።

**ቀጸላ** ፤ ቅጽል ፤ በስምና ፡ በግብር ፡ የሚጨመር ፡ ቃል ፤ የአክልንና ፡ የግብርን ፡ አኳኾን ፡ ጠባዩን ፡ መልኩን ፡ የሚገልጥና ፡ የሚያስረዳ ። ነዊኅ ፡ ሠናይ ፡ ጸዐዳ ፡ እንደ ፡ ማለት ።

**ቀጺመት** ፤ (ቃት ። ዕብ ፡ ቅጺዓህ ፤ ቃኔ ። ዐረ ፡ ቀጸብ) ፤ ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፤ የመቃ ፡ የሸንበቆ ፡ ዐይነት ። ጽጌ ፡ ቀጺመት ፡ ወቀናንም ፡ (ስንክ ፡ ነሐ፳፯ ። ዘፀ፴ ፡ ፳፫ ። ማሕ፬ ፡ ፲፬) ።

**ቀጺዕ** ፤ ዖት ፤ (ቀጸዐ ፡ ይቀጽዕ ፡ ይቀጽዕ ። ዕብ ፡ ቃጻዕ ። ዐረ ፡ ቀጠዐ) ፤ መቅጨት ፤ መቅጸት ፤ እየለኩ ፡ እየስተካከሉ ፡ መቍረጥ ፡ ማጠፍ ፤ ማጕበጥ ፡ ማረቅ ፤ ማስጕንበስ ፤ ማስጨነቅ ። የጫማ ፡ የብራና ፡ የማኅደር ፡ የልብስ ፤ የወገብ ፡ የደጋን ። እስ ፡ ይቀጽዑ ፡ ቀሚሰ ። ቀጽዕዎ ፡ ለነፍስየ ። ይቀጽዕ ፡ ዝሎ ፡ ሐቌ ። ያደነግፅ ፡ ልበ ፡ ወይቀጽዑ ፡ ከመ ፡ ማሕምም ፡ (ገድ ፡ አዳ ። መዝ ፡ ፶፮ ። ናሖ፪ ፡ ፲ ። ሚራ፴፭ ፡ ፳) ።

—፤ ማወቅ ፤ ዐውቆ ፡ መሥራት ፡ መቅጣት ፡ መደልደል ፡ ማስተካከል ፡ መጥረግ ፡ መመድመድ ፤ የሰው ፡ የቦታ ፡ የመንገድ ። አሠር ፡ ዘቀጻዕነ ። ፍኖትየ ፡ ወአሠርየ ፡ አንተ ፡ ቀጻዕከ ። ወቀጻዕክዋ ፡ በጾም ፡ ለነፍስየ ፡ (ኢዮ፳ ፡ ፳፯ ። መዝ ፡ ፻፴፰ ፡ ፷፰) ። ዘቀጻዕነ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዘአቅጻዕነ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ባለብሎዎችም ፡ ያዖጋንነው ፡ ወግ ፡ ያስተረክነው ፡ ታሪክ ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ።

**አቅጽዐ** ፤ አስቀጨ ፡ አስቀጣ ፡ አስጐበጠ ።

**ተቀጽዐ** ፤ ተቀጨ ፤ ተሠራ ፡ ተቀጣ ፤ ጐበጠ ፡ ፈራ ፡ ደነገጠ ። ወትትቀጻዕ ፡ ዡላ ፡ ነፍስ ። አረጋዊ ፡ ዘተቀጽዐ ፡ ዘባኑ ። ተቀጽዑ ፡ ወኢተርፈት ፡ ነፍሶሙ ፡ በላዕሌሆሙ ፤ (ሕዝ፴፰ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ተ፳፫ ። ኄሐ፺ ፡ ፩ ። ኢሳ፲፫ ፡ ፰) ።

**ቀጻዕ** ፤ **ቀጺ** ፤ **(ብ ፡ ቀጺት)** ፤ የእሳት ፡ እራት ፤ ብባሕርይ ፡ ፈቃዱ ፡ የሚቀጣ ፡ የሚቃጠል ፤ ቅጣት ፡ የሚቀበል ፤ ኋላም ፡ ቃድሶ ፡ የሚነግሥ ፡ የትንግሥኤ ፡ ሙታን ፡ ምሳሌ ። ዖፍ ፡ ዘይሰመይ ፡ ቀጺ ፤ (ሃይ ፡ አበ ፡ ኤጲ) ።

**ቀጽቀጸ** ፤ **(ቀጥቀጠ)** ፤ እንቈጨቈጨ ፡ ፈጨ ፡ ቈረጠመ ፤ ወዘወዘ ፤ አራደ ፡ አንቀጠቀጠ ፡ የደዌ ፡ የሐዘን ፡ የፍርሀት ። በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይቀጸቅጸኒ ፡ ሐቌየ ፤ (ኢሳ፳፩ ፡ ፫) ።

**ቅጽቃጼ** ፤ **(ቅጥቃጤ)** ፤ መፍጨት ፤ መፈጨት ፤ መወዝወዝ ፤ መቈርጠም ። ቍርጥማት ፤ ቃንዛ ፤ የደዌ ፡ የሐዘን ፡ ስሜት ። ፈውስ ፡ ዘያሴስል ፡ ቅጽቃጼ ፡ ሕማም ፤ (አፈ ፡ ድ፳፩) ።

**ቀጺር** ፤ **ሮት** ፤ **(ቀጸረ ፡ ይቀጽር ፡ ይቅጽር ። ዐረ ፡ ቀጸረ ። ዕብ ፡ ቃጻር ፤ ዐጨደ ፤ አነሰ)** ፤ መቅጠር ፤ ማጠር ፤ መጀጐል ፤ ማረድ ፡ መመሸግ ፤ በቤት ፡ በከተማ ፡ ዙሪያ ፡ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ መሥራት ፤ መከበብ ፤ ዙሪያውን ፡ መያዝ ። ወቀጸሩ ፡ ላዐለ ፡ አህጉር ፤ (ዮዲ፩ ፡ ፳) ። ሐጸረን ፡ ተመልከት ።

—፤ ቀጠሮ ፡ ማድረግ ፤ ቀን ፡ መቍረጥ ፤ መወሰን ፡ (ዐማርኛ) ። ዐደመን ፡ እይ ።

**ቀጻሪ** ፤ **(ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ጸርት)** ፤ የሚያጥር ፡ የሚቀጥር ፡ ቀጣሪ ፤ ቅጥር ፡ ሠሪ ።

**አቅጸረ** ፤ አስቀጠረ ፤ ቅጥር ፡ አሠራ ፡ አስከበበ ።

**ተቀጽረ** ፤ ተቀጠረ ፤ ታጠረ ፤ ተከበበ ።

**ቅጹር** ፤ **(ራን ፡ ራት ፡ ጽርት)** ፤ የታጠረ ፤ የተቀጠረ ። ሀገር ፡ ቅጽርት ፤ (ኢሳ፩ ፡ ፰) ።

**ቅጽር** ፤ **(ራት)** ፤ በቁሙ ፤ ቅጥር ፤ ዐጥር ፤ መካበቢያ ፡ የቤት ፡ የከተማ ። ሰእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይሕንጽ ፡ ብእሲ ፡ ቅጽረ ፡ ይርሐቅ ፡ እምቢጹ ፡ አሐተ ፡ ምሥጋረ ፡ እግር ። ሀገር ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ቅጽር ። ይጠቅሙ ፡ ለርእሶሙ ፡ ቅጽረ ። ኢያሪኮ ፡ እንተ ፡ የዐውዳ ፡ ሰብዐቱ ፡ ቅጽራት ፤ (ፍ ፡ ን ፡ ፴፯ ። ዘሌ፳፭ ፡ ፳፱ ። ምሳ፳፰ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳፯) ።

**ቌጼሩት** ፤ **(ዕብ ፡ ቅጹሮት)** ፤ ዐማጭሮች ፡ ታናናሾች ፤ ጠባቦች ፡ (ሕዝ፵፮ ፡ ፳) ።

**ቈጺር** ፤ **ሮት** ፤ **(ቈጸረ ፡ ይቈጽር ፡ ይቍጽር ። ዕብ ፡ ቃሻር ፤ ቃጣር ። ሱር ፡ ቀጣር)** ፤ መቋጠር ፤ መቀጠል ፤ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፤ ወይም ፡ አንዱን ፡ ባንዱ ፡ ማሰር ፡ ማቈር ፤ ማጽናት ፡ ማጠንከር ፤ መሰንገጥ ፡ መኰፍተር ፡ መጨምደድ ፤ የፊት ። ነሥአ ፡ ዲናረ ፡ ወርቅ ፡ ወቈጸሮ ፡ በጸርቅ ። ቈጸርዎ ፡ በልብሶሙ ። ቈጸሩ ፡ አማዑቶሙ ። ሐብል ፡ መንፈሳዊ ፡ ዘያዐርግ ፡ ልበ ፡ እምድር ፡ ወይቈጽሮ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ። ኢትቍጽሩ ፡ ገጸክሙ ። እፎ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ይቈጽር ፡ ገጾ ። ትካዝ ፡ ወቈጺረ ፡ ገጽ ፤ (ስንክ ፡ ታኅ፲ ። መጽ ፡ ምስ ። መዝ ፡ ፲፯ ። ፊልክ ፡ ፻፹፩ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፩ ። አፈ ፡ ተ፳፲) ።

—፤ ክፉ ፡ ማሰብ ፤ መፅነስ ፤ መተንኰል ፤ ማታለል ፤ መሸንገል ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘቈጸረ ፡ ከመ ፡ ይቅትል ። አንተሰ ፡ ትቈጽር ፡ በዘትትሜጠዋ ፡ ለነፍስየ ። ለመጋቢ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይቍጽር ፡ ለእመጋቢሁ ፡ ውስተ ፡ ሠዩጥ ፡ ወተሣይጦ ፤ (ዘፀ፳፩ ፡ ፲፬ ። ፩ነገ ፡ ፳፬ ፡ ፲፪ ። ፍ ፡ ን ፡ ፴) ።

—፤ መቍጠር ፤ ቍጥር ፡ ሒሳብ ፡ ማድረግ ፤ አንድ ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ማለት ። ኈለቈ ፡ ሐሰበ ፡ አንዘ ፡ ቈጠሮ ፡ ቈጠረ ፡ ማለት ፤ ዐማርኛው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ቈጻሪ** ፤ **(ሪት ፡ ርያን ፡ ያት)** ፤ የሚቈጥር ፤ የሚቋጥር ፤ አሳሪ ፡ ቋጣሪ ፤ ዐሳቢ ፡ ቈጣሪ ።

**አቍጸረ** ፤ አስቈጠረ ፤ አስቋጠረ ። አስተነኰለ ፤ አሳተ ፡ አባበለ ፤ ሐሰት ፡ ሸንገላ ፡ አስተማረ ። አቍጸሩ ፡ ሎቱ ፡ ዐደወ ። ያቈጽሩ ፡ ሎቱ ፡ ሰማዕተ ፡ ሐሰት ፤ (ግብ፮ ፡ ፲፩ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ተቈጽረ** ፤ ተቈጠረ ፤ ተቋጠረ ፤ ተሰበሰበ ። በከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ንዋየ ፡ ሰብኣ ፡ ዘተሰብረ ፡ እምነ ፡ ዘኢተሰብረ ፤ በተቈጽሮ ፤ ከማሁ ፡ ብእሲኒ ፡ በንባቡ ፤ (ፈላስ) ።

**ቍጹር** ፤ **(ራን ፡ ራት ፡ ጽርት)** ፤ የታሰረ ፤ የተቋጠረ ፤ ቍጥርጥር ። ቍጹር ፡ ውስተ ፡ አሥዋክ ። እንተ ፡ ቍጽርት ፡ ውስቴታ ። ቍጹረ ፡ ገጽ ፤ (ፊልክ ፡ ፻፲፯ ። ክብ ፡ ነገ ። ገድ ፡ አዳ) ።

**ቍጽረት** ፤ መቋጠር ፤ መዕ(ፀ)ነስ ፤ አቈጣጠር ፤ እስራት ፤ ቍጥራት ፤ ቍጥርጥርነት ፡ መጋጠሚያ ። አመ ፡ ሰቡዑ ፡ ለነሐሴ ፡ ቍጽረታ ። መካነ ፡ ቍጽረቱ ። ቍጽረቱ ፡ ከመ ፡ እብነ ፡ ኰኵሕ ። ቍጽረተ ፡ ዐራዙ ፤ (አዋል ። ኢዮ፵፩ ፡ ፳ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፴፭) ።

**ቈጻራ** ፤ ሽንገላ ፤ ስርቆት ፤ ቅጥፈት ። አግብእ ፡ ሎቱ ፡ ንዋዮ ፡ ወሀቦ ፡ ዘእንበለ ፡ ቈጻራ ፡ ወርዴ ፤ (ቀሌ) ።

**ቍጽር** ፤ **(ራት)** ፤ በቁሙ ፤ ቍጥር ። እስራት ፤ ግርፋት ፤ ዐለንጋ ፡ ጅራፍ ፡ ጢጢ ፡ ሳንባ ፡ ጠለፍ ፤ ክፉ ፡ ምክር ፤ ሽንገላ ፡ ተንኰል ። ኢታጽንዑ ፡ ቍጽረክሙ ። እስ ፡ ይጸብእዎ ፡ በቍጽር ። ይመክሩ ፡ በቍጽር ፡ ያመንስዉኒ ፤ (ኢሳ፳፰ ፡ ፳፪ ። ፴ ፡ ፴፪ ። መዝ ፡ ፴፩ ። ፴፯) ።

**ቍጽሮ** ፤ ጥልፍ ፤ ግብረ ፡ መርፌ ። መልበስተ ፡ ቍጽሮ ፤ (ዘፀ፳፰ ፡ ፬) ።

—፤ ቋጠሮ ፤ ቋጨራ ፤ የታሰረ ፡ የሣር ፡ የቅጠል ፡ ነዶ ፡ ኾቦ ። ቍጠሮ ፡ አቍጣሮ ፤ የመቍጠሪያ ፡ ጸሎት ።

**መቍጸርት** ፤ ጕንጕን ፡ ሽርብ ፤ ቋድ ፡ ጥብጣብ ፤ የልብስ ፡ ማስጌጫ ፡ መዘምዘሚያ ፤ ዝምዝማት ፤

ቍልፋ ፡ ተክሬስ ። ወመቍጸርቱ ፡ ወርቅ ፡ ዘግቡር ፡ በዕንቍ ፡ (ሚሊ፵፰ ፡ ፲፩) ።

—፤ መቍጠሪያ ፤ መቋጠሪያ ፡ መቈጣጠሪያ ፤ የቍጥር ፡ መማሪያ ።

**ተቃጸረ** ፤ ተቋጠረ ፤ ተቈጣጠረ ፡ ተሸናገለ ፤ ተሸነጋገለ ። ዘይከውን ፡ በውስቴቱ ፡ ተቃጽሮ ። ተቃጻርያን ፡ ምስለ ፡ እሲኣሁ ፡ (ፋ፡ ፡ ን ፡ ፴) ።

—፤ ተባበረ ፤ አንድ ፡ ልብ ፡ አንድ ፡ ሐሳብ ፡ ኾነ ፤ ሤራ ፡ ቈረጠ ፡ ተማማለ ፤ ለመግደል ፡ ለመወንጀል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ተቃጸረ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አስተቃጸረ ፡ ይላል ፤ የጣፈ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አስተቃጸሩ ፡ ሎቱ ፡ በዘሰሄ ፡ ማዕሌተ ፡ (፱ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፰) ።

**አስተቃጸረ** ፤ አቋጠረ ፤ አቈጣጠረ ፤ አስተሳሰረ ።

**ቀጻጼ** ፤ (ቀጸቢ ፤ ቀጸብ) ፤ ገበሎ ፡ ጕበና ፡ እንቃቅላ ፤ የዕሥሥት ፡ በይነት ፡ (አዋል) ።

**ቀፂው** ፤ **ዎት** ፤ (ቀፀወ ፡ ይቀፁ ፡ ይቅፁ ። ዕብ ፡ ቃጻህ ፤ ቈረጠ ፡ ለየ) ፤ መጣድ ፡ ማስረር ፤ መቀቀል ፡ ማንፈር ።

**መቅፀት** ፤ (ታት ፤ መቃዕው) ፤ ሸክላ ፤ ድስት ፡ ምንቸት ፤ ማሰሮ ፤ የሸክላ ፡ የብረት ። በእይቴ ፡ ይትፀረክ ፡ መቅፀት ፡ ምስለ ፡ ጽህርት ። መቅፀተ ፡ ብርት ፡ ፀቢይ ። ብሱል ፡ በመቅፀት ። ምንባረ ፡ መቅፀት ፡ (ሚራ፲፫ ፡ ፪ ። ዮሴፍ ። ዘሌ፮ ፡ ፳ ። ፲፰ ፡ ፴፰) ።

**ቀቀበ** ፤ (ነቀበ) ፤ ሰገበ ፤ ሰፋ ፤ ሸፈፈ ፡ ደጕሰ ፤ አለበሰ ፤ የሰይፍ ፡ የጕራዴ ፡ የሳንጃ ፡ የጦር ።

**ቀቀብ** ፤ (ባት ። ዕብ ፡ ንዳን ፤ ታዓር) ፤ ሰገባ ፤ አፎት ፤ ሽፋፍ ፤ ድርቁ ፡ የሰይፍ ፡ ቤት ፤ ማኅደር ። ኋወፅኣ ፡ ለመጥባሕትየ ፡ እምነ ፡ ቀቀባ ። አግብኣ ፡ ለመጥባሕትከ ፡ ውስተ ፡ ቀቀባ ። በልዑ ፡ ማእሰ ፡ ቀቀበ ፡ አስይፍቲሆሙ ፡ (ሕዝ፳፩ ፡ ፫ ፡ ፴ ። መጽ ፡ ምስ ፡ ዮሴፍ) ።

**ቈቀወ** ፤ ቍቁ ፡ አለ ፡ (በማርኛ) ።

**አስቈቀወ** ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ ሮኸ ፡ ዋይ ፡ አለ ፤ የወደደውን ፡ ስላጣ ፤ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ተንሰቀሰቀ ፤ አልቅሶ ፡ አስለቀሰ ፤ አሞሸ ፡ ቈዘመ ፤ ሙሾ ፡ አወጣ ፤ ተቀኘ ፡ ገጠመ ። ቀነየንና ፡ ነቀወን ፡ ሰንቀወን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ናቸው ። አስቈቀዉ ፡ ሰቈቃወ ። አስቈቀውነ ፡ ለክሙ ፡ ወኢበከይክሙ ። አንስት ፡ ይበክያሁ ፡ ወያስቈቅዋሁ ፡ ለተሙዝ ። እለ ፡ ይበክዩ ፡ ወያስቈቅዉ ፡ (ሚክ፪ ፡ ፬ ። ማቴ፲፩ ፡ ፲፯ ። ሕዝ፰ ፡ ፲፬ ። ቀሌ) ።

**መስቈቅው** ፤ (ቍት ፡ ቅውት ፤ ዋን ፡ ዋት) ፤ ጩኸ ፡ የሚያለቅስ ፤ አልቃሽ ፤ አስለቃሽ ፤ ገጣሚ ፡ ቀንቃኝ ፤ ሙሾ ፡ አውጭ ፤ ባለሙሾ ። መስቈቅው ፡ ወቍጹር ። ጸውዕዎን ፡ ለመስቈቅዋት ። ኢይደሉ ፡ ተዓስቦተ ፡ ሕሩማት ፡ ዘከመ ፡ መስቈቅዋት ፡ ወሰብአ ፡ ሥራይ ፡ (ገድ ፡ አዳ ። ኤር፱ ፡ ፲፯ ። ፍ ፡ ን ፡ ፴፯) ።


**ሰቈቃው** ፤ ጩኸት ፡ ዋይታ ፤ ልቅሶ ፡ ሙሾ ፤ የልቅሶ ፡ ግጥም ፤ ኀይለ ፡ ቃል ። ሰቈቃወ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ ። ንሥኢ ፡ ሰቈቃወ ፡ በከናፍርኪ ። ንሣእ ፡ ሰቈቃወ ፡ ባዕለ ፡ መላእክተ ፡ እስራኤል ፡ (ሰቈ ፡ ፩ ። ኤር፯ ፡ ፳፱ ። ሕዝ፲፱ ፡ ፩ ። ማቴ፪ ፡ ፲፰) ።

**ቈቅሐ** ፤—አጠራ ፤—ቀይቅሐ ።

**ቈቀየ** ፤—ቀቀተ ፤—ቀይቀየ ።

**ቃቂል** ፤ ቃጭል ፡ ታናሽ ፡ መረዋ ። ዘሩ ፡ ቀጭል ፡ ነው ።

**ቀቀኖ** ፤ (ጽር ፡ ኪክኖስ ። ዕብ ፡ ቃአት ፤ ቂቅ ። ሱር ፡ ቃቃእ ። ዐረ ፡ ቁቅ) ፤ ርኩም ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፲፱ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፲፯) ። ጕንባሕንና ፡ አቢ ፡ ጕንባሕን ፡ እድገ ፡ መረብን ፡ እይ ። ብኾርሙ ፡ ቀቃኑው ፤ በሴት ፡ አንቀጽ ፡ ሲኾን ፡ ቀቀኑት ፡ ቀቃኑት ፡ ያሰኛል ።



ቀቀኖ ፤

**ቈቍዖ** ፤ **ዖት** ፤ (ቈቍዐ ፡ ይቋቍዕ ፡ ይቈቍዕ ። ዕብ ፡ ቃዕቂዕ ፤ ወጋ ፡ በሳ ፡ ነቀሰ) ፤ መንቋቋት ፤ ቋ ፡ ቋ ፡ ማለት ፤ ያጥንት ። መጕረብ ፡ ማጕብጕብ ፤ መላጥ ፡ መመለጥ ፤ መብሰብ ፡ መገንጐን ፡ መክከም ፡ መጣመን ፤ የእጅና ፡ የእግር ። መክሳት ፡ መድረቅ ፤ መጢጋት ፤ መጕበቈል ፤ ሬሳ ፡ መምሰል ፤ የሰውነት ። ይቋቍዕ ፡ ኵሉ ፡ አዕፅምቲሁ ። ቈቍዓ ፡ ወቈስላ ፡ አጻብዒሆሙ ። እፎ ፡ ቈቍዐ ፡ በሐዊረ ፡ ፍኖት ፡ መከየደ ፡ እግርኪ ። ቈቍዐ ፡ ማእሰሙ ፡ ዲበ ፡ አዕፅምቲሆሙ ፡ (ኢዮ፴፫ ፡ ፲፱ ። ድር ፡ መድ ። ደራሲ ። ሰቈ፬ ፡ ፰) ።

**አቈቍዐ** ፤ አንቋቋ ፤ አቈሰለ ፤ አከሳ ፤ አደረቀ ። አከየ ፡ ልቡ ፡ ያቋቍዕ ፡ አዕፅምቲሁ ። ትጋሁ ፡ ለብዕል ፡ ያቋቍዕ ፡ አዕፅምተ ፡ (ሚራ፲፬ ፡ ፱ ። ፴፱ ፡ ፩) ።

**ቃቄር** ፤ (ራት ። ዕብ ፡ ቁርቁር) ፤ እንቍራሪት ፤ ትል ፡ እሙኝት ፤ ሌሊት ፡ የሚጮኽ ፡ የሚንጫጫ ። ወይነቅዉ ፡ ከመ ፡ ቃቄራት ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ቃር** ፤ (ዐረ ፡ ቂር ፤ ቃር) ፤ ሙጫ ፤ የዛፍ ፡ ደም ። ቃር ፡ ወፒሳ ፡ ወተይ ፡ (ስንክ ፡ ሐም፳) ።

**ቈር** ፤—ብርድ ፤—ቈሪር ፤—ቈረ ።

**ቀርአ** ፤—ቈረመ ፤ መታ ፤—ቀርዐ ።

**ቍርአ** ፤—በቁሙ ፡ ቍር ፤—ቍርዕ ።

**ቍርአን** ፤ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፤ መሐመድ ፡ ለወገኖቹ ፡ የጣፈው ፤ ርሱን ፡ ነቢይ ፡ ሐዋርያ ፡ ብለው ፡ የሚያምኑ ፡ እስላሞች ፡ ከሰማይ ፡ ወርዷል ፡ የሚሉት ። ፍ

ችው ፡ ንባብ ፡ ድጋም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዋንኛ ፡ ስሙ ፡ ግን ፡ ቍርቃን ፡ ነው ፤ ፈረቀን ፡ እይ ።

**ቀረበ ፤ በት ፤ (ቀርበ ፡ ይቀርብ ፡ ይቅረብ ። ዕብ ፡ ቃሬብ ። ሱር ፡ ቅሪብ ። ዐረ ፡ ቀሪበ)** ፤ መቅረብ ፤ መጠጋት ፤ መድረስ ፡ መንካት ፤ መለጠቅ ፡ መጣበቅ ፡ ልጥፍ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ሥጋና ፡ እንደ ፡ ቈርበት ፤ ወዳጅ ፡ ዘመድ ፡ ባለሟል ፡ መኾን ። ቅረብ ፡ ኀዘየ ። ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ቀሪበ ፡ ኀቤሁ ። ይቀርቡኒ ፡ በክናፍሪሆሙ ። ብ ፡ ዘመድ ፡ ዘይቀርብ ፡ እምኔየ ፡ (ሔኖ ፲፬ ፡ ፭ ። ሃይ ፡ አበ ። ኢሳ ፳፱ ፡ ፲፫ ። ሩት ፫ ፡ ፲፪) ።

— ፤ መቍረብ ፡ ቍርባን ፡ መቀበል ፤ መሳተፍ ። እለ ፡ ኢትቀርቡ ፡ ፃኡ ። ይባእ ፡ ወይትከነስ ፡ ወይቅረብ ። ይቅረቡ ፡ ቍርባነ ። ቅድመ ፡ ይቅረቡ ፡ ጳጳሳት ፡ ወእምድኅሬሁ ፡ ቀሳውስት ፡ (ኪዳ ። ቀሌ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፭ ፡ ፲፪ ። ቅዳ) ። ቀርበ ፡ ይቀርብ ፡ ይቅረብ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ቀረበ ፡ ይቈርብ ፡ ይቅርብ ፡ ይላል ፡ የአበሰና ፡ የገረመ ፡ ቤት ፡ ነው ። እለ ፡ ይቈርቡ ፡ ለእግዚ ። እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይቈርቡ ፡ መሥዋዕተ ። እንዘ ፡ ይቈርብ ። አው ፡ ቀረበ ፡ ቍርባኖሙ ፡ (ዘፀ ፲፱ ፡ ፳፪ ። ዘሌዋ ፳፩ ፡ ፮ ፡ ፳ ። ኪዳ ። ቢኖ ይ) ። ዳግመኛም ፡ በቀርበና ፡ በቀረበ ፡ ፈንታ ፡ ተቀረበ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይትቀረብ ፡ ቍርባነ ። እምዘይትቈረብ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፯) ። ሦስተኛ ፡ ደግሞ ፡ እንዳማርኛው ፡ ቈረበ ፡ አቍረበ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፤ አይሰኝም ። ሲምንት ፡ ኢትቈርቢ ፡ ቍርባነ ፡ ለፍርንጅ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ ፲፪) ።

**ቀራቢ ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ረብት)** ፤ የሚቀርብ ፤ የሚጠጋ ፤ ቀራቢ ፤ ቈራቢ ።

**ቅሩብ ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ርብት)** ፤ የቀረበ ፤ የቈረበ ፡ ቅርብ ፤ አጠገብ ፡ ዘመድ ፤ ዐጫር ፤ ጥቂት ። እለ ፡ ቅሩባን ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ። ቅሩብ ፡ ውእቱ ፡ ረኪቦታ ። ዘየኀድር ፡ ቅሩበ ፡ ቤታ ። ለቅሩብ ፡ ምናሴ ፡ ምታ ። እስመ ፡ ቅሩብ ፡ ዘመኑ ። ፍሥሓ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ቅሩብ ፡ ወኅዳጥ ፡ (አስቴ ፩ ፡ ፲፬ ። ሢራ ፶፩ ፡ ፳፮ ። ፲፬ ፡ ፳፬ ። ዮዲ ፲፮ ፡ ፳፬ ። ዮሴፍ ። ቀሌ) ።

**ቅርበት** ፤ መቅረብ ፡ አቀራረብ ፤ ቅርቢያ ፡ ቀረቤታ ፤ ቅርብነት ፡ (ቁር ፡ ጸላ) ።

**ቍርበት ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፤ ማእስ ፤ የሥጋ ፡ ልብስ ፤ ሥጋን ፡ ከናጥንቱ ፡ ከነሸማቱ ፡ ሰብስቦ ፡ የሚይዝ ፡ የሚገንዝ ።

**ቀርብ ፤ (ዕብ ፡ ቄሬብ)** ፤ ቀርበታ ፤ ውስጥ ፤ ውሳጣዊ ፤ ሆድ ፤ መሓው ፡ ኹለንተናው ፤ በእግርና ፡ በራስ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የንዋያተ ፡ ውስጥ ፡ ማጥን ፡ አቅማዳ ። ግራብን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ቍርባን ፤ (ናት ። ዕብ ፡ ቆርባን ። ሱር ፡ ቁርባና ። ዐረ ፡ ቊርባን)** ፤ በቁሙ ፡ መንፈሳዊ ፡ አምኃ ፤ ስለት ፤ መሥዋዕት ፤ መባእ ፤ ለአምላክ ፡ የሚቀርብ ፡ የሚሰዋ ፡ ገንዘብ ፤ ማናቸውም ፡ ኹሉ ። የመሥዋዕትን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። መሥዋዕተ ፡ ወቍርባነ ፡ ኢፈቀድከ ። አምጽኡ ፡ ቍርባኖሙ ፡ ቅድመ ፡ ምሥዋዕ ። መንፈቀ ፡ ሰዲድርክም ፡ ቍርባነ ፡ ለእግዚ ፡ (መዝ ፴፱ ። ዘኍል ፯ ። ዘፀ ፴ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭) ።

— ፤ መሥዋዕተ ፡ ወንጌል ፤ ጥሬ ፡ ስንዴና ፡ ወይን ፤ ከውሃ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሢማሬ ፡ የሌለበት ፤ በቍርባንነቱ ፡ ዕሙቅ ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ ያለበት ። በእንተ ፡ ሥርዐተ ፡ ቍርባን ። አኰቴተ ፡ ቍርባን ። አርአየሙ ፡ ሥርዐተ ፡ ምስጢር ፡ ዘቍርባን ። አንቀጽ ፡ በእንተ ፡ ቍርባን ፤ ወኢያዕርጉ ፡ ላዕለ ፡ ምሥዋዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ኅብስተ ፡ ሥርናይ ፡ ንጹሕ ፡ ወማየ ፡ ወይን ፡ ንጹሕ ፡ (ኪዳ ። ቅዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፫) ።

**አቅረበ ፤ (ያቀርብ ፡ ያቍርብ)** ፤ አቀረበ ፤ አስቀረበ ፡ አስጠጋ ፡ አሳጠረ ። አቅርቦ ፡ መሥዋዕተ ። ናቍርብ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ ኅብስተ ፡ ወዘንተ ፡ ጽዋዐ ። አቅረቡ ፡ ሎቱ ፡ አምኃሁ ። ጠይቅ ፡ ዘሎ ፡ ዘአቅረቡ ፡ ለከ ። አቅረብክምሙ ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ፡ ኀቤየ ። ወአቅረብኪ ፡ መዋዕለኪ ፡ (አፈ ፡ ድ ፲፰ ። ኩፋ ፡ ፴፩ ። ሢራ ፴፭ ፡ ፲፭ ። ኤር ፲፫ ፡ ፲፭ ። ሕዝ ፳፪ ፡ ፬) ።

— ፤ ማቍረብ ፡ ቍርባን ፡ መስጠት ፤ ማቀበል ። ኢታቅርብዎሙ ። ወያቅርብዎ ፡ ቍርባነ ፡ (ቀሌ ። ፈ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፪) ። በአቅረበ ፡ ፈንታ ፡ አስተቅረበ ፡ ይላል ፤ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ። ዘጠቢብ ፡ በርእሱ ፡ ያስተቈርብ ፡ ርእሶ ፡ (ሢራ ፳ ፡ ፲፫) ።

**መቅረቢ ፤ ርብ** ፤ የሚቀርብ ፤ የሚያቀርብ ፤ የሚያስቀርብ ፡ አቅራቢ ። ሎቱ ፡ ናቍርብ ፡ ዘውእቱ ፡ መቅርብ ፡ (ቅዳ ፡ አት) ።

**መቅረብ ፤ (ብት)** ፤ ቀራቢ ፤ ዘመድ ፤ ወዳጅ ። አሐዱ ፡ እምአግዋሪሁ ፡ ወመቅረቡ ፡ (ሲኖ ይ) ።

**ተቃረበ** ፤ በቁሙ ፤ ተቀራረበ ፤ ተጠጋ ፡ ተጠጋጋ ፤ ተሳሰፈ ፡ ተስባሰፈ ። ኢይትቃረብ ፡ ወኢይኑም ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ። እለ ፡ ይትቃረቡኒ ። እምተራክቦ ፡ ወተኣምኆ ፡ እንዘ ፡ ይትቃረቡ ። እንበለ ፡ ይትቃረቡ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፬ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፴፱ ። ቄድር ። ማቴዎ ፡ ፲፰) ። ቀረበ ፤ ቀርበ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተቃረበ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ኅፍረት ፡ ተቃርቦ ፡ ለበሊዐ ፡ እክለ ፡ ባዕድ ። አው ፡ ይትቃረብ ፡ ኀበ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ (ሢራ ፴፩ ፡ ፲፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፳) ።

**አስተቃረበ** ፤ አቃረበ ፤ አቀራረበ ። እሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ያስተቃርቡ ፡ ገራህተ ፡ ምስለ ፡ ገራህት ፡ (ኢሳ ፭ ፡ ፰ ። ዲድ ፡ ፮) ። አቅረበ ፡ አስተቅረበ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አስተቃረበ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ነሥአ ፡ ብእሴ ፡ ወኪያሁ ፡ አስተቃረቦ ፡ ለርእሱ ፡ (ቁር ፡ ጸላ) ።

**ምቅራብ ፤ (ባት)** ፤ መቅረቢያ ፤ ማቅረቢያ ፤ መቃረቢያ ፤ አዳራሽ ፡ ወልወል ፤ አይጸየፍ ። ነበሩ ፡ ውስተ ፡ ምቅራቡ ፡ ወአንበብዋ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡ (ዕገዘ ፡ ፲፱) ።

**ምቅራብ ፤ (ዕብ ፡ ሜልቃሐይም)** ፤ የቀ ንዲል ፡ መጥቀሻ ፤ መኩስተሪያ ፤ መቀስ ። ጽዋዓት ፡ ወ ምቅራባት ፡ (፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፳፪) ።

**ቀረብ ፤ (ብ ፡ አቅራብ)** ፤ የደጋ ፡ የቈላ ፡ እ ንበ.ይ ፡ እሾኻም ፤ ፍሬው ፡ ክብ ፡ እንክብል ፤ ሎሚ ፡ የ ሚያክል ። ምስክር ፡ የለውም ፤ ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ (ሉቃ ፲፭ ፡ ፲፪) ፡ ወእመኒ ፡ አንቀቅሖ ፡ ሰአሎ ፡ ዐቅራበኒ ፡ ይ ሁብ ፡ ያለውን ፤ እንቢይ ፤ ይሉታል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፤ እ ውነተኛ ፡ ፍችው ፡ እይ ይለም ። የጽርኡ ፡ አብነት ፡ ከጽ ርኢም ፡ የተቀዳው ፡ ኹሉ ፤ እመኒ ፡ ዓማ ፡ ሰአሎ ፡ አርዊ ፡ ምድርኑ ፡ ይሁብ ፡ ባለው ፡ አንጻር ፡ ጊንጥ ፡ እንደ ፡ ማ ለት ፡ በዐይን ፡ ፀቅራብኑ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፤ እንቢዮች ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ በአልፍ ፡ አቅራብ ፡ አይልም ።

**ቀራቢብ ፤ (ዐረብ)** ፤ ያልተሰፋ ፡ ልብስ ፤ ፈርጅ ፡ መዳ ፡ ጣቃ ። ቁማስን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አ ንድ ፡ ነው ።

**ቀርዱ** ፤ የተራራ ፡ ስም ፡ ታላቅ ፡ ተራራ ፤ ከአ ራራት ፡ ተራሮች ፡ አንዱ ።

**ቀርድ ፤ ቅርድ ፤ (ዐረ ፡ ቂርድ)** ፤ ዝን ጀሮ ፤ ጭላዳ ፤ ነጬጩው ፡ ጥቍሬው ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።

**ቀራዲን ፤ (ናት)** ፤ ዝንጀሮች ፡ ጭላዶች ። ሆባይን ፡ ተመልከት ።

**ቅርዳን ፤ (ዐረ ፡ ጊርደውን)** ፤ ያይጥ ፡ ገመር ፤ ታላቅ ፡ ዐይጥ ፤ ፍልፈል ፡ (አዋል) ።

**ቂራዲስ ፤ (ጽር ፡ ኪራዳስ ። ዕብ ፡ ቂር ሔሬስ)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ የሞአብ ፡ ክፍል ፤ ከሞአብ ፡ አገሮች ፡ አንዲቱ ። ዐደወ ፡ ቂራዲስ ፡ (ኤርሚ ፡ ፴፭ ። ኢሳ፲፮ ፡ ፲፩) ።

**ቆራሕ ፤—ገነት ፤—ቀወራህ ።**

**ቀርሐ ፤ ሐት ፤ (ቀርሐ ፡ ይቄርሕ ፡ ይቀ ርሕ ። ዕብ ፡ ቃራሕ)** ፤ መንጨት ፡ መላጨት ፤ መም ለጥ ፤ የጠጕር ። ይቄርሑ ፡ ርእሶሙ ፡ በእንቲኣኪ ፡ ወይቀንቱ ፡ ሠቀ ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፴፩) ። በርሐን ፡ እይ ።

—፤ መጨለጥ ፤ ማንቀር ፤ የውሃ ። ጸወበን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ወንድም ፡ ነው ።

(ጥሬ) **ቀራሕ** ፤ የሚነጭ ፤ የሚጨልጥ ፤ ጨላጭ ፡ አን ቃሪ ። ልጩ ፤ ንጩ ፤ ምልጥ ፡ መላጣ ፤ በራ ፤ ቡሓ ።

**ቀርሐት** ፤ ልጭታት ፡ ንጭታት ፤ በራንት ፤ በራ ፡ መኾን ። እንቃሪ ፤ ጭላጭ ፡ (አዋል) ።

**ቃርሐ ፤ (ዲ.ቃ ፡ ግ)** ፤ እቃሪ ፡ ተኩስ ፡ ፈላ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ቃርሕ** ፤ ቃር ፡ ትኩሳት ፤ የምግብ ፡ አለመስ ማማት ።

**ቂራጥ ፤ (ዐረብ ። ጽር ፡ ኬራቲዎን)** ፤ የሚዛን ፡ ስም ፤ ታናሽ ፡ ልክ ፤ ክብደቱ ፡ አራት ፡ የወይራ ፡ ፍሬ ፡ የሚያነሣ ፤ ወይም ፡ ከዚያ ፡ የሚያንስ ። የገንዘብ ፡ ስም ፡ ታናሽ ፡ ገንዘብ ፤ ፪ ፡ ሳንቲም ፡ ተሩብ ፤ ወይም ፡ ፪ ፡ ሳንቲም ፡ ብቻ ፡ የሚኾን ። ጸባሕት ፡ ባዕለ ፡ ዙሉ ፡ ክርስቲያን ፡ ለለ ፡ ቂራጥ ፡ በበ ፡ ዓመት ። ብእሲ ፡ ዘይወቅር ፡ አእባነ ፡ በቂራጠ ፡ ወርቅ ፡ ዙሎ ፡ ዕለቱ ። አስተዋፂአሙ ፡ ዘበበ ፡ ክልኤቱ ፡ ቂራጥ ፡ (አቡሻ ፡ ፶ ። ስንክ ፡ ግንቦ ። ወኔ፲፭) ።

**ቅርጥብ ፤ (ዐረ ፡ ቀርፀብ)** ፤ የሚነክስ ፡ የሚግጥ ፡ የሚያበላሽ ፤ በልቶ ፡ የማይጠግብ ፤ እንዳይጥ ፡ እንደ ፡ ምሥጥ ፡ ያለ ፡ አጥራ ፡ ዘራፊ ፡ ሌባ ፡ ቀጣፊ ። ባለመጽሐፎች ፡ ግን ፡ ጊንጥ ፡ ዳሞትራ ፡ ኩሽሽላ ፡ ይሉ ታል ። አባ ፡ ወቅዕለኒ ፡ ሰመዮ ፡ እልቅርጥብ ፡ እስመ ፡ ይነስክ ፡ እምዙሉ ፡ ገቦ ፡ (ፊልክ ፡ ፶፯) ።

**ቀርጣሎን ፡ ስ ፤ (ጽር ፡ ካርታሎስ ። ዕብ ፡ ቃርጢል ። ሱር ፡ ቃርጣላ ። ዐረ ፡ ቂርጠለት)** ፤ ቅርጫት ፡ የሪቅ ፡ የጐታ ፡ ዐይነት ፤ የወ ይን ፡ መልቀሚያ ፤ ዘላውን ፡ በርሱ ፡ እየከተቱ ፡ የሚ ጭኑበት ፡ የሚሸከሙበት ፤ እንደ ፡ ስፌት ፡ ብዙ ፡ ዐይ ነት ፡ ያለው ፤ ጉብ ፡ መሶብ ፡ እንቅብ ፡ አገልግል ፡ ቅን ብቻ ፡ የሚመስል ። ከፈርንና ፡ መሥየምትን ፡ እስፈሬ ድንና ፡ ከረቦን ፡ እይ ። ትነሥእ ፡ እምፍሬ ፡ ምድር ፡ ወትወዲ ፡ ውስተ ፡ ቀርጣሎን ። ወሜሙ ፡ አርእስቲ ሆሙ ፡ ውስተ ፡ ቀርጣሎስ ፡ (ዘዳ፳፯ ፡ ፪ ፡ ፬ ። ፬ነገ ፲ ፡ ፯) ።

**ቀርየ ፤ ዮት ፤ (ቀረየ ፡ ይቀሪ ፡ ይቅሪ ። ዕብ ፡ ቃራእ)** ፤ ማሻረት ፡ መጠንቈል ፤ አስማት ፡ መድገም ፤ ጋኔን ፡ አሾክሺኪ ፡ መጥራት ፡ ቅኔ ፡ ተመሪ ፡ ከባለቅኔው ፡ አፍ ፡ እየሰማ ፡ እንዲሞኽ ፤ ወይም ፡ እን ዳስተርጓሚ ፡ ከሾክሻኪው ፡ አፍ ፡ እየሰሙ ፡ ማውራት ፡ መለፍለፍ ፡ መቀባጠር ። ለምንት ፡ ሰረቅሙ ፡ ገይበ ፡ ብሩር ፡ ዘይሰቲ ፡ ወይቀሪ ፡ ቦቱ ፡ እግዚእየ ፡ (ዘፍ ፵፬ ፡ ፭) ።

—፤ መቅረት ፡ መትረፍ ፤ ቀሪ ፡ ትርፍ ፡ ውዝፍ ፡ መኾን ፡ (ዐማርኛ) ።

**ቀራዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት)** ፤ ሻርተኛ ፡ አስማት ፡ ደጋሚ ፤ ጋኔን ፡ ጠሪ ፤ ባላሾክሻኪ ።

**አቅረየ** ፤ አስሻረተ ፤ ጋኔን ፡ አስጠራ ፡ አስ ማት ፡ አስደገመ ።

**አቃረየ** ፤ መሥዋዕት ፡ ሠዋ ፤ አቀረበ ፤ እምኃ ፡ ሰጠ ። የእግዜርን ፡ ቃል ፡ ከነቢይ ፡ ከካህን ፡ ለመጠየቅ ። ኢየአክል ፡ ሊባኖስ ፡ ለአንድዶ ፡ ወዙሉ ፡ እንስሳ ፡ ለአ ቃርዮ ፡ (ኢሳ፵ ፡ ፲፯) ።

**ቀርያሲም ፤ (ጽር ፡ ካሪሲም)** ፤ ጣዖት ፤ ስመ ፡ ጣዖት ፡ (፪ዜና ፡ ፴፭ ፡ ፲፱) ።

**ቀሪም ፤ ሞት ፤ (ቀረመ ፡ ይቀርም ፡ ይቅ ርም ። ዐረ ፡ ቀረመ ። ዕብ ፡ ቃራም ፤ ቍር በት ፡ ሸፈነ ፤ ቍርበታም ፡ ኾነ)** ፤ መቃረም ፡ መልቀም ፤ ከማጀ ፡ የቀረውን ፡ የወደቀውን ፡ እልፍ ፡

እንቡጥ ፡ ዛላ ፡ ዝለላ ፡ መማረር ። ፀብኢ ፡ ክፍልየ ፡ እም ዘቀረምኪ ፤ እንዘት ፡ ትቅርም ፤ (ድር ፡ ሚክ) ። ብ ዙው ፡ መጽሐፍ ፡ ማን ፤ በቀረመ ፡ ፈንታ ፡ ተቀረመ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ትትቈረሞሙ ፡ ዘከመ ፡ ተቀ ረምክ ፡ ኪያየ ። ተቅራመ ፡ ይትቈረምዎሙ ፡ ከመ ፡ ወይን ፡ ለተረፈ ፡ እስራኤል ። ኢትትቀረም ፡ ሕን ባባተ ፡ ወይንከ ፤ (ለቊ ፳ ፡ ፳፱ ። ኤር ፮ ፡ ፱ ። ዘሌ ፲፱ ፡ ፲) ።

**ቀራሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት ፤ ረምት) ፤** የሚቀርም ፤ ቃራሚ ፤ ለቃሚ ። በቀራሚ ፡ ፈንታ ፡ ተቀ ራሚ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ተቀራሚ ፡ በለስ ፡ አነ ፡ (ዓሞጽ ፡ ፯፡፲፬) ።

**ቀርም ፤ (ማት ፤ አቅራም) ፤** በቁሙ ፤ ቃ ርሚያ ፤ ትራሚ ፤ ከጫጇች ፡ የቀረ ፡ ቅሬታ ። (ተረት) ፤ ሰው ፡ እንዳቀመሙ ፤ እኸል ፡ እንደ ፡ ቀርሙ ። ወይቱ ርፍ ፡ ቀርሙ ፡ ውስቴቱ ። ዘያስተጋብእ ፡ ቀርመ ፡ በ ማእረር ፤ (ኢሳ ፲፯ ፡ ፮ ። ሚክ ፯ ፡ ፩) ። በቀርም ፡ ፈንታ ፡ ቀሪም ፡ ይላል ፤ የጣፈ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ሠዊት ፡ ዘይወ ድቅ ፡ እምነ ፡ ቀሪሙ ፤ (ኢዮ ፳፱ ፡ ፳፱) ።

**ተቀርመ ፤** ተቃረመ ፤ ተለቀመ ፤ እልፉ ፡ እን ቡጡ ፡ ዛላው ።

**ቅሩም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ርምት) ፤** የተቃ ረመ ፤ የተለቀመ ፤ ቃርሞሽ ።

**ተቅራም ፤ (ማት) ፤** ቀርም ፤ ቃርሚያ ። ከመ ፡ ተቅራም ፡ አመ ፡ ቀሥም ። ተቅራመ ፡ ማእረር ። ዐቀ ብተ ፡ መቃብር ፡ አረፉ ፡ ኅጠተ ፡ ብፉር ፡ ጸዐዳ ፤ ወተ ቅራመ ፡ ብሩር ፡ መቃብረ ፡ አትረፉ ፡ ለእንግዳ ፤ (ሚ ክ፯ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ መስ ፲፩ ። ቅኔ) ።

**ተቃረመ ፤** ተቀራመተ ፤ ተቀረማመተ ፤ የሥጋ ፡ (በማርኛ) ።

**ተቃራሚ ፤** የሚቀራመት ፤ ተቀራማች ፤ ዐ ራጅ ፡ በጋማች ።

**ቅርመት ፤** መቃረም ፤ (ጥቃ) መቃረም ፤ አቀ ራረም ፤ ቅርሚያ ፡ ለቀማ ።

**—** ፤ መቀራመት ፤ ቅርምቻ ፤ ቀረመት ፤ ቅርምት ፤ አን ዱን ፡ ፍሪዳ ፡ ብዙ ፡ ኹኖ ፡ መግዛት ፡ ማረድ ፤ ሥጋውን ፡ ከፋፍሎ ፡ በሰፊ ፡ መውሰድ ።


**ቀርመዝ ፤ (ዐረ ፡ ቂርሚዝ) ፤** ቀይ ፡ ግምጃ ፤ እንድኪ ፡ ሻዊ ። ኳኳን ፡ ተመልከት ፡ (ኢሳ ፩ ፡ ፲፰) ።

**ቀርሜሎስ ፤ (ጽር ፡ ክርሚሎን ። ዕብ ፡ ክርሜል) ፤** የተራራ ፡ ስም ፤ ተራራ ፤ በባሕር ፡ ዳር ፡ ያለ ፤ ኤልያስ ፡ የጸለየበት ፡ (፫ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፴፪) ።

**ቀረን ፤ ኖት ፤ (ቀረነ ፡ ይቀርን ፡ ይቅ ርን ። ዕብ ፡ ቃራን) ፤** (መቀርናት) ፤ ቀንድ ፡ ማብ ቀል ፡ ማውጣት ፤ ቀንዳም ፡ ቀንደኛ ፡ ባለቀንድ ፡ መ ኾን ። መውጋት ፡ ማናፈር ፤ በቀንድ ፡ መቈፈር ፤ የበሬ ። ማስር ፡ ማቈራኘት ፤ ማጣመር ፡ ማቀናጀት ፤ የገበሬ ። ቅ ራና ፡ ቈራኛ ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ። ቀንድ ፡ መ ምሰል ፤ ቀንድ ፡ መኾን ፤ ቀንድ ፡ መባል ፤ ያገር ፡ ቀንድ ፡ እንዲሉ ። ማየል ፡ መበርታት ፤ መንገሥ ፡ መሠልጠን ፤ በላይ ፡ መኾን ። ቈንደየን ፡ ተመልከት ።

**ቀራኒ ፤ መቅርን ፤ (ብ ፡ መቃርንት) ፤** ቀንዳም ፡ የሚወጋ ፡ የሚቃወም ፤ ጠላት ፡ ደመኛ ፡ ወደ ረኛ ። እስመ ፡ እሉ ፡ እለ ፡ ይነሥኡ ፡ ርዴ ፡ መቃርን ቲሁ ፡ ለእግዚ ፤ (ዲድ ፡ ፳፩) ።

**ቀርን ፤ (ብ ፡ አቅርንት ። ዕብ ፡ ቄሬን ። ሱር ፡ ቃርና ። ዐረ ፡ ቀርን) ፤** ቀንድ ፤ ጥጕ ፡ ወን ከራ ፡ ደረቅ ፡ እንደ ፡ ዐጽቅ ፡ ኹኖ ፡ በእንስሳት ፡ ራስ ፡ የሚወጣ ፡ የሚያድግ ፡ የሚረዝም ፤ ጠማማ ፡ ቈልማማ ። የቀንድ ፡ መማሪያ ፡ ቴሌቴላ ፡ ዋንጫ ፤ የቀንድ ፡ ዐይነት ፡ ቀንድ ፡ የሚመስል ፡ ቀንዳ ፡ መለከት ፤ የገዢዎን ፡ ጥርስ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። አ ፡ ባሕም ፡ ዘኢይትኄየል ፡ በቀ ርኑ ። ከቡዳነ ፡ አቅርንት ። ንፍኁ ፡ ቀርነ ። ቀርነ ፡ ዝ ብጦ ። ቀርነ ፡ ነጌ ። ቀርነ ፡ ቅብዐ ። ንፍኆተ ፡ ቀርን ። ቃለ ፡ ቀርን ፤ (ቅዳ ። መገ ፡ ፴፱ ። ፹ ። ፺፯ ። ዓሞ ፫ ፡ ፲፭ ። ፩ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ። ፩ተስ ፡ ፬ ፡ ፲፮ ። ኢሳ ፲፰ ፡ ፫) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ነጋሪት ፡ ይሉታል ፤ ፍቹም ፡ እይዶ ስም ። ኢትንፍኁ ፡ ቀርነ ፡ ዘእንበለ ፡ በሆሳዕና ፤ (ድጓ) ። ጥፍርም ፡ የጣት ፡ ቀንድ ፡ ይባላል ። ሰላም ፡ ሰአጽፋረ ፡ እግርኪ ፡ አቅርንተ ፡ አጻብዐ ፡ ዐሠርቱ ፤ (ደራሲ) ።



ቀርን ፡

**—** ፤ ሥራ ፡ ምዕዛር ፡ የዐሓይ ፡ እግር ፤ ለጋ ፡ ጨረቃ ፤ ማእዝን ። ቀርነ ፡ ወርኅ ። እስክንድር ፡ ይሰመይ ፡ ዘ ክልኤ ፡ አቅርንቲሁ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ነግሠ ፡ በአቅ ርንተ ፡ ፀሓይ ፡ እምሥራቂሃ ፡ እስከ ፡ ምዕራቢሃ ፤ (አ ቀል ። አቡሻ ፡ ፵፰) ።

**—** ፤ ኀይል ፤ ጽንዕ ፤ ሥልጣን ፡ ንጉሥ ፡ መስፍን ። አ በቀል ፡ ቀርነ ፡ ለዳዊት ። ወያሌዕል ፡ ቀርነ ፡ መሲሑ ። አንሥአ ፡ ለነ ፡ ቀርነ ፡ መድኀኒት ። ይእቲ ፡ አሚረ ፡ ይ በቍል ፡ ቀርን ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ። ተሰብረ ፡ ቀርነ ፡ ሞአብ ፤ (መዝ ፡ ፻፴፩ ። ፩ነገ ፡ ፪ ፡ ፲ ። ሉቃ ፩ ፡ ፷፱ ። ሕዝ፳፱ ፡ ፳፩ ። ኤር፵፩ ፡ ፳፭) ። ዘአሐዱ ፡ ቀርኑ ፤ አው ራሪስ ። ቀርን ፡ ኅብስት ፤ ቍርማሚ ፡ ፓስቅ ፤ (መዝ ፡ ፳፩ ። ሕዝ፲፫ ፡ ፲፱) ።

**አቅረነ ፤** አቀረና ፤ ቀንድ ፡ አስመሰለ ፤ ቀንዳም ፡ አደረገ ፤ አስወጋ ።

**ተቃረነ ፤** ተዋጋ ፤ ተተማተመ ፤ ተቀራሸመ ፤ ተ ጣላ ፡ ተቃወመ ፤ ተከራከረ ፤ የሰው ፡ የእንስሳ ። ተግሕሡ ፡

እምዝሉ ፡ ዘይትቃረኑ ፡ ተቃርኖ ፡ ምስለ ፡ ሕግ ። ቀዳሚ ፡ ዘይትቃረነከ ፡ ተቃረኖ ፡ ምስሌሁ ። ይትቃረኑ ፡ ምስለ ፡ ዘሉ ፡ ሰብእ ፡ (ዲድ ፡ ፴፫ ። ቀሌ ። ፊተስ ፡ ፪ ፡ ፲፭) ።

**ተቃራኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት) ፤** ተቀኃ ፡ ተጣይ ፡ ወደረኛ ፡ ባለጋራ ። ዲያብሎስ ፡ ተቃራኒ ። ዘሉ ፡ ሕሡም ፡ ተቃራኒሁ ፡ ለሠናይ ። እስመ ፡ ፈውሰ ፡ ዘሉ ፡ ኃጢአት ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ተቃራኒ ፡ ለኃጢአት ። ፀር ፡ ተቃራንያን ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፳፮ ። ፈላስ ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፫ ። ጥበ፲፯ ፡ ፯) ።

**አስተቃረነ ፤** አዋጋ ፡ አጣላ ፤ አከራከረ ፤ አወዳደረ ።

**መስተቃርን ፤ (ንት ፡ ናን ፡ ናት) ፤** የሚያጣላ ፤ አጣይ ። የሚጠላ ፤ ተጣይ ፤ ባለጋራ ። ወእመሰ ፡ ተቃወመኒ ፡ መስተቃርን ። ዲፓሁ ፡ ለመስተቃርን ። ዘይከውን ፡ መስተቃርነ ፡ ለዝንቱ ፡ (አፈ ፡ ተ፴፰ ። ማር ፡ ይሶ፳ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ መጋ፫) ።

**ቀርንብ ፤ (ዐረ ፡ አርንብ ። ሱር ፡ አርንብ ። ዕብ ፡ አርኔቤት) ፤** ጥንቸል ፤ ገርሮዋ ፡ እንደ ፡ ቀንድ ፡ የኾነ ፤ ቀንድ ፡ የሚመስል ፤ ረዣዥምም ፤ ማር ፡ የምትበላ ፤ የምታመሰኳ ፡ ያሽኮኮ ፡ ወገን ።

**ቅርንብ ፤ (ብ ፡ ቀራንብት) ፤** ቅርነው ፤ ቀርናዊ ፡ ምርቅ ፡ ቂንድ ። ቅንድብ ፤ ሽፋሽፍት ፤ ከሽፋል ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ያይን ፡ መክደኛ ፤ ከንፈሩ ፡ ላዩና ፡ ታቹ ። ቅንድብ ፡ ቀርበቱ ፡ ላንቃው ፤ ሽፋሽፍት ፡ ጠጉሩ ፡ ጨፈቃው ፡ ምርቁ ፡ እንደ ፡ ቀንድ ፡ ኹኖ ፡ የበቀለው ፤ አፍሬው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ያሾቀለው ። ቈጽለ ፡ ወብርዐ ፡ ወሐሠረ ፡ ወቅርንበ ፡ ምርቅ ፡ ቂንድ ፡ (መቃ ፡ ገ፰) ። ሰላም ፡ ለቀራንብቲከ ፡ ከመ ፡ ክልኤ ፡ ክንፈ ፡ ኪሩብ ፡ እለ ፡ ይጼልላ ፡ ወትረ ፡ አዕይንቲከ ፡ ዘርግብ ። ጸጉረ ፡ ቀራንብቲሁ ። ነበስባሰ ፡ ቀራንብት ። ወቀራንብቲሁኒ ፡ የሐቶ ፡ ለዕጓለ ፡ መሕየው ። ቀራንብት ፡ ኀቤሁ ፡ ለዐይን ፡ እንዘ ፡ ቅሩባን ፡ ቀራንብት ፡ ኢይኔጽሩ ፡ ዐይን ፡ (ደራሲ ። ስንክ ፡ ማግ፲፫ ። መጽ ፡ ምስ ። መዝ ፡ ፲ ። ቅኔ) ። ሽፋልም ፡ ከሽፋሽፍት ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ቅንድብ ፡ ይባላል ። ሰብራይስጡ ፡ ከንፈር ፡ ከናፍር ፡ ሲል ፤ ላፉ ፡ ስፋታይም ፡ ስፋቶች ፡ ይላልና ፤ ሽፋሽፍት ፡ ከዚህ ፡ መጥቷል ፤ ፍችው ፡ ከንፈራዊ ፡ ሥዕርት ፡ ከንፈር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ለአፍም ፡ ይኾናል ፤ ጽሕምን ፡ ተመልከት ። ሽፋልም ፡ የዕብራይስጥ ፡ ነው ፡ (ሻፋል) ፡ ዐጭር ፡ ቀጭን ፡ ኰሳሳ ፡ ደካማ ፡ ልም ፡ ልገብጋ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የጠጉሩን ፡ ጠባይ ፡ ባሕርያዊ ፡ ሕጉን ፡ አለማደጉን ፡ ያሳያል ።

**ቀርነው ፤ ቀርነለው ፤** ቀርናዊ ፡ ቀርነ ፡ ላዊ ፤ ቀንዳም ፡ ቀንደ ፡ ቈልማማ ፡ ላዊን ፡ እይ ።

**—** ፤ ቀርነ ፡ ቅብዕ ፡ ወይም ፡ ቅብዐ ፡ ቀርን ። ከሌዊና ፡ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ ካህንና ፡ ንጉሥ ፡ የሚቀቡት ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ሽቱ ፡ ይሉታል ፡ (ጥሬ ፡ ሰዋ) ።

**ቀሬናዊ ፤ (ሱር ፡ ቁርያና ። ዐረ ፡ ቀሬይ) ፤** ቀርናጨ ፡ ድኻ ፡ ባለጌ ፡ ባላገር ። እፎ ፡ እትለአኮ ፡ ለዝንቱ ፡ ቀሬናዊ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲) ።

**ቀሬናዊ ፤ (ቀሬን ፤ ቂሬን ፤ ስመ ፡ ሀገር) ፤** የቀሬን ፡ ሰው ፡ አገሩ ፡ ቀሬን ፡ የሚባል ፤ የግብጽ ፡ አውራጃ ፡ የልብያ ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ። ብእሲ ፡ ቀሬናዊ ፡ ዘስሙ ፡ ስምዖን ፡ (ማቴ፳፯ ፡ ፴፪) ።

**ቀራንዮ ፤ (ጽር ፡ ክራኒዮ) ፤** ርእሳዊ ፡ ድማኅዊ ፡ መካነ ፡ ድማኅ ። ጎልጎታ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ቀራንዮ ፡ (ማቴ፳፯ ፡ ፴፫ ። ማር፲፭ ፡ ፳፪ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፲፯) ። ድማኅንና ፡ ጎልጎታን ፡ እይ ።


**ቀርኔን ፤** ቀሬን ፡ ስመ ፡ ሀገር ። ወእለሂ ፡ እምቀርኔን ፡ (ግብ፪ ፡ ፲) ።

**ቈርኔን ፤ ቈሬን ፡ (ጽር ፡ ክረኒ ። ዕብ ፡ ብሬክ) ፤** ኵሬ ፡ የውሃ ፡ መቋሚያ ፡ ጕድጓዳ ፡ በታ ፡ (፪ነገ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ። ፬ነገ ፡ ፳ ፡ ፳) ።

**ቈርኔን ፤ (ጽር ፡ ኩረኒ ። ዕብ ፡ ሐዳሽ) ፤** ሐዲስ ፡ መሣሪያ ፡ ያጠር ፡ ልብስ ። ባለብለቶች ፡ ግን ፡ ለይተው ፡ ቈገዝመን ፡ ይሉታል ፤ ያኸውም ፡ እንደ ፡ ጨቤ ፡ ያለ ፡ ጋሻጃግሬ ፡ የሚታጠቁት ፡ ታኅሽ ፡ ክሬ ፡ ነው ፡ (፪ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፲፮) ።

**ቀርንናእ ፤ (ዕብ ፡ ቅርናን) ፤** ቀንዳም ፡ ትል ፤ ቀባብ ፤ ዘጕል ፡ ልብሱ ፤ ቀንዱ ፡ ብርንድ ፡ የኾነ ፤ ልሕሱሕ ፤ ልጋጋም ። ሐለዚገዝግና ፡ ናእትን ፡ ተመልከት ።

**ቈርንናዕ ፤ ናዓት ፤ (ዕብ ፤ ጽፋርዴዕ ። ዐረ ፡ ፀፋዲዕ ። ሱር ፡ ዑርድዓናያ) ፤** ጓጕንቸር ፡ እንቍራሪት ። ጩኺ ፡ አቅራሪ ፡ ጨፋሪ ፡ ንጨጋሬ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቃቁርን ፡ እይ ። ይቀይእ ፡ ተከዚ ፡ ቈርንናዓተ ፡ (ዘፀ፰ ፡ ፪—፲፫) ።


ቀርንናእ ፤


ቈርንናዕ ፤

**ቀረዐ ፤ ዖት ፤ (ቀርዐ ፡ ይቀርዕ ፡ ይቅራዕ ። ዐረ ፡ ቀረዐ ። ዕብ ፡ ቃራዕ ፤ ቀደደ) ፤** ኰረዐ ፤ መቀኈሩት ፡ መቈረም ፤ መኰርኰም ፡ መምታት ፤ ራስን ፡ በበትር ፡ ቋ ፡ ኳ ፡ ከቶ ፡ ማድረግ ። ኰርዐን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**መቅርዕ ፤ (ብ ፡ መቃርዕ ። ዐረ ፡ ሚቅረዐት) ፤** መቀኈሪያ ፡ መቈረሚያ ፡ በትር ፤ የራስጌ ፡ ዱላ ፤ ወይም ፡ የራስ ፡ በሽታ ፤ የራስ ፡ ምታት ። በቅሥፈት ፡ መቃርዕ ፡ (አቡሻ ፡ ፶) ።

**ቍርዕ ፤ (ዓት) ፤** የራስ ፡ ቍር ፡ በርበሬ ፡ የብረት ፡ ቆብ ፡ ጌሬ ፡ (አዋል) ።

**ቀሪፍ ፤ ፎት ፤ (ቀረፈ ፡ ይቀርፍ ፡ ይቅርፍ ። ዐረ ፡ ቀለፈ ። ሱር ፡ ቅላፍ) ፤** መቅረፍ ፡ መላጥ ። ቈለፈን ፡ እዩ ፤ ለና ፡ ረ ፡ ተወራርሰዋል ፤ ቀረፈ ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ። ቀረፈ ፡ ሸለሎ ፡ ቅርፍት ። ቅርፍ ፡ ጸልዐ ፡ ዘንጢአት ፡ (ጥዐ፲፫ ፡ ፲፭ ። ደራሲ) ።

**ቅራፍ ፤ (ፋት) ፤** ቅራፊ ፤ ልጥ ። ሕልሳዐ ፡ ፈወሰ ፡ በጣዕመ ፡ ጼው ፡ ማየ ፡ ኢያሪኮ ፡ ሕሙመ ፤ ወበቅራፈ ፡ ዕፀ ፡ አውፅአ ፡ ማሕጼ ፡ ስጡመ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳) ።

**ቅርፍት ፤ (ፋት) ፤** በቁሙ ፤ ቅርፊት ፡ ልጥ ፤ እንቡጥ ፤ ቂንድ ፤ ገለባ ፡ ንፋሽ ፤ ቍርበት ፡ ጕለፈት ። ቅርፍተ ፡ ዕፀ ። ቅርፍተ ፡ ኅብስት ። ቅርፍተ ፡ ሮማን ። ቅርፍተ ፡ ተርሙስ ። ቅርፍተ ፡ ሥጋ ፡ (፬ነገ ፡ ፯ ፡ ፯ ። አዋል ። ማሕ፬ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ የካ፳፬ ። ቅዳ ፡ ያዕ ። ሕዝ፳፱ ፡ ፬) ።

**ቋረፈ ፤** ቈረፈ ፤ ቈራረፈ ፤ ቈራረጠ ፤ በጣጠሰ ። ይቋርፍ ፡ አራዊተ ፡ (አዋል) ።

**ቋርፍ ፤** የዋልድቦች ፡ ምግብ ፤ ሥራሥር ፤ እንደ ፡ ድንችና ፡ እንደ ፡ ሽንኵርት ፡ የሚላጥ ፤ የሚቀረፍ ።

**ቈሪፍ ፤ (ዐማርኛ) ፤** ገፈፊግ ፤ ገፈሪም ፤ ገፎው ፡ ታላላቅ ፡ የኾኑ ፤ ክልክ ፡ ያለፈ ። ቀርፋፋ ፡ ክርፋፋ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

**ቀሪጽ ፤ ጸት ፤ (ቀረጸ ፡ ይቀርጽ ፡ ይቅርጽ ። ዐረ ፡ ቀረጸ ። ዕብ ፡ ሐራጽ) ፤** መቅረጥ ፡ ማነጥ ፤ ማነጠጥ ፤ ምስል ፡ መሥራት ፤ መልክ ፡ ማውጣት ፡ ማስጌጥ ፤ መብጣት ፡ መክተፍ ፡ መተፍተፍ ። በሰዕ ፡ በንጺን ፡ በስሴዳ ፡ እብን ፡ መጣፍ ፡ መፈደል ፤ መንደፍ ፡ መፈልፈል ፤ ፊደሉን ፡ ማስመጥ ፡ ወይም ፡ ማሳበጥ ። ለዘሎሙ ፡ እሕዛብ ፡ ሀሰዎሙ ፡ ምግባራት ፡ ዘልማይ ፡ ዘትሜኒ ፡ በኄቤሆሙ ፤ ወበ ፡ ዘትከውን ፡ ኄሳረ ፡ በኄበ ፡ ካልእኒሃ ፡ ከመ ፡ ቀሪጸ ፡ ገጽ ፡ በኄበ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወኖባ ፡ ወከመ ፡ ተሳጽዮ ፡ ጽሕም ፡ በኄበ ፡ አፍርንጅ ። ወረከበ ፡ መጽሐፈ ፡ ዘቀረጸ ፡ ቀደምት ፡ ውስተ ፡ ኰኵሕ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፭ ። ኩፋ ፡ ፰) ።

**ተቀርጸ ፤** ተቀረጠ ፤ ተነጠጠ ፤ ተጣፈ ፡ ተነደፈ ። ናሁ ፡ ተአዘዘ ፡ ወተቀርጸ ። ወከመ ፡ ዝ ፡ ተጽሕፈ ፡ ወተቀርጸ ፡ በእንቲአሁ ። ሰንበት ፡ አይሁድ ፡ እንተ ፡ ተቀርጸት ፡ በጽላት ፡ ሰማይ ። ወሀበ ፡ ሙሴ ፡ በሰሌዳተ ፡ እብላቅ ፡ እለ ፡ ተቀርጻ ፡ በሆህያተ ፡ ዕብራይስጢ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፮ ። ፳፱ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ቅሩጽ ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ርጽት) ፤** የተቀረጠ ፤ የተጣፈ ፤ ያበጠ ፡ የሰመጠ ፤ መልክ ፡ ያለው ። ወረከብናሁ ፡ ለበትር ፡ ጽሑብ ፡ በንባብ ፡ ወቅሩጸ ፡ በትርጓሜ ፡ (ቅኔ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ላዊ) ።

**ቅርጸት ፤** መቅረጽ ፡ መቀረጽ ፡ አቀራረጽ ፤ ቅርጽ ፡ ጥፈት ፤ የፊደል ፡ መልክ ፤ እጅ ፡ እግር ፤ ጎርመት ፡ ቅንጣት ። ወጸሐፉ ፡ ላዕሌሁ ፡ በቀርጸተ ፡ ማኅተም ። የወጣ ፡ እንተ ፡ አሐቲ ፡ ቅርጸታ ፡ (ዘፀ፴፯ ፡ ፴፱ ። ማቴ፳ ፡ ፲፰ ። ቀሌ) ።

**ቀሪፀ ፤ (ዐረ ፡ ቀረፀ ። ሱር ፡ ቅራጥ) ፤** ቀረጠ ፤ ቀረጥ ፡ ተቀበለ ፡ (ዐማርኛ) ። ቈረጠ ፤ ሸለተ ፤ ላጨ ፤ ከረከመ ፤ የሕዋስ ፡ የጠጕር ፡ የጥፍር ። ቀረፀ ፡ እዝኖ ፡ ዘፀጋም ። ኢትቅርፀ ፡ እምኔከ ፡ አባለ ፡ ዘርዕ ። ኢይደሉ ፡ እምድኅረ ፡ ተመጥዎ ፡ ቍርባን ፤ ቀሪፀ ፡ አጽፋር ፡ ወተላጽዮ ፡ ጸጕር ። ኢይቅርፀ ፡ ጽፈሪሁ ። ኢታንኅ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእስከ ፡ ዳእሙ ፡ ቅርፀ ። ሶረ ፡ ኄበ ፡ ይቀርፀ ፡ አባግዒሁ ። ከመ ፡ በግዕ ፡ ዘኢይነብብ ፡ በቅድመ ፡ ዘይቀርፆ ። እምነ ፡ ቀዳሚ ፡ ዘቀረፀኩ ፡ (ፊልክ ፡ ፯ ። ፪፻፴ ። ቅዳ ። ቄድር ። ዲድ ፡ ፭ ። ዘፍ፴፰ ፡ ፲፱ ። ኢሳ፶፫ ፡ ፯ ። ጦቢ፭ ፡ ፺) ።

**ቀራፂ ፤ (ፂት ፡ ዕያን ፡ ያት) ፤** የሚቈርጥ ፤ ቈራጭ ፤ ቀራጭ ፡ ሸላች ፤ ላጭታ ። ጸውዑቶ ፡ ቀራፄ ፡ ወቀረፀት ። መላጼ ፡ ቀራፂ ፡ (መላ፲፯ ፡ ፲፱ ። ሕዝ፭ ፡ ፩) ።

**አቅረፀ ፤** አስቈረጠ ፡ አስቀረጠ ፤ ቀረጥ ፡ አስጠ ፡ አስቀበለ ። አቀረጠ ፤ ቀረጥ ፡ ሰጠ ።

**መቅረፅ ፤ (ብ ፡ መቃርፅ ። ዐረ ፡ ሚቅራፅ) ፤** መቅረጫት ፤ መቍረጫ ፤ መላጫ ፤ መቀስ ፡ ምላጭ ፤ የመስለው ፡ ኹሉ ። ይቤሎ ፡ ሰረድኡ ፡ ሀበኒ ፡ መጥባሕተ ፡ አው ፡ መቅረፀ ፡ ወመተረ ፡ ባቲ ፡ ልሳኖ ፡ (ስንክ ፡ ጳጕ፭) ። ሙዳየ ፡ ዔረግ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መቅረፅ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ቈረፅ ፡ ይቈርፅ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (ዓሞ፰ ፡ ፩) ።

**ተቀርፀ ፤** (ተቀረጠ) ፤ ተቈረጠ ፤ ተሸለተ ። እስከ ፡ ተቀርፀ ፡ ሥጋሁ ። መራዕይ ፡ እለ ፡ ተቀርፃ ። ተቀርፆ ፡ ሥዕርት ። አልቦ ፡ ዘይትቀረፀ ፡ ርእሶ ፡ ዘእንበለ ፡ ያእምር ፡ አባስ ፡ (ስንክ ፡ ማን፳፰ ። ማሕ፬ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ሐም፳፭ ። ሥር ፡ ጳኵ) ።

**ቅሩፅ ፤ (ፃን ፡ ፃት ፡ ዕት) ፤** የተቈረጠ ፤ ቍርጥ ፡ ሽልት ። ድኅረ ፡ ወድቀ ፡ መልዕልተ ፡ ምድር ፡ ርእሱ ፡ ቅሩፀ ። መራዕይ ፡ ቅሩፃት ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፲፰ ። ደራሲ) ።

**ቀረፅ ፤** በቁሙ ፤ ቀረጥ ፤ ነጋዴ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚያቀርጠው ፡ ገንዘብ ። ስመ ፡ ዕፅ ።

**ቀርቀር ፤ (ዕብ ፡ ቃርቆር) ፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ ከዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ያለ ። ባለብሉዮች ፡ ማን ፡ ገምቻ ፡ ቋጥኝ ፡ ይሉታል ፡ (መሳ፰ ፡ ፲) ።

**ቈርቀኈሮ ፤ ሮት ፤ (ቈርቈረ ፡ ይቈረቍር ፡ ይቈርቀኍር ። ዐረ ፡ ቀርቀረ ። ዕብ ፡ ቃርቄር) ፤** መቈርቈር ፤ መቀብቀብ ፤ የጥሪ ፤ ታሕቅሐን ፡ ተመልከት ። መራኈኽ ፡ ማስከካት ፤ ቍርቍሩ ፡ ማለት ፤ የድሮ ፡ የንቍራሪት ፤ ቃቈርንና ፡ ቈርንናትን ፡ እዩ ፤ ዘሩ ፡ ቈሪር ፡ ቈረ ፡ ነው ።

—፤ በቁሙ ፡ መቈርቈር ፤ መጕርበጥ ፡ አለመመቸት ፤ ማሳዘን ፡ ማስቈጣት ። የሐዘንን ፡ ፍቹ ፡ ተመልከት ። መመ

ሥረት፤ መገመር፤ ለማቅናት፤ ለመሥራት፤ ያገር፤ የከተማ፤ (ዐማርኛ)።

**ተቈርቈረ**፤ በቁሙ፤ ተቈረቈረ፤ ዐዘነ፤ ተቈጣ፤ ተናወጠ፤ ተንቀጠቀጠ፤ ከሐዘን፤ ከቍጣ፤ የተነሣ። ተመሠረተ፤ ተገመረ፤ ሀገሩ፤ ከተማው።

**ቍርቈር**፤ የተቈረቈረ፤ ያዘነ፤ የተቈጣ፤ ቍጡ።

**ቍርቍር**፤ ቍርቈራ፤ ሐዘን፤ ቍጣ፤ ብስጭት፤ ከርከር፤ ሙግት፤ ጩኸት፤ ፍጅት። ኢንፈር፤ ካሕድ፤ ቍርቍር፤ መፀት፤ ሁከት፤ (ኪዳ)።

**አንቈርቈረ**፤ (ዐማርኛ)፤ አንቈረቈረ፤ ተንቈረቈረ፤ የውሃ፤ የጥሬ፤ ለዜማም፤ ይኾናል።

**ቈርቈሮ**፤ በቁሙ፤ ጩኺ፤ ፈሳሽ።

**ቈረቈር**፤ በቁሙ፤ ንዌ፤ የራስ፤ ቋቍቻ። (ተረት)፤ በቡሓ፤ ላይ፤ ቈረቈር።

**ቀርቂስ**፤ (ዕብ፤ ቃርቃሽ፤ ሽክራ፤ የቃጭል፤ ቀጭላ)፤ መክን፤ ተውኔት፤ ብዙ፤ ዐይነት፤ ሥጋዊ፤ ጨዋታ፤ ያለበት። ለእመ፤ ከነ፤ አሐዱ፤ ዘየሐውር፤ ኅበ፤ ቀርቂስ፤ ለይኅድግ፤ አው፤ ለይስደድ፤ (መጽ፤ ቄስ፤ ፭፮)።

—፤ ገበጣ፤ ሰንጠረዥ። ካህን፤ ዘአዝለፈ፤ ተዋንዮ፤ ቀርቂስ፤ (ፍ፤ ነ፤ ፱)።

**ቀርቂሳዊ**፤ ገበጣ፤ ዐዋቂ፤ ተጫዋች። ቀርቂሳዊ፤ ዘይትዋነይ፤ ቀርቂሰ፤ (መጽ፤ ቄስ፤ ፭፻)።

**ቂርቆስ**፤ የሰው፤ ስም፤ ስማዕት፤ ከነናቱ፤ እሳት፤ የገባ፤ እንጌቤንን፤ እይ። ቂርቆስ፤ አንቀቅሖ፤ ተሠርዐ፤ ምስለ፤ እሙ፤ (ቅኔ። ስንክ፤ ጥር፲፭። ሐም ፲፱)።

**ቈረር**፤ ሮት፤ (ቈረ፤ ይቈርር፤ ይቍርር። ዕብ፤ ቃራር። ሱር፤ ቃር። ዐረ፤ ቀረ)፤ መቍረር፤ መብረድ፤ መቀዝቀዝ፤ ከሙቀት፤ መለየት፤ በራድ፤ ቀዝቃዛ፤ መኾን። ወናሁ፤ አብርሃም፤ ቈረ፤ ከመ፤ በረድ፤ (ኩፋ፤ ፳፫)። ተመይጠ፤ ተፈጸመ፤ በማለት፤ ፈንታ፤ ቈረ፤ ይላል፤ የመላሽ፤ ስሕተት፤ ነው። እስከ፤ ይቈርር፤ መዐተ፤ እኁከ፤ (ዘፍ፳፯፤ ፵፬። ኢዮ ፲፱፤ ፲፫። ኢሳ፭፤ ፳፱። ፲፤ ፳፭)።

**ቈሪር**፤ (ራን፤ ራት፤ ራር)፤ የቈረረ፤ የቀዘቀዘ፤ ቀዝቃዛ፤ በራዳ። ነፋስ፤ ቈሪር። ማይ፤ ቈሪር። ፀሓይ፤ ጥዒና፤ ቈሪራን፤ አዝርዕት። ቈራር፤ ወሙስንት፤ ምክር፤ (ሢራ፯፤ ፳። ምሳ፳፭፤ ፳፭። ስንክ፤ ሐም፲፪። ቄር፤ ጸላ)።

**ቍረት**፤ በቁሙ፤ መቀዝቀዝ፤ መብረድ፤ አቀዝቀዝ፤ አበራረድ። ቅዝቃዜ፤ ብርድ፤ ቈፈን። ቍረተ፤ ቱሳሔ፤ ዘርዕ። ቍረተ፤ ሥጋሁ፤ ኢያጥፍእ፤ ለእሳተ፤ መለኮቱ። ቍረተ፤ ኅሊና፤ (ፈ፤ መ፤ ፲፪፤ ፳። ያዕ፤ ዘእል። አርጋ፤ ፪)።

**ቍር**፤ በቁሙ፤ ብርድ፤ ቈፈን፤ ቅዝቃዜ። ይመውት፤ በቍር። ይርዕዱ፤ በእንተ፤ ቍር፤ እስመ፤ ክረምት፤ ውእቱ። ቍር፤ ወበረድ። እስመ፤ ብዙኅ፤ ቍራ፤ ለይእቲ፤ ሌሊት፤ (ኢዮ፴፯፤ ፲፰። ፮ዕዝ፤ ፱፤ ፯። ዘካ፲፬፤ ፯። ዮሐ፲፰፤ ፲፰)።

**አቍረረ**፤ አቀዘቀዘ፤ አስቀዘቀዘ፤ አበረደ፤ አስበረደ፤ አስታገሠ። ስትዩ፤ ማይ፤ ያቈርር፤ ላህበ፤ ጽምእ። ዝናም፤ ያቈርሮ፤ ለመርቄ። አቍረረ፤ ሙቀቶ። አቍርር፤ መዐተከ፤ (አፈ፤ ተ፳። ሢራ፲፰፤ ፲፮። ራልክ፤ ፶። ዘፀ፴፪፤ ፲፪)።

—፤ አቀረረ፤ ቀዳ፤ ጨመረ፤ አንቈረቈረ፤ ባፉ፤ ወይም፤ በሌላ። አቍረሩ፤ ማየ፤ በመንፈ፤ ወኢቀከዕወ፤ ማየ። ኢያቍርርኒ፤ ወኢይከድን፤ ቍርባኖ፤ በኀብስት፤ እምቅድመ፤ ሠርሖት፤ (ገድ፤ ዘሚ። ፍ፤ ነ፤ ፲፫)።

**መቍረሪ**፤ (ሪት፤ ርያን፤ ያት)፤ የሚያበርድ፤ አብራጅ፤ አቀዝቃዥ።

**መቍረር**፤ ርት፤ ማቍረሪያ፤ ማብረጃ፤ ማቀዝቀዣ፤ ማቅረሪያ፤ ማንቈርቈሪያ፤ ኰስኰስት፤ ሙቃም፤ ብርት፤ ልሕኵት። ማየ፤ መቍረር፤ የኰስኰስት፤ ውሃ፤ የቅዳሴ፤ ጠበል። ወማየ፤ መቍረርኒ፤ ኢይኄጥብ፤ ምንትኒ፤ እምአፍ፤ (ፍ፤ ነ፤ ፲፫)።

**አስቈረረ**፤ (ተቀ፤ ግ)፤ አስጠየፈ፤ አሸቈረረ፤ አስጠያፊ፤ ኾነ፤ ለሌላው። ተጠየፈ፤ ተሸቈረረ፤ ተጠያፊ፤ ኾነ፤ ጠላ፤ ተሰቀቀ፤ እንደ፤ ርኩስ፤ አየ፤ ሌላውን። ብእሴ፤ ደም፤ ወጕሕላዌ፤ ያስቈርር፤ እግዚ። ታስቈርር፤ ጣዖተ። ጸሊአቶ፤ ወአስቈርሮቶ፤ (መዝ፤ ፭። ሮሜ፪፤ ፳፪። ዮሴፍ)።

**መስቈርር**፤ (ርት፤ ራን፤ ራት)፤ የሚያስጠይፍ፤ አስጠያፊ፤ አስቀያሚ። የሚጠየፍ፤ ተጠያፊ፤ ተቀያሚ፤ ተሰቃቂ። አሕላማት፤ መስቈርርት፤ አስጠያፊ፤ (ራልክ፤ ፺፯፪)።

**ስቍሩር**፤ የተጠላ፤ የተነቀፈ፤ የረከሰ፤ ያስጠየፈ። የተጠየፈ፤ ሽቍራራ፤ ጥይፍተኛ። አክአብ፤ ንጉሥ፤ ወብእሲቱ፤ ስቍርርት፤ አስጠያፊ፤ (ስንክ፤ ጥር፯)።

**ሰቈራር**፤ (ቅጽልና፤ ጥሬ)፤ የሚያስጠይፍ፤ የሚያሰቅቅ፤ ከባድ፤ ግም፤ ጽሉእ፤ ርኩስ፤ ቅጽል። ጥይፍታ፤ ስቅቅታ፤ አልየው፤ አልሰማው፤ ማለት፤ ጥሬ። ሰቈራረ፤ ክንክሙኒ። ገበርክምዎ፤ ለጼናነ፤ ሰቈራረ። ሰቈራረ፤ ነፍሱ። ኢክነ፤ ሰቈራረ፤ ሰብሳብ፤ ዘበሕግ፤ ቅጽል፤ (ኢሳ፩፤ ፲፬። ዘፀ፭፤ ፳፩። ምሳ፩፤ ፲፮። ዲድ፤ ፴፫)። ማስነቱ፤ ዲቃላና፤ ቅጥይ፤ ስለ፤ ኾነ፤ መንገድ፤ ሰውጪ፤ መስቈርርና፤ አስቈራሪ፤ ሰቈራርና፤ ስቍሩር፤ አንዳንድ፤ ወገን፤ ናቸው።

**ቃሩራ**፤ (ዐረ፤ ቃሩረት። ትግ፤ ቈራረት)፤ በቁሙ፤ ቅዝቃዝ፤ ጠርሙዝ፤ የብርሌ፤ የብርጭቆ፤ ዐይነት፤ ሥራው፤ ቈሪር፤ ውሃ፤ የኾነ፤ ከብረት፤ ከልሕኵት፤ ያይደለ፤ (ዮሴፍ)።

**ቆሮስ**፤—መስፈሪያ፤—ቀወሮስ።

**ቅራስያ**፤—(ዐረ፤ እልቅራስያ)፤ ዕፅ፤

ፍሬ ፡ ዕፅ ፡ ፍሬነት ፡ እንደ ፡ እንኰይ ፡ ያለ ፤ ታናናሽ ፤ ፀጥንታም ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፲፰) ።

**ቀስ ፤—ቁስ ፤—ቀሲስ ፡ ቀስ ።**

**ቃስ ፤ (ዐረ ፡ ቂያስ ፤ ልክ ፤ መለኪያ) ፤** ገሳ ፤ የገሳ ፡ ልብስ ፡ ሱሪ ፡ ቀሚስ ፡ ልክኛ ፤ በልክ ፡ የተ ሰፋ ፡ ረዘሙ ፡ በጠረ ፡ የማይሱት ፡ ድርማንቅ ። **ልብስ ፡ ቃስ** ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፴፱ ። ዘሌ፲፮ ፡ ፬) ።

—፤ የሳይ ፡ ልብስ ፡ ጀባ ፡ ካባ ፡ መጐናጠፊያ ። **ዘይት ሞጣሕ ፡ ቃስ ። አስኬማ ፡ ልብሰ ፡ ቃስ ፡ አኮ ፡ ለአሮን ፡ ብርጕ ፡ ዘባኑ** ፡ (ደራሲ) ።

**ቈስጤ ፤—ቈሽት ፡ ጨንራ ፤—ቀሠጠ ።**

**ቍስጥ ፤ (ዐረ ፡ ቁስጥ ። ዕብ ፡ ቆሽጥ) ፤** ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ ስም ። ባለቅኔዎች ፡ ቀበርቾ ፡ ይሉታል ። **ዝክረ ፡ ስምኪ ፡ ሐዋዝ ፡ እምነ ፡ ክልበኑ ፡ ወቍስጥ ፡ ወእምነ ፡ ሰንበልት ፡ ምዑዝ** ፡ (ደራሲ) ።

**ቈስያ ፤ ያት ፤ (ዐረ ፡ ቁሻእ ። ዕብ ፡ ቂሹእ) ፤** የቅል ፡ የዱባ ፡ ወገን ፤ ያበሬ ፡ ያንኰሳ ፡ የሽ ክና ፡ ዐይነት ፤ ሞላላ ፤ ወጥ ፡ የሚኾን ፤ የሚቀቀል ፡ ቆሎ ፡ የሚበስል ፡ (ዘኍ፲፩ ፡ ፭) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ቈሽት ፤ የበሰለ ፡ ቋንጣ ፡ ይሉታል ።

**ቈሲል ፤ ሎች ፤ (ቈስለ ፡ ይቈስል ፡ ይ ቍስል ። ዕብ ፡ ክሻል ፡ ተሰናከለ) ፤** መቍሰል ፤ መነካት ፤ መመታት ፤ ቍስለኛ ፡ ቍስላም ፡ መኾን ፤ በ ደዌ ፡ በበትር ፡ በሥራ ፡ በሐዘን ። **አነ ፡ ጠቢብ ፡ ወአፈ ውሰሙ ፡ ሲድዉያን ፡ እለ ፡ ቈስሉ ፡ በደዌ ። ቈሰ ልኩ ፡ በቤተ ፡ ዐርክየ ። ወናሁ ፡ አበዊነ ፡ ቈስሉ ፡ በን ዲን** ፡ (በንክ ፡ ግንጽ፮ ። ዘክ፲፫ ፡ ፯ ። ፪ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፱) ።

**ቍሱል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ስልት) ፤** የቈሰለ ፤ የተነካ ፤ ንክ ፤ ውጋ ፤ ምት ። **ቍሱላነ ፡ ልብ** ፡ (ኢሳ፷፩ ፡ ፲፩ ። ፳፩ ፡ ፩) ።

**ቍስለት ፤** መቍሰል ፤ አቈሳሰል ፤ ቍስልነት ። ድካም ፤ ሐዘን ፤ ቍቅቍቅ ፡ (ዐማርኛ)

**ቍስል ፤ (ላት ፤ ቍሰል) ፤** በቍሙ ፤ የተ ነካ ፡ ገላ ፡ ደዌ ፡ በትር ፡ ያረፈበት ፤ ግርፋት ፡ ውጋታት ፤ መከራ ፤ ቂም ፡ ሐዘን ፡ ኀጢአት ። **ክመ ፡ ይትፈወስ ፡ እምቍስል ፡ ዘአቍሰልዎ ። ቍስለ ፡ ሕዝቡ ። እመ ፡ ብ ፡ ቍስል ፡ ክመ ፡ ቍስልየ ። ቍስለ ፡ ሞት ፤** (የሚ ገድል ፤ ለሞት ፡ የሚያበቃ) ። **እምጽሉ ፡ ቍስል ፡ የአኪ ፡ ቍስለ ፡ ልብ ። ወቍስለ ፡ አማዑት** ፡ (፪ዜና ፡ ፳፪ ፡ ፯ ። ኢሳ፴ ፡ ፳፮ ። ሰቈ፩ ፡ ፲፪ ። ራእ፲፫ ፡ ፫ ። ሚሪ ፳፭ ፡ ፲፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፶) ።

**አቍሰለ ፤** አቈሰለ ፤ አስቈሰለ ፡ አሳዘነ ። **ነደፍዎ ፡ ወአቍሰልዎ ። ትፍሥሕትክ ፡ ያቈስሎሙ ፡ ለጸላእ ትክ ። አነ ፡ አቍሰልኩ ፡ ነፍስየ** ፡ (፪ዜና ፡ ፳፪ ፡ ፭ ። ሚ ፋ፲፪ ፡ ፳ ። ዮሴፍ) ።

**አቍሳሊ ፤ መቍሰሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤** የሚያቈስል ፤ የሚያስቈስል ፤ አቍሳይ ፤ አስቈ ሳይ ፤ አሳዛኝ ፡ አስቀያሚ ። **ትካዝ ፡ መቍሰሌ ፡ ልብ ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ ደዌ ፡ ያቈስል ፡ ሥጋ** ፡ (ፊላስ) ።

**ቀሰመ ፤—ለቀመ ፤—ቀሚም ፡ ቀሠመ ።**

(ጥስ) **ቀስሞ ፡ ሞት ፤ (ቀሰመ ፡ ይቄስም ፡ ይ ቀስም ። አው ፡ ቀሲም ፡ ቀሰመ ፡ ይቀስም ፡ ይ ቅስም ። ዐረ ፡ ቀሰመ ፤ ከፈለ) ፤** ማጣፈጥ ፡ ማጠ ፋፈጥ ፤ መመጠን ፡ መቀመም ፤ ሰበሰበ ፡ ማዋሐድ ፡ ማ ዘመድ ፡ ለማጣፈጥ ። **በምንት ፡ ይቄስምዎ ፡ ለቀሲመ ፡ ልሳንየ** ፡ (ማርህ ፡ ፴ ። አርጋ) ። ሲጠብቅ ፡ የቀደሰ ፡ ሲሳሳ ፡ የቀተሰ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ በስዚህ ፡ ፀጀ ፡ ይኼዳል ።

**ቀሳሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤** የሚያጣ ፍጥ ፡ አጣፋጭ ፤ ቀማሚ ፤ ወጥ ፡ ቤት ።

**መቅስም ፤ መቅሰም ፤ (ብ ፡ መቃስም ፤ ማት) ፤** ማጣፈጫ ፤ ጨው ፤ ቅመም ፤ እንደ ፡ ማር ፡ ክ ብዙ ፡ ተቀምሞ ፡ እንዲ ፡ የኾነ ፤ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ወጥ ፤ በብዙ ፡ ቅመም ፡ የቀሠረ ፤ ሽታውና ፡ ጣዕሙ ፡ ልብ ፡ የሚመሥጥ ፤ እጅ ፤ የሚያስመጥጥ ። **ይትዐቀብ ፡ እመ ቃስማተ ፡ መብልዕ ፡ ወመስቴ ። እመ ፡ ብ ፡ ዘጥዕመ ፡ ዘከነ ፡ እመቃስማት ። ይፋድግ ፡ ሽሎ ፡ መቃስማት ። ኢይብልዕ ፡ መቃስማተ** ፡ (ቄድር ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭) ።

**ቀስም ፤** ቅመም ፤ ቀመመን ፡ ጣዕም ፡ ጥፍጥ ነት ፤ አጠፋፈጥ ፡ የቅመም ፡ የወጥ ። **ዘእንበለ ፡ ቀስም ። ወኢይብላዕ ፡ ቀስመ** ፡ (ቀሌ ። ቄድር) ።

**ተቀስመ ፤ ተቀሰመ ፤** ተጣፈጠ ፡ ተቀመመ ። **በምንት ፡ ይትቄሰም** ፡ (ማቴ፭ ፡ ፲፫) ።

(ላ ፡ ጥ) **ቅሱም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ስምት) ፤** የተጣ ፈጠ ፡ ጥፍጥ ፤ ቅምም ። **ነገሩ ፡ ቅሱም ፡ በጼው ፡ መለ ኮት ። ተግሣጽ ፡ ጥዑም ፡ ወዜና ፡ ቅሱም ፡ ክመ ፡ ጼው ። ቅሱም ፡ ማእድ** ፡ (ድጓ ። ፊላስ ። ስንክ ፡ ጥር፫) ።

**ቅሳሜ ፤** ማጣፈጥ ፤ መጣፈጥ ፡ መቀመም ፡ አቀ ማመም ፤ ቅመማ ፤ ቅመምነት ። **እምጽቡር ፡ ብሕበ ሔክ ፡ ወእምኔሁ ፡ ቅሳሜነ** ፡ (ኢዮ፴፪ ፡ ፯) ።

(ላ) **ቀሰመ ፤ (ዕብ ፡ ቃሳም ። ሱር ፡ ቅሳም) ፤** አሟረተ ፤ ጠንቈለ ፤ ገመተ ፡ መላ ፡ ጣለ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በቀሰመ ፡ ፈንታ ፡ አስተቃሰመ ፡ ይላል ፤ አይሬጊውን ፡ ባደሬራጊ ፤ የመላሽ ፡ በሕተት ፡ ነው ። **በከመ ፡ ሐሰበ ፡ ወአስተቃሰመ ፡ ለአማስኖቶሙ ። አስተቃስሚ ፡ ሲተ** ፡ (አስቴ፱ ፡ ፳፬ ። ፩ነገ ፡ ፳፰ ፡ ፰) ።

**አቅሰመ ፤ አስተቅሰመ ፤** አስሟረተ ፡ አስጠ ንቈለ ፤ መላ ፡ አስመታ ፤ ጨሌ ፡ ጠጠር ፡ አስጣለ ።

**አቅሳሚ ፤ መቅሰሚ ፤** አስጠንቋይ ፤ ጠን ቋይ ፡ ጠያቂ ።

**መቅስም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤** ጠንቋይ ፤ ሟርተኛ ፤ መለኛ ፤ ነቢየ ፡ ሐሰት ። **በመቅስም** ፡ ፈንታ ፡ **መስተቃስም** ፡ ይላል ፤ አያስኬድም ። **መስተቃስማን** ፡ (አ ርጋ ፤ ፫ ። ቀሌ ። ገድ ፡ ተክ) ። **መስተቅስም** ፡ ቢል ፡ ግን ፡ አስጠንቋይ ፡ ያሰኛል ፤ ከአስተቅሰመ ፡ ይስማማል ።

**መቅሰምት ፤ (ብ ፡ መቃስምት) ፤** የሕ ርት ፡ መማሪያ ፤ በየስሙና ፡ በየይነቱ ። ወነሥኡ ፡ መቃስምቲሆሙ ፡ ምስሌሆሙ ፡ (ዘኍ ፡ ፴፱ ፡ ፯) ።

**ምቅሰም ፤ (ማት) ፤** ማሕረጃ ፤ መጠንቈ ያና ፡ ማስጠንቈያ ፤ ቦታ ።

**ቀስም ፤ ቅስም ፤ (ማት) ፤** ሕርት ፡ ጥን ቈላ ፡ ነሲብ ፡ ማምት ፡ መላ ፤ ትንቢት ፡ ሐሰት ። መጽሐፍ ፡ ማን ፡ በቀስም ፡ ፈንታ ፡ መቅስም ፡ መቅስም ፡ መቃስም ፡ ይላል ፤ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ አያስኼም ። ስብአ ፡ መቅስም ። በሰዐም ፡ ዘመቅስም ። ሕልም ፡ ወሰ ግል ፡ ወመቃስም ፡ ከንቱ ፡ ውእቶሙ ፡ (ሲራ ፡ ፴ ፡ ፩ ። ኢያ ፡ ፲፫ ፡ ፳፪ ። ሚክ ፡ ፫ ፡ ፯) ።

**አስተቃሰመ ፤ (አደራራጊ) ፤** አጠናቈሰ ፡ አጠንቃቈሰ ፤ መላ ፡ አማታ ።

**መስተቃስም ፤** የሚያጠናቍል ፤ አጠናቋይ ፡ አጠንቋቋይ ።

**ቅስና ፤—ቍስንት ፤—ቀሲስ ፡ ቆሰ ።**

**ቈስቈስ ፤ (ብ ፡ ቈሳቍስ ፡ ሳት) ፤** የቤት ዕቃ ፤ ታናናሽ ፡ ስባሪ ፡ ሥንጥር ፡ ደጅ ፡ እፍ ፡ የመሰሰው ፡ ማጀት ፡ የጕረሠው ፡ ማናቸውም ፡ ኹሉ ፡ በየስሙና ፡ በያይነቱ ። ዠሎ ፡ ንዋያ ፡ ወቈስቈሶ ፡ ማህረኩ ። ወብ ዙኀ ፡ ቈሳቍሳት ። ወቈሳቍሳቲሆሙ ። ወበህየ ፡ ርኢኩ ፡ ዕፀወ ፡ ዘነኒ ፡ ፈድፋደ ፡ ቈስቈሰ ፡ መዐዛ ፡ (መቃ ። ገድ ፡ ተክ ። ዘፍ ፴፩ ፡ ፴፯ ። ሔኖ ፴፱ ፡ ፪) ። ቈስቈስ ፡ ቀስ ቀስ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ቅና ፡ ከ ፡ ቀወራሬ ሾች ፡ ስለ ፡ ኹሉ ፤ በቈሳቍስ ፡ ፈንታ ፡ ኩሳኵስ ፡ ይላል ። ዐራታተ ፡ ወኵሳኵሳተ ፡ ወሕጽሐልተ ፡ (ዲድ ፡ ፴፩) ።

**ቄሳር ፤—ስመ ፡ ንጉሥ ፤—ቀይሳር ።**

**ቀሲስ ፤ ሰት ፤ (ቀሰ ፤ ቀሰሰ ፡ ይቀስስ ፡ ይቅስስ ። ዕብ ፡ ቅሻሽ ። ሱር ፡ ቃሽ) ፤** ማር ጀት ፤ መሸምገል ፤ መቈሸሸ ፡ ቈሻሻ ፡ መኾን ፤ ቈሻሻ ፡ መልቀም ፡ ማጋበስ ፡ መሰብሰብ ። መቅሰስ ፡ ክህነ ፡ ቄስ ፡ መኾን ፤ ቅስና ፡ መሾም ። ምሥዋዒሆሙ ፡ በንበ ፡ ቀ ሰሱ ፡ ወዛቅኑ ፡ (ቀኖ ፡ ኒቅ ፡ ፳፱) ።

**ቀሲስ ፤ (ዐረ ፡ ቀሲስ ። ሱር ፡ ቃሺሽ) ፤** ቄስ ፤ ክህነ ፤ ሽማግሌ ። ቀሲስ ፡ ወዲያቆን ። እምነ ፡ ቀሲስ ፡ (ቅዳ ። ፪ዮሐ ፡ ፩) ።


**ቀስ ፤ ቀይስ ፤ (ትግ ፡ ቀሽ) ፤** ገዢ ፡ ከማው ፡ ቀሲስ ። አባ ፡ ገሪማ ፡ ቀስ ፡ ዘመደራ ። ወይቤልዎ ፡ ቀስ ፡ ወመኳንንት ፡ ለአባ ፡ ሊባኖስ ። ለእመ ፡ ሰረቀ ፡ አክሊሮስ ፡ ዘውእቱ ፡ ቀይስ ፡ ገበዝ ፡ ንዋያተ ፡ ምሥ ዋዕ ፡ (መዋሥ ። ፊ ፡ መ ፡ ፲፮ ፡ ፯) ።

**ቀሲሳን ፤ ቀሳውስት ፤** ቄሶች ፤ ቀሳውስ ቶች ። ትሚም ፡ ቀሲሳን ። ይጸውዕ ፡ ቀሳውስተ ፡ (ቲቶ ፩ ፡ ፭ ። ያዕ ፭ ፡ ፲፬) ። ኤጲስቆጶስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ቀሲስ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ምስለ ፡ ቀሳ ውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ (ፊልጵ ፩ ፡ ፩) ።

**ቅስና ፤** ቍስንት ፡ ቄስ ፡ መኾን ፤ የቄስ ፡ ማዕ ርግ ፤ የሹመቱ ፡ ስም ። ዘተሠይመ ፡ ሢመተ ፡ ቅስና ። ይነሥእ ፡ ሢመተ ፡ ቅስና ፡ በሕልያን ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፯ ፡ ፰) ።

**አቅሰሰ ፤** አቀሰሰ ፤ አስቀሰሰ ፤ ቅስና ፡ ሾመ ፤ አሾመ ፤ ቄስ ፡ አደረገ ፤ አስደረገ ።

**ቀስት ፤ (ዕብ ፡ ቄሼት ። ሱር ፡ ቊሽታ ። ዐረ ፡ ቀውስ) ፤** በቀጠው ፡ ደጋን ፤ ጕባብ ፤ ጕብጣ ፡ የጦር ፡ መማሪያ ። ቀስት ፡ ጠዋይ ። ቀስተ ፡ ብርት ፤ ቀስተ ፡ ደመና ። ቀስተ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ሆሴ ፯ ፡ ፲፮ ። መዝ ፡ ፲፯ ። ሕዝ ፩ ፡ ፳፰ ። ክፋ ፡ ፯) ።



ቀስት ፡

**ቀስተ ወ ፤** ቀሰተ ፡ ቀስት ፡ ሠራ ፤ ቀስት ፡ አስ መሰለ ፤ አጐበጠ ። ዐለበ ፤ ደጋን ፤ ሳበ ፤ ለጠጠ ፤ ነደፈ ፤ ፍላጻውን ፡ በቀስት ። ወቦአ ፡ ወቀስተወ ፡ ፍጽመ ፡ ኢዮአብ ፡ (፬ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፯) ።

**ቀስታዊ ፤** ቀስት ፡ ሠሪ ፤ ቀስተኛ ፡ ባለቀስት ፡ ነዳፊ ፡ ወርዋሪ ።

**ቀስታም ፡ (ማት) ፤** መንደርደሪ ፡ በትር ፡ ጕ መድ ፤ ዱላ ፤ ከቀስት ፡ ጋራ ፡ የሚያዝ ። በቀስታመ ፡ ኀ ይሉ ፡ ኢይከሞ ፡ ለጸርዊ ፡ ርኩስ ። በትርከ ፡ ወቀስታ ምከ ። ገሠጽከ ፡ ለዮናስ ፡ በቀስታመ ፡ ባሕር ፡ (ድጓ ። መዝ ፡ ፳፪ ። ቅኔ) ።



ቀስታም ፡

**ቀታ ፤ (ዐረ ፡ ቂሻእ) ፤** ቈስያ ፤ የዱባ ፡ ወገን ። እልቀታ ፡ ወሐምሐም ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፯) ።

**ቀቲው ፤ ዎት ፤ (ቀተወ ፡ ይቀቱ ፡ ይቅቱ ። ዐረ ፡ ወቀተ ፡ ጊዜ ፡ ወሰነ) ፤** መገበር ፤ ግብር ፡ መስጠት ፡ ገባር ፡ ተገዥ ፡ መኾን ። ጋላ ፡ በሬ ፡ ገበሬ ፡ ሲል ፤ ቆቲዮ ፡ ቆቲ ፡ የሚለው ፡ ከዚህ ፡ ይስማ ማል ። መቈታቸት ፡ ቍትቻ ፡ ማድረግ ፤ መወሬፈድ ፤ የቍትቻን ፡ ዕዳ ፡ ውርርድን ፡ መክፈል ። በቀተወ ፡ ፈንታ ፡ ቀተተ ፡ ይልና ፤ ጥሬውን ፡ ደግሞ ፡ ቀዶት ፡ እንደ ፡ ማ ለት ፡ ቀተት ፡ ይላል ፤ የመላሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ከመ ፡ ይግበር ፡ ቀተተ ፡ ምስሌሁ ። ወእለ ፡ ይሰትዩ ፡ በቀቶት ፡ (ዳን ፲፩ ፡ ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፩) ።

**ቀቶት ፤** ገባርነት ፡ ግብር ። ቍትቻ ፤ ውርርድ ፡ ውኸንብር ፤ የማጕስ ፡ የቍትቻ ፡ ዕዳ ፤ የውርርድ ፡ ገን ዘብ ። በእንተ ፡ ከመ ፡ ኢመፍትው ፡ ይስተዩ ፡ በቀ ቶት ፡ አስተዋፂኦሙ ። ወእንበሩ ፡ ቀቶተ ፡ በዝንቱ ፡ (ቀኖ ፡ ሎዶ ፡ ፶፭ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**አቅተወ** ፤ አስገበረ ፤ ገባር ፡ አደረገ ፤ አስጨነቀ ። አቈታቶ ፤ አወፈረደ ፡ ቍትቋ ፡ አስከፈለ ። ሚጢ ፡ በትረ ፡ እሴ ፡ ይትፌደዩ ፡ ወፀሰውዎሙ ፡ ለእሴ ፡ ያቀትዉ ። እፎ ፡ ተሰዐረ ፡ ዘያቀቱ ። አልቦ ፡ ምንትኒ ፡ ዘያቀት ውዎ ፤ አስገበረ ፡ (ኢሳ ፲ ፡ ፬ ። ፲፬ ፡ ፬ ። ዘዳ ፳፱ ፡ ፳) ።

**ቀቲል** ፤ ሎት ፤ (ቀተለ ፡ ይቀትል ፡ ይቅትል ። ዕብ ፡ ቃጣል ። ሱር ፡ ቅጣል ። ዐረ ፡ ቀተለ) ፤ መግደል ፤ መውጋት ፡ ማቍሰል ፤ መቍረጥ ፤ ማጥፋት ፡ ማድከም ፡ መጕዳት ። ይመክሩ ፡ ለቀቲል ። ቀተለ ፡ ርእሶ ፡ ለሊሁ ። ፀዔ ፡ ቀተሎ ፡ ለዝኩ ፡ ሐም ሐም ። በጾም ፡ ለብእናሆሙ ፡ ቀተሉ ፡ (ኢሳ ፲፬ ፡ ፯ ። ዮሴፍ ። ዮና ፬ ፡ ፯ ። ድጓ) ።

**ቀታሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ተልት) ፤ የሚገድል ፡ ገዳይ ፤ አጥፊ ። ቀታሊ ፡ ነፍስ ። ኮነትኒ ፡ ቀታሊተ ። ሞሎት ፡ ቀታልያን ። ቀተልት ፡ አበዊሆሙ ፡ (ሚሊ ፹፰ ፡ ፳፭ ። ሮሜ ፯ ፡ ፲ ። ኤር ፳፫ ፡ ፩ ። ፩ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፱) ። በቀቲል ፡ ፈንታ ፡ ቀታሊ ፡ ይባል ፡ በሕተት ፡ ነው ። ኢትግበርዋ ፡ ቀታሊተ ፡ ለምድርክሙ ፡ (ዘኍ ፴፭ ፡ ፴፫) ።

**ቀትል** ፤ (ላት) ፤ ግድያ ፡ ሰልፍ ፤ ውጊት ፤ መርነት ። ቀትል ፡ በመጥባሕት ። ገብሩ ፡ ቀትለ ። ጸብእ ፡ ወቀትል ። በሕገ ፡ ቀትል ። ቀትላት ፡ በይጣናት ፡ (ዮሴፍ ። ፩ዜና ፡ ፲ ፡ ፩ ። ያዕ ፬ ፡ ፩ ። ዮዲ ፯ ፡ ፲፩ ። ፊልክ) ።

**መቅትል** ፤ ተል ፤ (ብ ፡ መቃትል) ፤ መግደያ ፡ መግሪያ ። ገዳይ ፤ ባለመግሪያ ።

**ምቅታል** ፤ (ላት) ፤ መግደያ ፡ መገደያ ፤ ማስገደያ ፡ ቦታ ። መልዕልተ ፡ ምቅታል ፡ (፬ነገ ፡ ፳ ፡ ፳፰) ።

**አቅተለ** ፤ አስገደለ ፡ አስፈጀ ። በአቅትሎትከ ፡ ጳጳ ፪ አኒ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ተቀትለ** ፤ ተገደለ ፡ ሞተ ፡ ተመታ ፡ ታረደ ፡ ተወጋ ፡ ቈሰለ ፤ ጠፋ ፡ ቀበባሽ ፡ ረከሰ ። ረሰይክኑ ፡ ለተቀትሎ ። ተቀትሊት ፡ ሀገር ። እስመ ፡ ተቀተልከ ። ወተቀትለት ፡ ምድር ፡ በደም ፡ (መቢ ፫ ፡ ፬ ። ሕዝ ፴፫ ፡ ፳፩ ። ራእ ፭ ፡ ፱ ። መዝ ፻፭) ።

**ቅቱል** ፤ (ላን ፡ ላት ፤ ትልት) ፤ በሰው ፡ እጅ ፡ የሞተ ፡ የተገደለ ፤ የተወጋ ፤ የቈሰለ ፡ ቍስለኛ ፤ ማዳይ ፡ ሬሳ ። ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ ቅቱል ፡ በውስተ ፡ ምድር ። ቅቱላን ፡ በኵናት ፡ (ዘዳ ፳፩ ፡ ፩ ። ሶፎ ፪ ፡ ፲፪) ። ሰንት ፡ በማስት ፡ ፈንታ ፡ ቅቱል ፡ ይባል ፤ በሕተት ፡ ነው ። ፲ገር ፡ ቅልት ፡ (ኢሳ ፩ ፡ ፳) ።

**ቅትለት** ፤ (ታት) ፤ መግደል ፤ መገደል ፡ አገዳደል ፤ ግድያ ፡ ትግል ፡ ትግያ ፤ ጦርነት ። ወኢነስሑ ፡ ዓዲ ፡ እምኑ ፡ ቅትለቶሙ ። ዜና ፡ ቅትለቱ ፡ ለአልዓዛር ፡ ካህን ። ሰፍጠታት ፡ ሰይጣን ፡ ልባዊት ፤ ወቅትለታቲሁ ፡ ኅቡአት ፡ (ራእ ፱ ፡ ፳፩ ። ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፬) ።

**ተቃተለ** ፤ ተጋደለ ፡ ተገዳደለ ፡ ተዋጋ ፤ ተባለፈ ፡ ተጋጠመ ። ይዳልሑ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወይትቃተሉ ። ይትቃተልዎ ፡ ለይሁዳ ። ተቃተሎ ፡ ለመነክስ ፡ ኀሊና ፡ ዝሙት ። ንትቃተል ፡ ክልኤነ ፡ በባሕቲትነ ፡ (ማቴ ፳፬ ፡ ፲ ። ኢሳ ፲ ፡ ፳፩ ። ገድ ፡ ዳን ። ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲) ።

**አስተቃተለ** ፤ አጋደለ ፡ አገዳደለ ፤ አዋጋ ፡ አጣላ ፡ አፋጀ ፡ አማረሰ ፤ አስተባለቀ ። ብዙኃን ፡ አዐርከተ ፡ አስተቃተለ ። ከመ ፡ ያስተቃትሎሙ ፡ በኀጺን ፡ ወበረኀብ ፡ (ሚራ ፳፰ ፡ ፲፫ ። ራእ ፮ ፡ ፰) ።

**መስተቃትል** ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤ የሚጋደል ፡ የሚያጋድል ፡ አጋዳይ ፡ አገዳዳይ ፡ ተጋዳይ ፤ ዐርበኛ ፡ ተዋጊ ፡ ሰልፈኛ ። ብእሲ ፡ መስተቃትል ፡ ወተባዕ ። እደክ ፡ መስተቃትልት ፡ ወመዋኢት ። አሕዛብ ፡ መስተቃትላን ፡ (ሚራ ፳፯ ፡ ፳፯ ። ጥበ ፲ ፡ ፳ ። ኢሳ ፲፫ ፡ ፬) ።

**ምስትቅታል** ፤ መጋደያ ፡ መገዳደያ ፡ ማገዳደያ ፡ ቦታ ።

(ጥ) **ቀትሮ** ፤ ሮት ፤ (ቀተረ ፡ ይቄትር ፡ ይቀትር ። አው ፡ ቀቲር ፤ ቀተረ ፡ ይቀትር ፡ ይቅትር ። ዐረ ፡ ቀተረ) ፤ ማዋደድ ፡ ማዘመድ ፡ መቈራኘት ፡ መቀርቀር ፤ መደንቀር ፤ የንፍጠት ፡ የብረት ። መዝጋት ፡ መቈለፍ ፡ ማጕር ፡ መወርወር ፡ መሸኮር ፤ የመዝጊያ ። ዐጸው ፡ ኆኅተ ፡ ወቀተረ ። ዕጽዉ ፡ ኆኅተ ፡ ወቀትሩ ። ወጸአኒ ፡ ቀትርኒ ፡ ኆኅተ ፡ (መሳ ፫ ፡ ፳፫ ። ፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ። ሉቃ ፲፩ ፡ ፯) ።

—፤ በቁሙ ፡ መቀትር ፤ ማሸል ፡ ሹል ፡ ማድረግ ፤ ሰማዋደይ ። ቀትር ፡ መኸኝ ፡ የጊዜ ። ወቀቲሮ ፡ ጊዜ ፡ ስሱ ፡ ሰዓት ፡ (ሉቃ ፳፫ ፡ ፵፬) ።

—፤ ማጠን ፡ ማጤስ ፡ ማሸተት ፡ (ዕብ ፡ ወሱር ፤ ቃጣር ፡ ቅጣር ፡ ቋጠረ ፡ ዐጠን) ። በእንተ ፡ ዕጣኑ ፡ ለአሮን ፡ እንተ ፡ አቍረረ ፡ መዐተ ፡ ሞት ፡ ሰበ ፡ ቀተረ ፡ (አዋል) ።

**ቀትር** ፤ በቁሙ ፡ መንፈቀ ፡ መዓልት ፤ እኩለ ፡ ቀን ፤ ሸኛ ፡ ሰዓት ፡ የፀሐይ ፡ አናት ፡ ቀርነ ፡ ምዕዛሩ ፡ ምድርን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የሚወጋበት ። ይጼልለክ ፡ እምፀሐዩ ፡ ቀትር ። ቀትረ ፡ መዓልት ። ጊዜ ፡ ቀትር ። ብርሃነ ፡ ቀትር ። ጋኔነ ፡ ቀትር ፡ (ሚራ ፴፰ ፡ ፲፱ ። ፴፭ ፡ ፲፮ ። ማር ፲፯ ፡ ፴፫ ። ኢሳ ፲፮ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፺) ።

**ተቀትረ** ፤ **ተቀተረ** ፤ ተዘጋ ፡ ተሸጐረ ፡ ተወጋ ፡ ተቈንከረ ። ታጠነ ፡ ጤሰ ፤ ሸተተ ፤ መሚዕት ፡ ኸነ ። ዘበዮርዳኖስ ፡ ተጠምቀ ፡ ወዘበመስቀል ፡ ተቀትረ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ቅቱር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ትርት) ፤ የተዘጋ ፡ ዝግ ፤ ሽጕር ፡ ቅርቅር ። ቤተ ፡ ምቅሕ ፡ ዝጉሕ ፡ ወቅቱር ፡ (ማቢ ፭ ፡ ፳፫) ።

**ቅታሬ** ፤ **ቅታር** ፤ መጤስ ፤ መሸተት ። ሽቱ ፡ ዕጣን ፤ የተቀመመ ፡ የተጣፈጠ ፤ የደቀቀ ፡ የተወገጠ ። የዕጣን ፡ ሽታ ፤ መዐዛ ። ዕጣን ፡ ዘቅታሬ ፡ ደቂቅ ። ዕጣን ፡ ዘካልእ ፡ ቅታሬሁ ፡ (ዘፀ ፴ ፡ ፯ ፡ ፱ ፡ ፴፬—፴፰) ።

**ቅትር** ፤ (ራት) ፤ ቍንከር ፡ ቀኖት ፡ ምስማር ፤ ወስፌ ፡ አፊ ፡ ምግር ፤ ካስማ ፡ ችካል ፤ ማናቸውም ፡ ሹል ፡ የሾነ ፡ ኹሉ ። ኀጺን ፡ ብዙኅ ፡ ለቅትራት ፡ ኀዋ

ኀው ። ቅንው ፡ በቅትራተ ፡ ኅጻውንት ። ቅትራት ፡ ር ሱን ። ከመ ፡ ቅትራት ፡ ለአድግ ፡ (፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፫ ። መጽ ፡ ምስ ። መክ፲፱ ፡ ፲፩ ። ምሳ፳፯ ፡ ፫) ።

**ቀተተ ፤—ቈተቈ ፤—ቀተወ ።**

**ቆጽን ፤—ኵፍ ፡ ጫማ ፤—ቀወጽን ።**

**ቆጸረ ፤—ቈረጠመ ፤—ቀውጸረ ።**

**ቆጽሮስ ፤—ስመ ፡ ሀገር ፤ ደሴት ፤—ቀ ውጽሮስ ።**

**ቈጽርስስ ፤ (ጽር ፡ ኪፓሪሶስ ። ዕብ ፡ ብሮሽ)** ፤ የዛፍ ፡ ስም ፤ ጥድ ፡ የጥድ ፡ የዘግባ ፡ ዐይነት ፡ ማንዱ ፡ ነጭ ፤ ደቅማ ፡ የሚመስል ። ቈጽርስስ ፡ ወዘሉ ፡ ዕፀወ ፡ ገዳም ፡ (ኩፋ ፡ ፲፫ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፭ ። ፀ፩ ፡ ፵) ።

# ረ

**ረ** ፤ ኻያኛ ፡ ፊደል ፤ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በ አበገደ ፤ ስሙ ፡ ርእስ ፤ ቍጥሩ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ ረ ፡ (፪፻) ከልኢቱ ፡ ምእት ፡ ይባላል ።

**ርእይ ፡ ዮት ፤ (ርእየ ፡ ይሬኢ ፡ ይር እይ ። ዕብ ፡ ራኣህ ። ዐረ ፡ ረእይ)** ፤ ማየት ፡ መመልከት ፤ መትኰር ፤ ማስተዋል ፡ መመርመር ፡ ባይን ፡ መቈፈር ፡ ዐይኑን ፡ ልብን ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ መጣል ፡ መትከል ፤ አይቶ ፡ ማወቅ ፡ መረዳት ፤ ልኩን ፡ ማግኘት ። ዐየንን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ወንድም ፡ ነው ። መኑ ፡ ይ ጸግብ ፡ እምርእየ ፡ ሠናይቱ ። ይርአዩ ፡ ዕዉራን ። ርእዩ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ ዝ ። ኢትርአያኒ ፡ እስመ ፡ ሐነ ፡ ጸላም ፡ (ሚራ፵፱ ፡ ፳፱ ። ኢሳ፳፩ ፡ ፩ ። ኤር፱ ፡ ፲ ። ማሕ፩ ፡ ፮) ።

—፤ መስማት ፡ ማድመጥ ፤ ልብ ፡ ማድረግ ። ስጽንን ፡ እንዘ ፡ ትርእየ ፡ ሕልመ ፡ ሕቡከ ። ወርእየ ፡ ሕልመ ፡ አቡሁ ፡ ገብአ ፡ ማቴሳላ ። ወርእያ ፡ ደንገፀት ፡ እም ቃሉ ፡ (ሔኖ ። ሉቃ፩ ፡ ፳፱) ።

—፤ ማሰብ ፡ መመኘት ፤ መገምገም ፡ መገመት ፡ መጠ ንቈል ፡ ማሻረት ፡ ትንቢት ፡ መናገር ፤ መላ ፡ መምታት ። ልብየ ፡ ርእየት ፡ ብዙኀ ፡ ጥበበ ። ርኢኩ ፡ ሎቱ ፡ ዐ ስበ ፡ በዝኩ ፡ ወልድ ። ትሬእዩ ፡ በኮከበ ፡ በማይ ። ነ ቢያትኪ ፡ ርእዩ ፡ ለኪ ፡ ከንቶ ፡ (መክ፩ ፡ ፲፮ ። መቢ ፲፱ ፡ ፩ ። ኢሳ፵፯ ፡ ፲፫ ። ሰቈ፪ ፡ ፲፬) ። ሰማ ፡ ዐሰበ ፡ ገ መተ ፡ አሻረተ ፡ ቢል ፤ የማየትን ፡ ስልት ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምስጢሩ ፡ ከማየት ፡ አይወጣም ፡ ለሥራና ፡ ለነ ገር ፡ ኹሉ ፡ በዐይኑ ፡ ሥጋ ፡ ወይም ፡ በዐይኑ ፡ ልብ ፡ የ ሚታይ ፡ ሕልማዊ ፡ መልክ ፡ አለው ።

**ረእዩ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ አይት)** ፤ የሚያይ ፡ የሚያስተውል ፡ የሚጠነቀቅ ፤ መሠሪ ፡ ኮከብ ፡ ቈጣሪ ፡ ነቢይ ፡ ሐሳሚ ፤ ፈታኝ ፡ መርማሪ ። አ ፡ ልብ ዋን ፡ ረኣይያን ፡ ናሁ ፡ እንኩሙ ፡ እነሌ ፡ ስምዐ ፡ ለ ዛቲ ፡ ቃል ። ረኣይያነ ፡ ከዋክብት ። ረአይቱ ፡ ኮከብ ። ረአዩ ፡ ኀቡአት ። ረሰዩ ፡ ለወልዱ ፡ ረአዩ ፡ ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ (ግንዘ ። ሔኖ፷ ፡ ፫ ። ኪዳ ። አርጋ ፡ ፫ ። ዮሴፍ) ።

**ረአይ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ነቢይ ። ንሑር ፡ ኀበ ፡ ረኣይ ፤ እስመ ፡ ይብልዎ ፡ ሕዝብ ፡ ለነቢይ ፡ ረኣየ ። ቦኑ ፡ ረአይ ፡ ዝየ ። አይቴ ፡ ቤቱ ፡ ለረአይ ፡ (፩ነገ ፡ ፱ ፡ ፲፩ ፡ ፲፰) ።

**ራእይ ፤ (ያት)** ፤ በቁሙ ፡ ሕልም ፤ ትንቢት ፤ ጥንቈላ ፡ ኮከብ ፡ ቈጠራ ። ራእይ ፡ ዘርእየ ፡ ኢሳይያስ ። እስ ፡ ይሬእዩ ፡ ራእየ ። ኢርእዩ ፡ ራእየ ፡ በኀበ ፡ እ ግዚ ። ራእየ ፡ ኮከብ ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፩ ። ፀ፲ ፡ ፲፰ ። ሰቈ፪ ፡ ፱ ። ሔኖ፰ ፡ ፫) ። ራእይ ፡ ለንባቡና ፡ ለመጻሒ ።

—፤ ማየት ፤ አስተያየት ፡ ዐይን ፡ አገባለጥ ። እምራእዩ ፡ ይትዐወቅ ፡ ሰብእ ፡ (ሚራ፲፱ ፡ ፳፱) ።

—፤ መልክ ፤ ፊት ፡ ቅርጽ ፤ ገጽ ፤ ዐይን ፡ የሚያርፍበት ። ተወለጠ ፡ ራእዩ ። እሰ ፡ ሠናይ ፡ ራእዮን ። ጸሊም ፡ ከመ ፡ ሕመት ፡ ራእዮሙ ። ገጹ ፡ ከመ ፡ ራእየ ፡ መብ ረቅ ፡ (ማቴ፲፯ ፡ ፪ ። አስቴ፪ ፡ ፯ ። ሰቈ፬ ፡ ፰ ። ዳን፲ ፡ ፮) ።

**አርአየ ፤ አስተርአየ** ፤ አሳየ ፤ ገለጠ ፤ አበራ ፤ ነገረ ፤ አስተማረ ፤ አሳወቀ ፤ አስረዳ ። አርአዮሙ ፡ እደ ዊሁ ፡ ወሠናይቶ ። ከመ ፡ አርኢ ፡ ኀይልየ ፡ ላዕሌከ ። እግዚ ፡ ያርኢ ፡ ገጾ ፡ ላዕሌከ ። ነገር ፡ ዘአርአይኩከ ። አርእየኒ ፡ ወአእምር ። ምንተ ፡ ይብሉ ፡ ዘአስተር አዩ ። ዕፀ ፡ ዘያሬኢ ፡ ወያሌቡ ፡ ሠናየ ፡ ወእኩየ ፡ (ሚራ፲፮ ፡ ፯ ። ሮሜ፱ ፡ ፲፯ ። ዘኍ፯ ፡ ፳፯ ። ኤር፲፩ ፡ ፲፰ ። ፀ፯ ፡ ፱ ። ሮሜ፲፩ ፡ ፱ ። ዘፍ፱ ፡ ፱) ።

**አርአያ** ፤ በቁሙ ፤ ሥዕል ፤ አምሳል ፤ ዐይነት ፤ መልክ ፤ አካል ፤ አብነት ፡ መምር ። ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በ አርኣያነ ። በበ ፡ አርኣያሁ ። አርኣያሁ ፡ ለእግዚ ። ታ ሄኒ ፡ ገጸ ፡ ወታበረኑ ፡ አርአያሃ ። ብርሃን ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወአምሳለ ፡ አርአያሁ ። ኮነ ፡ አርኣያ ፡ ለዓለም ፡ ከመ ፡ ይንስሑ ። እስመ ፡ አርአያየ ፡ ወሀብኩክሙ ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፲፮ና ፡ ፳፯ ። ፱ቀር ፡ ፱ ፡ ፱ ። ሰንክ ፡ ጳጕ፭ ። ዕብ፩ ፡ ፫ ። ሚራ ፵፬ ፡ ፲፮ ። ዮሐ፲፫ ፡ ፲፭) ።

—፤ ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፤ እንደ ። አርአያ ፡ ይነ ውም ፡ ዘልፈ ። አርአያ ፡ ብዙኅ ፡ ዝናም ። አርአያ ፡ ከመዝ ፡ በረረ ፡ (ሰንክ ፡ ጥር፳፩ ። ጥቅ፳፭ ። ደራ.ሲ) ።

**ተርእየ** ፤ ታየ ፡ ተገለጠ ። ወተርእየት ፡ ማይ ፡ ርግዕት ። ኢትትረአይ ፡ ቅድሜየ ፡ ዕራቀከ ። መፍትው ፡ ለአንስት ፡ ይትረአያ ፡ በአርኣያ ፡ ህድአት ፡ ወበትሕትና ፡ ፍድፉድ ፡ (ጥበ፲፱ ፡ ፯ ። ዘፀ፳፫ ፡ ፲ ። ፈ፡ መ ፡ ፴፱ ፡ ፳) ። በተርአየ ፡ ፈንታ ፡ አስተርአየ ፡ ይባል ፤ የስሕተት ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ አያሰኝም ። ገባሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ዘያስተርኢ ፡ ወዘኢያስተርኢ ። አስተርአየ ፡ ዘኢያስተርኢ ፤ እሙን ፡ ኮነ ፡ አስተርእዮቱ ፡ (ጸሎ፡ ሃይ ። ድጓ) ። በአርአየ ፡ ቦታ ፡ አስተርአየ ፡ ቢል ፡ ማን ፡ ም ርመ ፡ ቀለሙ ፡ ሳይበ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ርትዕ ፡ እንጂ ፡ ጸያፍ ፡ አይኾንም ፤ ስሕተት ፡ አይባልም ።

**ርኡይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ኢት) ፤ የታየ ፡ የተገለጠ ፤ ግልጥ ፤ ጉልሕ ።

**ርእየት** ፤ ማየት ፤ መታየት ፤ አስተያየት ፤ መልክ ፤ አምሳል ፤ ዐይነት ። እፎ ፡ እክል ፡ ርእየተ ፡ እኪቶሙ ። ተወለጠ ፡ ርእየተ ፡ ገጹ ። ሕዝቅኤል ፡ ዘርእየ ፡ ርእየተ ፡ ስብሐቲሁ ። ይገብሮ ፡ ከመ ፡ ርእየተ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ። ከመ ፡ ርእየተ ፡ እሰቈጥሩ ፡ (አስቴ፰ ፡ ፮ ። ዳን፲ ፡ ፲፱ ። ሢራ፴፱ ፡ ፰ ። ኢሳ፵፩ ፡ ፲፫ ። ሕዝ፩ ፡ ፲) ።

**ምርኣይ** ፤ (ያት) ፤ ማያ ፤ ማሳያ ፤ መተያ ፤ ቦታ ፤ መስታዮት ፤ መነጽር ። ርኢይ ፤ ራእይ ፤ ርእየት ፤ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ምርኣይ ፡ ይባል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ምርኣየ ፡ አዕይንቲከ ፡ (ዘዳ፳፰ ፡ ፴፬) ። ምራ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ ማያ ፡ መጠንቈያ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ሕዝ፳፩ ፡ ፳፩) ።


**ተራአየ** ፤ ተያየ ፤ ተማሰለ ፤ ተመሳሰለ ፤ ተነጻጸረ ። ነዐ ፡ ንትራአይ ፡ ገጸ ፡ በገጽ ። የሐውሩ ፡ ክልኤቱ ፡ ኅቡረ ፡ እንዘ ፡ ኢይትራአዩ ፡ (፬ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፰ ። ዓሞ፫ ፡ ፫) ።

**አስተራአየ** ፤ አስተያየ ፡ አነጻጸረ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፤ ዐይን ፡ ለዐይን ።

**አስተርአየ** ፤ (አርአየ) ፤ አሳየ ፤ ገለጠ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ታየ ፡ አሳየ ፡ ብለው ፡ በኹለት ፡ ጾታ ፡ ይፈቱታል ፤ ታየ ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፤ አሳየ ፡ ማለት ፤ እውነት ። ወዘንተሰ ፡ አማነ ፡ ትቤሊ ፡ (ዮሐ፱ ፡ ፲፰) ።

**ረአመ** ፤—ሮኸ ፥ ነጐደ ፤—ርዒም ፡ ረዐመ ።

**ርኤም** ፤ (ማት ። ዕብ ፡ ርኤም ። ሱር ፡ ርማያ) ፤ ቀንዳም ፤ የበረሓ ፡ እንስሳ ፤ የዋሊያ ፡ ወገን ፡ ቀንደቹ ፡ ጠፍጣፎች ፤ ታላላቆች ፤ ባለብዙ ፡ ዐጽቆች ፡ የኾኑ ፤ ለያንዳንዱ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ዐጽቅ ፡ ያላቸው ፤ ዐጽቆቻቸው ፡ የእጅ ፡ ጣቶች ፡ የኹላብ ፡ ዕንጨቶች ፡ የሚመሳሰሉ ። የግእዝ ፡ ሙላሽ ፡ ግን ፡ ርኤም ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሐርማዝ ፡ ሐሬም ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ዘአሐዱ ፡ ቀርኑ ፡ ይባል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ (መዝ ፡ ፳፩ና ፡ ፳፫) ።



ርኤም ፡

**ረአሙት** ፤ (ዕብ ፡ ራእሞት) ፤ ውስጠ ፡ ብዙ ። ውድ ፡ ክቡር ፡ ዕቃ ፤ ጥሩ ፡ ገንዘብ ፡ ሸቀጥ ፤ በውድ ፡ የሚሸጥ ፡ የሚለወጥ ፤ ወርቅ ፡ ዕንቍ ፡ ዘጴ ፡ ሕቍ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡ (ሕዝ፳፯ ፡ ፲፮) ።

**ርኢስ** ፤ ሶት ፤ (ርእሰ ፡ ይርእስ ፡ ይርእስ ። ዐረ ፡ ረአሰ) ፤ መራስ ፤ ራስ ፡ መኾን ፤ ራስ ፡ መባል ፡ መሾም ፡ መላቅ ፡ መሠልጠን ፤ እንደ ፡ ጉልላት ፡ በላይ ፡ መኾን ። ተሰአከ ፡ ሰነግድ ፡ ከመ ፡ አብርሃም ፤ ወተቀሐት ፡ ለዘትርእስ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ ዳዊት ፡ (ፈልክ ፡ ፳ ። አርጋ ፡ ፭) ። በርእስ ፡ ፈንታ ፡ ተርእሰ ፡ ይባል ፤ አያሰኝም ። ኀበ ፡ ይትረአስ ፡ መስቀል ፡ ህየ ፡ መዊእ ። አጽፋር ፡ ዘተርእሳ ፡ ዲበ ፡ መልዕልቲሆን ፡ ለአእዳው ። ዘያጸንዐ ፡ ተርእሶተ ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፯ ። ስንክ ። አፈ ፡ ድ፴፬) ።

**ርኡስ** ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ እስት) ፤ ራስ ፡ የኾነ ፤ የተሾመ ፤ የሠለጠነ ፤ ንጉሥ ። እግዚ ፡ ሥሉጥ ፡ ወርኡስ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ። እግዚ ፡ ልዑል ፡ ወርኡስ ። ርእሰ ፡ ርኡሳን ፡ መኳንንት ። ርእስት ፡ አንቲ ፡ (አፈ ፡ ድ፪ ። ሃይ ፡ አበ ። አዋል ። ቅዳ) ።

**ራእስ** ፤ (ሳን ። ዐረ ፡ ረኢስ) ፤ አለቃ ፤ ሹም ፤ አበ ፡ ማኅበር ፤ ኤጲስቆጶስ ። ራእሳኒሆሙ ፡ ለክርስቲያን ፡ (አዋል) ። ራእስ ፡ ርእስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ርኡስ ፡ ይባል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ርኡሳኒሆሙ ፡ ለፌሎፍሊ ። ርኡሳኒ ፡ አእላፍ ። ርኡሳኒ ፡ ምእት ፡ (፩ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ና ፡ ፳ ። ፲፫ ፡ ፩ ። ፳፯ ፡ ፩) ።

**ርእስ** ፤ (ዕብ ፡ ሮሽ ። ሱር ፡ ሬሻእ ። ዐረ ፡ ረእስ) ፤ በቁሙ ፤ ራስ ፤ መክብብ ፡ ሕዋስ ፤ ከንገት ፡ በላይ ፡ ያለ ፤ ዐናት ፡ ጭንቅላት ፤ የናላ ፡ ቅል ፤ መዝመሪያ ፡ ክፍል ፤ በሥጋዊና ፡ በደማዊ ፡ ኹሉ ። ርእስ ፡ ወዘነብ ። ሰሊሁ ፡ ርእስ ፡ ወንሕነ ፡ አባል ። አልቦ ፡ ርእስ ፡ ዘየአኪ ፡ እምርእስ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ (ኢሳ፱ ፡ ፲፬ ። ሢራ፳፭ ፡ ፲፭ ። አፈ ፡ ድ፫) ።



ርእስ ፡

—፤ ሥዕርት ፤ የራስ ፡ ቡቃያ ፤ ፀምሩ ፡ ጠጕሩ ፤ ባሕር

ያዊ ፡ ማዕሩ ። ፀፈረት ፡ ርእሳ ። ወተላጸየ ፡ ርእሶ ፡ (ዮዲ ፲፮ ፡ ፩ ። ግብ ፲፰ ፡ ፲፰ ። ዘኍ ፮ ፡ ፲፱) ።

—፤ ጫፍ ፡ ቊንጮ ፡ መጨረሻ ፡ መደምደሚያ ፡ የዛፍ ፡ የቤት ፡ የሕንጻ ፡ የተራራ ። አርገ ፡ ዘነዋኅ ፡ ቆሙ ፡ ወይበጽሕ ፡ ደመናተ ፡ ርእሱ ። ማዕርግ ፡ ትክልት ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወርእሳ ፡ ይሰክፍ ፡ ሰማየ ። ርእሰ ፡ ማእዘንት ፡ ምሥራብ ። ሕፀ ፡ ርእሰ ፡ ደብር ፡ (ሕዝ ፴፩ ፡ ፫ ። ኩፋ ፳፯ ። ሉቃ ፬ ፡ ፱ና ፡ ፳፱) ።

—፤ የፊደል ፡ ስም ፡ ከያኛ ፡ ፊደል ፡ ረ ። ሬስን ፡ ተመልከት ።

—፤ ነፍስ ፡ ሰውነት ፡ ሥጋ ፡ ገላ ፡ መላው ፡ ኹለንተናው ፡ ከራስ ፡ ጠጕር ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍር ፡ ያለው ፡ ባንድነት ፡ እኔ ፡ የሚል ፡ አካል ፡ ቊመት ፡ ርስ ፡ ቀል ፡ ባስቤት ። ሬሳ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ ለሰንና ፡ ኪዮን ፡ አካልን ፡ ተመልከት ። ሰልየ ፡ በባሕኩ ፡ ርእስየ ። እቄድስ ፡ ርእስየ ። ከመ ፡ ያርዝሑ ፡ ርእሰሙ ። አአምር ፡ ርእስየ ፡ ከመ ፡ መሬት ፡ አነ ። ኢታዐቢ ፡ ርእስከ ። ያገብኡ ፡ ርእሰሙ ፡ ኀቤከ ፡ (ዮሐ ፲፯ ፡ ፲፱ ። ፲፮ ፡ ፲፱ ። ሮሜ ፲፩ ፡ ፳፱ ። ኢዮ ፵፪ ፡ ፮ ። ሚራ ፯ ፡ ፴ ። ዮዲ ፲ ፡ ፲) ።

—፤ ሥር ፡ መሠረት ፡ መገምገሚያ ፡ ጥንት ፡ መገኛ ፡ መባቻ ፡ ኀጕሥ ፡ በኵር ፡ አለቃ ። ርእሱ ፡ ለነገረ ፡ ጥበብ ። አነ ፡ ርእስ ፡ ወማኅለቅት ። ርእሰ ፡ መጽሐፍ ። አመ ፡ ርእሰ ፡ ሠርቅ ። ትሠይመኒ ፡ ርእሰ ፡ ሕዝብ ። ርእሰ ፡ ካህናት ። ርእሰ ፡ ዲያቆናት ። ጴጥሮስ ፡ ርእሰ ፡ ሐዋርያት ፡ (ሲራ ፴፱ ፡ ፲ ። ራእ ፳፪ ፡ ፲፫ ። መዝ ፴፱ ። ሕዝ ፵፮ ፡ ፩ ። መዝ ፲፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ነሐ ፳) ።

**አርእስት** ፡ (ታት) ፤ ራሶች ፡ ጫፎች ፡ መገር መሪያዎች ፡ አለቆች ። ቀጥቀጥከ ፡ አርእስቲሁ ፡ ለከይሲ ። መካን ፡ ዘይመትሩ ፡ ውስቴቱ ፡ አርእስታተ ። አርእስተ ፡ ጥቅም ። አርእስተ ፡ ነገር ። አርእስተ ፡ ምንባብ ። አርእስተ ፡ ዐሥርቱ ፡ ምእት ። አርእስተ ፡ መላእክት ፡ (መዝ ፸፫ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ። ምዕ ፵፭ ። መቅ ፡ ወን ። ግንዘ ። ሐዋ ። ኪዳ) ።

**ርእስና** ፤ ራስነት ፡ ባለቤትነት ፡ ኢሰቅነት ። ሠናየ ፡ ርእስና ። አመ ፡ ርእስና ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ ። ነሐሴ) ።

**አርአሰ** ፤ ሸመ ፡ አሳደገ ፡ ራስ ፡ አደረገ ፡ አላቀ ፡ አበለጠ ፡ በላይ ፡ አስቀመጠ ። ካህነ ፡ እግዚ ፡ ዘአርአሰ ፡ ህየንቴሁ ። ወአርአሶ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ። ኢፌ ፩ ፡ ፲) ።

**አርእሰ** ፤ እንተራስ ፡ አቀና ፡ ደገፈ ፡ የድውይ ።

**ተርእሰ** ፤ ተንተራሰ ፡ ተጠጋ ፡ ተደገፈ ። መጽሐፍ ፡ ማን ፡ እንዳማርኛው ፡ ተተርአሰ ፡ ይላል ፡ አያስኝም ። ተተርኢሶ ፡ ኖመ ። ያዕቆብ ፡ ቅዳሴ ፡ ተተርአሰ ፡ እብነ ፡ (ማርያ ፡ ፀሎ ። ቅኔ) ።

**ትርአስ** ፤ (ሳት) ፤ ትራስ ፡ መከዳ ፡ ራስጌ ፡ የመከዳ ፡ ቦታ ፡ ሃራስ ፡ በታች ፡ ቅርብ ፡ አጠገብ ። መንገለ ፡ ትርአሲሁ ። ሖረት ፡ ውስተ ፡ ምስካቡ ፡ መንገለ ፡ ትርአሱ ። ይነብሩ ፡ አሐዱ ፡ ትርአስ ፡ ወአሐዱ ፡ ትርጋፀ ። ረከበ ፡ ትርአሶ ፡ ኀብስተ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፮ ፡ ፯ ። ዮዲ ፲፫ ፡ ፯ ። ዮሐ ፳ ፡ ፲፪ ። ፫ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፮) ።

**መተርእስት** ፤ መንተራሻ ፡ ማንተራሻ ፡ ትራስ ፡ ብርኵማ ። የራስጌ ፡ ስይፍ ፡ ዱላ ፡ ሽጕጥ ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። መተርእስቱ ፡ እንተ ፡ በደቡሃ ፡ ያሰምክ ። መልእክት ፡ መተርእስተ ፡ ወዘበጠት ፡ ክሣዶ ፡ ወመተረት ፡ ርእሶ ፡ እምኔሁ ፡ (ዮዲ ፲፫ ፡ ፯ና ፡ ፰ ፡ ፲፭) ።

**ረቢብ** ፤ ቦት ፤ (ረበ ፤ ረበበ ፡ ይረብብ ፡ ይርብብ ። ሰብ ፡ ራብብ ። ዐረ ፡ ረበ) ፤ መብዛት ፡ መፈድፈድ ፡ መላቅ ፡ መብለጥ ፡ ማደግ ፡ መግነን ፡ መጕልበት ፡ መሠልጠን ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ መኾን ፡ በቍጥር ፡ በክብር ፡ በጌትነት ። ረቢ ፡ ረባን ፡ ረብዋት ፡ አርባብ ፡ የዚህ ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ።

—፤ መርበብ ፡ መዘርጋት ፡ መዘረር ፡ መስተር ፡ መወጠር ፡ መገተር ። መንሰንሰ ፡ መረብረብ ። ይኩና ፡ ኪዱቤን ፡ እንዘ ፡ ይረብባ ፡ ክነፊሆን ። ወረበብኩ ፡ ለሰማይ ፡ ከመ ፡ ሠቅ ። ይረብቡ ፡ መሣግረ ። አዘዘ ፡ ያምጽእ ፡ ሐመደ ፡ ወረበቦ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ቤት ፡ (ዘፀ ፳፭ ፡ ፳ ። መዝ ፻፫ ። ሕዝ ፳፮ ፡ ፲፬ ። ዳንኤ ፲፬) ።

**ረበቢ** ፡ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት) ፤ የሚዘረጋ ፡ ዘርጊ ፡ ነሳናሽ ።

**መረብ** ፤ (ሰብ ፡ ሚድባር) ፤ በረሓ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ያደን ፡ የወጥመድ ፡ ስፍራ ፡ የእንስሳት ፡ የአራዊት ፡ ወጥመድ ፡ አሽክላ ። ወክንኩ ፡ ከመ ፡ አድግ ፡ መረብ ፡ ዘገዳም ፡ (መዝ ፻፩) ።

**መረብ** ፤ (ሰብ ፡ ሙራእ ። ዐረ ፡ መራእ) ፤ የአዕዋፍ ፡ ፊኛ ፡ ያንገታቸው ፡ ኪስ ፡ ከረጢት ፡ በስተታች ፡ በደረት ፡ ያለው ፡ ጥሬ ፡ መቋጠሪያው ።

—፤ በቁሙ ፡ መረብ ፡ የሚባል ፡ አሞራ ፡ ባለታላቅ ፡ ፊኛ ፡ መጠኑ ፡ የርኩም ፡ እግሩ ፡ የሽመላ ፡ ላባው ፡ ክቡር ፡ በውድ ፡ የሚሸጥ ። በቀቀና ፡ ፈንታ ፡ አድግ ፡ መረብ ፡ እንዲል ፡ (መዝ ፻፩) ። አድግን ፡ እይ ።

**መርበብት** ፤ (ብ ፡ መረብብት) ፤ በቁሙ ፡ መረብ ፡ መርበብ ፡ ያግ ፡ ወጥመድ ፡ የሌላውም ፡ ኹሉ ፡ ወስክሣምት ፡ ማንቆ ፡ ሸምቀቆ ። ይወድዩ ፡ መርበብተ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ። ተክለ ፡ መርበብተ ፡ ከመ ፡ ይሥግር ፡



መርበብት ።

ባቲ ፡ አራዊተ ። መርበብተ ፡ ሕይወት ፡ (ማቴ ፬ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ ሚያዝያ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ።

**አርበበ፤(ሱር፡ ራውርበ)፤** አበዛ፣ አረባ፣ አከበረ። ረበበ፣ ቈለለ፣ ከመረ፤ አሳቀ፣ ታላቅ፣ አደረገ።

**ተረበ፤** ተዘረጋ፤ ተዘረረ። እምቅድመ፡ ይትረበባ፡ ሰማያት፡ (ቅዳ፡ አፈ። ዲዮስ)።

**ርቡብ፤(ባን፡ ባት፡ ብባት)፤** የተዘረጋ፤ ዝርግ፤ ስፉሕ። እደዊሁ፡ ርቡባቲሆን፡ (ዘፀ፳፯፡ ፳፱)።

**ርበት፤** መዘርጋት፣ ዝርግነት። ርበተ፡ ደመና፡ ርበተ፡ ፂሜ፡ (አርጋ፡ ፩)።

**ረብ፤(ዐረብ)፤** ጌታ፣ እግዜር። ሰፊ፣ ታላቅ፣ ብዙ፡ እጅግ። ሲያበዛ፡ ረበዋት፡ አርባብ፡ ይላል።

**አርባብ፤** የኪሩቤል፡ ስም፤ ጌቶች፣ አለቆች፣ ደምሳሾች። አርባብ፡ ኪሩቤል፡ ንበር፡ ዲበ፡ ሳሬል፡ ወዲበ፡ አርባዕቱ፡ አርባብ፡ (ቀሌ። አርጋ፣ ፫። ማሕ፱፡ ፲፯)።

**ረበዋት፤(ሀረ፡ ረብወት፤ ሩብት። ዕብ፡ ሪበ፤ ርባበ። ሱር፡ ሪቡ)፤** እልፍ፣ ወይም፡ ዐሥር፡ ሺሕ። በዐረብና፣ በዕብራይስጥ፣ በአራም፣ ቋንቋ፣ ማኅ፡ ዐሥር፡ እልፍ፤ ወይም፡ አእላፍ፡ ይባላል። ተስዐቱ፡ ምእት፡ ረበዋት፤ ፱፻—፻፻፡ ፱፡ ሚሊዮን፡ (ጠማር)።

—፤ እጅግ፣ ብዙ፣ የብዙ፣ ብዙ፣ ብዙቱ፣ እንዳሸዋና፣ እንደ፡ ኮከብ፡ ያለ። አስፈሪና፡ ምእልፊትን፡ እዩ። ረበዋተ፡ ረበዋት፡ ይሰግዱ፡ ሎቱ፡ (ቅዳ፡ ያዕ)።

**ረቢ፤(ዕብ፡ ራቢ)፤** የክበሬታ፡ ስም፤ ጌታዬ። ጌታ፤ አለቃ፡ ሹም፡ መምር፤ ሊቅ፤ ሽማግሌ፤ ቢ፡ ዝርዝር፡ ነው። ኢትሰመዩ፡ ረቢ። ሰነሁ፡ እንጋ፡ ረቢ። በሓ፡ ረቢ። ወይቤልዎ፡ ረቢ፡ ዘበትርጓሜሁ፡ ሊቅ፡ (ማቴ፳፫፡ ፯። ፳፮፡ ፵፱፡ ፵፱። ዮሐ፩፡ ፴፱)።

**ረቡኒ፤(ዕብ፡ ራቡኒ)፤** እግዚእየ፤ አምላኪየ፡ ሊቅየ፡ መምህርየ፡ (ዮሐ፳፡ ፲፮። ማር፲፡ ፶፩)።

**ረባን፤(ዕብ፡ ራባን)፤** ስሙ፡ ሊቃናት፤ ጌታ፤ አለቃ፤ መምር፤ መኰንን፡ ወይዘር፡ የነገሥታት፡ ዘር። ኄየርርረስ፡ ራባን፡ ሰባኬ፡ ትንሣኤሁ፡ ለመድኅን፡ (ድጓ)።

**ረበናት፤(ዕብ፡ ራባናን)፤** ጌቶች፡ አለቆች፡ ብልኆች፡ ዐዋቆች፡ ሽማግሎች፤ መምህራን፡ ሊቃውንት፡ ሹማምት። ረበናተ፡ ካህናት። ረበናቲሆሙ፡ ለሕዝብ። ሥርዐቱ፡ ረበናት። ረበናተ፡ ገዳመ፡ አስቄጥስ፡ (ኢሳ፴፮፡ ፱። ኤር፲፱፡ ፩። ማር፮፡ ፫። በነኑ፡ ጥርጅ። ግንዘ)።

**ረቢሕ፤ ሖት፤(ረብሐ፡ ይረብሕ፡ ይርባሕ። ዐረ፡ ረቢሐ። ዕብ፡ ራባህ። ሱር፡ ርባአ)፤** መርባት፤ መብዛት፤ መውለድ፡ መክበድ፡ መፋፋት፤ መንጋ፡ እንግልጋ፡ መኸን። የሰው፡ የከብት፡ የገንዘብ፡ ለማሰም፡ ይኸናል። ምናን፡ ዘበዝኁ፡ ወመክሊት፡ ዘረብሐ፡ (ቅዳ። ባታ)።

—፤ መርባት፤ መጥቀም፡ ማገልገል፡ ሥራ፡ መያዝ፡ ጕዳይ፡ መምላት። በእንተ፡ ዝኩ፡ ዘይረብሐከ፡ ወይበቍዐከ። ምንት፡ ይረብሖ፡ ለእመ፡ አንተ፡ አርታዕከ፡ ፍናዊከ። ይሜህሩ፡ በዘይረብሖሙ። ከመ፡ አርብሖ፡ ለክርስቶስ፡ (ሚክ፴፪፡ ፭። ኢዮ፳፪፡ ፫። ቈላ፩፡ ፲፩። ፊልጵ፫፡ ፰)።

—፤ መግዛት፤ ገንዘብ፡ ማድረግ፤ መሸጥ፤ መነገድ፡ ማትረፍ፤ ትርፍ፡ ጥቅም፡ ማግኘት፡ (ማቴ፲፮፡ ፳፮። ፳፭፡ ፲፮)። ኢይስቀጽስ፡ ኢያፍቅር፡ ይርባሕ። እመ፡ ረብሐ፤ ትንሣኤ፡ ብእሲት፡ መንፈቀ፡ ረባሖሙ። ምንተ፡ ረባሕነ፡ ዘዐቀብነ፡ ትእዛዞ። አንትሙ፡ ትረብሑ፡ በመዊእትሙ፡ ስመ፡ ክቡረ፡ (ሲኖዶ። ፍ፡ ነ፡ ፴፪፡ ፫። ሚል፫፡ ፲፬። ዮሴፍ)። በረብሐ፡ ፈንታ፡ ተረብሐ፡ ይባላል፡ ስሕተት፡ ነው። እንዘ፡ ኢትትረብሑ ምሙ፡ (፩ጴጥ፡ ፭፡ ፪)።

**ረባሒ፤(ሒት፡ ሕያን፡ ያት)፤** የሚረባ፡ የሚጠቅም፤ ጠቃሚ። ምጽዋት፡ ተናግዶ፡ አምላካዊት፡ ማእምንት፡ ረባሒት፡ ይእቲ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፲፩)።

**አርብሐ፤** አበዛዘ፤ አረባ፤ አበረባ፡ አበዛ፡ አስጠቀመ። እግዚአብሔር፡ ዘአርባሕከኒ፡ ዘሎ፡ ፍጥረተ፡ ዘዘ፡ ዚአሁ፡ ፍሬ። አርባሕከ፡ ትምክሕተ፡ በርእስከ፡ ወበሰብእከ፡ ኀሳረ፡ ወዝንጓጔ። ሐዘን፡ በእንተ፡ እግዚ፡ ያረብሕ፡ ሕይወተ፤ ወሐዘኑ፡ በእንተ፡ ዓለም፡ ያረብሕ፡ ሞተ። በሊዐኒ፡ ኢያረብሐኒ፡ (ቄስጠ። ዮሴፍ። ፍ፡ ነ፡ ፳፱። ፪ቆሮ፡ ፯፡ ፲)።

**ተረብሐ፤** ተገኘ፤ ተወሰደ፤ ትርፉ፡ ጥቅሙ፡ ዐረጠው። ዘተረብሐ፡ (ቄር፡ ጳላ)።

**ርቡሕ፤(ሓን፡ ሓት፡ ብሕት)፤** የረባ፡ የበዛ፤ የተረባ፡ የተጠቀመ፡ ብዙ፡ ትርፍ፡ ያገኘ።

**ርባሕ፤** ረባ፡ ረባታ፤ የሰዋሰው፡ ትምርት፡ አንዱን፡ ቃል፡ ባሥር፡ ሕዝብ፡ ባሥር፡ ንባብ፡ በዥ፡ መደብ፡ መዘርዘር፡ ማርባት።

**ረብሕ፤ ረባሕ፤(ሓት)፤** ብዙ፡ ትርፍ፤ መስድ፤ ዐረጣ፤ ርቢ፤ ጥቅም፡ ጠቀሜታ። እለ፡ ያፈቅሩ፡ ረባሐ። ፍትወተ፡ ረባሕ። ረባሕ፡ ርኩስት። ኢትትማከር፡ እንበይነ፡ ረባሕ፡ ምስለ፡ ሠያጢ። ረብሐ፡ ነፍስከ። አይኑ፡ ረባሕ፡ ለነ፡ በቀቲለ፡ ነፍሳቲነ። ፈልፈለ፡ ረባሕ። ረባሓተ፡ ጾም፡ (፩ጢሞ፡ ፫፡ ፫። ጥበ፲፱፡ ፱። ፈ፡ መ፡ ፲፫፡ ፩። ሚክ፴፯፡ ፲፩። ዕንባ፡ ታኅ፳፩። ዮሴፍ። ቅዳ። ፍ፡ ነ፡ ፲፩)። በረባሕ፡ ፈንታ፡ ርቡሕ፡ ይባላል፡ ስሕተት፡ ነው። ርቡሕ፡ ሲቱ፡ (ፊልጵ፩፡ ፳፩)።

**ረብሓዊ፤(ዊት፡ ውያን፡ ያት)፤** የሚያተርፍ፤ አትራፊ፤ ሸቃጭ፡ ቸርቻሪ፡ አዘዋሪ። ነጋዴ፡ ወረብሓዊ፡ (አፈ፡ ተ፲፮)።

**ያርብሕ፤(ሓን)፤** ሐርበኛ፡ ነደለኛ፤ የወንዶች፡ ባል፡ ዝግና፡ ሰውዐ፡ ዜና፤ መጠኑ፡ ቁመቱ፡ ኀይሉና፡ ጕልበቱ፡ ከሰው፡ ልክ፡ ያለፈ፡ የተረፈ፤ እንደ፡ ዔናቅ፡ ልጆች፡ ያለ። ጢጣኛሰንና፡ ኛፊልን፡ ተመልከት። ኀያል፡ ያርብሕ። ሥጋ፡ ያርብሕ። በንእሱ፡ ቀተለ፡ ያርብሐ። ከመ፡ ያርብሕ፡ ዘይሜርድ፡ ፍ

ኖቶ፡ (ኢሳ፫፡ ፱። ሕዝ፴፱፡ ፲፰። ሚራ፵፮፡ ፱። መገ፡ ፲፰)። ጎያሳን፡ ያርብሓን፡ በማለት፡ ፈንታ፡ እስ፡ ያርብሕ፡ ይባል፡ አያሰኝም፡ (ዘፍ፮፡ ፱። ፲፱፡ ፳። ዘኍ፲፫፡ ፴፱)።

**ያርብሓዊ፤** ገቢ፡ ከማሁ። ዔናቃዊ፤ የዔናቅ፡ ወገን፤ ሐርበኛ። ወናሁ፡ ያርብሓዊ፡ (፩ነገ፡ ፲፯፡ ፵፫)።

**ተራብሐ፤** ተራባ፤ ተባዛ፤ ተጠቃቀመ፡ ተገበያየ፤ ተሻሻጠ። ንትራባሕ፡ በትግብርት፡ እክልኒ፡ (ዓሞ፰፡ ፭)።

**አስተራብሐ፤** አራባ፡ አባዛ፤ አጠቃቀመ። አስተራብሖ፡ ንዋይ፡ (ጥ፡ ን፡ ፴፱)።

**መስተራብሕ፤ (ሒት፡ ሓን፡ ሓት)፤** የሚያራባ፡ የሚያባዛ። ወኢመስተራብሒት፡ (ዲድ፡ ፲፬)።

**ረብዖ፤ ዖት፤ (ረብዐ፡ ይሬብዕ፡ ይረብዕ። ዕብ፡ ራቤዕ)፤** አራት፡ ማድረግ፤ ካራት፡ መክፈል፡ አራት፡ ማለት። ዘያማስን፡ ሥባሴ፡ ወይሬብዕ፡ ጥምቀተ። ዘይሬብዖን፡ ለክንትሮሳት፡ ዓመታት፡ ከመ፡ ይኩና፡ ለሐጋይ፡ ወለክረምት፡ ለመፀው፡ ወለተወን፡ (ተረ፡ ቄር። መጽ፡ ምስ)።

**ረባዒ፤ (ዒት፡ ዕያን፡ ያት)፤** አራት፡ የሚያደርግ፡ የሚል፡ የሚከፍል። በብሕ፡ ልዩን፡ ይሰመዩ፡ ረባዕያኒ፡ ወእኮ፡ ሠላስያኒ፡ (መጽ፡ ምስ)።

**መረብዕ፡ (ዕት፡ ዓን፡ ዓት)፤** ገቢ፡ ከማሁ፡ ረባዒ።

**መርብዕት፤** አራት፡ ጉን፡ ወገን፤ ገጽ፡ ማእዝን፡ ላንድነት፡ አራት፡ ክፍል፤ ቅርጽ፡ ገጽ፡ ያለው። እንተ፡ መርብዕት። መርብዕተ፡ ማኅፈድ። መርብዕተ፡ መኣዝኒሃ፡ ለዓለም፡ ያንቀሳቅል። አሥረ፡ ልቡ፡ ለብእሲ፡ መርብዕተ፡ ያስተርኢ፡ (፫ነገ፡ ፯፡ ፴። ኩፋ፡ ፴፰። ኪዳ። ሚራ፴፮፡ ፲፰)።

**ተረብዐ፤** አራት፡ ኾነ፤ አራት፡ ተባለ፡ ካራት፡ ተከፈለ።

**ርቡዕ፤ (ዓን፡ ዓት፡ ብዕት)፤** አራት፡ የኾነ፡ አራት፡ ገጽ፡ ያለው፡ ምኅዛኑን፤ ዕሩየ፡ ማእዝን። ርቡዓኒ፡ ገጹ። መለኮት፡ አምላክ፡ ኢርቡዐ፡ አላ፡ ሥሉስ። ኅበ፡ አርባዕቱ፡ ርቡዓቲሁ። ርብዕተ፡ ትገብሩ። ወርብዕት፡ ይእቲ፡ ሀገር፡ በአምጣኒ፡ ኑኃ፡ ወግድማ፡ (አርጋ፡ ፫። መጽ፡ ምስ። ሕዝ፵፫፡ ፲፯። ዓ፳፡ ፳። ራእ፳፩፡ ፲፮)።

**ርባዔ፤** አራት፡ መኾን፤ አራትነት። ሊከነ፡ በሥላሴ፡ ዘነአምን፡ አላ፡ በርባዔ። እመ፡ ቦ፡ ዘያበውእ፡ ርባዔ፡ ውስተ፡ ሥላሴ፡ ውጉዘ፡ ውእቱ፡ (ተረ፡ ቄር፲፰። ያዕ፡ ዘእል)።

**ሩባዔ፤ (ዕያት)፤** ሩብነት፤ ሩብ፡ ካራት፡ አንድ፡ (አቡሻ፡ ፴፯)።

**ትርብዕት፤** አራትነት፤ አራት፡ እጅ፡ አራት፡ ዐምድ፤ አራት፡ ማእዝን። ትርብዕተ፡ ርቡዓን፡ ኪሩቤል፡ ወትሥልስተ፡ አምላክ፡ ዋሕድ። ወሀበ፡ ሎቱ፡ ህየንተ፡ አሐዱ፡ ትርብዕተ። ውስተ፡ ትርብዕት፡ ዓለም። በገበዋተ፡ ገል፡ ዘበትርብዕት፡ (ደራሲ። ፈልክ፡ ፫። ቅዳ። አርጋ፡ ፩)።

**ረቡዕ፤** የዕለት፡ ስም፡ ቍጥር። አራተኛ፡ አራት። ጾመ፡ ረቡዕ። አመ፡ ዕለተ፡ ዐሡሩ፡ ወረቡዑ። ረቡዐ፡ መዋዕለ፡ (ዘካ፰፡ ፲፱። ዘሌ፳፫፡ ፭። መሳ፲፩፡ ፵)።

**ራብዕ፤ (ዕት)፤** አራተኛ፤ ካራት፡ አንድ፤ ሩብ፤ ርብ። ወራብዖሙ፡ ይብዕል። በራብዕት፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ለሕዝቅያስ። ራብዕታ፡ ለሲን፡ (ዳን፲፩፡ ፱። ኤር፳፰፡ ፩። ዘፀ፳፱፡ ፵)።

**ራብዓዊ፤ ዩ፤ (ዊት፤ ዪት፤ ዒት)፤** ገቢ፡ ከማሁ፡ አራተኛ። ራብዓይ፡ አርዌ፡ (ዳን፯፡ ፲፱)።

**ራብዒት፤** የቍጥር፡ መደብ፤ የክነርሶስ፡ አራተኛ፤ አንዱ፡ ራብዒት፡ ፰፡ ኃምሲት፡ ይኾናል፡ (አቡሻ፡ ፲፩)።

**ርብዕ፤** የጊዜ፡ ቍጥር፤ አራት፤ ለሰፍርም፡ ይኾናል። ርብዐ፡ ለለ፡ ዓመት። ርብዐ፡ በእመት፡ (ኩፋ፡ ፳፱። ዘፀ፳፮፡ ፰)። በአርባዕቱ፡ ፈንታ፡ ርብዕ፡ ይባል፤ አያሰኝም። ዕሥራ፡ ወርብዐ፡ (ስንክ፡ ኅሠ፴)።

**አርባዕ፤** (የቤቶች)፡ አራት። አርባዐ፡ አዋልድ፡ ደናግል። አርባዐ፡ አህጉር። ዘየሐውር፡ በአርባዕ፡ (ግብ፳፩፡ ፱። ኢያ፳፩፡ ፲፰። ዘሌ፲፩፡ ፳)። በራብዕ፡ ፈንታ፡ አርባዕ፡ ይባል፤ አያሰኝም። ወበእንተ፡ አርባዐሰ፡ (ዓሞ፩፡ ፫)።

**አርባዕቱ፤ ቲ፤** (የወንዶች)፡ አራት፤ አራቱ፤ አራተኛው። ቱ፡ አርቲክል፡ ነው። አርባዕቱ፡ መኣዝኒ፡ ዓለም። አርባዕቱ፡ ነፋሳት። አርባዕቱ፡ አፍላጋት። አርባዕቱ፡ ጠባይዓት። አርባዕቱ፡ ወንጌላውያን፡ (ጥ፡ ን፡ ፱)። በአኃዝ፡ ብቻ፡ ወይም፡ እያቀናጁ፤ ፬፡ ፬ቱ፡ እያሉ፡ ይጥፋል፤ አይገባም፡ የጣፈ፡ ስሕተት፡ ነው። ኹለተኛም፡ አርባዕት፡ በማለት፡ ፈንታ፡ አርባዕቱ፡ ይባል። አርባዕቱ፡ እንስሳት፤ አርባዕቱ፡ ገጻት። አርባዕቱ፡ ምእት፡ (ሕዝ፩፡ ፭፡ ፮። ዘፍ፳፫፡ ፲፭)። ከአሐዱ፡ እስከ፡ ዐሠርቱ፡ ያለ፡ ቍጥር፤ ኹሉ፡ እንደዚህ፡ ነው፤ በግብር፡ ጊዜ፡ ግን፡ ከዕብነቱን፡ ማእዝ፡ ይወርሰዋል። ይነብሩ፡ ፈላስያኒ፡ አርባዕተ፡ ምእተ፡ ዓመተ። ወርኢኩ፡ አርባዕተ፡ አቅርንተ፡ (ዘፍ፲፭፡ ፲፫። ዘካ፩፡ ፲፰)።

**አርባዕት፤** የዜማ፡ ቃል፡ ትምርት፤ አራተኛ፡ ክፍል፤ ከውዳሴ፡ ማርያም፡ (ድጓ)።

**አርብዓ፤ (ሟ፤ መ)፤** የቍጥር፡ ስም፡ አርባ፡ አራት፡ ዐሥር፡ ወይም፡ ዐሥር፡ ጊዜ፡ አራት። አርብዓ፡ መዋዕለ፡ ወአርብዓ፡ ለያልየ። አርብዓ፡ ምእት። አርብዓ፡ ዓመት፡ (ማቴ፬፡ ፪። ፲፭፡ ፴፰። መገ፡ ፲፱)።

**አርብዓዊ፤** አርባኛ፤ ከርባ፡ አንድ።

**ረጊብ፤ በት፤ (ረገበ፡ ይረግብ፡ ይርግብ። ዐረ፡ ረጀበ)፤** መፍራት፤ መሥጋት፤ መታ

ወከ ፤ መርገብገብ ፡ መሽቈጥቈጥ ። መርገብ ፡ መላላት ፤ ጽንዕ ፡ ማጣት ፡ (በማርኛ) ።

**ርግብ ፤ (ብ ፡ አርጋብ) ፤** በቁሙ ፤ የቤት ፡ ወፍ ፤ እንደ ፡ ድሮ ፡ የሚያረቢት ፡ ፈሪ ፡ ምኑ ፤ ገር ፤ የዋህት ፡ ንጽሕት ፤ ሰላማዊት ። ኩኑ ፡ የዋሃነ ፡ ከመ ፡ ርግብ ። ይወርድ ፡ መንፈስ ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ። ርግብ ፡ ውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ለዘመዱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ማኅበረ ፡ አርጋብ ። እለ ፡ ይሠይጡ ፡ አርጋበ ፡ (ማቴ፳፩ ፡ ፲፪ ። ዮሐ፩ ፡ ፴፪ ። ቅኔ ። ሥር ፡ ጸሎ ። ዮሐ፪ ፡ ፲፬) ።



ርግብ ።

**ረገደ ፤—ብቍሙ ፤—ረገፀ ።**

**ረጊዝ ፤ ዘት ፤ (ረገዘ ፡ ይረግዝ ፡ ይርግዝ ። ዐረ ፡ ረከዘ ፤ ቸከለ ፡ መደረ ። ዕብ ፡ ራጋዝ ፤ ተቈጣ ፡ ወገሸ) ፤** መውጋት ፤ መዘርከት ፤ መደደቅ ፡ መትከል ፤ መብሳት ፡ መንደል ፤ መቸክቸክ ፤ መግደል ። (ተረከገዘ ፡ ማለት ፡ የረከዘ ፡ ዘር ፡ ነው) ። ረገዘ ፡ ውስተ ፡ ከርሣ ። እለ ፡ በኲናት ፡ ረገዝዎሙ ። አምጽእዎሙ ፡ ወርግዝዎሙ ፡ በቅድሜየ ፡ (መሳ፫ ፡ ፳፩ ። ኤር፲፰ ፡ ፫ ። ሉቃ፲፱ ፡ ፳፯) ።

—፤ ዘር ፡ መስጠት ፡ ማስረገዝ ፤ ማጥገብ ፡ ማንጠርዘዝ ፡ (በማርኛ) ።

—፤ ይዘ ፡ ማቆም ፤ መግታት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በረገዘ ፡ ፈንታ ፡ አርገዘ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ከመ ፡ ናርግዝ ፡ ሐመረ ፡ (ግብ፳፯ ፡ ፲፯) ። ሐገዘን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ነው ።

**አርገዘ ፤ (ዐማርኛ) ፤** አረገዘ ፡ ተነፋ ፡ ዐበጠ ፤ ተንዘረጠጠ ።

**ተረግዘ ፤** ተወጋ ። ነሥአ ፡ በይፉ ፡ ወተረግዘ ፡ ሰሲሁ ፡ (፩ነገ ፡ ፴፩ ፡ ፬ ፡ ፭ ። ግብ፲፯ ፡ ፳፯) ።


**ርጉዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ግዝት) ፤** የተወጋ ፤ ውጊ ። ኢየሱስ ፡ ርጉዘ ፡ ገቦ ፡ (ደራሲ) ። ሕሩድ ፡ ጥቡሕ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ርጉዝ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ብግዕ ፡ ከመ ፡ ዘርጉዝ ፡ (ራእ፭ ፡ ፮) ።

—፤ በቁሙ ፤ ያረገዘ ፤ የተረገዘ ። (ተረት) ፤ የጨነቀው ፡ እርጉዝ ፡ ያገባል ። የታዘለ ፡ በሰምድ ፤ የተረገዘ ፡ በሆድ ።

**ርግዘት ፤** መውጋት ፤ መወጋት ፤ አወጋግ ፤ ውግታት ፤ ቍስል ፡ ዕትራት ። አርአየኒ ፡ ርግዘተ ፡ ገቦሁ ፡ ዘየማን ፡ (ዲድ ፡ ፴ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ። ማርገዝ ፤ መረገዝ ፤ እርግዝና ፡ (ዐማርኛ) ።

**ተራገዘ ፤** ተዋጋ ፤ ተዛራከተ ፡ በሰይፍ ፡ ተማታ ፤ ተራረደ ፤ ተቀራደደ ። ይትራገዙ ፡ ውሉዶሙ ፡ (ሔኖ፲ ፡ ፲፱ ። ዳንኤ ፡ ፳፯) ።

**ራግዝ ፤ ዛት ፤** መቃን ፡ መቃኖች ፤ የግራና ፤ የቀኝ ፤ ቀንአን ፡ እዶ ። ራግዘተ ፡ መብእየ ። ሕቅፉ ፡ ራግዛቲሃ ፡ ወትዋኅዊን ። እምደምከሙ ፡ ንዝሁ ፡ ራግዘተ ፤ ኆኅትየ ፡ ቤት ፡ (ምሳ፰ ፡ ፴፬ ። ቀሌ ። ደራሲ ። ዘፀ፲፪ ፡ ፯) ።



ራግዛት ።

**ምርጕዝ ፤ (ብ ፡ መራጕዝ) ፤** በቁሙ ፤ ደጋፋ ፡ በትር ፤ እንደ ፡ ባላና ፡ እንደ ፡ መቃን ፡ ኹኖ ፡ የሚደግፍ ። ምርጕዝሙ ፡ ውስተ ፡ እዴሆሙ ። ምርጕዝ ፡ ጻድቃን ። ምርጕዝ ፡ ለርሥኣንየ ፡ (ዘካ፰ ፡ ፬ ። ኪዳ ። ድጓ) ።

**ተመርጐዘ ፤** ተመረ(ከ)ጐዘ ፡ በትር ፡ ያዘ ፤ ተደገፈ ። ተመርጕዘ ፡ ባቲ ። ሕእዳዊክ ፡ እለ ፡ ይትመረጐዙ ፡ በትረ ፡ ወርቅ ። ዘእንበለ ፡ ብትር ፡ ወተመርጕዘ ። እንዘ ፡ ይትመረጐዙ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ዘሙሴ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፮ ። ደራሲ ። ቀሌ ። ተረ ፡ ቄር፳፱) ።

**ምርጉዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ጕዝት) ፤** በትር ፡ የያዘ ፤ የተደገፈ ፤ የተመረጐዘ ፤ ባለምርጕዝ ፤ ድውይ ፡ ዐንካሳ ፡ ደካማ ።

**ረግሐ ፤ (ትግሬ) ፤** መላ ፡ ተመላ ፤ ምሉእ ፡ ኾነ ፡ ተደለደለ ፡ የጕድጓድ ፡ የመንገድ ። ረጋ ፡ ጸና ፡ ከረረ ፤ ደነገየ ፤ ድንጋይ ፡ ኾነ ። ረግዐን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**መርግሕ ፤ (ሓት ፤ መራግሕ) ፤** መርግ ፤ ቋጥኝ ፡ ናዳ ፡ ናደት ፤ ቃላቅ ፡ ደንጊያ ። ወውእቱሂ ፡ መርግሐ ፡ እሳት ፡ ይወድቅ ፡ ዲቤሆሙ ፡ (ራእ ፡ ባሮ) ።

**አመርግሐ ፤** ናደ ፡ ፈነቀለ ፤ አንከባለለ ፡ ገፋ ፡ መርግ ፡ ሰደደ ። አመርግሐ ፡ እብነ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ (ዮዲ፯ ፡ ፲፱) ።

**ረጊም ፤ ሞት ፤ (ረገመ ፡ ይረግም ፡ ይርግም ። ዕብ ፡ ራጋም ። ሱር ፡ ርጋም ፤ ወገረ ። ዐረ ፡ ረገመ ፤ ዐማ ፡ ነቀፈ) ፤** መርገም ፤ መስደብ ፤ ማሳደፍ ፡ ማርከስ ፡ ማቅለል ፡ ማኰሰስ ፤ ክፉ ፡ መመኘት ፤ ከበረከት ፡ ማውጣት ። ደንኑ ፡ ወኢትርግሙ ። ሰምንተ ፡ ይረግም ፡ ለእግዚእየ ። ዘይዘብጥ ፡ ወይረግም ፡ (ሮሜ፲፪ ፡ ፲፬ ። ፪ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፱ ። ሲኖዶ) ።

**ረጋሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤** በቁሙ ፤ የሚረግም ፡ የሚሰድብ ፡ ሰዳቢ ። ረጋሚ ፡ አው ፡ ሰካሪ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፩) ።

**መርገም ፤ (ማት)** ፤ በቁሙ ፤ ርግማን ፤ ስድብ ፤ ክበድ ፡ ቃል ። መጽአ ፡ መርገም ፡ ላዕሌነ ፡ ወመሐላ ። መሪር ፡ አፉሆሙ ፡ ወምሉእ ፡ መርገመ ። ኢይፃእ ፡ እምአፉሁ ፡ ቃለ ፡ መርገም ። ቡራኬ ፡ ወመርገም ፡ (ዳንኤ ፡ ፲፩ ። ሮሜ ፡ ፲፱ ። ዲድ ፡ ፲፯ ። ያዕ ፡ ፲) ።

**ተረግመ** ፤ ተረገመ ፤ ተሰደበ ፤ ማለ ፡ ተገዘተ ። ረገምኩ ፡ ወተረገምኩ ። አፍቅሮ ፡ ወኢትትረገም ፡ ላዕሌሁ ። ወእንዘ ፡ ይትረገም ፡ ወይምሕል ፡ (አዋል ። ቀሌ ። ማር ፲፬ ፡ ፸፩) ። ተርጕመን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ርጉም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ማምት)** ፤ በቁሙ ፤ የተረገመ ፤ ክፉ ፡ መጥፎ ፤ ውጉዝ ። ርጉመ ፡ ይኩን ። እመ ፡ ኢየውፃእክሙ ፡ እምኔክሙ ፡ ዘርጉም ። ሑሩ ፡ ርጉማን ፡ (ሚልክ ፡ ፲፬ ። ኢያ ፡ ፲፱ ። ማቴ ፳፭ ፡ ፵፩) ።


**ርግመት** ፤ መርገም ፤ መረገም ፤ ርግማን ፤ ርጉምነት ፡ (ሔኖ ፡ ፯ ፡ ፯) ።

**ተራገመ** ፤ በቁሙ ፤ ተረጋገመ ፤ ተሳደበ ፤ ተሰዳደበ ፤ ተማማለ ። ተራገሙ ፡ ወተማሐሉ ፡ ወቦኡ ፡ ኪዳነ ፡ (ነሐ ፲ ፡ ፳፱) ።

**ተርጐመ ፤—በቁሙ ፤—ተረጐ ፡ ተ ።**

**ረጊን ፤ ኖት ፤ (ረገነ ፡ ይረግን ፡ ይርግን ። ዐረ ፡ ረጀነ ፤ ረኩን)** ፤ አጥብቆ ፡ ማሰር ፤ መሳብ ፡ መገተር ፤ ማጥናት ፡ ማጠንከር ፤ የመርከብ ፡ የሸራ ። የረገዘን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፤ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ቀዘፈ ፡ ይሉታል ። ኰርጕንን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ።

**ረግን ፤ ራግን ፤ አው ፡ ራግንት ፡ ናት** ፤ ታንኳ ፤ ፍልኳ ፤ ጀልባ ፤ ታናሽ ፡ መርከብ ። ራግንና ፡ ራግናት ፡ እንደ ፡ ራግዛት ፡ የብዙ ፡ ነው ፤ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ረግን ፡ ራግንት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ራግናት ፡ ይላል ፡ (ግብ ፳፯ ፡ ፴ ፡ ፴፪) ። ውስተ ፡ ዘመጠነ ፡ ገዘ ፡ ዕበየ ፡ ሠርም ክሙ ፡ ራግናተ ፡ ቃላትየ ፡ እጽሕቅ ፡ አሑር ። ያዐ ድዉ ፡ ብድነ ፡ በራግናት ፡ (ተረ ፡ ቂር ፲፬ ። ሥር ፡ ጳዠ) ።



ረግን ፡

—፤ የመርከብ ፡ ገመድ ፤ ሸራ ፤ ከምሰሶው ፡ ጋራ ። ራግ ናቲሃ ፡ ለሐመር ፡ ሐብለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘኢይትበተክ ። ዘበራግናተ ፡ ወንጌሉ ፡ ቅዱስ ፡ (አርጋ ፡ ፮ና ፡ ፱) ።

**ረጊዕ ፤ ዖት ፤ (ረግዐ ፡ ይረግዕ ፡ ይርጋዕ ። ዕብ ፡ ራጋዕ)** ፤ መርጋት ፤ መጽናት ፤ መግዘፍ ፤ እንደ ፡ ጧቃና ፡ እንደ ፡ ዳቦ ፡ እንደ ፡ ደንጊያ ፡ መኾን ፤ የፈሳሽ ። መጨመት ፡ ዝም ፡ ስክም ፡ ጸጥ ፡ ማለት ፤ አለ መታወክ ፤ የልብ ፡ የሐሳብ ። ረግዐ ፡ ከመ ፡ ሐሊብ ፡ ልቦሙ ። ይረግዕ ፡ ከመ ፡ ሠምዕ ። እምከመ ፡ ረግዐ ፡ አስሐትያ ። ይረግዕ ፡ ማይ ፡ ወይከውን ፡ ከመ ፡ እብን ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ። ሚራ ፡ ፲፱ ። ስንክ ፡ ኅዳ ፲፱) ።

**ርጉዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ግዕት)** ፤ የረጋ ፡ የጠና ፤ የማይፈስ ፡ የማይታወክ ፤ ርጎ ፡ ዐይብ ። ይብር ፡ ርጉዕ ። አይብሬሃ ፡ ርጉዓን ። ነበርኩ ፡ ርጉዐ ፡ ቢደም ፡ ዐሠርተ ፡ አውራኀ ፡ እምዘርዐ ፡ ብእሲ ። በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ዐቢይ ፡ ፈለግ ፡ ወረከቦ ፡ ርጉዐ ፡ (መዝ ፡ ፷፯ ። ጥበ ፳ ፡ ፪ ። ዮሴፍ) ።

**ርግዐት** ፤ መርጋት ፡ አረጋግ ፤ ርጋታ ፤ ጸጥታ ፤ ዕረፍት ፤ ህይእት ፡ ጭምትነት ፡ (አዋል) ።

**አርግዐ** ፤ አረጋ ፤ አስረጋ ፤ አጸና ። አርጋዕከኒ ፡ ከመ ፡ ግብነት ። የዐቍር ፡ ማየ ፡ በማሕፀን ፡ ወያረግዕ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሥጋ ። ናረግዖሙ ፡ ለማያት ፡ በውስተ ፡ ደመናት ፡ ወንፈኑ ፡ በረደ ፡ ወአስሐትያ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ (ኢዮ ፲ ፡ ፲ ። ቅዳ ፡ ግሩ ። ቀሌ) ።

**መርግዕ ፤—መርግ ፡ ናደት ፤—ረግሐ ፡ መርግሕ ።**

**ረጊፍ ፤ ፎት ፤ (ረግፈ ፡ ረገፈ ፡ ይረግፍ ፡ ይርግፍ ። ረቀመ ፤ ሰርገወ)** ፤ መርገፍ ፤ ማርገፍ ፤ ማውረድ ፡ የፍሬ ፡ የቅጠል ። መሣል ፡ መመሰል ፤ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ መሥሬት ፤ አበባና ፡ ፍሬ ፡ ሐረግና ፡ ዘፍ ፡ እየሰመሰሉ ፡ መበገር ፡ መንደፍ ፤ መታታት ፡ መጥለፍ ፤ በስፌት ፡ በቀለም ፡ ማስጌጥ ።

**ርጉፍ ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ግፍት)** ፤ የረገፈ ፤ የተነጠፈ ፤ የተሸለመ ፡ የተጌጠ ፤ ዘፋም ፡ ቅጠላም ፤ ልብስ ፡ ምንባፍ ፡ ጸፍጸፍ ። ንጹፍ ፡ ወርጉፍ ፡ በሚላት ። ይኔውም ፡ ውስተ ፡ ምስካቢሁ ፡ ፈላስ ፡ ዘርጉፍ ፡ በልብሰ ፡ ሚላት ፡ (አስቴ ፳ ፡ ፳ ። ዮዲ ፲ ፡ ፳፰) ።

**መርገፍ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ ቀጭን ፡ ልብስ ፤ ጥሩ ፡ ግላስ ፤ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ ሐር ፡ የተሠራ ፤ የተጠለፈ ፤ ሸከሬ ፡ አማጮች ። (ግጥም) ፤ አባቶቻችን ፡ ለበቅሎቻቸው ፤ ኮርቻ ፡ ነበር ፡ ዐላባቸው ፤ የዛሬ ፡ ልጆች ፡ እጅግ ፡ ኩሩ ፤ ለመርገፉ ፡ ነው ፡ የሚጥሩ ።

**ረጊፅ ፤ ፆት ፤ (ረገፀ ፡ ይረግፅ ፡ ይርግፅ ። ዐረ ፡ ረከፀ ። ዕብ ፡ ራቃድ ። ሱር ፡ ራቁድ)** ፤ መርገጥ ፤ ማስረገጥ ፤ ማሽብሸብ ፤ ዳንኪራ ፡ መምታት ፤ መዝለል ፡ መፈንጨት ፤ መርገድ ፡ ማርገድ ፤ መርገድገድ ፡ እስክስታ ፡ መውረድ ፤ መወዝወዝ ፡ መቅመ

ይመይ ። አስረጋጭ ፡ እንዲሉ ። ፀሐሰን ፡ ተመልክት ፤ የዚህ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ነው ።

—፤ መረጋገጥ ፡ መጠቅጠቅ ፡ ማልፋት ፡ ማበራየት ፡ በር ግጫ ፡ መምታት ፤ መገርሰጥ ፤ የጭቃ ፡ የልብስ ፡ የንድ ፡ የቀርበት ፤ ለሰውም ፡ ይኸናል ። ባጥ ፡ ፈናጥ ፡ እንጣጥ ፡ ማለት ፤ ለመርገጥ ፡ የከብት ። **ረገፀ ፡ ምድረ ። ረጊፀ ፡ ውስተ ፡ ቀኖት ፡ በሊጎ ። ቦ ፡ ለዘረገፆ ፡ ወቦ ፡ ለዘወ ኀሮ ። ረገፆ ፡ በእገሪሁ ፡ ወወድቀ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወሞተ ። አው ፡ አብቅልተ ፡ ዘይረግፁ ፡** (ቀሌ ። ግብ፱ ፡ ፲ ። ክብ ፡ ነገ ። ስንክ ፡ የካ፲፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፯) ።

**ረጋጺ ፤ (ጺት ፡ ፅያን ፡ ያት)** ፤ የሚረግጥ ፡ ረጋጭ ፡ ረጋጅ ፡ አርጋጅ ።

**አርገፀ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ አስረገጠ ፡ መሳልዐ ፡ ጠየቀ ፡ ወይም ፡ ተናገረ ፤ እውነቱን ።

**ተረግፀ** ፤ ተረገጠ ፤ በርግጫ ፡ ተመታ ፡ ተናቀ ፡ ተጠቀጠቀ ። እውነት ፡ ኾነ ፤ ልክ ፡ ተገኘ ።

**ርጉፅ ፤ (ፃን ፡ ፃት ፡ ግፅት)** ፤ የተረገጠ ፡ ርግጥ ፤ እውነት ፤ ድርስ ፤ የነገር ፡ ልክ ።

**ርግፀት** ፤ መርገጥ ፤ መረገጥ ፤ አረጋገጥ ፤ ር ግጫ ። **ኢያንቲጉ ፡ እምሒቋሆሙ ፡ ርግፀተ ፤ እስከ ፡ መጠዉ ፡ ነፍሶሙ ፡ ክብርተ ፡** (ስንክ ፡ ሐምሸ) ።

**ተራገፀ** ፤ ተራገጠ ፤ ተረጋገጠ ፤ በርግጫ ፡ ተ ማታ ። (ተረት) ፡ አህያ ፡ ላህያ ፡ ቢራገጥ ፡ ጥርስ ፡ አይሳበር ።

—፤ ተፈራገጠ ፡ ፍርግጥግጥ ፡ አለ ፤ የጻዕር ፡ (መሳ፬ ፡ ፳፩ ። ፳ ፡ ፳፯ ። አቡሻ ፡ ፵፯) ።

**አስተራገፀ** ፤ አራገጠ ፡ አፈራገጠ ፤ የጋኔን ። **ይነፅዎ ፡ ወያስተራግፆ ፡** (ማር፩ ፡ ፳፮ ። ፱ ፡ ፲፰ ፡ ፳) ።

**ትርጋፅ** ፤ እግርጌ ፤ የእግር ፡ ቦታ ፤ መዘርጊያ ፤ መረጋገጫ ። **ትርኣስ ፡ ወትርጋፀ ። ግበሩ ፡ ሎሙ ፡ ቅ ድመ ፡ ቢድኖሙ ፡ አርባዕተ ፡ መሳቅስ ፤ በትርኣስ ፡ ወበትርጋፀ ፡ በየማን ፡ ወበፀጋም ፡** (ዮሐ፳ ፡ ፲፪ ። ግንዘ) ።

**መርገፅ** ፤ በቁሙ ፤ መርገጥ ፤ የበሬ ፡ ዕቃ ፡ ስም ፤ የወግል ፡ ወይም ፡ የከርፈስ ፡ ጠፍር ፡ ገበሬ ፡ ድግሩን ፡ ማረሻውን ፡ ከሞፈር ፡ ጋራ ፡ እየረገጠ ፡ የሚያስርበት ።

—፤ ርካብ ፡ የርካብ ፡ ጠፍር ። **ተጽዕኖ ፡ ላዕለ ፡ ፈረስ ፡ ወበጊዜሃ ፡ ተመትረ ፡ መርገፁ ፡** (ድር ፡ ማኅ) ።

**መረግፅ ፤ መረግድ** ፤ ርግድ ፤ ረገዳ ፤ ሽብ ሸብ ፡ ውዝወዛ ፤ ዳንኪራ ፡ እስክስታ ፤ ከበሮ ፡ ጭብጨባ ፡ ያለበት ። የፀሓይ ፡ ፀ ፡ አበራር ፡ በሀረብ ፡ እንደ ፡ ምድ ራጥ ፡ ድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ መረግፅ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መረ ግድ ፡ ይላል ። ንኡስ ፡ መረግድ ፡ በቢይ ፡ መረግድ ። **መ ረግድስ ፡ አምሳለ ፡ ኪዳተ ፡ ላሕም ፡** (ገድ ፡ አብርሀ) ።

**ምርጋፅ** ፤ መርገጫ ፤ መረገጫ ፤ ማስረገጫ ፤ ማርገጃ ፡ ማመርገጃ ፡ ቦታ ።

**ረግረግ ፤ (ዐረ ፡ ሪግሪግት)** ፤ በቁሙ ፤ ዐ ምዓም ፡ ውሃማ ፡ ቦታ ፤ ሲረግጡት ፡ የሚውጥ ፡ የሚያ ሠርግ ፡ የሚያረገርግ ፡ ፈሳ ፡ ቂጠማ ፡ ያለበት ፡ (ዐማርኛ) ። ከሐረገና ፡ ከመረገ ፡ ከ፪ቱ ፡ የወጣ ፡ ስም ፡ ነው ።

**ረግረገ ፤ አ ፤ ተ** ፤ ረገረገ ፡ አረገረገ ፡ ተረገ ረገ ። ኹሉም ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ።

**ረዳ ፤ (ዐረ ፡ ወርድ ። ዕብ ፡ ዌሬድ ። ሱር ፡ ዋርዳ ፤ ሮዳ ። ጽር ፡ ሮዶን)** ፤ ያበባ ፡ ዕን ጨት ፡ አበባው ፡ እጅግ ፡ የሚያምር ፤ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሽታው ፡ የሚጣፍጥ ፤ ልብ ፡ የሚመሥጥ ። **ጽጌ ፡ ረዳ ። ንትቀጸል ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ። ማርያም ፡ ድንግል ፡ ምዕ ዝት ፡ እምጽጌ ፡ ረዳ ፡** (ሚራ፳፱ ፡ ፲፱ ። ፶ ፡ ፳ ። ጥበ ፪ ፡ ፰ ። ዶራሲ) ።

**ረዳእ ፤ አት ፤ (ረድአ ፡ ይረድእ ፡ ይር ዳእ ። ዐረ ፡ ረደአ ። ዕብ ፡ ዓዛር ። ሱር ፡ ዕዛር)** ፤ መርዳት ፡ ማገዝ ፤ መደገፍ ፤ ጥቅ ፡ ጠበቃ ፡ መኾን ፤ አይ ዞኽ ፡ ማለት ፡ ማጽናናት ፡ ማበርታት ፤ ማዳን ፡ መፈወስ ፤ መቤዠት ። **ፃጽር ፡ ውስተ ፡ ረዷእትየ ። መጽአ ፡ ይር ድአኒ ። ዘረድአኪ ፡ ትምትሪ ፡ ርእሶ ። እረድአ ፡ ለ ዛቲ ፡ ሀገር ። መጽአ ፡ ወረድኦሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዔገ ሎሙ ፡ ለይጣን ፡** (መዝ ፡ ፳፩ ። ዳንኛ ፡ ፲፫ ። ዮዲ፲፫ ፡ ፲፰ ። ኢሳ፵፩ ፡ ፲ ። ግብ፲ ፡ ፴፰) ። በረድአ ፡ ፈንታ ፡ አር ድአ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **ዘአርድአ ፡ ለጴጥሮስ ፡ አርድአኒ ፡ ሊተኒ ። በላኤ ፡ ታርድአኒ ። ያቃልሉክ ፡ ወያረድኡክ ። ታረድእ ፡ ምስሌሁ ፡** (ግላ፪ ፡ ፰ ። ሉቃ፲ ፡ ፵ ። ዘፍ፲፰ ፡ ፳፪ ። ፳፫ ፡ ፳) ።

**ረዳኢ ፤ መርድኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት)** ፤ የሚረዳ ፤ የሚያግዝ ፤ ዐጋዥ ፡ ረዳት ፤ አይዞኽ ፡ ባይ ። **ዘአልቦ ፡ ረዳኢ ። እስመ ፡ ረዳኢቱ ፡ ይእቲ ። ረዳእያን ፡ በቀትል ፡** (ኢዮ፳፱ ፡ ፲፪ ። ሚራ፴፯ ፡ ፳፱ ። ፩ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፩) ። በመርድኢ ፡ ፈንታ ፡ መርዳኢ ፡ ይላል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ። **መርዳእያኒሁ ፡** (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፫) ።

**መርድእ ፤ (እት ፡ ኣን ፡ ኣት)** ፤ ዝኒ ፡ ከ ማሁ ። **ንግበር ፡ ሎቱ ፡ መርድአ ፡ ዘከማሁ ። ኢየኀ ሥሥ ፡ መርድአ ። እስመ ፡ ዓለም ፡ መርድእ ፡ ውእቱ ፡ ለጻድቃን ፡** (ኩፋ ፡ ፫ ። ቅዳ ፡ ኢጲ ። ጥበ፲፭ ፡ ፲፯) ። ረድ ኡት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መርድእ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **በመርድአ ፡ እግዚአብሔር ። አዘዘ ፡ ይኅድግ ፡ መርድአ ፡ ህርቃኖስ ፡** (ፊልክ ፡ ፯ ። ዮሴፍ) ።

**ረድእ ፤ (እት)** ፤ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፤ በቁሙ ፤ አገልጋይ ፤ ተማሪ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፤ ትምርትን ፡ የሚ ረዳና ፡ የሚያስረዳ ፤ አማኒ ፡ ምእመን ፤ እውነተኛ ፡ ክር ስቲያን ፤ የክርስቶስ ፡ ትምርት ፡ በጣም ፡ የገባው ፤ የተረ ዳው ። **ጉንደየ ፡ ረድኡ ፡ ለአባ ፡ ሲሶይ ፡ ፀሣርተ ፡ አ ውራኅ ። ረድእ ፡ ዘየፈቅሮ ፡ ወውእቱ ፡ ረድእ ፡ ዘ ከነ ፡ ሰማዕተ ። ረድእሙ ፡ ለሐዋርያት ። አሐቲ ፡ ረድ እት ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ጣቢታ ፡** (ፊልክ ፡ ፵፯ ። ዮሐ፳፩ ፡ ፳፬ ። ሃይ ፡ አበ ። ግብ፱ ፡ ፴፮) ። ለመደኛ ፡ እይ ።

**አርዳእ ፤ አርድእት** ፤ ረዳቾ ፡ ረዳቶች ፡ አ ገልጋዮች ፡ ተማሮች ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፤ ምእመናን ።

ይቤልዎ ፡ አርዳኢሁ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ለቢጹ ፡ አርዳኢ ። ሰብዓ ፡ ወክልኤቱ ፡ አርድእት ። ወተሰምዩ ፡ አርድእት ፡ ክርስቲያነ ፡ (ዮሐ፲፭ ፡ ፲፬ ፡ ፲፮ ። ቅዳ ። ግብ፲፩ ፡ ፳፮) ። በአማርኛ ፡ ፈንታ ፡ አርድእት ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወቀረቡሙ ፡ አርዳኢሁ ፡ ለበዓለ ፡ ገራህት ፡ (ማቴ፲፫ ፡ ፳፯) ።

**አርድአ** ፤ አረዳ ፤ አማጠነ ፡ ርዱኝ ፡ አለ ፤ ረዳት ፡ ለመነ ፤ ቡታ ፡ ሰደደ ። ነሃቢ ፡ አርድአ ፡ ነሀብተ ፡ ብሩር ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፰) ።

—፤ አስረዳ ፤ ረዳት ፡ ሰጠ ፤ ርዱ ፡ አለ ፤ አስደራጊ ።

—፤ አረዳ ፤ አስረዳ ፤ ገለጠ ፡ ነገረ ፤ አድራጊ ። ጠየቀኝ ፡ ተመልከት ።

**አርዳኢ** ፤ አርጂ ፤ አርጅ ፤ አስረጅ ።

**ተረድአ** ፤ ተረዳ ፤ ታገዘ ፤ ተጠረ ፤ ጡረተኛ ፡ ኾነ ። ዘይትረዳእ ፡ በመኳንንት ፡ ዝ ፡ ዓለም ። እለ ፡ ይትረድኡ ፡ በክልኤ ፡ ፍና ፡ (ቢኖ ደ ። ማር ፡ ይሥ፳ ፡ ፪) ።

—፤ ተረዳ ፤ የሞት ፡ ወሬ ፡ ሰማ ። ትምርት ፡ ገባው ፤ ዘለቀው ፤ ተረዳው ፡ (በማርኛ) ።

—፤ ተረዳ ፤ ታወቀ ፡ ጉላ ፡ ተገለጠ ፡ ርግጥ ፡ ኾነ ፤ ወሬው ፡ ትምርቱ ።

**ርዱእ** ፤ (ኣን ፡ ኢት ፡ ድእት) ፤ የተረዳ ፡ የተረዳው ፤ ትምርት ፡ ነገር ፡ የገባው ፤ ዐጋዥ ፡ ረዳት ፡ ያለው ። ዘየሐውር ፡ በጽድቅ ፡ ርዱእ ፡ (ምሳ፳፰ ፡ ፲፰) ።

**ርድእት** ፤ መርዳት ፤ መረዳት ፤ አረዳድ ፤ ረዳትነት ፤ ርዳታ ፡ ዕገዛ ፤ አይዞኽታ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ርድእት ፡ ረዲኦት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ረድኤት ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። በእንተ ፡ ረድኤተ ፡ ሕሙም ። ዘወፅአ ፡ ለረድኤትክሙ ፡ (ግብ፱ ፡ ፱ ። ኢር፴፯ ፡ ፯) ።

**ረድኤት** ፤ በቁሙ ፡ ርዳታ ፡ መልካም ፡ ሥራ ። በረድኤተ ፡ ኀይሉ ። በረድኤተ ፡ እግዚ ፡ (መዝ ፡ ፺፰ ። ኢሳ፫ ፡ ፯ ። ቂላ፪ ፡ ፲፪) ።

—፤ ረዳት ፡ ዐጋዥ ፤ ባልንጀራ ። እስ ፡ መጽኡ ፡ ረድኤተ ፡ ለዳዊት ። ረድኤትነ ፡ በትምህርት ። ወእሉ ፡ ዳእሙ ፡ ረድኤትየ ። ረድኤቱ ፡ ዘከማሁ ፡ (፩ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፴፫ ። ፩ተሰ ፡ ፫ ፡ ፪ ። ቂላ፬ ፡ ፲፩ ። ዘፍ፪ ፡ ፳) ። ኀይል ፡ ጽንዕ ፡ ኵሎሙ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ረድኤት ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ወትበሊ ፡ ረድኤቶሙ ፡ በሲኦል ፡ እምክብሮሙ ፡ (መዝ ፡ ፵፰) ።

**ተራድአ** ፤ ተራዳ ፤ ተረዳዳ ፤ ተጋገዘ ። ተራድኡ ፡ በበይናቲሆሙ ። እኁ ፡ ምስለ ፡ እኁ ፡ ዘይትራዳእ ። ትትራድእ ፡ ለምንታ ። ከመ ፡ ይትራድኡ ፡ ኅቡረ ፡ በየብስ ፡ ወበባሕር ፤ ወከመ ፡ ኢይትራድኡ ፡ ዘልፈ ፡ ፀረ ፡ ሮም ፡ ባዕሌሆሙ ፡ (ኢሳ፵፩ ፡ ፲፮ ። ምሳ፲፰ ፡ ፲፱ ። ፳፱ ፡ ፴ ። ዮሴፍ) ።

**አስተራድአ** ፤ አራዳ ፡ አረዳዳ ፤ አስተጋገዘ ።

**ረዶን** ፤ (ጽር ፡ ሬዶን) ፤ ሠረገላ ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ በቅሎ ፡ ይሉታል ። አፍራስ ፡ ወሬዶን ፡ (ራእ፲፰ ፡ ፲፫) ።

**ረድየ** ፤ ዮት ፤ (ረደየ ፡ ይረዲ ፡ ይርዲ ። ዐረ ፡ ረደየ ፤ አበዛ) ፤ ማበደር ፡ ማስነቃት ፤ ባሬጣ ፡ በወለድ ፡ መስጠት ።

**ረዳዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ደይት) ፤ ባሬጣ ፡ አበዳሪ ፡ ትርፍ ፡ ፈላጊ ።

**ተረድየ** ፤ ባሬጣ ፡ ወሰደ ፡ ተበደረ ። ወይም ፡ በሬጣውን ፡ ተቀበለ ፤ አበዳሪ ። ኢትትረደይ ፡ እምኔሁ ፡ ቢጽከ ፡ ኢርዴ ፡ ወርቅ ፡ ወኢርዴ ፡ እክል ፡ (ዘዳ፳፫ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩) ።

**ተረዳዪ** ፤ ተበዳሪ ፤ በሬጣ ፡ ከፋይ ። ወይም ፡ ተቀባይ ፤ ባላሬጣ ።

**ርዱይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ዲት) ፤ የተበደረ ፡ በሬጣ ፡ ያለበት ፤ ልቆኛ ።

**ርድየት** ፤ ባሬጣ ፡ ማበደር ፤ መበደር ፤ ተበዳሪነት ።

**ርዴ** ፤ በሬጣ ፤ የብድር ፡ ወለድ ፤ ፍድፋጅ ፤ አታት ፡ እልፍ ፤ ትርፍ ። ኢትንሣእ ፡ እምኔሁ ፡ ርዴ ። ኢትደጉ ፡ ነሚአ ፡ ርዴ ። ወዘኢለቀሐ ፡ ወርቆ ፡ በርዴ ፡ (ዘሌ፳፭ ፡ ፴፮ ። ኢር፲ ፡ ፰ ። መዝ ፡ ፲፬) ።

**ተራደየ** ፤ ተበዳደረ ፤ ባሬጣ ፡ በወለድ ፡ ተስማማ ። ኢትትራደዮ ፡ (ዘዐ፳፪ ፡ ፳፬) ።

**ረድፈ** ፤ ረደፈ ፤ (ረዲፍ ። ዕብ ፡ ራዳፍ ፤ ደግነ) ፤ ተከተለ ፤ ተከታተለ ፤ ተራደፈ ፤ በረጫ ፡ በተራ ።

**አርደፈ** ፤ አራደፈ ፡ አከታተለ ።

**ረድፍ** ፤ በቁሙ ፤ ተራ ፡ ጸታ ፡ ዕርከን ፡ ደራጃ ።

**ራህርሀ** ፤—ራራ ፤—ራኅርኀ ።

**ረዊድ** ፤ ዶት ፤ (ሮደ ፡ ይረውድ ፡ ይሩድ ። ዐረ ፡ ራደ ። ዕብ ፡ ሩድ ፤ ምልስ ፡ ቅልስ ፡ አለ ፤ ታወከ ÷ ተሸበረ) ፤ መዝመት ፤ መውጋት ፤ አደጋ ፡ መጣል ፤ ማሸነፍ ፤ መውረር ፡ መዝረፍ ፤ መክበብ ፡ ከቦ ፡ መያዝ ፡ ማሰር ፤ ቢያመልጥም ፡ መከተል ፡ ማሳደድ ፡ ማባረር ። ይረውዱ ፡ ወኢይክልዎሙ ። ሮዱ ፡ ወቀተሉ ፡ በይሁዳ ። ወኢሎፍሊ ፡ በጽሑ ፡ ወሮዱ ፡ አህጉረ ። ሮድዎ ፡ ወሰሐብዎ ። ወደፈኖሙ ፡ ማይ ፡ ለእለ ፡ ሮድዎሙ ። እስመ ፡ ሮዳ ፡ ጸላኢ ፡ ለነፍስየ ፡ (ዘካ፲ ፡ ፳ ። ፪ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰ ። ግብ፳ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፻፵፪ ። ፻፵፬) ።

**ረዋዲ** ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤ ዘማች ፡ አጥፊ ፤ አሸናፊ ፤ ወራሪ ፡ ዘራፊ ፡ አባራሪ ፤ ገርግና ። ረዋዴ ፡ በግዕ ። ወረዋድያን ፡ ኢይክሉ ፡ ጸቢኦቶ ፡ (አዋል ። ድጓ) ።

**ተሮደ** ፤ ተረውደ ፤ ተያዘ ፤ ተከበበ ፤ ተወረረ ፡ ተዘረፈ ፤ ተዘመተበት ።

**ርዉድ** ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ውድ) ፤ የተያዘ ፡ የተከበበ ፡ ድል ፡ የኾነ ፤ የተማረከ ፡ ምርኮ ።

**ሩደት** ፤ መዝመት ፤ መክበብ ፤ መክበብ ፤ ዘመቻ ፡ ግምገማ ፤ ወረራ ፡ ዘረፋ ፡ (አርጋ ፡ ፯) ።

**ሮዳስ ፤** የቀኖት ፡ ስም ፤ ዐምስተኛ ፡ ቀኖት ፤ ኵናተ ፡ ሐራዊ ፤ ወይም ፡ ዐምስተኛው ፡ ስቍረት ፤ ሮማ ዝተ ፡ ገበ ። ሮዳስ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ኃምስ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ። የሮዳስ ፡ ምስጢር ፡ መክበብ ፡ ስለ ፡ ኸነ ፡ ከሳ ደር ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ፤ የሳደርን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ።

**ሩዝ ፤ (ዐረ ፡ ሩዝ ፤ አሩዝ ። ሱር ፡ ሩዛ ። ዕብ ፡ አሬዝ) ፤** በቁሙ ፤ ነጭ ፡ ጥሩ ፡ እኽል ፤ የነጮች ፡ ምግብ ፤ በእስያና ፡ በኤውሮፓ ፡ በዝቶ ፡ የሚዘራ ፡ የሚ በቅል ፤ ቈላ ፡ ሙቀት ፡ ውሃማ ፡ መሬት ፡ የሚወድ ።

**ራዛ ፤** ሩዛዊ ፤ ኀጣቱ ፡ እንደ ፡ ሩዝ ፡ የኾነ ፤ ሩዝ ፡ የሚመስል ፡ አሞራ ፤ አንጭታ ፤ ባቢሳ ፤ አንበጣ ፡ በል ፤ ሽመላ ፤ ወይም ፡ ሌላ ። ለእመ ፡ ዳዐደዉ ፡ ቋ ዓት ፡ ከመ ፡ ራዛ ። ተኀፂበ ፡ ይዳዐዱ ፡ እምራዛ ። ን ህብ ፡ ወራዛ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፯ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፱ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፬ ፡ ፪) ።



ራዛ ።

**ሮዛ ፤ (ሮማይ) ፤** ረዳ ፤ ጽጌ ፡ ረዳ ።


**ረዊሕ ፡ ሖት ፤ (ሮሐ ፡ ይረውሕ ፡ ይ ሩሕ ። ዕብ ፡ ራዋሕ ። ዐረ ፡ ራሐ ፡ ዐረፈ ፡ ተነፈሰ) ፤** ማራገብ ፤ ማርገብገብ ፤ ማናፈስ ፡ መነስነስ ፤ መርጨት ፤ ማቃጨል ፤ የማርገቢያ ፡ የክንፍ ፡ የምንዛህ ፡ የጭራ ፡ የናብሲስ ፡ የመነሳንስ ። ዲያቆን ፡ ይረውሕ ። ዲያቆናት ፡ የዐውዱ ፡ ወይረውሑ ፡ በመራውሓት ፡ በአምሳለ ፡ አክናፈ ፡ ኪሩቤል ፡ (ኪዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱) ።

**ረዋሒ ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት) ፤** የሚያራ ግብ ፡ የሚያናፍስ ፤ የሚረጭ ፤ ነስናሽ ፤ አናፋሽ ።

**መርውሕ ፤ (ሕት ፡ ሓን ፡ ሓት) ፤** ዝኑ ፡ ከማሁ ፤ አናፋሽ ።


**ረውሕ ፤ (ዕብ ፡ ወዐረ ፡ ሩሕ) ፤** ነፋስ ፤ እ ስትንፋስ ፤ ነፍስ ፡ መንፈስ ፤ ዕረፍት ፡ ህድአት ። ዕፉፍ ፡ ህዱእ ፡ ወይም ፡ ርዉሕ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ረውሕ ፡ ይ ላል ። እንጦንዮስ ፡ ረውሕ ፡ (ስንክ ፡ የካ፳፭) ።

**መረውሕ ፤ (ብ ፡ መራውሕ ፤ ሓት ። ዐረ ፡ ሚርወሕ ፡ ሚርወሐት ። ሱር ፡ ማርዋ ሕታ) ፤** ማርገቢያ ፤ ማናፈሻ ፤ መነሳንስ ፤ ጭራ ፡ የጭራ ፡ ዐይነት ፡ ኹሉ ። ይቀሙ ፡ ክልኤቱ ፡ ዲያቆናት ፡ በገበ ዋተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወየአኀዙ ፡ መራውሓተ ፡ ዘግቡራት ፡ እምግብር ፡ ልሙጽ ፡ ወይስድዱ ፡ ጽንጽንያተ ፡ (ፍ ነ ፡ ፲፪) ።



መረውሕ ።

**መርዋሕት ፤ (ታት ። ቅብጥ) ፤** መረዋ ፡ መረዋት ፤ ቃጭል ፤ ታላቅ ፡ ታናሽ ፡ መካከለኛ ፡ በየዐይነቱ ። መርዋሕት ፡ ዘይሰማዕ ፡ ድምፁ ፡ እስከ ፡ ነዋኀ ፡ (አዋል) ።



መርዋሕት ።

**ምርዋሕ ፤ (ሓት) ፤** ምግዘራት ፤ ምንዛህ ፡ የ ውሃ ፡ መርጫ ፤ መፈንጠቂያ ። ይቢድዎ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመኀትው ፡ ወበመጻውዕት ፡ ወበምር ዋሕ ፡ ወበድባብ ። ወተረቂ ፡ መቃብሪሁ ፡ በማይ ፡ (ግንዘ) ።

**ተሮሐ ፤** ተራገበ ፤ ተርገበገበ ፤ ተነሰነሰ ፤ ተረጨ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ተሮሐ ፡ ተረውሐ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተራውሐ ፡ ይላል ፡ አያሰኝም ። ዘተጸፍዐ ፡ መልታሕቲሁ ፡ ተሰዐለ ፡ ወነበረ ፡ በየማኑ ፡ አቡሁ ፡ እንዘ ፡ ይትራዋሕ ፡ ሎቱ ፡ አክናፈ ፡ እሳት ፡ ዘሐራ ፡ ሰማይ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ረውዮ ፤ ዮት ፤ (ረወየ ፡ ይረዊ ፡ ይር ወይ ። ዕብ ፡ ራዋህ ። ዐረ ፡ ረዊየ ። ሱር ፡ ር ዊይ) ፤** መርካት ፤ ጠጥቶ ፡ መጥገብ ፤ አብዝቶ ፡ መጠ ጣት ፤ መራስ ፡ ጥምን ፡ ማብረድ ፤ ማራቅ ፡ ማስወገድ ። ትሰትዩ ፡ ወኢትረውዩ ። እለ ፡ ይሰትዩኒ ፡ ኢይረው ዩኒ ። እምከመ ፡ ረወየት ፡ መሬት ። ወይረውዩ ፡ እ ምጠለ ፡ ቤትከ ። ይረውዩ ፡ አድባረ ፡ በድው ፡ (ሐጌ ፩ ፡ ፮ ። ዓሞ ፬ ፡ ፰ ። ሢራ፳፬ ፡ ፳፩ ። መቃ ። መዝ ፡ ፴፭ና ፡ ፰፱) ። በረወየ ፡ ፈንታ ፡ ተረወየ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ሀሰዉ ፡ እለ ፡ ኢትረወዩ ። ንትረወይ ፡ እምዘመድ ኅን ፡ አንቅዕት ። እለ ፡ ይትሬወዩ ፡ ሕገ ፡ (ተረ ፡ ቄር ። ሢራ፪ ፡ ፲፯) ።

**ረዋዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤** የሚረካ ፤ ረኪ ፡ ብዙ ፡ የሚጠጣ ፤ ጠጭ ።

**አርወየ ፤** አረካ ፤ አብዝቶ ፡ አጠጣ ፤ አጠገበ ፤ አራሰ ፡ አረሰረሰ ፤ አጨቀየ ፤ ነከረ ። ጽዋዕከኒ ፡ ጽኑዕ ፡ ወያረዊ ። ሐወጽካ ፡ ለምድር ፡ ወአርወይካ ፤ አር ውዮ ፡ ለትለሚሃ ። ያረዊ ፡ ነፍሰ ፡ እምቃለ ፡ እግዚ ፈትለ ፡ አርዊ ፡ (መዝ ፡ ፳፪ ። ፷፬ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፰) ።

**መርወይ** ፤ (ብ ፡ መራውይ) ፤ የውሃ ፡ ዕቃ ፤ መጠጫ ፤ ማጠጫ ፤ ቅል ፡ መንቀል ። እምብዝኃ ፡ ንዋይ ፡ ጽድቀ ፡ ዘአፍቀርከ ፤ ሐወ ፡ ዘፀቈርከ ፡ በመርወይ ፡ (ድጓ) ።

**ተረውየ** ፤ ተጠጣ ፡ ተጠገበ ፤ ዝናሙ ፡ ጠሱ ፡ ውሃው ፡ ጠበሰ ።

**ርዉይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፤ ዊት ፡ ውይት) ፤ የረካ ፡ የጠገበ ፤ የተጠገበ ። ርዉይ ፡ ውእቱ ፡ ጽሉ ፡ ምድር ። ገነት ፡ ርውይት ። ሜስ ፡ ወምዝር ፡ እለ ፡ ርዉያን ፡ ኅበ ፡ ያኩር ፡ (ዘፍ፳፫ ፡ ፲ ። ኢሳ፶፰ ፡ ፲፩) ።

**ርውየት** ፤ መርካት ፤ ማርካት ፤ አረካክ ፤ ርካታ ፤ የውሃ ፡ ጥጋብ ።

**ሩማ** ፤ **አው ፡ እሩማ** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ በይሁዳ ፡ ክፍል ፡ ያለች ፤ የሴኬም ፡ አጠገብ ፡ (፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፴፮ ። መሳ፱ ፡ ፵፩) ።

**ሮም** ፤ **ሮሜ** ፤ **ሮምያ** ፤ የመዲና ፡ ስም ፡ የሮማውያን ፡ ከተማ ፡ ሮምስ ፡ ያቀናት ፡ የቈረቈራት ።

**ሮማን** ፤ (ናት ። ዕብ ፡ ሪሞን ። ሱር ፡ ሩማና ። ዐረ ፡ ሩማን) ፤ በቋሙ ፡ የተክል ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፤ ሕንባቡ ፡ ቅርፍቱ ፡ ቀይ ፡ ደባባ ፤ ውስጡ ፡ ጽፍቅ ፤ ፍሬ ፡ የተመላ ፤ ቅንጣቱ ፡ የበቈሎ ፡ ዐይነት ። ታሕተ ፡ ሮማን ። በለስ ፡ ወሮማን ፡ ወዘይት ። ፈረየ ፡ ሮማን ፡ (፩ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፪ ። ሐጌ፪ ፡ ፲፱ ። ማሕ፰ ፡ ፲፫ ። ፯ ፡ ፲፫) ። በሮማን ፡ አምሳል ፡ የተሠራ ፡ ሌላውም ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ መልኩ ፡ ሮማን ፡ ይባላል ። ሮማን ፡ ዘያክንት ። ሮማን ፡ ወርቅ ። ወሮማናት ፡ ላዕለ ፡ ከታሪት ፡ (ዘፀ ፳፰ ፡ ፴፫ ፡ ፴፬ ። ኤር፶፪ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫) ።



ሮማን ፡

**ረዊጽ** ፤ ጾት ፤ (ሮጸ ፡ ይረውጽ ፡ ይሩጽ ። ዕብ ፡ ራጽ ። ሱር ፡ ርሄጥ) ፤ መሮጥ ፤ መፈርጠጥ ፤ መሸሽ ፡ መኰብለል ፤ ማምለጥ ፤ መብረር ፡ መክንፍ ፤ መፍጠን ፡ መቀልጠፍ ፤ መቸኰል ፡ መጣደፍ ፡ ቶሎ ፡ ማለፍ ፤ በክኼድ ፡ በሥራ ፡ ፈጣን ፡ መኾን ። አእጋርኪ ፡ እለ ፡ ጻመዋ ፡ በረዊጽ ። ይረውጹ ፡ ከመ ፡ ሀየል ። ወሮጸ ፡ ንቤሁ ፡ በኀይል ። ሩጹ ፡ ወኢትቁሙ ። ንሩጽ ፡ በትዕግሥት ። ወሮጸ ፡ አብርሃም ፡ ኀበ ፡ ሳራ ፡ (ደራሲ ። ኢሳ፵፭ ፡ ፯ ። ዳንኤ ፡ ፯ ። ኤር፬ ፡ ፯ ። ዕብ፲፪ ፡ ፩ ። ዘፍ፲፰ ፡ ፮) ። ለሮጸን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ፤ ለንቀወ ፡ የንቀወ ፡ ዘር ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

**ረዋጺ** ፤ (ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት) ፤ የሚሮጥ ፡ ሯጭ ፤ ፈጣን ፤ ቀልጣፋ ። ኢይክል ፡ ረዋጺ ፡ አምሥጦ ። አፍራስ ፡ ረዋጽያን ። ኄር ፡ ረዋጺ ። መላእክት ፡ ረዋጽያን ፡ (ዓሞ፪ ፡ ፲፬ ። ፮ ፡ ፮ ። ምሳ፳፬ ፡ ፵፬ ። ኢሳ፲፰ ፡ ፪) ።

**ርዉጽ** ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ውጽት) ፤ የሮጠ ፡ የሚሮጥ ፤ ችኩል ፤ ፈጣን ። ለጎስ ፡ ህላዌ ፡ ርዉጽ ። ውስተ ፡ ሚጠት ፡ በሕቁ ፡ (ቄር) ። ርዉጻ ፡ ሩጦ ፡ ገሥግሦ ፤ ፈጥኖ ፡ ቸኵሎ ፤ እየሮጠ ፡ እየጋለበ ። ይመጽኡ ፡ መላእክት ፡ ርዉጻ ፡ (ሕዝ፩ ፡ ፲፬) ።

**ሩጻት** ፤ መሮጥ ፤ አሯሯጥ ። ሩጫ ፡ ፍጥነት ፡ ገድል ፡ ቅሩፋት ፤ መልክም ፡ ሥራ ። ሩጻተ ፡ አፍራስ ። ሩጻተ ፡ እንስሳ ። መጠነ ፡ ሩጻተ ፡ መብርቅት ። እለ ፡ ተጋደሉ ፡ ሠናየ ፡ ገድለ ፡ ወፈጸሙ ፡ ሩጻቶሙ ፡ ወሞቱ ። ሠናየ ፡ ሩጻት ፡ (ኤር፰ ፡ ፲፮ ። ጥበ፲፮ ፡ ፲፰ ። መጽ ፡ ምስ ። ዲድ ፡ ፳፮ ። አርጋ ፡ ፩) ። በሩጻት ፡ ፈንታ ፡ ምርዋጽ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ፈጸምኩ ፡ ምርዋጽየ ። ቀፈጸመ ፡ ምርዋጸ ። ረሰየ ፡ ምርዋጸ ፡ ለምህሮ ፡ ወለንግሥ ፡ (ግንዘ ። ስንክ ፡ መጋ፳ ። ነሐ፳) ።

**አሮጸ** ፤ አሮጠ ፤ አስሮጠ ፤ አስቸኰለ ፤ አጣደፈ ፤ ነዳ ፡ አባረረ ። አሮጹ ፡ አፍራሲሆሙ ። ያረውጽ ፡ ጋኔኑ ። ያረውጾሙ ፡ ለሐንካሳን ። ይትራድኡ ፡ ለአርውጾ ፡ ሐመር ፡ (፩ዕዝ ፡ ፪ ፡ ፵፱ ። ሉቃ፰ ፡ ፳፱ ። ቀሌ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**መርወጺ** ፤ የሚያሮጥ ፤ የሚያስሮጥ ፤ አራሚ ፡ አስኳሚ ፤ ጋላቢ ። መርወጼ ፡ አፍራስ ፡ (ቄስጠ) ።

**ምርዋጽ** ፤ (ጻት) ፤ መሮጫ ፡ ማስሮጫ ፡ የሩጫ ፡ ቦታ ፤ ሜዳ ፡ ስታታ ። ምርዋጸ ፡ ብእሲ ። ምርዋጸ ፡ ፈረስ ። ሖሩ ፡ ኀበ ፡ ምርዋጻት ፡ (ግብ፳ ፡ ፳፬ ። ዲድ ፡ ፴፫ ። አፈ ፡ ተ፯) ።

**ተራወጸ** ፤ ተራወጠ ፡ ተሯሯጠ ፡ ተሽቀዳደመ ። እምከመ ፡ መጽአ ፡ ድምፀ ፡ ጸባኢት ፡ የኀድጉ ፡ ኵሎ ፡ ወይትራወጹ ፡ ለቀትል ። ሕፃናት ፡ እለ ፡ ይትራወጹ ፡ ማእከለ ፡ ጉባኤ ። ኦ ፡ አንስት ፡ ዐቀባ ፡ ውሉደክን ፡ ከመ ፡ ኢይትራወጹ ፡ ዝየ ፡ ወዝየ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፭ ፡ ፯ ። ቄስጠ ። ማርያ ፡ ፳፭) ።

**ረዋቅ** ፤ (ዕብራ ፡ ወዐረ) ፤ ባሕታዊ ፡ ፈላስፋ ፤ ሚስት ፡ የሌለው ፤ ስመ ፡ ጥር ፡ ታላቅ ፤ የፈላስፎች ፡ ሊቅ ።

**ረዋቃዊ** ፤ ዩ ፤ (ውያን ፤ ይያን ። ዐረ ፡ እሩዋቂዩን) ፤ የረዋቅ ፡ ወገን ፤ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ወይም ፡ ትምርት ፡ ሕግ ፡ ሥርዐት ። ወካልኣን ፡ ይብሀሉ ፡ ረዋቃውያን ፡ (ግብ፲፯ ፡ ፲፰) ።

**ሮስ** ፤—ወንድ ፡ ልጅ ፤—ኀረስ ፡ ኀረሰ ።

**ረዊት** ፤ ቶት ፤ (ሮተ ፡ ይረውት ፡ ይሩት ። ዐረ ፡ ረተ ፤ ዐረተ) ፤ መወልወል ፡ መጥረግ ፤ ማሸት ፡ መፈግፈግ ፤ ማጠብ ፡ መፈተግ ፡ ንጹሕ ፡ ጥሩ ፡ ማድረግ ። በማይ ፡ ኢኀፀብኪ ፡ ወበጼው ፡ ኢሮትኪ ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፬) ።

**ሮጶሊ.ም** ፤ (ጽር ፡ ሮፖ'ፖ'ሊ. ። ዕብ ፡ ሮክሊ.ም) ፤ ነጋዶች ፤ የነጋዴ ፡ ሰጣሮች ፤ አገር ፡ ላገር ፡ መንደር ፡ ለመንደር ፡ እየዞሩ ፡ ቃናናሽ ፡ ነገር ፡ የሚሸጡ ፤ የሚሸቅጡ ፡ (ንሐሮ ፡ ፴) ።

**ራዛ** ፤—ነጫ ፡ **አሞራ** ፤—ሩዝ ፡ ረወዘ ።

**ረዚ.ም** ፤ ሞት ፤ (ረዝመ ፡ ይረዝም ፡ ይርዘም ። ዕብ ፡ ራዛም ። ሱር ፡ ርማ'ዘ ። ዐረ ፡ ረመዘ) ፤ ቀጺብ ፤ መጥቀስ ፤ ባይን ፡ ማመልከት ። መርዘም ፡ ማደግ ፡ መግነን ፤ መክበድ ፡ መታበይ ፡ መኩራት ፡ መቈነን ፤ ራስ ፡ መዞር ፤ መስከር ፡ እንቡዝ ፡ መኾን ። በመጥቀስም ፡ የመርዘም ፡ ምስጢር ፡ አስበት ፤ (ተረት) ፤ ቀንዱ ፡ ሰማይ ፡ ጠቀሰ ፡ ሚራው ፡ ምድር ፡ አበሰ ። ይመናና ፡ ጠቅሶ ፡ ከሰበው ፡ ደርሶ ። **እሰ ፡ ይገፊ.ትዑ ፡ ይመናቀ** ፡ (አዋል) ።

**ረዛሚ.** ፤ (ሚ.ት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤ የሚ.ጠቅስ ፡ ጠቃሽ ፡ ረዥም ፤ ትቢ.ተኛ ፤ ሰካር ።

**ርዙም** ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ዝምት) ፤ የረዘመ ፤ ረዥም ፤ መስሎ ፤ ቁመታም ፤ ምጡቅ ። ሰክር ፤ እንቡገ ። በርዙም ፡ ፈንታ ፡ መርዝም ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። **ቦአ ፡ ኀቤሃ ፡ ሰይጣን ፡ ወረሰያ ፡ ከመ ፡ መርዝመ ፡ ወይን ፡ ወአርስዓ ፡ ዐቲበ ፡ ገጻ ፡ ወሆከ ፡ ኅሊናሃ** ፡ (ቀሌ) ።

**ርዝመት** ፤ በቁሙ ፡ መርዘም ፤ አረዛዘም ፤ ረዥምነት ፤ ርዝማኒ ፤ ልዕልና ፤ ቁመት ፡ (ዐማርኛ) ።

**መርዘም** ፤ ትዕቢት ፡ ኵራት ፤ ነቀጥቃጥ ፤ እንባዜ ፡ እስክታ ፡ ፃሕስ ፤ ሑሰተ ፡ ርእስ ። **እምስካር ፡ ይትወለድ ፡ ምርዓት ፡ ወዝሙት ፡ ወሥሥዕት ፡ ፀርፈት ፡ ወትዕቢት ፡ ወመሐላ ፡ በሐሰት ፡ ወኢያሠንዮ ፡ በዝንጋዔ ፡ ወመርዘመ ፡ ርእስ ። ቅንአት ፡ ወፍትወተ ፡ አንስት ፡ ልበ ፡ ጠቢባን ፡ ያማስን ፤ ወዓዲ ፡ ስካር ፡ ወዘፈን ፡ ወመርዘመ ፡ ርእስ** ፡ (ቀሌ) ።

**አርዘመ** ፤ አረዘመ ፤ አስረዘመ ፤ ረዥም ፡ ምጡቅ ፡ አደረገ ፤ አስደረገ ። ርዝመት ፡ ለቁመትም ፡ ለሞላልነትም ፡ ይነገራል ፤ ምጥቀት ፡ ግን ፡ ለቁመት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ርሒ.ብ** ፤ ብት ፤ (ርሕበ ፡ ይርሕብ ፡ ይርሐብ ። ዕብ ፡ ራሐብ ። ዐረ ፡ ረሒ.በ) ፤ መስፋት ፤ መዘርጋት ፡ ሰፊ ፡ ዝርግ ፡ ሜዳ ፡ ወርዳም ፡ ጉናም ፡ መኾን ። **ርሕበት ፡ አረፍተ ፡ ባቢሎን ። ከመ ፡ ይርሐብ ፡ እምላዕሉ ። ርሕበ ፡ አፉየ ። ሠብሐ ፡ ወገዘፈ ፡ ወርሕበ** ፡ (ኤር፶፩ ፡ ፶፰ ። ሕዝ፲፮ ፡ ፯ ። ዳንኤ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፲፭) ። በርሕበ ፡ ፈንታ ፡ ተርሕበ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። **እምቅድመ ፡ ይትረሐብ ፡ ኑኝ ፡ አየራት ። ስፍሐ ፡ ምድር ፡ እምቅድመ ፡ ይትረሐብ** ፡ (ቅዳ ፡ አፈ ። መጽ ፡ ምስ ። ኤር፪ ፡ ፳፪) ።

**ርሒ.ብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ሕብት ፡ ረሓብ) ፤ ስፉሕ ፤ ሰፊ ፡ ዝርግ ፤ ወርዳም ፤ ጉናም ፤ ወርደ ፡ ትልቅ ። **ምድር ፡ ርሒ.ብ ። ርሒ.በ ፡ ልብ ። ወትእዛዝከሰ ፡ ርሒ.ብ ፡ ፈድፋደ ። ፍኖት ፡ እንተ ፡ ትወስድ ፡ ውስተ ፡ ሀጒል ፡ ርሕብት ፡ ይእቲ ። በምሕረቱ ፡ ርሕብት ። ወምድርሰ ፡ ረሓብ ። ዛቲ ፡ ባሕር ፡ ዐባይ ፡ ወረሓብ** ፡ (ኢሳ፴ ፡ ፩ ። አፈ ፡ ተ፲፱ና ፡ ፴፫ ። መዝ ፡ ፻፲፰ና ፡ ፻፫፫ ። ዘፍ፴፬ ፡ ፲ ። መሳ፲፰ ፡ ፲) ።

**ርሕበት** ፤ መስፋት ፡ አሰፋፍ ፤ ሰፊነት ፡ ወርዳምነት ፤ ስፋት ፤ ወርድ ። **ፈቂዶ ፡ ርሕበተ ፡ መካን ፡ ለጸብእ ። ትዕግሥት ፡ ወርሕበተ ፡ እንግድዓ** ፡ (ዮሴፉ ። ፈላስ) ።

**ርሕብ** ፤ **ራሕብ** ፤ ስፋት ፡ ወርድ ፡ ጕን ። **ኑኃ ፡ ወርሕባ ። ርሕበ ፡ ምድር ። ርሕበ ፡ ዓለም ፡ ኢ.ይገምራ ። ምንትኑ ፡ ራሕቡ ፡ ወኑኁ ። በራሕቡ ፡ ለዓለም ። ራሕበ ፡ ዘባኑ ። ውስተ ፡ ራሕበ ፡ ልብከ** ፡ (ዘፍ፲፫ ፡ ፲፯ ። ፲፫ ። ፲፯ ። ኤፌ፫ ፡ ፲፰ ። ሰንክ ፡ የካ፳ ። ኢዮ፲፰ ፡ ፳፯ ። ምሳ፳ ፡ ፫) ።

**አርሐበ** ፤ አሰፋ ፤ ዘረጋ ፤ ሰፊ ፡ አደረገ ፡ አበዛ ። **ለይርሕብ ፡ ብሔረ ። አርሐበ ፡ ለከ ፡ ደወለከ ። ኣርሒቢ ፡ መሃክሊ ፡ ዘይደብተራኪ ። ከመ ፡ ይርሕቡ ፡ ንኅሊተ ። አርሐበት ፡ ሶቶ ፡ ብዕሎ ፡ እምጻማሁ** ፡ (ዘፍ፱ ፡ ፳፯ ። ዘዳ፲፪ ፡ ፳ ። ኢሳ፶፬ ፡ ፪ ። ዮሴፍ ። ጥበ፲ ፡ ፲) ።

**አርሓቢ.** ፤ **መርሐቢ.** ፤ (ሕብ) ፤ የሚ.ያሰፋ ፤ አሰፊ ፡ ሰፊ ፡ አድራጊ ።

**መርሕብ** ፤ (ብ ፡ መራሕብት) ፤ ሰፊ ፡ ቦታ ፤ ሜዳ ፤ ስታታ ፤ ገባያ ፡ ጉባይ ፤ አደባባይ ። **ወአውፅኡኒ ፡ ውስተ ፡ መርሕብ ። ነንድር ፡ ውስተ ፡ መርሕብ ። መአዝነ ፡ መራሕብት** ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። ዘፍ፲፱ ፡ ፪ ። ማቴ፮ ፡ ፭) ።

**ርሕበ** ፤—**ተራበ** ፤—**ርኂብ ፡ ርኅበ** ።

**ርሕይ** ፤ ዮት ፤ (ርሕየ ፡ ይርሐ. ፡ ይርሐይ ። ዕብ ፡ ሬያሕ ። ሱር ፡ ራያሕ ። ዐረ ፡ ራሐ) ፤ መሽተት ፤ ማሽተት ፤ ማነፍነፍ ፡ ማፈንፈን ፤ ባፍንጫ ፡ መሳብ ፤ መማግ ።

**ረሓዪ.** ፤ (ዪ.ት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤ የሚ.ሸት ፡ የሚ.ያሸት ፤ ሸታች ፤ አሽታች ።

**ርሔ** ፤ (ሕያት) ፤ መልካም ፡ ጥሩ ፡ ሽታ ፤ የሽቱ ፡ መዐዛ ፤ ልብ ፡ የሚመሥጥ ፤ ባፍንጫ ፡ የሚ.ገባ ፡ የሚ.ጣፍጥ ። **ወጼና ፡ መዐዛ ፡ ሠናይ ፡ ዘይጼኑ ፡ እምሆሱ ፡ ርሔ ፡ አፈው** ፡ (ቀሌ ። አርጋ ። መጽ ፡ ምስ) ። መደብ ፡ ወይን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ርሔ ፡ ይላል ፤ የታሳሳተ ፡ ነው ። **መላትሒ.ሁ ፡ ከመ ፡ ርሔ ፡ አፈው ። ኣሰትየከ ፡ እምርሔ ፡ አፈውየ** ፡ (ማሕ፭ ፡ ፲፫ ። ፰ ፡ ፪) ።

**ርሔ** ፤ (ዕብ ፡ ሬሓን ። ዐረ ፡ ረይሐን) ፤ ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ ስም ፤ ሬሓን ፤ በቃናናሽ ፡ ሽክላ ፡ ዐፈር ፡ እየመሉ ፡ የሚተክሉት ፤ ጥሩ ፡ ሽታ ፡ ያለው ። **ዝክረ ፡ ስምኪ. ፡ ዘይምዕዝ ፡ እምርሔ** ፡ (ደራሲ.) ።

**ርሒ.ን** ፤ ኖት ፤ (ረሐነ ፡ ይርሕን ፡ ይርሐን ። ዐረ ፡ ረሐለ) ፤ መጫን ፡ ማሸከም ፤ መጉዝ.

ጕዝ ፤ የኮርቻ ። ተንሥአ ፡ በድባሕ ፡ ወረሐኒ ፡ አድግ ። ወረሐኑ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ላዕሌሆን ፤ (ዘፍ፵፱ ፡ ፲ ። ማቴ፳፩ ፡ ፯) ።

**ራሕን** ፤ ኮርቻ ፤ ምቹ ፤ ማላስ ፤ የጭንት ፡ ዕቃ ፤ ጭንት ።

**ርሒዕ ፤ ዖት ፤ (ርሕፀ ፡ ይርሕዕ ፡ ይርሐፅ ። ፀረ ፡ ረሐፀ ። ዕብ ፡ ራሐጽ)** ፤ ማጠብ ፤ መታጠብ ፤ በውሃ ፤ መነከር ፤ መዘፈቅ ። መውዛት ፡ መላብ ፤ መረስረስ ፡ መርጠብ ፤ መቅለጥ ፤ መቅለጥለጥ ፤ መፍራም ፡ ቀለጠ ፡ መኾን ። ይርሕፁ ፡ አፍራስ ፡ እምጽንዐ ፡ ኀይሉ ። ረሐፅከኒ ፡ ወሊምለምከኒ ፤ (ገድ ፡ ተክ ። ዘዳ፴፰ ፡ ፶፩) ።

—፤ መታጠክ ፤ መደረጥ ፤ መናወጥ ፤ መቈጣት ፤ መመግሸት ፤ መረጐኽ ፤ የባሕር ፡ የዛፍ ፤ ከፀሙሶ ፡ ነፋስ ፡ የተነሣ ፤ ለሰውም ፡ ይኾናል ። ወርሕፀት ፡ ነፍሱ ፡ ለንጉሥ ፡ ሶርያ ፤ (፬ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፩) ።

**ርሑዕ ፤ (ፃን ፡ ፃት ፡ ሕፅት ፤ ረሓፅ)** ፤ የታጠበ ፡ የላበ ፡ የወዛ ፤ ወዛም ፡ ላበታም ፤ የታወከ ፤ ህዉክ ፡ ኹሩ ፡ ወፍራም ፡ ቀለጠ ፤ ድልድል ፡ ቅምጥል ። አንተ ፡ ረሓፅኒ ፡ ወአንተሂ ፡ ድክምት ፤ (ዘዳ፳፰ ፡ ፶፮) ።

**ራሕፅ** ፤ ወገዝ ፡ ላበት ፤ ከገላ ፡ የሚፈልቅ ፡ የሚመነጭ ። ሁከት ፡ መታወክ ። ይጼውዕ ፡ በጊዜ ፡ ራሕፀ ፤ (ደራቢ) ።

**አርሐፀ** ፤ አወዛ ፤ አበወዛ ፡ አቅለጠለጠ ።

**መርሕፅ ፤ መርሐፂ** ፤ የሚያልብ ፡ የሚያወዛ ፡ የሚያስወዛ ።

**ርሒቅ ፤ ቆት ፤ (ርሕቀ ፡ ይርሕቅ ፡ ይርሐቅ ። ዕብ ፡ ራሐቅ ። ሱር ፡ ርሔቅ)** ፤ መራቅ ፤ መወገድ ፤ መነጠል ፤ መለየት ፤ መቈረጥ ፤ ተለይቶ ፡ መኼድ ፤ ገለል ፡ ፈቀቅ ፡ ማለት ፤ በታን ፤ ዘመድን ፡ መተው ፡ መልቀቅ ፤ ባዕድ ፡ መኾን ። ርሕቀ ፡ እምኔየ ፡ ረድኤቱ ። ነዋኑ ፡ ይርሕቁ ፡ እምኔየ ። ረሐቁ ፡ ረሐቁ ፡ ወፃኡ ፡ እምህየ ። ረሐቂ ፡ እምፀመፃ ። እግዚ ፡ ይርሕቅ ፡ ልቡ ፤ (ኢዮ፯ ፡ ፲፫ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፲፫ ። ፶፪ ፡ ፲፩ ። ፶፱ ፡ ፲፱ ። ኤር፲፯ ፡ ፭) ። በርሕቀ ፡ ፈንታ ፡ ተርሕቀ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እስ ፡ ይትረሐቁ ፡ እምእግዚአብሔር ፤ (ኢሳ፵፭ ፡ ፳፱) ።

**ረሓቂ ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት)** ፤ የሚርቅ ፡ የሚሸሽ ፤ ፈሪ ፤ እንቢተኛ ። ርኩሳን ፡ ወረሓቅያን ፡ እምስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፤ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ርሑቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ሕቅት)** ፤ የራቀ ፤ የወገደ ፤ ሩቅ ፤ ረዥም ፤ ብዙ ። ርሑቅ ፡ መዐት ። ርሑቅ ፡ ብሔር ። ርሑቅ ፡ ፍኖት ። ጊዜያት ፡ ርሑቃት ፤ (ዘፀ፴፬ ፡ ፯ ። ኢሳ፲፫ ፡ ፭ ። ፩ነገ ፡ ፳፯ ፡ ፲፫ ። ሕዝ፲፪ ፡ ፳፯) ።

**ርሕቀት** ፤ መራቅ ፤ አራራቅ ፡ ርቀት ፤ ሩቅነት ፤ ብዛት ፤ ርዝመት ። ሕበስኩ ፡ ላዕለ ፡ ነፍስየ ፡ በሑረትየ ፡ ኀበ ፡ ሮምያ ፡ ወርሕቀትየ ፡ እምህላዌ ፡ ንጉሥ ። ርሕቀተ ፡ ፍኖት ። ርሕቀተ ፡ መዋዕል ፤ (ዮሴፍ ። አፈ ፡ ተ፲፬ ። ጥበ፲፬ ፡ ፲፯) ።

**ርሕቅ** ፤ ርቀት ፤ ርቆሽ ፤ አራራቅ ፤ (አርጋ) ።

**ርሕቅና** ፤ ሩቅነት ፤ ርሕቀት ፤ ልዩነት ። ሰይእቲ ፡ ኢያፀርዓ ፡ ርሕቅና ፡ ዘመን ። ረከበ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ርሕቅና ፡ ዐቢየ ፤ (ስንክ ፡ ጳጉ፪) ።

**አርሐቀ** ፤ አራቀ ፡ አስራቀ ፡ አሶገደ ፤ ለየ ፤ ቈረጠ ። ከመ ፡ ያርሕቁኒ ፡ እመቅደስየ ። አርሕቅ ፡ መዐተ ፡ እምልብከ ። አርሕቃ ፡ ለሐዘን ፡ እምኔከ ። ጌጋይክሙ ፡ አርሐቀ ፡ ሠናይተ ፡ እምኔክሙ ። አርሐቅኒ ፡ እምሕይወትየ ፤ (ሕዝ፰ ፡ ፮ ። መክ፲፩ ፡ ፲ ። ሚራ፴፰ ፡ ፳ ። ኤር፭ ፡ ፳፭ ። ኢዮ፴ ፡ ፳፪) ። በአርሐቀ ፡ ፈንታ ፡ አስተርሐቀ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። እፎ ፡ ታስተርሕቅ ፡ ለዘኢይትረሐቅ ። እምደሪበ ፡ ድርሳን ፡ አስተርሐቀ ። ወአስተርሐቅዋ ፡ ለንጢአቶሙ ፤ (መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ታኅ፰ ። መዝ ፡ ፲፰፰) ።

**መርሐቂ ፤ መርሕቅ ፤ (ቅት ፡ ቃን ፡ ቃት)** ፤ የሚያርቅ ፡ የሚያሶግድ ፤ አራቂ ። ትሕትና ፡ መርሕቅኒ ፡ ወመድኀኒኒ ፡ እመሥገርተ ፡ ሰይጣን ፤ (ፊልክ ፡ ፻፶፱) ። ኽርስቶስኛም ፡ ማራቂያ ፡ ማስራቂያ ፡ ማሶገጃ ፡ ተብሎ ፡ በማድረግያነት ፡ ይፈታል ።

**ተራሐቀ** ፤ ተራራቀ ፤ ተለያየ ። ጊዜ ፡ ለተራሕቆ ። ኢይትራሐቁ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምካልኡ ። ተራሕቆ ፡ እምዓለም ፤ (መክ፫ ፡ ፭ ። ዮኤ፪ ፡ ፰ ። ፊልክ ፡ ፬) ።

**አስተራሐቀ** ፤ አራራቀ ፤ አለያየ ፤ ገላገለ ፤ ከፋፈለ ። ቆመ ፡ ማእከሎሙ ፡ ወአስተራሐቆሙ ። አስተራሕቅዎሙ ፡ ዘዘ ፡ ዚአሆሙ ፤ (፬ነገ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ። ዳን፲ ፡ ፶፩ ። ዘፍ፴፱ ፡ ፲፯) ።

**መስተራሕቅ** ፤ የሚያራርቅ ፤ የሚራራቅ ፤ ተራራቂ ፡ በመራራቅ ፡ በልዩነት ፡ ያለ ። በበዓላት ፡ እው ፡ በጊዜያት ፡ መስተራሕቃት ፤ (ፊልክ ፡ ፸፱) ።

**ርሒስ ፤ ሶት ፤ (ርሕሰ ፡ ይርሕስ ፡ ይርሐስ ፤ ርሕፀ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ራስ ፤ ረጠበ ። ዐረ ፡ ረሸ ፤ ረጨ)** ፤ መራስ ፤ መረስረስ ፤ መርጠብ ፡ መለስለስ ፤ መርከት ፤ መለዘብ ፤ ውሃ ፡ መጥገብ ። ይርሕሱ ፡ አድባር ፡ እምደምሙ ፤ (ኢሳ፴፬ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፯) ።

**ርሑስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ሕስት)** ፤ የራሰ ፡ የለሰለሰ ፤ ርጥብ ፤ ልሕሉሕ ፤ ውሃ ፡ ጠገብ ። ሰላም ፡ ለርእስኪ ፡ በቅብዐ ፡ ቅዳሴ ፡ ርሑስ ። ምድር ፡ ርሕስት ፡ ወጥልልት ፡ እማይ ፡ ትወልድ ፡ ዕፄያተ ፡ ብዙኀ ። አቅረበ ፡ ኀቤሁ ፡ ኅብስተ ፡ ይቡሰ ፡ ወርሑሰ ፡ በማይ ፡ ወላዕሌሁ ፡ ዘይት ፡ ወጼው ። ሕፍነ ፡ ዐተር ፡ ዘርሑስ ፡ በማይ ፤ (ደራቢ ። አፈ ፡ ተ፳፬ ። ፊልክ ፡ ፻፴፪ ። ስንክ ፡ ጥቅ፴)  ።

**አርሐበ** ፤ አራበ ፤ አስራበ ፤ ነከረ ፤ አረጠበ ፤ አረከ ፤ አጠገበ ። ያርሕበሙ ፡ ነፍኔፍ ፡ ወጠለ ፡ ገዳም ። እስከ ፡ ይሙሕዝ ፡ ሀፋ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ወያርሕብ ፡ ምድረ ፡ ኀበ ፡ ቆመ ። ወበአንብዕየ ፡ አርሐብኩ ፡ ምስካብየ ። (ኢዮ ፴፰ ፡ ፳፯ ። ገድ ፡ ተክ ። መዝ ፡ ፮ ። ሉቃ ፯ ፡ ፴፰) ።

**አርሓቢ** ፤ **መርሕብ** ፤ የሚያርብ ፤ የሚያረጥብ ፤ ነካሪ ።

**ምርሓብ** ፤ ማራሻ ፤ መንከሪያ ፤ ዕቃ ፡ ቦታ ።

**ርኅበ ፤—ሰፌ ፡ ኸነ ፤—ርሒብ ፡ ርሕበ ።**

**ርኂብ** ፤ **በት** ፤ **(ርኅበ ፡ ይርኅብ ፡ ይርኅብ ። ዕብ ፡ ራዔብ ፤ ዐረ ፡ ረዐበ ፡ ሰፋ)** ፤ መራብ ፤ በረኀብ ፡ መያዝ ፤ መጠውለግ ፤ ባዶ ፡ ሆድ ፡ መኾን ፤ ምግብ ፡ መፈለግ ፤ ልብላ ፡ ልብላ ፡ ማለት ፤ ለመብል ፡ መሠየት ፤ መጕምጀት ። ወመጽአ ፡ እምሐቅል ፡ ርኂቦ ። ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይርኅቡ ፡ ወይጸምኡ ። ርኅብኩ ፡ ወአብላዕክሙኒ ። ትናገራ ፡ ድመት ፡ በልሳነ ፡ ሰብእ ፡ ወትቤሎ ፡ ምንተ ፡ ትፈቅድ ፡ ወይቤላ ፡ ይርኅበኒ ፡ ወወሀበቶ ፡ ኅብስተ ፡ (ኩፋ ፡ ፴፱ ። ማቴ ፭ ፡ ፮ ። ፳፭ ፡ ፴፭ ። ስንክ ፡ መጋ ፲፯) ። በርኅበ ፡ ፈንታ ፡ ተርኅበ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፤ አያሰኝም ።

**ርኁብ** ፤ **(ብን ፡ ብት ፡ ኅብት)** ፤ የተራበ ፤ የተቸገረ ፤ ራብተኛ ፤ ራብ ፡ የያዘው ፤ ምግብ ፡ ያረዘው ። እስመ ፡ ርኁብ ፡ ሀገር ። ርኁባኒሆሙ ። ነፍስ ፡ ርኅብት ፡ (፱ነገ ፡ ፯ ፡ ፱ ። ማር ፰ ፡ ፫ ። ኢሳ ፶፪ ፡ ፯) ።

**ረኀብ** ፤ **አው ፡ ረኃብ** ፤ በቁሙ ፤ ራብ ፤ የምግብ ፡ ዕጦት ፤ ቀጠና ፤ ችጋር ፡ ባሕርያዊ ፡ ሕማም ፤ ጠባይዓዊ ፡ ሕግ ፡ በግድ ፡ ምግብ ፡ የሚያስፈልግ ። ይጠፍኡ ፡ በረኀብ ። ወአምጽአ ፡ ረኀበ ፡ ለብሔር ። ወተወክፈ ፡ ረኃበ ፡ እስመ ፡ ረኃብሰ ፡ አልቦቱ ፡ ኀጢአት ። አመጽአ ፡ ረኀበ ፡ እክል ፡ (ዮዲ ፯ ፡ ፲፱ ። መዝ ፡ ፻፬ ። ሃይ ፡ አበ ። ዓሞ ፰ ፡ ፰) ።

**አርኀበ** ፤ አስራበ ፡ ምግብ ፡ ነሣ ፤ ረኀብ ፡ አመጣ ። ምግብ ፡ አስፈለገ ፤ ልብላ ፡ ልብላ ፡ አሰኘ ፤ ረኀቡ ። አርኀበከ ፡ ወእምዝ ፡ መና ፡ ሴሰየከ ። አርኅብዎ ፡ ወአጽምእዎ ፡ (ዘዳ ፰ ፡ ፫ ። ፫ነገ ፡ ፳፱ ፡ ፳፯) ።

**መርኅብ** ፤ የሚያስርብ ፤ አስራቢ ።

**ርኂው** ፤ **ዎት** ፤ **(ርኅወ ፤ ረኅወ ፡ ይርኁ ፡ ይርኅው ። ርሕበ)** ፤ መከፈት ፡ መስፋት ፤ ክፍት ፡ ሰፊ ፡ ባዶ ፡ መኾን ። ኅዋን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ክፋል ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በርኅወ ፡ ፈንታ ፡ ተርኅወ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። በዝሉ ፡ ጊዜ ፡ ይትረኀዉ ፡ አናቅጺኪ ። ተርኅወ ፡ አስራብ ፡ ሰማይ ። ወከነ ፡ ዝ ፡ ምክንያተ ፡ ተርኅዎታ ፡ ለሀገር ፡ (ኢሳ ፷ ፡ ፲፩ ። ዘፍ ፯ ፡ ፲፩ ። ዮሴፍ) ።

**ረኃዊ** ፤ **(ዊት ፡ ውያን ፡ ያት)** ፤ የሚከፈት ፤ የሚከፋፈት ፤ ተከፋች ።

**ርኁው** ፤ **(ዋን ፡ ዋት ፡ ኁት)** ፤ የተከፈተ ፤ ክፍት ፤ ሰፊ ፤ ግልጥ ፤ ባዶ ፤ ኀዋ ። ርኁው ፡ ጕርኤየ ። ይረክብዎ ፡ ርኁወ ። ኆኅት ፡ ርኁት ። መሳክው ፡ ርኁዋት ። ርኁው ፡ ሉሙ ፡ መከነ ፡ ትዕግሥትየ ፡ (ኢዮ ፴፯ ፡ ፴፪ ። ዮሴፍ ። ራእ ፫ ፡ ፰ ። ሔኖ ፸፪ ፡ ፫ ። ሱቱ ፡ ዕዝ ፱ ፡ ፲፪) ።

**አርኀወ** ፤ ከፈተ ፤ አስከፈተ ፤ ገለጠ ፤ ሰበረ ፡ ድል ፡ አደረገ ። አርኀወት ፡ ኆኅተ ። አርኅዋ ፡ ለታቦት ። አርኀውከ ፡ ሰማየ ። አርኀወ ፡ ሀገረ ፡ (መቃ ፰ ፡ ፲፫ ። ኩፋ ፡ ፭ ። ኢሳ ፳፬ ፡ ፭ ። ዮሴፍ) ።

**መርኆ** ፤ **(ብ ፡ መራኁት ፤ ኃት)** ፤ መክፈቻ ፤ መክፈቻ ፤ ማስከፈቻ ። ነሥኡ ፡ መርኆ ፡ ወአርኀዉ ። እሙንቱ ፡ እለ ፡ ይእኅዙ ፡ መራኁተ ፡ ቤተ ፡ እግዚ ፡ (መሳ ፫ ፡ ፳፭ ። ፩ዜና ፡ ፱ ፡ ፳፯) ።



መርኆ ፡

**ርኅጸ ፤—ወዛ ፡ ላበ ፤—ርሐፀ ።**

**ርኅቀ ፤—ራቀ ፡ ወገደ ፤—ርሕቀ ።**

**ራኅርኖ** ፤ **ኖት** ፤ **(ራኅርኀ ፡ ይራኅርኅ ፡ ይራኅርኅ ። ዐረ ፡ ረኀ ፤ ረኅረኀ ። ዕብ ፡ ራከኽ)** ፤ መራራት ፤ መማራት ፤ መለዘብ ፤ መለስለስ ፡ መርጠብ ፡ ልሕሉሕ ፡ መኾን ፤ እንደ ፡ ሳንባና ፡ እንደ ፡ ጕበት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በራኅርኀ ፡ ፈንታ ፡ ተራኅርኀ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ተራኅርኀ ፡ ሎቱ ፡ ወሐረ ፡ ኀቤሁ ። ኢተራኅርኅ ፡ አሐዱሂ ፡ በላዕሌሁ ። ዘአሠነየ ፡ ግዕዘ ፡ ይጸንዕ ፡ ፍቅሩ ፡ ወይትራኅራኅ ፡ ላዕሌሁ ፡ ልበ ፡ ዙሉ ። ተራኅርኖተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። አዘዝነ ፡ ንሕነሂ ፡ በእንተ ፡ ተራኅርኖ ፡ ወምሕረት ፡ (ዮሴፍ ። አፈ ፡ ተ፲፩ ። ፈላስ ። ያዕ ፡ ዘእል ። ፈ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፪) ።

**ርኅሩኅ** ፤ **(ኃን ፡ ኃት ፡ ርኅት)** ፤ በቁሙ ፤ የራራ ፤ የገራ ፤ ገር ፡ ርሩ ፤ ወላላ ፤ ዐዛኝ ፤ መሓሪ ። ዘበ ፡ ተፋቅሮ ፡ ርኅሩኅ ፡ ወተዐጋሢ ፡ ውእቱ ። መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ ወርኅሩኅ ። ከነ ፡ ትሑተ ፡ ወርኅርኅ ፡ ልብ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፭ ። ጥበ ፲፪ ፡ ፲፱ ። ዮሴፍ) ።

**ርኅራኄ** ፤ በቁሙ ፤ መራራት ፤ ርሩነት ፤ ገርነት ፤ ገራምነት ። ናሁ ፡ ጸንዐ ፡ ርኅራኄነ ፡ ላዕለ ፡ ውሉደሙ ። ሃይማኖትነ ፡ ሃይማኖተ ፡ ምሕረት ፡ ወሣህል ፡ ወርኅራኄ ፡ (ዮሴፍ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፭ ፡ ፫) ።

**አራኅርኀ** ፤ አራራ ፤ አስራራ ፤ አማራራ ፤ አለዘበ ፤ መከረ ፡ አስተማረ ፤ ገር ፡ አደረገ ። ዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ታራኅርኅ ፡ ጠባይዒከ ፡ ወታሤኒ ፡ ግዕዘከ ። ከመ ፡ ያራኅርኅ ፡ ልበ ፡ እግዚእ ። ታራኅርኅ ፡ ልበ ፡ ላዕሌየ ፡ (ፈላስ ። መቃ ። ዮሴፍ) ።

**ረጢብ** ፤ **በት** ፤ **(ረጥበ ፡ ይረጥብ ፡ ይርጠብ ። ዕብ ፡ ራጣብ ። ሱር ፡ ራጤብ ። ዐረ ፡ ረጢበ)** ፤ መርጠብ ፤ መለምለም ፤ ርጥብ ፡ ውሃማ ፡ መ

ኾን ። ርጥባን ፡ መስጠት ፤ መቀስት ፡ አደጋ ፡ ለወደቀበት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ርጡብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ጥባት) ፤ የረጠበ ፤ ርጥብ ፤ ለጋ ፤ ለምለም ፡ ውሃማ ፤ ደማም ፤ ጭቃ ። ኣየ ብስ ፡ ዕፀ ፡ ርጡበ ። አነዳ ፡ ሳሕም ፡ ርጡብ ። ዕፀመ ፡ ሥጋሁ ፡ ተረክበ ፡ ምስለ ፡ ደም ፡ ርጡብ ። መሬት ፡ ርጡብ ፡ እብን ፡ ይቡስ ። ሳብዕቱ ፡ እዴሁ ፡ ለርጡብ ፡ (ሕዝ፲፯ ፡ ፳፬ ። ሉቃ፳፫ ፡ ፴፩ ። ገድ ፡ ተክ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፮ ። ሠኢ፲፪ ። ሉቱ ፡ ዕዝ፱ ፡ ፶፱) ።

**ርጥበት** ፤ በቁሙ ፤ መርጠብ ፤ አረጣጠብ ፤ ርጥ ብነት ፤ ርጥባን ። ይቡስ ፡ ዕፀ ፡ ዘአልቦ ፡ ርጥበት ። በከመ ፡ እሳት ፡ ያየብስ ፡ ርጥበተ ፡ ዕፀ ፡ (መቃ ። ፊልክ ፡ ፺) ።

**አርጠበ** ፤ አረጠበ ፤ አስረጠበ ፤ ርጥብ ፡ አደረገ ። አረጥብ ፡ ዕፀ ፡ ይቡሰ ፡ (ሕዝ፲፯ ፡ ፳፬) ።

**ተረጥበ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ ተረጠበ ፤ ተቀሰተ ፤ ርጥባን ፡ ቀስታ ፡ አገኘ ።

**ርጢን** ፤ (ናት ። ጽር ፡ ሬቲኒ ። ዐረ ፡ ራቲን ። ሱር ፡ ሬጢኒ) ፤ ጥሩ ፡ ሙጫ ፤ ዕጣን ፤ የ ዕጣን ፡ ዐይነት ፤ ከታወቁ ፡ ዕንጨቶች ፡ የሚገኝ ። ፈውስ ፤ መድኀኒት ፤ ከሙጫ ፡ ጋራ ፡ የሚቀመም ፤ በሙጫ ፡ ወ ለላ ፡ የሚለወስ ። አልቦኑ ፡ ርጢን ፡ ውስተ ፡ ገለዓድ ። ርጢናት ፡ ልምሉማት ፡ ወጽሩያት ፡ (ኤር፰ ፡ ፳፪ ። ፊ ፡ መ ፡ ፩ ፡ ፱ ። ዘፍ፴፯ ፡ ፳፭ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፲፯) ። ባለቅ ኔዎች ፡ ግን ፡ ረጠኑ ፡ ብለው ፡ ይገሳሉ ።

**ረዪም** ፤ ሞት ፤ (ረየመ ፡ ይረይም ፡ ይ ሪም ። ትግ ፡ ሬመ ። ዕብ ፡ ራም) ፤ ልዒል ፤ ዐ ሪማ ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ማለት ፤ መርዘም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ መው ጣት ፤ ማረግ ፤ መራቅ ፡ መምጠቅ ፡ መላቅ ፡ መብለጥ ፤ በላይ ፡ መቀመጥ ፤ ላይኛ ፡ ራስ ፡ ጫፍ ፡ ቍንጮ ፡ መጨ ረሻ ፡ መኾን ፤ እንደ ፡ ጕልላት ። ለዐለን ፡ ተመልከት ፤ የ ዚህ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ነው ።

**ራማ** ፤ (ማት ። ዕብ ፡ ራማህ) ፤ ልዕልና ፡ ምጥቀት ፡ ርዝመት ። ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፤ ኢዳጋ ፡ ቍሊልታ ፤ ተራራ ፡ ኩረብታ ፤ ደርብ ፡ ሰገነት ፤ የተራራ ፡ ላይ ፡ ሜዳ ፤ ሰቀት ፡ ያለ ፡ የተንጣለለ ። ሐነጽኪ ፡ ለኪ ፡ ባማ ፡ ወገበ ርኪ ፡ ለኪ ፡ ራማ ፤ ሐነጽኪ ፡ ራማተኪ ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፳፬ ። ፴፩) ።

—፤ ስመ ፡ አህጉር ፤ በብንያምና ፡ በንፍታሌም ፡ ዕፃ ፡ ያሉ ፡ (ኢያ፲፰ ፡ ፳፭ ። ፲፱ ፡ ፳፱ ። ኤር፴፩ ፡ ፲፭ ። ማቴ ፪ ፡ ፲፰) ።

—፤ ሰማይ ፤ የሰማይ ፡ ስም ፤ በኢዮርና ፡ በኤፈር ፡ መካ ከል ፡ ያለ ፤ ከሦስቱ ፡ ዓለመ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፤ የጠፈር ፡ ሦስተኛ ። በዱኒ ፡ ሀገረክሙ ፡ ሀገረ ፡ ሣልሲት ፡ ራማ ። ፀሓየ ፡ ቅዱሳን ፡ ዘራማ ። ምሕላነ ፡ ስማዕ ፡ እም ራማ ። ጊዜ ፡ ዕርገታ ፡ ውስተ ፡ ራማ ፡ (ደራሲ ። አዋል ። ድጓ) ።

**አርያም** ፤ (ማት) ፤ የራማ ፡ ብዥ ፤ ራማት ፡ አርያም ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ አርያማት ፡ የብዙ ፡ ብዙ ። መጽ ሐፍ ፡ ግን ፡ አርያምን ፡ እንደ ፡ ራማ ፡ ላንድ ፡ ብቻ ፡ አ ድርጎ ፡ ይናገራል ።

—፤ ልዕልና ፤ ምጥቀት ፤ ላዕል ፤ መልዕልት ። ሐነጸ ፡ መ ቅደሶ ፡ በአርያም ። እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ አርያም ። ከመ ፡ ያስርር ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ዕጕሊሁ ፡ (መዝ ፡ ፸፯ ። ኢሳ፴፯ ፡ ፱ ። ዕንባ ፡ ፱) ።

—፤ ሰማይ ፤ ሰማየ ፡ ሰማያት ፤ መጨረሻ ፡ ሰማይ ። ዐረገ ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ዴዊወከ ፡ ዴዋ ። እስከ ፡ ትለብሱ ፡ ኀይለ ፡ እምአርያም ። ወለከ ፡ ንፌኑ ፡ አኰቴተ ፡ እ ስከ ፡ አርያም ። እምቅድመ ፡ ይሕንጽ ፡ አየራተ ፡ ወ አርያማተ ፡ (መዝ ፡ ፷፯ ። ሉቃ፳፬ ፡ ፵፱ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

—፤ የድጓ ፡ ቃል ፡ ትምርት ፤ ኹለተኛ ፡ ክፍል ፡ ከውዳሴ ፡ ማርያም ፡ (ስንክ ፡ ግን፲፭) ።

**አርያማዊ** ፤ ላዕላዊ ፤ ሰማያዊ ፤ ዘሰማይ ። ፀ ሓየ ፡ ጽድቅ ፡ አርያማዊ ። አርያማዊት ፡ መቅደስ ፡ (ሳታ ። ደራሲ) ።

**ረይዖ** ፤ ዖት ፤ (ረየዐ ፡ ይሬይዕ ፡ ይረ ይዕ ። ዐረ ፡ ራዐ) ፤ መገሥት ፡ መቅጣት ፤ ማስሮጥ ፡ ማስኬድ ፤ ማስተማር ፡ ማስለመድ ፤ ማቅናት ፤ ማሠል ጠን ፡ የከብት ፡ የሰው ። አኀዘ ፡ ይረይዖሙ ፡ ለሰማዕ ያን ፡ (አፈ ፡ ድ፲፪) ።

**ረያዒ** ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት) ፤ የሚገራ ፤ ገሪ ፤ ቀጭ ፡ አስተማሪ ። ረያዔ ፡ አፍራስ ፡ (አዋል) ።

**አረየዐ** ፤ **አስተረየዐ** ፤ አሰለፈ ፤ አስጠረረ ። ያስተረይዖሙ ፡ ለመስተጋድላኒሁ ፡ (አፈ ፡ ድ፴፭) ።

**ተረየዐ** ፤ ተገራ ፤ ተማረ ፤ ተሠራ ፡ ተቀጣ ፤ ለ መደ ፤ ገራም ፡ ኾነ ። ፈረስ ፡ ዘኢተረየዐ ። እልክቱ ፡ ኢተረየዑ ፡ ወኢተመከሩ ፡ ወኢያእመኑ ፡ ሠናየ ፡ እ ምነ ፡ እኩይ ። እመሰ ፡ ተረየዐ ፡ ኅሊና ፡ ልብነ ፤ በም ንትኬ ፡ ይትረየዓ ፡ ኅሊናቲነ ፡ (ሢራ፴ ፡ ፰ ። አፈ ፡ ድ፰ ። ተግ፰) ።

**ርዩዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ይዕት) ፤ የተገራ ፤ ግር ፡ ገራም ፤ ምሁር ፡ ግሡጽ ፤ ልሙድ ።

**ርያዔ** ፤ መግራት ፤ መገራት ፤ አገራር ፤ ግሬ ፤ ግ ራት ፤ ተግሣጽ ፡ ትምርት ፤ ቅጣት ።

**ሬስ** ፤ (ዕብ ፡ ሬሽ) ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ዕሥ ራዊ ። ርእስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፵፫) ። ባማ ርኛ ፡ ግን ፡ ሬሶ ፡ ሬሳ ፡ ማለት ፡ ነው ። የሙት ፡ ዘር ፡ ቢሉ ፡ ወልደ ፡ ሬስ ፡ እንዲሉ ።

**ርኰ** ፤ ንጉሠ ፡ አዕዋፍ ። ……መሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ዖፍ ፡ ዘይሰመይ ፡ ርኵ ፡ በሀገረ ፡ ሲን ፤ ውሳጣይ ፤ ተ ብህለ ፡ ከመ ፡ ሶበ ፡ ይሰርር ፡ ይከድና ፡ ለሀገር ፡ በክ ነፊሁ ፡ ወይወርድ ፡ ዲበ ፡ ዕጓለ ፡ ነግያት ፡ ይመሥጥ ፡ ወያበልዖሙ ፡ ለውሉዱ ። ወይቤ ፡ አሐዱ ፡ ነጋዲ ፡ ርኢኩ ፡ በአሐዱ ፡ ደሴት ፡ እምደሰያተ ፡ ሲን ፡ ክል

ሌቱ ፡ አንቀቅሖ ፡ ከመ ፡ ክልኤቱ ፡ ደባትር ፡ ዐበይት ፡ ዘውእቱ ፡ አንቀቅሖ ፡ ዘርዝ ፡ (ጊ ፡ ወ ፡ ሐ ፡ ገ፴፭) ።

**ረኪብ ፡ በት ፤ (ረክበ ፤ ረከበ ፡ ይረክብ ፡ ይርከብ ። ዕብ ፡ ራክብ ። ሱር ፡ ርኪብ ። ዐረ ፡ ረኪበ)** ፤ መስረር ፡ ወደ ፡ ከብት ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ባቡርና ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ መውጣት ፤ መጫን ፡ መቀመጥ ፤ ተቀምጦ ፡ መኼድ ። መዝለል ፡ መከመር ፡ ፊጥ ፡ ማለት ፤ በላይ ፡ መኾን ፤ መታዘል ፤ ማግኘት ፡ መድረስ ፤ መንካት ፡ መያዝ ፡ መዳሰስ ፤ የወንድና ፡ የሴት ፡ የገንዘብ ፤ ለሌላም ፡ ይኾናል ። ጎሠሥክዎ ፡ ወኢረከብክዎ ። ደቂቆሙ ፡ ኢይረክቡ ፡ ንዋዮሙ ። ንሣእ ፡ ዘይረክበከ ። ለዘረከቦ ፡ ይርከቦ ። ረኪበ ፡ መድፍን ። ረከብዎ ፡ ውዱቀ ። ከመ ፡ ዝ ፡ ረከብኩ ፡ ጽሑፈ ፡ ውስተ ፡ መጻሕፍት ፡ (ማሕሮ ፡ ፪ ። ኢዮ፴፭ ፡ ፲፱ ። ማቴ፳ ፡ ፲፱ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፳፱ ። ሢራ፵ ፡ ፲፰ ። ሄኖ ፡ ፭ ፡ ፪ ። ኩፋ ፡ ፳፭) ። ረከብናሆሙ ፡ ይሰክቡ ፡ ጎቡረ ። ረከብናሃ ፡ በዝሙት ፤ ያዝ ፡ (ዳን፩ ፡ ፴፰ ። ዮሐ፰ ፡ ፬) ።

**ረካቢ ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት)** ፤ የሚስር ፤ ሰራሪ ፡ የሚያገኝ ፡ አግኚ ። ረካቢሆን ፡ ለኄራት ፡ (ምሳ ፲፯ ፡ ፰) ።

**ርክብ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፤ የኮርቻ ፡ ክንፍ ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ መውጫ ፡ መቈናጠጫ ፤ መረጋገጫ ። (ግጥም) ፤ ርካቡ ፡ ምን ፡ አለኝ ፡ ወይስ ፡ ዘለበቱ ፤ እኔን ፡ የገደለኝ ፡ ቅናቱ ፡ ቅናቱ ።

**ራኩብት ፤ (ባት ። ዐረ ፡ ረኩበት)** ፤ የግመል ፡ ወሳብሬ ፤ ባዝራ ፤ ድንጕላ ፤ ሯጭ ፡ ጋላቢ ። ራኩብ ፡ ባን ፡ የወንድ ፤ ት ፡ የሴት ። ዐይው ፡ እሰ ፤ ይጼሁ ፡ ራኩባት ፡ (ሄኖ ፡ ፴ ፡ ፲፪) ።

**መርከብ ፤ (ብ ፡ መራክብ ። ዐረ ፡ መርከብ ። ሱር ፡ ማርከብታ)** ፤ በቁሙ ፤ ሐመር ፤ የባሕር ፡ ባቡር ።

**መርከብ ፡ (ዕብ ፡ ሜርከብ)** ፤ ሠረገላ ፤ ፈረስ ፡ የሚያሮጠው ፤ ሰው ፡ የሚቀመጠው ።

**መራክብት ፤ (ዕብ ፡ ታኒም)** ፤ አክይስት ፤ ግሩማን ፡ አራዊት ፡ የሚሰሩ ፡ የሚወረወሩ ፡ (ኢሳ፲፫ ፡ ፳፪) ።

**አርከበ** ፤ መጫን ፤ አስጫነ ፤ አስቀመጠ ፤ አፈናጠጠ ። አስገኘ ፡ አስረከበ ፤ ሰጠ ፤ አስጨበጠ ። ትሕትና ፡ ዘምስለ ፡ ተዐግሦት ፡ ታረክብ ፡ ንጻርያተ ። ብዝኀ ፡ ስታይ ፡ ኢያረክብ ፡ ኀይለ ፡ ወኢያንጥእ ፡ ቍስለ ። ታረክቦሙ ፡ ሕይወተ ፡ (ማር፩ ፡ ፳ ። ሢራ፴፱ ፡ ፴ ። ሂርማ) ።

**ተረክበ** ፤ ተረከበ ፤ ተቀበለ ። ተገኘ ፤ ተያዘ ፤ ተመረመረ ። እምአይቴ ፡ ተረክበት ፡ ጥበብ ። ብእሲት ፡ እንተ ፡ ተረክበት ፡ በዝሙት ። ለእመ ፡ ተረክበ ፡ ካህን ፡ በሰሪቅ ። ስዉር ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይረክብዎ ፡ በኀሢና ፡ (ኢዮ፳፰ ፡ ፲፪ ። ዮሐ፰ ፡ ፫ ። ቄድር ። ቅዳ ፡ ኤጲ) ። ዘ ፡ ዘሎ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ተረክበ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወተረክበ ፡ ለሰሎሞን ፡ አርባዕቱ ፡ ምእት ፡ አፍራስ ፡ (፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፳፭) ።

**ተራከበ** ፤ ተረካከበ ፡ ተገናኘ ፤ ተጋጠመ ፤ ተላሳመ ፤ አንድ ፡ ኾነ ። ባዕል ፡ ወነዳይ ፡ ይትራከቡ ፡ ኅቡረ ። ተራከቡ ፡ በቀትል ። ጊዜ ፡ ተራከቦቱ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ። ወይትራከብ ፡ ቃላቲሆሙ ፡ ምስለ ፡ ጽራሕ ፡ ብካየ ፡ ጸላኢት ፡ (ምሳ፳፪ ፡ ፪ ። ፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፭ ፡ ፪ ። ጥበ፲፰ ፡ ፲) ።

**ርኩብ ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ክብት)** ፤ የተገኘ ፤ የተፈጠረ ፤ የተገናኘ ፤ ማኅኑ ፤ ኅብብር ። ዮም ፡ ርኩብ ፡ መስቀል ። ወክነፊሆሙ ፡ ስፉሓን ፡ ወርኩባን ፤ እኁዛት ፡ ወርኩባት ፡ (ድጓ ። ፪ዜና ፡ ፫ ፡ ፲፫ ። ሄኖ ፡ ፺ ፡ ፴፭) ። በርኩብ ፡ ፈንታ ፡ ርኩባዊ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ግዕዛት ፡ ርኩባውያት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፲፪) ።

**ርክበት ፤ (ታት)** ፤ ማግኘት ፡ መገኘት ፤ አገኛኘት ፤ ባሕርያዊ ፡ ሀብት ፡ ዕድል ። ርክበተ ፡ ንዋይ ። ርክበተ ፡ ወልዶሙ ። ርክበተ ፡ አዕፀምት ። ዘእስተ ፋጠነ ፡ ፈውሶተ ፡ ሕማሙ ፡ እምቅድመ ፡ ይስአን ፡ ርክበታተ ፡ መድኀኒታቲሁ ። ኀሊናቲሁ ፡ ወኀይላቲሁ ፡ ወርክበታቲሁ ፡ ዘውስጥ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፪ ፡ ፳ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፱ ። ጥር፲፱ ። ግንቦ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፳) ።

**ረክብ** ፤ ማግኛ ፡ መገኛ ፤ መገናኛ ፡ ቀን ፤ በዓል ፤ የትንሣኤ ፡ ፳፭ኛ ፤ የበዓለ ፡ ኀምሳ ፡ እኩሌታ ፡ ረቡ ፡ የሚውል ። ዋዜማ ፡ ዘረክበ ፡ ካህናት ፡ (ድጓ ። ዮሐ፳፩ ፡ ፲፬) ።

**ሩካቤ** ፤ በቁሙ ፤ መገናኘት ፤ ግንኝት ። ሩካቤ ፡ ዘበሕግ ። ሩካቤ ፡ ርስሐት ። ለእመ ፡ ረስሐ ፡ በሩካቤ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ። ቀሌ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ። ጥበ፯ ፡ ፪ ። ዲድ ፡ ፴፭) ።

**ምርካብ ፤ (ባት)** ፤ ማግኛ ፡ መገኛ ፤ ማስገኛ ፡ ቦታ ። ደመ ፡ ወገዝ ፤ ምንጻ ፤ የሙያ ፤ የጕልበት ፡ ዋጋ ፤ ጥቅም ፤ ትርፍ ፤ በሥራ ፡ የሚገኝ ። ዘኢ ፡ የሐርስ ፡ እንዘ ፡ ይቤሎ ፡ ምርካቦ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ። ግብ፲፱ ፡ ፳፭) ።

—፤ ሐሳብ ፤ ጥበብ ፤ ነገር ፤ ምስጢር ፤ ክልብ ፡ የሚገኝ ። ምርካብ ፡ ዘልብ ፡ ውፁእ ፡ (ቁር ፡ ጸላ) ።

**አስተርከበ ፤ (የአርከበ ፡ ድርብ)** ፤ አቀረበ ፤ አስነካ ። ወአስተርከቡ ፡ ወዐጻፉ ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ (ዮሐ፲፱ ፡ ፳፱) ።

—፤ ቀወ ፤ ገዛም ፡ አሰ ፤ ልብ ፡ አደረገ ፤ ነቃ ፡ ተጋ ፡ ተዘጋጀ ። አስተርክቡ ፡ ወአእምሩ ። ዘኢያስተረክቡ ፡ ተርጕሞተ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ። መፍትው ፡ ለነ ፡ ንጻሙ ፡ ወናስተብቍዕ ፡ ወናስተርክብ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ። ያስተርክብ ፡ ለጸሎት ። አስተርክቦት ፡ በጸሎት ። እመሰ ፡ ፈቀደ ፡ ሰብእ ፡ አስተርኪቦ ፡ ይትዋካሕ ፡ ምስሌሆሙ ፡ (መገ ፡ ፵፳ ። ቀሌ ። ግንዘ ። ኪዳ ። ቁር) ። በረከበ ፡ ፈንታ ፡ አስተርከበ ፡ ይላል ። ዳግመኛም ፡ ዕሩቀ ፡ ወኮስቱረ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ያስተረክብ ፡ ይላል ፤ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ። እስመ ፡ ኢያስተርከቡ ። ወመ

ጺሖ ፡ ይረክቦ ፡ እንዘ ፡ ያስተረክብ ፡ እዳወ ፡ (ማርቖ ፡ ፲፬ ፡፡ ማቴ፲፪ ፡ ፵፬ ፡፡ ሉቃ፲፩ ፡ ፳፭) ፡፡

**እስትርኩብ** ፤ ዝግጁ ፤ የነቃ ፤ የተጋ ፡ ትጉህ ፤ ለሥራ ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚገኝ ፡፡ ጳጳስ ፡ ይኩን ፡ እስትርኩብ ፡ ለምሥዋዕ ፡ ወለጸሎት ፡፡ ወውእቱ ፡ እስትርኩብ ፡ በጸሎት ፡ ወጾም ፡ (ኪዳ ፡ ቄድር) ፡፡

**እስተራከበ** ፤ አራከበ ፤ አጋባ ፡ የተክል ፡፡ አገናኘ ፡ አጋጠመ ፤ ሰበሰበ ፡፡ ወአስተራከቦ ፡ ምስለ ፡ ውሉዱ ፡፡ ኅበ ፡ ያስተራክቡ ፡ ክነፊሆሙ ፡፡ ወአስተራክብ ፡ ዘሎ ፡ ተዓይኑ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፲፱ ፡፡ ፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፳፪ ፡፡ ዘሌዋ ፡ ፫) ፡፡

**ርኅም** ፤ (ዐረ ፡ ሩኅም) ፤ እብን ፡ በረድ ፤ ነጭ ፡ ደንጊያ ፡፡ ንፍቀ ፡ ርኅም ፡፡ ዳሕል ፡ ዘእብነ ፡ ርኅም ፡፡ ምድሩ ፡ ለቀውድስ ፡ ከነ ፡ ርኅመ ፡ ወደመ ፡ ቅቱላን ፡ ይረግዕ ፡ ላዕለ ፡ ርኅም ፡ ወኢይየብስ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲፯ ፡፡ መስ፲ ፡፡ ዮሴፍ) ፡፡

**ርኩም** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፤ ቀቀኖን ፡ ቀመልከት ፡፡

**ረኵስ** ፤ ሰት ፤ (ረኵሰ ፡ ይረኵስ ፡ ይርኰስ ፡፡ ዕብ ፡ ራካሽ ፤ ግዛ ፡ ሰበሰበ) ፤ መርከስ ፤ መዋረድ ፤ ርካሽ ፤ ረኪስ ፡ መኸን ፤ የዋጋ ፡፡ ማደፍ ፤ መጕደፍ ፤ መኰለፍለፍ ፤ መጥፋት ፡ መበላሸት ፤ ነውረኛ ፤ መኾን ፡፡ መቅደስየ ፡ ረኵሰ ፡፡ ዘኢይበሊ ፡ ወዘኢይረኵስ ፡፡ ይረኵሳ ፡ አንስት ፡ (ሕዝ፳፫ ፡ ፫ ፡፡ ፩ዼጥ ፡ ፩ ፡ ፬ ፡፡ ዘካ፲፬ ፡ ፪) ፡፡

**ርኩስ** ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ኵስት) ፤ በቁሙ ፡ ያደፈ ፤ የጐደፈ ፤ የተንቀፈ ፤ የተዋረደ ፡ የተናቀ ፡፡ ርኩስ ፡ ከናፍርየ ፡፡ ኢቦአ ፡ ርኩስ ፡ ውስተ ፡ አፉየ ፡፡ መፀትኒ ፡ ወቍጥዓ ፡ ርኩሳን ፡ እሙንቱ ፡፡ መዋዕል ፡ ርኩሳት ፡ (ኢሳ፮ ፡ ፭ ፡፡ ግብ፲ ፡ ፲፬ ፡፡ ሚራ፳፮ ፡ ፴ ፡፡ ኩፋ ፡ ፯) ፡፡

**ርኵሰት** ፤ መርከስ ፡ አረካከስ ፡ ርኩስነት ፡፡ ርኵሰተ ፡ ዋሊጦስ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ፡፡

**ርኵስና** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡፡ በሑረተ ፡ አሕዛብ ፡ ሖሩ ፡ ወበርኵስና ፡ አረሚ ፡ ነበሩ ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲፭ ፡፡ መጋ፭) ፡፡

**ርኵስ** ፤ እድፍ ፤ ጕድፍ ፤ ርስሐት ፤ ኀጢአት ፡ ኀሲስ ፡ ምጤት ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፤ ነውር ፡ ገመና ፤ ርክስና ፡፡ ትነጽሑ ፡ እምርኵስክሙ ፡፡ ጽዋዐ ፡ ወርቅ ፡ ዘምሉእ ፡ ርኵሰ ፡፡ እስመ ፡ ኢጸውዐነ ፡ እግዚ ፡ ለርኵስ ፡ (ሕዝ፴፮ ፡ ፳፭ ፡፡ ራእ፲፯ ፡ ፬ ፡፡ ፩ተሰ ፡ ፬ ፡ ፯) ፡፡

**አርኰሰ** ፤ አረከሰ ፤ አስረከሰ ፤ አሳደፈ ፤ ሰደበ ፡ ነቀፈ ፤ ርኩስ ፡ አለ ፤ አሰኘ ፤ አሰደበ ፡ አስነቀፈ ፤ ሻረ ፡ አነወረ ፡ አስነወረ ፡፡ አርኰስከ ፡ ለውእቱ ፡ ምስካብ ፡፡ ኢታርኵሱ ፡ ርእሰክሙ ፡ በዝንቱ ፡ ኵሉ ፡፡ አርኰስክሙ ፡ ስምየ ፡፡ አርኰሱ ፡ ሰንበታትየ ፡፡ አርኰሱ ፡ ድንግለ ፡ (ዘፍ፵፱ ፡ ፬ ፡፡ ዘሌ፲፰ ፡ ፳፬ ፡፡ ሚል፩ ፡ ፯ ፡፡ ሕዝ፳ ፡ ፲፫ ፡፡ ዮዲ፱ ፡ ፪) ፡፡ በአርኰሰ ፡ ፈንታ ፡ አስተራኰሰ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡፡ ያስተራኵስዎ ፡ አሕዛብ ፡፡ ዘእግዚ ፡ አንጽሐ ፡ አንተ ፡ ኢታስተራኵስ ፡፡ ዘተከልአ ፡ እምተዋስቦ ፡ እንዘ ፡ ያስተራኵስ ፡፡ ብእሲት ፡ ዘአስተራኩበት ፡ ምታ ፡ ወከልአቶ ፡ ለኪበ ፡ ምስሌሃ ፡ ኀልያ ፡ ከመ ፡ ርኩስ ፡ ውእቱ ፡ ግብረ ፡ ተዋስቦ ፡ (ኢሳ፶፱ ፡ ፯ ፡፡ ግብ፲ ፡ ፲፭ ፡፡ ፈ ፡ መ ፡ ፬ ፡ ፩፭ ፡ ፩) ፡፡

**ተራኰሰ** ፤ ተራከሰ ፤ ተረካከሰ ፤ ተዳደፈ ፡፡ ይትራኰሱ ፡ ወይዜምዉ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፯) ፡፡

**አስተራኰሰ** ፤ አራከሰ ፤ አረካከሰ ፤ አስተዳደፈ ፡፡ ዐማርኛው ፡ አድራጊ ፡ ይመስላል ፡፡

**ራማ** ፤—ሰማይ ፤—ረየመ ፡፡

**ረሚሕ** ፤ ሖት ፤ (ረምሐ ፡ ይረምሕ ፡ ይርማሕ ፡፡ ዐረ ፡ ረመሐ) ፤ መውጋት ፡ መብሳት ፡ መቅደድ ፤ መዘርከት ፡፡

**ረምሕ** ፤ (ዕብ ፡ ሮማሕ ፡፡ ሱር ፡ ሩምሐ ፡፡ ዐረ ፡ ሩምሕ) ፤ ሠላጢን ፤ ዘገር ፤ አበታ ፡ ጦር ፡፡ ነሥአ ፡ ረምሐ ፡ በእዴሁ ፡ ወረገዞሙ ፡ ለክልኤሆሙ ፡፡ ረምሐ ፡ ዘይረግዝ ፡፡ ለረጊዘ ፡ አርዌ ፡ በረምሕ ፡፡ በረምሐ ፡ መስቀሉ ፡ ረጊዘ ፡ ሰይጣነ ፡ (ዘኍ፳፭ ፡ ፯ ፡፡ ኩፋ ፡ ፴፯ ፡፡ ደራሲ) ፡፡

**አርማሕ** ፤ (ሖት) ፤ ዘገሮች ፡ ሠላጢኖች ፡፡ እለ ፡ አርማሕ ፡ (፩ዜና ፡ ፲፪ ፡ ፳፬) ፡፡

**አርማሕ** ፤ የሰው ፡ ስም ፡ ጦረኛ ፡ ሐርበኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፤ በመሐመድ ፡ ዘመን ፡ የነበረ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ፡፡

**ረምሓይ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ የነበረ ፡ ንጉሥ ፤ የሰይፋይ ፡ ልጅ ፡፡ ሰይፋይ ፡ ወረምሓይ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ፡፡

**ረምይ** ፤ ዮት ፤ (ረመየ ፡ ይረሚ ፡ ይርሚ ፡፡ ዐረ ፡ ረመይ ፡፡ ዕብ ፡ ራማህ ፡፡ ሱር ፡ ርማእ) ፤ መጣል ፤ መወርወር ፤ ማሽቀንጠር ፡፡ መውጋት ፤ መምታት ፤ ማቍሰል ፡፡ ረመየ ፡ ሥዕሎ ፤ ወጋ ፡ (ስንክ ፡ የካ፳፭) ፡፡

**ረማዩ** ፤ (ዩት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ መይት) ፤ የሚጥል ፤ ጣይ ፡ ወርዋሪ ፤ ወጊ ፡ ቀንካሪ ፡፡

**ተረምየ** ፤ ተጣለ ፤ ተወጋ ፤ ቈሰለ ፡፡ መሰክት ፡ ተቀሥፈ ፡ ወኢሐመ ፤ ተቀነወ ፡ ወኢተሰቍረ ፤ ተረግዘ ፡ ወኢተረምየ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ፡፡

**ርሙይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሚት ፤ ምይት) ፤ የተጣለ ፤ የቈሰለ ፤ የተወጋ ፡ ውጋ ፡፡

**ርምየት** ፤ (ታት) ፤ መጣል ፤ መውጋት ፡ ማቍሰል ፤ መወጋት ፡ መቍሰል ፡፡ ውጋታት ፡ ስንበር ፡ ቍስል ፤ ዕበጥ ፡ ዕትራት ፡፡ ገሢሶ ፡ ገቦ ፡ ሥጋሁ ፡ ወርምየተ ፡ ስቍረተ ፡ ቅንዋቲሁ ፡፡ አርእየኒ ፡ ርምየታቲከ ፡፡ ከመ ፡ ርምየት ፡ (ቄር ፡፡ ፊልክ ፡ ፻፶፰ ፡፡ ዘሌ፲፫ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫) ፡፡

**ሮምያ** ፤—ያግር ፡ ስም ፤—ረወመ ፡፡

**ረምል ፤ (ዐረብ ። ዕብ ፡ ሐል) ፤** አሸዋ ፤ ጠጠር ፤ የወንዝ ፡ ደንጊያ ፤ ኰረት ።

**ረመለ ፤** አሸዋ ፡ ዘገን ፤ ጠንቈለ ፤ ባሸዋ ፡ አሟረተ ፤ ጠጠር ፡ ጣለ ።

**መርመሌ ፤ (ዕብ ፡ ታርሚል ። ሱር ፡ ታርማላ) ፤** መዝተኛ ፤ ፈኛ ፡ ከረጢት ፤ ቈርባብኛ ፤ ኩረኛ ፤ ቀሥናማት ፤ ከሩዱ ። መምጠቅን ፡ ተመልክቶ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። በመርመሌ ፡ ፈንታ ፡ መርመሬ ፡ ይባል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ኀምስተ ፡ አእባን ፡ ልሙጻተ ፡ ወክቡባተ ፡ ጸዊሮ ፡ በመርመሬ ፤ እስመ ፡ ዘክርስቶስ ፡ መርመሬ ፡ እንተ ፡ በምድር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ ወባቲ ፡ አእባን ፡ ክቡራት ፡ (ተረ ፡ ቄርሎ) ።

**ረሚም ፤ ሞት ፤ (ረመ ፤ ረመመ ፡ ይረምም ፡ ይርምም ። ዐረ ፡ ረመ ፤ ጠባ ፡ መጠጠ ። ዕብ ፡ ራማም ፤ ረገጠ ፡ አለፋ ፡ ዠለጠ) ፤** መራመም ፤ መፈግፈግ ፤ መዳመጥ ፡ ማጥራት ፤ በደንጊያ ፡ መፈተግ ፤ የብራና ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ጻፈ ፡ ይሉታል ።

**—፤** መርመም ፤ ዝም ፡ ጸጥ ፡ ረጋ ፡ ማለት ፤ አፍን ፡ ከንፈርን ፡ መግጠም ፡ መዝጋት ፤ ከሁከት ፡ ከነገር ፡ ማረፍ ። ጡት ፡ የጕረሠ ፡ ከመጥባት ፡ በቀር ፡ መናገር ፡ እንዳይችል ፡ እንደዚህ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በረመመ ፡ ፈንታ ፡ አርመመ ፡ አስተራመመ ፡ ይላል ፤ እያለኝም ። ባዕል ፡ ለእመ ፡ ነበበ ፡ ኵሉ ፡ ያረምም ። እንበለ ፡ አርምሞትኪ ። ኵሳ ፡ ምድር ፡ ትነብር ፡ ወታረምም ። አርመመ ፡ ባሕር ። አርመመ ፡ ኵሉ ፡ ዘበሰማይ ። እንዘ ፡ ይሴብሖ ፡ ሕፃን ፡ ለእግዚ ፡ መኑ ፡ ያስተራምም ፡ (ሚራጅ፫ ፡ ኳ፫ ። ማሕ፩ ፡ ፩ ። ዘካ፬ ፡ ፲፩ ። የናጸ ፡ ፲፫ ። ራእ፰ ፡ ፩ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**አርመመ ፤ (አስደረገ) ፤** አስረመመ ፤ አስረመመ ፤ ዝም ፡ አሰኘ ፤ ጸጥ ፡ አደረገ ፤ አፍ ፡ አሲያዘ ፤ ዕሻ ፡ ዝም ፡ በሉ ፡ አለ ፤ ዝምታ ፡ አስተማረ ። አርመሞሙ ፡ ለሰብእ ። አርምም ፡ አፉከ ። አ ፡ አፍ ፡ አመ ፡ ያረምመኪ ፡ ሞት ፡ እፎ ፡ ትከውኒ ። ያርምም ፡ ልሳዎ ፡ እምእኪት ። አንተ ፡ ትኴንን ፡ ኀይለ ፡ ባሕር ፡ ወታረምሞ ፡ ሲድምፀ ፡ ማዕበሉ ፡ (ዮሴፍ ። ሚራ፴፭ ፡ ፯ ። ግንዘ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲ ። መዝ ፡ ፹፰) ። በአርመመ ፡ ፈንታ ፡ አስተራመመ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወሌዋውያን ፡ ያስተራምሙ ። አስተራመመ ፡ ሁከታ ፡ ለነፍስ ። ባሕረ ፡ እምነ ፡ ተሀውኮ ፡ አስተራመመ ። ወናስተራምሞ ፡ ለዝሉፉ ፡ (ነሐ፰ ፡ ፲፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ሣ፫ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፯ ። አፈ ፡ ተ፳) ።

**አርማሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤** ዝም ፡ የሚያሰኝ ፤ አፍ ፡ የሚያሲዝ ። ዝም ፡ የሚል ፤ ዝም ፡ ባይ ፤ ዝምተኛ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሚዛን ፤ ዳኛ ፡ ብለው ፡ ይጨምሩበታል ። ካሕደ ፡ የነድግ ፡ አርማሚ ። እንዘ ፡ ተናጋሪ ፡ አርማሚ ። ብእሲት ፡ አርማሚት ፡ ወዐቃቢት ፡ ልሳን ፡ (ምሳ፲፰ ፡ ፲፫ ። ፊልክ ፡ ፶፭ ። ፈላስ) ።

**መርምም ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ። መርምመ ፡ ልሳን ፡ እምጽዋዔክሙ ። እስመ ፡ ጸላእትነ ፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡ ልሳነነ ፡ መርምመ ፡ እምእኪይ ፡ (ግንዘ) ።

**መስተራምም ፤ (አርማሚ ፡ መርምም) ፤** ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፡ ዝም ፡ የሚያሰኝ ። ዘመስተራምም ፡ በእንቲኣሁ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ሣ፫ ፡ ፳) ።

**መርመም ፤ (ብ ፡ መራምም) ፤** መራመሚያ ፤ ዐይናማ ፡ ደንጊያ ።

**አርምሞ ፤** ዝም ፡ ማሰኘት ፤ ዝም ፡ ማለት ። ዝምታ ፤ ዕረፍት ፤ ህድአት ። በአርምሞ ፡ ወበተሐክሞ ። ተናግሮ ፡ ብሩር ፡ ውእቱ ፡ አርምሞሰ ፡ ወርቅ ፡ ይእቲ ፡ (ምሳ፲፯ ፡ ፳፰ ። ፈላስ) ።

**ተረመ ፤** ተራመመ ፤ ብራናው ። ዝም ፡ ተባለ ፤ የዝም ፡ ብሎ ፡ ኸነ ፤ ተረሳ ፡ ቀረ ፤ ተደበቀ ፤ በምበጢርነት ። ኢይትረመም ፡ ስምዩ ፡ ወስምከ ፡ በታሕተ ፡ ሰማይ ። ትትረመም ፡ መሰኮቱ ፡ (ክፉ ፡ ፳፩ ። ቄር) ።

**ርሙም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ምምት) ፤** ዝም ፡ ያለ ፡ ዝምተኛ ፤ ሀዱእ ። እግዚአብሔር ፡ ርሙም ፡ በዑቃቤ ፡ ወኢመስተበቅል ፡ በይዋሂ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተራመመ ፤** ዝም ፡ ተባባለ ፤ ተፋዘዘ ። (ተረቅ) ፤ ሰጤም ፡ ዝም ፡ መጣፉም ፡ ዝም ።

**አስተራመመ ፤ (አደራራገ) ፤** ዝም ፡ አሰኘኘ ፤ ገላገለ ፤ እንዳይባባል ፡ አደረገ ።

**ሮማን ፤—በቁሙ ፤—ረወማን ።**

**ራምኖን ፤ (ጽር ፡ ራምኖስ) ፤** እሾኽም ፡ ዕንጨት ፤ ፍሬ ፡ ቢሰ ፤ ፍሬው ፡ የማይበላ ፤ ቅጠሉ ፡ የማያጠግብ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ይግ ፡ ይሉታል ። ዕፀ ፡ ራምኖን ፡ (መሳ፱ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭) ።

**ረሚፅ ፤ ፆት ፤ (ረመፀ ፡ ይረምፅ ፡ ይርምፅ ። ዐረ ፡ ረሚፀ ። ዕብ ፡ ራማጽ) ፤** መረመጥ ፤ መሸጐጥ ፤ ከፍሕም ፡ ውስጥ ፡ ማግባት ፤ ማዳፈን ፡ መቅበር ፤ ብርሾታ ፡ መጋገር ፤ መጥበስ ፡ መተኰስ ፤ መለብለብ ፡ ማቃጠል ፤ መወዘት ። ይረምፁ ፡ በእሳት ፡ (መ ፡ ፈ) ። በረመፀ ፡ ፈንታ ፡ አርመፀ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ታረምፆ ፡ ለሥጋነ ፡ (ያዕ፫ ፡ ፮) ።

**ረመፅ ፤ (ዕብ ፡ ሬሜጽ) ፤** በቁሙ ፤ ረመጥ ፤ ደቃቅ ፡ ፍሕም ፤ ትኵስ ፡ ሐመድ ፡ (መ ፡ ፈ) ።

**ረምፅ ፤** ርሚጦ ፤ ብርሾታ ፤ ጥብስ ፤ በፍሕም ፡ የሞቀ ፡ የበሰለ ።

**ረሚስ ፤ ሶት ፤ (ረምሰ ፡ ይረምስ ፡ ይርመስ ። ዕብ ፡ ራማስ ፤ ረገጠ ። ራማሽ ፤ ኼደ) ፤** መረመስ ፤ መወሸቅ ፤ መንከር ፡ መዝፈቅ ፤ መዘፍዘፍ ፤ ከውሃ ፡ ከጭቃ ፡ ከርጥብ ፡ ነገር ፡ ማግባት ፤ ማቡካት ፤ መለወስ ፤ የደቄት ። ማርመስመስ ፤ መርመስመስ ፤ የተሐዋስያን ፡ የእጅና ፡ የእግር ።

**ረምስ ፤ (ዐረ ፡ ረመሰ ። ዕብ ፡ ዶብራ ፤ ራፍሶዳ) ፤** የዕታ ፡ መርከብ ፡ ታንኳ ፤ በስተሳይ ፡ ጥግ ፡ ከሰላ ፡ የሌለው ፡ ዝርግ ፤ እንዳውድማ ፡ ያለ ።

**ረምስ** ፤ (ዕብ ፡ ሬሜሽ) ፤ እሙኃት ፤ ታናናሽ ፡ ተርመስማሽ ፡ የየብስና ፡ የባሕር ፡ ፍጥረት ።

**አርማስ** ፤ ታንኮች ፡ የዕቃ ፡ መርከቦች ፤ (አሙኃቶች) ። ናመጽአሙ ፡ ወንገብሮሙ ፡ ከመ ፡ አርማስ ፡ እንተ ፡ ባሕር ፡ (፪ዜና ፡ ፪ ፡ ፲፮ ። ፫ነገ ፡ ፭ ፡ ፱ ። ጥበ፲፱ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ መስ፲፰) ።

—፤ መጽሐፍ ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ውስጠ ፡ ብዙኅት ፡ ያለው ፤ ትርጓሜው ፡ የጉላ ፡ የተገለጠ ፤ ዕፍኝ ፡ ሽፍኝ ፡ ያድያደለ ። ይቤ ፡ በውስተ ፡ መጽሐፉ ፡ ዘሰመዮ ፡ አርማስ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**አርመስመሰ** ፤ (ረምሰ ። ዕብ ፡ ራማሽ) ፤ አርመስመሰ ፤ ተርመስመሰ ፤ በጅና ፡ በግሩ ፤ ምስጢሩ ፡ ሐዊርና ፡ ኅሚሦ ፡ ገሰ.ሰ ፡ ናቸው ፤ ከረሚስና ፡ ከመሬስ ፡ ከኹለቱ ፡ ዘር ፡ ተደቅሏል ። ወእንዘ ፡ ታርመሰምስ ፡ ጽዮን ፡ ብእሲት ፡ ኅባል ፤ ሰበረቶ ፡ ለአጽሎን ፡ ጻሕል ፡ (ቅኔ ። ሲኖዶ) ።

**ራምሴ** ፤ (ጽር ፡ ራሚሲ ። ዕብ ፡ ራዕምሴስ) ፤ ስሙ ፡ ሀገር ፤ ዮሴፍ ፡ በፈርዖን ፡ ትእዛዝ ፡ ላባቱና ፡ ለወንድሞቹ ፡ የሰጣቸው ፡ (ዘፍ፵፯ ፡ ፲፩) ። የፈረስ ፡ ጋማ ፡ ወይም ፡ ያንገቱ ፡ ጌጥ ፤ ከኩቴው ፡ ጋሬ ፡ ቃላቅ ፡ ድምጥ ፡ የሚሰጥ ፤ በተገናኝ ፡ ሬዓመ ፡ ፈረስ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ማሽከከቱንም ፡ ያሳያል ፤ ረዐመን ፡ እዩ ።

**ረምሰሰ** ፤—ዳሰሰ ፡ ዳበሰ ፤—መርሰሰ ።

**ረሚእ** ፤ አት ፤ (ረሥአ ፡ ይረሥእ ፡ ይርሣእ ። ዕብ ፡ ራዛህ ። ዐረ ፡ ረዘሐ ፤ ደከመ) ፤ ማርጀት ፤ መሸምገል ፤ መሸበት ፤ መድከም ፡ መታከት ፤ ማነስ ፡ መኰስስ ። አረገንና ፡ ልህቀን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ኅሮች ፡ ናቸው ። ሰረሚእ ፡ ፍጡነ ። ወርዘውኩኒ ፡ ወረሣእኩ ። እስከ ፡ እልህቅ ፡ ወእረሥእ ። ፈድፋደ ፡ ረሥአ ። ዘይረሥእ ፡ እምአቡከ ። እመ ፡ ረሥአ ፡ ሥርዉ ፡ በምድር ፡ (ኩፋ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፸፩ና ፡ ፲፰ ። ጦቢ ፲፬ ፡ ፫ ። ኢዮ፲፬ ፡ ፲ ። ፲፬ ፡ ፳) ።

**ርሡእ** ፤ (አን ፡ አት ፡ ሥእት) ፤ ያረጀ ፤ የሸመገለ ፤ አሮጌ ፤ ሽማግሌ ፤ ሽበታም ፡ (ዘፀ፫ ፡ ፲፮) ።

**ርሥአት** ፤ ማርጀት ፡ መሸምገል ። እርግና ፤ ሽምግልና ። አብርሃም ፡ ወሰደ ፡ በርሥአቱ ። ኢታስተአክዮ ፡ ለሰብእ ፡ በርሥአቱ ፡ (ዘፍ፳፭ ፡ ፰ ፡ ፯ ። ሢራ፰ ፡ ፯) ።

**ርሥእ** ፤ እርግና ፤ ሽምግልና ፤ ሽበት ። በርሥእ ፡ ሠናይ ። መዋዕለ ፡ ርሥእየ ። ማሕፀነ ፡ ርሥእ ። ርሥእ ፡ ወደዌ ፡ (ዘፍ፲፭ ፡ ፲፭ ። መዝ ፡ ፸ ። ሉቃ ፡ ዕዝ፫ ፡ ፳፯ ። ፊልክ ፡ ፶፪) ።

**ርሥአን** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ጹር ፡ ርሥአኒሁ ፡ ለአቡከ ። እምድኅረ ፡ ርሥአኑ ፡ ወድከመቱ ። ታወርዱ ፡ ርሥአንየ ፡ በሐዘን ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ (ሢራ፫ ፡ ፲፪ ። ፊልክ ፡ ፶፪ ። ዘፍ፵፬ ፡ ፳፱) ። ርሡኣን ፡ ወይም ፡ እእሩግ ፡ ልሂቃን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ርሥአን ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ሑር ፡ ወአስተጋብእ ፡ ርሥአኒሆሙ ፡ ለውሉደ ፡ እስራኤል ፡ (ዘፀ፫ ፡ ፲፮) ።

**ርሥእና** ፤ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፤ እርግና ፤ አሮጌነት ፡ (አፈ ፡ ተ፱ና ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ነሐ፳፱) ።

**አርሥአ** ፤ አስረጀ ፤ አሸበተ ፤ አሸመገለ ። ዘእንበለ ፡ ይብጻሕ ፡ ጊዜሁ ፡ ያረሥእ ፡ ትካዝ ። ብእሲት ፡ ነባቢት ፡ ታረሥእ ፡ ውርዝውና ፡ ምታ ፡ (ሢራ፴ ፡ ፳፬ ። ፈላስ) ።

**መርሥኢ** ፤ ኢ. ፤ የሚያስረጅ ፡ አርጅና ፡ የሚሰብ ፡ የሚያመጣ ።

**ረሥአ** ፤—ረሳ ፡ ዘነጋ ፤—ረሰዐ ፡ ረስዐ ።

**ረሥሀ** ፤—አደፈ ፤—ረሰሐ ፡ ረስሐ ።

**ርዒድ** ፤ ዶት ፤ (ርዕደ ፡ ይርዕድ ፡ ይርዐድ ። ዕብ ፡ ራዐድ ። ዐረ ፡ ረዐደ) ፤ መራድ ፤ መንበድበድ ፤ መፍራት ፡ መደንገጥ ፤ መብረክረክ ፡ መንቀጥቀጥ ። ያወሥአከኑ ፡ እንዘ ፡ ይርዕድ ። ይርዕዱ ፡ አድባር ፡ እምኔከ ። ርዕደኒ ፡ መንፈስየ ። ርዕደ ፡ ሙሴ ፡ ወስእነ ፡ ጠይቆቶ ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፴፬ ። ኢሳ፷፬ ፡ ፩ ። ዳን፯ ፡ ፲፭ ። ድጓ) ።

**ርዑድ** ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ዕድ) ፤ የራደ ፤ የተንቀጠቀጠ ፤ ብርክርክ ፤ ፈሪ ፡ ብቡ ። ወኮነ ፡ ርዑደ ፡ ወድንጉፀ ፡ ኵሎ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወቱ ። ተንሣእኩ ፡ ርዑድየ ፡ (ቀሌ ። ዳን፲ ፡ ፲፩) ።

**ረዓድ** ፤ በቁሙ ፤ ጥኑ ፡ ፍራት ፤ ብርክ ፤ እንቅጥቅጥ ፤ ከቁም ፡ የሚጥል ፤ ከቅምጥ ፡ የሚፈንቅል ። ኢይቀርብኪ ፡ ረዓድ ። ረዓደ ፡ ብርክ ። ፍርሀት ፡ ወረዓድ ፡ ወረደ ፡ ላዕሌሁ ፡ (ኢሳ፶፬ ፡ ፲፬ ። ናሑ፪ ፡ ፲ ። ሉቃ፩ ፡ ፲፪) ።

**አርዐደ** ፤ አራደ ፤ አስፈራ ፤ አናወጠ ፤ አንቀጠቀጠ ፤ አብረከረከ ። አርዐድካ ፡ ለቀላይ ። ዘበላዕሉ ፡ አንጐድጐደ ፡ ወዘበታሕቱ ፡ አርዐደ ፡ (ሉቃ ፡ ዕዝ፩ ፡ ፲፱ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**መርዕድ** ፤ (ዱት ፡ ዳን ፡ ዳት) ፤ የሚያርድ የሚያንቀጠቅጥ ፤ ድምጡና ፡ መልኩ ፡ የሚያስፈራ ። ደባትሪሁ ፡ ዘነድ ፡ ወሠረገላሁ ፡ መርዐድ ። ንጥረ ፡ መባርቅት ፡ መርዐድ ፡ (ሳታ ። መጽ ፡ ምስ) ።

—፤ ግምጃ ፤ ልብስ ፡ መንግሥት ፤ አርድ ፡ አንቀጥቅጥ ፡ የሚባል ፤ ጠብደንን ፡ ተመልከት ።

**ርዒው** ፤ ዎት ፤ (ርዕወ ፤ ረዐወ ፡ ይርዑ ፡ ይርዐው ። ዕብ ፡ ሬዒህ ፤ ሬዕ ፤ ቢጽ) ፤ መጥመድ ፤ ማቀናጀት ፤ ማጣመር ፤ ማዛወግ ፤ ጥንድ ፡ ማድረግ ።


**ረዓዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ዐውት) ፤ የሚጠምድ ፤ የሚያቀናጅ ፤ ጠማጅ ።

**መርዕው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ዑት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ጠማጅ ፤ አቀናጅ ።

**አርዐወ** ፤ አስጠመደ ፤ ጥመዱ ፡ አለ ።

**አርዑት** ፤ (ዐረ ፡ አርዑወት) ፤ መጥመጃ ፤ መጠመጃ ፤ ማስጠመጃ ፤ ቀንበር ፤ ሕግ ፡ ሥርዐት ፤ አገ

ዛዝ ፤ እግር ፡ ብረት ። አርዑተ ፡ ብዕራ ። ትወዲ ፡ አርዑተ ፡ ዲበ ፡ ክሣዱ ። ንሥኡ ፡ አርዑትየ ። አርዑት ፡ ዘሠርዑ ፡ ላዕሌሆሙ ። አርዑት ፡ ግብጽ ። አብእ ፡ እገሪከ ፡ ውስተ ፡ አርዑታ ፤ (ኢሳ፶ ፡ ፲፰ ። ኢዮ፴፱ ፡ ፲ ። ማቴ፲፩ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ። ኩፋ ፡ ፴፱ና ፡ ፵፱ ። ሢራ፮ ፡ ፳፬) ።



አርዑት ፤

**መርዐወ** ፤ (ዱ ፡ ቃ ፡ ግ) ፤ አጋባ ፤ አዛወገ ፤ ክለለ ፤ ሰረገ ፤ ሞሸረ ፤ ጨጐለ ፤ የጋብቻ ፡ በዓል ፡ አደረገ ።

**አመርዐወ** ፤ አወየዘረ ፤ አስወየዘረ ፤ ወይዘሮ ፡ አደረገ ፤ አስደረገ ፤ ሸለመ ፡ አስጌጠ ፡ አንቈጠቈጠ ። አመርዓዊ ፡ አረፍት ፤ (ፊልክ ፡ ፻፳፯) ።

**ተመርዐወ** ፤ ተጋባ ፤ ተሞሸረ ፤ ተክለለ ፤ ከሙሽሪትም ፡ ጋራ ፡ ተካየደ ፤ በሕግ ፡ ቀንበር ፡ ተጠመደ ፤ ከጫጉላ ፡ ገባ ፡ ተዋሐደ ። ጽርሕ ፡ ንጽሕት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ተመርዐወ ፡ ቃል ። ተመርዐወኒ ። ዘተመርዐዋ ፤ (ተረ ፡ ቄር፲፯ ። መጽ ፡ ምስ ። አርጋ) ።

**መርዓ** ፤ ጋብቻ ፡ ግቢ ፤ ተክሊል ፤ ሰርግ ፤ የደስታ ፡ በዓል ። ሰብ ፡ ተፈጸመ ፡ መዋዕለ ፡ መርዓ ። አዕበየ ፡ ለመርዓ ፡ አስቴር ። ልብሰ ፡ መርዓ ። ቤተ ፡ መርዓ ። መርዓ ፡ መንግሥት ። ለመርዓ ፡ ስምከ ፡ ይትገበር ፡ ኪብካብ ፤ (አስቴ፪ ፡ ፲፰ ። ፱ ፡ ፲፰ ። ማቴ፳፪ ፡ ፲፩ ። ሂርማ ። ገድ ፡ ላሊ ። ስንክ ፡ መጋቢ) ።

**መርዓዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ ሰርገኛ ፤ ዕድመኛ ። ሙሽራ ፤ ባል ፤ ወንድ ፤ ዐማች ። ደቂቀ ፡ መርዓዊ ። መርዓዊ ፡ ሰማያዊ ። ቅብሎ ፡ መርዓት ፡ ለመርዓዊሃ ። ኢይስክብ ፡ መርዓዊ ፡ ምስለ ፡ ሐማቱ ፤ (ማቴ፱ ፡ ፲፭ ። ቀሌ ። ድጓ ። ቄድር) ።

**መራዕው** ፤ መርዓውያን ፤ ሙሽሮች ፤ ባሎች ፤ ወንዶች ፤ ዐዲስ ፡ ያገቡ ፤ ዓመት ፡ ያልሞላቸው ።

**መርዓት** ፤ (ዊት) ፤ ሙሽሪት ፤ ሴት ፡ ሙሽራ ፤ የመርዓዊ ፡ ጣምራ ፤ ልጃገረድ ፤ ምራት ፤ የወንድ ፡ ልጅ ፡ ሚስት ። ዘቦቱ ፡ መርዓት ፡ መርዓዊ ፡ ውእቱ ። ከመ ፡ መርዓት ፡ ስርጉት ፡ ለምታ ። መርዓትየ ፡ እምሐማታ ፤ (ዮሐ፫ ፡ ፳፱ ። ራእ፳፩ ፡ ፪ ። ማቴ፲ ፡ ፴፭) ።

**መራዕዋት** ፤ መርዓውያት ፤ ሙሽሮች ፤ ልጃገረዶች ፤ ምራቶች ። እለ ፡ ውእቶን ፡ መራዕዋተ ፡ ክርስቶስ ። ከመ ፡ እማንቱ ፡ ይኩና ፡ መርዓውያቲሁ ፡ ለክርስቶስ ፤ (ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፲ ፡ ስንክ ፡ የካ፯) ። መራዕዋት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መራዕው ፡ እያለ ፡ የወንዶቹን ፡ ለሴቶች ፡ ያደርጋል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ቅዱሳት ፡ መራዕው ። ክልኤሆን ፡ መራዕዊሃ ፤ (ቄር ፡ ሩትን ፡ ፯ ፡ ፯ ። ሆሴ፬ ፡ ፲፫) ።

**ምርዕውና** ፤ ሙሽርነት ፤ ጋብቻ ፤ ሰርግ ። ለዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ኢያጽሐቀ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ምርዕውና ፤ (መዋሥ) ።

**ርዕይ** ፤ የት ፤ (ረዐየ ፡ ይርዒ ፡ ይርዐይ ። ዐረ ፡ ረዐይ ። ዕብ ፡ ራዓህ ። ሱር ፡ ርዓእ) ፤ መጠበቅ ፤ ወደ ፡ መልካም ፡ ቦታ ፡ መምራት ፤ መከተል ፤ መንዳት ፡ ማስምረት ፤ መመገብ ፡ ማብላት ። ረዐዩ ፡ ኖሎት ፡ ርእሶሙ ፡ ወኢረዐዩ ፡ አባግዕየ ። እርዕዮሙ ፡ ውስተ ፡ አድባረ ፡ እስራኤል ። ረዐይኬ ፡ አባግዕየ ። ረዐይኩከ ፡ በውስተ ፡ በድው ። ዘይርዒ ፡ ዘማተ ፤ የሚከተል ፤ (ሕዝ፴፬ ፡ ፰ ፡ ፲፫ ። ዮሐ፳፩ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ። ሆሴ ፲፫ ፡ ፭ ። ምሳ፳፱ ፡ ፫) ።

**ረዓዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ዐይት) ፤ ኖላዊ ፤ የሚጠብቅ ፡ ጠባቂ ፤ እረኛ ፤ ዐርበኛ ፤ ዝግና ።

**ረዐይት** ፤ (ዕብ ፡ ራዒም ፤ ርዒ ፡ ኢም) ፤ ሰብአ ፡ ትካት ፤ እኩያን ፡ ዐርበኞች ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚባሉ ፤ ኀይላቸውና ፡ መጠናቸው ፡ ከሰው ፡ ልክ ፡ ያለፈ ፡ የተረፈ ፤ እንደ ፡ ጥድና ፡ እንደ ፡ ዘግባ ፡ ያሉ ፤ ከጥድ ፡ ከዘግባም ፡ የሚበልጡ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ የሚሉ ፤ ገናኖች ፡ ረዣዥሞች ። ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ያባታቸውን ፡ ሕግ ፡ አፍርሰው ፡ ርግማናን ፡ ጥሰው ፡ ከቃየል ፡ ልጆች ፡ ቢጋቡ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ተወልደዋል ፤ (ዘፍ፮ ፡ ፩—፯) ። እማንቱሰ ፡ ፀንሳ ፡ ወወለዳ ፡ ረዐይተ ፡ ዐበይተ ፡ ወቆምሙ ፡ በበ ፡ ፴፻ ፡ በእመት ፤ እሉ ፡ በልዑ ፡ ኵሎ ፡ ጻማ ፡ ሰብእ ፡ እስከ ፡ ስእኑ ፡ ሴሰዮቶሙ ። ወተመይጡ ፡ ረዐይት ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ይብልዕዎሙ ፡ ለሰብእ ፤ ወወጠኑ ፡ የአብሱ ፡ በአዕዋፍ ፡ ወበአራዊት ፡ ወበኵሉ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወበዓማተ ፡ ባሕር ፤ ወተባልዑ ፡ ሥጋሆሙ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወሰትዩ ፡ ደመ ፡ እምኔሃ ፡ አሚሃ ፡ ሰከየቶሙ ፡ ምድር ፡ ለዐማፅያን ። ማኅበረ ፡ ረዐይት ። ዕቡያን ፡ ረዐይት ፤ (ሔኖ፯ ፡ ፪ ፡ ፬ ። ምሳ፳፩ ፡ ፲፯ ። ጥበ፲፬ ፡ ፮) ።

**ረዐይታዊ** ፤ ያርብሕ ፤ ያርብሓዊ ፤ ኀያለኛ ፡ ዝግና ፤ እንደ ፡ ረዐይት ፡ ያለ ፤ ያርብሕን ፡ ተመልከት ። ጎልያድ ፡ ረዐይታዊ ። ሶምሶን ፡ ረዐይታዊ ፤ (ስንክ ፡ ጥቅ፲፭ ። የካ፲፱ ። አርጋ ፡ ፴) ። ኀያል ፡ ጽኑዕ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ረዐይታዊ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ረዐይት ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ዝንቱ ፡ ቀደመ ፡ ይኩን ፡ ረዐይተ ፡ ወኀያዌ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤ (፩ዜና ፡ ፩ ፡ ፲) ።

**አርዐየ** ፤ አስጠበቀ ፤ ጠባቂ ፡ ሾመ ፤ ጠብቅልኝ ፡ አለ ፤ ዐደራ ፡ ሰጠ ።

**ተርዕየ** ፤ **ተረዐየ** ፤ ተጠበቀ ፤ ተሰማራ ፡ ሣር ፡ በላ ፤ ነጨ ፡ ጋጠ ። ይትረዐዩ ፡ ከመ ፡ አስዋር ፡ ወከመ ፡ አባግዕ ፡ ሐቅለ ። ተዘሳላት ፡ ወአባግዕ ፡ ይትረዐዩ ፡ ኅቡረ ። አባሕዝ ፡ እለ ፡ ኅጥኡ ፡ ዘይትረዐዩ ። ላሕም ፡ ዘይትረዐይ ፡ ማዕረ ። ትትረዐይ ፡ ማዕረ ፡ ከመ ፡ ላሕም ፤ (ኢሳ፭ ፡ ፲፯ ። ፷፭ ፡ ፳፭ ። ፳፰ ፡ ፳፮ ። ሰቈ፬ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፻፭ ። ዳን፬ ፡ ፴) ። በተርዕየ ፡ ፈንታ ፡ ተራዐየ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ይትራዐዩ ፡ ውስተ ፡ ቀርሜሎስ ። ኵሉ ፡ ዘመደ ፡ እንስሳ ፡ ይትራዐዩ ፡ ለውእቱ ፡ ማዕርር ፤ ይበልዩ ፡ ብሂል ፤ (ኤር፳፯ ፡ ፲፱ ። ሄርማ) ።

**ርዑይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ዒት) ፤ የተጠበቀ ፡ ጥብቅ ፤ የተሰማራ ፤ ሣር ፡ የጠገበ ፤ ቅልብ ።

**መርዐይ ፤ መርዒት ፤** መንጋ ፡ የእንስሳት ፡ ማኅበር ፤ ጉባኤ ፡ ሸንጎ ፡ እንግልጋ ፤ በየስሙ ፡ በየነገዱ ። ሰኵናሆሙ ፡ ለመርዔት ። መርዔተ ፡ አጣሊ ። አባግዐ ፡ መርዔት ። ኢትፍራህ ፡ አ ፡ ንኡስ ፡ መርዔት ፡ (ማሕ፩ ፡ ፯ ። ፀ ፡ ፩ ። ኤር፳፫ ፡ ፩ ። ሉቃ፲፪ ፡ ፴፪) ።

**መራዕይ ፤ ያት ፤ መርዔታት ፤** መንጎች ፤ መንጋዎች ፤ የሚንጋጉ ። መራዕየ ፡ አልሕምት ፡ ወመራዕየ ፡ አባግዕ ። መራዕየ ፡ አሕርው ። ዖሎት ፡ ወመራዕዩሆሙ ፡ (ኩፋ ፡ ፳ ። ማሮ፩ ፡ ፲፩ ። ኤር፺ ፡ ፲) ።

—፤ ሰራዊት ፤ ወታደር ፤ ጭፍራ ። መጋቤ ፡ መራዕይ ፡ (ዘና፵፭ ፡ ፵፱ ። ፵፯ ፡ ፵፯) ።

**ርዒም ፤ ሞት ፤ (ረዐመ ፡ ይርዕም ፡ ይርዐም ። ዕብ ፡ ራዐም ። ሱር ፡ ርዔም) ፤** መሬትኽ ፡ መንጉድ ፡ መትመም ፡ ማጕረምረም ፤ መድረቅረቅ ፤ መቈጣት ፤ መገንታት ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ መስጠት ። ሰላም ፡ ለጕርዔከ ፡ ንቃወ ፡ ቅዳሴ ፡ ዘረዐመ ፡ እስከ ፡ ይመልእ ፡ አርያም ፡ (ደራሲ) ።

**ረዓም ፤** ጩኸት ፡ ነጕዳ ፡ ጉማ ፤ ተሙማ ፡ የም ስጋና ፡ ዜማ ፡ (ሔኖ፹ ፡ ፪) ። ዘረዓም ፡ ወዘሰንባስ ፡ ይሰምዕ ። ረዓመ ፡ መላእክት ፡ (ደራሲ ። አዋል) ።

**ራፋ ፤ (ብ ፡ ራፋኢን ። ዕብ ፡ ርፋኢም) ፤** ረዐይታዊ ፤ ሐርበኛ ፡ ዠግና ፡ ነዊን ፡ ቆም ፤ የኤናቅ ፡ ዘር ፡ የናፊል ፡ ወገን ። ሕዝበ ፡ ራፋ ፤ ነገደ ፡ ራፋ ፤ ቤተ ፡ ራፋ ። ወቀዲሙሰ ፡ ይብልዋ ፡ ለምድረ ፡ ገለዓድ ፡ ምድረ ፡ ራፋ ፤ እስመ ፡ ምድረ ፡ ራፋኢን ፡ ይእቲ ። ወተወልደ ፡ ራፋይን ፡ ረዐይት ፡ እለ ፡ ዐሥር ፡ በእመት ፡ ወትስዕ ፡ በእመት ፡ ወሰምን ፡ በእመት ፡ እስከ ፡ ስብዕ ፡ በእመት ፡ ውእቱ ፡ ኑኆሙ ። ወማኅደሪሆሙ ፡ እምድረ ፡ ውሉደ ፡ አሞን ፡ እስከ ፡ ደብረ ፡ ሔርሞን ፤ ወቤተ ፡ መንግሥቶሙ ፡ ቅሮናኤም ፡ ወአስጣሮት ፡ ወአድራእ ፡ ወሚሱር ፡ ወቢያን ። ወአህጐሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምእከየ ፡ ምግባሮሙ ፤ እስመ ፡ ፀዋጋን ፡ ጥቀ ፡ እሙንቱ ፤ ወኀደሩ ፡ አሞሬዎን ፡ ህየንቴሆሙ ፡ እኩይ ፡ ወኃጥእ ፡ (፪ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፲፮—፳፪ ። ኩፋ ፡ ፳፱ ። ዘዳ፪ ፡ ፳ ፡ ፳፩) ።

**ረፈአ ፤ አት ፤ (ረፍአ ፡ ይረፍእ ፡ ይርፋእ ። ዕብ ፡ ራፋእ ። ዐረ ፡ ረፋአ) ፤** ማዳን ፡ መፈወስ ፤ ማከም ፡ መድኀኒት ፡ ማድረግ ፤ መጠገን ፡ ማደስ ፤ መስፋት ፡ መጥቀም ፤ መታታት ፡ መጥለፍ ፡ ማቈላለፍ ። ጊዜ ፡ ለሠጢጥ ፡ ወጊዜ ፡ ለረፊእ ፡ (መክ፫ ፡ ፯) ።

**ረፋኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት ፤ እት) ፤** የሚያድን ፡ የሚፈውስ ፤ ፈዋሽ ፤ ሰፊ ፡ ጠቃሚ ፤ ጠጋኝ ፡ ዐዳሽ ፤ ሐኪም ፡ ወጌሻ ። ረፋኢሆሙ ፡ ለድውያን ፡ (ዮዲ፱ ፡ ፲፩ ። ፪ነገ ፡ ፳፱ ፡ ፲) ።

**ሩፋኤል ፤ (ዕብ ፡ ርፋኤል) ፤** የመልአክ ፡ ስም ፤ ከኗቱ ፡ ሊቃናት ፡ አንዱ ፤ ፈውስ ፡ አምላክ ፤ ፈዋሴ ፡ አምላክ ፡ ዘሥዑም ፡ ዲበ ፡ ፈውስ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሩፋኤል ፡ ሥራዬ ፡ በዘአእመረ ፡ በዓሣሁ ፡ አሕየወ ፡ ዐዊረ ፡ (ቅኔ ። ጦቢ፲፩ ፡ ፯—፲፱) ። ወለአሕዱ ፡ እምኔሁ ፡ ይቤ ፡ ከመ ፡ ንምህሮ ፡ ለኖኅ ፡ ኵሎ ፡ ፈውሶሙ ። ከመ ፡ ይፈውስ ፡ በዕፀወ ፡ ምድር ። ወጸሐፈ ፡ ኖኅ ፡ ኵሎ ፡ ትዝምደ ፡ ፈውሳት ፡ (ኩፋ ፡ ፲) ።

**አርፍአ ፤** አስፈወሰ ፡ አሳከመ ፤ አሰፋ ፡ አስጠቀመ ።

**ተረፍአ ፤** ተፈወሰ ፤ ተሰፋ ፤ ታከመ ፤ ተጠቀመ ።

**ርፉእ ፤ (አን ፡ ኢት ፡ ፍእት) ፤** የተሰፋ ፤ የተጠለፈ ፤ ስፍ ፡ ጥልፍ ።

**ርፍአት ፤** መስፋት ፤ መሰፋት ፤ አሰፋፍ ፡ ስፌት ፤ ጥቅማት ። ከዳን ፡ ዘአልቦ ፡ ርፍአት ፡ (ዮሐ፲፱ ፡ ፳፫) ።

**ርፍእ ፤ (ኢት) ፤** ስፌት ፤ ጥልፍ ፤ ግብረ ፡ መርፌ ፤ በስፌት ፡ የወጣ ፡ ሥዕል ፡ ምስል ፤ ጥፈት ፡ ሐረግ ፡ መልክአ ፡ ፊደል ። አማልክተ ፡ ርፍእ ። ወአልባሰ ፡ ርፍእ ፡ ዲበ ፡ ርእሶሙ ፡ (ሕዝ፲፮ ፡ ፲፫ ። ፳፫ ፡ ፲፭) ።

**መርፍእ ፤ እት ፤ (ብ ፡ መራፍእት) ፤** መርፌ ፤ መስፊ ፤ የመርፌ ፡ ዐይነት ፡ ቅንካር ፡ የብረት ፡ እሾኽ ። ስቍረተ ፡ መርፍእ ። ግብረ ፡ መርፍእ ። ዘበመርፍእ ። አዘዘ ፡ ይቀንውዋ ፡ እደዊሃ ፡ ወእገሪሃ ፡ በመራፍእት ፡ በሊኃት ። ዘየኃትም ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ በመርፍእ ። ኢትኅትሙ ፡ አባለክሙ ፡ በመርፍእ ፡ (ማቴ፲፱ ፡ ፳፬ ። ዘፀ፳፯ ፡ ፲፯ ። ፴፯ ፡ ፳፩ ። ስንክ ፡ ጥር፴ ። ቄስጠ ፡ ፳፬) ።

**ምርፋእ ፤ (አት) ፤** መስፊያ ፡ ማስፊያ ፡ መስፊያ ፡ ቦታ ።

**ረፈደ ፤ ዶት ፤ (ረፍደ ፡ ይረፍድ ፡ ይርፈድ ። ዕብ ፡ ራፋድ ፤ ነጸፈ ። ዐረ ፡ ረፈደ ፤ ረድአ) ፤** መርፈድ ፤ ረፋድ ፡ መሆን ፤ የጊዜ ።

**አርፈደ ፤** በቈሙ ፤ አረፈደ ፤ አስረፈደ ፤ አቈየ ፡ አዘገየ ፤ ጊዜ ፡ አሳለፈ ፤ ለወጠ ፤ የኀሑን ፡ በጽባሕ ፡ የጽባሑን ፡ በንግህ ፡ የንግሁን ፡ በሠለስት ። (ተረት) ፤ ገባያ ፡ ላርፋጅ ፡ ቤት ፡ ክሲያን ፡ ለማላጅ ። አልቦ ፡ ዘይመጽእ ፡ መብልዐ ፡ ድዉያን ፡ ውስተ ፡ መስኅንተ ፡ አኅው ፡ ኀበ ፡ ያበስሉ ፡ ሎሙ ፤ አላ ፡ ይግበሩ ፡ ሎሙ ፡ ለድዉያን ፡ እንተ ፡ ባሕቲቶሙ ፤ ወኢያርፍዱ ፡ ውሂቦቶሙ ፡ ለእለ ፡ ይወዩ ፡ (ሥር ፡ ጳኰ) ። ፈረደንና ፡ ረደፈን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ።

**ሬፋን ፤ (ጽርእ ። ዕብ ፡ ኪዩን) ፤** የኮከብ ፡ ስም ፤ ኮከባዊ ፡ ጣዖት ፤ መዳቡት ፡ በሚሲት ፡ ወይም ፡ ባጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ አምሳል ፡ የተሠራ ፡ (ዓሞ፭ ፡ ፳፮ ። ግብ፯ ፡ ፵፫) ።

**ረፍዐ ፤ (ትግሬ ፡ ወዐረብ) ፤** አነሣ ፤ ተሸከመ ፤ ብቻውን ፡ ወይም ፡ የሳንባ ።

**ረፈ ፤ ረፈፈ ፤ (ትግሬ ። ዕብ ፡ ራፋሀ) ፤** ደከመ ፡ ዛለ ፤ ወደቀ ፡ አረፈቀ ።

**ረፈቀ ፤ ቆት ፤ (ረፈቀ ፡ ይረፍቅ ፡ ይርፍቅ ። ዕብ ፡ ራፋቅ ። ዐረ ፡ ረፈቀ) ፤** መርፈቅ ፤

መጠጋት ፡ መደገፍ ፤ እጅን ፡ መዳፍን ፡ እንደ ፡ ብርኵማ ፡ መንተራስ ፤ ወይም ፡ ጕንጭን ፡ አገጭን ፡ በመዳፍ ፡ ባላ ፡ ተሸክሞ ፡ መያዝ ። ረፈቀ ፡ ዲበ ፡ እንግድዓሁ ፤ ተጠጋ ፡ (ዮሐ፲፫ ፡ ፳፭) ።

—፤ መቀመጥ ፡ ማረፍ ፤ ስደቃን ፡ መክበብ ፡ ማቀፍ ፤ መኰልኰል ፤ ለመብል ፡ መሰለፍ ። ረፈቁ ፡ እብላዐ ። ምስካብ ፡ ዘዲቤሁ ፡ ትረፍቅ ፡ ሶበ ፡ ትመስሕ ። ረፈቀ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በድራር ፡ ዘዲበ ፡ ኪሩቤል ፡ ይነብር ፡ (ጦቢ፪ ፡ ፩ ። ዮዲ፲፪ ፡ ፲፭ ። ድጓ ። ማቴ፳፮ ፡ ፳) ።

—፤ መድከም ፡ ማረፈቅ ፤ መተኛት ፡ መውደቅ ፡ (ዐማርኛ) ።

ረፋቂ ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት) ፤ የሚረፍቅ ፡ የሚቀመጥ ፤ ከባቢ ፤ ኰልኳይ ፤ ግብረ ፡ በላ ። ዮሐንስ ፡ ረፋቂ ፡ ሕፅንከ ። ሦርዐ ፡ ማእደ ፡ ቅድመ ፡ ረፋቅያን ፡ ከመ ፡ ይብልዑ ፡ (ደራሲ ። ሥርዐ ፡ ቅዳ) ።

አርፈቀ ፤ አስቀመጠ ፤ አስጠጋ ፤ ሰፍራ ፡ ሰጠ ። አርፍቅዎሙ ፡ በበ ፡ ኅምሳ ። ውስተ ፡ ሕፅኑ ፡ አንበረከ ፤ ዲበ ፡ እንግድዓሁ ፡ አርፈቀከ ። ያርፍቀነ ፡ ውስተ ፡ ሕፅኑ ፡ ለመርዓዊ ፡ (ሉቃ፱ ፡ ፲፬ ። ድጓ ። መዋሥ) ።

—፤ አስረፈቀ ፤ ዝም ፡ አሰኘ ፤ አስታገሠ ፡ (ዐማርኛ) ፤ ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገባል ።

መርፈቅ ፤ መድረክ ። ወተሰዐሰ ፡ መርፈቀ ፡ ኖኅት ፡ (ኢሳ፮ ፡ ፬) ።

ምርፋቅ ፤ (ቃት) ፤ መርፈቂያ ፤ የሰደቃ ፡ ቤት ፤ የምግብ ፡ ቦታ ፤ ዳስ ፤ ደጀ ፡ ሰላም ፤ የመሸታ ፡ ቤት ። ኢትርፍቅ ፡ ውስተ ፡ ርእሰ ፡ ምርፋቅ ። ይርፍቁ ፡ በበ ፡ ምርፋቃቲሆሙ ። የሐውር ፡ ኀበ ፡ ምርፋቃት ፡ (ሉቃ፲፬ ፡ ፯—፲ ። ማር፳ ፡ ፴፱ ። አፈ ፡ ተ፴ ። ቀሌ) ።

—፤ ጋሬዳ ፤ የቍትቻ ፡ ድግስ ። ኢይግበሩ ፡ ምርፋቀ ፡ ሰስቴ ፡ (ቀኖ ፡ ሎዶቅ) ።

ረቅይ ፤ ዮት ፤ (ረቀየ ፡ ይረቂ ፡ ይርቂ ። ዐረ ፡ ረቂየ ። ዕብ ፡ ራቃሕ) ፤ ማዘም ፡ መሠረይ ፤ ዐዚም ፡ ማድረግ ። በውሃ ፡ ላይ ፡ መድገም ፤ ማነብነብ ፤ መጸለይ ፡ ማንበብ ፤ የአስማት ፡ የጸሎት ። ደግሞ ፡ ከበቴ ፡ በኋላ ፡ መርጨት ፡ መፈንጠቅ ፤ መበተን ፡ መነስነስ ፤ ማፍሰስ ፡ መቸለስ ። ጽምምት ፡ እንተ ፡ ኢትሰምዕ ፡ ቃለ ፡ ዘይረቅያ ። ረቃዪ ፡ ዘይረቂ ። ዘአልቦ ፡ ዘይረቅዮ ። እለ ፡ ይነዝሁ ፡ ማየ ፡ ረቅዮሙ ፡ ላዕሌሁ ፤ ደግመው ። እለ ፡ የዐውዱ ፡ ወይረቅዩ ፡ ወይጼውዑ ፡ (መዝ፶፯ ፡ ፬ ። መክ፲ ፡ ፲፩ ። ኤር፰ ፡ ፲፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፭ ፡ ፫ ። ግብ፲፱ ፡ ፲፫) ። ሰሚያሙ ፡ ወንጌለ ፡ ኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ያንብቡ ፡ እደ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወይርቅይዎሙ ፤ ወጥምቀቶሙሰ ፡ በመዋዕለ ፡ ጳሲካ ። ይርቂ ፡ ላዕሌሆሙ ። ትረቂ ፡ መቃብሪሁ ፡ በማይ ። አምጽኢ ፡ ማየ ፡ ወርቅዩ ፡ ወትሐዩ ፡ (ኪዳ ። ቀኖ ፡ ኒቅ፫፮ ። ማኅዘ ። ገድ ፡ ዳኅ) ።

—፤ ማሞቅ ፡ ማተኰስ ፤ ማሳብ ፡ ማውዘት ፤ ማፍላት ፡ ማንጠር ፤ ማጥራት ፡ ዐረቂ ፡ ማውጣት ።

ረቃዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ቀይት) ፤ የሚደግም ፡ የሚረጭ ፤ አስማታም ፡ ዐረቂ ፡ በውጭ ፤ ጪ ፤ ሽቱ ፡ አጣፋጭ ። ረቃይያን ። መፈክራነ ፡ ሕልም ፡ ወረቀይት ፡ (ኪዳ ። ኩፋ ፡ ፵) ።

ራቅይ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። መሠርይ ፡ ሰው ፡ ራቅይ ፡ (ቁስጠ) ።

አርቀየ ፤ አስደገመ ፤ አስረጨ ፤ አስሞቀ ፡ አስፈላ ፤ አስነጠረ ፡ ዐረቂ ፡ አሶጣ ።

ተረቅየ ፤ ተረጨ ፤ ተረጨበት ። ዲያቆን ፡ ይጥምቅ ፡ ዘተረቅየ ። ይትረቀይ ፡ እምካህን ፡ (ኪዳ) ።

ርቁይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ቂት) ፤ የታዘመ ፤ የተደገመበት ፤ የተረጨበት ። ርቁየ ፡ ተሰናን ፡ (አዋል) ።

ርቅየት ፤ መድገም ፤ ድጋም ፤ መድገኒት ፡ ጠበል ፡ መርጨት ፤ መረጨት ፤ አረማጨት ። እለ ፡ ይገብሩ ፡ ርቅየተ ። ጸሎተ ፡ ርቅየት ፡ ማይ ። ይርቂ ፡ ርቅየተ ፡ ንጹሰ ፡ ክርስቲያን ። ከመ ፡ ይስአሉ ፡ ዘእምኅቤከ ፡ ርቅየተ ፡ ወሕይወተ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፭ ፡ ፫ ። ፱ዜና ፡ ፴፫ ። ፳ ። ሲኖዶ ። ኪዳ ። ሊጦን) ።

ምርቃይ ፤ መድገሚያ ፤ መርጫ ፤ የጠበል ፡ ቦታ ፡ (ኪዳ) ።

መርቁ ፤ ሙቀት ፤ ትኵሳት ፤ ሐሩር ፤ በጋ ፡ ድርቅ ። ያጸልል ፡ እምነ ፡ መርቁ ፡ ታሕቴሃ ። አኮኑ ፡ ዝናም ፡ ያቈርሮ ፡ ለመርቁ ። መንፈሰ ፡ መርቁ ። ዐውሎ ፡ መርቁ ። ላዕብ ፡ ወመርቁ ፡ (ሢራ፲፬ ፡ ፳፯ ። ፲፰ ፡ ፲፮ ። ኢሳ፬ ፡ ፮ ። ኤር፲፰ ፡ ፲፯ ። አርጋ) ።

—፤ ቁላ ፤ በረሓ ፤ ሙቀታም ፡ ሐሩራም ። ብሔረ ፡ መርቁ ። ምድረ ፡ ካምስ ፡ መርቁ ፡ ይእቲ ፤ ወምድረ ፡ ሴምሰ ፡ ኢመርቁ ፡ ወኢደደክ ፡ አላ ፡ ቱስሕት ፡ ይእቲ ፡ በቍር ፡ ወበሞቅ ። ይባርክዎ ፡ ደደክ ፡ ወመርቁ ፡ (ሢራ፴፱ ፡ ፳፯ ። ኩፋ ፡ ፰ ። ዳን፫ ፡ ፷፰) ።

ረቀመ ፤ (ዐረ ። ዕብ ፡ ራቃም) ፤ ሣለ ፤ መሰለ ፤ ሐረግ ፡ ጣለ ፤ በጥልፍ ፡ በስፌት ፡ በግብረ ፡ መርፌ ። እስከ ፡ ሰብአ ፡ አዝማና ፡ ይረቅሙ ፡ ሥዕላ ፡ ዲበ ፡ አልባሲሆሙ ፡ (ዮሴፍ) ።

ረቂቅ ፤ ቆት ፤ (ረቀ ፡ ይረቅቅ ፤ ይርቅቅ ፤ ዐረ ። ዕብ ፡ ራቃቅ ። ሱር ፡ ራቅ ፤ ወረቀ ፤ ሜን) ፤ መርቀቅ ፤ መሣሣት ፤ መቅጠን ፤ እንደ ፡ ጉም ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ መኾን ፤ ከማዘፍ ፡ መራቅ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ጣፈ ፤ ይሉታል ።

ረቂቅ ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ቃቅ) ፤ በቁሙ ፤ የረቀቀ ፡ የሣሣ ፤ ሥሥ ፤ ቀጭን ፡ ደቃቃ ፤ ኰሳሳ ። መንፈስ ፡ ረቂቅ ። ይጠበልል ፡ በረቂቅ ። ቂጽለ ፡ ወርቅ ፡ ረቃቅ ። ረቂቀ ፡ ልብ ። ረቂቀ ፡ አባል ። ድግዱግ ፡ ወረቂቅ ፡ ሥጋሁ ፡ (ቅዳ ። ዘፍ፲፮ ፡ ፴፫ ። ፈላስ ። ገድ ፡ አዳ ። ስንክ ፡ ሐምሌ) ።

(ጥቀ) ርቀት ፤ በቁሙ ፤ መርቀቅ ፤ መፈቀቅ ፤ ረቂቅነት ፤ ምስጢርነት ። ኢሰምዕዎ ፡ በእንተ ፡ ርቀተ ፡ ቃሉ ።

ማዕበለ ፡ ርቀት ፡ ንባብ ፡ ዘእንበለ ፡ መጠን ፡ ገዘፈ ፡ (አፈ ፡ ድ፴፪ ። ቅ፯) ።

**አርቀቀ** ፤ አረቀቀ ፡ አስረቀቀ ፤ አማሳ ፡ አቀጠነ ፤ አስቀጠነ ፤ ፋቀ ፡ ፈቀፈቀ ፤ ራመመ ።

**ረቅ** ፤ (ቃት) ፤ ወረቀት ፤ ክርታስ ፤ ብራና ። ጽሒፈ ፡ ውዳሴኪ ፡ እምኢትልቀ ፡ ሶበ ፡ ኮነ ፡ ጥቀ ፤ ዝናመ ፡ ክረምት ፡ ቀለመ ፡ ወሰማይ ፡ ረቀ ፡ (ደራሲ) ። ፪ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፫ ፡ ድጓ) ።

**ራስ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፤ ርእስ ፤ ስመ ፡ ልዕልና ፤ የንጉሥ ፡ በታች ፡ የመኳንንቶች ፡ በላይ ። ወኀልቀ ፡ ብዙኃን ፡ መኳንንት ፤ ወሞቱ ፡ ራስ ፡ ማሕፀንቱ ፡ ወራስ ፡ ዐምዱ ፡ ወካልኣንሂ ፡ (ታሪ ፡ ግራኝ) ።


**ሬስ** ፤ —ስመ ፡ ፊደል ፤ ሬሳ ፤ —ርእሰ ፤ ረይስ ።

**ሮስ** ፤ —ወንድ ፡ ልጅ ፤ —ጓረስ ፡ ኀረሰ ።

**ረሰወ** ፤ ዎት ፤ (ረሰወ ፡ ይረሱ ፡ ይርሱ ። ዐረ ፡ ረሳ ። ዕብ ፡ ራሴን ፤ ለበበ) ፤ መልሕቅ ፡ መጣል ፤ ማቆም ፡ መግታት ፤ ማስጠጋት ፤ መወደብ ፤ ወደ ፡ ዋቡስ ፡ ማቅረብ ፤ የታንኳ ፡ የመርከብ ። በረሰወ ፡ ፈንታ ፡ አርሰወ ፡ አርሰየ ፡ ይላል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አርሰዩ ፡ ፅየ ፡ (ማርቈ ፡ ፶፫) ።

**ረሳዊ** ፤ መርሰው ፤ ወዳቢ ፤ መልሕቅ ፡ ጣይ ፤ ለጓሚ ፡ መርከብ ፡ አቋሚ ።

**መርሶ** ፤ (ዐረ ፡ ሚርሳት) ፤ መልሕቅ ፤ የመርከብ ፡ ልጓም ። እስመ ፡ መርሶ ፡ ሶበ ፡ ይረስውዎ ፡ ይክልእ ፡ ለሐመር ፡ ከመ ፡ ኢያንቀልቅል ፡ ለፌ ፡ ወለፌ ፡ (አፈ ፡ ድ፲፭ ። ዕብ፯ ፡ ፲፱) ።



መርሶ ፡

**መርሶ** ፤ (ዐረ ፡ ሙርሰን) ፤ ወደብ ፤ የመርከብ ፡ መቋሚያ ፤ ጽንፈ ፡ ባሕር ፡ ከፈረ ፡ ባሕር ፤ የባሕር ፡ ደጃፍ ፡ መውጫና ፡ መግቢያ ፤ ወይም ፡ ዙሪያ ። መርሶ ፡ አሕማር ። መርሖሙ ፡ ውስተ ፡ መርሶ ፡ ኀበ ፡ ፈቀዱ ። መርሶ ፡ ሕይወት ፡ እሙንቱ ፡ (ዘፍጥ፵፱ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፻፯ ። ኪዳ) ።

**መራስው** ፤ መልሕቆች ፤ ወደቦች ።

**መርስ** ፤ (ሳት) ፤ ጸጥታ ፤ ዝምታ ፤ ፍጹም ፡ ዕረፍት ፤ መርከብ ፡ ከወደብ ፡ ሲቆም ፡ የሚገኘው ። ወይም ፡ የባሕሩ ፡ ጠረፍ ፤ ወደቡ ፡ ገደቡ ። መርስ ፡ ወዛኅን ፡ ጥዑይ ። መካነ ፡ መርስ ፡ ሰለ ፡ ዘሎ ። ኀድፈኒ ፡ ውስቴቱ ፡ ዛኅን ፡ ወመርስ ፡ (አፈ ፡ ተ፲፰ ። ስንክ ፡ ጥቅ ፳ ። ኀዳ፫) ።

**መርሴ** ፤ (ትግሬ) ፤ የበር ፡ መዝጊያ ። ሲብዝ ፡ መርሰያት ፤ መራስይ ፡ ያሰኛል ።

**ረሲሐ** ፤ ሐት ፤ (ረስሐ ፡ ይረስሕ ፡ ይርሳሕ ። ረኀሰ ፤ ረስዐ) ፤ ማደፍ ፤ መጉደፍ ፤ መርከስ ፤ መበደል ፡ ማበስ ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ለስድብ ፡ ለፍርድ ፡ መመቸት ፤ ድልው ፡ መኾን ፤ እድፋም ፡ ጉድፋም ፡ ኀጥእ ፡ ኃጥእ ፡ መባል ። ልብሱ ፡ ለእመ ፡ ረስሐ ፡ ኢየኀፅብ ። ልብስ ፡ ዘኢረስሐ ። ለእመ ፡ ረስሐ ፡ በሩካቤ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ። ወለዘረስሐኒ ፡ ያረስሕዎ ። ረስሐ ፡ ውእቱ ፡ ለዘዝኔ ፡ (ፈላስ ። ግንዘ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፱ ። ራእ፳፪ ፡ ፲፩ ። ማቴ፳ ፡ ፳፩) ።

— ፤ ማበጥ ፡ መጉረብ ፤ መብሰዝ ። እገሪከ ፡ ኢረስሓ ፡ (ዘዳ፰ ፡ ፬) ።

**ርሱሕ** ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ስሕት) ፤ ያደፈ ፡ የረከሰ ፡ እድፋም ፤ በደለኛ ፤ ኀጢአተኛ ። ልብስ ፡ ርሱሕ ። እለ ፡ ገብርዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ምግባር ፡ ርሱሕ ። ርሱሓነ ፡ ኮኑ ፡ ለእለ ፡ ይዘልፍዎሙ ። ርሱሕ ፡ በቀትል ፡ (ያዕ ፪ ፡ ፪ ። ዘካ፫ ፡ ፫ ። ቀሌ ። ምዓ፳ ፡ ፳፫ ። ፳፰ ፡ ፲፯) ።

**ርስሐት** ፤ (ታት) ፤ ማደፍ ፤ መርከስ ። እድፍ ፤ ኀጢአት ፡ ነውር ፡ ገመና ፤ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ሥራ ፤ ሠሪዉን ፡ የሚያስንቅፍና ፡ የሚያስጠይፍ ። ከመ ፡ የኀፅቡ ፡ ርስሐተ ፡ በማይ ። የኀፅብ ፡ ርስሐቶሙ ፡ ለደቂቀ ፡ ጽዮን ። ርስሐት ፡ ርኩስ ። ይርከብክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ርስሐት ። ርስሐተ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ። ይኩን ፡ ንጹሐ ፡ እምዘሉ ፡ ነውራት ፡ ወርስሐታት ። ርስሐታተ ፡ ኀሊናት ፡ እኪት ፡ (ደራሲ ። ኢሳ፬ ፡ ፬ ። ኩፋ ፡ ፳፪ ። ፪ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ። ዲድ ፡ ፴፪ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፩ ፡ ፫ ። ፊልክ ፡ ፲፫) ።

**ርስሕ** ፤ **ርስሓ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ እድፍ ፡ ጉድፍ ፤ ኀጢአት ፡ ክፋት ።

**አርስሐ** ፤ አሳደፈ ፤ አሆለፈለፈ ፤ እድፋም ፡ ጉድፋም ፡ ነውረኛ ፡ አደረገ ። በፍርድ ። አሴ ፡ ሎቱ ፡ ለዘአርስሐ ፡ ሥጋሁ ፡ በፍትወተ ፡ ዝሙት ። መብዝኀቶሙ ፡ ለሰብእ ፡ ያረስሑ ፡ ነፍሶሙ ። ታረስሕ ፡ እፉከ ፡ በዙስሕ ። አርስሖሙ ፡ ዳንኤል ፡ እምቃሎሙ ። ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ከመ ፡ አርስሕዎ ፡ (ቀሌ ። አፈ ፡ ድ፲፪ ። ተግ፲፯ ። ዳንኤ ፡ ፳፩ ። ማቴ፳፯ ፡ ፫) ።

**አርሳሕስሐ** ፤ **አርሰሐስሐ** ፤ አጥብቆ ፡ አሳደፈ ፤ አረከሰ ፤ ፈጽሞ ፡ አነወረ ፤ አስነወረ ፤ ወቀሠ ፡ ፈረደ ፡ መሰከረ ፤ ነቀፈ ፡ ዘለፈ ። እንዘ ፡ ኢያርሳሐስሖሙ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ። ወያርሰሐስሖሙ ፡ ልቦሙ ። ወእመሰ ፡ ያርሰሐስሐነ ፡ ልብነ ። ኢይትረከብ ፡ በላዕሌሆሙ ፡ ወኢምንትኒ ፡ ዘያርሰሐስሖሙ ፡ እምእግዚእምላክሙ ፡ (ኪዳ ። ሮሜ፪ ፡ ፲፭ ። ፩ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፳ ። ቀሌ) ።

**ረስዮ** ፤ ዮት ፤ (ረሰየ ፡ ይሬሲ ፡ ይረሲ ። ረሰወ ፤ ገብረ ፤ ሤመ ፤ ወደየ) ፤ ማድረግ ፤ መፍጠር ፡ መሥራት ፤ ማሳመር ፡ ማስጌጥ ፤ ማበጀት ፤ ማዘጋጀት ፤ ማናቸውንም ። በረሰየ ፡ ፈንታ ፡ አስተረሰየ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። መኑ ፡ ያስተሬሲ ፡ ሀገረ ። አስተረሲ ፡

ለክሣዱየ ፡ ባዘግና ፡ ወቃማ ፤ (ሚልክ፩ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ ኀሐ፴) ።

—፤ ማስር ፡ ማበት ፤ ማግባት ፡ መክተት ፤ ማኖር ፡ ማስቀመጥ ። ረሰዩ ፡ አሕባለ ፡ ውስተ ፡ ክሣዱ ። ረሰይዎ ፡ ውስተ ፡ ላሕመ ፡ ብርት ። ረሰዩ ፡ መኃትወ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ ገበዋቲሁ ፤ (ስንክ ፡ ሚያ፴ ። ፲፯ ። የካ፱) ።

—፤ መሾም ፡ መሸለም ፡ ማሠልጠን ፤ ስምንና ፡ ግብርን ፡ ባሕርይን ፡ መለወጥ ፤ ሌላ ፡ ማድረግ ፤ ወይም ፡ ማስመሰል ፡ ማንጻጸር ፤ መጕዳት ። ረሰይኩከ ፡ አምላከ ፡ ለፈርዖን ። ነቢየ ፡ ረሰይኩከ ። በብእሲ ፡ ዐይን ፡ ረሰይኩከ ። ወበጥበብከ ፡ ረሰይከ ፡ ሰብአ ፡ ከመ ፡ ይኴንን ፡ ዘእምኔከ ፡ ተገብረ ። ወረሰዩ ፡ ለለ ፡ ሸሉ ፡ ክፍል ፡ ብእሴ ፡ ዘእሙር ፡ በኀይል ፤ ሾመ ፡ (ዘፀ፯ ፡ ፩ ። ኤር፩ ፡ ፭ ። ሕዝ፫ ፡ ፲፯ ። ጥበ፱ ፡ ፪ ። ዮሴፍ) ። ዘይሬስዮሙ ፡ ለመላእክቲሁ ፡ መንፈሰ ። ረሰያ ፡ ለምድር ፡ ጼወ ። ወረሰየ ፡ ለማይ ፡ ወይነ ። ረስዩ ፡ ከመ ፡ እኁከ ። ወረሰይዎ ፡ ከመ ፡ ሕብድ ። ሕልቦ ፡ ዘይሬስዮ ፡ ረምሐ ። ምንተ ፡ ይሬስየኒ ፡ ሰብእ ፤ (መዝ ፡ ፻፫ ። ፻፯ ። ቅዳ ። ሚሩ፴ ፡ ፴፱ ። ዮሴፍ ። ኢዮ፵፩ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፶፯) ።

**ረሳዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት) ፤ የሚያደርግ ፤ አድራጊ ፡ ፈጣሪ ፤ ሠያሚ ፡ አንባሪ ።

**አርሰየ** ፤—ወደበ ፤ አስጠጋ ፤—አርሰወ ፤ ረሰወ ።

**አረሰየ ፤ አስተረሰየ** ፤ አስደረገ ፡ አስጠረረ ፤ አስሰለፈ ፤ አስታጠቀ ። አስተረሰይኩኑ ፡ ለቀትል ፡ በንዋየ ፡ ሐቅል ። አስተረስዩ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ ዕደወ ፡ ወተቃተሉ ። ለምንት ፡ ታስተሬሲ ፡ አፍራሰ ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ ስንእ ። አስተረስዮ ፡ አንጻረ ፡ መንፈሰ ፡ ፀሪፍ ፤ (ኢዮ፴፱ ፡ ፳ ። ዘኍ፴፩ ፡ ፫ ። ኤር፲፱ ፡ ፳ ። ማር ፡ ይሥ፩ ፡ ፵) ።

**መረስዪ ፤ መስተረስዪ** ፤ የሚያስጠርር ፤ አስጠራሪ ፤ ሰልፍ ፡ አስተማሪ ።

**ተረሰየ** ፤ ተደረገ ፤ ለበሰ ፡ አጌጠ ፡ ተሸለመ ፤ ተጠረረ ፡ ታጠቀ ፡ ተሰለፈ ፤ ተዘጋጀ ። ተረሰይኩ ፡ ርትዐ ፡ ከመ ፡ ዐጽፍ ። ተረሳዩት ፡ ክብር ፡ በዑዳፌ ። ዘይትሬሰይ ፡ በሰርጕ ፡ አንስት ። መጽኡ ፡ ተረስዮሙ ። እለ ፡ ተረሰዩ ፡ ለቀትል ። መኑ ፡ ይትሬሰይ ፡ ለቀትል ፤ (ኢዮ፳፱ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፳ ። ቀሌ ። ግብ፳፭ ፡ ፳፫ ። ዘኍ፴፩ ፡ ፭ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፰) ። ትስምዕ ፡ ትከብር ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ትትሬሰይ ፡ ይላል ፤ የመጻሕፍት ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ዐይን ፡ እንተ ፡ ርእየተኒ ፡ ትትሬሰየኒ ። ትትሬሰዩ ፡ በብዕሎሙ ፤ (ኢዮ፳፱ ፡ ፲፩ ። ኢሳ፷፩ ፡ ፮) ።

**ርሱይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሲት) ፤ የተደረገ ፤ የተበጀ ፡ የተዘጋጀ ፡ ዝግጁ ፤ ያጌጠ ፡ የለበሰ ፤ የተጌጠ ፡ የተሸለመ ፡ ሽልም ፤ የታጠቀ ፡ የተሰለፈ ። ጽርሕ ፡ ርሱይ ። ቤት ፡ ርሱይ ። መንበረ ፡ ወርቅ ፡ ርሱይ ። ብእሲ ፡ ዘርሱይ ፡ በቀጠንት ፡ አልባስ ። ወአዋልዲሆሙኒ ፡ ርሱያት ። የዐቅብ ፡ ኀይል ፡ ዐጸዶ ፡ ርሱየ ፡ በንዋየ ፡ ሐቅል ። ርሱያኒ ፡ ነሐውር ፡ ምስለ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅልነ ፤ (ማር፲፬ ፡ ፲፭ ። ምሳ፳፭ ፡ ፳፬ ። ቀሌ ። ድጓ ። መዝ ፡ ፻፵፫ ። ሉቃ፲፩ ፡ ፳፩ ። ነሐ፱ ፡ ፳፫) ።

**ትርሲት** ፤ (ታት) ፤ ጌጥ ፡ ሽልማት ፡ መሣሪያ ፤ የክብር ፡ ልብስ ። ትርሲተ ፡ አብያት ። ትርሲቱ ፡ መርዓዊ ፡ ወመርዓት ። እንተ ፡ ባቲ ፡ ትርሲተ ፡ ዝሙት ። በሰብዋ ፡ ሸሎ ፡ ትርሲታ ። ቅንቲ ፡ ሐቌኪ ፡ ወልበሲ ፡ ትርሲተ ፡ መንግሥትኪ ፤ (ሚክ፪ ፡ ፱ ። ኢሳ፷፩ ፡ ፲ ። ምሳ፯ ፡ ፲ ። ሰቈ፩ ፡ ፮ ። ድጓ) ።

**ትርሲት** ፤ ልጅነት ፤ የልጅነት ፡ ክብር ፤ ጸጋ ፡ ሀብት ፤ ሕግ ፡ ሥርዐት ፤ አባት ፡ ለልጁ ፡ የሚሰጠው ። ትርሲተ ፡ ወልድ ። እለ ፡ ሎሙ ፡ ትርሲተ ፡ ውሉድ ፤ (ሮሜ፰ ፡ ፲፭ ፡ ፳፫ ። ፱ ፡ ፬ ። ኤፌ፩ ፡ ፭ ። ገላ፬ ፡ ፭) ።

**ረሲን ፤ ኖት** ፤ (ረስነ ፡ ይሬስን ፡ ይርሰን ። ዕብ ፤ ጋሐል) ፤ መርሰን ፡ መፈም ፤ መጋል ፡ መጋም ፡ መሞቅ ፡ መድመቅ ፤ ከእሳት ፡ መዋሐድ ፡ መመሳሰል ፡ መንደድ ፡ መቃጠል ፤ የማይያዝ ፡ የማይዳሰስ ፡ መኾን ። ለእመ ፡ ረስነት ፡ መቅፀት ። ለማያትኒ ፡ ይረስና ። ኢውዕየ ፡ ወኢረስነ ፡ ምንተ ፤ እንዘ ፡ ብሱበል ፡ የዐቀር ፡ እሳተ ። ወበከመ ፡ ኀጺን ፡ አው ፡ ዘይመስሎ ፡ ተራኪቦ ፡ ምስለ ፡ እሳት ፡ ይረስን ፡ ተወኪፎ ፡ ኪያሁ ፡ ወይትማሰል ፡ ምስለ ፡ እሳት ፡ ረሲኖ ፤ (ዮሴፍ ። ፪ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ። ስንክ ፡ ታኅ፳ ። ቄር ፡ ጸሳ) ።

**ርሱን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ስንት) ፤ የጋለ ፡ የጋመ ፤ የነጠረ ፡ የተፈተነ ። ብርት ፡ ርሱን ። ርሱናን ፡ አምሳለ ፡ ላህቡ ፡ ለብርት ፡ ሊባኖስ ። ርሱን ፡ ቃልከ ፡ ፈድፋደ ። ብሩር ፡ ርሱን ፡ ልሳኑ ፡ ጻድቅ ፤ (ዳን፲ ፡ ፮ ። ስንክ ፡ የካ፰ ። መዝ ፡ ፻፲፰ ። ምሳ፲ ፡ ፳) ።

**ርስንት** ፤ በቁሙ ፤ መጋል ፡ መጋም ፤ መንጠር ፡ መቅለጥ ፤ መፈተን ፡ መጠበስ ። ግለት ፡ ሙቀት ፡ ትኵሳት ። መከራሆሙ ፡ ለወርቅ ፡ ወለብሩር ፡ ርስነት ። ርስነቱ ፡ ለፍቅር ፤ (ምሳ፳፯ ፡ ፳፩ ። አርጋ ፡ ፫) ።

**ርስን ፤ ረስን** ፤ ግለት ፤ ግመት ፡ ሙቀት ፤ ዋዕይ ፤ ንዳት ፤ ትኵስ ፤ ትኵሳት ። በርስኑ ፡ ኀጺን ፡ ውዑይ ። ርስኑ ፡ መለኮት ፡ ገበሰት ፡ እዴሁ ። ይቈርር ፡ እንከ ፡ ርስኑ ፡ ጥብዐቶሙ ። ማዕተብ ፡ ረስን ፤ (ስንክ ፡ የካ፳፭ ። ድጓ ። ፈልክ ፡ ፴ ። ሥር ፡ ጻዥ) ።

**አርስን** ፤ አጋለ ፡ አጋመ ፤ አስጋለ ፡ አስጋመ ፤ ጠበሰ ፡ ተኰሰ ፤ አሞቀ ፡ አናደደ ፤ አቃጠለ ። አረስኖሙ ፡ ወአፈትኖሙ ። ከመ ፡ ብርት ፡ ዘአርሰንዎ ፡ በእሳት ። አርሰንዎ ፡ ለቅዱስ ፡ በሰናስለ ፡ እሳት ። ያረስን ፡ ልቦ ፡ በእንተ ፡ አፍቅሮ ፡ እግዚ ፤ (ኤር፱ ፡ ፯ ። ራእ፩ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ ታኅ፳ ። ፈልክ ፡ ፩) ።

**አርሳኒ ፤ መርሰኒ ፡ ስን** ፤ የሚያግል ፡ የሚያግም ፤ የሚጠብስ ፡ የሚተኵስ ፡ (አዋል) ።

**አርሳኒ ፤ አርሳንዮስ** ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ሮማዊ ፡ ቅዱስ ፤ ያበቈጣስ ፡ መነኰሴ ። ዘ ፡ ጽፍዐት ፡ ዘአርሳኒ ፤ (ፈልክ) ።

**ረሰዐ ፤ ዖት ፤ (ረስዐ ፡ ይረስዕ ፡ ይርሳዕ ። ዕብ ፡ ራሻዕ ፤ ኀጥአ) ፤** መርሳት ፤ መዘንጋት ፤ ማጣት ፤ ከልብ ፡ ከሐሳብ ፡ ማጥፋት ፤ ቸላ ፡ ቸል ፡ ቸለል ፡ ማለት ፤ መተው ፡ መናቅ ፤ አለማውሣት ። ረስዑ ፡ ነሚአ ፡ ኀብስት ። ይረስዕ ፡ ሊተ ፡ ኀጢአትየ ። ይረስዖ ፡ ለዘከነ ፡ ይፈቅዶ ። ኄረገ ፡ ለእግዚ ፡ ወረሳዕከ ። ትረስዕኑ ፡ ብእሲት ፡ ዕጓላ ፤ (ማቴ፲፮ ፡ ፭ ። ሚል፳፫ ፡ ፲፰ ። ማር ፡ ይሥ፩ ፡ ፲፩ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፲፰ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፲፭) ።

**ረሰዐ ፤ (ረሰሐ) ፤** መከፋት ፡ መባስ ፡ መጨከን ፤ መበደል ፡ መግፋት ፤ በግፍ ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ መሥራት ፤ ከጽድቅ ፡ መራቅ ፤ ግፈኛ ፡ ኃጥእ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ መኾን ፤ እንደ ፡ ፈርዖንና ፡ እንደ ፡ ሄሮድስ ። ምስጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ከመርሳት ፡ ይገባል ። ወበርእየ ፡ አሕባም ፡ ቦሙ ፡ ይረስዑ ፡ ወይፈርሁ ፤ ወዙሉ ፡ ግብሮሙ ፡ በሐሰት ፡ ይገብሩ ፤ (ሔኖ) ።

**ረሲዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ሳዕ) ፤** የሚረሳ ፡ ዝንጉ ፤ ግፈኛ ፡ ኃጥእ ፤ ክፉ ፡ መጥፎ ። ረሲዐ ፡ ዘረስዐ ፡ ቃለ ፡ መለኮት ፡ ዘተምህረ ። ዘይጌሥጽ ፡ ለረሲዐ ፡ ያሐይስ ፡ ርእሶ ። ይጐይይ ፡ ረሲዕ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘይዴግኖ ። ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢሖረ ፡ በምክረ ፡ ረሲዓን ፤ (ቀሌ ። ምሳ፱ ፡ ፯ ። ፳፰ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፩) ።

**ራስዕ ፤ (ዕት) ፤** የረሳ ፡ የዘነጋ ፡ ዝንጉ ፡ ልበ ፡ ቢስ ፤ ኃጥእ ፤ ሕገ ፡ ወጥ ። ኢትኩኑ ፡ ራስዐ ፡ ዘሰምዐ ። ከመ ፡ ሶበ ፡ ራስዕ ፡ ይወድቅ ፡ ውስተ ፡ ምንዳቤ ። ኢትኩንኑ ፡ ራስዐ ፡ ውስተ ፡ ሕግ ፤ (ያዕ፩ ፡ ፳፭ ። ዲድ ፡ ፫ ። ፩ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፳፩) ።

**ርስዐት ፤** መርሳት ፤ መዘንጋት ። ርሳታ ፡ ዝንጋታ ፤ ድንቍርና ፤ ኀጢአት ፡ ክፋት ። ርስዐት ፡ ዕሙቅ ። ወአስሐቶሙ ፡ ርስዐት ። ለዙሉ ፡ ግብር ፡ ቦቱ ፡ መከራ ፤ መከራሁ ፡ ለንጽሕ ፡ ዝሙት ፤ መከራሁ ፡ ለጽንዕ ፡ ድካም ፤ መከራሁ ፡ ለአእምሮ ፡ ርስዐት ። ልማደ ፡ እብሰት ፡ ወርስዐት ፤ (ጥበ፲፬ ፡ ፲፭ ። ፲፱ ፡ ፱ ። ፊላስ ። ጥበ፲፬ ፡ ፲፮ ። ሔኖ፷ ፡ ፱) ።

**ርስዓን ፤** ዝንጋዔ ፡ እበድ ፤ ኀጢአት ፡ ክፋት ። ረሲዐኒ ፡ ወርስዓኑ ፤ (ጥበ፲፱ ፡ ፱ ። መጽ ፡ ምስ ። ስንክ ፡ ጥቅ፱) ።

**ርስዕና ፤ (ናት) ፤** ረሲዕነት ፤ ዝንጋታ ፡ ቸልታ ፡ ኀጢአት ፡ ክፋት ፡ ግፈኛነት ። አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይገብሩ ፡ ርስዕናተ ፡ ወነገረ ፡ ሐሰት ፡ ይሴብሒ ፡ ወይከብሩ ፤ (ሔኖ፺፱ ፡ ፩) ።

**አርስዐ ፤** አስረሳ ፡ አስዘነጋ ፤ አረሳሳ ። አርሳዕከሙኒ ፡ ዘእፈቅድ ፡ እበሎ ። ያረስዖ ፡ ለሕዙን ፡ ሐዘኖ ። አርስዓ ፡ ዐቲበ ፡ ርእሳ ። ሐዘና ፡ ለልብ ፡ ያረስዕ ፡ ወይን ፤ (ዮሴፍ ። ገድ ፡ ዘሚ ። ቀሌ ። ሢራ፴፱ ፡ ፳፱) ።

— ፤ አሳተ ፤ አስከደ ፤ ኀጢአት ፡ አሠራ ። አርስዖ ፡ ምናሴ ፡ ለይሁዳ ፤ (ዲድ) ።

**መርስዒ ፤ ዕ ፤ (ዓን) ፤** የሚያስረሳ ፤ አስረሽ ፡ አረሳሽ ። መርስዒ ፡ ሐዘን ፡ መሬር ። ሐዘን ፡ ወፍሥሓ ፡ መርስዓን ፤ (ደራሲ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፫ ፡ ፱) ።

**ተረስዐ ፤** ተረሳ ፡ ተዘነጋ ፤ ጠፋ ፡ ታጣ ፡ ተሰወረ ፤ ራቀ ፡ ተለየ ፡ ባዕድ ፡ ኾነ ። ዙሉ ፡ ይትረሳዕ ። ተረስዐኒ ፡ በሊዐ ፡ እክል ። ተረስዐኒ ፡ ነገሩ ። አልቦ ፡ ዘተረስዐከ ። ተረስዐት ፡ እምዙሉ ፡ ሰብእ ። ይትረሳዕ ፡ ልቦሙ ፡ እምጥበብ ፤ (መክ፪ ፡ ፲፮ ። መዝ ፡ ፻፩ ። ዳን፪ ፡ ፭ ፡ ፰ ። ኢሳ፵ ፡ ፳፯ ። ኢዮ፳፰ ፡ ፳፩ ። ሔኖ፺፫ ፡ ፰) ።

**ርሱዕ ፤** የተረሳ ፤ የተዘነጋ ። ስሑት ፤ ርሱሕ ፤ ኃጥእ ፡ ኀጢአተኛ ፤ (ሄርማ ፡ ገ፺፭) ።

**ርሳስ ፤ (ዐረ ፡ ርጻጽ) ፤** በቁሙ ፤ የጥይት ፡ የጥፈት ። ቀለመ ፡ ርሳስ ፤ መጣፊያ ። ቀለም ፡ ዕንጨቱ ፡ ነው ፤ ባማርኛ ፡ ግን ፡ የርሳስ ፡ ቅጽል ።

**ረቲም ፤ ዎት ፤ (ረተመ ፡ ይረትም ፡ ይርትም ። ትግሬ ፡ ረትመ ። ዕብ ፡ ራታም) ፤** መጫን ፡ መጥመድ ፤ የፈረስ ፡ የሠረገላ ። መታመም ፡ በደዌ ፡ መጠመድ ፤ በሽተኛ ፡ መኾን ። ሐርተመን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ፤ ለንቀወ ፡ የንቀወ ፡ ውላጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

**ረቲዕ ፤ ዖት ፤ (ረትዐ ፡ ይረትዕ ፡ ይርታዕ ። ዕብ ፡ ራቶዕ ፤ ርዒድ ፡ ጸኒን) ፤** መርታት ፤ ማሸነፍ ፤ በሙግት ፡ በውጊት ። (ተረታ) ፡ ሳይረቱ ፡ አይበረቱ ። ረታዕከ ፡ አ ፡ ካልእየ ፤ (ቄር ፡ ጸላ) ።

— ፤ መቅናት ፤ ቀጥ ፡ ለጥ ፡ ማለት ፤ ቅን ፡ እውነተኛ ፡ መኾን ፤ አለመዛባት ፤ ማማር ፡ መበጀት ፡ መከናወን ፤ መጽናት ፤ መገባት ፤ የባሕርይ ፡ የግብር ፡ የነገር ። ጽድቅንና ፡ ቅንነትን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎሮች ፡ ናቸው ። ጠዋይ ፡ ኢይክል ፡ ረቲዐ ። ይረትዕ ፡ ልሳኑ ፡ በሃይም ። ሊተኒ ፡ ረትዐኒ ። ረትዐ ፡ መንግሥቱ ፡ ለፈርዖን ። በእንተ ፡ ጸሎቱ ፡ ይረትዕ ፡ ዓለም ። ወናሁ ፡ ይረትዕ ፡ ሊተ ፡ ተመክሮ ፤ (መክ፩ ፡ ፲፭ ። ኢሳ፴፪ ፡ ፬ ። ሉቃ፩ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፵ ። ስንክ ፡ የካ፳ ። ፪ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፭) ።

**ራትዕ ፤ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት) ፤** በቁሙ ፤ የረታ ፡ የቀና ፤ ቅን ፡ እውነተኛ ። ብእሲ ፡ ራትዕ ። ጻድቅ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ወራትዕ ። ወለራትዓን ፡ ይደልዎሙ ፡ ክብር ፤ (ኢዮ፩ ፡ ፩ ። ራእ፲፮ ፡ ፭ ። መዝ ፡ ፴፪) ። በራትዕ ፡ ፈንታ ፡ ርትዕ ፡ ይላል ፤ የተባባተ ፡ ነው ፤ (መዝ፲ ፡ ፫) ።

**ርቱዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ትዕት) ፤** የቀና ፤ ቀጥ ፡ ያለ ፤ የተካከለ ፤ ዐባጣ ፡ ጐባጣ ፡ ያይደለ ። ርቱዕ ፡ እገሪሆሙ ። ርቱዓኒ ፡ ልብ ። ፍናው ፡ ርቱዓት ። ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፤ (ሕዝ፩ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፻፳ ። ምሳ፰ ፡ ፲፫ ። ቅዳ) ።

**ርቱዕ ፤ (ይደሉ ፤ መፍትው) ፤** ይገባል ፤ የተገባ ፤ የሚገባ ፡ ግቡ ፤ አግባብ ። ርቱዕ ፡ ይትወከፍዎ ። ርቱዕ ፡ ታጥርዮ ። አኮ ፡ ርቱዕ ፡ ያስተአክይዎ ። ርቱዕ ፡ ትብክዩ ፡ ለዘሞተ ። ርቱዕ ፡ ይሑር ። ርቱዕ ፡ ይሙት ። ኢኮነ ፡ ርቱዐ ፡ ይኅድጎሙ ፡ ንጉሥ ፤ (፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፱ ። ኤር፴፱ ፡ ፯ ። ሢራ፲ ፡ ፳፫ ። ፳፪ ፡ ፲፩ ። ፴ንገ ፡ ፳ ፡ ፫ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፯ ። አስቴ፫ ፡ ፰) ። ቀመ ፡ ርቱዐ ፤ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ተሸፈሸፉ ። ሖረ ፡ ርቱዐ ፤ ቀንቶ ፡ አቅንቶ ፤

ፌት ፡ ለፌት ። ዘበርቱዐ ፡ ትኄንን ፤ ባገባብ ፡ በሚገባ ፡ በውነት ፡ በቅንነት ።

**ርቱዐ ፡ ሃይማኖት** ፤ የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ታላቅ ፡ መጣፍ ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የጣፉት ፤ አርቶዶክሳዊ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ርትዐት** ፤ መርታት ፡ ርታታ ። መቅናት ፡ አቀናን ፤ ቅንነት ፤ ቀጥታ ። ይቀልል ፡ ርትዐቱ ። ርትዐተ ፡ ልብ ። ወርትዐት ፡ መሰየልየ ፡ ሥጋ ፡ ይጸንዕ ፡ በበሕቁ ፡ (አፈ ፡ ድ፴፩ ። ፍ ፡ ን ፡ ፲ ፡ ፮ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ቄር) ።

**ርትዕ** ፤ (ዓት ። ዕብ ፡ ሚሽፋጥ ፤ ኤሜት ፤ ጽዳቃ) ፤ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፤ የቀና ፡ የተካከለ ፤ ሐሰትና ፡ ግፍ ፡ የሌለበት ፤ የሚገባ ፡ ሥራ ፤ ሕግ ፡ ትእዛዝ ፤ የተጣፈ ፡ የተወሰነ ፤ (ዘዐ፳፩ ፡ ፩—፴፮) ። ማህል ፡ ወርትዕ ፡ ተራከባ ፤ ርትዕሰ ፡ እምድር ። ፍትሐ ፡ ወርትዐ ፡ ተድላ ፡ መንበሩ ። ይቀንት ፡ ጽድቀ ፡ ወይትዐጸፍ ፡ ርትዐ ። ኢነበብክሙ ፡ ርትዐ ። ወኢንገብራ ፡ ለጽድቅ ፡ ወለርትዕ ። ሎግዮ ፡ ዘበነገረ ፡ ጽድቀ ፡ ወርትዐ ፡ (መዝ ፡ ፹፬ና ፡ ፹፰ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፭ ። ኢዮ፴፱ ፡ ፰ ። ፩ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፯ ። ሚራ፴፩ ፡ ፲) ። የጽድቅና ፡ የርትዕ ፡ ፍቻቸው ፡ ስለ ፡ ገጠመ ፡ በጽድቅ ፡ ፈንታ ፡ ርትዕ ፤ በርትዕ ፡ ፈንታ ፡ ጽድቅ ፡ ይላል ፤ ንባብ ፡ እንጂ ፡ ምስጢር ፡ አያፈርስም ፤ ስሕተትነቱ ፡ ጥቂት ፡ ነው ።

**አርትዐ** ፤ አስረታ ። አቀና ፤ አጠና ፤ አበጀ ፡ አዘጋጀ ፤ ቅን ፡ አደረገ ፤ አስደረገ ። አርታዕከ ፡ ነገረ ። ክመ ፡ ያርትዕ ፡ እገሪ ። አረትዐ ፡ መንበረ ፡ መንግሥቱ ። እግዚ ፡ አርትዐ ፡ ዓለመ ፡ በጥበቡ ። አርትዐ ፡ ኵሎ ፡ ጠዋየ ። አርትዐ ፡ ልበከ ። አርታዕኩ ፡ ነፍስየ ፡ (ቄር ፡ ጸሎ ። ሉቃ፩ ፡ ፫ ። ፩ዜና ፡ ፳፪ ፡ ፲ ። ኤር፲ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፵፫ ፡ ፯ ። ሚራ፪ ፡ ፲ ። ፲፬ ፡ ፳) ። በአርትዐ ፡ ፈንታ ፡ አስተራትዐ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እግዚ ፡ ዘይገብር ፡ ኵሎ ፡ ወያስተራትዐ ። ከመ ፡ ያስተራትዕ ፡ ፍትሐ ፡ ለማኅፈኑ ። ኤልያስ ፡ ይቀድም ፡ መጺአ ፡ ወያስተራትዐ ፡ ኵሎ ። ከመ ፡ ታስተራትዕ ፡ ዘተርፈ ። ናስተራትዐ ፡ ሃይማኖተ ፡ (ዓሞ፭ ፡ ፰ ። ሚራ፲፱ ፡ ፳፭ ። ማቴ፲፯ ፡ ፲፩ ። ቲቶ፩ ፡ ፭ ። ገድ ፡ ተክ) ።

**መርትዒ ፡ ዕ** ፤ የሚያቀና ፤ ቅን ፡ የሚያደርግ ። መርትዐ ፡ ጠበብት ፡ (ጥበ፯ ፡ ፲፭) ።

**ተረትዐ** ፤ ተረታ ፤ ተሸነፈ ፤ ድል ፡ ኾነ ።

**ተራትዐ** ፤ ተረታታ ፤ ተነጣጠረ ። ተቀናና ፤ ተዘገጃጀ ፤ ተከንዋወነ ፤ ተሳካ ። እስከ ፡ አመ ፡ ይትራትዕ ፡ (ዕብ፱ ፡ ፲) ።

**አስተራትዐ** ፤ አረታታ ። አቃና ፤ አቀናና ፤ አዘገጃጀ ። ታስተራትዕ ፡ ኵሎ ፡ ነፍስ ። ታስተራትዕ ፡ ምድረ ፡ (ዮዲ፲፩ ፡ ፯ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፰) ።

**መስተራትዕ** ፤ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት) ፤ የሚያቃና ፤ ፈጣን ፡ ቀልጣፋ ፤ ቁመታም ፡ ደረታም ፡ ጎደለኛ ፤ የጭፍራ ፡ አለቃ ፤ ባለወግ ፡ ጭፍራ ፡ ዘበኛ ፤ ያዥ ፡ ጨባጭ ፤ አሳሪ ፡ ቀጪ ፤ ፈላጭ ፡ ቈራጭ ፤ ሰያፊ ፡ ገራፊ ፤ ሰቃይ ፡ ገዳይ ። መስተራትዓኒ ፡ ሐራ ፡ (ማቴ፳፯ ፡ ፳፯ ። ማር፲፮ ፡ ፲፮ ። ዳዊ ፡ ፳፩ ። መቃ ፡ ፫) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በመስተራትዓን ፡ ፈንታ ፡ መስተራትዓት ፡ ይላል ፤ የጣፈ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

# ሰ

**ሰ** ፤ ኻያ ፡ አንደኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፤ ስሙ ፡ ሳት ፤ ሰዓት ፤ ቍጥሩ ፡ ፷ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ ስ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፤ ሦስት ፡ መቶ ፡ ይባላል ። ሠውት ፡ ሠና ፡ ሳት ፡ ስ ፡ ተዛውረው ፡ ስለ ፡ ተጣፉና ፡ ሳቱ ፡ ስ ፡ በሠውት ፡ ሠ ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የውጣ ፡ ሠረገ ፡ ቀርናዊ ፡ ነቍጣ ፡ ሲኾንበት ፡ ሸ ፡ ይባላል ። ከ ፡ በነቍጣ ፡ ምክንያት ፡ ኸ ፡ እንዲባል ፡ ይኸም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ፤ በጥንታዊው ፡ ባሮጌው ፡ ግእዝ ፡ ግን ፡ ሸ ፡ የሚባል ፡ ሠውት ፡ ሠ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሳቱ ፡ ስ ፡ አልነበረም ፤ የቀረውን ፡ በሠውት ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ።

**ሰ** ፤ (አገባብ) ፤ ሳ ፤ ስ ፡ ትቶ ፤ ማ ፤ ና ፡ ግን ፡ ይኾናል ፤ ምስጢሩና ፡ ስልቱ ፡ አፍራሽነት ፡ ነው ። ሳ ፡ ሲኾን ፡ በጥያቄ ፡ ቃል ፡ ይገባል ። ሊቅክሙሰ ፡ ኢይሁብኑ ፡ ጸባሕተ ፤ መምራችኹሳ ፡ (ማቴ፲፯ ፡ ፳፬) ። ሲከታትል ፡ ግን ፡ ፈተኛው ፡ ስ ፡ ወይም ፡ ትቶ ፤ ኋለኛው ፡ ሳ ፡ ይኾናል ። ጴጥሮስሰ ፡ ነስሐ ፡ በእንተ ፡ ዘክሕደ ፤ ይሁዳሰ ፡ ኢነስሐኑ ። አንተሰ ፡ መጻእከ ፡ እኁክሰ ፡ ተርፈኑ ። ይሁዳሳ ፤ ወንድምኸሳ ። ጥያቄ ፡ በሌለው ፡ ሲገባ ፡ እንዳወራረዱ ፡ ይፈታል ፤ ወልድየሰ ፡ ሞተ ፤ ልጄስ ፡ ሙቷል ፤ ልጄማ ፡ ሙቶ ። ሕያው ፡ ውእቱሰ ፤ ርሱስ ። አንተሰ ፡ አንተ ፡ ክመ ፤ አንተማ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አንተስ ፤ ያሰኛል ። ወእመሰ ፡ ታፈቅሩ ፡ ዘያፈቅረክሙ ፤ የሚወዳችኹንማ ። ና ፡ ሲኾን ፤ ይጸናሕሰ ፡ ይትርፍሰ ፡ እያለ ፡ በትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባል ። ትችና ፡ ስ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ ትቶ ፡ ሲኾን ፡ ወ ፡ ሂ ፡ ኒ ፡ ግን ፡ እየኾኑ ፡ ይከተሉታል ። ይህም ፤ ለዕሉያንሰ ፡ ይትቃወሞሙ ፡ ወለትሑታን ፡ ይሁቦሙ ፡ ክብረ ። ቃልሰ ፡ ቃለ ፡ ያዕቆብ ፡ ወእደው ፡ ዘዔሳው ። ለእድግሰ ፡ አቅሕም ፡ ወ

ለንብርኒ ፡ ገሥጸ ፡ እያለ ፡ ሊሳሙን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ስትፈታም ፡ ትቢተኞችን ፡ ይቃወማቸዋል ፤ ለትሑታን ፡ ግን ፡ ክብር ፡ ይሰጣቸዋል ፡ በል ። ግን ፡ ሲኾን ፡ እንበ ፡ እብለክሙ ። እንትሙሰ ፡ ሶበ ፡ ትጼልዩ ። ዘቲሰ ፡ እ ብእት ፡ ሽሎ ፡ ዘበ ፡ እያለ ፡ በኹሉ ፡ ይገባል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ስ ፡ ለማለት ፡ ሰን ፡ አለበታው ፡ ያስቀድማል ፤ የመላሽና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ በጽርእም ፡ በሰብሉ ይስጥም ፡ አይገኝ ። ይህም ፤ ሰብእሰ ፡ ገጸ ፡ ይሬኢ ፡ ወእግዚአብሔርሰ ፡ ልበ ፡ ይሬኢ ። እሙንቱሰ ፡ ተዐ ቅጹ ፡ ወወድቁ ፡ ወንሕነሰ ፡ ተንሣእነ ፡ ወረታዕነ ። ቤትየሰ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ፡ ይሰመይ ፡ ወእንትሙሰ ፡ ረሰ ይክምዎ ፡ በአተ ፡ ፈያት ፡ እያለ ፡ ሊሳሙን ፡ ኹሉ ፡ ያሳ ያል ። ዳግመኛም ፡ ተምኔትየ ፤ በእለትየ ። እስመ ፡ እፈቱ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ ይረትዐሰ ፡ ይርታዐ ፡ ፍኖትየ ። እፈ ቱሰ ፡ እፍልስ ፡ እያለ ፡ አሳንባቡ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ፡ (ዕርሻ ፡ ቍ፻፷፰) ።

ሰ ፤ (ዕብ ፡ ናእ) ፤ ትእምርተ ፡ ስኢል ፡ ዐቢይ ፤ የምልጃ ፡ የልመና ፡ ቃል ፡ እባክኽ ፤ እባክኽ ። ሲገባም ፡ በመጨረሻ ፡ ቃል ፤ በማልላይ ፡ አንቀጽ ፡ ይገባል ፤ ልመ ናው ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ነው ። የአን ፡ እፈታት ፡ ተመል ከት ፡ የዚህ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ነው ። አምላክ ፡ ኄያሳን ፡ ተ መየጥሶ ። ኦ ፡ እግዚኦ ፡ አድኅንሶ ፤ ሠርሕሶ ፡ (መዝ ፡ ፻፲ ። ፻፳፯) ። ኹለተኛም ፡ እንደ ፡ ሰብራይስጡ ፡ ኑ ፡ ኹኖ ፡ በንሕኑ ፡ ዝርዝር ፡ ይፈታል ። ይህም ፤ ተመየጥሶ ፤ ተመ የጠነ ፤ ተመየጥ ፤ ሰነ ። አድኅንሶ ፤ አድኅነነ ። ሠር ሕሶ ፤ ሠርሕነ ፤ ሠርሕ ፡ ሰነ ፡ እያለ ፡ መኺዱን ፡ ያሳ ያል ። (ዕርሻ ፡ ቍ፻፶) ።

ሰኢበ ፤—ረከሰ ፤—ሠአበ ።

ስኢል ፤ ሎት ፤ (ሰአለ ፡ ይስእል ፡ ይስ አል ። ዕብ ፡ ሻአል ። ሱር ፡ ሼእል ። ዐረ ፡ ሰአለ) ፤ መለመን ፤ መፈለግ ፡ መሻት ፤ እባክኽ ፡ ስጠኝ ፡ አድርግልኝ ፡ ማለት ፤ መማለድ ። መጠየቅ ፤ መመርመር ፤ ለማወቅ ፡ ለማግኘት ። ሐይወቱ ፡ ለነዳይ ፡ ስኢለ ፡ ምፅ ጽዋት ። ሰአሉ ፤ ወይትወሀበክሙ ፤ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘሰአለ ፡ ይነሥእ ፤ በአሊ ፡ ሰነ ፤ ለመነ ፡ (ሚሬ ፴፯ ፡ ፳፩ ። ማቴ፯ ፡ ፯) ። ይስእልዎሙ ፡ ለአማልክት ። ሶረት ፡ ትስእል ፡ ኄበ ፡ እግዚአብሔር ። በእንተ ፡ መኑ ፡ ትስ እል ፡ ወትጤይቅ ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፫ ። ዘፍ፳፬ ፡ ፳፱ ። ሔኖ ፳፩ ፡ ፭) ። ብዙው ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰአለ ፡ ፈንታ ፡ ተሰእለ ፤ ተሰአለ ፤ ተሰእሎት ፡ ይላል ፤ ባለቅኔዎችም ፡ እን ዲሁ ፡ ይላሉ ፤ የስሕተት ፡ ልማድ ፡ ነው ። የግስ ፡ ርባ ፡ አካኼድ ፡ የአዕማድ ፡ መንገድ ፡ ከአእመረ ፡ ጀምሮ ፡ እን ደሚገባው ፡ አልታወቀም ፤ አልተጠነቀቀም ። ወእመሂ ፡ ተስእልክዎሙ ፡ ኢይሰጠዉኒ ። ተሰአሎ ፡ በአቡከ ፡ ወይነግረከ ። ተስእሎት ፡ ዘተሰእልዎ ፡ ካልኣን ። ተሰ አሎ ፡ እግዚ ፡ ለኢዮብ ፡ (ኢሳ፷፭ ፡ ፳፰ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፯ ። ሰንክ ፡ የካ፲ ። ድጓ) ። ሰንአለን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ስ ፊጽ ፡ ነው ።

ሰአሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ አልት) ፤ የሚለምን ፤ የሚጠይቅ ፤ ለማኝ ፡ ጠያቂ ፤ ማላጅ ። ሰአ ሊተ ፡ ምሕረት ፡ ለኃጥአን ። ሰአሊት ፡ ሕይወተ ፡ ለነፍሳቲነ ፡ (ግንዘ ። ቅዳ ። ኤፍ ፡ ፭) ።

ሰአልት ፤ ለማኞች ፤ ጠያቆች ፤ መርማሮች ። የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ መጽሐፈ ፡ ሰገል ፤ የጥንቈላ ፡ መጽ ሐፍ ፤ እንዳወደ ፡ ነገሥት ፡ ያለ ።

መስእል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤ ጠንቋይ ፤ ጋኔን ፡ ሳቢ ፤ ሙት ፡ ጠሪ ፤ ባለስአልት ። አስጠንቋይ ፡ ጠንቋይ ፡ ጠያቂ ፡ (ሲኖ ዶ) ።

ምስኣል ፤ (ላት) ፤ መለመኛ ፤ መማለጃ ፡ መጠየቂያ ፡ ዐቃ ፤ ቤት ፡ ክሊያን ። ትኩን ፡ ምስኣለ ፡ ወምስጋደ ፡ ወምስትስራየ ፡ ኀጢአት ፡ (ቀሌ ። ድጓ ። እርጋ ፡ ፱) ።

አስአለ ፤ አስለመነ ፤ አስጠየቀ ፤ አስማለደ ፡ አማ ላጅ ፡ ላከ ። ዐቢየ ፡ ነቢየ ፡ ዮሐንስሀ ፡ አስአልነ ፤ ያስተ ምሕር ፡ በእንቲአነ ፤ ማህልከ ፡ ወትረ ፡ ይብጽሐነ ፡ (መዋሥ) ።

ተስእለ ፤ (ተደራጊ) ፤ ተለመነ ፤ ተጠየቀ ፤ ተመረመረ ፤ ተለማኝ ፡ ተጠያቂ ፡ ኾነ ።

ስኡል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ እልት) ፤ የተለመነ ፤ የተጠየቀ ፤ ልምን ፡ ጥይቅ ።

ስእለት ፤ (ታት) ፤ መለመን ፤ አለማመን ፤ ልመና ፤ ፍላጎት ፡ ምልጃ ፤ ጸሎት ፤ ጥየቃ ። ኀፈርኩ ፡ ስእለቶ ፡ ለንጉሥ ፡ ኄይለ ፡ ወአፍራሰ ። ስእለት ፡ ብየ ፡ እንተ ፡ እስእል ፡ እምኔከ ። ምንት ፡ ውእቱ ፡ ስእለትኪ ። ወከነ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ስእለት ። ለባእኩ ፡ ተዘካረ ፡ ስእለትክሙ ። ወተስእሎቱ ፡ ከመ ፡ እጽሐፍ ፡ ተዝካረ ፡ ስእለት ፡ (ዕዝ፰ ፡ ፳፪ ። ኩፋ ፡ ፴፭ ። አስቴ፯ ፡ ፪ ። ሄኖ ፡ ፲፫ ፡ ፬ ። መቢ፲፪ ፡ ፲፪ ። ሔኖ፲፫ ፡ ፪ ። ፲፱ ፡ ፯) ።

ተስእሎ ፤ ሎት ፤ (ታት) ፤ (ጥ ፡ ስጠ) መለመን ፤ መጠየቅ ፤ ተለማኝ ፡ ተጠያቂ ፡ መኾን ። ል ማዱ ፡ ግን ፡ አድራጊነት ፡ ነው ። ክፍል ፡ ቀዳሚ ፤ እም ተስእሎታተ ፡ ዜናሆሙ ፡ ለአበው ፡ መነኮሳት ፡ (ፈ ልክ ፡ ፭) ።

ተሳአለ ፤ (ተደራራጊ) ፤ ተለማመነ ፤ ተጠ ያየቀ ፤ ተመራመረ ፡ (ማቴ፲ ፡ ፲፭) ።

ተሳእሎ ፤ መጠያየቅ ፤ መመራመር ፤ ርስ ፡ በርሱ ።

አስተሳአለ ፤ አላመነ ፤ አለማመነ ፤ አጠያየቀ ፤ አሟገተ ፡ አከራከረ ፤ ተጠየቅ ፡ አሰኘ ።

ሰአለ ፤—ሣለ ፡ መሰለ ፤—ሥዒል ፡ ሠ ዐለ ።

ሰአለ ፤—ሳለ ፡ ሳላም ፡ ኾነ ፤—ሰዐለ ።

ሲኦል ፤ (ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሽኦል) ፤ በቁሙ ፤ ታሕተ ፡ ምድር ፤ ልበ ፡ ምድር ፤ መቃብር ፤ የግዞት ፡ ቦታ ፤ መከን ፡ ኃጥአን ፤ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ፀርብ ፡ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ የነበሩበት ። እክሉ ፡ ክሠት ፡ ሲኦል ፡ በቅድሜሁ ። ሞ

ትሂ ፡ ወሲኦል ፡ ይቤሉ ። ወኢድኅንከ ፡ ለነፍስየ ፡ እምሲኦል ፡ ታሕቲት ። መራኁተ ፡ ሞት ፡ ወሲኦል ። አናቅጸ ፡ ሲኦል ፡ (ኢዮ ፴፰ ፡ ፲፯ ። ፹፰ ፡ ፳፪ ። መዝ ፡ ፹፰ ። ራእ ፩ ፡ ፲፰ ። ማቴ ፲፮ ፡ ፲፰) ።

**ሰአመ ፤—ሰመ ፡ ለከፈ ፤—ስዒም ፡ ሰዐመ ።**

**ሲኢን ፤ ኖት ፤ (ስእነ ፡ ይስእን ፡ ይስአን ። ዕብ ፡ ሽኤን ፤ ንህየ ። ያሼን ፤ ኖመ) ፤** መሳን ፤ መድከም ፤ መታከት ፤ ኀይል ፡ ክሂል ፡ ሥልጣን ፡ ማጣት ፤ አለመቻል ፤ የማይቻለው ፡ መኾን ። ስእኑ ፡ አውሥአቶ ፡ ለኢዮብ ። አናብስት ፡ ስእኑ ፡ ይግስስዎ ። ኅሠሥኩ ፡ አእምሮ ፡ ወስእንኩ ። ለእመ ፡ ስእነ ፡ ብእሲ ፡ ለኪበ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ለአቅሞ ፡ ዘርዐ ፡ ወዝንቱ ፡ ስኢን ፡ ይከውን ፡ እምሥለስቱ ፡ ምክንያት ። ስኢነ ፡ ተፀግሦ ፡ (ኢዮ ፴፪ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ጳጉ ፭ ። ሉቃ ፡ ፅዝ ፲፫ ፡ ፳ ። ፊ ፡ መ ፡ ፲፪ ፡ ፳ ። ፩ተሰ ፡ ፫ ፡ ፩) ።

**ተስእነ ፤** ተሳነ ፡ አቃተ ፤ የማይቻል ፡ ኾነ ፡ ቸሎቱ ፡ ታጣ ። **እፈቅድ ፡ እምጻእ ፡ ኀቤክሙ ፡ ወይስእነኒ ። ወሶበ ፡ ተስእኖ ፡ ለሕግ ፡ ጸሪት ፡** (ሮሜ ፩ ፡ ፲፫ ። ፰ ፡ ፫) ።

**ስኡን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ እንት) ፤** የተሳነው ፤ ችሎት ፡ ያጣ ፤ የማይችል ፤ ደካማ ፡ ሕጹጽ ። **ኃጥእ ፡ ወስኡን ፡ ወእብድ ። መሐይምት ፡ ስኡን ። ብርከ ፡ ስኡናን ። ድካሞሙ ፡ ለስኡናን ፡** (ፊልክ ፡ ፩ ። ቄር ። ኢዮ ፬ ፡ ፬ ። ሮሜ ፲፭ ፡ ፩) ።

—፤ የሚሳን ፡ የሚያቅት ፡ ተስፋ ፡ የሚቀር ፤ የማይቻል ፡ ሥራ ። **አልቦ ፡ ስኡን ፡ በኀቤሁ ፡ ለዘሐሎ ፡ ይክል ፡** (ቄር) ።

**ስእንት ፤** መድከም ፤ ችሎት ፡ ማጣት ፤ ደካምነት ፤ ኢክህሊነት ። **ኢክነት ፡ ምክንያተ ፡ ስእነት ፡ ላዐሌሁ ፡ ለነገር ፡** (ቄር ፡ ፕ፷፭) ። ዕቅጸቶሙ ፡ ድቀቶሙ ፡ በማሰት ፡ ፈንታ ፡ ስእንቶሙ ፡ ይላል ፤ የመሳኘና ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ኤር ፲፰ ፡ ፳፫) ።

**ሳእን ፤—ጫማ ፡ መጫሚያ ፤—ሣእን ።**

**ሳእር ፤—፫ቁሙ ፡ ሣር ፤—ሥዒር ፡ ሥዕረ ።**

**ሰአረ ፤—ሻረ ፤—ስዒር ፡ ሰዐረ ።**

**ሶበ ፤—ጊዜ ፤—ሰዊብ ፡ ሰወበ ፤—ሶብ ።**

**ሰቢእ ፤ እት ፤ (ሰብአ ፡ ይሰብእ ፡ ይስባእ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሻባዕ ። ዐረ ፡ ሸቢዐ) ፤** ፈጽሞ ፡ መጥገብ ፤ መርካት ፤ አብገዘቶ ፡ ማግኘት ፤ የምግብ ፡ የገንዘብ ። መፅነስ ፡ ማርገዝ ፤ መንጠርዘዝ ፤ የሰብልና ፡ የሴት ። ሰብዐን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**አስብአ ፤** አጠገበ ፡ አስረገዘ ።

**ሰብእ ፤ (ዕብ ፡ ሽባእ ፤ ስባእ ፤ ሰመ ፡ ነገድ ፤ ሳባ) ፤** ባሕርያዊ ፡ ስም ፤ በቁሙ ፤ ሰው ፤ አዳም ፤ የአዳም ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፤ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ያለው ። ከነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፤ በነፍስ ፡ አካልነት ፡ የቆመ ፡ የተፈጸመ ፤ ሥጋ ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ነፍስ ፡ ብቻ ፡ ያይደለ ፡ ፍጹመ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፤ ፍጹመ ፡ ጸጋ ፡ ምሉአ ፡ ጸጋ ። **ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርኣያነ ፡** (ዘፍ ፩ ፡ ፳፮ ። ፪ ፡ ፯) ። ስምነቱ ፡ ጠቅላይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለወንድም ፡ ለሴትም ፤ ላንድም ፡ ለብዙም ፡ ይነገራል ፤ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ይህም ፤ **አንበ ፡ ዐዌ ፡ ወአኮ ፡ ሰብእ ፤ ምኑን ፡ በኀበ ፡ ሰብእ ። ሰብአ ፡ ወእንስሳ ፡ ታድኅን ። እሉ ፡ ሰብእ ፡ ዘሉ ፡ ሰብእ ፡** እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ። ዳግመኛም ፡ በሰምና ፡ በግብር ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ እየተናበበ ፡ እንዳወረዱ ፡ ይፈታል ።

**ሰብአ ፡ ቤት ፤** ቤተ ፡ ሰብ ፤ ዘመድ ፤ ወገን ፡ ነገድ ፤ ሎሌ ፡ ገረድ ፡ (ዘፍ ፴፩ ፡ ፪) ።

**ሰብአ ፡ ዐይን ፤** ጉበኛ ፡ ሰላይ ፤ ተመልካች ፤ አስተዋይ ፡ (ሕዝ ፫ ፡ ፲፯) ።

**ሰብአ ፡ ሐጽ ፡ ወቀስት ፤** ቀስተኞች ፤ ባለ ቀስቶች ፡ (ኢሳ ፳፩ ፡ ፲፯) ።

**ሰብአ ፡ አፍራስ ፤** ፈረሰኞች ፤ ፈረስ ፡ ፀዋቆች ፤ ለጓሞች ፡ ባልደራሶች ፡ (ኤር ፬ ፡ ፳፱) ።

**ሰብአ ፡ ምሥያጥ ፤** ገባያተኞች ፤ ነጋዶች ፡ ዐጣሮች ፡ ባለመደብሮች ፡ (ግብ ፲፯ ፡ ፭) ።

**ሰብአ ፡ ዜና ፤** ወሬኞች ፤ ወሬያሞች ፤ ወሬ ፡ ነጋሮች ፤ ባለምሥራቾች ፤ ታሪክ ፡ ዐዋቆች ፡ (ናሖ ፩ ፡ ፲) ።

**ሰብአ ፡ ሊዝያኒ ፤** ኮከበኞች ፡ ኮከብ ፡ ቈጣሮች ፤ የኮከብ ፡ ፈላስፎች ፤ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ (አቡሻ ፡ ፲፩) ።

**ሰብአዊ ፤ (ዊት) ፤** የሰው ፤ ሰዋም ፡ ባለሰው ፤ ሰውማ ፡ ሰውኛ ፤ በሰው ፡ ያደረ ፡ የተጠጋ ፤ ባሕርያዊ ፤ ጠባይዓዊ ። **መፍትው ፡ ይሰመይ ፡ ሰብአዊ ፡ ወአኮ ፡ ሰብአ ፤ እስመ ፡ ዘነደራ ፡ ለናዝሬት ፡ ተሰምየ ፡ ናዝራዊ ፡ ወኢተሰምየ ፡ ናዝሬተ ። ግብር ፡ ሰብአዊ ። አሕጽጽ ፡ አእምሮተከ ፡ ሰብአዊተ ፡** (ቄር ፡ ጸላ ። አፈ ፡ ድ ፴፫ ። ፊልክ ፡ ፹፪) ።

**ሰብኢት ፤** ሰዎች ፡ ወገኖች ፤ የቅርብ ፡ ዘመዶች ። **ሰብአቲሁ ፡** (ዘሌ ፳፩ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱) ።

**ሰብእና ፤** ሰውነት ፤ ሰው ፡ መኾን ፤ የሰው ፡ ባሕርይ ፤ አካሉ ፡ ገላው ፤ ኹለንተናው ፤ ኹለመናው ። **ሰብ ፡ ቀግህደ ፡ ሰብእናሁ ። ተውህበ ፡ በሰብእናሁ ። በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ሰብእናሆሙ ፡ ቀተሉ ። ሰብእና ፡ ዚአየ ፡ እሙር ፡** (ቀሌ ። ቄር ፡ ጸላ ። ድጓ ። አዋል) ።

**ተሰብአ ፤** ተወገበ ፤ ተረገዘ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፤ ሥጋ ፡ ለበሰ ፤ ነፍስንና ፡ ሥጋን ፡ ነሣ ፤ ተዋሐደ ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ ሰው ፡ ተባለ ፤ በሰው ፡ ስም ፡ ተጠራ ። **ተሠገወ ፡ ወተሰብአ ፡ እምድንግል ። ተሰብአ ፡ እምድንግል ። ተሰብአ ፡ እማርያም ። ውእቱ ፡ ይቤሎ ፡ ከመ ፡ ቃሉ ፡ ይሰባእ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ። ሰልየ ፡ በእደየ ፡ ለሐዙዋ ፡ ለድንግል ፡ እንተ ፡ እምኔሃ ፡ ተሰባእኩ ። አምላክ ፡ ተሰባኢ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡** (ዲድ ፡ ፲፱ ። ቀሌ ። ድጓ ። ማር ፡ ይሥ) ።

**ተሰብአ፤ እት፤** መፀነስ ፥ መረገዝ ፡፡ ሰው ፥ መኾን፤ ሥጋ ፥ መልበስ፤ የአዳምን ፥ ባሕርይ ፥ መንሣት ፡፡ ተሰብአተከ ፤ እመ ፤ ቦ ፤ ዘያስተሐቅር ፡ መኒኖ ፤ (ድራሲ ፡፡ አርጋ ፡ ፩) ፡፡

**ሰቡእ፤ (ኣን ፡ ኣት ፡ ብእት)፤** ሰው ፥ የኾነ ፥ ልቡስ ፥ ሥጋ ፡፡ ሰይጣን ፤ ሥግው ፤ ወጋኔን ፡ ሰቡእ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ፡፡

**ትስባኤ፤** ሰው ፥ መኾን ፥ ሰውነት ፤ የሰውነት ፥ ገላ ፤ ባሕርይ ፡፡ ሰብእናን ፥ ቀመልክት ፤ ከዚህ ፥ ጋራ ፥ አንድ ፥ ነው ፡፡ ዐሩቀ ፤ እመለኮት ፤ ረሰዩ ፤ ትስባኤ ፤ (ስንክ ፡ ጥቅ፲፱) ፡፡

**ትስብእት፤** ዝኒ ፥ ከማሁ ፤ ሰውነት ፥ ሰው ፤ ፍጹም ፥ የሰው ፥ ባሕርይ ፤ ኹለንታ ፥ ሰብእ ፤ ነፍስና ፥ ሥጋ ፤ ወይም ፥ ነፍስ ፥ ያለው ፥ ሥጋ ፡፡ ትስብእቱ ፤ ለዋሕድ ፡፡ መለኮት ፡ ወትስብእት ፤ (አምላክነትና ፥ ሰውነት ፤ አምላክና ፥ ሰው ፤ ወይም ፥ ቃልና ፥ ሥጋ) ፡፡ እመ ፤ ቦ ፤ ዘይቤ ፤ ጸየኬ ፤ ዘወለደት ፤ ድንግል ፤ ሚመ ፤ ትስብእተ ፤ ወሚመ ፤ መለኮተ ፡፡ ኢትፍልጥ ፤ ሊተ ፤ እምድኅረ ፤ ትድምርት ፤ እስመ ፤ ዘፈለጠ ፤ እንተ ፤ ባሕቲቱ ፤ ብእሴ ፤ ወእንተ ፤ ባሕቲቱ ፤ አምላክ ፤ ቃለ ፤ ክልኤተ ፤ ይሬስዮ ፤ ለዐማኑኤል ፤ (ቄር ፡ እሰት) ፡፡

**ሰቢብ፤ ቦት፤ (ሰብ፤ ሰበበ ፡ ይሰብብ ፡ ይስብብ ፡፡ ዕብ ፡ ሳብብ)፤** መዞር ፥ ማቀፍ ፥ መከበብ ፤ ዙሮ ፥ መግጠም ፤ መጠምጠም ፡፡ መፍሰስ ፤ መንዛት ፤ መረጨት ፥ መሠራጨት ፤ የመርዝ ፥ የስራዊት ፡፡ ወደጎሬታ ፤ ከመ ፤ ንስክተ ፤ አርዌ ፤ ምድር ፤ ትሰፍሕ ፤ ወከመ ፡ ዘእምቃግስት ፡ ይሰብቦ ፡ ሕምዙ ፤ (ምሳሽ፫ ፡ ፴፪) ፡፡

—፤ መሸበብ ፤ በሽባ ፥ መያዝ ፥ መሳብ ፡፡ መሰበብ ፤ ሰበብ ፥ መሻት ፤ ምክንያት ፥ መፈለግ ፤ በዙሪያ ፥ መኼድ ፤ ነገርን ፥ ለማፍረስ ፡፡ ሰወበን ፥ ቀመልክት ፤ የዚህ ፥ መንቲያ ፥ ነው ፡፡

**ሰባቢ፤** ከባቢ ፥ ጦር ፤ ዘበኛ ፥ ነጡር ፤ ጭፍራ ፥ ወታደር ፡፡ ሰባቢ ፤ ሰብብ ፥ ፈላጊ ፤ ሰበበኛ ፤ ሰበባም ፡፡

**ሰበብ፤** በቁሙ ፤ ምክንያት ፤ መነሻ ፤ የነገር ፥ ዙሪያ ፤ ከርክሬሻ ፡፡ (ተረት) ፤ በሰበቡ ፥ መምሬ ፥ ተሳቡ ፡፡

—፤ የጥርስ ፥ እድፍ ፤ ችክ ፤ ግርድ ፥ ሻከላ ፤ ኖራ ፥ (ትግሬ) ፡፡

**አስባብ፤** ሰበቦች ፤ በሰበብ ፥ ባሰባብ ፥ እንዲሉ ፡፡ ክባቦች ፤ ዘበኞች ፤ በዙሪያ ፥ ያሉ ፤ ጉያዎን ፥ ያርብሓን ፡፡ ወዕደውሰ ፤ እለ ፤ አስባብ ፤ ኵሎሙ ፤ በቅድመ ፤ አብያቲሆሙ ፤ ይቢቱ ፤ ወያጽንዑ ፤ ዐቂበ ፡፡ አንቅህዎሙ ፤ ለአስባቢሃ ፤ (ነሐ፯ ፡ ፫ ፡፡ ኤር፳፰ ፡ ፲፪) ፡፡

**ሰብድዓት፤ (ብ ፡ ሰበድዕት ፡፡ ዐረ ፡ ሸብዲዕ ፤ ጊንጥ)፤** እፍኝት ፤ ክፉ ፥ እባብ ፡፡ ትውልደ ፤ ሰባድዕት ፤ (ሉቃ፫ ፡ ፯) ፡፡

—፤ ስመ ፥ ነገድ ፤ የሰውና ፥ የአራዊት ፥ መልክ ፥ ያላቸው ፡፡ ኦጥፍኦ ፤ ሀገረ ፤ ሰባድዕት ፤ እለ ፤ ገጽሙ ፤ ሰብእ ፤ ወዘነበ ፤ አድግ ፤ ውስተ ፤ ሐቌሆሙ ፡፡ ወበጽሐ ፤ እስክንድር ፤ ኀበ ፤ ሰብድዓት ፤ ዘይበልዕዎ ፤ ሰብአ ፤ ወእንስሳ ፤ ወአራዊተ ፤ ዕፀወ ፤ ወአሥዕርተ ፤ እለ ፤ የሐይኩ ፤ እብነ ፤ ወይሰትዩ ፤ እሳተ ፤ ብሔሮሙ ፤ ጽኑዕ ፤ ወቦሙ ፤ አሐቲ ፤ ሙፃእ ፤ መጠነ ፤ ዕሥራ ፤ ወክልኤቱ ፤ በእመት ፡፡ ወጸለየ ፤ ኀበ ፤ እግዚ ፤……ወአስተቃረበ ፤ ሎቱ ፤ ክልኤተ ፤ አድባረ ፤ እለ ፤ ይብልዎሙ ፤ ምድቅሔል ፤ ቅርፍትሬን ፤ እስከ ፤ ይተርፍ ፤ ማእከሌሆን ፤ መጠነ ፤ ዕሥራ ፤ ወሠለስቱ ፤ በእመት ፤ ወአንበሮን ፤ ህየ ፤ ሰሰለደተ ፤ ብርት ፤ በከመ ፤ ነበሩ ፤ በምድረ ፤ ደቂቀ ፤ ያፌት ፤ ከመ ፤ ኢይፃኡ ፤ ሰብድዓት ፤ ወኢያጥፍኡ ፤ ሰብአ ፤ ወይጐዩዩ ፤ ሶበ ፤ ሰምዑ ፤ ቃለ ፤ ቀርን ፤ ወእንዚራ ፤ ወከበሮ ፤ (ክብ ፡ ነገ ፡፡ ዜና ፡ እስ ፡፡ ራእ፱ ፡ ፩—፲፩) ፡፡

**ሰብሐ፤—ሠባ ፡ ወፈረ፤—ሠቢሕ ፡ ሠብሐ ፡፡**

(ጥ) **ሰብሐ፤ ሐት፤ (ሰብሐ ፡ ይሴብሕ ፡ ይሰብሕ ፡፡ ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሸባሕ ፡፡ ዐረ ፡ ሰበሐ)፤** ማመስገን ፤ ማወደስ ፤ ማክበር ፥ ማግነን ፤ በክብርና ፥ በቃምራት ፥ መግለጥ ፤ ማብራት ፤ የክብር ፥ ብርሃን ፥ መስጠት ፡፡ ሰብሕዎ ፤ ለእግዚ ፤ ኵልክሙ ፤ አሕዛብ ፤ ወይሴብሕዎ ፤ ኵሎሙ ፤ ሕዝብ ፡፡ ሰብሐኒ ፤ በቅድመ ፤ ሊቃውንቲሆሙ ፤ ለእስራኤል ፡፡ እመሰ ፤ ለልየ ፤ ሰባሕኩ ፤ ርእስየ ፤ ኢይበቍዐኒ ፤ ስብሐትየ ፡፡ አባ ፤ በጽሐ ፤ ጊዜሁ ፤ ከመ ፤ ትሰብሖ ፤ ለወልድከ ፤ ወወልድከኒ ፤ ከመ ፤ ይሰብሕከ ፡፡ ሰብሖ ፤ ለምሕረትከ ፤ (መዝ ፡ ፻፲፯ ፡፡ ፩ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፴ ፡፡ ዮሐ፰ ፡ ፶፬ ፡፡ ፲፯ ፡ ፩ ፡፡ መዝ ፡ ፲፯) ፡፡

**ሰባሒ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት)፤** የሚያመሰግን ፤ አመስጋኝ ፤ ቀዳሽ ፥ አወዳሽ ፡፡ ይንእስ ፤ ሰባሒ ፤ እምተሰባሒ ፡፡ ሰባሕያን ፤ ወመተንብላን ፤ (አዋል ፡፡ መዋሥ ፡፡ አርጋ ፡ ፪) ፡፡

**ተሰብሐ፤** ተመሰገነ ፤ ከበረ ፤ ተገለጠ ፤ በራ ፥ ብሩህ ፥ ኾነ ፡፡ ይሴባሕ ፤ ስምየ ፤ በውስተ ፤ ኵሉ ፤ አሕዛብ ፡፡ ጥቀ ፤ ተሰብሐ ፤ ስምከ ፡፡ አመ ፤ ተሰብሐ ፤ ኢየሱስ ፡፡ ወተሰብሐ ፤ ሕብረ ፤ ገጹ ፤ (ሚል፩ ፡ ፲፩ ፡፡ መዝ ፡ ፰ ፡፡ ዮሐ፲፪ ፡ ፲፮ ፡፡ ዘፀ፴፬ ፡ ፳፱) ፡፡

**ስቡሕ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ብሕት)፤** የተመሰገነ ፤ ምስጉን ፤ ክቡር ፤ ክቡድ ፥ ልዑል ፤ ብሩህ ፥ ጽዱል ፡፡ ንሴብሖ ፤ ለእግዚ ፤ ስቡሐ ፤ ዘተሰብሐ ፡፡ ቃል ፤ ስቡሕ ፡፡ ወስቡሕ ፤ ራእዮሙ ፡፡ ዕፀው ፤ ስቡሓን ፤ (ዘፀ፲፭ ፡ ፩ ፡፡ ምሳጽ፭ ፡ ፳፯ ፡፡ ሔኖ፳፱ ፡ ፪ ፡፡ ፴፪ ፡ ፫) ፡፡

**ስባሔ፤ (ሕያት)፤** ማመስገን ፤ መመስገን ፤ አመስጋገን ፡፡ ውዳሴ ፥ ምስጋና ፤ ክብር ፤ ብርሃን ፡፡ አብዝኁ ፤ ስባሔሁ ፡፡ ርኢ ፤ ስባሔሆሙ ፡፡ ወሀበት ፤ ለእግዚ ፤ አኰቴተ ፤ ወስባሔ ፡፡ ዝማሬያት ፤ ወስባሕያት ፤ (ዮሴፍ ፡፡ ፊልክ ፡ ፻፲፭ ፡፡ ክፋ ፡ ፳፭ ፡፡ ፈ ፡ መ ፡ ፴፪ ፡ ፯) ፡፡

**ስብሐት፤ (ታት)፤** ዝኒ ፥ ከማሁ ፤ ውዳሴ ፥ ምስጋና ፤ ክብር ፥ ጌትነት ፤ አምላክዊ ፥ ብርሃን ፤ ጸዳል ፥ ምዕዛር ፡፡ ኢያረሙ ፤ እምስብሐቲን ፤ ስብሐተ ፤ ነግህ ፡፡

ሎቱ ፡ ስብሐት ። ወርኢነ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ከመ ፡ ስብ ሐተ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ። ወሀብክዎሙ ፡ ስብሐተ ፡ ዘ ወሀብከኒ ። አክሊለ ፡ ስብሐት ። ወስብሐተ ፡ እግዚ ፡ ብረቀ ፡ ላዕሌሆሙ ። ወምድር ፡ ብርሀት ፡ እምስብ ሐቲሁ ፡ (ቀሌ ። ሮሜ ፲፭ ፡ ፴፮ ። ዮሐ ፩ ፡ ፲፬ ። ፲፯ ፡ ፳፪ ። ሉቃ ፪ ፡ ፱ ። ሕዝ ፵፫ ፡ ፪ ። ራእ ፲፰ ፡ ፩) ።

**ሰበጠ** ፤—ቀረበ ፤ ተዘጋጀ ፤—ሠቢጥ ፡ ሠበጠ ።

**ሳባጥ** ፤—የወር ፡ ስም ፤—ሠባጥ ፡ ሣ ባጥ ።

**ሰቢክ** ፤ ኮት ፤ (ሰበከ ፡ ይሴብክ ፡ ይስ ብክ ፤ ከረዘ ። ዕብ ፡ ሳባ'ኽ ፤ ሰንሰለ ፡ ፀፈረ) ፤ መስበክ ፤ ማብሠር ፤ ማስተማር ፤ በታላቅ ፡ ቃል ፡ መ ጮኽ ፡ ማሰማት ፤ መልፈፍ ፤ መለፍለፍ ፤ ዐዋጅ ፡ መን ገር ፤ ማዜም ፡ መዘመር ፤ ማውራት ፡ መመስከር ። ፈነ ወኒ ፡ እስብክ ፡ ግዕዛነ ፡ ለፂውዋን ። በከመ ፡ ሰበኩ ፡ ነቢያት ። እፎኑ ፡ ይሰምዑ ፡ ዘኢሰበኩ ፡ሎሙ ፤ ወእ ፎኑ ፡ ይሰብኩ ፡ እንዘ ፡ ኢይትፌነዉ ። ይስብክ ፡ ሎቱ ፡ ፀዋዲ ፡ ውስተ ፡ መርሕብ ፡ ሀገር ። ይስብክ ፡ ዲያቆን ፡ ቅድመ ፡ ወንጌል ፡ እመዝሙረ ፡ ዳዊት ። ሰበከ ፡ በ ህየ ፡ በወንጌለ ፡ ኢየሱስ ፡ (ኢሳ ፷፩ ፡ ፩ ። ቀሌ ። ሮሜ ፲ ፡ ፲፬ ። አስቴ ፮ ፡ ፱ ፡ ፲፩ ። ሥር ፡ ቅዳ ። ስንክ ፡ መጋ ፲፩ ። ሠኒ ፳፯) ።

**ሰባኪ** ፤ (ኪት ፡ ክያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ የ ሚሰብክ ፤ የሚያስተምር ፤ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ። ክነ ፡ ሐዋርያ ፡ ወሰባኬ ፡ ወንጌል ። ዮሐንስ ፡ ሰባኬ ፡ ጥምቀት ። በ አፈ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወኀምስቱ ፡ ነቢያት ፡ ሰባክያን ፡ (ዲድ ፡ ፲ ። መዋሥ ። ማንዘ ። ፊልክ ፡ ፻፷) ።

**ምስባክ** ፤ (ካት) ፤ መስበኪያ ፡ ቦታ ፤ ከፍ ፡ ያለ ። ዲያቆን ፡ ከወንጌል ፡ በፊት ፡ የሚያዜመው ፡ መዝ ሙር ።

**ተሰብከ** ፤ ተሰበከ ፤ ተነገረ ። ወይሰበክ ፡ ዝ ፡ ወንጌለ ፡ መንግሥት ። ዘበነቢያት ፡ አቅደመ ፡ ተዐ ውቀ ፡ ወበሐዋርያት ፡ ተሰብከ ። ጥበብ ፡ ትሰበክ ፡ (ማቴ ፳፬ ፡ ፲፬ ። ኪዳ ። ምሳ ፩ ፡ ፳፩) ።

**ስብከት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፤ መስበክ ፤ መስ በክ ፤ አሰባበክ ፤ ሰበክ ፤ ትምርት ፤ ዐዋጅ ፤ ወሬ ፡ ታሪክ ። በነዋኅ ፡ ስብከት ። ስብክ ፡ ሎሙ ፡ በከመ ፡ ቀዳሚ ፡ ስብከት ። ንስማዕ ፡ ስብከተ ፡ ትንሣኤሁ ። ስብከተ ፡ ዘኢየሱስ ፡ (ምሳ ፱ ፡ ፫ ። ዮና ፫ ፡ ፪ ። ዲድ ፡ ፲፪ ። ቄር) ።

**ስብከተ ፡ ጌና** ፤ በዓል ፡ ስብከት ፤ የስብከት ፡ እሑድ ፤ ከታኅሣሥ ፡ ፮ ፡ እስከ ፲፫ ፡ የሚውል ፡ ወደ ፡ ጌና ፡ ወዳ፲፱ ፡ የማይወርድ ፡ የማይወጣ ። ዋዜማ ፡ ዘስ ብከት ፡ (ድጓ) ።

**ስባክ** ፤ (ዕብ ፡ ስበ'ኻ ። ዐረ ፡ ሸበከት) ፤ ዐይነ ፡ ርግብ ፤ የመረብ ፡ የመግለብ ፡ ዐይነት ፡ (፪ነገ ፡ ፳፭ ፡ ፲፯) ። ሳቤቅን ፡ ተመልከት ፤ የዕበክ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ሰብኮ** ፤ ኮት ፤ (ሰበከ ፡ ይሴብክ ፡ ይሰ ብክ ። ዕብ ፡ ሻፋ'ኽ ። ዐረ ፡ ሰፈከ) ፤ ማቅለጥ ፤ ማፍሰስ ፤ መፈጸፍለቅ ፤ እየመቱ ፡ እየጠፈጠፉ ፡ መሥራት ፡ መገብሰስ ፤ የማዕደን ፡ የሸክላ ። ወሀበት ፡ ክልኤተ ፡ ም እተ ፡ ብሩረ ፡ ለዘይሰብኮ ፡ ወይገብሮ ፡ ግልፎ ፡ ወሰ በኮ ፡ (መሳ ፲፯ ፡ ፬ ። ሕዝ ፳፪ ፡ ፳ ። ሚል ፫ ፡ ፫) ።

ሰባኪ ፤ የሚያቀልጥ ፡ የሚያፈስ ፤ አቅላጭ ፡ አፍ ሳሽ ። ሰባኬ ፡ ብሩር ፡ (አፈ ፡ ተጐ) ።

**ተሰብከ** ፤ ቀለጠ ፤ ፈሰሰ ፤ ተሠራ ። በከመ ፡ ይ ሰበክ ፡ ብሩር ፡ ትሰበኩ ፡ በማእከላ ፡ (ሕዝ ፳፪ ፡ ፳፪) ።

**ስቡክ** ፤ (ካን ፡ ካት ፡ ብክት) ፤ የቀለጠ ፡ የ ፈሰሰ ፡ ፍስ ፤ ቅጥቅጥ ። ወገብረ ፡ ባሕረ ፡ እንተ ፡ ብ ብርት ፡ ስብክት ፡ (፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፪ና ፡ ፬) ።

**ስብክ** ፤ (ብ ፡ ስብክዋት) ፤ ጣዖት ፤ ምስል ፤ አቅልጠው ፡ አፍስሰው ፡ ቀጥቅጠው ፡ ገብስሰው ፡ የሚሠ ሩት ። ስብክ ፡ ወርቅ ፡ ግብር ፡ በአምሳለ ፡ ዕፀ ። አማ ልክት ፡ ዘስብክ ። እሜርዎ ፡ ለግልፎክ ፡ ወለስብኮክ ። ከመ ፡ ኢትበል ፡ ስብክየ ፡ አዘዘኒ ፡ (ዮሴፍ ። ዘሌ ፲፱ ፡ ፬ ። ናሖ ፩ ፡ ፲፬ ። ኢሳ ፵፰ ፡ ፭) ።

**መስበክ** ፤ ት ፤ (ብ ፡ መሳብክ ፤ ት) ፤ የሸክላ ፡ ዕቃ ፤ እንስራ ፡ ማድጋ ፤ ገንቦ ፤ ማሰሮ ፡ ምን ቸት ። ይትቀጠቀጥ ፡ መስበክት ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅት ። መሳብክተ ፡ ማይ ፡ (መክ ፲፪ ፡ ፯ ። መዋሥ ። ዮሐ ፪ ፡ ፮ ፡ ፯ ። መሳ ፯ ፡ ፲፮ ፡ ፫ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፴፬) ።

—፤ የብረት ፡ ዕቃ ፤ መሣሪያ ፤ ወይም ፡ ቦታ ፤ መጥበሻ ፤ ማፍሰሻ ፤ ከውር ። ይሰበኩ ፡ በመስበኩ ። እለ ፡ ሰበ ክዎሙ ፡ ለአልሕምት ፡ በውስተ ፡ መስበክ ። እምነ ፡ መሳብክተ ፡ ኅጺን ። በመሳብክቲሁ ፡ ከመ ፡ ወርቅ ፡ በእሳት ፡ ፈተኖሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ። ፯ ፡ ፶፩ ። ፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፫ ። መዋሥ) ።

**ሰቢል** ፤ ሎት ፤ (ሰብለ ፡ ይሴብል ፡ ይስ ብል ። ዕብ ፡ ሳባል ፤ ጾረ ። ዐረ ፡ ሰቢለ ፤ ሰን በለ) ፤ ሰብል ፡ መኽን ፤ መዘርዘር ፡ መውለድ ፤ መፈወር ቋት ፤ መሸት ፤ ማፍራት ፤ ፍሬ ፡ መያዝ ፡ መሸከም ። ሰ ገም ፡ እንበለ ፡ ይስብል ፡ (ዘዐ፱ ፡ ፴፩) ።

**ሰብል** ፤ (ላት ፤ ዕብ ፡ ሽበሌት ። ሱር ፡ ሺብላ ። ዐረ ፡ ሰበል) ፤ በቁሙ ፤ ዝርዝር ፤ ወለዳ ፤ ጨርቃ ፡ ቀጭን ፡ እሸት ፤ ራስ ፡ ዛላ ፤ ዘለላ ፤ እልፍ ፡ ከነዎ ርቁና ፡ ከነቁንዱ ፡ (ማር ፬ ፡ ፳፰) ። ሰብለ ፡ ሥርናይ ፡ ወሰብብለ ፡ እክል ። ሀሰዉ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ሰብዐቱ ፡ ሰብላት ፡ ዘሠዊት ፡ ዘሠረጹ ፡ እምአሐዱ ፡ ብርዕ ። ወሰብሉኒ ፡ ይከውን ፡ ሠላሳ ፡ ኅጠተ ፡ (መቃ ፡ ገ፲፱ ። ዮሴፍ ። ፊልክ ፡ ፱) ።

**መስበልት** ፤ የእሸት ፡ ፍሬ ፤ ዛላ ፤ እልፍ ፤ ዝ ሪት ፡ አዝመራ ። ዐዘቅት ፡ ዘእንበለ ፡ ማይ ፤ ደመና ፡ ዘእንበለ ፡ ዝናም ፤ ሠዊት ፡ ዘእንበለ ፡ መስበልት ። አልቦሙ ፡ ኅጠት ፡ ለመስበልቶሙ ። ሖሩ ፡ መስተገ ብረ ፡ ገራውህ ፡ ሐጹረ ፡ አሥዋክ ፡ ያዐውድ ፡ ውስተ ፡ መስበልቱ ፡ (መጽ ፡ ምስ ፡ ገ፴፩ ። ፪፻፴፱ ። ፪፻፶)

**ሰንብል** ፤ (ዐረ ፡ ሱንቡለት) ፤ እሸት ፤ የእ ሸት ፡ ዘላ ፤ ነዶ ፤ ጥይት ። ቀዳሚ ፡ ነበሩ ፡ ደበውኡ ፡ ሰንብለ ፡ ወአስካለ ፡ ወይን ፤ ወናሁ ፡ ተፀርዐ ፡ ሰንብል ፡ ወተርፈ ፡ ወይን ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፱) ።

**ሰንቢል** ፤ የመጠጥ ፡ እሸት ፤ ዝርዝር ፡ መጠጥ ፤ ጻዕፍ ፤ ጉሽ ። ግሬዳ ፡ ማኅበራዊ ፡ ድግስ ። እሰ ፡ ይትልዉ ፡ አሠረ ፡ ወይን ፡ ወእደ ፡ ይከውን ፡ ሰንቢል ፡ (ምሳሼ፫ ፡ ፴) ።

**ሰንቡል** ፤ **ሰንበልት** ፤ ሰንቡል ፤ ጥሩ ፡ ሽቱ ፤ ናርዶሳዊ ፤ ከዕፀወ ፡ ዕጣን ፡ አንዱ ፤ ወይም ፡ ዛጉል ፤ የባሕር ፡ ሽቱ ፡ (ዘፀ፴ ፡ ፴፬) ። ከልበኔ ፡ ወሰንቡል ። ሰንበልት ፡ ምዑዝ ። ሰንበልት ፡ ቅድው ፡ (ኢዋ ። ደራሲ ። ሔኖ፴፪ ፡ ፩ ። ኩፋ ፡ ፫ና ፡ ፲፮) ።

**ሰንቡላ** ፤ (ዐረ ፡ እሰንቡለት) ፤ የከዋ ፤ የኮከብ ፡ ስም ፤ ከሥራ ፡ ኹለቱ ፡ መናዝል ፡ አንዱ ። ሽቱ ፡ የሽቱ ፡ ዘላ ፡ ሽቷም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ኮከብነቱም ፡ የን ሐሴ ፡ ነው ፤ ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ ፴ ፡ ዕለት ፡ ሳ፱ ፡ ኤክሮስ ፡ ይመግባል ፡ (አቡሻ ፡ ፫) ።

**ሽቦሌት** ፤ (ዕብራ) ፤ ሰብል ፤ ዝርዝር ፡ እሸት ፤ ራስ ፡ ዘላ ። ወይቤልዎ ፡ በል ፡ ሽቦሌት ፤ ወይቤ ፡ ሲቦሌት ፡ ወኢያርትዐ ፡ ነቢበ ፡ (መሳ፲፪ ፡ ፯) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ኀባቡን ፡ ሽሖሌት ፡ ይሉና ፡ ፍችውን ፡ ለባሕር ፡ ለገደል ፡ ያድርጉኛ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ሽቦሌት ፡ በል ፡ ማለት ፤ ደቂቀ ፡ ኤፍሬም ፡ የሸ ፡ ጸያፎች ፡ ናቸውና ፤ ኤፍሬማዊነቱን ፡ በገዛ ፡ አፉ ፡ ለማስመስከር ፡ ነው ። ሽሖሌት ፡ ያሉት ፡ ግን ፡ ሽሔሌት ፡ ነው ፤ ፍችውም ፡ የሽቱ ፡ ቡቃያ ፡ ቅጠል ፤ የባሕር ፡ ዛጉል ፤ ባሕረ ፡ ወጥ ፡ ሽቱ ፡ ሰንበልት ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ሳቢላኔስ** ፤ (ዕብ ፡ አቢሊን) ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ ሶርያዊ ፤ ወይናም ፡ በለሳም ፡ (ሉቃ፫ ፡ ፩) ።

**ሳብላንዮስ** ፤ (ጽርእ ። ዕብ ፡ ሳብላኒ) ፤ የሰይጣን ፡ ስም ፤ ከቡደ ፡ ጸር ፤ ብዙኅ ፡ ጸር ፤ ዘይጸውር ፡ ወዘያጸውር ፡ (መቃ ፡ ገ፳፱) ። ሳብላንዮስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሰልብልያኖስ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ወትእኅዞሙ ፡ ቅንአት ፡ ከመ ፡ ሰልብልያኖስ ፡ (ማሕ፳ ፡ ፩) ።

**ሰበን** ፤ (ጽር ፡ ሳባኖን ። ዕብ ፡ ሳብና) ፤ ነጭ ፡ ጥሩ ፡ ልብስ ፤ ሰንዱን ፤ በኀፅበት ፡ ጊዜ ፡ ከውሃ ፡ ሲወጡ ፡ የሚለበስ ።

**ሰበን** ፤ (ጽር ፡ ሱዳሪዎን ። ዕብ ፡ ሱዳር) ፤ ያንገትና ፡ የራስ ፡ የትከሻ ፡ ልብስ ፤ ሻል ፤ ሞጣሕት ፤ በላይ ፡ የሚለበስ ፤ ታናሽ ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ (ሉቃ፲፱ ፡ ፳ ። ዮሐ፲፩ ፡ ፵፬ ። ፳ ፡ ፯ ። ግብ፲፱ ፡ ፲፪) ።

**ሰበን** ፤ (ናት ። ጽር ፡ ኪዳሪስ ። ዕብ ፡ ፍኤር ፤ ጸኒፍ) ፤ የራስ ፡ ልብስ ፤ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ ቆብ ፡ ጥምጥም ፤ መጠምጠሚያ ። ደዩ ፡ ሰበነ ፡ ንጹሐ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ። ሰበን ፡ ዘዐሜ ፡ ይኩን ፡ ላዕለ ፡ ርእሰሙ ። ሰበኖሙ ፡ ይኩን ፡ ዐሥርተ ፡ በእመት ፡ (ዘካ፫ ፡ ፭ ። ሕዝ ፵፬ ፡ ፲፰ ። አቡሻ ፡ ፭ ። ገድ ፡ አዳ ፡ ገ፳፬፱) ። ቁዳርን ፡ ተመልከት ።

**ሰብዖ** ፤ ዖት ፤ (ሰብዐ ፡ ይሴብዕ ፡ ይሰብዕ ። ዕብ ፡ ሻቤዕ) ፤ መሰበት ፤ ሰባት ፡ ማድረግ ፤ ከሰባት ፡ መክፈል ። በስመ ፡ አብ ፡ ዘይሴብዖን ፡ ሰም ዐዋደ ፡ ሰንበታት ፡ ከመ ፡ ይኩና ፡ ሰኩፋሌ ፡ መዋዕል ፡ ወሰፍጻሜ ፡ ኢዮቤልዮሳት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ። የሞፈርን ፡ ቂጥ ፡ ከንኹሰንታናው ፡ ሰበት ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ማረሻና ፡ ከርፈስ ፡ (ወገል) ፡ ጠፍሩና ፡ ሞፈሩ ፡ ዕርፉና ፡ ድግሮቹ ፡ ሲደመሩ ፡ ፯ ፡ ናቸውና ፤ ሰበት ፡ ይይህንን ፡ ያሳያል ።

—፤ ማዘዝም ፤ አስማት ፡ መድገም ፤ እየመላለሱ ፡ ማንበብ ፡ ማንብነብ ፡ እስከ ፡ ፯ ፡ ጊዜ ።

**ሰባዒ** ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት) ፤ የሚሰብት ፡ ሰባች ፤ ሰባት ፡ አድራጊ ።

**መስበዒ** ፤ ብዕ ፡ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፤ አስማታም ፤ ባላስማት ። እሜኬራሕ ፡ መሀረ ፡ ዘሎ ፡ መስበዕያነ ፡ ወመታርያነ ፡ ሥርው ፡ (ሔኖ፰ ፡ ፫) ።

**ተሰብዐ** ፤ ተሰበተ ፤ ሰባት ፡ ኾነ ፤ ተባለ ፤ በሰባት ፡ ክፍል ፡ ተከፈለ ። ተሰብዖት ፡ (ኩፋ ፡ ፩) ።

**ስቡዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ብዕት) ፤ የተሰበተ ፤ ሰባት ፡ የኾነ ፤ የተባለ ፤ ሰባትነት ፡ ያለው ።

**ስባዔ** ፤ (ዕያት) ፤ መሰበት ፤ ሰባት ፡ ማድረግ ፤ ወይም ፡ ሰባት ፡ መኾን ፤ መባል ፤ ሰባትነት ።

**ሰብዑ** ፤ (ዕብ ፡ ሼባዕ ። ሱር ፡ ሽባዕ ። ዐረ ፡ ሰብዕ) ፤ የሴቶች ፡ ድምር ፤ ሰባት ። ገቢርም ፡ ይከታል ። ሰብዑ ፡ አንስት ። ሰብዑ ፡ አዋልድ ። ሰብዑ ፡ እኪያት ። ወነሥአ ፡ ሰብዑ ፡ ኅብስተ ፡ (ኢሳ፬ ፡ ፩ ። አስቴ ፪ ፡ ፱ ። ምሳ፳፮ ፡ ፳፭ ። ማቴ፲፭ ፡ ፴፮ ። ዘፍ፴፩ ፡ ፳፫—፴) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በወንዶች ፡ ድምር ፤ ሰብዑ ፡ ደቂቀ ፡ እያለ ፡ ይገኛል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

**ሰብዐቱ** ፤ ቲ ፤ የወንዶች ፡ ድምር ፡ (ዘ ፡ ፯) ፡ ሰባት ፤ ሰባቱ ፤ ሰባተኛው ፤ ሰባተኞቹ ። ሰብዐቱ ፡ አልሕምት ። ሰብዐቲ ፡ ኖሎት ። ሰብዐቱ ፡ አዕይንት ። ንድቅ ፡ ሊተ ፡ ሰብዐተ ፡ ምሥዋዓተ ፤ ወአስተዳሉ ፡ ሰብዐተ ፡ አልሕምተ ፡ ወሰብዐተ ፡ አባግዐ ፡ (ዘኍ፳፫ ፡ ፩ ። ሚክ፭ ፡ ፬ ። ዘካ፫ ፡ ፱ ። ዘኍ፳፫ ፡ ፩) ።

**ስቡዕ** ፤ የዕለት ፡ ቅጽል ፤ ሰባት ፤ ሰባተኛ ። እምድኅረ ፡ ሰቡዕ ፡ መዋዕል ። ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ። አመ ፡ ሰቡዕ ። በሰቡዕ ፡ ሠርቅ ፡ (ዘፍ፯ ፡ ፲ ። ዘሌ፲፭ ፡ ፲፫ ። ዘካ፯ ፡ ፩ ። ባሮ፰ ፡ ፱) ።

**ስቡዑ** ፤ ሰባቱ ፤ ሰባተኛው ። አመ ፡ ሰቡዑ ፡ ሰኑሐሴ ፡ (መቅ ፡ ታም) ።

**ሱባዔ** ፤ (ዕያት) ፤ በቁሙ ፤ ሰባት ፤ ፍጹም ፡ ቍጥር ፤ የዕለት ፡ የዓመት ። ወይከውን ፡ ሰምጽአቱ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ወሠላሳ ፡ ወሠለስቱ ፡ ሱባዔ ፡ ዕለታት ። በሱባዔ ፡ ሳብዕ ። ሱባዔ ፡ ዓመታት ። ወይዜክር ፡ ሰብዐተ ፡ ሱባዔያተ ፡ (ተረ ፡ ኤር ።

ኩፋ ፡ ፬) ። ሰንበትን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ክፍል ፡ ነው ፤ ን ፡ በለ ፡ ገባበት ፡ ተለይቷል ።

**ሱባዔያዊ** ፤ የሱባዔ ፡ ቀመር ፤ ቍጥር ፤ ባለሱባዔ ፡ (አቡሻ ፡ ፴፫) ።

**ሳብዕ** ፤ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት) ፤ ሰባተኛ ፤ ከሰባት ፡ አንድ ። በሳብዕ ፡ ወርኅ ። በሳብዕ ፡ ዓመት ። በሳብዕት ፡ ዕለት ። ሳብዕተ ፡ እዴሃ ፡ ለምድር ፡ (ዘሌዋ፳ ፡ ፳፱ ። ሕዝ፳ ፡ ፩ ። ዘፍ፪ ፡ ፪ ። ሱቱ ፡ ዕዝ፱ ፡ ፵፮) ።

**ሳብዓዊ ፡ ይ** ፤ (ዊት ፡ ዩት ፡ ዒት) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፤ ሰባተኛ ፤ ው ፡ (ዋ ፡ ይቱ) ።

**ስብዕ** ፤ የጊዜና ፡ የልክ ፡ ቅጽል ፤ ሰባት ። ስብዕ ፡ በአመት ። ከማሁ ፡ ገብረ ፡ እስከ ፡ ስብዕ ። ስብዐ ፡ ለዕለትየ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱ ። ፬ነገ ፡ ፬ ፡ ፴፭ ። መዝ ፡ ፻፲፰) ።

**ምስብዒት** ፤ ሰባት ፡ እጅ ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፤ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፤ መጠ ፡ ፵፱ ። ይፈዲ ፡ ምስብዒተ ። ይበርህ ፡ ምስብዒተ ፡ እምፀሓይ ። የኀሥሥ ፡ ይረስዩ ፡ ምስብዒተ ። ሰብዐቱ ፡ ዓመት ፡ ዘምስብዒት ፡ (ምሳ፯ ፡ ፴፩ ። ቀሌ ። ሚራ፯ ፡ ፲፱ ። ዘሌ፳፭ ፡ ፰) ።

**ትስብዕት** ፤ ሰባትነት ፤ ሰባተኛነት ፤ ሰባት ፡ እጅ ፤ ሰባት ፡ ዕጥፍ ። ወበዝኁ ፡ መክፈልተ ፡ ብንያም ፡ እመክፈልተ ፡ ኵሎሙ ፡ ትስብዕተ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፫) ።

**ሰብዓ** ፤ የቍጥር ፡ ስም ፤ በስድሳና ፡ በሰማኒያ ፡ ማኽል ፡ ያለ ፤ ሰባ ፡ (ዐ ፡ ፸) ፤ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ፤ ወይም ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ። ሰብዓ ፡ ብእሲ ። ሰብዓ ፡ ዓም ። ሰብዓ ፡ ክራማት ። ኢይብለከ ፡ እስከ ፡ ስብዕ ፡ አላ ፡ እስከ ፡ ሰብዓ ፡ ወስብዕ ። ሰብዓ ፡ ሰንበታት ፡ (ሕዝ፰ ፡ ፲፩ ። ዘካ፩ ፡ ፲፪ ። መዝ ፡ ፹፱ ። ማቴ፲፰ ፡ ፳፪) ።

**ስብዕ** ፤ **ስብዐት** ፤ (ታት ። ዕብ ፡ ሽቡዓ ፤ መሐላ) ፤ ዐዚም ፤ ሥራይ ፤ አስማት ፤ የጠንቋይ ፡ ጸሎት ፡ ፯ ፡ ፯ ፡ ጊዜ ፡ የሚጣፍ ፡ የሚደገም ፡ ጨሬ ፡ ገርገር ፤ ፉፎን ፡ ፉፎን ፤ ይህን ፡ የመሰለ ። ዘይገብር ፡ ስብዐ ፡ ወመቅሰመ ። አርማሮስ ፡ ፈትሐ ፡ ስብዐታተ ፡ (ቀሌ ፡ ገድሚዕ፬ ። ሔኖ፯ ፡ ፩) ።

**ሰቢቅ** ፤ **ቆት** ፤ (ሰበቀ ፡ ይሰብቅ ፡ ይስብቅ ። ሱር ፡ ሻበቅ) ፤ መተው ፡ መልቀቅ ፡ መጣል ፤ እንዲሞት ፡ እንዲጠፋ ። ማድረግ ። መስበቅ ፤ ማሳበቅ ፤ የእጅ ፡ የነገር ። መጨፈቅ ፡ መማገር ፤ ማያያዝ ፡ ማስተሳሰር ፤ የዕዕ ፡ የሐረግ ።

**ሰባቂ** ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ የሚሰብቅ ፤ የሚያሳብቅ ፡ ሰብቃኛ ፤ ሰብቃም ።

**ሳቤቅ** ፤ (ሱር ፡ ሲብቃ) ፤ ረዥም ፡ ዐጽቅ ፡ ሐረግ ፤ ማናቸውም ። ሐረግ ፡ ፊላ ፤ ቢሔ ፡ ዐረግ ።

**ሳቤቅ** ፤ (ጽር ፡ ሳቤክ ። ዕብ ፡ ስበኽ ። ሱር ፡ ሲላና ። ዐረ ፡ ዓበት) ፤ ጽፍቅ ፡ ዱር ፤ ቀጫጭን ፡ ዕንጨት ፡ ሐረግና ፡ ዐጽቅ ፤ ርስ ፡ በርሱ ፡ የተሳበቀ ፤ የተዋሰበ ፤ የተቈላለፈ ። ርእዩ ፡ ለግዐ ፡ እጉዝ ፡ አቅርንቲሁ ፡ በዕፀ ፡ ሳቤቅ ፡ ዕፀ ፡ ሳቤቅ ፡ ብሂል ፡ ዕፀ ፡ ስርየት ፡ መስቀል ፡ (ድጓ ። ዘፍ፳፪ ፡ ፲፫) ።

**ሰበቅታኒ** ፤ (ሱር ፡ ሽበቅታኒ ። ጽር ፡ ሳባኽታኒ ። ዕብ ፡ ዐዛብታኒ) ፤ ኀደገኒ ፤ ገደፍከኒ ፡ ተውኸኝ ፤ ጣልኸኝ ። ኤ ፡ ወልድ ፡ ክላሕ ፡ ከመ ፡ ዘሐመ ፡ ወበል ፡ ኤልማስ ፡ ላማ ፡ ሰበቅታኒ ፡ (ቅዳ ፡ አት ። ማቴ፳፯ ፡ ፵፮ ። ማር፲፭ ፡ ፴፬) ።

**ሰቢር** ፤ **ሮት** ፤ (ሰበረ ፡ ይሰብር ፡ ይስብር ። ዕብ ፡ ሻበር ። ሱር ፡ ትባር ። ዐረ ፡ ተበረ) ፤ መስበር ፤ መሰባበር ፤ መቀጥቀጥ ፤ ማንከት ፤ ማድቀቅ ፤ ማድከም ፤ (ድል ፡ ማድረግ ፤ ማሸነፍ) ። እሰብር ፡ አናቅጸ ፡ ብርት ። እለ ፡ ይሰብሩ ፡ ቍልፈተ ። ልሳን ፡ ድክምት ፡ ትሰብር ፡ አዕፅምተ ። ሐዘኑ ፡ ለልብ ፡ ይሰብሮ ፡ ለኀይል ። ለምንት ፡ ትሰብሩ ፡ ልብየ ፡ (ኢሳ፵፭ ፡ ፪ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱ ። ምሳ፳፭ ፡ ፲፭ ። ሚራ ፴፰ ፡ ፲፰ ። ግብ፳፩ ፡ ፲፫) ። ዘበረን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ነው ።

**ሰባሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ የሚሰብር ፤ የሚሰባብር ። ክይሲ ፡ አው ፡ አርዌ ፡ ሰባሪ ፡ (ፊልክ ፡ ፶፭) ።

**መስብር** ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤ የሚሰብር ፡ ሰባሪ ፤ መሰበሪያ ። መስብረ ፡ ርእስ ፤ መስብረ ፡ ብረክ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፭) ።

**አስበረ** ፤ አሰበረ ፡ ስበሩ ፡ አለ ፡ ድል ፡ አስደረገ ። አሸበረ ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።

**ተሰብረ** ፤ ተሰበረ ፤ ተሰባበረ ፤ ነከተ ፡ ነኰተ ፤ ተንቈጠቈጠ ። ድል ፡ ኾነ ፡ ተመታ ፡ ተሻረ ፡ ፈረሰ ፡ ተናደ ፡ ሸሸ ። ተሰብረ ፡ ጸወንክሙ ። በተሰብሮ ፡ ቍጽ ። ተመንደበ ፡ ሐመሮሙ ፡ ከመ ፡ ይሰበር ። ተሰብሩ ፡ ሕዝብ ፡ በቅድመ ፡ ፀሮሙ ። ተሰብሩ ፡ ሰብአ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወጐዩ ። ወተሰብረ ፡ ሰራዊቶሙ ፡ (ዩዲ፯ ፡ ፯ ፡ ጳጳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ። ፫ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፴፭ ። ዘኍ፲፬ ፡ ፲) ።

**ስቡር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ብርት) ፤ የተሰበረ ፡ ሰባራ ፤ ሠንጣቃ ፡ ንቅ ፤ ንክ ። ማዕጸ ፡ ስቡር ። ዘስቡር ፡ እግሩ ። ምስል ፡ ስቡር ፡ (ኩፋ ፡ ፵፱ ። ዘሌ፳፩ ፡ ፲፱ ። መሳ፯ ፡ ፳፫) ። ሐንካስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ስቡር ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። (፪ነገ ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ፰ ። ኢዮ፳፱ ፡ ፲፭ ። ሉቃ፯ ፡ ፳፪ ። ፲፬ ፡ ፳፩) ።

**ስብረት** ፤ መስበር ፤ መሰበር ፤ አሰባበር ፤ ሰበራ ፤ ስብራት ፤ ሰባርነት ፤ ጕዳት ፤ ትሕትና ፡ ሐዘን ። ስበራ ፡ (ሰበትር) ፡ ክልኤተ ፡ ስብረተ ፡ ወክነት ፡ ሠለስተ ፡ በትረ ። ስብረት ፡ ህየንተ ፡ ስብረት ። ሀጐል ፡ ወኪደት ፡ ወስብረት ፡ እምኀበ ፡ እግዚ ። ስብረተ ፡ ልብ ፡ (ክብ ፡ ነገ ። ዘሌ፳፬ ፡ ፳ ። ኢሳ፶፱ ፡ ፯ ። አፈ ፡ ተ፴፭) ።

**ስባር** ፤ (ራት) ፤ ስባሪ ፡ ፍላፋይ ፤ ገል ፡ እንክትካች ። ቍራሽ ፡ ብጣሽ ፡ ፍንካች ። ስባረ ፡ ማሕረጽ ፡ ስባራተ ፡ ማህው ፡ በሲኃት ። ስባረ ፡ እኔላ ፡ ተመርት ፡ (መሳ፱ ፡ ፶፫ ። ሚራ፴፫ ፡ ፲፱) ።

**ሰበረ** ፤ (ዕብ ፡ ሳባር ። ዐረ ፡ ጸበረ) ፤ ጸንዐ ፡ ቈየ ፤ ታገሠ ፤ ደጀ ፡ ጠና ።

**ሰብር** ፤ ትዕግሥት ፤ ደጅ ፡ ጥናት ፤ ሬት ።

**ሶበርት** ፤ ኮሶ ፤ የሆድ ፡ ትል ፤ ሹጥ ፤ ከጠፋ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ኹለት ፡ ወር ፡ የሚቈይ ፡ በሦስተኛ ፡ ወር ፡ የሚታይ ። የኮሶ ፡ መድኀኒት ፡ መራራ ፤ የሚዋጥ ፡ የሚቃም ፡ የሚጠጣ ። ለዘአበየ ፡ ሶበርት ። ሠያጤት ፡ ሶበርት ፤ (መ ፡ ፈ ። ታሪ ፡ ቴዎ) ።

**ሰብሳብ ፤—ጋብቻ ፡ ግቢ ፤—ወሰበ ።**

**ሰጊድ ፤ ዶት ፤ (ሰገደ ፡ ይሰግድ ፡ ይስግድ ። ዕብ ፡ ሳጋድ ። ሱር ፡ ስጊድ ። ዐረ ፡ ሰጀደ)** ፤ መስገድ ፤ መዋረድ ፤ ማጐንበስ ፡ መንበርከክ ፤ መደፋት ፤ በግንባር ፡ መውደቅ ፤ ግንባርን ፡ ምድር ፡ አስነክቶ ፡ መሬት ፡ ስሞ ፡ መመለስ ፤ የአምልኮና ፡ የአክብሮ ። ወይከውን ፡ ጸሎት ፡ በሰንበት ፡ ዘእንበለ ፡ ሰጊድ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ አላ ፡ በደኒን ፡ ወአትሕቶ ፡ ርእስ ። ከመ ፡ ለስሙ ፡ ይስግዱ ፡ ኵሉ ፡ ብርክ ። ሰገደ ፡ በብረኪሁ ። ይሰግዱ ፡ በገጾሙ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ሰገደት ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ። ወሶቤሃ ፡ ወድቀ ፡ ንጉሥ ፡ በገጹ ፡ ወሰገደ ፡ ለዳንኤል ፤ (ቀኖ ፡ ኒቅ ። ቆላ፪ ፡ ፲ ። ፪ዜና ፡ ፯ ፡ ፲፫ ። ሚራ፯ ፡ ፲፯ ። አስቴ፫ ፡ ፫ ። ዳን፪ ፡ ፵፯) ።

**ሰጋዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት)** ፤ የሚሰግድ ፤ ሰጋጅ ። ሰጋዲ ፡ ከመ ፡ መላእክት ። ሰጋድያን ፡ ለአምላክ ፡ ሰማይ ። በአማን ፡ ሰጋድያን ፤ (ደራሲ ። ስንክ ፡ መጋ፲፫ ። ዮሐ፬ ፡ ፳፫) ።

**ስጋድ ፤ (ትግሬ)** ፤ ዐንገት ፤ ሰጋጅ ፡ መስገጃ ።

**ስጉድ ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ግድ)** ፤ የሰገደ ፤ የተዋረደ ፤ በግንባሩ ፡ የተተከለ ። ረከቦ ፡ እንዘ ፡ ስጉድ ፡ በገጹ ። ስጉድ ፡ ውእቱ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤ (ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። መጋ፲፫) ። ቂሐት ፤ ቀይሓት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ስጉዳት ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ስጉዳት ፡ አዕይንቲሁ ፤ (ምሳ፳፫ ፡ ፳፱) ።

**ስግደት ፤ (ታት)** ፤ በቁሙ ፤ አሰጋገድ ፡ ስግዳ ፤ ስግደሽ ፡ መውደቅ ፡ መነሣት ። ይስግድ ፡ ኈምሳ ፡ ስግደተ ። ምስለ ፡ ስግደታት ፡ ብዙኃት ፤ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፭ ። ፊልክ ፡ ፪፻፷) ።

**አስገደ** ፤ አሰገደ ፡ አንበረከከ ። ሥጋ ፡ እንተ ፡ ነሥአ ፡ እምኔነ ፡ አስገደሙ ፡ ለመላእክት ፤ (አፈ ፡ ድ፭) ።

**መስገዲ** ፤ የሚያሰግድ ፤ አሰጋጅ ። መስገዲ ፡ ለኵሉ ፤ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ምስጋድ ፤ (ዐረ ፡ መስጊድ)** ፤ መስገጃ ፤ ማስገጃ ፤ መቅደስ ፡ አሪት ፤ ቤተ ፡ ክሲያን ፤ ቤተ ፡ ጣዖት ። ቤተ ፡ ጸሎት ፡ እንተ ፡ ተተክለት ፡ ለምስጋድ ። ምስጋደ ፡ አማልክት ፤ (ድጓ ። አርጋ ፡ ፬ ። አብጥ ፡ ፳፯) ።

**ተሰግደ** ፤ ተሰገደ ፤ ተስገደለት ፤ ስግደት ፡ አምልኮት ፡ ተቀበለ ፤ አምላክ ፡ ተባለ ። እመላእክት ፡ ይሰገድ ። ለግሙራ ፡ ኢይወፅእ ፡ እምተሰግዶ ፡ እምኔነ ፡ ወእምቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ዋሕድ ። አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘበተሰብእቱ ፡ ይሰገድ ፡ ወበመለኮቱ ፡ ይሰገድ ፤ (ተረ ፡ ቄር ፤ እሰት) ።

**ሰጋድ ፤ (ዕብ ፡ ሲግዳ ፤ ሻቁድ ። ሱር ፡ ሺግድታ)** ፤ የንጨት ፡ ስም ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ዕንጨት ፤ ፍሬው ፡ የሚበላ ፤ ለውዝ ፤ ሰገድ ። ዲፍራን ፡ ወሰጋድ ፤ (ኩፋ ፡ ፳፯) ።

**ሻጊህ ፤ (ዕብ ፡ ሾጌህ)** ፤ ጊጉይ ፤ ስሑት ፤ በስሕተት ፡ የበደለ ፤ (ሕዝ፵፭ ፡ ፳) ።

**ሰጊል ፤ ሎት ፤ (ሰገለ ፡ ይሰግል ፡ ይስግል ። ዕብ ፡ ሻጋል ፤ ዘመወ ። ሳከል ፤ ለበወ)** ፤ መጠንቈል ፤ ማሟረት ፤ መላ ፡ መምታት ፤ በመላ ፡ ማወቅ ፤ መፈልሰፍ ፡ መራቀቅ ፤ በውነት ፡ ወይም ፡ በሐሰት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰገለ ፡ ፈንታ ፡ አስገለ ፡ አስተሰገለ ፡ ተሰግለ ፡ ይላል ፤ ኹሉም ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ያሰግሉ ፡ ለኪ ፡ ወይነጽሩ ፡ ሰማየ ። እለ ፡ ያሰግሉ ፡ በእሳት ፡ ወበማይ ፡ ወበአዕዋፍ ፡ ወበአእባን ፤ በኮከብ ፡ ወበእሳት ። ዘያስተሰግል ፡ በዖፍ ። ተሰግሎ ፡ በተአምረ ፡ ሰማይ ። ዘይሴገል ፡ በበድን ፡ ርኩስ ፤ (ኢሳ፵፯ ፡ ፲፫ ። ቀሌ ። ዘዳ፲፰ ፡ ፲፩ ። ኩፋ ፡ ፲፩ ። ኪዳ) ። መትከል ፡ መዝራት ፤ ማፍራት ። ተከለንና ፡ ሰከለን ፡ ሰግላን ፡ እይ ።

**አስገለ** ፤ አስጠንቈለ ፤ ጠንቋይ ፡ ጠየቀ ፤ አስጠየቀ ።

**ሰገል ፤ (ላት)** ፤ ጥንቈላ ፡ ሟርት ፤ መላ ፡ ግምት ፤ ጥበብ ፡ ዕውቀት ። ሰገለ ፡ ይሴአል ። በንደበ ፡ ሰገልኪ ። ሰገል ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ። ሰብአ ፡ ሰገል ፤ (ሆሴ፬ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፵፯ ፡ ፱ ። ምሳ፲፮ ፡ ፲ ። ዳን፩ ፡ ፳) ።

**ሰገላዊ** ፤ የጥንቈላ ፡ ሰው ፤ ጠንቋይ ፤ አስጠንቋይ ። ሰገላውያን ፤ (ስንክ ፡ ታኅ፳፱) ።

**መሰግል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት)** ፤ ጠንቋይ ፤ ሟርተኛ ፤ ኮከብ ፡ ዐዋቂ ፤ ፈላስፋ ፤ መለኛ ። ሊመርዓቱ ፡ ፀርን ፡ ሲኦል ፡ ኢሳይያስ ፡ መሰግላ ፡ እመ ፡ ተስእለቶ ፡ ቅድመ ፡ ወጠየቀቶ ፡ በቃላ ፤ ዘመኑ ፡ ሥጋዊ ፡ ማኅቴምስ ፡ ያፈርሀኪ ፡ ይቤላ ፤ ወይትባአሰኪ ፡ ደም ፡ ዘተክዕወ ፡ በመሐላ ። መሰግለ ፡ ፀሓይ ። መሰግላን ፡ በአዕዋፍ ፤ (ቅኔ ። ሲኖዶ ። ዲድ ፡ ፲፫ ። ማቴ፪ ፡ ፩) ።

**ሰግላ ፤ (ዕብ ፡ ሺቅማህ ። ሱር ፡ ሺቅማእ)** ፤ ሾላ ፤ ባንባ ፤ ዋርካ ፤ የሾላ ፡ የበለስ ፡ ዐይነት ፤ የዱር ፡ የበረሓ ፡ በለስ ። ወትብልዋ ፡ ለዛቲ ፡ ሰግላ ።



ሰግላ ፡

ፀርገ ፡ ዲበ ፡ ሰግላ ፤ (ሉቃ ፲፯ ፡ ፯ ። ፲፱ ፡ ፱) ። በሰግላ ፡ ፈንታ ፡ በለስ ፡ በበለስ ፡ ፈንታ ፡ ሰግላ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ቀተለ ፡ ወይኖሙ ፡ በበረድ ፡ ወበለሰሙኒ ፡ በአስሐትያ ። አልቦ ፡ በለስ ፡ በውስተ ፡ ሰግላ ፤ (መዝ ፡ ፸፯ ። ኤርያ ፡ ፲፫) ።

**ሰጋልው ፤** ሾሎች ፤ የሾላ ፡ ዛፎች ፤ ሰንጨቆች ። ባዕለ ፡ ሰጋልው ። በከመ ፡ ሰጋልው ፤ (፩ዜና ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ። ፪ዜና ፡ ፩ ፡ ፲፭) ።

**ሰግላጥ ፤ (ዐረ ፡ ስጂላጥ ። ሱር ፡ ሲግላአ ፤ ሽቱ) ፤** ጥሩ ፡ ልብስ ፤ ዛፉም ፡ ቅጠላም ፡ ባለ ሐረግና ፡ ባላበባ ፤ ሐር ፡ ከታን ። ጥሩ ፡ ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ ዕንጨት ፤ ቅጠሉ ፡ አበባው ፡ ሐረጉ ፡ በጥሩ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ የሚሣል ። አልባሲሆን ፡ ዘሜላት ፡ ወዘሚራይ ፡ ወሰግላጥ ። ኢይትጌረይዎ ፡ ለጼናከሙ ፡ ጥንቁቅ ፤ ሰግላጥ ፡ ዘባሕር ፡ ወጽጌ ፡ ዘለይቅ ፤ (ኢሳ፫ ፡ ፳፩—፳፫ ። አርጋ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ ጥቅ፳) ።

**ሰጊም ፤ ሞት ፤ (ሰገመ ፡ ይሰግም ፡ ይስግም ። ዕብ ፡ ሻጌም ። ሱር ፡ ሻጋም ። ዐረ ፡ ሰገመ) ፤** ማሰር ፡ ማጣመር ፤ መዝጋት ፡ መግጠም ፤ መቈለፍ ፤ የመዝጊያ ፡ ያንደበት ።

**ተሰግመ ፤** ታሰረ ፤ ተዘጋ ፤ ተቈለፈ ፤ ድዳ ፡ ኾነ ፤ ደነቈረ ።

**ስጉም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ግምት) ፤** የታሰረ ፤ የተዘጋ ፤ ዝግ ፡ ቍልፍ ፤ ድዳ ፡ ደንቈሮ ። ስጉማን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ስግመት ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እስመ ፡ ስግመት ፡ እሙንቱ ፤ (ኩፋ ፡ ፲፱) ።

**ስግመት ፤** ድዳ ፡ መኾን ፤ መደንቈር ፤ ድዳነት ፤ ድንቍርና ።

**ሰገም ፤ ስገም ፤** ገብስ ፤ ምርቃም ፡ የብር ፡ እኽል ፤ ሰውም ፡ እንስሳም ፡ የሚበላው ፤ ቅንጣቱ ፡ ባመር ፡ የታፈነ ፡ የተሸፈነ ። ማእረረ ፡ ሰገም ፡ መስፈርተ ፡ ሰገም ። ኅብስተ ፡ ሰገም ። ንሣእ ፡ ለከ ፡ ሥርናየ ፡ ወሰገመ ፤ (ሩት፩ ፡ ፳፪ ። ፪ ፡ ፲፯—፳፫ ። ራእ፮ ፡ ፮ ። ዮሐ፮ ፡ ፱ ፡ ፲፫ ። ሕዝ፬ ፡ ፱



ስገም ፡

**ሰግም ፤ (ዐረ ፡ ሽሀም) ፤** ፍላጻ ፤ የቀስት ፡ ጦር ፤ የሚነደፍ ፡ የሚወረወር ፤ ማፉ ፡ እንደ ፡ ገብስ ፡ ራስ ፡ ያለ ፡ (ገድ ፡ አዳ) ።

**ሰግን ፤ (ዘግን) ፤** ሸገነ ፡ አማረ ፤ ተሾመ ፡ ተሸለመ ፡ አጌጠ ፤ ከበረ ፡ በለጠ ፡ ምስጉን ፡ ኾነ ።

**ሰጋኒ ፤ መስገኒ ፤ ግን ፤ ግን ፤** የሸገነ ፤ ሸገን ፤ ክቡር ፡ ምስጉን ። ዘገንንና ፡ መዝገንን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንቲያ ፡ ነው ።

**ሰገኖ ፤ (ዕብ ፡ ሱጋ ፤ ታናሽ ፡ ወፍ ። ሳጋን ፤ ሹም ፡ አለቃ) ፤** ሰጐን ፤ ታላቅ ፡ አሞራ ፤ ሰጋጋ ፤ ዐንገተ ፡ ረዥም ፤ ጠጕሩና ፡ ዕንቍላሉ ፡ በውድ ፡ የሚሸጥ ፡ ክቡር ። ለወንድም ፡ ለሴትም ፡ ይከታል ፤ እንደ ፡ ደርሆ ፡ ነው ። ፀጺደ ፡ ሰገኖ ፤ (ኢሳ፴፬ ፡ ፲፫ ። ዘሌ ፲፩ ፡ ፲፯ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፲፭) ። ሲያበዛ ፡ ሰጋንው ፤ ሰገኖታት ፡ ይላል ፤ (ገድ ፡ አዳ) ።



ሰገኖ ፡

**ሰገነት ፤** በቁሙ ፤ ተሥላስንና ፡ ገንትን ፡ እይ ፤ (በማርኛ) ።

**ሰጕዐ ፤ (ሰክዐ) ፤** ሳገ ፡ ሰነገ ፤ በላ ፤ ነደለ ። ያእትቱ ፡ ይመትሩ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ይሰጕዑ ፡ ይላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ይሰጕዑ ፡ እዝነኒ ፤ (ሕገ፳፫ ፡ ፳፭) ።

**ስጕርድ ፤ (ጽር ፡ ስከርዶን ። ቅብጥ ፡ ስኮርዶን ። ዕብ ፡ ሐጺር ። ዐረ ፡ ኩረት) ፤** ሽንኵርታዊ ፤ የነጭ ፡ ሽንኵርት ፡ ዐይነት ፤ ሣልሳይ ፡ ሽንኵርት ፡ የሚበላ ፤ ራሱ ፡ እጅግ ፡ የማያኰርት ፤ ቅጠሉ ፡ ወርዳም ፡ ረዥምም ፤ በሀገራችን ፡ የሌለ ። ዛሬ ፡ ማን ፡ ይገኛል ። ዐይነታቸው ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነጩንም ፡ ሽንኵርት ፡ ስጕርድ ፡ ስጕርንድ ፡ እያለ ፡ ይጥፋል ፤ ቶመትን ፡ ተመልከት ፤ (ዘኍ፲፩ ፡ ፭ ። ገድ ፡ ተክ ። መ ፡ ፈ) ።

**ሰዲድ ፤ ዶት ፤ (ሰደደ ፤ ሰደ ፡ ይሰድድ ፡ ይስድድ ። ዕብ ፡ ሻዳድ ። ዐረ ፡ ሸደ) ፤** መስደድ ፤ ማሳደድ ፤ ማብረር ፤ ማውጣት ፤ ማስጣት ፤ ማሰናበት ፤ መስየት ፤ መላክ ፤ ወስደኽ ፡ ስጥ ፤ ኺደኽ ፡ አምጣ ፡ ተከተል ፡ ማለት ፤ ፈንወን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ይሰድዱከ ፡ እምሰብእ ። ብፁዓን ፡ አንትሙ ፡ ሶበ ፡ ይሰድዱክሙ ። እመ ፡ ሰደዳ ፡ ብእሲ ፡ ለብእሲቱ ። አውጊዘክሙ ፡ ሰድድዎሙ ። ወሰደደት ፡ ኀቤሃ ፡ ብዙኃ ፡ አምኃ ፤ (ዳን፬ ፡ ፳፱ ። ማቴ፭ ፡ ፲፩ ። ኤር፫ ፡ ፩ ። ቀሌ ። ዮሴፍ) ።

**ሰዳዲ ፤ (ዲት ፡ ድያን ፡ ያት) ፤** የሚሰድ ፤ የሚያሳድድ ፤ አባራሪ ። ዝ ፡ አስማት ፡ ሰዳዲሆሙ ፡ ለአ

ጋንንት ። ፋኑኤል ፡ ሰዳዲ ፡ ሰይጣናት ። ሰዳዲ ፡ ወጻዓሊ ፤ (ማኅ፱ ። ደራሲ ። ፳ጠ.ሞ ፡ ፳ ፡ ፲፫) ።

**መስደዲ** ፤ ግእዝ ፡ ከማሁ ። መስደዴ ፡ ፀር ፡ (አቍል) ።

**አሰደደ** ፤ አሰደደ ፤ ከገር ፡ አሶጡ ፡ አስ ፤ ባዋጅ ፡ በትእዛዝ ፡ (ግብ፲፭ ፡ ፱) ።

**ተሰደ** ፤ ተሰደደ ፤ ተበተነ ፤ ተባረረ ፤ ተለየ ፤ ተከለከለ ፤ ጠፋ ፡ ታጣ ። ዐማፀያን ፡ ይሰደዱ ፡ እምውስቴታ ። ጊሜ ፡ እንተ ፡ ተሰደ ። ይሰደድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ። ይሰደዱ ፡ እምቍርባን ። ተሰዱ ፡ በዝናም ፡ ወበበረድ ፡ (ምሳ፳ ፡ ፳፬ ። ጥበ፰ ፡ ፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፲፫ ። ፰ ፡ ፭ ። ጥበ፲፮ ፡ ፲፮) ። ፈለሰን ፡ ተመልከት ።

**ሰዱድ** ፤ (ዳን ፡ ዳት ፡ ድድ) ፤ የተለየ ፤ የተሰደደ ፤ ስደተኛ ። ስዱድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ። ተስፋሆሙ ፡ ለስዱዳን ፡ (ሲኖ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፫ ። ኪዳ) ።

**ስደት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፤ መሰደድ ፡ መሰደድ ፤ መለየት ፤ በታኝ ፡ መልቀቅ ፤ ከሀገር ፡ ከዘመድ ፡ መራቅ ፤ መፍለስ ፡ መንቀል ። ስደተ ፡ ኅሊናተ ፡ ሕማማት ። ይኀበሩ ፡ ዙሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወቶሙ ፡ በስደት ። ምንዳቤ ፡ ወስደት ፡ (ፊልክ ፡ ፲፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፲፫ ። ማቴ፲፫ ፡ ፳፩) ።

**ሰድይ** ፤ ዮት ፤ (ሰደየ ፡ ይሰዲ ፡ ይስዲ ። ትግ ፡ ሰዬ) ፤ ማገዝ ፡ መርዳት ፤ መደገፍ ፡ ማጥናት ፤ አይዞኝ ፡ ማለት ።

**ሰዳዪ** ፤ ይ ፤ ዐጋዥ ፡ ረዳት ፡ አይዞኝ ፡ ባይ ፤ ተስፋ ፡ የሚሰጥ ፡ የሚያማክር ።

**ሽዳይ** ፤ (ዕብራ) ፤ ስመ ፡ አምላክ ፤ ኀያል ፤ ጽኑዕ ፤ ከሃሌ ፡ ኵሉ ፤ ልዑል ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ። **ኤልሻዳይ** ፤ (ኤል ፡ ሻዳይ) ፤ አምላክ ፡ ተስፋ ፤ ዘይሴፎ ፡ ኵሉ ፡ ኪያሁ ፤ ወዘያስተሴፎ ፡ (ዘፀ፮ ፡ ፲፱ ፡ ፲፬ ። ሕዝ፲ ፡ ፭) ።

**ሰድይ** ፤ ተስፋ ፡ አለኝታ ። አምላካዊ ፡ ቃል ፤ ከፈጣሪ ፡ በቀር ፡ ፍጡር ፡ ሊናገረው ፡ የማይቻል ። ጥዑመ ፡ ከናፍር ፡ ክርስቶስ ፡ እንተ ፡ ትነብብ ፡ ሰድየ ፡ (ደራሲ ። ዮሐ፲ ፡ ፴፭ ። ፲፬ ፡ ፱) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ሰደየ ፡ እማረ ፡ ብለው ፡ ይገቡና ፤ ሰድይን ፡ ያማረ ፡ ይሉታል ። ሰሀደንና ፡ ወሳይድን ፡ እይ ።


**ሰዶም** ፤ (ዕብ ፡ ስዶም) ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ ጌታ ፡ በመዐት ፡ ከገለበጣቸው ፡ ከ፭ቱ ፡ አህጉር ፡ አንዲቱ ፤ ታላቂቱ ። ሲድ ፡ ኖራ ፤ ም ፡ ዊ ፤ ሰዶም ፡ ሲዳዊት ፤ ዘሲዳውያን ፤ ኖራማ ፡ ኖራም ፡ ባለኖራ ፡ የኖራ ፡ አውራጃ ፡ አገር ፤ ፀዘቅተ ፡ ሲድ ፡ ቈላተ ፡ ሲድ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዘፍ ፲፫ ፡ ፲ ። ፲፬ ፡ ፲) ። ኋላም ፡ ባሕረ ፡ ጺው ፡ ኹኖ ፡ ያስጠማት ፡ ከኖራው ፡ ፀዘቅት ፡ የወጣ ፡ ውሃ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

**ሰዶማዊ** ፤ የሰዶም ፤ ሰዶምማ ፤ ሰዳም ፤ የሰዶምን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፤ ነውረኛ ፤ ወንዳገረድ ፡ (ቄድር) ።

**ሰዴማ** ፤ (ዕብ ፡ ሽዴማ ፤ ሽዴፋ) ፤ የሰለተ ፡ የደረቀ ፡ የበዘዘ ፤ ብርድ ፡ ቀጭ ፡ ዋግ ፡ የመታው ፡ ሰብል ፤ ገራህተ ፡ እክል ፡ ዐጸደ ፡ ተክል ፡ ማዕረ ፡ አንሕስት ፡ ወሰዴማ ፡ (፬ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፳፮) ።

**ሰዲሞት** ፤ (ጽር ፡ ሳዲሞት ። ዕብ ፡ ሻድሞት) ፤ የሰዴማ ፡ ብዙ ፤ እሕቃላት ፡ እሕቁል ፤ ገራውህ ፡ እክል ፤ አዕጻደ ፡ ተክል ። ሰዲሞተ ፡ ቄድሮን ፡ (፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፬) ።

**ሰደፍ** ፤ (ዐረብ) ፤ የባሕር ፡ እንስሳ ፤ ዕንቍ ፡ የሚወልድ ፤ ዐጥንቱ ፡ እንደ ፡ ቀንድ ፡ እንደ ፡ ዝሆን ፡ ጥርስ ፡ የሚነጠጥና ፡ የሚቀረጥ ፤ መስቀል ፡ መቍጠሪያ ፤ ያንገት ፡ ጌጥ ፡ መሣሪያ ፤ ዝሬር ፡ የሚኾን ፤ እስመ ፡ ሰደፍ ፡ ይወልዶ ፡ ለዕንቍ ፡ ሶበ ፡ ይትዌከፍ ፡ ኀይለ ፡ ነፋስ ፡ (ማር ፡ ይሥ፳፫) ።



ሰደፍ ፤

— ፤ የንፍጥ ፡ ሳት ፤ የጠመንዥ ፡ ዕንጨት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሰዲቅ** ፤ ቆት ፤ (ሰደቀ ፡ ይሰድቅ ፡ ይስድቅ ። ዕብ ፡ ራፋድ) ፤ መዘርጋት ፤ ማንጠፍ ፤ መንሰንስ ፡ መጐዝጐዝ ፡ ማመቻቸት ፤ የማእድ ፡ ያልጋ ። ማጋደም ፡ ማስተኛት ፤ የድውይ ፡ የሕፃን ፡ የሬሳ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ቀብ ፡ ዐሸ ፡ አለዘበ ፡ ይሉታል ። ሰደቁኒ ፡ በአክዋል ፡ እስመ ፡ (ሕምምተ ፡ ፍቅር ፡ አነ) ፡ ቍነደፍኩ ፡ በፍቅሩ ፡ (ማሕ፪ ፡ ፭) ።

**ሰዲቅ** ፤ (ዐረ ፡ ሰደከ ፤ ወደየ ። ዕብ ፡ ሳዳቅ ፤ ሠጠቀ) ፤ መጨፍለቅ ፡ አንዱን ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ጨምሮ ፡ ኹለት ፡ ሦስቱን ፡ አንድ ፡ ማድረግ ፤ የብረት ። መክፈል ፡ መሠንጠቅ ፡ መተርተር ፡ መፍለጥ ፤ ያክርማ ፡ የንጨት ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ኰላ ፡ ይሉታል ፤ ደመቀን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

— ፤ አብገዶ ፡ መቅበት ፤ በቅቤ ፡ መለወስ ፡ ማጨማለቅ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ተሰድቀ** ፤ ተጨፈለቀ ፤ ተሠነጠቀ ። ሥሳሴ ፡ እንተ ፡ ኢትሰደቅ ፡ ወኢትትፈለጥ ፡ በዕሪና ፡ (ቀረ ፡ ቄር፲፱) ። አካሲ ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ የማይጨፈለቅ ፡ ባሕርይዋ ፡ እንደንጨት ፡ የማይሠነጠቅ ፤ በአካል ፡ አንድ ፡ በባሕርይ ፡ ሦስት ፡ የማትባል ፤ የባሕርይ ፡ ምንታዌ ፡ ያካል ፡ ርባዔ ፡ የሌለባት ፡ ማለት ፡ ነው ። አይደናይንና ፡ ኢሎሄን ፡ መለኮትን ፡ እይ ።

**ሰዱቅ** ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ድቅት) ፤ የተዘረጋ ፡ ዝርግ ፤ ጭፍልቅ ፤ ሥንጥቅ ፤ የተቀባ ፡ ቅቡዕ ። ስዱቅ ፡ በአክዋል ፡ (ድጓ) ።

**ሰደቃ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፡ ማእድ ፡ ገበታ ፤ ጠረጴዛ ፤ አውራጅ ፤ እግር ፡ ያለው ፡ ዝርግ ፡ ሰታታ ።

**ስድቅ ፤ (ትግሬ ፡ ሽድቅ) ፤** የአፍ ፡ ማእዝን ፡ ግራና ፡ ቀኙ ፡ ማጠፊያው ።

**ሳዶቅ ፤ (ዕብ ፡ ጻዶቅ) ፤** የሰው ፡ ስም ፤ ጻድቅ ፤ እውነተኛ ፡ (፪ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፳፭) ። የሰዱቃውያን ፡ መምር ።

**ሰዱቃዊ ፤ (ውያን ። ዕብ ፡ ጽዱቂ ፤ ጽዱቂም) ፤** የሳዶቅ ፡ ወገን ፤ ተማሪው ፡ ደቀ ፡ መገዙሙሩ ፤ ባህሉ ፡ ከፈሪሳዊ ፡ የተለየ ፤ ከኦሪት ፡ በቀር ፡ ነቢያትን ፡ የማይቀበል ፤ መልአክ ፡ መንፈስ ፡ ትንሣኤ ፡ የለም ፡ የሚል ፤ መንፈሳዊን ፡ ኹሉ ፡ የሚክድ ፡ (ማቴ፳፪ ፡ ፳፫ ። ግብ ፳፫ ፡ ፰) ።

**ሰዴር ፤ ሮት ፤ (ሰደረ ፡ ይሰድር ፡ ይስድር ። ዕብ ፡ ሳዳር) ፤** መሰደር ፡ መደርደር ፤ በተራ ፡ ማኖር ፤ እንደ ፡ ጣት ፡ እንደ ፡ ደረት ፡ በጥንት ። ሴደርያ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ዐረከን ፡ ተመልከት ።

**ሳዶር ፤** የቀኖት ፡ ስም ፡ ችንካር ፡ ያይያለ ፡ ሴላ ፡ ዐይነት ፤ ደጋን ፡ ብረት ፤ እንደ ፡ ዝናር ፡ ኹሉ ፡ ከጡቶቹ ፡ በታች ፡ ሰውነቱን ፡ ከበ ፡ ዐቅፎ ፡ ደግፎ ፡ ከመስቀል ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፤ ወይም ፡ ገመድ ፡ ሰንሰለት ። ሳዶር ፤ ዘበትርጓሜሁ ፡ ካልእ ። ወፈትሑ ፡ ሐብለ ፡ እምሐቌሁ ፡ ዘተአሥረ ፡ ቦቱ ፡ ምስለ ፡ መስቀል ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ድር ፡ ማሕ) ። ሳዶር ፡ ከሴስ ፡ ባራት ፡ ችንካር ፡ ብቻ ፡ ከመስቀል ፡ ተጣብቆ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ መቆም ፡ አይቻልምና ፤ ካልእ ፡ ማለቱ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። አላዶርንና ፡ ዳናትን ፡ አደራንና ፡ ሮዳስን ፡ እይ ።

**ሰድሰ ፤ ሰት ፤ (ሰደሰ ፡ ይሴድስ ፡ ይሰድስ ። ዕብ ፡ ሻሼሀ) ፤** መሰደስ ፤ ስድስት ፡ ማድረግ ፤ ከስድስት ፡ መክፈል ።

**ሰዳሲ ፤ (ሲት ፡ ስያን ፡ ያት) ፤** የሚሰድስ ፤ ሰዳሽ ፤ ስድስት ፡ አድራጊ ።

**ተሰደሰ ፤** በቁሙ ፤ ስድስት ፡ ኾነ ፤ ስድስት ፡ ተባለ ፤ በስድስት ፡ ክፍል ፡ ተከፈለ ።

**ስዱስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ድስት) ፤** የተሰደሰ ፤ ስድስት ፡ የኾነ ፤ የተባለ ፤ ከስድስት ፡ የተከፈለ ።

**ስድሱ ፤ ስሱ ፤ (ዕብ ፡ ሼሽ ። ሱር ፡ ሽታ ። ዐረ ፡ ሲት) ፤** የቍጥር ፡ ስም ፤ የሱቶች ፡ ድምር ፤ ስድስት ፤ ባምስትና ፡ በሰባት ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ቍጥር ፤ ገቢርም ፡ ይከታል ፡ እንደ ፡ ሰብዑ ፡ ነው ። አዳብዐ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ በበ ፡ ስሱ ። ናሁ ፡ ስሱ ፡ ዘይጸልእ ፡ እግዚ ። ወእምድኅረ ፡ ስሱ ፡ መዋዕል ። ጊዜ ፡ ስሱ ፡ ሰዓት ፡ ወርኢኩ ፡ ስሱ ፡ ኀዋኀወ ፡ በምሥራቅ ፡ ወስሱ ፡ ኀዋኀወ ፡ በምዕራብ ፡ (፪ነገ ፡ ፳፩ ፡ ፳ ። ምሳ፮ ፡ ፲፮ ። ማቴ፲፯ ፡ ፩ ። ፳ ፡ ፭ ። ሔኖ ፡ ፺፪) ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ስለ ፡ ጣፊ ፡ ስሕተት ፤ በወንዶች ፡ አንቀጽ ፡ እየገባ ፡ ተጥፎ ፡ ይገኛል ።

**ስድስቱ ፤ ት ፤** ገነ ፡ ከማሁ ፤ የወንዶች ፡ ድምር ፤ ወ—፮ ። ስድስቱ ፡ ዕደው ። ወሰበ ፡ አሕዱ ፡ በበ ፡ ስድስቱ ፡ ክነፊሆሙ ። ስድስቱ ፡ ተወልዱ ፡ ሎቱ ፡ በኬብሮን ፤ ወነግሠ ፡ በህየ ፡ ሰብዐተ ፡ ዓመተ ፡ ወስድስተ ፡ አውራኀ ። ወሰደኩ ፡ ሎቱ ፡ ስድስተ ፡ ደቂቀ ፡ (ሕዝ፱ ፡ ፪ ። ኢሳ፮ ፡ ፪ ። ፩ዜና ፡ ፫ ፡ ፬ ። ዘፍ ፡ ፴ ፡ ፳) ።

**ስዳሴ ፤** መሰደስ ፤ ስደሳ ፤ ስድስት ፡ ማድረግ ፤ ስድስት ፡ መኾን ፡ መባል ፤ ስድስትነት ።

**ትስድስት ፤** ገነ ፡ ከማሁ ፤ ስድስትነት ፡ ስድስት ፡ መኾን ።

**ሰዱስ ፤** የዕለት ፡ ቅጽል ፤ ስድስት ፤ ስድስተኛ ። ሰዱሰ ፡ ዕለተ ፡ ተገበር ፡ ግብረከ ፡ እስመ ፡ በሰዱስ ፡ ዕለት ፡ ገብረ ፡ እግዚ ። አክኑ ፡ ሰዱስ ፡ መዋዕል ፡ ውእቱ ፡ በዘትገብሩ ። በሰዱሱ ፡ ሰጽልመት ። ወእመ ፡ ሰዱስ ፡ ዕለት ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፲ ። ሉቃ፲፫ ፡ ፲፬ ። ሐጌ፩ ፡ ፩ ። ማር፱ ፡ ፪ ። ድጓ) ።

**ስድስ ፤** የጊዜና ፡ የልክ ፡ የስፍር ፡ ቅጽል ፤ ስድስት ። ስድሰ ፡ ያድኅነከ ፡ እመንሱት ። ግድሙ ፡ ስድስ ፡ በእመት ። ዘዘርዐ ፡ ስድሰ ፡ ያአቱ ፡ ሥልሰ ። ወሰፈረ ፡ ውስቴቱ ፡ ስድሰ ፡ እክለ ፡ ሰገም ፡ (ኢዮ፭ ፡ ፲፱ ። ዳን፫ ፡ ፩ ። ኢሳ፭ ፡ ፲ ። ሩት፫ ፡ ፲፭) ።

**ሳድስ ፤ (ስት ፡ ሳን ፡ ሳት) ፤** የተራ ፡ ቅጽል ፤ ስድስተኛ ፤ ከስድስት ፡ አንድ ። በሳድስ ፡ ዓመት ። ወበሳድስ ፡ ወርኅ ። ወኮነ ፡ ሳድስተ ፡ ዕለተ ። ሳድስተ ፡ ኢፍ ፡ (ሕዝ፰ ፡ ፩ ። ሉቃ፩ ፡ ፳፮ ። ዘፍ፩ ፡ ፴፩ ። ሕዝ፵፮ ፡ ፲፫) ።

**ሳድሳዊ ፡ ይ ፤ (ዊት ፡ ሲት) ፤** ገነ ፡ ከማሁ ፤ ስድስተኛ ።

**ሳድሲት ፤** የቍጥር ፡ መደብ ፤ ስድስተኛ ፡ ክፍል ፤ የኅምሲት ፡ ስሳኛ ። ኬክሮስን ፡ እይ ።

**መስድስት ፤** ስድስት ፡ ወገን ፤ እመም ፤ ገዝም ፤ ትልም ፤ ዙር ፤ መሥመር ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።


**ምስድሲት ፤** ስድስት ፡ ዕጥፍ ፤ ለወ—፴፮ ። ስድስት ፡ እጅ ።

**ስድሳ ፤ ስሳ ፤** የቍጥር ፡ ስም ፤ ባምሳና ፡ በሰባ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ሠ—፷ ፤ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ስድስት ፤ ወይም ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ። ኑኑ ፡ ስሳ ፡ በእመት ። ስሳ ፡ እማንቱ ፡ ንግሥታት ። ቦ ፡ ዘምእት ፡ ወቦ ፡ ዘስሳ ። ኅረይ ፡ እንተ ፡ ስሳ ፡ (ዳን፫ ፡ ፩ ። ማሕ፮ ፡ ፰ ። ማቴ፲፫ ፡ ፰ ። ፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፱) ።

**ሰዊብ ፤ ቦት ፤ (ሶበ ፤ ሰወበ ፡ ይሰውብ ፡ ይሱብ ። ሰበበ) ፤** ማዘር ፤ መጠምጠም ፡ አዙሮ ፡ መግጠም ፤ ዙሪያ ፡ ክብ ፡ ማድረግ ፤ የማገር ፡ የስፌት ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**መሰብ ፤ (ዕብ ፡ ሞሻብ ፤ ምንባር ፡ ቦታ ፡ ዕቃ) ፤** በቁሙ ፤ የዳቦ ፡ ማጥን ፤ የንጀራ ፡ ታቦት ፤ አገልግል ፡ ሌማት ፡ ቅንብቻ ፡ ጉብ ፤ ሙዳየ ፡ ኅብስት ። መሰበ ፡ ወርቅ ፡ እንተ ፡ መና ። ስፋሕ ፡ የማነከ ፡ ባዕለ ፡ ዘቲ ፡ መሶብ ። ንሣእ ፡ መሰበ ፡ ኅብስት ፡ ወጻሕበ ፡ ወይን ፡ (ዕብ፱ ፡ ፬ ። ቅዳ ፡ ጎር) ።

**መሳውብ ፤** መሶቦች ፤ አገልግሎች ። ምስጢራቸው ፡ ሣጥንነትና ፡ ክብነት ፡ ነው ።



መሶብ ፡

**ሶብ ፤ ሶበ ፤ (ዐቢይ ፡ አገባብ ፤ እመ) ፤** ቢ ፡ ባ ፡ ብ ፤ ከ ፡ ካ ፤ ጊዜ ። ባ ፡ ካ ፡ መኾኑ ፡ ባሉታ ፡ ላይ ፡ ነው ። ብፁዓን ፤ አንትሙ ፡ ሶበ ፡ ይጸልኡክሙ ፡ ወይጼዕሉክሙ ፡ ወያወፅኡ ፡ ለክሙ ፡ ስመ ፡ እኩየ ፤ ቢ ። ሶበ ፡ አኮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌነ ። እምኀየሰ ፡ ሶበ ፡ ኢተወልደ ፤ ባ ። ሶበሰ ፡ ታፈቅሩኒ ። ሶበሰ ፡ እምዓለም ፡ አንትሙ ፤ ብ ። ሶበ ፡ እምዐጺብ ፡ ይድኅን ፡ ጻድቅ ። ሶበ ፡ እንዘ ፡ ሰብእ ፡ አንተ ፡ ትትቄየም ፡ ሰብአ ፤ ከ ። ወሶበ ፡ እንዘ ፡ ዘበምድር ፡ እነግረክሙ ፡ ኢተአምኑኒ ፤ ካ ። ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፤ ጊዜ ። አንዳንድ ፡ ባላገባቦች ፡ ቢ ፡ ባ ፡ ስ ፡ ምንው ፡ ይኾናል ፡ ይላሉ ፤ ምስክራቸው ፡ አያጠግብም ። ቢ ፡ ባ ፡ ስ ፡ ያሉት ፤ ቢ ፡ ባ ፡ ብ ፡ ከሰው ፡ ይገባል ። ምንው ፡ ያሉትም ፤ ሚ ፡ እምትን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሶበ ፡ ሞትን ፡ ብሎ ፡ ስላገኙት ፡ ነው ። የሚን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ። የሶበ ፡ ምስጢር ፡ ባፈታቱ ፡ ኹሉ ፡ ጊዜን ፡ አይለቅም ፡ (ዕር፲፱ ፡ ቍ፫፯ ፤ ፫፯) ።

**ሶቤ ፤ ሶቤሃ ፤** ያን ፡ ጊዜ ፤ ፈጥኖ ፤ ወዲያው ፤ ቶሎ ። ረኪቦ ፡ መጽሐፈ ፡ ሶቤ ። ይእተ ፡ ሶቤ ። ወቀትር ፡ ሶቤሃ ። ምዕረ ፡ አውሚአክ ፤ ሶቤሃ ፡ ፈጽም ፡ ቃለክ ፡ (ስንክ ፡ ሚያ፳ ። ማቴ፳፮ ፡ ፳፫ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፳፬ ። ሚራ፴፰ ፡ ፳፫) ። ለሶቤሃ ፤ እምሶቤሃ ፤ እስከ ፡ ሶቤሃ ፡ ቢል ፡ ፍችው ፡ ፩ ፡ ነው ። ሶቤሁ ፡ ሃ ፡ ከ ፡ ኪ ፡ የ ፤ ሶቤሆሙ ፡ ን ፡ ክሙ ፡ ን ፡ ነ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ አመ ፡ ይዘረዘራል ።

**ሶበርት ፤—ከሶ ፡ ሹጥ ፤—ሰበረ ።**

**ሰዊድ ፤ (ሰደ ፡ ይሰውድ ፡ ይሱድ ። ዕብ ፡ ሳድ ፤ ማረረ) ፤** መጫር ፤ መተርከስ ፤ መዘቅ ፡ ማፈስ ፤ ማንደድ ፡ መፍስቈስ ፤ የፍሕም ። መመሥረት ፤ መሠረት ፡ መጣል ፡ የሕንጻ ፡ የምክር ።

**መስወድ ፤ (ብ፤ ፡ መሳውድ) ፤** መጫሪያ ፡ መተርከሻ ፤ ገል ፡ ብረት ። እግር ፤ መሠረት ። መስወደ ፡ እሳት ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፫ ። ፴፰ ፡ ፫፱ ፡ ፫፫ ። ኤር፶፪ ፡ ፲፱) ። መሳውድት ፤ ወይም ፡ አእጋር ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ መሳውልት ፡ ይባላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕቶት ፡ ነው ። (ዘፀ፴፱ ፡ ፲ ። ፴፰ ፡ ፳፱) ።

**ሳውዳ ፤ (ዐረ ፡ ሰውዳኢ) ፤** የእሳት ፡ ጠባይ ፤ እሳታዊ ፡ ባሕርይ ፤ የሚያነድ ፡ የሚያሞቅ ፡ የሚያቃጥል ። ሕዘን ፡ ይትወለድ ፡ እምነ ፡ ሳውዳ ፡ (ፈላስ ፡ ገ፴፭) ።

**ሱዳን ፤** ጥቍር ፤ ጠቋራ ፤ ከሰልማ ፡ መልከ ፡ ሕብር ። የጥቍሮች ፡ የኩሽ ፡ ልጆች ፡ አገር ፤ የአፍሪቃ ፡ ክፍል ፤ ከግብጽ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፤ ማዮን ፡ ኤፌሶን ፡ የሚያጠጡት ። በጽርእና ፡ በግእዝ ፡ መጽሐፍም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይባላል ፤ ፍችው ፡ ጥቍር ፡ ማለት ፡ ነው ። ጥቍሩን ፡ ቅመም ፡ አበሱድ ፤ አበሱዳ ፡ እንዲሉት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሰውደት ፤ (ሐበብ) ፤** ስምጽ ፤ የእሳት ፡ ብላቴ ፡ ዐመድና ፡ ሊድ ፡ ወይም ፡ ኖራ ፡ የሚመስል ።

**ሶጠ ፤—መለሰ ፤—ሠዊጥ ፡ ሦጠ ።**

**ሰዊጥ ፤ ጠት ፤ (ሶጠ ፡ ይሰውጥ ፡ ይሱጥ ፤ ወደየ ። ዕብ ፡ ሻጥ ፡ ያሹጥ) ፤** መዋኘት ፤ መቅዘፍ ፤ መሸንቈጥ ፡ መግረፍ ፤ ሾጥ ፡ ማድረግ ። መጨመር ፡ ማፍሰስ ፤ መሻጥ ፤ መሽጐጥ ፤ ማዘንበል ፡ መቅዳት ፡ መገልበጥ ። አሰውጥ ፡ እምነ ፡ መንፈስየ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ። ሶጠ ፡ ቅብዐ ፡ ላዕለ ፡ ርእሳ ። ኢትሱጥ ፡ እሳቶሙ ፡ ለኃጥአን ። ሶጠት ፡ ቀሡታ ፡ ውስተ ፡ ምስታይ ። ሶጠ ፡ እምጻሕብ ፡ ውስተ ፡ ጻሕብ ፡ (ግብፀ ፡ ፲፯ ። ዘፍ፳፰ ፡ ፲፰ ። ሚራ፫ ፡ ፲ ። ዘፍ፳፬ ፡ ፳ ። ኤር፵፰ ፡ ፲፩) ።

—፤ ማዋሐድ ፤ አንድ ፡ ማድረግ ፤ የበጎ ። መቀላቀል ፤ መደባለቅ ፡ የክፉ ። ኮነ ፡ ሰብእ ፡ ሰዊጦ ፡ ርእሰ ፡ በዘኢኮነ ፡ ቀዳሚ ። አመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ ሶጣ ፡ ለነፍሱ ፡ ውስተ ፡ ሥጋሁ ፡ (ቄር ። ቅዳ ፡ አፈ) ። ሶጠ ፡ ልሳናቲሆሙ ፤ ቀላቀለ ፡ (ኩፋ ፡ ፲) ።

**ሰዋጢ ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት) ፤** የሚጨምር ፡ ጨማሪ ፤ ቀዛፊ ፤ ገራፊ ።

**አሶጠ ፤** አስጨመረ ፤ አስገረፈ ።

**ተሰውጠ ፤** ተጨመረ ፤ ገባ ፤ ተዋሐደ ፤ ተቀላቀለ ። ይሰወጥ ፡ ማይ ፡ ውስተ ፡ ሐመር ፡ እምገድ ። ዕፍረት ፡ ዘተሰውጠ ፡ (ማር፲፬ ፡ ፴፮ ። ማሕ፩ ፡ ፫) ።

**ስዉጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ውጥ) ፤** የተጨመረ ፤ የተጨማመረ ፤ የተቀላቀለ ፤ የተጨመረበት ። መዓር ፡ ስዉጥ ። ክርሥኪ ፡ ስዉጠ ፡ ሥርናይ ፡ (አዋል ። ማሕ፯ ፡ ፪) ።

**ሱጠት ፤** መጨመር ፤ ማዋሐድ ። ተጨማሪ ፡ መኾን ። ሱጠቱ ፡ ርእሱ ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ሰውጥ ፤ (ዕብ ፡ ሾጥ ። ሱር ፡ ሻውጣ ። ዐረ ፡ ሰውጥ) ፤** ዐለንጋ ፤ ለበቅ ፤ መሸንቈጫ ፤ ሾጥ ፡ ማድረጊያ ። ከመ ፡ ሰውጥ ፡ ለፈረስ ። ለገብር ፡ እኩይ ፡ ሰውጥ ፡ ወመቃይጽ ፡ (ምሳ፳፮ ፡ ፫ ። ሲራ፴ ፡ ፴፭) ።



ሰውጥ ፡

**ሰውጣት ፤ አስዋጥ ፤** ዐለንጋች ፤ መግረፊያዎች ። ይዝብጥዎ ፡ በአስዋጥ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፲፮) ።

**መሰጥ** ፤ (ብ ፡ መሳውጥ) ፤ ማፍሰሻ ፤ መጨመሪያ ፡ ጡት ፤ ወይም ፡ ጡታም ፡ ዕቃ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጥ ፡ ፈንታ ፡ መሰር ፡ መሳውር ፡ ይላል ። ባሰብሉዮችም ፡ የሰወረ ፡ ዘር ፡ መሰሏቸው ፤ ማፈኛ ፡ መክደኛ ፡ መግሳሊት ፡ መሰወሪያ ፡ ይሉታል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ። ሰብዐቱ ፡ መሳውር ፡ በዘይበቅይዋ ፡ ለመኃትዊሃ ፡ (ዘካ፬ ፡ ፪ ። መቃ ፡ ገ፲፰ ። ክብ ፡ ነገ ። ቀሌ ። ድጓ) ።

**ሰወየ** ፤—በሰለ ፡ ሸተ ፤—ሠወየ ።

**ሶከ** ፤—እሾኽ ፤—ሦከ ።

**ሶከር** ፤ (ራት ፤ ሰዋክር) ፤ ሸንኰር ፤ የስኳር ፡ አገዳ ፤ ማር ፡ ማር ። ጥንቅሽ ፡ ጥንቅሽ ፡ የሚል ። ስኳር ፤ ያገዳ ፡ ማር ፤ የማር ፡ ወለላ ። ይጥዕም ፡ ቃልየ ፡ እመዓር ፡ ወሶከር ። እመዓር ፡ ወሶከር ፡ ጥዕመኒ ፡ ለአፉየ ። ሜስ ፡ ዘአጣእጥእዎ ፡ በሶከር ፡ (ቀሌ ። መዝ ፡ ፲፰ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፳) ።



ሶከር ፤

**ሶልያና** ፤ (ጽር ፡ ሴሊኒ) ፤ ጨረቃ ፤ ድንግል ፡ ማርያም ። ጊዜ ፡ ዕረፍታ ፡ ለሶልያና ፡ (ድጓ) ።

**ሶልላ** ፤—ዐፈር ፡ ኰረት ፤—ሰሊል ፡ ሰለ ።

**ሱላማጢስ** ፤—ፍጽምት ፤—ሰሊም ፡ ሰለመ ።

**ሰም** ፤ ሳውም ፤ (ዕብ ፡ ሾሀም ። ጽር ፡ ሰርድዮን) ፤ የዕንቍ ፡ ስም ፤ ዕንቍ ፤ ክቡር ፡ ደንጊያ ። እብነ ፡ ሶም ። ቢረሌ ፡ ወሳውም ፡ (፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፪ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፳) ።

**ሱም** ፤ ሶመት ፤ (ዐረ ፡ ሱም ። ዕብ ፡ ሹሚም ። ሱር ፡ ቱማአ) ፤ ነጭ ፡ ሽንኵርት ፤ ቱማ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ እንኰርቦ ፤ አንደ ፡ ፀርበሬ ፡ ይሉታል ፤ ስጕርድን ፡ ተመልከት ። በጸለ ፡ ወሶመተ ። ስጕርድ ፡ ወሶመት ፡ (ዘኍ፲፩ ፡ ፭ ። ገድ ፡ ተክ) ።



ሶመት ፤

**ሰወነ** ፤—ቆበረ ፡ አለገገ ፤—ሠዊን ፡ ሠወነ ።

**ሰዐ** ፤—ሠዋ ፡ አቃጠለ ፤—ሠዊዕ ፡ ሦዐ ።

**ሰዊቅ** ፤ ቆት ፤ (ሶቀ ፡ ይሰውቅ ፡ ይሱቅ ፤ ዐመደ ። ዕብ ፡ ሾቄቅ ፤ ፈተወ) ፤ መሶቅ ፡ መደገፍ ፤ እንዳይወድቅ ፡ ማድረግ ፤ ደግፎ ፡ መያዝ ፡ መጠበቅ ፤ ማገዝ ፡ መርዳት ፤ ማጥናት ፡ ማበርታት ፡ አይዞኽ ፡ ማለት ፤ ማቆም ፡ መግታት ። አኮ ፡ ሰዕፀ ፡ ዘትሰውቆን ። ባዕል ፡ ሰእመ ፡ ተንተነ ፡ ይሰውቅዎ ፡ አዕርክቲሁ ። ሶቀነ ፡ ወአብጽሐነ ፡ እስከ ፡ ዛቲ ፡ ሰዓት ። ሶቀት ፡ ረድኤቱ ። ለሰዊቆትየ ፡ ሶበ ፡ እድኅፀ ። ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ ሶቀ ፡ ሎሙ ፡ ማየ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወኅለፉ ፡ (ገድ ፡ ላሊ ። ሚራ፲፫ ፡ ፳፩ ። ሲጦን ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፮ ። አርጋ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ሠኔ፳፯) ።

**ሰዋቂ** ፤ (ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት) ፤ የሚደግፍ ፡ ደጋፊ ፤ አይዞኽ ፡ ባይ ። ሰዋቄ ፡ ትንቱናን ፡ እምደኅፀ ። ኩነኒ ፡ ሰዋቄ ፡ ወምስማካ ። ምርጕዝ ፡ ሰዋቄ ፡ አብራክ ፡ (ደራሲ ። አዋል) ።

**ሶቅ** ፤ (ዕብ ፡ ሾቅ ። ሱር ፡ ሻቃ ። ዐረ ፡ ሳቅ) ፤ እግር ፡ ባት ፤ ከጕልበት ፡ እስከ ፡ ቍርጭምጭሚት ።

**አሶቀ** ፤ አስደገፈ ፤ ደጋፊ ፡ ሰጠ ።

**ተሰውቀ** ፤ ተደገፈ ፤ ተሸራሸ ፤ ከመውደቅ ፡ ዳነ ።

**ተሳወቀ** ፤ ተደጋገፈ ፤ ተጠናና ፤ አይዞኽ ፡ አይዞኽ ፡ ተባባለ ። እስመ ፡ ይሳወቃ ፡ በበይናቲሆን ፡ ወይዳንኖ ፡ በኀይሎን ፡ (ሄርማ ፡ ገ፲፭) ።

**ስዉቅ** ፤ (ቃን ፡ ቃት ፡ ውቅ) ፤ የተደገፈ ፤ የተደጋገፈ ፤ ድግፍ ፡ ድግፍግፍ ፤ ንብብር ።

**ስዋቅ** ፤ (ቃት ፤ አስዋቅ) ፤ ድጋፍ ፤ ደገፉ ፤ ምርጕዝ ፡ ባላ ፡ ወጋግራ ፤ ዐምድ ፡ ምሰሶ ። ኤፍሬም ፡ ስዋቀ ፡ ርእስየ ። ማረራ ፡ ለምድር ፡ ዲበ ፡ ማይ ፡ ወአጽንዓ ፡ ዘእንበለ ፡ ስዋቅ ። ስዋቀ ፡ አጽራሒሃ ። አስዋቅ ፡ (መዝ ፡ ፺፯ ። መቃ ፡ ገ፳፭ ። መጽ ፡ ምስ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

**መስወቅ** ፤ መሶቅ ፤ (ብ ፡ መሳውቅ) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ምክያደ ፡ መሳውቅ ፡ (ገድ ፡ ላሊ) ።


**መሶቅት** ፤ (መሳውቅት) ፤ የሴት ፡ አንቀጽ ። ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ።

**መሳውቃት** ፤ የብዙ ፡ ብዙ ። ድጋፎች ፤ ደገፋዎች ፡ (፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፲፪) ።

**ሱቅ** ፤ (ዐረብ ። ዕብ ፡ ሹቅ) ፤ መደብር ፤ ገባያ ፡ መሸጫና ፡ መግዣ ፡ ቤት ፡ ቦታ ፤ የከተማ ፡ ውስጥ ፤ የወደዱትና ፡ የፈለጉት ፡ የተመኙት ፡ ኹሉ ፡ የሚገኝበት ።

**ሶር** ፤ (ብ ፡ አስዋር ። ዕብ ፡ ሾር ፤ ብ ፡ ሽዋሪም) ፤ ተባት ፡ ላም ፤ በሬ ፤ አውራ ፡ ኰርማ ፤ ሚል ።

ገኙ ። ሶር ፡ አሐዱ ፡ እምውስተ ፡ አልሕምት ። ወወፅአ ፡ ሶር ፡ ጸዐዳ ። አልሕምት ፡ ብዙኃን ፡ ወአስዋር ፡ ሥቡሓን ። መጋዝእትየ ፡ ወአስዋርየ ፡ (ዘኍ፳፱ ፡ ፫ ። ሔኖ፹፰ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፷፩ ። ማቴ፳፪ ፡ ፬) ። ተውርን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።



ሶር ፡

**ሰውር** ፤—የኮከብ ፡ ስም ፤—ተውር ።

**ሰውሮ** ፤ ሮት ፤ (ሰወረ ፡ ይሴውር ፡ ይሰውር ፤ ኀብአ ። ዕብ ፡ ሻዌር ፤ ሸመቀ ፥ አደባ) ፤ መሰወር ፡ መደበቅ ፤ መሸሸግ ፡ ማራቅ ፤ መከለል ፡ መጋረድ ፤ ማልበስ ፡ መክደን ፤ መሸፈን ፡ መቅበር ፤ እንዳይታይና ፡ እንዳይገኝ ፡ ቢገኝም ፡ እንዳይታወቅ ፡ ማድረግ ፤ ራሱን ፡ ሰውነትን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ። ኀብአን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ኢትሰውር ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ። ሰውሮት ፡ ሰዐርክየ ፡ ኢየኀፍር ። ወይሴውር ፡ ኀፋያን ፡ በደመና ። ኀፍረቱ ፡ መስቀል ፡ ሰወርከ ፡ በዐርቃን ፡ ልብስ ፡ (፪ዕዝ ፡ ፲፬ ፡ ፮ ። ሚክ፳፪ ፡ ፳፭ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ቅኔ) ።

**ሰዋሬ** ፤ (ሬት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ የሚሰውር ፤ የሚደብቅ ፤ የሚታደግ ፡ ታዳጊ ። እግዚ ፡ ሰዋሬ ፡ ወከዳኒ ። ኀባኢት ፡ መሰኮት ፡ ወሰዋሪት ፡ ዘሎ ፡ ኀሊናት ፡ (አዋል ። ቅዳ ፡ ጎር) ።

**መሰውር** ፤ (ርት ፡ ራን ፡ ራት) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ። መክደኛ ፡ ክዳን ። ረዳኢ ፡ ወመሰውር ፡ (ዘፀ ፲፭ ፡ ፪ ። ሺ፮ ፡ ፫) ።

**ተሰወረ** ፤ በቁሙ ፤ ተሸሸገ ፡ ተደበቀ ፤ ራቀ ፡ ረቀቀ ፤ ታባ ፡ ጠፋ ፡ ዕልም ፡ አለ ፤ የማይታይ ፡ የማይገኝ ፡ ኾነ ። ለምንት ፡ ትሴወር ፡ እምኔየ ። ኢይሴወር ፡ እምቅድመ ፡ አዕይንትየ ፡ ኃጢአቶሙ ። ወተሰወረ ፡ እምአዕይንቲሆሙ ፡ (ኢዮ ፴፫ ፡ ፳፬ ። ኤር፲፮ ፡ ፲፯ ። ግብ፩ ፡ ፱) ።

**ስዉር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ውርት) ፤ በቁሙ ፤ ሽሽግ ፡ ድብቅ ፤ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፤ የማይታወቅ ። አከ ፡ በስዉር ። ስዉር ፡ ነገር ። ስዉር ፡ እምኔሆሙ ፡ (ዘኍ ፲፪ ፡ ፰ ። ምሳ፩ ፡ ፯ ። ሉቃ፲፰ ፡ ፴፬) ።

**ስዋሬ** ፤ መሰወር ፡ (ጥስ) መሰወር ፤ አሰዋወር ፤ ስውርነት ፤ ስወራ ፡ ድብታ ። በስዋሬከ ። መካነ ፡ ስዋሬ ፡ (ቅዳ ፡ ዮሐ ። ጎድ ፡ ተክ) ።

**ምስዋር** ፤ (ራት) ፤ መሰወሪያ ፤ መደበቂያ ፡ ቦታ ፤ ጓዳ ፡ ሰግዳዳ ፤ መቅደስ ፤ መጋረጃ ፤ አንባ ፡ ዋሻ ፤ ዕርድ ፡ ምሽግ ። ይትኀባእ ፡ በምስዋር ፡ ወይትረሳዕ ። ወረሰየ ፡ ጽልመተ ፡ ምስዋሮ ። እምድኅረ ፡ አረፍተ ፡ ምስዋር ። መንጦላዕተ ፡ ምስዋራቲሁ ፡ ለሕይው ። ዝንቱ ፡ መካን ፡ ኮነ ፡ ምስዋረ ፡ ህየንተ ፡ አልባስየ ። ምስዋር ፡ ረድኤት ። ሐገፋ ፡ ወምስዋር ፡ (ጥበ፲፯ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፲፰ ። ኑሐ፬ ፡ ፲፫ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ስንክ ፡ ግን ፳፫ ። ኪዳ ። አፈ ፡ ተ፴) ።

**መሶር** ፤ (ብ ፡ መሳውር) ፤ መሶጥ ፡ መሳውጥ ፤ መፈልመሪያ ፤ ማፍሰሻ ፤ ማንቈርቈሪያ ፡ ጡታም ፡ ዕቃ ፡ ማስሮ ። ሶጠን ፡ ተመልከት ፤ ጦ ፡ በጸሓፊ ፡ ስሕተት ፡ ሰረ ፡ ተሰውጦ ፡ መሳውር ፡ ተብሏል ፤ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ የሶጠ ፡ ዘር ፡ ነው ፤ ሰዊጥን ፡ አይለቅም ፡ (ዘካ፬ ፡ ፪ ። ቀሌ ። ድጓ) ። በሰወረ ፡ አፈታት ፡ ሲፈቱት ፡ ግን ፤ ማፈኛ ፡ መክደኛ ፡ መማላሊት ፡ ያሰኛል ፤ ባለብሎዎችም ፡ እንዲሁ ፡ ይሉታል ።

**ሶስዎ** ፤ ዎት ፤ (ሶሰወ ፡ ይሶሱ ። ዕብ ፡ ሺሺእ ፤ ሂዳዪ) ፤ መሰውሰው ፤ አስተውሶ ፡ መርገጥ ፤ ቀስ ፡ ብሎ ፡ መኼድ ፡ መራመድ ፤ እየዘገመ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ መውጣት ፡ መውረድ ፤ የዕርከን ፡ የመሰላል ፡ የዳገት ፡ የስገንት ። መሰላል ፡ ዕርከን ፡ መሥራት ፤ ምስሶ ፡ ማቆም ፡ መትከል ።

**ሶሳዊ** ፡ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ ዝግተኛ ፤ አስተውሶ ፡ ኺያጅ ፡ ወጪ ፡ ወራጅ ፤ ሰው ፤ ባለሰዋስው ።

**ሶሰው** ፤ ሰውሰው ፤ (ብ ፡ ሰዋስው) ፤ መሰላል ፤ ዕርከን ፤ ማዕረግ ፡ ምዕራግ ፡ ደረጃ ፤ መውጫ ፡ መውረጃ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሶስው ፡ ፈንታ ፡ ሰዋስው ፡ ይልና ፡ በሰዋስው ፡ ፈንታ ፡ ሰዋስዎት ፡ ይላል ፤ ዎት ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ሶስውም ፡ ቢኾን ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ውስጠ ፡ ብዙንትን ፡ ያሳያል ። ይረድእዎ ፡ ለአሐዱ ፡ ከመ ፡ ይትክል ፡ ሰዋስወ ፡ በኀበ ፡ ኀቡ ፡ አረፍት ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይነክኢ ፡ ካልእ ። ተክሉ ፡ ሰዋስወ ፡ ወዐርጉ ። አስተናበረ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ሰዋስዎተ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ። ዮሴፍ ። ዘፍ፳፰ ፡ ፲፪ ። ማር ፡ ይሥ፹፫) ።



ሰዋስው ፡

**ሰዋስው** ፤ በቁሙ ፤ የቋንቋ ፡ መጽሐፍ ፤ ግስ ፤ መዝገበ ፡ ቃል ። የቋንቋ ፡ ትምርት ፡ ሕግ ፡ ሥርዐት ፤ ዐዋጅ ፡ አገባብ ፤ አጣጣፋና ፡ አረባቡ ፡ አካኼዱ ፡ አነባቡ ፡ ተሰይቶ ፡ የሚታወቅበት ፤ እንደ ፡ መሰላል ፡ ብዙ ፡ ዕርከን ፡ ያለው ። መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ። ሖርኩ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ መምህረ ፡ ቅኔ ፡ ወሰዋስው ፡ (አዋል) ።

**ሰዋስዋዊ** ፤ ባለሰዋስው ፤ የሰዋስው ፡ መምር ፤ አገባብ ፡ ዐዋቂ ። የመሰላል ፡ ዐይነት ፤ ዕርከናም ፤ ባለማዕርግ ። ጽማዌ ፡ ሰዋስዋዊ ፡ (ማር ፡ ይሥ፲) ።

**አንሶሰወ** ፤ አመሳሰለ ፤ ተመሳሰለ ፤ ኼደ ፡ ተራመደ ፤ ዞረ ፡ ባከነ ፡ ምልስ ፡ ቅልስ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ ፤

ታች ፡ ታቹን ፡ አገር ፡ ሳገር ፡ መንደር ፡ ለመንደር ። ተላወሰ ፡ ተንቀሳቀሰ ። ኢረከቡ ፡ ማየ ፡ ዘይጸውር ፡ ሐመሮሙ ፡ ወጸመዉ ፡ ወኢተመክነዩ ፡ ከመ ፡ ያንሶስዉ ፡ ሐመረ ፤ አመሳሰሰ ፡ (በንክ ፡ ታኅ፲) ። አንሶሰውክኑ ፡ ውስተ ፡ አሥረ ፡ ቀላይ ። አንሶሰወ ፡ እስከ ፡ ሰኪምን ። ቀሲስ ፡ መፍትው ፡ ያንሶሱ ፡ ኅበ ፡ አብያተ ፡ ድዉያን ። ወአልቦ ፡ ዘያንሶሱ ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፲፮ ። ኩፋ ፡ ፲፫ ። ቢዳ ። ኤርጵ ፡ ፲) ።

**መንሰስው ፤ (ውት ፡ ሱት ፤ ዋን ፡ ዋት) ፤** የሚያመሳልስ ፤ የሚመሳለስ ፤ አመሳሳሽ ፤ ተመሳሳሽ ።

**ነሰሳው ፤ (ዋት) ፤** መመሳለስ ፡ ምልልስ ፤ ርቆ ፡ መኼድ ፡ መንቀሳቀስ ። ውስተ ፡ አየራት ፡ ነሰሳዉ ። ዘፍጡን ፡ ነሰሳዉ ። ኢተክህሎ ፡ ለህርቃኖስ ፡ ነሳሰው ፡ በእንተ ፡ ሰንበት ። ዘእንበለ ፡ ነፍስ ፡ ወኢነሰሳው ፡ (ቅዳ ፡ ኤጲ ። ጥበ፳ ፡ ፳፱ ። ዮሴፍ ። ጥበ፲፰ ፡ ፳) ።

**እንስሳ ፤ (ሳት) ፤** በቁሙ ፤ የቤት ፡ የዱር ፡ ከብት ፤ ባላራት ፡ እግር ፤ ማር ፡ ንሖቦ ፡ ውሃ ፡ ተንንሖቦ ፡ የሚኖር ፤ የሚበላ ፡ የማይበላ ። ለታውፅእ ፡ ምድር ፡ ዘመደ ፡ እንስሳ ። ኵሉ ፡ እንስሳ ፡ ይፈቅር ፡ ዘመዶ ። እንስሳ ፡ ገዳም ። ይባርክዎ ፡ ኵሉ ፡ አራዊት ፡ ወእንስሳ ። አርባዕቱ ፡ እንስሳ ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፳፬ ። ሢራ፲፫ ፡ ፲፮ ። መዝ ፡ ፻፵፰ ። ዳንኤ ፡ ፫፳ ። ሕዝ፩ ፡ ፭) ።

**እንስሳዊ ፤** የእንስሳ ፤ በእንስሳ ፡ ጠባይ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፤ እንስሰማ ፤ እንስሰኛ ። ጠባይዕ ፡ እንስሳዊት ። ፍትወት ፡ እንስሳዊት ። ይትልዉ ፡ ፍኖተ ፡ እንስሳዊት ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፳፱ ፡ ፩ ። ፊላክ ። ፊ ፡ መ ፡ ፲፩ ፡ ፩) ።

**አእንሰሰ ፤** እንስሳ ፡ አደረገ ፤ አሞኘ ፡ አታለለ ።

**ተአንሰሰ ፤** እንስሳ ፡ ኾነ ፡ ተሞኘ ፤ ከእንስሳት ፡ ማኅበር ፡ ገባ ፤ አንድ ፡ ኾነ ፤ በግብር ። እለ ፡ ይትአነሰሱ ፡ ምስለ ፡ እንስሳ ፡ ዘውእቱ ፡ ዝሙት ። ተአንሰሱ ፡ ከመ ፡ እንስሳ ። ረሰዮ ፡ ከመ ፡ አርዌ ፡ ገዳም ፤ ገሠጾ ፡ በተአርውዮ ፡ ወአንበሮ ፡ በተአንስሶ ፡ (ዲድ ፡ ፴፫ ። ቀሌ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**እንሱስ ፤ (ሳን ፡ ሳት ፡ ስስት) ፤** እንስሳ ፡ የኾነ ፤ ሞኝ ፡ አላዋቂ ። ከመ ፡ ኢይኩን ፡ እንሱሰ ፡ በአልባዊ ፡ ነፍሱ ፡ ውስተ ፡ ገጸ ፡ መንፈሰ ፡ ሕይወት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ሰሳን ፤ (ዕብ ፡ ሾሻን) ፤** አበባ ፤ ያበባ ፡ ዐይነት ፡ ቅርጽ ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፱) ።

**ሰስና ፤** ስመ ፡ ብእሲት ፤ አበቡት ፤ አበባ ። ዘአድኅና ፡ ለሶስና ፡ እምእደ ፡ ረበናት ፡ (ድጓ ። ሊጦን ። ዳን) ።

**ሰውተል ፤ (ብ ፡ ሰዋትል) ፤** ሾተል ፤ አፋ ፤ ረዥሙ ፡ ደቢት ፤ ዐጭር ፡ ሰይፍ ፤ ሹል ፡ ስለታም ። ኵይንው ፡ ወሰዋትል ፡ ዘእሳት ፡ (አዋል) ።



ሰውተል ፡

**ሰዘየ ፤—ለየ ፡ አደላ ፤—ሠዘየ ።**

**ሰዚር ፤ ሮት ፤ (ሰዘረ ፡ ይሰዝር ፡ ይስዝር ። ጠፍሐ) ፤** መሰንዘር ፤ በሰንዝር ፡ መለካት ፤ መቃጣት ፡ መዘርጋት ። ዘሰማየ ፡ ሰዘረ ፡ ወዘአይድባረ ፡ ደለወ ። ሰዘሮ ፡ ለሰማይ ፡ በሕፍኑ ። ዘሰማየ ፡ ሰዘርከ ፡ ወምድረ ፡ ሣረርከ ፡ (አዋል ። ስንክ ፡ ሚያ፮ ። ድጓ) ።

**ስዝር ፤ (ዕብ ፡ ዜሬት ። ሱር ፡ ዛርታ ። ዐረ ፡ ሽብር) ፤** ሰንዝር ፤ ማኽል ፡ እጅ ፤ የጋት ፡ ቁመት ፡ ከውራ ፡ ጣት ፡ ጫፍ ፡ እስከ ፡ ታናሽቱ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ጫፍ ። መኑ ፡ ሰፈሮ ፡ ለማይ ፡ በሕፍኑ ፡ ወለሰማይኒ ፡ በስዝሩ ። ኑኁ ፡ ስድስ ፡ በእመት ፡ ወስዝር ። ወለሕፃንኒ ፡ አሮን ፡ ቈመተ ፡ ግዘፍ ፡ አካል ፤ ስዝረ ፡ የዐብዮ ፡ ሙሴ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ (ኢሳ፵ ፡ ፲፪ ። ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፬ ። ቅኔ) ። ከንድ ፤ ልክ ፡ መጠን ፡ ጋት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ስንዝር ፡ ይላል ፡ የመሳሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (መሳ፲፫ ፡ ፲፮ ። ፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ። ሕዝ፵፫ ፡ ፳) ።

**ስሒብ ፤ ቦት ፤ (ሰሐበ ፡ ይስሕብ ፡ ይስሐብ ። ዐረ ፡ ሰሐበ ። ዕብ ፡ ሳሐብ) ፤** መሳብ ፡ መጐተት ፤ መምዘዝ ፡ ማውጣት ፤ ማቅረብ ፡ ማምጣት ፤ መወጠር ፡ መገተር ፡ መለጠጥ ፡ ማስፈራት ፡ ማስረዘም ፡ ማብዛት ። ይስሕቡ ፡ አንስቲያሆሙ ። ሰሐብዎ ፡ በመዐት ። እስሕብ ፡ ኵሎ ፡ ኀቤየ ። እለ ፡ ይስሕብዋ ፡ ለኀጢአቶሙ ፡ ከመ ፡ ሐብል ፡ ነዋኅ ። መንግሥቱ ፡ ለቡ ፡ ያነውኃ ፡ ነገረ ፡ ወይስሕብ ፡ ቃለ ፡ ያንጎጕ ፡ ሰማዒ ፡ (ኢሳ፲፫ ፡ ፲፯ ። ቅዳ ፡ አፈ ። ዮሐ፲፪ ፡ ፴፪ ። ኢሳ፭ ፡ ፲፰ ። አፈ ፡ ድርሳ) ።

**ሰሓቢ ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ሐብት) ፤** የሚስብ ፡ የሚጐትት ፤ ሳቢ ፡ ጐታች ። ሰሓብያነ ፡ አርዑት ፡ (አፈ ፡ ድርሳ) ።

**አስሐበ ፤** አሳበ ፤ አስጐተተ ፤ ሳቡ ፡ ጐትቱ ፡ አለ ።

**መስሕብ ፤ (ብት ፡ ባን ፡ ቢት) ፤** የሚስብ ፡ የሚያስብ ፤ ሳቢ ፡ አሳቢ ፡ አስጐታች ፤ ማራኪ ፡ አስማራኪ ።

**ተስሕበ ፤** ተሳበ ፡ ቀረበ ፤ ተማረከ ፤ ተጐተተ ። ተሰሓቢ ፡ በሐብለ ፡ ፍቅሩ ። ወይሰሐብ ፡ እንከ ፡ ብልቡ ። ተስሕበ ፡ ሰብእ ፡ ሰሥነ ፡ ላሕየ ፡ ምግባር ። ጠቢብ ፡ ኢይትአኀዝ ፡ በአፍቅሮቱ ፡ ለሐሳዊ ፡ ወኢይሰሐብ ፡ ሎቱ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ ። ፊልክ ፡ ፵፰ ። ጥበ፲፱ ፡ ፳ ። ፊላስ) ።

**ስሑብ ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ሕብት) ፤** የተሳበ ፤ የተጋደመ ፡ የደነነ ፡ የጸነነ ፤ ዝርግ ። የውጣ ፡ (፲) ዘእንበለ ፡ ጥውየት ፡ ኢድኑኑ ፡ ርእስ ፡ ወኢስሑበ ፡ አእጋር ፡ ከመ ፡ ባዕዳን ፡ ሆህያት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ስሕበት ፤** መሳብ ፤ መጐተት ፤ አሳሳቡ ፤ ስቦሽ ፡ ጐተታ ። በእንተ ፡ ስሕበቱ ፡ ለማርቆስ ፡ (አዋል) ።

**መስሐብ ፤ (ብ ፡ መሳሕብ) ፤** መሳቢያ ፤ የብረት ፡ መሣሪያ ፡ ብዙ ፡ ጥርስ ፡ ያለው ፤ ወይም ፡ እንዳ

ከፋ፡ ያለ። ወገብሩ፡ ሎቱ፡ መስሐበ፡ ኀጺን፡ (ስንክ፡ የካ፳፭)።

**ምስሓብ፤ (ባት)፤** መሳቢያ፤ ማሳቢያ፡ ቦታ፤ ለኮ፡ ገመድ፡ ሰንሰለት። ሕብለ፡ ምስሓብከ፡ (አዋል)።

—፤ አስማት፤ ድጋም፤ የጠንቋይ፡ ጸሎት፤ ዛርና፡ ጋኔን፡ የሚስብ፤ የሚያቀርብ። ምስሓበ፡ ዛር፤ ጋኔን፡ ሳቢ፡ እንዲሉ፡ (ዐማርኛ)።

**ሳሕበበ፤—ሸገተ፤—ሣሀበበ።**

**ስሒግ፤ ጎት፤ (ሰሐገ፡ ይስሕግ፡ ይስሐግ፤ ቀነየ። ዕብ፡ ሻአግ)፤** መሮኘ፡ መድረቅ ረቅ፤ ዋይ፡ ብሎ፡ ማልቀስ፤ ማሞሽ፡ መንሰቅሰቅ፤ ከሐዘን፡ ከጭንቅ፡ የተነሣ። መሳግ፡ መመስግ፤ ማግባት፡ መጨመር፡ መቀጠል፤ የጣሬ፡ የጥላ፡ የስሌን፡ የስፌት፡ የመሰለው፡ ኹሉ። መሻከር፡ መቈርቈር፤ መኰስኰስ፡ ማስቀቅ፤ እንዳብ፡ ጨንሬ፡ መኾን፤ የልብስ፡ የምንጣፍ፡ የጠባይ። መሰብሰብ፡ ማፈግ፤ ማስተኛት፡ ማስመስግ፤ የሰው፡ የእንስሳ።

**ሰሓጊ፤ (ጊት፡ ግያን፡ ያት፤ ሐግት)፤** የሚሮኽ፤ የሚስግ፤ የሚያፍግ፤ ሸካራ።

**ምስሓግ፤ (ጋት፤ መሳሕግት፤ ታት)፤** ሰቈቃው፤ ሙሾ፡ ልቅሶ፡ ዋይታ፤ የልቅሶ፡ ግጥም። ወአስቈቀዎ፡ ኤርምያስ፡ ለኢዮስያስ፤ ወይቤሉ፡ ኵሉ፡ ሐሰይት፡ ወሐሳይያት፡ ምስሓጋቲሆሙ፡ ላዕለ፡ ኢዮስያስ፡ እስከ፡ ዛቲ፡ ዕለት፤ ወሠርዕዋ፡ ለይእቲ፡ ምስሓግ፡ በኵሉ፡ እስራኤል፤ ወነያ፡ ጽሕፍት፡ ውስተ፡ ምስሓግ፡ (፪ዜና፡ ፴፭፡ ፳፭)።

**ምስሓግ፤ (ዕብ፡ ሬማህ)፤** ብዙ፡ ትል፤ እንደ፡ ሮማን፡ ፍሬ፡ ጽፍቅ፡ የኾነ፤ መግንዝ፡ የሬሳ፡ ጉዝጓዝ፤ ሰሌን፤ ማጥን። ተነጸፍከ፡ ምስሓገ፡ በታሕቴከ፡ (ኢሳ፲፬፡ ፲፩)።

—፤ ምሽግ፤ ምሳግ፡ በረት። የሙሾ፡ የልቅሶ፡ ቦታ፤ ማርገጃ፡ መቃብር፤ የሙት፡ ቤት። ኢትባእ፡ ምስሌሆሙ፡ ውስተ፡ ምስሓግ። ትግበር፡ ላቲ፡ ዳሰ፡ ኀበ፡ ትነብር፡ ውስቴ፡ ምስሓግ፡ ወትረ፡ (ኤር፲፮፡ ፭። ኢሳ፲፯፡ ፫)።

—፤ ምንጣፍ፡ ዳውገር፡ ገሣ። ጎሱር፡ ልብስ፤ ኰስኰሳ፤ ሸካራ፡ ከሰሌን፡ ጭረት፡ የሚሠራ፤ ተቢስ፤ ማቅ፡ ምንጣፍ፤ መናኒ፡ መነኵሴ፡ በረኸኛ፡ ሐዘንተኛ፡ የሚለብሰው። እኙ፡ ለባሴ፡ ምስሓግ፡ (ፊልክ፡ ፻፴፫)። ምስሓግ፡ በማለት፡ ፈንታ፡ መሳግሕት፡ መሳግሕታት፡ ይላል፤ ስሕተት፡ ነው፡ (ፊልክ፡ ፻፹፱)።

**ስሒው፤ ዎት፤ (ሰሕወ፡ ይስሑ፡ ይስሐው። ዕብ፡ ሳሓህ። ሱር፡ ስሓአ)፤** መሳብ፤ መጕተት፤ እየተሳቡ፡ መኼድ፤ የከይሲ፡ የዋና፡ የጉም፡ የደመና። እምቅድመ፡ ይስሐው፡ ግዘፈ፡ ደመናት፡ (ቅዳ፡ አፈ)።

—፤ ሻ፡ ማለት፡ መበተን፤ መድከም፡ መዛል፤ የልብ፡ የአእምሮ። ሰሕወ፡ ልቡ።

**ሰሓዊ፤ (ዊት፡ ውያን፡ ያት፤ ሐውት)፤** የሚሳብ፡ የሚጐተት፤ ዋነተኛ፤ ጉም፡ መርከብ።

**ሳሕው፤** የጉም፡ ሽንት፤ ተን፡ ጊሜ፤ ግዘፈ፡ ደመና፤ የሚጐተት፡ ሻ፡ ብትን፡ የሚል። መንፈስ፡ ይትከሀው፡ ከመ፡ ሳሕወ፡ ደመና። ጉባኤሆሙ፡ ለዐማፅያን፡ ከመ፡ ሳሕወ፡ ደመና፤ ወፍሥሓሆሙ፡ ከመ፡ ፆፍ፡ ሰራፊት። ከመ፡ ሳሕወ፡ ጊሜ፡ በገጸ፡ ምድር፡ (ጥበ፪፡ ፫። መቃ፡ ገ፲። አርጋ፡ ፩)።

**አስሐወ፤** ሳበ፡ ጐተተ፤ አሳበ፡ አስዋኘ። አወለቀ፤ አስወለቀ፤ አስገፈፈ፤ የልብስ። ኢጸንሐ፡ ለአስሕዎ፡ ሐመር፡ ሕላ፡ ቀነጸ፡ እምዴበ፡ ሐመር፡ ወተወርወ፡ ውስተ፡ ባሕር። አስሐወ፡ ሎሙ፡ ፊቃሮ፡ ቅድስተ፡ ወመጠዎሙ፡ ክሣዶ፡ ለጋላት፡ (መጽ፡ ምስ። ድጓ)።

**ስሒጥ፤ ጦት፤ (ሰሐጠ፡ ይስሕጥ፡ ይስሐጥ። ሱር፡ ሻሔጥ። ዕብ፡ ሻሔት። ዐረ፡ ሰሐተ)፤** መሸጥ፤ ሻጥ፡ ማድረግ፤ መንካት፤ መጣር፤ መቈንጠጥ፤ መጕዳት፡ መጕነጥ፤ መግደል፡ ማጥፋት፡ ማበላሸት። ኢሰሐጥዎ፡ ለዳንኤል። ወኢንደገ፡ ይስሐጦሙ፡ ለብእ። ኢትስሐጥ፡ ብእሴተ፡ ባዕድ። ኢትስሐጣ፡ ለድንግል። አልቦ፡ ዘይስሕጥ። ናሁ፡ ይእዜ፡ እሙንቱ፡ ሰሐጡነ፡ ወመጽኡ፡ ያውፅኡነ፡ እምርስትነ፡ (ዳን፯፡ ፲፰። መዝ፡ ፻፬። ሚራ፱፡ ፫፡ ፳። ፫ነገ፡ ፳፡ ፱። ፪ዜና፡ ፳፡ ፲፩)።

—፤ ማጣር፤ ጠብ፡ መፈለግ፤ መቈስቈስ፡ መቈራቈስ፤ የጦርነት። መኑ፡ ይቀድም፡ ስሒጠ፡ ወመኑ፡ ያስተሓኅዝ፡ ቀትለ፡ (፫ነገ፡ ፳፡ ፲፬)።

**ሰሓጢ፤ (ጢት፡ ጥያን፡ ያት)፤** የሚነካ፤ ጐናጭ፤ ቈንጣጭ። ያገር፡ ስም፤ የምጥዋ፡ አጠገብ።

**ተስሕጠ፤** ተነካ፡ ተጐዳ፤ ተጐነጠ፤ ተቈነጠጠ።

**ስሑጥ፤ (ጣን፡ ጣት፡ ሕጥ)፤** የተነካ፡ ንክ፤ የተጐነጠ፤ የተቈነጠጠ። የተሠራ፡ የተቀጣ፡ በሥራት፡ ያደገ፡ (ዐማርኛ)።

**ስሕጠት፤** መቈንጠጥ፤ (ጥቈ) መቈንጠጥ፤ አቈንጣጠጥ፤ ቍንጠጣ፤ ቍንጥጫ፤ ቍንጢጥ።

**ሰሐየ፤—ፈሰሰ፡ ቀለጠ፤—ሴሐ፡ ሰየሐ።**

**ስሒክ፤ ኮት፤ (ስሕከ፡ ይስሕክ፡ ይስሐክ። ዐረ፡ ሐሲከ)፤** መሻከር፤ መቅረፍረፍ፤ መቈጣት፡ እንደ፡ ሦከና፡ እንደ፡ ቀርፍት፡ እንዳርጀኛ፡ መኾን፤ የገላ፤ እንዳዬ፡ ፋሲል። (ዘፈን)፤ ከኛ፡ ኼደኽ፡ አገኘኸይ፡ ሌላ፤ አርጀኛ፡ ገላ። ወስሕከ፡ ሥጋየ፡ በኀጢአ፡ ቅብዕ። ትስሕክ፡ እምሥከ፡ ወአሜከላ፤ ወትጠዊ፡ እምአቅርንቲሁ፡ ለሀየል፡ (መዝ፡ ፻፰። መጽ፡ ምስ)።

—፤ መድረቅ፡ መንቃት፤ ማበጥ፡ መዘጋት፤ መስለል፡ መጕርነን፤ የጕረሮ፡ የቃል፤ ከደዌ፡ ከጩኸት፡ የተነሣ።

ስሕከ ፡ ጐርዒየ ፡፡ ወክልሐ ፡ ጢጦስ ፡ በውእቱ ፡ ዕለት ፡ እስከ ፡ ስሕከ ፡ ጐርዒሁ ፡ (መገ ፡ ፷፰ ፡፡ ዮሴፍ) ፡፡

**ስሑክ** ፤ (ካን ፡ ካት ፡ ሑክት) ፤ የሻከረ ፡ ሻካራ ፡ ቅርፍርፍ ፡፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ይቡስ ፡ ወስሑክ ፡ (አፈ ፡ ተሸ፱) ፡፡

**ስሕከት** ፤ መሻከር ፤ አሻካከር ፡ ሻክረት ፡ ሻካራነት ፡፡

**ሳሕክ** ፤ (ክት) ፤ ስሒ ፤ እንክን ፤ ምማቴ ፤ የገላ ፡ ንውር ፤ ዕከክ ፡ ብግር ፤ ቋቍቻ ፡ ቈረቈር ፤ የመስለው ፡ ኹሉ ፡፡ ሻካራ ፡ ጸጕር ፡ ቅርፍርፍ ፡ መኾን ፡፡ መመትን ፡ እይ ፤ ባላገር ፡ ግን ፡ ስሒ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሳክ ፡ ይላል ፡፡ ሳካም ፡ የለሽ ፡ እንዲሉ ፡ (የሴት ፡ ልጅ ፡ ስም) ፡፡ አድሕድ ፡ በቅብዕከ ፡ ለነፍስየ ፡ ሳሕካ ፡ (ስንክ ፡ ግንቿ)፡፡

**አስሐከ** ፤ አሻከረ ፤ አደረቀ ፤ ሻካራ ፡ ደረቅ ፡ አደረገ ፤ አስደረገ ፡፡ ጢስ ፡ ምንዣብ ፡ ያስሕክ ፡ ሥጋሁ ፡፡ አባላቲሁ ፡ አስሐከ ፡ በጾም ፡ (ሚ ፡ ራ፴፰ ፡ ፳፰ ፡፡ ስንክ ፡ ጥቅ፲፫) ፡፡

**አስሓኪ** ፤ **መስሕክ** ፤ የሚያሻክር ፤ አሻካሪ ፤ ሻካራ ፡ አድራጊ ፤ አስደራጊ ፡፡

**ሳሕል** ፤—ይቅርታ ፤—ሣሀሎ ፡ ሣሀለ ፡፡

**ስሒል** ፤ **ሎት** ፤ (ሰሐለ ፡ ይስሕል ፡ ይስሐል ፡፡ ዐረ ፡ ሰሐለ ፤ ስሕገለ) ፤ መሳል ፡ መስንገል ፤ ማስላት ፡ ማሾል ፤ መሞረድ ፡ መፈግፈግ ፤ እንዲስላና ፡ እንዲበላ ፡ እንዲሾል ፡ ማድረግ ፡፡ ዘይስሕል ፡ ሰይፈ ፡ ለቢጹ ፡ ይትቀተል ፡ ቦቱ ፡ ለሊሁ ፡፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይስሐሉ ፡ ኲናተ ፡ (ፈላስ ፡፡ ገድ ፡ ተክ) ፡፡

**ሰሓሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ሐልት) ፤ የሚስል ፡ የሚያሾል ፡ ሳይ ፡ አሿይ ፡፡

**ተስሕለ** ፤ ተሳለ ፤ ተሞረደ ፤ ሾለ ፡ ስለታም ፡ ኾነ ፡፡ እመ ፡ ተስሕለት ፡ መዐቱ ፡ (ምሳጽ፱ ፡ ጽ፫) ፡፡

**ስሑል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ሑልት) ፤ የተሳለ ፤ ስል ፡ ሹል ፤ ስለታም ፡፡ ስሑል ፡ ፈድፋደ ፡ እመጥባሕት ፡፡ አሕዳከ ፡ ስሑል ፡ (ምሳ፳ ፡ ፱ ፡፡ መዝ ፡ ፶፱) ፡፡

**ስሕለት** ፤ መሳል ፡ (ጥላ) መሳል ፡ አሳሳል ፤ ስሉሽ ፤ ስልንነት ፡ ሹልነት ፤ ስለት ፤ ሹለት ፡፡

**ምስሓል** ፤ (ላት) ፤ መሳያ ፤ መሳል ፡ ለኰቴ ፤ ልዝብ ፡ ደንጊያ ፡፡

**አስሐለ** ፤ አሳለ ፤ አስሞረደ ፤ ስል ፡ ሹል ፡ አስደረገ ፡፡

**ሳሕለለ** ፤ (ተቀ ፡ ግ) ፤ ደረቀ ፤ ከረረ ፤ እንደ ፡ መሳልና ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ኾነ ፡፡

**አንሳሕለለ** ፤ (ዲ ፡ ቃ ፡ ግ) ፤ አመሳለሰ ፤ ተመሳሰለ ፤ ምልስ ፡ ቅልስ ፡ አለ ፡፡ ስለት ፡ በመሳል ፡ ላይ ፡ ሞረድ ፡ በብረት ፡ ላይ ፡ እንዲመላለስ ፤ እንደዚያ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ ለእመ ፡ ርእከ ፡ ጠቢበ ፡ ጊሥ ፡ ኀቤሁ ፡ ወመድረከ ፡ ቤቱ ፡ ያንሳሕልል ፡ እገሪከ ፡ (ሢ ፡ ራ፮ ፡ ፴፮) ፡፡ ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ አደክመ ፡ ብለው ፡ ይጨምራሉ ፡፡

ስሕጸ ፤—ደፈረ ፤—ሥሒጸ ፡፡

**ሳሕስሐ** ፤ **ሐት** ፤ (ሳሕስሐ ፡ ይሳሐስሕ ፡ ይሳሕስሕ ፡፡ ዕብ ፡ ሳሓህ ፤ ዋኘ ፤ ዛዕዛዐ ፡፡ ዐረ ፡ ዘዕዘዐ) ፤ መታወክ ፡ መናወጥ ፤ መራድ ፡ መንቀጥቀጥ ፤ መላወስ ፡ መንቀሳቀስ ፡፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሳሕስሐ ፡ ፈንታ ፡ አንሳሕስሐ ፤ አንሶሐስሐ ፡ ይላል ፤ በሶበወ ፡ ፈንታ ፡ አንሶሰወ ፡ እንዲል ፡፡

**ሳሕሳሕ** ፤ (ትግሪኛ) ፤ ምናምንቴ ፤ ልክስክስ ፤ ወስዋሳ ፡ ወድ ፡ ሳሕሳሕ ፡ እንዲል ፡፡

**አንሳሕስሐ** ፤ አንጓጓ ፤ ቀሰቀሰ ፡ ወዘወዘ ፡ ነቀነቀ ፡፡ ተንጓጓ ፤ ተላወሰ ፤ ተንቀሳቀሰ ፡ ተንቃነቀ ፤ ተወላወለ ፡፡ ነፍስ ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ ታንሳሕስሖ ፡ ለሥጋ ፡፡ አልቦ ፡ ምንትኒ ፡ ግብር ፡ እምግብራት ፡ ዘያንሳሐስሖሙ ፡ ለከሓድያን ፡ ኀበ ፡ አንክሮ ፡፡ አሠንየትከ ፡ ለአግዓዚ ፡ ያንሳሐስሖ ፡ ለፍዳ ፤ ወአሠንየትከ ፡ ለቀቅይ ፡ ያንሳሐስሖ ፡ ለተመይጦ ፡ ኀቤከ ፡ ለስሒል ፡፡ ተስፋሁ ፡ ለክልብ ፡ ያንሳሐስሕ ፡ ዘነቦ ፡ ወእዘኒሁ ፡፡ ሥጋ ፡ ያንሳሐስሕ ፡ ኀበ ፡ ፍትወቱ ፡ ወያስተጥዕም ፡ ለነፍስ ፡ ምግባራተ ፡ ሕሡማተ ፡፡ ዘያንሳሕስሕ ፡ ሥጋሁ ፡ በእዴሁ ፡ እመሂ ፡ ተባዕት ፡ አው ፡ አንስት ፤ አንጓጓ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ፡፡ አፈ ፡ ተ፴፱ ፡፡ ፈላስ ፡ ገ፳፱ና ፡ ፻፱ ፡፡ ዮሴፍ ፡፡ ቄድር) ፡፡ ሞተ ፤ ወተገንዘ ፤ ዘእንበለ ፡ እስትንፋስ ፡ ወዘእንበለ ፡ አንሳሕስሖ ፡፡ ወአንሳሕስሐ ፡ ሥጋሁ ፡ ሰምዒት ፡፡ እመ ፡ ከሠትክሙ ፡ ዐሊወ ፡ ሮም ፡ ወአንሳሕሳሕክሙ ፡፡ እመ ፡ አርሐቁ ፡ ኀሊናተ ፡ እምቀዳሚሁ ፡ ለአንሳሕስሖቶሙ ፤ ተንጓጓ ፡ (ተረ ፡ ቄር ፡፡ ቀሌ ፡፡ ዮሴፍ ፡፡ ፈልክ ፡ ፴፭) ፡፡ አንሳሕስሖ ፡ ዘአርባዕቱ ፡ ጠባይዓት ፡ ለዐ ፡ ያንሳሕስሕ ፡ ደም ፡ በውስተ ፡ ሥጋ ፡ ዘውእቱ ፡ ጠባይዐ ፡ ማያዊ ፤ ይሬኢ ፡ ለብእ ፡ በንዋሙ ፡ ግብረ ፡ ሠናየ ፡ ወመስተፍሥሔ ፤ ወዓዲ ፡ ይሬኢ ፡ ሕብራተ ፡ ቀይሓተ ፡ ወፀዐተ ፡ ይምሂ ፡፡ ወለእመ ፡ አንሳሕስሐ ፡ ሳፍራ ፡ ዘውእቱ ፡ ጠባይዐ ፡ ነፋሳዊ ፤ ይሬኢ ፡ ተጋእዞተ ፡ ወአጽባእተ ፡ ወእሳተ ፡ ወሕብራተ ፡ ብዙኀ ፡ ወመኃትዋተ ፡ ወመባርቅተ ፡ ወይመስሎ ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ብሰኔ ፡ ወውስተ ፡ ፀሓይ ፡፡ ወሶበሂ ፡ ያንሳሐስሕ ፡ በልቀም ፡ ዘውእቱ ፡ ጠባይዐ ፡ መሬታዊ ፤ ይሬኢ ፡ አብሕርተ ፡ ወአፍላጋተ ፡ በረደ ፡ ወዝናማተ ፡ ወአስሐትያ ፡ ወሕብራተ ፡ ጸዐድዒዳተ ፡ ወከመ ፡ ዘይሰጥ ፡ ማየ ፡ ይመስሎ ፡፡ ወለእመ ፡ አንሳሕስሐ ፡ ሳውዳ ፡ ዘውእቱ ፡ ጠባይዐ ፡ እሳታዊ ፤ ይሬኢ ፡ ጽልመተ ፡ ወመቃብራተ ፡ ወሙታነ ፡ ወሥርዐተ ፡ ሐዘን ፡ ወለቢሰ ፡ ልብሰ ፡ ጸሊም ፤ ወይበውኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ፍርሀት ፡ ወረዓድ ፤ ተንጓጓ ፡ (ፈላስ ፡ ገ፲፯) ፡፡ ሕለሙን ፡ ተመልከት ፡ የዚህ ፡ ነገር ፡ ነው ፡፡

**አንሳሕሳሒ** ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት) ፤ የሚያንጓጓ ፤ ነቅናቂ ፤ አንጓሽ ፤ ተንጓሽ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡፡ እምከመ ፡ ተገሠጸ ፡ አንሳሕሳሒ ፡ ወከነ ፡ ፍጹመ ፡ ይትጌሠጽ ፡ ምግባራቲሁ ፡ እለ ፡ ይትገበሩ ፡ በዘያንሳሐስሕ ፡ ዘውእቱ ፡ ሥጋ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ንዋየ ፡ መሥቄ ፡ ለነፍስ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ፡፡

**ነስሕሳሕ** ፤ (ሓት) ፤ መነሣሣት ፤ መንቀሳቀስ ፤ እንግሥ ፤ ተንሣሽንት ። ውዝወዛ ፡ ንቅንቃ ፡ ቅስቀሳ ። ከመ ፡ ንዒ.ም ፡ ዘእንበለ ፡ ድምፅ ፡ ወኢነስሕሳሕ ። ሕእምሮ ፡ ወሰሚዐ ፡ ወርእይ ፡ ወኀሊና ፡ ወነስሕሳሕ ፡ (ፈልክ ፡ ፻፲ ። ቀሌ) ።

**ስሕተ** ፤ **ሰሐተ** ፤—ዐረፈ ፤—ሥኒት ፡ ሥኣተ ።

**ስሒት** ፤ ቶት ፤ (ስሕተ ፡ ይስሕት ፡ ይስሐት ፤ ጌገየ ። ዕብ ፡ ሻሔት ። ዐረ ፡ ሰሐተ ፤ ሰሐጠ) ፤ መሳት ፤ አለማግኘት ፤ ወርውሮ ፡ ተኵሶ ። (ተረት) ፤ ተውኑት ፡ የሚሻል ፡ ሐሰት ፤ ከመውጋት ፡ የሚሻል ፤ መሳት ። የሀይጺ ፡ ሥዐርተ ፡ ወኢይስሕቱ ፡ (መሳ፳ ፡ ፲፮) ።

—፤ መሳሳት ፡ ከመንገድ ፡ መውጣት ፤ መታለል ፡ መሸንገል ፤ መርሳት ፡ መዘንጋት ፤ ሳያውቁ ፡ መበደል ፤ ክፉ ፡ መሥራት ፤ ወይም ፡ እያወቁ ፡ ማጥፋት ፡ ማበላሸት ፤ አጥፊ ፡ መኾን ፤ ስሕጠን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ስሕቱ ፡ ግብጽ ፡ ብእሲ ፤ ዘዘ ፡ ዚአሁ ፡ ሖረ ፡ በፍኖቱ ፡ ወስሕተ ። ሰስሒት ፡ መኑ ፡ ይሌብዋ ። ስሕትነ ፡ እምፍኖተ ፡ ጽድቅ ። ኢይስሕቱ ፡ ወኢይፈልሱ ፡ እምነ ፡ ዐቅሞሙ ። ይስሕቱ ፡ ሠርቀ ፡ ወሰንበተ ። ብዙኃን ፡ እለ ፡ ስሕቱ ፡ በሥነ ፡ ብእሲት ። ዐ ፡ ዘይስሕት ፡ እንዘ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ልቡ ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፲፫ ። ፺፫ ፡ ፯ ። መገ ፡ ፲፰ ። ጥበ፳ ፡ ፮ ። ሔኖ፹፫ ፡ ፲ ። ኩፋ ፡ ፳ ። ሚራ፱ ፡ ፰ ። ፲፱ ፡ ፲፯) ።

**ሰሓቲ** ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤ የሚስት ፤ የሚሳሳት ፤ ሳች ፤ ተሳሳች ። ዐማፀያን ፡ ወሰሓትያን ፡ ወኃጥኣን ። ሰሓትያን ፡ ወአባስያን ፡ ንሕነ ፡ (ዲድ ። ቄድር) ።

**ተስሕተ** ፤ ተሳተ ፤ አመለጠ ፤ ሳይገኝ ፡ ቀረ ፤ ጊዜው ፡ ዐላማው ፡ መንገዱ ፡ ዕውቀቱ ።

**ስሑት** ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ሕት) ፤ የሳተ ፤ የተሳተ ፤ የተሳሳተ ፤ አሳዋቂ ። አብድ ፡ ስሑት ፡ ውእቱ ፡ ወጠቢብሂ ፡ ዘይትጌሠጽ ፡ እምካልኣኒሁ ። ጥበበ ፡ ስሑታን ፡ (ፈላስ ። ኪዳ) ።

**ስሕተት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፤ መሳት ፤ መሳሳት ፤ አላዋቂንት ፤ መጥፎ ፡ አካኼድና ፡ አነጋገር ፤ ሕግ ፡ ወጥ ፡ ሥራ ፤ ኀጢአት ፡ ክሕደት ። ፍኖተ ፡ ስሕተት ። ስሕተቶሙ ፡ እምአእምሮ ፡ እግዚ ። ስሕተተ ፡ ልቦሙ ። ስሕተተ ፡ አሕዛብ ። ዘእንበለ ፡ ስሕተት ። ዘስሕተታት ፡ በጠላ ፡ በትእዛዝከ ፡ (ጥበ፲፪ ፡ ፳፬ ። ፲፬ ፡ ፳፱ ። ኩፋ ፡ ፳ ። ፮ ። ስንክ ፡ ጳጉ፱ ። ኪዳ) ።

**አስሐተ** ፤ አሳተ ፤ አሳሳተ ፤ ከመንገድ ፡ አወጣ ፤ አታለለ ፤ አስካደ ፡ ኀጢአት ፡ አሠራ ። ወአስሐቶሙ ፡ ውስተ ፡ ቢድው ፡ ዘኢኮነ ፡ ፍኖተ ። ዘያስሕቶ ፡ ፍኖተ ፡ ለዕዉር ። ወለብዙኃን ፡ አስሐቶሙ ፡ ትዝኅርቶሙ ። ተሠነየት ፡ ጥቀ ፡ እስከ ፡ ታስሕት ፡ ዐይኖሙ ፡ ለዐይደው ። ዑቁ ፡ አልቦ ፡ ዘያስሕተክሙ ፤ እስመ ፡ ብዙኃን ፡ ይመጽኡ ፡ በስምየ ፡ ወብዙኃነ ፡ ያስሕቱ ። ሰሐቴዋን ፡ እንቲ ፡ አስሐታ ፡ ከይሲ ፡ (መገ ፡ ፳፯ ። ዘዳ ፳፯ ፡ ፲፰ ። ሢራ፫ ፡ ፳፬ ። ዮዲ፲ ፡ ፬ ። ማቴ፳፬ ፡ ፬ ፡ ፭ ። ኤፍ ፡ ፪) ።

**አስሐተ** ፤ (ዕብ ፡ ሂሽሒት) ፤ አጠፋ ፤ አበጠፋ ፤ ጕዳ ፤ አጥፊ ፡ ኾነ ፤ አበላሸ ።

**አስሓቲ** ፤ **መስሐቲ** ፤ ስቶ ፡ የሚያስት ፤ አሳች ፤ አሳሳች ፤ አጥፊ ፤ አበጠፊ ። ሰይጣን ፡ አስሓቲ ። እንበለ ፡ ያስሕቶ ፡ መስሐቲ ፡ (ቄድር ። ፈ ፡ መ ፡ ፫ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ድ፳፰) ።

**መስሕት** ፤ (ጥት) ታን ፡ ታት) ፤ ነዝኒ ፡ ከማሁ ። የነፍስ ፡ ዕንቅፋት ። ጋኔን ፡ መስሕት ። ኀይል ፡ መስሕት ። አጋንንት ፡ መስሕታን ። መስሕታት ፡ ለካልኣን ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፲፬ ። ፪ተሰ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ። ፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፩ ። ዲድ ፡ ፲፬) ። ደብር ፡ መስሕት ፤ የጣዖት ፡ ተራራ ፤ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ምሥዋዕ ፡ ጣዖት ፡ (፬ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፲፫) ።

**አስሐትያ** ፤ (ዕብ ፡ ቂጦር ፤ ጢስ) ፤ ውርጭ ፤ ዐመዳይ ፤ አጥፊ ፤ ቡቃያ ፡ የሚያደርቅ ፡ የሚያሳርር ፤ ቆማ ፡ የሚኾን ፤ ከውሃ ፡ ላይ ፡ ሲያርፍ ፡ የሚረጋ ። ከመ ፡ ዝቅ ፡ ውስተ ፡ አስሐትያ ። እሳት ፡ ወበረድ ፡ ወአስሐትያ ። ከመ ፡ አስሐትያ ፡ ቀጢን ። አስሐትያ ፡ ይረግዕ ፡ ዲበ ፡ ማይ ። ቀተለ ፡ ወይኖሙ ፡ በበረድ ፡ ወበለሶሙኒ ፡ በአስሐትያ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ። ፻፵፰ ። ጥበ፳ ፡ ፲፭ ። ሢራ፵፫ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፸፯) ።

**አስሐትያ** ፤ (ዕብ ፡ ሼሌግ ፤ ባራድ) ፤ ብትን ፡ በረዶ ፡ የውርጭ ፡ ዐይነት ፤ ጠጠር ፡ በረዶ ፡ የደንጊያ ፡ ዐይነት ፤ የውሃ ፡ በረዶ ፡ እብን ፡ በረድ ፤ የረጋ ፡ ውሃ ፡ ሱሕ ፡ ጠብ ፡ የሚያካክል ፤ የስኳር ፡ ዐይነት ፤ ከመጠጥ ፡ ጋብቶ ፡ የሚያረካ ፡ የሚያተዘቅዝ ፤ በሚዛን ፡ የሚሸጥ ። ከመ ፡ ፀአተ ፡ አስሐትያ ፡ በጊዜ ፡ ማእረር ። ወእምከመ ፡ ረግዐ ፡ አስሐትያ ፡ ይትፈለጽ ፡ ከመ ፡ ስባራት ፡ ማያው ፡ በሊኃት ። እብነ ፡ አስሐትያ ። ዝናም ፡ ወአስሐትያ ፡ አጥፍኡ ፡ እሳተ ፡ (ምሳ፳፭ ፡ ፲፫ ። ሢራ ፡ ፵፫ ፡ ፲፱ ። ሔኖ፻፩ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ሚያ፴) ።

**ስኂን** ፤ ኖት ፤ (ሰኀነ ፡ ይስኅን ፡ ይስኅን ። ዐረ ፡ ሰኂነ ። ሱር ፡ ሽሔን) ፤ መሞቅ ፡ መተኰስ ፤ መውቀት ፡ መንሣት ፤ ከፀሓይ ፡ ከእሳት ፡ መቅረብ ። ይትሥእ ፡ እምውስቴቱ ፡ ወይስኅን ። ይሰቍጹ ፡ አፍሓመ ፡ ወይስኅኑ ። ከመ ፡ ንስኅን ፡ እምጽንዐተ ፡ ቍር ። መዐተ ፡ ሥላሴ ፡ ዘኮነ ፡ አረጋዊ ፡ ዐድሜ ፡ ድኅረ ፡ እማየ ፡ አይኑ ፡ ወፀአ ፡ እመ ፡ ኢክህለ ፡ ቍረተ ፤ በምድረ ፡ ገሞራ ፡ ተረክበ ፡ እንዘ ፡ ይስኅን ፡ እሳተ ፡ (ኢሳ፵፬ ፡ ፲፭ ። ዮሐ፲፰ ፡ ፲፰ ። ግብ፳፰ ፡ ፪ ። ቅኔ) ።

**ስኁን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ኅንት) ፤ የሞቀ ፤ የተኰሰ ፤ ሙቀት ፡ የንሣ ፡ ትኩስ ።

**ስኂን** ፤ ልብን ፤ ልባንጃ ፤ ጥሩ ፡ ነጭ ፡ ዕጣን ፤ የማሬር ፡ ሙጫ ፡ የሚመስል ፤ የልብንጉ ፡ ፍቾ ፡ እዩ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ከርቤ ፡ ወስኂን ፡ (ማሕ፫ ፡ ፯ ። ፬ ፡ ፮ ። ዘፀ፴ ፡ ፴፬ ። ዘሌ፪ ፡ ፩) ። ሴቶች ፡ ከእሳት ፡

እግብተው ፡ የሚጥቁትና ፡ የማይጠሱት ፡ ሌላውም ፡ የጤስ ፡ ዕንጨት ፡ ኹሉ ፡ ስኒን ፡ ይባላል ።

**አስኀነ** ፤ አሞቀ ፡ አተኰሰ ፤ አበሰለ ፤ አንደደ ፡ አጤሰ ፤ ለማብሰል ።

**መስኀንት** ፤ የማድ ፡ ቤት ፤ ማብሰያ ፡ መቀቀያ ። አልቦ ፡ ዘያመጽእ ፡ መብልዐ ፡ ድዉያን ፡ ውስተ ፡ መስኀንቲ ፡ አኀው ፡ ሶበ ፡ ያበስሉ ፤ አላ ፡ ይገብሩ ፡ ሎሙ ፡ ለድዉያን ፡ እንተ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ (ሥር ፡ ጳኵ) ።

**ሰጢው** ፡ **ዎት** ፤ (ሰጠወ ፡ ይሰጡ ፡ ይስጡ) ፤ እው ፡

**ሰጥዎ** ፤ **ዎት** ፤ (ሰጠወ ፡ ይሴጡ ፡ ይሰጡ ፤ መጠወ ። ዕብ ፡ ያሻጥ) ፤ መስጠት ፤ ዕንካ ፡ ውሰድ ፡ ማለት ፤ እጅን ፡ መዘርጋት ። መጥራት ፡ መጠየቅ ።

**ሰጣዊ** ፤ **መሰጥው** ፤ የሚሰጥ ፡ ሰጪ ፤ ጠሪ ፡ ጠያቂ ፤ መላሽ ፡ ተየካሽ ። ኪያከ ፡ መሰጥወ ፤ ኪያከ ፡ ሰማዒ ፡ (ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ተሰጥወ** ፤ **ተሰጠወ** ፤ ተሰጠ ፤ ተሰጠው ፤ ተቀበለ ። ኢይምሰልከ ፡ ዘይሰጠወከ ፡ በእብእ ፡ ፀመባ ፡ ውዴቱ ፡ ዘሐሰት ፡ ኢትሰጠው ። ዘይሰጠወክሙ ፡ እግዚ ፡ በእደዊሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ሚራ ፻፶፱ ፡ ፲፰ ። ዘፀ ፳፫ ፡ ፭ ። ፩ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፰ ። ፫ዮሐ ፡ ፱) ።

—፤ መለሰ ፤ ተናገረ ፤ ምላሽ ፡ ሰጠ ፤ ታዘዘ ። ሰማ ፡ እሺ ፡ በጎ ፡ አለ ። ጸዋዕኩ ፡ ወአልቦ ፡ ዘተሰጥወኒ ። ኢተሰጥውዎ ፡ ቃለ ። ይጼውዑኒ ፡ ወእሰጠዎ ። ኢንፈቅድ ፡ ንሰጠውከ ፡ በዝንቱ ፡ ነገር ። ብጽሒ ፡ ፍጡነ ፡ ትሰጠዊዮ ፡ ዘይቤ ፡ (ኢሳ ፰ ፡ ፱ ። ፴፭ ፡ ፳፭ ። መገ ፡ ፩ ። ዳንኤ ፡ ፲፯ ። ደራሲ) ። ሰማ ፡ ታዘዘ ፡ እሺ ፡ በጎ ፡ አለ ፡ ማለት ፤ ምስጢሩ ፡ ከተቀበለ ፡ ይገባል ።

**ተሰጣዊ** ፤ (**ዊት ፡ ውያን ፡ ያት**) ፤ ጥያቂ ፤ ተቀባይ ፤ ተጠያቂ ፤ ምላሽ ፡ ሰጪ ፤ ተሰጠ ፡ አቅራቢ ። ተሰጣዊ ፡ ስእለታት ፡ (አረጋ ፡ ድ፲፯) ።

**ስጥው** ፤ (**ውት ፡ ዋን ፡ ዋት**) ፤ ውኩፍ ፤ የተሰጠ ፤ ተሰጪ ፤ ወይም ፡ ተቀባይ ፤ ውድ ፡ ክቡር ። ይኩን ፡ ውስተ ፡ ፍጽሙ ፡ ለአሮን ፡ ስጥወ ። ያበውእ ፡ ስጥወ ፡ (ዘፀ ፳፰ ፡ ፴፰ ። ዘሌ ፩ ፡ ፫) ።

**ስጣዌ** ፤ መስጠት ፤ መሰጠት ፤ አሰጣጥ ፤ ስጦታ ፤ ቅበላ ። ምላሽ ፡ መልስ ፤ አመላለስ ፤ ምለሳ ። ስጣዌ ፡ መልእክት ። ስጣዌ ፡ ስጣዌያት ፡ (አረጋ ። አዋል) ።

**ስጥወት** ፤ ገጹ ፡ ክማሁ ፤ መስጠት ፤ መመለስ ፤ ምላሽ ፡ ስጦታ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፯) ።

**ተሰጥዎ** ፤ መስጠት ፡ መቀበል ፤ ተሰጪ ፡ ተቀባይ ፡ ታዳይ ፡ መኾን ። መስማት ፡ መቀበል ፤ ምላሽ ፡ መስጠት ፤ መልስ ፡ መናገር ።

—፤ በቁሙ ፤ ተሰጠ ፤ የቅዳሴ ፡ ጸሎት ፤ ሕዝብ ፡ ለዲያቆን ፡ ለቄስ ፡ የሚመልሱት ፡ ቃል ፤ ተንሥኡና ፡ ሰላም ፡ ሲላቸው ፡ እግዚኦ ፡ ተማሀለን ፤ ምስለ ፡ መንፈስከ ፡ ማለት ፤ ይህን ፡ የመሰለ ። ተሰጠ ፡ ተቀባይ ፡ እንዲሉ ።

**ተሳጠወ** ፤ ተሟገተ ፤ ተከራከረ ፤ ተጠያየቀ ፤ ተወዳደረ ፤ እሰጥ ፡ እሰጥ ፡ ተባባለ ፤ በዳኛ ፡ ፊት ። ወይም ፡ ያለዳኛ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቃል ፤ እንደ ፡ ቄርሎስ ፡ እንደ ፡ ጳላድዮስ ፤ እንደ ፡ አንው ፡ እንደ ፡ ፊልክስዩስ ።

**አስተሳጠወ** ፤ አጠያየቀ ፤ አባባለ ፤ አከራከረ ፤ እንደ ፡ ቈስጠንጢኖስ ።

**ሰጢሕ** ፤ **ሖት** ፤ (**ሰጥሐ ፡ ይሰጥሕ ፡ ይስጣሕ ። ዐረ ፡ ሰጠሐ ። ዕብ ፡ ሻጣሕ ። ሱር ፡ ሽጣሕ**) ፤ ማስጣት ፡ መዘርጋት ፤ መዘረር ፡ መስተር ፤ ለፀሓይ ፡ መስጠት ። ሰጥሑ ፡ ወአይበሱ ። ወሰጥሐት ፡ ላዕሌሁ ፡ ዐረቦናተ ። ይሰጥሕዎሙ ፡ ለፀሓይ ፡ ወሲወርኅ ፡ (ዘኍ ፲፩ ፡ ፴፪ ። ፪ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ። ኤር ፰ ፡ ፪) ።

**ሰጣሒ** ፤ (**ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት**) ፤ የሚያሰጣ ፤ አስጭ ፤ ገላጭ ፡ ገላላጭ ። ኦ ፡ ሰጣሒሁ ፡ ለኀቡእ ፡ ወከባቲሁ ፡ ለዅሉ ፡ ክሡት ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**መስጥሕ** ፡ (**ብ ፡ መሳጥሕ**) ፤ ማስጫ ፡ መዘርጊያ ፤ መዘረሪያ ፤ መስቀሪያ ፤ መሣሪያ ፡ ቦታ ።

**መስጥሒ** ፤ **ሒ** ፤ (**ሰጣሒ**) ፤ የሚያሰጣ ፤ የሚዘረጋ ፤ አስጭ ፤ ገላጭ ።

**አስጥሐ** ፤ (ጥሰ) አሰጣ ፤ አስገሰጠ ፤ አስጡ ፡ ማስጡ ፡ አለ ።

**ተሰጥሐ** ፤ ተሰጣ ፡ ተዘረጋ ፤ ተገለጠ ፤ ለፀሓይ ፡ ተሰጠ ። ተነፅኆ ፡ ወተሰጥሐ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። አብድንት ፡ ይሰጥሓ ፡ ውስተ ፡ ገጸ ፡ ገዳም ። ትሰጣሕ ፡ ኀጢአትነ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ (ሄርማ ፡ ገ፳፭ ። መሳ ፡ ፳፭ ። ኤር ፲ ፡ ፳፪ ። አፈ ፡ ተ፴፭) ።

**ስጡሕ** ፤ (**ሓን ፡ ሓት ፡ ጥሕት**) ፤ የተሰጣ ፤ የተገለጠ ፤ ስጥ ፡ ግልጥ ፤ ዝርግ ፡ ሰፊ ፤ ገልባጣ ። እንዘ ፡ ስጡሕ ፡ ልብስ ። ዳእሙ ፡ ስጡሓነ ፡ ውስተ ፡ ገጸ ፡ ምድር ፡ ይከውኑ ። ወዅሉ ፡ ክሡት ፡ ወስጡሕ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንቲሁ ። እንዘ ፡ ስጡሕ ፡ ልቦሙ ፡ (ሥር ፡ ጳኵ ። ኤር፴፪ ፡ ፲፱ ። ዕብ ፬ ፡ ፲፫ ። ፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፬) ።

**ስጥሐት** ፤ ማስጣት ፤ መሰጣት ፤ አሰጣጥ ፤ ስጥነት ፤ ዝርግነት ፤ ግልጥነት ።

**ምስጣሕ** ፤ (**ሓት**) ፤ ማስጫ ፤ መስጫ ፤ ቦታ ፡ መሣሪያ ። ምስጣሐ ፡ መሥገርት ፡ (ሕዝ ፳፮ ፡ ፲፬) ።

**ሰጠጠ** ፤ **—ቀደደ** ፤ **—ሠጠጥ ፡ ሠጠጠ** ።

**ስጢጥራ** ፤ (**ጽር ፡ ስታቲር ። ዕብ ፡ ኤስቲራ**) ፤ የገንዘብ ፡ ስም ፤ ፋርሳዊ ፡ ገንዘብ ፤ አራት ፡ ድሪም ። ብር ፡ ሲኾን ፡ ፫ ፡ ፍራንክ ፡ ከ፳፱ ፡ ሳንቲም ። ወርቅ ፡ ሲኾን ፡ ፲፱ ፡ ፍራንክ ፡ ከ፹ ፡ ሳንቲም ፡ (ዲክሲ ፡ ላሩስ) ። ትርጓሜ ፡ ስጢጥራ ። ስጢጥራ ፡ ዘይቤ ፡ አርባዕቱ ፡ ድርህም ፡ (ማቴ ፲፯ ፡ ፳፯ ። ጥራ ፡ ሰዋ) ። ድርህምንና ፡ ሕፍንን ፡ ተመልከት ።

**ሰጢም ፤ ሞት ፤** (ሰጥመ ፡ ይሰጥም ፡ ይስጠም ። ዐረ ፡ ሰጠመ ። ዕብ ፡ ሳታም ፤ ዘጋ) ፤ መዘጋት ፡ መደፈን ፤ መቀበር ፡ መሰወር ። መስጠም ፡ ከባሕር ፡ ከረግረግ ፡ መግባት ፤ መጥለቅ ፤ መሥረግ ፤ መገንገጥ ፤ መዋጥ ፡ መስመጥ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በስጥመ ፡ ፈንታ ፡ ቀስጥመ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ፤ ተ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። እመ ፡ ተሰጥሙ ፡ ውስተ ፡ ቀላየ ፡ ባሕር ። ወረዉ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ፈለግ ፡ ወተሰጥሙ ። አልጸቀት ፡ ሐመር ፡ ለተሰጥሞ ። ተሰጢምነ ፡ በኀጣውኢነ ። ተሰጥሞ ፡ ውስተ ፡ ጣዕማት ፡ (ዓሞ፱ ፡ ፫ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ሚያ፳፰ ። ሱቱ ፡ ሰገ፯ ፡ ዓ፫ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፱) ።

**ስጡም ፤** (ማን ፡ ማት ፡ ጥምት) ፤ የሰጠመ ፤ የተሰጠመ ፤ ባሕር ፡ የዋጠው ፡ የሸፈነው ፤ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ የደፈነው ። ማሕጼ ፡ ስጡም ። እለ ፡ ስጡማን ፡ በግብረ ፡ ዓለም ። እለ ፡ ስጡማን ፡ ውስተ ፡ ዐምዓመ ፡ ኀጢአት ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። አፈ ፡ ተ፲፰ ። ግንዘ) ።

**ስጥመት ፤** በቁሙ ፤ መስጠም ፤ መሰጠም ፤ አሰጣጠም ፤ ውሃ ፡ መልበስ ፤ በውሃ ፡ መቀበር ። ከመ ፡ ሰብአ ፡ ኖኅ ፡ በስጥመት ፡ ውስተ ፡ ማይ ። ድኅኑ ፡ እምስጥመት ። ዘሞትከ ፡ በስጥመተ ፡ ማይ ። ውዕየት ፡ እሳት ፡ አው ፡ ስጥመት ፡ ሐመር ፡ (ፊልክ ፡ ፻፳፪ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፱ ። ሠኔ፯ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፱) ።

**አስጠመ ፤** አሰጠመ ፤ ከባሕር ፡ አገባ ፡ ጣለ ፤ አጠለቀ ፤ ደፈነ ፡ ቀበረ ፤ ዋጠ ፡ አሰመጠ ፤ አሰበሰ ። ያስጥምዎን ፡ ለኀጣውኢነ ። አስጥም ፡ ጽንዖሙ ። ያስጥም ፡ መራዕየ ፡ አሕርው ። አስጠሞሙ ፡ ወይን ። አፍላግ ፡ ኢያስጥሙከ ። ያስጥም ፡ ሐዝሐዘ ፡ ፈለግ ። ውሒዝ ፡ ዘይደፍና ፡ ወያስጥማ ፡ ለምድር ፡ (ሚክ፯ ፡ ፲፱ ። ዮዲ፱ ፡ ፳ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ኢሳ፳፫ ፡ ፯ ። ዓ፫ ፡ ፱ ። ኢዮ፵፩ ፡ ፴፫ ። ኢር፳፱ ፡ ፪) ።

**መስጥም ፤** (ምት ፡ ማን ፡ ማት) ፤ የሚያሰጥም ፤ የሚያጠልቅ ፤ የሚውጥ ፡ የሚያሰምጥ ። ወረውዎ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ መስጥም ። ልሳን ፡ መስጥም ። ልጐት ፡ ዘዝንቱ ፡ ሕይወት ፡ መስጥም ፡ (ስንክ ፡ የካ፲፯ ። መገ ፡ ፶፰ ። አፈ ፡ ተ፳፪) ።

**መስጠሚ ፤ ም ፤** ግእ ፡ ከማሁ ፡ መስጠሚያ ፤ ማስጠሚያ ። የሚያሰጥም ፤ አስጣሚ ። ቦታ ፤ አካል ። ማየ ፡ አይኅ ፡ መስጠሚ ፡ ዘርዑ ፡ ለቃየል ። ዮርዳኖስ ፡ መስጥመ ፡ አበሳ ። ሙሴ ፡ ወአሮን ፡ መስጥማነ ፡ ፈርዖን ፡ በኤርትራ ፤ ባርቅሂ ፡ ወዲቦራ ፡ መስጥማነ ፡ ወልዱ ፡ ሲሳራ ፡ በፈለገ ፡ ቂሶን ፡ (ዘሪፋ) ።

**ሳጥና ፤—ሰይጣን ፤—ሴጣን ።**

**ሰጢን ፤** (ዕብ ፡ ሺጣ ፤ ሺጢም) ፤ የንጨት ፡ ስም ፤ እሾኽም ፡ ግራርማ ፤ የግራር ፡ ዐይነት ፤ የማይነቅዝ ፡ የማይጠነቅን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ዕፀ ፡ ሰጢን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዕፀ ፡ ዘኢይነቅዝ ፡ ይላል ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፭ ፡ ፲ ። ፳፮ ፡ ፲፭ ፡ ፳፯ ፡ ፩ ። ፴፰ ፡ ፲፱ ። ፴፯ ፡ ፩ ። ፴ ፡ ፩) ።

**ሰጡቃጤ ፤** (ጽር ፡ ስታክቲ ። ዕብ ፡ ናጣፍ) ፤ የሙጫ ፡ ሽቱ ፤ የሚጤስ ፡ የሚታጠን ፤ ከታወቁ ፡ የሽቱ ፡ ዘሮች ፡ ከዕፀው ፡ ዕጣን ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ወለላ ፡ የሚፈስ ፡ የሚንጠፈጠፍ ፡ (ሲራ፳፬ ፡ ፲፭) ።

**ሰጢር ፤ ሮት ፤** (ሰጠረ ፡ ይሰጥር ፡ ይስጥር ። ትግሬ ፡ ሰጥረ ። ዕብ ፡ ሳታር ። ሱር ፡ ስታር ። ዐረ ፡ ሰተረ) ፤ መመስጠር ፤ ማመስጠር ፤ ማርቀቅ ፡ ማጥለቅ ፤ መሰወር ፡ መደበቅ ፤ ማልበስ ፡ መሸሸግ ፤ እንዳይታይ ፡ ማድረግ ።

**ምስጢር ፤** (ራት ። ጽር ፡ ሚስቲሪዮን) ፤ በቁሙ ፤ ስውር ፤ ኅቡእ ፡ ስዉር ፤ ሽሽግ ፡ ነገር ፡ ሐሳብና ፡ ምክር ። በዓላት ፡ በጕሃን ፡ ወመሥዋዕት ፡ በምስጢር ። ምስጢረ ፡ መንግሥት ፡ ሠናይ ፡ ለኀቢእ ። ምስጢረ ፡ ምክሩ ። ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ይኩን ፡ በምስጢር ፡ (ጥበ፲፬ ፡ ፲፭ ። ጦቢ፲፪ ፡ ፯ ። ቀሌ) ።

—፤ አምላካዊ ፡ ግብር ፤ መንፈሳዊ ፡ ረቂቅ ፤ የማይታይ ፡ የማይታወቅ ፤ የሚታመንና ፡ የሚደነቅ ፡ ብቻ ። አዕማደ ፡ ምስጢር ። በእንተ ፡ ትድምርት ፡ ቃል ፡ ዘበምስጢር ። ምስጢር ፡ ግሩም ፡ ምስጢር ፡ አምላካዊ ። ሥርዐተ ፡ ምስጢር ፡ ዘቍርባን ። ወይትመጦ ፡ እምስጢራት ፡ ቅዱሳት ፡ (ቄር ። አፈ ፡ ተ፲፯ ። ቅዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳) ።

**ምስጢራዊ ፤** ምስጢራም ፡ ምስጢረኛ ፡ ባለ ምስጢር ፤ ምስጢር ፡ የኾነ ፤ የምስጢር ፡ ሥራ ፤ ኅቡእ ፡ ረቂቅ ። ተዋሕዶተ ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ ምስጢራዊ ። ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ገብረ ፡ ድራረ ፡ ምስጢራዊተ ፡ (ያዕ ፡ ዘእል ። አቡሻ ፡ ፳፩) ።

**አመስጠረ ፤** (ሰጠረ) ፤ ምስጢር ፡ አደረገ ፡ ሰወረ ፡ ደበቀ ፤ አረቀቀ ። ነጽርኬ ፡ ዘከመ ፡ አመስጠረ ፡ እሙንቱ ፡ በአሐቲ ፡ ቃል ። አመስጠረ ፡ ፍካሬሁ ። በአመስጥሮ ፡ (አፈ ፡ ድርሳ ፡ ፳ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ተመስጠረ ፤** (ተሰጥረ) ፤ ምስጢር ፡ ኾነ ፤ ተሰወረ ፡ ተደበቀ ፤ ጠለቀ ፡ ረቀቀ ። እምልብኒ ፡ ተመስጠረ ፡ ወእምኅሊናኒ ፡ ተሰወረ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተመሳጠረ ፤** በቁሙ ፤ ተራቀቀ ፤ በስውር ፡ በምስጢር ፡ ተናገረ ፤ ተነጋገረ ። ተመሳጠረ ፡ ምስሌየ ። እትመሳጠር ፡ ምስለ ፡ ፍቁራንየ ። በተመሳጥሮ ፡ እትናገር ፡ ምስሌከ ፡ (አረጋ ፡ መልፀ፬ ፡ ዓ፫) ።

**ሰጥረጲሎን ፤** (ጽር ፡ ስትሮፒሎስ) ፤ የዛፍ ፡ ስም ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ፤ እንደ ፡ ጥድ ፡ መልክም ፡ ሽታ ፡ ያለው ፤ ዕንጨቱ ፡ የመሥዋዕት ፡ ሙጋድ ፡ የሚኾን ፡ (ኩፋ ፡ ፳፩) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሽንት ፡ ይሉታል ።

**ሰጠጽዮን ፤** (ጽር ፡ ስቲፒን ። ዐረ ፡ አስጡበት) ፤ የተልባ ፡ እግር ፡ ጭረት ፤ መናኛው ፡ ገለባው ፡ ግርዱ ፡ ገፈፎው ። (ዳንኤ ፡ ፳፱ ። ስንክ ፡ ሐም፳) ።

**ሰይ ፤** (ወይ ፤ አሌ ። ዕብ ፡ አይ ፤ ሆይ) ፤ ወዮ ፤ ዋይ ፤ የሐዘን ፡ ቃል ፤ ከጭንቅና ፡ ከምጥ ፡ የተ

ነማ ። ልየ ፡ ለከ ፡ ሎሙ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ወይና ፡ እንደ ፡ አሌ ፡ በለ ፡ ይዘምታል ። ሰይ ፡ ልየ ፡ ዘርሕቀ ፡ ማኅደ ርየ ፡ (መ·ዝ ፡ ፻፲፱) ።

**ሰይል** ፤ መከራ ፡ መቅሥፍት ፤ ፍርድ ፡ ቅጣት ፤ ቊንቅ ፡ ፍርሀት ፤ ይብላኝ ፡ ወዮልኝ ፡ የሚያሰኝ ። ይረ ክበሙ ፡ እምኄበ ፡ እግዚ ፡ ደይን ፡ ወሰይል ፤ ይረ ክብ ፡ ሰይለ ። አመ ፡ አደንገፅከ ፡ ሞተ ፡ ወሰዓተ ፡ ሰ ይል ፡ (ቀሌ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ፲፩) ።

**ሰይል ፤ (ዐረ ፡ ሰሊል ። ዕብ ፡ ሸሊል) ፤** ሽል ፡ ያደገ ፡ ዕንስ ፡ በሆድ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ በጣም ፡ ያል በሰለ ፤ ምጡ ፡ የሚያስጨንቅ ፤ ሰይ ፡ ዋይ ፡ አሌ ፡ የሚ ያሰኝ ። ኄበየት ፡ በነፍሳ ፡ ከመ ፡ ትቅትል ፡ ሰይላ ፡ (ቄድር) ።

**ሰይል ፤ (ዐረ ፡ ሰላን ። ዕብ ፡ ሸ፡ልያ) ፤** ምንሃር ፤ ሽላዊ ፤ አስጅ ፤ እንግዴ ፡ ሥጋ ፤ ከልጅ ፡ በኋላ ፡ የሚወጣ ።

**ሰይእ ፤ (ዐረ ፡ ሸይእ ። ዕብ ፡ ምእማ) ፤** አንዳች ፡ ጥቂት ፤ ምናምን ፤ ምንም ፡ ምን ፤ አክቶ ፡ ፈ ጽሞ ፤ ከንዱ ፡ ዘንዱ ። ምስጢሩ ፡ ሕርም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አንዳች ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳይኾን ፡ ክልከላን ፡ ምጥን ታን ፡ ዐደራን ፤ ወይም ፡ ችሎት ፡ ማጣትን ፡ አለመቻልን ፡ ያሳያል ፡ (፪ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፪ ። ፲፰ ፡ ፲፫) ።

**ሰይእ ፤ (ዕብ ፡ ሻውእ) ፤** ከንቱ ፤ ብላሽ ፤ ውሸት ፤ ባዶ ፤ ፍሬ ፡ ቢስ ፤ የማይረባ ።

**ሴብ ፤—ሸበተ ፤—ሠዪብ ፡ ሤበ ።**

**ሲሃት ፤ (ዐረ ፡ ሻሀት) ፤** ለማኝ ፤ ምስኪን ፤ ቍርጩ ፡ ድኻ ። ገዳመ ፡ ሲሃት ፤ ሙሴ ፡ ዘሲሃት ፡ (ስንክ ፡ መስ፳) ።

**ሰዩሕ ፤ ሖት ፤ (ሴሐ ፡ ይሰይሕ ፡ ይ ሲሕ ። ዐረ ፡ ሰሐ ። ሱር ፡ ሻሕ) ፤** ማፍሰስ ፡ ማቅ ለጥ ፤ መቀጥቀጥ ፤ ወይም ፡ መፍሰስ ፡ መቅለጥ ፤ የማዕደ ናት ። መታመም ፤ መሳል ፤ መሰልሰል ፡ መመንመን ፤ ድዉይ ፡ መኾን ። ከመ ፡ ኢይሲሕ ፡ ወኢይንበር ፡ መ ፃጕዐ ፡ ወኢይፀራዕ ፡ ግብረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ኪዳ ፡ ገ፳) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፤ ወገጠ ፡ ይሉታል ። ባለብሉዮ ችም ፡ በሴሐ ፡ ፈንታ ፡ ሰሐየ ፡ አስሐየ ፡ ይሉና ፤ ፍችውን ፡ አጠፋ ፡ አደረቀ ፡ ይሉታል ። ያሴሕዩዋ ፡ ለሕይወ ቶሙ ፡ መላእክት ፡ (ኢዮ፴፮ ፡ ፲፬) ።

(ጥያ) **ሰያሕ ፤ (ሕት ፤ ሰያሒ ፡ ሒት) ፤** ብር ፡ አፍሳሽ ፤ ወርቅ ፡ አቅላጭ ፤ አንጥረኛ ፡ ቀጥቃጭ ። ወገ ብረ ፡ (ምናሴ) ፡ ሰያሕተ ፤ ወማርያተ ፡ አብዝኀ ፡ (ዳድ ፡ ፳) ።

**ሰያሕ ፤ (ዐረብ) ፤** ቤተ ፡ ክሲያን ፡ ሳሚ ፤ ጠበ ለተኛ ፤ ጩኸ ፡ የሚዘምር ፤ ዘፋኝ ፡ እልል ፡ ባይ ።

**ሲሕ ፤ (ዕብ ፡ ሸሔፌት) ፤** የሳንባ ፡ ደዌ ፤ ታላቅ ፡ ሳል ፤ ኰብሽ ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፤ የሚያከሳ ፡ የሚያጠ ቍር ፤ የሚነፋ ፡ የሚያሳብጥ ፤ የሚያቈስል ፡ የሚያሳክክ ። ደዌ ፡ ሲሕ ፡ (ዘሌ፳፮ ፡ ፲፮ ። ዘዳ፳፰ ፡ ፳፪) ።

**ስያሕ ፤ (ሓት) ፤** አጕድ ፡ ከውር ፡ የእሳት ፡ ጕ ድጓድ ። ጽዋዕ ፡ ጽንሓሕ ፤ ለቃቃ ፡ አፈ ፡ ሰፊ ። ቶስሕት ፡ ውስተ ፡ ስያሓ ፡ ዘዚአሃ ፡ ወይነ ። ይስወጥ ፡ በስያ ሖሙ ፡ ቃለ ፡ ሰላምየ ፡ ዝንቱ ፤ በአምሳለ ፡ ወይን ፡ ዘምሉእ ፡ ቅድሐቱ ፤ ጽዋዕ ፡ (ምሳ፱ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ሐም ፲፱) ። ስያሐ ፡ ወርቅ ። ስያሐ ፡ ዕጣን ። መዕዛ ፡ ዕ ጣን ፡ ይትቈረብ ፡ በስያሐ ፡ ወርቅ ፡ (ገድ ፡ ተክ ። አርጋ ፡ ፪ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ሺሕ ፤ (ሓት ፡ ታት ፤ ዐማሬና ፡ ትግሬ) ፤** በቍሙ ፤ ሺ ፤ ዐሥር ፡ መቶ ፤ ወይም ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ። ከሰባማ ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ ባሮጌው ፡ ግእዝ ፡ መቶ ፡ ብሎ ፡ እልፍ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሺሕ ፡ የለም ፤ አለመኖሩም ፡ በአኃዙ ፡ ተራ ፡ ይታወቃል ፡ ፻ ፡ ብሎ ፡ ፻፻ ፡ በማለቱ ። በት ግሬም ፡ ቢኾን ፡ እልፍና ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ እልፍ ፡ የሚባለው ፡ ያው ፡ ሺሑ ፡ ነው ። ሺሑን ፡ አም ኣት ፡ ወይም ፡ ፲፻ ፡ ማለትና ፡ ዐሥሩን ፡ ሺሕ ፡ ፻፻ ፡ ማ ለት ፡ ከጽርእና ፡ ከቅብጥ ፡ የመጣ ፡ የሐዲስ ፡ ግእዝ ፡ ልማድ ፡ ነው ፤ ጥንታዊው ፡ ፊደል ፡ ያበገደ ፡ ተራ ፡ ቢፋ ለስ ፡ አኃዙም ፡ ተፋልሷል ። ከኹን ፡ በፊት ፡ ለሺሕ ፡ ለእ ምኣት ፡ እንደሌላው ፡ ቍጥር ፡ አኃዝ ፡ ምልክት ፡ አልነ በረውም ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ባቡጊዳ ፡ ሥርዐት ፡ ቀ ፡ ምእት ፡ እንዲባል ፡ ቄ ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ቀለበቱ ፡ አምኣት ፡ ይባላል ፤ ሺሕ ፡ ማለት ፡ ነው ። የእንና ፡ የጉን ፡ የቀን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ።

**ሺሓት** ፤ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ እልፍ ።

**ሺሓታት** ፤ መቶ ፡ ሺሕ ፤ ወይም ፡ ሺ ፡ ጊዜ ፡ መቶ ፤ ዐሥር ፡ እልፍ ። እለ ፡ አምኑ ፡ ኢከኑ ፡ ሺሓ ታተ ፡ ወኢአእላፋተ ፡ አላ ፡ አህጉርኒ ፡ ወበሓውርት ፡ (ፊልክ ፡ ፵፭) ።

**ሺዋ** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ ስመ ፡ ብእሲት ፤ ሽኋ ፡ ሽ ሒቱ ። ምስጢሩ ፡ ብዛት ፡ ብዙኅነት ፡ ነውና ፤ ሺሑ ፡ አሸዋ ፡ ከማለት ፡ ይስማማል ። (ታሪክ) ፤ ጥንታዊው ፡ የወሎ ፡ ባላባት ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ ለማሸው ፡ ባላባት ፡ ለወንድ ፡ ልጁ ፡ በሕግ ፡ አጋብቷት ፡ ስትኖር ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ል ጆቿን ፡ ይዛ ፡ አባቷን ፡ ለማየት ፡ ወሎ ፡ ኼደች ። አባ ቷም ፡ በልጆቿ ፡ ብዛት ፡ ተደንቆ ፡ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ምኖ ችሽ ፡ ናቸው ፡ ቢላት ፤ እኩሉ ፡ ልጆቼ ፡ እኩሉም ፡ የልጅ ፡ ልጆቼ ፡ አለችው ። ልጄ ፡ ሺዋ ፡ ልጄ ፡ ሺዋ ፤ ቀድሞም ፡ ስድርሽ ፡ ሺ ፡ ኹኚ ፡ ሺ ፡ ያድርግሽ ፡ ብዬ ፡ መርቄሽ ፡ ነበረ ፤ አኹንም ፡ እንደ ፡ ምርቃቴ ፡ ሺ ፡ ስለ ፡ ኾንሽ ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ስምሽ ፡ ሺዋ ፡ ይኹን ፡ ሺዋ ፡ ብ ዬሻለኹ ፡ አላት ። ርሷም ፡ እንደ ፡ ባሏ ፡ በቡራኬ ፡ ላይ ፡ ቡራኬ ፡ ጨምራ ፡ ሺዋ ፡ ተብላ ፡ ተመለሰች ። ልጆቿም ፡ ሺዎች ፡ የሺዋ ፡ ልጆች ፡ ተብለው ፡ በያሀጉሩ ፡ ተበትነው ፡ መንዝን ፡ ተጕለትን ፡ ይፋትን ፡ ቡልጋን ፡ ጠራን ፡ መ ርሐ ፡ ቤቴን ፡ ሌላውንም ፡ ኹሉ ፡ አቀኑ ። ከግሼ ፡ ከዳ ዬር ፡ እስከ ፡ ዝቋላና ፡ እስከ ፡ የረር ፡ ምሥራቁና ፡ ምዕ ራቡም ፡ ሳይቀር ፡ በርሷ ፡ ስም ፡ ሺዋ ፡ ተብሏል ። (ግ ጥም ፡ ስለ ፡ ስገሌ ፡ ጠር) ፤ ኋለኛው ፡ ባላባት ፡ ዝምድና ፡

ሲያፈርሱ ፡ ክወሎ ፡ ገሥግሠው ፡ ስገሌ ፡ ሲደርሱ ፤ በቅሎና ፡ መጫሚያ ፡ ስላልነበራቸው ፡ እዬ ፡ ጕድ ፡ እዬ ፡ ጕድ ፡ ያ ፡ (ሺዋ)እሸዋ ፡ ፈጃቸው ። ውሃ ፡ ውሃ ፡ ሲሉ ፡ ክረምቱማው ፡ ላይ ፤ መላእክት ፡ አንሥተው ፡ ወሰዷቸው ፡ ፲፱ ።

**ሴጠነ** ፤ **(ይሴጥን ፡ ይሴጥን ፤ ሴጥኖ ። ዕብ ፡ ሳጣን)** ፤ ከሰሰ ፡ አሳጣ ፤ አሳተ ፡ በጦር ፡ በነገር ፡ ተከተለ ።

**ሰይጣን** ፤ **(ዐረ ፡ ሸይጣን ። ዕብ ፡ ሳጣን ። ሱር ፡ ሳጣና)** ፤ ባለጋራ ፤ ጠላት ፤ ወደረኛ ፤ ከሳሽ ፡ አሳጭ ። በቁሙ ፤ መንፈስ ፡ ርኩስ ፤ ሳጥናኤል ፤ ዲያብሎስ ፤ ርሱ ፡ ራሱ ፤ ወይም ፡ ከሰራዊቱ ፡ አንዱ ። ወአቀመ ፡ ሰዴርሁ ፡ ሰይጣነ ፡ ላዕለ ፡ ስሎሞን ። ሑር ፡ እምድኅሬየ ፡ ሰይጣን ። ወሰይጣን ፡ ይቀውም ፡ በየማኑ ። (፩ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬ ። ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፳፫ ። መዝ ፡ ፻፰) ። ወሚካኤልኒ ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ሶበ ፡ ይትባሀሎ ፡ ለሰይጣን ። ወአርዌ ፡ ዐቢይ ፡ ዘስሙ ፡ ሰይጣን ። ርኢክዎ ፡ ለሰይጣን ፡ ወድቀ ፡ እምሰማይ ። (ይሁ ፡ ፱ ። ራእ ፲፪ ፡ ፱ ። ሉቃ ፲ ፡ ፲፰) ።

**ሰይጣናት** ፤ **ሰያጥንት** ፤ ሰይጣኖች ፤ ባለጋሮች ። አመረ ፡ ፈያተ ፡ ለኄብ ፡ ሰይጣናት ። ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ሲሳየ ፡ ለሰይጣናት ። ሰያጥንትኒ ፡ ይፈርሁ ፡ (ፊልክ ፡ ፳፰ ። አረጋ ፡ ድጓ) ።

**ሰይጣናዊ** ፤ የሰይጣን ፡ የባለጋራ ፤ ወገን ፡ ሥራ ። መልእክ ፡ ሰይጣናዊ ። ዝንቱ ፡ ልማድ ፡ ሰይጣናዊ ። ፍትወት ፡ ሰይጣናዊት ። መናስው ፡ ሰይጣናዊት ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፴ ። አፈ ፡ ተ፲፭ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፫ ። ፊልክ ፡ ፫) ።

**ተሰይጠነ** ፤ ሰይጣን ፡ ኾነ ፤ ሰይጣን ፡ ተባለ ። ኮከብ ፡ ጽባሕ ፡ ዘተሰይጠነ ፡ በትዕቢቱ ፡ (ማር ፡ ይሥ፱) ።

**ስይጣኔ** ፤ ሰይጣንነት ፤ ስብቅ ፡ ክስ ፤ የሰይጣን ፡ ሥራ ፤ ክፋ ፡ ሥልጣኔ ።

**ሳጥና** ፤ ሰይጣን ። **ሳጥናኤል** ፤ ሰይጣን ፡ ኤል ፤ ፀረ ፡ አምላክ ፤ ያምላክ ፡ ጠላት ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ ሥሉጥ ፡ ባለሻል ፡ ቅሩብ ፡ መንበር ፡ እንጂ ፡ መንጦላዕት ፡ ይሉታል ፤ የስሕተት ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ምኽት ፡ ይመስላል ። ሴስዮነ ፡ ከመ ፡ መና ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰላመክሙ ፡ ዳኅና ፤ እማኅበርነ ፡ ያስስል ፡ ሙስና ፡ ስዒሮ ፡ በጥዒና ፡ ሁከት ፡ ለሳጥና ። ሰራዊተ ፡ ሳጥናኤል ፡ (ደራሲ ። ድር ፡ ሚክ ። ቀሌ) ።

**ሰይል ፤—መክራ ፡ ሸል ፤—ሰይ ፡ ል ።**

**ሴመ ፤—ሾመ ፤—ሡዩም ፡ ሢመ ።**

**ሴነ ፤—ሸነ ፤—ሡዩን ፡ ሢን ።**

**ሰይፎ** ፤ **ፎት** ፤ **(ሰየፈ ፡ ይሴይፍ ፡ ይሰይፍ ። ዕብ ፡ ሳዬፍ)** ፤ መሰየፍ ፤ መምታት ፡ መቍረጥ ፤ መበጠስ ፤ መክፈል ፤ መለየት ። በመጥባሕት ፡ ሐፂዊ ፡ በሲኅ ፡ አመ ፡ ለርእሱ ፡ ሰየፉ ። ፀጋዐ ፡ ኅያል ፡ ዘይሰይፍ ፡ ወይክፍል ። ወእፎኬ ፡ ሴሰየፉክ ፡ አስይፍተ ፡ እሳት ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲ ። ቅዳ ፡ ያዕ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ሰያፊ** ፤ **ሰያፍ** ፤ **(ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ የፍት)** ፤ በቁሙ ፤ የሚቈርጥ ፤ የሚበጥስ ፤ ሰይፋም ፡ ሰይፈኛ ፡ ባለሰይፍ ፤ ፈላጭ ፡ ቈራጭ ፡ ባለወግ ። ይቤሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ ለሰያፍያን ፡ (ማር ፡ ይሥ፴፱ ። ዮሴፍ ። ስንክ ፡ መስ፲፰) ።

**ሰይፍ** ፤ **(ዐረ ፡ ሰይፍ ። ሱር ፡ ሳይፋ ። ዕብ ፡ ሳይፍ ፤ ሐሬብ)** ፤ በቁሙ ፤ መምቻ ፡ መቍረጫ ፤ መግደያ ፤ የሰልፍ ፡ መግሪያ ፤ ኹለት ፡ አፍ ፡ ያለው ፤ አፉ ። መተኑ ፡ ከማይ ፡ በሰይፍ ። ሰይፍ ፡ በሌኅ ፡ ዘክልኤ ፡ አፉሁ ። ቅንት ፡ ሰይፈከ ፡ (ስንክ ፡ ግን ፳፰ ። ራእ፩ ፡ ፲፮ ። መዝ ፡ ፵፬) ።



ሰይፍ ።

**አስያፍ** ፤ **አስይፍት** ፤ ሰይፎች ። ሰበንለ ፡ አስይፍትኒ ፡ ይረድእሙ ፡ (ፊልክ) ።

**ሴስዮ** ፤ **ዮት** ፤ **(ሴሰየ ፡ ይሴሲ ። ዕብ ፡ ሲስ ፤ ተሐሥየ)** ፤ መሴስይ ፤ መመገብ ፤ መቀለብ ፤ ምግብ ፡ መስጠት ፤ ግብር ፡ አግብቶ ፡ ማብላት ፡ ማጠጣት ፤ ደስ ፡ ማሰኘት ። ሴሰይክምሙ ፡ እክለ ፡ ወማየ ። ከመ ፡ እሴሲክሙ ። ሴሰይክሙኒ ፡ ለደቂቁ ። ሴሰዮሙ ፡ ለእቡሁ ፡ ወለአኀዊሁ ፡ ወለጥሪቶሙ ፡ ኀባውዘ ። ሎቱ ፡ አሚረ ፡ ይሴስይዎሙ ፡ (ለእናብስት) ፡ ክልኤተ ፡ ሰብአ ፡ ወክልኤተ ፡ አባግዐ ። አዘዘ ፡ ይሴስይዋ ፡ እምነ ፡ ዘይኀብሩ ፡ ሎቱ ፡ ሲሳዮ ፡ (፩ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፲፫ ። ዘፍ፵፯ ፡ ፲፪ ። ኢዮ፴፱ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፵፭ ። ዳን፲፫ ፡ ፴፪ ። ዮዲ፲፪ ፡ ፩) ።

**ሴሳዪ** ፤ **(ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ሰይት)** ፤ የሚሴስይ ፡ የሚመግብ ፤ የሚቀልብ ፤ መጋቢ ፡ ቀላቢ ።

**መሴስይ** ፤ **(ያን ፡ ያት ፡ ሲት)** ፤ ገዥ ፡ ከማሁ ። አነ ፡ እግዚ ፡ ፈጣሪሁ ፡ ወሰሓኪሁ ፡ መጋቢሁ ፡ ወፀቃቢሁ ፡ ወመሴስዩ ፡ ለሖሩ ፡ ዘሥጋ ። እወ ፡ እግዚእ ፡ መጋቤ ፡ ሖሩ ፡ እወ ፡ እግዚእ ፡ መሴስየ ፡ ሖሩ ። መሴሲት ፡ (ቀሌ ። ቅዳ ፡ ዲዮስ ። አርጋ ፡ ፭) ።

**ተሴሰየ** ፤ በቁሙ ፤ ተመገበ ፤ ተቀበለ ፤ በላ ፡ ጠጣ ፤ ጠገበ ፤ ተደሰተ ። ዘኢይፈቅድ ፡ ይትቀነይ ፡ ኢይሴሰይ ። እስ ፡ ይሴሰዩ ፡ እማእደ ፡ ንጉሥ ። አንስት ፡ ይሴሰያ ፡ እምግብረ ፡ እደዊሆን ። ተሴሰዩ ፡ እምዳማ ፡ እደዊሆሙ ። እምነ ፡ ዘአምጻእኩ ፡ እሴሰይ ፡ (፪ተሰ ፡ ፫ ፡ ፲ ። ዳን፩ ፡ ፲፫ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ጥር፲፯ ። ዮዲ፲፪ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፵) ።

**ሲሱይ** ፤ **(ያን ፡ ያት ፡ ሲት)** ፤ የተሴሰየ ፤ የሚቀለብ ፤ ቅልብ ፤ ሲሳያም ፤ ቀለብተኛ ፤ ባለድርጎ ፡ ባለቀለብ ።

**ሲሳይ** ፤ **(ያት)** ፤ በቁሙ ፤ ምግብ ፡ ቀለብ ፤ ድርጎ ፡ መና ፤ መፍቅድ ፡ ዕለት ፡ ቍርስ ፡ ምሳ ፡ እራት ። ሲሳየነ ፡ ዘለለ ፡ ዕለትነ ። ዘኢይረክብ ፡ ሲሳዮ ፡ እክለ ፡

ሰሲሳይ ፡፡ ዘእንበለ ፡ ሲሳይ ፡፡ ሲሳየ ፡ ቋዓት ፡ (ነሐ፩ ፡ ፲፰ ፡፡ ሚራ፲ ፡ ፳፯ ፡፡ ኢሳ፶፭ ፡ ፲ ፡፡ ኢዮ፳፱ ፡ ፯ ፡፡ ፴፰ ፡ ፵፩) ፡፡ ዐሰብ ፤ ረባሕ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሲሳይ ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ሉቃ፫ ፡ ፲፬ ፡፡ ፲፱ ፡ ፳፫) ፡፡

**ሲሲት** ፤ ገዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ሲሳይ ፡፡ ወሀብኩክሙ ፡ አራዊተ ፡ ለሲሲት ፡፡ ልብስ ፡ ወሲሲት ፡፡ ሲሲተ ፡ ልብ ፡ ቃሳቲሁ ፡ ለእግዚ ፡ (ኩፋ ፡ ፯ ፡፡ ፳፱ ፡፡ ቄር ፡ ጸባ) ፡፡

**ሲሴት** ፤ ዘማች ፡ አሞራ ፤ ተዋጊ ፡ ምግብ ፡ ፈላጊ ፤ ወይም ፡ ንጣቂ ፡ አውሬ ፡ ዐድኖ ፡ ፈልጎ ፡ የሚሰስይ ፡፡ ሲሴተ ፡ ወአውስተ ፡፡ ዕጕሊ ፡ አናብስት ፡ ይጥሕሩ ፡ ወይመሥጡ ፡ ወይስእሉ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ፡ ሲሳዮሙ ፡ (ሔኖ፹፱ ፡ ፲ ፡፡ መዝ ፡ ፻፫) ፡፡

**ሰያሳ** ፤ (ዐረብ) ፤ ፖሊቲክ ፤ የንገር ፡ አካኼድ ፡፡

**ሰክአ** ፤—ሰካ ፡ ደረደረ ፤—ሰኪዕ ፡ ሰክዐ ፡፡

**ሰኪብ** ፤ ቦት ፤ (ሰከበ ፡ ይሰክብ ፡ ይስክብ ፡፡ ዕብ ፡ ሻካብ ፡፡ ሱር ፡ ሽኬብ) ፤ መተኛት ፤ መጋደም ፤ መስጣት ፡ መዘርጋት ፤ ዚ ፡ ዘግ ፡ ማለት ፤ ወደ ፡ ሴት ፡ መግባት ፤ ማንቀላፋት ፡ መሞት ፡ መቀበር ፡፡ ሰኪበ ፡ ሰኪሮ ፡፡ ሰበ ፡ ይሰክብ ፡ ዲበ ፡ ምስካቡ ፡፡ ዘይሰክብ ፡ ብእሲተ ፡፡ ወሰከበ ፡ ምስለ ፡ አበዊሁ ፡ (ኩፋ ፡ ፯ ፡፡ ኢዮ፴፫ ፡ ፲፭ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ ፳ ፡፡ እዋል) ፡፡

**ሰካቢ** ፤ (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ከብት) ፤ የሚተኛ ፡ የሚጋደም ፤ ሰነፍ ፤ እንቅልፋም ፤ አበያ ፡ ድውይ ፡ ደካማ ፡፡

**ስኩብ** ፤ (ባን ፡ ባት ፡ ክብት) ፤ የተኛ ፡ የተጋደመ ፤ ገዝርግ ፤ የሞተ ፤ እንቅልፍ ፡ የወሰደው ፡፡ ሕፃን ፡ ስኩብ ፡ ውስተ ፡ ጎል ፡፡ ኮነ ፡ ስኩበ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡፡ ርእዩ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ እጐ ፡ ዘስኩብ ፡ ማእከሌክሙ ፡ በሃም ፡ ወጽሙም ፡፡ ስኩብ ፡ ኮንኩ ፡ በቤተ ፡ መባል ኢል ፡ እምሔውየ ፡ (ሉቃ፪ ፡ ፲፪ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭ ፡፡ ማንዘ ፡፡ ሔኖ፹፫ ፡ ፫) ፡፡

**ስክበት** ፤ መኛት ፤ መተኛት ፤ መጋደም ፤ መኻታ ፤ አተኛኘት ፤ አዘረጋግ ፡ (አርጋ ፡ ፪) ፡፡

**አስከበ** ፤ አተኛ ፡ አስተኛ ፤ አጋደመ ፤ አሰጣ ፡ ዘረጋ ፡፡ አስከቦ ፡ በክብዱ ፡ ባዕለ ፡ ምሥዋዕ ፡፡ አስከቡኪ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡፡ አስከበቶ ፡ ውስተ ፡ ዐራት ፡፡ አስከበቶ ፡ ውስተ ፡ ጎል ፡፡ በአረፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታስክቦ ፡ ለበድን ፡፡ አስከብዎሙ ፡ ለአእሩግ ፡ (ዘፍ፳፪ ፡ ፱ ፡፡ ኢሳ፶፩ ፡ ፳፪ ፡፡ ፩ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫ ፡፡ ሉቃ፪ ፡ ፯ ፡፡ ማንዘ ፡፡ ሰቈ፪ ፡ ፳፩) ፡፡

**መስከቢ** ፤ **መስክብ** ፤ የሚያስተኛ ፡ የሚያጋድም ፤ አስተኚ ፡ አጋዳሚ ፡፡ ማስተኛ ፡ ማጋደሚያ ፤ ምንጣፍ ፡ ዐልጋ ፡ ቦታ ፡፡

**ምስካብ** ፤ (ባት) ፤ መተኛ ፡ መጋደሚያ ፡ ቦታ ፡ ዐልጋ ፡ ምንጣፍ ፡ መቃብር ፤ የመኻታ ፡ ቤት ፡ ጢ ፡ ዚ ፡ ብሎ ፡ ፊጣ ፡ መስሎ ፡ የሚተኙበት ፡ የሚዘረጉበት ፡፡ ሐኖት ፤ ቤተ ፡ ዝሙት ፡፡ ወነበረ ፡ ዲበ ፡ ምስካቢሁ ፡፡ ምስካበ ፡ ኀጺን ፡፡ ወሀብዋ ፡ ምስካባቲሁ ፡ ወዘሎ ፡ ኀዋዮ ፡፡ ህየ ፡ ነጸፍኪ ፡ ምስካበኪ ፡፡ ውስተ ፡ ምስካበ ፡ ቢጽል ፡ ይነውሙ ፡፡ ምስካቢነ ፡ ዘበሕቁ ፡ (ዘፍ፵፯ ፡ ፪ ፡፡ ስንክ ፡ ማን፲፱ ፡፡ ዮዲ፲፫ ፡ ፲፩ ፡፡ ኢሳ፶፯ ፡ ፯ ፡፡ ኢዮ፳፭ ፡ ፲፫ ፡፡ ማሕ፩ ፡ ፲፮) ፡፡

**ሴኬቤቴናሆም** ፤ ያልታወቀ ፡ ጥሬ ፤ ባለቅኔዎች ፤ ሕቅፍ ፡ ደሮ ፤ የደሮ ፡ እመማት ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ፡፡ ሴኬቤቴ ፤ ስክብት ፤ ናሆም ፤ ንዋም ፤ ስክብተ ፡ ንዋም ፡ ማለት ፡ ይመስላል ፤ ፍችውም ፡ እንቅልፍ ፡ ያስተኛቸው ፤ የወሰዳቸው ፡ ያሰኛል ፡፡

**ሰከወ** ፤ (ሱር ፡ ስካእ ፡፡ ዕብ ፡ ሳከሀ) ፤ አየ ፡ ተመለከተ ፤ ዐይኑን ፡ ላከ ፡ አሾለከ ፤ ሰካ ፤ ትክ ፡ አደረገ ፡፡

**መስኮት** ፤ (ብ ፡ መሳክው) ፤ በቁሙ ፡ ክፍት ፤ ታናሽ ፡ ደጅ ፡ አፍ ፤ በግድግዳ ፡ በናስ ፡ በቤት ፡ በቅጥር ፡ ግንብ ፡ የሚሠራ ፤ የብርሃን ፡ የነፋስ ፡ መግቢያ ፤ ያይን ፡ መላኪያ ፡ ማሾለኪያ ፡፡ ዳንኤል ፡ ዘአርኀወ ፡ መስኮተ ፡ ቤቱ ፡፡ ሐወጸ ፡ ንጉሥ ፡ እንተ ፡ መስኮት ፡ ወርእየ ፡ ሰይሥሐቅ ፡፡ ዘይሔውጽ ፡ እንተ ፡ መሳክዊሃ ፡፡ መሳክው ፡ ለብርሃን ፤ መሳክው ፡ ለንጻሬ ፡ (ሃይ ፡ አበ ፡፡ ዳን፮ ፡ ፲ ፡፡ ዘፍ፳፮ ፡ ፰ ፡፡ ሚራ፲፬ ፡ ፳፫ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ፡፡

**አስከወ** ፤ አሳየ ፤ አስመለከተ ፤ ማያ ፡ መመልከቻ ፡ ኾነ ፡፡

**እስከ** ፤ **እስኩ** ፤ ዐቢይና ፡ ንኡስ ፡ አገባብ ፡፡ ፍቻቸውን ፡ በአልፍ ፡ ተራ ፡ ተመልከት ፡፡

**ሰኬዛ** ፤ (ጽር ፡ ስኪዛ) ፤ ፍላጻ ፤ ጕብጭ ፤ ሾል ፡ (፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፳—፳፪ ፤ ፴፮—፴፰) ፡፡

**ሰከሕክሐ** ፤—ዐይነ ፡ ምድር ፤—ከሐክሐ ፡፡

**ሰክይ** ፤ ዮት ፤ (ሰከየ ፡ ይሰኪ ፡ ይስኪ ፡፡ ዐረ ፡ ሸካ ፤ ሸከይ) ፤ መክሰስ ፤ በዳኛ ፡ መያዝ ፤ ማሳጣት ፤ ግፈኛ ፡ ወንጀለኛ ፡ ማድረግ ፡፡ ትሰክዩ ፡ ወትትኀጥቀሁ ፡፡ እመ ፡ ቦ ፡ ዘሰክይዎ ፡ ኀበ ፡ ፈታሒ ፡፡ ከመ ፡ ይስክይዎ ፡ ኀበ ፡ ቄሳር ፡፡ ይስክይዎሙ ፡ ለአርድእት ፡ በዘሐሰዉ ፡ (ኢሳ፶፰ ፡ ፫ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፱ ፡፡ ዮሴፍ ፡፡ ቄር ፡ ጸባ) ፡፡

—፤ መሸሽ ፤ መጠጋት ፤ የሙጥኝ ፡ ማለት ፤ ከገዳም ፡ ከቤተ ፡ ክሲያን ፡ ገብቶ ፡ መማጠን ፡ መደወል ፡ መራመን ፡ መማለል ፤ ለመዳን ፡፡ ይሰኪ ፡ ህየ ፡ ቀታሊ ፡፡ ከመ ፡ ይስኪ ፡ ህየ ፡፡ ሰከይኩ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ፡ ወሰአልክዎ ፡፡ ተወከፍ ፡ ዘሖልነ ፡ ሰክዮተ ፡ ወበቍዔተ ፡፡ ይሰክዩ ፡ ኀቤሁ ፡ (ዘኍ፴፭ ፡ ፲፩ ፡ ፲፭ ፡፡ ጥበ፳ ፡ ፳፩ ፡፡ ሊጦን ፡፡ ቀሌ) ፡፡

**ሰካዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ከይት) ፤ የሚከስ ፤ ከሳሽ ፤ ጠላት ፡ ባለጋራ ፡፡ ሰእመ ፡ ሰከየነ ፡ ሰካዪ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፯ ፡፡ ፍ ፡ ነ ፡ ፳፯ ፡፡ ፵፫ ፡ ፯) ፡፡

**መስክይ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡፡ ዝንቱ ፡ ኅብስት ፡ መስክይ ፡ ወመኰንን ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ፡፡

**አስከየ ፤** አስከሰሰ ፤ አስወቀሠ ፤ ከሳሽ ፡ አስነጣ ።

**እስኪት ፤** አባለ ፡ ዘርዕ ። ፍችውን ፡ በእስከ ፡ ተመልከት ።

**ተሰክየ ፤** ተከሰሰ ፤ ተወቀሠ ፤ በዳኛ ፡ ተያዘ ። ዘባቲ ፡ ንሰኪ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ሰኩይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ኪት ፡ ክይት) ፤** የተከሰሰ ፤ የተማጠነ ፤ የሙጥኝ ፡ ያለ ።

**ሰክየት ፤** መክሰስ ፤ መክሰስ ፤ አከሳሰስ ፤ ክሰሻ ፡ ክስ ፤ ምጥንታ ፤ ጩኸት ። ለእመ ፡ ሰከየ ፡ ስክየተ ፡ ዘጥዩቅ ፡፡ ስክየት ፡ ዲበ ፡ ጸላኢ ፡፡ በቃለ ፡ ስክየትየ ፡ (ፍ ፡ ን ፡ ፺፫ ፡ ፯ ። ቅዳ ፡ ያዕ ። ኪዳ) ።


**ምስካይ ፤ (ያት) ፤** መክሰሻ ፡ መከሰሻ ። መሸሻ ፡ መጠጊያ ፤ መማጠኛ ፤ የሙጥኝ ፡ መባያ ፤ መደወያ ፤ ገዳም ፡ ደብር ። አህጉር ፡ ዘምስካይ ፡፡ ምስካዮሙ ፡ ለግፉዓን ፡፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ለነፍስየ ፡ ደብረ ፡ ምስካያ ፡ (ዘኍ ፴፭ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ። ድጓ ። ደራሲ) ።

**ሳኰዮ ፤ ዮት ፤ (ሳኰየ ፡ ይሳኩ ። ዕብ ፡ ሻጋህ ። ሱር ፡ ሺጋእ) ፤** መሳት ፤ ከመንገድ ፡ መውጣት ፤ መዞር ፡ መባከን ፡ መንከራተት ፤ ከበረሓ ፡ መማባት ፤ መቅበዝበዝ ፤ አስመንገድ ፡ መኼድ ። ሳኰየት ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡፡ እንዘ ፡ የዐይል ፡ ወይሳኩ ፡፡ ወሳኩዩ ፡ ውስተ ፡ ቢድው ፡፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡ ትሳኰዩ ፡፡ ሥልስ ፡ ሳኰየት ፡ ሐመርየ ፡ (ዘፍጽ ፡ ፲፱ ። ፴፯ ፡ ፲፭ ። መዝ ፡ ፶፯ ። ኢሳ ፡ ፷ ፡ ፳፰ ። ፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭) ። ይሰበር ፡ ይትቀጠቀጥ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሳኰየ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ሆሴ ፡ ፰) ።

**ስኰየት ፤** መሳሳት ፤ ከመንገድ ፡ መውጣት ። እስመ ፡ ተዘከሩ ፡ በስኰየተ ፡ ምግባሮሙ ፡ (ጥበ ፲፱ ፡ ፲) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጸሓፊ ፡ ስሕተት ፤ ስክየት ፡ ይላል ። ባለቤቶችም ፡ ማክሰስ ፡ ማማጠን ፡ ብለው ፡ በስከየ ፡ አፈታት ፡ ይፈቱታል ።

**ሰኪል ፤ ሎት ፤ (ሰከለ ፡ ይሰክል ፡ ይስክል ። ተኪል ፡ ተከለ ፤ ሰገለ) ፤** ማበብ ፡ ማፍራት ፤ አበባ ፡ መጣል ፡ ፍሬ ፡ መያዝ ፤ መውለድ ፡ መሸከም ፤ የወይን ፡ የተምር ። ከመ ፡ ዐጸደ ፡ ወይን ፡ ዘሰከለ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**አስካል ፤ (ላት ። ዕብ ፡ ኤሽኮል ። ዐረ ፡ ኢሽካል ። ሱር ፡ እትካላ) ፤** የወይን ፡ ዐጽቅ ፤ ዘላ ፡ ዘለላ ፤ እንደ ፡ ማሽላ ፡ ራስ ፡ ያለው ፡ የሕንባቡ ፡ መውጫ ፡ መወለጃ ፡ ቂንዱ ፡ ቁረቁንዳው ፡ ከፍሬው ፡ ጋራ ፡ (ዘፍ ፵ ፡ ፲—፲፪) ። ጸናሕክዎ ፡ ለወይንየ ፡ ይፍረይ ፡ አስካለ ፡፡ አልቦ ፡ አስካል ፡ በውስተ ፡ ወይን ፡፡ ወደመ ፡ አስካል ፡ ሰትዩ ፡ ወይነ ፡፡ ይቀሥምሙ ፡ እምአሥዋክ ፡ አስካለ ፡፡ አስካለ ፡ በቀልት ፡ (ኢሳ ፭ ፡ ፪ ። ኤር ፰ ፡ ፲፫ ። ዘዳ ፴፪ ፡ ፲፬ ፡ ፴፪ ። ማቴ ፯ ፡ ፲፮ ። ሔኖ ፴፱ ፡ ፬) ። አበባና ፡ ፍሬ ፡ ሳለው ፡ ለዕንቀ·ሳል ፡ ሳይቀር ፡ ለርጉዝና ፡ ለድብድብ ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ። አስካል ፡ ዘጸገየ ፡፡ አስካለ ፡ አእምሮ ፡ እንተ ፡ ታሠርጽ ፡ ጥበበ ፡፡ አንቀቅሖ ፡ አስካለ ፡ ደርሆ ፡ (ማሕ ፡ ፲፱ ። አጥል) ።



አስካል ፡

**ሴክል ፤ (ሮማይ ፤ ሴኩሉም) ፤** የቀመር ፡ ስም ፤ አስካለ ፡ ዘመን ፤ መቶውን ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ መቶ ፡ ቅንጣት ፡ ሰብስቦ ፡ የያዘ ፡ ምእታዊ ፤ በዓለ ፡ ምእት ። በጭር ፡ ቃል ፡ ፻ ፡ ዓመት ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ሴኬሉ ፤ ሴክሉ ፤** የተሳሳተ ፡ ስም ፤ ከሲል ፡ ኪስሌው ፤ ታኅሣሥ ፡ (ሰገ ፲፰ ፡ ፩ ። ስንክ ፡ የካ፳) ።

**ሰኪም ፤ ሞት ፤ (ሰከመ ፡ ይሰክም ፡ ይስክም ። ዕብ ፡ ሻከም ፤ ሀሽኬም) ፤** ጸዊር ፤ መሸከም ፤ በጫንቃ ፡ በትከሻ ፡ ላይ ፡ መያዝ ፤ ማንሣት ። ተሐዝሉ ፡ በገቦክሙ ፡ ወትሰከሙ ፡ በመታክፍቲክሙ ፡፡ ረስዮ ፡ ለከማይድየ ፡ ያድንን ፡ ወይስክም ፡ አርዑተ ፡ ትእዛዝከ ፡ (ሕዝ፴፱ ፡ ፳፩ ። ስንክ ፡ ሠኔ፴) ፡ በሰከመ ፡ ፈንታ ፡ ተሰከመ ፡ ተሰክመ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ተሰከማ ፡ ለይእቲ ፡ ቀሥት ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፲፩ ። መሳ፲፯ ፡ ፫ ። ኢሳ፵፯ ፡ ፯ ። ማራ፯ ፡ ፳፭ ። ፲፫ ፡ ፲)) ።

**አስከመ ፤** አሸከመ ፤ አሲያዘ ፤ ጠመደ ፡ ጫነ ፤ አስደበለለ ፤ አስነገተ ። አስከማ ፡ ለአጋር ፡፡ ነሥአ ፡ ዕፀወ ፡ ወአስከሞ ፡ ለይሥሐቅ ፡፡ ያስክምዎ ፡ ለሰብእ ፡ ዲበ ፡ መትከፍቱ ፡ (ኩፋ ፡ ፲፯ና ፡ ፲፰ ። ማቴ፳፫ ፡ ፬ ። ግብ፲፭ ፡ ፲) ።

**መስከም ፤ ምስካም ፤ (ዕብ ፡ ሼኬም) ፤** መሸከሚያ ፡ መያዣ ፡ ማንሻ ፤ ምቹ ፤ ጫንቃ ፡ ትከሻ ።

**ተሰክመ ፤** ሸከም ፡ ኾነ ፤ በራስ ፡ በጫንቃ ፡ ተያዘ ፤ ታዘለ ፡ ተነገተ ፤ ሸከመ ።

**ሰኩም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ክምት) ፤** የተሸከመ ፤ ተሸካሚ ። ሸክም ፡ የኾነ ፤ የተጫነ ፤ በትከሻ ፡ ላይ ፡ የሚኼድ ፤ ሬሳ ፡ ቀኅበር ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**ስክመት ፤** መሸከም ፤ ማሸከም ፤ አሸካከም ፤ ሸከማ ፤ ተሸካሚነት ።

**ሰክም ፤ (ማት) ፤** ሸክም ፡ ጭነት ፤ ጓዝ ፡ እክት ። ጸረን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ገር ፡ ነው ።

**ሰክም ፤ (ትግሬ ፡ ሸክም) ፤** አገጭ ፤ ሸንጎበት ፤ የጽሕም ፡ በታ ፤ ታችኛው ፡ ከፍል ።

**ሰኪን ፤ ኖት ፤ (ሰከነ ፡ ይሰክን ፡ ይስክን ። ዕብ ፡ ሻከን ። ሱር ፡ ሽኬን ። ዐረ ፡ ሰከነ) ፤**

ማረፍ ፤ በታ ፡ መያዝ ፤ መኖር ፡ መቀመጥ ፤ መሸሬሸት ። በታ ፡ መፈለግ ፡ መለመን ፤ አስጠጉኝ ፡ አሳድሩኝ ፡ ማለት ፤ እንግዳ ፡ ድኻ ፡ ስደተኛ ፡ መኾን ፤ ሲዞሩና ፡ ሲለምኑ ፡ ውሎ ፡ የትም ፡ ከመሸበት ፡ ማደር ። ኀድየን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ምስኪን ፤ (ንት ፡ ናን ፡ ናት ። ዕብ ፡ ሚስኬን ። ሱር ፡ ሜስኪና ። ዐረ ፡ መስኪን) ፤** በቁሙ ፤ ቍርጩ ፡ ድኻ ፤ ጦም ፡ ዐዳሪ ፤ ቤት ፡ ንብረት ፡ ገንዘብ ፡ ርስት ፡ መጠጊያ ፡ የሌለው ፤ ጥገኛ ፡ ለማኝ ። ብፁዕ ፡ ዘይሌቡ ፡ ላዕለ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን ። ግዩር ፡ ወምስኪን ። ጸውዕ ፡ ነዳያነ ፡ ወምስኪናነ ። ዘለምስኪናን ፡ ወለልሕዋን ፡ ይናዝዞሙ ፡ (መዝ ፡ ፵፱ ። ቅዳ ፡ ቄር ። ሉቃ ፲፬ ፡ ፲፫ ። ኪዳ) ።

**መስከነ ፤** ምስኪን ፡ ኾነ ፤ ዓለምን ፡ ገንዘብን ፡ ናቀ ፤ ተወ ። ብፁዕ ፡ ዘመስከነ ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ (ፊእ ፡ ቢኖ) ።

**ምስኪንት ፤** ምስኪንነት ፤ ኀዲት ፤ ምናኔ ። ወምስኪንትየኒ ፡፡ ኖኅሰ ፡ አምሳሊ ፡ ምስኪንት ፡ (ቅዳ ። ፊልክ ፡ ፪፻፷) ።

**ሰከና ፤ ሰኰና ፤ (ብ ፡ ሰኳንው) ፤** በቁሙ ፤ መከየድ ፤ ማማ ፤ ውስጥ ፡ እግር ፤ ከተረከዝ ፡ እስከውራ ፡ ጣት ፡ ያለው ፤ ዝርጉ ፡ ጠፍጣፋው ። ውስጥ ፡ እጅም ፡ ይኾናል ። ሰኰና ፡ እገሪሃ ፡፡ እንሥአ ፡ ሰኰናሁ ፡ ላዕሌየ ፡፡ ዕቀቢ ፡ ሰኰናሆሙ ፡፡ እስመ ፡ ጽንፉ ፡ ሰኰናሁ ፡ ለሰብእ ፡ ወከተማሁ ፡ ለሰብእ ፡ በከመ ፡ ሰኰና ፡ እዴሁ ፡ (፪ነገ ፡ ፱ ፡ ፴፫ ። መዝ ፡ ፺ ። ዘፍጥ ፡ ፲፭ ። ሉቱ ፡ ዕዝ፰ ፡ ፲) ። ለእንስሳት ፡ ሲኾን ፡ ጥፍር ፡ ይባላል ። ሰኰና ፡ አፍራሲሆሙ ፡፡ ሰኰና ፡ እንስሳ ፡፡ ዘንፉቅ ፡ ሰኰናሁ ፡ (ኢሳ፭ ፡ ፳፰ ። ሕዝ፴፪ ፡ ፲፪ ። ዘሌ፲፭ ፡ ፫—፯) ።

**ሰኪኖን ፤ (ጽር ፡ ስኺኖስ) ፤** የዛፍ ፡ ስም ፤ እንደ ፡ ጥድ ፡ መልክም ፡ ሽታ ፡ ያለው ። ታሕተ ፡ ዕፀ ፡ ሰኪኖን ፡፡ መዐዛሁ ፡ ከመ ፡ ዘሰኪኖን ፡ (ዳን፩ ፡ ፶፱ ። ሔኖ፴ ፡ ፪) ።

**ሰኪዕ ፤ ዖት ፤ (ሰከዐ ፡ ይሰክዕ ፡ ይስካዕ ፤ ሰጐዐ ። ሱር ፡ ሻኬይ) ፤** መብሳት ፤ መስከት ፤ መስካት ፤ መደርደር ፤ ማግባት ፡ ማሳለፍ ፤ መቀርቀር ፡ መወተፍ ፤ የፈትል ፡ የመርፌ ፡ የደቃ ፡ የፈርጥ ።

**ተሰከዐ ፤** ተሰካ ፤ ተደረደረ ። ዘተሰክዐ ፡ በፈትለ ፡ ሜላት ፡፡ አስናኒከ ፡ አያተ ፡ አዕናቍ ፡ እለ ፡ ተሰክዓ ፡ (አርጋ ። ደራሲ) ።

**ሰኩዕ ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ክዕት) ፤** የተሰካ ፤ ስካ ፤ ድርድር ። ዕንቍ ፡ ግሉፍ ፡ ወሰኩዕ ፡ (፫ነገ ፡ ፲ ፡ ፰፪) ።

**ሰኰዐ ፤ (መሰከ) ፤** ጓበ ፡ ጐተተ ፤ አወጣ ፡ አገባ ፤ ከሆድ ፡ ከጕድጓድ ። ከካ ፤ አመሰኳ ፡ አመነ(ዘ)ዠኸ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰኰዐ ፡ ፈንታ ፡ እንዳማርኛው ፡ አመሰኰዐ ፡ ተመሰኰዐ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እምዝሉ ፡ እንስሳ ፡ ዘይትመሰኳዕ ፡ ኪያሁ ፡ ብልዑ ፡ (ዘሌ፲፩ ፡ ፫—፯ ። ዘዳ፲፬ ፡ ፮—፰) ። ከዚህስ ፡ ይልቅ ፡ ትግሬው ፡ (ሐባብ) ፡ መሰከዐ ፡ ይላልና ፤ ርሱ ፡ ይሻላል ፤ መሰከን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ሰኳዒ ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት ፤ ዕት) ፤** የሚከካ ፡ የሚያመሰኳ ፤ እንስሳ ፤ አግዝ ፤ ገብረ ፡ ጕንዳን ። ቃሕምን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ሰኳዕት ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ኀይል ፡ (ምሳ፴፬ ፡ ፳፮) ።

**ሰከረ ፤—ተከራየ ፤—ሠከረ ።**

**ሰኪር ፤ ሮት ፤ (ሰከረ ፡ ይሰክር ፡ ይስክር ። ዕብ ፡ ሻካር ። ሱር ፡ ሽካር ። ዐረ ፡ ሰኪረ) ፤** መስከር ፤ መርካት ፡ አብዝቶ ፡ መጠጣት ፤ ከሐዘን ፡ ከቍጣ ፡ ከመጠጥ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ እንቡዝ ፡ ቅብዝብዝ ፡ መኾን ፤ አእምሮ ፡ ማጣት ። ትሰክር ፡ ምድር ፡ እምደም ፤ ኢትስተዩ ፡ ወይነ ፡ ሰሰኪር ፡፡ ኢትስክሩ ፡ ወይነ ፡፡ እስመ ፡ ሰክሩ ፡ ዘእንበለ ፡ ወይን ፡ (ኢሳ፴፬ ፡ ፯ ። ዮሔ፯ ፡ ፬ ። ጦቢ፬ ፡ ፲፭ ። ምሳ፳፫ ፡ ፴፩ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፱) ።

**ሰካሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ክርት) ፤** የሚሰክር ፤ ስካር ፤ መጠጥ ፡ ወዳጅ ። እኩይ ፡ ወይን ፡ ለጸዓሲ ፡ ወለሰካሪ ፡፡ ብእሲት ፡ ሰካሪት ፡፡ ይሰቲ ፡ ምስለ ፡ ሰክርት ፡ (ምሳ፳ ፡ ፩ ። ሢራ፳፮ ፡ ፰ ። ማቴ፳፬ ፡ ፵፱) ። ሰካሪት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ጠባብ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ሰክር ፡ ይላል ። እመሂ ፡ ዘማዊት ፡ ወእመሂ ፡ ሰካር ፡ (ኪዳ) ።

**ስኩር ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ክርት) ፤** የሰከረ ፤ ልቡ ፡ የጠፋ ፤ አብዝቶ ፡ የጠጣ ፡ የጠገበ ። እንዘ ፡ ስኩር ፡ ውእቱ ፡፡ ጽጉባን ፡ ወስኩራን ፡፡ ወአምሰላ ፡ ዔሊ ፡ ከመ ፡ ስክርት ፡፡ ወስክርት ፡ ይእቲ ፡ እምደሞሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ (ሢራ፴፱ ፡ ፴፩ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፩ ። ፩ነገ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ። ራእ፲፯ ፡ ፯) ።

**ስክረት ፤** መስከር ፤ መጠጥ ፡ ማብዛት ፤ ስካር ፤ ሰካርነት ። ስክረት ፡ ይከውን ፡ ምክንያተ ፡ ለመፀት ፡ ወለፍትወት ፡ (ፊልክ ፡ ፸፱ ። ፩ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፫ ። ገላ፭ ፡ ፳፩) ።

**ስካር ፤** በቁሙ ፤ የመጠጥ ፡ ጥጋብ ፤ ናላ ፡ የሚያዞር ፡ ልብ ፡ የሚያጠፋ ፤ ሰውነትን ፡ የሚያዝል ፡ የሚያደክም ፤ የሚያስተኛ ። እለ ፡ ይሰትይዎ ፡ ለወይን ፡ ለስካር ፡፡ ነቂሆ ፡ ኖኅ ፡ እምንዋመ ፡ ስካሩ ፡፡ ብእሲ ፡ ሀካይ ፡ ዘአኅለቀ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ በስካር ፡ ወበዝሙት ፡፡ እመልእሙ ፡ ስካረ ፡ (ዮኤ፩ ፡ ፭ ። ቀሌ ። ዲድ ፡ ፫ ። ፍን ፡ ፶ ። ኤር፲፫ ፡ ፲፫) ።

**ሰክር ፤ (ዕብ ፡ ሼካር) ፤** ዐረቂ ፤ ጠጅ ፤ የሚያሰክር ፡ መጠጥ ። ጕራጌ ፡ ጠላ ፡ ሲል ፡ ሰኽር ፡ እንዲል ።

**አስከረ ፤** አሰከረ ፤ ልብ ፡ አጠፋ ፤ አረካ ፡ አጠገበ ። ስቴ ፡ ዘያሰክር ፡፡ ጽዋዕ ፡ ዘያሰክር ፡፡ ሰተዩ ፡ ደመ ፡ እስከ ፡ ያሰክሮሙ ፡፡ ታሰክራ ፡ ለዝላ ፡ ምድር ፡፡ አሰክሮን ፡ በደሞሙ ፡ ለአሕዛዩ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶ ። ቅዳ ፡ ሕር ። ሕዝ፴፱ ፲፱ ። ኤር፳፰ ፡ ፯ ። ዘዳ፴፪ ፡ ፵፪) ።

**ተሳከረ ፤** (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፤ ተሳሳተ ፤ የተራ ፡ የቍጥር ።

**ሰኰሰ ፤ ሶት ፤** (ሰኰሰ ፡ ይሴኵስ ፡ ይሰኵስ ። ዕብ ፡ ፋግ ፤ ሻሕ) ፤ ማነስ ፡ መጕደል ፤ ጥቂት ፡ መኾን ፤ ወይም ፡ በጭራሽ ፡ መጥፋት ፡ መቅረት ፡ መታጐል ፤ መፍዘዝ ፡ መቀዝቀዝ ። ወይሴኵሱ ፡ ሕቀ ፡ ክመ ፡ ይቅብዑ ፡ ንጉሠ ። ይሴኵስ ፡ ፍቅር ፡ እምእኑው ፡ (ሆሴ፭ ፡ ፲ ። ቀሌ ። ማቴ፳፬ ፡ ፲፪ ። ዲድ ፡ ፴፫) ።

**ሰኵት ፤** (ብ ፡ እስኳት) ፤ ሱቅ ፡ አደባባይ ፤ መተባበሪያ ። ጕግ ፡ ጕጕግ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ጕጕን ፡ ተመልክት ። እመ ፡ ሀሎ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ ቢጹ ፡ ሰኵት ፡ ወመርሕብ ። ሑር ፡ ሰኵት ፡ እንተ ፡ ይብልዋ ፡ ርትዕት ። በውስተ ፡ አስኳቲሃ ። አስኳተ ፡ ሀገር ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ። ግብ፲፱ ፡ ፲ ። ኢሳ፲፭ ፡ ፫ ። ሉቃ፲፬ ፡ ፳፩ ። ማቴ፳ ፡ ፪) ።

**ሰኪት ፤ ቶት ፤** (ሰከተ ፡ ይሰክት ፡ ይስክት ። ሱር ፡ ሽካት) ፤ መስፈር ፡ ሰፈር ፡ ማድረግ ፤ ብቻ ፡ መያዝ ፤ ማደር ፡ ማረፍ ።

**ሰክተተ ፤** ጕለተ ፡ ጣደ ፤ ተከለ ፡ ሰካ ፡ አዋደደ ፤ አሰረረ ፤ የድብት ፡ የምጣድ ፡ የዕምድ ። ሰክትት ፡ ጽሀርት ፡ (ሕዝ፳፱ ፡ ፩) ።

**ተሰክተተ ፤** ተጣደ ፤ ተዋደደ ፤ ተተከለ ።

**ስክቱት ፤** የተጕለተ ፤ የተጣደ ፤ ጕልት ።

**ስክትት ፤** (ቶት) ፤ ምዕማድ ፤ የዐምድ ፡ እግር ፤ ጕልቻ ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፲፱--፳፩) ። በዕብራይስጥ ፡ ግን ፡ (ዘፀ፴፯ ፡ ፳፱—፳፯) ።

**ሰክተየ ፤** (ይሰክቲ ፡ ይሰክቲ ። ከሰከተና ፡ ከሰከየ ፡ ከኹለቱ ፡ የተደቀለ) ፤ አባደመ ፡ ኄራ ፡ አስቈረጠ ፤ አማማለ ።

**ተሰክተየ ፤** (ይሰክተይ) ፤ ተሰማማ ፡ ተባበረ ፤ ተማማለ ፡ ኄራ ፡ ቈረጠ ፤ አሜረ ፡ ክፉ ፡ መከረ ፤ ዱለቱን ፡ ሤራውን ፡ በመሐላ ፡ አሰረ ። ተሰካተዩ ፡ በማዕሌቶሙ ፤ ወተሰካተዩ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ እምድኅሬሁ ፡ (መቃ ፡ ገ፲፬ ። መዝ ፡ ፹፪ ። ግብ፳፫ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬) ።

**ሰሊብ ፤ ቦት ፤** (ሰለበ ፡ ይሰልብ ፡ ይስልብ ። ዐረ ፡ ሰለበ ። ዕብ ፡ ሻላፍ ። ሱር ፡ ሽላፍ) ፤ መስለብ ፡ መቍረጥ ፤ የሥጋ ። ሰለባ ፡ እንዲሉ ፤ ዐለገን ፡ ተመልከት ። መግፈፍ ፡ ማውለቅ ፡ ማውጣት ፤ የልብስ ፡ የቈርበት ። መገፈፍ ፡ መቀማት ፤ መማረክ ፡ መንጠቅ ፤ የገንዘብ ፡ የልብ ። እሰልባ ፡ አልባሲሃ ፡ ወመዋጥሒሃ ። ይሰልቡ ፡ አልባሰ ፡ ዐስቀሙ ። ሰለብዎ ፡ አልባሲሁ ፤ ገፈፈ ፡ (ሆሴ፪ ፡ ፲፭ ። ሕዝ፳፮ ፡ ፲፯ ። ማቴ፳፯ ፡ ፴፩) ። አዕኑግ ፡ ዘሰለቡ ። ይሰልቦ ፡ ንዋዮ ፡ ሐቅሉ ። ሰለቦ ፡ ረምሐ ፡ እዴሁ ። ሰለብዎ ፡ ኩናቶ ። ተሀይድ ፡ አዕይንተ ፡ ወትሰልብ ፡ ልበ ፡ (መሳ፰ ፡ ፳፩ ። ሉቃ፲፩ ፡ ፳፪ ። ፩ዜና ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ። ሚክ፪ ፡ ፰ ። ክብ ፡ ነገ) ።

**ሰላቢ ፤** (ቢት ፡ ብያን ፡ ያት ፤ ለብት) ፤ በቁሙ ፤ የሚሰልብ ፤ የሚገፍ ፤ ሌባ ፡ ቀማሪ ፤ ቀማኛ ።

**ሰለባ ፤** በቁሙ ፤ የግዳይ ፡ ምልክት ፤ የቀማኛ ፡ የዘረፋ ፡ ገንዘብ ፤ ምርኮ ።

**ተሰልበ ፤** ተሰለበ ፤ ተገፈፈ ፤ ተቀማ ፤ ተማረከ ። ወኢንፈቅድ ፡ ንሰለብ ፡ ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ንልበስ ። ተሰልበ ፡ መንግሥቱ ። ተሰልበ ፡ ልብ ። ሰትየት ፡ ወይነ ፡ ወሶበ ፡ ተሰልበ ፡ ልባ ፡ እምስካረ ፡ ወይን ፡ (፪ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፬ ። ቂስጠ ። ገድ ፡ አዳ ። ስንክ ፡ ሠኔ፱) ።

**ስሉብ ፤** (ባን ፡ ባት ፡ ልብት) ፤ የተሰለበ ፤ የተገፈፈ ፤ ጕማዳ ፤ ስልብ ፤ ጃን ፡ ደረብ ።

**ስልበት ፤** መስለብ ፤ መሰለብ ፤ አሰባሰብ ፤ ስልበሽ ፤ ገፈፋ ፡ ቈረጣ ፡ ማዝረት ። ስልበተ ፡ ነፍስተ ፡ ሥጋ ፡ (ቆላ፪ ፡ ፲፩) ።

**ሰሊብ ፤** (ዐረ ፡ ጸሊብ ። ሱር ፡ ጽሊባ) ፤ ጸልበ ፤ መስቀል ። ጸለበን ፡ ተመልከት ።

**ሰልቢባ ፤** ክፉ ፡ የባሕር ፡ ነፋስ ፤ አውራቂስ ፤ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ የሚያስነሣ ። ወይእቲ ፡ ነፋስ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ሰልቢባ ፡ (ግብ፳፯ ፡ ፲፬) ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ልክስክስ ፡ ይሉታል ።

**ሰለደ ፤** (ሰሊድ ። ዕብ ፡ ሳላድ) ፤ የኋሊት ፡ ዘለለ ፤ ወደ ፡ ኋላ ፡ ኼደ ፡ አፈገፈገ ። በገርባው ፡ ወደቀ ፡ ተንጋለለ ፡ ተዘረጋ ። ኹልዱ ፡ ማለት ፡ ከሰለደ ፡ ወጥቷል ።

**ሰሌዳ ፤** (ጽር ፡ ሴሊዳ) ፤ ሉሕ ፡ ሰውሕ ፤ ጽሌ ፡ ገበታ ፤ ገበርግ ፡ ጠፍጣፋ ፤ ብራና ፡ ወረቀት ፤ ጠርብ ፡ ሳንቃ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ሰለተንና ፡ ሰፌደን ፡ ሎሐን ፡ እዩ ፤ የሰሊድ ፡ ጎር ፡ ናቸው ። ሰሌዳ ፡ ሥዕል ። ሰሌዳ ፡ እብን ። ሶበ ፡ አንበበ ፡ ሠለስተ ፡ ሰሌዳ ። ፍሉግ ፡ ይኩን ፡ ሰሌዳሁ ። ሰሌዳ ፡ መጽሐፍ ። ሰሌዳ ፡ በረድ ፡ ጸፍጸፈ ፡ ዐውዱ ፡ (ስንክ ፡ መስ፲ ። ኤር፲፯ ፡ ፩ ። ዓም ፡ ፳፫ ። ዘፀ፳፯ ፡ ፳ ። አዋል ። ቅዳ ፡ ኤጲ) ። ቀለም ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሰሌዳ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወቀብዎ ፡ በሰሌዳ ፡ (ኤር፳፪ ፡ ፲፬) ።

**ሰሌዳ ፤** (ዕብ ፡ ሺሌድ ፡ ሺሌዳ) ፤ ንድፍ ፡ ቢጋር ፤ ዐጥንትና ፡ ቈርበት ፤ ቅርጽ ፡ ቁመና ፡ ጭገራት ፡ ምልክት ።

**ሰሌዳት ፤ ሰላድው ፤** ስሌዶች ፤ ሰሌዳዎች ። ሰሌዳተ ፡ እብን ፡ ዘሕግ ። ሰሌዳተ ፡ ኅጺን ። ሰላድወ ፡ ዕፀ ፡ (አርጋ ። ስንክ ፡ ሐም፳ ። ግብጽ፫ ፡ ፵፬) ።

**ሰሊሖም ፤** (ጽር ፡ ሲሎአም ። ዐረ ፡ ሲሉዋም ። ዕብ ፡ ሺሎዋሕ) ፤ ፍንው ፤ ፈሳሽ ፡ ወራጅ ፤ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ኻያጅ ፤ መስኖ ። ምጥማቃተ ፡ ሰሊሖም ፡ (ዮሐ፱ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ። ሉቃ፲፫ ፡ ፬) ።

**ሰሊኖት ፤** (ዐረ ፡ ሰሊኅት ። ዕብ ፡ ቅጺዖት ። ጽር ፡ ከሲያ) ፤ ጥሩ ፡ ሽቱ ፤ የሽቱ ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፤ ቀረፋ ፡ (መዝ ፡ ፵፬ ። ሕዝ፳፯ ፡ ፲፱) ። በጎዘዝ ፡ ፈንታ ፡ ክበዝ ፡ እንዲል ፡ በሰሊኖት ፡ ፈንታ ፡ ሰሊክ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡

ክሩቅ ፡ የሚሸት ፡ እያሱ ፡ በስልክ ፡ ዘይቤ ፡ ይፈቱታል ። ኀነተ ፡ ሜዓ ፡ ወሰሊክ ። ከርቤ ፡ ወሜዓ ፡ ወሰሊክ ፡ (ስ ንክ ፡ ጥቅ፳፭ ። ገድ ፡ አዳ ። አንቀ ፡ ብር) ።

**ሰለጠ ፤—ሠለጠነ ፤—ሠሊጥ ፡ ሠለጠ ።**

**ሰልጠ ፤ ጠት ፤ (ሰለጠ ፡ ይሴልጥ ፡ ይሰልጥ ፤ ፈጸመ ። ዕብ ፡ ሻሌም) ፤** መጨረስ ፤ መፈጸም ፤ መምሳት ፤ ፍጹም ፡ ትክክል ፡ ማድረግ ፤ ሕጸጽን ፡ ማጥፋት ፤ የሥራ ፡ የነገር ። ዕዳን ፡ ብድርን ፡ ጨርሶ ፡ መክፈል ፡ መስጠት ። ዋጋን ፡ ገንዘብን ፡ ጨርሶ ፡ ማግኘት ፡ መቀበል ፡ መውሰድ ፤ ጥቂት ፡ ሳይቀር ። ሰሊጦሙ ፡ ግብሮሙ ። ሰፈራ ፡ ለመንግሥትከ ፡ ወሰለጣ ። እሴልጥ ፡ መዐትየ ፡ ላዕሌሆሙ ። ሰለጠ ፡ መዊተ ፤ ጨረሰ ፡ (ሉቃ ፲፪ ፡ ፶፫ ። ዳን ፭ ፡ ፳፯ ። ሕዝ ፭ ፡ ፲፫ ። ዮሐ ፲፱ ፡ ፴፱) ። ሰልጥ ፡ ዘትፈዲ ። ሰለጠኒ ፡ ዘሎ ፡ ውስተ ፡ ሕፅንየ ፤ ከፈለ ፡ (ማቴ ፲፰ ፡ ፳፭ ፡ ፴፬ ። ኢዮ ፲፱ ፡ ፳፯ ። ሉቃ ፲፪ ፡ ፶፰ ፡ ፶፱) ። ሰለጡ ፡ ዐስቦሙ ። ሰለጡ ፡ መክፈልቶሙ ፤ አገኙ ፡ (ማቴ ፮ ፡ ፲፮ ። ሉቃ ፮ ፡ ፳፬ ። ዘኍ ፴፬ ፡ ፲፭) ። መሰለጥ ፤ ሰላጣ ፡ ማብጀት ፤ ሽልጦ ፡ መጋገር ።

**ሰላጢ ፤ መሰልጥ ፤** የሚጨርስ ፤ የሚፈጽም ፤ ፈጻሚ ። ቃለ ፡ ነገር ፡ መሰልጥ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፳፭) ።

**አሰለጠ ፤** አስፈጸመ ፤ አስጨረሰ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰለጠ ፡ ፈንታ ፡ አሰለጠ ፡ አሰለጠ ፡ ይላል ፤ ያድራጊውን ፡ ባለደራጊ ። መብልዐ ፡ ኢያሰልጠነ ። ወኢያስለጠት ፡ ምንተኒ ፡ ዕሪት ። እስመ ፡ ጸሎተ ፡ ጻድቅ ፡ ትክል ፡ ወታሰልጥ ። መሀሮ ፡ ለወልድከ ፡ ወያሰልጠከ ። ምንት ፡ ያሰልጥ ፡ ይምየ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፰ ። ዕብ ፯ ፡ ፲፱ ። ያዕ ፭ ፡ ፲፮ ። ሲራ ፴ ፡ ፲፫ ። መዝ ፡ ፳፱) ።

**ተሰለጠ ፤ ተሰልጠ ፤** ተፈጸመ ፤ ተጨረሰ ፤ መላ ፡ ልክ ፡ ኾነ ። በዘይሴለጥ ፡ ሙስናሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ። ከመ ፡ ትሰለጥ ፡ ኀጢአት ። ከመ ፡ ኢይሰለጡ ፡ ዘእንበሌነ ። ዮም ፡ በጽሐ ፡ ወተሰልጠ ፡ ውስተ ፡ እዝኒክሙ ፤ (ዳን ፱ ፡ ፪ ። ፳፬ ። ዕብ ፲፩ ፡ ፵ ። ሉቃ ፬ ፡ ፳፩) ።

**ስሉጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ልጥ) ፤** የተጨረሰ ፤ ምሉእ ፡ ፍጹም ። ዓመተ ፡ ስሉጠ ፡ ስሳ ፡ ወሰቡዐ ፡ (ስ ንክ ፡ ጥር፳) ።

**ስላጤ ፤** መጨረስ ፤ ጭረሳ ፡ ጭራሽ ። ፍጻሜ ፤ ፍጹምነት ፤ ልመና ፡ ጸሎት ፤ ትርፍ ፡ ጥቅም ። ከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ስላጤከ ። ተወክፈ ፡ ሰኪሙ ፡ ስላጤክሙ ። ወተወከፍክ ፡ ስላጤሆሙ ፡ ከመ ፡ ተዐስዮሙ ፡ ዐስበ ፡ ጽድቆሙ ። ምንትኑ ፡ ስላጤሃ ፡ ለግዝረት ፡ (፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፭ ። ፪ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፲፯ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ሮሜ ፫ ፡ ፩) ።

**ሰሊጥ ፤ (ዐረ ፡ ሰሊጥ) ፤** ዘይት ፤ ቅባኑግ ፤ የዕንጨት ፡ ቅባት ። ይሴስይዎ ፡ ስንዳሴ ፡ ብሱለ ፡ ዘቱሱሕ ፡ በማይ ፡ ወበቅብዕ ፡ ወሰሊጥ ፡ ወመዓር ፡ ዘንህብ ፤ ያሰትይዎ ፡ ሜሰ ፡ ወሰሊጠ ። ሱብዐቱ ፡ ልጥረ ፡ ቅብዕ ፡ ዘሰሊጥ ፡ (ስንክ ፡ ጥር፲፯ ። ሐም፳) ።

**ሰሊጥ ፤ (ዐረ ፡ ሱምሱም ። ዕብ ፡ ሹምሹም) ፤** በቁሙ ፤ የእዝርዕት ፡ ወገን ፤ ፍሬው ፡ ታናናሽ ፤ ተልባ ፡ የሚያክክል ፤ ዘይታም ፤ ቅባታም ፤ ቅባኑግ ፡ የሚኾን ፤ ጥፍጥ ። ወፈነወ ፡ ዳራ ፡ ለእስክንድር ፡ ዘዐሶ ፡ ወሰሊጠ ፡ ወበልዓ ፡ እስክንድር ፡ ሰሰሊጥ ፤ ወይቤ ፡ በላዕክዋ ፡ ለሰሊጥ ፡ ጥዕምት ፡ ይእቲ ፤ ከመ ፡ ዝ ፡ እበልዖሙ ፡ ለሰራዊትከ ፡ (ዜና ፡ እስ) ።

**ሰሊክ ፤—ሽቱ ፤—ሰሊኖት ።**

**ስልክ ፤ (ዐረብ) ፤** በቁሙ ፤ ሽቦ ።

**ሰልክ ፤ ሰለክ ፤** በቁሙ ፤ ኬደ ፡ ሾለክ ፤ ሹልክ ፡ አለ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሰሊል ፤ ሎት ፤ (ሰለ ፤ ሰለለ ፡ ይሰልል ፡ ይስልል ። ዕብ ፡ ሻላል ፤ ሳላል) ፤** መስለል ፤ መሰለል ፤ ሰለል ፡ ማለት ። መሰላልና ፡ ስንሰለ ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ነው ። መሸለል ፡ ሽለላ ፡ ማድረግ ፤ የስፌት ፡ የቅርርት ። መምሳት ፡ ማስተካከል ፤ ለጥ ፡ ቀጥ ፡ ማድረግ ።

**ሰልላ ፤ (ዕብ) ፤** ዐፈር ፡ ኵረት ፡ ደንጊያ ፤ የሕንጻ ፡ የድልድል ፡ ማስተካከያ ። ወከዐው ፡ ላዕሌሃ ፡ ሰልላ ፡ (ሕዝ ፬ ፡ ፪ ። ፳፮ ፡ ፳፯) ። ሶልላ ፡ ባለው ፡ መሬድ ፡ ይላል ፤ የመላሽና ፡ የጣራ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ ግን ፡ መሬት ፡ ይላል ።

**ሰሊም ፤ ሞት ፤ (ሰለመ ፡ ይሰልም ፡ ይስልም ። ሱር ፡ ሽሌም ። ዕብ ፡ ሻላም ። ዐረ ፡ ሰሊመ) ፤** መሰለም ፤ ሰላምታ ፡ መስጠት ፤ በእጅና ፡ ባንገት ፡ በቃል ፤ ሰላም ፡ ለከ ፤ በሐ ፤ ሐዊላ ፤ እንዴት ፡ ዋልክ ፡ እንዴት ፡ ዐደርክ ፡ ጤና ፡ ይስጥኽ ፡ ማለት ፡ ዕርቅ ፡ ፍቅር ፡ ማድረግ ። መሸለም ፡ ማስጌጥ ፡ ማንቈጥቈጥ ። መሰለም ፤ እስላም ፡ መኾን ፤ የሙሐመድን ፡ ሕግ ፡ መቀበል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰለመ ፡ ፈንታ ፡ እንዳማርኛው ፡ አሰለመ ፡ ይላል ። እመ ፡ ቦ ፡ ዘአሰለመ ፡ በፈቃዱ ፡ ቀዋናሁ ፡ ሦለስቱ ፡ ዓመት ፡ (ቄድር) ።

**አስለመ ፤** (ጥ ፡ ሰለ) አሰለመ ፤ እስላም ፡ አደረገ ፤ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ። (ግጥም ፡ በራስ ፡ ዐሊ ፡ ጊዜ) ፤ የበጌምድር ፡ ደቂት ፡ ክፉ ፡ ነው ፡ ቢያ ፡ ሽርን ክት ፤ እኛስ ፡ አሰልመን ፡ በላነው ፡ ይብላኝ ፡ ለቀረ ፡ ሰው ።

**እስላም ፤ (ዐረ ፡ ኢስላም) ፤** በቁሙ ፤ የሙሐመድ ፡ ወገን ፤ በቍርአን ፡ በፉርቃን ፡ የሚያምን ። ሃይማኖተ ፡ እስላም ። አመ ፡ ነግሡ ፡ እስላም ፡ (አቡሻ ፡ ፺ ። ስንክ ፡ ታኅ፳፫) ። ጎንደሬን ፡ እይ ። (ግጥም ፤ በጋሎች ፡ ዘመን ፡ ከጋሎች ፡ መጋባት ፡ የፈለገ ፡ ዐምሐራ) ፤ ፍየሎቹን ፡ እላንት ፡ ከተከፈላችኹ ፤ ይችንስ ፡ ሳም ፡ ለኔ ፡ ስጡኝ ፡ እባካችኹ ።

**መስልም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት ። ዐረ ፡ ሙስሊም) ፤** ያሰለመ ፤ እስላም ። ንስሮ ፡ ከነ ፡ መስልመ ። መስልማን ፡ (ታምረ ፡ ማር ። አዋል) ።

**መስልማዊ ፤ (ዊት) ፤** የእስላም ፤ እስላም ፡ የኾነ ፤ ያሰለመ ። መስልማዊት ፡ (ቄድር) ።

**ተሳለመ ፤** ተሰላለመ ፤ ተገናኘ ፤ ተሳሳመ ፤ ሰላም ፡ ሰላም ፡ ተባባለ ፤ ተፋቀረ ፡ አንድ ፡ ኾነ ። እምድ

ኅረ ፡ ተሠይመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይሳለምዎ ፡ ኵሉ ፡ ሰለ ፡ አሐዱ ። በተሳልሞ ፡ ዚአሁ ። በላ ፡ በልዋ ፡ ተሳለ ምዋ ። ተካየዱ ፡ ለተሳልሞ ፡ ወለተራድኦ ፤ (ሲኖዶ ። ቀሌ ። ኪዳ ። ድጓ ። ዮሴፍ) ።

**ሱላሚ** ፤ መሳለም ፤ ሰላምታ ፤ ፍቅር ፡ ጥዒና ። መዋዕለ ፡ ፍሥሓ ፡ ወሱላሜ ፤ (ስንክ ፡ ንሐ፲፪) ።

**ሰላም** ፤ (**ሱር ፡ ሽላም ። ዕብ ፡ ሻሎም ። ዐረ ፡ ሰላም**) ፤ በቁሙ ፤ ፍጹም ፡ ጤና ፡ ዕረፍት ፤ ዕርቅ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፤ ደኅንነት ፤ ተድላ ፡ ደስታ ፤ ሰላምታ ፤ የቡራኬ ፡ የምርቃት ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ሲገናኝ ፡ ሲለያይ ፡ የሚ ለው ፡ የሚናገረው ፤ ወይም ፡ የሚጥፈው ። በሰላም ፡ የሐውር ፡ ወበሰላም ፡ ይትመየጥ ። ብዙኀ ፡ ሰላመ ፡ አድማዕነ ፡ በመዋዕሊከ ። ብፁዓን ፡ ገባርያነ ፡ ሰላም ። ሰላም ፡ በዲበ ፡ ሰላም ። ከመ ፡ ያእምር ፡ ሰላሞሙ ። ሰላሞሙ ፡ ለዐማፅያን ። ያቅርቡ ፡ ሎቱ ፡ ሰላመ ። ሰላመ ፡ ገብርኤል ፤ (ኩፋ ፡ ፳፯ ። ማብ፳፱ ፡ ፫ ። ማቴ፳ ፡ ፱ ። ኢሳ፶፯ ፡ ፲፱ ። ኩፋ ፡ ፴፱ ። መገ ፡ ፫፻፱ ። ኪዳ) ።

**ሰላማዊ** ፤ ፍቅረኛ ፤ ሰላምተኛ ፡ ባለሰላምታ ፤ የሰላም ። እንዘ ፡ ሰላማዊ ፡ አነ ። ትኩን ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሰላማዊተ ፤ (መገ ፡ ፻፲፱ ። ኪዳ) ።

**አስተሳለመ** ፤ አስታረቀ ፤ አስማማ ፤ አፋቀረ ፤ አንድ ፡ አደረገ ፤ አሳለመ ፤ አገናኘ ። ለመስተፃርራን ፡ አስተሳልሞሙ ። አስተሳለመ ፡ በመስቀሉ ፡ ዘበሰ ማይ ፡ ወዘበምድር ። ፈቀደ ፡ እስክንድር ፡ ያስተ ሳልሞሙ ። ታስተሳልም ፡ ለቢድን ፡ ኀበ ፡ ታቦት ፤ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፫ ፡ ፰ ። ቄር ። ዮሴፍ ። ግንዘ) ።


**መስተሳልም** ፤ የሚያፋቅር ፤ የሚያስታርቅ ፤ አስማሚ ፤ አሳላሚ ። ዐራቄ ፡ ኵሉ ፡ ወመስተሳልመ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፤ (ስንክ ፡ ኅዳ፳፯) ።

**ሰላማ** ፤ መታረቂያና ፡ ማስታረቂያ ፡ ቦታ ፡ ም ሥዋዕ ፤ የዕርቅና ፡ የፍቅር ፡ ምልክት ፡ የወንጌል ፡ ዐላማ ፡ መስቀል ፡ ያለበት ፤ ወይም ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ መስቀል ። በሰ ላማ ፡ ወበክቡር ፡ ደም ፡ እንተ ፡ በክርስቶስ ፡ ተገ ብረ ፤ (ቅዳ ፡ ሐዋ ። ቆላ፩ ፡ ፳) ።

**ሰላማ ፤ ሳሌም** ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ሰላማዊ ፡ ፍ ጹም ፤ ብእሴ ፡ ሰላም ። ሐተታውን ፡ በአስማት ፡ ተራ ፡ ተመልከት ።

**ሱላማጢስ** ፤ (**ዕብ ፡ ሹላሚት**) ፤ ፍጽ ምት ፤ ፍጽምተ ፡ ሥን ፤ ፍጽምተ ፡ አሚን ። ባለብሎዮች ፡ ግን ፡ ሰላማዊት ፡ ወሃቢተ ፡ ሰላም ፡ ይሉታል ፤ (ማሕ፮ ፡ ፲፫) ። ኹለተኛም ፡ በሱላሚት ፡ ፈንታ ፡ ሱላማጢስ ፡ እ ንደ ፡ ማለት ፡ ሰላመ ፡ ሰጣዊት ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ።

**ሲላን** ፤ (**ዐረ ፡ ሺላን ። ጽር ፡ ሴሊኖን**) ፤ እንስላል ፤ ፍሬው ፡ የከሙን ፡ ዐይነት ፤ ከዐረቂ ፡ ቅመም ፡ የሚገባ ። ርሔ ፡ ፊሓን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሲላን ፡ ይላል ፤ (ማቴ፳፮ ፡ ፯) ።



ሲላን ፡

**ሰለፈ** ፤ (**ዕብ ፡ ሻላፍ ፤ መልኅ**) ፤ በቁሙ ፤ ሰሰፈ ፡ ተሰለፈ ፤ ተፀረረ ፡ ተዘጋጀ ፤ ፊት ፡ ሰፊት ፡ ቆመ ፤ መዘዘ ፡ ነቀለ ፤ ሰይፉን ፡ ጐራዴውን ።

**ሰልፍ** ፤ (**ቀትል**) ፤ በቁሙ ፤ ውጊት ፡ ጦርነት ፤ ሰይፍ ፡ መማዘዝ ፤ መተራረድና ፡ መቀራደድ ፤ መዋጋት ፡ መዘራከት ፤ መታኰስ ፡ መጣበስ ። ወተጻብእዎ ፡ በጽ ኑዕ ፡ ሰልፍ ፤ (ሥር ፡ አኰ ፤ ታሪ ፡ ነገ) ።

**ሰለቀ ፤—አፈዘ ፡ ዘበተ ፤—ሠለቀ ፤ ተ ሣለቀ** ።

**ሰልሰለ ፤—አያያዘ ፤—ሰንሰለ ። ሰሊል ፡ ሰለ** ።

**ሰልዖ ፤ ዖት ፤ (ሰለተ ፡ ይሴልት ፡ ይሰ ልት ። ዕብ ፡ ሳሌት**) ፤ መንፋት ፤ በመንፊት ፡ መለ የት ፤ የሐሪጽ ። መጥረብ ፡ መሸለት ፤ መፍለጥ ፡ መሠን ጠቅ ፡ መሰባበር ፡ ማድቀቅ ፤ የዕፅ ። በቁሙ ፤ መሰለት ፡ መክደን ፡ ማልበስ ፤ የቤት ፡ የጣራ ። መድረቅ ፡ መቅጠን ፡ ማነስ ፡ መኰሰስ ፤ ወሰሰ ፡ መኾን ፤ የስብል ፡ ያገዘመራ ። መዘበት ፡ ማላገጥ ፡ መሣቅ ፡ መሣለቅ ፤ ማፌዝ ፡ መሳጥ ። መሰልቸት ፤ ሰልቹ ፡ መኾን ፤ ሰልቻ ፡ ማውጣት ።

**ሰላቲ** ፤ (**ቲት ፡ ትያን ፡ ያት**) ፤ የሚነፋ ፤ የ ሚሸልት ፤ ሰላች ፤ አላጋጭ ።

**ስላት** ፤ ዘበት ፤ ለግጥ ፤ ሣቅ ፡ ሥላቅ ፤ ምክን ያት ፡ ትፍሥሕት ። ከመ ፡ ኢትረሲክ ፡ ስላተ ፡ ጸላኢከ ። ኢይክውን ፡ ስላተ ፡ ጸላኢየ ፤ (ሚራ፴፱ ፡ ፲፩ ። ሚክ፯ ፡ ፰ ። መገ ፡ ፳፱ ፡ ፴፯) ። ስላች ፤ ቀጭን ፡ መንገድ ፤ ሥ ርጥ ፡ ማቋረጫ ፤ ለነገርም ፡ ይኾናል ።

**ስልት** ፤ በቁሙ ፤ የነገር ፡ የምስጢር ፡ አካኼድ ፤ ስላቹ ፡ ጐዳናው ፤ ረድፉና ፡ ተራው ፤ ልኩና ፡ መልኩ ፤ ንባቡ ፡ ሐሳቡ ፤ አጣጣፉ ፡ አነጋገሩ ። **ዘጸሐፈ ፡ በክል ኤቱ ፡ ስልት** ፤ (አዋል) ።

**ሰም ፤—በቁሙ ፤—ሰምይ ፡ ሰመየ** ።

**ሴመ ፤—ሸመ ፤—ሠዪም ፡ ሢመ** ።

**ሰምአ ፤—ሰማ ፤ መሰከረ ፤—ሰሚዕ ፡ ሰ ምዐ** ።

**ስማዝ** ፤ ሽንበቆ ፤ የጕሽ ፡ መቃ ፡ ቀለም ፤ በወ ንዝ ፡ ዳር ፡ በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ የሚበቅል ። ስማዝ ፡ ወብ ርዕ ፤ (ኢዮ፵ ፡ ፲፯) ።

**ስማኅ** ፤ (**ዕብ ፡ ሱማቅ**) ፤ ጣፊያ ፤ የጥቍር ፡ ቀይ ፤ ደባባ ። ስማኅ ፡ ብሂል ፡ ጣፍያ ፤ (ጥሬ ፡ ሰዋ) ።

**ሳሜጓ** ፤ (ዕብ ፡ ሳሜኽ) ፤ የፊደል ፡ ስም ፤ ሳምኬት ፡ ሰ ፡ (ሰቈ፩ ፡ ፲፭) ።

**ስመጥ** ፤ ዠርባ ፤ ሽንጥ ፤ የዠርባ ፡ ወንገነ ፤ ው ርጓዳው ፡ ጐድጓዳው ፤ ከማኽርፈት ፡ እስከ ፡ መንበርት ፡ ያለው ። ሐቌሁ ፡ ምስለ ፡ ስመጢሁ ፡ (ዘሌ፫ ፡ ፱) ።

**ሰምይ** ፤ ዮ·ት ፤ (ሰመየ ፡ ይሰሚ ፡ ይ ስሚ ። ዐረ ፡ ሰመ) ፤ መሰየም ፤ ስም ፡ መስጠት ፤ ስም ፡ ማውጣት ፤ በስም ፡ መጥራት ፤ እንግሌ ፡ ማለት ። ጸ ውዐን ፡ ተመልክት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ሰመያ ፡ በስመ ፡ ወልዱ ። ሰምዮ ፡ ስሞ ፡ ኢይዝራኤል ። ዘእንበለ ፡ ያእምር ፡ ሕፃን ፡ ሰምየ ፡ አቡሁ ፡ ወእሙ ። ኢይ ሰሚ ፡ እንከ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ። ኢትስምያኒ ፡ ኖሔሚን ፡ (ዘፍ፥፴ ፡ ፲፮ ። ሆሴ፩ ፡ ፬ ። ኢሳ፯ ፡ ፬ ። ኤ ር፵ ፡ ፲ ። ሩት፩ ፡ ፳) ።

—፤ መሰመይ ፤ ሰማይ ፡ ማድረግ ፤ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ማ ራቅ ፡ ማምጠቅ ። ሰመያ ፡ ለገነት ፡ ሰማየ ፡ በልዕል ናሃ ፡ (ፊልክ ፡ ፳) ።

**ሰማዩ** ፤ (ዩ·ት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ መይት) ፤ የሚሰይም ፡ ሰያሚ ፤ ስም ፡ አውጭ ፤ ሰመኛ ።

**አስመየ** ፤ አሰየመ ፤ ስም ፡ አስጠራ ፤ እንግሌ ፡ አ ሰኘ ፤ የክፉ ፡ የበጎ ። ዕደው ፡ እለ ፡ አስመዩ ፡ በኀይ ሎሙ ፡ (ሚራ፴፱ ፡ ፪ ። ዓ፬ ፡ ፫ ። ሕዝ፳፫ ፡ ፳፫) ።

**ተሰምየ** ፤ ተሰየመ ፤ ስም ፡ ተቀበለ ፤ ተጠራ ፡ ስሙ ፡ ተነግ ፡ ተወግ ፡ እንግሌ ፡ ተባለ ፤ ስመ ፡ ጥር ፡ ኾነ ። አሕዛብ ፡ እለ ፡ ተሰምዩ ፡ በስምከ ። ተሰምየ ፡ ስሙ ። ወተሰምየ ፡ ክርስቶስሀ ፡ በእንተ ፡ ዘተቀብዐ ፡ ምስ ሌነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ። በምግባር ፡ ወበቱስምዮ ፡ (ሚራ ፴፯ ፡ ፲፮ ። መክ፮ ፡ ፲ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ቄር ። ስንክ ፡ ሐም ፳፭) ።

(ጥሙ) **ስሙይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሚት) ፤ የተሰየመ ፤ የተጠራ ፤ ስመ ፡ ጥር ፡ ገናና ፤ የታወቀ ። ስሙይ ፡ በስመ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ ኀይለ ፡ ሰማይ ። ስሙያን ፡ ወጽዉ ዓን ፡ በኢየሱስ ። ስሙይ ፡ በሥነ ፡ አምልኮ ። እሬስ ዮሙ ፡ ስሙያነ ፡ በኵሉ ፡ ምድር ። አበው ፡ ክቡራን ፡ ወዕደው ፡ ስሙያን ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳ ። ደሁ ፡ ፩ ። ቄር ። ዘካ፫ ፡ ፲፱ ። አፈ ፡ ድ፳፪) ።

**ስም** ፤ (ብ ፡ አስማት ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሺም ። ዐረ ፡ ኢስም) ፤ በቁሙ ፤ ከባሕርይ ፡ ከግ ብር ፡ የሚወጣ ፤ በቃንቅና ፡ አካልነት ፡ ህላዌና ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ኹሉ ፡ በየክፍሉና ፡ በያካሉ ፡ በየ ራሱ ፡ ቅሉ ፤ በያይነቱና ፡ በየመልኩ ፡ በየነገዱ ፡ በየዘሩና ፡ በያባቱ ፡ በየዘመዱ ፡ ተለይቶ ፡ የሚጠራበት ፤ የሚታወቅ በት ። ወሰመዮሙ ፡ አዳም ፡ ለኵሎሙ ፡ በበ ፡ አስማቲ ሆሙ ፤ ወበከመ ፡ ጸውዖሙ ፡ ከማሁ ፡ ኮነ ፡ ስሞሙ ። አምኃ ፡ ቢጸነ ፡ በበ ፡ አስማቲሆሙ ። መኑ ፡ ስሙ ፡ ወ መኑ ፡ ስመ ፡ አቡሁ ፡ (ኩፋ ፡ ፫ ። ምሳ፳፱ ፡ ፳፯) ፡ ኹለተ ኛም ፡ ከዘር ፡ ከነባር ፡ ስለ ፡ ወጣ ፡ ጥሬ ፡ ይባላል ፤ ጥሬ ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ ዐማርኛው ፡ ጥሬ ፡ አጠራር ፡ ከማለት ፡ ይስማማል ። ጥሬነቱም ፡ ስመ ፡ ተጸውዖ ፤ ስመ ፡ ተቀብዖ ፡ ተብሎ ፡ በኹለት ፡ ዐይነት ፡ ይከፈላል ። ስመ ፡ ተጸውዖ ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ከፈጣሪውና ፡ ከጌታው ፡ ከአዳም ፡ እንደ ፡ ተሰየመ ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ከባት ፡ ከናት ፡ ከጌታ ፡ ከመ ቤት ፡ ከካህን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰይሞ ፡ የሚጠራ በት ፡ ነው ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፩—፳፯ ። ፪ ፡ ፲፱ ፡ ፳) ። ስመ ፡ ተቀ ብዖ ፡ ግን ፡ ከተጸውዖ ፡ ስም ፡ በኋላ ፡ በሹመት ፡ ጊዜ ፡ ከቀቢ ፡ ከሿሚ ፡ የሚሰጥ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ነው ፤ ጳጳስ ፡ ቄስ ፤ ንጉሥ ፡ ራስ ፤ ይህን ፡ የመሰለ ። በሰዋስው ፡ ዐዋጅ ፡ ቅጽል ፡ ባለቤት ፡ አክል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በስም ፡ ተጠግቶ ፡ ስም ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፤ ምስጢሩና ፡ ሙያው ፡ ቅጽልነት ፡ ነው ፤ የተቀብዖ ፡ ስም ፡ ለተጸውዖ ፡ ስም ፡ ቅጽል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። የተጸውዖ ፡ ስም ፡ ለተቀብዖ ፡ ስም ፡ ተናባቢና ፡ ዘርፍ ፡ ሲኾን ፡ የቅጽል ፡ አፈታት ፡ ይ ፈታል ። ይህም ፡ ነቢየ ፡ ሙሴ ፤ ካህነ ፡ አሮን ፤ ንጉሠ ፡ ዳዊት ፡ ብሎ ፤ ሙሴ ፡ የሚባል ፡ ነቢይ ፤ አሮን ፡ የሚ ባል ፡ ካህን ፤ ዳዊት ፡ የሚባል ፡ ንጉሥ ፡ እያሰኘ ፤ ሌላ ውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ክርስቶስ ፡ የኢየሱስ ፡ ቅጽል ፡ እ ንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ፤ ስምነቱና ፡ ባለቤትነቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ሲቀር ፡ ነው ፤ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ አንጻር ፡ እየው ፤ ቅጽል ፡ ባይኾን ፡ ግን ፡ ኢየሱስ ፡ ወክርስቶስ ፡ ያሰኝ ፡ ነበር ። ውስጠ ፡ ብዙነት ፡ የሌለው ፡ ስመ ፡ ተጸውዖ ፡ (አብርሃም ፡ ይሥሐቅ ፡ ያዕቆብ) ፡ በሙሻ ፡ ዘር ፡ መንገድ ፡ ካልኾነ ፡ በ ራሱ ፡ አይበዛም ፡ ይላሉ ፤ ይህም ፡ አብርሃማን ፡ ት ፡ በማ ለት ፡ ፈንታ ፡ አብርሃማውያን ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳ ያል ። ዳግመኛም ፡ መቃርስን ፡ ሲያበዛ ፡ መቃርሳት ፡ ብሎ ፡ ይገኛልና ፤ (ይኸውም ፡ ብፁዕ ፤ ብፁዓን ፡ ማለት ፡ ነው) ። ባንዱ ፡ ስም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከተጠሩበት ፡ በዚህ ፡ አን ጻር ፡ አብርሃማት ፡ ማለት ፡ ይገባል ፤ ስላልተለመደ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የማይበዛ ፡ ስምና ፡ ጥሬ ፡ አይገኝም ።

**ስማዊ** ፤ የስም ፤ ስሙኛ ፤ ስም ፡ አውጭ ፤ ስም ፡ ሰጭ ፤ ስማም ፤ ባለስም ፤ ስመ ፡ ጥር ። አስማታም ፡ ባለ ኀቡእ ፡ ስም ፤ አስማት ፡ የሚደግም ፤ የሚጥፍና ፡ የሚያ ነግት ፡ የሚያስነግት ፤ ስም ፡ የሚጠይቅ ፤ በስም ፡ የሚያ ሻርት ፤ ጠንቋይ ፡ መሠሪ ፤ ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

**መስም** ፤ ስም ፡ የተጠራበት ፡ ዕቃ ፡ ጥቅል ። ስም ፡ የሚኾን ፡ ቅጽል ፤ እንደ ፡ ተቀብዖ ፡ ስም ፡ ያለ ፤ በባዕድ ፡ ፊደል ፡ የሚነግ ፤ እግዚእ ፡ መስፍን ፡ መተር ጕም ፡ መፈክር ፡ መምህር ፡ ማእምር ፤ ይህን ፡ የመ ሰለ ፡ ኹሉ ። በባዕድ ፡ ዘርም ፡ ባይነግ ፡ ስምና ፡ ቅጽል ፡ የሚኾን ፡ ማናቸውም ፡ ጥሬ ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ በየራሱ ፡ ስ ምነት ፡ ስላለው ፤ እንደዚሁ ፡ መስም ፡ ይባላል ፤ ባለቅኔ ዎች ፡ ግን ፡ አይሉትም ።

**ሰማይ** ፤ (ብ ፡ ሰማያት ። ዕብ ፡ ሻማ ይም ። ሱር ፡ ሺማያእ ። ዐረ ፡ ሰማእ) ፤ በቁሙ ፤ ሰፋሕ ፡ ሰጡሕ ፡ ዝርግ ፤ ልዑል ፡ ምጡቅ ፤ ጠፈር ፡ ከፉ ሳችን ፡ በላይ ፡ ርቆ ፡ መጥቆ ፡ ኒል ፡ መስሎ ፡ የሚታይ ፤ የማየት ፡ ፍጻሜ ፡ ወሰን ፡ ደንበር ፤ ከርሱ ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡ የማያሳይ ፡ ግዙፍ ፡ መጋረጃ ፡ የምድር ፡ ባጥ ፤ መዋቅር ፡

ጣራ፤ ከእሳት ፡ ከውሃ ፡ የተሠራ ፤ በነፋሳት ፡ አሰማይ ፡ የቆመ ፤ ከበላዩ ፡ የውቅያኖስ ፡ ውሃ ፡ ሀኖስ ፡ የሰፈረበት ፡ ከበታቹ ፡ ግዙፋን ፡ ብርሃናት ፡ እንደ ፡ ፋኖስ ፡ የተሰቀሉበት ። ሰማይ ፡ ኹለት ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ሰ ፡ ማይ ፤ ፍችው ፡ እሳት ፡ ወማይ ። ልዑል ፡ ምጡቅ ፡ መባል ፡ የወል ፡ ኹኖ ፡ ለጥፈርም ፡ ለላይኞችም ፡ ሰማያተ ፡ ብርሃን ፡ ለተባሉት ፡ ለሰባቱ ፡ ኹሉ ፡ ይነገራል ፤ እሳት ፡ ወማይ ፡ ግን ፡ ለጠፈር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ በዕብራይስጥ ፤ ዊሎን ፤ ርቂዕ ፤ ሻሓቅ ፤ ዝቡል ፤ ምዖን ፤ ምኮን ፤ ዓርቦት ፡ ይባላሉ ። በግእዝም ፡ ኢረር ፤ ራማ ፤ ኢዮር ፤ ኢየሩሳሌም ፤ ሰማያዊት ፤ ሰማይ ፤ ውዱድ ፤ መንበረ ፤ መንግሥት ፤ ጽርሐ ፡ አርያም ፡ ይባላሉ ፤ በቀዳሚ ፡ ፈጠረ ፡ አምላክ ፡ ሰማያተ ፡ ያላቸው ፡ እሊህን ፡ ከጠፈር ፡ በላይ ፡ ያሉትን ፡ ነው ፤ ጠፈር ፡ ግን ፡ ግዙፍ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ቀጥሮ ፡ ወምድረ ፡ ካለው ፡ ነው ፤ ሰማይ ፡ የተባለ ፡ ስኛ ፡ ነውና ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፮—፱ ፡ ፲፱—፲፯) ፡ ሣልስ ፡ ሰማይ ። ሳብዕ ፡ ሰማይ ። ተርኅወ ፡ ሰማያት ፡ ወርኢኩ ፡ ራእየ ፡ አምላክ ። ሰማያት ፡ ይነግራ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚ ፡ ወግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ያየድዕ ፡ ጠፈር ። ይሴብሕዎ ፡ ሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ወማይኒ ፡ ዘመልዕልተ ፡ ሰማያት ፡ (፪ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ። ዕር ፡ ኢሳ፫ ፡ ፲፫ ። ሕዝ፩ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፲፰ ። ፻፵፰) ።

**ሰማያዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት) ፤ የሰማይ ፡ በሰማይ ፡ ያለ ፤ የሚኖር ፤ ከሰማይ ፡ የመጣ ፤ የሰማይ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፤ ሰማይም ፤ ሰማይማ ፤ የሰማይ ፡ ዐይነት ፤ ሰማይ ፡ የሚመስል ። አቡክሙ ፡ ሰማያዊ ። መርዓዊ ፡ ሰማያዊ ። ጸጋ ፡ ሰማያዊት ። በከመ ፡ ዝኩ ፡ ሰማያዊ ፡ ከማሁ ፡ ሰማያውያን ፡ (ማቴ፭ ፡ ፵፰ ። ቀሌ ። ቄድር ። ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፵፯—፵፱) ።

**ሰሚክ ፤ ክት** ፤ (ሰመከ ፡ ይሰምክ ፡ ይስምክ ። ዕብ ፡ ሳማኽ ። ሱር ፡ ስማኽ) ፤ መጠጋት ፡ መደገፍ ፤ ጥግ ፡ ደገፋ ፡ መያዝ ፤ ማመን ፡ መማጠን ፤ ትውክልት ፡ ተስፋ ፡ ማድረግ ፤ የሰው ። መናበብ ፡ መዛረፍ ፤ ዘርፍ ፡ ቅጽል ፡ መኾን ፤ የቃል ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰመከ ፡ ፈንታ ፡ አስመከ ፡ ይላል ። ላዕለ ፡ እግዚ ፡ ያሰምኩ ። አስመኩ ፡ በስመ ፡ እግዚ ። አስመኩ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ። ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ብነ ፡ ያሰምክ ። ናሰምክ ፡ በዙሉ ፡ ግብር ፡ ንበ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ። አስመክት ፡ ላዕለ ፡ ርእሰ ፡ ወሊታ ። ዝኩ ፡ ዘያሰምክ ፡ ንጉሥ ፡ ላዕለ ፡ እዴሁ ፡ (ሚክ፫ ፡ ፲፩ ። ኢሳ፶ ፡ ፲ ። ቀሌ ። ዮዲ፰ ፡ ፳፱ ። አፈ ፡ ተ፲፪ ። እስቴ ፡ ፳ ፡ ፩ ። ፬ነገ ፡ ፯ ፡ ፪) ።

**ሰማኪ** ፤ (ኪት ፡ ክያን ፡ ያት) ፤ የሚጠጋ ፤ የሚደገፍ ፤ ተስፋዊ ፤ ተናባቢ ።

**ስሙክ** ፤ (ክን ፡ ክት ፡ ምክት) ፤ የተጠጋ ፤ የተደገፈ ፤ ጥገኛ ፤ ባለጥግ ።

**ስምክት** ፤ መጠጋት ፡ መደገፍ ፤ መዋደድ ፡ መላከት ፤ አለመውለቅ ፤ አለመነቃነቅ ። እስመ ፡ ስምክተ ፡ መሰክት ፡ ዘዴበ ፡ ህላዌሁ ፡ ሠናይ ፡ (ቄር ፡ እስት) ።

**አስመከ** ፤ አስጠጋ ፤ አስደገፈ ፤ አንተራሰ ። አስምከኒ ፡ ላዕሌሆን ። አስመከ ፡ ርእሶ ፡ ውስተ ፡ ሙዳየ ፡ በለስ ። ያሰምክ ፡ መዝራዕቶ ፡ ቦቱ ። ሰወልደ ፡ ዕጓሊ ፡ መሐያውብ ፡ አልቦ ፡ ኀበ ፡ ያሰምክ ፡ ርእሶ ፡ (መሳ፲፮ ፡ ፳፮ ። ራእ ፡ ባሮ ። ኤር፲፯ ፡ ፳ ። ሉቃ፱ ፡ ፶፰) ።

**መስመክ ፡ ት** ፤ (ብ ፡ መሳምክ ፡ ት) ፤ ማስጠጊያ ፤ አንድ ፡ ማድረጊያ ፤ ጋድም ፤ ቅርቃር ፤ ችንክር ፡ መወርወሪያ ፤ ቍልፍ ። መስመክተ ፡ ሠርዌሁ ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፲፯) ።

—፤ ጕን ፤ ክፍል ፡ ማእዝን ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ ፡ ፲፱) ።

**ምስማክ** ፤ (ክት) ፤ መጠጊያ ፤ ድጋፍ ፤ ዐልጋ ፤ መከዳ ። ምስማከ ፡ ርእስየ ። ምስማኩ ፡ ዘወርቅ ። ውስተ ፡ ምስማከ ፡ ዘኅበ ፡ አረፍት ፡ (መኃ ፡ ፫፲ ። ማሕ፫ ፡ ፲ ። ፩ነገ ፡ ፳ ፡ ፳፭) ።

—፤ ምሰሶ ፡ ተራዳ ፤ ባላ ፡ ወጋፍ ። ዐውደ ፡ ምስማኩ ፡ ይእቲ ። አትርፉ ፡ ምስማካቲሃ ፡ (ሢራ፴፯ ፡ ፳፱ ። ኤር፳ ፡ ፲) ።

**ተሳመከ** ፤ ተጣጋ ፡ ተጠጋጋ ፤ ተደጋገፈ ፤ ተጠናና ፤ ተጋጠመ ፡ ተባበረ ። ተናበበ ፡ ተዛረፈ ። አዕጺድ ፡ ይሳመካ ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፫ ፡ ፳ ፡ ፲፯) ።

**አስተሳመከ** ፤ አዋደደ ፤ አጋጠመ ፤ አስማማ ። አናበበ ፤ አዛረፈ ።

**ሰመክ** ፤ (ዐረብ) ፤ ዓሣ ፤ ዘመደ ፡ ዓሣ ።

**ሳምኬት** ፤ (ሱር ፡ ሴምካት ። ዕብ ፡ ሳሜኽ) ፤ የፊደል ፡ ስም ፡ ሰ ፤ ፲፭ኛ ። ምስማክ ፡ ዐጋዥ ፡ ረዳት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (መኃ ፡ ፻፲፭ ። ሰቈ፩ ፡ ፲፭ ። ፪ ፡ ፲፭ ። ፫ ፡ ፵፪ ። ፬ ፡ ፲፭) ።

(ጥ) **ሰምኖ ፤ ኖት** ፤ (ሰመነ ፡ ይሴምን ፡ ይሰምን ። ዕብ ፡ ሽሚን ፤ ሠባ ፡ ወፈረ) ፤ መሰመን ፤ ስምንት ፡ ማድረግ ፤ ከስምንት ፡ መክፈል ፡ መትንትን ፤ የስፍር ፡ የቍጥር ፡ የማእገዝን ። ሽማ ፡ መሥራት ። መወፈር ፡ መሥባት ።

**ሰማኒ** ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት ፤ መንት) ፤ የሚሰምን ፤ ሰማኝ ፤ ስምንት ፡ አድራጊ ። ሸማኔ ።

(ሳ) **ሰማኒ** ፤ (ዕብ ፡ ሽሞኔ ። ሱር ፡ ትማኔ ። ዐረ ፡ ተማኒ) ፤ የሴቶች ፡ ድምር ፤ ሐ—፰ ፡ ስምንት ። ሰማኒ ፡ ክረምቱ ። ዐሥሩ ፡ ወሰማኒ ፡ አንስት ፡ ነሥአ ። አርብዓ ፡ ወሰማኒ ፡ (፩ነገ ፡ ፳፱ ፡ ፭ ። ፪ዜና ፡ ፲፩ ፡ ፳፩ ። ዘኍ፴፭ ፡ ፯) ።

**ሰማኒቱ** ፤ ቱ ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ። መጽሐፍ ፡ ለሴቶች ፡ ለወንዶች ፡ ያደርገዋል ፤ ዐዋጁ ፡ ግን ፡ ለሴቶች ፡ ብቻ ፡ ነው ። በሠላሳ ፡ ወሰማኒቱ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ። ወሰደ ፡ ዐሥራ ፡ ወሰማኒተ ፡ አትቡዐ ። ወአትረፈ ፡ ሰማኒተ ፡ ነፍሳተ ፡ እለ ፡ ዐቀቡ ፡ ቃሎ ፡ (፪ዜና ፡ ፲፯ ፡ ፭ ። ፲፩ ፡ ፳፩ ። ቅዳ ፡ ግሩ) ።

**ሰመንቱ** ፤ ቱ ፤ የወንዶች ፡ ድምር ፤ ስምንት ። ሰመንቱ ፡ ሰራዊት ። ዐሠርቱ ፡ ወሰመንቱ ፡ ዐ

ደው ። ተሰዓ ፡ ወሰመንቱ ፡ ዓም ፡ (ሚክ፭ ፡ ፭ ። ሉቃ ፲፫ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ። ሄኖ ፡ ፬ ፡ ፲፭) ።

**ተሰመነ** ፤ በቁሙ ፤ ስምንት ፡ ኾነ ፤ ተባለ ።

**ስሙን** ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ምንት) ፤ የሰመነ ፤ ስምንት ፡ የኾነ ፤ የተባለ ።

**ስምን** ፤ ስምንት ፤ የጊዜ ፡ የልክ ፡ ቅጽል ። ስ ምን ፡ በእመት ፡ (ኩፋ ፡ ፳፱) ።

**ሰሙን** ፤ የዕለት ፡ ቅጽል ፤ ሱባዔ ፤ ሰሞን ፤ ሳምንት ፤ ሰንበት ፤ ሰባት ፡ ቀን ፤ ከእሑድ ፡ እስከ ፡ ቀዳም ። ሰባቱን ፡ ዕለት ፡ ሰሙን ፡ ማለት ፡ ከእሑድ ፡ እስከ ፡ እሑድ ፡ ስምንት ፡ እያሉ ፡ ነው ፤ አስዚያ ፡ ስሕተት ፡ ይኾናል ። ሰሰ ፡ ሰሙኑ ፡ ትነግሥ ፡ ወሰሰ ፡ ሰሙኑ ፡ ትሰፍን ፤ ወሰሰ ፡ ሰሙኑ ፡ ትትቄመር ። ሕ ፡ ቅድስት ፡ ንዒ ፡ ንቤነ ፡ ሰሰ ፡ ሰሙኑ ። ሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ወሰሙነ ፡ ፍሥሕ ። ሰሙነ ፡ ሕርቃል ። ኀሙስ ፡ መዋዕለ ፡ በበ ፡ ሰሙን ፡ (ቀዳ ፡ እት ። አቡሻ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፲፭ ። ቢኖ ደ) ።

**ሰሙን** ፤ ስምንተኛ ። ሕመ ፡ ሰሙን ፡ ዕለት ፡ (ሉቃ፩ ፡ ፶፱ ። ፪ ፡ ፳፩) ። ሰሙንን ፡ ሰባትና ፡ ስምንት ፡ ስምንተኛ ፡ ማለት ፡ ፍችው ፡ ኹኖ ፡ አይደለም ፤ መላ ሽና ፡ ጣፊ ፡ ስቡዕ ፡ ሳምን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አስዚያ ቤው ፡ ሰሙን ፡ እያሉ ፡ ስላገቡት ፡ እንጂ ።

**ሳምን** ፤ ንት ፤ ስምንተኛ ። በሳምን ፡ ወርኅ ። ሕመ ፡ ሳምንት ፡ ዕለት ። ሳምኖሙ ፡ ውእቱ ፡ (ዘኍ፩ ፡ ፩ ። ዘሌ፱ ፡ ፩ ። ሉቃ፱ ፡ ፳፰ ። ራእ፲፯ ፡ ፲፩) ።

**ሳምናዊ ፡ ይ** ፤ (ዊት ፡ ዩት ፡ ኒት) ፤ ገዢ ፡ ከማሁ ፤ ስምንተኛ ።

**ሳምኒት** ፤ (ዕብ ፡ ሽሚኒት) ፤ ንዋየ ፡ ማሕሌት ፤ በገና ፡ ክራር ፤ ባለ፰ ፡ አውታር ። በእንተ ፡ ሳምኒት ፡ (መዝ ፡ ፲፩) ።

**ሰማንያ** ፤ በቁሙ ፤ የቍጥር ፡ ስም ፤ ፈ—ኞ ፤ ስምንት ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ፤ ወይም ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ስምንት ፡ (መዝ ፡ ፹፰ ። ማሕ፮ ፡ ፰ ። መሳ፫ ፡ ፴ ። ፴ ፡ ፳፭ ። ሉቃ፪ ፡ ፴፯ ። ፲፯ ፡ ፯) ።

**ሰሜን** ፤ (ዕብ ፡ ስሞል ። ሱር ፡ ስማል ። ዐረ ፡ ሺማል) ፤ በቁሙ ፤ የማእዝን ፡ ስም ፤ ግራ ፤ የግራ ፡ ማእዝን ፤ የየማን ፡ የቴማን ፡ የደቡብ ፡ የናጌብ ፡ ትይዩና ፡ አንጻር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፤ በመስዕና ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ ያለ ። ከባሕር ፡ ወይም ፡ ከመስዕ ፡ ተንሥቶ ፡ የጓሊት ፡ ቢቈጥሩ ፡ ሰሜን ፡ ስምንተኛ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ፤ የዚያቤው ፡ ዐይን ፡ ግራንትን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ሳምናይነትን ፡ ያሳያል ። ዲልማን ፡ ግን ፡ ሰሜንና ፡ ቴማን ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፤ ጣፈና ፡ መላሽ ፡ ቴማን ፡ ደቡብ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሰሜን ፤ በሰሜን ፡ ፈንታ ፡ ደቡብ ፡ እያሉ ፡ አላገባቡ ፡ የጣፉትን ፡ ምስክር ፡ አድርጎ ፡ ይጠቅሳል ፡ (ኤር፲፯ ፡ ፳፯ ። ዘካ፲፬ ፡ ፬ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፴፩) ። ይመጽኡ ፡ እምሥራቅ ፡ ወእምዕራብ ፡ እምሰሜን ፡ ወእምደቡብ ። ተንሥእ ፡ ሰሜን ፡ ወነዐ ፡ ደቡብ ። እመኒ ፡ ደቡብ ፡ ወእመኒ ፡ ሰሜነ ፡ (ሉቃ፲፫ ፡ ፳፱ ። ማሕ፬ ፡ ፲፯ ። መክ፲፩ ፡ ፫ ። ኤር፩ ፡ ፲፫ ። ሕዝ፩ ፡ ፬) ።

**ሰሜናዊ** ፤ የሰሜን ፡ ወገን ፤ አጠገብ ፤ በሰሜን ፡ ያለ ፤ ከሰሜን ፡ የመጣ ፤ ወደ ፡ ሰሜን ፡ የሚያይ ፡ (ራእ ፳፩ ፡ ፲፫ ። ሕዝ፵ ፡ ፳፫ ፡ ፴፭ ፡ ፵ ። ፵፩ ፡ ፲፩ ። ፵፯ ፡ ፬ ። ምሳ፳፭ ፡ ፳፫) ።

**ስሜን** ፤ (ዐማርኛ) ፤ ያገር ፡ ስም ፤ የጐንደር ፡ ሰሜን ፤ ፍጹም ፡ ደጋ ፤ ቆላ ፤ እንደ ፡ ሐርሞን ፡ በረዶ ፡ የሚፈላበት ፤ ተራራው ፡ ከተራራ ፡ ኹሉ ፡ የሚበልጥ ። የተራራው ፡ ራስ ፤ ማፉ ፡ መጨረሻው ፡ በረዶና ፡ ውርጭ ፡ ስፍርበት ፡ የሚኖር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አሻግሮና ፡ አሻቅቦ ፡ ሲያዩት ፡ ጉም ፡ ያፈነው ፡ ጭጋግ ፡ የሸፈነው ፡ ይመስላል ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ስሙ ፡ ቢሒት ፡ ይባላል ፤ ጥንተ ፡ ስሙ ፡ ግን ፡ ዳሸን ፡ ነው ። ባለጂዎግራፎች ፡ ቁመቱንና ፡ ከፍታውን ፡ ከባሕር ፡ ላይ ፡ ፭ ፡ ሺሕ ፡ ከ፫ ፡ ሜትር ፡ ነው ፡ ይሉታል ። (ተረት) ፤ ወጥ ፡ ይጣ ፡ ጐመን ፤ አገር ፡ ይጣ ፡ ስሜን ።

**ሳሜን** ፤ (ዕብ ፡ ሼሜን) ፤ ሥብ ፡ ሞራ ፡ ቅመማ ፤ ቅቤ ፡ ዘይት ፡ ቅባንግ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

**ሳሙን** ፤ (ዐረ ፡ ሳቡን) ፤ ሳሙና ፤ የልብስ ፡ የገላ ፡ ማጠቢያ ፡ ማጥሪያ ፤ ከሥብ ፡ ከሞራ ፡ ከዘይት ፡ ከመድ ፡ ከእንዶድ ፡ ከሌላም ፡ ዐይነት ፡ የሚሠራ ፤ ቅመሙ ፡ ስምንትነት ፡ ያለው ።

**ሰሚዕ** ፤ ዖት ፤ (ሰምዐ ፡ ይሰምዕ ፡ ይስማዕ ። ዕብ ፡ ሻማዕ ። ሱር ፡ ሽማዕ ። ዐረ ፡ ሰሚዐ) ፤ መስማት ፤ ማድመጥ ፤ ማስተዋል ፡ መቀበል ፤ በጆሮ ፡ በልብ ፤ የቃል ፡ የቋንቋ ። ፈተዉ ፡ ይስምዑ ፡ እንትሙ ፡ ዘትሰምዑ ፡ ወኢሰምዑ ። ሰምዑኒ ፡ ቃልየ ፡ እስመ ፡ ተከህሉኒ ። ሕልቦ ፡ ዘይሰምዖ ። ላዕለ ፡ ልሂቅ ፡ ኢትስማዕ ፡ ውዴተ ። ይሰምዖኑ ፡ ጸሎተ ። ንግረነ ፡ ቡርስተ ፡ እስመ ፡ ንሰምዕ ፡ (ማቴ፲፫ ፡ ፲፯ ። መዝ ፡ ፻፵ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፪ ። ኢዮ፳፯ ፡ ፱ ። ኢሳ፴፯ ፡ ፲፭) ።

—፤ መመስከር ፤ ምስክር ፡ መኾን ፤ ያዩትን ፡ የሰሙትን ፡ መንገር ፤ እየኹ ፡ ሰማኹ ፡ ማለት ። ኢትስማዕ ፡ ለቢጽከ ፡ ስምዐ ፡ ሐሰት ። ሰምዕዎ ፡ ዙሎሙ ፡ ወእንከርዎ ። ጽድቅ ፡ ውእቱ ፡ ስምዑ ፡ ዘሰምዐ ፡ በእንቲኣየ ። ወግብረ ፡ ሐዋርያትኒ ፡ ትሰምዕ ፡ ከመ ፡ ወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአምሳለ ፡ ልሳናተ ፡ እሳት ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፲፮ ። ሉቃ፬ ፡ ፳፪ ። ዮሐ፳ ፡ ፴፱ ። ፊልክ ፡ ፶፰) ።

**ሰማዒ** ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት ፡ ዕት) ፤ የሚሰማ ፡ የሚቀበል ፤ ሰሚ ፡ መስካሪ ፤ ምስክር ። ሰእለ ፡ በጽድቅ ፡ ይጼውዕዎ ፡ ሰማዒ ። ሰማዒ ፡ ስብሐተ ፡ ማሕሌት ። ሰማዒ ፡ ስእለቶሙ ። እዝነ ፡ ሰማዕያን ። ሰሊክሙ ፡ ሰማዕትየ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ እግዚ ። አሪት ፡ ወነቢያት ፡ ኮንዎ ፡ ሰማዕተ ፡ (ኢሳ፵፱ ፡ ፲፫ ። ፵፱ ፡ ፳ ። ዮሐ፲ ፡ ፳፰ ። ሮሜ፲ ፡ ፳፩) ።

**ሰማዕት** ፤ (ታት) ፤ በቁሙ ፤ የሚመሰክሩ ፡ መስካሮች ፤ ሰማዕቶች ፤ ሃይማኖታቸውን ፡ መስክረው ፡ በሰማዕትነት ፡ የሚሞቱ ። ሰማዕተ ፡ ሐሰት ። እስጢፋኖስ ፡ ቀዳሜ ፡ ሰማዕት ። በእንተ ፡ ሰማዕታት ፡ መዋ

ዕያን ። ዓመተ ፡ ስማዕታት ፡ (ማር ፲፬ ፡ ፶፰ ። ቅዳ ። አ ቡሻ) ። ስማዒ ፡ አንድ ፤ ስማዕት ፡ ብዙ ፤ ስማዕታት ፡ የ ብዙ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ስምዕ ፡ ስምዓት ፡ ስምዓታት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሰማዕት ፡ ሰማዕታት ፡ ይ ላል ፤ የጥሬውን ፡ ለውስጠ ፡ ዘ ፡ ስጥቶ ፤ አያስኼም ፤ እን ዱን ፡ ሰማዕት ፡ ማለት ፡ ያማርኛ ፡ ነው ። ሰማዕት ፡ ጕ ጕአ ። በዘቲ ፡ ዕለት ፡ ሰማዕተ ፡ ኮነ ። ያምጽኡ ፡ ሰማ ዕቶሙ ። በእንተ ፡ ፈታሒ ፡ ወሰማዕታት ፡ (ምሳ ፲፪ ፡ ፲፱ ። ስንክ ፡ ጥር ፲፮ ። ኢሳ ፵፫ ፡ ፱ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፫) ።

**አስምዐ** ፤ አሰማ ፤ አስደመጠ ፤ አረዳ ፡ አስረዳ ፡ አስታወቀ ፤ አስጠነቀቀ ፤ በሞት ፡ ነገረ ፤ አስመሰከረ ። ለጽ ሙማን ፡ ያስምዖሙ ። አስምዕኒ ፡ ቃለከ ። በሰማ ዕት ፡ አስምዐ ፡ ለነ ። አስምዕ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢየሀቡ ። አስምዕ ፡ ሰብአ ፡ ምእመናን ። ናስምዕ ፡ ለከሙ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ (ማር ፯ ፡ ፴፯ ። ማሕ ፪ ፡ ፲፬ ። ዘፍ ፵፫ ፡ ፫ ። ኩፋ ፡ ፴ ። ኢሳ ፷ ፡ ፪ ። ዮዲ ፯ ፡ ፳፰) ። ዳግመኛም ፡ በሰምዐ ፡ ፈንታ ፡ አስምዐ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። እስመ ፡ እግዚ ፡ አስምዐ ፡ ማእከሌከ ፤ ወማእ ከለ ፡ ብእሲትከ ፡ (ሚል ፪ ፡ ፲፬) ።

**መስምዕ** ፡ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት) ፤ የሚያሰማ ፤ አሰሚ ፤ አስሚ ፡ አስመስካሪ ።

**ምስማዕ** ፤ (ዓት) ፤ መስሚያ ፤ ማስሚያ ፡ የ ጆሮ ፡ ብሉን ፤ ውስጠኛይቱ ። ውስተ ፡ ምስማዐ ፡ እ ዝን ። ዝኩ ፡ ቃል ፡ ሰበ ፡ ይደምፅ ፡ በምስማዓቲነ ። ውስተ ፡ ጼዴቃት ፡ ምስማዓተ ፡ መንግሥት ፡ ኢይስ ማዕ ፡ ሥሕጸት ። ኢትስጥዎ ፡ በምስማዐ ፡ ሥሕጸት ፡ ዘላዕለ ፡ እግዚ ። ድኑነ ፡ ምስማዐ ፡ ወንጻሬ ፡ (መዝ ፡ ፲፯ ። አፈ ፡ ተ፲፯ ። ቄር ፡ ገ፯ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፫) ።

—፤ ቦታ ፤ ሸንጎ ፡ አደባባይ ። እመ ፡ ቦእከ ፡ ውስተ ፡ ምስማዐ ፡ ሰማይ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፰) ። ጥቃት ፡ ውርደት ፡ ትሕትና ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ምስማዕ ፡ ይላል ፤ አያስኼም ። አግብአ ፡ ኵሎ ፡ ኅሊና ፡ ውስተ ፡ ምስማዐ ፡ ክርስቶስ ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**ተሰምዐ** ፤ ተሰማ ፡ ተደመጠ ፤ ታወቀ ፡ ተረዳ ፤ ከፐሮ ፡ ከልብ ፡ ገባ ፤ ተወራ ፡ ተነገረ ፤ ተመሰከረ ፤ ስመ ፡ ጥር ፡ ኾነ ። ተሰምዐ ፡ ዝንቱ ፡ ውስተ ፡ እዝነ ፡ እግዚ ። ቃሉ ፡ ጠቢብ ፡ ይሰማዕ ፡ በውስተ ፡ እንግልጋ ። እ ስመ ፡ ተሰምዐት ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ። ግሙራ ፡ ኢተሰምዐ ፡ ነገር ፡ ዘከመ ፡ ዝ ላዕለ ፡ ሶስና ። ተሰምዐት ፡ ምድር ፡ ዘይሁዳ ፡ ወኤ ፍሬታ ፡ (ኢሳ ፷ ፡ ፱ ። ሚራ ፳፩ ፡ ፲፯ ። ሮሜ ፩ ፡ ፰ ። ዳን ፩ ፡ ፳፯ ። ቀሌ) ።

**ስሙዕ** ፤ (ዓን ፡ ዓት ፡ ምዕት) ፤ የሰማ ፤ የመስከረ ፡ የተሰማ ፤ የታወቀ ፡ ዕውቅ ፤ ስመ ፡ ጥር ። በር ባን ፡ ስሙዕ ። ምኔት ፡ ስሙዕ ። ክቡራን ፡ ወስሙ ዓን ፡ (ማቴ ፳፯ ፡ ፲፯ ። ፊልክ ፡ ፻፳፩ ። አፈ ፡ ድ፳፯) ።

**ስምዐት** ፤ (ታት) ፤ መስማት ፤ መመስከር ፤ አስማማ ፡ አመስካከር ፤ ስሞታ ፡ ምስክሩ ፤ ምስክርነት ።

**ስሙዓ** ፤ **ዓት** ፤ (ዕብ ፡ ሽሙዓ) ፤ ዜና ፤ ወሬ ፤ ስም ፡ ግብር ። ወፀአ ፡ ስሙዓቱ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ሶርያ ። ወሰምዑ ፡ ከሰዳውያን ፡ ስሙዓቶሙ ። እለ ፡ አልቦሙ ፡ ስሙዓት ። ወኮነት ፡ ስሙዓተ ፡ አሐዱ ፡ እ ምኔሆሙ ፡ እኪተ ፡ (ማቴ ፬ ፡ ፳፬ ። ፱ ፡ ፳፮ ። ኤር ፵፱ ፡ ፳ ። አፈ ፡ ድ፳፯ ። ፊልክ ፡ ፻፳፰) ።

**ስምዕ** ፤ ስሞታ ፤ ምስክሩ ፤ ምስክር ፤ ምስክር ነት ። ሰማዕት ፤ ሰማዕትነት ። በከመ ፡ ስምዕ ፡ ዘሰማዕ ክሙ ። ወንሕነኒ ፡ ንሰምዖ ፡ ሠናየ ፡ ስምዐ ፡ በላዕ ሌኒ ። መኑ ፡ የአምነነ ፡ ስምዐነ ። ቈርቆስ ፡ ዘኮነ ፡ ስ ምዐ ፡ ለክርስቶስ ። ወከመ ፡ ዝ ፡ ፈጸሙ ፡ ስምዖሙ ። ሐማመ ፡ ስምዕ ፡ (ዕር ፡ ኢሳ ፶ ፡ ፪ ። ጠቢ ፲ ፡ ፰ ። ኢሳ ፶፫ ፡ ፩ ። መዋሥ ። ስንክ ፡ ታኅ፴ ። አርጋ ፡ ፩) ።

**ስምዕ** ፤ (ዕብ ፡ ዔዱት) ፤ ሕግ ፡ ትእዛዝ ፤ አምላካዊ ፡ ፍርድ ፡ አገዛዝ ፤ የተጣፈ ፡ የተወሰነ ፤ ጽላት ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላት ፤ እግዜር ፡ ለሙሴ ፡ የሰጠው ። ስምዑ ፡ ለእግዚ ፡ እሙን ። ወእዕቀብ ፡ ስምዐ ፡ አፉከ ። እስመ ፡ ስምዐከ ፡ ለበውኩ ። ቤተ ፡ ስምዕ ። ደብተራ ፡ ስ ምዕ ፡ (መዝ ፲፰ ። ፻፲፰ ። ፻፳፰ ። ፲፮ ። ዐዜና ፡ ፳ ። ፴፱ ። ግብ ፯ ፡ ፵፬) ።

**ስምዓት** ፤ (ታት) ፤ ምስክሮች ፤ ጥቅሶች ፤ ቃ ሎች ፤ ከየመጽሐፉ ፡ ተለቅመው ፡ ተቀሥመው ፡ ባንድ ፡ ምእላድ ፡ የሚጣፉ ፡ እንደ ፡ ቄርሎስ ፡ እንደ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ቃላት ፡ ያሉ ። ንጽሕፍ ፡ ስምዓተ ፡ እመጽ ሐፈ ፡ ሊቃውንት ። ንፈቅድ ፡ ከመ ፡ ታብይእ ፡ ለነ ፡ ስምዓታተ ፡ (አዋል ። ፊልክ ፡ ፫) ።

(ጥግ) **ስማዔ** ፤ ስመ ፡ ጥርነት ፤ አበ ፡ እገሌ ፡ መባል ። ይቤ ፡ አረጋይ ፡ ኢታውትር ፡ ስማዔ ፡ እምሰብእ ፡ (ፊ ልክ ፡ ፪፻፴፪) ።

**ተሳምዐ** ፤ ተሳማ ፡ ተዳመጠ ፤ ተስማማ ፡ ተደ ማመጠ ፤ የቋንቋ ፡ (ዘፍ ፲፩ ፡ ፯) ።

**አስተሳምዐ** ፤ አሰማማ ፡ አደማመጠ ፤ እንዲ ሳሙ ፡ እንዲዳመጡ ፡ አደረገ ፤ የስልክና ፡ ያምኛር ።

**ሰምዕ** ፤—**ሠም** ፡ **ጧፍ** ፤—**ሠምዕ** ።

**ሰምረ** ፤—**ወደደ** ፡ **ፈቀደ** ፤—**ሠሚር** ፡ **ሠምረ** ።

**ሰሚር** ፤ **ሮት** ፤ (**ሰምረ** ፡ **ይሰምር** ፡ **ይ ስመር** ። **ዐረ** ፡ **ሰመረ**) ፤ መስመር ፤ ማማር ፤ ማፍ ራት ፡ መበጀት ፤ ደስ ፡ ማሰኘት ፤ ያገመራ ፡ ያታክልት ። ይፈሪ ፡ ወይሰምር ። በሰብዐቱ ፡ ዓመት ፡ ዘሰምረ ። እመሂ ፡ ይሰምር ፡ ዘርዖሙ ፡ በቅድሜሆሙ ። ሰ ምረ ፡ ፍሬሁ ። ወሰምረ ፡ ሎቱ ፡ ተግባሩ ። ከመ ፡ ይ ስመር ፡ በላዕሌክሙ ፡ ፍሬ ፡ ጽድቅ ፡ (ቆላ ፩ ፡ ፮ ፡ ፲ ። ኩፋ ፡ ፵፬ ። ኢዮ ፳፩ ፡ ፰ ። ሉቃ ፲፪ ፡ ፲፯ ። ፊልጵ ፩ ፡ ፲፩) ።

**ስሙር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ምርት) ፤ ያማረ ፡ የበጀ ፤ ያፈራ ፡ ፍሬያም ፤ ወፍራም ። ፍሬ ፡ ገራህት ፡ ስሙር ። ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ስሙር ። ከመ ፡ እክለ ፡ ማእ ረረ ፡ ስሙር ። ምድር ፡ ስምርት ። ዒያታት ፡ ስሙ

ራት ፡ (ኢሳ፷፰ ፡ ፲፭ ። ሆሴ፲፬ ፡ ፮ ። ኢዮ፳ ፡ ፳፯ ። ክፋ ፡ ፳፰ ። ፩ዜና ፡ ፱ ፡ ፵) ።

**ሰምር ፤ ሰመር ፤ (ብ ፡ ሰምራት ፤ አሰ ማር)** ፤ አዝመራ ፤ ያዝመራ ፡ መበጀት ፡ ብጀታ ፤ ፍሬ ፡ ዛላ ፡ ዘለላ ፤ እሸት ፡ ጕምር ፤ ንደ ፡ ክምር ፤ ምርት ፡ ቍልል ። በሰምረ ፡ ገራህቱ ፤ በሰምረ ፡ ዐጺደ ፡ ወይኑ ፤ ይፈዲ ፤ አስማሮ ፡ ይፈዲ ፡ (ዘዐ፳፬ ፡ ፱ ። አርጋ ፡ ፮) ።

**አስመረ** ፤ አበጀ ፡ አሳመረ ፤ አበቀለ ፡ አሳደገ ፤ ፍሬያም ፡ አደረገ ። እስከ ፡ ሶበ ፡ ደረውያ ፡ ሰም ድር ፡ ወያበቍል ፡ ወያሰምር ። አስምሮ ፡ አዝርዕት ። ወአ ስምሮ ፡ ሰማእረራ ። ያሰምር ፡ ማእረረ ፡ ጽድቅ ክሙ ፡ (ኢሳ፵፭ ፡ ፲ ። አርጋ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፷፬ ። ፪ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲) ።

**ሰማራግዶስ ፤ (ጽርእ)** ፤ ዕንቍ ፤ የዕንቍ ፡ ስም ። መረግድንና ፡ ኖርይስን ፡ እይ ።

**ሳን ፤ (ዕብ ፡ ሚን ፡ ሺን)** ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ኻያ ፡ አንደኛ ፤ ሠ ፤ ሸ ። ስን ፤ ጥርስ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሳን ፤ መባእክት ፡ ሰደዱ ፡ በከንቱ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፷፩—፻፸፰) ።

(ጥን) **ስን ፤—ጥርስ ፤—ሰኒን ፡ ሰነኑ ።**

**ሰኒአ ፤ አት ፤ (ሰንአ ፡ ይሰንእ ፡ ይሰ ናእ ። ዕብ ፡ ሳናእ ፤ ጠላ ÷ ተጣላ)** ፤ መግጠም ፤ መጋጠም ፤ መሳካት ፤ መስናኘት ፤ መስማማት ፡ ልክክ ፡ ማለት ፤ መቃረቅ ፡ መስላም ፡ መገናኘት ፤ ግጥም ፡ ስ ምም ፡ መኾን ፡ አለመጣላት ፤ አለመብለጥ ፡ አለማፈን ገጥ ፤ የማብር ፡ የነገር ፡ የቅኔ ፡ የመኪና ፡ የልብስ ፡ የጫማ ፡ ማሰሪያ ። ሥእንን ፡ እዩ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰንአ ፡ ፈንታ ፡ ተሰንአወ ፤ ተሰነአወ ፡ ይላል ፤ ወገ ስን ፡ ወቅሖን ፡ ነሰወን ፡ ተመልክት ፤ የዚህ ፡ መሰል ፡ ናቸው ።

**ሰንእ** ፤ ሰላም ፤ ዕርቅ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፤ ስም ምነት ፤ ወዳጅ ፡ ባልንጀራ ። ስንኝ ፤ ቤት ፡ የቅኔ ። በብ ሔረ ፡ ስንእ ፡ እንተ ፡ ትትአመን ። ምስሌየ ፡ ግበሩ ፡ ስንአ ። ሊይኩን ፡ ሰከ ፡ ስንእ ፡ ምስሌሁ ። ሰላም ፡ ለእለ ፡ ሞቱ ፡ ምስሌሁ ፡ በስንእ ። ሰላም ፡ ለመርክ ያኖስ ፡ ወሰመርቆሬዎስ ፡ ስንኡ ፡ (ኤር፲፪ ፡ ፭ ። ፬ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፴፩ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ሚያ፲ ። ጥቅ፳፰) ።

**ስንአ ፤ (ብ ፡ ስንአን)** ፤ ስምም ፡ ግጥም ፤ ቅን ፡ ደጎና ፡ እውነተኛ ፤ ብእሴ ፡ ሰላም ። እሉ ፡ ዕደው ፡ ስንኣን ፡ እሙንቱ ፡ ምስሌነ ። አመሰ ፡ ስንኣን ፡ አን ትሙ ። ጸብሑክ ፡ ስንኣኒክ ፡ (ዘፍ፴፬ ፡ ፳፩ ። ዓ፱ ፡ ፲፱ ፡ ፴፭ ፡ ፴፫ ፡ ፴፱ ። ዐብድ ፡ ፯) ። አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በስ ንኣን ፡ ፈንታ ፡ ስንእ ፡ ስንኣ ፡ እያለ ፡ የብዙውን ፡ ባንድ ፡ ይጥፋል ። ወዘሎሙ ፡ እለ ፡ ዐውዱ ፡ ስንእ ፡ ምስ ሌሁ ። ጸውዐ ፡ ኀቤሁ ፡ ባዕዳነ ፡ ብዙኃነ ፡ ስንኣሁ ፡ (፫ነገ ፡ ፱ ፡ ፳፱ ። ሉቃ ፡ ዕገ፲፫ ፡ ፲፯ ፡ ዓ፱) ።

**ሰንአወ ፤ (አስንአ)** ፤ አጋጠመ ፡ አስማማ ፤ አሳካ ፡ አሰናኘ ፤ አገናኘ ።

**ተሰናአወ ፤ (ተሰንአ ፤ ተሳንአ)** ፤ ተስ ማማ ፤ ተጋጠመ ፤ ተባበረ ፤ አንድ ፡ ልብ ፡ አንድ ፡ ሐሳብ ፡ ኾነ ። ጼወ ፡ ርክቡ ፡ ወተሰናአዉ ። ተሰናአወ ፡ የሳ ፍጥ ፡ ምስለ ፡ ንጉሠ ፡ እስራኤል ። ተሰናእዎ ፡ እ ሳት ፡ ወማይ ፡ በአሐዱ ፡ ህላዌ ። ተሰናአዉ ፡ በዝ ፡ ምክር ፤ ከመ ፡ ኢይሰናአዉ ፡ ባዕለ ፡ ወልጦ ፡ መጻሕ ፍት ። በእንተ ፡ ተሰናእዎተ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ሰምን ሾስና ። ተሰናአዉ ፡ ምስሌሃ ፡ ከመ ፡ የሀብዋ ፡ ንዋየ ፡ (ማርቆ ፡ ፶ ። ፫ነገ ፡ ፵፪ ፡ ፵፰ ። አርጋ ፡ ፪ ። ዮሴፍ ። ፈ ጠ ፡ ፲፪ ፡ ፫ ። ስንክ ፡ ግንቦ) ።

**ተሰናአዊ ፤ (ተሳናኢ)** ፤ የሚስማማ ፡ ተስ ማሚ ፤ ተባባሪ ። ተሰናኣውያን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

**ስንእው ፤ (ስኑእ)** ፤ የተስማማ ፤ ስምም ፤ ግጥም ። ጊዜ ፡ ኮነት ፡ ሀገርክሙ ፡ ሐንጽት ፡ ወሰራ ዊትክሙ ፡ ስንእዋን ፡ ወንብረትክሙ ፡ ርቱዕ ። ስን እው ፡ ምግባር ፡ ምስሊ ፡ ስንእዋኒሁ ፡ (ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ነሐ፳፫) ።

**ስንኣዊ ፤ (ስንእ)** ፤ ሱላሚ ፡ ሰላም ፤ መስማ ማት ፤ መጋጠም ፤ መገጣጠም ፤ ግጥምነት ፤ ስምምነት ። ተሰናአዉ ፡ ስንኣዌ ። ለሕይወት ፡ ኅቡረ ፡ በስንኣዌ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፱) ።

**አስተሰናአወ** ፤ አጋጠመ ፤ አገጣጠመ ፤ አስ ማማ ፤ አስታረቀ ፤ አንድ ፡ አደረገ ። እሊ ፡ ያስተሰናእዉ ፡ ሰግብረ ፡ ዝሙት ። አስተሰናእዎሙ ፡ በበይናቲሆሙ ። ይእቲ ፡ እንተ ፡ ታስተሰናኢ ። መኑ ፡ ያስተሰናእዎሙ ፡ ለአክልብት ፡ ምስለ ፡ አዝእብት ። ወልደ ፡ እግዚ ፡ አስተሰናአወ ፡ አናብስተ ፡ ምስለ ፡ ዳንኤል ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፮ ፡ ፲፫ ። አፈ ፡ ድ፬ ። ያዕ፫ ፡ ፲፯ ። ሚራ፲፫ ፡ ፲፰ ። ቢኖ ድ) ።

**አስተሰናአዊ** ፤ የሚያስማማ ፡ የሚያጋጥም ፤ አንድ ፡ የሚያደርግ ፤ አስታራቂ ። ልሳን ፡ አስተሰናኣ ዊት ፤ ይእቲ ፡ ማእከለ ፡ ዘተዘርወ ፡ (ፊላስ) ።

**መስተሰናእው** ፤ የሚያስማማ ፤ የሚስማማ ፤ አስማሚ ፤ ተስማሚ ። ፈቃዶሙ ፡ መስተሰናእውት ፡ (ፊልክ) ።

**ሰንአለ ፤ (ሰአለ ፤ ን ፡ ስሯጽ ፡ ነው)** ፤ አሰናበተ ፤ ሰቀቀ ፡ ፈታ ፤ ኺድልኝ ፡ አለ ፤ ለመነ ።

**ተሰንአለ** ፤ ተሰናበተ ፤ ተፈታ ፡ ተሰቀቀ ፤ የመ ኼድ ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀበለ ።

**ተሰናአለ** ፤ ተሰነባበተ ፤ ተመራረቀ ፤ ከመሳ ሳም ፡ ጋራ ፡ ደኅና ፡ ኹን ፡ ደኅና ፡ ኹን ፡ ተባባለ ። አ ኀዚዙ ፡ ይላሕዉ ፡ ወይብክዩ ፡ ወይሰናአሉ ፡ በበይና ቲሆሙ ። ከመ ፡ ይሕቅፎሙ ፡ ለውሉዱ ፡ ወየአም ኆሙ ፡ ወይሰናአሎሙ ። ተሰናአለ ፡ ወሳዲቶ ። ተሰ ናአልዎ ፡ በአስተርክቦ ፡ (ዮሴፍ ። ስንክ ፡ ሐም፲ ። ግ ንዛ) ።

**ስንኣሌ** ፤ መሰናበት ፤ መሰነባበት ፤ ስንብት ፤ የ ስንብት ፡ ቃል ፤ ቡራኬ ፡ ምርቃት ።

**ሰንቢል ፤ ሰንበልት ፤ ሰንቡላ ፤**—ሰብለ ።

**ሰንበለ ፤—ዐረብ ፡ ሰቢለ ፤—ሰቢል ፡ ሰብለ ።**

**ሰንቡዕ ፤ ሰንብዕ ፤ (ነቢዕ ፡ ነብዐ ። ዕብ ፡ ናሽብ ፤ ነፍኅ)** ፤ ሳንባ ፤ የልብ ፡ ሥር ፤ የትንፋሽ ፡ ምንጭ ፤ (፫ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፴፬ ። ፪ዜና ፡ ፲፰ ፡ ፴፫) ። አይቴ ፡ መካነ ፡ ጽንዐተ ፡ መንፈስ ፤ ደቤ ፡ በሰንቡዕ ፡፡ ረገዘ ፡ ውስተ ፡ ሰንብዑ ፡፡ ወጠቢባንሰ ፡ ይብሉ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተንጽፈ ፡ ሥብሕ ፡ ወሰንቡዕ ፡ በታሕቴሁ ፡ ሰልብ ፡ ከመ ፡ ይሀድእዎ ፡ ወያስተናፍስዎ ፡ በጊዜ ፡ መዐቱ ፡ እንዘ ፡ ይሜግብዎ ፡ ከመ ፡ እንቲ ፡ ሰፍነግ ፡ ልምሉም ፡ (ጎድ ፡ ተክ ። አፈ ፡ ተ፷) ።

**ሸንብራ** ፤ በቁሙ ፡ የታወቀ ፡ ያበባ ፡ እኽል ፤ ፍሬው ፡ ቀይና ፡ ጥቍር ፡ ነጭ ። መበለት ፡ እኪት ፡ ባሕረ ፡ ኤርትራ ፤ አስጠመቶ ፡ ለፈርዖን ፡ ሸንብራ ፤ (ቅኔ) ።

**ሰኖባር ፤ (ዐረ ፡ ሰነውበር)** ፤ የዛፍ ፡ ስም ፤ መልክም ፡ ሽታ ፡ ያለው ፤ የዝግባ ፡ ዐይነት ፡ (ሰንክ ፡ ሐም፳) ።

**ሰንበት ፤ (ሰብዐ ፤ ሰብዐት ። ዕብ ፡ ሻባት ። ሱር ፡ ሻብታ ። ዐረ ፡ ሰብት)** ፤ የዕለት ፡ ስም ፤ ሰባት ፤ ሰባተኛ ፡ ቀን ፤ ሰባተኛ ፡ ዓመት ፡ ማረፊያ ፡ ዕረፍት ፤ ቀዳም ፤ ዓመት ፡ ኀድገት ፤ ሱባዔ ፤ ሳምንት ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ዘፀ፲፮ ፡ ፳፫—፳፱ ። ፳ ፡ ፰ ። ማቴ፲፪ ፡ ፪ ። ቈላ፪ ፡ ፲፮ ። ሐዋ፳፩ ፡ ፲፱—፲፯ ። ግብ፲፯ ፡ ፪) ።

**ሰናብት ፤ ሰንበታት** ፤ ሰንበቶች ፤ ቀዳሞች ፤ ዓመተ ፡ ኀድገቶች ፤ በሱባዔ ፡ የሚቈጠሩ ፡ በዓላት ፤ አይቢላት ፤ ሱባዔያት ። ሰንበተ ፡ ሰናብት ፡፡ ወሀብክዎሙ ፡ ሰንበታትየ ፡፡ ሰብዑ ፡ ሰንበታት ፡፡ በዓለ ፡ ሰናብት ፡፡ ሰንበታተ ፡ መዋዕል ፡ ኀምስ ፡ ወክልኤቱ ፡፡ ሰንበታተ ፡ ዓመታት ፡፡ ሰብዓ ፡ ሰንበታት ፡ (ዘሌ፲፯ ፡ ፴፩ ። ሕዝ፳ ፡ ፲፫ ። ዘዳ፲፮ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ኩፋ፯ ፡ ፶ ። ዳን፱ ፡ ፳፬—፳፯) ።

**ሰንበተ ፡ ቀዳሚት** ፤ ሰንበተ ፡ አይሁድ ፤ ቅዳሜ ፤ የብሉይ ፡ ሰንበት ፤ የእሑድ ፡ ምሳሌ ፤ ሞዜማ ፡ ድሮ ፡ ማኅትሙ ፡ ኀተወን ፡ ተመልክቶ ። ኢይደልዎሙ ፡ ለክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ያፅርዑ ፡ ተገብሮ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ከመ ፡ አይሁድ ፤ አላ ፡ ይትገበሩ ፡ ከመ ፡ ክርስቲያን ፡፡ ወኢትትዐቀቡ ፡ ሰንበተ ፡ ከመ ፡ አይሁድ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱) ።

**ሰንበተ ፡ እሑድ** ፤ እሑድ ፡ የሚባል ፡ ሰንበት ፤ ሰንበተ ፡ ክርስቲያን ፤ ዐቢይ ፤ አማናዊ ፡ ሰንበት ፤ ቅዳሜ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ የሚብት ። ተንሥአ ፡ ክርስቶስ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡፡ ትንሣኤሁ ፡ ገብረ ፡ በሰንበት ፡፡ ወበእሑድ ፡ ሰንበት ፡፡ በከመ ፡ ተፈሥሐ ፤ ትማልም ፡ በበአታ ፡ ከማሁ ፡ ናስተፈንዋ ፡ በፍሥሓ ፡ በፀአታ ፡ (መዋሥ ። ዲድ ፡ ፴ ። ድጓ ። ማር፲፮ ፡ ፪ ። ሉቃ፳፬ ፡ ፩ ። ቅዳ ፡ አት) ። ወበእሑድ ፡ ሰንበት ፡ ያልቀና ፡ ኅባብ ፡ ነው ፤ ቀናው ፡ ግን ፡ ወበእሑድ ፡ እምሰንበት ፤ ወይም ፡ ወበእሑደ ፡ ሰንበት ፡ ያሰኛል ። ፍችውም ፡ ከሳምንቱ ፡ ባንደኛው ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፤ የተስቀሰበት ፡ ሳምንት ፡ ዐልፎ ፡ ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ሌላው ፡ ሱባዔ ፡ ኹለተኛው ፡ ሳምንት ፡ ሲጀመር ፡ ማለት ፡ ነው ።


**ሰንበታዊ** ፤ ሰንበቴ ፤ ሰንበት ፡ ነክ ፤ የሰንበት ፡ መዝሙር ፤ የሱባዔ ፡ ቍጥር ፤ የፊደል ፡ ቀመር ፤ ከግእዝ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ። ፊደላት ፡ ሰንበታውያን ፡ (አዋል) ።

**ሰንበተ** ፤ ሰነበተ ፡ ቀረ ፡ ቈየ ። ሰንበት ፡ ኾነ ፤ ተባለ ፤ ከበረ ፤ ተሾመ ፡ ተቀደሰ ።

**አሰንበተ** ፤ አከበረ ፤ አስከበረ ፤ ዐረፈ ፡ አሳረፈ ፤ ሰዘነ ፤ ሥራ ፡ ተወ ፡ ፈታ ፤ ስለ ፡ በዓል ። አሰንበተ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡፡ አሰንብቱ ፡ ሰንበታቲክሙ ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፴ ። ዘሌ፳፫ ፡ ፴፪ ። አፈ ፡ ድ፰) ።

**ሰንጐጎ ፤ ጎት ፤ (ሰንጐጐ ፡ ይሰነጕጕ ፡ ይሰንጕጕ ፤ ሰኒጕ ፡ ሰንጐ)** ፤ መሰንግ ፤ ባፍንጫ ፡ በቀሰበት ፡ ማግባት ፤ መስቀል ፡ መትከል ፤ ማጽናት ፡ ማበርታት ፤ የከሳብ ፡ የዘንግ ፡ የመጋረጃ ። መሸንጎት ፤ ሸንጎ ፡ ማድረግ ።

**ሰንጐጕ ፤ (ብ ፡ ሰናጕጕ)** ፤ ጽኑ ፡ ብርቱ ፡ የማይሰበር ፤ ክንዲን ፡ ከማዕደን ፡ የተሠራ ፡ ዕቃ ። ሰናጋ ፡ ሰናግ ፤ ኮሳብ ፡ የብረት ፡ ዘንግ ። ዘብርት ፡ ሰንጕጕ ፡፡ ንዋየ ፡ ብርት ፡ ቅድወ ፡ ወሰናጕጕ ፡ ዘከመ ፡ ወርቅ ፡ (፫ነገ ፡ ፯ ፡ ፴፩ ። ፩ሰዝ ፡ ፰ ፡ ፶፯) ። ወሰንጺናትሰ ፡ ገብርዎሙ ፡ ሰንጕጕ ፡ በዘይሰቅሉ ፡ ቦቱ ፡ መንጠዋልዐ ፡ (ገድ ፡ ተክ) ።



ሰንጕጕ ።

**ሴናጎግ ፤ (ጽርእ)** ፤ ምኵራብ ፤ ቤተ ፡ ጸሎት ፤ መሰብሰቢያ ፤ ከኒሳ ፡ ቤተ ፡ ክሲያን ፡ ጉባኤ ፡ ሸንጎ ፡ አደባባይ ።

**ስንዳሴ ፤ (ጽርእ ፡ ሴሚዳሊስ)** ፤ የስንዴ ፡ ደቂቅ ፤ ታጥቦ ፡ ተፈትጎ ፡ የተፈጨ ፤ ከዚያውም ፡ ንጹሑና ፡ ጥሩው ፡ መጀመሪያው ፡ ዐይነት ፤ መሥዋዕት ፡ የሚኾነው ። የደቂቅን ፡ ክፍልና ፡ ማዕርግ ፡ ሠወስትንቱን ፡ የማያውቁ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ስንዴ ፡ ይሉታል ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፮ ። ዘፀ፳፱ ፡ ፪ ። ዘሌ፪ ፡ ፩) ። ኅብስተ ፡ ስንዳሴ ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፭) ።

**ሰንደል ፤ (ዐረብ)** ፤ ስሙ ፡ ዕፅ ፡ ክቡር ፤ ሕቍ ፤ ጥሩ ፡ ጠንካራ ፡ ምዑዝ ፡ ዐጢን ፤ ሠናየ ፡ ጺና ። ወዘርኡ ፡ ዕፀው ፡ ክቡራን ፡ ከመ ፡ ዑድ ፡ ወሰንደል ፡ (ጊ ፡ ወሐ ፡ ገ፷፫) ።

**ሰንዱን ፤ (ናት ። ጽር ፡ ሲንዶን ። ዕብ ፡ ሳዲን)** ፤ ጥሩ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፤ በፍታ ፡ ሻሽ ፤ ልብሰ ፡ ከታን ፤ መጐናጸፊያ ። ባለብሉዮች ፡ ማማት ፡ ይሉታል ። ወሬዛ ፡ ዘይትዐጸፍ ፡ ሰንዱነ ፡፡ የኀፀብ ፡ በወይን ፡

ልብሶ ፡ ወበደመ ፡ አስካል ፡ ሰንዱኖ ። ኮነ ፡ አናሚ ፡ አልባሳቲ ፡ ቀጢንት ፡ ወሰንዱናት ፡ ክቡራት ፡ (ማርቆ፲፬ ፡ ፶፩ ። ዘፍጥ፵፱ ፡ ፲፩ ። ስንክ ፡ ግን፲፬) ።

**ሰንደቅ** ፤ (ዕብ ፡ ሳንዳቅ ፤ አስገዛሪ ፤ ሕፃንን ፡ በጭኑ ፡ የሚይዝ) ፤ በላማ ፡ ባንዲራ ፤ የባንዲራ ፡ ሰንጨት ፡ መሰቀያው ፡ ማንጠልጠያው ። ሰን ደቅ ፡ በላማ ፡ እንዲሉ ። ኀደገ ፡ ሰንደቀ ፡ ወነጋሪተ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ።

**ሰንዱቅ ፡ ወመንዱቅ** ፤ የዐረብ ፡ ተረት ፡ ሳን ዱቅ ፡ ወበንዱቅ ፤ ሣጥንና ፡ ዲቃላ ። ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ ማርና ፡ ዕጣን ፡ ይሉታል ፡ (ጥሬ ፡ ስዋ) ።

**ሲኖዲቆን ፤—ሲኖዶሳዊ ፤—ሲኖዶስ ።**

**ሰንደሮስ ፤ ስንድሪስ ፤ (ፋርስ ፡ ሰንደ ሩስ ። ዐረ ፡ ሲንደሩስ)** ፤ ሙጫ ፤ የዕጣን ፡ ዐይ ነት ፤ ነጭ ፡ ዕጣን ፤ መልካም ፡ ሽታ ፡ ያለው ። ሰንደ ሮስ ፡ ምስለ ፡ ጽርስቅላ ። ክርቤ ፤ ሚዓ ፤ ሎዘን ፤ ስን ድሪስ ፡ ከሚን ፡ ጥፉሕ ። ሠሰስቱ ፡ ሰቅል ፡ ሰንደ ሮስ ፡ (ማሕ፬ ፡ ፲፫ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ። ቄድር) ።

**ሲኖዶስ ፤ ሳት ፤ (ጽርእ)** ፤ ጉባኤ ፤ ሸንጎ ፤ የጳጳሳትና ፡ የሊቃውንት ፡ ማኅበር ፤ እክባ ፡ ስብሰባ ። መ ጽሐፈ ፡ ሲኖዶስ ፡ ዘጸሐፉ ፡ ኵሎሙ ፡ ጳጳሳት ። ቅድ ስት ፡ እንተ ፡ እምኵሉ ፡ ዓለም ፡ ሲኖዶስ ፡ ጉባኤ ፡ (ዘኤፌሶን) ። ካዕበ ፡ ለለ ፡ ዓመት ፡ ሲኖዶስ ፡ ይትገ በር ። ወለኵሉ ፡ ዘዐለወ ፡ ዘንተ ፡ ሕገ ፡ ሲኖዶስ ፡ ይወ ግዝ ፡ (ተረ ፡ ቄር፲፪ ። ቀኖ ፡ ኒቅ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፬) ።

—፤ የጉባኤ ፡ መጽሐፍ ፤ ጉባኤ ፡ ጳጳሳት ፡ የጣፈውና ፡ የወሰነው ፡ ያገገው ፡ የደነገገው ፡ ሕግ ፡ ሥርዐት ፤ ቀኖና ፡ ሃይማኖት ። ሲኖዶስ ፡ ዘአበው ፡ ሐዋርያት ፡ ቅዱ ሳን ። ሲኖዶስ ፡ ዘቀሌምንጦስ ። ሲኖዶስ ፡ ዘቅዱስ ፡ ባስልዮስ ። ሲኖዶስ ፡ ዘጉባኤ ፡ ስርድቅ ። ሲኖዶሳት ፡ (ሲኖ ደ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ሲኖዲቆን ፤ (ጽር ፡ ሲኖዲኮን)** ፤ ሲኖደ ሳዊ ፡ ዘሲኖዶስ ፤ ማኅበራዊ ፡ ጉባኤያዊ ። መተርጕማን ፡ ግን ፡ ቆንሲኖዲ ፡ ብለው ፡ ሊቅ ፡ ወማኅበር ፡ ይሉታል ። መልእክተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**ሰነው ፤ ምት ፤ (ሰነወ ፡ ይሰኑ ፡ ይስኑ ። ዐረ ፡ ሰና)** ፤ መመስን ፡ መስኖ ፡ ማውጣት ፤ ውሃን ፡ ገመልና ፡ በሬ ፡ በሚያዞረው ፡ በታላቅ ፡ መዘውር ፡ ከጕ ድጓድ ፡ ከዐዘቅት ፡ እያወጡ ፡ ማፍሰስ ፡ ማጠጣት ፤ ወደ ፡ ቡቃያና ፡ ወዳታክልት ፡ መውሰድ ፡ ማግባት ፤ መሳብ ፡ መጕተት ፤ እንደ ፡ ግብጦች ።

**መስኖ ፤ (ብ ፡ መሰንው)** ፤ በቁሙ ፤ የብይ ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ መሩት ፡ ወደ ፡ ወሰዱት ፡ የሚኼድ ። (ቀረት) ፤ ማየ ፡ ስሊሖም ፡ ዕዉር ፤ ኀበ ፡ ወሰድዎ ፡ የሐውር ።


**ሰኒሕ ፤ ሐት ፤ (ሰንሐ ፡ ይሰንሕ ፡ ይስ ናሕ ። ዕብ ፡ ሻናህ ፤ ተወለጠ)** ፤ መለዘብ ፤ መሻ ለጥ ፤ መመለጥ ፤ መበሕየት ፤ በራ ፡ መላጣ ፡ መኾን ፤ ነት ፡ ጉበት ፡ መምሰል ፡ የማኽል ፡ ራስ ። በርሐንና ፡ ቀርሐን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ናቸው ።

**ስኑሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ንሕት)** ፤ የለዘበ ፡ የሻለጠ ፤ ሙልጭ ፡ ቍልጭ ፡ ያለ ፤ በራ ፡ መላጣ ።

**ስንሐት** ፤ መለዘብ ፤ በራ ፡ ቡሓ ፡ መኾን ፤ በራ ነት ። ርእሱ ፡ ዘስንሐት ፡ (ዘሌ፲፫ ፡ ፵፩—፵፬) ።

**ሰንጢ ፤ ሰንጣ ፤—ዐማርኛ ፤—ሰነጸ ።**

**ሰንጠረዥ ፤ (ፋርስ ፡ ሸትረንክ ። ዐረ ፡ ሺጥረንግ)** ፤ በቁሙ ፤ የጨዋታና ፡ የመጫወቻ ፡ ስም ፡ መደቡ ፡ እንደ ፡ ጳፍጳፍ ፡ ያለ ፡ ጥቍርና ፡ ነጭ ፤ መጫወ ቻው ፡ የታነጠ ፡ የተነጠጠ ፡ የተቀረጠ ፡ ዕንጨት ፡ ስድ ስት ፡ ዐይነት ፡ ያለው ፤ ይኸውም ፡ ንጉሥ ፡ ንግሥት ፡ ፈት ፡ አውራሪ ፡ ፈረስ ፡ ግንብ ፡ እሽከር ፡ ይባላል ፤ የጨ ዎታውም ፡ ሐሳብና ፡ ምስጢር ፡ ፍጻሜ ፡ ጦርነት ፡ ነው ። ካህናት ፡ ኢይትባሀዩ ፡ ግብረ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ወገበጣ ፡ ወኵሎ ፡ ዘይመስሎ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፩ ፡ ፯) ።



ስንጠረዥ ፤

—፤ የቍጥር ፡ መደብ ፤ ቀመራዊ ፡ ቍጥር ፡ በየስልቱና ፡ በየቤቱ ፡ የሚጣፍበት ፡ ገጽ ፤ ያቡሻህር ፡ የመርሐ ፡ ዕዉር ፡ የመቅድሙ ፡ ወንጌል ፤ የስእልት ፡ የዐውደ ፡ ነገሥት ፡ የሌላ ውም ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ስንጠረዣዎም ፡ ባለስንጠረዥ ፡ እንዲሉ ።

**ሰነየ ፤ ሰኔ ፤—አማረ ፤—ሠነየ ፡ ሠኔ ።**

**ሰንዩ ፤ ዮት ፤ (ሰነየ ፡ ይሰኒ ፡ ይስኒ ። ዕብ ፡ ሻናህ ። ሱር ፡ ትናእ ። ዐረ ፡ ሰነይ)** ፤ መሰንየ ፤ መኽለት ፡ ኹለት ፡ ማድረግ ፤ ማጠፍ ፡ መደ ረብ ። በመልክ ፡ በባሕርይ ፡ መለወጥ ፤ ሌላ ፡ መኾን ፡ መምሰል ።

**ሳንይ ፤ ሳኒት ፤ (ዐረ ፡ ሳኒን)** ፤ የዕለት ፡ ቅ ጽል ፤ ኹለተኛ ፤ ካዕብ ፤ ካልኣይ ፡ መዓልት ። ቢሳኒት ፡ ዕለት ። በሳኒታ ፡ ለቀዳሚት ። እምሳኒተ ፡ ሰንበት ። ለለ ፡ ይጸብሕ ፡ ሳኒት ፡ (ዘኁ፯ ፡ ፲፰ ። ዘሌ፳፫ ፡ ፲፩ ፡ ፲፭ ። ስንክ ፡ የካ፳) ።

**ሳኒታ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ማግስት ፤ ነገታ ፡ ነገ ፤ ኹለተኛ ። በሳኒታ ፡ ፋሲካ ። ኢተአምር ፡ ዘትወልድ ፡ ሳኒታ ። ወበሳኒታ ፡ ካዕበ ። በሳኒታ ፡ ዕለት ፡ እምዘቀ ተለ ፡ (ዘኍ፴፫ ፡ ፫ ። ምሳ፳ ። ፳፰ ። ዮሐ፩ ፡ ፴፭ ። ኤር ፵፰ ፡ ፬) ።

**ሰኑይ ፤ (ዕብ ፡ ሼኒ)** ፤ የዕለት ፡ ስም ፤ ኹለ ተኛ ፤ ኹለት ፤ ስኖ ፡ የእሑድ ፡ ማግስት ፤ ሳኒታ ፡ ነገታ ። በሰኑይ ፡ ዕለት ። አመ ፡ ሰኑዩ ፡ ለሠርቅ ። እሑቲ ፡ ዕ ለት ፡ ሰኑየ ፡ መዋዕለ ፡ ኮነት ። ነበረ ፡ ሰኑየ ፡ መዋዕለ ። ዘሰኑይ ፤ ዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ (ሆሴ፮ ፡ ፪ ። ሕንገ ፡ ፳ ፡ ፴፱ ። ሚሬ፴፯ ፡ ፱ ። ዮሐ፲፩ ፡ ፮ ። እዋል) ።

**ሰንከሩር ፤ (ጽር ፡ ክሬኖን) ፤** አበባ ፤ ጽጌ ፡ ደንጐላ ። ወግልፈት ፡ ባዕሴሃ ፡ አምሳለ ፡ ሰንከሩር ፡ (፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፭) ። የደንጐላን ፡ ፍኙ ፡ ተመልከት ።

**ሰንከሪስ ፤ ሰንከሪሶን ፤ (ጽር ፡ ሲግኽሪሶን) ፤** ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፤ መሐር ፡ ተማሀል ፡ እናሕሲ ፤ ወይም ፡ ቅጽል ፤ መሐሪ ፡ መስተማህል ፡ ጎዳጌ ፡ በቀል ። ሰንከሪሶን ፡ እግዚእ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ሰብእ ፡ ዘየሐዩ ፡ እንበለ ፡ ኀጢአት ። አስተምሕር ፡ ለነ ፡ ሰአልናከ ፤ ዮሐንስ ፡ ሰንከሪስ ፡ (ግንዘ ። መዋሥ) ።

**ሰንክሳር ፤ (ዐረ ፡ ሲንክሳር ። ጽር ፡ ሲናክሳሪያ) ፤** የመጽሐፍ ፡ ስም ፤ ክመት ፡ እስክመት ፡ የሚነበብ ፡ የቅዱሳን ፡ ዜና ፤ ክየገድላቸው ፡ ባጭር ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡ የተሰበሰበ ፤ እሶድ ፡ ምእላድ ፡ እስትጉቡእ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሰንክሳር ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ጉባኤ ። ሰንክሳር ፡ ወደሳ ፡ ወንእዳ ፡ (ሰንክ ፡ መስ፩ ። ፳፫) ።

**ሰኒም ፤ ሞት ፤ (ሰነመ ፡ ይሰንም ፡ ይስንም ። ዐረ ፡ ሰኒመ) ፤** መርዘም ፤ ሻኛ ፡ ማውጣት ፤ እንደ ፡ ግመል ፡ መኾን ።

(ላ) **ስናም ፤ (ዐረ ፡ ሰናም) ፤** ሻኛ ፤ ጕብል ፤ በዠርባ ፡ በትክሻ ፡ ላይ ፡ የሚወጣ ፤ የድንክ ፡ የጕባጣ ፡ የተርካሳ ። ዘስናም ፡ (ዘሰናም) ፤ ሻኛማ ፡ ባለሻኛ ፡ ጕባጣ ፤ ድንክ ። ባሰብሱየች ፡ ግን ፡ የሰንን ፡ ዘር ፡ መስሏቸው ፤ ጥርሳም ፡ ገጣጣ ፡ መልክ ፡ ክፉ ፡ ይሉታል ፡ (ዘሌ፳፩ ፡ ፳ ። ፪ነገ ፡ ፳ ፡ ፲፩) ። በስናም ፡ ፈንታ ፡ ስንዓም ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ቀሌ) ።


**ሰኒን ፤ ኖት ፤ (ሰነነ ፡ ይሰንን ፡ ይስንን ። ዕብ ፡ ሻናን ። ዐረ ፡ ሰነ) ፤** መሞረድ ፡ መሳል ፤ ማሾል ፤ መዘርዘር ፡ ጥርስ ፡ ማውጣት ፤ ሹል ፡ ስል ፡ ጥርሳም ፡ ማድረግ ፤ የማጭድ ፡ የመጋዝ ፡ የብረት ፡ ኹሉ ። መንከስ ፡ መቀርጠፍ ፡ መዘብተር ፤ በጥርስ ፡ መቃወም ፡ የአራዊት ፤ ንዘረን ፡ እይ ።

**ሰናኒ ፤ መስንን ፤** የሚስል ፡ የሚያሾል ፤ ጥርስ ፡ የሚያወጣ ፤ የጥርስ ፡ ሐኪም ፤ ነካሽ ፡ ዘብታሪ ።

**ተሰነ ፤** ተሳለ ፡ ተሾለ ፡ ተሞረደ ፤ ጥርሳም ፡ ኾነ ። ተነከሰ ፤ ተዘበተረ ፡ ተጋጠ ፡ ተገመጠ ፡ ተነጨ ።

**ስኑን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ንንት ። ዕብ ፡ ሻኑን) ፤** የሾለ ፡ የተሳለ ፤ ጥርስ ፡ ያወጣ ፤ ስል ፡ ሹል ፡ ጥርሳም ፤ የተነከሰ ።

(ጥን) **ስን ፤ (ብ ፡ ስነን ፤ አስናን ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ሼን ። ዐረ ፡ ሲን) ፤** ጥርስ ፤ ከፊንጆ ፡ መንጋጋ ። ስን ፡ ቤዛ ፡ ስን ። ሐቀዩ ፡ ስነኒሆሙ ። ስነ ፡ አራዊት ፡ ምድር ። ስነ ፡ ሞሥርት ። አስናኒሃ ፡ ጽኑዕ ። ሰላም ፡ ለአስናኒከ ፡ (ማቴ፳ ፡ ፴፱ ። ስቈ፪ ፡ ፲፯ ። ሚራ፴፱ ፡ ፴ ። ስንክ ፡ ሚያ፴፫ ። ኩፋ ፡ ፴፭ ። ደራሲ) ።



ስን ፤

**ተሳነነ ፤** ተባላ ፡ ተናከሰ ፡ ተዘባተረ ፤ ጥርስ ፡ ለጥርስ ፡ ገጠመ ፤ ያራዊት ፡ የመኪና ። ተጣላ ፡ ተሟገተ ፡ ተከራከረ ። ኢትሳነን ፡ ምስለ ፡ መኰንን ። ኢትሳነን ፡ በቅሥት ፡ ጊጉይ ። ብእሲ ፡ ዘይሳነን ፡ ወይትዋቀሥ ። ዙሉ ፡ ለነፍሱ ፡ ይሳነን ፡ (ሢራ፰ ፡ ፲፱ ። ፲፩ ፡ ፱ ። ኤፍ፲፭ ፡ ፲ ። ሚክ፮ ፡ ፪) ።

**ተስናን ፤ (ናት) ፤** ጠብ ፡ ክርክር ፤ ሙግት ፡ ፍጅት ፤ ንግርንግር ፡ ጭቅጭቅ ። ዐዘቅቱ ፡ ተስናን ። የዐስየከ ፡ ቅሥት ፡ ወተስናን ። እመ ፡ ርኢክሙ ፡ ማእከለ ፡ አኀው ፡ ጋእዘ ፡ ወተስናነ ። ተስናነ ፡ ይሜጥሮስ ፡ (ዘፍ፲፱ ፡ ፯ ። ሢራ፳፱ ፡ ፳ ። ዲድ ፡ ፲ ። ግብ፲፱ ፡ ፴፰) ።

—፤ ፍርድ ፤ ቋንቋ ፤ የነገር ፡ ዐይነት ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ የማይመሳሰል ፡ ተጣይ ። ቤጐደየ ፡ ተስናን ። ይስሕቡክሙ ፡ ውስተ ፡ ተስናናት ። ወዘዘ ፡ ዚአሁ ፡ ቃሎሙ ፡ ወተስናኖሙ ፡ (ቀኖ ፡ ኒቅ ። ያዕ፪ ፡ ፯ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፲) ።

**አስተሳነነ ፤** አጣላ ፤ አሟገተ ፡ አከራከረ ፤ አፋረደ ። እስከ ፡ ታስተሳንኑ ። አስተሳንኖት ፡ (፩ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፭ ። ፊ ፡ መ ፡ ፳፫ ፡ ፺) ።

**መስተሳንን ፤ (ንንት ፡ ናን ፡ ናት) ፤** የሚያጣላ ፡ አጣይ ፤ ተጣይ ፡ ፈራሽ ።

**ሰንዐወ ፤—አጋጠመ ፤—ሰኒእ ፡ ሰንአ ።**

**ሰናፊል ፤ (ዐረ ፡ ስርዋል ። ዕብ ፡ ሳርባል) ፤** በቁሙ ፤ ሰሬ ፡ ሱሪ ፤ የእግር ፡ ቀሚስ ፡ ከወገብ ፡ እስከ ፡ ቍርጭምጭሚት ፡ የሚደርስ ፤ የወንዶች ፡ ልብልማ ፤ ድርማንቅ ፡ (አዋል) ።

**ሰኒጽ ፤ ጸት ፤ (ሰነጸ ፡ ይሰንጽ ፡ ይስንጽ ። ዕብ ፡ ሻኔጽ ፤ አጣበቀ ፡ አዋደደ) ፤** መሴነጥ ፤ መፋቅ ፡ መፈቅፈቅ ፤ ለማዋደድ ። ማለዘብ ፡ መንቀስ ፤ መኰላት ፤ ማደስ ፤ ማሳመር ፡ ማስጌጥ ፤ የዕፅ ፡ የሸክላ ፡ የብረት ። ሰንጠ ፡ ሰንጣ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ። ሰንአወን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ።

**ሰናጺ ፤ (ጺት ፡ ጽያን ፡ ያት) ፤** የሚሴነጥ ፡ ሰናጭ ፤ ነቃሽ ፡ አስጊያጭ ።

**ተሰንጸ ፤** ተሰነጠ ፤ ተፋቀ ፡ ለዘበ ፤ ተነቀሰ ፡ ተጌጠ ፡ ተዋበ ።

**ስኑጽ ፤ (ጻን ፡ ጻት ፡ ንጽት) ፤** የተሰነጠ ፡ ስንጥ ፤ ውብ ፡ ልዝብ ፤ ስምም ። በስኑጽ ፡ ፈንታ ፡ ስንጻት ፡ ይላል ፤ አያስኸም ። ኮሲ ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ ድደ ፡ ብሩር ፡ ስንጻት ፡ (ምሳ፳፭ ፡ ፲፩) ።

**ስንጸት ፤** ስንኣቂ ፤ ስምምነት ፤ አሰናንጥ ፤ ስነጣ ፡ ልዘባ ።

**ስንጽ ፤ ሰንጽ ፤** ንቅስ ፡ ንጥ ፤ መልክ ፡ ቅርጥ ፤ ጌጥ ፡ ፈርጥ ፤ የመሣሪያ ። ሽንጥ ፡ ሸንጣ ።

**ሰንቀወ፤(ነቀወ፤ ሰ፡ ባዕድ)፤** ሰነቃ፤ ሞዘቀ፤ መታ፡ አስፎጋኝ፤ ደረደረ፡ ከረከረ፤ ከመማሪ ያው፡ ጋራ፡ ፎጋኝ፡ አዜመ፤ ዘመረ፡ ገጠመ፤ አጕረመ ረመ። ያነዝሩ፡ ወይሰነቅዉ። ሠናየ፡ ሰንቅዊ። ከመ፡ ዘይሰነቀ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ ላሕ። ሰንቅዉ፡ ሎቱ፡ በመ ዝሙር፡(ኢዮ፳፩፡ ፲፪። ኢሳ፳፫፡ ፲፮። ሚራ፳፱፡ ፮። ዮዲ፲፯፡ ፩)። ነቀወን፡ እይ፤ የዚህ፡ ሥር፡ ነው።

**ሰንቃዊ፤(ዊት፡ ውያን፡ ያት)፤** የሚ መታ፡ የሚደረድር፤ የሚያስፎጋኝ፡ የሚፎጋኝ፡ የሚዘ ምር። ሕሳፍ፡ ሰንቃዊ፤ ዳዊት፡ ሰንቃዊ፡(መጽ፡ ምስ)።

**መሰንቅው፤(ዋን፡ ዋት፡ ቁት)፤** ዝኒ፡ ከማሁ፤ አዝማሪ፡ ዘማሪ፤ ዘፋኝ፡ ቀንቃኝ፡ መሪ።

**መሰንቆ፤(ብ፡ መሰናቅው፤ ቁት፡ ን ቆታት)፤** በቁሙ፤ ሙዚቃ፤ ዜማ። መሰንቆ፡ ወመ ዝሙር፡(ሚራ፵፡ ፳፩)። መሰናቅው። ቃሲ፡ መሰና ቁት። መሰንቆታት፡(አርጋ፡ ፫። ቅዳ። ራእ፲፬፡ ፪)። ከበሮ፡ እታሞ፡ ምሥጋር፡ በማለት፡ ፈንታ፡ መሰንቆ፡ ይላል፤ ስሕተት፡ ነው፡(መሳ፲፩፡ ፴፬። ፳፩፡ ፳፩። ፪ነገ፡ ፮፡ ፲፫)።



መሰንቆ፡

**መሰንቃዊ፤** ባለመሰንቆ፤ ዘፋኝ፡ አዝማሪ። ሕትዛዋዕ፡ ምስለ፡ መሰንቃዊት፡(ሚራ፱፡ ፬። ፊላስ)።

**ሙሲቂ፤(ዐረብ)፤** ሞዛቂ፤ ባለሙዚቃ። ዝ፡ ውእቱ፡ ሦራዕያን፡ ዜማ፡(ጊ፡ ወ፡ ሐ፡ ገ፲፯)።

**ተሰንቀወ፤** ተሰነቃ፡ ተመታ፡ ተደረደረ፤ ተ ከረከረ። ከመ፡ ይሰንቀው፡ ምዑዝ፡(አርጋ)።

**ስንቃዌ፤** አመታት፤ አደራደር፤ ምት፡ ድር ደራ፡ ክርክራ።

**ሰንሰለ፤ ሎት፤(ሰንሰለ፡ ይሰነስል፡ ይሰንስል። ሰሊል፡ ሰለ፡ ሰልሰለ። ዕብ፡ ሻ ልሴል)፤** ማሰር፡ መሰቀል፡ ማንጠልጠል፤ ማያያዝ፡ ማቈራኘት፡ ማቈላለፍ። መጽሐፍ፡ ማን፡ በሰንሰለ፡ ፈ ንታ፡ አሰንሰለ፡ ይላል፤ አያሰኝም። በከመ፡ አሰንሰለ፡ ወአስተኣንዘ፡ ወልደ፡ እግዚ፡ ህላዌ፡ ዚኣሁ፡ ምስለ፡ ሕቡሁ፤ ከማሁ፡ አሰንሰለ፡ ወአስተኣንዘ፡ ጳውሎስ፡ ህላዌ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ምስለ፡ ሕብ፡ ወወልድ፡(መጽ፡ ምስ፡ ገ፲፭)።

**ሰንሳሊ፤(ሊት፡ ልያን፡ ያት፤ ሰልት)፤** የሚያስር፤ የሚያይዝ፤ አሳሪ፡ ሰንሰለት፡ ሠሪ።

**ተሰንሰለ፤** ተያዘ፡ ታሰረ፡ ተቈራኘ፤ ከሰንሰለት፡ ገባ።

**ተሰናሰለ፤** ተሳሰረ፤ ተቈላለፈ፤ ተያያዘ፤ ተቈ ረኛኘ፤ ተገጣጠመ። ይሰናሰላ፡ በበይናቲሆን። ናሁኬ፡ ተሰናሰላ፡ ትእዛዛት፡ እሐቲ፡ በእሐቲ። እለ፡ ይዘ መዱ፡ ወይሰናሰሉ፡(ዘፀ፳፮፡ ፫። መጽ፡ ምስ። ፍ፡ ን፡ ፳፱፡ ፪)።

**ስንሱል፤(ላን፡ ላት፡ ስልት)፡** የተሳሰረ፤ የተቈራኘ፤ ቍርኝ። እሉ፡ ክልኤቱ፡ ግብራት፡ ስንሱ ላን፡ ወእኍዛን፡ በበይናቲሆሙ፡(አፈ፡ ተ፳፯)።

**ስንሳሌ፤** አስተሳሰር፤ እስራት፤ ቍራኝነት።

**ሰንሰል፤(ብ፡ ሰናስል፤ ላት። ዕብ፡ ሻርሸራ፤ ሻልሼሌት። ሱር፡ ሺሻልታ። ዐረ፡ ሲልሲሌት)፤** ሰንሰለት፡ ባለ፪፡ ፍንጅ፡ ባለ፫፡ ጠንግ፤ ማሰሪያ፡ ማቈራኛ፤ መስቀያ፡ ማንጠልጠያ። ሰናስል፡ ዘኀጺን። አሰሮ፡ በሰናስል። ሰናስለ፡ ወ ርቅ። እለ፡ ሙቁሓን፡ እደዊሆሙ፡ በሰናስል፡(ሰ ንክ፡ ኅዳ፳። ገድ፡ ተክ። አፈ፡ ተ፲። ኢዮ፴፯፡ ፰)።

**ሰንሰል፤(ዐማርኛ)፤** ስምዛ፤ የስምዛ፡ ዕን ጨት፡ ቅጠል፤ ሥሩ፡ እንደ፡ ሰንሰለት፡ እየተያያዘ፡ የሚዘምት፡ በጽቁ፡ የሚቈላለፍ። ሁስጺን፡ ተመልከት።

**ሰንሰረቀ፤(ቋት። ዕብ፡ ሲረቆን። ዐረ፡ ሰረቅ)፤** ጥሩ፡ ሐር፤ የሐር፡ ልብስ፡ ዘፋም፡ ቅጠላም፤ አበባ፡ ሐረግ፡ የተሣለበት። ስርግዋን፡ በጽጌ፡ ሰንሰ ረቀ። ሲይ፡ ወሰንሰረቋት። መዋጥሐ፡ሆን፡ ዘሰንሰ ረቀ፡(ሰንክ፡ ጥር፲፪። ራእ፲፰፡ ፲፪። ኢሳ፫፡ ፳፫)።

**ስናፔ፤(ጽር፡ ሲናፒ)፤** ሰናፍጭ፤ ቅንጣቱ፡ ታናናሽ፡ አገዳው፡ ታላላቅ፡ ቅጠሉና፡ ፍሬው፡ የሚሰን ፍጥ፡ የሚያስለቅስ፤ መራራ፡ ሐምጣጣ፤ መድኀኒት፡ የ ሚኾን፡(ማቴ፲፫፡ ፴፩። ፲፯፡ ፳። ማር፬፡ ፴፩)። ወናሁ፡ ፈነውኩ፡ ለከ፡ እነሂ፡ ስናፔ፡ ጠዐማ፤ ወተመጠዋ፡ ደራ፡ ለስናፔ፡ ወበልዓ፤ ወአንብዓ፡ አዕይንቲሁ፤ ወ አውፅኣ፡ እምአፉሁ፡ ወነደፋ። ወአእመረ፡ በዝ ንቱ፡ ከመ፡ ሰራዊቱ፡ መሪራን፡(ዜና፡ እስ)።



ስናፔ፡

**ሰንፔር፤(ጽር፡ ሳፕፊሮስ። ዕብ፡ ሳፊ(ፒ)ር)፤** ዕንቍ፡ የዕንቍ፡ ስም፤ ሕብሩ፡ ቀይ፤ ፍ ሕም፡ የሚመስል፡(ዘፀ፳፬፡ ፲። ሕዝ፩፡ ፳፮። ራእ ፳፩፡ ፲፱)።

**ሰዐደ**፤ (ዕብ፡ ሳዐድ)፤ ዐገዘ፡ ረዳ፡ ደገፈ። ሰደየን፡ እይ።

**ሰዐወ**፤ (ትግ፡ ሐበ)፤ ሮጠ፡ ፈረጠጠ፤ ዐ ሰፈ፡ ኼደ፤ ተራመደ።

**ስዓ**፤ ፋጣ፡ ጥድፊያ፡ ችኰላ፤ ያክኼድ።

**ሳዕ**፤ **ሰዐት**፤ **ሰዓት**፤ (ዕብ፡ ወሱር፡ ሻዓ። ዐረ፡ ሳዐት)፤ ሰዓ፤ ሰዓት፤ ጊዜ፤ የዕለት፡ ፳፬ኛ፡ ክፍል፤ ፷፡ ደቂቃ፤ ከ፳፬ቱ፡ ክፍል፡ አንዱ፤ ዘመን፡ ወራት። የሰዓት፡ መሣሪያ፡ ባላ፲፪፡ ክፍል። እምጊዜ፡ ጽባሕ፡ እስከ፡ ሳዐ፡ ዕለት፡ ይመሲ። በዙሉ፡ ጊዜ፡ ወበዙሉ፡ ሳዕ። ሰዓተ፡ ስቅለቱ፡ ስሱ፡ ሳዕ። ሳዐ፡ ሞቱ፡ ርሑቅ። በዙሉ፡ ሰዓት። መጠነ፡ አሐቲ፡ ሰ ዓት። መንፈቀ፡ ሰዓት። በአይ፡ ሰዓት። በስድስቱ፡ ሰዓት፡ (ስንክ፡ ማንፂ። አርጋ። መጽ፡ ምስ። ስንክ፡ ኅዳ፫። ዘሌ፲፯፡ ፪። ዳን፬፡ ፲፯። ራእ፰፡ ፩። ፫፡ ፫። ዕር፡ ኢሳ፱፡ ፳)። የፊደል፡ ስም፡ ሳት፡ ሰ። ሳትን፡ ተመል ከት፤ ይህ፡ ፪ኛ፡ ስም፡ ነው።

**ሰዐታት**፤ **ሰዓታት**፤ ሰዓቶች፤ ጊዜዎች፡ የ ዕለት፡ ክፍሎች፤ ዘመኖች፡ ወራቶች። እለ፡ ያሰግሉ፡ ውስተ፡ ሰዐታት፡ ወዕለታት፡ ወለያልይ። እምዕ ለት፡ እኪት፡ ወእምሰዓታተ፡ መንሱት። ለምንት፡ ይረስዖኒ፡ እግዚ፡ ለሰዓታትየ፡ (ቀሌ። ሊጦ። ኢዮ ፳፱፡ ፩)። ቪሑ፡ ዓመት፡ ፩፡ ዕለት፡ ተብሎ፡ ሲቈጠር፡ ግን፡ አንዱ፡ ሰዓት፡ ፲፭፡ ዓመት፡ ከ፫፡ ወር፡ ይኾ ናል። እስመ፡ ዐሠርቱ፡ ምእት፡ ዓመት፡ ከመ፡ አ ሐቲ፡ ዕለት፡ ውስተ፡ ስምዐ፡ ሰማያት፡ (ኩፋ፡ ፬። መዝ፡ ፹፱። ፪ጴጥ፡ ፫፡ ፰)።

**ሰዖዝገዘ**፤—**መፍዘግዘ**፤—**ዐዘዘ፡ አስዖ ዘዘ**።

**ሰዐለ**፤—**ለመነ፡ ጠየቀ**፤—**ሰአለ**።

**ሰዐለ**፤—**ሣለ፡ ፈጠረ**፤—**ሠዐለ**።

**ሰዐለ**፤ (ዐረ፡ ሰዐለ)፤ ሳለ፡ ሳኣም፡ ኸን፤ ኡሁ፡ ኡሁ፡ አለ፤ ዐነጠሰ።

**ሰዓል**፤ (ሱር፡ ሻዕላ። ዕብ፡ ሺዑል)፤ ሳል፤ ጉንፋን፤ ንጥሻ፡ ዕንጥስታ። ወሰእመ፡ መጽአ፡ ሰዓል፡ ለይሚጥ፡ ገጾ፡ ወይስዐል፡ (አረጋ፡ ድ፲፫)።

**ስዒም**፤ ሞት፤ (ሰዐመ፡ ይስዕም፡ ይ ስዐም። ዕብ፡ ናሻቅ)፤ መሳም፤ መሳለም፤ መጨም ጨም፤ በአፍ፡ በከንፈር፡ መንካት፡ መልከፍ። ዘእስ ዕሞ፡ ውእቱ፤ በስዒምኑ፡ ታገብእ። አንዘተ፡ ወሰዐ መቶ። እስከ፡ ይትሌቃሕ፡ ይስዕመከ፡ ርእስከ። አ ዘዘ፡ ከመ፡ ይስዐም፡ እግረ፡ አቡሁ። ሐአጋረ፡ ክር ስቶስ፡ ሎቱ፡ እንዘ፡ ትስዕሚ፡ (ሉቃ፳፪፡ ፵፰ና፡ ፸። ምሳ፳፡ ፲፫። ሚሬ፳፮፡ ፳። ዮሴፍ። ስንክ፡ ታኅ፳)።

**ሰዓሚ**፤ (ሚት፡ ምያን፡ ያት፤ ዐምት)፤ የሚስም፡ ሳሚ። ቤተ፡ ክሲያን፡ ሳሚ፡ እንዲሉ።

**ተስዕመ**፤ ተሳመ፤ ተጨመጨመ።

**ተሳዐመ**፤ ተሳሳመ፤ አፍ፡ ላፍ፡ ተገናኘ፤ ከን ፈር፡ ለከንፈር፡ ተጋጠመ። ተሓቀፉ፡ በበይናቲሆሙ፡ ወተሳዐሙ። ጽድቅ፡ ወሰላም፡ ተሳዐማ፡ (ስንክ፡ ሚያ፲፰። መዝ፡ ፹፬)።

**ስዕመት**፤ መሳም፤ (ጥሳ) መሳም፤ መሳሳም፤ አሳሳም፡ ስሞሽ። ስዕመተ፡ አፉሁ። ስዕመተ፡ ጸላኢ። ወሀቦሙ፡ ስዕመተ፡ ትእምርት፡ (ማሕ፩፡ ፪። ምሳ ፳፬፡ ፮። ዲድ፡ ፳፱)።

**ስዕነ**፤—**ተሳነ**፤—**ስእነ**።

**ሳዕን**፤—**ጫማ**፤—**ሣእን**።

**ሳዕር**፤—**ሣር**፤—**ሣዕር**፤ ሥዕረ።

**ስዒር**፤ ሮት፤ (ሰዐረ፡ ይስዕር፡ ይስ ዐር። ዕብ፡ ሻዐር፤ ከፈተ፡ ዘጋ)፤ መሻር፤ ማ ቀረድ፤ ማፍረስ፡ መናድ፤ ማሳለፍ፡ መለወጥ፤ ማሸነፍ፡ ድል፡ ማድረግ፤ ማጥፋት፡ መደምሰስ፤ መፍታት፡ ማሰ ናበት። ስዒረ፡ ጾም። ሰዐረኒ፡ እምግብየ። ያትብር፡ ነገሥታተ፡ ወይስዕር። ኢመጻእኩ፡ እስዐሮሙ፡ ለኦ ሪት፡ ወለነቢያት። ስዒሮ፡ ሞት፡ በሥጋ። ሰዐሮ፡ ለ ጣዖት። ንስዐር፡ ዝክሮ፡ እምድር። ወትስዕር፡ ዝክ ሮሙ፡ ኅቡረ። ሰዐሮ፡ ለገብርከ። ሰዐር፡ ሰብአ፡ (ቀሌ። ሉቃ፲፰፡ ፱። ዳን፪፡ ፳፩። ማቴ፭፡ ፲፯። ድጓ። ቅዳ። ምሳ፩፡ ፲፪። መዝ፡ ፱። ሉቃ፪፡ ፳፱። ማርኝ፡ ፴፯)። በሰዐረ፡ ፈንታ፡ አሰዐረ፡ ይላል፤ የመላሽ፡ ስሕ ተት፡ ነው፡ (ዘዳ፪፡ ፳፪። ፳፱፡ ፳፯። ኢያ፳፬፡ ፲፪)።

**ሰዓሪ**፤ (ሪት፡ ርያን፡ ያት፤ ዐርት)፤ የሚሽር፡ ሻሪ፤ አፍራሽ፤ አጥፊ፡ ደምሳሽ። ሰዓሬ፡ ሕግ። ሰዓርያነ፡ ሰንበት። ሰዐርተ፡ ጾም፡ (አዋል)።

**አስዐረ**፤ አሻረ፤ አስፈረሰ፤ አስጠፋ።

**ተስዕረ**፤ ተሻረ፡ ፈረሰ፤ ተሰበረ፤ ጠፋ፤ ተፈታ፡ ተለቀቀ። ይሰዐር፡ እምሚመቱ። ይሰዐር፡ ተዋስቦ። ተስዕረ፡ አርዑቶሙ። ባሕርኒ፡ ተስዕረት፡ እንከ። ተስዐርኪ፡ እምደዌኪ፡ (ቀሌ። ፍ፡ ን፡ ፳፱፡ ፩። ኢ ሳ፱፡ ፬። ራእ፳፩፡ ፩። ሉቃ፲፫፡ ፲፪)።

**ስዑር**፤ (ራን፡ ራት፡ ዕርት)፤ የተሻረ፡ ያለፈ፡ የቀረ፤ ሽር፡ ሹር። ስዑር፡ እምክህነት። ስዑር፡ ወውጉዝ፡ (አብጥሊ)። የሹም፡ ሽር። ቀዳም፡ ስዑር፤ ቅዳሜ፡ ሹር፡ (ዐማርኛ)።

**ስዕረት**፤ መሻር፤ (ጥሻ) መሻር፤ አሻሻር፤ ሽ ረት። ስዕረተ፡ ጾም። ስዕረተ፡ ሞት። ሠመርኩ፡ በስ ዕረቱ፡ ለናስጣርዮስ። ስዕረተ፡ ኪዳን፤ ስዕረተ፡ ክ ህነ፡ (ቀሌ። ተረ፡ ቄር። ዮሴፍ)።

**ሳዓር**፤ (ዕብ፡ ሻዐር)፤ ታላቅ፡ በር፤ የከ ተማ፡ የቤተ፡ ክሲያን፡ የቅጥር፡ ደጅ፡ አፍ።

**ሱዓሬም**፤ (ዕብ፡ ሾዓሬም)፤ ሰዓርያን፤ ሰዐርት፤ በረኞች፡ የሚከፍቱና፡ የሚዘጉ፡ የሚጠብቁ። (ኤርሚ፯፡ ፲፯)።

**ሳዕስዐ**፤ (ዕብ፡ ሻዕሴዐ)፤ ደበ፡ አበኘ፤ ተደ በተ፡ ደበ፡ አሰው።

**አንሳዕሰዐ** ፤ አፈሳ ፡ አገነፈለ ፤ አፍለቀለቀ ። ፈሳ ፡ ገነፈለ ፡ ተፍለቀለቀ ። ወያንሳዐስዓ ፡ ሲሲሖል ፡ ከመ ፡ ጽህርት ፡ (ኢዮ፡ ፵፩ ፡ ፳፫) ።

**ሳዕሳዕ** ፤—የቃል ፡ ምላሽ ፤—ማእዛእ ፤ ወሥእ ።

**ሰዓት** ፤—በቁሙ ፤—ሰዐወ ።

**ሳፍ** ፤ (ዕብራ) ፤ መድረክ ። ቅድመ ፡ ሳፍ ፡ (ሕዝ፵፩ ፡ ፲፮) ።

**ሰፌድ** ፤ ሰፈደ ። አው ፡ ሳፍዶ ፤ (ሳፈደ ። ዕብ ፡ ሻፋድ ፤ በሳ ፡ ነደለ) ፤ መሻፈድ ፡ መጐምዘዝ ፡ መድራት ፤ መኝጋበል ፡ መዘርጋት ፡ እንደ ፡ ሰፌድ ፡ መኾን ፤ የእንስት ።

**ሰፌድ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፤ ዝርግ ፤ ስ ታታ ፡ ስፌት ።

**ሰፍደል** ፤ (ብ ፡ ሰፋድል) ፤ ሥሥ ፡ ረቂቅ ፡ የሥጋ ፡ ክርታስ ፤ የፅንስና ፡ የሽል ፡ የሕፃን ፡ ልብስ ፤ ልጅ ፡ ሲወለድ ፡ ከማሕፀን ፡ ለብሶት ፡ ተጠቅሎበት ፡ የሚ ወጣ ። ኦ ፡ ዘታወፅኦ ፡ ለሕፃን ፡ እምሐቌ ፡ ብእሲ ፡ ወትፌንዎ ፡ ውስተ ፡ ክርሥ ፡ ብእሲት ፡ ወትጠበ ልሶ ፡ በሰፋድል ፡ ረቂቅ ፤ ወእንዘ ፡ ማይ ፡ ውእቱ ፡ ታረግዖ ፡ በጥበብከ ፡ ወትነፍኆ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈሰ ፡ ሕይወት ። ለባሴ ፡ ሰፋድል ፡ (ቅዳ ፡ አት ። አዋል) ።

**ሰፍዎ** ፤ **ዎት** ፤ (ሰፈወ ፡ ይሴፉ ፡ ይሰፉ ። ዕብ ፡ ጻፋህ ፤ ተነበ) ፤ ማማከት ፤ ተስፋ ፡ መስጠት ፡ በተስፋ ፡ ማጽናት ፤ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚኾነውን ፡ አስቀ ድሞ ፡ መንገር ፡ ማብሠር ፤ አይዞኽ ፡ ማለት ፤ ማስታ መን ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰፈወ ፡ ፈንታ ፡ አሰፈወ ፡ አስ ተሰፈወ ፡ ይላል ፤ አድራጊውን ፡ ባስደራጊ ፡ አንቀጽ ፤ አያ ስኻም ። አሰፈዎሙ ፡ ብዙኀ ፡ ንዋየ ። ለእመ ፡ ወሀቡ ፡ ወለእመ ፡ አሰፈዉ ፡ ሊድኅር ። አሰፈውክሙ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡ ሐሰተ ። ብዙኀ ፡ ያስተሴፍወከ ። ቦ ፡ ዘበ ኀፍረት ፡ ያስተሴፍዎ ፡ ለማኅፈሩ ፡ (ዮሴፍ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፭ ፡ ፫ ። ኤርምያ ፡ ፲፭ ። ሢራ ፲፫ ፡ ፯ ። ፳ ፡ ፳፫) ። ቀፈ ዮን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ክፋል ፡ ነው ።

**ሰፋዊ** ፤ **መሰፍው** ፤ የሚያማክት ፤ አማ ኪች ፤ ተስፋ ፡ ሰጭ ፤ አይዞኽ ፡ ባይ ።

**ተሰፈወ** ፤ ተስፋ ፡ አደረገ ፤ ታመነ ፤ ባለተስፋ ፡ ኾነ ። እሴፎ ፡ ሕይወትየ ። ምድር ፡ እንተ ፡ ትሴፎ ፡ ዝናመ ። ኪያየ ፡ ይሴፈዉ ፡ አሕዛብ ፡ (ኢዮ፪ ፡ ፲፬ ። ፳፱ ፡ ፳፫ ። ኢሳ፶፩ ፡ ፭) ።

**ስፍው** ፤ (**ዋን** ፡ **ዋት** ፡ **ፋት**) ፤ የታመነ ፡ የተወከለ ፤ በተስፋ ፡ ያለ ፤ ባለተስፋ ።

**ተስፋ** ፤ (**ፋት**) ፤ በቁሙ ፤ አለኝታ ፤ እምነት ፤ አገኛለኹ ፡ ማለት ፤ ጸጋ ፡ ሀብት ። ከመ ፡ ያጽንዓ ፡ ለተ ስፋ ፡ አበው ። እለ ፡ ቀብጹ ፡ ተስፋሆሙ ። እመ ፡ ቦ ፡ ተስፋ ፡ ለድኂን ። ኢታስተኀፍረኒ ፡ እምተስፋየ ። ይ ጽንሑ ፡ ተስፋሁ ፡ ለአብ ። እልክቱ ፡ ተስፋት ፡ (ሮሜ ፲፭ ፡ ፰ ። ሢራ ፲፯ ፡ ፳፬ ። ቀሌ ። መገ ፡ ፻፲፰ ። ግብ ፩ ፡ ፬ ። አፈ ፡ ድ፳፫) ።

**አሰፈወ** ፤ **አስተሰፈወ** ፤ (ሰፈወ) ፤ አስታ መነ ። ኀባቡ ፡ አስደራጊ ፤ ፍችው ፡ አድራጊ ። አና ። አስተ ፡ አሰቦታቸው ፡ ገብተዋል ።

**ሰፌሕ** ፤ **ሐት** ፤ (ሰፍሐ ፡ ይሰፍሕ ፡ ይስ ፋሕ ። ዐጕል) ፤ መስፋት ፡ መንሰራፋት ፤ መብዛት ፤ ሰፊ ፡ ዝርግ ፡ መኾን ፡ (ዘፍ፳፬ ፡ ፲፫ ። ምሳ፳፫ ፡ ፴፪ ። ጥበ፯ ፡ ፳፬ ። ፳ ፡ ፭ ። ፫ነገ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ። ፬ ፡ ፳፭) ። እም ቅድመ ፡ ይስፍሑ ፡ ደመናት ፡ (ቅዳ) ።

—፤ ማስፋት ፤ መዘርጋት ። ይሰፍሑ ፡ ሰርበታቲ ሆሙ ። እግዚ ፡ ዘሰፍሐ ፡ ሰማየ ። ሰፍሑ ፡ ሠቃቲ ሆሙ ። ሰፍሐት ፡ ማእደ ፡ ቅድሜሆሙ ። ሰፍሑ ፡ እደዊሆሙ ፡ ወነሥኡ ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፭ ። ዘካ፲፪ ፡ ፩ ። ዮዲ፬ ፡ ፲፩ ። ዮሴፍ ። ኩፋ ፡ ፳) ። በሰፍሐ ፡ ፈንታ ፡ አስ ፍሐ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ። አስፈሖሙ ፡ ርእ ሶሙ ፡ ውስተ ፡ አስትቶ ። ያስፍሕ ፡ እግዚ ፡ ለያ ፌት ። አስፍሐ ፡ እግዚ ፡ እደ ፡ ሰርሽ ፡ (ቂር ፡ ጸኣ ። ኩፋ ፡ ፺ ። ዮሴፍ) ።

**ተሰፍሐ** ፤ ተዘረጋ ፤ ተንሰራፋ ፤ ተነፋ ፡ ዐበጠ ። ተሰፍሐ ፡ እደ ፡ እኩያን ። የማኑ ፡ ለእግዚ ፡ ተሰፍ ሐት ፡ ውስተ ፡ ሰሉ ፡ ምድር ። ተሰፍሐት ፡ ሃይማ ኖት ፡ ርትዕት ፡ ውስተ ፡ ሰሉ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ። ተጠ ምቀ ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅት ፡ ናጥራን ፡ ወተሰፍሐ ፡ ሥ ጋሁ ፡ ወከነ ፡ ጸሊመ ፡ (ዮሴፍ ። ቀሌ ። ስንክ ፡ ግንቦ ። ጥቅ፲፫) ።

**ስፋሕ** ፤ (**ሓን** ፡ **ሓት** ፡ **ፍሕት**) ፤ የሰፋ ፡ ሰፊ ፤ ዝርግ ፤ ብዙ ። ምድር ፡ ሱርክት ፡ ወስፍሕት ። ከነፌሆሙ ፡ ስፋሓን ። እግዚ ፡ ስፋሐ ፡ ሀብት ፡ (ኩፋ ፡ ፳ ። ፩ዜና ፡ ፫ ፡ ፲፫ ። ግንዘ) ።

**ስፍሐት** ፤ መዘርጋት ፤ (ጥዘ) መዘርጋት ፤ አዘ ረጋግ ፤ ዝርግነት ፤ ስፋት ። በስፍሐተ ፡ እዴሁ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ። ስፍሐታ ፡ ለማኅደር ፡ (ቀሌ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫) ።

**ስፍሕ** ፤ ስፋት ፡ ሰፊነት ፤ የወርድ ፡ የጐን ፡ ፃ ራቱ ፡ ማእዝን ። ስፍሐ ፡ በሓውርት ። ስፍሐ ፡ ም ድር ። ወይኩን ፡ ስፍሐ ፡ ምጣኔ ፡ ማእከለ ፡ ቤት ፡ ወቤት ፡ ዐሥርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ መክየድ ፡ (ኢሳ፰ ፡ ፰ ። ዕንባ ፡ ፩ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯ ፡ ፪) ። በስፍሕና ፡ በርሕብ ፡ ፈንታ ፡ ጽፍሕ ፡ ይላል ፤ በጸሊብ ፡ ፈንታ ፡ ሰሊብ ፡ እንዲል ። ጽ ፍሐ ፡ መሠረቱ ፡ ሠላሳ ፡ በእመት ። ጽፍሑ ፡ ዕሥር ፡ በእመት ፡ (ዮዲ፩ ፡ ፪ ። ዘካ፭ ፡ ፪ ። ሕዝ፵፩ ፡ ፯) ።

**ምስፋሕ** ፤ መዘርጊያ ፤ (ጥዘ) መዘርጊያ ፤ ቦታ ። ምስፋሕ ፡ ወምስትግባእ ፡ (ቅዳ) ። መጽሐፍ ፡ ግን ፤ ምስፋሕ ፡ ወምስትጉቡእ ፡ ይላል ፤ አያስኻም ። ዳግመ ኛም ፡ በምስፋሕ ፡ ፈንታ ፡ ምስትስፋሕ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**መስፍሕ** ፤ (ብ ፡ **መሳፍሕ**) ፤ በቁሙ ፤ መ ስፍ ፤ የብረት ፡ ማስፊያ ፡ መቀጥቀጫ ፡ ታችኛው ፤ ሲመ

ይሻውም ፡ ይኻናል ። አንበረት ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ዲበ ፡ መስፍሕ ፡ ወዘበጡ ፡ ሐራ ። አዘዘ ፡ ያምጽኡ ፡ መስፍሐ ፡ ነሃቢ ፡ ወይስብሩ ፡ ቍየጺሆሙ ፡ (ስንክ ፡ ነሐሸ፳) ።



መስፍሕ ፤

**ሰፈጠ ፤ ጦት ፤ (ሰፈጠ ፡ ይሰፍጥ ፡ ይስፍጥ ። ዐረ ፡ ሰፋጠ ፤ ለገሰ ። ዕብ ፡ ሻፋጥ ፤ ዳኘ ፡ ፈረደ)** ፤ መሸፈጥ ፡ ማበል ፤ ማታለል ፡ መሸንገል ፤ መደለል ፡ ማባበል ፤ ማሞኘት ፡ ማቄል ፤ ማባት ፡ ከመንገድ ፡ ማውጣት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰፈጠ ፡ ፈንታ ፡ አሰፈጠ ፡ ይላል ፤ አያሰኛም ። **አስፍጢዮ ፡ ለምትኪ ። አስፍጣ ፡ ሊቱ ፡ ለዛቲ ፡ ብእሲት ። አርዌ ፡ ምድር ፡ አስፈጠተኒ ። ያስፍጡነ ፡ ውስተ ፡ ዘኢንክል ፡ ገቢረ ፡** (መሳ፲፬ ፡ ፲፭ ። ዮዲ፲፪ ፡ ፲፩ ። ዘፍ፫ ፡ ፲፫ ። ቀሌ) ።

**ሰፋጢ ፤ (ጢት ፡ ጥያን ፡ ያት)** ፤ የሚሸፍጥ ፤ የሚያታልል ፤ ሸፋጭ ፡ አታላይ ። **ይመውእሙ ፡ ጻሕቀ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወሰፋጢት ፡ ብዕል ፡** (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰) ።

**ተሰፍጠ** ፤ ተታለለ ፤ ተሸንገለ ፤ ተሞኘ ። **ሄሮድስ ፡ ተሰፍጠ ፡ በምክንያተ ፡ ዝሙት ። እስመ ፡ ይሰፈጥ ፡ እምሰይጣናት ። ተሰፍጠ ፡ ለፍትወት ፡** (ስንክ ፡ ጥቅ፱ ። ፈልክ ፡ ፲፵ ። ፲፰፱) ።

**ስፉጥ ፤ (ጣን ፡ ጣት ፡ ፍጥ)** ፤ የተሞኘ ፤ የተታለለ ፤ ተላላ ፤ ድልል ፡ ሽንግል ፤ ስሑት ። **አ ፡ ድንግል ፡ አኮ ፡ ወራዚት ፡ ስፉጣን ። ዘናዘዘኪ ፡** (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**ስፍጠት** ፤ መታለል ፡ ማታለል ፤ አታላይነት ፤ ተታላይነት ። **ስፍጠተ ፡ ብዕል ። ስፍጠታተ ፡ ሰይጣን ፡** (ማቴ፲፫ ፡ ፳፪ ። ፈልክ ፡ ፱) ።

**ምስፋጥ ፤ (ጣት)** ፤ ማታለያ ፡ መሸንገያ ፤ ማሳቻ ፡ ማሳሳቻ ።

**ሰፍይ ፤ ዮት ፤ (ሰፈየ ፡ ይሰፊ ፡ ይስፊ ፤ ረፍአ ። ዐረ ፡ ሰፈ ፤ ጐነጐነ ። ሽፋ ፤ ፈወሰ)** ፤ መስፋት ፡ መጥቀም ፤ ማያያዝ ፡ መሸለል ፤ የልብስ ፡ የጫማ ፡ ያክርማ ። **አኒም ፡ ወሰፍየ ፡ አልባስ ። ክመ ፡ ይስፊ ፡ ቀታነ ፡ አማእን ። ሰፍየ ፡ አስፈሬዳት ፡** (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፫ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳ ። ገድ ፡ ኪሮ) ።

**ሰፋዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት)** ፤ የሚሰፋ ፡ ሰፊ ፤ ጠላፊ ። **ሰፋዬ ፡ አማእን ፡** (ማብ፱ ፡ ፵፫) ።

**መስፌ ፤ (ብ ፡ መስፍያት ፡ መሳፍይ)** ፤ መስፈያ ፡ መሳፍቻ ፤ ወስፌ ፤ መርፌ ፤ የስፌት ፡ መኪና ። **እንዘ ፡ ይሰፊ ፡ በመስፌ ፡ ተሠጥቀ ፡ አጻብዒሁ ። ወለሰ ፡ ሸሉ ፡ ዐዲዎታ ፡ ለመስፌ ። ንዋየ ፡ መስፌ ፡** (ስንክ ፡ ሚያ፴ ። ፈልክ ፡ ፲፻፲፯ ። እዋል) ።



መስፌ ፤

**ተሰፍየ** ፤ ተሰፋ ፡ ተጠቀመ ፤ ተጋጠመ ፤ ተያያዘ ። **ወበዳግም ፡ ንፍኀተ ፡ ቀርን ፡ ይሰፈዩ ፡ አዕፅምት ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡** (ቅዳ ፡ ያዕ) ።

**ስፉይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ፈት ፡ ፍይት)** ፤ የተሰፋ ፡ ስፍ ፤ ጥልፍ ፤ ግብረ ፡ መርፌ ።

**ስፍየት** ፤ መስፋት ፤ መስፋት ፤ አሰፋፍ ፤ ስፍነት ፤ ስፌት ፡ ጥቅማት ፤ የስፌት ፡ ዕቃ ። **ስፉይ ፡ በሥላስ ፡ መዓርገ ፡ ስፍየት ፡** (ፈልክ ፡ ፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፴፩ ፡ ፰) ።

**ምስፋይ ፤ (ያት)** ፤ መስፈያ ፤ መስፊያ ፤ ማስፊያ ፤ ቦታ ፡ መሣሪያ ።

**ሴፌላ ፤ ሴፌል ፤ (ጽር ፡ ሴፈላ ። ዕብ ፡ ሽፌላ)** ፤ ቈላ ፡ ጐድጓዳ ፤ ዝብጥ ፡ ረባዳ ፤ ዝቅዝቃ ፡ ወዳቃ ፤ ወንዛወንዝ ፡ ሸለቆ ፡ (ዓብድ ፡ ፲፱ ። ፪ዜና ፡ ፳፯ ፡ ፲) ።

**ሰፈለ ፤ (ትግሬ)** ፤ አቋተ ፤ ደቀነ ፤ ለመናጨት ፡ ለማድቀቅ ፤ ለመቀጥቀጥ ፤ የደቈት ፡ የብረት ።

**ሰፌልያ** ፤ መዶሻ ፡ መራጃ ፤ መድሐ ፤ አለሎ ፤ ታችኛውንም ፡ ያሳያል ። **ነሃቢ ፡ ይዘብጥ ፡ በሰፌልያሁ ። ድምፀ ፡ ሰፈልያ ። ዘበጦ ፡ ነሃቢ ፡ በሰፌልያ ፡** (ኢሳ፵፩ ፡ ፯ ። ኤር፲ ፡ ፱ ። ሚሬ፴፰ ፡ ፳፰ ። ያዕ ፡ ዘእል) ። **በሰፌልያ ፡ ወበመዝረብ ፡ አባላቲክ ፡ እለ ፡ ተመትሩ ፡** (ደራሲ) ።

**ሰፈን ፤ ኖት ፤ (ሰፈነ ፡ ይሰፍን ፡ ይስፍን ። ሰፍሐ ፤ ሰፈፈ)** ፤ መስፈን ፤ መስፋት ፡ መብዛት ፤ መምላት ፡ መሸፈን ፤ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፡ መኾን ፤ ክኹሉ ፡ መድረስ ፤ እንደ ፡ ነፋስና ፡ እንደ ፡ ብርሃን ። **እስመ ፡ ዓዲሁ ፡ ኢሰፈነ ፡ ስብከቱ ፡ በላዕለ ፡ ኵሉ ። ዐብየ ፡ እከይ ፡ ወሰፈነ ፡ ጽልእ ፤ ሰፈነት ፡ ኀሰሣ ፡ እከይ ፡ ወዐመፃ ፡ ወዝሙት ። ሶበ ፡ ሰፈነ ፡ አሚን ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ። ናሁ ፡ ሰፈነት ፡ ወሰፈፈት ፡ እንበለ ፡ ንትጋ ፡** (አፈ ፡ ድ፱ ። ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፰ ፡ ፪ ። ደራሲ) ።

—፤ መሾም ፡ መንገሥ ፤ መሠልጠን ፤ በላይ ፡ መኾን ፤ ተሹሞ ፡ መግዛት ፤ ማዘዝ ። **መግብት ፡ እለ ፡ ይሰፍኑ ፡ ላዕለ ፡ ቅኔ ። ሰፈነ ፡ ላዕለ ፡ ብዙኃን ፡ አሕዛብ ። ሰፈነት ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ድንጋፄ ፡ እንተ ፡ ኢተሐዘብዋ ። ናሁ ፡ አማርያ ፡ ካህን ፡ ይሰፍነክሙ ። ዘይሰፍን ፡ ምኔተ ፡** (፩ዜና ፡ ፳፱ ፡ ፯ ። ዮሴፍ ። ጥበ፲፯ ፡ ፲፯ ። ፪ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ ። ፈልክ ፡ ፲፯) ።

**ሰፋኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት)** ፤ የሚገዛ ፡ ገዥ ፤ ጌታ ፤ ንጉሥ ፡ አለቃ ። **ከነ ፡ ሰፋኔ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ። አልቦሙ ፡ ሰፋኒ ፡** (፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፳፮ ። ፯ ፡ ፲፰ ። ፲፩ ፡ ፳፱ ። ፲፰ ፡ ፲፯) ። ሐለይት ፡ መስቈቅዋት ፡

ብማለት ፡ ፈንታ ፡ ሰፋንያት ፡ ይባል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (፪ ዜና ፡ ፴፭ ፡ ፳፭) ።

—፤ የሚሰፍን ፡ የሚመላ ፤ ሰፊ ፡ ምሉእ ። መንግሥቱ ፡ ሰፋኒት ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ኪዳ) ። በሰፋኒት ፡ ፈንታ ፡ ሰፋን ፡ ይባል ። አርአያ ፡ ሰሊደት ፡ ሰፋን ፡ (አረጋ) ።

**ስፉን** ፤ (ፍን ፡ ፍት ፡ ፍንት) ፤ የሰፈነ ፡ የ መላ ፤ ምሉእ ፡ ፍጹም ። ህላዌሁ ፡ ስፉን ። ስፍንት ፡ ከመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (አዋል ። ቅዳ ፡ አት) ።

**ስፍንት** ፤ ምላት ፡ ስፋት ፤ ብዛት ፤ ግዛት ፡ ሥ ልጣን ፤ ጌትነት ።

**መስፍን** ፤ ት ፤ (ብ ፡ መሳፍን ፤ ት) ፤ በቁሙ ፤ ገዥ ፡ ፈራጅ ፤ የወረዳ ፡ ሹም ፤ ራስ ፡ ደጃች ፡ አ ዝማች ፤ አበጋዝ ፡ አለቃ ፤ ነገድ ። ሜመ ፡ ሎሙ ፡ መሳ ፍንተ ። መስፍነ ፡ ሰርያ ። ወይእቲ ፡ መስፍኖን ፡ ለ አንስት ። መስፍነ ፡ ኀምሳ ። ዐሥርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ መሳፍንት ፡ (ግብ ፲፫ ፡ ፭ ። ሉቃ ፳ ፡ ፳ ። ዮሓ ፲፭ ፡ ፲፫ ። ኢሳ ፫ ፡ ፫ ። ዘፍ ፳፭ ፡ ፲፯) ።

**ምስፍና** ፤ መስፍንነት ፤ ሹመት ፡ ግዛት ፤ ሥል ጣን ፤ በትረ ፡ መንግሥት ። አመ ፡ ምስፍና ፡ ባርቅ ። ኢይወፅእ ፡ ምስፍና ፡ እምአባሉ ። እግዚ ፡ አዕበየ ፡ ክብርየ ፡ ወምስፍናየ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ (ጥበ ፡ ጠቢ ። ዘፍ ፵፱ ፡ ፲ ። ዮሴፍ) ።

**አስፈነ** ፤ አሰፋ ፡ አበዛ ፤ አሰፈነ ፡ አሠለጠነ ፡ (አርጋ) ።

**ስፊና** ፤ (ዕብራ) ፤ የነፋስ ፡ መርከብ ፡ ባለሸራ ፤ ነፋስ ፡ የሚነዳው ።

**ስፍን** ፤ (ዕብ ፡ ከማ ። ዐረ ፡ ከም) ፤ ንኡስ ፡ አገባብ ። የስፍር ፡ የቍጥር ፡ የልክ ፡ የመጠን ፡ ጥያቄ ፤ ስ ንት ፤ ምን ፡ ያኸል ። ሰቡ ፡ ስፍን ፡ ኍልቆሙ ። ስፍን ፡ ቦቱ ፡ ዲናራት ፡ ዘለቅሐ ። ስፍን ፡ እምኤዲስቆጸሳት ። ስፍነ ፡ ጊዜ ፡ ዘነትዐ ፡ ምጢእ ፡ ወውእቱ ፡ ተመይጠ ፡ ወከነ ፡ መዋኤ ። ስፍነ ፡ አህጉረ ፡ ጽኑዓነ ፡ እለ ፡ አመዝ ብሮን ፡ ወስፍነ ፡ አብያተ ፡ እለ ፡ አንኀሎን ፤ ወስፍነ ፡ ዕደወ ፡ ኃያላነ ፡ እለ ፡ ረበየ ፡ ይትዋነይዎሙ ፡ ዕጼ ያት ። ተአምር ፡ ስፍነ ፡ ነገሥት ፡ ርኩሳነ ፡ እለ ፡ ዐ ለዉ ፡ (ቀሌ ። አፈ ፡ ተ፲፩ ። ቢኖዶ ። ዮሴፍ ። ማንዘ ። ዲድ ፡ ፪) ።

**እስፍንቱ** ፤ ስንቱ ፡ ስንቶቹ ፤ ስንቶች ፤ ምን ፡ ያኸሎች ። በእስፍንቱ ፡ ዕለታት ። እስፍንቱ ፡ ዓመ ታት ፡ ዘነበርከ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ። እስፍንተ ፡ ይ ደልዎ ፡ ሰእጐ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ውስተ ፡ ማኅበር ። እስፍንተ ፡ ነፍሳተ ፡ ሰብአ ፡ ኀይለ ፡ ተአምርኪ ፡ ዘ መሀጠ ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ ። ፊልክ ፡ ፵፭ ። ደራሲ) ።

**ሰፍነግ** ፤ (ብ ፡ ሰፋንግ ። ጽር ፡ ስፖጎስ ። ዕብ ፡ ስፎግ ። ዐረ ፡ ስፍንጅ) ፤ በቁሙ ፤ የባሕር ፡ ቡቃያ ፡ እንጕዳይ ፤ ለስላሳ ፡ ዐይናማ ፡ የፈንገሬ ፡ ዐይንት ፤ የንላ ፡ ማጠቢያ ፡ መታጠቢያ ፤ ውሃ ፡ የሚመጥ ፡ የሚያ ንግ ። ሰፍነግ ፡ ልምሉም ። ምድር ፡ ተፈጥረት ፡ በአምሳለ ፡ ሰፍነግ ፡ እንተ ፡ ትነብር ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ፡ (አፈ ፡ ተ፳ ። ቀሌ ። ማቴ ፳፯ ፡ ፵፰ ። ማር ፲፭ ፡ ፴፮ ። ዮሐ ፲፱ ፡ ፳፱) ።

**ሰፈፍ** ፤ ፎት ፤ ሰፈፈ ፡ ይሰፍፍ ፡ ይስ ፍፍ ፤ ሰፈነ ። ዕብ ፡ ሳፋፍ ። ዐረ ፡ ሰፊ) ፤ መሰፈፍ ፡ መንሳፈፍ ፤ መሰፋት ፡ መምላት ፡ መንተርፈፍ ፤ መልቶ ፡ መትረፍ ፡ መትረፍረፍ ፤ ከልክ ፡ ማለፍ ፤ የፈሳሽ ። ናሕንሐንና ፡ ዛሕዝሐን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ናቸው ። ወለዝንቱ ፡ ግብር ፡ ናሁ ፡ ንሬእዮ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ ይሰ ፍፍ ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ። እምከመ ፡ ጸርዩ ፡ ልቡና ፡ ወኀሊና ፡ ኢይትዐደው ፡ እምዐቅሙ ፤ ወእ ምከመ ፡ ሰፈፈት ፡ ፍትወት ፡ ትከውን ፡ ሐጸ ፡ ቀ ታሌ ። ከመ ፡ ይስፍፉ ፡ መዛግብቲከ ፡ ብዙኀ ፡ ሥር ናየ ፡ ወወይነ ፡ ማሕበብትከ ፡ ይስፍፍ ። ከመ ፡ እ ብነ ፡ ፈለግ ፡ ይሰፍፍ ፡ (አፈ ፡ ተ፳፯ ። ፈላስ ። ምሳ፫ ፡ ፲ ። ኢዮ፳፱ ፡ ፳፱) ።

—፤ ማጥራት ፡ ማጥለል ፤ የጠላ ፡ የጠጅ ፡ የማር ፡ የወ ተት ።

**ስፉፍ** ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ፍፍት) ፤ የሰፈፈ ፤ የመላ ፡ የተረፈ ፤ የጠራ ፡ የጠለለ ። ሳሬ ፡ እንዲል ፡ ጥሩ ፡ ሲል ፡ (ዐረብ) ።

**ሰፈፍ** ፤ (ዐማርኛ) ፤ በቁሙ ፤ የማር ፡ ገለባ ፤ የጠላ ፡ ሐሠር ፡ ገፈት ።

**ሰፈር** ፤ ሮት ፤ (ሰፈረ ፡ ይሰፍር ፡ ይስ ፍር ። ዕብ ፡ ሳፋር) ፤ መስፈር ፡ መቍጠር ፤ መጣፍ ፡ መነመር ፤ መለካት ፡ መመጠን ፤ ከልክ ፡ ከሚዛን ፡ ከቍና ፡ ከላዳን ፡ ከመዝገብ ፡ ማግባት ፤ ይህን ፡ ያኸል ፡ ማለት ። ስእኑ ፡ ኍልቆቶ ፡ ወሰፈረ ፡ እምነ ፡ ብዝኁ ። በመስ ፈርት ፡ ዘሰፈርክሙ ፡ ይሰፍሩ ፡ ለክሙ ። መኑ ፡ ዘሰ ፈሮ ፡ ለማይ ፡ በሕፍኑ ። ሰፈራ ፡ እግዚ ፡ ለመንግሥ ትከ ። ከመ ፡ ይስፍራ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ (ኩፋ ፡ ፵ ። ማቴ ፯ ፡ ፪ ። ኢሳ ፵ ፡ ፲፪ ። ዳን ፡ ፭ ፡ ፳፮ ። ዘካ ፪ ፡ ፪) ።

—፤ መስፈር ፤ በቁሙ ፡ ቦታ ፡ መያዝ ፤ ሲኼዱ ፡ ውሎ ፡ ማረፍ ፤ መጠለል ፤ ድንኳን ፡ መትከል ፤ ለማደር ። ግዐዘ ፡ እምነ ፡ አራራ ፡ ወሰፈረ ፡ ውስተ ፡ ዱቂ ፡ (ታሪ ፡ ነገ) ።

**ሰፋሪ** ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት) ፤ በቁሙ ፤ የሚ ሰፍር ፤ የሚቈጥር ፤ ቈጣሪ ፡ ነማሪ ።

**አሰፈረ** ፤ አሰፈረ ፡ አስቈጠረ ፤ ሰፈሩ ፡ ቈጠሩ ፡ አለ ። ያሰፍር ፡ ሥርናየ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፫) ።

**ተሰፍረ** ፤ ተሰፈረ ፤ ተለካ ። ኢይሰፈር ፡ ኆጻ ፡ ባሕር ፡ (ኤር ፴፫ ፡ ፳፪) ።

**ስፉር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ፍርት) ፤ የተሰፈረ ፤ የተለካ ። ኢምጡን ፡ ወኢስፉር ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ስፍረት** ፤ መስፈር ፤ መሰፈር ፤ አሰፋፈር ፤ ስፍ ሮሽ ፡ ሰፈራ ፤ አርምሻ ። እለ ፡ ያሰግሉ ፡ በስፍረተ ፡ እግር ፡ ወበመስፈርተ ፡ እድ ፡ (ቀሌ) ።

**ስፍር ፤** በቁሙ ፤ ልክ ፡ መጠን ፤ ይህን ፡ ያኽል ፡ የሚባል ፤ አኀዝ ፡ ቍጥር ። የዐረብ ፡ ዜሮ ።

**መስፈርት ፤ (ቃት ፤ መሳፍር ፡ ት) ፤** መስፈሪያ ፤ መቍጠሪያ ፤ ልክ ፡ መጠን ፡ ሚዛን ። ንግ በር ፡ መስፈርተ ፡ ንስቲተ ። መስፈርተ ፡ ኢፍ ። መሳ ፍር ፡ ክልኤ ። ወሀቦ ፡ ሜጦ ፡ ለውእቱ ፡ መካን ፡ በመ ስፈርተ ፡ ወርቅ ፡ ስድስቱ ፡ ምእት ። ኢይግበሩ ፡ ዐ መፃ ፡ በውስተ ፡ ሐሳበ ፡ አውራኅሆሙ ፡ ወኢበመሳ ፍረ ፡ ሚዛኖሙ ፡ (ዓሞ፰ ፡ ፭ ። ሩት፪ ፡ ፲፯ ። ምሳ፳ ፡ ፲ ። ፩ዜና ፡ ፳፭ ፡ ፳፩ ። መቃ ፡ ፲፫) ።

**ሰፈር ፤** በቁሙ ፤ ስፍራ ። ማኅፍ ፡ ዳርቻ ፡ ዘርፍ ። ዘፈርንና ፡ ዘርፍን ፡ ጽፍርንም ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አ ንድ ፡ ነው ።

**ምስፋር ፤ (ራት) ፤** መስፈሪያ ፡ መሳፈሪያ ፤ ሰፈር ፡ ስፍራ ፡ ቦታ ፤ ምዕራፍ ።

**ስፍራ ፤ (ትግ ፡ ወዐረ) ፤** በቁሙ ፤ ማእድ ፡ ሰደቃ ።

**እስፌር ፤** ዓምና ፤ ያለፈው ፡ ዓመት ፤ ስፍሩና ፡ ቍጥሩ ፡ የመባለት ። ምስክር ፡ ሳይኖረው ፡ ባላገባቦቹ ፡ ይሉታል ፤ አሚርን ፡ ተመልከት ፡ (ደቂቅ ፡ አገባብ) ።

**ሳፍራ ፤ (ዐረ ፡ ጸፍራ) ፤** የነፋስ ፡ ባሕርይ ፤ ነፋሳዊ ፡ ጠባይ ። ሳፍራ ፡ ዘውእቱ ፡ ጠባይዐ ፡ ነፋ ሳዊ ። ፀንስ ፡ ይትወለድ ፡ እምኔይለ ፡ ሳፍራ ። ሀ ኬት ፡ ይትወለድ ፡ እምኔ ፡ ሳፍራ ፡ (ፈላስ ፡ ገ፲፯ ፡ ፴ ፡ ፹፰) ።

**ሶፎር ፤ (ጽር ፡ ሶፊር ። ዕብ ፡ ኦፊር) ፤** የወርቅ ፡ አገር ። ኦፊርን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አ ንድ ፡ ነው ። እብነ ፡ ፈለገ ፡ ሶፎር ፡ (ኢዮ፳፪ ፡ ፳፬) ።

**ሶፎር ፤ (ጽር ፡ ሳፕፊሮስ ። ዕብ ፡ ሳፊር) ፤** ዕንቍ ፡ የዕንቍ ፡ ስም ። ሰንፔርን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ጣፊና ፡ መላሽ ፡ በሰንፔር ፡ ፈንታ ፡ ሶፎር ፡ እያሉ ፡ ኹለት ፡ ስም ፡ አድርገውታል ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፯ ። የካ፱ ። ድጓ ። አርጋ ፡ ፮) ።

**ሰፈርጐል ፤ (ዐረ ፡ ሰፈርጃል) ፤** የተክል ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፤ ፍሬው ፡ ብጫ ፡ የትርንጎ ፡ ዐይነት ፤ መ ጠኑ ፡ ከትርንጎ ፡ የሚያንስ ፤ ጣፍጣ ፡ (ቈስጠ ፡ ፴፱ ። ቢኖይ) ።



ሰፈርጐል ፤

**ስፋሪዳ ፤ (ጽር ፡ ስፊሪዲያ) ፤** ክብ ፡ እን ክብል ፡ ድንብልብል ፤ እንደ ፡ ኳስ ፡ ያለ ። ስፋሪዳ ፡ ዘኀ ጺን ፡ እለ ፡ ርቡዕት ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳) ።

**ሰቅ ፤—በቁሙ ፡ ማቅ ፤—ሡቅ ።**

**ሳቀየ ፤—በቁሙ ፤—ማቀየ ።**

**ሰቅይ ፤ ዮት ፤ (ሰቀየ ፡ ይሰቂ ፡ ይስቂ ። ዐረ ፡ ሰቀይ ። ዕብ ፡ ሻቆህ ። ሱር ፡ ሽቂይ) ፤** ማጠጣት ፡ ማርካት ፤ መጠጥ ፡ መስጠት ፤ መጨመር ። እሰቅያ ፡ ለገነት ። ይፈለፍል ፡ ነቅዐ ፡ ወይሰቂ ። ዘይ ሰቅዮሙ ፡ ለአድባር ። ሰቀዮኒ ፡ ማየ ። ሰብዐቱ ፡ መ ሳውር ፡ በዘይሰቅይዎን ፡ ለመኃትዊሃ ፡ (ሚራ፳፱ ፡ ፴፭ ። ዮኤ፫ ፡ ፲፰ ። መገ፤ ፡ ፲፫ ። አፈ ፡ ድሻ ። ዘካ፴ ፡ ፪) ።

**ሰቃዪ ፤ መስቀዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ቀይት) ፤** የሚያጠጣ ፡ አጠጭ ፡ ጨ ፤ ዐዳይ ፡ ሰጪ ። ሰቃዩ ፡ አትክልት ። ሥሁዓን ፡ በላዕያን ፡ ወሰቃይ ያን ፡ ወሰካርያን ፡ (አዋል ። መቃ) ።

**ተሰቅየ ፤** ተጠጣ ፤ ውሃው ። ጠጣ ፡ ረካ ፡ ጠ ገበ ። ወምድርሰ ፡ እምነ ፡ ዝናም ፡ ትሰቀይ ፡ ማየ ፡ (ዘዳ፲፩ ፡ ፲፩) ።

**ስቁይ ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ቂት ፡ ቅይት) ፤** የጠጣ ፡ የረካ ፡ የጠገበ ። ስቁይ ፡ እማይ ፡ (ኢዮ፲፭ ፡ ፲፮) ።

**ስቅየት ፤** መጠጣት ፡ (ጥጠ) መጠጣት ፤ ማጠ ጣት ፤ አጠጣጥ ፡ (አርጋ ፡ ፫) ።

**መስቂ ፤ (ብ ፡ መሳቅይ) ፤** ማጠጫ ፤ መ ጠጥ ፡ መስጫ ፤ መቅጃ ፡ መገልበጫ ። የሸማኔ ፡ ዕቃ ፡ መ ወርወሪያ ፤ ማጉን ፡ ሰድር ፡ ወይም ፡ ግራውን ፡ ለዝሐ ፡ የሚያጠጣበት ። ቀናዲለ ፡ ወመሳቅየ ፡ መኃትወ ፡ ወ መሳውረ ። ንዋየ ፡ መስቂ ፡ (ክብ ፡ ነገ ። ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ።



መስቂ ፤

**ምስቃይ ፤ (ያት) ፤** ቦይ ፡ መትረብ ፤ የመስኖ ፡ ውሃ ፡ የሚሳብ ፡ የሚጐተት ። ዘቦቱ ፡ ምስቃይ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ይደልዎ ፡ ለረኪበ ፡ ፍኖት ፡ ኀበ ፡ በዊእ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

**ሰቂል ፤ ሎት ፤ (ሰቀለ ፡ ይሰቅል ፡ ይስ ቅል ። ዕብ ፡ ሻቃል ። ሱር ፡ ሽቃል ፤ ትቃል ። ዐረ ፡ ተቀለ ፤ ሸቀለ) ፤** መስቀል ፡ ማንጠልጠል ፤ መ መዘን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ማንሣት ፤ ማንን ። ዘገብረ ፡ ሰማየ ፡ ወሰቀሎ ። ሰቀላ ፡ ለምድር ፡ ዲበ ፡ ዐራቃ ። ንሕነ ፡ ሰ ቀልናሁ ፡ ለሰማይ ፡ ዘእንበለ ፡ ዐምድ ። ሰቀለ ፡ መ ንጠዋልዐ ፡ ዘወርቅ ። መትክል ፡ በዘይሰቅሉ ፡ ቦቱ ፡ ኵሎ ፡ ንዋየ ። ሰቀሉ ፡ ምስሌሁ ፡ ክልኤተ ፡ ፈያተ ። ሰቀልዎ ፡ መልዕልተ ፡ ዕፀ ፡ ፄዊኑ ፡ (ኢሳ፵፬ ፡ ፳፬ ። ኢዮ ፳፮ ፡ ፯ ። ቀሌ ። አፈ ፡ ተ፳፭ ። ሕዝ፲፭ ፡ ፫ ። ድጓ ። ዮሐ ፲፱ ፡ ፲፰ ። ስንክ ፡ መጋ፱) ።


**ሰቃሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ ቀልት) ፤** የሚሰቅል ፤ የሚያንጠለጥል ፤ መዛኝ ፡ ሰቃይ ። አይሁድ ፡ ሰቃልያን ፡ (ቀሌ) ።

**አስቀለ ፤** አሰቀለ ፤ አስመዘነ ።

**ተሰቅለ** ፤ ተሰቀለ ፡ ተመዘነ ፤ ተያዘ ፡ ተንጠለ ጠለ ። ተሰቅለ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ። ምንትኒ ፡ ዘይሰቀል ፡ ቦቱ ፡ ኅሲናሁ ። ይሰቀሉ ፡ በአጽምዖቲሆሙ ። በእላ ፡ ክልኤ ፡ ትእዛዛት ፡ ተሰቅሉ ፡ ኦሪት ፡ ወነቢያት ፤ (፩ኢጥ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ። ፊልክ ፡ ፩፻፬ ። ሉቃ ፲፱ ፡ ፵፰ ። ማቴ ፳፪ ፡ ፵) ።

**ስቁል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ቅልት) ፤ የተሰቀለ ፡ የተንጠለጠለ ፤ እንጥልጥል ። ዲበ ፡ ምንት ፡ ስቁል ፡ ሕላ ቃቲሃ ። ወይከውኑ ፡ ስቁላነ ፡ ቦቱ ። ዘስቁል ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ። ነጸሩ ፡ ጦማረ ፡ ስቁለ ፡ ማእከለ ፡ ሰማይ ፡ ወም ድር ። ሕግ ፡ ወነቢያት ፡ ስቅልት ፡ ውስተ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚ ፡ ወፍቅረ ፡ ቢጽ ። ተግባሮሙ ፡ ስቁል ፡ በእግ ዚአ ፡ መናፍስት ። ስቁል ፡ በሰጽሲጸ ፡ በቅል ፡ (ኢዮ ፴፰ ፡ ፮ ። ኢሳ፳፪ ፡ ፳፬ ። ዘዳ፳፩ ፡ ፳፫ ። መጽ ፡ ጦማ ። ፊልክ ፡ ፺፰ ። ሔኖ፴፰ ፡ ፪) ።

**ስቅለት** ፤ በቁሙ ፤ መሰቀል ፤ መሰቀል ፤ አሰ ቃቀል ፤ ሰቀላ ፡ ስቅሎሽ ፤ ስቁልነት ። ስቅለቱ ፡ ለኢየ ሱስ ። በእንተ ፡ ስቅለትከ ፡ ወሞትከ ፡ (ቀሌ ። ማኅ፱) ።



ስቅለት ፡

**ሰቀላ** ፤ (ብ ፡ ሰቃልው) ፤ በቁሙ ፤ ቤት ፡ ድንኳን ፡ ሞላላ ፡ ዠላላ ፤ ክብና ፡ ምእዙን ፡ ያይደለ ። በአምሳለ ፡ ሰቀላ ። ገብርተ ፡ ሰቀላ ። ቦአ ፡ ውስተ ፡ ሰ ቀላሁ ፡ ወሰከበ ። ሠለስቱ ፡ ሰቃልው ። በሰቃልው ፡ ወበአጐበር ፡ (ገድ ፡ ተክ ። ግብ፲፰ ፡ ፫ ። ኩፉ ፡ ፯ ። ማቴ ፲፯ ፡ ፬ ። መቅ ፡ ታም) ።

**ሰቅል** ፤ ሰቅሎስ ፡ ን ፤ (ጽር ፡ ሲክሎስ ። ዕብ ፡ ሼቄል) ፤ የሚዛን ፡ ደንጊያ ፤ ብረት ፡ ርሳስ ፤ ኻያ ፡ አበሊ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ዲድርክም ፡ የሚያነሣ ። የገንዘብ ፡ ስም ፤ ወርቅ ፡ ብር ፡ እንደ ፡ ዲድርክም ፡ ያለ ፤ እ ስራኤል ፡ ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሚሰጡት ፤ አንዱ ፡ ሰቅል ፡ ፪ ፡ ድሪም ፡ ወይም ፡ ፳ ፡ ጌራ ፤ ጌራና ፡ አበሊ ። ሰቅልና ፡ ዲድርክም ፡ ትክክል ፡ ናቸው ፤ ሃው ፡ ሰቅል ፡ ፩ ፡ ምናን ፡ ይኾናል ፡ (ዘፀ፴ ። ፳፫ ፡ ፳፬ ። ፴፱ ፡ ፩ ፡ ፪ ። መሳ፳ ፡ ፳ ። ሕዝ፴ ፡ ፲ ። ፵፭ ፡ ፲፪) ።

**መስቀል** ፤ (ዕብ ፡ ሚሽቃል ፤ ሚዛን) ፤ በቁሙ ፤ መስቀያ ፤ መመዘኛ ፤ መሰቀያ ፤ መንጠልጠያ ፤ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ። ይጹር ፡ መስቀለ ፡ ሞቱ ። እምነት ፡ ዘመስቀለ ፡ ክርስቶስ ። አስተርእዮቱ ፡ ለ መስቀል ። እስመ ፡ ነገረ ፡ መስቀሉሰ ፡ እበድ ፡ ው እቱ ፡ በኀበ ፡ ህጉላን ፡ (ማር፰ ፡ ፴፬ ። ስንክ ፡ መስ፲፯ ። መጋ፲ ። ፩ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፯) ።

**መስቀላት** ፤ **መሳቅል** ፤ መስቀሎች ፤ መከራ ዎች ፡ (ስንክ ፡ ታኅ፯ ፡ ፲፯ ። መጋ፲ ። ግን፱ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፴፩) ።

**መስቀላዊ** ፤ የመስቀል ፡ ወገን ፤ ዐይነት ፤ ም ልክት ፤ መስቀልኛ ፡ ማ ፤ ባለመስቀል ፤ መስቀላም ። አ ምላክ ፡ መስቀላዊ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**መስቅለ** ፤ መስቀል ፡ ኾነ ፤ መስቀል ፡ መሰለ ፤ ተመሳቀለ ።

**ምስቁል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ቅልት) ፤ የተመሳ ቀለ ፤ ምስቅል ፤ መስቀልማ ። ምስቁለ ፡ አእዳው ። ይ ግበር ፡ መንዲለ ፡ ምስቁለ ፡ ኅዐለ ፡ መታክፍቲሁ ፡ (ፊ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፰ ። ፴፭ ፡ ፭) ።

**አመስቀለ** ፤ አመሳቀለ ፤ መስቀል ፡ አደረገ ።

**ሰቂማ** ፤ **ሰቂሞን** ፤ (ጽር ፡ ሲኪማ ። ዕብ ፡ ሽኬም) ፤ ሴኬም ፡ ስመ ፡ ሀገር ፡ ቦታ ፤ ያዕቆብ ፡ ከሴኬም ፡ አባት ፡ ከኤሞር ፡ የገዛት ፤ ኋላም ፡ ለዮሴፍ ፡ የሰጣት ፡ (ዘፍ፴፫ ፡ ፲፰—፳ ። ፵፰ ፡ ፳፪ ። መገ ፡ ፫፱ ። ፫፯) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ምርኾ ፡ ይሉታል ፤ ባለቅኔም ችም ፡ ሰቀመ ፡ ማረከ ፡ ብለው ፡ ይገባሉ ፤ ኹሉም ፡ ስሕ ተት ፡ ነው ። ኤሞር ፡ የሀገሪቱ ፡ ቀንድ ፡ ዋና ፡ ባላባት ፡ ገዥ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በልጁ ፡ ስም ፡ ሴኬም ፡ አሰኝቷታል ። ያዕቆብም ፡ ዳስና ፡ በረት ፡ ስለ ፡ ሠራባት ፡ ሱኮት ፡ ብሏ ታል ። ሴኬም ፡ ህየ ፡ በደና ፡ ተሀጕለ ፡ ወበሰራ ፡ አቤ ሜሌክ ፡ ቀተለ ፡ (ቅኔ ። ዘፍ፴፬ ፡ ፩—፴) ። የማእገዝ ፡ መላ ሾች ፡ ሴኬምን ፡ ሰቂማ ፡ ሰላሉት ፡ ኀባቡም ፡ ምስጢ ሩም ፡ ተሳስቷል ፤ ሰቂማና ፡ ሴኬም ፡ ፩ ፡ ስም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አይደለም ።

**ሰቀ፡ቀ፡** ፤ **ቆት** ፤ (ሰቄቄ ፡ ይሰቀ፡ቀ፡ ፡ ይስቀ፡ቀ፡ ። ዕብ ፡ ሽቃቅ ፤ ሹቅ ። ዐረ ፡ ሽቅ) ፤ መፈለግ ፡ መሻት ፤ መመኘት ፡ መጐምዠት ፤ መውደድ ፡ መጣጣት ፤ ባንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ መውደቅ ፤ ልሙትበት ፡ ማለት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰቄቄ ፡ ፈንታ ፡ ተሰቄቄ ፡ ይ ላል ። ኢተሰቄቀ ፡ ንዋየክሙ ። ኀፍረት ፡ ተሰቀፉቀ ፡ ን ዋየ ፡ ባዕድ ። ዘኢይሰቄቀው ፡ ንዋየ ፡ ባዕድ ፡ በዐመፃ ፡ (ግብ፳ ፡ ፴፫ ። ፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፰ ። ቀሌ) ።

**ተሰቄ** ፤ **ተሰቄቄ** ፤ ተሻ ፡ ተፈለገ ፡ ተወደደ ፤ ገንዘቡ ።

**አሰቄቄ** ፤ **አስተሰቄቄ** ፤ አሻ ፡ አስፈለገ ፤ አስ መኘ ፡ አስጐመዠ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ።

**ሰቄቃው** ፤—**ጩኸት** ፤—**ቄቀወ** ፡ **እስ** **ቄቀወ** ።

**ሰቀ፡ር** ፤ **ሮት** ፤ (ሰቄረ ፡ ይሰቀ፡ር ፡ ይስ ቀ፡ር ፤ ነቄረ ። ዕብ ፡ ዳቃር ፤ ወጋ ፡ ሰነቀረ) ፤ መሸንቈር ፤ መሰርሰር ፡ መብሳት ፡ መንደል ፤ መፋር ፡ መ ቈፈር ፤ ለመብሳት ። ለአእባን ፡ ኢይክል ፡ ይስቀ፡ሮሙ ፡

ማይ ፤ ይሰቀሩ ፡ ሕብያቲ ። ኢይስቀሮ ፡ ቀስተ ፡ ብርት ። ትስቍር ፡ አንፎ ፡ በኅርወት ። ይስቍር ፡ እዝኑ ፡ ጥይዕተ ። ስቁረ ፡ እዘኒሆሙ ፡ (ዮሴፍ ። ኢዮሳጅ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ። ቅዳ ፡ ዮሐ ። ቀሌ) ።

**ሰቋሪ** ፤ (ሬት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ቁርት) ፤ የሚሽነቍር ፡ የሚበሳ ፤ ሰርሳሪ ፡ ሽንቋሪ ።

**መስቌር** ፤ (ብ ፡ መሳቍር) ፤ መሽንቈሪያ ፤ መብሻ ፡ መሰርሰሪያ ፤ ወስፌ ፡ አሬ ፡ ምሣር ።

**መስቀር** ፤ (ዕብ ፡ ሚሽቃር) ፤ የተሳበና ፡ የዱሊ ፡ ቤት ፤ ዘጉሉ ፡ ልብሱ ፡ መደበቂያውና ፡ መሽንቀሪያው ። መርከብ ፤ ታቦተ ፡ ኖኅ ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ ባለ መስኮት ፡ ማለት ፡ ነው ። ጸረበ ፡ ሎቱ ፡ መስቀረ ፡ ዐቢየ ፡ ወነበረ ፡ ደቤሃ ፡ ወሠሰስቱ ፡ አልሕምት ፡ ነበሩ ፡ ምስሌሁ ፡ በይእቲ ፡ መስቀር ። ወውእቱ ፡ መስቀር ፡ ይጸቢ ፡ ደበ ፡ ማይ ። መስቀረ ፡ ዕፀ ። እትአመን ፡ ባቲ ፡ እስመ ፡ አርኣያ ፡ መስቀር ፡ ይእቲ ፡ (ገድ ፡ አዳ ። ሔኖቭ፱ ፡ ፩ ፡ ፮ ፡ ፳ ። አርጋ ፡ ፫ ። ድጓ) ።

**አስቈረ** ፤ አሽንቈረ ፤ አስበሳ ፡ አስነደለ ።

**ተሰቍረ** ፤ ተሽነቈረ ፤ ተሰረሰረ ፡ ተበሳ ፡ ተነደለ ። ተሰቍረ ፡ እዱ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፳፰) ።

**ስቁር** ፤ (ራን ፡ ራት ፡ ቍርት) ፤ የተሸነቈረ ፡ ሽንቁር ፡ ብስ ፡ ንዳላ ፡ ሥንጥቅ ። ጻሕብ ፡ ስቁር ። ጽሕድ ፡ ስቍርት ። እብን ፡ ስቁር ፡ (ሚራ፳፫ ፡ ፲፪ ። ምሳ፳፫ ፡ ፳፮ ። ስንክ ፡ መስ፩) ።

**ስቍረት** ፤ መሽንቈር ፤ መብሳት ፤ መበሳት ፤ አበሳስ ፡ ብስ ፡ ንዳላ ፡ ሽንቍር ፤ ሽንቍርነት ። ረከብኩ ፡ ስቍረተ ፡ ውስተ ፡ አረፍት ። ፈነወ ፡ እዴሁ ፡ እንተ ፡ ስቍረት ። ስቍረተ ፡ መርፍእ ። ስቍረተ ፡ ኰኵሕ ። ሶበ ፡ ሕብአ ፡ መራንቱ ፡ ውስተ ፡ ስቍረቱ ፡ ለማጹን ፡ ተርኅወ ፡ ፍጡነ ። ደይ ፡ እዴከ ፡ ውስተ ፡ ስቍረት ፡ እዴየ ፡ (ሕዝ፰ ፡ ፯ ። ማሕ፭ ፡ ፬ ። ማቴ፲፱ ፡ ፳፬ ። ዘፀ፴፫ ፡ ፳፪ ። ስንክ ፡ ሠኔ፲፪ ። ኪዳ) ።

**ስቍሩር** ፤ ሰቈራር ፤—የተጠላ ፤ የሚያስጠይፍ ፤—ቈሪር ፡ ቈረ ፡ አስቈረረ ።

**ሲቃርዮን** ፤ (ጽር ፡ ሲካሪያን) ፤ ሰደወ ፡ ደም ፤ መጥባሕታውያን ፤ ሾተላሞች ፤ ባለሾተሎች ፡ ሾተል ፡ ታጣቆች ፤ ሽፍቶች ፡ ወንበዴች ፡ (ግብ፳፩ ፡ ፴፰) ። ሲካ ፡ የሾተል ፡ ስም ፡ ስም ።

**ሰቆጽዮን** ፤ (ጽር ፡ ስኮፒያን ። ዕብ ፡ ሚጽፋ) ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ መሴፋ ፤ በብንያም ፡ ክፍል ፡ ያለች ። ማያ ፡ መመልከቻ ፡ በር ፡ ዐንገት ፤ ጕበኛ ፡ ዘበኛ ፡ የሚቆምበት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (፫ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፳፪ ። ኢያ፲፰ ፡ ፳፮) ። መሴፋ ፡ (ሚጽፋ) ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩ ፡ ብዙ ፡ አገሮች ፡ ናቸው ፡ (ኢያ፲፭ ፡ ፴፰ ። መሳ፳ ፡ ፩ ። ፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፯) ።

**ሲራ** ፤—ሚራይ ፤—ሜረየ ።

**ሰረበ** ፤—ማገ ፤—ሠረበ ።

**ሳራብ** ፤—ሳማ ፡ ዶቢ ፤—ማራብ ።

**ሰርባ** ፤ (ትግሬ) ፤ ቋንቋ ፡ ባት ።

**ሰሪብ** ፤ ቦት ፤ (ሰረበ ፡ ይሰርብ ፡ ይስርብ ። ዐረ ፡ ሰሪበ) ፤ መፍሰስ ፡ መውረድ ፤ መጕረፍ ፡ መንኳኳት ፤ መንደልደል ፡ መንቧቧት ፤ መንባቢት ፡ የዝናም ፡ የውሃ ። ከጥሬው ፡ በቀር ፡ አንቀጹ ፡ አይገኝም ።

**ሰርብ** ፤ ሰረብ ፤ (ብ ፡ አስራብ) ፤ ቧቧቴ ፡ ኳኳቴ ፤ የዝናም ፡ የገደል ፡ የማዕበል ፡ ውሃ ፤ ምንጭ ፡ ፀዘቅት ፡ ወንዝ ፡ (ቦንቧ) ፡ አሸንዳ ፤ መስኖ ። አስራበ ፡ ሰማይ ። አስራበ ፡ ማይ ። አስራበ ፡ ቀላይ ። ቃለ ፡ ነቢያት ፡ ዘይውሕዝ ፡ ከመ ፡ አስራበ ፡ ወርቅ ፡ ንጹሕ ። ለእመ ፡ አውሐዘ ፡ እግዚ ፡ አስራበ ፡ እክል ፡ እምሰማይ ፡ (ዘፍ፯ ፡ ፲፩ ። ጥበ፲፯ ፡ ፲፯ ። አርጋ፫ ። መዝ ፡ ግ፭ ። ፬ነገ ፡ ፯ ፡ ፪) ።

**ሰሬግ** ፤ ጎት ፤ (ሰረገ ፡ ይሰርግ ፡ ይስርግ ፤ ሰርገወ ። ዐረ ፡ ሰሪጀ ። ዕብ ፡ ሳራግ ። ሱር ፡ ስራግ) ፤ መሥራት ፡ መታተት ፤ መጥለፍ ፡ ማቈላለፍ ፤ ሥሪ ፡ ወጥ ፡ ማድረግ ፤ የሹራብ ፡ የቀሚስ ፡ የመርገፍ ። መሰረግ ፤ ሰርግ ፡ ማድረግ ፡ መደገስ ፤ የሰርጉን ፡ ቤትና ፡ የሰርጉን ፡ ልብስ ፡ መሸለም ፡ ማስጌጥ ፤ ማንቈጥቈጥ ። ረቀመንና ፡ ረገፈን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ናቸው ።

**ሰራጊ** ፤ ሰርጋዊ ፤ የሚያስጌጥ ፡ የሚሸልም ፤ አስጊያጭ ፡ ሸላሚ ፤ ሰርገኛ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሰረገና ፡ በሰርገወ ፡ ፈንታ ፡ አሰርገወ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። አሰርገወ ፡ ዕበያ ፡ ለጥበቤሁ ። አሰርገኩኪ ፡ ሰርጐ ። አሰርገከ ፡ ሰማየ ፡ ፀሓየ ፡ ወወርኀ ። አሰርገካ ፡ ለምድር ። አሰርገዎ ፡ ነገረ ፡ (ሚራ፴፪ ፡ ፳፩ ። ሕዝ፲፮ ፡ ፲፩ ። መዋሥ ። ድጓ ። ተረ ፡ ቁር) ።

**ሰርግ** ፤ በቁሙ ፤ ከብከብ ፤ መርዓ ፤ የጋብቻ ፡ በዓል ፡ ድግስ ፤ የሚያጌጡበት ፡ የሚሸለሙበት ።

**ሰርጐ** ፤ (ጓት) ፤ ጌጥ ፡ ሽልማት ፡ የሰርግ ፡ የበዓል ፡ ልብስ ፤ መርዓዊና ፡ መርዓት ፡ ዘመይቻቸውም ፡ የሚለብሱት ። ሰርጐ ፡ ወርቅ ። ሰርጐ ፡ ያክንት ። ሰርጐ ፡ መርዓት ። ትረስዕኑ ፡ መርዓት ፡ ሰርጓ ። ሰርጐ ፡ ቤት ። ሰርጐሃ ፡ ለሰማይ ። ሰርጓቲሆሙ ፡ ሰርጐ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ። ሰርጓተ ፡ ለማይ ፡ (ዘፀ፴፪ ፡ ፪ ። ሚራ፯ ፡ ፴፬ ። ኢሳ፷፩ ፡ ፲ ። ኤር፫ ፡ ፴፪ ። ሕዜና ፡ ፳፱ ፡ ፲፱ ። ዘዳ፲፯ ፡ ፫ ። መቅ ፡ ታም ። ኤር፰ ፡ ፪) ።

**አሰርገወ** ፤ (አድራጊ) ፤ ሰረገ ፤ ሰርገወ ፤ የሰረገን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ።

**አሰርገወ** ፤ (አስደራጊ) ፤ አስጌጠ ፡ አሸለመ ፤ ሽልማት ፡ አለበ ።

**ተሰርገወ** ፤ ተጌጠ ፤ ተሸለመ ፤ ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ ተቀበለ ፤ ለበሰ ፤ ተፀረረ ። ተሰርገወት ፡ አውቃፋተ ። ተሰርገወት ፡ አዕኑጊሃ ። ብእሲት ፡ ዘተሰርገወት ፡ ሰርጓተ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ። አኮ ፡ በተሰርግዎ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ። ተሰርገወት ፡ ምድረ ፡ ገነት ፡ በሥነ ፡ ጽጌያት ፡ (ዮዲ፲ ፡ ፬ ። ሆሴ፪ ፡ ፲፫ ። ፊ ፡ መ ፡ ፴፬ ፡ ፳ ። ፩ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፫ ። ቀሌ) ።

**ሰርግው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ጕት) ፤ ያጌጠ ፡ የተጌጠ ፤ የተሸለመ ፡ ሽልም ፤ ሽልምልም ። ሰርግው ፡ ንዴቅ ። ሰርግዋን ፡ በወርቅ ። ርሱያት ፡ ወሰርግዋት ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰርጕት ፡ ከመ ፡ መርዓት ፡ (ሶቃ ፳፩ ፡ ፳ ። ኢሳ፷ ፡ ፳፪ ። መዋሥ ። ቀሌ) ።

**ስርጋዌ** ፤ (ውያት) ፤ ማጌጥ ፡ መጌጥ ፤ አጌያጌያጥ ። ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ ልብስ ፤ መሣሪያ ። አንስት ፡ ምእመናት ፡ ኢይትመክሓ ፡ በስርጋዌሆን ። ስርጋዌሃ ፡ ለሰማይ ። ተዐበዩ ፡ ብነ ፡ በስርጋዌሆሙ ፤ ስርጋዌሰ ፡ ለአፍራስ ፡ በመ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፴፬ ፡ ፳ ። ሢራ፵፫ ፡ ፱ ። ቅኔ) ።

**ሰርግውና** ፤ ሽልምነት ፤ ሰርጓኝነት ፡ ሙሽርነት ።

**ሰረገላ** ፤—በቊሙ ፤—ሠርገለ ።

**ሰርዶ** ፤ የሣር ፡ ስም ፤ ጥሩ ፡ ሣር ፤ ትሖግ ።

**ሰርድዮን** ፤ (ጽር ፡ ሳርዲዎስ ፤ ሳርዲዎን ። ዕብ ፡ ኦሀም) ፤ ዕንቍ ፤ የዕንቍ ፡ ስም ፤ ክቡር ፡ ደንጊያ ። ስምን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። እብነ ፡ ሰርድዮን ። ዕንቈ ፡ ሰርድዮን ። ወሳድስት ፡ በሰርድዮን ፤ (ዘፀ፳፰ ፡ ፲፯ ። ምሳ፳፰ ፡ ፲፪ ። ራእ ፳፩ ፡ ፳) ።

**ሰርዲኖ** ፤ (ጽር ፡ ሳርዲኖን ። ዕብ ፡ አዶም) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ዕንቍ ፡ ቀይሕ ፡ (ራእ፬ ፡ ፫) ።

**ሰርዶንክስ** ፤ (ጽር ፡ ሳርዶኒክስ ። ዕብ ፡ ያሀሎም) ፤ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፤ ዕንቍ ፤ ብርቱ ፡ ጠንካራ ፤ ሕብሩ ፡ ይህ ፡ የማይባል ፤ ባለሶስራ ፡ ባለምዕዛር ፡ (ራእ፳፩ ፡ ፳) ።

(ጥሬ) **ሰረወ** ፤—ነቀለ ፡ አጠፋ ፤—ሠረወ ።

**ሰሪው** ፤ ዎት ፤ (ሰረወ ፡ ይሰሩ ፡ ይስሩ ። ዕብ ፡ ሳራህ ። ዐረ ፡ ሰረይ) ፤ መዋጋት ፡ መታገል ፤ መበርታት ፡ ማየል ፤ ማሸነፍ ፡ መጣል ፤ ድል ፡ መንሣት ፤ አሸንፎ ፡ መግዛት ።

**ሰርዌ** ፤ (ብ ፡ ስረው ፤ ሰራዊት ። ዕብ ፡ ጽባእ ፤ ጽብአት ። ዐረ ፡ ሰሪየት ፤ ብዙ ፡ ፈረሰኛ) ፤ ሰራዊት ፤ ጭፍራ ፤ ወታደር ፤ ዘማች ፤ የጦር ፡ ሕዝብ ፤ ሰልፈኛ ። ፋኮል ፡ መልአከ ፡ ሰርዌሁ ። ሶቤክ ፡ መልአከ ፡ ሰርዌሆሙ ፡ ብእሲ ፡ ጽኑዕ ፡ (ዘፍ፳፩ ፡ ፳፪ ፡ ፴፪ ። ፩ዜና ፡ ፲፱ ፡ ፲፰ ። ዳን፰ ፡ ፲፩) ። ንእማን ፡ መልአከ ፡ ስረዊሆሙ ፡ ለሶርያ ፡ (፬ነገ ፡ ፭ ፡ ፩ ። ፳፭ ፡ ፲፱) ። መላእክተ ፡ ሰራዊት ። ሰራዊት ፡ ብዙኃን ፡ ወጽኑዓን ። ሰራዊተ ፡ አሕዛብ ። ሰራዊተ ፡ መላእክት ። ገብርኤል ፡ ሊቀ ፡ ሰራዊተ ፡ ሰማያት ፡ (አስቴ፩ ፡ ፫ ። ዮኤ፪ ፡ ፩ ። ሕዝ፳፫ ፡ ፳፬ ። ቅዳ ። ሰንክ ፡ ሠኔ፲፫) ።

—፤ የሰራዊት ፡ ክፍል ፤ ክቢ ፤ ቍርጥ ፤ በያበጋዙና ፡ በያለቃው ፡ የሚገዛ ፡ የሚሰለፍ ፡ (ኢዮ፩ ፡ ፲፯ ። ፩ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፲፩ ። መሳ፱ ፡ ፴፬ ፡ ፵፫) ።

**ሰርዌ** ፤ (ብ ፡ ሰራው ። ዕብ ፡ ሳር ፤ ሳሪም) ፤ የጦር ፡ አበጋዝ ፤ አዝማች ፡ አለቃ ፤ ደምሳሽ ፡ ጠቅላይ ፤ ገዥ ፡ አዛዥ ።

**ሰሮጸ** ፤ ሰርወጸ ፤ (ረዊጽ ፡ ሮጸ ፡ ሰ ። ዕብ ፡ ራጻጽ) ፤ ሰረወጠ ፤ ሰርውጥ ፡ አለ ፤ ወለም ፡ አለ ፤ ዞረ ፤ ወለቀ ፤ ተሰበረ ፤ የሥር ፡ የኸርማት ፡ ያጥንት ፤ ከሩጫ ፡ ብዛት ፡ የቀነጣ ። ዐሸ ፡ ጠገን ፤ ሸበለቀ ፡ አሰረ ።

**ሰርዋጽ** ፤ ስሩጽ ፤ (ጻት) ፤ ማጥኛ ፡ መጠገኛ ፡ ማጥበቂያ ፤ ሽብልቅ ፡ ውሻል ፤ ስባሪ ፡ ሥንጣሪ ፡ ሥንጣቂ ፡ ሥንባጭ ። ይበውእ ፡ ሰርዋጽ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ወያቈስሎ ፡ (፬ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ። ኢሳ፴፮ ፡ ፮) ።

—፤ ማቅኛ ፤ ማስረጃ ፡ ማስታወቂያ ፤ እንደ ፡ ዚቅ ፡ እንደ ፡ ሽብልቅ ፡ በነገር ፡ መካከል ፡ የሚገባ ፡ ትርፍ ፡ ቃል ። ሰርዋጽ ፡ እምቃለ ፡ መምህር ፡ ጎሩይ ፡ አባዲሁ ፡ ለዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፰) ።

—፤ ወሰምታ ፤ ውሊቃት ፡ ስብራት ፤ ቅጭታት ፤ ጕስምት ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሰረዘ** ፤—በቊሙ ፤—ሠረዘ ።

(ጥር) **ሰርሐ** ፤—አቀና ፡ አበጀ ፤—ሠርሐ ።

**ሰሪሕ** ፤ ሓት ፤ (ሰርሐ ፡ ይሰርሕ ፡ ይስራሕ ። ዕብ ፡ ጣራሕ) ፤ መስራት ፡ መጣር ፤ መሸከም ፡ መደብለል ፤ መድከም ፡ መዛል ፡ ከስራ ፡ ከሸክም ፡ የተነሣ ። ሰሪሖ ፡ ወሊታ ፡ ኀዲገ ። ኢትስራሕ ፡ ሎሙ ፡ ባሕቲትከ ። እንተ ፡ ብዙኀ ፡ ሰርሐት ፡ ለክሙ ። በእንተ ፡ እለ ፡ ይሰርሑ ፡ ከመ ፡ ትባርክ ፡ ፍሬ ፡ ተግባሮሙ ። በሥሉ ፡ ስራሕየ ፡ ዘሰራሕኩ ። ትረክብ ፡ ሰሪሐከ ፡ (አዋል ። ዘኍ፲፩ ፡ ፲፯ ። ሮሜ፲፮ ፡ ፯ ። ቅዳ ። መክ፪ ፡ ፲፱ ። ሢራ፲፫ ፡ ፳፮) ። ሠርዐን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ፤ ሠርዐ ፡ የብልኅት ፤ ሰርሐ ፡ የጕልበት ።

**ሰራሒ** ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት ፤ ሕት) ፤ የሚሰራ ፡ የሚጥር ፤ የሚደክም ፡ የሚሸከም ፤ ሰራተኛ ።

**ስሩሕ** ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ርሕት) ፤ የጣረ ፡ የደከመ ፤ ድኩም ። ስሩሓን ፡ ወክቡዳነ ፡ ጾር ። ስሩሓን ፡ ለግቢረ ፡ ፈቃዱ ፡ (ማቴ፲፩ ፡ ፳፰ ። ዲድ ፡ ፳፮) ።

**ስራሕ** ፤ (ሓት) ፤ ድካም ፡ ሸክም ፤ ጣር ፡ ጋር ፤ ሐሳብ ፡ ምኞት ፤ መከራ ፡ ጭንቅ ፤ ችጋር ። ርኢ ፡ ሕማምየ ፡ ወስራሕየ ። ዕለተ ፡ ስራሕ ፡ ወምንዳቤ ። ስራሑ ፡ ለመንበርቱ ። ስራሓቲሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓለም ። ስራሕ ፡ እኩይ ። በጻማ ፡ ወበስራሕ ፡ (መዝ ፡ ፳፬ ። ሔኖ፴፰ ፡ ፪ ። ፩ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ። ድጓ ። መክ፩ ፡ ፲፫ ። ፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፯) ።

**አስርሐ** ፤ አሰራ ፤ አደከመ ፤ አሸከመ ፤ አሰለቸ ። ብእሲ ፡ ኃጥእ ፡ ያሰርሖ ፡ ለቢጹ ። አስርሕዎሙ ፡ ለእለ ፡ ለቅሕዎሙ ። አስራሕክሙ ፡ ብዙኃነ ፡ በሕግ ። ለምንት ፡ ታሰርሑኒ ፡ (ሢራ፳፰ ፡ ፱ ። ፳፱ ፡ ፬ ። ሚል፪ ፡ ፳ ። ኢዮ፲፱ ፡ ፳፪) ።

**መስርሕ** ፤ (ሕት ፡ ሓን ፡ ሓት) ፤ የሚያደ ክም ፤ አይክሚ ። ምግባራት ፡ መስርሕ(ሓ)ት ፡ (ፊ ልክ ፡ ፺፫) ።

**ሳርሐ** ፤—በራ ፤—ሣርን ።

**ሰርጣን** ፤ **ሸርጣን** ፤ (ዐረ ፡ ሰረጣን ። ዕብ ፡ ሳርጣን) ፤ ጕርምጥ ፤ የጕርምጥ ፡ ዐይነት ፤ እግ ራም ፤ ታናሽ ፡ የውሃ ፡ እንስሳ ። ኮከብ ፤ ካ፲፪ቱ ፡ መና ግል ፡ አንዱ ። ኮከብነቱም ፡ የሠኔ ፡ ነው ፤ ከፀሐይ ፡ ጋራ ፡ ፴፭ ፡ ዕለት ፡ ፳፯ ፡ ኬክሮስ ፡ ይመግባል ፡ (አቡሻ ፡ ፱) ።



ሰርጣን፡

(ጥሬ) **ሰረየ** ፤—መዳኒት ፡ ሰጠ ፤—ሠረየ ።

**ሰርይ** ፤ **ዮት** ፤ (ሰረየ ፡ ይሰሪ ፡ ይስሪ ። ሱር ፡ ሽራእ ። ዐረ ፡ ሰራእ) ፤ መስረይ ፤ መፍ ታት ፤ መተው ፡ መልቀቅ ፤ ማንጻት ፡ ማውጣት ፤ ከኀጢ እት ፤ ተንድግ ፡ ለክ ፤ ኩን ፡ ፍቱሐ ፤ ይቅር ፡ ለእግዜር ፤ ማለት ፤ ዕዳን ፡ በደልን ፡ ማቅለል ፤ የቂስ ፡ የተበዳይ ። ይስሪ ፡ ለከ ፡ ኀጢአተከ ። ከመ ፡ እስረይ ፡ ሎሙ ፡ ኀ ጢአቶሙ ። እግዚ ፡ ሰረየ ፡ በእንተ ፡ እኪት ። ስረይ ፡ ሊተ ፡ ሰኃጥእ ፡ እግዚኦ ፡ (ሚራ፳፰ ፡ ፪ ። ኢሳ፴፰ ፡ ፴፱ ። ዘፀ፴፫ ፡ ፲፱ ። ሉቃ፲፰ ፡ ፲፫) ።

**ሰራዪ** ፤ **መስረዪ** ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ረይት) ፤ ይቅር ፡ ባይ ፡ ዕዳን ፡ በደልን ፡ የሚተው ፡ የሚ ያቀል ፤ ይቅር ፡ የሚል ። መሓሪ ፡ እከውን ፡ ወሰራዪ ፡ ለአበሳሆሙ ። እግዚ ፡ ሰራዪ ፡ ኀጢአትነ ። ሰራይ ያን ፡ ኀጣውእ ። ቍርባን ፡ ሰራዪ ፡ ኀጢአት ፡ (፪ዜና ፡ ፯ ፡ ፲፱ ። ቅዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፱) ።

**አስረየ** ፤ **አስተስረየ** ፤ አስተሰረየ ፤ ይቅር ፡ አሰኘ ፤ ይቅርታ ፡ ለመነ ፤ አማለደ ፤ በካሳ ፡ በጸሎት ፡ በመ ሥዋዕት ። ያስተስሪ ፡ ሎሙ ፡ ካህን ። ካህን ፡ ዘያስተ ስሪ ፡ ኀጣውአ ፡ ሕዝብ ፡ (ዘሌ፬ ፡ ፳ ። ፱ ፡ ፯ ። ፲፪ ፡ ፯ ፡ ፰ ። ፲፬ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**መስተስርይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሪት ፡ ርዪት) ፤ የሚያስተሰርይ ፤ አስተስራዪ ፤ አማላጅ ፡ አስታራቂ ። ከመ ፡ ትኩን ፡ መስተስርየ ፡ ኀጢአት ። ጊዶስ ፡ ዘሎሙ ፡ ቅ ዱሳን ፡ መስተስርየ ፡ ኀጢአትየ ። ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መስተስርየ ፡ ዘሉ ፡ ጌጋይ ፡ (ቀሌ ። መጽ ፡ ምስ ። ደ ራሲ) ።

**ምስትስራይ** ፤ (ያት) ፤ ማስተሰረያ ፤ ቦታ ፡ መሣሪያ ። ምስኣል ፡ ወምስትስራየ ፡ ኀጢአት ፡ (ቀሌ ። መቃ ። ድጓ) ። በምስትስራይ ፡ ፈንታ ፡ ስርየት ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ወግብሮ ፡ ስርየተ ፡ (ሮሜ፫ ፡ ፳፭) ።

**ተሰርየ** ፤ ተሰረየ ፤ ተፈታ ፡ ቀለለ ፤ ይቅር ፡ ተ ባለ ፤ ጠፋ ፡ ተፋቀ ፤ ተደመሰሰ ። ኢትሰረይ ፡ ለክሙ ፡ ዛቲ ፡ ኀጢአትክሙ ። በምጽዋት ፡ ይሰረይ ፡ ኀጢ አት ። ዘእንበለ ፡ ይትነዛህ ፡ ደም ፡ ኢይሰረይ ። ኢተ ሰርየ ፡ ሎቱ ፡ ኀጢአቱ ፡ (ኢሳ፳፪ ፡ ፲፬ ። ምሳ፲፭ ፡ ፳፯ ። ዕብ፱ ፡ ፳፪ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ስሩይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ሪት) ፤ የተሰረየ ፤ የተ ሰረየለት ፤ ስርየት ፡ ያገኘ ።

**ስርየት** ፤ በቁሙ ፤ መስረይ ፤ መሰረይ ፤ ይቅ ርታ ፤ ዕርቅ ፡ ፍቅር ። ታቦት ፡ መንበር ። ሰአሉ ፡ ሰነ ፡ ስርየተ ፡ ኀጢአት ። ቤተ ፡ ስርየት ፡ (መዋሥ ። ሔኖ ፲፫ ፡ ፮ ። ኩፋ ፡ ፲፭ ። አፈ ፡ ድ፳ ። ፩ዜና ፡ ፳፰ ፡ ፳) ።

**ተሳረየ** ፤ ተካካሰ ፤ ተራረቀ ፤ ይቅር ፡ ተባባለ ።

**አስተሳረየ** ፤ አካካሰ ፤ አስታራረቀ ፤ ይቅር ፡ አባ ባለ ፡ (አርጋ) ።

**ሰርክ** ፤ **ሲራክ** ፤—በቁሙ ፤—ሠረከ ።

**ሸሪም** ፤ (ዕብራ) ፤ ሐለይት ፤ መዘምራን ። ሕዋራተ ፡ ሸሪም ፡ (ሕዝ፵ ፡ ፵፬) ።

**ሰርም** ፤—ረግረግ ፤—ሠረመ ።

**ሰርን** ፤ በቁሙ ፤ ያፍንጫ ፡ ዐጥንት ፤ ኵሸኵሽ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሳሮን** ፤—ስመ ፡ ሀገር ፤—ሣሮን ።

**ስርናይ** ፤—ስንዴ ፤—ሥዕረ ።

**ሲርኖን** ፤ (ጽር ፡ ሲሪኖን) ፤ ሰጐን ፤ ሰገኖ ። አዋልደ ፡ ሲርኖን ፡ (ሚል፩ ፡ ፫) ።

**ሴርኒስ** ፤ (ጽር ፡ ሲሬኔስ) ፤ ግዢ ፡ ከማሁ ፤ ሰጐን ። ዖፎስ ፡ አዕዋፍ ፡ ወሴርኒስ ፡ (ኢሳ፴፫ ፡ ፳) ።

**ሰራፊ** ፤ (ዕብ ፡ ጸሬፍ) ፤ እንጥረኛ ፤ ብር ፡ አፍሳሽ ፤ ዳኝ ፡ ሸላሚ ። ወልደ ፡ ሰራፊ ፡ (ነሐ፫ ፡ ፴፩) ።

**ሰሪፍ** ፤ **ፎት** ፤ (ሰረፈ ፡ ይሰርፍ ፡ ይስ ርፍ ። ዕብ ፡ ሳራፍ) ፤ ማንደድ ፡ ማቃጠል ፤ ማጤስ ፡ ማጠን ፤ የመሥዋዕት ፡ የቍርባን ፤ የዕፅና ፡ የማዕር ፡ የሌ ላውም ፡ ኹሉ ። መብሳት ፡ መንደል ፡ መሰርሰር ።

**መስረፍ** ፤ መብሻ ። መስረፈ ፡ እንፍ ፡ (ስ ንክ ፡ ጥር፲፭) ።

**ሰራፊ** ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት ፤ ረፍት) ፤ የሚያነድ ፡ የሚያጤስ ፤ የሚያጥን ፡ ዐጣኝ ።

**ሱራፊ** ፤ ግዢ ፡ ከማሁ ፤ መልአክ ፤ ከካህናተ ፡ ሰማይ ፡ አንዱ ። ዘውገ ፡ ሱራፊ ። ሱራፊ ፡ ካህን ፡ ወኪ ሩብ ፡ ቀሲስ ። አዝዚዮ ፡ ለሱራፊ ፡ ዘሰማይ ፡ ቀሲስ ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፲፯ ። ድጓ ። ደራሲ) ።

**ሱራፌን** ፤ **ል** ፡ **ም** ፤ (ጽር ፡ ሴራፊም ። ዕብ ፡ ስራፊም) ፤ ስመ ፡ ነገድ ፤ ልዑላን ፡ መላእክት ፤ ሊቃናት ፤ ዐጠንት ፤ ካህናት ፤ የሰማይ ፡ ቀሳውስት ፤ ቀዳ ሾች ። ሱራፌን ፡ ይቀውሙ ፡ ዐውዶ ። ወተፈነወ ፡ ኀ ቤየ ፡ አሐዱ ፡ እምሱራፌል ። ኪሩቤም ፡ ወሱራ ፌም ፡ (ራእ፬ ፡ ፱ ። ኢሳ፮ ፡ ፪ ፡ ፮ ። ቅዳ) ። በን ፡ ፈንታ ፡ ል ፡ ም ፡ ማለት ፡ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ አያሰኝም ።

**ሴሬቅ** ፤—ጥሩ ፡ ወይን ፤—ሜሬቅ ።

**ሰረቀ** ፤—ወጣ ፡ ባተ ፤—ሠረቀ ።

**ሰረቅ** ፤ **ቆት** ፤ (ሰረቀ ፡ ይሰርቅ ፡ ይስርቅ ። ዐረ ፡ ሰረቀ ። ዕብ ፡ ሳራቅ) ፤ መስረቅ ፤ መደበቅ ፤ ሳይታዩ ፡ መውሰድ ፡ ማንሣት ፤ መሳብ ፡ መጐተት ፤ ማጥፋት ፡ ማበላሸት ፤ የገንዘብ ፡ የነገር ። ይኄይስ ፡ ሰሪቅ ፡ እምሐስዎ ። ትፍሪት ፡ ሰሪቅ ፡ እምንዋየ ፡ ማሕፀንት ። ዘይሰርቁ ፡ በሚዛን ። ሰረቀቶ ፡ ወነሥአቶ ፡ ሰሪቃ ። ሰረቀ ፡ ርእሶ ። እለ ፡ ይሰርቁ ፡ ቃልየ ፡ (ሚራ፳ ፡ ፳፭ ። ማ፳ ፡ ፲፱ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፮ ። ፪ዜና ፡ ፳፪ ፡ ፲፭ ። አፈ ፡ ድ፳፯ ። ኤር፳፫ ፡ ፴) ። አንዳንድ ፡ መጣፍ ፡ በሰረቀ ፡ ፈንታ ፡ አሰረቀ ፡ ይላል ፤ አያስኬድም ። እስመ ፡ ሃይማኖት ፡ እንተ ፡ ተወፈይነ ፡ ያሰርቁ ፡ (ቁር ፡ ጳላ) ።

**ሰራቂ** ፤ (**ቂት ፡ ቅያን ፡ ያት** ፤ **ረቅት**) ፤ በቁሙ ፡ የሚሰርቅ ፤ የሚደብቅ ፤ ሌባ ፡ ቀጣፊ ። ከመ ፡ ኀፍረቱ ፡ ሰራቂ ፡ ሶበ ፡ ይእኀዝዎ ። ሰረቅተ ፡ ሰብእ ። ሱቱፋን ፡ ሰረቅት ። በእንተ ፡ ዘነኒ ፡ ሰረቅት ፡ (ኤር፪ ፡ ፳፮ ። ፩ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲ ። ኢሳ፩ ፡ ፳፫ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፱) ።

**አስረቀ** ፤ አሰረቀ ፤ ሰረቀ ፡ አለ ፤ ስርቆት ፡ አስተማረ ።

**ተሰርቀ** ፤ ተሰረቀ ፤ ተደበቀ ፡ ጠፋ ፡ ኰበለለ ፤ ተሰረቀበት ፡ ገንዘቡ ። ተሰርቀ ፡ ንዋዩ ፡ እምቤቱ ። ዘተሰርቀ ፡ ንዋዩ ። ማኅደር ፡ ዘኢይሰረቅ ፡ (ፊልክ ፡ ፳፫ ። አፈ ፡ ተ፲፭ ። ቅዳ ፡ ዮሐ) ።

**ስሩቅ** ፤ (**ቃን ፡ ቃት ፡ ርቅት**) ፤ የተሰረቀ ፤ የተደበቀ ፤ የስርቆት ፡ ገንዘብ ።

**ስርቀት** ፤ መስረቅ ፡ መሰረቅ ፡ አሰራረቅ ፤ ስርቆት ፤ ሌብነት ።

**ስርቅ** ፤ ስርቆት ፡ ሽ ፤ ስርቂያ ፡ ቅጥፈታ ፤ የሌባ ፡ ሥራ ። ስርቅ ፡ ወሕብል ። ዝሙት ፡ ወስርቅ ። ነሥአ ፡ ዘስርቅ ፡ (ጥበ፲፬ ፡ ፳፭ ። ማር፯ ፡ ፳፪ ። ሕዝ፲፰ ፡ ፲፫) ።

**ሰርቅ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ስርቆት ። ማየ ፡ ሰርቅ ። ንዋየ ፡ ሰርቅ ፡ (ምሳ፱ ፡ ፲፯ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፯ ፡ ፩) ።

**ተሳረቀ** ፤ በቁሙ ፤ ተጣፋ ፤ ተቀላቀለ ፤ ተበላሸ ።

**አስተሳረቀ** ፤ አሳረቀ ፡ አሰራረቀ ፤ አቀላቀለ ፤ አደባለቀ ። እመሰኬ ፡ ሐሰተ ፡ ህላዌ ፡ ዘወልድ ፡ ንነግር ፡ ዘተሰገወ ፡ ግብረ ፡ ነአምን ፡ ተስሕተ ፡ ወኑሣት ፡ ወናስተሳርቅ ፡ ህላዌ ፡ ትስብእት ፡ እንተ ፡ በላዕሌሁ ፡ (ቁር ፡ ጳላ) ።

**ሳረረ** ፤—ሠራ ፡ መሠረተ ፤—ሣረረ ።

**ሰሪር** ፤ **ሮት** ፤ (ሰረ ፤ ሰረረ ፡ ይሰርር ፡ ይስርር ። ዐረ ፡ ሳረ ። ዕብ ፡ ሳራር ፤ መለከ) ፤ መስረር ፤ በላይ ፡ መኽን ፤ መከመር ፡ መታዘል ፤ መሰቀል ፤ ያለሌ ፡ ያውራ ፡ የጋባቢ ። (ተረት) ፤ ቀኝም ፡ ሰረሩ ፡ ግራም ፡ ሰረሩ ፡ መገናኛው ፡ ከሩ ። መርዘም ፡ ማደግ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ መውጣት ፤ መንጠራራት ፤ የቁመት ።

—፤ መዝለል ፡ መር ፡ ቸር ፡ ባጥ ፡ እንጣጥ ፡ ፊናጥ ፡ ማለት ፤ መወርወር ፤ ያንበሳ ፡ የነምር ፡ የቀራጋሚ ፡ ከብት ። ትሰርር ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ። ይሰርሩ ፡ ከመ ፡ ነምር ። ሰረረ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ዓማ ። ሰረረ ፡ ራጉኤል ፡ ወሰዐሞ ፡ (ሚራ፳፰ ፡ ፳፫ ። ዕን፩ ፡ ፰ ። ጦቢ፮ ፡ ፫ ። ፯ ፡ ፯) ።

—፤ መክነፍ ፡ መብረር ፤ ወዳየር ፡ መውጣት ፡ ከምድር ፡ መራቅ ፡ መምጠቅ ፤ ምድርን ፡ መተው ፡ መልቀቅ ፤ ምድር ፡ ደኅና ፡ ቀይ ፡ ማለት ፤ የአዕዋፍ ። መኑ ፡ ይሁበኒ ፡ ክንፈ ፡ ከመ ፡ ርግብ ፡ እስርር ፡ ወአዕርፍ ። ወበክልኤ ፡ ክንፍ ፡ ይሰሩ ። ይሰርራ ፡ ደመናት ፡ ከመ ፡ አዕዋፍ ። ሰረረት ፡ ታቦት ፡ ዮኅ ፡ መልዕልተ ፡ ማያት ፡ በክነፈ ፡ ነፋስ ። እምነ ፡ ምድር ፡ ይሰርር ፡ ኀሊናሁ ፡ ለጴጥሮስ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ሰማይ ፡ (መዝ ፡ ፶፬ ። ኢሳ፮ ፡ ፪ ። ሚራ፵፫ ፡ ፲፬ ። ቀሌ) ።

**ሰራሪ** ፤ (**ሪት ፡ ርያን ፡ ያት**) ፤ የሚሰር ፡ የሚበር ፤ በራሪ ፡ ዘላይ ። ንስር ፡ ሰራሪ ። ዖፍ ፡ ሰራሪት ። ከመ ፡ አዕዋፍ ፡ ዘይሰርራ ፡ ወሰራርያት ። አግማል ፡ ሰራርያን ፡ (ግንዝ ። መቃ ። ምሳ፳፯ ፡ ፪ ። ፍ ፡ ን ፡ ፵፯) ።

**አስረረ** ፤ በቁሙ ፤ በላይ ፡ አደረገ ፤ ጣደ ። (ተረት) ፤ ከበሮውን ፡ አስረሽ ፡ ምችው ። አጠፋ ፡ አራቀ ፡ አበረረ ። ኀልየ ፡ ንዋይ ፡ ያሰርር ፡ ንዋመ ። ያሰርር ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ዕጉሊሁ ፡ (ሚራ፴፩ ፡ ፩ ። ዕን፪ ፡ ፱) ።

**ተሰረ** ፤ ተሰረረ ፡ ተወጣበት ፤ ተጠቃ ፡ በቃኙ ፡ ኾነ ። (ተረት) ፤ ኾሮብ ፡ ሊሰር ፡ ኺዶ ፡ ተሰሮ ፡ ገባ ። ተጣደ ፤ በጕልቻ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። ማሰሮ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ስሩር** ፤ (**ራን ፡ ራት ፡ ርርት**) ፤ የተሰረረ ፤ የተጠቃ ። የሰረረ ፤ በላይ ፡ የኾነ ፤ የታዘለ ፡ የተከመረ ፤ ያረፈ ፡ የሰፈረ ፤ የከነፈ ፡ የበረረ ፤ ብር ፡ ብር ፡ የሚል ፡ ክንፉም ፡ እግሩ ፡ ቀላል ። መንፈስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዲቤሁ ፡ ስርርት ። ስርርት ፡ ይእቲ ፡ ወምርዕት ፡ (ስንክ ፡ ጥቅ፳ ። ምሳ፯ ፡ ፲፭) ።

**ስረት** ፤ መስረር ፡ መብረር ፡ መወርወር ፤ አወራወር ፤ ውርወራ ። ስረተ ፡ ደመናት ፤ ተዳድቆተ ፡ ስረቱ ፡ (መቃ ። አርጋ ፡ ፩ ። ጥበ፳ ፡ ፲፩) ።

**ስሬር** ፤ **ሰሬር** ፤ (ዐረብ ፡ ወጕራጌ) ፤ ዐልጋ ፤ ቈጥ ፤ ማማ ፡ ቍራ ፤ የዛፍ ፡ ላይ ፡ ሰፍራ ።

(ጥ) **ስር** ፤ ቆም ፡ ቁመት ፤ ርዝመት ፤ ከፍታ ፤ የቤት ፡ የመርከብ ። ወሠላሳ ፡ እመት ፡ ስራ ፡ (ዘፍ፮ ፡ ፲፭) ።

**ሰር** ፤ የሞፈር ፡ ቀጥ ፤ ሽኛው ፡ ጕባባው ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሰሪራ** ፤ የሽቱ ፡ ውሃ ፤ ጥሩ ፡ ሽቱ ፡ ልብ ፡ የሚመሥጥ ፤ ከሩቅ ፡ የሚሸት ። ንቂጥሩን ፡ እይ ። ከመ ፡ ሰሪራ ፡ ወከልበኔ ፡ (ሔኖ፴፩ ፡ ፩) ።

**ሰረሰር** ፤ በቁሙ ፤ የዠርባ ፡ ዐጥንት ፡ (ዐማርኛ) ።

ሰራሴሮት ፤ (ጽር ፡ ሴርሴሮት ። ዕብ ፡ ሻርሽሮት) ፤ ሰንሰለት ፤ የሰንሰለት ፡ ዐይነት ፡ (፪ዜና ፡ ፫ ፡ ፲፮) ።

ሱርስት ፤ (ጽር ፡ ሲሪስቲ ። ዕብ ፡ አራ ሚ ት) ፤ አራማዊ ፤ የአራም ፡ ቋንቋ ፤ ታችኛው ፤ አሶራ ውያን ፡ ከለዳውያን ፡ የሚናገሩበት ፤ የዐረብ ፡ የግእዝ ፡ የዕብራይስጥ ፡ ወንድም ። ፈታ ፡ ለነ ፡ እግዚኦ ፡ መንፈስ ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ ነ.ድ ፡ አርኣያ ፡ አንበቦሙ ፡ በገሃድ ፡ ለ ሐዋርያት ፡ ኄራን ፡ ንቡራነ ፡ ኢ.ድ ፡ ያንብበነ ፡ በሱር ስት ፡ ወሚጺድ ። ንግረነ ፡ ሱርስተ ፡ (ደራሲ ። ኢ.ሳ፴፯ ፡ ፲፩) ።

ሳሬት ፤— ሸረሪት ፤— ሠረየ ።

ሱርትዮን ፤ (ዕብ ፡ ሼሩት ፤ አገልግ ሎት ። ምሽሬት ፤ አገልጋይ) ፤ የኪሩቤል ፡ ስም ፤ (ሳረተ ፤ ሳራቲ) ፡ ሳራትያን ፤ አገልጋዮች ፤ የውስጥ ፡ አሽከ ሮች ። በራ ፡ መራ ፡ መሲጠን ፡ ሱርትዮን ፡ (መዋሥ) ።

ሱርትዮን ፤ (ዐረ ፡ ጹራ ፤ ጹረት ። ዕብ ፡ ጹራት ፤ ሥዕል ፡ አርኣያና ፡ አምሳል) ፤ የኪ ሩቤል ፡ ስም ። የሰው ፡ የእንስሳ ፡ የንስር ፡ የአንበሳ ፡ አም ሳል ፡ ማለት ፡ ነው ። ግምሻን ፡ ሶራ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ፤ በላዩ ፡ የሚሣለውን ፡ ወፍና ፡ ዛፍ ፡ ያመለክ ታል ፤ ጣዎስን ፡ እይ ። በስረት ፡ ዘይቤ ፡ ቢፈቱት ፡ ግን ፡ ገጸ ፡ ንስርን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ክንፋቸውን ፡ ብቻ ፡ ያ ባያል ።

ስሱ ፤ ስሳ ፤— ስድስት ፡ ስድሳ ፤— ሰደሰ ።

ሶሰወ ፤— ወጣ ፡ ወረደ ፤— ሰውሰወ ።

ሴሰየ ፤— በቁሙ ፤— ሰይሰየ ።

(ተ) ሰስሎ ፤ ሎት ፤ (ሰሰለ ፡ ይሴስል ፡ ይሰ ስል ። ሰረረ ፤ ኀለፈ) ፤ መሸሽ ፡ መራቅ ፡ መወገድ ፤ መለየት ፡ ተነጥሎ ፡ መኼድ ። ዘኢ.ይሴስል ፡ እምቅ ድመ ፡ ዐይንከ ። ኢ.ይሴስሉ ፡ ወትረ ፡ እመንበረ ፡ መ ርዓዊ ። ሰሰለ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚ. ፡ እምኔሁ ። ሰሰለ ፡ ዮሴፍ ፡ ወሖረ ። ርኢኩ ፡ እበደሙ ፡ ለአብዳን ፡ ወሰ ሰልኩ ፡ (ዘፀ፲፫ ፡ ፲፯ ። መዋሥ ። ፈ ፡ መ ፡ ፱ ፡ ፮ ። ዮሴፍ ። ፈላስ) ።

— ፤ ማለፍ ፡ መጥፋት ፤ መሻር ፡ መቅረት ፤ ከፀታው ፡ መ ታጣት ፤ መልቀቅ ። ወርኢኩ ፡ ሰማየ ፡ ሐዲሰ ፡ ወም ድረ ፡ ሐዳሰ ፤ እስመ ፡ ሰሰለ ፡ ሰማይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወ ምድርኒ ፡ ቀዳሚት ። ይሴስላ ፡ ግብተ ፡ ነፍሳቲ ፡ ዐ ማፀያን ። መሥዋዕት ፡ ይሴስል ፡ ወይሰዐር ። ወእ ምዝ ፡ ሰሰለ ፡ ጽልመት ፡ ወአስተርአየ ፡ ብርሃን ፡ (ራእ ፳፩ ፡ ፩ ። ፪ኢዮ ፡ ፫ ፡ ፲ ። ምሳ፲፩ ፡ ፴ ። አፈ ፡ ድ፲፰ ፡ ዲድ ፡ ፳፱) ። በሰሰለ ፡ ፈንታ ፡ ተሰሰለ ፡ ይላል ፤ በሕተት ፡ ነው ። ተሰበልክዎ ፡ አነ ፡ ለሐናንያ ፡ (ቀሌ) ።

ሰሳሊ ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤ የሚሸሽ ፡ የሚርቅ ፡ የሚወገድ ፤ ኀላፊ ፡ ጠፊ ።

ስሱል ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ስልት) ፤ የራቀ ፡ የ ወገደ ፤ ርቁ ፡ የኼደ ፤ ልዩ ፡ ባዕድ ።

ስሳሌ ፤ መራቅ ፡ መወገድ ፤ አራራቅ ፤ ርቀት ፡ ሽሽት ፤ ኅልፈት ፡ ጥፋት ፤ መለየት ። ስሳሌሆሙ ፡ ለሰ ማይ ፡ ወምድር ። ስሳሌሃ ። በኢ.ስሳሌ ። ስሳሌ ፡ ዚኣየ ፡ እምኔክሙ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። አፈ ፡ ድ፲፰ ። ጥበ ፡ ጠቢ ። ፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፱) ።

አሰሰለ ፤ አራቀ ፡ አስራቀ ፡ አስወገደ ፤ አጠፋ ፡ አስጠፋ ። አሰሰለት ፡ ሡቀ ። ይቤ ፡ ያሰስሉ ፡ ዘሎ ፡ በ ብአ ፡ እምቅድሜሁ ። አሰስል ፡ ፍትወተ ፡ እምኔየ ። አሴስሎሙ ፡ እማእከለ ፡ ምድር ። ለአሰስሎ ፡ (ዮዲ ፲ ፡ ፫ ። ዘፍ፵፰ ፡ ፩ ። ሚራ፳፫ ፡ ፳ ። ኩፋ ፡ ፩ ። ሔኖ ፡ ፩) ።

አሰሳሊ ፤ መሰስል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤ የሚያርቅ ፤ የሚያስርቅ ፤ አራቂ ፡ አስራቂ ፤ አስወጋጅ ። አሰሳሌ ፡ እከያት ። ጸሎት ፡ መድኀኒት ፡ ውእቱ ፡ ወ አሰሳሌ ፡ ዘሎ ፡ ኀጣውእ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ። አፈ ፡ ተ፳፯) ።

ሰሲን ፤ (ሰሰነ ፤ ይሰስን) ፤ መሴሰን ፤ ቀ ልን ፡ ሚስትን ፡ መከድ ፤ ሌላ ፡ መውደድ ፤ ዐልፎ ፡ ተርፎ ፡ መኼድ ። ማሸፍረት ፡ መጠንቈል ፤ ጣዖት ፡ ማም ለክ ፡ ለሰይጣን ፡ መስገድ ።

ሰሳኒ ፤ (ኒት ፡ ንያን ፡ ያት) ፤ የሚሴሰን ፤ ሴሳኝ ፤ ሴሰኛ ፤ ሸፍተኛ ፤ መምለኬ ፡ ጣዖት ።

ሰሰን ፤ (ናት) ፤ ሴሰኝነት ፤ ቃላቅ ፡ ኀጢአት ፤ ክልክ ፡ ያለፈ ፡ የተረፈ ፡ ዝሙት ፤ አምልኮ ፡ ጣዖት ። ዛቲስ ፡ ትጤአት ፡ ሰሰን ፡ እኪት ፡ ይእቲ ፡ (ሸነገ ፡ ፲፳ ፡ ፳፫ ። አርጋ ፡ ፱) ።

ሶሳን ፤— አበባ ፤— ሰውሳን ።

ሳት ፤ (ዕብ ፡ ስታው ። ዐረ ፡ ሽታ) ፤ ስሙ ፡ ፈደል ፡ ሸ፳ኛ ፡ ሰ ። ክረምት ፡ የዝናም ፡ ወራት ፡ ማለት ፡ ነው ። ጸሐፍት ፡ ግን ፡ ሳት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እሳት ፡ ይሉታል ፤ ጥንተ ፡ ስሙ ፡ ሰን ፡ እንጂ ፡ እን ፡ አ ይሸምና ፤ ሠውት ፡ ሠን ፡ ንጉሥ ፡ እንደሚሉት ፡ ይህም ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። ፪ኛ ፡ ስሙ ፡ ሰዐት ፡ ይባላል ፤ ምስ ጢሩ ፡ ከዚያው ፡ ይገባል ።

ሰትይ ፤ ዮት ፤ (ሰትየ ፡ ይሰቲ ፡ ይስተይ ። ዕብ ፡ ሻታህ ። ሱር ፡ ሼቲይ) ፤ መጠጣት ፤ መጐ ንጨት ፤ መጠጥን ፡ በአፍ ፡ መቀበል ፤ መሳብ ፡ መጕተት ፤ ወደ ፡ ሆድ ፡ ማግባት ፤ ፋት ፡ ገጭ ፡ ጕርጕጭ ፡ ማድረግ ። በሊዐ ፡ ወሰትይ ። ንብላዕ ፡ ወንስተይ ። ስተይ ፡ ማየ ፡ እምቀሦትከ ። በነበ ፡ ይሰትዩ ፡ ወይነ ። ስተዩ ፡ ምስሌነ ፡ (ሩት፫ ፡ ፫ ። ኢሳ፳፪ ፡ ፲፫ ። ምሳ፭ ፡ ፲፭ ። ሚራ፴፭ ፡ ፭ ። ዮዲ፲፪ ፡ ፲፯) ።

ሰታዪ ፤ (ዪት ፡ ይያን ፡ ያት ፤ ተይት) ፤ የሚጠጣ ፡ ጠጭ ፤ መጠጥ ፡ ወዳጅ ። በላዔ ፡ ሥጋ ፡ ወሰ ታዪ ፡ ደም ። ኢትኩን ፡ ሰታዬ ። ኢትኩኑ ፡ ሰታይያነ ፡ ብዙኅ ፡ ወይን ፡ (ድጓ ። ምሳ፳፫ ፡ ፳ ። ዲድ ፡ ፯) ።

አስተየ ፤ አጠጣ ፤ አስጠጣ ፤ ጠጡልኝ ፡ አጠ ጡልኝ ፡ አለ ። ከመ ፡ ኣስትዮሙ ፡ ለሕዝብየ ። ለዘይ ላሑ ፡ አስትዮ ፡ ወይነ ። ጸዘዘ ፡ ያስትይዋ ፡ እምነ ፡ ወይኑ ። ዘያስትዮ ፡ ለቢጹ ፡ በዘይመውት ፡ (ኢሳ፵፫ ፡ ፳ ። ሚራ፴፱ ፡ ፳፱ ። ዮዲ፲፪ ፡ ፲ ። ዕንባ ፡ ፪፲፭) ።

**አስታዪ** ፤ **መስተዪ** ፤ የሚያጠጣ ፡ የሚያስ ጠጣ ፤ አጠጭ ፡ አስጠጭ ፤ ዐዳይ ፡ ስጭ ።

**መስቴ** ፤ መጠጫ ፡ ብርሌ ፡ ዋንጫ ። መሸታ ፡ መጠጥ ፤ ተቀድቶ ፡ የሚሰጥ ። መብልዕ ፡ ወመስቴ ። መስቴ ፡ መኰንን ፡ (ቅዳ ። ኪዳ ። ሮሜ ፲፬ ፡ ፲፯ ። ቈላ ፪ ፡ ፲፮) ።

**ምስታይ** ፤ ማጠጫ ፤ መጠጫ ፡ ቦታ ፤ ገንዳ ፤ የመሸታ ፡ ቤት ። ወሶጠት ፡ ቀሡታ ፡ ፍጡነ ፡ ውስተ ፡ ምስታይ ። ገብላት ፡ ዘምስታየ ፡ ማይ ። ምንባረ ፡ ምስታይ ፡ (ዘፍ፳፬ ፡ ፳ ። ፴ ፡ ፴፰ ። ዮሴፍ) ።

**ተሰትየ** ፤ ተጠጣ ፤ መጠጥ ፡ ኾነ ። ዘተበልዐ ፡ ወተሰትየ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፶፪ ። ክፋ ፡ ፲ ። ቅዳ) ።

**ስቱይ** ፤ (ያን ፡ ያት ፡ ቲት ፤ ትይት) ፤ የተጠጣ ። የጠጣ ፤ የረካ ፤ መጠጥ ፡ የጠገበ ። ኢትገሥጽ ፡ ብጹከ ፡ እንዘ ፡ ስቱይ ፡ ወይነ ፡ (ሢራ ፴፩ ፡ ፴፩) ።

**ስትየት** ፤ መጠጣት ፤ አጠጣጥ ፤ መጠጥ ። ድ ዉይ ፡ ዘይሔዝዞ ፡ ጠቢብ ፡ ከመ ፡ ይትከላእ ፡ እምነ ዊም ፡ ወስትየት ፡ ወሲሲት ፡ (ፊልክ ፡ ፳) ።

**ስቴ** ፤ **ስታይ** ፤ (ያት) ፤ መጠጥ ፤ ፈሳሽነት ፡ ያለው ። የሚያረካ ፡ የሚያሰክር ። ስቴ ፡ ወአብዝኆቱ ፡ ሙስና ፡ ልቦሙ ፡ ለጠቢባን ። ንዋየ ፡ ስቴ ። ዘወሀበ ፡ ስቴ ፡ ሕምዘ ። ስታይ ፡ ወአንስት ፡ ያስሕታሁ ፡ ለጠ ቢብ ። ዝሙት ፡ ወስታይ ፡ ወስካር ። ዘይሠርባ ፡ ለኀ ጢአት ፡ ከመ ፡ ስታይ ፡ (ሲኖዶ ። ዘሌ ፲፩ ፡ ፴፬ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፬ ። ሢራ ፲፱ ፡ ፪ ። ሆሴ ፬ ፡ ፲፩ ። ኢዮ ፲፭ ፡ ፲፮) ።

(ጥ) **ሰት** ፤ ፈሳ ፤ ቁጠማ ፤ ግራምጣ ። ውስተ ፡ ሰት ፡ ወስማዝ ፡ (ኢዮ፡ጥ ፡ ፲፯) ።

**ሰቲዕ** ፤ **ዖት** ፤ (ሰትዐ ፡ ይሰትዕ ፡ ይስ ታዕ ። ዕብ ፡ ሻታዕ) ፤ መፍራት ፡ መጠውለግ ፤ መ ኽመልመል ፡ መድረቅ ፤ ከመጠጥ ፡ ዕጦት ፡ የተነሣ ፤ የቡ ቃያ ፡ የተክል ፡ የምላስ ። (ኢሳ፵፩ ፡ ፲፯) ።

—፤ ፈርቶ ፡ መገበር ፤ መገዛት ፤ ግብር ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ መስጠት ።

**አስትዐ** ፤ አስፈራ ፡ አስገበረ ፡ ግብር ፡ አምጡ ፡ አለ ።

**አስትዓ** ፤ ግብር ፡ እጅ ፡ መንሻ ፤ በረከት ፤ በው ድም ፡ በግድም ፡ የሚሰጥ ። አስትዓ ፡ መንፈሳዊት ። ናሁ ፡ አስትዓክሙ ። ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ክብሩ ፡ ወአ ስትዓሁ ፡ እምዐበይተ ፡ ሀገር ፡ (ቄር ። ጀንገ ፡ ፴ ፡ ጃ፯ ። ሔኖ፶፫ ፡ ፭ ። ፪ዜና ፡ ፭ ፡ ፲፯ ። ድጓ) ። ሲበዛ ፡ አስትዓት ፤ አስታዕ ፡ ያሰኛል ።

**ሳትፎ** ፤ **ፎት** ፤ (ሳተፈ ፡ ይሳትፍ ። ዕብ ፡ ሻታፍ ። ሱር ፡ ሻውቴፍ ። ዐረ ፡ ሽረከ) ፤ ማሳተፍ ፤ ማጕረፆ ፡ መወተፍ ። መግጠም ፡ ማጋጠም ፤ ማገናኘት ፡ ማስተባበር ፤ አንዱን ፡ ከንዱ ፡ ጋራ ፡ ማዛወግ ፤ አንድ ፡ ማድረግ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በሐቀረ ፡ ፈንታ ፡ አ ስተሐቀረ ፡ እንዲል ፤ በሳተፈ ፡ ፈንታ ፡ አስተሳተፈ ፡ ይ ላል ፤ አድራጊውን ፡ ባደራራጊ ። ታስተሳትፍ ፡ ኀሊና ፡ መንግሥትክሙ ። አስተሳተፈከ ፡ በመንግሥትየ ። ተ ዘምዶ ፡ ሥጋዊ ፡ ያስተሳትፍ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ። ያስተ ሳትፍዎሙ ፡ እምስጢር ፡ ቅዱስ ፡ (ቄር ። ፈላስ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፵፩ ። ፈ ፡ መ ፡ ፯ ፡ ፲፫) ።

**ሳታፊ** ፤ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት) ፤ የሚያሳ ትፍ ፡ አሳታፊ ፤ የሚያገናኝ ፤ የሚያስተባብር ።

**ተሳተፈ** ፤ በቁሙ ፤ ተገናኘ ፤ ተባበረ ፤ ተዋሐደ ፤ አንድ ፡ ኾነ ፤ በግብር ፡ በነገር ። ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ተሳት ፎታ ፡ ያውስባ ፡ በሰብሳብ ፡ ሕጋዊ ። እመ ፡ ኮንኩ ፡ ምስሌክሙ ፡ እምተሳተፍኩክሙ ፡ በዐመፃክሙ ። ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይሳተፍ ፡ በጸሎት ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ቍርባን ። ተሳተፍነ ፡ ምስለ ፡ ወልድከ ፡ ወኮነ ፡ አሐደ ፡ ሥጋ ። ወበዝ ፡ ተሳተፍክሙ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ኮኑ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳ ፡ ፭ ። ዮሴፍ ። ፈ ፡ መ ፡ ፬ ፡ ፬ ። ገ፡ማሬ ። ዕብ፲ ፡ ፴፫) ።

**ተሳታፊ** ፤ የሚሳተፍ ፤ የሚተባበር ፤ ተባባሪ ፤ ተካፋይ ። ተሳታፍያን ፡ ውስቴቱ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፴፯) ።

**ሱቱፍ** ፤ (ፋን ፡ ፋት ፡ ትፍት) ፤ የተሳተፈ ፤ የተባበረ ፤ አንድ ፡ የኾነ ፤ ሽሪክ ። ሰላም ፡ ለእራኅከ ፡ መክፈልተ ፡ ሕማማት ፡ ሱቱፍ ። እመ ፡ ቦ ፡ ብእ ሲት ፡ ዘኮነት ፡ ሱትፍት ፡ ምስለ ፡ ሰይጣን ። ሱቱ ፋነ ፡ ሰረቅት ። ሱቱፋነ ፡ ጻማ ፡ ወሕማም ። ሱቱፋነ ፡ ንሕነ ፡ በሲይናቲነ ። ሰላም ፡ ወርትዕ ፡ ሱቱፋነ ፡ ይኩ ኑ ፡ (ደራሲ ። ፈ ፡ መ ፡ ፳፩ ፡ ፲፬ ። ኢሳ፩ ፡ ፳፫ ። ስንክ ፡ ጥር፳፯ ። ፩ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፯ ። ሔኖ፲፩ ፡ ፪) ።

**ሱታፌ** ፤ መሳተፍ ፤ መተባበር ፤ ማኅበርነት ፡ ድ ርገት ፤ አንድነት ። ተባባሪ ፤ ሽሪክ ፡ ጓደኛ ፤ ባልንጀራ ፤ ማ ኅበረተኛ ። አባ ፡ ጴጥሮስ ፡ አብ ፡ ሱታፌ ፡ መንፈሳው ያን ፡ አስተጋብአ ፡ ብዙኃነ ፡ ሰብአ ፡ ወሐነጸ ፡ አድባ ራተ ፡ ወሠርዐ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሱታፌ ፡ በግብረ ፡ እደዊ ሆሙ ፡ ወሲሳዮሙ ። ከመ ፡ አንትሙኒ ፡ ትኩኑ ፡ ሱ ታፌ ፡ ምስሌነ ። አነ ፡ ሱታፌከ ፡ በኵሉ ፡ ግብርከ ። እኁክሙ ፡ ወሱታፌክሙ ። አስቴር ፡ ሱታፌ ፡ መን ግሥትነ ። ለእመ ፡ ተጸብአ ፡ ካህን ፡ ምስለ ፡ ካህን ፡ ሱታፌሁ ፡ (ስንክ ፡ ግን፲፭ ። ፩ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፫ ። ዮሴፍ ። ራእ፩ ፡ ፱ ። አስቴ፳ ፡ ፲፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፱) ።

**ሱታፍ** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ከመ ፡ ንኩን ፡ ሱታፎ ፡ ለጽድቅ ። ሰላም ፡ ለሕፀንኪ ፡ ሊጥበበ ፡ ሰማይ ፡ ም ዕራፉ ፡ ዘኢይትረከብ ፡ ሱታፉ ። ጥዑመ ፡ ዜና ፡ ጊዮ ርጊስ ፡ ለሐሲበ ፡ ዕጕልት ፡ ሱታፉ ፡ (፪ዮሐ ፡ ፰ ። ደ ራሲ ። ፩ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፩ ። ፩ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፳፫) ።

**ስትፍና** ፤ ሱታፌነት ፤ ተባባሪነት ፤ ሽሪክነት ። አልቦ ፡ ዘረብሐ ፡ እምስትፍና ፡ መሰኮት ፡ (ቄር ፡ ጸላ) ።

**አስተሳተፈ** ፤ (ሳተፈ) ፤ አሳተፈ ፤ አስተባ በረ ። ሳተፈን ፡ ተመልከት ፤ የባረከ ፡ ቤት ፡ ተደራጊው ፡ ከተደራራጊው ፡ እንዲደረብ ፡ አደራራጊውም ፡ ካድራጊው ፡

አንቀጽ ፡ ይደረባል ። ናፈቀንና ፡ ማህሌን ፡ ማረረን ፡ ተመልከት ።

**መስተሳትፍ**፤(ፍት ፡ ፋን ፡ ፋት)፤ የሚያሳትፍ ፡ አሳታፊ ፤ የሚሳተፍ ፡ ተሳታፊ ፤ ሱቱፍ ።

**ሰተረ፤—ሠንተረ፤—ሠተረ ።**

**ሰቲር ፤ ሮት ፤ (ሰተረ ፡ ይሰትር ፡ ይስትር ። ዕብ ፡ ፋራሽ)** ፤ መስተር ፤ መዘርጋት ፡ ማዘጋጀት ፤ ማለብ ፡ መደገን ፤ ሰውሮ ፡ ማኖር ፤ መሰወር ፤ የገመድ ፡ የወጥመድ ። ሰጠረን ፡ ሰፍሐንና ፡ ሰጥሐን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ናቸው ። ንብሉ ፤ ሲተ ፤ መሥገርተ ፤ ወሰተሩ ፡ አሕባለ ፡ መሣግር ፡ (መዝ ፡ ፻፵) ። መሸተር ፡ ማስጊዎ ፡ (ዐማርኛ) ።

**ሰታሪ ፤ (ሪት ፡ ርያን ፡ ያት ፤ ተርት)** ፤ የሚሰትር ፤ የሚዘረር ፤ የሚዘረጋ ፡ ዘርጊ ።

**ሰቲት ፤ ቶት ፤ (ሰተ ፤ ሰተተ ፡ ይሰትት ፡ ይስትት ። ዕብ ፡ ሻታት)** ፤ መቅናት ፡ መንሳተት ፤ ሰተት ፡ ማለት ፤ መውደቅ ፡ መዘርጋት ፤ እንደ ፡ ስክተት ፡ እንደ ፡ መሠረት ፡ መኸን ፤ መዋረድ ፡ መረገጥ ፤ መናቅ ።

**ስቱት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ቶት)** ፤ ሰተት ፡ ያለ ፤ የቀና ፡ የተንሳተተ ፤ ዝርግ ፡ ወዳቃ ፤ የተናቀ ፡ የተጠቃ ። በስቱት ፡ ፈንታ ፡ መስትት ፡ ይባል ፤ አያሰኝም ። ከመ ፡ ኢይኩን ፡ እግዚእየ ፡ መስትተ ፡ ወዘኢይበቍዕ ፡ (ዮዲ ፲፩ ፡ ፲፩) ።

**አስተተ** ፤ አዋረደ ፡ አዋደቀ ፡ አጣጣለ ፤ ናቀ ፡ አቃለለ ፤ ተወ ፡ ቸል ፡ አለ ፤ አስታጐለ ። እሴ ፡ አስተትዎ ፡ ለጻድቅ ። ዘያስትት ፡ ግብረ ፡ እግዚ ፡ ውእቱኒ ፡ ያስትቶ ። ኢታስትት ፡ ቃሎ ፡ ለእግዚኦር ። አስቲተነ ፡ ሕይወተ ። ኢታስትት ፡ ገቢረ ፡ ምጽዋት ። ኢታስትት ፡ ተግባረ ፡ እደዊከ ፡ (ጥበ ፡ ፲ ። ምሳ ፲፫ ፡ ፲፫ ። ዮዲ ፲፩ ፡ ፲ ። ዕብ ፲፪ ፡ ፫ ። ሢራ ፯ ፡ ፲ ። ፲፭) ።

**መስተቲ ፤ መስትት ፤ (ታን)** ፤ የሚንቅ ፤ የሚያቃልል ፤ የሚያስታጕል ፤ ዕቡይ ፤ ሀካይ ። እመ ፡ ገብረ ፡ ዐመፃ ፡ ወክህ ፡ ዕቅፍተ ፡ ወመስትተ ፡ ለእሊኣሁ ፡ ጥምቀት ። ከመ ፡ ኢንኩን ፡ መስትታነ ፡ (ሲኖ ። ዲዲ ፡ ፱ ። ፪ዕገ ፡ ፲፪ ፡ ፲፯) ።

**ሰጸለክስ ፤ (ጽር ፡ ስፓላክስ ። ዕብ ፡ ሀቲንሻሜት ፤ ጤሌፍ)** ፤ ፍልፈል ፤ ያይጥ ፡ ገመር ። ሰኩና ፤ ጥፍር ፤ መዳፍ ፡ ውስጥ ፡ እግር ፤ የእንስሳትና ፡ የአራዊት ። ለሰውም ፡ ይኸናል ፤ ኸብ ፡ አይበላሽ ፡ እንዲሉ ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፴ ። ፩ነገ ፡ ፶ ፡ ፴፭) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ እሥሥት ፡ ይሉታል ፤ ፍችው ፡ አይደለም ።

**ሰጺራ ፤ (ጽር ፡ ስፒራ)** ፤ መለዮ ፡ ምልክት ፤ የባንዲራ ፡ ዐይነት ፤ በወታደሮች ፡ ልብስ ፡ ባንገትጌው ፡ በእጅጌው ፡ የሚደረግ ። ሠገራተ ፡ ሰጺራ ፤ ሕዝበ ፡ ሰጺራ ። ምልክት ፡ ያላቸው ፤ ምልክታሞች ፤ ባለምልክቶች ፡ (ማር ፲፭ ፡ ፲፮ ። ዮሐ ፲፰ ፡ ፫ ። ግብ ፲ ፡ ፩) ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፤ የጭፍራ ፡ ስም ፡ ብለው ፡ ይፈቱታል ። ሠገረን ፡ ተመልከት ።

**ሰጺራ ፤ (ጽር ፡ ሳፕፊረስ ። ዕብ ፡ ሻፒራ)** ፤ ስመ ፡ ብእሲት ፤ ሶፎራዊት ፡ ሰንፔራዊት ፤ ሰንቀኛ ፡ ውቢት ፡ ሉሲት ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ ሽቱ ፡ ይሉታል ፤ ሶፎርን ፡ እይ ፡ (ግብ ፭ ፡ ፩) ።

**ሲፓራ ፤ (ዕብ ፡ ጺፖራ)** ፤ ገዝኒ ፡ ክማሁ ፤ ስመ ፡ ብእሲት ፤ ያፍ ፡ ሳሕቢት ፤ የመስቀል ፡ ወፍ ፡ (ዘፀ ፪ ፡ ፳፩) ።

# ተ

**ተ** ፤ ደኃራይ ፡ ፊደል ፤ ኻያ ፡ ኹለተኛ ፤ መጨረሻና ፡ መደምደሚያ ፤ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፤ ስሙ ፡ ታዊ ፤ ታው ፤ ቍጥሩ ፡ አራት ፡ መቶ ፤ እኅገዝ ፡ ሲኾን ፡ ተ ፡ (፬፻) አርባዕቱ ፡ ምእት ፡ ይባላል ።

**ተ** ፤ የርባታ ፡ ተውሳክ ፤ የመደረግና ፡ የመደራረግ ፡ ልማድ ። ቀተለ ፤ ተቀትለ ፤ ተቃተለ ። ከፈለ ፤ ተከፍለ ፤ ተካፈለ ። ፈለጠ ፤ ተፈልጠ ፤ ተፋለጠ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ኹለተኛም ፤ በ፳ ፡ ፊደላት ፡ (ተደዘጠጸሰ) ፡ ከሚነሡ ፡ በቀር ፤ በግስ ፡ ኹሉ ፡ ሳድስ ፡ ሰራዊት ፡ ለሩቅ ፡ ሴትና ፡ ላሬ ፡ ቅርቦች ፡ የትንቢት ፡ አንቀጽ ፡ ሥርው ፡ ይኾናል ። ይህም ፤ ቀተለት ፡ ለክ ፡ ኪ ፡ ክሙ ፡ ን ፡ ብሎ ፤ ትቀትል ፡ ሊ ፡ ሉ ፡ ላ ፡ እያለ ፡ ሌላውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳያል ። ተደዘጠጸሰን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ በሚነሡ ፡ ግን ፡ ሥርውነት ፡ የለውም ፤ ንኡል ፡ ነው ። ይህም ፤ ተተክለ ፡ ይትከል ፤ ተደመረ ፡ ይደመር ፤ ተዘርዐ ፡ ይዘራዕ ፤ ተጠውመ ፡ ይጠወም ፤ ተጸውዐ ፡ ይጼዋዕ ፤ ተሰብሐ ፡ ይሴባሕ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ሦስተኛም ፤ አብዝኛ ፡ ምእላድ ፡ እየኾነ ፡ በመጨረሻ ፡ ቃል ፡ በዘር ፡ በንባር ፡ በአርእስትና ፡ በሳቢ ፡ ዘር ፡ ባንዲትና ፡ በብዙ ፡ ሴት ፡ ቅጽል ፡ ይገባል ። በጥሬ ፡ ሲገባ ፤ ወህበ ፡ ብሎ ፡ ሀብት ፤ ሐመየ ፡ ሐሜት ፤ ፈነወ ፡ ፍኖት ። በማብዛት ፡ ሲገባ ፤ ብዕል ፡ ብዐላት ፤ ገድል ፡ ገድላት ፤ ኀይል ፡ ኀይላት ።

በንባር ፡ ሲገባ ፤ ማይ ፡ ማያት ፤ ሰማይ ፡ ሰማያት ፤ ኮከብ ፡ ከዋክብት ፡ ይላል ። በአርእስት ፡ ሲገባ ፤ ቀቲል ፡ ቀቲሎት ፤ ቀዊሞት ፡ ገቢሮት ። በሳቢ ፡ ዘር ፡ ሲገባ ፤ ቅትለት ፡ ቁመት ፡ ግብረት ፡ ይላል ። በሴቶች ፡ ቅጽል ፡ ሲገባ ፤ ላንዲቱ ፡ ቀታሊት ፡ ገባሪት ፡ ሠናይት ፡ ክብርት ፤ ለብዙዎች ፡ ቀታልያት ፡ ገባርያት ፡ ሠናያት ፡ ክቡራት ፡ ይላል ። ትእምርት ፡ ትዕግሥት ፡ ትውክልት ፤ ይህን ፡ የመሰሉ ፤ ባዕድ ፡ ከምእላድ ፡ ይባላል ። ተ ፡ ከባዕድ ችም ፡ ከምእላድችም ፡ ይቈጠራል ፤ እንደ ፡ ወ ፡ ከኹል ፡ ገብ ፡ ነው ።

**ታአዶኮስ** ፤ (ጽር ፡ ቴዎቶኮስ) ፤ ወላዲተ ፡ አምላክ ፤ እመ ፡ አምላክ ።

**ተአኃ** ፤—ወንድምነት ፤—አኀወ ።

**ታእካ** ፤—አዳራሽ ፤—ዐከወ ።

**ተአኪያሃ** ፤ (ጽር ፡ ቴዎቶኮስ) ፤ ወላዲተ ፡ አምላክ ። በመዮ ፡ ሊድርሰኒ ፡ ድርሰነ ፡ ተአኪያሃ ፡ ማርያም ፤ ዘውእቱ ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ብሂል ፡ (ያዕ ፡ ዘእል) ።

**ታኦሎጎስ** ፤ (ጽር ፡ ቴዎሎጉስ) ፤ ሎጎስ ፡ ቴዎ ፤ ነባቤ ፡ አምላክ ፤ ነባቤ ፡ መለኮት ። ጎርጎርዮስ ፡ ታኦሎጎስ ፤ ዮሐንስ ፡ ታኦሎጎስ ፡ (ያዕ ፡ ዘእል) ። በታኦሎጎስ ፡ ፈንታ ፡ ቴዎሎጎስ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኹሉ ፤ አዛውሮ ፡ ቴዎጎሎስ ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ። ስንክ ፡ መስ ፱ ። ድጓ) ።

**ታኦማጎሲስ** ፤ (ጽር ፡ ቴዎማኽስ) ፤ ፀረ ፡ አምላክ ፤ እንደ ፡ ማኒኖ ፡ እንደ ፡ ፍሬማሶን ፡ ያለ ፡ ፍጹም ፡ ከሓዲ ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ አርዮስ ፡ እንደ ፡ መቅዶንዮስ ፡ ያለ ፡ ፍጹም ፡ መናፍቅ ። (ሥላሴ ፡ ቅኔ) ፤ እልፍ ፡ ዐላውያን ፤ ማኒስ ፡ ክነ ፡ የዐብዮሙ ፡ ምስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወአብ ፡ እስከ ፡ አኀጥአነ ፡ ወልደ ፤ እስመ ፡ ምስለ ፡ ባዕድ ፡ ተናገረ ፡ ባዕደ ፤ ወእምዐላውያን ፡ ኀጥአ ፡ ዘይመስሎ ፡ አሐደ ፤ ዐመፃ ፡ ካልአ ፡ ኀበ ፡ ፈቀደ ፤ ሰባልዮስ ፡ በዝ ፡ እስመ ፡ ኢሰመደ ፤ ወከመ ፡ ዝ ፡ አርዮስ ፡ አክሐደ ። ታኦማጎሲስ ፤ ዘበትርጓሜሁ ፡ ፀረ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**ታኦንትያ** ፤ (ጽርእ) ፤ አምላክ ፡ ሐመ ፡ በህላዌሁ ፤ ቴዎሐ ፡ ውላጤ ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ግብር ፡ የሚሉ ፡ የመናፍቃን ፡ ባህል ። ተሳረቀንና ፡ አስተሳረቀን ፡ እይ ፤ ሰረቀ ።

**ታኦፊላ** ፤ (ጽር ፡ ቴዎፊሌ) ፤ ቴዎፍሎስ ፤ ፍቁረ ፡ አምላክ ፤ መፍቀሬ ፡ አምላክ ፡ (ግብሐ ፡ ፩) ።

**ታኦርያ** ፤ (ጽርእ) ፤ ሠናይ ፡ መሠንይ ፤ አው ፡ ሰማያዊ ፡ ብርሃናዊ ። ዘይሰመይ ፡ ታኦርያ ፡ ዘውእቱ ፡ ራእይ ፡ ልቡናዊ ፡ (ማር ፡ ይሥሐ ፡ ፩) ።

**ታኦስ** ፤ (ጽር ፡ ቴዎስ) ፤ አምላክ ። ታኦስ ፡ ናይናን ፡ ኦ ፡ አምላክ ፡ መሐረን ፡ (ግብ ፡ ሕማ) ።

**ቴአስ** ፤ (ጽርእ) ፤ ስመ ፡ ሀገር ፤ የቦታ ፡ ስም ። አንስት ፡ እለ ፡ ትመጽአ ፡ እምነ ፡ ቴአስ ፡ ንዓ ፡ (ኢሳ ፳፯ ፡ ፲፩) ። ዕብራይስጡ ፡ ግን ፤ ግእዙ ፡ እምነ ፡ ቴአስ ፡ ንን ፡ ባለው ፡ ምኢሮት ፡ አታ ፡ ይላል ፤ ያውዕያሃ ፡ ያንድዳሃ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቦታንና ፡ አገርን ፡ አያሳይም ።

**ታኦስክንድሳውያን** ፤ (ጽርእ) ፤ ቀታልያን ፡ አምላክ ፤ ባምላክነቱ ፡ ታመመ ፡ ሞተ ፡ የሚሉ ፡ (ሃይ ፡ አበ) ።

**ትቤ** ፤—ትባለች ፤—ብሂል ።

**ትብሌ** ፤ **ትብላይ** ፤ **ትብልያ** ፤ (ሮማይ ፡ ታቡላ ፤ ገበታ ። ዕብ ፡ ሐሼን) ፤ ልብስ ፡ ተክህኖ ፤ የደረት ፡ ሳንቃ ፤ ሴደርያ ። ትብልያ ፡ ዘመቅፈርት ። ትብልያ ፡ ዘልብሰ ፡ መትከፍት ፡ (ዘፀ ፳፰ ፡ ፯ ፡ ፰ ። ፴፮ ፡ ፲፪) ። በትብልያ ፡ ፈንታ ፡ ኢፉድ ፤ በኢፉድ ፡ ፈንታ ፡ ትብልያ ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ እየቅል ፡ ነው ።

**ተብያስ** ፤ ስመ ፡ ሀገር ። አባ ፡ ሲሶይ ፡ ተብያሳዊ ፡ (ፊልክ) ።

**ተቤሳ** ፤ **ተቤስ** ። (ዕብ ፡ አፌር ። ጽር ፡ ቴላሞን) ፤ ግልባቤ ፡ ገጽ ፤ ሠርመዲ ፡ ቀጸላ ፤ የፊት ፡ መሸፈኛ ። ወአሰረ ፡ ተቤሳ ፡ ውስተ ፡ አዕይንቲሁ ፡ (፩ነገ ፡ ፳ ። ፴፰ ፡ ፵፩) ።

**ተቤሳ** ፤ (ዕብ ፡ ኤፌር ። ዐረ ፡ ቲብን) ፤ ትቢያ ፡ ዐፀፋ ፤ ደቃቅ ፡ ዐፈር ፤ ፀመድ ፤ እብቅ ። ሐራሲ ፡ ትጉህ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘአሰንታሁ ፡ ተመልአ ፡ ቀኖተ ፡ ኀጺን ፡ ተቤሳ ፡ (ቅኔ) ።

**ተቢዕ** ፤ **ዖት** ፤ (ተብዐ ፡ ይተብዕ ፡ ይትባዕ ፤ ጠብዐ ። ዐረ ፡ ተቢዐ ፤ ተለወ ። ዕብ ፡ ታባዕ ፤ ሻ ፡ ፈለገ) ፤ መትባት ፡ መጨከን ፤ ጨካኝ ፡ ቈራጥ ፡ ወንድ ፡ መኾን ፤ መድፈር ፤ አለመፍራት ፡ አለማመንታት ። ጽናዕ ፡ ወትባዕ ። ትብዑ ፡ ወጽንዑ ። ከመ ፡ ኢይትባዕ ፡ ላዕሌክ ፡ (ኢያ፩ ፡ ፮ ። ፲ ፡ ፳፭ ። ሚራ፳ ፡ ፲፩) ። መትባት ፡ ለብረት ፡ ሳንደበት ፡ ይነገራል ። እሳ ፡ የተባ ፡ ነው ፤ ብረቱን ፡ አትባው ፤ ውሃ ፡ ብረት ፡ ያጠናል ፡ እንዲሉ ። የብረት ፡ ትባት ፡ ሥራው ፡ ካለቀለት ፡ በኋላ ፡ በእሳት ፡ ማሞ ፡ ከውሃ ፡ መማባት ፡ ነው ፤ አለዚያ ፡ አይጠነክርም ፡ ይባላል ።

(ጥ) **ተብዖ** ፤ **ዖት** ፤ (ተብዐ ፡ ይቴብዕ ፡ ይተብዕ) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ሲጠብቅ ፡ የሰብሐ ፤ ሲላላ ፡ የገብረ ።

**ተባዒ** ፤ (ዒት ፡ ዕያን ፡ ያት ፤ ዕት) ፤ የሚጨክን ፤ ጨካኝ ፤ ደፋር ፡ ቈራጥ ። ብእሲ ፡ ተባዕ ። ተባዕያን ፡ ምስሌሆሙ ። ዕደው ፡ ስሙያን ፡ ወተባዕት ፡ (ኢሳ፰ ፡ ፰ ። ፴፱ ፡ ፯ ። ሶፎ ፡ ፲፪ ፡ ፴) ።

**ተባዕ** ፤ (ዕት ፡ ዓን ፡ ዓት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ብእሲ ፡ መስተቃትል ፡ ወተባዕ ። ጽኑዕ ፡ ወተባዕ ። ሐራዊ ፡ ተባዕ ። ከመ ፡ ዕደው ፡ ተባዓን ፡ (ሚራ፳፰ ፡ ፳፰ ። ፳፱ ፡ ፲፩ ፡ ፳፰ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ፳፱ ። ዮኤ፪ ፡ ፯) ።

(ባ) **ትቡዕ** ፤ (ብዕት) ፤ የተባ ፡ ትብ ፤ ጨካኝ ፤ ቈራጥ ። እመሰ ፡ ከንክሙ ፡ ትቡዓነ ፡ ወጽኑዓነ ፡ (ዮሴፍ) ።

**ትብዐት ፤** መትባት ፤ አተባብ ፤ አጨካከን ፤ ጨካኝነት ፤ ወንድነት ። እመ ፡ ትፈቅዱ ፡ ትክሥቱ ፡ ትብዐተክሙ ፡ ወጽንዐተክሙ ፡ ፃኡ ፡ አፍአ ፡ ሀገር ፡ (ዮሴፍ) ።

**ትብዕ ፤ (ዓት) ፤** ትባት ፤ ጭካኔ ፡ ጭከና ፤ ድፍረት ፡ ጉብዝና ፤ የወንድነት ፡ ሥራ ። ፈርሁ ፡ ሜዶን ፡ እምነ ፡ ትብዓ ፡ (ዮዲ ፲፮ ፡ ፲ ። ስንክ ፡ መስ ፲)።

**ትብዕና ፤** ትብነት ፤ ወንድነት ፤ ጨካኝነት ፤ ጭከና ። ብዙኃን ፡ ወኀያላን ፡ በጽንዕ ፡ ወበትብዕና ፡ ወብእፍራስ ፡ (፪ዜና ፡ ፲፮ ፡ ፰) ።

**ተባዕት ፤ (ብ ፡ አትቡዕ) ፤** በቁሙ ፡ ተባት ፤ ወንድ ፤ አውራ ፤ አለሌ ። ተባዕተ ፡ ወእንስተ ፡ ገብሮሙ ። ወለደት ፡ ተባዕተ ። ደርሆ ፡ ተባዕት ። አፍራስ ፡ አትቡዕ ። አባግዕ ፡ አትቡዕ ። ደቂቅ ፡ አትቡዕ ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፳፯ ። ኢሳ፷፮ ፡ ፯ ። ፪ዜና ፡ ፱ ፡ ፳፰ ። ፲፯ ፡ ፲፭ ። ፴፭ ፡ ፲፯) ።

**ተባዕታዊ ፡ ይ ፤** ወንድ ፤ ወንዳዊ ፤ ወንድማ ፤ ወንዳወንድ ፤ ብርቱ ። ሕፃን ፡ ተባዕታዊ ። ዐንበሬ ፡ ተባዕታይ ። መንፈስ ፡ ባሕር ፡ ተባዕታይ ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፳፯ ፡ ፳ ። ሔኖ፳ ፡ ፷ ፡ ፲፯) ።

**አትብዐ ፤** አተባ ፤ አስተባ ፤ አጨከነ ፤ አስጨከነ ፤ ወንድ ፡ አደረገ ።

**ተታብዐ ፤** ተጨካከነ ፤ ተጻናና ፡ አይዞኽ ፡ አይዞኽ ፡ ተባባለ ። ተታቢዖሙ ፡ (ዘፍ፵፱ ፡ ፳፰) ።

**አስተታብዐ ፤** አጨካከነ ፤ አጻናና ። ለአስተታብዖ ፡ ለቅድመ ፡ ጸባኢት ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ታቦር ፤ (ዕብራ) ፤** የተራራ ፡ ስም ፤ ታላቅ ፡ ረዥም ፡ ተራራ ፤ በናዝሬት ፡ አጠገብ ፡ በስተምሥራቅ ፡ ያለ ፤ ጌታ ፡ ምስጢረ ፡ መንግሥቱን ፡ ለነቢያት ፡ ለሐዋርያት ፡ የገለጸበት ። (መሳ፬ ፡ ፮ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፹፰) ። በዓለ ፡ ዕርገት ፡ ወበዓለ ፡ ኀምሳ ፡ ወበዓለ ፡ ታቦር ፡ ዘቦቱ ፡ ተወለጠ ፡ ወአእመሩ ፡ አርዳኢሁ ፡ ስብሐተ ፡ መለኮቱ ። ወሪዶሙ ፡ እምደብር ፡ እምደብረ ፡ ታቦር ፡ አዘዞሙ ፡ ኢይንግሩ ፡ ዘርእዩ ፡ በደብር ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይትፌጸም ፡ በዐድሜሁ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱ ። ድጓ ፤ ሠለ) ።

**ታቦት ፤ (ታት ። ቀብጥ ፡ ቴቢ ። ዕብ ፡ ቴብ ፤ ቴቡታ ። ዐረ ፡ ታቡት) ፤** መርከብ ፤ ማጥን ፤ ሙዳየ ፡ ምጽዋት ፡ ሙዳየ ፡ ምጢት ፡ (ኩፋ ፡ ፭ ። ዘፍ፮ ፡ ፲፱) ። ንፍቀ ፡ ታቦት ፡ (ማቴ፳፬ ፡ ፴፰ ። ፩ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፳) ። ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ከመ ፡ ብዙኅ ፡ ወርቅ ፡ ዘተረከበ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ። ንዋየ ፡ ቤት ፡ ለአዳም ፡ ወአንበሮ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ፡ በምሥራቅ ፡ ገነት ፡ (፪ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፲ ። ቀሌ) ። ምስጢሩ ፡ ቦታነትና ፡ ማኅደርነት ፡ ነው ። አንቲሙ ፡ ታቦት ፡ ለንጉሥ ፡ (፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፱) ። ባለቅኔዎች ፡ ማን ፡ የቤት ፡ ጥሬ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

**ታቦት ፤ (ዕብ ፡ አሮን) ፤** የቁም ፡ ማጥን ፤ ዐሥርቱ ፡ ቃላት ፡ የተጣፉባቸው ፡ የኹለቱ ፡ ጽላት ፡ ማኅደር ። ታቦት ፡ ዘመርጡል ። ታቦተ ፡ ሕግ ። ታቦተ ፡ እግዚአብሔር ። ታቦት ፡ በወርቅ ፡ ልቡጥ ፡ እምኀበ ፡ ዘግቡር ፡ እምዕፀ ፡ ዘኢይነቅዝ ፡ (ዘፀ፳፭ ፡ ፲ ። ፴፯ ፡ ፩ ። ዘኍ፲፬ ፡ ፵፬ ። ፩ዜና ፡ ፲፫ ፡ ፫ ። ኤፍ ፡ ፩) ።

**ታቦት ፤** መንበር ፡ ምሥዋዕ ፤ በመንበር ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ ፡ ጽላት ። ጸሎት ፤ እምቅድመ ፡ ያልብስ ፡ ታቦተ ። ወይኩን ፡ ታቦት ፡ ዘይፈልስ ፡ እመካን ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ከመ ፡ እብነ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ (ቅዳ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፩) ።

**ተቤሳ ፤—ግልባቤ ፤ ጸበል ፤—ተብየሰ ።**

**ተብሲል ፤—ንፍሮ ፤—በሰለ ።**

**ቶማቢጥ ፤ (ዐረብ) ፤** ሽንት ፡ ቅዘን ። ገብጥ ንና ፡ ተርቢዝን ፡ እይ ።

**ተጌሀ ፤ ሆት ፤ (ተግሀ ፡ ይተግሀ ፡ ይትጋሀ) ፤** መትጋት ፤ መንቃት ፤ መጠበቅ ፡ ማስተዋል ፤ እንቅልፍን ፡ ሀኬትን ፡ መተው ፤ ማይባት ፡ ማሸመቅ ። ዘይትግህ ፡ ውስተ ፡ አናቅጽየ ። ትግሁ ፡ እንከ ። ነምር ፡ ይትግህ ፡ ላዕለ ፡ አህጉሪክሙ ፡ (ምሳ፰ ፡ ፴፬ ። ማቴ፳፬ ፡ ፵፪ ። ኤር፭ ፡ ፮) ።

—፤ ማስብ ፡ ማስተንተን ፤ መውደድ ፡ መፍቀድ ፤ መቸኰል ፡ ማረበድ ። እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይተግሁ ፡ ለነፍስክሙ ። ይትግህ ፡ ለሠናይትክሙ ። ትግሂ ፡ ለመፍቅድየ ፡ በከመ ፡ ትተግህ ፡ እም ፡ ለውሉዳ ። ይተግሁ ፡ በሌሊት ፡ ወበመዓልት ፡ አንብቦ ፡ መጻሕፍት ። እተግህ ፡ አነ ፡ ከመ ፡ እግበር ፡ ዘነበብኩ ። ተጋህኩ ፡ ለአፀርዮ ፡ ፈቃዱ ፡ (ዕብ፲፫ ፡ ፲፯ ። አፈ ፡ ድ፳፱ ። አርጋ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳፯ ። ኤር፩ ፡ ፲፪ ። ዮሴፍ) ።

**ተጋሂ ፤ (ሂት ፡ ህያን ፡ ያት) ፤** የሚተጋ ፤ ትጉ ፤ ዐባቢ ። ጳጳስ ፡ ይኩን ፡ ተጋሄ ። ተጋህያን ፡ ለዘሱ ፡ ርዝስ ፡ ወአከይ ፡ (ቢዳ ። ቀሌ) ።

**ትጉህ ፤ (ሃን ፡ ሃት ፡ ግህት) ፤** በቁሙ ፤ የተጋ ፡ የነቃ ፤ እንቅልፍ ፡ የሌለው ። ትጉህ ፡ ለገቢረ ፡ ሠናይ ። ውእቱሰ ፡ ትጉህ ፡ ለአሕሥሞትየ ። ትጉሃን ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ኢይነውሙ ። ትግህት ፡ ንህብ ፡ (ዲድ ፡ ፬ ። ዮሴፍ ። መዋሥ ። ስንክ ፡ መስ፳፭) ።

**ትግሀት ፤ (ሃት) ፤** መትጋት ፤ አተጋግ ፤ ትጉህነት ፤ ትጋት ፤ እንቅልፍ ፡ ማጣት ። ሌሊተ ፡ ተኖልዎሙ ፡ ትግሀታተ ፡ ከንቱ ፡ ኢይምጽአሙ ። ቅዱስ ፡ ብሶይ ፡ መዓልተ ፡ ጸሎታተ ፡ ወሌሊተ ፡ ትግሀታተ ፡ ፈጸመ ፡ (ቅዳ ፡ ያዕ ። ድጓ) ።

**ትጋህ ፤ (ሃት) ፤** ትጋት ፡ ንቃት ፤ የእንቅልፍ ፡ ዕጦት ፤ ሐሳብ ፡ ፈቃድ ። በጻሕቅ ፡ ብዙኅ ፡ ወበትጋህ ፡ ፍድፉድ ። ኅሠሥዎ ፡ በትጋህ ፡ ፀቢይ ። ወለት ፡ ትጋህ ፡ ኅቡአ ፡ ይእቲ ፡ ለአቡሃ ። ትጋሁ ፡ ዘከመ ፡ ያቅሕም ፡ ብዕራይሁ ። ትጋሆሙ ፡ ለገሥጾትነ ፡ (አፈ ፡ ድ፴፬ ። አቡሻ ፡ ፶ ። ሢራ፴፪ ፡ ፱ ። ፴፰ ፡ ፳፯ ። አፈ ፡ ድ፳፱) ።

**አትግሀ ፤** አተጋ ፤ አነቃ ፤ እንቅልፍ ፡ አሳጣ ። አትግሀነ ፡ ለስብሐቲከ ። እፎኑመ ፡ ፈድፋደ ፡ ሕማ

ማተ፡ እግዚእ፡ ክርስቶስ፡ ያተግሀነ። ክቡድ፡ ሕማም፡ ያተግህ፡ ወእልቦ፡ ንዋም፡ (ስንክ፡ መስከረም። እሑ፡ ድርሳን። ሲራ፡ ፴፬፡ ፩)።

**ቴገን**፤ ጤገን፤ ምጣድ፤ እቶን፡ (ዘሌዋ፡ ፲፩)።

**ቴጉን**፤ ጤጉን፤ የበሰለ፡ የተጋገረ። ኅብስተ፡ ቴጉን፡ (ዘሌዋ፡ ፪)። ጤገንን፡ ተመልከት፤ ከዚህ፡ ጋራ፡ አንድ፡ ነው፤ ሌማውያን፡ ጠ፡ የሚሉትን፡ ያፈታውያን፡ ተ፡ ስላሉት፡ ኹለት፡ ይመስላል። ባለብሉዮች፡ ጉልቻ፡ ይሉታል።

**ተጌር፤ ሮት፤ (ተገረ፡ ይተግር፡ ይትግር። ዐረ፡ ታጀረ። ዕብ፡ ታጌር)**፤ መንገድ፤ ርቆ፡ መኼድ፤ ንጋዴ፡ መኾን። መንቀል፡ መትከል፤ መሳብ፡ መገተር፤ የእግር፡ የድንኳን፡ የከስማ፡ የአውታር።

**መትግር፡ ት፤ (ብ፡ መታግር፡ ት)**፤ ወተር፤ አውታር፤ የድንኳን፡ ገመድ። መታክሊሆን፡ ወመታግሪሆን። መታግርቲሆን፡ (ዘኍ፡ ፴፯። ፬፡ ፴፪)።

**መታግርት፤ (ዕብ፡ ፍቃዲም)**፤ ሰንበሮች፤ ቅርጾች፡ የታነጡ፡ የተነጠጡ፤ ያበጡ፡ የሰመጡ፤ ፈቅዐን፡ ተመልከት። ወመታግርተ፡ ገብረ፡ ባቲ፡ (፫ነገ፡ ፮፡ ፳፱)።

**መታግር**፤ ምስሶዎች፤ ወጋግራ፡ ባላ፤ ዋልታ፡ ሠረገላ። ለኅዋኅዊሃ፡ ወለመሳክዊሃ፡ ወለመታግሪሃ፡ ወለአዕማድኒ፡ (ገድ፡ ተክ)።

**ትግሬ፤ ትጋሬ፤ (ዐረ፡ ታጅር። ዕብ፡ ታጋር)**፤ ነጋዴ፡ ዐጣሪ፤ ሸያጭ፡ ሸቃጭ፡ ቸርቻሪ። የቋንቋ፡ ስም፤ ሴማዊ፡ ግእዛዊ፡ ቋንቋ፤ ሐበሾች፡ የሚናገሩበት፡ ከዐረብና፡ ከዕብራይስጥ፡ ሱታፌነት፡ ያለው። ስመ፡ ሀገር፡ በመረብና፡ በተክዚ፡ በደንከልና፡ በባሕር፡ መካከል፡ ያለ፡ ክፍል።

**ትግራይ**፤ ትግሬኛ፤ የትግሬ፡ ወገን፤ በትግሬና፡ ባማርኛ፡ ማኽል፡ ያለ፡ ቋንቋና፡ ሕዝብ፤ ቋንቋነቱ፡ ከማርኛ፡ ይልቅ፡ ለትግሬ፡ ለግእዝ፡ የሚቀርብ።

**ቴግሬ፤ (ጽርእ)**፤ ጤግሮሳዊ፤ ክፉ፡ ጨካኝ፡ ነብር፤ ጤግሮስን፡ እይ። ዲያብሎስም፡ በተንኰሉና፡ በመርዛምነቱ፡ እባብ፡ እንዲባል፤ በጨካኝነቱ፡ ቲግር፡ ይባላል፡ (ሄርማ፡ ገ፳፭)። የሰውን፡ ጠባይ፡ የሚመረምሩ፡ ፈላስፎች፡ የጣፉት፡ ታሪክ፡ ግን፡ ትግሬና፡ ትግራይ፡ የሕዝብ፡ ስም፡ ሲኾን፤ ንባቡም፡ ምስጢሩም፡ ቲግር፡ ቴግሬ፡ ከማለት፡ የወጣ፡ የጠባይ፡ ስም፡ ነው፤ የግብር፡ አይደለም፡ ይላል።



ቴግሬ፡

**ቴማሬ፤ (ዕብራ)**፤ ቍጣ፡ ብስጭት፤ መፈጥታ፡ ቅሰት፤ ጠብ፡ ጠበኝነት።

**ቴዱ፤ ቴዳ፤—ግናይ፥ትእምርት፤—ተየዱ፡ ዳ።**

**ተድባብ፤—ብጥ፡ ጣራ፤—ደበበ።**

**ቴሀ፤—ዞረ፡ ቀላወጠ፤—ተየሀ።**

**ትሄ፤ (ያት። ጽር፡ ቴኤ፡ ሄ። ዕብ፡ ታእ)**፤ ታናሽ፡ ዕልፍኝ፤ ዕቃ፡ ቤት፤ እንደ፡ ጕርጆ፡ እንደ፡ ጓዳ፡ ያለ። ለቂንድና፡ ለማር፡ ለፈፍ፡ ሳይቀር፡ ቤትነት፡ ላለው፡ ክፍል፡ ለታናናሽ፡ ኹሉ፡ ይነገራል፡ (ሕዝቅ፡ ፳፡ ፲፡ ፲፪፡ ፲፫)።

**ታው**፤ ስመ፡ ፊደል፤ ካያ፡ ኹለተኛ፡ ተ፤ ምልክት፡ ዐላማ፡ ማለት፡ ነው፤ መስቀል፡ ትእምርተ፡ መስቀል፡ እንደ፡ ማለት። ሔትዮትን፡ እይ፤ ከዚህ፡ ጋራ፡ አንድ፡ ነው፡ (መዝ፻፲፰፡ ፻፷፱—፻፸፮። ሰቈ፩፡ ፳፪። ፪፡ ፳፪። ፫፡ ፷፮። ፬፡ ፳፪)።

**ታው፤ (ዐማርኛ፤ ትእዛዝ፡ አንቀጽ)**፤ ተው፤ አትንካ፤ በቃ። ምስጢሩ፡ ደኅራዊነት፡ ነው፤ አዳም፡ የፍጥረት፡ ፍጻሜ፡ እንደ፡ ኾነ፡ ታውም፡ የፊደል፡ ፍጻሜ፡ ነውና፡ መከተቾነቱን፡ ያሳያል። (ታረት)፤ መተው፡ ነገሬን፡ ከተተው።

**ተወሀውሀ፤—በራ፡ ተመላለሰ፤—ወሀውሀ።**

**ቴዎሎጎስ**፤ ነባቤ፡ መለኮት። ታኦሎጎስና፡ ቴዎሎጎስ፡ አንድ፡ ስም፡ ናቸው፤ ባለዜሞችና፡ ባለሐዲሶች፡ ግን፡ ቴዎሎጎስን፡ ነዊን፡ እስኪት፡ ይሉታል፤ የተሳሳተ፡ ነው።

**ቴዎሎጊያ**፤ ሲቅ፤ መተርጕም፤ የሊቃውንት፡ መጽሐፍ፤ ብሉያትንና፡ ሐዲሳትን፡ እየጠቀሰ፡ የሚፈታ፤ ምስጢረ፡ ሥላሴን፡ ምስጢረ፡ ሥጋዌን፡ አምልቶ፡ አስፍቶ፡ የሚናገር፤ እንዳፈ፡ ወርቅ፡ እንደ፡ ቄርሎስ፡ ድርሳን፡ ያለ፡ የጉባኤ፡ መጽሐፍ፤ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ የምታምነው፡ የምትቀበለው።

(ጥ) **ቱማ፤ (ሱር፡ ቱማእ)**፤ ሶመት፤ ነጭ፡ ሽንኵርት። ሊደብርኩ፡ ባዕለ፡ ሰግላ፡ ወሊባዕለ፡ በጸል፤ ወሊባዕለ፡ ቱማ፡ (ፍ፡ ነ፡ ፲፮። ሲኖ)።

**ቶማስ፤ (ጽር። ዕብ፡ ቶማእ)**፤ የሰው፡ ስም፤ ከ፲፪ቱ፡ ሐዋርያት፡ አንዱ። መንታ፤ መንትያ፡ ኹለትያ፤ ፅንሱና፡ ልደቱ፡ ከወንድም፡ ጋራ፡ የኾነ፡ ብቻውን፡ ያይደለ፡ ማለት፡ ነው፡ (ማቴ፲፡ ፫)።

**ቶማስስ**፤ ስመ፡ ፀሐይ፤ የኦርያሬስ፡ ኹለተኛ። ወአስማቲ፡ ለፀሓይ፡ ከመ፡ ዝ፤ አሐዱ፡ ኦርያሬስ፡ ወካልኡ፡ ቶማስስ፡ (ሔኖ፸፰፡ ፩)።

**ተወን**፤ በልግ፤ ዘመነ፡ በልግ፡ ጸደይ፤ የበጋ፡ የብላጊ፡ ዝናም። ዘመነ፡ ሐጋይ፡ ወተወን። ዝናመ፡ ተወን፡ ወመፀው። ተክልአ፡ ጠል፡ ወተወን። ይሁብ፡ ዝናመ፡ ተወን፡ (ፍ፡ ነ፡ ፩። ኤርም፡ ፭፡ ፳፬። ፫፡ ፫። ዘካ፲፡ ፩። ድጓ)።

**ተወነ ፤** በለገ ፤ ዘነመ ፤ በልግ ፡ ኾነ ።

**ተዋነየ ፤—ተጨዋወተ ፤—ዋነየ ።**

**ተውር ፤ (ዐረ ፡ ሰውር ፤ ተውር) ፤** ስመ ፡ ኮከብ ፡ ኣሳናዊ ፤ ከሦሩ ፡ ኹለቱ ፡ መናዝሎች ፡ አንዱ ። ፍችው ፡ በሬ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ፴፩ ፡ ዕለት ፡ ከ፲፪ ፡ ኪክሮስ ፡ ይመግባል ። **እልተውር** ፡ (አቡሻ) ።

**ቶራ ፤ (ዕብራ) ፤** ሕግ ፡ ሥርዐት ፤ ኦሪት ፤ ዐሠርቱ ፡ ቃላት ።

**ቶራ ፤ (ሱር ፡ ቃውራ ፤ ሰር ። ዕብ ፡ ያሕሙር) ፤** ቦኽር ፡ የበረሓ ፡ እንስሳ ፤ የፈቆና ፡ የዋሊያ ፡ ወገን ፤ ቀንዱ ፡ ረዥም ፡ ዐጽቃም ፡ ባለብዙ ፡ ቅጥይ ፤ ኸራቱ ፡ ዐጭር ፡ የሥጋ ፡ ዐይነት ፤ ወተታም ፡ (ዘዳ፲፬ ፡ ፭) ። **ወይጠል ፡ ወቶራ ፡ ወሀየላት ። ሐሊብ ፡ ቶራ** ፡ (መቃ ፡ ገ፭ ። ስንክ ፡ መስ፲፱) ።



ቶራ ፡

**ቶራት ፤** ቶሮች ፤ ቶራዎች ። **ትራት ፡ ወእሊሕምተ ፡ ገዳም** ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፵፬ ፡ ፪ ። ስንክ ፡ ግንጃ፫) ።

**ቶርማን ፤ (ትግሬ) ፤** ጋይም ፤ ሠረገላ ።

**ቶሬን ፤ (ዕብራ) ፤** የመርከብ ፡ ምሰሶ ፡ ዐምድ ፡ ተራዳ ፤ የሸራ ፡ ያሳማ ፡ መስቀያ ፡ (ኢሳ፴ ፡ ፲፯) ።

**ቶስሐ ፡ ሐት ፤ (ቶስሐ ፡ ይቶስሕ ። ዕብ ፡ ቃዌስ ፤ ሜረየ) ፤** መቀላቀል ፤ መደባለቅ ፤ መበረዝ ፤ መጨመር ፡ መክለስ ፤ የፈሳሽ ። **መያስያንኪ ፡ ይቶስሑ ፡ ማየ ፡ ውስተ ፡ ወይን ። ቶስሐ ፡ ሐሊበ ፡ ወንጌል ፡ ምስለ ፡ ጸቃውዐ ፡ አሪት ። ኅዳጠ ፡ ወይነ ፡ ቶስሕ ። እለ ፡ ይቶስሑ ፡ ባዕለ ፡ ወርቅ ፡ ብኑረ ፡ አው ፡ ንሓበ** ፡ (ኢሳ፩ ፡ ፳፪ ። መጽ ፡ ምስ ። ፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፳፫ ። ፈ ፡ መ ፡ ፲፱ ፡ ፱) ።

—፤ ማዋደድ ፡ ማስማማት ፤ መጨማመር ። **ቶስሐ ፡ ለነፍስትነ ። ትቶስሕዋ ፡ ለጥበብ ፡ በንጹሕ ፡ ልብ ። ቶስሕ ፡ ውዳሴ ፡ ውስተ ፡ ገሥጾቶሙ** ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፳፬ ። ሄርማ ። አፈ ፡ ድ፲) ።

**ቶሳሒ ፤ (ሒት ፡ ሕያን ፡ ያት) ፤** የሚቀላቅል ፡ የሚጨምር ፤ ጨማሪ ፡ ደባላቂ ።

**ተቶስሐ ፤** ተቀለቀለ ፤ ተበረዘ ፤ ተጨመረ ፤ ተዘነቀ ፤ ተደበለቀ ። **ወይን ፡ ዘኢተቶስሐ ፡ ከመ ፡ ንጉሥ ፡ ፀማዊ ፡ ወዘተቶስሐስ ፡ ከመ ፡ ንጉሥ ፡ ራትዐ ። ውሒዛቱ ፡ ሊቃንያ ፡ በደም ፡ ይቶሳሕ ። ተቶስሐ ፡ ደምሙ ፡ በደመ ፡ መባእ ። ወተቶስሐ ፡ አብድንት ፡ ካህናት ፡ ምስለ ፡ አብድንቲ ፡ ነኪራን** ፡ (ፈላስ ። ኪዳ ። ዮሴፍ) ።

**ተቋስሐ ፤ ተተዋስሐ ፤** ተቀላቀለ ፤ ተደባለቀ ፤ ተበራረዘ ፤ ተጨማመረ ፤ ተዘነቀ ፡ ተዘናነቀ ። **ከመ ፡ ኢይትዋስሑ** ፡ (ቴስጠ ፡ ፺፪) ።

**ቱሱሕ ፤ (ሓን ፡ ሓት ፡ ስሕት) ፤** የተቀላቀለ ፤ ቅልቅል ፤ ድብልቅ ፤ ዝንጕርጕር ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ብቻ ፡ ያይደለ ። **ወይን ፡ ምስለ ፡ ከርቤ ፡ ቱሱሕ ። ወትካትበ ፡ ሰማያት ፡ ቱሱሕ ፡ ምስለ ፡ ማይ ፡ ወምድሬ ፡ ሀለወት ፡ ምስለ ፡ ማይ ። ሥናይ ፡ ዘይረክብ ፡ ሰብእ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ቱሱሕ ፡ በጻማ ፡ ወድካም ። እስመ ፡ ቱስሕት ፡ በቍር ፡ ወሞቅ** ፡ (ማር፲፭ ፡ ፳፫ ። ቀሌ ። ዮሴፍ ። ኩፋ ፡ ፳) ።

—፤ ተጣይ ፡ ርባ ፤ ቶማሳዊ ፡ ግስ ፤ በመጥበቅና ፡ በመላላት ፡ በመንቃ ፡ መንገድ ፡ የሚኼድ ፡ ሲጠብቅ ፡ ቀደሱን ፡ ሲላላ ፡ ቀተለን ፡ የሚመስል ። (ማስረጃ) ፤ **አሚር ፤ አመረ ፡ የአምር ፡ ይእምር ። መሲል ፤ መሰለ ፡ ይመስል ፡ ይምስል ። ተቢዐ ፤ ተብዐ ፡ ይተብዕ ፡ ይትባዕ ፤** የቀተለ ። **አምሮ ፡ አመረ ፡ ይኤምር ፡ የአምር ። መስሎ ፡ መሰለ ፡ ይሜስል ፡ ይመስል ። ተብዖ ፡ ተብዐ ፡ ይቴብዕ ፡ ይተብዕ ፤** የቀደሰ ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ።

**ቱስሕት ፤** የተቀላቀለች ፤ ቅልቅል ። መቀላቀል ፡ ቅልቅልነት ፡ ቅልቀላ ፡ ድብለቃ ። ጭማሪ ፡ ተውሳክ ። **እስመ ፡ ድኩም ፡ ቱስሕተ ፡ ነፍስትክሙ ። ትድምርት ፡ ዘእንበለ ፡ ቱስሕት ፡ ወሚጠት ። አክራጦን ፡ ዘአልቦቱ ፡ ቱስሕት ። ሐሊብ ፡ ነባቢ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ቱስሕት** ፡ (፩ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፭ ። ቄር ፡ ጳላ ፤ ተረ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፪) ።

**ቱሳሔ ፤ (ሕያት) ፤** ግእ ፡ ከማሁ ፤ መቀላቀል ፡ (ጥቀ) መተላቀል ፤ አቀላቀል ፤ ቅልቅልነት ፤ ቅልቅል ፡ መኾን ፤ እንደ ፡ ማርና ፡ እንደ ፡ ወተት ፤ እንደ ፡ ውሃና ፡ እንደ ፡ መሬት ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ደቄትና ፡ እንደ ፡ ይቄት ። ቅልቀላ ፡ ድብለቃ ፤ ጭመራ ፤ ብረዛ ፤ ክለሳ ፤ ጭማሪ ፡ ተውሳክ ። **ቍረተ ፡ ቱሳሔ ፡ ዘርዐ ። አሕላም ፡ ይትወለዱ ፡ እምቱሳሕያተ ፡ ጠባይዓት ፡ አርባዕቱ ። ሕንብርትከ ፡ ሕንብርተ ፡ መንፈስ ፡ ረቂቅ ፡ ዘቱሳሔሁ ፡ መብረቅ** ፡ (ፈ ፡ መ ፡ ፲፪ ፡ ፭ ። ፈላስ ። ደራሲ) ።

**ተዋሲማ ፤ (ዐረ ፡ ቃሱም ፤ ብ ፡ ተዋሲም) ፤** ጫማ ፡ መጫሚያ ፤ ወይም ፡ የኮከብ ፡ ስም ፤ ኹለቱ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ (አቡሻ ፡ ፶) ።

**ተውት ፤ (ቅብጥ) ፤** ስመ ፡ ወርኅ ፤ መዠመሪያ ፡ ወር ፤ መስከረም ፡ (አቡሻ ፡ ፳) ።

**ቱት ፤ (ዐረ ፡ ወዕብ) ፤** የዛፍ ፡ ስም ፤ ቅጠሉን ፡ የሐር ፡ ትሎች ፡ የሚበሉት ፤ ፍሬው ፡ ጥፍጥ ፡ ያጋም ፡ የእንጆሪ ፡ ዐይነት ፤ ዐጽቃም ፡ ቅጠላም ።

**ተወተ ፤** ቃታ ፤ ጕንጕን ፤ አዋሰበ ፤ አሰረ ፡ ዐዘበ ፤ የጥራዝ ፡ የድጕስ ፡ የጫማ ፡ ያሮት ። ሠረከን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ መንትያ ፡ ነው ።

**ቶታን ፤ (ናት) ፤** በቁሙ ፡ ማኅበረ ፡ ማረ ፡ ጠፍር ። ትታን ፡ አማእን ፤ (ዘፍ ፲፱ ፡ ፳፫ ። መሳ ፳ ፡ ፫ ። ኢ ሳ ፭ ፡ ፳፮ ። ማርቆ ፡ ፯) ።

**ተሐግ ፤ ትሐግ ፤** ስምስም ፡ ማር ፡ ሰርዶ ፤ የሰርዶ ፡ ዐይነት ፡ ጨሌ ፡ አበቃቀሉ ፡ ችግ ፡ ችፍርግ ፡ ያለ ። ከመ ፡ አባግዕ ፡ ውስተ ፡ ተሐግ ። በኀዳገ ፡ መርዔት ፡ ውስተ ፡ ተሐግ ፤ (ሚልክ ፡ ፯ ። ስንክ ፡ ግንቦ) ።

**ትሒል ፤ ሎት ፤ (ትሕለ ፡ ይትሕል ፡ ይትሐል ። ዕብ ፡ ታሓል ፤ ሀትሒል) ፤** መገ መር ፤ መቅደም ፤ ዠማሪ ፡ ቀዳማዊ ፡ መኾን ፤ በሥራ ፡ ኹሉ ። መዠር ፡ መንከርተት ፡ ስመቀላወጥ ፤ ዘዋሪ ፡ ቀላ ዋጭ ፡ መኾን ፡ ዘየድግሱ ፡ ቤት ፡ ከሰው ፡ አስቀድሞ ፡ መ ገኘት ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በቅሕለ ፡ ፈንታ ፡ ተቅሕለ ፡ ተታ ሐለ ፡ ይላል ፤ አያስኝም ። ወአነሂ ፡ አዐውድ ፡ ወእተ ሐል ። እለ ፡ በተታሕሎ ፡ የሐይጡ ። ከመ ፡ እለ ፡ ያንሶ ሰዉ ፡ ወይቴሕሉ ፡ (ኢዮ ፲ ፡ ፲ ። ፴ ፡ ፱ ። አፈ ፡ ተ፲፯) ።

**ተሓሊ ፤ መትሕል ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤** የሚዠር ፡ የሚቀላውጥ ፤ ዘዋሪ ፡ ቀላዋጭ ፡ አውታታ ፡ ከ ርታታ ፡ ተበል ፡ ተበል ፡ የሚል ፤ አብድ ፡ እንዝህሉል ። ወይከውኑ ፡ መትሕላነ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ። አንበ ረከብኩ ፡ ነገረ ፡ እንዘ ፡ ኣነብብ ፡ መጻሕፍቲከ ፡ ዘፈ ኖከ ፡ ሊተ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ መትሕላን ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ ፍጹማነ ፡ ወአልቦሙ ፡ አእምሮ ፡ ጥዩቀ ፡ (ሆሴ ፱ ፡ ፲፯ ። ሃይ ፡ አበ ፡ ብንያ) ።

**ትሒት ፤ ዶት ፤ (ተሐተ ፡ ይቴሕት ፡ ይትሐት) ፤** መተቸት ፤ ታች ፡ ታች ፡ ማለት ፤ ወደ ፡ ታች ፡ መውረድ ፡ መዋረድ ፤ ዝቅ ፡ ገዝቅ ፡ ማለት ፤ ትሑት ፡ ታሕት ፡ ታችኛ ፡ ዝቅተኛ ፡ መኾን ፤ ማነስ ፡ ጎሎ ፡ አነ ፡ ማለት ፡ ከትቢትና ፡ ከልዕልና ፡ መሸሽ ፡ መራቅ ፤ ዐቅምን ፡ ማወቅ ። ዠሉ ፡ ማዕምቅ ፡ ይምላእ ፡ ወዠሉ ፡ ደ ብር ፡ ወወግር ፡ ይትሐት ፡ (ኢሳ ፵ ፡ ፬ ። ሉቃ ፫ ፡ ፭) ። መጻሕፍትና ፡ ባለቅኔዎች ፡ ግን ፡ በሰዐለ ፡ ፈንታ ፡ ተሰ ዐለ ፡ እንዲሉ ፡ በተሐተም ፡ ፈንታ ፡ ተቅሕተ ፡ ይላሉ ፤ አያስኝም ፡ ግስንቱ ፡ ወዕእንና ፡ መጽአን ፡ ጌሠን ፡ ፈሰ ብን ፡ የመሰለ ፡ በጕል ፡ ነውና ፤ እንደ ፡ ገቢር ፡ ግስ ፡ የመ ደረግ ፡ ልማድ ፡ ተን ፡ አይፈልግም ። ተትሕትከ ፡ ሎቱ ። ብእሲት ፡ ትትአዘዝ ፡ ወትትሐት ፡ ለምታ ። በከመ ፡ ወልድ ፡ ይቴሕት ፡ ለአቡሁ ፡ ከማሁ ፡ ዲያቆንኒ ፡ ይተሐት ፡ ለኤጲስቆጶስ ። ተትሕተ ፡ እስከ ፡ ምድር ። ተትሕተ ፡ እምዐበዩ ። ዘይቴሕት ፡ እምኔክ ፡ (አስቴ ፲፮ ፡ ፲፫ ። ዲድ ፡ ፫ ። ፬ ። ኢሳ ፳፭ ፡ ፲፪ ። ኩፋ ፡ ፳፱ ። ዳን ፱ ፡ ፴፱) ።

**ተሓቲ ፤ (ቲት ፡ ትያን ፡ ያት) ፤** ታች ፡ ታች ፡ የሚል ፤ የሚዋረድ ፤ ተዋራጅ ፤ የትቢት ፡ ጠላት ፡ የትሕ ትና ፡ ወዳጅ ።

**ትሑት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ሕት) ፤** በቁሙ ፤ የተዋረደ ፤ የተናቀ ፤ ወራዳ ፡ ታናሽ ፤ ድኻ ፡ ዜጋ ፤ ታዛዥ ፡ ተገዥ ፡ ፈቃደኛ ፤ እሺ ፡ በን ፡ ባይ ፤ ዐፋራም ፡ ፈሪ ። ት ሑት ፡ ምስለ ፡ ዐቢይ ። ወራእዩኒ ፡ ምኑን ፡ ወት ሑት ፡ እምዙሉ ፡ ሰብእ ። ሕዝብ ፡ ትሑታን ። ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ትሑታነ ፡ ወይትአዘዙ ። ትሑታነ ፡ ልብ ። ትሑታነ ፡ ገጽ ። ወእለ ፡ ይደልዎ ፡ ለመለኮት ፡ ክርስ ቶስ ፡ ንነግር ፡ ወትሑታተሰ ፡ ለትስብእቱ ፡ አወፈይነ ። ጠባብ ፡ ወትሕት ፡ (ኩፋ ፡ ፵፫ ። ኢሳ ፶፫ ፡ ፫ ። ፲፪ ፡ ፯ ። ዲድ ፡ ፵፱ ። ዳን ፫ ፡ ፴፱ ። ሐዋርያት ፡ ፰ ። ቄር ። ድጓ) ።

**ታሕት ፡ ቱ ፤ (ዕብ ፡ ታሐት ። ሱር ፡ ታ ሕታ ። ዐረ ፡ ተሕት) ፤** ደቂቅ ፡ አገባብ ። ታች ፤ ም ድር ፤ እግር ፡ ሥር ፤ የላዕል ፡ የሰማይ ፡ የርእስ ፡ አንጻር ። አከ ፡ ዘቦቱ ፡ ለመለኮት ፡ ላዕል ፡ ወታሕት ። በሰማይ ፡ በላዕሉ ፡ ወበምድር ፡ በታሕቱ ። አንትሙሰ ፡ እም ታሕቱ ፡ አንትሙ ። እምሐቌሁ ፡ እስከ ፡ ታሕቱ ። ጸ ውዑ ፡ ቢጸክሙ ፡ ታሕተ ፡ ወይንክሙ ። እምታሕተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ (ቅዳ ፡ ሕር ። ዮሐ ፫ ፡ ፫ ። ዮሐ ፰ ፡ ፳፫ ። ሕዝ ፩ ፡ ፳፯ ። ዘካ ፫ ፡ ፲ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፴) ።

**ታሕተ ፤** በታች ፡ ወደ ፡ ታች ። ንበር ፡ ታሕተ ። ወረደ ፡ ታሕተ ። ተወረው ፡ ታሕተ ።

**ታሕታዊ ፡ ይ ፤ (ዊት ፡ ይት ፡ ቲት) ፤** የታች ፡ ታችኛ ፤ መጨረሻ ፤ በታች ፡ ያለ ። ከንፈሩ ፡ ታ ሕታይ ፡ የዐቢ ። ታሕታይ ፡ ማኅደር ። ሀገረ ፡ ታሕ ታይት ፡ ወላዕላይት ። ሲኦል ፡ ታሕቲት ። ግብ ፡ ታሕ ቲት ። ቀላይ ፡ ታሕቲት ፡ (ኪዳ ። ቀሌ ። ፩ዜና ፡ ፯ ፡ ፳፬ ። መዝ ፡ ፹፭ ። ዕብራ ፡ ፺፬ ። ኩፋ ፡ ፭) ።

**ትሕትና ፤** በቁሙ ፤ ትሑትንት ፤ ዝቅታ ፤ ውር ደት ፤ የልዕልና ፡ አንጻር ፡ ወደረኛ ፤ የትቢት ፡ ደመኛ ። ሕ ፡ ትሕትና ፡ ዘመጠነ ፡ ዝ ፡ ትሕትና ። በትሕትና ፡ ረ ከበ ፡ ልዕልና ። ኢትእመን ፡ ትሕትናሁ ፡ (ቅዳ ፡ አፈ ። መዋሥ ። ዮሴፍ) ።

**አትሐተ ፤** አዋረደ ፤ ዝቅ ፡ አደረገ ፤ አስጐንበሰ ። ትዕቢት ፡ ብእሴ ፡ ያቴሕት ። አትሐቱ ፡ ርእሶሙ ፡ ወ ለገዱ ። ያቴሕት ፡ ርእሶ ፡ ታሕተ ፡ ለኵናኑ ፡ (ምሳ ፳፱ ፡ ፳፫ ። ዘፍ ፳፬ ፡ ፳፮ ። ሚራ ፲ ፡ ፲፯) ። አርትዐ ፡ ሠርሐ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አትሐተ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ኢሳ ፵፰ ፡ ፲) ።

**አትሓቲ ፤ መትሐቲ ፤** የሚያዋርድ ፤ አዋ ራጅ ። ለከ ፡ ናቴሕት ፡ ዘአንተ ፡ መትሐቲ ፡ ለዠሉ ፡ (ቅዳ ፡ ሕር) ።

**መትሕት ፤ (ጥሬና ፡ ቅጽል) ፤** ታሕት ፤ ት ሑት ። ታች ፤ ጕድጓድ ፤ ሸለቆ ፤ ጥልቅ ፡ ዕሙቅ ፡ ሲኦል ፡ ገሃነም ። በመትሕተ ፡ ምድር ። ውስተ ፡ መትሕተ ፡ እሳት ። ነበረ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ልዑል ፡ ወዮሐናኒ ፡ ወ እሊአሁ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ መትሕት ። ባሕር ፡ መት ሕት ፡ (መዝ ፡ ፻፴፰ ። ሔኖ ፲ ፡ ፲፫ ። ዮሴፍ) ።

**መትሕተ ፡ ታሕቲት ፤** የታች ፡ ታች ፤ መጨ ረሻ ፡ ታች ፤ እንጦርጦስ ፡ (ቀሌ) ።

**መትሕታዊ ፤** ታሕታዊ ፤ ዘታሕት ፤ ታችኛ ፡ የ ታች ። ልዑላዊ ፡ ወመትሕታዊ ፡ (ፊልክ ፡ ፻፳፭) ።

**ታኅሣሥ ፤-ወር ፤ ክትክታ ፤ -ኀሠሠ ።**

**ተጥላስ ፤ (ሳት ። ሮማይ ፡ ቲቱሊስ ። ዐረ ፡ እተጥላሳት)** ፤ አንቀጽ ፤ ምዕራፍ ፤ ክፍል ፤ መልእክት ፤ የጉባኤ ፡ የማኅበር ፡ መጽሐፍ ፤ ቀኖና ፤ የመጽሐፍ ፡ ስምና ፡ አርእስት ፤ ማስታወቂያ ። ጠስ ፡ ዘውእቱ ፡ ተጥላሳት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ መቅ) ። ተጥላስና ፡ አብጥሊስ ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ነው ፤ ኹለት ፡ አይደለም ፤ አብጥሊስን ፡ እይ ። ፍካሬ ፡ አብጥሊስ ፡ እው ፡ ተጥላሳት ፡ ቀኖና ፡ ውእቱ ፡ በልሳነ ፡ ጽርእ ፡ (ሲኖዶ) ። ጽርኡ ፡ ከሮማይስጥ ፡ ስለ ፡ ወሰደው ፡ ጽርእ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ቃሉ ፡ የላቲን ፡ ነው ።

**ተይ ፤ (ጽር ፡ ቲዮን)** ፤ ዲን ፡ ድኝ ፤ ዳኤራ ፤ ክብሪት ። እሳት ፡ ወተይ ፡ (መዝ ፡ ፲ ። ዘፍ፲፱ ፡ ፳፬ ። ራእ፱ ፡ ፲፯) ።

**ቴዱ ፤ (ዕብ ፡ ቶዳ)** ፤ ቡራኬ ፡ ምስጋና ፤ ግናይ ፡ አኰቴት ። አንቀጸ ፡ ቴዱ ፡ (፫ ፡ ነገ) ።

**ቴዳ ፤ (ብ ፡ ቴዳት ። ጽር ፡ ቲታ)** ፤ የስም ፡ ምልክት ፤ እስክንድር ፡ በእስክንድርያ ፡ ቀብሮት ፡ በነበረው ፡ በወርቅ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ተጥፎ ፡ አባ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ያገኘው ። መዝገብ ፡ ዘጽሑፍ ፡ ውስቴቱ ፡ ሠለስቱ ፡ ቴዳት ፡፡ ወተርጐሞሙ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ለሠለስቱ ፡ ቴዳት ፡ ወይቤ ፤ አሐዱ ፡ ቴዳ ፡ ዘቴዎስ ፡ ወአሐዱ ፡ ዘቴዎፍሎስ ፡ ወአሐዱ ፡ ዘቴዎዶስዮስ ፤ ወከፈሎ ፡ ለዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ኀበ ፡ ሠለስቱ ፡ ክፍል ፡ (አቡሻ ፡ ፶ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፰) ።

**ቴዳብ** ፤ ዳቢት ፤ ጕን ፤ የጕን ፡ ሥጋ ፤ የጕድን ፡ ዘርፍ ። ጕድን ፡ ተዳቢት ፡ እንዲሉ ። (ይባቤ) ፤ ዲያብሎስ ፡ በትቢቱ ፡ ተወጋ ፡ ዳቢቱ ።

**ተዩሀ ፤ ሆት ፤ (ቴሀ ፡ ይተይሀ ፡ ይቲሀ ። ዐረ ፡ ተሀ ። ዕብ ፡ ታሀሀ)** ፤ መዞር ፡ መቀላወጥ ፤ ከሰው ፡ ደጅ ፡ መቀመጥ ፤ ሲበሉ ፡ ማየት ፡ ማፍጠጥ ፤ እንደ ፡ ውሻ ፡ መኾን ። ትሕለን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። (ተረት) ፤ አጕንብቦ ፡ በላን ፡ ተኝተኽ ፡ ቀላውጠው ።

—፤ ማሰር ፡ ቾብ ፡ ማድረግ ፤ የቅጥቅጥ ፡ የጭራሮ ።

**ተያሂ ፤ (ሂት ፡ ህያን ፡ ያት)** ፤ የሚቀላውጥ ፡ ቀላዋጭ ፤ አፍጣጭ ።

**ትያህ ፤ (ሃት)** ፤ ዙረት ፤ ቅልውጥ ፤ ባይጠሩ ፡ መሮጥ ፤ ኺደ ፡ ማፍጠጥ ።

**ቲሃ** ፤ ቾብ ፡ ሽግ ፡ ዳቦት ፡ የጭራሮ ፡ መብራት ።

**ትያጥራ ፤ ትያጥሮን ፤ (ጽር ፡ ቲአትራ)** ፤ ስመ ፡ ሀገር ፡ በታናሽ ፡ እስያ ፡ ያለች ፡ (ራእ፩ ፡ ፲፩ ። ፪ ፡ ፲፰) ።

**ትያጥሮን ፡ (ጽር ፡ ቴአትሮን)** ፤ የማቅ ፡ የጨዋታ ፡ ቤት ፤ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ የጥጋብ ፡ ጨዋት ፡ ምሳሌና ፡ ተረት ፡ ምትሀትና ፡ ውሽት ። ዘትያጥሮን ፡፡ ቤተ ፡ ትያጥሮን ፡ (ኪዳ ። ስንክ ፡ ሐም፳ ። ታኅ፲፱ ። መጋ፲፯) ።


**ቴሌም ፤ (ጽር ፡ ቴሜን ። ዕብ ፡ አብ)** ፤ ቆፋርተኛ ፡ ጠንቋይ ፤ ዘጐል ፡ ጣይ ፤ ጋኔን ፡ ሳቢ ፡ ባላሾክ ሺኪ ፤ ምትሀታም ፡ መሠሪ ፤ ሙት ፡ ጠሪ ፤ ሬሳ ፡ አናጋሪ ፤ መንቅሂ ፡ ምዉት ፤ ካህን ፡ ጣዖት ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ የእባብ ፡ ምስል ፡ ጣዖት ፡ ይሉታል ፡ (፪ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፯) ።

**ቴማን ፤ (ዕብራ)** ፤ የማእዝን ፡ ስም ፤ ናጌብ ፡ ደቡብ ፤ የደቡብ ፡ ነፋስ ፤ በደቡብ ፡ ያለ ፡ ሀገርና ፡ ሕዝብ ፤ የመን ፤ መላው ፡ የዐረብ ፡ አገር ። የማንን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ሚያም ፡ ገጸከ ፡ መንገለ ፡ ቴማን ፡፡ እግዚ ፡ ይመጽእ ፡ እምቴማን ፡ (ሕዝ፳፩ ፡ ፩ ። ዕን፫ ፡ ፫) ።

—፤ ስመ ፡ ነገድ ፤ የዔሳው ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፤ የኤዶምያስ ፡ ሕዝብና ፡ መዲና ፤ ከዐረቦች ፡ ነገድ ፡ የተለየ ፡ (ዘፍ፴፮ ፡ ፲፩ ። ኤር፵፱ ፡ ፯ ። ኢዮ፪ ፡ ፲፩) ።

**ቲን ፤ ቴና ፤—ርሕብ ፤ ግዘፍ ፤—ተኒን ፡ ቶነ ።**

**ቴፈን ፤ ተይፈን ፤ (ዐረ ፡ የፈን)** ፤ ወይፈን ፤ ያደገ ፡ የደረሰ ፤ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ያለ ፤ የሚያፈነፍን ፡ የሚንጠላጠል ። ሐማሴኖች ፡ ዘራብዕ ፡ ይሉታል ።



ተይፈን ።

**ተያፍን ፤ ትያፍን** ፤ ወይፋፍን ፤ ወይፈኖች ፤ ወይፋፍኖች ። ኵሉ ፡ ነገሩ ፡ ተያፍን ፡ ወብዕራ ፤ እስከ ፡ ያገርር ፡ ትያፍኒሁ ፡፡ ከመ ፡ ተያፍን ፡ ወብዕራ ፡ (ሚራ፴፰ ፡ ፳፭ ፡ ፳፯ ። ስንክ ፡ ግን፲፭) ።

(ጥ) **ተክዘ ፤ ዘት ፤ (ተከዘ ፡ ይቴክዝ ፡ ይትክዝ)** ፤ መተከዝ ፤ መወዝወዝ ፤ እህህ ፡ ማለት ፤ አጥብቆ ፡ ማዘን ፤ መትክንከን ፤ መጨነቅ ፡ ማሰብ ። ተከዘት ፡ ነፍስየ ፡ እስከ ፡ ለሞት ፡፡ ተከዘ ፡ ዮናስ ፡ ዐቢየ ፡ ትካዘ ፡፡ በእሉ ፡ ሠለስቱ ፡ ተከዘኒ ፡ ልብየ ፡፡ ኢይቴክዝ ፡ በእንተ ፡ ቤቱ ፡፡ አልቦ ፡ ዘይቴክዝ ፡ በእንቲኣኪ ፡፡ ተከዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስእለቶሙ ፤ ዐሰበ ፡ (ማር፲፱ ፡ ፴፱ ። ዮና፬ ፡ ፩ ። ሚራ፳፯ ፡ ፳፰ ። ምሳ፳፱ ፡ ፴፱ ። ኤር፲፭ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ ሚያ፲፱) ።

—፤ መፍሰስ ፡ መጕረፍ ፤ መውረድ ፡ መኼድ ፤ አለመታገድ ፤ የውሃ ፡ የእንባ ፡ የጎሊና ።

**ትኩዝ ፤ (ዛን ፡ ዛት ፡ ክዛት)** ፤ ያዘነ ፡ የተከዘ ፤ በጽኑ ፡ ሐዘን ፡ የተያዘ ፤ የሚያስብ ፡ የሚጨነቅ ፤ ሐሳብና ፡ ጭንቅ ፡ የያዘው ፡ የወዘወዘው ። ሕሙም ፡ ወትኩዝ ፡፡ ትኩዝየ ፡ አንሶሱ ፡፡ ወሖረ ፡ ትኩዞ ፡፡ ሕዙን ፡ ወትኩዝ ፡ ልብ ፡ (ሮሜ፲፰ ፡ ፳፪ ። መዝ ፡ ፴፯ ። ማር፲ ፡ ፳፪ ። ኤፍ ፡ ፪) ።

**ትክዜ** ፤ (ዝያት) ፤ በቁሙ ፤ መተከዝ ፤ አተካከዝ ፤ ትካዝ ፤ ሐዘን ፡ ጭንቅ ፤ ሐሳብ ፤ አሀሆታ ።

**ትካዝ** ፤ (ዛት) ፤ ጭንቅ ፡ ሐሳብ ፤ ጉዳይ ፡ መፍቅድ ፤ ዕጦት ፡ ችግር ፤ ንግድ ፡ ተግባረ ፡ እድ ። ዘእንበለ ፡ ሐዘን ፡ ወትካዝ ። ብዙኃት ፡ እማንቱ ፡ ትካዛተ ፡ ዓለም ። ትካዝ ፡ ብእሲ ፡ ኀቤኪ ። ኢትንግር ፡ ቅድመ ፡ ነኪር ፡ ትካዘከ ። ምስለ ፡ ማእምራን ፡ ይኩን ፡ ትካዝከ ። ዘኢይኄሊ ፡ ትካዘ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ (ኢዮ፲፩ ፡ ፲፰ ። አፈ ፡ ተ፳ ። ፫ነገ ፡ ፪ ፡ ፲፱ ። ሢራ፰ ፡ ፲፰ ። ፱ ፡ ፲፭ ። ዲድ ፡ ፫) ።

**አተከዘ** ፤ በቁሙ ፤ አሳዘነ ፡ አስተከዘ ፤ አስጨነቀ ፤ አሳሰበ ። ኢታተክዞ ፡ እንዘ ፡ ፍሡሕ ፡ ውእቱ ። ቀሠፍክሙ ፡ ወአተከዝክሙ ። ምንተ ፡ አተከዝኩከ ፡ (ሢራ፴፱ ፡ ፴፩ ። ጥበ፲፩ ፡ ፲፪ ። ሚክ፮ ፡ ፫) ።

**መተክዝ** ፤ (ዝት ፡ ዛን ፡ ዛት) ፤ የሚያሳዝን ፤ የሚያስተክዝ ፤ አስተካዥ ።

**ተከዚ** ፤ ፈሳሽ ፡ ጐርፍ ፤ ወራጅ ፡ ውሃ ፤ ስመ ፡ ፈለግ ። ገርዎ ፡ ውስተ ፡ ተከዚ ። ተከዜ ፡ ግብጽ ። ውሒዘ ፡ ማይ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምነ ፡ ተከዚ ። ተከዜ ፡ ጤግሮስ ። ተከዜ ፡ ኤፍራጥስ ። አመ ፡ ዕሥሩ ፡ ወረቡዑ ፡ ለሐምሌ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ገብረ ፡ ሎቱ ፡ እግዚ ፡ ተአምረ ፡ ለንጉሥ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፤ ወዐደዎ ፡ ለተከዚ ፡ በእግር ፡ እምድኅረ ፡ ጕዕዓን ፡ ሐዋርያት ፡ (ዘፀ፩ ፡ ፳፪ ። ፪ዜና ፡ ፺ ፡ ፷ ። ሢራ፳፬ ፡ ፴ ። ጦቢ፯ ፡ ፩ዜና ፡ ፳ ፡ ፱ ። ታሪ ፡ ግሬ) ።

**ተኬሳ** ፤ (ብ ፡ ተከይስ) ፤ ትክሻ ፤ ብራኳ ። ወነደፎ ፡ ማእከለ ፡ ተኬሳሁ ። ሳዊሮስ ፡ አንበሳ ፤ አገዳ ፡ ዕልዋን ፡ ዘይሰብር ፡ ወዘመናፍቃን ፡ ተኬሳ ። ወይጸውርዎ ፡ በተኬሳሆሙ ፡ (፩ነገ ፡ ፱ ፡ ፳፱ ። ስንክ ፡ የካ፲፱ ። አረጋ ፡ መ፴፯) ።

**ተኪል** ፤ ሎት ፤ (ተከለ ፡ ይተከል ፡ ይትክል ። ሱር ፡ ትክል ። ዕብ ፡ ሻታል ። ዐረ ፡ ወከለ ፤ ተኪለ) ፤ መትከል ፤ መቀብቀብ ፡ መቸከል ፤ የካስማ ። ከመሬት ፡ መሻጥ ፤ መወተፍ ፡ መሸጐጥ ፤ ማቆም ፡ ማጽናት ፤ የተክል ። ተክሉ ፡ ደብተሪሆሙ ። ተከለት ፡ መትከለ ። ተክሉ ፡ ወይነ ። ትክሉ ፡ አቅማሐ ፡ (ጥበ፲፭ ፡ ፪ ። መሳ፬ ፡ ፳፩ ። መዝ ፡ ፻፮ ። ኤር፴፯ ፡ ፳) ።

—፤ መክፈል ፤ መተካት ፤ ምትክ ፡ ማቆም ፡ መስጠት ፤ የሰው ፡ የከብት ። ዘበረቀ ፡ ላሕመ ፡ አው ፡ በግዐ ፡ ይትክል ፡ ህየንተ ፡ አሐዱ ፡ ትኅምስተ ። እመ ፡ ወግአ ፡ ላሕም ፡ ላሕመ ፡ ወሞተ ፡ ይትክል ፡ ላሕመ ፡ ህየንተ ፡ ላሕም ፡ (ዘፀ፳፪ ፡ ፩ ። ፳፩ ፡ ፴፯) ።

—፤ መወሰን ፡ መቍረጥ ፤ ማገግ ፡ መደንገግ ፤ ሕግ ፡ ማቆም ። ሥርዐተ ፡ ይትክል ፡ (ቅዳ ፡ ሐዋ) ።

—፤ መግፋት ፤ መድፋት ፡ ማዳፋት ፤ መወርወር ፡ መገፍተር ፤ መጣል ፡ በማንባር ፡ መትከል ፤ መንዳት ፡ መጕንጕስ ፡ ማስቸኰል ፤ ይጋፉሪ ፡ የዘበኛ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በተክለ ፡ ፈንታ ፡ አትክለ ፡ ይላል ፤ አይሰኝም ። ነዳይ ፡ እመ ፡ ተዐቅፈ ፡ ያቴክልዎ ። ታቴክሉ ፡ ነዳየ ፡ በውስተ ፡ ኆኅት ። ያቴክልዎ ፡ ለመስቀል ። አውፅእዎ ፡ እንዘ ፡ ያቴክልዎ ፡ (ሢራ፲፫ ፡ ፳፫ ። ዓሞ፭ ፡ ፲፪ ። ቄር ። ባሮ) ።

**ተካሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት) ፤ የሚተክል ፡ ተካይ ፤ ተካል ፡ ዐጋይ ። አቡየ ፡ ተካሊሁ ፡ (ዮሐ ፲፭ ፡ ፩) ።

**አትከለ** ፤ አስተከለ ፤ አስተካ ፡ አስከፈለ ። አስደፋ ፡ አስገፋ ፤ አስገፈተረ ።

**መትከል** ፤ (ብ ፡ መታክል) ፤ መትከያ ፤ ማስተከያ ። ካስማ ፤ ችካል ፤ ኵላብ ፡ መንዘረር ፡ የዕቃ ፡ መስቀያ ፡ የዕንጨት ፡ የብረት ፡ ምስማር ። ነሥአት ፡ መትከለ ። መትከል ፡ በዘይሰቅሉ ፡ ቦቱ ፡ ኵሎ ፡ ንዋየ ። መታክል ፡ ወመታግር ፡ (መሳ፬ ፡ ፳፩ ። ሕዝ፲፭ ፡ ፫ ። ዘኍ፫ ፡ ፴፯) ። በመትከል ፡ ፈንታ ፡ መትክልት ፡ መታክልት ፡ ይላል ፡ በሴት ፡ አንቀጽ ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ።

**ተተክለ** ፤ ተተከለ ፤ ተቀበቀበ ፤ ተሠራ ፤ ተመሠረተ ፤ ቆመ ፤ ተወሰነ ። ይእቲ ፡ መሳጺ ፡ ተተክለት ፡ ዲበ ፡ ከሣዱ ፡ ወሞተ ። ተመልኂ ፡ እምሥርውኪ ፡ ወተተከሊ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ። ተተክለ ፡ ደብተራሁ ። ቤተ ፡ ጸሎት ፡ እንተ ፡ ተተክለት ፡ ለምስጋድ ። ተተክለት ፡ ፍትወት ፡ በጠባይዐ ፡ እንስሳዊት ። ተተክለ ፡ ብርሃን ፡ በአምሳለ ፡ ዐምድ ። በዘተተክለ ፡ ዐድሜ ፡ (ገድ ፡ ኪሮ ። ሉቃ፲፯ ፡ ፮ ። ኩፋ ፡ ፲፫ ። ድጓ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፳፱ ፡ ፭ ። ስንክ ፡ የካ፱ ። ተረ ፡ ቄር) ።

**ትኩል** ፤ (ላን ፡ ላት ፡ ክልት) ፤ የተተከለ ፤ ትክል ፤ የቆመ ፤ የተሠራ ። ትኩል ፡ ዕፀ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሐማ ። ዕፀ ፡ ትክልት ፡ ኀበ ፡ ሙኃዘ ፡ ማይ ። ማዕርግ ፡ ትክልት ፡ ውስተ ፡ ምድር ። በዓላት ፡ ትኩላት ። ዲያቆናት ፡ ትኩላን ፡ ለመልእክተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (አስቴ፯ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፩ ። ኩፋ ፡ ፳፯ ። አብጥ ፡ ፳) ።

**ትክለት** ፤ መትከል ፤ መተከል ፤ አተካከል ፤ ትክልነት ፡ ተከላ ፤ ትክለኛ ። (ቅዳ ። አርጋ ፡ ፭) ። ኢትጸጊ ፡ ሥርወ ፡ ትክለትከ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ተክል** ፤ (ላት ፤ አትክልት) ፤ በቁሙ ፤ ፍሬያም ፡ ዕንጨት ፤ ዛፍ ፤ ቅመም ፤ ቅጠላቅጠል ፡ የሚበላ ፡ የሚሸተት ፤ ገንታዊ ፡ ዕፅ ፤ ሕግ ፡ ሥርዐት ። ከመ ፡ ትትክሉ ፡ ኵሎ ፡ ተክለ ፡ ወኵሎ ፡ ዕፀ ። እኩይ ፡ ተክል ፡ ገብረ ፡ ሥርወ ፡ ላዕሌሆሙ ። ኢበልዐ ፡ ፍሬያተ ፡ አትክልት ። ኵላ ፡ ተክል ፡ እንተ ፡ ኢተከላ ፡ አቡየ ፡ ትሠሮ ፡ (ኩፋ ፡ ፯ ። ሢራ፫ ፡ ፳፰ ። ስንክ ፡ ግን፲፰ ። ማቴ ፲፭ ፡ ፲፫) ።

—፤ ችግኝ ፤ ፍል ፤ የተክል ፡ ቡቃያ ፤ ግልግል ፤ ገና ፡ እየፈለሰ ፡ የሚተከል ፤ ወይም ፡ ተተክሎ ፡ የጸደቀ ፤ ከጽጌ ፡ ከፍሬ ፡ ያልደረሰ ። ልጅ ፤ አማኒ ፡ ምእመን ። ሐዲስ ፡ ተክል ። ተክለ ፡ ስም ። ወኢይኩን ፡ ዘእምሐዲስ ፡ ተክል ፡ ከመ ፡ ኢይትዐበይ ። ተክለ ፡ ርትዕ ፤ ተክለ ፡ ጽድቅ ፡ (ኢዮ፲፱ ፡ ፱ ። ሕዝ፴፱ ፡ ፳፱ ። ፩ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፮ ። ኩፋ ፡ ፩ ፡ ፲፮) ።

—፤ ምትክ ። ይፍዲ ፡ ሳሕመ ፡ ተክለ ፡ ሳሕሙ ። ሚዎ ፡ ተክሎሙ ። ተወልደ ፡ ሴት ፡ ተክለ ፡ አቤል ፤ (ዘፀ፳፭ ፡ ፴፮ ። ፫ነገ ፡ ፳ ፡ ፳፭ ። ዘሬፉ) ። ባላንባቦች ፡ ማን ፡ ስለ ፡ ፈንታ ፡ ይሉታል ።

**ተኰላ ፤ (ዕብ ፡ ሹዓል ። ሱር ፡ ታዓል ። ዐረ ፡ ሸዐላብ)** ፤ በቁሙ ፤ የበረሓ ፡ ውሻ ፤ የቀበሮ ፡ ወንድም ፤ ተንኰለኛ ፡ ፎጉም ። የቍንጽልን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። የግእዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በተኵላ ፡ ፈንታ ፡ ቍንጽል ፡ እንዲል ፤ በግእዝ ፡ ፈንታ ፡ ተኵላ ፡ ይላል ፤ የመላሽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ሰብ ፡ ርእየ ፡ ተዅላ ፤ ይመ ሥጠን ፡ ተዅላ ፡ (ዮሐ ፲ ፡ ፲፪) ። የግእዝን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ፤ ስለ ፡ ቍንጽል ፡ የጠቀስነው ፡ ቃል ፡ ተኵላ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ስለ ፡ ተኵላም ፡ የጠቀስነውና ፡ ያልጠቀስ ነው ፡ ተኵላ ፡ የሚል ፡ ኹሉ ፡ ግእዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በቁሙ ፡ ተኵላ ፡ እንዳይመስልኽ ፡ ያማርኛውን ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ እይ ።



ተኵላ ፡

**ተኵላት ፤ ተኲሉት** ፤ ተኵሎች ፡ የበረሓ ፡ ውሾች ። ይትረዐዩ ፡ ተዅላት ፡ ምስለ ፡ አባግዕ ። ከመ ፡ አባግዕ ፡ ማእከለ ፡ ተኲሉት ፡ (ኢሳ፷፭ ፡ ፳ ። ማቴ፲ ፡ ፲፮) ።

**ተኵላ ፤ (ዕብ ፡ ሻሒል)** ፤ አንበሳ ፤ ስመ ፡ አንበሳ ። ላዕለ ፡ ተዅላ ፡ ወከይሲ ፡ ትጼዐን ፡ (መዝ ፡ ፺) ።

**ተከፈ ፤ (ዕብ ፡ ካታፍ)** ፤ ተሸከመ ፤ ሸከ ምን ፡ በትከሻ ፡ ያዘ ፡ አኖረ ፡ አስቀመጠ ፤ ትከሻውን ፡ ለሸክም ፡ ሰጠ ።

**መትከፍ ፡ ት ፤ (ብ ፡ መታክፍ ፡ ት ። ዕብ ፡ ካቴፍ ። ሱር ፡ ካትፉ ። ዐረ ፡ ኪትፍ)** ፤ ጫንቃ ፤ የጡንቻ ፡ ራስ ፤ የእጅ ፡ መብቀያ ፤ የደንደስ ፡ ጫፍ ፤ ያንገት ፡ የማኽራት ፡ ግራና ፡ ቀኝ ። ማኽራትም ፡ ከመትከፍ ፡ ጋራ ፡ ጫንቃ ፡ ይባላል ፤ ሐዳፍን ፡ ተመልከት ። ሰላም ፡ ለመትከፍትከ ፡ ከመ ፡ ልብሰ ፡ ክህ ነት ፡ ሎግዮ ፡ ጊዜ ፡ ፀአተ ፡ ፍትሕ ፡ ዘጾረ ፡ አርዑተ ፡ መስቀል ፡ በቀራንዮ ። ይጸውርዎን ፡ በመትከፍት ። አትሕት ፡ መታክፍቲከ ፡ ወተሰከማ ። ወሀባ ፡ ለአ ጋር ፡ ወአንበረ ፡ ዲበ ፡ መትከፍታ ። ይጼዐን ፡ በመ ታክፉ ፡ (ደራሲ ። ኢሳ፵፱ ፡ ፳፪ ። ሚሬ፳ ፡ ፳፭ ። ዘፍ ፳፩ ፡ ፲፬ ። ስንክ ፡ ሐምሌ፳) ።

**ተኰሰ ፤ (ዐማርኛ)** ፤ በቁሙ ፤ አቃጠለ ፤ በእ ሳት ፡ ወይም ፡ በጋለ ፡ ብረት ። ዐደውኒ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይ ትዅሱ ፡ ቤተ ፡ ንግሥት ፡ (ድር ፡ ሚክ ። መ ፡ ፈ) ።

**ተኪት ፤ ቶት ፤ (ተከተ ፡ ይተክት ፡ ይ ትክት)** ፤ መታከት ፤ መድከም ፤ የጕልበት ፡ (ዐማርኛ) ።

—፤ ማለፍ ፡ መቅደም ፡ ኋላ ፡ መኾን ፡ መቈየት ፡ መዘ ግየት ፤ የጊዜ ፡ የዘመን ።

—፤ መድማት ፤ ደም ፡ መኾን ፤ ደም ፡ ማየት ፤ በዚሁ ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ መቈየት ፤ የሴቶች ። ዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ኢትቀረብ ፡ ኀበ ፡ ይወልዳ ፡ ወይተክታ ፡ (አዋል) ።

**ትኩት ፤ (ታን ፡ ታት ፡ ትክት)** ፤ የታከተ ፡ ታካታ ። ደም ፡ የሚያይ ፤ ደማም ፤ መርገማም ። ኢይ ክል ፡ ተንሥአ ፡ ቅድሜከ ፤ እስመ ፡ ትክት ፡ አነ ። ሰከቡ ፡ ምስለ ፡ ትክት ። ከመ ፡ ርሡሰ ፡ ትክት ። ኀራስ ፡ ወት ክት ፡ (ዘፍ፴፩ ፡ ፴፭ ። ሕዝ፳፪ ፡ ፲ ። ፴፮ ፡ ፲፯ ። ቀሌ) ።

**ትክቶ** ፤ ደም ፡ አደፍ ፡ ግዳጅ ፡ የሴቶች ፡ አበባ ። ኀደጋ ፡ ለሳራ ፡ ትክቶ ፡ አንስት ። መዋዕለ ፡ ትክቶሃ ። ጸርቀ ፡ ትክቶ ። ደመ ፡ ትክቶሆን ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፲፩ ። ዘሌ ፲፪ ፡ ፪ ። ኢሳ፷፬ ፡ ፮ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**አትከተ** ፤ አታከተ ፡ አሳለፈ ፡ አቈየ ፡ አደማ ፡ ደም ፡ አሳየ ። ያተክት ፡ ወያስተኀልፍ ፡ ዕድሜሁ ፡ አቈየ ፡ (ሚሬ፳፱ ፡ ፳፭) ።

**ትካት** ፤ ዱሮ ፤ ጥንት ፡ ቀድሞ ፤ ያለፈ ፡ የቈየ ፡ ጊዜ ፡ ዘመን ። ኹለተኛም ፤ ትላንት ፡ ከትላንት ፡ በስቲያ ፤ ዓምና ፡ ሐች ፡ ዓምና ፤ የመዲያኛው ፡ ያለኛል ። ሰብአ ፡ ትካት ። መዋዕለ ፡ ትካት ። ምትየ ፡ ዘትካት ። እምት ካት ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ። ወስሙስ ፡ ለውእቱ ፡ ብ ሔር ፡ ትካቲሁ ፡ ሎዝ ። ቀዳሚየ ፡ ቃል ፡ አልብየ ፤ ወ ትካትየ ፡ (ኢዮ፳፱ ፡ ፪ ። ሆሴ፪ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፺፪ ። ዘፍ ፳፰ ፡ ፲፱ ። ዘፀ፬ ፡ ፲) ።

**ተላብ ፤ ተላቤ** ፤ ተልባ ፤ ከታን ። ተላቤ ፡ ዘ ኢነሥአ ፡ ፍሬሁ ። እመ ፡ ዘራዕከ ፡ ከሙነ ፡ ተአር ርኑ ፡ ተላቤ ። ተላቤ ፡ ወሰገም ፡ ማሰነ ፡ (ስንክ ፡ ሐም ሌ፳ ። መቃ ፡ ገ፳ ። ዘፀ፱ ፡ ፴፩) ።



ተላቤ ፡

**ተሊው ፤ ዎት ፤ (ተለወ ፡ ይተሉ ፡ ይ ትሉ ። ዕብ ፡ ታላ ። ሱር ፡ ትላ ፤ ሰቀለ ። ዐረ ፡ ተላ ፤ ተጋ)** ፤ መከተል ፡ መምሰል ፤ መውደድ ፤ ተከ ትሎ ፡ መኼድ ፤ ልብን ፡ ሐሳብን ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ መስቀል ፡ ማንጠልጠል ፤ ማሰር ፡ ማቈራኘት ፡ ርሱን ፡ መጠበቅ ፤ ተግቶ ፡ ማየት ፡ መመልከት ፤ የሎሌ ፡ የተማሪ ፡ የሕዝብ ። ንዑ ፡ ትልዉኒ ፤ ወተለውዎ ፡ ብዙኃን ፡ አሕ ዛብ ። ሠናይ ፡ ተሊዎቱ ፡ ለእግዚ ። ኀደግነ ፡ ተሊ

ዎት ፡ ለአምላክነ ። ይሚጦ ፡ ህየንቴሁ ፡ ካልአ ፡ ዘይ ተልዎ ። ዘይተልዋ ፡ ለዘማ ። ተለወ ፡ ነፍሱ ፡ ኀቤሃ ፡ ጥቀ ። እመ ፡ ተለወ ፡ ልብየ ፡ ብእሲተ ፡ ብእሲ ። ተ ለወት ፡ ነፍሰሙ ፡ ኀበ ፡ ጣዖት ፡ (ማቴ ፲ ፡ ፳ ፡ ፳፰ ። ሚራ ፴፮ ፡ ፲ ። ኢሳ ፶፱ ፡ ፲፫ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፱ ። ሚራ ፲፱ ፡ ፪ ። ጦቢ ፯ ፡ ፲፫ ። ኢዮ ፴፩ ፡ ፱ ። ኩፋ ፡ ፲፱) ። ደጊንን ፡ ለክፉ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ተለወ ፡ ግን ፡ ለክፉም ፡ ለበጎም ፡ ይኾናል ፤ የዶ ጊንን ፡ ፍቺ ፡ ተመልከት ። ደገናሙ ፡ ወተለዎሙ ። ኢተለውዎሙ ፡ ድኅሬሆሙ ። ሑሩ ፡ ፍጡነ ፡ ወት ልውዎሙ ፤ የክፉ ፡ (ዘፍ ፲፬ ፡ ፲፬ ። ፴፰ ፡ ፳ ። ኢያ ፪ ፡ ፭) ። ተሉ ፡ ቶሎ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ተላዊ** ፤ (ዊት ፡ ውያን ፡ ያት ፤ ለውት) ፤ የሚከተል ፤ የሚመስል ፤ መሳይ ፡ ተከታይ ፤ ተማሪ ፡ ተባ ባሪ ፤ ተስማሚ ። ተላዊሆሙ ፡ ለሐዋርያት ። ተላው ያን ፡ ለኀበ ፡ ቃሉ ። ተለውተ ፡ አሠሮሙ ፡ ለተንባላት ። ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ኢኮነ ፡ ተላዌ ፡ ለሕግ ፡ ጠባይዕ ፡ (ሃይ ፡ አበ ። ፊልክ ፡ ፫ ። መጽ ፡ ምስ ። አፈ ፡ ድ፳፮) ።

**ትልው** ፤ **መትልው** ፤ (ዋን ፡ ዋት ፡ ሉት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ የመሰለ ፡ የተከተለ ፤ ስምም ፤ የሚከተል ፤ ተከታይ ፤ ምክትል ። ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘ ሮሜ ፡ መትልወ ፡ ጴጥሮስ ። ትጉልቊ ፡ እምቀዳ ሚት ፡ ዕለት ፡ በበ ፡ መትልው ። ወመትልወ ፡ ዝ ንቱ ። ስማዕ ፡ መትልወ ፡ ዝንቱ ። ዝ ፡ ውእቱ ፡ ም ዑዝ ፡ ለመትልወ ፡ ወይን ። አናጕንስጢስ ፡ ያንብብ ፡ ዘንተ ፡ ወዘመትልው ፡ ቀሲስ ፡ (ቀኖ ፡ ኒቅ ። አቡሻ ፡ ፱ ። አፈ ፡ ድ፭ ። ፫ ። ምሳ ፲፪ ፡ ፲፭ ። ኪዳ) ።

**መትለው** ፤ **ልው** ፤ **ትሎ** ፤ (ብ ፡ መታ ልው) ፤ ኋላ ፡ መጨረሻ ፤ ቀጥሎ ፤ ተከትሎ ፤ ወዲያው ። ዘበመትልወ ፡ በዓለ ፡ እግዚእክ ፡ ኮነ ፡ በዓልክ ። መት ልወ ፡ ሐጋይ ። ወመትሎሁ ፡ ይበል ። ለዝ ፡ መዋኢ ፡ እንዘ ፡ ይኔጽር ፡ አክሊሎ ፤ በዕለተ ፡ ፈለሰ ፡ አዕረፈ ፡ መትሎ ፡ (መዋሥ ፤ ድጓ ። አዋል ። ኪዳ ። ስንክ ፡ ሐምሌ ፲፯) ።

—፤ ተራ ፤ ረድፍ ፤ ማዕርግ ፤ ተከታታይነት ፡ ያለው ። በበ ፡ መትልው ። ሥዩማን ፡ በበ ፡ መትሎሆሙ ። በ ላም ፡ ለአብርሃም ፡ ወለይሥሐቅ ፡ በመትሎ ፤ ወለ ሣልሳይ ፡ ያዕቆብ ። ስምዐነ ፡ አምላክነ ፡ ወለባመከ ፡ ሀበነ ፡ እስመ ፡ ወሀብከነ ፡ ዘሎ ፤ ስብሐተ ፡ ዚአከ ፡ ንንግር ፡ እምትካት ፡ ዘሀሎ ፤ በበ ፡ መዓርግ ፡ ወበበ ፡ መትሎ ፡ (ሉቃ ፩ ፡ ፫ ። ሲኖ ዶ ። ስንክ ፡ ሚያዝያ ። ድራሲ) ።

**ትልወት** ፤ **ትሉት** ፡ (ታት) ፤ መከተል ፤ አከታተል ፤ ተከታይነት ፤ ክተላ ። በትልወቱ ፡ ወልድ ። ትልወተ ፡ ሔጺስቆጳስ ፡ (አዋል) ።

—፤ የቤት ፡ ልጅ ፡ ገንዘብ ፤ ማዕጋ ፡ መዳረያ ፡ ክባቷ ፡ ቤት ፡ ይዛው ፡ ኅድታው ፡ አስከትትኅው ፡ የምትኼድ ። እመ ፡ ፈቀደ ፡ ያስተዋስብ ፡ ወለቶ ፡ ይሁባ ፡ ትልወታ ፡ በአ ምጣነ ፡ ክሂሎቱ ። ይደሉ ፡ እንከ ፡ አውስቦ ፡ ዘእን በለ ፡ ትልወት ፡ ወኢሕፄ ። ትሎት ፡ ዘአምጽአቶ ፡ ኀ ቤሁ ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፬ ፡ ፭ ፡ ፪ ፡ ፯) ።

**አትለወ** ፤ አስከተለ ፤ ቅልዉ ፡ አለ ፤ ተከታይ ፡ ሰጠ ፤ አሰደደ ። ከመ ፡ ኢያትልዉ ከሙ ፡ ድኅረ ፡ አማ ልክቲሆሙ ። አተሉ ፡ መጥባሕትየ ፡ ድኅሬሆሙ ። ብፁዕ ፡ ዘኢያትለወ ፡ ልቦ ፡ ድኅረ ፡ ንዋይ ፡ (፫ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፪ ። ፱ ። ሕዝ፭ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ። ሚራ፴፩ ፡ ፰) ።

—፤ ጨመረ ፡ ቀጠለ ። ወእመሰ ፡ አትለወ ፡ አብሰ ። ወእምዝ ፡ አትለወ ፡ ወይቤ ። ወእምዝ ፡ ታተሉ ፡ እ ስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ። ዳንኤል ፡ ዘፈከረ ፡ ሕ ልመ ፡ ንጉሥ ፡ በቃሉ ፤ ወተርጕሞቶ ፡ ፍጡነ ፡ ያ ተሉ ፡ (ሄርማ ። አፈ ፡ ድ፬ ። ግንዘ ። ስንክ ፡ መጋቢት) ።

**ተታለወ** ፤ ተከታተለ ፤ ተራደፈ ፤ ተከታታይ ፡ ኾነ ። እንዘ ፡ ይታለዉ ፡ አሐዱ ፡ ድኅረ ፡ አሐዱ ። ይ ታለዎ ፡ ዝንቱ ፡ መርገም ። መከራ ፡ ብዙኅ ፡ እንተ ፡ ተታለወት ። ዘእንበለ ፡ ቀዲም ፡ ወተታልዎ ፡ (ስንክ ፡ ታኅሣሥ ። ዘጳጕ ፡ ፲፱ ። አፈ ፡ ድ፳፮ ። አዋል) ።

**አስተታለወ** ፤ አከታተለ ፤ አራደፈ ። እንዘ ፡ ያስተታልዎን ፡ ለአሐቲ ፡ ድኅረ ፡ አሐቲ ። በአስተታ ልዎ ። አለ ፡ ያስተታልዎሙ ፡ (ስንክ ፡ መስከ ። አቡሻ ፡ ፱ ። ዮሴፍ ፡ ፯) ።

**መስተታልው** ፤ የሚያራድፍ ፤ የሚያከታትል ፤ አከታታይ ።

**ተሊም** ፤ ሞት ፤ (ተለመ ፡ ይትልም ፡ ይ ትልም ። ዕብ ፡ ታሌም) ፤ መትለም ፤ መሠንጠቅ ፤ ዕርሻ ፡ መኽመር ፤ ማረስ ፤ በፈር ፡ ላይ ፡ ፈር ፡ እየጨመሩ ፡ መኼድ ፡ መመላለስ ።

**ትልም** ፤ (ዕብ ፡ ቴሌም ፤ ትላም ። ዐረ ፡ ተለም) ፤ በቁሙ ፤ ፈር ፤ ስለት ፡ የኼደበት ፡ ሥንጥቅ ። ትልመ ፡ ገራውሂከ ። ኢትዝራዕ ፡ ውስተ ፡ ትልም ፡ ኀ ጢአት ። ኢንደንግፅ ፡ ወኢናጽንን ፡ ትልመነ ፡ (ኢዮ ፴፱ ፡ ፲ ። ሚራ ፯ ፡ ፫ ። አፈ ፡ ተ፳) ።

**ትለም** ፤ **አትላም** ፤ **አትልምት** ፤ ትል ሞች ፤ ፈሮች ። አርውዮ ፡ ለትለሚሃ ። ዘከመ ፡ የሐ ርስ ፡ ትለሚሁ ። አውፅአ ፡ ሠለስተ ፡ አትላመ ። ሐ ረሰ ፡ ሠላሰ ፡ አትልምተ ፡ (መዝ ፡ ፷፬ ። ሚራ ፴፰ ፡ ፳፮ ። ገድለ ፡ ሕፃን ፡ ሞአ ። ስንክ ፡ ኅዳር ፳ ። ሐምሌ) ።

**ቴሌም** ፤—**ማርተኛ** ፤—**ተየሌም** ።

**ተልሚድ** ፤—**ተማሪ** ፤—**ለመደ** ።

**ተላዕ** ፤ (ዓት) ፤ ደረት ፤ ፍርንባ ፤ ካንገት ፡ እ ስከ ፡ ሆድ ፡ ያለ ፡ ክፍል ፡ (ዘፀ ፡ ፳፱ ፡ ፳፯ ፡ ፳፯ ። ዘሌ ፯ ፡ ፴) ።

**ተልፍዮስ** ፤ (ጽር ፡ ታልፒዮስ ። ዕብ ፡ ታልፈዮት) ፤ የዘበኞች ፡ ቤት ፤ የሰልፍ ፡ መሣሪያ ፤ ጋሻ ፡ ጦር ፡ ሰይፍ ፡ ቀስት ፡ የሚሰቀልበት ፡ (ማሕ ፡ ፬ ፡ ፬) ።

**ተሙዝ** ፤ (ዕብ ፡ ታሙዝ ። ሱር ፡ ታ ሙዝ) ፤ ስመ ፡ ወርኅ ፡ ራብዕ ፤ ሐምሌ ። በራብዕ ፡ ወ ርኅ ፡ ዘውእቱ ፡ ወርኀ ፡ ተሙዝ ፡ (ዮሴፍ ። መጽ ፡ ምስ) ።


—፤ ስመ ፡ ጣዖት ፤ የአምልኮው ፡ ሥርዐት ፡ ሙሾና ፡ ል ቅሶ ፡ የኾነ ፡ (ሕዝ፰ ፡ ፲፬) ።

**ትማልም** ፤ (ዕብ ፡ ትሞል ፤ ኤትሞል ። ሱር ፡ ኤትማል) ፤ ትላንት ፤ ዓምና ፤ ያለፈ ፡ ቀን ፡ ጊዜና ፡ ዘመን ። በከመ ፡ ቀተልኮ ፡ ትማልም ። ዘትማ ልም ፡ ወዮም ፡ (ዘፀ፪ ፡ ፲፬ ። ዕብ፲፫ ፡ ፰)

**ተሚም** ፤ ሞት ፤ (ተመ ፡ ይተምም ፡ ይ ትምም ፤ ዐረ ፡ ወትግ ። ዕብ ፡ ታም ፤ ፈጸመ ፤ ተፈጸመ ፤ መላ ፡ ልክ ፡ ኹኔ) ፤ መትመም ፤ ፈጽሞ ፡ መርሞኽ ፤ መክሰል ፡ ማስገምገም ፤ ማግማት ፡ ማጕረም ረም ፤ የሰማይ ፡ የዝናም ፡ ያታሞ ፡ የነጋሪት ፡ ለበውም ፡ ይኾናል ። አታሞ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ተማም** ፤ በቁሙ ፤ ፍጹም ፤ ልክ ፡ ምሉ ፡ ሕ ጸጽ ፡ የሌለበት ።

**ተመን** ፤ (ዕብ ፡ ታኒን ። ሱር ፡ ታኔን ። ዐረ ፡ ቲኒን) ፤ እባብ ፡ ዘንዶ ፤ አርጃኖ ፤ የባሕር ፡ የየ ብስ ። ተመን ፡ ዐቢይ ። በአምሳለ ፡ ተመን ፡ ወአራ ዊት ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፬ ። ኪዳ ። ገድ ፡ ተክ ። አሉሻ ፡ ፯) ።



ተመን ፡

**ተመናት** ፤ **አትማን** ፤ እባቦች ፤ ዘንዶዎች ። ተመናት ፡ ወአናብስት ፡ (ስንክ ፡ ግን፲፱) ።

**ቴማን** ፤—ደቡብ ፤—ተየማን ።

**ተምዐ** ፤—ተቈጣ ፡ ዐዘነ ፤—መዕዐ ።

**ተመዓኒ** ፤ (ዕብ ፡ ቴማኒ) ፤ ቴማናዊ ፤ ደቡ ባዊ ፤ ስመ ፡ ኮከብ ፤ ካራቱ ፡ ዐበይት ፡ ከዋክብት ፡ አንዱ ፤ ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ ያመት ፡ ርቦ ፡ ፺፩ ፡ ዕለት ፡ የሚመግብ ። ምልክኤል ፡ ዘይሰመይ ፡ ስሙ ፡ ተመዓኒ ፡ ወፀሓየ ፡ ወዘሰ ፡ መዋዕል ፡ ዘበሥልጣኑ ፡ ዚአሁ ፡ ይመልክ ፡ ተስዓ ፡ ወአሐዱ ፡ ዕለት ፡ (ሔኖ ፡ ፹፬) ።

**ተምር** ፤ **ተመርት** ፤ (ዐረ ፡ ተምር ። ዕብ ፡ ታማር) ፤ በቁሙ ፤ ሰሌን ፡ ዘንባባ ፤ የሰሌን ፡ ፍሬ ፤ ሕንባቡ ፡ ዛላው ፡ ዘለላው ፤ የሚበላው ። ወይየ ፡ ማይ ፡ ጥዑም ፡ ወኀሰታት ፡ ወበቀልታት ፡ ወተምር ፡ ብዙኀ ። ፍሬ ፡ በለስ ፡ ወተምር ። ቂሐተ ፡ ተምር ፡ ወጽዕዳዌ ፡ ፀምር ። እምነ ፡ ተመርተ ፡ ቈላ ። በቀ ልተ ፡ ተመርት ። ፀመርተ ፡ ተመርት ፡ ዘበቀልት ፡ (ስ ንክ ፡ ጥር፳፪ ። ሚያዝ ። አፈ ፡ ተ፲፪ ። ክፋ ፡ ፳፬ ። ዘኍ ፴፫ ፡ ፱ ። ዮሐ፲፪ ፡ ፲፫) ። ተምር ፡ ተመርት ፡ ፍሬውና ፡ ዛፉ ፤ በቀልት ፡ ማንዱ ፤ ፀመርት ፡ ቅጠሉ ።



ተምር ፡

**ተምራት** ፤ **ተመርታት** ፤ ተምሮች ፤ የተ ምር ፡ ፍሬዎች ።

**ተሜርጋብ** ፤—ሣጥን ፤—ኤርጋብ ።

**ቶማስ** ፤—የሰው ፡ የፀሓይ ፡ ስም ፤—ተ ወማስ ።

**ትንብክ** ፤ (ትግ ፡ ወዐረ) ፤ ትንባኾ ፤ የታ ወቀ ፡ ቅጠል ፤ ጢሱና ፡ ደቁቁ ፡ ባፍና ፡ ባፍንጫ ፡ የሚ ጠጣ ፤ የሚጕረሥ ፤ በቅብጠት ፡ በቅንጠት ፡ የሚለመድ ፤ ኹሉ ፡ የማይፈልገው ።

**ተንብሎ** ፤ **ሎት** ፤ (ተንበለ ፡ ይተነብል ፡ ይተንብል ፤ ነበ ፤ ነበየ ፤ ብህለ) ፤ መለመን ፤ መጸለይ ፤ መማለድ ፤ ማማለድ ፤ ማላጅ ፡ አማላጅ ፡ መ ኾን ፤ ዕርቅ ፡ ፍቅር ፡ ይቅርታ ፡ መፈለግ ፤ ማረኝ ፡ ማር ልኝ ፡ ማለት ። ወንሕነሰ ፡ ንተነብል ፡ በአምሳለ ፡ ክር ስቶስ ። ዘበእንቲኣሁ ፡ እተነብል ፡ ሙቅሕየ ። ወይ ተነብል ፡ ሎሙ ። በእሎ ፡ ለጊዮርጊስ ፡ ከመ ፡ ይተን ብል ፡ በእንቲኣሁ ፡ ኀበ ፡ እግዚ ። ማርያም ፡ ትተነ ብል ፡ ለደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ መሕያው ፡ ኀበ ፡ ወልዳ ። ተን ብሊ ፡ በእንቲኣነ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፳ ። ኤፌ፮ ፡ ፳ ። ዕብ፯ ፡ ፳፭ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳ ። ሚያ፳፩ ። ድጓ) ።

**ተንባሊ** ፤ (ሊት ፡ ልያን ፡ ያት ፤ በልት) ፤ የሚለምን ፡ የሚጸልይ ፤ ማላጅ ፡ አማላጅ ፤ አቈላማጭ ። ምጽዋት ፡ ተንባሊት ፡ ይእቲ ። ማርያም ፡ ተንባ ሊተ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ (አፈ ፡ ተ፴፪ ። ስንክ ፡ ሚያ፳) ።

**መተንብል** ፤ (ልት ፡ ላን ፡ ላት) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ። ልሳን ፡ መተንብልት ፡ ዘይረክብ ፡ ሰብአ ፡ መፍቅዶ ። ኄራን ፡ መተንብላን ፡ እለ ፡ ይስእሉ ፡ ም ሕረተ ፡ ለውሉደ ፡ ሰብእ ። መተንብላን ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ። ደናግል ፡ ሠናያት ፡ ወመተንብላት ፡ (ፈላስ ። ድጓ ። ስንክ ። ኅዳ፲፫ ። መዋሥ) ።

**ተንበል** ፤ **ባል** ፤ (ብ ፡ ተናብል ፤ ልት) ፤ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፤ አማላጅ ፤ አስታራቂ ። አኮ ፡ በተን ባል ፡ ወአኮ ፡ በመልአክ ። ይምጽኡ ፡ ተናብልት ፡ እ ምግብጽ ። ፈነወ ፡ ተናብልተ ፡ ድኅሬሁ ፡ (ኢሳ፷፫ ፡ ፱ ። መዝ ፡ ፷፯ ። ሉቃ፲፱ ፡ ፲፬) ።

**ተንበል** ፤ (ብ ፡ ተንበላት) ፤ ስመ ፡ ነገድ ፡ እስላማዊ ፤ ከሊፋ ፡ የሙሐመድ ፡ ተከታይ ፤ ተፈናዊ ፡ ፍኖው ፡ ማለት ፡ ነው ። ተንባለ ፡ አምላክ ፡ ቢል ፤ ረሱል ፡

አኅሀ ፡ እንዲል ፡ (ዐረብ) ። እምቅድመ ፡ ይንግሡ ፡ ተንባላት ፡ በግብጽ ። እምሥጋዌ ፡ እስከ ፡ ተንባላት ፡ ስድስቱ ፡ ምእት ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ዓመት ። እምሰማዕታት ፡ እስከ ፡ ተንባላት ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ሠላሳ ፡ ወሰመንቱ ። ሐሳበ ፡ ተንባላት ። ምስለ ፡ ተንባላት ፡ ወአይሁድ ። ለእመ ፡ ዘመወ ፡ ማእምን ፡ አው ፡ ማእምንት ፡ በተንባላት ። ነቢየ ፡ ተንባላት ፡ (ስንክ ፡ ጥር፳ ። መር ፡ ዕዉ ። አቡሻ ፡ ፬ ። ቂድር ። ገድ ፡ ተክ) ።

**ተንበላታዊ ፡ ይ ፤** እስላም ፤ የክሊፋ ፡ ወገን ፤ ሙሐመዳዊ ። ውእቱ ፡ ተንባላታዊ ። ብእሲት ፡ ተንባላታዊት ፡ አው ፡ አረማዊት ። ዘይክውን ፡ ተንባላታየ ፡ (ስንክ ፡ ኅዳ፬ ። መጋ፳፯ ። ቢኖ ፡ ደ) ።

**ትንባሌ ፡ ል ፤** መለመን ፤ አለማመን ፤ ጸሎት ፡ ልመና ፤ ምልጃ ፡ ቍልምጫ ። አንግፍኒ ፡ በትንባሌ ፡ እምብካይ ፡ ወወይሊ ፡ (ደራሲ ። ስንክ ፡ መስ፭ ። ኅዳ፲፬ ። ጥር፴) ።

**ትንብልና ፤** ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ልመና ፡ ምልጃ ፤ አማላጅነት ። በትንብልናሃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ። በዐሠርቱ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ትንብልናከ ። በትንብልና ፡ ማህልክ ፡ (ሳታት ። ድጓ) ።

**ታናክ ፤ ቴናክ ፤** ስመ ፡ ዕፅ ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ዕንጨት ፤ እንደ ፡ ጥድና ፡ እንደ ፡ ወይራ ፡ መልክም ፡ ሽታ ፡ ያለው ፤ ለመሥዋዕት ፡ ሙጋድ ፡ የሚኾን ። ቡራቴ ፡ ወቴናክ ፡ (ኩፋ ፡ ፳፩) ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ጠይ ፡ ይሉታል ።

**ተንከራ ፤ ር ፤ (ዐረ ፡ ተንከር ። ዕብ ፡ ፒፕዳ ። ጽር ፡ ቶፓዚዮን) ፤** ጥሩ ፡ ጠንካራ ፡ ዕንቍ ፤ ዐይነቱ ፡ ሐመልሚል ፤ ቅጠልያ ፡ አረንጓዴ ፤ ወይም ፡ ብጫቴ ፤ የወራ ፡ የበሰለ ፡ ቅጠል ፡ የሚመስል ። ወኢይትዔረይ ፡ ተንከራ ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ (ኢዮ፳፰ ፡ ፲፱) ።

—፤ ሙሸዘር ፤ የማዕደናት ፡ መጣብቅ ። ጠነከረ ፡ ቸንከረ ፡ ችንካር ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ ወጥቷል ።

**ተንከተም ፤—ታንኳ ፤ ድልድይ ፤—ከተመ ።**

**ተኒን ፤ ኖት ፤ (ተነ ፡ ይተንን ፡ ይትንን ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ትናን) ፤** መትነን ፤ መብነን ፤ መጤስ ፡ መትጕልጐል ፤ ብን ፡ ትን ፡ ማለት ። መስፋት ፡ መዘርጋት ፤ ሰፊ ፡ ወርዳም ፡ ቁመታም ፡ መኾን ።

**አትነነ ፤** አተነነ ፤ አበነነ ፤ አጤሰ ፡ አስጤሰ ።

**ተን ፤** በቁሙ ፤ ተንታ ፤ ጢስ ፡ ብናኝ ። ዴበ ፡ አርእስተ ፡ አድባር ፡ ለተነ ፡ ፂሜ ፡ ዘያጠይሰ ። ቱነ ፡ ጢስ ። ለእሳት ፡ ይቀድሞ ፡ ተነ ፡ ጢሱ ። ዘእንበለ ፡ ይደመር ፡ ለብርሃነ ፡ እሳት ፡ ተን ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ዮኤ፫ ፡ ፫ ። ሚራ፳፱ ፡ ፳፱ ። ፊልክ ፡ ፻፶፴፯) ።

**ትን ፤ ቲን ፤ ቴን ፤** ወርድ ፡ ስፋት ፤ ቁመት ፤ ወፍር ። ትኑ ፡ ወርሐቡ ፡ ወቲኑ ፡ (ቀሙ) ፡ ዕሥራ ፡ በእመት ። ወስዝር ፡ ቴና ፡ (ግዘፉ) ፡ ሲይእቲ ፡ ባሕር ፡ እንተ ፡ ብርት ፡ (፪ዜና ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ፭) ።

(ጥኗ) **ታኒን ፤ (ዕብራ) ፤** ስመ ፡ አራዊት ፡ ዐበይት ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፤ መደበኛው ፡ ግን ፡ ዐዞ ፡ ነው ፤ ለዘንዶና ፡ ላርጃኖም ፡ ይኾናል ፤ ተመንን ፡ እይ ።

**ትንንያ ፤ (ዕብ ፡ ዐሮብ) ፤** ትንኝ ፤ ቅማል ፤ ጸጼት ፤ ታናሽ ፡ ተናካሽ ፡ ፍጥረት ። ዐኮትንና ፡ ጸጼትን ፡ ተመልከት ። ዐኮት ፡ ወትንንያ ። በትንንያ ፡ ወበጽንጽንያ ። መራዱ ፡ ትንንያ ፡ (መዝ ፡ ፸፱ ። ኩፋ ፡ ፵፰ ። ጥበ፲፱ ፡ ፲) ።

**ተንተነ ፤** ተነተነ ፡ ከፋፈለ ፤ ለመስጠት ፡ ለማደል ። ነተንንና ፡ አስተንተንን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ተፍገመገመ ፤ ተንገደገደ ፤ ተወዘወዘ ፤ ተጨነቀ ። ተንተንኩ ፡ ለወዲቅ ። ትተነትን ፡ ከመ ፡ ስኩር ፡ ወትጸንን ። ባዕል ፡ ለእመ ፡ ተንተነ ፡ ይሰውቅዎ ፡ አዕርክቲሁ ። እምቀትለ ፡ ወለተ ፡ ሕዝብየ ፡ ተንተንኩ ። አሐዝን ፡ ለሞትከ ፡ ወእተነትን ፡ ለድክትምናየ ፡ (መዝ ፡ ፻፲፯ ። ኢሳ፳፱ ፡ ፳ ። ሲራ፲፫ ፡ ፳፩ ። ኤር፰ ፡ ፳፩ ። ዮሴፍ) ።

**ትንቱን ፤ (ናን ፡ ናት ፡ ትንት) ፤** የተፍገመገመ ፤ የተገፋ ፡ የተደፋ ፤ የተሰናከለ ፤ ሊወድቅ ፡ የቀረበ ። ከመ ፡ ትሱቁኒ ፡ ለትንቱን ። የሀብከ ፡ ለትንቱን ፡ እግዚ ፡ ትንማሴ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፳፯ ። ደራሲ) ።

**ትንታኔ ፤** መፍገምገም ፤ መንገድገድ ፤ ውዝወዛ ፤ ጭንቅ ፤ እወድቅ ፡ አልወድቅ ፡ ማለት ፤ ጽንት ። ሱቁኒ ፡ ጊዜ ፡ ትንታኔ ። ወበጻሕኩ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ኀበ ፡ ትንታኔ ፡ ወሀጐል ። ወአጽንዖ ፡ እንበለ ፡ ትንታኔ ፡ ሃይማኖተ ፡ ርትዕተ ፡ (ስንክ ፡ መጋ፮ ። ዮሴፍ ። ተረ ፡ ቄር፲፩) ።

**አተንተነ ፤** አፍገመገመ ፤ ገፋ ፡ አዳፋ ፤ ወዘወዘ ፤ ነቀነቀ ፤ አስጨነቀ ። ብእሲ ፡ ዘያተነትኖ ፡ ስካረ ፡ ወይን ። ሶበ ፡ አተንተኖ ፡ ሰይጣን ፡ ዝሙት ። አተከዘኒ ፡ ወአተንተነኒ ፡ (ኤር፳፫ ፡ ፱ ። ፊልክ ፡ ፯ ። ዮሴፍ) ።

**አስተንተነ ፤—ዐሰበ ፡ ተጋ ፤—ነቲን ፡ ነትነ ።**

**ትንታግ ፤—ክፋይ ፡ ትርኳሽ ፤—ነቲግ ፡ ነትገ ።**

**ተፈእ ፤ እት ፤ (ተፍአ ፡ ይተፍእ ፡ ይትፋእ ። ዕብ ፡ ቱፍ ። ዐረ ፡ ተፈፈ ፤ ተፈለ) ፤** መትፋት ፤ ምራቅን ፡ እክ ፡ እንትፍ ፡ ጢቅ ፡ ማለት ፤ መቀርሸት ፡ ማስመለስ ። አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይትፍኡ ፡ ምራቀ ። ተፍአት ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ። እንዘ ፡ ይተፍእ ፡ ሕምዘ ፡ ባዕሌነ ፡ (መጽ ፡ ምስ ። ቀሌ ። ተረ ፡ ቄር) ።

**ተፋኢ ፤ (ኢት ፡ እያን ፡ ያት) ፤** የሚተፋ ፤ ትፋታም ፤ ቀርሻታም ። ተፋእያነ ፡ ሕምዘ ፡ ከይሲ ፡ ወአርዌ ፡ ምድር ፡ (ኪዳ) ።

**ትፍአት ፤** መትፋት ፤ አተፋፍ ፤ ትፋት ፤ ምራቅ ። ተፍአ ፡ ትፍአተ ፡ (ዘኁ፲፱ ፡ ፲፬) ።

**ትፋእ ፤** ትፋት ፤ አክታ ። ይመጽአኒ ፡ ትፋእ ፡ ከመ ፡ እቂአ ፡ (አረጋ ፡ መ፲) ።

**አትፍአ ፤** አስተፋ ፤ አስቀረሸ ፤ ጢቅ ፡ ጢቅ ፡ አሰኘ ።


**ትፋሕ ፤ (ዕብ ፡ ታፉዋሕ ። ዐረ ፡ ቱፋሕ) ፤** የተክል ፡ ዕንጨት ፡ ስም ፤ ፍሬው ፡ ክብ ፡ እንክብል ፤ ሥጋማ ፡ ጥፍጥ ። ኮልን ፡ እይ ፤ ተና ፡ ጠ ፡ ተወራራሾች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በትፋሕ ፡ ፈንታ ፡ ጥፋሕ ፡ ይላል ፡ (ስንክ ፡ ሐምሌ) ። አዘዘ ፡ ያምጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ትፋሐ ፤ አነዳ ፡ ትፋሕ ። ወፈነወ ፡ ንጉሥ ፡ ትፋሐ ፡ ለብእሲቱ ፤ ወይእቲኒ ፡ ፈነወት ፡ ውእተ ፡ ትፋሐ ፡ ለዩሲኑስ ፤ እስመ ፡ ሕሙም ፡ ውእቱ ፤ ወሰበ ፡ ሖረ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ የሐውጾ ፡ ርእየ ፡ ለውእቱ ፡ ትፋሕ ፤ ወይቤላ ፡ ሀብኒ ፡ ትፋሐ ፡ ዘፈነውኩ ፡ ለኪ ፡ ወትቤሎ ፡ በላዕክዎ ፡ (ዮሴፍ ። ዮሐ ፡ መደ) ።

**ተፉሕ ፤ (ሐት ። ዐረ ፡ በጣጣ) ፤** ድንች ፤ ትፋሕማ ፡ የምድር ፡ ትፋሕ ፤ ወጥ ፡ የሚኾን ።

**ተፈየ ፤ (ሰፈወ ፤ ተሰፈወ) ፤** አመነ ፤ ታመነ ፤ ተስፋ ፡ አደረገ ። አነ ፡ እተፌ ፡ ከመ ፡ ለእመ ፡ ነበርከ ፡ ውስተ ፡ በአትከ ፡ በስመ ፡ እግዚ ፡ ትትረከብ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ እንጦንዮስ ። ተኀድግኑ ፡ ግብረከ ፡ ወትትተፌ ፡ ላዕሌሁ ። እተፊ ፡ ላዕሌክሙ ። በሃይማኖትከ ፡ እስመ ፡ ነፍስየ ፡ ትተፌ ፡ (ፊልክ ፡ ሃ፱ ። ኢዮ ፴፱ ፡ ፲፩ ። ፪ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፯) ።

**ትፈላ ፤ (ዕብራ) ፤** ጸሎት ፡ ልመና ፡ ምሕላ ። ለጸሎት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ላትፈላ ፡ እንዲል ፡ (ኅሐ፲፩ ፡ ፲፯) ።

**ተቅዳ ፤ (ዐረ ፡ ተቅደት ። ዕብ ፡ ጋድ) ፤** ድንብላል ፤ የድንብላል ፡ ፍሬ ፤ ታናናሽ ፡ ድንብልብል ፤ ቅመም ፡ የሚኾን ። ድቁቅ ፡ ከመ ፡ ተቅዳ ። ወከመ ፡ ፍሬ ፡ ተቅዳ ፡ (ዘፀ፲፮ ፡ ፲፱ ፡ ፴፩ ። ዘኍ ፲፩ ፡ ፯) ።



ተቅዳ ፡

**ቴቆሔ ፤ (ዕብ ፡ ትቆዕ) ፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ ዘይሁዳ ፤ የዘይሁት ፡ አገር ፤ በይሁዳ ፡ ክፍል ፡ ያለች ፡ (፪ነገ ፡ ፲፬ ፡ ፪ ። ዓሞ፩ ፡ ፩ ። ፪ዜና ፡ ፳ ፡ ፳) ። ባለቅኔዎች ፡ ማን ፡ የፈረሰ ፡ አገር ፡ ይሏታል ። በምቅዋመ ፡ አእዱግ ፡ ይቀብኑ ፡ አፍራሰ ፡ ቴቁሔ ፡ (ቅኔ) ።

**ተቀዋም ፤—መቅረዝ ፤—ቀዊም ፡ ቆመ ።**

**ቱቋል ፤ (ሱር ፡ ትቋል) ፤** ሰቀለ ፤ ደለወ ፤ መዘነ ፡ (ዳንኤ ፡ ፭፳) ።

**ትርእስ ፤—ትራስ ፡ ራስጌ ፤—ርእሰ ፡ ትርአስ ።**

**ተርቢዝ ፤—አተላ ፡ ሐሠር ፤—ተብሪዝ ፤ በረዘ ።**

**ተርጐመ ፤ (ዲቃ ፡ ግ ፤ ረገመ ፡ ተረግመ ። ዕብ ፡ ወሱር ፡ ታርጌም ። ዐረ ፡ ተርገመ) ፤** ተረጐመ ፤ ቃልን ፡ በቃል ፡ ለወጠ ፤ ገለበጠ ፤ መጽሐፍን ፡ ቀዳ ፡ መለሰ ፤ ከቋንቋ ፡ ወደ ፡ ቋንቋ ። ወይም ፡ በዚያው ፡ ባንዱ ፡ ቋንቋ ፤ አንድም ፡ እያለ ፡ ፈታ ፡ አፍታታ ፡ ዘረዘረ ፤ ቁሞ ፡ ለበክ ፡ አስተማረ ፤ ላንዱ ፡ ትንጣት ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ብዙ ፡ ፍካሬ ፡ ሰጠ ። ወከነ ፡ ዮሴፍ ፡ ይተረጉም ፡ ሎሙ ፡ ዘይትናገሮሙ ፡ ጢጦስ ፡ በልሳነ ፡ ሮም ፡ ወያየድያሙ ፡ በልሳነ ፡ ዕብራውያን ። በእንተ ፡ ተርጉሞቱ ፡ እምልሳነ ፡ ጽርእ ፡ ኀበ ፡ ዐረቢ ። ተርጕሞ ፡ ቃለ ፡ መጻሕፍት ። ተርጕም ፡ ለነ ፡ (ዮሴፍ ። ፍ ፡ ነ ፡ መቅ ። ቀሌ ። ፊልክ ፡ ፴) ።

**ተርጓሚ ፤ (ሚት ፡ ምያን ፡ ያት) ፤** በቁሙ ፤ የሚተረጉም ፤ የሚፈታ ፡ ፈች ፡ አስረጅ ። አኮሰ ፡ ውዳሴ ፡ ለተርጓምያን ፡ (ፊልክ) ።

**ትርጕማን ፤ (ዐረ ፡ ተርጁማን ። ሱር ፡ ታርግማና ። ዕብ ፡ ሜሊጽ) ፤** በቁሙ ፤ አስተርጓሚ ፤ አምኻር ፤ አነጋጋሪ ፤ ማእከል ፡ ኹኖ ፡ ያንዱን ፡ ቃል ፡ ላንዱ ፡ የሚያሰማ ፡ ኹለት ፡ ቋንቋ ፡ በጥቂ ፤ አፍ ፡ ጠበቃ ፡ አስታራቂ ። ወእሙንቱሰ ፡ ኢያእመሩ ፡ ከመ ፡ ይሰምዖሙ ፡ ዮሴፍ ፤ እስመ ፡ ትርጕማን ፡ ሀሎ ፡ ማእከሎሙ ፡ (ዘፍ፵፪ ፡ ፳፫) ።

**አተርጐመ ፤** አስተረጐመ ፤ አስቀዳ ፤ አስገለበጠ ፤ አስመለሰ ። ዜናሁ ፡ ሲብልማይ ፡ (በጥሊሞስ) ፡ ንጉሥ ፡ ዘከመ ፡ አተርጐመ ፡ ኦሪተ ፤ ዐሠሩ ፡ ወአርባዕተ ፡ መጻሕፍተ ፡ እምልሳነ ፡ ዕብራይስጥ ፡ ኀበ ፡ ልሳነ ፡ ዮናናውያን ፡ (ዮሴፍ) ።

**መተርጕም ፤ (ምት ፡ ማን ፡ ማት ። ዕብ ፡ ምታርጌም) ፤** የሚተረጉም ፤ የሚያስተረጉም ፤ ተርጓሚ ፤ አስተርጓሚ ፤ ሊቅ ፡ መፈክር ፤ ትርጁማን ፡ አምኻር ። አባ ፡ ሰላማ ፡ መተርጕም ። ይቤ ፡ መተርጕም ። ለብዙኃን ፡ እመተርጕማን ። መተርጕመ ፡ አሕላማት ። መተርጕመ ፡ ልሳኖሙ ፡ (ስንክ ፡ ኅሐ፳ ። ፊልክ ። ፍ ፡ ነ ፡ ፯፩ ። ፲፩ ። አሞል) ።

**ተተርጐመ ፤** ተተረጐመ ፤ ተቀዳ ፡ ተገለበጠ ፤ ተመለሰ ። ተፈታ ፡ ምስጢሩ ፡ ታወቀ ፡ ተገለጠ ። ዝቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ተተርጕመት ፡ እምልሳነ ፡ ዐረቢ ፡ ለግእዝ ፡ በእዴ ፡ ዕንባቆም ፡ ወሚካኤል ፡ ግብጻዊ ። ዘኢያብቁሰ ፡ ቀርነ ፡ ወጽፍረ ፤ ይተረጕም ፡ ዘአልቦ ፡ ትዕግልት ።

**ትርጉም ፤ (ማን ፡ ማት ፡ ጕምት) ፤** በቁሙ ፤ የተተረጐመ ፤ የተፈታ ።

**ትርጓሜ፤**(ምያት)፤ ባቢና፡ ጥሬ፡ ዘር። መተርጕም፤(ጥተ) መተርጕም፡ አተረጓጕም፡ አቀዳድ፡ አመላለስ፤ ትርጕማ፤ አፈታት፤ ዘይቤ፤ አወጣጥ፤ ምስጢር፡ አገላለጥ። በቁሙ፤ ፍች፤ የንባብ፤ ፍሬ፤ ምስጢሩ፡ ስልቱ፡ ውስጡ፡ ሐሳቡ። ከመ፡ ዝ፡ ትርጓሜሁ፡ እመጽሐፈ፡ ሶርያ። በትርጓሜ፡ መጻሕፍት፡ ቅዱሳት። ትርጓሜ፡ ስሙ። መምህረ፡ ትርጓሜ። ይቤ፡ ዮሐንስ፡ አፈ፡ ወርቅ፡ በትርጓሜሁ፡ ዘንተ፡ ክፍለ፤ (ኢዮ፡ማ፱፡ ፲፰። ቀሌ። ሰብ፮፡ ፬። ስንክ፡ ጥቅ፳። ፍ፡ ነ፡ ፵፳)።

**ትርያ፤**(ዐረ፡ ቱርያ)፤ ጠራው፤ ጕዑኣን፡ ከዋክብት። ዘገብሮ፡ ለትርያ። ኅቡረ፡ ትክልት፤ ተአኅዘ፡ ለትርያ፡(ኢዮ፡፴፰፡ ፴፩። ፴፱፡ ፴፩)። ጠራው፡ ኪማ፡ ሰኬላ፤ አንድ፡ ወገን፡ ናቸው።

**ታሪክ፤**(ካት። ዐረ፡ ታእሪክ)፤ በቁሙ፤ ያለፈ፡ የተጣፈ፡ ወሬ፡ አንቲካ፡ ዜና፡ የዘመን፡ ቍጥር፡ ዓመተ፡ ምሕረት። ዝንቱ፡ መጽሐፈ፡ ታሪክ። ውስተ፡ ታሪክ፡ ጉባኤ፡ ማልስ። ወእሙንቱ፡ ይገብሩ፡ ክልኤተ፡ ታሪካተ፤ ታሪክ፡ ሥጋዊ፡ ወታሪክ፡ ዲዮቅልጥያኖስ፡(ታሪ፡ ነገ። ያዕ፡ ዘእል። አቡሻ፡ ፰)።

**ተረክ፤**(ዐረ፡ ተረከ፤ ኀደገ)፤ በቁሙ፡ ታሪክ፡ ተረክ፤ ጣፈ፡ አወራ። ነተረክ፡ ነትራክ፡ ማለት፡ ከዚህ፡ ወጥቷል።

**ተርሜን፤**(ጽር፡ ራትሜን። ዕብ፡ ሮቴም)፤ ስመ፡ ዕፅ፡ ዐቢይ፤ የዱር፡ የበረሓ፡ ዛፍ፤ ዐጽቃም፡ ቅጠላም። በሰብሰብዮች፡ ግን፡ ክትክታ፡ ደደሆ፡ ይሉታል። ሖረ፡ ፍኖተ፡ በድው፡ ወነበረ፡ ታሕተ፡ ዕፀ፡ ተርሜን፡(፫ነገ፡ ፲፱፡ ፬)።

**ተርሙስ፤**(ጽር፡ ቴርሙስ። ዐረ፡ ቱርሙስ)፤ ግብጦ፤ አዳጕራ፤ የመኖ፡ ዐይነት። ሐባ፡ ቅፍፊ፡ ኢይጥዕም፡ ዘእንበለ፡ ተርሙስ፡ መሪር። ኮነ፡ ይሴሰይ፡ ሐሠረ፡ ተርሙስ፡ ሆሎ፡ አሚረ። ወሶበ፡ ፈቀደ፡ ይትጋደል፡ ነበረ፡ ሰማንየ፡ ዕለተ፡ እንዘ፡ ይበልዕ፡ ሐመደ፡ ምስለ፡ ተርሙስ፡(ስንክ፡ ኅዳ፰። መጋ፲፱። የካ፳፱)።

**ቶሬን፤—ተራዳ፤—ተውር።**

**ተረፍ፤ ፎት፤**(ተርፈ፤ ተረፈ፡ ይተርፍ፡ ይትርፍ። ዐረ፡ ተሪፈ። ዕብ፡ ያታር። ሱር፡ ዬታር)፤ መትረፍ፤ መትረፍረፍ፤ መብዛት፡ መብለጥ፤ ከልክ፡ ማለፍ፤ ተርፎ፡ መቅረት፡ መኖር፡ መዳን፡ ማምለጥ፤ እልፍ፡ ትርፍ፡ ቀሪ፡ ውዝፍ፡ መትን። ምንን፡ ተመልከት፡ የዚህ፡ ጎር፡ ነው። አክሎሙ፡ ወተርፎሙ። ወዘተርፈ፡ እምዝ፡ ይኩን፡ ለመልአክ። አስተጋብኡ፡ ዘተርፈ። አልቦ፡ ዘይተርፍ፡ እምኔሆሙ። ትርፍ፡ ባዕለ፡ ልማድከ። ወትትርፍ፡ ምድሮሙ፡ በድወ። እመ፡ ሞተት፡ ብእሲት፡ ወተርፈ፡ ምታ፡(ዘፀ፲፮፡ ፳። ሕዝ፵፰፡ ፳፩። ማቴ፲፬፡ ፳። ኤር፲፩፡ ፳፫። ፈልክ፡ ፫፰። ኢሳ፳፡ ፲፩። ፍ፡ ነ፡ ፵፪፡ ፫)።

**ተራፊ፤**(ፊት፡ ፍያን፡ ያት)፤ በቁሙ፤ የሚተርፍ፤ የሚቀር፤ ቀሪ፤ ነዋሪ። ሕዝብ፡ ተራፍያን፡ በምድር። ሆሎሙ፡ ተራፍያነ፡ ይሁዳ፡(ኤር፵፬፡ ፯። ፶፡ ፳)።

**ትሩፍ፤**(ፋን፡ ፋት፡ ርፍት)፤ የቀረ፡ የተረፈ፤ ቀሪ፡ ትርፍ። በእንተ፡ ትሩፋን። እሬስያ፡ ትርፍተ። ሕገጋት፡ ትሩፋት። ምግባራት፡ ትሩፋት፡(መዝ፡ ፳። ሚክ፬፡ ፯። ፈ፡ መ፡ ፭፡ ፩። አፈ፡ ተ፫)።

—፤ የበለጠ፤ የተሻለ፤ ብዙ፡ ፍጹም፤ መንፈሳዊ። ግብር፡ ትሩፍ፡ ኢ.ወሊ.ድ፡ ምስለ፡ ኂሩት። አይ፡ እምኔሆሙ፡ ዘትሩፍ። ብእሲ፡ ኄር፡ ወጠቢብ፡ ወትሩፍ። ትሩፈ፡ ምግባር። አብ፡ ቅዱስ፡ ወትሩፍ፡(ጥበ፬፡ ፩። ፈልክ፡ ፲፱። ዮሴፍ። ስንክ፡ የካ፳። ፈ፡ መ)።

—፤ መንፈሳዊ፡ ሥራ፤ ተውሳክ፡ ምግባር፤ በሕግና፡ በትእዛዝ፡ ላይ፡ የሚጨመር፤ ሰው፡ በፈቃዱ፡ ወደ፡ የሚሠራው፤ ክሥር፡ አንድ፡ አውጥቶ፡ ደግሞ፡ ከዘጠኝ፡ መስጠት፤ ይህን፡ የመሰለ፡(ማቴ፭፡ ፴፱—፵፩)። ገቢረ፡ ትሩፋት። ምግባረ፡ ትሩፋት። ተሰምዐ፡ ዜና፡ ትሩፋቲሁ፡ ወአእምሮቱ፡ ወቅድስናሁ። አግዐዞሰ፡ እምግብረ፡ ትሩፋት፡ ይእቲ፡(ፈ፡ መ፡ ፬፡ ፱። ስንክ፡ የካ፲፱። ጳጕ፭። ፍ፡ ነ፡ ፴፩)።

**ትራፍ፤**(ፋት)፤ ትራፌ፡ ትርፍ፡ ትርፍታ፤ ብልጫ፡ ላቂያ፤ ቅሬታ፡ ቅሬት። ትደኑ፡ ትራፋቲሆሙ፡ ለሕፃናቲሆሙ። ትራፋተ፡ ነገር፡ ነዋ፡ ጽሑፋን፡ እሙንቱ። ወናሁመ፡ ተበየነ፡ ውስተ፡ ቃላተ፡ እግዚእነ፡ ትራፈ፡ ገዳፍያን፡ መምለክያን። ትራፋተ፡ ነገሥት። ትራፋተ፡ ዐውድ፡(መዝ፡ ፲፯። ስር፡ ኢሳ፬፡ ፯። ፈልክ፡ ፫። አቡጥ፡ ፴፩። መር፡ ዕጣ)።

**ተረፍ፤**(ፋት)፤ ዝኒ፡ ከማሁ፡ ትራፊ፡ ትርፍ፡ ቅሬታ፤ መጨረሻ። ተረፈ፡ ቤተ፡ ይሁዳ። ዘርዖሙ፡ ወተረፎሙ። ዝንቱ፡ ኀሠሣ፡ ከመ፡ ተረፍ፡ ውእቱ። እምተረፈ፡ ልብ፡ ይነብብ፡ አፍ። ተረፈ፡ ነቢያት፡ ሱቱኤል። ተረፈ፡ ኤርምያስ። ተረፈ፡ ቄርሎስ፡(ሶፎ፪፡ ፯። ኢሳ፲፩፡ ፳፪። አፈ፡ ድ፳፬። ማቴ፲፪፡ ፴፬። ዮሐ፲፯። ስንክ፡ ሐም፯)።

**ተረፍ፤**(ዕብ፡ ማማእ)፤ ከውድ፡ ቃል፡ ትንቢት፡ ራእይ፤ በነቢያት፡ አፍ፡ የሚነገር፤ የሬተኛው፡ ነቢይ፡ ተናግሮለት፡ ከዚ.ያ፡ የቀረ፡ የተረፈ። ተረፈ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡(ሚልክ፡ ፩። ዕንባ፡ ፩፡ ፯)።

**አትረፈ፤** አተረፈ፤ አዳነ፡ አስቀረ፤ ተወ፤ አበዛ፤ ትርፍ፡ አገኘ። አትረፈ፡ ለነ፡ ዘርዐ። ወአትረፈ፡ በማዕተ፤ ነፍሳተ። እመ፡ ቦ፡ ዘሞተ፡ ወአትረፈ፡ ውሉደ። ወታተርፍዎ፡ ለዘሎሉ። እለ፡ ያተርፍዎ፡ ለእክል፡(ኢሳ፩፡ ፱። ቅዳ፡ ግሩ። ፍ፡ ነ፡ ፶፪። ፀቅሮ፡ ፬፡ ፰። ሉቃ፲፪፡ ፲፯)።

**መትርፍ፤** የሚያተርፍ፤ አትራፊ፤ አስቀሪ። ይክውኑ፡ መትርፋነ፡ ውሉደሙ፡(ኩፋ፡ ፲፩)።

**ተራፊን**፤ (**ጽር፡ ቴራፊን። ዕብ፡ ትራፊም**)፤ ጣዖታት፤ አብያተ፡ ጣዖት፤ ምስላተ፡ ጣዖት፤ የሰው፡ ምስሎች፡ አሻንጉሊቶች፤ የሟርት፡ መሣሪያ፤ ንዋያተ፡ ሰገል፤ የቀድሞ፡ ሰዎች፡ የሚያመልኩት፡ የሚያሟርቱበት፡ (መሳ፲፯፡ ፭። ፲፰፡ ፲፬። ፲፯፡ ፳። ፩ነገ፡ ፳፫፡ ፳፬። ፪ዜና፡ ፴፫፡ ፲፱። ሕዝ፳፩፡ ፳፩)።

**ትርሳ**፤ የባሕር፡ አውሬ፡ ዝርባው፡ ጋሻ፡ የሚመስል። ወለወልታኒ፡ ገብርዎ፡ እምነ፡ ትርሳ፡ ዘሀሎ፡ ውስተ፡ ባሕር፤ እስመ፡ ዘባኑ፡ ይመስል፡ ከመ፡ ወልታ፡ (ጊ፡ ወ፡ ሐ፡ ገ፳፫)።

**ተርሴስ**፤ (**ጽር፡ ቃርሲስ። ዕብ፡ ታርሺሽ**)፤ ስመ፡ ዕንቍ፡ የብርሌና፡ የመስታዮት፡ ዐይነት፤ እንደ፡ ውሃ፡ የሚያጥበረብር፡ (ማሕ፭፡ ፲፬። ዳን፲፡ ፮። ሕዝ፩፡ ፲፮)።

—፤ ስመ፡ ነገድ፤ ስመ፡ ሀገር፡ (ዘፍ፲፡ ፬። ዮናስ፡ ፫። ሕዝ፳፯፡ ፲፪)።

**ተስዖ**፤ **ዖት**፤ (**ተስዐ፡ ይቴስዕ፡ ይትስዕ። ዕብ፡ ታሼዕ**)፤ መዘጠን፤ ዘጠኝ፡ ማድረግ፤ ከዘጠኝ፡ መክፈል፤ ዘጠኝ፡ ማስት። ወይም፡ ዘጠኝ፡ መኾን፡ መባል፤ ከዘጠኝ፡ መክፈል።

**ተሳዒ**፤ **መተስዕ**፤ የሚዘጥን፡ ዘጠኝ፡ ዘጠኝ፡ ባይ፤ ከዘጠኝ፡ ከፋይ።

**ትሱዕ**፤ (**ዓን፡ ዓት፡ ስዕት**)፤ የዘጠነ፡ ዘጠኝ፡ የኾነ፤ የተባለ፤ የተከፈለ።

**ትሳዔ**፤ **ተሱዐት**፤ መዘጠን፤ ዘጠኝ፡ ማድረግ፤ ዘጠኝ፡ መኾን፤ አዘጣጠን፤ ዝጠና፡ ዘጠኝነት።

**ተስዑ**፤ የሴቶች፡ ድምር፤ (ጠ—፱) ዘጠኝ። ዐሥራ፡ ወተስዑ፡ አህጉር። ወጊዜ፡ ተስዑ፡ ሰዓት፡ (ኢያ፲፭፡ ፴፪፡ ፶፬፡ ፶፯። ፳፭፡ ፲፯። ማቴ፳፡ ፭። ፳፯፡ ፵፭)።

**ተስዐቱ፡ ት**፤ የወንዶች፡ ድምር፤ ዘጠኝ። ተስዐቱ፡ ቅዱሳን። ተስዐቱ፡ በዓላት። ተስዐቱ፡ እሙንቱ። ኅዲጎ፡ ተስዓ፡ ወተስዐተ፡ ነገደ፡ (ታሪ፡ ነገ። ድር፡ መድ። ሚ፡ሉ፳፭፡ ፯። ድጓ)።

**ተሱዕ**፤ **ተሱዓት**፤ ዝኒ፡ ከማሁ፤ ዘጠኝ፡ ዘጠንኛ። ሰላም፡ እብል፡ ዕደወ፡ ተሱዐ፤ ወአምኃቲሁ፡ ሠላሳ፡ ወሰብዓ። አመ፡ ተሱዑ፡ ለጽልመት። ሠርክ፡ ወሌሊተ፡ ወጊዜ፡ ተሱዓት፡ ሰዓት፡ (ስንክ፡ ሚያዝ፳። ሐጌ፩፡ ፩። ሥር፡ ጳጕ። ማቴ፳፯፡ ፵፯። ግብ፫፡ ፩)።

**ትስዕ**፤ የልክ፡ የጊዜ፡ ቅጽል፤ ዘጠኝ። ትስዐ፡ በእመት፡ ኑኃ። ሰፈረ፡ ትስዐ፡ በበ፡ ትስዐ፡ ወበበ፡ ዐሥር፡ (ዘዳ፫፡ ፲፩። ዘሬፋ)።

**ታስዕ**፤ (**ዕት፡ ዓን፡ ዓት**)፤ ዘጠኝኛ፤ ከዘጠኝ፡ አንድ። በታስዐ፡ ዓመት። አመ፡ ዐሡሩ፡ ወረቡዑ፡ ለታስዐ፡ ወርኅ። ወበታስዐት፡ ዕለት፡ (ሕዝ፳፬፡ ፩። ሐጌ፪፡ ፲። ዘኍ፯፡ ፷)።

**ታስዓዊ፡ ይ**፤ (**ዊት፡ ዒት**)፤ ዝኒ፡ ከማሁ፤ ዘጠኝኛ፤ ዘጠኝኛው፤ ከዘጠኝ፡ አንዱ።

**ተስዓ**፤ ዘጠና፤ (ጸ—፺) ዘጠኝ፡ ጊዜ፡ ዐሥር፤ ወይም፡ ዐሥር፡ ጊዜ፡ ዘጠኝ። ተስዓ፡ ዓም፡ ሳኒ። ወዔሊበ፡ ወልደ፡ ተስዓ፡ ዓም። ሠለስቱ፡ ምእት፡ ወተስዓ፡ ዕለት። ተስዓ፡ ወተስዐቱ፡ (ዘፍ፲፯፡ ፲፯፡ ፳፬። ፩ነገ፡ ፬፡ ፲፭። ሕዝ፬፡ ፭። ማቴ፲፰፡ ፲፪፡ ፲፫)።

**ተስፋ**፤—**በቁሙ**፤—**ሰፍዎ፡ ሰፈወ፡ ተሰፈወ**።

**ታስሬ**፤ **ታስሬን**፤ (**ዕብ፡ ታሽሬ። ሱር፡ ቴሽሬን**)፤ ስመ፡ ወርኅ፡ ዕርያዊ፤ ጥቅምትና፡ ኅዳር። እሊህ፡ ኹለቱ፤ ታስሬን፡ ቀዳማይ፡ ታስሬን፡ ደኃራይ፡ ይባላሉ። ወበወርኀ፡ ታስሬ፡ (ዮሴፍ)።

**ቲቶ**፤ ተውት፤ ስመ፡ ወርኅ፤ መስከረም። ተውትን፡ ተመልከት፤ ከዚህ፡ ጋራ፡ አንድ፡ ነው። ሠርቀ፡ ቲቶ፤ የመስከረም፡ መባቻ፡ (መር፡ ስዉ)።

**ቲቶ**፤ የሰው፡ ስም፤ የጳውሎስ፡ ረድ፡ (ገላ፪፡ ፩)።

**ቶታን**፤—**በቁሙ**፤—**ተወተ**።

**ቶጳዝዮን**፤ (**ጽር፡ ቶፓዚዮን። ዕብ፡ ፊ፡ ፐጥዳ**)፤ ዕንቍ፤ የዕንቍ፡ ስም፤ ብጫቱ። ቶንከራን፡ ተመልከት፤ ከዚህ፡ ጋራ፡ አንድ፡ ነው፡ (ዘፀ፳፰፡ ፲፯)።

# ጰ

**ጰ** ፤ ትርናፍ ፡ ጺ.ቃላ ፡ ፊደል ፤ በመልክ ፡ በተራ ፡ ፳፭ኛ ፤ መልኩ ፡ ከጸ ፡ ድምፁ ፡ ከበ ፡ የተደ.ቀለ ፤ በመ ጊት ፡ ጳይት ፤ ይኸውም ፡ ቤት ፡ በይት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ቍጥሩ ፡ ፺፻ ፤ አኃዝ ፡ ሲኾን ፡ ጰ ፡ በብዐቱ ፡ ምእት ፡ ይባላል ፤ ያቡጊዳን ፡ አኃዝ ፡ ተመልከት ። የኋላ ፡ ሰዎች ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነቍጣ ፡ ጨምረው ፡ ጸን ፡ ጰ ፡ ብለውታል ፤ ከግእዝ ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ በሳባ ፡ ፊደል ፡ ግን ፡ ዲ.ቃል ነቱና ፡ ድርብነቱ ፡ በመልክም ፡ በድምፅም ፡ የበ ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ የቀድሞ ፡ ቅርጹ ፡ አሠራረዙ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ፀንና ፡ የፀጸ ፡ ፀን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። ጳና ፡ ፐ ፡ ምንም ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ቢኾኑ ፡ በምስጢር ፡ አንድ ፡ ጎርመት ፡ ናቸው ፤ ጰ ፡ ሲላላ ፡ ፐ ፤ ፐ ፡ ሲጠብቅ ፡ ደግሞ ፡ ጰ ፡ ይባል ፡ ነበረ ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ ሲታወቅ ፡ በ ጳና ፡ በፐ ፡ የሚጣፍ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፤ በጽርእና ፡ በቅብጥ ፡ በሮማይስጥ ፡ በዕብራይስጥም ፡ ፐ ፡ ኹኖ ፡ ይገኛል ። ጳና ፡ ፐ ፡ ለግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ በውድ ፡ እንጂ ፡ በግድ ፡ አ ይፈለጉም ፤ እንሆ ፡ ዐረቦች ፡ ጴጥሮስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጲላ ጦስ ፤ ወይም ፡ ፔትሮስ ፡ ፓውሎስ ፡ ፒላቶስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ቡጥሩስ ፡ ቡሉስ ፡ ቢላጦስ ፡ ይላሉና ፤ ዕብራውያ ንም ፡ ፌጥሮስ ፡ ፎሉስ ፡ ፊላጦስ ፡ ይላሉና ፤ ለግእዝም ፡ በጳና ፡ በፐ ፡ ፈንታ ፡ በ ፤ ወይም ፡ ፈ ፡ ይበቃው ፡ ነበር ። ከጽርእና ፡ ከቅብጥ ፡ ከሮማይስጥ ፡ ቃል ፡ የመጣ ፡ የ ውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ያልተተረጐመ ፡ ፍጹም ፡ ጥሬና ፡ ንባር ፡ ስም ፤ ወይም ፡ ጋላና ፡ ወላሞ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ለግእዝና ፡ ላማርኛ ፡ ለትግሬም ፡ ለትግሪኛም ፡ ቢኾን ፡ ጳንና ፡ ፐን ፡ የሚያስፈልግ ፡ ቃል ፡ የለም ፤ አይገኝም ። ከጥንት ፡ የነበረ ፡ የግእዝ ፡ ፊደል ፡ አለመኾኑ ፤ የኋላ ፡ ቅጥል ፡ መኾኑ ፡ ዲ.ቃልነቱ ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ። ጰ ፡ በ ጋልኛ ፡ ተርጓል ፤ ፐም ፡ በወላምኛ ፡ ይገኛል ፤ ጋልኛ ፡ ግን ፡ ሴማዊና ፡ ሳባዊ ፡ ይመስላል ።

**ጳጕሜን** ፤ (ጽር ፡ ሄፓጎሜኔ) ፤ በቁሙ ፤ ቋግሜ ፤ ጭማሪ ፡ ተውሳክ ፤ ፭ ፡ ቀን ፡ ታሩብ ። ኹለተ ኛም ፡ ከፀውደ ፡ ወርኅ ፡ ስለ ፡ ተረፈና ፡ ባመት ፡ መጨ ረሻ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ተረፍ ፡ ይባላል ። ሩቡ ፡ ደግሞ ፡ ባራ ተኛ ፡ ዓመት ፡ ይመላና ፡ ፮ ፡ የነበረው ፡ ፯ ፡ ይባላል ፤ ይ ህም ፡ ስድስተኛ ፡ ጳግሜ ፡ አራቱ ፡ ወንጌላውያን ፡ በሰዓ ትና ፡ በኬክሮስ ፡ ካራት ፡ አድርገው ፡ ስለ ፡ ተካፈሉት ፤ እንዳምስተኛው ፡ ከአበቅቴ ፡ ገብቶ ፡ አይቈጠርም ። ስድ ስተኛነቱም ፡ ላለፈው ፡ ለሉቃስ ፡ ጳግሜ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለሚመጣው ፡ ለዮሐንስ ፡ ጳግሜ ፡ አ ይደለምና ፤ ዮሐንስም ፡ በመስከረም ፡ አንድ ፡ ባተ ፡ እ ንጂ ፡ በጳግሜ ፡ አልባተምና ፤ በዮሐንስ ፡ ዘመን ፡ በዓለ ፡ ልደትን ፡ በጳግሜ ፡ ምክንያት ፡ ማፋለስ ፡ ታላቅ ፡ ስሕ ተት ፡ ነው ። ይህም ፡ ስሕተት ፡ የተዠመረ ፡ ባዒ ፡ ፀምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ ነው ። ማውረድና ፡ ማፋለስ ፡ ከኾነም ፡ በልደት ፡ ብቻ ፡ ምን ፡ መጥቷል ፤ ኹሉንም ፡ ከመት ፡ እስከመት ፡ መናድ ፡ ያስፈልጋል ፤ ትንሣኤም ፡ ቀዳሚ ፡ ይውላል ።

**ጳዴሬ** ፤ (ጽር ፡ ፖዲሬስ) ፤ የላይ ፡ ልብስ ፤ ጥሩ ፡ ክቡር ፡ በርኖስ ፤ ጀባ ፡ ካባ ፡ መጐናጠፊያ ፤ ነገሥ ታት ፡ ካህናት ፡ የሚለብሱት ። ልብሰ ፡ እንግድዓ ፤ የደ ረት ፡ ልብስ ፡ ሳንቃ ፤ ከአልባሰ ፡ ክህነት ፡ አንዱ ። **ዘይ ለብስ ፡ ጳዴረ ። ልብሰ ፡ ጳዴር** ፡ (ሕዝ፱ ፡ ፪ ። ሚራ ጅ፮ ፡ ፰ ። ራእ፩ ፡ ፲፫ ። ዘፀ፳፰ ፡ ፬) ።

**ጳውሎስ** ፤ (ጽር ፡ ፓፍሎስ ። ሮማይ ፡ ፓውሉስ) ፤ ንኡስ ፤ ትንሽ ።

**ጳውቄና** ፤ (ጽር ፡ ፔፍኪ.ና) ፤ ዕንጨት ፤ ሎሕ ፡ ጠርብ ፡ የሚኾን ፤ የሚታንጥ ፡ የሚቀረጥ ፤ እንደ ፡ ጥድ ፡ እንደ ፡ ዘግባ ፡ ያለ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ለይተው ፡ ጥድ ፡ ኰሓ ፡ ይሉታል ፡ (፪ነገ ፡ ፭ ፡ ፲ ። ፮ ፡ ፲፭ ፡ ፴ ። ፱ ፡ ፲፩ ። ፪ዜና ፡ ፪ ፡ ፰) ።

**ጳዝዮን** ፤ (ጽር ፡ ቶፓዚዎን) ፤ ብሩሕ ፡ ዕንቍ ፤ ወራውሬ ፡ (ዘፀ፳፰ ፡ ፲፯ ። ፴፯ ፡ ፲፯ ። ሕዝ፳፰ ፡ ፲፫) ። በወራውሬ ፡ ፈንታ ፡ ጳዝዮን ፡ በጳዝዮን ፡ ፈንታ ፡ ወራውሬ ፡ ይላል ፡ (ራእ፳፩ ፡ ፳) ።

**ጳዝዮን** ፤ (ዕብ ፡ ፓዝ ። ጽር ፡ ቶፓዚ ዮን) ፤ ፋዝ ፤ የአፌዝ ፡ ወርቅ ፤ ጥሩ ፡ ወርቅ ። ፎዘን ፡ ተ መልከት ። **እምወርቅ ፡ ወእምጳዝዮን** ፡ (መዝ ፡ ፻፲፰) ።

**ጳሒን** ፤ (ቅብጥ ፡ ፓዖኒ) ፤ ስመ ፡ ወርኅ ፤ ሠኔ ። በኢ.ናህን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ስ ንክ ፡ ሠኔ፲፱) ። ዳግመኛም ፡ በጳሒን ፡ ፈንታ ፡ ጵዮን ፡ ይላል ፤ ፍችው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ጳጦስ** ፤ (ጽር ፡ ባቶስ) ፤ ባጦስ ፤ የሾክ ፡ ቍ ጥቋጦ ፤ ሐመልማል ። ባጦስንና ፡ ሳቤቅን ፡ ተመልከት ። **በኀበ ፡ ዕፀ ፡ ጳጦስ** ፡ (ሉቃ ፡ ዕዝ፱ ፡ ፫ ። ማር፲፪ ፡ ፳፮ ። ግብ፯ ፡ ፴፭ ። ዲድ ፡ ፴፯ ። ድጓ) ።

**ጴጥያስ** ፤ ጲ.ጦን ፤ (ጽር ፡ ፒቲስ ፤ ፒቲ ዩስ) ፤ ጥሩ ፡ የተከለ ፡ ዕንጨት ፡ ዛፍ ፤ ምዑዝ ፡ ገናና ። ጤጤንን ፡ ተመልከት ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። **ዕፀ ፡ ጴጥ ያስ** ፡ (ሕዝ፴፩ ፡ ፰ ። ኩፋ ፡ ፳፩) ።

**ጴጥራ** ፤ (ጽር ፡ ፔትራ) ፤ ኰኵሕ ፤ ንጥፍ ፡ ደንጊያ ፤ ጭንጫ ።

**ጴጥሮስ** ፤ (ጽር ፡ ፔትሮስ) ፤ ኰኵሓዊ ፤ ዘኰኵሕ ፤ ብእሲ ፡ ኰኵሕ ። የግእዝ ፡ መላሽ ፡ ግን ፡ በጴ ጥሮስ ፡ ፈንታ ፡ ኰኵሓዊ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኰኵሕ ፡ ይ

ላል ፤ የተሳሳተ ፡ ነው ፤ አያሰኝም ። ጴጥሬና ፡ ጴጥሮስ ፡ ልዩ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ኵሎሓዊና ፡ ኵሎሕም ፡ ልዩ ፡ ናቸው ። ወኵሎሙሰ ፡ ክርስቶስ ፡ ሃይማኖቶ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘተብህለ ፡ በአፉ ፡ ጴጥሮስ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፤ እስመ ፡ ይቤ ፡ ወዲበ ፡ ዛቲ ፡ ኵሎሙ ፡ አሐንዳ ፡ ሰቤተ ፡ ክርስቲያንየ ፤ ከመ ፡ ዘይቤ ፡ ወዲበ ፡ ዛቲ ፡ ሃይማኖትከ ፡ (ትር ፡ ወን ። ማቴ ፲፮ ፡ ፲፰ ። ፩ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲—፲፫ ። ፲ ፡ ፬) ።

**ጵዮን ፤—ሡኔ ፤—ጷሒን ።**

**ጳይት ፤ ጴት ፤** ስመ ፡ ፊደል ፡ ጸ ። በዩት ፡ ቤት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ጳና ፡ በ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ጳንጠቆስቴ ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ ብለውም ፡ የሚፈቱ ፡ አሉ ።

**ጳኵምስ ፤ (ቀብጥ ፡ ፓኾን ፤ ፓሾንስ) ፤** ስመ ፡ ወርኅ ፤ ማንቦት ፡ (ስንክ ፡ ሠኔ፲፱) ።

**ጳኵሚስ ፤ (ቀብጥ ፡ ፓኹም) ፤** ስመ ፡ ስብእ ፤ ዐቢይ ፡ መነኮስ ፤ የእንጦንስ ፡ ሦስተኛ ፤ እንጦንስ ፡ መቃርስንና ፡ ጳላሞንን ፤ ጳላሞን ፡ ጳኵሚስን ፤ ጳኵሚስ ፡ ቴዎድሮስን ፤ ቴዎድሮስ ፡ አረጋዊ ፡ ዘደብረ ፡ ዳሞን ፡ ይወልዳል ። ጳኵሚስ ፡ ፵ ፡ ዘመን ፡ ምሉ ፡ አበ ፡ ማኅበር ፡ ኹኖ ፡ የኖረ ፡ ነው ። ራእይ ፡ ዘአባ ፡ ጳኵሚስ ። ሥርዐተ ፡ ጳኵሚስ ።

**ጳኵሲማ ፤ (ጽር ፡ ፓክሳማስ ። ዕብ ፡ ፓክሳም) ፤** ደረቅ ፡ ዳቦ ፤ ኰርንኰራት ፤ የለከት ፡ የብስኩት ፡ ዐይነት ፤ እንዳይነቅዝና ፡ እንዳይሻግት ፡ ታምሶ ፡ ተጠብሶ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ የሚኖር ፡ የመነኮሳት ፡ ምግብ ። ክልኤቱ ፡ አእናግ ፡ ዐይጠ ፡ ፊሰገ ፡ ወነበሩ ፡ ይብልዑ ፤ ወጠምዐ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ጳኵሲማሁ ፤ ወይቤሎ ፡ ካልኡ ፡ በምንት ፡ ታርሕሳ ፡ ወታስተፌሥሖ ፡ ለልብከ ። በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ይበልዕ ፡ አሐደ ፡ ጳኵሲማ ። ወይትሜጦ ፡ አሐደ ፡ ጳኵሲማ ፡ እምኅብስት ፡ ወሐምል ፡ (ፊልክ ፡ ፸፰ ። ስንክ ፡ ታኅ፲፰ ። ፲፯) ።

**ጲክሶን ፤ (ጽር ፡ ፒክሶስ) ፤** እሾኽም ፡ ዛፍ ፤ ግራር ፤ የግራር ፡ ዐይነት ። ስጢንን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ብሔረ ፡ አርዝ ፡ ወዕፀ ፡ ጲቅሶን ፡ (ኢሳ፷፩ ፡ ፲፱) ።

**ጳላጢኖስ ፤ (ጽር ፡ ፕላታኖስ) ፤** የዛፍ ፡ ስም ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ፤ ታላቅ ፡ ገናና ፡ እንደ ፡ ዋርካና ፡ እንደ ፡ ዘግባ ፡ ያለ ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ሰይተው ፡ ዥላ ፡ ብሳና ፡ ለውዝ ፡ ገውዝ ፡ ይሉታል ። ዋዔኩ ፡ ከመ ፡ በቀልት ፤ ወዐበይኩ ፡ ከመ ፡ ጳላጢኖስ ፡ (ሢራ፳፬ ፡ ፲፬) ።

**ጲላጦስ ፤** ስመ ፡ ስብእ ።

**ጳላሞን ፤** ስመ ፡ ስብእ ።

**ጵልንትዩ ፤ (ጽር ፡ ፕሊንቲዩ ። ዕብ ፡ ማልኬን) ፤** የጣዖት ፡ በታ ፤ ምሥዋዕ ፡ ጣዖት ፤ ደቂቀ ፡ እሞን ፡ ሞሎኽ ፡ ለሚባል ፡ ጣዖት ፡ ልጆቻቸውን ፡ የሚጠብሱበት ፡ የሚያቃጥሉበት ፤ የሞሎኽን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። ባለብሉዮች ፡ ግን ፡ ግዞት ፡ የግዞት ፡ ቤት ፡ ይሉታል ፡ (፪ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፴፩) ።

**ጳልቃን ፤ (ጽር ፡ ፔሌካን) ፤** ርኩም ። ቀቀናን ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። መምህራን ፡ ግን ፡ የከራድዮንን ፡ ለጳልቃን ፡ ሰጥተው ፡ ይፈታሉ ። ከራድዮንን ፡ እይ ።

**ጳሊስ ፤ (ጽር ፡ ፖሊስ) ፤** መዲና ፤ ታላቅ ፡ ከተማ ። ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ስምዖን ፡ ዘእስክንድርያ ፡ ጳሊስ ፡ (ስንክ ፡ ሐም፳፯) ።

**ጳንገለ ፤ (ጽር ፡ አፓንጌሊን ፤ ገንጸለ) ፤** ቀዳ ፤ መለሰ ፤ ተረጐመ ፤ ገለበጠ ፤ ጣፈ ። አነበበ ፤ አየ ፡ አስተዋለ ፤ ተመለከተ ፤ የመጽሐፍ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጳንገለ ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ ጽርኡ ፡ አጳንገለ ፡ ይላል ፤ አያሰኝም ። ዘየጳነግል ፡ መጻሕፍተ ፡ እግዚ ፡ ዘብሉይ ፡ ወዘሐዲስ ። ይደልዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ የኄሊ ፡ ተኃሥሦ ፡ ወአጳንግሎ ፡ መጻሕፍት ፡ በበ ፡ መትልው ። ፈከረ ፡ ሐዲስ ፡ ወአጳንገለ ፡ ብሉየ ። አጳንገለ ፡ ሎሙ ፡ መጻሕፍተ ፡ በነገረ ፡ ብሔሮሙ ፤ መለሰ ፡ (ቀሌ ። ዲድ ፡ ፬ ። ስንክ ፡ ኅዳ፳ ። አዋል) ። ያጳንግሉ ፡ መጻሕፍተ ። ውስተ ፡ ጳሎታቲሆሙ ፡ ወአጳንግሎቶሙ ። ይደሉ ፡ ለውጡናን ፡ ከመ ፡ ያብዝኁ ፡ አጳንግሎ ፡ ውስተ ፡ ትእዛዛት ፡ ወውስተ ፡ ትሩፋት ፤ ተመለከተ ፡ (ሥር ፡ ጳኰ ። ፊልክ ፡ ፸፫ ። ፻፵፯) ።

**ጳንገለ ፤ (ፈንገለ) ፤** ፈነገለ ፤ ፈንጋይ ፡ ኾነ ። ግንጸለን ፡ እይ ።

**ጳንጋሊ ፤ መጳንግል ፤** የሚቀዳ ፡ የሚመልስ ፤ አንባቢ ፡ ተመልካች ። መጳንግል ፡ ዘይቤ ፡ ተርጓሚ ፡ ወአንባቤ ፡ መጽሐፍ ፡ በቃል ፡ (ጥሬ ፡ ስዋ) ።

**አጳንገለ ፤** (አስደራጊ) ፤ አስቀዳ ፡ አስመለሰ ፡ አስተረጐመ ፤ አሳየ ፡ አስነበበ ፤ አስመለከተ ።

**ጵንጋሌ ፤** መቅዳት ፡ መገልበጥ ፤ አገለባበጥ ፤ ግልበጣ ፡ ምለሳ ፤ ንባብ ፡ ምልከታ ።

**ጳንጤን ፤ ጳንጦስ ፤ (ጽር ፡ ፖንቶን) ፤** ስመ ፡ ሀገር ፤ በእስያ ፡ ውስጥ ፡ ያለች ፡ (ግቤሐ፳፮ ፡ ፪ ። ፩ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፩) ።

**ጳንጠቆስጤ ፤ ቴ ፤ (ጽር ፡ ፔንቲኮስቲ) ፤** በዓለ ፡ ኀምሳ ፤ የፋሲካ ፡ ዐምሳኛ ፤ በዓለ ፡ ሠዊት ፤ ጳራቅሊጦስ ። በዓለ ፡ ጳንጠቆስጤ ፡ ቅድስት ። መዋዕለ ፡ ጳንጠቆስጤ ። በላም ፡ ለድሜጥሮስ ፡ ሐጋጊ ፡ አጽዋም ፡ እምስቴ ፤ ወሠራዒ ፡ መብልዐ ፡ በጳንጠቆስቴ ፡ (ጦቢ፪ ፡ ፩ ። ግብ፪ ፡ ፩ ። ፳ ፡ ፲፮ ። ስንክ ፡ ጥቅ፲፪) ።

**ጵኒኖ ፤ (ጽር ፡ ፒኒኑ ። ዕብ ፡ ፍኒኒም) ፤** ዕንቍ ፤ የዕንቍ ፡ ስም ፤ ሰደፍ ፡ ወይም ፡ ሉላ ፡ (እዮቤ፳ ፡ ፲፰) ።

**ጵርድክይሴ ፤ (ጽር ፡ ፔርዲክስ) ፤** ድርንቅ ፡ የበሐር ፡ ቆቅ ፤ ወይም ፡ ዕረኝ ፡ (ገድ ፡ ባሊ) ።

**ጵርዮን ፤ ኒ ፡ ዮኖስ ፤ (ጽር ፡ ፕሪዮን) ፤** የሰው ፡ ወጥመድ ፤ መጋዝ ፤ ጥርሳም ፡ ብረት ፤ መኪና ፡

የሚቈርጥ ፡ የሚበጣጥስ ። አንበሮሙ ፡ ውስተ ፡ ጵርዮን ፡ (፪ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፴፩ ። ዮዲ፫ ፡ ፱) ።

**ጳራልያ** ፤ (ጽር ፡ ፓራሊዮስ) ፤ የባሕር ፡ ዳር ፤ ጽንፍ ፡ ጠረፍ ፤ ወደብ ፡ ገደብ ፤ አጠገብ ፡ ጎረ ፡ ቤት ። ጳራልያ ፡ ዘምድረ ፡ ከነዓን ። ሰብአ ፡ ጳራልያ ፡ (ዘዳ፩ ፡ ፯ ። ኢያ፲፩ ፡ ፫ ። ሕዝ፳፭ ፡ ፲፮) ።

**ጳሬኑ** ፤ (ጽር ፡ ፓሬኑ) ፤ ጥሩ ፡ ደንጊያ ፤ ፍጹም ፡ ነጭ ፤ የእብነ ፡ በረድ ፡ ዐይነት ። ዕንቍ ፤ የዕንቍ ፡ ስም ።

**ጵርንሰ** ፤ (ጽር ፡ ፓሪኒስ) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ዕንቍ ፡ (አስቴ፩ ፡ ፮) ።

**ጵርፍርዮና** ፤ (ጽር ፡ ፖርፊሪዮና) ፤ የባሕር ፡ ዶሮ ፤ የማይበላ ፡ (ዘዳ፲፬ ፡ ፲፰) ።

**ጳራቅሊጦስ** ፤ (ጽር ፡ ፓራክሊቶስ ። ዕብ ፡ ፕራቅሊጥ) ፤ አማላጅ ፡ አስታራቂ ፤ አፍ ፡ ጠበቃ ፤ ትርጁማን ፡ አምጃር ፤ እያጣፈጠ ፡ የሚናገር ፤ ስብ ቃል ፡ ከፋ ፡ ማር ፡ ጡብ ፡ የሚል ። ወእመኒ ፡ ቦ ፡ ዘአበሰ ፡ ብነ ፡ ኀበ ፡ አብ ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጻድቅ ። ወአሩየ ፡ ሙሴ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ጸደፈ ፤ ጳራቅሊጦስ ፡ አሮን ፡ ይኩነኒ ፡ አፈ ፡ (፩ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፩ ። ድራሲ) ።

—፤ ናዝዚ ፡ መጽንዒ ፤ መስተፍሥሒ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። በዓለ ፡ ኀምሳ ፤ የትንሣኤ ፡ ፃምሳኛ ፡ የዕርገት ፡ ዐሥረኛ ፤ እሑድ ፡ ቀን ፡ የሚውል ። እስእሎ ፡ ለአብ ፡ ይፈኑ ፡ ለክሙ ፡ ጳራቅሊጦስሀ ፡ ካልአ ። ወቡሩክ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ መጽንዒ ፡ ሥልነ ። ዕለተ ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ ዘውእቱ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ኀምሳ ፡ (ዮሐ፲፬ ፡ ፲፮ ። ቅዳ ። አቡሻ ፡ ፴፰) ።

**ጵርስፎራ** ፤ (ጽር ፡ ፕሮስፎራ) ፤ መባእ ፡ ኅብስት ፤ ሰንበቴ ፡ እንደ ፡ ዘቲና ፡ እንደ ፡ ተስፋ ፡ ያለ ፤ ወይም ፡ ኅብስተ ፡ አኰቴት ፤ ምእመናን ፡ የሚያቀርቡት ፡ ቍርባን ። ጵርስፎራ ፡ ዘሰንበት ። ወያብእ ፡ አርባዕተ ፡ ጵርስፎራ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወሠለስተ ፡ በካልኣን ፡ ዕለታት ፡ (ኪዳ ። ሥር ፡ ቅዳ) ።

**ጵርጵማ** ፤ (ጽርእ) ፤ ስሙ ፡ ብእሲት ፤ መበለት ፤ ኤልያስን ፡ ያስተናገደች ፡ (ሉቃ፬ ፡ ፳፮) ። ይህ ፡ ስም ፡ የተገኘ ፡ ከንኮበሮች ፡ መምህር ፡ ከየኔታ ፡ ወልደ ፡ ሥሉስ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ርሳቸው ፡ ከመምህራቸው ፡ አፍ ፡ ወይም ፡ ከአዋልድ ፡ መጽሐፍ ፡ አግኝተው ፡ እንዲህ ፡ ይሉ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

**ጵሩጳጣ** ፤ (ጽር ፡ ፕሮባታ) ፤ አባግዕ ፤ በጎች ፤ የበግ ፡ መንጎች ።

**ጵሩጳጥቂ** ፤ (ጽር ፡ ፕሮባቲኪ) ፤ አባግዒ ፤ ዘአባግዕ ፤ የበጎች ። አንቀጸ ፡ ጵሩጳጥቂ ፡ (ነሐ፫ ፡ ፩ ። ዮሐ፭ ፡ ፪) ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ ዘብዙኃን ፡ ዘፈውስ ፡ ዘበዓል ፡ ይሉታል ።

**ጳስጦፎርያ** ፤ (ጽር ፡ ፓስቶፎርዮን) ፤ የዕቃ ፡ ቤት ፤ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ (ኤር፴፭ ፡ ፬) ።

**ጵስጥቂስ** ፤ (ጽር ፡ ፒስቲኪስ) ፤ ጥሩ ፡ ሽቱ ፤ ውድ ፡ ክቡር ፡ (ዮሐ፲፪ ፡ ፫) ።

**ጳሲካ** ፤ (ጽር ፡ ፓስኻ) ፤ ፍሥሕ ፤ ፋሲካ ። ወይገብሩ ፡ ጳሲካ ፡ (ኩፋ ፡ ፵፱ ። ፶) ።

**ጳጲራ** ፤—ፓፒራ ።

**ጳጳስ** ፤ (ሳት ። ጽር ፡ ፓፓስ) ፤ ቄስ ፤ ቆሞስ ፤ ዐርክ ፡ ኤጲስቆጶስ ። ሢመተ ፡ እዴሆሙ ፡ ለጳጳሳት ፡ (፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፬) ። ቄሱ ፡ ጳጳስ ፡ እንዲባል ፡ ጳጳሱ ፡ ደግሞ ፡ ቄስ ፡ ይባላል ፡ (፪ዮሐ ፡ ፩ ። ፊልጵ፩ ፡ ፩) ።

—፤ ኤጲስቆጶስ ፤ ሠያሚ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ። ዘይፈቅድ ፡ ይሠየም ፡ ጳጳሰ ፡ (፩ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፩ ። ቲቶ ፩ ፡ ፯ ። ግብ፳ ፡ ፳፰ ። ኪዳ) ። ክልኤቱ ፡ ምእት ፡ ጳጳሳት ፡ (ስንክ ፡ መስ፲፪) ።

—፤ በቁሙ ፤ ጳጳስ ፤ መጥሮጶሊስ ፤ የኤጲስቆጶሳት ፡ አለቃ ፤ ሺማ ፤ አዛዥ ። ወለእመ ፡ ሢመ ፡ ጳጳስ ፡ አሐደ ፡ ኤጲስቆጶሰ ፡ እምኤጲስቆጶሳት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፬) ።

**ሊቀ ፡ ጳጳስ** ፤ በቁሙ ፤ በትረ ፡ ያሬክ ፤ የጳጳሳትና ፡ የኤጲስቆጶሳት ፡ አለቃ ፤ ደምሳሽ ። እሊህም ፡ ሦስቱ ፡ ሊቃናት ፤ ራስና ፡ ንጉሥ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ናቸው ። ወይርአይ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ወትእዛዝ ፡ ዘይገብርዎ ፡ ጳጳሳቲሁ ፡ ወኤጲስቆጶሳቲሁ ፡ ውስተ ፡ በሓውርቲሆሙ ፡ ዘተሠይሙ ፡ ባዕሌሆን ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፬) ።

**አጳጰሰ** ፤ ጳጳስ ፡ አደረገ ፤ ጵጵስና ፡ ሾመ ፤ ጳጳስ ፡ አለ ፤ ጳጳስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አሰኘ ። ብውሕ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ያጳጵስ ፡ ጳጳሳተ ፡ በከመ ፡ ያጳጵሱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፬) ።

**አጳጳሲ** ፤ **መጳጵስ** ፤ የሚያጳጵስ ፤ አጳጳሽ ፤ ጳጳስ ፡ ሺማ ፤ ሊቀ ፡ ጳጳስ ።

**ተጳጰሰ** ፤ በቁሙ ፤ ጳጳስ ፡ ኾነ ፤ ተሾመ ፤ ጳጳስ ፡ ተባለ ። ሰላም ፡ ለጳውሎስ ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ዘተጳጰሰ ። እስከ ፡ ተኀርየ ፡ ለተጳጵሶ ፡ (ስንክ ፡ ግንቦ፳፮) ።

**ጵጱስ** ፤ (ሳን) ፤ የጳጳሰ ፤ የተጳጳሰ ፤ ጳጳስ ፡ የኾነ ፤ የተሾመ ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ጵጳሴ** ፤ መጳጳስ ፤ አጳጳጳስ ፤ ጳጳስ ፡ መኾን ፤ ጵጳሳ ፡ ጳጳስነት ። ሢመተ ፡ ጵጳሴ ፡ (ስንክ ፡ መስ፱) ።

**ጵጵስና** ፤ ጳጳስነት ፤ ክዊን ፡ ጳጳስ ፤ የጳጳስ ፡ ማዕርግ ። ወሶበ ፡ ተሠይመ ፡ ጵጵስና ፡ ዝንቱ ፡ ዘዝኩር ፡ በስመ ፡ ሊቃናት ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ ፬) ።

# ፐ

**ፐ** ፤ የጽ ፡ ኹለተኛ ፤ ትርፍ ፡ ዲቃላ ፤ ጽርእዊ ፡ ፊደል ፤ በመልክ ፡ በተራ ፡ ፳፯ኛ ፤ የፈ ፡ ድርብ ፤ ስሙ ፡ ፒ ፤ ፔ ፤ ይኸውም ፡ ፊ ፡ ፌ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ከፈ ፡ ቀጥሎ ፡ መጻ ፉም ፡ የፈ ፡ ድርብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። ፐ ፡ መባሉ ፡ በግ እዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በጽርእና ፡ በቅብጥ ፡ በላቲን ፡ ታው ፡ ቱ ፡ ይባላል ፤ መጨረሻ ፡ ፊደል ፡ መኾኑም ፡ ተ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ጳን ፡ ጳንጠቆስቴና ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ ብለ ው ፡ የሚፈቱ ፡ ግን ፡ ይህንንም ፡ ፓኖስ ፡ ፑኔፍማቶስ ፡ ይሉ ታል ፤ ፋኖስ ፡ መንፈስ ፡ ማለት ፡ ነው ። ስማንያ ፡ የምን ለው ፡ እጕዝ ፡ (፹) ፡ በጽርእና ፡ በቅብጥ ፡ ፐ ፡ ይባላል ፤ ፈ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዕብራውያንም ፡ ነጥብ ፡ እየጨመሩ ፡ ፈን ፡ ፐ ፡ ይሉታል ። ፐ ፡ ድርብነቱ ፡ የፈ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ስምንትነትን ፡ ሳይለቅ ፡ የስምንት ፡ መቶ ፡ እጕዝ ፡ ይኾ ናል ፤ ይህም ፡ ጸ ፡ ፯፻ ፤ ፐ ፡ ፰፻ ፤ ኀ ፡ ፱፻ ፤ ቈ ፡ ፲፻ ፤ እ ፡ እልፍ ፡ እያለ ፡ መኼዱን ፡ ያሳያል ፤ ያቡጊዳን ፡ እ ጕዝ ፡ ተመልከት ። በዕብራይስጥም ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ፈ ፡ አለ ፡ አባትና ፡ ልጅ ፤ አባቱ ፡ ፹ ፤ ልጁ ፡ ፰፻ ፡ ይባላል ።

**ፔክ ፤ (ዕብ ፡ ፑኽ ፤ ኰል ፤ ክቡር ፡ ደንጊያ)** ፤ ነጭ ፡ ደንጊያ ፤ እብነ ፡ በረድ ። ማርደም ፡ ድንግል ፡ መንበር ፡ ዘእብነ ፡ ፔክ ፡ (ደራሲ ። ሔኖ ፲፰ ፡ ፰) ።

**ፒላስ ፡ ሳ ፤ (ጽርእ)** ፤ ደጅ ፡ አፍ ፡ በር ፤ አ ጐበር ። የፊላስን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አ ንድ ፡ ነው ። ማርደም ፡ ፒላሰ ፡ መለኮት ። ይጠባሕ ፡ መርዓዊ ፡ ለምሳሐ ፡ መሀይምናን ፡ በውስተ ፡ ፒላ ሳሃ ፡ ለመርዓት ። አብአቶኪ ፡ ውስተ ፡ ፒላሳሁ ፡ ለወ ልድ ፡ (አርጋ ፡ ፫ ። መጽ ፡ ምስ) ።

**ፒሎፓዴር** ፤ የሰው ፡ ስም ፤ መርቆሬዎስ ፡ (ድጓ) ።

**ፓና ፤ (ብ ፡ ፓናት ። ጽር ፡ ፓኖስ ፤ ፋኖስ)** ፤ ፋና ፤ ፋኖስ ፤ ከውጭ ፡ ሲወጡ ፡ የሚያበሩት ፤ ባለቅዘዝ ፡ ባለመስታዮት ። ዘሩም ፡ ምስጢሩም ፡ የፈነወ ፡ ነው ። አመ ፡ የአኀዘከ ፡ መጽኡ ፡ በመኅትወ ፡ ጽጕ ፡ ወፓና ። ወበፓናት ፡ (ደራሲ ። ዮሐ ፲፰ ፡ ፫) ።

**ፓንዋማንጦን ፤ (ጽር ፡ ፑኔፍማቶን)** ፤ መንፈስ ፡ (ቅዱስ) ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ቅዳሴ) ።

**ፐንትዮን ፤ (ጽር ፡ ፐሊንቲዮን)** ፤ አበ ቅቴ ፡ ፀሓይ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በፐንት ፡ ፈንታ ፡ ጥንት ፡ ይላል ፤ ፐና ፡ ጥ ፡ ተመሳሳዮች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ጥ ፡ በስሕ ተት ፡ ገብቷል ። መምህራንም ፡ የወጠነ ፡ ዘር ፡ መስሏ ቸው ፡ ጥንተ ፡ ፀሓይ ፡ ዕለተ ፡ ፀሓይ ፡ እያሉ ፡ በጥንት ፡ ዘይቤ ፡ ይፈቱታል ። ጥንትዮን ፡ ብሂል ፡ ጥንተ ፡ ብር ሃን ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ፕሬዝቢጤር ፤ (ጽር ፡ ፕሬስቢቴሮስ)** ፤ ቆሞስ ፡ ካህን ፡ ቄስ ፤ ወይም ፡ የተሾመበት ፡ በታውና ፡ ደብሩ ፡ ቤቱ ፡ ማኅደሩ ። በፐ ፡ ፈንታ ፡ ጠርዝቤጤር ፡ ጤርዜቤጤር ፡ ይላል ፤ የጣፊ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ (መጽ ፡ ምስ) ።

**ፒርልዩ ፤ (ጽርእ)** ፤ ባለቅኔዎች ፡ ቀንጠፋ ፡ ይሉታል ፤ እንጃ ። ወልድ ፡ ለእመ ፡ ተበቅለ ፡ ፒርልዩ ፡ (ቅኔ) ።

**ፒሳ ፤ (ጽርእ)** ፤ ዝፍት ፤ ሙጫ ፤ የሙጫ ፡ ቅጥራን ። አስፈሊጥን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ጎር ፡ ነው ። ወት ቀብዓ ፡ በፒሳ ። ወወደዩ ፡ ውስተ ፡ እሳቱ ፡ ቶየ ፡ ወፒሳ ። ዘገሠሠ ፡ ፒሳ ፡ ይትአኀዝ ፡ ቦቱ ፡ (ዘፍጽ ፡ ፯፱ ። ዳንኤ ፡ ፳፪ ። ሢራ ፲፫ ፡ ፩) ።

**ፓሳ ፤ (ዕብ ፡ ፓሳሕ ፤ ፔሳሕ)** ፤ ፋሲካ ፤ መ ሥዋዕት ። ዘተወከፍከ ፡ ለኢዮስያስ ፡ በፓሳ ፡ (አዋል ። ጥበ ፡ ጠቢ) ።

**ፓሲካ ፤ (ጽር ፡ ፓስኻ)** ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ፍ ሥሕ ፤ ፋሲካ ። የፋሲካን ፡ ፍች ፡ ተመልከት ። ጽዋዐ ፡ ፓሲካ ፡ ምሉአ ፡ ድኅረ ፡ ሰሰጥከ ፡ ሰትየ ፡ (ደራሲ) ።

**ፕስልቴ ፤ (ጽር ፡ ፕሳልቲሪዮን)** ፤ መዝ ሙር ፤ ግናይ ፤ ማሕሌይ ፤ የሚያዜሙት ፤ የሚያስተዛዝ ሉት ፡ ምስጋና ፡ ጸሎት ። ወያንብቡ ፡ እንከ ፡ መዝሙረ ፡ ወማሕሌተ ፡ አርባዕተ ፤ አሐዱ ፡ ዘሙሴ ፡ ወአሐዱ ፡ ዘሰሎሞን ፡ ወዘባዕዳንሂ ፡ ነቢያት ፡ ከመ ፡ ዘፕስልቴ ፤ ወክልኤቱ ፡ ፕስልቴ ፡ (ኪዳ) ።

**ፓፒራ ፤ (ጽር ፡ ፓፒሮስ)** ፤ መንድደ ፡ እ ሳት ፤ የጋዝና ፡ የዝፍት ፡ የከብሪት ፡ ወገን ። ፒሳ ፡ ወፓ ፒራ ፡ (መቃ ፡ ገ፪) ። ነደን ፡ ተመልከት ።

**ፕፕሬ ፤ (ጽር ፡ ፔፔሪ ። ዐረ ፡ ባባሪ)** ፤ በርበሬ ፤ በየመልኩና ፡ በያይነቱ ፤ ይልቁንም ፡ ቀንድ ያው ። ዕፀ ፡ መዐዛ ፡ ወቀናንሞ ፡ ወፕፕሬ ፡ (ሔኖ፴፪ ፡ ፩) ።

**ፐፒራ ፤ ፐፒር ፤ (ጽር ፡ ፖርፊራ ። ዕብ ፡ አርጋማን)** ፤ የቀለም ፡ ስም ፤ ዝኅንን ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፤ ደባበ ፤ ቅላቱ ፡ በጣም ፡ ያልደመቀ ። ሠያጢተ ፡ ፐፒራ ፡ (ግብ ፲፮ ፡ ፲፬) ። ባለሐዲሶች ፡ ግን ፡ እንደድ ፡ ይሉታል ።

**ፐፒረለይ ፤ (ጽር ፡ ፖርፊራ ፤ ከኪኖስ)** ፤ ቀይ ፡ ሐር ፤ ዝኅንን ፡ ፀምር ፤ ቀይ ፡ ቀለም ፡ የገባ ፡ የሐር ፡ ፈትል ፤ ጕፍላ ፡ (ዘፀ፴፰ ፡ ፯ ። ዕብ፱ ፡ ፲፱ ። አፈ ፡ ድ፲፯) ። አዝዘ ፡ ሎሙ ፡ ማዕተበ ፡ ረስን ፡ ዘመስቀል ፡ ዘፐፒራ ፡ ውስቴቱ ፡ (ሥር ፡ ጳኵ) ።

# የዋና ፡ ዋና ፡ ግድፈትና ፡ ስሕተት ፡ ማረሚያ ።

| ገጽ ፡ | ዐምድ ፡ | መሥመር ፡ | ግድፈት ፡ | የታረመ ፡ |
|---|---|---|---|---|
| ፯ | | ፲፫ | ቋንና ፡ | ቋንቋና ፡ |
| ፳፱ | | ፴ | በሐዱ ፡ | በአሐዱ ፡ |
| ፶፯ | | ፴፭ | ይሆን ፡ | ይኸን ፡ |
| ፻፱ | | ፳ | ተለዋጡ ፡ | ተለዋወጡ ፡ |
| ፪፻፲፯ | ፪ | ፳፫ | በሕቴቱ ፡ | በሕቴቱ ፡ |
| ፪፻፵፰ | ፩ | ፴ | በጎ ፡ | በጎበ ፡ |
| ፫፻፶፫ | ፪ | ፴፯ | ገድ ፡ | ነገድ ፡ |
| ፫፻፹፫ | ፪ | ፲ | ተዋሐደ ፡ | ተወሐደ ፡ |
| ፬፻፺፯ | ፩ | ፲፯ | ወጥው ት ፡ | ወጥውቅት ፡ |
| ፭፻፳፩ | ፪ | ፳፫ | ታታለል ፡ | ትታለል ፡ |
| ፮፻፱ | ፩ | ፳፫ | ፍሱ ፡ | ነፍሱ ፡ |
| ፮፻፳፬ | ፩ | ፳፬ | ኑጎት ፡ | ነጎት ፡ |